# መጽሐፍ ቅዱስ



# ኦሪት ዘፍጥረት

## የፍጥረት አጀማመር

1 በመጀመሪያ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰማያት
ንና ምድርን ፈጠረ። 2ምድርም ቅርጽ የለ
ሽና ባዶ ነበረች፡፡[ሀ] የምድርን ጥልቅ ስፍራ
ሁሉ ጨለማ ውጦት ነበር፡፡ የእግዚአብሐ
ኄርም (ኤሎሂም) መንፈስ በውሆች ላይ ይረብብ
ነበር፡፡

3ከዚያም እግዚአብሔር (ኤሎሂም) “ብርሃን ይሁን”
አለ፤ ብርሃንም ሆነ፡፡ 4እግዚአብሔርም (ኤሎሂም)
ብር ሃኑ መልካም እንደ ሆነ አየ፤
ብርሃኑን ከጨለማ ለየ፡፡ 5እግዚአብሔርም
(ኤሎሂም) ብርሃ ኑን “ቀን”፣ ጨለማውን “ሌሊት”
ብሎ ጠራው። መሸ፤ ነጋም፤ የመጀመሪያ
ቀን፡፡
6እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣ “ውሃን ከውሃ
የሚለይ
ጠፈር በውሆች መካከል ይሁን” አለ፡፡
7ስለዚህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ጠፈርን አድ
ርጎ ከጠፈሩ በላይና ከጠፈሩ በታች ያለ
ውን ውሃ ለየ፤ እንዳለውም ሆነ፡፡ 8እግዚአ
ብሔር (ኤሎሂም) ጠፈርን፣ “ሰማይ” ብሎ ጠራ
ው፡፡ መሸ፤ ነጋም፤ ሁለተኛ ቀን፡፡
9ከዚያም እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣ “ከሰማይ
በታች ያለው ውሃ በአንድ ስፍራ ይከ
ማች፤ ደረቁ ምድር ይገለጥ” አለ፤ እን
ዳለውም ሆነ፡፡ 10እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ደረ
ቁን ምድር፣ “የብስ”፣ በአንድነት የተሰ
በሰበውን ውሃ፣ “ባሕር” ብሎ ጠራው፡፡
እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ይህ መልካም እንደ ሆነ
አየ፡፡
11እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣ “ምድር ዕፀዋትንም፣
እንደየወገናቸው ዘር የሚሰጡ ተክሎች
ንና በምድር ላይ ዘር ያዘሉ ፍሬ የሚያ
ፈሩ ዛፎችን እንደየወገናቸው ታብቅል”
አለ፤ እንዳለውም ሆነ፡፡ 12ምድር ዕፀዋትን፣
እንደየወገናቸው ዘር የሚሰጡ ተክሎችንና
በውስጣቸው ዘር ያለባቸው ፍሬ የሚያ
ፈሩትን ዛፎች በየወገኑ አበቀለች፡፡ እግዚ
አብሔርም (ኤሎሂም) ይህ መልካም እንደ ሆነ
አየ፡፡
13መሸ፤ ነጋም፤ ሦስተኛ ቀን፡፡
14ከዚያም እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣ “ቀኑን ከሌሊ
ት እንዲለዩ፣ የዓመት ወቅቶች፣
ቀናትና ዓመ ታት የሚጀምሩበትንም
እንዲያመለክቱ፣ 15ለምድር ብርሃን
የሚሰጡ ልዩ ልዩ ብርሃናት በሰማይ
ይሁኑ” አለ፤ እንዳለውም ሆነ፡፡ 16እግዚአብሐ
ኄር (ኤሎሂም)፣ ለምድር ብርሃን ይሰጡ ዘንድ
ሁለት ታላላቅ ብርሃናት አደረገ፤ ታላቁ
ብርሃን በቀን እንዲሠለ ጥን፣ ታናሹ
ብርሃን በሌሊት እንዲሠለ ጥን አደረገ፡፡
እንዲሁም ከዋክብትን አደ ረገ፡፡
17ለምድር ብርሃን እንዲሰጡ እነዚህን
በሰማይ ጠፈር አኖራቸው፡፡ 18ይኸውም
በቀንና በሌሊት እንዲሠለጥኑ፣
ብርሃንን ከጨለማ እንዲለዩ ነው፡፡ እግዚ
አብሔርም (ኤሎሂም) ይህ መልካም እንደ ሆነ
አየ፡፡ 19መሸ፤ ነጋም፣ አራተኛ ቀን፡፡
20እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣ “ውሆች ሕይወት
ባላ ቸው በሕያዋን ፍጡራን ይሞሉ፤
ወፎች ከምድር በላይ በሰማይ ጠፈር
ይብረሩ” አለ፡፡ 21በዚህ መሠረት፣ እግዚ
አብሔር (ኤሎሂም) በባሕር ውስጥ የሚኖሩ
ታላላቅ ፍጡ ራንን፣ በውሃ ውስጥ
የሚርመሰመሱ ሕይ ወት ያላቸውን
ነገሮች ሁሉ እነደየወገና ቸው እንዲሁም
ክንፍ ያላቸውን ወፎች ሁሉ እንደየወገናቸው
ፈጠረ፤ እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ይህ መልካም
እንደ ሆነ አየ፡፡ 22እግዚአብሔርም (ኤሎሂም)፣ “ብዙ
ተባዙ፤ የባሕርንም ውሃ ሙሏት፤ ወፎችም
በምድር ላይ ይብዙ” ብሎ ባረካቸው፡፡
23መሸ፤ ነጋም፤ አምስተኛ ቀን፡፡
24እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣ “ምድር ሕያዋን ፍጡራ
ንን እንደየወገናቸው፣ ከብቶችን፣ በምድር
ላይ የሚሳቡ ፍጡራንንና የዱር እንስሳ
ትን እያንዳንዱን እንደ ወገኑ ታስገኝ”
አለ፤ እንዳለውም ሆነ፡፡ 25እግዚአብሔር
(ኤሎሂም) የዱር እንስሳትን
እንደየወገናቸው፣ ከብቶችን
እንደየወገናቸው፣ እንዲሁም በምድር ላይ
የሚሳቡ ፍጡራንን እንደየ ወገናቸው
አደረገ፡፡ እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ይህ
መልካም እንደ ሆነ አየ፡፡
26እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣ “ሰውን በመልካ
ችን፣ በአምሳላችን እንሥራ፤ በባሕር ዓሦች፣
በሰማይ ወፎች፣ በከብቶች፣ በምድር[ሰ] ሁሉ
ላይ፣ እንዲሁም በምድር በሚሳቡ ፍጡራ
ን
ሁሉ ላይ ሥልጣን ይኑራቸው” አለ፡፡

1፥1 ቀ‐6፡21፡27፤ ዘፍ2፥3፤14፥19፤2ነገ 19፥15፤ነህ9፥6፤ኢዮ 9፥8፤37፥16፡18፤38፥ 4፤መዝ90፥2፤96፥5፤ 102፥25፤104፥2፡5፤ 115፥15፤121፥2፤ 136፥5፡6፤146፥6፤ምሳ 8፥23፤ኢሳ37፥16፤ 40፥21፡22፡28፤41፥4፡ 26፤ 42፥5፤44፥24፤ 45፥12፡18፤51፥13፡ 15፤ኤር10፥12፤27፥5፤ 32፥17፤ዮሐ1፥1-2፤ሐሥ 14፥15፤17፥24፤ኤፌ3፥9፤ ቈላ1፥16፤ዕብ3፥4፤ 11፥3፤ራእ4፥11፤ 10፥6 1፥2 ዘፍ2፥7፤8፥2፤ ዘዳ32፥11፤ኢዮ7፥12፤ 26፥8፤33፥4፤38፥9፤ መዝ36፥6፤42፥7፤104፥ 6፡30፤107፥24፤ምሳ 30፥4፤ኢሳ23፥1፤24፥ 10፤27፥10፤31፥5፤32፥ 14፡15፤34፥11፤45፥ 18፤ኤር4፥23፤ 1፥3 ቀ‐6፤መዝ33፥ 6፡9፤148፥5፤2ቆሮ4፥ 6፤ዕብ11፥3፤ 1ዮሐ1፥5-7 1፥4 ቀ‐10፡12፡14፡ 18፡21፡25፡31፤ዘፀ10፥ 21-23፤ኢዮ6፥10፤38፥ 19፤መዝ18፥28፤104፥ 20፡31፤105፥28፤119፥ 68፤ኢሳ42፥16፤45፥7፤ ኤር31፥35 1፥5 ቀ‐8፡10፡13፡ 19፡23፡31፤ዘፍ2፥19፡ 23፤መዝ74፥16 1፥6 ቀ‐1፡3፡9፤መዝ 24፥2፤136፥6፤ኢሳ 44፥24፤2ጴጥ3፥5 1፥7 ቀ‐9፡11፡15፡ 24፤ዘፍ7፥11፤ኢዮ26፥ 10፤38፥8-11፡16፤ መዝ68፥33፤148፥4፤ ምሳ8፥28፤ 1፥8 ቀ‐5፤ኢዮ9፥8፤ 37፥18፤መዝ19፥1፤10 4፥2፤ኢሳ40፥22፤44፥ 24፤45፥12፤ኤር10፥ 12፤ዘካ12፥1 1፥9 ቀ‐7፤ኢዮ38፥ 8-11፤መዝ33፥7፤95፥ 5፤104፥6-9፤ምሳ8፥ 29፤ኤር5፥22፤ዮና1፥ 9፤ሐጌ2፥6፤2ጴጥ3፥5 1፥10 ቀ‐4፡5፤ኢዮ 38፥8፤95፥5፤መዝ33፥7 ፤90፥2፤95፥4 1፥11 ቀ‐7፡12፡21፡ 24፡25፤ዘፍ2፥5፤6፥20፤ 7፥14፤ዘሌ11፥14፡19፡ 22፤ዘዳ14፥13፡18፤ መዝ65፥9-13፤
104፥14፤1ቆሮ15፥38 1፥12 ቀ‐4፡11 1፥13 ቀ‐5 1፥14 ቀ‐ 4፤ዘፍ8፥22፤መዝ74፥16፤104፥19፤136፥7፤ኤር10፥2፤31፥35-36፤ 33፥20፡25 1፥15 ቀ‐7 1፥16 ዘዳ4፥19፤17፥3፤ኢዮ9፥9፤31፥26፤ 38፥7፡31-33፤መዝ8፥3፤36፥6፤74፥16፤104፥19፤136፥8፡9፤መክ12፥2፤ ኢሳ40፥26፤ኤር8፥2፤31፥35፤43፥13፤ሕዝ8፥16፤አሞ5፥8፤ያዕ1፥17 1፥18 ቀ‐4፤ኤር33፥20፡25 1፥19 ቀ‐5 1፥20 ዘፍ2፥19፤መዝ 146፥6 1፥21 ቀ‐1፡4፡11፤ዘፍ8፥17፤9፥1፡7፡19፤ዘሌ26፥9፤ኢዮ3፥8፤ 7፥12፤መዝ74፥13፤104፥25-26፤148፥7፤ኢሳ27፥1፤ሕዝ32፥2፤36፥ 11፤47፥27 1፥22 ቀ‐28፤ዘፍ8፥17፤9፥17፡19፤47፥27፤ዘሌ26፥ 9፤ሕዝ36፥11 1፥23 ቀ‐5 1፥24 ቀ‐7፡11፤ዘፍ2፥19 1፥25 ቀ‐4፡11፤ዘፍ7፥21-22፤ኤር27፥5 1፥26 ቀ‐27፤ዘፍ3፥5፡22፤5፥3፤ 9፥2-6፤11፥7፤መዝ8፥5-8፤82፥6፤89፥6፤100፥3፤ኢሳ6፥8፤45፥18 ፤ሐ ሥ17፥28-29፤1ቆሮ11፥7፤2ቆሮ4፥4፤ቈላ1፥15፤3፥10፤ያዕ3፥9

[ሀ]2 ወይም *ሆነች*

[ሰ]26 ዕብራይስጡም እንደዚሁ ሲሆን ሱርስቱ ግን *የዱር እንስ ሳት ሁሉ* ይለዋል፡፡

[27]ስለዚህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰውን በራሱ መልክ
ፈጠረው፤
በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) መልክ ፈጠረው፤
ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።

[28]እግዚአብሔርም (ኤሎሂም)፣ “ብዙ ተባዙ፤ ምድ
ርን ሙሏት፤ ግዟትም፤ የባሕርን ዓሦች፣
የሰማይን ወፎች፣ እንዲሁም በምድር ላይ
የሚንቀሳቀሱትን ሕያዋን ፍጡራንን ሁሉ
ግዟቸው” ብሎ ባረካቸው።
[29]እግዚአብሔርም (ኤሎሂም)፣ እንዲህ አለ፤ “በም
ድር ላይ ያሉትን ዘር የሚሰጡ ተክሎ
ችን ሁሉ፣ በፍሬያቸው ውስጥ ዘር ያለ
ባቸውን ዛፎች ሁሉ ምግብ ይሆኑላችሁ
ዘንድ ሰጥቻችኋለሁ። [30]እንዲሁም ለምድር
አራዊት ሁሉ፣ ለሰማይ ወፎች ሁሉ፣ በም
ድር ላይ ለሚንቀሳቀሱ ሕያዋን ፍጡራን
ሁሉ ማንኛውም ለምለም ተክል ምግብ
እንዲሆናቸው ሰጥቻለሁ” እንዳለውም ሆነ።
[31]እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ያደረገውን ሁሉ አየ፤
እነሆም፣ እጅግ መልካም ነበረ። መሸ፤
ነጋም፤ ስድስተኛ ቀን።

2 የሰማያትና የምድር፣ በውስጣቸውም ያሉት
ሁሉ አፈጣጠር በዚህ ሁኔታ ተከናወነ።

[2]እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ይሠራ የነበረውን ሥራ
በሰባተኛው ቀን ላይ ፈጽሞ ነበር፤ ስለዚህ
ከሠራው ሥራ ሁሉ በሰባተኛው ቀን ዐረፈ።[ሐ]
[3]እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰባተኛውን ቀን ባረከው፤
ቀደሰውም፤ ካከናወነው የመፍጠር ሥራው
ሁሉ ያረፈው በሰባተኛው ቀን ነውና።

## አዳምና ሔዋን

[4]እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም)ሰማያትንና
ምድርን በፈጠረ ጊዜ የተከናወኑት እንደዚህ
ነበረ፤
እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ሰ
ማያት ንና ምድርን ሲፈጥር [5]የሜዳ
ቁጥቋጦ ገና በምድር[መ] ላይ አልታየም፤
የሜዳ ተክልም ገና አልበቀለም፤ ምክንያቱ
ም እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) በመሬት
ላይ ገና ዝናብ አላዘነበም ነበር፤ ምድርንም
የሚያለማ ሰው አልነበረም። [6]ነገር ግን
ውሃ[ሠ] ከመ ሬት እየመነጨ የምድርን ገ
ጽ ያረሰርስ ነበር። [7]እግዚአብሔር አምላክ
(ያህዌ ኤሎሂም)ከም ድር ዐፈር ወስዶ ሰውን[ረ]
አበጀው፤ በአፍን ጫውም የሕይወት
እስትንፋስ እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ
ሆነ።
[8]እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌኤሎሂም) በምሥራቅ፣
በዔድን የአትክልት ስፍራ አዘጋጀ፤ ያበጀ
ውንም ሰው በዚያ አኖረው። [9]እግዚአብሔር
አምላክም (ያህዌኤሎሂም) ለዐይን የሚያስደስት ለመ
ብልም መልካም የሆነውን ዛፍ ሁሉ ከምድር
አበቀለ፤ በአትክልቱ ቦታ መካከልም የሕ
ይወት ዛፍ ነበረ፤ እንዲሁም መልካምና ክፉን
መለየት የሚያስችለው የዕውቀት ዛፍ ነበረ።
[10]የአትክልት ስፍራውን የሚያጠጣ ወንዝ
ከዔድን ይፈስ ነበር፤ ከዚያም በአራት ተከ
ፍሎ ይወጣ ነበር። [11]የመጀመሪያው፣ ወርቅ
በሚገኝበት በሐዊላ ምድር ዙሪያ ሁሉ
የሚፈሰው የፊሶን ወንዝ ነው። [12]ኤውላጥ
ምርጥ የሆነ ወርቅ፣ መልካም መዐዛ[ሰ] ያለው
ከርቤና የከበረ ድንጋይ የሚገኙበት ምድር
ነው። [13]ሁለተኛው፣ በኢትዮጵያ[ሸ] ምድር ዙሪያ
ሁሉ የሚፈሰው የግዮን ወንዝ ነው። [14]ሦስተ
ኛው፣ ከአሦር በስተ ምሥራቅ የሚፈሰው
የጤግሮስ ወንዝ ሲሆን፣ አራተኛው የኤፍ
ራጥስ ወንዝ ነው።
[15]እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ሰውን
ወስዶ እንዲያለማትና እየተንከባከበ እንዲጠ
ብቃት በዔድን የአትክልት ስፍራ አስቀ
መጠው። [16]እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም)
ሰውን እንዲህ በማለት አዘዘው፤ “በአትክ
ልት ስፍራው ውስጥ ከሚገኝ ከማንኛውም
ዛፍ ፍሬ ትበላለህ። [17]ነገር ግን መልካምና
ክፉን ከሚያሳውቀው ዛፍ አትብላ፤ ምክን
ያቱም ከእርሱ በበላህ ቀን በእርግጥ ትሞ
ታለህ።”
[18]ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ
ኤሎሂም)፣ “ሰው ብቻውን መሆኑ መልካም
አይደለምና የሚስማማውን ረዳት አበጅለ
ታለሁ” አለ።
[19]እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) የዱር
አራዊትንና የሰማይ ወፎችን ከምድር ሠርቶ
ነበር፤ ለእያንዳንዳቸውም ምን ስም እንደ
ሚያወጣላቸው ለማየት ወደ አዳም አመጣ
ቸው። አዳም ሕይወት ላላቸው ፍጡራን
ሁሉ ያወጣላቸው ስም መጠሪያቸው ሆነ።
[20]ስለዚህ አዳም[ቀ] ለከብቶች፣ ለሰማይ ወፎች፣
ለዱር አራዊት ሁሉ ስም አወጣላቸው።
ይሁን እንጂ ለአዳም ተስማሚ ረዳት አል
ተገኘለትም ነበር። [21]እግዚአብሔር አምላክም
(ያህዌ ኤሎሂም) በአዳም ላይ ከባድ እንቅልፍ ጣለበት፤

1፥27 ቀኑ1:26፤ዘፍ 2፥7፤5፥1:2፤ዘዳ4፥32፤መዝ103፥14፤119፥73፤ማቴ19፥4፤ማር 10፥6፤ገላ3፥28
1፥28 ቀኑ22:26፤ዘፍ6፥1፤17፥6፤33፥5፤ኢሱ24፥3፤መዝ8፥6-8፤113፥9፤115፥16፤127፥3:5፤ሐሥ17፥26
1፥29 ዘፍ9፥3፤ዘዳ 12፥15፤መዝ104፥14፤1ጢሞ4፥3
1፥30 ዘፍ2፥7፤7፥22፤ኢዮ38፥41፤መዝ78፥25፤104፥14:27፤111፥5፤136፥25፤145፥15፤147፥9
1፥31 ቀኑ4:5፤መዝ 104፥24፤136፥5፤ምሳ 3፥19፤ኤር10፥12፤1ጢሞ4፥4
2፥1 ዘዳ4፥19፤17፥3፤2ነገ17፥16፤21፥3፤መዝ104፥2፤ኢሳ44፥24፤45፥12፤48፥13፤51፥13
2፥2 ቀኑ2-3፤ዘፀ20፥11፤31፥17፤34፥21፤ዘዳ5፥14፤ዮሐ5፥17፤ዕብ4፥4
2፥3 ዘፍ1፥1፤ዘፀ16፥23፤20፥10፤23፥12፤31፥15፤35፥2፤ዘሌ23፥3፤ነህ9፥14፤መዝ95፥11፤ኢሳ58፥13፤ኤር 17፥22፤ዕብ4፥1-11
2፥4 ዘፍ1፥1፤5፥1፤6፥9፤10፥1፤11፥10:27፤25፥12:19፤36፥1:9፤37፥2፤ኢዮ38፥8-11
2፥5 ዘፍ1፥11፤ኢዮ 38፥28፤መዝ65፥9-10፤ኤር10፥13
2፥7 ዘፍ1፥2:27:30፤3፥19:3፤4፥2፤18፥27፤ኢዮ4፥19፤10፥9፤12፥10፤17፥16፤27፥3፤32፥8፤33፥4፤34፥14:15፤መዝ90፥3፤103፥14፤104፥29፤መክ3፥20፤12፥7፤ኢሳ2፥22፤29፥16፤42፥5፤43፥1:21፤44፥2፤57፥16፤ኤር18፥6፤ሕዝ37፥5፤ሐሥ17፥25፤1ቆሮ15፥45:47
2፥8 ቀኑ10:15፤ዘፍ 3፥23:24፤4፥16፤13፥10፤ኢሳ51፥3፤ሕዝ 28፥13፤31፥9:16፤36፥35፤ኢል2፥3
2፥9 ዘፍ3፥22:24፤ሕዝ31፥8፤47፥12፤ምሳ3፥18፤11፥30፤ራእ 2፥7
2፥10 ቀኑ8፤ዘኍ24፥6፤መዝ46፥4፤ሕዝ47፥5
2፥11 ዘፍ10፥7፤25፥18
2፥12 ዘኍ11፥7
2፥17 ዘፍ15፥18፤31፥21፤41፥1፤ዘፀ 23፥31፤ዘኍ22፥5፤ዘዳ1፥7፤11፥24፤ኢሱ1፥4፤2ሳሙ8፥3፤1ነገ4፥21፤2ነገ23፥29፤24፥7፤1ዜና5፥9፤18፥3፤2ዜና35፥20፤ኤር13፥4፤46፥2፤51፥63፤ዳን10፥4፤ራእ9፥14 2፥15 ቀኑ8 2፥16 ዘፍ3፥1-2 2፥17 ዘፍ3፥1:3:11:7፤5፥5፤9፥29፤ዘዳ30፥15:19፤ኤር42፥16፤ሕዝ3፥18፤ሮሜ5፥12፤6፥23 2፥18 ምሳ31፥11፤1ቆሮ11፥9፤1ጢሞ2፥13 2፥19 ዘፍ1፥5:20:24፤መዝ8፥7 2፥20 ዘፍ3፥20፤4፥1

[ሐ]2 ወይም ***አቈመ***፤ በቍ 3 ላይም እንዲሁ
[መ]5 ወይም ***መሬት***፤ በቍ 6 ላይም እንዲሁ
[ሠ]6 ወይም ***ጭጋግ***
[ረ]7 በዕብራይስጥ ሰው (**አዳም**) የሚለው ቃል፣ **መሬት** (**አዳማኸ**) ከሚለው ቃል ጋር በድምፅ ይመሳሰላል፤ በፍቺም ሳይዛመድ አይቀርም፤ **አዳም** የመጀመሪያው ሰው ስምም ነው (ዘፍ 2፥20 ይመ)
[ሰ]12 ወይም ***መልካም ዕንቁ***
[ሸ]13 ደቡብ ምሥራቅ መስጴጦምያ ሊሆን ይችላል
[ቀ]20 ወይም ***ሰው***

አንቀላፍቶም ሳለ ከጐድኑ አንዲት ዐጥንት[ሀ]
ወስዶ፣ ስፍራውን በሥጋ ሞላው። [22]እግዚአ
ብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ከአዳም
የወሰዳትን
ዐጥንት[ተ] ሴት አድርጎ ሠራት፤ ወደ አዳ
ምም አመጣት።

[23]አዳምም እንዲህ አለ፤

"እነሆ፤ ይህች ዐጥንት ከዐጥንቴ፣
ሥጋም ከሥጋዬ ናት።
ከወንድ ተገኝታለችና ሴት[ቸ] ትባል።"

[24]ስለዚህ ሰው ከአባቱና ከእናቱ ተለ
ይቶ ከሚስቱ ጋር ይጣመራል፤ ሁለቱም
አንድ ሥጋ ይሆናሉ።
[25]አዳምና ሚስቱ፣ ሁለቱም ዕራቍታቸውን
ነበሩ፤ ይሁን እንጂ አይተፋፈሩም ነበር።

## የሰው ውድቀት

3 እባብ እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ከፈ
ጠራቸው የዱር አራዊት ሁሉ ተንኰለኛ
ነበረ፤ ሴቲቱንም፣ "በእርግጥ እግዚአብሔር
(ኤሎሂም)፣ 'በአትክልቱ ስፍራ ካሉ ዛፎች ከማና
ቸውም እንዳትበሉ' ብሎአልን?"'አላት።
[2]ሴቲቱም እባቡን እንዲህ አለችው፤ "በአ
ትክልቱ ስፍራ ካሉት ዛፎች ፍሬ መብላት
እንችላለን፤ [3]ነገር ግን እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
'በአትክልቱ ስፍራ መካከል ከሚገኘው ዛፍ
ፍሬ እንዳትበሉ፤ እንዳትነኩትም፤ አለበለዚያ
ትሞታላችሁ' ብሎአል።"
[4]እባቡም ሴቲቱን እንዲህ አላት፤ "መሞት
እንኳ አትሞቱም፤ [5]ከፍሬው በበላችሁ ጊዜ ዐይ
ናችሁ እንደሚከፈትና መልካምና ክፉን በ
ማ ወቅ፣ እንደ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
እንደምት ሆኑ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
ስለሚያውቅ ነው።"
[6]ሴቲቱ የዛፉ ፍሬ ለመብል መልካም፣
ለዐይን የሚያስደስትና ጥበብንም ለማግኘት
የሚያጓጓ እንደ ሆነ ባየች ጊዜ፣ ከፍሬው
ወስዳ በላች፤ ከእርሷም ጋር ለነበረው ለባሏ
ሰጠችው፤ እርሱም በላ። [7]የሁለቱም ዐይኖች
ተከፈቱ፤ ዕራቍታቸውን መሆናቸውንም ተገ
ነዘቡ። ስለዚህ የበለስ ቅጠል ሰፍተው አገ
ለደሙ።
[8]ቀኑ መሸትሸት ሲል፣ እግዚአብሔር አም
ላክ (ያህዌ ኤሎሂም) በአትክልቱ ስፍራ ሲመላለስ
አዳምና ሔዋን ድምፁን ሰምተው ከእግዚ
አብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ፊት በዛፎቹ
መካከል ተሸሸጉ። [9]እግዚአብሔር አምላክ
(ያህዌ ኤሎሂም) ግን አዳምን ተጣርቶ፣ "የት
ነህ?" አለው።
[10]አዳምም፣ "ድምፅህን በአትክልቱ ስፍራ
ሰማሁ፤ ዕራቍቴን ስለ ሆንሁ ፈራሁ፤ ተሸ
ሸግሁም" ብሎ መለሰ።

2፥21 ዘፍ15፥12፤ 1ሳሙ26፥12፤ ኢዮ 33፥15
2፥22 1ቆሮ11፥8፡9፡ 12፤ 1ጢሞ2፥13
2፥23 ዘፍ1፥5፤ 29፥ 14፤ 1ቆሮ11፥8፤ ኤፌ 5፥28-30
2፥24 ሚል2፥15፤ ማቴ19፥5፤ ማር10፥7- 8፤ 1ቆሮ6፥16፤ ኤፌ 5፥31
2፥25 ዘፍ3፥7፡10- 11፤ ኢሳ47፥3፤ ሰቆ1፥8
3፥1 ዘፍ2፥17፤ ኢዮ 1፥7፤ 2፥2፤ 2ቆሮ11፥3፤ ራእ12፥9፤ 20፥2
3፥2 ዘፍ2፥16
3፥3 ዘፍ2፥17
3፥4 ዮሐ8፥44፤ 2ቆሮ11፥3
3፥5 ዘፍ1፥26፤ 14፥ 18፡19፤ መዝ7፥8፤ ኢሳ 14፥14፤ ሕዝ28፥2
3፥6 ዘኍ30፥7-8፤ ኤር44፥15፡19፡24፤ 2ቆሮ11፥3፤ 1ጢሞ 2፥14፤ 1ዮሐ2፥16፤ ያዕ 1፥14-15
3፥7 ቍ21፤ ዘፍ2፥25
3፥8 ዘሌ26፥12፤ ዘዳ 23፥14፤ ኢዮ13፥16፤ 23፥7፤ 31፥33፤ 34፥22፡ 23፤ መዝ5፥5፤ 139፥7- 12፤ ኢሳ29፥15፤ ኤር 16፥17፤ 23፥24፤ 49፥ 10፤ ራእ6፥15-16 ዘፀ 19፥16፤ 20፥18፤ ዘዳ 5፥5፤ 1ሳሙ12፥18
3፥9 ዘፍ4፥9፤ 16፥8፤ 18፥9፤ 1ነገ19፥9፡13
3፥10 ዘፍ2፥25፤ ሚክ7፥17
3፥11 ዘፍ2፥17:25
3፥12 ዘፍ2፥22
3፥13 ሮሜ7፥11፤ 2ቆሮ11፥3፤ 1ጢሞ 2፥14
3፥14 ዘዳ28፥15- 20፤ መዝ72፥9፤ ኢሳ 49፥23፤ 65፥25
3፥15 ዘፍ16፥11፤ መሳ13፥5፤ ኢሳ7፥14፤ 8፥3፤ 9፥6፤ ማቴ1፥23፤ ሉቃ1፥31፤ ዮሐ8፥44፤ ሐሥ13፥10፤ ሮሜ16፥ 20፤ ገላ4፥4፤ ዕብ2፥14፤ 1ዮሐ3፥8፤ ራእ12፥17
3፥16 መዝ48፥5-6፤ ኢሳ13፥8፤ 21፥3፤ 26፥ 17፤ ኤር4፥31፤ 6፥24፤ ሚክ4፥9፤ 1ቆሮ11፥3፤ ኤፌ5፥22፤ 1ጢሞ2፥15
3፥17 ዘፍ2፥17፤ 5፥29 ፤ 6፥13፤ 8፥21፤ 29፥32፤ 31፥42፤ 47፥9፤ ዘፀ3፥7፤ ዘኍ35፥33፤ ኢዮ5፥7፤ 7፥1፤ 14፥1፤ መዝ66፥11፤ 106፥39፤ 127፥2፤ መክ 1፥13፤ 2፥23፤ ኢሳ24፥ 5፤ 54፥9፤ ኤር3፥1፤ 20፥ 18፤ ሮሜ8፥20-22

[11]እግዚአብሔርም (ያህዌ)፣ "ዕራቍትህን መሆ
ንህን ማን ነገረህ? 'ከእርሱ እንዳትበላ' ብዬ
ካዘዝሁህ ዛፍ በላህን?" አለው።
[12]አዳምም፣ "ይህች ከእኔ ጋር እንድት
ኖር የሰጠኸኝ ሴት፣ እርሷ ከዛፉ ፍሬ
ሰጠችኝና በላሁ" አለ።
[13]እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ሴቲተ
ን፣ "ይህ ያደረግሽው ምንድን ነው?"
አላት። እርሷም፣ "እባብ አሳሳተኝና በላሁ"
አለች።
[14]እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም)
እባብን እንዲህ አለው፤ "ይህን ስለ ሠራ
ህ፣
"ከከብቶችና ከዱር እንስሳት ሁሉ
ተለይተህ የተረገምህ ሁን፤
በሕይወትህ ዘመን ሁሉ፣ በደረትህ
እየተሳብህ ትሄዳለህ፤
ዐፈርም ትበላለህ።

[15]በአንተና በሴቲቱ፣
በዘርህና በዘሯ መካከል፣
ጠላትነትን አደርጋለሁ፤
እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤[ኀ]
አንተም ተረከዙን ትቀጠቅጣለህ።"

[16]ሴቲቱንም እንዲህ አላት፤

"በምጥ ጊዜ ጭንቅሽን አበዛለሁ፤
በሥቃይም ትወልጃለሽ፤
ፍላጐትሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፤
እርሱም የበላይሽ ይሆናል።

[17]አዳምንም እንዲህ አለው፤ "የሚስትህን
ቃል ሰምተህ፣ 'ከእርሱ አትብላ' ብዬ ያዘ
ዝሁህን ዛፍ በልተሃልና፣

"ከአንተ የተነሣ ምድር የተረገመች ትሁን፤
በሕይወትህ ዘመን ሁሉ
ምግብህን ጥረህ ግረህ ከእርሷ ታገኛለህ።

[18]ምድርም እሾኽና አሜከላ
ታበቅልብሃለች፤
ከቡቃያዋም ትበላለህ።
[19]ከምድር ስለ ተገኘህ፣
ወደ መጣህበት መሬት እስክትመለስ
ድረስ
እንጀራህን በፊትህ ላብ ትበላለህ፤
ዐፈር ነህና
ወደ ዐፈር ትመለሳለህ።"
[20]አዳምም['] የሕያዋን ሁሉ እናት ናትና
ሚስቱን ሔዋን[ኘ] ብሎ ጠራት። [21]እግዚ
አብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ከቈዳ ልብስ
አዘጋጅቶ አዳምንና ሚስቱን አለበሳቸው።

3፥18 ኢዮ31፥40፤ መዝ104፥14፤ ኢሳ5፥6፤ ዕብ6፥8 3፥19 ዘፍ2፥ 7፤ 14፥18፤ ዘዳ8፥3፡9፤ 23፥4፤ ሩት1፥6፤ 2፥14፤ ኢዮ7፥21፤ መዝ104፥ 23፤ 146፥4፤ 1ቆሮ15፥47፤ 2ተሰ3፥10፤ ዕብ9፥27 3፥20 ዘፍ2፥20፤ 2ቆሮ11፥3፤ 1ጢሞ2፥13 3፥21 ቍ7

[ሀ]21 ወይም *ከሰው የጐን ክፍል ወስዶ* [ተ]22 ወይም *ክፍል*
[ቸ]23 *ሰው የሚል ትርጕም ያለው የዕብራይስጥ ቃል ሴት የሚል ትርጕም ካለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው*

22ከዚያም እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም)
፣ "ሰው መልካምንና ክፉውን ለይቶ በ
ማወቅ ረገድ አሁን ከእኛ እንደ አንዱ
ሆኗል፤ አሁን ደግሞ እጁን ዘርግቶ ከሕ
ይወት ዛፍ ቀጥፎ እንዳይበላ፣ ለዘላለምም
እንዳይኖር ይከልከል" አለ። 23ስለዚህ
የተገኘበትን ምድር እንዲያርስ፣ እግዚ
አብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ሰውን ከዔድን
የአትክልት ስፍራ አስወጣው፤ 24ሰውንም
ካስወጣው በኋላ፣ ወደ
ሕይወት ዛፍ የሚወስደውን መንገድ ለመጠበቅ
ኪሩቤልንና በየአቅጣጫው የምትገለ ባበጥ
ነበልባላዊ ሠይፍ ከዔድን በስተ ምሥራቅ
አኖረ።[አ]

## ቃየንና አቤል

4 አዳም ሚስቱን ሔዋንን ተገናኛት፤ እር
ሷም ፀንሳ ቃየንን[ከ] ወለደች፤ "በእግዚ
አብሔር (ያህዌ) ርዳታ ወንድ ልጅ አገኘሁ" አለች።
2ደግሞም ወንድሙን አቤልን ወለደች።
አቤል የበግ እረኛ፣ ቃየንም ዐራሽ ነበር።
3በአንድ ወቅት፣ ቃየን ከምድር ፍሬ ለእ
ግዚአብሔር (ያህዌ) መሥዋዕት አቀረበ። 4አቤ
ልም መጀመሪያ ከተወለዱት በጎች መካከል
ስባቸውን መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ። እግዚ
አብሔር (ያህዌ) ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ
ተመለከተ፤ 5በቃየንና በመሥዋዕቱ ግን አል
ተደሰተም፤ ስለዚህ ቃየን ክፉኛ ተናደደ፤ ፊቱም
ጠቈረ።
6እግዚአብሔር አምላክም (ያህዌ ኤሎሂም) ቃየንን
እንዲህ አለው፤ "ለምን ተናደድህ? ለምንስ
ፊትህ ጠቈረ? 7መልካም ብታደርግ ተቀባይ
ነትን አታገኝምን? መልካም ባታደርግ ግን፣
ኀጢአት በደጅህ እያደባች ናት፤ ልታሸን
ፍህ ትፈልጋለች፤ አንተ ግን ተቈጣጠራ
ት።"
8ቃየንም ወንድሙን አቤልን፣ "እስቲ
ና፤ ወደ መስኩ እንውጣ"[ኸ] አለው፤ በመስ
ኩም ሳሉ፣ ቃየን ወንድሙን አቤልን አጠ
ቃው፤ ገደለውም።
9ከዚያም፣ እግዚአብሔር (ያህዌ) ቃየንን፣
"ወንድምህ አቤል የት ነው?" አለው።
ቃየንም፣ "አላውቅም፤ እኔ የወንድሜ ጠባቂ
ነኝን?" ሲል መለሰ።
10እግዚአብሔርም (ያህዌ) እንዲህ አለ፤ "ምን
ድነው ያደረግኸው? ስማ! የወንድምህ ደም
ከምድር ወደ እኔ ይጮኻል። 11እንግዲህ
የተረገምህ ነህ፤ የወንድምህን ደም ከእጅህ
ለመቀበል አፏን ከከፈተችው መሬት ትሰ
ደዳለህ። 12ብታርሳትም ፍሬዋን አትለግስህም፤
በምድር ላይ ኰብላይና ተንከራታች ትሆ
ናለህ።"
13ቃየንም እግዚአብሔርን (ያህዌ) እንዲህ
አለው፤ "ቅጣቴ ልሸከመው ከምችለው በላይ
ነው። 14እነሆ፤ ዛሬ ከምድሪቱ አባረርኸኝ፤
ከፊትህም እሸሸጋለሁ፤ በምድር ላይ ኰብላ
ይና ተንከራታች እሆናለሁ፤ የሚያገኘኝም
ሁሉ ይገድለኛል።"
15እግዚአብሔር (ያህዌ) ግን፣ "የለም! እንደ
ርሱ አይሆንም፤[ወ] ማንም ቃየንን ቢገድል፣
ሰባት ዕጥፍ የበቀል ቅጣት ይቀበላል"
አለው፤ ስለዚህ፣ ያገኘው ሁሉ
እንዳይገድለው እግ ዚአብሔር (ያህዌ)
በቃየን ላይ ምልክት አደ ረገለት።
16ቃየንም ከእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት
ወጥቶ ሄዶ፣ ከዔድን በስተ ምሥራቅ
በምትገኝ ኖድ[ዐ] በተባለች ምድር ተቀመጠ።
17ቃየን ሚስቱን ተገናኛት፤ እርሷም ፀንሳ
ሄኖክን ወለደች። ቃየን የቈረቈረውን ከተማ
በልጁ ስም ሄኖክ ብሎ ጠራው። 18ሄኖክ ኢራ
ድን ወለደ፤ ኢራድም መሑያኤልን፣ መሑ
ያኤልም ማቱሣኤልን፣ ማቱሣኤልም ላሜሕን
ወለደ።
19ላሜሕ ሁለት ሚስቶች አገባ፤ የአንደ
ኛዋ ስም ዓዳ፣ የሁለተኛዋም ጺላ ነበር።
20ዓዳ ያባልን ወለደች፤ እርሱም በድንኳን
ለሚኖሩ ከብት አርቢዎች አባት ነበረ።
21ወንድሙም ዩባል ይባላል፤ እርሱም የበ
ገና ደርዳሪዎችና የዋሽንት ነፊዎች አባት
ነበረ። 22ሴላም ደግሞ ቱባልቃይን የተባለ
ወንድ ልጅ ነበራት፤ እርሱም ከብረትና ከናስ
ልዩ ልዩ መሣሪያዎችን እየቀረጸ የሚሠራ[ዘ]
ነበር። የቱባልቃይን እኅት ናዕማ ትባል
ነበር።
23ላሜሕ ሚስቶቹን እንዲህ አላቸው፤

"ዓዳና ጺላ ሆይ ስሙኝ፤
የላሜሕ ሚስቶች ሆይ አድምጡኝ፤
አንድ ሰው ቢያቈስለኝ፣
ጕልማሳው ቢጐዳኝ፣ ገደልሁት፤[ዠ]
24ቃየንን የሚገድል ሰባት ጊዜ ቅጣት ካገኘው፣
የላሜሕ ገዳይማ ሰባ ሰባት ጊዜ ቅጣት
ያገኘዋል።"

25አዳም እንደ ገና ሚስቱን ተገናኛት፤
እርሷም ወንድ ልጅ ወለደች። "ቃየን

3፥22 ዘፍ1፥26፤ 2፥9፤ራእ2፥7
3፥23 ዘፍ2፥7፡8
3፥24ዘፍ2፥8፡9፤ዘፀ 25፥18-22፤1ሳሙ 4፥4፤2ሳሙ6፥2፤22፥11፤1ነገ6፥27፤8፥6፤ 2ነገ19፥15፤2ዜና5፥8፤ ኢዮ40፥19፤መዝ18፥10፤80፥1፤99፥1፤104፥4፤ኢሳ27፥1፤37፥16 ፤ሕዝ10፥1፤28፥16
4፥1 ቀኍ17፡25፤ ዘፍ2፥20፤ዕብ11፥4፤ 1ዮሐ3፥12፤ይሁ1፥11
4፥2 ዘፍ2፥7፤ማቴ 23፥35፤ሉቃ11፥51፤ ዕብ11፥4፤12፥24 4፥3 ዘኍ18፥12፤ ዘሌ2፥1-2፤ኢሳ43፥23፤ኤር41፥5
4፥4 ዘፀ13፥2፡12፤ ዘዳ15፥19፤ዘሌ3፥16፤ 2ዜና29፥35፤ዕብ11፥4
4፥6 ዮና4፥4
4፥7 ዘፍ44፥16፤ዘኍ 32፥23፤ኢሳ59፥12፤ ኢዮ11፥15፤22፥27፤ መዝ27፥3፤46፥2፤ ሮሜ6፥16
4፥8 ማቴ23፥35፤ ሉቃ11፥51፤1ዮሐ 3፥12፤ይሁ1፥11
4፥9 ዘፍ3፥9፤ዮሐ 8፥44
4፥10 ዘፍ9፥5፤37፥20፡26፤ዘፀ21፥12፤ዘኍ 35፥33፤ዘዳ21፥7፡9፤ 2ሳሙ4፥11፤ኢዮ16፥18፤24፥2፤31፥38፤ መዝ9፥12፤106፥38፤ ዕብ12፥24፤ራእ6፥9-10
4፥11 ዘዳ11፥28፤ 2ነገ2፥24
4፥12 ቀኍ14፤ዘዳ28፥15-24፤መዝ37፥25፤ 59፥15፤109፥10
4፥14 ቀኍ12፤ዘፍ 9፥6፤ዘፀ21፥12፡14፤ ዘሌ24፥17፤ዘኍ35፥19፡21፡27፡33፤ዘዳ 28፥64-67፤28፥64-7፤ 1ነገ2፥32፤2ነገ11፥16፤ 17፥18፤መዝ51፥11፤1 39፥7-12፤ኤር 7፥15፤52፥3
4፥15 ቀኍ24፤ዘፀ21፥20፤ዘሌ26፥21መዝ 79፥12፤ሕዝ9፥4፡6
4፥16 ዘፍ2፥8፤ ይሁ1፥11
4፥17 ቀኍ1፤መዝ 55፥9፤49፥11
4፥19 ዘፍ6፥2፤29፥28፤ዘዳ21፥15፤ሩት 4፥11፤1ሳሙ1፥2
4፥21 ዘፍ31፥27፤ ዘፀ15፥20፤1ሳሙ16፥16፤1ዜና25፥3፤ኢዮ 21፥12፤30፥31፤መዝ 33፥2፤43፥4፤150፥4፤ ኢሳ16፥11፤ዳን3፥5
4፥22 ዘፀ35፥35፤1ሳሙ13፥19፤2ነገ24፥14 4፥23 ዘፍ9፥5-6፤ዘፀ 20፥13፤21፥12፤23፥7፤ዘሌ19፥18፤24፥17፤ዘዳ27፥24፤32፥35 4፥24 ቍ15፤ዘዳ32፥35፤2ነገ9፥7፤መዝ18፥47፤94፥1፤ኢሳ35፥4፤ ኤር51፥56፤ናሆ1፥2፤ማቴ18፥22

[ኀ]15 ወይም *ይመታል*
[ነ]20 ወይም *ሰውየው*፤ በ4፥1ም እንዲሁ
[ኘ]20 *ሔዋን* ማለት *ሕያው* ማለት ሳይሆን አይቀርም
[አ]24 ወይም *ፊት ለፊት አስቀመጠ*
[ከ]1 *ቃየን* የሚለው ስም *ማምጣት* ወይም *ማግኘት* የሚል ትርጕም ካላቸው የዕብራይስጥ ቃላት ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው
[ኸ]8 *እስቲ ና፣ ወደ መስኩ እንውጣ* የሚለው ሐረግ በአራተ ሳምራውያን፣ በሰብዓ ሊቃናት፣ በቩልጌትና፣ በሱርስት የሚገኝ ሲሆን በማሶሬቲክ ጽሑፍ ውስጥ ግን የለም
[ወ]15 ዕብራይሰጡ ከሰብዓ ሊቃናት፣ ከቩልጌትና ከሱርስቱ ጋር ተመ ሳሳይ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን *መልካም!* ይለዋል
[ዐ]16 ኖድ ማለት መቅበዝበዝ ማለት ለው (ቍ12 እና 14 ይመ)
[ዘ]22 ወይም *ለሚሠሩት ሁሉ መመሪያ የሚሠጥ*
[ዠ]23 ወይም እገድላለሁ

በገደለው በአቤል ፈንታ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ምትክ ሰጠኝ" ስትል ስሙን ሴት[የ] ብላ ጠራ
ችው፡፡ 26ለሴትም ደግሞ ወንድ ልጅ ተወ
ለደለት፤ ስሙንም ሄኖስ አለው፡፡
በዚያም ዘመን ሰዎች *የእግዚአብሔርን*
(ያህዌ) ስም መጥራት[ደ] ጀመሩ፡፡

## ከአዳም እስከ ኖኅ

5 የአዳም የትውልድ ሐረግ እንደሚከተ
ለው ነው፦
እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰውን ሲፈጥረው በራሱ
አምሳል አበጀው፤ 2ወንድና ሴት አድርጎ
ፈጠራቸው፤ ባረካቸው፤ በተፈጠሩም ጊዜ
"ሰው"[ጀ] ብሎ ጠራቸው፡፡
3አዳም፣ ዕድሜው 130 ዓመት በሆነ ጊዜ፣
እርሱን ራሱን የሚመስል ወንድ ልጅ ወለደ፤
ስሙንም ሴት ብሎ ጠራው፡፡ 4ሴት ሄኖ
ስን ከወለደ በኋላ አዳም 800 ዓመት ኖረ፤
ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችንም ወለደ፤
5አዳም በአጠቃላይ 930 ዓመት ከኖረ በኋላ
ሞተ፡፡
6ሴት፣ ዕድሜው 105 ዓመት ሲሆን ሄኖ
ስን ወለደ፤ 7ሴት ሄኖስን ከወለደ በኋላ
807 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች
ልጆችንም ወለደ፡፡ 8ሴት በአጠቃላይ 912
ዓመት ከኖረ በኋላ ሞተ፡፡
9ሄኖስ፣ ዕድሜው 90 ዓመት በሆነ ጊዜ
ቃይናንን ወለደ፤ 10ሄኖስ ቃይናንን ከወለደ
በኋላ 815 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና
ሴቶች ልጆችንም ወለደ፡፡ 11ሄኖስ በአጠቃ
ላይ 905 ዓመት ከኖረ በኋላ ሞተ፡፡
12ቃይናን፣ ዕድሜው 70 ዓመት ሲሆን
መላልኤልን ወለደ፤ 13ቃይናን መላልኤልን
ከወለደ በኋላ 840 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወን
ዶችና ሴቶች ልጆችንም ወለደ፡፡ 14ቃይናን
በአጠቃላይ 910 ዓመት ከኖረ በኋላ ሞተ፡፡
15መላልኤል፣ ዕድሜው 65 ዓመት በሆነ
ጊዜ ያሬድን ወለደ፤ 16መላልኤል ያሬድን
ከወለደ በኋላ 830 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወን
ዶችና ሴቶች ልጆችንም ወለደ፡፡ 17መላል
ኤል በአጠቃላይ 895 ዓመት ከኖረ በኋላ
ሞተ፡፡
18ያሬድ፣ ዕድሜው 162 ዓመት ሲሆን
ሄኖክን ወለደ፤ 19ያሬድ ሄኖክን ከወለደ
በኋላ 800 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና
ሴቶች ልጆችንም ወለደ፡፡ 20ያሬድ በአጠ
ቃላይ 962 ዓመት ከኖረ በኋላ ሞተ፡፡
21ሄኖክ፣ ዕድሜው 65 ዓመት በሆነ ጊዜ
ማቱሳላን ወለደ፤ 22ሄኖክ ማቱሳላን ከወለደ
በኋላ አካሄዱን ከእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ጋር በ
ማድረግ
300 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች
ልጆችንም ወለደ፡፡ 23ሄኖክ በአጠቃላይ
365 ዓመት ኖረ፤ 24ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚ
አብሔር (ኤሎሂም) ጋር አደረገ፤ እግዚአብሔር
(ኤሎሂም) ስለ ወሰደውም አልተገኘም፡፡
25ማቱሳላ፣ ዕድሜው 187 ዓመት ሲ
ሆን ላሜሕን ወለደ፤ 26ማቱሳላ ላሜሕን
ከወለደ በኋላ፣ 782 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች
ወንዶ ችና ሴቶች ልጆችንም ወለደ፤
27ማቱሳላ በአጠቃላይ 969 ዓመት ከኖረ በኋላ
ሞተ፡፡
28ላሜሕ፣ ዕድሜው 182 ዓመት በሆነ
ጊዜ፣ ልጅ ወለደ፡፡ 29ስሙንም "እግዚአብሐ
ር (አዶናይ) በረገማት ምድር ከልፋታችንና
ከጉ ልበታችን ድካም ያሳርፈናል" ሲል
ኖኅ[ገ] ብሎ
ጠራው፡፡ 30ላሜሕ ኖኅን ከወለደ በኋላ፣ 595
ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች
ልጆችንም ወለደ፡፡ 31ላሜሕ በአጠቃላይ
777 ዓመት ከኖረ በኋላ ሞተ፡፡
32ኖኅ ዕድሜው 500 ዓመት ሲሆን ሴምን፣
ካምንና ያፌትን ወለደ፡፡

## የጥፋት ውሃ

6 ሰዎች በምድር ላይ እየበዙ ሲሄዱ ሴቶች
ልጆች ተወለዱላቸው፡፡ 2የእግዚአብሔር
(ኤሎሂም) ወንዶች ልጆች የሰዎችን ሴቶች ልጆች
ውብ ሆነው አዩአቸው፤ ከመካከላቸውም የመ
ረጧቸውን አገቡ፡፡ 3*እግዚአብሔርም* (ያህዌ)፣
"ሰው ሟች[ጠ] ስለ ሆነ መንፈሴ እያዘነ[ጨ]
ከእርሱ ጋር ለዘላለም አይኖርም፤ ዕድሜው
120 ዓመት ይሆናል" አለ፡፡
4የእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ልጆች የሰዎችን ሴቶች
ልጆች ተገናኝተው ልጆች በወለዱ ጊዜም
ሆነ ከዚያም በኋላ ኔፊሊም የተባሉ ሰዎች
በምድር ላይ ነበሩ፡፡ እነርሱም በጥንቱ
ዘመን በጀግንነታቸው ከፍ ያለ ዝና ያተረፉ
ናቸው፡፡
5*እግዚአብሔር* (ያህዌ) አምላክ የሰው ዐመፅ
በምድር ላይ የበዛና የልቡም ሐሳብ ዘወ
ትር ወደ ክፋት ብቻ ያዘነበለ መሆኑን ተመ
ለከተ፡፡ 6*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሰውን በም
ድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፤ ልቡም እጅግ
አዘነ፡፡ 7ስለዚህም *እግዚአብሔር* (ያህዌ)፣ "የፈጠ
ርሁትን የሰው ዘር ከምድረ ገጽ አጠፋለሁ፤
ከሰው እስከ እንስሳ በምድር ላይ ከሚሳቡ
ፍጡራን እስከ ሰማይ ወፎች አጠፋለሁ፤
ስለ ፈጠርኋቸው ተጸጽቻለሁና" አለ፡፡ 8ኖኅ
ግን *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ዘንድ ሞገስን አገኘ፡፡

**4፥25** ቀኑ1፥8፤ዘፍ5፥3፤1ዜና1፥1
**4፥26** ዘፍ5፥6፤12፥8፤13፥4፤21፥33፤22፥9፤26፥25፤33፥20፤35፥1፤ዘፀ17፥15፤1ነገ18፥24፤1ዜና1፥1፤መዝ116፥17፤ኢል2፥32፤ሶፎ3፥9፤ሉቃ3፥38፤ሐሥ2፥21
**5፥1** ዘፍ1፥27፤2፥4፤1ዜና1፥1፤ቆላ3፥10
**5፥2** ዘፍ1፥27፡28፤ማቴ19፥4፤ማር10፥6፤ገላ3፥28፤
**5፥3** ዘፍ1፥26፤4፥25፤ሉቃ3፥38፤1ቆሮ15፥49
**5፥5** ዘፍ2፥17፤ዕብ9፥27
**5፥6** ዘፍ4፥26፤ሉቃ3፥38
**5፥9** 1ዜና1፥2፤ሉቃ3፥37
**5፥12** 1ዜና1፥2፤ሉቃ3፥37
**5፥15** 1ዜና1፥2፤ሉቃ3፥37
**5፥18** 1ዜና1፥3፤ሉቃ3፥37፤ይሁ1፥14
**5፥21** 1ዜና1፥3፤ሉቃ3፥37
**5፥22** ቀኍ24፤ዘፍ6፥9፤17፥1፤24፥40፤48፥15፤2ነገ20፥3፤መዝ116፥9፤ሚክ6፥8፤ሚል2፥6
**5፥24** ቀኍ22፤2ነገ2፥1፡11፤መዝ49፥15፤73፥24፤89፥48፤ዕብ11፥5
**5፥25** 1ዜና1፥3፤ሉቃ3፥36
**5፥29** ዘፍ3፥17፤1ዜና1፥3፤ሉቃ3፥36፤ሮሜ8፥20
**5፥32** ዘፍ6፥10፤7፥6፡11፤8፥13፤9፥18፤10፥1፤1ዜና1፥4፤ኢሳ 65፥20፤ሉቃ3፥36
**6፥1** ዘፍ1፥28
**6፥2** ቀኍ4፤ዘፍ4፥19፤ዘዳ21፥11፤ኢዮ1፥6፤2፥1
**6፥3** ኢዮ10፥9፤34፥14፤መዝ78፥39፤103፥14፤ኢሳ40፥6፤57፥16፤ገላ5፥16-17፤1ጴጥ3፥20
**6፥4** ቀኍ2፤ዘፍ11፥4፤ዘኍ13፥33
**6፥5** ዘፍ8፥21፤38፥7፤ኢዮ34፥26፤መዝ14፥1-3፤ኤር1፥16፤44፥5፤ሕዝ3፥19
**6፥6** ዘፀ32፥14፤1ሳሙ15፥11፡35፤2ሳሙ24፥16፤1ዜና21፥15፤ኢሳ63፥10፤ኤር18፥7-10፤ኤፌ4፥30
**6፥7** ቀኍ17፤ዘፍ7፥4፡21፤ዘዳ28፥63፤29፥20፤ሕዝ33፥28፤ሶፎ1፥2፡18
**6፥8** ዘፍ19፥19፤39፥4፤ዘፀ33፥12፡13፡17፤34፥9፤ዘኍ11፥15፤ሩት2፥2፤ሕዝ14፥14፤ሐሥ7፥46፤ሉቃ1፥30

[የ]25 *ሴት* ማለት *ሰጠ* ሳይሆን አይቀርም
[ደ]26 ወይም *ማወጅ*
[ጀ]2 በዕብራይስጥ *አዳም* ማለት ነው
[ገ]29 *ኖኅ* የሚለው ስም *መጽናናት* የሚል ትርጉም ካለው የዕብራ
ይስጥ ቃል ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው
[ጠ]3 ወይም *በስባሽ*
[ጨ]3 ወይም *መንፈሴ አይኖርም*

9የኖኅ ታሪክ እንደሚከተለው ነው፤ ኖኅ
በዘመኑ ከነበሩት ሰዎች ሁሉ ይልቅ ጻድቅና
ከበደል የራቀ ሰው ነበር፤ አካሄዱንም ከእግ
ዚአብሔር (ኤሎሂም) ጋር አደረገ።
10ኖኅም ሴም፣ ካምና ያፌት የሚባሉ
ሦስት ወንዶች ልጆች ነበሩት።
11ምድር በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ፊት በክፉ ሥራ
ረከሰች፤ በዐመፅም ተሞላች። 12እግዚአብሔር
(ኤሎሂም) ምድር ምን ያህል በክፉ ሥራ እንደ
ረከሰች አየ፤ እነሆ፤ ሰው ሁሉ አካሄዱን አበ
ላሽቶ ነበርና 13ስለዚህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
ኖኅን እንዲህ አለው፦ "ሰውን ሁሉ ላጠፋ
ነው፤ ምድር በሰው ዐመፅ ስለ ተሞላች በእ
ርግጥ ሰውንም ምድርንም አጠፋለሁ። 14አንተ
ግን በጎፈር[ጸ] ዕንጨት መርከብ ሥራ፤
ለመር ከባም ክፍሎች አብጅላት፤ ውስጧንና
ውጭ ዋን በቅጥራን ለብጠው። 15እንዲህ
አድር ገህ ሥራት፦ ርዝመቷ 140 ሜትር፣
ወርዷ 23 ሜትር፣ ከፍታዋ 13.5 ሜትር
ይሁን። 16ለመርከቧ ጣራ አብጅላት፣ ጣራና
ግድግዳው በሚጋጠምበት ቦታ ግማሽ ሜትር
ክፍተት ተው፤[ጸ] ከጐኗ በር አውጣላት፤ ባለ
ሦስት ፎቅ አድርገህ ሥራት። 17እኔም
ከሰማይ በታች የሕይወት እስትንፋስ
ያለባቸውን ሕያ ዋን ፍጡራን ሁሉ ለማጥፋት
እነሆ፤ በምድር ላይ የጥፋት ውሃ አወርዳለሁ፤
በምድር ላይ ያለ ሁሉ ይጠፋል። 18ካንተ
ጋር ግን ቃል
ኪዳን እመሠርታለሁ። አንተና ወንዶች ልጆ
ችህ፣ ሚስትህና የልጆችህ ሚስቶች ከአንተ
ጋር ወደ መርከቧ ትገባላችሁ። 19ከአንተ ጋር
በሕይወት እንዲቈዩ ከሕያዋን ፍጡራን ሁሉ
ተባዕትና እንስት እያደረግህ ሁለት ሁለቱን
ወደ መርከቧ ታስገባለህ። 20ከእያንዳንዱ
የወፍ ወገን፣ ከእያንዳንዱ የእንስሳ ወገን፣
በምድር ላይ ከሚሳቡ ፍጥረት ሁሉ በየወገና
ቸው በሕይወት ይቈዩ ዘንድ ሁለት ሁለት
እየሆኑ ወደ አንተ ይመጣሉ። 21ለአንተና
ለእነርሱ የሚያስፈልገውን ምግብ ሁሉ
አከማች።"
22ኖኅም ሁሉን እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
እንዳዘ ዘው አደረገ።

7 እግዚአብሔር (ያህዌ) ኖኅን እንዲህ አለው፤
"በዚህ ትውልድ መካከል አንተን ጻድቅ
ሆነህ አግኝቼሃለሁና ቤተ ሰብህን በሙሉ
ይዘህ ወደ መርከቧ ግባ። 2ከንጹሕ እንስ
ሳት ሁሉ ሰባት ሰባት[θ] ተባዕትና እንስት፣
3ንጹህ ካልሆኑት እንስሳት ደግሞ ሁለት
ሁለት ተባዕትና እንስት 3እንዲሁም ከወ
ፎች ወገን ሁሉ ሰባት ተባዕትና ሰባት እን
ስት፣ በምድር ላይ ለዘር እንዲተርፉ ከአንተ
ጋር ታስገባለህ። 4ከሰባት ቀን በኋላ አርባ ቀንና
አርባ ሌሊት በምድር ላይ ዝናብ አዘንባለሁ፤
የፈጠርሁትንም ሕያው ፍጡር ሁሉ ከም
ድር ገጽ አጠፋለሁ።"
5ኖኅም እግዚአብሔር (ያህዌ) ያዘዘውን ሁሉ
አደረገ።
6የጥፋት ውሃ በምድር ላይ በወረደ ጊዜ
ኖኅ የ600 ዓመት ሰው ነበር። 7ኖኅና ወን
ዶች ልጆቹ፣ ሚስቱና የልጆቹ ሚስቶች
ከጥፋት ውሃ ለመትረፍ ወደ መርከቧ ገቡ።
8ንጹሕ ከሆኑትና ንጹሕ ካልሆኑት እንስሳት፣
ከወፎችና በምድር ላይ ከሚሳቡ ፍጡራን ሁሉ
ጥንድ ጥንድ፣ 9ተባዕትና እንስት ሆነው
ወደ ኖኅ መጡ፤ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ኖኅን
ባዘዘውም መሠረት ወደ መርከቧ ገቡ።
10ከሰባት ቀንም በኋላ የጥፋት ውሃ በምድር
ላይ መጣ።
11ኖኅ በተወለደ በ600ኛው ዓመት፣
በሁ ለተኛው ወር፣ ከወሩም በዐሥራ
ሰባተኛው ቀን፣ በዚያ ቀን የታላቁ ጥልቅ
ምንጮች በሙሉ ተነደሉ፤ የሰማይ
መስኮቶችም ተከ ፈቱ፤ 12አርባ ቀንና
አርባ ሌሊት በምድር ላይ ዝናብ ዘነበ።
13በዚያኑ ዕለት ኖኅና ልጆቹ ሴም፣ ካምና
ያፌት፣ እንዲሁም ሚስቱና ሦስቱ የል
ጆቹ ሚስቶች ወደ መርከቧ ገቡ። 14ከዱር
እንስሳት ከየወገኑ፣ ከቤት እንስሳት ከየወ
ገኑ፣ በምድር ላይ ከሚሳቡ ፍጡራን ከየወገና
ቸው፣ ከወፎችም ከየወገናቸውና ክንፍ ያላ
ቸው ሁሉ አብረዋቸው ገቡ። 15የሕይወት
እስትንፋስ ያለባቸው ፍጡራን በሙሉ ጥንድ
ጥንድ እየሆኑ ወደ ኖኅ በመምጣት መርከቧ
ውስጥ ገቡ። 16ከሕያዋንም ፍጡራን ሁሉ
እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ኖኅን ባዘዘው መሠረት ተባ
ዕትና እንስት እየሆኑ ገቡ፤ ከዚያም እግዚ
አብሔር (ያህዌ) ከውጭ ዘጋበት።
17የጥፋት ውሃም ለአርባ ቀናት ያለማቋ
ረጥ በምድር ላይ ዘነበ፤ ውሃው እየጨመረ
በሄደ መጠን መርከቧን ከምድር ወደ ላይ
አነሣት። 18ውሃው በምድር ላይ በጣም እየ
ጨመረና ከፍ እያለ ሲሄድ፣ መርከቧ በው
ሃው ላይ ተንሳፈፈች። 19ውሃው በጣም ከፍ
በማለቱ፣ ከሰማይ በታች ያሉትን ታላላቅ
ተራሮች ሁሉ ሸፈናቸው። 20ውሃው ከተራ
ሮቹ ጫፍ በላይ 7 ሜትር ያህል ከፍ አለ።
21በምድር ላይ የነበሩ ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ፦
ወፎች፣ የቤት እንስሳት፣ የዱር እንስሳት
በምድር የሚርመሰመሱ ፍጡራን፣ ሰዎችም

6፥9 ዘፍ2፥4፤5፥22፤17፥1፤27፥1፤ዘዳ18፥13፤2ሳሙ22፥24፤ኢዮ1፥1፤4፥6፤9፥21፤12፥4፤31፥6፤መዝ15፥2፤18፥23፤19፥13፤37፥37:39፤ምሳ2፥7፤ኤር15፥1፤ሕዝ14፥14፡20፤ዳን10፥11፤ሉቃ1፥6፤ዕብ11፥7፤2ጴጥ2፥5
6፥10 ዘፍ5፥32፤ሉቃ3፥36
6፥11 ዘዳ31፥29፤መሳ2፥19፤መዝ7፥9፤73፥6፤ዕዝ7፥23፤8፥17፤28፥16፤ሚል2፥16
6፥12 ዘፀ32፥7፤ዘዳ4፥16፤9፥12፡24፤መዝ14፥1-3
6፥13 ቍ17፤ዘፍ7፥4፡21-23፤ዘዳ28፥63፤ኢዮ34፥15፤2ነገ8፥19፤ዕዝ9፥14፤ኢሳ5፥6፤24፥1-3፤ኤር44፥11: 27፤ሕዝ7፥2-3
6፥14 ዘፀ2፥3፤ዕብ11፥7፤1ጴጥ3፥20
6፥17 ቍ7፥13፤መዝ29፥10፤2ጴጥ2፥5
6፥18 ዘፍ7፥1፡7፡13፤9፥9-16፤17፥7፤19፥12፤ዘፀ6፥4፤34፥10፡27፤ዘዳ29፥13፡14-15፤መዝ25፥10፤74፥20፤106፥45፤ኢሳ55፥3፤ኤር32፥40፤ሕዝ16፥60፤ሐጌ2፥5፤1ጴጥ3፥20
6፥19 ዘፍ7፥15
6፥20 ዘፍ1፥11፤7፥3፡15
6፥22 ዘፍ7፥5፡9፡16፤ዘፀ7፥6፤39፥43፤40፥16፡19፡21፡23፡25፡27፡29፡32
7፥1 ዘፍ6፥9፡18፤ሕዝ14፥14፤ማቴ24፥38፤ሉቃ17፥26-27፤ዕብ11፥7፤1ጴጥ3፥20፤2ጴጥ2፥5
7፥2 ቍ8፤ዘፍ8፥20፤ዘሌ10፥10፤11፥1-47፤ዘዳ14፥3-20፤ሕዝ44፥23፤ሐጌ2፥12፤ሐሥ10፥14-15
7፥3 ዘፍ6፥20
7፥4 ቍ12፡17፤ዘፍ8፥2፤6፥7፡13፤ዘፀ24፥18፤32፥1፤34፥28፤ዘኍ13፥25፤ዘዳ9፥9፡11፡18፡25፤10፥10፤1ሳሙ17፥16፤1ነገ13፥34፤19፥8፤ኢዮ37፥6፡13፤ማቴ4፥2፤ኤር28፥16፤
7፥5 ዘፍ6፥22
7፥6 ዘፍ5፥32
7፥7 ዘፍ6፥18
7፥8 ቍ2
7፥9 ዘፍ6፥22
7፥10 ቍ4
7፥11 ዘፍ1፥7፤5፥32፤8፥2፡4፡14፤2ነገ7፥2፤ኢዮ28፥11፤መዝ36፥6፤42፥7፤78፥23፤ምሳ8፥24፤ኢሳ51፥10፤24፥18፤ሕዝ26፥19፤ሚል3፥10 7፥12 ቍ4፤1ሳሙ12፥17፤ኢዮ28፥26 7፥13 ዘፍ6፥18፤8፥16፤1ጴጥ3፥20፤2ጴጥ2፥5 7፥14 ዘፍ1፥11 7፥15 ቍ8-9፤ዘፍ6፥19 7፥16 ዘፍ6፥22 7፥17 ቍ4 7፥19 መዝ104፥6 7፥20 ዘፍ8፥4-5፤2ጴጥ3፥6 7፥21 ዘፍ6፥7፡13፤2ጴጥ3፥6

[ጸ]14 በዕብራይስጥ የዚህ ቃል ትርጒም አይታወቅም
[ጸ]16 ወይም *ለብርሃን መግቢያ አድርገህ፣ ሥራ*
[θ]2 ወይም *ሰባት ጥንድ፤* በቍ 3ም እንዲሁ

በሙሉ ጠፉ:: 22በአፍንጫቸው የሕይወት
እስትንፋስ ያላቸው በየብስ የነበሩ ፍጡራን
ሁሉ ሞቱ:: 23ሕይወት ያላቸው ፍጡራን
ሁሉ ከምድር ገጽ ጠፉ፤ ሰዎችና እንስሳት
በምድር ላይ የሚሳቡ ፍጡራንና የሰማይ
ወፎች ከምድር ላይ ጠፉ፤ ኖኅና ከእርሱ
ጋር በመርከቧ ውስጥ የነበሩት ብቻ ተረፉ::
24ውሃውም ምድርን ሸፍኖ መቶ አምሳ ቀን
ቈየ::

8 እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ኖኅንና በመርከቧ
ውስጥ ከእርሱ ጋር የነበሩትን የዱርና
የቤት እንስሳት ሁሉ አሰበ፤ በምድር ላይ
ነፋስ እንዲነፍስ አደረገ፤ ውሃውም
ጐደለ:: 2የጥ ልቁ ምንጮችና የሰማይ
ውሃ መስኮቶች ተዘጉ፤ ዝናቡም መዝነቡን
አቆመ:: 3ውሃው ከምድር ላይ ቀስ በቀስ
እየቀነሰ መጣ፤ ከመቶ አምሳ ቀን በኋላም
ጐደለ:: 4በሰባ ተኛው ወር፣ በዐሥራ
ሰባተኛው ቀን መር ከቧ በአራራት ተራሮች
ላይ ዐረፈች:: 5ውሃው እስከ ዐሥረኛው ወር
ድረስ እየቀነሰ መጣ፤ በዐሥረኛው ወር፣
በመጀመሪያው ቀን የተ ራሮቹ ጫፎች
ታዩ::
6ከአርባ ቀን በኋላ ኖኅ የሠራውን የመ
ርከቧን መስኮት ከፍቶ፣ 7ቍራን ወደ ውጭ
ላከ፤ ቍራውም ውሃው ከምድር ላይ እስ
ኪደርቅ ድረስ ወዲያና ወዲህ ይበር ነበር::
8ከዚያም በኋላ፣ ኖኅ ውሃው ከምድር ገጽ ጐድሎ
እንደ ሆነ ለማወቅ ርግብን ላከ፤ 9ነገር ግን
ውሃው የምድርን ገጽ ገና እንደ ሸፈነ ስለ
ነበር፣ ተመልሳ ኖኅ ወዳለበት መርከብ
መጣች፤ እርሱም እጁን ዘርግቶ ተቀበላት፤
ወደ መርከቢቱም አስገባት:: 10ሰባት ቀን
ከቈየ በኋላ ኖኅ ርግቧን እንደ ገና ላካት::
11እርሷም ወደ ማታ ተመለሰች፤ እነሆም
የለመለመ የወይራ ቅጠል በአፏ ይዛ ነበር፤
ያን ጊዜ ኖኅ ውሃው ከምድር ላይ መጕ
ደሉን ዐወቀ:: 12ሰባት ቀንም ቈይቶ ርግ
ቧን እንደ ገና ላካት፤ በዚህ ጊዜ ግን ርግቧ
ወደ እርሱ አልተመለሰችም::
13ኖኅ በተወለደ በ601ኛው ዓመት፣ በመ
ጀመሪያው ወር፣ ከወሩም በመጀመሪያው
ቀን ውሃው ከምድር ላይ ደረቀ:: 14ኖኅ
በመርከቡ ላይ ያለውን ክዳን አንሥቶ ተመ
ለከተ፤ የመሬቱም ገጽ እንደ ደረቀ አየ::
በሁለተኛው ወር፣ በሃያ ሰባተኛው ቀን ምድ
ሪቱ ሙሉ በሙሉ ደረቀች::
15ከዚያም እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ኖኅን እንዲህ
አለው፤ 16"አንተና ሚስትህ፣ ልጆችህና
የልጆችህ ሚስቶች ከመርከቧ ውጡ::
17እንዲዋለዱ፣ እንዲራቡና በምድር ላይ
እንዲበዙ፣ ከአንተ ጋር ያሉትን እንስሳትና
በምድር ላይ የሚሳቡ ሕያዋን ፍጡራንን

7፥22 ዘፍ1፥30
7፥23 ኢዮ14፥19፤
21፥18፤22፥11፥16፤
መዝ90፥5፤ኢሳ28፥2፤
ማቴ24፥39፤ሉቃ17፥2
7፤ዕብ11፥7፤1ጴጥ
3፥20፤2ጴጥ2፥5፤
7፥24 ዘፍ8፥3፤
ኢዮ12፥15
8፥1 ዘፍ9፥15፤19፥
29፤21፥1፤30፥22፤ዘፀ
2፥24፤14፥21፤ዘኍ10፥
9፤ኢሱ2፥10፤3፥16
፤ሩት4፥13፤1ሳሙ1፥
11፥19፤2ነገ20፥3፤1ዜና
16፥15፤ነህ1፥8፤5፥19፤
13፥14፥22፥31፤ኢዮ
12፥15፤14፥13፤መዝ
66፥6፤105፥42፤106፥4
፤ኢሳ11፥15፤44፥27፤
ናሆ1፥4፤ሉቃ1፥54፥72
8፥2 ዘፍ7፥4፥11
8፥3 ዘፍ7፥24
8፥4 ዘፍ7፥11፥20፤
2ነገ19፥37፤ኤር51፥27
8፥6 ዘፍ7፥12
8፥7 ቀኍ11፤ዘሌ11፥
15፤ዘዳ14፥14፤1ነገ17፥
4፥6፤ኢዮ38፥41፤መዝ
147፥9፤ምሳ30፥17፤
ኢሳ34፥11፤ሉቃ12፥24
8፥8 ኢዮ30፥31፤
መዝ 55፥6፤74፥19፤
ማሕ2፥12፥14፤ኢሳ
38፥14፤59፥11፤60፥8፤
ኤር48፥28፤ሕዝ7፥
16፤ሆሴ7፥11፤11፥
11፤ናሆ2፥7፤ማቴ3፥
16፤10፥16ዮሐ1፥32
8፥11 ቀኍ7
8፥13 ዘፍ5፥32
8፥14 ዘፍ7፥11
8፥16 ዘፍ7፥13
8፥17 ዘፍ1፥22
8፥18 1ጴጥ3፥20፤
2ጴጥ2፥5
8፥20 ዘፍ7፥8፤12፥
7-8፤13፥18፤22፥2፥
9፥13፤26፥25፤33፥20፤
35፥7፤ዘፀ10፥25፤17፥
15፤20፥24፤24፥4፤40፥
29፤ዘሌ1፥3፤4፥29፤6፥8
-3፤ዘኍ6፥11፤መሳ
6፥26፤11፥31፤1ሳሙ
20፥29፤ኢዮ1፥5፤42፥8
8፥21 ዘፍ3፥17፤
6፥5፤9፥11፥15፤ዘፀ
29፥18፥25፤ዘሌ1፥9፥
13፤2፥9፤4፥31፤ዘኍ
15፥3፥7፤መዝ51፥5፤
ኢሳ54፥9፤ኤር17፥9፤
44፥11፤ማቴ15፥19፤
ሮሜ1፥21፤2ቆሮ2፥15
8፥22 ዘፍ1፥14፤ኢሱ
3፥15፤መዝ67፥6፤74፥1
7፤ኤር5፥24፤ዘካ14፥8
9፥1 ዘፍ1፥22
9፥2 ዘፍ1፥26
9፥3 ዘፍ1፥29፤
ሐሥ10፥15፤ቆላ2፥16
9፥4 ዘሌ3፥17፤7፥
26፤17፥10-14፤

ሁሉ ይዘሃቸው ውጣ::"
18ኖኅም ከልጆቹ፣ ከሚስቱና ከልጆቹ ሚስ
ቶች ጋር ወጣ:: 19እንስሳቱ ሁሉ፣ ወፎችም፣
በምድር የሚንቀሳቀሱ ሁሉ በየወገናቸው
ከመርከቧ ወጡ::
20ከዚያም ኖኅ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) መሠ
ዊያ ሠራ፤ መሠዊያው ላይ ንጹሕ ከሆ
ኑት እንስሳት ሁሉ፣ እንዲሁም ንጹሕ
ከሆኑት ወፎች የሚቃጠል መሥዋዕት አቀ
ረበ፤ 21" እግዚአብሔርም (ያህዌ) ደስ የሚያሰኘ
ውን መዐዛ አሸተተ፤ በልቡም እንዲህ አለ፤
"ምንም እንኳ ሰው ገና ከልጅነቱ ጀምሮ ሐሳቡ
ወደ ክፋት ያዘነበለ ቢሆንምፊ በእርሱ ምክ
ንያት ሁለተኛ ምድርን አልረግማትም፤
አሁን እንዳደረግሁት ሕያዋን ፍጡራንን
ዳግመኛ አላጠፋም::

22"ምድር እስካለች ድረስ፣
የዘር ወቅትና መከር፣
ሙቀትና ቅዝቃዜ
በጋና ክረምት፣
ቀንና ሌሊት፣
አይቋረጡም::"

## እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር የገባው ኪዳን

9 እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ኖኅንና ልጆቹን እን
ዲህ ሲል ባረካቸው፤ "ብዙ ተባዙ፤ ምድ
ርንም ሙሏት፤ 2አስፈሪነታችሁና አስደንጋ
ጭነታችሁ፡- በዱር አራዊት፣ በሰማይ አዕ
ዋፍ፣ በደረት በሚሳቡ ተንቀሳቃሽ ፍጡሮ
ችና በባሕር ዓሦች ሁሉ ላይ ይሁን፤ በእ
ጃችሁ ተሰጥተዋል:: 3ሕያውና ተንቀሳቃሽ
ፍጡር ሁሉ ምግብ ይሁናችሁ፤ ለምለሙን
ዕፀዋት እንደ ሰጠኋችሁ፣ አሁን ደግሞ ሁሉን
ሰጠኋችሁ::
4"ነገር ግን ሕይወቱ፣ ማለት ደሙ ገና
በውስጡ ያለበትን ሥጋ አትብሉ:: 5ሰውን
የገደለ ሁሉ ስለሚቹ ደም ተጠያቂ ነው፤
የሚቹን ሰው ደም ከገዳዩ፣ ከእንስሳም ይሁን
ከሰው እሻለሁ::

6"የሰውን ደም የሚያፈስ ሁሉ፣
ደሙ በሰው እጅ ይፈሳል፤
በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) አምሳል፣
እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰውን ሠርቶታልና::
7እናንተ ግን ብዙ ተባዙ፤ ዘራችሁ በም
ድር ላይ ይብዛ፤ ይንሠራፉ::"
8እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ኖኅንና አብረውት ያሉ
ትን ልጆቹን እንዲህ አላቸው፤ 9"እነሆ፤ ከእ
ናንተና ከእናንተ በኋላ ከሚመጣው ዘራችሁ

19፥26፤ዘዳ12፥16፥23-25፤15፥23፤1ሳሙ14፥33፤ሕዝ33፥25፤ሐሥ
15፥20፥29 9፥5 ዘፍ4፥10፤42፥22፤50፥15፤ዘፀ21፥28-32፤1ነገ
2፥32፤2ዜና24፥22፤መዝ9፥12 9፥6 ዘፍ1፥26፤4፥14፤መሳ9፥24፤
ማቴ26፥52 9፥7 ዘፍ1፥22 9፥9 ቀኍ11፤ዘፍ6፥18
ፊ21 ወይም ስለሆነ

ጋር ኪዳኔን እመሠርታለሁ፤ 10እንዲሁም ከእ
ናንተ ጋር ከነበሩት ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ፦
ከወፎች፣ ከቤት እንስሳት፣ ከዱር
እንስሳት፣ ከእናንተ ጋር ከመርከቧ ከወጡት
በምድር ላይ ካሉት ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ
ጋር ኪዳን እገባ ለሁ። 11ከእንግዲህ ሕ
ይወት ያለው ፍጡር ሁሉ በጥፋት ውሃ
እንደማይጠፋ፣ ዳግመኛም ምድርን የሚያጠፋ
ውሃ ከቶ እንደማይመጣ ከእናንተ ጋር ኪዳን
እገባለሁ።”
12እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) እንዲህ አለ፤ በእ
ኔና በእናንተ መካከል፣ ከእናንተም ጋር
ካሉ ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ ጋር ከሚመጣ
ውም ትውልድ ሁሉ ጋር፣ የማደርገው
የኪዳኑ ምልክት ይህ ነው፤ 13ቀስተ ደመና
ዬን በደመና ላይ አደርጋለሁ፤ ይህም በእ
ኔና በምድር መካከል ለገባሁት ኪዳን ምል
ክት ይሆናል። 14ደመናን በምድር ላይ በጋ
ረድሁና ቀስቴም በደመና ላይ በሚታይበት
ጊዜ ሁሉ፣ 15ከእናንተና ከሕያዋን ፍጡራን
ሁሉ ጋር የገባሁትን ኪዳን አስባለሁ፤ ሕይ
ወት ያለውንም ሁሉ ያጠፋ ዘንድ፣ ከእ
ንግዲህ የጥፋት ውሃ ከቶ አይመጣም።
16ቀስቱ በደመና ላይ ተገልጦ በማይበት
ጊዜ ሁሉ፣ በእኔና በምድር ላይ ባሉ ሕያ
ዋን ፍጡራን መካከል ያለውን ዘላለማዊ ኪዳን
አስባለሁ።”
17ስለዚህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ኖኅን፣ “ይህ
በእኔና በምድር ላይ በሚኖሩ ሕያዋን ሁሉ
መካከል የገባሁት ኪዳን ምልክት ነው” አለው።

## የኖኅ ልጆች

18ከመርከቧ የወጡትም የኖኅ ልጆች ሴም፣
ካምና ያፌት ነበሩ፤ ካም የከነዓን አባት
ነው። 19ሦስቱ የኖኅ ልጆች እነዚህ ሲሆኑ፣
በምድር ላይ የሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ የተገ
ኙት ከእነዚሁ ነው።
20ኖኅ ገበሬ ነበረና ወይን ተከለ፤[ተ] 21ከወ
ይኑም ጠጅ ጠጥቶ ሰከረና በድንኳኑ ውስጥ ዕር
ቃኑን ተኛ። 22የከነዓን አባት፣ ካም የአባቱን ዕር
ቃን ሥጋ አየ፤ ወደ ውጭም ወጥቶ ለሁ
ለቱ ወንድሞቹ ነገራቸው። 23ሴምና ያፌት
ግን ልብስ ወስደው በጫንቃቸው ላይ አደ
ረጉና የአባታቸውን ዕርቃን ሥጋ እንዳያዩ
ፊታቸውን አዙረው የኋሊት በመሄድ የአባታ
ቸውን ዕርቃን ሥጋ ሸፈኑ።
24ኖኅ ከወይን ጠጁ ስካር ሲነቃ፣ ታናሽ
ልጁ ያደረገበትን ዐወቀ፤ 25እንዲህም አለ፤

“ከነዓን የተረገመ ይሁን፤
ለወንድሞቹም፣ የባሪያ ባሪያ ይሁን።”
26ደግሞም፤

“የሴም አምላክ እግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) ይባረክ፤
ከነዓንም የሴም[ሀ] ባሪያ ይሁን።”

9፥11 ቍ9:16፤ዘፍ 8፥21፤ኢሳ24፥5፤ 33፥8፤ሆሴ6፥7
9፥12 ቍ17፤17፥ 11:12፤ዘፀ12፥14፤ዘሌ 3፥17፤6፥18፤17፥7፤ ዘኍ10፥8
9፥13 ቍ14፤ሕዝ 1፥28፤ራእ4፥3፤10፥1
9፥14 ቍ13
9፥15 ዘፍ8፥1:21፤ ዘፀ2፥24፤6፥5፤34፥10 ፤ዘሌ26፥42:45፤ዘዳ7፥ 9፤መዝ89፥34፤103፤ 18፤105፥8፤106፥45፤ ሕዝ16፥60
9፥16 ቍ11:13፤ዘፍ 17፥7:13:19፤2ሳሙ 7፥13፤23፥5፤መዝ105፥ 9-10፤ኢሳ9፥7፤54፥ 10፤55፥3፤59፥21፤61፥ 8፤ኤር31፥31-34፤ 32፥40፤33፥21፤ሕዝ 16፥60፤37፥26፤ ዕብ13፥20
9፥17 ቍ12
9፥18 ቍ25-27፤ዘፍ 5፥32፤10፥6:15፤ሉቃ3 ፥36
9፥19 ዘፍ1፥22፤5፥ 32፤10፥32፤11፥4:8:9
9፥21 ዘፍ19፥35
9፥22 ዕን2፥15
9፥25 ቍ18፤ዘፍ 25፥23፤27፥12:29: 37:40፤37፥10፤49፥8፤ ዘፀ20፥5፤ዘኍ24፥18፤ ኢሱ9፥23፤መዝ79፥8፤ ኢሳ14፥21፤ኤር31፥ 29፤32፥18
9፥26 ዘፍ14፥20፤ ዘፀ18፥10፤መዝ7፥17፤ 1ነገ9፥21
9፥27 ዘፍ10፥2-5፤ ኤፌ2፥13-14፤3፥6
9፥29 ዘፍ2፥17
10፥1 ቍ32፤ዘፍ 2፥4፤5፥32፤1ዜና1፥4
10፥2 ኢሳ66፥19፤ ሕዝ27፥13:19፤32፥26 ፤38፥2:6፤39፥1:6፤ ራእ20፥8
10፥3 ኤር51፥27፤ ሕዝ27፥14፤38፥6
10፥4 ዘኍ24፥24፤ መዝ48፥7፤72፥10፤ ኢ ሳ2፥16፤23፥1:6:10: 12:14፤60፥9፤66፥19፤ ኤር2፥10፤10፥9፤ሕዝ 27፥6:7:12:25፤38፥13 ፤ዳን11፥30፤ዮና1፥3
10፥5 ዘፍ9፥27
10፥6 ዘፍ9፥18፤2ነገ 19፥9፤2ዜና12፥3፤16፥ 8፤ኢሳ11፥11፤18፥1፤ 20፥3፤43፥3፤ኤር46፥9፤ ሕዝ27፥10፤30፥4:9፤ 38፥5፤ናሆ3፥9፤ሶፎ2፥12፤ 3፥10
10፥7 ዘፍ2፥11፤25፥3፤ 1ነገ10፥1፤1ዜና1፥32፤ 2ዜና9፥1፤ኢዮ1፥15፤

27“እግዚአብሔር (ኤሎሂም) የያፌትን[ለ] ግዛት ያስፋ፤
ያፌት በሴም ድንኳኖች ይኑር፤
ከነዓንም የእርሱ[ሐ] ባሪያ ይሁን” አለ።
28ኖኅ ከጥፋት ውሃ በኋላ 350 ዓመት
ኖረ፤ 29ኖኅ በአጠቃላይ 950 ዓመት ኖሮ ሞተ።

## የኖኅ ልጆች ትውልድ

10 የኖኅ ልጆች የሴም፣ የካምና የያ
ፌት ትውልድ ይህ ነው፤ እነር
ሱም ራሳቸው ከጥፋት ውሃ በኋላ ወንዶች
ልጆችን ወለዱ።

## የያፌት ዝርያዎች

10፥2-5 ተጓ ምብ - 1ዜና 1፥5-7

2የያፌት ልጆች፦[መ]
ጋሜር፣ ማጎግ፣ ማዴ፣ ያዋን፣ ቶቤል፣
ሞሳሕ፣ ቴራስ ናቸው።
3የጋሜር ልጆች፦
አስከናዝ፣ ራፋት፣ ቴርጋማ ናቸው።
4የያዋን ልጆች፦
ኤሊሳ፣ ተርሴስ፣ ኪቲም፣ ሮዳኢ[ሠ] ናቸው።
5ከእነዚህም በየነገዳቸው፣ በየጐሣቸውና በየ
ቋንቋቸው ተከፋፍለው በባሕር ዳርና በደ
ሴቶች፣ በየምድራቸው የሚኖሩ ሕዝቦች ወጡ።

## የካም ዝርያዎች

10፥6-20 ተጓ ምብ - 1ዜና 1፥8-16

6የካም ልጆች፦
ኩሽ፣ ምጽራይም፣ [ረ]ፉጥ፣ ከነዓን ናቸው።
7የኩሽ ልጆች፦
ሳባ፣ ኤውላጥ፣ ሰብታ፣ ራዕማ፣ ሰበቅታ
ናቸው።

የራዕማ ልጆች፦
ሳባ፣ ድዳን ናቸው።
8ኩሽ የናምሩድ አባት[ሰ] ነበረ፤ ናምሩድም
በምድር ላይ ኀያል ሰው እየሆነ ሄደ። 9*በእ
ግዚአብሔር* (ያህዌ) *ፊት* ብርቱ አዳኝ ነበረ፤
ስለዚህም፣ “*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) *ፊት* እንደ
ናምሩድ ብርቱ አዳኝ” ይባል ነበር። 10የግ
ዛቱም የመጀመሪያ ከተሞች፦ ባቢሎን፣ ኦሬክ፣

6፥19፤16፥11፤መዝ72፥10:15፤ኢሳ21፥13፤43፥3፤60፥6፤ኤር6፥20፤ 25፥23-24፤49፥8፤38፥13፤ሕዝ27፥15:20:22፤38፥13፤ኢል3፥8
10፥8 ሚክ5፥6 10፥9 ዘፍ25፥27፤27፥3፤2ዜና14፥9፤16፥8፤ኢሳ 18፥2 10፥10 ዘፍ11፥2:9፤14፥1፤2ዜና36፥17፤ዕዝ4፥9፤ኢሳ10፥9፤ 13፥1፤47፥1፤ኤር21፥2፤25፥12፤50፥1፤አሞ6፥2፤ዘካ5፥11

[ተ]20 ወይም *የመጀመሪያ ነበር*
[ሀ]26 ወይም የእርሱ ባሪያ ይሁን
[ለ]27 *ያፌት* የሚለው ቃል *መዝርጋት* የሚል ትርጉም ካለው የዕብራይ ስጥ ቃል ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው
[ሐ]27 ወይም *የእነርሱ*
[መ]2 *ልጆች* ማለት *ዘርዐ ትውልዶች* ወይም *ወራሾች* ወይም *ሕዝቦች* ማለት ሊሆን ይችላል፤ በቍ 3:4:6:7:20-23: 29 እና 31 እንዲሁ
[ሠ]4 ጥቂት የማሶሬቲክ የጥንት ጽሑፎች፣ ከአሪተ ሳምራውያን፣ ሰብዐ ሊቃናትና አብዛኞቹ የማሶሬቲክ የጥናት ጽሑፎች የሚሉት *ዶዳኒም* ነው
[ረ]6 ቍ13ትንም ጨምሮ ግብፅን ያመለክታል
[ሰ]8 ቍ13:15:24 እና 26ትን ጨምሮ *አባት* ማለት *ቅድመ አያት* ወይም *ተተኪ* ወይም *መሥራች* ማለት ሊሆን ይችላል።

አርካድና ካልኔ ናቸው፤ እነዚህ በ[ሸ]ሰናዖር[ቀ] ምድር ነበሩ። 11ከዚያም ምድር ወደ አሦር ወጥቶ ነነዌን፣ ረሆቦትን፣[በ] ካለህን 12እንዲሁም በነነዌና በካለህ መካከል ሬሰን ቄረ ቄረ፤ ታላቋንም ከተማ መሠረተ።

13ምጽራይም፦

የሉዳማውያን፣ የዕሚማውያን፣ ላህቢያውያን፣ የነፍታሌማውያን፣ 14የፈትሩሲማውያን፣ ፍልስጥኤማውያን የተገኙባቸው የከስሉሂማውያን፣ የቀፍቶሪማውያን አባት ነበረ።

15ከነዓንም፦

የበኵር ልጁ[ተ] የሲዶን፣ የኬጢያውያን፣ 16የኢያቡሳውያን፣ የአሞራውያን፣ የጌርሳውያን አባት ነበረ፤ 17እንዲሁም የኤዊያውያን፣ የዐርኪዋናውያን፣ የሲኒያውያን፣ 18የአራዴዎናውያን፣ የሰማሪናውያን፣ የአማቲያውያን አባት ነበረ።

ከጊዜ በኋላ የከነዓን ጐሣዎች በየስፍራው ተሠራጩ፤ 19የከነዓን ወሰን ከሲዶና አንሥቶ በጌራራ በኩል እስከ ጋዛ ይደርሳል፤ ከዚያም በሰዶም በኩል ገሞራን፣ አዳማንና ሰቦይን ይዞ እስከ ላሣ ይዘልቃል።

20እነዚህም በየጐሣቸውና በየቋንቋቸው፣ በየምድራቸውና በየነገዳቸው ይኖሩ የነበሩ የካም ዝርያዎች ናቸው።

## የሴም ዝርያዎች

10፥21-31 ተጓ ምብ - ዘፍ 11፥10-27፤ 1ዜና 1፥17-27

21ለያፌት ታላቅ ወንድም[ቸ] ለሴም ደግሞ ወንዶች ልጆች ተወለዱለት፤ እርሱም የዔቦር ልጆች ሁሉ ቅደመ አያት ነው።

22የሴም ልጆች፦

ኤላም፣ አሦር፣ አርፋክስድ፣ ሉድ፣ አራም ናቸው።

23የአራም ልጆች፦

ዑፅ፣ ሁል፣ ጌቴር፣ ሞሶሕ[ኀ] ናቸው።

24አርፋክስድ ሳላን ወለደ፤[ነ]

ሳላም ዔቦርን ወለደ።

25ለዔቦርም ሁለት ወንዶች ልጆች ተወለዱለት፤

አንደኛው ልጅ በዘመኑ ምድር ተከፍላ ስለ ነበር ፍሌቅ[ኘ] ተባለ፤ ወንድሙም ዮቅጣን ተባለ።

26ዮቅጣንም፦ የኤልሞሳድ፣ የሣሌፍ፣ የሐስረሞት፣ የያራሕ፣ 27የሀደራም፣ የአውዛል፣ የደቅላ አባት ነበረ፤ 28እንዲሁም የዖባል፣ የአቢማኤል፣ የሳባ፣ 29የኦፊር፣ የኤውላጥ፣ የዮባል አባት ነበረ፤ እነዚህ ሁሉ የዮቅጣን ልጆች ናቸው።

30መኖሪያ ስፍራቸውም እስከ ሶፋር ድረስ ይዘልቃል።

31እነዚህም በየጐሣቸውና በየቋንቋቸው፣ በየምድራቸውና በየነገዳቸው ይኖሩ የነበሩ የሴም ዝርያዎች ናቸው።

32የኖኅ ወንዶች ልጆች ጐሣዎች እንደ ትውልዳቸው በየነገዳቸው እነዚህ ነበሩ። ከጥፋት ውሃ በኋላ ሕዝቦች በምድር ላይ የተሠራጩት ከእነዚሁ ነው።

## የባቤል ግንብ

11 በዚያን ጊዜ ሰዎች ሁሉ የሚናገሩ ትና የሚግባቡበት ቋንቋ አንድ ብቻ ነበር። 2ሰዎቹም ምሥራቁን[አ] ይዘው ሲጓዙ፣ በሰናዖር[ከ] አንድ ሜዳ አግኝተው በዚያ ሰፈሩ።

3እነርሱም እርስ በርሳቸው፣ "ኑ፤ ጡብ እንሥራ፤ እስኪበቃውም በእሳት እንተኵሰው" ተባባሉ። በድንጋይ ፈንታ ጡብ፣ ለማያያዣም ቅጥራን ተጠቀሙ። 4ከዚያም "ለስማችን መጠሪያ እንዲሆንና በምድር ላይ እንዳንበተን፣ ኑ፤ ከተማና ሰማይ የሚደርስ ግንብ ለራሳችን እንሥራ" አሉ።

5እግዚአብሔር (ያህዌ) ግን ሰዎቹ ይሠሩ የነበሩትን ከተማና ግንብ ለማየት ወረደ። 6እግዚአብሔርም (ያህዌ) እንዲህ እንደ አንድ ሕዝብ አንድ ቋንቋ በመናገር ይህን ማድረግ ከጀመሩ፣ ከእንግዲህ ያቀዱትን ሁሉ ማከናወን አያዳግታቸውም። 7ኑ እንውረድ፤ እርስ በርሳቸውም እንዳይግባቡ ቋንቋቸውን እንደበላልቀው።"

8ስለዚህ እግዚአብሔር (ያህዌ) በምድር ሁሉ ላይ በታተናቸው፤ ከተማዋንም መሥራት አቆሙ። 9እግዚአብሔር (ያህዌ) በዚያ የመላውን ዓለም ቋንቋ ስለ ደበላለቀ የከተማዪቱ ስም ባቤል[ኸ] ተባለ። ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሰዎቹን በምድር ሁሉ በተናቸው።

10፥11 2ነገ19፥36፤ መዝ83፥8፤ ኢሳ37፥37፤ ሚክ5፥6፤ ዮና1፥2፤ 3፥2፡3፤4፥11፤ ናሆ1፥1፤ ሶፎ2፥13
10፥14 ዘፍ21፥32፡34፤26፥1፡8፤ ዘዳ2፥23፤ 1ዜና1፥12፤ ኢሱ13፥2፤ መሳ3፥3፤ ኢሳ14፥31፤ ኤር47፥1፡4፤ አሞ9፥7
10፥15 ቍ 19፤ ዘፍ 9፥18፤15፥20፤23፥3፡20፤25፥10፤26፥34፤27፥46፤49፥32፤ ዘፀ4፥22፤ ዘኍ1፥20፤3፥2፤13፥29፤18፥15፤26፥5፤33፥4፤ ኢሱ1፥4፤11፥8፤ መሳ10፥6፤ 1ሳሙ26፥6፤ ኢሳ23፥2፡4፤ ኤር25፥22፤27፥3፤47፥4፤ ሕዝ16፥3፤28፥21፤32፥30፤ ኢል3፥4፤ ዘካ9፥2
10፥16 ዘፍ15፥18-21፤ ዘፀ3፥8፤ ዘኍ13፥29፤21፥13፤32፥39፤ ዘዳ1፥4፤7፥1፤ ኢሱ2፥10፤ መሳ19፥10፤ 1ዜና11፥4፤ 2ዜና8፥7፤ ዕዝ9፥1
10፥17 ዘፍ34፥2፤36፥2፤ ዘፀ3፥8፤ ዘዳ7፥1፤ መሳ3፥3 10፥18 ዘፍ12፥6፤13፥7፤50፥11፤ ሕዝ27፥8፤ ዘፀ13፥11፤ ዘኍ13፥29፤14፥25፤21፥3፤33፥40፤ ዘዳ1፥7፤ መሳ1፥1፤ 1ዜና18፥3
10፥19 ቍ 15፤ ዘፍ11፥31፤12፥1፤13፥12፤14፥2፤17፥8፤24፥3፤26፥34፤27፥46፤28፥1፡6፡8፤31፥18፤35፥6፤37፥1፤49፥13፤ ዘሌ25፥38 ዘዳ2፥23፤29፥23፤ ኢሱ10፥41፤11፥22፤15፥47፤19፥28፤ መሳ1፥18፡31፤6፥4፤16፥1፡21፤18፥28፤ 1ሳሙ6፥17፤ 2ሳሙ24፥6፤ 2ዜና14፥13፤ ኤር25፥20፤47፥1፤ አሞ1፥6፤ ሶፎ2፥4
10፥21 ቍ 24፤ ዘኍ24፥24
10፥22 ዘፍ14፥1፤ ዘኍ24፥22፡24፤ መሳ3፥10፤ 1ነገ11፥25፤19፥15፤20፥34፤22፥31፤ 2ነገ5፥1፤8፥7፤ ኢሳ11፥11፤21፥2፤ ኤር25፥25፤49፥34፤ ሕዝ27፥23፤32፥24፤ ዳን8፥2፤ ሉቃ3፥36
10፥23 ዘፍ22፥21፤ ኢዮ1፥1፤ ኤር25፥20፤ ሰቆ4፥21
10፥24 ቍ 21፤ ሉቃ3፥35
10፥27 ሕዝ27፥19
10፥28 1ነገ10፥1፤ ኢዮ6፥19፤ መዝ72፥10፡15፤ ኢሳ60፥6፤ ሕዝ27፥22
10፥29 1ነገ9፥28፤10፥11፤ 1ዜና29፥4፤ ኢዮ22፥24፤28፥16፤ መዝ45፥9፤ ኢሳ13፥12 10፥32 ቍ 1፤ ዘፍ9፥19 11፥1 ቍ 6 11፥2 ዘፍ10፥10 11፥3 ዘፍ14፥10፤ ዘፀ1፥14፤5፥7፤ ኢሳ9፥10፤ ኤር43፥9፤ አሞ5፥11 11፥4 ዘፍ6፥4፤9፥19፤ ዘዳ1፥28፤4፥27፤6፥10፤9፥1፤30፥3፤ 1ነገ22፥17፤ አስ3፥8፤ ኢዮ20፥6፤ መዝ44፥11፤ ኤር31፥10፤40፥15፤51፥53፤ ሕዝ6፥8፤ ኢል3፥2 11፥5 ቍ 7፤ ዘፍ18፥21፤ ዘፀ3፥8፤19፥11፡18፡20፤ መዝ18፥9፤144፥5 11፥6 ቍ 1 11፥7 ቍ 5፤ ዘፍ1፥26፤42፥23፤ ዘዳ28፥49፤ ኢሳ28፥11፤33፥19፤ ኤር5፥15፤ 1ቆሮ14፥2፡11 11፥8 ዘፍ9፥9፤ ዘዳ32፥8፤ ሉቃ1፥51 11፥9 ዘፍ10፥10፤ መዝ55፥9፤ ኢሳ2፥10፡21፤13፥14፤24፥1፤ ሐሥ2፥5-11

[ሸ]10 ወይም *ኦሬክና አርካድ፣ ሁሉም በ...*
[ቀ]10 ባቢሎን ነው
[በ]11 ወይም *ነነዌ ከነከተማዋ አደባባዮች*
[ተ]15 ወይም *ከሲዶናውያን የመጀመሪያው*
[ቸ]21 ወይም *ሴም፣ የ...ታላቅ ወንድም*
[ኀ]23 ሰብዐ ሊቃናትንና 1ዜና 1፥17 *ይመ*፤ በዕብራይስጡ *ማሽ* ይለዋል።
[ነ]24 ከዕብራይስጡ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ሰብዐ ሊቃናት ግን *የቃይናን አባት፣ ቃይናንም የ...አባት ነበረ* ይላል
[ኘ]25 *ፍሌቅ* ማለት ክፍፍል ማለት ነው
[አ]2 ወይም *ከምሥራቅ፣ በምሥራቅ*
[ከ]2 ባቢሎንን ያመላክታል
[ኸ]9 ባቢሎንን ያመላክታል። *ባቤል* የሚለው ቃል *ድንግርታ* የሚል ትርጕም ካለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር አንድ ዐይነት ድምፅ አለው።

## ከሴም እስከ አብራም
11፥10-27 ተጓ ምብ - ዘፍ 10፥21-37፤ 1ዜና 1፥17-27

10የሴም ትውልድ ይህ ነው፡-
ሁለት ዓመት ከጥፋት ውሃ በኋላ ሴም
በ100 ዓመቱ አርፋክስድን ወለደ:: 11ሴም፣
አርፋክስድን ከወለደ በኋላ 500 ዓመት ኖረ፤
ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ::
12አርፋክስድ በ35 ዓመቱ ሳላን ወለደ፤
13ሳላንን ከወለደ በኋላ አርፋክስድ 403 ዓመት
ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶችን ወለደ::[ወ]
14ሳላ በ30 ዓመቱ ዔቦርን ወለደ፤ 15ዔቦ
ርን ከወለደ በኋላ ሳላ 403 ዓመት ኖረ፤
ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ::
16ዔቦር በ34 ዓመቱ ፋሌቅን ወለደ፤ 17ፋሌ
ቅን ከወለደ በኋላ ዔቦር 430 ዓመት ኖረ፤
ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ::
18ፋሌቅ በ30 ዓመቱ ራግውን ወለደ፤
19ራግውንን ከወለደ በኋላ ፋሌቅ 209 ዓመት
ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ::
20ራግው በ32 ዓመቱ ሴሮሕን ወለደ፤
21ሴሮሕን ከወለደ በኋላ ራግው 207 ዓመት
ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ::
22ሴሮሕ በ30 ዓመቱ ናኮርን ወለደ፤ 23ናኮ
ርን ከወለደ በኋላ ሴሮሕ 200 ዓመት ኖረ፤
ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ::
24ናኮር በ29 ዓመቱ ታራን ወለደ፤ 25ታራ
ን ከወለደ በኋላ ናኮር 119 ዓመት ኖረ፤
ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ::
26ታራ 70 ዓመት ከሆነው በኋላ አብራ
ምን፣ ናኮርንና ሐራንን ወለደ::
27የታራ ትውልድ ይህ ነው፡-
ታራ፣ አብራምን ናኮርንና ሐራንን
ወለደ፤
ሐራንም ሎጥን ወለደ:: 28ሐራን፣ አባቱ ታራ
ገና በሕይወት እንዳለ በከለዳውያን ምድር
በምትገኘው በተወለደባት ከተማ በዑር ሞተ::
29አብራምና ናኮር ሁለቱም ሚስት አገቡ፤
የአብራም ሚስት ሦራ ስትባል፣ የናኮር
ሚስት ደግሞ ሚልካ ትባል ነበር፤ ሚል
ካም የሐራን ልጅ ናት፤ ሐራንም የሚልካና
የዮስካ አባት ነበረ:: 30ሦራ መካን ነበረች፤
ልጅ አልነበራትም::
31ታራ ልጁን አብራምን፣ ሐራን የወለደ
ውን የልጅ ልጁን ሎጥን እንዲሁም የአብ
ራምን ሚስት ምራቱን ሦራን ይዞ ወደ
ከነዓን ለመሄድ በከለዳውያን ምድር ከም
ትገኘው ከዑር አብረው ወጡ፤ ነገር ግን ካራን
በደረሱ ጊዜ በዚያ ተቀመጡ::
32ታራ 205 ዓመት ኖሮ በካራን ሞተ::

## የአብራም መጠራት

12 እግዚአብሔር (ያህዌ) አብራምን እንዲህ
አለው፤ “አገርህን፣ ወገንህንና
የአባትህን ቤት ትተህ እኔ ወደማሳይህ
ምድር ሂድ::
2“ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፤
ደግሞም እባርክሃለሁ፤
ስምህን ገናና አደርገዋለሁ፤
ለሌሎች በረከት ትሆናለህ::
3የሚባርኩህን እባርካለሁ፤
የሚረግሙህን እረግማለሁ፤
በምድር የሚኖሩ ሕዝቦች፣
በአንተ አማካይነት ይባረካሉ::”
4ስለዚህ አብራም እግዚአብሔር (ያህዌ) እን
ዳዘዘው ወጣ፤ ሎጥም አብሮት ሄደ:: አብራም
ከካራን ሲወጣ ዕድሜው 75 ዓመት ነበረ::
5አብራምም ሚስቱን ሦራንና የወንድሙን
ልጅ ሎጥን አስከትሎ በካራን ሳሉ ያፈሩትን
ሀብትና የነበራቸውን አገልጋዮች ይዘው በመ
ጓዝ ከነዓን ምድር ገቡ::
6አብራም ትልቁ የሞሬ ዛፍ እስከሚገኝ
በት እስከ ሴኬም ድረስ በምድሪቱ ዘልቆ
ሄደ:: በዚያን ጊዜ ከነዓናውያን በዚሁ ምድር
ይኖሩ ነበር:: 7እግዚአብሔርም (ያህዌ) ለአብራም
ተገለጠ፣ “ይህችን ምድር ለዘርህ እሰጣ
ለሁ” አለው:: እርሱም ለተገለጠለት አምላክ
(ያህዌ) በዚያ ስፍራ መሠዊያ ሠራ::
8ከዚያም ተነሥቶ ከቤቴል በስተ ምሥራ
ቅ ወዳሉት ተራሮች ሄደ፤ ቤቴልን በምዕራ
ብ፣ ጋይን በምሥራቅ አድርጎ ለእግዚ
አብሔር (ያህዌ) መሠዊያ ሠራ፤ የእግዚአብሐ
ሔርን (ያህዌ) ስም ጠርቶ ጸለየ:: 9አብራምም
ከዚያ ተነ ሥቶ ወደ ኔጌብ ሄደ::

## አብራም በግብፅ አገር
12፥10-20 ማመ - ዘፍ 20፥1-18፤ 26፥1-11

10በዚያም ምድር ጽኑ ራብ ገብቶ ነበር፤
ከዚህም የተነሣ አብራም ለጥቂት ጊዜ በዚያ

**11፥10** ዘፍ2፥4፤ ሉቃ3፥36
**11፥12** ሉቃ3፥35
**11፥14** ሉቃ3፥35
**11፥16** ሉቃ3፥35
**11፥18** ሉቃ3፥35
**11፥20** ሉቃ3፥35
**11፥22** ሉቃ3፥34
**11፥24** ሉቃ3፥34
**11፥26** ኢሱ24፥2፤ 2ነገ19፥12፤ኢሳ37፥12፤ሕዝ27፥23፤ ሉቃ3፥34
**11፥27** ቊ29:31፤ ዘፍ2፥4፤12፥4፤13፥1፡5፡8፡12፤14፥12፤19፥1፤31፥53፤ሉቃ17፥28፤2ጴጥ2፥7
**11፥28** ቊ31፤ዘፍ 15፥7፤ነህ9፥7፤ኢዮ 1፥17፤16፥11፤ሕዝ 23፥23፤ሐሥ7፥4
**11፥29** ቊ27፡31፤ ዘፍ12፥5፡11፤16፥1፤ 17፥15፤22፥20፡23፤ 24፥10፡15፡24፤29፥5
**11፥30** ዘፍ16፥1፤ 18፥11፤25፥21፤29፥31፤30፥1፡22፤መሳ13፥2፤1ሳሙ1፥5፤መዝ 113፥9፤ሉቃ1፥7፡36
**11፥31** ቊ27:28:29፤ዘፍ10፥19፤12፥4፤ 38፥11፤27፥43፤28፥5፡10፤29፥4፤ዘሌ18፥15፤ 20፥12፤ሩት1፥6፡22፤ 2፥20፤4፥15፤1ሳሙ4፥19፤2ነገ19፥12፤1ዜና2፥4፤ሕዝ22፥11፤27፥23፤ሚክ7፥6፤ሐሥ7፥4
**11፥32** ኢሱ24፥2
**12፥1** ዘፍ10፥19፤ 15፥7፤20፥13፤24፥4፡23፡40፤26፥2፤ኢሱ24፥3፤ሐሥ7፥3፤ዕብ11፥8
**12፥2** ዘፍ13፥16፤ 15፥5፤17፥2፡4፤18፥18፤22፥17:18፤24፥1፡35፤ 25፥11፤26፥3፡4፤28፥3፡4፡14፤32፥12፤35፥11፤41፥49፤46፥3፤47፥27፤48፥4፡16፡19፤ዘፀ 1፥7፤5፥5፤20፥24፤32፥13፤ዘኍ22፥12፤23፥8፡20፤24፥9፤ዘዳ1፥10፤ 10፥22፤13፥17፤26፥5፤ኢሱ11፥4፤24፥3፤ 2ሳሙ17፥11፤1ነገ3፥8፤4፥20፤1ዜና27፥23፤ 2ዜና1፥9፤ነህ9፥23፤ መዝ67፥6፤107፥38፤ 115፥12፤ኢሳ6፥13፤ 10፥22፤19፥24፤44፥3፤ 48፥19፤51፥2፤54፥3፤60፥22፤61፥9፤65፥23፤ኤር4፥2፤33፥22፤ ሚክ4፥7፤ሐጌ2፥19፤ ዘካ8፥13ሚል3፥12
**12፥3** ዘፍ15፥5፤18፥18፤22፥18፤26፥4፤27፥29፤28፥4፡14፤ዘፀ23፥22፤ዘኍ24፥9፤ዘዳ9፥5፤30፥7፤መዝ72፥17፤ ኢሳ19፥25፤ሐሥ3፥25፤ገላ3፥8 **12፥4** ዘፍ11፥27:31፤16፥3፡16፤ 17፥1፡17፡24፤21፥5 **12፥5** ቊ16፤ዘፍ11፥29:31፤13፥2፡6፤16፥3፤ 31፥18፤46፥6፤14፥14፤15፥3፤17፥23፤መክ2፥7፤ዕብ11፥8 **12፥6** ዘፍ10፥18፤33፥18፤35፥4፤37፥12፤ዘዳ11፥30፤ኢሱ17፥7፤20፥7፤24፥1:26፤ መሳ7፥1፤8፥31፤9፥6፤21፥19፤1ነገ12፥1፤መዝ60፥6፤108፥7፤ዕብ11፥9 **12፥7** ዘፍ8፥20፤13፥4፡15፡17፤15፥18፤17፥8፤18፥1፤23፥18፤24፥7፤26፥ 2-4፤28፥13፤35፥1:12፤48፥4፤50፥24፤ዘፀ3፥8፤6፥3፡4፡8፤13፥5፡11፤ 32፥13፤33፥1፤ዘኍ10፥29፤11፥12፤ዘዳ1፥8፤2፥31፤9፥5፤11፥9፤30፥5፤ 34፥4፤2ነገ25፥ 21፤1ዜና16፥16፤2ዜና20፥7፤መዝ105፥9-11፤ኤር 25፥5፤ሕዝ47፥14፤ሐሥ7፥2:5፤ሮሜ4፥13፤ገላ3፥16፤ዕብ11፥8 **12፥8** ዘፍ4፥26፤8፥20፤13፥3፤26፥25፤28፥11፡19፤35፥1:8:15፤ኢሱ 7፥2፤8፥9፤12፥9፤1ሳሙ7፥16፤1ነገ12፥29፤ዕዝ2፥28፤ነህ7፥32፤ኤር 49፥3፤ሆሴ12፥4፤አሞ3፥14፤4፥4፤ዕብ11፥9 **12፥9** ዘፍ13፥1፡3፤ 20፥1፤24፥62፤ዘኍ 13፥17፤33፥ 40፤ዘዳ34፥3፤ኢሱ10፥40 **12፥10** ዘፍ41፥27፡30፡54፡56፡57፤42፥5፤ 43፥1፤47፥4፡13:20፤ሩት1፥1፤ 2ሳሙ21፥1፤2ነገ8፥1፤መዝ105፥16:19

[ወ]12-13 ከዕብራይስጡ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ሰብዐ ሊቃናት ግን (በተጨማሪ ሉቃ 3፥35-36 እና የዘፍ 10-24 ማብ ይመ) እን ዲሁ ይሉታል፤ 12 *በ35 ዓመት ቃይናንን ወለደ፤ 13 ቃይና ንን ከወለደ በኋላ፣ አርፋክስድ 430 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወን ዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ፤ ቃይናንም 130 ዓመት ከኖረ በኋላ ሳላን ወለደ፤ ሳላንን ከወለደ በኋላ፣ ቃይናን 330 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ* ይላል::

ለመኖር ወደ ግብፅ ወረደ። [11]ግብፅ ለመግ
ባት ጥቂት ሲቀረው አብራም ሚስቱን ሦራን
እንዲህ አላት፤ “መቼም አንቺ ውብ ሴት
መሆንሽን ዐውቃለሁ፤ [12]ግብፃውያን አንቺን
በሚያዩበት ጊዜ፣ ‘ይህች ሚስቱ ናት’ ብለው
እኔን ይገድላሉ፤ አንቺን ግን ይተዉሻል።
[13]ስለዚህ ለአንቺ ሲሉ እንዲንከባከቡኝ፣ ሕይ
ወቴም እንድትተርፍ፣ ‘እኅቱ ነኝ’ በዪ።”

[14]አብራም በግብፅ አገር እንደ ደረሰ ግብ
ፃውያን፣ ሦራ እጅግ ውብ ሴት እንደ ሆነች
አዩ፤ [15]የፈርዖንም ሹማምት ባዩአት ጊዜ፣
ለፈርዖን አድንቀው ነገሩት፤ ወደ ቤተ መንግ
ሥትም ወሰዷት። [16]በእርሷም ምክንያት ፈርዖን
አብራምን አክብሮ አስተናገደው፤ በጎችና
ከብቶች፣ ተባዕትና እንስት አህዮች፣ ወንድና
ሴት አገልጋዮች እንዲሁም ግመሎችን ሰጠው።

[17]*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) በአብራም ሚስት
በሦራ ምክንያት ፈርዖንንና ቤተ ሰዎቹን በጽኑ
ደዌ መታቸው። [18]ከዚያም ፈርዖን አብራ
ምን አስጠርቶ እንዲህ አለው፤ “ይህ ያደ
ረግህብን ነገር ምንድን ነው? ‘ሚስትህ እንደ
ሆነች ለምን አልነገርኸኝም?’ [19]ለምን ‘እኅቴ
ናት’ አልኸኝ? ሚስቴ ላደርጋት ነበር። በል
አሁንም ሚስትህ ይህችው፤ ይዘሃት ሂድ!”
[20]ከዚያም ፈርዖን ስለ አብራም ለባለሟ
ሎቹ ትእዛዝ ሰጠ፤ እነርሱም አብራምን
ከሚስቱና ከንብረቱ ሁሉ ጋር አሰናበቱት።

### የአብራምና የሎጥ መለያየት

**13** አብራም ሚስቱንና ንብረቱን ሁሉ
ይዞ ከግብፅ ወደ ኔጌብ ሄደ፤ ሎጥም
አብሮት ነበረ። [2]አብራም በከብት፣ በብ
ርና በወርቅ እጅግ በልጽጎ ነበር።

[3]አብራም ከኔጌብ ተነሥቶ እስከ ቤቴል
ተጓዘ፤ ቀድሞ በቤቴልና በጋይ መካከል ድን
ኳኑን ከተከለበት፣ [4]ለመጀመሪያ ጊዜም መሠ
ዊያ ካቆመበት ስፍራ ደረሰ፤ በዚያም የእ
*ግዚአብሔርን* (ያህዌ) ስም ጠራ።

[5]ከአብራም ጋር አብሮት ይጓዝ የነበረው
ሎጥ በጎች፣ ከብቶችና ድንኳኖች ነበሩት።
[6]ሆኖም ሁለቱ አንድ ላይ ሲኖሩ ስፍራው
አልበቃቸውም፤ ንብረታቸው እጅግ ብዙ ስለ
ነበር፣ አብረው መኖር አልቻሉም። [7]ይህም
በመሆኑ በአብራምና በሎጥ እረኞች መካ
ከል ጠብ ተፈጠረ። በዚያን ዘመን ከነዓና
ውያንና ፌርዛውያን በዚያው አገር ይኖሩ
ነበር።

[8]አብራምም ሎጥን እንዲህ አለው፤ “እኛ
ወንድማማቾች ነንና በአንተና በእኔ ወይም
በእረኞቻችን መካከል ጠብ ሊኖር አይገባም።
[9]ይኸው እንደምታየው አገሩ ሰፊ ነው፤ ብን
ለያይ ይሻላል። አንተ ግራውን ብትመርጥ፣

12፥11 ቀኍ14፤ዘፍ 11፥29፤24፥16፤26፥7፤29፥17፤39፥6
12፥13 ዘፍ20፥2፤26፥7
12፥14 ቀኍ11
12፥16 ቀኍ5፤ዘፍ24፥35፤26፥14፤30፥43፤32፥5፤34፥23፤47፥17፤ኢዮ1፥3፤31፥25
12፥17 2ነገ15፥5፤1ዜና16፥21፤ኢዮ30፥11፤መዝ105፥14፤ኢሳ53፥4፡10
12፥18 ዘፍ20፥9፤26፥10፤29፥25፤31፥26፤44፥15፤ዕዝ16፥3፤ኢሳ43፥27፤51፥2
12፥19 ዘፍ20፥5፤26፥9
13፥1 ዘፍ11፥12፤12፥9፤45፥25
13፥2 ዘፍ12፥5፤26፥13፤32፥15፤ኢዮ1፥3፤ምሳ10፥22
13፥3 ዘፍ12፥8፡9፤ኢሱ7፥2
13፥4 ዘፍ4፥26፤12፥7
13፥5 ዘፍ11፥27
13፥6 ዘፍ12፥5፤33፥9፤36፥7
13፥7 ዘፍ10፥18፤12፥6፤15፥20፤26፥20፡21፤34፥30፤ዘፀ3፥8፤ዘኍ20፥3፤መሳ1፥4
13፥8 ዘፍ11፥27፤19፥9፤ዘፀ2፥14፤ዘኍ16፥13፤መዝ133፥1፤ምሳ15፥18፤20፥3
13፥9 ዘፍ20፥15፤34፥10፤47፥6፤ኤር40፥4
13፥10 ዘፍ2፥8-10፤4፥2፤14፥8፤19፥17-30፤46፥7፤ዘኍ13፥29፤33፥48፤ዘዳ29፥23፤34፥3፤1ነገ7፥46፤2ዜና4፥17፤ኢዮ39፥6፤መዝ107፥34፤ኢሳ15፥5፤51፥3፤ኤር4፥26፤48፥34፤ሕዝ31፥8-9
13፥12 ቀኍ10፤ዘፍ 10፥19፤11፥27፤19፥17፡25፡29፤14፥12
13፥13 ዘፍ3፥9፤18፥20፤19፥4፡5፤20፥6፤39፥9፤ዘኍ32፥23፤1ሳሙ12፥23፤2ሳሙ12፥13፤መዝ51፥4፤ኢሳ1፥10፤3፥9፤ሕዝ16፥49-50፤2ጴጥ2፥8
13፥14 ዘፍ28፥14፤32፥12፤48፥16፤ዘዳ3፥27፤13፥17፤ኢሳ54፥3
13፥15 ዘፍ12፥7፤ገላ3፥16
13፥16 ዘፍ12፥2፤16፥10፤17፥20፤21፥13፡18፤25፥16፤ዘኍ23፥10
13፥17 ቀኍ15፤ዘኍ13፥17-25፤ዘፍ12፥7፤15፥7

እኔ ወደ ቀኝ እሄዳለሁ፤ አንተ ቀኙን ብት
መርጥ፣ እኔ ወደ ግራ አመራለሁ።”

[10]ሎጥ ዐይኑን አቅንቶ ሲመለከት፣ የዮ
ርዳኖስ ረባዳ ሜዳ እንደ *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ገነት፣ በዞዓር አቅጣጫ እንዳለው እንደ
ግብፅ ምድር ውሃማ ቦታ ሆኖ አገኘው።
እንዲህም የነበረው *እግዚአብሔር* (ያህዌ) የሰ
ዶምንና የገሞራን ከተሞች ከማጥፋቱ በፊት
ነው። [11]ሎጥ የዮርዳኖስን ረባዳ ሜዳ በሙሉ
መርጦ ወደ ምሥራቅ አመራ፤ ሁለቱ ሰዎች
በዚሁ ተለያዩ። [12]አብራም መኖሪያውን በከ
ነዓን ምድር አደረገ፤ ሎጥ ግን በረባዳው ሜዳ
ውስጥ ባሉት ከተሞች መካከል በሰዶም አቅ
ራቢያ ድንኳኑን ተከለ። [13]የሰዶም ሰዎች ግን
ክፉዎችና *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት እጅግ
ኃጥኣን ነበሩ።

[14]ሎጥ ከተለየው በኋላ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
አብራምን እንዲህ አለው፤ ካለህበት ስፍራ
ቀና ብለህ ወደ ሰሜንና ወደ ደቡብ፣ ወደ
ምሥራቅና ወደ ምዕራብ ተመልከት፤ [15]ዐይ
ንህ የሚያየውን ምድር ሁሉ ለአንተና ለዘ
ርህ ለዘላለም እሰጣለሁ። [16]ዘርህን እንደ ምድር
ትቢያ አበዛዋለሁ፤ ማንም የምድርን ትቢያ
ሊቈጥር እንደማይችል ሁሉ የአንተም ዘር
የማይቈጠር ይሆናል። [17]እንግዲህ ምድሪቱን
ስለምሰጥህ ተነሥ፤ በርዝመቷም፣ በስፋቷም
ተመላለስባት።”

[18]አብራምም ድንኳኑን ነቀለ፤ ሄዶም ኬብ
ሮን በሚገኙት ትልልቅ የመምሬ ዛፎች
አጠገብ ተቀመጠ፤ በዚያም *ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) *መሠዊያ ሠራ*።

### አብራም ሎጥን መታደጉ

**14** አምራፌል የሰናዖር[0] ንጉሥ፣ አር
ዮክ የእላሳር ንጉሥ፣ ኮሎዶጎምር
የኤላም ንጉሥ፣ ቲድዓል የጎይም ንጉሥ
በነበሩበት ዘመን፣ [2]ከሰዶም ንጉሥ ከበላ፣
ከገሞራ ንጉሥ ከብርሳ፣ ከአዳማ ንጉሥ
ከሰነአብ፣ ከሰቦይ ንጉሥ ከሰሜበር፣ እንዲ
ሁም ዞዓር ከተባለች ከቤላ ንጉሥ ጋር ለመ
ዋጋት ወጡ። [3]እነዚህ የኋለኞቹ አምስቱ ነገ
ሥታት በሲዲም ሸለቆ፣ በጨው ባሕር[#] ተሰ
በሰቡ። [4]እነርሱም ዐሥራ ሁለት ዓመት ለኮ
ሎዶጎምር ከተገዙ በኋላ በዐሥራ ሦስተ
ኛው ዓመት ዐመፁ።

[5]በዐሥራ አራተኛው ዓመት ኮሎዶጎምርና

13፥18 ዘፍ8፥20፤14፥13፡24፤18፥1፤23፥2፡17፡19፤25፥9፤35፥27፤37፥14፤49፥30፤50፥13፤ዘኍ13፥22፤ኢሱ10፥3፡36፤መሳ1፥10፤1ሳሙ30፥31፤2ሳሙ2፥1፡3፡11፤1ዜና11፥1 14፥1 ቀኍ4፡9፡17፤ዘፍ10፥10፡22
14፥2 ዘፍ10፥19፤13፥10 14፥3 ቀኍ8፡10፤ዘኍ34፥3፡12፤ዘዳ3፥17፤ኢሱ3፥16፤12፥3፤15፥2፡5፤18፥19 14፥4 ቀኍ1 14፥5 ቀኍ1፤ዘፍ15፥20፤ዘዳ2፥10፡11፡20፤3፥11፡13፤ኢሱ12፥4፤13፥12፤17፥15፤1ዜና20፥4

[0]1 በቍ 9 ላይ ያለውንም ጨምሮ ባቢሎንን ያመላክታል።
[#]3 የሙት ባሕር ማለት ነው

ከርሱ ጋር የተባበሩት ነገሥታት ወጡ፤ ራፋ
ይምን በአስጣሮት ቃርናይም፣ ዙዚምን በሃም፣
ኑሚምን በሴዊ ቂርያታይም፣ 6የሖር ሰዎ
ችንም በተራራማው አገር በሴይር በረሓማ
አጠገብ እስካለው እስከ ኤልፋራን ድረስ
ድል አደረጓቸው። 7ከዚያም ተመልሰው ዓይን
ሚስፖጥ ወደ ተባለው ወደ ቃዴስ መጡ፤
የአማሌቃውያንና በሐሴስ ታማር ይኖሩ የነ
በሩትን የአሞራውያንን ግዛት በሙሉ ድል
አድርገው ያዙ።

8ከዚያም የሰዶም፣ የገሞራ፣ የአዳማ፣ የሰ
ቦይ እንዲሁም ዞዓር የተባለችው የቤላ ነገ
ሥታት በሲዲም ሸለቆ ሰራዊታቸውን አስተባ
በሩ፤ 9እነዚህ አምስቱ፣ በኤላም ንጉሥ በኮ
ሎዶጎምር፣ በጎይም ንጉሥ በቲድዓል፣ በሰ
ናዖር ንጉሥ በአምራፌል፣ በእላሳር ንጉሥ
በአርዮክ፣ በእነዚህ በአራቱ ላይ ዘመቱባቸው።
10በሲዲም ሸለቆ ብዙ የቅጥራን ጕድጓዶች
ስለ ነበሩ የሰዶምና የገሞራ ነገሥታት ሲሸሹ
ከሰዎቻቸው አንዳንዶቹ በነዚህ ጕድጓዶች
ውስጥ ወደቁ፤ የቀሩትም ወደ ተራሮች ሸሹ።
11አራቱ ነገሥታትም በሰዶምና በገሞራ ያገ
ኙትን ሀብትና ምግብ ሁሉ ዘርፈው ሄዱ።
12የአብራም ወንድም ልጅ ሎጥ፣ ሰዶም ይኖር
ስለ ነበር እርሱንም ማርከው ንብረቱንም ዘር
ፈው ሄዱ።

13ከዚህም ያመለጠ አንድ ሰው መጥቶ
ለዕብራዊው ለአብራም ይህን ነገረ፤ አብራም
በዚያ ጊዜ ይኖር የነበረው በአሞራዊው
መምሬ ታላላቅ ዛፎች አጠገብ ነበር። መምሬ፣
ወንድሞቹ[ሠ] አስኮና አውናን የአብራም
የኪዳን አጋሮቹ ነበሩ። 14አብራም የወንድ
ሙን ልጅ መማረክ እንደ ሰማ በቤቱ ተወ
ልደው አድገው የሠለጠኑ 318 ጦረኞች አሰልፎ
እስከ ዳን ድረስ ገሠገሠ። 15አብራም ጠላቶቹ
ን
ለማጥቃት ሰራዊቱን ሌሊቱን በቡድን በቡ
ድን ከፋፍሎ ከደማስቆ በስተ ሰሜን እስከ
ሚገኘው እስከ ሖባ ድረስ አሳደዳቸው። 16አብ
ራም ጠላት የማረከውን በሙሉ አስጣለ፤ የወን
ድሙን ልጅ ሎጥን፣ ንብረቱን እንዲሁም
ሴቶቹንና ሌሎቹን ምርኮኞች አስመለሰ።

17አብራም ኮሎዶጎምርንና አብረውት የተ
ሰለፉትን ነገሥታት ድል አድርጎ ሲመለስ፣
የሰዶም ንጉሥ፣ "የንጉሥ ሸለቆ" ተብሎ በሚጠ
ራው በሴዊ ሸለቆ ሊቀበለው ወጣ።

18የልዑል እግዚአብሔር (ኤል-ኤልዮን) ካህን የነ
በረው የሳሌም[የ] ንጉሥ መልከ ጼዴቅም እን
ጀራና የወይን ጠጅ ይዞ ወጣ፤ 19አብራምንም
እንዲህ ሲል ባረከው፤

"ሰማይንና ምድርን የፈጠረ[ደ] ልዑል
እግዚአብሔር (ኤል-ኤልዮን) አብራምን ይባርክ፤
20ጠላቶችህን አሳልፎ በእጅህ የሰጠህ፣
ልዑል እግዚአብሔር (ኤል-ኤልዮን) ይባረክ።"
አብራምም ካመጣው ሁሉ ዐሥራትን ሰጠው።

21የሰዶም ንጉሥም አብራምን፣ ሰዎቹን ለእኔ
ስጠኝ፤ ንብረቱን ግን ለራስህ አስቀር" አለው።

22አብራም ግን ለሶዶም ንጉሥ እንዲህ
አለው፤ "ሰማይንና ምድርን ወደ ፈጠረ ወደ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ)፣ ወደ ልዑል አምላክ
(ኤል-ኤልዮን) እጆቼን አንሥቻለሁ፤ 23'አብራምን
አበለጸግሁት' እንዳትል፣ ብጣሽ ክርም ሆነ
የጫማ ማሰሪያ እንኳ ከአንተ አንዳች አል
ፈልግም። 24ሰዎቹ ከበሉትና ከእኔ ጋር ከሄ
ዱት ሰዎች ድርሻ በስተቀር ለራሴ አን
ዳች ነገር አልቀበልም፤ አውናን፣ ኤስኮልና
መምሬ ድርሻቸውን ይውሰዱ።"

### እግዚአብሔር ለአብራም የገባው ኪዳን

15 ከዚህም በኋላ፣ *የእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ቃል እንዲህ ሲል በራእይ ወደ አብ
ራም መጣ፤

"አብራም ሆይ፤ አትፍራ፤
እኔ ለአንተ ጋሻህ ነኝ፤[ጀ]
ታላቅ ዋጋህም[ገ] እኔው ነኝ።

2አብራምም፣ "*እግዚአብሔር* (ያህዌ) አምላክ
ሆይ፤ ያለ ልጅ የቀረሁ ስለ ሆንሁ፣ የቤቴ
ወራሽ[ጠ] የደማስቆ ሰው ኤሊዔዘር ነው፤
ታዲያ ምን ትሰጠኛለህ?" አለው። 3አንተ
ልጆች ስላልሰጠኸኝ፣ ከቤቴ አገልጋይ አንዱ
ወራሼ መሆኑ አይቀርም"

4በዚህ ጊዜ *የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ቃል እን
ዲህ ሲል መጣለት፤ "ይህ ሰው ወራሽህ
አይሆንም፤ ነገር ግን ከአብራክህ የሚከፈል
ልጅ ወራሽህ ይሆናል።" 5ወደ ውጪም አው
ጥቶ፣ "ቀና ብለህ ወደ ሰማይ ተመልከት፤
እስቲ መቍጠር ከቻልህ፣ ከዋክብቱን ቍጠ
ራቸው፤ ዘርህም እንዲሁ ይበዛል" አለው።

6አብራም *እግዚአብሔርን* (ያህዌ) አመነ፤ እር
ሱም ጽድቅ አድርጎ ቈጠረለት።

**14÷6** ዘፍ21÷21፤32÷3፤33÷14፡16፤36÷8:20፤ዘኍ10÷12፤12÷16፤13÷3፡26፤ዘዳ1÷2፤2÷1:5:12፡22፤ኢሱ11÷17፤24÷4፤1ዜና4÷42፤ኢሳ34÷5፤ሕዝ25÷8፤35÷2፤አሞ1÷6፤ዕን3÷3 **14÷7** ዘፍ16÷14፤20÷1፤ዘፀ17÷8፤ዘኍ13÷26:29፤14÷25፤20÷1፤24÷20፤25÷17፤32÷8፤ዘዳ1÷2:4፤25÷17፤ኢሱ2÷10፤10÷41፤13÷4፤መሳ3÷13፤6÷3፤10÷12፤11÷16፤12÷15፤1ሳሙ14÷48፤15÷2፤28÷18፤2ሳሙ1÷1፤1ዜና4÷43፤2ዜና20÷2፤መዝ29÷8፤83÷7፤ሕዝ48÷28 **14÷8** ቍ3፤ዘፍ13÷10፤ዘዳ29÷23፤ሆሴ11÷8 **14÷9** ቍ1፤ዘፍ10÷22 **14÷10** ቍ3:17፡21፤ዘፍ11÷3፤19÷17፡30፤ኢሱ2÷16፤መዝ11÷1 **14÷11** ቍ16፡21 **14÷12** ዘፍ11÷27 **14÷13** ዘፍ13÷18፤37÷28፤39÷14፡17፤40÷15፤41÷12፤43÷32፤ዘፀ3÷18፤ዘኍ13÷23፤32÷9፤ዘዳ1÷24፤1ሳሙ4÷6፤14÷11 **14÷14** ቍ12፤ዘፍ12÷5፤ዘዳ4÷9፤34÷1፤መሳ18÷29፤1ነገ15÷20፤ምሳ22÷6 **14÷15** ዘፍ15÷2፤መሳ7÷16፤2ሳሙ8÷5፤1ነገ20÷34፤2ነገ16÷9፤ኢሳ7÷8፤8÷4፤10÷9፤17÷1፤ኤር49÷23፡27፤ሕዝ27÷18፤አሞ1÷3-5 **14÷16** ቍ11፤1ሳሙ30÷8፡18 **14÷17** ቍ1፡10፤2ሳሙ18÷18 **14÷18** ቍ22፤ዘፍ3÷19፤መሳ9÷13፤19÷19፤አስ1÷10፤መዝ7÷8፡17፤76÷2፤104÷15፤110÷4፤ምሳ31÷6፤መክ10÷19፤ማሕ1÷2፤ዳን7÷27፤ዕብ5÷6፤7÷2፡17፡21 **14÷19** ቍ18፡22፤ዘፍ1÷1፤24÷3፤ኢሱ2÷11፤መዝ148÷5፤ማቴ11÷25፤ዕብ7÷6 **14÷20** ዘፍ9÷26፤24÷27፤28÷22፤ዘዳ14÷22፤26÷12፤ሉቃ18÷12፤ዕብ7÷4 **14÷21** ቍ10፡11 **14÷22** ቍ10፡18፡19፤ዘፀ6÷8፤ዘኍ14÷30፤ዘዳ32÷40፤ነህ9÷15፤ሕዝ20÷5፤ዳን12÷7፤ራእ10÷5-6 **14÷23** 1ሳሙ15÷3፡19፤2ነገ5÷16፤አስ8÷11፤9÷10፡15 **14÷24** ዘፍ 13÷18 **15÷1** ዘፍ21÷17፤26÷24፤46÷2:3፤ዘፀ14÷13፤20÷20፤ዘኍ12÷6፤24÷4፤ዘዳ33÷29፤ሩት1÷20፤1ሳሙ15÷10፤2ሳሙ7÷4፤22÷3፡31፤1ነገ6÷11፤12÷22፤2ነገ6÷16፤2ዜና20÷15፡17፤ኢዮ33÷15፤መዝ3÷3፤5÷12፤18÷2:20፤27÷1፤28÷7፤33÷20፤37÷25፤58÷11፤84÷11፤119÷114፤144÷2፤ምሳ2÷7፤30÷5፤ኢሳ3÷10፤7÷4፤41÷10፡13-14፤43÷1፡5፤ኤር1÷8:13፤ሕዝ3÷16፤ዳን10÷1፤ሐጌ2÷5 **15÷2** ቍ8፤ዘፍ14÷15፤ኢሳ49÷22፤ኤር44÷26፤ሕዝ5÷11፤16÷48፤ሐሥ7÷5 **15÷3** ዘፍ12÷5፤24÷2፡34 **15÷4** ገላ4÷28 **15÷5** ዘፍ12÷2፤ኢዮ11÷8፤35÷5፤መዝ8÷3፤147÷4፤ኤር30÷19፤33÷22፤ሮሜ4÷18፤ዕብ11÷12 **15÷6** መዝ106÷31፤ሮሜ4÷3፡20-24፤ገላ3÷6፤ያዕ2÷23

[ሠ]13 ወይም *ዘመድ*፤ ወይም *ጓድ*
[የ]18 ኢየሩሳሌም ናት
[ደ]19 ወይም በቍ 22 ላይ ያለውንም ጨምሮ *ባለቤት* ሊሆን ይችላል
[ጀ]1 ወይም *ገዥ*
[ገ]1 ወይም ዋጋህም እጅግ ታላቅ ይሆናል
[ጠ]2 በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጕም አይታወቅም

7ደግሞም እግዚአብሔር፣ “ይህችን ምድር
ላወርስህ፣ ከከለዳውያን ምድር፣ ከዑር
ያወጣሁህ እግዚአብሔር (ያህዌ) እኔ ነኝ”
አለው።
8አብራምም፣ “እግዚአብሔር (ያህዌ) አምላክ
ሆይ፤ ይህችን ምድር እንደምወርሳት በምን
ዐውቃለሁ?” አለ።
9እግዚአብሔርም (ያህዌ) “እያንዳንዳቸው ሦስት
ዓመት የሆናቸው አንዲት ጊደር፣ አንድ
ፍየልና አንድ በግ፣ በተጨማሪም አንድ ዋኖ
ስና አንድ ርግብ አብረህ አቅርብልኝ” አለው።
10አብራምም እነዚህን ሁሉ አቀረበለት፤
ቈርጦም ሁለት ቦታ ከከፈላቸው በኋላ፣ እያ
ንዳንዱን ክፍል በሌላው ወገን ትይዩ አስ
ቀመጠ፤ ዋኖሷንና ርግቧን ግን ለሁለት አል
ከፈላቸውም። 11አሞሮችም ሥጋውን ለመ
ብላት ወረዱ፤ አብራም ግን አባረራቸው።
12ፀሓይ ልትገባ ስትል አብራም እንቅ
ልፍ ወሰደው፤ የሚያስፈራም ድቅድቅ ጨለማ
መጣበት። 13እግዚአብሔርም (ያህዌ) እንዲህ
አለው፤ “ዘርህ በባዕድ አገር ስደተኛ እንደ
ሚሆን በእርግጥ ዕወቅ፤ አራት መቶ ዓመ
ትም በባርነት ተረግጦ ይገዛል። 14ነገር ግን
በባርነት የሚገዛቸውን ሕዝብ እፈርድበታ
ለሁ፤ ከዚያም ብዙ ሀብት ይዘው ይወጣሉ።
15አንተ ግን ወደ አባቶችህ በሰላም ትሄዳ
ለህ፤ ዕድሜም ጠግበህ ወደ መቃብር ትወ
ርዳለህ፤ 16በአራተኛውም ትውልድ ዘርህ
ወደዚህ ምድር ይመለሳል፤ የአሞራውያን
ኀጢአት ገና ጽዋው አልሞላምና።”
17ፀሓይ ገብታ ከጨለመ በኋላ የምድጃ ጢ
ስና የሚንበለበል ፋና ታየ፤ በተከፈለውም
ሥጋ መካከል ዐለፈ። 18በዚያ ዕለት እግዚ
አ ብሔር (ያህዌ) ለአብራም እንዲህ ሲል ኪ
ዳን ገባለት፤ “ከግብፅ ወንዝ[ጨ] ጀምሮ እስከ
ታላቁ የኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ያለውን
ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ፤ 19የምሰጣቸውም
የቄናውያንን፣ የቄኔዛውያንን፣
የቃድሞናውያንን፣
20የኬጢያውያንን፣ የፌርዛውያንን፣ የራፋይ
ምን፣ የአሞራውያንን፣ የከነዓናውያንን፣ የጌር
ጌሳውያንንና የኢያቡሳውያንን ምድር ነው።”

## አጋርና እስማኤል

16 የአብራም ሚስት ሦራ፣ ልጆች አል
ወለደችለትም ነበር፤ እርሷም አጋር
የምትባል ግብፃዊት አገልጋይ ነበረቻት።
2አብራምንም፣ “እግዚአብሔር (ያህዌ) ልጅ እን
ዳልወልድ አድርጎኛል። ምናልባት በእርሷ
በኩል ልጆች አገኝ እንደሆን ሂደህ ከአገ
ልጋዬ ጋር ተኛ” አለችው።
አብራምም ሦራ ባለችው ተስማማ። 3አብ
ራም በከነዓን ምድር ዐሥር ዓመት ከኖረ

15፥7 ዘፍ11፥28፤ 12፥1፤13፥17፤17፥8፤ 28፥4፤35፥12፤48፥4፤ ዘፀ6፥8፤20፥2፤ዘዳ9፥ 5፤ሐሥ7፥3፡4፤ዕብ11፥8
15፥8 ቀኍ2፤ዘዳ12፥ 20፤19፥8፤ሉቃ1፥18
15፥9 1ሳሙ1፥24፤ ዘሌ1፥14፤5፥7፡11፤12፥ 8፤ዘኍ19፥2፤ዘዳ21፥ 3፤ሆሴ4፥16፤አሞ4፥1
15፥10 ቀኍ17፤ዘሌ 1፥17፤5፥8፤ኤር34፥18
15፥11 ዘዳ28፥26፤ ኤር7፥33
15፥12 ዘፍ2፥21
15፥13 ቀኍ16፤ዘፀ1፥ 11፤3፥7፤5፥6፡10-14፡ 18፤6፥5፤12፥40፤ዘኍ2 0፥15፤ዘዳ5፥15፤12፥ 40፤ኢዮ3፥18፤ሐሥ7፥ 16፡17፤ገላ3፥17
15፥14 ዘፍ50፥24፤ ዘፀ3፥8፤6፥6-8፤12፥25፡ 32-8፤ዘኍ10፥29፤ ኢሱ1፥2፤ሐሥ7፥7
15፥15 ዘፍ25፥8፤ 35፥29፤47፥30፤49፥ 29፤ዘፀ23፥26፤ዘዳ31፥ 16፤34፥7፤ኢሱ14፥11 ፤መሳ8፥32፤2ሳሙ7፥ 12፤1ነገ1፥21፤1ዜና 29፥28፤ኢዮ5፥26፤21፥ 23፤42፥17፤መዝ49፥ 19፤91፥16፤ምሳ3፥16፤ 9፥11፤ኢሳ 65፥20
15፥16 ቀኍ13፤ዘፍ 28፥15፤46፥4፤48፥21፤ 50፥24፤ዘፀ3፥8፡17፤ 12፥40፤ዘሌ18፥28፤ ኢሱ13፥4፤መሳ10፥11 ፤1ነገ21፥26፤2ነገ16፥ 3፤21፥11፤ሕዝ16፥3
15፥17 ቀኍ10፤መሳ 7፥16፡20፤15፥4፡5
15፥18 ዘፍ12፥7፤ 17፥2፡4፡7፤ዘፀ6፥4፤ 34፥10፡27፤ዘኍ34፥5፤ 1ዜና16፥16ኢሱ15፥ 4፡47፤1ነገ8፥65፤2ነገ 24፥7፤2ዜና7፥8፤መዝ1 05፥9፤ኢሳ27፥12፤ ኤር37፥5፤46፥2፤ሰቆ 4፥17፤ሕዝ30፥22፤ 47፥19፤2፥14 15፥19 ዘኍ24፥21፤ መሳ1፥16፤4፥11፡17፤5 ፥24፤1ሳሙ15፥6፤ 27፥10፤30፥29፤ 1ዜና2፥55
15፥20 ዘፍ10፥15፤ 13፥7፤14፥5፤ዘዳ7፥1
15፥21 ዘፍ10፥16፤ ኢሱ3፥10፤24፥11፤ ነህ9፥8
16፥1 ቀኍ3-4፡8፡15፤ ዘፍ11፥29፡30፤21፥14 ፤24፥61፤25፥12፤27- 61፤29፥24፡29፤31፥ 33፤46፥18፤ሉቃ1፥7፡ 36፤ገላ4፥24-25
16፥2 ዘፍ19፥32፤ 29፥31፤30፥2-4፡9-10

በኋላ ሚስቱ ሦራ ግብፃዊት አገልጋይዋን አጋ
ርን ሚስት እንድትሆነው ለባሏ ሰጠችው። 4አብ
ራምም ከአጋር ጋር ተኛ፤ እርሷም ፀነሰች።
አጋርም ነፍሰ ጡር መሆኗን ባወቀች ጊዜ
እመቤቷን መናቅ ጀመረች። 5ሦራም አብ
ራምን፣ “ለደረሰብኝ በደል ተጠያቂው
አንተ ነህ፤ አገልጋዬ ዕቅፍህ ውስጥ
እንድትገባ እኔው ሰጠሁህ፤ አሁን ግን ይኸ
ው ማርገዟን ስታውቅ ትንቀኝ ጀመር፤
እግዚአብሔር (ያህዌ) በአንተና በእኔ መካከል
ይፍረድ” አለችው።
6አብራምም፣ “አገልጋይሽ እንደሆነች በእ
ጅሽ ውስጥ ናት፤ የፈለግሽውን አድርጊባት”
አላት። ከዚያም ሦራ ስላሠቃየቻት አጋር
ጥላት ኰበለለች።
7የእግዚአብሔር (ያህዌ) መልአክ አጋርን በአ
ንድ የውሃ ምንጭ አጠገብ በምድረ በዳ
አገኛት፤ ምንጩም ወደ ሱር በሚወስደው
መንገድ ዳር ነበር። 8መልአኩም፣ “የሦራ
አገልጋይ አጋር ሆይ፤ ከየት መጣሽ? ወዴ
ትስ ትሄጃለሽ?” አላት፤
እርሷም፣ “ከእመቤቴ ከሦራ ኰብልዬ መም
ጣቴ ነው” ብላ መለሰች።
9የእግዚአብሔርም (ያህዌ) መልአክ፣ “ወደ
እመቤትሽ ተመለሽ፤ ለእርሷም ተገዥላት”
አላት። 10ደግሞም መልአኩ፣ “ዘርሽን እጅግ
አበዛለሁ፤ ከብዛቱም የተነሣ ሊቈጠር አይ
ችልም” አላት።
11የእግዚአብሔርም (ያህዌ) መልአክ በተጨ
ማሪ እንዲህ አላት፤

“እነሆ፤ ፀንሰሻል፤
ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ፤
እግዚአብሔር (ያህዌ) ችግርሽን ተመልክቶአል፤
ስሙን እስማኤል[ጸ] ትዪዋለሽ።
12እርሱም እንደ ዱር አህያ ይሆናል፤
እጁንም ባገኘው ሰው ሁሉ ላይ ያነሣል፤
ያገኘውም ሁሉ እጁን ያነሣበታል፤
ከወንድሞቹ ሁሉ ጋር እንደ ተጣላ
ይኖራል።”[ጸ]

16፥3 ዘፍ12፥4፡5 16፥4 ቀኍ1፤ዘፍ30፥1፤1ሳሙ1፥6 16፥5 ዘፍ 31፥53፤ዘፀ5፥21፤መሳ11፥27፤1ሳሙ24፥12፡15፤26፥10፡23፤መዝ50፥6፤ 75፥7 16፥6 ዘፍ31፥50፤ኢሱ9፥25 16፥7 ቀኍ11፡14፤ዘፍ20፥1፤ 21፥17፡19፤22፥11፡15፤24፥7፡40፤25፥18፤31፥11፤48፥16፤ዘፀ፥2፤ 14፥19፤15፥22፤23፥20፡23፤32፥34፤33፥2፤ዘኍ22፥22፤መሳ2፥1፤6፥ 11፤13፥3፤1ሳሙ15፥7፤27፥8፤2ሳሙ24፥16፤1ነገ19፥5፤2ነገ1፥3፤ 19፥35፤መዝ34፥7፤ዘካ1፥11፤ሐሥ5፥19 16፥8 ቀኍ1፤ዘፍ3፥9
16፥10 ዘፍ13፥16 16፥11 ቀኍ7፤ዘፍ3፥15፤12፥2-3፤17፥19፤ 18፥19፤21፥13፤29፥32፤31፥42፤37፥25፡28፤39፥1፤ዘፀ2፥24፤3፥7፡9፤ 4፥31፤ዘኍ20፥16፤ዘዳ26፥7፤ነህ9፥7፤ኢሱ44፥1፤መሳ8፥24፤1ሳሙ9፥16፤ አሞ3፥2፤ማቴ1፥21፤ሉቃ1፥13፡31፤ሐሥ5፥19 16፥12 ዘፍ25፥18፤ ኢ ዮ6፥5፤11፥12፤24፥5፤39፥5፤መዝ104፥11፤ኤር2፥24፤ሆሴ8፥9

[ጨ]18 *ወይም ደረቅ ወንዝ*
[ጸ]11 *እስማኤል ማለት እግዚአብሔር ይሰማል ማለት ነው*
[ጸ]12 ወይም *በስተ ምሥራቅ ይኖራል*

13እርሷም ያናገራትን እግዚአብሔርን (ያህዌ)፣
ኤልሮኢ ብላ ጠራችው፤ ምክንያቱም “የሚ
ያየኝን አሁን አየሁት”[θ] ብላ ነበርና። 14ከዚህ
የተነሣ የዚያ ምንጭ ስም፣ “ብኤርለሃይሮኢ”[ፊ]
ተብሎ ተጠራ፤ እስካሁንም በቃዴስና በባሬድ
መካከል ይገኛል።
15አጋር ለአብራም ወንድ ልጅ ወለደች
ለት፤ አብራምም ስሙን እስማኤል ብሎ
ጠራው። 16አብራም፣ አጋር እስማኤልን በወ
ለደች ጊዜ ዕድሜው 86 ዓመት ነበር።

## የግዝረት ኪዳን

17 አብራም ዕድሜው 99 ዓመት በሆነ
ጊዜ፣ እግዚአብሔር (ያህዌ) ተገልጦ
ለት እንዲህ አለው፤ “እኔ ኤልሻዳይ”[T]
ነኝ፤ በፊቴ ተመላለስ፤ ነቀፋም አይኑርብህ፤
2በእኔና በአንተ መካከል የተመሠረተውን ኪ
ዳን አጸናለሁ፤ ዘርህንም እጅግ አበዛለሁ።”
3አብራም በግንባሩ መሬት ላይ ተደፋ፤
እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) እንዲህ አለው፤ 4“እነሆ፤
የምገባልህ ኪዳን ይህ ነው፤ የብዙ ሕዝ
ቦች አባት ትሆናለህ። 5ከእንግዲህ ወዲያ
ስምህ አብራም[υ] መባሉ ቀርቶ አብርሃም
ይሆናል፤ የብዙ ሕዝቦች አባት አድርጌሃለ
ሁና። 6ዘርህን እጅግ አበዛለሁ፤ ብዙ ሕዝ
ብም አደርግሃለሁ፤ ነገሥታትም ከአንተ ይወ
ጣሉ። 7በእኔና በአንተ፣ ከአንተም በኋላ
ከዘርህ ጋር ከትውልድ እስከ ትውልድ የዘ
ላለም ኪዳኔን እመሠርታለሁ፤ በዚህም የአ
ንተና ከአንተም በኋላ የዘርህ አምላክ (ኤሎሂም)
እሆናለሁ። 8ይህችን አሁን በእንግድነት
የምትኖርባትን የከነዓንን ምድር በሙሉ
ለአንተና ከአንተም በኋላ ለዘርህ ለዘላለም
ርስት አድርጌ እሰጣለሁ፤ አምላካቸውም
(ኤሎሂም) እሆናለሁ።”
9ከዚያም እግዚአብሔር (ኤሎሂም) አብርሃምን እን
ዲህ አለው፤ “በአንተም በኩል፣ አንተና ከአ
ንተ በኋላ የሚመጣው ዘርህ ከትውልድ እስከ
ትውልድ ኪዳኔን ትጠብቃላችሁ። 10አንተና
ከአንተም በኋላ የሚመጣው ዘርህ የም
ትጠብቁት ኪዳን ይህ ነው፤ በመካከላችሁ
ያለ ወንድ ሁሉ ይገረዝ። 11ስለዚህ ሁላችሁም
ሸለፈታችሁን ትገረዛላችሁ፤ ይህም በእኔና
በእናንተ መካከል ላለው ኪዳን ምልክት ይሆ
ናል። 12የሚመጣውም ትውልድ ሁሉ፣ ማን
ኛውም ወንድ ልጅ፣ ስምንት ቀን ሲሞላው
ይገረዝ፤ እንደዚሁም በቤትህ የተወለደውና
ከውጭ በገንዘብ የተገዛ ባዕድ ሁሉ ይገረዝ።
13በቤትህ የተወለደም ሆነ በገንዘብህ የተ
ገዛ ሁሉ መገረዝ አለበት፤ በሥጋችሁ የሚ
ፈጸመው ይህ ኪዳኔ የዘላለም ኪዳን ይሆናል።
14የሥጋ ሸለፈቱን ያልተገረዘ ማንኛውም ወንድ
ኪዳኔን በማፍረሱ ከወገኖቹ ይወገድ።”
15እግዚአብሔር (ኤሎሂም) አብርሃምን እንዲህ
አለው፤ “ሦራን ከእንግዲህ ሦራ ብለህ አትጠ
ራትም፤ ስሟ ከዛሬ ጀምሮ ሣራ ይሁን።
16እኔ እባርካታለሁ ከእርሷም ወንድ ልጅ
እሰጥሃለሁ፤ የብዙም ሕዝቦች እናት ትሆን
ዘንድ እባርካታለሁ፤ የሕዝቦችም ነገሥታት
ከእርሷ ይወጣሉ።”
17አብርሃምም በግንባሩ መሬት ላይ ተደፋ፤
ሣቀና በልቡ፣ “እንዲያው ምንስ ቢሆን
የመቶ ዓመት ሽማግሌ የልጅ አባት መሆን
ይችላልን? ሣራስ በዘጠና ዓመቷ ልጅ መው
ለድ ትችላለችን?” አለ። 18አብርሃም እግዚ
አብሔርን (ኤሎሂም)፣ “እስማኤልን ብቻ ባርከህ
ባኖርህልኝ” አለው።
19እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) እንዲህ አለ፤ “ይሁን
እሺ፤ ነገር ግን ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅ
ትወልድልሃለች፤ ስሙንም ይስሐቅ[^] ብለህ
ትጠራዋለህ፤ እኔም ከእርሱ በኋላ ለዘሩ
ሁሉ የሚሆን የዘላለም ኪዳን ከእርሱ ጋር
እገባለሁ። 20ስለ እስማኤልም ቢሆን ልመ
ናህን ሰምቼሃለሁ፤ እርሱንም እባርከዋለሁ፤
ፍሬያማም አደርገዋለሁ፤ እጅግም አበዛዋ
ለሁ፤ የዐሥራ ሁለት አለቆች አባት ይሆ
ናል፤ ታላቅም ሕዝብ አደርገዋለሁ። 21ኪዳ
ኔን ግን የዛሬ ዓመት በዚሁ ጊዜ ሣራ ከም
ትወልድልህ ልጅ፣ ከይስሐቅ ጋር አደርጋ
ለሁ።” 22እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ከአብርሃም ጋር
መነጋገሩን ከፈጸመ በኋላ ወደ ላይ ወጣ።
23በዚያችም ዕለት አብርሃም እግዚአብሔር
(ያህዌ) ባዘዘው መሠረት ልጁን እስማኤልን፣
በቤቱ ውስጥ የተወለዱትንና ከውጭ በገን
ዘቡ የገዛቸውን ወንዶች በሙሉ ገረዛቸው።
24አብርሃም ሲገረዝ ዕድሜው 99 ዓመት ነበር።
25ልጁም እስማኤል ሲገረዝ 13 ዓመቱ ነበር።
26አብርሃምና ልጁ እስማኤል፣ ሁለቱም በዚ
ያኑ ቀን ተገረዙ። 27በአብርሃም ቤት ያሉ ወን
ዶች ሁሉ፣ በቤቱ የተወለዱትም ሆኑ ከውጭ
በገንዘብ የተገዙ ከእርሱ ጋር ተገረዙ።

**16፥13** ዘፍ32፥30፤ 33፥10፤ዘፀ24፥10፤ 33፥20፡23፤ዘኍ12፥8፤ መሳ6፥22፤13፥22፤ መዝ139፥1-12፤ኢሳ6፥5 **16፥14** ቍ7፤ዘፍ14፥7፤24፥62፤25፥11 **16፥15** ቍ1፤ዘፍ 17፥18፤21፥9፤25፥12፤28፥9፤ገላ4፥22 **16፥16** ዘፍ12፥4 **17፥1** ዘፍ5፥22፤ 12፥4፡7፤20፥5፤28፥3፤ 35፥11፤43፥14፤48፥3፤ 49፥25፤ዘፀ6፥3፤ዘዳ 18፥13፤ሩት1፥20፤ 1ነገ3፥6፤9፥4፤ኢዮ1፥1፤5፥17፤6፥4፡14፤22፥21፤33፥16፡19፤መዝ 15፥2፤18፥23፤78፥72፤101፥2፤ኢሳ13፥6፤ ሚክ6፥9፤ኢል1፥15 **17፥2** ዘፍ12፥2፤ 15፥8፤22፥16-18 **17፥3** ቍ17፤ዘፍ 18፥2፤19፥1፤33፥3፤ ዘፀ18፥7፤ዘኍ14፥5፤ ኢሱ5፥14፤7፥6፤መሳ 13፥20፤ሕዝ1፥28፤ 3፥23 **17፥4** ቍ16፤ዘፍ 12፥2፤15፥18፤25፥23 **17፥5** ቍ15፤ዘፍ 32፥28፤35፥10፤37፥3፡13፤43፥6፤46፥2፤1ነገ 18፥31፤2ነገ17፥34፤ 1ዜና1፥34፤ነህ9፥7፤ ኢሳ48፥1፤ዮሐ1፥42፤ ሮሜ4፥17 **17፥6** ቍ16፡19፤ዘፍ 1፥28፤18፥10፤21፥1፤22፥17፤26፥22፤28፥3፤35፥11፤36፥31፤41፥52፤47፥27፤48፥4፤49፥22፤ዘሌ26፥9፤ዘዳ7፥13፤ኢሳ51፥2፤ማቴ1፥6 **17፥7** ዘፍ6፥18፤9፥16፤15፥18፤ዘፀ ፥7፤20፥2፤29፥45፡46፤ዘሌ11፥44-45፤18፥2፤22፥33፤ 25፥38፤26፥9፡12፡15፡45፤ዘኍ15፥41፤ዘዳ4፥20፤7፥6፡21፤29፥13፤ 2ሳሙ7፥24፤ኤር14፥9፤ሮሜ፥8፤ገላ3፥16፤ ዕብ13፥20፤ራእ21፥7 **17፥8** ቍ7፤ዘፍ 10፥19፤12፥7፤15፥7፤23፥4፤28፥4፤35፥27፤ 37፥1፤ዘፀ6፥4፤1ዜና 29፥15፤ኤር31፥1 **17፥9** ዘፍ18፥19፤ 22፥18፤ዘፀ19፥5፤ ዘዳ5፥2 **17፥10** ቍ23፤ዘፍ 21፥4፤ዘሌ12፥3፤ኢሱ 5፥2፡5፡7፤ዮሐ7፥22፤ሐሥ7፥8፤ሮሜ4፥11 **17፥11** ዘፍ9፥12፤ ዘፀ2፥48፤ዘዳ10፥16፤ ሮሜ4፥11 **17፥12** ዘፍ9፥12፤ 21፥4፤ዘሌ12፥3፤ ኢሱ5፥2፤ሉቃ1፥59 **17፥13** ዘፍ9፥16፤ዘፀ12፥44፡48 **17፥14** ቍ23፤ዘፀ24-26፤12፥15፡19፤30፥33፤ዘሌ7፥20፡25፤17፥4፤18፥29፤ 19፥8፤20፥17፤ዘኍ9፥13፤15፥30፤19፥13፤ዘዳ17፥12፤ኢሱ5፥2-8፤ኢዮ 38፥15፤መዝ37፥28፤ሕዝ44፥7 **17፥15** ቍ5፤ዘፍ11፥29 **17፥16** ቍ4፡6፤ዘፍ24፥60፤ኢሳ29፥22፤ገላ4፥31 **17፥17** ቍ3፤ዘፍ12፥4፤ 18፥11፡12፡13፤21፥6፡7፤24፥1፡36፤ኤር20፥15፤ሉቃ1፥18፤ሮሜ4፥19፤ ገላ4፥23፤ዕብ11፥11 **17፥18** ዘፍ16፥15፤21፥11 **17፥19** ቍ6፥ 21፤ዘፍ9፥16፤16፥11፤18፥14፤21፥2፤26፥3፤50፥24፤ዘፀ13፥11፤ዘዳ 1፥8፤1ሳሙ1፥20፤ማቴ1፥21፤ሉቃ1፥13፡31፤ገላ3፥16 **17፥20** ዘፍ 13፥16፤25፥12-16፡18፤48፥19 **17፥21** ቍ19፤ዘፍ18፥10፡14፤ዘፀ 34፥10 **17፥22** ዘፍ18፥33፤35፥13፤ዘኍ12፥9 **17፥23** ቍ5፥ 10፡14፤ዘፍ12፥5 **17፥24** ዘፍ12፥4፤ሮሜ4፥11 **17፥25** ዘፍ16፥ 16 **17፥27** ዘፍ14፥14

[θ]13 ወይም *በኋላዬ አየሁት*
[ፊ]14 *ብኤርለሃይሮኢ* ማለት *የሚያየኝ ‘የሕያው’ ምንጭ* ማለት ነው
[T]1 *ሁሉን የሚገዛ* ማለት ነው
[υ]5 *አብራም* ማለት *የከበረ አባት* ማለት ነው
[^]19 *ይስሐቅ* ማለት *ይሥቃል* ማለት ነው

### ሦስቱ እንግዶች

18 ቀትር ላይ አብርሃም በመምሬ
ትልልቅ ዛፎች አቅራቢያ በምት
ገኘው ድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ *እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ተገለጠለት፤ 2ቀና ብሎም
ሲመለከት፣ ሦስት ሰዎች ቆመው አየ፤ ወዲ
ያውም ከድንኳኑ ደጃፍ ተነሥቶ፣ ፈጥኖ
ወደ ሰዎቹ ሄደ፤ ወደ መሬት ዝቅ ብሎም
እጅ ነሣ።

3አብርሃምም እንዲህ አለ፤ “ጌታዬ፤[ሐ] በፊ
ትህ ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ፣ ባሪያህን አል
ፈህ አትሂድ፤ 4ጥቂት ውሃ ይምጣላችሁና
እግራችሁን ታጠቡ፤ እዚህም ከዛፉ ሥር ዐረፍ
በሉ። 5ወደ እኔ ወደ አገልጋያችሁ ከመጣ
ችሁ፣ እህል ቀምሳችሁ ትበረቱ ዘንድ ምግብ
ላቅርብላችሁና ጕዞአችሁን ትቀጥላላችሁ።”

እነርሱም፣ “መልካም፤ እንዳልኸው አድ
ርግ” አሉት።

6አብርሃም በፍጥነት ሣራ ወዳለችበት
ወደ ድንኳኑ ገብቶ፣ “ቶሎ ብለሽ ሦስት
*መስፈሪያ*[ሠ] ስልቅ ዱቄት አቡኪና ቂጣ ጋግሪ”
አላት።

7ከዚያም ወደ መንጋው በጥድፊያ ሄዶ፣
አንድ ፍርጥም ያለ ሥጋው ገር የሆነ ጥጃ
መርጦ ለአገልጋዩ ሰጠው፤ አገልጋዩም ጥጃ
ውን ዐርዶ አዘጋጀው። 8አብርሃምም እርጎ፣
ወተትና የተዘጋጀውን የጥጃ ሥጋ አቀረበ
ላቸው፤ ሲበሉም ዛፉ ሥር አጠገባቸው ቆሞ
ነበር።

9እነርሱም አብርሃምን፣ “ሚስትህ ሣራ የት
አለች?” ብለው ጠየቁት።

እርሱም፣ “ድንኳን ውስጥ ናት” አላቸው።

10*እግዚአብሔርም* (ያህዌ)፣[ሠ] “የዛሬ ዓመት
በዚሁ ጊዜ በእርግጥ ተመልሼ እመጣለሁ፤
ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅ ትወልዳለች” አለው።

ሣራም በዚህ ጊዜ ከበስተ ጀርባው ካለው
ከድንኳኑ ደጃፍ ሆና ትሰማ ነበር። 11በዚ
ያን ጊዜ አብርሃምና ሣራ አርጅተው፣ ዕድሜ
አቸው ገፍቶ ነበር፤ ሣራም ልጅ የመውለ
ጃዋ ዕድሜ ዐልፎ ነበር። 12ሣራ በልቧ፣
“ካረጀሁና ጌታዬም[ረ] ከደከመ በኋላ በዚህ
ነገር መደሰት ይሆንልኛል?” ብላ ሣቀች።

13*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) አብርሃምን እንዲህ
አለው፤ “ሣራ፣ ‘ካረጀሁ በኋላ ልጅ እን
ዴት አድርጌ እወልዳለሁ’ ስትል ለምን
ሣቀች? 14*ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) የሚሳነው ነገር
አለን? የዛሬ ዓመት በተባለው ጊዜ ተመ
ልሼ እመጣለሁ፤ ሣራም ልጅ ይኖራታል።”

15ሣራ ስለ ፈራች፣ “ኧረ አልሣቅሁም”
ብላ ዋሸች።

እርሱ ግን፣ “ሣቅሽ እንጂ” አላት።

**18፥1** ዘፍ12፥7፤13፥18፤19፥1፤23፥10፡18፤34፥20፡24፤ሩት4፥1፤መዝ69፥12፤ሐሥ7፥2፤ዕብ11፥9
**18፥2** ቍ16፡22፤ዘፍ17፥3፤19፥1፡10፤24፥63፤32፥24፤43፥28፤ኢሱ5፥13፤መሳ13፥6-11፤ሆሴ12፥3-4፤ዕብ13፥2
**18፥3** ዘፍ19፥19፤32፥4፡18፡20፤33፥5፤39፥4፤ሩት2፥2፡10፡13፤1ሳሙ1፥18፤አስ2፥15
**18፥4** ዘፍ19፥2፤24፥32፤43፥24፤መሳ19፥21፤2ሳሙ11፥8፤ሉቃ7፥44
**18፥5** መሳ13፥15፤19፥5
**18፥6** ዘፍ19፥3፤2ሳሙ13፥8
**18፥7** 1ሳሙ28፥24፤ሉቃ15፥23
**18፥8** መሳ4፥19፤5፥25፤6፥19፤ኢሳ7፥15፡22
**18፥9** ዘፍ3፥9፤24፥67፤ዕብ11፥9
**18፥10** ዘፍ17፥6፡21፤21፥2፤2ነገ4፥16፤ሮሜ9፥9
**18፥11** ዘፍ11፥30፤17፥17፤ሉቃ1፥18፤ሮሜ4፥19፤ዕብ11፥11-12
**18፥12** ዘፍ17፥17፤1ጴጥ3፥6
**18፥13** ዘፍ17፥17
**18፥14** ቍ10፤ዘፍ17፥19፤ኢዮ42፥2፤ኢሳ40፥29፤50፥2፤51፥9፤ኤር32፥17፡27፤ማቴ19፥26፤ሮሜ4፥21፤9፥9፤ገላ4፥23
**18፥16** ቍ2
**18፥17** ዘፍ19፥24፤ኢዮ1፥16፤መዝ107፥34፤አሞ3፥7
**18፥18** ዘፍ12፥2፤ገላ3፥8
**18፥19** ዘፍ16፥11፤17፥9፤22፥12፡18፤26፥5ዘዳ4፥9-10፤6፥7፤ኢሱ24፥15፤2ሳሙ8፥15፤መዝ17፥2፤99፥4፤ኢሳ14፥1፤ኤር23፥5፤ኤፌ6፥4
**18፥20** ዘፍ19፥13፤13፥13፤ኢሳ1፥10፤ኤር23፥14፤ሕዝ16፥46
**18፥21** ዘፍ11፥5
**18፥22** ቍ2፤ዘፍ19፥1፡27
**18፥23** ዘፀ23፥7፤ዘሌ4፥3፡22፡27፤ዘኍ16፥22፤ዘዳ27፥25፤2ሳሙ24፥17፤መዝ11፥4-7፤94፥21፤ሕዝ18፥4፤2ጴጥ2፥9
**18፥24** ቍ26፤ኤር5፥1

### አብርሃም ስለ ሰዶም ማለደ

16ሰዎቹም ለመሄድ ሲነሡ፣ ቍልቍል
ወደ ሰዶም ተመለከቱ፤ አብርሃምም ሊሸ
ኛቸው አብሮአቸው ወጣ። 17*እግዚአብሔ
ርም* (ያህዌ) እንዲህ አለ፤ “እኔ የማደርገውን
ነገር ከአብርሃም እሰውራለሁን? 18አብር
ሃም በእውነት ታላቅና ብርቱ ሕዝብ ይሆ
ናል፤ የምድር ሕዝቦችም ሁሉ በእርሱ ይባ
ረካሉ። 19ትክክለኛና ቀና የሆነውን በማድ
ረግ *የእግዚአብሔርን* (ያህዌ) መንገድ ይጠብቁ
ዘንድ ልጆቹንና ከእርሱ በኋላ ቤተ ሰቦቹን
እንዲያዝ መርጬዋለሁ፤ ይኸውም *እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ
ሁሉ እንዲፈጸም ነው።”

20ደግሞም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) እንዲህ አለ፤
“በሰዶምና በገሞራ ላይ የሚሰማው ጩኸት
እጅግ በዝቶአል፤ ኀጢአታቸውም እጅግ ከፍ
ቶአል፤ 21አድራጎታቸው እኔ ዘንድ እንደ
ደረሰው ጩኸት መሆኑን ለማየት ወደዚያው
እወርዳለሁ፤ እንደዚያ ካልሆነም ዐውቃለሁ።”

22ሰዎቹም ፊታቸውን ወደ ሰዶም አቅን
ተው ሄዱ፤ አብርሃም ግን *በእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ፊት እንደ ቆመ ነበር።[ሸ] 23አብርሃምም
ወደ እርሱ ቀረብ ብሎ እንዲህ አለ፤ “በእ
ርግጥ ጻድቁን ከኀጢአተኛው ጋር አብረህ
ታጠፋለህን? 24አምሳ ጻድቃን በከተማዪቱ
ቢገኙ፣ በውኑ ነዋሪዎቹን ሁሉ ታጠፋለህን?
በውስጧ ለሚገኙ አምሳ ጻድቃን ስትል
ከተማዪቱን አትምርምን?[ቀ] 25እንዲህስ አይ
ሁን፤ ጻድቁን ከኀጢአተኛው ጋር እንዴት
ትገድለዋለህ? ይህን የመሰለው አድራጎት
ከአንተ ይራቅ፤ የምድር ሁሉ ዳኛ[በ] በቅን
አይፈርድምን?”

26*እግዚአብሔርም* (ያህዌ)፣ “በሰዶም ከተማ
አምሳ ጻድቃን ባገኝ ለእነርሱ ስል አገሪቱን
በሙላ እምራለሁ” አለ።

27ደግሞም አብርሃም እንዲህ አለ፤ “እኔ
ከንቱ፣ ትቢያና ዐመድ ሆኜ ሳለሁ ከጌታ
(አዶናይ) ጋር ለመናገር እንዴ ደፍሬአለሁ፤
28ለመሆኑ ከአምሳው ጻድቃን አምስት ቢጐ
ድሉ በአምስቱ ሰዎች ምክንያት መላ ከተማ
ዋን ታጠፋለህን?”

**18፥25** ዘፍ20፥4፤44፥7፡17፤ዘዳ1፥16-17፤32፥4፤መሳ11፥27፤2ዜና19፥7፤ዕዝ9፥15፤ነህ9፥33፤ኢዮ8፥3-7፡20፤9፥15፤34፥10፤36፥23፤መዝ7፥11፤58፥11፤75፥7፤94፥2፤119፥137፤ኢሳ3፥10-11፤5፥20፤ሕዝ18፥25፤ዳን 4፥37፤9፥14፤አሞ 5፥15፤ሚል2፥17፤ 3፥18፤ሮሜ3፥6፤ዕብ12፥23 **18፥26** ቍ24

[ሐ]3 ወይም *ጌታ ሆይ* [ሠ]6 22 ሊትር ገደማ ይሆናል
[ሠ]10 ዕብራይስጡ ከዚያም እርሱ ይለዋል [ረ]12 ወይም *ባሌ*
[ሸ]22 ከማሶሬቲኩ ጽሑፍ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን የጥንት ዕብራውያን የጸፉት ትውፊት ግን *እግዚአብሔር ግን በአብርሃም ፊት እንደ ቆመ ነበር* ይላል
[ቀ]24 ወይም *ይቅርታ ማድረግ* ሊሆን ይችላል፤ ይህም በቍ26 ላይ ያለውንም ጨምሮ ነው።
[በ]25 ወይም *ገዥ*

እርሱም፣ “አርባ አምስት ጻድቃን ባገኝ
አላጠፋትም” አለ፡፡
29አብርሃምም እንደ ገና፣ “ምናልባት አርባ
ጻድቃን ቢገኙስ?” አለ
እርሱም፣ “ለአርባው ስል እምራታለሁ”
አለ፡፡
30ደግሞም አብርሃም፣ “ጌታ ዬ (አዶናይ)
አይ ቈጣ፤ እባክህ ልናገር፤ ሠላሳ ጻድቃን
ብቻ ቢገኙስ?”
እርሱም፣ “ሠላሳ ባገኝ አላጠፋትም” ብሎ
መለሰ፡፡
31አብርሃምም፣ “ከጌታ (አዶናይ) ጋር
እናገር ዘንድ መቼም አንዴ ደፍሬአለሁና
ምና ልባት ሃያ ብቻ ቢገኙስ?” አለ፡፡
እርሱም፣ “ሃያ ቢገኙ፣ ለእነርሱ ስል
እምራታለሁ” አለ፡፡
32አብርሃምም፣ “ጌታ ዬ (አዶናይ) አይቈጣ፤
አንድ ጊዜ ብቻ ልናገር፤ ምናልባት ዐሥር
ብቻ ቢገኙስ?” አለ፡፡
እርሱም “ስለ ዐሥሩ ስል አላጠፋትም”
ብሎ መለሰ፡፡
33እግዚአብሔር (ያህዌ) ከአብርሃም ጋር
ንግግሩን ከጨረሰ በኋላ ሄደ፤ አብርሃምም
ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡

## ሰዶምና ገሞራ ጠፉ

19 ሁለቱ መላእክት ምሽት ላይ ሰዶም
ደረሱ፤ ሎጥም በሰዶም ከተማ
መግቢያ በር ተቀምጦ ነበር፤ ሎጥም መላእ
ክቱን ሲያይ ሊቀበላቸው ብድግ አለ፤ በግ
ምባሩም ወደ ምድር ተደፍቶ እጅ ነሣ
ቸው፡፡ 2እርሱም፣ “ጌቶቼ፤ እባካችሁ ወደ
እኔ ወደ ባሪያችሁ ቤት ጎራ በሉ፤ ከዚ
ያም እግራችሁን ታጠቡ፤ አድራችሁም ጧት
በማለዳ ጕዞአችሁን ትቀጥላላችሁ” አላቸው፡፡
እነርሱም፣ “አይሆንም፤ እዚሁ አደባባይ
ላይ እናድራለን” አሉት፡፡
3ሎጥ ግን አጥብቆ ስለ ለመናቸው አብ
ረውት ወደ ቤቱ ገቡ፤ ከዚያም ቂጣ ጋግሮ
አቀረበላቸውና በሉ። 4ከመተኛታቸውም በፊት፣
የሰዶም ከተማ ነዋሪዎች የሆኑ ወንድ ወጣ
ቶችና ሽማግሌዎች ከያካባቢው መጥተው
ቤቱን ከበቡት፡፡ 5ሎጥንም ጠርተው፣ “በዚ
ህች ምሽት ወደ ቤትህ የገቡት ሰዎች የት
አሉ? ሩካቤ ሥጋ እንድንፈጽምባቸው ወደ
ውጭ አውጣልን” አሉት፡፡
6ሎጥም ሊያነጋግራቸው ወደ ውጭ ወጣ፤
መዝጊያውን ከበስተ ኋላው ዘግቶ፣ 7እንዲህ
አለ፤ “ወዳጆቼ ሆይ፤ እባካችሁ እንዲህ ያለ
ውን ክፉ ነገር አታድርጉ፡፡ 8እነሆ፤ ወንድ የ
ማ ያውቁ ሁለት ሴቶች ልጆች አሉኝ፡፡
እነር ሱን ላውጣላችሁና የፈለጋችሁትን
አድርጉባ ቸው፡፡ በእነዚህ ሰዎች ላይ ግን
አንዳች ነገር አታድርጉባቸው፤ እኔን
ብለው ወደ ቤቴ ገብተዋልና፡፡”
9እነርሱም፣ “ዞር በል! ይህ ሰው ራሱ ትና
ንት ተሰዶ የመጣ ነው፤ ዛሬ ደግሞ ዳኛ
ልሁን ይላል፡፡ ዋ! በእነርሱ ካሰብነው የከፋ
እንዳናደርስብህ!” አሉት፤ ከዚያም ሎጥን
እየገፈታተሩ የበሩን መዝጊያ ለመስበር ተን
ደረደሩ፡፡
10ከቤቱ ውስጥ የነበሩት እንግዶች ግን
እጃቸውን በመዘርጋት ስበው ወደ ውስጥ
አስገቡት፤ በሩንም ዘጉ፡፡ 11ከዚያም በሩን
እንዳያገኙት በቤቱ ደጃፍ ላይ የተሰበሰቡ
ትን ወጣቶችና ሽማግሌዎች ዐይን አሳወሩ፡፡
12ሁለቱ ሰዎችም ሎጥን እንዲህ አሉት፤
“በከተማዋ ውስጥ የሚኖሩ የአንተ የሆኑ
ሰዎች አሉህ? ዐማቾች፣ ወንዶችና ሴቶች
ወይም ሌሎች ዘመዶች ካሉህ ቶሎ ብለህ
ከዚህ እንዲወጡ አድርግ፤ 13ይህን ስፍራ
ልናጠፋው ነው፡፡ በሕዝቦቿ ላይ ወደ እግዚ
አብሔር (ያህዌ) የቀረበው ጩኸት ታላቅ በመ
ሆኑ፣ እንድናጠፋት እግዚአብሔር
ልኮናል፡፡”
14ሎጥ ከቤቱ ወጥቶ የሴት ልጆቹ እጮ
ኞች† የሆኑትን ዐማቾቹን፣ “እግዚአብሔር
(ያህዌ) ይህችን ከተማ ሊያጠፋት ነውና በፍ
ጥነት ከዚህ ስፍራ ውጡ” አላቸው፤ ዐማ
ቾቹ ግን የሚቀልድ መሰላቸው፡፡
15ሲነጋጋም መላእክቱ ሎጥን፣ “ከከተማ
ዪቱ ጋር አብራችሁ እንዳትጠፉ፣ ሚስት
ህንና ሁለቱን ሴት ልጆችህን ይዘህ ከዚህ
ቦታ በፍጥነት ውጣ” ብለው አቻኰሉት፡፡
16ሎጥ ሲያመነታም፣ እግዚአብሔር (ያህዌ)
ስለ ራራላቸው ሰዎቹ የእርሱን፣ የሚስቱ
ንና የሁለት ሴቶች ልጆቹን እጅ ይዘው
ከከተማዪቱ በደኅና አወጧቸው፡፡ 17እንዳ
ወጧቸውም፣ መልአኩ፣ “ሕይወታችሁን ለማ
ትረፍ ፈጥናችሁ ሽሹ፤ መለስ ብላችሁ ወደ
ኋላችሁ አትመልከቱ፤ ከረባዳው ስፍራ እንኳ
ቆም አትበሉ፤ ወደ ተራራው ሽሹ፤ አለበለ
ዚያ ትጠፋላችሁ” አላቸው፡፡
18ሎጥም እንዲህ አላቸው፤ “ጌቶቼ ሆይ፤‡
እባካችሁ እንደዚህስ አይሁን፤ 19እነሆ፤ እኔ
ባሪያህ አንዴ በፊትህ ሞገስ አግኝቻለሁ፤ ሕይ
ወቴን ለማዳን ታላቅ ርኅራኄ አድርገህል
ኛል፤ እኔ እንደሆንሁ ወደ ተራሮቹ ሽሽቼ
ማምለጥ ስለማልችል የሚወርደው መዓት
ደርሶ ያጠፋኛል፡፡ 20እነሆ፤ ወደዚያ ሽሽቶ
ለማምለጥ ቅርብ የሆነች ትንሽ ከተማ አለች፤
ወደ እርሷ ልሽሽ፤ በጣም ትንሽ አይደለችም

18፥27 ዘፍ2፥7፤ ኢዮ2፥8
18፥30 ቆኑ32፤ዘፍ 44፥18፤ዘፀ32፥22
18፥32 ቆኑ30፤ መሳ6፥39፤ኤር5፥1
18፥33 ዘፍ17፥22፤ 31፥55፤ዘፀ31፥18
19፥1 ዘፍ11፥27፤ 17፥3፤18፥1:2:22፤ 48፥12፤ሩት2፥10፤ 1ሳሙ25፥23፤2ሳሙ 14፥33፤2ነገ2፥15፤ ዕብ13፥2
19፥2 ዘፍ18፥4፤ ሉቃ7፥44፤መሳ19፥ 15፡20
19፥3 ዘፍ18፥6፤ 33፥11፤ዘፀ12፥39፤ ኢ ዮ31፥32
19፥4 ዘፍ13፥13
19፥5 ዘፍ13፥13፤ ዘሌ18፥22፤ዘዳ23፥ 18፤መሳ19፥22፤ ሮሜ 1፥24-27
19፥6 መሳ19፥23
19፥8 መሳ19፥24፤ 2ጴጥ2፥7-8
19፥9 ዘፍ13፥8፤ 23፥4፤ሐሥ7፥27
19፥10 ዘፍ18፥2
19፥11 ዘዳ28፥28-29፤2ነገ6፥18፤ሐሥ 13፥11
19፥12 ዘፍ6፥18
19፥13 ዘፍ18፥20፤ ዘፀ12፥29፤2ሳሙ24፥ 16፤2ነገ19፥35፤1ዜና 21፥12:15፤2ዜና32፥ 21፤መዝ78፥49፤ኤር 21፥12፤25፥18፤44፥ 22፤51፥45
19፥14 ዘኍ16፥21፤ ዘፀ9፥21፤1ነገ13፥18፤ ኤር5፥12፤43፥2፤ሉቃ 17፥28፤ራእ18፥4
19፥15 ዘኍ16፥26፤ ኢዮ21፥18፤መዝ58፥ 9፤73፥19፤90፥5፤ራእ 18፥4
19፥16 ዘፀ34፥6፤ መዝ33፥18-19፤ 2ጴጥ2፥7
19፥17 ቆኑ19፡26፤ ዘፍ13፥12፤14፥10፤ 1ነገ19፥3፤ኤር48፥6፤ ማቴ24፥16
19፥19 ቆኑ17፡30፤ ዘፍ6፥8፤18፥3፤24፥ 12፤39፥21፤40፥14፤ 47፥29፤ሩት1፥8፤ 2፥20፤3፥10

†14 ወይም *ሴት ልጆቹን ያገቡትን* ‡18 ወይም *እንደዚህስ አይሁን ጌታ፤ ወይም እንደዚህስ አይሁን ጌታዬ*

እንዴ? ወደዚያ ብሸሽ እኮ ሕይወቴ ትተ
ርፋለች::”
21እርሱም እንዲህ አለው፤ “ይሁን እሺ፣
ልመናህን ተቀብያለሁ፤ ያልካትንም ከተማ
አላጠፋትም:: 22አንተ እዚያ እስክትደርስ
ድረስ አንዳች ማድረግ ስለማልችል ቶሎ
ብለህ ወደዚያ ሽሽ” ስለዚህም የዚያች ከተ
ማ ስም ዞዓርጎ ተባለ::
23ሎጥ ዞዓር ሲደርስ ፀሓይ በምድሩ
ላይ ወጥታ ነበር:: 24ከዚያም *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) በሰዶምና በገሞራ ላይ ከሰማይ *ከእግ
ዚአብሔር* (ያህዌ) ዘንድ የሚያቃጥል ዲንና
እሳት አዘነበባቸው:: 25እነዚያንም ከተሞ
ችና ረባዳውን ምድር በሙሉ፣ በከተሞቹም
የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ፣ የምድሩን ቡቃያ
ሳይቀር ገለባበጠው:: 26የሎጥ ሚስት ግን
ወደ ኋላዋ ስለ ተመለከተች የጨው ዐምድ
ሆና ቀረች::
27አብርሃም በማግስቱ፣ ማለዳ ተነሥቶ ከዚህ
ቀደም *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ቆሞ ወደ
ነበረበት ቦታ ሄደ:: 28ሰዶምንና ገሞራን፣
እንዲሁም በረባዳው ስፍራ የሚገኘውን ምድር
ሁሉ ቍልቍል ተመለከተ፤ ከእቶን የሚወጣ
የመሰለ ጥቅጥቅ ያለ ጢስ ከምድሪቱ ወደ
ላይ ሲትጐለጐል አየ::
29እንደዚህ አድርጎ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
በረባዳው ስፍራ የነበሩትን ከተሞች ሲያጠፋ
አብርሃምን አሰበው፤ ስለዚህም የሎጥ መኖ
ሪያ የነበሩትን ከተሞች ካጠፋው መዓት
ሎጥን አወጣው::

## ሎጥና ሴት ልጆቹ

30ሎጥ በዞዓር መኖርን ስለ ፈራ፣ ከዚያ
ተነሥቶ ከሁለቱ ሴት ልጆቹ ጋር በአቅራ
ቢያው ወደሚገኙት ተራሮች ሄደ፤ መኖሪያ
ውንም ከሁለት ሴት ልጆቹ ጋር በዋሻ ውስጥ
አደረገ:: 31አንድ ቀን ታላቂቱ ልጅ፣ ታናሺ
ቱን እንዲህ አለቻት፤ “አባታችን አርጅቶ
አል፤ በምድር ሁሉ እንደሚኖሩ ሰዎች ወግ
አብሮን የሚተኛ ወንድ በአካባቢያችን የለም::
32ስለዚህ አባታችንን የወይን ጠጅ እናጠጣ
ውና ከእርሱ ጋር እንተኛ፤ የትውልድ ሐረ
ጋችን እንዳይቋረጥ ዘር ከአባታችን እናት
ርፍ::”
33በዚያችም ምሽት አባታቸውን የወይን ጠጅ
አጠጡት፤ ከዚያም ትልቋ ልጁ ሄዳ ከአ
ባቷ ጋር ተኛች፤ እርሱ ግን ስትተኛም ሆነ
ስትነሣ አላወቀም ነበር::
34በማግስቱም ታላቂቱ ልጅ ታናሺቱን፣
“እኔ ትናንትና ማታ ከአባቴ ጋር ተኝቻለሁ፤
ዛሬም እንደ ገና የወይን ጠጅ እናጠጣው፤
አንቺም ደግሞ ከእርሱ ዘንድ ገብተሽ ተኚ፤
በዚህም የትውልድ ሐረጋችን እንዳይቋረጥ
ከአባታችን ዘር ማትረፍ እንችላለን” አለቻት::
35በዚያችም ምሽት ደግሞ አባታቸውን የወ
ይን ጠጅ አጠጡት፤ ትንሿ ልጁም ሄዳ
ከአባቷ ጋር ተኛች፤ እርሱ ግን ስትተኛም
ሆነ ስትነሣ አላወቀም ነበር::
36ስለዚህ ሁለቱም የሎጥ ሴት ልጆች
ከአባታቸው አረገዙ:: 37ትልቋ ልጁ ወንድ
ልጅ ወለደች፤ ስሙንም ሞዓብ ብላ ጠራ
ችው፤ እርሱም የዛሬዎቹ ሞዓባውያንነ አባት
ነው:: 38ትንሿ ልጁም እንደዚሁ ወንድ ልጅ
ወለደች፤ ስሙንም ቤንአሚኘ ብላ ጠራችው፤
እርሱም የዛሬዎቹ አሞናውያን አባት ነው::

## አብርሃምና አቤሜሌክ

20፥1-18 ተጓ ምብ - ዘፍ 12፥10-20፤ 26፥1-11

20 አብርሃም ከዚያ ተነሥቶ ወደ ኔጌብ
አካባቢ ሄዶ በቃዴስና በሱር መካ
ከል ሰፈረ፤ ለጥቂት ጊዜም በጌራራ ተቀ
መጠ:: 2በዚያም አብርሃም ሚስቱን ሣራን፣
“እህቴ ናት” ይል ነበር:: ስለዚህ የጌራራ
ንጉሥ አቢሜሌክ መልእክተኛ ልኮ ሣራን
ወሰዳት::
3እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) በአንድ ሌሊት
በሕልም ወደ አቢሜሌክ መጥቶ፣ “እነሆ፤
በወሰድሃት ሴት ምክንያት ምውት ነህ፤
እርሷ ባለ ባል ናት” አለው::
4አቢሜሌክም ገና አልደረሰባትም ነበርና
እንዲህ አለ፤ “ጌታ ሆይ፤ በደል ያልፈጸመ
ውን ሕዝብ ታጠፋለህን? 5‘እኅቴ ናት’
ያለኝ ራሱ አይደለምን? ደግሞስ ራሷም
ብትሆን፣ ‘ወንድሜ ነው’ አላለችምን? እኔ
ይህን ያደረግሁት በቅን ልቦናና በንጹሕ
እጅ ነው::”
6እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) በሕልሙ እንዲህ አለው፤
“አንተ ይህን ያደረግኸው በቅን ልቦና መሆ
ኑን ዐውቄአለሁ፤ በእኔም ላይ ኀጢአት እን
ዳትሠራ የጠበቅሁህና እንዳትነካትም ያደ
ረግሁት ለዚሁ ነው:: 7አሁንም ሚስቱን ለሰ
ውዬው መልስለት፤ ነቢይ ነውና ይጸልይል
ሃል፤ አንተም ትድናለህ፤ ባትመልስለት ግን
አንተም ሆንህ የአንተ የሆነ ሁሉ እንደም
ትሞቱ ዕወቅ::”
8በማግስቱም ማለዳ፣ አቢሜሌክ ሹማም
ንቱን ሁሉ ጠርቶ፣ የሆነውን ሁሉ ነገራቸው፤
እነርሱም ታላቅ ፍርሀት አደረባቸው:: 9ከዚያም

**19፥21** 1ሳሙ25፥35፤2ሳሙ14፥8፤ኢዮ42፥9
**19፥22** ዘፍ13፥10
**19፥23** ዘፍ13፥10
**19፥24** ዘፍ18፥17፤ዘሌ10፥2፤ዘዳ29፥23፤ኢዮ18፥15፤መዝ11፥6፤ኢሳ1፥9፤13፥19፤30፥33፤34፥9፤ኤር49፥18፤50፥40፤አሞ4፥11፤ማቴ10፥15፤ሉቃ17፥29፤ሕዝ38፥22
**19፥25** ቍ24፤ዘፍ13፥12፤መዝ107፥34፤ኢሳ1፥10፤ኤር20፥16፤23፥14፤ሰቆ4፥6፤ሕዝ16፥48፤26፥16፤ሶፎ3፥8፤ሐጌ2፥22
**19፥26** ቍ17፤ሉቃ17፥32
**19፥27** ዘፍ18፥22
**19፥28** ዘፍ15፥17፤ዘፀ19፥18፤ራእ9፥2፤18፥9
**19፥29** ዘፍ8፥1፤13፥12፤14፥12፤ሕዝ14፥16፤2ጴጥ2፥7
**19፥30** ቍ19:22፤ዘፍ13፥10፤14፥10
**19፥32** ቍ34:36፤ዘፍ16፥2፤38፥18
**19፥33** ቍ35
**19፥34** ቍ32
**19፥35** ቍ33፤ዘፍ9፥21
**19፥36** ቍ32
**19፥37** ዘፍ36፥35፤ዘፀ15፥15፤ዘኍ22፥4፤24፥17፤25፥1፤ዘዳ2፥9፤መሳ3፥28፤ሩት1፥4፡22፤1ሳሙ14፥47፤22፥3-4፤2ሳሙ8፥2፤2ነገ1፥1፤3፥4፤ዕዝ9፥1፤መዝ108፥9፤ኢሳ15፥1፤25፥10፤ኤር25፥21፤48፥1፤ሕዝ25፥8፤ሶፎ2፥9
**19፥38** ዘኍ21፥24፤ዘዳ2፥19፤23፥3፤ኢሱ12፥2፤መሳ3፥13፤10፥6፡7፤1ሳሙ11፥1-11፤14፥47፤1ዜና19፥1፤2ዜና20፥23፤26፥8፤27፥5፤ነህ2፥19፤4፥3፤ኤር25፥21፤40፥14፤49፥1፤ሕዝ21፥28፤25፥2፤አሞ1፥13
**20፥1** ዘፍ12፥9፤14፥7፤16፥7፤18፥1፤26፥1፡3፡6፡17
**20፥2** ቍ14፤ዘፍ12፥13:15፤21፥22፤26፥1
**20፥3** ቍ7፤ዘፍ26፥11፤28፥12፤31፥10፡24፤37፥5፡9፤40፥5፤41፥1፤ዘፀ10፥7፤12፥33፤ዘኍ12፥6፤22፥9፡20፤ዘዳ13፥1፤1ዜና16፥21፤ኢዮ33፥15፤መዝ105፥14:38፤ዳን2፥1፤4፥5 **20፥4** ዘፍ18፥25 **20፥5** ዘፍ12፥19፤17፥1፤መዝ7፥8፤25፥21፤26፥6፤41፥12 **20፥6** ዘፍ13፥13፤መዝ41፥4፤51፥4፤1ሳሙ25፥26፡34 **20፥7** ቍ3:17፤ዘፀ8፥8፤ዘኍ11፥2፤12፥13፤ዘዳ18፥18፤34፥10፤1ሳሙ7፥5፤1ነገ13፥6፤2ነገ3፥11፤5፥3፤1ዜና16፥22፤ኢዮ42፥8፤መዝ9፥5፤105፥5፤ኤር18፥20፤37፥3፤42፥2

ጎ22 *ዞዓር* ማለት *ትንሽ* ማለት ነው
ነ37 *ሞዓብ* የሚለው ቃል *ከአባት* የሚል ትርጒም ካለው የዕብ
ራይስጥ ቃል ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው::
ኘ38 *ቤንአሚ* ማለት የሕዝቤ ልጅ ማለት ነው

አቢሜሌክ አብርሃምን አስጠርቶ እንዲህ
አለው፤ “ይህ ያደረግህብን ነገር ምንድን
ነው? ምን በደልሁህና ነው በእኔና በግዛቴ
ላይ እንዲህ ያለውን ታላቅ የጥፋት መዘዝ
ያመጣብህን? በእውነቱ መደረግ የማይገባውን
ነው ያደረግህብን::” 10ከዚያም አቢሜሌክ፣
“ለመሆኑ ይህን ያደረግህበት ምክንያት
ምንድን ነው?” ሲል አብርሃምን ጠየቀው::
11አብርሃምም አቢሜሌክን እንዲህ አለው፤
“እዚህ ቦታ ፈሪሀ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) አለ
መኖሩን ተገነዘብሁ፤ ሰዎቹም ለሚስቴ ሲሉ
ይገድሉኛል ብዬ ሠጋሁ፤ 12ደግሞም እኮ
በእርግጥ እኅቴ ናት፤ ከአንድ እናት ባንወ
ለድም በአባት አንድ ነን፤ ኋላም አገባኋት::
13እግዚአብሔር (ኤሎሂም) አዞኝ ከአባቴ ቤት ወጥቼ
በየአገሩ ስዞር፣ ‘ለእኔ ያለሽን ፍቅር በዚህ
ግለጭልኝ፤ በየደረስንበት ስፍራ ሁሉ “እርሱ
ወንድሜ ነው” በዪ’ ብያት ነበር::”
14ከዚያም አቢሜሌክ፣ በጎችና የቀንድ ከብ
ቶች፣ ወንድና ሴት አገልጋዮችን ለአብር
ሃም ሰጠው፤ ሚስቱን ሣራንም መለሰለት::
15አቢሜሌክም አብርሃምን፣ “እነሆ፤ አገሬ
አገርህ ናት፤ በፈቀድህበት ስፍራ መኖር
ትችላለህ” አለው::
16ሣራንም፣ “እነሆ፤ ለወንድምሽ ለአብር
ሃም 1000 ጥሬ ብር[ኣ] እሰጠዋለሁ፤ ይህም
በአንቺ ላይ ለተፈጸመው በደል ካሣ እን
ዲሆንና አብረውሽ ያሉ ሁሉ እንዲያውቁት
ነው፤ በዚህም ንጽሕናሽ ይረጋገጣል” አላት::
17ከዚያም አብርሃም ወደ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
ጸለየ፤ እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) አቢሜሌክን፣
ሚስቱንና ሴት አገልጋዮቹን ፈወሳቸው፤
እንደ ገናም ልጅ ለመውለድ በቁ:: 18እግ
ዚአብሔር (ያህዌ) በአብርሃም ሚስት በሣራ
ምክንያት፣ በአቢሜሌክ ቤት የሚገኙትን ሴቶች
ማሕፀናቸውን ሁሉ ዘግቶ ነበርና::

## የይስሐቅ መወለድ

21 እግዚአብሔር (ያህዌ) በተናገረው መሠረት
ሣራን አሰባት፤ የገባውንም ተስፋ ፈጸ
መላት:: 2ሣራ ፀነሰች፤ ልክ እግዚአብሔር (ኤሎ
ሂም) ባለው ጊዜ ለአብርሃም ወንድ ልጅ
ወለደ ችለት:: 3አብርሃም፣ ሣራ
የወለደችለትን ልጅ ስሙን ይስሐቅ[ከ]
አለው:: 4አብርሃም፣ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
ባዘዘው መሠረት ልጁን ይስሐቅን በተወለደ
በስምንተኛው ቀን ገረዘው:: 5አብርሃም፣ ልጁ
ይስሐቅ ሲወለድለት፣ ዕድሜው መቶ ዓመት
ነበረ::
6ሣራም፣ “እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሣቅ አድ
ሎኛል፤ ስለዚህ፣ ይህን የሚሰማ ሁሉ ከእኔ
ጋር ይሥቃል” አለች:: 7ደግሞም፣ “ለመ
ሆኑ፣ ‘ሣራ ልጆች ታጠባለች’ ብሎ ለአብ
ርሃም ማን ተናግሮት ያውቅ ነበር? ይኸው
በስተርጅናው ወንድ ልጅ ወለድሁለት”
አለች::

## የአጋርና የእስማኤል መባረር

8ሕፃኑ አደገ፤ ጡት መጥባቱንም ተወ::
አብርሃምም ይስሐቅ ጡት በጣለባት ዕለት
ታላቅ ድግስ ደገሰ:: 9በሌላ በኩል ደግሞ፣
ግብፃዊቷ አጋር ለአብርሃም የወለደችለት
እስማኤል፣ በይስሐቅ ሲያሾፍበት ሣራ አየች፤
10አብርሃምንም፣ “ይህችን ባሪያ ከነልጇ አባ
ርልኝ፤ ምንም ቢሆን የዚህች ባሪያ ልጅ፣ ከልጄ
ከይስሐቅ ጋር ውርስ አይካፈልም አለች::”
11እስማኤል ልጁ ስለ ሆነ ነገሩ አብርሃ
ምን እጅግ አስጨነቀው:: 12እግዚአብሔርም
(ኤሎሂም) አብርሃምን እንዲህ አለው፤ “ስለ ልጁም
ሆነ ስለ አገልጋይህ አሳብ አይግባህ፤ ዘር
የሚጠራልህ በይስሐቅ በኩል ስለ ሆነ፣ ሣራ
የምትልህን ሁሉ ስማ:: 13የአገልጋይህም
ልጅ የራስህ ልጅ ስለ ሆነ፣ እርሱንም ታላቅ
ሕዝብ አደርገዋለሁ::”
14በማግስቱ አብርሃም ማልዶ ተነሣ::
ጥቂት ምግብ ወስዶ፣ ውሃ በእርኮት አድ
ርጎ ለአጋር ሰጣት፤ በትከሻዋም አሸክሞአት
ከነልጇ አሰናበታት:: እርሷም ሄደች፤ በቤ
ርሳቤህም ምድረ በዳ ትንከራተት ጀመር::
15በእርኮት የነበረው ውሃ ባለቀ ጊዜ፣ ልጁን
ከአንድ ቍጥቋጦ ሥር አስቀመጠችው::
16ከዚያም፣ “ልጁ ሲሞት ዐይኔ አያይም”
ብላ፣ የቀስት ውርወራ ያህል ርቃ ዐረፍ
አለች፤ እርሷም[ኸ] እየተንሰቀሰቀች ታለቅስ
ጀመር::
17እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) የልጁን ጩኸት ሰማ::
የእግዚአብሔር (ኤሎሂም) መልአክ ከሰማይ አጋ
ርን እንዲህ አላት፤ “አጋር ሆይ፤ ምን ሆነ
ሻል? ልጅሽ ከተኛበት ሲያለቅስ እግዚአብሔር
(ኤሎሂም) ሰምቶታል፤ ስለዚህ አትፍሪ:: 18ተነ
ሥተሽ ልጁን አንሺው፤ ያዢውም፤ ታላቅ
ሕዝብ አደርገዋለሁና::”
19እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ዐይኖቿን ከፈተላት፤
የውሃ ጕድጓድም አየች፤ ሄዳም በእርኮቱ
ውሃ ሞልታ ልጇን አጠጣች::
20እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ከልጁ ጋር ነበር፤ ልጁም
እያደገ ሄደ፤ መኖሪያውንም በምድረ በዳ
ውስጥ አደረገ፤ ጐበዝ ቀስተኛም ሆነ:: 21በፋራን
ምድረ በዳ ሳለም፣ እናቱ ከግብፅ አንዲት
ሴት አምጥታ አጋባችው::

## በቤርሳቤህ የተደረገው ስምምነት

22በዚያን ጊዜ አቢሜሊክ ከሰራዊቱ አለቃ
ከፊኮል ጋር ሆኖ አብርሃምን እንዲህ

[ኣ]16 11.5 ኪ.ግ. ገደማ ይሆናል::
[ከ]3 ይስሐቅ ማለት ይሥቃል ማለት ነው
[ኸ]16 ዕብራይስጡና ሰብዐ ሊቃናት ልጁ ይላሉ::

20፥9 ዘፍ12፥18፤ 34፥7
20፥11 ዘፍ12፥12፤ 31፥31፤42፥18፤ነህ5፥15፤ኢዮ31፥23፤መዝ36፥1፤ምሳ16፥6
20፥12 ዘፍ12፥13
20፥13 ዘፍ12፥1:13፤ዘዳ26፥5፤1ዜና16፥20፤ኢሳ30፥28፤63፥17
20፥14 ቍ2፤ዘፍ12፥16
20፥15 ዘፍ13፥9፤45፥18
20፥17 ቍ7፤ኢዮ42፥9
20፥18 ዘፍ12፥17
21፥1 ዘፍ8፥1፤17፥6:21:18፥14፤1ሳሙ2፥21፤ገላ4፥23፤ዕብ11፥11
21፥2 ዘፍ17፥19፤30፥6፤18፥10፤ገላ4፥22፤ዕብ11፥11
21፥3 ዘፍ16፥11፤17፥19፤ኢሱ24፥3
21፥4 ዘፍ17፥10:12፤ሐሥ7፥8
21፥5 ዘፍ12፥4፤ዕብ6፥15
21፥6 ዘፍ17፥17፤ኢዮ8፥21፤መዝ126፥2፤ኢሳ12፥6፤35፥2፤44፥23፤52፥9፤54፥1
21፥7 ዘፍ17፥17
21፥8 1ሳሙ1፥23
21፥9 ዘፍ16፥15፤39፥14፤ገላ4፥29
21፥10 ዘፍ39፥17፤25፥6፤ገላ4፥30
21፥11 ዘፍ17፥18
21፥12 ማቴ1፥2፤ሮሜ9፥7፤ዕብ11፥18
21፥13 ዘፍ13፥16
21፥14 ቍ31:32፤ዘፍ16፥1፤22፥19፤26፥33፤28፥10፤46፥1:5፤ኢሱ15፥28፤19፥2፤መሳ20፥1፤1ሳሙ3፥20፤1ዜና4፥28፤ነህ11፥27
21፥16 ኤር6፥26፤አሞ8፥10፤ዘካ12፥10
21፥17 ዘፀ3፥7፤15፥1፤16፥7፤22፥11:15፤ዘኍ20፥16፤ዘዳ26፥7፤መዝ6፥8
21፥18 ዘፍ17፥20
21፥19 ዘፍ16፥7፤ዘኍ22፥31
21፥20 ዘፍ26፥3:24፤28፥15፤39፥2:21:23፤ሉቃ1፥66
21፥21 ዘፍ14፥6፤24፥4:38፤28፥2፤34፥4:8፤መሳ14፥2
21፥22 ቍ23:32፤ዘፍ20፥2፤26፥26:28፤28፥15፤31፥3:5:42፤39፥2:3፤1ሳሙ3፥19፤

አለው፤ “በምታደርገው ነገር ሁሉ እግዚአ
ብሔር (ኤሎሂም) ከአንተ ጋር ነው፡፡ [23]እንግዲ
ህ እኔንና ልጆቼን፣ ዘሬንም በመሸንገል
አን ዳች ክፉ ነገር እንዳታደርስብን በእግዚ
አብሔር (ኤሎሂም) ፊት ማልልኝ፡፡ እኔ ለአንተ
ቸርነት እንዳደረግሁ፣ አንተም ለእኔና
በእንግድነት ለተቀመጥህባት ለዚች ምድር
ቸርነት አድርግ፡፡”
[24]አብርሃምም፣ “እሺ፤ እምላለሁ” አለ፡፡
[25]ከዚያም አብርሃም፣ የአቢሜሌክ አገል
ጋዮቹ ነጥቀው ስለ ያዙበት የውሃ ጕድጓድ
መከፋቱን ለአቢሜሌክ ገለጠለት፡፡ [26]አቢሜ
ሌክም፣ “መቼም ይህን ድርጊት ማን እንደ
ፈጸመ በበኩሌ አላውቅም፤ አንተም አልነገ
ርኸኝም፤ ነገሩንም ገና አሁን መስማቴ ነው”
አለው፡፡
[27]ስለዚህ አብርሃም፣ በጎችና ከብቶች አም
ጥቶ ለአቢሜሌክ ሰጠው፤ ሁለቱም በመካ
ከላቸው የስምምነት ውል አደረጉ፡፡ [28]አብ
ርሃም ከመንጋው ሰባት እንስት በጎች ለየ፤
[29]አቢሜሌክም፣ “እነዚህን ሰባት እንስት
በጎች ለይተህ ለብቻ ያቆምሃቸው ለምንድ
ነው?” ሲል አብርሃምን ጠየቀው፡፡
[30]አብርሃምም፣ “ይህን የውሃ ጕድጓድ
የቈፈርሁ እኔ ለመሆኔ ምስክር እንዲሆን
እነዚህን ሰባት እንስት በጎች እንካ ተቀበ
ለኝ” አለው፡፡
[31]ስለዚህ ቦታው፣ ሁለቱ ተማምለው የተ
ስማሙበት ስፍራ በመሆኑ ቤርሳቤህ[ሠ] ተባለ፡፡
[32]በቤርሳቤህ የስምምነት ውል ካደረጉ
በኋላ፣ አቢሜሌክና የሰራዊቱ አለቃ ፊኮል
ወደ ፍልስጥኤማውያን ምድር ተመለሱ፡፡
[33]አብርሃምም በቤርሳቤህ የተምር ዛፍ ተከለ፤
በዚያም የዘላለም አምላክን (ኤል ኦላም) ስም
ጠራ፡፡ [34]አብርሃምም በፍልስጥኤማውያን
ምድር ለረጅም ጊዜ በእንግድነት ኖረ፡፡

## አብርሃም ተፈተነ

22 ከዚህ ሁሉ በኋላ እግዚአብሔር (ኤሎ
ሂም) አብርሃምን ፈተነው፤ “አብር
ሃም!” አለው፡፡ እርሱም “አቤቱ! አለሁ” አለ፡፡
[2]እግዚአብሔርም (ኤሎሂም)፣ “የምትወደውን አን
ዱን ልጅህን፣ ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያ ምድር
ሂድ፤ እኔ በማመለክትህ በአንዱ ተራራ
ላይ የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው”
አለው፡፡
[3]በማግስቱ ጠዋት አብርሃም ማልዶ ተነሣ፤
አህያውን ጭኖ፣ ሁለት አገልጋዮቹንና ልጁን
ይስሐቅን ይዞ፣ ለመሥዋዕት የሚበቃውን ዕን
ጨት ከቈረጠ በኋላ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ወዳ
መለከተው ቦታ ለመሄድ ጕዞውን ጀመረ፤
[4]በሦስተኛው ቀን አብርሃም ቀና ብሎ ቦታ
ውን ከሩቅ ተመለከተ፤ [5]አገልጋዮቹንም “እና
ንተ አህያውን ይዛችሁ እዚህ ቈዩን፤ እኔና
ልጄ ግን ወደዚያ ሄደን ለእግዚአብሔር
ሰግደን እንመለሳለን” አላቸው፡፡
[6]አብርሃም ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚ
ሆነውን ዕንጨት ወስዶ፣ ልጁን ይስሐቅን አሸ
ከመው፤ እሳቱንና ቢላዋውንም ራሱ ያዘ፡፡
ሁለቱም አብረው ሄዱ፡፡ [7]ይስሐቅም አባቱን
አብርሃምን፣ “አባቴ ሆይ” አለው፡፡
አብርሃምም፣ “እነሆኝ፤ አለሁ ልጄ” አለው፡፡
ይስሐቅም፣ “እሳቱና ዕንጨቱ ይኸው፤
ነገር ግን የሚቃጠለው መሥዋዕት የት አለ?”
ብሎ ጠየቀ፡፡
[8]አብርሃምም፣ “ልጄ ሆይ፤ ለሚቃጠለው
መሥዋዕት የሚሆነውን በግ እግዚአብሔር
(ኤልሮኢ)ራሱ ያዘጋጃል” አለው፡፡ ሁለቱም አብ
ረው ጕዞአቸውን ቀጠሉ፡፡
[9]እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ወዳመለከተው ቦታ
እንደ ደረሱ፣ አብርሃም መሠዊያ ሠራ፤ በላዩም
ላይ ዕን ጨት ረበረበ፤ ልጁን ይስሐቅንም
አስሮ በመ ሠዊያው ዕንጨት ላይ
አጋደመው፡፡ [10]ከዚያም ልጁን ለማረድ እ
ጁን ዘርግቶ ቢላዋ ውን አነሣ፡፡ [11]*የእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) መል አክ ግን ከሰማይ፣
“አብርሃም፤ አብርሃም፤” ብሎ ጠራው፤
አብርሃምም፣ “እነሆ፤ አለሁ” አለ፡፡
[12]እርሱም፣ “እጅህን በብላቴናው ላይ አታ
ሳርፍ፤ ምንም ጕዳት አታድርስበት፤ እነሆ፤
እግዚአብሔርን (ኤሎሂም) እንደምትፈራ
ተረድቻ ለሁ፤ ልጅህን፣ ያውም አንዱን
ልጅህን ለእኔ ለመስጠት አልሳሳህምና፡፡”
አለው፡፡
[13]አብርሃም ቀና ብሎ ሲመለከት በቍ
ጥቋጦ መካከል ቀንዶቹ የተጠላለፉ አንድ
አውራ በግ ከበስተ ኋላው አየ፤ ወደዚያው
ሄዶ በጉን አመጣና የሚቃጠል መሥዋዕት
አድርጎ ሠዋው፡፡ [14]ከዚህም የተነሣ፣ አብ
ርሃም የዚያን ስፍራ ስም፣ “*እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ያዘጋጃል” (ያህዌ ይርኤ) ብሎ ጠራው፡፡ እስከ
ዛሬም ድረስ፣ “*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ተራራ
ላይ ይሰጣል” ተብሎ ይነገራል፡፡
[15]*የእግዚአብሔርም* (ያህዌ) መልአክ አብር
ሃምን ከሰማይ ዳግመኛ ጠራው፤ [16]እንዲህም
አለው፤ “*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) በራሴ ማልሁ
አለ፤ አንዱን ልጅህን ለእኔ ለመስጠት አል
ሳሳህምና፣ [17]በእርግጥ እባርክሃለሁ፤ ዘርህን
እንደ ሰማይ ከዋክብት፣ እንደ ባሕር ዳር

16፥18፤2ዜና1፥1፤መዝ 46፥7፤ኢሳ7፥14፤8፥8፤10፤41፥10፤43፥5
**21፥23** ቍ22:31፤ ዘፍ25፥33፤26፥31፤ 31፥53፤1ሳሙ24፥21፤ኢሱ2፥12፤1ነገ 2፥8፤
**21፥25** ዘፍ26፥15፤18፤20-22
**21፥27** ቍ31፤32፤ ዘፍ26፥28፤31፤31፥44፤53
**21፥30** ቍ25፤ዘፍ 26፥25፤32፤31፥44፤47፤48፤50፤52፤ኢሱ22፥27፤24፥27፤28፥34፤ ኢሳ19፥20፤ሚል2፥14
**21፥31** ቍ14፤23፤27
**21፥32** ቍ14፥22፤27፤ዘፍ10፥14
**21፥33** ዘፍ4፥26፤ ዘፀ15፥18፤ዘዳ32፥40፤ 33፥27፤1ሳሙ22፥6፤ 31፥13፤ኢዮ36፥26፤ መዝ10፥16፤45፥6፤ 90፥2፤93፥2፤102፥24፤ 103፥19፤146፥10፤ ኢሳ40፥28፤ኤር10፥10፤ዕን1፥12፤ 3፥6፤ ዕብ13፥8
**21፥34** ዘፍ10፥14
**22፥1** ቍ11፤ዘፍ31፥11፤46፥2፤ዘፀ15፥25፤ 16፥4፤20፥20፤ዘዳ8፥2፤16፤13፥3፤መሳ2፥22፤3፥1፤1ሳሙ3፥4፤6፤8፤ 2ዜና32፥31፤መዝ66፥10፤ኢሳ6፥8፤ዕብ11፥17፤ያዕ1፥12-13
**22፥2** ቍ9:12፤16፤ ዘፍ8፥20፤2ዜና3፥1፤ ዮሐ3፥16፤ዕብ11፥17፤ 1ዮሐ4፥9
**22፥3** ኢሱ8፥10
**22፥5** ዘፀ24፥14
**22፥6** ቍ10፤መሳ 19፥29፤ዮሐ19፥17
**22፥7** ዘፀ29፥38-42 ፤ዘሌ1፥10፤ራእ13፥8
**22፥8** ቍ13፤14፤ ዮሐ1፥29
**22፥9** ቍ2፤ዘፍ4፥26፤8፥20፤ዘሌ1፥7፤ 1ነገ18፥33፤ዕብ11፥17-19፤ያዕ2፥21
**22፥10** ቍ3፤6፤ ዘፍ18፥9
**22፥11** ቍ1፤ዘፍ 16፥7፤21፥17፤46፥2
**22፥12** ቍ2፤ዘፍ 18፥19፤42፥18፤ዘፀ 18፥21፤1ሳሙ15፥22፤ ኢዮ1፥1፤37፥24፤ምሳ 8፥13፤ያዕ2፥21-22፤ ዮሐ3፥16፤1ዮሐ4፥9
**22፥13** ቍ8፤ዘፍ 8፥20፤ሮሜ8፥32
**22፥14** ቍ8፤ዘፀ 17፥15፤መሳ6፥24፤ ኢሳ30፥29
**22፥15** ዘፍ16፥7፤
21፥17 **22፥16** ቍ2፤ዘፀ13፥11፤32፥13፤33፥1፤ኢሳ45፥23፤62፥8፤ ኤር22፥3፤44፥26፤49፥13፤51፥14፤አሞ6፥8፤ሉቃ1፥73፤ዕብ6፥13
**22፥17** ዘፍ12፥2፤15፥5፤24፥60፤26፥24፤ዘፀ32፥13፤ዘዳ7፥7፤ 28፥62፤ኢሳ9፥2፤ሆሴ1፥10፤ሮሜ9፥27፤ዕብ 6፥14፤11፥12

[ሠ]31 *ቤርሳቤህ ማለት ሰባት የውሃ ጕድጓድ ወይም የመሐላ የውሃ ጕድጕድ ማለት ሊሆን ይችላል፡፡*

አሸዋም አበዛዋለሁ። ዘሮችህም የጠላቶቻቸ
ውን ደጆች ይወርሳሉ፤ 18ቃሌን ስለ ሰማህ
የምድር ሕዝቦች ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ።”
19ከዚያም አብርሃም ወደ አገልጋዮቹ ተመ
ለሰ፤ ተያይዘውም ወደ ቤርሳቤህ ሄዱ፤
አብርሃምም በቤርሳቤህ ኖረ።

## የናኮር ልጆች

20ከዚህ በኋላ እንዲህ ተብሎ
ለአብርሃም ተነገረው፤ “ሚልካም ደግሞ
የልጆች እናት ሆናለች፤ ለወንድምህም ለናኮር
ወንዶች ልጆ ችን ወልዳለች። 21እነርሱም
የበኵር ልጁ ዑፅና ወንድሙ ቡዝ፣ የአራም
አባት ቀሙኤል፣ 22ኮዛት፣ ሐዞ፣
ፊልዳሥ፣ የድላፍና ባቱ ኤል ናቸው።”
23ባቱኤልም ርብቃን ወለደ። ሚልካ
ለአብርሃም ወንድም ለናኮር የወለደ ችለት
እነዚህ ስምንት ወንዶች ልጆች ናቸው። 24ከእነዚ
ህም ሌላ የናኮር ቁባት ሬናሕ ደግሞ ጥባሕ
፣ ገአም፣ ተሐሽና ሞክሳ የተባሉ ወንዶች
ልጆች ወለደችለት።

## የሣራ ሞት

23 ሣራ አንድ መቶ ሃያ ሰባት ዓመት
ኖረች፤ 2በከነዓን ምድር፣ በቂርያት
አርባቅ ማለትም በኬብሮን ከተማ ሞተች፤
አብርሃምም ለሣራ ሊያለቅስና ሊያዝን መጣ።
3ከዚያም አብርሃም ከተቀመጠበት ከሚ
ስቱ ሬሳ አጠገብ ተነሣ፤ ኬጢያውያንንም[0]
እንዲህ አላቸው፤ 4“እኔ ለአገሩ እንግዳ፣
ለሰዉ ባዳ ሆኜ በመካከላችሁ የምኖር ነኝና
ለመቃብር የምትሆን ቦታ ሽጡልኝ፤ የሚ
ስቴንም ሬሳ ልቅበርበት።”
5ኬጢያውያንም ለአብርሃም እንዲህ ሲሉ
መለሱለት፤ 6“ስማን ጌታዬ፤ አንተ እኮ በእኛ
ዘንድ እንደ ኀያል መስፍን ነህ፤ ከመቃ
ብር ቦታችን በመረጥኸው ስፍራ ሬሳህን
መቅበር ትችላለህ፤ ማናችንም ብንሆን የሞ
ተብህን ሰው እንዳትቀብርበት የመቃብር
ቦታችንን አንከለክልህም።”
7ከዚያም አብርሃም ተነሥቶ የአገሬውን
ሕዝብ፣ ኬጢያውያንን እጅ ነሣ፤ 8እንዲ
ህም አላቸው፤ እንድቀብር ከፈቀዳችሁ
ልኝ፣ አንዴ ስሙኝና የሰዓርን ልጅ ኤፍሮ
ንን ስለ እኔ ሆናችሁ ለምኑልኝ። 9ይኸ
ውም በዕርሻው ድንበር ላይ ያለችውን መክ
ፈላ የተባለችውን ዋሻውን እንዲሸጥልኝ ነው፤
በመካ ከላችሁም የመቃብር ቦታ እንድ
ትሆነኝ በሙሉ ዋጋ እንዲሸጥልኝ ለምኑልኝ።
10ኬጢያዊው ኤፍሮንም እዚያው መካከ
ላቸው ተቀምጦ ስለ ነበር፣ ወደ ከተማው
በር መግቢያ መጥተው የተሰበሰቡት ኬጢ
ውያን በሙሉ እየሰሙ ለአብርሃም እንዲህ
ሲል መለሰለት፤ 11“እንዲህ አይደለም ጌታዬ፤
አድምጠኝ፤ ዕርሻውን በውስጡ ካለው ዋሻ
ጋር ውሰደው፤ እነሆ፤ በወገኖቼ ኬጢያው
ያን ፊት ሰጥቼሃለሁ፤[″] ሬሳህን ቅበርበት።”
12አብርሃም እንደ ገና የአገሬውን ሕ
ዝብ እጅ ነሣና 13ሁሉም እየሰሙት፣ የዕ
ርሻ ውን ቦታ ዋጋ ልክፈል፤ እባክህን
ተቀበለ ኝና ሬሳዬን ልቅበርበት” አለው።
14ኤፍሮንም ለአብርሃም እንዲህ ሲል መለሰ
ለት፤ 15“የመሬቱ ዋጋማ አራት መቶ ጥሬ
ብር[ቸ] ነው፤ ታዲያ ይህ በእኔና በአንተ
መካ ከል ምን ቁም ነገር አለው? ይልቅስ
ሬሳ ህን ቅበርበት” አለው።
16አብርሃምም፣ ኤፍሮን በኬጢያውያን ፊት
በተናገረው ዋጋ ተስማማ፤ በወቅቱም የን
ግድ መለኪያ መሠረት አራት መቶ ጥሬ
ብር መዘነለት።
17በዚህ ሁኔታ፣ በመምሬ አጠገብ በመ
ክፈላ ያለው የኤፍሮን ዕርሻ ቦታ ከነዋሻው
በክልሉ ካሉት ዛፎች ሁሉ ጭምር ለአብ
ርሃም በርስትነት ተላለፈ፤ 18ወደ ከተማው
በር በመጡት ኬጢያውያንም ሁሉ ፊት
የአብርሃም ንብረት መሆኑም ተረጋገጠለት።
19ከዚህም በኋላ አብርሃም በከነዓን ምድር፣
በመምሬ አጠገብ፣ መክፈላ በተባለች ዕርሻ ውስጥ
ባለችው ዋሻ የሚስቱን የሣራን ሬሳ ቀበረ፤
ይህችም ኬብሮን ናት። 20ስለዚህ ዕር ሻውና
ውስጡ የሚገኘው ዋሻ የመቃብር ቦታ እንዲ
ሆን፣ ከኬጢያውያን ለአብርሃም
በርስትነት ተላለፈለት።

## የይስሐቅና የርብቃ ጋብቻ

24 በዚህ ጊዜ አብርሃም ሸመገለ፤ ዕድሜ
ውም ገፋ፤ እግዚአብሔርም (ያህዌ)
አብርሃምን በሁሉ ነገር ባረከው። 2አብርሃም
የንብረቱ ሁሉ ኀላፊ፣ የቤቱ ሁሉ አዛዥ[የ]
የሆነውን አረጋዊ አገልጋዩን እንዲህ አለው፤
“እጅህን ከጭኔ በታች አድርግ፤ 3ልጄን፣
በመካከላቸው ከምኖር ከከነዓናውያን ሴቶች
ልጆች ጋር እንዳታጋባው በሰማይና በምድር
አምላክ በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ማልልኝ።
4ነገር ግን ወደ አገሬ፣ ወደ ገዛ ዘመዶቼ
ሄደህ ለልጄ ለይስሐቅ ሚስት ትፈልግለ
ታለህ።”
5አገልጋዩም፣ “ሴቲቱ ከእኔ ጋር ወደዚህ
ምድር ለመምጣት ፈቃደኛ ባትሆን ምን
አደርጋለሁ? ልጅህን አንተ ወደ መጣህ
በት አገር ልውሰደውን?” ሲል ጠየቀው።
6አብርሃምም እንዲህ አለው፤ “ምንም ቢሆን
ልጄን ወደዚያ እንዳትመልሰው ተጠንቀቅ፤

[0]3 ወይም *የኬጢ ልጆች*፤ ቍ5:7:10:16:18 እና 20 እንዲሁ
[″]11 ወይም *ሸጬልሃለሁ*
[ቸ]15 4.5 ኪ.ግ. ገደማ ይሆናል
[የ]2 ወይም *ታላቅ*

22፥18 ቍ10፤ዘፍ 12፥2፡3፤17፥2፡9፤መዝ 105፥9፤ሐሥ3፥25፤ ገላ3፥8
22፥19 ዘፍ21፥14፤ 26፥23፤28፥10
22፥20 ዘፍ11፥29
22፥21 ዘፍ10፥23፤ ኢዮ32፥2፤ኤር25፥23
22፥22 ዘፍ24፥15፡ 47፤25፥20
22፥23 ዘፍ11፥29፤ 24፥15
22፥24 ዘፍ25፥6፤ 35፥22፤36፥12፤መሳ 8፥31፤2ሳሙ3፥7፤1ነገ 2፥22፤11፥3፤1ዜና1፥3 2፤ማሕ6፥8
23፥2 ዘፍ13፥18፤ 24፥67፤ኢሱ14፥15፤1 5፥13፤20፥7፤21፥11
23፥3 ዘፍ10፥15
23፥4 ዘፍ17፥8፤19፥ 9፤49፥30፤ዘፀ ፥22፤ዘሌ25፥23፤መዝ3 9፥12፤ 105፥12፤119፥19፤ዕብ 11፥9፡13፤ሐሥ7፥16
23፥6 ዘፍ14፥14- 16፤24፥35
23፥8 ዘፍ25፥9
23፥9 ቍ17፡19፤ ዘፍ25፥9፤47፥30፤49፥3 0፤50፥13
23፥10 ቍ18፤ዘፍ 18፥1፤ዘዳ22፥15፤25፥7 ፤ኢሱ20፥4፤ሩት4፥ 11፤2ሳሙ15፥2፤2ነገ 15፥35፤መዝ127፥5፤ ምሳ31፥23፤ኤር26፥ 10፤36፥10
23፥11 2ሳሙ24፥23
23፥15 ሕዝ45፥12
23፥16 2ሳሙ14፥ 26፤24፥24፤ኤር32፥ 9፤ዘካ11፥12
23፥17 ቍ9፤ ዘፍ 13፥18
23፥18 ቍ10፤ዘፍ 12፥7፤18፥1
23፥19 ቍ9፤ ዘፍ 13፥18፤49፥31፤ኢሱ 14፥13፤1ዜና29፥27
23፥20 ዘፍ10፥15፤ 35፥29፤47፥30፤49፥ 30፤50፥5፡13፤ኤር 32፥10
24፥1 ቍ35፤ዘፍ 12፥2፤17፥17፤ኢሱ 23፥1፤ገላ3፥9
24፥2 ቍ9፤ዘፍ15፥ 3፤39፥4-6፤47፥29
24፥3 ቍ7፡37፤ዘፍ 10፥15-19፤14፥19፤ 47፥31፤50፥25፤ዘኍ 20፥14፤ዘዳ7፥3፤ 2ቆሮ 6፥14፡17
24፥4 ቍ29፤ዘፍ12፥ 1፤21፥2፤መሳ14፥3
24፥5 ቍ39፤ዕብ 11፥15
24፥6 ቍ8

7ከአባቴ ቤት፣ ከትውልድ አገሬ ያወጣኝና፣
‘ለዘርህ ይህችን ምድር እሰጣለሁ’ ብሎ
በመ
ሐላ ተስፋ የገባልኝ የሰማይ አምላክ *እግዚ
አብሔር* (ኤሎሂም ያህዌ) መልአኩን ከፊትህ ይል
ካል፤ ለልጄም ሚስት ከዚያ ታመጣለታለህ::
8ሴቲቱ አብራህ ወደዚህ ለመምጣት ፈቃ
ደኛ ካልሆነች ግን ካስማልሁህ መሐላ ነጻ
ትሆናለህ፤ ነገር ግን ወደዚያ አትውሰ
ደው” አለው:: 9ስለዚህም አገልጋዩ እጁን
ከጌታው ከአብርሃም ጭን በታች አድርጎ
ስለዚህ ጒዳይ ማለለት::
10አገልጋዩም ከጌታው ግመሎች መካ
ከል ዐሥሩን ወሰደ፤ ምርጥ ምርጡንም ዕቃ
ሁሉ ጭኖ፣ የናኮር ከተማ ወደምትገኝበት
ወደ ሰሜን ምዕራብ መስጴጦምያ ተጓዘ::
11እዚያም እንደ ደረሰ፣ ግመሎቹን ከከተ
ማው ውጭ የውሃ ጒድጓድ አጠገብ አን
በረከከ፤ ጊዜውም ጥላ የበረደበት፣ ሴቶች
ውሃ ለመቅዳት የሚወጡበት ነበር::
12ከዚያም እንዲህ ሲል ጸለየ፣ “የጌታዬ
የአብርሃም አምላክ *እግዚአብሔር* (ኤሎሂም
ያህዌ) ሆይ፤ በዛሬው ቀን ጒዳዬን አሳካልኝ፤
ለጌ ታዬ ለአብርሃም ቸርነትህን አሳየው፤
13እነሆ፤ እኔ በዚህ ምንጭ አጠገብ ቆሜ
አለሁ፤ የከ ተማዪቱ ሴቶች ልጆች ውሃ
ለመቅዳት ወደ ዚህ ይመጣሉ:: 14እንግዲህ፣
‘እንስራሽን አው ርጂና ውሃ አጠጪኝ’ ስላት፣
‘እንካ ጠጣ፤ ግመሎችህንም ላጠጣልህ’
የምትለኝ ቈንጆ እርሷ ለባሪያህ ለይስሐቅ
የመረጥካት ትሁን፤ በዚህም ለጌታዬ
ቸርነትህን እንዳሳየኸው ዐው ቃለሁ::”
15እርሱም ገና ጸሎቱን ሳይጨርስ፣ እነሆ፤
ርብቃ እንስራዋን በትከሻዋ ላይ አድርጋ
ብቅ አለች:: እርሷም ከአብርሃም ወንድም
ከናኮርና ከሚስቱ ከሚልካ የተወለደው የባቱ
ኤል ልጅ ነበረች:: 16ልጃገረዲቱ እጅግ
ውብና ወንድ ያልደረሰባት ድንግል ነበረች::
ወደ ምንጩም ወርዳ ውሃ በእንስራዋ ሞልታ
ተመለሰች::
17አገልጋዩም ወደ እርሷ ፈጥኖ ቀረበና፣
“እባክሽ ከእንስራሽ ጥቂት ውሃ አጠጪኝ”
አላት::
18እርሷም፣ “ጌታዬ፤ ጠጣ” አለችው፤ ፈጥ
ናም እንስራዋን ወደ እጇ አውርዳ አጠጣ
ችው::
19እርሱን ካጠጣችው በኋላ፣
“ግመሎችህም
ጠጥተው እስኪጠግቡ ድረስ ውሃ እቀዳላ
ቸዋለሁ” አለች:: 20ፈጥናም በእንስራው ውስጥ
የነበረውን ውሃ በገንዳ ውስጥ ገለበጠች፤
እየሮጠች ከጒድጓዱ ውሃ እያመላለሰች
ግመሎቹ እስኪበቃቸው ድረስ አጠጣቻቸው::

24፥7 ቍ3፤ዘፍ12፥1:7፤16፥7፤ሮሜ4፥13፤ገላ3፥16
24፥8 ቍ6:41፤ኢሱ2፥12:17:20፤9፥20
24፥9 ቍ2፤ዘፍ32፥4፤33፥8
24፥10 ቍ19:22:30:47:53፤ዘፍ11፥29፤43፥11፤45፥23፤ዘኁ23፥7፤ዘዳ23፥4፤መሳ3፥8፤1ነገ10፥2፤1ዜና12፥40፤ኢሳ30፥6
24፥11 ቍ13፤ዘፍ29፥2:9-10፤ዘፀ2፥15:16፤1ሳሙ9፥11፤ዮሐ4፥7
24፥12 ቍ21:27:40:42:48:51:56፤ዘፍ19፥19፤26፥24፤27፥20፤28፥13፤31:42:53፤32፥9፤43፥23፤46፥3፤ዘፀ3፥6:15:16፤4፥5፤ኢሱ2፥12፤ነህ1፥11፤1ነገ18፥36፤ኢዮ10፥12፤መዝ75፥9፤94፥7
24፥13 ቍ11:43፤ዘፍ29፥8
24፥14 ቍ18:19:44:46፤ኢሱ2፥12፤መሳ6፥17:37፤1ሳሙ14፥10፤1ነገ13፥3፤መዝ86፥17፤ኢሳ38፥7፤ኤር44፥29
24፥15 ቍ45፤ዘፍ11፥29፤22፥22:23
24፥16 ዘፍ12፥11፤ዘዳ22፥15-21
24፥17 ቍ45፤1ነገ17፥10፤ዮሐ4፥7
24፥18 ቍ14
24፥19 ቍ10:14
24፥20 ቍ46
24፥21 ቍ12
24፥22 ቍ10:47፤ዘፍ41፥42፤ኢሳ3፥21፤ሕዝ16፥11-12
24፥23 ቍ47፤መሳ19፥15፤20፥4
24፥24 ቍ29:47፤ዘፍ11፥29
24፥25 ቍ32፤መሳ19፥19
24፥26 ቍ48:52፤ዘፀ4፥31፤12፥27፤1ዜና29፥20፤2ዜና20፥18
24፥27 ቍ12:48:49፤ዘፍ12፥1፤14፥20፤32፥10፤47፥29፤ዘፀ18፥10፤ኢሱ2፥14፤ሩት4፥14፤1ሳሙ25፥32፤2ሳሙ18፥28፤1ነገ1፥48፤8፥56፤መዝ28፥6፤41፥13፤68፥19፤98፥3፤106፥48፤ሉቃ1፥68
24፥28 ዘፍ29፥12
24፥29 ቍ4፤ዘፍ25፥20፤27፥43፤28፥2:5፤29፥5:12:13
24፥30 ቍ10፤ሕዝ23፥42

21አገልጋዩም አንዲት ቃል ሳይናገራት፣ *እግ
ዚአብሔር* (ያህዌ) መንገዱን አሳክቶለት እንደ
ሆነ ወይም እንዳልሆነ ለማወቅ ልጂቱን
በአንክሮ ይከታተል ነበር::
22ግመሎቹ ጠጥተው ካበቁ በኋላ ሰውዬው
ስድስት ግራም የሚጠጋ የወርቅ አምባ
ሮች አውጥቶ፣ 23“ለመሆኑ አንቺ የማን
ልጅ ነሽ? በአባትሽ ቤት የምናድርበት ስፍራ
ይገኝ እንደ ሆነ፣ እባክሽ ንገሪኝ” ብሎ ጠየ
ቃት::
24እርሷም፣ “እኔ፣ ሚልካ ለናኮር የወለ
ደችለት፣ የባቱኤል ልጅ ነኝ” አለችው፤ 25ደግ
ሞም፣ “በቤታችን በቂ ገለባና ድርቆሽ እን
ዲሁም ለእናንተ የሚሆን ማደሪያ አለን”
አለችው::
26ሰውየውም ተደፍቶ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ሰገደ፤ 27እንዲህም አለ፤ “ቸርነቱንና ታማ
ኝነቱን ከጌታዬ ያላጓደለ፣ እኔንም ወደ
ጌታዬ ዘመዶች ቤት የመራኝ፣ የጌታዬ
የአብርሃም አምላክ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) የተ
መሰገነ ይሁን::”
28ልጂቷ ሮጣ ሄዳ፣ የሆነውን ሁሉ ለእ
ናቷ ቤተ ሰቦች ነገረች:: 29ርብቃም ላባ
የተባለ ወንድም ነበራት፤ እርሱም ሰው
የው ወዳለበት የውሃ ጒድጓድ ፈጥኖ ሄደ::
30እኅቱ ያደረገችውን የወርቅ ቀለበትና
አምባሮች እንዳየ፣ እንዲሁም ርብቃ ሰው
የው ያላትን ስትናገር እንደ ሰማ፣ ወዲያ
ውኑ ወደ ሰውየው ሄደ፤ በምንጩም ዳር
ከግመሎቹ አጠገብ ቆሞ አገኘው፤ 31እር
ሱንም “አንተ *የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ቡሩክ
ሆይ፤ ና፤ እዚህ ውጭ የቆምኸው ለምን
ድን ነው? እነሆ፤ ለአንተ ማረፊያ ለግመ
ሎችህም ማደሪያ አዘጋጅቻለሁ” አለው::
32ሰውየው ከላባ ጋር ወደ ቤት ሄደ፤ የግ
መሎቹ ጭነት ተራገፎ ገለባና ድርቆሽ
ተሰጣቸው፤ ለእርሱና አብረውት ለነበሩት
ሰዎች የእግር ውሃ ቀረበላቸው:: 33ለሰውየ
ውም ማዕድ ቀረበለት፤ እርሱ ግን፣ “የመ
ጣሁበትን ጒዳይ ሳልናገር እህል አልቀም
ስም” አለ::
ላባም፣ “እሺ፤ ተናገር” አለው::
34እርሱም እንዲህ አለ፤ “እኔ
የአብርሃም አገልጋይ ነኝ፤ 35*እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ጌታ ዬን እጅግ ባርኮታል፤ እርሱም
በልጽጓል፤ በጎችና ከብቶች፣ ብርና ወርቅ፣
ወንድና ሴት አገልጋዮች፣ ግመሎችና
አህዮች ሰጥ ቶታል:: 36የጌታዬ ሚስት ሣ
ራ በስተርጅ ናዋ[ደ] ወንድ ልጅ
ወልዳለታለች፤ ጌታዬም ያለውን ሀብት
ሁሉ ለልጁ ሰጥቶታል::

24፥31 ዘፍ26፥29፤መዝ115፥15 24፥32 ቍ25፤ዘፍ18፥4
24፥34 ዘፍ15፥3 24፥35 ቍ1፤ዘፍ12፥2:16፤23፥6 24፥36
ዘፍ17፥17፤25፥5፤26፥14

[ደ]36 *ወይም በስተርጅናው*

37ጌታዬ እንዲህ ሲል አማለኝ፤ ‘ከዚህ ከምኖርበት አገር፣ ከከነዓናውያን ሴቶች ልጆች ጋር ልጄን አታጋባው፤ 38ነገር ግን ወደ አባቴ ቤት፣ ወደ ዝዛ ወገኖቼ ሄደህ ለልጄ ሚስት አምጣለት’::

39“እኔም ጌታዬን፣ ‘ሴቲቱ ከእኔ ጋር ወደ ዚህ ለመምጣት ባትፈቅድስ?’ ብዬ ጠየቅሁት::

40“እርሱም እንዲህ አለኝ፤ ‘አካሄዴን በፊቱ ያደረግሁ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) መልአኩን ከአንተ ጋር ይልካል፤ ከገዛ ወገኖቼና ከአባቴ ቤት፣ ለልጄ ሚስት እንድታመጣለት መንገድህን ያቃናል:: 41ወደ ወገኖቼ ከሄድህ፣ ከመሐላው የተፈታህ ትሆናለህ፤ እነርሱ እንኳ ልጂቱን አንሰጥም ቢሉህ፣ ከመሐላው ንጹሕ ትሆናለህ’ አለኝ::

42“እኔም ዛሬ ወደ ውሃው ጕድጓድ ስደርስ እንዲህ ብዬ ጸለይሁ፤ ‘የጌታዬ የአብርሃም አምላክ *እግዚአብሔር* (ኤሎሂም ያህዌ) ሆይ፤ ፈቃድህ ቢሆን የመጣሁበትን ጒዳይ አቃናልኝ፤ 43እነሆ፤ በምንጩ አጠገብ ቆሜአለሁ፤ ውሃ ልትቀዳ የምትመጣውን ኮረዳ፣ “ከእንስራሽ ውሃ አጠጪኝ” ስላት፣ 44እሺ ጠጣ፤ ለግመሎችህም እቀዳላቸዋለሁ” የምትለኝ እርሷ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ለጌታዬ ልጅ የመረጣት ትሁን::’

45በልቤ የምጸልየውን ጸሎት ገና ሳልጨርስ፣ ርብቃ እንስራዋን በትከሻዋ ላይ አድርጋ ብቅ አለች፤ ወደ ምንጩም ወርዳ ውሃ ቀዳች:: እኔም፣ ‘እባክሽ፤ ውሃ አጠጪኝ’ አልኳት::

46“እርሷም ፈጥና እንስራዋን ከትከሸዋ አውርዳ፣ ‘ጠጣ፤ ግመሎችህንም አጠጣለሁ’ አለች:: እኔም ጠጣሁ፤ ግመሎቹንም አጠጣች::

47“‘ለመሆኑ የማን ልጅ ነሽ’ ብዬ ጠየቅኋት::

“እርሷም፣ ‘ሚልካ ለናኮር የወለደችለት፣ የባቱኤል ልጅ ነኝ’ አለችኝ::

“ከዚያም ቀለበቱን አደረግሁላት፤ አምባሩንም በእጇ አስገባሁላት:: 48ተደፍቼም *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) ሰገድሁ፤ ለጌታዬ ወንድም የልጅ ልጅ የሆነችውን ቈንጆ፣ ለጌታዬ ልጅ እንዳገኝለት በቀና መንገድ የመራኝ የጌታዬ የአብርሃምን አምላክ *እግዚአብሔርን* (ኤሎሂም ያህዌ) አመሰገንሁ:: 49እንግዲህ አሁን ለጌታዬ በጎነትና ታማኝነት የምታሳዩ ከሆነ ሐሳባችሁን አስታውቁኝ፤ ካልሆነ ግን ቍርጡን ንገሩኝና የምሄድበትን ልወስን::”

50ላባና ባቱኤል እንዲህ ሲሉ መለሱ፤ “ነገሩ *ከእግዚአብሔር* (ያህዌ) ስለሆነ በዚህም

24፥37 ቍ3፤ዘፍ 50፥5፡25
24፥38 ዘፍ21፥21
24፥39 ቍ5
24፥40 ቍ12፤ዘፍ 5፥22፤12፥1፤16፥7
24፥41 ቍ8
24፥42 ቍ12
24፥43 ቍ13:14፤ ምሳ30፥19፤ኢሳ 7፥14
24፥44 ቍ14
24፥45 ቍ15፡17፤ 1ሳሙ1፥13፤ዮሐ4፥7
24፥46 ቍ18-20
24፥47 ቍ10:22: 23፡24፤ዘፍ22፥22፤ ኢሳ3፥19፤ሕዝ16፥ 11-12
24፥48 ቍ12: 26፡27
24፥49 ቍ27
24፥50 ዘፍ22፥22፤ 31፥7፡24፡29፡42፤48፥ 16፤መዝ118፥23
24፥51 ቍ12
24፥52 ቍ26
24፥53 ቍ10፤ዘፍ 45፥22፤ዘፀ3፥22፤ 12፥35፤2ነገ5፥5
24፥54 ቍ56፡59፤ ዘፍ30፥25
24፥55 መሳ19፥4
24፥56 ቍ12፡54
24፥57 መሳ19፥3
24፥58 ሩት1፥16
24፥59 ቍ54፤ዘፍ 35፥8
24፥60 ዘፍ17፥16፤ 22፥17፤27፥4፡19፤28፥ 1፤31፥55፤48፥9፡15፡ 20፤ኢሱ22፥6፤መዝ 127፥5፤ምሳ27፥11
24፥61 ዘፍ16፥1፤ 30፥3፤46፥25
24፥62 ዘፍ12፥9፤ 16፥14
24፥63 ኢሱ1፥8፤ መዝ1፥2፤18፥2፤ 77፥12፤119፥15፡ 27፡48፡97፡148፤ 143፥5፤145፥5
24፥64 ዘፍ31፥17፡ 34፤1ሳሙ30፥17
24፥65 ዘፍ38፥14፤ ማሕ1፥7፤4፥1፡3፤ 6፥7፤ኢሳ47፥2
24፥67 ዘፍ18፥9፤ 23፥1-2፤31፥33፤25፥ 20፤29፥18፡20፤34፥3፤ 49፥31፤መሳ16፥4

ሆነ በዚያ ምንም ማለት አንችልም:: 51ርብቃ ይቻትልህ፤ ይዘሃት ሂድ፤ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) እንደተናገረው ለጌታህ ልጅ ሚስት ትሁነው::”

52የአብርሃም አገልጋይ ያሉትን በሰማ ጊዜ በምድር ላይ ተደፍቶ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) ሰገደ:: 53ከዚያም የወርቅና የብር ጌጣጌጥ፣ እንዲሁም ልብሶች አውጥቶ ለርብቃ ሰጣት፤ ደግሞም ለወንድሟና ለእናቷ ከፍ ያለ ዋጋ ያላቸው ስጦታዎች ሰጣቸው:: 54እርሱና አብረውት የነበሩ ሰዎችም በልተው፣ ጠጥተው እዚያው ዐደሩ፤

በማግስቱ ጠዋት ሲነሡ፣ የአብርሃም አገልጋይ፣ “እንግዲህ ወደ ጌታዬ እንድመለስ አሰናብቱኝ” አለ::

55ወንድሟና እናቷም፣ “ልጂቷ ከእኛ ጋር ቢያንስ ዐሥር ቀን ያህል ትቈይና ከዚያ በኋላ ልትሄድ[ጀ] ትችላለች::” ብለው መለሱ::

56እርሱ ግን፣ “*እግዚአብሔር* (ያህዌ) መንገዴን አቅንቶልኛልና አታዘግዩኝ፤ ወደ ጌታዬ እንድመለስ አሰናብቱኝ” አላቸው::

57እነርሱም፣ “ለማናቸውም ልጂቱን እንጥራትና ትጠየቅ” አሉ:: 58ስለዚህ ርብቃን ጠርተው፣ “ከዚህ ሰው ጋር መሄድ ትፈቅጃለሽ?” ሲሉ ጠየቋት::

እርሷም፣ “አዎን፤ እሄዳለሁ” አለች::

59ከዚያም እኅታቸውን ርብቃን ከሞግዚቷ ጋር፣ እንዲሁም የአብርሃምን አገልጋይና አብረውት የነበሩትን ሰዎች አሰናበቷቸው:: 60ርብቃንም እንዲህ ብለው መረቋት፤

“እኅታችን ሆይ፤ እልፍ አእላፋት ሁኚ፤
ዘርሽ የጠላቶቹን ደጆች ይውረስ”::

61ከዚያም ርብቃና አገልጋዮቿ ተዘጋጁ፤ ግመሎቻቸውም ላይ ወጥተው ሰውየውን ተከተሉት፤ በዚህ ሁኔታ አገልጋዩ ርብቃን ይዟት ሄደ::

62በዚህን ጊዜ፣ ይስሐቅ በኔጌብ ይኖር ስለ ነበር፣ ከብኤርላሃይሮኢ መጥቶ ነበር:: 63እርሱም አንድ ምሽት ላይ በጥሞና[ገ] ለመቈየት ወደ መስክ ወጣ አለ፤ ቀና ብሎ ሲመለከትም፣ ግመሎች ከሩቅ ሲመጡ አየ:: 64ርብቃም እንደዚሁ አሻግራ ስትመለከት፣ ይስሐቅን አየች፤ ከግመልም ወረደች፤ 65አገልጋዩንም፣ “ይህ ሊገናኘን በመስኩ ውስጥ ወደዚህ የሚመጣው ሰው ማን ነው?” ስትል ጠየቀችው::

አገልጋዩም፣ “ጌታዬ ነው” ብሎ መለሰላት፤ እርሷም መሸፈኛዋን ተከናነበች::

66አገልጋዩም ያደረገውን ሁሉ ለይስሐቅ ነገረው:: 67ይስሐቅም ርብቃን ወደ እናቱ

[ጀ]55 ወይም *ልትሄጂ*
[ገ]63 በዕብራይስጥ የዚህ ቃል ትርጒም አይታወቅም

ወደ ሣራ ድንኳን ይዟት ገባ፤ አገባትም፤
ሚስት ሆነችው፤ እርሱም ወደዳት። ይስሐ
ቅም ከእናቱ ሞት ተጽናና።

### የአብርሃም መሞት

25፥1-4 ተጓ ምብ - 1ዜና 1፥32-33

25 አብርሃም ኬጡራ የተባለች ሌላ
ሚስት አገባ።[ጠ] 2እርሷም፦ ዘምራ
ንን፣ ዮቅ ሳንን፣ ሜዳንን፣ ምድያምን፣
የስቦቅንና ስዌሕን ወለደችለት። 3ዮቅሳንም
ሳባንና ድዳንን ወለደ፤ የድዳንም ልጆች፦
አሦራውያን፣ ለጡ ሳውያንና ለኡማውያን
ናቸው። 4የምድያም ልጆች፦ጌፌር፣ ዔፌር፣
ሄኖኅ፣ አቢዳዕና ኤል ዳድ ናቸው። እነዚህ
ሁሉ የኬጡራ ልጆች ናቸው።
5አብርሃም ያለውን ሀብት ሁሉ ለይስሐቅ
አወረሰው፤ 6ለቁባቶቹ ልጆች ግን በሕይ
ወት እያለ ስጦታ አደረገላቸው፤ ከልጁ ከይ
ስሐቅም ርቀው እንዲኖሩ ወደ ምሥራቅ
ምድር ሰደዳቸው።
7አብርሃም በጠቅላላው መቶ ሰባ አምስት
ዓመት ኖረ። 8ከዚያም ዐረፈ፤ ዕድሜ ጠግቦ
በመልካም ሽምግልና ሞተ፤ ወደ ወገኖቹም
ተሰበሰበ። 9ልጆቹ ይስሐቅና እስማኤል በመ
ምሬ አጠገብ በምትገኝ በኬጢያዊው በሰዓር
ልጅ በኤፍሮን ዕርሻ በመክፈላ ዋሻ ቀበሩ
ት፤ 10ይህም የዕርሻ ቦታ አብርሃም ከኬጢ
ያው ያን[ጨ] የገዛው ነበር፤ ከሚስቱ ከሣራ
አጠገብ በዚያ ተቀበረ። 11አብርሃም
ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ይስሐቅን
ባረ ከው፤ በዚህ ጊዜ ይስሐቅ
በብኤርላሃይሮኢ አቅራቢያ ይኖር ነበር።

### የእስማኤል ልጆች

25፥12-16 ተጓ ምብ - 1ዜና 1፥29-31

12ግብፃዊቷ የሣራ አገልጋይ አጋር፣ ለአ
ብርሃም የወለደችለት የእስማኤል ትውልድ
ይህ ነው።
13የእስማኤል ልጆች ስም እንደ ዕድሜ
ያቸው ቅደም ተከተል እንዲህ ነው፦ የእስ
ማኤል የበኵር ልጅ ነብዳኤል፣ መብሳም፣
14ማስማዕ፣ ዱማ፣ ማሣ፣ ነባዮት፣ ቄዳር፣
15ኩዳን፣ ቴማን፣ ኢጡር፣ ናፌስና ቄድ
ማ። 16እነዚህ የእስማኤል ልጆች ነበሩ፤
እነርሱም በኖሩባቸውና በሰፈሩባቸው ቦታ
ዎች የዐሥራ ሁለት ነገድ አለቆች ስሞች
ናቸው። 17እስማኤል በጠቅላላው መቶ
ሠላሳ ሰባት ዓመት ኖረ፤ ከዚያም ሞተ፤
ወደ ወገኖቹም ተሰበሰበ። 18ዘሮቹም መኖ
ሪያቸውን ከግብፅ ድንበር አጠገብ፣ ወደ
አሦር በሚወስደው መንገድ፣ በኤውላጥና
በሱር መካከል አደረጉ፤ ከወንድሞቻቸ
ውም ሁሉ ጋር በጠላትነት ኖሩ።[ጸ]

25፥2 ዘፍ36፥35፤ 37፥28፡36፤ዘፀ2፥15፤ ዘኍ22፥4፤25፥6፡18፤ 31፥2፤ኢሱ13፥21፤ መሳ6፥1፡3፤7፥1፤8፥1፡ 22፡24፤9፥17፤1ነገ11፥ 18፤ኢዮ2፥11፤8፥1፤ መዝ83፥9፤ኢሳ9፥4፤ 10፥26፤60፥6፤ኤር 25፥25፤ዕን3፥7
25፥3 ዘፍ10፥7
25፥4 ኢሳ60፥6
25፥5 ዘፍ24፥36
25፥6 ዘፍ21፥10፤ 22፥24፤29፥1፤መሳ 6፥3፡33፤1ነገ4፥30፤ ኢዮ1፥3፤ሕዝ25፥4
25፥7 ቍ26፤ዘፍ 12፥4፤35፥28፤47፥9፡ 28፤50፥22፡26፤ኢዮ 42፥16
25፥8 ቍ17፤ዘፍ 15፥15፤35፥29፤49፥ 29፡33፤ዘኍ20፥24፤ 31፥2፤ዘዳ31፥14፤32፥5 0፤34፥5
25፥9 ዘፍ13፥18፤ 23፥8፡9፤35፥29፤47፥ 30፤49፥31፤50፥13
25፥10 ዘፍ10፥15
25፥11 ዘፍ12፥2፤ 16፥14
25፥12 ዘፍ2፥4፤16፥ 1፤17፥20፤21፥18፤
25፥13 ዘፍ28፥9፤ 36፥3፤መዝ120፥5፤ ማሕ1፥5፤ኢሳ21፥16፤ 42፥11፤60፥7፤ኤር 2፥10፤49፥28፤ሕዝ27፥21
25፥14 ኢሱ15፥52፤ ኢሳ21፥11፤አብ1፥1
25፥15 1ዜና5፥19፤ ኢዮ6፥19፤ኢሳ21፥14 ፤ኤር25፥23
25፥16 ዘፍ13፥16፤ 17፥20፤መዝ83፥6
25፥17 ቍ8
25፥18 ዘፍ17፥20፤ 21፥18፤16፥7፡12
25፥19 ዘፍ2፥4
25፥20 ቍ26፤ዘፍ 24፥29፡67፤26፥34፤28 ፥2፡5፡6፤30፥20፤31፥ 18፡20፡4፤35፥9፡26፡28 ፤46፥15፤48፥7፤ዘዳ 26፥5
25፥21 ዘፍ11፥30፤ 30፥17፡22፤1ሳሙ1፥ 17፡23፤1ዜና5፥20፤ 2ዜና33፥13፤ዕ8፥23፤ መዝ127፥3
25፥22 ዘፀ18፥15፤ 28፥30፤33፥7፤ዘሌ24፥ 12፤ዘኍ9፥6-8፤27፥5 ፡21፤ዘዳ17፥9፤መሳ 18፥5፤1ሳሙ9፥9፤10፥ 22፤14፥36፤22፥10፤ 1ነገ22፥8፤2ነገ3፥11፤ 22፥13፤ኢሳ30፥2፤ ኤር21፥2፤37፥7፡17፤ ሕዝ14፥7፤20፥1፡3
25፥23 ዘፍ9፥25፤

### ያዕቆብና ዔሳው

19የአብርሃም ልጅ የይስሐቅ ትውልድ ይህ
ነው፤
አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፤ 20ይስሐቅ ርብ
ቃን ሲያገባ ዕድሜው አርባ ዓመት ነበር፤
ርብቃ በሰሜን ምዕራብ መስጴጦምያ የሚ
ኖረው የሶርያዊው የባቱኤል ልጅ፣ የሶር
ያዊውም የላባ እኅት ነበረች።
21ይስሐቅ፣ ርብቃ መካን ስለ ነበረች
ስለ እርሷ ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ) ጸለየ፤
እግዚአብሔርም (ያህዌ) ጸሎቱን ሰማ፤ ርብ
ቃም ፀነሰች። 22ልጆቹም በማሕፀኗ ውስጥ
እርስ በርሳቸው ይጋፉ ጀመር፤ እርሷም
"ለምን እንዲህ ይሆንብኛል?" ብላ እግዚአብሐ
ሮን (ያህዌ) ለመጠየቅ ሄደች።
23እግዚአብሔርም (ያህዌ) እንዲህ አላት፤

"ወገኖች በማሕፀንሽ አሉ፤
ሁለትም ሕዝቦች ከውስጥሽ ተለያይተው
ይወጣሉ፤
አንደኛው ከሌላው ይበረታል፤
ታላቁም ለታናሹ አገልጋይ ይሆናል"
አላት።

24የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስም፣ እነሆ፤ በማሕ
ፀንዋ መንታ ወንዶች ልጆች ነበሩ። 25በመ
ጀመሪያ የተወለደው መልኩ ቀይ፣ ሰውነ
ቱም በሙሉ ጠጕር የለበሰ ነበር፤ ስለዚህ
ስሙ ዔሳው[ጸ] ተባለ። 26ከዚያም ወንድሙ
ተወለደ፤ በእጁም የዔሳውን ተረከዝ ይዞ
ወጣ፤ ከዚህም የተነሣ ስሙ ያዕቆብ[θ] ተባለ።
ርብቃ ልጆቿን ስትወልድ፣ ይስሐቅ የሥ
ልሳ ዓመት ሰው ነበር።
27ልጆቹም አደጉ፤ ዔሳው ጐበዝ ዐዳኝ፣
የበረሓም ሰው ሆነ፤ ያዕቆብ ግን ጭምት፣
ከድንኳኑ የማይወጣ ሰው ነበር። 28ይስሐቅ
ከዐደን የመጣ ሥጋ ደስ ይለው ስለ ነበር፣ ዔሳ
ውን ይወደው ነበር፤ ርብቃ ግን ያዕቆብን
ትወደው ነበር።
29አንድ ቀን ያዕቆብ ወጥ እየሠራ ሳለ ዔሳው
እጅግ ተርቦ ከዱር መጣ። 30ዔሳውም ያዕ
ቆብን፣ "ቶሎ በል፤ በጣም ርቦኛልና ከዚህ
ቀይ ወጥ አብላኝ" አለው። ስለዚህም ስሙ
ኤዶም ተባለ።

17፥4፤48፥14፡19፤ሮሜ9፥11-12 25፥24 ዘፍ38፥27፤ሉቃ1፥57፤ 2፥6 25፥25 ዘፍ27፥1፡ 11፡15፤1ሳሙ16፥12 25፥26 ቍ7፡20፤ ዘፍ27፥36፤32፥27፤38፥29፤ዘዳ23፥7፤ኢሱ24፥4፤ሆሴ12፥3፤አብ1፥ 10፡12 25፥27 ቍ29፤ዘፍ10፥9፤27፥3፡5 25፥28 ዘፍ27፥3፡4፡ 6፡9፡14፡19፤3፥73 25፥29 ቍ27፤2ነገ4፥38-40 25፥30 ቍ34፤ዘፍ 32፥3፤36፥1፡8-9፡19፤ዘኍ20፥14፤ዘዳ23፥7፤መዝ137፥7፤ኤር25፥ 21፤ 40፥11፤49፥7

[ጠ]1 ወይም *አግብቶ ነበር* [ጨ]10 ወይም *የኬጢ ልጆች*
[ጸ]18 ወይም *በስተ ምሥራቅ ኖሩ*
[ጸ]25 *ዔሳው* ማለት *ጠጕራማ* ማለት ነው፤ በተጨማሪ *ኤዶም* ተብሎ ተጠርቶአል፤ ትርጕሙም *ቀይ* ማለት ነው
[θ]26 *ያዕቆብ* ማለት *ተረከዝ ይይዛል* ማለት ነው፤ በምሳሌያዊ አገላለጽ *ያታልላል* ማለት ነው

31ያዕቆብም፣ “በመጀመሪያ ብኵርናህን ሸጥ
ልኝ” አለው።
32ዔሳውም፣ “እነሆ፣ ልሞት ደርሻለሁ፤
ታዲያ ብኵርናው ምን ያደርግልኛል!” አለ።
33ያዕቆብም ዔሳውን፣ “እንግዲያማ፣ አስ
ቀድመህ ማልልኝ” አለው፤ ስለዚህም ማለ
ለት፤ ብኵርናውንም ለያዕቆብ ሸጠለት።
34ያዕቆብም ለዔሳው እንጀራና የምስር ወጥ
ሰጠው፤ እርሱም ከበላና ከጠጣ በኋላ ተነ
ሥቶ ሄደ።
ዔሳው ብኵርናውን እንዲህ አድርጎ አቃ
ለላት።

## ይስሐቅና አቢሜሌክ

26፥1-11 *ማመ* - *ዘፍ* 12፥10-20፤ 20፥1-18

26 ቀድሞ በአብርሃም ዘመን ከደረ
ሰው ራብ ሌላ፣ በአገሩ ላይ ራብ
ሆነ። ይስሐቅም የፍልስጥኤም ንጉሥ አቢሜ
ሌክ ወደሚኖርበት ወደ ጌራራ ሄደ።
2በዚያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ለይስሐቅ
ተገልጦ እንዲህ አለው፤ “እኔ በምነግርህ
ምድር ተቀመጥ እንጂ፣ ወደ ግብፅ
አትውረድ፤ 3ለጥቂት ጊዜ እዚሁ አገር
ተቀመጥ፤ እኔም ካንተ ጋር እሆናለሁ፤
እባርክሃለሁም፤ ይህን ምድር በሙሉ
ለአንተና ለዘርህ በመስጠት ለአባትህ
ለአብርሃም በመሐላ የገባሁለትን ቃል አ
ጸናለሁ። 4ዘርህን እንደ ሰማይ ከዋክብት
አበዛለሁ፤ ይህን ምድር በሙሉ ለዘርህ
እሰጣለሁ፤ የምድር ሕዝቦ ችም ሁሉ
በዘርህ አማካይነት ይባረካሉ፤ 5ይኸውም
አብርሃም ቃሌን ሰምቶ፣ ድንጋ ጌዬን፣
ትእዛዜን፣ ሥርዐቴንና ሕጌን በመጠ በቁ
ነው።” 6ስለዚህ ይስሐቅ በጌራራ ተቀ
መጠ።
7የዚያም አገር ሰዎች ስለ ሚስቱ በጠየ
ቁት ጊዜ፣ “እኅቴ ናት” አለ፤ ምክንያቱም፣
“ሚስቴ ናት ብል ርብቃ ቈንጆ ስለ ሆነች፣
ያገሬው ሰዎች በእርሷ ምክንያት ይገድሉ
ኛል” በማለት ፈርቶ ነበር።
8ይስሐቅ ብዙ ጊዜ በዚያ ከኖረ በኋላ፣
የፍልስጥኤም ንጉሥ አቢሜሌክ አንድ ቀን
ወደ ውጭ ሲመለከት፣ ይስሐቅ ሚስቱን
ርብቃን ሲዳራት አየ። 9አቢሜሌክም ይስሐ
ቅን ጠርቶ፣ “እርሷ ሚስትህ ሆና ሳለች፣
እንዴት እኅቴ ናት ትላለህ?” አለው።
ይስሐቅም፣ “በእርሷ ሰበብ፣ ሕይወቴን
እንዳላጣ ብዬ ነው” አለው። 10አቢሜሌ
ክም መልሶ፣ “እንዲህ ያለ ነገር ያደረግህ
ብን ለምንድን ነው? ከሰዎቻችን አንዱ ሚስ
ትህን ቢደፍራት ኖሮ በእኛ ላይ በደል
አስከትለህብን ነበር እኮ!” አለው።
11አቢሜሌክም፣ “ይህን ሰው ወይም ሚስ
ቱን የነካ በሞት ይቀጣል” የሚል ትእዛዝ
ለሕዝቡ ሁሉ አወጣ።
12ይስሐቅም በዚያች ምድር ዘር ዘራ፣ *እግ
ዚአብሔርም* (ያህዌ) ባረከለትና በዚያኑ ዓመት
መቶ ዕጥፍ አመረተ። 13ሰውየውም እጅግ
ባለ ጠጋ እስኪሆን ድረስ ሀብት በሀብት
ላይ እየተጨመረለት ሄደ። 14ብዙ የበግና
የፍየል መንጋ፣ ብዙ ከብት፣ ብዙ አገልጋ
ዮችም ስለ ነበሩት፣ ፍልስጥኤማውያን ተመ
ቀኙት። 15ከዚህ የተነሣ ፍልስጥኤማው
ያን፣ አባቱ አብርሃም በሕይወት በነበረ
በት ጊዜ፣ የአብርሃም አገልጋዮች የቈፈሩአ
ቸውን የውሃ ጕድጓዶች በሙሉ ዐፈር
ሞልተው ደፈኑዋቸው።
16አቢሜሌክም ይስሐቅን፣ “ከእኛ ይልቅ
ኀያል ሆነሃልና አገራችንን ልቀቅልን” አለው።
17ይስሐቅም ያን ቦታ ትቶ ሄደ፤ በጌራራ
ሸለቆም ተቀመጠ። 18ይስሐቅም በአባቱ በአ
ብርሃም ጊዜ ተቈፍረው የነበሩትን፣ አባቱ
ከሞተ በኋላ ፍልስጥኤማውያን የደፈኑአቸ
ውን የውሃ ጕድጓዶች እንደ ገና እንዲከ
ፈቱ አደረገ፤ አባቱ ቀድሞ ባወጣላቸው
ስምም መልሶ ጠራቸው።
19የይስሐቅ አገልጋዮች በሸለቆው ውስጥ
ሲቈፍሩ፣ ከጕድጓዱ የሚፈልቅ ውሃ አገኙ።
20የጌራራ እረኞች ግን፣ “ውሃው የእኛ
ነው” በማለት ከይስሐቅ እረኞች ጋር ጠብ
አነሡ፤ ከዚህ የተነሣ ይስሐቅ ያን የውሃ ጕድ
ጓድ ኤሴቅ^ፊ ብሎ ጠራው፤ በጕድጓዱ ምክ
ንያት ተጣልተውታልና። 21አሁንም እንደ ገና
ሌላ የውሃ ጕድጓድ ቈፈሩ፤ አሁንም ሌላ
ግጭት ተፈጠረ፤ ስለዚህ የውሃ ጕድጓዱን
ስጥና^ፐ ብሎ ጠራው። 22ይስሐቅም ያን ቦታ
ትቶ ሌላ ስፍራ ላይ የውሃ ጕድጓድ አስ
ቈፈረ፤ በዚህ ጊዜ ግን አንድም ሰው ጠብ
አላነሣበትም፤ ስለዚህ ያን የውሃ ጕድ
ጓድ፣ “አሁን *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሰፊ ቦታ
ሰጥቶናል፤ እኛም በምድር ላይ እንበዛ
ለን” ሲል ርአቦት^ሀ ብሎ ጠራው።
23ከዚያም ይስሐቅ ወደ ቤርሳቤህ ወጣ።
24በዚያም ሌሊት *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ተገለጠለ
ትና፣ “እኔ የአባትህ የአብርሃም አምላክ (ኤሎ
ሂም) ነኝ፤ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፤ እባር
ክሃለሁ፤ ስለ አገልጋዬም ስለ አብርሃም
ስል ዘርህን አበዛለሁ” አለው።
25ይስሐቅም በዚያ ስፍራ መሠዊያ ሠርቶ፣
*የእግዚአብሔርን* (ያህዌ) ስም ጠራ፤ ድንኳ
ንም ተከለ፤ አገልጋዮቹም በዚያ የውሃ ጕድ
ጓድ ቈፈሩ።

ፊ20 *ኤሴቅ* ማለት *ክርክር* ማለት ነው
ፐ21 *ስጥና* ማለት *ተቃውሞ* ማለት ነው
ሀ22 *ርአቦት* ማለት *ክፍል (የቤት)* ማለት ነው

25፥31 ዘጸ21፥16-17፤1ዜና5፥1-2
25፥33 ዘፍ 21፥23፤27፥36፤47፥31፤ዕብ12፥16
25፥34 ቆኈ30
26፥1 ዘፍ10፥14፤12፥10፤20፥1፤ዘጻ32፥24፤መሳ10፥6
26፥2 ዘፍ12፥1፡7፤46፥3
26፥3 ቆኈ12፤ዘፍ 12፥2፡7፤17፥19፤20፥1፤21፥20፤27፥45፤31፥3፡5፤32፥9፤35፥3፤48፥21፤ዘፀ3፥12፤33፥14-16፤ዘኍ23፥21፤ዘዳ 31፥23፤ኢሱ1፥5፤ኢሳ 43፥2፤ኤር1፥8፡19፤ሐጌ1፥13፤ሐሥ7፥5
26፥4 ቆኈ24፤ዘፍ12፥2፡3፡7፤48፥4፤ዘኍ10፥36፤ሐሥ 3፥25፤ገላ3፥8
26፥5 ዘፍ18፥19፤ዘሌ18፥4፡5፡26፤19፥19፡37፤20፥8፡22፤25፥18፤26፥3፤ዘኍ15፥40፤ዘዳ4፥40፤6፥2፤11፥1፤1ነገ2፥3፤መዝ119፥80፡112፤ሕዝ18፥21
26፥6 ዘፍ20፥1
26፥7 ዘፍ12፥13
26፥8 ዘፍ10፥14
26፥9 ዘፍ12፥19
26፥10 ዘፍ12፥18
26፥11 ዘፍ20፥3፤1ሳሙ24፥6፤26፥9፤መዝ105፥15
26፥12 ቆኈ3፤ማቴ 13፥8
26፥13 ዘፍ13፥2፤ዘዳ8፥18
26፥14 ዘፍ12፥16፤24፥36፤32፥23፤37፥11
26፥15 ዘፍ21፥25፡30
26፥16 ቆኈ27፤ዘፀ 1፥9፤መሳ11፥7፤መዝ 105፥24-25
26፥17 ዘፍ20፥1
26፥18 ዘፍ21፥30
26፥20 ዘፍ13፥7፤21፥25
26፥21 ዘፍ13፥7
26፥22 ዘፍ17፥6፤36፥37፤መዝ18፥19፤ኢሳ33፥20፤54፥2፤አሞ9፥11
26፥23 ዘፍ22፥19
26፥24 ቆኈ4፤ዘፍ 15፥1፤17፥7፤21፥20፤22፥17፤24፥12፤28፥14፤30፥27፤39፥5፤ዘጸ13፥17፤ኢሱ8፥1
26፥25 ዘፍ4፥26፤8፥20፤21፥30፤ሐሥ 2፥21

[26]አቢሜሌክም ከአማካሪው ከአዘኮትና ከሰ
ራዊቱ አዛዥ ከፊኮል ጋር ከጌራራ ተነ
ሥቶ ይስሐቅ ወዳለበት ስፍራ መጣ። [27]ይስሐ
ቅም፣ “ጠልታችሁኝ ካባረራችሁኝ በኋላ፣
አሁን ደግሞ ለምን መጣችሁ?” ብሎ ጠየቃ
ቸው።

[28]እነርሱም እንዲህ አሉ፤ “እግዚአብሐ
ር (ያህዌ) ከአንተ ጋር መሆኑን በግል
ጽ ተረድ ተናል፤ ስለዚህም፣ ‘በመሐላ የጸና
ውል በመ ካከላችን መኖር አለበት’ አልን፤
ይህም በእ ኛና በአንተ መካካል የሚጸና
ውል ነው፤ አሁንም ከአንተ ጋር
ስምምነት እናድርግ፤ [29]አንተን እንዳልጠ
ጐዳንህ፣ ነገር ግን በጎነ ትን እንዳሳየንህና
በሰላም እንደ ሸኘንህ ሁሉ፣ አንተም ክፉ
እንዳታደርግብን በመ ካከላችን ውል
ይደረግ፤ አንተን እንደሆን መቼም እግዚ
አብሔር (ያህዌ) ባርኮሃል።”

[30]ይስሐቅም ድግስ ደግሶ፣ አበላቸው፤
አጠጣቸው። [31]በማግስቱም በማለዳ ተነ
ሥተው፣ በመካከላቸው መሐላ ፈጸሙ። ይስሐ
ቅም አሰናበታቸው፤ እነርሱም በሰላም ሄዱ።

[32]በዚያኑ ዕለት፣ የይስሐቅ አገልጋዮች
መጥተው ስለ ቈፈሩት የውሃ ጕድጓድ ነገሩት፤
“ውሃ እኮ አገኘን!” አሉት። [33]እርሱም የው
ሃውን ጕድጓድ ሳቤህ^ አለው፤ ከዚያም የተ
ነሣ የከተማዪቱ ስም እስከ ዛሬ ድረስ
ቤርሳቤህ ተብሎ ይጠራል።

[34]ዔሳው አርባ ዓመት በሆነው ጊዜ፣
የኬ
ጢያዊውን የብኤሪን ልጅ ዮዲትን እንዲ
ሁም የኬጢያዊውን የኤሎንን ልጅ ቤሴ
ሞትን አገባ፤ [35]በእነዚህም ሴቶች ምክን
ያት የይስሐቅና የርብቃ ልብ ያዝን ነበር።

## ይስሐቅ ያዕቆብን ባረከው

[27] ይስሐቅ አርጅቶ፣ ዐይኖቹ ደክመው
ማየት በተሳናቸው ጊዜ፣ ታላቁን
ልጁን ዔሳውን ጠርቶ፣ “ልጄ ሆይ” አለው።

እርሱም፣ “እነሆ፤ አለሁ” አለ።

[2]ይስሐቅም እንዲህ አለ፤ “ይኸው እኔ አር
ጅቻለሁ፤ የምሞትበትንም ቀን ዐላውቅም
[3]ስለዚህ የአደን መሣሪያህን:- የፍላጻ ኰሮ
ጆህንና ቀስትህን ይዘህ ወደ ዱር ሂድ፤
አድነህም አምጣልኝ። [4]ከመሞቴ በፊት
እንድመርቅህ የምወደውን ዐይነት ጣዕም
ያለው ምግብ አዘጋጅተህ አብላኝ።”

[5]ይስሐቅ ለልጁ የተናገረውን ርብቃ ትሰማ
ስለ ነበር፣ ዔሳው የታዘዘውን ለማምጣት
ለዐደን እንደ ወጣ፣ [6]ርብቃ ለልጇ ለያዕ
ቆብ እንዲህ አለችው፤ “አባትህ ዔሳውን፣
[7]‘ከመሞቴ በፊት በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት
እንድመርቅህ፣ ጥሩ ጣዕም ያለው ምግብ
እንድበላ አዘጋጅልኝ።’ ሲለው ሰምቻለሁ፤ [8]ልጄ
ሆይ፤ እንግዲህ የምነግርህን በጥሞና ስማኝ፤
የምልህንም አድርግ። [9]ተነሣና ወደ መንጋው
ሂደህ ሁለት ፍርጥም ያሉ የፍየል ጠቦ
ቶች አምጣልኝ፤ እኔም አባትህ፣ የሚወደ
ውን ዐይነት ምግብ አዘጋጅለታለሁ፤ [10]እር
ሱም ከመሞቱ በፊት እንዲመርቅህ፣ ይዘህ
ለት ግባና ይብላ።”

[11]ያዕቆብም እናቱን ርብቃን እንዲህ አላት፤
“ወንድሜ ዔሳው ሰውነቱ ጠጕራም ነው፤
የእኔ ገላ ግን ለስላሳ ነው። [12]ታዲያ፣ አባቴ
ቢዳስሰኝ እንዳታለልሁት ያውቃል፤ ይህ ከሆነ
ደግሞ፣ በምርቃት ፈንታ ርግማን አተር
ፋለሁ ማለት ነው።”

[13]እናቱም፣ “ልጄ ሆይ፤ የአንተ ርግማን
በእኔ ላይ ይድረስ፤ ግድ የለህም፤ እንደ
ነገርሁህ ሄደህ ጠቦቶቹን አምጣልኝ” አለ
ችው።

[14]እርሱም ሄዶ ጠቦቶቹን ለእናቱ አመ
ጣላት፤ እርሷም ልክ አባቱ እንደሚወደው ዐይ
ነት አጣፍጣ ጥሩ ምግብ አዘጋጀችለት።
[15]ከዚያም ርብቃ በቤት ያስቀመጠችውን የታ
ላቁን ልጇን የዔሳውን ምርጥ ልብስ አን
ሥታ ለታናሹ ልጇ ለያዕቆብ አለበሰችው።
[16]እንዲሁም የዐንገቱን ለስላሳ ክፍል የጠቦ
ቶቹን ቈዳ አለበሰችው። [17]ከዚያም ያሰናዳ
ችውን ጣፋጭ መብልና እንጀራ ለያዕቆብ
ሰጠችው።

[18]ያዕቆብም ወደ አባቱ ሄዶ፣ “አባቴ ሆይ፤
አለ፤ ይስሐቅም፣ “እነሆ፤ አለሁ ልጄ፤ ለመ
ሆኑ አንተ ማን ነህ?” አለው።

[19]ያዕቆብም አባቱን፣ “እኔ የበኵር ልጅህ
ዔሳው ነኝ፤ ያዘዝኸኝን አድርጌአለሁ፤ እስቲ
ቀና በልና እንድትመርቀኝ አድኜ ካመጣ
ሁት ብላ” አለ።

[20]ይስሐቅ ልጁን፣ “ልጄ ሆይ፤ ከመቼው
ቀናህና መጣህ?” ሲል ጠየቀው። ያዕቆብም፣
“እግዚአብሔር አምላክህ (ያህዌ ኤሎሂም) አሳካልኝ”
ብሎ መለሰለት።

[21]ይስሐቅም ያዕቆብን፣ “ልጄ ሆይ፤ አንተ
በእርግጥ ልጄ ዔሳው መሆንህን እንዳውቅ፣
እስቲ ቀረብ በልና ልዳብስህ” አለው።

[22]ያዕቆብም ወደ አባቱ ወደ ይስሐቅ
ተጠጋ፤ አባቱም በእጁ እየዳሰሰው፣ “ይህ
ድምፅ የያዕቆብ ድምፅ ነው፤ እጆቹ ግን
የዔሳው እጆች ናቸው” አለ። [23]እጆቹ እንደ
ወንድሙ እንደ ዔሳው እጆች ጠጕራም ስለ
ሆኑ፣ ይስሐቅ ያዕቆብን ለይቶ ማወቅ አል
ቻለም፤ ስለዚህ ባረከው። [24]ይስሐቅም፣ “በእ
ርግጥ አንተ ልጄ ዔሳው ነህ?” ሲል ጠየቀው።

ያዕቆብም፣ “አዎን፤ ነኝ” ብሎ መለሰ።

^33 ሳቤህ ማለት መሐላ ወይም ሰባት ማለት ሊሆን ይችላል

26፥26 ዘፍ21፥22
26፥27 ቍ16
26፥28 ዘፍ21፥22፡27፤ኢሱ9፥6
26፥29 ዘፍ24፥31፤31፥29፡52
26፥30 ዘፍ31፥54፤ዘፀ18፥12፤24፥11፤1ሳሙ20፥27
26፥31 ዘፍ21፥23፡27
26፥32 ዘፍ21፥30
26፥33 ዘፍ21፥14
26፥34 ዘፍ10፥15፤25፥20፤28፥9፤36፥2፤ኢሱ3፥10፤1ሳሙ26፥6፤1ነገ10፥20
26፥35 ዘፍ27፥46፤28፥8፤ኢዮ7፥16
27፥1 ዘፍ25፥25፤48፥10፤ዘዳ34፥7፤1ሳሙ3፥2
27፥2 ዘፍ47፥29፤1ነገ2፥1
27፥3 ዘፍ25፥27
27፥4 ቍ7፡10፡25፡31፤ዘፍ24፥60፤25፥28፤49፥28፤ዘዳ33፥1፤ዕብ11፥20
27፥5 ዘፍ25፥27
27፥6 ዘፍ25፥28
27፥7 ቍ4
27፥8 ቍ13፡43
27፥9 ዘፍ25፥28፤1ሳሙ16፥20
27፥10 ቍ4
27፥11 ዘፍ25፥25
27፥12 ቍ22፤ዘፍ9፥25
27፥13 ቍ8፤ማቴ27፥25
27፥14 ዘፍ25፥28
27፥15 ቍ27፤ዘፍ25፥25፤ማሕ4፥11
27፥16 ቍ22-23
27፥18 ቍ32
27፥19 ቍ4:32፤ዘፍ25፥28
27፥20 ዘፍ24፥12
27፥21 ቍ12
27፥22 ቍ12፤ዘፍ45፥4
27፥23 ቍ16

25ከዚያም፣ “በል እንግዲህ ልጄ፤ እንድ
መርቅህ፣ አድነህ ካመጣኸው አቅርብልኝና
ልብላ” አለው፡፡
ያዕቆብም ምግቡን ለአባቱ አቀረበለት፤
የወይን ጠጅም አመጣለት፤ እርሱም በላ፤ ጠጣም፡፡
26ከዚያም አባቱ ይስሐቅ፣ ያዕቆብን፣ “ልጄ
ሆይ፤ እስቲ ቀረብ በልና ሳመኝ” አለው፡፡
27ያዕቆብም ቀርቦ ሳመው፤ ይስሐቅ የያዕ
ቆብን ልብስ ካሸተተ በኋላ እንዲህ ብሎ
መረቀው፤

“እነሆ፤ የልጄ ጠረን፣
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) እንደ ባረከው፣
እንደ መስክ መዐዛ ነው፡፡

28እግዚአብሔር (ኤሎሂም) የሰማይን ጠል፣
የምድርንም በረከት፣
የተትረፈረፈ እህልና የወይን ጠጅ
ይስጥህ፡፡

29መንግሥታት ይገዙልህ፤
ሕዝቦችም ተደፍተው እጅ ይንሡህ፤
የወንድሞችህ ጌታ ሁን፤
የእናትህም ልጆች ተደፍተው እጅ
ይንሡህ፤
የሚረግሙህ የተረገሙ ይሁኑ፤
የሚባርኩህ የተባረኩ ይሁኑ፡፡”

30ይስሐቅ ያዕቆብን መርቆ እንዳበቃ፣
ያዕቆብ ገና ከአባቱ ዘንድ ሳይወጣ ወዲያ
ውኑ፣ ወንድሙ ዔሳው ከዐደን ተመለሰ፡፡
31እርሱም ደግሞ ጣፋጭ ምግብ በማዘጋጀት
ለአባቱ አቅርቦ፣ “አባቴ ሆይ፤ እንድትመ
ርቀኝ፣ እስቲ ቀና በልና ካደንሁት ብላ”
አለው፡፡
32አባቱ ይስሐቅም፣ “አንተ ደግሞ ማን
ነህ?” ሲል ጠየቀው፡፡ እርሱም፣ “እኔማ የበ
ኵር ልጅህ ዔሳው ነኝ” አለው፡፡
33በዚህ ጊዜ ይስሐቅ ክፉኛ እየተንቀጠ
ቀጠ፣ “ታዲያ ቀደም ሲል አድኖ ያመጣ
ልኝ ማን ነበር? አንተ ከመምጣትህ በፊት
በልቼ መረቅሁት፤ እርሱም በእርግጥ
የተባ ረከ ይሆናል” አለው፡፡
34ዔሳው የአባቱን ቃል ሲሰማ፣ ድምፁን
ከፍ በማድረግ ምርር ብሎ አለቀሰ፤ አባቱ
ንም፣ “አባቴ ሆይ፤ እኔንም ደግሞ እባክህ
መርቀኝ” አለው፡፡
35ይስሐቅም፣ “ወንድምህ መጥቶ አታሎኝ
ምርቃትህን ወስዶብሃል” አለው፡፡
36ዔሳውም፣ “ይህ ሰው ያዕቆብ መባሉ
ትክክል አይደለምን? እኔን ሲያታልለኝ ይህ
ሁለተኛ ጊዜው ነው፤ መጀመሪያ ብኵርና
ዬን ወሰደብኝ፤ አሁን ደግሞ ምርቃቴን
ቀማኝ” አለ፡፡ ቀጥሎም፣ “ታዲያ ለእኔ ያስ

27፥25 ቍ4
27፥27 ቍ15፤ዘፍ 31፥28፡55፤33፥4፤ 48፥10፤ዘፀ4፥27፤ 18፥7፤ሩት1፥9፤ 1ሳሙ20፥41፤2ሳሙ 14፥33፤19፥39፤መዝ 65፥9-13፤ዕብ11፥20
27፥28 ቍ37፡39፤ ዘፍ49፥25፤ዘሌ26፥20 ፤ዘኍ18፥12፤ዘዳ7፥ 13፤33፥13፡28፤2ሳሙ 1፥21፤2ነገ18፥32፤ ኢዮ18፥16፤29፥19፤ መዝ4፥7፤65፥9፤72፥ 16፤ምሳ3፥20፤ኢሳ 26፥19፤36፥17፤ኤር 31፥12፤40፥10፤ሆሴ 14፥5፤ሐጌ1፥10፤ ዘካ8፥12፤
27፥29 ቍ33፤ዘፍ 9፥25፤12፥3፤25፥23፤ 37፥7፤2ሳሙ8፥14፤ መዝ68፥31፤72፥11፤ ኢሳ19፥21፡23፤27፥ 13፤45፥14፡23፤49፥7 ፡23፤60፥12፡14፤66፥ 23፤ኤር12፥17፤ዳን 2፥44፤ዘካ14፥17-18
27፥31 ቍ4
27፥32 ቍ18፡19
27፥33 ቍ29፡35
27፥34 ዘፀ12፥32 ፤ዕ ብ12፥17
27፥35 ቍ19፡45፤ ኤር9፥4፤12፥6
27፥36 ዘፍ25፥26፡ 33፤29፥25፤31፥20፡ 26፤34፥13፤1ሳሙ 28፥12፤ዕብ12፥16-17
27፥37 ቍ28፤ዘዳ 16፥13፤ዕዝ6፥9፤ኢሳ 16፥10፤ኤር40፥12
27፥38 ዘፍ29፥11፤ ዘኍ14፥1፤መሳ2፥4፤21፥ 2፤ሩት1፥9፤1ሳሙ11፥ 4፤30፥4፤ዕብ12፥17
27፥39 ቍ28፤ዘፍ 36፥6፤ዕብ11፥20
27፥40 ዘፍ9፥25፤ 2ሳሙ8፥14፤2ነገ 8፥20-22
27፥41 ቍ42፤ዘፍ 31፥17፤32፥11፤37፥ 4፤49፥23፤50፥4፡10፡ 15፤ዘኍ20፥29፤ 1ሳሙ17፥28፤ሆሴ 10፥14፤አብ1፥10
27፥42 ቍ41፤ዘፍ 32፥3፡11፤33፥4
27፥43 ቍ8፤ዘፍ 11፥31፤24፥29
27፥44 ዘፍ31፥38፡41
27፥45 ቍ35፤ዘፍ 26፥3
27፥46 ዘፍ10፥15- 19፤26፥35፤ኢዮ7፥7
28፥1 ዘፍ24፥3፡60
28፥2 ዘፍ25፥20፤ 21፥21፤24፥29
28፥3 ዘፍ12፥2፤ 17፥1፡6፤48፥16፤ዘኍ

ቀረኸው ምንም ምርቃት የለም?” ብሎ ጠየቀ፡፡
37ይስሐቅም ለዔሳው፣ “በአንተ ላይ የበ
ላይነት እንዲኖረው፣ ወንድሞቹ ሁሉ አገ
ልጋዮቹ እንዲሆኑ፣ እህሉ፣ የወይን ጠጁም
የተትረፈረፈ እንዲሆንለት መርቄዋለሁ፡፡
ታዲያ ልጄ፣ ለአንተ ምን ሳደርግልህ እች
ላለሁ?” ሲል መለሰለት፡፡
38ዔሳውም አባቱን፣ “አባቴ ሆይ፤ ምር
ቃትህ ይህችው ብቻ ናትን? እባክህ አባቴ፣
እኔንም መርቀኝ” አለው፤ ድምፁንም ከፍ
አድርጎ አለቀሰ፡፡
39አባቱ ይስሐቅም እንዲህ ሲል መለሰለት፤

“መኖሪያህ ከምድር በረከት፣
ከላይም ከሰማይ ጠል የራቀ ይሆናል፤
40በሰይፍ ትኖራለህ፤
የወንድምህም አገልጋይ ትሆናለህ፡፡
አምርረህ በተነሣህ ጊዜ ግን፣
ቀንበሩን ከጫንቃህ ላይ፣
ወዲያ ትጥላለህ፡፡”

## ያዕቆብ ወደ ላባ ሸሸ

41አባቱ ያቆብን ስለ መረቀው፣ ዔሳው
በያዕቆብ ላይ ቂም ያዘ፤ በልቡም፣ “ግድ
የለም፤ የአባቴ መሞቻው ተቃርቦአል፤ ከል
ቅሶው በኋላ ወንድሜን ያዕቆብን እገድላለሁ”
ብሎ አሰበ፡፡
42ርብቃ፣ ታላቁ ልጇ ዔሳው ያሰበው በተ
ነገራት ጊዜ ታናሹን ልጇን ያዕቆብን አስጠ
ርታ እንዲህ አለችው፤ “ወንድምህ ዔሳው
ሊገድልህ ጊዜ እየጠበቀ ነው፤ 43አሁንም፣
ልጄ ሆይ፤ እኔ የምልህን አድርግ፤ በካራን
ምድር ወደሚኖረው ወደ ላባ ቶሎ ሽሽ፡፡
44የወንድምህ ቍጣ እስከሚበርድ እዚያው
ቈይ፤ 45ነገር ግን ቍጣው በርዶለት ያደረ
ግህበትን ከረሳ በኋላ፣ እንድትመለስ እል
ክብህና ትመጣለህ፡፡ ሁለታችሁንም በአንድ
ቀን ለምን ልጣ?”
46ከዚያም ርብቃ ይስሐቅን፣ “ዔሳው ባገባ
ቸው በኬጢያውያን ሴቶች ምክንያት መኖር
አስጠልቶኛል፤ ያዕቆብም ከዚሁ አገር ከኬጢ
ያውያን ሴቶች ሚስት የሚያገባ ከሆነ፣
ሞቴን እመርጣለሁ” አለችው፡፡

28 ይስሐቅ ያዕቆብን አስጠርቶ ከመረ
ቀው[ሐ] በኋላ፣ እንዲህ ሲል አዘዘው፤
“ምንም ቢሆን ከነዓናዊት ሴት አታግባ፡፡
2አሁኑኑ ተነሥተህ በሰሜን ምዕራብ መስ
ጴጦምያ ወደሚኖረው፣ ወደ እናትህ አባት
ወደ ባቱኤል ቤት ሂድ፤ እዚያም ከአጎ
ትህ ከላባ ሴቶች ልጆች መካከል አንዷ
ቷን አግባ፡፡ 3ሁሉን ማድረግ
የሚችል

[ሐ]1 ወይም *ሰላምታ ከሰጠው*

አምላክ[መ] ይባርክህ፤ ብዙ ሕዝብ እስክት
ሆን ድረስ ልጆች አፍራ፤ ዘርህን ያብዛው።
4እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ለአብርሃም ሰጥቶ የነበ
ረውን አንተም በስደት የምትኖርበትን ይህ
ችን ምድር ርስት አድርጎ ያወርስህ ዘንድ፣
ለአብርሃም የሰጠውን በረከት ለአንተና ለዘርህ
ይስጥ። 5ይስሐቅም ያዕቆብን በሰሜን ምዕራብ
መስጴጦምያ ወደሚኖረው፣ የያዕቆብና የዔ
ሳው እናት የርብቃ ወንድም ወደ ሆነው ወደ
ሶርያዊው የባቱኤል ልጅ ወደ ላባ ላከው።
6ዔሳው፣ ይስሐቅ ያዕቆብን መርቆ ሚስት
እንዲያገባ ወደ ሰሜን ምዕራብ መስጴጦ
ምያ እንደ ላከውና በባረከውም ጊዜ ከነዓ
ናዊት ሴት እንዳያገባ ትእዛዝ እንደ ሰጠው
ሰማ። ያዕቆብ የአባት የእናቱን ፈቃድ
ለመፈጸም፣ ወደ መስጴጦምያ መሄዱንም
ተረዳ። 8በዚህም የከነዓናውያን ሴቶች በአ
ባቱ በይስሐቅ ዘንድ የቱን ያህል የተጠሉ
መሆናቸውን ተገነዘበ፤ 9ስለዚህም ወደ እስ
ማኤል ሄደ፣ የአብርሃም ልጅ እስማኤል
የወለዳትን፣ የነባዮትን እኅት ማዕሌትን
በሚስቶቹ ላይ ተጨማሪ አድርጎ አገባ።

## ያዕቆብ በቤቴል ያየው ሕልም

10ያዕቆብ ከቤርሳቤህ ተነሥቶ ወደ ካራን
ሄደ። 11ወደ አንድ ስፍራ እንደ ደረሰም
ፀሓይዋ ጠልቃ ስለ ነበር፣ ዐዳሩን በዚያ
አደረገ፤ በአቅራቢያው ከነበሩትም ድንጋ
ዮች አንዱን ተንተርሶ ተኛ። 12በሕ
ልሙም፣
ጫፉ ሰማይ የሚደርስ መሰላል በምድር
ላይ ቆሞ፣ በላዩም የእግዚአብሔር (ኤሎሂም) መላ
እክት ሲወጡና ሲወርዱ አየ። 13እግዚአ
ብሔርም (ያህዌ) ከጫፉ ላይ[ሠ] ቆሞ እንዲህ
አለ፤ "የአባትህ የአብርሃም አምላክ (ኤሎሂም)፣
የይስሐቅ አምላክ (ኤሎሂም) እኔ እግዚአብሐ
ር (ያህዌ) ነኝ፤ የተኛህበትን ምድር
ለአንተና ለዘርህ እሰጣለሁ። 14ዘርህ እንደ
ምድር አሸዋ ይበዛል፤ በምዕራብና በምሥ
ራቅ፣ በሰሜንና በደቡብ ትስፋፋለህ፤
የምድርም ሕዝ ቦች ሁሉ በአንተና በዘርህ
አማካይነት ይባ ረካሉ። 15እኔ ከአንተ
ጋር ነኝ፤ በምትሄድ በት ስፍራ ሁሉ እጠ
ብቅሃለሁ፤ ወደዚ ችም ምድር
እመልስሃለሁ፤ የሰጠሁህን ተስፋ እስከምፈ
ጽምልህ ድረስ አልተውህም።"
16ያዕቆብም ከእንቅልፉ ሲነቃ፣ "በእውነት
እግዚአብሔር (ያህዌ) በዚህ ስፍራ አለ፤ እኔ
ግን ይህን አላወቅሁም ነበር" አለ። 17እርሱም
በፍርሀት፣ "ይህ ስፍራ እንዴት የሚያስፈራ
ነው! ይህስ ሌላ ሳይሆን የእግዚአብሔር (ያህዌ)
ቤት መሆን አለበት፤ የሰማይ ደጅ ነው"
አለ።
18ያዕቆብም በማግስቱ ማልዶ ተነሣ፣ ተን

6፥24፤ሩት2፥4፤መዝ
129፥8፤134፥3፤ኤር
31፥23
28፥4 ዘፍ12፥2፡3፤
15፥7፤17፥8
28፥5 ዘፍ11፥31፤
24፥29፤25፥20፤ሆሴ
12፥12
28፥6 ቍ1
28፥8 ዘፍ10፥15-
19፤26፥35
28፥9 ዘፍ16፥15፤
25፥13፤26፥34
28፥10 ዘፍ11፥31፤
21፥14
28፥11 ቍ18፤ዘፍ
12፥8
28፥12 ዘፍ20፥3፤
37፥19፤ዮሐ1፥51
28፥13 ዘፍ12፥7፤
24፥12፤35፥7፡9፤46፥
4፤48፥3፡16፡21፤49፥
25፤50፥17
28፥14 ዘፍ12፥2፡
3፤13፥14፤26፥4፡24፤
ሐሥ3፥25፤ገላ3፥8
28፥15 ቍ20፡21፡
22፤ዘፍ15፥16፤21፥
20፤30፥25፤31፥30፤
35፥10፤ዘሌ26፥42፤
ዘዳ 31፥6፡8፤ኢሱ
1፥5፤ነህ4፥14፤መዝ
9፥10፤105፥10፤121፥
5፡7-8
28፥16 1ነገ3፥15፤
ኤር31፥26
28፥17 ቍ22፤ዘፍ
32፥2፤ዘፀ3፥5፤19፥21፤
ኢሱ5፥15፤1ዜና22፥1
፤2ዜና3፥1፤መዝ68፥
24፡35
28፥18 ቍ11፡22፤
ዘፍ31፥13፡45፡51፤
35፥14፤ዘፀ24፥4፤ዘሌ
8፥11፤ኢሱ4፥9፤24፥
26፡27፤ኢሳ19፥19
28፥19 ዘፍ12፥8፤
35፥6፤ 48፥3፤መሳ
1፥23፡26፤ኢሱ16፥2፤
18፥13
28፥20 ቍ15፤ዘፍ
31፥13፤ዘሌ7፥16፤22፥
18፤23፥38፤27፥2፡9፤
ዘኍ6፥2፤15፥3፤ዘዳ
12፥6፤መሳ11፥30፤
1ሳሙ1፥21፤2ሳሙ
15፥8፤1ጢሞ6፥8
28፥21 ቍ15፤መሳ
11፥31፤ዘፀ15፥2፤ዘዳ
26፥17፤ኢሱ24፥18፤
መዝ48፥14፤118፥28
28፥22 ቍ17፡18፤
ዘፍ14፥20፤ዘኍ18፥
21፤1ሳሙ7፥12፤ሉቃ
18፥12
29፥1 ዘፍ25፥6
29፥2 ቍ3፡8፡10፤
ዘፍ24፥11
29፥3 ቍ2፡8 29፥4
ዘፍ11፥31፤
42፥7፤መሳ19፥17
29፥5 ዘፍ11፥29

ተርሶት ያደረውን ድንጋይ አንሥቶ እንደ ሐው
ልት አቆመው፤ በዐናቱም ላይ የወይራ ዘይት
አፈሰሰበት። 19ያንን ቦታ ቤቴል[ረ] ብሎ
ሰየመው፤ ቀደም ሲል ግን የከተማዪቱ ስም
ሎዛ ነበር።
20ከዚያም ያዕቆብ እንዲህ ሲል ተሳለ፤
"እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ከእኔ ጋር ቢሆን
በም ሄድበትም መንገድ ቢጠብቀኝ፣
የምበላው ምግብ፣ የምለብሰውን ልብስ ቢ
ሰጠኝ 21ወደ አባቴ ቤት በደኅና ቢመልሰኝ፣
እግዚአብሔር አምላኬ (ያህዌ ኤሎሂም) ይሆናል፤
22ይህ ሐው ልት አድርጌ ያቆምሁት
ድንጋይ፣ የእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ቤት
ይሆናል፤ ከምትሰጠኝም ሀብት ሁሉ፣ ከዐ
ሥር እጅ አንዱን ለአንተ እሰጣለሁ።"

## ያዕቆብ መስጴጦምያ ደረሰ

29 ያዕቆብም ጕዞውን ቀጠለ፤ የምሥ
ራቅም ሰዎች ወደሚኖሩበት ምድር
ደረሰ። 2እዚያም በአንድ ሜዳ ላይ ሦስት
የበግ መንጋዎች ተኝተው በነበሩበት አጠ
ገብ የውሃ ጕድጓድ አየ። የበግ መንጋዎቹ
የሚጠጡት ከዚሁ ጕድጓድ ሲሆን፣ የጕ
ድጓዱም አፍ ትልቅ የድንጋይ መክደኛ
ነበረው። 3መንጎቹ ሁሉ በጕድጓዱ አጠ
ገብ በሚሰበሰቡበት ጊዜ፣ እረኞች ድንጋዩን
ያንከባልሉና በጎቹን ውሃ ያጠጣሉ፤ ከዚ
ያም ድንጋዩን በቦታው መልሰው የጕድጓ
ዱን አፍ ይገጥሙታል።
4ያዕቆብም እረኞቹን፣ "ወንድሞቼ፤ ከየት
ነው የመጣችሁት?" ብሎ ጠየቃቸው።
እነርሱም፣ "ከካራን ነን" አሉት።
5እርሱም፣ "የናኮርን የልጅ ልጅ ላባን
ታውቁታላችሁ?" አላቸው።
እነርሱም፣ "አዎን እናውቀዋለን" አሉት።
6ያዕቆብም፣ "ለመሆኑ ደኅና ነው?" አላቸው።
እነርሱም፣ "አዎን ደኅና ነው፤ ልጁም
ራሔል እነሆ፤ በጎች እየነዳች በመምጣት
ላይ ነች" አሉት።
7ያዕቆብም፣ "እንደምታዩት ጊዜው ገና
ነው፤ መንጎቹ የሚገቡበት ሰዓት አይደለም፤
ታዲያ፣
ለምን በጎቹን አጠጥታችሁ ወደ ግጦሽ አት
መልሷቸውም?" አላቸው።
8እነርሱም፣ "መንጎቹ ሁሉ ተሰብስበው
ድንጋዩ ከጕድጓዱ አፍ ካልተንከባለለ በስ
ተቀር አንችልም፤ ከዚያም በጎቹን እናጠ
ጣቸዋለን" አሉ።

29፥6 ዘፍ30፥22-24፤35፥16፤46፥19፡22፤ዘፀ2፥16 29፥8 ቍ2፤
ዘፍ24፥13

[መ]3 በዕብራይስጥ ኤልሻዳይ ማለት ነው
[ሠ]13 ወይም በዚህ በአጠገቡ
[ረ]19 ቤቴል ማለት የእግዚአብሔር ቤት ማለት ነው

⁹ያዕቆብ ከእረኞቹ ጋር በመነጋገር ላይ ሳለ፣
ራሔል፣ እረኛ ነበረችና የአባቷን በጎች
እየነዳች መጣች:: [10]ያዕቆብ የእናቱን ወን
ድም የላባን ልጅ ራሔልን፣ እንዲሁም
የአጎቱን የላባን በጎች ሲያይ፣ ወደ ጕድ
ጓዱ ሄዶ ድንጋዩን ከጕድጓዱ አፍ አን
ከባለለ፤ የአጎቱንም በጎች አጠጣ:: [11]ከዚ
ያም ያዕቆብ ራሔልን ሳማት፤ ድምፁንም
ከፍ አድርጎ አለቀሰ:: [12]ያዕቆብም የአባቷ
ዘመድና የርብቃ ልጅ መሆኑን ለራሔል
ነገራት፤ እርሷም ሮጣ ሄዳ ይህንኑ ለአባቷ
ነገረችው::
[13]ላባም የእኅቱ ልጅ ያዕቆብ መምጣቱን
እንደ ሰማ፣ ሊቀበለው ፈጥኖ ወጣ:: ዐቅፎ
ከሳመውም በኋላ፣ ወደ ቤቱ ይዞት ሄደ::
ያዕቆብም ሁኔታውን ሁሉ ለላባ ነገረው::
[14]ላባም ያዕቆብን፣ “አንተማ የዐጥንቴ
ፍላጭ የሥጋዬ ቊራጭ ነህ” አለው::

## ያዕቆብ ልያንና ራሔልን አገባ

ያዕቆብ አንድ ወር ሙሉ አብሮት ከተ
ቀመጠ በኋላ፣ [15]ላባ ያዕቆብን፣ “ዘመዴ
በመሆንህ ብቻ በነጻ ልታገለግለን አይገባ
ምና ደመወዝህ ምንድን ነው?” አለው::
[16]ላባ ሁለት ሴቶች ልጆች ነበሩት፤ የታ
ላቂቱ ስም ልያ የታናሺቱ ራሔል ነበር::
[17]ልያ ዐይነ ልም[ሰ] ስትሆን ራሔል ግን ቊመ
ናዋ ያማረ መልኳም የተዋበ ነበር:: [18]ያዕ
ቆብም ራሔልን ስለ ወደዳት፣ “ታናሺቱ
ልጅህን ራሔልን የምትድርልኝ ከሆነ ሰባት
ዓመት አገለግላለሁ” አለው::
[19]ላባም መልሶ፣ “ለሌላ ሰው ከምድራት
ላንተ ብድራት ይሻላል፤ እዚሁ አብረኸኝ
ተቀመጥ” አለው:: [20]ያዕቆብም ራሔልን ለማ
ግኘት ሲል ሰባት ዓመት አገለገለ፤ አጥብቆ
ይወዳትም ስለ ነበረ፣ ሰባት ዓመት እንደ
ጥቂት ቀን ሆኖ ታየው::
[21]ከዚያም ያዕቆብ ላባን፣ “እነሆ፤ የተባባ
ልነው ጊዜ አብቅቶአል፤ ስለዚህ ሚስቴን
አስረክበኝና የባልና የሚስት ወጋችንን እና
ድርስ” አለው::
[22]ስለዚህ ላባ የአካባቢውን ሰዎች በሙሉ ጠ
ርቶ ሰርግ አበላ:: [23]ሲመሽ ግን ላባ ልጁን
ልያን አምጥቶ ለያዕቆብ ሰጠው፤ ያዕቆ
ብም አብሮአት ተኛ:: [24]ላባም ዘለፋ የተ
ባለች አገልጋዩን ለልጁ ለልያ ደንገጡር
እንድትሆን ሰጣት::
[25]ሲነጋም እነሆ፤ ልያ ሆና ተገኘች፤
ስለዚህም ያዕቆብ ላባን፣ “ምነው፣ እንዲህ
ጕድ ሠራኸኝ? ያገለገልኩህ ለራሔል ብዬ
አልነ በረምን? ታዲያ ለምን ታታልለኸኛለህ?”
አለው::

29፥9 ዘፀ2፥16
29፥10 ቍ2፡3፡16፤ ዘፍ24፥11፤ዘፀ2፥17
29፥11 ቍ13፤ዘፍ 33፥4፤42፥24፤43፥30፤ 45፥2፡14-15፤46፥29 ፤50፥1፡17፤ሩት1፥9
29፥12 ቍ15፤ዘፍ 24፥28-29
29፥13 ዘፍ24፥29፤ 33፥4፤45፥14-15፤ 48፥10፤ዘፀ4፥27፤18፥ 7፤ሉቃ15፥20
29፥14 ዘፍ2፥23፤ 37፥27፤መሳ9፥2፤2ሳሙ 5፥1፤19፥12-13፤20፥1 ፤ነህ5፥5፤ኢሳ58፥7
29፥15 ቍ12፤ዘፍ 30፥28፡32፤31፥7፡41
29፥16 ቍ9-10፡ 17፡23፡28፡30፤ዘፍ 30፥9፤35፥23፤47፥30፤ 49፥31፤ሩት4፥11
29፥17 ቍ16፤ዘፍ 12፥11
29፥18 ቍ20፡27፡ 30፤ዘፍ24፥67፤30፥ 26፤ሆሴ12፥12
29፥20 ቍ18፤ዘፍ 31፥15፤ማሕ8፥7፤ ሆሴ12፥12
29፥21 መሳ15፥1
29፥22 መሳ14፥10፤ ኢሳ25፥6፤ዮሐ2፥1-2
29፥23 ቍ16
29፥24 ዘፍ16፥1፤ 30፥9
29፥25 ዘፍ12፥18፤ 27፥36
29፥26 መሳ15፥2፤ 1ሳሙ14፥49፤18፥17፡ 20፤2ሳሙ6፥23
29፥27 ቍ18፤ዘፍ 31፥41፤መሳ14፥12
29፥28 ቍ16፤ዘፍ 4፥19
29፥29 ዘፍ16፥1፤ 30፥3፤35፥22፤49፥4፤ ዘዳ22፥30፤1ዜና5፥1
29፥30 ቍ16፡20
29፥31 ቍ33፤ዘፍ 11፥30፤16፥2፤ዘዳ 21፥15-17፤ሩት 4፥13፤1ሳሙ1፥19፤ መዝ127፥3
29፥32 ዘፍ16፥11፤ 30፥23፤ዘፍ37፥21፤46፥ 8፤48፥5፡14፤49፥3፤ ዘፀ6፥14፤ዘኍ1፥5፡20፤ 26፥5፤ዘዳ33፥6፤ኢሱ 4፥12፤ሩት4፥13፤1ሳሙ 1፥20፤1ዜና5፥1፡3
29፥33 ቍ31፤ዘፍ 34፥25፤46፥10፤48፥5፤ 49፥5፤ዘፀ6፥15፤ዘኍ 1፥6፡22፤34፥20፤1ዜና 4፥24፤ሕዝ48፥24
29፥34 ዘፍ30፥20 ፤34፥25፤46፥11፤49፥5- 7፤ዘፀ፥1፤6፥16፡19፤ ዘኍ1፥47፤3፥17-20፤ 26፥57፤ዘዳ33፥8፤1ሳሙ1፥2-4፤1ዜና6፥1፡16፤23፥6-24 29፥35 ዘፍ30፥9፤35፥23፤37፥26፤38፥1፤43፥8፤44፥14፡18፤46፥12፤49፥8፤ 1ዜና2፥3፤4፥1፤ኢሳ48፥1፤ማቴ1፥2-3 30፥1 ዘፍ11፥30፤16፥4፤ ዘሌ18፥18፤ኢሳ49፥21፤54፥1 30፥2 ዘፍ16፥2፤50፥19፤ዘዳ 32፥35፤2ነገ5፥7

[26]ላባም እንዲህ አለው፤ “በአገራችን ታላቋ
እያለች ታናሿን መዳር የተለመደ አይደ
ለም፤ [27]ይህን የጫጕላ ሳምንት ፈጽምና፣
ሌላ ሰባት ዓመት የምታገለግለን ከሆነ፣
ታናሺቱን ደግሞ እንሰጥሃለን::
[28]ያዕቆብም በነገሩ ተስማማ፤ ከልያ ጋር
ተሞሽሮ ሰባት ቀን ከቈየ በኋላ፤ ላባ ልጁን
ራሔልን ለያዕቆብ ዳረለት፤ [29]ባላ የተባ
ለች አገልጋዩንም ደንገጡር እንድትሆናት
ለራሔል ሰጣት:: [30]ያዕቆብ ከራሔልም ጋር
ተኛ፤ ራሔልን ከልያ አብልጦ ወደዳት፤
ከዚያም የተነሣ ሌላ ሰባት ዓመት ላባን
አገለገለው::
[31]እግዚአብሔር (ያህዌ) ልያ እንዳልተወደ
ደች ባየ ጊዜ ማሕፀኗን ከፈተላት፤ ራሔል
ግን መካን ነበረች:: [32]ልያ ፀነሰች፤ ወንድ
ልጅም ወለደች፤ “እግዚአብሔር (ያህዌ) መከ
ራዬን ስለ ተመለከተልኝ፣ ከእንግዲህ ባሌ
ይወደኛል” ስትል ስሙን ሮቤል[ሸ] አለችው::
[33]እንደ ገናም ፀንሳ ወለደች፤ እርሷም
“እግዚአብሔር (ያህዌ) እንዳልተወደድኩ ሰምቶ
ይህን ልጅ በድጋሚ ሰጠኝ’ አለች:: ከዚያም
የተነሣ ስምዖን[ቀ] ብላ ጠራችው::
[34]አሁንም እንደ ገና ፀነሳ ወንድ ልጅ ወለደች፤
እርሷም፣ ሦስት ወንዶች ልጆች ስለ ወለድ
ሁለት ከእንግዲህ ባሌ ያቀርበኛል” አለች፤
ስለዚህ ሌዊ[በ] ብላ ጠራችው::
[35]እንደ ገና ፀንሳ አሁንም ወንድ ልጅ
ወለደች፤ እርሷም፣ “እንግዲህ እግዚአብሔ
ርን (ያህዌ) አመሰግናለሁ” አለች፤ ስሙንም
ይሁዳ[ተ] ብላ ጠራችው:: ከዚያም በኋላ
መውለድ አቆመች::

30 ራሔል ለያዕቆብ አንድም ልጅ
እን ዳልወለደችለት ባየች ጊዜ
በእ ኅቷ ቀናች:: ስለዚህ ያዕቆብን፣ “ልጅ
ስጠኝ፤ አለበለዚያ እሞታለሁ” አለችው::
²ያዕቆብም ራሔልን ተቈጥቶ “እኔ እን
ዳትወልጂ ያደረገሽን እግዚአብሔርን (ኤሎሂም) መሰ
ልኹሽን?” አላት::

[ሰ]17 ወይም አደጋ የማይችል ዐይን
[ሸ]32 ሮቤል የሚለው ቃል ሥቃዬን ተመልክቶ የሚል ትርጕም ካለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው፤ የስሙ ትርጕም ግን ማየት፣ ልጅ ማለት ነው::
[ቀ]33 ስምዖን ማለት የሚሰማ ማለት ሊሆን ይችላል::
[በ]34 ሌዊ የሚለው ቃል የተያያዘ የሚል ትርጕም ካለው የዕብራይስጥ ቃል የመጣ ሲሆን ከዚሁ ቃል ጋር አንድ ዐይነት ድምፅ አለው::
[ተ]35 ይሁዳ የሚለው ቃል ውዳሴ የሚል ትርጕም ካለው የዕብራስጥ ቃል ጋር አንድ ዐይነት ድምፅ አለው::

3እርሷም፣ “እነሆ፤ አገልጋዬ ባላ አለችልህ፤
ልጆች እንድትወልድልኝና እኔም ደግሞ
በእርሷ አማካይነት ልጆች እንዳገኝ ከእ
ርሷ ጋር ተኛ” አለችው።
4ስለዚህም አገልጋይዋን ባላን ሚስት እን
ድትሆነው ሰጠችው፤ ያዕቆብም አብሮአት
ተኛ፤ 5እርሷም ፀነሰች፤ ወንድ ልጅም ወለ
ደችለት። 6ራሔልም፣ “እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ፈር
ዶልኛል፣ ልመናዬንም ሰምቶ ወንድ ልጅ
ሰጥቶኛል” አለች። ስለዚህ ስሙን ዳን
ብላ አወጣችለት።
7የራሔል አገልጋይ ባላ እንደ ገና ፀነ
ሰች፤ ለያዕቆብም ሁለተኛ ወንድ ልጅ ወለ
ደች። 8ራሔልም፣ “እኅቴን ብርቱ ትግል
ገጥሜ አሸነፍሁ” አለች፤ ስሙንም ንፍታ
ሌም ብላ አወጣችለት።
9ልያም ልጅ መውለድ ማቆሟን እንደ
ተረዳች፣ አገልጋይዋን ዘለፋን ሚስት እን
ድትሆነው ለያዕቆብ ሰጠችው። 10የልያ
አገ ልጋይ ዘለፋም ለያዕቆብ ወንድ ልጅ
ወለደችለት፤ 11ልያም፣ “ምን ዐይነት መታ
ደል[ቸ] ነው” አለች፤ ስሙንም ጋድ[ኀ] ብላ
አወጣችለት።
12የልያም አገልጋይ ዘለፋ፤ ለያዕቆብ ሁለ
ተኛ ወንድ ልጅ ወለደችለት፤ 13ልያም፣
“ምንኛ ደስተኛ ሆንሁ! ከእንግዲህ ሴቶች
ደስተኛዋ ይሉኛል” አለች፤ ስሙንም አሴር[ነ]
ብላ አወጣችለት። 14ስንዴ በሚታጨድበት
ወቅት፣ ሮቤል ወደ ሜዳ ወጣ እንኮይም
አግኝቶ ለእናቱ ለልያ አመጣላት። ራሔ
ልም ልያን፣ “እባክሽን ልጅሽ ካመጣልሽ
እንኮይ ስጪኝ” አለቻት።
15ልያም፣ “ባሌን የቀማሽኝ አነሰና የል
ጄን እንኮይ ደግሞ ልትወስጂ አማረሽ?”
አለቻት።
ራሔልም፣ “ስለ ልጅሽ እንኮይ ዛሬ ከአ
ንቺ ጋር ይደር” አለቻት።
16በዚያች ምሽት ያዕቆብ ከዕርሻ ሲመ
ለስ፣ ልያ ወጥታ ተቀበለችውና፣ “በልጄ
እንኮይ ስለ ተከራየሁህ የዛሬው አዳርህ
ከእኔ ጋር ነው” አለችው፤ ያዕቆብም በዚያች
ሌሊት ከእርሷ ጋር አደረ።
17እግዚአብሔር (ኤሎሂም) የልያን ጸሎት ሰማ፤ ፀ
ነ ሰች፤ ለያዕቆብም አምስተኛውን ወንድ
ልጅ ወለደች። 18ልያም፣ “አገልጋዬን ለባሌ
በመስጠቴ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ከሶኛል” አለች፤
ስሙንም ይሳኮር[ኘ] ብላ አወጣችለት።
19ልያ አሁንም ደግማ ፀነሰች፤ ለያዕቆብም
ስድስተኛውን ወንድ ልጅ ወለደች። 20እር
ሷም፣ “እግዚአብሔር (ኤሎሂም) በከበረ ስጦታ ዐድ
ሎኛል፣ ስድስት ወንዶች ልጆች ስለ ወለ

30፥3 ቀኁ7፤ዘፍ 16፥2፤24፥61፤29፥29
30፥4 ቀኁ9፡18፤ዘፍ 16፥3-4
30፥6 ቀኁ23፤ዘፍ 21፥2፤46፥23፤49፥16-17፤ዘኍ26፥42-43፤ኢ.ሱ19፥40-48፤መሳ1፥34፤13፥2፤18፥2፤ሩት4፥13፤1ሳሙ 1፥20፤መዝ35፥24፤43፥1፤ኤር4፥15፤8፥16፤ሕዝ48፥1
30፥7 ቀኁ3
30፥8 ዘፍ32፥28፤35፥25፤46፥24፤49፥21፤ዘኍ1፥42፤26፥48፤ዘዳ33፥23፤መሳ4፥6፤5፥18፤1ዜና7፥13፤ሆሴ12፥3-4
30፥9 ቀኁ4፤ዘፍ29፥16፡24፡35
30፥10 ዘፍ46፥18
30፥11 ዘፍ35፥26፤46፥16፤49፥19፤ዘፀ1፥4፤ዘኍ1፥24፤26፥28፤ኢ.ሱ4፥12፤1ዜና5፥11፤12፥8፤ኤር49፥1
30፥13 ሩት4፥14፤ዘፍ35፥26፤46፥17፤49፥20፤ዘኍ1፥40፤26፥47፤ዘዳ33፥24፤ ኢ.ሱ19፥24-31፤1ዜና 7፥30-31፤መዝ127፥3-5፤ሉቃ1፥48
30፥14 ቀኁ15፡16፤ዘፀ34፥22፤መሳ15፥1፤ሩት2፥23፤1ሳሙ6፥13፤12፥17፤ማሕ7፥13
30፥15 ዘፍ38፥16፤ዘኍ16፥9፡13፤ኢ.ሳ7፥13፤ሕዝ16፥33፤34፥18፤ሆሴ9፥1
30፥16 ቀኁ14
30፥17 ዘፍ25፥21
30፥18 ቀኁ4፤ዘፍ 46፥13፤49፥14፤ዘኍ 1፥8፡28፡29፤26፥25፤ዘዳ27፥12፤33፥18፤ኢ.ሱ17፥10፤19፥17፤21፥6፡28፤መሳ5፥15፤10፥1፤1ዜና7፥1
30፥20 ዘፍ29፥34፤35፥23፤46፥14፤49፥13፤ዘኍ1፥30፤26፥27፤34፥25፤ዘዳ33፥18፤መሳ5፥18፤1ጴጥ3፥7
30፥21 ዘፍ34፥1፤46፥15
30፥22 ዘፍ8፥1፤11፥30፤25፥21
30፥23 ቀኁ6፤ዘፍ29፥32፤ኢ.ሳ4፥1፤25፥8፤45፥17፤54፥4፤ሉቃ1፥25
30፥24 ዘፍ29፥6፤32፥22፤33፥2፡7፤35፥17፡24፤37፥2፤39፥1፤49፥22-26፤ዘዳ33፥13፤1ሳሙ4፥20 30፥25 ዘፍ24፥54፤ 28፥15
30፥26 ዘፍ29፥18

ደሁለት፣ ከእንግዲህ ባሌ አክብሮ ይይዘኛል”።
አለች፤ ስሙንም ዛብሎን[አ] አለችው።
21ከዚያም በኋላ ሴት ልጅ ወለደች፤ ስም
ዋንም ዲና አለቻት።
22እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ራሔልን ዐሰባት፤
ልመናዋንም ሰምቶ ማሕፀንዋን ከፈተላት።
23ከዚያም ፀንሳ፣ ወንድ ልጅ ወለደችና “እግዚ
አብሔር (ኤሎሂም) ዕፍረቴን አስወገደልኝ” አለች፤
24ስሙንም፣ “እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሌላ ወንድ
ልጅ ጨምሮ ይስጠኝ ስትል፣ ዮሴፍ”[ከ] አለ
ችው።

## የያዕቆብ መንጎች መብዛት

25ራሔል ዮሴፍን ከወለደች በኋላ ያዕቆብ
ላባን እንዲህ አለው፤ “ወደ ገዛ ቤቴ፣ ወደ
አገሬ እንድመለስ አሰናብተኝ፤ 26የድካሜ
ዋጋ የሆኑትን ሚስቶቼንና ልጆቼን ስጠ
ኝና ይዤአቸው ልሂድ፤ መቼም የቱን
ያህል እንዳገለገልኹህ ታውቃለህ” አለው።
27ላባም እንዲህ አለው፤ “በጎ ፈቃድህ ቢሆን፣
እባክህ እዚሁ ከእኔ ጋር ተቀመጥ፤ ምክን
ያቱም እግዚአብሔርም (ያህዌ) በአንተ ምክ
ንያት እንደ ባረከኝ በንግርት ተረድቻለሁ፤[ኸ]
28ይልቅስ ይገባኛል የምትለውን ደሞዝ
ንገረኝና እከፍልሃለሁ።”
29ያዕቆብም እንዲህ አለው፤ “መቼም እን
ዴት እንዳገለገልሁህ፣ ከብቶችህ በእኔ ጥበቃ
ምን ያህል እንደ ተመቻቸው አንተ ታው
ቃለህ። 30እኔ ከመምጣቴ በፊት ጥቂት
የነበረው ሀብትህ ዛሬ ተትረፍርፎአል፣
በተሰማራሁበት ሁሉ እግዚአብሔር (ያህዌ) በረ
ከቱን አብዝቶልሃል። ታዲያ፣ ስለ ራሴ
ቤት የማስበው መቼ ነው?”
31ላባም፣ “ታዲያ ምን ልስጥህ?” ሲል ጠየ
ቀው።
ያዕቆብም መልሶ እንዲህ አለው፤ “ምንም
አትስጠኝ፤ ነገር ግን የምጠይቅህን አንዲት
ነገር ብቻ ብታደርግልኝ ከብቶችህን ማገ
ዴን እቀጥላለሁ፤ 32በመንጎቹ መካከል ዛሬ
ልዘዋወርና ከበጎቹ መካከል ዝንጕርጕር የሆ
ኑትን፣ ነቍጣ ያለባቸውንና ጥቋቁሮቹን እን
ዲሁም ከፍየሎቹ ነቍጣ ያለባቸውንና ዝን
ጕርጕሮቹን ልምረጥ፤ እነዚህ ደሞዜ ይሁኑ።

30፥27 ቀኁ30፤ዘፍ26፥24፤31፥38፤33፥10፤44፥5፡15፤50፥4፤ዘሌ 19፥26፤ዘኍ22፥7፤23፥23፤24፥1፤ዘዳ28፥11፤ኢ.ሱ13፥22፤2ሳሙ6፥11፤2ነገ17፥17፤አስ2፥15፤ኤር27፥9 30፥28 ዘፍ29፥15 30፥29 ዘፍ31፥6፡38-40 30፥30 ቀኁ27፤1ጢሞ5፥8 30፥32 ቀኁ33፡35፡39፡40፤ዘፍ29፥15፤31፥8፡12

[ቸ]11 ወይም *ጭፍራ እየመጣ ነው*
[ኀ]11 *ጋድ* ማለት *መልካም ዕድል* ወይም *ሰራዊት* ማለት ነው
[ነ]13 *አሴር* ማለት *ደስተኛ* ማለት ነው
[ኘ]18 *ይሳኮር* የሚለው ቃል *ሽልማት* የሚል ትርጉም ካለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር አንድ ዐይነት ድምፅ አለው
[አ]20 *ዛብሎን* ማለት *ማክበር* ማለት ነው
[ከ]24 *ዮሴፍ* ማለት *እርሱ ይጨምር* ማለት ነው
[ኸ]27 ወይም *እየበለጸግሁና እግዚአብሔርም በአንተ ምክንያት እየባረከኝ ነው*

[33]ወደፊት ደሞዜን ለመቈጣጠር በምትመ
ጣበት ጊዜ ታማኝነቴ ይታወቃል፤ በመን
ጋዎቹ መካከል ዥንጕርጕር ወይም ነቍጣ
የሌለበት ፍየል፣ ወይም ጥቁር ያልሆነ ቢገኝ
ያ እንደ ተሰረቀ ይቈጠር"።
[34]ላባም፣ "እሺ፣ ይሁን፤ ባልኸው ተስማ
ምቼአለሁ" አለው። [35]ነገር ግን በዚያኑ ዕለት
ከተባት ፍየሎች ሽመልመሌ የሆኑትን ወይም
ነቍጣ ያለባቸውን ሁሉ፣ እንዲሁም ከእን
ስት ፍየሎች ነቍጣ ያለባቸውን ዝንጕር
ጕር የሆኑትን ሁሉ፣ ማንኛውንም ነጭ ያለ
በትን ሁሉ መረጠ፤ ደግሞም ጥቋቁር የሆ
ኑትንም በጎች ሁሉ ለየና ወንዶች ልጆቹን
አስጠበቃቸው። [36]ከዚያም በእርሱና በያዕ
ቆብ መካከል የሦስት ቀን መንገድ ርቀት
እንዲኖር አደረገ፤ ያዕቆብም የቀሩትን የላ
ባን መንጎች ማገዱን ቀጠለ።
[37]ነገር ግን ያዕቆብ እርጥብ የልብን፣ የለ
ውዝንና የኤርሞን በትሮች ወሰደ፤ ቅርፊ
ታቸውንም በቀጭን ልጦ እያነሣ የበትሮቹ
ግንድ ነጩ እንዲታይ፣ ሽመልመሌ መልክ
እንዲኖራቸው አደረገ። [38]የላጣቸውንም በት
ሮች መንጎቹ ውሃ ለመጠጣት ሲመጡ ከፊት
ለፊት እንዲያዩአቸው በማጠጫ ገንዳዎቹ
ሁሉ አስቀመጠ። መንጎቹም ስሜታቸው ሲነ
ሣሣና ውሃ ለመጠጣት ሲመጡ፣ [39]በትሮቹን
ፊት ለፊት እያዩ ይሳረሩ ነበር፤ ሽመል
መሌ፣ ዝንጕርጕርና ነቍጣ የጣለባቸውንም
ግልገሎች ወለዱ። [40]ያዕቆብ ግልገሎቹን
ለብቻ ለያቸው፤ የቀሩትንም የላባ መንጎች
ሽመልመሌና ጥቋቁር በሆኑት ትይዩ አቆ
ማቸው፤ በዚህም መሠረት የራሱ መንጋ
ከላባ መንጋ ጋር እንዳይቀላቀል ለብቻ ለየ።
[41]ያዕቆብም ብርቱ እንስቶች አውራ ፈልገው
በሚቅበጠበጡበት ጊዜ፣ በትሮቹ አቅራቢያ
እንዲጠቁ በትሮቹን በውሃ ገንዳዎቹ ውስጥ
ፊት ለፊታቸው ያስቀምጥ ነበር፤ [42]ደካማ
በሆኑት እንስቶች ፊት ግን፣ በትሮቹን
አያስቀምጥም ነበር፤ ስለዚህ ደካማ ደካ
ማዎቹ ለላባ ሲሆኑ፣ ብርቱ ብርቱዎቹ ለያዕ
ቆብ ሆኑ። [43]በዚህም ሁኔታ ይህ ሰው
እጅግ ባለ ጠጋ ሆነ፤ የብዙ መንጎች፣ የሴ
ትና የወንድ አገልጋዮች፣ እንዲሁም የግ
መሎችና የአህዮች ባለቤት ሆነ።

### ያዕቆብ ከላባ ቤት ኰበለለ

31 የላባ ወንዶች ልጆች፣ "ያዕቆብ የአ
ባታችንን ሀብት እንዳለ ወስዶታል፤
ይህ ሁሉ እርሱ ያካበተውም ሀብት ከአባታ
ችን የተገኘ ነው" እያሉ ሲያወሩ ያዕቆብ
ሰማ። [2]የላባ አመለካከት ከቀድሞው የተለ
ወጠበት መሆኑንም ያዕቆብ ተረዳ።
[3]እግዚአብሔርም (ያህዌ) ያዕቆብን፣ "ወደ
አባ ቶችህና ዘመዶችህ አገር ተመለስ፤
እኔም ካንተ ጋር እሆናለሁ" አለው።
[4]ስለዚህም ያዕቆብ መንጎቹ ወደ ተሰ
ማሩበት መስክ እንዲመጡ፣ ራሔልንና
ልያን አስጠራቸው፤ [5]እንዲህም አላቸው፤
አባታችሁ ስለ እኔ ያለው አመለካከት እንደ
ቀድሞው አለመሆኑን ተረድቻለሁ፤ ቢሆንም
የአባቴ አምላክ (ኤሎሂም) አልተለየኝም፤ [6]መቼም
ባለኝ ዐቅም አባታችሁን ማገልገሌ ከእና
ንተ የተሰወረ አይደለም። [7]አባታችሁ ደሞ
ዜን ዐሥር ጊዜ እየለዋወጠ አታልሎኛል፣
ሆኖም እንዲጎዳኝ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
አልፈ ቀደለትም። [8]እርሱ፣ 'ደሞዝህ
ዝንጕርጕ ሮቹ ይሆናሉ' ሲለኝ፣ መንጎቹ
ሁሉ ዝን ጕርጕር ወለዱ፤ ደግሞም
'ደሞዝህ ሽመል መሌዎቹ ይሆናሉ' ሲለኝ፣
መንጎቹ ሁሉ ሽመልመሌ መልክ
ያላቸውን ወለዱ፤ [9]ስለ ዚህ እግዚአብሔር (ኤሎ
ሂም) የአባታችሁን ከብቶች ወስዶ ለእኔ
ሰጠኝ።
[10]"እንስሳቱ በሚጠቁበት ወራት፣ የሚ
ያጠቋቸው አውራ ፍየሎች መልካቸው፣ ሽመ
ልመሌ፣ ዝንጕርጕርና ነቍጣ ያለባቸው
መሆናቸውን ዐይኔን አንሥቼ በሕልሜ አየሁ።
[11]የእግዚአብሔርም (ኤሎሂም) መልአክ፣ 'ያዕ
ቆብ' አለኝ፤ እኔም፣ 'እነሆ አለሁኝ'
አልሁት። [12]እርሱም 'መንጎቹን የሚያጠ
ቋቸው አውራ ፍየሎች ሁሉ ሽመልመሌ
መልክ ያላቸው፣ ዝንጕርጕርና ነቍጣ
ያለባቸው መሆናቸ ውን ቀና ብለህ
ተመልከት፤ ላባ በአንተ ላይ የሚፈጽመውን
ድርጊት ሁሉ አይቻለሁና፤ [13]የድንጋይ ሐ
ውልት በማቆም ዘይት ቀብ ተህ የተሳልጠ
ህባት የቤቴል አምላክ (ኤል) እኔ ነኝ፤
አሁንም ይህን አገር ፈጥነህ ልቀቅ ወደ
ተወለድህበትም ምድር ተመል ሰህ ሂድ'
አለኝ።"
[14]ራሔልና ልያም እንዲህ ብለው
መለሱ ለት፤ "ከአባታችን ሀብት
የምናገኘው ምን ውርስ አለ? [15]እኛን
የሚያየን እንደ ባዕድ አይደለምን?
ደግሞም እኮ እኛን ሸጦናል፣
የተሸጥንበትንም ዋጋ ራሱ በልቶታል። [16]እግ
ዚአብሔር (ኤሎሂም) ከአባታችን ወስዶ ለአንተ
የሰጠው ሀብት ሁሉ የእኛና የልጆቻችን ነው፤
ስለዚህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) የነገረህን ሁሉ አድ
ርግ።"
[17]ከዚያም ያዕቆብ ልጆቹንና ሚስቶቹን
ግመሎች ላይ አስቀመጠ፤
[18]በመስጴጦምያ ካፈራው ሀብት ሁሉ ጋር
ከብቶቹን በሙሉ ወደ ፊት አስቀደመ፤
ወደ አባቱም ወደ ይስሐቅ አገር፣ ወደ
ከነዓን ምድር ጕዞ ውን ቀጠለ።
[19]ላባ በጎቹን ሊሸልት ሄዶ ሳለ፣ ራሔል
የአባቷን ቤት የጣዖታት ምስል ሰረቀች።

30፥33 ቍ32፤ዘፍ 31፥39
30፥35 ቍ32፤ዘፍ 31፥1
30፥36 ዘፍ31፥22፤ ዘፀ3፥18፤5፥3፤8፥27
30፥37 ቍ38፡41፤ ኤር1፥11፤ሕዝ31፥8
30፥38 ቍ37፡41፤ ዘፀ2፥16፤ኤር2፥24
30፥39 ቍ32፡41
30፥40 ቍ32
30፥41 ቍ37፡38
30፥42 ዘፍ31፥1፡9፡ 16፡43
30፥43 ዘፍ12፥16
31፥1 ዘፍ30፥35፡ 42
31፥2 ቍ5
31፥3 ቍ13፤ዘፍ 21፥22፤26፥3፤32፥9፤ ዘዳ30፥3፤ኢሳ10፥21፤ 35፥10፤ኤር30፥3፤ 42፥12
31፥5 ቍ2፡29፡42፡ 53፤ዘፍ21፥22፤26፥3፤ 43፥23፤ዳን2፥23
31፥6 ዘፍ30፥29
31፥7 ቍ 41፡52፤ ዘፍ24፥50፤29፥15፤ ዘሌ6፥2፤ዘኍ14፥22፤ ኢዮ19፥3፤አሞ8፥5
31፥8 ዘፍ30፥32
31፥9 ዘፍ30፥42፤ ኢዮ39፥2፤ሕዝ31፥6
31፥10 ዘፍ20፥3
31፥11 ዘፍ16፥7፤ 20፥3፤22፥1፤ዘፀ3፥4
31፥12 ዘፍ30፥32፤ ዘፀ3፥7
31፥13 ቍ3፤ዘፍ 28፥10-22
31፥14 2ሳሙ20፥ 1፤1ነገ12፥16
31፥15 ዘፍ29፥20፤ ዘዳ15፥3፤23፥20፤ሩት 2፥10፤2ሳሙ15፥19፤ 1ነገ8፥41፤አብ1፥11
31፥16 ዘፍ30፥42
31፥17 ዘፍ24፥63- 64፤27፥41
31፥18 ዘፍ10፥9፤ 12፥5፤25፥20፤35፥27
31፥19 ቍ30፡32፡ 34-35፤ዘፍ35፥2፤38፥ 12፤13፤ኢሱ24፥14፤ መሳ17፥5፤18፥14፡17፡ 24፡30፤1ሳሙ7፥3፤ 19፥13፤25፥2፡4፡7፤ 2ሳሙ13፥23፤2ነገ23፥ 24፤ሆሴ3፥4

[20]ያዕቆብም ቢሆን፣ መኰብለሉን
ለሶርያ ዊው ለላባ ሳይገልጥለት በመቅረቱ
አታል ሎታል። [21]ያዕቆብ የእርሱ
የሆነውን ሁሉ ይዞ፣ የኤፍራጥስን ወንዝ
ተሻግሮ ወደ ኰረብታማው አገር፣ ወደ
ገለዓድ አመራ።

### ላባ ያዕቆብን ተከታተለው

[22]የያዕቆብ መኰብለል ለላባ በሦስተኛው
ቀን ተነገረው። [23]ላባ ዘመዶቹን ይዞ ተነሣ፤
ያዕቆብንም ሰባት ቀን ተከታትሎ ገለዓድ
በተባለ ኰረብታማ አገር ደረሰበት። [24]ከዚ
ያም እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ለሶርያዊው ለላባ
በሕልም ተገልጦ፣ "ያዕቆብን፣ ክፉም ሆነ
ደግ፣ እንዳትናገረው ተጠንቀቅ" አለው።
[25]ያዕቆብ ገለዓድ በተባለው ኰረብታማ
አገር ድንኳኑን ተክሎ ሳለ፣ ላባ ደረሰበት፤
ላባና ዘመዶቹም በዚያው ሰፈሩ። [26]ከዚ
ያም ላባ ያዕቆብን እንዲህ አለው፤ "ምን
ማድረግህ ነው? አታልለኸኛል፤ ልጆቼን
የጦር ምርኮኛ ይመስል አካልበህ ወሰድሃ
ቸው። [27]ለመሆኑ ለምን ተደብቀህ ሄድህ?
ለምንስ አታለልኸኝ? ብትነግረኝ ኖሮ፣
በደስታና በዘፈን በከበሮና በበገና አልሸኝ
ህም ነበር? [28]የልጆቼን ልጆችና ልጆቼንም
ስሜ ብሰናበት ምን ነበረበት? የሠራኸው
የጅል ሥራ ነው። [29]ልጐዳችሁ እችል ነበር፤
ዳሩ ግን ባለፈው ሌሊት የአባታችሁ አምላክ
(ኤሎሂም) 'ያዕቆብን፣ ክፉም ሆነ ደግ እንዳ
ትናገረው ተጠንቀቅ' አለኝ። [30]አንተ ወደ
አባትህ ቤት ለመመለስ ስለ ናፈቅህ ሄደ
ሃል፤ ነገር ግን የቤቴን የጣዖት ምስል
የሰረቅኸው ለምንድ ነው?"
[31]ያዕቆብም ለላባ እንዲህ ሲል መለሰ
ለት፤ "ሴቶች ልጆችህን በኀይል ነጥቀህ ታስ
ቀርብኛለህ ብዬ ስለ ፈራሁ ነው። [32]ነገር
ግን ከእኛ መካከል የአንተን የጣዖታት ምስል
ደብቆ የተገኘ ሰው ካለ ይሙት። ያንተ የሆነ
አንዳች ነገር ከኔ ዘንድ ቢገኝ፣ አንተው ራስህ
ዘመዶቻችን ባሉበት ፈልግና ውሰድ።" ይህን
ሲል፣ ራሔል የጣዖታቱን ምስል መስረ
ቋን ያዕቆብ አያውቅም ነበር።
[33]ላባም ወደ ያዕቆብ፣ ድንኳንና ወደ
ልያ ድንኳን እንዲሁም ወደ ሁለቱ ደን
ገጡሮቿ ድንኳኖች ገባ፤ ነገር ግን ምንም
አላገኘም። ከልያ ድንኳን ከወጣ በኋላ ወደ
ራሔል ድንኳን ገባ። [34]ራሔል የጣዖታቱን
ምስል ከግመሏ ኮርቻ ሥር ሸሽጋ፣ በላዩ
ተቀምጣበት ነበር፤ ላባም ድንኳኑን አንድ
በአንድ በርብሮ ምንም ሊያገኝ አልቻለም።
[35]ራሔልም አባቷን፣ "በፊትህ ተነሥቼ
መቆም ስላልቻልሁ፣ ጌታዬ አትቈጣ፤ የወር
አበባዬ መጥቶ ነው።" አለችው፤ ስለዚህ በረ
በረ፤ የጣዖታቱን ምስል ግን ማግኘት አል
ቻለም።
[36]በዚህ ጊዜ ያዕቆብ ተቈጣ፤ ላባንም እን
ዲህ ሲል ወቀሰው፤ "እስቲ ወንጀሌ ምን
ድን ነው? ይህን ያህል የምታሳድደኝ ኀጢ
አቴ ምን ቢሆን ነው? ዕቃዬን አንድ በአ
ንድ በርብረሃል፤ ታዲያ፣ የአንተ ሆኖ ያገ
ኘኸው ዕቃ የትኛው ነው? ካለ፣ እስቲ
በአንተም በእኔም ዘመዶች ፊት አቅርብና
እነርሱ ያፋርዱን።
[38]ሃያ ዓመት አብሬህ ኖሬአለሁ፤ በዚህ
ጊዜ ውስጥ ከመንጋህ አንድ ጠቦት እንኳ
አልበላሁም። [39]አውሬ የሰበረውንም ቢሆን
እተካ ነበር እንጂ፣ ትራፊውን ለምልክት
ነት አምጥቼ አላውቅም፤ በቀንም ሆነ በሌ
ሊት የተሰረቁትን ሁሉ ስታስከፍለኝ ኖረ
ሃል። [40]ቀን በሐሩር ሌሊት በቊር ተቃጠ
ልሁ፤ እንቅልፍም በዐይኔ አልዞር አለ፤ [41]ሃያ
ዓመት በቤትህ የኖርሁት በዚህ ሁኔታ
ነበር፤ ዐሥራ አራት ዓመት ለሁለቱ ልጆ
ችህ ብዬ አገለገልሁ፤ ስድስት ዓመት ስለ
መንጋዎችህ ስል አገለገልሁ፤ ይህም ሆኖ
ደመወዜን ዐሥር ጊዜ ለዋውጠኽብኛል። [42]የአ
ባቴ አምላክ (ኤሎሂም)፣ የአብርሃም አምላክ (ኤሎ
ሂም)፣ የይስሐቅም ፍርሀት ከእኔ ጋር
ባይሆን ኖሮ ባዶ እጄን ሰድደኸኝ ነበር፤
እግዚአ ብሔር (ኤሎሂም) ግን መከራዬን
አይቶ፣ ልፋ ቴን ተመልክቶ ትናንት ሌሊ
ት ገሠጸህ።"
[43]ላባም ለያዕቆብ እንዲህ ሲል መለሰ
ለት፤ "ሴቶቹም፣ ልጆቹም የእኔው ልጆች
ናቸው፣ መንጎቹም ቢሆኑ የራሴ ናቸው።
ታዲያ፣ በእነዚህ ሴቶች ልጆቼና በወለዷ
ቸው ልጆቻቸው ላይ ዛሬ ምን ማድረግ እች
ላለሁ? [44]በል አሁን ቃል ኪዳን እንጋባ፤ ኪዳ
ኑም በአንተና በእኔ መካከል ምስክር ይሁን።"
[45]ያዕቆብም ድንጋይ ወስዶ ሐውልት አድ
ርጎ አቆመው፤ [46]ከዚያም ዘመዶቹን፣ "ድን
ጋይ ሰብስቡ" አላቸው። እነርሱም ድንጋይ
እያመጡ ከመሩ፤ በክምሩም አጠገብ ምግብ
በሉ። [47]ላባም ክምር ድንጋዩን ይጋርሠሀ
ዱታ[w] ብሎ ጠራው፤ ያዕቆብ ደግሞ ገለዓድ[o]
አለው።
[48]ላባም "ይህ ክምር ድንጋይ በእኔና በአ
ንተ መካከል ዛሬ ምስክር ነው" አለው።
ጋልዒድ ተብሎ የተጠራውም በዚሁ ምክ
ንያት ነው፤ [49]ደግሞም ምጽጳ[″] ተባለ፤
ምክንያቱም ላባ እንዲህ ብሎአልና፤ [50]"ልጆ
ቼን ብትበድላቸው ወይም ሌሎች ሚስቶች

31፥20 ቍ27፤ዘፍ 25፥20፤27፥36
31፥21 ቍ22:23፡ 25፤ዘፍ2፥14፤37፥25፤ ዘፀ2፥15፤14፥5፤ዘኍ 26፥30፤32፥1፤ዘዳ3፥ 10፤ኢሱ12፥2፤1ነገ 18፥46፤19፥3፤ኤር 22፥6፤26፥21
31፥22 ቍ21፤ዘፍ 30፥36
31፥23 ቍ21:37፤ ዘፀ14፥9
31፥24 ዘፍ20፥3፤ 24፥50፤25፥20
31፥25 ቍ21
31፥26 ዘፍ12፥18፤ 27፥36፤34፥29፤1ሳሙ 30፥2-3
31፥27 ቍ20፤ዘፍ 4፥21፤ዘፀ15፥20፤መሳ 11፥34፤1ሳሙ10፥5፤ 2ሳሙ6፥5፤መዝ68፥ 25፤ኢሳ24፥8፤ ኤር31፥4
31፥28 ዘፍ27፥27፤ ሩት1፥14፤ሐሥ20፡37
31፥29 ቍ5:7፤ዘፍ 24፥50፤26፥29
31፥30 ቍ19፤ዘፍ 28፥15፤44፥8፤ኢዮ 29፥2
31፥31 ዘፍ20፥11
31፥32 ቍ19፤ ዘፍ44፥9
31፥33 ቍ37፤ ዘፍ16፥1፤24፥67
31፥34 ቍ19:37፤ ዘፍ24፥63-64፤44፥12
31፥35 ቍ19፤ዘፀ 20፥12፤ዘሌ15፥19-23፤ 19፥3:32፤ዘዳ21፥18፤ 27፥16፤ኤር35፥18
31፥36 1ሳሙ19፥ 5፤20፥32፤23፥23፤ 24፥11
31፥37 ቍ33:23፤ ዘዳ1፥16፤16፥18
31፥38 ዘፍ27፥44፤ 30፥27
31፥39 ዘፍ30፥33፤ ዘፀ22፥13
31፥40 መዝ132፥ 4፤2ቆሮ11፥27
31፥41 ቍ7፤ዘፍ 27፥44፤29፥15:30፤ 30፥32
31፥42 ቍ5:53፤ ዘፍ3፥17፤21፥22፤24፥ 12:50፤46፥1፤ዘፀ3፥ 15፤መዝ124፥1-2
31፥43 ዘፍ30፥32፡42
31፥44 ዘፍ21፥27፡30
31፥45 ዘፍ28፥18
31፥46 ቍ48፡51፡52
31፥47 ዘፍ21፥30
31፥48 ቍ46፤ዘፍ 21፥30፤ኤር29፥23፤ 42፥5
31፥49 ኢሱ11፥3፤ መሳ10፥17፤11፥29

[w]47 *ይጋርሠሀዱታ* የሚለው ቃል በአረማይስጥ *የኪዳን ክምር ድንጋይ* ማለት ነው
[o]47 *ገለዓድ* የሚለው ቃል በዕብራይስጥ *የኪዳን ክምር ድንጋይ* ማለት ነው
[″]49 *ምጽጳ* የሚለው ቃል *መጠበቂያ ማማ* ማለት ነው

በላያቸው ላይ ብታገባ፣ ማንም ከእኛ ጋር
ባይኖርም እንኳ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) በአን
ተና በእኔ መካከል ምስክር መሆኑን አት
ርሳ።"

51ደግሞም ላባ ያዕቆብን እንዲህ አለው፤
"ክምር ድንጋዩ እነሆ፤ በአንተና በእኔ መካ
ከል ያቆምሁትም ሐውልት እነሆ፤ 52ይህን
ክምር ድንጋይ አልፌ አንተን ለማጥቃት
ላልመጣ፣ አንተም ይህን ክምር ድንጋይና
ይህን ሐውልት አልፈህ እኔን ለማጥቃት
ላትመጣ፣ ይህ ክምር ድንጋይ ምስክር
ነው፤ ይህም ሐውልት ምስክር ነው።
53የአ ብርሃም አምላክ፣ የናኮር አምላክ፣
የአባታቸ ውም አምላክ (ኤሎሂም)
በመካከላችን ይፍረድ ብን"።

ስለዚህ ያዕቆብ በአባቱ በይስሐቅ ፍር
ሀት ማለ። 54ያዕቆብ በኰረብታማው አገር
ላይ መሥዋዕት አቀረበ፤ ዘመዶቹንም ምግብ
እንዲበሉ ጋበዛቸው፤ እነርሱም ከበሉ በኋላ
እዚያው አደሩ።

55በማግስቱም ማለዳ ላባ የልጅ ልጆቹን
እንዲሁም ሴቶች ልጆቹን ስሞ መረቃቸው፤
ከዚያም፣ ወደ አገሩ ተመለሰ።

## ያዕቆብ፣ ወንድሙን ዔሳውን ሊገናኝ ተዘጋጀ

32 ያዕቆብም ደግሞ ጕዞውን ቀጠለ፤
የእግዚአብሔርም (ኤሎሂም) መላእክት ተገና
ኙት፤ 2ባያቸውም ጊዜ፣ "ይህ የእግዚአብሔር
(ኤሎሂም) ሰፈር ነው" አለ፤ የዚያንም ቦታ ስም
መሃናይም[ዡ] አለው።

3ያዕቆብም በኤዶም አገር ሴይር በተባለው
ምድር ወደሚኖረው ወንድሙ ወደ ዔሳው
መልእክተኞችን አስቀድሞ ላከ፤ 4እንዲ
ህም ብሎ አዘዛቸው፤ "ጌታዬን ዔሳውን
እንዲህ ትሉታላችሁ፤ 'አገልጋይህ ያዕቆብ
እንዲህ ብሎአል በሉት፤ "ከላባ ዘንድ ተቀ
ምጬ እስከ አሁን ድረስ እዚያው ኖርሁ፤
5ከብቶች፣ አህዮች፣ የበግና የፍየል መን
ጎች እንደዚሁም የወንድና የሴት አገልጋ
ዮች አሉኝ፤ አሁንም ይህን መልእክት ለጌ
ታዬ መላኬ በጎ ፈቃድህን እንዳገኝ በማ
ሰብ ነው።"

6የተላኩትም ሰዎች ወደ ያዕቆብ ተመል
ሰው፣ "ወደ ወንድምህ ወደ ዔሳው ሄደን
ነበር፤ እርሱም ሊቀበልህ በመምጣት ላይ ነው፤
አራት መቶ ሰዎችም አብረውት አሉ" አሉት።

7ያዕቆብም ቢታላቅ ፍርሀትና ጭንቀት ተውጦ፣
አብረውት የነበሩትን ሰዎች ሁለት ቦታ[ዩ] ከፈ
ላቸው፤ በጎቹን ፍየሎቹን ከብቶቹንና ግመ
ሎቹንም ሁለት ቦታ ከፈላቸው፣ 8"ዔሳው
መጥቶ በአንደኛው ላይ አደጋ ቢጥል፣ ሌላው
ክፍል[ዩ] ሊያመልጥ ይችላል" ብሎ አስቦ ነበር።

9ያዕቆብ እንዲህ ሲል ጸለየ፤ "የአባቴ
የአብርሃም አምላክ፣ የአባቴ የይስሐቅ
አም ላክ (ኤሎሂም) ሆይ፤ 'ወደ አገርህና ወደ
ዘመዶችህ ተመለስ፤ እኔም በጎ ነገር አደ
ርግልሃለሁ' ያልኸኝ እግዚአብሔር (ያህዌ) ሆይ፤
10እኔ ባሪያህ እስካሁን ላደረግህልኝ ቸርነትና
ታማኝነት ብቁ አይደለሁም፤ ዮርዳኖስን
ስሻገር በእጄ ላይ ከነበረው በትር በስተ
ቀር ምንም አልነበረኝም፤ አሁን ግን ይኸው
ሁለት ሰራዊት ሆኛለሁ። 11ከወንድሜ ከዔ
ሳው እጅ እንድታድነኝ እለምንሃለሁ፤
መጥቶ እኔንም ሆነ እነዚህን እናቶች ከነ
ልጆቻቸው ያጠፋናል ብዬ ፈርቻለሁና፤
12ነገር ግን፣ አንተ ራስህ፣ 'አበለጽግሃለሁ፤
ዘርህንም ሊቈጠር እንደማይቻል እንደ ባሕር
አሸዋ አበዛዋለሁ' ብለኸኛል።"

13በዚያችም ሌሊት ያዕቆብ እዚያው አደረ፤
ካለው ሀብት ለወንድሙ ለዔሳው እጅ መንሻ
እነዚህን መረጠ:- 14ሁለት መቶ እንስት ፍየ
ሎችና ሃያ አውራ ፍየሎች፣ ሁለት መቶ
እንስት በጎችና ሃያ አውራ በጎች፣ 15ሠላሳ
የሚያጠቡ ግመሎች ከነግልገሎቻቸው፣ አርባ
ላሞችና ዐሥር ኮርማዎች፣ ሃያ እንስት አህ
ዮችና ዐሥር ተባት አህዮች። 16እነዚህንም
በየመንጋው ለይቶ፣ የሚነዱአቸውን ጠባ
ቂዎች መደበላቸው፤ ጠባቂዎቹንም፣ "እና
ንተ ቀድማችሁኝ ሂዱ፣ መንጋዎቹንም አራ
ርቃችሁ ንዱአቸው" አላቸው።

17ቀድሞ የሚሄደውንም እንዲህ ሲል አዘ
ዘው፤ ዔሳው አግኝቶህ፣ 'የማን ነህ? ወዴ
ትስ ትሄዳለህ? የምትነዳውስ ይህ ሁሉ ከብት
የማን ነው?' ብሎ ቢጠይቅህ፣ 18'የአገልጋ
ይህ የያዕቆብ ናቸው፤ ለጌታዬ ለዔሳው እጅ
መንሻ የሰደዳቸው ናቸው፤ እርሱም ከበስተ
ኋላችን እየመጣ ነው' ብለህ ንገረው፣"

19እንዲሁም ሁለተኛውን፣ ሦስተኛውንና
መንጎችን የሚነዱትን ሌሎቹንም ሁሉ እን
ዲህ ሲል አዘዛቸው፤ "ዔሳውን ስታገኙት
ይህንኑ ትነግሩታላችሁ፤ 20በተለይም አገል
ጋይህ ያዕቆብ ከኋላችን እየመጣ ነው' ማለ
ትን አትዘንጉ።" ይህንም ያዘዘው፣ "ዔሳው
ከእኔ ጋር ከመገናኘቱ በፊት እጅ መን
ሻዬ አስቀድሞ ቢደርሰው ምናልባት ልቡ ይራ
ራና በሰላም ይቀበለኛል" ብሎ ስላሰበ
ነበር። 21ስለዚህ የያዕቆብ እጅ መንሻ ከእ
ርሱ አስቀድሞ ተላከ፤ እርሱ ራሱ ግን
እዚያው በሰፈሩበት ቦታ አደረ።

31፥50 ዘፍ16፥6፤ 21፥30፤ዘጸ4፥26፤31፥19፤ኢሱ24፥27፤መሳ 11፥10፤1ሳሙ12፥5፤ 20፥14፡23፡42፤ኢዮ 16፥19፤ኤር7፥11፤ 29፥23፤42፥5፤ሚክ 1፥2
31፥51 ቊ46፤ዘፍ 28፥18
31፥52 ቊ 7:46፤ ዘፍ21፥30፤26፥29
31፥53 ቊ42፤ዘፍ 11፥27፤16፥5፤21፥ 23፡27፤24፥12
31፥54 ዘፍ26፥30፤ 46፥1፤ዘፀ24፥5፤ዘሌ 3፥1
31፥55 ቊ28፤ዘፍ 18፥33፤24፥60፤ዘፀ 39፥43፤ሩት1፥9
32፥1 ዘፍ16፥11፤ 2ነገ6፥16-17፤1ዜና 21፥15፤መዝ34፥7፤35፥5፤91፥11፤ዳን6፥22 19፥32፤1ነገ2፥8፤4፥14 ፤1ዜና6፥80
32፥2 ዘፍ28፥17፤ ኢሱ13፥26፡30፤21፥ 38፤2ሳሙ2፥8፡29፤ 17፥24
32፥3 ዘፍ14፥6፤25፥ 30፤27፥41-42፤36፥ 16፤ዘኍ21፥21፤24፥ 18፤መሳ11፥17
32፥4 ዘፍ18፥3፤ 24፥9፤31፥41
32፥5 ዘፍ12፥16፤ 24፥9፤33፥8፡10፡15፤3 4፥11፤47፥25፡29፤ 50፥4፤ሩት2፥13
32፥6 ዘፍ33፥1
32፥7 ቊ10:11፤ ዘፍ33፥1፤35፥3፤መዝ 4፥1፤77፥2፤107፥6
32፥9 ዘፍ24፥12፤ 26፥3፤28፥13፤ 31፥12
32፥10 ቊ7፤ዘፍ 24፥27፤38፥18፤ 47፥31፤ዘኍ17፥2
32፥11 ቊ7፤ዘፍ 27፥41፤43፥18፤መዝ 59፥2
32፥12 ዘፍ12፥2፤ 13፥14፤22፥17፤1ነገ 4፥20፡29፤ሆሴ1፥10፤ ሮሜ9፥27
32፥13 ቊ13-15፡ 18፡20፡21፤ዘፍ33፥10 ፤43፥11፡15፡25፡26፤ 1ሳሙ16፥20፤ምሳ 18፥16፤21፥14
32፥14 ዘኍ7፥88
32፥15 ዘፍ13፥2፤ 42፥26፤45፥23
32፥16 ዘፍ33፥8
32፥18 ቊ13፤ዘፍ 18፥3
32፥20 ቊ13፤ዘፍ 18፥3፤33፥10፤ዘፀ28፥ 38፤ዘሌ1፥4፤1ሳሙ 9፥7፤25፥19፤2ነገ8፥8፤ኤር40፥5፤ሚል1፥8
32፥21 ቊ31

[ዡ]2 *መሃናይም* ማለት *ሁለት ጐራ* ማለት ነው
[ዩ]7 ወይም *ጐራ*፤ በቊ 10 ላይ ያለውም እንዲሁ
[ዩ]8 ወይም *ጐራ*

### ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር የገጠመው ትግል

22በዚያች ሌሊት ያዕቆብ ተነሣ፤ ሁለቱን
ሚስቶቹን እንዲሁም ሁለቱን ሴት አገልጋ
ዮቹንና ዐሥራ አንድ ልጆቹን ይዞ በያቦቅ
መልካ ተሻገረ። 23ወንዙን አሻግሮ ከሸኛ
ቸው በኋላ፣ ጓዙን ሁሉ ሰደደ። 24ያዕቆብ
ግን ብቻውን እዚያው ቀረ፤ አንድ ሰውም
እስኪነጋ ድረስ ሲታገለው አደረ። 25ያም
ሰው ያዕቆብን ታግሎ ማሸነፍ እንዳቃተው
በተረዳ ጊዜ፣ የጭኑን ሹልዳ ነካው፤ በግብ
ግቡም የያዕቆብ ጭን ከመጋጠሚያው ላይ
ተናጋ። 26በዚያን ጊዜ ሰውየው፣ "እንግዲህ
መንጋቱ ስለ ሆነ ልቀቀኝና ልሂድ" አለው።
ያዕቆብም፣ "ካልባረክኸኝ አልለቅህም"
አለው።
27ሰውየውም፣ "ስምህ ማን ነው?" አለው።
እርሱም፣ "ያዕቆብ ነው" አለ።
28ሰውየውም፣ "ከእግዚአብሔርም (ኤሎሂም)፣ ከሰ
ዎችም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና ከእንግዲህ
ስምህ እስራኤል[ጀ] እንጂ፣ ያዕቆብ አይባልም"
አለው።
29ያዕቆብም፣ "እባክህ ስምህን ንገረኝ"
ብሎ ጠየቀው።
ሰውዬውም፣ "ስሜን ለማወቅ ለምን ፈለ
ግህ?" አለው፤ በዚያም ስፍራ ባረከው።
30ስለዚህ ያዕቆብ፣ "እግዚአብሔርን (ኤሎሂም) ፊት
ለፊት አይቼ እንኳ ሕይወቴ ተርፋለች" ሲል፣
የዚያን ቦታ ስም ጵኒኤል[ገ] አለው።
31ጵኒኤልንም[ጠ] እንዳለፈ ፀሓይ ወጣችበት፤
እርሱም በጭኑ ምክንያት ያነክስ ነበር።
32ከዚህም የተነሣ የእስራኤል ልጆች እስከ
ዛሬ ድረስ ሹልዳን ከጭኑ ጋር የሚያገናኘ
ውን ሥጋ አይበሉም፤ ምክንያቱም በጭኑ
መጋጠሚያ ላይ ያለው የያዕቆብ ሹልዳ
ተነክቶ ነበር።

### የያዕቆብና የዔሳው መገናኘት

33 ያዕቆብ አሻግሮ ተመለከተ፤ እነሆ
ዔሳው አራት መቶ ሰዎች አስከትሎ
እየመጣ ነበር። ስለዚህ ልጆቹን ለልያ፣
ለራሔልና ለሁለቱ አገልጋዮች አከፋፈላ
ቸው። 2ከዚያም ሁለቱን አገልጋዮች ከነል
ጆቻቸው አስቀደመ፤ ልያንና ልጆቿንም
አስከተለ፤ ራሔልንና ዮሴፍን ግን ከሁሉ
ኋላ እንዲሆኑ አደረገ። 3እርሱ ራሱም
ቀድሞአቸው ሄደ፤ ወንድሙም ዘንድ እስ
ኪደርስ ድረስ ሰባት ጊዜ ወደ መሬት
ለጥ ብሎ እጅ ነሣ።
4ዔሳው ግን ሊገናኘው ወደ እርሱ ሮጦ
ሄዶ ዐቀፈው፤ በዐንገቱም ላይ ተጠምጥሞ
ሳመው፤ ሁለቱም ተላቀሱ። 5ከዚያም ዔሳው
ቀና ብሎ ሲመለከት ሴቶቹንና ልጆቹን
አየ፤ እርሱም፣ "እነዚህ አብረውህ ያሉት
እነማን ናቸው?" ብሎ ጠየቀው።
ያዕቆብም መልሶ፣ "እነዚህማ እግዚአብሔር
(ኤሎሂም) በቸርነቱ ለእኔ ለአገልጋይህ የሰጠኝ
ልጆች ናቸው" አለው።
6በዚህ ጊዜ ሁለቱ ሴት አገልጋዮችና
ልጆቻቸው ቀርበው እጅ ነሡ፤ 7ከዚያም
ልያና ልጆቿ መጥተው እጅ ነሡ፤ በመ
ጨረሻም ዮሴፍና ራሔል መጡ፤ እነርሱም
ቀርበው እጅ ነሡ።
8ዔሳውም፣ "ወደ እኔ ተነድቶ የመጣው
ይህ ሁሉ መንጋ ምንድን ነው?" አለው።
እርሱም፣ "ጌታዬ ሆይ፤ በአንተ ዘንድ
ሞገስ ባገኝ ብዬ ነው" አለው።
9ዔሳው ግን፣ "ወንድሜ ሆይ፤ እኔ በቂ
አለኝ፤ የራስህን ለራስህ አድርገው" አለው።
10ያዕቆብም፣ "የለም፣ እንዲህ አይደ
ለም፤ በአንተ ዘንድ ሞገስ አግኝቼ እንደ
ሆነ፣ እጅ መንሻዬን ተቀበል፤ በመልካም
ሁኔታ ተቀብለኸኝ ፊትህን ማየት መቻሌ
ራሱ፣ የእግዚአብሔርን (ኤሎሂም) ፊት የማየት
ያህል እቈጥረዋለሁ። 11እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
በቸርነቱ አሟልቶ ስለ ሰጠኝ የሚያስፈልገኝ
ሁሉ አለኝና ያቀረብኹልህን እጅ መንሻ
እባክህ ተቀበለኝ" አለው። ያዕቆብ አጥብቆ
ስለ ለመነው፣ ዔሳው እጅ መንሻውን ተቀ
በለ።
12ዔሳውም "በል ተነሥና ጕዟችንን እን
ቀጥል፤ እኔም እሄዳለሁ" አለው።
13ያዕቆብ ግን እንዲህ አለው፤ "ጌታዬ፣
እንደምታየው ልጆቼ ይህን ያህል የጠኑ
አይደሉም፣ ለሚያጠቡት በጎችና ጥገቶች
እንክብካቤ ማድረግ አለብኝ፤ እንስሳቱ
ለአንዲት ቀን እንኳ በጥድፊያ ቢነዱ
በሙሉ ያልቃሉ። 14ስለዚህ ጌታዬ፣ አንተ
ቀድመኸኝ ሂድ፤ እኔም በምነዳቸው እን
ስሳትና በልጆቼ ጕዞ ዐቅም ልክ እያዘገ
ምሁ ሴይር ላይ እንገናኛለን።"
15ዔሳው፣ "እንግዲያስ ከሰዎቼ ጥቂቶቹን
ልተውልህ" አለው።
ያዕቆብ ግን፣ "ለምን ብለህ? በአንተ ዘንድ
ሞገስ ማግኘቴ ብቻ ይበቃኛል" አለው።
16ስለዚህ ዔሳው በዚሁ ዕለት ወደ
ሴይር ለመመለስ ተነሣ። 17ያዕቆብ ግን ወደ
ሱኮት[ጨ] ሄደ፤ እዚያም ለራሱ መጠለያ፣
ለከብቶቹም በረት ሠራ፤ ከዚህም የተነሣ
የቦታው ስም ሱኮት ተባለ።

[ጀ]28 *እስራኤል* ማለት *ከእግዚአብሔር ታገለ* ማለት ነው።
[ገ]30 *ጵኒኤል* ማለት *የእግዚአብሔር ፊት* ማለት ነው።
[ጠ]31 በዕብራይስጥ *ጵኑኤል* ማለት ሲሆን *የጵኒኤል* አማራጭ ትር ጕም ነው። [ጨ]17 *ሱኮት* ማለት *መጠለያዎች* ማለት ነው።

32፥22 ዘፍ30፥24፤ ዘኍ21፥24፤ዘዳ2፥37፤ 3፥16፤ኢሱ12፥2
32፥23 ዘፍ26፥14
32፥24 ዘፍ18፥2፤ ዳን10፥8
32፥25 ቍ32
32፥26 ሆሴ12፥4
32፥27 ዘፍ25፥26
32፥28 ዘፍ17፥5፤ 30፥8፤ኢሳ1፥26፤56፥ 5፤60፥14፤62፥2፡4፡ 12፤65፥15
32፥29 ዘፍ25፥11፤ 35፥9፤48፥3፤ዘፀ3፥13 ፤6፥3፤መሳ13፥17፡18
32፥30 ዘፍ16፥13፤ 1ቆሮ13፥12
32፥31 መሳ8፥9
32፥32 ቍ25
33፥1 ዘፍ32፥6፡7
33፥2 ቍ6፤ዘፍ 30፥24
33፥3 ቍ6፡7፤ዘፍ 17፥3፤37፥7-10፤42፥ 6፤43፥26፤44፥14፤ 48፥12፤1ሳሙ20፥ 41፤2ነገ5፥10፡14
33፥4 ዘፍ27፥41- 42፤29፥11፤ሉቃ 15፥20
33፥5 ዘፍ18፥3፤48፥ 9፤መዝ127፥3፤ኢሳ 8፥18
33፥6 ቍ2፡3
33፥7 ቍ2፡3፤ዘፍ 30፥24
33፥8 ዘፍ24፥9፤ 32፥5፡14-16
33፥9 ቍ11፤ዘፍ 13፥6
33፥10 ዘፍ16፥13፤ 30፥27፤32፥5፡13፡20
33፥11 ቍ9፤ዘፍ 19፥3፤30፥26፡43፤ 1ሳሙ25፥27
33፥13 ቍ8፤ኢሳ 40፥11፤ኤር31፥8
33፥14 ዘፍ14፥6፤ ዘፀ12፥38
33፥15 ዘፍ32፥5
33፥16 ዘፍ14፥6
33፥17 ኢሱ13፥ 27፤መሳ8፥5፡6፡8፡ 14-16፤1ነገ7፥46፤ 2ዜና4፥17፤መዝ 60፥6፤108፥7

[18]ያዕቆብ ከሰሜን ምዕራብ መስጴጦምያ
ከተመለሰ በኋላ፣ በከነዓን ወዳለችው ወደ
ሴኬም በደኅና ደረሰ፤[ጰ] በከተማዪቱም
ፊት ለፊት ሰፈረ። [19]ድንኳኑን
የተከለበትንም ቦታ ከኤሞር ልጆች በመቶ
ጥሬ ብር ገዛ፤ ኤሞርም የሴኬም አባት
ነበር። [20]በዚያም መሠዊያ አቁሞ፣ ኤል
ኤሎሂ እስራኤል[ጸ] ብሎ ጠራው።

## የያዕቆብ ልጅ ተደፈረች

34 ልያ ለያዕቆብ የወለደችለት ሴት
ልጅ ዲና፣ አንድ ቀን የዚያን
አገር ሴቶች ለማየት ወጣች። [2]ሴኬም
የተባለው የአገሩ ገዢ የኤዊያዊ የኤሞር
ልጅ ባያት ጊዜ ይዞ በማስገደድ ደፈራ
ት። [3]ልቡ በያዕቆብ ልጅ በዲና ተማረከ፤
ልጂቷንም በጣም ወደዳት፤ በጣፈጠም
አንደበት አናገራት። [4]ሴኬምም አባቱን
ኤሞርን፣ “ይህ ችን ልጅ አጋባኝ”
አለው።

[5]ያዕቆብ፣ ልጁን ዲናን ሴኬም እንዳስነ
ወራት ሰማ፤ በዚህ ጊዜ ወንዶች ልጆቹ
ከብቶቹን በመስክ ያግዱ ነበር፤ ያዕቆብም
ልጆቹ እስኪመለሱ ድረስ ታግሦ ቈየ።

[6]ከዚያም የሴኬም አባት ኤሞር፣ ያዕቆ
ብን ሊያነጋግረው ወጣ። [7]የያዕቆብ ወን
ዶች ልጆችም የተፈጸመውን ድርጊት እንደ
ሰሙ ወዲያውኑ ከመስክ መጡ፤ ሴኬም
መደረግ የማይገባውን አስነዋሪ ነገር በእስ
ራኤል ላይ በመፈጸም፣ የያቆብን ልጅ ስለ
ደፈረ ዐዘኑ፤ ክፉኛም ተቈጡ።

[8]ኤሞር ግን እንዲህ አላቸው፤ “ልጄ ሴኬም
ልቡ በልጃችሁ ፍቅር ተነድፎአል፤ እባካችሁ
እንዲያገባት ፍቀዱለት። [9]በጋብቻ እንተሳ
ሰር፣ ሴት ልጃችሁን ስጡን፣ የእኛንም ሴቶች
አግቡ። [10]አብራችሁንም መኖር ትችላላችሁ፤
አገራችን አገራችሁ ናት፤ ኑሩባት፤ ነግዱባት፤[ፀ]
ሀብት ንብረትም አፍሩባት።”

[11]ሴኬም ደግሞ የዲናን አባትና ወንድ
ሞቿን እንዲህ አላቸው፤ “በእናንተ ዘንድ
ሞገስ ላግኝ እንጂ የተጠየቅሁትን ሁሉ እሰ
ጣለሁ፤ [12]ጥሎሽ ብትሉኝ ጥሎሽ፣ ስጦታ
ብትሉም የፈለጋችሁትን ያህል እሰጣለሁ፣
ብቻ ልጂቱን እንዳገባ ፍቀዱልኝ።”

[13]የያዕቆብ ወንዶች ልጆችም፣ በእኅታቸው
በዲና ላይ ስለ ተፈጸመው ነውር፣ የሆዳቸ
ውን በሆዳቸው ይዘው፣ ለሴኬምና ለአባቱ
ለኤሞር መልስ ሰጡ፤ [14]እንዲህም አሉአቸው፤
“እኅታችንን ላልተገረዘ ሰው ብንሰጥ ውርደት
ስለሚሆንብን፣ እንዲህ ያለውን ነገር አናደ
ርገውም። [15]ሆኖም የምንስማማበት አንድ
መንገድ ብቻ አለ፤ ይህም ወንዶቻችሁን ሁሉ
ገርዛችሁ እኛን የመሰላችሁ እንደ ሆን ነው።
[16]ከዚያ በኋላ ሴቶች ልጆቻችንን እንድርላ
ችኋለን፤ አብረን እንኖራለን፤ አንድ ሕዝ
ብም እንሆናለን። [17]በመገረዙ የማትስማሙ
ከሆነ ግን ልጃችንን[ፊ] ይዘን እንሄዳለን።”

[18]ያቀረቡትም ሐሳብ ለኤሞርና ለልጁ
ለሴኬም መልካም መስሎ ታያቸው። [19]ከአ
ባቱ ቤተ ሰብ ሁሉ እጅግ የተከበረው ይህ
ወጣት የያዕቆብን ልጅ እጅግ ወዶአት
ስለ ነበር፣ ያሉትን ለማድረግ ጊዜ አልወ
ሰደበትም። [20]ስለዚህ ኤሞርና ልጁ ሴኬም
ይህንኑ ለወገኖቻቸው ለመንገር ወደ ከተማ
ቸው በር ሄዱ፤ [21]እንዲህም አሏቸው፤ “እነዚህ
ሰዎች ወዳጆቻችን ናቸው፤ በአገራችን እን
ዲኖሩ፣ ተዘዋውረውም እንዲነግዱ እንፍ
ቀድላቸው፤ ምድሪቱ እንደሆን ለእኛም
ለእነርሱም ትበቃለች። ሴቶች ልጆቻቸ
ውን እናገባለን፤ እነርሱም የእኛን ሴቶች
ያገባሉ። [22]ሆኖም ሰዎቹ ከእኛ ጋር እንደ አንድ
ሕዝብ ሆነው አብረውን ለመኖር ፈቃደ
ኞች የሚሆኑት፣ የእኛ ወንዶች እንደ እነ
ርሱ የተገረዙ እንደ ሆን ብቻ ነው። [23]ታዲ
ያ እንዲህ ብናደርግ ከብታቸው
ንብረታቸው፣ እንስሶቻቸው ሁሉ የእኛው
ይሆኑ የለምን? ስለዚህ ባሉት እንስማማ፤
እነርሱም አብረውን ይኑሩ።”

[24]ከከተማዪቱ በር ውጪ የተሰበሰቡት
ሁሉ በኤሞርና በልጁ በሴኬም ሐሳብ ተስ
ማሙ፤ በከተማዪቱም ያሉት ወንዶች ሁሉ
ተገረዙ።

[25]በሦስተኛውም ቀን የሁሉም ቍስል
ገና ትኵስ ሳለ ከያዕቆብ ልጆች ሁለቱ፣
የዲና ወንድሞች ስምዖንና ሌዊ፣ ሰይፋቸ
ውን መዘው ሳይታሰብ ወደ ከተማዪቱ
ገብተው ወንዶቹን በሙሉ ገደሏቸው።
[26]ኤሞርንና ሴኬምንም በሰይፍ ገድለው፣
እኅታቸውን ዲናን ከሴኬም ቤት አውጥ
ተው ይዘዋት ተመለሱ። [27]የያዕቆብ ልጆች
ሁሉ በሬሳ ላይ እየተረማመዱ እኅታቸው
የተደፈረችበትን ከተማ[ፐ] ዘረፉ። [28]የበግና
የፍየል መንጎቻቸውን፣ ከብቶቻቸውንና አህ
ዮቻቸውን እንዲሁም በከተማዪቱና በአካ
ባቢው የሚገኘውን ንብረታቸውን ሁሉ
ወሰዱባቸው፤ [29]ሀብታቸውን ሁሉ ዘርፈው
ሴቶቻቸውንና ሕፃኖቻቸውን ሁሉ ማርከው
በየቤቱ ያገኙትን ሁሉ ይዘው ሄዱ።

33፥18 ዘፍ25፥20፤ 12፥6
33፥19 ዘፍ12፥8፤ 34፥2:10፡16፡21፤47፥27፤ኢሱ24፥32፤መሳ 9፥28፤ዮሐ4፥5፤ሐሥ 7፥16
33፥20 ዘፍ4፥26፤ 8፥20
34፥1 ዘፍ30፥21
34፥2 ዘፍ10፥17፤ 33፥19፤ ዘዳ21፥14፤ 2ሳሙ13፥14
34፥3 ቍ19፡26፤ ዘፍ24፥67፤50፥21፤ ኢሳ14፥1፤40፥2
34፥4 ዘፍ21፥21
34፥5 ቍ2፡13፡27፤ ዘፍ35፥22፤49፥4፤ዘዳ 27፥20፤33፥6፤1ዜና 5፥1
34፥6 መሳ14፥2-5
34፥7 ዘፍ20፥9፤39፥19፤49፥6-7፤ዘዳ22፥21፤መሳ19፥23፤20፥6፤2ሳሙ12፥5፤13፥12:21፤አስ7፥7፤ምሳ6፥34፤ኤር29፥23፤ 1ቆሮ5፥2
34፥8 ዘፍ21፥21፤ ዘዳ21፥11
34፥9 ቍ16፡21፤ ዘዳ7፥3፤ኢሱ23፥12
34፥10 ቍ23፤ዘፍ 13፥9፤33፥19፤42፥34፤ 46፥34፤47፥6፡27
34፥11 ዘፍ32፥5
34፥12 ዘፀ22፥16፤ ዘዳ22፥29፤1ሳሙ 18፥25
34፥13 ቍ5፤ዘፍ 27፥36
34፥14 ዘፍ17፥14፤ መሳ14፥3፤1ሳሙ31፥ 4፤ኢሳ52፥1
34፥15 ቍ22፤ዘፀ 12፥48፤1ሳሙ11፥2
34፥16 ቍ9፤ዘፍ 33፥19 34፥19 ቍ3፤ ዘፍ49፥3፤ 1ዜና11፥21
34፥20 ዘፍ18፥1
34፥21 ቍ9፤ዘፍ 33፥19
34፥22 ቍ15
34፥23 ቍ10፡28፤ ዘፍ12፥16
34፥24 ዘፍ18፥1
34፥25 ዘፍ29፥33፡ 34፤49፥5፡7፤ኢሱ5፥8፤ መሳ18፥7፡10፡27፤ሕ ዝ38፥11፤ሚል2፥16
34፥26 ቍ3፡7፤ ዘፍ48፥22
34፥27 ቍ5፤2ነገ 21፥14
34፥28 ቍ23፤ዘፍ 43፥18
34፥29 ዘፍ31፥26፤ ዘኍ14፥3፤31፥9፡53፤ ዘዳ2፥35፤ኢሱ7፥21፤
2ነገ8፥12፤ኢሳ13፥16፤ሰቆ5፥11፤አሞ1፥13፤ዘካ14፥2

[ጰ]18 ወይም *ሳሌም ደረሰ*
[ጸ]20 *ኤል ኤሎሄ እስራኤል* ማለት *የእስራኤል አምላክ እግዚ አብሔር* ወይም *የእስራኤል አምላክ ኀያል ነው ማለት* ነው።
[ፀ]10 ወይም *በነጻነት መንቀሳቀስ*፤ ቍ 21 ላይ ያለውም
[ፊ]17 በዕብራይስጥ *ሴት ልጅን* ያመለክታል
[ፐ]27 ወይም *እኅታቸው ተደፍራለችና የያዕቆብ ልጆች...*

30ያዕቆብም ስምዖንና ሌዊን እንዲህ አላ
ቸው፤ “በዚህ አገር በሚኖሩት በከነዓናውያንና
በፌርዛውያን ዘንድ እንደ ጥምብ አስቈጠ
ራችሁኝ፣ ጭንቀትም እንዲደርስብኝ አድ
ርጋችኋል። እኛ በቍጥር አነስተኞች ነን፤
ተባብረው ቢነሡብኝና ቢያጠቁኝ እኔና
ቤተ ሰቤ መጥፋታችን አይደለምን?”
31እነርሱ ግን፣ “ታዲያ፤ እኅታችንን
እንደ ዝሙት አዳሪ ይድፈራት?” አሉት።

## ያዕቆብ ወደ ቤቴል ተመለሰ

35 እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ያዕቆብን፣ “ተነሥና
ወደ ቤቴል ውጣ፤ እዚያም ተቀመጥ፤
ከወንድምህ ከዔሳው ሸሽተህ በሄድህ ጊዜ
ለተገለጠልህ አምላክ (ኤል) በዚያ መሠዊያ
ሥራ” አለው።
2ስለዚህም ያዕቆብ ለቤቱ ሰዎችና አብ
ረውት ለነበሩት ሁሉ እንዲህ አላቸው፤
“በእናንተ ዘንድ ያሉትን ባዕዳን አማል
ክት አስወግዱ፤ ሰውነታችሁን አንጹ፤ ልብ
ሳችሁንም ለውጡ። 3ተነሥተን ወደ ቤቴል
እንውጣ፤ እዚያም በመከራዬ ጊዜ ለሰማኝ፣
በሄድሁበትም ስፍራ ሁሉ ላልተለየኝ አም
ላክ (ኤል) መሠዊያ እሠራለሁ።” 4ስለዚህ በእ
ነርሱ ዘንድ የነበሩትን ባዕዳን አማልክት ሰብ
ስበው፣ የጆሮ ጒትቾቻቸውን አውልቀው
ለያዕቆብ ሰጡት። ያዕቆብም ወስዶ ሴኬም
አጠገብ ካለው ወርካ ዛፍ ሥር ቀበራቸው።
5ያንንም ቦታ ለቀው ሄዱ፤ እግዚአብሔርም
(ኤሎሂም) በዙሪያቸው በነበሩት ከተሞች ሁሉ
ላይ ፍርሀትና ድንጋጤ ስለ ለቀቀባቸው
ያሳደዳቸው አልነበረም።
6ያዕቆብና አብረውት የነበሩት ሰዎች ሁሉ፣
በከነዓን ወደምትገኘው፣ ቤቴል ወደ ተባለ
ችው ወደ ሎዛ ደረሱ። 7ያዕቆብም በዚያ
ስፍራ መሠዊያ ሠርቶ፣ ስሙን ኤል-ቤቴል[ሀ]
አለው፤ ምክንያቱም ከወንድሙ ሸሽቶ በሄደ
ጊዜ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) የተገለጠለት በዚህ
ቦታ ነበር።
8በዚህ ጊዜ የርብቃ ሞግዚት ዲቦራ ሞተች፤
ከቤቴል ዝቅ ብሎ በሚገኘው የዋርካ ዛፍ
ሥር ተቀበረች። ከዚህ የተነሣም ያ ቦታ
አሎንባኩት[ለ] ተባለ።
9ያዕቆብ ከሰሜን ምዕራብ መስጴጦምያ
ከተመለሰ በኋላ፣ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ለያዕቆብ
ዳግመኛ ተገለጠለት፤ ባረከውም። 10እግዚአ
ብሔርም (ኤሎሂም)፣ “እስካሁን ስምህ ያዕቆብ[ሐ]
ነበረ፤ ከእንግዲህ ያዕቆብ ተብለህ አትጠራም፤
ነገር ግን ስምህ እስራኤል[መ] ይባላል” አለው።
ስለዚህም እስራኤል ብሎ ጠራው።
11ደግሞም እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ያዕቆብን እን
ዲህ አለው፤ “እኔ ሁሉን ማድረግ የሚችል[ሠ]

34፥30 ዘፍ13፥7፤ 35፥26፤43፥6፤46፥27፤ ዘፀ1፥5፤5፥21፡23፤6፥9፤ዘኍ11፥11፤ዘዳ10፥22፤26፥5፤1ሳሙ13፥4፤27፥12፤2ሳሙ10፥6፤1ዜና16፥19፤19፥6፤ መዝ105፥12
34፥31 ቍ2
35፥1 ቍ3፡7፤ዘፍ 4፥26፤8፥20፤12፥7፤8፤ 27፥43፤12፥7
35፥2 ዘፍ18፥19፤ 31፥19፤ዘፀ19፥10፡14፤ ዘኍ8፥7፡21፤19፥19፤ ኢሱ24፥14፡15
35፥3 ቍ1፤ዘፍ32፥7፤26፥3፤መሳ2፥15
35፥4 ቍ8፤ ዘፍ12፥6፤24፥22፤ዘፀ 32፥3፤35፥22፤መሳ 8፥24፤ምሳ25፥12
35፥5 ዘፀ15፥16፤ 23፥27፤ዘዳ2፥25፤ኢሱ 2፥9፤1ሳሙ7፥10፡13፥7፤14፥15፤2ዜና14፥14፤17፥10፤20፥29፤ መዝ9፥20፤105፥14፤ኢሳ19፥17፤ዘካ14፥13
35፥6 ዘፍ10፥19፤ 28፥19
35፥7 ቍ1፤ዘፍ8፥20፤28፥13፡19
35፥8 ቍ4፤ዘፍ12፥8፤24፥59፤1ሳሙ10፥3
35፥9 ዘፍ25፥20፤ 28፥13፤32፥29
35፥10 ዘፍ17፥5
35፥11 ዘፍ12፥2፤ 17፥1፡6
35፥12 ዘፍ12፥7፤ 15፥7፤28፥13
35፥13 ዘፍ17፥22
35፥14 ዘፍ28፥18፡22፤ዘፀ29፥40፤ዘሌ23፥13፤ዘኍ6፥15፡17፤15፥5፤28፥7፡14፤2ሳሙ 23፥16፤2ዜና29፥35
35፥15 ዘፍ12፥8
35፥16 ቍ19፤ዘፍ 29፥6፤48፥7፤ሩት1፥2፤4፥11፤1ሳሙ17፥12፤ሚክ5፥2
35፥17 ዘፍ30፥24፤ 38፥28፤ዘፀ1፥15
35፥18 ቍ24፤ዘፍ 42፥4፤43፥16፡29፤45፥12፡14፤49፥27፤ዘኍ 1፥36፤ዘዳ33፥12፤ 1ሳሙ4፥21፤14፥3
35፥19 ቍ16፤ዘፍ 48፥7፤ኢሱ19፥15፤ መሳ12፥8፤17፥7፤19፥1፡18፤ሩት1፥1፡19፤ 1ሳሙ17፥12፤ሚክ 5፥2
35፥20 ኢሱ4፥9፤ 7፥26፤8፥28፤10፥27፤1 ሳሙ6፥18፤10፥2
35፥21 ኢሱ15፥21
35፥22 ዘፍ22፥24፤

አምላክ ነኝ፤ ብዛ ተባዛ፤ ሕዝብና የሕዝ
ቦች ማኅበር ከአንተ ይወጣሉ፤ ነገሥታትም
ከአብራክህ ይከፈላሉ። 12ለአብርሃምና ለይ
ስሐቅ የሰጠኋትን ምድር ለአንተ እሰጥ
ሃለሁ፤ ከአንተም በኋላ ይህችኑ ምድር
ለዘርህ እሰጣለሁ።” 13እግዚአብሔርም (ኤሎሂም)
ከእርሱ ጋር ከተነጋገረበት ስፍራ ወደ ላይ
ወጣ።
14ያዕቆብ እግዚእብሔር (ኤሎሂም) ከእርሱ
ጋር በተነጋገረበት ስፍራ የድንጋይ ሐውልት
አቆመ፤ በሐውልቱ ላይ የመጠጥ ቍርባን
አፈሰሰ፤ ዘይትም አፈሰሰበት። 15ያዕ
ቆብም፣ እግዚአ ብሔር (ኤሎሂም) ከእርሱ ጋር
የተነጋገረበትን ስፍራ ቤቴል[ረ] ብሎ ጠራ
ው።

## የራሔልና የይስሐቅ መሞት

35፥23-26 ተጓ ማብ - 1ዜና 2፥1-2

16ከዚያም ከቤቴል ተነሥተው ሄዱ፤ ኤፍ
ራታ ለመድረስ ጥቂት ሲቀራቸው ራሔ
ልን ምጥ ያዛት፤ ምጡም ጠናባት። 17ምጡ
አስጨንቆአት ሳለ፣ አዋላጇ፣ “አይዞሽ አት
ፍሪ፤ ሌላ ወንድ ልጅ ልትገላገይ ነው”
አለቻት። 18እርሷ ግን ሕይወቷ ልታልፍ
በማጣጣር ላይ ሳለች፣ ልጇን ቤንኦኒ[ሰ]
አለችው፤ አባቱ ግን ብንያም[ሸ] አለው።
19ራሔልም ሞተች፤ ወደ ኤፍራታ በሚ
ወስደው መንገድ በቤተልሔም ተቀበረች።
20ያዕቆብም በራሔል መቃብር ላይ ሐው
ልት አቆመ፤ እስከዛሬም የራሔል መቃ
ብር ምልክት ይኸው ሐውልት ነው።
21እስራኤልም ጒዞውን በመቀጠል ከጋ
ዴር ወንዝ ባሻገር ድንኳኑን ተከለ። 22እስ
ራኤልም በዚያ ምድር ሳለ፣ ሮቤል ከአ
ባቱ ቁባት ከባላ ጋር ተኛ፤ እስራኤልም
ድርጊቱን ሰማ።

ያዕቆብ ዐሥራ ሁለት ልጆች ነበሩት፤ እነ
ርሱም፦

23የልያ ልጆች፦
የያዕቆብ የበኵር ልጅ ሮቤል፣
ስምዖን፣ ሌዊ፣ ይሁዳ፣ ይሳኮር፣
ዛብሎን፤
24የራሔል ልጆች፦
ዮሴፍ፣ ብንያም፤
25የራሔል አገልጋይ የባላ ልጆች፦
ዳን፣ ንፍታሌም፤

[ሀ]7 *ኤል ቤቴል* ማለት *የቤቴል አምላክ* ማለት ነው።
[ለ]8 *አሎንባኩት* ማለት *የለቅሶ ዋርካ* ማለት ነው።
[ሐ]10 *ያዕቆብ* ማለት *ተረከዝ ይይዛል* ማለት ነው፤ በምሳሌያዊ አገላለጽ *ያታልላል* ማለት ነው።
[መ]10 *እስራኤል* ማለት *ከእግዚአብሔር ጋር ታገለ* ማለት ነው።
[ሠ]11 በዕብራይስጥ *ኤልሻዳይ* ማለት ነው።
[ረ]15 *ቤቴል* ማለት *የእግዚአብሔር ቤት* ማለት ነው።
[ሰ]18 *ቤንኦኒ* ማለት *የመከራዬ ልጅ* ማለት ነው።
[ሸ]18 *ብንያም* ማለት *የቀኜ ልጅ* ማለት ነው።

26የልያ አገልጋይ የዘለፋ ልጆች፦
ጋድ፣ አሴር ናቸው።
እነዚህ ያዕቆብ በሰሜን ምዕራብ መስጴ
ጦምያ ሳለ የተወለዱለት ወንዶች ልጆች
ነበሩ።
27ያዕቆብ አባቱ ወዳለበት ወደ መምሬ
መጣ፤ አብርሃምና ይስሐቅ የኖሩባት፣ ቂር
ያትአርባቅ ወይም ኬብሮን የተባለችው ቦታ
ናት። 28ይስሐቅ መቶ ሰማንያ ዓመት
ኖረ፤ 29አርጅቶ፣ ዕድሜ ጠግቦ ሞተ፤ ወደ
ወገኖቹ ተሰበሰበ፤ ልጆቹም ዔሳውና ያዕ
ቆብ ቀበሩት።

**የዔሳው ዝርያዎች**

36፥10-14 ተጓ ማብ - 1ዜና 1፥35-37
36፥20-28 ተጓ ማብ - 1ዜና 1፥38-42

36 ኤዶም የተባለው የዔሳው ትው
ልድ ይህ ነው፦
2ዔሳው ከከነዓን ሴቶች አገባ፤ እነር
ሱም፦ የኬጢያዊው የዔሎን ልጅ ዓዳን፣
የኤዊያዊው የፅብዖን ልጅ ዓና የወለዳት አህ
ሊባማ፣ 3እንዲሁም የነባዮት እኅት የሆን
ችው የእስማኤል ልጅ ቤሴሞት ነበሩ።
4ዓዳ ለዔሳው ኤልፋዝን ወለደችለት፤
ቤሴሞት ደግሞ ራጉኤልን ወለደችለት።
5እንደዚሁም አህሊባማ የዑስን፣ የዕላምንና
ቆሬን ወለደችለት፤ እነዚህ ዔሳው በከነዓን
አገር የወለዳቸው ልጆች ናቸው።
6ዔሳው ሚስቶቹን፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆ
ቹን፣ ቤተ ሰቦቹን በሙሉ እንደዚሁም
የቀንድ ከብቶቹንና ሌሎቹንም እንስሳት
ሁሉ በከነዓን ምድር ያፈራው ሀብት እን
ዳለ ይዞ ከወንድሙ ከያዕቆብ ራቅ ወዳለ
ቦታ ሄደ። 7ብዙ ሀብት ስለነበራቸው
አብረው መኖር አልቻሉም፤ የነበሩበትም
ስፍራ ከከብቶቻቸው ብዛት የተነሣ ሊበቃ
ቸው አልቻለም። 8ስለዚህ ኤዶም የተባ
ለው ዔሳው መኖሪያውን በተራራማው አገር
በሴይር አደረገ።
9በሴይር ተራራማ አገር የሚኖሩ የኤዶ
ማውያን አባት፣ የዔሳው ዝርያዎች እነዚህ
ናቸው፤
10የዔሳው ልጆች ስም፦
የዔሳው ሚስት የዓዳ ልጅ ኤልፋዝና
የዔሳው ሚስት የቤሴሞት ልጅ ራጉኤል፤
11የኤልፋዝ ልጆች፦
ቴማን፣ ኦማር፣ ስፎ፣ ጎቶምና ቄኔዝ፤
12የዔሳው ልጅ ኤልፋዝ ትምናዕ የም
ትባል ቁባት ነበረችው፤ እርሷም አማ
ሌቅን ወለደችለት፤ የዔሳው ሚስት
የዓዳ የልጅ ልጆች እነዚህ ናቸው።
13የራጉኤል ልጆች፦
ናሖት፣ ዛራ፣ ሣማና ሚዛህ፤ እነዚህ
ደግሞ የዔሳው ሚስት የቤሴሞት የልጅ
ልጆች ናቸው።
14የፅብዖን የልጅ ልጅ፣ የዓና ልጅ የዔ
ሳው ሚስት አህሊባማ ለዔሳው የወ
ለደቻቸው ልጆች፦
የዑስ፣ የዕላማና ቆሬ፤
15ከዔሳው ዝርያዎች እነዚህ የነገድ አለ
ቆች ነበሩ፤
የዔሳው የበኵር ልጅ የኤልፋዝ ልጆች፦
አለቃ ቴማን፣ አለቃ ኦማር፣ አለቃ
ስፎ፣ አለቃ ቄኔዝ፣ 16አለቃ ቆሬ፣[ቀ]
አለቃ ጎቶምና አለቃ አማሌቅ፤ እነ
ዚህ በኤዶም ምድር ከኤልፋዝ የተ
ገኙ የነገድ አለቆች፣ የዓዳ የልጅ
ልጆች ነበሩ።
17የዔሳው ልጅ ራጉኤል ልጆች፦
አለቃ ናሖት፣ አለቃ ዛራ፣ አለቃ
ሣማና አለቃ ሚዛህ፤ እነዚህ በኤዶም
ምድር ከራጉኤል የተገኙ የነገድ
አለቆች፣ የዔሳው ሚስት የቤሴሞት
የልጅ ልጅ ነበሩ።
18የዔሳው ሚስት የአህሊባም ልጆች፦
አለቃ የዑስ፣ አለቃ የዕላማና፣ አለቃ
ቆሬ፤ እነዚህ ከዓና ልጅ፣ ከዔሳው
ሚስት ከአህሊባማ የተገኙ የነገድ አለ
ቆች ነበሩ። 19እነዚህም ኤዶም የተ
ባለው የዔሳው ልጆችና የነገድ አለ
ቆቻቸው ነበሩ።
20በዚያች ምድር ይኖሩ የነበሩ የሖሪው
የሴይር ልጆች እነዚህ ነበሩ፦
ሎጣን፣ ሦባል፣ ፅብዖን፣ ዓና፣ 21ዲሶን፣
ኤጽርና ዲሳን፤ እነዚህ በኤዶም የነ
በረው የሴይር ልጆች፣ የሖሪውያን
የነገድ አለቆች ነበሩ።
22የሎጣን ልጆች፦
ሖሪና ሔማም፤[በ] የሎጣንም እኅት ቲም
ናዕ ትባል ነበር።
23የሦባል ልጆች፦
ዓልዋን፣ ማኔሐት፣ ዔባል፣ ስፎና
አውናም፤
24የፅብዖን ልጆች፦
አያና ዓና፤ ይህ ዓና የአባቱን የፅብ
ዖንን አህዮች ሲጠብቅ፣ የፍል ውሃ
ምንጮችን[†] በምድረ በዳ ያገኘ
ሰው ነው።

[ቀ]16 ከማሶሬቲኩ ጽሑፍ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን በአሪተ ሳምራ ውያን ግን (በተጨማሪ ዘፍ 36፥11 እና 1ዜና 1፥36 ይመ) ውስጥ "ቆሬ" የሚለው ቃል የለም
[በ]22 *ሔማም* የሚለው የዕብራይስጥ ቃል *ሖማም* ለሚለው ቃል አማራጭ ትርጉም ነው (1ዜና 1፥39 ይመ)።
[†]24 ከቩልጌት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ሱርስቱ ግን *የተገኘ ውሃ* ይለዋል፤ በዕብራይስጥ የዚህ ቃል ትርጉም አይታወቅም።

29፥29፤34፥5፤ዘሌ 18፥8
**35፥23** ዘፍ29፥16፤ 43፥33፤46፥8፤29፥35፤ 30፥20
**35፥24** ቍ18፤ ዘፍ30፥24
**35፥25** ዘፍ30፥8፤ 37፥2
**35፥26** ዘፍ25፥20፤ 30፥11፡13፤34፥30፤ 37፥2፤ዘፀ1፥1-4
**35፥27** ዘፍ13፥18፤ 17፥8፤23፥2፤31፥18፤ ኢሱ15፥54፤መሳ1፥ 10፤ነህ11፥25
**35፥28** ዘፍ25፥7፡20
**35፥29** ዘፍ15፥15፤ 23፥20፤25፥8፡9
**36፥1** ዘፍ2፥4፤ 25፥30
**36፥2** ቍ14፡18፡ 24፡25፤ዘፍ10፥17፤ 26፥34፤28፥8-9፤ 1ዜና1፥40
**36፥3** ቍ4፡10፡13፡ 17፤ዘፍ25፥13
**36፥4** ቍ3፤1ዜና 1፥35
**36፥5** ቍ14፡18፤ 1ዜና1፥35
**36፥6** ዘፍ12፥5፤ 27፥39
**36፥7** ዘፍ13፥6
**36፥8** ዘፍ14፥6፤25፥ 30፤ዘዳ2፥4
**36፥9** ቍ1፡43፤ ዘፍ2፥4
**36፥10** ቍ3
**36፥11** ቍ15-16፤ 1ዜና1፥45፤ኢዮ2፥11 ፤4፥1፤ኤር49፥7፡20፤ ሕዝ25፥13፤አሞ1፥ 12፤አብ1፥9፤ዕን3፥3
**36፥12** ቍ16፤ዘፍ 22፥24፤ዘፀ17፥8፡16፤ ዘኍ24፥20፤ዘዳ25፥17 ፡19፤1ሳሙ15፥2፤ 27፥8
**36፥13** ቍ3
**36፥14** ቍ2፡5
**36፥15** ቍ11፡19፡ 40፤ዘፀ15፥15፤ኢዮ 2፥11፤ኤር49፥7፤ሕዝ 25፥13፤አሞ1፥12፤ ዕን3፥3
**36፥16** ቍ11፡12፤ ዘፍ32፥3፤ዘፀ15፥15፤ ዘኍ20፥14፤33፥37
**36፥17** ቍ3፤1ዜና 1፥37
**36፥18** ቍ2፡5
**36፥19** ቍ15፤ዘፍ 25፥30፤1ዜና1፥35
**36፥20** ቍ29፤ዘፍ 14፥6
**36፥21** ቍ30
**36፥24** ቍ2፤ኢሱ 15፥19፤ኢዮ1፥14

25የዓና ልጆች:-
ዲሶንና የዓና ሴት ልጅ አህሊባማ፤
26የዲሶን[ቸ] ልጆች:-
ሔምዳን፣ ኤስባን፣ ይትራንና ክራን፤
27የኤጽር ልጆች:-
ቢልሐን፣ ዛዕዋንና ዓቃን፤
28የዲሳን ልጆች:-
ዑፅና አራን።
29የሖሪውያን የነገድ አለቆች እነዚህ ነበሩ:-
ሎጣን፣ ሦባል፣ ፅብዖን፣ ዓና፣
30ዲሶን፣ ኤጽርና ዲሳን፤ እነዚህ በሴ
ይር ምድር እንደየነገዳቸው የሖሪው
ያን የነገድ አለ ቆች ነበሩ።

## የኤዶም ነገሥታት

36፥31-43 ተጓ ማብ - 1ዜና 1፥43-54

31ንጉሥ በእስራኤል ከመንገሡ በፊት፣[ኀ]
በኤዶም የነገሡ ነገሥታት እነዚህ ነበሩ:-
32የቢዖር ልጅ ባላቅ በኤዶም ነበር፤
የከተማውም ስም ዲንሃባ ይባል ነበር።
33ባላቅ ሲሞት፣ የባሶራው የዛራ ልጅ ኢዮ
ባብ በምትኩ ነገሠ።
34ኢዮባብ ሲሞት፣ የቴማኒው ሑሳም በም
ትኩ ነገሠ።
35ሑሳም ሲሞት፣ የምድያምን ሰዎች በሞዓብ
ምድር ድል ያደረጋቸው የባዳድ ልጅ ሃዳድ
በምትኩ ነገሠ፤ የከተማውም ስም ዓዊት
ይባል ነበር።
36ሃዳድ ሲሞት፣ የመሥሬቃው ሠምላ በም
ትኩ ነገሠ።
37ሠምላ ሲሞት፣ በወንዙ[ነ] አጠገብ ያለው
የርሆቦቱ ሳኦል በምትኩ ነገሠ።
38ሳኦል ሲሞት፣ የዓክቦር ልጅ በኣልሐናን
በምትኩ ነገሠ።
39የዓክቦር ልጅ በኣልሐናን ሲሞት፣
ሃዳር በምትኩ ነገሠ፤ የከተማውም ስም ፋው
ይባል ነበር፤ የሚስቱም ስም መሂጣብኤል
ሲሆን፣ እርሷም የሜዛሃብ ልጅ መጥሬድ
የወለደቻት ነበረች።
40ከዔሳው የተገኙት የነገድ አለቆች ስም፣
እንደየነገዳቸውና እንደየአገራቸው ይህ ነው:-
ቲምናዕ፣ ዓልዋ፣ የቴት፣ 41አህሊባማ፣
ኤላ፣ ፊኖን፣ 42ቄኔዝ፣ ቴማን፣ ሚብ
ሳር፣ 43መግዲኤልና ዒራም፤ እነዚህ፣
በያዙት ምድር እንደየይዞታቸው ከኤ
ዶም የተገኙ የነገድ አለቆች ነበሩ።
ይህም ዔሳው፣ የኤዶማውያን አባት ነው።

## የዮሴፍ ሕልሞች

37 ያዕቆብ አባቱ በኖረበት በከነዓን ምድር
ተቀመጠ። 2የያዕቆብ ትውልድ ታሪክ
ይህ ነው።
ዮሴፍ የዐሥራ ሰባት ዓመት ወጣት በነ
በረ ጊዜ፣ ከአባቱ ሚስቶች ከባላና ከዘለፋ
ከተወለዱት ወንድሞቹ ጋር የአባቱን በጎ
ችና ፍየሎች ይጠብቅ ነበር። እርሱም ስለ
ወንድሞቹ ድርጊት ለአባቱ መጥፎ ወሬ
ይዞለት መጣ።
3እስራኤል ዮሴፍን በስተርጅናው ስለ
ወለደው፣ ከልጆቹ ሁሉ አብልጦ ይወደው
ነበር፤ በኅብረ ቀለማት ያጌጠ[ኘ] እጀ ጠባ
ብም አደረገለት። 4ወንድሞቹም፣ አባታ
ቸው ከእነርሱ አብልጦ የሚወደው መሆ
ኑን ሲያዩ፣ ዮሴፍን ጠሉት፤ በቅን አን
ደበትም ሊያናግሩት አልቻሉም።
5ዮሴፍም ሕልም አለመ፤ ሕልሙንም
ለወንድሞቹ ሲነግራቸው የባሰ ጠሉት።
6እርሱም እንዲህ አላቸው፤
"ያየሁትን
ሕልም ልንገራችሁ አድምጡኝ 7እኛ ሁላ
ችን በዕርሻ ውስጥ ነዶ እናስር ነበር፤ የእኔ
ነዶ በድንገት ተነሥታ ቀጥ ብላ ቆመች፤
የእናንተም ነዶዎች ዙሪያዋን ከበው ለእኔ
ነዶ ሰገዱላት።"
8ወንድሞቹም፣ "ለካስ በላያችን ለመንገሥ
ታስባለህና! ለመሆኑ አንተ እኛን ልት
ገዛ!" አሉት፤ ስለ ሕልሙና ስለ ተናገረው
ቃል ከፊት ይልቅ ጠሉት። 9እንደ ገናም
ሌላ ሕልም አለመ፤ ለወንድሞቹም፣ "እነሆ፤
ሌላ ሕልም አለምሁ፤ ፀሓይና ጨረቃ፣ ዐሥራ
አንድ ከዋክብትም ሲሰግዱልኝ አየሁ" ብሎ
ነገራቸው።
10ሕልሙን ለአባቱና ለወንድሞቹ በነገራ
ቸው ጊዜ፣ አባቱ "ይህ ያየኸው ሕልም ምን
ድን ነው? እኔና እናትህ ወንድሞችህም በፊትህ
ወደ ምድር ተጐንብሰን በእርግጥ ልንሰ
ግድልህ ነው?" ሲል ገሠጸው። 11ወንድ
ሞቹ ቀኑበት፤ አባቱ ግን ነገሩን በልቡ
ያዘው።

## ወንድሞቹ ዮሴፍን ሸጡት

12ከዚህም በኋላ የዮሴፍ ወንድሞች የአባ
ታቸውን በጎችና ፍየሎች ለማሰማራት
ወደ ሴኬም አካባቢ ሄዱ፤ 13እስራኤልም
ዮሴፍን "እንደምታውቀው ወንድሞችህ
መንጎቹን በሴኬም አካባቢ አሰማርተዋል፤
በል ተነሥ፣ ወደ እነርሱ ልላክህ።" አለው።
ዮሴፍም "ይሁን እሺ" አለው።
14ያዕቆብም፣ "ሂደህ ወንድሞችህም፣ መንጎ
ቹም ደኅና መሆናቸውን አይተህ ወሬያቸ
ውን አምጣልኝ" አለው፤ ከኬብሮንም ሸለቆ
ወደ ሴኬም ላከው።

36፥25 ቍ2
36፥29 ቍ20
36፥30 ቍ21
36፥31 ዘፍ17፥6
36፥33 ኢሳ34፥6፤63፥1፤ኤር49፥13፥22
36፥34 ኤር49፥7፤ሕዝ25፥13፤አብ1፥9
36፥35 ዘፍ19፥37፤25፥2፤ዘኍ21፥11፤22፥1፤ዘጸ1፥5፤መሳ3፥30፤ሩት1፥1፥6
36፥37 ዘፍ26፥22
36፥40 ቍ15
36፥43 ቍ9
37፥1 ዘፍ10፥19፤17፥8
37፥2 ዘፍ2፥4፤30፥24፤35፥25፥26፤41፥46፤46፥32፤1ሳሙ2፥24፤16፥11፤17፥15፤2ሳሙ5፥4፤መዝ78፥71፤አሞ7፥15
37፥3 ቍ23፥31፥32፤ዘፍ17፥5፤25፥28፤43፥27፥34፤44፥20፤45፥22፤1ሳሙ1፥4-5፤2ሳሙ13፥18-19፤አስ2፥9
37፥4 ቍ24፤ዘፍ27፥41፤ሐሥ7፥9
37፥5 ቍ8፥10፤ዘፍ20፥3፤28፥12
37፥7 ቍ9፥10፤ዘፍ27፥29፤42፥6፥9፤43፥26፥28፤44፥14፤50፥18፤ሩት2፥7፥15፤2ሳሙ1፥2፤9፥6
37፥8 ቍ5፤ዘፍ41፥44፤42፥10፤44፥16፥18፤48፥22፤49፥26፤ዘዳ33፥16
37፥9 ቍ7፤ዘፍ28፥12፤ዘዳ4፥19፤17፥3፤ራእ12፥1
37፥10 ቍ5፥7፤ዘፍ9፥25፤33፥3፤ሩት2፥16፤መዝ9፥5፤68፥30፤106፥9፤119፥21፤ኢሳ17፥13፤54፥9፤ዘካ3፥2
37፥11 ዘፍ26፥14፤ሐሥ7፥9፤ሉቃ2፥19፥51
37፥12 ዘፍ12፥6
37፥13 ዘፍ17፥5፤33፥19
37፥14 ዘፍ13፥18፤1ሳሙ17፥18

[ቸ]26 በዕብራይስጥ *ዲሳን፣ የዲሶን* አማራጭ ትርጒም ነው።
[ኀ]31 ወይም *እስራኤላዊ መንግሥት በእነርሱ ላይ ከመንገሡ በፊት*
[ነ]37 የኤፍራጥስ ወንዝ ሊሆን ይችላል
[ኘ]3 በዕብራይስጥ *በኅብረ ቀለማት ያጌጠ* የሚለው ሐረግ ትር
ጒም አይታወቅም፤ በቍ 23 እና 32 ላይ ያለውም እንዲሁ

ዮሴፍም ሴኬም በደረሰ ጊዜ፣ 15ሜዳ ላይ
ወዲያ ወዲህ ሲባዝን አንድ ሰው አግኝ
ቶት "ምን እየፈለግህ ነው?" ሲል ጠየቀው።
16ዮሴፍም፣ "ወንድሞቼን እየፈለግኋቸው
ነው፤ መንጎቻቸውን የት እንዳሰማሩ ልት
ነግረኝ ትችላለህ?" አለው።
17ሰውየውም፣ "ከዚህ ሄደዋል፤ ደግሞም፣
'ወደ ዶታይን እንሂድ' ሲሉ ሰምቻቸዋ
ለሁ" አለው።
ከዚያም ዮሴፍ ወንድሞቹን ፍለጋ ሄደ፣
ዶታይን አቅራቢያም አገኛቸው። 18ወንድ
ሞቹም ዮሴፍ ወደ እነርሱ ሲመጣ በሩቅ
አዩት፤ ወደ ነበሩበትም ስፍራ ከመድረሱ
በፊት ሊገድሉት ተማከሩ።
19እነርሱም እንዲህ ተባባሉ፤ "ያ ሕልም
ዐላሚ መጣ፤ 20ኑ እንግደለውና ከጕድጓ
ዶቹ በአንዱ ውስጥ እንጣለው፤ ከዚያም፣
'ክፉ አውሬ ነጥቆ በላው' እንላለን፤ እስቲ
ሕልሞቹ ሲፈጸሙ እናያለን።"
21ሮቤል ግን ይህን ምክር ሲሰማ ከእጃ
ቸው ሊያድነው ፈለገ እንዲህም አለ፤
"ሕይወቱ በእጃችን አትለፍ፤ 22የሰው ደም
አታፍስሱ፤ እዚህ ምድረ በዳ፣ ጕድጓድ
ውስጥ ጣሉት እንጂ እጃችሁን አታንሡ
በት።" ሮቤል ይህን ያለው ሕይወቱን ከእጃ
ቸው አትርፎ ወደ አባቱ ሊመልሰው አስቦ
ነበር።
23ዮሴፍ ወደ ወንድሞቹ እንደ ደረሰ፣
የለበሳትን በኅብረ ቀለማት ያጌጠች እጀ
ጠባቡን ገፈፉት፤ 24ይዘውም ወደ ጕድጓድ
ጣሉት፤ ጕድጓዱም ውሃ የሌለበት ደረቅ
ነበር።
25ምግባቸውን ለመብላት ተቀመጡ፤ አሻ
ግረው ሲመለከቱም ከገለዓድ የሚመጡ
እስማኤላውያን ነጋዴዎች የግመል ጓዝ
አዩ። ነጋዴዎቹ ሽቶ፣ በለሳን ከርቤ በግ
መሎቻቸው ጭነው ወደ ግብፅ የሚወርዱ
ነበሩ።
26ይሁዳም ወንድሞቹን እንዲህ አላቸው፤
"ወንድማችንን መግደልና አሟሟቱን መደ
በቅ ምን ይጠቅመናል? 27ከዚህ ይልቅ ለእ
ስማኤላውያን ነጋዴዎች እንሽጠው፤ እጃች
ንን ግን በእርሱ ላይ አናንሣ። ምንም ቢሆ
ንኮ ወንድማችን፣ ሥጋችን ነው" ወንድሞ
ቹም በሐሳቡ ተስማሙ።
28የምድያም ነጋዴዎችም እነርሱ ዘንድ
እንደ ደረሱ፣ ወንድሞቹ ዮሴፍን ከጕድጓድ
አውጥተው ለእስማኤላውያን በሃያ ጥሬ ብር
ሸጡላቸው፤ እነርሱም ዮሴፍን ወደ ግብፅ
ወሰዱት።
29ሮቤል ወደ ጕድጓዱ ተመልሶ ሲያይ፣
ዮሴፍን በማጣቱ ልብሱን በሐዘን ቀደደ።

37፥17 2ነገ6፥13
37፥18 1ሳሙ19፥1፤2ዜና24፥21፤መዝ31፥13፡20፤37፥12፡32፤ማቴ12፥14፤ማር14፥1፤ሐሥ23፥12
37፥19 ዘፍ28፥12
37፥20 ቍ22:31-33፤ዘፍ4፥10፤50፥20፤ዘሌ 26፥6፡22፤ዘዳ32፥24፤2ነገ17፥25፤ኤር38፥6-9፤ሕዝ34፥25
37፥21 ዘፍ29፥32፤42፥22
37፥22 ቍ20:29-30
37፥23 ቍ3
37፥24 ቍ4፤ዘፍ49፥23፤ኤር38፥6፤41፥7፤ሕዝ22፥27
37፥25 ቍ28፤ዘፍ16፥11፤31፥21፤39፥1፤43፥11፤ዘፀ30፥23፤መዝ45፥8፤105፥17፤ምሳ7፥17፤ማሕ1፥13፤4፥1፤ኤር8፥22፤22፥6፤46፥11፤ማቴ2፥11
37፥26 ዘፍ4፥10፤29፥35
37፥27 ዘፍ29፥14፤42፥21
37፥28 ቍ36፤ዘፍ16፥11፤25፥2፤39፥1፤45፥4-5፤ዘፀ21፥16፤ዘሌ27፥5፤መዝ105፥17፤ኤር12፥6፤38፥13፤ማቴ26፥15፤ሐሥ7፥9
37፥29 ቍ34፤ዘፍ44፥13፤ዘኍ14፥6፤ ኢሱ7፥6፤2ሳሙ1፥11፤2ነገ2፥12፤5፥7፤11፥14፤22፥11፤ኢዮ1፥20፤2፥12፤ኢሳ36፥22፤37፥1፤ኤር36፥24፤41፥5፤ኢል2፥13
37፥30 ቍ22
37፥31 ቍ3፤ራእ19፥13
37፥32 ቍ3
37፥33 ቍ20፤ዘፍ42፥13፡38፤44፥20፡28
37፥34 ቍ29፤ዘፍ50፥3፡10፡11፤ዘኍ20፥29፤ዘዳ34፥8፤2ሳሙ3፥31፤1ነገ20፥31፤21፥27፤2ነገ6፥30፤19፥1-2፤ኢዮ16፥15፤መዝ69፥11፤ኢሳ3፥24፤15፥3፤22፥12፤32፥11፤37፥1፤ኤር48፥37፤49፥3፤ኢል1፥13
37፥35 ዘፍ29፥31፤42፥38፤44፥22፡2ሳሙ12፥17፡23፤ኢዮ2፥11፤15፥11፤16፥5፤42፥11፤መዝ77፥2፤ኤር31፥15
37፥36 ቍ28፤ዘፍ25፥2፤39፥1፤40፥3፤41፥10፡12፤1ሳሙ22፥14
38፥1 ቍ12:20፤ዘፍ

30ወደ ወንድሞቹም ተመልሶ፣ "ብላቴናው
ጕድጓድ ውስጥ የለም፤ የት አባቴ ል
ሂድ?" አለ።
31ከዚያም የዮሴፍን እጀ ጠባብ ወሰዱ፤
አንድ ፍየልም ዐርደው እጀ ጠባቡን በደሙ
ነከሩት። 32በኅብረ ቀለማት ያጌጠችውን
እጀ ጠባብ ወደ አባታቸው ወስደው፣ "ይህን
ወድቆ አገኘነው፤ የልጅህ እጀ ጠባብ መሆን
አለመሆኑን እስቲ እየው" አሉት።
33እርሱም ልብሱን ዐውቆት፣ "ይህማ የልጄ
እጀ ጠባብ ነው!፤ ክፉ አውሬ በልቶታል፣
በእርግጥም ዮሴፍ ተቦጫጭቋል" አለ።
34ከዚህ በኋላ ያዕቆብ ልብሱን ቀደደ፤
ማቅም ለብሶ ስለ ልጁ ብዙ ቀን አለቀሰ፤
35ወንዶችና ሴቶች ልጆቹም ሁሉ ሊያጽናኑት
መጡ፤ እርሱ ግን ሊጽናና ባለመቻሉ
"በሐዘን እንደ ተኵራመትሁ ልጄ ወዳ
ለበት መቃብር[ሀ] እወርዳለሁ" አለ። ስለ
ልጁም አለቀሰ።
36በዚህ ጊዜ፣ የምድያም[ለ] ነጋዴዎች
ዮሴ ፍን፣ ወደ ግብፅ ወስደው፣ ከፈርዖን
ሹማ ምንት አንዱ ለነበረው ለዘበኞች
አለቃ፣ ለጲጥፋራ ሸጡት።

## ይሁዳና ትዕማር

38 በዚያም ወራት ይሁዳ ከወንድ
ሞቹ ተለይቶ፣ ኤራስ ወደ ተባለ
ዓዶሎማዊ ሰው ወረደ፤ እርሱም ዘንድ
ለመኖር ቤቱ ገባ። 2እዚያም ሳለ፣ ይሁዳ
የከነዓናዊውን የሴዋን ሴት ልጅ አየ፤ እር
ሷንም አግብቶ አብሯት ተኛ፤ 3እርሷም ፀንሳ
ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙም ዔር ተባለ።
4እንደ ገናም ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች፤
ስሙን አውናን አለችው። 5አሁንም ደግማ
ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙንም ሴሎም
ብላ አወጣችለት፤ እርሱንም የወለደችው
ክዚብ በተባለ ቦታ ነበር።
6ይሁዳ የበኵር ልጁን ዔርን፣ ትዕማር
የምትባል ሚስት አጋባው። 7የይሁዳ የበ
ኵር ልጅ ዔር ግን በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ፊት
ክፉ ነበር፤ እግዚአብሔርም (ያህዌ) ቀሠፈው።
8በዚህ ጊዜ ይሁዳ አውናንን፣ "ዋርሳዋ
እንደ መሆንህ ከወንድምህ ሚስት ጋር ሩካቤ
ሥጋ በመፈጸም የወንድምህን ስም የሚያስጠራ
ለት ዘር ተካለት" አለው። 9አውናን ግን
የሚወለደው ልጅ የእርሱን ስም የሚያስጠ
ራ እንደማይሆን ስላወቀ፣ ከወንድሙ
ሚስት ጋር ሩካቤ-ሥጋ በፈጸመ ቍጥር
የወንድ ሙንም ስም የሚያስጠራ ልጅ
እንዳይወልድ

[ሀ]35 በዕብራይስጡ ሲኦል ይለዋል
[ለ]36 ከኦሪተ ሳምራውያን፣ ከሰብዓ ሊቃናት፣ ከቩልጌትና ከሱር
ስት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን የማሶሬቲክ ጽሑፍ ግን ሜዳና
ውያን ይለዋል።

ዘሩን በምድር ላይ ያፈስ ነበር። 10ይህም
በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ክፉ አድራጎት
ሆኖ ስለ ተገኘ፣ እርሱንም እግዚአብሔር
(ያህዌ) በሞት ቀሠፈው።
11ከዚያም ይሁዳ ምራቱን ትዕማርን፣ "ልጄ
ሴሎም ለአካለ መጠን እስኪደርስ ድረስ
ወደ አባትሽ ቤት ሄደሽ መበለት ሆነሽ
ብት ኖሪ ይሻላል" አላት፤ ይህን ያለውም፣
ሴሎም እንደ ወንድሞቹ ተቀሥፎ
ይሞትብኛል ብሎ ስለ ሠጋ ነበር። ትዕማርም
እንዳላት ሄደች፤ በአባቷም ቤት ተቀመጠ
ች።
12ከብዙ ጊዜ በኋላ የሹዓ ልጅ፣ የይሁዳ
ሚስት ሞተች። ይሁዳ ከሐዘኑ ከተጽናና
በኋላ ከዓዶላማዊው ከሒራ ጋር የበጎቹን
ጠጕር የሚሸልቱ ሰዎች ወዳሉበት ወደ ተምና
ሄደ።
13ሰዎቹም ለትዕማር፣ "ዐማትሽ የበጎቹን
ጠጕር ወደሚሸልቱ ሰዎች ዘንድ ወደ ተምና
እየሄደ ነው" አሏት። ይህን እንደ ሰማች
14የመበለትነት ልብሷን አውልቃ፣ ማንነቷ
እንዳይታወቅ ፊቷን በሻሽ ተከናንባ ወደ
ተምና በሚወስደው መንገድ ዳር ባለች ኤና
ይም በተባለች ከተማ መግቢያ ላይ ተቀ
መጠች፤ ይህን ያደረገችው፣ ሴሎም ለአ
ካለ መጠን ቢደርስም፣ እርሷን እንዲያገባ
አባቱ አለ መፈለጉን ስላወቀች ነው።
15ፊቷ በሻሽ ተሸፋፍኖ ሲያያት፣ ይሁዳ
ዝሙት ዐዳሪ መሰለችው። 18ምራቱ መሆኗ
ን ባለማወቁ፣ እርሷ ወዳለችበት ወደ መን
ደሩ ዳር ጠጋ ብሎ፣ "እባክሽ አብሬሽ
ልተኛ" አላት። እርሷም፣ "አብሬህ ብተኛ ምን
ትሰጠኛለህ?" ብላ ጠየቀችው።
17"ከመንጋዬ መካከል አንድ የፍየል ጠ
ቦት እልክልሻለሁ" አላት። እርሷም መልሳ፣
"ጠቦ ቱን እስክትልክልኝ ድረስ ምን መያዣ
ትሰጠኛለህ?" ብላ ጠየቀችው።
18"ታዲያ ምን መያዣ ልስጥሽ?" አላት።
እርሷም፣ "የማኅተም ቀለበትህን ከነማሰሪ
ያው፣ እንደዚሁም ይህን በትርህን ስጠኝ"
አለችው። የጠየቀችውን ሁሉ ሰጣትና አብ
ሯት ተኛ፤ እርሷም ፀነሰች። 19ከዚያም ወደ
መኖሪያዋ ተመልሳ፣ ሻሽዋን አውልቃ እንደ
ወትሮዋ የመበለት ልብሷን ለበሰች።
20ይሁዳ በመያዣ ስም የሰጣትን ዕቃ
ዎች ለማስመለስ የፍየሉን ጠቦት በዓዶሎ
ማዊ ወዳጁ እጅ ላከላት፣ መልእክተኛው
ግን ሴትየዋን ሊያገኛት አልቻለም።
21"በኤናይም ከተማ መግቢያ ከመንገዱ
ዳር የነበረች ያቺ ዝሙት ዐዳሪ የት ደረ
ሰች?" ሲል ጠየቃቸው። ሰዎቹም፣ "በዚህ
አካባቢ ኧረ ምንም ዝሙት ዐዳሪ ታይታ
አትታወቅም" አሉት።
22መልእክተኛውም ወደ ይሁዳ ተመ
ልሶ፣ "ሴቲቱን ላገኛት አልቻልኩም፤
ነዋሪዎቹም 'በዚህ አካባቢ እንደዚህች ያለች
ዝሙት ዐዳሪ የለችም' አሉኝ" ብሎ ነገ
ረው።
23ይሁዳም፣ "እንግዲህ መያዣውን እንደ
ያዘች ትቅር፤ አለዚያ መሣቂያ እንሆና
ለን። ለነገሩማ ይህን ፍየል ላክሁ፤ አን
ተም ፈልገህ አላገኘሃትም" አለ።
24ከሦስት ወር ያህል በኋላ፣ "ምራትህ
ትዕማር ዘማዊ ሆናለች፤ ከዚህም የተነሣ
አርግዛለች" ተብሎ ለይሁዳ ተነገረው።
ይሁዳም፣ "አውጧትና በእሳት ተቃጥላ
ትሙት" አለ።
25እርሷም ተይዛ በምትወሰድበት ጊዜ
ለዐማትዋ፣ "እኔ ያረገዝሁት የእነዚህ ዕቃ
ዎች ባለቤት ከሆነ ሰው ነው" ስትል ላከ
ችበት፤ ደግሞም፣ "የማኅተሙ ቀለበት
ከነማንጠልጠያውና በትሩ የማን እንደ
ሆነ እስቲ ተመልከት" አለችው።
26ይሁዳም ዕቃዎቹን ዐውቆ፣ "ልጄ ሴሎም
እንዲያገባት ባለማድረጌ፣ እርሷ ከእኔ ይልቅ
ትክክል ናት" አለ። ከዚያም በኋላ ከእርሷ
ጋር አልተኛም።
27የመውለጃዋ ጊዜ እንደ ደረሰም ፅንሷ
መንታ መሆኑ ታወቀ። 28በምትወልድበትም
ጊዜ አንደኛው እጁን አወጣ፤ አዋላጇቱም፣
"ይህኛው መጀመሪያ ወጣ" ስትል በእጁ ላይ
ቀይ ክር አሰረችለት፤ 29ነገር ግን፣ እጁን
መልሶ ሲያስገባ ወንድሙ ተወለደ። አዋላ
ጂቱም "አንተ እንዴት ጥሰህ ወጣህ!"
አለች፤ ከዚያም ስሙ ፋሬስ[ኸ] ተባለ። 30ከዚያ
በኋላ እጁ ላይ ቀይ ክር የታሰረለት ወን
ድሙ ተወለደ፣ ስሙም ዛራ[ሠ] ተባለ።

## ዮሴፍና የጲጥፋራ ሚስት

39 በዚህ ጊዜ ዮሴፍ ወደ ግብፅ ተወ
ስዶ ነበር፤ ከፈርዖን ሹማምንት
አንዱ የሆነውም የዘበኞች አለቃ፣ ግብፃዊው
ጲጥፋራ ወደዚያ ከወሰዱት ከእስማኤላው
ያን ነጋዴዎች እጅ ገዛው።
2እግዚአብሔር (ያህዌ) ከዮሴፍ ጋር ነበረ፤
ኑሮው ተቃናለት፤ እርሱም በግብፃዊው አሳ
ዳሪው ቤት ኖረ። 3አሳዳሪውም እግዚአብሔር
(ያህዌ) ከእርሱ ጋር እንዳለና ሥራውንም

29÷35፤2ዜና11÷7፤
ኢሱ12÷15፤15÷35፤
1ሳሙ22÷1፤2ሳሙ
23÷13
**38÷2** ቀኍ12፤1ዜና
2÷3
**38÷3** ቀኍ6፤ዘፍ
46÷12፤ዘኍ26÷19
**38÷4** ቀኍ8፡9፤ዘፍ
46÷12፤ዘኍ26÷19
**38÷5** ዘኍ26÷20፤
1ዜና2÷3፤4÷21
**38÷6** ቀኍ11፡13
**38÷7** ቀኍ10፤ዘፍ
6÷5፤46÷12፤ዘሌ
10÷1-2፤1ዜና2÷3
**38÷8** ዘዳ25÷5-6፤ሩ
ት4÷5፤ማቴ22÷24-28
**38÷10** ቀኍ7፤ዘዳ
25÷7-10
**38÷11** ቀኍ6፡14፡
26፤ዘፍ11÷31፤ሩት
1÷8፤1÷13
**38÷12** ቀኍ1፡2፡14፤
ዘፍ31÷19፤ኢሱ15÷
10፡57፤19÷43፤መሳ
14÷1፡2፤2ዜና28÷18
**38÷13** ቀኍ6፤ዘፍ
31÷19
**38÷14** ቀኍ11፡12፡19
፤ዘፍ24÷65፤ኤር3÷2
**38÷15** መሳ11÷1፤
16÷1
**38÷16** ዘፍ30÷15፤
39÷7፡12፤42÷23፤ዘሌ
18÷15፤20÷12፤ሩት
1÷6፤2ሳሙ13÷11
**38÷17** ቀኍ20፤
መሳ15÷1
**38÷18** ቀኍ25፤ዘፍ
19÷32፤32÷10፤ዘፀ4÷
2፤1ነገ21÷8፤አስ3÷12፤
8÷8፤ማሕ8÷6፤ኢሳ
49÷16፤ኤር22÷24፤
ሐጌ2÷23፤2ቆሮ
1÷22፤ኤፌ1÷13
**38÷19** ቀኍ14
**38÷20** ቀኍ1፡17
**38÷21** ዘፍ19÷5፤
ዘሌ19÷29፤ዘዳ22÷
21፤ 23÷17፤2ነገ
23÷7፤ሆሴ4÷14
**38÷23** ቀኍ18፤ዘፀ
32÷25፤ኢዮ12÷4፤
ኤር20÷7፤ሰቆ3÷14
**38÷24** ዘሌ20÷10፡
14፤21÷9፤ዘዳ22÷21፡
22፤ኢሱ7÷25፤መሳ
15÷6፤1ሳሙ31÷12፤
ኢዮ31÷11፡28፤ሕዝ
16÷38
**38÷25** ቀኍ18
**38÷26** ቀኍ11፤
1ሳሙ24÷17
**38÷27** ዘፍ25÷24
**38÷28** ቀኍ30፤ዘፍ
35÷17
**38÷29** ዘፍ25÷26፤
46÷12፤ዘኍ26÷20፡21
፤ሩት4÷12፡18፤
2ሳሙ5÷20፤6÷8፤
1ዜና2÷4፤9÷4፤ኢሳ28÷21፤ማቴ1÷3 **38÷30** ቀኍ28፤ዘፍ46÷12፤
1ዜና2÷4፤ነህ11÷24 **39÷1** ዘፍ30÷24፤37÷25፡36 **39÷2**
ዘፍ21÷20፡22፤ኢሱ1÷5፤6÷27፤መሳ1÷19፤1ሳሙ18÷14፤ሐሥ7÷9
**39÷3** ቀኍ23፤ዘፍ21÷22፤1ሳሙ18÷14፤2ነገ18÷7፤2ዜና
20÷20፤መዝ1÷3፤128÷2፤ኢሳ33÷6

[ኸ]29 ፋሬስ ማለት ጥሶ መውጣት ማለት ነው
[ሠ]30 ዛራ የሚለው *ደማቅ ቀይ* ወይም *ብሩህ* እንደ ማለት ነው

ሁሉ እንዳከናወለት ባየ ጊዜ፣ [4]ዮሴፍ በእ
ርሱ ዘንድ ሞገስ አገኘ፤ የቅርብ አገልጋዩም
ሆነ፡፡ ጲጥፋራ በቤቱ ላይ ሾመው፤ ያለውንም
ሀብት ሁሉ በኀላፊነት ሰጠው፡፡ [5]ዮሴፍ
በጲጥፋራ ቤትና ባለው ሀብት ሁሉ ላይ
ከተሾመበት ጊዜ ጀምሮ *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) የግብፃዊውን ቤት ባረከ፣ *የእግዚ
አብሔርም* (ያህዌ) በረከት በግቢም በውጭም
ባለው የጲጥፋራ ሀብት ንብረት ሁሉ ላይ
ሆነ። [6]ስለዚህ ጲጥፋራ ባለው ሁሉ ላይ
ሥልጣን ሰጠው፤ የቀረበለትንም ከመመገብ
በስተቀር፣ ማናቸውንም ጕዳይ በዮሴፍ
ላይ ጥሎ ነበር፡፡
ዮሴፍ ጥሩ ቍመና ያለውና መልከ መል
ካም ነበር፤ [7]እያደርም የጌታው ሚስት ዐይኗን
ጣለችበት፤ አፍ አውጥታም፣ "አብረኸኝ
ተኛ" አለችው፡፡
[8]እርሱ ግን ፈቃደኛ አልሆነም፤ እንዲ
ህም አላት፤ "ጌታዬ ያለውን ሁሉ በኀላፊ
ነት ስለ ሰጠኝ፣ በቤቱ ውስጥ ስላለው
ሁሉ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም፡፡
[9]በዚህ ቤት ላይ ከእኔ የበለጠ ኀላፊነት
ያለው ማንም የለም፤ እርሱ ያልሰጠኝ ነገር
ቢኖር፣ አንቺን ብቻ ነው፤ ያውም ሚስቱ
ስለሆንሽ ነው፤ ታዲያ፣ እኔ ይህን ክፉ
ድርጊት ፈጽሜ እንዴት በእግዚአብሔር (ኤሎ
ሂም) ፊት ኀጢአት እሠራለሁ?" [10]ምንም
እንኳ ዮሴፍን በየቀኑ ብትጐተጕተውም፣
አልሰማትም፤ ከእርሷ ጋር መተኛቱ ይቅ
ርና አብሯትም መሆን አልፈቀደም፡፡
[11]አንድ ቀን ዮሴፍ የዕለት ተግባሩን ለማ
ከናወን ወደ ቤት ገባ፤ ከቤቱ አገልጋዮ
ችም አንድም ሰው በቤት ውስጥ አልነ
በረም፡፡ [12]እርሷም ልብሱን ጨምድዳ ይዛ "በል
አብረኸኝ ተኛ" አለችው፡፡ እርሱ ግን ልብ
ሱን እጇ ላይ ጥሎ ሸሽቶ ከቤት ወጣ፡፡
[13]እርሷም ልብሱን እጇ ላይ ጥሎ ሸሽቶ
መውጣቱን ባየች ጊዜ፣ [14]የቤት አገልጋዮቿ
ን
ጠራች፤ እንዲህም አለቻቸው፤ "አያችሁ፤
ለካስ ይህ ዕብራዊ የመጣው መሣለቂያ ሊያ
ደርገን ኖሮአል! እዚህ ድረስ ሰተት ብሎ
ገብቶ ካልተኛሁሽ አለኝ፤ እኔም ጩኸቴን
ለቀቅሁት፤ [15]ለእርዳታ መጮኼን ሲሰማም፣
ልብሱን ከአጠገቤ ጥሎ ሸሽቶ ከቤት
ወጣ፡፡"
[16]ጌታውም ወደ ቤት እስኪመለስ ድረስ፣
ልብሱን አጠገቧ አቆየችው፡፡ [17]ታሪኩንም
እንዲህ ስትል ነገረችው፤ "አንተ ያመጣኸው
ዕብራዊ ባሪያ መሣቂያ ሊያደርገን ወዳ
ለሁበት ሰተት ብሎ ገባ፤ [18]ታዲያ እኔ
ድረሱልኝ ብዬ ስጮኽ ልብሱን አጠገቤ
ጥሎ ሸሽቶ ወጣ፡፡"

39፥4 ቍ8፡22፤ዘፍ 6፥8፤18፥3፤40፥4፤42፥37፤47፥6፤1ነገ11፥28፤ምሳ22፥29
39፥5 ዘፍ26፥24፤ዘዳ28፥3፤2ሳሙ6፥11፤መዝ128፥4
39፥6 ዘፍ12፥11፤24፥2፤ዘፀ2፥2፤1ሳሙ9፥2፤16፥12፤17፥42፤አስ2፥7፤ዳን1፥4
39፥7 ዘፍ38፥16፤ምሳ7፥15-18
39፥8 ቍ4፤ምሳ6፥23-24
39፥9 ዘፍ41፥33፡40፤13፥13፤ዘኍ22፥34
39፥10 አስ3፥4
39፥11 ቍ14፤ዘፀ18፥20፤ዘዳ1፥18
39፥12 ቍ15፤ዘፍ38፥16፤2ሳሙ13፥11፤ምሳ5፥8፤7፥13፤2ጢሞ2፥22
39፥14 ቍ11፤ዘፍ14፥13፤21፥9፤ዘዳ22፥24፡27
39፥15 ቍ12
39፥17 ዘፍ14፥13፤21፥10፤ዘፀ20፥16፤23፥1፡7፤ዘዳ5፥20፤መዝ101፥5
39፥19 ዘፍ34፥7፤አስ1፥12
39፥20 ዘፍ40፥3፤41፥10፤መዝ105፥18
39፥21 ዘፍ19፥19፤21፥20፤ዘፀ3፥21፤11፥3፤12፥36፤አስ2፥9፤መዝ106፥46፤ምሳ16፥7፤ዳን1፥9
39፥22 ቍ4
39፥23 ቍ3፤ዘፍ21፥20፤ዘኍ14፥43
40፥1 ቍ9፡13፡16፡20፡21፤ነህ1፥11
40፥2 ዘፍ41፥10፤አስ2፥21፤ምሳ16፥14፡15፤19፥12
40፥3 ዘፍ37፥36፤39፥20
40፥4 ቍ7፤ዘፍ37፥36፤39፥4፤42፥17
40፥5 ዘፍ20፥3፤41፥11
40፥7 ቍ4፤ነህ2፥2
40፥8 ዘፍ41፥8፡15፡16፡25፡28፡32፤ዘዳ29፥29፤ዳን2፥22፡28፡47
40፥9 ቍ1
40፥10 ኢሳ27፥6፤35፥1-2፤ሆሴ14፥7

[19]ጌታውም "ባሪያህ እንዲህ አደረገኝ" ብላ
ሚስቱ የነገረችውን ታሪክ ሲሰማ፣ ተቈጣ፡፡
[20]ጌታውም ዮሴፍን ወስዶ፣ የንጉሥ እስረ
ኞች ወደ ተጋዙበት እስር ቤት አስገባው፡፡
ይሁን እንጂ ዮሴፍ እዚያ እስር ቤት
ባለበት ጊዜ ሁሉ፣ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ከእርሱ ጋር ነበረ፤ ቸርነቱንም አበዛለት፣
በወህኒ አዛዡም ዘንድ ሞገስን ሰጠው፡፡
[22]ስለ ዚህ የወህኒው አዛዥ ዮሴፍን
የእስረኞች ሁሉ አለቃ አደረገው፤ በእስር
ቤቱ ላለውም ነገር ሁሉ ኀላፊ ሆነ፡፡ [23]እግዚ
አብሔር (ኤሎሂም) ከዮሴፍ ጋር ሆኖ ሥራውን
ሁሉ ያሳካ ለት ስለ ነበር፣ የወህኒ ቤት
አዛዡ በዮ ሴፍ ኀላፊነት ሥር ስላለው
ስለማንኛውም ጕዳይ ሐሳብ አይገባውም
ነበር፡፡

## የመጠጥ አሳላፊውና የእንጀራ ቤቱ

40 ከዚህም በኋላ የግብፅ ንጉሥ የመ
ጠጥ አሳላፊና እንጀራ ቤቱ ጌታ
ቸውን የግብፅን ንጉሥ በደሉት፡፡ [2]ፈርዖንም
በመጠጥ አሳላፊዎቹ አለቃና በእንጀራ ቤቱ
አዛዥ፣ በሁለቱም ሹማምንቱ ላይ ክፉኛ
ተቈጣ፤ [3]በዘበኞቹ አለቃ ቤት ወዳለው
ዮሴፍ ወደ ተጋዘበትም እስር ቤት አስገ
ባቸው፡፡
[4]የዘበኞቹም አለቃ እስረኞቹን ለዮሴፍ
አስረከባቸው፤ ዮሴፍም በሚያስፈልጋቸው
ይረዳቸው ነበር፡፡
እስር ቤት ገብተው ጥቂት እንደ
ቈዩም፣ [5]ታስረው የነበሩት የግብፅ የን
ጉሥ የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃና የእንጀራ
ቤቱ አዛዥ፣ በአንድ ሌሊት የየራሳቸ
ውን ሕልም አዩ፤ የሁለቱም ሕልም ለየራሱ
የተለየ ፍቺ ነበረው፡፡
[6]በማግስቱ ጧት ዮሴፍ ወደ እነርሱ
ሲገባ ተክዘው አገኛቸው፡፡ [7]ስለዚህም፣ "ምነው
ዛሬስ ፊታችሁ ላይ ሐዘን ይነበባል?" በማ
ለት አብረውት በጌታው ግቢ የታሰሩትን
የፈርዖን ሹማምት ጠየቃቸው፡፡
[8]እነርሱም "ሁለታችንም ሕልም አየን፤
ነገር ግን የሚተረጕምልን ሰው አጣን"
ሲሉ መለሱለት፡፡
ዮሴፍም፣ "ሁልጊዜስ ቢሆን የሕልም ትር
ጓሜ ከእግዚአብሔር (ኤሎሂም) የሚገኝ አይ
ደለምን? እስቲ ያያችሁትን ሕልም ንገሩኝ"
አላቸው፡፡
[9]ስለዚህ የመጠጥ አሳላፊዎቹ አለቃ እን
ዲህ ሲል ሕልሙን ለዮሴፍ ነገረው፤ ከፊት
ለፊቴ አንዲት የወይን ተክል አየሁ፤
[10]ተክሏም ሦስት ሐረጎች ነበሯት፤ ወዲ
ያው አቈጥቍጣ አበበች፤ ዘለላዎቿም ተን
ዠርግገው በሰሉ፡፡ [11]የፈርዖንንም ጽዋ ይዤ
ነበረ፤ የወይኑን ፍሬ ለቅሜ በጽዋው ውስጥ

ጨምቄ ጽዋውን በእጁ ሰጠሁት፡፡”
12ዮሴፍም እንዲህ አለው፤ “እንግዲህ
የሕልሙ ትርጓሜ ይህ ነው፤ ሦስቱ ሐረግ
ሦስት ቀን ነው፤ 13በሦስት ቀን ውስጥ
ፈርዖን ከእስር ቤት ያወጣሃል፣ ወደ ቀድሞ
ሹመትህም ይመልስሃል፤ በፊት የመጠጥ
አሳላፊ በነበርህበት ጊዜ ታደርግ እንደነበ
ረው ሁሉ የፈርዖንን ጽዋ በእጁ ትሰጠዋ
ለህ፡፡ 14እንግዲህ፣ በጎ ነገር በገጠመህ ጊዜ፣
እኔን አስበህ ቸርነት አድርግልኝ፤ ስለ እኔም
ለፈርዖን ንገርልኝ፤ ከዚህም እስር ቤት
አስወጣኝ፤ 15ከዕብራውያን ምድር ወደዚህ
የመጣሁት በአፈና ነው፤ አሁንም ቢሆን
እዚህ እስር ቤት የተጣልሁት አንዳች
ጥፋት ኖሮብኝ አይደለም፡፡”
16የእንጀራ ቤት አዛዡም፣ ለመጠጥ አሳ
ላፊዎቹ አለቃ ሕልም፣ የተሰጠው ፍቺ ደስ
የሚያሰኝ መሆኑን ሲሰማ፣ የራሱን ሕልም
ለዮሴፍ እንዲህ ሲል ነገረው፤ “እኔም
ደግሞ
ሕልም አይቻለሁ፤ ሦስት መሶቦች[ዐ] በራሴ ላይ
ተሸክሜ ነበር፤ 17በላይኛው መሶብ ውስጥ
ለፈርዖን የተዘጋጀ የተለያየ ምግብ ነበረበት፤
ወፎችም ራሴ ላይ ካለው መሶብ ይበሉ
ነበር፡፡”
18ዮሴፍም እንዲህ ሲል መለሰለት፤
“የሕልሙ ፍቺ ይህ ነው፤ ሦስቱ መሶብ
ሦስት ቀን ነው፤ 19በሦስት ቀን ውስጥ
ፈርዖን ከእስር ቤት ያወጣሃል፤ በዕንጨ
ትም ላይ ይሰቅልሃል፤[ዘ] ወፎችም ሥጋህን
ይበሉታል፡፡”
20በሦስተኛውም ቀን የፈርዖን የልደት
በዓል ነበረ፤ ለሹማምቱም ሁሉ ግብር
አበላ፡፡ በዚያኑ ዕለትም የመጠጥ አሳላፊዎ
ችን አለቃና የእንጀራ ቤት አዛዡን ሹማ
ምቱ ካሉበት ከእስር ቤት አወጣቸው፡፡
21የመጠጥ አሳላፊዎቹን አለቃ ወደ ቀድሞ
ሹመቱ መለሰው፤ እርሱም እንደ ቀድሞው
ጽዋውን ለፈርዖን በእጁ ይሰጠው ጀመር፤
22የእንጀራ ቤት አዛዡን ግን ልክ ዮሴፍ
እንደ ተረጐመላቸው ሰቀለው፡፡[ዠ]
23የሆነው ሆኖ፣ የመጠጥ አሳላፊዎቹ አለቃ
ዮሴፍን አላስታወሰውም፤ ረሳው፡፡

### የፈርዖን ሕልም

41 ድፍን ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ
ፈርዖን ሕልም ዐለመ፤ በሕ
ልሙም፣ በዐባይ ወንዝ ዳር ቆሞ ነበር፤
2እነሆ መልካቸው ያማረ፣ ሥጋቸው የወፈረ
ሰባት ላሞች ከወንዙ ወጥተው በወንዙ ዳር
የበቀለውን ሣር ይበሉ ጀመር፡፡ 3ቀጥሎም
መልካቸው የከፋ ዐጥንታቸው የወጣ፣ ሌሎች
ሰባት ላሞች ከወንዙ ወጥተው አስቀድ

40፥12 ቀ፡16:18፤ ዘፍ41፥12:15:25፤ ዳን2፥36፤4፥19
40፥13 ቀ፡1:19: 20፤ኢሱ1፥11፤3፥ 2፤ዕዝ8፥32፤ነህ2፥11
40፥14 ቀ፡23፤ዘፍ 19፥19፤41፥9፤1ሳሙ 20፥14፡42፤25፥31፤ 2ሳሙ9፥1፤1ነገ2፥7፤ መክ9፥15፤ሉቃ23፥42
40፥15 ዘፍ14፥13፤ 39፥20፤ኢዮ13፥27
40፥16 ቀ፡1:12፤ አሞ8፥1-2
40፥18 ቀ፡12
40፥19 ቀ፡13:22፤ ዘዳ21፥22-23፤28፥ 26፤1ሳሙ17፥44፤ 2ሳሙ21፥10፤1ነገ 14፥11፤16፥4፤21፥ 24፤አስ2፥23፤7፥10፤ሕ ዝ39፥4
40፥20 ቀ፡1:13፤ አስ2፥18፤ማቴ14፥6- 10፤ማር6፥21
40፥21 ቀ፡1:13፤ 2ነገ25፥27፤ኤር52፥ 31፤ማር6፥21
40፥22 ቀ፡19፤ዘፍ 41፥13፤መዝ105፥19
40፥23 ቀ፡14፤መክ 1፥11
41፥1 ቀ፡17፤ዘፍ 2፥14፤20፥3፤ዘፀ 1፥22፤2፥5፤7፥15
41፥2 ቀ፡18:26፤ ዘፀ2፥3፤ኢዮ40፥21፤ ኢሳ19፥6፤ኤር5፥28
41፥4 ቀ፡7
41፥5 ኢሱ13፥3፤ 2ነገ4፥42፤1ዜና13፥ 5፤ኢሳ23፥3፤ኤር2፥18
41፥6 ዘፀ10፥13፤ 14፥21፤ኢዮ6፥26፤ 11፥2፤15፥2፤መዝ 11፥6፤48፥7፤ኢሳ11፥ 15፤27፥8፤ኤር4፥11፤ 18፥17፤ሕዝ19፥12፤ 27፥26፤ሆሴ12፥1፤ 13፥15፤ዮና4፥8
41፥7 ቀ፡4
41፥8 ቀ፡24፤ዘፍ 40፥8፤ዘፀ7፥11:22፤ ኢዮ7፥14፤ዳን1፥20፤ 2፥1:2:3:4፥:5፥19: 27፤4፥7:18፤5፥7
41፥9 ዘፍ40፥14
41፥10 ዘፍ37፥36፤ 39፥20፤40፥2
41፥11 ዘፍ40፥5
41፥12 ዘፍ14፥13፤ 37፥36፤39፥17፤40፥4: 12
41፥13 ዘፍ40፥22
41፥14 ዘፍ35፥2፤ 45፥22፤ሩት3፥3፤ 2ሳሙ12፥20፤መዝ 105፥20፤ኢሳ18፥2:7
41፥15 ዘፍ40፥8: 12፤ዳን4፥18፤5፥16

መው ከወጡት ላሞች አጠገብ ቆሙ፡፡ 4እነ
ዚህ መልካቸው የከፋና ዐጥንታቸው
የወጣ ላሞች፣ እነዚያን ያማሩና የወፈሩ
ላሞች ሲውጡአቸው አየ፤ ከዚያም ፈርዖን
ከእንቅልፉ ነቃ፡፡
5ፈርዖንም እንደ ገና እንቅልፍ ወስዶት
ሳለ፣ ሌላ ሕልም አየ፡፡ በሕልሙም በአ
ንድ የእህል አገዳ ላይ፣ ፍሬያቸው የተን
ዠረገገና ያማረ ሰባት የእሸት ዛላዎች
ሲወጡ አየ፡፡ 6ከዚያም የቀጨጩና በምሥ
ራቅ ነፋስ ተመትተው የደረቁ ሰባት የእሸት
ዛላዎች ወጡ፡፡ 7የቀጨጩት የእሸት ዛላ
ዎች፣ ፍሬያቸው የተንዠረገገውን ሰባቱን
ያማሩ ዛላዎች ዋጡአቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ፈር
ዖን ከእንቅልፉ ነቃ፤ ነገሩ ሕልም ነበር፡፡
8በነጋታውም ፈርዖን መንፈሱ ታወከ
በት፤ ስለዚህ በግብፅ አገር ያሉትን አስማ
ተኞችና ጥበበኞች በሙሉ አስጠርቶ
ሕልሞቹን ነገራቸው፣ ይሁን እንጂ ሕል
ሞቹን ሊተረጕምለት የቻለ አንድም ሰው
አልተገኘም፡፡
9በዚያን ጊዜ የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ
ፈርዖንን እንዲህ አለው፤ “የሠራሁት በደል
ዛሬ ታወሰኝ፡፡ 10በአንድ ወቅት ፈርዖን
እኔንና የእንጀራ ቤት አዛዡን ተቈጥቶ
በዘበኞቹ አለቃ ግቢ አስሮን ነበር፡፡ 11ሁለ
ታችንም በአንዲት ሌሊት የተለያየ ሕልም
አየን፤ የእያንዳንዳችንም ሕልም የየራሱ
ትርጕም ነበረው፡፡ 12በዚያን ጊዜ የዘበኞች
አለቃ አገልጋይ የሆነ አንድ ዕብራዊ
ወጣት ከእኛ ጋር እስር ቤት ነበር፡፡ ሕል
ማችንን በነገርነው ጊዜ፣ ፍቺውን ነገ
ረን፤ ለእያንዳንዳችንም እንደ ሕልማችን
ተረጐመልን፤ 13ነገሩም ልክ እርሱ እንደ
ተረጐመልን ሆነ፤ እኔ ወደ ቀድሞ ሹመቴ
ተመለስሁ፤ የእንጀራ ቤት አዛዡም ተሰ
ቀለ[የ]፡፡
14ፈርዖን ዮሴፍን እንዲያመጡት ትእ
ዛዝ ሰጠ፤ ከእስር ቤትም በጥድፊያ ይዘውት
መጡ፤ ጠጕሩንም ከተላጨና ልብሱን ከለ
ወጠ በኋላ ፈርዖን ፊት ቀረበ፡፡
15ፈርዖንም ዮሴፍን፣ “ሕልም አይቼ
ነበር፤
ሕልሜን ሊተረጕምልኝ የቻለ አንድም ሰው
አልተገኘም፤ አንተ ግን ሕልም ሲነገርህ የመ
ተርጐም ችሎታ እንዳለህ ሰማሁ” አለው፡፡
16ዮሴፍም ፈርዖንን፣ “እኔ የመተርጐም
ችሎታ የለኝም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
ለፈርዖን የሚሻውን ትርጕም ይሰጠዋል”
አለው፡፡

[ዐ]16 ወይም *ሦስት የሸንበቆ ቅርጫቶች*
[ዘ]19 ወይም *በእንጨትም ላይ ይወጋሃል*
[ዠ]22 ወይም *ወጋው*
[የ]13 ወይም *ተወጋ*

17ከዚህ በኋላ ፈርዖን ዮሴፍን እንዲህ አለው፤
“በሕልሜ በዐባይ ወንዝ ዳር ቆሜ ነበር።
18ሥጋቸው የወፈረና መልካቸው ያማረ ሰባት
ላሞች ከወንዙ ወጥተው በወንዙ ዳር የበቀ
ለውን ሣር ሲበሉ አየሁ። 19ከእነርሱም
በኋላ፣ ዐቅመ ደካማ፣ መልካቸው እጅግ
የከፋና ዐጥንታቸው የወጣ ሌሎች ሰባት
ላሞች ወጡ፤ እነዚያን የመሰሉ የሚያስከፉ
መልክ ያላቸው ላሞች በግብፅ ምድር ከቶ
አይቼ አላውቅም። 20ዐጥንታቸው የወጣና
አስከፊ መልክ ያላቸው ላሞች መጀመሪያ
የወጡትን፣ ሥጋቸው የወፈረውን ሰባቱን
ላሞች ዋጧ ቸው። 21ከዋጧቸውም በኋላ፣ ያው
የበፊቱ መልካቸው ስላልተለወጠ እንደ
ዋጧቸው ማንም ሊያውቅ አይችልም ነበር፤
ከዚያም ከእንቅልፌ ነቃሁ።
22እንደዚሁም፣ በሕልሜ በአንድ የእህል
አገዳ ላይ ፍሬያቸው የፋፋና ያማሩ ሰባት
እሸት ዛላዎች ወጥተው አየሁ። 23ቀጥሎም
በምሥራቅ ነፋስ ተመተው የቀጨጩና
የደረቁ ሌሎች ሰባት ዛላዎች ወጡ።
24የቀጨጩት የእሸት ዛላዎችም ሰባቱን
ያማሩ የእሸት ዛላዎች ዋጧቸው፤ ይህን
ኑም ለአስማተኞች ነገርሁ፤ ነገር ግን
ማንም ሊፈታው አልቻለም።”
25ዮሴፍም ለፈርዖን እንዲህ አለው፤
“ሁለቱም የፈርዖን ሕልሞች ተመሳሳይና
አንድ ዐይነት ናቸው፤ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
ወደ ፊት የሚያደርገውን ለፈርዖን
ገልጦለታል። 26ሰባቱ የሚያማምሩ
ላሞች፣ ሰባት ዓመ ታት ናቸው፣ ሰባቱም
የሚያማምሩ የእሸት ዛላዎች ሰባት ዓመታት
ናቸው፤ ሕልሙም አንድና ተመሳሳይ
ነው። 27ከእነርሱም በኋላ ዐጥንታቸው
የወጣ አስከፊ መልክ ያላቸው ሰባት ላሞች፣
ሰባት ዓመታት ናቸው፤ እንደዚሁም ፍሬ
አልባ የሆኑትና በምሥ
ራቅ ነፋስ ተመትተው የደረቁት ሰባት የእ
ሸት ዛላዎች ሰባት የራብ ዓመታት ናቸው።
“አስቀድሜ ለፈርዖን እንደተናገርኩት፣
እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ወደ ፊት የሚያደርገ
ውን ነገር ለፈርዖን ገልጦለታል። 29በመላው
የግብፅ ምድር እጅግ የተትረፈረፈ ጥጋብ
የሚሆንባቸው ሰባት ዓመታት ይመጣሉ።
30ከዚህ በኋላ ግን በተከታታይ ሰባት የራብ
ዓመታት ይሆናሉ። የራቡ ዘመን አገሪቱን
እጅግ ስለሚጐዳት፣ በግብፅ የነበረው
ያለፈው የጥጋብ ዘመን ሁሉ ጨርሶ አይታ
ወስም። 31ከጥጋቡ ዓመታት በኋላ የሚመጣው
የራብ ዘመን እጅግ ጽኑ ከመሆኑ የተነሣ፣
ቀደም ሲል የነበረው የጥጋብ ዘመን
ፈጽሞ ይረሳል። 32ሕልሙ ለፈርዖን በሁለት
መልክ በድጋሚ መታየቱ፣ ነገሩ ከእግዚአብሔር
(ኤሎሂም) ዘንድ የተቈረጠ ስለ ሆነ ነው፤ ይህን

41፥16 ዘፍ40፥8
41፥17 ቍ1
41፥18 ቍ2
41፥24 ቍ8
41፥25 ዘፍ40፥8፡12፤ኢሳ46፥11፤ዳን2፥45
41፥26 ቍ2
41፥27 ዘፍ12፥10
41፥28 ዘፍ40፥8
41፥29 ቍ47
41፥30 ቍ54:56፤ዘፍ12፥10፤45፥6፡11፤47፥13፤መዝ105፥16
41፥32 ዘፍ40፥8፤ዳን2፥5
41፥33 ቍ39፤ዘፍ39፥9
41፥34 ቍ48፤ዘፍ24፡26፤47፥14፡1ሳሙ8፥15
41፥35 ቍ48
41፥36 ቍ56፤ዘፍ42፥6፤47፥14
41፥37 ዘፍ45፥16፤አስ2፥4፤ኢሳ19፥11
41፥38 ዘኍ27፥18፤ዘዳ34፥9፤ዳን2፥11፤4፥8-9፡18፤5፥11፡14
41፥39 ቍ33፤ዳን2፥11፤5፥11
41፥40 ዘፍ39፥9፤1ነገ4፥6፤2ነገ15፥5፤አስ10፥3፤መዝ105፥21-22፤ኢሳ22፥15፤36፥3፤ሐሥ7፥10
41፥41 ቍ43፡55፤ዘፍ42፥6፤45፥8፡13፡26፤አስ8፥2፤ኤር40፥7፤ዳን6፥3
41፥42 ዘፍ24፥22፤ዘፀ25፥4፤1ሳሙ17፥38፤18፥4፤1ነገ19፥19፤አስ3፥10፤6፥8፡11፤8፥2፤8:15፤መዝ73፥6፤ማሕ4፥9፤ኢሳ3፥18፤ሕዝ16፥11፤ዳን5፥7:16፡29፤ዘካ3፥4
41፥43 ቍ41፤ዘፍ46፥29፤50፥9፤አስ6፥9፤10፥3፤ኢሳ2፥7፤22፥18
41፥44 ዘፍ37፥8፤አስ10፥2፤መዝ105፥22
41፥45 ቍ50፤ዘፍ46፥20፡27፤ዘፀ2፥16፤አስ2፥7፤ሕዝ30፥17

ንም እግዚአብሔር (ኤሎሂም) በቅርብ ጊዜ ይፈ
ጽመዋል።
33እንግዲህ ፈርዖን ብልኅና አስተዋይ ሰው
ፈልጎ፣ በመላው የግብፅ ምድር ላይ አሁ
ኑኑ ይሹም። 34እንደዚሁም በሰባቱ የጥ
ጋብ ዓመታት ከሚገኘው ምርት፣ አንድ
አምስተኛው እንዲሰበሰብ የሚያደርጉ ኀላፊ
ዎችን ይሹም። 35እነርሱም በሚመጡት
የጥጋብ ዓመታት ከሚገኘው ምርት ሁሉ
ይሰብስቡ፤ በፈርዖንም ሥልጣን ሥር ያከ
ማቹ፤ ለምግብ እንዲሆኑም በየከተማው
ይጠበቁ። 36የሚከማቸው እህል፣ ወደ ፊት
በግብፅ አገር ላይ ለሚመጣው የሰባት
ዓመት ራብ መጠባበቂያ ይሁን፤ በዚህም
ሁኔታ አገሪቱ በራብ አትጠፋም።”
37ዕቅዱንም ፈርዖንና ሹማምንቱ ሁሉ
መል
ካም ሆኖ አገኙት። 38ፈርዖንም፣ “የእግዚአ
ብሔር (ኤሎሂም) መንፈስ[ደ] ያለበት እንደዚህ ያለ
ሰው ማንን ልናገኝ እንችላለን?” ብሎ ጠየ
ቃቸው።
39ፈርዖን ዮሴፍን እንዲህ አለው፤ “እግዚ
አብሔር (ኤሎሂም) ይህን ሁሉ ስለ ገለጠልህ፣
እንዳንተ ያለ አስተዋይና ብልኅ ሰው
የለም። 40አንተ በቤተ መንግሥቴ የበላይ
ትሆናለህ፤
ሕዝቤም ሁሉ ለሥልጣንህ ይገዛል፤ እኔ
ከአንተ የምበልጠው በዙፋኔ ብቻ ይሆናል።”

## ዮሴፍ በግብፅ ተሾመ

41ከዚያም፣ ፈርዖን ዮሴፍን “በመላዪቱ የግ
ብፅ ምድር ላይ ኀላፊ አድርጌሃለሁ” አለው።
42ፈርዖንም ባለማኅተሙን ቀለበት ከጣቱ
አውልቆ በዮሴፍ ጣት ላይ አደረገው፤
እንዲሁም ከጥሩ የተልባ እግር የተሠራ ልብስ
አለበሰው፤ በዐንገቱም የወርቅ ሐብል አጠ
ለቀለት። 43በማዕረግ ከእርሱ ሁለተኛ ሰው
አድርጎ፣ በሠረገላ ላይ አስቀመጠው[ጀ] ሰዎችም
በፊቱ፣ “እጅ ንሡ” እያሉ ይጮኹ ነበር፤
በዚህ ሁኔታም በግብፅ ምድር ሁሉ ላይ
ሾመው።
44ከዚህ በኋላ ፈርዖን ዮሴፍን፣ “እኔ
ፈርዖን ነኝ፤ ሆኖም በመላዪቱ ግብፅ ያላ
ንተ ትእዛዝ እጁንም ሆነ እግሩን ልውስ
የሚያደርግ አይኖርም” አለው። 45ፈርዖ
ንም ዮሴፍን ጻፍናት ፐዕናህ ብሎ ስም
አወጣለት። እንዲሁም የሄልዮቱ[ጠ] ከተማ ካህን
የጶጥፌራ ልጅ አስናትን አጋባው። ዮሴፍም
በመላዪቱ የግብፅ ምድር ተዘዋወረ።

[ደ]38 ወይም *የአማልክት መንፈስ*
[ጀ]43 ወይም *በማዕረግ ሁለተኛ በሆነው የእርሱ ሠረገላ ላይ፤ ወይም በሁለተኛ ሠረገላው ላይ*
[ገ]43 ወይም *ስገዱ*
[ጠ]45 በቍ 50 ላይ ያለውንም ጨምሮ ሆልዮፓሊስን ያመለክታል

46ዮሴፍ የግብፅ ንጉሥ ፈርዖንን ማገ
ልገል ሲጀምር፣ ዕድሜው ሠላሳ ዓመት
ነበር። ዮሴፍም ከፈርዖን ፊት ወጥቶ የግ
ብፅን ምድር በሙሉ ዞረ።
47በሰባቱም የጥጋብ ዓመታት ምድሪቱ የተ
ትረፈረፈ ሰብል ሰጠች። 48በእነዚያ ሰባት
የጥጋብ ዓመታት፣ ዮሴፍ በግብፅ አገር
የተገኘውን ምርት ሰብስቦ በየከተሞቹ አከ
ማቸ፤ በእያንዳንዱ ከተማ ከየአቅራቢያው
የተመረተውን እህል እንዲከማች አደረገ።
49ዮሴፍ ብዛቱ እንደ ባሕር አሸዋ የሚሆን
የእህል ሰብል አከማቸ፤ ሰብሉ እጅግ
ከመብዛቱ የተነሣ ልኩን መስፈርና መመ
ዝገብ አልቻለም ነበር።
50ሰባቱ የራብ ዓመታት ከመምጣቱ በፊት፣
የሄልዮቱ ካህን የጶጥፌራ ልጅ አስናት ለዮሴፍ
ሁለት ወንዶች ልጆች ወለደችለት። 51ዮሴ
ፍም፣ "እግዚአብሔር (ኤሎሂም) መከራዬን ሁሉ፣
የአባቴንም ቤት እንድረሳ አድርጎኛል" በማ
ለት የመጀመሪያ ልጁን ስም ምናሴ[ጫ] አለው።
52እንደዚሁም፣ "መከራ በተቀበልኩበት ምድር
እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ፍሬያማ አደረገኝ" ሲል
ሁለተኛ ልጁን ኤፍሬም[ጰ] አለው።
53በግብፅ ምድር የነበረው ሰባቱ የጥጋብ
ዘመን ዐለፈና 54ዮሴፍ አስቀድሞ እንደ
ተናገረው የሰባቱ ዓመት የራብ ዘመን
ጀመረ። ሌሎች አገሮች ሁሉ ሲራቡ፣
በመላው የግብፅ ምድር ግን ምግብ ነበር።
55ራቡ በመላው የግብፅ ምድር መስፋፋት
ሲጀምር፣ ሕዝቡ ምግብ ይሰጠን በማለት
ወደ ፈርዖን ጮኸ። ፈርዖንም ግብፃውያ
ኑን፣ "ወደ ዮሴፍ ሂዱና የሚላችሁን አድ
ርጉ" አላቸው።
56ራቡ በአገሩ ላይ እየተስፋፋ ስለ ሄደ፣
ዮሴፍ ጐተራዎቹን ከፍቶ እህሉ ለግብፃው
ያን እንዲሸጥ አደረገ፤ ምክንያቱም ራቡ
በመላዩቱ ግብፅ ጸንቶ ነበር። 57ራቡ በመ
ላው ዓለም ጸንቶ ስለ ነበር፣ የየአገሩ
ሰዎች ሁሉ ከዮሴፍ ዘንድ እህል ለመ
ሸመት ወደ ግብፅ ምድር መጡ።

## የዮሴፍ ወንድሞች ወደ ግብፅ ሄዱ

42 ያዕቆብ በግብፅ እህል መኖሩን ሲሰማ፣
ልጆቹን እንዲህ አላቸው፤ "ለምን
እርስ በርስ ትተያያላችሁ? 2በግብፅ እህል
መኖሩን ሰምቻለሁ፤ ስለዚህ ከመሞት
መሰንበት ይሻላልና ወደዚያው ወርዳችሁ
እህል ሸምቱልን" አላቸው።
3ከዚያም ዐሥሩ የዮሴፍ ወንድሞች እህል
ለመሸመት ወደ ግብፅ ወረዱ። 4ነገር ግን
ያዕቆብ የዮሴፍን ወንድም ብንያምን፣ ክፉ
ነገር ይደርስበታል በሚል ፍርሀት ከወንድ
ሞቹ ጋር አላከውም። 5ራቡ በከነዓንም በመ
በርታቱ፣ እህል ለመሸመት ወደ ግብፅ ከሄዱት
ሰዎች መካከል የእስራኤል ልጆችም ነበሩ።
6በዚህ ጊዜ ዮሴፍ የምድሪቱ ገዥ ነበር፤
ለአገሩ ሰዎች ሁሉ እህል የሚሸጥላቸው
እርሱ ነበር። የዮሴፍ ወንድሞችም እንደ
ደረሱ፣ ከፊቱ ቀርበው ወደ ምድር ለጥ
ብለው እጅ ነሡት። 7ዮሴፍም ወንድሞቹን
ገና ሲያያቸው ወዲያውኑ ዐወቃቸው፤
ነገር ግን እንደማያውቃቸው ሆኖ፣ "ከየት
የመጣችሁ ናችሁ?" ብሎ በቍጣ ቃል
ተናገራቸው። እነርሱም፣ "እህል፤ ለመሸመት
ከከነዓን ምድር የመጣን ነን" ብለው መለ
ሱለት።
8ዮሴፍ ወንድሞቹን ቢያውቃቸውም እንኳ
እነርሱ ግን አላወቁትም። 9በዚህ ጊዜ ስለ
ወንድሞቹ ያየው ሕልም ትዝ አለውና፣ "ሰላ
ዮች ናችሁ፤ የመጣችሁት አገራችን በየት
ኛው በኩል ለጥቃት የተጋለጠች መሆኗን
ለመሰለል ነው" አላቸው።
10እነርሱም እንዲህ አሉት፤ "ጌታችን
ሆይ፤ እንዲህስ አይደለም፤ አገልጋዮችህ
የመጣነው እህል ለመሸመት ነው፤ 11ሁላ
ችንም የአንድ አባት ልጆች ነን፤ አገልጋ
ዮችህ የታመንን ሰዎች እንጂ ሰላዮች አይደ
ለንም።"
12እርሱም መልሶ፣ "አይደለም፤ በየት
በኩል ለጥቃት የተጋለጠች መሆኗን
ለመሰለል ነው" አላቸው።
13እነርሱ ግን መልሰው፣ "እኛ አገልጋዮ
ችህ በከነዓን አገር ከሚኖር ከአንድ ሰው የተ
ወለድን ዐሥራ ሁለት ወንድማማቾች
ነን። ትንሹ ወንድማችን አባታችን ዘንድ
ሲሆን፣ አንዱ ግን የለም" አሉት።
14ዮሴፍም እንዲህ አላቸው፤ "ነገርኋችሁ
እኮ፤ ሰላዮች ናችሁ! 15ታናሽ ወንድማችሁ
እዚህ እስካልመጣ ድረስ ከዚህ ንቅንቅ
እንደማትሉ በፈርዖን ስም እምላለሁ፤ ማን
ነታችሁ የሚረጋገጠውም በዚህ ነው።
16በሉ፣ ከእናንተ አንዱን ላኩና ወንድማ
ችሁን ይዞ ይመለስ፤ የቀራችሁት ግን የተ
ናገራችሁት ቃል እስኪረጋገጥ ድረስ፣
እስር ቤት ትቈያላችሁ። እንደተናገራችሁት
ካል ሆነ ግን፣ በፈርዖን ስም እምላለሁ፤
ሁላ ችሁም ሰላዮች ናችሁ" አላቸው።
17ሁሉንም ሦስት ቀን በእስር አቈያቸው።
18በሦስተኛውም ቀን ዮሴፍ እንዲህ አላ
ቸው፤ "እኔ እግዚአብሔርን (ኤሎሂም) ስለምፈራ

41፥46 ዘፍ37፥2፤ 1ሳሙ8፥11፤16፥21፤ ምሳ22፥29፤ዳን1፥19
41፥47 ቁ29
41፥48 ቁ34
41፥49 ዘፍ12፥2
41፥50 ቁ45
41፥51 ዘፍ46፥20፤ 48፥1፡14፡18፡20፤49፥ 3፤50፥23፤ዘኍ1፥34፤ ዘዳ33፥17፤ኢሱ4፥12፤ 17፥1፤1ዜና7፥14
41፥52 ዘፍ17፥6፤ 46፥20፤48፥1፡5፤50፥ 23፤ዘኍ1፥32፤26፥28፤ ዘዳ33፥17፤ኢሱ14፥ 4፤መሳ5፥14፤1ዜና7፥ 20፤2ዜና30፥1፤መዝ 60፥7፤ኤር7፥15፤ አብ1፥19
41፥54 ዘፍ12፥10 ፤ሐሥ7፥11
41፥55 ቁ41፤ዘዳ 32፥24፤2ዜና20፥9፤ ኢሳ51፥19፤ኤር5፥ 12፤27፥8፤42፥16፤ 44፥27፤ዮሐ2፥5
41፥56 ቁ30፡36፤ ዘፍ12፥10
41፥57 ዘፍ12፥10፤ 42፥5፤47፥15
42፥1 ሐሥ7፥12
42፥2 ቁ19፡33፤ ዘፍ43፥2፡4፡8፤44፥25፤ 47፥19፤መዝ33፥18-19
42፥3 ቁ10፤ዘፍ 43፥20
42፥4 ቁ38፤ዘፍ 35፥18
42፥5 ቁ13፡29፤ ዘፍ12፥10፤31፥18፤ 41፥57፤45፥17፤ዘዳ 32፥24፤ሐሥ7፥11
42፥6 ዘፍ33፥3፤ 41፥36፡41፤ ነህ 5፥14
42፥7 ቁ30፤ዘፍ 29፥4
42፥8 ዘፍ37፥2
42፥9 ቁ12፡14፡ 16፡30፤ ዘፍ 37፥7፤ ዘዳ1፥22፤ኢሱ2፥1፤ 6፥22፤
42፥10 ቁ3፤ዘፍ 37፥8
42፥11 ቁ13፡15፡ 16፡19፡20፡31፡34፤ዘፍ 44፥7፡9፡16፡19፡21፡31 ፤46፥34፤47፥3
42፥12 ቁ9
42፥13 ቁ5፡11፡ 24፡32፡36፤ዘፍ29፡33 ፤ 37፥33፤43፥7፤44፥8፤4 6፥31፤47፥1፤ኤር 31፥15
42፥14 ቁ9
42፥15 ቁ11፤ዘፍ 43፥3፡5፡7፤44፥21፡ 23፤1ሳሙ17፥55
42፥16 ቁ11፡9፡

[ጫ]51 ምናሴ የሚለው ቃል መርሳት የሚል ትርጒም ካለው የዕብራ ይስጥ ቃል የወጣ ሲሆን ከዚሁ ቃል ጋር አንድ ዐይነት ድምፅ አለው
[ጰ]52 ኤፍሬም የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ዕጥፍ ፍሬያማ የሚል ትርጒም ካለው ቃል ጋር እንድ ዐይነት ድምፅ አለው።

እንዲህ በማድረግ ሕይወታችሁን አት
ርፉ፡፡ [19]ታማኝ ሰዎች ከሆናችሁ፣ ከመካከ
ላችሁ አንዱ እዚህ እስር ቤት ሲቈይ፣ የቀራ
ችሁት ግን ለተራቡት ቤተ ሰቦቻችሁ
እህል ትወስዱላቸዋላችሁ፤ [20]ታናሽ ወንድ
ማችሁን ግን ይዛችሁ መምጣት አለባ
ችሁ፤ በዚህም የተናገራችሁት ቃል እውነተ
ኛነት ይረጋገጣል፤ እናንተም ከመሞት
ትተርፋላችሁ፡፡" እነርሱም ይህንኑ ለመፈ
ጸም ተስማሙ፡፡
[21]እርስ በርሳቸውም፣ "ይኸው በወንድማ
ችን ላይ ባደረስነው በደል ምክንያት ቅጣ
ታችንን እየተቀበልን ነው፡፡ እርሱ እንደ
ዚያ ተጨንቆ ስለ ሕይወቱ ሲማጠነን፣ እኛ
አልሰማነውም ነበር፤ ይህ መከራ የደረሰ
ብንም በዚሁ ምክንያት ነው" ተባባሉ፡፡
[22]ሮቤልም መልሶ፣ "በዚህ ልጅ ላይ፣ 'ክፉ
ነገር አታድርጉ' ብዬ አልነበረምን? እና
ንተ ግን አልሰማችሁኝም፤ ስለዚህም ደሙ
ከእጃችን ይፈለጋል" አላቸው፡፡ [23]ዮሴፍ
የሚያነጋግራቸው በአስተርጓሚ ስለ ሆነ
የሚነጋገሩትን እንደሚሰማቸው አላወቁም
ነበር፡፡
[24]ከፊታቸውም ዘወር ብሎ አለቀሰ፤ ከዚ
ያም ወደ እነርሱ ተመልሶ እንደ ገና
አነጋገራቸው፤ ስምዖንንም ከእነርሱ ለይቶ
ዐይናቸው እያየ አሰረው፡፡
[25]በስልቻዎቻቸው እህል እንዲሞሉላቸው፤
ብሩንም በያንዳንዱ ሰው ስልቻ ውስጥ መል
ሰው እንዲያስቀምጡና ለጕዞአቸው ስንቅ
እንዲያሲዟቸው ዮሴፍ ትእዛዝ ሰጠ፡፡ ይህም
ከተደረገላቸው በኋላ፣ [26]እህላቸውን
በአህዮ ቻቸው ጭነው ጕዞአቸውን ቀጠ
ሉ፡፡
[27]በመንገድም ለዐዳር ሰፍረው ሳሉ፣
ከእነርሱ አንዱ ከያዘው እህል ላይ ለአ
ህያው ለመስጠት ስልቻውን ሲፈታ፣ በስ
ልቻው አፍ ላይ ብሩን አገኘ፡፡ [28]እርሱም
ወንድሞቹን፣ "እረ ብሬ ተመልሶልኛል፤
ይኸው ስልቻዬ ውስጥ አገኘሁት" አላቸው፡፡
ሁሉም ልባቸው በድንጋጤ ተሞልቶ
እየተንቀጠቀጡ በመተያየት፣ "እግዚአብሔር (ኤሎ
ሂም) ምን ሊያመጣብን ይሆን?" አሉ፡፡
[29]በከነዓን ምድር ወዳለው ወደ አባ
ታቸው ወደ ያዕቆብ ከደረሱ በኋላ፣
ያጋጠማቸውን ሁሉ እንዲህ ብለው ነገሩት፤
[30]"የአገሩ ጌታ የሆነው ሰው ምድሪቱን እን
ደምንሰልል ቈጥሮን በቍጣ ተናገረን፡፡
[31]እኛ ግን እንዲህ አልነው፤ 'እኛ የታመ
ንን ሰዎች እንጂ ሰላዮች አይደለንም፡፡
[32]እኛ የአንድ አባት ልጆች የሆን፣ ዐሥራ
ሁለት ወንድማማቾች ነን፤ አንዱ የለም፤
ታናሽ ወንድማችን ግን ከአባታችን ጋር

15፥19
42፥17 ዘፍ40፥4
42፥18 ዘፍ20፥11፤ 22፥12፤ዘሌ19፥14፤ 25፥43፤2ሳሙ23፥3
42፥19 ቍ2፡11፡16
42፥20 ቍ15
42፥21 ዘፍ37፥26-28፤45፥5
42፥22 ዘፍ9፥5፤ 37፥21-22፤45፥24
42፥23 ዘፍ11፥7፤ 38፥16
42፥24 ቍ13፤ዘፍ 29፥11፤43፥14፡23
42፥25 ቍ 27፡35፤ ዘፍ 43፥2፡12፡18፡21፤ 44፥1፡8፤ 45፥21፡23፤ ኤር40፥5
42፥26 ዘፍ32፥15፤ 44፥13፤45፥17፤1ሳሙ 25፥18፤ኢሳ30፥6
42፥27 ቍ25፤መሳ 19፥19፤ኢዮ39፥9፤ ኢ ሳ1፥3
42፥28 ዘፍ43፥23፤ ኢሱ2፥11፤5፥1፤7፥5፤ ማር5፥33
42፥29 ቍ5፤ዘፍ 44፥24
42፥30 ቍ7፡9
42፥31 ቍ11
42፥32 ቍ13
42፥33 ቍ2
42፥34 ቍ11፡24፤ ዘፍ34፥10
42፥35 ቍ25፤ዘፍ 43፥18
42፥36 ቍ13፡24
42፥37 ዘፍ39፥4፤ 43፥9፤44፥32
42፥38 ቍ4፤ዘፍ 37፥33፡35፤44፥29፡ 34፤48፥7

43፥1 ዘፍ12፥10
43፥2 ዘፍ42፥2፡25
43፥3 ቍ8፤ዘፍ44፥ 14፡18፤42፥15፤ 46፥28
43፥4 ዘፍ42፥2
43፥5 ዘፍ42፥15፤ 44፥26፤2ሳሙ3፥13
43፥6 ቍ8፡11፤

በከነዓን ይገኛል፡፡'
[33]"ከዚህ በኋላ የአገሩ ጌታ የሆነው
ሰው እንዲህ አለን፤ 'ታማኝ ሰዎች
መሆናችሁን የማውቀው በዚህ ነው፤
ከእናንተ መካከል አንዱን ወንድማችሁን
እዚህ እኔ ዘንድ ትታ ችሁ የተቀራችሁት
ለተራቡት ቤተ ሰቦቻ ችሁ እህል
ይዛችሁላቸው ሂዱ፡፡ [34]ነገር ግን ታናሽ
ወንድማችሁን ወደ እኔ አምጡት፡፡ በዚ
ያንም ጊዜ ታማኝ ሰዎች እንጂ ሰላ ዮች
አለመሆናችሁን ዐውቃለሁ፤ ወንድማች ሁንም
መልሼ እሰጣችኋለሁ፤ እናንተም
በምድሪቱ እንደ ልብ ለመዘዋወር ትችላ
ላችሁ፡፡" '
[35]እህሉንም ሲዘረግፉ በየስልቾቻቸው
ውስጥ ብራቸው እንደ ተቋጠረ ተገኘ፤ የእ
ያንዳንዳቸውን የተቋጠረ ብር ሲያዩም፣
እነርሱም ሆኑ አባታቸው ደነገጡ፡፡ [36]አባ
ታቸው ያዕቆብም፣ "ያለ ልጅ እኮ አስቀራ
ችሁኝ፤ ዮሴፍ የለም፤ ስምዖንም የለም፤
አሁን ደግሞ ብንያምን ልትወስዱ ትፈ
ልጋላችሁ፤ እረ ምን ጒድ ነው የመጣ
ብኝ!" አላቸው፡፡
[37]በዚህን ጊዜ ሮቤል አባቱን፣ "መልሼ
ባላመጣው፣ ሁለቱን ወንዶች ልጆቼን ግደ
ላቸው፤ ኀላፊነቱን ለእኔ ተውልኝ፤ እኔው
መልሼ አመጣዋለሁ" አለው፡፡
[38]ያዕቆብም፣ "ልጄ አብሮአችሁ ወደዚያ
አይወርድም፤ ወንድሙ እንደሆን ሞቶ
አል፤ የቀረው እርሱ ብቻ ነው፡፡ ይዛች
ሁት ስትሄዱ በመንገድ ላይ አደጋ ቢደር
ስበት፣ ሽበቴን በመሪር ሐዘን ወደ መቃ
ብር[a] ታወርዱታላችሁ" አላቸው፡፡

**የዮሴፍ ወንድሞች ዳግመኛ ወደ ግብፅ መሄዳቸው**

43 ራቡ አሁንም በምድሪቱ ላይ
እንደ ጸና ነበር፤ [2]ከግብፅ ያመጡ
ትንም እህል በልተው ከጨረሱ በኋላ፣
አባታቸው "እስቲ እንደ ገና ወርዳችሁ፣
ጥቂት እህል ሸምቱልን" አላቸው፡፡
[3]ይሁዳ ግን እንዲህ አለው፤ "ያ ሰው 'ወን
ድማችሁን ይዛችሁ ካልመጣችሁ ዳግመኛ
ፊቴን አታዩም' ብሎ በጥብቅ አስጠንቅቆ
ናል፤ [4]ወንድማችን ከእኛ ጋር እንዲወርድ
ከፈቀድህ ወደዚያ ሄደን እህል እንሸምት
ልሃለን፤ [5]እርሱን የማትልከው ከሆነ ግን
እኛም ወደዚያ አንወርድም፤ ያም ሰው፣
'ወንድማች ሁን ይዛችሁ ካልመጣችሁ
ዳግመኛ ፊቴን አታዩም' ብሎናል፡፡"
[6]እስራኤልም፣ "ሌላ ወንድም አለን ብላ
ችሁ ለዚያ ሰው በመንገር ለምን ይህን

[a]38 ዕብራይስጡ ሲኦል ይለዋል

ችግር እንዲደርስብኝ አደረጋችሁ?” ሲል
ጠየቃቸው።
7እነርሱም፣ “ሰውየው ስለ ራሳችንና ስለ
ቤተ ሰባችን አጥብቆ ጠየቀን፤ እንደ
ገናም አባታችሁ አሁንም በሕይወት አለ?
ሌላስ ወንድም አላችሁ’ ሲል ጠየቀን።
እኛም ለጥያቄው መልስ ሰጠነው። ታድያ፣
‘ወንድማችሁን ይዛችሁ ወደዚህ እንድት
መጡ’ እንደሚል እንዴት ማወቅ እንችል
ነበር?” ብለው መለሱለት።
8ይሁዳም አባቱን እስራኤልን እንዲህ
አለው “ልጁን ከእኔ ጋር ስደደው፤ እኛም
በቶሎ እንሂድ፤ ይህ ከሆነ፣ አንተም፣
እኛም፣ ልጆቻችንም አንሞትም፤ እንተርፋ
ለን። 9ስለ ልጁ ደኅንነት እኔ ራሴ ኀላፊ
ነኝ፤ ስለ እርሱም በግል ተጠያቂ እሆና
ለሁ፤ እርሱንም በደኅና መልሼ ባላመጣ
ውና እዚህ በፊትህ ባላቆመው ለዘላለም
በደለኛ እኔ ልሁን። 10ይህን ያህል ባንዘ
ገይ ኖሮ፣ እስካሁን ሁለት ጊዜ ደርሰን
መመለስ በቻልን ነበር።”
11ከዚህ በኋላ አባታቸው እስራኤል እንዲህ
አላቸው፤ “ነገሩ እንዲህ ከሆነስ ይህን አድ
ርጉ፤ ምድሪቱ ከምታፈራው ምርጥ
ነገሮች ጥቂት በለሳን፣ ጥቂት ማር፣ ሽተ
ት፣ ከርቤ ተምርና ለውዝ በየስልቻችሁ
ይዛችሁ ለዚያ ሰው እጅ መንሻ
ውሰዱለት። 12በየስል ቾቻችሁ አፍ ላይ
የተገኘውን ብር መመ ለስ ስላለባችሁ፣ ዕ
ጥፍ ገንዘብ ያዙ፤ ያ በየ ስልቾቻችሁ
ውስጥ የተገኘው ብር ምናል ባት በስሕ
ተት የመጣ ሊሆን ይችላል። 13ወንድ
ማችሁንም ይዛችሁ ወደ ሰውዬው በቶሎ
ሂዱ። 14ሌላውን ወንድማችሁንና
ብንያምን ይዛችሁ ለመመለስ እንድትችሉ
ሁሉን የሚችል[θ] አምላክ በምሕረቱ የዚያን
ሰው ልብ ያራራላችሁ። እንግዲህ ልጆቼ
ንም ባጣ ምን አደርጋለሁ፤ ያመጣውን
እቀበላለሁ።”
15ሰዎቹም እጅ መንሻውን፣ የብሩን ዕጥፍ
እንዲሁም ብንያምን ይዘው ተነሡ፤ ወደ
ግብፅም በፍጥነት ወረዱ፤ ዮሴፍም ፊት
ቀረቡ። 16ዮሴፍ ብንያምን ከወንድሞቹ
ጋር ባየው ጊዜ የቤቱን አዛዥ፣ “እነዚህን
ሰዎች ወደ ቤት ይዘሃቸው ሂድ፤ ዛሬ
ቀትር ላይ አብረውኝ ስለሚበሉ ፍሪዳ
ተጥሎ ምሳ ይዘጋጅ” አለው።
17አዛዡም ዮሴፍ የነገረውን አደረገ፤
ሰዎቹንም ወደ ዮሴፍ ቤት ወሰዳቸው።
18ሰዎቹም ወደ ዮሴፍ ቤት በመወሰዳቸው
ፈሩ፤ እነርሱም፣ “ወደዚህ የመጣነው፣
ቀደም ሲል እዚህ መጥተን ስንመለስ በየስ
ልቾቻችን ውስጥ ተመልሶ በተጨመረው
ብር ሰበብ ነው። ሰውዬው ጥቃት ሊፈ
ጽምብን፣ አስገድዶ ባሮቹ ሊያደርገንና
አህዮቻችንን ሊቀማን ይፈልጋል” ብለው
ሠጉ።
19ወደ ዮሴፍ ቤት አዛዥ ቀርበው፣ በቤቱ
መግቢያ ላይ አነጋገሩት፤ 20እንዲህም
አሉት፤ ለመጀመሪያ ጊዜ እህል ለመሸ
መት ወደዚህ መጥተን ነበር፤ 21ነገር ግን
ለዐዳር በሰፈርንበት ቦታ የየስልቾቻችንን
አፍ ስንከፍት፣ እያንዳንዳችን በስልቾ
ቻችን አፍ ላይ፣ ብራችንን ሙሉውን አገ
ኘነው። ገንዘቡንም ይኸው መልሰን ይዘን
መጥተናል። 22አሁንም እህል መሸመቻ
የሚሆነን ተጨማሪ ብር ይዘን መጥተ
ናል፤ ያኔ ገንዘቡን በየስልቾቻችን ውስጥ
ማን መልሶ እንዳስቀመጠው ግን አናው
ቅም” አሉት።
23የቤቱ አዛዥም፣ “አይዞአችሁ አትፍሩ፤
በየስልቾቻችሁ ውስጥ ያገኛችሁትን ገን
ዘብ የሰጣችሁ የእናንተም የአባቶቻችሁም
አምላክ (ኤሎሂም) ነው፤ እኔ እንደሆንኩ ብሩ
ን ተቀብያለሁ” አላቸው። ከዚያም
ስምዖንን አውጥቶ አገናኛቸው።
የቤቱ አዛዥ ሰዎቹን ወደ ዮሴፍ ቤት
አስገብቶ እግራቸውን የሚታጠቡበት ውሃ
አቀረበላቸው፤ ለአህዮቻቸውም የሚበሉት
ገፈራ ሰጣቸው። 25ምሳ በዚያ እንደሚበሉ
ተነግሯቸው ስለ ነበር፣ ዮሴፍ በቀትር
ከመግባቱ በፊት እጅ መንሻዎቻቸውን
ለማበርከት ተዘጋጁ።
26ዮሴፍም ወደ ቤቱ ሲገባ ያመጧቸውን
እጅ መንሻዎች አበረከቱለት፤ ወደ መሬት
ዝቅ ብለውም እጅ ነሡት። 27ዮሴፍም
ስለ ደኅንነታቸው ጠየቃቸው፤ ከዚያም “ሽማ
ግሌ አባት እንዳላችሁ ነግራችሁኝ ነበር፤ ደኅና
ነው? አሁንም በሕይወት አለ?” አላቸው።
28እነርሱም መልሰው፣ “አገልጋይህ አባ
ታችን አሁንም በሕይወት አለ፤ ደኅና
ነው’። በማለት ወደ መሬት ዝቅ ብለው
በአክብሮት እጅ ነሡት።
29ዮሴፍ በዐይኑ ሲቃኝ የእናቱን ልጅ
ብንያምን አየና፣ “ያ የነገራችሁኝ ታናሽ ወንድ
ማችሁ ይህ ነው?” ብሎ ጠየቃቸው። ብንያ
ምንም፣ “ልጄ፤ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ይባር
ክህ” አለው። 30ዮሴፍ ወንድሙን በማየቱ
ስሜቱ በጥልቅ ስለ ተነካ፣ ፈጥኖ ከፊታቸው
ገለል አለ፤ ሰወር ያለ ቦታም ፈልጎ፣ ዕልፍኙ
ውስጥ አለቀሰ።
31ፊቱን ከታጠበ በኋላ፣ ተመልሶ፣ ስሜ
ቱን በመቈጣጠር፣ “ማእድ ይቅረብ” አለ።

θ14 ዕብራይስጡ ኤልሻዳይ ይላል።

ዘፍ17፥5፤34፥30
43፥7 ቀ27፤ዘፍ 42፥13:15፤ 44፥19፤ 45፥3
43፥8 ቀ3:6፤ዘፍ 29፥35፤42፥2፤መዝ 33፥18-19
43፥9 ዘፍ42፥37፤ 44፥10:17፤1ሳሙ 23፥20፤ፊሞ1፥18-19
43፥10 ዘፍ45፥9
43፥11 ቀ6፤ዘፍ 24፥10፤32፥13፤37፥25፤ዘፀ30፥23፤1ነገ 10፥2፤ሕዝ27፥17:22
43፥12 ቀ15፤ዘፍ 42፥25፤ዘፀ22፥4:7፤ ምሳ6፥31
43፥13 ቀ3
43፥14 ዘፍ17፥1፤ 42፥24፤ዘዳ13፥7፤መዝ 25፥6፤2ሳሙ18፥33፤ አስ4፥16
43፥15 ቀ12፤ዘፍ 45፥9-13፤47፥2:7፤ ማቴ2፥11
43፥16 ቀ17:24: 26:31፤ዘፍ35፥18፤ 44፥1:4:12፤2ሳሙ 19፥17፤ኢሳ22፥15፤ ሉቃ 15፥23
43፥17 ቀ16
43፥18 ዘፍ32፥11፤ 34፥28፤42፥25:35፤ 44፥14፤44፥9፤14:16: 33፤50፥18፤34፥28
43፥19 ቀ16
43፥20 ዘፍ42፥3
43፥21 ቀ15፤ዘፍ 42፥25
43፥23 ዘፍ24፥12፤ 31፥5፤42፥24:28፤ዘፀ 3፥6
43፥24 ቀ16፤ዘፍ 18፥4
43፥25 ቀ16፤ዘፍ 32፥13
43፥26 ቀ16፤ዘፍ 32፥13፤33፥3፤ማቴ 2፥11
43፥27 ቀ7፤ዘፍ 37፥3
43፥28 ዘፍ44፥24: 27:30፤18፥2፤37፥7፤ ዘፀ18፥7
43፥29 ዘፍ35፥18፤ 42፥13፤ዘኍ6፥25፤ መዝ67፥1፤119፥58፤ ኢሳ30፥18-19፤33፥2
43፥30 ዘፍ29፥11፤ ዮሐ11፥33:38
43፥31 ቀ16፤ዘፍ 45፥1፤ኢሳ30፥18፤ 42፥14፤63፥15፤ 64፥12

32ለዮሴፍ ለብቻው ቀረበለት፤ ለወንድሞቹም ለብቻቸው ቀረበላቸው፤ እንዲሁም ከእርሱ ጋር ለሚበሉት ግብፃውያን ደግሞ ሌላ ገበታ ቀረበላቸው፤ ምክንያቱም ግብፃውያን ከዕብራውያን ጋር አብሮ መመገብን እንደ ጸያፍ ይቈጥሩት ነበር። 33ወንድማማቾቹ ከበኵሩ እስከ ታናሹ እንደየዕድሜአቸው በዮሴፍ ፊት በተርታ ተቀምጠው ነበር፤ በመገረምም እርስ በርሳቸው ተያዩ። 34ከዮሴፍ ገበታ ላይ እየተነሣ ለእያንዳንዳቸው ምግብ ሲቀርብ፣ የብንያም ድርሻ ከሌሎቹ አምስት ዕጥፍ ነበር። እነርሱም እንዲህ ባለ ሁኔታ አብረው ተደሰቱ፤ እስኪረኩም ጠጡ።

## የብር ዋንጫ በስልቻ

44 ከዚህ በኋላ ዮሴፍ ለቤቱ አዛዥ እንዲህ ሲል መመሪያ ሰጠው፤ “የሰዎቹ ስልቻ የሚይዘውን ብር በየስልቻቸው አፍ ክተተው። 2ከዚያም የብር ዋንጫዬን በታናሹ ወንድማቸው ስልቻ አፍ ከእህሉ ዋጋ ጋር ጨምረው።” አዛዡም ዮሴፍ እንዳለው አደረገ።

3ጎሕ ሲቀድ ሰዎቹ ከነአህዮቻቸው ተሸኙ። 4ከከተማው ምንም ያህል ርቀው ሳይሄዱ፣ ዮሴፍ የቤቱን አዛዥ እንዲህ አለው፤ “እነዚያን ሰዎች ቶሎ ድረስባቸውና፣ ‘ለበጎ ነገር ስለምን ክፉ መለሳችሁ? 5ይህ ጌታዬ የሚጠጣበት፣ የተሰወረ ነገርም የሚያውቅበት ጽዋ አይደለምን? የፈጸማችሁት ድርጊት ክፉ ነው’ በላቸው።

6የቤቱ አዛዥም እንደ ደረሰባቸው፣ ልክ እንደተባለው ተናገራቸው። 7እነርሱ ግን እንዲህ አሉት፤ “ጌታችን እንዲህ ያለ ነገር ለምን ይናገራል? እኛ አገልጋዮችህ እንዲህ ያለውን ነገር አናደርገውም። 8ከዚህ ቀደም በየስልቾቻችን አፍ የተገኘውን ብር ከከነዓን እንኳ መልሰን አምጥተናል፤ ታዲያ አሁን ብር ወይም ወርቅ ከጌታህ ቤት እንዴት እንሰርቃለን? 9የጠፋው ዕቃ ከአገልጋዮችህ የተገኘበት ይሙት፤ የቀረነው የጌታችን ባሮች እንሁን።”

10እርሱም “መልካም ነው፤ እንዳላችሁት ይሁን፤ ጽዋው የተገኘበት ሰው ባሪያዬ ይሆናል፤ የቀራችሁት ግን ከበደሉ ነጻ ትሆናላችሁ” አላቸው።

11እያንዳንዱ ሰው ጭነቱን ወዲያውኑ አራግፎ ስልቻውን ፈታ። 12ከዚያም አዛዡ ፍተሻውን ከታላቁ ጀምሮ እስከ ታናሹ ድረስ ቀጠለ። በመጨረሻም፣ ጽዋው በብንያም ስልቻ ውስጥ ተገኘ። 13በዚህ ጊዜ ልብሳቸውን በሐዘን ቀደዱ፤ ሁሉም ስልቾቻቸውን በየአህዮቻቸው ጭነው ወደ ከተማዪቱ ተመለሱ።

43፥32 ዘፍ14፥13፤ 46፥34፤ዘፀ8፥26፤ገላ 2፥12
43፥33 ዘፍ35፥23፤ 42፥13፤44፥12
43፥34 ዘፍ37፥3፤ 2ነገ25፥30፤ሉቃ 15፥23
44፥1 ዘፍ42፥25፤ 43፥16
44፥2 ቊ5፡8፡10፡ 12፡16
44፥3 መሳ19፥9
44፥4 ዘፍ43፥16፤ መዝ 35፥12፤ 38፥20፤ 109፥5፤ ምሳ 17፥13፤ ኤር18፥20
44፥5 ቊ2፤ዘፍ30፥ 27፤ዘዳ18፥10-14
44፥7 ዘፍ18፥25፤ 42፥11
44፥8 ቊ2፤ዘፍ31፥ 30፤42፥13:25፤ 43፥15፤
44፥9 ቊ10፤ዘፍ 42፥11፤31፥32፤ 43፥18
44፥10 ቊ2፡9፡17፡ 33፤ዘፍ43፥9
44፥12 ቊ2፤ዘፍ 31፥34፤43፥16:33
44፥13 ዘፍ37፥29፤ 42፥26
44፥14 ቊ16፤ዘፍ 29፥35፤33፥3፤ 43፥3:18
44፥15 ዘፍ12፥18፤ 30፥27
44፥16 ቊ2:14፡ 22፡24፤ዘፍ37፥8፤42፥ 11፤43፥18፤መዝ 26፥6፤73፥13
44፥17 ቊ10፤ዘፍ 18፥25፤43፥9
44፥18 ቊ16፤ዘፍ 18፥30፤29፥35
44፥19 ዘፍ42፥11፤ 43፥7
44፥20 ዘፍ37፥3፡ 33፤42፥13
44፥21 ዘፍ42፥11፡ 15
44፥22 ቊ16፤ዘፍ 37፥35
44፥23 ዘፍ42፥15፤ 43፥5
44፥24 ቊ16፤ዘፍ 42፥29፤43፥28
44፥25 ዘፍ42፥2
44፥26 ዘፍ43፥5
44፥27 ዘፍ43፥28፤ 46፥19

14ይሁዳና ወንድሞቹ ወደ ዮሴፍ ቤት ሲገቡ፣ እርሱ ገና ከቤቱ አልወጣም ነበር። እነርሱም ከፊቱ መሬት ላይ ተደፉ። 15ዮሴፍም፣ “ለምን እንዲህ ያለ ነገር አደረጋችሁ? እንደ እኔ ያለ ሰው ስውር ነገርን የሚያውቅበት ልዩ ጥበብ እንዳለው አታውቁ ምን?” ሲል ጠየቃቸው።

16ይሁዳም፣ “ከእንግዲህ ለጌታችን ምን ማለት እንችላለን? ምንስ እንመልሳለን? እንዲህ ካለው በደል ንጹሕ መሆናችንን ማስረዳትስ እንዴት ይቻለናል? እግዚአብሔር (ኤሎሂም) የእኛን የአገልጋዮችህን በደል ገልጦአል፤ ከእንግዲህ ጽዋው የተገኘበት ብቻ ሳይሆን ሁላችንም ባሮችህ ነን” አለ።

17ዮሴፍም፣ “ይህንንስ ፈጽሞ አላደርገውም፤ ባሪያዬ የሚሆነው ጽዋው የተገኘበት ሰው ብቻ ነው፤ የቀራችሁት በሰላም ወደ አባታችሁ ተመለሱ” አላቸው።

18ይሁዳም ወደ ዮሴፍ ቀረብ ብሎ፣ “ጌታዬ ሆይ፤ እኔ አገልጋይህ አንዲት ቃል ብቻ ልናገር፤ አንተም የፈርዖን ያህል የተከበርህ ስለሆንህ፣ እባክህን እኔን አገልጋይህን አትቈጣኝ። 19ጌታዬ ‘አባት ወይም ወንድም አላችሁ?’ ብሎ አገልጋዮቹን ጠይቄ ነበር። 20እኛም፣ ‘አዎን፣ ሽማግሌ አባት አለን፤ አባታችንም በስተርጅና የወለደው ትንሽ ልጅ አለው፤ ወንድምየው ሞቶአል፤ ከአንድ እናት ከተወለዱት ልጆች መካከል የተረፈው እርሱ ብቻ ነው፤ አባቱም በጣም ይወደዋል’ ብለንህ ነበር።

21“ከዚያም አንተ አገልጋዮችህን፣ ‘እንዳየው ወደ እኔ አምጡት’ አልኸን። 22እኛም ለጌታዬ ‘ልጁ ከአባቱ ሊለይ አይችልም፤ ከተለየው ደግሞ አባትየው ይሞታል’ አልንህ። 23አንተ ግን እኛን አገልጋዮችህን፣ ‘ታናሽ ወንድማችሁ አብሮአችሁ ወደዚህ ካልመጣ ዳግመኛ ፊቴን አታዩም’ አልኸን። 24እኛም ወደ አገልጋይህ ወደ አባቴ በተመለስን ጊዜ አንተ ጌታዬ ያልኸንን ነገር ነው።

25“ከዚያም አባታችን ‘እስቲ ተመልሳችሁ ጥቂት እህል ሸምቱልን’ ሲለን፤ 26‘መሄድ አንችልም፤ መሄድ የምንችለው ታናሽ ወንድማችን አብሮን ሲሄድ ብቻ ነው። ታናሽ ወንድማችንን ይዘን ካልሄድን በስተቀር፣ የሰውየውን ፊት ማየት አንችልም’ አልነው።

27“አገልጋይህ አባቴም እንዲህ አለን፤ ‘ሚስቴ ሁለት ወንዶች ልጆች እንደ ወለደችልኝ ታውቃላችሁ፤ 28አንዱ በወጣበት

በመቅረቱ፣ “በእርግጥ የአውሬ እራት
ሆኖአል” አልሁ፤ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ይኸ
ው የውሃ ሽታ ሆኖ ቀርቶአል። 29አሁን
ደግሞ ይህን ልጅ ወስዳችሁ አንዳች ጕዳት
ቢደርስበት ሽበቴን በመሪር ሐዘን ወደ
መቃብር[ፊ] ታወርዱታላችሁ።’

30“እንግዲህ አሁን ልጁን ሳንይዝ ወደ
አገልጋይህ ወደ አባቴ ብመለስ፣ ሕይወቱ
ከልጁ ሕይወት ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ስለ
ሆነ፣ 31የልጁን ከእኛ ጋር አለመኖር ሲያይ
አባቴ ይሞታል። ከዚህም የተነሣ እኛ አገ
ልጋዮችህ የአባታችንን ሽበት በመሪር ሐዘን
ወደ መቃብር እናወርደዋለን። 32እኔ አገ
ልጋይ፣ ‘ልጅህን መልሼ ሳላመጣ ብቀር፣
ለዘላለም በደለኛ አድርገህ ቍጠረኝ’ በማ
ለት፣ ስለ ልጁ ደኅንነት በአባቴ ፊት ራ
ሴን ዋስ አድርጌአለሁ።

33“ስለዚህ አሁን፣ አገልጋይህ በልጁ
ፈንታ የአንተ የጌታዬ ባሪያ ሆኜ እዚሁ
ልቅር፤ ልጁ ግን ከወንድሞቹ ጋር ይመለስ።
34ልጁን ሳልይዝ እንዴት ተመልሼ ወደ
አባቴ እሄዳለሁ? ፈጽሞ አላደርገውም፤
እባክህ በአባቴ ላይ የሚደርሰውን መከራ
እንዳይ አታድርገኝ።”

## ዮሴፍ ለወንድሞቹ ራሱን ገለጠ

45 በዚያን ጊዜ ዮሴፍ አጠገቡ በነ
በሩ ሰዎች ፊት ስሜቱን ሊገታ
ባለመቻሉ፣ “እዚህ ያሉትን ሰዎች በሙሉ
አስወጡልኝ” ብሎ ጮኾ ተናገረ፤ ስለዚ
ህም ዮሴፍ ራሱን ለወንድሞቹ በገለጠበት
ጊዜ፣ ከእርሱ ጋር ሌላ ማንም ሰው አል
ነበረም። ዮሴፍም ድምፁን ከፍ
አድርጎ
በማልቀሱ፣ ግብፃውያን ሰሙት፤ ወሬውም
ወደ ፈርዖን ቤተ ሰዎች ደረሰ።

3ዮሴፍም ወንድሞቹን፣ “እኔ ዮሴፍ
ነኝ፤ ለመሆኑ አባቴ እስካሁን በሕይወት
አለ?” ሲል ጠየቃቸው። ወንድሞቹ ግን
በፊቱ ተደናግጠው ስለ ነበር መልስ ሊሰ
ጡት አልቻሉም።

4ዮሴፍም ወንድሞቹን፣ “እስቲ ወደ እኔ
ቀረብ በሉ” አላቸው፤ ወደ እርሱም በቀ
ረቡ ጊዜ እንዲህ አለ፤ “ወደ ግብፅ የሸ
ጣችሁኝ ወንድማችሁ እኔ ዮሴፍ ነኝ፤
5አሁንም በመሸጣችሁ አትቈጩ፤ በራሳ
ችሁም ዐትዘኑ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር (ኤሎ
ሂም) ሕይወት ለማዳን ሲል ከእናንተ አስ
ቀድሞ እኔን ወደዚህ ልኮኛል። 6በምድር
ላይ ራብ ከገባ ይኸው ሁለት ዓመት ሆነ፤
ከዚህ በኋላም የማይታረስባቸውና ሰብል የማ
ይሰበሰብባቸው አምስት ዓመታት ገና አሉ።
7ነገር ግን እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሕ

44፥28 ዘፍ37፥33፤
45፥26፡28፤ 46፥30፤
48፥11
44፥29 ዘፍ37፥35፤
42፥38
44፥30 ዘፍ43፥28፤
1ሳሙ18፥1፤2ሳሙ
1፥26
44፥31 ቍ22፤ዘፍ
37፥35፤42፥11
44፥32 ዘፍ42፥37
44፥33 ቍ10፤ዘፍ
43፥18፤ዮሐ15፥13
44፥34 ዘፍ42፥38፤
አስ8፥6
45፥1 ዘፍ43፥31፤
2ሳሙ13፥9
45፥2 ቍ16፤ዘፍ
29፥11፤ሐሥ7፥13
45፥3 ቍ15፤ዘፍ
43፥7፤44፥20፤ኢዮ
21፥6፤23፥15፤ማቴ
17፥6፤ማር6፥49-50
45፥4 ዘፍ27፥21-
22፤37፥28
45፥5 ቍ7-8፤ዘፍ
42፥21፡22፤50፥20፤
ኢዮ10፥12፤መዝ
105፥17
45፥6 ዘፍ41፥30
45፥7 ቍ5፤ዘፍ49፥
18፤ዘፀ15፥2፤1ሳሙ
14፥45፤25፥9፤2ነገ
13፥5፤19፥4፡30፡31፤
ዕዝ9፥8፡13፤አስ4፥14፤
ኢሳ1፥9፤10፥20፡21፤
11፥11፡16፤25፥9፤46፥
3፤ኤር6፥9፤42፥2፡
50፥20፤ሚክ4፥7፤
5፥7፤7፥7፤ሶፎ2፥7
45፥8 ቍ5፤ዘፍ41፥
41፤መሳ17፥10፤2ነገ
6፥21፤13፥14
45፥9 ዘፍ43፥10፡
15፤ሐሥ7፥14
45፥10 ዘፍ46፥6-
7፡28፡34፤47፥1፡11፡
27፤50፥8፤ዘፀ8፥22፤
9፥26፤10፥24
45፥11 ዘፍ41፥30፤
47፥12፤50፥21፤መዝ
102፥17
45፥12 ዘፍ35፥18፤
ማር6፥50
45፥13 ዘፍ41፥41፤
43፥15፤ሐሥ7፥14
45፥14 ዘፍ29፥13፤
35፥18
45፥15 ቍ3፤ዘፍ
29፥11፡13፤46፥4፤
ሉቃ15፥20
45፥16 ቍ2፤ዘፍ
50፥7፤41፥37፤ሐሥ
7፥13
45፥17 ዘፍ42፥5፡26
45፥18 ቍ20፤ዘፍ
20፥15፤46፥34፤47፥
6፡11፡27፤ዕዝ9፥12፤
መዝ37፥19፤ኢሳ1፥
19፤ኤር40፥4
45፥19 ቍ21፡27፤
ዘፍ46፥5፤ዘኍ7፥3-8

ይወታችሁን በታላቅ ማዳን ለመታደግና[ፐ]
ዘራችሁ ከም ድር ላይ እንዳይጠፋ በ
ማሰብ ከእናንተ አስቀድሞ ወደዚህ ላከኝ።

8“ስለዚህ አሁን ወደዚህ የላከኝ እግዚአብሔር
(ኤሎሂም) እንጂ እናንተ አይደላችሁም፤ እር
ሱም ለፈርዖን እንደ አባት፣ በቤት
ንብረቱ ላይ ጌታ፣ እንዲሁም በግብፅ
ምድር ላይ ገዥ አደረገኝ። 9አሁንም
በፍ ጥነት ወደ አባቴ ተመልሳችሁ እንዲህ
በሉት፤ ‘ልጅህ ዮሴፍ እንዲህ ይላል፤ ‘እግዚ
አብሔር (ኤሎሂም) የመላው ግብፅ ጌታ
አድርጎኛል፤ ስለዚህ ሳትዘገይ ወደ እኔ ና።
10ልጆችህን፣ የልጅ ልጆችህን፣ በጎችህን፣
ፍየሎችህን፣ ከብቶችህንና ያለህን ሁሉ ይዘህ
በአቅራቢያዬ በጌሤም ትኖራለህ። 11ገና
ወደ ፊት የሚመጣ የአምስት ዓመት ራ
ብ ስላለ፣ በዚያ የሚያስፈልጋችሁን እኔ
እሰጣችኋ ለሁ፤ ያለበለዚያ ግን አንተና ቤተ
ሰዎችህ ያንተም የሆነው ሁሉ፣ ችግር ላይ
ትወ ድቃላችሁ።’

12“ፊታችሁ ሆኜ የማናግራችሁ እኔ ዮሴፍ
ራሴ መሆኔን እናንተም ሆናችሁ ወንድሜ
ብንያም በዐይናችሁ የምታዩት ነው።
13በግብፅ ስላለኝ ክብርና ስላያችሁትም
ሁሉ ለአባቴ ንገሩት፤ አባቴንም በፍጥነት
ይዛችሁት ኑ።

14ከዚያም በወንድሙ በብንያም ዐንገት
ላይ ተጠምጥሞ አለቀሰ፤ ብንያምም እያለቀሰ
ዮሴፍን ዐቀፈው። 15የቀሩትንም ወን
ድሞቹን አንድ በአንድ እየሳመ አለቀሰ። ከዚ
ያም ወንድሞቹ ከእርሱ ጋር መጨዋወት
ጀመሩ።

16የዮሴፍ ወንድሞች መምጣት በፈርዖን
ቤተ መንግሥት በተሰማ ጊዜ፣ ፈርዖንና ሹማ
ምንቱ ሁሉ ደስ አላቸው። 17ፈርዖንም
ዮሴፍን እንዲህ አለው፤ “ለወንድሞችህ
እንዲህ ብለህ ንገራቸው፤ ‘እንዲህ አድ
ርጉ፤ አህዮቻችሁን ጭናችሁ ወደ ከነዓን
ምድር ተመለሱ። 18ከዚያም አባታችሁንና
ቤተ ሰባችሁን ይዛችሁ ወደ እኔ ኑ፤
እኔም እጅግ ለም ከሆነው የግብፅ ምድር
እሰጣችኋለሁ፤ በምድሪቱ በረከት ደስ ብሎ
አችሁ ትኖራላችሁ።’ 19“ደግሞም እንዲህ
ብለህ እዘዛቸው፤ ‘ይህን አድርጉ፤ ከግብፅ
ምድር ልጆቻችሁንና ሚስቶቻችሁን የም
ታጓጉዙበት ሠረገላዎች ወስዳችሁ፣ አባታ
ችሁን ይዛችሁት ኑ። 20ስለ ንብረታችሁ
ምንም አታስቡ፣ ከግብፅ ምድር እጅግ
ለም የሆነው የእናንተ ይሆናልና።’ ”

21የእስራኤልም ልጆች ይህንኑ አደረጉ።

[ፊ]29 ቍ31 ላይ ያለውንም ጨምሮ ዕብራይስጡ ሲኦል ይለዋል
[ፐ]7 ወይም በሕይወት እንደ ተረፉ ታላቅ ሰራዊት ለመታደግ

ዮሴፍም ፈርዖን ባዘዘው መሠረት ሠረገላ
ዎች አቀረበላቸው፤ የመንገድም ስንቅ አስ
ያዛቸው:: 22ለእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት
የክት ልብስ ሰጣቸው፤ ለብንያም ግን
ሦስት መቶ ጥሬ ብርና አምስት የክት ልብስ
ሰጠው:: 23ለአባቱም በግብፅ ምድር ከሚ
ገኘው የተመረጠ ነገር በዐሥር አህዮች፣
እንደዚሁም ለመንገዱ ስንቅ የሚሆነው
እህል፣ ዳቦና ሌላ ምግብ በዐሥር እንስት
አህዮች አስጭኖ ሰደደለት:: 24ከዚህ በኋላ
ወንድሞቹን አሰናበታቸው፤ ከእርሱም ሲሰ
ናበቱ፣ መንገድ ላይ እንዳትጣሉ" አላ
ቸው::
25እነርሱም ከግብፅ ወጥተው በከነዓን ምድር
ወደሚኖረው ወደ አባታቸው ወደ ያዕቆብ
መጡ:: 26አባታቸውንም፣ "እነሆ ዮሴፍ በሕ
ይወት አለ፤ እንዲያውም በግብፅ ምድር ሁሉ
ገዥ ሆኖአል" ብለው ነገሩት:: ያዕቆብም
በድንጋጤ ክው አለ፤ ሊያምናቸውም አል
ቻለም:: 27ነገር ግን ዮሴፍ የነገራቸውን
ሁሉ ሲያጫውቱትና እርሱንም ወደ ግብፅ
ለማጓጓዝ ዮሴፍ የላከለትን ሠረገላዎች
ሲያይ የአባታቸው የያዕቆብ መንፈስ ታደሰ::
28ከዚያም እስራኤል፤ "ልጄ ዮሴፍ በሕይወት
አለ፤ ከመሞቴ በፊት ሄጄ ልየው" አለ::

## ያዕቆብ ወደ ግብፅ ሄደ

46 እስራኤልም ጓዙን ሁሉ ጠቅልሎ
ተነሣ፤ ቤርሳቤህም ሲደርስ፣ ለአባቱ
ለይስሐቅ አምላክ (ኤሎሂም) መሥዋዕት ሠዋ::
2እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ሌሊት በራእይ
ለእስራኤል ተገልጦ "ያዕቆብ፣ ያዕቆብ"
ብሎ ጠራው:: እርሱም፣ "እነሆ፣ አለሁ"
አለ:: 3እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፤
"እኔ የአባትህ አምላክ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ነኝ፤
ወደ ግብፅ ለመውረድ አትፍራ፤ በዚያ
ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁና፤ 4አብሬህ ወደ
ግብፅ እወርዳለሁ፤ ከዚያም መልሼ አወጣሃ
ለሁ፤ የዮሴፍ የራሱ እጆችም ዐይኖችህን
ይገጥሚቸዋል::"
5ከዚህ በኋላ ያዕቆብ ከቤርሳቤህ ተነሣ፤
የእስራኤል ወንዶች ልጆችም አባታቸውን
ያዕቆብን፣ ልጆቻቸውንና ሚስቶቻቸውን ፈር
ዖን ሊያዕቆብ በላካቸው ሠረገላዎች ላይ አወ
ጧቸው:: 6ከብቶቻቸውንና በከነዓን ምድር
ያፈሩትን ሀብት ንብረታቸውን ይዘው፣ ያዕ
ቆብና ዘሮቹ በሙሉ ወደ ግብፅ ወረዱ::
7ወደ ግብፅም የወረደው፣ ወንዶች ልጆቹ
ንና ወንዶች የልጅ ልጆቹን፣ ሴቶች ልጆቹንና
ሴቶች የልጅ ልጆቹን ማለት ዘሮቹን ሁሉ
ይዞ ነው::
8ወደ ግብፅ የወረዱት የእስራኤል ልጆች፣

45፥20 ቍ18፤ዘፍ 46፥6፡32
45፥21 ቍ19፤ዘፍ 42፥25
45፥22 ዘፍ24፥53፤ 37፥3፤41፥14፤መሳ 14፥12፡13፤2ነገ5፥22
45፥23 ዘፍ24፥10፤ 42፥25፡26
45፥24 ዘፍ42፥21-22
45፥25 ዘፍ13፥1፤ 42፥29
45፥26 ዘፍ41፥41፤ 44፥28፤1ነገ10፥7
45፥27 ቍ19
45፥28 ዘፍ44፥28፤ ሉቃ16፥31
46፥1 ቍ5፤ዘፍ21፥ 14፤31፥42፡54
46፥2 ዘፍ15፥1፤ 17፥5፤22፥1
46፥3 ዘፍ12፥2፤ 15፥1፤26፥2፤28፥13፤ ዘፀ1፥7
46፥4 ቍ29፤ዘፍ 15፥16፤28፥13፤45፥ 14-15፤50፥1
46፥5 ቍ1፤ዘፍ 21፥14፤45፥19
46፥6 ዘፍ12፥5፤ 45፥20፤ዘኍ20፥15፤ ዘዳ26፥5፤ኢሱ24፥4፤ 1ሳሙ12፥8፤መዝ 105፥23፤ኢሳ52፥4 ፤ሐሥ7፥15
46፥7 ቍ6፤ ዘፍ13፥10፤45፥10
46፥8 ዘፍ29፥32፤ 35፥26፤ዘፀ1፥1፤ዘኍ 26፥4
46፥9 ዘፀ6፥14፤ዘኍ 1፥20፤26፥5፡6፡7፤ 1ዜና5፥3
46፥10 ዘፍ29፥33፤ ዘፀ6፥15፤ዘኍ26፥12፡ 13፡14
46፥11 ዘፍ29፥34፤ ዘፀ6፥16፡19፤ዘኍ3፥ 17፡20፡21፡27፡33፤ 4፥29፡38፤26፥57፤ 1ዜና6፥19፤23፥12
46፥12 ዘፍ29፥35፤ 38፥3፡4፡7፡29፡30፤ ዘኍ26፥19፡21፤ 1ዜና2፥5፤ማቴ1፥3
46፥13 ዘፍ30፥18፤ ዘኍ26፥23፡24፤መሳ 10፥1፤1ዜና7፥1
46፥14 ዘፍ30፥20
46፥15 ዘፍ25፥20፤ 29፥31-35፤30፥21
46፥16 ዘፍ30፥11፤ ዘኍ1፥25፤26፥15
46፥17 ዘፍ30፥13
46፥18 ዘፍ16፥1፤ 30፥10
46፥19 ዘፍ29፥6፤ 44፥27
46፥20 ዘፍ41፥45፡ 51፡52፤ዘኍ26፥28-37

ያዕቆብ ዘሮቹ እነዚህ ናቸው፡-

የያዕቆብ የበኵር ልጅ ሮቤል::
9የሮቤል ልጆች፡-
ሄኖኅ፣ ፈሉሶ፣ አስሮን እና ከርሚ ናቸው::
10የስምዖን ልጆች፡-
ይሙኤል፣ ያሚን፣ ኦሃድ፣ ያኪን፣
ጾሐርና ከከነዓናዊቷ ሴት የተወለደው
ሳኡል ናቸው::
11የሌዊ ልጆች፡-
ጌድሶን፣ ቀዓትና ሜራሪ ናቸው::
12የይሁዳ ልጆች፡-
ዔር፣ አውናን፣ ሴሎም፣ ፋሬስ እና
ዛራ ናቸው:: ነገር ግን ዔርና አውናን
በከነዓን ምድር ሞቱ::
13የይሳኮር ልጆች፡-
ቶላ፣ ፉዋ፣[ሀ] ዮብና ሺምሮን ናቸው፤
14የዛብሎን ልጆች፡-
ሴሬድ፣ ኤሎንና ያሕልኤል ናቸው፤
15እነዚህ ወንዶች ልጆች ያዕቆብ በሰሜን
ምዕራብ መስጴጦምያ ሳለ፣ ልያ የወለደች
ለት ናቸው:: ሴቷን ዲናን ጨምሮ፣ የወን
ዶችና የሴቶች ልጆቹ ቍጥር ሠላሳ
ሦስት ነው::
16የጋድ ልጆች፡-
ጽፎን፣[ለ] ሐጊ፣ ሹኒ፣ ኤስቦን፣
ዔሪ፣ አሮዲና አርኤሊ ናቸው፤
17የአሴር ልጆች፡-
ዩምና፣ የሱዋ፣ የሱዊና በሪዓ ናቸው፤
እኅታቸውም ሤራሕ ናት፤
የበሪዓ ልጆች፡-
ሐቤርና መልኪኤል ናቸው፤
18እነዚህ ዐሥራ ስድስት ልጆች ሁሉ፣ ላባ
ለልጁ ለልያ ከሰጣት ከዘለፋ ላይ ያዕቆብ
የወለዳቸው ናቸው::

19የያዕቆብ ሚስት የራሔል ልጆች፡-
ዮሴፍና ብንያም ናቸው፤ 20በግብፅም
የሄልዮቱ[ሐ] ከተማ ካህን የጶጥፌራ ልጅ
አስናት፣ ምናሴንና ኤፍሬምን ለዮሴፍ
ወለደ ችለት::
21የብንያም ልጆች፡-
ቤላ፣ ቤኬር፣ አስቤል፣ ጌራ፣ ናዕማን፣
አኪ፣ ሮስ፣ ማንፌን
ሑፊምና አርድ ናቸው::
22እነዚህ ዐሥራ አራቱ፣ ራሔል ለያዕ
ቆብ የወለደችለት ልጆችና የልጅ ልጆች
ናቸው::

[ሀ]13 ከኦሪት ሳምራውያንና ከሱርስቱ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን (1ዜና 7፥1 ይመ) የማሶሬቲክ ጽሑፍ ግን *ፉቫ* ይለዋል::
[ለ]16 ከኦሪት ሳምራውያንና ከሰብዓ ሊቃናት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን (ዘኍ 26፥15 ይመ) የማሶሬቲክ ጽሑፍ ግን *ጸፎን* ይለዋል
[ሐ]20 ሆሲዮፖሊስን ያመለክታል

23የዳን ልጅ፡-
ሑሺም ነው፤
24የንፍታሌም ልጆች፡-
ያሕጽኤል፣ ጉኒ፣ ዬጽርና ሺሌም ናቸው፤
25እነዚህ ሰባቱ ልጆች ሁሉ ላባ ለልጁ
ለራሔል ከሰጣት ከባላ ላይ ያዕቆብ የወ
ለዳቸው ናቸው፡፡
26ከያዕቆብ ጋር ወደ ግብፅ የሄዱት የገዛ
ዘሮቹ ብዛት ሥልሳ ስድስት ሲሆን ይህ ቍጥር
ግን የልጆቹን ሚስቶች አይጨምርም፡፡
27ዮሴፍ በግብፅ የወለዳቸውን ሁለት ልጆች[መ]
ጨምሮ፣ ወደ ግብፅ የወረደው የያዕቆብ ቤተ
ሰብ ቍጥር ሰባ ነበር፡፡
28ያዕቆብም ወደ ጌሤም ለመሄድ መመ
ሪያን ይቀበል ዘንድ፣ ይሁዳን አስቀድሞ
ወደ ዮሴፍ ላከው፡፡ እነርሱም ጌሤም ሲደ
ርሱ፣ 29ዮሴፍ ሠረገላውን አዘጋጅቶ፤ አባቱን
እስራኤልን ለመቀበል ወደ ጌሤም አመራ፡፡
ዮሴፍ አባቱ ዘንድ እንደ ደረሰ፣ ዐንገቱ ላይ[ረ]
ተጠምጥሞ ለረጅም ጊዜ አለቀሰ፡፡
30እስራኤልም ዮሴፍን፣ "በሕይወት መኖ
ርህን ስላየሁ፣ ከእንግዲህ ብሞትም አይቈ
ጨኝ" አለው፡፡
31ከዚህ በኋላ ዮሴፍ ወንድሞቹንና የአባ
ቱን ቤተ ሰዎች እንዲህ አላቸው፤ "ወደ
ፈርዖን ወጥቼ አናግረዋለሁ፤ እንዲህም
እለዋለሁ፣ 'በከነዓን ምድር የሚኖሩት ወን
ድሞቼና የአባቴ ቤተ ሰዎች ወደ እኔ
መጥተዋል፡፡ 32ሰዎቹ ከብት የሚጠብቁ
ስለሆኑ እረኞች ናቸው፤ ሲመጡም በጎቻቸ
ውን፣ ፍየሎቻቸውንና ከብቶቻቸውን እን
ዲሁም ያላቸውን ሁሉ ይዘው መጥተ
ዋል፡፡' 33ፈርዖን አስጠርቶአችሁ፣ 'ሥራችሁ
ምንድን ነው?' ብሎ ቢጠይቃችሁ፣ 34እና
ንተ 'እኛ ባሮችህ ሥራችን ከልጅነታችን
ጀምሮ ልክ እንደ አባቶቻችን ከብት ማር
ባት ነው' ብላችሁ መልሱለት፡፡ ከዚያም
ግብፃውያን ከብት አርቢዎችን እንደ ጸያፍ
ስለሚቈጥሩ፣ በጌሤም ምድር እንድትኖሩ
ይፈቅድላችኋል፡፡"

47 ዮሴፍም ወደ ፈርዖን ሄዶ፣ "አባ
ቴና ወንድሞቼ በጎቻቸውን፣ ፍየ
ሎቻቸውን እንዲሁም ያላቸውን ሁሉ
ይዘው ከከነዓን አገር መጥተው በጌሤም ሰፍ
ረዋል" አለው፡፡ 2ከወንድሞቹም መካከል
አምስቱን መርጦ፣ ፈርዖን ፊት አቀረባ
ቸው፡፡
3ፈርዖን የዮሴፍን ወንድሞች፣ "ሥራ
ችሁ ምንድነው?" ሲል ጠየቃቸው፡፡
እነርሱም ፈርዖንን፣ "እኛ አገልጋዮችህ
ልክ እንደ አባቶቻችን ከብት አርቢዎች ነን"
አሉት፤ 4ደግሞም፣ "በከነዓን ምድር ራብ
እጅግ የጸና በመሆኑ በጎችና ፍየሎች
የሚሰማሩበት በማጣታቸው፣ ለጊዜው እዚህ
ለመኖር መጥተናል፤ አሁንም ባሮችህ በጌ
ሤም ምድር እንድንኖር እንድትፈቅድልን እን
ለምንሃለን" አሉት፡፡
5ፈርዖንም ዮሴፍን እንዲህ አለው፤ "አባ
ትህና ወንድሞችህ ወደ አንተ መጥተዋል፤
6የግብፅ ምድር እንደ ሆነ በእጅህ ነው፤
አባትህንና ወንድሞችህን ምርጥ በሆነው ምድር
አስፍራቸው፤ በጌሤም ይኑሩ፡፡ ከመካከላቸው
ልዩ ችሎታ ያላቸው መኖራቸውን የምታ
ውቅ ከሆነ፣ የከብቶቼ ኀላፊዎች አድርጋ
ቸው፡፡"
7ከዚህ በኋላ ዮሴፍ አባቱን ያዕቆብን ቤተ
መንግሥት አግብቶ በፈርዖን ፊት አቀረበው፤
ያዕቆብ ፈርዖንን ከመረቀው[ሰ] በኋላ 8ፈርዖን፣
"ለመሆኑ ዕድሜህ ምን ያህል ነው?" ሲል
ያዕቆብን ጠየቀው፡፡
9ያዕቆብም ለፈርዖን፣ "በምድር ላይ በእ
ንግድነት ያሳለፍኩት ዘመን 130 ዓመት
ነው፤ ይህም አባቶቼ በእንግድነት ከኖሩበት
ዘመን ጋር ሲነጻጸር አጭር ነው፤ ችግር የበ
ዛበትም ነበር" ሲል መለሰለት፡፡ 10ከዚያም
ያዕቆብ ፈርዖንን መርቆ፣ ተሰናብቶት ወጣ፡፡
11ዮሴፍም አባቱንና ወንድሞቹን በግብፅ
እንዲኖሩ አደረገ፤ ፈርዖን በሰጠውም ትእ
ዛዝ መሠረት ምርጥ ከሆነው ምድር ራም
ሴን በርስትነት ሰጣቸው፡፡ 12ዮሴፍም ለአ
ባቱ፣ ለወንድሞቹና ለመላው የአባቱ ቤተ
ሰዎች በልጆቻቸው ቍጥር ልክ ቀለብ
እንዲሰፈርላቸው አደረገ፡፡

### የራቡ ዘመንና የዮሴፍ አመራር

13በመላው ምድር እህል ባለመኖሩ ራቡ
እየጸና ሄደ፤ ከዚህ የተነሣም ግብፅና ከነዓን
በራብ እጅግ ተጐዱ፤ 14ዮሴፍ የግብፅና
የከነዓን ሰዎች እህል በመሸመት የከፈ
ሉትን ገንዘብ ሁሉ ሰብስቦ ወደ ፈርዖን
ቤተ መንግሥት አስገባ፡፡ 15የግብፅና የከ
ነዓን ሕዝቦችም ገንዘባቸው ባለቀ ጊዜ፣
ግብፃውያን ሁሉ ወደ ዮሴፍ ቀርበው፣ 'የምን
በላው እህል ስጠን፤ ገንዘባችን አልቆብ
ናል፤ ዐይንህ እያየ እንዴት በራብ እን
ለቅ?" አሉት፡፡
16ዮሴፍም፣ "ከብቶቻችሁን አምጡ፤ ገን
ዘባችሁ ካለቀ በከብቶቻችሁ ለውጥ እህል

[መ]27 ከዕብራይስጡ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ሰብዓ ሊቃናት ግን *ዘጠኝ ልጆች* ይለዋል
[ሠ]27 ከዕብራይስጡ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን (ዘፀ 1፥5 እና ማብ ይመ) ሰብዐ ሊቃናት ግን (ሐሥ 7፥14 ይመ) *ሰባ አምስት* ይለዋል
[ረ]29 ዕብራይስጡ *በላዩ ላይ* ይለዋል
[ሰ]7 ወይም *ሰላምታ ካቀረበ*

46፥21 ዘኍ26፥38-41፤1ዜና7፥6-12፤8፥1:3
46፥22 ዘፍ29፥6
46፥23 ዘፍ30፥6፤ ዘኍ26፥42
46፥24 ዘፍ30፥8
46፥25 ዘፍ24፥61፤ 30፥8
46፥26 ቍ5-7፤ዘፀ 1፥5፤ዘዳ10፥22
46፥27 ዘፍ34፥30፤ 41፥45፤ሐሥ7፥14
46፥28 ዘፍ43፥3፤ 45፥10
46፥29 ቍ1:4:30፤ ዘፍ29፥11፤32፥28፤ 41፥43፤47፥29:31፤ ሉቃ15፥20
46፥30 ቍ29፤ዘፍ 44፥28
46፥31 ዘፍ42፥13፤ 45፥10
46፥32 ዘፍ37፥2፤ 45፥20፤ 47፥3
46፥33 ዘፍ47፥3
46፥34 ዘፍ34፥10፤ 42፥11፤43፥32፤ 45፥10፤47፥3
47፥1 ዘፍ42፥13፤ 46፥31
47፥2 ዘፍ43፥15
47፥3 ዘፍ42፥11፤ 46፥32:33
47፥4 ዘፍ46፥34፤ ዘፀ12፥10፤ሩት1፥1፤ 1ነገ18፥5፤ኤር14፥5-6፤ኢል1፥18
47፥6 ዘፍ13፥9፤ 34፥10፤39፥4፤45፥ 18፤ዘፀ18፥21:25፤ ዘዳ1፥13:15፤2ዜና 19፥5፤መዝ15፥2
47፥7 ቍ10፤ዘፍ 43፥15፤2ሳሙ14፥ 22፤19፥39፤1ነገ 8፥66
47፥9 ዘፍ3፥17፤ 25፥7፤መዝ39፥4:12፤ 89፥47፤ኢዮ8፥9
47፥10 ቍ7
47፥11 ዘፍ45፥10፤ 18፤ዘፀ1፥11፤12፥37፤ ዘኍ33፥3:5
47፥12 ዘፍ45፥11
47፥13 ዘፍ12፥10፤ 41፥30
47፥14 ዘፍ41፥34: 36፤ዘፀ7፥23፤8፥24፤ ኤር43፥9
47፥15 ቍ16:18: 19፤ዘፍ41፥57፤ዘፀ 16፥3
47፥16 ቍ15:18: 19
47፥17 ዘፍ12፥16፤ ዘፀ14፥9

እሰጣችኋለሁ አለ። [17]ስለዚህ ከብቶቻቸውን
ወደ ዮሴፍ አመጡ፤ እርሱም በፈረሶቻቸው፣
በበጎቻቸው፣ በፍየሎቻቸው፣ በከብቶቻቸ
ውና በአህዮቻቸው ለውጥ እህል ሰጣቸው።
በከብቶቻቸው ልዋጭ ባገኙት ምግብ የዚ
ያን ዓመት ራብ እንዲወጡት አደረገ።
[18]ያም ዓመት ካለፈ በኋላ ሕዝቡ በሚቀ
ጥለው ዓመት ወደ ዮሴፍ መጥተው እንዲህ
አሉት፣ "እንግዲህ ከጌታችን የምንሰው
ረው ምንም ነገር የለም፤ ገንዘባችን አል
ቆአል፤ ከብቶቻችንንም አስረክበንሃል፤ እንግ
ዲህ ለጌታችን የምንሰጠው፣ ከመሬታች
ንና ከእኛ ከራሳችን በስተቀር፣ አንዳች
ነገር የለም። [19]ታዲያ፣ እያየኸን እንዴት
እንለቅ? መሬታችንስ ለምን ጠፍ ሆኖ
ይቅር? እኛንና መሬታችንን ውሰድና በለ
ውጡ እህል ስጠን፤ እኛ የፈርዖን ገባሮች
እንሁን፤ መሬታችንም የእርሱ ርስት ይሁን፤
እኛም እንዳንሞት መሬታችንም ጠፍ ሆኖ
እንዳይቀር የምንዘራው ዘር ስጠን።"
[20]ስለዚህ ዮሴፍ የግብፅን ምድር ሁሉ
ለፈርዖን ገዛለት፤ ራቡም እጅግ ስለጸና
ባቸው ግብፃውያን ሁሉ አንዳቸውም ሳይ
ቀሩ መሬታቸውን ሸጡ፤ ምድሪቱም የፈ
ርዖን ርስት ሆነች። [21]ዮሴፍም የግብፅን
ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር[ሸ] የፈርዖን ገባር
አደረገው። [22]ሆኖም ዮሴፍ የካህናቱን መሬት
አልገዛም፤ ምክንያቱም ካህናቱ ከፈርዖን ቋሚ
ድርጎ ስለሚያገኙና ፈርዖን ከሚሰጣቸው
ድርጎ በቂ ምግብ ስለ ነበራቸው ነው፤ ከዚ
ህም የተነሣ መሬታቸውን አልሸጡም።
[23]ዮሴፍ ሕዝቡን እንዲህ አላቸው፤ "እነሆ፣
ዛሬ እናንተንም መሬታችሁንም ለፈርዖን
ገዝቻችኋለሁና ይህን ዘር ወስዳችሁ በመሬት
ላይ ዝሩ። [24]መከሩ በሚሰበሰብበት ጊዜ ግን
ከአምስት እጅ አንዱን ለፈርዖን ታስገባላ
ችሁ፤ ከአምስት እጅ አራቱን ደግሞ ለመ
ሬታችሁ ዘር፣ እንዲሁም ለራሳችሁ፣
ለቤተ ሰቦቻችሁና ለልጆቻችሁ ምግብ ታደ
ርጉታላችሁ።"
[25]እነርሱም፣ "እንግዲህ ሕይወታችንን አትር
ፈህልናል፤ በጌታችን ፊት ሞገስ ካገኘን፣ ለፈ
ርዖን ገባሮች እንሆናለን" አሉት።
[26]ስለዚህ ዮሴፍ የምርቱ አንድ አም
ስተኛ ለፈርዖን እንዲገባ የሚያዝ የመ
ሬት ሕግ አወጣ፤ ይህም ሕግ እስከ ዛሬ ይሠ
ራበታል። በዚያን ጊዜ በፈርዖን እጅ ያል
ገባው መሬት የካህናቱ ብቻ ነው።
[27]በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን በግብፅ
አገር በጌሤም ይኖሩ ነበር፤ በዚያም ሀብት
ንብረት አፈሩ፤ ቍጥራቸውም እጅግ እየ
በዛ ይሄድ ጀመር።

47፥18 ቀኍ15፡16
47፥19 ቀኍ15፡16፡ 21፡25፤ዘፍ42፥2
47፥20 ዘፍ12፥10
47፥21 ቀኍ19
47፥22 ቀኍ26፤ዘዳ 14፥28-29
47፥23 ነህ5፥3፤ኢሳ 55፥10፤61፥11
47፥24 ዘፍ41፥34
47፥25 ቀኍ19፤ዘፍ 32፥5
47፥26 ቀኍ22፤ዘፍ 41፥34
47፥27 ዘፍ1፥22፤ 12፥2፤17፥6፤33፥19፤4 5፥10፡18
47፥28 ዘፍ25፥7፤ መዝ105፥23
47፥29 ዘፍ19፥19፤ 24፥2:27፤27፥2፤32፥ 5፤46፥29፤መሳ1፥ 24፤2ሳሙ2፥6
47፥30 ዘፍ15፥15፤ 23፥20፤25፥9፤29፥ 16፤50፥25፤ዘፀ13፥ 19፤ኢሱ24፥32፤ሐሥ 7፥15-16
47፥31 ዘፍ21፥23፤ 32፥10፤24፥3፤46፥ 29፤ኢሱ2፥20፤መሳ 15፥12፤1ሳሙ24፥ 21፤30፥15፤1ነገ1፥ 47፤ዕብ11፥21
48፥1 ዘፍ41፥ 52፤ዕብ11፥21
48፥2 ቀኍ8፡9፡11፡ 14፡20
48፥3 ዘፍ17፥1፤ 28፥13፡19፤32፥29
48፥4 ዘፍ12፥2:7፤ 15፥7፤17፥6፤28፥13
48፥5 ዘፍ29፥32፡ 33፤41፥50-52፤1ዜና 5፥1
48፥7 ዘፍ25፥20፤ 35፥19፤42፥38፤ሩት 1፥2፤1ሳሙ16፥4
48፥8 ቀኍ2፡10
48፥9 ዘፍ24፥60፤ 33፥5

[28]ያዕቆብ በግብፅ ዐሥራ ሰባት ዓመት ኖረ፤
ዕድሜውም አንድ መቶ አርባ
ሰባት
ዓመት ነበር። [29]እስራኤልም የሚሞትበት
ጊዜ መቃረቡን እንደ ተረዳ ልጁን ዮሴፍን
አስጠርቶ እንዲህ አለው፤ "በአንተ ዘንድ
ሞገስ ካገኘሁ እጅህን በጭኔ ላይ አኑረህ፣
በጎነትንና ታማኝነትን ልታደርግልኝ ቃል
ግባልኝ፤ በምሞትበት ጊዜ በግብፅ አትቅ
በረኝ፤ [30]እኔም ከአባቶቼ ጋር ሳንቀላፋ፣
ከግብፅ አውጥተህ እነርሱ በተቀበሩበት
ቦታ ቅበረኝ።"
ዮሴፍም፣ "እሺ፣ እንዳልከኝ አደርጋ
ለሁ" አለ።
[31]ያዕቆብም፣ "በል ማልልኝ" አለው። ዮሴ
ፍም ማለለት፤ እስራኤልም በዐልጋው ራስጌ
ላይ ሆኖ ጐንበስ አለ።[ቀ]

### ምናሴና ኤፍሬም

48 ከጥቂት ጊዜ በኋላም፣ "አባትህ
ታሞአል" ተብሎ ለዮሴፍ ስለ
ተነገረው ሁለቱን ልጆቹን ምናሴንና ኤፍ
ሬምን ይዞ ሄደ። [2]ለያዕቆብ፣ "ልጅህ
ዮሴፍ ወደ አንተ መጥቶአል" ተብሎ በተ
ነገረው ጊዜ፣ እስራኤል ተበረታትቶ ዐል
ጋው ላይ ተቀመጠ።
[3]ያዕቆብም ዮሴፍን እንዲህ አለው፤
"ሁሉን የሚችል አምላክ[በ] በከነዓን ምድር
ሎዛ በምትባል ቦታ ተገለጠልኝ፤ ባረከኝም፤
[4]እንዲህም አለኝ፤ 'ፍሬያማ አደርግሃለሁ፣
ይህችንም ምድር ከአንተ በኋላ ለሚነሡ
ዘሮችህ የዘላለም ርስት አድርጌ እሰጣቸዋ
ለሁ።'
[5]"ወደዚህ ከመምጣቴ በፊት በግብፅ
የወ ለድሃቸው ሁለቱ ልጆችህ ከእንግዲህ
የእኔ ልጆች ሆነው ይቈጠራሉ፤ ሮቤልና
ስምዖን ልጆቼ እንደ ሆኑ ሁሉ፣
ኤፍሬምና ምና ሴም ልጆቼ ይሆናሉ።
[6]ከእነርሱ በኋላ የሚወለዱልህ ልጆች ግን፣
የአንተ ይሁኑ፤ በርስት ድልድላቸው ግን
በወንድሞቻቸው ስም ይቈጠራሉ። [7]ከሰሜ
ን ምዕራብ መስ ጴጦምያ መልስ ኤፍራታ
ለመድረስ ጥቂት ሲቀረኝ፣ እናትህ ራሔል
በከነዓን ምድር ሞታብኝ ዐዘንሁ። እኔም
ወደ ኤፍራታ ማለት ወደ ቤተልሔም
በሚወስደው መን ገድ ዳር ቀበርኋት።"
[8]እስራኤልም የዮሴፍን ልጆች ባየ ጊዜ፣
"እነዚህ እነማን ናቸው?" ሲል ጠየቀ፤
[9]ዮሴፍም፣ "እነዚህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) የሰጠ
ኝ

[ሸ]21 ከኦሪተ ሳምራውያንና ከሰብዐ ሊቃናት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን (ቩልጌትንም ይመ) የማሶሬቲኩ ጽሑፍ ግን *ሕዝቡን ወደ ከተሞች አጋዘ* ይለዋል።
[ቀ]31 ወይም *እስራኤልም በዐልጋው ራስጌ በኩል ሰገደ*
[በ]3 ዕብራይስጡ *ኤልሻዳይ* ይላል

ልጆች ናቸው” ብሎ ለአባቱ መለሰለት፤
እስራኤልም፣ “አቅርባቸውና ልመርቃቸው”
አለ፡፡
10በዚህ ጊዜ እስራኤል ዐይኖቹ በእር
ጅና ምክንያት በመድከማቸው አጥርቶ
ማየት ይሳነው ነበር፤ ስለዚህ ዮሴፍ ልጆ
ቹን አባቱ ዘንድ አቀረባቸው፤ አባቱም
ስሞ ዐቀፋቸው፡፡
11እስራኤልም ዮሴፍን፣ “ዐይንህን እንደ
ገና ዐያለሁ ብዬ አላሰብኩም ነበር፤ እግዚአ
ብሔር (ኤሎሂም) ግን ልጆችህን ጭምር ለማ
የት አበቃኝ” አለው፡፡
12ዮሴፍም ልጆቹን ከእስራኤል ጒልበት
ፈቀቅ በማድረግ አጐንብሶ በግንባሩ መሬት
ላይ ተደፋ፡፡ 13ከዚያም ዮሴፍ ሁለቱን ልጆ
ቹን ይዞ ኤፍሬምን ከራሱ በስተ ቀኝ፣
ከእስራኤል በስተ ግራ፣ ምናሴን
ደግሞ
ከራሱ በስተ ግራ፣ ከእስራኤል በስተ ቀኝ
በኩል አቀረባቸው፡፡ 14እስራኤል ግን ቀኝ
እጁን በታናሹ በኤፍሬም ራስ ላይ አኖረ፤
ግራ እጁንም በቀኝ እጁ ላይ አስተላልፎ
በበኵሩ በምናሴ ራስ ላይ አኖረ፡፡
15ከዚህ በኋላ ዮሴፍን ባረከ፤ እንዲህም
አለው፤

“አባቶቼ አብርሃምና ይስሐቅ በፊቱ
የተመላለሱት እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣
ለእኔም እስከ ዛሬ ድረስ
በዘመኔ ሁሉ እረኛ የሆነኝ
አምላክ (ኤሎሂም)፣
16ከጒዳትም ሁሉ የታደገኝ መልአክ፣
እርሱ እነዚህን ልጆች ይባርክ፤
እነርሱም በስሜ፣
በአባቶቼ በአብርሃምና በይስሐቅ ስም ይጠሩ
፤
በምድር ላይ እጅግ ይብዙ፡፡

17ዮሴፍ፣ አባቱ ቀኝ እጁን በኤፍሬም ራስ
ላይ ማድረጉን ሲያይ ተከፋ፤ ከኤፍሬም
ራስ ላይ አንሥቶ በምናሴ ራስ ላይ ለማ
ኖር የአባቱን እጅ ያዘ፤ 18ዮሴፍም፣ “አባቴ
ሆይ፤ እንዲህ አይደለም በኵሩ ይህኛው ስለ
ሆነ፣ ቀኝ እጅህን እርሱ ራስ ላይ አድ
ርግ” አለው፡፡
19አባቱ ግን፣ “ዐውቃለሁ፤ ልጄ ዐውቃ
ለሁ፤ እርሱም እኮ ሕዝብ ይሆናል፤ ታላቅም
ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ታናሽ ወንድሙ ከእ
ርሱ ይበልጣል፤ ዘሮቹም ታላቅ ሕዝቦች ይሆ
ናሉ” ብሎ እምቢ አለው፡፡ 20በዚያን ዕለት
ባረካቸው፤ እንዲህም አላቸው፤

“በአንተ ስም እስራኤል እንዲህ ብሎ
ይመርቃል፤
‘እግዚአብሔር (ኤሎሂም) እንደ ኤፍሬምና
እንደ ምናሴ ያድርጋችሁ፡፡’”
በዚህ ሁኔታም ኤፍሬምን ከምናሴ አስ
ቀደመው፡፡
21ከዚህ በኋላ እስራኤል ዮሴፍን እንዲህ
አለው፤ እኔ የምሞትበት ጊዜ ተቃርቦ
አል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
ከእናንተ ጋር ይሆናል፤ ወደ
አባቶቻችሁም ምድር መልሶ ያገባችኋል፡፡
22እነሆ በሰይፌና በቀ ስቴ ከአሞራውያን
እጅ የወሰድኳትን ዐምባ ከወንድሞችህ ድርሻ
አብልጬ ለአንተ ሰጥ ቼሃለሁ፡፡”†

## ያዕቆብ ልጆቹን ባረከ

49፥1-28 ማገብ - ዘዳ 33፥1-29

49 ከዚህ በኋላ ያዕቆብ ልጆቹን ሁሉ
አስጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ “በኋ
ለኛው ዘመን ምን እንደሚደርስባችሁ እነግራ
ችሁ ዘንድ ተሰብሰቡ፡፡

2“እናንተ የያዕቆብ ልጆች ሆይ፤
ተሰብሰቡና ስሙ፤
አባታችሁ እስራኤልንም አድምጡ፤

3“ሮቤል፣ አንተ የበኵር ልጄ ነህ፤
ኀይሌና የጒብዝናዬም መጀመሪያ፤
በክብር ትልቃለህ በኀይልም
ትበልጣለህ፡፡
4እንደ ውሃ የዋለልህ ነህና እልቅና
አይኖርህም፤
የአባትህን መኝታ ደፍረሃል፤
ምንጣፌንም አርክሰሃል፡፡

5ስምዖንና ሌዊ ወንድማማቾች፣
ሰይፎቻቸው‡ የዐመፅ መሣሪያዎች ናቸው፡፡
6ወደ ሸንጎአቸው አልግባ፤
ጉባኤያቸው ውስጥ አልገኝ፤
በቍጣ ተነሣሥተው ሰዎችን ገድለዋል፤
የበሬዎችንም ቋንጃ እንዳሻቸው
ቈራርጠዋል፡፡
7እጅግ አስፈሪ የሆነ ቍጣቸው፣
ጭከና የተሞላ ንዴታቸው የተረገመ
ይሁን፤
በያዕቆብ እበትናቸዋለሁ፤
በመላው እስራኤልም አሠራጫቸዋለሁ፡፡

8“ይሁዳ፣ⁿ ወንድሞችህ ይወድሱሃል፤
እጅህም የጠላቶችህን ዐንገት ዐንቆ ይይዛል፤
የአባትህ ልጆች በፊትህ ተደፍተው
ይሰግዱልሃል፡፡
9“አንተ የአንበሳ ደቦል ይሁዳ፤
ከዐደንህ የምትመለስ ልጄ፣

48፥10 ዘፍ27፥1፡ 27፤29፥13
48፥11 ቊ2፤ዘፍ 44፥28፤50፥23፤ኢዮ 42፥16፤መዝ103፥17፤ 128፥6
48፥12 ዘፍ19፥1፤ 33፥3፤37፥10፤ 50፥23፤ኢዮ3፥12
48፥13 መዝ16፥8፤ 73፥23፤110፥1፤ማቴ 25፥33
48፥14 ቊ2፡17፡ 18፤ዘፍ25፥23፤29፥ 32፤41፥51
48፥15 ዘፍ5፥22፤ 24፥60፤49፥24፤ 2ሳሙ5፥2፤መዝ23፥ 1፤80፥1፤ኢሳ40፥11፤ ኤር23፥4
48፥16 ዘፍ12፥2፤ 13፥4፤16፥7፤24፥50፤ 28፥3፡13፤2ሳሙ4፥9፤ 1ዜና5፥1፤መዝ71፥4፤ ኤር15፥21፤ሕዝ47፥ 13፤ዳን3፥17፤ዕብ 11፥21
48፥17 ቊ13፡14
48፥18 ቊ14
48፥19 ዘፍ12፥2፤ 17፥20፤25፥23
48፥20 ቊ2፤ዘፍ 24፥60፤41፥51፤ዘሌ 9፥22፤ዘኍ2፥18፡20፤ 6፥23፤10፥23፤ዘዳ10፥ 8፤21፥5፤ሩት4፥11፤ ኤር31፥9፤ዕብ11፥21
48፥21 ዘፍ15፥16፤ 26፥3፤28፥13፤ዘዳ30፥ 3፤መዝ126፥1፤ኤር 29፥14፤ሕዝ34፥13
48፥22 ዘፍ34፥26፤ 37፥8፤ኢሱ24፥32፤ ዮሐ4፥5
49፥1 ዘኍ24፥14፤ ዘዳ31፥29፤ኤር23፥ 20፤ዳን28፥45
49፥2 ቊ16፡28፤ ኢ ሱ24፥1፤መዝ 34፥11
49፥3 ዘፍ29፥32፤ 34፥19፤41፥51፤ዘዳ 21፥17፤መዝ78፥51፤ 105፥36
49፥4 ዘፍ29፥29፤ 34፥5፤ኢሳ57፥20፤ ኤር49፥23
49፥5 ዘፍ29፥33፡ 34፤34፥25፤ምሳ4፥17
49፥6 ዘፍ34፥26፤ ኢሱ11፥6፡9፤2ሳሙ 8፥4፤1ዜና18፥4፤ መዝ1፥1፤ምሳ1፥15፤ ኤፌ5፥11
49፥7 ዘፍ34፥7፡25፤ ኢሱ19፥1፡9፤21፥1-42
49፥8 ዘፍ9፥25፤ 29፥35፤ዘዳ28፥48፤ 1ዜና5፥2
49፥9 ቊ27፤ዘኍ 23፥24፤24፥9፤ኢዮ 38፥39፤መዝ7፥2፤10፥

†22 ወይም *ከወንድሞችህ ድርሻ አብልጬ ለአንተ አንድ ክፍል እሰጥሃለሁ*
‡5 በዕብራይስጥ የዚህ ቃል ትርጒም አይታወቅም
ⁿ8 *ይሁዳ* የሚለው ቃል *ውዳሴ* የሚል ትርጒም ካለው የዕብራይስጥ ቃል የመጣ ሲሆን፣ ከዚሁ ቃል ጋር አንድ ዐይነት ድምፅ አለው

እንደ አንበሳ ያደፍጣል፤ በምድርም ላይ
ይተኛል፤
እንደ እንስት አንበሳም ያደባል፤
ታዲያ ማን ሊቀሰቅሰው ይደፍራል?
10በትረ መንግሥት ከይሁዳ እጅ አይጠ
ወጣም፤
የገዥነት ምርኵዝም ከእግሮቹ መካከል።
ገዥነት የሚገባው እስኪመጣ ድረስ፣[ነ]
ሕዝቦች ሁሉ ይታዘዙታል።
11አህያውን በወይን ግንድ፣
ውርንጫውንም በምርጡ የወይን ሐረግ
ቅርንጫፍ ላይ ያስራል፤
ልብሱን በወይን ጠጅ፣
መጐናጸፊያውንም በወይን ጭማቂ ያጥባል።
12ዐይኖቹ ከወይን ጠጅ የቀሉ፣
ጥርሶቹም ከወተት ይልቅ የነጡ ይሆናሉ።

13"ዛብሎን፣ በባሕር ዳር ይኖራል፤
የመርከቦች መጠጊያም ይሆናል፤
ወሰኑም እስከ ሲዶና ይደርሳል።

14"ይሳኮር፣ ዐጥንተ ብርቱ አህያ፣
በጭነት[ኘ] መካከል የሚተኛ፣
15ማረፊያ ቦታው መልካም፣
ምድሪቱም አስደሳች መሆኗን ሲያይ፣
ትከሻውን ለሸክም ያመቻቻል፤
ተገድዶም ያገለግላል።

16"ዳን፣[አ] ከእስራኤል ነገዶች እንደ አንዱ
ሆኖ፣
በራሱ ሕዝብ ላይ ይፈርዳል።
17ዳን የመንገድ ዳር እባብ፣
የመተላለፊያም መንገድ እፉኝት ነው፤
ጋላቢው የኋሊት እንዲወድቅ፣
የፈረሱን ሰኰና ይነክሳል።
18"እግዚአብሔር ሆይ (ያህዌ)፤ ማዳንህን
እጠባበቃለሁ።

19"ጋድን[ከ] ወራሪዎች አደጋ ይጥሉበታል፤
እርሱ ግን ዱካቸውን ተከታትሎ
ብድሩን ይመልሳል።

20"አሴር ማእደ ሰፊ ይሆናል፤
ለነገሥታትም የሚስማማ ምግብ
ያቀርባል።

21"ንፍታሌም ነጻ እንደ ተለቀቀች፣
የሚያማምሩም ግልገሎች[ኸ]
እንደምትወልድ ሚዳቋ ነው።

22ዮሴፍ፤ ፍሬያማ የወይን ተክል፣
በምንጭ ዳር የተተከለ ወይን ነው።
ሐረጎቹ ቅጥርን ያለብሳሉ።[ወ]
23ቀስተኞች በጭካኔ አጠቁት፤
በጥላቻም ነደፉት።
24ነገር ግን በያዕቆብ ኀያል አምላክ ክንድ፣[ዐ]
እረኛው በሆነው በእስራኤል ዐለት፣
ቀስቱ ጸና፤
ጠንካራ ክንዱም ቀለጠፈ።

25አንተን በሚረዳህ በአባትህ አምላክ፣
በሚባርክህ፣ ሁሉን ማድረግ በሚችል
አምላክ፣[ዘ]
ከላይ ከሰማይ በሚገኝ ረድኤት፣
ከምድር ጥልቅ በሚገኝ በረከት፣
ከማሕፀንና ከጡት በሚገኝ ምርቃት
ይባርክሃል።
26ከጥንት ተራሮች በረከት፣
ከዘላለም ኰረብቶች ምርቃት ይልቅ፣
የአባትህ በረከት ይበልጣል፤[ዠ]
ይኸ ሁሉ በዮሴፍ ራስ ላይ ይውረድ፤
በወንድሞቹ መካከል አለቃ በሆነውም
ግንባር ላይ ይረፍ።[የ]

27ብንያም፣ ነጣቂ ተኵላ ነው፤
ያደነውን ማለዳ ይበላል፤
የማረከውን ማታ ይከፋፈላል።

28እነዚህ ሁሉ ዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል
ነገዶች ናቸው። ይህም እያንዳንዳቸውን ተገቢ
በሆነው በረከት አባታቸው ሲባርካቸው
የተናገረው ቃል ነው።

## የያዕቆብ መሞት

29ከዚህ በኋላ ያዕቆብ እንዲህ ሲል አዘዛ
ቸው፤ "እነሆ፤ ወደ ወገኖቼ የምሰበሰብበት
ጊዜ ደርሶአል፤ በኬጢያዊው በኤፍሮን ዕርሻ
ውስጥ ባለችው ዋሻ ከአባቶቼ ዘንድ ቅበሩኝ፤
30ይህ በከነዓን ምድር፣ በመምሬ አጠገብ፣
በማክፌላ ዕርሻ ውስጥ ያለው ዋሻ፣ የመ
ቃብር ቦታ እንዲሆን አብርሃም ከኬጢያ
ዊው ኤፍሮን ላይ ከነዕርሻ ቦታው የገዛው
ነው። 31በዚያ አብርሃምና ሚስቱ ሣራ
ተቀብረዋል፤ በዚያ ይስሐቅና ሚስቱ ርብቃ
ተቀብረዋል፤ እኔም ልያን የቀበርኋት እዚ
ያው ነው፤ 32ዕርሻውና ዋሻው የተገዙት
ከኬጢያውያን[ደ] ላይ ነው።"
33ያዕቆብ እነዚህን ቃላት ለልጆቹ ተናግሮ
እንዳበቃ፣ እግሮቹን በዐልጋው ላይ ሰብስቦ፣
የመጨረሻ ትንፋሹን ተነፈሰ፤ ወደ
ወገኖ
ቹም ተሰበሰበ።

9፤17፥12፤22፥13፤104፥21፤ሕዝ19፥2:5፤ሚክ5፥8፤ራእ5፥5፤
49፥10 ዘኍ24፥17፥19፤መሳ1፥1-2፤20፥18፤1ዜና5፥2፤28፥4፤መዝ2፥9፤60፥7፤72፥8-11፤98፥3፤108፥8፤110፥2፤ኢሳ2፥4፤26፥18፤42፥1:4፤45፥22፤48፥20፤49፥6፤51፥5፤ሕዝ21፥27
49፥11 ዘዳ8፥8፤32፥14፤መሳ5፥10፤10፥4፤2ነገ18፥32፤ኢሳ63፥2፤ዘካ9፥9
49፥12 ማሕ5፥12
49፥13 ዘፍ10፥19፤30፥20
49፥14 ዘፍ30፥18፤መሳ5፥16፤መዝ68፥13
49፥15 ኢሱ19፥17-23፤1ነገ4፥6፤5፥13፤9፥21፤ሕዝ29፥18፤ኢሳ14፥2፤31፥8
49፥16 ቀኁ2፤ዘፍ30፥6
49፥17 ቀኁ19፤መሳ18፥27፤ኤር18፥17፤አሞ9፥3
49፥18 ዘፍ45፥7፤መዝ40፥1-3፤119፥166፥174
49፥19 ቀኁ17፤ዘፍ30፥11
48፥20 ዘፍ30፥13፤ኢሳ25፥6፤ኢዮ29፥6
49፥21 ዘፍ30፥8፤ኢዮ39፥1
49፥22 ዘፍ17፥6፤30፥24፤መዝ80፥10፤128፥3፤ሕዝ19፥10
49፥23 ዘፍ27፥41፤37፥24፤1ዜና10፥3
49፥24 ዘፍ48፥15፤ዘዳ32፥4፥15፥18፥31፤ኢዮ29፥20፤34፤132፥2:5፤1ሳሙ2፥2፤2ሳሙ22፥32፤መዝ18፥2:31:34፤19፥14፤78፥35፤89፥26፤132፥2:5፤144፥1፤ኢሳ1፥24፤10፥34፤17፥10፤26፥4፤30፥29፤44፥8፤49፥26፤60፥16፤63፥12፤ዕን1፥12
49፥25 ዘፍ17፥1፤27፥28፤28፥13፤ዘፀ18፥4፤ዘዳ7፥13፤28፥4፤መዝ27፥9፤107፥38፤ምሳ10፥22፤ኢሳ66፥11
49፥26 ዘፍ37፥8፤1ዜና5፥1፤ሕዝ47፥13፤ዕን3፥6
49፥27 ቀኁ9፤ዘፍ35፥18፤ዘኍ31፥11፤ዘዳ2፥35፤መሳ8፥24፤20፥12-13፤ኢሱ7፥21፤8፥2፤22፥8፤ዕን1፥8፤ሶፎ3፥3
49፥28 ቀኁ2፤ዘፍ27፥4
49፥29 ዘፍ15፥15፤25፥8፡9፤50፥16:25፤2ሳሙ2፥32፤19፥37 49፥30 ዘፍ13፥18፤23፥4:9:20 49፥31 ዘፍ23፥19: 20፤24፥67፤25፥9፤29፥16
49፥32 ዘፍ10፥15 49፥33 ዘፍ25፥8 ፤ሐሥ7፥15

[ነ]10 ወይም ሴሎ እስኪመጣ ድረስ ወይም ክብር የሚገባው እስኪመጣ ድረስ
[ኘ]14 ወይም በሰፈር ሜዳ የሚነድ እሳት
[አ]16 ዳን ማለት ፍትሕ ይሰጣል ማለት ነው
[ከ]19 ጋድ ማለት ማጥቃት እንዲሁም ወራሪ ሰራዊት ማለት ነው
[ኸ]21 ወይም ነጻ፤ ውብ ቃሎችን የሚናገር
[ወ]22 ወይም ዮሴፍ የዱር የፈረስ ግልገል፣ በምንጭ ዳር ያለ የፈረስ ግልገል፣ በባለ ዕርከን ኰረብታ ላይ የዱር አህያ ነው
[ዐ]23-24 ወይም ቀስተኞች ያጠቃሉ... ያስፈነጥራሉ... ይኖራሉ... ይቈያሉ
[ዘ]25 ዕብራይስጡ ሻዳይ ይለዋል
[ዠ]26 ...ከአያት ቅድማያቶቼ... ታላቅ ነው
[የ]26 ወይም ከ... የተለየ
[ደ]32 ወይም ከኬጢ ልጆች

50 ዮሴፍ በአባቱ ፊት ተደፍቶ አለ
ቀሰ፣ ሳመውም። 2ከዚያም የአባቱ
የእስራኤል ሬሳ እንዳይፈርስ ባለ መድኀኒት
የሆኑ አገልጋዮቹ በመድኀኒት እንዲቀቡት
አዘዘ። ባለ መድኀኒቶቹም እንዳይፈርስ
ሬሳውን፣ በመድኀኒት ቀቡት። 3ሬሳው እን
ዳይፈርስ መድኀኒት መቀባቱ በአገሩ ልማድ
መሠረት አርባ ቀን ወሰደባቸው፤ ግብፃው
ያንም ሰባ ቀን አለቀሱለት።
4የሐዘኑ ጊዜ እንዳበቃ ዮሴፍ የፈርዖንን
ቤተ ሰዎች እንዲህ አላቸው፤ “በፊታችሁ
ሞገስ አግኝቼ ከሆነ፣ ለፈርዖን እንዲህ
ብላችሁ ንገሩልኝ፣ 5‘የምሞትበት ጊዜ ስለ
ተቃረበ፣ በከነዓን ምድር ራሴ ቈፍሬ ባዘ
ጋጀሁት መቃብር እንድትቀብረኝ’ ሲል
አባቴ አስምሎኛል፤ ስለዚህ ወደዚያ ሄጄ
አባቴን ልቅበር ከዚያም እመለሳለሁ።”
6ፈርዖንም፣ “ባስማለህ መሠረት ሄደህ አባ
ትህን ቅበር” አለው።
7ከዚያም ዮሴፍ አባቱን ለመቅበር ወጣ፤
የፈርዖን ሹማምንት በሙሉ፣ የቤተ መንግ
ሥቱ ከፍተኛ ባለ ሥልጣኖች እንዲሁም የግ
ብፅ ከፍተኛ ባለ ሥልጣኖች ሁሉ ተከተሉት።
8እንደዚሁም የዮሴፍ ቤተ ሰዎች፣ ወን
ድሞቹና ሌሎችም የአባቱ ቤተ ሰዎች
በሙሉ አብረውት ሄዱ። በጌሤም የቀሩ
ት
ሕፃናት ልጆቻቸው፣ የበግ፣ የፍየልና የከ
ብት መንጋዎቻቸው ብቻ ነበሩ። 9እንዲሁም
ሠረገሎችና ፈረሰኞች[ጀ] አብረውት ወጡ፤
አጀቡም እጅግ ብዙ ነበረ።
10እነርሱም በዮርዳኖስ ማዶ ካለው
አጣድ ከተባለው ዐውድማ ሲደርሱ፣ ድም
ፃቸውን ከፍ በማድረግ ምርር ብለው አለ
ቀሱ፤ ዮሴፍም በዚያ ለአባቱ ሰባት ቀን
ልቅሶ ተቀመጠ። 11በዚያ የሚኖሩ ከነዓ
ናውያን በአጣድ ዐውድማ የተደረገውን
ልቅሶ ባዩ ጊዜ፣ “ይህ ለግብፃውያን መራራ
ልቅሶአቸው ነው” አሉ። በዮርዳኖስ አጠገብ
ያለው የዚያ ቦታ ስም አቤል[ገ] ምጽራይም
ተብሎ መጠራቱም ከዚሁ የተነሣ ነበር።
12የያዕቆብ ልጆችም አባታቸው እንዳዘዛ
ቸው አደረጉ፤ 13አስከሬኑን ወደ ከነዓን ምድር
ወስደው አብርሃም ከኬጢያዊው ከኤፍሮን
ላይ ከነዕርሻው በገዛው፣ በመምሬ አጠ
ገብ፣ በማክፌላ ዕርሻ በሚገኘው ዋሻ ውስጥ
ቀበሩት።
14ዮሴፍ አባቱን ከቀበረ በኋላ፣ ከወን
ድሞቹና ለአባቱ ቀብር አብረውት ሄደው
ከነ በሩት ሁሉ ጋር ወደ ግብፅ ተመለሰ።

50፥1 ዘፍ29፥11፤ 46፥4
50፥2 ቁ-26፤2ዜና 16፥14፤ ማቴ26፥12፤ ማር16፥1፤ዮሐ19፥39-40
50፥3 ዘፍ37፥34፤ ዘዳ1፥3
50፥4 ቁ-7፤ዘፍ 27፥41፤30፥27፤32፥5
50፥5 ቁ-24፤ዘፍ 24፥37፤47፥31፤2ሳሙ 18፥18፤2ዜና16፥14፤ ኢሳ22፥16፤ማቴ8፥21 ፤27፥60
50፥7 ቁ-4፤ዘፍ45፥16
50፥8 ቁ-14፤ ዘፍ45፥10
50፥9 ዘፍ41፥43
50፥10 ዘፍ27፥41፤ 37፥34፤ዘሌ10፥6፤ ዘኍ15፥20፤ሩት 3፥2፤1ሳሙ31፥13፤ 2ሳሙ1፥17፤3፥33፤ 24፥18፤2ዜና35፥25፤ 1ነገ22፥10፤ኢዮ2፥ 13፤ሕዝ3፥15፤32፥ 16፤ሐሥ8፥2፤
50፥11 ዘፍ10፥18፤ 37፥34
50፥12 ዘፍ49፥29
50፥13 ዘፍ13፥18፤ 23፥9፥20፤25፥9
50፥14 ቁ-8
50፥15 ቁ-17፤ዘፍ 9፥5፤27፥41፤37፥28፤ ሶፎ3፥11፤1ጴጥ3፥9
50፥16 ዘፍ49፥29
50፥17 ቁ-15፤ዘፍ 28፥13፤29፥11፤ማቴ 6፥14
50፥18 ዘፍ37፥7፤ 43፥18
50፥19 ዘፍ30፥2፤ ዘፀ32፥34፤ሮሜ12፥ 19፤ዕብ10፥30
50፥20 ዘፍ37፥20፤ 45፥5፤አስ4፥14፤ኢሳ 4፥14፤10፥7፤ሚክ 4፥11-12፤ሮሜ8፥28
50፥21 ዘፍ34፥3፤ 45፥11፤ኤፌ4፥32
50፥22 ዘፍ25፥7፤ ኢሱ24፥29
50፥23 ዘፍ41፥51፡ 52፤48፥11፡12፤ዘኍ 26፥29፤27፥1፤32፥ 39፡40፤36፥1፤ዘዳ 3፥15፤ኢሱ13፥31፤ 17፥1፤መሳ5፥14፤ ኢዮ42፥16
50፥24 ቁ-5፤ዘፍ 15፥14፤13፥17፤17፥ 19፤12፥7፤15፥16፤ ሩት1፥6፤መዝ35፥2፤ 106፥4፤ኢሳ38፥14
50፥25 ዘፍ24፥37፤ 47፥29-30፤49፥29፤ ዕብ11፥22
50፥26 ቁ-2፤ዘፍ 25፥7፤ዘዳ1፥6

## ዮሴፍ ወንድሞቹን እንደማይበቀላቸው አረጋገጠ

15የዮሴፍ ወንድሞች ከአባታቸው ሞት
በኋላ፣ “ከፈጸምንበት በደል የተነሣ ዮሴፍ
ቂም ይዞ ቢበቀለን ምን እናደርጋለን?” ተባ
ባሉ። 16ስለዚህ እንዲህ የሚል መልእክት
ወደ ዮሴፍ ላኩ፤ “አባትህ ከመሞቱ በፊት
እንዲህ የሚል ትእዛዝ አስተላልፎ ነበር፤
17‘ለዮሴፍ፣ “ወንድሞችህ በአንተ ላይ የፈ
ጸሙትን ኀጢአትና ክፉ በደል ይቅር
በላቸው” ብላችሁ ንገሩት።’ አሁንም፣ የእ
ኛን የአባትህን አምላክ (ኤሎሂም) አገልጋዮች ኀጢ
አት ይቅር በለን።” መልእክታቸው ሲደ
ርሰው ዮሴፍ አለቀሰ።
18ከዚያም ወንድሞቹ መጡና በፊቱ ተደ
ፍተው፣ “እኛ የአንተ ባሮች ነን” አሉት።
19ዮሴፍ ግን እንዲህ አላቸው፤ “አትፍሩ፤
እኔን በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ቦታ ማን አስቀ
መጠኝ? 20እናንተ እኔን ለመጒዳት አስባ
ችሁ አድርጋችሁት ነበር፤ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
ግን ዛሬ እንደሚታየው ሁሉ የብዙዎችን ሕይ
ወት ለማዳን ለበጎ ነገር አዋለው። 21አሁ
ንም ቢሆን አትፍሩ፤ ለእናንተና ለልጆቻ
ችሁ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አደርግላች
ኋለሁ” በማለት አረጋግጦ፣ በደግ ቃል
አናገራቸው።

## የዮሴፍ መሞት

22ዮሴፍ ከአባቱ ቤተ ሰቦች ጋር በግብፅ
ተቀመጠ፤ አንድ መቶ ዐሥር ዓመትም ኖረ፤
23የኤፍሬምንም የልጅ ልጆች እስከ ሦስት
ትውልድ ድረስ አየ። የምናሴ ልጅ ማኪር
የወለዳቸውም ልጆች በዮሴፍ ጭን ላይ
ተወለዱ።
24ከዚህ በኋላ ዮሴፍ ወንድሞቹን፣ “እነሆ፤
የመሞቻዬ ጊዜ ተቃርቦአል፤ እግዚአብሐ
ርም (ኤሎሂም) በረድኤቱ ይጐበኛችሁና ከዚህ
አገር ያወጣችኋል፤ ለአባቶቻችን ለአብርሃም፣
ለይ ስሐቅና ለያዕቆብ በመሐላ ተስፋ ወደ
ሰጣቸው ምድር ያገባችኋል” አላቸው።
25ዮሴፍም የእስራኤልን ልጆች፣ “እግዚአብሔር
(ኤሎሂም) በረድኤቱ ያስባችኋል፤ በዚያን ጊዜ ዐፅ
ሜን ከዚህ አገር ይዛችሁ እንድትወጡ”
ሲል አስማላቸው።
26ዮሴፍም በመቶ ዐሥር ዓመቱ ሞተ፤
ሬሳው እንዳይፈርስ በአገሩ ደንብ በመድኀኒ
ት ከደ ረቀ በኋላ ሣጥን ውስጥ
አስገብተው በግ ብፅ ምድር አስቀመጠ
ት።

[ጀ] 9 ወይም *ሠረገለኞች*

[ገ] 11 *አቤል ምጽራይም* ማለት *የግብፃውያን ሐዘን* ማለት ነው

# ኦሪት ዘፀአት

### እስራኤላውያን በጭቆና ሥር

1 ቤተ ሰቦቻቸውን ይዘው ከያዕቆብ ጋር
ወደ ግብፅ የሄዱት የእስራኤል ልጆች
ስሞች እነዚህ ናቸው፡ኛ [2]ሮቤል፣ ስምዖን፣
ሌዊ፣ ይሁዳ፣ [3]ይሳኮር፣ ዛብሎን፣ ብንያም፣
[4]ዳን፣ ንፍታሌም፣ ጋድና አሴር። [5]የያዕ
ቆብ ዘር ጠቅላላ ብዛት ሰባ[ሀ] ሲሆን፣ ዮሴፍ
ግን ቀደም ብሎ በግብፅ ነበረ።
[6]ከጊዜ በኋላ ዮሴፍና ወንድሞቹ ያም
ትውልድ በሙሉ ሞቱ፤ [7]ይሁን እንጂ እስ
ራኤላውያን እየተዋለዱ በዙ፤ ቍጥራቸው
እጅግ ከመጨመሩም የተነሣ የግብፅን
ምድር ሞሏት።
[8]በግብፅም፣ ስለ ዮሴፍ የማያውቅ አዲስ
ንጉሥ ነገሠ። [9]እርሱም ሕዝቡን እንዲህ
አላቸው፤ "እነሆ፤ እስራኤላውያን በቍጥር
በልጠውናል፤ ከእኛም ይልቅ እየበረቱ ነው፤
[10]ቍጥራቸው እንዳይጨምር፣ ጦርነት ቢነሣ
ከጠላቶቻችን ጋር አብረው እንዳይወጉንና
ከምድሪቱም ኰብልለው እንዳይሄዱ ዘዴ እን
ፈልግ።"
[11]ስለዚህ እያስጨነቁ የግዳጅ ሥራ
የሚያሠሯቸውን አሠሪ አለቆች ሾሙባ
ቸው። እስራኤላውያንም ፊቶምና ራምሴ
የተባሉ ንብረት ማከማቻ ከተሞችን ለፈ
ርዖን ሠሩለት። [12]ነገር ግን ባስጨነቋቸው
መጠን የእስራኤላውያን ቍጥር በዛ፤ በም
ድሪቱም እየተስፋፉ ሄዱ፤ ከዚህም የተነሣ
ግብፃውያኑ እስራኤላውያንን እጅግ ፈሯ
ቸው፤ [13]ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታም ያሠ
ሯቸው ጀመር። [14]ጭቃ በማስቦካት፣ ጡብ
በማሠራትና በእርሻም ሁሉ እያስጨነቁ
ከባድ ሥራ እንዲሠሩ በማድረግ ሕይወታ
ቸውን አስመረሩ፤ ግብፃውያኑ በሚያሠሯ
ቸው ከባድ ሥራ ሁሉ ፈጽሞ አይራሩላቸ
ውም ነበር።
[15]የግብፅም ንጉሥ ሲፓራና ፉሐ የተ
ባሉትን ዕብራውያን ሴቶች አዋላጆች እን
ዲህ አላቸው፤ [16]"የዕብራውያንን ሴቶች በማ
ማጫው ድንጋይ ላይ በምታዋልዱበት ጊዜ
የሚወለደው ሕፃን ወንድ ከሆነ ግደሉት፤
ሴት ከሆነች ግን በሕይወት ትኑር።" [17]አዋ
ላጆቹ ግን እግዚአብሔርን (ኤሎሂም) ስለፈሩ የግ
ብፅ ንጉሥ ያዘዛቸውን አልፈጸሙም፤ ወንዶ
ቹንም ልጆች በሕይወት እንዲኖሩ ተዉ
አቸው። [18]ንጉሡም አዋላጆቹን ጠርቶ፣
"ለምንድን ነው ወንዶቹን ልጆች በሕይ
ወት እንዲኖሩ የተዋችኋቸው? አላቸው።
[19]እነርሱም፣ "የዕብራውያን ሴቶች እንደ
ግብፃውያን ሴቶች አይደሉም፤ ብርቱዎች
ስለ ሆኑ አዋላጆች ከመድረሳቸው በፊት
ይወልዳሉ" ሲሉ ለፈርዖን መለሱለት።
[20]ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
ለአዋላጆቹ መልካም ሆነላቸው፤ ሕዝቡም
በቍጥር እየበዛና እያየለ ሄደ። [21]አዋላጆ
ቹም እግዚአብሔርን (ኤሎሂም) በመፍራታቸው
ቤተ ሰብ ሰጣቸው።
[22]ፈርዖንም፣ "የሚወለደውን ወንድ ልጅ[ለ]
ሁሉ ዐባይ ወንዝ ውስጥ ጣሉት፤ ሴት ልጅ
ሁሉ ግን በሕይወት ትኑር" ሲል ሕዝቡን
አዘዘ።

### የሙሴ መወለድ

2 በዚያን ጊዜ ከሌዊ ነገድ የሆነ አንድ
ሰው አንዲት ሌዋዊት ሴት አገባ።
[2]እርሷም ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ሕፃኑ
መልከ መልካም መሆኑን ባየች ጊዜ ሦስት
ወር ሸሸገችው። [3]ከዚያ በላይ ልትሸሽገው
ባልቻለች ጊዜ ግን የደንገል ቅርጫት
ወስዳ፣ በዝፍትና በቅጥራን ለቀለቀችው፤
ሕፃኑንም በውስጡ አስተኝታ ቅርጫቱን
ዐባይ ወንዝ ዳር ቄጠማ መካከል አስቀ
መጠችው። [4]የሕፃኑም እኅት የሚደርስበ
ትን ነገር ለማወቅ ራቅ ብላ ቆማ ታይ
ነበር።
[5]በዚህ ጊዜ የፈርዖን ልጅ ልትታጠብ
ወደ ዐባይ ወንዝ ወረደች፤ በምትታጠ
ብበትም ጊዜ ደንገጥሮቿ በወንዙ ዳር
ወዲያና ወዲህ ይሉ ነበር፤ በቄጠማውም
መካከል የተቀመጠ ቅርጫት አይታ ከደንገ
ጥሮቿ አንዷን እንድታመጣው ላከቻት።
[6]ቅርጫቱን ስትከፍተው ሕፃኑን በውስጡ
አየች፤ ያለቅስ ስለ ነበርም አዘነችለትና፣
"ከዕብራውያን ሕፃናት አንዱ መሆን አለ
በት" አለች።
[7]የሕፃኑ እኅት ለፈርዖን ልጅ፣ "ሕፃ
ኑን እያጠባች የምታሳድግልሽ ከዕብራውያን
ሴቶች መካከል ሞግዚት ላምጣልሽን?
አለቻት።

1፥1 ዘፍ46፥8
1፥4 ዘፍ35፥22-26፤ ዘኍ1፥20-43
1፥5 ዘፍ46፥26
1፥6 ዘፍ50፥26፤ ሐሥ 7፥15
1፥7 ቍ9፤ዘፍ12፥2፤ ዘዳ7፥13፤ሕዝ16፥7
1፥8 ኤር43፥11፤ 46፥2
1፥9 ቍ7፤ ዘፍ26፥16
1፥10 ዘፍ15፥13፤ ዘፀ3፥7፤18፥11፤ መዝ64፥2፤71፥10፤ 83፥3፤105፥24-25፤ ኢሳ53፥3፤ሐሥ7፥17-19
1፥11 ዘፍ15፥13፤ 47፥11፤ዘፀ2፥11፤ 3፥7፤5፥4፡10፡13፡14፤6፥6-7፤ኢሱ9፥27፤ 1ነገ9፥21፤1ዜና22፥2፤ ኢሳ60፥10፤1ነገ9፥19፤ 2ዜና8፥4
1፥13 ቍ14፤ ዘፍ15፥13-14፤ ዘፀ5፥21፤16፥3፤ ዘሌ25፥43፡46፡53፤ ዘዳ4፥20፤26፥6፤ 1ነገ8፥51፤ መዝ129፥1፤ ኢሳ30፥6፤48፥10፤ ኤር11፥4
1፥14 ዘፍ11፥3፤ ዘፀ2፥23፤3፥9፤ ዘኍ20፥15፤ዘዳ26፥6፤ 1ሳሙ10፥18፤ 2ነገ13፥4፤ዕዝ9፥9፤ ኢሳ14፥3፤ መዝ66፥11፤81፥6፤ ሐሥ7፥19
1፥15 ዘፍ35፥17
1፥16 ቍ22
1፥17 ቍ21፤ 1ሳሙ22፥17፤ምሳ16፥6፤ ዳን3፥16-18፤ ሐሥ4፥18-20፤5፥29
1፥19 ዘሌ19፥11፤ ኢሱ2፥4-6፤ 1ሳሙ19፥14፤ 2ሳሙ17፥20
1፥20 ምሳ11፥18፤ 22፥8፤መክ8፥12፤ ኢሳ3፥10፤ ዕብ6፥10
1፥21 ቍ17፤ 1ሳሙ2፥35፤ 2ሳሙ7፥11፡27-29፤ 1ነገ11፥38፤14፥10
1፥22 ቍ16፤ ዘፍ41፥1፤ሐሥ7፥19
2፥1 ቍ2፤ ዘፍ29፥34፤ዘፀ6፥20፤ ዘኍ26፥59
2፥2 ዘፍ39፥6፤ ዕብ11፥23
2፥3 ዘፍ6፥14፤ 41፥2፤ኢዮ8፥11፤ ኢሳ18፥2፤ ሐሥ7፥21
2፥4 ዘፀ15፥20
2፥5 ዘፀ7፥15፤8፥20

[ሀ]5 የማሶሬቱ ቅጅ (ዘፍ46፥27 ይመ)፣ የሙት ባሕር ጥቅልል እንዲሁም የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም (ሐሥ7፥14 እና የዘፍ 46፥7 ማብ ይመ)፣ *ሰባ አምስት* ይላሉ።
[ለ]22 የማሶሬቱ ቅጅ፣ ኦሪተ ሳምራውያን፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም እንዲሁም ታርጕም *ከዕብራውያን የሚወለደውን* ይላሉ።

8የፈርዖንም ልጅ፣ “መልካም፣ ሂጂ” አለ
ቻት። ልጂቱም ሄዳ የሕፃኑን እናት ይዛ
መጣች። 9የፈርዖንም ልጅ ሴቲቱን፣
“ይህን ሕፃን ወስደሽ እያጠባሽ አሳድጊልኝ፤
ደመ ወዝ እከፍልሻለሁ” አለቻት። ሴትዮ
ዋም ሕፃኑን ወስዳ አሳደገችው። 10ሕፃኑም
ባደገ ጊዜ ወደ ፈርዖን ልጅ አመጣችው
ልጇም ሆነ፤ እርሷም፣ “ከውሃ አውጥቼዋለ
ሁና” ስትል ስሙን ሙሴ[ሐ] ብላ ጠራችው።

## ሙሴ ወደ ምድያም ምድር ሸሸ

11ሙሴ ካደገ በኋላ አንድ ቀን ወገኖቹ
ወደሚገኙበት ስፍራ ወጣ፤ በዚያም ተገድ
ደው ከባድ ሥራ ሲሠሩ ተመለከተ፤ ዕብ
ራዊ ወገኑንም አንድ ግብፃዊ ሲደበድበው
አየ። 12ሙሴም አካባቢውን ቃኝቶ ማንም
አለመኖሩን ካረጋገጠ በኋላ፣ ግብፃዊውን
ገድሎ አሸዋ ውስጥ ደበቀው። 13በማግሥ
ቱም በወጣ ጊዜ ሁለት ዕብራውያን እርስ
በርሳቸው ሲጣሉ አየ፤ ጥፋተኛውንም፣
“የገዛ ወገንህን የምትመታው ለምንድን
ነው?” አለው።

14ሰውየውም፣ “አንተን በእኛ ላይ ገዥና
ዳኛ ማን አደረገህ? ግብፃዊውን እንደ ገደ
ልኸው እኔንም ልትገድለኝ ትፈልጋለህን?”
አለው። ሙሴም፣ “ለካስ ያደረግሁት ነገር
ታውቆአል!” በማለት ፈራ።

15ፈርዖንም ይህን በሰማ ጊዜ፣ ሙሴን
ሊገድለው ፈለገ፤ ሙሴ ግን ከፈርዖን ሸሽቶ
ወደ ምድያም ሄደ፤ እዚያም እንደ ደረሰ
በአንድ የውሃ ጉድጓድ አጠገብ ተቀመጠ።
16የምድያም ካህን ሰባት ሴቶች ልጆች
ነበሩት፤ እነርሱም ወደ ውሃው ጕድጓድ
መጥተው የአባታቸውን በጎች ውሃ ለማጠ
ጣት ገንዳውን ሞሉት። 17እረኞችም መጥ
ተው ሴቶቹን ሲያባርሯቸው ሙሴ ከተቀመ

[ሐ]10 በዕብራይስጥ ሙሴ የሚለው የቃል ድምፅ፣ *ማውጣት* ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው።

ጠበት ተነሥቶ ተከላከለላቸው፤ በጎቻቸ
ውንም አጠጣላቸው።

18ሴቶቹም ወደ አባታቸው ወደ ራጉ
ኤል በተመለሱ ጊዜ፣ “ዛሬስ ያለወትሮ
አችሁ እንዴት ፈጥናችሁ ተመለሳችሁ?”
አላቸው።

19እነርሱም፣ “አንድ ግብፃዊ ከእረኞች
እጅ አዳነን፤ እንዲያውም ውሃ ቀድቶ በጎ
ቻችንን አጠጣልን” አሉት።

20አባታቸውም፣ “ሴቶች ልጆቼን የት
አለ? ለምን ትታችሁት መጣችሁ? ጥሩትና
አብሮን እንጀራ ይብላ” አላቸው።

21ሙሴም ከሰውየው ጋር ለመኖር ተስ
ማማ፤ ራጉኤልም ልጁን ሲፓራን ዳረ

2÷10 1ሳሙ1÷20፤ 2ሳሙ22÷17
2÷11 ዘፀ1÷11፤ ሐሥ7÷23፤ ዕብ11÷24-26፤
2÷13 ሐሥ7÷26
2÷14 ዘፍ13÷8፤ ሐሥ7÷27
2÷15 ዘፍ31÷21፤ ዘፀ4÷19፤ዕብ11÷27
2÷16 ዘፍ24÷11፤ 30÷38፤ዘፀ3÷1፤ 18÷1፤
2÷17 ዘፍ29÷10፤ 1ሳሙ30÷8፤ መዝ31÷2፤
2÷18 ዘፀ3÷1፤ 4÷18፤ 18÷1፡5፡12፤ ዘኁ10÷29
2÷20 ዘፍ18÷2-5
2÷21 ዘፀ4÷25፤ 18÷2፤ዘኁ12÷1
2÷22 ዘፍ23÷4፤ መሳ18÷30፤ ዕብ11÷13
2÷23 ቀኍ24፤ ዘፀ4÷19፤1÷14፤ ዘፀ 3÷7፡9፤6÷5፤ ዘኁ20÷15-16፤ ዘዳ26÷7፤መሳ2÷18፤ 1ሳሙ12÷8፤መዝ5÷2፤1 8÷6፤39÷12፤81÷7፤ 102÷1ሐሥ7÷30፤ ያዕ5÷4
2÷24 ዘፍ8÷1፤ 9÷15፤ 15÷15፤ 17÷4፤22÷16-18፤ 26÷3፤28÷13-15፤ ዘፀ32÷13፤ 2ነገ 13÷23፤ መዝ105÷10፡42፤ ኤር14÷21
2÷25 ዘፀ3÷7፤ 4÷31፤ሉቃ1÷25
3÷1 ቀኍ12፤ ዘፀ2÷18፡16፤4÷27፤ 17÷6፤18÷5፤19÷1-11፤24÷13፤33÷6፤ ዘዳ1÷2፡6፤4÷10፡11፡ 15፤5÷2፤29÷1፤ መሳ1÷16፤1ነገ19÷8፤ ሚል4÷4፤
3÷2 ቀኍ4፤ ዘፍ16÷7፤ዘፀ12÷23፤ 19÷18፤2÷2-6፤ዘዳ 33÷16፤1ነገ19÷12፤ ማር12÷26፤ ሉቃ20÷37፤ ሐሥ5÷19፤7÷30
3÷4 ዘፍ31÷11፤ ዘፀ4÷5፤19÷3፤ ዘሌ1÷1፤1ሳሙ3÷4፤ ኢሳ6÷8
3÷5 ዘፍ28÷17፤ ኤር30÷21፤ ሐሥ 7÷33
3÷6 ዘፍ24÷12፤ ዘፀ4÷5፤24÷11፤ 33÷20፤ መሳ13÷22፤ 1ነገ 19÷13፤ኢዮ13÷11፤ 23÷16፤30÷15፤

ለት። 22ሲፓራም ወንድ ልጅ ወለደች፤
ሙሴም፣ “በባዕድ አገር መጻተኛ ነኝ” ሲል
የልጁን ስም ጌርሳም[መ] ብሎ ጠራው።

23ከብዙ ዓመት በኋላ፣ የግብፅ ንጉሥ
ሞተ፤ እስራኤላውያንም በባርነት ከደረሰ
ባቸው ግፍ የተነሣ ይጮኹ ነበር፤ ከባርነት
ቀንበር ለመላቀቅ ያሰሙት ጩኸት ወደ
እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ደረሰ። 24እግዚአብሔርም
(ኤሎሂም) የጩኸታቸውን ሲቃ ሰማ፤ ከአብር
ሃም፣ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ጋር የገባውንም
ቃል ኪዳን አሰበ። 25እግዚአብሔርም (ኤሎሂም)
እስራኤላውያንን ተመለከተ፤ ስለ እነርሱም
ገደደው።

## ሙሴና የሚንበለበለው ቍጥቋጦ

3 አንድ ቀን ሙሴ የምድያም ካህን የሆነ
ውን የአማቱን የዮቶር በጎችና ፍየ
ሎች እየጠበቀ ሳለ፣ መንጋውን እየነዳ
ወደ ምድረ በዳው ዳርቻ አምርቶ የእግዚ
አብሔር (ኤሎሂም) ተራራ ተብሎ ወደሚጠራ
ው ወደ ኮሬብ ቀረበ።

2እዚያም *የእግዚአብሔር* (ያህዌ) መልአክ
በቍጥቋጦው ውስጥ በሚንቀለቀል የእሳት
ነበልባል መካከል ተገለጠለት። ሙሴም
ቍጥቋጦው በእሳት ቢያያዝም እንኳ፣ አለ
መቃጠሉን አየ። 3ሙሴም፣ “ቍጥቋጦው
ለምን እንደማይቃጠል ቀረብ ብዬ ይህን
አስገራሚ ነገር ልመልከት” አለ።

4ሙሴ ሁኔታውን ለመመልከት መቅረ
ቡን *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ባየ ጊዜ፣ ከቍ
ጥቋጦው ውስጥ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
“ሙሴ፣ ሙሴ” ብሎ ጠራው፤ ሙሴም
አቤቱ እነሆኝ አለው። 5እግዚአብሔርም (ኤሎሂም)፣
“ወደዚህ እንዳትቀርብ፤ ይህች የቆምባት
ምድር የተቀደሰች ስለሆነች ጫማህን
አውልቅ” አለው 6ቀጥሎም፣ “እኔ
የአባቶችህ የአብ ርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያዕ
ቆብ አምላክ (ኤሎሂም) ነኝ” አለው። በዚህ ጊዜ
ሙሴ እግዚአብሔርን (ኤሎሂም) ፊት ለፊት
ማየት ስለ ፈራ ፊቱን ሸፈነ።

7ከዚያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ)፣ እንዲህ
አለ “በግብፅ አገር የሚኖሩትን የሕዝቤን
መከራ አይቻለሁ፤ ከአሠሪዎቻቸው ጭካኔ
የተነሣ የሚያሰሙትንም ጩኸት ሰምቻለሁ፤
ሥቃያቸውንም ተረድቼአለሁ። 8ስለዚህም

ኢሳ6÷5፤ማቴ22÷32፤ማር12÷26፤ሉቃ20÷37፤ሐሥ3÷13፤7÷32፤
3÷7 ቀኍ16፤ ዘፍ16÷11፤ዘፀ÷10፤ 2÷25፤1ሳሙ1÷11፤9÷16፤ ነህ9÷9፤ መዝ106÷44ሐሥ7÷34 3÷8 ቀኍ17፤ዘፍ11÷5፤12÷7፤ 15÷14፤ 18-21፤ዘፀ13÷5፤33÷3፤ዘሌ20÷24፤ዘኁ13÷27፤ዘዳ1÷25፤ 6÷3፤8÷7-9፤ 11÷9፤26÷9፤27÷3፤ኢሱ5÷6፤ 11÷3፤ መሳ3÷3፤ 2ሳሙ24÷7፤ዕዝ9÷1፤ ኤር11÷5፤32÷22፤ሕዝ20÷6፤ሐሥ7÷34

[ሐ]10 በዕብራይስጥ ሙሴ የሚለው የቃል ድምፅ፣ *ማውጣት* ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው።
[መ]22 በዕብራይስጥ ጌርሳም የሚለው ቃል ድምፅ፣ *መጻተኛ በዚያ አለ* ከሚለው ሐረግ ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው።

ከግብፃውያን እጅ ልታደጋቸውና ማርና
ወተት ወደምታፈሰው ሰፊና ለም ወደ
ሆነችው ወደ ከነዓናውያን፣ ኬጢያውያን፣
አሞራውያን፣ ፌርዛውያን ኤዊያውያንና
ኢያቡሳውያን ምድር ሳወጣቸው ወርጃለሁ።
9አሁንም የእስራኤል ልጆች ጩኸት ወደ
እኔ ደርሷል፤ ግብፃውያን የሚያደርሱባቸውን
ግፍ አይቻለሁ። 10በል እንግዲህ ና፤ ሕዝ
ቤን፣ የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ ምድር
እንድታወጣቸው ወደ ፈርዖን እልክሃለሁ"።

11ሙሴ እግዚአብሔርን (ኤሎሂም)፣ "ወደ ፈር
ዖን የምሄድና የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ
የማወጣ እኔ ማን ነኝ? አለው።

12እግዚአብሔርም (ኤሎሂም)፣ "እኔ ከአንተ ጋር
እሆናለሁ፤ እኔ የላክሁህ ለመሆኑ ምልክቱ
ይህ ነው፤ ሕዝቡን ከግብፅ ካወጣሃቸው
በኋላ በዚህ ተራራ ላይ እግዚአብሔርን (ኤሎ
ሂም) ታመልካላችሁ" አለው።

13ሙሴም እግዚአብሔርን (ኤሎሂም)፣ "ወደ
እስራኤል ልጆች ሄጄ፣ 'የአባቶቻችሁ አም
ላክ ወደ እናንተ ልኮኛል' ስላቸው 'ስሙ
ማን ነው?' ብለው ቢጠይቁኝ ምን እላቸዋ
ለሁ?" አለው።

14እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ሙሴን፣ "እኔ፣ ያለ
ሁና የምኖር ነኝ[ሠ] (ያህዌ)፤ ስለዚህም፣ 'ያለና
የሚኖር' ልኮኛል ብለህ ንገራቸው" አለው።

15ደግሞም እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሙሴን፣
"የአባቶቻችሁ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ
አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ የሆነው *እግዚ
አብሔር*[ሬ] (ያህዌ) ወደ እናንተ ልኮኛል፤ ስሜም
ለዘለዓለም ይኸው ነው፤ ወደፊት በተከታ
ታይ በሚነሣው ትውልድ ሁሉ የምታሰ
በው በዚህ ስም ነው ብለህ ለእስራኤል
ልጆች ንገራቸው" አለው።

16"ሂድና የእስራኤልን አለቆች ሰብስ
በህ፣ የአባቶቻችሁ የአብርሃም፣ የይስሐቅና
የያዕቆብ አምላክ የሆነው *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ተገለጠልኝና እንዲህ አለኝ፤ ጐብኘቻች
ኋለሁ፤ በግብፅ የደረሰባችሁንም አይቻ
ለሁ። 17ስለዚህም በግብፅ ከምትቀበሉት
መከራ አውጥቼ ማርና ወተት ወደምታ
ፈሰው ወደ ከነዓናውያን፣ ወደ ኬጢያው
ያን፣ ወደ አሞራውያን፣ ወደ ፌርዛውያን፣
ወደ ኤዊያውያንና ኢያቡሳውያን ምድር አገ
ባችኋለሁ ብሎአል ብለህ ንገራቸው" አለኝ።

18 "የእስራኤል አለቆችም ይሰሙሃል።
አንተና የእስራኤል አለቆች ወደ ግብፅ
ንጉሥ ትሄዱና፣ 'የዕብራውያን አምላክ *እግ
ዚአብሔር* (ያህዌ) ተገለጠልን፤ ስለዚህም ወደ
ምድረ በዳ የሦስት ቀን መንገድ ተጒዘን
ለአምላካችን ለ*እግዚአብሔር* (ያህዌ) መሥዋዕት
እንድናቀርብ ፍቀድልን' ብላችሁ ትነግሩ
ታላችሁ። 19የግብፅ ንጉሥ ግን በኀያል
ክንድ ካልተገደደ በስተቀር መቼም እንደ
ማይለቃችሁ አውቃለሁ። 20ስለዚህ እኔ
እጄን ድንቅ የሆኑ ታምራትን እዚያው
እመካከላቸው በማድረግ ክንዴን ዘርግቼ
ግብፃውያንን እመታቸዋለሁ፤ ከዚያም በኋላ
እንድትሄዱ ይለቃችኋል።

21ይህ ሕዝብ በግብፃውያን ዘንድ የመ
ወደድን ጸጋ እንዲያገኝ ስለማደርግ በምት
ወጡበት ጊዜ ባዶ እጃችሁን አትሄዱም።
22እያንዳንዷ ዕብራዊት ከጎረቤቷም ይሁን
አብራት ከምትኖረው ግብፃዊት የብርና
የወርቅ ጌጣጌጦች እንደዚሁም ልብስ እንድ
ትሰጣት ትጠይቅ። እነዚህንም ሁሉ ወስዳችሁ
ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁን ታስጌጧቸ
ዋላችሁ፤ ታለብሷቸዋላችሁም። በዚህም
መንገድ የግብፃውያኑን ሀብት በእጃችሁ
አግብታችሁ ትወጣላችሁ።"

## ለሙሴ የተሰጡ ምልክቶች

4 ሙሴም "ባያምኑኝስ፤ ቃሌን ባይቀበ
ሉስ፤ '*እግዚአብሔር* (ያህዌ) አልተገለጠ
ልህም' ቢሉኝስ?" ብሎ መለሰ። 2*እግዚአ
ብሔርም* (ያህዌ)፣ "በእጅህ የያዝሀት እርሷ
ምንድን ናት?" ሲል ጠየቀው፤ እርሱም
መልሶ፣ "በትር ናት" አለው።

3*እግዚአብሔርም* (ያህዌ)፣ "መሬት ላይ ጣላት"
አለው።

ሙሴ በትሩን መሬት ላይ ጣላት፤ እባ
ብም ሆነች፤ ከአጠገቧም ሸሸ። 4*እግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) ሙሴን፣ "በል እጅህን ዘር
ጋና ጅራቷን ያዛት" አለው። ሙሴም እጁን
ዘርጎቶ ሲይዛት እባቧ ተለውጣ በእጁ ላይ
እንደ ገና በትር ሆነች። 5*እግዚአብሔርም*
(ያህዌ) "ይህ የሆነው የአባቶቻቸው አምላክ፣
የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕ
ቆብ አምላክ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) የተገለጠ
ልህ መሆኑን እንዲያምኑ ነው" አለው።

6*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) ደግሞ፣ "እጅህን
ብብትህ ውስጥ አስገባ" አለው። ሙሴም
እጁን ብብቱ ውስጥ አስገባ፤ ከብብቱ

3፥9 ዘፀ1፥14፤ ዘኍ10፥9
3፥10 ዘፀ4፥12፤ 6፥13፡26፤12፥41፡ 5120፥2፤ዘዳ4፥20፤ ኢሱ24፥5፤1ሳሙ12፥6፡ 8፤መዝ105፥26፤ 1ነገ8፥16፤ሚክ6፥4፤ሐ ሥ7፥34
3፥11 ዘፀ4፥10፤ 6፥12፡30፤መሳ6፥15፤1 ሳሙ9፥21፤15፥17፤ 18፥18፤2ሳሙ7፥18፤ 2ዜና2፥6፤ኢሳ6፥5፤ ኤር1፥6
3፥12 ቍ1፤ዘፍ 26፥3፤ዘፀ14፥22፤ዘኍ 26፥10፤ኢሱ2፥12፤ መሳ6፥17፤መዝ86፥ 17፤ኢሳ7፥14፤8፥18፤ 20፥3፤ኤር44፥29፤ ሐሥ7፥7፤ሮሜ8፥31፤
3፥13 ዘፍ32፥29
3፥14 ዘፀ6፥2-3፤ ዮሐ8፥58፤ዕብ13፥8፤ራ እ1፥8፤4፥8
3፥15 ዘፍ24፥12፤ 31፥42፤ዘፀ6፥3፡7፤ 15፥3፤23፥21፤ 34፥5- 7፤ዘሌ24፥11፤ ዘዳ28፥58፤መዝ30፥4፤ 83፥18፤96፥2፤97፥12፤ 135፥13፤145፥21 ኢሳ42፥8፤ኤር16፥21፤ 33፥2፤ሆሴ12፥5፤ መዝ45፥17፤72፥17፤ 102፥12፤ዳን2፥23፤ 102፥12፤ዳን2፥23፤
3፥16 ዘፍ24፥12፤ ዘፀ4፥29፡31፤17፥5፤ ዘሌ4፥15፤ዘኍ11፥16፤ 16፥25፤ዘዳ5፥23፤ 19፥12፤መሳ8፥14፤ ሩት4፥2፤2ነገ19፥16፤ 2ዜና6፥20፤ መዝ33፥18፤66፥7፤ ምሳ31፥23፤ሕዝ8፥11፤
3፥17 ቍ8፤ዘፍ 15፥16፤46፥4፤ዘፀ6፥6
3፥18 ዘፍ14፥13፤ 30፥36፤ዘፀ4፥1፡8፡23፡ 31፤5፥1፡3፤6፥11፡12፡ 30፤7፥16፤8፥20፡27፤ 9፥13፤10፥9፡26፤ ዘኍ23፥4፡16
3፥19 ዘፀ4፥21፤6፥6፤ 7፥3፤10፥1፤11፥9፤ ዘዳ4፥34፤2ዜና6፥32
3፥20 ዘፀ4፥21፤ 6፥1፡6፤7፥3፡4-5፤ 9፥15፤11፥1፡9፡10፤ 12፥31-33፤13፥3፡9፡ 14፡16፤15፥6፡12፤ 34፥10፤ዘኍ14፥11፤ ዘዳ3፥24፤4፥34፡37፤ 5፥15፤6፥22፤7፥8፤ 26፥8፤2ነገ17፥36፤ 2ዜና6፥32፤ነህ9፥10፤ መዝ71፥972፥18፤ 77፥14፤78፥43፤ 86፥10፤105፥27፤ 106፥22፤118፥15-16፤ 135፥9፤136፥4፡12፤ ኢሳ41፥10፤63፥12፤ ኤር21፥5፤32፥20፤51፥25፤ዳን9፥15፤ሚክ7፥15፤ሐሥ 7፥36
3፥21 ዘፍ39፥21፤ዘፀ11፥2፤2ዜና30፥9፤ነህ1፥11፤መዝ105፥37፤ 106፥46፤ ኤር42፥12 3፥22 ዘፍ 15፥14፤ ዘፀ11፥2፤12፥35፤ ዕዝ1፥4፡6፤ 7፥16፤ኢዮ27፥16-17፤መዝ105፥37፤ሕዝ39፥10፤ 29፥10
4፥1 ዘፀ3፥18 4፥2 ቍ17፡20፤ዘፍ38፥18፤ዘፀ7፥19፤ 8፥5፡16፤14፥16፡21፤17፥5-6፡9፤ዘኍ17፥2፤20፥8፤ኢሱ8፥18፤ መሳ6፥21፤1ሳሙ 14፥27፤2ነገ4፥29 4፥3 ዘፀ7፥8-12፡15
4፥5 ቍ31፤ዘፀ3፥6 ፤14፥31፤19፥9 4፥6 ዘሌ13፥2፡11፤ ዘኍ12፥10፤ዘዳ24፥92ነገ5፥1፡27፤2ዜና 26፥21

ሠ14 ወይም *እኔ የምሆነው እኔኑ ነው* ማለት ሊሆን ይችላል።
ሬ15 በዕብራይስጥ እግዚአብሔር የሚለው ቃል ድምፅ በቍ 14 ላይ፣ *እኔ ነኝ* ከሚለው ሐረግ ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው። ያህዌ የሚለውም የቃል ውልደት *እኔ ነኝ* ከሚለው ሐረግ ነው።

ውስጥ ባወጣት ጊዜ እጁ እንደ በረዶ ለምጽ[ሰ]
ሆነች::
7“አሁንም ደግሞ እጅህን ወደ ብብትህ
መልሰህ አስገባ” አለው:: ሙሴም እጁን
መልሶ ብብቱ ውስጥ አስገባ፤ እንደገና እጁን
ከብብቱ ውስጥ ባወጣት ጊዜ፣ ተመልሳ
እንደ ሌላው የሰውነቱ ክፍል ሆነች::
8*እግዚአብሔርም* (ያህዌ)፣ “እንግዲህ ባያ
ምኑህ ወይም የመጀመሪያውን ታምራዊ
ምልክት ባይቀበሉ እንኳ ሁለተኛውን ያም
ናሉ:: 9እነዚህን ሁለት ምልክቶች ባያምኑ
ወይም ቃልህን ባይቀበሉ ግን፣ ከአባይ
ወንዝ ጥቂት ውሃ ቀድተህ በደረቅ ምድር
ላይ አፍስሰው:: ከወንዙም ቀድተህ ያፈሰ
ስኸው ውሃ በምድር ላይ ደም ይሆናል::”
10ሙሴም *እግዚአብሔርን* (ያህዌ)
ጌታ (አዶናይ) ሆይ፣ ቀድሞም ሆነ፣ አንተ
ከባሪያህ ጋር ከተነጋገርህ ወዲህ፣ ከቶ
አንደበተ ርቱዕ ሰው አይደለሁም:: እኔ
ኮልታፋና ንግግር የማልችል ሰው ነኝ”
አለው::
11*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) ሙሴን፣ “ለሰው
አንደበቱን የሰጠው ማነው? ሰውን ደንቆሮ
ወይም ዲዳ የሚያደርገው ማነው? ዓይን
የሚሰጥ ወይም ዕውር የሚያደርገውስ ማነው?
እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) አይደለሁምን?”
12በል አሁን ሂድ፤ እኔ እንድትናገር
አደርግሃለሁ፤ የምትናገረውንም አስተም
ርሃለሁ” አለው:: 13ሙሴ ግን፣ “ጌታ ሆይ
(አዶናይ)፤ እባክህ ሌላ ሰው ላክ” አለው::
14በዚህ ጊዜ *የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ቍጣ
በሙሴ ላይ ነደደ፣ “ሌዋዊው ወንድምህ
አሮን አለ አይደል? እርሱ ጥሩ እንደሚና
ገር ዐውቃለሁ፤ እንዲያውም አሁን ወደ
አንተ እየመጣ ነው፤ በሚያይህም ጊዜ ከልቡ
ደስ ይለዋል:: 15ለእርሱ ትነግረዋለህ፤ የሚ
ናገራቸውንም ቃላት በአንደበቱ ታኖራ
ለህ፤ ሁለታችሁም በትክክል እንድትናገሩ
እረዳችኋለሁ፤ ምን ማድረግ እንዳለባ
ችሁም አስተምራችኋለሁ:: 16አንተ እንደ
አምላኩ ሆነህ ትነግረዋለህ፤ እርሱም እንደ
አንደበትህ ሆኖ ለሕዝቡ ይናገርልሃል::
17ታምራዊ ምልክት እንድታሳይባት ይህችን
በትር በእጅህ ይዘህ ሂድ::”

## ሙሴ ወደ ግብፅ ተመለሰ

18ሙሴም ወደ አማቱ ወደ ዮቶር ተመ
ልሶ ሄደና፣ “ወገኖቼ እስካሁን በሕይወት
መኖራቸውን አይ ዘንድ ወደ ግብፅ ተመ
ልሼ እንድሄድ እባክህ ፍቀድልኝ” አለው::
ዮቶርም፣ “ሂድ፤ በሰላም ያግባህ”
አለው::
19ሙሴ በምድያም ሳለ *እግዚአብሔር*

4፥7 2ነገ5፥14፤ ማቴ8፥3፤ ሉቃ17፥12-14
4፥8 ቍ30፤ ዘፀ3፥18፤መሳ6፥17፤ 1ነገ13፥3፤ኢሳ7፥14፤ ኤር 44፥29
4፥9 ዘፀ7፥17-21
4፥10 ዘፀ3፥11
4፥11 መዝ94፥9፤ 146፥8፤ማቴ11፥5፤ ሉቃ1፥20፡64፤ ዮሐ10፥21
4፥12 ቍ15-16፤ ዘፀ3፥10፤ዘኍ23፥5፤ ዘዳ18፥15፡18፤ኢሳ 50፥4፤51፥16፤ኤር 1፥9፤ማቴ10፥19-20፤ ማር13፥11፤ሉቃ 12፥12
4፥13 ዮና1፥1-3
4፥14 ቍ27፤ዘኍ 11፥1፡10፡33፤12፥9፤ 16፥15፤22፥22፤ 24፥10፤32፥13፤ዘዳ 7፥25፤ኢሱ7፥1፤ኢዮ 17፥8፤1ሳሙ10፥2-5
4፥15 ቍ30፤ ዘኍ23፥5፡12፡16፤ ዘዳ18፥18፤ኢሱ1፥8፤ ኢሳ51፥16፤59፥21፤ ኤር1፥9፤31፥33
4፥16 ዘፀ7፥1-2፤ ዘኍ33፥1፤ ኤር15፥19፤36፥6፤ መዝ77፥20፤105፥26፤ ሚክ6፥4
4፥17 ቍ2፥20፤ ዘፀ17፥9፤7፥9-21፤ 8፥5፡16፤9፥22፤ 10፥12-15፡21-23፤ 14፥15-18፡26፤ ዘኍ14፥11፤ዘዳ4፥34 መዝ74፥9፤78፥43፤ 105፥27
4፥19 ዘፀ2፥15፡23፤ ማቴ2፥20
4፥20 ቍ2፤ ዘፀ2፥22፤18፥3፤ ሐሥ7፥29
4፥21 ዘፀ3፥19፡20፤ 7፥3፡13፤8፥15፡32፤ 9፥12፡17፡35፤10፥1፡ 20፡27፤11፥10፤14፥4፡ 8፤ዘዳ2፥30፤ ኢሱ11፥20፤1ሳሙ6፥6፤ መዝ105፥25፤ ኢሳ6፥10፤63፥17፤ ዮሐ12፥40፤ሮሜ9፥18
4፥22 ዘፍ10፥15፤ ዘዳ32፥6፤ኢሳ9፥6፤ 63፥16፤64፥8፤ ኤር3፥19፤31፥9፤ ሆሴ11፥1፤ሚል2፥10፤ ሮሜ9፥4፤2ቆሮ6፥18
4፥23 ዘፍ49፥3፤ ዘፀ3፥18፤5፥1፤7፥16፤ 11፥5፤12፥12፡29፤ ዘኍ8፥17፤33፥4፤ መዝ78፥51፤105፥ 36፤135፥8፤136፥10

(ያህዌ)፣ “አንተን ሊገድሉህ የሚፈልጉ ሰዎች
ሁሉ ሞተዋልና ተመልሰህ ወደ ግብፅ ሂድ”
አለው:: 20ስለዚህ ሙሴ ሚስቱንና ልጆቹን
በአህያ ላይ አስቀምጦ፣ ወደ ግብፅ አገር መመ
ለስ ጀመረ፤ የእግዚአብሔርንም (ኤሎሂም) በትር
በእጁ ይዞ ነበር::
21*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፣ “ወደ ግብፅ በምትመለስበት ጊዜ
በሰጠሁህ ኀይል የምትሠራቸውን ታምራት
ሁሉ በፈርዖን ፊት መፈጸም እንዳለብህ
አትዘንጋ:: እኔ ግን ሕዝቡን እንዳይለቅ
ልቡን አደነድነዋለሁ:: 22ስለዚህ ለፈርዖን
እንዲህ በለው፤ ‘*እግዚአብሔር* (ያህዌ) እንዲህ
ይላል፤ እስራኤል የበኵር ልጄ ነው፤
23“ያመልከኝ ዘንድ ልጄን ልቀቀው” ብዬህ
ነበር፤ አንተ ግን እንዳይሄድ ከለከልኸው፤
ስለዚህ የበኵር ልጅህን እገድላለሁ::’”
24ሙሴ[ሸ] በጕዞ ላይ በእንግዳ ማረፊያ
ስፍራ ውስጥ ሳለ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) አግ
ኝቶት ሊገድለው ፈልጎ ነበር:: 25ሚስቱ
ሲፓራ ግን ስለታም ባልጩት ወስዳ ልጇን
ገረዘችው፤ በሸለፈቱ የሙሴን እግር በመን
ካትም[ቀ] “አንተ ለእኔ የደም ሙሽራዬ
ነህ” አለችው:: 26ስለዚህም *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ተወው፤ “አንተ የደም ሙሽራ ነህ” ያለ
ችው በግርዛቱ ምክንያት ነው::
27*እግዚአብሔር* (ያህዌ) አሮንን፣ “ሙሴን
እንድታገኘው ወደ ምድረ በዳ ሂድ”
አለው:: እርሱም ሙሴን በእግዚአብሔር (ኤሎ
ሂም) ተራራ አገኘው፤ ሳመውም:: 28ሙሴም
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) እንዲናገር የላከውን ቃል
በሙሉና እንዲፈጽማቸው ስላዘዘው ታም
ራዊ ምልክቶች ሁሉ ለአሮን ነገረው::
29ሙሴና አሮን ሄዱና የእስራኤልን ሕዝብ
አለቆች በአንድነት ሰበሰቡ፤ 30አሮንም *እግ
ዚአብሔር* (ያህዌ) ለሙሴ የነገረውን ቃል
በሙሉ ነገራቸው:: ታምራቱንም በሕዝቡ
ፊት አደረገ:: 31ሕዝቡም አመኑ፣ *እግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) ስለ እነርሱ የሚገደው መሆኑ
ንና መከራቸውን ማየቱን በሰሙ ጊዜ ተን
በረከኩ፤ በስግደትም አመለኩት::

## ጭድ አልባ ሸክላ

5 ከዚህ በኋላ ሙሴና አሮን ወደ ፈርዖን
ሄደው፣ “የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔ
ር*

17፥14፤ኢሱ5፥2፡3 4፥25 ዘፀ2፥21፤ዘፍ 4፥27 ዘፍ27፥27፤ 29፥13፤ዘፀ3፥1 4፥28 ቍ16 4፥29 ዘፀ3፥16 4፥30 ቍ8 4፥31 ዘፍ16፥11፤24፥26፤ዘፀ፥18፤2፥25 5፥1 ዘፀ4፥23፤3፥18

[ሰ]6 በዕብራይስጥ፣ *ለምጽ* የሚባለው ቆዳን ለሚያጠቁ በሽታዎች ሁሉ የሚውል እንጂ ቁምጥናን ወይም ለምጽን የሚያሳይ አይደለም::

[ሸ]24 ወይም፣ *የሙሴ ልጅ* ሊሆን ይችላል:: ዕብራይስጡ፣ *እርሱ* ይላል::

[ቀ]25 ወይም *ወደ ሙሴ እግር በመቅረብም* ሊባል ይችላል።

(ኤሎሂም ያህዌ) 'በምድረ በዳ በዓል እንዲያደር
ግልኝ ሕዝቤን ልቀቅ' ይላል" አሉት።
2ፈርዖንም "እንድታዘዘውና እስራኤልን
እንድለቅለት ለመሆኑ ይህ *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ማነው?" *እግዚአብሔርን* (ያህዌ) አላው
ቅም፤ እስራኤልንም አለቅም" አለ።
3እነርሱም፣ "የዕብራውያን አምላክ (ኤሎ
ሂም) ለእኛ ተገልጦልናል፤ የሦስት ቀን
መንገድ ወደ ምድረ በዳው ተጕዘን
ለአምላካችን *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) መሥዋዕ
ት እንድንሠዋ ፍቀድልን፤ አለዚያ ግን
በመቅሠፍት ወይም በሰይፍ ይመታናል"
አሉት።
4የግብፅ ንጉሥም፣ "እናንተ ሙሴና
አሮን፤ ለምንድነው ሕዝቡን ሥራ የምታስ
ፈቱት? በሉ እናንተም ወደየሥራችሁ ተመ
ለሱ!" 5ፈርዖንም፣ "እነሆ፤ አሁን የምድ
ሪቱ ሕዝብ እጅግ ብዙ ነው፤ እናንተም
እንዳይሠሩ እያደረጋችኋቸው ነው" አለ።
6በዚያኑ ዕለት ፈርዖን ለባሪያ ተቈጣ
ጣሪዎቹና ለሕዝቡ አለቆች እንዲህ ሲል
ትእዛዝ ሰጠ፤ 7"ለጡብ ሥራ የሚያስፈል
ጋቸውን ጭድ ካለበት ቦታ ሄደው ራሳ
ቸው ያምጡ እንጂ ከእንግዲህ እናንተ
እንዳታቀርቡላቸው። 8ሆኖም ቀድሞ በሚ
ያቀርቡት ሸክላ ልክ ሠርተው እንዲያቀ
ርቡ አድርጓቸው። የሥራ ድርሻቸውን
አትቀንሱ። ሰነፎች ናቸው፤ 'ሄደን ለአም
ላካችን መሥዋዕት እንሠዋ' የሚሉትም ለዚህ
ነው። 9ለሐሰት ወሬ ስፍራ ሳይሰጡ ተግተው
እንዲሠሩ ሥራውን አክብዱባቸው።"
10ከዚያም የባሪያ ተቈጣጣሪዎቹና አለ
ቆቹ ወጥተው ለሕዝቡ፦ "ፈርዖን የሚለው
ይህ ነው፤ 'ከእንግዲህ ጭድ አልሰጣችሁም፤
11ሂዱና የራሳችሁን ጭድ ከየትም ፈልጋ
ችሁ አምጡ፤ የሥራ ድርሻችሁ ግን ከቶ
አይቀነስም' " አሉ። 12ስለዚህም ሕዝቡ
በጭድ ፈንታ ገለባ ለመሰብሰብ በግብፅ
ምድር ሁሉ ተሰማሩ።
13የባሪያ ተቈጣጣሪዎቹም "በየዕለቱ መሥ
ራት የሚገባችሁ ሥራ ቀድሞ ጭድ
ስናቀርብላችሁ ከምትሠሩት ሥራ ማነስ
የለበትም" እያሉ ያጣድፏቸው ነበር። 14የሥ
ራው የቅርብ ኀላፊዎች ተደርገው በፈርዖን
የባሪያ ተቈጣጣሪዎች የተመደቡት እስራ
ኤላውያንም፣ "የትናንቱንም ሆነ የዛሬውን
ሸክላ ሥራ ድርሻችሁን እንደ ቀድሞው
ለምን አላሟላችሁም?" እየተባሉ ይጠየቁና
ይገረፉ ነበር።
15ከዚያም ሥራውን በቅርብ ሆነው
የሚቈጣጠሩት እስራኤላውያን ኀላፊዎች
ፈርዖን ፊት ቀርበው እንዲህ ሲሉ አቤቱታ
አቀረቡ፤ "እኛን ባሮችህን እንደዚህ የምታ
ደርገን ለምንድን ነው? 16ለእኛ ለባሮችህ
ጭድ ሳያቀርቡልን ሸክላ ሥሩ ይሉናል፤
ጥፋቱ የገዛ ሰዎችህ ሆኖ ሳለ እኛ ባሮችህ
ግን እንገረፋለን።"
17ፈርዖንም እንዲህ አለ፤ "ልግመኞችሄ
እናንተ ልግመኞችሄ እየደጋገማችሁ እን
ሂድ '*ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) እንሠዋ' የምት
ሉት ለዚህ ነው። 18በሉ አሁንም ወደ ሥራ
ችሁ ተመለሱ፤ ምንም ጭድ አይሰጣችሁም፤
ያም ሆኖ ግን የተመደበላችሁን ሸክላ ማም
ረት አለባችሁ።"
19እስራኤላውያን ኀላፊዎችም፣ "በየቀኑ
የምትሠሩት ሸክላ ቍጥሩ ቀድሞ ከሚሠ
ራው ሸክላ ማነስ የለበትም" ተብሎ ሲነገ
ራቸው ችግር ላይ መውደቃቸውን ተረዱት።
20ከፈርዖን ዘንድ እንደተመለሱ ሲጠብቋ
ቸው የነበሩትን ሙሴንና አሮንን አግኝ
ተው፣ 21"*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ይይላችሁ፤
ይፍረድባችሁም ፈርዖንና ሹማምንቱ እን
ዲጠየፉን አደረጋችሁ፤ እንዲገድሉን በእጃ
ቸው ሰይፍ ሰጣችኋቸው" አሏቸው።

## እግዚአብሔር እንደሚታደግ ተስፋ ሰጠ

22ሙሴም ወደ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ተመልሶ፦ "አቤቱ ጌታ (አዶናይ) ሆይ፤ በዚ
ህ
ሕዝብ ላይ መከራ ያመጣኸው ለምንድን
ነው? የላክኸኝ ለዚሁ ነው? 23በአንተ ስም
እናገር ዘንድ ወደ ፈርዖን ከሄድሁበት ጊዜ
ጀምሮ፣ እርሱ በዚህ ሕዝብ ላይ፣ አበሳ
አምጥቶአል፤ አንተም ሕዝብህን ከቶ
አልታደግኸውም" አለው።

6 ከዚያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን፣
"አሁን በፈርዖን ላይ የማደርገውን
ታያለህ፤ ከኀያሉ እጄ የተነሣ እንዲሄዱ፣
ይለቃቸዋል፤ ከኀያሉም እጄ የተነሣ ከአገሩ
ያስወጣቸዋል" አለው።
2እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ሙሴን አለው፤
"እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ። 3ሁሉን
የሚችል አምላክ[በ] (ኤሎሂም) ሆኜ ለአብርሃም፣
ለይስሐቅ፣ ለያዕቆብ ተገለጥሁላቸው፤ ነገር
ግን *እግዚአብሔር* (ያህዌ) በተባለው ስሜ[ተ] ራ
ሴን አልገ ለጥሁላቸውም።[ቸ] 4በእንግድነት
የሚኖሩባትን የከነዓንን ምድር
እንድሰጣቸው ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን
ገብቻለሁ። 5ደግሞም በግ
ብፃውያን ሥር በባርነት ሆነው ያሰሙትን
የእስራኤላውያንን የሥቃይ ድምፅ ሰምቻ
ለሁ ኪዳኔንም አስታውሻለሁ።
6"ስለዚህ ለእስራኤላውያን እንዲህ በላ
ቸው፤ 'እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ፤ ከግ

[በ]3 ዕብራይስጡ፣ *ኤልሻዳይ* ይለዋል።
[ተ]3 የዘፀ 3፥15 ማብ ይመ
[ቸ]3 ወይም እግዚአብሔር በተባለው ስሜ ራሴን አልገለጥሁላቸውምን?

4፥24 ዘኍ22፥22
5፥2 ዘፀ3፥19፤ መሳ2፥10፤ኢዮ21፥15፤ሚል3፥14
5፥3 ዘፍ30፥36፤ ዘሌ26፥25፤ዘኍ14፥12፤ዘዳ28፥21፤ 2ሳሙ24፥13
5፥4 ዘፀ1፥11፤6፥6-7
5፥5 ዘፍ12፥2
5፥6 ዘፍ15፥13
5፥7 ዘፍ11፥3
5፥8 ቍ14፡17፡18፤ ዘፀ10፥11
5፥10 ቍ13፤ ዘፀ1፥11
5፥11 ቍ19
5፥14 ቍ16፤ ኢሳ10፥24
5፥17 ቍ8
5፥18 ዘፍ15፥13
5፥21 ዘፍ16፥5፤ 34፥30፤ዘፀ1፥13፤ 14፥11፤16፥3፤ ዘኍ14፥3፤20፥3
5፥22 ዘኍ11፥11፤ ዘዳ1፥12፤ኢሱ7፥7
5፥23 ኤር4፥10፤ 20፥7፤ሕዝ14፥9
6፥1 ዘፀ3፥20፤ 11፥1፤12፥31፡33፡39፤ ዘዳ5፥15
6፥2 ቍ6፡7፡8፡29፤ ዘፀ3፥14፡15፤7፥5፡ 17፤8፥22፤10፥2፤ 12፥12፤14፥4፡18፤ 16፥12፤ዘሌ11፥44፤ 18፥21፤20፥7፤ ኢሳ25፥3፤41፥20፤ 43፥11፤ 49፥23፤ 60፥16፤ሕዝ13፥9፤ 25፥17፤36፥38፤ 37፥6፡13፤ኢል2፥27
6፥3 ዘፍ17፥1፤ ዘፀ3፥14፡15፤ 2ሳሙ7፥26፤ መዝ48፥10፤61፥5፤ 68፥4፤83፥18፤99፥3፤ኢሳ52፥6፤ዮሐ8፥58
6፥4 ዘፍ6፥18፤ 12፥7፤15፥18፤17፥8፤ሐሥ7፥5፤ሮሜ4፥13፤ ገላ3፥16፤ ዕብ11፥8-10
6፥5 ዘፍ 9፥15፤ ዘፀ2፥23፤ሐሥ7፥34፤
6፥6 ቍ7፤

ብፃውያን ቀንበር አወጣችኋለሁ፡፡ ለእነርሱ
ባሪያ ከመሆን ነጻ አወጣችኋለሁ፤ በተዘ
ረጋች ክንድና በታላቅ ፍርድ እቤዣችኋ
ለሁ፡፡ 7የራሴ ሕዝብ አደርጋችኋለሁ፤ እኔም
አምላክ (ኤሎሂም) እሆናችኋለሁ ከግብፃውያን
ቀንበር ያላቀቅኋችሁ እኔ እግዚአብሔር
አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) መሆኔንም
ታውቃላችሁ፡፡ 8ከዚያም ለአብርሃም፣
ለይስሐቅ፣ ለያዕቆብ እሰጣችኋለሁ ብዬ
ወደማልሁላቸው ምድር አመጣችኋለሁ፤
ርስት አድርጌ እሰ ጣችኋለሁ፡፡ እኔ እግዚ
አብሔር (ያህዌ) ነኝ፡፡’ ”

9ሙሴ ይህን ለእስራኤላውያን ነገራ
ቸው፤ ተስፋ ከመቍረጣቸውና ከአስከፊ እስ
ራታቸው የተነሣ ግን አላዳመጡትም፡፡

10ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን
እንዲህ አለው፤ 11“ሂድና ለግብፅ ንጉሥ
ለፈርዖን እስራኤላውያን ከአገሩ እንዲወጡ
ይፈቅድላቸው ዘንድ ንገረው፡፡”

12ሙሴ ግን እግዚአብሔርን (ያህዌ)፣ “እስ
ራኤላውያን ያልሰሙኝ፣ ፈርዖን እንዴት
ይሰማኛል፤ እኔ ለራሴ ተብታባ ሰው ነኝ”[ነ]
አለው፡፡

## የሙሴና የአሮን የትውልድ መዝገብ

13በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር (ያህዌ) ስለ
እስራኤላውያንና ስለ ግብፅ ንጉሥ ስለ
ፈርዖን ለሙሴና ለአሮን ነገራቸው፤ እስራ
ኤላውያንንም ከግብፅ እንዲያወጡ አዘዛ
ቸው፡፡

14የየቤተ ሰቡ[ነ] አለቆች እነዚህ ነበሩ፤
የእስራኤል የበኵር ልጅ የሮቤል ልጆች፣
ሄኖኅ፣ ፈሉስ፣ አስሮን፣ ከርሚ፣ እነዚህ
የሮቤል ነገድ ናቸው፡፡

15የስምዖን ወንዶች ልጆች፣ ይሙኤል፣
ያሚን፣ አሃድ፣ ያኪን፣ ጾሐርና የከነዓናዊ
ቷም ልጅ ሳኡል ነበሩ፡፡ እነዚህ የስምዖን
ነገድ አባቶች ናቸው፡፡

16በትውልዳቸው መሠረት የሌዊ ወን
ዶች ልጆች ስሞች እነዚህ ነበሩ፤ ጌድሶን፣
ቀዓትና ሜራሪ ናቸው፤ ሌዊ መቶ ሠላሳ
ሰባት ዓመት ኖረ፡፡

17የጌድሶን ወንዶች ልጆች በትውልዳ
ቸው ሎቤኒና ሰሜኢ ነበሩ፡፡

18የቀዓት ወንዶች ልጆች
እንበረም፣ ይስዓር፣ ኬብሮንና ዑዝኤል
ነበሩ፤ ቀዓት መቶ ሠላሳ ዓመት ኖረ፡፡

19የሜራሪ ወንዶች ልጆች ሞሖሊና ሙሲ
ነበሩ፡፡ በትውልዳቸው መሠረት የሌዌ ነገዶች
እነዚህ ናቸው፡፡

20እንበረም የአጎቱን እናት ዮካብድን
አገባ፤ እርሷም አሮንና ሙሴን ወለደችለት፡፡
እንበረም መቶ ሠላሳ ሰባት ዓመት ኖረ፡፡

21የይስዓር ወንዶች ልጆች፣ ቆሬ፣ ናፌግና

ዘፀ3፥8፡19፡20፤
12፥17፡51፤15፥13፤
16፥16፤18፥1፤19፥1፤
20፥2፤29፥46፤ዘሌ22፥
33፤26፥13፤ዘዳ6፥12፤
7፥8፤9፥26፤1ዜና17፥
21፤ኢዮ19፥25፤መዝ
9፥16፤19፥14፤34፥
22፤74፥2፤77፥15፤
81፥10፤105፥27፤
107፥2፤136፥11፤ኢሳ
29፥22፤35፥9፤43፥1፤
44፥23፤48፥20፤ኤር
2፥6፤15፥21፤31፥11፤
32፥21፤50፥34፤ሆሴ
13፥4፤አሞ2፥10፤
ሚክ6፥4፤ሐሥ13፥17
6፥7 ቍ2፤ ዘፍ17፥7፤
ዘፀ34፥9፤1ነገ20፥13፡
28፤ኢሳ43፥10፤48፥
7፤ሕዝ11፥19-20፤
39፥6፤ኢል3፥17፤
ሮሜ9፥4
6፥8 ዘፍ12፥7፤
14፥22፤ዘፀ3፥8፤ዘሌ
18፥21፤መዝ136፥
21-22፤ ኤር11፥5፤ሕ
ዝ20፥6፤ራእ10፥5-6
6፥9 ዘፍ34፥30፤
ዘፀ2፥23
6፥11 ቍ29፤
ዘፀ3፥18
6፥12 ዘፀ3፥18፤
4፥10
6፥13 ዘፀ3፥10
6፥14 ዘፍ29፥32፤ዘፀ
13፥3፤ዘኍ1፥1፤26፥4
6፥15 ዘፍ29፥33
6፥16 ዘፍ29፥34፤
46፥11፤ዘኍ3፥17፤
ኢሱ21፥7፤1ዜና6፥1፡16
6፥17 ዘኍ3፥18፤
1ዜና6፥17
6፥18 ዘኍ3፥19፡
27፤1ዜና6፥2፡18፤
23፥12
6፥19 ዘኍ3፥20፡33፤
1ዜና6፥19፤23፥21
6፥20 ዘፀ2፥1-2፤
ዘኍ26፥59፤
1ዜና23፥13
6፥21 1ዜና6፥38
6፥22 ዘሌ10፥4፤
ዘኍ3፥30፤1ዜና15፥8፤
2ዜና29፥13
6፥23 ዘፀ24፥1፤
28፥1፤ዘሌ10፥1፡6፡
12፡16፤ዘኍ1፥7፤
2፥3፤3፥2፡32፤4፥28፤
16፥37፡39፤26፥60፤
ዘዳ10፥6፤ኢሱ14፥1፤
ሩት4፥19፡20፤1ዜና
6፥3፤24፥1፤1ዜና2፥10፤
6፥22፡37ማቴ1፥4
6፥24 ቍ21፤
ዘኍ16፥1፤
6፥25 ዘኍ25፥7፡
11፤ 31፥6፤ኢሱ24፥
33፤መዝ 106፥30
6፥26 ዘፀ3፥10፤7፥4፤
12፥17፡ 41፡51
6፥27 ዘፀ5፥1፤ዘኍ
3፥1፤መዝ77፥20

ዝክሪ ነበሩ፡፡

22የዑዝኤል ወንዶች ልጆች፣ ሚሳኤል፣
ኤልጻፉንና ሥትሪ ነበሩ፡፡

23አሮንም የአሚናዳብን ልጅ፣ የነአሶንን
እኅት ኤልሳቤጥን አገባ፤ እርሷም
ናዳብንና
አብዩድን፣ አልዓዛርንና ኢታምርን ወለደ
ችለት፡፡

24የቆሬ ወንዶች ልጆች፣ አሴር፣ ሕል
ቃናና አብያሳፍ ነበሩ፤ እነዚህ የቆሬ ነገድ
ጐሣ ናቸው፡፡

25የአሮን ልጅ አልዓዛር ከፉትኤል
ሴት ልጆች አንዷን አገባ፤ እርሷም ፊንሐ
ስን ወለደችለት፤ እነዚህ እንደየነገዳቸው
የሌዋውያን ጐሣዎች አለቆች ነበሩ፡፡

26እግዚአብሔር (ያህዌ) “እስራኤላውያንን
በየሰራዊታቸው ከግብፅ አውጡ” ብሎ
የነገራቸው እነዚህኑ አሮንንና ሙሴን ነበር፡፡

27ስለ እስራኤላውያን ከግብፅ መው
ጣት፣ የግብፅን ንጉሥ ፈርዖንን ያናገሩ
ትም እነዚሁ ነበሩ፡፡

28እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን በግብፅ
በተናገረው ጊዜ፣ 29እንዲህ አለው፤ “እኔ
እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ፤ የነገርሁህን ሁሉ
ለግብፅ ንጉሥ ለፈርዖን ንገረው፡፡”

30ሙሴ ግን እግዚአብሔርን (ያህዌ) እንዲህ
አለው፤ “ፈርዖን ምን ብሎ ይሰማኛል?
አንደበቴ ኮልታፋ ነው፡፡”

7 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ “ልብ በል፤ እኔ አንተን ለፈ
ርዖን እንደ አምላክ (ኤሎሂም) አድርጌሃለሁ፤
ወንድምህ አሮንም ያንተ ነቢይ ይሆናል፡፡
2እኔ የማዝህን ሁሉ ትናገራለህ፤ ወንድምህ
አሮንም እስራኤላውያንን ከአገሩ እንዲወጡ
ይለቃቸው ዘንድ ለፈርዖን ይነግረዋል፡፡
3እኔ ግን የፈርዖንን ልብ አደነድናለሁ፤
ታምራዊ ምልክቶችንና ድንቆችን በግብፅ
ላይ በብዛት ባደርግም እንኳ፣ አይሰማችሁም፡፡
4ከዚያም እጄን በግብፅ ላይ አደርጋለሁ፤
በኀያል ፍርድም ሰራዊቴን፣ ሕዝቤን እስ
ራኤላውያንን አወጣለሁ፤ 5እጄን በግብፅ
ላይ ስዘረጋና እስራኤላውያንንም ከዚያ
ሳወጣ፣ ግብፃውያን እኔ እግዚአብሔር
(ያህዌ) መሆኔን ያውቃሉ፡፡”

6፥29 ቍ2 6፥30 ዘፀ3፥11 7፥1 ዘፀ4፥15፡16፤ሐሥ14፥12
7፥3 ዘፀ3፥20፤4፥21፤ 10፥1፤ሐሥ7፥36፤ ሮሜ9፥18
7፥4 ቍ13፡16፡22፤ ዘፀ8፥15፡19፤9፥12፤ 11፥9፤3፥20፤6፥26፤
ሐሥ7፥36
7፥5 ዘፀ6፥2፤3፥20፤ መዝ138፥7፤ሕዝ6፥ 14፤25፥13

[ነ]12 ዕብራይስጡ በዚህ ስፍራና ቍ30 ላይ፣ ያልተገረዘ ከንፈር ይላል
[ነ]14 በዚህ ስፍራና በቍ 25 ላይ፣ ያለው ቤተ ሰብ የዕብራይስጥ ቃል ከጐሣም የበለጠ ነው፡፡

6ሙሴና አሮን እግዚአብሔር (ያህዌ) እንደ
አዘዛቸው አደረጉ። 7ፈርዖንን ባነጋገሩበት
ጊዜ ሙሴ ዕድሜው ሰማንያ ዓመት፣ አሮን
ደግሞ ሰማንያ ሦስት ነበር።

### የአሮን በትር እባብ ሆነች

8እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴንና አሮንን
እንዲህ አላቸው፣ 9"ፈርዖን፣ 'ታምር አሳ
ዩኝ' ባላችሁ ጊዜ፣ አሮንን እንዲህ
በለው፤ 'በትርህን ውሰድና በፈርዖን ፊት
ጣላት፤' ከዚያም እባብ ትሆናለች።"
10ስለዚህ ሙሴና አሮን ወደ ፈርዖን
ሄደው እግዚአብሔር (ያህዌ) እንዳዘዛቸው
አደረጉ። አሮን በትሩን በፈርዖንና በሹማ
ምንቱ ፊት ጣላት፤ እባብም ሆነች። 11ከዚ
ያም ፈርዖን ጠቢባኑንና መተተኞቹን ጠራ፤
የግብፅ አስማተኞችም በድብቅ ጥበባቸው
ያንኑ አደረጉ፤ 12እያንዳንዱ የያዛትን በትር
ጣለ፤ እባብም ሆነች። ነገር ግን የአሮን
በትር የእነርሱን በትሮች ዋጠች። 13ሆኖም
የፈርዖን ልብ ደነደነ፤ እግዚአብሔር (ያህዌ)
ተናግሮ እንደነበረውም አላዳመጣቸውም።

### የደም መቅሠፍት

14ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እን
ዲህ አለው፤ "የፈርዖን ልብ ደነደነ፤ ሕዝቡን
ለመልቀቅ አልፈቀደም። 15ወደ ውሃው በሚ
ሄድበት ጊዜ ማልደህ ወደ ፈርዖን ሂድ፤
እንድታገኘውም በአባይ ዳር ተጠባበቅ፤
ወደ እባብ ተለውጣ የነበረችውንም በትር
በእጅህ ያዝ። 16ከዚያም እንዲህ በለው፤
'የዕብራውያን አምላክ እግዚአብሔር (ኤሎሂም
ያህዌ) "ሕዝቤ በምድረ በዳ ያመልኩኝ ዘንድ
እንዲሄዱ ልቀቃቸው፤" ብዬ እንድነግርህ
ላከኝ፤ አንተ ግን እስካሁን ድረስ እሺ አላ
ልህም። 17እግዚአብሔር (ያህዌ) የሚለው
ይህ ነው፤ "እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) እንደ
ሆንሁ በዚህ ታውቃለህ፤ እይ በዚህች
በእጄ በያዝኳት በትር የአባይን ውሃ እመ
ታለሁ። ወደ ደምም ይለወጣል። 18በዐባይ
ወንዝ ውስጥ ያለው ዓሣ ይሞታል፤ ወንዙ
ይከረፋል፤ ግብፃውያንም ውሃውን መጠ
ጣት አይችሉም።' "
19እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን አለው፤ "አሮ
ንን፣ 'በትርህን ውሰድና በግብፅ ውሆች ላይ፣
ይኸውም በምንጮች፣ በቦዮች፣ በኵሬዎችና
በውሃ ማጠራቀሚያዎች ላይ እጅህን
ዘርጋ' ብለህ ንገረው፤ ወደ ደምም ይለወ
ጣሉ። ከእንጨትና ከድንጋይ በተሠሩ ውሃ
መያዣዎች ውስጥም ሳይቀር በግብፅ
ምድር ደም በየቦታው ይሆናል።"
20ሙሴና አሮን እግዚአብሔር (ያህዌ)
እንደ አዘዛቸው አደረጉ። እርሱም በንጉ

7፥6 ቍ2፡10፡20፤
ዘፍ6፥22
7፥7 ዘዳ31፥2፤
34፥7፤ሐሥ7፥23፡30
7፥9 ዘፀ4፥2-5፤
ዘዳ6፥22፤2ነገ19፥29፤
መዝ78፥43፤86፥17፤
105፥27፤135፥9፤ ኢ
ሳ7፥11፤37፥30፤
38፥7-8፤55፥13፤
ዮሐ2፥11
7፥11 ቍ22፤
ዘፍ41፥8፤ዘፀ8፥7፡18፤
22፥18፤ዘዳ18፥10፤
1ሳሙ6፥2፤2ነገ21፥6፤
ኢሳ2፥6፤4
7፥12 ኤር27፥9፤
ሚል3፥5፤ማቴ24፥24፤
2ጢሞ3፥8
7፥13 ቍ4፤ዘፀ4፥21
7፥14 ቍ22፤
ዘፀ8፥15፡32፤9፥7፤
10፥1፡20፡27
7፥15 ዘፍ41፥1፤
ዘፀ8፥20
7፥16 ቍ4፤ዘፀ3፥18
7፥17 ቍ19-21፤
ዘፀ4፥9፤6፥2፤14፥25፤ራ
እ11፥6፤16፥4
7፥18 ቍ21፡24፤
መዝ78፥44፤
ኢሳ19፥6
7፥19 ዘፀ4፥2፤
14፥21፤2ነገ5፥11
7፥20 ቍ6፤
ዘፀ17፥5፤መዝ78፥44፤
105፥29፤114፥3፤
ዕን3፥8
7፥22 ቍ11፡13፡
14፤ዘፍ41፥8፤
ዘፀ8፥19፤
መዝ105፥28፤
ማቴ24፥24
7፥24 ቍ18
8፥1 ዘፀ3፥12፤4፥23፤
5፥1፤9፥1
8፥2 መዝ78፥45፤
105፥30፤ራእ16፥13
8፥3 ዘፀ10፥6፤
12፥34
8፥5 ዘፀ4፥2፤7፥9-20፤
9፥23፤10፥13፡21-22፤
14፥27፤4፥17
8፥6 መዝ78፥45፤
105፥30
8፥7 ዘፀ7፥11፤
ማቴ24፥24
8፥8 ቍ25፡28፤
ዘፀ9፥28፤10፥8፡17፡
24፤12፥31ዘኍ21፥7፤
1ሳሙ12፥19፤1ነገ13፥
6፤ኤር10፥6፤42፥2፤46
፥9፤49፥19፤ሚክ7፥18፤
ሐሥ8፥24
8፥9 ዘፀ9፥5

ሡና በሹማምንቱ ፊት በትሩን አንሥቶ
የዐባይን ወንዝ ውሃ መታ። ውሃውም
በሙሉ ወደ ደም ተለወጠ። 21በዐባይ
ያሉት ዓሦች ሞቱ፤ ወንዙም ከመከርፋቱ
የተነሣ ግብፃውያኑ ውሃውን ሊጠጡት
አልቻሉም። በግብፅ ምድር ሁሉ ደም
ነበረ።
22የግብፅ አስማተኞች በድብቅ ጥበባ
ቸው ተመሳሳይ ነገር አደረጉ፤ የፈርዖንም
ልብ ደነደነ፤ ልክ እግዚአብሔር (ያህዌ)
እንደ ተናገረው ሙሴንና አሮንን አልሰ
ማቸውም። 23ተመልሶ ወደ ቤተ መንግሥቱ
ገባ እንጂ ይህንን ከቍም ነገር አልቈጠ
ረውም። 24ግብፃውያን ሁሉ የወንዙን ውሃ
መጠጣት ባለመቻላቸው ውሃ ለማግኘት የዐ
ባይን ዳር ይዘው ጕድጓድ ቈፈሩ።
25እግዚአብሔር (ያህዌ) ዐባይን ከመታ ሰባት
ቀን አለፈ።

### የጓጉንቸር መቅሠፍት

8 ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን
አለው፤ "ወደ ፈርዖን ዘንድ ሂደህ፣
እንዲህ በለው፤ 'እግዚአብሔር (ያህዌ) የሚለው
ይህ ነው፤ "እኔን ያመልኩኝ ዘንድ ሕዝቤን
ልቀቅ። 2እነርሱን ለመልቀቅ እምቢ ብትል
አገርህን ሁሉ በጓጉንቸር መቅሠፍት እመ
ታዋለሁ። 3ዐባይ በጓጉንቸሮች ይሞላል፤
ወጥተውም ወደ ቤተ መንግሥትህና ወደ
መኝታ ክፍልህ፣ ወደ አልጋህም ወደ ሹማ
ምንቶችህና ወደ ሕዝብህ ቤቶች፣ ወደ
ምድጆችህና ወደ ቡሃቃዎችህ ይገባሉ።
4ጓጉንቸሮቹ ወደ አንተና ወደ ሕዝብህ
ወደ ሹማምንቶችህም ሁሉ ይመጡባ
ችኋል።' "
5ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን
አለው፣ "አሮንን፣ 'በትርህን ይዘህ በምን
ጮች፣ በቦዮችና በኵሬዎች ላይ እጅህን
ዘርጋ፤ ጓጉንቸሮችም በግብፅ ምድር ላይ
እንዲወጡ አድርግ' " በለው።
6አሮንም በግብፅ ውሆች ላይ እጁን
ዘረጋ፤ ጓጉንቸሮችም ወጥተው ምድሪቱን
ሸፈኑ። 7ሆኖም ግን አስማተኞቹ በድብቅ
ጥበባቸው ተመሳሳይ ነገር ሠሩ፤ እነርሱም
በግብፅ ምድር ላይ ጓጉንቸሮች እንዲወጡ
አደረጉ።
8ፈርዖንም ሙሴንና አሮንን አስጠርቶ
እንዲህ አላቸው፤ ጓጉንቸሮቹን ከእኔና
ከሕዝቤ ያርቅ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር
(ያህዌ) ጸልዩልኝ፤ ከዚያም ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) መሥዋዕትን ትሠዉ ዘንድ ሕዝቡ
እንዲሄዱ እፈቅዳለሁ።
9ሙሴም ፈርዖንን፣ "በዐባይ ወንዝ ካሉት
በቀር ከአንተና ከቤቶችህ ጓጉንቸሮቹ

እንዲወገዱ ለአንተ፣ ለሹማምንቶችህና
ለሕዝብህ የምንፀልይበትን ጊዜ
እንድትወስን ለአንተ ትቸዋለሁ” አለው።
[10]ፈርዖንም፣ “ነገ ይሁን” አለው። ሙሴም
እንዲህ ብሎ መለሰ፤ “እንደ አምላካችን
እንደ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ያለ ማንም
እንደ ሌለ ታውቅ ዘንድ አንተ እንዳልኸው
ይሆናል። [11]ጓጒንቸሮቹም ከአንተና ከቤቶ
ችህ፣ ከሹማምንቶችህና ከሕዝብህ ተወግደው
በዐባይ ወንዝ ብቻ ይወሰናሉ።”
[12]ሙሴና አሮን ከፈርዖን ዘንድ ከተመ
ለሱ በኋላ፣ በፈርዖን ላይ *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ስላመጣቸው ጓጒንቸሮች ሙሴ ወደ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ጮኸ። [13]*እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ሙሴ እንደ ለመነው አደረገ፤ ጓጒንቸ
ሮቹም በየቤቱ ውስጥ፣ በየአጥር ግቢውና
በየሜዳው ሞቱ። [14]በአንድ ላይ ሰብስበው
ከመሯቸው፤ ምድሪቱም ከረፋች። [15]ፈርዖን
ችግሩ ጋብ ማለቱን ባየ ጊዜ ግን ልክ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) እንደ ተናገረው ልቡን
በማደንደን ሙሴንና አሮንን አልሰማቸውም።

## የተባይ መቅሠፍት

[16]ከዚያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን፣
“አሮንን ‘በትርህን ሰንዝረህ የምድርን ትቢያ
ምታ’ በለው፤ ከዚያም በግብፅ ምድር ያለው
ትቢያ ሁሉ ተናካሽ ትንኝ ይሆናል” አለው።
[17]እነርሱም እንዲሁ አደረጉ፣ አሮን በትሩን
እንደ ያዘ እጁን ሲዘረጋና የምድሩን ትቢያ
ሲመታ፣ በግብፅ ምድር ያለው ትቢያ
ሁሉ ተናካሽ ትንኝ ሆነ። ሰውንም ሆነ
እንስሳውን ተናካሽ ትንኝ ወረረው። [18]ነገር
ግን አስማተኞቹ በድብቅ ጥበባቸው ተና
ካሽ ትንኞችን ለመፍጠር ሲሞክሩ
አልቻሉም። ተናካሽ ትንኞቹም ከሰውና
ከእንስሳው ላይ አልወረዱም ነበር። [19]አስ
ማተኞቹም ፈርዖንን፣ “ይህ *የእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ጣት ነው” አሉት፤ ነገር ግን የፈርዖን
ልብ ደንድኖ ስለ ነበር፣ ልክ *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) እንደተናገረው አልሰማቸው አለ።
[20]ከዚህ በኋላ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን
እንዲህ አለው፤ “በጧት ተነሥተህ ፈርዖን
ወደ ውሃ በሚወርድበት ጊዜ ከፊቱ ቀር
በህ እንዲህ በለው፤ ‘*እግዚአብሔር* (ያህዌ)
የሚለው ይህ ነው፤ ያመልኩኝ ዘንድ ሕ
ዝቤን ልቀቅ። [21]ሕዝቤ እንዲሄዱ ባትለ
ቃቸው፣ በአንተና በሹማምንትህ ላይ፣
በሕዝብህና በቤቶችህ ላይ የዝንብ መንጋ
እሰዳለሁ። ያረፉበት መሬት እንኳ ሳይቀር፣
የግብፃውያን ቤቶች ሁሉ ዝንብ ብቻ
ይሆናሉ።
[22]“ ‘በዚያች ዕለት ግን ሕዝቤ የሚኖር
ባትን የጌሤምን ምድር የተለየች አደርጋታ
ለሁ፤ እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) በዚህች ምድር
እንዳለሁ ታውቅ ዘንድ የዝንብ መንጋ በዚያ
አይኖርም። [23]በሕዝቤና በሕዝብህ መካከል
ልዩነት አደርጋለሁ፤ ይህ ታምራዊ ምልክት
ነገ ይሆናል[ኘ]።’ ”
[24]*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) እንዲሁ አደ
ረገ፤ አስጨናቂ የዝንብ መንጋ በፈርዖን
ቤተ መንግሥትና በሹማምንቶቹ ቤቶች
ላይ ወረደ፤ መላው የግብፅ ምድር ከዝንቡ
የተነሣ ተበላሽቶ ነበር።
[25]ከዚያም ፈርዖን ሙሴንና አሮንን
አስጠርቶ፣ “ሂዱና በዚሁ ምድር ለአምላካ
ችሁ ሠዉ” አላቸው።
[26]ሙሴ ግን እንዲህ አለ፤ “ይህ ትክክል
አይሆንም፤ ለአምላካችን *ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) የምናቀርበው መሥዋዕት በግብፃውያን
ዘንድ አስጸያፊ ነው፤ ታዲያ በእነርሱ ዐይን
አስጸያፊ የሆነውን መሥዋዕት ብናቀርብ
አይወግሩንምን? [27]ለአምላካችን *ለእግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) እርሱ እንዳዘዘን መሥዋዕት
መሠዋት ወደ ምድረ በዳ የሦስት ቀን
መንገድ መሄድ አለብን።
[28]ፈርዖንም፣ “ለአምላካችሁ *ለእግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) በምድረ በዳ መሥዋዕት እንድ
ትሠዉ እፈቅድላችኋለሁ፤ ነገር ግን ርቃ
ችሁ እንዳትሄዱ። ለእኔም ጸልዩልኝ” አላ
ቸው።
[29]ሙሴም እንዲህ አለ፤ “ከአንተ እንደ
ተለየሁ ወዲያውኑ ወደ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
እጸልያለሁ፤ ነገም ዝንቡ ሁሉ ከፈርዖን፣
ከሹማምንቶቹና ከሕዝቡ ይወገዳል። ብቻ
ሕዝቡ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) መሥዋዕት እን
ዲሠዉ ባለመፍቀድ ከዚህ ቀደም ፈረዖን
አታሎ እንዳደረገው አሁንም እንዳያደርግ
እርግጠኛ ይሁን።”
[30]ከዚያም ሙሴ ከፈርዖን ተለይቶ
ወደ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ጸለየ። [31]*እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ሙሴ የለመነውን አደረገ።
የዝንቡም መንጋ ከፈርዖን፣ ከሹማምንቶቹና
ከሕዝቡ ተወገደ፤ አንድም ዝንብ እንኳ
አልቀረም። [32]በዚህም ጊዜ እንኳን ፈርዖን
ልቡን አደነደነ እንጂ፣ ሕዝቡን አለቀቀም።

## የእንስሳት እልቂት

9 ከዚያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን
እንዲህ አለው፤ “ወደ ፈርዖን ሂድና
እንዲህ በለው፤ ‘የዕብራውያን አምላክ (ኤሎ
ሂም) *እግዚአብሔር* (ያህዌ) የሚለው ይህ ነው፤
“ያመልኩኝ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ።” [2]አሁንም
እንዳይሄዱ ብታደርግና ብትከለክላቸው፣

8፥10 ዘፀ9፥14፤ 15፥11፤ዘዳ3፥24፤ 4፥35፤33፥26፤ 2ሳሙ7፥22፤ 1ነገ8፥23፤ 1ዜና17፥20፤2ዜና6፥14፤መዝ71፥19፤86፥8፤ 89፥6፤113፥5፤ ኢሳ40፥18፤42፥8፤ 46፥9፤ኤር10፥6፤49፥19፤ሚክ7፥18
8፥13 ያዕ5፥16-18
8፥15 ዘፀ7፥14፤ መክ8፥11
8፥16፤ ዘፀ 4፥2
8፥17 መዝ105፥31
8፥18 ዘፀ9፥11፤ ዳን5፥8፤ዘፀ7፥11
8፥19 ዘፀ7፥5፥22፤ 10፥7፤12፥33፤31፥18፤ 1ሳሙ6፥9፤ነህ9፥6፤መዝ8፥3፤33፥6፤ ሉቃ11፥20
8፥20 ዘፀ3፥18፤ 7፥15፤9፥13
8፥22 ዘፍ45፥10፤ ዘፀ7፥5፤9፥4፤6፥26፥ 29፤10፥23፤11፥7፤ 12፥13፤19፥5፤ ዘዳ4፥20፤7፥6፤14፥2፤ 26፥18፤1ነገ8፥36፤ ኢዮ36፥11፤ መዝ33፥12፤ 135፥4፤ሚል3፥17
8፥23 ዘፀ9፥4፤6፤ 10፥23፤11፥7፤12፥ 13፥23፥27
8፥24 መዝ78፥45፤ 105፥31
8፥25 ቍ8፤ ዘፀ9፥27፤10፥16፤ 12፥31
8፥26 ዘፍ43፥32
8፥27 ዘፍ30፥36፤ ዘፀ3፥18
8፥28 ቍ8፤ ኤር37፥3፤ሐሥ8፥24
8፥29 ቍ15፤ ዘፀ9፥30፤10፥11፤ ኢሳ26፥10
8፥30 ቍ12፤ ዘፀ9፥33፤10፥18
8፥32 ዘፀ7፥14
9፥1 ዘፀ8፥1

[ኘ]23 የሰብዓ ሊቃናትና የቩልጌት ትርጒም እንደ ዕብራይስጡ፣ *ዐርነት ነገ ይሆናል* ይላሉ።

[3]የእግዚአብሔር (ያህዌ) እጅ በመስክ ላይ ባሉት
እንስሳት፣ በፈረሶችህና በአህዮችህ፣ በግመ
ሎችህና በቀንድ ከብቶችህ፣ በበጎችህና
በፍየሎችህ ላይ አስከፊ መቅሠፍት ያመጣ
ብሃል። [4]ነገር ግን እግዚአብሔር (ያህዌ)
በእስራኤልና በግብፅ እንስሳት መካከል
ልዩነት ያደርጋል፤ ይኸውም የእስራኤል
የሆነ ማንኛውም እንስሳ እንዳይሞት ነው።' ”
[5]እግዚአብሔር (ያህዌ) ጊዜን ወስኖ፣ እን
ዲህ አለ፤ “በነገው ዕለት እግዚአብሔር
(ያህዌ) በምድሪቱ ላይ ይህን ያደርጋል።”
[6]በማግሥቱም እግዚአብሔር (ያህዌ) ነገሩን ፈጸ
መው፤ የግብፃውያን እንስሳት በሙሉ አለቁ፤
ነገር ግን የእስራኤላውያን ከሆኑት እንስ
ሳት አንድም አልሞተም። [7]ፈርዖን ያጣሩ
ዘንድ ሰዎች ልኮ ከእስራኤላውያኑ እንስ
ሳት አንድም እንኳን አለመሞቱን ተገነዘበ።
ያም ሆኖ ልቡ እንደ ደነደነ ስለ ነበር፣ ሕዝ
ቡን አልለቀቀም።

## የእባጭ መቅሠፍት

[8]ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴንና
አሮንን አላቸው፤ “ከምድጃው እፍኝ ዐመድ
ወስዳችሁ፣ ሙሴ በፈርዖን ፊት ወደ
ሰማይ ይበትነው። [9]በግብፅ ምድር ሁሉ
ትቢያ ይሆናል፤ በምድሪቱ ሁሉ በሚገ
ኙት ሰዎችና እንስሳት ላይ መግል የያዘ
እባጭ ይወጣል።”
[10]ስለዚህ ከምድጃው ዐመድ ወስደው
በፈርዖን ፊት ቆሙ፤ ሙሴም ወደ ሰማይ
በተነው፤ መግል የያዘ እባጭም በሰዎችና
በእንስሳት ላይ ወጣ። [11]በእነርሱና በግብፃ
ውያን ሁሉ ላይ እባጭ ወጥቶ ስለ ነበር፣
አስማተኞቹ በሙሴ ፊት መቆም አልቻ
ሉም። [12]እግዚአብሔር (ያህዌ) ግን የፈርዖንን
ልብ አደነደነ፤ እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ
እንደ ተናገረውም፣ ሙሴንና አሮንን መስ
ማት አልፈለገም።

## የበረዶ መቅሠፍት

[13]ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን
እንዲህ አለው፤ “ማልደህ በጧት ተነሣ፤
ከፈርዖን ፊት ቀርበህ እንዲህ በለው፤ 'የዕ
ብራውያን አምላክ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
የሚለው ይህ ነው፤ ያመልኩኝ ዘንድ ሕዝ
ቤን ልቀቅ፤ [14]አለዚያ በአንተ በሹማምንቶ
ችህና በሕዝብህ ላይ የመቅሠፍቴን መዓት
ሁሉ አሁን አወርድብሃለሁ፤ ይኸውም በም
ድር ሁሉ እንደ እኔ ያለ ማንም እንደሌለ
ታውቅ ዘንድ ነው። [15]አሁን እጄን ዘርግቼ
አንተንና ሕዝብህን ከገጸ ምድር ሊያጠ
ፋችሁ በሚችል መቅሠፍት በመታኋችሁ
ነበር። [16]ነገር ግን ኀይሌን እንዳሳይህና

9፥3 ዘፀ7፥4፤ዘሌ26፥25፤1ሳሙ5፥6፤ኢዮ13፥21፤መዝ32፥4፤39፥10፤78፥50፤አሞ4፥10፤ሐሥ13፥11
9፥4 ቍ26፤ ዘፀ8፥23
9፥6 ቍ19-21፤ ዘፀ11፥5፤12፥29፤ መዝ78፥48-50
9፥7 ዘፀ7፥14፡22፤8፥32
9፥9 ዘሌ13፥18፡19፤ዘዳ28፥27፡35፤2ነገ20፥7፤ኢዮ2፥7፤ኢሳ38፥21፤ራእ16፥2
9፥11 ዘፀ8፥18
9፥12 ዘፀ4፥21፤7፥4
9፥13 ዘፀ3፥18
9፥14 ዘፀ8፥10፤15፥11፤1ሳሙ2፥2፤2ሳሙ7፥22፤1ነገ8፥23፤1ዜና17፥20፤መዝ35፥10፤71፥19፤86፥8፤89፥6፤ኢሳ46፥9፤ኤር10፥6፤ ሚክ7፥18
9፥15 ዘፀ3፥20
9፥16 ዘፀ14፥4፡17፡31፤ምሳ16፥4፤መዝ20፥6፤25፥11፤68፥28፤71፥18፤106፥8፤109፥21፤ ሮሜ9፥17
9፥18 ቍ23፡24፤ ዘፀ10፥6፤ኢሱ10፥11፤መዝ78፥47-48፤105፥32፤148፥8፤ኢሳ30፥30፤ሕዝ38፥22፤ሐጌ2፥17፤
9፥20 ምሳ13፥13
9፥21 ዘፍ19፥14፤ ሕዝ33፥4-5
9፥23 ቍ18፤ዘፀ20፥18፤1ሳሙ7፥10፤12፥17፤መዝ18፥13፤29፥3፤68፥33፤77፥17፤104፥7፤ራእ8፥7፤16፥21
9፥24 ቍ18
9፥25 መዝ105፥32-33፤ሕዝ13፥13
9፥26 ቍ4፤ ኢሳ32፥18-20፤ ዘፀ10፥23፤11፥7፤12፥13፤አሞ4፥7
9፥27 ቍ34፤ ዘፀ10፥16፤ዘኍ14፥40፤ዘዳ1፥41፤ኢሱ7፥11፤መሳ10፥10፤1ሳሙ15፥24፤24፥17፤26፥21፤መዝ11፥7፤116፥5፤119፥137፤129፥4፤145፥17፤ኤር12፥1፤ሰቆ1፥18
9፥28 ዘፀ8፥8፤ ሐሥ8፥24
9፥29 ቍ33፤ ዘፀ19፥5፤1ነገ8፥22፡38፤ኢዮ11፥13፤41፥11፤ምሳ24፥1፤መዝ24፥1፤50፥12፤77፥2፤88፥9፤143፥6፤ኢሳ1፥15፤1ቆሮ10፥26
9፥30 ዘፀ8፥29

ስሜም በምድር ዙሪያ ሁሉ እንዲታወቅ
ለዚህ አስነሥቼሃለሁ።[a] [17]እስካሁንም በሕ
ዝቤ ላይ እንደ ተነሣህ ነው፤ ይሄዱም
ዘንድ አትለቃቸውም። [18]ስለዚህ ነገ በዚህ
ጊዜ ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ እስካ
ሁን ድረስ በግብፅ ላይ ወርዶ የማያውቅ
አስከፊ የበረዶ ማዕበል እልካለሁ። [19]ከብቶ
ችህና በመስክ ላይ ያለህ ማንኛውም ነገር
ወደ መጠለያ ይገቡ ዘንድ አሁን ትእዛዝ
ስጥ፤ ምክንያቱም በረዶው ወደ መጠለያ
ባልገቡትና በመስክ ላይ በቀሩት በማንኛ
ውም ሰውና እንስሳት ላይ ወርዶባቸው
ስለሚሞቱ ነው።
[20]የእግዚአብሔርን (ያህዌ) ቃል የፈሩት
የፈርዖን ሹማምንቶች፣ ባሮቻቸውንና ከብቶ
ቻቸውን ለማስገባት ተጣደፉ። [21]የእግዚአ
ብሔርን (ያህዌ) ቃል ችላ ያሉት ግን ባሮቻ
ቸውንና ከብቶቻቸውን በመስክ ላይ እንደ
ነበሩ ተዉአቸው።
[22]ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን፣
“በመላይቱ የግብፅ ምድር ባሉት ሰዎች፣
በእንስሳት እንዲሁም በምድሪቱ ላይ በሚበ
ቅሉት ነገሮች ሁሉ ላይ በረዶ እንዲ
ወርድ እጅህን ወደ ሰማይ አንሣ” አለው።
[23]ሙሴ በትሩን ወደ ሰማይ ባነሣ ጊዜ
እግዚአብሔር (ያህዌ) ነጐድጓድና በረዶ አወረደ፤
መብረቅም በምድሪቱ ላይ ሆነ። እግዚ
አብሔር (ያህዌ) በግብፅ ምድር በረዶ አዘነበ፤
[24]በረዶ ወረደ፤ መብረቅም አብረቀረቀ፤
ግብፅ ሐገር ከሆነችበት ዘመን አንሥቶ
በምድሪቱ ሁሉ እንደዚህ ያለ አስከፊ ማዕ
በል ሆኖ አያውቅም። [25]በመላው ግብፅ
በረዶ በመስክ ላይ ያለውን ሁሉ፣ ሰዎ
ችንና እንስሳትንም መታ፤ በመስክ ላይ
የበቀለውን ሁሉ አጠፋ፤ ዛፉን ሁሉ ባዶ
አስቀረ። [26]በረዶ ያልወረደበት ቢኖር እስ
ራኤላውያን የሚኖሩበት የጌሤም ምድር
ብቻ ነበር።
[27]ከዚያም ፈርዖን ሙሴንና አሮንን
አስጠራ፤ እንዲህም አላቸው፤ 'አሁንስ በድ
ያለሁ፤ እግዚአብሔር (ያህዌ) ትክክል ነው፤
እኔና ሕዝቤ ግን ስተናል። [28]መብረቅና
በረዶ በዝቶብናልና ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ)
ጸልዩልን፤ እንድትሄዱ እለቃችኋለሁ፤ ከዚህ
በኋላ በዚህ የመኖር ግዴታ የለባችሁም።
[29]ሙሴም መልሶ፣ “ከከተማዋ በወጣሁ
ጊዜ፣ እጆቼን ለጸሎት ወደ እግዚአብሔር
(ያህዌ) እዘረጋለሁ፤ አንተም ምድር የእግዚአ
ብሔር (ያህዌ) እንደ ሆነች ታውቅ ዘንድ
መብረቁ ያቆማል፤ ከእንግዲህ በኋላ በረዶ
አይኖርም። [30]ሆኖም አንተና ሹማምንቶችህ

[a]16 ወይም፣ ለዚህ ምሕረቴን አሳይቼሃለሁ

አሁንም ቢሆን እግዚአብሔር (ያህዌ) አምላ
ክን እንደማትፈሩ ዐውቃለሁ::
[31]ተልባው አብቦ፣ ገብሱም ፍሬ ይዞ
ስለነበር፣ ተልባውና ገብሱ ከጥቅም ውጭ
ሆኑ:: [32]ስንዴውና አጃው ግን በዚያ ወቅት
ባለማፍራቱ አልጠፋም ነበር::
[33]ከዚያም ሙሴ ከፈርዖን ተለይቶ ከከ
ተማው ወጣ:: እጆቹን ወደ እግዚአብሔር
(ያህዌ) ዘረጋ፤ ነጎድጓዱና በረዶው ቆመ፤ ዝና
ቡም በምድሪቱ ላይ መዝነቡን አቆመ::
[34]ፈርዖንም ዝናቡ፣ በረዶውና ነጎድጓዱ
መቆሙን ባየ ጊዜ እንደገና በደለ፤ እርሱና
ሹማምንቶቹ ልባቸውን አደነደኑ:: [35]ስለዚህ
የፈርዖን ልብ ደነደነ፤ እግዚአብሔር (ያህዌ)
ለሙሴ እንደ ተናገረውም እስራኤላውያን
ይሄዱ ዘንድ አልለቀቃቸውም::

## የአንበጣ መንጋ መቅሠፍት

10 ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን
እንዲህ አለው፤ "ተመልሰህ ወደ
ፈርዖን ሂድ፤ እነዚህን ታምራዊ ምልክቶች
በመካከላቸው ለማድረግ የፈርዖንንና የሽ
ማምንቱን ልብ አደንድኛለሁና፤ [2]ይኸውም
ግብፃውያንን እንዴት አድርጌ እንደ ቀጣ
ኋቸውና በመካከላቸውም ምልክቶቼን እን
ዴት እንዳደረግሁ ለልጆቻችሁና ለልጅ
ልጆቻችሁ እንድትነግሩና እኔ እግዚአብሔር
(ያህዌ) መሆኔንም እንድታውቁ ነው::"
[3]ሙሴና አሮን ወደ ፈርዖን ሄደው
እንዲህ አሉት፤ "የዕብራውያን አምላክ
እግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) እንዲህ ይላል፤ 'ራ
ስህን በፊቴ ለማዋረድ እስከ መቼ እምቢ
ትላ ለህ? ሕዝቤ ያመልኩኝ ዘንድ
ልቀቃቸው:: [4]እንዳይሄዱ ብትከለክላቸው ነገ
በአገርህ ላይ አንበጣዎችን አመጣለሁ::
[5]አንበጣዎቹም ምድሪቱ እስከማትታይ
ድረስ ይሸፍኗታል፤ በመስክህ ላይ እያቈጠ
ቈጠ ያለውን ዛፍ ሁሉ ሳይቀር ከበረዶ
የተረፈውንም ጥቂቱን ሁሉ ይበሉታል::
[6]የአንተን፣ የሹማምንትህ ንና የግጠ
ብፃውያንን ቤቶች ሁሉ ይሞሏቸ ዋል፤
ይህም አባቶችህም ሆኑ ቅድመ አያ ቶችህ
በዚህች ምድር ከሰፈሩበት ጊዜ ጀምሮ
እስካሁን ድረስ ከቶ አይተውት የማ ያውቀ
ት ነው::'" ሙሴም ተመለሰና ከፈር ዖን
ተለይቶ ሄደ::
[7]የፈርዖንም ሹማምንት፣ "ይህ ሰው እስከ
መቼ ወጥመድ ይሆንብናል? አምላካቸውን
እግዚአብሔርን (ያህዌ) እንዲያመልኩ ሰዎቹን
ልቀቃቸውና ይሂዱ:: ግብፅ መጥፋቷን እስ
ካሁን አልተገነዘብህምን? አሉት::
[8]ከዚያም ሙሴና አሮን ወደ ፈርዖን
እንዲመጡ ተደረገ፤ "ሂዱ አምላካችሁን
እግዚአብሔርን (ያህዌ) አምልኩ፤ ነገር ግን
መሄድ የሚገባቸው የትኞቹ ናቸው?" አለ::
[9]ሙሴም፣ "ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በዓል
ልናከብር ስለሆነ ወጣቶቻችንንና ሽማግሌ
ዎቻችንን፣ ወንድና ሴት ልጆቻችንን፣ የበግና
የፍየል መንጋዎቻችንን እንዲሁም የቀንድ
ከብቶቻችንን ይዘን እንሄዳለን" አለ::
[10]ፈርዖንም እንዲህ አለ፤ "ከሴቶቻችሁና
ከልጆቻችሁ ጋር እንድትሄዱ እለቃችኋለሁ
እግዚአብሔር (ያህዌ) ከእናንተ ጋር ይሁን ነገር
ግን ተንኰል አስባችኋል::[ከ] [11]አይሆንም ወን
ዶቹ ብቻ እንዲሄዱና እግዚአብሔርን (ያህዌ)
እንዲያመልኩ አድርጉ፤ የጠየቃችሁት ይህንኑ
ነው::" ከዚያም ሙሴና አሮን ከፈርዖን ፊት
እንዲወጡ ተደረገ::
[12]እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን፣ "የአንበጣ
መንጋ ምድሪቱን እንዲወር ከበረዶ የተረፈ
ውን ሁሉና በማሳም ላይ የበቀለውን ሁሉ
ጠርጎ እንዲበላ እጅህን በግብፅ አገር ላይ
ዘርጋ" አለው::
[13]ስለዚህ ሙሴ በግብፅ አገር ላይ በት
ሩን ዘረጋ፤ እግዚአብሔርም (ያህዌ) በዚያን
ቀንና ሌሊት በሙሉ በምድሪቱ ላይ
የምሥራቅ ነፋስ እንዲነፍስ አደረገ፤ በማ
ግሥቱም ነፋሱ አንበጣዎችን አመጣ::
[14]እነርሱም ግብፅን በሙሉ ወረሩ፤ ስፍር
ቍጥር የሌላቸው ሆነው የሀገሪቱን ዳር
ድንበር ሁሉ አለበሱ:: እንዲህ ያለ የአንበጣ
መዓት ከዚህ ቀደም አልነበረም፤ ወደ
ፊትም ደግሞ አይኖርም:: [15]ምድሩ
ሁሉ ጠቍሮ እስኪጨልም ድረስ አለበ
ሱት:: ከበረዶ የተረፈውን በመስክ ላይ የበ
ቀለውንና በዛፍ ላይ ያለውን ፍሬ ሁሉ፣ ጠር
ገው በሉ:: በግብፅ ምድር ሁሉ በዛፍ ላይ
ወይም በተክል ላይ አንዳች ቅጠል አልተረ
ፈም ነበር::
[16]ከዚያም ፈርዖን ሙሴንና አሮንን በፍ
ጥነት አስጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ "በአም
ላካችሁ በእግዚአብሔር (ያህዌ) በእናንተም ላይ
ኀጢአት ሠርቻለሁ፤ [17]እንግዲህ አሁን አንድ
ጊዜ ደግሞ ኀጢአቴን ይቅር በሉኝና ይህንን
ቀሣፊ መዓት እንዲያስወግድልኝ አምላካች
ሁን እግዚአብሔርን (ያህዌ) ለምኑልኝ::"
[18]ሙሴም ከፈርዖን ዘንድ ወደ እግዚአ
ብሔር (ያህዌ) ጸለየ:: [19]ከዚያም እግዚአብሔር
(ያህዌ) ነፋሱን ወደ ብርቱ የምዕራብ ነፋስ
ለወጠው ያም ነፋስ አንበጣዎቹን እየነዳ
ወደ ቀይ ባህር[ሸ] ከተታቸው፤ በግብፅ ምድር
በየትኛውም ቦታ አንድም አንበጣ አልቀ
ረም:: [20]እግዚአብሔር (ያህዌ) ግን የፈርዖንን
ልብ አደነደነ፤ ፈርዖንም እስራኤላውያን

9፥31 ዘዳ8፥8፤ ሩት1፥22፤2፥23፤ 2ሳሙ14፥30፤17፥28፤ ኢሳ28፥25፤ ሕዝ4፥9፤ኢል1፥11
9፥32 ኢሳ28፥25
9፥35 ዘፀ4፥21
10፥1 ዘፀ4፥21፤ 3፥19፤7፥3፤ ኢሱ24፥17፤ነህ9፥10፤ መዝ74፥9፤ 105፥26-36
10፥2 ዘፀ6፥2፤ 12፥26-27፤13፥8፡14፤ ዘዳ4፥9፤6፥20፤32፥7፤ ኢሱ4፥6፤1ሳሙ6፥6፤ መዝ44፥1፤71፥18፤ 78፥4፡5፤ኢል1፥3
10፥3 1ነገ21፥29፤ 2ነገ22፥19፤ 2ዜና7፥14፤12፥7፤ 33፥23፤34፥27፤ ኢዮ42፥6፤ኢሳ58፥3፤ ዳን5፥22፤ያዕ4፥10፤ 1ጴጥ5፥6
10፥4 ዘፀ8፥2፤ 9፥2፤ዘዳ28፥38፤ ምሳ30፥27፤ መዝ105፥34፤ ኢል1፥4፤ራእ9፥3
10፥5 ቍ15፤ ዘፀ9፥32፤ኢል1፥4
10፥6 ዘፀ9፥18፤ ኢል2፥9
10፥7 ዘፍ20፥3፤ ዘፀ8፥19፤23፥33፤ 34፥12፤ዘዳ7፥16፤ 12፥30፤20፥18፤ አሱ23፥13፤ መሳ2፥3፤8፥27፤16፥5፤1ሳሙ18፥21፤መዝ 106፥36፤መክ7፥26፤
10፥8 ዘፀ8፥8
10፥9 ዘፀ3፥18
10፥12 ዘፀ7፥19
10፥13 ቍ4፡21-22፤ዘፀ4፥17፤8፥5፡ 17፤9፥23፤1 4፥15-16፤26፥27፤ 17፥5፤ዘኍ20፥8፤ 1ነገ8፥37፤መዝ78፥46፤105፥34፤ አሞ4፥9፤ናሆ3፥16
10፥14 ዘዳ28፥38፤ መዝ78፥46፤ኢሳ33፥4፤ኢል1፥4፤2፥1-11፡ 25፤አሞ4፥9
10፥15 ዘዳ28፥38፤ መዝ105፥34-35፤ ኢል1፥4፤አሞ7፥2፤ ሚል3፥11
10፥16 ዘፀ8፥25፤ 9፥27
10፥17 ዘፀ 8፥8፤1ሳሙ15፥25
10፥18 ዘፀ8፥30
10፥20 ዘፀ4፥21

[ከ]10 ወይም፣ ተጠንቀቁ፤ ችግር ተዘጋጅቶላችኋል!

እንዲሄዱ አልፈቀደም።

## የጨለማ መቅሠፍት

[21]ከዚያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን፣
“በግብፅ ላይ ድቅድቅ ጨለማ እንዲወርድ
እጅህን ወደ ሰማይ ዘርጋ” አለው። [22]ሙሴም
እጁን ወደ ሰማይ ዘረጋ፤ በመላው ግብፅ
ላይ ለሦስት ቀናት ድቅድቅ ያለ ጨለማ
ሆነ። [23]በነዚያ ሦስት ቀናት ውስጥ አንዱ
ሌላውን ማየት ወይም ከነበረበት ቦታ
መንቀሳቀስ አይችልም ነበር። ይሁን እንጂ
እስራኤላውያን በሚኖሩበት ስፍራ ሁሉ
ብርሃን ነበር።

[24]ከዚያም ፈርዖን ሙሴን አስጠርቶ፣
“ሂዱችሁ *እግዚአብሔርን* (ያህዌ) አምልኩ፤ ሴቶ
ቻችሁና ልጆቻችሁ ሳይቀሩ አብረዋችሁ
ይሂዱ፤ በጎቻችሁ፣ ፍየሎቻችሁና የጋማ
ከብቶቻችሁ ብቻ እዚሁ ይቅሩ” አለው።

[25]ሙሴም እንዲህ አለው፤ “ለአምላካችን
*ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) መሥዋዕትና የሚቃጠል
መሥዋዕት እንድንሠዋ ፍቀድልን፤ [26]እንስ
ሶቻችን ሁሉ አብረው መሄድ አለባቸው።
አንድ ሰኰና እንኳን አይቀርም። ከእንስሶቻ
ችን መካከል ለአምላካችን *ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) አምልኮ የምናቀርባቸው ይኖራሉ፤
ሆኖም እዚያ ከመድረሳችን በፊት *እግዚ
አብሔርን* (ያህዌ) ለማምለክ የምናቀርባቸው
እንስሳት የትኞቹ እንደ ሆኑ አስቀድመን
ለይተን ማወቅ አንችልም።”

[27]ነገር ግን *እግዚአብሔር* (ያህዌ) የፈርዖንን
ልብ አደነደነ፤ ፈርዖንም ሕዝቡን መልቀቅ
አልፈቀደም። [28]ፈርዖን ሙሴን፣ “ከፊቴ ጥፋ!
ስማ! ሁለተኛ እኔ ዘንድ እንዳትደርስ!
ፊቴን ባየህበት በዚያ ቀን ፈጽመህ
እንደምትሞት ዕወቅ” አለው።

[29]ሙሴም፣ “እንዳልከው ይሁን! እኔም
ዳግመኛ ከፊትህ አልደርስም” አለው።

## በበኵሮች ላይ የወረደ መቅሠፍት

**11** *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ “በፈርዖንና በግብፅ ላይ
አንድ ሌላ መቅሠፍት አወርድባቸዋለሁ፤
ከዚያም በኋላ ፈርዖን ይለቃችኋል፤ ሲለቃ
ችሁም አንዳችሁን ሳያስቀር ያስወጣችኋል።
[2]ለእስራኤል ሕዝብ ለወንዶቹም ሆነ ለሴቶቹ
የብርና የወርቅ ዕቃዎች ከየጎረቤቶቻቸው
ስጡን ብለው እንዲወስዱ ንገራቸው። [3]*እግዚ
አብሔርም* (ያህዌ) እስራኤላውያን በግብፃውያን
ዘንድ ሞገስ እንዲያገኙ አደረጋቸው። ሙሴም
በግብፅ ምድር በፈርዖን ሹማምንትና በመላው
ሕዝብ ዘንድ እጅግ የተከበረ ሰው ሆነ።

[4]ከዚህ በኋላ ሙሴ እንዲህ አለ፤ “*እግ
ዚአብሔር* (ያህዌ) የሚለው ይህ ነው፤ ‘እኩለ

10፥21 ዘዳ28፥29
10፥22 መዝ105፥28፤ ኢሳ13፥10፤45፥7፤ 50፥3፤ራእ16፥10
10፥23 ዘፀ8፥22፤ አሞ4፥7
10፥24 ቍ8-10፤ ዘፍ45፥10፤ ዘፀ8፥8
10፥25 ዘፍ8፥20፤ ዘፀ18፥12
10፥27 ዘፀ4፥21
10፥29 ዘፀ11፥8፤ ዕብ11፥27
11፥1 ዘፀ3፥20፤6፥1
11፥2 ዘፀ3፥21፡22
11፥3 ዘፍ39፥21፤ ዘዳ34፥11፤2ሳሙ7፥98 ፥13፤22፥44፤23፥1፤አስ 9፥4፤መዝ89፥27
11፥4 ዘፀ12፥23፡ 29፤ኢዮ34፥20፤ መዝ81፥5
11፥5 ዘፀ4፥23፤ ኢሳ47፥2
11፥6 ዘፀ12፥30፤ ምሳ21፥13፤አሞ5፥17
11፥7 ዘፀ8፥22
11፥8 ዘፀ12፥31-33፤ ዕብ11፥27
11፥9 ዘፀ3፥20፤7፥4
11፥10 ዘፀ4፥21፤ ሮሜ2፥5
12፥2 ቍ18፤ ዘፀ13፥4፤23፥15፤ 34፥18፤40፥2፤ ዘዳ16፥1
12፥3 ቍ21፤ ማር14፥12፤1ቆሮ5፥7
12፥5 ዘፀ29፥1፤ ዘሌ1፥3፤3፥1፤4፥3፤ 22፥18-21፤ 23፥12፤ ዘኍ6፥14፤15፥8፤ 28፥3፤ዘዳ15፥ 21፤17፥1፤ዕብ9፥14፤ 1ጴጥ1፥19
12፥6 ቍ19፤ ዘፀ16፥12፤ዘሌ23፥5፤ ዘኍ9፥1-3፤5፥11፤ ዘዳ16፥4፡6፤ኢሱ5፥ 10፤2ዜና30፥2
12፥7 ቍ13፡23፤ ሕዝ9፥6

ሌሊት ሲሆን በመላው የግብፅ ምድር ላይ
አልፋለሁ። [5]በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠው
ከፈርዖን ልጅ አንሥቶ የወፍጮ መጅ ገፊ
እስከ ሆነችው እስከ ባሪያይቱ ልጅ ድረስ
በግብፅ ምድር በኵር ሆኖ የተወለደ ወንድ
ልጅ ሁሉ ይሞታል፤ እንዲሁም የቀንድ
ከብቱ በኵር በሙሉ ያልቃል። [6]በግብፅ
ምድር ሁሉ ከዚህ በፊት ያልተሰማ ወደ
ፊትም የማይሰማ ታላቅ ዋይታ ይሆናል።
[7]በእስራኤላውያን ዘንድ ግን በሰውም ሆነ
በእንስሳት ላይ ውሻ እንኳ አይጮኽባቸ
ውም።’ በዚህም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) በግብፃ
ውያንና በእስራኤላውያን መካከል ልዩነት
የሚያደርግ መሆኑን ታውቃላችሁ። [8]ሹማ
ምንትህ በሙሉ ወደ እኔ ይመጣሉ፤ እጅ
እየነሡም ‘አንተም ሆንህ የምትመራቸው
ሰዎች በሙሉ ውጡልን’ ብለው ይለምኑ
ኛል፤ እኔም ከዚያ በኋላ እሄዳለሁ።” ከዚ
ያም ሙሴ በታላቅ ቍጣ ከፈርዖን ዘንድ
ወጣ።

[9]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን “ድንቅ ሥራ
ዎቼ በግብፅ ምድር በብዛት ይታዩ ዘንድ
ፈርዖን እናንተን አይሰማችሁም” አለው።
[10]ሙሴና አሮንም እነዚህን ድንቅ ታምራት
በፈርዖን ፊት አደረጉ። ነገር ግን *እግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) የፈርዖንን ልብ አደነደነ፤ ፈር
ዖንም እስራኤላውያን ከአገሩ ለቀው እንዲ
ሄዱ አልፈቀደም።

## የፋሲካ በዓል

12፥14-20 ተጓ ምብ - ዘሌ 23፥4-8፤ ዘኍ 28፥16-25፤
ዘዳ 16፥1-8

**12** *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴንና አሮንን
በግብፅ እንዲህ አላቸው፤ [2]“ይህ ወር
ለእናንተ የወር መጀመሪያ፣ የዓመቱም መጀ
መሪያ ይሁንላችሁ። [3]ለመላው የእስራኤል
ሕዝብ ይህንን ንገሩ፤ ይህ ወር በገባ በአ
ሥረኛው ቀን እያንዳንዱ ሰው አንዳንድ
ጠቦት ለቤተ ሰቡ፣ አንዳንድ ጠቦት ለአባቱ
ቤት ያዘጋጅ። [4]ማንኛውም ቤተሰብ ለአንድ
ሙሉ ጠቦት ቍጥሩ አነስተኛ ከሆነ፣ በጐ
ረቤት ያሉትን ሰዎች ቍጥር እስከ ቅርብ
ከሆነው ጋር መካፈል ይኖርበታል፤ እያን
ዳንዱ ሰው በሚበላው መጠንም ምን ያህል
ጠቦት እንደሚያስፈልግ መወሰን ይኖርባ
ችኋል። [5]የምትመርጡት ጠቦት በግ ወይም
ፍየል ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ምንም
ነውር የሌለበትና አንድ ዓመት የሞላው
ተባዕት መሆን አለበት። [6]ወሩ በገባ እስከ
አሥራ አራተኛው ቀን ድረስ ጠብቋቸው።
በዚያ ምሽት ጀምበር ስትጠልቅ የእስራ
ኤል ሕዝብ ሁሉ ይረዷቸው። [7]ከዚያም
ከደሙ ወስደው የጠቦቶቹ ሥጋ የሚበላ

በትን የእያንዳንዱን ቤት ደጃፍ መቃንና
ጉበን ይቀቡ። [8]ሥጋውንም በዚያችው ሌሊት
በእሳት ላይ ጠብሰው ከመራራ ቅጠልና
ካልቦካ ቂጣ ጋር ይብሉት። [9]ጥሬውን
ሥጋ ወይም ቅቅሉን አትብሉ፤ ነገር ግን
ጭንቅላቱን፣ እግሮቹንና ሆድ ዕቃውን
በእሳት ላይ ጠብሳችሁ ብሉት። [10]ከሥጋው
ተርፎ አይደር፤ ያደረ ቢኖር ግን በእሳት
ይቃጠል። [11]ስትበሉም ልብሳችሁን ለብሳ
ችሁ፣ ባጭር ታጥቃችሁ፣ ጫማችሁን አድ
ርጋችሁ በትራችሁን ይዛችሁ በጥድፊያ
ብሉት፤ የእግዚአብሔር (ያህዌ) ፋሲካ ነው።
[12]"እኔም በዚያች ሌሊት በግብፅ ምድር
ላይ አልፋለሁ፤ ከሰውም ከእንስሳም የተወለ
ደውን የበኵር ልጅ ሁሉ እገድላለሁ፤ የግ
ብፅን አማልክት ሁሉ እፈርድባቸዋለሁ፤
እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ። [13]ደሙም ያላ
ችሁበትን ቤት ለይቶ የሚያሳይ ምልክት
ይሆንላችኋል፤ እኔ ደሙን በማይበት ጊዜ
እናንተን አልፋለሁ፤ ግብፅን ስቀጣ መቅሠ
ፍቱ አይደርስባችሁም።
[14]"ይህን ቀን መታሰቢያ ታደርጉታላ
ችሁ፤ በሚቀጥሉት ትውልዶች ሁሉ ቋሚ
ሥርዐት ሆኖ የእግዚአብሔር (ያህዌ) በዓል
አድርጋችሁ ታከብሩታላችሁ። [15]ለሰባት
ቀናት እርሾ የሌለበትን ቂጣ ብሉ፤
በመጀመሪያው ቀን እርሾን ሁሉ ከቤታ
ችሁ አስወግዱ፤ በነዚህ ሰባት ቀናት እርሾ
ያለበትን ቂጣ የበላ ማንኛውም ሰው ከእስ
ራኤል ይወገድ። [16]በመጀመሪያውና በሰባ
ተኛው ቀን የተቀደሰ ጉባዔ አድርጉ።
በእነዚህ ቀናት ምንም ዐይነት ሥራ አት
ሥሩ፤ የምትሠሩት ሥራ ቢኖር ለእያንዳንዱ
ምግብ ማዘጋጀት ብቻ ይሆናል።
[17]የቂጣን በዓል አክብሩ፤ ሰራዊታችሁን
ከግብፅ ምድር ያወጣሁት በዚች ዕለት ነውና።
ይህን ዕለት ለሚቀጥለው ትውልድ ቋሚ
ሥርዐት በማድረግ አክብሩት። [18]ከመጀመ
ሪያው ወር ከአሥራ አራተኛው ቀን ምሽት
እስከ ሃያ አንደኛው ቀን ምሽት ድረስ
እርሾ የሌለበት ያልቦካ ቂጣ ትበላላችሁ።
[19]ለሰባት ቀን እርሾ በቤታችሁ አይኑር፤
መጻተኛም ሆነ የአገር ተወላጅ እርሾ
ያለበትን ቂጣ የበላ ከእስራኤል ማኅበር
ይወገድ። [20]እርሾ ያለበትን ምንም ነገር
አትብሉ፤ በምትኖሩበት ስፍራ ሁሉ ያልቦካ
ቂጣ ነዉ መብላት ያለባችሁ።
[21]ከዚያም ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ
አለቆች በሙሉ አስጠርቶ እንዲህ አላቸው፤
"ቶሎ ሄዳችሁ ለየቤተ ሰቦቻችሁ የሚሆን
ጠቦት መርጣችሁ የፋሲካን በግ እረዱ።
[22]ከዚያም ጭብጥ የሂሶጵ ቅጠል በመውሰድ፣
በሳህን ውስጥ ካለው ደም ነክራችሁ የየቤ
ቶቻችሁን ጉበንና ግራ ቀኝ መቃኑን ቀቡ።
ከእናንተ አንድም ሰው እስኪነጋ ድረስ ከቤቱ
አይውጣ። [23]እግዚአብሔር (ያህዌ) ግብፃውያንን
ለመቅሠፍ በምድሪቱ ላይ በሚያልፍበት ጊዜ
በጉበኑና በመቃኑ ላይ ያለውን ደም ሲያይ
ያንን ደጃፍ አልፎ ይሄዳል፤ ቀሣፊውም ወደ
ቤታችሁ ገብቶ እንዳይገድላችሁ ይከለክ
ለዋል።
[24]"እናንተም ሆነ ልጆቻችሁ ይህን
መመሪያ ቋሚ ሥርዐት አድርጋችሁ ትጠ
ዘዛላችሁ። [25]እግዚአብሔር (ያህዌ) እሰጣችኋለሁ
ብሎ በገባው ቃል መሠረት ወደ ምድሪቱ
ስትገቡ ይህን ሥርዐት ጠብቁ። [26]ልጆቻ
ችሁ ስለ ሥርዐቱ ምንነት ሲጠይቋችሁ፣
[27]'ግብፃውያንን በቀሠፈ ጊዜ፣ በግብፅ ምድር
የእስራኤላውያንን ቤት አልፎ በመሄድ
ቤታችንን ላተረፈ፣ ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
የፋሲካ መሥዋዕት ነው' ብላችሁ ንገሯ
ቸው።" ከዚያም ሕዝቡ አጐነበሱ፤ ሰገ
ዱም። [28]እስራኤላውያንም እግዚአብሔር
(ያህዌ) ሙሴንና አሮንን እንዳዘዛቸው አደረጉ።
[29]እኩለ ሌሊት ላይ እግዚአብሔር (ያህዌ)
በግብፅ ምድር በዙፋን ላይ ከተቀመጠው
ከፈርዖን የበኵር ልጅ ጀምሮ በጨለማ
እስር ቤት ውስጥ እስካለው እስረኛ የበኵር
ልጅ ድረስ ያለውንና የእንስሳቱን በኵሮች
ሁሉ ቀሠፋቸው። [30]ፈርዖን፣ ሹማምንቱና
የግብፅ ሕዝብ በሙሉ ሌሊቱን ከመኝታ
ቸው ተነሡ፤ እነሆ በመላይቱ ግብፅ ለቅ
ሶና ዋይታ ነበር፤ ሰው ያልሞተበት አንድም
ቤት አልነበረምና።

## ከግብፅ መውጣት

[31]ፈርዖን ሙሴንና አሮንን ሌሊቱን
አስጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ "ተነሡ እናንተና
እስራኤላውያን ከሕዝቤ መካከል ውጡ!
ሂዱ፤ በጠየቃችሁት መሠረት እግዚአብሔርን
(ያህዌ) አምልኩ፤ [32]እንዳላችሁት የበግና የፍየል
መንጋችሁን፣ የቀንድና የጋማ ከብቶቻችሁን
ይዛችሁ ሂዱ፤ እኔንም ባርኩኝ።"
[33]ግብፃውያን አገራቸውን በአስቸኳይ
ለቀው እንዲወጡላቸው እስራኤላውያንን
አጣደፏቸው። "አለበለዚያማ ሁላችንም ማለ
ቃችን ነው" አሉ። [34]ስለዚህ ሕዝቡ ያልቦካ
ውን ሊጥ በየቡሆ ዕቃው አድርገው በጨርቅ
ጠቅልለው በትከሻቸው ተሸከሙ። [35]እስራ
ኤላውያን ሙሴ እንዳዘዛቸው የብርና የወርቅ
ዕቃዎች እንደዚሁም ልብስ እንዲሰጧቸው

12፥8 ቍ10፡19-20፤ዘፀ13፥3፤16፥19፤23፥18፤34፥25፤ዘሌ7፥15፤ዘኍ9፥11፡12፤ዘዳ16፥3-4፡7፤2ዜና35፥13፤1ቆሮ5፥8
12፥9 ዘፀ29፥13፡17፡22፤ዘሌ3፥3
12፥10 ቍ8፤ዘፀ13፥7፤29፥34፤ዘሌ22፥30፤ዘዳ16፥4
12፥11 ቍ13፡21፡27፡33፡43፤ዘሌ23፥5፤ዘኍ9፥2፡4፤28፥16፤ዘዳ16፥1፡3፤ኢሱ5፥10፤2ነገ23፥21፡23፤2ዜና30፥1፤ዕዝ6፥19፤ኢሳ31፥5፤48፥20፤52፥12፤ሕዝ45፥21
12፥12 ቍ29፤ዘፀ4፥23፤6፥2፤13፥15፤15፥11፤18፥11፤ዘኍ33፥4፤2ዜና2፥5፤መዝ95፥3፤97፥9፤135፥5፤ኢሳ10፥33፤19፥1፤31፥8፤37፥36፤ኤር 43፥12፤44፥8፤አሞ5፥17፤
12፥13 ቍ11፡23፤ዘፀ 8፥23፤ዕብ11፥28
12፥14 ቍ17፡24፤ዘፀ13፥5፡10፡9፤23፥14፤27፥21፤32፥5፤ዘሌ3፥17፤10፥9፤16፥29፤17፥7፤23፥14፤24፥3፤ዘኍ18፥23
12፥15 ዘፍ17፥14፤ዘፀ13፥6-7፤23፥15፤34፥18፤ዘሌ23፥6፤ዘኍ28፥17፤ዘዳ16፥3፤1ቆሮ5፥7
12፥16 ዘኍ29፥35
12፥17 ቍ41፤ዘፀ6፥6፡26፤13፥3፤23፥15፤34፥18፤ዘሌ3፥17፤19፥36፤ዘዳ16፥16፤2ዜና8፥13፤30፥21፤ዕዝ6፥22፤ማቴ26፥17፤ሉቃ22፥1፤ሐሥ12፥3፤
12፥18 ቍ2
12፥19 ዘፍ17፥14፤ዘኍ9፥14፤15፥14፤35፥15፤ዘዳ1፥16፤ኢሱ8፥33
12፥20 ዘሌ3፥17፤ዘፀ13፥6፤ዘኍ35፥29፤ሕዝ6፥6
12፥21 ቍ11፤ማር14፥12-16
12፥22 ዘሌ14፥4፡6፤ዘኍ19፥18፤መዝ51፥7፤ዕብ11፥28
12፥23 ቍ7፡13፤ ዘፍ16፥7፤ኢሳ19፥22፤37፥36፤ኤር6፥26፤48፥8፤1ቆሮ10፥10፤11፥28፤ራእ7፥3

12፥24 ቍ14 12፥25 ዘፍ15፥14፤ ዘፀ3፥17 12፥26 ዘፀ10፥2 12፥27 ቍ11፤ዘፍ 24፥26፤ዘፀ8፥23 12፥28 ቍ50 12፥29 ዘፍ19፥13፤ ዘፀ4፥23፤9፥6፤11፥4፤ 12፥30 ዘፀ11፥6 12፥31 ዘፀ8፥8 12፥32 ዘፍ27፥ 34፤ ዘፀ10፥9፡26 12፥33 ቍ11፤ዘፍ20፥ 3፤ዘፀ6፥1፤8፥19፤ 1ሳሙ6፥6 12፥34 ዘፀ 8፥3 12፥35 ዘፍ24፥5 3፤ ዘፀ3፥22፤

ግብፃውያኑን ጠየቋቸው። 36*እግዚአብሔር*
(ያህዌ) በግብፃውያን ፊት ለእስራኤላውያን
ሞገስ ስለሰጣቸው፣ የጠየቋቸውን ሁሉ ሰጧ
ቸው፤ ስለዚህ የግብፃውያንን ንብረት በዝ
ብዘው ወሰዱ።
37እስራኤላውያን ከራምሴ ተነሥተው ወደ
ሱኮት ሄዱ፤ ከሴቶቹና ከልጆቹ ሌላ፣ ስድስት
መቶ ሺህ እግረኛ ወንዶች ነበሩ። 38ከእነ
ርሱም ጋር ቍጥሩ የበዛ ሌላ ድብልቅ ሕዝብ
አብሮአቸው ወጣ፤ እንዲሁም አያሌ የበግ፣
የፍየል፣ የጋማና የቀንድ ከብት መንጋ ይዘው
ወጡ። 39ከግብፅ ይዘው ከወጡት ሊጥ
ያልቦካ ቂጣ ጋገሩ፤ ሊጡ አልቦካም ነበር፤
ምክንያቱም ከግብፅ በጥድፊያ እንዲወጡ
ስለተደረጉ፣ ለራሳቸው ምግብ ለማዘጋጀት
ጊዜ አልነበራቸውም።
40እንግዲህ እስራኤላውያን በግብፅ[ሠ] የኖሩ
በት ዘመን አራት መቶ ሠላሳ ዓመት
ነበር።
41ልክ አራት መቶ ሠላሳው ዓመት በተ
ፈጸመ ዕለት *የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ሰራዊት
ሁሉ ግብፅን ለቆ ወጣ።
42*እግዚአብሔር* (ያህዌ) በዚያች ሌሊት እነ
ርሱን ከግብፅ ለማውጣት ዘብ የቆመበት
በመሆኑ፣ ለሚቀጥሉት ትውልዶች ሁሉ
*እግዚአብሔርን* (ያህዌ) ያከብሩ ዘንድ፣ በዚ
ያች ሌሊት እስራኤላውያን ሁሉ ዘብ መቆም
ይኖርባቸዋል።

## የፋሲካ በዓል እንዴት መከበር እንዳለበት

43*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴንና አሮንን
እንዲህ አላቸው፤ "የፋሲካ በዓል አከባበር
ሥርዐት እንዲህ ነው፤ ባዕድ የሆነ ሰው
ከፋሲካው ምግብ አይብላ፤ 44በገንዘብ የገ
ዛኸው ማንኛውም ባሪያ ከገረዝኸው በኋላ
መብላት ይችላል 45ነገር ግን ለጊዜው
የተቀመጠ እንግዳና ቅጥር ሠራተኛ መብ
ላት የለበትም።
46"ምግቡ በአንድ ቤት ውስጥ መበላት
አለበት፤ ምንም ሥጋ ከቤት እንዳይወጣ፤
ምንም አጥንት እንዳትሰብሩ። 47የእስራኤል
ሕዝብ ሁሉ በዓሉን ማክበር ይኖርበታል።
48"በመካከላችሁ የሚኖር መጻተኛ *የእግ
ዚአብሔርን* (ያህዌ) የፋሲካ በዓል ማክበር ቢፈ
ልግ፣ በቤተ ሰቡ ያሉት ወንዶች ሁሉ መገ
ረዝ አለባቸው፤ ከዚያም እንደ ተወላጅ
ተቈጥሮ የሥርዐቱ ተካፋይ ይሁን። ያልተገ
ረዘ ወንድ ግን የፋሲካን ምግብ አይብላ።
49ይህም ሕግ በዜጋውም ሆነ በመካከላችሁ
በሚኖሩት መጻተኞች ላይ እኩል ተፈጻ
ሚነት ይኖረዋል።"
50እስራኤላውያን በሙሉ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ሙሴንና አሮንን ያዘዘውን ሁሉ ፈጸሙ።
51በዚያችው ዕለት *እግዚአብሔር* (ያህዌ) እስ
ራኤላውያንን በየሰራዊታቸው አድርጎ ከግብፅ
ምድር አወጣቸው።

## በኵር ሁሉ ለእግዚአብሔር መቀደሱ

13 *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን አለው፤
2"*መጀመሪያ* የተወለደውን ወንድ
ሁሉ ለእኔ ቀድስልኝ፤ ከእስራኤላውያን
መካከል የእናቱ የበኵር ልጅ የሆነው
ማሕፀን ከፋች ሰውም ሆነ እንስሳ የእኔ
ነው።"
3ከዚያም ሙሴ ሕዝቡን እንዲህ አለ፤
"ከባርነት ምድር ከግብፅ የወጣችሁባትን
ይህችን ዕለት አስታውሱ፤ ምክንያቱም *እግ
ዚአብሔር* (ያህዌ) በኀያል ክንዱ አውጥቶአች
ኋል። እርሾ ያለበትን ማንኛውንም ነገር
አትብሉ። 4እነሆ በዚች ዕለት በአቢብ
ወር ወጥታችኋል። 5*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ለእ
ናንተ ለመስጠት ሲል ቀድሞ ለአባቶቻችሁ
ወደ ማለላቸው ማርና ወተት ወደምታፈሰው
ወደ ከነዓናውያን፣ ኬጢያውያን፣ አሞራ
ውያን፣ ኤዊያውያን፣ ኢያቡሳውያን ምድር
በምትገቡበት ጊዜ ይህን በዓል በዚህ ወር
ታከብራላችሁ። 6ለሰባት ቀን ያለ እርሾ
የተጋገረ ቂጣ ትበላላችሁ። በሰባተኛውም
ቀን *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) በዓል ታደርጋ
ላችሁ። 7በእነዚህም ሶስት ቀናት ያልቦካ
ቂጣ ትበላላችሁ፤ በእናንተ ዘንድ እርሾ
ያለበት ነገር ፈጽሞ አይገኝ፤ በምድራች
ሁም አዋሳኝ በየትኛውም ቦታ እርሾ ፈጽሞ
አይኑር። 8በዚያችም ዕለት፣ 'እኔ ይህን የማ
ደርገው ከግብፅ ምድር በወጣሁበት ጊዜ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ስላደረገልኝ ነገር ነው'
ብለህ ለልጅህ ንገረው። 9*የእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ሕግ በከንፈራችሁ ላይ እንዲሆን ይህ
በዓል ለእናንተ በእጃችሁ ላይ እንደታሰረ
ምልክት፣ በእግራችሁ ላይ እንደሚገኝ መታ
ሰቢያ ይሆንላችኋል። *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
በኀያል ክንዱ ከግብፅ አውጥቶአችኋልና።
10ይህን ሥርዐት በተወሰነው ጊዜ በየዓመቱ
ጠብቁት።
11"*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ለእናንተና ለቀደ
ሙት አባቶቻችሁ በመሐላ በሰጠው ተስፋ
መሠረት ወደ ከነዓናውያን አገር በሚያስገ
ባችሁና ምድሪቱንም ለእናንተ በሚሰጣችሁ
ጊዜ፣ 12የእናቱን ማሕፀን የሚከፍተውን
ሁሉ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) ትሰጣላችሁ፤ እን
ደዚሁም እንስሶቻችሁ በመጀመሪያ የወለ
ዷቸው ወንዶች ሁሉ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ይሆናሉ። 13ከአህያ በመጀመሪያ የተወለደ
ውን ውርንጫ ግን በጠቦት ትዋጁታላችሁ፤

12፥36 ዘፍ39፥21፤ ዘፀ3፥22
12፥37 ዘፍ12፥2፤ 47፥11፤ዘፀ13፥20፤ 38፥26፤ዘኍ1፥46፤ 2፥32፤11፥13፡21፥26፤ 51፤33፥3-5
12፥38 ዘኍ11፥4፤ ኢሱ8፥35
12፥39 ዘፀ3፥20፤ 11፥1
12፥40 ዘፍ15፥13፤ ሐሥ7፥6፤ገላ3፥17
12፥41 ዘፀ3፥10፤ 6፥26
12፥42 ዘፀ13፥10፤ ዘሌ3፥17፤ዘኍ9፥3፤ ዘዳ16፥1፡6
12፥43 ቍ11፡48፤ ዘኍ9፥14፤15፥14፤ 2ዜና6፥32-33፤ኢሳ14፥ 1፤56፥3፡6፤ 60፥10
12፥44 ዘፍ17፥12-13
12፥45 ዘሌ22፥10
12፥46 ዘኍ9፥12፤ መዝ22፥14፤34፥20፤5 1፥8፤ምሳ17፥22፤ ዮሐ19፡36
12፥48 ቍ49፤ ዘሌ19፥18፡34፤ 24፥22፤ዘኍ9፥14፤ 10፥32፤ሕዝ44፥7
12፥49 ዘሌ24፥22፤ ዘኍ15፥15-16፡29፤ ዘዳ1፥16
12፥50 ቍ28
12፥51 ዘፀ3፥10፤ 6፥6፡26
13፥2 ቍ12፡ 13፡15፤ዘፀ22፥29፤ 34፥20፤ዘሌ27፥26፤ ዘኍ3፥13፤8፥17፤ 18፥15፤ዘዳ15፥19፤ ነህ10፥36፤ሉቃ2፥23
13፥3 ቍ14፤ዘፀ 3፥20፤7፥4፤12፥8፤ ዘሌ26፥13፤ዘኍ1፥1፤9 ፥1፤22፥5፤26፥4፤ዘዳ4፥ 45፤5፥6፤ መዝ81፥10፤114፥1
13፥4 ዘፀ12፥2
13፥5 ቍ11፤ ዘፀ3፥8፤12፥25-26
13፥6 ዘፀ12፥15-20
13፥8 ዘፀ10፥2፤ መዝ78፥5-6
13፥9 ቍ16፤ ዘፀ3፥20፤ዘዳ6፥8፤ 11፥18፤ምሳ3፥3፤ ኢሳ44፥5፤ማቴ23፥5
13፥10 ዘፀ12፥14፤ መዝ75፥2፤102፥13
13፥11 ቍ5፤ ዘፍ12፥7፤17፥19፤ 22፥16፤ዘዳ1፥8፤ መዝ105፥42-45
13፥12 ዘፍ4፥4፤ ዘሌ27፥26፤ ዘኍ3፥13፤18፥15፡ 17፤ሉቃ2፥23
13፥13 ቍ15፤ ዘሌ27፥11፤

ሠ40 ማሶሬቲክ ቅጂ፣ አራተ ሳምራውያንና የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም *በግብፅና በከነዓን* ይላሉ

አህያውን ካልዋጀኻችሁት ግን አንገቱን ስበሩት። ከወንድ ልጆቻችሁ መካከል በኵር የሆኑትን ሁሉ ዋጁ።

[14]“በሚመጡት ዘመናት ልጅህ፣ ‘ይህ ምን ማለት ነው?’ ብሎ ቢጠይቅህ እንዲህ በለው፤ ‘ከባርነት ምድር ከግብፅ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) በኀያል ክንዱ አወጣን፤ [15]ፈርዖን እኛን አለቅም ብሎ ልቡን ባደነደነ ጊዜ ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳ ድረስ በኵር ሆኖ በግብፅ የተወለደውን ሁሉ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ገደለው። እንግዲህ በመጀመሪያ የእናቱን ማሕፀን የከፈተውን ወንድ ሁሉ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) የምሠዋውና የልጆቼ በኵር ሆኖ የተወለደውን ወንድ ልጅ ሁሉ የምዋጀው በዚህ ምክንያት ነው። [16]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) በኀያል ክንዱ እኛን ከግብፅ ያወጣን ስለሆነ ይህ ሥርዐት በእጅህም ሆነ በግንባርህ ላይ እንደ ምልክት ይሆናል።”

## ቀይ ባሕርን መሻገር

[17]ፈርዖን ሕዝቡን በለቀቀ ጊዜ አቋራጭ ቢሆንም እንኳ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) በፍልስጥ ኤም ምድር በሚያልፈው መንገድ አልመራቸውም “ጦርነት ቢያጋጥማቸው ሐሳባቸ ውን ለውጠው ወደ ግብፅ ይመለሱ ይሆ ናል” ብሎአልና። [18]ስለዚህ *እግዚአብሔር* (ኤሎሂም) ሕዝቡን ዙሪያ በሆነው በምድረ በዳው መንገድ ወደ ቀይ ባሕር[o] መራቸው፤ እስራኤላውያንም ለጦርነት ዝግጁ ሆነው ከግብፅ ወጡ። [19]ዮሴፍ፤ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) በእርግጥ ይጐበኛችኋል፤ በዚያን ጊዜም ዐፅሜን ይዛችሁ ከዚች ምድር መውጣት አለባችሁ[#] ብሎ የእስራኤልን ልጆች አስ ምሎአቸው ስለ ነበር ሙሴ የዮሴፍን ዐፅም ይዞ ወጣ። እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሕዝቡን ዙሪያ በሆነው በምድረ በዳው መንገድ ወደ ቀይ ባህር መራቸው፤ እስራኤላውያንም ለጦርነት ዝግጁ ሆነው ከግብፅ ወጡ።

[20]እነርሱም ከሱኮት ከተነሡ በኋላ ከምድረ በዳው ጥግ ባለው በኤታም ሰፈሩ። [21]ስለዚህ በቀንም ሆነ በሌሊት መጓዝ ይችሉ ዘንድ፣ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) በቀን በመንገዳቸው ሊመራቸው በደመና ዓምድ፣ በሌሊት ደግሞ ብርሃን ሊሰጣቸው በእሳት ዓምድ በፊታቸው ይሄድ ነበር። [22]በቀንም ሆነ በሌሊት የደመናውና የእሳቱ ዓምድ ከሕዝቡ ፊት የተለየበት ጊዜ አልነበረም።

# 14

ከዚያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን አለው፤ [2]“እስራኤላውያን ተመልሰው በሚግዶልና በባሕሩ መካከል ባለው በፊሀሒሮት አጠገብ እንዲሰፍሩ ንገራቸው፤ በበኣልዛፎንም አንጻር በባሕሩ አጠገብ ይስፈሩ። [3]‘ፈርዖን እስራኤላውያን ግራ ተጋብተው በምድረ በዳ በመቅበዝበዝ ይንከራተታሉ’ ብሎ ያስባል። [4]እኔም የፈርዖንን ልብ ስለ ማደነድነው ያሳድዳቸዋል፤ ነገር ግን በፈርዖንና በሰራዊቱ ሁሉ ለራሴ ክብርን አገኛለሁ፤ ግብፃውያንም እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) መሆኔን ያውቃሉ።” እስራኤላውያንም ይህንኑ አደረጉ።

[5]የግብፅ ንጉሥ ሕዝቡ መሄዳቸው በተነገረው ጊዜ፣ ፈርዖንና ሹማምንቱ ስለ እነርሱ የነበራቸውን አሳብ በመለወጥ፣ “ምን ማድረጋችን ነው? እስራኤላውያን እንዲሄዱ ለቀቅናቸው፤ አገልግሎታቸውንም አጣን” አሉ። [6]ስለዚህ ሠረገላው እንዲዘጋጅለት አደረገ፤ ሰራዊቱንም ይዞ ተንቀሳቀሰ። [7]ስድስት መቶ ምርጥ ሠረገላዎችን ከሌሎች የግብፅ ሠረገላዎች ጋር ከነጦር አዛዦቻቸው አሰልፎ ተነሣ። [8]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) የንጉሡን የፈርዖንን ልብ ስለ አደነደነው በልበ ሙሉነት ከግብፅ የሚወጡትን እስራኤላውያን አሳደዳቸው። [9]ግብፃውያን፣ ይኸውም የፈርዖን ፈረሶችና ሠረገላዎች፣[#1] ፈረሰኞችና እግረኞች ሁሉ እስራኤላውያንን አሳደዷቸው፤ በበአልዛፎን አንጻር በባሕሩ አጠገብ በፊሀሒሮት ሰፍረው ሳሉ ደረሱባቸው።

[10]ፈርዖን በቀረበ ጊዜ እስራኤላውያን ቀና ብለው ተመለከቱ፤ እነሆ፣ ግብፃውያን ይከታተሏቸው ነበር፤ እነርሱም በታላቅ ፍርሃት ወደ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ጮኹ። [11]እነርሱም ሙሴን እንዲህ አሉት፤ “በምድረ በዳ እንድንሞት ያመጣኸን በግብፅ መቃብር ቦታ ጠፍቶ ነውን? ከግብፅ አውጥተህ ምን አደረግህልን? [12]በግብፅ ሳለን፣ ‘ተወን እባክህ፤ ግብፃውያንን እናገልግል’ አላልንህም ነበርን? በምድረ በዳ ከምንሞት ግብፃውያንን ብናገለግል ይሻል ነበር!”

[13]ሙሴም ለሕዝቡ መለሰላቸው፤ “አትሸበሩ፣ ጸንታችሁ ቁሙ፤ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ዛሬ የሚያደርግላችሁን መታደግ ታያላችሁ፤ ዛሬ የምታዩአቸውን ግብፃውያንን ዳግም አታዩአቸውም። [14]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ስለ እናንተ ይዋጋል፤ እናንተ ያለባችሁ መታገሥ ብቻ ነው።

[15]ከዚያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤ “ለምን ትጮኹብኛላችሁ? ይልቅስ እስራኤላውያንን ወደፊት እንዲ

ዘፀ34፥20፤ኢሳ66፥3፤ ዘኍ3፥46-47፤18፥15
13፥14 ዘፀ10፥2፤ 20፥2፤ዘዳ7፥8፤28፥68
13፥15 ቊ2
13፥16 ቊ9
13፥17 ዘፀ14፥11፤ ዘኍ14፥1-4፤ዘዳ 17፥16፤ሆሴ11፥5
13፥18 ዘፀ15፥22፤ ኢሱ1፥14፤4፥13፤መዝ 136፥16፤ሕዝ20፥10
13፥19 ዘፍ47፥29-30፤ኢሱ24፥32፤ ሐሥ7፥16፤ዕብ11፥22
13፥20 ዘፀ12፥37፤ ዘኍ33፥6
13፥21 ዘፀ 14፥19፡ 24፤24፥16፤33፥9-10፤ 32፥1፤33፥14፤ 34፥5፤40፥38፤ ዘኍ9፥16፤12፥5፤ 14፥14፤ዘዳ1፥33፤2፥7፤ 31፥8፤መሳ4፥14፤ 5፥4፤ነህ9፥12፥19፤ መዝ68፥7፤77፥20፤ 78፥14፤99፥7፤ 105፥39፤ኢሳ4፥5፤ ኤር2፥2፤ ዕን3፥13፤ 1ቆሮ10፥1፤
13፥22 ነህ9፡19
14፥2 ቊ9፤ ዘኍ33፥7፤ኤር44፥1፤ ሕዝ29፥10
14፥4 ቊ8፡17፡23፤ ዘፀ4፥21፤6፥2፤9፥16፤ መዝ71፥11፤ሕዝ32፥ 15፤ሮሜ9፥17፡22-23
14፥5 ዘፍ31፥21፤ መዝ105፥25
14፥7 ዘፀ15፥4
14፥8 ዘፀ11፥10፤ዘኍ 33፥3፤ሐሥ13፥17
14፥9 ቊ2፡6-7፡25 ዘፍ47፥17፤ዘፀ15፥9፤ ኢሱ24፥6፤ኢሳ43፥17
14፥10 ዘፀ15፥25፤ ኢሱ24፥7፤ነህ9፥9፤ መዝ5፥2፤34፥17፤ 50፥15፤107፥6፡28
14፥11 ዘፀ5፥21፤ 16፥3፤17፥3፤ዘኍ11፥1፤ 14፥22፤20፥4፤21፥5፤ ዘዳ9፥7፤መዝ106፥7-8
14፥12 ዘፀ5፥21፤ 15፥24፤17፥2፤ መዝ106፥7-8
14፥13 ቊ30፤ ዘፍ15፥1፤1ሳሙ 12፥16፤ 2ዜና20፥17
14፥14 ቊ25፤ ዘፀ15፥3፤ዘዳ1፥30፤ 3፥22፤20፥4፤ኢሱ 10፥14፤23፥3፥10፤ 1ሳሙ12፥16፤2ሳሙ 5፥24፤2ዜና20፥29፤ ነህ4፥20፤መዝ24፥8፤ 35፥1፤37፥7፤46፥10፤1 16፥7፤ኢሳ42፥13፤ 28፥12፤30፥15፤ኤር 41፥12፤ሕዝ32፥15፤ ዘካ2፥13
14፥15 ኢሱ7፥10

[o]18 በዕብራይስጡ *ያምሱፍ* ይላል። ትርጒሙም *የሸምበቆ ባሕር* ማለት ነው።
[#]19 ዘፍ50፥25 ይመ።
[#1]9 በዚህ ስፍራና በቊ17፡18፡23 እንዲሁም በቊ28 *ሠረገለኞ*

ኋዙ ንገራቸው፤ 16ውሃውን ለመክፈል በትርህን
አንሣና እጅህን በባሕሩ ላይ ዘርጋ፤ እስራ
ኤላውያን በባሕሩ ውስጥ በየብስ ይሻገራሉ።
17ተከትለዋቸው እንዲገቡም የግብፃውያንን
ልብ አጸናለሁ፤ በፈርዖንና በሰራዊቱ ሁሉ፣
በሠረገሎቹና በፈረሰኞቹ ለራሴ ክብርን
አገኛለሁ። 18በፈርዖንና በሰራዊቱ ሁሉ፣
በከበርሁ ጊዜ ግብፃውያን እኔ *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) እንደሆንሁ ያውቃሉ።

19ከዚያም ከእስራኤል ሰራዊት ፊት ፊት
ሆኖ ሲሄድ የነበረው የእግዚአብሔር (ኤሎሂም)
መልአክ ተመለሰና ወደ ኋላቸው መጣ፤
የደመናውም ዓምድ እንዲሁ ከፊት ተነሥቶ
ከኋላቸው ቆመ፤ 20በግብፅና በእስራኤል
ሰራዊት መካከል በመሆን፣ ሌሊቱን ሙሉ
ደመናው በአንድ በኩል ጨለማን ሲያመጣ፣
በሌላው በኩል ብርሃን አመጣ፤ ስለዚህ ሌሊ
ቱን በሙሉ አንዱ ወደ ሌላው ሊጠጋ አልቻ
ለም።

21ሙሴ እጁን በባሕሩ ላይ ዘረጋ፤ *እግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) ሌሊቱን በሙሉ ብርቱ የምሥራቅ
ነፋስ አስነሥቶ ባሕሩን ወደ ኋላ በማሸሽ
ደረቅ ምድር አደረገው፤ ውሃው ተከፈለ፤
22እስራኤላውያን ውሃው በግራና በቀኝ
እንደ ግድግዳ ሆኖ በየብስ በባሕሩ ውስጥ
አለፉ።

23ግብፃውያንም አሳደዷቸው፤ የፈርዖን
ፈረሶች፣ ሰረገሎችና ፈረሰኞች በሙሉ ተከ
ትለዋቸው ወደ ባሕሩ ገቡ። 24ሲነጋጋም
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) በእሳትና በደመና ዓምድ
ሆኖ በግብፃውያን ሰራዊት ላይ ሽብር ላከባ
ቸው። 25መንዳት እንዳይችሉም የሠረገላ
ዎቹን መሽከርከሪያዎች አቄላለፈባቸው[የ]
ግብፃውያኑም፣ "ከእስራኤላውያን እንሽሽ!
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ግብፅን እየተዋጋላቸው
ነው" አሉ።

26ከዚያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን፣
"ውሃው ግብፃውያንን ሠረገሎቻቸውንና
ፈረሰኞቻቸውን ተመልሶ እንዲሸፍናቸው
እጅህን በባሕሩ ላይ ዘርጋ" አለው። 27ሙሴም
እጁን በባሕሩ ላይ ዘረጋ፤ ንጋት ላይም
ባሕሩ ወደ ቀድሞ ቦታው ተመለሰ። ግብ
ፃውያን ከውሃው ሸሹ፤[ጸ] *እግዚአብሔርም*
(ያህዌ) ግብፃውያንን በባሕሩ ውስጥ ጣላቸው።
28ውሃውም ተመልሶ እስራኤላውያንን ተከ
ትለው ወደ ባሕሩ የገቡትን ሠረገሎች፣
ፈረሰኞች፣ መላውን የግብፅ ሰራዊት
ሁሉ ሸፈነ። አንድም እንኳ አልተረፈም።

29እስራኤላውያን ግን ውሃው ግራና
ቀኝ እንደ ግድግዳ ሆኖ፣ በደረቅ ምድር
ባሕሩን ተሻገሩ። 30በዚያች ዕለት *እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) እስራኤልን ከግብፃውያን
እጅ አዳናቸው፤ እስራኤልም የግብፃውያን
ሬሳ በባሕሩ ዳርቻ ወድቆ ተመለከቱ።
31እስራኤላውያን *እግዚአብሔር* (ያህዌ) በግብፃ
ውያን ላይ ያደረገውን ታላቅ ኀይል ባዩ
ጊዜ፣ *እግዚአብሔርን* (ያህዌ) ፈሩ፤ *በእግዚ
አብሔርና* (ያህዌ)፣ በባሪያው በሙሴም አመኑ።

### *የሙሴና የማርያም መዝሙር*

15 ከዚያም ሙሴና እስራኤላውያን ይህን
*መዝሙር ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) ዘመሩ፤

"ከፍ ከፍ ብሎ ከብሮአልና፣
*ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) እዘምራለሁ፤
ፈረሱንና ፈረሰኛውን፣
በባሕር ውስጥ ጥሎአልና።
2*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ብርታቴና
ዝማሬዬ ነው፤
ድነቴም ሆነልኝ፤
እርሱ አምላኬ ነው፤
አመሰግነዋለሁ፤
የአባቴ አምላክ (ኤሎሂም) ነው፤ እኔም
ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ።
3*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ተዋጊ ነው፤
ስሙም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነው።

4የፈርዖንን ሠረገሎችና ሰራዊት፣
ባሕር ውስጥ ጣላቸው፤
ምርጥ የሆኑት የፈርዖን ሹማምንት፣
ቀይ ባሕር ውስጥ ሰጠሙ።
5ቀላያትንም ለበሱ፤
እንደ ድንጋይ ወደ ጥልቁ ወረዱ።
6"አቤቱ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሆይ፤
ቀኝ እጅህ በግርማ ከበረ፤
አቤቱ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሆይ፤
ቀኝ እጅህ ጠላትን አደቀቀ።
7በግርማህ ታላቅነት፣
የተቃወሙህን ጣልዩቸው፤
ቍጣህን ሰደድህ፤
እንደ ገለባም በላቸው።
8በአፍንጫህ እስትንፋስ፣ ውሆች ተቈለሉ፤
ፈሳሾችም እንደ ግድግዳ ቆሙ፤
የጥልቁ ውሃ ባሕሩ ውስጥ ረጋ።

**14፥16** ቍ27፤ዘፀ 4፥2፤ኢሳ10፥26
**14፥17** ቍ4፤ ዘፀ 4፥21
**14፥18** ዘፀ6፥2፤ ሕዝ32፥15
**14፥19** ዘፍ16፥7፤ ዘፀ13፥21፤ኢሳ26፥7፤ 42፥16፤49፥10፤ 52፥12፤58፥8፤63፥9፤1 ቆሮ10፥1
**14፥20** ኢሱ24፥7
**14፥21** ቍ22፤ዘፍ 8፥1፤41፥6፤ዘፀ4፥2፤ 7፥19፤15፥8፤2ሳሙ 22፥16፤1ነገ19፥11፤ 2ነገ2፥8፤ኢዮ26፥12፤ 38፥1፤40፥6፤መዝ 74፥13፤78፥13፤114፥5 ፤136፥13፤ኢሳ14፥ 27፤23፥11፤51፥15፤ 63፥12፤ኤር31፥35፤ ኤር23፥19፤ናሆ1፥3፤ ሐሥ7፥36
**14፥22** ቍ7፥16፥ 21፥29፤ዘፀ3፥12፤ 15፥8፥19፤ዘኍ33፥8፤ዘ ዳ31፥6-8፤ ኢሱ፤3፥13፥16-17፤ 4፥22፤24፥6፤ ነህ9፥11፤መዝ66፥6፤ 77፥19፤78፥13፤ 106፥9፤ ኢሳ11፥15፤41፥10፤ 43፥5፥16፤44፥27፤ 50፥2፤51፥10፤63፥11፥ 13፤ኤር46፥28፤ ናሆ1፥4፤ዕብ11፥29 1ቆሮ10፥1
**14፥23** ቍ7
**14፥24** ዘፀ13፥21፤ 23፥27፤ኢሱ10፥10፤ 1ሳሙ5፥9፤7፥10፤ 14፥15፤2ሳሙ5፥24፤ 2ነገ7፥6፤19፥7፤ 1ቆሮ10፥1
**14፥25** ቍ9፥14፤ ዘዳ32፥31፤1ሳሙ2፥2፤4 ፥8
**14፥27** ቍ28፤ ዘፀ15፥1፥21፤ዘዳ1፥40፤ 2፥1፤11፥4፤ኢሱ4፥18፤ መዝ78፥53፤106፥11፤ 136፥15፤ዕብ11፥29
**14፥28** ቍ23፥27፤ ዘፀ15፥5፥19፤ኢሱ24፥7፤ መሳ4፥16፤ነህ9፥11
**14፥29** ቍ21፥22፤ 2ነገ2፥8፤ኢሳ24፥11፤ መዝ74፥15፤78፥13
**14፥30** ቍ29፤ 1ሳሙ14፥23፤1ዜና11 ፥14፤መዝ44፥7፤ 106፥8፥10፥21፤ኢ ሳ43፥3፤50፥2፤51፥9- 10፤60፥16፤63፥8፥11
**14፥31** ዘፀ4፥5፤ 9፥16፤20፥18፤ዘዳ31፥1 3፤ኢሱ4፥24፤1ሳሙ 12፥18፤መዝ22፥4፤40፥ 3፤76፥7፤106፥12፤112 ፥1፤147፥5፤ዮሐ2፥11፤ 11፥45
**15፥1** ዘፀ14፥27፤ ዘኍ21፥17፤ዘዳ11፥4፤መሳ5፥1፥3፤2ሳሙ22፥1፤1ዜና16፥9፤ኢዮ36 ፥24፤መዝ13፥6፤21፥13፤ 27፥6፤61፥8፤76፥6፤59፥16፤104፥33፤105፥ 72፤106፥12፤ኢሳ12፥ 5፥6፤42፥10፤44፥23፤ኤር51፥21
**15፥2** ዘፍ28፥21፤ 45፥7፤ዘፀ14፥13፤ዘዳ 10፥21፤2ሳሙ22፥47፤ መዝ18፥1፥2፥46፤22፥ 3፤25፥5፤27፥1፤30፥1፤34፥3፤35፥27፤59፥17፤ 62፥2፤99፥5፤103፥19፤ 107፥32፤108፥5፤109፥ 1፤118፥14፥28፤145፥ 11፤148፥14፤ኢሳ12፥2፤24፥15፤25፥1፤ኤር17፥14፤ዳን4፥37፤ዮና2፥9፤ዕን3፥18
**15፥3** ዘፀ3፥15፤ 14፥14፤ራእ19፥11 **15፥4** ዘፀ14፥6-7፤ኤር 51፥21 **15፥5** ቍ10፤ዘፀ14፥28፤ነህ9፥11 **15፥6** ዘፀ3፥20፤ ዘኍ 24፥8፤1ሳሙ2፥10፤ኢዮ40፥14፤ መዝ2፥9፤16፥11፤ 17፥7፤21፥8፤ 63፥8፤74፥11፤77፥10፤89፥13፤98፥1፤118፥15፤138፥7 **15፥7** ዘፀ 24፥17፤ ዘዳ4፥24፤9፥3፤33፥ 26፤መዝ2፥5፤18፥8፤59፥13፤78፥49-50፤ 150፥2፤ኤር12፥13፤ 25፥38፤ዕብ12፥29 **15፥8** ዘፀ14፥21፥22፤ ኢ ሱ3፥13፤መዝ18፥15፤46፥2፤78፥13፤ኢሳ43፥16

[የ]25 ወይም፣ *የሠረገላዎቻቸው መሽከርከሪያዎች ዘለው ወጡ*
[ጸ]27 ወይም፣ *ወደ ውሃው ሸሹ*

9“ጠላት፣
‘አሳድዳቸዋለሁ፤ እማርካቸዋለሁ፤
ምርኮን እካፈላለሁ፤
ነፍሴ በእነርሱ ትጠግባለች፤
ሰይፌን እመዛለሁ፤
እጄም ትደመስሳቸዋለች አለ።
10አንተ ግን እስትንፋስህን አነፈስህ፤
ባሕርም ከደናቸው፤
በኀያላን ውሆች፣
እንደ ብረት ሰጠሙ።
11“አቤቱ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሆይ፤
ከአማልክት መካከል፣
እንደ አንተ ማን አለ?
በቅድስናው የከበረ፣
በክብሩ የሚያስፈራ፣
ድንቆችን የሚያደርግ፣
እንደ አንተ ማን አለ?
12ቀኝ እጅህን ዘረጋህ፤
ምድርም ዋጠቻቸው።
13‘በማይለወጠው ፍቅርህ፣
የተቤዠኻቸውን ሕዝብህን ትመራለህ፤
እነርሱን በብርታትህ፣
ወደ ቅዱስ ማደሪያህ ትመራቸዋለህ።
14አሕዛብ ይሰማሉ፤ ይንቀጠቀጡማል፤
የፍልስጥኤምን ሕዝብ ሥቃይ
ይይዛቸዋል።
15የኤዶምም አለቆች ይርዳሉ፤
የሞአብ አለቆች በእንቅጥቃጤ ይያዛሉ፤
የከነዓን ሕዝብ ይቀልጣሉ።
16አቤቱ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሆይ፤ ሕዝብህ
እስከሚያልፉ ድረስ፣
የተቤዠኻቸው ሕዝብህ እስኪያልፉ ድረስ፣
ድንጋጤና ሽብር በእነርሱ ላይ ይመጣል፤
በክንድህ ብርታት፣
እንደ ድንጋይ የማይንቀሳቀሱ ይሆናሉ።
17*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሆይ፤ ማደሪያህ
እንዲሆን በሠራኸው ስፍራ፣
ጌታ (አዶናይ) ሆይ፤ እጆችህ በሠሩት
መቅደስ፣
በርስትህ ተራራ ላይ፣
ታመጣቸዋለህ፤ ትተክላቸዋለህም።
18*እግዚአብሔር* (ያህዌ)፣
ከዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሣል።”

19የፈርዖን ፈረሶች፣ ሠረገሎቹና[ጀ] ፈረሰ
ኞቹ ወደ ባሕሩ በገቡ ጊዜ *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) የባሕሩን ውሃ በላያቸው ላይ መለሰባ
ቸው፤ እስራኤላውያን ግን በባሕሩ ውስጥ
በደረቅ ምድር ተሻገሩ። 20ከዚያም የአሮን
እኅት ነቢይቱ ማርያም ከበሮዋን አንሥታ
ያዘች፤ የቀሩትም ሴቶች ሁሉ ከበሮ ይዘው
እያሸበሸቡ ተከተሏት።

21ማርያምም፣
“ፈረሱንና ፈረሰኛውን፣
በባሕር ውስጥ ጥሎአል፤
*ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) ዘምሩ፤
እጅግ ከፍ ከፍ ብሎአልና”
እያለች ዘመረችላቸው።

## የማራና የኤሊም ውሃ

22ከዚያም ሙሴ እስራኤልን ከቀይ
ባሕር እየመራቸው ወደ ሱር ምድረ በዳ
ሄዱ፤ ለሦስት ቀናት ውሃ ሳያገኙም
በምድረ በዳ ተጓዙ። 23ማራ በደረሱ ጊዜ ውሃው
መራራ ስለ ነበር ሊጠጡት አልቻሉም፤
ቦታው ማራ ተብሎ የተጠራውም ከዚህ የተነሣ
ነው።[ገ] 24ሕዝቡም በሙሴ ላይ በማጉረም
ረም፣ “ምን እንጠጣ?” አሉ።
25ከዚያም ሙሴ ወደ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ጮኸ፤ *እግዚአብሔርም* (ያህዌ) አንዲት ዛፍ
አሳየው፤ እርሷንም ወደ ውሃው ጣላት፤ ውሃ
ውም ጣፋጭ ሆነ።
በዚያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሕግና ሥርዐት
አበጀላቸው፤ በዚያም ሥፍራ ፈተናቸው።
26እርሱም አለ፤ “የአምላካችሁን *የእግዚአብሔርን*
(ያህዌ) ድምፅ በጥንቃቄ ብትሰሙ፣ በፊቱም
ትክክል የሆነውን ብትፈጽሙ፣ ትእዛዛቱን
ልብ ብትሉና ሥርዐቱንም ሁሉ ብትጠብቁ፣
በግብፃውያን ላይ ያመጣሁባቸውን ማንኛው
ንም ዐይነት በሽታ በእናንተ ላይ አላመጣም፤
ፈዋሻችሁ እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝና።”
27ከዚያም ዐሥራ ሁለት ምንጮችና ሰባ
የዘንባባ ዛፎች ወዳሉበት ወደ ኤሊም መጡ፤
እነርሱም በውሃው አጠገብ በዚያ ሰፈሩ።

## መናና ድርጭት

16 መላው የእስራኤል ማኅበር ከግብፅ
በወጡ በሁለተኛው ወር በዐሥራ
አምስተኛው ቀን ከኤሊም ተነሥተው በኤ
ሊምና በሲና መካከል ወደምትገኘው ወደ
ሲን ምድረ በዳ መጡ። 2በምድረ በዳ
ውም መላው ማኅበር በሙሴና በአሮን
ላይ አጒረመረሙ። 3እስራኤላውያንም እነ

**15፥9** ዘፀ14፥5-9፤ ዘዳ28፥45፤መሳ5፥30፤ መዝ7፥5፤ኢሳ9፥3፤ 53፥12፤ሰቆ1፥3፤ ሉቃ11፥22
**15፥10** ቍ5፤ ኢዮ4፥9፤15፥30፤ ነህ9፥11፤መዝ29፥3፤ 32፥6፤77፥19፤ ኢሳ11፥4፤30፥33፤ 40፥7
**15፥11** ዘፀ3፥20፤ 8፥10፤14፥4፤ዘሌ19፥2፤1 ሳሙ2፥2፤ 1ዜና16፥29፤መዝ4፥2፤ 8፥1፤26፥8፤77፥13፤ 99፥3፤110፥3፤ ኢሳ6፥3፤35፥2፤ 40፥5፤46፥5፤ራእ4፥8
**15፥12** ዘፀ7፥5፤ ዘኍ16፥32፤26፥10፤ ዘዳ11፥6፤መዝ106፥17
**15፥13** ቍ17፤ ዘፀ6፥6፤ነህ9፥12፤ ኢዮ33፥28፤ መዝ68፥16፤71፥23፤ 76፥2፤77፥20፤78፥54፤ 106፥10፤ኢሳ1፥27፤ 41፥14፤43፥14፤ 44፥22-24፤51፥10፤ 63፥9፤ቲቶ2፥14
**15፥14** ቍ16፤ ዘፀ23፥27፤ዘዳ2፥25፤ ኢሱ2፥9፤5፥1፤9፥24፤ 1ሳሙ4፥7፤አስ8፥17፤ መዝ48፥6፤83፥7፤ 96፥9፤99፥1፤114፥7፤ ኢሳ13፥8፤ሕዝ38፥20፤
**15፥15** ዘፍ36፥15፤ ዘኍ22፥3፤ዘዳ2፥4፤ ኢሱ2፥9፥24፤መዝ11 4፥7
**15፥16** ቍ14፤ ዘፍ35፥5፤ዘዳ2፥4፤ 1ሳሙ25፥37፤ መዝ74፥2፤2ጴጥ2፥1
**15፥17** ቍ13፤ ዘፀ23፥20፤32፥34፤ 33፥12፤ዘዳ33፥19፤ 2ሳሙ7፥10፤መዝ2፥6፤3 ፥4፤15፥1፤44፥2፤ 78፥54፥68፥69፤80፥8፥ 15፤114፥2፤132፥13- 14፤133፥3፤ኢሳ5፥2፤ 60፥21፤ኤር2፥21፤11፥ 17፤24፥6፤ዳን9፥16፤ኢ ል2፥1፤አሞ9፥15፤ አብ1፥16፤ሶፎ3፥11፤
**15፥18** ዘፍ21፥33፤ መዝ9፥7፤29፥10፤ 55፥19፤66፥7፤80፥1፤ 102፥12፤145፥13፤ ሰቆ5፥19
**15፥19** ዘፀ14፥22፥28
**15፥20** ቍ21፤ዘፍ 4፥21፤31፥27፤ዘፀ2፥4፤ ዘኍ12፥1፤20፥1፤መሳ 4፥4፤11፥34፤21፥21፤ 26፥59፤ 1ሳሙ18፥6፤ 2ሳሙ6፥5፥14፥16፤ 2ነገ22፥14፤1ዜና4፥17፤ 6፥3፤2ዜና34፥22፤ነህ6 ፥14፤መዝ30፥11፤ 81፥2፤ 149፥3፤150፥4፤ማሕ6፥13፤ኢሳ8፥3፤30፥32፤ኤር31፥4፥13፤ሕዝ 13፥17
**15፥21** ዘፀ14፥27፤1ሳሙ18፥7፤አሞ2፥15፤ሐጌ2፥22
**15፥22** ዘፍ16፥7፤ዘፀ17፥1፥3፤ዘኍ20፥2፥5፤33፥14፤መዝ78፥52፤ 107፥5፤17፥3፤ዘኍ14፥2፤20፥3፤11፥4፥34፤ዘዳ8፥3፤12፥20፤ መዝ78፥18፤106፥14፤ኤር44፥17፤
**15፥23** ዘኍ33፥8፤ሩት1፥20
**15፥24** ዘፀ14፥12፤16፥2፤17፥3፤ዘኍ14፥2፤ኢሱ9፥18፤መዝ78፥ 18፥42፤106፥13፥25፤ሕዝ16፥43፤ማቴ6፥31
**15፥25** ዘፍ22፥1፤ ዘፀ 14፥10፤መሳ3፥4፤2ነገ2፥21፤4፥41፤6፥6፤ኢዮ23፥10፤መዝ81፥7፤ ኢ ሳ48፥10
**15፥26** ዘፀ19፥5-6፤20፥2-17፤23፥22፥ 25-26፤ዘኍ 33፥9፤ዘዳ7፥12፥15፤11፥13፤15፥5፤28፥1፤28፥27፥58-60፤32፥39፤ 1ሳሙ5፥6፤2ነገ20፥5፤ መዝ25፥11፤30፥2፤ 41፥3-4፤103፥3፤ 107፥20፤ኤር11፥6፤30፥17፤ሆሴ11፥3፤15፥27
**15፥27** ዘኍ33፥9
**16፥1** ዘፀ6፥6፤ 12፥1-2፤17፥1፤ ዘኍ33፥11፥12
**16፥2** ዘፀ15፥24፤ 1ቆሮ10፥10
**16፥3** ዘፍ47፥15

[ጀ]19 ወይም፣ ሠረገለኞች
[ገ]23 ማራ ማለት መራራ ማለት ነው

ርሱን እንዲህ አሏቸው፣ “በሥጋ መቀቀያው
ምንቸት ዙሪያ ተቀምጠን የፈለግነውን ያህል
ምግብ መመገብ በምንችልበት በግብፅ ሳለን፣
ምነው በእግዚአብሔር (ያህዌ) እጅ ሞተን
ባረፍነው ኖሮ! እናንተ ግን ይህ ሁሉ ጉባኤ
በራብ እንዲያልቅ ወደዚህ ምድረ በዳ
አመጣችሁን” አሏቸው።
4ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን
አለው፤ “ከሰማይ እንጀራ አዘንብላችኋለሁ።
ሕዝቡም በየቀኑ እየወጡ ለዕለት የሚበቃቸ
ውን ይሰብስቡ፤ በዚህም ትእዛዛቴን ይጠ
ብቁ እንደ ሆነ እፈትናቸዋለሁ። 5በስድስ
ተኛው ቀን በሌሎቹ ዕለታት ከሚሰበስቡት
እጥፍ ሰብስበው ያዘጋጁ።
6ስለዚህ ሙሴና አሮን ለእስራኤላውያን
ሁሉ፣ እንዲህ አሉ፤ “ከግብፅ ምድር ያወ
ጣችሁ እግዚአብሔር (ያህዌ) መሆኑን በዛሬ
ይቱ ምሽት ታውቃላችሁ። 7በእርሱ ላይ
ያሰማችሁትን ማጉረምረም ሰምቷልና በማ
ለዳ የእግዚአብሔርን (ያህዌ) ክብር ታያላችሁ፤
ለመሆኑ በእኛስ ላይ የምታጉረመርሙት
እኛ ምንድን ነንና ነው?” አሏቸው። 8ሙሴም
ንግግሩን በመቀጠል፣ “በእርሱ ላይ ማጉረ
ምረማችሁን ሰምቶአልና በምሽት የምትበሉትን
ሥጋ፣ በማለዳም የምትፈልጉትን ያህል
እንጀራ በሚሰጣችሁ ጊዜ እግዚአብሔር
(ያህዌ) መሆኑን ታውቃላችሁ፤ እኛ ማን
ነን? በእኛ ላይ አይደለም ያጉረመረ
ማችሁት፤ በእግዚአብሔር (ያህዌ) ላይ ነው
እንጂ” አላቸው።
9ከዚያም ሙሴ አሮንን፣ “ ‘ማጉረምረ
ማችሁን እርሱ ሰምቶአልና ወደ እግዚ
አብሔር (ያህዌ) ፊት ቅረቡ’ ብለህ ለመላው
የእስራኤል ማኅበር ተናገር” አለው።
10አሮንም ለመላው የእስራኤል ማኅበር
ሲናገር ሳለ ወደ ምድረ በዳው ተመለከቱ፤
በዚያም የእግዚአብሔር (ያህዌ) ክብር በደመ
ናው ላይ ተገልጦ ይታይ ነበር።
11እግዚአብሔርም (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 12“የእስራኤላውያንን ማጉረምረም
ሰምቻለሁ፤ ይህን ንገራቸው፤ ‘ፀሐይ ከመ
ጥለቋ በፊት ሥጋ ትበላላችሁ፤ ሲነጋም እን
ጀራ ትበላላችሁ፤ ከዚያም እኔ እግዚአብሔር
አምላካችሁ ዱያህዌ አሎሂምዕ መሆኔን
ታውቃላችሁ።’ ”
13በዚያች ምሽት ድርጭቶች መጥተው
ሰፈሩን አለበሱት፤ በነጋውም በሰፈሩ ዙሪያ
ጤዛ ተኝቶበት ነበር። 14ጤዛው ከረገፈ
በኋላ በሜዳው ላይ ስስ የሆነ አመዳይ
የሚመስል የተጋገረ ነገር በምድረ በዳው
ላይ ታየ። 15እስራኤላውያንም ይህን ባዩ
ጊዜ ምን እንደ ሆነ ባለማወቃቸው እርስ
በርሳቸው፣ “ይህ ነገር ምንድን ነው?” ተባ
ባሉ።
ሙሴም፦ “ይህ ትበሉት ዘንድ እግዚአብሔር
(ያህዌ) የሰጣችሁ እንጀራ ነው አላቸው።
16እግዚአብሔር (ያህዌ) ያዘዘው ይህ ነው፤
‘እያንዳንዱ የሚያስፈልገውን ያህል ይሰብ
ስብ፤ በድንኳናችሁ ባለው ሰው ልክ ለእያ
ንዳንዱ አንድ ጎሞር[ጦ] ውሰዱ’ ” ብሎ እግ
ዚአብሔር (ያህዌ) አዞአል።
17እስራኤላውያንም እንደ ተነገራቸው
አደረጉ፤ አንዳንዶች አብዝተው፣ አንዳን
ዶች ደግሞ አሳንሰው ሰበሰቡ። 18የሰበሰቡትን
በጎሞር በሰፈሩ ጊዜ ብዙ የሰበሰበው አልተ
ረፈውም ጥቂት የሰበሰበውም አልጐደለበትም
እያንዳንዱ የሰበሰበው የሚያስፈልገውን ያህል
ሆነ።
19ሙሴም፣ “ማንም ከዚህ ለነገ ምንም
ማስተረፍ የለበትም” አላቸው።
20ሆኖም ግን አንዳንዶቹ ሙሴ የተናገረ
ውን ቸል በማለት ከሰበሰቡት ውስጥ ከፊሉን
አስተርፈው አሳደሩ፤ በማግሥቱም ጠዋት
ተልቶ መሽተት ጀመረ፤ ስለዚህ ሙሴ
ተቈጣቸው።
21በየማለዳው እያንዳንዱ የሚያስፈልገውን
ያህል ሰበሰበ፤ ፀሐዩ እየበረታ በሄደም ጊዜ
ቀለጠ። 22ስድስተኛው ቀን ለእያንዳንዱ
ሰው ሁለት ሁለት ጎሞር[ጨ] አድርገው እጥፍ
ሰበሰቡ፤ የማኅበሩም አለቆች ወደ ሙሴ
መጥተው ይህንኑ ነገሩት። 23እርሱም አላቸው፤
“እግዚአብሔር (ያህዌ) ያዘዘው ይህ ነው፤ ‘ነገ
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የተቀደሰ ሰንበት በመ
ሆን፣ የዕረፍት ቀን ይሆናል። ስለዚህ መጋገር
የምትፈልጉትን ጋግሩ፤ መቀቀል የምትፈል
ጉትን ቀቅሉ። የተረፈውን አስቀምጡ፤ እስከ
ጧትም ድረስ አቆዩት።
24ስለዚህ ሙሴ እንዳዘዘው እስከ ጧት
ድረስ አቆዩት፤ አልሸተተም፤ ወይም አልተ
ላም። 25ሙሴም እንዲህ አለ፤ “ዛሬውኑ
ብሉት፤ ዛሬ የእግዚአብሔር (ያህዌ) ሰንበት
ነውና። ዛሬ በመሬት ላይ ምንም አታገኙም።
26ስድስት ቀን ትሰበስቡታላችሁ፤ በሰባተኛው
ቀን በሰንበት ዕለት ግን ምንም ነገር አይ
ኖርም።”
27ሆኖም አንዳንዶቹ በሰባተኛው ቀን
ለመሰብሰብ ወጡ፤ ነገር ግን ምንም አላገ
ኙም። 28ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን
አለው፤ ትእዛዞቼንና መመሪያዎቼን ለመፈ
ጸም እስከ መቼ እምቢ ትላላችሁ[ጰ]? 29እግ
ዚአብሔር (ያህዌ) ሰንበትን የሰጣችሁ መሆኑን
ልብ በሉ፤ በስድስተኛው ቀን ለሁለት ቀን
የሚሆን እንጀራ የሰጣችሁ ለዚህ ነው።

[ጦ]16 ይህ በቍጥር 18፡32፡33 እንዲሁም 36 ላይ ተጠቅሶአል፤ ወደ ሁለት ሊትር ያህል ይሆናል።
[ጨ]22 ምናልባት ወደ 4.5 ሊትር ሊደርስ ይችላል።

16÷4 ቍ14-15፤ ዘፍ22÷1፤ዘዳ8÷3፤ ነህ9÷15፤መዝ78÷24፤ 105÷40፤ዮሐ6÷31
16÷5 ቍ22፤ ዘሌ25÷21
16÷6 ዘፀ6÷6
16÷7 ቍ10፡12፤ ዘፀ24÷16፤29÷43፤ 33÷18፡22፤40÷34፤ ዘሌ9÷6፤ዘኍ11÷1፡ 18፤14÷2፡27፡28፤ 16÷11፡19፡42፤ 17÷5፤ዘዳ5÷24፤ 1ነገ8÷11፤መዝ63÷2፤ ኢሳ6÷3፤35÷2፤ 40÷5፤44÷23፤60÷1፤6 6÷18፤ሕዝ1÷28፤ 10÷4፤43÷5፤ ዕን2÷14፤ሐጌ2÷7፤ ዮሐ11÷40፤
16÷8 ቍ7፤ ዘኍ23÷21፤ዘዳ33÷5 መሳ8÷23፤ 1ሳሙ8÷7፤12÷12፤ ማቴ10÷40፤ ሮሜ13÷2፤1ተሰ4÷8
16÷10 ቍ7፤ ዘፀ13÷21፤40÷34-35፤ 1ነገ8÷10፤2ዜና7÷1፤ ሕዝ10÷4፤ዮሐ11÷4
16÷12 ቍ7፤ ዘፀ6÷2፤20÷2
16÷13 ዘኍ11÷9፡ 31፤መዝ78÷27-28፤ 105÷40፤106÷15
16÷14 ቍ31፤ ዘኍ11÷7-9፤ ዘዳ8÷3፡16፤ መዝ105÷40
16÷15 ቍ4፤ ዘዳ8÷16፤ነህ9÷20፤ ዮሐ6÷31
16÷16 ቍ32፡36
16÷18 2ቆሮ8÷15
16÷19 ቍ23፤ ዘፀ12÷10
16÷20 ቍ24፤ ዘፀ32÷19
16÷22 ቍ5፤ ዘፀ34÷31
16÷23 ዘፍ2÷3፤ ዘፀ20÷8፤ዘዳ5÷13-14
16÷26 ቍ23
16÷28 ኢሱ9÷14፤ መዝ78÷10፤ 106÷13፤107÷11፤ 119÷1፤ኤር32÷23

በሰባተኛው ቀን እያንዳንዱ ሰው ባለበት
ይቆይ፤ ማንም አይወጣም::” 30ስለዚህ ሕዝ
ቡም በሰባተኛው ቀን ዐረፉ::

31የእስራኤልም ሕዝብ ምግቡን መና
አሉት[ጰ]፤ እርሱም እንደ ድንብላል ዘር
ነጭ፣ ጣሙም ከማር እንደ ተጋገረ ቂጣ
ነበር:: 32ሙሴም አለ፤ “እግዚአብሔር (ያህዌ)
ያዘዘን ይህ ነው፤ ‘ከግብፅ ባወጣኋችሁ ጊዜ
በምድረ በዳ እንድትበሉ የሰጠኋችሁን
እንጀራ ያዩ ዘንድ አንድ ጎሞር መና ወስ
ደህ ለሚመጡት ትውልዶች አቆየው::’ ”

33ስለዚህ ሙሴ አሮንን፣ “አንድ ማሰሮ
ወስደህ አንድ ጎሞር መና አስቀምጥበት፤
ለሚመጡት ትውልዶች እንዲቆይም በእግ
ዚአብሔር (ያህዌ) ፊት አስቀምጠው” አለው::

34እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዳዘዘው
አሮን፣ መናው ይጠበቅ ዘንድ በምስክሩ ፊት
አስቀመጠው:: 35እስራኤላውያን ወደ መኖ
ሪያቸው ምድር እስኪመጡ ድረስ ለአርባ
ዓመት መና በሉ፤ ወደ ከነዓን ድንበር እስ
ከሚደርሱ ድረስ መና በሉ::

36አንድ ጎሞር የኢፍ መስፈሪያ አንድ ዐሥ
ረኛ ነው::

## ከዐለት የፈለቀ ውሃ

17 መላው የእስራኤል ማኅበር ከሲና
ምድረ በዳ ተነስቶ እግዚአብሔር
(ያህዌ) እንዳዘዘው ከስፍራ ወደ ስፍራ ተጕዞ፤
በራፊዲም ሰፈረ፤ ነገር ግን ሕዝቡ የሚጠ
ጡት ውሃ አልነበረም:: 2ስለዚህ፣ “የምንጠ
ጣው ውሃ ስጠን” በማለት ሙሴን ተጣሉት::

ሙሴም፣ “እኔን ለምን ትጣሉኛላችሁ?
እግዚአብሔርንስ (ያህዌ) ለምን ትፈታተኑታላ
ችሁ?” አለ::

3ነገር ግን ሕዝቡ በዚያ ተጠምተው ስለ
ነበር፣ በሙሴ ላይ አጕረመረሙ:: እነር
ሱም፣ “እኛና ልጆቻችን እንዲሁም ከብቶቻ
ችን በውሃ ጥም እንድናልቅ፣ ከግብፅ ለምን
አወጣኸን?” አሉት::

4ከዚያም ሙሴ “በዚህ ሕዝብ ምን ላድ
ርግ? በድንጋይ ሊወግሩኝ ተዘጋጅተዋል”
ብሎ ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ) ጮኸ::

5እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ እንዲህ መለ
ሰለት፤ “ከሕዝቡ ፊት ሂድ፤ ከእስራኤል
አለቆች አንዳንዶቹን እንዲሁም ዐባይን
የመታህባትን በትር ያዝና ሂድ:: 6ኮሬብ
አጠገብ ባለው ዐለት በዚያ እኔ በአንተ
ፊት እቆማለሁ:: ዐለቱን ምታው፤ ከእር
ሱም ሕዝቡ የሚጠጡት ውሃ ይወጣል::”
ስለዚህ ሙሴ በእስራኤል አለቆች ፊት
ይህንኑ አደረገ:: 7ስፍራውንም ማሳህና[ፀ]
መሪባ[ፈ] ብሎ ጠራው፤ እስራኤላውያን ጠብ

16፥31 ቍ14
16፥33 ዕብ9፥4፤ ራእ2፥17
16፥34 ዘፀ25፥16፡ 21፡22፤27፥21፤31፥18፤ 40፥20፤ዘሌ16፥13፤ዘኍ 1፥50፤7፥89፤10፥11፤1 7፥4፡10፤ዘዳ10፥2፤ 1ነገ8፥9፤ 2ዜና5፥10
16፥35 ዘኍ14፥33፤ 33፥38፤ዘዳ1፥3፤2፥7፤8 ፥2-4፤ኢሱ5፥6፡12፤ መሳ3፥11፤ነህ9፥21፤ መዝ95፥10አሞ5፥25፤ ዮሐ6፥31፡49
16፥36 ቍ16፤ዘሌ 5፥11፤6፥20፤ዘኍ5፥ 15፤15፥4፤ 28፥5
17፥1 ቍ8፤ዘፀ16፥1፤ 19፥2፤ዘኍ33፥15፤ 20፥5፤ 21፥5፤33፥14
17፥2 ዘፀ14፥12፤ ዘኍ20፥2፤33፥14፤ ዘዳ6፥16፤መዝ78፥ 18፡41፤106፥14፤ 107፥5፤ማቴ4፥7፤ 1ቆሮ10፥9
17፥3 ዘፀ14፥11፤ 15፥22፡24
17፥4 ዘኍ14፥10፤ 1ሳሙ30፥6፤ዮሐ8፥59
17፥5 ዘፀ4፥2፤ 10፥12-13፤7፥20
17፥6 ዘፀ3፥1፤ ዘኍ20፥8፡11፤ዘዳ8፥ 15፤መሳ15፥9፤ 2ነገ3፥20፤ነህ9፥15፤መ ዝ74፥15፤78፥ 15- 16፤105፥41፤ 107፥35፤114፥8፤ ኢሳ30፥25፥35፥6፤ 43፥19፤48፥21፤ 1ቆሮ10፥4
17፥7 ዘዳ6፥16፤ 9፥22፤33፥8፤ ዘኍ20፥13፡24፤ 27፥14፤መዝ81፥7፤ 95፥8፤106፥32
17፥8 ቍ1፤ ዘፍ36፥12
17፥9 ዘፀ4፥17፤ 24፥13፤32፥17፤33፥11፤ ዘኍ11፥28፤27፥22፤ ዘዳ1፥38፤ኢሱ1፥1፤ ሐሥ7፥45
17፥10 ቍ10-12፤ ዘፀ24፥14፤31፥2
17፥11 ያዕ5፥16
17፥12 ኢሱ8፥26
17፥13 ቍ8
17፥14 ቍ13፤ ዘፍ36፥12፤ዘፀ24፥4፤ 32፥33፤34፥27፤ ዘኍ24፥7፤33፥2፤ ዘዳ29፥20፤31፥9፤ መሳ3፥13፤1ሳሙ30፥1 7-18፤ኢዮ18፥17፤ 19፥23፤መዝ9፥5፤ 34፥16፤83፥7፤ 109፥15፤ሕዝ18፥4፤ኢሳ 30፥8፤ኤር36፥2፤45፥1፤5 1፥60

ፈጥረው፣ እግዚአብሔር (ያህዌ) ከእኛ ጋር
ነው ወይስ አይደለም” በማለት እግዚአብሔ
ርን (ያህዌ) ተፈታትነዋልና::

## አማሌቃውያን ተሸነፉ

8አማሌቃውያን መጥተው እስራኤላው
ያንን ራፊዲም ላይ ወጉ፤ 9ሙሴም ኢያ
ሱን፣ “ከሰዎቻችን አንዳንዶቹን ምረጥና
አማሌቃውያንን ለመውጋት ውጣ፤ በነገው
ዕለት የእግዚአብሔርን (ኤሎሂም) በትር በእጆቼ
ይዤ በኰረብታው ጫፍ ላይ እቆማለሁ::”

10ስለዚህ ኢያሱ ሙሴ ባዘዘው መሠረት
ከአማሌቃውያን ጋር ተዋጋ፤ ሙሴ፣ አሮ
ንና ሖርም ወደ ኰረብታው ጫፍ ወጡ::
11ሙሴ እጆቹን ወደ ላይ በሚያነሣበት ጊዜ
ሁሉ እስራኤላውያን ድል ያደርጉ ነበር::
እጆቹን ባወረደ ጊዜ ግን አማሌቃውያን
ያሸንፉ ነበር:: 12የሙሴ እጆች እየዛሉ በሄዱ
ጊዜ ድንጋይ ወስደው ከበታቹ አደረጉ፤
እርሱም ተቀመጠበት፤ አሮንና ሖርም አንዱ
በአንዱ በኩል ሌላውም በሌላ በኩል ሆነው
እጆቹን ወደላይ ያዙ:: ይኸውም እጆቹ ፀሓይ
እስክትጠልቅ ድረስ ጸንተው እንዲቆዩ ነው::
13ስለዚህ ኢያሱ የአማሌቃውያንን ሰራዊት
በሰይፍ ድል አደረገ::

14ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን፣
“ሲታወስ እንዲኖር ይህን በጥቅልል መጽሐፍ
ላይ ጻፈው፤ ኢያሱም መስማቱን አረጋግጥ፤
ምክንያቱም የአማሌቃውያንን ዝክር ከሰ
ማይ በታች ፈፅሜ እደመስሳለሁ” አለው::

15ሙሴም መሠዊያውን ሠርቶ፣ “እግዚ
አብሔር (ያህዌ) አርማዬ ነው” ብሎ ሰየመው::
16“እጆች ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ) ዙፋን ተዘር
ግተዋልና፤[ፐ] እግዚአብሔር (ያህዌ) አማሌቃው
ያንን ከትውልድ እስከ ትውልድ ይዋጋ
ቸዋል” አለ::

## ዮቶር ወደ ሙሴ መጣ

18 የምድያም ካህን የሙሴ አማት
ዮቶር፣ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ለሙሴና
ለሕዝቡ ለእስራኤል ያደረገላቸውን ሁሉ
እንዲሁም እግዚአብሔር (ያህዌ) እስራኤልን
ከግብፅ እንዴት እንዳወጣቸው ሰማ::

2ሙሴ ሚስቱን ሲፓራን ከመለሳት
በኋላ አማቱ ዮቶር እርሷንና ሁለት ወንድ
ልጆቿን ተቀብሏቸው ነበር:: 3ሙሴ፣ “በባዕድ

17፥15 ዘፍ8፥20፤22፥14 17፥16 ዘኍ24፥7፤1ሳሙ15፥8፡32፤1ዜና 4፥43፤ አስ3፥1፤8፥3፤9፥5፡24 18፥1 ዘፀ2፥16፤ 2፥18፤6፥6 18፥2 ዘፀ 2፥21 18፥3 ዘፀ2፥22፤ 4፥20፤ሐሥ7፥29

[ጰ]28 ዕብራይስጡ የብዙ ቍጥር ያሳያል:: [ጰ]31 መና ማለት፣ ምንድን ነው? ማለት ነው (ቍ 15 ይመ):: [ፀ]7 ማሳህ ማለት መፈተን ማለት ነው:: [ፈ]7 መሪባ ማለት መጣላት ማለት ነው:: [ፐ]16 ወይም፣ *ምክንያቱም እጅ በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ ተዘርግቶአል ...*

አገር መጻተኛ ነኝ” ለማለት የመጀመሪያ
ልጁን ስም ጌርሳም[ሀ] አለው:: 4“የአባቴ
አምላክ ረዳቴ ነው፤ ከፈርዖን ሰይፍ አድኖ
ኛልና” ለማለት ደግሞ ሁለተኛውን ልጁን
አልዓዛር[ለ] አለው::
5የሙሴ አማት ዮቶር ከሙሴ ወንድ
ልጆችና ሚስት ጋር ሆኖ በምድረ በዳ ከእግዚ
አብሔር (ኤሎሂም) ተራራ አጠገብ ወደ ሰፈረበት
ወደ ሙሴ መጣ:: 6ዮቶር፣ “እኔ አማትህ
ዮቶር፣ ከሚስትህና ከሁለት ወንዶች
ልጆቿ ጋር እየመጣን ነው” ሲል መልእ
ክት ላከበት::
7ስለዚህ ሙሴ አማቱን ሊቀበለው ወጣ፤
ዝቅ ብሎ እጅ በመንሣትም ሳመው፤ ከዚ
ያም ሰላምታ ተለዋውጠው ወደ ድንኳኑ ገቡ::
8ሙሴም እግዚአብሔር (ያህዌ) ለእስራኤል ሲል
በፈርዖንና በግብፃውያን ላይ ያደረገውን ሁሉ፣
በመንገድም ላይ ስላጋጠማቸው መከራ ሁሉና
እግዚአብሔርም (ያህዌ) እንዴት እንዳዳናቸው
ለአማቱ ነገረው:: 9ዮቶርም እግዚአብሔር
(ያህዌ) እነርሱን ከግብፃውያን እጅ በመታደግ
ለእስራኤል ያደረገውን በጎ ነገር ሁሉ በመስ
ማቱ ተደሰተ:: 10እንዲህም አለ፤ “ከግብፃ
ውያን እጅና ከፈርዖን ለታደጋችሁ፣ ከግብ
ፃውያን እጅ ሕዝቡን ለታደገ ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) ምስጋና ይሁን":: 11“እግዚአብሔር (ያህዌ)
ከአማልክት ሁሉ በላይ ኀያል እንደ ሆነ አሁን
ዐወቅሁ፤ እስራኤልን በትዕቢት ይዘው በነበ
ሩት ሁሉ ላይ ይህን አድርጎአልና::” 12ከዚ
ያም የሙሴ አማት ዮቶር የሚቃጠል መሥ
ዋዕትና ሌሎች መሥዋዕቶች ለእግዚአብሔር
(ኤሎሂም) አቀረበ፤ አሮንም ከሙሴ አማት
ጋር በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ፊት እንጀራ
ለመ ብላት ከእስራኤል አለቆች ሁሉ ጋር
መጣ::
13በማግሥቱ ሙሴ ሕዝቡን ለመዳኘት
ተቀመጠ፤ እነርሱም በዙሪያው ከጧት እስከ
ማታ ድረስ ቆሙ:: 14አማቱም ሙሴ ለሕዝቡ
የሚያደርገውን ሁሉ ባየ ጊዜ፣ “ምን ማድ
ረግህ ነው? እነዚህ ሁሉ ሰዎች ከጧት እስከ
ማታ በዙሪያህ ቆመው ሳለ፣ ብቻህን በፍርድ
ወንበር ላይ ለምን ትቀመጣለህ?” አለው::
15ሙሴም እንዲህ ብሎ መለሰለት፤ “ምክ
ንያቱም ሰዎቹ የእግዚአብሔርን ዱኤሎሂምዕ ፈቃድ
በመፈለግ ወደ እኔ ይመጣሉ:: 16ክርክር
በኖራቸው ቍጥር ጕዳያቸው ወደ እኔ
ይመጣል፤ ለግራና ለቀኙ የሚሆነውን እኔ
ወስኜ የእግዚአብሔርን ዱኤሎሂምዕ ሥርዐትና ሕጎች
እነግራቸዋለሁ::”
17የሙሴ አማት መልሶ እንዲህ አለው::
“የምትሠራው መልካም አይደለም:: 18አን
ተና ወደ አንተ የሚመጡት እነዚህ ሰዎች
የምታደርጉት ነገር ቢኖር ራሳችሁን ማድከም

18፥4 ዘፍ49፥25፤ ዘዳ33፥29፤1ዜና23፥15
18፥5 ዘፀ3፥1
18፥7 ዘፍ17፥3፤ 29፥13፤43፥28
18፥8 ዘፀ15፥6፥16፤ ዘኍ20፥14፤ነህ9፥32፤ መዝ81፥7
18፥9 ኢሱ21፥45፤ 1ነገ8፥66፤ነህ9፥25፤መ ዝ145፥7፤ኢሳ63፥7
18፥10 ዘፍ9፥26፤ 24፥27
18፥11 ዘፀ1፥10፤ 12፥12፤1ዜና16፥25፤ለ ሉቃ1፥51
18፥12 ዘፍ31፥54፤ 26፥30፤ዘፀ3፥1፤ 10፥25፤20፥24፤ 24፥5፤ዘሌ1፥2-9፤ ዘዳ12፥7
18፥15 ቍ19፤ ዘፍ25፥22
18፥16 ቍ15፤ ዘፀ24፥14፤ዘሌ24፥12፤ ዘኍ15፥34፤ ዘዳ1፥17፤2ዜና19፥7፤ ምሳ24፥23፤ሚል2፥9
18፥18 ዘኍ11፥11፥ 14፥17፤ዘዳ1፥9፥12
18፥19 ቍ15፤ ዘፀ3፥12፤ዘኍ27፥5
18፥20 ዘፍ39፥11፤ ዘዳ4፥1፥5፤5፥1፤ መዝ119፥12፥26፥68፤ 143፥8
18፥21 ዘፍ22፥12፤ 47፥6፤ዘፀ23፥8፤ ዘኍ1፥16፤7፥2፤ 10፥4፤ዘዳ16፥18፥19፤1 ሳሙ12፥3፤ ዕዝ7፥25፤መዝ15፥5፤ ምሳ17፥23፤28፥8፤ መክ7፥7፤ሕዝ18፥8፤ 22፥12፤ሐሥ6፥3
18፥22 ዘሌ24፥11፤ ዘኍ11፥17፤ዘዳ1፥9፥ 17-18፤
18፥25 ዘኍ1፥16፤ 7፥2፤11፥16፤ዘዳ1፥13- 15፤16፥18፤ 18፥26 ቍ22፤ ዘዳ1፥17፤16፥18፤ 2ዜና19፥5ዕዝ7፥25፤
18፥27 ዘኍ10፥29-30
19፥1 ዘፀ6፥6፤ ዘኍ1፥1፤3፥14፤ 33፥15
19፥2 ቍ17፤ዘፀ3፥1፤ 17፥1፤ ዘዳ5፥2-4
19፥3 ዘፀ3፥4፤ 20፥21፤25፥22፤ ሐሥ7፥38
19፥4 ዘዳ29፥2፤ 32፥11፤33፥12፤ ኢሱ24፥7፤ መዝ103፥5፤ ኢሳ31፥5፤40፥31፤ ሕዝ16፥6፤ኤር4፥13፤ 48፥40፤ራእ12፥14
19፥5 ዘፍ17፥9፤ ዘፀ3፥1፤8፥1፥22፤

ነው፤ ሥራው ለአንተ ከባድ ሸክም ነው፤
ብቻህን ልትወጣው አትችልም:: 19ምክር
እሰጥሃለሁና አሁን እኔን አድምጠኝ፤ እግዚ
አብሔር ዱኤሎሂምዕ ከአንተ ጋር ይሁን:: አንተ
በእግዚአብሔር ዱኤሎሂምዕ ፊት ዱየሕዝብ
ተወካይ መሆን አለብህዕ፤ ክርክራቸውን
ወደ እርሱ ታቀርባለህ:: 20ሥርዐቶቹንና ሕ
ጎቹን አስ ተምራቸው፤ እንዴት መኖር
እንዳለባቸ ውና ምን መሥራት
እንደሚገባቸው አሳያ ቸው:: 21ነገር ግን
ችሎታ ያላቸውን ሰዎች ከሕዝቡ ሁሉ
ምረጥ፤ እነዚህም ሰዎች እግዚአ ብሔርን ዱኤሎ
ሂምዕ የሚፈሩ፣ ታማኞችና በማታ ለል
የሚገኘውን ጥቅም የሚጸየፉ ይሁኑ::
የሺህ፣ የመቶ፣ የአምሳ፣ የዐሥር፣ አለቃ
አድርገህ ሹማቸው:: 22በማንኛውም ጊዜ
ሕዝቡን ይዳኙ፤ ቀላሉን ነገር እነርሱ ይወ
ስኑ፤ አስቸጋሪ የሆነውን ጕዳይ ሁሉ ግን
ለአንተ እንዲያቀርቡ አድርግ፤ ሥራውን
ስለሚያግዙህ ሸክምህ ይቃለላል:: 23አንተ
ይህን ብታደርግና እግዚአብሔርም ዱኤሎሂምዕ
ይህንኑ ቢያዝህ፣ ድካምህን መቋቋም
ትችላለህ፤ እነዚህም ሰዎች ሁሉ ረክተው
ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ::
24ሙሴ አማቱን ሰማ፤ ያለውንም ሁሉ
ፈጸመ:: 25ከእስራኤል መካከል ችሎታ ያላ
ቸውን ሰዎች መረጠና፤ የሕዝብ መሪዎች፣
በሺዎች፣ በመቶዎች፣ በአምሳዎች በዐሥ
ሮች ላይም አለቆች አደረጋቸው:: 26ሁል
ጊዜም የሕዝብ ዳኞች ሆነው አገለገሉ፤
አስቸጋሪ ጉዳዮችን ወደ ሙሴ አመጡ፤
ቀላል የሆነውን ራሳቸው ወሰኑ:: 27ከዚ
ያም ሙሴ አማቱን በጕዞው ሸኘው፤
ዮቶርም ወደ አገሩ ተመለሰ::

## በሲና ተራራ ላይ

19 በሶስተኛው ወር እስራኤላውያን
ከግብፅ ለቀው በወጡበት በዚያችው
ዕለት ወደ ሲና ምድረ በዳ መጡ:: 2ከራፊ
ዲም ከተነሡ በኋላ ወደ ሲና ምድረ በዳ
ገቡ፤ እስራኤልም በዚያ በምድረ በዳው በተ
ራራው ፊት ለፊት ሰፈሩ::
3ከዚያም ሙሴ ወደ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
ወጣ፤ እግዚአብሔርም (ያህዌ) ከተራራው ጠራ
ውና እንዲህ አለው፤ “ለያዕቆብ ቤት የም
ትለው ለእስራኤልም ሕዝብ የምትናገረው
ይህ ነው፤ 4‘በግብፅ ላይ ያደረግሁትን፣ በን
ስርም ክንፍ ተሸክሜ ወደ ራሴ እንዴት
እንዳመጣኋችሁ እናንተ ራሳችሁ አይታች
ኋል:: 5አሁንም በፍጹም ብትታዘዙኝና ቃል
ኪዳኔን ብትጠብቁ እነሆ ከአሕዛብ ሁሉ

[ሀ]3 በዕብራይስጥ ጌርሳም የሚለው የቃል ድምፅ፣ *መጻተኛ በዚያ አለ* ከሚለው ሐረግ ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው::
[ለ]4 አልዓዛር ማለት፣ *አምላኬ ረዳት ነው* ማለት ነው::

እናንተ የተወደደ ርስቴ ትሆናላችሁ፤ ምንም
እንኳ ምድር ሁሉ የእኔ ብትሆንም፣ 6እና
ንተ[ሐ] ለእኔ የመንግሥት ካህናት የተቀደሰ
ሕዝብ ትሆናላችሁ፤’ ለእስራኤላውያን የምት
ነግራቸው ቃሎች እነዚህ ናቸው።”
7ስለዚህ ሙሴ ተመልሶ የሕዝቡን አለ
ቆች አስጠራ፤ እንዲናገር እግዚአብሔር (ያህዌ)
ያዘዘውን ቃሎች ሁሉ ነገራቸው። 8ሕዝቡም
ሁሉ በአንድ ላይ “እግዚአብሔር (ያህዌ) ያለውን
ሁሉ እናደርጋለን” ብለው መለሱ፤ ስለዚህ
ሙሴ እነርሱ ያሉትን መልሶ ወደ እግዚ
አብሔር (ያህዌ) ወሰደ።
9እግዚአብሔርም (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ “ከአንተ ጋር ስናገር ሕዝቡ እንዲ
ሰሙኝና እምነታቸውን ምንጊዜም በአንተ
ላይ እንዲጥሉ በከባድ ደመና ወደ አንተ
እመጣለሁ” ከዚያም ሙሴ ሕዝቡ ያሉትን
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) ነገረው።
10እግዚአብሔርም (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ “ወደ ሕዝቡ ሂድና ዛሬና ነገ ቀድ
ሳቸው፤ ልብሳቸውን እንዲያጥቡ አድርግ፤
11በሦስተኛውም ቀን ይዘጋጁ፤ ምክንያቱም
በዚያ ቀን በሕዝቡ ፊት እግዚአብሔር
(ያህዌ) በሲና ተራራ ላይ ይወርዳል። 12በተራ
ራው ዙሪያ ለሕዝቡ ወሰን አበጅተህ እንዲህ
በላቸው፤ ‘ወደ ተራራው እንዳትወጡ ወይም
ግርጌውን እንዳትነኩ ተጠንቀቁ፤ ማንም
ተራራውን ቢነካ በርግጥ ይሞታል። 13በድንጋይ
ይወገራል ወይም በቀስት ይወጋል፤ ምንም
እጅ በእርሱ ላይ አያርፍም፤ ሰውም ሆነ
እንስሳ በሕይወት እንዲኖር አይተውም።’
ወደ ተራራው መውጣት የሚችሉት ከፍ
ባለ ድምፅ መለከት በተነፋ ጊዜ ብቻ ነው።
14ሙሴ ከተራራው ወርዶ ወደ ሕዝቡ ከሄደ
በኋላ ቀደሳቸው፤ ልብሳቸውንም አጠቡ። 15ከዚ
ያም ለሕዝቡ፣ “ለሦስተኛው ቀን ራሳችሁን
አዘጋጁ፤ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከማድረግ
ተቈጠቡ” አላቸው።
16በሦስተኛውም ቀን ጧት ከባድ ደመና
በተራራው ላይ ሆኖ ነጎድጓድና መብረቅ
እንዲሁም ታላቅ የቀንደ መለከት ድምፅ
ነበር፤ በሰፈሩ ያሉት ሁሉ ተንቀጠቀጡ።
17ከዚያም ሙሴ ከእግዚአብሔር (ያህዌ) ጋር
ለማገናኘት ሕዝቡን ከሰፈር ይዞ ወጣ፤
ከተራራውም ግርጌ ቆሙ። 18የሲና ተራራ
እግዚአብሔር (ያህዌ) በእሳት ስለወረደበት
በጢስ ተሸፍኖ ነበር። ጢሱ ከምድጃ እንደ
ሚወጣ ጢስ ወደ ላይ ተትጐለጐለ፤ ተራ
ራውም በሙሉ[መ] በኀይል ተናወጠ። 19የመለ
ከቱም ድምፅ እያየለ መጣ። ከዚያም ሙሴ
ተናገረ፤ እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) በድምፅ መለሰ
ለት።[ሠ]

34፥9፤9፥29፤15፥26፤ ዘዳ6፥3፤ መዝ78፥10፤ኤር7፥23፤1 ቆሮ10፥26፤ቲቶ2፥14
19፥6 ዘፍ18፥19፤ ዘሌ11፥44-45፤ ዘዳ4፥37፤7፥6፤26፥19፤28፥9፤29፥13፤33፥3፤ኢሳ4፥3፤61፥6፤ 62፥12፤66፥21፤ ኤር2፥3፤አሞ3፥2፤ 1ጴጥ2፥5፤
19፥7 ዘፀ18፥12፤ ዘሌ4፥15፡30፤9፥1፤ ዘኍ16፥25፤ 1ሳሙ8፥10
19፥8 ዘፀ24፥3፡7፤ ዘዳ5፥27፤26፥17
19፥9 ቍ16፤ ዘፀ 4፥5፤20፥21፤24፥15–16፤33፥9፤34፥5፤ዘዳ 4፥11፡12፡36፤2ሳሙ 22፥10፡12፤2ዜና 6፥1፤መዝ18፥11፤ 97፥2፤99፥7፤ማቴ17፥5፤ዮሐ12፥29-30፤
19፥10 ቍ14፡22፤ ዘፍ35፥2፤ዘሌ11፥44፤ዘኍ11፥18፤1ሳሙ 16፥5፤ኢል2፥16፤ዕብ 10፥22፤ራእ22፥14
19፥11 ቍ3፥16፡ 20፤ዘፍ11፥5፤ዘፀ 3፥1፤24፥16፤31፥18፤ 34፥2፡4፡29፡32፤ዘሌ 7፥38፤26፥46፤27፥34፤ ዘኍ3፥1፤ዘዳ10፥5፤ ነህ9፥13ገላ4፥24-25
19፥12 ቍ23
19፥13 ቍ21፤ዘፀ 34፥3፤ኢሱ6፥4፤ 1ዜና15፥28፤መዝ81፥3፤98፥6፤ዕብ12፥20
19፥14 ዘፍ35፥2
19፥15 1ሳሙ21፥4፤ 1ቆሮ7፥5
19፥16 ቍ9፤ዘፍ 3፥10፤1ሳሙ2፥10፤ 1ሳሙ13፥7፤14፥15፤ 28፥5፤መዝ99፥1፤ኢሳ 29፥6፤ዕብ12፥18-19፡ 21፤ራእ4፥1
19፥17 ቍ2፤ ዘዳ4፥11
19፥18 ዘፍ19፥28፤ ዘፀ3፥2፤20፥18፤24፥17፤ዘሌ9፥24፤ዘዳ4፥11፡24፡33፡36፤5፥4፤ 9፥3፤መሳ5፥5፤2ሳሙ22፥8፤1ነገ18፥24፡38፤ 1ዜና21፥26፤2ዜና7፥1፤መዝ18፥7፡8፤68፥8፤104፥32፤ኢሳ2፥19፤ 5፥25፤6፥4፤ 41፥15፤ 64፥1፤ኤር4፥24፤10፥10፤ሚክ1፥4፤ናሆ1፥5፤ዕን3፥6፡10፤ሐጌ2፥6፤ ዕብ12፥ 18፤ራእ9፥2፤15፥8
19፥19 ቍ9፤ዘዳ4፥33፤ነህ9፥13፤መዝ81፥7
19፥20 ቍ11
19፥21 ቍ13፤ዘፀ 24፥10-11፤

20እግዚአብሔር (ያህዌ) በሲና ተራራ ጫፍ
ላይ ወረደ፤ ሙሴን ወደ ተራራው ጫፍ
ጠራው፤ ሙሴም ወጣ። 21እግዚአብሔርም
(ያህዌ) እንዲህ አለው፤ “ሕዝቡ እግዚአብሔርን
(ያህዌ) ለማየት በመጣደፍ ብዙዎቹ እንዳይጠፉ
ውረድና አስጠንቅቃቸው 22ወደ እግዚአብሔር
(ያህዌ) የሚቀርቡት ካህናት እንኳ ራሳቸውን
መቀደስ አለባቸው፤ አለዚያ እግዚአብሔር
(ያህዌ) ቍጣውን ያወርድባቸዋል።”
23ሙሴ እግዚአብሔርን (ያህዌ) እንዲህ
አለው፤ “ሕዝቡ ወደ ሲና ተራራ ሊወጡ
አይችሉም፤ ምክንያቱም አንተ ራስህ ‘በተ
ራራው ዙሪያ ወሰን አድርግ፤ የተቀደሰም
በማድረግ ለየው’ በማለት አስጠንቅቀኸና
ልና።”
24እግዚአብሔርም (ያህዌ) እንዲህ አለ፤
“ውረድና አሮንን ከአንተ ጋር ይዘኸው
ውጣ፤ ካህናቱና ሕዝቡ ግን ወደ እግዚአብሔር
(ያህዌ) ለመምጣት መጣደፍ የለባቸውም፤ አለ
ዚያ እርሱ ቍጣውን ያወርድባቸዋል።”
25ስለዚህ ሙሴ ወደ ሕዝቡ ወርዶ ነገ
ራቸው።

## ዐሥርቱ ትእዛዛት

20፥1-17 ተጓ ምብ - ዘዳ 5፥6-21

20 እግዚአብሔር (ኤሎሂም) እነዚህን ቃሎች
ሁሉ እንዲህ ብሎ ተናገረ፤
2“ከግብፅ ከባርነት ምድር ያወጣሁህ
እግዚአብሔር አምላክህ (ያህዌ ኤሎሂም) እኔ ነኝ።
3“ከእኔ በቀር[ሬ] ሌሎች አማልክት አይ
ኑሩህ።
4“በላይ በሰማይ ወይም በታች በምድር
ካለው ወይም በውሃ ውስጥ ከሚኖሩት
ነገሮች በማናቸውም ምስል ለራስህ ጣዖ
ትን አታብጅ። 5አትስገድላቸው፤ አታም
ልካቸውም፤ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ
(ያህዌ ኤሎሂም) የሚጠሉኝን ልጆች
ከአባቶቻቸው
ኀጢአት የተነሣ እስከ ሦስትና አራት

ዘኍ4፥20፤1ሳሙ6፥19 19፥22 ቍ24፤ ዘሌ10፥3፤1ሳሙ16፥5፤ 2ሳሙ6፥7፤2ዜና29፥5፤ኢል2፥16፤ 19፥23 ቍ11፡12 19፥24 ቍ22፤ዘፀ24፥1፡9፤ 20፥1 ዘዳ10፥4፤ ነህ9፥13፤መዝ119፥9፤147፥19፤ሚል4፥4 20፥2 ዘፍ15፥7፤17፥7፤ዘፀ6፥6፤13፥3፤16፥12፤ዘሌ 19፥2፤20፥7፤ኢሳ43፥3፤ሕዝ20፥6፡19 20፥3 ቍ23፤ዘፀ34፥14፤ ዘዳ6፥14፤ 13፥10፤2ነገ17፥35፤መዝ44፥20፤81፥9፤ኤር1፥16፤7፥6፡9፤11፥13፤19፥4፤25፥6፤35፥15 20፥4 ቍ5፡23፤ ዘፀ32፥8፤ 34፥17፤ዘሌ19፥4፤26፥1፤ዘዳ4፥15-19፡23፤27፥15፤2ሳሙ7፥22፤ 1ነገ14፥9፤2ነገ17፥12ኢሳ40፥19፤42፥8፤44፥9 20፥5 ዘፍ9፥25፤ ዘፀ 23፥13፡24፤34፥7፤34፥14፤ዘሌ26፥39፤ዘኍ14፥18፤ዘዳ4፥24፤ ኢሱ23፥7፤24፥19፤መሳ6፥10፤2ነገ17፥35፤ኢሳ44፥15፡17፡19፤ 46፥6፤ናሆ1፥2፤ኤር32፥18፤20፥6፤

[ሐ]6 ወይም ምድር ሁሉ የእኔ ርስት ናት፤ እናንተ ...
[መ]18 ብዙ የዕብራይስጥ ቅጆችና የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም፣ ሕዝቡ ሁሉ ይላሉ።
[ሠ]19 ወይም፣ እግዚአብሔርም በነጐድጓድ መለሰለት
[ሬ]3 ወይም፣ ከእኔ ጋር

ትውልድ ድረስ የምቀጣ ቀናተኛ አምላክ
(ኤሎሂም) ነኝ፤ 6ነገር ግን ለሚወዱኝና ትእ
ዛዛቴን ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ
ድረስ ፍቅርን የማሳይ ነኝ።
7“የእግዚአብሔር (ያህዌ) የአምላክህን
ስም ያለ አግባብ አታንሣ፤ እግዚአብሔር
(ያህዌ) ስሙን ያለ አግባብ የሚያነሣውን
በደል አልባ አያደርገውምና።
8“የሰንበትን ቀን ቅዱስ አድርገህ አክ
ብር። 9ስድስት ቀን ትሠራለህ፤ ሥራ
ህንም ሁሉ አከናውን። 10ሰባተኛው
ቀን ግን ለአምላክህ ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
ሰንበት ነው። በዕለቱ አንተም ሆንህ
ወንድ ልጅህ ወይም ሴት ልጅህ፣ ወንድ
አገልጋይህ ወይም ሴት አገልጋይህ፣
ወይም እንስሳትህ፣ ወይም በግቢህ ያለ
መጻተኛ ምንም ሥራ አትሠሩም። 11እግዚ
አብሔር (ያህዌ) ሰማይንና ምድርን፤ ባሕ
ርንና በውስጡም ያሉትን ሁሉ በስድስት
ቀን ፈጥሮ፤ በሰባተኛው ቀን አርፎአልና።
ስለዚህ እግዚአብሔር (ያህዌ) የሰንበትን
ቀን ባረከው፤ ቀደሰውም።
12 ‘አባትህንና እናትህን አክብር፤ እግዚ
አብሔር አምላክህ (ያህዌ ኤሎሂም) በሚሰጥህ ምድር
ዕድሜህ እንዲረዝም።
13“አትግደል።
14“አታመንዝር።
15“አትስረቅ።
16“በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር።
17“የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤ የባልንጀ
ራህን ሚስት ወይም የእርሱን ወንድ
አገልጋይ ሆነ ሴት አገልጋይ፣ በሬውን
ንም ሆነ አህያውን ወይም የእርሱ
የሆነውን ማናቸውንም ነገር አትመኝ።
18“ሕዝቡም መብረቁንና ነጎድጓዱን የተራ
ራውን መጤስና የመለከቱን ድምፅ ባዩና
በሰሙ ጊዜ በፍርሃት ተንቀጠቀጡ፤ በርቀ
ትም ቆሙ፤ 19ሙሴን፣ “አንተ ራስህ ተና
ገረን፤ እኛም እናደምጥሃለን፤ እግዚአብሔር
(ኤሎሂም) እንዲናገረን አታድርግ፤ አለበለዚያ
መሞታችን ነው” አሉት።
20ሙሴም ለሕዝቡ፣ “አትፍሩ፤ ኀጢአት
እንዳትሠሩ የእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ፍርሃት
ከእ ናንተ ጋር ይሆን ዘንድ፣ እግዚአብሔር
(ኤሎሂም) ሊፈትናችሁ መጥቶአል” አላቸው።
21እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ወዳለበት ጥቅጥቅ
ወደ ሆነው ጨለማ ሙሴ ቀርቦ ሳለ፣ ሕዝቡ
በርቀት ቆመው ነበር።

### ጣዖቶችና መሠዊያዎች

22ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን
አለው፤ “ለእስራኤላውያን ይህን ንገራቸው፤
‘ከሰማይ ሆኜ እንደ ተናገርኋችሁ እናንተ
ራሳችሁ አይታችኋል፤ 23ከእኔ በቀር ሌሎች
አማልክት አይኑሯችሁ፤ ከብር ወይም ከወርቅ
ለእናንተ አማልክትን አታብጁ።
24“ ‘የጭቃ መሠዊያን ሥራልኝ፤ በእር
ሱም ላይ የሚቃጠልና የኅብረት መሥዋዕ
ትን[ሰ] ከበጎችህ፣ ከፍየሎችህና ከቀንድ ከብ
ቶችህ ሠዋልኝ፤ ስሜ እንዲከበር በማደርግ
በት ቦታ ሁሉ ወደ አንተ እመጣና እባ
ርክሃለሁ። 25ከድንጋይ መሠዊያ የምትሠ
ራልኝ ከሆነ፣ ከጥርብ ድንጋይ አትሥራ፤
መሣሪያ የነካው ከሆነ ታረክሰዋለህና።
26ወደ መሠዊያዬም በደረጃ አትውጣ፤ አለ
ዚያ ኀፍረተ ሥጋህ ይገለጣል’።

21 “በፊታቸው የምትደነግጋቸው ሥርዐ
ቶች እነዚህ ናቸው፤

### ዕብራዊ አገልጋይ

21፥2-6 ተጓ ምብ - ዘዳ 15፥12-18፤ 21፥2-11 ማመ - ዘሌ 25 39-55

2“ዕብራዊ አገልጋይ ብትገዛ ስድስት ዓመት
ያገልግልህ፤ በሰባተኛው ዓመት ግን ያለም
ንም ክፍያ በነጻ ይሂድ። 3ብቻውን መጥቶ
ከሆነ፣ ብቻውን በነጻ ይሂድ፤ ነገር ግን
ሲመጣ ባለ ሚስት ከሆነ፣ እርሷ አብራው
ትሂድ። 4ጌታው ሚስት አጋብቶት ወንድ
ወይም ሴት ልጅ ከወለደችለት፣ ሴትዮዋና
ልጆቿ የጌታቸው ይሆናሉ፤ ሰውዬው ብቻ
በነጻ ይሂድ።
5“ነገር ግን አገልጋዩ፤ ‘ጌታዬን፤ ሚስ
ቴንና ልጆቼን እወዳለሁ ነጻ ሆኜ አል
ሄድም’ ቢል፣ 6ጌታው ወደ ዳኞች[ሸ] ይውሰ
ደው፤ ወደ በር ወይም ወደ በሩ መቃን ወስዶ
ጆሮውን በወስፌ ይብሳው፤ ከዚያም ዕድሜ
ዘመኑን የእርሱ አገልጋይ ይሆናል።
7“አንድ ሰው ሴት ልጁን አገልጋይ
እንድትሆን ቢሸጣት፣ እንደ ወንዶቹ አገል
ጋዮች በነጻ መሸኘት የለባትም። 8ለእርሱ
ትሆነው ዘንድ የመረጣትን ጌታዋን ደስ
ባታሰኘ፣[ቀ] በዎጆ ይስደዳት፤ ለባዕዳን ይሸጣት
ዘንድ መብት የለውም፤ ምክንያቱም ለእርሷ
ያለውን ታማኝነት አጓድሏልና። 9ለወንድ
ልጁ ትሆን ዘንድ መርጧት ከሆነ እንደ ራሱ

20፥6 ዘፀ34፥7፤ዘኁ 14፥18፤ዘዳ7፥9፤ ኤር32፥18፤ሉቃ1፥50፤ ሮሜ11፥28
20፥7 ዘፀ22፥28፤ ዘሌ18፥21፤19፥12፤ 22፥2፤24፥11፡16፤ ዘዳ6፥13፤10፥20፤ ኢዮ2፡5፡9፤መዝ63፥11፤ ኢሳ8፥21፤ሕዝ20፥39፤ 39፥7፤ማቴ 5፥33
20፥8 ዘፀ16፥23፤ 31፥13-16፤35፥3፤ ዘሌ19፥3፡30፤26፥2፤ ኢሳ56፥2፤ኤር17፥ 21-27፤ሕዝ22፥8
20፥9 ዘፀ23፥12፤ 31፥13-17፤34፥21፤ 35፥2-3፤ዘሌ23፥3፤ ሉቃ13፥14
20፥10 ዘፍ2፥3፤ዘፀ 31፥14፤ዘሌ23፥38፤ ዘኁ28፥9፤ኢሳ56፥2፤ ሕዝ 20፥12፡20
20፥11 ዘፍ1፥3- 2፥1፤2፥2፤ዘፀ1፥17፤ ዕብ4፥4
20፥12 ዘፍ4፥23፤ 31፥35፤ዘዳ5፥16፤ 6፥2፤11፥9፤25፥15፤ ኤር35፥7
20፥13፤ ማቴ5፥21፤ 15፥4፤ 19፥18፡19፤ማር 7፥10፤10፥19፤ሉቃ 18፥20፤ሮሜ13፥9፤ ኤፌ6፥2፡3፤ያዕ2፥11
20፥14 ዘሌ18፥20፤ 20፥10፤ዘኁ5፥12፡13፡ 29፤ምሳ6፥29፡32፤ማቴ 5፥27፤19፥18፤ማር10፥ 19፤ሉቃ18፥20፤ሮሜ 13፥9፤ያዕ2፥11
20፥15 ዘሌ19፥11፡ 13፤ሕዝ18፥7፤ማቴ 19፥18፤ማር10፥19፤ ሉቃ18፥20፤ሮሜ13፥9
20፥16 ዘፀ23፥1፡7፤ ዘሌ19፥11፡18፤መዝ 50፥ 20፤101፥5፤ 119፥29፤ኤር9፥3፡5፤ ማቴ19፥18፤ማር10፥ 19፤ሉቃ3፥14፤18፥20
20፥17 ሉቃ12፥15፤ሮ ሜ7፥7፤13፥9፤ኤፌ 5፥3፤ዕብ13፥5
20፥18 ዘፍ310፤ዘፀ 14፥31፤19፥16-19፤ ዘዳ4፥36፤ኢሳ58፥1፤ ኤር6፥17፤ሕዝ33፥3፤ ዕብ12፥18-19፤ራእ 1፥10፤
20፥19 ዘዳ5፥5፡23- 27፤18፥16፤ ኢዮ37፥ 4፡5፤40፥9፤መዝ29፥ 3-4፤ገላ3፥19
20፥20 ዘፍ15፥1፤22፥ 1፤ዘዳ4፥10፤6፥2፡24፤1 0፥12፤ኢዮ1፥8፤2፥3፤ 28፥28፤መዝ111፥10፤ 128፥1፤ምሳ1፥7፤3፥7፤ 8፥13፤14፥16፤16፥6፤ መክ12፥13፤ኢሳ8፥13
20፥21 ዘፀ19፥9፤ዘዳ5፥22፤መዝ18፥9፤68፥4፤ 97፥2፤ኢሳ19፥1
20፥22 ዘዳ5፥24፡26፤ነህ9፥13 20፥23 ቆ3፤ዘፀ22፥20፤32፥4፡ 8፡31፤34፥17፤ዘዳ29፥17-18፤ነህ9፥18 20፥24 ዘፍ8፥20፤12፥2፤ 22፥17፤ዘፀ18፥12፤27፥1፡5፤40፥29፤ዘኁ16፥38፤ዘዳ12፥5፤16፥6፡ 11፤26፥2፤ ኢሱ8፥30፤1ነገ9፥3፤2ነገ16፥14፤21፥4፡7፤2ዜና4፥1፤ 2ዜና6፥6፤12፥13፤ዕዝ3፥2፤ዕዝ6፥12፤ሕዝ43፥13 20፥25 ኢሱ8፥ 31፤1ነገ6፥7 20፥26 ሕዝ43፥17 21፥1 ዘፀ24፥3፤34፥32፤ዘዳ 4፥14፤6፥1 21፥2 ቆ7፤ዘፀ22፥3፤ኤር34፥8፡14 21፥5 ዘዳ15፥16
21፥6 ዘፀ22፥8-9፤ ዘዳ17፥9፤19፥17፤ 25፥1፤ኢዮ39፥9፤ 41፥4፤መዝ40፥6

[ሰ]24 በትውፊት፣ የሰላም መሥዋዕት በመባል ይታወቃል።
[ሸ]6 ወይም፣ ወደ ፈራጆች [ቀ]8 ወይም፣ ጌታዋ ይሆን ዘንድ አይምረ
ጣት

ልጅ የሚገባትን መብት ይስጣት:: 10ሌላ
ሴት ቢያገባ፣ ለመጀመሪያ ሚስቱ ምግቧን፣
ልብሷንና የጋብቻ መብቷን አይከልክላት::
11እነዚህን ሦስት ነገሮች የማያሟላላት
ቢሆን፣ ያላንዳች የገንዘብ ክፍያ በነጻ መሄድ
ይኖርባታል::

### በሕይወት ላይ ለሚደርስ ጉዳት

12"ሰውን ደብድቦ የገደለ ሞት ይገባ
ዋል:: 13ሆኖም እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ፈቅዶ
ሰውየው ሳያውቅ በድንገት አድርጎት ከሆነ፣
እኔ ወደ ምወስነው ስፍራ ይሽሽ:: 14አንድ
ሰው በተንኰል ሆን ብሎ ሌላውን ቢገድል፣
ከመሠዊያዬ ተወስዶ ይገደል::

15"አባቱን ወይንም እናቱን የሚመታ[ሀ]
ይገደል::

16"አንዱ ሌላውን ጠልፎ የሸጠ ወይም
በተያዘ ጊዜ ከእጁ ላይ የተገኘበት ይገ
ደል::

17"አባቱን ወይንም እናቱን የሚሰድብ
ይገደል::

18ሰዎች ተጣልተው አንዱ ሌላውን
በድንጋይ ወይም በቡጢ[+] ቢመታውና ተመ
ቺው ሳይሞት በአልጋ ላይ ቢውል፣ 19በትሩ
ንም ይዞ ደጅ ለደጅ የሚል ቢሆን፣ በዱላ
የመታው ሰው አይጠየቅበትም፤ ሆኖም ለተ
ጐጂው ሰው ለባከነበት ጊዜ ገንዘብ ይክፈል፤
ፈጽሞ እስኪድን ክትትል ያድርግለት::

20"አንድ ሰው ወንድ ወይም ሴት
ባሪያውን በዱላ ቢመታና ባሪያውም በዚህ
የተነሣ ቢሞት መቀጣት አለበት፤ 21ነገር
ግን ከአንድ ወይም ከሁለት ቀን በኋላ
ባሪያው ቢነሣ መቀጣት የለበትም፤ ባሪያው
ንብረቱ ነውና::

22"በጥል ላይ ያሉ ሰዎች ነፍሰ ጡር
ሴት ቢመቱና እርሷም ያለጊዜዋ ብትወ
ልድ፣[ቸ] ጉዳቱም ለክፉ የማይሰጥ ቢሆን፣
ጉዳት ያደረሰባት ሰው የሴትዮዋ ባል የጠየ
ቀውንና ፈራጆቹ የፈቀዱትን ካሣ ሁሉ
መክፈል አለበት:: 23ነገር ግን የከፋ ጉዳት
ቢደርስ ሕይወት በሕይወት፣ 24ዓይን በዓ
ይን፤ ጥርስ በጥርስ፣ እጅ በእጅ፣ እግር
በግር፣ 25ቃጠሎ በቃጠሎ፣ ቍስል በቍስል፣
ግርፋት በግርፋት ታስከፍላለህ::

26"አንድ ሰው የወንድ ወይም የሴት
አገልጋዩን ዐይን መትቶ ቢያጠፋ፣ ስለ ዐ
ይን ካሣ አገልጋዩን ነጻ ይልቀቀው::
27የወንድ ወይም የሴት አገልጋዩን ጥርስ
ቢሰብር፣ ስለ ጥርስ ካሣ አገልጋዩን ነጻ
ይልቀቀው::

28"በሬ አንድን ወንድ ወይም ሴት ወግቶ
ቢገድል፣ በሬው በድንጋይ ተወግሮ ይሙት፤
ሥጋውም አይበላ፤ ነገር ግን የበሬው ባለ
ቤት በኀላፊነት አይጠየቅም:: 29ሆኖም በሬው
የመውጋት ዐመል ያለበት ሆኖ ለባለቤቱም
ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ሳለ በበረት ሳያስ
ቀረው ቀርቶ አንድን ወንድ ወይም ሴት ቢገ
ድል፣ በሬው በድንጋይ ይወገር፤ ባለቤቱም
እንዲሁ ተወግሮ ይሙት:: 30ሆኖም ካሣ
እንዲከፍል ከተጠየቀ፣ የተጠየቀውን ሁሉ
በመክፈል ሕይወቱን ይዋጅ:: 31አንድ በሬ
አንድን ወንድ ወይም ሴት ልጅ ቢወጋ
በዚሁ ሕግ መሠረት ይፈጸም:: 32አንድ በሬ
ወንድ ወይም ሴት ባሪያን ቢወጋ ባለቤቱ
ሠላሳ የብር ሰቅል[ኀ] ለባሪያው ጌታ መክፈል
አለበት፤ በሬውም በድንጋይ ይወገር::

33"አንድ ሰው ጒድጓድን ከፍቶ ቢተው፣
ወይም ጒድጓድ ቆፍሮ ሳይከደነው ቢቀርና
በሬ ወይም አህያ ቢገባበት፣ 34የጒድጓዱ
ባለቤት ኪሳራ ይክፈል፤ ለባለቤቱ መክፈል
አለበት፤ የሞተውም እንስሳ ለእርሱ ይሆናል::

35"የአንድ ሰው በሬ የሌላውን ሰው በሬ
ወግቶ ቢገድለው፣ በሕይወት ያለውን በሬ
ሸጠው ገንዘቡንና የሞተውን እንስሳ እኩል
ይካፈሉ:: 36ሆኖም በሬው የመዋጋት ዐመል
ያለው መሆኑ ከታወቀ፣ ባለቤቱም በረት
ሳይዘጋበት ቢቀር፣ ባለቤቱ በሬውን በበ
ሬው ፈንታ ይክፈል፤ የሞተውም እንስሳ
ለእርሱ ይሆናል::

### ንብረትን ስለ መጠበቅ

22 "አንድ ሰው በሬ ወይም በግ ሰርቆ
ቢያርድ ወይም ቢሸጥ በአንድ
በሬ ምትክ አምስት በሬዎች፤ በአንድ በግ
ምትክ አራት በጎች ይክፈል::

2"አንድ ሌባ በር ሲሰብር ተይዞ ቢደበ
ደብና ቢሞት፣ ተከላካዩ የደም ባለ ዕዳ
አይሆንም፤ 3ነገር ግን ፀሓይ ከወጣች በኋላ
ከተፈጸመ፣[ነ] ሰውየው በነፍስ ግድያ ይጠ
የቃል::

"ሌባ የሰረቀውን መክፈል አለበት፤
ምንም ከሌለው ግን የሰረቀውን ይከፍል
ዘንድ ይሸጥ::

4"የሰረቀው እንስሳ በሬ ወይም አህያ፣
ወይም በግ ከነሕይወቱ በእጁ ከተያዘ እጥፍ
መክፈል አለበት::

5"አንድ ሰው ከብቶቹን በመስክ ወይም
በወይን ቦታ አሰማርቶ እንዲሁ ስድ ቢለቃ
ቸውና የሌላውን ሰው መስክ ቢግጡ፣ ምርጥ
ከሆነው ከራሱ መስክ ወይም የወይን ቦታ
መክፈል አለበት::

21፥10 1ቆሮ7፥3-5
21፥12 ቍ15፡17፤ ዘፍ4፥14፡23፤ዘፀ31፥15፤ዘሌ20፥9፡10፤ 24፥16፤27፥29፤ዘኍ 1፥51፤35፥16፡30-31፤ ዘዳ13፥5፤19፥11፤ 22፥22፤ 27፥16፤ኢዮ 31፥11፤ ምሳ20፥20፤ ማቴ26፥52
21፥13 ዘኍ35፥10-34፤ ዘዳ4፥42፤ 19፥2-13፤ኢሱ20፥9
21፥14 ዘፍ4፥8፤ ዘኍ35፥20፤ዘዳ19፥11-12፤1ነገ2፥28-34፤ 2ሳሙ3፥27፤ 20፥10፤ዕብ10፥26፤
21፥16 ዘፍ37፥28፤ ዘፀ22፥4፤ዘዳ24፥7
21፥17 ቍ12፤ ዘዳ5፥16፤ማቴ15፥4፤ ማር7፥10
21፥21 ዘሌ25፥44-46
21፥22 ቍ30
21፥23 ዘሌ24፥19፤ ዘዳ19፥21
21፥24 ቍ23፤ ማቴ5፥38
21፥28 ቍ32፤ ዘፍ9፥5
21፥29 ቍ36
21፥30 ቍ22
21፥32 ዘፍ37፥28፤ ዘካ11፥12-13፤ማቴ 26፥15፤27፥3፡9
21፥33 ሉቃ14፥5
21፥36 ቍ29
22፥1 ዘሌ6፥1-7፤ 2ሳሙ12፥6፤ምሳ6፥31፤ሉቃ19፥8
22፥2 ዘኍ35፥27፤ ኢዮ24፥16፤ ኤር2፥34፤ሆሴ7፥1፤ ማቴ6፥19-20፤ 24፥43፤
22፥3 ቍ1፤ ዘፀ21፥2፤ማቴ18፥25
22፥4 ዘፍ43፥12፤ 1ሳሙ12፥5
22፥5 ቍ1

[ሀ]15 ወይም፣ *የሚገድል*
[+]18 ወይም፣ *በዕቃ*
[ቸ]22 ወይም፣ *ቢያስወርዳት*
[ኀ]32 ወደ 0.3 ኪሎ ግራም ይደርሳል
[ነ]3 ወይም፣ *ከመታው*

6“እሳት ተነሥቶ ወደ ቍጥቋጦ ቢዘም
ትና ክምርን ወይም ያልታጨደን እህል
ወይም አዝመራውን እንዳለ ቢበላ፣ እሳቱን
ያቀጣጠለው ሰው ካሣ ይክፈል።
7“አንድ ሰው ብሩ ወይም ንብረቱ ያለ
ሥጋት ይጠበቅለት ዘንድ ለጎረቤቱ ሰጥቶ ሳለ
ቢሰርቅበትና፣ ሌባው ቢያዝ እጥፍ ይክፈል፤
8ሌባው ካልተያዘ ግን፣ የቤቱ ባለቤት በን
ብረቱ ስርቆት ላይ እጁ ይኑርበት ወይም
አይኑርበት ይታወቅ ዘንድ ዳኞች ፊት[ኘ]
ይቅረብ። 9አንድ ሰው በሬን፣ አህያን፣
በግን፣ ልብስን፣ ወይም ማናቸውንም ንብ
ረት ያለአግባብ በባለቤትነት ይዞ ሳለ፣
‘የኔ ነው’ ባይ ቢመጣና ክርክር ቢነሣ፣ ባለ
ጉዳዮቹ ነገሩን ለዳኞች ያቅርቡት፤ ዳኞቹ
ጥፋተኛ ነው ያሉትም[አ] ለጎረቤቱ እጥፉን
ይክፈል።
10“አንድ ሰው አህያ፣ በሬ፣ በግ፣ ወይም
ማናቸውንም እንስሳ በጎረቤቱ ዘንድ በአደራ
አስቀምጦ ሳለ እንስሳው ቢሞት፣ ወይም
ጉዳት ቢደርስበት፣ ወይም ሰው ሳያይ ተነ
ድቶ ቢወሰድ፣ 11በሁለቱ መካከል ያለው
አለመግባባት መፍትሄ የሚያገኘው፣ ጎረቤቱ
የሌላውን ሰው ንብረት እንዳልወሰደ *በእግ
ዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት በመማል ነው። ባለቤቱም
ይህን መቀበል አለበት፤ የካሣም ክፍያ
አይጠየቅም። 12እንስሳው ከጎረቤት ተሰርቆ
ከሆነ ግን፣ ለባለቤቱ ካሣ መክፈል አለበት።
13በዱር አራዊት ተበልቶ ከሆነ፣ ከአውሬ
የተረፈውን ማስረጃ አድርጎ በማቅረብ፣
ስለ ተበላው እንስሳ ካሣ እንዲከፍል አይጠ
የቅም።
14“አንድ ሰው ከጎረቤቱ እንስሳ ተውሶ
ሳለ ባለቤቱ በሌለበት ቢጎዳ ወይም ቢሞት
ካሣ መክፈል አለበት። 15ባለቤቱ ከእንስሳው
ጋር ከሆነ ግን፣ ተበዳሪው መክፈል የለበ
ትም፤ እንስሳው ከተከራየም ለኪራይ የተከ
ፈለው ገንዘብ ኪሳራውን ይሸፍናል።

## ማኅበራዊ ኀላፊነት

16“አንድ ሰው ያልታጨችን ልጃገረድ
አታልሎ ክብረ ንጽሕናዋን ቢያጎድል፣ የማ
ጫዋን ዋጋ ከፍሎ ሚስት ያድርጋት።
17እርሷን ለእርሱ የልጅቷ አባት በሚስት
ነት ለመስጠት ከቶ የማይፈቅድ ቢሆን፣
ለድንግሎች መከፈል የሚገባውን ማጫ
አሁንም ቢሆን መክፈል ይገባዋል።
18“መተተኛ ሴት በሕይወት እንድት
ኖር አትፍቀድ።
19“ከእንስሳ ጋር ሩካቤ ሥጋ የሚፈ
ጽም ሰው ይገደል።
20“*ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) በቀር ለሌላ አማ
ልክት የሚሠዋ ይጥፋ[ከ]።

22፥6 ቍ1፤ መሳ15፥5
22፥7 ቍ10፤ ዘፍ43፥12፤ዘሌ6፥2
22፥8 ዘፀ21፥6
22፥9 ቍ8፤ ዘዳ25፥1
22፥10 ቍ7
22፥11 ዘሌ6፥3፤ 1ነገ8፥31፤2ዜና6፥22ዕብ6፥16
22፥12 ቍ1
22፥13 ዘፍ31፥39
22፥14 ቍ1
22፥15 ዘሌ19፥13፤ ኢዮ17፥5
22፥16 ዘፍ34፥12፤ ዘዳ22፥28
22፥18 ዘፀ7፥11፤ ዘሌ19፥26፡31፤ 20፥27፤ዘዳ18፥11፤ 1ሳሙ28፥3፤ 2ዜና33፥6፤ኢሳ57፥3
22፥19 ዘሌ18፥23፤ 20፥15፤ዘዳ27፥21
22፥20 ዘፀ20፥23፤ 34፥15፤ዘሌ17፥7፤ 27፥29፤ዘኍ25፥2፤ዘዳ 13፥5፤17፥2-5፤ 18፥20፤32፥17፤ 1ነገ18፥40፤19፥1፤ 2ነገ10፥25፤23፥20፤ 2ዜና15፥13፤ መዝ106፥37፤
22፥21 ዘፀ23፥9፤ ዘሌ19፥33፤24፥22፤ ዘኍ15፥14፤ዘዳ1፥16፤10፥19፤24፥17፤ 27፥19፤ሕዝ22፥29፤ ዘካ7፥10፤ሚል3፥5
22፥22 ቍ26፤ ዘዳ10፥18፤24፥6፡10፡12፡17፤ኢዮ22፥6፡9፤ 24፥3፡21፤መዝ68፥5፤146፥9፤ምሳ23፥10፤ ኢሳ1፥17፤ኤር7፥5፡6፤21፥12፤22፥3፤ ሕዝ18፥5-9፡12፤ ዘካ7፥9-10፤ ሚል3፥5፤ያዕ1፥27
22፥23 ዘዳ10፥18፤ 15፥9፤24፥15፤ ኢዮ34፥28፤35፥9፤ መዝ10፥14፡17፤ 12፥5፤18፥6፤34፥15፤ሉቃ18፥7፤ያዕ5፥4
22፥24 መዝ109፥9፤ ሰቆ5፥3
22፥25 ዘሌ25፥35-37፤ዘዳ15፥7-11፤23፥20፤ነህ5፥7፡10፤ መዝ15፥5፤ ሕዝ18፥8
22፥26 ቍ22፤ምሳ20፥16፤ሕዝ33፥15፤አሞ2፥8
22፥27 ዘፀ34፥6፤ ዘዳ4፥31፤24፥13፡17፤2ዜና30፥9፤ነህ9፥17፤ ኢዮ22፥6፤24፥7፤ 29፥11፤31፥19-20፤ ሕዝ18፥12፡16፤ መዝ99፥8፤103፥8፤ 116፥5፤145፥8፤

21መጻተኛውን አትበድሉት ወይም አታ
ስጨንቁት፤ እናንተ በግብፅ መጻተኛ ነበ
ራችሁና።
22“ባል በሞተባት ወይም አባትና እናት
በሌለው ልጅ ላይ ግፍ አትዋሉ። 23ግፍ
ብትውሉባቸውና ወደ እኔ ቢጮኹ፣ ጩኸ
ታቸውን በእርግጥ እሰማለሁ። 24ቍጣዬ
ይነሣል፤ በሰይፍም እገድላችኋለሁ፤ ሚስቶ
ቻችሁ መበለቶች፣ ልጆቻችሁም አባት የለሽ
ይሆናሉ።
25“ከሕዝቤ መካከል ችግረኛ ለሆነው ለአ
ንዱ ገንዘብ ብታበድሩ፣ እንደ አራጣ አበዳሪ
አትሁኑ፤ ወለድ አትጠይቁት[ኸ]። 26የጎረቤ
ትህን ልብስ መያዣ አድርገህ ብትይዝ ሲመሽ
መልስለት፤ 27ምክንያቱም ለሰውነቱ መሸፈኛ
ያለው ልብስ ያ ብቻ ነው፤ ሌላ ምን ለብሶ
ይተኛል? ወደ እኔ ሲጮህ እኔ እሰማለሁ፤
እኔ ርኅሩኅ ነኝና።
28“በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ላይ የስድብ ቃል
አታሰማ[ወ]፤ ወይም የሕዝብህን መሪ አትርገም።
29“የእህልህን ወይም የወይን ጠጅህን
በኵራት ለእኔ ከማቅረብ ወደ ኋላ አትበል።
“የወንድ ልጆችህን በኵር ለእኔ ስጠኝ።
30ከቀንድ ከብትህና ከበጎችህም እንዲሁ አድ
ርግ፤ ለሰባት ቀን ከእናቶቻቸው ጋር ይቆዩ፤
በስምንተኛው ቀን ግን ለእኔ ሰጠኝ።
31“እናንተ ለእኔ ቅዱስ ሕዝብ ትሆናላችሁ፤
ስለዚህ አውሬ የዘነጠለውን የእንስሳ ሥጋ
አትብሉ፤ ለውሾች ስጡት።

## የፍትህና የምሕረት ሕጎች

23 የሐሰት ወሬ አትንዛ፤ ተንኰል ያለ
በትን ምስክርነት በመስጠት ክፉ
ውን ሰው አታግዝ።
2“ክፉ በማድረግ ብዙዎችን አትከተል፤
በሕግ ፊት ምስክርነት ስትሰጥ፣ ከብዙዎቹ
ጋር ተባብረህ ፍትሕ አታጣምም። 3በዳኝ
ነት ጊዜ ለድኻው አታድላ።

ኢል2፥13፤ዮና4፥2 22፥28 ዘፀ20፥7፤2ሳሙ16፥5፡9፤19፥21፤1ነገ21፥10፤2ነገ2፥23፤ መዝ102፥8፤ መክ10፥20፤ሐሥ23፥5 22፥29 ዘፀ13፥2፤ 23፥15፡16፡19፤34፥20፡26፤ዘሌ19፥24፤23፥10፤ ዘኍ8፥16-17፤18፥13፤ 28፥26፤ዘዳ18፥4፤26፥2፡10፤1ሳሙ6፥3፤ነህ10፥35ምሳ3፥9፤ሚል3፥10፤ሉቃ2፥23 22፥30 ዘፍ17፥12፤ ዘፀ34፥19፤ዘሌ12፥3፤22፥27፤ዘዳ15፥19 22፥31 ዘፀ19፥6፤ ዘሌ19፥2፤22፥31፤ዘሌ7፥24፤17፥15፤ 22፥8፤ዘዳ14፥21፤ዕዝ9፥2፤ሕዝ4፥14፤44፥31 23፥1 ዘፍ39፥17፤ዘፀ20፥16፤ዘዳ5፥20፤19፥16-21፤መዝ27፥12፤35፥11፤ምሳ19፥5፤ማቴ19፥18፤ ሉቃ3፥14፤ሐሥ6፥11 23፥2 ቍ3፡6፡9፤ዘሌ19፥15፡33፤ዘዳ 1፥17፤16፥19፤24፥17፤27፥19፤1ሳሙ8፥3፤ኢዮ31፥34 23፥3 ዘዳ1፥17

[ኘ]8 በዚህም ሆነ በቍጥር 9 ላይ ያለው፣ *እግዚአብሔር ፊት*
[አ]9 ወይም፣ *እግዚዘአብሔር ጥፋተኛ ነው ያለውም* [ከ]20 የዕብራይስጡ ቃል አንድን ነገር ወይም አንድን ሰው ፈጽሞ በማጥፋት ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር መስጠትን የሚያመለክት ነው።
[ኸ]25 ወይም፣ *ከልክ በላይ የሆነ ወለድ አትጠይቁ* [ወ]28 ወይም፣ *ዳኞችን አትሳደብ* ።

4“የጠላትህ በሬ ወይም አህያ ሲባዝን ብታገኘው ወደ እርሱ መልሰው። 5የሚጠላህ ሰው አህያ፣ ጭነት ከብዶት ወድቆ ብታየው ርዳው እንጂ ትተኸው አትሂድ።

6“በዳኝነት ጊዜ በድኻው ላይ ፍርድ አታጓድልበት። 7ከሐሰት ክስ ራቅ፤ በደል የሌለበትን ወይም ትክክለኛውን ሰው ለሞት አሳልፈህ አትስጥ፣ በደለኛውን ንጹሕ አላደርግምና።

8“ጉቦ አትቀበል፤ ጉቦ፣ አጥርተው የሚያዩትን ሰዎች ዐይን ያሳውራል፤ የጻድቃንንም ቃል ያጣምማልና።

9“መጻተኛውን አትጨቍን፤ በግብፅ መጻተኛ ስለ ነበራችሁ፣ መጻተኛ ምን እንደሚሰማው እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁና።

## የሰንበት ሕጎች

10“ስድስት ዓመት በእርሻህ ላይ ዝራ፤ አዝመራንም ሰብስብ፤ 11ነገር ግን በሰባተኛው ዓመት ምድሪቱን ሳትጠቀምባትና ሳታርሳት እንዲሁ ተዋት፤ ከዚያም በወገንህ መካከል ያሉት ድኾች ከእርሷ ምግብ ያገኛሉ፤ የዱር አራዊትም ከእነርሱ የተረፈውን ይበላሉ። በወይን ቦታህና በወይራ ዛፎችህም ላይ እንዲሁ አድርግ።

12“ስድስት ቀን ሥራህን ሥራ፤ በሬህና አህያህ በቤትህ የተወለደው ባሪያና መጻተኛው ያርፉ ዘንድ በሰባተኛው ቀን ምንም አትሥራ።

13ያልኳችሁን ሁሉ ታደርጉ ዘንድ ተጠንቀቁ፤ የሌሎችን አማልክት ስም አትጥሩ፤ ከአፋችሁም አይስሙ።

## ሦስቱ ዐውደ ዓመታዊ በዓላት

14በዓመት ሦስት ጊዜ ለእኔ በዓልን ታከብራላችሁ።

15“ያልቦካ የቂጣ በዓልን አክብር፤ እን ዳዘዝኩህ ሰባት ቀን እርሾ የሌለውን ቂጣ ብላ፤ ይህንንም በአቢብ ወር በተወሰነ ቀን አድርግ፤ በዚያ ወር ከግብፅ ወጥተሃልና።

“ማንም በፊቴ ባዶ እጁን አይቅረብ።

16“በማሳህ ላይ በዘራኸው እህል በኵራት የመከርን በዓል አክብር።

“በዓመቱ መጨረሻ በማሳህ ላይ ያለውን እህልህን ስትሰበስብ የመክተቻውን በዓል አክብር።

17“በዓመት ሦስት ጊዜ ወንድ ሁሉ በጌታ በእግዚአብሔር (አዶናይ ያህዌ) ፊት ይቅረብ።

18የመሥዋዕትን ደም እርሾ ካለበት ነገር ጋር አድርገህ ለእኔ አታቅርብ።

“የበዓል መሥዋዕቴ ስብ እስከ ንጋት ድረስ አይቆይ።

19“የምድርን ምርጥ ፍሬ በኵራት ለአምላክህ ለእግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) አምጣ።

“ጠቦት ፍየልን በእናቱ ወተት አትቀቅል።

## የእግዚአብሔር መልአክ መንገድ ስለ መምራቱ

20“እነሆ፤ በጕዞ ላይ ሳለህ የሚጠብቅህንና ወዳዘጋጀሁልህ ስፍራ የሚያስገባህን መልአክ በፊትህ ልኬልሃለሁ። 21በጥንቃቄ ተከተለው፤ የሚናገረውንም ልብ ብለህ አድምጠው፤ አታምፅበት። ስሜ በርሱ ላይ ነውና ዐመፅህን ይቅር አይልም። 22የሚናገረውን በጥንቃቄ ብታደምጥና ያልኩህን ሁሉ ብታደርግ ለጠላቶችህ ጠላት እሆናለሁ፤ የሚቃወሙህን እቃወማለሁ። 23መልአኬ በፊትህ ይሄዳል፤ አንተንም ወደ አሞራውያን፣ ወደ ኬጢያውያን፣ ወደ ፌርዛውያን፣ ወደ ከነዓናውያን፣ ወደ ኤዊያውያንና ኢያቡሳውያን ምድር ያስገባሃል፤ እኔም እነርሱን አጠፋቸዋለሁ። 24ለአማልክቶቻቸው አትስገድ፤ ወይም አታምልካቸው፤ ወይም ልምዳቸውን አትከተል፤ እነርሱን ማፈራረስ አለብህ፤ የአምልኮ ድንጋዮቻቸውንም ሰባብር። 25አምላክህን እግዚአብሔርን (ያህዌ) አምልክ፤ በረከቱም በምትበላውና በምትጠጣው ላይ ይሆናል፤ በሽታንም ከአንተ ዘንድ አርቃለሁ። 26በምድርህም የሚያስወረዳት ወይም መካን ሴት አትኖርም፤ ረጅም ዕድሜም እሰጥሃለሁ።

27“በሚያጋጥሙህ አሕዛብ ሁሉ ላይ ማስፈራቴን በፊትህ እልካለሁ፤ ግራም አጋባቸዋለሁ፤ ጠላቶችህ ሁሉ ወደ ኋላ ተመልሰው እንዲሸሹ አደርጋለሁ። 28ኤዊያውያንን፣ ከነዓናውያንን፣ ኬጢያውያንን ከመንገድህ ለማስወጣት ተርብን በፊትህ እሰዳለሁ። 29ነገር ግን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አላወጣቸውም፤ ምክንያቱም ምድሪቱ፣ ባድማ ሆና፣ የዱር አራዊት ይበዙባችኋል። 30ቀኁጥርህ ጨምሮ ምድሪቱን ለመውረስ እስክትበቃ ድረስ ጥቂት በጥቂት ከፊታችሁ አባርራቸዋለሁ።

31“ድንበርህን ከቀይ ባሕር[o] እስከ ፍልስጥኤም ባሕር፤[u] ከምድረ በዳው እስከ ወንዙ[w] ድረስ አደርገዋለሁ፤ በምድሪቱም ላይ የሚኖሩትን ሰዎች አሳልፌ እሰጥሃለሁ፤

23፥4 ዘሌ6፥3፤ 19፥11፤ዘዳ22፥1-3፤ ሮሜ12፥20
23፥5 ዘዳ22፥4
23፥6 ቍ2፤ዘዳ 23፥16፤ምሳ22፥22
23፥7 ዘፍ18፥23፤ ዘፀ20፥16፤34፥7፤ ዘዳ19፥18፤25፥1፤ ማቴ27፥4፤ኤፌ4፥25
23፥8 ዘፀ18፥21፤ ዘሌ19፥15፤ዘዳ10፥17፤ 27፥25፤ኢዮ15፥34፤ 36፥18፤መዝ26፥10፤ ምሳ6፥35፤15፥27፤ 17፥8፤ኢሳ1፥23፤ 5፥23፤ሚክ3፥11፤7፥3
23፥9 ቍ2፤ዘፀ 22፥21፤ዘሌ19፥33-34፤ ሕዝ22፥7
23፥11 ዘሌ25፥1-7፤ ነህ10፥31
23፥12 ዘፍ2፥2-3፤ ዘፀ20፥9፤ሉቃ13፥14
23፥13 ቍ32፤ ዘዳ4፥9፡23፤12፥3፤ 18፥20፤ኢሱ23፥7፤ መዝ16፥4፤ዘካ13፥2፤ ሆሴ2፥17፤1ጢሞ4፥16
23፥14 ቍ17፤ ዘፀ12፥14፤34፥23፡24፤ ዘዳ16፥16፤1ነገ9፥25፤ 2ዜና8፥13፤ሕዝ46፥9
23፥15 ዘፀ12፥2፡ 17፤22፥29፤ማቴ26፥ 17፤ ሉቃ22፥1፤ሐሥ 12፥3
23፥16 ዘሌ23፥15-21፤ዘፀ22፥29፤34፥22፤ ዘሌ23፥34፡39፡42፤ዘኍ 28፥26፤ዘዳ16፥9፡13፡1 6፤31፥10፤2ዜና8፥13፤ ዕዝ3፥4፤ነህ8፥14፤ ኤር40፥10፤ዘካ14፥16
23፥17 ቍ14
23፥18 ዘፀ12፥8፤ 34፥25፤ ዘሌ2፥11
23፥19 ዘፀ22፥29፤ 34፥22፡26፤ዘኍ18፥12፤ ዘዳ14፥21
23፥20 ዘፍ16፥7፤ዘፀ 15፥17 23፥21 ዘፀ 3፥15፤ ዘኍ17፥10፤ ዘዳ 9፥7፤18፥19፤29፥ 20፤ 31፥27፤ኢሱ24፥ 19፤ 2ነገ24፥4፤መዝ 25፥7፤78፥8፡40፡56፤ 106፥33፤107፥11፤ኤር 13፥15፤ ሰቆ1፥171 ዮሐ5፥16
23፥22 ዘፍ12፥3፤ዘፀ 15፥26፤ኢሳ41፥11 ኤር30፥20
23፥23 ዘኍ13፥29፤ 21፥21፤ኢሱ3፥10፤ 24፥8፡11፤ዕዝ9፥1፤ መዝ135፥11 23፥24 ዘፀ20፥5፤ 34፥13፤ ዘሌ18፥3፤ 20፥23፤26፥1፤ ዘኍ 33፥52፤ዘዳ7፥5፤9፥4፤1 2፥3፡30-31፤16፥22፤ መሳ2፥2፤2ነገ18፥4፤
23፥14፤1ነገ14፥23፤ 2ነገ3፥2፤10፥26፤ 17፥10፤2ዜና14፥3፤ ኢሳ27፥9፤ ኤር10፥2 23፥25 ዘፀ15፥26፤ ዘሌ26፥3-13፤ዘዳ7፥12-15፤28፥1-14፤ ማቴ4፥10 23፥26 ዘፍ15፥15፤ ዘሌ26፥3-4፤ዘዳ4፥1፡40፤7፥14፤ 28፥4፤ 32፥47፤ሚል3፥11፤ መዝ90፥10 23፥27 ዘፍ35፥5፤ ዘፀ 15፥14፤14፥24፤ዘዳ7፥23፤2ሳሙ22፥41፤መዝ18፥40፤21፥12 23፥28 ዘፀ 33፥2፤34፥11፡24፤ዘኍ13፥29፤ዘዳ4፥38፤7፥20፤11፥23፤18፥12፤ ኢሱ3፥10፤24፥11፡12፤መዝ78፥55 23፥29 ዘዳ7፥22 23፥30 ኢሱ23፥5
23፥31 ዘፍ2፥14፤ዘዳ7፥24፤9፥3፤34፥2፤ኢሱ21፥44፤24፥12፡18፤ ዕዝ 4፥20፤መዝ80፥8

[o]31 በዕብራይስጥ፣ *ያም ሱፍ* ይባላል፤ ይኸውም፣ *የደንገል ባሕር*። [u]31 *የሜዲትራንያን*
[w]31 *የኤፍራጥስ*

አንተም አሳደህ ከፊትህ ታስወጣቸዋለህ::
32ከእነርሱም ሆነ ከአማልክቶቻቸው ጋር
ኪዳን አታድርግ:: 33በምድርህ ላይ እንዲ
ኖሩአት ፍቀድላቸው፤ አለዚያ እኔን እንድ
ትበድል ያደርጉሃል፤ አማልክቶቻቸውን ማም
ለክ በርግጥ ወጥመድ ይሆንብሃልና::”

### ቃል ኪዳኑ ስለ መጽናቱ

24 ከዚያም ሙሴን “አንተና አሮን፣
ናዳብና አብድዩ ከሰባዎቹ የእስራ
ኤል አለቆች ጋር ወደ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ኑ፤ ከሩቅም ስገዱ አለው፤ 2ነገር ግን ወደ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሊቀርብ የሚችለው ሙሴ
ብቻ ነው:: ሌሎቹ መቅረብ የለባቸውም
ሕዝቡም ከእርሱ ጋር መምጣት የለበትም::”

3ሙሴ ወደ ሕዝቡ ሄዶ *የእግዚአብሔርን*
(ያህዌ) ቃሎችና ሕጎች ሁሉ በነገራቸው ጊዜ
በአንድ ድምፅ ሆነው፣ “*እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ያለውን ሁሉ እናደርጋለን” አሉ:: 4ከዚያም
ሙሴ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ያለውን ሁሉ ጻፈ::
በማግሥቱም ማልዶ ተነሥቶ፣ በተራራው
ግርጌ መሠዊያን ሠራ፤ አሥራ ሁለቱን የእ
ስራኤልን ነገዶች የሚወክሉ ዐሥራ ሁለት
የድንጋይ ዐምዶችን አቆመ:: 5ከዚያም ወጣት
ወንድ እስራኤላውያንን ላከ፤ እነርሱም
የሚቃጠል መሥዋዕት[የ] አቀረቡ፤ ወይፈኖችን
የኅብረት መሥዋዕት አድርገው *ለእግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) ሠዉ:: 6ሙሴ የደሙን እኩሌታ
ወስዶ በጎድጓዳ ሣህኖች አኖረው፤ የቀረው
ንም እኩሌታ በመሠዊያው ላይ ረጨው::
7ከዚያም የኪዳኑን መጽሐፍ ወስዶ ለሕዝቡ
አነበበላቸው፤ እነርሱም፣ “*እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ያለውን ሁሉ እናደርጋለን፤ እንታዘዛለን”
አሉ::

8ከዚያም ሙሴ ደሙን ወሰደ፤ ሕዝ
ቡም ላይ ረጭቶ፣ “ይህ እነዚህን ቃሎች በሰጠ
ጊዜ፣ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ከእናንተ ጋር የገ
ባው የቃል ኪዳኑ ደም ነው” አላቸው::

9ሙሴና አሮን፣ ናዳብና አብድዩ እንደ
ዚሁም ሰባዎቹ የእስራኤል አለቆች ወደ ተራ
ራው ወጡ፣ 10የእስራኤልንም አምላክ (ኤሎሂም)
አዩ፤ ከእግሩም በታች እንደ ብሩህ ሰማይ
የጠራ የሰንፔር[ደ] ወለል ነበር:: 11ሆኖም
እግዚአብሔር (ኤሎሂም) በእስራኤል ሕዝብ
አለቆች
ላይ እጁን አላነሣባቸውም:: እግዚአብሔርን
(ኤሎሂም) አዩ፣ በሉ፤ ጠጡም::

12*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን፣ “በተራራው
ላይ ወደ እኔ ና፤ በዚህም ቆይ፤ እኔም
መመሪያ እንዲሆናቸው ሕግና ትእዛዛት
የጻፍኩባቸውን የድንጋይ ጽላቶች እሰጥሃ
ለሁ” አለው::

13ከዚያም ሙሴ ከረዳቱ ከኢያሱ ጋር
አብሮ ሄደ፤ ሙሴም ወደ እግዚአብሔር (ኤሎ
ሂም) ተራራ ወጣ:: 14እርሱም ሽማግሌዎችን
“ወደ እናንተ እስክንመለስ ድረስ በዚህ ቆዩ፤
አሮንና ሖር ከእናንተ ጋር ናቸው፤ ክርክር
ያለው ሰው ቢኖር ወደ እነርሱ ይሂድ::”
አላቸው::

15ሙሴ ወደ ተራራ ሲወጣ ደመናው ተራ
ራውን ሸፈነ፤ 16*የእግዚአብሔርም* (ያህዌ) ክብር
በሲና ተራራ ላይ ወረደ፣ ደመናውም ተራ
ራውን እስከ ስድስት ቀን ድረስ ሸፈነው፤
በሰባተኛውም ቀን *እግዚአብሔር* (ያህዌ) በደ
መናው ውስጥ ሆኖ ሙሴን ጠራው::
17ለእስራኤላውያን *የእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ክብር በተራራው ጫፍ ላይ እንደሚባላ
እሳት ሆኖ ይታይ ነበር 18ከዚያም ሙሴ
ወደ ተራራው ሲወጣ ደመናው ውስጥ
ገባ፤ በተራራውም ላይ አርባ ቀንና አርባ
ሌሊት ቆየ::

### ለመገናኛው ድንኳን የሚቀርቡ ስጦታዎች

25፥1-7 ተጓ ምብ - ዘፀ 35፥4-9

25 *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን አለው፤
2“ስጦታ እንዲያመጡልኝ ለእስራ
ኤላውያን ንገራቸው:: ይሰጥ ዘንድ ልቡ ካነ
ሣሣው ከእያንዳንዱ ሰው ስጦታን ተቀበ
ልልኝ:: 3ከእነርሱ የምትቀበላቸው ስጦታ
ዎች እነዚህ ናቸው:- ወርቅ፣ ብርና፣ ነሐስ፣
4ሰማያዊ፣ ሐምራዊ፣ ቀይ ማግና የበፍታ ድር
ልብስ፣ የፍየል ጠጕር፣ 5ቀይ የተነከረ የአ
ውራ በግ ቆዳ፣ የለፋ ቆዳ፣ የግራር ዕን
ጨት፣ 6የመብራት ወይራ ዘይት፣ ለቅብዓ
ዘይቱና ጣፋጭ መዓዛ ላለው ዕጣን የሚ
ሆኑ ቅመሞች፣ 7በኤፉድና በደረት ኪስ
ላይ የሚሆኑ መረግዶችና ሌሎች ዕንቍዎች::

8“ከዚያም መቅደስ እንዲሠሩልኝ አድ
ርግ፤ እኔም በመካከላቸው አድራለሁ:: 9
ማደሪያ ድንኳኑንና በውስጡ ያለውን ዕቃ
ሁሉ ልክ እኔ በማሳይህ ዕቅድ መሠረት
ሥሩት::

### የቃል ኪዳኑ ታቦት

25፥10-20 ተጓ ምብ - ዘፀ 37፥1-9

10“ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፣ ወርዱ
አንድ ክንድ ተኩል፣ ከፍታው አንድ ክንድ
ተኩል የሆነ ታቦት ከግራር እንጨት[ጀ] እንዲ

23፥32 ዘፍ26፥28፤ ዘፀ34፥12፤ዘዳ7፥2፤ ኢ.ሱ9፥7፤መሳ2፥2፤ 1ሳሙ11፥1፤1ነገ15፥19፤ 20፥34፤ሕዝ17፥13
23፥33 ዘፀ10፥7
24፥1 ቍ9፤ዘፀ6፥23፤ 19፥24፤ ዘኍ11፥6
24፥2 ዘኍ12፥6-8
24፥3 ዘፀ19፥8፤ 21፥1፤ኢ.ሱ24፥24፤ ገላ3፥19
24፥4 ዘፍ8፥20፤ 28፥18፤ዘፀ17፥14፤ ዘዳ27፥2
24፥5 ዘፍ31፥54፤ ዘሌ1፥3
24፥6 ዘፀ14፥15፤ 32፥31፤ዘሌ1፥11፤ 3፥2፡8፡13፤5፥9፤ መዝ99፥6፤ማቴ26፥ 28፤ዕብ9፥18
24፥7 ዘፀ19፥8፤ 2ነገ23፥2፡21፤ ኤር40፥3፤42፥6፡21፤ 43፥2፤ዕብ9፥19
24፥8 ዘሌ26፥3፤ ዘዳ5፥2-3፤ኢ.ሱ24፥25፤ 2ነገ11፥17፤ ኤር11፥4፡8፤31፥32፤ 34፥13፤ዘካ9፥11፤ ማቴ26፥28፤ ሉቃ22፥20፤ዕብ9፥19፡ 20፤1ጴጥ1፥2
24፥9 ቍ1
24፥10 ዘፍ16፥13፤ ዘኍ12፥6፤ኢዮ26፥16፤ ኢ.ሳ6፥1፤ 54፥11፤ ሕዝ1፥1፡26፤8፥3፤ 10፥1፤40፥2፤ ዮሐ 1፥18፤ራእ4፥3
24፥11 ቍ10፤ዘፀ 3፥6፤19፥21፤ሕዝ 44፥3፤ማቴ26፥29
24፥12 ዘፀ31፥18፤ 32፥15-16፤ 34፥1፡ 28፡29፤ ዘዳ4፥13፤ 5፥22፤8፥3፤9፥9፡10፡ 11፤10፥4፤2ቆሮ3፥3
24፥13 ዘፀ3፥1፤ 17፥9
24፥14 ዘፀ17፥10፤ 18፥16 24፥15 ዘፀ 19፥9፤ማቴ17፥5
24፥16 ዘፀ16፥7፤19፥ 11፤ዘሌ9፥23፤ዘኍ14፥ 10፤1ሳሙ4፥21፡22፤መዝ 99፥7፤ሕዝ8፥4፤11፥22
24፥17 ዘፀ15፥7፤ 19፥18፤ዕብ12፥18፡29
24፥18 ዘፍ7፥4፤ 1ነገ19፥8፤ማቴ4፥2
25፥2 ዘፀ35፥21፡ 22፡26፡27፡29፤36፥ 2፤2ነገ12፥4፤1ዜና 29፥5፡7፡9፤2ዜና24፥ 10፤29፥31፤ዕዝ2፥68፤ ነህ7፥70-72፤2ቆሮ8፥ 11-12፤9፥7
25፥4 ዘፀ28፥4-8
25፥5 ዘኍ4፥6፡10፤ ዘዳ10፥3

25፥6 ዘፀ27፥20፤ 30፥1፡7፡22-32፡35፤ 35፥28፤39፥37፤31፥11፤ 35፥28፤ዘሌ16፥12፤ ዘኍ4፥16፤7፥14፤2ዜና13፥11 25፥7 ዘፀ28፥4፡ 6-14፤29፥5፤መሳ8፥27፤ሆሴ3፥4፤ዘሌ8፥8 25፥8 ዘፀ29፥45፤36፥1-5፤ዘሌ 4፥6፤ 10፥4፡7፤21፥12፡23፤ 26፥11-12፤ዘኍ3፥28፤5፥3፤ዘዳ12፥11፤ 1ነገ 6፥13፤ዘካ2፥10፤2ቆሮ 6፥16፤ዕብ9፥1-2 25፥9 ቍ40፤ዘፀ 26፥30፤27፥8፤31፥11፤ 39፥32፡42፡43፤ዘኍ 8፥4፤1ዜና28፥11፡ 19፤ሐ ሥ7፥44፤ዕብ 8፥5 25፥10 ዘዳ10፥1-5፤ 1ነገ6፥19፤ዕብ9፥4

[የ]5 በትውፊት፣ *የሰላም መሥዋዕት* በመባል ይታወቃል::
[ደ]10 ወይም፣ *ላፒስ ላዚሊ* ተብሎ መተርጐም ይችላል::
[ጀ]10 ርዝመቱ 1.1 ሜትር፣ ጐኑና ርዝመቱ 0.7 ሜትር ያህል ነው::

ሡሩ አድርግ። [11]ውስጡንም ውጭውንም
በንጹሕ ወርቅ ለብጠው፤ በዙሪያውም የወ
ርቅ ክፈፍ አብጅለት። [12]አራት የወርቅ ቀለበ
ቶች ሠርተህ ሁለቱን በአንድ በኩል
ሁለቱን በሌላ በኩል ከአራቱ እግሮች ጋር
አያይዝ። [13]ከዚያም መሎጊያዎችን ከግራር
ዕንጨት ሥራ፤ በወርቅም ለብጣቸው። [14]መሎ
ጊያዎችንም መሸከሚያ እንዲሆኑ በታቦቱ
ማእዘኖች ላይ ባሉት ቀለበቶች ውስጥ
አስገባቸው። [15]መሎጊያዎቹ ከታቦቱ ቀለበ
ቶች ውስጥ ምንጊዜም መውጣት የለባቸውም።
[16]የምሰጥህንም ምስክር በታቦቱ ውስጥ አኑር።
[17]"ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፣ ወርዱ
አንድ ክንድ ተኩል[ገ] የሆነ የስርየት መክደኛ[ጠ]
ከንጹሕ ወርቅ ሥራለት። [18]በስርየት መክ
ደኛው ዳርና ዳር ላይ የሚሆኑ ከወርቅ
የተቀረጹ ሁለት ኪሩቤል ሥራ። [19]አንዱን
ኪሩብ በአንደኛው፣ ሁለተኛውን ኪሩብ
በሌላኛው ዳር አድርግ በሁለቱም ጫፎች
ሁለቱን ኪሩቤል ከስርየት መክደኛው ጋር
አንድ ወጥ አድርገህ ሥራቸው። [20]ኪሩቤልም
ክንፎቻቸውን ወደ ላይ በመዘርጋት የስርየት
መክደኛውን በክንፎቻቸው ይሸፍኑ፤ እርስ
በርሳቸው ትይዩ በመሆንም ፊታቸውን ወደ
ስርየት መክደኛው ያድርጉ። [21]የስርየት
መክደኛውን በታቦቱ አናት ላይ አስቀ
ምጠው፤ እኔ የምሰጥህን ምስክሩንም በታ
ቦቱ ውስጥ አስቀምጥ። [22]በምስክሩ ታቦት
ላይ ባሉት በሁለቱ ኪሩቤል መካከል፣
በስርየት መክደኛው ላይ በዚያ እኔ ከአንተ
ጋር እገናኛለሁ፤ ለእስራኤላውያን የሚሆኑ
ትን ትእዛዞቼንም እሰጥሃለሁ።

### የኅብስቱ ማስቀመጫ ጠረጴዛ

25፥23-29 ተጓ ምብ ዘፀ 37፥10-16

[23]ርዝመቱ ሁለት ክንድ፣ ወርዱ አንድ
ክንድ፣ ከፍታው አንድ ክንድ ተኩል[ጨ] የሆነ
ጠረጴዛ ከግራር ዕንጨት ሥራ። [24]በንጹሕ
ወርቅ ለብጠው፤ በዙሪያውም የወርቅ ክፈፍ
አድርግለት። [25]ዙሪያውንም አንድ ስንዝር[ጸ]
ስፋት ያለው ጠርዝ አብጅለት፤ በጠርዙም
ዙሪያ የወርቅ ክፈፍ አድርግለት። [26]ለጠ
ረጴዛው አራት የወርቅ ቀለበቶች ሠርተህ፣
አራቱ እግሮች ባሉበት በአራቱ ማእዘኖች
ላይ አያይዘው። [27]ጠረጴዛውን ለመሸከም
የሚያገለግሉትን መሎጊያዎች ይይዙ ዘንድ፣
ቀለበቶቹ ከክፈፉ አጠገብ ይሁኑ። [28]መሎጊያ
ዎቹን ከግራር ዕንጨት ሥራቸው፤ በወርቅ
ለብጣቸው፤ ጠረጴዛውንም ተሸከምባቸው።
[29]ለመጠጥ ቍርባን መፍሰሻ ይሆኑም ዘንድ
ዝርግ ሳሕኖችንና ወጭቶችን፣ እንዲሁም
ማንቆርቆሪያዎቹንና ጎድጓዳ ሳሕኖቹን ከን
ጹሕ ወርቅ ሥራቸው። [30]በማንኛውም ጊዜ
በፊቴ እንዲሆን ኅብስተ ገጹን በዚህ ጠረ

25፥11 ቍ24፤ ዘፀ30፥3
25፥12 ቍ26፤ ዘፀ30፥4
25፥13 ቍ28፤ዘፀ 27፥6፤30፥5፤ 37፥28
25፥14 ዘፀ27፥7፤ 40፥20፤1ዜና15፥15
25፥15 1ነገ8፥8
25፥16 ዘፀ16፥34፤ ዕብ9፥4
25፥17 ቍ21፤ ዘሌ16፥13፤ሮሜ3፥25
25፥18 ዘፀ26፥1፡ 31፤36፥35፤ 1ነገ6፥23፡27፤8፥6፤ 2ዜና3፥10-13፤ ዕብ9፥5
25፥20 ዘፍ3፥24፤ ዘፀ37፥9፤1ነገ8፥7፤ 1ዜና28፥18፤ዕብ9፥5
25፥21 ቍ10-15፤ ዘፀ16፥34፤26፥34፤ 40፥20፤ዘዳ10፥5፤ ዕብ9፥4
25፥22 ዘፀ19፥3፤ 29፥42፤30፥6፡36፤ ዘሌ1፥1፤16፥2፤ ዘኍ7፥89፤17፥4፤ 1ሳሙ4፥4፤2ሳሙ6፥2፤ 22፥11፤2ነገ19፥15፤ 1ዜና13፥6፤28፥18፤ መዝ18፥10፤80፥1፤ 99፥1፤ኢሳ37፥16፤ ኤር3፥16
25፥23 ቍ30፤ዘፀ 26፥35፤40፥4፡22፤ዘሌ 24፥6፤ ዘኍ3፥31፤ 1ነገ7፥48፤1ዜና28፥ 16፤2ዜና4፥8፡19፤ሕዝ 41፥22፤ 44፥16፤ዕብ 9፥2
25፥28 ቍ13
25፥29 ዘኍ4፥7
25፥30 ዘፀ35፥13፤ 39፥36፤40፥4፡23፤ዘሌ 24፥5-9፤ዘኍ4፥7፤ 1ሳሙ21፥4-6፤1ነገ 7፥48፤1ዜና23፥29
25፥31 ዘፀ26፥35፤ 31፥8፤35፥14፤39፥37፤ 40፥4፡24፤ዘሌ24፥4፤ ዘኍ3፥31፤1ነገ7፥49፤2 ዜና4፥7፤ዘካ4፥2፤ዕብ 9፥2፤ራእ1፥12
25፥36 ቍ18፤ ዘኍ8፥4
25፥37 ዘፀ27፥21፤ 30፥8፤ዘሌ24፤3-4፤ ዘኍ8፥2፤1ሳሙ3፥3፤ 2ዜና13፥11
25፥38 ቍ37፤ ዘኍ4፥9
25፥40 ቍ9፤ ሐሥ7፥44፤ዕብ8፥5
26፥1 ዘፀ25፥18፤ 29፥42፤40፥2፤ ዘሌ8፥10፤ዘኍ1፥50፤ኢ ሱ22፥19፡29፤ 2ሳሙ7፥2፤ 1ነገ1፥39፤ ሐሥ7፥44፤ዕብ8፥2፡ 5፤13፥10፤ራእ21፥3፤
26፥2 ቍ8

ጴዛ ላይ አስቀምጥ።

### የመብራቱ መቅረዝ

25፥31-39 ተጓ ምብ - ዘፀ 37 17-24

[31]ከንጹሕ ወርቅ መቅረዝ ሥራ፤ መቆሚ
ያና ዘንግ አብጅለት፤ ጽዋ መሰል አበባዎች፤
እንቡጦችና የፈነዱ አበባዎች ከመቅረዙ ጋር
ወጥ ሆነው ይሠሩ። [32]ከመቅረዙ ግራና ቀኝ
ጎን ጋር የተያያዙ፣ በአንዱ በኩል ሦስት
በሌላው በኩል ሦስት በድምሩ ስድስት
ቅርንጫፎች ይኑሩት። [33]ከመቅረዙ ጋር የተ
ያያዙት ስድስቱ ቅርንጫፎች እያንዳንዳቸው
እንቡጥና ቀንበጥ ያሏቸው የለውዝ አበባ ቅርጽ
ያሏቸው ሦስት ጽዋ መሰል አበባዎች፤ ጋር
ያኑሯቸው። [34]በመቅረዙም ላይ አበባዎች
እንቡጥና ቀንበጥ ያሏቸው አራት የለውዝ
አበባ ቅርጽ ያሏቸው ጽዋዎች ይኑሩ። [35]በመ
ቅረዙ ላይ ላሉት ለስድስቱ ቅርንጫፎች
እንቡጥ በመጀመሪያዎቹ ጥንድ ቅርንጫፎች
ሥር፣ ሁለተኛውም እንቡጥ በሁለተኛው
ጥንድ ሥር፣ ሦስተኛውም እንቡጥ በሦስተ
ኛው ጥንድ ሥር ይሁን። [36]ዕንቡጦቹና ቅርን
ጫፎቹ ሁሉ ከመቅረዙ ጋር አንድ ወጥ
ሆነው ከንጹሕ ወርቅ ተቀርጸው ይሠሩ።
[37]"ከዚያም ሰባት መብራቶች ሠርተህ
ከመቅረዙ ፊት ለፊት ለሚገኘው ስፍራ
ብርሃን እንዲሰጡ ከመቅረዙ ላይ አስቀ
ምጣቸው። [38]መኰኰስተሪያና የኵስታሪ ማስ
ቀመጫ ሳህኖቹም ከንጹሕ ወርቅ ይሠሩ።
[39]ለመቅረዙና ለዕቃዎቹ ሁሉ የሚያስፈል
ገው አንድ መክሊት ንጹሕ ወርቅ ነው።
[40]በተራራው ላይ ባሳየሁህ ዕቅድ መሠረት
መሥራትህን ልብ በል።

### የማደሪያው ድንኳን

26፥1-37 ተጓ ምብ - ዘፀ 36፥8-38

26 "በቀጭኑ ከተፈተለ የበፍታ ድርና
በሰማያዊ፣ በሐምራዊና በቀይ ማግ
በተሠሩ ዐሥር መጋረጃዎች ማደሪያ ድንኳኑን
ሥራ፤ እጀ ብልኅ ሠራተኛም ኪሩቤልን ይጥለ
ፍባቸው። [2]መጋረጃዎች ሁሉ እኩል ይሁኑ፤
የእያንዳንዱ መጋረጃ ርዝመት ሃያ ስምንት
ክንድ ወርዱም አራት ክንድ[ጸ] ይሁን። [3]አም
ስቱን መጋረጃዎች አገጣጥመህ ስፋ፤ የቀሩ
ትንም አምስት መጋረጃዎች እንደዚሁ
አገጣጥመህ ስፋቸው። [4]ከዳር በኩል ባለው
መጋረጃ ጠርዝ ላይ፣ ከሰማያዊ ጨርቅ የተ
ሠሩ ቀለበቶች አድርግ፤ በሌላውም የመጋረጃ
ጠርዝ ላይ እንዲሁ አድርግ። [5]ቀለበቶችን
ትይዩ በማድረግ አምሳ ቀለበቶችን በአንደኛው

[ገ]17 ርዝመቱ 1.1 ሜትር፣ ጐኑና ርዝመቱ 0.7 ሜትር ያህል ነው።
[ጠ]17 በትውፊት፣ *የጸጋው ዙፋን* በመባል ይታወቃል።
[ጨ]23 ርዝመቱ 0.9 ሜትር፣ ጐኑና 0.5 ርዝመቱ 0.7 ሜትር ያህል ነው
[ጸ]25 ወደ 8 ሳንቲ ሜትር ያህል ነው።
[ጸ]2 ርዝመቱ 12.5 ሜትር ወርዱ 1.8 ሜትር ያህል ነው።

ጠርዝ መጋረጃ፣ አምሳ ቀለበቶችንም በሌ
ላው ጠርዝ መጋረጃ አድርግ። 6ከዚያም
የመገናኛው ድንኳን አንድ ወጥ ይሆን ዘንድ
መጋረጃዎቹን በአንድ ላይ ለማያያዝ አምሳ
የወርቅ ማያያዣዎችን ሥራ።
7“ማደሪያ ድንኳኑን ከላይ ሆነው የሚሸ
ፍኑ ዐሥራ አንድ የፍየል ጠጕር መጋረጃ
ዎች ሥራ። 8ዐሥራ አንዱም መጋረጃዎች
እኩል ይሁኑ፤ የእያንዳንዱ ርዝመት ሠላሳ
ክንድ ወርዱም አራት ክንድ[ፀ] ይሁን።
9አምስቱን መጋረጃዎች በአንድ ላይ፣
እንደዚሁም ስድስቱን መጋረጃዎች በአንድ
ላይ አድርገህ ስፋቸው፤ ከማደሪያው ድንኳን
ፊት ለፊት ስድስተኛውን መጋረጃ እጠፍና
በላዩ ላይ ደርበው። 10በአንድ በኩል ባለው
መጨረሻ መጋረጃ ጠርዝ ላይ አምሳ ቀለበ
ቶችን፣ እንዲሁም በሌላ በኩል ባለው
መጨረሻ መጋረጃ ጠርዝ ላይ አምሳ ቀለበ
ቶችን አድርግ። 11ከዚያም አምሳ የናስ ማያ
ያዣዎችን ሥራ፤ ድንኳኑን አንድ ወጥ
አድርጎ ለማያያዝ በቀለበቶቹ ውስጥ ጨም
ራቸው። 12ስለ ድንኳኑ መጋረጃዎች ትርፍ
ቁመትም፣ ትርፍ ግማሽ መጋረጃ ከማደሪ
ያው ድንኳን ጀርባ ላይ እንዲንጠለጠል
ይሁን። 13የድንኳኑ መጋረጃዎች በሁለቱም
ጐኖች አንድ ክንድ ርዝመት[ፈ] ይኖራቸዋል፤
የተረፈውም የማደሪያውን ድንኳን ጎኖች
እንዲሸፍን ሆኖ ይንጠለጠላል፤ 14ለድን
ኳኑ በቀይ የተነከረ የአውራ በግ ቆዳ
ልብስ አብጅ፤ በላዩም ላይ የአቆስጣ ቆዳ
ይሁን[ፐ]።
15“ለማደሪያው ድንኳን ከግራር ዕንጨት
ወጋግራዎችን አብጅ። 16እያንዳንዱም ወጋግራ
ርዝመቱ ዐሥር ክንድ ወርዱም አንድ ክንድ
ተኩል[ሀ] ይሁን፤ 17ሁለት ጒጦችም ጎን ለጎን
ይሁኑለት፤ የማደሪያውን ድንኳን ወጋግራ
ዎች ሁሉ በዚሁ መልክ አብጅ 18ለማደ
ሪያው ድንኳን ክፍል ሃያ ወጋግራዎችን
ሥራ። 19ከሥራቸው የሚሆኑ አርባ የብር
መቆሚያዎችን አብጅ፤ በእያንዳንዱ ጒጠት
ሥር አንድ መቆሚያ ሲሆን፣ ለእያንዳንዱም
ወጋግራ ሁለት መቆሚያዎች ይኑሩ።
20በሌላው ጎን፣ ከማደሪያው ድንኳን በስተ
ሰሜን በኩል ሃያ ወጋግራዎችን አብጅ፤
21በእያንዳንዱም ወጋግራ ሥር ሁለት ሁለት
መቆሚያ ሆኖ አርባ የብር መቆሚያዎችን
አብጅ። 22በዳር በኩል ለሚገኘው ይኸውም
በምዕራብ ጠርዝ ላለው የማደሪያው ድንኳን
ስድስት ወጋግራዎች አብጅ። 23ዳርና ዳር
ላሉት ማእዘኖች ሁለት ወጋግራዎች አብጅ።
24በእነዚህ ሁለት ማእዘኖች ላይ ከታች እስከ
ላይ ድረስ ድርብ ሲሆኑ በአንድ ቀለበት
ውስጥ የሚገጥሙ መሆን አለባቸው፤ በሁለ

26፥6 ቍ11
26፥8 ቍ2
26፥11 ቍ6
26፥14 ዘኍ3፥25፤
4፥25
26፥19 ቍ21፡25፡
32፤ዘፀ38፥27
26፥21 ቍ19
26፥30 ዘፀ25፥9፤
40፥2፤ዘኍ9፥15
26፥31 ዘፀ25፥18፤
ዘኍ4፥5፤2ዜና3፥14፤
ማቴ27፥51፤
ሉቃ23፥45፤ዕብ9፥3
26፥32 ቍ19
26፥33 ዘፀ27፥21፤
35፥12፤40፥3፡21፤
ዘሌ16፥2፡16፤ዘኍ
3፥31፤4፥5፤1ነገ6፥16፤
7፥50፤8፥6፤2ዜና
3፥8፡14፤5፥7፤ሕዝ
41፥4፤ዕብ9፥2-3
26፥34 ዘፀ25፥21፤
30፥6፤37፥6፤
ዘሌ16፥2፤ዕብ9፥5
26፥35 ዘፀ 25፥23፡
31፤ዕብ9፥2
26፥36 ዘፀ35፥15፤
40፥5፡28፤መዝ45፥14፤
ሕዝ16፥10፤26፥16፤
27፥7
27፥1 ዘፀ20፥24፤
40፥6፤1ነገ8፥64
27፥2 ዘፀ29፥12፤
30፥2፤37፥25፤
ዘሌ4፥7፤1ነገ1፥50፤
2፥28፤መዝ118፥27፤ኤ
ር17፥1፤ሕዝ43፥15፤
አሞ3፥14፤ዘካ9፥15

ቱም ወገን እንዲሁ መሆን አለበት። 25ስለዚህ
ስምንት ወጋግራዎች አሉ፤ እንዲሁም ዐሥራ
ስድስት የብር መቆሚያዎች ሲኖሩ፣ ለእያን
ዳንዱ ወጋግራ ሁለት ሁለት መቆሚያ
ይሆናል።
26“ደግሞም ከግራር ዕንጨት አግዳሚ
ዎችን አብጅ፤ በአንድ በኩል ላሉት የማደ
ሪያው ድንኳን ወጋግራዎች አምስት፣ 27በሌ
ላው ጎን ላሉት አምስት፣ በማደሪያው ድን
ኳን ዳር በምዕራብ በኩል ባሉት ወጋግራ
ዎች አምስት አብጅ። 28መካከለኛው
አግዳሚ በወጋግራዎቹ መካከል ከጫፍ
እስከ ጫፍ ይተላለፍ። 29ወጋግራዎቹን
በወርቅ ለብጣቸው፤ አግዳሚዎቹን ለመያዝ
የወርቅ ቀለበቶች አብጅ፤ አግዳሚዎቹንም
በወርቅ ለብጣቸው።
30“ማደሪያ ድንኳኑንም በተራራው ላይ
ባየኸው ዕቅድ መሠረት ትከለው።
31“ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊ፣ ከቀይ ማግና
በቀጭኑ ከተፈተለ በፍታ መጋረጃ አብጅ፤
እጀ ብልህ ሠራተኛም ኪሩቤልን ይጥ
ለፍበት። 32በወርቅ በተለበጡ ከግራር ዕን
ጨት በተሠሩና በአራቱ የብር መቆሚያዎች
ላይ በቆሙት በአራቱ ምሰሶዎች፣ በወርቅ
ኵላቦች ላይ አንጠልጥለው። 33መጋረጃዎን
በማያያዣዎቹ ላይ ስቀለው፤ የምስክሩንም
ታቦት ከመጋረጃው በስተኋላ አስቀምጠው፤
መጋረጃውም መቅደሱን ከቅድስተ ቅዱሳኑ
ይለያል። 34በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ በምስ
ክሩ ታቦት ላይ የማስተስረያውን ክዳን አስቀ
ምጥ። 35ጠረጴዛውን ከመገናኛው ድንኳን
በሰሜን በኩል ከመጋረጃው ውስጥ አስቀ
ምጠው፤ መቅረዙንም ከእርሱ ትይዩ በማድ
ረግ በደቡብ በኩል አድርገው።
36“ለድንኳኑ ደጃፍ ከሰማያዊ፣ ከሐም
ራዊ፣ ከቀይ ማግና በቀጭኑ ከተፈተለ በፍታ
በጥልፍ ዐዋቂ የተጠለፈ መጋረጃ አብጅ።
37ለዚህም መጋረጃ የወርቅ ኵላቦችንና ከግ
ራር እንጨት የተሠሩ፣ በወርቅ የተለበጡ
አምስት ምሰሶዎችን አብጅ፤ አምስት የናስ
መቆሚያዎችንም አብጅላቸው።

## የሚቃጠል መሥዋዕት ማቅረቢያ መሠዊያ

27፥1-8 ተጓ ምብ - ዘፀ 38፥1-7

27 “ከፍታው ሦስት ክንድ[ለ] የሆነ መሠ
ዊያ ከግራር ዕንጨት ሥራ፤ ርዝ
መቱ አምስት፣ ስፋቱም አምስት ክንድ
ሆኖ ባለ አራት ማእዘን[ሐ] ይሁን። 2ቀንዶቹና

[ፀ]8 ርዝመቱ 13.5 ሜትር ወርዱ 1.8 ሜትር ያህል ነው።
[ፈ]13 ርዝመቱ 0.5 ሜትር ያህል ነው።
[ፐ]14 ይህ የባሕር አውሬ ነው።
[ሀ]16 ርዝመቱ 4.5 ሜትር፣ ወርዱ 0.7 ሜትር ያህል ነው።
[ለ]1 ወደ 1.3 ሜትር ያህል ነው።
[ሐ]1 ርዝመቱ ወርዱ 2.3 ሜትር ያህል ነው

መሠዊያው አንድ ወጥ ይሆኑ ዘንድ በአራ
ቱም ማእዘኖች ላይ ቀንድ አድርግለት፤መሠ
ዊያውንም በነሐስ ለብጠው። 3ዕቃዎቹን
ሁሉ ይኸውም የዐመድ ማስወገጃ ምንቸቶ
ችን፣ መጫሪያዎችን፣ ጐድጓዳ ሳሕኖችን፣ ሜን
ጦዎችንና የፍም መያዣዎችን ከነሐስ አብ
ጃቸው። 4ዐመድ ማውረጃ የሚሆን እንደ
መረብ የሆነ የነሐስ ፍርግርግ አድርግለት
በአራቱም የመረብ ማእዘኖች ላይ የነሐስ
ቀለበቶች አብጅ። 5እስከ መሠዊያው ወገብ
እንዲደርስ በመሠዊያው ዙሪያ ባለው እርከን
ሥር አድርገው። 6የግራር ዕንጨት መሎ
ጊያዎችን ለመሠዊያው ሠርተህ በነሐስ ለብ
ጣቸው። 7በሽክም ጊዜ በመሠዊያው ሁለቱም
ጎኖች እንዲሆኑ፣ መሎጊያዎቹ በቀለበቶቹ
ውስጥ ይግቡ። 8መሠዊያውን ውስጡን ባዶ
ከሆኑ ሳንቃዎች አብጀው፤ ልክ በተራራው
ላይ ባየኸው መሠረት ይበጅ።

## የመገናኛው ድንኳን አደባባይ

27፥9-19 ተጓ ምብ - ዘፀ 38፥9-20

9"ለመገናኛው ድንኳን አደባባይ አብጅ
ለት፤ በደቡብ በኩል ርዝመቱ አንድ መቶ
ክንድ[መ] ይሁን፣ ከቀጭን በፍታ የተፈተሉ
መጋረጃዎች፣ 10ሃያ ምሰሶዎች፣ ሃያ የነሐስ
መቆሚያዎች፣ የብር ኩላቦችና በምሰሶዎ
ቹም ላይ ዘንጎች ይኑሩት። 11በሰሜኑም በኩል
አንድ መቶ ክንድ ርዝመት ያላቸው መጋረ
ጃዎች ይሁኑ፤ ሃያ ምሰሶዎቹ፣ ሃያ የነሐስ
መቆሚያዎች፣ የብር ኩላቦችና በምሰሶዎ
ችም ላይ ዘንጎች ይኑሩ።

12"የአደባባዩ ምዕራብ ጫፍ ስፋቱ
አምሳ ክንድ[ሠ] ሆኖ ዐሥር ምሰሶዎችና ዐሥር
መቆሚያዎች ያሉት መጋረጃዎች ይኑሩት።
13በምሥራቅ ጫፍ በፀሓይ መውጫ በኩል
ያለው አደባባይ አሁንም አምስት ክንድ
ስፋት ይኑረው። 14ሦስት ምሰሶዎችና ሦስት
መቆሚያዎች ያሏቸው ርዝመታቸው ዐሥራ
አምስት ክንድ[ረ] የሆነ መጋረጃዎች በአንድ
በኩል ባለው ደጃፍ ይሁኑ። 15ሦስት ምሰሶ
ዎች ሦስት መቆሚያዎች ያሏቸው ርዝመ
ታቸው ዐሥራ አምስት ክንድ የሆነ መጋረ
ጃዎች በሌላው በኩል ይሁኑ።

16"ለአደባባዩ መግቢያ አራት ምሰሶዎችና
አራት መቆሚያዎች ያሉት ከሰማያዊ፣ ከሐ
ምራዊ፣ ከቀይ ማግና ከቀጭን በፍታ የተፈተለ፣
ጥልፍ ጠላፊ የጠለፈበት ሃያ ክንድ ርዝመት[ሰ]
ያለው መጋረጃ ይሁን። 17በአደባባዩ ዙሪያ
ያሉት ምሰሶዎች ሁሉ የብር ዘንጎች፣ ኩላቦ
ችና የነሐስ መቆሚያዎች ይኑሯቸው። 18አደ
ባባዩ ርዝመቱ አንድ መቶ ክንድ፣ ስፋቱ
አምሳ ክንድ[ሸ] ሆኖ፣ በቀጭኑ ከተፈተለ
ማግ ቁመታቸው አምስት ክንድ[ቀ] የሆነ

27፥3 ዘኍ4፥14፤ 7፥13፤1ነገ7፥40፡45፤2 ነገ12፥13፤1ዜና 28፥17፤ኤር52፥18
27፥6 ዘፀ25፥13
27፥7 ዘፀ25፥14፡28
27፥8 ዘፀ25፥9
27፥9 ዘፀ35፥17፤ 40፥8፡33፤ዘሌ6፥16፡ 26፤ሕዝ40፥14፤ 42፥1
27፥16 ዘፀ40፥33፤ 36፥37
27፥20 ዘፀ25፥6
27፥21 ዘፀ16፥34፤ 25፥37፤28፥43፤ 29፥9፡42፤30፥21፡ 36፤33፥7፤ዘሌ1፥1፤ 3፥17፤6፥26፤8፥3፡ 31፤16፥34፤17፥7፤ ዘኍ1፥1፤18፥23፤ 19፥21፤ 31፥54፤ ኢሱ18፥1፤1ነገ1፥39፤ 1ሳሙ30፥25
28፥1 ዘፀ6፥23፤ 24፥9፤ዘሌ8፥2፡30፤ 21፥1፤ዘኍ18፥1-7፤ ዘዳ18፥5፤1ሳሙ2፥ 28፤መዝ99፥6፤ ዕብ5፥1፡4
28፥2 ቍ40፤ ዘፀ29፥5፡29፤31፥10፤ 35፥19፤39፥1፤ ዘሌ8፥7-9፡30፤ 16፥32፤ ዘኍ20፥ 26-28
28፥3 ዘፀ31፥3፡ 6፤35፥10፡25፡35፤ 36፥1፤ዘዳ34፥9፤ ኢሳ11፥2፤1ቆሮ12፥8 ኤፌ1፥17
28፥4 ቍ15-30፡ 31-35፡37፡39፤ ዘፀ25፥7፤ዘሌ10፥5
28፥5 ዘፀ25፥4
28፥6 ዘፀ25፥7
28፥8 ዘፀ29፥5

መጋረጃዎችና የነሐስም መቆሚያዎች ያሉት
ይሁን። 19ጥቅማቸው ምንም ዓይነት ይሁን፣
ለመገናኛው ድንኳን አገልግሎት የሚውሉ
ዕቃዎች በሙሉ የድንኳኑና የአደባባዩ ካስ
ማዎችም ሁሉ ሳይቀሩ ከነሐስ የተሠሩ
ይሁኑ።

## የመቅረዙ ዘይት

27፥20-21 ተጓ ምብ - ዘሌ 24፥1-3

20"መብራቶቹ ባለማቋረጥ እንዲበሩ
ለመብራቱ የሚሆን ተወቅጦ የተጠለለ
ንጹሕ ዘይት እንዲያመጡልህ እስራኤላ
ውያንን እዘዛቸው። 21በመገናኛው ድንኳን
ውስጥ ከመጋረጃው በስተውጭ ይኸውም
ከምስክሩ ታቦት ፊት ለፊት፣ አሮንና ወንድ
ልጆቹ መብራቶቹን ከምሽት እስከ ንጋት
*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት እንዲበሩ ያድርጉ፤
ይህም በእስራኤላውያን ዘንድ ከትውልድ
እስከ ትውልድ የዘላለም ሥርዐት ይሆናል።

## ልብሰ ተክህኖ

28 "ካህናት ሆነው ያገለግሉኝ ዘንድ
ከእስራኤላውያን መካከል ወንድምህ
አሮንን ከወንዶች ልጆቹ ከናዳብ፣ ከአብ
ዩድ፣ ከአልዓዛርና ከኢታምር ጋር ወደ አንተ
አቅርባቸው። 2ለእርሱም ማዕረግና ክብር
ለመስጠት ለወንድምህ ለአሮን የተቀደሱ
መጐናጸፊያዎችን አብጅለት። 3ካህን ሆኖ
እንዲያገለግለኝ የተለየ ይሆን ዘንድ ጥበብ
ለሰጠኋቸው በዚህ ጕዳይ ላይ ጥበበኛ ለሆኑ
ሰዎች ሁሉ ለአሮን መጐናጸፊያዎችን እንዲ
ሠሩለት ንገራቸው። 4የሚሠሯቸው መጐናጸፊ
ያዎች የደረት ልብስ ኤፉድ ቀሚስ፣ ጥልፍ
ሸሚዝ፣ ጥምጥምና መታጠቂያ ናቸው፤ ካህን
ሆነው ያገለግሉኝ ዘንድ የተቀደሱ መጐና
ጸፊያዎችን ለአሮንና ለወንድ ልጆቹ ይሠ
ራሉ። 5ወርቅ፣ ሰማያዊ፣ ሐምራዊ፣ ቀይ
ማግና እንዲሁም ቀጭን በፍታ ይጠቀሙ።

## ኤፉድ

28፥6-14 ተጓ ምብ - ዘፀ 39፥2-7

6"የጥልፍ ዐዋቂዎች ኤፉዱን ከወርቅ፣
ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊ፣ ከቀይ ማግና በቀ
ጭኑ ከተፈተለ በፍታ ይሥሩት። 7መተሳ
ሰር እንዲችል ሆኖ፣ ዳርና ዳር ከሚገኙት
ከሁለቱ ጐኖች ጋር የተያያዙ ሁለት የት
ከሻ ንጣዮች ይኑሩት። 8በጥበብ የተጠለ
ፈው የወገብ መታጠቂያ ከወርቅ፣ ከሰ
ማያዊ፣ ከሐምራዊ፣ ከቀይ ማግና በቀጭኑ
ከተፈተለ ሐር ከኤፉድ ጋር አንድ ወጥ

[መ]9 በዚህና በቍጥር 11 ላይ ወደ 46 ሜትር ያህል ነው።
[ሠ]12 በዚህና በቍጥር 13 ላይ ወደ 23 ሜትር ያህል ነው።
[ረ]14 በዚህና በቍጥር 15 ላይ ወደ 6.9 ሜትር ያህል ነው።
[ሰ]16 ወደ 9 ሜትር ያህል ነው።
[ሸ]18 ርዝመቱ 46 ሜትር፣ ወርዱ 23 ሜትር ያህል ነው።
[ቀ]18 ወደ 2.3 ሜትር ያህል ነው።

ሆኖ የተሠራ ይሁን።
9“ሁለት የመረግድ ድንጋዮች ውሰድና
የእስራኤልን ልጆች ስሞቻቸውን ቅረጽባ
ቸው። 10እንደ ልደታቸው ቅደም ተከተል
ስድስቱን ስሞች በአንዱ ድንጋይ ላይ የቀሩ
ትንም ስሞች በሌላው ላይ ቅረጽባቸው።
11የቅርጽ ሠራተኛ ማኅተም እንደ ሚቀርጽ
የእስራኤልን ልጆች ስም በሁለቱ ድንጋዮች
ላይ ቅረጽ፤ ከዚያም ድንጋዮቹን በወርቅ
ፈርጥ ክፈፋቸው፤ 12ለእስራኤል ልጆች
መታሰቢያ ድንጋዮች ይሆኑ ዘንድ በኤፉዱ
ትከሻ ላይ ካሉት ንጣዮች ጋር አያይዛቸው፤
*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት መታሰቢያ እንዲ
ሆኑ አሮን ስሞቹን በትከሻው ላይ ይሸከ
ማቸው። 13የወርቅ ፈርጦችን አብጅ፣
14እንደ ገመድ ያሉ ሁለት በንጹሕ ወርቅ
የተጐነጐኑ ድሪዎችን አብጅተህ ከፈርጡ
ጋር አያይዛቸው።

## የደረት ኪስ

28፥15-28 ተጓ ምብ - ዘፀ 39፥8-21

15“የፍርድ መስጫውን የደረት ኪስ ብልኀ
ሠራተኛ እንደሚሠራው አድርገህ አብጀው፤
ልክ እንደ ኤፉዱ ከወርቅ፣ ከሐምራዊ፣
ከቀይ ማግና በቀጭኑ ከተፈተለ በፍታ አብ
ጀው። 16ርዝመቱ አንድ ስንዝር፣ ስፋቱ
አንድ ስንዝር[*] ሆኖ ባለ አራት ማእዘንና
በድርቡ የታጠፈ ይሁን። 17ከዚያም በላዩ
ላይ በአራት ረድፍ የከበሩ ድንጋዮች አድ
ርግበት፤ በመጀመሪያው ረድፍ ሰርዲዮን፣
ቶጳዝዮን፣ የሚያበረቀርቅ ዕንቁ፤ 18በሁለተ
ኛውም ረድፍ በሉር፣ ሰንፔር[†]፣ አልማዝ፤
19በሦስተኛው ረድፍ ያክንት፣ ኬልቄዶን፣
አሜቴስጢኖስ፤ 20በአራተኛውም ረድፍ
ቢረሌ፣ መረግድና ኢያስጴድ[‡] አድርግበት፤
በወርቅ ፈርጥም ክፈፋቸው። 21የዐሥራ ሁለቱ
ነገዶች ስሞች እንደ ማኅተም የተቀረጸባ
ቸው ለእያንዳንዱ የእስራኤል ልጆች ስም
ዐሥራ ሁለት ድንጋዮች ይሁኑ።
22“ለደረት ኪሱ ከንጹሕ ወርቅ እንደ
ገመድ ሆኖ የተጌጠ ጕንጕን አብጅለት።
23ለእርሱም ሁለት የወርቅ ቀለበቶች አብ
ጅተህ ከደረት ኪሱ ሁለት ጎኖች ጋር አያ
ይዘው። 24ሁለቱን የወርቅ ጕንጕኖች በደረት
ኪሱ ጐኖች ላይ ካሉት ቀለበቶች ጋር
አያይዛቸው። 25ሌሎቹን የጕንጕን ጫፎች
በፊት ላይ ካለው ኤፉድ በትከሻው ላይ
ካሉት ንጣዮች ጋር በማጋጠም ከሁለቱ
የወርቅ ፈርጦች ጋር አያይዛቸው። 26ሁለት
የወርቅ ቀለበቶች አበጅተህ ከኤፉዱ ቀጥሎ
ባለው በውስጠኛ ጠርዝ ላይ፣ በሌላ በኩል
ካሉት ሁለት የደረት ኪስ ጕኖች ጋር አያ
ይዛቸው። 27ሁለት ተጨማሪ የወርቅ ቀለበቶች
አበጅተህ ከኤፉዱ መታጠቂያ ከፍ ብሎ
ከመጋጠሚያው አጠገብ ካለው በኤፉዱ
ፊት ለፊት፣ በትከሻ ላይ ካሉት ንጣዮች
ግርጌ ጋር አያይዘው። 28የደረት ኪሱም ቀለ
በቶች፣ የደረት ኪሱ ከኤፉዱ ጋር እንዳይላ
ቀቅ፣ ከመታጠቂያው ጋር በማገናኘት በሰ
ማያዊ ገመድ ከኤፉዱ ቀለበቶች ጋር ይያ
ያዙ።
29“አሮን ወደ መቅደሱ በሚገባበት ጊዜ
*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ለዘላለም መታሰ
ቢያ ይሆን ዘንድ የእስራኤልን ልጆች
ስሞች በፍርድ መስጫው ደረት ኪስ በልቡ
ላይ ይሸከም። 30ወደ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት
በሚገባበት ጊዜ በአሮን ልብ ላይ ይሆኑ
ዘንድ ኡሪሙንና ቱሚሙን በደረት ኪሱ
አድርግ፤ ስለዚህ አሮን ሁልጊዜ ለእስራ
ኤላውያን የፍርድ መስጫውን *በእግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) ፊት በልቡ ላይ ይሸከማል።

## ሌሎቹ አልባሳት

28፥31-43 ተጓ ምብ - ዘፀ 39፥22-31

31“የኤፉዱ ቀሚስ ሙሉ በሙሉ ከሰማ
ያዊ ጨርቅ ይሁን፤ 32ከላይ በኩል በመካከሉ
ዐንገትጌ አድርገህ አብጀው፤ እንዳይቀደድም
በማስገቢያው ዙሪያ እንደ ክሳድ ያለ ዝም
ዝም ጠርዝ[§] ሥራለት። 33በጨርቁ ጠርዝ
ዙሪያ ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊና ከቀይ ማግ
ሮማኖቹን፣ በመካከሉም የወርቅ ሻኵራ
ዎችን አብጅ። 34የወርቅ ሻኵራዎቹና ሮማ
ኖቹ በጨርቁ ጠርዝ ዙሪያ በመፈራረቅ
ይሆናሉ። 35አሮንም በአገልግሎቱ ጊዜ ይህን
መልበስ አለበት፤ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት
ወደ መቅደሱ በገባና ከመቅደሱ ሲወጣ
እንዳይሞት የሻኵራዎቹ ድምፅ ይሰማል።
36“ከንጹሕ ወርቅ ዝርግ ሳሕን አበጅ
ተህ፣ “ቅዱስ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ)” በማ
ለት በማኅተም ላይ እንደሚቀረጽ ቅረጸው።
37ከመጠምጠሚያው ጋር እንዲያያዝ ሰማ
ያዊ ፈትል እሰርበት፤ እርሱም በመጠ
ምጠሚያው ፊት በኩል ይሁን። 38ይህም
በአሮን ግንባር ላይ ይሆናል፤ እስራኤላውያን
ለይተው በሚያቀርቧቸው በማናቸውም የተ
ቀደሱ ስጦታዎች ውስጥ ያለውን በደል
ይሸከማል፤ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ተቀባ
ይነት እንዲኖራቸው ሁልጊዜ በአሮን ግን
ባር ላይ ይሆናል።
39“ሸሚዙን ከቀጭን በፍታ ሥራ፤ መጠ
ምጠሚያውንም ከቀጭን በፍታ አብጀው፤
መታጠቂያውንም ጥልፍ ጠላፊ የሠራው
ይሁን። 40የአሮን ወንድ ልጆች ክብርና

[*]16 ወደ 22 ሴንቲ ሜትር ያህል ነው። [†]18 ወይም፣ *ላፒስ ላዙሊ* [‡]20 የእነዚህ የከበሩ ማዕድኖች ትክክለኛ ማንነት በትክ ክል አይታወቅም። [§]32 በዕብራይስጡ የዚህ ቃል ትክክለኛ ፍቺው አይታወቅም።

28፥9 መኃ8፥6፤ ኢሳ49፥16፤ሐጌ2፥23
28፥12 ቍ29፤ ዘፀ30፥16፤ዘኍ10፥10፤ 31፥54፤ዘዳ33፥12፤ ኢዮ31፥36፤ ኢሱ4፥7፤ዘካ6፥14
28፥15 ዘፀ25፥7
28፥17 ሕዝ28፥13፤ ራእ21፥19-20
28፥20 ሕዝ1፥16፤ 10፥9፤ዳን10፥6
28፥21 ኢሱ4፥8፤ ራእ21፥12
28፥29 ቍ43
28፥30 ዘሌ8፥8፤ ዘኍ27፥21፤ዘዳ33፥8፤ 1ሳሙ28፥6፤ ዕዝ2፥63፤ነህ7፥65
28፥33 ዘኍ13፥23፤ 1ሳሙ14፥2፤1ነገ7፥18፤ማሕ4፥3፤ ኤር52፥22፤ ኢል1፥12፤ሐጌ2፥19
28፥36 ቍ37፤ ዘፀ29፥6፤ዘሌ8፥9፤ ዘካ14፥20
28፥38 ዘፍ32፥20፤ ዘሌ5፥1፤10፥17፤ 16፥22፤22፥9፡16፡20፡27፤23፥11፤ዘኍ18፥1፤ ኢሳ53፥5፡6፡11፤ ኢሳ56፥7፤ሕዝ4፥4-6፤ዕብ9፥28፤ 1ጴጥ2፥24
28፥39 ቍ4፤ ዘፀ29፥6፤ዘሌ16፥4፤ ሕዝ24፥17፡23፤ 44፥18
28፥40 ቍ2፡4፤ ዘፀ29፥8-9፤39፥41፤ 40፥14፤ዘሌ8፥13

ማዕረግ እንዲኖራቸው ሸሚዞችን፣ መታጠቂያዎችን፣ የራስ ማሰሪያዎችን አብጅላቸው:: 41እነዚህን ልብሶች ለአሮንና ለወንድ ልጆቹ ካለበስህ በኋላ ቅባቸው፤ ካናቸው፤ ካህናት ሆነው ያገለግሉኝም ዘንድ ቀድሳቸው::

42"ከወገብ ጀምሮ እስከ ጭን የሚደርስ ሰውነትን የሚሸፍን ከበፍታ የተሠራ የውስጥ ቁምጣ አብጅ:: 43አሮንና ወንድ ልጆቹ ወደ መገናኛው ድንኳን በሚገቡበት ጊዜ ወይም በመቅደሱ ለማገልገል ወደ መሠዊያው ሲቀርቡ፣ በደል ፈጽመው እንዳይሞቱ እነዚህን መልበስ አለባቸው::

"ለአሮንና ለትውልዶቹ ይህ የዘላለም ሥርዐት ይሆናል::

## የካህናት መቀደስ

29፥1-37 ተጓ ምብ - ዘሌ 8፥1-36

29 "ካህናት ሆነው እንዲያገለግሉኝ ትቀድሳቸው ዘንድ የምታደርገው ይህ ነው፤ ነውር የሌለባቸው አንድ ወይፈንና ሁለት አውራ በጎች ውሰድ፤ 2እርሾ ከሌለው ከምርጥ የስንዴ ዱቄት ቂጣ፣ በዘይት የተለወሰ የቂጣ እንጎቻና በዘይት የተቀባ ኅብስት ጋግር:: 3በሌማት ላይ አድርገህ ከወይፈኑና ከሁለቱ አውራ በጎች ጋር አቅርባቸው:: 4ከዚያም አሮንና ወንድ ልጆቹን ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ በማምጣት በውሃ እጠባቸው:: 5ልብሶቹን ወስደህ ለአሮን አልብሰው፤ ሸሚዝ፣ የኤፉድ ቀሚስ፣ ኤፉዱንና የደረት ኪሱን አልብሰው፤ ኤፉዱን በእርሱ ላይ በጥበብ በተሠራ መታጠቂያ እሠረው:: 6መጠምጠሚያውን በራሱ ላይ በማድረግ የተቀደሰውን አክሊል ከመጠምጠሚያው ጋር አያይዘው:: 7ቅብዐ ዘይት ወስደህ በራሱ ላይ በማፍሰስ ቅባው:: 8ወንዶች ልጆቹን አምጥተህ ሸሚዞች አልብሳቸው:: 9የራስ ማሰሪያዎችንም አድርግላቸው'፤ ከዚያም አሮንንና ወንዶች ልጆቹን መታጠቂያዎችን አስታጥቃቸው፤ ክህነት የዘላለም ሥርዐት ይሆንላቸዋል፤ በዚህም መንገድ አሮንንና ወንዶች ልጆቹን ትክናቸዋለህ::

10"ወይፈኑን በመገናኛው ድንኳን ፊት ለፊት በማምጣት አሮንና ወንዶች ልጆቹ በራሱ ላይ እጆቻቸውን ይጫኑበት:: 11በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ላይ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት እረደው:: 12ከወይፈኑ ደም ወስደህ በመሠዊያው ቀንዶች ላይ በጣቶችህ አድርግበት፤ የቀረውንም ከመሠዊያው ሥር አፍስሰው:: 13ከዚያም በሆድ ዕቃዎች ያለውን ስብ ሁሉ፣ የጉበቱን መሸፈኛና ሁለቱንም ኵላሊቶች በዙሪያቸው ካለው ስብ ጋር ወስደህ በመሠዊያው ላይ አቃጥላቸው::

28፥41 ዘፀ29፥7-9፤ 30፥30፤40፥13፥15፤ ዘሌ4፥3፤6፥20፡22፤ 8፥1-36፤10፥7፤ 21፥12፤ዘኍ3፥3፤ 35፥25፤ዕብ7፥28
28፥42 ዘሌ6፥10፤ 16፥4፡23፤ሕዝ44፥18
28፥43 ቍ29፤ ዘፀ27፥21፤30፥20፡ 21፤27፥21ዘሌ16፥ 13፤22፥9፤ዘኍ1፥51፤ 4፥15፡20፤18፥22
29፥1 ቍ21፡44፤ ዘሌ20፥7፤ኢሱ3፥5፤ 1ዜና15፥12፤ ሕዝ43፥23
29፥2 ቍ23፤ ዘሌ2፥1፡4፤6፥19-23፤ ዘኍ6፥15
29፥3 ቍ15፡19
29፥4 ዘፀ40፥12፤ ዘሌ14፥8፤16፥4፤ ዕብ10፥22
29፥5 ዘፀ28፥2፡8
29፥6 ዘፀ28፥36፡ 39፤ኢሳ3፥23፤ዘካ3፥5
29፥7 ቍ21፤ ዘፀ28፥41፤30፥25፡ 30፡31፤37፥29፤ 40፥9፤ዘሌ21፥10፤ 1ሳሙ10፥1፤ 1ነገ1፥39፤መዝ89፥20፤ 133፥2፤141፥5 29፥8 ዘፀ28፥4፤ ዘሌ16፥4
29፥9 ዘፀ28፥40፤ 27፥21፤40፥15፤ ዘኍ3፥10፤18፥7፤25፥13፤ ዘዳ18፥5፤መሳ17፥5፤ 1ሳሙ2፥30፤1ነገ12፥31
29፥10 ቍ19፤ ዘሌ1፥4፤4፥15፤ 16፥21፤ዘኍ8፥12
29፥11 ዘሌ1፥5፡ 11፤4፥24፤6፥16፡ 25፤14፥13
29፥12 ዘፀ27፥2፤ ዘሌ4፥7፤9፥9
29፥13 ቍ22፤ዘፀ 12፥9፤ዘሌ1፥8፤3፥3፡ 5፡9፤4፥10፤6፥12፤7፥3፡ 5፡31፤9፥10፤ዘኍ18፥ 17፤1ሳሙ2፥15፤1ነገ8 ፥64፤2ዜና7፥7፤29፥35፤ 35፥14፤ኢሳ43፥24፤ሕዝ 44፥15፤
29፥14 ዘሌ4፥12፡ 21፤16፥27፤ዘኍ19፥3- 5፤ናሆ3፥6፤ሚል2፥ 3፤ዕብ13፥11
29፥15 ቍ3፡10፤ ዘሌ3፥2፤2ዜና29፥23
29፥17 ዘሌ1፥9፡13
29፥18 ዘፍ8፥21፤ 2ቆሮ2፥15
29፥19 ቍ3፡10
29፥20 ቍ16፤ ዘሌ1፥5፡11፤3፥2፤14፥1 4፡25
29፥21 ቍ1፡7፤ ዕብ9፥22

14ነገር ግን የወይፈኑን ሥጋ፣ ቆዳውንና የማይበላውን አሰስ ገሠስ ሥጋ ከሰፈር ውጭ አቃጥለው፤ የኀጢአት መሥዋዕት ነው::

15"ከሁለቱ አውራ በጎች አንዱን ወስደህ፣ አሮንና ወንዶች ልጆቹ በራሱ ላይ እጃቸውን ይጭኑበታል:: 16አውራውንም በግ እረደው፤ ደሙንም ወስደህ በመሠዊያው ላይ ዙሪያውን እርጨው:: 17አውራ በጉን በየብልቱ ቈራርጠህ፣ የሆድ ዕቃውንና እግሮቹን አጥበህ ከራሱና ከሌሎቹ ቁርጥራጭ ብልቶች ጋር አኑረው:: 18ከዚያም አውራ በጉን በሙሉ በመሠዊያው ላይ አቃጥለው፤ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) የሚቃጠል መሥዋዕት ጣፋጭ መዓዛና *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) በእሳት የሚቀርብ መሥዋዕት ነው::

19"ሌላውን አውራ በግ ወስደህ አሮንና ወንዶች ልጆቹ በራሱ ላይ እጆቻቸውን ይጭኑበታል:: 20አውራውንም በግ እረደው፤ ከደሙም ወስደህ የአሮንንና የወንዶች ልጆቹን የቀኝ ጆሮዎቻቸውን ጫፍ የቀኝ እጆቻቸውን አውራ ጣቶች፣ የቀኝ እግራቸውንም አውራ ጣቶች ቅባቸው፤ ከዚያም ደሙን በመሠዊያው ላይ ዙሪያውን እርጨው:: 21በመሠዊያው ላይ ካለው ደምና ከቅብዐ ዘይቱ ወስደህ በአሮንና በልብሶቹ ላይ እንዲሁም በወንዶች ልጆቹና በልብሶቻቸው ላይ እርጨው:: ከዚያም እርሱና ወንዶች ልጆቹ እንዲሁም ልብሶቻቸው የተቀደሱ ይሆናሉ::

22"ከዚህ አውራ በግ ስቡን፣ ላቱን፣ በሆድ ዕቃው ውስጥ ያለውን ስብ፣ የጉበቱን ሽፋን፣ ሁለቱን ኵላሊቶችና በዙሪያቸው ያለውን ስብና ቀኙን ወርች ውሰድ፤ ይህ የክህነት አውራ በግ ነው:: 23*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት በሌማት ካለው ያለ እርሾ ከተጋገረው ቂጣ፣ ዳቦ፣ በዘይት የተሠራ እንጎቻና ኅብስት ውሰድ:: 24እነዚህን ሁሉ በአሮንና በወንዶች ልጆቹ እጆች ላይ በማኖር እንደ ሚወዘወዝ መሥዋዕት *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ወዝውዛቸው:: 25ከዚያም ከእጃቸው ወስደህ ከሚቃጠለው መሥዋዕት ጋር *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) መልካም መዓዛ እንዲሆን በመሠዊያው ላይ አቃጥለው፤ ይህም *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) በእሳት የሚቃጠል መሥዋዕት ነው:: 26ለአሮን ክህነት የአውራ በጉን ፍርምባ ከወሰድህ በኋላ እንደሚወዘወዝ መሥዋዕት *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ወዝውዘው ይህም የአንተ ድርሻ ይሆናል::

29፥22 ቍ13 29፥24 ዘሌ7፥30፤ 9፥21፤10፥15፤14፥12፤ 23፥11፡20፤ ዘኍ6፥20፤8፥11፡13፡15 29፥25 ቍ18 29፥26 ዘሌ7፥31፡34

'9 ዕብራይስጡ፣ *የሰላም መሥዋዕት አድርግላቸው* ይላል::

27“ለአሮንና ለወንዶች ልጆቹ ለክህነት
የሆኑትን የአውራውን በግ ብልቶች፣ ቀድሳ
ቸው። የተወዘወዘውን ፍርምባና የቀረበ
ውን ወርች 28ለአሮንና ለወንዶች ልጆቹ
የዘወትር የእስራኤላውያን ድርሻ የሚሆነው
ይህ ነው፤ ከኅብረት መሥዋዕታቸው[ኘ] እስ
ራኤላውያን ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የሚያቀ
ርቡት ነው።

29“የአሮን የተቀደሱ ልብሶች ለትውል
ዶቹ ይሆናሉ፤ ይኸውም በእነርሱ ይቀቡና
ክህነትን ይቀበሉ ዘንድ ነው። 30ካህን በመ
ሆን እርሱን የሚተካውና በመቅደሱ ለማገ
ልገል ወደ መገናኛው ድንኳን የሚመጣው
ወንድ ልጅ ሰባት ቀን ይለብሳቸዋል።

31“የክህነቱን አውራ በግ ወስደህ ሥጋ
ውን በተቀደሰ ስፍራ ቀቅለው። 32አሮንና
ወንዶች ልጆቹ በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ
ላይ የአውራውን በግ ሥጋና በሌማት ያለ
ውን ዳቦ ይብሉ። 33ለክህነታቸውና ለመቀ
ደሳቸው ማስተስረያ የሆኑትን እነዚህን
መሥዋዕቶችን ይብሉ፤ የተቀደሱ ስለ ሆኑ
ሌላ ማንም አይብላቸው። 34ከክህነቱ የአውራ
በግ ሥጋ ወይም ከቂጣው እስከ ንጋት ድረስ
ቢተርፍ አቃጥለው፤ የተቀደሰ ስለሆነ መበ
ላት የለበትም።

35“ክህነታቸውን በሰባት ቀን በመፈጸም
ለአሮንና ለወንዶች ልጆቹ ያዘዝሁህን ሁሉ
አድርግላቸው። 36ለማስተስረያ የሚሆን አንድ
ወይፈን የኀጢአት መሥዋዕት አድርገህ
በየዕለቱ ሠዋ፤ ለመሠዊያውም ማስተስረያ
በማቅረብ መሠዊያውን አንጻው፤ ትቀድሰ
ውም ዘንድ ቅባው። 37ለሰባት ቀን ለመሠ
ዊያው ማስተስረያ በማድረግ ቀድሰው፤
ከዚያም መሠዊያው እጅግ የተቀደሰ ይሆ
ናል፤ የሚነካውም ሁሉ የተቀደሰ ይሆናል።

38“በየዕለቱ ያለማቋረጥ በመሠዊያው ላይ
የምታቀርበው ይህ ነው፤ ዓመት የሞላቸው
ሁለት የበግ ጠቦቶች፤ 39አንዱን በማለዳ፣
ሌላውን በምሽት አቅርብ። 40ከመጀመሪያው
የበግ ጠቦት ጋር የኢፍ መስፈሪያ አንድ
ዐሥረኛ[አ] ምርጥ ዱቄትን ተወቅጦ ከተጠ
ለለ ሩብ ኢፍ[ከ] ዘይት ጋር ለውስና ሩብ
ኢን ወይንን ደግሞ የመጠጥ መሥዋዕት በማ
ድረግ አቅርብ። 41ሌላውን የበግ ጠቦት
በማለዳው እንደ ቀረበው ተመሳሳይ ከሆነው
የእህልና የመጠጥ መሥዋዕት ጋር በምሽት
ሠዋው፤ ይህም ጣፋጭ መዓዛና ለእግዚ
አብሔር (ያህዌ) በእሳት የሚቀርብ መሥዋዕት
ነው።

42“ይህ የሚቃጠል መሥዋዕት በእግዚ
አብሔር (ያህዌ) ፊት በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ
ላይ በሚመጡት ትውልዶች ዘወትር ይደረ
ጋል፤ በዚያ እገናኝሃለሁ፤ እናገርሃለሁም፤
43በዚያ ደግሞ ከእስራኤላውያን ጋር እገና
ኛለሁ፤ ስፍራውም በክብሬ ይቀደሳል።

44“ስለዚህ የመገናኛው ድንኳንና መሠዊ
ያውን እኔ እቀድሳለሁ፤ ካህናት ሆነው
እንዲያገለግሉኝ አሮንና ወንድ ልጆቹን
እቀድሳለሁ። 45ከዚያም በእስራኤላውያን
መካ ከል እኖራለሁ፤ አምላካቸውም (ኤሎ
ሂም) እሆናለሁ። 46በመካከላቸውም እኖር
ዘንድ ከግብፅ ያወጣኋቸው እኔ አምላካቸው
እግዚአብሔር (ያህዌ) መሆኔን ያውቃሉ፤ እኔ
እግዚአብሔር (ያህዌ) አምላካቸው ነኝ።

### የዕጣን መሠዊያ

30፥1-5 ተጓ ምብ - ዘፀ 37፥25-28

30 ዕጣን የሚጤስበት መሠዊያ ከግ
ራር ዕንጨት ሥራ። 2ርዝመቱና
ጐኑ ባለ አንድ አንድ ክንድ[ኸ] የሆነ ከፍታ
ውም ሁለት ክንድ የሆነ አራት ማእዘን
ይሁን፤ ከመሠዊያው ጋር አንድ ወጥ የሆኑ
ቀንዶች ይኑሩት። 3ላዩን፣ ጐኖቹን ሁሉና
ቀንዶቹን በንጹሕ ወርቅ ለብጣቸው፤ ዙሪያ
ውን የወርቅ ክፈፍ አብጅለት። 4መሠዊያ
ውን ለመሸከም የሚያገለግሉትን መሎጊያዎች
የሚይዙ፣ ከክፈፉ በታች ትይዩ የሆኑ
ሁለት የወርቅ ቀለበቶችን ለመሠዊያው
አብጅ። 5መሎጊያዎቹንም ከግራር እንጨት
ሠርተህ በወርቅ ለብጣቸው። 6መሠዊያውን
ከመጋረጃው ፊት ለፊት፣ ይኸውም ከምስ
ክሩ ታቦት ፊት፣ ከምስክሩ በላይ ካለው
እኔ አንተን ከምገናኝበት ከስር የት መክ
ደኛው ፊት አስቀምጠው።

7“አሮን መብራቶቹን በሚያዘጋጅበት
ጊዜ፣ በየማለዳው ደስ የሚያሰኝ ሽታ ዕጣን
በመሠዊያው ላይ ያጢስ። 8ምሽት ላይ
መብራቶቹን በሚያበራበትም ጊዜ ዕጣኑን
ማጠን አለበት፤ ይኸውም በሚመጡት ትው
ልዶች ሁሉ ዕጣኑ በእግዚአብሔር (ያህዌ)
ፊት ዘወትር እንዲጤስ ነው። 9በዚህም መሠ
ዊያ ላይ ሌላ ዕጣን ወይም ሌላ የሚቃጠል
መሥዋዕት ወይም የእህል መሥዋዕት አታ
ቅርብ፤ የመጠጥ መሥዋዕትም አታፍስበት።
10አሮን በዓመት አንድ ጊዜ በቀንዶቹ ላይ
ማስተስረያ ያደርግበታል፤ ይህ ዓመታዊ
ማስተስረያ በሚመጡት ትውልዶች ሁሉ

29፥27 ዘፀ22፥29፤ ዘሌ7፥31፡34፤ዘኍ18፥11፡12፤ዘዳ18፥3
29፥28 ቀኍ22-27፤ ዘሌ7፥30፡34፤10፥15
29፥29 ዘፀ28፥2፤ ዘሌ16፥4፤ዘኍ20፥28
29፥30 ዘሌ6፥22፤ ዘኍ 3፥3፤20፥28
29፥31 ዘሌ7፥37፤ 10፥14፤ዘኍ19፥9፤ 2ዜና13፥9፤ሕዝ42፥13
29፥32 ማቴ12፥4
29፥33 ዘሌ22፥10፡13
29፥34 ዘፀ12፥10
29፥36 ቀኍ33፡37፤ ዘፀ30፥10፤40፥10፤ ዘሌ1፥4፤4፥20፤16፥16፤ ዘኍ6፥11፤7፥10፤ 8፥12፡19፤16፥46፤ 25፥13፤2ዜና29፥24፤ዕብ10፥11
29፥37 ዘፀ30፥28-29፤40፥10፤ሕዝ 43፥25፤ማቴ23፥19
29፥38 ዘሌ23፥2፤ ዘኍ28፥3-8፤1ዜና 16፥40፤2ዜና8፥13፤ ሕዝ46፥13-15፤ ዳን12፥11
29፥39 ዘኍ28፥4፡ 8፤1ነገ18፥36፤2ዜና 13፥11፤ዕዝ3፥3፤መዝ 141፥2፤ዳን9፥21
29፥40 ዘፍ35፥14፤ ዘፀ30፥24፤ዘሌ 23፥37፤ዘኍ15፥4፤ 28፥5፤2ነገ16፥13
29፥41 ዘሌ2፥1፤ 5፥13፤10፥12፤ ዘኍ4፥16፤6፥17፤ 1ነገ18፥64፤18፥29፡ 36፤2ነገ3፥20፤16፥15፤ ዕዝ9፥4፡5፤መዝ141፥2፤ ኢሳ43፥23፤ዳን9፥21
29፥42 ቀኍ43፤ዘፀ 25፥42፤26፥1፡22፤ 27፥21፤30፥8፡10፥21፡3 1፤31፥13፤33፥9፡11፤ ዘኍ7፥89፤ሕዝ 46፥15
29፥43 ዘፀ33፥18፤ 40፥34፤ዘሌ9፥6፡ 1ነገ8፥11፤2ዜና5፥ 14፤7፥2፤መዝ26፥8፤ 85፥9፤ሕዝ1፥28፤ 43፥5፤ ሐጌ1፥8፤2፥7
29፥44 ቀኍ1
29፥45 ዘፍ17፥7፤ ዘፀ25፥8፤ዘኍ35፥34፤ ዮሐ14፥17፤ሮሜ 8፥10፤ 2ቆሮ6፥16
29፥46 ዘፍ17፥7፤ ዘፀ6፥6፤19፥4-6፤ ዘዳ5፥6፤መዝ114፥1፤ ሐጌ2፥5
30፥1 ዘፀ25፥6፤ 37፥29፤40፥5፡26፤ ዘኍ4፥11፤1ነገ6፥20፤ ሕዝ41፥22፤25፥6፤ 37፥29፤ሉቃ1፥11፤ ዕብ9፥4፤ራእ8፥3

30፥2 ዘፀ27፥2፤ ራእ9፥13 30፥3 ዘፀ25፥11 30፥4 ዘፀ25፥12
30፥5 ዘፀ25፥13 30፥6 ዘፀ25፥22፤26፥34 30፥7 ዘፀ25፥6፤
40፥27፤ዘኍ3፥10፤ዘዳ33፥10፤1ሳሙ2፥28፤1ዜና6፥49፤2ዜና2፥4፤
26፥18፤29፥7 30፥8 ዘፀ25፥37፤29፥42 30፥9 ዘሌ10፥1፤ዘኍ
16፥7፡40 30፥10 ዘፀ29፥14፡ 42፤ዘሌ4፥3፤6፥25፤ 7፥7፤8፥2፡
14፤9፥7፤ 16፥2፤16፥18-19፡30፤ 23፥27፡28፤25፥9፤ ዘኍ6፥11

[ኘ]28 በትውፊት፣ *የሰላም መሥዋዕት* በመባል ይታወቃል
[አ]40 ይህ ምናልባት 2 ሊትር ያህል ነው።
[ከ]40 ይህ ምናልባት 1 ሊትር ያህል ነው።
[ኸ]2 ርዝመቱና ጐኑ 0.5 ሜትር፣ ከፍታው 0.9 ሜትር ያህል ነው።

ለማስተስረያ ከሚሆን የኀጢአት መስዋዕት
ደም ጋር መደረግ አለበት፤ ይህም ለእግዚ
አብሔር (ያህዌ) እጅግ ቅዱስ ነው።"

## የማስተስረያ ገንዘብ

11ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን
አለው፤ 12"የእስራኤላውያንን ጠቅላላ ቈጠራ
በምታደርግበት ጊዜ እያንዳንዱ ሰው በሚ
ቈጠርበት ወቅት ለሕይወቱ ቤዛ የሚሆን
ዎጆ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) መክፈል አለበት፤
በዚህም ዐይነት ስትቈጥራቸው በእነርሱ
ላይ መቅሠፍት አይመጣም። 13ማንም ወደ
ተቈጠሩት ዘንድ የሚያልፍ ሃያ አቦሊ
በሚመዝን በመቅደሱ ሰቅል ሚዛን ግማሽ
ሰቅል[ሠ] መስጠት አለበት፤ ይህ ግማሽ ሰቅል
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የሚቀርብ መሥዋዕት
ነው። 14ዕድሜያቸው ሃያ ዓመትና ከሃያ
በላይ ሆኖ ወደ ተቈጠሩት ያለፉት ሁሉ፣
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) መሥዋዕት ማቅረብ
አለባቸው። 15ለሕይወታችሁ ማስተስረያ እን
ዲሆን ለእግዚአብሔር (ያህዌ) መሥዋዕት በም
ታቀርቡበት ጊዜ ባለጠጋው ከግማሽ ሰቅል
በላይ፣ ድኻውም አጕድሎ አይስጥ። 16የማስ
ተሰረያውን ገንዘብ ከእስራኤላውያን ተቀብ
ለህ ለመገናኛው ድንኳን አገልግሎት አው
ለው፤ ለሕይወታችሁ ማስተስረያ በማድረግ
በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት የእስራኤላውያን
ማስተስረያ ይሆናል።"

## የመታጠቢያ ሰን

17ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን
አለው፤ 18"ለመታጠቢያ ከናስ ማስቀመጫው
ጋር የናስ ሰን አብጅ፤ በመገናኛው ድንኳንና
በመሠዊያው መካከል አስቀምጠህ ውሃ
አድርግበት። 19አሮንና ወንዶች ልጆቹ በው
ስጡ ባለው ውሃ እጃቸውንና እግራቸውን
ይታጠቡበታል። 20ወደ መገናኛው ድንኳን
በሚገቡበት ጊዜ ሁሉ እንዳይሞቱ በውሃ
ይታጠቡ፤ እንዲሁም ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
የእሳት መሥዋዕት ለማቅረብ ወደ መሠዊያው
ለማገልገል በሚቀርቡበት ጊዜ፣ 21እንዳይ
ሞቱ እጃቸውንና እግራቸውን ይታጠባሉ፤
ይህም በሚመጡት ትውልዶች ሁሉ ለአሮንና
ለትውልዶቹ የዘላለም ሥርዐት ይሆናል።"

## ቅብዐ ዘይት

22ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን
አለው፣ 23"ምርጥ ቅመሞችን፣ አምስት
መቶ ሰቅል[ዐ] ፈሳሽ ከርቤ፣ ግማሽ ይኸውም
ሁለት መቶ አምሳ ሰቅል ጣፋጭ ቀረፋ፣ ሁለት
መቶ አምሳ ሰቅል ጠጅ ሣር፣ 24አምስት
መቶ ሰቅል ብርጕድ ውሰድ፤ ሁሉም እንደ
መቅደሱ ሰቅልና አንድ የኢን መስፈሪያ[ዘ]

30፥12 ዘፀ38፥25፡26፤ዘኍ1፥2፡49፤4፥2፡29፤14፥29፡12፤26፥2፤31፥26፡50፤ዘዳ28፥58-61፤2ሳሙ24፥1፤24፥13፤1ነገ8፥37፤2ነገ12፥4፤ማቴ20፥28
30፥13 ቍ24፤ ዘፀ38፥24፡26፤ ዘሌ5፥15፤27፥3፡25፤ ዘኍ3፥47፤7፥13፤18፥16፤ሕዝ4፥10፤45፥12፤ማቴ17፥24
30፥14 ዘፀ38፥26፤ ዘኍ1፥3፡18፤14፥29፤26፥2፤32፥11፤ 2ዜና25፥5
30፥15 ምሳ22፥2፤ ኤፌ6፥9
30፥16 ቍ12፤ ዘፀ38፥25-28፤ 2ዜና24፥5፤ዘኍ31፥54
30፥18 ዘፀ31፥9፤35፥16፤38፥8፤39፥39፤40፥7፡30፤ 1ነገ7፥38፤2ዜና4፥6
30፥19 ዘፀ29፥4፤40፥12፡31-32፤ዘሌ8፥6፤መዝ26፥6፤ዮሐ13፥10፤ዕብ10፥22
30፥20 ዘፀ28፥43
30፥21 ዘፀ27፥21፤29፥42
30፥23 ዘፍ43፥11፤37፥25፤ምሳ7፥17፤ማሕ4፥14፤ኢሳ43፥24፤ኤር6፥20
30፥24 ቍ13፤ መዝ45፥8፤ሕዝ27፥19
30፥25 ቍ35፤ዘፀ29፥7፤37፥29፤1ዜና9፥30፤1ሳሙ9፥16
30፥26 ዘፀ40፥9፤ ዘሌ8፥10፤ዘኍ7፥1
30፥29 ዘፀ29፥37፤ ዘሌ6፥18፡27፤8፥10-11፤ማቴ23፥17
30፥30 ዘፀ28፥41፤29፥7፤ዘሌ8፥2፡12፡30፤10፥7፤16፥32፤21፥10፡12፤1ዜና15፥12፤መዝ133፥2
30፥31 ዘፀ29፥7፡42
30፥32 ቍ25፡37
30፥33 ቍ38፤ ዘፍ17፥14
30፥34 ማሕ3፥6
30፥35 ቍ25፤ ዘፀ25፥6
30፥36 ቍ32፤ ዘፀ25፥22፤29፥37፤ ዘሌ2፥3
30፥37 ቍ32
30፥38 ቍ33
31፥2 ዘፀ17፥10፤36፥1፡2፤37፥1፤38፥22፤1ዜና2፥20፤2ዜና1፥5
31፥3 ዘፀ28፥3፤ 1ነገ7፥14፤1ቆሮ12፥4

የወይራ ዘይት ይሁን፤ 25እነዚህን በቀማሚ
እንደ ተሠራ እንደሚሸት ቅመም የተቀደሰ
ቅብዐ ዘይት አድርግ፤ የተቀደሰ ቅብዐ
ዘይት ይሆናል፤ 26ከዚያም የመገናኛውን
ድንኳን፣ የምስክሩን ታቦት፣ 27ጠረጴዛ
ውንና ዕቃዎቹን ሁሉ፣ መቅረዙንና ዕቃዎቹን፣
የዕጣን መሠዊያውን፣ 28የሚቃጠል መሥዋዕት
መሠዊያውንና ዕቃዎቹን ሁሉ እንዲሁም
የመታጠቢያ ሰኑን ከነመቆሚያው እንድ
ትቀባበት ይሁን። 29እጅግ የተቀደሱ ይሆኑም
ዘንድ ቀድሳቸው፤ የሚነካቸውም ሁሉ የተቀደሰ
ይሆናል።

30ካህናት ሆነው ያገለግሉኝ ዘንድ አሮን
ንና ወንዶች ልጆቹን ቅባቸው፤ ቀድሳቸ
ውም። 31ለእስራኤላውያን ንገራቸው፤ 'በሚ
መጡት ትውልዶች ሁሉ ይህ የእኔ የተቀ
ደሰ የቅብዐት ዘይት ይሆናል፤ 32በማንም
ሰው ሰውነት ላይ አታፍስሱት፤ በተመሳሳይ
መንገድ ምንም ዘይት አትሥሩ፤ የተቀደሰ
ነው፤ ቅዱስ መሆኑን ልብ በሉ። 33ተመሳሳይ
ዐይነት የሠራና ከካህናት ሌላ በማንም ሰው
ላይ ያፈሰሰ ሁሉ ከወገኑ ይወገድ።

## ዕጣን

34ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን
አለው፤ "ተመጣጣኝ በማድረግ የጣፋጭ ሽቱ
ቅመሞች፣ የሚንጠባጠብ ሙጫ፣ በዛጐል
ውስጥ የሚገኝ ሽቱ፣ የሚሸት ሙጫ፣ እና
ንጹሕ ዕጣን ወስደህ፣ 35በቀማሚ እንደ ተሠራ
ጣፋጭ መዐዛ ያለው የተቀመመ ዕጣን
አብጅ፤ በጨው የተቀመመ፣ ንጹሕና የተ
ቀደሰ ይሁን። 36ከእርሱም ጥቂቱን ወቅጠህ
ዱቄት በማድረግ አልመህ በመገናኛው
ድንኳን ከምስክሩ ፊት ለፊት ከአንተ ጋር
በምገናኝበት ስፍራ አስቀምጠው፤ ለአንተ
እጅግ የተቀደሰ ይሆናል። 37ለራስህ በዚያ
ዐይነት መንገድ ምንም ዐይነት ዕጣን አታ
ብጅ። ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የተቀደሰ መሆኑን
ልብ በል። 38በመልካም ሽታው ይደሰት
ዘንድ እርሱን አስመስሎ የሚሠራ ሁሉ
ከወገኑ የተወገደ ይሁን።

## ባስልኤልና ኤልያብ

31፥2-6 ተጓ ምብ - ዘፀ 35፥30-35

31 ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን
እንዲህ አለው፤ 2"እነሆ፤ ከይሁዳ
ነገድ የሆር የልጅ ልጅ የሆነውን የኡሪን
ልጅ ባስልኤልን መርጬዋለሁ። 3በሁሉም
ዐይነት የእጅ ጥበብ ሥራ፣ ብልሃት፣ ችሎ
ታና ዕውቀት እንዲኖረው የእግዚአብሔርን
(ኤሎሂም) መንፈስ ሞልቼዋለሁ፤ 4ይኸውም በወ

[ሠ]13 በዚህና በቍጥር 15 ላይ 6 ግራም ያህል ነው።
[ዐ]23 ወደ 6 ኪሎ ግራም ያህል ነው።
[ዘ]24 ወደ 4 ሊትር ያህል ነው።

ርቅ፣ በብርና በናስ ለሚሠሩት ሥራዎች
በጥበብ የተሠሩ ጌጦችን እንዲያበጅ፣ 5ድን
ጋዮችን እንዲቆፍርና እንዲጠርብ ከዕን
ጨትም ጥርብ እንዲያወጣ፣ ሁሉንም ዐይ
ነት የእጅ ጥበብ ሥራዎችን እንዲያከና
ውን ነው:: 6በተጨማሪም ከዳን ነገድ
የሆነውን የአሂሳሚክን ልጅ ኤልያብን እን
ዲረዳው መርጬዋለሁ፤ እንዲሁም ያዘዝሁህን
ሁሉ ያደርጉ ዘንድ ለእጅ ጥበብ ዐዋቂ
ዎች ሁሉ ብልሃትን ሰጥቻቸዋለሁ፤ 7ይኸ
ውም የመገናኛውን ድንኳን፣ የምስክሩን
ታቦት በላዩ ላይ ካለው ከስርየት መክደኛው
ጋር፣ ሌሎች የድንኳኑን መገልገያ ዕቃዎች
ሁሉ፣ 8ጠረጴዛውን ከነዕቃዎቹ፣ ከንጹሕ
ወርቅ የተሠራውን የወርቅ መቅረዝ ከነዕ
ቃዎቹ፣ የዕጣኑን መሠዊያ፣ 9የሚቃጠል
መሥዋዕት መሠዊያውን ከነዕቃዎቹ፣ ሰኑን፣
ከእነማስቀመጫው፣ 10ከፈትል የተሠሩ ልብሶ
ችን ይኸውም የካህኑን የአሮንን የተቀደሱ
ልብሶችንና ካህናት ሆነው ሲያገለግሉ የሚለ
ብሷቸውን የወንድ ልጆቹ ልብሶች፣ 11እን
ዲሁም የመቀደሱ የሆነውን ቅብዐ ዘይትና
ጣፋጭ ሽታ ያለውን ዕጣን እንዲሠሩ ነው፤
ልክ እኔ እንዳዘዝሁህ ያብጁቸው::

## ሰንበት

12ከዚያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን
እንዲህ አለው፤ 13“ለእስራኤላውያን ንገራ
ቸው፤ ‘ሰንበቴን ማክበር አለባችሁ፤ ይህም
በእኔና በእናንተ መካከል በሚመጡት ትው
ልዶች ሁሉ ምልክት ይሆናል፤ ይኸውም
የምቀድሳችሁ[ሠ] እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
እንደ ሆንሁ እንድታውቁ ነው::
14“ለእናንተ ቅዱስ ነውና ሰንበትን አክ
ብሩ፤ ማንም ቢሽረው በሞት ይቀጣል፤
በዚያ ቀን ማንም የሚሠራ ቢኖር ከወገኑ
ተነጥሎ ይለይ:: 15ስድስት ቀን ሥራ ይሠ
ራል፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለ*እግዚአብሔር*
(ያህዌ) የተቀደሰ የዕረፍት ሰንበት ነው፤ በሰ
ንበት ቀን ማንም ቢሠራ በሞት መቀጣት
አለበት:: 16እስራኤላውያን በሚመጡት
ትውልዶች ሁሉ ሰንበትን በመጠበቅ
የዘላለም ኪዳን አድርገው ማክበር
አለባቸው፤ 17በእኔና በእስራኤላውያን መካ
ከል ለዘላለም ምልክት ይሆናል፤ ምክንያቱም
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሰማይንና ምድርን በስ
ድስት ቀን ሠርቶ፣ በሰባተኛው ቀን ከሥራ
ታቅቦ ዐርፎአልና::’ ”
18*እግዚአብሔር* (ያህዌ) በሲና ተራራ ላይ
ለሙሴ መናገሩን ከፈጸመ በኋላ፣ በእግዚ
አብሔር (ኤሎሂም) ጣት የተጻፈባቸውን የድጠ
ንጋይ ጽላቶች፣ ሁለቱን የምስክር ጽላቶች
ለእርሱ ሰጠው::

31፥6 ዘፀ28፥3፤ 36፥1፡2፤38፥23፤ 1ነገ7፥14፤2ዜና2፥14
31፥7 ዘፀ36፥8-38፤ 37፥1-5፡6፤40፥20
31፥8 ዘፀ37፥10-16፤ 17-24፤ዘሌ24፥4፤ 37፥25-28
31፥9 ዘፀ30፥18፤ 38፥3፤ዘኍ4፥14
31፥10 ዘፀ28፥2
31፥11 ዘፀ30፥22-32፤37፥29፤25፥6፡9
31፥13 ቍ17፤ዘፀ 20፥8፤29፥42፤ዘሌ 11፥44፤20፥8፤21፥8፤ ኢሳ56፥4፤ሕዝ20፥12 ፡20፤37፥28
31፥14 ዘፀ35፥2፤ ዘኍ15፥32-36
31፥15 ዘፍ 2፥3፤ ዘፀ20፥8-11፤35፥2፤ ዘሌ16፥29፤23፥3፤ ዘኍ29፥7
31፥16 ዘፀ20፥8
31፥17 ቍ13፤ ዘፍ2፥2-3፤ዘፀ20፥9፤ ኢሳ56፥2፤58፥13፤ 66፥23፤ኤር17፥21-22፤ሕዝ20፥12፡20
31፥18 ዘፀ19፥11፤ 24፥12፤32፥15-16፤ 34፥1፡28፤ዘዳ4፥13፤ 9፥10፤2ቆሮ3፥3፤ ዕብ9፥4
32፥1 ቍ23፤ዘፍ 7፥4፤ዘፀ13፥21፤ዘዳ 9፥9-12፤ሐሥ7፥40
32፥2 መሳ8፥24-27
32፥4 ቍ8፡24፡35፤ ዘፀ20፥23፤ዘዳ9፥16፤ መሳ17፥3-4፤1ነገ12፥ 28፤14፥9፤2ነገ10፥29 ፤17፥16፤2ዜና13፥8፤ ነህ9፥18፤መዝ106፥ 19፤ኢሳ30፥22፤ 42፥17፤ሆሴ8፥6፤ 10፥5፤ሐሥ7፥41
32፥5 ዘሌ23፥2፡ 37፤2ነገ10፥20፤ ኢል2፥15
32፥6 ቍ17-19፤ ዘፀ20፥24፤34፥15፤ ዘሌ3፥1፤4፥10፤6፥12፤9 ፥4፤22፥21፤ዘኍ6፥ 14፤25፥2፤ዘዳ27፥7፤መ ሳ20፥26፤መሳ19፥4፤ሩ ት3፥3፤ 1ሳሙ 1፥9፤2ሳሙ11፥11፤ 1ነገ13፥23፤18፥42፤ ነህ8፥12፤ኢዮ1፥4፤ መክ5፥18፤8፥15፤ ኤር16፥8፤ሕዝ43፥27 ፤ሐሥ7፥41፤ 1ቆሮ10፥7፤
32፥7 ቍ4፡11፤ ዘፍ6፥11-12፤ ዘፀ33፥1፤ሕዝ20፥8
32፥8 ቍ4፤ዘፀ 20፥4፤22፥20፤1ነገ 12፥28፤ኤር7፥26፤ 16፥12፤ሕዝ23፥8፤ ሚል2፥8፤3፥7

## የወርቅ ጥጃ

32 ሕዝቡ ሙሴ ከተራራው ላይ ሳይ
ወርድ ብዙ እንደ ቆየ ባዩ ጊዜ፣
ወደ አሮን ተሰብስበው፣ “ናና በፊታችን
የሚሄዱ አማልክት[የ] ሥራልን፤ ያ ከግብፅ
ያወጣን ሙሴ ምን እንዳገኘው አናውቅም
አሉት::
2አሮንም፣ “የሚስቶቻችሁን፣ የወንድና
የሴት ልጆቻችሁን የጆሮ ወርቅ አውልቃ
ችሁ ወደ እኔ አምጡ” ብሎ መለሰላቸው::
3ሕዝቡም ሁሉ የጆሮ ወርቃቸውን አውል
ቀው ወደ አሮን አመጡ:: 4እርሱም የሰጡትን
ወስዶ በመሣሪያ በመቅረጽ በጥጃ ምስል
ጣዖት አድርጎ ሠራው፤ ከዚያም እነርሱ፣
“እስራኤል ሆይ፤ ከግብፅ ያወጡህ አማል
ክት[ደ] እነዚህ ናቸው” አሉ::
5አሮን ይህን ባየ ጊዜ በወርቅ ጥጃው
ፊት ለፊት መሠዊያ ሠርቶ፣ “ነገ ለ*እግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) በዓል ይሆናል” ብሎ ዐወጀ::
6በማግሥቱ ሕዝቡ በማለዳ ተነሥተው የሚ
ቃጠል መሥዋዕት ሠዉ፤ የኅብረት መሥዋ
ዕት[ጀ] አቀረቡ፤ ከዚህም በኋላ ይበሉና ይጠጡ
ዘንድ ተቀመጡ፤ ሊዘፍኑም ተነሡ::
7ከዚያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን፣
‘ከግብፅ ያወጣኻቸው ሕዝብህ ሰተዋልና
ውረድ አለው፤ 8ካዘዝኋቸው ፈቀቅ ለማለት
ፈጣኖች ሆኑ፤ ለራሳቸውም በጥጃ ምስል
የተቀረጸ ጣዖትን ሠሩ፤ ለእርሱም ሰገዱለት፤
ሠዉለትም፤ እንዲሁም፣ ‘እስራኤል ሆይ፤
ከግብፅ ምድር ያወጡህ አማልክትህ እነዚህ
ናቸው’ አሉ::
9*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ “እነዚህን ሕዝብ አይቻቸዋለሁ፤ አን
ገተ ደንዳናዎችም ናቸው፤ 10አሁንም በእነርሱ
ላይ፣ ቍጣዬ እንዲነድና እንዳጠፋቸው
ተወኝ፤ ከዚያም አንተን ለታላቅ ሕዝብ አደር
ግሃለሁ::”
11ነገር ግን ሙሴ የአምላኩን *የእግዚአ
ብሔርን* (ኤሎሂም ያህዌ) ቸርነት ፈለገ፤ እንዲ
ህም አለ፤ “*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሆይ በታላቅ
ሥልጣንህና በኀያል ክንድህ ከግብፅ ባወጣኸው
ሕዝብህ ላይ ቍጣህ ለምን ይነዳል?

32፥9 ዘፀ33፥3፡5፤ 34፥9፤ዘዳ9፥6፡13፤ 10፥16፤31፥27፤መሳ2፥19፤ 2ነገ17፥14፤2ዜና30፥8፤36፥13፤ነህ9፥16፤መዝ78፥8፤ምሳ29፥1፤ኢሳ 46፥12፤48፥4፤ኤር7፥26፤ ሕዝ2፥4፤ሆሴ4፥16፤ሐሥ7፥51 32፥10 ዘፀ22፥24፤33፥3-5፤ዘኍ14፥12፤16፥21፡45፤ዘዳ9፥14፡19፤1ሳሙ2፥25፤ መዝ106፥23፤ኤር 7፥16፤11፥14፤ 14፥11፡12፤ሕዝ20፥13 32፥11 ቍ13፤ዘዳ 9፥18፡26፤1ሳሙ7፥9፤2ሳሙ21፥1፤2ዜና15፥2፤1ነህ1፥ 10፤መዝ9፥10፤34፥4፤106፥23፤ 136፥12፤ኢሳ 9፥13፤ኤር15፥

[ሠ]13 ወይም፣ *ቅዱስ አድርጌ የምለያችሁ* [የ]1 በዚህ እንዲሁም በቍጥር 23 እና 31 ላይ *አምላክ* [ደ]4 በዚህና በቍጥር 8 ላይ፣ *ይህ አምላካችሁ ነው*:: [ጀ]6 በትውፊት፣ *የሰላም መሥዋዕት* በመባል ይታወቃል::

12ግብፃውያን፣ ‘በተራራዎቹ ላይ ሊገድላቸው
ከገጸ ምድርም ሊያጠፋቸው ስለ ፈለገ ነው
ያወጣቸው’ ለምን ይበሉ? ከክፉ ቍጣህ
ተመለስ፤ ታገሥ፤ በሕዝብህም ላይ ጥፋት
አታምጣ። 13ለባሪያዎችህ ለአብርሃም፣ ለይስሐ
ቅና ለእስራኤል፣ ‘ዘርህን እንደ ሰማይ ከዋ
ክብት አበዛዋለሁ፤ ለዘርህም ተስፋ አድርጌ
የሰጠኋቸውን ይህችን ምድር ሁሉ እሰጣ
ቸዋለሁ፤ ለዘላለምም ርስታቸው ትሆናለች’
በማለት በራስህ የማልኸውን አስታውስ።”
14ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ታገሠ፤ በሕዝ
ቡም ላይ አመጣባቸዋለሁ ያለውን ጥፋት
አላመጣባቸውም።

15ሙሴም ሁለቱን የምስክር ጽላቶች
በእጆቹ ይዞ ከተራራው ወረደ፤ ጽላቶቹም
ከፊትና ከኋላ በሁለቱም ጎኖች ተጽፎባቸው
ነበር። 16ጽላቶቹ የእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሥራ
ነበሩ፤ በጽላቶቹ ላይ የተቀረጸ ጽሕፈትም
የእግዚአብሔር (ያህዌ) ጽሕፈት ነበር።

17ኢያሱ የሕዝቡን የጩኸት ድምፅ በሰማ
ጊዜ ሙሴን፣ “በሰፈሩ ውስጥ የጦርነት
ድምፅ አለ” አለው። 18ሙሴም

“የድል ድምፅ አይደለም፤
የሽንፈትም ድምፅ አይደለም፤
የምሰማው የዘፈን ድምፅ ነው”
ብሎ መለሰለት።

19ሙሴ ወደ ሰፈሩ ደርሶ ጥጃውንና
ጭፈራውን ባየ ጊዜ ቍጣው ነደደ፤ ጽላቶ
ቹን ከእጁ በመወርወር ከተራራው ግርጌ
ሰባበራቸው። 20የሠሩትን ጥጃ ወስዶ በእሳት
አቃጠለው፤ ከዚያም ዱቄት እስኪሆን ፈጨው፤
በውሃ ላይ በተነው፤ እስራኤላውያንም እን
ዲጠጡት አደረገ።

21አሮንንም፣ “ወደዚህ አስከፊ ኀጢ
አት ትመራቸው ዘንድ እነዚህ ሕዝብ ምን
አደረጉህ?” አለው።

22አሮንም መልሶ፣ “ጌታዬ ሆይ አትቈጣ
ብሎ መለሰለት፤ ይህ ሕዝብ ሁል ጊዜ ለክ
ፋት ያዘነበለ መሆኑን አንተ ታውቃለህ፤
23እነርሱም ‘በፊታችን የሚሄዱ አማልክት
ሥራልን፤ ይህ ከግብፅ ያወጣን ሙሴ ምን
እንዳገኘው አናውቅም’ አሉኝ። 24ስለዚህ፣
‘ማንኛውም ዐይነት የወርቅ ጌጣጌጥ ያለው
ሁሉ ያውልቀው’ አልኋቸው፤ ከዚያም ወር
ቁን ሰጡኝ፤ ወደ እሳቱ ጣልሁት፤ ይህም
ጥጃ ወጣ”

25ሕዝቡ ከቍጥጥር ውጭ እንደ ሆኑ፣ አሮ
ንም መረን እንደ ለቀቃቸውና በጠላቶቻቸ
ውም ዘንድ መሳለቂያ እንደ ሆኑ ሙሴ
አስተዋለ። 26ስለዚህ በሰፈሩ መግቢያ ላይ
ቆሞ፣ “የእግዚአብሔር (ያህዌ) የሆነ ሁሉ ወደ
እኔ ይምጣ” አለ፤ ሌዋውያኑም ሁሉ ከእርሱ
ጋር ሆኑ።

27ከዚያም፣ “የእስራኤል አምላክ እግዚ
አብሔር (ያህዌ) የሚለው ይህ ነው፤ ‘እያንዳ
ንዱ ሰው በወገቡ ላይ ሰይፍ ይታጠቅ፤ በሰ
ፈር ውስጥ ከዳር እዳር እየተመላለሰ እያን
ዳንዱ ወንድሙን፣ ጓደኛውንና ጎረቤቱን
ይግደል’ ” አላቸው። 28ሌዋውያኑ ሙሴ
እንዳዘዛቸው ፈጸሙ፤ በዚያኑም ዕለት ከሕ
ዝቡ ሦስት ሺህ ያህል አለቁ። 29ከዚያም
ሙሴ፣ “በራሳችሁ ወንዶች ልጆችና ወንድ
ሞች ላይ በመነሣታችሁ፣ በዛሬዋ ቀን ለእ
ግዚአብሔር (ያህዌ) የተለያችሁ ሆናችኋል፤
በዛሬዋም ዕለት ባርኳችኋል” አለ።

30በማግሥቱም ሙሴ ሕዝቡን፣ “እጅግ
የከፋ ኀጢአት ሠርታችኋል፤ አሁን ግን
ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ) እወጣለሁ፤ ምናልባት
ኀጢአታችሁን ማስተስረይ እችል ይሆናል”
አላቸው።

31ስለዚህ ሙሴ ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ)
ተመልሶ እንዲህ አለው፤ “ወዮ እነዚህ ሕዝብ
የሠሩት ምን ዐይነት የከፋ ኀጢአት ነው!
ለራሳቸውም የወርቅ አማልክት ሠሩ። 32አሁን
ግን አቤቱ ኀጢአታቸውን ይቅር በል፤ ያለዚያ
ግን ከጻፍኸው መጽሐፍ እኔን ደምስሰኝ።”
33እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ እንዲህ ሲል
መለሰለት፤ “የበደለኝን ሁሉ ከመጽሐፌ
እደመስሰዋለሁ፤ 34አሁን ሂድ፤ ሕዝቡን ወደ
ተናገርኩት ስፍራ ምራው፤ መልአኬም በፊ
ትህ ይሄዳል፤ ሆኖም የምቀጣበት ጊዜ
ሲደርስ፣ ስለ ኀጢአታቸው እቀጣቸዋለሁ።”

35አሮን በሠራው ጥጃ ባደረጉት ነገር
እግዚአብሔር (ያህዌ) ሕዝቡን በመቅሠፍት መታ።

33 ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን
አለው፤ “አንተና ከግብፅ ያወጣኸው
ሕዝብህ ይህን ስፍራ ለቃችሁ ‘ለዘርህ እሰ
ጣለሁ’ በማለት ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና
ለያዕቆብ በመሐላ ተስፋ ወደ ገባሁላችሁ
ምድር ሂዱ። 2መልአክን በፊትህ በመ
ላክ፣ ከነዓናውያንን፣ አሞራውያንን፣ ኬጢ
ያውያንን፣ ፌርዛውያንን፣ ኤዊያዊያንንና
ኢያቡሳውያንን አስወጣለሁ። 3ማርና ወተት
ወደምታፈሰው ምድር ውጡ፤ ነገር ግን
አንገተ ደንዳና ሕዝብ ስለሆናችሁ፣ በመን
ገድ ላይ እንዳላጠፋችሁ እኔ ከእናንተ ጋር
አልሄድም።”

4ሕዝቡም እነዚህን አሳዛኝ ቃላት በሰሙ
ጊዜ ይተክዙ ጀመር፤ ማንም ሰው አንዳች
ጌጥ አላደረገም። 5እግዚአብሔርም (ያህዌ)
ሙሴን፣ “እስራኤላውያንን፣ ‘እናንተ አንገተ
ደንዳና ሕዝብ ናችሁ፤ ለአንዳፍታ እንኳ

32፥12 ቀኁ14፤ዘፀ 33፥13፤ ዘኍ14፥13-16፤ ዘዳ9፥28
32፥13 ዘፍ12፥7፤ 15፥5፤22፥7፡16፡17፤ ዘፀ2፥24፤33፥13፤ዕብ 6፥13
32፥14 ዘዳ9፥19፤ 1ሳሙ15፥11፤ 2ሳሙ24፥16፤ 1ነገ21፥29፤1ዜና21፥15፤መዝ106፥45፤ ኤር18፥8፤26፥3፡19፤አሞ7፥3፡6፤ ዮና3፥10
32፥15 ዘፀ19፥18፤ 31፥18፤34፥4፡29፤ ዘዳ9፥15፤ 2ቆሮ3፥3፤ዕብ9፥4 32፥16 ዘፀ 24፥12
32፥17 ዘፀ17፥9
32፥19 ቀኁ6፤ዘፀ 34፥1፤ዘዳ9፥16፡17፤ዕዝ9፥3፤መዝ119፥53፡ 158፤1ቆሮ10፥7
32፥20 ዘዳ7፥25፤9፥21፤12፡3፤ኢሱ7፥1፤2ነገ 23፥6፤ 1ዜና14፥12፤ 2ዜና34፥7፤ሚክ1፥7
32፥22 ዘፍ18፥30፤ ዘዳ9፥24፤28፥20፤2ነገ 21፥15፤ዕዝ9፥13፤ነህ 9፥28፤ኤር4፥4፤44፥3፤ ሕዝ6፥9 32፥23 ቀኁ1፤ሐሥ7፥40
32፥24 ቀኁ4
32፥25 ዘፍ38፥23
32፥27 ዘኍ25፥3፡ 5፤ዘዳ33፥9፤ሕዝ9፥5
32፥30 ዘሌ1፥4፤4፥20፡26፤5፥6፡10፡13፤ 6፥7፤1ሳሙ12፥20፤ መዝ25፥11፤ 85፥2
32፥31 ዘፀ20፥23፤ 34፥9፤ዘዳ9፥18
32፥32 ዘኍ14፥19፤ መዝ69፥28፤ሕዝ13፥9፤ዳን7፥10፤12፥1፤ሚል 3፥16፤ሉቃ10፥20፤ ሮሜ9፥3
32፥33 ዘፀ17፥14፤ ኢዮ21፥20፤ራእ3፥5
32፥34 ዘፍ50፥19፤ ዘፀ3፥17፤14፥19፤15፥17፤ዘዳ32፥35፤መዝ89፥32፤94፥23፤99፥8፤109፥20፤ኢሳ27፥1፤ ኤር5፥9፤11፥22፤23፥2፤ 44፥13፡29፤ሆሴ12፥2፤ ሮሜ2፥5-6
32፥35 ቀኁ4
33፥1 ዘፍ12፥7፤ ዘፀ 13፥11፤ዘኍ14፥23፤ ዕብ6፥13
33፥2 ዘፀ14፥19፤ 23፥28
33፥3 ዘፀ3፥8፤ 32፥9፡10፤ሐሥ7፥51
33፥4 ዘኍ14፥39፤ አስ4፥1፤ዕዝ9፥3፤መዝ 119፥53
33፥5 ዘፀ32፥9፡10

ከእናንተ ጋር አብሬአችሁ ብሄድ አጠፋችሁ
ነበር፤ አሁንም ጌጣጌጦቻችሁን አውልቁ፤
እናንተን ምን ማድረግ እንዳለብኝ እወስ
ናለሁ ብለህ ንገራቸው” አለው። 6ስለዚህ
እስራኤላውያን በኮሬብ ተራራ ላይ ጌጣጌጦቻ
ቸውን አወለቁ።

## የመገናኛው ድንኳን

7ሙሴ “የመገናኛው ድንኳን” ብሎ የጠ
ራውን በመውሰድ፣ ከሰፈሩ ውጭ ራቅ
ባለ ቦታ ላይ ይተክለው ነበር። እግዚአ
ብሔርን (ያህዌ) መጠየቅ የሚፈልግ ሁሉ
ከሰፈሩ ውጭ ወዳለው ወደ መገናኛው
ድንኳን ይሄድ ነበር። 8ሙሴ ወደ ድንኳኑ
በወጣ ጊዜ ሕዝቡ በመነሣት ወደ ድንኳኑ
እስኪገባ ድረስ በየድንኳኖቻቸው ደጃፍ
ላይ ቆመው ይጠባበቁ ነበር። 9ሙሴ ወደ
ድንኳኑ ገብቶ እግዚአብሔር (ያህዌ) ከሙሴ
ጋር እየተነጋገረ ሳለ የደመናው ዐምድ ወርዶ
በመግቢያው ላይ ይቆም ነበር። 10ሕዝቡ
የደመናውን ዓምድ በድንኳኑ ደጃፍ ላይ ቆሞ
ሲያዩት ሁሉም በየድንኳኖቻቸው ደጃፍ ላይ
ቆመው ይሰግዱ ነበር። 11ሰው ከባልንጀራው
ጋር እንደሚነጋገር እግዚአብሔር (ያህዌ)
ከሙሴ ጋር ፊት ለፊት ይነጋገር ነበር፤
ከዚያም ሙሴ ወደ ሰፈሩ ይመለሳል፤ ረዳቱ
የነበረው ብላቴናው የነዌ ልጅ ኢያሱ ግን
ከድንኳኑ አይለይም ነበር።

## ሙሴና የእግዚአብሔር ክብር

12ሙሴ እግዚአብሔርን (ያህዌ) አለው፤ “እነ
ዚህን ሕዝብ ምራ’ ብለህ ነግረኸኝ ነበር፤
ከእኔ ጋር የምትልከው ማን እንደሆነ ግን
አላሳወቅኸኝም፤ ‘አንተን በስም አውቅሃለሁ፤
በፊቴም ሞገስ አግኝተሃል’ ብለህ ነበር።
13በእኔ ደስ ተሰኝተህ ከሆነ፣ አንተን ዐውቅ
ህና ያለማቋረጥ በፊትህ ሞገስ አገኝ ዘንድ
መንገድህን አስተምረኝ፤ ይህ ሕዝብ የአንተ
ሕዝብ መሆኑን አስታውስ።”
14እግዚአብሔር (ያህዌ) “ህልዎቴ ከአንተ
ጋር ይሄዳል፤ ዕረፍትም እሰጥሃለሁ” ብሎ
መለሰ።
15ከዚያም ሙሴ እንዲህ አለው፤ “ህልዎ
ትህ ከእኛ ጋር ካልሄደ ከዚህ አትስደደን።
16አንተ ከእኛ ጋር ካልሄድህ፣ አንተ በእኔና
በሕዝብህ መደሰትህን ሌላው እንዴት ያው
ቃል? እኔንና ሕዝብህንስ በገጸ ምድር
ከሚገኙት ከሌሎቹ ሕዝቦች ሁሉ ልዩ የሚ
ያደርገን ሌላ ምን አለ?”
17እግዚአብሔርም (ያህዌ) ሙሴን፣ “በአንተ
ደስ ስላለኝና በስም ስለማውቅህ፣ የጠየቅኸ
ውን ያንኑ አደርጋለሁ” አለው።
18ከዚያም ሙሴ “እባክህ፤ ክብርህን አሳ
የኝ” አለው።
19እግዚአብሔር (ያህዌ) እንዲህ አለ፤ “መል
ካምነቴ ሁሉ በፊትህ እንዲያልፍ አደርጋ
ለሁ፤ በፊትህም ስሜን እግዚአብሔርን (ያህዌ)
ዐውጃለሁ፤ ለምምረው ምሕረት አደርጋለሁ፤
ለምራራለትም ርኅራኄ አደርጋለሁ፤ 20ነገር
ግን፣ ማንም እኔን አይቶ መኖር ስለማይ
ችል፣ ፊቴን ማየት አትችልም።
21ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) እንዲህ
አለ፤ “በአጠገቤ ስፍራ አለ እንተም በዐለት
ላይ ትቆማለህ፤ 22ክብሬ በዚያ ሲያልፍ
በዐለቱ ስንጥቅ ውስጥ አደርግሃለሁ፤ በዚ
ያም እስከማልፍ ድረስ በእጄ እጋርድሃ
ለሁ፤ 23ከዚያም እጄን አነሣለሁ፤ ጀርባ
ዬንም ታያለህ፤ ፊቴ ግን መታየት የለበ
ትም።”

## አዲሶቹ የድንጋይ ጽላቶች

34 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን አለው፤
“እንደ መጀመሪያዎቹ ያሉ ሁለት
የድንጋይ ጽላቶች ጥረብ፤ እኔም አንተ
በሰበርካቸው በመጀመሪያዎቹ ጽላቶች ላይ
የነበሩትን ቃሎች እጽፍባቸዋለሁ። 2በማ
ለዳ ተዘጋጅተህ ወደ ሲና ተራራ ውጣ፤
በዚያ በተራራው ጫፍ ላይ በፊቴ ቁም፤
3ከአንተ ጋር ማንም እንዳይመጣ ወይም
በተራራው ላይ በየትኛውም ቦታ እንዳይ
ታይ፤ የበግና የፍየል መንጋዎች የቀንድ
ከብቶችም እንኳ፣ በተራራው ፊት ለፊት
መጋጥ የለባቸውም።”
4ስለዚህ ሙሴ እንደ መጀመሪያዎቹ
ያሉ ሁለት የድንጋይ ጽላቶች ጠርቦ፣
እግዚአብሔር (ያህዌ) እንዳዘዘው በማለዳ ወደ
ሲና ተራራ ወጣ፤ ሁለቱን የድንጋይ ጽላ
ቶችም በእጆቹ ያዘ። 5ከዚያም እግዚአ
ብሔር (ያህዌ) በደመና ወረደ፤ በዚያም ከእ
ርሱ ጋር ቆሞ ስሙን እግዚአብሔርን
(ያህዌ) ዐወጀ። 6እርሱም በሙሴ ፊት እንዲህ
እያለ እያወጀ አለፈ፤ “እግዚአብሔር
(ያህዌ) ሩኅሩኅ ቸር አምላክ እግዚአብሔር
(ያህዌ) ለቍጣ የዘገየ፣ ፍቅሩና ታማኝነቱ
የበዛ፣ 7ፍቅርን ለሺዎች የሚጠብቅ፣ ክፋ
ትን፣ ዐመፅንና ኀጢአትን ይቅር የሚል
በደለኛውን ግን ሳይቀጣ ዝም ብሎ አይተ
ውም፤ በአባቶች ኀጢአት ልጆችን የልጅ
ልጆቻቸውን እስከ ሦስትና አራት ትውልድ
ይቀጣል።”
8ሙሴም ወዲያውኑ ወደ መሬት ዝቅ
ብሎ ሰገደ፤ 9“አቤቱ ጌታ (አዶናይ) ሆይ፤
በፊ

33፥6 ዘፀ3፥1
33፥7 ዘፍ25፥22፤ ዘፀ27፥21፤1ነገ22፥5
33፥8 ቍ10፤ ዘኍ16፥27
33፥9 ዘፀ13፥21፤ 19፥9፤29፥42፤31፥18፤ ዘዳ31፥15፤1ቆሮ10፥1፤ መዝ99፥7
33፥10 ቍ8
33፥11 ዘፀ17፥9፤ ዘኍ12፥8፤ዘዳ5፥4፤ 34፥10
33፥12 ቍ17፤ዘፍ 6፥8፤ዘፀ3፥10፤15፥17፤ ኢሳ43፥1፤45፥3፤49፥ 1፤ ዮሐ10፥14-15፤ 2ጢሞ2፥19
33፥13 ዘፀ3፥7፤ዘዳ 9፥26፡29፤መዝ25፥4፤2 7፥11፤51፥13፤77፥15፤ 86፥11፤103፥7፤143፥8
33፥14 ዘፀ13፥21፤ ዘዳ4፥37፤12፥9፡10፤ 25፥19፤1ነገ8፥56፤2፥4 ፤ኢሱ1፥13፤11፥23፤ 21፥44፤22፥4፤23፥1፤ ኢሳ63፥9፡14፤ኤር 31፥2፤ሐጌ1፥13፤2፥ 4፤ማቴ11፥28፤ዕብ4፥ 1-11
33፥15 ቍ3፤ዘፀ 34፥9፤2ነገ13፥23፤17፥ 18፤23፥27፤24፥20፤መ ዝ51፥11፤80፥3፡7፡19፤ ኤር7፥15፤52፥3
33፥16 ዘፀ34፥5፡ 10፤ 40፥34፡35፤ዘሌ 20፥24፡26፤ዘኍ9፥15፤ 14፥14፤23፥9፤ዘዳ4፥7፡ 32፡34፤32፥9፤33፥28
33፥17 ዘፍ6፥8፤ዘፀ 34፥28፤ዘዳ9፥18፡25፤ 10፥10፤ ያዕ5፥16
33፥18 ዘፀ16፥7፤ ዮሐ1፥14፤12፥41፤1ጢ ሞ6፥16፤ራእ15፥8
33፥19 ዘፀ6፥3፤34፥ 5-7፤1ነገ19፥11፤ሮሜ 9፥15
33፥20 ዘፍ16፥13፤ ዘፀ3፥6፤ዘዳ5፥26፤ዮሐ 1፥18
33፥22 ዘፍ49፥24፤ 1ነገ19፥9፤መዝ27፥5፤ 31፥20፤62፥7፤91፥1፡4፤ ኢሳ2፥21፤49፥2፤ 51፥16፤ኤር4፥29
34፥1 ዘፀ24፥12፤ 32፥19፤ዘዳ10፥2፡4
34፥2 ዘፀ19፥11
34፥3 ዘፀ19፥13
34፥4 ዘፀ32፥15፤ ዘዳ10፥3
34፥5 ዘፀ13፥21፤ 19፥9፤6፥3፤33፥19
34፥6 ዘፍ19፥16፤ ዘፀ22፥27፤ዘኍ14፥18፡ 20፤መዝ61፥7፤78፥38፤ 86፥15፤108፥4፤115፥1፤ 138፥2፤143፥1፤ኤር15፥ 15፤ሰቆ3፥23፤ሮሜ፥4፤

34፥7 ዘፀ20፥5፡6፤23፥7፤ዘዳ5፥10፤1ነገ8፥30፤ኢሱ24፥19፤ኢዮ7፥20-21፤ 9፥28፤10፥14፤መዝ86፥5፤103፥3፤130፥4፡8፤ኢሳ43፥25፤ዳን9፥9፤ሚክ6፥1-6፤ ናሆ1፥3፤1ዮሐ1፥9 34፥9 ዘፀ6፥7፤19፥5፤ 32፥9፤33፥13፡ 15፤ዘኍ 6፥7፤ 11፥15፤14፥19፤19፥5፤ዘዳ4፥20፤7፥6፤9፥26፡29፤14፥2፤26፥18፤32፥9፤

ትህ ሞገስ አግኝቼ ከሆነ፣ ጌታ (አዶናይ)
ከእኛ ጋር ይሂድ፤ ይህ አንገተ ደንዳና ሕዝብ
ቢሆ ንም እንኳ፣ ክፋታችንንና ኀጢ
አታችንን ይቅር በል፤ እንደ ርስትህም
አድርገህ ውሰደን።”
10ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) እንዲህ
አለ፤ “ከአንተ ጋር ቃል ኪዳን አደርጋለሁ፤
ከዚህ ቀደም በዓለም ሁሉ ለየትኛውም ሕዝብ
ከቶ ያልተደረገ፣ በሕዝብህ ሁሉ ፊት ድንቅ
አደርጋለሁ፤ በመካከላቸው አብረሃቸው
የምትኖር ሕዝብ እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ)
ለአንተ የማደርግልህ ሥራ የቱን ያህል
አስፈሪ እንደ ሆነ ያያሉ። 11ዛሬ የማዝህን
ፈጽም፤ አሞራውያንን፣ ከነዓናውያንን፣
ኬጢያውያንን፣ ፌርዛውያንን፣ ኤዊያውያን
ንና ኢያቡሳውያንን በፊትህ አስወጣቸዋለሁ።
12ከምትሄድበት አገር ነዋሪዎች ጋር ቃል
ኪዳን እንዳታደርግ ተጠንቀቅ፤ አለዚያ
በመካከልህ ወጥመድ ይሆኑብሃል። 13መሠ
ዊያዎቻቸውን ሰባብሩ፤ የማምለኪያ ዐም
ዶቻቸውን አድቅቁ[ገ]፤ የአሼራ ዐፀዶቻቸው
ንም ቍረጡ። 14ስሙ ቀናተኛ የሆነው
እግዚአብሔር (ያህዌ) ቀናተኛ አምላክ (ኤሎሂም) ነውና
ሌላ አምላክ አታምልክ።
15“በምድሪቱ ከሚኖሩት ጋር ቃል ኪዳን
እንዳታደርግ ተጠንቀቅ፤ ምክንያቱም አምላ
ኮቻቸውን ተከትለው ባመነዘሩና መሥዋዕ
ትም ባቀረቡላቸው ጊዜ ይጋብዙሃል፤ አንተም
መሥዋዕታቸውን ትበላለህ። 16ለወንዶች
ልጆችህም ሴቶች ልጆቻቸውን ስታጭላቸውና
እነዚህም ሴቶች ልጆች አምላኮቻቸውን በመ
ከተል ሲያመነዝሩ፣ ወንዶች ልጆችህን ተመ
ሳሳይ ድርጊት እንዲፈጽሙ ያነሣሷቸዋል።
17“ቀልጠው የሚሠሩ አማልክትን አታ
ብጅ።
18“የቂጣን በዓል አክብር። እንዳዘዝ
ኩህም ለሰባት ቀን እርሾ ያልገባበት ቂጣ
ብላ፤ ይህንንም በተወሰነው ጊዜ በአቢብ ወር
አድርግ፤ በዚያ ወር ከግብፅ ወጥተሃልና።
19“የመንጋህ ወይም የበግና የፍየልህ፣
የቀንድ ከብትህ ተባዕት በኵር ሁሉ ሳይ
ቀር፣ ከማሕፀን በኵር ሆኖ የሚወጣ ሁሉ
የእኔ ነው። 20የአህያን በኵር በበግ ጠቦት
ዋጀው፤ ካልዋጀኸው ግን አንገቱን ስበ
ረው። በኵር ወንድ ልጆችህን ሁሉ ዋጅ።
“ማንም በፊቴ ባዶ እጁን አይቅረብ።
21“ስድስት ቀን ሥራ፤ በሰባተኛው ቀን
ግን ዕረፍ፤ በእርሻና በመከር ወቅት እንኳ
ቢሆን ማረፍ አለብህ።
22“የሰባቱን ሱባዔ በዓል ከስንዴው መከር
በኵራቶች ጋር፣ እንዲሁም የመከተቻ በዓ
ልን በዓመቱ መጨረሻ[ጠ] ላይ አክብር። 23በዓ
መት ሦስት ጊዜ ወንድ ሁሉ በእስራኤል
አምላክ (ኤሎሂም) በልዑል እግዚአብሔር (ያህዌ)
ፊት ይቅረብ። 24አሕዛብን ከፊትህ አስ
ወጣለሁ፤ ድንበርህን አሰፋለሁ፤ በዓመት
ሦስት ጊዜ በአምላክህ በእግዚአብሔር (ያህዌ)
ፊት ለመቅረብ ስትወጣ፣ ምድርህን ማንም
አይመኝም።
25“እርሾ ካለው ከማንኛውም ነገር ጋር
የደም መሥዋዕት ለእኔ አታቅርብ፤ ከፋሲካ
በዓል የተረፈው መሥዋዕት እስከ ማለዳ
አይቆይ።
26“የአፈርህን ምርጥ በኵራት ለአምላክህ
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) ቤት አምጣ። “ጠቦት
ፍየልን በእናቱ ወተት አትቀቅል።”
27ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን፣
“እነዚህን ቃሎች ጻፋቸው፤ በእነዚህ ቃሎች
መሠረት ከአንተና ከእስራኤል ጋር ቃል
ኪዳን አድርጌአለሁና” አለው። 28ሙሴ
እህል ሳይበላ ውሃም ሳይጠጣ ከእግዚአብሔር
(ያህዌ) ጋር አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በዚያ
ነበር፤ በጽላቶቹ ላይ የቃል ኪዳኑን ቃሎች፣
ዐሥርቱ ትእዛዛትን ጻፈ።

## የሚያበራው የሙሴ ፊት

29ሙሴ ሁለቱን የምስክር ጽላቶች በእ
ጆቹ ይዞ ከሲና ተራራ በወረደ ጊዜ ከእግ
ዚአብሔር (ያህዌ) ጋር ከመነጋገሩ የተነሣ ፊቱ
እንደሚያበራ አላወቀም ነበር። 30አሮንና
እስራኤላውያን ሁሉ ሙሴን ባዩት ጊዜ ፊቱ
ያበራ ነበር፤ ወደ እርሱ ለመቅረብም ፈር
ተው ነበር። 31ሙሴ ግን ጠራቸው፤ ስለዚህ
አሮንና የማኅበሩ መሪዎች ወደ እርሱ
ተመለሱ፤ እርሱም አናገራቸው። 32ከዚያም
በኋላ እስራኤላውያን ሁሉ ወደ እርሱ ቀረቡ፤
እግዚአብሔር (ያህዌ) በሲና ተራራ የሰጠ
ውን ትእዛዞች ሁሉ ሰጣቸው።
33ሙሴ ለእነርሱ ተናግሮ ከጨረሰ በኋላ
በፊቱ ላይ መሸፈኛ አደረገ። 34ከእርሱ ጋር
ለመነጋገር ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ) ህል
ዎት በሚገባበት ጊዜ ሁሉ ግን፣ እስከሚ
ወጣ ድረስ መሸፈኛውን ያነሣ ነበር፤ በወ
ጣም ጊዜ የታዘዘውን ለእስራኤላውያን ነገ
ራቸው። 35ፊቱ የሚያበራ መሆኑን አዩ፤
ከዚያም ሙሴ ከእግዚአብሔር (ያህዌ) ጋር
ለመነጋገር ተመልሶ እስኪሄድ ድረስ መሸፈ
ኛውን መልሶ በፊቱ ላይ ያደርግ ነበር።

## የሰንበት ሥርዐቶች

35 ሙሴ የእስራኤልን ማኅበረሰብ ሁሉ
ሰብስቦ እንዲህ አላቸው፤ “እግዚ

ያዕ5፥11 1ነገ8፥30፡51፡53፤ 1ሳሙ10፥1፤2ሳሙ14፥16፤2ዜና6፥21፤ መዝ19፥12፤25፥11፤ 28፥9፤33፥12፤74፥2፤79፥1፤94፥14፤106፥5፡40፤ኢሳ19፥25፤63፥17፤ኤር10፥16፤33፥8፤51፥19፤ ሆሴ14፥2፤ሚክ7፥18፤ዘካ2፥12
34፥10 ዘዳ6፥18፤9፥15፤15፥18፤ዘፀ3፥20፤33፥16፤ዘዳ 5፥2-3
34፥11 ዘፀ23፥28፤ ዘዳ6፥25፤ኢሱ11፥15
34፥12 ዘፀ10፥7፤ መሳ2፥2
34፥13 ዘፀ23፥24፤ ዘኍ33፥52፤ዘዳ7፥5፤12፥3፤መሳ6፥26፤1ነገ15፥13፤2ዜና15፥16፤17፥6፤34፥3-4፤ሚክ5፥14
34፥14 ዘፀ20፥3፡5፤ ኢሳ9፥6
34፥15 ቍ12፤ዘፀ22፥20፤32፥6፡8፤ዘዳ23፥6፤31፥16፤መሳ2፥17፤2ነገ17፥8፤1ዜና5፥25፤2ዜና11፥15፤ዕዝ9፥12፤ አሞ2፥4፤1ቆሮ8፥4
34፥16 ዘዳ7፥3፡4፤ 12፥31፤17፥17፤20፥18፤ ኢሱ23፥12፤መሳ3፥6፤ 14፥3፤1ነገ11፥1፡2፡4፤ 16፥31፤2ነገ21፥3-5፤ ዕዝ9፥2፤10፥3፤ነህ10፥30፤13፥25፡26፤መዝ106፥34-41፤ ሚል2፥11
34፥17 ዘፀ20፥4
34፥18 ዘፀ12፥2፡15፡17፤ቴ26፥17፤ሉቃ22፥1፤ሐሥ12፥3
34፥19 ዘፀ13፥2
34፥20 ዘፀ13፥2፡13፤22፥29፤ዘዳ16፥16፤ ሕዝ 46፥9
34፥21 ዘፍ2፥2-3፤ነህ13፥15፤ ኢሳ56፥2፤58፥13
34፥22 ቍ26፤ዘፀ23፥16፡19፤ዘሌ2፥12፡14፤7፥13፤23፥10፡17፤ ዘኍ28፥26
34፥23 ዘፀ23፥14
34፥24 ዘፀ23፥28፤ ዘዳ12፥20፤19፥8፤ ኢ.ዮ12፥23
34፥25 ዘፀ12፥8፤ 23፥18፤
34፥26 ዘፀ22፥29፤ 23፥19፤ዘኍ18፥12
34፥27 ዘፍ6፥18፤ 15፥18፤ዘፀ17፥14
34፥28 ቍ1፤ ዘፍ7፥4፤ዘፀ31፥18፤ ዘዳ4፥13፤9፥9፥18፤ 10፥4፤፤ዕዝ10፥6፤ ማቴ4፥2፤ሉቃ4፥2
34፥29 ቍ35፤ዘፀ19፥11፤32፥15፤መዝ34፥5፤ኢሳ60፥5፤ማቴ17፥2፤2ቆሮ3፥7፡13
34፥31 ዘፀ16፥22
34፥32 ዘፀ21፥1፤ 35፥1፡4 34፥33 2ቆሮ3፥13 34፥35 ቍ29
35፥1 ዘፀ34፥32

[ገ]13 አሼራ የምትባለውን ጣዖት አምላክ ምስል ማለት ነው።

*አብሔር* (ያህዌ) እንድትፈጽሟቸው ያዘዛችሁ
ነገሮች እነዚህ ናቸው፤ [2]ስድስት ቀን ሥራ
ይሠራል፤ ሰባተኛው ቀን ግን *ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) የሰንበት ዕረፍት፣ የተቀደሰ ቀን ይሆን
ላችኋል፤ በዕለቱ ማናቸውንም ዐይነት ሥራ
የሚሠራ ቢኖር ሞት ይገባዋል። [3]በሰንበት
ቀን በማናቸውም መኖሪያዎቻችሁ ውስጥ
እሳት አታንድዱ።”

## ለመገናኛው ድንኳን ዕቃዎች

35፥4-9 ተጓ ምብ - ዘፀ 25፥1-7
35፥10-19 ተጓ ምብ - ዘፀ 39፥32- 41

[4]ሙሴ ለእስራኤላውያን ማኅበረሰብ ሁሉ
እንዲህ አላቸው፤ “*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ያዘ
ዘው ይህ ነው፤ [5]ካላችሁ ንብረት ሁሉ
*ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) መሥዋዕት አቅርቡ፤
ፈቃደኛ የሆነ ማንም *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ)
የወርቅ፣ የብር፣ የናስ መባ ያምጣ፣ [6]ሰማ
ያዊ፣ ሐምራዊና ቀይ ማግ፤ ቀጭን ሐር፣
የፍየል ጠጕር፣ [7]ቀይ የተነከረ የአውራ
በግ ቆዳ፣ እንዲሁም አቆስጣ ቆዳ[ጨ]፣ የግራር
ዕንጨት፤ [8]ለመብራት የወይራ ዘይት፣ ለቅ
ብዐ ዘይቱና ለጣፋጭ ሽታ ዕጣን ቅመም፤
[9]በኤፉዱና በደረት ኪሱ ላይ የሚሆኑ መረ
ግዶችና ሌሎች ዕንቍዎችን መባ አድርጎ
ያምጣ።

[10]“በመካከላችሁ ጥበበኞች የሆኑ ሁሉ
መጥተው *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ያዘዘውን ሁሉ
ይሥሩ፤ [11]የመገናኛውን ድንኳን ከነድንኳኑና
ከነመደረቢያው፣ ማያያዦዎችን፣ ክፈፎችን፣
አግዳሚዎችን፣ ቋሚዎችንና መሠረቶችን፤
[12]ታቦቱን ከነመሎጊያዎቹ፣ የስርየት መክደ
ኛውንና የሚሸፍነውን መጋረጃ፤ [13]ጠረጴዛ
ውን ከነመሎጊያዎቹ፣ ዕቃዎቹን ሁሉና
የህልዎቱን ኅብስት፤ [14]ለመብራት የሆነውን
መቅረዝ ከነዕቃዎቹ፣ ቀንዲሎችንና ለመ
ብራት የሚሆነውን ዘይት፤ [15]የዕጣን መሠ
ዊያውን ከነመሎጊያዎቹ፣ ቅብዐ ዘይቱንና
ጣፋጭ ሽታ ያለውን ዕጣን፤ በመገናኛው
ድንኳን ደጃፍ ላይ የሚሆነውን የመግቢያ
መጋረጃ፤ [16]የሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊ
ያውን ከናስ መጫሪያው፣ መሎጊያዎቹ
ንና ዕቃዎቹን ሁሉ፣ የናስ ሰኑን ከነማስ
ቀመጫው፣ [17]ያደባባዩን መጋረጃዎች ከነም
ሶሶዎቻቸውና ከነመሠረቶቹ፣ ያደባባዩን መግ
ቢያ መጋረጃ፤ [18]ለመገናኛው ድንኳንና ለአ
ደባባዩ የሚሆኑ የድንኳን ካስማዎችና ገመ
ዶቻቸው፤ [19]በመቅደሱ ውስጥ ለማገልገል
የሚለበሱ የፈትል ልብሶችን ይኸውም
የካህኑ የአሮንን የተቀደሱ ልብሶችንና ካህ
ናት ሆነው ሲያገለግሉ የሚለብሷቸውን የወ
ንዶች ልጆቹን ልብሶች ይሥሩ።”

[20]ከዚያም የእስራኤል ማኅበረሰብ ሁሉ
ከሙሴ ፊት ወጡ፤ [21]ፈቃደኛ የነበረና
ልቡን ያነሣሣው ሁሉ በመምጣት ለመገናኛው
ድንኳን ሥራ፣ ለአገልግሎቱ ሁሉና ለተ
ቀደሱ ልብሶች የሚሆን *ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) መባ አመጡ። [22]ፈቃደኛ የነበሩ ሁሉ፣
ወንዶችም ሴቶችም መጥተው ከሁሉም ዐይ
ነት የወርቅ ጌጦች አመጡ የአፍንጫ ጌጠ
ችን፣ ሎቲዎችን፣ ቀለበቶችን፣ ድሪዎችንና
ጌጣ ጌጦችን ሁሉ አመጡ፤ ሁሉም ወርቃ
ቸውን እንደሚወዘወዝ መሥዋዕት *ለእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) አቀረቡ። [23]ሰማያዊ፣ ሐምራዊ
ወይም ቀይ ማግ ወይም ቀጭን ሐር ወይም
የፍየል ጠጕር፣ ቀይ የተነከረ የአውራ በግ
ቆዳ ወይም የአቆስጣ ቆዳ አመጡ። [24]የብር
ወይም የናስ መባ ማቅረብ የቻሉ ሁሉ
*ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) መባ አድርገው አመጡ፤
የግራር ዕንጨት ያለው ሁሉ አስፈላጊ
በሆነው ሥራ እንዲውል አመጣው። [25]ጥበበኞች
የሆኑ ሴቶች ሁሉ በእጃቸው ፈተሉ፤
የፈተሉትንም ሰማያዊ ሐምራዊ ወይም ቀይ
ማግ ወይም ቀጭን በፍታ አመጡ።
[26]ፈቃደኛ የነበሩና ጥበቡ ያላቸው ሴቶች
ሁሉ የፍየል ጠጕር ፈተሉ። [27]መሪዎቹም
ኤፉድና በደረት ኪሱ ላይ እንዲሆን የከበሩ
ድንጋዮችንና ሌሎች ዕንቍዎች አመጡ።
[28]እንዲሁም ለመብራቱ፣ ለቅብዐ ዘይቱና
ለጣፋጭ ሽታ ዕጣን የሚሆኑ ቅመሞችንና
የወይራ ዘይትን አመጡ። [29]ፈቃደኛ የሆኑ
እስራኤላውያን ወንዶችና ሴቶች ሁሉ፣
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) በሙሴ በኩል እንዲያከ
ናውኑት ላዘዛቸው ሥራ ሁሉ የበጎ ፈቃድ
ስጦታዎችን *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) አመጡ።

## ባስልኤልና ኤልያብ

35፥30-35 ተጓ ምብ - ዘፀ 31፥2-6

[30]ከዚያም ሙሴ እስራኤላውያንን አላቸው፤
“እነሆ፣ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ከይሁዳ ነገድ
የሆነውን የሆር ልጅ፣ የኡሪን ልጅ ባስል
ኤልን መርጦአል። [31]በጥበብ፣ በችሎታና
በዕውቀት፣ በማናቸውም ዐይነት ሙያ
የእግዚአብሔርን (ኤሎሂም) መንፈስ ሞልቶበታል፤
[32]ይኸውም በወርቅ፣ በብርና በናስ የጥበብ
ሥራ እንዲሠራ ነው፤ [33]ድንጋዮችን እንዲጠ
ርብና እንዲያወጣ፣ የዕንጨት ሥራ እንዲ
ሠራና ማንኛውንም ዐይነት የጥበብ ሙያ
እንዲያከናውን ነው። [34]እንዲሁም ለእርሱና
ከዳን ነገድ ለሆነው ለአሂሳሚክ ልጅ ለኤ
ልያብ፣ ለሁለቱም ሌሎችን የማስተማር
ችሎታ ሰጣቸው። [35]የጥበብ ባለሙያዎች፣
ዕቅድ አውጭዎች፣ በሰማያዊ በሐምራዊና
በቀይ ማግ፣ በቀጭን ሐር ጥልፍ ጠላፊዎችና

35፥2 ዘፍ2፥3፤ ዘፀ31፥14፤34፥21፤ ዘዳ5፥13-14
35፥3 ዘፀ16፥23
35፥8 ዘፀ25፥6
35፥10 ዘፀ31፥6፤ 39፥43
35፥11 ዘፀ26፥1-37፤36፥8-38
35፥12 ዘፀ25፥10-22፤26፥33፤37፥1-9
35፥13 ዘፀ25፥23-30፤37፥10-16
35፥14 ዘፀ25፥31
35፥15 ዘፀ30፥1-6፤37፥25-28፤30፥25፡34-38፤26፥36
35፥16 ዘፀ27፥1-8፤30፥18፤38፥1-7
35፥17 ዘፀ27፥9፤ 38፥9-20
35፥18 ዘፀ27፥19፤ 38፥20
35፥19 ዘፀ28፥2
35፥23 ዘፀ39፥1
35፥25 ዘፀ28፥3
35፥27 ዘፀ25፥2፤ 1ዜና29፥6፡8
35፥28 ዘፀ25፥6
35፥29 ቍ4-9፤ ዘፀ 25፥2፤1-7፤ 36፥3፤2ነገ12፥4
35፥31 ቍ35፤2ዜና2፥7፡14
35፥34 ዘፀ31፥6፤2 ዜና2፥14
35፥35 ቍ31

[ጠ]22 መስከረም፣ ጥቅምትና ኅዳር ማለት ነው። [ጨ]7 በዚህና በቍጥር 23 ላይ አንዳንድ ቅጂዎች፣ *የለፋ የአቆስጣ ቆዳ* ይላሉ።

ፈታዮች፤ ሁሉም ዋና የጥበብ ባለሙያዎችና ዕቅድ አውጭዎች በመሆን ማንኛውንም ዐይነት ሥራ ያከናውኑ ዘንድ በጥበብ ሞልቶአቸዋል።

36 ስለዚህ የመቅደሱን የግንባታ ሥራ ሁሉ እንዴት ማከናወን እንዳለባቸው *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ጥበብንና ችሎታን የሰጣቸው፣ ባስልኤል፣ ኤልያብና ጥበበኛ የሆኑ ሰዎች ሁሉ ሥራውን ልክ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) እንዳዘዘው ይሥሩት።”

2ከዚያም ሙሴ ባስልኤልንና ኤልያብን እንዲሁም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ችሎታ የሰጣቸውን፣ መጥተው ሥራውን ለመሥራት ፈቃደኛ የሆኑትን ጥበብ ያላቸውን ሰዎች ሁሉ አስጠራ። 3የመቅደሱን የግንባታ ሥራ ለማከናወን እስራኤላውያን ያመጡትን ስጦታ ሁሉ ከሙሴ ተቀበሉ፤ ሕዝቡ የበጎ ፈቃድ ስጦታዎችን በየማለዳው ማምጣታቸውን ቀጠሉ። 4ስለዚህ የመቅደሱን ሥራ ሁሉ ይሠሩ የነበሩ ጥበበኞች የሆኑ ባለሙያዎች ሁሉ ሥራቸውን ትተው መጡ፤ 5ሙሴንም፣ “ሕዝቡ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) እንዲሠራ ካዘዘው ሥራ ከበቂ በላይ እያመጡ ነው” አሉት። 6ከዚያም ሙሴ ትእዛዝ ሰጠ፤ ይህንንም ቃል ወደ ሰፈሩ ላኩት፤ “ማንም ወንድ ወይም ሴት ለመቅደሱ ሌላ ምንም ስጦታ ማድረግ የለበትም፤” ስለዚህ ሕዝቡ ትርፍ እንዳያመጡ ተከለከሉ፤ 7ምክንያቱም ሥራውን ሁሉ ለማከናወን በእጃቸው ያለው ከበቂ በላይ ነበረ።

### የማደሪያው ድንኳን

36፥8-38 ተጓ ምብ - ዘፀ 26፥1-37

8የሥራ ችሎታ ካላቸው ሰዎች መካከል ጥበበኛ የሆኑ ሰዎች ሁሉ የማደሪያውን ድንኳን በቀጭኑ ከተፈተለ በፍታና ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊና ከቀይ ማግ፣ በጥልፍ ዐዋቂ፣ ኪሩቤል ከተጠለፉበት ከዐሥር መጋረጃዎች ሠሩት። 9መጋረጃዎቹም ሁሉ ተመሳሳይ መጠን ያላቸው ሲሆን፣ ቁመታቸው ሃያ ስምንት ክንድ፣ ወርዳቸው አራት ክንድ[ጰ] ነበር። 10አምስቱን መጋረጃዎች ባንድ ላይ በማጋጠም ሰፏቸው፤ የቀሩትን አምስቱንም እንዲሁ አደረጉ። 11ተጋጥሞ ከተሰፋው መጋረጃ ጠርዝ ጫፍ ላይ ከሰማያዊ ግምጃ ቀለበቶችን አበጁ፤ ተጋጥሞ በተሰፋው በሌላው መጋረጃ ጫፍ ላይም ተመሳሳይ ነገር አደረጉ። 12በአንደኛው መጋረጃ ላይ አምሳ ቀለበቶችን በሌላው ተጋጥሞ ከተሰፋው በስተ መጨረሻ ካለው መጋረጃ ላይ አምሳ ቀለበቶችን እርስ በርሳቸው ትይዩ በማድረግ ሠሩት። 13ከዚያም አምሳ የወርቅ ማያያዣዎችን ሠሩ፤

36፥1 ዘፀ28፥3፤ 25፥8
36፥2 ዘፀ25፥2፤ 31፥2፡6፤
36፥3 ዘፀ35፥29
36፥5 2ዜና24፥14፤ 31፥10፤ 2ቆሮ8፥2-3
36፥7 1ነገ7፥47
36፥13 ቍ18
36፥18 ቍ13

የማደሪያው ድንኳን አንድ ወጥ ይሆን ዘንድም ተጋጥመው የተሰፉትን ሁለቱን መጋረጃዎች አያያዙባቸው።

14ከማደሪያው በላይ ለሚሆነው ድንኳን ከፍየል ቆዳ የተሠሩ በጠቅላላ ዐሥራ አንድ መጋረጃዎችን ሠሩ። 15ዐሥራ አንዱ መጋረጃዎች ተመሳሳይ ልክ ሲኖራቸው፣ ቁመታቸው ሠላሳ ክንድ፣ ወርዳቸውም አራት ክንድ[ጰ] ነበር። 16አምስቱን መጋረጃዎች በአንድ በኩል፣ ሌሎቹን ስድስት መጋረጃዎች ደግሞ በሌላ በኩል አንድ ላይ አያያዟቸው። 17በስተመጨረሻ በሚገኘው መጋረጃ ጠርዝ ላይ አምሳ ቀለበቶችን፣ በሌላ በኩል ባለው በስተ መጨረሻ በሚገኘው መጋረጃ ጠርዝ አምሳ ቀለበቶችን አበጁ። 18ድንኳኑን አንድ ወጥ አድርጎ ለማያያዝም አምሳ የናስ ማያያዣዎችን ሠሩ። 19ከዚያም ለድንኳኑ መሸፈኛ የሚሆን ቀይ ከተነከረ የአውራ በግ ቆዳ ሠሩ፤ በላዩ ላይ የሚሆንም የአቆስጣ ቆዳ[ፀ] አበጁ።

20ለማደሪያው ድንኳን ከግራር ዕንጨት ወጋግራዎችን አበጁ። 21እያንዳንዱም ወጋግራ ቍመቱ ዐሥር ክንድ፣ ስፋቱ አንድ ክንድ ተኩል[ፊ] ነበር፣ 22ትይዩ የሆኑ ሁለት ጕጦች ነበሩት፤ የማደሪያውን ድንኳን ወጋግራዎች በዚህ መልክ ሠሩ። 23በደቡብ በኩል ላለው የማደሪያው ድንኳን ሃያ ወጋግራዎችን አበጁ፤ 24ለእያንዳንዱ ጕጠት አንድ መቆሚያ፣ ለእያንዳንዱም ወጋግራ ሁለት መቆሚያ ሆኖ አርባ የብር መቆሚያዎችን አበጁ። 25በስተሰሜን በኩል ላለው የማደሪያ ድንኳን ሃያ ወጋግራዎችን ሠሩ፤ 26ለእያንዳንዱ ወጋግራ ሁለት መቆሚያ የሆኑ አርባ የብር መቆሚያዎችን ሠሩ። 27በዳር በኩል ይኸውም በስተ ምዕራብ ጫፍ ባለው ማደሪያ ድንኳን ስድስት ወጋግራዎችን ሠሩ። 28ዳርና ዳር ላሉት የማደሪያው ድንኳን ማእዘኖችም ሁለት ወጋግራዎችን ሠሩ። 29በእነዚህ ሁለት ማእዘኖች ላይ ከታች አንሥቶ እስከ ላይ ድረስ ወጋግራዎቹ በአንድ ላይ ተነባብረው በአንድ ቀለበት ውስጥ ተገጥመው ነበር፤ ሁለቱም አንድ አካል ሆነው ተሠርተው ነበር። 30ስለዚህ ስምንት ወጋግራዎችና ለእያንዳንዱም ወጋግራ ሁለት መቆሚያዎች ሆነው ዐሥራ ስድስት የብር መቆሚያዎች ነበሩ።

31እንደዚሁም ከግራር እንጨት አግዳሚዎችን ሠሩ፤ በማደሪያው ድንኳን በአንድ በኩል ላሉት ወጋግራዎች አምስት አግዳሚዎችን ሠሩ፤ 32በሌላ በኩል ላሉት አምስት አግዳሚዎች፣ በምዕራብ በኩል በማደ

[ጰ]9 ቁመቱ 1.1 ሜትር፣ ወርዱ 1.8 ሜትር ይህል ማለት ነው።

ሪያው ድንኳን ዳር ላይ ላሉት ወጋግራዎች
አምስት አግዳሚዎችን ሠሩ። 33በወጋግራ
ዎቹ መካከል ከዳር እስከ ዳር እንዲዘረጋ
ሆኖ መካከለኛውን አግዳሚ ሠሩ። 34ወጋግ
ራዎቹን በወርቅ ለበጧቸው፤ አግዳሚዎቹን
ለመያዝም የወርቅ ቀለበቶችን ሠሩ፤ እንዲ
ሁም አግዳሚዎቹን በወርቅ ለበጧቸው።
35ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊ፣ ከቀይ ማግና
በቀጭኑ ከተፈተለ በፍታ፣ በእጅ ጥበብ
ባለ ሙያ ኪሩቤል የተጠለፉበት መጋረጃ
አበጁ። 36ለእርሱም አራት ምሰሶዎች ከግ
ራር ዕንጨት ሠርተው በወርቅ ለበጧቸው፤
ለእነርሱም አራት የወርቅ ኵላቦችንና አራት
የብር መቆሚያዎችን አበጁላቸው። 37በድ
ንኳኑ መግቢያ ጥልፍ ጠላፊ እንደሚሠራው
ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊ፣ ከቀይ ማግና በቀ
ጭኑ ከተፈተለ በፍታ መጋረጃ አበጁለት፤
38ለእነርሱም ኵላቦች ያሏቸው አምስት ምሰሶ
ዎች ሠሩላቸው፤ የምሰሶዎቹን አናቶችና ዘን
ጎች በወርቅ በመለበጥ አምስቱን መቆሚያ
ዎች ከነሓስ ሠሩ።

## የኪዳኑ ታቦት
37፥1-9 ተጓ ምብ - ዘፀ 25፥10-20

37 ባስልኤል ርዝመቱ ሁለት ክንድ
ተኩል፣ ወርዱ አንድ ክንድ ተኩል[ፐ]፣
ከፍታው አንድ ክንድ ተኩል የሆነ ታቦት
ከግራር ዕንጨት ሠራ። 2በውስጥና በውጭ
በንጹሕ ወርቅ ለበጠው፤ በዙሪያውም የወ
ርቅ ክፈፍ አበጀለት። 3አራት የወርቅ
ቀለበቶችን ሠርቶ ሁለት ቀለበቶችን በአ
ንድ በኩል፣ ሁለት ቀለበቶችንም በሌላ
በኩል አድርጎ ከአራቱ እግሮቹ ጋር አያያዛ
ቸው። 4ከዚያም መሎጊያዎችን ከግራር ዕን
ጨት ሠርቶ በወርቅ ለበጣቸው። 5መሎጊ
ያዎቹንም መሸከሚያ እንዲሆኑ በታቦቱ
ጐንና ጐን ባሉት ቀለበቶች ውስጥ አስገ
ባቸው።
6ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል[ሀ]፣ ወር
ዱም አንድ ክንድ ተኩል የሆነ ከንጹሕ
ወርቅ የስርየት መክደኛ ሠራ። 7ከዚያም
ከተቀጠቀጠ ወርቅ ሁለት ኪሩቤልን ከመክ
ደኛው ጫፎች ላይ ሠራ። 8አንዱን ኪሩብ
በአንዱ ጫፍ ላይ፣ ሁለተኛውንም ኪሩብ
በሌላው ጫፍ ላይ ሠራ፤ ከሁለቱ ጫፎች
ላይ ከክዳኑ ጋር አንድ ወጥ አድርጎ ሠራ
ቸው፤ 9ኪሩቤልም የስርየት ክዳኑን በመሸ
ፈን ክንፉቻቸውን ወደ ላይ ዘርግተው ነበር፤
ኪሩቤል ወደ ስርየት መክደኛው እየተመለ
ከቱ እርስ በርሳቸው ገጽ ለገጽ ነበሩ።

## የኅብስት ማስቀመጫው ጠረጴዛ
37፥10-16 ተጓ ምብ - ዘፀ 25፥23-29

10ርዝመቱ ሁለት ክንድ፣ ወርዱ አንድ

36፥35 ዘፀ39፥38፤ ማቴ27፥51፤ሉቃ23፥45፤ዕብ9፥3
36፥37 ዘፀ27፥16
37፥1 ዘፀ30፥6፤ 31፥2፤39፥35፤ ዘዳ10፥3
37፥2 ቍ11፥26
37፥6 ዘፀ26፥34፤ 31፥7፤ዕብ9፥5
37፥7 ሕዝ41፥18
37፥9 ዘዳ10፥3፤ዕብ 9፥5
37፥10 ዕብ9፥2

37፥11 ቍ2
37፥14 ቍ27
37፥17 ዕብ9፥2፤ ራእ1፥12
37፥22 ቍ17፤ ዘኍ8፥4
37፥23 ዘፀ40፥4፡25

ክንድ፣ ከፍታውም አንድ ክንድ ተኩል
የሆነ ጠረጴዛ ከግራር ዕንጨት ሠሩ[ለ]።
11ከዚያም በንጹህ ወርቅ በመለበጥ በዙሪ
ያው የወርቅ ክፈፍ አበጁለት። 12በዙሪያውም
ስፋቱ አንድ ስንዝር[ሐ] የሆነ ጠርዝ በማበጀት
በጠርዙ ላይ የወርቅ ክፈፍ አደረጉበት።
13ለጠረጴዛው አራት የወርቅ ቀለበቶች
አበጅተው አራቱ እግሮች ካሉበት ከአራቱ
ማእዘኖች ጋር አያያዟቸው። 14ጠረጴዛውን
ለመሸከም የሚያገለግሉትን መሎጊያዎች
እንዲይዙ ቀለበቶቹ ከጠርዙ አጠገብ ሆኑ።
15ጠረጴዛውን ለመሸከም የሚያገለግሉት
መሎጊያዎች ከግራር ዕንጨት የተሠሩና
በወርቅ የተለበጡ ነበሩ። 16የጠረጴዛ
ውን ዕቃዎች ይኸውም ዝርግ ሳሕኖችን፣
ድስቶችንና ጐድጓዳ ሳሕኖችን እንዲሁም
የመጠጥ መሥዋዕቱ ማፍሰሻ የሆኑትን
ማንቈርቈሪያዎች ከንጹሕ ወርቅ ሠሯ
ቸው።

## መቅረዙ
37፥17-24 ተጓ ምብ - ዘፀ 25፥31-39

17መቅረዙን ከንጹሕ ወርቅ ሠሩት፤
መቆሚያውንና ዘንጉን ቀጥቅጠው አበጁት፤
የአበባ ቅርጽ ያላቸው ጽዋዎች፣ እንቡጦችና
የፈኩ አበቦች ከእርሱ ጋር አንድ ወጥ
ሆነው ተሠርተው ነበር። 18ሦስቱ በአንድ
በኩል ሦስቱ በሌላ በኩል በመሆን ስድስት
ቅርንጫፎች ከመቅረዙ ጐኖች ተሠርተው
ነበር። 19ከእንቡጦችና ከፈኩ አበቦች ጋር
የለውዝ አበባ የሚመስሉ ሦስት ጽዋዎች
በአንዱ ቅርንጫፍ ላይ፣ ሦስቱ ደግሞ በሚ
ቀጥለው ቅርንጫፍ ላይ ነበሩ፤ ከመቅረዙ
ለወጡት ለስድስቱም ቅርንጫፎች ሁሉ እን
ዲሁ ነበር። 20እንቡጦችና የፈኩ አበቦች
ያሉባቸው የለውዝ አበባ የሚመስሉ አራት
ጽዋዎች በመቅረዙ ላይ ነበሩ። 21አንደኛው
እንቡጥ ከመቅረዙ ወጣ ብለው በሚገኙት
በመጀመሪያው ጥንድ ቅርንጫፎች ሥር
ሁለተኛውም እምቡጥ በሁለተኛው ጥንድ
ሥር እንዲሁም ሦስተኛው እንቡጥ በሦስተ
ኛው ጥንድ ሥር ነበር፣ በስድስቱም ቅርን
ጫፎች እንዲሁ ነበር። 22እንቡጦቹና ቅርን
ጫፎቹ ሁሉ ከንጹሕ ወርቅ ተሠርተው
ከመቅረዙ ጋር አንድ ወጥ ነበሩ።
23የመቅረዙን ሰባት መብራቶች፣ እን
ዲሁም መኮስተሪያዎችንና የኵስታሪ ማስቀ

[ጸ]15 ቁመቱ 13.5 ሜትር፣ ወርዱ 1.8 ሜትር ያህል ማለት ነው።
[ፀ]19 ይህ የባሕር አውሬ ነው፤
[ፈ]21 ቁመቱ 4.5 ሜትር ወርዱ 0.7 ሜትር ያህል ማለት ነው።
[ፐ]1 ከፍታው 1.1 ሜትር ወርዱና ርዝመቱ 0.7 ሜትር ያህል ማለት ነው።
[ሀ]6 ርዝመቱ 1.1 ሜትር ወርዱ 1.1 ሜትር ያህል ማለት ነው።
[ለ]10 በዚህና በቍጥር 11-29 ባሉት ክፍሎች፣ሥሩ
[ሐ]12 ወደ 8 ሳንቲ ሜትር ያህል ማለት ነው።

መጫዎችን ከንጹሕ ወርቅ ሠሩ። 24መቅረዙንና ዕቃዎቹን ሁሉ ከአንድ መክሊት[መ] ንጹሕ ወርቅ ሠሩ።

### የዕጣን መሠዊያው

37፥25-28 ተጓ ምብ - ዘፀ 30፥1-5

25የዕጣን መሠዊያውን ከግራር ዕንጨት ሠሩ፤ ርዝመቱ አንድ ክንድ፣ ወርዱ፣ አንድ ክንድ፣ ከፍታው ሁለት ክንድ[ሠ] ነበር፤ ቀንዶቹም ከእርሱ ጋር አንድ ወጥ ሆነው ተሠርተው ነበር። 26ላዩን፣ ጐኖቹን ሁሉና ቀንዶቹን በንጹሕ ወርቅ ለበጧቸው፤ በዙሪያው የወርቅ ክፈፍ አበጁ። 27ለሸክም የሚሆኑትን መሎጊያዎች ለመያዝ ትይዩ የሆኑ ከክፈፉሥር ሁለት የወርቅ ቀለበቶችን ሠሩ። 28መሎጊያዎቹን ከግራር ዕንጨት ሠሩ፤ በወርቅም ለበጧቸው።

29እንዲሁም የተቀደሰውን ቅብዐ ዘይትና የሽቶ ቀማሚ ሥራ የሆነውን፣ ንጹሕና መልካም መዐዛ ያለውን ዕጣን ሠሩ።

### የሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊያ

38፥1-7 ተጓ ምብ - ዘፀ 27፥1-8

38 ከፍታው ሦስት ክንድ[ሬ] የሆነ የሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊያ ከግራር ዕንጨት ሠሩ[ሰ]፤ ርዝመቱ አምስት ክንድ፣ ወርዱ አምስት ክንድ የሆነ ባለ ዐራት ማእዘን ነበረ። 2ቀንዶቹና መሠዊያው አንድ ወጥ ይሆኑ ዘንድ በአራቱም ማእዘኖች ላይ አራት ቀንድ ሠሩ፣ መሠዊያውንም በናስ ለበጡት። 3ዕቃዎቹንም ሁሉ ይኸውም ምንቸቶቹን፣ መጫሪያዎቹን፣ መርጫ ጐድጓዳ ሳህኖቹን፣ ሜንጦዎቹንና የእሳት መያዣዎቹን ከናስ ሠሯቸው። 4ለመሠዊያውም ከጠርዝ በታች ሆኖ ከመሠዊያው ግማሽ ቁመት ላይ የሚሆን የናስ ፍርግርግ ማንደጃ ሠሩ። 5ለናሱ ፍርፍርግ ማንደጃ አራት ማእዘኖች መሎጊያዎቹን እንዲይዙ የናስ ቀለበቶችን ሠሩ። 6መሎጊያዎቹን ከግራር ዕንጨት ሠርተው በናስ ለበጧቸው። 7መሠዊያውን ለመሸከም በመሠዊያው ጐኖች ይሆኑ ዘንድ መሎጊያዎቹን በቀለበቶቹ ውስጥ አስገቧቸው፤ ውስጡንም ክፍት በማድረግ ከሳንቃዎች ሠሩት።

### የመታጠቢያው ሳሕን

8የናስ መታጠቢያ ሳሕንና የናስ መቆሚያውን በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ላይ ከሚያገለግሉት ሴቶች መስተዋት ሠሩት።

### አደባባዩ

38፥9-20 ተጓ ምብ - ዘፀ 27፥9-19

9ቀጥሎም አደባባዩን ሠሩ፤ የደቡቡ ክፍል ርዝመት አንድ መቶ ክንድ[ሸ] ሲሆን፣ በቀጭኑ ከተፈተለ በፍታ የተሠሩ መጋረጃዎች ነበሩት፤ 10ሃያ ምሰሶዎችና ሃያ የናስ መቆሚያዎች፣ የብር ኰላቦችና በምሰሶዎቹ ላይ ዘንጎች ነበሩት። 11የሰሜኑም ክፍል ቁመቱ አንድ መቶ ክንድ ነበር፤ ሃያ ምሰሶዎችና ሃያ የናስ መቆሚያዎች፣ የብር ኰላቦችና በምሰሶዎቹም ላይ ዘንጎች ነበሩት።

12የምዕራቡ ጫፍ ወርዱ አምሳ ክንድ[ቀ] ነበር፤ ዐሥር ምሰሶዎችና ዐሥር መቆሚያዎች እንዲሁም የብር ኰላቦችና በምሰሶዎቹም ላይ ዘንጎች ያሉት መጋረጃዎች ነበሩት። 13በፀሓይ መውጫ በኩል ያለው የምሥራቁም ጫፍ ወርዱ አምሳ ክንድ ነበር። 14ከሦስት ምሰሶዎችና ከሦስት መቆሚያዎች ጋር ርዝመታቸው ዐሥራ አምስት ክንድ[በ] የሆነ መጋረጃዎች በአንድ በኩል ባለው መግቢያ ላይ ነበሩ፤ 15ከሦስት ምሰሶዎችና ከሦስት መቆሚያዎች ጋር ርዝመታቸው ዐሥራ አምስት ክንድ የሆኑ መጋረጃዎች በአደባባዩ መግቢያ በሌላው በኩል ነበሩ።

16በአደባባዩ ዙሪያ ያሉት መጋረጃዎች በሙሉ በቀጭኑ ከተፈተለ በፍታ የተሠሩ ነበሩ። 17የምሰሶዎቹ መቆሚያዎች ናስ ነበሩ፤ ኰላቦቹና በምሰሶዎቹ ላይ ያሉት ዘንጎች ከብር የተሠሩ ነበሩ፤ ጫፎቻቸውም በብር ተለብጠው ነበር፤ ስለዚህ የአደባባዩ ምሰሶዎች ሁሉ የብር ዘንጎች ነበሯቸው።

18በአደባባዩ መግቢያ ላይ ያለው መጋረጃ ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊ፣ ከቀይ ማግና የጥልፍ ባለሙያ ከጠለፈው፣ በቀጭኑ ከተፈተለ በፍታ የተሠራ ነበር፤ ቁመቱ ሃያ ክንድ[ተ]፣ እንደ አደባባዩ መጋረጃዎች ከፍታው አምስት ክንድ ነበረ፤ 19አራት ምሰሶዎችና አራት መቆሚያዎች ነበሩት፤ ኰላቦቻቸውና ዘንጎቻቸው የብር ሲሆኑ፣ ጫፎቻቸው በብር ተለብጠው ነበር። 20የማደሪያው ድንኳንና የአደባባዩ ዙሪያ ካስማዎች ሁሉ ከናስ የተሠሩ ነበሩ።

### ለአገልግሎት የዋሉ ዕቃዎች

21ለማደሪያው ድንኳን፣ ይኸውም ለምስክሩ ድንኳን ሙሴ ባዘዘው፣ በካህኑ በአሮን ልጅ በኢታማር መሪነት ሌዋውያኑ በጻፉት መሠረት የዕቃዎቹ ቍጥር ይህ ነው። 22ከይሁዳ ነገድ የሆር የልጅ ልጅ፣ የኡሪ ልጅ የሆነው ባስልኤል፣ እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን ያዘዘውን ሁሉ አደረገ። 23ከእርሱም ጋር ከዳን ነገድ የሆነው የአሂሳማክ ልጅ ኤልያብ፣ ዕቅድ አውጭና የእጅ ጥበብ ባለሙያ፣ በሰማያዊ፣ በሐምራዊ፣ በቀይ

37፥25 ዘፀ27፥2፤ 30፥34-36፤ ሉቃ1፥11፤ዕብ9፥4፤ራእ8፥3፤9፥13
37፥27 ቀኍ14
37፥28 ዘፀ25፥13
37፥29 ዘፀ31፥11፤ 30፥1፡25፤39፥38
38፥2 2ዜና1፥5
38፥3 ዘፀ31፥9
38፥8 ዘፀ30፥18፤ 40፥7፤ዘዳ23፥17፤ 1ሳሙ2፥22፤ 1ነገ14፥24
38፥20 ዘፀ35፥18
38፥21 ዘኍ1፥50፡ 53፤4፥28፡33፤8፥24፤9፥15፤10፥11፤17፥7፤1ዜና23፥32፤ 2ዜና24፥6፤ ሐሥ7፥44፤ራእ15፥5
38፥22 ዘፀ31፥2
38፥23 ዘፀ31፥6

[መ]24 ወደ 34 ኪሎ ግራም ያህል ማለት ነው። [ሠ]25 ርዝመቱ ወርዱ 0.5 ሜትር ከፍታው 0.9 ሜትር ያህል ማለት ነው። [ሬ]1 ርዝመቱ 1.3 ሜትር ያህል ማለት ነው። [ሰ]1 ወይም ሥራ [ሸ]9 ወደ 46 ሜትር ያህል ነው። [ቀ]12 ወደ 23 ሜትር ያህል ነው። [በ]14 ወደ 6.9 ሜት ያህል ነው። [ተ]18 ወደ 9 ሜትር ያህል ነው።

ማግና በቀጭን በፍታ ጥልፍ ጠላፊ ነበር፡፡
24ለመቅደሱ ሥራ ሁሉ ከመወዝወዙ ስጦታ
በመቅደሱ ሰቅል መሠረት የዋለው ጠቅላላ
ወርቅ ሃያ ዘጠኝ መክሊትና ሰባት መቶ
ሠላሳ ሰቅል[ቸ] ነበረ፡፡
25በቈጠራው ወቅት ተቈጥረው ከነበሩት
ማኅበረሰብ የተገኘው ብር ለመቅደሱ ሰቅል
አንድ መቶ መክሊትና አንድ ሺህ ሰባት
መቶ ሰባ አምስት ሰቅሎች[ኀ] ነበሩ፤ 26ከተ
ቈጠሩት ጋር አብረው ከሆኑት ሃያና
ከሃያ ዓመት በላይ የሆናቸው ስድስት መቶ
ሦስት ሺህ አምስት መቶ አምሳ ሰዎች
የሰጡት እንደ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን በአ
ንድ ሰው አንድ ቤካ ይኸውም ግማሽ
ሰቅል[ነ] ነበረ፡፡ 27አንድ መቶ የብር መክሊ
ቶች[ኘ] የመቅደሱንና የመጋረጃዎቹን መቆሚ
ያዎች ለመሥራት አገልግሎት ላይ ውለው
ነበር፤ ይኸውም ከአንድ መቶ መክሊቶች
አንድ መቶ መቆሚያዎች ሲሆን፣ ለእያን
ዳንዱ መቆሚያ አንድ መክሊት ማለት
ነው፡፡ 28አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰባ አም
ስት ሰቅሎችን[አ] ለምሰሶዎቹ ኰላቦች፣ የም
ሰሶዎቹን አናት ለመለበጥና ዘንጎቻቸውንም
ለመሥራት አገልግሎት ላይ ውለው ነበር፡፡
29ከመወዝወዙ ስጦታ የሆነው ናስ ሰባ
መክሊትና ሁለት ሺህ አራት መቶ ሰቅል[ከ]
ነበረ፡፡ 30ለመገናኛው ድንኳን መግቢያ ለናስ
መሠዊያው ከናስ መጫሪያው፣ ለዕቃዎቹም
ሁሉ መቆሚያዎቹን ለመሥራት አገልግ
ሎት ላይ አውለውት ነበር፤ 31ለአደባባዩ
ዙሪያ፣ ለመግቢያው እንዲሁም ለማደሪያው
ድንኳን ካስማዎች ሁሉና ለአደባባዩ ዙሪያ
ሁሉ እንዲሁ አገልግሎት ላይ አውለውት
ነበር፡፡

## የካህናት አልባሳት

**39** ለመቅደሱ አገልግሎት ከሰማያዊ፣
ከሐምራዊና ከቀይ ማግ የተፈተሉ
ልብሶችን ሠሩ፤ እንዲሁም *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ሙሴን እንዳዘዘው ለአሮን የተቀደሱ
ልብሶችን ሠሩ፡፡

### ኤፉድ
39፥2-7 ተጓ ምብ - ዘፀ 28፥6-14

2ኤፉዱን ከወርቅ፣ ከሰማያዊ፣ ከሐምራ
ዊና ከቀይ ማግ፣ በቀጭኑ ከተፈተለ ሐር
ሠሩት[ኸ]፤ 3ጥበበኛ ባለሙያ እንደሚሠራው
በሰማያዊ፣ በሐምራዊ፣ በቀይ ማግና በቀ
ጭን በፍታ ይሠራ ዘንድ ወርቁን በስሱ
ቀጥቅጠው እንደ ክር ቈራረጡት፡፡ 4ለኤ
ፉዱ ከሁለቱ ጐኖቹ ጋር ተያይዘው ያሉትን
የትከሻ ንጣዮችን ሠሩ፤ ይኸውም ማያ
ያዝ እንዲቻል ነው፡፡ 5በጥበብ የተፈተለው
መታጠቂያ በተመሳሳይ መልክ ሆኖ *እግ
ዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዳዘዘው፣ ከኤ
ፉዱ ጋር አንድ ወጥ የሆነና ከወርቅ፣ ከሰ
ማያዊ፣ ከሐምራዊና ከቀይ ማግ፣ በቀጭኑ
ከተፈተለ ሐር የተሠራ ነበረ፡፡
6የከበሩ መረግዶችን በወርቅ ፈርጦች
በመክፈፍ፣ እንደ ማኅተም የእስራኤልን
ልጆች ስሞች ቀረጹባቸው፡፡ 7ከዚያም *እግ
ዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዳዘዘው በኤፉዱ
የትከሻ ንጣዮች ላይ ለእስራኤል ልጆች
እንደ መታሰቢያ ድንጋዮች አያያዟቸው፡፡

### የደረት ኪስ
39፥8-21 ተጓ ምብ - ዘፀ 28፥15-28

8የደረት ኪሱንም ጥበበኛ ባለሙያ እን
ደሚሠራው ሥራ በተመሳሳይ መንገድ ሠሩት፤
እንደ ኤፉዱም ከወርቅ፣ ከሰማያዊ፣ ከሐም
ራዊና ከቀይ ማግ በቀጭኑም ከተፈተለ
በፍታ ሠሩት፡፡ 9ርዝመቱ አንድ ስንዝር
ወርዱም አንድ ስንዝር[ሠ] ሲሆን፣ ጥንድ ድርብ
ሆኖ ባለ አራት ማእዘን ነበረ፡፡ 10ከዚያም
የከበሩ ድንጋዮችን በአራት ረድፍ በላዩ
ላይ አደረጉበት፤ በመጀመሪያው ረድፍ
ሰርድዮን፣ ቶጳዝዮንና የሚያብረቀርቅ ዕንቍ
ነበር፤ 11በሁለተኛውም ረድፍ በሉር፣ ሰን
ፔርና[ዐ] አልማዝ፣ 12በሦስተኛውም ረድፍ ያክ
ንት፣ ኬልቄዶንና አሜቴስጢኖስ፣ 13በአራ
ተኛውም ረድፍ ቢረሌ፣ መረግድና ኢያስጲድ[ዘ]
ነበረ፤ በወርቅ ፈርጥ ላይ ተደርገው ነበር፡፡
14ለእያንዳንዱ የእስራኤል ልጆች ስም አን
ዳንድ ሆኖ፣ በእያንዳንዱ ላይ እንደ ማኅተም
ከዐሥራ ሁለቱ ነገዶች የአንዱ ስም የተቀ
ረጸበት ዐሥራ ሁለት ድንጋዮች ነበሩ፡፡
15ለደረት ኪሱም ልክ እንደ ገመድ
ከንጹሕ ወርቅ የተጐነጐኑ ድሪዎችን አበጁ
ለት፡፡ 16ሁለት የወርቅ ፈርጦችንና ሁለት
የወርቅ ቀለበቶችን ሠርተው ቀለበቶቹን
ከደረት ኪሱ ሁለት ጐኖች ጋር አያያ
ዟቸው፡፡ 17ሁለቱን የወርቅ ድሪዎች በደ
ረት ኪሱ ጐንና ጐን ካሉት ቀለበቶች ጋር
አያያዟቸው፤ 18የድሪዎቹን ሌሎች ጫፎች
ከፊት ካለው ከኤፉዱ የትከሻ ንጣዮች ጋር
በማገናኘት ከሁለቱ የወርቅ ፈርጦች ጋር
አያያዟቸው፡፡ 19ሁለት የወርቅ ቀለበቶችን
ሠርተው ከኤፉዱ ቀጥሎ ካሉት ከሌሎቹ
ሁለት የደረት ኪስ ጐኖች ጋር ከውስጠ
ኛው ጠርዝ ላይ አያያዟቸው፡፡ 20ከዚያም
ሁለት ተጨማሪ የወርቅ ቀለበቶችን ሠር

38፥24 ዘፀ30፥13፡16
38፥25 ዘፀ30፥12
38፥26 ዘፀ12፥37፤ 30፥12፡13፡14፤
38፥27 ዘፀ26፥19
39፥1 ቍ41፤ ዘፀ28፥2፤35፥19፡23
39፥7 ዘሌ24፥7፤ ኢሱ4፥7
39፥8 ዘሌ8፥8
39፥14 ራእ21፥12

[ቸ]24 የወርቁ መጠን ወደ አንድ ሜትሪክ ቶን ያህል ነው፡፡ [ኀ]25 የብሩ መጠን 3.4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው፡፡ [ነ]26 ወደ 5.5 ግራም ያህል ነው፡፡ [ኘ]27 ወደ 3.4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው፡፡ [አ]28 ወደ 20 ኪሎ ግራም ያህል ነው፡፡ [ከ]29 የናሱ መጠን 2.4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው፡፡ [ኸ]2 በዚህ እንዲሁም በቍጥር 7፡8 እና 22 ላይ፣ *ሥራ*፡፡ [ሠ]9 ወደ 22 ሳንቲ ሜትር ያህል ነው፡፡ [ዐ]11 ወይም *ላፒስ ላዙሊ* [ዘ]13 ከእነዚህ የከበሩ ማዕድኖች መካከል አንዳንዶቹ ማንነታቸው አይታወቅም፡፡

ተው ልክ ከኤፉዱ መታጠቂያ በላይ፣
ከመጋጠሚያው አጠገብ፣ ከኤፉዱ ፊት
ለፊት ካሉት ከትከሻ ንጣዮች ጋር አያያ
ዟቸው። 21እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዳ
ዘዘው የደረት ኪሱ ከኤፉዱ ተነጥሎ ለብ
ቻው እንዳይንጠለጠል የደረት ኪሱን ቀለበ
ቶች ከመታጠቂያው ጋር በማገናኘት፣ ከኤ
ፉዱ ቀለበቶች ጋር በሰማያዊ ፈትል አሠ
ሯቸው።

## ሌሎች የክህናት አልባሳት

39፥22-31 ተጓ ምብ - ዘፀ 28፥31-43

22የኤፉዱን ቀሚስ በሸማኔ ሥራ ሙሉ
በሙሉ ከሰማያዊ ጨርቅ ሠሩት፤ 23ይህም
እንደ ክሳዱ ቀድ ከቀሚሱ መካከል ላይ
አንገትጌ[ዡ] ነበረው፤ እንዳይተረተርም በአንገ
ትጌው ዙሪያ ላይ ቅምቅማት ነበረው።
24በቀሚሱ ጠርዝ ዙሪያ ከሰማያዊ፣ ከሐም
ራዊና ከቀይ ማግ እንዲሁም በቀጭኑ ከተፈተለ
በፍታ ላይ ሮማኖቹን አደረጉ። 25ከንጹሕ
ወርቅም ሻኩራዎችን ሠሩ፤ እነዚህንም በሮ
ማኖቹ መካከል በጠርዙ ዙሪያ አደረጉ።
26እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዳዘዘው
ለአገልግሎት ይለበሱ ዘንድ ሻኩራዎቹና ሮማ
ኖቹ በቀሚሱ ጠርዝ ዙሪያ ላይ ተሰባጥ
ረው ይገኙ ነበር።

27ለአሮንና ለወንዶች ልጆቹ የሸማኔ ሥራ
የሆነውን ከቀጭን በፍታ ሸሚዞችን ሠሩ፤
28እንዲሁም ከቀጭን በፍታ ጥምጥምን፣ የሐር
ቆቦቹንና በቀጭኑ ከተፈተለም በፍታ ሱሪዎ
ችን ሠሩ። 29መታጠቂያው እግዚአብሔር
(ያህዌ) ሙሴን እንዳዘዘው በቀጭኑ ከተፈ
ተለ በፍታና ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊና ከቀይ
ማግ፣ የጥልፍ ጠላፊ ሥራ ሆኖ የተሠራ
ነበረ።

30ከንጹሕ ወርቅ የተቀደሰውን አክሊል
ሰሌዳ ሠርተው፣ በማኅተም ላይ እንደ ተቀ
ረጸ ጽሑፍ፣ "ቅዱስ ለእግዚአብሔር (ያዌ)"
የሚል ቀረጹበት፤ 31ከዚያም እግዚአብሔር
(ያህዌ) ሙሴን እንዳዘዘው ከመጠምጠሚያው
ጋር ለማያያዝ ሰማያዊ ፈትል አሠሩበት።

## ሙሴ የማደሪያውን ድንኳን መቈጣጠሩ

39፥32-41 ተጓ ምብ - ዘፀ 35፥10-19

32በዚህ መሠረት የማደሪያው ድንኳን፣
የመገናኛው ድንኳን ሥራ በሙሉ ተጠና
ቀቀ፤ እስራኤላውያን ልክ እግዚአብሔር
(ያህዌ) ሙሴን እንዳዘዘው ሁሉን ነገር ሠሩ።
33ከዚያም የማደሪያውን ድንኳን ወደ ሙሴ
አመጡት፤ እነዚህም ድንኳንና ዕቃዎቹ ሁሉ፣
ማያያዣዎቹ፣ ክፈፎቹ፣ አግዳሚዎቹ፣ ምሰ
ሶዎቹና መቆሚያዎቹ፤ 34ቀይ ከተነከረ የአ
ውራ በግ ቆዳ የተሠራ መደረቢያ፣ የለፋ
የአቆስጣ ቆዳ[የ] መደረቢያና መከለያ መጋረጃ፤

39፥27 ዘሌ6፥10፤
8፥2
39፥28 ቀኍ31፤
ዘፀ28፥4፤ዘሌ8፥9፤
ኢሳ61፥10
39፥30 ኢሳ23፥18፤
ዘካ14፥20
39፥31 ቀኍ28
39፥32 ዘፀ25፥9
39፥33 ዘፀ25፥8-
40፤36፥8-38
39፥35 ዘፀ37፥1
39፥36 ዘፀ25፥23፡
30፤37፥10-16
39፥37 ዘፀ25፥6፡
31-39
39፥38 ዘፀ30፥
1-10፡22-32፡34-38፤
36፥35፤37፥25-29
39፥39 ዘፀ27፥1-8፤
30፥18፤38፥1-7
39፥40 ዘፀ27፥9-19፤
38፥9-20
39፥41 ቀኍ1
39፥42 ዘፀ25፥9
39፥43 ዘፍ31፥55፤
ዘፀ25፥9፤35፥10፤
ዘሌ9፥22፡23፤ዘኍ
6፥23-27፤ዘዳ21፥5፤
26፥15፤2ሳሙ6፥18፤
1ነገ8፥14፡55፤1ዜና
16፥2፤2ዜና30፥27
40፥2 ቀኍ17፡34፡
35፤ዘፀ12፥2፤26፥30፤
ዘሌ1፥1፤3፥2፤6፥26፤
9፥23፤16፥16፤
ዘኍ1፥1፤7፥89፤9፥1፤1
1፥16፤17፥4፤20፥6፤ኢ
ሱ18፥1፤19፥51፤
ኤር7፥12
40፥3 ዘፀ26፥33
40፥4 ዘፀ25፥23፡
30፡31
40፥5 ዘፀ30፥1
40፥6 ዘፀ27፥1፤
2ነገ16፥14፤2ዜና4፥1
40፥7 ዘፀ30፥18
40፥8 ዘፀ27፥9
40፥9 ዘፀ30፥26፤
ዘኍ7፥1
40፥10 ዘፀ29፥36
40፥12 ዘፀ29፥4፤

35የምስክሩ ታቦት፣ ከመሎጊያዎቹና ከስር
የት መክደኛው ጋር፤ 36ጠረጴዛው ከዕቃ
ዎቹ ሁሉና ከኅብስተ ገጹ ጋር፤ 37ከንጹሕ
ወርቅ የሆነው መቅረዝ ከተደረደሩት
መብራቶችና ከዕቃዎቹ ሁሉ ጋር፣ የመብ
ራቱም ዘይት፣ 38የወርቅ መሠዊያው፣ ቅብዐ
ዘይቱ፣ መልካም መዐዛ ያለው ዕጣን እንዲ
ሁም የድንኳኑ መግቢያ መጋረጃ፣ 39የናስ
መሠዊያው ከናስ መጫሪያው፣ መሎጊያ
ዎቹና ዕቃዎቹ ሁሉ ጋር፤ የመታጠቢያው
ሳሕን ከነማስቀመጫው፣ 40የአደባባዩ መጋረጃ
ዎች ከምሰሶዎቹና ከመቆሚያዎቹ ጋር፣ የአደ
ባባዩ መግቢያ መጋረጃ፣ ገመዶቹና የአደ
ባባዩ ድንኳን ካስማዎች፣ የማደሪያው
የመገናኛው ድንኳን ዕቃዎች ሁሉ፤ 41በመ
ቅደሱ ሲያገለግሉ የሚለበሱት የተፈተሉት
ቀሚሶች፣ ለካህኑ ለአሮን የተቀደሱት ቀሚ
ሶችና ወንዶች ልጆቹ ካህናት ሆነው ሲያገለ
ግሉ የሚያደርጓቸው ቀሚሶች ናቸው።

42እስራኤላውያን ልክ እግዚአብሔር (ያህዌ)
ሙሴን እንዳዘዘው ሥራውን ሁሉ አከና
ወኑ። 43ሙሴ ሥራውን አየ፤ ልክ እግዚአ
ብሔር (ያህዌ) እንዳዘዘው መሥራታቸውንም
ተመለከተ፤ ስለዚህ ባረካቸው።

## የማደሪያውን ድንኳን መትከል

40 ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን
አለው፤ 2"ማደሪያውን ይኸውም
የመገናኛውን ድንኳን በወሩ የመጀመሪያ
ቀን ትከለው፤ 3የምስክሩን ታቦት በውስጡ
አኑር፤ ታቦቱንም በመጋረጃው ጋርደው።
4ጠረጴዛውንም ወደ ውስጥ አምጥተህ ዕቃ
ዎቹን በላዩ ላይ አሰናዳ፤ ከዚያም መቅረ
ዙን አስገብተህ መብራቶቹን በቦታቸው አስ
ቀምጥ። 5የዕጣኑን የወርቅ መሠዊያ በምስ
ክሩ ታቦት ፊት ለፊት አስቀምጠው፤ ከማ
ደሪያውም መግቢያ ላይ መጋረጃውን አድርግ።

6"የሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊያውን
በማደሪያው መግቢያ ፊት ለፊት፣ በመገ
ናኛው ድንኳን አስቀመጠው። 7የመታጠቢ
ያውን ሰን በመገናኛው ድንኳንና በመሠዊ
ያው መካከል አኑርበት፤ ውሃም አኑርበት።
8በዙሪያውም የአደባባዩን ቅጥር ትከል፤
መጋረጃውንም በአደባባዩ መግቢያ ላይ አድ
ርገው።

9"ቅብዐ ዘይቱን ወስደህ ማደሪያውንና
በውስጡ ያለውን ሁሉ ቅባ፤ እርሱንና ዕቃ
ውን ሁሉ ቀድስ፤ የተቀደሰም ይሆናል።
10ከዚያም የሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊያ
ውንና ዕቃዎቹን ሁሉ ቅባ፤ መሠዊያውን
ቀድስ እጅግም የተቀደሰ ይሆናል። 11የመ

[ዡ]23 በዕብራይስጡ የዚህ ቃል ትርጒም በትክክል አይታወቅም።
[የ]34 ይህ የባሕር አውሬ ነው።

*ታጠቢያው ሰንና ማስቀመጫውን ቅባ፤*
*ቀድሳቸውም።*
12“*አሮንና ወንዶች ልጆቹን ወደ መገና*
*ኛው ድንኳን መግቢያ አምጥተህ በውሃ እጠ*
*ባቸው።* 13*ከዚያም አሮንን የተቀደሰውን*
*ልብስ አልብሰው፤ ካህን ሆኖ ያገለግለኝ*
*ዘንድ ቅባው፤ ቀድሰውም* 14*ወንዶች ልጆቹን*
*አምጥተህ ሸሚዝ አልብሳቸው።* 15*ካህናት*
*ሆነው ያገለግሉኝ ዘንድ ልክ አባታቸውን*
*እንደ ቀባህ ቅባቸው፤ መቀባታቸውም በሚ*
*መጡት ትውልዶች ሁሉ ለሚቀጥል ክህ*
*ነት ነው።”* 16*ሙሴ ሁሉንም ነገር ልክ*
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) *እንዳዘዘው አደረገ።*
17*እንዲሁም በሁለተኛው ዓመት፣ የመ*
*ጀመሪያው ወር በገባ በመጀመሪያው ቀን*
*የማደሪያው ድንኳን ተተከለ።* 18*ሙሴ*
*የማደሪያውን ድንኳን በተከለ ጊዜ፣ መቆ*
*ሚያዎቹን በቦታቸው አኖረ፤ ወጋግራዎቹን*
*አቆመ አግዳሚዎቹን አስገባ፤ ምሰሶዎቹንም*
*ተከለ።* 19*ከዚያም እግዚአብሔር* (ያህዌ) *እንዳዘ*
*ዘው ድንኳኑን በማደሪያው ላይ፣ መደረቢ*
*ያውንም በድንኳኑ ላይ ዘረጋው።*
20*ምስክሩን ወስዶ በታቦቱ ውስጥ አስቀ*
*መጠው፤ መሎጊያዎቹንም ከታቦቱ ጋር*
*አያያዛቸው፤ የስርየት መክደኛውንም በላዩ*
*ላይ አደረገው።* 21*ከዚያም እግዚአብሔር*
(ያህዌ) *እንዳዘዘው ታቦቱን ወደ ማደሪያው ድን*
*ኳን አስገብቶ መከለያ መጋረጃውን ሰቀለ፤*
*የምስክሩንም ታቦት ጋረደው።*
22*ሙሴ ጠረጴዛውን በመገናኛው ድንኳን*
*ውስጥ፣ ከማደሪያው በስተ ሰሜን ከመጋረ*
*ጃው ውጭ አኖረው፤* 23*እግዚአብሔር* (ያህዌ)
*እንዳዘዘውም ኅብስቱን በላዩ ላይ በእግዚ*
*አብሔር* (ያህዌ) *ፊት አኖረ።*
24*መቅረዙን በመገናኛው ድንኳን ውስጥ*
*ከጠረጴዛው ትይዩ ከማደሪያው ድንኳን በስተ*
*ደቡብ በኩል አኖረው፤* 25*እግዚአብሔር*
(ያህዌ) *እንዳዘዘውም መብራቶቹን በእግዚ*
*አብሔር* (ያህዌ) *ፊት አበራ።*

26*ሙሴ የወርቅ መሠዊያውን በመገና*
*ኛው ድንኳን ውስጥ ከመጋረጃው ፊት*
*ለፊት አኖረው፤* 27*እግዚአብሔር* (ያህዌ) *እንዳ*
*ዘዘውም መልካም መዐዛ ያለውን ዕጣን*
*አጠነበት።* 28*ከዚያም መጋረጃውን በማደሪያው*
*ድንኳን መግቢያ ላይ ሰቀለው።*
29*የሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊያውንም*
*በማደሪያው፣ በመገናኛው ድንኳን መግቢያ*
*ላይ አኖረው፤ እግዚአብሔር* (ያህዌ) *እንዳዘ*
*ዘውም የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የእህ*
*ሉን መሥዋዕት በላዩ ላይ አቀረበ።*
30*የመታጠቢያውን ሰን በመገናኛው ድን*
*ኳንና በመሠዊያው መካከል አስቀመጠ፤*
*ለመታጠቢያም ውሃ አደረገበት፤* 31*ሙሴና*
*አሮን፣ ወንዶች ልጆቹም እጆቻቸውንና*
*እግሮቻቸውን ይታጠቡበት ነበር።* 32*እግዚ*
*አብሔር* (ያህዌ) *ሙሴን እንዳዘዘው ወደ መገ*
*ናኛው ድንኳን በገቡና ወደ መሠዊያው*
*በቀረቡ ቍጥር ይታጠቡ ነበር።*
33*ከዚያም ሙሴ በማደሪያውና በመሠዊ*
*ያው ዙሪያ አደባባዩን ተከለ፤ በአደባባዩም*
*መግቢያ ላይ መጋረጃውን ሰቀለ፤ እንደዚህ*
*አድርጎ ሙሴ ሥራውን ፈጸመ።*

### *የእግዚአብሔር ክብር*

34*ከዚያም ደመናው የመገናኛውን ድን*
*ኳን ሸፈነ፤ የእግዚአብሔርም* (ያህዌ) *ክብር ማደ*
*ሪያውን ሞላ።* 35*ደመናው በላዩ ላይ ስለ*
*ነበረና የእግዚአብሔርም* (ያህዌ) *ክብር ማደ*
*ሪያውን ስለሞላው፣ ሙሴ ወደ መገናኛው*
*ድንኳን መግባት አልቻለም።*
36*በእስራኤላውያን ጕዞ ሁሉ ደመናው*
*ከማደሪያው ላይ በተነሣ ጊዜ፣ ይጓዙ ነበር፤*
37*ደመናው ካልተነሣ ግን፣ እስከሚነሣበት*
*ቀን ድረስ አይጓዙም ነበር።* 38*ስለዚህ በጕዞ*
*አቸው ሁሉ ወቅት፣ በእስራኤል ቤት*
*ፊት ሁሉ የእግዚአብሔር* (ያህዌ) *ደመና በቀን*
*ከማደሪያው በላይ፣ በሌሊትም እሳቱ በደመ*
*ናው ውስጥ ነበር።*

30፥19፤ዘኍ8፥9
**40፥13** ዘፀ28፥41፤ ዘሌ8፥12
**40፥14** ዘፀ28፥40፤ ዘሌ10፥5
**40፥15** ዘፀ29፥9
**40፥16** ዘፍ6፥22
**40፥17** ቍ2፤ ዘኍ7፥1
**40፥18** ዘፀ36፥20-34፤2ዜና1፥3
**40፥19** ዘፍ 6፥22፤ዘፀ36፥19
**40፥20** ዘፀ16፥34፤ ዕብ 9፥4፤ 25፥21፤ 25፥17-22፤26፥34፤ 31፥7
**40፥21** ዘፍ6፥22፤ ዘፀ26፥33
**40፥22** ዘፀ25፥23
**40፥23** ዘፍ6፥22፤ ዘፀ25፥30፤ዘሌ24፥5-8፤
**40፥24** ዘፀ25፥31
**40፥25** ዘፍ6፥22፤ ዘፀ37፥23
**40፥26** ዘፀ30፥1
**40፥27** ዘፍ6፥22
**40፥28** ዘፀ26፥36
**40፥29** ዘፍ6፥22፤ ዘፀ20፥24፤29፥38-42
**40፥30** ቍ7፤ዘፀ 30፥18
**40፥31** ዘፀ30፥19-21
**40፥32** ዘፍ6፥22፤ ዘፀ30፥20
**40፥33** ዘፀ27፥9፡ 16፤38፥9-20
**40፥34** ዘፀ16፥7፤ 19፥16፤ዘሌ16፥2፤ዘኍ 9፥15-23፤1ነገ8፥12፤ 2ዜና5፥13ኢሳ6፥4፤ ሕዝ10፥4፤ዮሐ1፥14፤ 12፥41፤ራእ15፥8
**40፥35** ዘፀ16፥10፤ 1ነገ8፥11፤2ዜና5፥ 13-14፤7፥2
**40፥36** ዘኍ9፥17-23፤10፥13
**40፥38** ዘፀ13፥21፤ 1ቆሮ10፥1

# ኦሪት ዘሌዋውያን

## የሚቃጠል መሥዋዕት

1 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን ጠራው፤ ከመገ
ናኛውም ድንኳን እንዲህ ሲል ተናገረው፤
2“እስራኤላውያንን ተናገራቸው፤ እንዲህም
በላቸው፤ ከእናንተ ማንም ሰው ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) ከእንስሳ ወገን መባ በሚያቀርብበት
ጊዜ ከላሙ፣ ከበጉ፣ ወይም ከፍየሉ መንጋ
መካከል ያቅርብ።
3“ ‘መባው በሚቃጠል መሥዋዕትነት ከላ
ሞች መንጋ መካከል የሚቀርብ ከሆነ፣ እን
ከን የሌለበትን ተባዕቱን መሥዋዕት በእግዚ
አብሔር (ያህዌ) ዘንድ ተቀባይነት እንዲ
ያገኝ በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ላይ
ያቅርበው። 4የሚቃጠል መሥዋዕት ሆኖ
በሚቀርበው እንስሳ ራስ ላይም እጁን
ይጫን፤ ይህም ያስተሰርይለት ዘንድ
በምትኩ ተቀባይነት ያገኛል። 5ወይፈኑን
በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ይረደው፤ ካህናቱ
የአሮን ልጆችም ደሙን አምጥተው በመገና
ኛው ድንኳን ደጃፍ ባለው በመሠዊያው
ዙሪያ ሁሉ ይርጩት። 6እርሱም የሚቃጠ
ለውን መሥዋዕት ቈዳ ይግፈፍ፤ ብልቱንም
ያውጣው። 7የካህኑ የአሮን ልጆች በመ
ሠዊያው ላይ ዕንጨት ረብርበው እሳት
ያንድዱበት። 8ካህናቱ የአሮን ልጆች ጭንቅ
ላቱንና ሥቡን ጨምረው ብልቶቹን በመ
ሠዊያው ላይ በሚነደው ዕንጨት ላይ
ይደር ድሩት፤ 9አቅራቢው የሆድ ዕቃውንና
እግሮቹን በውሃ ይጠብ፤ ካህኑም መባውን
ሁሉ በመሠዊያው ላይ ያቃጥል፤ ይህም
በእሳት የሚቀርብ፣ ሽታውም እግዚአብሔርን
(ያህዌ) ደስ የሚያሰኝ የሚቃጠል መሥዋዕት
ይሆናል።
10“ ‘መባው በሚቃጠል መሥዋዕትነት
ከበግ ወይም ከፍየል መንጋ መካከል የሚቀ
ርብ ከሆነ፣ እንከን የሌለበትን ተባዕቱን
ያቅርብ። 11የሚቀርበውን መሥዋዕት ከመ
ሠዊያው በስተ ሰሜን በኩል በእግዚአብሔር
(ያህዌ)ፊት ይረደው፤ ካህናቱ የአሮን ልጆ
ችም ደሙን በመሠዊያው ላይ ዙሪያውን
ሁሉ ይርጩት። 12አቅራቢው ብልቶቹን
ያውጣ፤ ካህኑም ጭንቅላቱንና ሥቡን
ጨምሮ በመሠዊያው ላይ በሚነደው ዕ
ንጨት ላይ ይደርድረው፤ 13አቅራቢው
የሆድ ዕቃውንና እግሮቹን በውሃ ይጠብ፤
ካህኑ መባውን ሁሉ አምጥቶ በመሠዊያው
ያቃጥል፤ ይህም በእሳት የሚቀርብ፣
ሽታውም እግዚአብሔርን (ያህዌ) ደስ
የሚያሰኝ የሚቃጠል መሥዋዕት
ይሆናል።
14“ ‘ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በሚቃጠል መሥ
ዋዕትነት የሚቀርበው መባ ከወፎች ወገን
ከሆነ፣ ዋኖስ ወይም የርግብ ጫጩት ያቅ
ርብ። 15ካህኑም ወደ መሠዊያው ያምጣው፤
ራሱን ቈልምሞ ይቀንጥሰው፤ የተቈረጠ
ውንም ራስ በመሠዊያው ላይ ያቃጥል፤
ደሙም በመሠዊያው አጠገብ ይንጠፍጠፍ፤
16ከሆድ ዕቃውም ጥሬ ቤቱን[ሀ] ለይቶ ከላባ
ዎቹ ጋር ከመሠዊያው በስተ ምሥራቅ
በኩል፣ ዐመድ በሚፈስበት ስፍራ ይጣ
ለው። 17በክንፎቹ በኩል ለሁለት ይሰንጥ
ቀው፤ ነገር ግን ጨርሶ አያለያየው፤ ካህ
ኑም በመሠዊያው ላይ በሚነደው ዕንጨት
ላይ ያቃጥለው፤ ይህም በእሳት የሚቀርብ፣
ሽታውም እግዚአብሔርን (ያህዌ) ደስ የሚያሰኝ
የሚቃጠል መሥዋዕት ይሆናል።”

## የእህል ቍርባን

2 “ ‘ማንኛውም ሰው የእህል ቍርባን
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በሚያቀርብበት
ጊዜ፣ ዱቄቱ የላመ ይሁን፤ ዘይት ያፍስበት፤
ዕጣንም ይጨምርበት፤ 2ወደ ካህናቱም ወደ
አሮን ልጆች ያምጣው። ካህኑ ከላመው
ዱቄትና ከዘይቱ አንድ እፍኝ ሙሉ ያንሣ
ለት፤ ዕጣኑንም ሁሉ ይውሰደው፤ ይህንም
በእሳት የሚቀርብ፣ ሽታውም እግዚአብሔርን
(ያህዌ) ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት አድርጎ
ለመታሰቢያ በመሠዊያው ላይ ያቃጥለው።
3የተረፈውም የእህሉ ቍርባን ለአሮንና
ለልጆቹ ይሰጥ፤ ይህም ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) በእሳት ከሚቀርበው ቍርባን እጅግ
የተቀደሰ ክፍል ነው።
4“ ‘በማብሰያ ምድጃ የተጋገረ የእህል
ቍርባን በምታቀርብበት ጊዜ፣ ከላመ
ዱቄት ተዘጋጅቶ እርሾ ሳይገባበት በዘይት
ተለውሶ የተጋገረ ኅብስት ይሁን፤ አለዚ
ያም[ለ] ያለ እርሾ በስሱ ተጋግሮ ዘይት
የተቀባ ቂጣ ይሁን። 5የእህል ቍርባንህ
በምጣድ የሚጋገር ከሆነ፣ እርሾ ሳይገባበት
በዘይት ከተለወሰ ከላመ ዱቄት ይዘጋጅ።
6ቈራርሰህ ዘይት አፍስበት፤ ይህ የእህል

1፥1 ዘፀ3፥4፤ 25፥22፤27፥21፤40፥2
1፥2 ዘሌ7፥16፡38፤ 22፥21፤23፥38፤ 27፥9፤22፥18-19፤ ዘኍ15፥3
1፥3 ቀ5፡10፤ ዘፍ8፥20፤ዘፀ12፥5፤ ዘሌ6፥25፤17፥9፤ 22፥19፡20፡27፤ ዘኍ6፥16፤ዘዳ12፥ 5-6፡11፤ዕዝ8፥35፤ ኢሳ58፥5፤ ሚል1፥8፤ዕብ9፥14፤ 1ጴጥ1፥19
1፥4 ቀ3፤ ዘፍ32፥20፤ዘፀ29፥10፡ 15፡36፤32፥30፤ ዘሌ4፥29፤6፥25፤ ሕዝ45፥15፤
1፥5 ቀ3፤ ዘፀ29፥1፡11፡20፤ ዘሌ3፥2፡8፤8፥2፤10፥6፤ 21፥1፤ዘኍ15፥8፤ ዘዳ18፥3፤መዝ50፥9፤ 69፥31፤ዕብ12፥24፤ 1ጴጥ1፥2
1፥6 ዘፀ29፥17፤ ዘሌ7፥8፤
1፥7 ቀ17፤ ዘፍ22፥9፤ ዘሌ3፥5፤6፥12
1፥8 ቀ12፤ዘፀ 29፥13፤ዘሌ8፥20፤ 9፥13
1፥9 ቀ3፡13፤ዘፍ8፥21፤ ዘፀ 29፥17፡18፤ዘሌ2፥2፤3፥ 5፡16፤6፥22፤9፥14፤17፥ 6፤23፥8፡25፡36፤ ዘኍ18፥17፤ 8፥6፡11- 13፡19፤ኤፌ5፥2
1፥10 ቀ3፤ ዘፍ22፥7፤ ዘፀ12፥5፤ዘሌ3፥12፤ 4፥23፡28፤5፥6፤ ዘኍ15፥11
1፥11 ዘፀ29፥11፡20
1፥12 ቀ8
1፥13 ቀ9፤ ዘፀ29፥17፤ ዘሌ6፥22፤ዘዳ12፥27
1፥14 ዘፍ15፥9፤ ሉቃ2፥24
1፥15 ዘሌ5፥8፡9
1፥16 ዘሌ4፥12፤ 6፥10፤ዘኍ4፥13
1፥17 ቀ7፤ ዘፍ15፥10
2፥1 ቀ2፡15፡16፤ ዘፀ29፥2፡40፡41፤ ዘሌ5፥11፤6፥14-18፤ 7፥12፤24፥7፤ ዘኍ15፥4፤28፥5፤ ነህ13፥9፤ኢሳ43፥23
2፥2 ቀ9፡16፤ ዘሌ1፥9፤5፥11፡12፤6፥15፤24፥7፤ዘኍ5፥26፤18፥8፤መዝ16፥5፤ 73፥26፤ኢሳ1፥13፤53፥12፤ 5፥6፤66፥3
2፥3 ቀ10፤ ዘፀ30፥36፤ ዘሌ6፥16፤10፥2፡13
2፥4 ዘፀ29፥2፤ዘሌ7፥9፡12፤ 8፥26፤ 26፥26
2፥5 ዘሌ6፥21፤ 7፥9፤ሕዝ4፥3

[ሀ]16 ለዚህ ቃል የዕብራይስጡ ትርጓሜ በእርግጠኝነት አይታወቅም።
[ለ]4 ወይም እንዲሁም

ቍርባን ነው። 7የእህል ቍርባንህ በመጥ
በሻ የሚበስል ከሆነ፣ ከላመ ዱቄትና ከዘይት
ይዘጋጅ። 8በዚህ ሁኔታ የተዘጋጀውን የእህል
ቍርባን ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ) አምጥተህ
ለካህኑ አስረክብ፤ ካህኑም ወደ መሠዊያው
ይወስደዋል፤ 9ከእህሉም ቍርባን ላይ ለመ
ታሰቢያ የሚሆነውን ክፍል ያነሣና በእሳት
የሚቃጠል፣ ሽታውም እግዚአብሔርን
(ያህዌ) ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት አድርጎ
በመሠዊያው ላይ ያቃጥለዋል።
10የተረፈውም ቍርባን ለአሮንና ለልጆቹ
ይሰጥ፤ ይህም ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
በእሳት ከሚቀርበው ቍርባን እጅግ
የተቀደሰ ክፍል ነው።

11" 'ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በእሳት በም
ታቀርቡት ቍርባን ውስጥ እርሾ ወይም
ማር ጨምራችሁ ማቃጠል ስለማይገባችሁ፣
በምታቀርቡት በማንኛውም የእህል ቍርባን
እርሾ አይኑርበት። 12እነዚህን የበኵራት
ቍርባን አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
ማቅረብ ትችላላችሁ፤ ነገር ግን ሽታው
ደስ የሚያሰኝ ቍርባን ሆነው በመሠዊያ
ላይ ለመቃጠል አይቀርቡም። 13የምታቀር
በውን የእህል ቍርባን ሁሉ በጨው
ቀምመው፤ የአምላክህ (ኤሎሂም) የቃል ኪዳን ጨው
ከእህል ቍርባንህ አይታጣ፤ በቍርባንህም
ላይ ጨው ጨምርበት።

14" 'የእህል በኵራት ቍርባን ለእግዚ
አብሔር (ያህዌ) በምታመጣበት ጊዜ፣ የተ
ፈተገና በእሳት የተጠበሰ እሸት አቅርብ።
15ዘይት ጨምርበት፤ ዕጣንም በላዩ አስቀ
ምጥ፤ ይህ የእህል ቍርባን ነው። 16ካህኑም
ከተፈተገው እህልና ከዘይቱ ወስዶ፣ ከዕ
ጣኑ ሁሉ ጋር ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በእሳት
የሚቀርብ መታሰቢያ አድርጎ ያቃጥል።

## የኅብረት መሥዋዕት

3 " 'ማንኛውም ሰው የሚያቀርበው ቍር
ባን ከላሞች መንጋ የሚቀርብ የኅብረት
መሥዋዕት[ሐ] ከሆነ፣ እንከን የሌለበትን
ተባዕት ወይም እንስት በእግዚአብሔር
(ያህዌ) ፊት ያቅርብ። 2በሚያቀርበው እንስሳ
ራስ ላይ እጁን ይጫን፤ በመገናኛው ድንኳን
ደጃፍ ላይ ይረደው፤ ካህናቱም የአሮን ልጆች
ደሙን በመሠዊያው ላይ ዙሪያውን ይር
ጩት። 3ከኅብረት መሥዋዕቱ ለእግዚ
አብሔር (ያህዌ) በእሳት የሚቀርብ ቍርባን
አድርጎ ያምጣ፤ የሆድ ዕቃውን የሚሸፍ
ነውን ሥብ፣ በሆድ ዕቃው ላይ ያለውን
ሥብ ሁሉ፣ 4ሁለቱን ኵላሊቶች፣ በኵላሊ
ቶቹ ላይና በጐድኑ አጠገብ ያለውን ሥብ
እንዲሁም የጕበቱን መሸፈኛ ከኵላሊቶቹ
ጋር አንድ ላይ አውጥቶ ያቅርብ። 5የአሮንም
ልጆች በመሠዊያው በሚነደው ዕንጨት
ላይ ባለው በሚቃጠለው መሥዋዕት ላይ
አድርገው ያቃጥሉት፤ ይህም በእሳት የሚ
ቀርብ፣ ሽታውም እግዚአብሔርን (ያህዌ) ደስ
የሚያሰኝ መሥዋዕት ይሆናል።

6" 'ከበግ ወይም ከፍየሉ መንጋ ለእግ
ዚአብሔር (ያህዌ) የኅብረት መሥዋዕት የሚያቀ
ርብ ከሆነ፣ እንከን የሌለበትን ተባዕት
ወይም እንስት ያቅርብ። 7መሥዋዕቱ
የበግ ጠቦት ከሆነም፣ በእግዚአብሔር (ያህዌ)
ፊት ያምጣው፤ 8በጠቦቱ ራስ ላይ እጁን
ይጫን፤ በመገናኛው ድንኳን ፊት ለፊት
ይረደው፤ የአሮንም ልጆች ደሙን በመ
ሠዊያው ላይ ዙሪያውን ይርጩት። 9ከኅብ
ረት መሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በእ
ሳት የሚቀርብ ቍርባን አድርጎ ያምጣ፤
ሥቡን፣ እስከ ጀርባ ዐጥንቱ ድረስ የተቈረጠ
ላቱን በሙሉ፣ የሆድ ዕቃውን የሸፈነውን
ሥብ፣ ከሆድ ዕቃው ጋር የተያያዘውን
ሥብ ሁሉ፣ 10ሁለቱን ኵላሊቶች፣ ኵላሊ
ቶቹ ላይና በጐድኑ አጠገብ ያለውን ሥብ
እንዲሁም የጕበቱን መሸፈኛ ከኵላሊቶቹ
ጋር አብሮ አውጥቶ ያቅርብ። 11ካህኑም
ይህን ሁሉ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በእሳት
የሚቀርብ የመብል ቍርባን አድርጎ በመ
ሠዊያው ላይ ያቃጥል።

12" 'መሥዋዕቱ ፍየል ከሆነ፣ በእግዚ
አብሔር (ያህዌ) ፊት ያቅርብ፤ 13በራሱም ላይ
እጁን ይጫንበት፤ በመገናኛው ድንኳን ፊት
ለፊት ይረደው፤ የአሮንም ልጆች ደሙን
በመሠዊያው ላይ ዙሪያውን ይርጩት።
14ከሚያቀርበውም መሥዋዕት ላይ ለእግዚ
አብሔር (ያህዌ) በእሳት የሚቀርብ ቍርባን
አድርጎ ያቅርብ፤ የሆድ ዕቃውን የሚሸፍ
ነውን ሥብ፣ ከሆድ ዕቃው ጋር የተያያ
ዘውን ሥብ ሁሉ፣ 15ሁለቱን ኵላሊቶች፣
በኵላሊቶቹ ላይና በጐድኑ አጠገብ ያለውን
ሥብ፣ እንዲሁም የጕበቱን መሸፈኛ
ከኵላሊቶቹ ጋር አብሮ አውጥቶ
ያቅርብ። 16ካህኑም ይህን ሁሉ በእሳት
የሚቀርብና ሽታውም ደስ የሚያሰኝ
የመብል ቍርባን አድርጎ በመሠዊያው
ላይ ያቃጥል፤ ሥብ ሁሉ የእግዚአብሔር
(ያህዌ) ነው።

17" 'በምትኖሩበት ስፍራ ሁሉ፣ ሥብ
ወይም ደም ከቶ አትብሉ፤ ይህ ለመጪው
ትውልድ ሁሉ የተሰጠ የዘላለም ሥርዐት
ነው።' "

## የኀጢአት መሥዋዕት

4 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ ሲል
ተናገረው፤ 2"ለእስራኤል ሕዝብ እን
ዲህ በላቸው፤ 'ማንም ሰው ባለማወቅ ኀጢ

[ሐ]1 በትውፊት የሰላም መሥዋዕት ይባላል፤ እንዲሁም ቍ 3፡6፡9 ይመ።

2፥7 ዘሌ7፥9
2፥9 ቍ2፤ዘፍ8፥21
2፥10 ቍ3፤ ዕዝ2፥63
2፥11 ዘፀ23፥18፤ ዘሌ6፥16
2፥12 ዘፀ34፥22
2፥13 ዘኍ18፥19፤ 2ዜና13፥5፤ ሕዝ43፥24፤ማር9፥49
2፥14 ዘፀ34፥22፤ ዘኍ15፥20፤ዘዳ16፥13፤26፥2፤ሩት3፥2
2፥15 ቍ1
2፥16 ቍ1፡2፤ ዘኍ4፥16፤ ኤር14፥12
3፥1 ቍ6፤ዘፀ12፥5፤ 32፥6፤ዘሌ7፥11-34፤ 17፥5
3፥2 ዘፀ24፥6፤ 29፥15፡20፤40፥2፤ ዘሌ1፥5፤17፥6፤ ዘኍ8፥10፤18፥17
3፥3 ዘፀ29፥13፤ 12፥9
3፥4 ቍ10፤ ዘፀ29፥13፤ዘሌ4፥9
3፥5 ቍ11፡16፤ ዘፀ29፥13፡38-42፤ ዘሌ1፥7፡9፤7፥29-34፤ ዘኍ28፥3-10
3፥6 ቍ1፤ ዘሌ22፥21፤ ዘኍ15፥3፡8
3፥7 ዘሌ17፥3፡8-9፤ ዘኍ15፥5፤28፥5፡7፡8፤ 1ነገ8፥62
3፥8 ዘሌ1፥5
3፥9 ኢሳ34፥6፤ ኤር46፥10፤ ሕዝ39፥19፤ ሶፎ1፥7
3፥11 ቍ5፡16፤ ዘሌ9፥18፤21፥6፡17፤ ዘኍ28፥2
3፥12 ዘሌ1፥10፤ 4፥3
3፥13 ዘፀ24፥6፤ ዘሌ1፥5
3፥15 ዘሌ7፥4
3፥16 ቍ5፡11፤ ዘፍ4፥4፤ዘሌ1፥9፤ 7፥31፤1ሳሙ2፥16
3፥17 ዘፍ9፥4፡12፤ ዘፀ12፥14፡20፤ 27፥21፤ዘሌ7፥25-26 17፥10-16፤ ዘዳ12፥16፤ ሐሥ15፥20
4፥2 ቍ13፡22፡27፤ ዘሌ5፥15-18፤ 22፥14፤ዘኍ15፥22፡ 24-29፤35፥11-15፤ ኢሱ20፥3፡9፤ዕብ9፥7

አት ቢሠራ፣ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) አታድርጉ
ብሎ ካዘዛቸውም አንዱን ተላልፎ ቢገኝ፣
3" 'የተቀባውም ካህን በሕዝቡ ላይ
በደል የሚያስከትል ኀጢአት ቢሠራ፣ ስለ
ሠራው ኀጢአት እንከን የሌለበት አንድ
ወይፈን *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) የኀጢአት
መሥዋዕት አድርጎ ያቅርብ:: 4ወይፈኑን
በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ *በእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ፊት ያቅርብ፤ እጁንም በወይፈኑ ራስ
ላይ ይጫን፤ *በእግዚአብሔርም* (ያህዌ) ፊት
ይረደው:: 5የተቀ ባው ካህን ከወይፈኑ ደም
ጥቂት ወስዶ ወደ መገናኛው ድንኳን
ይግባ፤ 6ጣቱንም በደሙ ውስጥ ነክሮ
ከመቅደሱ መጋረጃ ትይዩ፣ *በእግዚአብሐ*
*ር* (ያህዌ) ፊት ሰባት ጊዜ ይርጨው:: 7ካህኑ
ከደሙ ጥቂት ወስዶ በመገናኛው ድንኳን
ውስጥ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ያለጠ
ውንና ሽታው ጣፋጭ የሆነ ዕጣን
የሚታጠንበትን መሠዊያ ቀንዶች
ይቀባ:: የተረፈውን የወይፈኑን ደም ሁሉ
በመገናኛው ድንኳን መግቢያ ላይ ባለው
በሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊያ ግርጌ
ያፍሰው፤ 8ለኀጢአት መሥዋዕት
ከሚቀርበው ወይፈን ሥቡን ሁሉ ያውጣ፤
ይኸውም:- የሆድ ዕቃውን የሚሸፍነውን
ሥብና ከሆድ ዕቃው ጋር የተያያዘውን
ሥብ፣ 9ሁለቱንም ኩላሊቶች፣ በኩላሊ
ቶቹ ላይና በጎድኑ አጠገብ ያለውን ሥብ
እንዲሁም የጒበቱን መሸፈኛ ከኩላሊ
ቶቹ ጋር አብሮ አውጥቶ ያቅርብ፤ 10ለኅ
ብረት መሥዋዕት[መ] ከሚቀርበው ወይፈን[ሠ]
እንዳወጣ ሁሉ ሥቡን ያውጣ፤ ካህኑም
የሚቃጠል መሥዋዕት በሚቀርብበት መሠ
ዊያ ላይ ያቃጥለው:: 11ነገር ግን የወ
ይፈኑን ቈዳና ሥጋውን ሁሉ፣ ጭንቅላቱንና
እግሮቹን፣ ሆድ ዕቃውንና ፈርሱን፣ 12የወ
ይፈኑን ብልት ሁሉ ከሰፈር ውጭ ዐመድ
ወደሚፈስበት በአምልኮው ሥርዐት መሠረት
ንጹሕ ወደ ሆነው ስፍራ ይውሰደው፤ በተቈ
ለለው ዐመድ ላይ ዕንጨት አንድዶ ያቃ
ጥለው::
13" 'መላው የእስራኤል ሕዝብ ባለ
ማወቅ ኀጢአት ቢሠራ፣ አታድርጉ ብሎ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ካዘዘውም አንዱን
ተላልፎ ቢገኝ፣ ይህ ሕዝብ ጥፋቱ ባይታ
ወቀውም በደለኛ ነው:: 14የሕዝቡ ጉባኤ
ኀጢአት መሥራቱን በተረዳ ጊዜ፣ ለኀጢ
አት መሥዋዕት የሚሆን አንድ ወይፈን
በመገናኛው ድንኳን ፊት ያቅርብ:: 15የሕ
ዝቡም ሽማግሌዎች *በእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ፊት እጆቻቸውን በወይፈኑ ራስ ላይ ይጫኑ፤
ወይፈኑም *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ይታ
ረድ:: 16የተቀባውም ካህን ከወይፈኑ ደም
ጥቂት ወስዶ ወደ መገናኛው ድንኳን
ይግባ:: 17ጣቱን በደሙ ውስጥ ነክሮ፣
በመጋረጃው ትይዩ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ፊት ሰባት ጊዜ ይርጨው:: 18ከደሙ
ጥቂት ወስዶ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ
*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ያለውን የመ
ሠዊያ ቀንዶች ይቀባ፤ የተረፈውን ደም
ሁሉ በመገናኛው ድንኳን መግቢያ ላይ
ባለው በሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊያ
ግርጌ ያፍሰው:: 19ከወይፈኑም ሥቡን
ሁሉ ወስዶ በመሠዊያው ላይ ያቃጥል፤
20ለኀጢአት መሥዋዕት ባቀረበው ወይፈን
ላይ እንዳደረገው ሁሉ፣ በዚህኛውም
ወይፈን ያድርግ፤ በዚህም መሠረት ካህኑ
ስለ ሕዝቡ ያስተሰርያል፤ እነርሱም ይቅር
ይባላሉ:: 21ወይፈኑንም ከሰፈር ውጭ
ያውጣው፤ የመጀመሪያውን ወይፈን
እንዳቃጠለው ሁሉ ይህኛውንም
ያቃጥል፤ ይህም ስለ
ሕዝቡ የሚቀርብ የኀጢአት መሥዋዕት
ነው::
22" 'አንድ የሕዝብ መሪ ባለማወቅ ኀጢ
አት ቢሠራ፣ አምላኩም *እግዚአብሔር* (ኤሎ
ሂም ያህዌ) አታድርጉ ብሎ ከከለከላቸው
ትእዛዛት አንዱን ተላልፎ ቢገኝ እርሱ
በደለኛ ነው:: 23ኀጢአት መሥራቱን በተ
ረዳ ጊዜ እንከን የሌለበትን ተባዕት ፍየል
የግሉ መሥዋዕት አድርጎ ያቅርብ:: 24እጁ
ንም በፍየሉ ራስ ላይ ይጫን፤ የሚቃጠል
መሥዋዕት በሚታረድበትም ስፍራ *በእግዚ*
*አብሔር* (ያህዌ) ፊት ይረደው፤ ይህም የኀጢ
አት መሥዋዕት ነው:: 25ካህኑም ከመሥዋዕቱ
ደም በጣቱ ጥቂት ወስዶ የሚቃጠል
መሥ ዋዕት የሚቀርብበትን መሠዊያ
ቀንዶች ይቀባ፤ የተረፈውንም ደም ሁሉ
በመሠዊያው ግርጌ ያፍሰው:: 26የኅብረት
መሥዋዕቱን እንዳቃጠለ ሁሉ ሥቡንም
በሙሉ በመሠዊያው ላይ ያቃጥል፤ በዚህም
መሠረት ካህኑ የሰውየውን ኀጢአት
ያስተሰርይለ ታል፤ ሰውየውም ይቅር
ይባላል::
27" 'ከሕዝቡ መካከል አንዱ ሰው ባለ
ማወቅ ኀጢአት ቢሠራ፣ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
አታድርጉ ብሎ ከከለከላቸው ትእዛዛት
አንዱን ተላልፎ ቢገኝ እርሱ በደለኛ
ነው:: 28ኀጢአት መሥራቱን በተረዳ ጊዜ፣
እንከን የሌለባትን እንስት ፍየል ስለ
ፈጸመው ኀጢአት የግሉ መሥዋዕት
አድርጎ ያቅርብ:: 29እጁን ለኀጢአት
መሥዋዕት በቀረበችው ፍየል ራስ ላይ
ይጫን፤ የሚ ቃጠል መሥዋዕት
በሚታረድበት ስፍራም

4፥3 ቍ14፥24፥32፤ ዘፍ18፥23፤ዘፀ12፥5፤ 28፥41፤30፥10፤ ዘሌ3፥12፤5፥6-13፤ 8፥14፤9፥2-22፤ 10፥16፤16፥3፥5፤ 19፥16፤ዘኍ15፥27፤ መዝ66፥15፤ ሕዝ 43፥19፥23፤ ዕብ9፥13-14
4፥4 ቍ15፥24፤ ዘሌ1፥3፤ዘኍ8፥12
4፥5 ቍ16፤ ዘሌ16፥14
4፥6 ቍ7፤ዘፀ25፥8፤ 24፥8፤ዘሌ16፥14፥19
4፥7 ቍ18፥30፥34፤ ዘፀ27፥2፤29፥12፤ ዘሌ5፥9፤8፥15፤9፥9፤ 16፥18
4፥8 ቍ 19፤
4፥9 3፥4
4፥10 ዘፀ29፥13፤ 32፥6፤ዘሌ9፥4
4፥11 ዘፀ29፥14፤ ዘሌ8፥17፤9፥11፤ ዘኍ19፥5
4፥12 ዘፀ29፥14፤ ዘሌ1፥16፤6፥11፥30፤ 8፥17፤9፥11፤10፥14፤16፥3፤ዘኍ19፥9፤ ዕብ13፥11
4፥13 ቍ2
4፥14 ቍ3፤ ዘኍ15፥24
4፥15 ቍ4፤ ዘፀ3፥16፤19፥7፤ 29፥10፤ዘሌ8፥14፥22፤ ዘኍ8፥10፤2ዜና29፥23
4፥16 ቍ5
4፥17 ቍ6፤ ዘኍ19፥4፥18
4፥18 ቍ7፤ ዘሌ5፥9፤6፥30፤8፥15፤10፥18፤17፥6፤ 2ዜና29፥22
4፥19 ቍ8፥26
4፥20 ቍ26፥31፥ 35፤ዘፀ29፥36፤ 32፥30፤ዘኍ15፥25፤ ሮሜ3፥25፤ ዕብ10፥10-12
4፥21 ቍ12፤ ዘሌ16፥5፥15፤ 2ዜና29፥21
4፥22 ቍ2፤ ዘኍ31፥13
4፥23 ቍ3፤ ዘሌ1፥10
4፥24 ቍ3፥4፤ ዘሌ6፥25
4፥25 ዘሌ9፥9፤ 16፥18፤ሕዝ43፥20፥ 22
4፥26 ዘፀ32፥30፤ ዘሌ5፥10፤12፥8
4፥27 ቍ2
4፥28 ቍ3፤ ዘሌ1፥10፤5፥6፤ ሕዝ40፥39፤44፥27
4፥29 ቍ4፥24፤ ዘፍ8፥20፤ዘሌ1፥4

[መ]10 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል፤ እንዲሁም ቍ 26፥31፥35 ይመ::
[ሠ]10 የዕብራይስጡ ቃል ተባዕትንና እንስትን ሊያጠቃልል ይችላል::

ይረዳት። [30]ካህኑ በጣቱ ከደሚ ጥቂት
ወስዶ የሚቃጠል መሥዋዕት የሚቀርብበትን
መሠዊያ ቀንዶች ይቅባ፤ የተረፈውንም
ደም ሁሉ በመሠዊያው ግርጌ ያፍሰው።
[31]ሥቡን ከኅብረት መሥዋዕት በወጣበት
አኳኋን ሥቡን ሁሉ ያውጣ፤ ካህኑም ሽታው
እግዚአብሔርን (ያህዌ) ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት
አድርጎ በመሠዊያው ላይ ያቃጥለው፤ በዚ
ህም መሠረት ካህኑ የሰውየውን ኀጢአት
ያስተሰርይለታል፤ ሰውየውም ይቅር ይባ
ላል።
[32]“ ‘ስለ ኀጢአት መሥዋዕት የበግ ጠቦት
የሚያቀርብ ከሆነ፣ እንከን የሌለባትን እን
ስት ያቅርብ። [33]እጁን በጠቦቷ ራስ ላይ
ይጫን፤ የሚቃጠል መሥዋዕት በሚታረ
ድበት ስፍራም የኀጢአት መሥዋዕት አድርጎ
ይረዳት። [34]ካህኑም ከኀጢአት መሥዋዕቱ
ደም በጣቱ ጥቂት ወስዶ የሚቃጠል
መሥዋዕት የሚቀርብበትን መሠዊያ ቀንዶች
ይቅባ፤ የተረፈውንም ደም ሁሉ በመ
ሠዊያ ግርጌ ያፍሰው። [35]ሥቡ ከኅብረት
መሥዋዕት ጠቦት በወጣበት አኳኋን
ሥቡን ሁሉ ያውጣ፤ ካህኑም በመሠዊያው
ላይ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በእሳት በሚቀር
በው መሥዋዕት ላይ ያቃጥለው። በዚህ
መሠረት ሰውየው የሠራውን ኀጢአት
ካህኑ ያስተሰረይለታል፤ ሰውየውም ይቅር
ይባላል።

5 “ ‘አንድ ሰው ስላየውና ስለሚያውቀው
ነገር ሕጋዊ ምስክርነቱን እንዲሰጥ
ተጠይቆ ቃሉን ለመስጠት ፈቃደኛ ባይ
ሆን፣ ይህ ሰው ኀጢአት ሠርቶአልና ይጠ
የቀበታል።
[2]“ ‘ማንኛውም ሰው ሳያውቅ በሥርዐቱ
መሠረት የተከለከለውን ርኩስ ነገር
ቢነካ፣ ይኸውም፦የረከሰ የአውሬ በድን
ወይም የረከሰ የቤት እንስሳ በድን ወይም
በደረቱ እየተሳበ የሚንቀሳቀሰውን የረከሰ
ፍጥረት በድን ቢነካ ይህ ሰው ረክሶአል፤
በደለኛም ነው።
[3]“ ‘ወይም የሰውን ርኵሰት ይኸውም
ርኵስ የሚያደርገውን ማናቸውንም ነገር
ሳያውቅ ቢነካ፣ ነገሩን ባወቀ ጊዜ በደለኛ
ይሆናል።
[4]“ ‘ሰዎች በሚምሉበት በማናቸውም
ነገር፣ በጎ ወይም ክፉ ለማድረግ ሳያስብ
በግዴለሽነት ቢምል በኋላ ግን ነገሩን
ባወቀ ጊዜ በደለኛ ይሆናል።
[5]“ ‘ማንኛውም ሰው ከእነዚህ በአንዱ
በደለኛ ሆኖ ቢገኝ፣ የትኛውን ኀጢአት
እንደሠራ ገልጾ መናዘዝ አለበት፤ [6]ስለ
ኀጢአቱም ቅጣት የኀጢአት መሥዋዕት
እንድትሆነው ከመንጋው አንዲት የበግ
ወይም የፍየል እንስት ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) ያቅርብ፤ ካህኑም ስለ ኀጢአቱ ያስተ
ሰረይለታል።
[7]“ ‘ሰውየው ስለ ሠራው ኀጢአት በግ
ለማቅረብ ዐቅሙ ካልፈቀደ ሁለት ዋኖሶች
ወይም ሁለት የዋኖስ ጫጩቶች የመጀ
መሪያውን ለኀጢአት መሥዋዕት፣ ሁለተ
ኛውን ለሚቃጠል መሥዋዕት ለእግዚአ
ብሔር (ያህዌ) ያቅርብ። [8]ወደ ካህኑም ያም
ጣቸው፤ እርሱም ለኀጢአት መሥዋዕት
የምትሆነውን አስቀድሞ ያቅርብ፤ ራሷን
ዐንገቷ ላይ ይቈልምም፤ ነገር ግን ቈርጦ
አይጣል፤ [9]ከኀጢአት መሥዋዕቱም ጥቂት
ደም ወስዶ በመሠዊያው ዙሪያ ላይ
ይርጨው፤ የተረፈውም ደም ሁሉ በመ
ሠዊያው ግርጌ ይፍሰስ፤ ይህም የኀጢአት
መሥዋዕት ነው። [10]ካህኑም ቀደም ሲል
በታዘዘው መሠረት ሁለተኛዋን የሚቃጠል
መሥዋዕት አድርጎ ያቅርብ፤ ካህኑም የሰው
የውን ኀጢአት ያስተሰረይለታል፤ ሰውየውም
ይቅር ይባላል።
[11]“ ‘ሰውየው ሁለት ርግቦች ወይም
ሁለት የዋኖስ ጫጩቶች ለማቅረብ ዐቅሙ
ካልፈቀደ፣ ስለ ሠራው ኀጢአት የኢፍ
መስፈሪያ[ረ] አንድ ዐሥረኛ የላመ ዱቄት
ለኀጢአት መሥዋዕት ያቅርብ፤ ነገር ግን
የኀጢአት መሥዋዕት ስለሆነ ዘይት አያፍ
ስበት፤ ዕጣንም አይጨምርበት፤ [12]ከዚያም
ለካህኑ ያቅርብ፤ ካህኑም ለመታሰቢያ እን
ዲሆን ዕፍኝ ሙሉ ይዝገንለት፤ በእሳት
ከሚቀርበውም ቍርባን በላይ አድርጎ
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በመሠዊያው ላይ በእ
ሳት ያቃጥለው፤ ይህም የኀጢአት መሥዋዕት
ነው። [13]ሰውየው ከእነዚህ በአንዱ ኀጢ
አት ቢሠራ፣ ካህኑ በዚህ ሁኔታ ያስተሰር
ይለታል፤ ሰውየውም ይቅር ይባላል።
ከመሥዋዕቱ የተረፈውም እንደ እህል
ቍርባን ሁሉ ለካህኑ ይሆናል።’ ”

## የበደል መሥዋዕት

[14]እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ [15]“ማንኛውም ሰው በደል ቢፈጽም
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) ከተቀደሰ ከማናቸውም
ነገር በማጕደል ኀጢአት ቢሠራ፣ ከመንጋው
እንከን የሌለበትን አውራ በግ የበደል
መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
ያቅርብ። የዋጋውም ግምት በቤተ መቅ
ደሱ ሰቅል[ሰ] መሠረት ተመዝኖ በጥሬ
ብር ይሁን፤ ይህም የበደል መሥዋዕት
ነው። [16]ከተቀደሱ ነገሮች ያጐደለውንም
ይተካ፤

[ረ] 11 ሁለት ሊትር ገደማ ይሆናል
[ሰ] 15 11.5 ግራም ይሆናል።

4፥30 ቍ7
4፥31 ቍ20፡35፤ ዘፍ8፥21፤ዘሌ1፥4
4፥32 ዘፀ29፥38፤ ዘሌ1፥3፤9፥3፤14፥10
4፥33 ቍ29፤ ዘሌ1፥4፡5
4፥34 ቍ7
4፥35 ቍ31
5፥1 ቍ17፤ ዘፀ28፥38፤ዘሌ7፥18፤ 17፥16፤19፥8፤ 20፥17፤24፥15፤ ዘኍ5፥31፤9፥13፤ 15፥31፤19፥20፤ 30፥15፤ምሳ29፥24፤ ማቴ26፥63፤
5፥2 ቍ3፤ ዘሌ7፥21፤11፥8፡11፡ 24-40፤13፥45፤ ዘዳ14፥8፤ዘኍ19፥22አ.ዮ15፥16፤ መዝ51፥5፤ኢሳ6፥5፤ 52፥11፤ 64፥6፤ ሕዝ36፥17፤ሐጌ2፥13
5፥3 ዘሌ7፥20፤ 11፥25፤14፥19፤ 21፥1፤ዘኍ5፥2፤9፥6፤1 9፥7፡11-16፤ ሕዝ44፥25
5፥4 ዘኍ30፥6፡8፤ ኢሳ41፥23
5፥5 ዘሌ16፥21፤ 26፥40፤ዘኍ5፥7፤ ኢ. ሱ7፥19፤ 1ነገ8፥47፤ምሳ28፥13
5፥6 ዘፀ32፥30፤ ዘሌ1፥10፤4፥3፡28
5፥7 ቍ11፤ ዘፍ15፥9፤ዘሌ12፥8፤14 ፥21፤14፥22፡30፤ 27፥8፤ዘኍ6፥10
5፥8 ዘሌ1፥15፡17
5፥9 ዘፀ24፥6፤ ዘሌ1፥15፤4፥7
5፥10 ዘፀ32፥30፤ ዘሌ1፥14-17፤4፥26፤ 1ዜና15፥13
5፥11 ቍ7፤ ዘፍ15፥9፤ዘፀ16፥36፤ ዘሌ2፥1
5፥12 ዘፀ2፥2፤ ዘሌ2፥9
5፥13 ዘፀ29፥41፤ 32፥30፤ዘሌ2፥3
5፥15 ቍ16፡18፤ ዘፀ29፥3፤30፥13፤ ዘሌ4፥2፤6፥5፡6፤7፥1፡7 ፤14፥12- 17፤19፥21፡22፤22፥14 ፤ዘኍ5፥8፤ 6፥12፡14፤ 15፥6፤18፥9፤28፥11፤1 ሳሙ6፥3፤ ዕዝ10፥19፤ ኢሳ53፥10
5፥16 ቍ15፤ ዘሌ6፥4፤27፥13፤ ዘኍ5፥7
5፥17 ቍ1፡15
5፥18 ቍ15፤

የዚህንም ተመን አንድ አምስተኛ በላዩ ጨምሮ ለካህኑ ይስጥ፤ ካህኑም ከበጉ ጋር የበደል *መሥዋዕት* አድርጎ በማቅረብ ያስተሰርይለታል፤ ሰውየውም ይቅር ይባላል።

17“ ‘ማንኛውም ሰው ኀጢአት ቢሠራ፣ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) አታድርጉ ብሎ ከከለከላቸው ትእዛዛት ሳያውቅ አንዱን ተላልፎ ቢገኝ በደለኛ ነው፤ በኀጢአቱም ይጠየቅበታል። 18እርሱም ከመንጋው ለበደል *መሥዋዕት* የሚሆን እንከን የሌለበት አውራ በግ ወደ ካህኑ ያምጣ፤ ዋጋውም ተመጣጣኝ ይሁን። ካህኑም በዚህ ሁኔታ ሰውየው ሳያውቅ ስለ ፈጸመው ስሕተት ያስተሰርይለታል፤ ሰውየውም ይቅር ይባላል። 19ይህ የበደል *መሥዋዕት* ነው። ሰውየውም *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ጥፋት በመፈጸሙ በደለኛ[ሽ] ነው።”

# 6

*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤ 2“ማንኛውም ሰው በዐደራ የተሰጠውን ወይም በመያዣነት የተቀበለውን በመካድና ባልንጀራውን በማጭበርበር ኀጢአት ቢሠራ፣ *እግዚአብሔርንም* (ያህዌ) ቢበድል ወይም ባልንጀራውን ቢቀማው ወይም ቢያታልለው፣ 3ወይም የጠፋ ነገር አግኝቶ አላየሁም ቢል ወይም በሐሰት ቢምል ወይም ሰዎች የሚያደርጉትን እንዲህ ያለውን ማናቸውንም ኀጢአት ቢሠራ፣ 4በዚህ ሁኔታ ኀጢአት ቢሠራና በደለኛ ቢሆን፣ የሰረቀውን ወይም የቀማውን ወይም በዐደራ የተሰጠውን ወይም ጠፍቶ ያገኘውን ይመልሳል፤ 5በሐሰት የማለበትንም ሁሉ ይመልስ፤ የበደል *መሥዋዕቱን* በሚያቀርብበት ጊዜ የወሰደውን በሙሉ የዋናውን አንድ አምስተኛ በመጨመር ለባለ ንብረቱ ይመልስ። 6ከመንጋውም እንከን የሌለበትን ዋጋው ተመጣጣኝ የሆነ አውራ በግ ስለ በደሉ *መሥዋዕት* አድርጎ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) ለማቅረብ ወደ ካህኑ ያምጣ፤ 7በዚህም ሁኔታ ካህኑ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ያስተሰረ ይለታል፤ ሰውየውም ስለ ፈጸመው ስለ ማንኛውም በደል ይቅር ይባላል።

## የሚቃጠል መሥዋዕት

8*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤ 9“አሮንና ልጆቹን እንዲህ ብለህ እዘዛቸው፤ ‘ስለሚቃጠለው *መሥዋዕት* አቀራረብ የምትከተለው *ሥርዐት* ይህ ነው፡- የሚቃጠለው *መሥዋዕት* ሌሊቱን ሁሉ እስኪነጋ ድረስ በመሠዊያው ላይ ባለው ማንደጃ ላይ ይቀመጥ፤ እሳቱም በመሠዊያው ላይ ዘወትር ሲነድ ይደር። 10ካህኑም ከበፍታ የተሠራ የውስጥ ሱሪውን ካጠለቀ

ዘሌ6÷6፤14÷12፤
5÷19 2ነገ12÷16
6÷2 ዘፍ31÷7፤ ዘፀ22÷7፤ዘሌ19÷11፤ ዘኁ5÷6፤መዝ73÷27አ ር9÷4፡5፤ ሐሥ5÷4፤ቈላ3÷9
6÷3 ዘፀ23÷4፤ 22÷11
6÷4 ዘሌ5÷16፤ ሕዝ33÷15፤ ሉቃ19÷8
6÷5 ዘሌ5÷15፤ ዘኁ5÷7
6÷6 ዘሌ5÷15፤ ዘኁ5÷8
6÷7 ዘፀ32÷30
6÷9 ቀኍ12፤ ዘሌ7÷37
6÷10 ዘፀ28÷39-42፡43፤39÷27፤28፤ ዘሌ1÷16
6÷11 ዘሌ4÷12
6÷12 ዘፀ29÷13፤ 32÷6፤ዘሌ1÷7
6÷14 ዘሌ2÷1፤ ዘኁ6÷15፤15፡4፤ 28÷13
6÷15 ዘሌ2÷1፡2፡9
6÷16 ቀኍ26፤ ዘፀ27÷9፤29÷11፡31፤ ዘሌ2÷3፡11፤8÷31፤ 10÷13፤16÷24፤24÷9ዘ ኁ18÷10፤ ሕዝ44÷29
6÷17 ቀኍ29፤ ዘፀ29÷28፤40÷10፤ ዘሌ7÷7፤10÷12፡16፡18፤21÷22፤24÷9፤ ዘኁ5÷9፤18÷9፡10
6÷18 ቀኍ29፤ ዘፍ9÷12፤ዘፀ30÷29፤ ዘሌ2÷3፤7÷6፤ ዘኁ5÷9፤18÷9-10
6÷20 ዘፀ16÷36፤ 28÷41፤29÷2፤ ዘሌ23÷13፤ ዘኁ4÷16፤5÷15፤ 28÷5
6÷21 ዘሌ2÷5
6÷22 ዘፀ28÷41፤ 29÷30፤ዘሌ1÷9

በኋላ፣ የበፍታ ቀሚሱን ይልበስ፤ እሳቱ በመሠዊያው ላይ *መሥዋዕቱን* ከበላው በኋላ የሚቀረውን ዐመድ አንሥቶ፣ በመሠዊያው አጠገብ ያፍስስ። 11ከዚያም ልብሱን አውልቆ ሌላ ልብስ ይቀይር፤ ዐመዱንም ተሸክሞ ከሰፈር ውጭ በአምልኮው ሥርዐት መሠረት ንጹሕ ወደ ሆነ ስፍራ ይውሰድ። 12በመሠዊያው ላይ ያለው እሳት ዘወትር ይንደድ፤ ምን ጊዜም አይጥፋ። ካህኑ ጧት ጧት እሳቱ ላይ ማገዶ ይጨምር፤ በእሳቱ ላይ የሚቃጠለውን *መሥዋዕት* ያዘጋጅ፤ በዚህም ላይ የኅብረት *መሥዋዕቱን*[ቀ] ሥብ ያቃጥል። 13በመሠዊያው ላይ ያለው እሳት ዘወትር ይንደድ፤ ምን ጊዜም አይጥፋ።

## የእህል ቍርባን

14“ ‘የእህል ቍርባን *ሥርዐት* ይህ ነው፡- የአሮን ልጆች ቍርባኑን በመሠዊያው ትይዩ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ያቅርቡት። 15ካህኑ ከላመው ዱቄትና ከዘይቱ አንድ ዕፍኝ ያንሣለት፤ በእህሉ ቍርባን ላይ ያለውንም ዕጣን በሙሉ ይውሰድ፤ ይህንም፣ ሽታው *እግዚአብሔርን* (ያህዌ) ደስ የሚያሰኝ *መሥዋዕት* አድርጎ፣ ለመታሰቢያ በመሠዊያው ላይ ያቃጥለው። 16የተረፈውንም አሮንና ልጆቹ ይብሉት፤ እርሾ ሳይገባበት በተቀደሰው ስፍራ፣ በመገናኛው ድንኳን ቅጥር ግቢ ውስጥ አደባባዩ ላይ ይብሉት። 17ያለ እርሾ መጋገር አለበት፤ በእሳት ከሚቀርብልኝ ቍርባን ይህን የእነርሱ ድርሻ አድርጌ ሰጥቻቸዋለሁ። ይህም፣ እንደ ኀጢአት *መሥዋዕትና* እንደ በደል *መሥዋዕት* ሁሉ እጅግ የተቀደሰ ነው። 18ማንኛውም ከአሮን ዘር የተወለደ ወንድ ሊበላው ይችላል፤ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) ከሚቀርበው የእሳት ቍርባን ለእርሱ የተመደበ የዘላለም ድርሻው ነው፤ የሚነካውም ሁሉ[በ] ቅዱስ ይሆናል።’ ”

19*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤ 20“አሮን ወይም ልጆቹ በተቀቡበት ዕለት[ተ] *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) የሚያቀርቡት ቍርባን ይህ ነው፡- የኢፍ[ቸ] አንድ ዐሥረኛው የላመ ዱቄት ግማሹን ለጧት፣ ግማሹን ለማታ የዘወትር የእህል ቍርባን አድርገው ያቅርቡት። 21በሚገባ በዘይት ተለውሶ በምጣድ ላይ ይጋገር፤ ከዚያም የእህሉን ቍርባን ቈራርሰህ[ኀ] ሽታው *እግዚአብሔርን* (ያህዌ) ደስ የሚያሰኝ ይሆን ዘንድ አቅርብ። 22በእርሱ

[ሽ]19 ወይም *ለፈጸመው በደል ሙሉ የኀጢአቱ ማስተሰረያ ነው።*
[ቀ]12 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል።
[በ]18 ወይም *የሚነካው ሰው ሁሉ፤* እንዲሁም ቍ 27 ይመ
[ተ]20 ወይም *በተቀባበት ዕለት አሮን እና ልጆቹ*
[ቸ]20 ሁለት ሊትር ገደማ ይሆናል
[ኀ]21 የዚህ ቃል የዕብራይስጡ ትርጓሜ በእርግጠኝነት አይታወቅም

ቦታ ተቀብቶ ካህን የሚሆነው ልጁ ይህን
ያዘጋጅ፤ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የተመደበ ድርሻ
ነውና ፈጽሞ ይቃጠል። 23ካህኑ የሚያቀር
በው የእህል ቍርባን ሁሉ ፈጽሞ ይቃጠል
እንጂ አይበላ።”

## የኀጢአት መሥዋዕት

24እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤
25“አሮንንና ልጆቹን እንዲህ በላቸው፤ ስለ
ኀጢአት መሥዋዕት አቀራረብ የምትከተለው
ሥርዐት ይህ ነው፤ የሚቃጠል መሥዋዕት
በሚታረድበት ስፍራ የኀጢአቱም መሥዋዕት
እዚያው በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ይታረድ፤
ይህም እጅግ ቅዱስ ነው። 26መሥዋዕቱንም
የሚያቀርበው ካህን ይብላው፤ ይህም በተቀ
ደሰው ስፍራ በመገናኛው ድንኳን ቅጥር
ግቢ ውስጥ፣ በአደባባዩ ላይ ይበላ። 27ሥጋ
ውን የሚነካ ሁሉ የተቀደሰ ይሆናል፤
ደሙ በልብስ ላይ ቢረጭ፣ ያን ልብስ
በተቀደሰ ስፍራ እጠብ። 28ሥጋው
የተቀቀ ለበት የሸክላ ዕቃ ይሰበር፤
የናስ ዕቃ ከሆነ ግን ተፈግፍጎ በውሃ
ይታጠብ። 29ከካህናት ወገን የሆነ ወንድ
ሁሉ ከዚህ መብላት ይችላል፤ ይህም
እጅግ ቅዱስ ነው። 30ነገር ግን ደሙ ለ
ማስተሰረያ እንዲሆን ወደ መገናኛው
ድንኳን ወደ ቅድስት የቀረበው የኀጢ
አት መሥዋዕት ሁሉ በእሳት ይቃጠል
እንጂ አይበላ።

## የበደል መሥዋዕት

7 “‘እጅግ ቅዱስ የሆነው የበደል መሥ
ዋዕት የአቀራረብ ሥርዐት ይህ ነው፦
2የሚቃጠል መሥዋዕት በሚታረድበት ስፍራ
የበደሉም መሥዋዕት እዚያው ይታረድ፤
ደሙም በመሠዊያው ላይ ዙሪያውን ይረጭ።
3ሥቡን በሙሉ ያቅርብ፤ ይኸውም፦ ላቱን፣
የሆድ ዕቃውን የሚሸፍነውን ሥብ፣ 4ሁለቱ
ኵላሊቶች፣ በኵላሊቶቹ ላይና በጐድኑ
አጠገብ ያለውን ሥብ እንዲሁም ከኵላሊ
ቶቹ ጋር የሚወጣውን የጕበቱን ሽፋን
አብሮ ያቅርብ። 5ካህኑም ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) በእሳት የሚቀርብ አድርጎ በመሠዊያው
ላይ ያቃጥል፤ ይህም የበደል መሥዋዕት
ነው። 6ከካህን ወገን የሆነ ወንድ ሁሉ ከዚህ
መብላት ይችላል፤ ነገር ግን በተቀደሰ ስፍራ
ይበላ፤ ይህም እጅግ ቅዱስ ነው።
7“‘የኀጢአት መሥዋዕትና የበደል መሥ
ዋዕት አቀራረብ ሥርዐት አንድ ነው፤
መሥዋዕቶቹ የስርየቱን ሥርዐት ለሚያስ
ፈጽመው ካህን ይሰጣሉ። 8ስለ ማንኛውም
ሰው የሚቃጠል መሥዋዕት የሚያቀርበው
ካህን ቈዳውን ለራሱ ይውሰድ። 9በማብሰያ
ምድጃ የተጋገረ፣ በመቀቀያ ወይም በም

6፥25 ዘፀ29፥11፤ 30፥10፤ዘሌ1፥3፤ 4፥24
6፥26 ቍ16፤ ዘፀ27፥9፡21፤40፥2
6፥27 ዘፀ29፥37፤ ዘሌ10፥10፤ ሕዝ44፥19፤46፥20፤ ሐጌ2፥12
6፥28 ዘሌ11፥33፤ 15፥12፤ዘኍ19፥15
6፥29 ቍ17፡18፤ ሕዝ42፥13
6፥30 ዘሌ4፥12፡18፤ ሕዝ45፥15
7፥1 ዘሌ5፥15፤ ሕዝ40፥39
7፥3 ዘፀ29፥13
7፥4 ዘሌ3፥15
7፥5 ዘፀ29፥13
7፥6 ዘሌ6፥18፤ ሕዝ42፥13
7፥7 ቍ6፤ ዘፀ30፥10፤ ዘሌ2፥3፤5፥15፤6፥17፡26፤14፥13፤ዘኍ5፥8፤2ነገ12፥16፤ 1ቆሮ9፥13፤10፥18
7፥8 ዘሌ1፥6
7፥9 ዘሌ2፥4፡5፡7
7፥12 ቍ13፡15፤ ዘሌ2፥1፡4፤22፥29፤ ዘኍ6፥19፤መዝ50፥14፤54፥6፤107፥22፤116፥17፤ኤር33፥11፤ 44፥19
7፥13 ቍ12፤ ዘፀ34፥22፤ ዘሌ23፥17፤ አሞ4፥5
7፥15 ዘፀ12፥10
7፥16 ዘፍ28፥20፤ ዘፀ35፥29፤ ዘሌ1፥2፤19፥5-8፤ 22፥18፡21፤23፥38፤ ዘኍ15፥3፤29፥39፤ ዘዳ12፥6፤23፥21-23፤መዝ54፥6፤ ሕዝ46፥12
7፥17 ዘፀ12፥10፤ ዘሌ19፥6
7፥18 ዘሌ5፥1፤ 19፥7፤ዘኍ18፥27፤ 2ዜና33፥16
7፥20 ዘፍ17፥14፤ ዘሌ5፥3፤22፥3-7
7፥21 ዘሌ5፥2
7፥23 ዘሌ17፥3፤ ዘዳ14፥4
7፥24 ዘፀ22፥31

ጣድ የበሰለ ማንኛውም የእህል ቍርባን
ለሚያቀርበው ካህን ይሰጥ። 10ማናቸውም
በዘይት የተለወሰ ወይም ደረቅ የእህል
ቍርባን ለአሮን ልጆች ሁሉ እኩል ይሰጥ።

## የኅብረት መሥዋዕት

11“ ‘አንድ ሰው ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
የኅብረት መሥዋዕት[ነ] በሚያቀርብበት ጊ
ዜ፣ ሊከተለው የሚገባው ሥርዐት ይህ
ነው፦
12“‘መሥዋዕቱን የሚያቀርበው ለምስጋና
መግለጫ ከሆነ፣ ከምስጋና መሥዋዕቱ ጋር
ያለ እርሾ የተጋገረና በዘይት የተለወሰ
ኅብስት እርሾ ሳይገባበት በሥቡ ተጋግሮ
ዘይት የተቀባ ቂጣ በሚገባ ታሽቶ በዘይት
የተለወሰም የላመ ዱቄት ኅብስት አብሮ
ያቅርብ። 13ለምስጋና ከሚሆነው የኅብረት
መሥዋዕት ጋር በእርሾ የተጋገረ ኅብስት
ያቅርብ። 14ከእያንዳንዱም ዐይነት አንዳንድ
አንሥቶ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የተለየ ቍር
ባን በማድረግ ያቅርብ፤ ይህም የኅብረት
መሥዋዕቱን ደም ለሚረጨው ካህን ይሰጥ።
15ለምስጋና የሚሆነው የኅብረት መሥዋዕት
ሥጋ፣ በቀረበበት ዕለት ይበላ እንጂ
አንዳች አይደር።
16“‘መሥዋዕቱ ስእለት በመፈጸሙ ወይም
በበጎ ፈቃድ የሚቀርብ ከሆነ፣ በቀረበበት
ዕለት ይበላ፤ የተረፈውም ሁሉ በማግስቱ
ይበላ። 17እስከ ሦስት ቀን የቆየ ማንኛ
ውም የመሥዋዕቱ ሥጋ ይቃጠል። 18ማንኛ
ውም የኅብረት መሥዋዕት ሥጋ በሦስተኛው
ቀን ከተበላ ተቀባይነት የለውም፤ ርኵስ
በመሆኑ ላቀረበው ሰው ዋጋ አይኖረውም፤
ከዚያም የበላ ሰው የበደል ዕዳ
ይሆንበታል።
19“ ‘ርኩስ ከሆነ ነገር ጋር የተነካካ ሥጋ
ይቃጠል እንጂ አይበላ። ሌላውን ሥጋ ግን
በሥርዐቱ መሠረት ንጹሕ የሆነ ማንኛውም
ሰው ይብላ፤ 20ነገር ግን ንጹሕ ያልሆነ ማን
ኛውም ሰው ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የቀረበውን
የትኛውንም የኅብረት መሥዋዕት ሥጋ
ቢበላ፣ ከሕዝቡ ፈጽሞ ይወገድ። 21ማንኛውም
ሰው የሰውን ርኵሰት ወይም ርኩስ እንስ
ሳን ወይም ማንኛውንም ርኩስ ነገር ቢነካና
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) ከቀረበው የኅብረት
መሥዋዕት ሥጋ ቢበላ፣ ያ ሰው ፈጽሞ ከሕ
ዝቡ ይወገድ።

## ሥብና ደም መብላት መከልከሉ

22እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 23“ለእስራኤላውያን እንዲህ በላቸው፤
‘የበሬ ወይም የላም፣ የበግ ወይም የፍየል
ሥብ አትብሉ። 24ሞቶ የተገኘው ወይም

[ነ]11 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል፤ እንዲሁም ቍ 13-37 ይመ

አውሬ የገደለው ከብት ሥብ ለሌላ ተግ
ባር ይዋል እንጂ አይበላ:: 25ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) በእሳት ከሚቀርብ፟ እንስሳ ሥብ
የሚበላ ማንኛውም ሰው ከሕዝቡ ይወገድ::
26በየትኛውም ቦታ ብትኖሩ የማንኛውንም
የወፍ ዘር ወይም የእንስሳ ደም አትብሉ::
27ማንኛውም ሰው ደም ቢበላ፣ ያ ሰው
ከሕዝቡ ይወገድ::' "

## የካህኑ ድርሻ

28እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 29"ለእስራኤላውያን እንዲህ በላቸው፤
'የኅብረት መሥዋዕት ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ስለ ራሱ
መሥዋዕት አድርጎ ከዚሁ ላይ ለእግዚ
አብሔር (ያህዌ) ያቅርብ:: 30በእሳት ለእግዚ
አብሔር (ያህዌ) የሚቀርበውን መሥዋዕት በራ
ሱ እጅ ያቅርበው፤ ሥቡን ከፍርምባው
ጋር ያቅርብ፤ ፍርምባውን መሥዋዕት
አድርጎ በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት
ይወዝውዘው:: 31ካህኑ ሥቡን በመሠዊያው
ላይ ያቃጥል፤ ፍርምባው ግን ለአሮንና
ለልጆቹ ይሰጥ:: 32የኅብረት መሥዋዕ
ታችሁን የቀኝ ወርች ላካህኑ የተለየ
አድርጋችሁ ስጡት:: 33የኅብ ረት መሥዋዕ
ቱን ደምና ሥብ የሚያቀ ርበው የአሮን
ልጅ ቀኝ ወርቹን የራሱ ድርሻ አድርጎ
ይውሰድ:: 34ከእስራኤላውያን የኅብረት
መሥዋዕት ላይ የተወዘወዘውን ፍርምባና
የቀረበውን ወርች ወስጃለሁ፤ ለካህኑ
ለአሮንና ለልጆቹም ከእስራኤላ ውያን
የሚያገኙት መደበኛ ድርሻቸው እንዲሆን
ሰጥቻቸዋለሁ::' "

35ካህናት ሆነው እግዚአብሔርን (ያህዌ)
እንዲያገለግሉ በቀረቡ ቀን፣ በእሳት ለእግዚ
አብሔር (ያህዌ) ከቀረበው መሥዋዕት ላይ
ለአሮንና ለልጆቹ የተመደበላቸው ድርሻ
ይህ ነው:: 36ካህናቱ በተቀቡበት ቀን፣ እስ
ራኤላውያን መደበኛ ድርሻ አድርገው
ከትውልድ እስከ ትውልድ ይህን እንዲ
ሰጧቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) አዘዘ::

37እንግዲህ የሚቃጠል መሥዋዕት፣ የእ
ህል ቍርባን፣ የኀጢአት መሥዋዕት፣ የበደል
መሥዋዕት፣ የክህነት ሹመት መሥዋዕ
ትና የኅብረት መሥዋዕት ሥርዐት ይህ
ነው፤ 38ይህም፣ በሲና ምድረ በዳ እስራ
ኤላውያን መሥዋዕታቸውን ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) እንዲያቀርቡ ባዘዛቸው ቀን በሲና
ተራራ ላይ ለሙሴ የሰጠው ሥርዐት ነው::

## አሮንና ልጆቹ ካህናት ሆነው መሾማቸው

8፥1-36 ተጓ ምብ ዘፀ 29፥1-37

8 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤
2"አሮንንና ልጆቹን፣ ልብሰ ተክህኖውን፣
የመቅቢያ ዘይቱን፣ ለኀጢአት መሥዋዕት
የሚሆነውን ወይፈን፣ ሁለቱን አውራ
በጎችና እርሾ ሳይገባበት የተጋገረው ቂጣ
ያለበትን መሶብ አምጣ፤ 3ማኅበሩን
በሙሉ በመገና ኛው ድንኳን ደጃፍ
ሰብስብ::" 4ሙሴም እግዚአብሔር (ያህዌ)
እንዳዘዘው አደረገ፤ ማኅ በሩም በመገናኛው
ድንኳን ደጃፍ ተሰበሰበ::

5ሙሴም ማኅበሩን፣ "እግዚአብሔር (ያህዌ)
እንዲደረግ ያዘዘው ይህ ነው" አላቸው::
6ሙሴም አሮንንና ልጆቹን ወደ ፊት
አወጣቸው፤ በውሃም አጠባቸው:: 7አሮንን
እጀ ጠባብ አለበሰው፤ መቀነት አስታጠ
ቀው፤ ቀሚስ አጠለቀለት፤ ኤፉድ ደረበለት፤
በልዩ ጥበብ በተጠለፈው መታጠቂያ ኤፉ
ዱን አስታጠቀው፤ በላዩም አሰረው፤ 8የደረት
ኪሱን በላዩ አደረገለት፤ በደረት ኪሱም
ውስጥ ኡሪምንና ቱሚምን አኖረ:: 9እግዚ
አብሔር (ያህዌ) ባዘዘውም መሠረት፣ ሙሴ
ጥምጥሙን በአሮን ራስ ላይ አደረገ፤
በጥምጥሙም ላይ በፊት ለፊቱ በኩል
የተቀደሰውን አክሊል አደረገለት::

10ሙሴም መቅቢያ ዘይቱን ወሰደ፤
ማደሪያ ድንኳኑንና በውስጡ የሚገኘውን
ሁሉ ቀብቶ ቀደሰ:: 11ከዘይቱም ጥቂት
ወስዶ በመሠዊያው ላይ ሰባት ጊዜ ረጨ፤
ይቀድሳቸውም ዘንድ መሠዊያውን ከነመገ
ልገያ ዕቃው ሁሉ እንዲሁም የመታጠቢያ
ሳሕኑን ከነማስቀመጫው በዘይት ቀባ::
12ከመቅቢያ ዘይቱም በአሮን ራስ ላይ
አፈሰሰ፤ የተቀደሰ እንዲሆንም ቀባው::
13እግዚአብሔርም (ያህዌ) ባዘዘው መሠረት
ሙሴ፣ የአሮንን ልጆች ወደፊት አቅርቦ
እጀ ጠባብ አለበሳቸው፤ መታጠቂያ አስታጠ
ቃቸው፤ ቆብም ደፋላቸው::

14ሙሴም የኀጢአት መሥዋዕት የሆነ
ውን ወይፈን አመጣ፤ አሮንና ልጆቹም
በወይፈኑ ራስ ላይ እጃቸውን ጫኑ::
15ሙሴም ወይፈኑን ዐረደ፤ ደሙንም
ወስዶ መሠዊያውን ያነጻ ዘንድ በጣቱ
የመሠዊያውን ቀንዶች ሁሉ ቀባ፤ የቀረ
ውንም ደም በመሠዊያው ሥር አፈሰሰው::
ለመሠዊያውም እንዲህ አድርጎ ያስተሰር
ይለት ዘንድ ቀደሰው:: 16ሙሴም የሆድ
ዕቃውን የሚሸፍነውን ሁሉ፣ የጕበቱን
ሽፋን፣ ኵላሊቶችንና ሥባቸውን ወስዶ
በመሠዊያው ላይ አቃጠለ:: 17ሙሴም
እግዚአብሔር (ያህዌ) ባዘዘው መሠረት ወይ
ፈኑን፣ ቈዳውን፣ ሥጋውንና ፈርሱን ከሰፈር
ውጭ አቃጠለ::

18ሙሴ ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚሆ
ነውን አውራ በግ አቀረበ፤ አሮንና ልጆቹም

7፥26 ዘፍ9፥4
7፥27 ዘፍ9፥4
7፥30 ዘፀ29፥4
7፥31 ዘፀ29፥13፡27
7፥32 ዘፀ29፥27፤ ዘሌ10፥14፡15፤ ዘኍ5፥9፤6፥20፤ 18፥18
7፥34 ዘፀ29፥22፡ 27፤ ዘሌ10፥15፤ ዘኍ6፥20፤1ሳሙ 9፥24፤
7፥36 ዘሌ8፥12፡30
7፥37 ዘፀ29፥31፤ ዘሌ6፥9፡14
7፥38 ዘፀ19፥11፤ ዘሌ1፥2፤26፥46፤ ዘኍ36፥13፤ዘዳ4፥5፤ 29፥1
8፥2 ቀኍ18፡22፤ ዘፀ28፥1፡2፡4፡43፤ 29፥2-3፤30፥10፡ 23-25፡30፤39፥27፤ ዘሌ1፥5
8፥3 ዘኍ8፥9
8፥5 ዘፀ29፥1
8፥6 ዘፀ29፥4፤ 30፥19፤ሐሥ22፥16
8፥7 ዘፀ28፥4
8፥8 ዘፀ25፥7፤ 28፥30
8፥9 ዘፀ28፥2፡36፤ 39፥28፤ዘሌ21፥10
8፥10 ቀኍ2፤ ዘፀ26፥1፤30፥26
8፥11 ዘፀ30፥29
8፥12 ዘፀ30፥30፤ ዘሌ7፥36
8፥13 ዘፀ28፥4፡ 39፡40፤39፥27፤ ዘሌ21፥10
8፥14 ዘፀ30፥10፤ ዘሌ4፥3፡15
8፥15 ዘሌ4፥7፡ 18፤ሕዝ43፥20፤ ዕብ9፥22
8፥17 ዘሌ4፥11፡12
8፥18 ቀኍ2

፟25 ወይም በእሳት ከቀረበው

እጃቸውን በበጉ ላይ ጫኑ። 19ሙሴም
በጉን ዐርዶ ደሙን በመሠዊያው ላይ ዙሪ
ያውን ረጨ። 20በጉንም በየብልቱ ቈራ
ረጠ፤ ጭንቅላቱን፣ ብልቶቹንና ሥቡን
አቃጠለ። 21ሆድ ዕቃውንና እግሮቹን
በውሃ አጠበ፤ ሙሴም *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ባዘዘው መሠረት፣ በጉን በሙሉ *ለእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) በእሳት የሚቀርብ፣ ሽታውም
ደስ የሚያሰኝ የሚቃጠል መሥዋዕት
አድርጎ በመሠዊያው ላይ አቃጠለው።
22ሙሴ ለቅድስና የሚሆነውን ሌላ
አውራ በግ አቀረበ፤ አሮንና ልጆቹም እጆ
ቻቸውን በበጉ ራስ ላይ ጫኑ። 23ሙሴ
አውራ በጉን ዐረደ፤ ከደሙም ጥቂት
ወስዶ የአሮንን ቀኝ ጆሮ ጫፍ፣ የቀኝ
እጁን አውራ ጣትና የቀኝ እግሩን አውራ
ጣት አስነካ፤ 24የአሮንንም ልጆች ወደ
ፊት ጠራ፤ ከደሙም ጥቂት ወስዶ የቀኝ
ጆሮአቸውን ጫፍ፣ የቀኝ እጃቸውን አውራ
ጣትና የቀኝ እግራቸውን አውራ ጣት አስ
ነካ፤ የቀረውንም ደም በመሠዊያው ላይ
ዙሪያውን ረጨ። 25ሥቡን፣ ላቱን፣ ሆድ
ዕቃውን የሚሸፍነውን ሥብ ሁሉ፣ የጕበቱን
ሽፋን፣ ሁለቱን ኵላሊቶችና ሥባቸውን
እንዲሁም ቀኝ ወርቹን ወሰደ፤ 26*በእግዚ
አብሔርም* (ያህዌ) ፊት ካለው፣ ያለ እርሾ
የተጋገረ ዳቦ ካለበት መሶብ ላይ አንድ
ኅብስት፣ አንድ በዘይት የተጋገረ ዳቦ
እንዲሁም ስስ ቂጣ ወስዶ በሥቦቹና በቀኝ
ወርቹ ላይ አኖረ። 27እነዚህንም ሁሉ ለአሮ
ንና ለልጆቹ በእጃቸው ሰጣቸው፤ እነርሱም
የሚወዘወዝ መሥዋዕት አድርገው *በእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ፊት ወዘወዙት። 28ሙሴም
ከእጃቸው ተቀብሎ፣ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ)
በእሳት የሚቀርብ፣ ሽታውም ደስ የሚያ
ሰኝ መሥዋዕት አድርጎ በመሠዊያው ላይ
በሚቃጠለው መሥዋዕት ላይ አቃጠለው።
29ሙሴም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ባዘዘው መሠ
ረት፣ ድርሻው የሆነውን ክህነት የመጠ
ስጫውን አውራ በግ ፍርምባ ወስዶ
የሚወዘወዝ መሥዋዕት በማድረግ *በእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ፊት ወዘወዘው።
30ቀጥሎም ሙሴ በመቅቢያው ዘይትና
በመሠዊያው ላይ ካለው ደም ጥቂት ወስዶ፣
በአሮንና በልብሱ እንዲሁም በአሮን ልጆ
ችና በልብሳቸው ላይ ረጨ፤ በዚህም ሁኔታ
አሮንንና ልብሱን፣ ልጆቹንና ልበሳቸውን
ቀደሰ።
31ሙሴም አሮንና ልጆቹን እንዲህ አላ
ቸው፤ "ሥጋውን በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ
ቀቅሉት፤ በዚያም፣ 'አሮንና ልጆቹ ይብሉት'
ተብዬ በታዘዝሁት[አ] መሠረት፣ በክህነት
መስጫው መሥዋዕት መሶብ ውስጥ ካለው

8፥20 ዘሌ1፥8
8፥22 ቍ2፤ዘሌ4፥15
8፥23 ዘሌ14፥14፡25
8፥24 ዕብ9፥18-22
8፥25 ዘሌ3፥3-5
8፥26 ዘሌ2፥4
8፥27 ዘኍ5፥25
8፥29 ዘሌ7፥31-34
8፥30 ዘፀ28፥1፡2፤ ዘሌ7፥36
8፥31 ዘሌ6፥16
8፥33 ዘሌ14፥8፤ 15፥13፡28፤ ዘኍ19፥11፤ ሕዝ43፥25
8፥34 ዕብ7፥16
8፥35 ዘሌ18፥30፤ 22፥9፤ዘኍ3፥7፤9፥19ዘ ዳ11፥1፤1ነገ2፥3፤ ሕዝ48፥11፤ዘካ3፥7
9፥1 ዘሌ4፥15፤ ሕዝ43፥27
9፥3 ቍ8፡15፤ ዘሌ4፥3፡32፤10፥16
9፥4 ዘፀ29፥43፤ 32፥6፤ዘሌ4፥10፤
9፥6 ዘፀ16፥7
9፥7 ዘፀ30፥10፤ ዘሌ16፥6፤ ዕብ5፥1፡3፤7፥27
9፥8 ዘሌ4፥1-12፤ 10፥19

ኅብስት ጋር ብሉት፤ 32የተረፈውንም ሥጋና
ኅብስት በእሳት አቃጥሉ። 33የክህነት መቀ
በያችሁ ሥርዐት እስከሚፈጸምበት እስከ
ሰባት ቀን ድረስ በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ
ቆዩ፤ ሥርዐቱንም ለመፈጸም ሰባት ቀን
ይወስዳልና። 34ዛሬ የተፈጸመው ይህ ሥርዐት
ለእናንተ ማስተሰረያ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ያዘ ዘው ነው። 35እንዳትሞቱ ሰባቱን
ቀንና ሌሊት ከመገናኛው ድንኳን ደጃፍ
አትለዩ፤ *የእግዚአብሔርንም* (ያህዌ) ሥርዐ
ት ጠብቁ፤ የታዘዝሁት እንዲህ
ነውና።" 36አሮንና ልጆቹም *እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) በሙሴ አማካይነት
ያዘዘውን ሁሉ አደረጉ።

## ካህናቱ አገልግሎታቸውን ጀመሩ

9 በስምንተኛውም ቀን ሙሴ አሮንንና
ልጆቹን እንዲሁም የእስራኤልን ሽማ
ግሌዎች ጠራቸው፤ 2አሮንንም እንዲህ አለው፤
"የኀጢአት መሥዋዕት እንዲሆንልህ አንድ
እንቦሳ እንዲሁም የሚቃጠል መሥዋዕት
እንዲሆንልህ አንድ አውራ በግ፣ ወስደህ፣
*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት አቅርባቸው፤ ሁለ
ቱም እንከን የሌለባቸው ይሁኑ። 3እስራ
ኤላውያንንም እንዲህ በላቸው፤ 'ለኀጢአት
መሥዋዕት አንድ አውራ ፍየል፣ ለሚቃጠል
መሥዋዕት እንከን የሌለባቸውን የአንድ
ዓመት እምቦሳና የአንድ ዓመት ጠቦት፣
4ለኅብረት መሥዋዕት[ከ] አንድ በሬና[ኸ] አንድ
አውራ በግ በዘይት ከተለወሰ የእህል ቍር
ባን ጋር *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ለመ
ሠዋት አቅርቡ፤ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ዛሬ
ይገለጥላችኋልና።' "
5እነርሱም ሙሴ ያዘዛቸውን ሁሉ ወደ
መገናኛው ድንኳን ደጃፍ አመጡ፤ ሕዝቡም
በሙሉ ቀርበው *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት
ቆሙ። 6ሙሴም፣ "*የእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ክብር ይገለጥላችሁ ዘንድ፣ እንድታደርጉት
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ያዘዛችሁ ይህ ነው"
አለ።
7ሙሴ አሮንን፣ ወደ መሠዊያው ቀር
በህ የኀጢአት መሥዋዕትህንና የሚቃጠ
ለውን መሥዋዕትህን ሠዋ፤ ለራስህና ለሕ
ዝቡም አስተሰርይ፤ *እግዚአብሔርም* (ያህዌ)
ባዘዘው መሠረት የሕዝቡን መሥዋዕት
አቅርብ፤ አስተሰርይላቸውም" አለው።
8አሮንም ወደ መሠዊያው መጥቶ ስለ
ራሱ የኀጢአት መሥዋዕት የቀረበውን

[አ]31 ወይም *ብዬ ባዘዝሁት*
[ከ]4 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል፤ እንዲሁም ቍ 18፥22 ይመ።
[ኸ]4 የዕብራይስጥ ቃል ተባዕትና እንስትን ሊያጠቃልል ይችላል፤ እንዲሁም ቍ 18፡19 ይመ

እምቦሳ ዐረደው፡፡ 9ልጆቹም ደሙን አመጡ
ለት፤ እርሱም ጣቱን በደሙ ውስጥ ነክሮ
የመሠዊያውን ቀንዶች ቀባ፤ የተረፈውንም
ደም በመሠዊያው ግርጌ አፈሰሰው፡፡
10*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን ባዘዘው መ
ሠረት የኀጢአት መሥዋዕቱን ሥብ፣
ኵላሊቶቹንና የጕበቱን ሽፋን በመ
ሠዊያው ላይ አቃጠለው፤ 11ሥጋውንና
ቍርበቱንም ከሰፈሩ ውጭ በእሳት አቃጠ
ለው፡፡

12ከዚህ በኋላ አሮን የሚቃጠለውን
መሥዋዕት ዐረደ፤ ልጆቹ ደሙን አቀበ
ሉት፤ እርሱም ደሙን በመሠዊያው ላይ
ዙሪያውን ረጨ፡፡ 13ልጆቹም የሚቃጠ
ለውን መሥዋዕት ብልት አንድ በአንድ፣
ጭንቅላቱን ሳይቀር አምጥተው ሰጡት፤
እርሱም በመሠዊያው ላይ አቃጠለው፡፡
14የሆድ ዕቃውንና እግሮቹን አጥቦ በመ
ሠዊያው ላይ ካለው ከሚቃጠለው መሥዋ
ዕት በላይ አቃጠለ፡፡ 15አሮንም የሕዝቡን
መሥዋዕት አቀረበ፤ ስለ ሕዝቡ የኀጢአት
መሥዋዕት የሆነውን ፍየል ወስዶ ዐረደው፤
እንደ ፊተኛው ሁሉ ይህንም በኀጢአት
መሥዋዕትነት ሠዋው፡፡

16የሚቃጠለውንም መሥዋዕት አምጥቶ
በሥርዐቱ መሠረት አቀረበው፡፡ 17የእህል
ቍርባኑን አመጣ፤ ከላዩም እፍኝ ሙሉ
ወስዶ ጧት ጧት ከሚቀርበው የሚቃጠል
መሥዋዕት በተጨማሪ በመሠዊያው ላይ
አቃጠለ፡፡

18አሮንም ስለ ሕዝቡ የኅብረት መሥ
ዋዕት የቀረቡትን በሬውንና አውራ በጉን
ዐረደ፤ ልጆቹም ደሙን አመጡለት፤ እር
ሱም ደሙን በመሠዊያው ላይ ዙሪያውን
ረጨ፡፡ 19የበሬውንና የአውራ በጉን ሥብ፦
ላቱን፣ የሆድ ዕቃውን የሚሸፍነውን ሥብ፤
ኵላሊቶቹንና የጕበቱን ሽፋን፣ 20በፍር
ምባዎቹ ላይ አስቀመጡ፤ አሮንም ሥቡን
በመሠዊያው ላይ አቃጠለ፤ 21ፍርምባዎ
ቹንና የቀኝ ወርቹንም ሙሴ ባዘዘው መሠ
ረት፣ የመወዝወዝ መሥዋዕት አድርጎ
*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ወዘወዘው፡፡

22አሮንም እጆቹን ወደ ሕዝቡ ዘርግቶ
ባረካቸው፤ የኀጢአት መሥዋዕቱን፣ የሚ
ቃጠለውን መሥዋዕትና የኅብረቱን መሥ
ዋዕት ካቀረበ በኋላ ወረደ፡፡

23ከዚህ በኋላ፣ ሙሴና አሮን ወደ መገ
ናኛው ድንኳን ገቡ፤ ከዚያ ሲወጡም ሕዝ
ቡን ባረኩ፤ *የእግዚአብሔርም* (ያህዌ) ክብር
ለሕዝቡ ሁሉ ተገለጠ፡፡ 24እሳት *ከእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ዘንድ ወጥቶ፣ በመሠዊያው
ላይ የነበረውን በላ፤ ሕዝቡም ሁሉ ይህን
ባዩ ጊዜ እልል አሉ፤ በግምባራቸውም
ተደፉ፡፡

## የናዳብና የአብዩድ መሞት

10 የአሮን ልጆች ናዳብና አብዩድ
እያንዳንዳቸው ጥናዎቻቸውን ወስ
ደው ፍም አደረጉባቸው፤ ዕጣንም ጨመሩ
ባቸው፤ እርሱ ያላዘዛቸውን፣
ያልተፈቀደውን እሳት *በእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ፊት አቀረቡ፡፡ 2ከዚህም የተነሣ እሳት
*ከእግዚአብሔር* (ያህዌ) ዘንድ ወጥቶ በላቸው፤
*በእግዚአብሔርም* (ያህዌ) ፊት ሞቱ፡፡

3ሙሴም አሮንን እንዲህ አለው፤ "*እግዚ
አብሔር* (ያህዌ)፦
'ወደ እኔ በሚቀርቡት መካከል፣
ቅድስናዬን እገልጣለሁ፤
በሕዝቡም ሁሉ ፊት፣
እከበራለሁ' ብሎ የተናገረው ይህን ነው፡፡"
አሮንም ዝም አለ፡፡

4ሙሴ የአሮንን አጎት የዑዝኤልን
ልጆች ሚሳኤልንና ኤልጻፋንን ጠርቶ፣
"ወደዚህ ኑና ወንድሞቻችሁን አንሡ፤
ከመቅደሱም ደጃፍ አርቃችሁ፣ ከሰፈር
ወደ ውጭ ውሰዷቸው" አላቸው፡፡
5እነርሱም መጥተው ሙሴ ባዘዛቸው መ
ሠረት፣ ሚቶቹ የክህ ነት ቀሚሳቸውን
እንደ ለበሱ ተሸክመው ከሰፈር ወደ ውጭ
አወጧቸው፡፡

6ሙሴም አሮንንና የአሮንን ልጆች፣
አልዓዛርንና ኢታምርን እንዲህ አላቸው፤
"እንዳትሞቱ፣ በሕዝቡም ላይ ቍጣ እንዳ
ይመጣ ጠጕራችሁን አትንጩ፤[ሠ] ልብሳች
ሁንም አትቅደዱ፤ ነገር ግን *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) በእሳት ስላጠፋቸው ሰዎች ወንድሞ
ቻችሁ እስራኤላውያን ሊያለቅሱላቸው ይች
ላሉ፡፡ 7*የእግዚአብሔር* (ያህዌ) የመቅቢያ ዘይት
በላያችሁ ነውና እንዳትሞቱ ከመገናኛው
ድንኳን አትውጡ፡፡" እነርሱም ሙሴ እንዳ
ላቸው አደረጉ፡፡

8*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) አሮንን እንዲህ
አለው፤ 9"እንዳትሞቱ አንተና ልጆችህ ወደ
መገናኛው ድንኳን በምትገቡበት ጊዜ
የወይን ጠጅ ወይም ሌላ የሚያሰክር መጠ
ጥ አትጠጡ፤ ይህም በልጅ ልጃችሁ ዘንድ
የሚጠበቅ ዘላለማዊ ሥርዐት ነው፡፡ 10የተቀ
ደሰውንና ያልተቀደሰውን፣ ርኩሱንና
ንጹሑን ለዩ፤ 11*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) በሙሴ
አማካይነት የሰጣቸውን ሥርዐት ሁሉ ለእስ
ራኤላውያን አስተምሩ፡፡

12ሙሴም አሮንንና የተረፉትን ልጆቹን

9፥9 ቈ12፥18፤ ዘፀ29፥12፤ሕዝ43፥20
9፥11 ዘሌ4፥11፡12
9፥12 ቍ9፤ዘሌ10፥19
9፥13 ዘሌ1፥8
9፥14 ዘሌ1፥9
9፥15 ዘሌ4፥27-31
9፥16 ዘሌ1፥1-13
9፥17 ዘሌ3፥5
9፥18 ዘሌ3፥1-11
9፥21 ዘፀ29፥24፡26
9፥22 ዘፍ48፥20፤ ዘፀ39፥43፤ ሉቃ24፥50
9፥23 ዘፀ40፥2፤ 24፥16
9፥24 ዘፀ19፥18፤ መሳ6፥21፤13፥20፤ 1ነገ18፥39
10፥1 ቍ2፤ ዘፀ6፥23፤24፥1፤ 28፥1፤30፥9፤ ዘሌ16፥1፡12፤ ዘኍ3፥2-4፤ ዘኍ11፥1፤16፥7፡18፡3 5፡46፤26፥61፤ 1ነገ7፥50፤2ነገ25፥151 ዜና6፥3፤2ዜና4፥22ኤ ር52፥19፤ ኢሳ6፥6፤ሕዝ8፥11
10፥2 ዘፍ19፥24፤ 38፥7፤ዘኍ11፥1፤ 16፥35፤1ዜና24፥2፤ ኢዮ1፥16፤ መዝ2፥12፤50፥3፤ 106፤18፤ኢሳ29፥6
10፥3 ዘፀ14፥4፤ 19፥22፤30፥29፤ ዘሌ21፥6፤22፥32፤ ዘኍ16፥5፤20፥13፤ ኢ ሳ5፥16፤44፥23፤ 49፥3፤55፥5፤ 60፥21፤ሕዝ28፥22፤ 38፥16
10፥4 ዘፀ6፥18፡22፤ 25፥8፤ሐሥ5፥6፡9፡10
10፥5 ዘሌ8፥13
10፥6 ዘፍ50፥3፡ 10፤ዘፀ6፥23፤ ዘሌ13፥45፤21፥10፤ ዘኍ1፥53፤5፥18፤ 16፥22፤20፥29፤ ኢሱ7፥1፤22፥18፤ 1ሳሙ 25፥1፤ ኤር41፥5፤ማር14፥63
10፥7 ዘፀ25፥8፤ 28፥41
10፥9 ዘፍ9፥21፤ ዘፀ12፥14፤29፥40፤ ዘሌ23፥13፤ዘኍ6፥3፤1 5፥5፤ 28፥7፤ ዘዳ14፥26፤28፥39፤ 29፥6፤ መሳ13፥4፤ ምሳ23፥29-35፤ 31፥4፡7፤ኢሳ5፥22፤ 22፥13፤28፥1፡7፤ 29፥9፤56፥12፤ ኤር35፥6፤ሕዝ44፥21፤ ሆሴ4፥11፤ሚክ2፥11፤ ዕን2፥15-16፤ ሉቃ1፥15፤ኤፌ5፥18፤ 1ጢሞ3፥3፤ቲቶ1፥17
10፥10 ዘፍ7፥2፤ ዘሌ6፥27፤14፥57፤ 20፥25፤ሕዝ22፥26
10፥11 ዘዳ17፥10፡ 11፤24፥8፤25፥1፤ 33፥10፤2ዜና15፥3፤ 17፥7፤ዕዝ7፥25፤ ነህ8፥7፤ምሳ4፥27፤ ሐጌ2፥11፤ሚል2፥7
10፥12 ዘፀ29፥41፤ ዘሌ6፥14-18

[ሠ]6 ወይም *አትላጩ*

አልዓዛርንና ኢታምርን እንዲህ አላቸው፤ “በእሳት ለእግዚአብሔር (ያህዌ) ከቀረበው የእህል ቊርባን የቀረውን ወስዳችሁ ያለ እርሾ ጋግሩት፤ እጅግ ቅዱስ ስለሆነ በመሠዊያው አጠገብ ብሉት፤ [13]ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በእሳት ከሚቀርበው መሥዋዕት ያንተና የልጆችህ ድርሻ ይህ ስለሆነ፣ በተቀደሰ ስፍራ ብሉት፤ እንዲህ ታዝዣለሁና:: [14]ከእስራኤላውያን የኅብረት መሥዋዕት[o] ላይ የእናንተ ድርሻ ሆኖ ስለተሰጠ፣ የተወዘወዘውን ፍር ምባና የቀረበውን ወርች አንተ፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆችህ በአምልኮው ሥርዐት መሠረት ንጹሕ በሆነ ስፍራ ብሉት:: [15]የቀረበውን ወርችና የተወዘወዘውን ፍርምባ በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት የመወዝወዝ መሥዋዕት ሆኖ በእሳት ከቀረበው ሥብ ጋር ይምጣ:: ይህም እግዚአብሔር (ያህዌ) ባዘዘው መሠረት ለአንተና ለልጆችህ ለዘላለም የተመደበ ድርሻ ይሆናል::”

[16]ሙሴ ለኀጢአት መሥዋዕት የሚቀርበውን ፍየል አጥብቆ ፈለገ፤ መቃጠሉንም በተረዳ ጊዜ የተረፉትን የአሮንን ልጆች አልዓዛርንና ኢታምርን ተቈጣቸው፤ እንዲህም አላቸው፤ [17]“የኀጢአት መሥዋዕቱን ለምን በተቀደሰው ስፍራ አልበላችሁትም? እጅግ የተቀደሰ ነው፤ በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ስርየት በማስገኘት የሕዝቡን ኀጢአት እንድታስወግዱበት የተሰጣችሁ ነበር፤ [18]ደሙ ወደ ተቀደሰው ስፍራ ስላልገባ፣ በሰጠሁት ትእዛዝ መሠረት ፍየሉን በተቀደሰው ስፍራ መብላት ይገባችሁ ነበር::”

[19]አሮንም ሙሴን፣ “እነሆ፤ በዛሬው ቀን የኀጢአት መሥዋዕታቸውንና የሚቃጠል መሥዋዕታቸውን በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት አቀረቡ፤ እኔም እንዲህ ያለ ነገር የደረሰብኝ ሰው ነኝ፤ ታዲያ፣ ዛሬ የኀጢአት መሥዋዕቱን ብበላ ኖሮ እግዚአብሔርስ (ያህዌ) ደስ ይለው ኖሮአልን?” አለው:: [20]ሙሴም ይህን በሰማ ጊዜ መልሱ አረካው::

## የተፈቀደና ያልተፈቀደ መብል

11፥1-23 ተጓ ምብ ዘዳ 14፥3-20

**11** እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴንና አሮንን እንዲህ አላቸው፤ [2]“እስራኤላውያንን እንዲህ በሏቸው፤ ‘በየብስ ከሚኖሩ እንስሳት ሁሉ የምትበሏቸው እነዚህ ናቸው፡- [3]ሰኰናው የተሰነጠቀውን የሚያመሰኳውን ማንኛውንም እንስሳ መብላት ትችላላችሁ::

[4]“ ‘የሚያመሰኩ ሆነው ሰኰናቸው ያልተሰነጠቀ ወይም ሰኰናቸው የተሰነጠቀ ሆኖ የማያመሰኩትን አትብሉ፤ ግመል ያመሰኳል፤ ሰኰናው ስላልተሰነጠቀ ግን በእናንተ ዘንድ ርኩስ ይሁን:: [5]ሽኮኮ ያመስኳል፤ ሰኰናው ስላልተሰነጠቀ ግን በእናንተ ዘንድ ርኩስ ይሁን:: [6]ጥንቸል ያመሰኳል፤ ሰኰናው ስላል ተሰነጠቀ ግን በእናንተ ዘንድ ርኩስ ይሁን:: [7]ዐሳማ ሰኰናው የተሰነጠቀ ቢሆ ንም ስለ ማያመሰኳ በእናንተ ዘንድ ርኩስ ይሁን:: [8]የእነዚህን እንስሳት ሥጋ አትብሉ፤ ጥንባቸውንም አትንኩ፤ በእናንተ ዘንድ ርኩሶች ይሁኑ::

10፥13 ዘሌ6፥16፤ ሕዝ42፥13
10፥14 ዘፀ29፥31፤ ዘሌ4፥12፤ዘኍ5፥9
10፥15 ዘፀ29፥28፤ ዘሌ7፥34፤
10፥16 ዘሌ9፥3
10፥17 ዘፀ28፥38፤ ዘሌ6፥24-30፤ ሕዝ42፥13
10፥18 ዘሌ4፥18፤ 6፥17፡26
10፥19 ዘሌ9፥12
11፥2 ሐሥ10፥12-14
11፥4 ሐሥ10፥14
11፥7 ኢሳ65፥4፤ 66፥3፡17
11፥8 ዘሌ5፥2፤ ዕብ9፥10
11፥10 ቍ12
11፥11 ዘሌ5፥2
11፥12 ቍ10
11፥14 ዘፍ1፥11
11፥15 ዘፍ8፥7
11፥18 ኢሳ13፥21፤ 14፥23፤34፥11፡13፤ ሰፎ2፥14
11፥19 ዘፍ1፥11፤ ኢሳ2፥20፤ዘካ5፥9
11፥20 ሐሥ10፥14
11፥22 ማቴ3፥4፤ ማር1፥6
1፥24 ቍ27-40፤ ዘሌ5፥2፤13፥3፤14፥46፤ 15፥5፤22፥6፤ ዘኍ19፥7፡19
11፥25 ቍ28፤ ዘፀ19፥10፤ዘሌ13፥6፡ 34፤14፥8፡47፤15፥5፤ 16፥26፤ዘኍ8፥7፤ 19፥7፡8፤31፥24

[9]“ ‘በባሕሮችና በወንዞች ውሃ ውስጥ ከሚኖሩት ፍጡሮች ክንፍና ቅርፊት ያላቸውን መብላት ትችላላችሁ፤ [10]ነገር ግን በባሕሮችና በወንዞች ውስጥ ከሚኖሩት ፍጡሮች ሁሉ፣ ከሚንፏቀቁት ወይም በውሃ ውስጥ ከሚኖሩት ሕይወት ካላቸው ሌሎች ፍጡሮች መካከል ክንፍና ቅርፊት የሌላቸው በእናንተ ዘንድ አስጸያፊዎች ይሁኑ፤ [11]በእናንተ ዘንድ አስጸያፊ ስለ ሆኑ ሥጋቸውን አትብሉ፤ በድናቸውንም ትጸየፋላችሁ፤ [12]ክንፍና ቅርፊት የሌለው ማንኛውም በውሃ ውስጥ የሚኖር ፍጡር በእናንተ ዘንድ አስጸያፊ ይሁን::

[13]“ ‘ከአዕዋፍ ወገን እነዚህን ትጸየፋላችሁ፤ ጸያፍ ስለሆኑም አትብሏቸው፡- ንስር፣ ጥንብ አንሣ፣ ግልገል አንሣ፣ [14]ጭላት፣ ማንኛውም ዐይነት ጭልፊት፣ [15]ማንኛውም ዐይነት ቁራ፣ [16]ሰጎን፣ ጠላቋ፣ ዝይ፣ ማንኛውም ዐይነት በቋል፣ [17]ጕጕት፣ ርኩም፣ ጋጋኖ፣ [18]የውሃ ዶሮ፣ ይብራ፣ ስደተኛ አሞራ፣ [19]ሽመላ፣ ማንኛውም ዐይነት ሳቢሳ፣ ጅንጁላቴ ወፍና የሌሊት ወፍ::[″]

[20]“ ‘ክንፍ ኖሮአቸው በአራት እግር የሚንቀሳቀሱ ነፍሳት ሁሉ በእናንተ ዘንድ አስጸያፊዎች ይሁኑ:: [21]ነገር ግን ክንፍ ኖሮአቸው በአራት እግር ከሚንቀሳቀሱ ነፍሳት መካከል ከምድር በሚፈናጠሩበት እግራቸው አንጓ ያለባቸውን መብላት ትችላላችሁ:: [22]ከእነዚህ ማንኛውንም ዐይነት አንበጣ፣ ፌንጣና ኵብኵባ መብላት ትችላላችሁ:: [23]ነገር ግን ክንፍ ኖሮአቸው በአራት እግር የሚንቀሳቀሱትን ፍጥረታት ተጸየፏቸው::

[24]“ ‘ከእነዚህ የተነሣ ትረክሳላችሁ፤ የእነዚህን በድን የሚነካ ሁሉ እስከ ማታ ድረስ ርኵስ ይሆናል:: [25]የእነዚህንም በድን የሚያነሣ ሰው ሁሉ ልብሱን ይጠብ፤ ሆኖም እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ነው::

[26]“ ‘ሰኰና ያለው፣ ነገር ግን ሰኰናው ያልተሰነጠቀና የማያመሰኳ ማንኛውም እንስሳ በእናንተ ዘንድ ርኩስ ይሁን:: የእነዚህንም በድን የሚነካ ሰው ሁሉ ይረክሳል:: [27]አራት

[o]14 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል
[″]19 በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ያሉ የእያንዳንዱ አዕዋፍ፣ ነፍሳትና እንስሳት ትክክለኛ ማንነታቸው በትክክል አይታወቅም

እግር ካላቸው እንስሳት ሁሉ በመዳፋቸው
የሚሄዱት በእናንተ ዘንድ ርኩሳን ናቸው፤
በድናቸውንም የሚነካ ሁሉ እስከ ማታ
ድረስ ርኵስ ይሆናል። 28የእነዚህን በድን
የሚያነሣ ሰው ልብሱን ይጠብ፤ ሆኖም
እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ይሆናል፤ እንስሳተ
-ም በእናንተ ዘንድ ርኵሳን ናቸው።
29“ ‘ምድር ለምድር ከሚንቀሳቀሱ እን
ስሳት መካከል እነዚህ በእናንተ ዘንድ ርኩ
ሳን ናቸው፦ ሙጭልጭላ፣ ዐይጥ፣ እን
ሽላሊት በየወገኑ፣ 30ዔሊ፣ ዐዞ፣ ገበሎ፣
አርጃኖ፣ ዕሥሥት። 31ምድር ለምድር ከሚ
ንቀሳቀሱ እንስሳት ሁሉ መካከል እነዚህ
በእናንተ ዘንድ ርኩሳን ናቸው፤ ከእነዚህም
የሞተውን የሚነካ ሁሉ እስከ ማታ ድረስ
ርኩስ ይሆናል። 32በድኑ በማንኛውም ዕቃ
ላይ ቢወድቅ ያ ዕቃ ከዕንጨት፣ ከጨርቅ፣
ከቈዳ ወይም ከበርኖስ የተሠራ ቢሆን
ርኩስ ይሆናል፤ በውሃ ውስጥ ይደረግ፤
ሆኖም ርኩስ ነው፤ ከዚያም በኋላ ንጹሕ
ይሆናል። 33በድኑም በሸክላ ዕቃ ውስጥ
ቢወድቅ፣ በውስጡ ያለ ነገር ሁሉ ርኩስ
ስለሚሆን ዕቃውን ስበሩት። 34ማንኛውም
ምግብ እንዲህ ካለው ዕቃ ውሃ ቢፈስበት
ይረክሳል፤ ከዚህ ዕቃ የሚጠጣውም ነገር
ሁሉ ርኵስ ነው፤ 35ከበድናቸው አንዱ
የወደቀበት ነገር ሁሉ ይረክሳል፤ ምድጃም
ይሁን ማሰሮ ይሰበር፤ ርኩሳን ናቸው፤
እናንተም ተጸየፏቸው። 36ነገር ግን ምንጭ
ወይም የውሃ ማጠራቀሚያ ጕድጓድ ንጹሕ
እንደ ሆነ ይቈያል፤ ሆኖም በድኑን የነካ
ይረክሳል። 37በሚዘራ ዘር ላይ በድን ቢወ
ድቅ ዘሩ ንጹሕ እንደሆነ ይቆያል። 38ነገር
ግን በዘሩ ላይ ውሃ ከፈሰሰበት በኋላ በድን
ቢወድቅበት ዘሩ በእናንተ ዘንድ ርኩስ
ነው።
39“ ‘እንድትበሉ ከተፈቀደላችሁ እንስ
ሳት አንዱ ቢሞት፣ በድኑን የሚነካ ማንኛ
ውም ሰው እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ይሆ
ናል። 40ማንም ሰው ከበድኑ ቢበላ ልብሱን
ይጠብ፤ ሆኖም እስከ ማታ ድረስ ርኩስ፤
በድኑን የሚያነሣ ልብሱን ይጠብ፤ ሆኖም
እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ይሆናል።
41“ ‘ምድር ለምድር የሚንቀሳቀስ ማንኛ
ውም ፍጡር ጸያፍ ነው፤ አይበላም። 42ምድር
ለምድር የሚንቀሳቀሰውን ፍጡር ሁሉ፣
ይኸውም በደረቱ የሚሳበውን ወይም በአራት
እግር የሚሄደውን ወይም ብዙ እግሮች
ያሉትን አትብሉ፤ ጸያፍ ነው። 43በእነዚህ
ፍጡራን ሁሉ ራሳችሁን አስጸያፊ አታድ
ርጉ፤ በእነርሱም ራሳችሁን በማጕደፍ
አት ርከሱ። 44እኔ እግዚአብሔር

11፥28 ዕብ9፥10
11፥29 ቈ41፤ ኢሳ66፥17
11፥32 ዘሌ15፥12፤ ዘኍ19፥18፤31፥20
11፥33 ዘሌ6፥28
11፥39 ቈ40፤ ዘሌ17፥15፤22፥4፡8፤ ዘኍ19፥11፤ዘዳ14፥21፤ ሕዝ4፥14፤44፥31
11፥40 ቈ25፡39፤ ዘሌ14፥8፤17፥15፤ 22፥8፤ሕዝ44፥31፤ ዕብ9፥10
11፥43 ቈ44፤ ዘሌ20፥25፤22፥5
11፥44 ቈ43፤ ዘፀ6፥2፡7፤19፥10፤ 20፥2፤22፥31፤31፥13ዘ ሌ19፥2፤20፥7፤ ዘኍ15፥40፤ዘዳ14፥2ኢ ሱ3፥5፤ 7፥13፤ 24፥19፤ 1ሳሙ2፥2፤ 1ዜና15፥12፤ 2ዜና29፥5፤35፥6፤ ኢዮ6፥10፤ መዝ99፥3፤ኢሳ43፥3፤ 51፥15፤ሕዝ20፥5፤ ኤፌ1፥4፤1ተሰ4፥7፤ 1ጴጥ1፥15፡16
11፥45 ዘፍ17፥7፤ ዘፀ19፥6፤ዘሌ25፥38፡ 55፤1ጴጥ1፥16
11፥47 ዘሌ10፥10
12፥2 ዘሌ15፥19፤ 18፥19፤ኢሳ64፥6፤ ሕዝ18፥6፤22፥10፤ 36፥17
12፥3 ዘፍ17፥10፤ ዘፀ22፥30፤ሉቃ1፥59
12፥6 ዘፀ29፥38፤ ዘሌ5፥7፤23፥12፤ ዘኍ6፥12፡14፤7፥15፤ሉ ቃ2፥22
12፥8 ዘፍ15፥9፤ ዘሌ4፥26፤5፥7፤ 14፥22፤ሉቃ2፥22-24
13፥2 ቈ3፡4፡9፡ 10፡15፡19፡28፡38፡ 39፡43፤ዘፀ4፥6፤ ዘሌ14፥3፡32፡56፤ ዘኍ5፥2፤ዘዳ24፥8

አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ቅዱስ ነኝና እናንተም
ተለዩ፤ ቅዱሳንም ሁኑ፤ ምድር ለምድር
በሚንቀሳቀስ በማን ኛውም ፍጡር ራ
ሳችሁን አታርክሱ። 45አምላ ካችሁ (ኤሎሂም)
እሆን ዘንድ ከግብፅ ምድር ያወጣኋችሁ
እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ፤ ስለዚህ እኔ
ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ።
46“ ‘እንስሳትንና አዕዋፍን፣ በውሃ ውስጥ
የሚኖሩትንና ምድር ለምድር የሚንቀሳቀ
ሱትን ፍጥረታት ሁሉ በሚመለከት የተሰጠ
ሕግ ይህ ነው። 47በዚህም በርኩሱና በንጹሑ
መካከል፣ እንዲሁም ሕይወት ካላቸው ፍጡ
ራን የሚበሉትንና የማይበሉትን ትለያላ
ችሁ።’ ”

## ከወሊድ በኋላ የመንጻት ሥርዐት

12 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2“እስራኤላውያንን እንዲህ
በላቸው፤ ሴት አርግዛ ወንድ ልጅ በምትወ
ልድበት ጊዜ፣ ልክ እንደ ወር አበባዋ ጊዜ
እስከ ሰባት ቀን ትረክሳለች። 3ሕፃኑም
በስምንተኛው ቀን ይገረዝ። 4ሴትዮዋም
ከደሟ እስክትነጻ ድረስ ሠላሳ ሦስት ቀን
ትቆይ፤ የመንጻቷም ወራት እስኪፈ
ጸም ድረስ ማንኛውንም የተቀደሰ ነገር
አትንካ፤ ወደ ቤተ መቅደስም አትግባ።
5ነገር ግን የወለደችው ሴት ልጅ ከሆነ፣
እንደ ወር አበባዋ ጊዜ ሁለት ሳምንት
ትረክሳለች፤ ከዚያም ከደሟ እስክትነጻ
ስድሳ ስድስት ቀን ትቆይ።
6“ ‘ሴትዮዋ ወንድ ወይም ሴት ልጅ
ዋን ወልዳ የመንጻትዋ ጊዜ ሲፈጸም፣ ለሚ
ቃጠል መሥዋዕት የአንድ ዓመት ጠቦት፣
ለኀጢአት መሥዋዕት አንድ የዋኖስ ጫጩት
ወይም አንድ ርግብ ወደ መገናኛው ድንኳን
ደጃፍ ወስዳ ካህኑ ዘንድ ታቅርብ። 7ካህኑም
በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ያቅርበው፤ ያስተ
ሰርይላትም፤ ሴትዮዋም ከደሟ ፈሳሽ
ትነጻለች።
“ ‘ሴትዮዋ ወንድ ወይም ሴት ብትወልድ
ሕጉ ይኸው ነው። 8ጠቦት ለማምጣት ዐቅ
ምዋ ካልፈቀደ፣ ሁለት ርግቦች ወይም
ሁለት የዋኖስ ጫጩቶች፣ አንዱ ለሚቃጠል
መሥዋዕት፣ ሌላው ደግሞ ለኀጢአት መሥ
ዋዕት ታቅርብ፤ በዚህም ካህኑ ያስተሰር
ይላታል፤ እርስዋም ትነጻለች።’ ”

## ተላላፊ የቈዳ በሽታ

13 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴንና አሮንን
እንዲህ አላቸው፤ 2“ማንኛውም ሰው
በሰውነቱ ቈዳ ላይ ዕብጠት ወይም ችፍታ
ቋቍቻ ቢወጣበትና ይህም ወደ ተላላፊ
የቈዳ በሽታ[ዡ] የሚለወጥበት ከሆነ፣ ወደ

ካህኑ አሮን ወይም ካህናት ከሆኑት ልጆቹ[የ]
ወደ አንዱ ያምጡት:: 3ካህኑም በሰውየው
ቈዳ ላይ ያለውን ቍስል ይመርምር፤
በቍስሉ በተበከለው አካባቢ ያለው ጠጕር
ወደ ነጭነት ተለውጦ ቢያገኘውና ቦታው
ጐድጐዶ[ዶ] ወደ ውስጥ ቢገባ፣ ይህ ተላላፊ
የቈዳ በሽታ ነው:: ካህኑም መርምሮ ይህን
ባወቀ ጊዜ፣ ሰውየው በአምልኮው ሥርዐት
መሠረት ርኵስ መሆኑ ይገለጽ::
4በቈዳው ላይ ያለው ቋቊቻ ነጭ ሆኖ ቢ
ታይ ነገር ግን ከቈዳው በታች ዘልቆ
ባይገባና በቦ ታው ላይ የሚገኘው ጠጕር
ወደ ነጭነት ባይለወጥ፣ ካህኑ በሽተኛውን
ሰባት ቀን ያግልለው:: 5በሰባተኛውም ቀን
ካህኑ በሽ ተኛውን ይመርምረው፤ ቍስሉ
ለውጥ ካላ መጣና በቈዳውም ላይ
ካልተስፋፋ እንደገና ሰባት ቀን ያግልለጠ
ው:: 6በሰባተኛው ቀን ካህኑ እንደገና
ይመርምረው፤ ቍስሉ ከከሰ መና በቈዳው
ላይ ካልተስፋፋ፣ ካህኑ ሰውየው ንጹሕ
መሆኑን ያስታውቅ፤ ቍስሉ ችፍታ እንጂ
ሌላ አይደለም:: ሰውየው ልብሱን ይጠብ፤
ንጹሕም ይሆናል:: 7ራሱን ለካህን አሳይቶ
መንጻቱ ከታወቀ በኋላ፣ ችፍታው
በቈዳው ላይ እየተስፋፋ ከሆነ፣ እንደገና
ካህኑ ፊት ይቅረብ፤ 8ካህኑም
ይመርምረው፤ ችፍታው በቈዳው ላይ ተስፋ
ፍቶ ከተገኘ ካህኑ ሰው የው ርኩስ መሆ
ኑን ያስታውቅ፤ ተላላፊ የቈዳ በሽታ ነው::
9“ማንኛውም ሰው ተላላፊ የቈዳ በሽታ
ከያዘው፣ ወደ ካህኑ ያምጡት፤ 10ካህኑም
ይመርምረው፤ በሰውነቱ ላይ ጠጕሩን
ወደ ነጭነት የለወጠ ነጭ ዕባጭ ካለና
በዕብጠቱም ውስጥ ቀይ ሥጋ ቢታይ፣
11ሥር የሰደደ የቈዳ በሽታ ነውና
ሰውየው ርኩስ መሆኑን ካህኑ ያስታውቅ፤
ርኩስ መሆኑ ግልጽ ስለ ሆነም ሰውየውን
አያግልለው::
12“ደዌው በአካላቱ ሁሉ ላይ በመውጣት
በሽተኛውን ከራስ ጠጕር እስከ እግር ጥፍር
ያለበሰው መሆኑን ካህኑ እስካየ ድረስ፣
13ካህኑ ይመርምረው፤ ደዌው የሰው የውን
ሰውነት ሙሉ በሙሉ ሸፍኖት ከተገኘ፣ ያ
ሰው ንጹሕ መሆኑን ያስታውቅ፤ ሙሉ
በሙሉ ነጭ ስለ ሆነ ንጹሕ ነው:: 14ነገር
ግን ቍስሉ አመርቅዞ ቀይ ሥጋ ቢታይበት
ርኩስ ይሁን:: 15ካህኑም የተገለጠውን ቀይ
ሥጋ በሚያይበት ጊዜ ርኩስ መሆኑን
ያስታውቅ፤ ቀይ ሥጋ ርኩስ ስለ ሆነ፣
ተላላፊ በሽታ ነው:: 16ቀይ ሥጋ ተለውጦ
ከነጣ ግን ወደ ካህኑ ይሂድ፤ 17ካህኑም
ይመርምረው፤ ቍስሎች ወደ ነጭነት ተለ
ውጠው ከተገኙ፣ የታመመው ሰው ንጹሕ
መሆኑን ካህኑ ያስታውቅ፤ ንጹሕም ይሆናል::
18“አንድ ሰው በገላው ላይ ዕባጭ ወጥቶ
ቢድን፣ 19ዕባጩ በነበረበት ቦታ ላይም
ነጭ ዕብጠት ወይም ነጣ ያለ ቀይ ቋቊቻ
ቢታይ፣ ካህኑ ዘንድ ይቅረብ:: 20ካህኑም
ይመርምረው፤ ከቈዳው በታች ዘልቆ የገባ
ቢሆን በቦታውም ያለው ጠጕር ቢነጣ፣
ሰውየው ርኩስ መሆኑን ካህኑ ያስታውቅ::
21ነገር ግን ካህኑ በሚመረምርበት ጊዜ
ነጭ
ጠጕር በውስጡ ከሌለ፣ ዘልቆ ካልገባና
የከሰመ ቢሆን፣ ካህኑ ሰባት ቀን ያግልለጠ
ው:: 22በቈዳው ላይ ተስፋፍቶ ካገኘውም፣
ርኩስ መሆኑን ካህኑ ያስታውቅ፤ የሚተላለፍ
ነው:: 23ቋቊቻው ግን ባለበት ከቈየና ወደ
ሌላ ስፍራ ካልተስፋፋ፣ የዕባጩ ጠባሳ
እንጂ ሌላ አይደለም፤ ካህኑም ንጹሕ
መሆኑን ያስታውቅ::
24“አንድ ሰው እሳት ቈዳውን ቢያቃ
ጥለውና በተቃጠለው ስፍራ ነጣ ያለ ቀይ
ወይም ነጭ ቋቊቻ ቢታይበት፣ 25ካህኑ
ይመርምረው፤ ቋቊቻው ባለበትም ቦታ
ያለው ጠጕር ቢነጣና ከቈዳው በታች
ዘልቆ ቢገባ፣ በቃጠሎው ሰበብ ከውስጥ
የወጣ ተላላፊ በሽታ ነው፤ ሰውየው ርኩስ
መሆኑን ካህኑ ያስታውቅ፤ ተላላፊ የቈዳ
በሽታ ነው:: 26ነገር ግን ካህኑ በሚመ
ረምርበት ጊዜ ነጭ ጠጕር የሌለበት፣
ከቈዳውም በታች ዘልቆ ያልገባና የከሰመ
ቢሆን፣ ካህኑ ሰውየውን ሰባት ቀን ያግል
ለው:: 27በሰባተኛው ቀን ካህኑ ይመርም
ረው፤ በሽታውም በቈዳው ላይ ተስፋፍቶ
ቢያገኘው፣ ሰውየው ርኩስ መሆኑን ካህኑ
ያስታውቅ፤ ተላላፊ የቈዳ በሽታ ነው::
28ቋቊቻ ባለበት ከቈየና በቈዳው ላይ
ካልተስፋፋ፣ ይልቁንም እየከሰመ ከሄደ፣
በቃጠሎው ሰበብ የተከሠተ ዕብጠት ነውና
ካህኑ ንጹሕ መሆኑን ያስታውቅ፤ የቃጠ
ሎው ጠባሳ እንጂ ሌላ አይደለም::
29“በወንድ ወይም በሴት ዐናት ወይም
አገጭ ላይ ቍስል ቢወጣ፣ 30ካህኑ ቍስሉን
ይመርምር፤ ከቈዳው በታች ዘልቆ ከገባ፣
በውስጡም ያለው ጠጕር ቢጫና ቀጭን
ከሆነ ያ ሰው ርኩስ መሆኑን ካህኑ ያስታ
ውቅ፤ የሚያሳክክ የራስ ወይም የአገጭ
ተላላፊ በሽታ ነው:: 31ካህኑ እንዲህ ዐይነ
ቱን ቍስል በሚመረምርበት ጊዜ፣ ከቈዳው
በታች ዘልቆ ካልገባና በውስጡም ጥቍር
ጠጕር ከሌለ፣ ካህኑ ሰውየውን ሰባት ቀን

13፥3 ቍ8፡11፡ 20፡30፤ዘሌ21፥1፤ ዘኍ9፥6
13፥4 ቍ2፡5፡21፡ 26፡33፡46፤ዘሌ14፥38 ዘኍ12፥14፡15፤ ዘዳ24፥9
13፥5 ቍ27፡32፡ 34፡51፤ዘሌ14፥9
13፥6 ቍ13፡17፡ 23፡28፡34፤ዘሌ11፥25 ፤14፥8፡9፡20፤ 48፤15፥8፤ዘኍ8፥7፤ ማቴ8፥3፤ ሉቃ5፥12-14
13፥7 ሉቃ5፥14
13፥11 ዘፀ4፥6፤ ዘሌ14፥8፤ዘኍ12፥10 ማቴ8፥2
13፥15 ቍ2
13፥17 ቍ6
13፥18 ዘፀ9፥9
13፥19 ቍ2፡24፡ 42፤ዘሌ14፥37
13፥20 ቍ2
13፥23 ቍ6
13፥25 ቍ11
13፥26 ቍ4
13፥27 ቍ5
13፥28 ቍ2
13፥29 ቍ43፡44
13፥31 ቍ4

[ቸ]2 በትውፊት ለምጽ፤ የዕብራይስጡ ቃል ከቈዳ ጋር ለያይዘ በሽታ አንድ ነው:: በዚህ ምዕራፍ ሌላ ስፍራ ይገኛል::
[የ]2 ወይም *ዘሮቹ*
[ዶ]3ወይም *ከሌላው የቈዳ ክፍል ጠልቆ ቢገባ፤* በዚህ ምዕራፍ በሌላ ስፍራም ይገኛል::

ያግለለው:: 32ካህኑም በሰባተኛው ቀን
ቍስሉን ይመርምር፤ የሚያሳክከው ቦታ
ያልሰፋ፣ ቢጫ ጠጕር የሌለውና ከቈዳው
በታች ዘልቆ ያልገባ ከሆነ፣ 33ከቈሰለው
ቦታ በስተቀር ጠጕሩን ይላጭ፤ ካህኑ ሰባት
ተጨማሪ ቀን ሰውየውን ያግልል:: 34ካህኑ
በሰባተኛው ቀን የሚያሳክከውን የሰውየውን
ቍስል ይመርምር፤ በቈዳው ላይ ካልሰፋና
ከቈዳው በታች ዘልቆ ካልገባ ካህኑ ያ
ሰው ንጹሕ መሆኑን ያስታውቅ፤ ልብሱን
አጥቦ ንጹሕ ይሁን:: 35ንጹሕ መሆኑ ከተገለጠ
በኋላ ግን የሚያሳክከው ቍስል ተስፋፍቶ
ቢገኝ፣ 36ካህኑ ይመርምረው፤ ቍስሉ
በቈዳው ላይ ከሰፋ፣ ካህኑ የጠጕሩን ቢጫ
መሆን አለመሆን ማየት አያሻውም፤ ሰው
የው ርኩስ ነው:: 37ነገር ግን ቍስሉ በካህኑ
አመለካከት ለውጥ ያላሳየ ከሆነና በውስጡ
ጥቍር ጠጕር ካበቀለ ቍስሉ ድኖአል፤
ሰውየው ነጽቶአል፤ ካህኑም ንጹሕ መሆኑን
ያስታውቅ::

38"በወንድ ወይም በሴት ቈዳ ላይ
ቋቍቻ ቢወጣ፣ 39ካህኑ ይመርምራቸው፤
ቋቍቻው ዳለቻ ከሆነ በቈዳ ላይ የወጣ
ጕዳት የማያስከትል ችፍታ ነው፤ ሰውየውም
ንጹሕ ነው::

40"አንድ ሰው የራሱ ጠጕር ከዐናቱ
አልቆ መላጣ ቢሆን ንጹሕ ነው:: 41ጠጕሩ
ከፊት ለፊት ተመልጦ ራሰ በራ ቢሆንም
ንጹሕ ነው:: 42ነገር ግን በመላጣው
ወይም በበራው ላይ ነጣ ያለ ቀይ ቍስል
ቢወ ጣበት፣ ያ ከመላጣው ወይም ከበራው
የወጣ ተላላፊ በሽታ ነው:: 43ካህኑ
ይመርምረው፤ በመላጣው ወይም በበራው
ላይ ያበጠው ተላላፊ የቈዳ በሽታ
የሚመስል ነጣ ያለ ቍስል ከሆነ፣
44ሰውየው ደዌ አለበት፤ ርኵስም ነው፤
በራሱ ላይ ካለው ቍስል የተነሣም
ሰውየው ርኩስ መሆኑን ካህኑ
ያስታውቅ::

45"እንዲህ ያለ ተላላፊ በሽታ ያለበት
ሰው የተቀደደ ልብስ ይልበስ፤ ጠጕሩን
ይግለጥ፤[፳] እስከ አፍንጫውም ድረስ ተሸፋ
ፍኖ 'ርኩስ ነኝ! ርኩስ ነኝ!' እያለ ይጮኽ::
46ተላላፊ በሽታው እስካለበት ጊዜ ድረስ
ርኩስ ነው፤ ብቻውን ይቀመጥ፤ ከሰፈር
ውጪም ይኑር::

### በልብስ ላይ የሚታይ ተላላፊ በሽታ

47"ከበግ ጠጕር ወይም ከበፍታ የተሠራ
ማንኛውም ዐይነት ልብስ በተላላፊ በሽታ
ቢበከል፣ 48በሸማኔ ዕቃ ወይም በእጅ የተ
ሠራ ማንኛውም ዐይነት የበግ ጠጕር
ወይም የበፍታ ልብስ፣ ወይም
ማንኛውም ቈዳ ወይም ከቈዳ የተሠራ
ነገር ቢሆን፣ 49በል ብስ ወይም በዐጐዛ፣
በሸማኔ ዕቃ በተሠራ ወይም በእጅ በተጠ
ለፈ ወይም ከቈዳ በተሠራ ዕቃ ላይ
አረንጓዴ ወይም ቀይ መሳይ ደዌ ቢከ
ሠት፣ እየሰፋ የሚሄድ ተላላፊ በሽታ ስለ
ሆነ ካህኑ ይየው:: 50ካህኑ ደዌ ውን
ይመርምር፤ በደዌ የተበከለውንም ዕቃ
ሰባት ቀን ያግልል:: 51በሰባተኛውም ቀን
ይመርምረው፤ ደዌው በልብሱ፣ በሸማኔ
ዕቃ በተሠራው ወይም በእጅ በተጠለፈው
ጨርቅ ወይም ለማናቸውም አገልግሎት
በሚውል ዐጐዛ ላይ ተስፋፍቶ ቢገኝ፣
ክፉ ደዌ ነው፤ ዕቃውም ርኩስ
ነው:: 52ልብሱን ወይም በሸማኔ ዕቃ
የተሠራውን ወይም በእጅ የተጠለፈውን
የበግ ጠጕር ወይም በፍታ ወይም ደዌው
ያለበትን ማንኛውንም ከቈዳ የተሠራ ዕቃ
ያቃጥል፤ ደዌው ክፉ ነውና፤ ዕቃው
ይቃጠል::

53"ነገር ግን ካህኑ በሚመረምርበት ጊዜ
ደዌው በልብሱ ወይም በሸማኔ ዕቃ በተ
ሠራው ወይም በእጅ በተጠለፈው ጨርቅ
ላይ፣ ወይም ከቈዳ በተሠራው ዕቃ ላይ
ተስፋፍቶ ካልተገኘ፣ 54ካህኑ ደዌው ያለበት
ነገር እንዲታጠብ ይዘዝ፤ ዕቃውንም ሰባት
ቀን ደግሞ ያግልል:: 55ደዌው ያለበት ዕቃ
ከታጠበ በኋላ ካህኑ ይመርምረው፤ ደዌው
ባይስፋፋም እንኳ መልኩን ካልለወጠ፣
ርኩስ ነው፤ ደዌው የወጣው በውስጥም
ሆነ በውጭ ዕቃው በእሳት ይቃጠል::
56ዕቃው ከታጠበ በኋላ ካህኑ በሚመረምርበት
ጊዜ ደዌው ከስሞ ቢገኝ፣ በደዌ የተበከ
ለውን ቦታ ከልብሱ ወይም ከቈዳው ወይም
በሸማኔ ዕቃ ከተሠራው ወይም በእጅ
ከተጠለፈው ጨርቅ ቀዶ ያውጣ:: 57ነገር
ግን ደዌው በልብሱ ወይም በሸማኔ ዕቃ
በተሠራው ወይም በእጅ በተጠለፈው
ጨርቅ ላይ ወይም ከቈዳ በተሠራው ዕቃ
ላይ ቢታይ፣ መስፋፋቱ ስለ ሆነ ደዌው
ያለበት ማንኛውም ነገር በእሳት ይቃጠል::
58ታጥቦ ከደዌ የጠራ ልብስ ወይም በሸ
ማኔ ዕቃ የተሠራ ወይም በእጅ የተጠለፈ
ጨርቅ ወይም ከቈዳ የተሠራ ማንኛውም ዕቃ
እንደ ገና ይታጠብ፤ ንጹሕም ይሆናል::"

59ከበግ ጠጕር ወይም ከበፍታ የተሠ
ራ ልብስ ወይም በሸማኔ ዕቃ የተሠራ
ወይም በእጅ የተጠለፈ ጨርቅ ወይም
ከቈዳ የተሠራ ማንኛውም ዕቃ በደዌ ቢ
በከል፣ ንጹሕ ወይም ርኩስ መሆኑን ለ
ማወቅ ሕጉ ይህ ነው::

### ከተላላፊ የቈዳ በሽታ የመንጻት ሥርዐት

14 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2"የታመመው ሰው እንዲ

13፥32 ቍ5
13፥34 ቍ5፤ ዘሌ11፥25
13፥36 ቍ30
13፥40 ዘሌ21፥5፤ 2ነገ2፥23፤ ኢሳ3፥24፤ 15፥2፤22፥12፤ ሕዝ27፥31፤29፥18፤ አሞ8፥10፤ ሚክ1፥16
13፥45 ዘሌ5፥2፤ 10፥6፤ሕዝ24፥17፡ 22፤ሰቆ4፥15፤ ሚክ3፥7፤ሉቃ17፥12
13፥46 ዘኍ5፥1-4፤ 12፥14፤2ነገ7፥3፤ 15፥5
13፥49 ማር1፥44
13፥50 ሕዝ44፥23
13፥51 ቍ5፤ ዘሌ14፥44
13፥52 ቍ55፥57
14፥2 ዘሌ13፥57፤ ዘዳ24፥8፤ማቴ8፥2-4፤ ማር1፥40-44፤ ሉቃ5፥12-14፤17፥14

[፳]45 ወይም ራሱንም አይሸፍን

ነጻ ወደ ካህኑ በሚወስዱት ጊዜ ሥርዐቱ
እንዲህ ነው:- 3ካህኑ ከሰፈር ወደ ውጭ
ወጥቶ ይመርምረው፤ ሰውየው ከተላላፊ
የቈዳ በሽታው[ገ] ተፈውሶ ከሆነ፣ 4ካህኑ
ስለሚነጻው ሰው፣ ለመብላት ከተፈቀደው
የወፍ ዐይነት ሁለት ከነሕይወታቸው፣ የዝ
ግባ ዕንጨት፣ ደመቅ ያለ ቀይ ድርና ሂሶጵ
እንዲያመጣ ይዘዝ:: 5ካህኑም ከወፎቹ አንዱን
በሸክላ ዕቃ ውስጥ ባለ የምንጭ ውሃ ላይ
እንዲታረድ ይዘዝ:: 6በሕይወት ያለውንም
ወፍ ከዝግባው ዕንጨት፣ ደመቅ ካለው
ቀይ ድርና ከሂሶጵ ጋር በምንጩ ውሃ
ላይ በታረደው ወፍ ደም ውስጥ ይንከር::
7ከተላላፊ በሽታ የሚነጻውንም ሰው ሰባት
ጊዜ ይርጨው፤ መንጻቱንም ያስታውቅ፤ በሕ
ይወት ያለውንም ወፍ ወደ ውጭ ይልቀ
ቀው::

8"የሚነጻው ሰው ልብሱን ይጠብ፤ ጠጕ
ሩን በሙሉ ይላጭ፤ ሰውነቱን በውሃ ይታጠብ፤
በሥርዐቱም መሠረት ንጹሕ ይሆናል::
ከዚህም በኋላ ወደ ሰፈር መግባት ይችላል፤
ነገር ግን ሰባት ቀን ከድንኳኑ ውጭ
ይቈይ:: 9በሰባተኛውም ቀን ጠጕሩን በሙሉ
ይላጭ፤ ራሱን፣ ጢሙን፣ ቅንድቡንና
ሌላውንም ጠጕር ሁሉ ይላጭ:: ልብሱን
ይጠብ፤ ሰውነቱን በውሃ ይታጠብ፤ ንጹሕም
ይሆናል::

10"በስምንተኛው ቀን ነውር የሌለባቸ
ውን ሁለት ተባዕት የበግ ጠቦቶችና ነውር
የሌለባትን አንዲት የዓመት እንስት በግ
ያቅርብ፤ እንዲሁም ለእህል ቍርባን የሚ
ሆን በዘይት የተለወሰ የኢፍ ሦስት ዐሥ
ረኛ[ጠ] የላመ ዱቄት ያቅርብ፤ ደግሞ አንድ
ሎግ[ጨ] ዘይት ያምጣ:: 11ሰውየው የነጻ
መሆኑን የሚያስታውቀው ካህን የሚነጻውን
ሰውና መሥዋዕቶቹን በመገናኛው ድንኳን
ደጃፍ ላይ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ያቅርብ::

12"ካህኑም ከተባዕቱ ጠቦቶች በመውሰድ
ከሎግ ዘይቱ ጋር የበደል መሥዋዕት
አድርጎ ያቅርብ፤ የሚወዘወዝ መሥዋዕት በ
ማድረግም *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት
ይወዝውዛቸው:: 13ጠቦቱንም፣ የኀጢአት
መሥዋዕትና የሚቃ
ጠል መሥዋዕት በሚታረድበት
በተቀደሰው ስፍራ ይረደው፤ የኀጢአት
መሥዋዕቱ ለካ ህኑ እንደሚሰጥ ሁሉ
የበደል መሥዋዕቱም ለካህኑ ይሰጥ፤
ይህም እጅግ የተቀደሰ ነው:: 14ካህኑ
ከበደል መሥዋዕቱ ደም ወስዶ የሚነጻውን
ሰው ቀኝ ጆሮ ታችኛውን ጫፍ፣ የቀኝ እ
ጁን አውራ ጣትና የቀኝ እግሩን አውራ
ጣት ያስነካ:: 15ካህኑም ከሎግ ዘይት ወስዶ
በራሱ ግራ እጅ መዳፍ ውስጥ ይጨምር፤
16የቀኝ እጁንም ጣት በመዳፉ በያዘው

14፥3 ዘሌ13፥2፡46
14፥4 ቍ6፡49፡
51፡52፤ዘፀ12፥22፤
ዘኍ19፥6፤መዝ51፥7
14፥5 ቍ50
14፥6 ቍ4
14፥7 ቍ51፡53፤
2ነገ5፥10፡14፤
ኢሳ52፥15፤
ሕዝ36፥25
14፥8 ቍ9፡20፤
ዘፀ29፥4፤ዘሌ11፥25፤
13፥11፤15፥5፤17፥15፤
22፥6፤ዘኍ5፥2፡3፤
12፥14፡15፤19፥7፡8፡
20፤ 31፥24፤
2ዜና26፥21
14፥9 ዘሌ13፥5፡6፤
ዘኍ6፥9፤ዘዳ21፥12
14፥10 ቍ12፡15፡
21፡24፤ዘሌ2፥1፤4፡32
ዘኍ6፥10፤15፥9፤
28፥20፤ማቴ8፥4፤
ማር1፥44፤ሉቃ5፥14
14፥11 ዘኍ6፥10፡16
14፥12 ዘፀ29፥24፤
ዘሌ5፥18
14፥13 ዘፀ29፥11፤
ዘሌ6፥24-30፤7፥7
14፥14 ዘፀ29፥20
14፥15 ቍ26
14፥16 ቍ27
14፥17 ቍ28
14፥18 ቍ31፤
ዘሌ15፥15
14፥19 ቍ31፤
ዘሌ5፥3፤15፥15
14፥20 ቍ8፤
ዘሌ15፥30
14፥21 ቍ22፡32፤
ዘሌ5፥7
14፥22 ዘሌ5፥7፤
15፥30
14፥23 ቍ10፡11፤
ዘሌ15፥14፡29
14፥24 ቍ10፡12፤
ዘኍ6፥14
14፥25 ዘፀ29፥20
14፥26 ቍ15
14፥29 ቍ18

ዘይት ውስጥ በመንከር *በእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ፊት ሰባት ጊዜ በጣቱ ይርጭ::
17ካህኑ በመዳፉ ውስጥ ከቀረው ዘይት
ጥቂቱን ወስዶ የሚነጻውን ሰው ቀኝ ጆሮ
ታችኛውን ጫፍ፣ የቀኝ እጁን አውራ
ጣትና የቀኝ እግሩን አውራ ጣት በበደል
መሥዋዕቱ ደም ላይ ደርቦ ይቅባ::
18በመዳፉ ላይ የቀረውንም ዘይት
በሚነጻው ሰው ራስ ላይ ያድርግ፤ *በእግዚ
አብሔርም* (ያህዌ) ፊት ያስተሰርይለት::

19"ካህኑም የኀጢአት መሥዋዕቱን ያቅ
ርብ፤ ከርኵሰቱ ለሚነጻውም ሰው ያስተሰ
ርይለት፤ ከዚህ በኋላ የሚቃጠለውን መሥ
ዋዕት ይረድ፤ 20ከእህል ቍርባኑም
ጋር በመሠዊያው ላይ በማቅረብ ያስተሰጠ
ርይለት፤ ሰውየውም ንጹሕ ይሆናል::

21"ሰውየው ድኻ ከሆነና እነዚህን ለማቅ
ረብ ዐቅሙ ካልፈቀደለት፣ ማስተሰረያ
እንዲሆነው የሚወዘወዝ አንድ ተባዕት
የበግ ጠቦት ለበደል መሥዋዕት፣ በዘይት
የተለወሰ የኢፍ አንድ ዐሥረኛ[ጸ] የላመ
ዱቄት ለእህል ቍርባን ያቅርብ፤ ደግሞም
አንድ ሎግ ዘይት ያምጣ፤ 22እንዲሁም
ሁለት ርግቦች ወይም ሁለት የዋኖስ
ጫጩቶች ዐቅሙ የፈቀደውን አንዱን ለኀጢ
አት መሥዋዕት፣ ሌላውን ለሚቃጠል
መሥዋዕት ያቅርብ::

23"እነዚህንም በስምንተኛው ቀን ስለ
መንጻቱ ሥርዐት ወደ ካህኑ ወደ መገናኛው
ድንኳን ደጃፍ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት
ያቅርብ:: 24ካህኑም ለበደል መሥዋዕት የሚ
ሆነውን የበግ ጠቦትና አንድ ሎግ ዘይት
ይቀበል፤ የሚወዘወዝ መሥዋዕት በማድረ
ግም *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት
ይወዝውዛቸው:: 25ለበደል መሥዋዕት
የሚሆነውንም የበግ
ጠቦት ይረድ፤ ከደሙም ጥቂት ወስዶ
የሚነጻውን ሰው የቀኝ ጆሮ ታችኛ ጫፍ፣
የቀኝ እጁን አውራ ጣትና የቀኝ እግሩን
አውራ ጣት ያስነካ፤ 26ከዘይቱም ጥቂቱን
በግራ እጁ መዳፍ ውስጥ ያፍስስ፤ 27የቀኝ
እጁንም ጣት በመዳፉ በያዘው ዘይት ውስጥ
በመንከር *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ሰባት
ጊዜ ይርጭ:: 28በመዳፉ ከያዘው ዘይት
ጥቂቱን ወስዶ የበደል መሥዋዕቱን ደም
ባስነካበት ቦታ፣ ይኸውም የሚነጻውን ሰው
ቀኝ ጆሮ ጫፍ፣ የቀኝ እጁን አውራ ጣትና
የቀኝ እግሩን አውራ ጣት ያስነካ:: 29ካህኑ

[ገ]3 በትውፊት *ለምጽ* ይባላል:: የዕብራይስጡ ቃል ከቈዳ ጋር ለተያያዘ በሽታ አንድ ቃል ነው፤ በዚህ ምዕራፍ በሌላ ስፍራም ይገኛል::
[ጠ]10 6.5 ሊትር ገደማ ይሆናል
[ጨ]10 0.3 ሊትር ገደማ ይሆናል፤ እንዲሁም ቍ 12:15:21:24 ይመ
[ጸ]21 2 ሊትር ገደማ ይሆናል

*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ያስተሰርይለት
ዘንድ በመዳፉ ከያዘው ዘይት የቀረውን
በሚነጻው ሰው ራስ ላይ ያፍስ፤ 30ካህኑም
ርግቦቹን ወይም የዋኖሶቹን ጫጩቶች የሰ
ውየው ዐቅም የፈቀደውን ይሠዋል፤ 31ከእነዚ
ህም አንዱን[ጸ] ለኀጢአት መሥዋዕት፣ ሌላ
ውን ለሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ ከእህሉ
ቍርባን ጋር ያቅርብ፤ በዚህም ሁኔታ
ካህኑ ለሚነጻው ሰው *በእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ፊት ያስተሰርይለታል።”
32ተላላፊ የቈዳ በሽታ ይዞት የሚነጻ
በትን መደበኛ መሥዋዕት ለማቅረብ ዐቅም
ላነሠው ሰው ሕጉ ይህ ነው።

## ልብስ ላይ ከሚታይ ተላላፊ በሽታ መንጻት

33*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴንና አሮንን
እንዲህ አላቸው፤ 34“ርስት አድርጌ ወደምሰ
ጣቸው ወደ ከነዓን ምድር በገባችሁ ጊዜ፣
በዚያ አገር አንዱን ቤት በተላላፊ በሽታ
የበከልሁ እንደሆነ፣ 35ባለቤቱ ወደ ካህኑ
ሄዶ፣ ‘በቤቴ ውስጥ ተላላፊ በሽታ የሚመ
ስል ነገር አይቻለሁ’ ብሎ ይንገረው። 36ካህኑ
ወደዚያ ቤት በመግባት በሽታውን መርምሮ
ርኩስ መሆኑን ከማስታወቁ በፊት፣ ቤቱን
ባዶ እንዲያደርጉት ይዘዝ፤ ከዚህ በኋላ ካህኑ
ወደ ቤቱ ገብቶ ይመርምር። 37በግድ
ግዳው ላይ ያለውን ተላላፊ በሽታ በሚመረ
ምርበት ጊዜ፣ መልኩ ወደ አረንጓዴነት
ወይም ወደ ቀይነት የሚያደላ የተቦረቦረ
ነገር በግድግዳው ቢታይ፣ 38ካህኑ ከቤቱ
ወደ ደጅ ወጥቶ ቤቱን ሰባት ቀን ይዝ
ጋው። 39ካህኑም በሰባተኛው ቀን ቤቱን
ለመመርመር ይመለስ፤ ተላላፊው በሽታ
በግድግዳው ተስፋፍቶ ቢገኝ፣ 40የተበከሉት
ድንጋዮች ተሰርስረው እንዲወጡና ከከተማው
ውጭ ባለው ርኩስ ስፍራ እንዲጣሉ
ይዘዝ፤ 41የቤቱ ግድግዳ በሙሉ በውስጥ
በኩል እንዲፋቅና ፍቅፋቂው ከከተማው
ውጭ ባለው ርኩስ ስፍራ እንዲደፋ ያድ
ርግ። 42በወጡትም ድንጋዮች ቦታ ሌሎች
ድንጋዮች አምጥተው ይተኩ፤ ሌላም ጭቃ
ወስደው ቤቱን ይምረጉ።
43“ድንጋዮቹ ወጥተው፣ ቤቱ ከተፈቀ
ፈቀና ከተመረገ በኋላ ተላላፊው በሽታ
እንደገና በቤቱ ውስጥ ከታየ፣ 44ካህኑ ሄዶ
ይመርምረው፤ ተላላፊው በሽታ በቤቱ ውስጥ
ተስፋፍቶ ከተገኘ፣ አደገኛ በሽታ ነው፤
ቤቱም ርኩስ ነው። 45ስለዚህ ቤቱ ይፍረስ፤
ድንጋዩ፣ ዕንጨቱና ምርጊቱ በሙሉ ከከተማ
ውጭ ባለው ርኩስ ስፍራ ይጣል።
46“ቤቱ ተዘግቶ ሳለ ማንኛውም ሰው
ቢገባበት፣ ያ ሰው እስከ ማታ ድረስ ርኩስ
ይሆናል። 47በዚያ ቤት ገብቶ የተኛ ወይም

14፥30 ዘሌ5፥7
14፥31 ቍ18፡19፡22፤ዘሌ5፥7፤15፥15፡30
14፥32 ቍ21፤ዘሌ13፥2
14፥34 ዘፍ12፥5፤17፥8፤48፥4፤ዘፀ6፥4፤ዘኍ13፥2፤27፥12፤32፥22፤ዘዳ3፥27፤7፥1፤32፥49
14፥37 ዘሌ13፥19
14፥38 ዘሌ13፥4
14፥39 ዘሌ13፥5
14፥40 ቍ45
14፥44 ዘሌ13፥51
14፥46 ዘሌ11፥24
14፥47 ዘሌ11፥25
14፥48 ዘሌ13፥6
14፥49 1ነገ4፥33
14፥50 ቍ5
14፥51 ቍ4፡6፡7፤መዝ51፥7
14፥53 ቍ7፡20
14፥54 ዘሌ13፥2
14፥55 ዘሌ13፥47-52
14፥56 ዘሌ13፥2
14፥57 ዘሌ10፥10
15፥2 ቍ16፡32፤ዘሌ22፥4፤ዘኍ5፥2፤2ሳሙ3፥29፤ማቴ9፥20
15፥5 ዘሌ11፥25፤14፥8፤11፥24

የበላ ማንኛውም ሰው ልብሶቹን ይጠብ።
48“ነገር ግን ቤቱ ከተመረገ በኋላ ካህኑ
ሊመረምረው በሚመጣበት ጊዜ ተላላፊው
በሽታ ሳይስፋፋ ቢገኝ፣ በሽታው ስለለቀ
ቀው ቤቱ ንጹሕ መሆኑን ያስታውቅ።
49ቤቱንም ለማንጻት ሁለት ወፎች፣ የዝግባ
ዕንጨት፣ ደመቅ ያለ ቀይ ድርና ሂሶጵ
ያቅርብ። 50ከወፎቹም አንዱን በሸክላ ዕቃ
ውስጥ ባለ የምንጭ ውሃ ላይ ይረድ።
51የዝግባውን ዕንጨት፣ ሂሶጱን፣ ደመቅ
ያለውን ቀይ ድርና በሕይወት ያለውን
ወፍ ወስዶ በታረደው ወፍ ደምና
በምንጩ ውሃ ውስጥ ይንከር፤ ቤቱንም
ሰባት ጊዜ ይርጭ። 52ቤቱንም በወፉ
ደም፣ በምንጩ ውሃ፣ በሕይወት ባለው
ወፍ፣ በዝግባው ዕንጨት፣ በሂሶጱና
ደመቅ ባለው ቀይ ድር ያንጻው። 53በሕ
ይወት ያለውንም ወፍ ከከተማ ወደ ውጭ
ይልቀቀው፤ በዚህ ሁኔታ ለቤቱ ያስተሰር
ይለታል፤ ቤቱም ንጹሕ ይሆናል።”
54ይህ ሕግ ለማንኛውም ተላላፊ የቈዳ
በሽታ፣ ለሚያሳክክ ሕመም፣ 55በልብስና
በቤት ላይ ለሚመጣ ተላላፊ በሽታ፣ 56ለዕ
ብጠት፣ ለችፍታ ወይም ለቋቍቻ፣ 57አንድ
ነገር ንጹሕ ወይም ርኩስ መሆኑ የሚታወ
ቅበት ነው። ይህ ተላላፊ የቈዳ በሽታ
እንዲሁም በልብስና በቤት ላይ ለሚወጣ
ተላላፊ በሽታ የሚያገለግል ሕግ ነው።

## የሚያረክስ የሰውነት ፈሳሽ

15 *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴንና አሮ
ንን እንዲህ አላቸው፤ 2“ለእስራ
ኤላውያን እንዲህ ብላችሁ ንገሯቸው፤
‘ማንም ሰው ከሰውነቱ ፈሳሽ ነገር ቢወጣ
ያ ሰው ርኩስ ነው። 3ከሰውነቱ የሚወጣው
ፈሳሽ መፍሰሱን ቢቀጥል ወይም ባይቀጥል
ሰውየው ርኩስ ነው፤ ፈሳሹም ርኵሰት
የሚያስከትለው እንደዚህ ነው፦
4“ ‘ፈሳሽ ነገር የሚወጣው ሰው የተኛ
በት የትኛውም መኝታ ርኩስ ይሆናል፤ እርሱ
የተቀመጠበት ማንኛውም ነገር ርኩስ
ይሆናል። 5ዐልጋውን የነካ ማንኛውም
ሰው ልብሱን ይጠብ፤ ሰውነቱንም በውሃ
ይታጠብ፤ እስከ ማታ ድረስ ግን ርኩስ
ይሆናል። 6ፈሳሽ ነገር የሚወጣው ሰው
በተቀመጠበት በየትኛውም ነገር ላይ
የተቀመጠ ሰው ሁሉ ልብሱን ይጠብ፤
ሰውነቱንም በውሃ ይታጠብ፤ እስከ ማታ
ድረስ ግን ርኩስ ይሆናል።

[ጸ]31 የሰብዓ ሊቃናትና የሱርሰት ትርጕሞች ከዚህ ጋር ይስማ
ማሉ፤ ዕብራይስጡ 31*የሰውየው ዐቅም የፈቀደውን ያህል
አንዱን ለኀጢአት* ይላል

[7]“ ‘ፈሳሽ ነገር የሚወጣውን ሰው የነካ
ማንኛውም ሰው ልብሱን ይጠብ፤ ሰውነ
ቱንም በውሃ ይታጠብ፤ እስከ ማታ ድረስ
ግን ርኩስ ይሆናል።
[8]“ ‘ፈሳሽ ነገር የሚወጣው ሰው ንጹሕ
በሆነ ሰው ላይ ቢተፋ፣ የተተፋበት ሰው
ልብሱን ይጠብ፤ ሰውነቱንም በውሃ ይታ
ጠብ፤ እስከ ማታ ድረስ ግን ርኩስ
ይሆናል።
[9]“ ‘ፈሳሽ ነገር የሚወጣው ሰው የተቀ
መጠበት ኮርቻ ሁሉ ርኩስ ይሆናል፤
[10]ከበ ታቹ ያለውንም ነገር ሁሉ የነካ
ማንም ሰው እስከ ማታ ድረስ ርኩስ
ይሆናል። እነዚህንም ነገሮች የሚያነሣ
ማንም ሰው ልብሱን ይጠብ፤ ሰውነቱንም
በውሃ ይታ
ጠብ፤ እስከ ማታ ድረስ ግን ርኩስ ይሆ
ናል።
[11]“ ‘ፈሳሽ ነገር የሚወጣው ሰው እጁን
በውሃ ሳይታጠብ ሌላውን ሰው ቢነካ፣ የተ
ነካው ሰው ልብሱን ይጠብ፤ ሰውነቱንም
በውሃ ይታጠብ፤ እስከ ማታ ድረስ ግን
ርኩስ ይሆናል።
[12]“ ‘ፈሳሽ ነገር የሚወጣው ሰው የነካው
የሸክላ ዕቃ ይሰበር፤ ከዕንጨት የተሠራ ዕቃ
ከሆነ በውሃ ይታጠብ።
[13]“ ‘ፈሳሽ ነገር የሚወጣው ሰው
ከፈሳሹ ሲነጻ፣ በሕጉ መሠረት ለመንጻቱ
ሰባት ቀን ይቍጠር፤ ልብሱን ይጠብ፤
ሰውነቱንም በምንጭ ውሃ ይታጠብ፤ ንጹሕ
ም ይሆናል። [14]በስምንተኛውም ቀን ሁለት
ርግቦች ወይም ሁለት የዋኖስ ጫጩቶች
ይዞ በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ *በእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ፊት በመቅረብ ለካህኑ
ይስጥ። [15]ካህኑም አንዱን ለኀጢአት መሥዋዕ
ት፣ ሌላውንም ለሚቃጠል መሥዋዕት
ያቅርብ፤ በዚህ መሠረት ስለ ፈሳሹ
*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ለሰውየው
ያስተሰርይለታል።
[16]“ ‘አንድ ሰው ዘሩ በሚፈስበት ጊዜ
ሰውነቱን በሙሉ በውሃ ይታጠብ፤ እስከ
ማታ ድረስ ግን ርኩስ ይሆናል። [17]የፈሰ
ሰው ዘር የነካው ማንኛውም ልብስ ወይም
ቍርበት በውሃ ይታጠብ፤ እስከ ማታ
ድረስ ግን ርኩስ ይሆናል። [18]አንድ ሰው
ከአንዲት ሴት ጋር ግብረ ሥጋ ፈጽሞ ዘር
ቢፈሰው፣ ሁለቱም በውሃ ይታጠቡ፤ እስከ
ማታ ድረስ ግን ርኩሳን ይሆናሉ።
[19]“ ‘ሴት ጊዜውን እየጠበቀ
የሚመጣው የደም መፍሰስ ቢኖርባት፣
የወር አበባዋ ርኵሰት እስከ ሰባት ቀን
ይቆያል፤ በዚህ ጊዜ ማንም ሰው ቢነካት
እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ይሆናል።

[20]“ ‘በወር አበባዋ ጊዜ የምትተኛበት
ማንኛውም ነገር ርኩስ ይሆናል፤ የተቀ
መጠችበትም ነገር ርኩስ የሆናል። [21]መኝ
ታዋን የነካ ማንኛውም ሰው ልብሱን
ይጠብ፤ ሰውነቱንም በውሃ ይታጠብ፤ እስከ
ማታ ድረስ ግን ርኩስ ይሆናል። [22]የተቀ
መጠችበትን ማንኛውም ነገር የነካ ሰው
ልብሱን ይጠብ፤ ሰውነቱንም በውሃ
ይታጠብ፤ እስከ ማታ ድረስ ግን ርኩስ
ይሆናል፤ [23]መኝታዋን ወይም የተቀመጠ
ችበትን ማንኛውም ነገር የነካ ሰው እስከ
ማታ ድረስ ርኩስ ይሆናል።
[24]“ ‘አንድ ሰው ከእርሷ ጋር ቢተኛና
የወር አበባዋ ቢነካው፣ እስከ ሰባት ቀን
ድረስ ርኩስ ይሆናል፤ እርሱ የሚተኛበት
መኝታ ሁሉ ርኩስ ይሆናል።
[25]“ ‘ሴት ከወር አበባዋ ጊዜ ሌላ ብዙ
ቀን ደም ቢፈስሳት፣ ወይም የወር አበባዋ
ጊዜ ካለፈ በኋላ የደሙ መፍሰስ ባይቋረጥ፣
ልክ እንደ ወር አበባዋ ጊዜ፣ ደም መፍ
ሰሱ እስኪቆም ድረስ ርኩስ ትሆናለች።
[26]ደሟ መፍሰሱን በቀጠለበት ጊዜ ሁሉ፣
የምትተኛበት ማንኛውም መኝታ ልክ
በወር አበባዋ ጊዜ እንደነበረው መኝታ ርኩስ
ይሆናል፤ የምትቀመጥበትም ማንኛውም
ነገር ልክ እንደ ወር አበባዋ ጊዜ ርኩስ
ይሆናል። [27]እነዚህንም የሚነካ ማንኛውም
ሰው ርኩስ ይሆናል፤ ልብሱን ይጠብ፤
ሰውነቱንም በውሃ ይታጠብ፤ እስከ ማታ
ድረስ ግን ርኩስ ይሆናል።
[28]“ ‘ከደምዋ ፍሳሽ ሳትነጻ ሰባት ቀን
ትቍጠር፤ ከዚያም በኋላ በሥርዐቱ መሠ
ረት ንጹሕ ትሆናለች። [29]በስምንተኛውም
ቀን ሁለት ርግቦች ወይም ሁለት የዋኖስ
ጫጩቶች ይዛ በመቅረብ በመገናኛው
ድንኳን ደጃፍ ለካህኑ ትሰጣለች። [30]ካህኑም
አንዱን ለኀጢአት መሥዋዕት፣ ሌላውንም
ለሚቃጠል መሥዋዕት ያቅርብ፤ በዚህ
መሠረት ስለፈሳሽዋ ርኵሰት *በእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ፊት ያስተሰርይላታል።
[31]“ ‘በመካከላቸው ያለችውን ማደሪያዬን[θ]
እንዳያረክሱና በርኵሰታቸው እንዳይሞቱ፣
እስራኤላውያንን ከሚያረክሳቸው ነገር
ለዩአቸው።’ ”
[32]ፈሳሽ ነገር የሚወጣውን፣ ዘሩም
በመፍሰሱ ርኩስ የሆነውን ሰው ሁሉ፣
[33]በወር አበባ ላይ ያለችን ሴት፣ ፈሳሽ
ነገር የሚወጣቸውን ወንድ ወይም ሴት፣
በሥርዐቱ መሠረት ርኩስ ከሆነች ሴት
ጋር የሚተኛውን ወንድ በሚመለከት ሕጉ
ይኸው ነው።

[θ]31 ወይም *የመገናኛ ድንኳኔን*

15፥7 ቍ16፥19፤ ዘሌ22፥4፡5
15፥8 ዘኍ12፥14
15፥10 ዘኍ19፥10
15፥12 ዘሌ6፥28፤ 11፥32
15፥13 ቍ5፤ ዘሌ8፥33
15፥14 ዘሌ14፥22
15፥15 ዘሌ5፥7፤ 14፥18፡19፡31
15፥16 ቍ2፡5፤ ዘዳ23፥10፡11
15፥18 1ሳሙ21፥4
15፥19 ቍ24
15፥21 ቍ27
15፥24 ቍ19፤ ዘሌ12፥2፤18፥19፤ 20፥18፤ሕዝ18፥6
15፥25 ማቴ9፥20፤ ማር5፥25፤ሉቃ8፥43
15፥29 ዘሌ14፥22
15፥30 ዘሌ5፥10፤ 14፥20፡31፤18፥19፤ 2ሳሙ11፥4፤ ማር5፥25፤ሉቃ8፥43
15፥31 ዘሌ20፥3፤ ዘኍ5፥3፤19፥13፡20፤2ሳሙ15፥25፤ 2ነገ21፥7፤ መዝ33፥14፤74፥7፤ 76፥2፤ሕዝ5፥11፤ 23፥38
15፥32 ቍ2
15፥33 ቍ19፡24፡25

## የስርየት ቀን

16፥2-34 ተጓ ምብ – ዘሌ 23፥26-32፤ ዘኍ 29፥7-11

16 በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት በቀረቡ
ጊዜ ከሞቱት፣ ከሁለቱ የአሮን
ልጆች ሞት በኋላ እግዚአብሔር (ያህዌ)
ሙሴን ተናገረው:: 2እግዚአብሔር (ያህዌ)
ሙሴን እንዲህ አለው “እኔ በስርየቱ
መክደኛ ላይ በደመና ውስጥ እገለጣለሁና፣
ወንድምህ አሮን በመጋረጃው ውስጥ
ወዳለው ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ማለት
በታቦቱ ላይ ወዳለው ወደ ስርየቱ
መክደኛ ፊት፣ በፈ ለገ ጊዜ ሁሉ
እንዳይገባና እንዳይሞት ንገረው:: 3ወደ
ተቀደሰው ስፍራ በሚገባ በት ጊዜ፣ አሮን
እንዲህ ያድርግ:- ለኀጢአት መሥዋዕት
አንድ ወይፈን፣ ለሚቃጠል መሥዋዕት
አንድ አውራ በግ ይዞ ይምጣ፤
4የተቀደሰውን የበፍታ ቀሚስ ይልበስ፤
በሰውነቱ ላይ የሚያርፈውን ከበፍታ የተ
ሠራውን የውስጥ ሱሪ ያጥልቅ፤ የበፍታውን
መታጠቂያ ይታጠቅ፤ የበፍታውን መጠ
ምጠሚያ ይጠምጥም፤ ልብሶቹ የተቀደሱ
በመሆናቸው እነዚህን ከመልበሱ በፊት
ሰውነቱን በውሃ ይታጠብ:: 5ከእስራኤል
ማኅበረ ሰብ ለኀጢአት መሥዋዕት ሁለት
ተባዕት ፍየሎች፣ ለሚቃጠል መሥዋዕት
አንድ አውራ በግ ይውሰድ::

6“አሮን ለራሱና ለቤተ ሰቡ ማስተሰረያ
ይሆን ዘንድ፣ ወይፈኑን የኀጢአት መሥ
ዋዕት አድርጎ ስለ ራሱ ያቅርብ፤ 7ሁለ
ቱንም አውራ ፍየሎች ወስዶ በመገናኛው
ድንኳን ደጃፍ በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት
ያቁማቸው:: 8አሮንም አንዱን ዕጣ ለእግ
ዚአብሔር (ያህዌ)፣ ሌላውን ለሚለቀቀው
ፍየል[ፊ] ለማድረግ በሁለቱ ፍየሎች ላይ ዕጣ
ይጣል:: 9በዕጣ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የደ
ረሰውንም ፍየል አምጥቶ ለኀጢአት መሥ
ዋዕት በማድረግ ይሠዋ:: 10ወደ ምድረ በዳ
ተለቅቆ ማስተሰረያ ይሆን ዘንድ፣ እንዲ
ለቀቅ ዕጣ የወጣበትን ፍየል ከነሕይወቱ
በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ያቅርብ::

11“አሮን ለራሱና ለቤተ ሰቡ ማስተሰረያ
ይሆን ዘንድ ወይፈኑን የኀጢአት መሥ
ዋዕት አድርጎ ስለ ራሱ ያቅርብ፤ ወይፈኑ
ንም ስለ ራሱ የኀጢአት መሥዋዕት አድርጎ
ይረድ:: 12በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ካለው
መሠዊያ ፍም ተወስዶ የተሞላበትን ጥና
ይያዝ፤ ሁለት እጅ ሙሉ መልካም መዐዛ
ያለው ዕጣን ይውሰድ፤ እነዚህንም ወደ
መጋረጃው ውስጥ ይዞ ይግባ:: 13እንዳይሞ
ትም የዕጣኑ ጢስ በምስክሩ ላይ ያለውን
ስርየት መክደኛ ይሸፍነው ዘንድ፣ በእግዚ
አብሔር (ያህዌ) ፊት ዕጣኑን በእሳቱ ላይ

16፥1 ዘሌ10፥10
16፥2 ዘፀ25፥22፤ 26፥34፡33፤30፥10፤ 40፥34፤2ሳሙ22፥10፤ዕብ6፥19፤9፥7፡25፤ 10፥19፤6፥19
16፥3 ቀኍ5፡6፤ ዘሌ4፥1-12፤ ዕብ9፥24፡25
16፥4 ቀኍ32፤ ዘፀ28፥39፡42፤29፥4፡ 29፡30፤ዘሌ8፥13፤ 21፥10፤ዘኍ20፥26፡ 28፤ሕዝ9፥2፤ 44፥17-18፤ዕብ10፥22
16፥5 ቀኍ20፤ ዘሌ4፥3፡13-21፤ 2ዜና29፥23፤ መዝ50፥9
16፥6 ዘሌ9፥7፤ ዕብ7፥27፤9፥7፡12
16፥8 ቀኍ10፥26፤ ዘኍ26፥55፡56፤ 33፥54፤34፥13፤ ኢሱ4፥2፤18፥6፤ መሳ20፥9፤ ነህ10፥34፤አስ3፥7፤ 9፥24፤ መዝ22፥18፤ ምሳ16፥33
16፥10 ኢሳ53፥4-10፤ሮሜ3፥25
16፥11 ቀኍ6፡24፡33
16፥12 ዘፀ25፥6፤ 30፥34-38፤ ዘሌ10፥1፤ራእ8፥5
16፥13 ዘፀ25፥17፤28፥43
16፥14 ዘሌ4፥5፡ 6፤ዕብ9፥7፡13፡25
16፥15 ዘሌ4፥13-21፤ዘኍ19፥19፤ ኢሳ52፥15፤ ሕዝ36፥25፤ ዕብ7፥27፤9፥3፡7፡ 12፤13፥11
16፥16 ዘፀ26፥33፤ 29፥4፡36፤40፥2፤ ሮሜ 3፥25፤ዕብ9፥25
16፥18 ዘሌ4፥7፡25
16፥19 ሕዝ43፥20
16፥20 ቀኍ5
16፥21 ዘፀ29፥10፤ ዘሌ5፥5
16፥22 ዘፀ28፥38፤ ኢሳ53፥12
16፥23 ዘፀ28፥42፤ ሕዝ42፥14
16፥24 ቀኍ3-5፡11፤ ዘሌ1፥3፤6፥16

ይጨምረው:: 14ከወይፈኑም ደም ወስዶ
በስርየቱ መክደኛ ፊተኛው ወገን ላይ
በጣቱ ይርጭ፤ ደግሞም በስርየቱ መክደኛ
ትይዩ በጣቱ ሰባት ጊዜ ይርጭ::

15“ፍየሉንም ለሕዝቡ የኀጢአት መሥ
ዋዕት አድርጎ ይረደው፤ ደሙንም ወደ
መጋረጃው ውስጥ ወስዶ በወይፈኑ ደም
እንዳደረገው በዚህኛው ያድርግ፤ ደሙን
በስርየቱ መክደኛ ላይ፣ እንዲሁም በመክ
ደኛው ትይዩ ይርጭ:: 16ከእስራኤላውያን
ርኵሰትና ዐመፅ፣ ከየትኛውም ኀጢአታ
ቸው ይነጻ ዘንድ በዚህ ሁኔታ ለቅድስተ
ቅዱሳኑ ያስተሰርይለታል፤ በርኵሰታቸው
መካከል በእነርሱ ዘንድ ላለችውም የመገ
ናኛዋ ድንኳን እንደዚሁ ያደርጋል:: 17አሮን
ለማስተሰረይ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ከገባ
በት ጊዜ ጀምሮ ለራሱ፣ ለቤተሰቡና ለእስ
ራኤል ማኅበረ ሰብ ሁሉ አስተሰርዮ
እስኪወጣ ድረስ ማንም ሰው በመገናኛው
ድንኳን ውስጥ አይገኝ::

18“ከዚያም መጥቶ በእግዚአብሔር
(ያህዌ) ፊት ወዳለው መሠዊያ ይምጣ፤ ለመ
ሠዊያውም ያስተሰርይለት፤ ከወይፈኑና
ከፍየሉ ደም ወስዶ የመሠዊያውን ቀንዶች
ሁሉ ያስነካ፤ 19ከእስራኤላውያንም ርኵሰት
መሠዊያውን ለማንጻትና ለመቀደስ ከደሙ
ወስዶ በጣቱ ሰባት ጊዜ ይርጭበት::

20“አሮን ለቅድስተ ቅዱሳኑ፣ ለመገናኛው
ድንኳንና ለመሠዊያው የሚያደርገውን ስር
የት ከፈጸመ በኋላ በሕይወት ያለውን ፍየል
ወደ ፊት ያቅርበው፤ 21ሁለት እጆቹን
በሕይወት ባለው ፍየል ራስ ላይ ይጫን፤
በላዩም የእስራኤላውያንን ክፋትና ዐመፅ፣
ኀጢአታቸውን ሁሉ በሙሉ ይናዘዝበት፤
እነዚህንም በፍየሉ ራስ ላይ ይጫን፤ ፍየሉ
ንም ለዚሁ ተግባር በተመደበ ሰው እጅ
ወደ ምድረ በዳ ይስደደው:: 22ፍየሉም ኀጢ
አታቸውን ሁሉ ተሸክሞ ወደ ምድረ በዳ
ይሄዳል፤ ሰውየውም ፍየሉን ሰው ሊኖርበት
በማይችል ስፍራ ይልቀቀው::

23“ከዚህ በኋላ አሮን ወደ መገናኛው
ድንኳን ሄዶ፣ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ሊገባ
ሲል የለበሳቸውን የበፍታ ልብሶች አው
ልቆ፣ በዚያው ይተዋቸው:: 24በተቀደሰውም
ስፍራ ሰውነቱን በውሃ ይታጠብ፤ የዘወ
ትር ልብሱንም ይልበስ፤ ከዚያም ወጥቶ
ለራሱ ማስተሰረያ የሚቃጠል መሥዋዕት
ያቅርብ፣ ለሕዝቡም ማስተሰረያ የሚቃጠል
መሥዋዕት ያቅርብ:: 25የኀጢአት መሥዋዕ
ቱንም በመሠዊያው ላይ ያቃጥል::

ፊ8 የሚወገደው ፍየል ማለት ነው፤ ዕብራይስጡ ዐዛዜል ይላል፤ እንዲሁም ቀኍ 10፡26 ይመ

26“የሚለቀቀውን ፍየል የወሰደው ሰው
ልብሱን ይጠብ፤ ሰውነቱንም በውሃ ይታ
ጠብ፤ ከዚህ በኋላ ወደ ሰፈር መግባት
ይችላል። 27ደማቸው ለማስተሰረያነት ወደ
ቅድስተ ቅዱሳን የገባው፣ ለኀጢአት መሥ
ዋዕት የቀረቡት ወይፈንና ፍየል ከሰፈር
ውጭ ተወስደው ቈዳቸው፣ ሥጋቸውና
ፈርሳቸው ይቃጠል። 28እነዚህንም የሚያ
ቃጥል ሰው ልብሱን ይጠብ፤ ሰውነቱንም
በውሃ ይታጠብ፤ ከዚህ በኋላ ወደ ሰፈር
መግባት ይችላል።

29“ለእናንተ የተሰጣችሁ የዘላለም ሥርዐ
ት ይህ ነው፦ ሰባተኛው ወር በገባ በዐ
ሥረ ኛው ቀን ሰውነታችሁን አድክሙ፤[ፐ]
የአገሩ ተወላጅም ሆነ በመካከላችሁ
የሚኖር መጻ ተኛ ምንም ሥራ አይሥራ፤
30የምትነጹበት ስርየት በዚች ዕለት
ይደረግላችኋልና በእግዚአብሔርም (ያህዌ)
ፊት ከኀጢአታችሁ ሁሉ ትነጻላችሁ።
31ይህች የፍጹም ዕረፍት ሰንበት ናት፤
ሰውነታችሁን አድክሙባት፤ የዘላለም
ሥርዐት ናት። 32ሊቀ ካህናት ለመሆን
አባቱን በመተካት የተቀባና የተሾመ ካህን
ያስተሰርይ፤ የተቀደሰውንም የበፍታ
ልብስ ይልበስ፤ 33ለቅድስተ ቅዱሳኑ፣
ለመገናኛው ድንኳንና ለመሠዊያው፣ ለካህና
ቱና ለማኅበረ ሰቡ ሁሉ ያስተስርይ።

34“ይህ የዘላለም ሥርዐት ይሁናችሁ፤
በዚህም ሥርዐት መሠረት ለኀጢአት ሁሉ
በዓመት አንድ ጊዜ ስርየት ይደ
ረግ።” እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዳዘዘ
እንዲሁ ተደረገ።

## ደም መብላት ስለ መከልከሉ

17 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2“ለአሮንና ለልጆቹ፣ ለእስ
ራኤላውያንም ሁሉ እንዲህ ብለህ ንገራ
ቸው፤ ‘እግዚአብሔር (ያህዌ) ያዘዘው ይህ ነው፤
3ማንኛውም እስራኤላዊ በሰፈር ውስጥ
ወይም ከሰፈር ውጭ በሬ፣[ሀ] በግ ወይም
ፍየል ቢያርድ፣ 4በእግዚአብሔር (ያህዌ) ማደ
ሪያ ፊት ለእግዚአብሔር (ያህዌ) መሥዋዕት
አድርጎ ለማቅረብ ወደ መገናኛው ድንኳን
ደጃፍ ባያመጣው፣ ያ ሰው በከንቱ ደም
እንዳፈሰሰ ይቈጠራል፤ ደም በማፍሰሱም
ከወገኖቹ ተለይቶ ይጥፋ። 5እስራኤላውያን
የሚሠዉትን መሥዋዕት ወደ እግዚአብሔር
(ያህዌ) የሚያመጡበት ምክንያት ከዚሁ
የተነሣ ነው። ይህንም ካህኑ ዘንድ
በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ አምጥተው
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የኅብረት መሥዋዕት[ለ]
በማድረግ ያቅ ርቡ። 6ካህኑም ደሙን
በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ባለው በእግዚ
አብሔር (ያህዌ) መሠዊያ ላይ ይርጭ፤

16፥26 ቍ8፤ ዘሌ11፥25፤1 4፥8
16፥27 ዘፀ29፥14
16፥28 ዘኍ19፥8፡10
16፥29 ቍ31፤ ዘፀ12፥14፡19፤ 31፥15፤ዘሌ23፥27፡ 28፡32፤25፥9፤ ዘኍ29፥7፤ኢሳ58፥3
16፥30 ዘፀ30፥10፤ መዝ51፥2፤ኤር33፥8ሕ ዝ36፥33፤ ዘካ13፥1፤ኤፌ5፥26
16፥31 ዕዝ8፥21፤ ኢሳ58፥3፡5፤ ዳን10፥12፤ ሐሥ27፥9
16፥32 ቍ4፤ ዘፀ28፥2፤30፥30
16፥33 ቍ11፡ 16-18፤ሕዝ45፥18
16፥34 ዘፀ27፥21፤ ዕብ9፥7፡25
17፥2 ዘሌ10፥6፡12
17፥3 ዘሌ3፥7፤ 7፥23
17፥4 ቍ9፤ ዘዳ17፥14፤ ዘዳ12፥5-21፤ 1ነገ8፥4፤2ዜና1፥3
17፥5 ዘሌ3፥1፤ ሕዝ43፥27
17፥6 ዘሌ1፥9፤ 3፥2፤4፥18
17፥7 ዘፍ9፥12፤ ዘፀ12፥14፤22፥20፤ 34፥15፤ኤር3፥6፡9፤ ሕዝ23፥3፤ 1ቆሮ10፥20
17፥9 ቍ4፤ ዘሌ1፥3፤3፥7
17፥10 ዘፍ9፥4
17፥11 ቍ14፤ ዕብ9፥22
17፥13 ዘሌ7፥26፤ ሕዝ24፥7፤33፥25፤ ሐሥ15፥20
17፥14 ዘፍ9፥4
17፥15 ዘፀ22፥31፤ ዘሌ7፥24፤11፥40፤ 14፥8
17፥16 ዘሌ5፥1
18፥2 ዘፍ17፥7
18፥3 ቍ24-30፤ ዘፀ23፥24፤ ዘዳ18፥9፤ 2ነገ16፥3፤17፥8፤ 1ዜና5፥25

ሥቡንም እግዚአ ብሔርን (ያህዌ) ደስ
የሚያሰኝ ሽታ እንዲሆን ያቃጥል። 7ከዚህ
በፊት ላመነዘሩባቸው አጋንንት[ሐ] ከእንግዲህ
ወዲህ ማንኛውንም መሥዋዕት ሊሠዉ
አይገባም። ይህ ለእነ ርሱና ከእነርሱ በኋላ
ለሚነሣው ትውልድ ሁሉ የዘላለም ሥርዐ
ት ይሁን።’

8“እንዲህም በላቸው፤ ‘የሚቃጠል መሥ
ዋዕት ወይም ሌላ መሥዋዕት የሚያቀርብ
ማንኛውም እስራኤላዊ ወይም በመካከላቸው
የሚኖር ማንኛውም መጻተኛ፣ 9ወደ መገና
ኛው ድንኳን ደጃፍ ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
ባያቀርብ፣ ያ ሰው ከወገኖቹ ተለይቶ ይጥፋ።

10“ ‘ማንኛውም እስራኤላዊ ወይም በመካ
ከላቸው የሚኖር ማንኛውም መጻተኛ ደም
ቢበላ፣ ደም በሚበላው በዚያ ሰው ላይ
ፊቴን አከብድበታለሁ፤ ከወገኖቹም ለይቼ
አጠፋዋለሁ፤ 11የፍጡር ሕይወት በደሙ
ውስጥ ነውና፤ በመሠዊያ ላይ ለሕይወታችሁ
ማስተስረያ እንዲሆን ደሙን ሰጥቻችኋለሁ፤
ለሰውም ሕይወት ስርየት የሚያስገኝ ደም
ነው። 12ስለዚህ እስራኤላውያንን፣ “ከእናንተ
ማንም ደም አይብላ፤ በመካከላችሁ የሚኖር
መጻተኛም ቢሆን ደም አይብላ” አልሁ።

13“ ‘እንዲበላ የተፈቀደውን ማንኛውንም
እንስሳ ወይም ወፍ አድኖ የያዘ ማንኛውም
እስራኤላዊ ወይም በመካከላችሁ የሚኖር
ማንኛውም መጻተኛ ደሙን ከውስጡ ያፍ
ስስ፤ ዐፈርም ያልብሰው፤ 14የማንኛውም
ፍጡር ሕይወት ደሙ ነውና። ስለዚህ እስ
ራኤላውያንን፣ “የፍጡር ሁሉ ሕይወት ደሙ
ነውና የማንኛውንም ፍጡር ደም አትብሉ፤
የበላው ሰው ሁሉ ተለይቶ ይጥፋ” አልኋ
ቸው።

15“ ‘ሞቶ የተገኘውን ወይም አውሬ
የዘነጠለውን የበላ ማንኛውም የአገር ተወ
ላጅ ወይም መጻተኛ ልብሱን ይጠብ፤ ሰው
ነቱንም በውሃ ይታጠብ፤ በሥርዐቱ መሠ
ረት እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ይሆናል፤
ከዚያም በኋላ ንጹሕ ይሆናል። 16ልብሱን
ባያጥብ፣ ሰውነቱንም ባይታጠብ ግን ኀጢ
አት ሠርቶአልና ይጠየቅበታል።’ ”

18 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2“ለእስራኤላውያን እንዲህ
ብለህ ንገራቸው፤ ‘እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ)
አምላካችሁ (ኤሎሂም) ነኝ፤ 3በኖራችሁበት
በግብፅ እነርሱ እንደሚያደርጉት
አታድርጉ፤ እኔ

[ፐ]29 ወይም *ጹሙ*፤ እንዲሁም ቍ 31 ይመ
[ሀ]3 የዕብራይስጡ ቃል ተባዕትና እንስትን ሊያጠቃልል ይችላል።
[ለ]5 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል
[ሐ]7 ወይም *የፍየል ጣዖታት*

በማስገባችሁ በከነዓን እንደሚያደርጉትም
አታድርጉ፤ ልማዳቸውንም አትከተሉ። 4ሕጌን
ታዘዙ፤ ሥርዐቴንም በጥንቃቄ ጠብቁ፤ እኔ
*እግዚአብሔር* አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ።
5ሥርዐቴንና ሕጌን ጠብቁ፤ እነዚህን
የሚጠብቅ በሕይወት ይኖርባቸዋልና፤ እኔ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።

6“ ‘ማንም ሰው ግብረ ሥጋ ለመፈጸም
ወደ ማንኛውም የሥጋ ዘመዱ አይቅረብ፤
እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።

7“ ‘ከእናትህ ጋር ግብረ ሥጋ በመፈ
ጸም አባትህን አታዋርድ፤ እናትህ ናት፤
ከእርሷ ጋር በግብረ ሥጋ አትገናኝ።

8“ ‘ከአባትህ ሚስት ጋር ግብረ ሥጋ
አትፈጽም፤ ይህ አባትህን ያዋርዳል።

9“ ‘ከእኅትህ ጋር ግብረ ሥጋ አትፈጽም፤
በቤት ወይም በውጭ የተወለደች ብትሆን
ከአባትህ ወይም ከእናትህ ሴት ልጅ ጋር
በግብረ ሥጋ አትገናኝ።

10“ ‘ከወንድ ልጅህ ሴት ልጅ ወይም
ከሴት ልጅህ ሴት ልጅ ጋር ግብረ ሥጋ
አትፈጽም፤ ይህ አንተን ያዋርዳል።

11“ ‘የአባትህ ሚስት፣ ለአባትህ ከወለደ
ቻት ሴት ልጅ ጋር ግብረ ሥጋ አትፈ
ጽም፤ እኅትህ ናት።

12“ ‘ከአባትህ እኅት ጋር ግብረ ሥጋ
አትፈጽም፤ እርሷ የአባትህ የሥጋ ዘመድ
ናት።

13“ ‘ከእናትህ እኅት ጋር ግብረ ሥጋ
አትፈጽም፤ እርሷ የእናትህ የሥጋ ዘመድ
ናትና።

14“ ‘ከአባትህ ወንድም ሚስት ጋር ግብረ
ሥጋ በመፈጸም፣ የአባትህን ወንድም አታዋ
ርድ፤ እርሷ አክስትህ ናት።

15“ ‘ከምራትህ ጋር ግብረ ሥጋ አትፈ
ጽም፤ የልጅህ ሚስት ናት፤ ከእርሷም ጋር
በግብረ ሥጋ አትገናኝ።

16“ ‘ከወንድምህ ሚስት ጋር ግብረ
ሥጋ አትፈጽም፤ ይህ ወንድምህን
ያዋርዳል።

17“ ‘ከእናቲቱና ከሴት ልጇ ጋር ግብረ
ሥጋ አትፈጽም፤ ከወንድ ልጇ ሴት ልጅ
ወይም ከሴት ልጇ ሴት ልጅ ጋር ግብረ
ሥጋ አትፈጽም፤ እነርሱ የሥጋ ዘመዶቿ
ናቸው፤ ይህም ጸያፍ ነው።

18“ ‘ሚስትህ በሕይወት እያለች እኅቷን
ጣውንት አድርገህ አታግባት፤ ከእርሷም ጋር
ግብረ ሥጋ አትፈጽም።

19“ ‘በወር አበባዋ ርኵሰት ጊዜ ግብረ
ሥጋ ለመፈጸም ወደ ሴት አትቅረብ።

20“ ‘ከባልንጀራህ ሚስት ጋር ግብረ ሥጋ
በመፈጸም፣ ራስህን በእርሷ አታርክስ።

21“ ‘ከልጆችህ ማንኛውንም ለሞሎክ
እንዲሠዋ[m] አሳልፈህ አትስጥ፤ የአምላክህንም
(ኤሎሂም) ስም አታርክስ፤ እኔ *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ነኝ።

22“ ‘ከሴት ጋር እንደሚደረገው ሁሉ
ከወንድ ጋር አትተኛ፤ ይህ አስጸያፊ ነው።

23“ ‘ከእንስሳ ጋር ግብረ ሥጋ በመፈ
ጸም ራስህን አታርክስ። ሴትም ከእንስሳ ጋር
ግብረ ሥጋ ለመፈጸም ራስዋን አታቅርብ፤
ይህ አስጸያፊ ምግባር ነው።

24“ ‘ከእነዚህ በአንዱ እንኳን ራሳችሁን
አታርክሱ፤ ከፊታችሁ የማሳድዳቸው አሕ
ዛብ በእነዚህ ሁሉ ረክሰዋልና። 25ምድሪ
ቱም ሳትቀር ረከሰች፤ እኔም ስለ ኀጢአቷ
ቀጣኋት፤ ስለዚህ የሚኖሩባትን ሰዎች
ተፋቻቸው። 26እናንተ ግን ሥርዐቴንና ሕጌን
ጠብቁ፤ እናንተ የአገር ተወላጆችና በመካከ
ላችሁ የሚኖሩ መጻተኞች ከእነዚህ አስ
ጸያፊ ድርጊቶች ማንኛውንም አትፈ
ጽሙ። 27ከእናንተ በፊት በምድሪቱ የኖሩ
ሰዎች እነዚህን አስጸያፊ ነገሮች ሁሉ ስለ
ፈጸሙ፣ ምድሪቱ ረክሳለች። 28እናንተም
ምድሪቱን ብታረክሷት፣ ከእናንተ በፊት
የነበረውን ሕዝብ እንደ ተፋች እንዲሁ
እናንተንም ትተፋችኋለች።

29“ ‘ከእነዚህ አስጸያፊ ድርጊቶች ማንኛ
ውንም የሚፈጽም ሰው ሁሉ ከወገኑ ተለ
ይቶ ይጥፋ። 30ትእዛዜን ጠብቁ፤ ከእናንተ
በፊት በምድሪቱ የኖሩ ሰዎች ካደረጓቸው
አስጸያፊ ድርጊቶች አንዱንም አትፈጽሙ፤
በእነዚህም ራሳችሁን አታርክሱ፤ እኔ *እግዚ
አብሔር* አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ።

## ልዩ ልዩ ሕግጋት

19 *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2“ለመላው የእስራኤል ሕዝብ
ጉባኤ እንዲህ ብለህ ተናገራቸው፤ ‘እኔ
*እግዚአብሔር* አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ቅዱስ
ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ።

3“ ‘ከእናንተ እያንዳንዱ እናቱንና አባቱን
ያክብር፤ ሰንበታቴን ጠብቁ፤ እኔ *እግዚ
አብሔር* አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ።

4“ ‘ወደ ጣዖታት ዘወር አትበሉ፤
ወይም ከቀለጠ ብረት ለራሳችሁ አማልክት
አትሥሩ፤ እኔ *እግዚአብሔር* አምላካችሁ (ያህዌ
ኤሎሂም) ነኝ።

5“ ‘የኅብረት መሥዋዕት[w] ለ*እግዚአብሔር*
(ያህዌ) በምታቀርቡበት ጊዜ፣ መሥዋዕታችሁ

18፥4 ቍ2፤ ዘፍ26፥5፤ዘዳ4፥1፤ 1ነገ11፥11፤ ኤር44፥10፡23፤ ሕዝ11፥12
18፥5 ዘፍ26፥5፤ ዘዳ4፥1፤ነህ9፥29፤ ኢሳ55፥3፤ሕዝ18፥9፤ 20፥11፤አሞ5፥4-6፤ ማቴ19፥17፤ ሮሜ10፥5፤ገላ3፥12
18፥7 ቍ8፤ ዘሌ20፥11፤ዘዳ27፥20 ሕዝ22፥10
18፥8 ዘፍ35፥22፤ ዘሌ20፥11፤ዘዳ22፥30 27፥20፤1ቆሮ5፥1
18፥9 ቍ11፤ ዘሌ20፥17፤ዘዳ27፥22 2ሳሙ13፥13፤ ሕዝ22፥11
18፥12 ቍ13፤ ዘሌ20፥19
18፥13 ቍ12፡14፤ ዘሌ20፥20
18፥14 ቍ13
18፥15 ዘፍ11፥31፤ 38፥16፤ሕዝ22፥11
18፥16 ዘሌ20፥21፤ ማቴ14፥4፤ማር6፥18
18፥17 ዘሌ20፥14፤ ዘዳ27፥23
18፥18 ዘፍ30፥1
18፥19 ዘሌ15፥24፡ 25-30
18፥20 ዘፀ20፥14፤ ማቴ5፥27፡28፤ 1ቆሮ6፥9፤ዕብ13፥4
18፥21 ዘፀ6፥2፤ ዘሌ19፥12፤ 20፥2-5፤21፥6፤ ዘዳ9፥4፤12፥31፤ 18፥10፤1ነገ11፥5፡7፡3 3፤2ነገ16፥3፤17፥17፤2 1፥6፤ 23፥10፤ 2ዜና28፥1-4፤33፥6፤ መዝ106፥37፡38፤ ኢሳ48፥11፤57፥5፡9፤ ኤር7፥30፡31፤19፥5፤3 2፥35፤49፥1፤ ሕዝ 16፥20፤22፥26፤ 36፥20፤አሞ2፥7፤ ሶፎ1፥5፤ሚክ6፥7፤ ሚል1፥12
18፥22 ዘፍ19፥5፤ ዘሌ20፥13፤ዘዳ23፥18 ሮሜ1፥27፤1ቆሮ6፥9
18፥23 ዘፀ22፥19፤ ዘሌ20፥15፤ዘዳ27፥21
18፥24 ቍ3፡27፡ 30፤ዘሌ20፥23፤ ዘዳ9፥4፤18፥12
18፥25 ቍ28፤ ዘሌ20፥22፡23፤ ዘኍ35፥34፤ዘዳ9፥5፤1 2፥31፤18፥12፤21፥23፤ ኢዮ20፥15፤ ኤር51፥34
18፥26 ዘፍ26፥5
18፥28 ቍ25፤ ዘሌ20፥22፤ዕዝ9፥11፤ ሰቆ1፥17

18፥30 ቍ2፤ ዘሌ8፥35 19፥2 ዘፀ20፥2፤ 15፥11፤ዘሌ11፥44፤ 20፥26፤ዘኍ14፥5፤መዝ68፥26፤1ጴጥ1፥16 19፥3 ዘፀ20፥8፡12፤ ዘሌ11፥44 19፥4 ዘፀ20፥4፤ዘሌ11፥44፤መሳ17፥3፤መዝ96፥5፤ 115፥4-7፤ 135፥15

[m]21 ወይም *በእሳት ውስጥ እንዲያልፍ*
[w]5 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል

ተቀባይነት እንዲያገኝላችሁ አድርጋችሁ
አቅርቡ። 6 *መሥዋዕቱም* ባቀረባችሁት ዕለት
ወይም በማግሥቱ ይበላ፤ እስከ ሦስተኛው
ቀን የተረፈ ማንኛውም ነገር ይቃጠል።
7 በሦስተኛውም ቀን ቢበላ ርኩስ ነው፤
ተቀባይነትም የለውም። 8 ከ*መሥዋዕቱ*
የሚበላ ማንኛውም ሰው *ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) የተቀደሰውን ነገር አርክሶአልና ይጠ
የቅበታል፤ ያም ሰው ከወገኑ ተለይቶ ይጥፋ።
9 " 'የምድራችሁን መከር በምትሰበስ
ቡበት ጊዜ፣ በእርሻችሁ ዳርና ዳር ያለውን
አትጨዱ፤ ቃርሚያውንም አትልቀሙ።
10 የወይንህን እርሻ አትቃርም፤ የወደቀውንም
አትልቀም፤ ለድኾችና ለመጻተኞች ተውላቸው፤
እኔ *እግዚአብሔር* አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም)
ነኝ።

11 " 'አትስረቁ፤

" 'አትዋሹ፤

" 'ከእናንተ አንዱ ሌላውን አያታል።

12 " 'በስሜ በሐሰት አትማሉ፤ በዚህም
የአምላካችሁን (ኤሎሂም) ስም አታርክሱ፤ እኔ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።

13 " 'ባልንጀራህን አታጭበርብር፤ አትቀ
ማው፤

" 'የሙያተኛውን ደመወዝ ሳትከፍል
አታሳድር።

14 " 'ደንቈሮውን አትርገም፤ በዐይነ
ስውሩም ፊት ዕንቅፋት አታኑር፤ ነገር
ግን አምላክህን (ኤሎሂም) ፍራ፤ እኔ *እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ነኝ።

15 " 'ፍርድ አታዛቡ፤ ለድኻው አታድ
ላለት፤ ለትልቁም ሰው ልዩ አክብሮት
አትስጥ፤ ለብርቱው አታዳላ፤ ነገር ግን
ለባለንጀራህ በትክክል ፍረድ።

16 " 'በሕዝብህ *መካከል* ሐሜት አትንዛ፤

" 'የባልንጀራህን ሕይወት አደጋ ላይ
የሚጥል ማንኛውንም ነገር አታድርግ፤ እኔ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።

17 " 'ወንድምህን በልብህ አትጥላው፤ የበ
ደሉ ተካፋይ እንዳትሆን ባልንጀራህን በግ
ልጽ ገሥጸው።

18 " 'ወገንህን አትበቀል፤ ወይም ምቀኛ
አትሁንበት፤ ነገር ግን ባልንጀራህን እንደ
ራስህ ውደድ፤ እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።

19 " '*ሥርዐቴን* ጠብቁ፤

" 'የተለያዩ እንስሳትን አታዳቅል፤

" 'በዕርሻህ ላይ ሁለት ዐይነት ዘር
አትዝራ፤

" 'ከሁለት ዐይነት ነገር የተሠራ ልብስ
አትልበስ።

20 " 'አንድ ሰው ለሌላ ከታጨች ሴት
ባሪያ ጋር ግብረ ሥጋ ቢፈጽም፣ ሴቲቱም
ያልተዋጀች ወይም ነጻ ያልወጣች ብትሆን
ይቀጣል፤ ነገር ግን ሴቲቱ ነጻ ስላልወጣች
አይገደሉም። 21 ሰውየውም ለበደል *መሥ
ዋዕት* የሚሆን አንድ አውራ በግ ወደ
*መገናኛው* ድንኳን ደጃፍ *ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ያምጣ። 22 ካህኑም በበደል *መሥዋዕቱ*
አውራ በግ፣ ሰውየው ስለ ሠራው ኀጢ
አት *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ያስተሰር
ይለታል፤ ኀጢአቱም ይቅር ይባልለታል።

23 " 'ወደ ምድሪቱ ገብታችሁ ማንኛ
ውንም ዐይነት ፍሬ የሚሰጥ ዛፍ በምትተ
ክሉበት ጊዜ፣ ፍሬው ለመብላት የተከለከለ
*መሆኑን* ዕወቁ፤ ለሦስት ዓመትም የተከለ
ከለ' በመሆኑ አይበላ። 24 በአራተኛውም
ዓመት ፍሬው ሁሉ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ)
የተቀደሰ የምስጋና *መሥዋዕት* ይሆናል።
25 በአምስተኛው ዓመት ግን ፍሬውን ትበላላ
ችሁ፤ በዚህም ሁኔታ ፍሬው ይበዛላች
ኋል፤ እኔ *እግዚአብሔር* አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎ
ሂም) ነኝ።

26 " 'ደም ያለበትን ማንኛውንም ሥጋ
አትብሉ፤

" 'ጥንቈላ ወይም አስማት አትሥሩ።

27 " 'የራስ ጠጕራችሁን ዙሪያ አትከር
ከሙ፤ ጢማችሁንም አሳጥራችሁ አትቀኑ
ረጡ።

28 "'ለሞተ ሰው ሰውነታችሁን አትንጩ፤
በሰውነታችሁም ላይ ንቅሳት አታድርጉ፤
እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።

29 " 'ምድሪቱ ወደ ግልሙትና አዘንብላ
በርኵሰት እንዳትሞላ፣ ሴት ልጅህ ጋለሞታ
ትሆን ዘንድ አታዋርዳት።

30 " 'ሰንበታቴን ጠብቁ፤ መቅደሴንም
አክብሩ፤ እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።

31 " '"እንዳትረክሱባቸው ወደ ሙታን ጠሪ
ዎች ዘወር አትበሉ፤ መናፍስት ጠሪዎችንም
አትፈልጉ፤ እኔ *እግዚአብሔር* አምላካችሁ
(ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ።

32 "'ዕድሜው ለገፋ ተነሥለት፤ ሽማግ
ሌውን አክብር፤ አምላክህንም (ኤሎሂም) ፍራ፤
እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።

33 " '*መጻተኛ* በምድራችሁ ላይ አብሮ
አችሁ በሚኖርበት ጊዜ አትበድሉት፤
34 አብሮአችሁ የሚኖረው *መጻተኛ* እንደ ገዛ
ወገናችሁ ይታይ፤ እንደ ራሳችሁም ውደ
ዱት፤ እናንተም በግብፅ *መጻተኞች* ነበራ

19፥6 ዘሌ7፥16-17
19፥7 ዘሌ7፥18
19፥8 ዘፍ17፥14፤ ዘሌ5፥1፤22፥2፡15፡16 ዘኍ18፥32
19፥9 ዘሌ23፥10፡ 22፤ዘዳ24፥19-22፤ ሩት2፥2፡3፡7፡16፡17፤ ኢዮ24፥10
19፥10 ቍ9፤ ዘዳ24፥19፡20፡21
19፥11 ዘፀ20፥15፡ 16፤23፥4፤ዘሌ6፥2፤ ሉቃ3፥14፤ኤፌ4፥25
19፥12 ዘፀ3፥13፤ 20፥7፤ዘዳ18፥19፤ ኢሳ42፥8፤ኤር5፥2፤ 7፥9፤34፥16፤44፥16፡ 26፤ምሳ18፥10፤ ሚል3፥5፤ማቴ5፥33፤
19፥13 ዘፀ20፥15፤ 22፥15፡25-27፤ ዘሌ25፥14፡17፤ ዘዳ24፥15፤ኢዮ7፥2፤ 24፥12፤31፥39፤ ኢሳ16፥14፤ ኤር22፥13፤ ሚል3፥5፤ማቴ20፥8፤ 1ጢሞ5፥18፤ያዕ5፥4
19፥14 ቍ32፤ ዘፀ4፥11፤ዘሌ21፥18፤ 25፥17፡36፤ዘዳ27፥18
19፥15 ዘፀ23፥2፡8፤ ዘዳ24፥17፤ኢዮ13፥8፡ 10፤32፥21፤34፥19፤ ምሳ24፥23፤28፥21፤ሚ ል2፥9፤ያዕ2፥1-4
19፥16 ዘፀ23፥7፤ ዘዳ10፥17፤27፥25፤ መዝ15፥3፡5፤31፥13፤4 1፥6፤101፥5፤ ኤር6፥28፤9፥4፤ ሕዝ22፥9፡12
19፥17 ማቴ18፥15፤ 1ዮሐ2፥9
19፥18 ቍ34፤ ዘፍ4፥23፤ዘፀ12፥48፤ 20፥16፤መዝ103፥9፤ ማቴ5፥43፤19፥16፤ 22፥39፤ማር12፥31፤ ሉቃ10፥27፤ ዮሐ13፥34፤ ሮሜ12፥19፤ገላ5፥14፤ ዕብ10፥30፤ያዕ2፥8
19፥19 ዘፍ26፥5፤ ዘዳ22፥9፡11
19፥20 ዘዳ22፥23-27
19፥21 ዘሌ5፥15
19፥22 ዘሌ5፥15
19፥24 ዘፀ22፥29
19፥26 ዘፍ9፥4፤ 30፥27፤ዘፀ22፥18፤ 2ነገ17፥17፤ ኢሳ44፥25
19፥27 ዘሌ21፥5፤ ዘዳ14፥1፤ 2ሳሙ10፥4-5፤ ኤር41፥5፤48፥37፤ ሕዝ5፥1-5
19፥28 ዘሌ21፥5፤ ዘዳ14፥1፤1ነገ18፥28፤
ኤር16፥6፤41፥5፤47፥5 19፥29 ዘፍ34፥7፤ ዘሌ21፥9፤ዘዳ23፥18
19፥30 ዘፀ20፥8፤ ዘሌ26፥2 19፥31 ዘፀ22፥18፤ ዘሌ20፥6፤ 1ሳሙ28፥7-20፤1ዜና10፥13፤ 2ነገ21፥6፤23፥24፤ኢሳ8፥19፤19፥3፤ 29፥4፤47፥12፤65፥4 19፥32 ቍ14፤ ዘሌ11፥44፤25፥17፤ 1ነገ12፥8፤ኢዮ29፥8፤ 32፥4፤ምሳ23፥22፤ ሰቆ5፥12፤1ጢሞ5፥1
19፥34 ቍ፤ዘፀ12፥48፤22፥1፤23፥9፤ዘዳ10፥19፤23፥7፤መዝ146፥9

'23 ዕብራይስጡ *ያልተገረዘ* ይላል

ችሁና፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ (ያህዌ
ኤሎሂም) ነኝ::
[35]“ ‘በመስፈሪያ ወይም በሚዛን አታጭ
በርብሩ:: [36]እውነተኛ መለኪያ፣ እውነተኛ
መመዘኛ፣ እውነተኛ የኢፍ[ሰ] መስፈሪያ፣
እውነተኛ የኢን[ሸ] መስፈሪያ ይኑራችሁ::
ከግብፅ ምድር ያወጣኋችሁ እኔ እግዚአብሔር
አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ:: [37]“ ‘ሥርዐ
ቴንና
ሕጌን ሁሉ ጠብቁ፤ ተከተሏቸውም፤ እኔ
እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ::’ ”

## ኀጢአት የሚያስከትለው ቅጣት

20 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ [2]“ለእስራኤላውያን እንዲህ
በላቸው፤ ‘ከልጆቹ አንዱን ለሞሎክ
የሚሰጥ[ቀ] ማንኛውም እስራኤላዊ ወይም
በእስራኤል የሚኖር መጻተኛ ይገደል፤
እርሱንም የአ ገሩ ሕዝብ በድንጋይ
ይውገረው:: [3]ልጁን ለሞሎክ በመስጠት
መቅደሴን አርክሶአልና፣ ቅዱሱን ስሜንም
አቃልሎአልና፣ በዚያ ሰው ላይ ጠላት
እሆንበታለሁ፤ ከወገኖቹም ለይቼ አጠ
ፋዋለሁ:: [4]የአገሩ ሕዝብ፣ ሰውየው ል
ጁን ለሞሎክ ሲሰጥ አይተው ቸል ቢሉ፣
ባይገድሉትም፣ [5]በዚያ ሰውና በቤተ ሰቡ
ላይ ጠላት እሆናለሁ፤ እርሱንና ከሞሎክ
ጋር በማመንዘር እርሱን የተከተሉትን
ሁሉ ከሕዝባቸው መካከል ለይቼ አጠ
ፋቸዋለሁ::
[6]“ ‘ወደ ሙታን ጠሪዎችና ጠንቋዮች
ዘወር በማለት፣ በሚከተላቸውና ከእነርሱም
ጋር በሚያመነዝር ሰው ላይ ጠላት እሆንበ
ታለሁ፤ ከወገኖቹም ለይቼ አጠፋዋለሁ::
[7]“ ‘ራሳችሁን ቀድሱ፤ ቅዱሳንም ሁኑ፤
እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም)
ነኝና:: [8]ሥርዐቴን ጠብቁ፤ አድርጉትም፤
የምቀድ ሳችሁ እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ)
ነኝ::[በ]
[9]“ ‘አባቱን ወይም እናቱን የሚረግም
ማንኛውም ሰው ይገደል፤ አባቱን ወይም
እናቱን ረግሞአልና፤ ደሙ በራሱ ላይ ነው::
[10]“ ‘አንድ ሰው ከባልንጀራው ሚስት
ጋር ቢያመነዝር፣ አመንዝራውና አመንዝ
ራዪቱ ይገደሉ::
[11]“ ‘አንድ ሰው ከአባቱ ሚስት ጋር
ግብረ ሥጋ ቢፈጽም አባቱን አዋርዶአል፤
ሰውየውና ሴትዮዋ ይገደሉ፤ ደማቸው በራ
ሳቸው ላይ ነው::
[12]“ ‘አንድ ሰው ከልጁ ሚስት ጋር
ግብረ ሥጋ ቢፈጽም፣ ሁለቱም ይገደሉ፤ ነውር
አድርገዋልና ደማቸው በራሳቸው ላይ ነው::
[13]“ ‘አንድ ወንድ ከሴት ጋር ግብረ
ሥጋ እንደሚፈጽም ሁሉ ከወንድ ጋር ቢፈ
ጽም፣ ሁለቱም አስጸያፊ ድርጊት ፈጽመ
ዋልና ይገደሉ፤ ደማቸው በራሳቸው ላይ
ነው::
[14]“ ‘አንድ ሰው አንዲትን ሴትና
እናትዋን ቢያገባ፣ አድራጐቱ ጸያፍ ነው፤
በመካከ ላችሁ እንዲህ ዐይነት ርኵሰት
እንዳይገኝ ሰውየውና ሴቶቹ በእሳት
ይቃጠሉ::
[15]“ ‘ማንኛውም ሰው ከእንስሳ ጋር ግብረ
ሥጋ ቢፈጽም፣ ይገደል፤ እንስሳዪቱንም
ግደሏት::
[16]“ ‘አንዲት ሴት ወደ እንስሳ
ቀርባ ግብረ ሥጋ ብትፈጽም፣ ሴቲቱንና
እንስ ሳውን ግደሉ፤ ደማቸው በራሳቸው ላይ
ነው::
[17]“ ‘አንድ ሰው የአባቱ ወይም የእናቱ
ልጅ የሆነችውን እኅቱን አግብቶ ግብረ
ሥጋ ቢፈጽም፣ አድራጎቱ አሳፋሪ ነው፤
በሕዝባቸው ፊት ከሕዝባቸው ተለይተው
ይጥፉ:: ሰውየው እኅቱን አዋርዶአልና
ይጠየቅበታል::
[18]“ ‘ማንኛውም ሰው በወር አበባዋ ጊዜ
ከሴት ጋር ግብረ ሥጋ ቢፈጽም፣ የፈሳሿን
ምንጭ ገልጦአልና፣ እርሷም የፈሳሿን
ምንጭ ገልጣለችና፣ ሁለቱም ከሕዝባቸው
መካከል ተለይተው ይጥፉ::
[19]“ ‘ከእናትህም ሆነ ከአባትህ እኅት ጋር
ግብረ ሥጋ አትፈጽም፤ ይህ የሥጋ ዝምድ
ናን ማቃለል ስለ ሆነ ሁለታችሁም ትጠየ
ቁበታላችሁ::
[20]“ ‘ማንኛውም ሰው ከአጎቱ ሚስት
ጋር ግብረ ሥጋ ቢፈጽም፣ አጎቱን አዋርዶ
አልና ሁለቱም ይጠየቁበታል፤ ያለ ልጅም
ይሞታሉ::
[21]“ ‘ማንኛውም ሰው የወንድሙን ሚስት
ቢያገባ አድራጐቱ ርኵሰት ነው፤ ወንድሙን
አዋርዶአልና፣ ያለ ልጅም ይቀራሉ::
[22]“ ‘እንድትኖሩባት እናንተን የማስገባባት
ምድር እንዳትተፋችሁ ሥርዐቴንና ሕጌን
ጠብቁ፤ አድርጉም:: [23]ከፊታችሁ የማሳድ
ዳቸውን አሕዛብ ልማድ አትከተሉ፤ እነዚ
ህን ሁሉ በማድረጋቸው ተጸየፍኋቸው::
[24]እናንተ ግን፣ “ምድራቸውን ትወርሳላችሁ፤
ማርና ወተት የምታፈሰውን አገር ርስት
አድርጌ እሰጣችኋለሁ” አልኋችሁ፤ ከአሕ
ዛብ የለየኋችሁ እኔ እግዚአብሔር
አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ::
[25]“ ‘ንጹሕ በሆኑትና ንጹሕ ባልሆኑት
እንስሳት እንዲሁም ንጹሕ በሆኑትና ንጹሕ

19፥35 ዘጻ25፥13-16
19፥36 ዘፀ12፥17፤ ዘጻ25፥13-15፤ መሳ6፥19፤ 1ሳሙ1፥24፤17፥17፤ሩት2፥17፤ኢዮ31፥6፤ምሳ11፥1፤ 20፥10፤ ሕዝ45፥10፡11፤ ሆሴ12፥7፤ ሚክ6፥11
19፥37 ዘፍ26፥5፤ 2ነገ17፥37፤ 2ዜና7፥17፤ መዝ119፥5፤ሕዝ18፥9
20፥2 ቍ10፡27፤ ዘፍ26፥11፤ ዘፀ19፥12፤ ዘሌ24፥14፤ዘኍ15፥35፡36፤ዘጻ21፥21፤ ኢሱ7፥25
20፥3 ቍ5፡6፤ ዘሌ15፥31፤18፥21፤ 23፥30፤መዝ74፥7፤ 79፥1፤ኤር7፥30፤ ሕዝ5፥11
20፥4 ዘጻ17፥2-5
20፥6 ቍ3፤ ዘሌ19፥31
20፥7 ዘፀ6፥2፤ 20፥2፤29፥1፤31፥13፤ዘሌ11፡44፡45፤ ኤፌ1፥4፤1ጴጥ1፥16
20፥8 ዘፍ26፥5፤ ዘፀ31፥13፤ሕዝ20፥12
20፥9 ቍ11፤ ዘፀ20፥12፤21፥17፤ ዘጻ21፥20፥21፤ 22፥30፤27፥16፤ ኢሱ2፥19፤ 2ሳሙ1፥16፤3፥29፤ 1ነገ2፥37፤ ኤር35፥16፤ ሕዝ18፥13፤22፥7፤ 33፥4፡5፤ሚል1፥6፤ 2፥10፤ማቴ15፥4፤ ማር7፥10
20፥10 ዘፍ38፥24፤ ዘፀ20፥14፤21፥12፤ ዘጻ5፥18፤22፥22፤ ዮሐ8፥5
20፥11 ቍ9፤ ዘሌ18፥7፡8
20፥12 ዘፍ11፥31፤ 38፥16
20፥13 ዘሌ18፥22
20፥14 ዘሌ18፥17፤ 21፥9፤ዘሌ18፥8፤ ዘኍ16፥39፤ዘጻ27፥23፤መሳ14፥15፤15፥6
20፥15 ቍ10፤ ዘፀ22፥19
20፥17 ዘፍ17፥14፤ ዘሌ5፥1፤18፥9
20፥18 ዘሌ15፥24፤ሕዝ18፥6
20፥19 ዘሌ18፥12
20፥20 ቍ21፤ ዘፍ15፥2፤ዘሌ18፥13
20፥21 ቍ20፤ ዘሌ18፥16፤ማቴ14፥4፤ ማር6፥18
20፥22 ዘፍ26፥5፤ ዘሌ18፥25-28 20፥23 ዘሌ18፥3፡ 24፡25
20፥24 ዘፀ3፥8፤ 33፥16፤ዘኍ14፥8፤ 16፥14
20፥25 ዘሌ10፥10፤ ዘጻ14፥3-21፤ ሐሥ10፥14

[ሰ]36 ኢፍ የደረቅ ነገር መለኪያ/መስፈሪያ ነው
[ሸ]36 ኢን የፈሳሽ ነገር መለኪያ ነው
[ቀ]2 ወይም *የሚሠዋ*፤ እንዲሁም ቍ 3፡4 ይመ
[በ]8 ወይም *ቅዱስ አድርጌ የምለያችሁ*

ባልሆኑት ወፎች መካከል ልዩነት አድርጉ፡፡
ርኩስ ነው ብዬ በለየሁት በማንኛውም
እንስሳ ወይም ወፍ ወይም በምድር ላይ
በሚንቀሳቀስ በማንኛውም ነገር ራሳችሁን
አታርክሱ፡፡ 26እናንተ ለእኔ ቅዱሳን ትሆኑ
ልኛላችሁ፤[ተ] እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ቅዱስ
ነኝና፤ የኔ ትሆኑ ዘንድ ከአሕዛብ መካከል
ለይቻችኋለሁ፡፡
27“ ‘ከመካከላችሁ ሙታን ጠሪ ወይም
መናፍስት ጠሪ የሆነ ማንኛውም ወንድ
ወይም ሴት ይገደል፤ በድንጋይም ይወገሩ፤
ደማቸው በራሳቸው ላይ ነው፡፡’ ”

## ለካህናት የተሰጠ መመሪያ

21 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ “ለካህናቱ ለአሮን ልጆች
ንገራቸው፤ እንዲህም በላቸው፤ ‘ማንኛውም
ሰው ከዘመዶቹ መካከል ስለ ሞተው ሰው
ራሱን አያርክስ፤ 2ነገር ግን የቅርብ ዘመ
ዶቹ ስለሆኑት እናቱ፣ አባቱ፣ ወንድ ልጁ፣
ሴት ልጁ፣ ወይም ወንድሙ፣ 3እንዲ
ሁም ባለማግባቷ ከእርሱ ጋር ስለ
ምትኖር እኅቱ ራሱን ሊያረክስ ይችላል፡፡
4ከእርሱ ጋር በጋብቻ ለሚዛመዱት[ቸ] ግን
ራሱን አያርክስ፡፡
5“ ‘ካህናት ዐናታቸውን አይላጩ፤ የጢ
ማቸውን ዙሪያ አይላጩ፤ ሰውነታቸውንም
አይንጩ፤ 6ለአምላካቸው (ኤሎሂም) የተቀደሱ
ይሁኑ፤ የአምላካቸውንም (ኤሎሂም) ስም
አያርክሱ፡፡ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በእሳት
የሚቀርበውን መሥዋዕት የአምላካቸውን (ኤሎ
ሂም) ምግብ ስለሚ ያቀርቡ ቅዱሳን ይሁኑ፡፡
7“ ‘ካህናት በዝሙት የረከሱትንም ሆነ
ከባሎቻቸው የተፋቱትን ሴቶች አያግቡ፤
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የተቀደሱ ናቸውና፡፡
8የአምላክህን (ኤሎሂም) ምግብ የሚያቀርብ ነውና
ቀድሰው፤ እኔ የምቀድሳችሁ[ኀ] እግዚአብሔር
(ያህዌ) ቅዱስ ነኝና ቅዱስ ይሁንላችሁ፡፡
9“ ‘የካህን ሴት ልጅ ዝሙት አዳሪ
ሆና ራሷን ብታረክስ፣ አባቷን ታዋርዳለች፤
በእሳት ትቃጠል፡፡
10“ ‘ከወንድሞቹ መካከል ተለይቶ በራ
ሱ ላይ ዘይት የፈሰሰበትና የክህነት ልብስ
እንዲለብስ የተቀባው ካህን የራስ ጠጕሩን
አይንጭ፤[ነ] ወይም ልብሱን አይቅደድ፡፡
11አስከሬን ወዳለበት ስፍራ አይግባ፤ ስለ
አባቱም ሆነ ስለ እናቱ ራሱን አያርክስ፡፡
12የተቀደሰበት የአምላኩ (ኤሎሂም) የቅባት
ዘይት በላዩ ስለ ሆነ የአምላኩን (ኤሎሂም)
መቅደስ ትቶ በመሄድ መቅደሱን
አያርክስ፤ እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ፡፡
13“ ‘ካህኑ የሚያገባት ሴት ድንግል
ትሁን፡፡ 14ባል የሞተባትን፣ የተፋታችውን

20፥26 ቀኍ8፤ ዘፀ33፥16፤ዘሌ19፥2፤ ዘዳ14፥2፤ኢሱ24፥19 2ነገ19፥22፤ መዝ99፥3
20፥27 ቀኍ2፤ ዘፀ22፥18፤ ዘሌ19፥31፤24፥14
21፥1 ቀኍ11፤ ዘፀ28፥1፤ዘሌ1፥5፤ 5፥3፤13፥3፤ዘኍ5፥2፤ 6፥6፤19፥11፤31፥19
21፥2 ቀኍ11
21፥3 ዘኍ6፥6
21፥5 ዘሌ13፥40፤ 19፥28፤ኤር7፥29፤ 16፥6፤ሕዝ5፥1፤ 44፥20
21፥6 ቀኍ8፡17፡ 22፤ዘፀ19፥22፤ ዘሌ3፥11፤10፥3፤18፥2 1፤22፥25፤ዕዝ8፥28
21፥7 ቀኍ13፡14፤ ሕዝ44፥22
21፥8 ቀኍ6፤ ዘፀ31፥13፤ዘሌ3፥11
21፥9 ዘፍ38፥24፤ ዘሌ19፥29
21፥10 ዘፀ29፥7፤ ዘሌ8፥7-9፤13፤ 10፥6፤16፥4
21፥11 ቀኍ2፤ ዘሌ19፥28፤ዘኍ5፥2፤6 ፥6፤9፥6፤19፥11፡13፡14 ፤31፥19
21፥12 ዘፀ25፥8፤ 28፥41
21፥13 ሕዝ44፥22
21፥17 ቀኍ6፡18፡ 21፡23
21፥18 ዘሌ19፥14፤ 22፥19-25፤ 2ሳሙ4፥4፤9፥3፤ 19፥26
21፥20 ዘሌ22፥24፤ ዘዳ23፥1፤ኢሳ56፥3
21፥21 ቀኍ17፤ ዘሌ3፥11፤22፥19
21፥22 1ቆሮ9፥13
21፥23 ቀኍ17፤ ዘፀ 25፥8፤ዘሌ20፥8
22፥2 ዘፀ20፥7፤ ዘሌ19፥8፤ሕዝ44፥8፤ ማቴ5፥33
22፥3 ዘሌ7፥20፡ 21፤ዘኍ19፥13፤ ዕዝ8፥28
22፥4 ዘሌ15፥2- 15፤11፥24-28፡39

ወይም በዝሙት ዐዳሪነት የረከሰችውን
ሴት አያግባ፤ ነገር ግን ከወገኖቹ መካከል
ድንግሊቱን ያግባ፡፡ 15በወገኖቹ መካከል
ዘሩን አያርክስ፡፡ እርሱን የምቀድሰው[ኘ]
እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ፡፡’ ”
16እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 17“አሮንን እንዲህ በለው፤ ‘በሚቀ
ጥሉት ትውልዶች ከዘርህ እንከን ያለበት
ማንኛውም ሰው የአምላኩን (ኤሎሂም)
ምግብ ይሠዋ ዘንድ አይቅረብ፡፡ 18ዕውር
ወይም አንካሳ፣ የፊቱ ገጽታ ወይም
የሰውነቱ ቅርጽ የተበላሸ ማንኛውም
የአካል ጕድ ለት ያለበት ሰው
አይቅረብ፡፡ 19እንዲሁም እግሩ ወይም እጁ
ሽባ የሆነ፣ 20ጐባጣ ወይም ድንክ፣
ማንኛውም ዐይነት የዐይን እንከን
ያለበት፣ የሚያዥ ቍስል ወይም እከክ
ያለበት ወይም ጃንደረባ አይቅረብ፡፡
21ከካህኑ ከአሮን ዘር ማንኛውም ዐይነት
የአካል ጕድለት ያለበት ሰው ለእግዚአ
ብሔር (ያህዌ) በእሳት የሚቀርብ መሥዋዕት
ሊያቀርብ አይምጣ፤ እንከን ያለበት ስለ
ሆነ፣ የአምላኩን (ኤሎሂም) ምግብ ለማቅረብ
አይምጣ፡፡ 22እርሱም የተቀደሰውንና
እጅግ ቅዱስ የሆነውን የአምላኩን (ኤሎሂም)
ምግብ ይብላ፡፡ 23ነገር ግን እንከን ያለበት
ስለሆነ መቅደሴን እንዳያረክስ ወደ
መጋረጃው አይቅረብ ወይም ወደ መ
ሠዊያው አይጠጋ፤ የምቀድሳቸው[አ] እኔ
እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ፡፡’ ”
24ሙሴም ይህን ለአሮን፣ ለልጆቹና
ለእስራኤላውያን ሁሉ ነገራቸው፡፡

22 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2“እስራኤላውያን ቀድሰው
ለእኔ የለዩትን ቅዱስ መሥዋዕት በአክ
ብሮት ባለመያዝ፣ ቅዱስ ስሜን እንዳ
ያረክሱ ለአሮንና ለልጆቹ ንገራቸው፤ እኔ
እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ፡፡
3“እንዲህም በላቸው፤ ‘በሚቀጥሉት ትውል
ዶች ከዘርህ በሥርዐቱ መሠረት ንጹሕ
ያልሆነ ማንኛውም ሰው፣ እስራኤላውያን
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) ለይተው ወዳቀረቡት
ቅዱስ መሥዋዕት ቢቀርብ ያ ሰው ከፊቴ
ይወገድ፤ እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ፡፡
4“ ‘ከአሮን ዘር ተላላፊ የቈዳ በሽታ[ከ]
ያለበት ወይም ከሰውነቱ ፈሳሽ ነገር የሚወ

[ተ]26 ወይም *ለእኔ ቅዱሳን ትሆኑልኛላችሁ*
[ቸ]4 ወይም *እንደ መሪነቱ በሕዝቡ መካከል ራሱን አያርክስ፡፡*
[ኀ]8 ወይም *ቅዱስ አድርጌ የምለያችሁ እኔ እግዚአብሔር*
[ነ]10 ወይም *ጠጕሩን አይላጭ፡፡*
[ኘ]15 ወይም *ቅዱስ አድርጌ የምለየው*
[አ]23 ወይም ቅዱስ አድርጌ የምለያቸው
[ከ]4 በትውፊት ለምጽ ይባላል፤ የዕብራይስጡ ቃል ለምጽ ብቻ ሳይሆን ከቈዳ ጋር የተያያዘ በሽታን ያመለክታል

ጣው ማንኛውም ሰው እስኪነጻ ድረስ
ቅዱሱን መሥዋዕት አይብላ፤ እንዲሁም
በአስከሬን የረከሰውን ነገር ወይም የዘር
ፈሳሽ ያለበትን ሰው ቢነካ፣ 5ወይም በደ
ረቱ የሚሳብ የሚያረክስ ነገርን ወይም
የሚያረክስ ማንኛውንም ሰው ቢነካ፣ የቱንም
ዐይነት ርኵሰት ቢሆን፣ 6እንዲህ ያለውን
ማንኛውንም ነገር የሚነካ እስከ ማታ
ድረስ ርኩስ ይሆናል፤ ሰውነቱንም በውሃ
ካልታጠበ፣ ለእግዚአብሔር የተቀደሰውን
መሥዋዕት አይብላ። 7ፀሓይ በምትጠልቅበት
ጊዜ ንጹሕ ይሆናል፤ ከዚያም በኋላ የተቀ
ደሰውን መሥዋዕት መብላት ይችላል፤
ምግቡ ነውና። 8እንዳይረክስ ማንኛውንም
ሞቶ የተገኘውን ወይም አውሬ የዘነጠለውን
አይብላ፤ እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ።

9" 'ካህናት ትእዛዛቴን በመናቅ በደለኛ
እንዳይሆኑና እንዳይሞቱ ይጠብቋቸው፤ የምቀ
ድሳቸው[ኸ] እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ።

10" 'ከካህን ቤተሰብ በቀር የካህኑ እንግ
ዳም ሆነ ቅጥር ሠራተኛ የተቀደሰውን
መሥዋዕት አይብላ። 11ነገር ግን ካህኑ
በገንዘብ የገዛው ወይም በቤቱ የተወለደ
ባሪያ ቢኖረው፣ ያ ባሪያ ከካህኑ ድርሻ
መብላት ይችላል። 12የካህን ልጅ፣ ካህን
ያልሆነ ሌላ ሰው ካገባች፣ ከተቀደሰው
መሥዋዕት መብላት አትችልም። 13ይሁን
እንጂ የካህኑ ልጅ ባሏ ቢሞት ወይም
ብትፋታ፣ ልጆችም ባይኖሩዋትና እንደ
ልጅነት ጊዜዋ በአባቷ ቤት ለመኖር ብት
መለስ፣ ከአባቷ ድርሻ መብላት ትችላለች፤
ያልተፈቀደለት ሰው ግን ከተቀደሰው
መሥዋዕት መብላት አይችልም።

14" 'ማንኛውም ሰው ባለማወቅ የተቀደ
ሰውን መሥዋዕት ቢበላ፣ የመሥዋዕቱን
አንድ አምስተኛ ጨምሮ ለካህኑ ይተካ።
15እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የሚ
ያቀርቡትን የተቀደሰ መሥዋዕት ካህናቱ
አያርክሱት፤ 16ይህንኑ የተቀደሰ መሥዋዕት
እንዲበሉና ቅጣት የሚያስከትል በደል
እንዲፈጽሙ አያድርጉ፤ የምቀድሳቸው
እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ።

## ለእግዚአብሔር መቅረብ የማይገባው መሥዋዕት

17እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤
18"ለአሮን፣ ለልጆቹና ለእስራኤላውያን በሙሉ
እንዲህ ብለህ ተናገር፤ 'ከእናንተ ማንኛ
ውም እስራኤላዊ ወይም በእስራኤል
የሚኖር መጻተኛ ስእለት ለመፈጸም
ወይም የበጎ ፈቃድ ስጦታ ለማበርከት
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የሚቃጠል መሥዋዕ
ት የሚያቀርብ ቢሆን፣ 19መሥዋዕታችሁ
ተቀባይነት እንዲኖረው ከላም ወገን
ወይም ከበጎች ወይም ከፍየሎች እንከን

22፥5 ዘሌ11፥24-28፡43፤15፥7
22፥6 ዘሌ11፥24፤14፥8፤ሐጌ2፥13
22፥7 ዘኍ18፥11
22፥8 ዘፀ22፥31፤ዘሌ11፥39፡40፡44፤
22፥9 ቍ16፤ዘፀ28፥38፡43፤ዘሌ8፥35፤20፥8፤
22፥10 ቍ13፤ዘፀ12፥45፤29፥33
22፥11 ዘፍ17፥13፤ዘፀ12፥44
22፥14 ዘሌ4፥2፤5፥15
22፥15 ዘሌ19፥8፤ዘኍ18፥32
22፥16 ቍ9፤ዘፀ28፥38፤ዘሌ20፥8፤ዘኍ18፥11
22፥18 ቍ21፤ዘፍ28፥20፤ዘሌ1፥2፤7፥16፤ዘኍ15፥8፡16፤19፥10፤ኢሱ8፥33፤መዝ22፥25፤76፥11፤116፥18፤
22፥19 ዘሌ1፥2፡3፤21፥18-21፤ዘኍ28፥11፤ዘዳ15፥21፤
22፥20 ዘፀ28፥38፤ዘሌ1፥3፤ዘዳ15፥21፤17፥1፤ሕዝ43፥23፤45፥18፤46፥6፤ሚል1፥8፤ዕብ9፥14፤1ጴጥ1፥19፤
22፥21 ዘፀ12፥5፤32፥6፤ዘሌ1፥2፤3፥6፤7፥16፤አሞ4፥5፤ሚል1፥14
22፥24 ዘሌ21፥20
22፥25 ዘሌ21፥6፤1፥3፤ 3፥1፤ዘኍ19፥2
22፥27 ዘፀ22፥30፤28፥38፤ዘሌ1፥3፤
22፥28 ዘዳ22፥6፡7
22፥29 ዘሌ7፥12
22፥30 ዘሌ7፥15፤11፥44
22፥31 ዘፀ22፥31፤ዘዳ4፥2፡40፤መዝ105፥45፤
22፥32 ዘሌ10፥3፤18፥21፤20፥8

የሌለበትን ተባዕት ያቅርብ። 20እንከን
ያለበትን ማንኛውንም ነገር አታቅርቡ፤
መሥዋዕታችሁ ተቀባይነት አይኖረውምና።
21ማንኛውም ሰው ስእለት ለመፈጸም
ወይም የበጎ ፈቃድ ስጦታ ለማ በርከት
ከላም ወይም ከበግ ወይም ከፍየል መንጋ
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የኅብረት መሥዋ
ዕት[ሠ] ሲያቀርብ፣ ተቀባይነት ይኖረው
ዘንድ ፍጹም የሆነውንና ነውር የሌለበትን
ያቅ ርብ። 22ዕውር ወይም ሰባራ ወይም
ጒን ድሽ ወይም ማንኛውንም ዐይነት
እከክ ወይም ቋቍቻ ወይም የሚመግል
ቍስል ያለበትን እንስሳ ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) አታቅርቡ፤ ከነዚህ መካከል
የትኛውንም በመሠዊያው ላይ በእሳት
የሚቃጠል መሥ ዋዕት አድርጋችሁ
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) አታቅርቡ። 23አካሉ
ከመጠን በላይ የረዘ መን ወይም ያጠረን
በሬ[ዐ] ወይም በግ የበጎ ፈቃድ ስጦታ
አድርጋችሁ ማቅረብ ትችላላችሁ፤ ይሁን
እንጂ ስእለት ለመፈጸም ተቀባይነት
አይኖረውም፤ 24አባለዘሩ የተ ቀጠቀጠ
ወይም የተኰላሸ፣ የተሰነጠቀ ወይም
የተቈረጠ ማንኛውንም እንስሳ ለእግዚ
አብሔር (ያህዌ) አታቅርቡ፤ እነዚህንም
በምድራችሁ አትሠው። 25እንደነዚህ ያሉትን
እንስሳት ከባዕዳን በመቀበል
ለአምላካችሁ (ኤሎሂም) ምግብ አድርጋችሁ
አታቅርቡ፤ ነውር ስላለባቸው ፍጹም አይደ
ሉምና ተቀባይነት አይኖራቸውም።' "

26እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 27"ጥጃ ወይም የበግ ግልገል ወይም
የፍየል ግልገል በሚወለድበት ጊዜ ሰባት
ቀን ከእናቱ ጋር ይቈይ፤ ከስምንተኛው
ቀን ጀምሮ ግን ተቀባይነት ያለው ለእግ
ዚአብሔር (ያህዌ) በእሳት የሚቀርብ መሥዋዕት
ይሆናል። 28ላምን ከጥጃዋ፣ በግንም
ከግልገሏ ጋር በአንድ ቀን አትረዱ።

29"ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የምስጋና መሥ
ዋዕት በምታቀርቡበት ጊዜ፣ መሥዋዕታችሁ
ተቀባይነት እንዲኖረው አድርጋችሁ አቅር
ቡት። 30መሥዋዕቱ በዚያኑ ዕለት ይበላ፤
ለሚቀጥለውም ቀን አታሳድሩ፤ እኔ እግዚ
አብሔር (ያህዌ) ነኝ።

31"ትእዛዛቴን ጠብቁ፤ አድርጓቸውም፤
እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ። 32ቅዱሱን ስሜን
አታርክሱ፤ እኔ ቅዱስ መሆኔ በእስራኤላ
ውያን ዘንድ ይታወቅ፤ የምቀድሳችሁ[ዘ]
[ዠ]

[ኸ]9 ወይም ቅዱስ አድርጌ የምለያቸው፤ እንዲሁም ቍ 16 ይመ።
[ሠ]21 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል።
[ዐ]23 የዕብራይስጡ ቃል ተባዕትና እንስትን ሊያጠቃልል ይችላል።
[ዘ]32 ወይም *የቀደስኋችሁ*
[ዠ]32 ወይም *ቅዱስ አድርጌ የምለያችሁ*

እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ፡፡ 33አምላካችሁ
(ኤሎሂም) እሆን ዘንድ ከግብፅ ምድር ያወጣ
ኋችሁ እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ፡፡

23 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2“ለእስራኤላውያን እንዲህ
ብለህ ተናገር፤ ‘የተቀደሱ ጉባኤዎች ብላችሁ
የምትዋጇቸው የተመረጡ የእግዚአብሔር
(ያህዌ) በዓላት እነዚህ ናቸው፤

## ሰንበት

3“ ‘ሥራ የምትሠሩበት ስድስት ቀን
አላችሁ፤ ሰባተኛው ቀን ግን የዕረፍት ሰን
በት፣ የተቀደሰ ጉባኤ ዕለት ነው፡፡ የእግ
ዚአብሔር (ያህዌ) ሰንበት ስለ ሆነ፣ በምት
ኖሩበት ስፍራ ሁሉ ምንም ዐይነት ሥራ
አትሥሩበት፡፡

## የፋሲካና የቂጣ በዓል

23፥4-8 ተጓ ምብ - ዘፀ 12፥14-20፤ ዘኍ 28፥16-25፤ ዘዳ 16፥1-8

4“ ‘የተመረጡ የእግዚአብሔር (ያህዌ) በዓ
ላት ብላችሁ በተወሰኑላቸው ጊዜያት የምታ
ውጇቸው የተቀደሱ ጉባኤዎች እነዚህ
ናቸው፤ 5የመጀመሪያው ወር በገባ በዐሥራ
አራተኛው ቀን ምሽት የእግዚአብሔር (ያህዌ)
ፋሲካ በዓል ይጀመራል፡፡ 6በዚያው ወር
በዐሥራ አምስተኛው ቀን የእግዚአብሔር
(ያህዌ) የቂጣ በዓል ይጀመራል፤ ሰባት ቀንም
ያለ እርሾ የተጋገረ ቂጣ ትበላላችሁ፡፡ 7በመጀ
መሪያው ቀን የተቀደሰ ጉባኤ አድርጉ፤
የዕለት ተግባራችሁንም አታከናውኑ፡፡ 8ሰባት
ቀን በእሳት የሚቃጠል መሥዋዕት ለእግዚ
አብሔር (ያህዌ) አቅርቡ፤ በሰባተኛው ቀን የተ
ቀደሰ ጉባኤ አድርጉ፤ በዚያ ዕለት
የተለመደ ተግባራችሁን አታከናውኑ፡፡’ ”

## የበኵራት ስጦታ በዓል

9እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤
10“ለእስራኤላውያን እንዲህ ብለህ ተናገር፤
‘እኔ ወደምሰጣችሁ ምድር ገብታችሁ መከር
በምትሰበስቡበት ጊዜ ከሰበሰባችሁት እህል
የመጀመሪያውን ነዶ ለካህኑ አቅርቡ፤
11ነዶው ተቀባይነት እንዲያገኝላችሁም በእግ
ዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ይወዝውዘው፤ ካህኑ
ነዶውን የሚወዘውዘው በሰንበት ቀን ማግ
ስት ነው፡፡ 12ነዶውን በምትወዘውዙበት
ቀን እንከን የሌለበትን የአንድ ዓመት
ተባዕት የበግ ጠቦት የሚቃጠል መሥዋዕት
እንዲሆን ለእግዚአብሔር (ያህዌ) አቅርቡ፤
13ከዚህም ጋር ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በእሳት
የሚቀርብ፣ ሽታውም ደስ የሚያሰኝ እን
ዲሆን ሁለት ዐሥረኛ የኢፍ[የ] መስፈሪያ በዘይት
የተለወሰ የላመ ዱቄት ለእህል ቍርባን፣
አንድ አራተኛ የኢን[ዶ] መስፈሪያ የወይን ጠጅ

22፥33 ዘፍ17፥7፤ ዘፀ6፥6፤
23፥2 ቍ4:21: 27:37:44፤ ዘኍ29:30፤ ሕዝ44:24፤ ቈላ2፥16፤
23፥3 ቍ7:21: 35፤ዘፀ20፥9:10፤ ዘኍ28:6፤ዕብ4፥9: 10፤
23፥4 ናሆ1፥15
23፥5 ዘፀ12፥6:11
23፥6 ዘፀ12፥17:19
23፥7 ቍ3:8
23፥8 ዘሌ1፥9
23፥10 ዘፀ22፥29፤ 34፥22፤ዘሌ19፥9፤ ዘኍ15፥2:18፤ ሮሜ11፥16
23፥11 ዘፀ28፥38፤ 29፥24
23፥12 ዘፀ12፥5፤ ዘሌ12፥6፤
23፥13 ቍ17፤ ዘፍ35፥14፤ ዘሌ 2፥14-16፤ 6፥20፤ 10፥9፤24፥5፤ ዘኍ15፥6፤28፥9
23፥14 ዘፀ34፥26፤ ዘሌ3፥17፤ዘኍ10፥8፤1 5፥21፤ኢሱ5፥11፤ 1ሳሙ17፥17፤25፥182 ሳሙ17፥28፤ ሩት2፥14፤ኤር2፥3
23፥16 ሐሥ2፥1፤ 20፥16
23፥17 ቍ13፤ ዘፀ 34፥22
23፥18 ቍ13፤ ዘፀ 29፥41፤30፥9፤ 37፥16፤ኤር19፥13፤ 44፥18
23፥20 ዘፀ29፥24
23፥21 ቍ3:2፤ ዘፀ32፥5፤
23፥22 ዘሌ19፥9: 10፤ዘዳ24፥19-21፤ ሩት2፥2:15
23፥24 ቍ27:36፤ ዘሌ25፥9፤ዘኍ10፥9: 10፤29፥1፤31፥6፤ 2ነገ11፥14፤ 2ዜና13፥12፤ዕዝ3፥1፤ መዝ98፥6

ለመጠጥ ቍርባን አቅርቡ፡፡ 14ስጦታውን
ለአምላካችሁ (ኤሎሂም) እስከምታቀርቡበት
እስ ከዚያ ቀን ድረስ እንጀራም ቢሆን፣ ቈሎ
ወይም እሸት አትብሉ፤ ይህም በምትኖሩ
በት ስፍራ ሁሉ ለሚመጡት ትውልዶች
የዘላለም ሥርዐት ነው፡፡

## የመከር በዓል

23፥15-22 ተጓ ምብ - ዘኍ28:26-31፤ ዘዳ 16፥9-12

15“ ‘የሚወዘወዘውን የነዶ መሥዋዕት
ካቀረባችሁበት የሰንበት ማግስት አንሥታ
ችሁ ሰባት ሙሉ ሳምንታት ቍጠሩ፡፡
16እስከ ሰባተኛው ሰንበት ማግስት ድረስ
አምሳ ቀን ቍጠሩ፤ ከዚያም የአዲስ እህል
ቍርባን ለእግዚአብሔር (ያህዌ) አቅርቡ፡፡
17በሁ ለት ዐሥረኛ የኢፍ መስፈሪያ
የላመ ዱቄት፣ በእርሾ የተጋገረ ሁለት
እንጀራ ለሚወዘወዝ መሥዋዕት፣ የበኵራት
ስጦታ እንዲሆን ከየቤታችሁ ለእግዚአብሐ
ር (ያህዌ) አምጡ፡፡ 18ከእንጀራውም ጋር
ሰባት ነውር የሌለባቸው የአንድ ዓመት
ተባዕት የበግ ጠቦቶች፣ አንድ ወይፈንና
ሁለት አውራ በጎች አቅርቡ፤ እነዚህም
ከእህል ቍርባናቸውና ከመጠጥ
ቍርባናቸው ጋር ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
የሚቃጠል መሥዋዕት ይሆናሉ፤ ይህም
በእሳት የሚቀርብ ሽታውም እግዚአብሐ
ርን (ያህዌ) ደስ የሚያሰኝ መሥዋ
ዕት ነው፡፡ 19እንዲሁም አንድ ተባዕት ፍየል
ለኀጢአት መሥዋዕት፣ ሁለት የአንድ ዓመት
ተባዕት ጠቦቶችም ለኅብረት መሥዋዕት[ጀ]
አቅርቡ፡፡ 20ካህኑም ሁለቱን የበግ ጠቦቶች
ከበኵራቱ እንጀራ ጋር የሚወዘወዝ መሥ
ዋዕት አድርጎ በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት
ይወዘውዛቸዋል፤ እነዚህም ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) ቅዱስ መሥዋዕት፣ የካህኑም ድርሻ
ናቸው፡፡ 21በዚያኑ ዕለት የተቀደሰ ጉባኤ
ዐውጁ፤ የተለመደ ተግባራችሁንም አታከ
ናውኑ፤ ይህም በምትኖሩበት ስፍራ ሁሉ
ለሚመጡት ትውልዶች የዘላለም ሥርዐት
ነው፡፡
22“ ‘የምድራችሁን መከር በምትሰበስ
ቡበት ጊዜ፣ የዕርሻችሁን ዳርና ዳር አት
ጨዱ፤ ቃርሚያውን አትልቀሙ፤ እነዚ
ህንም ለድኾችና ለእንግዶች ተዉላቸው፤
እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም)
ነኝ፡፡’

## የመለከት በዓል

23፥23-25 ተጓ ምብ - ዘኍ 29፥1-6

23እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 24“እስራኤላውያንን እንዲህ በላቸው፤
‘የሰባተኛው ወር የመጀመሪያ ቀን ዕረፍት

[የ]13 4.5 ሊትር ገደማ ይሆናል፤ እንዲሁም ቍ17 ይመ
[ዶ]13 1 ሊትር ገደማ ይሆናል
[ጀ]19 በትውፊት የሰላም መሥዋዕት ይባላል

ይሁንላችሁ፤ በዚሁ በመለከት ድምፅ የሚ
ከበር የተቀደሰ ጉባኤ ይኑራችሁ:: 25መሥ
ዋዕትን በእሳት ለእግዚአብሔር (ያህዌ) አቅርቡ
እንጂ የተለመደ ተግባራችሁን አታከናው
ኑበት::’ ”

## የስርየት ቀን

23፥26-32 ተጓ ምብ - ዘሌ 16፥2-34፤ ዘኍ 29፥7-11

26እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 27“የሰባተኛው ወር ዐሥረኛ ቀን
የስርየት ቀን ነው፤ የተቀደሰ ጉባኤ አድ
ርጉ፤ አንጻች ነገርም አትብሉ፤[ገ] መሥዋዕ
ትም በእሳት ለእግዚአብሔር (ያህዌ) አቅርቡ::
28በእግዚአብሔር (ያህዌ) በአምላካችሁ (ኤሎሂም)
ፊት ለእናንተ ስርየት የሚደረግበት የስር
የት ቀን ስለ ሆነ፣ በዚያ ዕለት ምንም ሥራ
አትሥሩ:: 29በዚያ ዕለት ሰውነቱን የሚያ
ጐሳቍል ማንኛውም ሰው ከወገኖቹ
መካከል ተለይቶ ይጥፋ:: 30በዚያ ዕለት
ማንኛውንም ሥራ የሚሠራውን ሰው ሁሉ
ከወገኖቹ መካከል ለይቼ አጠፋዋለሁ::
31ማንኛውንም ሥራ ከቶ አትሥሩበት፤ ይህ
በምትኖሩበት ስፍራ ሁሉ ለልጅ ልጆቻችሁ
የዘላለም ሥርዐት ነው:: 32ይህ ለእናንተ የዕረፍት
ሰንበት ስለ ሆነ፣ ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ*
በወሩም ከዘጠነኛው ቀን ምሽት ጀምራችሁ
እስከሚቀጥለው ቀን ምሽት ድረስ ሰንበታ
ችሁን አክብሩ::”

## የዳስ በዓል

23፥33-43 ተጓ ምብ - ዘኍ 29፥12-39፤ ዘዳ 16፥13-17

33እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 34“እስራኤላውያንን እንዲህ በላቸው፤
‘ሰባተኛውም ወር በገባ በዐሥራ አምስተኛው
ቀን የእግዚአብሔር (ያህዌ) የዳስ በዓል ይጀም
ራል፤ እስከ ሰባት ቀንም ይቆያል:: 35የመ
ጀመሪያው ቀን የተቀደሰ ጉባኤ ነውና
የተለመደ ተግባራችሁን አታከናውኑበት::
36ሰባት ቀን መሥዋዕቱን በእሳት ለእግዚ
አብሔር (ያህዌ) አቅርቡ፤ በስምንተኛው ቀን
የተቀደሰ ጉባኤ አድርጉ፤ መሥዋዕትን በእ
ሳት ለእግዚአብሔር (ያህዌ) አቅርቡ፤ የተለመደ
ተግባራችሁንም አታከናውኑበት::
37“ ‘የሚቃጠል መሥዋዕትንና የእህል
ቍርባንን፣ መሥዋዕትንና የመጠጥ ቍርባ
ንን በተመደበላቸው ቀን ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) በእሳት ለማቅረብ፣ የተቀደሱ ጉባ
ኤዎችን የምታውጁባቸው የእግዚአብሔር
(ያህዌ) በዓላት እነዚህ ናቸው:: 38እነዚህ
መሥዋዕቶች ለእግዚአብሔር (ያህዌ) ሰንበት
ከምታቀርቡት፣ ከስጦታችሁ፣[ጠ] ከስእለታች
ሁና ከበጎ ፈቃድ ስጦታችሁ በተጨማሪ
የምታቀርቧቸው ስጦታዎች ናቸው::
39“ ‘የምድራችሁን ፍሬ ከሰበሰባችሁ

23፥25 ቍ21፤ ዘሌ1፥9
23፥27 ቍ2፡24፤ ዘፀ30፥10፤ ዘሌ16፥29፤
23፥28 ቍ31
23፥29 ዘፍ17፥14፤ ዘሌ7፥20፤ዘኍ5፥2
23፥30 ዘሌ20፥3
23፥31 ዘሌ3፥17
23፥32 ዘሌ16፥31፤ ነህ13፥19
23፥34 ዘፀ23፥16፤ 1ነገ8፥2፤ሐጌ2፥1፤ ዮሐ7፥2
23፥35 ቍ2፡3
23፥36 ቍ24፤ ዘሌ1፥9፤1ነገ8፥2፤ 2ዜና7፥9፤ነህ8፥18፤ ዮሐ7፥37፤
23፥37 ቍ13
23፥38 ዘፀ20፥10፤ ዘሌ1፥2፤7፥16፤ 2ዜና2፥4፤ሕዝ45፥17
23፥39 ዘፀ23፥16፤ ኢሳ62፥9፤
23፥40 ዘዳ12፥7፤ 14፥26፤28፥47፤ ነህ8፥10፡14-17፤ መዝ9፥2፤66፥6፤ 105፥43፤118፥27፤ 137፥2፤ኢሳ44፥4፤ ኢል2፥26
23፥42 ዘፀ23፥16
23፥43 መዝ78፥5
24፥3 ዘፀ12፥14
24፥4 ዘፀ25፥31
24፥5 ዘፀ25፥30፤ ዘሌ23፥13፤ዕብ9፥2፤
24፥6 ዘፀ25፥23-30፤ዘኍ4፥7
24፥7 ዘሌ2፥1፤2፥2

በኋላ በሰባተኛው ወር ከዐሥራ አምስተኛው
ቀን ጀምራችሁ ሰባት ቀን ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) በዓል አክብሩ፤ የመጀመሪያው ቀን
የዕረፍት ዕለት ነው፤ ስምንተኛውም ቀን
እንደዚሁ የዕረፍት ዕለት ይሆናል::
40በመ ጀመሪያው ቀን የመልካም ዛፍ ፍሬ፣
የዘንባባ ዝንጣፊ፣ የለመለመ ዛፍ ቅርንጫፍ
የአኻያ ዛፍ ቅርንጫፍ ይዛችሁ ሰባት ቀን
በአምላ ካችሁ በእግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ)
ፊት ደስ ይበላችሁ:: 41በየዓመቱም የእግዚ
አብሔር (ያህዌ) በዓል አድርጋችሁ ሰባት ቀን
አክብሩ፤ ይህም ለልጅ ልጃችሁ የዘላለም
ሥርዐት ነው፤ በሰባተኛውም ወር አክብሩ
ት:: 42ሰባት ቀን ዳስ ውስጥ ተቀመጡ፤
በትውልዱ እስራኤላዊ የሆነ ሁሉ ዳስ
ውስጥ ይሰን ብት፤ 43በዚህም እኔ እስራ
ኤላውያንን ከግብፅ ባወጣሁ ጊዜ፣ ዳስ
ውስጥ እንዲቀመጡ ማድረጌን የልጅ
ልጆቻችሁ ያውቃሉ፤ እኔ እግዚአብሔር
አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ::’ ”
44በዚህ ሁኔታም ሙሴ የተመረጡትን
የእግዚአብሔር (ያህዌ) በዓላት ለእስራኤላውያን
አስታወቀ::

## በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት የሚቀርብ ዘይትና ኅብስት

24፥1-3 ተጓ ምብ - ዘፀ27፡20-21

24 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2“መብራቶቹ ያለማቋረጥ
እንዲያበሩ ከወይራ ተጨምቆ የተጠለለ
ዘይት እንዲያመጡልህ እስራኤላውያንን እዘዛ
ቸው:: 3አሮንም በመገናኛው ድንኳን ውስጥ
ከምስክሩ መጋረጃ ውጭ በእግዚአብሔር
(ያህዌ) ፊት ያሉትን መብራቶች ከምሽት
እስከ ንጋት ያለ ማቋረጥ ያሰናዳቸው፤
ይህም ለትውልዶቻችሁ ሥርዐት ነው::
4በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት በንጹሕ የወርቅ
መቅረዝ ላይ ያሉት መብራቶች ያለማቋረጥ
መሰናዳት አለባቸው::
5“የላመ ዱቄት ወስደህ ዐሥራ ሁለት
ኅብስት ጋግር፤ እያንዳንዱ ኅብስትም በሁ
ለት ዐሥረኛ የኢፍ[ጨ] መስፈሪያ ዱቄት
ይጋገር:: 6እነዚህንም ስድስት ስድስቱን
በሁለት ረድፍ በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት
ባለው የንጹሕ ወርቅ ጠረጴዛ ላይ አኑራ
ቸው:: 7ከኅብስቱ ጋር የመታሰቢያ ድርሻ
ሆኖ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በእሳት የሚቀ
ርብ መሥዋዕት እንዲሆን ንጹሕ ዕጣን

[ገ]27 ወይም ጹሙ፤ እንዲሁም ቍ 29፡32 ይመ
*32 ወይም ጹሙ
[ጠ]38 ወይም እነዚህ በዓላት ከእግዚአብሔር ሰንበታት በተጨ ማሪ የምታቀርቡአቸው ናቸው፤ ስጦታዎቹም
[ጨ]5 4.5 ሊትር ገደማ ይሆናል

በእያንዳንዱ ረድፍ ላይ አኑር፡፡ 8ኅብስቱ
የእስራኤልን ሕዝብ ይወክል ዘንድ ዘወ
ትር በየሰንበቱ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት
ይደርደር፤ ይህም የዘላለም ቃል ኪዳን
ነው፡፡ 9ኅብስቱ የአሮንና የልጆቹ ድርሻ
ነው፤ በተቀደሰ ስፍራም ይበሉታል፤ *ለእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) በእሳት ከሚቀርበው መሥ
ዋዕት እጅግ የተቀደሰ ድርሻቸው
ነውና፡፡”

## እግዚአብሔርን መስደብ የሚያስከትለው ቅጣት

10እናቱ እስራኤላዊት፣ አባቱ ግብፃዊ
የሆነ አንድ ሰው በእስራኤላውያን መካ
ከል ወጣ፤ በሰፈርም ውስጥ ከአንድ እስራ
ኤላዊ ጋር ተጣሉ፡፡ 11የእስራኤላዊቱ ልጅ
*የእግዚአብሔርን* (ያህዌ) ስም በማቃለል
ሰደበ፤ ስለዚህም ወደ ሙሴ አመጡት፤
የሰውየው እናት ስም ሰሎሚት ነበር፤
እርሷም ከዳን ወገን የተወለደው የደብራይ
ልጅ ነበረች፡፡ 12*የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፈቃ
ድም ግልጽ እስኪሆንላቸው ድረስ በግዞት
አኖሩት፡፡

13*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 14“ተሳዳቢውን ከሰፈር ወደ ውጭ
አውጣው፤ ሲሳደብ የሰሙት ሁሉ እጃቸውን
በራሱ ላይ ይጫኑበት፤ ማኅበሩም ሁሉ
በድንጋይ ይውገረው፡፡ 15እስራኤላውያንን
እንዲህ በላቸው፤ ‘ማንም ሰው አምላኩን
(ኤሎሂም) ቢሳደብ ኀጢአት ሠርቶአልና ይጠ
የቅበታል፡፡ 16*የእግዚአብሔርን* (ያህዌ) ስም የሚ
ሳደብ ማንኛውም ሰው ይገደል፤ ማኅበሩ
ሁሉ ይውገሩት፤ መጻተኛም ሆነ የአገር
ተወላጅ *የእግዚአብሔርን* (ያህዌ) ስም ከሰደበ
ይገደል፡፡

17“ ‘ሰውን ደብድቦ የገደለ ይገደል፡፡
18የሌላውን ሰው እንስሳ ደብድቦ የገደለ
ማንኛውም ሰው ያንኑ ዐይነት እንስሳ ይተ
ካለት፡፡ 19ማንኛውም ሰው በባልንጀራው
ላይ ጉዳት ቢያደርስ የዚያው ዐይነት
ጉዳት ይፈጸምበት፤ 20ይኸውም በስብራት
ፈንታ ስብራት፣ በዐይን ፈንታ ዐይን፣
በጥርስ ፈንታ ጥርስ ማለት ነው፡፡ በሌላው
ሰው ላይ ያደረሰው ጉዳት በእርሱም ላይ
ይድረስበት፤ 21እንስሳ የገደለ ማንኛውም
ሰው በገደለው ፈንታ ይተካ፤ ሰው የገደለ
ግን ይገደል፡፡ 22ለመጻተኛው ሆነ ለአገር
ተወላጅ አንድ ዐይነት ሕግ ይኑራችሁ፤
እኔ *እግዚአብሔር አምላካችሁ* (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ፡፡’
”

23ሙሴም ይህን ለሕዝቡ ነገራቸው፤
እነርሱም ተሳዳቢውን ከሰፈር ወደ ውጭ
ወስደው በድንጋይ ወገሩት፤ እስራኤላው
ያንም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዳዘ
ዘው አደረጉ፡፡

## የሰባተኛው ዓመት ዕረፍት

25 *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን በሲና
ተራራ ላይ እንዲህ አለው፤ 2“ለእ
ስራኤላውያን እንዲህ ብለህ ተናገር፤ ወደ
ምሰጣችሁ ምድር በምትገቡበት ጊዜ ምድሪቱ
ራስዋ *የእግዚአብሔርን* (ያህዌ) ሰንበት ታክ
ብር፡፡ 3ስድስት ዓመት በዕርሻህ ላይ ዝራ፤
ስድስት ዓመት ወይንህን ግረዝ፤ ፍሬው
ንም ሰብስብ፡፡ 4በሰባተኛው ዓመት ግን
ምድሪቱ የዕረፍት ሰንበት ታድርግ፤
ይህም *የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ሰንበት ነው፡፡
በዕርሻህ ላይ አትዝራ፤ ወይንህንም አትግረዝ፡፡
5ሳይዘራ የበቀለውን አትጨደው፤ ካልተገ
ረዘው የወይን ተክልህ ፍሬ አትሰብስብ፡፡
ምድሪቱ የአንድ ዓመት ዕረፍት ታድርግ፡፡
6ምድሪቱም በሰንበት ጊዜዋ የምታስገኘው
ማንኛውም ፍሬ ለአንተ፣ ለወንድ ባሪ
ያህ፣ ለሴት ባሪያህ፣ ለቅጥር ሠራተኛህና
ከአንተ ጋር ለሚኖር መጻተኛ ምግብ
ይሁን፤ 7እንዲሁም ለቤት እንስሶችህና
በምድርህ ለሚኖሩ የዱር አራዊት ምድ
ሪቱ የምታበቅለው ሁሉ መኖ ይሁን፡፡

## የኢዮቤልዩ ዓመት

25፡8-38 *ማመ* - *ዘዳ* 15፡1-11
25፡39-55 *ማመ* - *ዘፀ* 21፡2-11፤ *ዘዳ* 15፡12-18

8“ ‘ሰባት የሰንበት ዓመታት ማለትም
ሰባት ጊዜ ሰባት ዓመታትን ቍጠር፤ ሰባቱ
የሰንበት ዓመታትም አርባ ዘጠኝ ዓመታት
ይሆናሉ፡፡ 9ከዚያም በኋላ በሰባተኛው ወር
በዐሥረኛው ቀን፣ መለከት ይነፋ፤ በማስ
ተስረያ ቀንም በምድራችሁ ሁሉ መለከት
ንፉ፡፡ 10አምሳኛውን ዓመት ቀድሱ፤ በም
ድሪቱ ሁሉ ላሉ ነዋሪዎች በሙሉ ነጻነት
ዐውጁ፤ ይህም ኢዮቤልዩ ይሁንላችሁ፤
ከእ ናንተ እያንዳንዱ ወደ ቤተ ሰቡ
ርስት፣ ወደ ወገኑም ይመለስ፡፡
11የአምሳኛው ዓመት ኢዮቤልዩ ይሁንላችሁ፤
አትዝሩ፤ ሳትዘሩት የበቀለውን አትጨዱ፤
ካልተገረዘውም የወ ይን ሐረግ ፍሬ
አትሰብስቡ፡፡ 12ኢዮቤልዩ ስለሆነ ለእናንተ
የተቀደሰ ይሁን፤ ሳትዘሩት በሜዳ
የበቀለውን ብሉ፡፡

13“ ‘በዚህ በኢዮቤልዩ ዓመት
እያንዳንዱ ሰው ወደ ርስቱ ይመለስ፡፡

14“ ‘ከወገንህ ከአንዱ መሬት ብትገዛ
ወይም ብትሸጥለት፣ አንዱ ሌላውን ኢያታል፡፡
15ከኢዮቤልዩ በኋላ ያሉትን ዓመታት ብዛት
መሠረት በማድረግ ከወገንህ ትገዛለህ፤
እርሱም የቀሩትን የመከር ዓመታት ብዛት
መሠረት በማድረግ ይሸጥልሃል፡፡ 16የዓ
መቱ ቊጥር ከበዛ ዋጋውን ጨምር፤ የዓ
መቱ ቊጥር ካነሰም፣ ዋጋውን ቀንስ፤
ምክንያቱም የሚሸጥልህ የዓመቱን የምርት

24፥8 *ዘፀ*25፥30፤ *ዘኍ*4፥7፤1*ዜና*9፥32፤2*ዜና*2፥4፤*ማቴ*12፥5
24፥9 *ዘሌ*6፥16፡17፤*ማቴ*12፥4፤*ማር*2፥26፤*ሉቃ*6፥4፤
24፥11 *ዘፀ*3፥15፤18፥22፤20፥7፤31፥2፤*ዘኍ*1፥4፤7፥2፤10፥1513፥2፤17፥2፤2*ነገ*6፥33፤*ኢሱ*7፥18፤1*ነገ*7፥14*ኢዮ*1፥11፤
24፥12 *ዘፀ*18፥16
24፥14 *ቍ*23፤*ዘሌ*20፥2፤*ዘዳ*13፥9፤17፥5፡7፤*ሐሥ*7፥58
24፥15 *ዘፀ*22፥28፤*ዘሌ*5፥1
24፥16 *ዘፀ*21፥12፤22፥28፤1*ነገ*21፥10፡13፤*ማቴ*26፥66፤*ማር*14፥64፤*ዮሐ*10፥33፤19፥7፤*ሐሥ*7፥58
24፥17 *ቍ*21፤*ዘፍ*9፥6፤*ዘፀ*21፥12፤*ዘዳ*27፥24
24፥18 *ቍ*21
24፥20 *ዘፀ*21፥24፤*ማቴ*5፥38
24፥21 *ቍ*17፡18
24፥22 *ዘፀ*12፥49፤22፥21፤*ዘኍ*9፥14፤ *ሕዝ*47፥22፤
24፥23 *ቍ*14

25፥1 *ዘፀ*19፥11
25፥3 *ዘፀ*23፥10
25፥4 *ቍ*5፡6፡20፤*ዘሌ*26፥35፤2*ዜና*36፥21፤*ኢሳ*36፥16፤ 37፥30
25፥5 *ቍ*4፡11፤*ዘፍ*40፥10፤*ዘኍ*6፥3፤13፥20፤*ዘዳ*23፥24፤2*ነገ*19፥29፤*ነህ*13፥15*ኢሳ*5፥2፤
25፥6 *ቍ*4
25፥7 *ዘፀ*23፥11
25፥9 *ዘፀ*30፥10፤*ዘሌ*16፥29፤23፥24፤*ዘኍ*10፥8፤*ኢሱ*6፥4፤*መሳ*3፥27፤7፥16፤1*ሳሙ*13፥3፤*ኢሳ*27፥13፤*ዘካ* 9፥14፤
25፥10 *ቍ*11፡27፡28፡50፤*ዘሌ*27፥17፡21*ዘኍ*36፥4፤*ኢሳ*61፥1፤*ኤር*34፥8፡15፡17፤*ሕዝ*46፥17፤*ሉቃ*4፥19፤
25፥11 *ቍ*5፡10
25፥13 *ቍ*10
25፥14 *ዘሌ*19፥13፤1*ሳሙ*12፥3፡4፤1*ቆሮ*6፥8
25፥15 *ቍ*27፤*ዘሌ*27፥18፡23
25፥16 *ቍ*27፡51፡52

መጠን ነውና። [17]አንዱ ሌላውን አያታል፤
አምላክህን (ኤሎሂም) ፍራ፤ እኔ እግዚአብሔር
አምላ ካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ።

[18]“ ‘ሥርዐቴን ጠብቁ፤ ሕጌን በጥንቃቄ
አድርጉ፤ በምድሪቱም በሰላም ትኖራላችሁ።
[19]ምድሪቱ ፍሬዋን ትሰጣለች፤ እስክትጠ
ግቡ ትበላላችሁ፤ በዚያም በሰላም ትኖ
ራላችሁ። [20]እናንተም፣ “ካልዘራን ወይም
ሰብላችንን ካልሰበሰብን በሰባተኛው ዓመት
ምን እንበላለን?” በማለት ትጠይቁ ይሆ
ናል። [21]በስድስተኛው ዓመት በረከቴን
እሰድድላችኋለሁ፤ ምድሪቱም ለሦስት ዓመት
የሚበቃ ፍሬ ትሰጣለች። [22]በስምንተኛው
ዓመት በምትዘሩበት ጊዜ፣ የምትበሉት
ቀድሞ ከሰበሰባችሁት ሰብል ይሆናል፤
የዘጠነኛውን ዓመት መከር እስክትሰበስቡ
ድረስ ከዚሁ እህል ትበላላችሁ።

[23]“ ‘መሬት ለዘለቄታ አይሸጥ፤ ምክን
ያቱም ምድሪቱ የእኔ ናት፤ እናንተም መጻ
ተኞችና እንግዶች ናችሁ። [24]ርስት አድር
ጋችሁ በምትይዙት ምድር ሁሉ መሬት
የሚዋጅበት እንዲኖር አድርጉ።

[25]“ ‘ከወገንህ አንዱ ደኽይቶ ርስቱን
ቢሸጥ፣ የቅርብ ዘመዱ መጥቶ ወገኑ
የሸጠውን ይዋጅለት። [26]ነገር ግን ሰውየው
ርስቱን የሚዋጅለት ምንም ዘመድ ባይኖረ
ውና፣ እርሱ ራሱ መዋጀት የሚችልበትን
ሀብት ቢያገኝ፣ [27]ርስቱን ከሸጠበት ጊዜ
ጀምሮ ያለውን የሽያጭ ዘመን በመቍጠር
የዋጋውን ልዩነት ለገዛው ሰው ይመልስ፤
እርሱም ወደ ገዛ ርስቱ ይመለስ። [28]ነገር
ግን ዋጋውን መመለስ ካልቻለ፣ የሸጠው
ርስት እስከ ኢዮቤልዩ ዓመት ድረስ የገ
ዢው ንብረት ሆኖ ይቈያል፤ በኢዮቤ
ልዩ ዓመት ለባለቤቱ ይመለሳል፤ ሰውየውም
ወደ ርስቱ ይመለሳል።

[29]“ ‘ማንኛውም ሰው ቅጥር በተሠራለት
ከተማ ውስጥ የሚገኝ መኖሪያ ቤቱን ቢሸጥ
ከሸጠበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አንድ ዓመት
ሊዋጀው ይችላል፤ የመዋጀት መብቱ እስከ
አንድ ዓመት ድረስ ነው። [30]አንዱ ዓመት
ከማለቁ በፊት መዋጀት ካልቻለ ግን፣
ቅጥር በተሠራለት ከተማ ውስጥ ያለው
ቤት የገዢውና የልጅ ልጆቹ ንብረት ሆኖ
ይቀራል፤ በኢዮቤልዩ አይመለስለትም።
[31]ቅጥር በዙሪያው ባልተሠራለት መንደር
ውስጥ የሚገኙ ቤቶች ግን እንደ ዕርሻ
መሬት ተቈጥረው ሊዋጁ ይችላሉ፤ በኢ
ዮቤልዩም ይመለሳሉ።

[32]“ ‘ነገር ግን ሌዋውያን የራሳቸው በሆ
ኑት ከተሞች ውስጥ የሚገኙትን ቤቶቻ
ቸውን ምን ጊዜም የመዋጀት መብት አላ

25፥17 ዘሌ19፥13፡14፡32፤ኢዮ31፥16፤ምሳ22፥22፤ኤር7፥5፡6፤21፥12፤22፥3፡15፤ዘካ7፥9-10፤1ተሰ4፥6፤
25፥18 ቍ19፤ ዘፍ26፥5፤ዘሌ26፥4፡5፤ዘዳ12፥10፤33፥28፤ ኢዮ5፥22፤መዝ4፥8፤ኤር23፥6፤30፥10፤32፥37፤ 33፥16፤ሕዝ28፥26፤34፥25፤38፥14
25፥19 ቍ18፤ ዘሌ26፥4፤ዘዳ11፥14፤28፥12፤ኢሳ55፥10፤
25፥20 ቍ4
25፥21 ዘፀ16፥5፤ ዘዳ28፥8፡12፤መዝ133፥3፤134፥3፤147፥13፤ሕዝ44፥30፤ ሐጌ2፥19፤ ሚል3፥10፤
25፥22 ዘሌ26፥10
25፥23 ዘፍ23፥4፤ ዘፀ19፥5፤ዘኍ36፥7፤1ነገ21፥3፤ ሕዝ46፥18፤ ዕብ11፥13
25፥24 ቍ29፡48፤ ሩት4፥7፤ኤር32፥8
25፥25 ቍ48፤ ዘሌ27፥13፡19፡31፤ ሩት2፥20፤4፥4፤ ኤር32፥7፤
25፥26 ቍ49
25፥27 ቍ10፡15
25፥28 ቍ10፤ ዘሌ27፥24፤
25፥32 ዘኍ35፥1-8፤ኢሱ21፥2
25፥34 ዘኍ35፥2-5፤ ሕዝ48፥14
25፥35 ዘዳ15፥8፤ 24፥14፡15፤ መዝ37፥21፡26፤ ምሳ21፥26፤ሉቃ6፥35
25፥36 ዘፀ22፥25፤ ዘሌ19፥32፤ ኤር15፥10፤
25፥37 ዘፀ22፥25
25፥38 ዘፍ10፥19፤ 17፥7
25፥39 1ነገ5፥13፤ 19፥22፤ኤር34፥14
25፥40 ቍ53
25፥41 ቍ28፤ ኤር34፥8
25፥42 ቍ38
25፥43 ዘፍ42፥18፤ ዘፀ1፥13፤ ሕዝ34፥4፤ቈላ4፥1፤
25፥47 ነህ5፥5፤ ኢዮ24፥9
25፥48 ቍ24፡25
25፥49 ቍ26
25፥50 ቍ10፤ ኢዮ7፥1፤14፥6፤ ኢሳ16፥14፤21፥16

ቸው። [33]ሌዋውያን በከተማቸው ያለውን
ቤታቸውን ቢሸጡና መዋጀት ባይችሉ፣
በኢዮቤልዩ ይመለሳል፤ በሌዋውያን ከተ
ሞች የሚገኙ ቤቶች በእስራኤላውያን መካ
ከል የሌዋውያን ንብረት ናቸውና። [34]በከ
ተሞቻቸው ዙሪያ ያለው የግጦሽ መሬት
ግን አይሸጥ፤ ለዘላለም ቋሚ ንብረታቸው
ነውና።

[35]“ ‘በመካከልህ ከወገንህ አንዱ ቢደ
ኽይ፣ ራሱንም መርዳት ባይችል፣ በመካከልህ
ይኖር ዘንድ መጻተኛውን ወይም እንግዳ
ውን እንደምትረዳ እርዳው። [36]ወገንህ በመ
ካከልህ ይኖር ዘንድ ምንም ዐይነት ወለድ[*]
አትቀበለው፤ አምላክህን (ኤሎሂም) ፍራው።
[37]ገንዘብህን በዐራጣ አታበድረው፤ ምግብህንም
በትርፍ አትሽጥለት። [38]የከነዓንን ምድር
ልሰጥህና አምላክህ (ኤሎሂም) ልሆን፣ ከግብፅ
ያወጣሁህ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ (ያህዌ
ኤሎሂም) ነኝ።

[39]“ ‘ከወገንህ አንዱ ከመካከልህ ቢደኽ
ይ፣ ራሱንም ለአንተም ቢሸጥ፣ እንደ ባሪያ
አድ ርገህ አታሠራው። [40]በመካከልህ እንዳለ
ቅጥር ሠራተኛ ወይም እንደ እንግዳ
አድርገህ ቍጠረው፤ እስከ ኢዮቤልዩ ዓ
መትም ይሥራልህ፤ [41]ከዚያም በኋላ እርሱና
ልጆቹ በነጻ ይለቀቁ፤ ወደ ቤተ ሰቡና
ወደ አባቶቹ ንብረት ይመለስ። [42]እስራ
ኤላውያን ከግብፅ ያወጣኋቸው አገልጋዮቼ
ስለሆኑ እንደ ባሪያ አይሸጡ። [43]በጭካኔ
አትግዛቸው፤ ነገር ግን አምላክህን (ኤሎሂም) ፍራ
።

[44]“ ‘የሚኖሩህ ወንዶችና ሴቶች ባሪያ
ወችህ፣ በዙሪያህ ካሉት አሕዛብ መካከል
የገዛሃቸው ባሪያዎች ይሁኑ። [45]እንደዚሁም
በመካከላችሁ ከሚኖሩት መጻተኞችና ከተ
ወለዱት ወገናቸው ባሪያዎችን ግዙ፤
ንብረ ታችሁም ይሁኑ። [46]እነርሱንም እንደ
ንብረት ለልጆቻችሁ አውርሷቸው፤ በሕ
ይወታቸው ዘመን ሁሉ ባሪያዎች ይሁኑ
አችሁ፤ እስራኤላውያን ወገኖቻችሁን ግን
በጭካኔ አትግ ዟቸው።

[47]“ ‘በመካከላችሁ የሚኖር መጻተኛ
ወይም እንግዳ ሀብታም ቢሆንና ከወገናችሁ
አንዱ ደኽይቶ በመካከላችሁ ለሚኖር መጻ
ተኛ ወይም ከመጻተኛው ወገን ለአንዱ
ራሱን ቢሸጥ፣ [48]ከተሸጠ በኋላ ሊዋጅ
ይችላል። ከዘመዶቹም አንዱ፦ [49]አጎቱ ወይም
የአጎቱ ልጅ ወይም ከወገኖቹ ማንኛውም
የሥጋ ዘመዱ ይዋጀው፤ ሀብት ካገኘም
ራሱን መዋጀት ይችላል። [50]እርሱም ራሱን
ከሸጠበት ዓመት አንሥቶ እስከ ኢዮቤ

[*]36 ወይም እጅግ ብዙ ወለድ፤ እንዲሁም ቍ 37 ይመ

ልዩ ዓመት ድረስ ያለውን ጊዜ ከገዛው ሰው
ጋር በመሆን ይቈጠር፤ ነጻ የሚለቀቅበ
ትም ዋጋ በእነዚያ ዓመታት ለአንድ ቅጥር
ሠራተኛ በሚከፈለው መሠረት ይተመ
ናል። [51]ብዙ ዓመት የሚቀረው ከሆነም፣
እርሱን ለመግዛት ከተከፈለው ዋጋ ላይ
በቀረው ዓመት መጠን ለሚዋጅበት መልስ
ይክፈል። [52]እስከ ኢዮቤልዩ ድረስ የሚቀ
ረው ጥቂት ዓመት ከሆነም፣ በቀረው ዓ
መት መጠን የሚዋጅበትን መልስ ይክጠ
ፈል። [53]ከዓመት እስከ ዓመት እንደ ቅጥር
ሠራተኛ ይኑር፤ አሳዳሪውም በፊትህ
በጭካኔ አይግ ዛው።
[54]“ ‘ከእነዚህ መንገዶች በአንዱ እንኳ
መዋጀት ባይችል፣ እርሱና ልጆቹ በኢ
ዮቤልዩ ዓመት በነጻ ይለቀቁ፤ [55]እስራኤ
ላውያን ለእኔ አገልጋዮቼ ናቸውና። እነርሱ
ከግብፅ ምድር ያወጣኋቸው አገልጋዮቼ
ናቸው፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ (ያህዌ
ኤሎሂም) ነኝ።

## በመታዘዝ የሚገኝ በረከት

26 “ ‘ትሰግዱላቸው ዘንድ ጣዖታትን
አታብጁ፤ ምስል ወይም የማም
ለኪያ ዐምድ አታቁሙ፤ በምድራችሁም
ላይ የተቀረጸ ድንጋይ አታኑሩ፤ እኔ እግዚ
አብሔር አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ።
[2]“ ‘ሰንበታቴን ጠብቁ፤ መቅደሴን አክ
ብሩ፤ እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ።
[3]“ ‘በሥርዐቴ ብትሄዱ፤ ትእዛዜንም በጥን
ቃቄ ብትጠብቁ፣ [4]ዝናብን በወቅቱ እሰጣች
ኋለሁ፤ ምድሪቱ እህልዋን፣ የሜዳ ዛፎችም
ፍሬያቸውን ይሰጣሉ። [5]የምትወቁት እህል፣
የወይን ዘለላ እስከምትቈርጡበት ጊዜ፣
የምትቈርጡትም የወይን ዘለላ፣ እህል
እስከምትዘሩበት ጊዜ ያደርሷችኋል፤ ምግባ
ችሁን እስክትጠግቡ ትበላላችሁ፤ በምድራ
ችሁም ላይ በጸጥታ ትኖራላችሁ።
[6]“ ‘በምድሪቱ ላይ ሰላምን እሰጣለሁ፤
ትተኛላችሁ፤ ማንም አያስፈራችሁም። ክፉ
አራዊትን ከምድሪቱ አስወግዳለሁ፤ ሰይፍም
በምድራችሁ ላይ አያልፍም። [7]ጠላቶቻ
ችሁን ታሳድዳላችሁ፤ እነርሱም በፊታችሁ
በሰይፍ ይወድቃሉ። [8]ከእናንተ አምስቱ
መቶውን፣ መቶውም ዐሥሩን ሺህ ያሳድ
ዳሉ፤ ጠላቶቻችሁም በፊታችሁ በሰይፍ
ይወድቃሉ።
[9]“ ‘ፊቴን ወደ እናንተ እመልሳለሁ፤
እንድታፈሩና እንድትበዙም አደርጋችኋለሁ፤
ቃል ኪዳኔንም ከእናንተ ጋር አጸናለሁ።
[10]የዓምናውን እህል እየበላችሁ ከጐተራው
ሳያልቅ ለዘንድሮው እህል ደግሞ ቦታ
ታስለቅቃላችሁ። [11]ማደሪያዬን* በመካከ
ላችሁ አደርጋለሁ፤ ነፍሴም አት
ጸየፋችሁም። [12]በመካከላችሁ እመላለሳለሁ፤
አምላካችሁ (ኤሎሂም) እሆናለሁ፤ እናንተም ሕ
ዝቤ ትሆና ላችሁ። [13]ለግብፃውያን
ባሪያዎች እንዳትሆኑ ከግብፅ ምድር
ያወጣኋችሁ እኔ እግዚአብሔር
አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ፤ የባር ነት
ቀንበራችሁን ሰብሬ ቀና ብላችሁ
እንድትሄዱ አድርጌአችኋለሁ።

## አለመታዘዝ የሚያስከትለው ቅጣት

[14]“ ‘ነገር ግን ባትሰሙኝ፣ እነዚህን ትዕ
ዛዛት ባትጠብቁ፣ [15]ሥርዐቴን ብትንቀ
ቁ፣
ሕጌን ብታቃልሉ፣ ትእዛዛቴንም ሁሉ ባለ
መፈጸም ቃል ኪዳኔን ብታፈርሱ፣ [16]እኔም
ይህን አደርግባችኋለሁ፤ ድንገተኛ ድንጋጠ
ን፣ የሚቀሥፍ፣ ዐይናችሁን የሚያጠፉና
ሰውነ ታችሁን የሚያመነምን ትኩሳት
አመጣባች ኋለሁ፤ እህል የምትዘሩት
በከንቱ ነው፤
ጠላቶቻችሁ ይበሉታልና። [17]በጠላቶቻችሁ
ድል እንድትሆኑ ፊቴን በእናንተ ላይ
አከብድባችኋለሁ፤ የሚጠሏችሁ ይገዟችኋል፤
ማንም ሳያሳድዳችሁም ትሸሻላችሁ።
[18]“ ‘ከዚህ ሁሉ በኋላ ባትታዘዙኝ፣ ስለ
ኀጢአታችሁ ሰባት ዕጥፍ እቀጣችኋለሁ፤
[19]የትዕቢታችሁን ኀይል እሰብራለሁ፤ ሰማ
ያችሁን እንደ ብረት፣ ምድራችሁንም እንደ
ናስ አደርጋለሁ። [20]ኀይላችሁ በከንቱ ያል
ቃል፤ ምድራችሁ እህሏን፣ የምድሪቱ ዛፎ
ችም ፍሬዎቻቸውን አይሰጡምና።
[21]“ ‘በእኔ ላይ ማመፅ ብትቀጥሉና ባት
ታዘዙኝ እንደ ኀጢአታችሁ መጠን ሰባት
ዕጥፍ መቅሠፍት እጨምርባችኋለሁ። [22]የዱር
አራዊትን እሰድባችኋለሁ፤ ልጆቻችሁን
ይነጥ ቋችኋል፤ ከብቶቻችሁን ያጠ
ፋባችኋል፤ ቍጥራችሁ ይመነምናል፤
መንገዶቻችሁም ሰው አልባ ይሆናሉ።
[23]“ ‘በዚህ ሁሉ ግን ወደ እኔ ባትመለሱ፣
በእኔም ላይ ማመፃችሁን ብትቀጥሉ [24]እኔም
ጠላት እሆንባችኋለሁ፤ ስለ ኀጢአታች
ሁም ሰባት ዕጥፍ አስጨንቃችኋለሁ።

25፥52 ቀኍ16
25፥53 ቈላ4፥1
25፥55 ዘሌ11፡44፡45
26፥1 ዘፀ20፥4፤ 23፥24፤ዘኍ33፥52፤ መዝ97፥7፤ኢሳ48፥5፤ ኤር44፥19፤ዕን2፥18፤
26፥2 ዘፀ20፥8፤ ዘሌ19፥30
26፥3 ዘፍ26፥5፤ ዘፀ24፥8፤ዘዳ6፥17፤ 7፥12፤11፥13፡22፤ 28፥1፡9
26፥4 ዘፀ23፥26፤ ዘሌ25፥19፤ዘዳ11፥14፤ 28፥12፤ኢዮ5፥10፤ 14፥9፤መዝ65፥9፤ 67፥6፤68፥9፤104፥13፤ 147፥8፤ኤር5፥24፤ ሆሴ6፥3፤ኢል2፥23፤ ዘካ10፥1፤
26፥5 ዘሌ25፥18፤ ዘዳ6፥11፤11፥15፤ ሕዝ36፥29-30፤ ኢል2፥19፡26፤
26፥6 ቀኍ22፤ ዘፍ37፥20፤ ኢዮ11፥18፡19፤ መዝ3፥5፤4፥8፤ 29፥11፤37፥11፤ 85፥8፤147፥14፤ ምሳ3፥24፤ኢሳ17፥2፤ 26፥3፤54፥13፤60፥18ኤር30፥10፤ሐጌ2፥9፤ ሚክ 4፥4፤ሶፎ3፥13፤
26፥7 መዝ18፥37፤ 44፥5
26፥8 ዘዳ28፥7፤ 32፥30፤ኢሱ23፥10፤ መሳ15፥15፤ 1ዜና12፥14፤ ኢሳ30፥17፤
26፥9 ዘፍ1፥22፤ 17፥6፡7፤ነህ9፥23
26፥10 ዘሌ25፥22
26፥11 ቀኍ15፡43፡ 44፤ዘፀ25፥8፤ ዘዳ31፥6፤ 1ሳሙ12፥22፤ 1ነገ6፥13፤2ነገ17፥15 መዝ74፥7፤76፥2፤ ሕዝ37፥27
26፥12 ዘፍ3፥8፤ 17፥7፤ዘፀ6፥7፤ ኤር7፥23፤11፥4፤ 24፥7፤30፥22፤31፥1፤ዘካ13፥9፤2ቆሮ6፥16
26፥13 ዘፀ6፥6፤ 13፥3፤ዘሌ11፥44፤ ኢሳ10፥27፤ኤር2፥20፤ 27፥2፤28፥10፤30፥8፤ ሕዝ30፥18፤34፥27፤ ሆሴ11፥4
26፥14 ዘዳ28፥15-68፤ሚል2፥2
26፥15 ቀኍ11፤ ዘፍ17፥7
26፥16 ቀኍ 39፤ ዘዳ28፥22፡35፤ መዝ78፥33፤ መሳ6፥3-6፤ 1ሳሙ2፥33፤ኢዮ31፥8 መዝ107፥17፤
26፥25 ዘፀ5፥3፤ 9፥3፤ዘኍ16፥46፤ ሕዝ4፥17፤24፥23፤ 33፥10፤
26፥17 ቀኍ36፡37፤ዘሌ17፥10፤ ዘዳ28፥7፡25፡48፤ኢሱ7፥4፡12፤ መሳ2፥15፤1ነገ8፥33፤2ዜና6፥24፤ መዝ53፥5፤ 106፥41፤ምሳ28፥1፤ ኢሳ30፥17፤ ኤር19፥7፤21፥7፤ ሕዝ15፥7፤
26፥18 ቀኍ14፡21፤ መዝ99፥8፤ኤር21፥14፤አሞ3፥14
26፥19 ዘዳ28፥23፤ኢዮ38፥38፤ መዝ10፥4፤73፥6፤ ኢሳ16፥6፤25፥11፤28፥1-3፤ኤር13፥9፤48፥29፤ሕዝ24፥21፤ አሞ6፥8፤ሶፎ3፥11፤
26፥20 ዘዳ11፥17፤ 28፥24፡38፤ መዝ127፥1፤ ኢሳ17፥11፤49፥4፤ኤር12፥13፤ሚክ6፥15፤ሐጌ1፥6፤
26፥21 ቀኍ18፥41፤ዘፍ4፥15
26፥22 ዘፍ37፥20፤ዘዳ28፥62፤ ኤር42፥2፤5፥6፤14፥16፤15፥3፤16፥4፤ሕዝ14፥15
26፥23 ኤር2፥30፤ 5፥3፤7፥28፤17፥23፤32፥33፤ሶፎ3፥2
26፥24 2ሳሙ22፥27

*11 ወይም የመገናኛ ድንኳኔን

[25]ቃል ኪዳኔን ስላፈረሳችሁ፣ በላያችሁ
ሰይፍ በማምጣት እበቀላችኋለሁ፤ በከተሞ
ቻችሁ ውስጥ በምትሰበሰቡበት ጊዜ ቸነፈር
እሰድባችኋለሁ፤ ለጠላትም እጅ አልፋችሁ
ትሰጣላችሁ። [26]የእንጀራችሁ እህል እንዲ
ቋረጥ በማደርግበት ጊዜ፣ ዐሥር ሴቶች በአ
ንድ ምጣድ ላይ እንጀራ ይጋግራሉ፤ እን
ጀራውንም በሚዛን መዝነው እናንተም
ትበላላችሁ፤ ግን አትጠግቡም።
[27]“ ‘በዚህ ሁሉ ግን ባትታዘዙኝ፣ በእኔም
ላይ ማመፃችሁን ብትቀጥሉ፣ [28]እኔም
በቍጣዬ እመጣባችኋለሁ፤ ስለ ኀጢአታ
ችሁም እኔው ራሴ ሰባት ዕጥፍ እቀጣች
ኋለሁ። [29]የወንዶች ልጆቻችሁን ሥጋና
የሴቶች ልጆቻችሁን ሥጋ ትበላላችሁ።
[30]የኰረብታ መስገጃዎቻችሁን እደመስሳለሁ፤
የዕጣን መሠዊያዎቻችሁን አፈርሳለሁ፤
በድኖ ቻችሁን በድን በሆኑት ጣዖቶቻችሁ
ላይ እጥላለሁ፤ ነፍሴም ትጸየፋችኋለች።
[31]ከተ ሞቻችሁን አፈራርሳለሁ፤
መቅደሶቻችሁንም ወና አደርጋለሁ፤
ጣፋጭ ሽታ ያለውን መሥዋዕታችሁንም
አልቀበልም። [32]በዚያ የሚኖሩ ጠ
ላቶቻችሁ እስኪደነቁ ድረስ፣ ምድሪቱን
ባድማ አደርጋታለሁ። [33]በአሕዛብ መካከል
እበትናችኋለሁ፤ ሰይፌን መዝዤም
አሳድዳችኋለሁ። ምድራችሁ ባድማ፣
ከተሞቻችሁም ፍርስራሽ ይሆናሉ። [34]ምድሪቱ
ባድማ በሆነችበት ጊዜ ሁሉና እናንተም
በጠላቶቻችሁ ምድር በምትኖሩበት ወቅት
ምድሪቱ በሰንበት ዓመቷ ትደሰ ታለች፤
ምድሪቱም በሰንበቷ ታርፋለች፤
ትደሰታለችም። [35]ምድሪቱ እናንተ በነበራ
ችሁባት ጊዜ በሰንበት ያላገኘችውን ዕረ
ፍት፣ ባድማ በምትሆንበት ጊዜ ሁሉ
ታገኛለች።
[36]“ ‘ከእናንተ በሕይወት የተረፉትን፣
በጠላቶቻቸው ምድር ሳሉ ድንጋጤ እሰድባ
ቸዋለሁ፤ ነፋስ የሚያንቀሳቅሰው የቅጠል
ድምፅ ያስበረግጋቸዋል፤ የሚያሳድዳቸውም
ሳይኖር ከሰይፍ እንደሚሸሹ ይሮጣሉ፤
ይወድቃሉም። [37]የሚያሳድዳቸው ሳይኖር
ከሰይፍ እንደሚሸሹ እርስ በርሳቸው
ይሰነካ ከላሉ፤ በጠላቶቻችሁም ፊት መቆም
አትችሉም። [38]በአሕዛብ መካከል ታልቃላችሁ፤
የጠላቶቻችሁም ምድር ትውጣችኋለች።
[39]ከእናንተ የተረፉት በጠላቶቻቸው
ምድር በራሳቸው ኀጢአትና በአባቶቻቸው
ኀጢአት ምክንያት መንምነው ያልቃሉ።
[40]“ ‘ነገር ግን ለእኔ ያልታመኑበትንና
በእኔም ላይ ያመፁበትን የራሳቸውን ኀጢ
አትና የአባቶቻቸውን ኀጢአት ቢናዘዙ፣
[41]ይኸውም፣ እኔ ጠላት እንድሆንባቸውና
ወደ ጠላቶቻቸው ምድር እንድሰዳቸው ያደ
ረገኝን ኀጢአት ቢናዘዙ፣ ያልተገረዘው
ልባቸው ቢዋረድና ስለ ኀጢአታቸው የሚ
ገባውን ቅጣት ቢቀበሉ፣ [42]በዚያ ጊዜ
ከያዕቆብ ጋር የገባሁትን ኪዳኔን፣ ከይስሐ
ቅም ጋር የገባሁትን ኪዳኔን፣ ደግሞም ከአ
ብርሃም ጋር የገባሁትን ኪዳኔን አስባለሁ፤
ምድሪቱንም አስባታለሁ። [43]ምድሪቱ እነርሱ
ለቀዋት ስለሄዱ ባዶ ትቀራለች፤ እነርሱ
በሌሉበት ጊዜም ባድማ ሆና በሰንበትዋ
ትደሰታለች፤ ሕጌን በማቃለላቸውና ሥርዐ
ቴን በመናቃቸው፣ የኀጢአታቸውን ቅጣት
ይቀበላሉ። [44]በዚህ ሁሉ ግን ከእነርሱ ጋር
የገባሁትን ኪዳኔን በማፍረስ፣ በጠላቶቻቸው
ምድር ሳሉ ፈጽሜ እስካጠፋቸው ድረስ አልተ
ዋቸውም፤ አልጸየፋቸውምም፤ እኔ እግዚ
አብሔር አምላካቸው (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ።
[45]ስለ እነርሱም ስል፣ አምላካቸው (ኤሎሂም)
እሆን ዘንድ አሕዛብ እያዩ ከግብፅ ምድር
ካወጣኋቸው አባቶቻቸው ጋር የገባሁትን ኪ
ዳን አስባለሁ፤ እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ)
ነኝ።’ ”
[46]እግዚአብሔር (ያህዌ) በራሱና በእስራ
ኤላውያን መካከል በሲና ተራራ ላይ በሙሴ
በኩል ያቆማቸው ሥርዐቶች፣ ሕጎችና ደንቦች
እነዚህ ናቸው።

## ስለ ስጦታ የወጣ ሕግ

27 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ [2]“ለእስራኤላውያን እንዲህ
ብለህ ተናገር፤ ‘ማንኛውም ሰው ተመጣጣኙን
ዋጋ በመክፈል ለእግዚአብሔር (ያህዌ) ሰውን
ለመስጠት የተለየ ስእለት ቢሳል፣ [3]ዕድሜው
ከሃያ እስከ ሥልሳ ዓመት ለሆነ ወንድ፣
በቤተ መቅደሱ ሰቅል[θ] ሚዛን መሠረት፣
ግምቱ አምሳ ጥሬ ሰቅል[ፊ] ብር ይሁን።
[4]ለሴት ከሆነ ግምቱ ሠላሳ ሰቅል[T] ይሁን።

1ነገ8፥37፤ኤር5፥17፤15፥3፤47፥6፤50፥28፤51፥6፥11፤ሕዝ11፥8፤14፥17፤21፥4፤33፥2፤ዕን3፥5፤
26፥26 1ነገ8፥37፤18፥2፤2ነገ4፥38፤6፥25፤8፥1፤25፥3፤መዝ105፥16፤ኢሳ3፥1፤9፥20፤ኤር37፥21፤52፥6፤ሕዝ4፥16፥17፤5፥16፤14፥13፤ሆሴ4፥10፤ሚክ6፥14
26፥27 ቍ14
26፥28 ቍ18 ዘዳ32፥19፤መሳ2፥14 መዝ78፥59፤106፥40፤ዘዳ7፥10፤ ኢዮ34፥11፤ኢሳ59፥18፤65፥6-7፤66፥6፤ኤር17፥10፤25፥29፤ኢል3፥4
26፥29 2ነገ6፥29፤ኤር19፥9፤ሰቆ4፥10፤ሕዝ5፥10፤ዘዳ28፥53
26፥30 ዘዳ12፥2፤1ሳሙ9፥12፤10፥5፤1ነገ3፥2፥4፤12፥31፤13፥2፥32፤2ነገ17፥29፤23፥20፤2ዜና34፥3፤መዝ78፥58፤106፥40፤ኢሳ17፥8፤21፥9፤27፥9፤ኤር50፥2፤ሕዝ6፥3፥6፥13፤16፥16፤አሞ6፥8፤7፥9
26፥31 2ነገ22፥19፤ነህ1፥3፤መዝ74፥3-7፤ኢሳ1፥7፤3፥8፥26፤6፥11፤24፥12፤61፥4፤63፥18፤64፥11፤ኤር4፥7፤9፥11፤25፥11፤34፥22፤44፥2፥6፥22፤ሰቆ2፥7፤ሕዝ24፥21፤36፥33፤አሞ5፥21፥22፤7፥9፤8፥10፤ሚክ2፥4፤3፥12፤ሰፎ2፥5፤3፥6
26፥32 1ነገ9፥8፤2ዜና29፥8፤ኢሳ5፥6፤52፥14፤ኤር9፥11፤12፥11፤18፥16፤19፥8፤25፥11፤26፥9፤33፥10፤34፥22፤44፥22፤48፥39፤ሕዝ5፥14፤26፥16፤27፥35፤28፥19
26፥33 ቍ31፤ዘዳ4፥27፤28፥64፤1ሳሙ15፥22፤ነህ1፥8፤ኢዮ36፥11፤መዝ44፥11፤106፥27፤ኤር4፥11፤7፥34፤9፥16፤13፥24፤31፥10፤40፥3፥15፤42፥16፤50፥17፤ኢሳ49፥19፤ሕዝ5፥10፤12፥15፤17፥21፤20፥23፤22፥15፤34፥6፤ኢል3፥2፤ዘካ7፥14፤አሞ9፥4
26፥34 ቍ43፤2ዜና36፥21፤ኢሳ1፥7፤ ኤር7፥34፤ 25፥11፤44፥6፤ሕዝ33፥29
26፥35 ዘሌ25፥4 26፥36 ቍ17፤ 2ነገ25፥5፤ኢዮ13፥25፤መዝ58፥7፤ሰቆ1፥3፥ 6፤4፥19፤ሕዝ21፥7 26፥37 ኢሱ7፥12፤ኤር6፥21፤13፥16፤ 46፥16፤ሕዝ3፥20፤ ናሆ3፥3
26፥38 ዘዳ4፥26፤ኢዮ4፥9፤36፥12፤ መዝ1፥6፤ኢሳ1፥28፤ኤር16፥4፤44፥27 26፥39 ቍ16፤ዘፀ20፥5፤ኢሳ14፥21፤ኢሳ24፥16 26፥40 ዘሌ5፥5፤መዝ32፥5፤38፥18፤ነህ9፥2፤መዝ106፥6፤ኤር3፥12-15፤14፥20፤ሆሴ5፥15፤ ሉቃ15፥18፤1ዮሐ1፥9 26 41 ቍ21፤ዘዳ10፥16፤30፥6፤2ዜና7፥14፤ 12፥6፤ኢሳ6፥7፤33፥24፤40፥2፤53፥5፥6፥11፤ ኤር4፥4፤9፥25፥26፤ሕዝ20፥43፤44፥7፥9፤ሐሥ7፥51 26፥42 ዘፍ28፥15፤35፥11-12፤26፥5፤ዘፀ2፥24፤ዘኍ11፥20፤14፥31፤ 1ሳሙ8፥7 26፥43 ቍ11፤መዝ9፥25፤106፥24ኢሳ6፥11፤ 32፥14፤62፥4፤ኤር2፥15፤44፥2፤ሰቆ1፥1፤ሕዝ20፥13፤ሕዝ36፥4 26፥44 ቍ11፥33፤ዘዳ4፥31፤መሳ2፥1፤2ነገ17፥20፤25፥11፤ 2ዜና6፥36፤36፥20፤ኤር4፥27፤5፥10፤30፥11፤31፥37፤33፥26፤51፥5፤ሮሜ11፥2 26፥45 ዘፀ6፥8፤ዘሌ25፥38፤ዘዳ4፥31 26፥46 ዘፀ19፥11፤ ዘሌ7፥38፤27፥34
27፥2 ዘፍ28፥20 27፥3 ዘፀ30፥13

[θ]3 0.6 ኪሎ ግራም ገደማ ይሆናል፤ እንዲሁም ቍ16 ይመ
[ፊ]3 11.5 ግራም ገደማ ይሆናል፤ እንዲሁም ቍ 25 ይመ
[T]4 0.3 ኪሎ ግራም ገደማ ይሆናል

[5]ዕድሜው ከአምስት እስከ ሃያ ዓመት ለሆነ
ሰው፣ ወንድ ከሆነ ግምቱ ሃያ ሰቅል፣[ሀ]
ሴት ከሆነች ግምቷ ዐሥር ሰቅል[ለ] ይሁን።
[6]ዕድሜው ከአንድ ወር እስከ አምስት ዓመት
ለሆነ ሰው፣ ወንድ ከሆነ ግምቱ አምስት
ሰቅል[ሐ] ጥሬ ብር፣ ለሴት ከሆነ ሦስት
ሰቅል[መ] ጥሬ ብር ይሁን። [7]ሥልሳ ዓ
መት ወይም ከዚያ በላይ ለሆነ ሰው፣
ወንድ ከሆነ ግምቱ ዐሥራ አምስት ሰቅል፣
ሴት ከሆነች ዐሥር ሰቅል ይሁን።
[8]ስእለት የተሳለው ድኻ ከሆነና ግምቱን
መክፈል ካልቻለ ግን፣ ለስጦታ ያሰበውን
ሰው ወደ ካህኑ ያምጣ፤ ካህኑም የተሳለው
ሰው ባለው ዐቅም መሠረት መክፈል
የሚገባውን ይተምንለታል።
[9]" 'ሰውየው የተሳለው ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) መሥዋዕት ሆኖ መቅረብ የሚችል
እንስሳ ከሆነ፣ እንዲህ ያለው ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) የተሰጠ እንስሳ የተቀደሰ ይሆናል።
[10]ሰውየው መልካም የሆነውን እንስሳ መልካም
ባልሆነው፣ መልካም ያልሆነውንም መልካም
በሆነው አይለውጥ ወይም አይተካ፤ አን
ዱን እንስሳ በሌላው ከተካም ሁለቱ የተቀ
ደሱ ይሆናሉ። [11]እንስሳው በሥርዐቱ
መሠረት የረከሰ፣ ለእግዚአብሔርም (ያህዌ)
መሥዋዕት ሆኖ መቅረብ የማይገባው ከሆነ፣
ሰውየው እንስሳውን ወደ ካህኑ ያቅርብ፤
[12]መልካም ቢሆን ወይም ባይሆን፣ ካህኑ
ዋጋውን ይወስን፤ የካህኑም ውሳኔ የጸና
ይሆናል። [13]ባለቤቱ እንስሳውን መዋጀት
ከፈለገ ግን፣ በተተመነው ዋጋ ላይ አንድ
አምስተኛ መጨመር አለበት።
[14]" 'አንድ ሰው ቤቱን ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) ይሆን ዘንድ ቢቀድስ፣ መልካም ቢሆን
ወይም ባይሆን ካህኑ ዋጋውን ይተምን፤
ካህኑም የተመነው ዋጋ የጸና ይሆናል።
[15]ቤቱን የቀደሰው ሰው መልሶ ሊዋጀው
ከፈለገ ግን፣ የዋጋውን አንድ አምስተኛ
በዋጋው ላይ መጨመር አለበት፤ ቤቱም
ዳግመኛ የራሱ ይሆናል።
[16]" 'አንድ ሰው ከወረሰው ርስት ላይ
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የዕርሻ መሬት ቢቀ
ድስ፣ ዋጋው የሚተመነው ለመሬቱ በሚያ
ስፈልገው ዘር መጠን ይሆናል፤ ይኸውም
ለአንድ ሆሜር[ሠ] መስፈሪያ የገብስ ዘር
አምሳ ሰቅል ጥሬ ብር ነው። [17]ሰውየው ዕ
ርሻውን የቀደሰው በኢዮቤልዩ ዓመት
ከሆነ፣ የተወ ሰነው ዋጋ አይለወጥም። [18]ዕ
ርሻውን የሚቀ ድሰው ከኢዮቤልዩ በኋላ
ከሆነ ግን፣ ካህኑ ዋጋውን የሚተምነው
እስከሚመጣው የኢዮቤልዩ ዓመት ድረስ
ባሉት ዓመታት ቍጥር ልክ ነው፤
የተተመነውም ዋጋ ይቀነሳል። [19]ዕርሻውን
የቀደሰው ሰው መልሶ መዋጀት ከፈለገ፣
በዋጋው ላይ አንድ አምስተኛ መጨመር
አለበት፤ ከዚያ በኋላ
ዕርሻው እንደገና የራሱ ይሆናል። [20]ዕር
ሻውን ባይዋጅ ወይም ለሌላ ሰው አሳልፎ
ቢሸጥ፣ ከዚያ በኋላ ሊዋጀው አይችልም።
[21]እርሻው በኢዮቤልዩ በሚለቀቅበት ጊዜ
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) እንደተሰጠ ዕርሻ ተቈ
ጥሮ ቅዱስና የካህናቱ[ረ] ንብረት ይሆናል።
[22]" 'አንድ ሰው የወረሰው ርስት ያልሆ
ነውን፣ በገንዘቡ የገዛውን የዕርሻ መሬት
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) ቢቀድስ፣ [23]ካህኑ
የእርሻውን መሬት ዋጋ እስከ ኢዮቤልዩ
ዓመት ድረስ ባለው ጊዜ መጠን ይተም
ናል፤ ሰውየው የተተመነውን ዋጋ ለእግዚ
አብሔር (ያህዌ) የተቀደሰ አድርጎ በዚያኑ
ዕለት ይክፈል። [24]በኢዮቤልዩ ዓመትም
የዕርሻው መሬት የቀድሞው ባለ ርስት
ለነበረው፣ ለሸጠውም ሰው ይመለሳል። [25]እያ
ንዳንዱ ዋጋ የሚተመነው በቤተ መቅደሱ
ሰቅል ልክ ሆኖ አንዱ ሰቅል ሃያ ጌራ ነው።
[26]" 'የእንስሳት በኵር ቀድሞውኑ የእግ
ዚአብሔር (ያህዌ) ስለ ሆነ፣ ማንም ሰው
የእንስሳትን በኵር ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
መቀደስ አይችልም፤ በሬም[ሰ] ሆነ በግ
የእግ ዚአብሔር (ያህዌ) ነውና። [27]እንስሳው
ርኩስ ከሆነ ግን፣ ባለቤቱ በተተመነው
ዋጋ ላይ አንድ አምስተኛ ጨምሮ ሊዋጀው
ይችላል፤ የማይዋጀው ከሆነ ግን በተተመነው
ዋጋ ይሸጥ።
[28]" 'ነገር ግን ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
ተለይቶ የተሰጠ[ሸ] ማንኛውም ነገር፦ ሰውም
ሆነ እን ስሳ ወይም በውርስ የተገኘ
መሬት አይሸ ጥም፤ አይዋጅምም።
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የተሰጠ ማንኛውም
ነገር እጅግ የተቀደሰ ነውና።
[29]" 'እንዲጠፋ የተወሰነ ማንኛውም ሰው
አይዋጅም፤[ቀ] መገደል አለበት።
[30]" 'ከዕርሻ ምርትም ሆነ ከዛፍ ፍሬ፣
ማንኛውም ከምድሪቱ የሚገኝ ዐሥራት
የእግዚአብሔር (ያህዌ) ነው፤ ለእግዚአብሔርም
(ያህዌ) የተቀደሰ ነው። [31]አንድ ሰው ከዐሥ
ራቱ የትኛውንም መዋጀት ቢፈልግ፣ በዋ

[ሀ]5 0.2 ኪሎ ግራም ገደማ ይሆናል
[ለ]5 110 ግራም ገደማ ይሆናል፤ እንዲሁም ቍ 7 ይመ
[ሐ]6 55 ግራም ገደማ ይሆናል
[መ]6 35 ግራም ገደማ ይሆናል
[ሠ]16 220 ሊትር ገደማ ይሆናል
[ረ]21 ወይም *የካህኑ*
[ሰ]26 የዕብራይስጡ ቃል ተባዕትና እንስትን ሊያጠቃልል ይችላል
[ሸ]28 የዕብራይስጡ አገላለጽ አንድን ነገር ወይም ሰውን እንደ ማይመለስ ሆኖ ለእግዚአብሔር መስጠትን ያመለክታል።
[ቀ]29 የዕብራይስጡ አገላለጽ አንድን ነገር ወይም ሰውን ሙሉ በሙሉ በማስወገድ እንደማይመለስ ሆኖ ለእግዚአብሔር መስጠትን ያመለክታል

27፥5 ዘፍ37፥28
27፥6 ዘኍ3፥47፤ 18፥16
27፥8 ቍ12፡14፤ ዘሌ5፥11
27፥9 ቍ21፡26፡ 28፤ዘፍ28፥20፤ ዘፀ40፥9፤ዘሌ1፥2፤ ዘኍ6፥20፤18፥17፤ ዘዳ15፥19
27፥10 ቍ33
27፥11 ቍ27፤ ዘፀ 13፥13፤ ዘኍ18፥15
27፥13 ዘሌ5፥16፤ 25፥25
27፥15 ቍ13፡20
27፥18 ዘሌ25፥10፡ 15
27፥19 ዘሌ25፥25
27፥21 ቍ9፡28፤ ዘሌ25፥10፤ዘኍ18፥14 ፤ሕዝ44፥29
27፥23፤ ዘሌ25፥15
27፥24 ዘሌ25፥28
27፥25 ዘፀ30፥13፤ ዘኍ3፥47፤ ሕዝ45፥12
27፥26 ዘፀ13፥12
27፥27 ቍ11
27፥28 ዘኍ18፥14፤ ኢሱ6፥17-19
27፥29 ዘዳ7፥26
27፥30ዘኍ18፥26፤ ዘዳ7፥6፤12፥6፡17፤ 14፥22፡28፤ 2ዜና31፥6፤ዕዝ9፥2፤ ነህ10፥37፤ 12፥44፤ 13፥5፤ኢሳ6፥13፤ ሚል3፥8፤
27፥31 ዘሌ5፥16፤ 25፥25

ጋው ላይ አንድ አምስተኛ መጨመር
አለበት። [32]ከቀንድ ከብቶች፣ ከበጎችና
ከፍየሎች መንጋ የሚወጣው ዐሥራት
ከእረኛ በትር በታች ከሚያልፉት ዐሥረኛው
እንስሳ ይሆናል፤ ይህም ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) የተቀደሰ ነው። [33]ሰውየው መልካም
የሆነውን መልካም ካልሆነው አይለይ
ወይም አይተካ፤ አንዱን በሌላው ቢተካ
ግን ሁለቱም እንስሳት የተቀደሱ ይሆናሉ፤
ሊዋጁም አይችሉም።

[34]እግዚአብሔር (ያህዌ) በሲና ተራራ ላይ
በሙሴ አማካይነት ለእስራኤል ሕዝብ የሰጣ
ቸው ትእዛዛት እነዚህ ናቸው።

27፥32 መዝ89፥32፤
ኤር33፥13፤
ሕዝ20፥37
27፥33 ቍ10፤
ዘኍ18፥21
27፥34 ዘፀ19፥11፤
ዘሌ7፥38፤ሐሥ7፥38

# ኦሪት ዘኍልቍ

## የሕዝብ ቈጠራ

1 እስራኤላውያን ከግብፅ በወጡ በሁለተ
ኛው ዓመት፣ በሁለተኛው ወር፣ በመ
ጀመሪያው ቀን በሲና ምድረ በዳ ሳሉ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን በመገናኛው
ድንኳን ውስጥ ተናገረው፤ እንዲህም አለው፤
2“የወንዶቹን ስም አንድ በአንድ በመዘ
ርዘር መላውን የእስራኤል ማኅበረ ሰብ
በየጐሣቸውና በየቤተ ሰባቸው ቍጠሯ
ቸው። 3በመላው እስራኤል ያሉትን ዕድሜ
ያቸው ሃያና ከዚያም በላይ ሆኖ ለውጊያ
ብቁ የሆኑትን ወንዶች ሁሉ አንተና
አሮን በየምድባቸው ቍጠሯቸው።
4ከየነገዱ የአባቶች ቤት ተጠሪ የሆነ አንድ
ሰው ከእናንተ ጋር ይሁን። 5የሚረዷችሁም
ሰዎች ስም የሚከተለው ነው፦

“ከሮቤል የሰዲዮር ልጅ ኤሊሱር፤
6ከስምዖን የሱሪሰዳይ ልጅ ሰለሚኤል፤
7ከይሁዳ የአሚናዳብ ልጅ ነአሶን፤
8ከይሳኮር የሶገር ልጅ ናትናኤል፤
9ከዛብሎን የኬሎን ልጅ ኤልያብ፤
10ከዮሴፍ ልጆች ከኤፍሬም የዓሚሁድ
ልጅ ኤሊሳማ፤
ከምናሴ የፍዳሱር ልጅ ገማልኤል
11ከብንያም የጋዴዮን ልጅ አቢዳን፤
12ከዳን የአሚሳዳይ ልጅ አኪዔዘር፤
13ከአሴር የኤክራን ልጅ ፋግኤል፤
14ከጋድ የራጉኤል ልጅ ኤሊሳፍ፤
15ከንፍታሌም የዔናን ልጅ አኪሬ።”

16እነዚህ ከማኅበረ ሰቡ የተመረጡ የየነ
ገዱ አለቆች ሲሆኑ እነርሱም የእስራኤል
ጐሣዎች መሪዎች ነበሩ።
17ሙሴና አሮን ስማቸው የተጠቀሰውን
እነዚህን ሰዎች ወሰዱ፤ 18ከዚያም በሁለተ
ኛው ወር በመጀመሪያው ቀን ማኅበረ ሰቡን
በሙሉ በአንድነት ሰበሰቧቸው። የተሰበሰ
ቡትም በየጐሣቸውና በየቤተ ሰባቸው የት
ውልድ ሐረጋቸውን ተናገሩ፤ 19*እግዚአብሔ
ር* ሙሴን ባዘዘው መሠረት ዕድሜአቸው
ሃያ ዓመትና ከዚያም በላይ የሆነ ወንዶች
ስማቸው አንድ በአንድ ተመዘገበ። እንዲህ
አድርጎም በሲና ምድረ በዳ ቈጠራቸው።

20ከእስራኤል የበኵር ልጅ ከሮቤል ዝርያ
ዕድሚያቸው ሃያ ዓመትና ከዚያ በላይ
ሆኖ በሰራዊቱ ውስጥ ለማገልገል
ብቁ የሆኑት ወንዶች ሁሉ በየጐሣ
ቸውና፣ በየቤተ ሰባቸው መዝገብ መሠ
ረት ስማቸው አንድ በአንድ ተጻፈ።
21ከሮቤል ነገድ የተቈጠሩት አርባ
ስድስት ሺህ አምስት መቶ ነበሩ።
22ከስምዖን ዝርያ፦
ዕድሜያቸው ሃያ ዓመትና ከዚያም በላይ
ሆኖ ለመዋጋት ብቁ የሆኑት ወን
ዶች ሁሉ በየጐሣቸውና በየቤተ
ሰባቸው መዝገብ መሠረት ስማቸው
አንድ በአንድ ተጻፈ። 23ከስምዖን
ነገድ የተቈጠሩት አምሳ ዘጠኝ ሺህ
ሦስት መቶ ነበሩ።
24ከጋድ ዝርያ፦
ዕድሜያቸው ሃያ ዓመትና ከዚያም
በላይ ሆኖ ለመዋጋት ብቁ የሆኑት
ወንዶች ሁሉ በየጐሣቸውና፣ በየቤተ
ሰባቸው መዝገብ መሠረት ስማቸው
አንድ በአንድ ተጻፈ። 25ከጋድ
ነገድ የተቈጠሩትም አርባ አምስት
ሺህ ስድስት መቶ አምሳ ነበሩ።
26ከይሁዳ ዝርያ፦
ዕድሜያቸው ሃያ ዓመትና ከዚያም
በላይ ሆኖ ለመዋጋት ብቁ የሆኑት
ወንዶች ሁሉ በየጐሣቸውና፣ በየቤተ
ሰባቸው መዝገብ መሠረት ስማቸው
አንድ በአንድ ተጻፈ። 27ከይሁዳ ነገድ
የተቈጠሩትም ሰባ አራት ሺህ ስድ
ስት መቶ ነበሩ።
28ከይሳኮር ዝርያ፦
ዕድሜአቸው ሃያ ዓመትና ከዚያም
በላይ ሆኖ ለመዋጋት ብቁ የሆኑት
ወንዶች ሁሉ በየጐሣቸውና፣ በየቤተ
ሰባቸው መዝገብ መሠረት ስማቸው
አንድ በአንድ ተጻፈ። 29ከይሳኮር ነገድ
የተቈጠሩትም አምሳ አራት ሺህ አራት
መቶ ነበሩ።
30ከዛብሎን ዝርያ፦
ዕድሜያቸው ሃያ አመትና ከዚያም
በላይ ሆኖ ለመዋጋት ብቁ የሆኑት
ወንዶች ሁሉ በየጐሣቸውና፣ በየቤተ
ሰባቸው መዝገብ መሠረት ስማቸው
አንድ በአንድ ተጻፈ። 31ከዛብሎን
ነገድ የተቈጠሩትም አምሳ ሰባት ሺ
ህ አራት መቶ ነበሩ።
32ከዮሴፍ ልጆች፦
ከኤፍሬም ዝርያ ዕድሜያቸው ሃያ ዓመ
ትና ከዚያም በላይ ሆኖ ለመዋጋት
ብቁ የሆኑት ወንዶች ሁሉ በየጐሣ
ቸውና በየቤተ ሰባቸው መዝገብ መ

1፥1 ቍ18፤ዘፀ6፥14፤19፥1፤27፥21፤40፥2
1፥2 ቍ18፤ዘፀ30፥11-16፤ዘኍ3፥40
1፥3 ቍ20፤ዘፀ4፥14፤30፥14፤ዘኍ17፥3፤ኢሱ5፥4፤1ዜና5፥18
1፥4 ቍ16፤ዘፀ18፥21፤ዘሌ24፥11፤ዘኍ7፥2፤30፥1፤31፥26፤34፥18፤ዘዳ1፥15፤ኢሱ7፥1፤22፥14
1፥5 ዘፍ29፥32፤ዘኍ2፥10፤7፥30፤10፥8፤17፥2፤ራእ7፥5
1፥6 ቍ22፤ዘኍ2፥12፤7፥36፡41፤10፥19፤25፥14
1፥7 ቍ26፤ዘፍ29፥35፤ዘፀ6፥23፤ ዘኍ7፥12፤ሩት4፥20፤1ዜና2፥10፤መዝ78፥68፤ማቴ1፥4፤ሉቃ3፥32
1፥8 ዘፍ30፥18፤ዘኍ፤2፥5፤7፥18፤10፥15
1፥9 ቍ30፤ዘኍ2፥7፤7፥24፤10፥16
1፥10 ቍ32፤ዘኍ2፥18፤7፥48፡53፤10፥22፤ቍ34፤2፥20፤7፥54፤10፥23
1፥11 ዘኍ2፥22፤7፥60፤10፥24፤መዝ68፥27
1፥12 ቍ38፤ዘኍ2፥25፤7፥66፤10፥25
1፥13 ቍ40፤ዘኍ2፥27፤7፥72፤10፥26
1፥14 ቍ24፤ዘኍ2፥14፤7፥42፤10፥20
1፥15 ቍ42፤ዘኍ2፥29፤7፥78፤10፥27
1፥16 ቍ4፤ዘፀ18፥ 25፤ዘኍ32፥28
1፥18 ቍ1፡2፤ዘፀ30፥14፤ዕዝ2፥59፤ዕብ7፥3
1፥19 ዘፀ30፥12፤ዘኍ26፥63፤31፥49
1፥20 ዘፍ10፥15፤29፥32፤46፥9፤ራእ7፥5
1፥21 ዘኍ26፥7
1፥22 ዘፍ29፥33፤ራእ7፥7
1፥23 ዘኍ26፥14
1፥24 ዘፍ30፥11፤ኢሱ13፥24-28፤ራእ7፥5
1፥25 ዘፍ46፥16፤ዘኍ26፥18፤1ዜና5፥11
1፥26 ቍ7፤ማቴ1፥2፤ራእ7፥5
1፥27 ዘኍ26፥22
1፥28 ዘፍ30፥18፤

ሠ ረት ስማቸው አንድ በአንድ
ተጻፈ። 33ከኤፍሬም ነገድ የተቈጠሩ
ትም አርባ ሺህ አምስት መቶ ነበሩ
።

34ከምናሴ ዝርያዎች፡-
ዕድሜያቸው ሃያ ዓመትና ከዚያም
በላይ ሆኖ ለመዋጋት ብቁ የሆኑት
ወንዶች ሁሉ በየጐሣቸውና በየቤተ
ሰባቸው መዝገብ መሠረት ስማቸው
አንድ በአንድ ተጻፈ። 35ከምናሴ
ነገድ የተቈጠሩትም ሠላሳ ሁለት ሺህ
ሁለት መቶ ነበሩ።

36ከብንያም ዝርያ፡-
ዕድሜያቸው ሃያ ዓመትና ከዚያም
በላይ ሆኖ ለመዋጋት ብቁ የሆኑት
ወንዶች ሁሉ በየጐሣቸውና፣ በየቤተ
ሰባቸው መዝገብ መሠረት ስማቸው
አንድ በአንድ ተጻፈ፤ 37ከብንያም ነገድ
የተቈጠሩትም ሠላሳ አምስት ሺህ
አራት መቶ ነበሩ።

38ከዳን ዝርያ፡-
ዕድሜያቸው ሃያ ዓመትና ከዚያም
በላይ ሆኖ ለመዋጋት ብቁ የሆኑት
ወንዶች ሁሉ በየጐሣቸውና፣ በየቤተ
ሰባቸው መዝገብ መሠረት ስማቸው
አንድ በአንድ ተጻፈ። 39ከዳን ነገድ
የተቈጠሩትም ሥልሳ ሁለት ሺህ
ሰባት መቶ ነበሩ።

40ከአሴር ዝርያ፡-
ዕድሜያቸው ሃያ ዓመትና ከዚያም
በላይ ሆኖ ለመዋጋት ብቁ የሆኑት
ወንዶች ሁሉ በየጐሣቸውና፣ በየቤተ
ሰባቸው መዝገብ መሠረት ስማቸው
አንድ በአንድ ተጻፈ 41ከአሴር ነገድ
የተቈጠሩት አርባ አንድ ሺህ አም
ስት መቶ ነበሩ።

42ከንፍታሌም ዝርያ፡-
ዕድሜያቸው ሃያ ዓመትና ከዚያም
በላይ ሆኖ ለመዋጋት ብቁ የሆኑት
ወንዶች ሁሉ በየጐሣቸውና፣ በየቤተ
ሰባቸው መዝገብ መሠረት ስማቸው
አንድ በአንድ ተጻፈ። 43ከንፍታ
ሌም ነገድ የተቈጠሩትም አምሳ
ሦስት ሺህ አራት መቶ ነበሩ።

44በሙሴና በአሮን፣ እያንዳንዳቸውም ቤተ
ሰባቸውን በወከሉት በዐሥራ ሁለቱ የእስ
ራኤል አለቆች የተቈጠሩት ወንዶች እነ
ዚህ ናቸው። 45ስለዚህ እስራኤላውያን ሁሉ
ዕድሜያቸው ሃያ ዓመትና ከዚያም በላይ
ሆኖ በእስራኤል ሰራዊት ውስጥ ለመዋ
ጋት ብቁ የሆኑት በየቤተ ሰባቸው ተቈጠሩ፤
46ጠቅላላ ቍጥራቸውም ስድስት መቶ
ሦስት ሺህ አምስት መቶ አምሳ ነበር።

47የሌዊ ነገድ ቤተ ሰቦች ግን ከሌሎች
ጋር አብረው አልተቈጠሩም፤ 48እግዚአብሔር
(ያህዌ) ሙሴን እንዲህ ብሎት ነበርና፤
49"የሌዊን ነገድ አትቍጠር፤ በእስራኤላ
ውያንም ቈጠራ ውስጥ አታስገባው፤ 50በዚህ
ፈንታ ሌዋውያንን በምስክሩ ማደሪያ፣
በውስጡ ባሉት በመገልገያ ዕቃዎች ሁሉ
እንዲሁም ከዚሁ ጋር በተያያዙ በማና
ቸውም ነገሮች ላይ ኀላፊዎች ይሁኑ፤
ማደሪያውንና በውስጡ ያሉትን የመገል
ገያ ዕቃዎች ይሸከሙ፤ በውስጡ ያገልግሉ፤
ድንኳናቸውንም በዙሪያው ይትከሉ። 51ማደ
ሪያው በሚነሣበት ጊዜ ሌዋውያን ይነቀ
ሉት፤ ማደሪያው በሚተከልበትም ጊዜ
ሌዋውያን ያቁሙት፤ ሌላ ሰው ቢቀርብ
ግን ይገደል። 52እስራኤላውያን በየምድባ
ቸው ድንኳናቸውን ይትከሉ፤ እያንዳን
ዱም ሰው በየሰፈሩና በየዐርማው ሥር
ይስፈር። 53ሌዋውያን ግን በእስራኤላው
ያን ማኅበረ ሰብ ላይ ቍጣ እንዳይወ
ርድ ድንኳኖቻቸውን በምስክሩ ማደሪያ
ዙሪያ ይትከሉ፤ የምስክሩ ማደሪያ ድንኳን
ኀላፊዎች ሌዋውያን ናቸው።

54እስራኤላውያንም እግዚአብሔር (ያህዌ)
ሙሴን ባዘዘው መሠረት ይህን ሁሉ አደ
ረጉ።

### የየነገዱ አሰፋፈር

2 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴንና አሮንን እን
ዲህ አላቸው፤ 2"እስራኤላውያን ከም
ስክሩ ድንኳን ትይዩ ዙሪያውን ጥቂት ራቅ
ብለው እያንዳንዱ ሰው በየዐርማውና በየ
ቤተ ሰቡ ምልክት ሥር ይስፈር።"

3"በምሥራቅ በኩል በፀሓይ መውጫ
የይሁዳ ምድብ በየሰራዊቱና በዐርማቸው
ሥር ይስፈር፤ የይሁዳ ሕዝብ አለቃ
የአሚናዳብ ልጅ ነአሶን ነው፤ 4የሰራ
ዊቱም ብዛት ሰባ አራት ሺህ ስድስት
መቶ ነው።

5"ከእነዚህ ቀጥሎ የይሳኮር ነገድ ይሰ
ፍራል፤ የይሳኮር ሕዝብ አለቃ የሶገር
ልጅ ናትናኤል ሲሆን፤ 6የሰራዊቱም
ብዛት አምሳ አራት ሺህ አራት መቶ
ነው።

7"ከዚያም የዛብሎን ነገድ ይቀጥ
ላል፤ የዛብሎን ሕዝብ አለቃ የኬሎን
ልጅ ኤልያብ ሲሆን፣ 8የሰራዊቱም
ብዛት አምሳ ሰባት ሺህ አራት መቶ
ነው።

9በየሰራዊታቸው ሆነው ከአይሁድ ምድብ
የተመዘገቡ አንድ መቶ ሰማንያ ስድ
ስት ሺህ አራት መቶ ናቸው፤ እነዚህ
አስቀድመው ይወጣሉ።

ራእ7፥7
1፥29 ዘፍ30፥18፤
ዘኍ26፥25
1፥30 ዘፍ30፥20፤
ራእ7፥8
1፥31 ዘኍ26፥27
1፥32 ዘፍ49፥26፤
41፥52
1፥33 ዘኍ26፥37፤
1ዜና7፥20
1፥34 ዘፍ41፥51፤
ራእ7፥6
1፥36 ዘፍ35፥18፤
2ዜና17፥17ኤር32፥
44፤አብ1፥19፤ራእ7፥8
1፥37 ዘኍ26፥41
1፥38 ዘፍ30፥6፤
ዘዳ33፥22
1፥39 ዘኍ26፥43
1፥40 ዘፍ30፥13፤
ዘኍ26፥44፤ራእ7፥6
1፥41 ዘኍ26፥47
1፥42 ዘፍ30፥8፤
ራእ7፥6
1፥43 ዘፀ1፥1-4፤
ዘኍ2650
1፥44 ዘኍ26፥64
1፥45 ቍ3፤
ዘኍ2፥32፤14፥29
1፥46 ዘፀ12፥37፤
2ሳሙ24፥9
1፥47 ዘኍ3፥17-20
፤4፥3፡49
1፥50 ዘፀ16፥34፤
25፥9፤26፥1፤ዘኍ3፥
31፤ሐሥ7፥21፥12፤
26፥1፤ዘኍ3፥38፤
4፥5፡15
1፥52 ዘኍ10፥14፤
መዝ20፥5፤ማሕ2፥4፤
6፥4
1፥53 ዘፀ38፥21፤
ዘኍ2፥10፤3፥23፡29፡
38፤16፥46፤18፥24፡5፤
29፡38፤ዘሌ10፥6፤ዘዳ
9፥22
2፥2 መዝ74፥4፤
ኢሳ31፥9፤ኤር4፥21
2፥3 ዘፀ6፥23
2፥5 ዘኍ10፥15፤
1፥8
2፥7 ዘኍ1፥9፤
10፥16
2፥9 ዘኍ10፥14፤
መሳ1፥1

10“በደቡብ በኩል የሮቤል ምድብ ሰራ
ዊት በዐርማቸው ሥር ይሆናል፤ የሮ
ቤል ሕዝብ አለቃ የሰዲዮር ልጅ
ኤሊሱር ሲሆን፣ 11የሰራዊቱም ብዛት
አርባ ስድስት ሺህ አምስት መቶ
ነው።

12“ከእነዚህ ቀጥሎ የስምዖን ነገድ
ይሰፍራል፤ የስምዖን ሕዝብ አለቃ የሱሪ
ሰዳይ ልጅ ሰለሚኤል ሲሆን፣ 13የሰራ
ዊቱም ብዛት አምሳ ዘጠኝ ሺህ ሦስት
መቶ ነው።

14“ከዚያም የጋድ ነገድ ይቀጥላል፤
የጋድ ሕዝብ አለቃ የራጉኤል[ሀ] ልጅ
ኤሊሳፍ ሲሆን፣ 15የሰራዊቱም ብዛት
አርባ አምስት ሺህ ስድስት መቶ አምሳ
ነው።

16በየሰራዊታቸው ሆነው ከሮቤል
ምድብ የተመዘገቡት ወንዶች በሙሉ
አንድ መቶ አምሳ አንድ ሺህ አራት
መቶ አምሳ ናቸው፤ እነዚህ ቀጥለው
ይመጣሉ።

17“ከዚህ በኋላ የመገናኛው ድን
ኳንና የሌዋውያን ምድብ በመካከል
ሆነው ይጓዛሉ፤ እያንዳንዳቸውም አሰፋፈ
ራቸውን በመከተል ቦታቸውን ጠብ
ቀው በዐርማቸው ሥር ይጓዛሉ።

18በምዕራብ በኩል የኤፍሬም ምድብ
ሰራዊት በዐርማቸው ሥር ይሆናል፤ የኤ
ፍሬም ሕዝብ አለቃ የዓሚሁድ ልጅ
ኤሊሳማ ሲሆን፣ 19የሰራዊቱም ብዛት
አርባ ሺህ አምስት መቶ ነው።

20“ከእነዚህም የምናሴ ነገድ ይቀጥላል፣
የምናሴ ሕዝብ አለቃ የፍዳሱር ልጅ
ገማልኤል ሲሆን፣ 21የሰራዊቱም ብዛት
ሠላሳ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ነው።

22ከዚያም የብንያም ነገድ ይቀጥላል፣
የብንያም ሕዝብ አለቃ የጋዴዮን ልጅ
አቢዳን ሲሆን፣ 23የሰራዊቱም ብዛት
ሠላሳ አምስት ሺህ አራት መቶ
ነው።

24በየሰራዊታቸው ሆነው ከኤፍሬም
ምድብ የተመዘገቡት ወንዶች በሙሉ
አንድ መቶ ስምንት ሺህ አንድ መቶ
ናቸው፤ እነዚህ ሦስተኛ ሆነው ይመጣሉ።

25“በሰሜን በኩል የዳን ምድብ ሰራ
ዊት በዐርማው ሥር ይሆናል፤ የዳን
ሕዝብ አለቃ የአሚሳዳይ ልጅ አኪዔ
ዘር ሲሆን፣ 26የሰራዊቱም ብዛት ሥልሳ
ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ነው።

27“የአሴር ነገድ ከእነዚህ ቀጥሎ ይሰ
ፍራል፤ የአሴር ሕዝብ አለቃ የኤክራን
ልጅ ፋግኤል ሲሆን፣ 28የሰራዊቱም ብዛት
አርባ አንድ ሺህ አምስት መቶ ነው።

29ከዚያም የንፍታሌም ነገድ ይቀጥ
ላል፤ የንፍታሌም ሕዝብ አለቃ የዔ
ናን ልጅ አኪሬ ሲሆን፣ 30የሰራዊቱም
ብዛት አምሳ ሦስት ሺህ አራት መቶ
ነው።

31“በየሰራዊታቸው ሆነው ከዳን ምድብ
የተመዘገቡት ወንዶች ሁሉ አንድ መቶ
አምሳ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ናቸው፤
እነርሱም በዐርማቸው ሥር በመጨ
ረሻ ይመጣሉ።

32በየቤተ ሰባቸው፣ በየምድባቸውና
በየሰራዊታቸው የተመዘገቡት እስራ
ኤላውያን ስድስት መቶ ሦስት ሺህ
አምስት መቶ አምሳ ናቸው፤ 33ያም
ሆኖ ግን *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን
ባዘዘው መሠረት ሌዋውያኑ ከሌሎቹ
እስራኤላ ውያን ጋር አልተቈጠሩም።

34ስለዚህ እስራኤላውያን *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ሙሴን ያዘዘውን ሁሉ አደረጉ፤ በየዐ
ርማውም ሥር የሰፈሩትና፣ እያንዳንዳ
ቸው በየጐሣቸውና በየቤተ ሰባቸው የተጓ
ዙት በዚህ ሁኔታ ነበር።

## ሌዋውያን

3 *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን በሲና ተራራ
ላይ ባነጋገረው ጊዜ የአሮንና የሙሴ
ትውልድ ይህ ነበር፤ 2የአሮን ልጆች የበ
ኵሩ ስም ናዳብ፣ የሌሎቹም አብዩድ
አልዓዛርና ኢታምር ይባላል። 3እርሱ
ለክህ ነት አገልግሎት የለያቸው፣ ካህናት
ለመ ሆን የተቀቡት የአሮን ወንድ
ልጆች ስም ይህ ነው፤ 4ናዳብና አብዩድ
ግን በሲና ምድረ በዳ ባልተፈቀደ እሳት
*ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) መሥዋዕት ባቀረቡ ጊዜ
እዚያው እፊቱ ወድቀው ሞቱ። ወንዶች
ልጆች ስላልነ በሯቸውም አልዓዛርና ኢ
ታምር ብቻ አባ ታቸው አሮን በሕይወት
በነበረበት ዘመን በክህነት ያገለግሉ ነበር።

5*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 6“የሌዊን ነገድ አምጥተህ ካህኑን
አሮንን በአገልግሎቱ እንዲረዱት ከፊቱ
አቁማቸው፤ 7በመገናኛው ድንኳን የማደሪ
ያውን አገልግሎት በመፈጸም ለእርሱና ለማ
ኅበረ ሰቡ ሁሉ የሚያስፈልጉትን ተግባሮች
ያከናውኑ፤ 8የማደሪያውን ሥራ በመሥራ
ትና የእስራኤላውያንን ግዴታ በመወጣት
የመገናኛውን ድንኳን ሁሉ ይጠብቁ። 9ሌዋ
ውያኑን ለአሮንና ለልጆቹ ስጥ፤ እነርሱም

[ሀ]14 ብዙ የማሶሬቲክ፣ የአሪት ሳምራውያንና የቩልጌት ቅጆች *ጸዑኤል* ይላሉ (ዘኍ 1፥14 ይመ)፤ አያሌ የማሶሬቲክ ቅጆች ግን ከዚህ ይስማማሉ።

2፥10 ዘኍ 1፥5፡53
2፥12 ዘኍ 1፥6፤ 10፥19
2፥14 ዘኍ 1፥14፤ 10፥20
2፥16 ዘኍ 10፥18
2፥17 ዘኍ 1፥50፤ 10፥21
2፥18 ዘፍ 48፥20፤ ዘኍ 1፥10፤53፤ኤር 31፥18-20
2፥20 ዘፍ 48፥20፤ ዘኍ 1፥10
2፥22 ዘኍ 1፥11፤ 10፥24
2፥24 ዘኍ 10፥22፤ መዝ 80፥2
2፥25 ዘኍ 1፥12፤ 3፤10፥25
2፥27 ዘኍ 1፥13፤ 10፥26
2፥29 ዘኍ 1፥15፤ 10፥27
2፥31 ዘኍ 10፥25፤ ኢሱ 6፥9
2፥32 ዘኍ 1፥45፤ ዘፀ 12፥37
2፥33 ዘኍ 1፥47፤ 26፥57-62
3፥1 ዘፀ 6፥27፤ 19፥11
3፥2፤ ዘፀ 6፥23፤ ዘኍ 1፥20
3፥3 ዘፀ 28፥41፤ 29፥30
3፥4 ዘሌ 10፥1፡2፡ 6፡12፤ዘኍ 4፥28፤ 1ዜና 24፥1
3፥6 ዘኍ 8፥6-22፤ 18፥1-7፤ዘዳ 10፥8፤ 31፥9፤1ዜና 15፥2፤ 2ዜና 29፥11
3፥7 ዘኍ 1፥53፤ 8፥19፤ዘሌ 8፥35

ከእስራኤላውያን ተለይተው ለእርሱ[ሰ] ፈጽ
መው የተሰጡ ናቸው። 10አሮንንና ልጆቹን
ሹማቸው፤ እነርሱም ክህነታቸውን ይጠብቁ፤
ሌላ ሰው ማደሪያውን ቢቀርብ ግን ይገደል።”
11*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 12“እነሆ፤ በኵር ሆኖ በሚወለደው
ሁሉ ምትክ ሌዋውያኑን ከእስራኤላውያን
ወስጃለሁ፤ ስለዚህ ሌዋውያን የእኔ ናቸው፤
13በኵር የሆነ ሁሉ የእኔ ነውና። በግብፅ
ምድር በኵር የሆነውን ሁሉ በመታሁ ዕለት
ከሰውም ሆነ ከእንስሳ ማናቸውንም የእስራ
ኤልን በኵር ለራሴ ለይቻለሁ፤ የእኔ ይሁን።
እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነኝ።”
14*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን በሲና ምድረ
በዳ፣ 15“ሌዋውያንን በየቤታቸውና በየጐሣ
ቸው ቍጠር፤ የምትቈጥረውም አንድ ወርና
ከዚያ በላይ የሆነውን ወንድ ሁሉ ነው” አለው።
16ስለዚህ ሙሴ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ቃል
በታዘዘው መሠረት እነዚህን ቈጠራቸው።

17የሌዊ ልጆች ስም
ጌድሶን፣ ቀዓትና ሜራሪ ነው።
18የጌድሶን ልጆች ጐሣ ስም
ሎቢኒና ሰሜኢ ነው።
19የቀዓት ጐሣዎች፤
እንበረም፣ ይስዓር፣ ኬብሮን፣ ዑዝኤል።
20የሜራሪ ጐሣዎች፤
ሞሖሊና ሙሲ።

እንግዲህ የሌዋውያን ጐሣዎች በየቤተ
ሰባቸው ሲቈጠሩ እነዚህ ናቸው።

21የሎቤናና የሰሜአ ጐሣዎች ከጌርሶን
ወገን ናቸው፤ እነዚህ የጌርሶን ጐሣዎች
ነበሩ። 22አንድ ወርና ከዚያ በላይ ሆኖአቸው
የተቈጠሩት ወንዶች በሙሉ ብዛታቸው
ሰባት ሺህ አምስት መቶ ነበር። 23የጌር
ሶን ጐሣዎች በምዕራብ በኩል ከማደሪያው
ድንኳን ጀርባ ይሰፍራሉ። 24የጌርሶን ጐሣ
ዎች ቤተ ሰቦች አለቃ የዳኤል ልጅ ኤሊ
ሳፍ ይሆናል። 25የጌድሶናውያን ኀላፊነት በመ
ገናኛው ድንኳን ማደሪያውንና ድንኳኑን፣
መደረቢያዎቹን እንዲሁም በመገናኛው ድን
ኳን ደጃፍ ላይ ያለውን መጋረጃ፣ 26የአደ
ባባዩን መጋረጃዎች፣ ማደሪያ ድንኳኑንና
መሠዊያውን የሚጋርደውን የአደባባዩን መግ
ቢያ መጋረጃ፣ ገመዶቹንና ከነዚሁ ጋር ተያ
ይዞ አገልግሎት የሚሰጠውን ሁሉ መጠ
በቅ ይሆናል።
27የእንበረማውያን፣ የይስዓራውያን፣ የኬ
ብሮናውያንና የዑዝኤላውያን ጐሣዎች ከቀዓት
ወገን ናቸው፤ እነዚህ የቀዓት ጐሣዎች ነበሩ
። 28አንድ ወርና ከዚያ በላይ ሆኖአቸው
የተ ቈጠሩት ወንዶች በሙሉ ብዛታቸው
ስም ንት ሺህ ስድስት መቶ[ሐ] ሲሆን፣ ቀዓ
ታው ያንም መቅደሱን የመጠበቅ
ኀላፊነት ነበራቸው። 29የቀዓት ጐሣዎች ከ

3፥9 ቀሁ12፥45፤ ዘኍ8፥19፤18፥6
3፥10 ዘፀ29፥9፤ 30፥7፤ዘኍ1፥51
3፥12 ቀኍ9፥41፤ዘፀ 13፥2፤ዘኍ8፥14፥16፥ 18፥16፤9ነህ13፥29፤ሚል2፥4
3፥13 ዘፀ13፥12፤ ዘሌ11፥44
3፥14 ዘፀ19፥1
3፥15 ቀሁ22፤39፤ ዘኍ1፥19፤18፥16፤ 26፥62
3፥17 ዘፍ29፥34፤ 46፥11፤ዘፀ6፥16፤ ዘኍ1፥47፤ኢሱ21፤4፥ 6፤1ዜና15፥4፤23፤6፤ 2ዜና29፤12
3፥18 ዘፀ6፥17
3፥19 ዘፀ6፥18
3፥20 ዘፍ46፥11፤ ዘፀ6፥19
3፥21 ዘፍ46፥11፤ ዘፀ6፥17
3፥23 ዘኍ2፥18
3፥25 ዘፍ25፥9፤ ዘፀ26፥14፥36፤40፥2፤ ዘኍ4፥25፤7፥1
3፥26 ቀኍ31፤ዘፀ 27፥9፤35፥18፤ዘኍ 4፥26
3፥27 ዘፍ46፥11፤ ዘፀ6፥18፤ዘኍ4፥15፥ 37፤1ዜና26፥23
3፥28 ቀሁ15፤ዘኍ 4፥4፥15፤ዘፀ25፥8፤ 30፥13፤2ዜና30፥19፤ መዝ15፥1፤20፥2፤ ሕዝ44፥27
3፥29 ዘኍ1፥53
3፥30 ዘፀ6፥22
3፥31 ቀኍ26ዘፀ 25፥10-22፥23፥31፤ 26፥33፤ዘኍ1፥50፤ 4፥5፥15፤18፥3ዘዳ10፥ 1-8፤1ዜና28፥15፤2ዜና 5፥2፤ኤር3፥16፤52፥19
3፥32 ቀሁ28ዘፀ6፥ 23፤ዘኍ4፥19፤18፥3
3፥33 ዘፀ6፥19፤ ዘፍ46፥11
3፥34 ቀሁ15
3፥35 ዘኍ2፥25
3፥36 ዘኍ4፥32፤ 18፥3፤ዘፀ26፥15-25፥ 26-29፤35፥20-29፤ 36፥36
3፥37 ዘፀ27፥10-17፥19
3፥38 ዘኍ1፥53፤ 2፥3፤1ዜና9፥27፤23፥ 32፤ቀሁ7፥10፤ዘኍ1፥ 51፤18፥5
3፥39 ቀሁ15፤ ዘኍ26፥62
3፥40 ቀሁ15፤ ዘኍ1፥2
3፥41 ቀሁ12፤ ዘሌ11፥44

ማደሪያው ድንኳን በደቡብ በኩል ይሰፍራ
ሉ። 30የቀዓት ጐሣዎች ቤተ ሰቦች አለቃ
የዑዝኤል ልጅ ኤሊሳፈን ይሆናል።
31እነርሱም ታቦቱን፣
ጠረጴዛውን፣ መቅረዙን፣ መሠዊያዎቹን፣
ለመቅደሱ አገልግሎት የሚውሉትን ዕቃ
ዎች፣ መጋረጃዎችንና ከነዚህ ጋር
ተያይዞ አገልግሎት የሚሰጠውን ሁሉ
ይጠብቃሉ። 32ዋናው የሌዋውያን አለቃ
የካህኑ የአሮን ልጅ አልዓዛር ነው፤
እርሱም መቅደሱን ለመጠበቅ ኀላፊ
በሆኑት ላይ ተሹሞ ነበር።
33የሞሖላውያንና የሙሳያውያን
ጐሣዎች ከሜራሪ ወገን ናቸው፤ እነዚህም
የሜራሪ ጐሣዎች ነበሩ። 34አንድ ወርና
ከዚያ በላይ ሆኖአቸው የተቈጠሩት ወንዶች
ሁሉ ብዛ ታቸው ስድስት ሺህ ሁለት
መቶ ነበር። 35የሜራሪም ጐሣዎች ቤተ
ሰቦች አለቃ የአቢካኢል ልጅ ሱሪኤል
ይሆናል፤ የሜራሪም ጐሣዎች ከማደሪያው
ድንኳን በሰሜን በኩል ይሰፍራሉ። 36ሜራ
ሪያውያንም የማደ ሪያውን ድንኳን
ሳንቃዎች፣ መወርወሪያ ዎች፣ ምሰሶዎች፣
ምሰሶዎቹ የሚቆሙባ ቸውን እግሮች፣ የ
ማደሪያ ዕቃዎችን ሁሉና ከነዚሁ ጋር
ተያይዞ አገልግሎት የሚሰጠውን ሁሉ
ለመጠበቅ ተሹመው ነበር። 37እንዲሁም
የአደባባዩን ዙሪያ ምሰሶዎች ከነመቆሚያ
እግሮቻቸው፣ ከነካስማቸውና
ከነገመዶቻቸው ይጠብቃሉ።
38ሙሴ፣ አሮንና ልጆቹ ከማደሪያው
ድንኳን በምሥራቅ በኩል በፀሓይ መውጫ
ከመገናኛው ድንኳን ፊት ለፊት ይሰፍራሉ፤
እነርሱም እስራኤላውያንን ወክለው ማደ
ሪያ ድንኳኑን ለመጠበቅ ኀላፊዎች ይሆ
ናሉ፤ ወደ ማደሪያው ድንኳን የሚቀርብ
ማንኛውም ሌላ ሰው ግን ይገደል።
39አንድ ወርና ከዚያ በላይ ሆኖአቸው፣
ሙሴና አሮን በእግዚአብሔር ትእዛዝ በየ
ጐሣቸው የቈጠሩአቸው የሌዋውያን ወን
ዶች ልጆች ጠቅላላ ብዛት ሃያ ሁለት ሺህ
ነበር።
40*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ “በኵር ሆነው የተወለዱትን፣
አንድ ወርና ከዚያ በላይ የሆናቸውን እስራ
ኤላውያን ወን ዶች ሁሉ ቍጠር፤ ዝርዝ
ራቸውንም ያዝ። 41በኵር በሆኑት በእስራ
ኤላውያን ልጆች ሁሉ ምትክ
ሌዋውያንን እንዲሁም በኵር በሆኑት
በእስራኤላውያን ከብቶች ሁሉ ምትክ
የሌዋውያንን ከብቶች ለእኔ አድርጋቸው፤

[ሰ]9 ብዙ የማሶሬቲክ ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ጥቂት የማ
ሶሬቲክ፣ የአራተ ሳምራውያንና የሰባ ሊቃናት ቅጆች ግን
*ለእኔ* ይላሉ።
[ሐ]28 የዕብራይስጡ ትርጉም ከዚህ ጋር ይስማማል አንዳንድ
የሰባ ሊቃናት ቅጆች ግን *ስምንት ሺህ ሦስት መቶ* ይላሉ።

እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ።”
[42]ስለዚህ ሙሴ እግዚአብሔር ባዘዘው
መሠረት የእስራኤላውያንን በኵር ሁሉ
ቈጠረ፤ [43]አንድ ወርና ከዚያ በላይ ሆኖ
አቸው በየስማቸው የተመዘገቡት ወንድ
በኵሮች ሁሉ ብዛታቸው ሃያ ሁለት ሺህ
ሁለት መቶ ሰባ ሦስት ነበር።
[44]ደግሞም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እን
ዲህ አለው፤ [45]“በእስራኤላውያን በኵ
ሮች ምትክ ሌዋውያኑን፣ በከብቶቻቸውም
ምትክ የሌዋውያኑን ከብቶች ውሰድ፤
ሌዋውያኑም የእኔ ይሁኑ፤ እኔ እግዚአ
ብሔር (ያህዌ) ነኝ። [46]ቍጥራቸው ከሌዋው
ያን ቍጥር በሁለት መቶ ሰባ ሦስት
በልጦ የተገኘውን እስራኤላውያን በኵሮች
ለመዋጀት፣ [47]ለእያንዳንዱ በኵር ክብደቱ
ባለ ሃያ አቦሊ በሆነው በቤተ መቅደሱ
ሰቅል[መ] ሚዛን ልክ አምስት አምስት ሰቅል
ተቀበል፤ [48]የተረፉትንም እስራኤላውያን
ለመዋጀት ገንዘቡን ለአሮንና ለልጆቹ ስጥ።”
[49]ስለዚህ ሙሴ በሌዋውያኑ ተዋጅተው
ቍጥራቸው ትርፍ ከሆነው በኵሮች ላይ
የመዋጃውን ገንዘብ ተቀበለ፤ [50]ከእስራኤላ
ውያን በኵሮች ላይ በቤተ መቅደሱ ሰቅል
ልክ አንድ ሺህ ሦስት መቶ ስልሳ
አምስት ሰቅል[ሠ] ሰበሰበ። [51]ሙሴም በእግዚ
አብሔር (ያህዌ) ቃል በታዘዘው መሠረት
የመዋጃውን ገንዘብ ለአሮንና ለልጆቹ
ሰጣቸው።

### ቀዓታውያን

4 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴንና አሮንን እን
ዲህ አላቸው፤ [2]“ከሌዋውያን ወገን የቀዓት
ዘር የሆኑትን በየጐሣቸውና በየቤተ ሰባ
ቸው ቍጠሩ። [3]እንዲሁም በመገናኛው
ድንኳን ውስጥ ይሠሩ ዘንድ ለማገልገል
የሚመጡትን ከሠላሳ እስከ አምሳ ዓመት
የሆናቸውን ወንዶች ሁሉ ቍጠሩ።
[4]“በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የቀዓታው
ያን ሥራ ንዋየ ቅዱሳቱን መጠበቅ ነው።
[5]ሰፈሩ ሲነሳ አሮንና ልጆቹ ገብተው የሚ
ከልለውን መጋረጃ ያውርዱ፤ የምስክሩንም
ታቦት ይጠቅልሉበት፤ [6]ከዚያም በአቆስ
ጣው ቍርበት ይሸፍኑት፤ ሙሉ በሙሉ
ሰማያዊ የሆነ መጐናጸፊያ በላዩ ላይ
ይዘርጉበት፤ መሎጊያዎቹንም በየቦታው
ያስገቡ።
[7]“በገጸ ኅብስቱ ገበታ ላይ ሰማያዊ ጨርቅ
ይዘርጉበት፤ በላዩም ላይ ወጭቶች፣ ጭል
ፋዎች፣ ጽዋዎች፣ ለመጠጥ ቍርባን የሚ
ሆኑትን ማንቈርቈሪያዎች እንዲሁም ሁል
ጊዜ ከዚያ የማይታጣውን ኅብስት ያስቀ
ምጡ። [8]በእነዚህም ላይ ቀይ ጨርቅ ይዘ
ርጉ፤ የአቆስጣውን ቍርበት ደርበውም
መሎጊያዎቹን በየቦታቸው ያስገቡ።
[9]“ደግሞም ሰማያዊ ጨርቅ ወስደው
ማብሪያ መቅረዙንና መብራቶቹን፣ መኰስ
ተሪያዎቹንና የኵስታሪ መቀበያዎቹን፣
እንዲሁም ለዚሁ አገልግሎት የሚውሉትን
የዘይት ዕቃዎች ይሸፍኑበት። [10]ከዚያም
ይህንና ከዚሁ ጋር የተያያዙትን ዕቃዎች
ሁሉ በአቆስጣ ቍርበት መሸፈኛ ጠቅልለው
በመሸከሚያ ሳንቃ ላይ ያስቀምጡት።
[11]“በወርቅ መሠዊያ ላይ ሰማያዊ ጨርቅ
ዘርግተው በአቆስጣ ቍርበት በመሸፈን መሎ
ጊያዎቹን በየቦታቸው ያስገቡ።
[12]“እንዲሁም በመቅደሱ ውስጥ ለአገልግ
ሎት የሚሆኑትን ዕቃዎች በሙሉ ወስ
ደው በሰማያዊ ጨርቅ በአቆስጣ ቍርበት
በመሸፈን በመሸከሚያው ሳንቃ ላይ ያስቀ
ምጡት።
[13]“ከናሱ መሠዊያ ላይ ዐመዱን ጠር
ገው ሐምራዊ ጨርቅ ያልብሱት፤ [14]ከዚያም
ለመሠዊያው አገልግሎት የሚውሉትን ዕቃ
ዎች በሙሉ፤ የእሳት ማንደጃዎቹን፣ ሜን
ጦዎቹን፣ የእሳት መጫሪያዎቹንና ጐድጓዳ
ሳሕኖችን በላዩ ላይ ያድርጉ፤ በእነዚህም
ላይ የአቆስጣ ቍርበት መሸፈኛ አልብሰው
መሎጊያዎቹን በየቦታቸው ያስገቡ።
[15]“አሮንና ልጆቹ መቅደሱንና ዕቃዎቹን፣
ንዋየ ቅዱሳቱንም በሙሉ ሸፍነው ከጨ
ረሱ በኋላ ሰፈሩ ለመንቀሳቀስ ዝግጁ
ሲሆን ቀዓታውያን ለመሸከም ይምጡ፤
እንዳይሞቱ ግን ንዋየ ቅዱሳቱን መንካት
የለባቸውም፤ ስለዚህ በመገናኛው ድንኳን
ውስጥ ያሉትን እነዚህን ዕቃዎች የሚሸ
ከሙ ቀዓታውያን ናቸው።
[16]“የካህኑ የአሮን ልጅ አልዓዛር በመብራ
ቱ ዘይት፣ ደስ የሚያሰኝ ሽታ ባለው ዕ
ጣን፣ ዘወትር በሚቀርበው በእህል
ቍርባንና በቅብዐ ዘይቱ ላይ ኀላፊነት
ይኖረዋል፤ እንደዚሁም ማደሪያውንና
በውስጡ ያለውን ሁሉ መቅደሱንና ዕቃዎቹ
ን ጭምር ይጠብቃል።”
[17]እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴንና አሮንን እን
ዲህ አላቸው፤ [18]“የቀዓት ጐሣዎች ከሌዋ
ውያን ተለይተው እንዳይጠፉ፤ [19]ወደ
ንዋየ ቅዱሳቱ በሚቀርቡበትም ጊዜ በሕ
ይወት እንዲኖሩ እንጂ እንዳይሞቱ አንተ
ይህን አድርግላቸው፤ አሮንና ልጆቹ ወደ
መቅደሱ ይግቡ፤ እያንዳንዱንም ሰው በየሥ
ራው ላይ ይደልድሉት፤ ምን መሸከም
እንዳለበትም ያስታውቁት። [20]ቀዓታውያን

3፥43 ቍ15፥39
3፥45 ቍ9፤ ዘሌ11፥44
3፥46 ዘፀ13፥13፤ ዘኍ18፥15
3፥47 ዘሌ27፥6፡25፤ዘፀ30፥13
3፥48 ቍ50፡51
3፥49 ቍ48
3፥50 ቍ41፡45፡46-48
4፥2 ዘፀ30፥12
4፥3 ቍ23ዘኍ1፥47፤8፥25፤1ዜና23፥3፡24፡27፤ዕዝ3፥8
4፥4 ቍ19፤ ዘኍ3፥28፤7፥9
4፥5 ዘኍ1፥51፤ ዘፀ26፥31፡33፤ 1ዜና23፥26
4፥6 ዘፀ25፥5፡13-15፤1ነገ8፥7፤2ዜና5፥8
4፥7 ዘፀ25፥30፤ 39፥36ዘሌ24፥6፤ ኤር52፥19
4፥8 ዘፀ26፥26-28
4፥9 ዘፀ25፥38
4፥10 ቍ12
4፥11 ዘፀ30፥1፡4
4፥12 ቍ10፤ ዘኍ3፥31
4፥13 ዘፀ27፥1-8፤ ዘሌ1፥16፤ዘኍ3፥31
4፥14 ዘፀ31፥9፤ 27፥3፡6፤ዘኍ7፥84፤ 1ዜና28፥17፤2ዜና4፥8፡11፡16፤ኤር52፥18
4፥15 ቍ4፤5፤ዘፀ28፥43፤ዘኍ1፥51፤3፥27፤7፥9፤2ሳሙ6፥6፡7
4፥16 ዘፀ25፥6፤ 29፥41ዘሌ6፥14-23፤ 10፥6፤29፥41፤ ዘኍ 3፥32
4፥19 ቍ15፡27፤ ዘኍ3፥32
4፥20 ዘፀ19፥21

[መ]47 አምሳ አምስት ግራም ያህል ነው።
[ሠ]50 አሥራ አምስት ኪ.ግ. ተኩል ያህል ነው።

ግን ንዋየ ቅዱሳቱን ለአንድ አፍታ እንኳን
ለማየት አይግቡ፤ ቢገቡ ይሞታሉ።”

### ጌድሶናውያን

21እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤
22“ጌድሶናውያንንም በየቤተ ሰባቸውና
በየጐሣቸው ቍጠራቸው፤ 23ከሠላሳ እስከ
አምሳ ዓመት የሆናቸውን በመገናኛው
ድንኳን ውስጥ ይሠሩ ዘንድ ለማገልገል
የሚመጡትን ወንዶች ሁሉ ቍጠር።
24“የጌድሶናውያን የሥራና የሸክም አገል
ግሎታቸው ይህ ነው፤ 25እነርሱም የማደሪ
ያውን መጋረጃዎች፣ የመገናኛውን ድንኳን፣
መደረቢያውንና በላዩ ላይ ያለውን የአቆ
ስጣ ቍርበት፣ የመገናኛውን ድንኳን
ደጃፍ መጋረጃዎች ይሸከሙ፤ 26እንዲሁም
በማደሪያውና በመሠዊያው ዙሪያ ያሉትን
የአደባባዩን መጋረጃዎች፣ የአደባባዩን
ደጃፍ መጋረጃ፣ ገመዶችና ለዚሁ አገልግ
ሎት የሚውሉትን ዕቃዎች ሁሉ ይሸከሙ፤
በዚህም ያገልግሉ። 27የጌድሶናውያን አገልግ
ሎት ሁሉ፣ ሸክምም ሆነ ሌላ ሥራ አሮንና
ልጆቹ በሚሰጡት አመራር መሠረት ይሆ
ናል። የሚሸከሙትን ሁሉ በኀላፊነት ታስረ
ክቧቸዋላችሁ። 28እንግዲህ የጌድሶናውያን
ጐሣዎች በመገናኛው ድንኳን የሚኖራ
ቸው አገልግሎት ይህ ነው፤ ተግባራቸውም
በካህኑ በአሮን ልጅ በኢታምር አመራር
ሥር ይሆናል።

### ሜራሪያውያን

29“ሜራሪያውያንን በየጐሣቸውና በየቤተ
ሰቦቻቸው ቍጠራቸው፤ 30እንዲሁም በመ
ገናኛው ድንኳን ውስጥ ይሠሩ ዘንድ ለማ
ገልገል የሚመጡትን ከሠላሳ እስከ አምሳ
ዓመት የሆናቸውን ወንዶች ሁሉ ቍጠር።
31በመገናኛው ድንኳን ውስጥ አገልግሎቶ
ቻቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ ተግባራቸው
ይህ ነው፤ የማደሪያውን ሳንቃዎች፣ መወ
ርወሪያዎች፣ ምሰሶዎችንና መቆሚያ እግሮ
ቻቸውን፣ ይሸከማሉ፤ 32እንደዚሁም በአደባባዩ
ዙሪያ ያሉትን ምሰሶዎች ከነመቆሚያ
እግሮቻቸው፣ ካስማዎችን፣ ገመዶችን፣ ከእነ
ዚሁ ጋር ያሉትን ዕቃዎች ሁሉና ማንኛ
ውም ለአገልግሎቱ አስፈላጊ የሆኑትን
ነገሮች ሁሉ ይሸከማሉ። እያንዳንዱ ሰው
የሚሸከመውን ዕቃ ለይታችሁ በስሙ መድ
ቡለት። 33እንግዲህ የሜራሪያውያን ጐሣ
ዎች በካህኑ በአሮን ልጅ በኢታምር ሥር
ሆነው በመገናኛው ድንኳን ሲሠሩ አገል
ግሎታቸው ይህ ነው።”

4፥23 ቍ3
4፥25 ዘፀ26፥14፤
27፥10-18፤ዘኍ3፥25
4፥26 ዘፀ27፥9፡16፤
ዘኍ3፥26
4፥27 ቍ19፤
ዘኍ3፥25፡26
4፥28 ዘኍ7፥7፤
ዘፀ6፥23
4፥29 ዘፀ30፥12፤
ዘፍ46፥11
4፥31 ዘኍ3፥36
4፥32 ዘኍ3፥37
4፥33 ዘፀ38፥21
4፥34 ቍ2
4፥35 ቍ3
4፥37 ዘኍ3፥27
4፥38 ዘፍ46፥11
4፥43 ቍ3
4፥45 ቍ29
4፥46 ዘኍ1፥19
4፥47 ቍ3
4፥48 ዘኍ3፥39
4፥49 ዘኍ1፥47
5፥2 ዘሌ13፥2፡3፤
15፥2፤21፥11፤ዘኍ
9፥6-10፤ማቴ9፥20

### የሌዋውያን ጐሣዎች ቈጠራ

34ሙሴ፣ አሮንና የማኅበረ ሰቡ አለቆች
ቀዓታውያንን በየጐሣቸውና በየቤተ ሰባቸው
ቈጠሯቸው። 35ከሠላሳ እስከ አምሳ ዓመት
ሆኖአቸው በመገናኛው ድንኳን ውስጥ
ለማገልገል የመጡት ወንዶች ሁሉ፣ 36በየ
ጐሣቸው የተቈጠሩት ሁለት ሺህ ሰባት
መቶ አምሳ ነበሩ። 37ይህ ከቀዓት ጐሣ
ዎች ሁሉ በመገናኛው ድንኳን ያገለገሉት
ሰዎች ጠቅላላ ድምር ነው። ሙሴና
አሮን፣ እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ አማካ
ይነት በሰጠው ትእዛዝ መሠረት እነዚህን
ቈጠሯቸው።
38ጌድሶናውያን በየጐሣቸውና በየቤተ
ሰባቸው ተቈጥረው ነበር። 39በመገናኛው
ድንኳን ውስጥ ይሠሩ ዘንድ ለማገልገል
የሚመጡት ከሠላሳ እስከ ሃምሳ ዓመት
የሆናቸው ወንዶች ሁሉ፣ 40በየጐሣቸውና
በየቤተ ሰባቸው የተቈጠሩት ሁለት ሺህ
ስድስት መቶ ሠላሣ ነበሩ። 41ይህ ከጌድሶን
ጐሣዎች በመገናኛው ድንኳን ያገለገሉት
ሰዎች ጠቅላላ ድምር ነው፤ እግዚአብሔር
(ያህዌ) በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ሙሴና
አሮን እነዚህን ቈጠሯቸው።
42ሜራሪያውያንም በየጐሣቸውና በየቤተ ሰባ
ቸው ተቈጥረው ነበር። 43በመገናኛው
ድንኳን ውስጥ ይሠሩ ዘንድ ለማገልገል
የሚመጡት ከሠላሳ እስከ አምሳ ዓመት
የሆናቸው ወንዶች ሁሉ፣ 44በየጐሣቸው
የተቈጠሩት ሦስት ሺህ ሁለት መቶ ነበሩ።
45ይህ የሜራሪ ጐሣዎች ጠቅላላ ድምር
ነው፤ እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ አማካይነት
በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ሙሴና አሮን
እነዚህን ቈጠሯቸው።
46ስለዚህ ሙሴ፣ አሮንና የእስራኤል አለ
ቆች ሌዋውያኑን በየጐሣቸውና በየቤተ
ሰባቸው ቈጠሯቸው፤ 47ከሠላሳ እስከ አምሳ
ዓመት ሆኖአቸው በመገናኛው ድንኳን ውስጥ
አገልግሎት ለመስጠትና ለመሸከም የመጡት፣
48ቍጥራቸው ስምንት ሺህ አምስት መቶ
ሰማንያ ነበሩ። 49እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ
አማካይነት በሰጠው ትእዛዝ መሠረት እያ
ንዳንዱ በየአገልግሎቱና በየሸክም ሥራው
ተደለደለ፤ ስለዚህም እግዚአብሔር (ያህዌ)
ሙሴን ባዘዘው መሠረት ቈጠራቸው።

### የሰፈሩ መንጻት

5 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2“ተላላፊ የቆዳ በሽታʻ ያለ
በትን ወይም ማንኛውም ዐይነት ፈሳሽ

ʻ2 በተለምዶ ለምጽ ማለት ነው፤ የዕብራይስጡ ትርጒም ለም
ጽን ብቻ ሳይሆን የተለያዩ የቆዳ በሽታዎችን የሚያመለክት
ነው።

ከሰውነቱ የሚወጣውን ወይም ሬሳ በመን
ካቱ በሥርዐቱ መሠረት የረከሰውን ሰው
ሁሉ ከሰፈር እንዲያስወጡ እስራኤላው
ያንን እዘዝ፤ 3ወንድም ሆነ ሴት አስወጡ፤
እኔ በመካከላቸው የምኖርበትን ሰፈራቸ
ውን እንዳያረክሱ ከሰፈር አስወጧቸው።”
4እስራኤላውያን ይህንኑ አደረጉ፤ ሰዎቹንም
ከሰፈር አስወጧቸው፤ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ሙሴን ባዘዘውም መሠረት ፈጸሙ።

## የካሳ አከፋፈል

5*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤
6“እስራኤላውያንን እንዲህ በላቸው፤ ‘ወን
ድም ሆነ ሴት በማናቸውም ረገድ ሌላ
ውን ቢበድልና ከዚህም የተነሣ *በእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ዘንድ ያለውን ታማኝነት
ቢያጓድል ያ ሰው በደለኛ ነው 7በሠራው
ኀጢአት ይናዘዝ፤ ስለ በደሉም ሙሉ ካሳ
ይክፈል፤ የተመደበበትም ካሳ ላይ አንድ
አምስተኛ በመጨመር በደል ላደረሰበት
ሰው ይስጥ፤ 8ነገር ግን ይህ ሰው ካሳውን
የሚቀበልለት ዘመድ ከሌለው ካሳው *ለእግ
ዚአብሔር* (ያህዌ) ስለሚሆን ማስተስረያ እን
ዲሆነው ከሚያቀርበው አውራ በግ ጋር
ለካህኑ ይስጥ። 9እስራኤላውያን የሚያመ
ጧቸው የተቀደሱ ስጦታዎች ሁሉ ለተ
ቀባዩ ካህን ይሆናሉ፤ 10የእያንዳንዱ ሰው
የተቀደሰ ስጦታ ለካህኑ ይሆናል፤ ለካህኑ
የሚሰጠውም ሁሉ የራሱ ይሆናል።’ ”

## በአመንዝራነት ስለሚጠረጠሩ ሚስቶች

11ከዚህ በኋላ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን
እንዲህ አለው፤ 12“እስራኤላውያንን ተናገራ
ቸው፤ እንዲህም በላቸው፤ ‘አንዲት ባለ
ትዳር ሴት ወደ ሌላ ወንድ በማዘንበል
ለባሏ ያላትን ታማኝነት አጒድላ፣ 13ከሌላ
ሰው ጋር ብትተኛ፣ ይህም እጅ ከፍንጅ
ባለመያዟ ምክንያት ይህ ከባሏ ቢደበቅ፣
የሚመሰክር ርባት ሰው ባይኖርና
መርከሷም ባይገለጥ፣ 14ባሏ የቅናት
መንፈስ አድሮበት ቢጠረጥ ርና በርግጥም
ጐድፋ ብትገኝ ወይም ባሏ የቅናት
መንፈስ አድሮበት ቢጠረጥርና እርሷ ግን
ጐድፋ ባትገኝ፣ 15ወደ ካህኑ ይውሰዳት፤
ስለ እርሷም አንድ ኪሎ[ሰ] ገብስ ዱቄት
ለቍርባን ይውሰድ፤ በላዩ ላይ ዘይት
አያፍስስበት፤ ዕጣንም አይጨ ምርበት፤
ይህ ስለ ቅናት የቀረበ የእህል ቍርባን
በደልን የሚያሳስብ የመታሰቢያ ቍርባን
ነውና።

16“ ‘ካህኑ ሴትየዋን ያመጣትና *በእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ፊት እንድትቆም ያደርጋ
ታል፤ 17ከዚያም የተቀደሰ ውሃ በሸክላ ዕቃ
ቀድቶ በማደሪያው ድንኳን ካለው ወለል
ጥቂት ዐፈር ቈንጥሮ በውሃው ውስጥ ይጨ
ምራል። 18ካህኑ ሴትየዋን *በእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ፊት እንድትቆም ካደረገ በኋላ የጠ
ጒሯን መሸፈኛ ይገልጣል፤ ስለ ቅናት
የቀረበውን የመታሰቢያ ቍርባን በእጇ
ያስይዛታል፤ ከዚያም ካህኑ ርግማን የሚያ
መጣውን መራራ ውሃ በእጁ ይይዛል።
19ካህኑም ሴትየዋን ያስምላታል፤ እንዲ
ህም ይላታል፤ “ሌላ ወንድ አብሮሽ ካልተኛ
በትዳር ላይ ሆነሽ ወደ ርኩሰት ካላዘነበ
ልሽ ይህ ርግማን የሚያመጣ መራራ ውሃ
ጒዳት አያድርስብሽ፤ 20ነገር ግን በትዳር
ላይ እያለሽ ወደ ርኵሰት በማዘንበል ከባ
ልሽ ሌላ ከወንድ ጋር በመተኛት ከጐደ
ፍሽ”፣ 21እዚህ ላይ ካህኑ እንዲህ በማለት
ሴትየዋን በርግማን መሐላ ያስምላታል፤
“*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ጭንሽን እያሰለለና[ሸ] ሆድ
ሽን እያሳበጠ በሕዝብሽ መካከል ርግማ
ንና መሐላ ያድርግብሽ፤ 22ይህን ርግማን
የሚያመጣ ውሃ በጠጣሽ ጊዜም ሆድሽን
ያሳብጠው፤ ጭንሽን ያሰልለው፤” “ ‘ሴትየ
ዋም፣ “አሜን፤ አሜን” ትበል።

23“ ‘ካህኑ እነዚህን መርገሞች በሰሌዳ
ላይ ይጻፍ፤ በመራራውም ውሃ ይደምስ
ሳቸው። 24ርግማን የሚያመጣውንም ውሃ
ሴትየዋ እንድትጠጣ ያድርግ፤ ውሃውም
ወደ ሰውነቷ ገብቶ የመረረ ሥቃይ ያስከት
ልባታል። 25ካህኑ ለቅናት የቀረበውን የእህል
ቍርባን ይቀበላት፤ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት
ወዝውዞ ወደ መሠዊያው ያቅርበው።
26ካህኑ የመታሰቢያ ቍርባን እንዲሆን
እፍኝ የእህል ቍርባን ከዚያ ወስዶ በመ
ሠዊያው ላይ ያቃጥለው፤ ከዚያም በኋላ
ሴቲቱ ውሃውን እንድትጠጣ ያድርግ።
27ራሷን በማጒደፍ ለባሏ ያላትን ታማኝ
ነት አጒድላ ከሆነ፣ ርግማን የሚያመጣ
ውን ውሃ እንድትጠጣ ሲደረግ ውሃው ወደ
ሰውነቷ ገብቶ ክፉ ሥቃይ ያመጣባታል፤
ሆዷ ያብጣል[ቀ]፤ ጭኗ ይሰልላል፤ በሕዝቦቿም
ዘንድ የተረገመች ትሆናለች። 28ዳሩ ግን
ሴትየዋ ካልጐደፈችና ነውር ከሌለባት ከበ
ደሉ ነጻ ትሆናለች፤ ልጆችም ትወልዳለች።

29“ ‘እንግዲህ የቅናት ሕግ ይህ ነው፤
አንዲት ሴት በትዳር ላይ እያለች ወደ ሌላ
ሄዳ ከረከሰች፣ 30ወይም አንድ ሰው ሚስ
ቱን ከመጠርጠሩ የተነሣ የቅናት መንፈስ
ሲያድርበት *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ያቁ
ማት፤ ካህኑም ሕጉ በሙሉ በሴቲቱ ላይ
ተፈጻሚነት እንዲኖረው ያድርግ። 31ባልየ
ውም ከበደል ንጹሕ ይሆናል፤ ሴትየዋ

5፥3 ዘፀ29፥45፤ ዘሌ26፥12፤2ቆሮ6፥16
5፥6 ዘሌ5፥14-6፥7፤ 6፥2
5፥7 ዘሌ5፥5፡16፤ ሉቃ19፥8
5፥8 ዘሌ5፥15፤ 6፥6፡7
5፥9 ዘሌ6፥17
5፥10 ዘሌ7፥29-34
5፥12 ቍ19-21፤ ዘፀ20፥14
5፥13 ዘፀ20፥14
5፥14 ቍ30፤ምሳ 6፥34፤27፥4፤ ማሕ8፥6
5፥15 ቍ18፡25፤ ዘፀ16፥36፤ዘሌ6፥20 ፤ሕዝ21፥23፤29፥16
5፥18 ቍ15፡19፤ ዘሌ10፥6፤1ቆሮ11፥6
5፥19 ቍ12፡18፡29
5፥20 ቍ12
5፥21 ኢሱ6፥26፤ 1ሳሙ14፥24፤ነህ 10፥29
5፥22 ቍ18፤መዝ 109፥18፤ዘዳ27፥15
5፥23 ኤር45፥1
5፥25 ዘሌ8፥27
5፥26 ዘሌ2፥2
5፥27 ኢሳ43፥28፤ 65፥15፤ኤር26፥6፤ 29፥18፤42፥18፤ 44፥12፡22፤ዘካ8፥13
5፥29 ቍ19
5፥30 ቍ14
5፥31 ዘሌ5፥1

[ሰ]15 የኢፍ መስፈሪያ አንድ አሥረኛ ማለት ነው።
[ሸ]21 *ሴቶች ያስወርዱ ወይም መካን ይሁኑ* ማለት ነው።
[ቀ]27 *ትመክናለች* ወይም *ታስወርዳለች* ማለት ነው።

ግን በበደሏ ምክንያት የሚመጣውን ፍዳ
ትቀበላለች::” ’

## የናዝራዊነት ሥርዐት

**6** *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ [2]“እስራኤላውያንን ተናገራ
ቸው፤ እንዲህም በላቸው፣ ‘ወንድም ሆነ
ሴት ናዝራዊ ይሆን ዘንድ ራሱን *ለእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ለመለየት ስእለት ቢሳል፣
[3]ከወይን ጠጅና ከሌላም ከሚያሰክር መጠጥ
ይታቀብ፤ የወይንም ሆነ የሚያሰክር የሌላ
መጠጥ ኾምጣጤ አይጠጣ፤ እንዲሁም
የወይን ጭማቂ አይጠጣ፤ የወይን ፍሬም
ሆነ ዘቢብ አይብላ:: [4]በናዝራዊነቱ ወቅት
ከወይን ተክል የሚገኘውን ማንኛውም ነገር፣
የወይኑን ዘር፣ ግልፋፊውንም እንኳ ቢሆን
አይብላ::
[5]“ ‘ስእለት ተስሎ ራሱን በለየበት ጊዜ
ሁሉ ምላጭ ራሱን አይንካው፤ *ለእግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) የተለየበት ጊዜ እስኪያበቃ ድረስ
የተቀደሰ ይሁን፤ የራስ ጠጕሩንም ያሳድግ::
[6]*ራሱን ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) በለየበት ጊዜ
ሁሉ ወደ ሬሳ አይቅረብ:: [7]*ራሱን* ለእግዚአ
ብሔር (ኤሎሂም) የለየበት ምልክት በራሱ ላይ
ስላለ አባቱም ይሁን እናቱ፣ ወንድሙም
ይሁን እኅቱ ቢሞቱ ለእነርሱ ሲል እንኳ
ራሱን አያርክስ:: [8]*ራሱን* በለየበት ጊዜ
ሁሉ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) የተቀደሰ ነው::
[9]“ ‘ድንገት ሰው አጠገቡ ሞቶ ለእግዚአ
ብሔር የተለየበትን ጠጕሩን ቢያረክስበት፣
በሚነጻበት ዕለት ማለት በሰባተኛው ቀን
ጠጕሩን ይላጭ:: [10]በስምንተኛው ቀን
ሁለት ዋኖስ ወይም ሁለት የርግብ
ጫጩቶች ይዞ ወደ መገናኛው ድንኳን
ደጃፍ ወደ ካህኑ ዘንድ ያምጣ:: [11]ካህኑም
አንዱን ለኀጢአት መሥዋዕት ሌላውን
ማስተስረያ እንዲሆንለት የሚቃጠል
መሥዋዕት አድ ርጎ ያቅርበው፤ በሬሳ
አጠገብ በመገኘቱ ኀጢአት ሠርቶአልና::
በዚያኑ ዕለት ጠጕሩን ይቀድስ:: [12]*ራሱን*
የተለየ ያደረገበትን ጊዜ *ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) መቀደስ አለበት፤ እንዲሁም
የአንድ ዓመት ተባት ጠቦት የበደል
መሥዋዕት አድርጎ ያምጣ:: ያለ ፉት
ቀኖች አይቈጠሩም፤ በተለየበት ጊዜ
ረክሶአልና::
[13]“ ‘እንግዲህ ናዝራዊ የመለየቱ ጊዜ ሲያ
በቃ ሥርዐቱ ይህ ነው፤ ወደ መገናኛው
ድንኳን ደጃፍ እንዲመጣ ይደረጋል::
[14]እዚያም መሥዋዕቱን *ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ያቅርብ፤ ይኸውም፣ እንከን የሌለበት
የአንድ ዓመት ተባዕት ጠቦት ለሚቃጠል
መሥዋዕት፣ እንከን የሌለበት የአንድ ዓ
መት እንስት ጠቦት ለኀጢአት መሥዋዕ
ት እን ዲሁም እንከን የሌለበት አውራ
በግ ለኅብ ረት መሥዋዕት[ሀ] ሲሆን፣
[15]ከእነዚህም ጋር የሚቀርበውን የእህልና
የመጠጥ ቍርባን ያለ እርሾ የተጋገረ
ቂጣ ማለት ከላመ ዱቄት በዘይት
የተለወሱ ዕንጎቻዎች እን ዲሁም በስሱ
የተጋገረና ዘይት የተቀባ ስስ ቂጣ
ያምጣ::
[16]“ ‘ካህኑ እነዚህን የኀጢአት መሥዋዕ
ትና የሚቃጠል መሥዋዕት በማድረግ
*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ያቀርባል:: [17]በመ
ሶብ ያለውን እርሾ የሌለበት ቂጣ እንዲ
ሁም አውራ በጉን የኅብረት መሥዋዕት
አድርጎ ከእህሉና ከመጠጡ ቍርባን ጋር
*ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) ያቅርብ::
[18]“ ‘ከዚያም ናዝራዊው ተስሎ የተለየበ
ትን ጠጕር በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ
ይላጨው፤ ጠጕሩንም ወስዶ ከኅብረቱ
መሥዋዕት ሥር በሚነደው እሳት ውስጥ
ይጨምረው::
[19]“ ‘ናዝራዊው ተስሎ የተለየበትን ጠጕር
ከተላጨ በኋላ፣ ካህኑ የተቀቀለውን የአው
ራውን በግ ወርች እንዲሁም ከመሶቡ ላይ
እርሾ የሌለበትን አንድ ወፍራምና አንድ
ስስ ቂጣ ወስዶ ናዝራዊው ያስይዘው [20]ከዚ
ያም ካህኑ የሚወዘወዝ መሥዋዕት በማድ
ረግ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ይወዘውዛ
ቸዋል፤ እነዚህም የተቀደሱ ናቸው:: ከተ
ወዘወዘው ፍርምባና ከቀረበው ወርች ጋር
የተቀደሱ የካህኑ ድርሻ ይሆናሉ:: ከዚህ
በኋላ ናዝራዊው የወይን ጠጅ መጠጣት
ይችላል::
[21]“ ‘ስእለቱን ለመፈጸም *ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ለሚሳል ናዝራዊ ሕጉ ይኸው ነው፤ ሊቀ
ርብ ከሚችለው በላይ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ለመስጠት ቃል ለሚገባው ነገር እንደ
ናዝራዊነቱ በተሳለው መሠረት መሆን አለ
በት:: በናዝራዊነት ሕግ መሠረት የተሳ
ለውን ስእለት መፈጸም ይገባዋል::’ ”

## የካህናት ቃለ ቡራኬ

[22]*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) ሙሴን አለው፤
[23]“አሮንንና ልጆቹን እንዲህ በላቸው፤
‘እስራኤላውያንን በምትባርኩበት ጊዜ
እንዲህ በሉአቸው፤

[24]“ ‘*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ይባርክህ፤
ይጠብቅህም፤
[25]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊቱን ያብራልህ፤
ይራራልህም፤
[26]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊቱን ይመልስልህ፤
ሰላሙንም ይስጥህ::’ ”

6፥2 ቀኍ5፡6፤ዘፍ 28፥20፤ሐሥ21፥23፤ መሳ13፥5፤16፥17
6፥3 ዘሌ10፥9፤ 25፥5፤ሩት2፥14፤ መዝ69፥21፤ምሳ 0፥26፤ሉቃ1፥15
6፥5 መዝ52፥2፤ 57፥4፤59፥7፤ኢሳ 7፥20፤ሕዝ5፥1፤ 1ሳሙ1፥11
6፥6 ዘሌ21፥1-3፤ ዘኍ19፥11-22
6፥7 ዘኍ9፥6
6፥9 ቀኍ18፤ ዘሌ14፥9
6፥10 ዘሌ5፥7፤ 14፥10፡11
6፥11 ዘፍ8፥20፤ ዘፀ29፥36፤30፥10
6፥12 ዘሌ5፥15፤ 12፥6
6፥13 ሐሥ21፥26፤ ዘሌ14፥11
6፥14 ዘፀ12፥5፤ ቀኍ11፤ዘሌ3፥1፤4፥3፤ 5፥15፤14፥10
6፥15 ዘሌ2፥1፤ 6፥14፤ዘፍ35፥14፤ ዘፀ29፥2
6፥16 ዘሌ1፥3፤ ቀኍ10፡11
6፥17 ዘፀ29፥41፤ ዘሌ3፥1፤23፥13
6፥18 ቀኍ9፤ ሐሥ21፥24
6፥19 ዘሌ7፥12
6፥20 ዘሌ7፥30፡ 34፤27፥9፤መክ9፥7
6፥21 ቀኍ2፡13
6፥23 ዘዳ21፥5፤ 1ዜና23፥13
6፥24 ዘፍ28፥3፤ ዘዳ28፥3-6፤1ሳሙ 2፥9፤መዝ17፥81፤ 28፥9፤128፥5
6፥25 ዘፍ43፥29፤ ኢዮ29፥24፤መዝ4፥6 ፤25፥16፤31፥16፤80፥3 ፤86፥16፤119፥29፡ 135
6፥26 መዝ4፥6፡8፤ 44፥3፤29፥11፤37፡11፡ 37፤127፥2፤ኢሳ 14፥7፤ኤር33፥6፤ ዮሐ14፥27

[ሀ] 14 በተለምዶ *የድኅነት መሥዋዕት* ማለት ነው

27“በዚህ ሁኔታ ስሜን በእስራኤላውያን
ላይ ያደርጋሉ፤ እኔም እባርካቸዋለሁ።”

## ማደሪያው ድንኳን ሲመረቅ የቀረቡ ስጦታዎች

7 ሙሴ የማደሪያ ድንኳኑን ተክሎ ካበቃ
በኋላ ማደሪያ ድንኳኑንና ዕቃዎቹን
ሁሉ ቀባቸው፤ ቀደሳቸውም፤ እንደዚሁም
መሠዊያውንና ዕቃዎቹን በሙሉ ቀባ
ቸው፤ ቀደሳቸውም። 2ከዚያም የእስራኤል
አለቆች ሆነው ከተቈጠሩት ነገዶች ኀላፊ
ዎች የነበሩት የየቤተ ሰቡ መሪዎች ስጦታ
ቸውን አቀረቡ። 3ስድስት የተሸፈኑ ሠረገ
ሎችና ዐሥራ ሁለት በሬዎች ይኸውም ከያን
ዳንዱ አለቃ አንዳንድ በሬ እንዲሁም ከየሁ
ለቱ አለቆች አንድ ሠረገላ ስጦታ አድር
ገው ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት አመጡ፤
እነዚህንም በማደሪያው ድንኳን ፊት አቀረ
ቧቸው።
4እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤
5“በመገናኛው ድንኳን ለአገልግሎት እን
ዲውሉ እነዚህን ከእነርሱ ተቀበል፤ ለእያን
ዳንዳቸውም ለአገልግሎታቸው በሚያስፈ
ልጋቸው መጠን ለሌዋውያኑ ስጣቸው።”
6ስለዚህ ሙሴ ሠረገሎቹንና በሬዎቹን
ወስዶ ለሌዋውያኑ ሰጣቸው፤ ለጌድሶናውያን
ለአገልግሎታቸው በሚያስፈልጋቸው መጠን
ሁለት ሠረገሎችና አራት በሬዎች ሰጠ።
8ለሜራሪያውያንም ለአገልግሎታቸው በሚ
ያስፈልጋቸው መጠን አራት ሠረገሎችና
ስምንት በሬዎች ሰጠ። እንግዲህ እነዚህ
ሁሉ በካህኑ በአሮን ልጅ በኢታምር ኀላፊ
ነት የሚመሩ ነበሩ። 9በኀላፊነት የተሰጧ
ቸውን ንዋያተ ቅዱሳት በትከሻቸው መሸ
ከም ስለነበረባቸው፣ ሙሴ ለቀዓታውያን
ምንም አልሰጣቸውም።
10መሠዊያው በተቀባበት ቀን አለቆች
የመሠዊያውን መቀደስ ምክንያት በማድ
ረግ ስጦታዎችን አመጡ፤ በመሠዊያውም
ፊት አቀረቡ። 11እግዚአብሔርም (ያህዌ) ሙሴን፣
“የመሠዊያውን መቀደስ ምክንያት በማድ
ረግ እያንዳንዱ አለቃ ስጦታውን በቀን
በቀኑ ያቅርብ” አለው።
12በመጀመሪያው ቀን ስጦታውን ያቀረ
በው ከይሁዳ ነገድ የአሚናዳብ ልጅ ነአሶን
ነበር፤
13ስጦታውም፣ እያንዳንዱ ለእህል ቍር
ባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ ልም
ዱቄት የተሞላ በቤተ መቅደሱ ሰቅል
ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሚመዝን
የብር ሳሕንና ሰባ ሰቅል የሚመዝን ከብር
የተሠራ ጐድጓዳ ሳሕን፣ 14ዐሥር
ሰቅል የሚመዝን በዕጣን የተሞላ የወ
ርቅ ጭልፋ፣ 15ለሚቃጠል መሥዋዕት
አንድ ወይፈን፣ አንድ አውራ በግ፣
አንድ ዓመት የሆነው የበግ ጠቦት፣
16ለኀጢአት መሥዋዕት አንድ ተባዕት
የፍየል ጠቦት፣ 17እንዲሁም ለኅብረት
መሥዋዕት የሚቀርብ ሁለት በሬ፣
አምስት አውራ በግ፣ አምስት ተባዕት
ፍየል እንዲሁም አንድ ዓመት የሆና
ቸው አምስት ተባዕት የበግ ጠቦቶች
ነበሩ። እንግዲህ የአሚናዳብ ልጅ ነአ
ሶን ያቀረበው ስጦታ ይህ ነበር።

18በሁለተኛው ቀን የይሳኮር አለቃ የሶገር
ልጅ ናትናኤል ስጦታውን አመጣ፤
19ስጦታውም፣ እያንዳንዱ ለእህል ቍር
ባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ ልም
ዱቄት የተሞላ በቤተ መቅደሱ ሰቅል
ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሚመዝን
የብር ሳሕንና ሰባ ሰቅል የሚመዝን ከብር
የተሠራ ጐድጓዳ ሳሕን፣ 20ዐሥር
ሰቅል የሚመዝን በዕጣን የተሞላ የወ
ርቅ ጭልፋ፣ 21ለሚቃጠል መሥዋዕት፣
አንድ ወይፈን፣ አንድ አውራ በግ፣
አንድ ዓመት የሆነው የበግ ጠቦት፣
22ለኀጢአት መሥዋዕት አንድ ተባዕት
የፍየል ጠቦት፣ 23እንዲሁም ለኅብረት
መሥዋዕት የሚቀርብ ሁለት በሬ፣
አምስት አውራ በግ፣ አምስት ተባዕት
ፍየል እንዲሁም አንድ ዓመት የሆና
ቸው አምስት ተባዕት የበግ ጠቦቶች
ነበሩ። እንግዲህ የሶገር ልጅ ናትና
ኤል ያቀረበው ስጦታ ይህ ነበር።

24በሦስተኛው ቀን የዛብሎን ሕዝብ አለቃ
የኬሎን ልጅ ኤልያብ ስጦታውን አመጣ፤
25ስጦታውም፣ እያንዳንዱ ለእህል ቍር
ባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ ልም
ዱቄት የተሞላ በቤተ መቅደሱ ሰቅል
ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሚመዝን
የብር ሳሕንና ሰባ ሰቅል የሚመዝን ከብር
የተሠራ ጐድጓዳ ሳሕን፣ 26ዐሥር
ሰቅል የሚመዝን በዕጣን የተሞላ የወ
ርቅ ጭልፋ፣ 27ለሚቃጠል መሥዋዕት፣
አንድ ወይፈን፣ አንድ አውራ በግ፣
አንድ ዓመት የሆነው የበግ ጠቦት፣
28ለኀጢአት መሥዋዕት አንድ ተባዕት
የፍየል ጠቦት፣ 29እንዲሁም ለኅብረት
መሥዋዕት የሚቀርብ ሁለት በሬ፣
አምስት አውራ በግ፣ አምስት ተባዕት
ፍየል እንዲሁም አንድ ዓመት የሆና
ቸው አምስት ተባዕት የበግ ጠቦቶች
ነበሩ። እንግዲህ የኬሎን ልጅ ኤል
ያብ ያቀረበው ስጦታ ይህ ነበር።

30በአራተኛው ቀን የሮቤል ሕዝብ አለቃ

6፥27 ዘጸ28፥10፤ 2ሳሙ7፥23፤2ዜና 7፥14፤ነህ9፥10፤ኤር 25፥29፤ሕዝ36፥23
7፥1 ቍ84፡88፤ ዘፀ30፥26፤40፥9፡10፡17፤2ዜና7፥9
7፥2 ዘኍ1፥5-16፡19
7፥3 ዘፍ45፥19፤ 1ሳሙ6፥7-14፤ 1ዜና13፥7
7፥7 ዘኍ4፥24-26፡28
7፥8 ዘኍ4፥31-33
7፥9 ዘኍ4፥4፡15
7፥10 ቍ1፤ዘፀ 29፥36፤2ዜና7፥9
7፥12 ዘኍ1፥7
7፥13 ቍ85፤ዘፀ 27፥3፤30፥13፤ዘሌ2፥1፤ 27፥3-7፤ዘኍ 6፥15፤15፥4
7፥14 ቍ20፡86፤ ዘፀ25፥6፤1ነገ7፥50፤ 2ነገ25፥14፤2ዜና 4፥22፤24፥14
7፥15 ዘፀ24፥5፤ 29፥3፤ዘኍ28፥11፤ ዘሌ1፥3
7፥16 ዘሌ4፥3
7፥17 ዘሌ3፥1፤ ዘኍ1፥7
7፥18 ዘኍ1፥8
7፥20 ቍ14
7፥24 ዘኍ1፥9
7፥30 ዘኍ1፥5

የሰዲዮር ልጅ ኤሊሱር ስጦታውን አመጣ፤
31ስጦታውም፣ እያንዳንዱ ለእህል ቍር
ባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ ልም
ዱቄት የተሞላ በቤተ መቅደሱ ሰቅል
ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሚመዝን
የብር ሳሕንና ሰባ ስቅል የሚመዝን ኩበር
የተሠራ ጐድጓዳ ሳሕን፣ 32ዐሥር
ሰቅል የሚመዝን በዕጣን የተሞላ የወ
ርቅ ጭልፋ፣ 33ለሚቃጠል መሥዋዕት
አንድ ወይፈን፣ አንድ አውራ በግ፣
አንድ ዓመት የሆነው የበግ ጠቦት፣
34ለኀጢአት መሥዋዕት አንድ ተባዕት
የፍየል ጠቦት፣ 35እንዲሁም ለኅብረት
መሥዋዕት የሚቀርብ ሁለት በሬ፣
አምስት አውራ በግ፣ አምስት ተባዕት
ፍየል እንዲሁም አንድ ዓመት የሆና
ቸው አምስት ተባዕት የበግ ጠቦቶች
ነበሩ፡፡ እንግዲህ የስዲዮር ልጅ ኤሊ
ሱር ያቀረበው ስጦታ ይህ ነበር፡፡

36በአምስተኛው ቀን የስምዖን ሕዝብ አለቃ
የሱሪሰዳይ ልጅ ስለሚኤል ስጦታውን
አመጣ፤
37ስጦታውም፣ እያንዳንዱ ለእህል ቍር
ባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ ልም
ዱቄት የተሞላ በቤተ መቅደሱ ሰቅል
ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሚመዝን
የብር ሳሕንና ሰባ ሰቅል የሚመዝን ኩበር
የተሠራ ጐድጓዳ ሳሕን፣ 38ዐሥር ሰቅል
የሚመዝን በዕጣን የተሞላ የወርቅ ጭልፋ፣
39ለሚቃጠል መሥዋዕት አንድ ወይ
ፈን፣ አንድ አውራ በግ፣ አንድ ዓመት
የሆነው የበግ ጠቦት፣ 40ለኀጢአት መሥ
ዋዕት አንድ ተባዕት የፍየል ጠቦት፣
41እንዲሁም ለኅብረት መሥዋዕት የሚ
ቀርብ ሁለት በሬ፣ አምስት አውራ
በግ፣ አምስት ተባዕት ፍየል እንዲ
ሁም አንድ ዓመት የሆናቸው አም
ስት የበግ ጠቦቶች ነበሩ፡፡ እንግዲህ
የሱሪሰዳይ ልጅ ስለሚኤል ያቀረበው
ስጦታ ይህ ነበር፡፡

42በስድስተኛው ቀን የጋድ ሕዝብ አለቃ የራ
ጉኤል ልጅ ኤሊሳፍ ስጦታውን አመጣ፤
43ስጦታውም፣ እያንዳንዱ ለእህል ቍር
ባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ ልም
ዱቄት የተሞላ በቤተ መቅደሱ ሰቅል
ሚዛን መቶ ሰላሳ ሰቅል የሚመዝን
የብር ሳሕንና ሰባ ሰቅል የሚመዝን ኩበር
የተሠራ ጐድጓዳ ሳሕን፣ 44ዐሥር
ስቅል የሚመዝን በዕጣን የተሞላ የወ
ርቅ ጭልፋ፣ 45ለሚቃጠል መሥዋዕት፣
አንድ ወይፈን፣ አንድ አውራ በግ፣
አንድ ዓመት የሆነው የበግ ጠቦት፣

7፥36 ዘኍ1፥6
7፥42 ዘኍ1፥14

46ለኀጢአት መሥዋዕት አንድ ተባዕት
የፍየል ጠቦት፣ 47እንዲሁም ለኅብረት
መሥዋዕት የሚቀርብ ሁለት በሬ፣
አምስት አውራ በግ፣ አምስት ተባዕት
ፍየል እንዲሁም አንድ ዓመት የሆና
ቸው አምስት የበግ ጠቦቶች ነበሩ፡፡
እንግዲህ የራጉኤል ልጅ ኤሊሳፍ ያቀ
ረበው ስጦታ ይህ ነበር፡፡

48በሰባተኛው ቀን የኤፍሬም ሕዝብ አለቃ
የዓሚሁድ ልጅ ኤሊሳማ ስጦታውን አመጣ፤
49ስጦታውም፣ እያንዳንዱ ለእህል ቍር
ባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ ልም
ዱቄት የተሞላ በቤተ መቅደሱ ሰቅል
ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሚመዝን
የብር ሳሕንና ሰባ ሰቅል የሚመዝን ኩበር
የተሠራ ጐድጓዳ ሳሕን፣ 50ዐሥር ሰቅል
የሚመዝን በዕጣን የተሞላ የወርቅ ጭልፋ፣
51ለሚቃጠል መሥዋዕት አንድ ወይፈን፣
አንድ አውራ በግ፣ አንድ ዓመት የሆ
ነው የበግ ጠቦት፣ 52ለኀጢአት መሥ
ዋዕት አንድ ተባዕት የፍየል ጠቦት፣
53እንዲሁም ለኅብረት መሥዋዕት የሚ
ቀርብ ሁለት በሬ፣ አምስት አውራ በግ፣
አምስት ተባዕት ፍየል እንዲሁም አንድ
ዓመት የሆናቸው አምስት ተባዕት የበግ
ጠቦቶች ነበሩ፡፡ እንግዲህ የዓሚሁድ
ልጅ ኤሊሳማ ያቀረበው ስጦታ ይህ
ነበር፡፡

54በስምንተኛው ቀን የምናሴ ሕዝብ አለቃ
የፍደሱር ልጅ ገማልኤል ስጦታውን አመጣ፤
55ስጦታውም፣ እያንዳንዱ ለእህል ቍር
ባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ ልም
ዱቄት የተሞላ በቤተ መቅደሱ ሰቅል
ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሚመዝን
የብር ሳሕንና ሰባ ሰቅል የሚመዝን ኩበር
የተሠራ ጐድጓዳ ሳሕን፣ 56ዐሥር ሰቅል
የሚመዝን በዕጣን የተሞላ የወርቅ ጭልፋ፣
57ለሚቃጠል መሥዋዕት አንድ ወይፈን፣
አንድ አውራ በግ፣ አንድ ዓመት የሆ
ነው የበግ ጠቦት፣ 58ለኀጢአት መሥ
ዋዕት አንድ ተባዕት የፍየል ጠቦት፣
59እንዲሁም ለኅብረት መሥዋዕት የሚ
ቀርብ ሁለት በሬ፣ አምስት አውራ
በግ፣ አምስት ተባዕት ፍየል እንዲ
ሁም አንድ ዓመት የሆናቸው አም
ስት ተባዕት የበግ ጠቦቶች ነበሩ፡፡
እንግዲህ የፍደሱር ልጅ ገማልኤል
ያቀረበው ስጦታ ይህ ነበር፡፡

60በዘጠነኛው ቀን የብንያም ሕዝብ አለቃ
የጋዴዮን ልጅ አቢዳን ስጦታውን አመጣ፤
61ስጦታውም፣ እያንዳንዱ ለእህል ቍር
ባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ ልም

ጹቄት የተሞላ በቤተ መቅደሱ ሰቅል
ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሚመዝን
የብር ሳሕንና ሰባ ሰቅል የሚመዝን ከብር
የተሠራ ጐድጓዳ ሳሕን፣ 62ዐሥር ሰቅል
የሚመዝን በዕጣን የተሞላ የወርቅ ጭልፋ፣
63ለሚቃጠል መሥዋዕት አንድ ወይፈን፣
አንድ አውራ በግ፣ አንድ ዓመት የሆ
ነው የበግ ጠቦት፣ 64ለኀጢአት መሥ
ዋዕት አንድ ተባዕት የፍየል ጠቦት፣
65እንዲሁም ለኅብረት መሥዋዕት የሚ
ቀርብ ሁለት በሬ፣ አምስት አውራ በግ፣
አምስት ተባዕት ፍየል እንዲሁም አንድ
ዓመት የሆናቸው አምስት ተባዕት የበግ
ጠቦቶች ነበሩ። እንግዲህ የጋዴዮን ልጅ
አቢዳን ያቀረበው ስጦታ ይህ ነበር።

66በአሥረኛው ቀን የዳን ሕዝብ አለቃ የአ
ሚሳዳይ ልጅ አኪዔዘር ስጦታውን አመጣ፤
67ስጦታውም፣ እያንዳንዱ ለእህል ቍር
ባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ ልም
ጹቄት የተሞላ በቤተ መቅደሱ ሰቅል
ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሚመዝን የብር
ሳሕንና ሰባ ሰቅል የሚመዝን ከብር
የተሠራ ጐድጓዳ ሳሕን፣ 68ዐሥር ሰቅል
የሚመዝን በዕጣን የተሞላ የወርቅ
ጭልፋ፣ 69ለሚቃጠል መሥዋዕት አንድ
ወይፈን፣ አንድ አውራ በግ፣ አንድ
ዓመት የሆነው የበግ ጠቦት፣ 70ለኀጢ
አት መሥዋዕት አንድ ተባዕት የፍየል
ጠቦት፣ 71እንዲሁም ለኅብረት መሥ
ዋዕት የሚቀርብ ሁለት በሬ፣ አምስት
አውራ በግ፣ አምስት ተባዕት ፍየል
እን ዲሁም አንድ ዓመት የሆናቸው
አምስት ተባዕት የበግ ጠቦቶች ነበሩ።
እንግዲህ የአሚሳዳይ ልጅ አኪዔዘር
ያቀረበው ስጦታ ይህ ነበር።

72በዐሥራ አንደኛው ቀን የአሴር ሕዝብ
አለቃ የኤክራን ልጅ ፋግኤል ስጦታ አመጣ፤
73ስጦታውም፣ እያንዳንዱ ለእህል ቍር
ባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ ልም
ጹቄት የተሞላ በቤተ መቅደሱ ሰቅል
ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሚመዝን የብር
ሳሕንና ሰባ ሰቅል የሚመዝን ከብር
የተሠራ ጐድጓዳ ሳሕን፣ 74ዐሥር ሰቅል
የሚመዝን በዕጣን የተሞላ የወርቅ
ጭልፋ፣ 75ለሚቃጠል መሥዋዕት አንድ
ወይፈን፣ አንድ አውራ በግ፣ አንድ
ዓመት የሆ ነው ተባዕት የበግ ጠቦት፣
76ለኀጢአት መሥዋዕት አንድ ተባዕት
የፍየል ጠቦት፣ 77እንዲሁም ለኅብረት
መሥዋዕት የሚቀርብ ሁለት በሬ፣
አምስት አውራ በግ፣ አምስት ተባዕት
ፍየል እንዲሁም አንድ ዓመት የሆና
ቸው አምስት ተባዕት የበግ ጠቦቶች
ነበሩ። እንግዲህ የኤክራን ልጅ ፋግ
ኤል ያቀረበው ስጦታ ይህ ነበር።

78በዐሥራ ሁለተኛው ቀን የንፍታሌም ሕዝብ
አለቃ የዔናን ልጅ አኪሬ ስጦታውን አመጣ፤
79ስጦታውም፣ እያንዳንዱ ለእህል ቍር
ባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ ልም
ጹቄት የተሞላ በቤተ መቅደሱ ሰቅል
ሚዛን መቶ ሠላሳ ሰቅል የሚመዝን የብር
ሳሕንና ሰባ ሰቅል የሚመዝን ከብር
የተሠራ ጐድጓዳ ሳሕን፣ 80ዐሥር ሰቅል
የሚመዝን በዕጣን የተሞላ የወርቅ
ጭልፋ፣ 81ለሚቃጠል መሥዋዕት አንድ
ወይፈን፣ አንድ አውራ በግ፣ አንድ ዓመት
የሆነው ተባዕት የበግ ጠቦት፣ 82ለኀጢ
አት መሥዋዕት አንድ ተባዕት የፍ
የል ጠቦት፣ 83እንዲሁም ለኅብረት
መሥዋዕት የሚቀርብ ሁለት በሬ፣
አምስት አውራ በግ፣ አምስት ተባዕት
የበግ ጠቦቶች ነበሩ። እንግዲህ የዔናን
ልጅ አኪሬ ያቀረበው ስጦታ ይህ
ነበር።

84መሠዊያው በተቀባ ቀን የእስራኤል አለ
ቆች የመሠዊያውን መቀደስ ምክንያት በማ
ድረግ ያቀረቡአቸው ስጦታዎች እነዚህ
ናቸው፤ ዐሥራ ሁለት የብር ሳሕኖች፣ ዐሥራ
ሁለት ከብር የተሠሩ ጐድጓዳ ሳሕኖ
ችና ዐሥራ ሁለት የወርቅ ጭልፋዎች፣
85እያንዳንዱ የብር ሳሕን መቶ ሠላሳ ሰቅል፣
እያንዳንዱም ጐድጓዳ ሳሕን ሰባ ሰቅል፣
ባጠቃላይም የብር ሳሕኖቹ ክብደት በመ
ቅደሱ ሰቅል ሚዛን ሁለት ሺህ አራት
መቶ ሰቅል ይመዝን† ነበር። 86ዕጣን የሞ
ላባቸው ዐሥራ ሁለቱ የወርቅ ጭልፋዎ
ችም እያንዳንዳቸው በመቅደሱ ሰቅል ሚዛን
ዐሥር ሰቅል መዘኑ፤ ባጠቃላይ የወርቅ ጭል
ፋዎቹ ክብደት አንድ መቶ ሃያ ሰቅል‡
ነበር። 87ለሚቃጠል መሥዋዕት የቀረቡት
እንስሳት የእህል ቊርባናቸውን ጨምሮ
ድምራቸው፦ ዐሥራ ሁለት ወይፈን፣ ዐሥራ
ሁለት አውራ በግ፣ ዐሥራ ሁለት አንድ
ዓመት የሆናቸው ተባዕት የበግ ጠቦቶች
ሆነ፤ እንዲሁም ለኀጢአት መሥዋዕት የቀ
ረቡ ዐሥራ ሁለት ተባዕት ፍየሎች ነበሩ።
88ለኅብረት መሥዋዕት የቀረቡት እንስሳት
ድምር ሃያ አራት በሬ፣ ሥልሳ አውራ በግ፣
ሥልሳ ተባዕት ፍየልና ሥልሳ አንድ ዓመት
የሆናቸው ተባዕት የበግ ጠቦቶች ነበር፤ እን
ግዲህ መሠዊያው ከተቀባ በኋላ ለመሠዊያው
መቀደስ የቀረቡ ስጦታዎች እነዚህ ናቸው።

†85 ሃያ ስምንት ኪ.ግ. ያህል ነው።
‡86 አንድ ኪ.ግ. ተኩል ያህል ነው።

7፥48 ዘኍ1፥10
7፥53 ዘኍ1፥10
7፥54 ዘኍ1፥10
7፥60 ዘኍ1፥11
7፥66 ዘኍ1፥12
7፥72 ዘኍ1፥13
7፥78 ዘኍ1፥15

7፥84 ቀኍ1፡10፡
14፤ዘኍ4፥14
7፥85 ቀኍ13
7፥86 ቀኍ13
7፥87 ቀኍ13፡15፡16
7፥88 ቀኍ1፡10፡
17፤ዘፍ32፥14
7፥89 ዘፀ40፥2፤
16፥34፤29፥42፤40፥2ዘ
ኍ3፥31፤መዝ80፥1፤9
9፥1

89ሙሴ ከእግዚአብሔር (ያህዌ) ጋር ለመነ
ጋገር ወደ መገናኛው ድንኳን በገባ ጊዜ
ከምስክሩ ታቦት መክደኛ በላይ በሁለቱ
ኪሩቤል መካከል ድምፅ ሲናገረው ሰማ፤
አነጋገረውም።

## የመብራቶቹ አቀማመጥ

8 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤
2“አሮንን ተናገረው፤ እንዲህም
በለው፤ ‘ሰባቱን መብራቶች በየቦታቸው
በምታስ ቀምጥበት ጊዜ በመቅረዙ ፊት
ለፊት ላለው አካባቢ ብርሃን ይሰጣሉ’ ”

3አሮንም እንዲሁ አደረገ፤ እግዚአብሐ
ር (ያህዌ) ሙሴን ባዘዘው መሠረት መብራ
ቶቹ በመቅረዙ ላይ ሆነው ፊት ለፊት
እንዲያ በሩ አስቀመጣቸው። 4የመቅረዙ
አሠራር እንዲህ ነበር፤ ከመቆሚያው እስከ
አበቦቹ ያለው ከተቀጠቀጠ ወርቅ የተሠራ
ሲሆን፣ የመቅረዙም አሠራር እግዚአብሐ
ር (ያህዌ) ለሙሴ ባሳየው መሠረት ነበር።

## የሌዋውያን ለአገልግሎት መለየት

5እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤
6“ሌዋውያኑን ከእስራኤላውያን መካከል ለይ
ተህ በሥርዐቱ መሠረት አንጻቸው። 7ስታ
ነጻቸውም እንዲህ አድርግ፤ በሚያነጻ ውሃ
እርጫቸው፤ ገላቸውን በሙሉ ተላጭተው
ልብሳቸውን ይጠቡ፤ በዚህም ይንጹ። 8በዘ
ይት ከተለወሰ ልም ዱቄት የእህል ቍርባን
ጋር አንድ ወይፈን ይውሰዱ፤ ከዚያም
ለኀጢአት መሥዋዕት የሚሆን ሌላ ወይ
ፈን አንተ ትወስዳለህ። 9ሌዋውያኑን ወደ
መገናኛው ድንኳን ፊት አምጣ፤ መላው
ንም የእስራኤል ማኅብረ ሰብ ሰብስብ፤
10ሌዋውያኑን በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት
አቅርብ፤ ከዚያም እስራኤላውያን እጃቸ
ውን ይጫኑባቸው። 11ከዚያም አሮን ሌዋ
ውያኑን የእግዚአብሔርን (ያህዌ) አገልግሎት
ለማከናወን ዝግጁ እንዲሆኑ ከእስራኤላ
ውያን መካከል እንደሚወዘወዝ መሥዋዕት
በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ያቅርባቸው።
12“ሌዋውያኑ እጃቸውን በወይፈኖቹ ራ
ስ ላይ ከጫኑ በኋላ ለሌዋውያኑ
ማስተስረያ ይሆኑ ዘንድ የኀጢአት
መሥዋዕት፣ ሌላ ውን የሚቃጠል
መሥዋዕት አድርገህ ለእ ግዚአብሔር (ያህዌ)
አቅርባቸው። 13ከዚያም ሌዋውያኑን
በአሮንና በልጆቹ ፊት አቁማ ቸው፤
እንደሚወዘወዝ መሥዋዕት አድርገ ህም
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) አቅርባቸው። 14በዚህ መ
ሠረት ሌዋውያኑን ከእስራኤላውያን ትለ
ያቸዋለህ፤ እነርሱም የእኔ ይሆናሉ።
15“ሌዋውያኑን ካነጻሐቸውና እንደሚወዘ
ወዝ መሥዋዕት አድርገህ ካቀረብሀቸው

8፥2 ዘፀ25፥37
8፥4 ዘፀ25፥9፡18፡36
8፥6 ዘሌ22፥2፤ ኢሳ1፥16፤52፥11
8፥7 ዘፍ35፥2፤ዘኍ6፥9፤19፥9፡17፤31፥23፤ ዘሌ14፥8፡9፤ ዘዳ21፥12
8፥8 ዘሌ2፥1፤ 4፥3፤ዘኍ15፥8-10
8፥9 ዘፀ40፥12፤ ዘሌ8፥3
8፥10 ዘሌ3፥2፤ ሐሥ6፥6
8፥11 ዘፀ29፥24
8፥12 ዘፀ29፥10፡ 36፤ዘሌ1፥3፤4፥3፤ ዘኍ6፥11
8፥13 ዘፀ29፥24
8፥14 ዘኍ3፥12
8፥15 ዘፀ29፥24፤ 40፥2
8፥16 ዘኍ1፥20፤ 3፥12
8፥17 ዘፀ4፥23፤ 13፥2፤22፥29
8፥18 ዘኍ3፥12
8፥19 ዘኍ3፥7፡ 9፤16፥46
8፥21 ቍ7፡12፤ ዘፍ35፥2፤ዘኍ16፥47
8፥22 ቍ11
8፥24 ዘፀ38፥21፤ 1ዜና23፥3
8፥25 ዘኍ4፥3
8፥26 ቍ11
9፥1 ዘፀ40፥2፤ ዘኍ1፥1
9፥2 ቍ7፤ዘፀ12፥11
9፥3 ዘፀ12፥6፡42፤ 12፥2-11፡43-49፤ ዘሌ23፥5-8፤ ዘዳ 16፥1-8

በኋላ አገልግሎታቸውን ለመፈጸም ወደ
መገናኛው ድንኳን ይመጣሉ፤ 16እነርሱም
ሙሉ በሙሉ የእኔ እንዲሆኑ የተሰጡኝ
እስራኤላውያን ናቸው፤ ከማንኛዪቱም እስ
ራኤላዊት በተወለደ በኵር ወንድ ልጅ
ምትክ የራሴ እንዲሆኑ ወስጃቸዋለሁ።
17ከሰውም ሆነ ከእንስሳ በእስራኤል የተወ
ለደ ማንኛውም በኵር ተባዕት የእኔ ነው፤
በግብፅ የነበረውን በኵር ሁሉ በመታሁ ጊዜ
የእኔ እንዲሆኑ ለይቻቸዋለሁ። 18በእስራ
ኤል በተወለዱት ተባዕት በኵሮች ሁሉ
ምትክም ሌዋውያኑን ወስጃለሁ። 19እስራ
ኤላውያንን ወክለው በመገናኛው ድንኳን
ውስጥ የሚፈጸመውን አገልግሎት እንዲያከ
ናውኑና እስራኤላውያን ወደ ተቀደሰው
ስፍራ ቢቀርቡ እንዳይቀሠፉ ያስተሰርዩ
ላቸው ዘንድ፣ ከእስራኤላውያን ሁሉ መካ
ከል ሌዋውያኑን ስጦታ አድርጌ ለአሮንና
ለልጆቹ ሰጥቻቸዋለሁ።”

20ሙሴና አሮን እንዲሁም የእስራኤል
ማኅበረ ሰብ ሁሉ እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን
ባዘዘው መሠረት በሌዋውያኑ አደረጉ።
21ሌዋውያኑ ራሳቸውን አነጹ፤ ልብሶቻቸ
ውንም አጠቡ፤ ከዚያም አሮን እንደሚወዘ
ወዝ መሥዋዕት በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት
አቀረባቸው፤ እንዲነጹም ማስተስረያ አደ
ረገላቸው። 22ከዚህ በኋላ ሌዋውያኑ በአሮ
ንና በልጆቹ ኀላፊነት ሥር ሆነው ድንኳን
ውስጥ የሚፈጸመውን አገልግሎት ለማከናወን
ገቡ። እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን ባዘዘው
መሠረት አስፈላጊውን በሌዋውያኑ አደረጉ።
23እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤
24“ሌዋውያንን የሚመለከተው ደንብ ይህ
ነው፤ በመገናኛው ድንኳን አገልግሎት ለመሳ
ተፍ ሃያ አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ
የሆናቸው ወንዶች ይመጣሉ፤ 25ዕድሜያ
ቸው አምሳ ዓመት ሲሞላ ግን መደበኛ
አገልግሎታቸውን ይተዉ፤ ዳግም ሥራ
አይሥሩ። 26ከዚያ በኋላ ወንድሞቻቸው
በመገናኛው ድንኳን ሥራቸውን በሚያከና
ውኑበት ጊዜ ያግዟቸዋል እንጂ ራሳቸው
መሥራት የለባቸውም። ኀላፊነታቸውን
እንዲወጡ የምታሰማራቸው በዚህ መልኩ
ነው።”

## የፋሲካ በዓል

9 ከግብፅ ምድር በወጡ በሁለተኛው
ዓመት፣ በመጀመሪያው ወር እግዚአ
ብሔር (ያህዌ) ሙሴን በሲና ምድረ በዳ ተና
ገረው፤ እንዲህም አለው፤ 2“እስራኤላው
ያን በተወሰነው ጊዜ የፋሲካን በዓል እንዲ
ያከብሩ አድርግ፤ 3በዓሉንም በዚህ ወር
በዐሥራ አራተኛው ቀን ፀሓይ በምትጠል

ቅበት ጊዜ በተወሰነው ሕግና ሥርዐት
መሠረት ሁሉ አክብሩ።”
4ስለዚህ ሙሴ ፋሲካን እንዲያከብሩ ለእ
ስራኤላውያን ነገራቸው፤ 5እነርሱም በመጀ
መሪያው ወር፣ በዐሥራ አራተኛውም
ቀን ፀሓይ በምትጠልቅበት ጊዜ በሲና
ምድረ በዳ ፋሲካ አደረጉ፤ እስራኤላውያን
እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን ባዘዘው መሠ
ረት ሁሉንም አደረጉ።
6አንዳንዶቹ ግን የሰው ሬሳ በመንካታ
ቸው በሥርዐቱ መሠረት ረክሰው ስለ ነበር
በዚያን ዕለት የፋሲካን በዓል ማክበር አል
ቻሉም፤ ስለዚህም በዚያኑ ዕለት ወደ ሙሴና
ወደ አሮን መጥተው፣ 7ሙሴን፣ “በሬሳ
ምክንያት ረክሰናል፤ ታዲያ የእግዚአብሔ
ርን (ያህዌ) መሥዋዕት ከሌሎቹ እስራኤላው
ያን ጋር ሆነን በተወሰነው ጊዜ እንዳናቀ
ርብ ለምን እንከለከላለን?” አሉት።
8ሙሴም፣ “እግዚአብሔር (ያህዌ) ስለ እና
ንተ የሚያዘውን እስካውቅ ድረስ ጠብቁ”
ሲል መለሰላቸው።
9ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እን
ዲህ አለው፤ 10“እስራኤላውያንን እንዲህ
በላቸው፤ ‘ከእናንተ ወይም ከዘሮቻችሁ ማን
ኛውም ሰው በሬሳ ምክንያት ቢረክስ ወይም
ሩቅ መንገድ ቢሄድ የእግዚአብሔርን (ያህዌ)
ፋሲካ ማክበር ይችላል፤ 11ይህንም በሁለ
ተኛው ወር፣ በዐሥራ አራተኛው ቀን ፀሓይ
በምትጠልቅበት ጊዜ ያክብሩ፤ የፋሲካውንም
በግ እርሾ ከሌለበት ቂጣና ከመራራ ቅጠል
ጋር ይብሉት። 12እስኪ ነጋ ድረስ ከዚህ ምንም
አያስተርፉ፤ ከዐጥንቱም ምንም አይስበሩ፤ ፋሲ
ካን በሚያከብሩበት ጊዜ ሥርዐቱን በሙሉ
መጠበቅ አለባቸው። 13በሥርዐቱም መሠ
ረት ንጹሕ የሆነ ወይም ሩቅ መንገድ ያል
ሄደ ሰው ፋሲካን ሳያከብር ቢቀር፣ ያ
ሰው የእግዚአብሔርን (ያህዌ) መሥዋዕት
በተወሰነው ጊዜ አላቀረበምና ከወገኖቹ ፈጽሞ
ይለይ፤ ያም ሰው የኀጢአቱን ዋጋ ይቀ
በላል።
14“ ‘በመካከላችሁ የሚኖር መጻተኛ የእ
ግዚአብሔርን (ያህዌ) ፋሲካ ለማክበር ቢፈ
ልግ በሕጉና በሥርዐቱ መሠረት መፈጸም
አለበት፤ ለመጻተኛውም ሆነ ለአገሬው ተወ
ላጅ የሚኖራችሁ ሕግ አንድ ይሁን’ ”

## ከማደሪያው በላይ የነበረው ደመና

15ማደሪያው በተተከለ ዕለት ደመናው
የምስክሩን ድንኳን ሸፈነው፤ ከምሽት
እስከ ንጋት ድረስ ማደሪያውን የሸፈነው
ደመና እሳት ይመስል ነበር። 16ይህ በዚህ
ሁኔታ ቀጠለ፤ ደመናው ማደሪያውን ሸፈ
ነው፤ በሌሊትም የእሳት መልክ ነበረው።

9፥4 ቍ2፤ዘፀ12፥11
9፥5 ቍ1፡3፤ ዘፀ12፥6
9፥6 ዘፀ18፥15፤ ዘሌ5፥3፤13፥3፤21፥11፤ ዘኍ27፥2
9፥7 ቍ2
9፥8 ዘፀ18፥15፤ ዘሌ24፥12፤ዘኍ15፥34፤27፥5፡21፤መዝ 85፥8
9፥10 ቍ6፤ 2ዜና30፥2
9፥11 ዘፀ12፥6፡8
9፥12 ቍ3፤ዘፀ12፥8፡46፤ዮሐ19፥36
9፥13 ዘፍ17፥14
9፥14 ዘፀ12፥19፡43
9፥15 ዘፀ13፥21፤ 26፥30፤33፥16፤ 38፥21
9፥16 ዘፀ40፥38
9፥17 ቍ21፤ 1ቆሮ10፥1
9፥18 ዘፀ40፥37
9፥19 ዘፀ40፥37፤ ዘሌ8፥35
10፥2 ቍ8፡9፤ዘኍ 31፥6፤33፥3፤ነህ4፥18፤12፥35፤መዝ47፥5፤ 98፥6፤150፥3፤ኤር4፥5፡19፤6፥1፤ሆሴ5፥8፤ 8፥1፤አሞ3፥6፤ ኢል2፥1፡15
10፥4 ዘፀ18፥21
10፥5 ቍ14
10፥6 ቍ18
10፥7 ኤር4፥5፤6፥1፤ሕዝ33፥3፤ኢል2፥1፤1ቆሮ14፥8
10፥8 ዘፍ9፥12፤ ዘኍ15፥14፤35፥29
10፥9 ዘፍ8፥1፤ዘፀ3፥9፤ዘሌ23፥24፤መሳ2፥18፤6፥9፤1ሳሙ10፥18፤2ነገ13፥4፤2ዜና13፥12፤መዝ106፥4፡42

17ደመናው ከድንኳኑ ላይ በሚነሣበት ጊዜ
እስራኤላውያን ጕዞአቸውን ይጀምሩ ነበር፤
ደመናው በሚቆምበት ቦታ ደግሞ ይሰፍሩ
ነበር፤ 18እስራኤላውያን ጕዞ የሚጀምሩ
ትም ሆነ የሚሰፍሩት በእግዚአብሔር (ያህዌ)
ትእዛዝ ነበር። ደመናው በድንኳኑ ላይ
በሚቈይበት ጊዜ ሁሉ ከሰፈር አይንቀ
ሳቀሱም ነበር። 19ደመናው በድንኳኑ ላይ
ብዙ ቀን ቢቈይም እስራኤላውያን የእግዚ
አብሔርን (ያህዌ) ትእዛዝ ይጠብቃሉ እንጂ
ተነሥተው አይጓዙም። 20አንዳንድ ጊዜ
ደመናው በድንኳኑ ላይ የሚቈየው ለጥ
ቂት ቀን ብቻ ነበር፤ በእግዚአብሔር (ያህዌ)
ትእዛዝ ይሰፍራሉ፤ በእግዚአብሔር (ያህዌ) ትእ
ዛዝ ጕዞ ይጀምራሉ፤ 21አንዳንድ ጊዜ ደግሞ
ደመናው ከምሽት እስከ ንጋት ብቻ ይቈ
ያል፤ ደመናው ንጋት ላይ ሲነሣም ጕዞአ
ቸውን ይጀምራሉ፤ ቀንም ይሁን ሌሊት
ደመናው ከተነሣ ጕዞ ይጀምራሉ። 22ደመ
ናው በድንኳኑ ላይ ለሁለት ቀንም ይሁን
ለወር ወይም ለዓመት ቢቈይ፣ እስራኤላ
ውያን በሰፈር ይቈያሉ እንጂ ጕዞአቸውን
አይቀጥሉም። 23በእግዚአብሔር (ያህዌ) ትእ
ዛዝ ይሰፍራሉ፤ በእግዚአብሔርም (ያህዌ)
ትእዛዝ ይጓዛሉ፤ እነርሱም በሙሴ አማካ
ይነት የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ትእ
ዛዝ ይጠብቁ ነበር።

## የብር መለከቶች

10 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2“ከተቀጠቀጠ ብር ሁለት
መለከት አብጅ፤ ማኅበረ ሰቡን ለመጥሪ
ያና ከሰፈራቸው እንዲነሡም ለመቀስቀሻ
አድርጋቸው። 3ሁለቱ መለከቶች ሲነፉ
ማኅበረ ሰቡ በሙሉ በመገናኛው ድንኳን
ደጃፍ አንተ ዘንድ ይሰብሰብ፤ 4ነገር ግን
አንዱ መለከት ብቻ ከተነፋ አለቆች ማለት
የእስራኤል ጐሣ መሪዎች አንተ ዘንድ
ይሰብሰቡ፤ 5መለከቱ ከፍ ባለ ድምፅ ሲነፋ
በስተ ምሥራቅ የሰፈሩት ነገዶች ጕዞ ይጀ
ምሩ፤ 6መለከቱ ከፍ ባለ ድምፅ ለሁለተኛ
ጊዜ ሲነፋ በስተ ደቡብ የሰፈሩት ነገዶች
ጕዞ ይጀምሩ፤ ከፍ ያለው ድምፅ ጕዞ ለመ
ጀመር ምልክት ይሆናል። 7ማኅበሩን ለመ
ሰብሰብ መለከቶች ይነፉ፤ ነገር ግን ድምፁ
አይጩኽ።
8“መለከቶቹን ካህናቱ የአሮን ልጆች ይንፉ፤
ይህም ለእናንተና ለሚመጡት ትውልድ
የዘላለም ሥርዐት ይሁን። 9በገዛ ምድራ
ችሁ በግፍ በመጣባችሁ ጠላት ላይ ስት
ዘምቱ መለከቶቹን ከፍ ባለ ድምፅ ንፉ፤
በእግዚአብሔር (ያህዌ) በአምላካችሁ (ኤሎሂም)
ትታሰ ባላችሁ፤ ከጠላታችሁም እጅ

ትድናላችሁ:: [10]እንዲሁም በደስታችሁ
ቀናት ማለት በተ ደነገጉት በዓሎቻችሁና
የወር መባቻ በዓል ስታከብሩ በሚቃጠል
መሥዋዕታችሁና በኅብ ረት መሥዋዕ
ታችሁ[ኀ] ላይ መለከቱን ንፉ፤ እነዚህም
በአምላካችሁ (ኤሎሂም) ፊት መታሰቢያ
ይሆኑላ ችኋል:: እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ)
አምላካችሁ (ኤሎሂም) ነኝ::”

### እስራኤላውያን ከሲና ተነሡ

[11]በሁለተኛው ዓመት፣ ሁለተኛው ወር በገባ
በሃያኛው ቀን ደመናው ከምስክሩ ማደሪያ
ላይ ተነሣ:: [12]ከዚያም እስራኤላውያን ከሲና
ምድረ በዳ ተነሥተው ደመናው በፋራን
ምድረ በዳ እስኪያርፍ ድረስ ከአንዱ ቦታ
ወደ ሌላው ቦታ ተጓዙ:: [13]እግዚአብሔር
(ያህዌ) በሙሴ አማካይነት በሰጠው ትእዛዝ
መሠረትም ለመጀመሪያ ጊዜ ተጓዙ::
[14]በመጀመሪያ የይሁዳ ሰፈር ሰራዊት
በዐርማቸው ሥር ሆነው ተጓዙ፤ አለቃ
ቸውም የአሚናዳብ ልጅ ነአሶን ነበር::
[15]የይሳኮር ነገድ ሰራዊት አለቃም የሰገር
ልጅ ናትናኤል ነበር:: [16]እንዲሁም የዛብሎን
ነገድ ሰራዊት አለቃ የኬሎን ልጅ ኤል
ያብ ነበር:: [17]ከዚህ በኋላ ማደሪያው ተነ
ቀለ፤ ድንኳኑን የተሸከሙት ጌድሶናውያ
ንና ሜራሪያውያንም ጕዞ ጀመሩ::
[18]ቀጥሎም የሮቤል ሰፈር ሰራዊት በዐር
ማቸው ሥር ሆነው ተጓዙ፤ አለቃቸ
ውም የሰዲዮር ልጅ ኤሊሱር ነበር::
[19]የስምዖን ነገድ ሰራዊት አለቃም የሱሪሰ
ዳይ ልጅ ሰለሚኤል ነበር:: [20]እንዲሁም
የጋድ ነገድ ሰራዊት አለቃ የራጉኤል ልጅ
ኤሊሳፍ ነበር:: [21]ከዚህ በኋላ ቀዓታውያን
ንዋያተ ቅዱሳቱን ተሸክመው ተጓዙ፤ እነ
ርሱ ከመድረሳቸው በፊት ማደሪያው ተተ
ክሎ ነበር::
[22]ቀጥሎም የኤፍሬም ሰፈር ሰራዊት
በዐርማቸው ሥር ሆነው ተጓዙ፤ አለቃቸ
ውም የዓሚሁድ ልጅ ኤሊሳማ ነበር:: [23]እን
ዲሁም የምናሴ ነገድ ሰራዊት አለቃ የፍ
ዳሱር ልጅ ገማልኤል ነበር:: [24]የብንያም
ነገድ ሰራዊት አለቃም የጋዴዮን ልጅ
አቢዳን ነበር::
[25]በመጨረሻም የዳን ሰፈር ሰራዊት ለሁ
ሉም ክፍሎች የኋላ ደጀን በመሆን በዐር
ማቸው ሥር ተጓዙ፤ አለቃቸውም የአሚሳ
ዳይ ልጅ አኪዔዘር ነበር:: [26]እንዲሁም
የአሴር ነገድ ሰራዊት አለቃ የኤክራን
ልጅ ፋግኤል ነበር:: [27]እንዲሁም የንፍታ
ሌም ነገድ ሰራዊት አለቃ የዔናን ልጅ
አኪሬ ነበር:: [28]እንግዲህ የእስራኤል ሰራ
ዊት የጕዞ አሰላለፍ ሥርዐት ይህ ነበር::

10፥10 ዘሌ1፥3፤3፥1፤11፥44፤23፥24፤ ዘኍ6፥14፤28፥11፤ 1ሳሙ20፥5፡24፤2ነገ4፥23፤2ዜና8፥13፤ መዝ81፥3፤ኢሳ1፥13፤ሕዝ45፥17፤46፥6፤ አሞ8፥5
10፥11 ዘፀ38፥21፤ 40፥17፤ዘኍ9፥17
10፥12 ዘፍ14፥6፤ ዘዳ1፥1፤33፥2
10፥13 ዘዳ1፥6
10፥14 ዘኍ1፥7፡ 52፤2፥3-9
10፥15 ዘሌ24፥11፤ ዘኍ1፥8
10፥16 ዘኍ1፥9፤2፥7
10፥17 ቍ21፤ ዘኍ4፥21-32
10፥18 ዘኍ1፥5፤ 2፥10-16
10፥19 ዘኍ1፥6
10፥20 ዘኍ1፥14
10፥21 ቍ17፤ ዘኍ2፥17፤4፥20
10፥22 ዘኍ1፥10፤ 2፥24
10፥23 ዘኍ1፥10
10፥24 ዘኍ1፥11
10፥25 ዘኍ1፥12፤ 2፥31
10፥26 ዘኍ1፥13
10፥27 ዘኍ1፥15
10፥29 ዘፍ12፥7፤ 15፥14፤ዘፀ2፥18፤ 3፥1፤መሳ4፥11
10፥30 ዘፀ18፥27፤ ማቴ21፥29
10፥31 ኢዮ29፥15
10፥32 ዘፀ12፥48፤ ዘዳ10፥18፤መዝ22፥27-31፤67፥5-7
10፥33 ቍ12፤ ዘዳ1፥33፤10፥8፤31፥9፤ ኢሱ3፥3፤መሳ20፥27፤2ሳሙ15፥24፤ ኤር31፥2
10፥34 ዘኍ9፥15-23
10፥35 ዘዳ5፥9፤ 7፥10፤32፥41መሳ5፥31፤ሳሙ2፥1፤2ዜና6፥41፤መዝ17፥13፤44፥26፤68፥1፤2፤9፤92፤94፥2፤132፤8፤1ኢሳ 17፥12-14፤59፥18
10፥36 ዘፍ15፥5፤ 26፥4፤ዘዳ1፥10፤10፥22፤ነህ 9፥23፤ኢሳ 52፥8፤63፥17
11፥1 ዘፀ4፥14፤14፥11፤16፥7፤ዘሌ10፥2፤ ዘኍ12፥2፤21፥28፤ዘዳ 1፥34፤መዝ፤78፤63፤ ኢሳ26፥11፤ሰቆ3፥39
11፥2 ዘፍ20፥7፤ ዘኍ21፥7፤ዘዳ9፥19፡20፤ 1ሳሙ2፥25፤12፥23፤ መዝ106፥23፤ዮና2፥1
11፥3 ዘዳ9፥22፤ ዘኍ16፥35፤

[29]በዚህ ጊዜ ሙሴ የሚስቱን አባት የም
ድያማዊውን የራጉኤልን ልጅ ኦባብን፣ “እነሆ፤
እግዚአብሔር፣ (ያህዌ) ‘እሰጣችኋለሁ’ ወዳለን
ምድር ጕዞ ጀምረናል፤ በመልካም ሁኔታ
ስለምናኖርህ ከእኛ ጋር ሂድ፤ እግዚአብሔር
(ያህዌ) ለእስራኤል በጎ ነገር ለማድረግ ቃል
ገብቶአልና አለው::”
[30]እርሱም መልሶ፣ “ይህስ አይሆንም፤ አል
ሄድም፤ ወደ አገሬና ወደ ወገኖቼ ተመ
ልሼ እሄዳለሁ” አለው::
[31]ሙሴ ግን እንዲህ አለ፤ “እባክህ
አትለ የን፤ በምድር በዳ ውስጥ የት
መስፈር እንደሚገባን አንተ ታውቃለህ፤ ዐ
ይናችንም ትሆናለህ:: [32]ከእኛ ጋር ብትሄድ
እግዚአብሔር (ያህዌ) ከሚያደርግልን መልካም
ነገር ሁሉ እኛም እናደርግልሃለን::”
[33]ስለዚህ ከእግዚአብሔር (ያህዌ) ተራራ
ተነሥተው የሦስት ቀን መንገድ ተጓዙ፤
የእግዚአብሔር (ያህዌ) ቃል ኪዳን ታቦትም
በእነዚያ ሦስት ቀናት ውስጥ የሚያረፉ
በትን ቦታ በመፈለግ ፊት ፊታቸው ይሄድ
ነበር:: [34]ከሰፈራቸው በሚነሡበት ጊዜ የእ
ግዚአብሔር (ያህዌ) ደመና ቀን ቀን ከላያቸው
ነበር::
[35]ታቦቱ ለጕዞ በተነሣ ጊዜ ሁሉ ሙሴ፣
“እግዚአብሔር (ያህዌ) ሆይ፤ ተነሥ!
ጠላቶችህ ይበተኑ፤
የሚጠሉህም ከፊትህ ይሸሹ” ይል ነበር::
[36]ባረፉ ጊዜም፣
“እግዚአብሔር (ያህዌ) ሆይ፤
በብዙ ሺህ ወደሚቈጠሩት
እስራኤላውያን ተመለስ” ይል ነበር::

### ከእግዚአብሔር የወረደ እሳት

11 በዚህ ጊዜ ሕዝቡ ስለ ደረሰባቸው
ችግር በእግዚአብሔር (ያህዌ) ላይ
አጕ ረመረሙ፤ እግዚአብሔርም (ያህዌ)
ማጕረም ረማቸውን በሰማ ጊዜ በጣም
ተቈጣ፤ ከዚያም የእግዚአብሔር (ያህዌ)
እሳት በመካከላ ቸው ነደደች፤ ከሰፈሩም
ዳርቻ ጥቂቱን በላች:: [2]ሕዝቡ ወደ ሙሴ
ጮኸ፤ ሙሴም ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ)
ጸለየ፤ እሳቲቱም
ጠፋች:: [3]ከዚህ የተነሣም የቦታው ስም፣
“ተቤራ”[ነ] ተባለ፤ የእግዚአብሔር (ያህዌ) እሳት
በመካከላቸው ነዳለችና::

### እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የላከላቸው ድርጭት

[4]ድብልቁ ሕዝብ ሌላ ምግብ ጐመጀ፤
እስራኤላውያንም እንዲህ እያሉ ያጕረመ
ርሙ ጀመር፤ “ምነው የምንበላው ሥጋ

[ኀ]10 በተለምዶ የድነት መሥዋዕት ማለት ነው
[ነ]3 ተቤራ ማለት ማቃጠል ማለት ነው

ባገኘን ኖሮ! 5በግብፅ ያለምንም ዋጋ የበላ
ነው ዓሣ እንዲሁም ዱባው፣ በጢኹ፣ ኵራቱ፣
ነጭ ሽንኩርቱ ትዝ ይለናል፡፡ 6አሁን ግን
የምግብ ፍላጎታችን ጠፍቶአል፤ ከዚህ መና
በስተቀር የምናየው የለም!”

7መናው እንደ ድንብላል ዘር ትንንሽ ሆኖ
የሙጫ መልክ ነበረው፡፡ 8ሕዝቡ ተዘዋውሮ
በመልቀም በወፍጮ ከፈጨ ወይም በሙ
ቀጫ ከወቀጠ በኋላ በምንቸት ይቀቅለው
ወይም ይጋግረው ነበር፤ ጣዕሙም በወይራ
ዘይት የተጋገረ ያህል ይጣፍጥ ነበር፡፡ 9ጤዛው
ሌሊት በሰፈር ላይ በሚወርድበት ጊዜ መና
ውም እንዲሁ ይወርድ ነበር፡፡

10ሙሴ፣ ሕዝቡ ሁሉ በየቤተ ሰቡ፣ በየድን
ኳኑ ደጃፍ ሆኖ ሲያለቅስ ሰማ፡፡ *እግዚአ
ብሔርም* (ያህዌ) እጅግ ተቈጣ፤ ሙሴም
ተጨነቀ፡፡ 11እርሱም *እግዚአብሔርን* (ያህዌ)
እንዲህ ሲል ጠየቀው፤ “እንዲህ ያለውን
መከራ በባሪያህ ላይ ለምን አመጣህ? የዚ
ህን ሕዝብ ሁሉ ሸክም የጫንህብኝስ ምን
አስቀይሜህ ነው? 12ይህን ሁሉ ሕዝብ የፀነስ
ሁት እኔ ነኝን? እኔስ ወለድሁትን? ታዲ
ያ ሞግዚት ሕፃን እንደምትታቀፍ በክንዴ
ታቅፌ ለቀድሞ አባቶቻቸው ትሰጣቸው
ዘንድ በመሐላ ቃል ወደ ገባህላቸው ምድር
እንዳስገባቸው የምትነግረኝ ለምንድነው?
13ለዚህ ሁሉ ሕዝብስ ሥጋ ከወዴት አመ
ጣለሁ? ሁሉም ‘የምንበላው ሥጋ ስጠን’
እያሉ ያለቅሱብኛል፡፡ 14እጅግ ከብዶኛልና
ይህን ሁሉ ሕዝብ ብቻዬን ልሸከም አልች
ልም፡፡ 15እንዲህስ ከምታደርገኝ በፊትህ
ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ አሁኑኑ ግደለኝ፤
የሚደርስብኝን ጥፋት አልይ፡፡”

16*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤
“በሕዝቡ መካከል በመሪነትና በአልቅና ብቃት
አላቸው የምትላቸውን ሰባ የእስራኤል ሽማ
ግሌዎች አምጣልኝ፤ ካንተም ጋር ይቆሙ
ዘንድ ወደ መገናኛው ድንኳን እንዲመጡ
አድርግ፡፡ 17ወደዚያም ወርጄ አነጋግርሃ
ለሁ፤ ባንተ ላይ ካለው መንፈስ ወስጄ
በእነርሱ ላይ አደርጋለሁ፤ የሕዝቡንም ሸክም
ብቻህን እንዳትሸከም እነርሱ ያግዙሃል፡፡

18“ለሕዝቡ እንዲህ ብለህ ንገራቸው፤
‘ነገ ሥጋ ትበላላችሁና ራሳችሁን በመቀ
ደስ ተዘጋጁ’፡፡ “በግብፅ ተመችቶን ነበር፤
አሁን ግን ሥጋ ማን ይሰጠናል!” ብላችሁ
ያለቀሳችሁትን *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሰምቶ
አል፤ ስለዚህ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሥጋ ይሰ
ጣችኋል፤ እናንተም ትበላላችሁ፡፡ 19የምት
በሉትም ለአንድ ወይም ለሁለት ቀን
ወይም ለአምስት፣ ለዐሥር ወይም ለሃያ
ቀን አይደለም፤ 20ነገር ግን በአፍንጫችሁ

ኢዮ1፥16፤ኢሳ10፥17
11፥4 ቍ18፤ዘፀ16፥3
11፥5 ዘፀ16፥3፤
ዘኍ21፥5
11፥6 ዘፀ16፥14
11፥7 ዘፍ2፥12፤ዘፀ
16፥31 11፥8 ዘፀ
16፥16
11፥9 ዘፀ16፥13
11፥10 ቍ4
11፥11 ዘፍ34፥30፤
ዘፀ5፥22፤18፥18
11፥12 ዘፍ12፥7፤
ዘፀ13፥5፤ዘኍ14፥16፤
ኢሳ40፥11፤49፥23፤
66፥11፡12
11፥13 ዘፀ12፥37፤
ዮሐ6፥5-9
11፥14 ዘፀ18፥18
11፥15 ዘፀ32፥32፤
1ነገ19፥4፤ኢዮ6፥9፤
7፥15-16፤9፥21፤
10፥1፤ኢሳ38፥12፤
ዮና4፥3
11፥16 ዘፀ3፥16፤
18፥25፤40፥2
11፥17 ቍ25፡29፤
ዘፀ18፥18፤19፥20፤
1ሳሙ10፥6፤2ነገ2፥9፡
15፤3፥12፤ኢሳ32፥15፤
40፥5፤63፥11፤ኤር19፥
1፤ኢል 2፥28፤ሐጌ
2፥5
11፥18 ዘፀ16፥7፤
19፥10፤መዝ78፥20፤ሐ
ሥ7፥39
11፥20 ቍ33፤
ዘሌ26፥43፤ኢሱ24፥
27፤መሳ8፥23፤1ሳሙ
10፥19፤ኢዮ20፥13፡
23፤31፥28፤መዝ78፥
29፤106፥14፡15፤ኢሳ
59፥13፤ሆሴ13፥11

11፥21 ዘፀ12፥37
11፥22 ማቴ15፥33
11፥23 ዘኍ23፥19፤
1ሳሙ15፥29፤ኢሳ
50፥2፤59፥1፤ሕዝ
12፥25፤24፤14
11፥25 ቍ17፡26፡
29፤ዘፀ19፥9፤ዘኍ12፥
5፤24፥2፤መሳ3፥10፤
1ሳሙ10፥6፡10፤
19፥20፤23፤2ዜና
15፥1ሐሥ2፥17
11፥26 ቍ25፤1ዜና
12፥18፤ራእ1፥10
11፥28 ዘፀ17፥9፤
33፥11፤ዘኍ13፥8፤26፥
65፤ኢሱ1፥1፤14፥
10፤ ማር9፥38-40
11፥29 ቍ17፤ዘኍ
27፥18፤1ሳሙ10፥5፤
19፥20፤2ዜና24፥19፤አ
ር7፥25፤44፥4፤
1ቆሮ14፥5
11፥31 ዘፀ16፥13፤
መዝ78፥26-28

እስኪወጣና እስኪያንገፈግፋችሁ ድረስ ወር
ሙሉ ትበሉታላችሁ፤ በመካከላችሁ ያለ
ውን *እግዚአብሔርን* (ያህዌ) ንቃችሁ በፊቱ፣
“ለምን ከግብፅ ወጣን?” ብላችሁ አልቅሳ
ችኋልና፡፡”

21ሙሴ ግን እንዲህ አለ፤ “እነሆ እኔ
በስድስት መቶ ሺህ እግረኛ መካከል እገ
ኛለሁ፤ አንተ ደግሞ ‘ወር ሙሉ የሚበሉ
ትን ሥጋ እኔ እሰጣቸዋለሁ!’ ብለሃል፤
22ታዲያ ስንት የበግ፣ የፍየልና የከብት
መንጋ ቢታረድላቸው ይበቃ ይሆን? በባሕር
ያለው ዓሣ ሁሉ ቢያዝ ሊዳረሳቸው ይችላ
ልን?”

23*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) ለሙሴ፣ “በውኑ
*የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ክንድ ይህን ያህል አጭር
ነውን? የነገርሁህ ቃል እውነት መሆን
አለ መሆኑን አሁኑኑ ታየዋለህ” ሲል መለ
ሰለት፡፡

24ሙሴም ወጣና *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ያለ
ውን ለሕዝቡ ነገራቸው፤ ከሕዝቡም ሽማግ
ሌዎች ሰባውን ሰብስቦ በድንኳኑ ዙሪያ
እንዲቆሙ አደረጋቸው፡፡ 25ከዚያም *እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) በደመና ወርዶ ተናገረው፤
በሙሴ ላይ ከነበረውም መንፈስ ወስዶ በሰ
ባው ሽማግሌዎች ላይ አሳደረባቸው፤ መን
ፈሱ ባደረባቸውም ጊዜ ትንቢት ተናገሩ፤
ከዚያ በኋላ ግን አልደገሙትም፡፡ኘ

26ኤልዳድና ሞዳድ የተባሉ ሁለት ሰዎች
ግን ሰፈር ውስጥ ቀርተው ነበር፤ እነ
ርሱም ከሽማግሌዎቹ ጋር ተቈጥረው ሳለ
ወደ ድንኳኑ አልሄዱም ነበር፤ ሆኖም የእ
ግዚአብሔር መንፈስ በእነርሱም ላይ ስላ
ደረባቸው ሰፈር ውስጥ እያሉ ትንቢት
ተናገሩ፡፡ 27አንድ ወጣትም ሮጦ በመሄድ፣
“ኤልዳድና ሞዳድ ሰፈር ውስጥ ትንቢት
ይናገራሉ” ብሎ ለሙሴ ነገረው፡፡

28ከወጣትነቱ ጀምሮ የሙሴ ረዳት የነበ
ረው የነዌ ልጅ ኢያሱም ተነሥቶ፣ “ጌታዬ
ሙሴ ሆይ፤ ከልክላቸው እንጂ!” ሲል ተናገረ፡፡

29ሙሴ ግን መልሶ፣ “ስለ እኔ ተቈርቍ
ረህ ነውን? *የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ሕዝብ ሁሉ
ነቢያት ቢሆኑ፣ *እግዚአብሔርም* (ያህዌ)
መንፈሱን ቢያሳድርባቸው ምንኛ ደስ
ባለኝ!” አለ፤ 30ከዚያም ሙሴና የእስራኤል
ሽማግሌዎች ወደ ሰፈር ተመለሱ፡፡

31በዚህ ጊዜ ነፋስ *ከእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ዘንድ ወጥቶ ድርጭቶችን ከባሕር ወደ
ሰፈር አመጣ፤ በየአቅጣጫውም ከፍታው
ሁለት ክንድ፣ኣ ርቀቱም የአንድ ቀን መን
ገድ ያህል እስኪሆን ድረስ በሰፈሩ ዙሪያ

ኘ25 *ትንቢት ተናገሩ፤ ከዚያ በኋላም ትንቢት መናገራቸውን አላቆሙም* የሚሉ አሉ፡፡ ኣ31 አንድ ሜትር ያህል ነው፡፡

ከመራቸው፤ 32በዚያን ዕለት ቀንና ሌሊቱን
በሙሉ፣ በማግሥቱም ሙሉውን ቀን እን
ደዚሁ ሕዝቡ ወጥቶ ድርጭቶች ሰበሰበ፤
ከዐሥር የቆሮስ[ከ] መስፈሪያ ያነሰ የሰበሰበ
ማንም አልነበረም፤ የሰበሰቡትንም በሰፈሩ
ዙሪያ ሁሉ አሰጡት። 33ነገር ግን ሥጋው
ገና በጥርስና በጥርሳቸው መካከል ሳለ አላ
ምጠው ሳይውጡት *የእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ቍጣ በላያቸው ነደደ፤ እግዚአብሔርም ሕዝ
ቡን በታላቅ መቅሠፍት ክፉኛ መታ። 34ሌላ
ምግብ ለማግኘት የጐመጁትን ሰዎች በዚያ
ስለ ቀበሩአቸው የቦታው ስም "ቂብሮት
ሃታአባ"[ኸ] ተባለ።

35ሕዝቡም ከቂብሮት ሃታአባ ወደ ሐጼ
ሮት ተጕዘው እዚያው ሰፈሩ።

## ማሪያምና አሮን ሙሴን ተቃወሙ

12 ሙሴ ኢትዮጵያዊት ሴት አግ
ብቶ ነበርና ባገባት ኢትዮጵያ
ዊት ምክንያት ማርያምና አሮን ይነቅፉት
ጀመር። 2እነርሱም፣ "ለመሆኑ *እግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) የተናገረው በሙሴ አማካ
ይነት ብቻ ነውን? በእኛስ አልተናገረም?"
ተባባሉ፤ *እግዚአብሔርም* (ያህዌ) ይህን ሰማ።

3ሙሴ በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ
ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው ነበር።

4ወዲያው *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን፣
አሮንንና ማርያምን፣ "ሦስታችሁም ውጡና
ወደ መገናኛው ድንኳን ኑ" አላቸው፤ ሦስ
ቱም ወጥተው ሄዱ። 5ከዚያም *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) በደመና ዐምድ ወረደ፤ በድንኳኑም
ደጃፍ ቆሞ አሮንንና ማርያምን ጠራቸው፤
ሁለቱም ወደ እርሱ በቀረቡ ጊዜ፣ 6እንዲህ
አላቸው፤ "ቃሌን አድምጡ፤

"*የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ነቢይ በመካከላችሁ
ቢኖር፣
በራእይ እገለጥለታለሁ፤
በሕልምም እናገረዋለሁ።
7ለአገልጋዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም፤
እርሱ በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው።
8እኔ ከእርሱ ጋር የምነጋገረው ፊት ለፊት
ነው፤
በግልጽ እንጂ በልዩ ዘይቤ አይደለም፤
እርሱ *የእግዚአብሔርን* (ያህዌ) መልክ ያያል።
ታዲያ እናንተ አገልጋዬን ሙሴን
ትቃወሙ ዘንድ
ለምን አልፈራችሁም?"

9*የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ቍጣ በላያቸው
ነደደ፤ እርሱም ትቶአቸው ሄደ።

10ደመናው ከድንኳኑ ላይ በተነሣ ጊዜ፣
እነሆ፤ ማርያም በለምጽ[ሠ] ተመታች፤ እንደ
በረዶም ነጣች። አሮንም ወደ እርሷ ዘወር

11፥33 ቊ18-20፤ ዘኍ14፥18፤ዘዳ 9፥7፤ መሳ2፥12፤መዝ78፥30፤ 106፥15፡29፤2ነገ22፥17፤ኢሳ10፥16፤ኤር 44፥3፤ሕዝ8፥17
11፥34 ዘኍ33፥16፤ ዘዳ9፥22
11፥35 ዘኍ33፥17
12፥1 ዘፀ15፥20፤ 2፥21
12፥2 ዘኍ16፥3፤ 11፥1
12፥3 ማቴ11፥29
12፥5 ዘፀ13፥21፤ ዘኍ11፥25
12፥6 ዘፍ15፥1፤ 20፥3፤1ሳሙ3፥7፡21፤ 20፥3፤ማቴ27፥19፤ ዕብ1፥1
12፥7 ዘዳ34፥5፤ኢሱ 1፥1-2፤መዝ105፥26 ዕብ3፥2-5
12፥8 ዘፀ20፥4፤ 24፥2፤መሳ14፥12፤ 1ነገ10፥1፤ኢዮ19፥26 ፤መዝ17፥15፤49፥4፤ 140፥13፤ምሳ1፥6፤ ኢሳ6፥1ዳን5፥12
12፥9 ዘፍ17፥22፤ ዘፀ4፥14
12፥10 ዘፀ4፥6፤ 40፥2፤ዘሌ13፥11፤ዘዳ 24፥9፤2ነገ5፥1፡27፤ 2ዜና16፥12፤21፥12-15፤26፥19
12፥11 2ሳሙ19፥ 19፤24፥10
12፥13 ዘፀ15፥26፤ መዝ6፥2፤147፥3፤ኢሳ 1፥6፤30፥26፤53፥5፤ ኤር17፥14፤ሆሴ6፥1
12፥14 ዘሌ13፥46፤ ዘዳ25፥9፤ኢዮ17፥6፤ 30፥9-10፤ኢሳ50፥6
12፥15 ዘሌ13፥4፤ 14፥8
12፥16 ዘፍ21፥21፤ ዘኍ11፥35፤10፥12፤ 15፥32
13፥2 ቊ16፤ዘዳ 1፥22፤ዘሌ14፥34፤ 24፥11፤ኢሱ1፥3
13፥3 ዘኍ1፥16
13፥6 ቊ30፤ዘኍ 14፥6፡24፤34፥19፤ዘዳ1፥36፤መሳ1፥12-15
13፥8 ዘኍ11፥28
13፥16 ቊ2፡8፤ ዘዳ32፥44
13፥17 ቊ2፤ኢሱ 14፥7፤ዘፍ12፥9፤ዘዳ1፥7፤ኢሱ9፥1፤መሳ1፥9

ሲል ለምጽ ወርሶአት አየ፤ 11ሙሴንም
እንዲህ አለው፣ "ጌታዬ ሆይ፤ በስንፍናችን
የሠራነውን ኀጢአት እባክህ አትቍጠ
ርብን። 12እርሷንም በእናቱ ማሕፀን ሳለ ሞቶ
ግማሽ አካሉ ከተበላ በኋላ የተወለደ ጭንጋፍ
መስላ እንድትቀር አታድርግ።"

13ስለዚህም ሙሴ፣ "*አምላክ* (ኤሎሂም)
ሆይ፤ እባክህ ፈውሳት" ብሎ ወደ *እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ጮኸ።

14*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) ለሙሴ፣ "አባቷ
እፊቷ ላይ ቢተፋባት እስከ ሰባት ቀን
በኀፍረት መቈየት አይገባትምን? አሁንም
ከሰፈር ውጭ ሰባት ቀን እንድትገለል
አድርግ፤ ከዚያ በኋላ ግን ልትመለስ ትች
ላለች" ሲል መለሰለት። 15ስለዚህም ማር
ያም ከሰፈር ውጭ ሰባት ቀን ተገለለች፤
ከዚያ እስክትመለስም ሕዝቡ ጕዞውን አል
ቀጠለም ነበር።

16ከዚያ በኋላ ሕዝቡ ከሐጼሮት ተነሣ፤ በፋ
ራን ምድረ በዳም ሰፈረ።

## ከነዓንን መሰለል

13 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2"ለእስራኤላውያን የም
ሰጠውን የከነዓንን ምድር እንዲሰልሉ
ጥቂት ሰዎች ላክ፤ ከእያንዳንዱም የአባ
ቶች ነገድ አለቃ ይላክ።"

3ስለዚህ ሙሴ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ትእ
ዛዝ ከፋራን ምድረ በዳ እነዚህን ላካቸው፤
ሁሉም የእስራኤላውያን አለቆች ነበሩ፤ 4ስማ
ቸውም እንደሚከተለው ነው፤

ከሮቤል ነገድ፣ የዘኩር ልጅ ሳሙኤል፤
5ከስምዖን ነገድ፣ የሱሬ ልጅ ሰፈጥ፤
6ከይሁዳ ነገድ፣ የዩፎኒ ልጅ ካሌብ፤
7ከይሳኮር ነገድ፣ የዮሴፍ ልጅ ይግአል፤
8ከኤፍሬም ነገድ፣ የነዌ ልጅ አውሴ፤
9ከብንያም ነገድ፣ የራፋ ልጅ ፈልጢ፤
10ከዛብሎን ነገድ፣ የሰዲ ልጅ ጉዲኤል፤
11ከምናሴ ነገድ ይህም የዮሴፍ ነገድ
ነው፤ የሱሲ ልጅ ጋዲ፤
12ከዳን ነገድ፣ የገማሊ ልጅ ዓሚኤል፤
13ከአሴር ነገድ፣ የሚካኤል ልጅ ሰቱር፤
14ከንፍታሌም ነገድ፣ የያቢ ልጅ ናቢ፤
15ከጋድ ነገድ፣ የማኪ ልጅ ጉዲኤል።

16እንግዲህ ምድሪቱን እንዲሰልሉ ሙሴ
የላካቸው ሰዎች ስም ይህ ነው። ሙሴ ለነዌ
ልጅ ለአውሴ፣ "ኢያሱ" የሚል ስም አወ
ጣለት።

17ሙሴም ከነዓንን እንዲሰልሉ በላካቸው
ጊዜ እንዲህ አላቸው፤ "ነጌብን ዘልቃችሁ

[ኸ]34 የምኞት መቃብር ማለት ነው።
[ሠ]10 በዕብራይስጡ ትርጒም ለምጽ ብቻ ሳይሆን፣ የተለያዩ የቆዳ በሽታዎችንም ያመለክታል።

ወደ ተራራማው አገር ግቡ። 18ምድሪቱ ምን እንደምትመስልና የሚኖሩባትም ሰዎች ብርቱዎች ወይም ደካሞች፣ ጥቂቶች ወይም ብዙዎች መሆናቸውን እዩ። 19የሚኖሩባት ምድር ምን ዐይነት ናት? መልካም ወይስ መጥፎ? የሚኖሩባቸውስ ከተሞች ምን ይመስላሉ? በግንብ ያልታጠሩ ናቸው ወይስ የተመሸጉ? 20ዐፈሩስ እንዴት ያለ ነው? ለም ወይስ ደረቅ? ደናም ወይስ ደን አልባ? በተቻለ መጠን ከምድሪቱ ፍሬ ይዛችሁ ኑ። ወቅቱ የወይን ፍሬ መብሰል የጀመረበት ጊዜ ነበር።

21ስለዚህ ወጥተው ከጺን ምድረ በዳ አንሥቶ በሌቦ° ሐማት በኩል እስከ ረአብ ድረስ ዘልቀው ምድሪቱን አጠኑ። 22በኔጌብ በኩል አልፈው አኪመን፣ ሴሲና ተላሚ የተባሉ የዔናቅ ዝርያዎች ወደሚኖሩበት ወደ ኬብሮን መጡ። ኬብሮን የተመሠረተችው ጣኔዎስ በግብፅ ምድር ከመቈርቈሯ ሰባት ዓመት አስቀድሞ ነበር። 23ወደ ኤሽኮል" ሸለቆ በደረሱ ጊዜ የወይን ዘለላ ያንዠረገገ አንድ ቅርንጫፍ ቈረጡ፤ ይህንንም ከሮማንና ከበለስ ጋር በመሎጊያ አድርገው ለሁለት ተሸከሙት። 24እስራኤላውያን የወይን ዘለላ ስለ ቈረጡባትም ያች ስፍራ የኤሽኮል ሸለቆ ተባለች። 25ምድሪቱንም አሥሠው ከአርባ ቀን በኋላ ተመለሱ።

## ሰላዮቹ ያቀረቡት የአሠሣ ውጤት

26ሰዎቹም፣ ሙሴና አሮን መላውም የእስራኤላውያን ማኅበረ ሰብ ወዳሉበት በፋራን ምድረ በዳ ወደምትገኘው ወደ ቃዴስ ተመለሱ፤ ያዩትንም ለእነርሱና ለማኅበሩ ሁሉ አስረዱ፤ የምድሪቱንም ፍሬ አሳዩአቸው። 27ለሙሴም እንዲህ ብለው ነገሩት፤ "ወደ ላክኸን ምድር ዘልቀን ገባን፤ ማርና ወተት የምታፈስስ ናት፤ ፍሬዋም ይኸው። 28በዚያ የሚኖሩት ሰዎች ግን ኀያላን ሲሆኑ፣ ከተሞቹም የተመሸጉና ትላልቅ ናቸው፤ እንዲያውም የዔናቅን ዝርያዎች በዚያ አይተናል። 29አማሌቃውያን የሚኖሩት በኔጌብ፣ ኬጢያውያን ኢያቡሳውያንና አሞራውያን በኰረብታማው አገር፣ ከነዓናውያን የሚኖሩት ደግሞ በባሕሩ አቅራቢያና በዮርዳኖስ ዳርቻ ነው።"

30ከዚያም ካሌብ ሕዝቡን በሙሴ ፊት ጸጥ አሰኝቶ፣ "እንውጣ! ምድራቸውን እንውረስ፤ ማሸነፍም እንችላለን" አላቸው።

31ከእነርሱ ጋር የወጡት ሰዎች ግን፣ "ከእኛ ይልቅ ብርቱዎች ስለ ሆኑ፣ ልናሸንፋቸው አንችልም" አሉ። 32እነዚህም ስለ ሰለሏት ምድር በእስራኤላውያን መካከል እንዲህ የሚል መጥፎ ወሬ አሠራጩ፤ "ያየናት ምድር የሚኖሩባትን ሰዎች የምትበላ ናት፤ እዚያ ያየናቸው ሰዎች ሁሉ ግዙፎች ናቸው፤ 33ኔፊሊምንም በዚያ አይተናል፤ የዔናቅ ዝርያዎች የመጡት ከኔፊሊም ነው። ራሳችንን ስናየው እንደ አንበጣ ነበርን፤ በእነርሱ ዐይን የታየነውም በዚሁ መልክ ነበር።

## የሕዝቡ ማመፅ

14 በዚያች ሌሊት ማኅበረ ሰቡ ሁሉ ድምፁን ከፍ አድርጎ ጮኸና አለቀሰ። 2እስራኤላውያን በሙሉ በሙሴና በአሮን ላይ አጒረመረሙ፤ ማኅበሩም ሁሉ እንዲህ አሉአቸው፤ "ምነው በግብፅ ወይም በዚህ ምድረ በዳ ሞተን ባረፍነው ኖሮ! 3*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ወደዚች ምድር የሚያመጣን ለምንድነው? በሰይፍ እንድንወድቅ ነውን? ሚስቶቻችንና ልጆቻችንም ይማረካሉ፤ ታዲያ ወደ ግብፅ መመለሱ አይሻለንም?" 4እርስ በርሳቸውም፣ "አለቃ መርጠን ወደ ግብፅ እንመለስ" ተባባሉ።

5ከዚያም ሙሴና አሮን እዚያ በተሰበሰቡት በመላው እስራኤላውያን ማኅበር ፊት በግንባራቸው ተደፉ። 6ምድሪቱን ከሰለሏት መካከል የነበሩት የነዌ ልጅ ኢያሱና የዩፎኒ ልጅ ካሌብ ልብሳቸውን ቀደዱ፤ 7ለመላው የእስራኤል ማኅበርም እንዲህ አሉ፤ "ዞረን ያየናትና የሰለልናት ምድር እጅግ ሲበዛ መልካም ናት። 8*እግዚአብሔር* (ያህዌ) በእኛ ደስ ከተሰኘብን ማርና ወተት ወደምታፈሰው ወደዚያች ምድር መርቶ ያገባናል፤ ለእኛም ይሰጠናል። 9ብቻ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ላይ አታምፁ፤ እንደ እንጀራ እንጐርሳቸዋለንና የምድሪቱን ሰዎች አትፍሩአቸው። ጥላቸው ተገፎአል፤ *እግዚአብሔርም* (ያህዌ) ከእኛ ጋር ነውና አትፍሯቸው።"

10መላው ማኅበር ግን በድንጋይ ሊወግሯቸው ተነጋገሩ፤ ከዚያም *የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ክብር በመገናኛው ድንኳን ለእስራኤላውያን ሁሉ ተገለጠ። 11*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤ "ይህ ሕዝብ እስከ መቼ ይንቀኛል? እነዚህን ሁሉ ታምራት

13፥20 ዘዳ1፥25፤ ዘሌ25፥5
13፥21 ዘኍ20፥1፤ 34፥8፤27፥14፤33፥36፤ ዘዳ32፥51፤ኢያ13፥5፤15፥1፤19፥28፤መሳ1፥31፤3፥3፤18፥28፤ 2ሳሙ10፥6፤1ነገ8፥65፤2ነገ14፥25፤1ዜና6፥75፤13፥5፤2ዜና7፥8፤አር52፥9፤ሕዝ47፥16፡20፤አሞ6፥14
13፥22 ቍ28፤ዘፍ13፥18፤23፥19፤ዘዳ2፥10፤9፥2፤ኢያ11፥21፤15፥13፡14፤መሳ1፥10፡20፤መዝ78፥12፡43፤ኢሳ19፥11፡13፤30፥4፤ሕዝ30፥14
13፥23 ዘፍ3፥7፤14፥13፤ዘፀ28፥33፤ዘኍ20፥5፤ዘዳ8፥8፤2ነገ18፥31፤ነህ13፥15
13፥25 ዘፍ7፥4፤ ዘኍ14፥34
13፥26 ዘፍ14፥6፡7፤ ዘኍ32፥8፤ዘዳ1፥25
13፥27 ዘፀ3፥8፤ዘዳ1፥25፤ኤር2፥7
13፥28 ቍ22፤ዘዳ1፥28፤9፥1፡2፤ኢያ14፥12
13፥29 ቍ17፤ዘፍ10፥15፡16፡18፤13፥10፤14፥7ዘፀ3፥8፤ዘኍ22፥1፤32፥5፤ዘዳ1፥1፤7፥1፤20፥17፤ኢያ1፥2፤መሳ3፥28፤1ነገ9፥20፤10፥29፤2ነገ7፥6፤ መዝ42፥6
13፥30 ቍ6
13፥31 ዘዳ9፥1፤ ኢያ14፥8
13፥32 ዘኍ14፥36፡37፤ዘዳ1፥28፤ሕዝ36፥13፡14፤አሞ2፥9
13፥33 ቍ28፤ዘፍ6፥4፤ዘዳ1፥28፤ኢያ11፥22፤14፥12፤ መክ12፥5፤ኢሳ40፥22
14፥1 ዘፍ27፥38፤ዘፀ33፥4፤ዘኍ25፥6፤ዘዳ1፥45፤መሳ20፥23፡26፤ 2ሳሙ3፥32፤ኢዮ31፥29
14፥2 ዘፀ15፥24፤ 16፥3፤ዘኍ11፥1፤16፥13፤20፥4፤21፥5፤ዕብ3፥16
14፥3 ቍ31ዘፍ34፥29፤ዘፀ5፥21፤ ዘዳ1፥39፤መዝ109፥11፤ኢሳ33፥4፤ሕዝ7፥21፤ 25፥7፤26፥5፤ ሐሥ7፥39
14፥4 ነህ9፥17
14፥5 ዘሌ9፥24፤ 19፥2፤ዘኍ16፥4፡22፡45፤20፥6፤ኢያ5፥14፤ 2ሳሙ14፥4፤1ዜና21፥16፤ሕዝ1፥28
14፥6 ዘፍ37፥29፡34፤ዘኍ11፥28፤ መሳ11፥35፤ዕዝ9፥3፤አስ4፥1፤2ሳሙ13፥31፤2ነገ19፥1፤ማር14፥63
14፥7 ዘኍ13፥27፤ዘዳ1፥25 14፥8 ዘኍ13፥27፤ ዘዳ1፥2-17፥8፤10፥15፤መዝ18፥19፤22፥8፤37፥23፤41፥11፤56፥9፤147፥11፤ምሳ11፥20፤ኢሳ62፥4፤ሚል2፥17 14፥9 ቍ24ዘፍ21፥22፤26፥24፤ ዘዳ1፥21፡26፡30፤7፥18፤9፥7፡23፡24፤20፥1፤2ዜና13፥12፤32፥7፤ መዝ118፥6፤ኤር15፥20፥41፥18፤42፥11፤46፥28፤ሐጌ1፥13
14፥10 ዘፀ17፥4፤ 24፥16 14፥11 ዘፀ3፥20፤4፥17፤23፥21፤10፥1፤ዘኍ15፥31፤16፥30፤ዘዳ1፥32፤1ሳሙ2፥17፤ሕዝ31፥14፤ ሚል1፥ 13፤መዝ78፥22፤106፥24፤ዮሐ3፥15

°21 ወይም *በከተማዋ መግቢያ በኩል*
"23 ዘለላ ማለት ነው።

በመካከሉ እያደረግሁ የማያምንብኝስ እስከ
መቼ ነው? [12]በቸነፈር እመታዋለሁ፤ እደ
መስሰዋለሁም፤ አንተን ግን ብርቱና ታላቅ
ለሆነ ሕዝብ አደርግሃለሁ፡፡”
[13]ሙሴ *እግዚአብሔርን* (ያህዌ) እንዲህ አለው፤
“ነገሩን ግብፃውያን ቢሰሙትስ! ይህን ሕዝብ
በኀይልህ ከመካከላቸው አወጥተኸዋልና፤
[14]የተደረገውንም በዚች ምድር ለሚኖሩት
ሰዎች ይነግሯቸዋል፡፡ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ሆይ፤ አንተ ከዚህ ሕዝብ ጋር መሆንህን፣
ደግሞም አንተ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሆይ፤
ፊት ለፊት እንደታየህና ደመናህ በላያቸው
እንደ ሆነ፣ አንተም ቀን በደመና ዐምድ
ሌሊትም በእሳት ዐምድ እፊት እፊታቸው
እየሄድህ እንደ መራሃቸው ቀድሞውኑ ሰም
ተዋል፡፡ [15]ታዲያ ይህን ሁሉ ሕዝብ በአ
ንድ ጊዜ ብትፈጀው ዝናህን የሰሙ ሕዝ
ቦች፣ [16]‘*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ለዚህ ሕዝብ
ይሰጠው ዘንድ በመሐላ ቃል ወደ ገባለት
ምድር ሊያስገባው ባለመቻሉ በምድረ በዳ
ፈጀው’ ይሉሃል፡፡
[17]“አሁንም እንዲህ ስትል በተናገርኸው
መሠረት የጌታ ኀይል ይገለጥ፤ [18]‘*እግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) ለቍጣ የዘገየ፣ ፍቅሩ የበዛ፣
ኀጢአትንና ዐመፃን ይቅር የሚል፣ በደ
ለኛውን ግን ሳይቀጣ የማይተው፣ ስለ አባ
ቶቻቸውም ኀጢአት ልጆችን እስከ ሦስ
ትና አራት ትውልድ የሚቀጣ ነው፡፡’ [19]ከግ
ብፅ ከወጡበት ጊዜ አንሥቶ እስካሁን ድረስ
ይቅር እንዳልሃቸው ሁሉ እንደ ፍቅርህ
ታላቅነት መጠን እባክህ አሁንም የዚ
ህን ሕዝብ ኀጢአት ይቅር በል፡፡”
[20]*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) እንዲህ ሲል
መለሰለት፤ “በጠየቅኸው መሠረት ይቅር
ብያቸዋለሁ፤ [21]ይሁን እንጂ ሕያው እንደ
መሆኔና *የእግዚአብሔርም* (ያህዌ) ክብር ምድ
ርን ሁሉ የሞላ እንደ መሆኑ መጠን፣ [22]ክብ
ሬን ደግሞም በግብፅና በምድረ በዳ ያደረ
ግኋቸውን ታምራት አይተው ካልታዘዙ
ኝና ዐሥር ጊዜ ከተፈታተኑኝ ሰዎች አንዳቸ
ውም፣ [23]ለአባቶቻቸው እሰጣቸው ዘንድ
በመሐላ ቃል የገባሁላቸውን ምድር አያዩ
ዋትም፡፡ የናቀኝ ማንኛውም ሰው ፈጽሞ
አያያትም፤ [24]አገልጋዬ ካሌብ ግን የተለየ
መንፈስ ስላለውና በፍጹም ልቡ የተከተ
ለኝ በመሆኑ ሄዶባት ወደ ነበረችው ምድር
አስገባዋለሁ፤ ዘሮቹም ይወርሷታል፡፡ [25]አማ
ሌቃውያንና ከነዓናውያን በሸለቆው የሚ
ኖሩ ስለ ሆነ በነገው ዕለት ተመልሳችሁ
በቀይ ባሕር[ቸ] መንገድ ወደ ምድረ በዳው
ሂዱ፡፡”
[26]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴንና አሮንን
እንዲህ አላቸው፤ [27]“ይህ ክፉ ማኅበረ ሰብ
በእኔ ላይ የሚያጕረመርመው እስከ መቼ
ነው? የእነዚህን ነጭናጮች እስራኤላው
ያን ማጕረምረም ሰምቻለሁ፡፡ [28]ስለዚህ
እንዲህ በላቸው፤ ‘*እግዚአብሔር* (ያህዌ) እንዲ
ህ ይላል፤ እኔ ሕያው ነኝ፤ ስትናገሩ የሰማ
ኋችሁን እነዚያን ነገሮች አደርግባችኋለሁ፤
[29]በተደረገው ቈጠራ መሠረት፣ ሃያ ዓመት
ወይም ከዚያ በላይ የሆናችሁና በእኔም
ላይ ያጕረመረማችሁ ሁሉ በድናችሁ በዚህ
ምድረ በዳ ይወድቃል፡፡ [30]መኖሪያችሁ እን
ድትሆን በጽኑ ወደ ማልሁላችሁ ምድር
ከዮፎኒ ልጅ ከካሌብና ከነዌ ልጅ ከኢያሱ
በስተቀር ከእናንተ አንዳችሁም አትገ
ቡባትም፡፡ [31]ይማረካሉ ያላችኋቸውን ልጆቻ
ችሁን ግን አገባቸዋለሁ፤ እናንተ የናቃች
ኋትን ምድር እነርሱ ይደሰቱባታል፡፡ [32]እና
ንተ ግን፣ በድናችሁ በዚሁ ምድረ በዳ
ወድቆ ይቀራል፡፡ [33]ካለማመናችሁ የተነሣ
ከእናንተ የመጨረሻው በድን እዚሁ ምድረ
በዳ እስኪወድቅ ድረስ፣ ልጆቻችሁ መከራ
እየበሉ አርባ ዓመት እረኞች ይሆናሉ፡፡
[34]ምድሪቱን ለመሰለል በቈያችሁ በት አርባ
ቀን ልክ እያንዳንዱ ዓመት እንደ አንድ
ዕለት ተቈጥሮ ስለ ኀጢአታችሁ አርባ
ዓመት መከራ ትቀበላላችሁ፤ ምን ያህል
በእናንተ ላይ እንደ ተነሣሁም ታውቃላ
ችሁ፡፡ [35]እኔ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ይህን
ተናግሬአለሁ፤ ደግሞም አንድ ሆኖ በተነ
ሣብኝ በዚህ ክፉ ማኅበረ ሰብ ሁሉ ላይ
እነዚህን ነገሮች አደርጋለሁ፤ መጨረሻ
ቸው በዚሁ ምድረ በዳ ይሆናል፤ እዚሁም
ይሞታሉ፡፡’ ”
[36]ከዚህ በኋላ ምድሪቱን እንዲሰልሉ ሙሴ
ልኳቸው የነበሩትና ከዚያ ተመልሰው ስለ
ምድሪቱ ክፉ ወሬ በማሠራጨት ማኅበረ
ሰቡ በሙሉ እንዲያጕረመርሙበት ያደረጉ፣
[37]ስለ ምድሪቱም ክፉ ወሬ በማሠራጨት
ተጠያቂ የሆኑት እነዚሁ ሰዎች ተቀሥ
ፈው *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ሞቱ፡፡
[38]ምድሪቱን እንዲሰልሉ ከተላኩት ሰዎች
በሕይወት የተረፉት የነዌ ልጅ ኢያሱና
የዩፎኒ ልጅ ካሌብ ብቻ ነበሩ፡፡
[39]ሙሴም ይህን ለእስራኤላውያን ሁሉ
በነገራቸው ጊዜ ክፉኛ አዘኑ፡፡ [40]በማግሥ
ቱም ጠዋት ማልደው ወደ ተራራማው አገር
ወጡ፤ እንዲህም አሉ፣ “ኀጢአት ሠርተና
ልና *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ተስፋ ወደ ሰጠን
ስፍራ እንወጣለን”፡፡
[41]ሙሴ ግን እንዲህ አለ፤ “*የእግዚአብሔ
ርን* (ያህዌ) ትእዛዝ ለምን ትጥሳላችሁ? ይህም

ቸ25 በዕብራይስጥ ትርጕሙ *ያም ሱፍ* የሚል ሲሆን የሸምበቆ
ባሕር ማለት ነው፡፡

**14፥12** ዘፀ5፥3፤ 30፥12፤32፥10፤ዘዳ9፥14፤29፥20፤32፥26፤መዝ109፥13
**14፥13** ዘፀ32፥11-14፤መዝ106፥23
**14፥14** ዘፀ13፥21፤15፥14፤33፥16፤ዘኍ5፥3፤16፥3፤ዘዳ5፥4፤34፥10፤ኢሱ2፥9
**14፥16** ዘፀ32፥12፤ዘኍ11፥12፤ኢሱ7፥7
**14፥18** ዘፀ20፥5፡6፤34፥6፤መዝ145፥8፤ዮና4፥2፤ያዕ5፥11
**14፥19** ዘፀ34፥9፤1ነገ8፥34፤መዝ78፥38፤85፥2፤103፥3፤106፥45
**14፥20** ዘፀ34፥6፤መዝ99፥8፤106፥23፤ሚክ7፥18-20
**14፥21** ቍ28፤ዘሌ9፥6፤ ዘዳ32፥40፤መሳ8፥19፤ሩት3፥13፤1ሳሙ14፥39፤19፥6፤መዝ72፥19፤ኢሳ6፥3፤40፥5፤49፥18፤ኤር4፥2፤ሕዝ5፥11፤ዕን2፥14፤ሶፎ2፥9
**14፥22** ቍ11፤ዘፀ14፥11፤17፥7፤32፥1፤መዝ81፥7፤1ቆሮ10፥5
**14፥23** ቍ11፡16፤ዘፀ33፥1፤ ዘኍ32፥11፤ዘዳ1፥34፤መዝ95፥11፤106፤26፤ዕብ3፥18
**14፥24** ቍ 6-9፤ዘኍ13፥6፤26፥65፤32፥12፤ዘዳ1፥36፤ኢሱ14፥8፡14፤መዝ25፥13፤37፥9፡11
**14፥25** ዘፍ10፥18፤14፥7፤ዘፀ23፥31፤ዘኍ21፥4፤14፥7፤ዘዳ1፥40፤1ነገ9፥26
**14፥27** ዘፀ16፥12፤ዘዳ1፥34፡35
**14፥28** ቍ21፤ዘኍ33፥56
**14፥29** ቍ23፡30፡32፤ዘፀ30፥12፤ዘኍ1፥45፤26፥65፤32፥13፤1ቆሮ10፥5፤ዕብ3፥17፤ይሁ1፥5
**14፥30** ቍ29፤ዘፀ6፥8፤ዘኍ11፥28፤13፥6፤ዘዳ32፥40፤ነህ9፥15፤መዝ106፥26፤ሕዝ20፥5፤36፥7
**14፥31** ዘሌ26፥43
**14፥32** ቍ29፡35
**14፥33** ቍ34፤ዘፀ16፥35፤ሐሥ13፥18፤ዕብ3፥9
**14፥34** ቍ33፤ዘኍ13፥25
**14፥35** ቍ32 ዘኍ23፥19
**14፥36** ቍ2፤ዘኍ13፥4-16፡32
**14፥37** ዘኍ13፥32፤

አይሳካላችሁም! 42እግዚአብሔር (ያህዌ)
ከእና ንተ ጋር ስላይደለ አትውጡ፤ በጠ
ላቶቻ ችሁ ድል ትመታላችሁ፤ 43አ
ማሌቃውያ ንና ከነዓናውያን በዚያ
ያጋጥሟችኋልና። እግዚአብሔርን (ያህዌ)
ስለተዋችሁትና እር ሱም ከእናንተ ጋር
ስለማይሆን በሰይፍ ትወድቃላችሁ።”
44ሙሴም ሆነ የእግዚአብሔር (ያህዌ) ታቦት
ከሰፈር ሳይነሡ በስሜት ተገፋፍተው ብቻ
ወደ ተራራማው አገር ወጡ። 45በዚህ ጊዜ
በተራራማው አገር የሚኖሩት አማሌቃው
ያንና ከነዓናውያን ወርደው ወጉአቸው፤
እስከ
ሔርማ ድረስም አሳደዱአቸው።

## ተጨማሪ ቍርባን

15 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2“እስራኤላውያንን ተናገራ
ቸው፤ እንዲህም በላቸው፤ ‘እንድትኖሩበት
ወደምሰጣችሁ ምድር ከገባችሁ በኋላ፣
3ስእለታችሁን ለመፈፀም ወይም የበጎ
ፈቃድ ስጦታ ለማድረግ ወይም በተወሰኑ
በዓሎቻችሁ ሽታው እግዚአብሔርን (ያህዌ)
ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት ከላም ወይም
ከበግ መንጋ በእሳት ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
ስታቀርቡ 4መሥዋዕቱን ይዞ የሚመጣው
ሰው በኢን[የ] አንድ አራተኛ ዘይት የተለወሰ
የኢፍ[ደ] አንድ ዐሥረኛ የላመ ዱቄት የእ
ህል ቍርባን ለእግዚአብሔር (ያህዌ) ያቀር
ባል። 5ለሚቃጠል ወይም ለዕርድ መሥዋዕት
ከሚቀርብ ከእያንዳንዱ የበግ ጠቦት ጋር
የኢን አንድ አራተኛ የወይን ጠጅ የመጠጥ
ቍርባን አብራችሁ አዘጋጁ።
6“ ‘ከአውራ በግ ጋር በኢን[ጀ] ሢሶ ዘይት
የተለወሰ የኢፍ[ገ] ሁለት ዐሥረኛ ልም ዱቄት
የእህል ቍርባን አዘጋጁ፤ 7እንዲሁም
ለመጠጥ ቍርባን የሚሆን የኢን አንድ
ሦስተኛ የወይን ጠጅ አዘጋጁ፤ ይህንም
እግዚአብሔርን (ያህዌ) ደስ የሚያሰኝ ሽታ
ያለው አድርጋችሁ አቅርቡ።
8“ ‘አንዱን ወይፈን ለተለየ ስለት ወይም
ለኅብረት የሚቀርብ የሚቃጠል መሥዋዕት[ጠ]
ወይም የዕርድ መሥዋዕት አድርጋችሁ ለእ
ግዚአብሔር (ያህዌ) በምታዘጋጁበት ጊዜ፣
9ከወይፈኑ ጋር በግማሽ ኢን[ጨ] ዘይት የተ
ለወሰ የኢፍ[ጰ] ሦስት ዐሥረኛ የላመ ዱቄት
አብራችሁ አምጡ። 10እንዲሁም ለመጠጥ
ቍርባን የሚሆን ግማሽ ኢን የወይን ጠጅ
አቅርቡ፤ ይህም በእሳት የሚቀርብና ሽታው
እግዚአብሔርን (ያህዌ) ደስ የሚያሰኝ መሥ
ዋዕት ይሆናል። 11እያንዳንዱ ወይፈን ወይም
አውራ በግ፣ እያንዳንዱ የበግም ሆነ የፍ
የል ጠቦት በዚህ ሁኔታ ይዘጋጅ። 12ባዘ
ጋጃችሁት ቍጥር ልክ ይህን ለእያንዳንዱ

16፥49፤25፥9፤26፥1፤3
1፥16፤1ቆሮ10፥10፤ዕ
ብ3፥17፤ዘዳ4፥3
14፥38 ቍ24፥30፤
32ዘኍ13፥4-16፤
ኢሱ14፥6
14፥39 ቍ28-35፤
ዘፀ33፥4
14፥40 ቍ45፤ዘኍ
13፥17፤ዘፀ9፥27
14፥41 2ዜና24፥20
14፥42 ዘዳ1፥42
14፥43 ቍ45፤ዘፍ
39፥23፤ዘኍ13፥29፤
መሳ1፥19፤3፥13፤ዘዳ
31፥8፤ኢሱ6፥27፤መሳ
1፥19፤6፥16፤1ሳሙ3፥
19፤18፥14፤2ዜና1፥1
14፥44 ዘኍ31፥6፤
ዘዳ1፥43
14፥45 ቍ40፡43፤
ዘኍ21፥3፤ዘዳ1፥44፤
ኢሱ12፥14፤15፥30፤
19፥4፤መሳ1፥17፤1ሳ
ሙ30፥30፤1ዜና4፥30
15፥2 ዘሌ23፥10
15፥3 ቍ24፤ዘሌ
1፥2፡3፡9፤7፥16፤
23፥1-44፤ዘኍ
28፥13፤ዕዝ1፥4
15፥4 ዘፀ16፥36፤
ዘሌ6፥14
15፥5 ዘፍ35፥14፤
ዘሌ3፥7፤10፥9
15፥6 ዘሌ5፥15፤
23፥13፤ዘኍ28፥12፤
29፥14፤ሕዝ46፥14
15፥7 ቍ5፤ዘሌ
1፥9፤23፥13፤ዘኍ
28፥14፤29፥18
15፥8 ዘፀ12፥5፤
ዘሌ1፥5፤3፥6፤22፥18
15፥9 ዘሌ2፥1፤
14፥10
15፥10 ዘሌ1፥9፤
23፥13፤ዘኍ28፥14
15፥12 ዕዝ7፥17
15፥13 ዘሌ1፥9፤
16፥29
15፥14 ቍ25ዘፀ
12፥19፡43፤22፥21፤
ዘሌ3፥17፤22፥18፤
ዘኍ10፥8
15፥15 ቍ14፡21
15፥16 ዘፀ12፥49፤
ዘሌ22፥18፤ዘኍ9፥14
15፥18 ዘሌ23፥10
15፥19 ዘኍ18፥8፤
ኢሱ5፥11፡12
15፥20 ዘፍ50፥10፤
ዘሌ2፥14፤23፥14፤
ዘኍ18፥27
15፥21 ዘሌ23፥14
፤ሕዝ44፥30፤ሮሜ
11፥16
15፥22 ዘሌ4፥2
15፥23 ቍ21
15፥24 ቍ3፡25፡
26፤ዘሌ5፥15፤4፥14፤
2፥1፤23፥13፤4፥3፤
ዘኍ6፥15

አድርጉ።
13ማናቸውም የአገር ተወላጅ የሆነ በእ
ሳት የሚቀርብ ሽታው እግዚአብሔርን (ያህዌ)
ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት በሚያቀርብበት
ጊዜ እነዚህን ነገሮች በዚሁ ሁኔታ ያድርግ።
14ለሚቀጥሉት ትውልዶች ሁሉ መጻተኛ
ወይም በመካከላችሁ የሚኖር ማናቸውም ሰው
በእሳት የሚቀርብ ሽታው እግዚአብሔርን
(ያህዌ) ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት በሚያቀር
ብበት ጊዜ ልክ እናንተ እንደምታደርጉት
ያድርግ። 15ማኅበረ ሰቡ ለእናንተም ሆነ
በመካከላችሁ ለሚኖር መጻተኛ አንድ ዐይነት
ደንብ ይኖረዋል፤ ይህም በሚቀጥሉት ትው
ልዶች ሁሉ የማይሻር ሥርዐት ነው። እና
ንተም ሆናችሁ መጻተኞቹ በእግዚአብሔር (ያህዌ)
ፊት እኩል ትታያላችሁ፤ 16ለእናንተም
ሆነ በመካከላችሁ ለሚኖር መጻተኛ ይኸው
ሕግና ሥርዐት እኩል ተፈጻሚነት ይኖ
ረዋል።’ ”
17እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤
18“እስራኤላውያንን ተናገራቸው፤ እንዲ
ህም በላቸው፤ ‘እኔ ወደምወስዳችሁ ምድር
ገብታችሁ፣ 19የምድሪቱን በረከት ስትመ
ገቡ ከዚሁ ላይ አንሥታችሁ ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) ቍርባን አቅርቡ። 20ይህንም ከመጀ
መሪያው ዱቄት ላይ ኅብስት ጋግራችሁ
ከዐውድማ እንደ ተገኘ ቍርባን አድርጋ
ችሁ አምጡ። 21በሚቀጥሉት ትውልዶች
ሁሉ ከመጀመሪያው ዱቄት ላይ አንሥ
ታችሁ ይህን ቍርባን ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) ትሰጣላችሁ።

## ባለማወቅ ስለሚደረግ ኀጢአት የሚቀርብ መሥዋዕት

22“ ‘እንግዲህ ካለማወቅ የተነሣ እግዚአ
ብሔር (ለያህዌ) ለሙሴ ከሰጣቸው ትእዛዛት
አንዱን ሳትፈጽሙ ብትቀሩ፣ ይህም ማለት
23እግዚአብሔር (ያህዌ) ትእዛዛቱን ከሰጠ
በት ዕለት ጀምሮ በተከታታይ ትውልዶች
በሙሴ አማካይነት ያዘዛችሁን እነዚህን
ትእዛዛት ሁሉ ባታደርጉ፣ 24ይህም የተፈ
ጸመው ሆን ተብሎ ሳይሆንና ማኅበረ
ሰቡም ሳያውቀው ከሆነ፣ ማኅበረ ሰቡ በሙሉ
ሽታው እግዚአብሔርን (ያህዌ) ደስ የሚያ
ሰኝ አድርጎ አንድ ወይፈን በእሳት ለሚ
ቃጠል መሥዋዕት ያቅርብ፤ ከዚሁም ጋር
ሥርዐቱ የሚጠይቀውን የእህል ቍርባንና

[የ]4 ሁለት ሊትር ያህል ነው።
[ደ]4 አንድ ሊትር ያህል ነው።
[ጀ]6 አራት ተኩል ሊትር ያህል ነው።
[ገ]6 አንድ ሊትር ያህል ነው።
[ጠ]8 በተለምዶ የድነት መሥዋዕት ይባላል።
[ጨ]9 ስድስት ተኩል ሊትር ያህል ነው።
[ጰ]9 ሁለት ሊትር ያህል ነው።

የመጠጥ ቍርባን ደግሞም ለኀጢአት
መሥዋዕት ተባዕት ፍየል ያቅርብ። [25]ካህ
ኑም ለመላው የእስራኤል ማኅበረ ሰብ
ያስተሰርያል፤ እነርሱም ይቅር ይባላሉ፤
ምክንያቱም ባለማወቅ የተፈጸመ ስለ ሆነና
ስለ ስሕተታቸውም በእሳት የሚቃጠል
መሥዋዕትና የኀጢአት መሥዋዕት ለእግ
ዚአብሔር (ለያህዌ) ስላቀረቡ ነው። [26]ባለ
ማወቅ የተደረገውን ስሕተት ሁሉም የፈ
ጸሙት ስለ ሆነ፣ መላው የእስራኤል ማኅ
በረ ሰብና በመካከላቸው የሚኖር መጻተኛ
ሁሉ ይቅር ይባላል።
[27]" 'ነገር ግን አንድ ሰው ካለማወቅ የተ
ነሣ በግሉ ኀጢአት ቢሠራ ግን ለኀጢአት
መሥዋዕት የአንድ ዓመት እንስት ፍየል
ያምጣ። [28]ከዚያም ካህኑ፣ ባለማወቅ ኀጢ
አት ሠርቶ ለተሣሣተው ሰው በእግዚአ
ብሔር (ያህዌ) ፊት ያስተሰርይለታል፤ ስር
የት በሚደረግለትም ጊዜ ሰውየው ይቅር ይባ
ላል። [29]ያገር ተወላጅ እስራኤላዊ ይሁን
ወይም መጻተኛ ባለማወቅ ኀጢአት ከሠራ
በማናቸውም ሰው ላይ ሕጉ እኩል ተፈ
ጻሚነት ይኖረዋል።
[30]" 'ያገር ተወላጅም ይሁን መጻተኛ ሆን
ብሎ ኀጢአት የሚሠራ ማንኛውም ሰው ግን
እግዚአብሔርን (ያህዌ) ስለሚያቃልል ያ ሰው
ከወገኖቹ ተለይቶ ይጥፋ። [31]የእግዚአብሔርን
(ያህዌ) ቃል ስለ ናቀ፣ ትእዛዛቱንም ስለ
ጣሰ ያ ሰው በእርግጥ ተለይቶ መጥፋት
አለበት፤ ጥፋቱ የራሱ ነው።' "

## ሰንበትን የሻረው በሞት ተቀጣ

[32]እስራኤላውያን በምድረ በዳ በነበሩ
በት ጊዜ አንድ ሰው በሰንበት ቀን ዕ
ንጨት ሲለቅም ተገኘ። [33]ዕንጨት ሲ
ለቅም ያገኙ ትም ሰዎች ሰውየውን ወደ
ሙሴ፣ ወደ አሮንና ወደ መላው የእስራ
ኤል ማኅበር አመጡት፤ [34]በሰውየው ላይ
ምን መደረግ እንዳለበት ግልጽ የሆነ ነገር
ባለመኖሩ በጥበቃ ሥር እንዲቈይ
አደረጉት። [35]ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ)
ሙሴን፣ "ሰውየው ይሙት፤ መላውም
ማኅበር ከሰፈር ውጭ በድንጋይ
ይውገረው" አለው፤ [36]ስለዚህ እግዚአብሐ
ር (ያህዌ) ሙሴን ባዘዘው መሠ ረት
ማኅበሩ ሰውየውን ከሰፈር አውጥቶ እስኪ
ሞት ድረስ በድንጋይ ወገረው።

## ስለ ልብስ ዘርፍ የተሰጠ መመሪያ

[37]እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤
[38]"እስራኤላውያንን ተናገራቸው፤ እንዲ
ህም በላቸው፤ 'በሚቀጥሉት ትውልዶች
ሁሉ በየልብሳችሁ ጫፍ ላይ ዘርፍ አድ
ርጉ፤ እያንዳንዱም ዘርፍ ሰማያዊ ጥለት
ይኑረው። [39]ልባችሁ የተመኘውን፣ ዐይና
ችሁ ያየውን ሁሉ ተከትላችሁ እንዳታመ
ነዝሩ እነዚህን ዘርፎች በማየት የእግዚ
አብሔርን (የያህዌ) ትእዛዛት በማስታወስ እን
ድትታዘዙ ማስታወሻ ይሆኑአችኋል። [40]ስለ
ዚህ ትእዛዛቴን ሁሉ ለመፈጸም ታስባላ
ችሁ፤ ለአምላካችሁም (ኤሎሂም) የተቀደሳችሁ
ትሆናላችሁ። [41]አምላካችሁ (ኤሎሂም) እሆን ዘንድ
ከግብፅ ምድር ያወጣኋችሁ እኔ አምላካችሁ
እግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) ነኝ። እኔ እግዚአ
ብሔር አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ።

## ቆሬ፣ ዳታንና አቤሮን

16 የሌዊ ልጅ፣ የቀዓት ልጅ፣ የይስዓር
ልጅ የሆነው ቆሬ፣ ከሮቤልም
ነገድ የኤልያብ ልጆች ዳታንና አቤሮን
እንዲሁም የፍሌት ልጅ ኦን በክፉት
ተነሣሥ ተው፣ [2]ሙሴን ተቃወሙት።
ከእነዚህም ጋር ታዋቂ የማኅበረ ሰቡ
መሪዎች የሆ ኑና በጉባኤ አባልነት
የተመረጡ ሁለት መቶ አምሳ እስራ
ኤላውያን አብረው ነበሩ። [3]እነዚህም
ሙሴንና አሮንን ለመቃወም ግንባር
ፈጥረው በመምጣት፣ "ምነው ከልክ
አላለፋችሁም! የማኅበረ ሰቡ አባላት ሁሉ
እያንዳንዳቸው የተቀደሱ ናቸው፤ እግዚአ
ብሔርም (ያህዌ) ከእነርሱ ጋር ነው፤ ታዲያ
በእግዚአብሔር (ያህዌ) ማኅበር ላይ የምትታ
በዩት ለምንድነው?" አሉአቸው።
[4]ሙሴም ይህን ሲሰማ በግንባሩ መሬት
ላይ ተደፋ፤ [5]ቆሬንና ተከታዮቹን በሙሉ
እንዲህ አላቸው፤ "የእርሱ የሆነውና የተቀ
ደሰው ማን መሆኑን እግዚአብሔር (ያህዌ)
ነገ ጠዋት ይለያል፤ ወደ ራሱም ያመ
ጣዋል፤ የሚመርጠውን ሰው ወደ ራሱ
እንዲቀርብ ያደርገዋል። [6]ቆሬ፣ አንተና
ተከታዮችህ ሁሉ እንዲህ አድርጉ፤ ጥናዎ
ችን ውሰዱ፤ [7]በማግስቱም በእግዚአብሔር
(ያህዌ) ፊት እሳትና ዕጣን ጨምሩባቸው፤
እግዚአብሔር (ያህዌ) የሚመርጠውም ያ ሰው
ቅዱስ ይሆናል፤ እናንት የሌዊ ልጆች፤
ከልክ ያለፋችሁትስ እናንተ ናችሁ!"
[8]ደግሞም ሙሴ ቆሬን እንዲህ አለው፤
"እናንት ሌዋውያን አድምጡ! [9]የእስራ
ኤል አምላክ (ኤሎሂም) እናንተን ከቀሩት እስ
ራኤላውያን ማኅበረ ሰብ መለየቱና በእግዚ
አብሔር (ያህዌ) ማደሪያ አገልግሎት እንድትፈ
ጽሙ ወደ ራሱ ማቅረቡ፣ እንድታገለግ
ሏቸውም በማኅበረ ሰቡ ፊት እንድትቆሙ
ማድረጉ አይበቃችሁምን? [10]አንተንና ከአን
ተም ጋር ወገኖችህ የሆኑትን ሌዋውያንን
ሁሉ ወደ ራሱ አቅርቧችኋል፤ እናንተ ግን
የክህነቱንም ሥራ ደርባችሁ ለመያዝ ይኸው
ትራራጣላችሁ። [11]አንተና ተከታዮችህ ሁሉ

15፥25 ቍ14፥22፡24፤ዘሌ4፥3፡20፤ሮሜ3፥25
15፥26 ቍ24
15፥27 ዘሌ4፥3፡27፤ዘኍ6፥14
15፥28 ዘሌ4፥20፤ዘኍ8፥12፤28፥22
15፥29 ዘፀ12፥49
15፥30 ቍ14፤ዘፍ17፥14፤ዘኍ14፥40-44፤ዘዳ1፥43፤17፥13፤ኢዮ31፥22፤መዝ19፥13፤2ነገ19፥6፡20፤ኢሳ37፥6፡23፤ሕዝ20፥27
15፥31 ዘሌ5፥1፤ዘኍ14፥11፤1ሳሙ15፥23፡26፤2ሳሙ11፥27፤12፥9፤መዝ119፥126፤ምሳ13፥13፤ሕዝ18፥20
15፥32 ዘፀ31፥14፡15፤35፥2፡3፤ዘኍ12፥16
15፥34 ዘኍ9፥8
15፥35 ዘፀ31፥14፡15፤ዘሌ20፥2፤ሉቃ4፥29፤ሐሥ7፥58
15፥36 ዘፀ31፥14፤ዘሌ20፥2፤ኤር17፥21
15፥38 ዘሌ3፥17፤ዘኍ10፥8፤ዘዳ22፥12፤ማቴ23፥5
15፥39 ዘሌ17፥7፤ዘዳ4፥23፤6፥12፤መሳ2፥17፤መዝ73፥27፤78፥37፤106፥39ኤር3፥2፤7፥24፤ሕዝ20፥16፤ሆሴ4፥12
15፥40 ዘፍ26፥5፤ዘሌ11፥44፤ዘዳ11፥13፤መዝ103፥18፤119፥56፤ሮሜ12፥1፤ቈላ1፥22፤1ጴጥ1፥15
15፥41 ዘፍ17፥7፤ዘፀ20፥2
16፥1 ቍ24፤ዘፀ6፥24፤ዘኍ26፥8፤ዘዳ11፥6፤መዝ106፥17፤ይሁ1፥11
16፥2 ዘኍ1፥16፤26፥9፤27፥3
16፥3 ቍ7፤ዘፀ19፥6፤ዘኍ12፥2፤14፥14፤መዝ106፥16
16፥4 ዘኍ14፥5
16፥5 ዘሌ10፥3፤ዘኍ17፥5፤መዝ65፥4፤105፥26፤ኤር30፥21፤50፥44፤2ጢሞ2፥19
16፥6 ቍ7፡16፤ዘሌ10፥1፤ራእ8፥3
16፥7 ቍ5፡6፤ዘሌ10፥1፤ዘፀ30፥9
16፥9 ዘፍ30፥15፤ዘኍ3፥6፤ዘዳ10፥8፤17፥12፤21፥5፤1ሳሙ2፥11፤መዝ134፥1፤ሕዝ44፥11
16፥10 ዘኍ3፥10፤18፥7፤መሳ17፥5፡12
16፥11 ቍ41፤ዘፀ

አባሪ ተባባሪ ሆናችሁ የተነሣችሁት በእግዚ
አብሔር (ያህዌ) ላይ ነው፤ ለመሆኑ ታጕ
ረመርሙበት ዘንድ አሮን ማነው?”
12ከዚያም ሙሴ የኤልያብን ልጆች ዳታ
ንና አቤሮንን አስጠራቸው፤ እነርሱ ግን
እንዲህ አሉ፤ “እኛ አንመጣም! 13በምድረ
በዳ ልትገድለን ማርና ወተት ከምታፈ
ሰው ምድር ያወጣኸን አይበቃህም? አሁን
ደግሞ በእኛ ላይ ጌታ መሆን ያምርሃል?
14ከዚህም በቀር አንተ ማርና ወተት ወደ
ምታፈሰው ምድር አላመጣኸንም፤ ወይም
ዕርሻዎችንና የወይን ተክል ቦታዎች አላወ
ረስከንም፡፡ ታዲያ የእነዚህን ሰዎች ዐይን
ታወጣለህን?[ጸ] በጭራሽ አንመጣም!”
15ሙሴም በጣም ተቈጣ፤ እግዚአብሔር
ንም (ያህዌ) “ቍርባናቸውን አትቀበል፤ እኔ
ከእነዚህ ሰዎች የወሰድኩት አንድ አህያ እንኳ
የለም፤ አንዳቸውንም አልበደልሁም” አለ፡፡
16ሙሴም ቆሬን እንዲህ አለው፤ “አን
ተና ተከታዮችህ እንዲሁም አሮን ነገ በእ
ግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ትቀርባላችሁ፡፡ 17እያ
ንዳንዱም ሰው ጥናውን ይወስዳል፤ ባጠ
ቃላይ ሁለት መቶ አምሳ ጥናዎች ይሆናሉ፤
በዚያም ላይ ዕጣን ጨምሮ በእግዚአብሔር
(ያህዌ) ፊት ያቀርባል፤ አንተና አሮንም ጥና
ዎቻችሁን እንደዚሁ ታቀርባላችሁ፡፡ 18እያን
ዳንዱ ሰው ጥናውን በመያዝ ፍም አድር
ጎበት፣ ዕጣን ጨምሮበት ከሙሴና ከአሮን
ጋር በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ቆመ፡፡
19ቆሬም እነርሱን በመቃወም ተከታዮቹን
ሁሉ በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ በሰበሰ
ባቸው ጊዜ፣ የእግዚአብሔር (ያህዌ) ክብር
ለመላው ማኅበር ተገለጠ፡፡ 20እግዚአብሔ
ርም (ያህዌ) ሙሴንና አሮንን እንዲህ አላ
ቸው፤ 21“ሁሉንም በአንድ ጊዜ እንዳጠፋ
ቸው እናንተ ከዚህ ማኅበር ተለዩ፡፡”
22ሙሴና አሮን ግን በግንባራቸው
ተደፍ ተው፣ “የሰብአዊ ፍጡር ሁሉ
መንፈስ አምላክ (ኤሎሂም) የሆንህ እግዚአብሐ
ር (ያህዌ) ሆይ፤ አንድ ሰው ኀጢአት በሠራ
በመላው ማኅበር ላይ ትቈጣለህን?” ሲሉ
ጮኹ፡፡
23ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን
እንዲህ አለው፤ 24“ማኅበሩን ‘ከቆሬ፣ ከዳ
ታንና ከአቤሮን ድንኳኖች ራቁ’ በላቸው፡፡”
25ሙሴ ተነሥቶ ወደ ዳታንና አቤሮን ሄደ፤
የእስራኤልም ሽማግሌዎች ተከተሉት፡፡ 26እር
ሱም፣ “ከእነዚህ ክፉ ሰዎች ድንኳን
ራቁ! የእነርሱ የሆነውን ማንኛውንም
ነገር አትንኩ፤ ያለበለዚያ በእነርሱ ኀጢ
አት ሁሉ እናንተም ትጠፋላችሁ” ሲል ማኅ
በሩን አስጠነቀቀ፡፡ 27ስለዚህ እነርሱ ከቆሬ፣
ከዳታንና ከአቤሮን ድንኳን ራቁ፡፡ ዳታንና
አቤሮን ወጥተው ከሚስቶቻቸው፣
ከልጆቻቸ ውና ከሕፃናቶቻቸው ጋር
በየድንኳኖቻቸው ደጃፍ ላይ ቆመው ነበር፡፡
28ሙሴም እንዲህ አለ፤ “እነዚህን ነገ
ሮች ሁሉ እንዳደርግ እግዚአብሔር (ያህዌ)
እንደ ላከኝና ከራሴም እንዳይደለ በዚህ
ታውቃላችሁ፤ 29እነዚህ ሰዎች እንደማንኛ
ውም ሰው አሟሟት የሚሞቱ ቢሆኑና
በሌሎች ሰዎች ላይ የሚደርሰው ብቻ የሚ
ደርስባቸው ከሆነ፣ እኔን እግዚአብሔር (ያህዌ)
አልላከኝም፡፡ 30ይሁን እንጂ እግዚአብሔር (ያህዌ)
ፈጽሞ አዲስ የሆነ ነገር አምጥቶ ምድር
አፏን ከፍታ እነርሱንና የእነርሱ የሆነ
ውን ሁሉ ብትውጥና በሕይወታቸው ወደ
መቃብር[ፀ] ቢወርዱ፣ ሰዎቹ እግዚአብሔ
ርን (ያህዌ) የናቁ መሆናቸውን የምታውቁት
ያን ጊዜ ነው፡፡”
31ይህን ሁሉ ተናግሮ እንደ ጨረሰ የቆ
ሙባት ምድር ተሰነጠቀች፤ 32አፏንም ከፍታ
ሰዎቹን ከነቤተ ሰቦቻቸው እንዲሁም የቆሬን
ሰዎች በሙሉ፣ ንብረታቸውንም ሁሉ ዋጠች፡፡
33እነርሱም ካላቸው ከማናቸውም ነገር ጋር
ከነሕይወታቸው ወደ መቃብር ወረዱ፤ ምድ
ራቱም በላያቸው ተከደነችባቸው፤ ጠፉ፤ ከማ
ኅበረ ሰቡም ተወገዱ፡፡ 34ከጩኸታቸውም
የተነሣ በአካባቢያቸው የነበሩት እስራኤላ
ውያን ሁሉ፣ “ምድሪቱ እኛንም እኮ ልት
ውጠን ነው” ብለው ሸሹ፡፡
35እሳትም ከእግዚአብሔር (ያህዌ) ዘንድ ወርዳ
የሚያጥኑትን ሁለት መቶ አምሳ ሰዎች
በላቻቸው፡፡
36እግዚአብሔርም (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 37“ጥናዎቹ የተቀደሱ ናቸውና
ከተቃጠሉት ሰዎች ዘንድ ወስደህ በውስ
ጣቸው ያለውን ፍም አርቆ እንዲደፋ ለካ
ህኑ ለአሮን ልጅ ለአልዓዛር ንገረው፤ 38እነዚ
ህም ሕይወታቸውን ለማጥፋት ኀጢአት የሠሩ
ሰዎች ጥና ናቸው፤ ጥናዎቹም በእግዚአብሔር
(ያህዌ) ፊት የቀረቡና የተቀደሱ በመሆናቸው
ለመሠዊያው መለበጫ እንዲሆኑ ቀጥቅጠህ
አሣሣቸው፤ እነዚህም ለእስራኤላውያን ማስ
ጠንቀቂያ ይሁኑ፡፡”
39ከዚህ የተነሣም ካህኑ አልዓዛር የተ
ቃጠሉት ሰዎች አምጥተዋቸው የነበሩትን
የናስ ጥናዎች ሰብስቦ የመሠዊያው መለ
በጫ እንዲሆኑ ቀጠቀጣቸው፤ 40ይህን ያደ
ረገውም፣ እግዚአብሔር (ያህዌ) በሙሴ አማ
ካይነት ባዘዘው መሠረት ነው፤ ይህም
ከአሮን ዘር በስተቀር ማንም ሰው በእግዚ
አብሔር (ያህዌ) ፊት ቀርቦ ዕጣን እንዳያጥን

16፥7፤1ቆሮ10፥10
16፥12 ቍ1፥14፡27
16፥13 ዘፍ13፥8፤ ዘኍ13፥27፤14፥2፤ ሐሥ7፥27፡35
16፥14 ቍ12፤ዘፀ 22፥5፤23፥11፤ዘሌ20፥ 24፤23፥11፤ዘኍ20፥5፤ መሳ16፥21፤1ሳሙ 11፥2፤1ነገ4፥25፤ነህ 13፥15፤መዝ105፥33፤ ኤር5፥17፤39፥7፤ሆሴ2 ፥12፤ኢል2፥22፤ ሐጌ2፥19፤ዘካ3፥10
16፥15 ዘፀ4፥14፤ 1ሳሙ12፥3
16፥16 ቍ6
16፥17 ሕዝ8፥11
16፥18 ዘሌ10፥1
16፥19 ቍ42፤ዘፀ 16፥7፤ዘኍ14፥10፤ 20፥2፤6
16፥21 ቍ24፤ዘፍ 19፥14፤ዘፀ32፥10
16፥22 ዘፍ18፥23፤ ዘሌ10፥6፤ዘኍ14፥5፤2 7፥16፤ኢዮ12፥10፤ 21፥20፤27፥8፤33፥4፤3 4፥14፤ኤር32፥27፤ ሕዝ18፥4፤ዕብ12፥9
16፥25 ዘፀ19፥7
16፥26 ዘፍ19፥15፤ ኢሳ52፥11፤ኤር51፥6
16፥27 ቍ12፡32፤ ዘፀ33፥8፤ኢሱ7፥24፤ ኢሳ13፥16፤14፥21
16፥28 ዘፀ3፥12፤ 1ነገ18፥36፤ዮሐ5፥36፤ 6፥38
16፥29 ዘኍ24፥13፤ ኢዮ31፥2፤መክ3፥19
16፥30 ቍ33፤ዘፍ 37፥35፤ዘኍ14፥11፤1 ሳሙ2፥6፤ኢዮ5፥26፤ 21፥13፤መዝ9፥17፤16፥ 10፤55፥15፤141፥7፤ኢ ሳ5፥14፤14፥11፤ 38፥18፤ሕዝ26፥20
16፥31 ኢሳ64፥1-2 ፤ሕዝ47፥1-12፤ ሚክ1፥3-4፤ዘካ14፥4
16፥32 ዘፀ15፥12
16፥33 ቍ30፤ መክ9፥10
16፥35 ዘሌ10፥2፤ ዘኍ11፥1-3፤26፥10፤ ራእ11፥5
16፥37 ቍ6፤ዘፀ 6፥23
16፥38 ዘፀ20፥24፤ 38፥1-7፤ዘሌ10፥1፤ ዘኍ26፥10፤ዘዳ28፥46 ፤ምሳ20፥2፤ኤር44፥ 29፤ሕዝ14፥8፤ 2ጴጥ2፥6
16፥39 ዘሌ20፥14፤ 2ዜና26፥18
16፥40 ዘፀ30፥1፡9፤ ዘኍ3፥102ኛዜና26፥1 8፤2ነገ12፥3፤2ዜና26፥ 18፤ኢሳ1፥13፤ 66፥3፤ኤር41፥5፤ 44፥3

[ጸ]14 ባሪያ ታደርጋቸዋለህ፤ ወይም ታታላቸዋለህ ማለት ነው፡፡
[ፀ]30 በዕብራይስጥ ሲኦል ማለት ነው፡፡

ያለበለዚያ ግን፣ እንደ ቆሬና እንደ ተከ
ታዮቹ እንደሚሆን ለእስራኤላውያን የተሰጠ
ማስጠንቀቂያ ነበር።
41በማግሥቱም መላው የእስራኤል ማኅ
በረ ሰብ፣ "እናንተ *የእግዚአብሔርን* (ያህዌ)
ሕዝብ ገድላችኋል" በማለት በሙሴና በአ
ሮን ላይ አጕረመረሙ።
42ማኅበሩም ሙሴንና አሮንን ለመቃ
ወም በተሰበሰቡ ጊዜ ወደ መገናኛው ድን
ኳን ዘወር ሲሉ ደመና ድንኳኑን በድንገት
ሸፍኖት አዩ፤ *የእግዚአብሔርም* (ያህዌ)
ክብር ተገለጠ። 43ከዚያም ሙሴና አሮን
ወደ መገናኛው ድንኳን ፊት ለፊት ሄዱ።
44*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 45"በቅጽበት አጠፋቸዋለሁና ከዚህ
ማኅበር ራቅ"እነርሱም በግንባራቸው ተደፉ።
46ከዚያም ሙሴ አሮንን፣ "*ከእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ዘንድ ቍጣ ወጥቶ መቅሠፍት ጀም
ሮአልና ጥናውን ወስደህ ዕጣን በመጨ
መር ከመሠዊያው እሳት አድርግበት፤ ፈጥ
ነህም ወደ ማኅበሩ ሄደህ አስተሰርይላቸው"
አለው። 47ስለዚህ አሮን፣ ሙሴ በነገረው
መሠረት ወደ ማኅበሩ መካከል ሮጦ ገባ፤
መቅሠፍቱም ቀደም ብሎ በሕዝቡ መካ
ከል መስፋፋት ጀምሮ ነበር፤ ሆኖም አሮን
ዕጣኑን ዐጥኖ አስተሰረየላቸው። 48እርሱም
በሕይወት ባሉትና በሞቱት መካከል ቆመ፤
መቅሠፍቱም ተከለከለ። 49ይሁን እንጂ በቆሬ
ምክንያት የሞቱትን ሳይጨምር ዐሥራ አራት
ሺህ ሰባት መቶ ሰዎች ተቀሥፈው ሞቱ።
50ከዚያም መቅሠፍቱ ቆመ፤ አሮንም ሙሴ
ወዳለበት ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ ተመ
ለሰ።

### የአሮን በትር ማቈጥቈጥ

**17** *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2"ለእስራኤላውያን ንገራቸ
ውና ከየነገዱ አለቆች አንዳንድ፣ ባጠቃ
ላይ ዐሥራ ሁለት በትር ተቀበል፤ የያንዳን
ዱንም ሰው ስም በየበትሩ ላይ ጻፈው።
3ለያንዳንዱ የነገድ አለቃ አንዳንድ በትር
መኖር ስላለበት በሌዊ በትር ላይ የአሮ
ንን ስም ጻፍ። 4በትሮቹንም እኔ ከአንተ
ጋር በምገናኝበት በመገናኛው ድንኳን
ውስጥ ከምስክሩ ፊት ለፊት አስቀምጣ
ቸው። 5እኔ የምመርጠው ሰው በትርም
ታቈጠቍጣለች፤ እስራኤላውያን በእናንተ
ላይ ነጋ ጠባ የሚያደርጉትንም ማጕረም
ረም በዚህ እገታለሁ።
6ሙሴም ለእስራኤላውያን ተናገራቸው፤
አለቆቻቸውም በቀደሙት በያንዳንዱ አባ
ቶች ስም ዐሥራ ሁለት በትር ሰጡት፤

16፥42 ቍ19፤ዘፀ 16፥7፤ዘኍ14፥10
16፥45 ዘፀ32፥10
16፥46 ዘፀ29፥36፤ ዘሌ10፥1፡6፤26፥25፤ ዘኍ1፥53፤8፥19፤መዝ 106፥29
16፥47 ዘኍ25፥6-8
16፥48 ዘኍ25፥8፤ መዝ106፥30
16፥49 ቍ32
17፥2 ዘፍ32፥10፤ ዘፀ4፥2፤ዘኍ1፥4
17፥3 ዘኍ1፥3
17፥4 ቍ7፤ዘፀ 16፥34፤25፥22፤40፥2
17፥5 ቍ8፤ዘፀ 16፥7፤ዘኍ16፥5
17፥7 ዘፀ38፥21
17፥8 ቍ2፡7፡10፤ ዘኍ1፥50፤ሕዝ 17፥24፤ዕብ9፥4
17፥9 ቍ2
17፥10 ቍ8፤ዘፀ 23፥21፤ዘዳ9፥24፤መዝ 66፥7፤68፥18፤ምሳ 24፥21
17፥12 መሳ13፥22፤ ኢሳ6፥5፤15፥1
17፥13 ዘኍ1፥51
18፥1 ዘፀ28፥38
18፥2 ዘኍ3፥10
18፥3 ቍ7፤ዘኍ 1፥51፤3፥32
18፥4 ዘኍ3፥38
18፥5 ቍ3፤ ዘሌ6፥12

የአሮን በትርም በበትሮቹ መካከል ነበ
ረች። 7ሙሴም በትሮቹን ወስዶ በምስክሩ
ድንኳን ውስጥ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት አኖ
ራቸው።
8በማግስቱ ሙሴ ወደ ምስክሩ ድንኳን
ሲገባ በሌዊ ቤት ስም የቀረበችው የአሮን
በትር ማቈጥቈጥ ብቻ ሳይሆን እንቡጥ
አውጥታ፣ አብባና ለውዝ አፍርታ አገኛት።
9ከዚያም ሙሴ በትሮቹን *ከእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ፊት አውጥቶ ወደ እስራኤላውያን
ሁሉ አመጣቸው፤ እነርሱም አዩ፤ እያንዳን
ዱም ሰው የየራሱን በትር ወሰደ።
10*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን፣ "የአሮን
በትር ለዐመፀኞቹ ምልክት እንድትሆን መል
ሰህ በምስክሩ ፊት ለፊት አኑራት፤ እነ
ርሱ እንዳይሞቱም በእኔ ላይ የሚያደርጉትን
ማጕረምረም ይህ ይገታዋል" አለው።
11ሙሴም ልክ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
እንዳዘዘው አደረገ።
12ከዚያም እስራኤላውያን ሙሴን እንዲህ
አሉት፤ "እነሆ መሞታችን ነው! ጠፋን፤
ሁላችንም መጥፋታችን ነው! 13ወደ *እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ማደሪያ የሚጠጋ እንኳ
ማንኛውም ሰው ቢሆን ይሞታል፤ ሁላች
ንም ልንጠፋ ነው እንዴ?"

### የካህናትና የሌዋውያን ተግባር

**18** *እግዚአብሔር* (ያህዌ) አሮንን እንዲህ
አለው፤ "መቅደሱን በተመለከተ
ስለ ሚፈጸም በደል አንተ፣ ልጆችህና
የአባትህ ቤተ ሰቦች ኀላፊነቱን ትሸከማላ
ችሁ፤ ክህነቱን በተመለከተ ስለሚፈጸም
በደል ግን ኀላፊነቱ የሚወድቀው በአን
ተና በልጆችህ ላይ ብቻ ነው። 2አንተና
ልጆችህ በምስክሩ ድንኳን ፊት በምታገለ
ግሉበት ጊዜ አብረዋችሁ እንዲሆኑና እንዲ
ረዱአችሁ ከአባትህ ነገድ ሌዋውያንን
አምጣቸው። 3እነርሱም በአንተ ኀላፊነት
ሥር ሆነው የድንኳኑን አገልግሎት በሙሉ
ያከናውኑ፤ ይሁን እንጂ ወደ መቅደሱ
ዕቃዎችም ሆነ ወደ መሠዊያው አይጠጉ፤
ከተጠጉ ግን እነርሱም አንተም ትሞታላ
ችሁ። 4እነርሱም የመገናኛውን ድንኳን
ለመንከባከብ ማለትም በድንኳኑ ውስጥ
የሚሠራውን ሥራ ሁሉ ኀላፊነት በመው
ሰድ አብረዋችሁ ይሁኑ፤ ከዚህ በተረፈ
ግን እናንተ ወዳላችሁበት ማንም ሰው
አይጠጋ።
5"በእስራኤላውያን ላይ ዳግም ቍጣ እን
ዳይደርስባቸው የመቅደሱና የመሠዊያው
እንክብካቤ ኀላፊነት የሚመለከተው እናን
ተን ይሆናል። 6ከእስራኤላውያን መካከል
ወገኖቻችሁን ሌዋውያንን ለእናንተ ስጦታ

አድርጌ እኔ ራሴ መርጫቸዋለሁ፤ በመገና
ኛው ድንኳን ውስጥ የሚከናወነውን ሥራ
ሁሉ እንዲሠሩ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) የተ
ሰጡ ናቸው:: 7ይሁን እንጂ በመሠዊያው
ላይ የሚደረገውንና በመጋረጃ ውስጥ ያለ
ውን ማንኛውንም የክህነት አገልግሎት
የምትፈጽሙት አንተና ልጆችህ ብቻ ናችሁ፤
የክህነቱን አገልግሎት ስጦታ አድርጌ ሰጥ
ቻችኋለሁ:: ከእናንተ በስተቀር ወደ መቅ
ደሱ የሚጠጋ ቢኖር ግን ይገደል::"

## ለካህናትና ለሌዋውያን የሚሰጡ መባዎች

8ከዚያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) አሮንን እን
ዲህ አለው፤ "ለእኔ በሚቀርበው መባ ላይ
ኀላፊነትን የሰጠሁህ እኔው ራሴ ነኝ፤ እስ
ራኤላውያን የሚያቀርቡልኝም የተቀደሰ
መባ ሁሉ ለአንተና ለልጆችህ መደበኛ ድር
ሻችሁ እንዲሆን ሰጥቻችኋለሁ:: 9ለእኔ
ከሚቀርብልኝ እጅግ ከተቀደሰው መባ
ሁሉ፣ በእሳት የማይቃጠለው የራስህ ድርሻ
ይሆናል፤ እጅግ የተቀደሰ አድርገው ከሚ
ያመጡልኝ ስጦታ ከእህል ቍርባንም ሆነ
ከኀጢአት ወይም ከበደል መሥዋዕት የሚ
ነሣው ሁሉ የአንተና የልጆችህ ድርሻ ነው::
10እጅግ ቅዱስ መሆኑን በማሰብ በተቀደሰ
ስፍራ ብላው፤ እያንዳንዱም ወንድ ከዚሁ
ይብላ፤ ይህ ለአንተም የተቀደሰ ነው::
11"እስራኤላውያን ከሚያቀርቡት ስጦታ፣
ከሚወዘወዘው ቍርባን ተለይቶ የሚቀ
መጠው ስጦታ ሁሉ የአንተ ይሁን:: ይህ
ንም ለአንተ፣ ለወንድና ለሴት ልጆችህ
መደበኛ ድርሻ አድርጌ ሰጥቻችኋለሁ:: ከቤተ
ሰዎችህ በሥርዐቱ መሠረት የነጻ ማንኛውም
ሰው ከዚሁ መብላት ይችላል::
12"እስራኤላውያን የመከር በኵራት
አድ ርገው *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) የሚሰጡትን
ምርጥ የወይራ ዘይት በሙሉ፣ ምርጥ
የሆነውን አዲስ የወይን ጠጅና እህል ሁሉ
ለእናንተ ሰጥቻችኋለሁ:: 13*ለእግዚአብሔር*
(ያህዌ) የሚያ መጡት የምድሪቱ በኵር ፍሬ
ሁሉ የአ ንተ ይሆናል:: ከቤተ ሰዎችህ
በሥርዐቱ መሠረት ንጹሕ የሆነ
ማንኛውም ሰው ይህን መብላት ይችላል::
14"*ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፈጽሞ የተሰጠ[ፊ]
በእስራኤል ያለ ማንኛውም ነገር ሁሉ የአ
ንተ ነው:: 15ማሕፀን የሚከፍትና *ለእግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) የተሰጠ ሰውም ሆነ እንስሳ
የአንተ ነው፤ ነገር ግን ማንኛውም በኵር
ሆኖ የተወለደውን ወንድ ልጅና ንጹሕ
ካልሆነ እንስሳ በኵር ሆኖ የተወለደውን
ተባዕት ሁሉ ዋጀው:: 16እነዚህም አንድ ወር
ሲሆናቸው ሃያ ጌራ በሚመዝነው በቤተ
መቅደሱ ሰቅል[ፐ] ልክ፣ በተወሰነው በመዋጃው

18፥6 ዘኍ3፥8፡9
18፥7 ቀ-3፡20፤ዘፀ 29፥9፤40፥13፤ዘኍ 3፥10፤ዕብ5፥4፤9፥3፡6
18፥8 ዘፀ18፥1፤ ዘሌ2፥2፤6፥16፤7፥6፡31 -34፡36፤ዘዳ 18፥1፤2ዜና31፥4
18፥9 ዘሌ2፥1፤ 5፥15፤6፥17፡25
18፥10 ዘሌ6፥16፡17፡18
18፥11 ዘፀ29፥26፤ ዘሌ7፥30፡31-34፤ 13፥3፤22፥1-16፤ ዘኍ6፥20
18፥12 ዘፍ4፥3፤ዘፀ 23፥19፤34፥26፤ዘፀ 7፥13፤11፥14፤12፥17፤ 28፥51፤2ነገ18፥32፤ 2ዜና31፥5፤ነህ10፥35፡ 37፤ኤር31፥12፤ሕዝ 23፥41፤ሆሴ2፥8፤ኢል 1፥10፤ሐጌ1፥11
18፥13 ቀ-11፤ ዘፀ29፥27
18፥14 ዘሌ27፥21፤ ኢሱ6፥17-19
18፥15 ዘፍ10፥15፤ ዘፀ13፥2፡13፤ ዘኍ3፥46
18፥16 ዘፀ30፥13፤ ዘሌ27፥6፤ዘኍ3፥15፡47
18፥17 ዘፀ29፥13፤ ዘሌ1፥9፤3፥2፤27፥9
18፥18 ቀ-11፤ ዘሌ7፥30
18፥19 ዘሌ2፥13፤ 2ነገ12፥4
18፥20 ቀ-24፤ዘኍ 26፥62፤ዘዳ10፥9፤12፥1 2፤14፥27፤18፥1-2፤ ኢሱ13፥33፤ሕዝ 44፥28
18፥21 ቀ-24፤ዘፍ 28፥22፤ዘሌ27፥30- 33፤ዘኍ1፥53፤31፥28፤ ዘዳ14፥22፤ነህ10፥37፤ 13፥5፤ሚል3፥8፤ ዕብ7፥5
18፥22 ዘፀ28፥43
18፥23 ቀ-20፤ዘፀ 12፥14፤27፥21፤ዘኍ 10፥8፤26፥62፤ ዘዳ10፥9፤ሕዝ44፥10
18፥24 ዘሌ27፥30፤ ዘዳ26፥12
18፥26 ቀ-21፡28፤ ነህ10፥38
18፥27 ቀ-12፡30፤ ዘፍ50፥10፤ዘሌ7፥18፤ዘ ዳ15፥14፤መሳ6፥37፤ሩ ት3፥3፡6፡14፤ 1ሳሙ23፥1

ዋጋ በአምስት ሰቅል ጥሬ ብር ትዋጀዋለህ::
17"የተቀደሱ ስለሆኑ የበሬ፣ የበግ ወይም
የፍየል በኵር የሆኑትን አትዋጃቸውም፤ ደ
ማቸውን በመሠዊያው ላይ ትረጨዋለህ፤
ሥባቸውንም ሽታው *እግዚአብሔርን* (ያህዌ)
ደስ የሚያሰኝ እንዲሆን በእሳት የሚቀርብ
መሥዋዕት አድርገህ ታቃጥለዋለህ:: 18የሚወ
ዘወዘው ቍርባን ፍርምባና የቀኙ ወርች
የአንተ እንደ ሆነ ሁሉ የእነዚህም ሥጋ
የአንተ ይሆናል:: 19እስራኤላውያን *ለእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ከሚያቀርቡት ከተቀደሰ
ቍርባን የሚለየው ሁሉ ለአንተ፣ ለወን
ድና ለሴት ልጆችህ መደበኛ ድርሻ አድ
ርጌ ሰጥቻችኋለሁ፤ ይህም *በእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ፊት ለአንተና ለዘሮችህ ዘላለማዊ
የጨው ኪዳን ነው::"
20*እግዚአብሔር* (ያህዌ) አሮንን እንዲህ አለው፤
"ከምድራቸው የምትካፈለው ርስት፣ ከእነ
ርሱም የምታገኘው ድርሻ የለህም፤ በእስራ
ኤላውያን መካከል ድርሻህና ርስትህ እኔ
ነኝ::
21"በመገናኛው ድንኳን በሚያገለግሉበት
ጊዜ ለሚሠሩት ሥራ ደመወዝ እንዲሆና
ቸው ከእስራኤል የሚወጣውን ዐሥራት ሁሉ
ለሌዋውያን ርስት አድርጌ ሰጥቻቸዋለሁ::
22አድራጎቱ ኀጢአት ስለ ሆነ ሞት እንዳ
ያስከትልባቸው ከእንግዲህ ወዲያ እስራኤ
ላውያን ወደ መገናኛው ድንኳን አይጠጉ::
23በመገናኛው ድንኳን የሚከናወነውን ሥራ
የሚሠሩት ሌዋውያን ናቸው፤ በዚያም ለሚ
ፈጸመው በደል ኀላፊነቱን ይሸከማሉ:: ይህም
ለሚመጡት ትውልዶች የዘላለም ሥርዐት
ነው፤ ሌዋውያን በእስራኤላውያን መካከል
ርስት አይሰጣቸውም:: 24በዚህ ፈንታም
እስራኤላውያን መባ አድርገው *ለእግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) የሚያቀርቡትን ዐሥራት ለሌዋ
ውያን ርስት አድርጌ ሰጥቻቸዋለሁ፤ እኔም
እነርሱን በተመለከተ፣ 'በእስራኤላውያን
መካከል ርስት አይኖራቸውም' ያልኩት
በዚሁ ምክንያት ነው::"
25*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤
26"ሌዋውያንን ተናገራቸው፤ እንዲህም በላ
ቸው፤ 'ርስት አድርጌ የምሰጣችሁን ዐሥራ
ት ከእስራኤላውያን በምትቀበሉበት ጊዜ፣
እናንተ ተም ካገኛችሁት ላይ አንድ ዐ
ሥርኛ በማ ውጣት *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) መባ
አድርጋችሁ ታቀርባላችሁ:: 27ቍርባናችሁም
ከዐውድማ እንደ ገባ እህል ወይም
ከመጭመቂያ እንደ

[ፊ]14 የዕብራይስጡ ትርጕም አንድን ነገር ወይም አንድን ሰው በማይለወጥ ውሳኔ ለእግዚአብሔር መስጠትን ያመለክታል::
[ፐ]16 አምሳ አምስት ግራም ያህል ነው::

ወጣ ወይን ሆኖ ይቈጠርላችኋል። 28እና
ንተም ከእስራኤላውያን ላይ ከምትቀበሉት
ዐሥራት ሁሉ በዚሁ ዐይነት ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) መባ ታቀርባላችሁ፤ ከዚሁም የእግዚአ
ብሔር (ያህዌ) ድርሻ የሆነውን ዐሥራት ለካህኑ
ለአሮን ትሰጣላችሁ። 29ከምትቀበሉት
ሁሉ ምርጥና እጅግ የተቀደሰውን ክፍል
የእግ ዚአብሔር (ያህዌ) ድርሻ አድርጋችሁ
ታቀር ባላችሁ።

30"ሌዋውያንን እንዲህ በላቸው፤ 'ምርጥ
የሆነውን ክፍል በምታቀርቡበት ጊዜ፣ እንደ
ዐውድማ ምርት ወይም እንደ ወይን መጭ
መቂያ ውጤት ሆኖ ይቈጠርላችኋል።
31የቀረው ግን በመገናኛው ድንኳን ለሰጣ
ችሁት አገልግሎት ደመወዛችሁ ስለ ሆነ፣
እናንተና ቤተ ሰዎቻችሁ በየትኛውም ስፍራ
ልትበሉት ትችላላችሁ። 32የተመረጠውን
ክፍል ካቀረባችሁ በዚህ በደለኞች አትሆ
ኑም፤ ደግሞም የተቀደሰውን የእስራኤላው
ያንን መባ አታረክሱም፤ አትሞቱምም።

## የመንጻት ሥርዐት ውሃ

19 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴንና አሮ
ንን እንዲህ አላቸው፤ 2"እግዚአብሔር
(ያህዌ) ያዘዘው፣ ሕጉ የሚጠይቀው ሥርዐት
ይህ ነው፤ እንከን ወይም ነውር የሌለባት
ንና ቀንበር ተጭኖባት የማያውቅ አንዲት
ቀይ ጊደር እንዲያመጡልህ ለእስራኤላው
ያን ንገራቸው። 3ለካህኑ ለአልዓዛርም ስጠ
ው፤ ከሰፈሩ አውጥተውም በፊቱ
ይረድዋት። 4ከዚያም ካህኑ አልዓዛር ጣቱን
በደሙ ውስጥ ነክሮ፣ ወደ መገናኛው
ድንኳን ፊት አቅ ጣጫ ሰባት ጊዜ
ይርጨው። 5እርሱ እየተ መለከተም ጊ
ደሯን ያቃጥሏት፤ ቈዳዋም፣ ሥጋዋም፣
ደሚም፣ ፈርሷም ጭምር ይቃጠል። 6ካህኑ
የዝግባ ዕንጨት፣ ሂሶጵና ብሩህ ቀይ ክር
ወስዶ ጊደሪቱ በምትቃጠልበት እሳት
ውስጥ ይጨምር። 7ከዚህ በኋላ ካህኑ
ልብሱን በውሃ ማጠብ፣ ሰውነቱንም መታጠብ
አለበት፤ ከዚያም ወደ ሰፈሩ ሊመለስ ይች
ላል፤ ይሁን እንጂ በሥርዐቱ መሠረት እስከ
ማታ ድረስ የረከሰ ይሆናል። 8የሚያቃጥ
ለውም ሰው እንደዚሁ ልብሱን ማጠብ፣ ሰው
ነቱንም በውሃ መታጠብ አለበት፤ እርሱም
ደግሞ እስከ ማታ ድረስ የረከሰ ይሆናል።

9"ንጹሕ የሆነ ሰው የጊደሯን ዐመድ አፍሶ
ከሰፈሩ ውጭ በመውሰድ በሥርዐቱ መሠ
ረት ንጹሕ በሆነ ስፍራ ያኑረው፤ ይህም
ለመንጻቱ ውሃ እንዲውል በእስራኤል ማኅ
በረ ሰብ የሚጠበቅ ይሆናል፤ ከኀጢአትም
ለመንጻት ይጠቅማል። 10የጊደሯን ዐመድ
የሚያፈሰውም ሰው እንደዚሁ ልብሱን ማጠብ
አለበት፤ ያም ሰው እስከ ማታ ድረስ የረከሰ
ይሆናል፤ ይህም ለእስራኤላውያን እንዲ
ሁም በመካከላቸው ለሚኖሩ መጻተኞች
የሚሆን ዘላለማዊ ሥርዐት ነው።

11"የሞተን ሰው በድን የሚነካ ማን
ኛውም ሰው እስከ ሰባት ቀን የረከሰ ይሆ
ናል። 12በሦስተኛውና በሰባተኛውም ቀን
ሁለመናውን በውሃው ያንጻ፤ ንጹሕም
ይሆናል። በሦስተኛውና በሰባተኛው ቀን
ሁለመናውን ካላነጻ ግን ንጹሕ አይሆንም።
13የሞተን ሰው በድን ነክቶ ራሱን ያላነጻ
ማንኛውም ሰው የእግዚአብሔርን (ያህዌ)
ማደሪያ ያረክሳል፤ ያም ሰው ከእስራኤል
ተለይቶ ይጥፋ። የሚያነጻው ውሃ ስላል
ተረጨበት ርኩስ ነው፤ ከርኩሰቱም አል
ተላቀቀም።

14"አንድ ሰው በድንኳን ውስጥ በሚሞ
ትበት ጊዜ የሚፈጸመው ሥርዐት የሚከ
ተለው ነው፤ ወደ ድንኳኑ የሚገባም ሆነ
በዚያ ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው እስከ
ሰባት ቀን ድረስ የረከሰ ይሆናል፤ 15እንዲ
ሁም ያልተከደነ ማንኛውም ክፍት ዕቃ
የረከሰ ይሆናል።

16"ሜዳ ላይ በሰይፍ የተገደለውን ወይም
እንዲሁ የሞተውን ወይም ደግሞ ዐፅም ወይም
መቃብር የሚነካ ማንኛውም ሰው እስከ
ሰባት ቀን ድረስ የረከሰ ይሆናል።

17"ለረከሰውም ሰው፣ ለማንጻት
ከተቃጠለው የጊደር ዐመድ ላይ ማሰሮ
ውስጥ በማ ድረግ በላዩ የምንጭ ውሃ
ይጨምሩበት። 18ከዚያም በሥርዐቱ መ
ሠረት ንጹሕ የሆነ ሰው ሂሶጵ ወስዶ
በውሃው ውስጥ ከነከ ረው በኋላ
ድንኳኑን፣ በውስጡ ያሉ ትን ዕቃዎች
ሁሉ፣ እዚያ የነበሩትንም ሰዎች ሁሉ
ይርጫቸው። እንዲሁም የሰው
ዐፅም ወይም መቃብር ወይም ደግሞ የተገ
ደለውን ወይም እንዲሁ የሞተውን ሰው
የነካው ማንኛውንም ሰው ይርጭ። 19የነጻው
ሰው ያልነጻውን ሰው በሦስተኛውና በሰባ
ተኛው ቀን ይርጨው፤ በሰባተኛው ቀን ያን
ጻው፤ የሚነጻውም ሰው ልብሱን ይጠብ፤
ገላውንም በውሃ ይታጠብ፤ ማምሻውም ላይ
የነጻ ይሆናል። 20ይሁን እንጂ አንድ የረከሰ
ሰው ራሱን ሳያነጻ ከቀረ የእግዚአብሔርን
(ያህዌ) መቅደስ አርክሶአልና ከማኅበረ ሰቡ
ተለይቶ ይጥፋ፤ የሚያነጻው ውሃ ያልተረ
ጨበት ስለ ሆነ ርኩስ ነው። 21ይህም ለእ
ነርሱ የዘላለም ሥርዐት ነው።

"የሚያነጻውን ውሃ የሚረጨውም ሰው
ልብሱን ይጠብ፤ የሚያነጻውንም ውሃ የሚ
ነካ ማንኛውም ሰው እስከ ማምሻው ድረስ

18፥28 ሚል3፥8
18፥30 ቍ27
18፥31 ቍ23
18፥32 ቍ29፤ ዘሌ19፥8፤22፥15
19፥2 ዘፍ15፥9፤ ዘሌ22፥19-25፤ዘዳ 21፥3፤1ሳሙ6፥7፤ ዕብ9፥13
19፥3 ዘፀ29፥14፤ ዘኍ3፥4
19፥4 ዘሌ4፥17
19፥5 ዘፀ29፥14
19፥6 ቍ18፤ ዘሌ14፥4፤መዝ51፥7
19፥7 ዘሌ11፥25፤ 14፥8
19፥9 ቍ13ዘፍ 35፥2፤ዘፀ29፥31፤ዘሌ 4፥12፤ዘኍ8፥7፤ ዕብ9፥13
19፥10 ዘሌ3፥17፤ 15፥10፤14፥46፤22፥18
19፥11 ዘሌ8፥33፤ 21፥1፤ዘኍ31፥19
19፥12 ቍ19፡20፤ ዘኍ31፥19፤2ዜና 26፥21
19፥13 ቍ22፤ዘሌ 7፥20፤15፥31፤21፥11፤ 22፥3፤2ዜና36፥14፤መ ዝ79፥1፤ሐጌ2፥13
19፥15 ዘሌ6፥28
19፥16 ዘኍ31፥19፤ 1ነገ13፥2፤2ነገ23፥6፡ 14፤ሕዝ6፥5፤ማቴ 23፥27፤ዘሌ5፥3
19፥17 ቍ9፤ ዘኍ8፥7
19፥18 ቍ6፡16፤ ዘፀ12፥22፤ዘሌ4፥17
19፥19 ዘፍ35፥2፤ ዘሌ16፥14-15፤ዘኍ 31፥19፤ሕዝ36፥25፤ ዕብ10፥22
19፥20 ቍ12፤ ዘሌ 14፥8፤15፥31፤ መዝ74፥7
19፥21 ዘፀ27፥21
19፥22 ዘሌ5፥2፤ 15፥4-12
20፥1 ቍ14፤ዘፀ 15፥20፤ዘኍ13፥21፡ 26፤33፥36፤ዘዳ1፥46፤

የረከሰ ይሆናል፡፡ [22]የረከሰ ሰው የሚነካው
ማናቸውም ነገር ይረክሳል፤ ይህን የነካ ሰው
ደግሞ እስከ ማምሻው ድረስ የረከሰ ይሆናል፡፡”

## ከዐለት የፈለቀ ውሃ

20 በመጀመሪያው ወር መላው የእስ
ራኤል ማኅበረ ሰብ ወደ ጺን
ምድረ በዳ መጥተው በቃዴስ ተቀመጡ፤
እዚያ ማርያም ሞተች፤ ተቀበረችም፡፡
[2]በዚህ ጊዜ ለማኅበረ ሰቡ የሚሆን ውሃ
አልነበረም፤ ሕዝቡም ሙሴንና አሮንን
በመቃወም ተሰበሰቡ፡፡ [3]ሙሴን ተጣሉት፤
እንዲህም አሉት፤ “ወንድሞቻችን *በእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ፊት በሞቱ ጊዜ ምነው
እኛም ያኔ ሞተን ባረፍነው ኖሮ! [4]*የእግዚ
አብሔርን* (ያህዌ) ማኅበረ ሰብ ወደዚህ
ምድረ በዳ ያመጣችሁት ለምንድነው! ከነ
ከብቶቻችን እዚሁ እንድናልቅ ነውን?
[5]ከግብፅ አውጥታችሁ እህል ወይም በለስ፣
ወይን ወይም ሮማን ወደሌለበት ወደዚህ
ክፉ ቦታ ያመጣችሁንስ ለምንድነው? የሚ
ጠጣ ውሃ እንኳ ይታጣ!”
[6]ሙሴና አሮን ከማኅበረ ሰቡ ወደ መገ
ናኛው ድንኳን ደጃፍ ሄደው በግንባራቸው
ተደፉ፤ *የእግዚአብሔርም* (ያህዌ) ክብር ተገ
ለጠላቸው፡፡ [7]*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) ሙሴን
እንዲህ አለው፤ [8]“በትሪቱን ውሰድ፤ አን
ተና ወንድምህ አሮን ማኅበሩን በአንድነት
ሰብስቡ፤ እነርሱም እያዩ ዐለቱን ተናገሩት፤
ዐለቱም ውሃ ያወጣል፡፡ አንተም ለማኅበረ
ሰቡ ከዐለቱ ውሃ ታወጣላቸዋለህ፤ እነርሱና
ከብቶቻቸውም ይጠጣሉ፡፡”
[9]ስለዚህም ሙሴ ልክ እንደታዘዘው በት
ሩን *ከእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ወሰደ፡፡
[10]እርሱና አሮንም ማኅበሩን በዐለቱ ፊት
አንድ ላይ ሰበሰቡ፤ ሙሴም፣ “እናንት ዐመ
ፀኞች አድምጡ፤ ከዚህ ዐለት እኛ ለእና
ንተ ውሃ ማውጣት አለብን?” አላቸው፡፡
[11]ከዚያም ሙሴ እጁን ዘርግቶ በበትሩ ዐ
ለ ቱን ሁለት ጊዜ መታው፤ ውሃውም
ተን ዶለዶለ፤ ማኅበረ ሰቡና
ከብቶቻቸውም ጠጡ፡፡
[12]ነገር ግን *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴንና
አሮንን፣ “በእስራኤላውያን ፊት እኔን ቅዱስ
አድርጋችሁ ለማክበር ስላልታመናችሁብኝ
ይህን ማኅበረ ሰብ ወደምሰጠው ምድር
ይዛችሁ አትገቡም” አላቸው፡፡
[13]እስራኤላውያን *ከእግዚአብሔር* (ያህዌ) ጋር
የተጣሉበት፣ እርሱም ቅዱስ መሆኑን
በመካከላቸው የገለጠበት ይህ የመሪባ[ሀ] ውሃ
ነበር፡፡

መሳ11፥17፤መዝ
29፥8
20፥2 ዘፀ15፥22፤
17፥1፤ዘኍ16፥19
20፥3 ቍ13፤ዘፍ
13፥7፤ዘፀ5፥21፤17፥2፤
21፥18፤ዘኍ14፥2፤
16፥31-35
20፥4 ዘፀ14፥11፤
ዘኍ14፥2፡3፤16፥13
20፥5 ዘፀ17፥1፤
ዘኍ13፥23፤16፥14
20፥6 ዘፀ40፥2፤
ዘኍ14፥5፤16፥19
20፥8 ዘፀ4፥2፤
10፥12-13፤17፥6፤
ኢሳ41፥18፤43፥20፤
ኤር31፥9
20፥9 ዘኍ17፥2፡10
20፥10 ቍ8፤
መዝ106፥32፡33
20፥11 ዘፀ17፥6፤
ኢሳ33፥21
20፥12 ቍ24፤
ዘኍ27፥14፤ዘዳ1፥37፤
3፥27፤32፥51፤
ኢሳ5፥16፤8፥13
20፥13 ቍ3፤ዘፀ
17፥7፤ዘሌ10፥3
20፥14 ቍ1፡16፤
ዘፍ፤24፥3፤25፥30፤
36፥16፤ዘፀ18፥8፤
ዘዳ4፥39፤ኢሱ2፥11፤
9፥9
20፥15 ዘፍ15፥13፤
46፥6፤ዘፀ1፥14
20፥16 ቍ14፡23፤
ዘፍ16፥11፤21፥17፤ዘፀ
2፥23፤12፥42፤14፥19፤
ዘኍ33፥37፤ዘዳ26፥8
20፥17 ቍ20፤
ዘኍ21፥22፤ዘዳ2፥27፤
መሳ11፥17
20፥18 ቍ14፤
ዘኍ21፥23
20፥19 ዘፀ12፥38፤
ዘዳ2፥6፡28
20፥20 ቍ14፡
17፡18
20፥21 ዘኍ21፥4፡
23፤ዘዳ2፥8፤መሳ11፥18
20፥22 ዘኍ33፥
37፤34፥7፤ዘዳ1፥46፤
32፥50
20፥23 ቍ16
20፥24 ቍ10፤
ዘፍ25፥8፤ዘፀ17፥7
20፥25 ዘኍ33፥38
20፥26 ቍ24፤ዘፀ
28፥1-4፤40፥13፤ዘሌ
16፥4፤ዘኍ27፥13፤

## ኤዶም እስራኤል እንዳያልፍ ከለከለ

[14]ሙሴ ከቃዴስ ለኤዶም ንጉሥ እንዲህ
ሲል መልእክተኞች ላከ፤
“ወንድምህ እስራኤል የሚለው ይህ
ነው፤ የደረሰብን መከራ ሁሉ ምን እንደ
ሆነ አንተም ታውቃለህ፡፡ [15]የቀድሞ
አባቶቻችን ወደ ግብፅ ወረዱ፤ እኛም
እዚያ ብዙ ዘመን ኖርን፡፡ ግብፃውያን
እኛንም አባቶቻችንንም አሠቃዩን፤ [16]ወደ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) በጮኽን ጊዜ ግን
ጩኸታችንን ሰማ፤ መልአክ ልኮም
ከግብፅ አወጣን፡፡
“አሁንም ያለነው እዚሁ ቃዴስ በግ
ዛትህ ድንበር ላይ ባለችው ከተማ ነው፡፡
[17]ስለዚህ በአገርህ እንድናልፍ እባክህን
ፍቀድልን፤ በየትኛውም ዕርሻ ወይም
የወይን ተክል ውስጥ አንገባም፤ ከየት
ኛውም ጒድጓድ ውሃ አንጠጣም፡፡ የን
ጉሡን አውራ ጐዳና ይዘን ከመንዝ
በስተቀር፣ ግዛትህን አልፈን እስክን
ሄድ ድረስ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አን
ልም፡፡”
[18]ኤዶም ግን እንዲህ ሲል መለሰ፤
“በዚህ በኩል አታልፉም፤ እናልፋ
ለን የምትሉ ከሆነ በሰልፍ ወጥተን
በሰይፍ እንመታችኋለን፡፡”
[19]እስራኤላውያንም መልሰው፣
“አውራውን መንገድ ይዘን እንሄዳለን፤
እኛም ሆንን ከብቶቻችን የትኛውንም
ውሃችሁን ከጠጣን ዋጋውን እንከፍላ
ለን፤ በእግር አልፈን መሄድ ብቻ እንጂ
ሌላ ምንም አንፈልግም፡፡” አሏቸው፡፡
[20]ኤዶምም እንደ ገና፣
“በዚህ ማለፍ አትችሉም፡፡” የሚል
መልስ ሰጣቸው፡፡
ከዚያም ኤዶም ብዙና ኀይለኛ የሆነ ሰራ
ዊት አሰልፎ ሊወጋቸው ወጣ፤ [21]ስለዚህ
ኤዶም በግዛቱ አልፈው እንዳይሄዱ ስለ
ከለከላቸው እስራኤላውያን ተመለሱ፡፡

## የአሮን መሞት

[22]መላው የእስራኤል ማኅበረ ሰብ ከቃዴስ
ተነሥቶ ወደ ሖር ተራራ መጣ፡፡ [23]*እግዚ
አብሔርም* (ያህዌ) በኤዶም ወሰን አጠገብ ባለው
በሖር ተራራ ሙሴንና አሮንን እንዲህ
አላቸው፤ [24]“አሮን ወደ ወገኖቹ ይሰበሰ
ባል፤ ሁለታችሁም በመሪባ ውሃ በትእዛዜ
ላይ ዐምፃችኋልና ለእስራኤላውያን ወደ
ምሰጣት ምድር አይገባም፡፡ [25]አሮንንና ልጁ
ን አልዓዛርን ወደ ሖር ተራራ ይዘሃቸው
ውጣ፡፡ [26]አሮን ወደ ወገኖቹ ስለሚሰበሰብ

[ሀ]13 *መሪባ* ማለት መጣላት ማለት ነው፡፡

ልብሱን አውልቀህ ልጁን አልዓዛርን አል
ብሰው፤ አሮንም እዚያው ይሞታል።”
27ሙሴ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) እንዳዘዘው
አደረገ፤ መላው ማኅበረ ሰብ እያያቸው ወደ
ሖር ተራራ ወጡ። 28ሙሴም የአሮንን ልብስ
አውልቆ ልጁን አልዓዛርን አለበሰው፤ አሮ
ንም እዚያው ተራራው ጫፍ ላይ ሞተ።
ከዚያም ሙሴና አልዓዛር ከተራራው ወረዱ፤
29መላው ማኅበረ ሰብም አሮን መሞቱን
በተረዳ ጊዜ፣ የእስራኤል ቤት በሙሉ ሠላሳ
ቀን አለቀሰለት።

## የዓራድ መደምሰስ

21 በኔጌብ ይኖር የነበረው ከነዓና
ዊው የዓራድ ንጉሥ እስራኤል
በአታሪም መንገድ መምጣቱን በሰማ ጊዜ
በእስራኤላውያን ላይ አደጋ ጥሎ ጥቂቶቹን
ማረከ። 2በዚያን ጊዜ እስራኤል፣ “ይህን
ሕዝብ አሳልፈህ በእጃችን ከሰጠኸን ከተ
ሞቻቸውን ፈጽሞ እንደመስሳለን”[ለ] ሲል
*ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) ተሳለ። 3*እግዚአብሐ
ርም* (ያህዌ) የእስራኤልን ልመና ሰምቶ
ከነዓናው ያንን በእጃቸው አሳልፎ
ሰጣቸው፤ እነር ሱም ሰዎቹንና
ከተሞቻቸውን ፈጽመው ደመሰሱ፤ ከዚህ
የተነሣም ስፍራው ሖርማ[ሐ] ተባለ።

## ከናስ የተሠራው እባብ

4እስራኤላውያን በኤዶም ዞረው ለመ
ሄድ ስላሰቡ ከሖር ተራራ ተነሥተው ወደ
ቀይ ባሕር[መ] በሚወስደው መንገድ ተጓዙ፤
ይሁን እንጂ ሕዝቡ በመንገድ ሳለ ትዕግሥቱ
አለቀ፤ 5በእግዚአብሔርና (ኤሎሂም) በሙሴም
ላይ ተነሥተው፣ “በምድረ በዳ
እንድንሞት ከግብፅ ያወጣችሁን
ለምንድነው? ምግብ የለ! ውሃ የለ! ይህን
የማይረባ ምግብ ሰውነታችን ተ
ጸይፎታል” ሲሉ ተናገሩ።
6በዚህ ጊዜ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) መርዘኛ
እባቦች ሰደደባቸው፤ ሕዝቡን ነደፉ፤ ብዙ
እስራኤላውያንም ሞቱ። 7ሕዝቡም ወደ
ሙሴ መጥቶ፣ “*በእግዚአብሔርና* (ያህዌ) በአ
ንተ ላይ በመናገራችን በድለናል፤ እባቦቹን
ከእኛ እንዲያርቅልን ወደ *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ጸልይልን” አለ፤ ሙሴም ስለ ሕዝቡ
ጸለየ።
8*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን፣ “እባብ ሠር
ተህ በዕንጨት ላይ ስቀለው፤ የተነደፈ
ውም ሁሉ ወደ እርሱ በማየት ይድናል”
አለው፤ 9ስለዚህ ሙሴ የናስ እባብ ሠርቶ
በዕንጨት ላይ ሰቀለ፤ ከዚያም በእባብ
የተነደፈ ማናቸውም ሰው ወደ ናሱ እባብ
በተመለከተ ጊዜ ይድን ነበር።

31፥2
20፥27 ዘኍ33፥38
20፥28 ቀኍ26፤ዘፀ
29፥29፤ዘኍ33፥38፤
ዘዳ10፥6፤32፥50
20፥29 ዘፍ27፥41፤
ዘሌ10፥6፤ዘዳ32፥50፤3
4፥8
21፥1 ዘፍ12፥9፤
ዘኍ 13፥17፤33፥40፤
ዘዳ1፥7፤ኢሱ12፥14፤
መሳ1፥9፥16
21፥2 ቀኍ3፤ዘሌ
7፥16፤ዘፀ22፥20፤
ዘዳ2፥34፤ኢሱ2፥10፤
8፥26፤ኤር25፥9፤
50፥21
21፥3 ቀኍ2፤ዘፍ
10፥18፤ዘኍ14፥45
21፥4 ዘኍ14፥25፤
20፥21፥22፤ዘዳ2፥1፥8፤
11፥14፤መሳ11፥18
21፥5 ዘፀ14፥11፤
ዘኍ11፥5፥20፤14፥2፥3
፤20፥5፤መዝ78፥19
21፥6 ቀኍ7፤ዘዳ8፥
15፤32፥33፤ኢዮ20፥
14፤መዝ58፥4፤140፥3
፤ኤር8፥17፤1ቆሮ10፥9
21፥7 ዘፀ8፥8፤ዘኍ
11፥2፤14፥40፤1ሳሙ
7፥8፤መዝ78፥34፤ኤር
27፥18፤37፥3፤ሆሴ
5፥15፤ሐሥ8፥24
21፥8 ዮሐ3፥14
21፥9 2ነገ18፥4፤
ዮሐ3፥14-15
21፥10 ዘኍ33፥43
21፥11 ዘፍ36፥35፤
ዘኍ33፥44፤ዘዳ34፥8፤
ኤር40፥11
21፥12 ዘዳ2፥13፥14
21፥13 ዘፍ10፥16፤
ዘኍ22፥36፤ዘዳ2፥24፤
ኢሱ12፥1፤መሳ11፥13
፥18፤2ነገ10፥33፤ኢሳ
16፥2፤ኤር48፥20
21፥14 1ሳሙ17፥
47፤18፥17፤25፥28
21፥15 ቀኍ28፤ዘዳ
2፥9፥18፤ኢሳ15፥1
21፥16 ዘኍ25፥1፤
33፥49፤መሳ9፥21፤
ኢሳ15፥8
21፥17 ዘፀ15፥1
21፥20 ዘኍ23፥14፤
ዘዳ3፥17፥27፤34፥1፤
ኢሱ12፥3፤13፥20
21፥21 ዘፍ32፥3፤
ዘፀ23፥23፤ዘኍ32፥
33፤ዘዳ1፥4፤ኢሱ2፥
10፤12፥2፥4፤13፥10፤
መሳ11፥19-21፤1ነገ
4፥19፤ነህ9፥22፤መዝ
135፥11፤136፥19፤
ኤር48፥45
21፥22 ዘኍ20፥17

## ወደ ሞዓብ የተደረገው ጒዞ

10እስራኤላውያን ተጓዙ፤ በኦቦትም ሰፈሩ፤
11ከዚያም ከኦቦት ተነሥተው፣ በፀሓይ መውጫ
ትይዩ ባለው ምድረ በዳ በዒዮዓባሪም ሰፈሩ።
12ከዚያም ተጒዘው በዘሬድ ሸለቆ ሰፈሩ።
13ከዚያም ተነሥተው እስከ አሞራውያን ግዛት
በሚዘልቀው ምድረ በዳ ባለው በአርኖን
አጠገብ ሰፈሩ፤ አርኖን በሞዓብና በአሞራ
ውያን መካከል የሚገኝ የሞዓብ ወሰን ነው።
14እንግዲህ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) የጦርነት
መጽሐፍ እንዲህ ተብሎ የተጻፈው በዚሁ
የተነሣ ነው፤

“…በሱፋ[ሠ] ውስጥ የሚገኘው ዋሄብ
አርኖንና 15ወደ ዔር የሚወስዱት
በሞዓብ ድንበርም የሚገኙት የሸለቆች
ተረተሮች።”

16ከዚያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ለሙሴ፣ “ሰዎ
ቹን በአንድነት ሰብስባቸውና ውሃ እሰጣቸ
ዋለሁ” ወዳለበት ብኤር ወደተባለው የውሃ
ጒድጓድ ጒዞአቸውን ቀጠሉ።
17ከዚያም እስራኤል ይህን መዝሙር
ዘመረ፤

“አንተ ምንጭ ሆይ ፍለቅ!
እናንተም ዘምሩለት፤
18ልዑላን ለቈፈሩት፣
የሕዝብ አለቆች በበትረ
መንግሥታቸውና በበትሮቻቸው
ላጐደጐዱት፣
የውሃ ጒድጓድ ዘምሩለት።”

ከዚህ በኋላ ከምድረ በዳው ወደ መቴና ሄዱ፤
19ከመቴና ወደ ነሃሊኤል፣ ከነሃሊኤልም ወደ
ባሞት፣ 20ከባሞትም ፈስጋ ላይ ሆኖ ምድረ
በዳው ቊልቊል ወደሚታይበት በሞዓብ
ወደሚገኘው ሸለቆ ተጓዙ።

## የሴዎንና የዐግ ድል መሆን

21እስራኤል ወደ አሞራውያን ንጉሥ
ወደ ሴዎን እንዲህ የሚሉ መልእክተኞች
ላከ፤

22“በአገርህ አልፈን እንድንሄድ ፍቀድ
ልን፤ ወደ የትኛውም ዕርሻ ሆነ የወ
ይን አትክልት አንገባም፤ ወይም ከየ
ትኛውም ጒድጓድ ውሃ አንጠጣም።
ከግዛትህ እስክንወጣ ድረስም የንጉ
ሡን አውራ ጐዳና አንለቅም።”

ለ2 የዕብራይስጡ ትርጒም አንድን ነገር ወይም አንድን ሕዝብ ፈጽሞ በመደምሰስ፣ በማይሻር ውሳኔ ለእግዚአብሔር መስጠትን ያመለክታል።
ሐ3 መደምሰስ ወይም ማጥፋት ማለት ነው።
መ4 በዕብራይስጥ *ያም ሱፍ* ሲሆን፣ የደንገል ባሕር ማለት ነው።
ሠ14 የዕብራይስጡ ትርጒም አይታወቅም።

23ሴዎን ግን እስራኤል በግዛቱ ውስጥ
እንዲያልፍ አልፈቀደም፤ ሰራዊቱን በሙሉ
አሰባስቦ እስራኤልን ለመውጋት ወደ ምድረ
በዳው ወጣ፤ ያህጽ እንደ ደረሰም ከእስራ
ኤል ጋር ጦርነት ገጠመ። 24እስራኤል ግን
በሰይፍ መታው፤ ከአርኖን እስከ ያቦቅ
ድረስ ያለውንም ምድሩን ወሰደበት፤
ይሁን እንጂ የአሞናውያን ወሰን የተመሸገ
ስለ ነበር ከያቦቅ አላለፈም። 25እስራ
ኤልም ሐሴቦንና በአካባቢዋ ያሉትን መን
ደሮች ጨምሮ የአሞራውያንን ከተሞች
በሙሉ በመያዝ እዚያው ተቀመጠ። 26ሐሴ
ቦን የቀድሞውን የሞዓብን ንጉሥ ወግቶ
እስከ አርኖን ድረስ ያለውን ምድሩን
የወሰደበት የአሞራውያን ንጉሥ የሴዎን
ከተማ ነበረች።
27እንግዲህ ባለቅኔዎች እንደዚህ ያሉት
ለዚህ ነው፤

"ወደ ሐሴቦን ኑ፣ እንደ ገና ትገንባ፤
የሴዎንም ከተማ ተመልሳ ትሠራ፤

28"እሳት ከሐሴቦን ወጣ፤
ነበልባልም ከሴዎን ከተማ ተንቦገቦገ፤
የሞዓብን ዔር፣
በአርኖን ከፍታዎች የሚኖሩትንም በላ።
29ሞዓብ ሆይ፤ ወዮልህ!
የከሞስ ሕዝብ ሆይ፤ ተደመሰስህ!
ወንዶች ልጆቹን ለሽሽት፣
ሴቶች ልጆቹን ለምርኮ፣
ለአሞራውያን ንጉሥ ለሴዎን አሳልፎ
ሰጥቶአል።

30"እኛ ግን ገለበጥናቸው፤
ሐሴቦን እስከ ዴቦን ድረስ ተደመሰሰች፤
እስከ ኖፋ ድረስ ያሉትን፣
እስከ ሜድባ የተዘረጉትን
እንዳሉ አፈራርሰናቸዋል።"

31ስለዚህም እስራኤል በአሞራውያን
ምድር ተቀመጠ።
32ሙሴ ሰላዮችን ወደ ኢያዜር ከላከ በኋላ
እስራኤላውያን በአካባቢዋ ያሉትን መንደ
ሮች በመያዝ እዚያ የነበሩትን አሞራው
ያን አባረሩአቸው። 33ከዚያም ተመልሰው
ወደ ባሳን የሚወስደውን መንገድ በመያዝ
ሄዱ፤ የባሳን ንጉሥ ዐግና መላ ሰራዊቱም
ኤድራይ ላይ ጦርነት ሊገጥማቸው ወጡ።
34*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን፣ "እርሱን
ከመላው ሰራዊቱና ከምድሩ ጋር በእጅህ አሳ
ልፎ ሰጥቼሃለሁና አትፍራው። በሐሴቦን ሆኖ
ይገዛ በነበረው በአሞራውያን ንጉሥ በሴ
ዎን ላይ ያደረግህበትን ሁሉ በእርሱም ላይ
አድርግበት" አለው።

**21፥23** ዘኍ20፥18፡21፤ዘዳ2፥32፤ኢሱ13፥18፤21፥36፤መሳ11፥20፤ኢሳ15፥4፤ኤር48፥21፡34
**21፥24** ቍ35፤ዘፍ19፥38፤32፥22፤ዘኍ32፥33፤ዘዳ2፥33፡37፤3፥3፡4፤29፥7፤ኢሱ13፥10፤መሳ2፥37፤11፥13፡22፤መዝ፤135፥10-11አሞ2፥9
**21፥25** ቍ30፤ዘኍ13፥29፤32፥3፤ዘዳ1፥4፤29፥7፤ኢሱ9፥10፤12፥2መሳ10፥11፤11፥26ኢሳ15፥4፤16፥8፤ኤር48፥2፡34፤አሞ2፥10
**21፥26** ቍ11፡13፤21፤ዘኍ13፥29፤ዘዳ29፥7፤መዝ135፥11
**21፥28** ቍ15፤ዘኍ11፥1፤22፥41፤ዘዳ12፥2፣ኢሱ13፥17፤ኢሳ15፥2፤ኤር19፥5፤48፥45
**21፥29** ዘኍ24፥17፤መሳ10፥6፤11፥24፤ሩት1፥15፤2ሳሙ8፥2፤መዝ60፥8፤1ነገ11፥7፡33፤2ነገ፤23፥13፤1ዜና18፥2፤ኢሳ15፥5፤16፥2፤25፥10ኤር48፥7፡46
**21፥30** ዘኍ32፥3፤ኢሱ13፥9፡16፡17፤ነህ11፥25፤1ዜና19፥7 ኢሳ15፥2፤ኤር48፥18፡22፤
**21፥31** ዘኍ13፥29
**21፥32** ዘኍ32፥1፡3፡35፤ኢሱ2፥1፤6፥22፤7፥2፤ኢሱ13፥25፤መሳ18፥2፤2ሳሙ10፥3፤2ሳሙ24፥5፤1ዜና19፥3፤1ዜና6፥81፤ኢሳ16፥8፤ኤር48፥32
**21፥33** ዘኍ32፥33፤ዘዳ1፥4፤3፥1፡3፡4፡10፥31፥4፤32፥14፤ኢሱ2፥10፤9፥10፤12፥4፤13፥12፡30፡31፤19፥37፤1ነገ4፥13፡19፤ነህ9፥22፤መዝ135፥11፤136፥20
**21፥34** ዘዳ3፥2
**21፥35** ቍ24ኢሱ9፥10
**22፥1** ዘኍ13፥29፤21፥11፤31፥12፤33፥48፤ዘዳ32፥49፤ኢሱ2፥1፡7
**22፥2** ዘኍ23፥1-3፤ኢሱ24፥9፤መሳ11፥25፤ሚክ6፥5፤ራእ2፥14
**22፥3** ዘፀ15፥15
**22፥4** ዘፍ19፥37፤25፥2፤ዘኍ32፥17፡18፡29፤ኢዮ5፥25፤መዝ72፥16
**22፥5** ቍ7፤ዘፍ2፥14፤ዘፀ13፥3ዘኍ24፥25፤31፥8፡16፤

35ስለዚህም እስራኤላውያን ዐግን ከልጆቹና
ከመላው ሰራዊቱ ጋር አንድም ሳይቀሩ ሁሉ
ንም ፈጇቸው፤ ምድሩንም ወረሱ።

## ባላቅ በለዓምን አስጠራ

22 ከዚህ በኋላ እስራኤላውያን ወደ
ሞዓብ ሜዳ ተጕዘው ከዮርዳኖስ
ወንዝ አጠገብ ከኢያሪኮ[ሬ] ማዶ ሰፈሩ።
2በዚህ ጊዜ የሴፎር ልጅ ባላቅ፣ እስራኤል
በአሞራውያን ላይ ያደረገውን ሁሉ አየ፤
3ሞዓብም ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ ተሸበረ፤
በእርግጥም ሞዓብ በእስራኤላውያን ምክን
ያት በፍርሀት ተውጦ ነበር።
4ሞዓባውያንም የምድያምን ሽማግሌ
ዎች፣ "በሬ የመስክ ሣር ጠራርጎ እንደሚበላ
ሁሉ፣ ይህም ሰራዊት በዙሪያችን ያለውን
ሁሉ ጠራርጎ የሚያጠፋ ነው" አሏቸው።
ስለዚህ በዚያን ጊዜ የሞዓብ ንጉሥ የነ
በረው የሴፎር ልጅ ባላቅ፣ 5ከወንዙ[ሰ] ዳር
ባለች በትውልድ አገሩ በምትገኝ በፋቱራ
የነበረውን የቢዖርን ልጅ በለዓምን እን
ዲጠሩት መልእክተኞች ላከ፤ እንዲህም
አለ፤

እነሆ ከብዛቱ የተነሣ ምድሩን የሸ
ፈነ ሕዝብ ከግብፅ ወጥቶ በአቅራቢ
ያዬ ሰፍሮአል። 6ስለዚህ ይህን ሕዝብ
መቋቋም ስለማልችል መጥተህ ርገም
ልኝ፤ ምናልባትም ድል አድርጌ ከአ
ገሪቱ ላስወጣቸው የምችለው ከዚያ
በኋላ ሊሆን ይችላል፤ አንተ የምት
ባርከው ቡሩክ፣ የምትረግመውም ርጉም
እንደሚሆን ዐውቃለሁና።"

7የሞዓብና የምድያም ሽማግሌዎችም ለሟ
ርት የሚከፈለውን ዋጋ ይዘው ሄዱ፤ በለዓም
ዘንድ በደረሱ ጊዜም የባላቅን መልእክት
ነገሩት።
8በለዓምም፣ "*እግዚአብሔር* (ያህዌ) የሚ
ሰጠኝን መልስ አመጣላችኋለሁና የዛሬን
ሌሊት እዚሁ ዕደሩ" አላቸው። ስለዚህም
የሞዓብ አለቆች ከእርሱ ዘንድ ቈዩ።
9እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ወደ በለዓም መጥቶ፣
"ከአንተ ጋር ያሉት እነዚህ ሰዎች እነማን
ናቸው?" ሲል ጠየቀው።
10በለዓምም እግዚአብሔርን (ኤሎሂም) እንዲህ
አለው፤ "የሞዓብ ንጉሥ የሴፎር ልጅ
ባላቅ ይህን መልእክት ልኮብኛል፤ 11'ከግብፅ
የወጣ ሕዝብ የምድሩን ገጽ አጥለቅልቆ
ታል፤ ስለዚህ መጥተህ ርገምልኝ፤ ምናል
ባት ልዋጋቸውና ላባርራቸው የምችለው
ከዚያ በኋላ ሊሆን ይችላል።' "

[ሬ]1 በዕብራይስጥ *የኢያሪኮ ዮርዳኖስ* የሚባል ሲሆን፣ ይህም የዮርዳኖስ ወንዝ የጥንት ስም ሳይሆን አይቀርም።
[ሰ]5 የኤፍራጥስ ወንዝ ነው።

12እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ግን በለዓምን፣
"አብረሃቸው አትሂድ፤ የተባረከ ሕዝብ ስለ
ሆነም አትርገመው" አለው።
13በማግሥቱ ጠዋት በለዓም ተነሥቶ
የባላቅን አለቆች፣ "አብሬአችሁ እንዳልሄድ
እግዚአብሔር (ያህዌ) ከልክሎኛልና እናንተ
ወደ አገራችሁ ተመለሱ አላቸው።"
14ስለዚህ የሞዓብ አለቆች ወደ ባላቅ
ተመልሰው፣ "በለዓም አብሮን ለመምጣት
እምቢ አለን" አሉት።
15ከዚያም ባላቅ ከፊተኞቹ ይልቅ ቍጥ
ራቸው የበዛና ይበልጥ የተከበሩ ሌሎች
አለቆች ላከ። 16እነርሱም ወደ በለዓም
መጥተው እንዲህ አሉት፤ "የሴፎር ልጅ
ባላቅ ይህን እንድንነግርህ ልኮናል፤ ወደ
እኔ ለመምጣት የሚያግድህ ምንም ነገር
አይኑር፤ 17ወሮታህን በእጅጉ እከፍላለሁ፤
የምትለውንም ሁሉ አደርጋለሁ፤ ስለዚህ
መጥተህ ይህን ሕዝብ ርገምልኝ።"
18በለዓም ግን እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"ሌላው ይቅርና ባላቅ በብርና በወርቅ የተ
ሞላ ቤተ መንግሥቱን ቢሰጠኝ እንኳ፣ የአ
ምላኬን የእግዚአብሔርን (ኤሎሂም ያህዌ) ትእዛዝ
በመጣስ ከዚያ ያለፈ ወይም ያነሰ ማንኛ
ውንም ነገር ማድረግ አልችልም። 19አሁ
ንም ሌሎቹ እንዳደረጉት ሁሉ፣ እናንተም
ዛሬ እዚሁ ዕደሩና እግዚአብሔር (ያህዌ)
ምን እንደሚለኝ ደግሞ ልወቅ።"
20በዚያች ሌሊት እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ወደ
በለዓም መጥቶ፣ "እነዚህ ሰዎች የመጡት
እንድትሄድላቸው እስከ ሆነ ድረስ አብረሃ
ቸው ሂድ፤ ነገር ግን እኔ የምነግርህን
ብቻ አድርግ።"

## የበለዓም አህያ

21በለዓም በጠዋት ተነሣ፤ አህያውንም
ጭኖ ከሞዓብ አለቆች ጋር ሄደ። 22ይሁን
እንጂ በለዓም በሄደ ጊዜ እግዚአብሔር (ኤሎ
ሂም) በጣም ተቈጥቶ ስለ ነበር የእግዚ
አብሔር (ያህዌ) መልአክ ሊቃወመው
በመንገዱ ላይ ቆመ። በለዓምም በአህያው
ላይ ተቀምጦ ነበር፤ ሁለት አሽከሮቹም
አብረው ነበሩ። 23አህያዪቱም የእግዚ
አብሔር (ያህዌ) መልአክ የተመዘዘ ሰይፍ
ይዞ በመንገድ ላይ መቆሙን ባየች ጊዜ
ከመንገድ ወጥታ ዕርሻ ውስጥ ገባች፤ በለዓ
ምም ወደ መንገዱ እንድትመለስ መታት።
24ከዚያም የእግዚአብሔር (ያህዌ) መልአክ
በሁለቱም በኩል ግንብ ባለበት በሁለት
የወይን ተክል ቦታ መካከል በሚገኝ ጠባብ
መተላለፊያ ላይ ቆመ። 25አህያዪቱም የእ
ግዚአብሔርን (ያህዌ) መልአክ ባየች ጊዜ

ዘዳ23፥4፤ኢሱ13፥22፤ነህ13፥2፤ሚክ6፥5፤2ጴጥ2፥15
22፥6 ቍ11፡12፡17፤ዘኍ23፥7፡11፡13፤24፥9፡10
22፥7 ዘፍ30፥27
22፥8 ቍ19
22፥9 ቍ20፤ዘፍ20፥3፤ዘኍ23፥5፤24፥4፡16
22፥12 ዘፍ12፥2
22፥17 ቍ6፡37፤ዘኍ24፥11
22፥18 ቍ38፤ዘኍ23፥12፡26፤24፥13፤1ነገ22፥142ዜና18፥13፤ኤር42፥4፤
22፥19 ቍ8
22፥20 ቍ35፡38፤ዘፍ20፥3፤ዘኍ23፥5፡12፡16፡26፤24፥13፤2ዜና18፥13
22፥22 ዘፍ16፥7፤ዘፀ4፥14፤መሳ13፥3፡6፡13
22፥23 ቍ25፡27፤ኢሱ5፥13
22፥27 ዘኍ11፥1፤ያዕ1፥19
22፥28 ቍ32፤2ጴጥ2፥16
22፥29 ቍ33፤ዘዳ25፥4፤ምሳ12፥10፤27፥23-27፤ማቴ15፥19
22፥31 ዘፍ21፥19
22፥33 ቍ29
22፥34 ዘፍ39፥9፤ዘኍ14፥40፤1ሳሙ15፥24፡30፤2ሳሙ12፥13፤24፥10፤ኢዮ33፥27፤መዝ51፥4
22፥36 ቍ2፤ዘኍ21፥13

ወደ ግንቡ ተጠግታ የበለዓምን እግር አጣ
በቀችው፤ ስለዚህም እንደ ገና መታት።
26የእግዚአብሔርም (ያህዌ) መልአክ ወደ
ፊት ሄድ ብሎ ወደ ቀኝም ሆነ ወደ ግራ
መተላለፊያ በሌለበት ጠባብ ቦታ ላይ
ቆመ። 27አህያዪቱም የእግዚአብሔርን (ያህዌ)
መልአክ ባየች ጊዜ ከበለዓም በታች ተኛች፤
በለዓም ተቈጥቶ ነበርና በበትሩ ደበደባት።
28ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) የአህያዪቱን
አፍ ከፈተ፤ በለዓምንም፣ "እንዲህ አድርገህ
ሦስት ጊዜ የመታኸኝ ምን አድርጌህ ነው?"
አለችው።
29በለዓምም መልሶ አህያዪቱን፣ "ስላላገ
ጥሽብኝ ነዋ! በእጄ ሰይፍ ይዤ ቢሆን
ኖሮ አሁኑኑ በገደልሁሽ ነበር" አላት።
30አህያዪቱም ደግሞ በለዓምን እንዲህ አለ
ችው፣ "ከብዙ ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ
የተቀመጥክብኝ አህያህ አይደለሁምን? ታዲያ
ይህን የመሰለ ነገር የማድረግ ልማድ ነበ
ረኝ?"
እርሱም፣ "በጭራሽ!" አላት።
31በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር (ያህዌ) የበለዓ
ምን ዐይን ከፈተ፤ እርሱም የእግዚአብሔር
(ያህዌ) መልአክ የተመዘዘ ሰይፍ እንደ ያዘ
መንገዱ ላይ ቆሞ አየ፤ ጐንበስ ብሎም
በግንባሩ ተደፋ።
32የእግዚአብሔርም (ያህዌ) መልአክ እንዲህ
ሲል ጠየቀው፤ "አህያህን እንዲህ አድርገህ
ሦስት ጊዜ የመታሃት ስለ ምንድነው?
መንገድህ በፊቴ[ሸ] ጠማማ ስለ ሆነ ልቃወምህ
መጥቻለሁ። 33አህያዪቱ አይታኝ ሦስቱ
ንም ጊዜ ከፊቴ ዞር ባትልማ ኖሮ
በእውነት እስካሁን አንተን በገደልሁህ አህ
ያዪቱን ግን በሕይወት በተውኳት ነበር።
34በለዓምም የእግዚአብሔርን (ያህዌ) መል
አክ፣ "ኀጢአት ሠርቻለሁ፤ እኔን ለመቃ
ወም መንገዱ ላይ መቆምህን አላወቅሁም፤
አሁንም ደስ የማትሰኝ ከሆነ እመለሳለሁ"
አለው።
35የእግዚአብሔርም (ያህዌ) መልአክ በለዓ
ምን፣ "መሄዱን ከሰዎቹ ጋር ሂድ፤ ነገር
ግን እኔ የምነግርህን ብቻ ተናገር" አለው።
ስለዚህ በለዓም ከባላቅ አለቆች ጋር ሄደ፡
36በለዓም በመምጣት ላይ መሆኑን
ባላቅ በሰማ ጊዜ በግዛቱ ዳርቻ በአርኖን
ወሰን ላይ ወደምትገኘው ወደ ሞዓብ ከተማ
ሊቀ በለው ወጣ። 37ባላቅ በለዓምን፣
"በቶሎ እንድትመጣ ልኬብህ
አልነበረምን? ለምን አልመጣህም?
በእርግጥ ወሮታህን ልከፍል የማልችል
ሆኜ ነውን?" አለው።

[ሸ]32 የዚህ ጥገኛ ሐረግ የዕብራይስጡ ትርጒም አይታወቅም።

38በለዓምም፣ “ይኸው አሁን መጥቻለሁ፤
ግን እንዲያው ማንኛውንም ነገር መናገር
እችላለሁን? እኔ መናገር የሚገባኝ እግዚአ
ብሔር (ኤሎሂም) በአፌ ያስቀመጠውን ብቻ ነው”
ብሎ መለሰለት።
39ከዚያም በለዓም ከባላቅ ጋር ወደ ቂር
ያት ሐጾት ሄደ። 40ባላቅም ከብቶችና
በጎች ሠዋ፤ ከፊሉንም ለበለዓምና ከእርሱ
ጋር ለነበሩት አለቆች ሰጣቸው። 41በማግስቱ
ጠዋት ባላቅ በለዓምን ወደ ባሞት በኣል
አወጣው፤ እዚያም ሆኖ ሕዝብ በከፊል አየ።

## የመጀመሪያው የበለዓም ንግር

23 በለዓም፣ “እዚህ ሰባት መሠዊያ ሥራ
ልኝ፤ ሰባት ኮርማዎችና ሰባት
አውራ በጎችም አዘጋጅልኝ” አለው። 2ባላ
ቅም በለዓም እንደ ነገረው አደረገ፤ ሁለቱም
በእያንዳንዱ መሠዊያ ላይ አንድ ኮርማና
አንድ አውራ በግ አቀረቡ።
3ከዚያም በለዓም ባላቅን፣ “እኔ ወደዚያ
ስሄድ፣ አንተ እዚሁ መሥዋዕትህ አጠገብ
ቈይ፤ ምናልባትም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሊ
ገናኘኝ ይመጣ ይሆናል፤
የሚገልጥልኝንም ሁሉ እነግርሃለሁ”
አለው። ከዚያም በለዓም ወደ አንድ ገላጣ
ኰረብታ ሄደ።
4እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ተገናኘው፤ በለዓ
ምም፣ “እነሆ፤ ሰባት መሠዊያዎች አዘጋ
ጅቻለሁ፤ በእያንዳንዱም ላይ አንድ ኮር
ማና አንድ አውራ በግ አቅርቤአለሁ”
አለው።
5እግዚአብሔርም (ያህዌ) በበለዓም አፍ መል
እክት አስቀምጦ፣ “ወደ ባላቅ ተመልሰህ
ይህን መልእክት ንገረው” አለው።
6እርሱም ተመልሶ ሲሄድ ባላቅን ከመ
ላው የሞዓብ አለቆች ጋር በመሠዊያው
አጠገብ ቆሞ አገኘው። 7ከዚያም በለዓም
ንግሩን እንዲህ ሲል ጀመረ፤

“ባላቅ ከአራም አመጣኝ፣
የሞዓብ ንጉሥ ከምሥራቅ ተራሮች።
‘ና ያዕቆብን ርገምልኝ፤
መጥተህም እስራኤልን አውግዝልኝ’
አለኝ።
8እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ያልረገመውን፣
እኔ እንዴት ረግማለሁ?
እግዚአብሔር (ያህዌ) ያላወገዘውንስ፣
እንዴት አወግዛለሁ?
9ከዐለታማ ተራሮች ጫፍ ሆኜ
አያቸዋለሁ፤
በከፍታዎቹም ላይ ሆኜ
እመለከተዋለሁ፤
ተለይቶ የሚኖረውን፣
ራሱንም ከሌሎች ሕዝቦች ጋር
የማይቈጥረውን፣
ሕዝብ አያለሁ።
10የያዕቆብን ትቢያ ማን ቈጥሮ
ይዘልቃል?
የእስራኤልንስ ሩብ ማን
ይቈጥረዋል።
የጻድቁን ሞት እኔ ልሙት፤
ፍጻሜዬም የእርሱ ዐይነት ፍጻሜ
ትሁን!”

11ባላቅም በለዓምን፣ “እንዴት እንዲህ ታደ
ርገኛለህ? ጠላቶቼን እንድትረግምልኝ አመ
ጣሁህ፤ አንተ ግን ባረክሃቸው እንጂ ምንም
አላደረግህልኝም!” አለው።
12እርሱም መልሶ “እግዚአብሔር (ያህዌ) በአፌ
ያስቀመጠውን መናገር አይገባኝምን?” አለው።

## ሁለተኛው የበለዓም ንግር

13ከዚህ በኋላ ባላቅ፣ “እነርሱን ማየት ወደ
ምትችልበት ወደ ሌላ ቦታ እንሂድ፤ እዚያም
ሁሉን ሳይሆን በከፊል ብቻ ታያቸዋለህ፤
እዚያም ሆነህ እነርሱን ርገምልኝ” አለው።
14ስለዚህም በፈስጋ ተራራ ጫፍ ላይ ወዳለው
ወደ ጾፊም ሜዳ ወሰደው፤ እዚያም ሰባት
መሠዊያ ሠርቶ በእያንዳንዱ ላይ አንድ ኮር
ማና አንድ አውራ በግ ሠዋ።
15በለዓምም ባላቅን፣ “እርሱን ለመገና
ኘት ወደዚያ ስሄድ፣ አንተ እዚሁ መሥ
ዋዕትህ አጠገብ ቈይ” አለው።
16እግዚአብሔር (ያህዌ) በለዓምን ተገናኘው፤
በአፉም መልእክት አስቀምጦ፣ “ወደ ባላቅ
ተመለስና ይህን መልእክት ንገረው” አለው።
17እርሱም ተመልሶ ሲሄድ ባላቅን ከመላው
የሞዓብ አለቆች ጋር በመሠዊያው አጠገብ
ቆሞ አገኘው፤ ባላቅም፣ “እግዚአብሔር (ያህዌ)
ምን አለ?” ሲል ጠየቀው።
18ከዚያም ንግሩን እንዲህ ሲል ጀመረ፤

“ባላቅ ሆይ ተነሣ፤ አድምጠኝ፤
የሴፎር ልጅ ሆይ ስማኝ፤
19ይዋሽ ዘንድ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰው
አይደለም፤
ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ
አይደለም፤
ተናግሮ አያደርገውምን?
ተስፋ ሰጥቶስ አይፈጽመውምን?
20እባርክ ዘንድ ትእዛዝ ተቀብያለሁ፤
እርሱ ባርኳል፤ እኔም ልለውጠው
አልችልም።
21“በያዕቆብ መጥፎ ነገር አልተገኘም፤
በእስራኤልም* ጕስቍልና
አልታየም፤

*21 በያዕቆብ ላይ ወይም በእስራኤል ላይ እንከን አለማግኘቱን ያመለክታል።

22፥38 ዘኍ23፥5፡ 16፡26
22፥40 ዘኍ23፥1፡ 14፡29፤ሕዝ 45፡23
22፥41 ዘኍ21፥ 28፤23፥13
23፥1 ዘኍ22፥40
23፥2 ቍ14፡30
23፥3 ቍ15
23፥4 ቍ16
23፥5 ዘዐ4፥12፤ 4፥15፤ዘኍ22፥20፤ ኢሳ59፥21
23፥6 ቍ17
23፥7 ቍ18፤ዘፍ 24፥10፤ዘኍ22፥5፡6፤2 4፥3፡21፤ኢሱ24፥9፤ 2ሳሙ23፥1፤2ነገ5፥1፤ ነህ13፥2
23፥8 ቍ20፤ዘኍ 22፥12፤ኢሳ43፥13
23፥9 ዘዐ33፥16፤ ዘኍ22፥41፤ዘዳ32፥8
23፥10 ዘፍ13፥16፤ መዝ16፥3፤116፥15፤ኢሳ 57፥1፤መዝ 37፥37
23፥11 ዘኍ22፥6፤ 24፥10፤ኢሱ24፥10፤ ነህ13፥2
23፥12 ዘኍ22፥18፡ 20
23፥13 ቍ27፤ዘኍ 22፥6፡41
23፥14 ቍ2፤ዘኍ 21፥20፤27፥12
23፥16 ዘዐ4፥15፤ ዘኍ22፥38
23፥17 ቍ6
23፥18 ቍ7፤ ዘኍ22፥2
23፥19 ዘፍ22፥17፤ ዘኍ11፥23፤1ሳሙ15፥ 29፤2ሳሙ7፥25፤ኢዮ 9፥32፤12፥13፤36፥5፤ መዝ33፥11፤89፥34፤ 102፥27፤110፥4፤119፥ 38፤ኢሳ55፥9፤ኤር 4፥28፤7፥16፤ሆሴ 11፥9፤ሚል3፥6፤ ቲቶ1፥2፤ዕብ6፥18፤ 7፥21፤ያዕ1፥17
23፥20 ቍ5፡8፡16፤ ዘፍ22፥17፤ዘኍ22፥ 12፤24፥1፤ኢዮ9፥12
23፥21 ዘፍ26፥3፤ ዘዐ29፥45፡46፤ዘዳ 4፥7፤32፥15፤33፥5፤መ ዝ32፥2፡5፤34፥17- 18፤85፥2፤89፥15-18፤ 145፥18፤ኢሳ33፥24፤ 40፥2፤44፥2፤ኤር50፥2 0፤ዘካ2፥10፤ሮሜ4፥7- 8

*እግዚአብሔር* አምላኩ (ያህዌ ኤሎሂም)
ከእርሱ ጋር ነው፣
የንጉሡም እልልታ በመካከላቸው
ነው፡፡
22እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ከግብፅ አወጣቸው፤
ብርታታቸውም እንደ ጎሽ ብርታት
ነው፡፡
23በያዕቆብ ላይ የሚሠራ አስማት
የለም፤
በእስራኤልም ላይ የሚሠራ ሟርት
አይኖርም፤
ለያዕቆብና ለእስራኤል፣
'እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ያደረገውን እዩ!'
ይባልላቸዋል፡፡
24ሕዝቡ እንደ እንስት አንበሳ ይነሣል፤
ያደነውን እስኪያነክት፣
የገደለውንም ደም እስኪጠጣ፣
እንደሚያርፍ አንበሳ ሆኖ ይነሣል፡፡"

25በዚህ ጊዜ ባላቅ በለዓምን፣ "እንግዲያ
ውስ ፈጽሞ አትርገማቸው፤ ፈጽሞም አትመ
ርቃቸው!" አለው፡፡
26በለዓምም፣ "*እግዚአብሔር* (ያህዌ) የሚለ
ኝን ሁሉ ማድረግ እንዳለብኝ አልነገርሁህ
ምን?" ሲል መለሰለት፡፡

## ሦስተኛው የበለዓም ንግር

27ከዚህ በኋላ ባላቅ በለዓምን፣ "በል እን
ግዲያው ወደ ሌላ ቦታ ልውሰድህ፤ ከዚያ
ሆነህ እንድትረግምልኝ ምናልባት እግዚአ
ብሔር (ኤሎሂም) ይፈቅድልህ ይሆናል" አለው፡፡
28ባላቅም በለዓምን ምድረ በዳው ቍል
ቍል ወደሚታይበት ወደ ፌጎር ጫፍ
አወጣው፡፡
29በለዓምም፣ "ሰባት መሠዊያዎች እዚህ
ሥራልኝ፤ ሰባት ኮርማዎችና ሰባት አውራ በጎ
ችም አዘጋጅልኝ አለው፡፡ 30ባላቅም በለዓም
እንደ ነገረው አደረገ፤ በእያንዳንዱም መሠ
ዊያ ላይ አንድ ኮርማና አንድ አውራ በግ
ሠዋ፡፡

24 በለዓምም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) እስ
ራኤልን መባረክ እንደ ወደደ ባየ ጊ
ዜ፣ እንደ ሌላው ጊዜ ሁሉ አስማት
ለመሻት አልሄደም፤ ነገር ግን ፊቱን ወደ
ምድረ በዳ መለሰ፡፡ 2በለዓም አሻግሮ ተመ
ልክቶ እስራኤል በየነገድ በየነገዱ ሆኖ
መስፈሩን ሲያይ የእግዚአብሔር (ኤሎሂም) መን
ፈስ በላዩ መጣበት፤ 3ንግሩንም እንዲህ ሲል
ጀመረ፤

"የዚያ ዐይኑ የተከፈተለት፣
የቢዖር ልጅ የበለዓም ንግር፣
4የዚያ የአምላክን (ኤሎሂም) ቃል
የሚሰማ፣
ሁሉን የሚችል[ሀ] የአምላክን ራእይ
የሚያይ፣
ከመሬት የተደፋው ዐይኖቹም
የተከፈቱለት ሰው ንግር፤

5"ያዕቆብ ሆይ፤ ድንኳኖችህ፣
እስራኤል ሆይ፤ ማደሪያዎችህ
እንዴት ያማሩ ናቸው!

6"እንደ ሸለቆዎች፣
በወንዝ ዳር እንዳሉም የአትክልት
ስፍራዎች ተዘርግተዋል፤
*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) እንደ ተተከሉ
ሬቶች፣
በውሃም አጠገብ እንዳሉ ዝግባዎች
ናቸው፡፡
7ከማድጋቸው ውሃ ይፈሳል፤
ዘራቸውም የተትረፈረፈ ውሃ
ያገኛል፤

"ንጉሣቸው ከአጋግ ይልቃል፤
መንግሥታቸውም ከፍ ከፍ ይላል፤

8"እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ከግብፅ አወጣቸው፤
ብርታታቸውም እንደ ጎሽ ብርታት
ነው፤
ጠላቶች የሆኑአቸውን ሕዝብ
ያነክታሉ፤
ዐጥንቶቻቸውን ያደቅቃሉ፤
በፍላጻቻቸው ይወጓቸዋል፡፡
9እንደ አንበሳ አድፍጠዋል፤
እንደ እንስቲቱም አንበሳ
አድብተዋል፤
ሊቀሰቅሳቸውስ የሚችል ማን ነው?

"የሚባርኩህ ቡሩክ፣
የሚረግሙህም ርጉም ይሁኑ!"

10ከዚያም ባላቅ፣ በበለዓም ላይ እጅግ
ተቈጣ፤ እጆቹንም አጨብጭቦ እንዲህ አለው፤
"ጠላቶቼን እንድትረግምልኝ ጠራሁህ፤ አንተ
ግን ሦስቱንም ጊዜ ባረክሃቸው፡፡ 11በል ቶሎ
ወደ ቤትህ ሂድልኝ፤ ወሮታህን አሳምሬ
ልከፍልህ ነበር፤ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ግን
እንዳታገኝ ከለከለህ፡፡"
12በለዓምም ለባላቅ እንዲህ ሲል መለሰ
ለት፤ ወደ እኔ ለላክሃቸው ሰዎች እንዲህ
ብዬ ነግሬአቸው አልነበረምን? 13'ሌላው
ይቅርና ባላቅ በብርና በወርቅ የተሞላ
ቤተ መንግሥቱን ቢሰጠኝ እንኳ፣ *እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) የሚለውን ብቻ ከመናገር
በስተቀር *ከእግዚአብሔር* (ያህዌ) ትእዛዝ
ውጭ በራሴ ሐሳብ በጎም ሆነ ክፉ ማድ
ረግ አልችልም፡፡' 14እንግዲህ ወደ ሕዝቤ

**23፥22** ዘኍ24፥8፤ ኢሱ2፥10፤9፥9፤ዘዳ 33፥17፤ኢዮ39፥9፤ መዝ22፥21፤29፥6፤ 92፥10፤ኢሳ34፥7
**23፥23** ቀኍ3፤ዘፍ 30፥27፤ዘኍ24፥1
**23፥24** ዘፍ49፥9፤ ዘኍ24፥9፤ኢሳ49፥ 26ሕዝ19፥2፤ ናሆ2፥11
**23፥26** ዘኍ22፥18፡ 20
**23፥27** ቀኍ13፤ ዘኍ24፥10
**23፥28** ዘኍ25፥3፡ 18፤31፥16፤ዘዳ3፥29፤ 4፥3፤ኢሱ22፥17፤መዝ 106፥28፤ሆሴ9፥10
**23፥30** ቀኍ2
**24፥1** ዘኍ23፥20፡ 23፡28
**24፥2** ዘኍ11፥25፡ 26
**24፥3** ቀኍ15
**24፥4** ዘፍ15፥1ዘኍ 22፥9
**24፥5** ኤር4፥20፤ 30፥18፤ሚል2፥12
**24፥6** ዘፍ2፥10፤ ኢዮ 29፥19፤መዝ 1፥3፤45፥8፤104፥16፤ ማሕ4፥14ሕዝ31፥5
**24፥7** ዘፀ17፥8-16፤ ዘዳ28፥1፤2ሳሙ5፥12፤ 1ዜና14፥2፤መዝ 89፥27፤145፥11-13
**24፥8** ዘፀ15፥6፤ 2ሳሙ18፥14፤መዝ 45፥5፤ኤር50፥17
**24፥9** ዘፍ12፥2፡3፤ ዘኍ23፥24
**24፥10** ቀኍ3-9፤ዘፀ 4፥14፤ዘኍ22፥6፤23፥7 -10፤11፡18-24፤ዘዳ 23፥5፤ኢዮ27፥23፤ 34፥37፤ሰቆ2፥15፤ሕዝ 21፥14፤22፥13፤ 25፥6
**24፥11** ቀኍ14፡25፤ ዘኍ22፥17
**24፥12** ዘኍ22፥18
**24፥13** ዘኍ22፥18፡ 20
**24፥14** ዘፍ49፥1፤ ዘኍ31፥8፡16፤ሚክ 6፥5

[ሀ]4 በዕብራይስጥ *ሻዳይ* ማለት ነው፡፡

እመለሳለሁ፤ ይሁን እንጂ በሚመጣው ዘመን
ይህ ሕዝብ በሕዝብህ ላይ የሚያደርገውን
ና ልንገርህ።”

## አራተኛው የበለዓም ንግር

15ከዚያም እንዲህ ሲል ንግሩን ጀመረ፤

“የቢያር ልጅ የበለዓም ንግር፤
የዚያ ዐይኑ የተከፈተለት ሰው
ንግር፡፡
16የዚያ የአምላክን (ኤሎሂም) ቃል የሚሰ
ማ፣
ከልዑልም ዕውቀትን ያገኘው፣
ሁሉን ከሚችለው ራእይ
የሚገለጥለት፣
መሬት የተደፋው፣ ዐይኖቹም
የተገለጡለት ሰው ንግር፤

17“አየዋለሁ፤ አሁን ግን አይደለም፤
እመለከተዋለሁ፤ በቅርቡ ግን
አይደለም፤
ኮከብ ከያዕቆብ ይወጣል፤
በትረ መንግሥት ከእስራኤል
ይነሣል፡፡
የሞዓብን ግንባሮች፣
የሤትንም ወንዶች ልጆች ራስ
ቅል† ያደቃል፡፡
18ኤዶም ይሸነፋል፤
ጠላቱ ሴይርም ድል ይሆናል፤
እስራኤል ግን እየበረታ
ይሄዳል፡፡
19ገዥ ከያዕቆብ ይወጣል፤
የተረፉትንም የከተማዪቱን ነዋሪዎች
ይደመስሳል፡፡”

## የመጨረሻዎቹ የበለዓም ንግሮች

20ከዚያም በለዓም አማሌቅን አይቶ
ንግሩን እንዲህ ሲል ጀመረ፤

“አማሌቅ ከሕዝቦች የመጀመሪያው
ነበር፤
በመጨረሻ ግን ይደመሰሳል፡፡”

21ቄናውያንንም አይቶ ንግሩን እንዲህ
ሲል ጀመረ፤

“መኖሪያህ አስተማማኝ ነው፤
ጐጆህም በዐለት ውስጥ ተሠርቶአል፤
22ያም ሆኖ ግን እናንት ቄናውያን፤
አሶር በምርኮ ሲወስዳችሁ
ትደመሰሳላችሁ፡፡”

23ከዚያም ንግሩን ቀጠለ፤

“አቤት! አምላክ (ኤሎሂም) ይህን
ሲያደርግ ማን ይተርፋል?
24መርከቦች ከኪቲም ዳርቻዎች
ይመጣሉ፤

24፥16 ዘፍ14፥18፤ ዘኍ22፥9፤ኢሳ14፥14
24፥17 19፥37፤ዘፍ 49፥10፤ዘኍ21፥29፤ ዘዳ23፥6፤ኢሳ15፥1-16፥14፤ኤር48፥45፤ ማቴ2፥2፤ራእ1፥7
24፥18 ዘፍ9፥25፤ 14፥6፤ዘዳ1፥44፤ኢሱ 12፥7፤15፥10፤መሳ 5፥4፤2ሳሙ8፥12፤ 1ዜና18፥11፤መዝ 60፥8፤ኢሳ11፥14፤ አሞ9፥12፤አብ1፥2
24፥19 ዘፍ49፥10፤ ሚክ 5፥2
24፥20 ዘፍ14፥7፤ ዘፀ17፥14፤ዘዳ25፥19፤ 1ሳሙ15፥20፤30፥17-20፤2ሳሙ8፥12፤ 1ዜና18፥11
24፥21 ዘፍ15፥19፤ መዝ37፥27፤ምሳ1፥33 ፤ኢሳ32፥18፤ሕዝ 34፥27
24፥22 ዘፍ10፥22
24፥24 ቍ20፥22፤ ዘፍ10፥4፤21
24፥25 ዘኍ22፥5
25፥1 ዘፍ19፥37፤ ዘኍ21፥16፤31፥16፤ ኢሱ2፥1፤ኢሳ66፥11፤ ኤር5፥7፤7፥9፤9፥2፤ ኢል3፥18፤ሚክ6፥5፤ 1ቆሮ10፥8፤ራእ2፥14
25፥2 ዘፀ20፥5፤ 32፥6፤ዘዳ32፥38፤ 1ቆሮ10፥20
25፥3 ዘኍ23፥28፤ ዘዳ4፥19፤መሳ2፥19፤ 1ነገ9፥9፤ኤር1፥16፤ 44፥3
25፥4 ዘፀ32፥12፤ ዘኍ7፥2፤13፥3፤ዘዳ4፥3፤ 13፥17፤ኢሱ7፥26፤ 2ሳሙ21፥6፤2ነገ23፥26፤2ዜና28፥11፤29፥10፤30፥8፤ዕዝ10፥14፤ኤር44፥3
25፥5 ዘፀ32፥27፤ ሆሴ9፥10
25፥6 ዘፍ25፥2፤ ዘኍ14፥1፤መሳ2፥4፤ሩት1፥9፤1ሳሙ11፥4፤ 2ሳሙ15፥30፤ዕዝ 10፥1፤መዝ126፥6፤ ኤር41፥6
25፥7 ዘፀ6፥25፤ኢሱ 22፥13፤መሳ5፥8፤20፥28፤1ሳሙ13፥19፥22፤ 1ነገ18፥28፤መዝ35፥3 ፤46፥9፤ኢል3፥10፤ ሚክ4፥3
25፥8 መዝ106፥30
25፥9 ዘኍ14፥37፤ 31፥16፤1ቆሮ10፥8
25፥11 ዘፀ20፥5፤ዘዳ 32፥16፤21፤መዝ 78፥58፤106፥30
25፥12 ኢሳ11፥9፤ 54፥10፤ሕዝ34፥25፤ 37፥26፤ሚል2፥4፥5

አሦርንና ዔቦርን ይይዛሉ፤
እነርሱም ደግሞ ይደመሰሳሉ፡፡

25ከዚህ በኋላ በለዓም ተነሥቶ ወደ ቤቱ
ተመለሰ፤ ባላቅም መንገዱን ቀጠለ፡፡

## ሞዓብ እስራኤልን አሳሳተ

25 እስራኤላውያን በሰጢም በነበሩ
በት ጊዜ ወንዶቹ ከሞዓብ ሴቶች
ጋር ማመንዘር ጀመሩ፡፡ 2እነዚህም ሴቶች
ወደ አምላኮቻቸው መሥዋዕት ሕዝቡን
ጋበዙ፤ ሕዝቡም መሥዋዕቱን በላ፤ ለአማ
ልክቱም ሰገደ፡፡
3ስለዚህ እስራኤል የፌጎርን በኣል በማ
ምለክ ተባበረ፤ *የእግዚአብሔርም* (ያህዌ)
ቍጣ በላዩ ነደደ፡፡
4*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን፣ “አስፈሪው
*የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ቍጣ ከእስራኤል እን
ዲመለስ የሕዝቡን አለቆች ሁሉ ወስደህ
ግደልና በጠራራ ፀሓይ ላይ *በእግዚአብሔር*
(ያህዌ) ፊት ስቀላቸው” አለው፡፡
5ሙሴም የእስራኤልን ዳኞች፣ “እያንዳ
ንዳችሁ የፌጎርን በኣል በማምለክ የተባ
በሩትን ሰዎቻችሁን ግደሉ አላቸው፡፡”
6ከዚህ በኋላ ሙሴና መላው የእስራኤል
ማኅበር በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ላይ
እያለቀሱ ሳለ፣ አንድ እስራኤላዊ እነርሱ
እያዩት አንዲት ምድያማዊት ሴት ይዞ
ወደ ቤተ ሰቡ መጣ፡፡ 7የካህኑ የአሮን ልጅ
የአልዓዛር ልጅ ፊንሐስ ይህን ባየ ጊዜ ማኅ
በሩን ትቶ ጦሩን በእጁ በመያዝ፣ 8እስራ
ኤላዊውን ተከትሎ ወደ ድንኳኑ ገባ፤
ጦሩንም ወርውሮ እስራኤላዊውንና ሴቲቱን
አጣምሮ ወጋቸው፤ ከዚያም በእስራኤላው
ያን ላይ የወረደው መቅሠፍት ተከለከለ፤
9ሆኖም በመቅሠፍቱ የሞተው ሰው ቍጥር
ሃያ አራት ሺህ ደርሶ ነበር፡፡
10*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤
11“የካህኑ የአሮን ልጅ፣ የአልዓዛር ልጅ
ፊንሐስ እኔ ለክብሬ በመካከላቸው እንደ
ምቀና ስለ ቀና ቍጣዬን ከእስራኤላውያን
መልሶታል፤ ስለዚህ እኔም በቅናቴ ጨርሶ
አላጠፋኋቸውም፤ 12ስለዚህ እነሆ እኔ የሰላም
ቃል ኪዳኔን ከእርሱ ጋር እንደማደርግ
ንገረው፡፡ 13ለአምላኩ (ኤሎሂም) ክብር ቀንቶ
ለእስራኤላውያን ስላስተሰረየላቸው፣ እርሱና
ልጆቹ ዘላቂ የክህነት ቃል ኪዳን ይኖራ
ቸዋል፡፡
14ከምድያማዊቷ ሴት ጋር የተገደለው
እስራኤላዊ የሰሉ ልጅ ዘንበሪ ይባላል፤ የስ
ምዖናውያን ቤተ ሰብ አለቃ ነበር፡፡
15እንዲሁም የተገደለችዋ ምድያማዊት ሴት

†17 የአሪተ ሳምራውያኑ ቅጅ *የራስ ቅል* ሲል፣ በማሶሬቲክ ቅጅ ግን ያቃሉ ትርጒም አይታወቅም፡፡

ከስቢ ትባላለች፤ እርሷም ከምድያማውያን
ቤተ ሰብ የአንዱ ነገድ አለቃ የሆነው የሱር
ልጅ ነበረች።
16*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤
17"*ምድያማውያንን እንደ ጠላት ቈጥራ
ችሁ ፍጇቸው። 18ይኸውም ፌጎር ላይ በተፈ
ጸመው ድርጊትና በፌጎር ምክንያት በመ
ጣው መቅሠፍት በተገደለችው በምድያ
ማዊው አለቃ ልጅ፣ በእኅታቸው በከስቢ
አታልለው የጠላትነት ሥራ ስለሠሩባችሁ
ነው።*"

## ሁለተኛው የሕዝብ ቈጠራ

**26** ከመቅሠፍቱ በኋላ *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ሙሴንና የካህኑን የአሮንን ልጅ
አልዓዛርን እንዲህ አላቸው፤ 2"*ዕድሜ
ያቸው ሃያ ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸ
ውን፣ በእስራኤልም ጦር ሰራዊት ውስጥ
ለማገልገል ብቃት ያላቸውን ሁሉ ከመ
ላው የእስራኤል ማኅበረ ሰብ ከየቤተ ሰቡ
ቍጠሩ።*" 3ስለዚህ ሙሴና ካህኑ አልዓዛር
ከኢያሪኮ[ቸ] ማዶ በዮርዳኖስ አጠገብ ባለው
በሞዓብ ሜዳ ለሕዝቡ እንዲህ ሲሉ ተና
ገሩ፤ 4"*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን ባዘዘው
*መሠረት ዕድሜያቸው ሃያና ከዚያ በላይ
የሆነውን ቍጠሩ።*"
ከግብፅ የወጡት እስራኤላውያንም እነ
ዚህ ነበሩ፤
5የእስራኤል የበኵር ልጅ የሆነው የሮቤል
ዘሮች እነዚህ ነበሩ፤
በሄኖኅ በኩል፣ የሄኖኀውያን ጐሣ፤
በፈለስ በኩል፣ የፈሉሳውያን ጐሣ፤
6በአስሮን በኩል፣ የአስሮናውያን ጐሣ፤
በከርሚ በኩል፣ የከርማውያን ጐሣ፤
7እነዚህ የሮቤል ጐሣዎች ሲሆኑ፤ ከእነዚህም
የተቈጠሩት አርባ ሦስት ሺህ ሰባት መቶ
ሠላሳ ነበሩ።
8የፈሉስ ልጅ ኤልያብ ሲሆን፣ 9የኤልያብ
ልጆች ደግሞ፣ ነሙኤል ዳታንና አቤሮን
ነበሩ። እነዚሁ ዳታንና አቤሮን በሙሴና
በአሮን ላይ ያመፁ የማኅበሩ ሹማምንት ሲሆኑ፣
ቆሬና ተከታዮቹ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ላይ
ባመፁ ጊዜ እነርሱም በነገሩ ነበሩበት።
10ሁለት መቶ አምሳዎቹን ሰዎች እሳት
በበላቻቸው ጊዜ የቆሬ ተከታዮች ሲሞቱ
እነዚህን ደግሞ ምድር ተከፍታ ከእርሱ
ጋር ዋጠቻቸው፤ መቀጣጫም ሆኑ፤ 11የቆሬ
የዘር ሐረግ ግን አልጠፋም።

12የስምዖን ዘሮች በየጐሣቸው እነዚህ ነበሩ፤
በነሙኤል በኩል፣ የነሙኤላውያን
ጐሣ፤
በያሚን በኩል፣ የያሚናውያን ጐሣ፤
በያኪን በኩል፣ የያኪናውያን ጐሣ፤
13በዛራ በኩል፣ የዛራውያን ጐሣ፤
በሳኡል በኩል፣ የሳኡላውያን ጐሣ፤
14እነዚህ የስምዖን ጐሣዎች ሲሆኑ፣ ከእነዚህ
የተቈጠሩትም ሃያ ሁለት ሺህ ሁለት
መቶ ነበሩ።

15የጋድ ዘሮች በየጐሣዎቻቸው እነዚህ ነበሩ፤
በጽፎን በኩል፣ የጽፎናውያን ጐሣ፤
በሐጊ በኩል፣ የሐጋውያን ጐሣ፤
በሹኒ በኩል፣ የሹናውያን ጐሣ፤
16በኤስና በኩል፣ የኤስናናውያን
ጐሣ፤
በዔሪ በኩል፣ የዔራውያን ጐሣ፤
17በአሮዲ[ኀ] በኩል፣ የአሮዳውያን ጐሣ፤
በአርኤሊ በኩል፣ የአርኤላውያን ጐሣ፤
18እነዚህ የጋድ ጐሣዎች ሲሆኑ፣ ከነዚህ
የተቈጠሩት አርባ ሺህ አምስት መቶ ነበሩ
።

19ዔርና አውናን የይሁዳ ልጆች ነበሩ፤
ነገር ግን በከነዓን ምድር ሞተዋል።
20የይሁዳ ዘሮች በየጐሣቸው እነዚህ ነበሩ፤
በሴሎም በኩል፣ የሴሎማውያን ጐሣ፤
በፋሬስ በኩል፣ የፋሬሳውያን ጐሣ፤
በዛራ በኩል፣ የዛራውያን ጐሣ፤
21የፋሬስ ዘሮች በየጐሣቸው እነዚህ ነበሩ፤
በኤስሮም በኩል፣ የኤስሮማውያን
ጐሣ፤
በሐሙል በኩል፣ የሐሙላውያን
ጐሣ፤
22እነዚህ የይሁዳ ጐሣዎች ሲሆኑ፣ ከእነዚህ
የተቈጠሩት ሰባ ስድስት ሺህ አምስት መቶ
ነበሩ።

23የይሳኮር ዘሮች በየጐሣቸው እነዚህ ነበሩ፤
በቶላ በኩል፣ የቶላውያን ጐሣ፣
በፉዋ በኩል፣ የፉዋውያን ጐሣ፣
24በያሱብ በኩል፣ የያሱባውያን ጐሣ፣
በሺምሮን በኩል፣ የሺምሮናውያን ጐሣ፤
25እነዚህ የይሳኮር ጐሣዎች ሲሆኑ፣ ከእነዚህ
የተቈጠሩት ሥልሳ አራት ሺህ ሦስት መቶ
ነበሩ።

26የዛብሎን ዘሮች በየጐሣቸው እነዚህ
ነበሩ፤
በሴሬድ በኩል፣ የሴሬዳውያን ጐሣ፤
በኤሎን በኩል፣ የኤሎናውያን ጐሣ፣
በያሕልኤል በኩል፣ የያሕልኤላውያን
ጐሣ፤
27እነዚህ የዛብሎን ጐሣዎች ሲሆኑ፣ ከእነዚህ
የተቈጠሩት ሥልሳ ሺህ አምስት መቶ ነበሩ።

28የዮሴፍ ዘሮች በምናሴና በኤፍሬም በኩል
ያሉት በየጐሣቸው እነዚህ ነበሩ፤

[ቸ]3 በዕብራይስጥ *የኢያሪኮ ዮርዳኖስ* የሚባል ሲሆን፤ ይህም
የዮርዳኖስ ወንዝ የጥንት ስም ሳይሆን አይቀርም።
[ኀ]17 በአራተ ሳምራውያኑ ቅጅ *አሮዲ*፣ በማሶሬቲክ ቅጅ *አሮድ*
ተብሎአል።

**25፥13** ቍ11፤ዘፀ 29፥9፡36፤1ነገ19፥10፤ 2ነገ10፥16፤መዝ106፥31፤ኤር33፥18፤ሮሜ 3፥25
**25፥14** ቍ6፤ ዘኍ1፥6
**25፥15** ቍ18፤ዘኍ 31፥8፤ኢሱ13፥21፤ ዕን3፥7
**25፥16** ዘኍ31፥7
**25፥17** ዘፀ23፥22፤ ዘኍ31፥1-3፤ዘዳ21፥1 ፤መሳ2፥16-18፤1ሳሙ 17፥9፡35፤2ነገ9፥27፤ 10፥25፤ነህ9፥27፤መዝ 8፥2፤21፥8፤74፥23
**25፥18** ዘኍ23፥28
**26፥1** ዘኍ14፥37፤ 25፥8
**26፥2** ዘፀ30፥11-16፤ዘኍ1፥3
**26፥3** ቍ63፤ዘኍ 22፥1፤33፥48፤ኢሱ 13፥32
**26፥4** ዘፀ6፥14፤ 13፥3
**26፥5** ዘፍ46፥9፤ ዘኍ1፥20፤ 1ዜና5፥3
**26፥6** ዘፍ46፥9፤ 1ዜና5፥3
**26፥9** ዘኍ10፥16፤ 16፥1፡2
**26፥10** ዘፀ3፥12፤ 15፥12፤ዘኍ16፥35፡ 38
**26፥11** ዘፀ6፥24፤ ዘኍ16፥33፤ዘዳ5፥9፤2 4፥16፤2ነገ14፥6፤2ዜና 25፥4፤ሕዝ18፥20
**26፥12** ዘፍ46፥10፤ 1ዜና4፥24
**26፥13** ዘፍ46፥10
**26፥14** ዘፍ46፥10፤ ዘኍ1፥23
**26፥15** ዘፍ46፥16
**26፥18** ዘፍ30፥11፤ ዘኍ1፥25፤ኢሱ 13፥24-28
**26፥19** ዘፍ38፥3፡ 4፡7
**26፥20** ዘፍ38፥5፡ 29፤ኢሱ7፥17
**26፥21** ዘፍ38፥29 ፤ሩት4፥19፤1ዜና 2፥9
**26፥22** ዘኍ1፥27
**26፥23** ዘፍ46፥13
**26፥24** ዘፍ46፥13
**26፥25** ዘፍ30፥18
**26፥26** ዘኍ1፥30
**26፥27** ዘፍ30፥20
**26፥28** ዘፍ41፥52፤ ዘኍ1፥32፤36፥1

[29]የምናሴ ዘሮች፤
በማኪር በኩል፣ የማኪራውያን ጐሣ፤
ማኪርም የገለዓድ አባት ነው፤
በገለዓድ በኩል፣ የገለዓዳውያን ጐሣ፤
[30]የገለዓድ ዘሮች እነዚህ ነበሩ፤
በኢዔዝር በኩል፣ የኢዓዝራውያን
ጐሣ፣
በኬሌግ በኩል፣ የኬሌጋውያን ጐሣ፣
[31]በአሥሪኤል በኩል፣ የአሥሪኤላው
ያን ጐሣ፣
በሴኬም በኩል፣ የሴኬማውያን
ጐሣ፣
[32]በሸሚዳ በኩል፣ የሸሚዳውያን ጐሣ፣
በኦፌር በኩል፣ የኦፌራውያን ጐሣ፣
[33]የኦፌር ልጅ ሰለጰዓድ ወንዶች
ልጆች አልነበሩትም፤ ልጆቹ ሴቶች
ብቻ ነበሩ፤ እነርሱም ማህለህ፣ ኑዓ፣
ዔግላ፣ ሚልካና ቲርጻ ይባላሉ።
[34]እነዚህ የምናሴ ጐሣዎች ሲሆኑ፣ ከእነዚህ
የተቈጠሩት አምሳ ሁለት ሺህ ሰባት
መቶ ነበሩ።

[35]የኤፍሬም ዘሮች በየጐሣቸው እነዚህ ነበሩ፤
በሱቱላ በኩል፣ የሱቱላውያን ጐሣ፣
በቤኬር በኩል፣ የቤኬራውያን ጐሣ፣
በታሐን በኩል፣ የታሐናውያን ጐሣ፤
[36]የሱቱላ ዘሮች እነዚህ ነበሩ፤
በዔዴን በኩል፣ የዔዴውናውያን ጐሣ፤
[37]እነዚህ የኤፍሬም ጐሣዎች ሲሆኑ፣ ከእነ
ዚህ የተቈጠሩት ሠላሳ ሁለት ሺህ አም
ስት መቶ ነበሩ።
እነዚህም በየጐሣቸው የተቈጠሩ የዮሴፍ
ዘሮች ነበሩ።

[38]የብንያም ዘሮች በየጐሣቸው እነዚህ ነበሩ፤
በቤላ በኩል፣ የቤላውያን ጐሣ፣
በአስቤል በኩል፣ የአስቤላውያን ጐሣ፣
በአኪራን በኩል፣ የአኪራናውያን ጐሣ፣
[39]በሶፋን[ነ] በኩል፣ የሶፋናውያን ጐሣ፣
በሑፋም በኩል፣ የሑፋማውያን ጐሣ፤
[40]የቤላ ዘሮች በአርድና በናዕማን በኩል፤
በአርድ በኩል፣ የአርዳውያን ጐሣ፣
በናዕማን በኩል፣ የናዕማናውያን ጐሣ፤
[41]እነዚህ የብንያም ጐሣዎች ሲሆኑ፣ ከእ
ነዚህም የተቈጠሩት አርባ አምስት ሺህ
ስድስት መቶ ነበሩ።

[42]የዳን ዘሮች በየጐሣቸው እነዚህ ነበሩ፤
በስምዔ በኩል፣ የሰምዔያውያን ጐሣ
ዎች።
እነዚህ እንግዲህ የዳን ጐሣዎች ሲሆኑ፣
[43]ሁሉም የሰምዔያውያን ጐሣዎች ነበሩ፤
ከእነዚህ የተቈጠሩት ደግሞ ሥልሳ አራት
ሺህ አራት መቶ ነበሩ።

26፥29 ዘፍ50፥23፤ ዘኍ1፥34፤መሳ11፥1
26፥30 ዘኍ27፥1፤ 36፥1፤ኢሱ17፥2፤መሳ 6፥11፤8፥2፤1ዜና7፥14፡ 17
26፥33 ዘኍ27፥1፤ 3፤36፥2፤11፤ኢሱ 17፥3፤1ዜና7፥15
26፥34 ዘኍ1፥35
26፥35 ዘኍ1፥32
26፥37 ዘኍ1፥33
26፥38 ዘፍ46፥21፤ ዘኍ1፥36፤1ዜና8፥40
26፥40 ዘፍ46፥21
26፥41 ዘኍ1፥37
26፥42 ዘፍ46፥23፤ ዘኍ1፥38፤መሳ18፥19
26፥44 ዘኍ1፥40
26፥47 ዘኍ1፥41
26፥48 ዘፍ30፥8
26፥50 ዘኍ1፥42፡ 43
26፥51 ዘፀ12፥37
26፥53 ቍ55፤ኢሱ 11፥23፤14፥1፤ሕዝ 45፥8
26፥54 ዘኍ33፥ 54፤35፥8
26፥55 ዘሌ16፥8
26፥57 ዘፍ46፥11
26፥58 ዘፀ6፥20
26፥59 ዘፀ2፥1፡4፤ 6፥20፤15፥20

[44]የአሴር ዘሮች በየጐሣቸው እነዚህ ነበሩ፤
በዩምና በኩል፣ የዩምናውያን ጐሣ፣
በየሱዋ በኩል፣ የየሱዋውያን ጐሣ፣
በበሪዓ በኩል፣ የበሪዓውያን ጐሣ፤
[45]እንዲሁም በበሪዓ ዘሮች በኩል፣
በሔቤር በኩል፣ የሔቤራውያን ጐሣ፣
በመልኪኤል በኩል፣ የመልኪኤላ
ውያን ጐሣ።
[46]አሴር ሤራሕ የምትባል ልጅ ነበረ
ችው።
[47]እነዚህ የአሴር ጐሣዎች ሲሆኑ፣ ከእነዚህ
የተቈጠሩት አምሳ ሦስት ሺህ አራት
መቶ ነበሩ።

[48]የንፍታሌም ዘሮች በየጐሣቸው እነዚህ ነበሩ፤
በያሕጽኤል በኩል፣ የያሕጽኤላውያን
ጐሣ፣
በጉኒ በኩል፣ የጉናውያን ጐሣ፣
[49]በሺሌም በኩል፣ የሺሌማውያን ጐሣ፤
[50]እነዚህ የንፍታሌም ጐሣዎች ሲሆኑ፣ ከእ
ነዚህ የተቈጠሩት አርባ አምስት ሺህ አራት
መቶ ነበሩ።
[51]ባጠቃላይ የእስራኤል ወንዶች ቍጥር
ስድስት መቶ አንድ ሺህ ሰባት መቶ
ሠላሳ ነበር።
[52]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ [53]“ምድሪቱ በስማቸው ቍጥር
ልክ ተደልድላ በርስትነት ለእነርሱ ትሰጥ።
[54]በርከት ያለ ቍጥር ላለው ጐሣ ሰፋ
ያለውን ርስት፣ አነስ ያለ ቍጥር ላለው
ጐሣ ደግሞ አነስ ያለውን ስጥ፤ ርስቱንም
እያንዳንዱ በዝርዝሩ ላይ በተመለከተው
ቍጥር መሠረት ይረከባል። [55]የመሬት ድል
ድሉም በዕጣ ይሁን፤ እያንዳንዱ የሚወ
ርሰውም በየነገድ አባቶቹ ስም ይሆናል።
[56]እያንዳንዱም ርስት በትልልቆቹና በትን
ንሾቹ ነገዶች መካከል በዕጣ ይደለደላል።

[57]በየጐሣቸው የተቈጠሩት ሌዋውያን እነዚህ
ነበሩ፤
በጌድሶን በኩል፣ የጌድሶናውያን ጐሣ፣
በቀዓት በኩል፣ የቀዓታውያን ጐሣ፣
በሜራሪ በኩል፣ የሜራራውያን ጐሣ፤
[58]እነዚህም ደግሞ የሌዊ ጐሣዎች ነበሩ፤
የሊብናውያን ጐሣ፣
የኬብሮናውያን ጐሣ፣
የሞሖላውያን ጐሣ፣
የሙሳውያን ጐሣ፣
የቆሬያውያን ጐሣ።
ቀዓት የእንበረም ቅድመ አያት ነበር፤
[59]ሚስቱ ዮካብድ ትባል ነበር፤ እርሷም

[ነ]39 ጥቂት የማሶሬቲክ፣ የአሪተ ሳምራውያን፣ የቩልጌትና የሱር ስት ቅጆች *ሶፋን* የሚሉ ሲሆን፣ አያሌ የማሶሬቲክ ቅጆች ግን *ሼፉፋም* ይላሉ።

በግብፅ አገር ከሌዋውያን የተወለደች
የሌዊ ዘር ነበረች። ከእንበረምም አሮ
ንን፣ ሙሴንና እኅታቸውን ማርያምን
ወለደች። 60አሮንም የናዳብና የአብዮድ፣
የአልዓዛርና የኢታምር አባት ነበር።
61ነገር ግን ናድብና አብዩድ ባለተፈ
ቀደ እሳት *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) *መሥ*
*ዋዕት* ስላቀረቡ ሞቱ።

62አንድ ወርና ከዚያ በላይ የሆናቸው
ሌዋውያን ወንዶች ሁሉ ተቈጥረው *ሃያ*
*ሦስት ሺህ* ሆኑ፤ እነርሱም ከሌሎቹ እስራ
ኤላውያን ጋር ርስት ተካፋዮች ስላልነበሩ
አብረዋቸው አልተቈጠሩም።
63ሙሴና ካህኑ አልዓዛር ከኢያሪኮ ማዶ
በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ ካለው ከሞዓብ
ሜዳ ላይ የእስራኤልን ሕዝብ በቈጠሩበት
ወቅት የተቈጠሩት እነዚህ ናቸው። 64ሙሴና
ካህኑ አሮን በሲና ምድረ በዳ እስራኤላው
ያንን በቈጠሩ ጊዜ ከእነዚህ ከተቈጠሩት
መካከል አንዳቸውም አልነበሩም፤ 65ምክን
ያቱም በእርግጥ በምድረ በዳ እንደሚሞቱ
ያን ጊዜ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነግሮአቸው
ነበር፣ ከዮፎኒ ልጅ ከካሌብና ከነዌ ልጅ
ከኢያሱ በስተቀር ከእነርሱ የተረፈ ማንም
ሰው አልነበረም።

## የሰለጰዓድ ሴት ልጆች

27 የምናሴ ልጅ፣ የማኪር ልጅ፣ የገ
ለዓድ ልጅ፣ የአፌር ልጅ፣ የሰለጰዓድ
ሴት ልጆች ከዮሴፍ ልጅ ከምናሴ ጐሣ
ዎች ነበሩ፤ ስማቸውም ማህለህ፣ ኑዓ፣ ዔግላ፣
ሚልካና ቲርጻ ይባላል። እነርሱም፣ 2ወደ
መገናኛው ድንኳን መግቢያ ቀረቡ፤ በሙሴ፣
በካህኑ በአልዓዛር፣ በመሪዎችና በመላው
ማኅበርም ፊት ቆመው እንዲህ አሉ፤
3"አባታችን በምድረ በዳ ሞተ፤ ተባብረው
*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ላይ ካመፁት ከቆሬ
ተከታዮች ጋር አልነበረም፤ የሞተው ግን
በራሱ ኀጢአት ሲሆን፣ ወንዶች ልጆችም
አልነበሩትም። 4ታዲያ አባታችን ወንድ
ልጅ ባለመውለዱ ስሙ ከጐሣዎቹ ተለ
ይቶ እንዴት ይጠፋል? ለእኛም በአባታ
ችን ዘመዶች መካከል ርስት ስጡን።"
5ስለዚህ ሙሴ ጕዳያቸውን ወደ *እግዚአ*
*ብሔር* (ያህዌ) አቀረበ፤ 6*እግዚአብሔርም*
(ያህዌ) እንዲህ አለው፤ 7"የሰለጰዓድ ልጆች
ጥያቄ ትክክል ነው፤ በእርግጥ
በአባታቸው ዘመዶች መካከል ድርሻቸውን
ርስት አድ ርገህ ልትሰጣቸው ስለሚገባ
የአባታቸውን ድርሻ ለእነርሱ
አስተላልፍላቸው።
8"እስራኤላውያንን እንዲህ በላቸው፤ 'አንድ
ሰው ወንድ ልጅ ሳይተካ ቢሞት ውርሱን

26÷60 ዘፀ6÷23
26÷61 ዘሌ10÷1-2፤ዘኍ3÷4
26÷62 ዘኍ1÷47፤2÷33፤3÷39፤18÷23
26÷63 ቍ3፤ዘኍ1÷19፤22÷1
26÷64 ዘኍ1÷44፤14÷29
26÷65 ዘኍ11÷28፤13÷6፤14÷28፤1ቆሮ10÷5
27÷1 ዘፍ50÷23፤ዘኍ26÷30፡33፤ኢሱ17÷2፡3፤1ዜና2÷21
27÷2 ዘፀ40÷2፡17፤ዘኍ1÷16፤9÷6፤31÷13፤32÷2፤36÷1
27÷3 ዘኍ16÷2፤26÷33፡65
27÷5 ዘፍ25÷22፤ዘፀ18÷19፤ዘኍ9÷8
27÷7 ቍ8፤ኢሱ17÷4፤ኢዮ42÷15
27÷11 ዘኍ35÷29
27÷12 ዘኍ23÷14፤33÷47፤ዘሌ14÷34፤ዘዳ3÷23-27፤32÷48-52፤ኤር22÷20
27÷13 ዘኍ20÷12፡28፤31÷2፤ዘዳ4÷22፤31÷14፤32÷50፤1ነገ2÷1
27÷14 ዘፀ17÷7፤ዘኍ20÷1፡2-5፡12
27÷16 ዘኍ16÷22፤ኢዮ21÷20
27÷17 1ነገ22÷17፤2ዜና18÷16፤ሕዝ34÷5፤ዘካ10÷2፤ማቴ9÷36
27÷18 ቍ23፤ዘፍ41÷38፤ዘኍ11÷25-29፤ዘዳ34÷9፤ሐሥ6÷6
27÷19 ቍ23፤ዘዳ3÷28፤31÷7፡14፡23
27÷20 ኢሱ1÷16፡17
27÷21 ዘፍ25÷22፤ዘፀ28÷30፤ኢሱ9÷14፤መዝ106÷13፤ኢሳ8÷19፤ሐጌ1÷13፤ሚል2÷7፤3÷1
27÷23 ቍ19

ለሴት ልጁ አስተላልፉ። 9ሴት ልጅ ከሌ
ለችው ደግሞ ውርሱን ለወንድሞቹ ስጡ።
10ወንድሞች ከሌሉትም ውርሱን ለአባቱ ወን
ድሞች ስጡ። 11አባቱ ወንድሞች ከሌሉት
ውርሱ ከጐሣው መካከል ቅርብ ለሆነ ዘመዱ
ይሰጥ፤ እርሱም ይውረሰው። ይህም *እግዚ*
*አብሔር* (ያህዌ) ሙሴን ባዘዘው መሠረት
ለእስራኤላውያን ሕጋዊ *መመሪያ* ይሆና
ቸዋል።' "

## ኢያሱ በሙሴ እግር ተተካ

12ከዚያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እን
ዲህ አለው፤ "በዓባሪም ሸንተረር ላይ ወዳ
ለው ወደዚህ ተራራ ውጣና ለእስራኤላው
ያን የሰጠኋቸውን ምድር እይ። 13ካየኸ
ውም በኋላ አንተም እንደ ወንድምህ እንደ
አሮን ወደ ሕዝብህ ትሰበሰባለህ፤ 14ምክን
ያቱም ማኅበረ ሰቡ በጺን ምድረ በዳ
ባለው ውሃ አጠገብ ባመፁ ጊዜ እኔን በሕ
ዝቡ ፊት ቅዱስ አድርጋችሁ ለማክበር
ሁለታችሁም ትእዛዜን ስላልጠበቃችሁ ነው።"
ይህም በጺን ምድረ በዳ በቃዴስ የሚገኝ
የመሪባ ውሃ ነው።
15ሙሴ *እግዚአብሔርን* (ያህዌ) እንዲህ አለው፤
16"የሰብአዊ ፍጡር ሁሉ መንፈስ *አምላክ*
(ኤሎሂም) የሆነ ጌታ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) በዚህ
ማኅበረ ሰብ ላይ ሰው ይሹም፤ 17እርሱም፣
*የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ሕዝብ እረኛ እንደሌ
ለው የበግ መንጋ እንዳይሆን በፊቱ የሚ
ወጣና የሚገባ፣ መርቶ የሚያወጣውና የሚ
ያገባው እንዲሆን ነው።"
18ስለዚህም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን
እንዲህ አለው፤ "*መንፈስ ቅዱስ*[ኘ] ያደረበ
ትን የነዌን ልጅ ኢያሱን ወስደህ እጅህን
ጫንበት። 19በካህኑ በአልዓዛርና በመላው
ማኅበር ፊት እንዲቆም አድርገው፤ በፊታ
ቸውም ሹመው፤ 20መላው የእስራኤል ማኅ
በረ ሰብ እንዲታዘዝለትም ከሥልጣንህ ከፍ
ለህ ስጠው። 21እርሱም *በእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ፊት ሆኖ በኡሪም በመጠየቅ ውሳኔ በሚ
ያስገኝለት በካህኑ በአልዓዛር ፊት ይቆ
ማል፤ እርሱም ሆነ መላው የእስራኤል ማኅ
በረ ሰብ በአልዓዛር ትእዛዝ ይወጣሉ፤ በእ
ርሱም ቃል ይገባሉ።"
22ሙሴም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) እንዳዘዘው
አደረገ፤ ኢያሱንም ወስዶ በካህኑ በአልዓዛ
ርና በመላው የእስራኤል ማኅበር ፊት አቆ
መው፤ 23ከዚያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
በሙሴ
አማካይነት ባዘዘው መሠረት እጁን በራሱ
ላይ ጭኖ ሾመው።

[ኘ]18 ወይም *መንፈስ*

### የየዕለቱ መሥዋዕት

28 እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2“ይህን ትእዛዝ ለእስራ
ኤላውያን ስጣቸው፤ ‘ሽታው ደስ እንዲ
ያሰኘኝ በእሳት የሚቀርብልኝን የምግብ
ቍርባን የተወሰነውን ጊዜ ጠብቃችሁ አቅ
ርቡልኝ’ በላቸው። 3ደግሞም እንዲህ በላ
ቸው፤ ‘በእሳት ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የምታቀ
ርቡት መሥዋዕት ይህ ነው፤ አንድ ዓመት
የሆናቸውንና እንከን የሌለባቸውን ሁለት
ተባዕት የበግ ጠቦቶች መደበኛ የሚቃጠል
መሥዋዕት በማድረግ በየዕለቱ አቅርቡ።
4አንዱን ጠቦት ጠዋት ሌላውን ደግሞ
ማታ አቅርቡ፤ 5ከዚህም ጋር ተወቅጦ በተ
ጠለለ በሂን[ኣ] አንድ አራተኛ የወይራ ዘይት
የተለወሰ የኢፍ[ከ] አንድ ዐሥረኛ ልም
ዱቄት የእህል ቍርባን አዘጋጁ። 6ይህም
ሽታው ደስ እንዲያሰኝ በእሳት ለእግዚአ
ብሔር (ያህዌ) የሚቀርብ ምሥዋዕት ሲሆን፣
በሲና ተራራ የተደነገገ መደበኛ የሚቃጠል
መሥዋዕት ነው። 7ከእያንዳንዱ ጠቦት ጋር
አብሮት የሚቀርበውም የመጠጥ ቍርባን
ፈልቶ የወጣለት የሂን አንድ አራተኛ መጠጥ
ይሆናል፤ የመጠጡንም ቍርባን በተቀደሰው
ቦታ ላይ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) አፍስሱት።
8ሁለተኛውንም ጠቦት ጠዋት ባቀረባች
ሁት ዐይነት አድርጋችሁ ከእህል ቍርባኑና
ከመጠጥ ቍርባኑ ጋር ማታ አቅርቡት፤
ይህም ሽታው እግዚአብሔርን (ያህዌ) ደስ የሚ
ያሰኝ በእሳት የሚቀርብ መሥዋዕት ነው።

### የሰንበት መሥዋዕት

9“ ‘በሰንበት ዕለት፣ አንድ ዓመት የሆና
ቸውንና እንከን የማይገኝባቸውን ሁለት
ተባዕት የበግ ጠቦቶች መሥዋዕት ከመጠጥ
ቍርባኑና በዘይት ከተለወሰ የኢፍ[ኸ] ሁለት
ዐሥረኛ ልም ዱቄት ጋር አቅርቡ። 10ይህም
ከመጠጥ ቍርባኑ ጋር በመደበኛነት ከሚቀ
ርበው የሚቃጠል መሥዋዕት ሌላ በየሰንበቱ
የሚቀርብ የሚቃጠል መሥዋዕት ነው።

### የየወሩ መሥዋዕት

11“ ‘በየወሩ መባቻ እንከን የሌለባቸውን
ሁለት ወይፈኖች፣ አንድ አውራ በግ፣ ዓመት
የሆናቸውን ሰባት ተባዕት የበግ ጠቦቶችን
የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጋችሁ ለእግ
ዚአብሔር (ያህዌ) አቅርቡ። 12ከእያንዳንዱ
ወይፈን ጋር ለእህል ቍርባን የሚሆን በዘ
ይት የተለወሰ የኢፍ[ወ] ሦስት ዐሥረኛ ልም
ዱቄት፣ ከአውራውም በግ ለእህል ቍርባን
የሚሆን በዘይት የተለወሰ የኢፍ ሁለት ዐሥ
ረኛ ልም ዱቄት ይቀርባል፤ 13እንደዚሁም
ከእያንዳንዱ የበግ ጠቦት ጋር ለእህል

28፥2 1፥9፤3፥11፤ ዘሌ23፥1-44
28፥3 ዘፀ12፥5፤ 29፥38፤አሞ4፥4
28፥4 ዘፀ29፥39
28፥5 ዘሌ2፥1፤ 6፥20፤ዘኍ29፥6
28፥6 ዘፀ19፥3፤ ዘሌ1፥3፡9
28፥7 ዘሌ3፥7፤ 10፥9፤23፥13፤ዘኍ 3፥28፤6፥15
28፥8 ቍ2፤ዘፀ 29፥39፤ዘሌ1፥9፤3፥7
28፥9 ቍ3፡5፤ዘፀ 20፥10፤ዘሌ23፥13 ማቴ12፥5
28፥10 ቍ3፤ ዘሌ23፥38
28፥11 ዘሌ1፥3፤ 5፥15፤ዘኍ7፥15፤ 10፥10
28፥12 ቍ20፤ዘኍ 15፥6፡9፤29፥3
28፥13 ቍ21፤ዘሌ 1፥9፤6፥14፤ዘኍ15፥3
28፥14 ቍ11፤ዘኍ 15፥7፤2ዜና2፥4፤ዕዝ 3፥5
28፥15 ቍ3፡23፡ 24፡30፤ዘሌ4፥3፤ዘኍ 29፥16፡19
28፥16 ዘፀ12፥11፤ 2ዜና30፥13፤35፥1
28፥17 ዘፀ12፥15፡ 19
28፥18 ዘፀ12፥16
28፥19 ቍ11፤ ዘሌ1፥9
28፥20 ቍ12፤ ዘሌ14፥10
28፥21 ቍ13
28፥22 ዘሌ4፥3፤ ዘኍ15፥28ሮሜ8፥3
28፥24 ዘሌ1፥9

ቍርባን የሚ ሆን በዘይት የተለወሰ የኢፍ
አንድ ዐሥረኛ ልም ዱቄት አቅርቡ፤
ይህም ለሚቃጠል መሥዋዕት ሲሆን ሽታው
ደስ የሚያሰኝና በእሳት ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
የሚቀርብ መሥዋዕት ነው። 14ከእያንዳንዱ
ወይፈን ጋር ለመጠጥ ቍርባን የሚሆን
የኢን[ዐ] ግማሽ የወይን ጠጅ፣ ከአውራው በግ
ጋር የኢን[ዘ] አንድ ሦስተኛ፣ ከእያንዳንዱም
የበግ ጠቦት ጋር የኢን አንድ አራተኛ የወ
ይን ጠጅ ይቅረብ፤ ይህም በየወሩ መባቻ
ዓመቱን ሙሉ የሚቀርብ የሚቃጠል
መሥዋዕት ነው። 15ከመጠጥ ቍርባኑ ጋር
በመደበኛነት ከሚቀርበው የሚቃጠል መሥ
ዋዕት ሌላ አንድ ተባዕት ፍየል የኀጢአት
መሥዋዕት ሆኖ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) ይቀ
ርባል።

### ፋሲካ

28፥16-25 ተጓ ምብ - ዘፀ 12፥14-20፤ ዘሌ 23፥4-8፤ ዘዳ
16፥1-8

16“ ‘የመጀመሪያው ወር በገባ በዐሥራ አ
ራ ተኛው ቀን የእግዚአብሔር (ያህዌ) ፋሲካ
በዓል ይከበራል። 17በዚሁ ወር በዐሥራ
አምስተ ኛው ቀን በዓል ይሆናል፤ እስከ
ሰባትም ቀን ድረስ ያለ እርሾ የተጋገረ
ቂጣ ብሉ። 18በመጀመሪያው ቀን
የተቀደሰ ጉባኤ አድርጉ፤ የዘወትር ተግባራ
ችሁንም አትሥሩበት። 19እንከን የሌለባቸው
ሁለት ወይፈኖች፣ አንድ አውራ በግና ዓ
መት የሆናቸው ሰባት ተባዕት የበግ ጠ
ቦቶች በእሳት የሚቃጠል መሥዋዕት በ
ማድረግ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) አቅርቡ።
20ከእያን ዳንዱም ወይፈን ጋር ለእህል
ቍርባን የሚሆን በዘይት የተለወሰ የኢፍ
ሦስት ዐሥ ረኛ ልም ዱቄት፣ ከአውራ
ውም በግ ጋር የኢፍ ሁለት ዐሥረኛ ልም
ዱቄት አቅ ርቡ፤ 21ከሰባቱም የበግ ጠ
ቦቶች ከእያንዳ ንዳቸው ጋር የኢፍ አንድ ዐ
ሥረኛ ልም ዱቄት አዘጋጁ። 22በተጨ
ማሪም ማስተስ ረያ እንዲሆናችሁ አንድ
ተባዕት ፍየል የኀጢአት መሥዋዕት
አድርጋችሁ አቅ ርቡ። 23እነዚህንም ጧት
ጧት በመደበ ኛነት ከሚቀርበው
የሚቃጠል መሥዋዕት ጋር አቅርቧቸው።
24በዚህም ዐይነት ሽታው እግዚአብሔርን ደስ
የሚያሰኝ ሆኖ በየዕለቱ
ለሰባት ቀን በእሳት ለሚቀርብ መሥዋዕት
የምግብ ቍርባን አዘጋጁ፤ ይህም ከመጠጥ
ቍርባኑ ጋር በመደበኛነት ከሚቀርበው
የሚቃጠል መሥዋዕት ጋር ሆኖ በተጨማሪ

[ኣ]5 አንድ ሊትር ያህል ነው።
[ከ]5 ሁለት ሊትር ያህል ነው።
[ኸ]9 አራት ተኩል ሊትር ያህል ነው።
[ወ]12 ስድስት ተኩል ሊትር ያህል ነው።
[ዐ]14 ሁለት ሊትር ያህል ነው።
[ዘ]14 አንድ ሊትር ያህል ነው።

ይቀርባል። [25]በሰባተኛው ቀን የተቀደሰ
ጉባኤ አድርጉ፤ የዘወትር ተግባርም አት
ሥሩበት።

## የሳምንቱ በዓል
28፥26-31 ተጓ ምብ - ዘሌ 23፥15-22፤ ዘዳ 16፥9-12

[26]" 'በየሳምንቱ በሚደረገው በዓል፣ አዲስ
የእህል ቍርባን ለእግዚአብሔር (ያህዌ) በም
ታቀርቡበት በፍሬ በኵራት ቀን የተቀደሰ
ጉባኤ አድርጉ፤ የዘወትር ተግባርም አት
ሥሩበት። [27]ሁለት ወይፈኖች፣ አንድ አው
ራ በግና ዓመት የሆናቸውን ሰባት ተባዕ
ት የበግ ጠቦቶች ሽታው እግዚአብሔርን
(ያህዌ) ደስ የሚያሰኝ አድርጋችሁ የሚቃጠል
መሥዋዕት አቅርቡ። [28]ከእያንዳንዱም
ወይ ፈን ጋር ለእህል ቍርባን የሚሆን
በዘይት የተለወሰ የኢፋ ሦስት ዐሥረኛ፣
ከአውራው በግ ጋር የኢፍ ሁለት ዐሥረኛ
ልም ዱቄት ይቀርባል፤ [29]ከሰባቱም
የበግ ጠቦቶች ከእ ያንዳንዳቸው ጋር የኢ
ፉ አንድ ዐሥረኛ ልም ዱቄት ይቅረብ።
[30]በተጨማሪም ማስ ተስረ ያ እንዲሆንላችሁ
አንድ ተባዕት ፍየል አቅርቡ። [31]ከእህል
ቍርባኑ ጋር በመደበኛ ነት ከሚቀርበው
የሚቃጠል መሥዋዕት በተጨማሪ እነዚህን
ከመጠጥ ቍርባናቸው ጋር አቅርቡ።
እንስሳቱም እንከን የሌላ ቸው
መሆናቸውን አረጋግጡ።

## የመለከት በዓል
29፥1-6 ተጓ ምብ - ዘሌ 23፥23-25

# 29
" 'በሰባተኛው ወር በመጀመሪያው
ቀን የተቀደሰ ጉባኤ አድርጉ፤ የዘ
ወትር ሥራም አትሥሩበት፤ ይህም የመለ
ከት ድምፅ የምታሰሙበት ቀናችሁ ነው።
[2]እንከን የሌለባቸውን አንድ ወይፈን፣ አንድ
አውራ በግና ዓመት የሆናቸው ሰባት ተባዕት
የበግ ጠቦቶች ሽታው እግዚአብሔርን (ያህዌ)
ደስ የሚያሰኝ የሚቃጠል መሥዋዕት አድ
ርጋችሁ አቅርቡ። [3]ከወይፈኑ ጋር ለእህል
ቍርባን የሚሆን የኢፍ[ፕ] ሦስት ዐሥረኛ፣
ከአውራውም በግ ጋር የኢፍ ሁለት ዐሥ
ረኛ፣[የ] በዘይት የተለወሰ ልም ዱቄት አቅ
ርቡ፤ [4]ከእያንዳንዱም ሰባት የበግ ጠቦት
ጋር በዘይት የተለወሰ የኢፍ አንድ ዐሥ
ረኛ[ደ] ልም ዱቄት አዘጋጁ። [5]ማስተስረያ
እንዲሆናችሁም አንድ ተባዕት ፍየል የኀጢ
አት መሥዋዕት በማድረግ በተጨማሪ አቅ
ርቡ። [6]እነዚህ እንግዲህ በተደነገገው መሠ
ረት ከእህል ቍርባናቸውና ከመጠጥ ቍር
ባናቸው ጋር በየዕለቱና በየወሩ ከሚቀርቡት
የሚቃጠሉ መሥዋዕቶች ሌላ ተጨማሪ ሆነው፣
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) ሽታቸው ደስ የሚያ
ሰኝ በእሳት የሚቀርቡ መሥዋዕቶች ናቸው።

28፥26 ቍ18፤ዘፀ 34፥22፤23፥16
28፥27 ቍ19
28፥28 ቍ12
28፥29 ቍ13
28፥30 ቍ15
28፥31 ቍ3፡19
29፥1 ዘኍ28፥18
29፥2 ቍ36፤ዘሌ1፥3፡9፤ዘኍ28፥2፡3፡11
29፥3 ቍ14፤ዘኍ28፥12
29፥4 ዘኍ28፥13
29፥5 ዘኍ28፥15
29፥6 ዘሌ1፥9፤ዘኍ28፥2፡3፡5፡7፡11
29፥7 ዘፀ31፥15፤ሐሥ 27፥9
29፥8 ቍ2
29፥9 ቍ3፡18፤ዘኍ28፥12
29፥10 ዘኍ28፥13
29፥11 ቍ5፡6፤ዘሌ16፥3፤ዘኍ28፥15
29፥12 ዘሌ23፥24፤1ነገ8፥2፤12፥32
29፥13 ቍ2፤ዘኍ28፥2፡3
29፥14 ቍ3፤ዘኍ15፥6
29፥15 ቍ4፤ዘኍ28፥13
29፥16 ቍ5፡6፤ዘኍ28፥15
29፥17 ቍ2፤ዘሌ23፥36፤ዘኍ28፥3

## የማስተስረያ ቀን
29፥7-11 ተጓ ምብ - ዘሌ 16፥2-34፤ 23፥26-32

[7]" 'በዚሁ በሰባተኛው ወር በዐሥረኛውም
ቀን የተቀደሰ ጉባኤ አድርጉ፤ ራሳችሁን
አዋርዱ፤[ጀ] ሥራም አትሥሩ። [8]ሁሉም እን
ከን የሌለባቸው አንድ ወይፈን፣ አንድ
አውራ በግና ዓመት የሆናቸው ሰባት ተባዕት
የበግ ጠቦቶች፣ ሽታው እግዚአብሔርን (ያህዌ)
ደስ የሚያሰኝ የሚቃጠል መሥዋዕት አድ
ርጋችሁ አቅርቡ። [9]ከወይፈኑ ጋር ለእህል
ቍርባን የሚሆን የኢፍ ሦስት ዐሥረኛ፣
ከአውራ በጉ ጋር የኢፍ ሁለት ዐሥረኛ
በዘይት የተለወሰ ዱቄት አቅርቡ፤ [10]ከሰ
ባቱ የበግ ጠቦቶችም ከእያንዳንዳቸው ጋር
በዘይት የተለወሰ የኢፍ አንድ ዐሥረኛ
ልም ዱቄት አዘጋጁ። [11]ማስተስረያ እንዲ
ሆንም ለኀጢአት መሥዋዕት ከሚቀርበው
እንዲሁም ከእህሉ ቍርባንና ከመጠጡ
ቍርባን ጋር በመደበኛነት ቀርቦ ከሚቃጠ
ለው መሥዋዕት ሌላ አንድ ተባዕት ፍየል
የኀጢአት መሥዋዕት አድርጋችሁ በተጨ
ማሪ አቅርቡ።

## የዳስ በዓል
29፥12-39 ተጓ ምብ - ዘሌ 23፥33-43፤ ዘዳ 16፥13-17

[12]" 'በሰባተኛው ወር በዐሥራ አምስተኛው
ቀን የተቀደሰ ጉባኤ አድርጉ፤ የዘወትር ሥ
ራ አትሥሩ፤ ለእግዚአብሔርም (ያህዌ) የሰባት
ቀን በዓል አክብሩ። [13]ሁሉም እንከን
የሌለባ ቸው ዐሥራ ሦስት ወይፈኖች፣
ሁለት አውራ በጎችና ዓመት የሆናቸው ዐ
ሥራ ሁለት ተባዕት የበግ ጠቦቶች የሚቃጠ
ል መሥዋዕት በማድረግ ሽታው እግዚ
አብሔ ርን (ያህዌ) ደስ እንዲያሰኝ በእሳት
አቅርቡ [14]ከዐሥራ ሦስቱ ወይፈኖች
ከእያንዳንዳቸው ጋር የኢፍ ሦስት ዐ
ሥረኛ፣ ከሁለቱ አውራ በጎችም
ከእያንዳንዳቸው ጋር የኢፍ ሁለት
ዐሥረኛ በዘይት የተለወሰ ልም ዱቄት
የእህል ቍርባን አቅርቡ፤ [15]እንዲሁም ከዐ
ሥራ አራቱ ተባዕት የበግ ጠቦቶች ከእያን
ዳንዳቸው ጋር የኢፍ አንድ ዐሥረኛ በዘይት
የተለወሰ ልም ዱቄት የእህል ቍርባን አቅ
ርቡ። [16]ከእህሉ ቍርባንና ከመጠጡ ቍር
ባን ጋር በመደበኛነት ከሚቀርበው የሚ
ቃጠል መሥዋዕት ሌላ አንድ ተባዕት ፍየል
የኀጢአት መሥዋዕት አድርጋችሁ በተጨ
ማሪ አቅርቡ።
[17]" 'በሁለተኛው ቀን ሁሉም እንከን
የሌ ለባቸው ዐሥራ ሁለት ወይፈኖች፣
ሁለት አውራ በጎችና ዓመት የሆናቸው ዐሥራ
አራት

[ፕ]3 ስድስት ተኩል ሊትር ያህል ነው።
[የ]3 አራት ተኩል ሊትር ያህል ነው።
[ደ]4 ሁለት ሊትር ያህል ነው።
[ጀ]7 ወይም *ጹሙ*

ተባዕት የበግ ጠቦቶች አቅርቡ፡፡ 18ከወይፈ
ኖቹ፣ ከአውራ በጎቹና ከበግ ጠቦቶቹ ጋር
በተወሰነው ቍጥር መሠረት የእህል ቍር
ባናቸውንና የመጠጥ ቍርባናቸውን አብራ
ችሁ አቅርቡ፡፡ 19ደግሞም ከእህሉ ቍርባ
ንና ከመጠጡ ቍርባን ጋር በመደበኛነት
ከሚቀርበው የሚቃጠል መሥዋዕት ሌላ
አንድ አውራ ፍየል የኀጢአት መሥዋዕት
አድርጋችሁ በተጨማሪ አቅርቡ፡፡

20“ ‘በሦስተኛው ቀን ሁሉም እንከን የሌ
ለባቸው ዐሥራ አንድ ወይፈኖች፣ ሁለት
አውራ በጎችና ዓመት የሆናቸው ዐሥራ አራት
ተባዕት የበግ ጠቦቶች አቅርቡ፡፡ 21ከወይ
ፈኖቹ፣ ከአውራ በጎቹና ከበግ ጠቦቶቹ
ጋር የእህል ቍርባናቸውንና የመጠጥ ቍር
ባናቸውን በተወሰነው ቍጥር መሠረት አብ
ራችሁ አቅርቡ፡፡ 22ደግሞም ከእህሉ ቍር
ባኑና ከመጠጡ ቍርባን ጋር በመደበ
ኛነት ከሚቀርበው የሚቃጠል መሥዋዕት
ሌላ አንድ ተባዕት ፍየል የኀጢአት መሥ
ዋዕት አድርጋችሁ በተጨማሪ አቅርቡ፡፡

23“ ‘በአራተኛው ቀን ሁሉም እንከን የሌ
ለባቸው ዐሥር ወይፈኖች፣ ሁለት አውራ
በጎችና ዓመት የሆናቸው ዐሥራ አራት ተባዕት
የበግ ጠቦቶች አቅርቡ፡፡ 24ከወይፈኖቹ፣ ከአ
ውራ በጎቹና ከጠቦቶቹ ጋር የእህል ቍር
ባናቸውንና የመጠጥ ቍርባናቸውን በተደነገ
ገው ቍጥር መሠረት አቅርቡ፡፡ 25ደግሞም
ከእህሉ ቍርባኑና ከመጠጡ ቍርባን ጋር
በመደበኛነት ከሚቀርበው የሚቃጠል
መሥ ዋዕት ሌላ አንድ ተባዕት ፍየል
የኀጢአት መሥዋዕት አድርጋችሁ በተጨ
ማሪ አቅርቡ፡፡

26“ ‘በአምስተኛው ቀን ሁሉም እንከን
የሌለባቸው ዘጠኝ ወይፈኖች፣ ሁለት አውራ
በጎችና ዓመት የሆናቸው ዐሥራ አራት ተባዕት
የበግ ጠቦቶች አቅርቡ፡፡ 27ከወይፈኖቹ፣
ከአውራ በጎቹና ከጠቦቶቹ ጋር የእህል
ቍርባናቸውንና የመጠጥ ቍርባናቸውን
በተወሰነው ቍጥር መሠረት አቅርቡ፡፡
28ደግሞም ከእህሉ ቍርባኑና ከመጠጡ
ቍርባን ጋር በመደበኛነት ከሚቀርበው የሚ
ቃጠል መሥዋዕት ሌላ አንድ ተባዕት ፍየል
የኀጢአት መሥዋዕት አድርጋችሁ በተጨ
ማሪ አቅርቡ፡፡

29“ ‘በስድስተኛው ቀን ሁሉም እንከን የሌ
ለባቸው ስምንት ወይፈኖች፣ ሁለት አውራ
በጎችና ዓመት የሆናቸው ዐሥራ አራት ተባዕት
የበግ ጠቦቶች አቅርቡ፡፡ 30ከወይፈኖቹ፣ ከአውራ
በጎቹና ከበግ ጠቦቶቹ ጋር የእህል ቍር
ባናቸውንና የመጠጥ ቍርባናቸውን በተወሰ
ነው ቍጥር መሠረት አቅርቡ፡፡ 31ደግሞም
ከእህሉ ቍርባንና ከመጠጡ ቍርባን ጋር
በመደበኛነት ከሚቀርበው የሚቃጠል መሥ
ዋዕት ሌላ አንድ ተባዕት ፍየል የኀጢአት
መሥዋዕት አድርጋችሁ በተጨማሪ
አቅርቡ፡፡

32“ ‘በሰባተኛው ቀን ሁሉም እንከን የሌ
ለባቸው ሰባት ወይፈኖች፣ ሁለት አውራ
በጎችና ዓመት የሆናቸው ዐሥራ አራት
ተባዕት የበግ ጠቦቶች አቅርቡ፡፡ 33ከወይ
ፈኖቹ፣ ከአውራ በጎቹና ከበግ ጠቦቶቹ
ጋር የእህል ቍርባናቸውንና የመጠጥ ቍር
ባናቸውን በተወሰነው ቍጥር መሠረት
አቅርቡ፡፡ 34ደግሞም ከእህሉ ቍርባንና
ከመጠጡ ቍርባን ጋር በመደበኛነት ከሚ
ቀርበው የሚቃጠል መሥዋዕት ሌላ አንድ
ተባዕት ፍየል የኀጢአት መሥዋዕት አድ
ርጋችሁ በተጨማሪ አቅርቡ፡፡

35“ ‘በስምንተኛው ቀን የተቀደሰ ጉባኤ
አድርጉ፤ የዘወትር ሥራም አትሥሩ፡፡ 36ሁሉም
እንከን የሌለባቸው አንድ ወይፈን፣ አንድ
አውራ በግና ዓመት የሆናቸው ሰባት ተባዕት
የበግ ጠቦቶች የሚቃጠል መሥዋዕት በማ
ድርግ ሽታው እግዚአብሔርን (ያህዌ) ደስ የሚ
ያሰኝ ቍርባን በእሳት አቅርቡ፡፡ 37ከወይ
ፈኑ፣ ከአውራ በጉና ከበግ ጠቦቶቹ ጋር
የእህል ቍርባናቸውንና የመጠጥ ቍርባና
ቸውን በተወሰነው ቍጥር መሠረት አቅርቡ፡፡
38ደግሞም ከእህሉ ቍርባንና ከመጠጡ ቍር
ባን ጋር በመደበኛነት ከሚቀርበው የሚ
ቃጠል መሥዋዕት ሌላ አንድ ተባዕት
ፍየል የኀጢአት መሥዋዕት አድርጋችሁ
በተጨማሪ አቅርቡ፡፡

39በስእለትና በበጎ ፈቃድ ከምታቀርቧቸው
ቍርባኖች በተጨማሪ የሚቃጠሉ መሥ
ዋዕቶቻችሁን፣ የእህል ቍርባኖቻችሁን፣ የመ
ጠጥ ቍርባኖቻችሁንና የኅብረት መሥዋዕ
ቶቻችሁን[፩] በተወሰኑት በዓሎቻችሁ ላይ
ለእግዚአብሔር (ለያህዌ) አቅርቡ’ ”

40ሙሴም እግዚአብሔር (ያህዌ) ያዘዘውን ሁሉ
ለእስራኤላውያን ነገራቸው፡፡

## ስእለት

30 ሙሴ ለእስራኤል የነገድ አለቆች
እንዲህ አላቸው፤ “እግዚአብሔር
(ያህዌ) ያዘዘው ይህ ነው፤ 2አንድ ሰው ለእ
ግዚአብሔር (ያህዌ) ስእለት በሚሳልበት
ወይም አንድ ነገር ለማድረግ በመሐላ ራሱን
ግዴታ ውስጥ በሚያስገባበት ጊዜ ቃሉን
ሳያጥፍ ያለውን ሁሉ መፈጸም አለበት፡፡

3“በአባቷ ቤት የምትኖር ሴት ልጅ
ለእ ግዚአብሔር (ለያህዌ) ስእለት ብትሳል
ወይም አንድ ነገር ለማድረግ በመሐላ ራሷን
ግዴታ ውስጥ ብታስገባ፣ 4አባቷም መሳሏን
ወይም

29፥18 ቍ9፤ዘኍ 15፥4-12፤28፥7
29፥19 ቍ6፤ዘኍ 28፥3፡15
29፥20 ቍ17
29፥21 ቍ18
29፥35 ዘሌ23፥36
29፥36 ቍ2፤ ዘሌ1፥9
29፥39 ዘሌ1፥3፤ 3፥1፤7፥16፤23፥2፤ ዘኍ 6፥2፤1ዜና 23፥31፤2ዜና31፥3
30፥1 ዘኍ1፥4
30፥2 ዘዳ23፥21-23፤መሳ11፥35፤ኢዮ 22፥27፤መዝ22፥25፤ 50፥14፤61፥5፡8፤76፥ 11፤116፥14፤ምሳ20፥2 5፤መክ5፥4፡5፤ኢሳ 19፥21፤ዮና1፥16፤ 2፥9
30፥4 ቍ7

[፩]39 በተለምዶ የደኅንነት መሥዋዕት ይባላል፡፡

ራሷን ግዴታ ውስጥ ማስገባቷን ሰምቶ ምንም
ነገር ሳይላት ቢቀር ስእለቶቿ በሙሉ፣ ራሷ
ንም ግዴታ ውስጥ ያስገባችባቸው ነገሮች
ሁሉ መፈጸም ይኖርባቸዋል:: 5አባቷ ይህ
ንኑ ሰምቶ ከከለከላት ግን የትኛውም ስእ
ለቷ ወይም ራሷን ግዴታ ውስጥ ያስገባች
በት መሐላ አይያዝባትም፤ የከለከላት አባቷ
ስለ ሆነ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ነጻ
ያደርጋታል::

6“እንዲሁም ከተሳለች ወይም አምልጦ
አት ተናግራ ራሷን ግዴታ ውስጥ ካስ
ገባች በኋላ ባል ብታገባ፣ 7ባሏም ሰምቶ
ምንም ነገር ሳይላት ቢቀር ስእለቶቿ ወይም
ራሷን ግዴታ ውስጥ ያስገባችባቸው ነገ
ሮች መፈጸም ይኖርባቸዋል:: 8ሆኖም ባሏ
ይህንኑ ሰምቶ ከከለከላት ግን ለመፈጸም
የተሳለችውንም ሆነ አምልጦአት ተናግራ
ራሷን ግዴታ ውስጥ ያስገባችበትን ነገር
ስለሚያስቀር *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ከዚህ ነጻ
ያደርጋታል::

9“ባሏ የሞተባት ወይም ከባሏ የተፋታች
ሴት የትኛውም ስእለቷ ወይም የገባችበት
ግዴታ ሁሉ የጸና ይሆናል::

10“ከባሏ ጋር የምትኖር ሴት ብትሳል
ወይም አንድ ነገር ለማድረግ በመሐላ ራሷን
ግዴታ ውስጥ ብታስገባና 11ባሏም ይህንኑ
ሰምቶ ምንም ነገር ባይላትና ባይከለክላት
ግን ስእለቶቿም ሆኑ ለማድረግ ራሷን ግዴታ
ውስጥ ያስገባችባቸው ነገሮች ሁሉ የጸኑ
ይሆናሉ:: 12ባሏ ሰምቶ እንዲቀሩ ካደረገ
ግን ስእለቶቿንም ሆነ ለማድረግ ቃል የገ
ባቻቸውን ነገሮች የመፈጸም ግዴታ የለባ
ትም፤ ባሏ እንዲቀሩ ስላደረጋቸው *እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ነጻ ያደርጋታል:: 13የትኛው
ንም ስእለቷን ወይም ራሷን ለመከላከል
በመሐላ የታሰረችበትን ሁሉ ባሏ ሊያ
ጸናው ወይም ሊያፈርሰው ይችላል:: 14ይሁን
እንጂ ባሏ ግን ስለ ጒዳዩ ከዕለት ወደ ዕለት
ምንም ነገር ሳይላት ቢቀር ስእለቶቿን
ወይም ራሷን ግዴታ ውስጥ ያስገባች
ባቸውን ነገሮች ሁሉ እያጸናላት ነው
ማለት ነው፤ ስለ ነገሮቹ ሰምቶ ምንም
ነገር ሳይላት በመቅረቱ አጽንቶላታል:: 15ስለ
ነገሮቹ ከሰማ በኋላ እንዲቀሩ ካደረገ ግን
ለፈጸመችው በደል በኀላፊነት የሚጠየ
ቀው ራሱ ነው::”

16እነዚህ እንግዲህ በባልና በሚስት፣
በአ ባትና አብራው በቤት ውስጥ በምትኖር
ልጁ መካከል ያለውን ግንኙነት
አስመልክቶ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ለሙሴ
የሰጠው ሥርዐቶች ናቸው::

30፡5 ቊ8፡12፡15
30፡6 ዘሌ5፡4
30፡8 ቊ5፤ዘፍ3፡6
30፡12 ኤፌ5፡22፤ ቈላ3፡18
30፡15 ቊ5
31፡2 ዘፍ25፡2፤ ዘኍ20፡26
31፡3 መሳ11፡36፤ 1ሳሙ24፡12፤2ሳሙ 4፡8፤22፡48፤መዝ 94፡1፤149፡7፤ኢሳ 34፡8፤ኤር11፡20፤ 46፡10፤ሕዝ25፡17
31፡5 ቊ6፡21
31፡6 ቊ5፤ዘፀ 6፡25፤ዘኍ10፡2፤ 14፡44
31፡7 ዘኍ25፡16፤ ዘዳ20፡13፤መሳ21፡11 ፤1ነገ11፡15፡16
31፡8 ዘፍ34፡29፤ ዘኍ22፡5፤24፡14፤ 25፡15፤ኢሱ13፡21፤ 22
31፡9 ቊ15፤ዘፍ 34፡29
31፡10 ዘፍ25፡16፤ ኢሱ6፡24፤8፡28፤11፡ 11፤መሳ18፡27፤1ዜና 6፡54፤መዝ69፡25፤ ሕዝ25፡4
31፡11 ቊ26፤ ዘዳ20፡14፤2ዜና28፡8
31፡12 ቊ32፡53፤ ዘፍ49፡27፤ዘፀ15፡9፤ ዘኍ22፡1፤27፡2
31፡14 ቊ48፤ዘፀ 18፡21፤ዘዳ1፡15፤ 2ሳሙ18፡1
31፡16 ዘኍ22፡5፤ 23፡28፤24፡14፤25፡1- 9፤14፡37፤2ጴጥ2፡15
31፡17 ዘዳ7፡2፤ 20፡16-18፤ መሳ21፡11

### *ምድያማውያንን መበቀል*

**31** *እግዚአብሔር* (ያህዌ) *ሙሴን፤* 2“*ለእስ
ራኤላውያን ምድያማውያንን ተበ*
ቀልላቸው፤ ከዚያም ወደ ወገኖችህ ትከ
ማቻለህ” አለው::

3ስለዚህ ሙሴ ሕዝቡን እንዲህ አላ
ቸው፤ “ምድያማውያንን ለመውጋት እንዲ
ሄዱና ስለ *እግዚአብሔርም* (ያህዌ) እንዲ
በቀሏቸው ከሰዎቻችሁ ጥቂቶቹን
ለጦርነት አዘጋጁ:: 4ከእያንዳንዱም የእስራ
ኤል ነገድ አንዳንድ ሺህ ሰው ለጦርነቱ
ላኩ::” 5ስለ ዚህ ከእስራኤል ጐሣዎች
ተወጣጥቶ ከእያ ንዳንዱ ነገድ አንድ ሺህ
በአጠቃላይ ዐሥራ ሁለት ሺህ ሰው ለጦርነት
ተዘጋጀ:: 6ሙሴም የቤተ መቅደሱን ንዋየ
ቅዱሳትና ምልክት መስጫ የሆኑትን
መለከቶች ከያዘው ከካ ህኑ ከአልዓዛር
ልጅ ከፊንሐስ ጋር ከየነ ገዱ አንዳንድ ሺ
ህ ሰው ለጦርነት ላከ::

7*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን ባዘዘው መሠ
ረት ከምድያም ጋር ተዋጉ፤ ወንዱንም በሙሉ
ፈጁት፤ 8ከተገደሉትም መካከል አምስቱ የም
ድያም ነገሥታት ኤዊ፣ ሮቆም፣ ሱር፣
ሑርና ሪባ ይገኙባቸዋል፤ የቢዖርን ልጅ በለዓ
ምንም በሰይፍ ገደሉት:: 9ከዚያም እስራ
ኤላውያን የምድያማውያን ሴቶችና ሕፃ
ናት ማረኩ፤ የቀንድ ከብቶቻቸውን፣ የበ
ግና የፍየል መንጋዎቻቸውን ሁሉ ነዱ፤ ሀብ
ታቸውንም በሙሉ ወሰዱ:: 10ምድያማውያኑ
የሚኖሩባቸውን ከተሞች ሁሉ ሰፈሮቻቸው
ንም በሙሉ አቃጠሉ:: 11ሰውና እንስሳትን
ጨምሮ የማረኩትንና የዘረፉትን ሁሉ እን
ዳለ አጋዙት:: 12የማረኳቸውን ሰዎች፣ የነ
ዱአቸውን እንስሳትና የዘረፉትን ሀብት
በሙሉ፣ ከኢያሪኮ[ጣ] ማዶ፣ በዮርዳኖስ አጠገብ፣
በሞዓብ ወዳለው፣ ሙሴና ካህኑ አልዓዛር እን
ዲሁም መላው የእስራኤላውያን ማኅበር
ወዳሉበት ሰፈራቸው አመጡአቸው::

13ሙሴ፣ ካህኑ አልዓዛርና የማኅበረ ሰቡ
መሪዎች በሙሉ ሊቀበሉአቸው ከሰፈር
ወጡ:: 14ሙሴም ከጦርነት በተመለሱት
በሰራዊቱ አዛዦች ማለትም በሻለቆችና
በመቶ አለቆች ላይ ተቈጣ::

15እርሱም እንዲህ አላቸው፤ “ሴቶችን ሁሉ
እንዴት በሕይወት ትተውአቸዋላችሁ?” 16የበ
ለዓምን ምክር ተቀብለው በፌጎር በተፈ
ጸመው ድርጊት እስራኤላውያን *ከእግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) እንዲመለሱና *የእግዚአብሔ
ርም* (ያህዌ) ሕዝብ እንዲቀሠፍ ያደረጉት
እነርሱ ናቸው:: 17አሁንም ወንዶቹን ልጆች
ሁሉ፣ ወንድ ያወቀትንም ሴቶች በሙሉ

[ጣ]12 በዕብራይስጥ *የኢያሪኮ ዮርዳኖስ* ማለት ሲሆን፣ ይህም
የዮርዳኖስ ወንዝ የጥንት ስም ሳይሆን አይቀርም::

ግደሉዋቸው፤ 18ነገር ግን ወንድ ያላወቁትን ልጃገረዶች ሁሉ ለራሳችሁ አስቀሩአቸው፡፡

19“ከእናንት መካከል ሰው የገደለ ወይም የተገደለውን የነካ ሁሉ ከሰፈር ውጭ ሰባት ቀን ይቈይ፡፡ በሦስተኛውና በሰባተኛው ቀን ራሳችሁንና ምርኮኞቻችሁን አንጹ፡፡ 20ማናቸውንም ልብስ እንዲሁም ከቈዳ፣ ከፍየል ጠጕር ወይም ከዕንጨት የተሠራ ማንኛውንም ነገር አንጹ፡፡”

21ከዚያም ካህኑ አልዓዛር ወደ ጦርነት ሄደው የነበሩትን ወታደሮች እንዲህ አላቸው፤ “*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ለሙሴ የሰጠው የሕጉ ሥርዐት ይህ ነው፤ 22ወርቅ፣ ብር፣ ናስ፣ ብረት፣ ቈርቈሮ፣ እርሳስ 23እንዲሁም እሳትን መቋቋም የሚችል ማንኛውም ነገር በእሳት ውስጥ ማለፍ አለበት፤ ከዚያም ንጹሕ ይሆናል፤ ይህም ሆኖ መንጻት አለበት፡፡ እሳትን መቋቋም የማይችል ማንኛውም ነገር በዚሁ ውሃ ውስጥ ማለፍ አለበት፡፡ 24በሰባተኛው ቀን ልብሳችሁን እጠቡ፤ ትነጻላችሁም፤ ከዚያም ወደ ሰፈር መግባት ትችላላችሁ፡፡”

## ምርኮን መከፋፈል

25*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤ 26“አንተ፣ ካህኑ አልዓዛርና በማኅበረ ሰቡ ውስጥ ያሉት የየቤተ ሰቡ አለቆች ሆናችሁ የተማረከውን ሕዝብና እንስሳት ሁሉ ቍጠሩ፡፡ 27ምርኮውንም ለሁለት ከፍላችሁ በጦርነቱ ለተካፈሉት ወታደሮችና ለቀረው ማኅበረ ሰብ አከፋፍሉት፡፡ 28በጦርነቱ ከተካፈሉት ወታደሮች ድርሻ ላይ፣ ከሰውም ሆነ ከቀንድ ከብት፣ ከአህያ፣ ከበግ ወይም ከፍየል ከየአምስት መቶው አንዱን *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) ግብር አውጣ፡፡ 29ይህንንም ግብር ከድርሻቸው ላይ ወስደህ *የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፈንታ በማድረግ ለካህኑ ለአልዓዛር ስጠው፡፡ 30ከእስራኤላውያን እኩሌታ ድርሻ ደግሞ ከሰውም ይሁን ከቀንድ ከብት፣ ከአህያ፣ ከበግ፣ ከፍየል ወይም ከሌሎች እንስሳት ከየአምሳው አንዳንድ መርጠህ፣ *የእግዚአብሔርን* (ያህዌ) ማደሪያ ድንኳን በኀላፊነት ለሚጠብቁ ሌዋውያን ስጣቸው፡፡” 31ሙሴና ካህኑ አልዓዛርም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዳዘዘው አደረጉ፡፡

32ወታደሮቹ ማርከው ከወሰዱለት ምርኮ ውስጥ የቀረው ይህ ነበር፤ ስድስት መቶ ሰባ አምስት ሺህ በግ፣ 33ሰባ ሁለት ሺህ የቀንድ ከብት፣ 34ሥልሳ አንድ ሺህ አህያ 35ወንድ ያላወቁ ሠላሳ ሁለት ሺህ ሴቶች፡፡

36በጦርነቱ ላይ የነበሩት ወታደሮች እኩሌታ ድርሻ ይህ ነበር፤ ሦስት መቶ ሠላሳ ሰባት ሺህ አምስት መቶ በግ፤ 37ከነዚህም *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) የተሰጠ ግብር ስድስት መቶ ሰባ አምስት ነበር፡፡

38ሠላሳ ስድስት ሺህ የቀንድ ከብት፣ ከነዚህም *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) የተሰጠው ግብር ሰባ ሁለት ነበር፡፡

39ሠላሳ ሺህ አምስት መቶ አህያ፣ ከነዚህም *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) የተሰጠው ግብር ሥልሳ አንድ ነበር፡፡

40ዐሥራ ስድስት ሺህ ሰው፤ ከነዚህም *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) የተሰጠው ግብር ሠላሳ ሁለት ነበር፡፡

41ሙሴም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) እንዳዘዘው *የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ድርሻ የሆነውን ግብር ለአልዓዛር ሰጠው፡፡

42ሙሴ ከዘመቱት ሰዎች የለየው የእስራኤላውያን እኩሌታ ድርሻ ማለትም፣ 43የማኅበረ ሰቡ ድርሻ ይህ ነበር፤ ሦስት መቶ ሠላሳ ሰባት ሺህ አምስት መቶ በግ፣ 44ሠላሳ ስድስት ሺህ የቀንድ ከብት፣ 45ሠላሳ ሺህ አምስት መቶ አህያ፣ 46ዐሥራ ስድስት ሺህ ሰው፡፡ 47ከእስራኤላውያን እኩሌታ ድርሻ ላይ፣ ሙሴ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) እንዳዘዘው ከየአምሳው ሰውና እንስሳ አንዳንድ መርጦ *የእግዚአብሔርን* (ያህዌ) ማደሪያ ድንኳን በኀላፊነት ለሚጠብቁ ሌዋውያን ሰጣቸው፡፡

48ከዚያም በኋላ በሰራዊቱ ክፍሎች ላይ የተሾሙት የሻለቆችና የመቶ አለቆች ወደ ሙሴ ቀርበው፣ 49እንዲህ አሉት፤ “እኛ አገልጋዮችህ በእጃችን ሥር ያሉትን ወታደሮች ቈጥረናል፤ አንድም የጐደለ የለም፡፡ 50ስለዚህ እያንዳንዳችን ያገኘነውን የወርቅ ጌጣ ጌጥ፣ የእግር ዐልቦዎች፣ የእጅ አንባሮች፣ የጣት ቀለበቶች፣ የጆሮ ጕትቻዎችና የዐንገት ሐብሎች *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ማስተስረያ እንዲሆነን መባ አድርገን *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) አምጥተናል፡፡”

51ሙሴና ካህኑ አልዓዛር በጌጣ ጌጥ መልክ የተሠራውን ወርቅ ሁሉ ተቀበሉአቸው፡፡ 52ሙሴና አልዓዛር ከሻለቆቹና ከመቶ አለቆቹ በመቀበል ስጦታ አድርገው *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ) ያቀረቡት ወርቅ ዐሥራ ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ሰቅል[ጪ] መዘነ፡፡ 53እያንዳንዱም ወታደር ለራሱ የወሰደው ምርኮ ነበረው፡፡ 54ሙሴና ካህኑ አልዓዛር ወርቁን ከሻለቆቹና ከመቶ አለቆቹ ተቀብለው *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ለእስራኤላውያን መታሰቢያ እንዲሆን ወደ መገናኛው ድንኳን አመጡት፡፡

ጪ52 አንድ መቶ ዘጠና ኪ.ግ. ያህል ነው፡፡

31፥19 ዘሌ21፥1፤ ዘኍ19፥12፡16
31፥20 ዘሌ11፥32፤ ዘኍ19፥19
31፥21 ቍ5
31፥22 ኢሱ6፥19፤ 22፥8
31፥23 ዘኍ8፥7፤ 1ቆሮ3፥13
31፥24 ዘሌ11፥25፤ 14፥8
31፥26 ቍ11፡12፤ ዘኍ1፥4፡19
31፥27 ኢሱ22፥8፤ 1ሳሙ25፥13፤ 30፥24
31፥28 ቍ37-41፤ ዘኍ18፥21
31፥30 ዘኍ3፥7፤ 18፥3
31፥32 ቍ12
31፥37 ቍ38-41
31፥41 ቍ21፡28፤ ዘኍ5፥9፤18፥8
31፥48 ቍ14
31፥49 ዘኍ1፥19፤ ኤር23፥4
31፥50 ዘፀ30፥16
31፥53 ዘዳ34፥29፤ ዘጸ20፥14
31፥54 ዘፀ27፥21፤ 28፥12፤40፥2
32፥1 ቍ24፡36፤ ዘፍ31፥21፤ዘፀ12፥38፤ ዘኍ21፥32፤መሳ5፥16

## ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉ ነገዶች

32 እጅግ ብዙ የሆነ የቀንድ ከብት፣
የበግና የፍየል መንጋዎች የነበሩ
አቸው የሮቤልና የጋድ ነገዶች የኢያዜርና
የገለዓድ ምድር ለከብት ምቹ ስፍራዎች
መሆናቸውን አዩ። 2ስለዚህ ወደ ሙሴ፣ ወደ
ካህኑ ወደ አልዓዛርና ወደ ማኅበረ ሰቡ መሪ
ዎች መጥተው እንዲህ አሉ፤ 3“አጣሮት፣
ዲቦን፣ ኢያዜር፣ ኒምራ፣ ሐሴቦን፣ ኤል
ያሊ፣ ሴባማ፣ ናባውና፣ ባያን፣ 4*እግዚአብሔር*
(ያህዌ) በእስራኤል ሕዝብ ፊት እንዲሸነፍ
ያደረገው ይህ ሁሉ ምድር ለከብት ምቹ
ነው፤ እኛ አገልጋዮችህም ከብቶች አሉን።”
5“በፊትህ ሞገስ ያገኘን ከሆነ ይህ ምድር
ለእኛ ለአገልጋዮችህ በርስትነት ይሰጠን፤
ዮርዳኖስንም እንድንሻገር አታድርገን” አሉ።

6ሙሴም የጋድንና የሮቤልን ነገዶች እን
ዲህ አላቸው፤ “እናንተ እዚህ ተቀምጣችሁ
ወገኖቻችሁ ወደ ጦርነት ይሂዱ? 7እስራ
ኤላውያን ተሻግረው *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ወደ ሰጣቸው ምድር እንዳይገቡ ተስፋ
የምታስቈርጧቸው ለምድን ነው? 8አባቶ
ቻችሁ ምድሪቱን እንዲሰልሉ ከቃዴስ በርኔ
በላክኋቸው ጊዜም ያደረጉት ይህንኑ ነበር።
9ወደ ኤሽኮል ሸለቆ ሄደው ምድሪቱን ካዩ
በኋላ፣ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ወደ ሰጣቸው
ምድር እንዳይገቡ እስራኤላውያንን ተስፋ
አስቈረጧቸው። 10በዚያም ቀን *የእግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) ቍጣ ነደደ፤ እንዲህም ሲል
ማለ፤ 11‘በፍጹም ልባቸው ስላልተከተሉኝ ከግ
ብፅ ከወጡት፣ ዕድሜያቸው ሃያ ዓመትና
ከዚያ በላይ የሆናቸው ሰዎች አንዳቸውም
ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ልሰጥ
በመሐላ ቃል የገባሁላቸውን ምድር አያዩ
ዋትም፤ 12*እግዚአብሔርን* (ያህዌ) በፍጹም
ልባቸው ተከትለውታልና፣ ከቄኔዛዊው ከዮ
ፎኒ ልጅ ከካሌብና ከነዌ ልጅ ከኢያሱ
በስተቀር አንዳቸውም አያዩዋትም።’ 13*የእግ
ዚአብሔርም* (ያህዌ) ቍጣ በእስራኤል ላይ
ስለ ነደደ፣ በፊቱ ክፉ ነገር ያደረገው ያ
ትውልድ በሙሉ እስኪያልቅ ድረስ አርባ
ዓመት በምድረ በዳ እንዲንከራተቱ አደረ
ጋቸው።

14“እናንት የኀጢአተኞች ልጆች ይኸው
በአባቶቻችሁ እግር ተተክታችሁ *እግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) በእስራኤል ላይ ይበልጥ እን
ዲቈጣ ታደርጋላችሁ። 15እርሱን ከመከ
ተል ብትመለሱ አሁንም ይህን ሁሉ ሕዝብ
በምድረ በዳ ይተወዋል፤ ለሚደርስበትም
ጥፋት ምክንያቱ እናንተው ትሆናላችሁ።”

16ከዚህ በኋላ ወደ እርሱ ቀርበው እንዲህ
አሉት፤ “እዚህ ለከብቶቻችን በረቶች፣
ለሴቶቻችንና ለልጆቻችን ከተሞች መሥ
ራት እንወዳለን፤ 17ይሁን እንጂ ወደ ስፍ
ራቸው እስክናገባቸው ድረስ ታጥቀንና
በእስራኤላውያን ፊት ግንባር ቀደም ሆነን
ለመሄድ ዝግጁ ነን፤ በዚህም ጊዜ ሴቶ
ቻችንና ልጆቻችን በምድሪቱ ላይ ካሉት
ነዋሪዎች እንዲጠበቁ በተመሸጉ ከተሞች
ይኖራሉ። 18እኛም እያንዳንዱ እስራኤላዊ
ርስ
ቱን እስኪወርስ ድረስ ወደየቤታችን አንመ
ለስም። 19ድርሻችንን ከዮርዳኖስ ወንዝ
በስተ ምሥራቅ ስላገኘን፣ ከዮርዳኖስ ማዶ
ከእነ ርሱ ጋር የምንካፈለው አንዳችም
ርስት አይኖርም።”

20ከዚያም ሙሴ እንዲህ አላቸው፤ “ይህን
ብታደርጉ ማለትም *በእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ፊት ታጥቃችሁ ለጦርነት ብትዘጋጁ፣ 21እን
ዲሁም ጠላቶቹን ከፊቱ አሳዶ እስኪያ
ስወጣ ድረስ ሁላችሁም በእግዚአብሔር
ፊት ለጦርነት ዝግጁ ሆናችሁ ዮርዳኖስን
ብትሻገሩ፣ 22ምድሪቱ *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ከተገዛች በኋላ ልትመለሱ ትችላላችሁ፤ *ለእ
ግዚአብሔርና* (ያህዌ) ለእስራኤል ካለባችሁም
ግዴታ ነጻ ትሆናላችሁ፤ ይህችም ምድር
*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ርስታችሁ ትሆ
ናለች።

23“ይህን ባታደርጉ ግን *እግዚአብሔርን*
(ያህዌ) ትበድላላችሁ፤ ኀጢአታችሁ እንደ
ሚያገኛችሁም ዕወቁ። 24ለሴቶቻችሁና ለል
ጆቻችሁ ከተሞች፣ ለበግና ለፍየል መንጎ
ቻችሁም ጕረኖች ሥሩላቸው፤ የገባችሁ
በትን የተስፋ ቃል ግን ፈጽሙ።”

25የጋድና የሮቤል ሰዎች ሙሴን እንዲህ
አሉት፤ “እኛ አገልጋዮችህ ጌታችን ያዘዘ
ንን እንፈጽማለን። 26ልጆቻችንና ሚስቶቻ
ችን፣ የበግና የፍየል እንዲሁም የከብት መን
ጎቻችን እዚሁ በገለዓድ ከተሞች ይቀራሉ፤
27ባሮችህ ግን ልክ ጌታችን እንዳለው እያ
ንዳንዱ ሰው ለጦርነት ዝግጁ ሆኖ *በእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ፊት ለመዋጋት እንሻገራለን።”

28ከዚያም ሙሴ ለካህኑ ለአልዓዛር፣ ለነዌ
ልጅ ለኢያሱና ለእስራኤል ነገድ ቤተ
ሰብ አለቆች እነርሱን አስመልክቶ ትእዛዝ
ሰጠ፤ 29እንዲህም አላቸው፤ “የጋድና የሮቤል
ወንድ ሁሉ፣ እያንዳንዱ ለጦርነት በመዘ
ጋጀት *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ከእናንተ
ጋር ዮርዳኖስን የሚሻገር ከሆነ፣ ምድሪቱም
በእጃችሁ ስትገባ የገለዓድን ምድር ርስት
አድርጋችሁ ስጧቸው። 30ለጦርነት ተዘጋ
ጅተው ከእናንተ ጋር ካልተሻገሩ ግን፣
ርስታቸውን አብረዋችሁ በከነዓን መካፈል
አለባቸው።”

31የጋድና የሮቤል ሰዎች እንዲህ ሲሉ

32፥2 ዘሌ4፥22፤ ዘኍ27፥2
32፥3 ቍ1፤34፤36፤ 37፤38፤ዘኍ21፥25፡ 30፤33፥47፤ዘዳ32፥49፤ 34፥1፤ኢሱ13፥17፡ 19፡27፤16፥2፡7፤18፥3፤ 1ዜና5፥8፤ኢሳ15፥4፤ 16፥8፡9፤ኤር48፥32፡ 34፤ሕዝ25፥9
32፥4 ዘኍ21፥34፤ ዘፀ12፥38
32፥5 ዘኍ13፥29
32፥7 ዘኍ13፥27-14፥4
32፥8 ዘኍ13፥3፡ 26፤ዘዳ1፥19-25
32፥9 ዘኍ13፥23፤ ዘዳ1፥24
32፥10 ዘኍ11፥1፤ 14፥20-23
32፥11 ዘፀ30፥14፤ ዘኍ1፥1፤14፥23፡ 28-30
32፥12 ዘኍ14፥24፡ 30፤መዝ63፥8
32፥13 ዘፀ4፥14፤ ዘኍ14፥28-35፤ 26፥64፡65
32፥14 ቍ10፤ዘዳ 1፥34፤መዝ78፥59
32፥15 ዘዳ30፥17-18፤2ዜና7፥20
32፥16 ቍ24፡36፤ ዘፀ12፥38፤ዘዳ3፥19፤ 1ሳሙ24፥3፤መዝ 50፥9፤78፥70
32፥17 ዘኍ22፥4፤ ዘዳ3፥18፤20፤ኢሱ 4፥12፡13
32፥18 ኢሱ22፥1-4
32፥19 ቍ22፡29፤ ዘኍ21፥33፤ኢሱ 12፥1፤22፥7
32፥20 ቍ17
32፥21 ቍ17
32፥22 ዘሌ14፥34፤ ዘዳ3፥18-20፤ኢሱ22፥4
32፥23 ዘፍ4፥7፤ኢሳ 3፥9
32፥24 ቍ1፡16፤ ዘኍ30፥2
32፥25 ቍ29፤ኢሱ 1፥16፡18፤22፥2
32፥26 ቍ16፡24፤ ኢሱ1፥14፤12፥2፤ 22፥9፤2ሳሙ2፥9፤ 1ዜና5፥9
32፥27 ቍ17፡21
32፥28 ቍ29፤ዘኍ 1፥16፤11፥28ዘዳ 3፥18-20፤ኢሱ1፥13
32፥29 ቍ19፤ዘኍ 22፥4
32፥30 ቍ23፡29፡32
32፥31 ቍ29

መለሱለት፤ “ባሪያዎችህ እግዚአብሔር (ያህዌ)
ያለውን ያደርጋሉ፤ [32]ለጦርነት ዝግጁ ሆነን
በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ወደ ከነዓን እን
ሻገራለን፤ የምንወርሰው ርስት ግን ከዮርዳ
ኖስ ወዲህ እዚሁ ይሆናል።”
[33]ከዚያም ሙሴ፣ የአሞራውያንን ንጉሥ
የሴዎንን ግዛትና የባሳንን ንጉሥ የዐግን ግዛት
ማለትም ምድሪቱንና ከነከተሞቿ በዙሪያዋ
ያለውን ግዛት በሙሉ ለጋድና ለሮቤል
ነገዶች እንዲሁም ለዮሴፍ ልጅ ለምናሴ
ነገድ እኩሌታ ሰጣቸው።
[34]የጋድ ልጆች፤ ዲቦንን፣ አጣሮትን፣ አሮዔ
ርን፣ [35]ዓጥሮትሾፋንን፣ ኢያዜርን፣ ዮግብ
ሃን፣ [36]ቤትነምራንና ቤትሃራንን የተመሸጉ
ከተሞች አድርገው ሠሩአቸው፤ እንዲሁም
ለበግና ለፍየል መንጎቻቸው ጒረኖዎች
አበጁላቸው። [37]የሮቤልም ልጆች ሐሴቦ
ንን፣ ኤልያሊንና ቂርያታይምን [38]እንዲ
ሁም ስማቸው የተለወጠውን ናባውን፣ በአ
ልሜዎንን፣ ሴባማንን ዐደሱ፤ ላደሷቸውም
ከተሞች ስም አወጡላቸው።
[39]የምናሴ ልጅ የሆነው የማኪር ዘሮች ወደ
ገለዓድ ሄደው ምድሪቱን በመያዝ፣ እዚያ
የነበሩትን አምራውያን አሳደዱአቸው፤ [40]ስለ
ዚህ ሙሴ ገለዓድን የምናሴ ዘሮች ለሆ
ኑት ለማኪራውያን ሰጣቸው፤ እነርሱም
መኖሪያቸውን በዚያው አደረጉ። [41]ከም
ናሴ ነገድ የሆነው ኢያዕር መኖሪያቸውን
ወስዶ፣ “የኢያዕር መንደሮች” ብሎ ሰየ
ማቸው። [42]እንዲሁም ኖባህ ቄናትንና በዙ
ሪያዋ ያሉትን መንደሮች በመያዝ በራሱ
ስም፣ “ኖባህ” ብሎ ጠራቸው።

## እስራኤላውያን ከግብፅ እስከ ሞዓብ ሲጓዙ የሰፈሩባቸው ቦታዎች

33 እስራኤላውያን በየነገዳቸው ተከፋፍ
ለው በሙሴና በአሮን መሪነት ከግ
ብፅ ወጥተው፣ በጒዞ ላይ ሳሉ የሰፈሩባቸው
ቦታዎች እነዚህ ናቸው፤ [2]ሙሴም በጒዞአ
ቸው ላይ ሳሉ የሰፈሩባቸውን ቦታዎች
በእግዚአብሔር (ያህዌ) ትእዛዝ መዘገበ፤ በየ
ቦታው እየሰፈሩ ያደረጉት ጒዞም ይህ ነው፤
[3]እስራኤላውያን በመጀመሪያው ወር
በዐሥራ አምስተኛውም ቀን በፋሲካ
ማግስት ከራምሴ ተነሡ፤ ግብፃውያን
ሁሉ እያዩአቸውም በልበ ሙሉነት
ተጓዙ። [4]በዚህ ጊዜ ግብፃውያን እግዚ
አብሔር (ያህዌ) ከመካከላቸው የገደ
ለባቸውን በኵሮቻቸውን ይቀብሩ ነበር፤
እግዚአብሔር (ያህዌ) በግብፅ አማልክት
ላይ ፈርዶ ነበር።
[5]እስራኤላውያን ከራምሴ ተነሥተው

32፥32 ቍ17፡30፤ ኢ.ሱ12፥6
32፥33 ቍ19፤ዘኍ21፥21፡24፤34፥14፤ ዘዳ2፥26፤36፤ኢ.ሱ1፥12፤12፥5፡6፤13፥24-28፤1ሳሙ13፥7
32፥34 ዘዳ2፥36፤3፥12፤4፥48፤ኢ.ሱ12፥2፤13፥9፤መሳ11፥26፤1ሳሙ30፥28፤1ዜና5፥8፤ኤር48፥19
32፥35 ቍ3፤ መሳ8፥11
32፥36 ቍ1፡3
32፥37 ቍ3፤ዘኍ21፥25፤ኢ.ሱ13፥19፤ 1ዜና6፥76፤ኤር48፥1፡23፤ሕዝ25፥9
32፥38 ቍ3፤ኢ.ሳ15፥2፤ኤር48፥1፡22
32፥39 ዘፍ10፥16፤50፥23፤ዘኍ26፥29፤ ዘዳ2፥36
32፥40 ዘፍ50፥23፤ ዘዳ3፥15
32፥41 ዘዳ3፥14፤ ኢ.ሱ13፥30፤መሳ10፥4፤1ዜና2፥23፤1ነገ4፥13
32፥42 መሳ8፥11፤ 1ዜና2፥23፤1ሳሙ15፥12፤2ሳሙ18፥18፤ መዝ49፥11፤ኢ.ሳ22፥16፤56፥5
33፥1 ዘፀ4፥16፤ 6፥26፤17፥1፤40፥36፤ዘኍ1፥1
33፥2 ቍ1፤ዘፀ17፥14
33፥3 ዘፍ47፥11፤ዘፀ14፥8፤ዘኍ10፥2፤ ኢ.ሱ5፥10
33፥4 ዘፀ4፥23፤12፥12፤2ዜና24፥24፤ኤር15፥3፤ሕዝ14፥21
33፥5 ዘፀ12፥37
33፥6 ዘፀ13፥20
33፥7 ዘፀ14፥2፡9
33፥8 ዘፀ14፥2፡22፤15፥23
33፥9 ዘፀ15፥27
33፥10 ዘፀ16፥1
33፥11 ዘፀ16፥1
33፥14 ዘፀ15፥22፤17፥2
33፥15 ዘፀ17፥1፤19፥1
33፥16 ዘኍ11፥34
33፥17 ዘኍ11፥35
33፥20 ኢ.ሱ10፥29፤12፥15፤15፥42፤21፥13፤2ነገ8፥22፤19፥8፤23፥31፤1ዜና6፥57፤2ዜና21፥10፤ኢ.ሳ37፥8፤ኤር52፥1
33፥30 ዘዳ10፥6
33፥31 ዘዳ10፥6

በሱኮት ሰፈሩ።
[6]ከሱኮትም ተነሥተው በምድረ በዳው
ዳርቻ በምትገኘው በኤታም ሰፈሩ።
[7]ከኤታም ተነሥተው ከበኣልዛፎን በስተ
ምሥራቅ ወዳለችው ወደ ፊሀሒሮት
በመመለስ በሚግዶል አጠገብ ሰፈሩ።
[8]ከፊሀሒሮት* ተነሥተው በባሕሩ ውስጥ
በማለፍ ወደ ምድረ በዳው ሄዱ፤ ከዚ
ያም በኤታም ምድረ በዳ ሦስት ቀን
ተጒዘው በማራ ሰፈሩ።
[9]ከማራ ተነሥተው ዐሥራ ሁለት የውሃ
ምንጮችና ሰባ የተምር ዛፎች ወደ ነበሩ
በት ወደ ኤሊም መጥተው በዚያ ሰፈሩ።
[10]ከኤሊም ተነሥተው በቀይ ባሕር*
አጠገብ ሰፈሩ።
[11]ከቀይ ባሕር ተነሥተው በሲን ምድረ
በዳ ሰፈሩ።
[12]ከሲን ምድረ በዳ ተነሥተው በራ
ፍቃ ሰፈሩ።
[13]ከራፍቃ ተነሥተው በኤሉስ ሰፈሩ
።
[14]ከኤሉስ ተነሥተው በራፊዲም ሰፈሩ፤
በዚያም ሕዝቡ የሚጠጣው ውሃ አልነ
በረም።
[15]ከራፊዲም ተነሥተው በሲና ምድረ
በዳ ሰፈሩ።
[16]ከሲና ምድረ በዳ ተነሥተው በቂብ
ሮት ሃታቫ ሰፈሩ።
[17]ከቂብሮት ሃታቫ ተነሥተው በሐ
ጼሮት ሰፈሩ።
[18]ከሐጼሮት ተነሥተው በሪትማ ሰፈሩ።
[19]ከሪትማ ተነሥተው በሬሞን ዘፋ
ሬስ ሰፈሩ።
[20]ከሬሞን ዘፋሬስ ተነሥተው በልብና
ሰፈሩ።
[21]ከልብና ተነሥተው በሪሳ ሰፈሩ።
[22]ከሪሳ ተነሥተው በቀሄላታ ሰፈሩ።
[23]ከቀሄላታ ተነሥተው በሻፍር ተራራ
ሰፈሩ።
[24]ከሻፍር ተራራ ተነሥተው በሐራዳ
ሰፈሩ።
[25]ከሐራዳ ተነሥተው በመቅሄሎት ሰፈሩ።
[26]ከማቅሄሎት ተነሥተው በታሐት
ሰፈሩ።
[27]ከታሐት ተነሥተው በታራ ሰፈሩ።
[28]ከታራ ተነሥተው በሚትቃ ሰፈሩ።
[29]ከሚትቃ ተነሥተው በሐሽሞና
ሰፈሩ።
[30]ከሐሽሞና ተነሥተው በሞሴሮት ሰፈሩ።
[31]ከሞሴሮት ተነስተው በብኔያዕ
ቃን ሰፈሩ

*8 ብዙ የማሶሬቲክ፣ የኦሪተ ሳምራውያንና የቩልጌት ቅጆች *ከፊሀሒሮት ተነሥተው* የሚሉ ሲሆን፤ አያሌ የማሶሬቲክ ቅጆች ግን *ከፊሃሒሮት ፊት ለፊት ተነሥተው* ይላሉ።
*10 በዕብራይስጥ *ያም ሱፍ* የሚል ሲሆን፣ የደንገል ባሕር ማለት ነው።

32ከብኔያዕቃን ተነሥተው በሖርሃጊ
ድጋድ ሰፈሩ።
33ከሖርሃጊድጋድም ተነሥተው በዮጥ
ባታ ሰፈሩ።
34ከዮጥባታ ተነሥተው በዔብሮና
ሰፈሩ።
35ከዔብሮና ተነሥተው በዔጽዮንጋ
ብር ሰፈሩ።
36ከዔጽዮንጋብር ተነሥተው በጺን
ምድረ በዳ ባለችው በቃዴስ ሰፈሩ።
37ከቃዴስ ተነሥተው በኤዶም ዳርቻ
ባለው በሖር ተራራ ሰፈሩ። 38*በእግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ትእዛዝ ካህኑ አሮን
ወደ ሖር ተራራ ወጣ፤ እዚያም እስራ
ኤላውያን ከግብፅ በወጡ በአርባኛው
ዓመት፣ በአምስተኛው ወር፣ ከወሩም
በመጀመሪያው ቀን ሞተ። 39አሮን በሖር
ተራራ ላይ ሲሞት፣ ዕድሜው መቶ
ሃያ ሦስት ዓመት ነበር።
40በከነዓን በምትገኘው በኔጌብ የሚ
ኖረው ከነዓናዊው የዓራድ ንጉሥ፣
የእስራኤላውያንን መምጣት ሰማ።
41እነርሱም ከሖር ተራራ ተነሥተው
በሴልሞና ሰፈሩ።
42ከሴልሞና ተነሥተው በፉኖን ሰፈሩ።
43ከፉኖን ተነሥተው በአቦት ሰፈሩ።
44ከአቦት ተነሥተው በሞዓብ ዳርቻ
በምትገኘው በኢየአባሪም ሰፈሩ።
45ከኢይም ተነሥተው በዲቦንጋድ
ሰፈሩ።
46ከዲቦንጋድ ተነሥተው በዓልሞን
ዲብላታይም ሰፈሩ።
47ከዓልሞንዲብላታይም ተነሥተው
በናባው አጠገብ በሚገኙት በዓብሪም
ተራራዎች ላይ ሰፈሩ።
48ከዓብሪም ተራራዎች ተነሥተው ከኢ
ያሪኮ ማዶ በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ
ባለው በሞዓብ ሜዳ ላይ ሰፈሩ።
49እዚያም በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ
በሞዓብ ሜዳ ከቤት የሺሞት እስከ አቤ
ልስጢም ባለው ስፍራ ሰፈሩ።

50ከኢያሪኮ ማዶ በዮርዳኖስ አጠገብ ባለው
በሞዓብ ሜዳ፣ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን
እንዲህ አለው፤ 51"እስራኤላውያንን ተናገ
ራቸው፤ እንዲህም በላቸው፤ 'ወደ ከነዓን
ለመግባት ዮርዳኖስን ስትሻገሩ፣ 52የምድ
ሪቱን ነዋሪዎች በሙሉ ከፊታችሁ አሳዳ
ችሁ አስወጧቸው፤ የተቀረጹ ምስሎቻቸውንና
ቀልጠው የተሠሩ ጣዖቶቻቸውን በሙሉ
አጥፉ፤ እንዲሁም በኰረብታ ላይ የተሠሩ
ትን መስገጃዎቻቸውን ሁሉ አፈራርሱ።
53ምድሪቱን ርስት አድርጌ ሰጥቻችኋለሁና
ውረሷት፤ ኑሩባትም። 54ምድሪቱንም በየጠ
ጐሣ ዎቻችሁ በዕጣ ተከፋፈሉ። ከፍ ያለ
ቍጥር ላለው ሰፋ ያለውን፣ ዝቅተኛ
ቍጥር ላለው ደግሞ አነስተኛውን ስጡ፤
ምንም ይሁን ምን በዕጣ የወጣላቸው፣ የየራ
ሳቸው ርስት ይሆናል። አከፋፈሉም
በየአባቶቻችሁ ነገ ዶች አንጻር ይሁን።
55" 'የምድሪቱን ነዋሪዎች አሳዳችሁ ሳታ
ስወጧቸው ብትቀሩ ግን፣ እንዲኖሩ የተዋቸ
ኋቸው ሰዎች ለዐይናችሁ ስንጥር፣ ለጐና
ችሁም እሾኽ ይሆኑባችኋል፤ በምትኖሩ
በትም ምድር ችግር ይፈጥሩባችኋል።
56እኔም በእነርሱ ላይ ለማድረግ ያሰብ
ሁትን በእናንተ ላይ አደርግባችኋለሁ።' "

33፥33 ዘጸ10፥7
33፥35 ዘጸ2፥8፤ 1ነገ9፥26፤22፥48
33፥36 ዘኍ13፥21
33፥37 ዘፍ36፥16፤ ዘኍ20፥16፡22
33፥38 ዘፀ16፥35፤ ዘኍ20፥25-28፤ 27፥13
33፥40 ዘፍ10፥18፤ 12፥9፤ዘኍ21፥1
33፥43 ዘኍ21፥10
33፥44 ዘኍ21፥11
33፥47 ዘኍ27፥12፤ 32፥3
33፥48 ዘፍ13፥10፤ ዘኍ22፥1፤26፥3፤ 27፥12፤ኢሱ12፥9
33፥49 ዘኍ21፥16፤ ኢሱ12፥3፤13፥20፤ ሕዝ25፥9
33፥50 ቍ48
33፥51 ዘኍ34፥2፤ ኢሱ3፥17
33፥52 ዘሌ 26፥1፤ መዝ 106፥34-36
33፥53 ዘጸ11፥31፤ 17፥14፤ኢሱ1፥11፤ 21፥43
33፥54 ዘሌ16፥8፤ ዘኍ26፥54፤35፥8፤ 36፥2፤ኢሱ18፥10
33፥55 ኢሱ23፥13፤ መሳ2፥3፤መዝ106፥36 ፤ኢሳ55፥13፤ሕዝ 2፥6፤28፥24፤ሚክ 7፥4፤2ቆሮ12፥7
33፥56 ዘኍ14፥28
34፥1 ዘፍ17፥8፤2፤ ዘኍ33፥51፤ዘጸ1፥7-8፤ኢሱ23፥4፤መዝ 78፥54-55፤105፥ 11፤ ሕዝ47፥15
34፥3 ዘፍ14፥3፤ ዘኍ13፥21፤ኢሱ 15፥1-3
34፥4 ዘኍ32፥8፤ኢ ሱ15፥3፡4መሳ1፥36
34፥5 ዘፍ15፥18
34፥6 ኢሱ1፥4፤9፥1 ፤15፥12፡47፤23፥4፤ ሕዝ47፥10፡15፡ 19-20፤48፥28
34፥7 ሕዝ47፥15-17፤ዘኍ 20፥22
34፥8 ዘኍ13፥21፤ ኢሱ13፥5
34፥10 ኢሱ 15፥5
34፥11 ዘጸ3፥17፤ ኢሱ11፥2፤13፥27፤ 15፥32፤21፥16፤2ነገ 23፥33፤25፥6፡21፤ 1ዜና4፥32፤ኤር39፥5፤ 52፥9፡27

## የከነዓን አዋሳኞች

34 *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ
አለው፤ 2"እስራኤላውያንን እዘዛ
ቸው፤ እንዲህም በላቸው፤ 'ርስት አድርጋ
ችሁ በዕጣ ወደምትካፈሏት ወደ ከነዓን ምድር
በምትገቡበት ጊዜ አዋሳኞቿ እነዚህ ይሆናሉ፤
3" 'የደቡብ ድንበራችሁ በኤዶም ወሰን ላይ
ካለው ከጺን ምድረ በዳ ጥቂቱን ይጨምራል፤
በምሥራቅም በኩል የደቡብ ድንበራችሁ
ከጨው ባሕር[ፀ] ጫፍ ይጀምርና 4በአቅረቢም
መተላለፊያ አቋርጦ እስከ ጺን ይሄድና በስተ
ደቡብ እስከ ቃዴስ በርኔ ይዘልቃል፤ ከዚያም
በሐጻር አዳር ዐልፎ እስከ ዓጽሞን ይደር
ስና 5ዞሮ ከግብፅ ወንዝ ደረቅ መደብ ጋር
በመገናኘት መጨረሻው ባሕሩ[ፈ] ይሆናል።
6" 'የምዕራቡ ድንበራችሁ ደግሞ የታላቁ
ባሕር ዳርቻ ይሆናል። በምዕራቡ በኩል
ያለው ወሰናችሁም ይኸው ነው።
7" 'የሰሜን ድንበራችሁን ከታላቁ ባሕር
እስከ ሖር ተራራ ምልክት አድርጉበት፤ 8ከሖር
ተራራ እስከ ሌቦሐማት[ፐ] እንደዚሁ አድርጉ፤
ከዚያም ወሰኑ እስከ ጽዳድ ይሄድና 9እስከ
ዚፍሮን በመቀጠል መጨረሻው ሐጻርዔ
ናን ይሆናል፤ በሰሜን በኩል ያለው ወሰ
ናችሁ ይኸው ነው።
10" 'ለምሥራቁ ድንበራችሁም እንደዚሁ
ከሐጻርዔናን እስከ ሴፋማ ምልክት አድር
ጉበት። 11ወሰኑም ከሴፋማ አንሥቶ ከዓ
ይን በስተ ምሥራቅ እስካለው እስከ ሪብላ
ቍልቍል ይወርድና ከኪኔሬት ባሕር[ሀ]
በስተ ምሥራቅ እስካሉት ሸንተረሮች ድረስ
ይዘልቃል። 12ከዚያም ወሰኑ የዮርዳኖስን
ወንዝ ተከትሎ መጨረሻው የጨው ባሕር
ይሆናል።

[ፀ]3 ሙት ባሕር ነው።
[ፈ]5 የሜድትራኒያን ባሕር ነው።
[ፐ]8 ወይም *እስከ ሊቦሐማት መግቢያ ድረስ*
[ሀ]11 የገሊላ ባሕር ማለት ነው።

“ ‘እንግዲህ በዙሪያዋ ካሉት ወሰኖቿ
ጋር ምድራችሁ ይህች ናት፡፡’ ”
13ሙሴ እስራኤላውያንን እንዲህ ብሎ አዘ
ዛቸው፤ “ይህችን ምድር ርስት አድር
ጋችሁ በዕጣ ደልድሉ፤ *እግዚአብሔርም*
(ያህዌ) ለዘጠኙና ለግማሹ ነገድ እንድትሰጥ
አዞአል፤ 14የሮቤል ነገድ ቤተ ሰቦች፣ የጋድ
ነገድ ቤተ ሰቦች እንዲሁም የምናሴ ነገድ
እኩሌታ ርስታቸውን ተቀብለዋልና፡፡ 15እነ
ዚህ ሁለቱ ነገዶችና እኩሌታው ነገድ ከዮ
ርዳኖስ በስተ ምሥራቅ፣ ከኢያሪኮ ማዶ
በፀሓይ መውጫ በኩል ርስታቸውን ተቀ
ብለዋል፡፡”
16*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤
17“ምድሪቱን ርስት አድርገው የሚያከፋፍ
ሏችሁ ካህኑ አልዓዛርና የነዌ ልጅ ኢያሱ
ናቸው፤ 18ምድሪቱን በማከፋፈሉ እንዲረ
ዱም ከየነገዱ አንዳንድ መሪ ውሰዱ፡፡ 19ስማ
ቸውም ይህ ነው፤

ከይሁዳ ነገድ፣
የዮፎኒ ልጅ ካሌብ፤
20ከስምዖን ነገድ፣
የዓሚሁድ ልጅ ሰላሚኤል፤
21ከብንያም ነገድ፣
የኪስሎን ልጅ ኤልዳድ፤
22የዳን ነገድ መሪ፣
የዩግሊ ልጅ ቡቂ፤
23የዮሴፍ ልጅ የምናሴ ነገድ መሪ፣
የሱፊድ ልጅ አኒኤል፤
24የዮሴፍ ልጅ የኤፍሬም ነገድ መሪ፣
የሺፍጣን ልጅ ቀሙኤል፤
25የዛብሎን ነገድ መሪ፣
የፈርናክ ልጅ ኤሊሳፈን፤
26የይሳኮር ነገድ መሪ፣
የሖዛ ልጅ ፈልጢኤል፤
27የአሴር ነገድ መሪ፣
የሴሌሚ ልጅ አሒሁድ፤
28የንፍታሌም ነገድ መሪ፣
የዓሚሁድ ልጅ ፈዳሄል፡፡”

29እነዚህ በከነዓን ምድር ለእስራኤላው
ያን ርስት እንዲያከፋፍሉ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ያዘዛቸው ሰዎች ናቸው፡፡

## ለሌዋውያን የተሰጡ ከተሞች

35 ከኢያሪኮ[ሰ] ማዶ በዮርዳኖስ ወንዝ
አጠገብ፣ በሞዓብ ሜዳ *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ሙሴን እንዲህ አለው፤ 2“ከሚወ
ርሱት ርስት ላይ ለሌዋውያን የሚኖሩባቸ
ውን ከተሞች እንዲሰጧቸው እስራኤላው
ያንን እዘዛቸው፤ በየከተሞቹ ዙሪያም የግ
ጦሽ መሬት ስጧቸው፡፡ 3ከተሞቹ ለእነርሱ
መኖርያ፣ የግጦሽ መሬቱ ለከብቶቻቸው፣

34፥13 ዘሌ16፥8፤ ኢሱ13፥6፤18፥10፤ 14፥1-5፤ኢሳ49፥8፤ 65፥9፤ሕዝ45፥1፤ ሚክ2፥5
34፥14 ዘኍ32፥19፤ ዘዳ33፥21፤ኢሱ14፥3
34፥17 ዘኍ11፥28፤ ዘዳ 1፥38
34፥18 ዘኍ1፥4፤ ኢሱ14፥1
34፥19 ቊ29፤ዘፍ 29፥35፤ዘኍ26፥65፤ ዘዳ33፥7፤መዝ60፥7
34፥20 ዘፍ29፥33
34፥21 ዘፍ49፥27፤ መሳ5፥14፤መዝ 68፥27
34፥23 ዘኍ1፥34
34፥24 ዘኍ1፥32
34፥25 ዘፍ30፥20
34፥27 ዘኍ1፥40
34፥29 ቊ19
35፥1 ዘኍ22፥1
35፥2 ዘሌ25፥32-34፤ኢሱ14፥3፡4፤ 21፥1-42
35፥3 ዘዳ18፥6፤ ኢሱ14፥4፤21፥2
35፥5፤ ዘሌ25፥34፤ ኢሱ3፥42ዜና11፥14፤ 13፥9፤23፥2፤31፥19
35፥6 ቊ11፤ኢሱ 21፥13
35፥8 ዘኍ26፥54፤ 33፥54
35፥10 ዘኍ33፥51፤ ዘዳ 9፥1፤ኢሱ1፥2፡11
35፥11 ቊ22-25፤ ዘፀ21፥13
35፥12 ቊ19፤24፡25፤26፡27፡28፤ዘዳ 19፥6፤ኢሱ 20፥3፤ 2ሳሙ14፥11
35፥13 ቊ6፡14
35፥16 ዘፀ21፥12
35፥19 ቊ12፡21

ለበግና ለፍየል መንጎቻቸውና ለሌሎቹም እን
ስሶቻቸው ይሆናሉ፡፡
4“በየከተሞቹ ዙሪያ ለሌዋውያኑ የምትሰ
ጧቸውም የግጦሽ መሬት ከከተማው ቅጥር
አንድ ሺህ ክንድ[ሐ] ይዘረጋል፡፡ 5ከዚያም
ከተማውን መካከል በማድረግ ወደ ምሥ
ራቅ ሁለት ሺህ ክንድ፣[መ] ወደ ደቡብ ሁለት
ሺህ ክንድ፣ ወደ ምዕራብ ሁለት ሺህ
ክንድ፣ ወደ ሰሜን ሁለት ሺህ ክንድ
ከከተማው ውጭ ለካ፤ እነዚህንም ቦታዎች
ለከተሞቹ የግጦሽ መሬት ያደርጓቸዋል፡፡

## የመማጸኛ ከተሞች

35፥6-34 ማመ - ዘዳ 4፥41-43፤ 19፥1-14፤ ኢሱ 20፥1-9

6“ለሌዋውያኑ ከምትሰጧቸው ከተሞች ስድ
ስቱ፣ ሰው የገደለ ሸሽቶ የሚጠጋባቸው መማ
ጸኛ ከተሞች ይሆናሉ፤ በተጨማሪም አርባ
ሁለት ከተሞች ስጧቸው፤ 7የግጦሽ መሬ
ቶቻቸውን ጨምሮ በጠቅላላው አርባ ስም
ንት ከተሞች ለሌዋውያኑ ስጧቸው፡፡ 8እስ
ራኤላውያን ከወረሷት ምድር ላይ ለሌዋ
ውያኑ የምትሰጧቸው ከተሞች እያንዳንዱ
ነገድ እንዳለው ድርሻ መጠን ይሆናል፡፡ ብዙ
ካለው ነገድ ላይ ብዙ ከተሞች እንዲሁም
ጥቂት ካለው ነገድ ላይ ጥቂት ከተሞችን
ውሰዱ፡፡”
9ከዚያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን እን
ዲህ አለው፤ 10“እስራኤላውያንን እንዲህ
ብለህ ንገራቸው፤ ‘ወደ ከነዓን ለመግባት
ዮርዳኖስን በምትሻገሩበት ጊዜ፣ 11ሳያስ
በው ሰው የገደለ ሰው ሸሽቶ የሚጠጋባ
ቸው ከተሞች እንዲሆኑ መማጸኛ
ከተሞችን ምረጡ፡፡ 12እነዚህም፣ ነፍሰ ገዳዩ
በማኅበሩ ዘንድ ለፍርድ ከመቅረቡ በፊት
እንዳይሞት ከደም ተበቃዩ የሚሸሽባቸው
የመማጸኛ ከተሞች ይሆናሉ፡፡ 13እነዚህ
ለሌዋውያኑ የምትሰጧቸው ስድስት
ከተሞች መማጸኛ ከተሞቻችሁ ይሆናሉ፡፡
14ስለዚህ ከዮርዳኖስ ወዲህ ሦስቱን እንዲ
ሁም በከነዓን ሦስቱን የመማጸኛ ከተሞች
አድርጋችሁ ስጡ፡፡ 15እነዚህም ስድስት
ከተሞች ሳያስበው ሰው የገደለ ማንኛውም
ሰው እንዲሸሽባ ቸው ለእስራኤላውያን፣
ለመጻተኞችና በመ ካከላቸው ለሚኖር ለ
ማንኛውም ሕዝብ የመማጸኛ ቦታዎች
ይሆናሉ፡፡
16“ ‘አንድ ሰው ሌላውን እንዲሞት በብ
ረት ቢመታው ነፍሰ ገዳይ ነው፤ በሞትም
ይቀጣል፡፡ 17ወይም አንድ ሰው መግደል
የሚችል ድንጋይ በእጁ ቢይዝና ሌላውን
ሰው እንዲሞት ቢመታው ነፍሰ ገዳይ ነው፤

[ሰ]1 በዕብራይስጥ *የኢያሪኮ ዮርዳኖስ* ማለት ሲሆን፣ ይህም የዮርዳኖስ ውንዝ የጥንት ስም ሳይሆን አይቀርም፡፡
[ሐ]4 አራት መቶ አምሳ ሜትር ያህል ነው፡፡

ሙ5 ዘጠኝ መቶ ሜትር ያህል ነው፡፡

በሞትም ይቀጣል፡፡ 18ወይም አንድ ሰው
መግደል የሚችል ዕንጨት በእጁ ቢይዝና
ሌላውን ሰው እንዲሞት ቢመታው ነፍሰ
ገዳይ ነው፤ በሞትም ይቀጣል፡፡ 19ደም
መላሹም ነፍሰ ገዳዩን ይግደለው፤ ባገኘ
ውም ጊዜ ይግደለው፡፡ 20አንድ ሰው አስ
ቦበት ሌላውን በክፋት ገፍትሮ ቢጥለው
ወይም እንዲሞት ሆን ብሎ አንዳች ነገር
ቢወረውርበት 21ወይም ደግሞ በጥላቻ ተነሣ
ሥቶ በእጁ ቢመታውና ቢሞት፣ ያ ሰው
በሞት ይቀጣል፤ ነፍስ ገዳይ ነው፤ ደም መላ
ሹም ገዳዩን ባገኘው ጊዜ ይግደለው፡፡

22“ ‘ነገር ግን በጥላቻ ሳይሆን እንዲያው
በድንገት አንዱ ሌላውን ገፍትሮ ቢጥለው
ወይም ሳያስበው አንዳች ነገር ቢወረውር
በት 23ወይም መግደል የሚችል ድንጋይ
ሳያይ ጥሎበት ቢሞት፣ ጠላቱ ስላልሆነና
ሊጐዳውም አስቦ ያላደረገው ስለ ሆነ፣ 24
ማኅ በሩ በዚህ ሰውና በደመኛው መካከል
በእነዚህ ደንቦች መሠረት ይፍረድ፡፡ 25
ማኅበሩም በነ ፍሰ ገዳይነት የተከሰሰውን
ሰው ከደመኛው እጅ በማስጣል ወደ
ሸሸበት ወደ መማጸ
ኛው ከተማ ይመልሰው፤ የተቀደሰ ዘይት
የተቀባው ሊቀ ካህን እስኪሞትም ድረስ
በዚያ ይቈይ፡፡

26“ ‘ሆኖም ተከሳሹ ሰው ሸሽቶ ከተጠጋ
በት መማጸኛ ከተማ ክልል ከወጣ፣ 27ደም
ተበቃዩም ከከተማው ውጭ ካገኘው፣ ተከ
ሳሹን ሊገድለው ይችላል፤ በነፍሰ ገዳይነ
ትም አይጠየቅም፡፡ 28ተከሳሹም ሊቀ ካህ
ናቱ እስኪሞት ድረስ በመማጸኛው ከተማ
ይቈይ፤ ወደ ገዛ ርስቱ መመለስ የሚች
ለው ከሊቀ ካህናቱ ሞት በኋላ ብቻ ነው፡፡

29“ ‘እንግዲህ በየትኛውም በምትኖሩ
በት ስፍራ፣ በሚመጡት ትውልዶች ሁሉ
የም ትፈጽሚቸው ሕጋዊ ግዴታዎቻችሁ
እነዚህ ናቸው፡፡

30“ ‘ሰው የገደለ ማንኛውም ሰው በሞት
የሚቀጣው ምስክሮች ሲመሰክሩበት ብቻ
ነው፤ ይሁን እንጂ ማንም ሰው በአንድ ምስ
ክር ብቻ በሞት አይቀጣም፡፡

31“ ‘በሞት መቀጣት ስላለበት ሰው የነ
ፍስ ዋጋ አትቀበሉ፤ ፈጽሞ መሞት አለበት፡፡

32“ ‘ወደ መማጸኛ ከተማ ሸሽቶ ስለ ገባ
ስለ ማንኛውም ሰው የደም ዋጋ በመቀበል
ሊቀ ካህናቱ ከመሞቱ በፊት ወደ አገሩ
ተመልሶ ሄዶ እዚያ እንዲኖር አታድርጉ፡፡

33“ ‘ደም ምድሪቱን ስለሚያረክሳት፣ ደም
ለፈሰሰባትም ምድር ስርየት ሊደረግላት የሚ
ችለው በሌላ ሳይሆን በዚያው ደሙን ባፈ
ሰሰው ሰው ደም ብቻ በመሆኑ፣ የምትኖሩ
ባትን ምድር በደም አታርክሷት፤ 34የምትኖሩ
ባትን፣ እኔም የማድርባትን ምድር አታር
ክሷት እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) በእስራኤ
ላውያን መካከል እኖራለሁና፡፡’ ”

35፥20 ዘፀ21፥14
35፥21 ቀኍ19፤ ዘፀ21፥14
35፥22 ዘፀ21፥13
35፥24 ቀኍ12
35፥25 ቀኍ32፤ ዘፀ28፥41፤29፥7
35፥29 ዘኍ10፥8፤ 27፥11፤ዘፀ12፥20
35፥30 ዘዳ17፥6፤ 19፥15፤ማቴ18፥16፤ ዮሐ7፥51
35፥31 ዘፀ21፥30፤ ኢዮ6፥22፤መዝ 49፥8፤ምሳ13፥8
35፥33 ዘፍ4፥10
35፥34 ዘሌ18፥24፡ 25፤ዘፀ29፥45

## የሰለጰዓድ ሴት ልጆች ርስት

36፥1-12 ተጓ ምብ - ዘኍ 27፥1-11

36 ከዮሴፍ ዝርያ ጐሣዎች የሆኑ የም
ናሴ ልጅ፣ የማኪር ልጅ፣ የገለዓድ
ጐሣ የቤተ ሰብ አለቆች ወደ ሙሴና
የእስራኤላውያን ቤተ ሰቦች አለቆች ወደ
ሆኑት መሪዎች ቀርበው ተናገሩ፤ 2እንዲ
ህም አሉ፤ “ምድሪቱን በዕጣ ከፋፍለህ ለእ
ስራኤላውያን ርስት አድርገህ እንድት
ሰጣቸው እግዚአብሔር (ያህዌ) አንተን
ጌታዬን ባዘዘ ጊዜ የወንድማችንን የሰለጰዓድን
ድርሻ ለሴቶች ልጆቹ እንድትሰጥ
አዞሃል፡፡ 3ከሌ ሎች የእስራኤል ነገዶች ባል
ቢያገቡ ድርሻ ቸው ከእኛ የዘር ርስት ላይ
ተወስዶ የሚ ያገቧቸው ሰዎች ላሉበት ነገድ
ይተላለፋል፤ ይህ ከሆነ ደግሞ በዕጣ
ከተደለደለልን ርስት ላይ ከፊሉ ሊቀነስብን
ነው፡፡ 4የእስራኤላውያን ዓመተ ኢዮቤልዩ
በሚመጣበት ጊዜ የእነርሱ ድርሻ ወደ
ባሎቻቸው ነገድ ይጨመራል፤ ይህ ከሆነም
ድርሻቸው ከአባ ቶቻችን ነገድ ርስት ላይ
ይወሰዳል፡፡”

5ከዚህ በኋላ ሙሴ እግዚአብሔር (ያህዌ)
በተናገረው መሠረት እስራኤላውያንን እን
ዲህ ሲል አዘዛቸው፤ “የዮሴፍ ነገድ የተና
ገረው ትክክል ነው፤ 6እንግዲህ የሰለጰዓ
ድን ሴት ልጆች በተመለከተ እግዚአብሔር
(ያህዌ) የሚያዘው ይህ ነው፤ ከአባታቸው ነገድ
ወገን እስከ ሆነ ድረስ የወደዱትን ማግ
ባት ይችላሉ፡፡ 7እያንዳንዱ እስራኤላዊም
ከቀደሙት አባቶቹ በወረሰው ርስት ይጽና፤
በእስራኤል ከአንዱ ነገድ ወደ ሌላው
ነገድ የሚተላለፍ ርስት አይኖርም፡፡ 8እያ
ንዳንዱ እስራኤላዊ የየአባቶቹን ርስት
መውረስ ስላለበት፣ በማንኛውም የእስራ
ኤል ነገድ ውስጥ ርስት የምትወርስ የትኛ
ዪቱም ሴት፣ ከአባቷ ነገድ ወገን የሆነውን
አንዱን ማግባት አለባት፡፡ 9እያንዳንዱ የእ
ስራኤል ነገድ የወረሰውን መሬት እንዳለ
ማቈየት ስላለበት፣ ርስት ከአንዱ ነገድ
ወደ ሌላው ነገድ አይተላለፍም፡፡”

10ስለዚህም የሰለጰዓድ ሴት ልጆች እግዚአ
ብሔር (ያህዌ) ሙሴን እንዳዘዘው አደረጉ፡፡ 11የሰ
ለጰዓድ ሴት ልጆች፤ ማህለህ፣ ቲርጻ፣ ዔግላ፣
ሚልካ፣ ኑዓ ከአባታቸው ወንድሞች ልጆች
ጋር ተጋቡ፡፡ 12ከዮሴፍ ልጅ ከምናሴ ዝርያ
ጐሣዎች ጋር በመጋባታቸው፣ ርስታቸው
በዚያው በአባታቸው ጐሣና ነገድ እጅ
እንዳለ ቀረ፡፡

36፥1 ዘፍ50፥23፤ ዘኍ26፥28፡30፤27፥2
36፥2 ዘኍ26፥33፤ 33፥54
36፥4 ዘሌ25፥10
36፥7 ዘሌ25፥23
36፥8 1ዜና23፥22
36፥11 ዘኍ26፥33
36፥12 1ዜና7፥15

| | | |
|---|---|---|
| 13ከኢያሪኮ[ሠ] ማዶ፣ በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ፣ በሞዓብ ሜዳ ሳሉ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) በሙሴ አማካይነት ለእስራኤላውያን | 36፥13 ዘሌ7፥38፤ 27፥34፤ዘኍ22፥1 | የሰጣቸው ትእዛዞችና ደንቦች እነዚህ ናቸው። <br><br> [ሠ]13 በዕብራይስጥ ***የኢያሪኮ ዮርዳኖስ*** የሚል ሲሆን፣ ይህም የዮርዳኖስ ወንዝ የጥንት ስም ሳይሆን አይቀርም። |

# ኦሪት ዘዳግም

## እስራኤል ከኮሬብ እንዲነሡ የተሰጠ ትእዛዝ

1 ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ዓረባ በተ
ባለው ምድረ በዳ ከሱጳ ትይዩ፣ በፋ
ራንና በጦፌል፣ በላባን፣ በሐጼሮትና በዲ
ዛሃብ መካከል ሳሉ፣ ሙሴ ለእስራኤል ሁሉ
የተናገረው ቃል ይህ ነው። 2(በሴይር ተራራ
መንገድ ከኮሬብ እስከ ቃዴስ በርኔ ዐሥራ
አንድ ቀን ያስሄዳል)።
3በአርባኛው ዓመት፣ በዐሥራ አንደኛው ወር
ከወሩም በመጀመሪያው ቀን እስራኤላውያንን
በሚመለከት እግዚአብሔር (ያህዌ) ያዘዘውን ሁሉ
ሙሴ ለእነርሱ ነገራቸው። 4ይህ የሆነው
በሐሴቦን ይገዛ የነበረውን የአሞራውያንን
ንጉሥ ሴዎንና በአስታሮት ይገዛ የነበረውን
የዐግን ንጉሥ ባሳንን በኤድራይ ድል ካደረገ
በኋላ ነው።
5ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ በሞዓብ ምድር
ሳሉ፣ ሙሴ ይህን ሕግ እንዲህ እያለ መግ
ለጥ ጀመረ፤
6"እግዚአብሔር አምላካችን (ያህዌ ኤሎሂም)
በኮሬብ እንዲህ አለን፤ 'እነሆ በዚህ ተራራ
ለረጅም ጊዜ ቈይታችኋል። 7ሰፈር ነቅላችሁ ወደ
ኰረብታማው የአሞራውያን አገር ጕዞ
ቀጥሉ፤ ከዚያም በዓረባ፣ በተራሮቹ፣
በምዕራብ ኰረ ብታዎች ግርጌ፣ በኔጌብና
በባሕሩ ዳርቻ ወዳሉት አጐራባች ሕዝቦች
ሁሉ ሂዱ፤ እን ዲሁም ወደ ከነዓናውያን
ምድርና ወደ ሊባ ኖስ፣ እስከ ታላቁ ወንዝ
እስከ ኤፍራጥስ ድረስ ዝለቁ። 8እነሆ፤
ይህችን ምድር ሰጥቻ ችኋለሁ፤ እንግዲህ እግዚ
አብሔር (ያህዌ) ለአባ ቶቻችሁ ለአብርሃም፣
ለይስሐቅና ለያዕቆብ ከእነርሱም በኋላ
ለዘሮቻቸው ሊሰጥ የማለላ ቸውን ምድር
ገብታችሁ ውረሱ።"

## የመሪዎች መሾም

9"እኔም በዚያን ጊዜ እንዲህ አልኋችሁ፤
ብቻዬን ልሸከማችሁ አልችልም፤ 10አምላ
ካችሁ እግዚአብሔር (ያህዌ አሎሂም) ቍጥራችሁን ጨም
ሮአል፤ ስለዚህ ዛሬ እናንተ እንደ ሰማይ
ከዋክብት በዝታችኋል። 11አሁንም የአባቶ
ቻችሁ አምላክ እግዚአብሔር (ያህዌ አሎሂም) ሺህ ጊዜ ያብ
ዛችሁ፤ በሰጠውም ተስፋ መሠረት ይባርካ
ችሁ! 12ይሁን እንጂ ችግራችሁን፣ ሸክማች
ሁንና ክርክራችሁን ሁሉ ብቻዬን እንዴት
አድርጌ መሸከም እችላለሁ? 13ጥበበኞችን፣
አስተዋዮችንና የተከበሩ ሰዎችን ከየነገዳ
ችሁ ምረጡ፤ እኔም በእናንተ ላይ እሾማቸ
ዋለሁ።"
14እናንተም፣ "ይደረግ ዘንድ ያቀረብኸው
ሐሳብ መልካም ነው" ብላችሁ መለሳችሁልኝ።
15ስለዚህ እኔም የየነገዶቻችሁን አለቆች
ጥበበኞችንና የተከበሩትን ሰዎች ተቀብዬ፣
ሻለቆች፣ መቶ አለቆች፣ አምሳ አለቆችና ዐሥር
አለቆች እንዲሁም የየነገዱ ሹማምንት በማ
ድረግ በእናንተ ላይ ሥልጣን እንዲኖራቸው
ሾምኋቸው። 16በዚያን ጊዜም ዳኞቻችሁን
እንዲህ ስል አዘዝኋቸው፤ "በወንድሞቻችሁ
መካከል የሚነሣውን ክርክር ያለ አድልዎ
እዩት፤ ሙግቱ ወንድማማች በሆኑ እስራ
ኤላውያን መካከል ወይም በአንድ እስራ
ኤላዊና በመጻተኛ መካከል ቢሆን፣ በትክክል
ፍረዱ። 17በፍርድ አድልዎ አታድርጉ፤ ትልቁ
ንም ትንሹንም እኩል እዩ፤ ፍርድ የእግዚ
አብሔር ስለሆነ፣ ማንኛውንም ሰው አት
ፍሩ። ከዐቅማችሁ በላይ የሆነውን ሁሉ ወደ
እኔ አምጡት፤ እኔ አየዋለሁ።" 18በዚያን ጊዜ
ማድረግ የነበረባችሁን ሁሉ ነገርኋችሁ።

## የሰላዮች መላክ

19ከዚያም አምላካችን እግዚአብሔር
(ያህዌ) ባዘዘን መሠረት ከኮሬብ ተነሥተን
እንዳያችሁት በዚያ ጭልጥ ባለና በሚያስፈራ
ምድረ በዳ ዐልፈን፣ በኰረብታማው በአሞ
ራውያን አገር በኩል ወደ ቃዴስ በርኔ
መጣን። 20እኔም፣ እንዲህ አልኋችሁ፤ "አም
ላካችን እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ወደሚሰጠን
ወደ ኰረብታማው የአሞራውያን አገር ደርሳ
ችኋል፤ 21እነሆ፤ እግዚአብሔር (ያህዌ) ምድሪቱን
ሰጥቶአችኋል፤ አሁንም የአባቶቻችሁ አምላክ
እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በነገራችሁ መሠረት
ውጡ፤ ውረሷትም፤ አትፍሩ፤ አትደንግጡም።"
22ከዚያም ሁላችሁ ወደ እኔ መጥታችሁ፣
"ምድሪቱን እንዲሰልሉልን ሰዎች አስቀድመን
እንላክ፤ እነርሱም ወደዚያ የሚያደርሰንን
መንገድና የምንሄድባቸውን ከተሞች በማ
ጥናት ተመልሰው ይነግሩናል" አላችሁ።
23ይህም ሐሳብ መልካም መስሎ ታየኝ፤
እኔም ከእያንዳንዱ ነገድ አንዳንድ ሰው በ
ማድ ረግ ከእናንተ ዐሥራ ሁለት ሰዎች
መረ ጥሁ። 24እነርሱም ተነሥተው ወደ
ኰረብ ታማው አገር ከወጡ በኋላ ወደ
ኤሽኮል ሸለቆ መጥተው ምድሪቱን ሰለሉ።

1፥1 ቍ7፤ዘኍ10፥12፤
13፥29፤ዘዳ2፥8፤3፥17፤4፥
46፤ኢ.ሱ3፥16፤
8፥14፤11፥2፤ሕዝ47፥8
1፥2 ቍ19፤
ዘፍ14፥7፤ዘፀ3፥1፤
ዘኍ24፥18፤ዘዳ2፥14፤
9፥23፤ኢ.ሱ15፥3
1፥3 ዘፍ50፥3፤
ዘኍ14፥33፤32፥13፤
ዘዳ4፥1-2፤8፥2፤
34፥8፤ኢ.ሱ4፥19፤
ዕብ3፥7-9፤
1፥4 ዘፍ10፥16፤
14፥7፤ዘኍ21፥21-
26፤21፥33-35፤
ዘዳ3፥10፤ኢ.ሱ9፥10፤
12፥4፤1ዜና11፥44
1፥5 ዘኍ21፥11
1፥6 ዘፀ3፥1፤
ዘኍ10፥13፤ዘዳ2፥3
1፥7 ቍ1፤19፤
ዘፍ2፥14፤10፥18፤
ዘኍ21፥1፤ዘዳ2፥24፤7፥
1፤11፥24፤
ኢ.ሱ10፥5፤11፥16፤
12፥8፤2ሳሙ24፥7፤
1፥8 ዘፀ13፥11፤
ዘኍ14፥23፤34፥2፤ ኢ.
ሱ23፥13፤
ዕብ6፥13-14
1፥9 ዘፀ18፥18፤
ዘኍ11፥14፤
መዝ38፥4
1፥10 ቍ11፤
ዘፍ15፥5፤22፥17፤
ዘኍ10፥36፤ዘዳ7፥13፤
ኢ.ሳ51፥2፤60፥22፤
ሕዝ16፥7፤33፥24
1፥11 ቍ8፥10፤
ዘፀ32፥13፤2ሳሙ
24፥3፤1ዜና21፥3
1፥12 ዘፀ
5፥22፤18፥18
1፥13 ዘፍ47፥6
1፥15 ዘፍ47፥6፤
ዘፀ5፥14፤18፥25፤
ዘኍ1፥4፤11፥16፤
31፥14፤
ኢ.ሱ1፥10፤
3፥2፤1ሳሙ8፥12፤
22፥7፤1ነገ14፥27
1፥16 ዘፍ31፥37፤
ዘፀ12፥19፤49፤
22፥21፤1ነገ3፥9፤
መዝ72፥1፤ዮሐ7፥24
1፥17 ዘፀ18፥16፥
26፤ዘሌ19፥15፤
ምሳ29፥25፤
ሐሥ10፥34፤ያዕ 2፥1
1፥18 ዘፍ39፥11
1፥19 ቍ2፤7፤
ዘኍ13፥26፤
ዘዳ2፥7፤8፥15፤32፥10፤መዝ136፥16፤ ኤር2፥2፥6፤ሆሴ13፥5፤ 1፥21
ዘኍ14፥9፤ ዘዳ7፥18፤9፥23፤ኢ.ሱ1፥6፤9፥18፤8፥1፤
10፥8፤2ሳሙ10፥12፤ መዝ27፥14፤ 1፥22 ዘፍ42፥9፤ዘኍ13፥1-3
1፥23 ዘኍ13፥1-3 1፥24 ዘኍ13፥21-25፤32፥9

25ከምድራቱም ፍሬ ወደ እኛ ይዘው በመ
ምጣት፣ “አምላካችን እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎ
ሂም) የሚሰጠን ምድር መልካም ናት” ብለው
ነገሩን።

### በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ

26እናንተ ግን ለመውጣት ፈቃደኞች አል
ነበራችሁም፤ በአምላካችን በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎ
ሂም) ትእዛዝ ላይ ዐመፃችሁ። 27በየድንኳ
ኖቻችሁ ሆናችሁ እንዲህ ስትሉ አጒረ
መረማችሁ፤ “እግዚአብሔር (ያህዌ) ጠልቶናል፤
ስለዚህም ከግብፅ ያወጣን አሞራውያን እንዲ
ያጠፉን፣ በእጃቸው አሳልፎ ሊሰጠን ነው።
28ታዲያ ወዴት መሄድ እንችላለን? ወንድ
ሞቻችን፣ ‘ሰዎቹ ከእኛ ይልቅ ብርቱዎችና
ቁመተ ረጃጅሞች፣ ከተሞቹም ትልልቆችና
እስከ ሰማይ በሚደርስ ቅጥር የታጠሩ ናቸው፤
እንዲያውም በዚያ የዔናቅን ልጆች አይተ
ናቸዋል’ ሲሉ እንድንፈራ አድርገውናል።”

29እኔም አልኋችሁ፤ “አትሸበሩ፤ አትፍ
ሯቸውም። 30በፊታችሁ የሚሄደው አምላካ
ችሁ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ከዚህ በፊት
ዐይናችሁ እያየ በግብፅ እንዳደረገላችሁ ሁሉ፣
አሁንም ለእናንተ ይዋጋል፤ 31በምድረ በዳው
እንደ አደረገው ሁሉ። በዚያም አባት ልጁን
እንደሚሸከም፣ እናንተን አምላካችሁ እግዚአብሐ
ር (ያህዌ ኤሎሂም) እዚህ ስፍራ እስክ ትደርሱ
በመ ጣችሁበት መንገድ ሁሉ እንዴት
እንደ ተሸከማችሁ አይታችኋል።”

32ይህም ሆኖ በአምላካችሁ በእግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) አልታመናችሁም፤ 33በጒዞ ላይ
ሳላችሁ የምትሰፍሩባቸውን ቦታዎች ለመ
ፈለግና የምትሄዱበትን መንገድ ለማሳየት
እርሱ ሌሊት በእሳት፣ ቀን በደመና ይመ
ራችሁ ነበር።

34እግዚአብሔርም (ያህዌ) እናንተ ያላችሁትን
በሰማ ጊዜ ተቈጣ፤ ማለም፤ 35“ለቀደሙት አባ
ቶቻችሁ ለመስጠት የማልሁላቸውን መልካሚ
ቱን ምድር፣ ከዚህ ክፉ ትውልድ አንድም
ሰው አያያትም፤ 36ከዮፎኒ ልጅ ከካሌብ በስተ
ቀር የሚያያት የለም፤ እርሱ ያያታል፤
እግዚአብሔርን (ያህዌ) በፍጹም ልቡ ስለ ተከተለ፣
የረገ ጣትን ምድር ለእርሱና ለዘሮቹ
እሰጣለሁ።”

37በእናንተ ምክንያት እግዚአብሔር (ያህዌ)
እኔን ተቈጥቶ እንዲህ አለኝ፤ “አንተም
ብትሆን አትገባባትም። 38ረዳትህ የነዌ ልጅ
ኢያሱ ግን ይገባባታል፤ ምድሪቱን እንዲ
ወርሱ እስራኤልን የሚመራ እርሱ ስለ ሆነ፣
አበረታታው። 39ይማረካሉ ያላችኋቸው ታናና
ሾች፣ ክፉና በጎውን ለይተው የማያውቁት
ልጆቻችሁ ምድሪቱን ይገቡባታል፤ ለእነርሱም
እሰጣቸዋለሁ፤ እነርሱም ይወርሷታል። 40እና
ንተ ግን፣ ተመልሳችሁ ወደ ቀይ ባሕር[ህ]
የሚወስደውን መንገድ ይዛችሁ ወደ ምድረ
በዳው ተጓዙ።”

41እናንተ፣ “እግዚአብሔርን (ያህዌ) በድለናል፤ አም
ላካችሁ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ባዘዘንም መሠ
ረት ወጥተን እንዋጋለን ብላችሁ መለሳች
ሁልኝ። ወደ ተራራማው አገር መሄድ
ቀላል መስሎ ስለ ታያችሁ፣ እያንዳንዳችሁ
የጦር መሣ ሪያችሁን ታጥቃችሁ
ተነሣችሁ።

42እግዚአብሔር (ያህዌ) ግን፣ “እኔ ከእናንተ
ጋር አልሆንምና ወጥታችሁ እንዳትዋጉ፤
በጠላቶቻችሁ ድል ትነሣላችሁ ብለህ ንገ
ራቸው” አለኝ።

43እኔም ነገርኋችሁ፤ እናንተ ግን አላዳመ
ጣችሁም፤ በእግዚአብሔር (ያህዌ) ትእዛዝ ላይ
ዐምፃችሁ፤ በትዕቢታችሁ ወደ ኰረብታማዪቱ
አገር ዘመታችሁ። 44በነዚያ ኰረብቶች ላይ
የሚኖሩት አሞራውያን ሊወጓችሁ ወጡ፤ እንደ
ንብ ሰራዊትም ሆነው አባረሯችሁ፤ ከሴይር
አንሥቶ እስከ ሔርማ ድረስ አሳደው መቷ
ችሁ። 45እናንተም ተመልሳችሁ መጥታችሁ
በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት አለቀሳችሁ፤ ነገር ግን
እግዚአብሔር (ያህዌ) ልቅሶአችሁን አልሰማም፤
አላዳመጣችሁምም። 46ስለዚህ ያን ያህል ጊዜ
በማጥፋት በቃዴስ ብዙ ቀን ቈያችሁ።

### በምድረ በዳ መንከራተት

2 ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ባዘዘኝ መሠ
ረት ተመለስን፤ ቀይ ባሕርን[^] ይዘን
ወደ ምድረ በዳው ተጓዝን፤ በሴይር ኰረ
ብታማ አገር ዙሪያ ለረጅም ጊዜ ተንከራ
ተትን።

2ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) እንዲህ አለኝ፤
3“በዚህ በኰረብታማ አገር ዙሪያ እስኪበቃችሁ
ተንከራታችኋል፤ አሁን ግን ወደ ሰሜን ተመ
ለሱ። 4ለሕዝቡም እነዚህን ትእዛዞች ስጣ
ቸው፤ ሴይር በሚኖሩት በወንድሞቻችሁ በዔ
ሳው ዘሮች ግዛት ዐልፋችሁ ትሄዳላችሁ፤
እነርሱ ይፈሯችኋል፤ ቢሆንም ከፍ ያለ ጥን
ቃቄ አድርጉ። 5ከየትኛውም ምድራቸው ላይ
ለጫማችሁ መርገጫ ታህል እንኳ መሬት
ስለማልሰጣችሁ፣ ለጦርነት አታነሣሷቸው።
ኰረብታማውን የሴይርን አገር ርስት አድርጌ ለዔ
ሳው ሰጥቼዋለሁ። 6ከዚያ ለምትበሉት
ምግብም ሆነ ለምትጠጡት ውሃ በጥሬ
ብር ትከፍሏቸዋላችሁ።”

7አምላካችሁ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
በእጃችሁ ሥራ ሁሉ ባርኮአችኋል፤ በዚህ
ጭልጥ ባለው ምድረ በዳ ባደረጋችሁት
ጒዞ ጠብቆአችኋል። በእነዚህ አርባ ዓመታት
እግዚአብሔር ከእናንተ

1፥25 ዘኍ13፥27፤14፥7፤ኢሱ1፥2
1፥26 ዘኍ14፥1-4፡9
1፥27 ዘዳ9፥28፤ መዝ106፥25
1፥28 ዘኍ13፥32፡33፤ዘዳ9፥1-3
1፥29 ዘዳ3፥22፤ 7፥18፤ 20፥1፡3፤ 31፥6ነህ4፥14
1፥30 ዘፀ14፥14
1፥31 ዘፀ19፥4፤ ዘዳ32፥10-12፤ መዝ28፥9፤ኢሳ46፡3-4፤ 63፥9፤ኤር31፥32፤ ሆሴ11፡3፤ሐሥ13፥18፤
1፥32 ዘኍ14፥11፤ ዘዳ9፥23፤መዝ78፥22፤ 106፥24፤ሶፎ3፥2፤ ዕብ3፥19፤ይሁዳ1፥5
1፥33 ዘፀ13፥21፤ ዘኍ9፥15-23፤ 10፡33፤ ነህ9፥12፤መዝ78፥14፤
1፥34 ዘኍ11፥1፤ 32፥14፤14፥23፡28-30፤ ሕዝ20፥15፤ዕብ3፥11
1፥35 ዘኍ14፥29
1፥36 ዘኍ13፥6፤ 14፥24
1፥37 ዘኍ27፥13፤ መዝ106፥32
1፥38 ዘኍ11፥28፤ ዘዳ3፥28፤31፥7፤ ኢሱ11፥23፤ መዝ78፥55፤136፥21
1፥39 ዘኍ14፥3፤ ኢሳ7፥15-16
1፥40 ዘፀ14፥27፤ መሳ11፥16
1፥42 ዘኍ14፡41-43
1፥44 ዘኍ14፥45፤ 24፥18፤መዝ118፥12
1፥45 ዘኍ14፥1፤ ኢዮ27፥9፤35፥13፤ መዝ18፥41፤28፥1፤ 39፥12፤66፥18፤ ምሳ1፥28፤28፥9፤ ኢሳ1፥15፤ኤር14፥12፤ ሰቆ3፥8፤ሚክ3፥4፤ ዮሐ9፥31
1፥46 ዘኍ20፥1
2፥1 ዘፀ14፥27፤ ዘኍ21፥4፤24፥18
2፥3 ዘዳ1፥6
2፥4 ቊ1፤ዘፍ36፡8፤ ዘፀ15፥16፤ ዘኍ20፥14-21፤ ዘዳ15፥16
2፥5 ኢሱ24፥4
2፥7 ቊ14፤ ዘፀ13፡21፤ ዘኍ14፡33፤ 32፥13፤ዘዳ1፥19፤ 8፥2-4፤ኢሱ5፥6፤ ነህ9፥21፤አሞ2፥10

[ህ]40 ዕብራይስጡ፣ ያም ሳውፍ ይለዋል፤ ይኸውም፣ የደንገል ባሕር ማለት ነው።
[^]2 ዕብራይስጡ፣ ያም ሳውፍ ይለዋል፤ ይኸውም የደንገል ባሕር ማለት ነው።

ጋር ነበርና አንዳችም ነገር አላጣችሁም።
8ስለዚህ በሴይር የሚኖሩ የዔሳው ዘሮች
የሆኑ ወንድሞቻችንን ዐልፈናቸው ሄድን፡፡
ከኤላትና ከጽዮንጋብር ከሚመጣው ከዓረባ
መንገድ ተመልሰን፣ በሞአብ ምድረ በዳ
መንገድ ተጓዝን፡፡
9ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ)፣ "ከሞዓ
ባውያን ምድር አንዳችም መሬት ስለማል
ሰጣችሁ አታስቸግሯቸው፤ ለጦርነትም አታ
ነሣሷቸው፤ ዔርን ለሎጥ ዘሮች ርስት አድ
ርጌ ሰጥቻቸዋለሁ" አለኝ፡፡
10በዚያም ጠንካራና ቍጥራቸው የበዛ
እንዲሁም እንደ ዔናቃውያን ረጃጅም የሆኑ
ኤሚ ማውያን ይኖሩ ነበር፡፡ 11እነዚህም
እንደ ዔና ቃውያን ሁሉ ራፋይማውያን
ናቸው ተብለው ይገመቱ ነበር፤ ሞዓባውያን
ግን ኤሚማውያን ብለው ይጠሯቸዋል፡፡
12ሖራውያን ቀድሞ በሴይር ይኖሩ ነበር፤
የዔሳው ዘሮች ግን ከዚያ አሳደው
አስወጧቸው፡፡ እግዚአብሔር (ያህዌ) ርስት
አድርጎ በሰጠው ምድር ላይ እስራኤል
እንዳደረገው ሁሉ፣ እነዚህም ሖራውያንን
ከፊታቸው አጥፍተው መኖሪያቸውን እዚያው
አደረጉ፡፡
13ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) "አሁኑኑ ተነ
ሡና የዘሬድን ደረቅ ወንዝ ተሻገሩ" አለን፤
እኛም ወንዙን ተሻገርን፡፡
14ቃዴስ በርኔን ከለቀቅንበት ጊዜ አንሥቶ
የዘሬድን ደረቅ ወንዝ እስከ ተሻገርንበት ጊ
ዜ ድረስ ሠላሳ ስምንት ዓመት ዐለፈ፡፡ በዚ
ያን ጊዜም ለጦርነት ብቁ የሆኑት የዚያ
ትውልድ
ወንዶች ሁሉ እግዚአብሔር (ያህዌ) ስለ እነርሱ
አስቀድሞ በማለው መሠረት ከሰፈሩ ፈጽ
መው ዐለቁ፡፡ 15ከሰፈር ፈጽሞ እስኪያጠፉ
ቸውም ድረስ የእግዚአብሔር (ያህዌ) እጅ በእ
ነርሱ ላይ ነበር፡፡
16በሕዝቡ መካከል የነበሩት የመጨረሻ
ዎቹ ተዋጊዎች ከሞቱ በኋላ፣ 17እግዚአብሔር
(ያህዌ) እንዲህ አለኝ፤ 18"የሞዓብ ዳርቻ ዔርን
ዛሬውኑ ታልፋላችሁ፡፡ 19ከየትኛውም የአሞና
ውያን ምድር ለእናንተ ርስት ስለማልሰጣችሁ፣
አሞናውያን ዘንድ በደረሳችሁ ጊዜ አታስቸ
ግሯቸው፤ ለጦርነትም አታነሣሡአቸው፡፡ ያን
ቦታ ርስት አድርጌ ለሎጥ ዘሮች ሰጥቻቸዋለሁ፡፡"
20ያም ደግሞ በዚያ ይኖሩ የነበሩት የረፋይ
ማውያን ምድር እንደ ሆነ ይቈጠር ነበር፤
አሞናውያን ግን ዘምዙማውያን ብለው ይጠ
ሯቸው ነበር፡፡ 21ዘምዙማውያን ብርቱዎች፣
ቍጥራቸው የበዛና እንደ ዔናቃውያን ቁመተ
ረጃጅሞች ነበሩ፤ እግዚአብሔር (ያህዌ) ከእ
ነርሱ ፊት አጠፋቸው፤ እነርሰም አሳደዷቸው
በምትካቸውም ሰፈሩበት፡፡ 22እግዚአብሔር (ያህዌ)
ሖራውያንን ከፊታቸው ባጠፋ ጊዜ፣ በሴይር

2፥8 ዘኍ20፥21፤
21፥4፤ 33፥35፤
ዘዳ1፥1፤1ነገ9፥26
2፥9 ዘፍ19፥38፤
ዘኍ21፥15፤መዝ83፥8
2፥10 ዘፍ14፥5፤
ዘኍ13፥22፡33
2፥11 ዘፍ14፥5
2፥12 ዘፍ14፥6፤
ዘኍ21፥25፡35
2፥13 ዘኍ21፥12
2፥14 ቍ7፤
ዘኍ14፥29-35፤
ዘዳ1፥2፤1፥34-35፤
ኢሱ5፥6
2፥15 መዝ106፥26፤
ይሁዳ1፥5
2፥18 ዘኍ21፥15
2፥19 ቍ9፤
ዘፍ19፥38፤2ዜና20፥10
2፥20 ዘፍ14፥5
2፥21 ቍ10
2፥22 ዘፍ14፥6
2፥23 ዘፍ10፥14፡
19፤ኢሱ13፥3፤
18፥23፤2ነገ17፥31፤
ኤር47፥4፤አሞ9፥7
2፥24 ዘኍ21፥13-14፤
ዘዳ1፥7፤3፥6፤
መሳ11፥13፡18
2፥25 ዘፍ35፥5፤
ዘፀ15፥14-16፤
ዘዳ11፥25፤ኢሱ2፥9፡
11፤1ዜና14፥17፤
2ዜና14፥14፤17፥10፤2
0፥29፤ኢሳ2፥19፤
13፥13፤19፥16፤
2፥26 ዘዳ1፥4፤
20፥10፤ኢሱ13፥18፤
መሳ11፥21-22፤
21፥13፤2ሳሙ20፥19፤
1ዜና6፥79
2፥27 ዘኍ21፥21-22
2፥28 ዘዳ23፥4፤
ዘኍ20፥19
2፥30 ዘፀ4፥21፤
14፥7፤መሳ14፥4፤
1ነገ12፥15፤ሰቆ3፥65፤
ሮሜ9፥18
2፥31 ዘፍ12፥7
2፥32 ዘኍ21፥23
2፥33 ዘፀ23፥31፤
ዘኍ21፥24፤ዘዳ7፥2፤3
1፥5
2፥35 ዘፍ34፥29፤
49፥27፤ዘዳ3፥7

ለሚኖሩት የዔሳው ዘሮች ያደረገው ይህንኑ
ነበር፡፡ እነርሱም አሳደው በማስወጣት ባስ
ለቀቁት ስፍራ ላይ እስከ ዛሬ ይኖራሉ፡፡
23እስከ ጋዛ ድረስ ባሉት መንደሮች የኖሩትን
ኤዋውያን በተመለከተም፣ ከከፍቶር[ሐ] ወጥ
ተው የመጡት ከፍቶራውያን እነርሱን አጥ
ፍተው መኖሪያቸውን እዚያው አደረጉ፡፡

## የሐሴቦን ንጉሥ የሴዎን ድል መነሣት

24"አሁኑኑ ተነሡና የአርኖንን ወንዝ ተሻ
ገሩ፤ እነሆ፣ የሐሴቦንን ንጉሥ፣ አሞራዊውን
ሴዎንንና አገሩን በእጃችሁ ሰጥቻችኋለሁ፤
ምድሩን መውረስ ጀምሩ፤ ጦርነት ግጠሙት።
25ከሰማይ በታች ባሉ አሕዛብ ሁሉ ላይ፣
ማስደንገጣችሁና ማስፈራታችሁ እንዲያድ
ርባቸው ከዚህች ከዛሬዋ ዕለት እጀምራ
ለሁ፡፡ ስለ እናንተ ሰምተው ይርበተበታሉ፤
ከእናንተ የተነሣም ይጨነቃሉ፡፡"
26ከቅዴሞት ምድረ በዳም ለሐሴቦን ንጉሥ
ለሴዎን የሰላም ቃል እንዲያደርሱለት እንዲህ
በማለት መልእክተኞች ላክሁ፤ 27"በአገርህ
አቋርጠን እንድናልፍ ፍቀድልን፤ ከዋናው
መንገድ አንወጣም፤ ቀኝም ግራም አንልም፡፡
28የምንበላውን ምግብ፣ የምንጠጣውንም ውሃ፣
በጥሬ ብር ሽጥልን፡፡ በእግር እንድናልፍ ብቻ
ፍቀድልን፤ 29በሴይር የሚኖሩ የዔሳው ዘሮችና
በዔር የሚኖሩ ሞዓባውያን እንዳደረጉልን
ሁሉ፣ አንተም አምላካችን እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ወደሚሰጠን ምድር ለመግባት
ዮርዳ ኖስን እስክንሻገር ድረስ እንደዚሁ
አድርግልን፡፡" 30ይሁን እንጂ የሐሴቦን ንጉሥ
ሴዎን እንድናልፍ አልፈቀደልንም፡፡ ምክንያተ
ም አም ላካችሁ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
አሁን እንዳ ደረገው ሁሉ እርሱን በእጃችሁ
አሳልፎ ለመ ስጠት መንፈሱን
አደንድኖት፣ ልቡንም
አጽንቶት ነበር፡፡
31እግዚአብሔርም (ያህዌ)፣ "እነሆ፣ ሴዎንንና
አገሩን ለእናንተ አሳልፌ ልሰጣችሁ ተነሥቻ
ለሁ፤ አሁንም እርሱን አሸንፋችሁ ምድሩን
ለመውረስ ተነሡ" አለኝ፡፡
32ሴዎንና መላው ሰራዊቱ በያህጽ ጦርነት
ሊገጥሙን በወጡ ጊዜ፣ 33አምላካችን እግ
ዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በእጃችን ላይ ጣለው፤
እኛም፣ እርሱን ከወንድ ልጆቹና ከመላው
ሰራዊቱ ጋር አንድ ላይ መታነው፡፡ 34በዚ
ያን ጊዜ ከተሞቹን በሙሉ ወስደን የሚ
ኖሩባቸውን ወንዶች፣ ሴቶችና ልጆቻቸውን
ጭምር ፈጽመን አጠፋናቸው[መ]፤ አንዳቸውንም
በሕይወት አላስቀረንም፡፡ 35ከብቶቻቸውንና
ከየከተሞቻቸው ያገኘነውን ምርኮ ግን ለራ

[ሐ]23 ቀርጤስ ነች
[መ]34 የዕብራይስጡ ቃል አንድን ነገር ወይም አንድን ሰው ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠትን የሚያሳይ ነው፡፡

ሳችን አደረግን። [36]በአርኖን ሸለቆ ጫፍ
ካለችው ከአሮዔርና በሸለቆው ውስጥ ከም
ትገኘዋ ከተማ አንሥቶ እስከ ገለዓድ ካሉት
ከተሞች አንዳቸውም እንኳ ሊገቱን አልቻ
ሉም። *አምላካችን* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
ሁሉንም አሳልፎ ሰጠን። [37]ይሁን እንጂ
*አምላካችን* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በሰጠው
ትእዛዝ መሠረት፣ ወደ ማናቸውም የአሞ
ናውያን ምድር ወይም በያቦቅ ወንዝ መው
ረጃ ወዳለው ምድር፣ ወይም ደግሞ በኰረብ
ቶች ወዳሉት ከተሞች ዙሪያ ዐልፋችሁ
አልሄዳችሁም።

## የባሳን ንጉሥ የዐግ መሸነፍ

3 ከዚያም፣ ተመልሰን የባሳንን መንገድ
ይዘን ወጣን፤ የባሳን ንጉሥ ዐግም ከመ
ላው ሰራዊቱ ጋር ሆኖ በኤድራይ ጦርነት
ሊገጥመን ተነሣ። [2]*እግዚአብሔር* (ያህዌ)፣ "እር
ሱን፣ መላው ሰራዊቱንና ምድሩን በእጅህ አሳ
ልፌ ስለ ሰጠሁህ፣ አትፍራው፤ ሐሴ ቦንን
ይገዛ በነበረው በአሞራውያን ንጉሥ በሴዎን
ላይ ያደረግህበትን በእርሱም ላይ አድርግ
በት" አለኝ።

[3]ስለዚህ *አምላካችን* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎ
ሂም) የባሳንን ንጉሥ ዐግንና ሰራዊቱን ሁሉ እን
ደዚሁ በእጃችን ላይ ጣላቸው፤ እኛም አንድ
እንኳ በሕይወት ሳናስቀር አጠፋናቸው።
[4]በዚያን ጊዜ ከተሞቹን ሁሉ ያዝን፤ የዐግ
ግዛት ከሆነው፣ በባሳን ከሚገኘው ከጠ
ቅላላው የአርጎብ ክልል ሥልሳ ከተሞች
ውስጥ፣ እኛ ያልያዝነው አንድም ከተማ
አልነበረም። [5]እነዚህ ከተሞች ሁሉ ከፍ
ባሉ ቅጥሮች፣ በመዝጊያዎችና በመወር
ወሪያዎች የተመሸጉ ነበሩ፤ እንዲሁም ቅጥር
የሌላቸው አያሌ መንደሮች ነበሩ። [6]በእያ
ንዳንዱ ከተማ ያሉትን ወንዶቹን፣ ሴቶቹንና
ልጆቻቸውን ጭምር በማጥፋት፣ በሐሴቦን
ንጉሥ በሴዎን ላይ እንዳደረግነው ሁሉ፣
እነዚህንም ፈጽመን ደመሰስናቸው[ሠ]። [7]ከብ
ቱን በሙሉና ከየከተሞቻቸው የማረክነውን
ሁሉ ግን ለራሳችን አደረግን።

[8]ስለዚህ በዚያን ጊዜ ከዮርዳኖስ በስተ
ምሥራቅ የሚገኘውን፣ ከአርኖን ሸለቆ እስከ
አርሞንዔም ተራራ ያለውን ግዛት፣ ከእነዚህ
ከሁለቱ የአሞራውያን ነገሥታት ላይ ወሰ
ድንባቸው። [9]አርሞንዔምን፣ ሲዶናውያን ሢር
ዮን ብለው ሲጠሩት፣ አሞራውያን ግን
ሳኔር ይሉታል። [10]በከፍታው ቦታ ላይ የሚገ
ኙትን ከተሞች በሙሉ፣ ገለዓድን እንዳለ፣
እስከ ሰልካና እስከ ኤድራይ ያለውን
ባሳንን ሁሉ እንዲሁም በባሳን ውስጥ የሚገ
ኙትን የዐግ ግዛት ከተሞች በእጃችን
አደረግን። [11]ከራፋይማውያን ወገን የተረፈ

2፥36 ዘኍ32፥34፡39፤መዝ44፥3
2፥37 ቀ፡18-19፤ ዘፍ32፥22፤ዘኍ21፥24
3፥1 ዘኍ32፥19፡21፥33
3፥2 ኢ.ሱ10፥8፤ 2ነገ 19፥6፤ኢ.ሳ7፥4
3፥3 ዘኍ21፥24፡35
3፥4 ቀ፡13፤ ዘኍ21፥24፡33
3፥6 ዘዳ2፥24
3፥7 ዘዳ2፥35
3፥8 ዘኍ32፥33፤ ዘዳ4፥48፤ ኢ.ሱ11፥3፡17፤12፥1፤ 13፥5፡8-12፤መሳ3፥3፤ 1ዜና5፥23፤መዝ42፥6፤ 89፥12፤133፥3፤ መሓ4፥8
3፥9 1ዜና5፥23፤ መዝ29፥6፤መሓ4፥8፤ ሕዝ27፥5
3፥10 ኢ.ሱ12፥5፤ 1ዜና5፥11
3፥11 ዘፍ14፥5፤ ኢ.ሱ13፥25፤15፥60፤ 2ሳሙ11፥1፤12፥26፤ 17፥27፤1ዜና20፥1፤ ኤር49፥2፤ሕዝ21፥20፤ 25፥5፤አሞ1፥14
3፥12 ዘዳ2፥36
2፥13 ዘፍ14፥5፤ ዘዳ29፥8
3፥14 ዘኍ32፥41፤ ኢ.ሱ12፥5፤13፥11፡ 13፤ 19፥47፤2ሳሙ10፥6፤ 23፥34፤2ነገ25፥23፤ 1ዜና4፥19፤ መዝ49፥11፤ኤር40፥8
3፥15 ዘፍ50፥23፤ ዘኍ32፥39-40
3፥16 ዘኍ21፥24
3፥17 ዘፍ14፥3፤ ዘኍ34፥11፤ዘዳ1፥1፤ ሳሙ2፥29፤4፥7፤ ሕዝ 47፥8
3፥18 ዘኍ32፥17፤ ኢ.ሱ1፥13
3፥19 ዘኍ32፥16፤ ኢ.ሱ1፥14

የባሳን ንጉሥ ዐግ ብቻ ነበር። ዐልጋው[ረ]
ከብረት የተሠራ ቁመቱም ዘጠኝ ክንድ፣
ስፋቱ ደግሞ አራት ክንድ[ሰ] ነበር። ይህም
እስካሁን በአሞናውያን ከተማ በረባት
ይገኛል።

## እስራኤላውያን ምድሪቱን መከፋፈላቸው

[12]በዚያን ጊዜ ከያዝነው ምድር ላይ በአ
ርኖን ሸለቆ አጠገብ ካለችው ከአሮዔር
አንሥቶ በስተ ሰሜን ያለውን ግዛት፣
በተጨማሪም ኰረብታማውን የገለዓድ
አገር እኩሌታ ከነከተሞቹ ለሮቤላውያንና
ለጋዳውያን ሰጠኋቸው። [13]ቀሪውን የገለዓድ
ምድርና የዐግ ግዛት የሆነውን ባሳንን
በሙሉ ለምናሴ ነገድ እኩሌታ ሰጠሁ።
በባሳን የሚ ገኘው መላው የአርጎብ ክልል የራ
ፋይማውያን ምድር በመባል ይታወቅ ነበር።
[14]ከምናሴ ነገድ የሆነው ኢያዕር፣ እስከ
ጌሹራውያ ንና እስከ ማዕካታውያን ወሰን
ድረስ የሚገኘውን መላውን የአርጎብ ምድር
ወሰደ፤ ምድሪቱም በስሙ ተጠራች[ሸ]፤ ከዚሁ
የተነሣ ባሳን እስከ ዛሬ ድረስ ሓቦት ኢያዕር
ትባላለች። [15]ገለዓድንም ለማኪር ሰጠሁት።
[16]ነገር ግን የሸለቆውን እኩሌታ ወሰን በማ
ድረግ ከገለዓድ አንሥቶ እስከ አርኖን
ሸለቆ፣ ከዚያም የአሞናውያን ድንበር እስከ
ሆነው እስከ ያቦቅ ወንዝ ያለውን ግዛት
ለሮቤላውያንና ለጋዳውያን ሰጠኋቸው።
[17]የምዕራቡ ወሰን፣ በዓረባ የሚገኘው ዮር
ዳኖስ ሲሆን፣ ይኸውም ከፈስጋ ተረተሮች
በታች፣ ከኪኔሬት አንሥቶ የጨው ባሕር[ቀ]
እስከሚባለው እስከ ዓረባ ባሕር ድረስ ነው።

[18]በዚያን ጊዜ እኔ እንዲህ ብዬ አዘዝኋችሁ፤
"*አምላካችሁ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
ይህችን ምድር ርስት አድርጎ ለእናንተ
ሰጥቶአችኋል፤ ይሁን እንጂ የአካል ብቃት
ያላቸው ሰዎ ቻችሁ ሁሉ ለጦርነት ዝግጁ
ሆነው ከወን ድሞቻችሁ ከእስራኤላውያን
ፊት በመ ቅደም መሻገር አለባቸው።
[19]ሆኖም ሚስ ቶቻችሁና ልጆቻችሁ፣ (ብዙ
ከብቶች እን ዳሏችሁም ስለማውቅ)
ከብቶቻችሁም በሰጠኋችሁ ከተሞች ውስጥ
ይቈዩ፤ [20]ይኸውም፣ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ለእናንተ
እንዳደረገው ሁሉ ወንድሞቻችሁን እስኪ
ያሳርፋቸውና *አም ላካችሁ* እግዚአብሔር (ያህዌ
ኤሎሂም) ከዮርዳኖስ ማዶ የሚሰጣቸውን ምድር
እነርሱም እንደዚሁ እስኪወርሱ ድረስ ነው፤
ከዚያ በኋላ እያን ዳንዳችሁ ወደ ሰጠኋችሁ
ርስት ትመለ ሳላችሁ።"

[ሠ]6 የ2፥34 አማራጭ ትርጒም ይመ።
[ረ]11 ወይም፣ *ድንጋይ ተጠርቦ የተዘጋጀ የሬሳ ሣጥን*
[ሰ]11 ቁመቱ 4 ሜትር ስፋቱ 1.8 ሜትር ያህል ነው።
[ሸ]14 ወይም፣ *የኢያዕር መኖሪያ ተብላ ተጠራች*
[ቀ]17 ይኸውም የሙት ባሕር ነው።

## ሙሴ ዮርዳኖስን እንዳይሻገር መከልከሉ

[21]በዚያን ጊዜ ኢያሱን እንዲህ ስል አዘዝ
ሁት፤ “አምላካችሁ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) በእ
ነዚህ በሁለቱ ነገሥታት ላይ ያደረገውን ሁሉ
በገዛ ዓይንህ አይተሃል፤ አሁንም ዐልፈህ
በምትሄድባቸው መንግሥታት ላይ ሁሉ እግ
ዚአብሔር ይህንኑ ይደግመዋል። [22]*አምላካችሁ*
እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ራሱ ይዋጋላችኋልና
አትፍሯቸው።”

[23]በዚያን ጊዜ *እግዚአብሔርን* (ያህዌ) እንዲህ
ብዬ ለመንሁት፤ [24]“ጌታ *እግዚአብሔር* (አዶናይ
ያህዌ) ሆይ፣ ታላቅነትህንና ብርቱ ክንድህን
ለእኔ ለባሪያህ እነሆ፣ ማሳየት ጀምረሃል፤
ለመሆኑ በሰማይም ሆነ በምድር፣ አንተ
የምታደርጋቸውን ሥራዎችና ታላላቅ ድርጊቶች
መፈጸም የሚችል አምላክ ማነው?
[25]አሁንም ከዮርዳኖስ ማዶ ያለችውን
ያችን መልካሚቱን ምድር፣ ውብ
የሆነችውን ኰረ ብታማ አገርና ሊባኖስን
እንዳይ ፍቀድልኝ።”

[26]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ግን በእናንተ ሰበብ
ተቈጥቶኝ ነበርና አልሰማኝም፤ *እግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) እንዲህ አለኝ፤ “ይበቃል፤ ከእ
ንግዲህ ወዲያ ስለዚህ ነገር አታንሣብኝ።
[27]ወደ ፈስጋ ተራራ ጫፍ ውጣ፤ ወደ ምዕ
ራብና ወደ ሰሜን፣ ወደ ደቡብና ወደ
ምሥራቅም ተመልከት። አንተ ዮርዳኖስን
ስለማትሻገር፣ ምድሪቱን በዐይንህ ብቻ
እያት። [28]ነገር ግን ሕዝቡን መርቶ በማ
ሻገር የምታያትን ምድር እንዲወርሱ የሚያ
ደርጋቸው ስለ ሆነ፣ ኢያሱን ላከው፤ አደፋ
ፍረው፤ አበረታታውም።” [29]ስለዚህ እኛ
በቤተ ፌጎር አጠገብ ባለው ሸለቆ ውስጥ
ቈየን።

## ሙሴ እስራኤላውያን እንዲታዘዙ ማስጠንቀቁ

4 አሁንም እስራኤል ሆይ፤ በሕይወት
እንድትኖሩ፣ የአባቶቻችሁ *አምላክ* እግ ዚ
አብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ወደሚሰጣችሁ ምድር እን
ድትገቡና እንድትወርሱ የማስተምራችሁን
ሥርዐትና ሕግ ስሙ፤ ጠብቋቸውም። [2]ባዘዝ
ኋችሁ ላይ አትጨምሩ፤ ከእርሱም አትቀ
ንሱ፤ ነገር ግን የምሰጣችሁን የአምላካችሁን
*የእግዚአብሔርን* (ያህዌ) ትእዛዞች ጠብቁ።
[3]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) በብዔልፌጎር ላይ ምን
እንዳደረገ በዐይናችሁ አይታችኋል፤ አምላ
ካችሁ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ከመካከላችሁ
ብዔልፌጎርን የተከተሉትን ሁሉ አጥፍቶ
አቸዋል፤ [4]አምላካችሁን *እግዚአብሔርን*
(ያህዌ) የተከተላችሁት እናንተ ሁላችሁ ግን
ይኸው እስከ ዛሬ በሕይወት አላችሁ።
[5]ገብታችሁ በምትወርሷት ምድር፣ እንድ
ትፈጽሟቸው እግዚአብሔር *አምላኬ* (ኤሎሂም
ያህዌ) ባዘዘኝ መሠረት ሥርዐትንና ሕግን
አስተምሬአችኋለሁ። [6]በጥንቃቄ ጠብቋቸው፤
ስለ እነዚህ ሥርዐቶች ሁሉ ለሚሰሙና፣
“በእውነቱ ይህ ታላቅ ሕዝብ የቱን ያህል
ጥበበኛና አስተዋይ ነው” ለሚሉ ሕዝቦች
ይህ ጥበባችሁንና ማስተዋላችሁን ይገልጣልና።
[7]በምንጠራው ጊዜ ሁሉ *አምላካችን* እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ለእኛ ቅርብ እንደ ሆነ አማልክቱ
የሚቀርቡት ሌላ ታላቅ ሕዝብ ማነው? [8]ዛሬ
እኔ በፊታችሁ እንዳ ስቀመጥሁት ሕግ ያለ፣
ጽድቅ የሆነ ሥርዐትና ሕግ ያሉት ሌላ ታላቅ
ሕዝብስ ማነው?

[9]ዐይኖቻችሁ ያዩዋቸውን ነገሮች እንዳትረሱ፣
ደግሞም በሕይወት እስካላችሁ ድረስ ከል
ባችሁ እንዳይጠፉ ብቻ ተጠንቀቁ፣ ነቅታ
ችሁም ራሳችሁን ጠብቁ። እነዚህን ለልጆ
ቻችሁና ከእነርሱ በኋላ ለሚወለዱት ልጆ
ቻቸው አስተምሯቸው። [10]“በምድሪቱ
በሚ ኖሩበት ጊዜ ሁሉ እኔን ማክበር እንዲ
ማሩ፣ ለልጆቻቸውም እንዲያስተምሩ ቃሌን
ይሰሙ ዘንድ ሕዝቡን በፊቴ ሰብስብ” ባለኝ
ጊዜ፣ በኮሬብ *በአምላካችሁ* በእግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ፊት የቆማችሁበትን ዕለት
አስታውሱ። [11]ተራራው በጥቍር ደመናና
በድቅድቅ ጨለማ ተውጦ ሳለ ነበልባሉ ሰ
ማይ እስከሚደርስ ድረስ በተቃጠለ ጊዜ
መጥታችሁ ከተራ ራው ግርጌ ቆማችሁ።
[12]ከዚያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) በእሳቱ
ውስጥ ሆኖ ተናገራችሁ፤ እናንተም የቃሉን
ድምፅ ሰማችሁ፤ መልክ ግን አላያችሁም፤ ድምፅ
ብቻ ነበርና። [13]እርሱ ኪዳኑን ይኸውም
እንድትከተሏቸው ያዘዛችሁን ዐሥርቱን
ትእዛ ዛት ዐወጀላችሁ፤ ከዚያም በሁለት
የድንጋይ ጽላቶች ላይ ጻፋቸው፤
[14]ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ በምት ወርሷት ምድር
ውስጥ የምትከተሏቸውን ሥርዐትና ሕግ
እንዳስተምራችሁ በዚያን ጊዜ *እግዚአብሐ
ር* (ያህዌ) አዘዘኝ።

## ጣዖትን ማምለክ ስለ መከልከሉ

[15]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) በኮሬብ ተራራ
ላይ በእሳት ውስጥ በተናገራችሁ ቀን
ምንም
ዐይነት መልክ ኩዮ አላያችሁም፤ ስለዚህ ለራ
ሳችሁ ተጠንቀቁ፤ [16]ይኸውም እንዳትረክሱ፣
በወንድ ወይም በሴት መልክ በማናቸውም
ዐይነት ምስል የተቀረጸ ጣዖት ለራሳችሁ
እንዳታበጁ፣ [17]ወይም በምድር ላይ የሚኖር

3÷22 ዘፀ14÷14፤ ዘዳ1÷29፤7÷18፤ 20÷1፤31÷6፤ 2ዜና32÷8፤መዝ23÷4፤ ኢሳ41÷10
3÷23 ዘዳ1÷37፤ 31÷2፤32÷52፤34÷4
3÷24 ዘፀ8÷10፤ ዘዳ5÷24፤11÷2፤32÷3፤ 8÷10፤2ሳሙ7÷22፤ መዝ71÷16፤106÷2፤ 145÷12፤150÷2
3÷25 ዘዳ1÷7፤ 4÷22፤ኢሱ1÷4፤9÷1፤ 11÷17፤12÷7፤13÷5፤ መሳ3÷3፤9÷15፤ 1ነገ4÷33
3÷26 ቍ27፤ ዘዳ1÷37፤31÷2
3÷27 ቍ26፤ ዘፍ13÷14፤ዘኍ20÷12፤ 21÷20፤27÷120 ዘዳ32÷52
3÷28 ዘኍ27÷18-23፤ ዘዳ31÷7፤ዘዳ1÷38፤ 31÷3፤23
3÷29 ዘኍ23÷28፤ ዘዳ4÷46፤34÷6፤ ኢሱ13÷20
4÷1 ዘሌ18÷4፡5፤ ዘዳ1÷3፤30÷15-20፤ ሮሜ10÷5
4÷2 ዘሌ22÷31፤ ዘዳ10÷12-13፤ 12÷32፤ኢሱ1÷7፤ ምሳ30÷6፤ኤር26÷2፤ መክ12÷13፤ ራእ22÷18-19
4÷3 ዘኍ25÷1-9፤ መዝ106÷28
4÷5 ዘፀ18÷20፤ ዘሌ27÷34፤መዝ71÷17፤1 19÷102፤ኤር32÷33፤ ዕዝ9÷11
4÷6 ዘዳ29÷9፤ 30÷19-20፤32÷46-47፤ 1ነገ2÷3፤መዝ19÷7፤ 119÷98፤ምሳ1÷7፤ ኢዮ1÷1፤28÷28፤ መዝ111÷10፤ ምሳ2÷5፤3÷7፤9÷10፤ መክ12÷13፤ ሕዝ 5÷5፤2ጢሞ3÷15
4÷7 ቍ32-34፤ ዘኍ23÷21፤2ሳሙ7÷2 3፤መዝ46÷1፤ ሐሥ17÷27
4÷8 መዝ89÷14፤ 97÷2፤119÷7፡62፡144 ፡160፡172፤ሮሜ3÷2
4÷9 ዘፍ14÷14፤ 18÷19፤ዘፀ10÷2፤ 23÷13፤ዘዳ6÷20- 25፤ኤፌ6÷4
4÷10 ቍ9፤ዘፀ3÷1፤ 20÷20፤12÷1፤ዘዳ12÷1 ፤14÷23፤ 17÷19፤ 31÷12-13፤ መዝ2÷11፤111÷10፤ 147÷11፤ኢሳ8÷13፤ ኤር32÷40

4÷11 ዘፀ3÷1፤ 19÷9፡17፡18፤መዝ18÷11፤97÷2 4÷12 ዘፀ19÷9፤ 20÷22፤ዘዳ5÷4፡22፤ ዮሐ5÷37፤ማቴ3÷17፤ ዕብ12÷19
4÷13 ዘፀ24÷12፤ ዘዳ9÷9፤ሮሜ9÷4 4÷14 ዘፀ21÷1
4÷15 ዘፀ3÷1፤ኢሱ23÷11፤ኢሳ40÷18፤41÷22-24፤ ሚል2÷15
4÷16 ዘፍ6÷11-12፤ ዘፀ20÷4-5፤ዘዳ9÷12፤ 31÷29፤ 32÷5፤ መሳ2÷19፤ ሮሜ1÷23 4÷17 ሮሜ1÷23

የማናቸውንም እንስሳ ወይም በአየር ላይ
የሚበር የማናቸውንም ወፍ፣ [18]ወይም በደረቱ
የሚሳብ የማናቸውንም ፍጡር ወይም በውሃ
ውስጥ የሚኖር የማናቸውንም ዓሣ ምስል
እንዳታደርጉ ነው:: [19]ወደ ሰማይ ቀና ብለህ
ፀሓይን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን፣ የሰማይ
ሰራዊትንም ሁሉ በምትመለከትበት ጊዜ፣
ወደ እነርሱ እንዳትሳብና እንዳትሰግድላቸው፣
*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ከሰማይ በታች
ላሉ ሕዝቦች ሁሉ ድርሻ አድርጎ የሰጣቸውን
ነገሮች እንዳታመልክ ተጠንቀቅ፤ [20]እናንተን
ግን ልክ ዛሬ እንደ ሆናችሁት ሁሉ ርስቱ
ትሆኑለት ዘንድ፣ *አምላካችሁ* እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) እናንተን ከብረት ማቅለጫ ምድጃ፣
ከግብፅ አውጥቶ አመጣችሁ::

[21]በእናንተም ምክንያት እግዚአብሔር እኔን
ተቈጣኝ፤ የዮርዳኖስንም እንዳልሻገርና *አምላካችሁ*
እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ርስት አድርጎ ወደ
ሚሰጣችሁ ወደ መልካሚቱ ምድር እንዳልገባ
ማለ:: [22]እኔም በዚህች ምድር እሞታለሁ፤
ዮርዳኖስን አልሻገርም፤ እናንተ ግን
ልትሻገሩ ነው፤ ያችንም መልካም ምድር
ትወርሳ ላችሁ:: [23]*አምላካችሁ* እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ከእናንተ ጋር የገባውን ኪዳን
እንዳትረሱ ተጠንቀቁ፤ *አምላካችሁ* እግዚ
አብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) የከለከለውን ጣዖት በ
ማናቸውም ዐይ ነት መልክ ለራሳችሁ አታብ
ጁ:: [24]*አምላ ካችሁ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
የሚባላ እሳት ቀናተኛም አምላክ (ኤሎሂም)
ነውና::

[25]ልጆችንና የልጅ ልጆችን ከወለዳችሁና
በምድሪቱም ላይ ለረጅም ጊዜ ከኖራችሁ
በኋላ ራሳችሁን በማርከስ ማንኛውንም ዐይነት
ጣዖት ብታበጁ፣ *በአምላካችሁም* በእግዚአብሐ
ኔር (ያህዌ ኤሎሂም) ፊት ክፉት በማድረግ
ለቍጣ ብታነሣሡት፣ [26]ዮርዳኖስን ተሻግራ
ችሁ ከምት ወርሷት ምድር ላይ ፈጥናችሁ
እንደምትጠፉ በዚህ ቀን ሰማይንና ምድርን
በእናንተ ላይ ምስክሮች አድርጌ እጠራለሁ፣
በዚያ ቦታ ብዙ ዘመን አትኖሩም፤ ፈጽሞ
ትጠፋላችሁ:: [27]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) እናንተን
በአሕዛብ መካ ከል ይበትናችኋል፤ እግዚአብሔር
በሚበትናችሁ አሕዛብ መካከል
የምትተርፉት ጥቂቶቻ ችሁ ብቻ ናችሁ::
[28]እዚያም፣ ማየት ወይም መስማት ወይም
መብላት ወይም ማሽተት በማይችሉ በሰው
እጅ በተሠሩ የዕንጨትና የድንጋይ አ
ማልክት ታመልካላችሁ:: [29]ነገር ግን እዚያም
ሆናችሁ *አምላካችሁን* እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎ
ሂም) በፍጹም ልባችሁና በፍጹም ነፍሳችሁ
ብትፈልጉት ታገኙታላችሁ:: [30]ስትጨነቅና
ይህ ሁሉ ነገር ሲደርስብህ ያን ጊዜ፣
በኋለኞቹ ዘመናት ወደ አምላክህ ወደ *እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ትመለሳለህ፤ ትታዘዝ ለታ

4፥19 ዘፍ1፥16፤
2፥1፤37፥9፤ዘኍ25፥3፤
ዘዳ13፥5፤17፥3፤
2ነገ23፥11፤ኤር8፥2፤4
3፥13፤ ሕዝ8፥16፤
ኢዮ31፥26፤
ሮሜ1፥25
4፥20 ዘፍ17፥7፤
ዘፀ1፥13፤3፥10፤8፥22፤
34፥9፤ቲቶ2፥14
4፥21 ዘኍ20፥12፤
ዘዳ1፥37
4፥22 ዘኍ27፥13-14፤
ዘዳ3፥25
4፥23 ቍ9፤
ዘፀ20፥4
4፥24 ዘፀ15፥7፤
19፥18፤20፥5፤
ዕብ12፥29
4፥25 ቍ16፥23፤
1ነገ11፥6፤15፥26፤
16፥25፥30፤2ነገ17፥2፥
17፤21፥2
4፥26 ዘፍ31፥50፤
ዘዳ6፥15፤7፥4፤
30፥18-19፤31፥28፤
32፥1፤መዝ50፥4፤
ምሳ14፥5፤ኢሳ1፥2፤
34፥1፤ኤር6፥19፤
ሚክ6፥2፤
4፥27 ዘሌ26፥33፤
ዘዳ28፥36፥64፤29፥28፤1
ነገ8፥46፤2ነገ17፥6፤
መዝ44፥11፤106፥27፤
ኢሳ17፥6፤21፥17፤
ኤር3፥8፤ሚክ1፥16፤
አብ1፥5
4፥28 ዘዳ13፥2፤
28፥36፥64፤29፥17፤
1ሳሙ26፥19፤
መዝ115፥4-8፤
135፥15-18፤
ኢሳ8፥19፤ 26፥14፤
44፥17-20፤
ኤር5፥19፤16፥13፤
ሐሥ19፥26፤ራእ9፥20
4፥29 ዘዳ6፥5፤
30፥1-3፥10፤
1ሳሙ7፥3፤13፥12፤
1ነገ8፥48፤ 2ነገ13፥4፤
2ዜና7፥14፤15፥4፤33፥12፤
መዝ78፥34፤119፥58፤
ኢሳ45፥19፥
22፤55፥6፤ኤር26፥19፤
29፥13፤ ዳን9፥13፤
ሆሴ3፥5፤አሞ5፥4፤
4፥30 ዘሌ26፥41፤
ዘዳ30፥2፤ 31፥17፤
21፥29፤ 1ነገ8፥48፤
ነህ1፥9፤መዝ4፥1፤18፥1፤
46፥1፤59፥16፤ 107፥6፤
ኤር3፥1፥12፥22፤4፥1፤
18፥11፤ 23፥20፤
ሆሴ3፥5፤ኢል2፥12፤
ዕብ1፥2
4፥31 ዘፀ34፥6፤
ዘሌ26፥44፥45፤
ዘዳ31፥6፥8፤ኢሱ1፥5፤
1ነገ8፥57፤1ዜና28፥9፥
20፤ነህ9፥31፤
መዝ9፥10፤27፥9፤
71፥9፤111፥4፤
ኢሳ42፥16፤ዕብ13፥5

ለህም:: [31]*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
*መሐሪ* አምላክ (ኤሎሂም) ነውና፣ አይተውህም
ወይም አያጠፋህም፤ ወይም ደግሞ ለአባቶችህ
በመሐላ ያጸናላቸውን ቃል ኪዳን አይረ
ሳም::

### *እግዚአብሔር* አምላክ ነው

[32]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሰውን በምድር
ላይ ከፈጠረበት ቀን ጀምሮ እናንተ ከመኖ
ራችሁ በፊት ስለ ነበረው የቀድሞ ዘመን
ጠይቁ፤ ከአንዱ የሰማይ ጫፍ እስከ ሌላው
የሰማይ ጫፍ ድረስ ጠይቅ፤ እንደዚህ ያለ
ታላቅ ነገር ከቶ ተደርጎ ወይስ እንደዚህ
ዐይነት ነገር ከቶ ተሰምቶ ያውቃልን?
[33]ከእሳት ውስጥ የእግዚአብሔርን (ኤሎሂም) ድምፅ
እንደ እናንተ የሰማና በሕይወት የኖረ ከቶ
ሌላ ሕዝብ አለን? [34]*አምላካችሁ* እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) በዐይናችሁ እያያችሁ ለእናንተ
በግብፅ እንዳደረገው ሁሉ በፈተና፣ በታምራዊ
ምልክቶችና በድንቆች፣ በጦርነት፣ በጸናች
እጅና በተዘረጋች ክንድ ወይም በታላቅና
በአስፈሪ *ሥራዎች* ከሌላ ሕዝብ መካከል
አንድን ሕዝብ የራሱ ለማድረግ የቻለ አምላክ
አለን?

[35]*እግዚአብሔር* እርሱ አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም)
መሆኑን፣ ከእርሱም በቀር ሌላ አምላክ
አለ መኖሩን ታውቁ ዘንድ እነዚህን ነገሮች
እንድ ታዩ ተደረገ:: [36]ሊገሥጽህ ድምፁን
ከሰማይ እንድትሰማ አደረገ፤ በምድርም ላይ
አስፈሪ እሳቱን አሳየህ፤ ከእሳቱም ውስጥ
ቃሉን ሰማህ:: [37]አባቶችህን ከመውደዱ የተ
ነሣና ከእነርሱም በኋላ ዘራቸውን ስለ መረጠ፣
ከአንተ ጋር በመሆን በታላቅ ኀይሉ ከግብፅ
አወጣህ፤ [38]ዛሬ እንደ ሆነው ሁሉ ከአንተ
ይልቅ ታላቅና ብርቱ የሆኑትን አሕዛብ
ከፊትህ በማስወጣት ወደ ምድራቸው አስገ
ብቶህ ለአንተ ርስት አድርጎ ለመስጠት ነው::

[39]እንግዲህ በላይ በሰማይ፣ በታችም
በምድር *እግዚአብሔር* እርሱ አምላክ (ያህዌ ኤሎ
ሂም) መሆኑን ዛሬ ዕወቅ፤ በልብህም ያዘው፤
ሌላም የለም:: [40]ለአንተና ከአንተም በኋላ
ለልጆችህ መልካም እንዲሆንላችሁ፣ *አምላክህ*
እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ለዘላለም በሚሰጥህም
ምድር ዕድሜህ

4፥32 ቍ7፤ዘፍ1፥27፤ዘዳ28፥64፤30፥1፤ 32፥7፤2ሳሙ7፥23፤
ኢሳ45፥12፤ ኤር9፥16፤ማቴ24፥31 4፥33 ዘፀ20፥22፤ዘዳ5፥24-26
4፥34 ዘፀ3፥20፤ 4፥17፤14፥30፤15፥11፤ ዘዳ5፥15፤6፥21፤7፥19፤
15፥15፤26፥8፤29፥3፤34፥12፤1ዜና16፥12፤መዝ9፥1፤ 40፥5፤45፥4፤
65፥5፤ኢሳ7፥12፤ ኤር32፥20፤ 4፥35 ቍ39፤ ዘፀ8፥10፤ዘዳ7፥9፤
32፥4፥12፤1ሳሙ2፥2፤ 1ነገ8፥60፤2ነገ19፥19፤ኢሳ43፥10፤ማር12፥32
4፥36 ዘፀ19፥19፤ ዘዳ8፥5፤ዕብ12፥25፤
4፥37 ዘፀ3፥20፤ 33፥14፤ ዘዳ7፥8፤10፥15፤23፥5፤33፥3፤
መዝ44፥3፤ኤር31፥3፤ሆሴ11፥1፤ሚል1፥2፤2፥11
4፥38 ዘኍ34፥14-15፤ ዘዳ7፥1፤9፥5 4፥39 ቍ35፤ዘፀ8፥10፤
15፥11 4፥40 ቍ1፤ ዘፍ26፥5፤ዘፀ23፥26፤ ዘሌ22፥31፤ ዘዳ5፥16፥
29፤11፥1፤12፥25፤ መዝ105፥45፤ኢሳ3፥10፤ 48፥18፤ኤፌ6፥2-3

እንዲረዝም፣ ዛሬ እኔ የማዝህን ሥርዐቱንና
ሕግጋቱን ጠብቅ።

### የመማፀኛ ከተሞች

4፥41-43 ማመ - ዘኍ 35፥6-34፤ ዘዳ 19፥1-14፤ ኢሱ 20፥1-9

41በዚያን ጊዜ ሙሴ ከዮርዳኖስ በስተ
ምሥራቅ ሦስት ከተሞችን ለየ፤ 42ይኸውም
የቈየ ጠላትነት ሳይኖር፣ በድንገት ባልጀራ
ውን የገደለ ማናቸውም ሰው ሸሽቶ ከእነዚህ
ከተሞች ወደ አንዲቱ በመሄድ ሕይወቱን
ማትረፍ ይችል ዘንድ ነው። 43ከተሞቹም
በምድረ በዳው በከፍተኛ ቦታ ላይ የም
ትገኘው ቦሶር ለሮቤላውያን፣ በገለዓድ የምት
ገኘው ራሞት ለጋዳውያን፣ በባሳን ያለችው
ጎላን ለምናሴያውያን ነበሩ።

### ስለ ሕጉ የተሰጠ ማብራሪያ

44ሙሴ በእስራኤላውያን ፊት የደነገገው
ሕግ ይህ ነው። 45ከግብፅ በወጡ ጊዜ ሙሴ
ለእስራኤላውያን የሰጣቸው መመሪያዎች፣
ሥርዐቶችና ሕጎች እነዚህ ናቸው፤ 46ይህም
ከግብፅ በወጡ ጊዜ በሙሴና በእስራ
ኤላውያን ድል በተደረገው፣ በሐሴቦን በነገ
ሠው፣ በአሞራውያን ንጉሥ በሴዎን ምድር፣
ከዮር ዳኖስ በስተ ምሥራቅ በቤተ ፌጎር
አጠገብ ባለው ሸለቆ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ
ነው። 47ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ
ያለውን፣ የእር ሱን ምድርና የባሳንን
ንጉሥ የዐግን፣ የሁ ለቱን አሞራውያን
ነገሥታት ምድር ርስት አድርገው ወሰዱ።
48ይህም ምድር በአርኖን ሸለቆ ዳርቻ ካለው
ከአሮዔር አንሥቶ እስከ ሴዎን[ᑎ] ተራራ
ማለትም እስከ አርሞንዔም የሚደርስ ሲ
ሆን፣ 49በዮርዳኖስ ምሥራቅ ያለ ውን ዓረባን
በሙሉና ከፈስጋ ተረተር በታች ያለውን የዓ
ረባ ባሕር[†] ያጠቃልላል።

### ዐሥርቱ ትዕዛዛት

5፥6-21 ተጓ ምብ - ዘፀ 20፥1-17

5 ሙሴ እስራኤልን ሁሉ ጠርቶ እንዲህ
አላቸው፤ “እስራኤል ሆይ፤ በዛሬዋ ዕ
ለት በጆሮአችሁ የምነግራችሁን ሥርዐትና ሕግ
ስሙ፤ አጥኗቸው፤ በጥንቃቄም ጠብቋቸው።
2አምላካ ችን እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በኮሬብ
ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን ገብቶአል። 3እግዚ
አብሔር ይህን ቃል ኪዳን የገባውም
ከአባቶቻችን ጋር ሳይሆን፣ ዛሬ እዚህ በሕ
ይወት ከምንገኘው ከእኛ ከሁላችን ጋር ነው።
4እግዚአብሔር (ያህዌ)እናንተን በተራራው ላይ
በእሳት ውስጥ ሆኖ ፊት ለፊት አነጋገራ
ችሁ። 5እናንተ ግን እሳቱን በመፍራት
ወደ ተራራው ስላል ወጣችሁ፣ በዚያን ጊ
ዜ የእግዚአብሔርን (ያህዌ) ቃል ለእናንተ እነግ
ራችሁ ዘንድ እኔ በእግዚአብሔርና (ያህዌ)
በእናንተ መካከል ቆምሁ፤ እርሱም እንዲህ
አለ፤

6“ከባርነት ምድር፣ ከግብፅ ያወጣሁህ
አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) እኔ
ነኝ።
7“ከእኔ በቀር[‡] ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ።
8በላይ በሰማይ፣ በታች በምድር ላይ፣
ባለው ወይም ከምድር በታች ውሃ ውስጥ
በሚኖር በማንኛውም ዐይነት ምስል
ለራስህ ጣዖትን አታብጅ፤
9እኔ አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)፣ የሚጠ
ሉ ኝን ስለ አባቶቻቸው ኀጢአት እስከ
ሦስ ትና እስከ አራት ትውልድ ድረስ
ልጆቻ ቸውን የምቀጣ ቀናተኛ አምላክ
ነኝና። ለእ ነርሱ አትስገድላቸው፤ ወይም
አታምል ካቸው። 10ለሚወዱኝና
ትእዛዛቴን ለሚጠብቁ ግን እስከ ሺህ
ትውልድ ቸርነትንና ፍቅርን እገልጣለሁ።
11“እግዚአብሔር (ያህዌ) ስሙን በከንቱ የሚያ
ነሣውን ሳይቀጣው አይቀርምና፤
የአምላክህን የእግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም)
ስም በከንቱ አታንሣ።
12“አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
ባዘዘህ መሠረት የሰንበትን ቀን ቀድስህ
አክብ ረው። 13ስድስት ቀን ሥራ፤
ተግባርህንም ሁሉ አከናውን።
14ሰባተኛው ቀን ግን የአምላክህ የእግዚ
አብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ሰንበት ነው። በዚህም
ቀን አንተም ሆንህ ወንድ ወይም ሴት
ልጅህ፣ ወንድ አገልጋይህም ሆነ ሴት
አገልጋይህ በሬህ፣ አህያህ ወይም
ማናቸውም እንስሳህ፣ ወይም ደግሞ
በደጅህ ያለ እንግዳ ምንም ዐይነት ሥ
ራ አትሥሩ። ይህም አንተ እንዳረፍህ
ሁሉ ወንድ አገልጋይህም ሆነ ሴት
አገልጋ ይህ እንዲያርፉ ነው። 15በግብፅ
ሳለህ አንተም ባሪያ እንደ ነበርህ፣ ከዚ
ያም አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በ
ጸናች እጅና በተዘረጋ ክንድ እንዳወጣህ
አስታ ውስ፤ ስለዚህ አምላክህ እግዚአብሐ
ር (ያህዌ ኤሎሂም) የሰንበትን ቀን ታከብረው
ዘንድ አዘዘህ።
16“አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በሚሰጥህ
ምድር ላይ ዕድሜህ እንዲረዝምና መልካም
እንዲሆንልህ፣ አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ
ኤሎሂም) ባዘዘህ መሠረት አባትህንና እናትህን
አክብር።
17“አትግደል።
18“አታመንዝር።
19“አትስረቅ።
20“በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር።
21“የባልንጀራህን ሚስት አትመኝ። በባልን
ጀራህ ቤትም ሆነ በመሬቱ፣ በወንድ ሆነ

4፥42 ዘፀ21፥13
4፥43 ኢሱ21፥38፤ 1ነገ22፥3፤2ነገ8፥28፤9፥14
4፥46 ዘኍ21፥26
4፥48 ዘዳ2፥36፤ 3፥8፤9
5፥1 ዘፀ18፥20
5፥2 ዘፍ17፥9፤ዘፀ 3፥1፤19፥5፤ኤር11፥2፤ ዕብ9፥15፤ 10፥15-17
5፥3 ዘኍ26፥63-65፤ ዘዳ11፥2-7፤ዕብ8፥9
5፥4 ዘኍ14፥14፤ ዘዳ4፥12፤ዘፀ19፥18
5፥5 ዘፍ3፥10፤ ገላ3፥19፤ዕብ12፥18-21
5፥6 ዘፀ13፥3፤ 29፥46፤ዘሌ26፥1፤ ዘዳ6፥4፤መዝ81፥10
5፥8 ዘሌ26፥1፤ ዘዳ4፥15-18፤ መዝ78፥58፤97፥7
5፥9 ዘፀ34፥7፤ ዘኍ26፥11፤10፥35፤ 14፥18
5፥10 ዘፀ34፥7፤ ዘኍ14፥18፤ዘዳ7፥9፤ ነህ1፥5፤ኤር32፥18፤ ዳን9፥4
5፥11 ዘሌ19፥12፤ ዘዳ10፥20፤ መዝ139፥20፤ ማቴ5፥33-37
5፥12 ዘፀ16፥23-30፤ 31፥13-17፤ማር2፥27-28
5፥14 ዘፍ2፥2፤ ኤር17፥21፡24፤ 34፥9-11፤ኢዩ31፥13፤ ማቴ12፥2፤ማር2፥27፤ ዕብ4፥4፤
5፥15 ዘፍ15፥13፤ ዘፀ6፥1፤ዘዳ4፥34፤ መዝ108፥6፤ ኤር32፥21፤
5፥16 ዘፀ21፥17፤ ዘሌ19፥3፤ዘዳ4፥40፤ 11፥9፤ምሳ3፥1-2፤ ሕዝ22፥7፤ሚል1፥6፤ ማቴ15፥4፤19፥19፤ ማር7፥10፤10፥19፤ ሉቃ18፥20፤ኤፌ6፥2-3
5፥17 ዘፍ9፥6፤ ዘሌ24፥17፤መክ3፥3፤አ ር40፥15፤41፥3፤ ማቴ5፥21-22፤ 19፥19፤ማር10፥19፤ ሉቃ18፥20፤ሮሜ 13፥9፤ያዕ2፥11
5፥18 ዘሌ20፥10፤ ማቴ5፥27-30፤ 19፥18፤ማር10፥19፤ ሉቃ18፥20፤ሮሜ13፥9፤ ያዕ2፥11
5፥19 ዘሌ19፥11፤ ማቴ19፥19፤ማር10፥ 19፤ ሉቃ18፥20፤ ሮሜ13፥9
5፥20 ዘፀ23፥1፤ማቴ 19፥18፤ማር10፥19፤ ሉቃ18፥20
5፥21 ሮሜ7፥13፥9

ᑎ48 የዕብራይስጡና የሱርስቱ ትርጒም፣ ሢርዮን ይለዋል (ዘዳ 3፥9 ይመ)
†49 ይኸውም የሙት ባሕር ነው።
‡7 ወይም ፣ ከፊቴ ተብሎ መተርጐም ይችላል።

በሴት አገልጋዩ፣ በበሬውም ሆነ በአህ
ያው ወይም የእርሱ በሆነው ነገር ላይ ዐ
ይ ንህን አትጣል።”
22*እግዚአብሔር* (ያህዌ) በተራራው ላይ በእሳቱ፣
በደመናውና በድቅድቁ ጨለማ ውስጥ ለማ
ኅበራችሁ ሁሉ በከፍተኛ ድምፅ የተናገራ
ችሁ ትእዛዛቱ እነዚህ ናቸው፤ የጨመረውም
ሌላ የለም፤ ትእዛዛቱንም በሁለት የድን
ጋይ ጽላቶች ላይ ጽፎ ሰጠኝ።
23ተራራው በእሳት ሲቃጠል፣ ከጨለማው
ውስጥ ድምፁን በሰማችሁ ጊዜ እናንተ የየነገ
ዶቻችሁ አለቆችና ሽማግሌዎቻችሁም በሙሉ
ወደ እኔ ዘንድ መጣችሁ፤ 24እንዲህም አላችሁ፤
“*አምላካችን* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ክብሩንና
ግርማውን አሳይቶናል፤ ከእሳቱም ውስጥ
ድምፁን ሰምተናል። እግዚአብሔር አነጋግ
ሮትም እንኳ፣ ሰው በሕይወት ሊኖር እንደ
ሚችል በዛሬው ቀን አይተናል። 25ከእንግዲህ
*የአምላካችንን* የእግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) ድምፅ
ብንሰማ እንሞታለን፤ ይህችም ታላቅ እሳት
ፈጽማ ታጠፋናለች፤ ታዲያ ለምን እንሙት?
26ለመሆኑ ከእሳት ውስጥ ሆኖ ሲናገር እኛ
እንደ ሰማነው ሁሉ፣ የሕያው እግዚአብሔርን
(ኤሎሂም) ድምፅ ሰምቶ በሕይወት ለመኖር የቻለ
ከሥጋ ለባሽ ማን አለ? 27አንተ ቅረብ፤ *አምላ
ካችን* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) የሚለውን ሁሉ
አዳምጥ፤ ከዚያም *አምላካችን* እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) የሚነግርህን ሁሉ ንገረን፤ እኛም
እንሰማለን፤ እናደርገዋለንም።”
28ይህን ስትነግሩኝ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሰማ፤
*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) አለኝ፤ “ይህ ሕዝብ ምን
እንዳለህ ሰምቻለሁ፤ ያሉትም ሁሉ መልካም
ነው። 29ታዲያ ለእነርሱም ሆነ ለልጆቻቸው
ለዘላለም መልካም እንዲሆንላቸው፣ እኔን
እንዲፈሩና ሁልጊዜ ትእዛዞቼን ሁሉ እንዲጠ
ብቁ እንደዚህ ያለ ልብ ቢኖራቸው ምናለ!
30ሂደህ ወደየድንኳናቸው እንዲመለሱ ንገራ
ቸው። 31አንተ ግን እንዲወርሷት በምሰጣቸው
ምድር እንዲጠብቋቸው የምታስተምራቸውን
ትእዛዞች፣ ሥርዐቶችና ሕጎች ሁሉ እንድሰጥህ
እዚሁ ከእኔ ዘንድ ቈይ።”
32እንግዲህ *አምላካችሁ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎ
ሂም) ያዘዛችሁን ለመፈጸም ተጠንቀቁ፤ ቀኝም
ግራም አትበሉ። 33በምትወርሷት ምድር በሕ
ይወት ለመኖር እንድትችሉ፣ መልካም እንዲ
ሆንላችሁና ዕድሜያችሁም እንዲረዝም፣
*አምላካችሁ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ባዘዛችሁ
መንገድ ሁሉ ሂዱ።

### *አምላክህን* እግዚአብሔርን ውደድ

6 ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ በምትወርሷት
ምድር እንድትጠብቁት አስተምራችሁ
ዘንድ *አምላካችሁ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
የሰጠኝ ትእ ዛዝ፣ ሥርዐትና ሕግ ይህ ነው፤
2ይኸውም፣ የምሰጣችሁን ሥርዐቱንና
ትእዛዙን ሁሉ በመጠበቅ፣ ዕድሜያችሁ እንዲ
ረዝም፣ አንተ፣ ልጆችህና ከእነርሱ በኋላ
የሚመጡት ልጅ ቻቸው በሕይወት
ዘመናችሁ ሁሉ *አምላ ካችሁን* እግዚአብሔርን
(ያህዌ ኤሎሂም) ትፈሩት ዘንድ ነው። 3እንግዲህ እስ
ራኤል ሆይ ስማ፤ የአባ ቶችህ *አምላክ* እግዚ
አብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በሰጠህ ተስፋ መሠረት፣
ማርና ወተት በምታፈሰው ምድር መልካም
እንዲሆንልህና እጅግ እን ድትበዛ፣
ትእዛዙንም ትጠብቅ ዘንድ ጥንቃቄ አድርግ።
4እስራኤል ሆይ ስማ፤ *አምላካችን* እግዚአብሐ
ኔር (ያህዌ ኤሎሂም) አንድ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ነው¹። 5*አምላክህን* እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም)
በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም
ኀይልህ ውደድ። 6ዛሬ የምሰጥህን እነዚህን
ትእዛዛት በልብህ ያዝ። 7ለልጆችህም አስጠ
ናቸው፤ በቤ ትህ ስትቀመጥ፣ በመንገድም
ስትሄድ፣ ስትተኛና ስትነሣም ስለ እነርሱ
ተናገር። 8በእጅህ ላይ ምልክት አድርገህ
እሰራቸው፤ በግንባርህም ላይ ይሁኑ። 9በቤትህ
መቃኖች በግቢህም በሮች ላይ ጻፋቸው።
10*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
ለአንተ ለመስጠት ለአባቶችህ
ለአብርሃም፣ ለይ ስሐቅና ለያዕቆብ ወደ
ማለላቸው ምድር ሲያስገባህ፣ በዚያም ያልሠ
ራሃቸውን ታላላቅና ያማሩ ከተሞችን፣ 11የራ
ስህ ባልነበሩ መልካም ነገሮች ሁሉ የተሞሉ
ቤቶችን ያልቈፈ ርሃቸውን የውሃ
ጕድጓዶች፣ ያልተከልሃቸ ውን የወይን
ተክሎችና የወይራ ዛፎች ሲሰ ጥህና
በልተህም ስትጠግብ፣ 12ከባርነት ምድር
ከግብፅ ያወጣህን *እግዚአብሔርን* (ያህዌ)
እንዳትረሳ ተጠንቀቅ!
13*አምላክህን* እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) ፍራ፤
እርሱን ብቻ አገልግል፤ በስሙም ማል።
14በዙሪያህ ያሉ ሕዝቦች የሚያመልኳቸውን
ሌሎች አማልክት አትከተል፤ 15ምክንያ
ቱም በመካከልህ ያለው *አምላክህ* እግዚአ
ብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ቀናተኛ አምላክ (ኤሎ
ሂም) ስለ ሆነ፣ በአንተም ላይ ቍጣው
ስለሚነድ፣ ከምድር ገጽ ያጠፋሃል። 16በ
ማሳህ እንዳደረ ጋችሁት *አምላካችሁን* እግዚ
አብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) አት ፈታተኑት።
17*አምላካችሁ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) የሰጣችሁን
ትእዛዞች፣ መመሪያዎችና ሥርዐቶች
በጥንቃቄ ጠብቁ። 18መልካም እንዲሆን ልህና
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ለአባቶችህ በመሐላ

5፥22 ዘፀ20፥21፤ 24፥12
5፥23 ዘፀ3፥16
5፥24 ዘፀ19፥19፤ ዘዳ3፥24፤4፥34፤8፥5፤11፥2፤ ኢሳ53፥4፤
5፥25 ዘፀ20፥18-19፤ ዘዳ18፥16፤ዕብ12፥19
5፥26 ዘፀ33፥20፤ ዘዳ4፥33፤መሳ6፥22-23፤ 13፥22፤ኢሳ6፥5
5፥27 ዘፀ19፥8፤ 24፥7
5፥28 ዘዳ18፥17
5፥29 ቍ33፤ ዘዳ4፥1፡40፤12፥25፤22፥7፤ኢሱ22፥5፤ መዝ78፥7፤81፥8፡13፤
5፥31 ዘፀ24፥12
5፥32 ዘዳ4፥29፤ 10፥12፤17፥11፡20፤ 28፥14፤ኢሱ1፥7፤ 1ነገ15፥5፤2ነገ22፥2፤ ምሳ4፥27
5፥33 ቍ29፤ ኢሳ3፥10፤ኤር7፥23፤ 38፥20፤ሉቃ1፥6፤
6፥2 ዘፍ26፥5፤ ዘፀ20፥12፡20፤ዘዳ4፥9፤ 1ሳሙ12፥24፤
6፥3 ዘፍ15፥5፤ ዘፀ3፥8፤13፥5፤19፥5፤ ዘዳ5፥33፤32፥13-14፤
6፥4 ዘዳ4፥35፡39፤ ነህ9፥6፤መዝ86፥10፤ ኢሳ44፥6፤ዘካ14፥9፤ ማር12፥29፤ ዮሐ10፥30፤1ቆሮ8፥4፤ ኤፌ4፥6፤ያዕ2፥19
6፥5 ዘዳ4፥29፤ 10፥12፤11፥1፡22፤ ኢሱ22፥5፤ 1ሳሙ12፥24፤ ማቴ22፥37፤ ማር12፥30፤ ሉቃ10፥27፤
6፥6 ቍ8፤ዘዳ11፥18፤ 30፥14፤32፥46፤ ምሳ3፥3፤መዝ26፥2፤ 37፥31፤40፥8፤ 119፥11፤ኢሳ51፥7፤ ኤር17፥1፤31፥33፤ ሕዝ40፥4
6፥7 ዘዳ4፥9፤11፥19፤ ምሳ22፥6፣ኤፌ6፥4
6፥8 ቍ6፤ዘፀ13፥9፤ ማቴ23፥5
6፥9 ዘዳ11፥20
6፥10 ዘፍ11፥4፤ ዘዳ12፥29፤19፥1፤ ኢሱ24፥13፤ መዝ105፥44
6፥11 ዘሌ26፥5፤ ዘዳ8፥10፤14፥29፤ 31፥20ኤር2፥13፤
6፥12 ዘዳ4፥9፡23፤ 2ነገ17፥38፤ መዝ44፥17፤78፥7፤ 103፥2፡20፡3፤መዝ33፥8፤
6፥13 ዘፀ20፥7፤ ዘዳ13፥4፤1ሳሙ7፥3፤3
ማቴ4፥10፤5፥33፤ ሉቃ4፥4፡8፤ 6፥15 ዘዳ4፥24፤ 5፥9
6፥16 ዘፀ17፥2፤ማቴ4፥7፤ሉቃ4፥12 6፥17 ዘሌ26፥3፤ ዘዳ11፥22፤ መዝ119፥4፡ 56፡100፡134፡168 6፥18 ዘዳ4፥40፤ 2ነገ18፥6፤ኢሳ 36፥7፤ 38፥3

¹4 ወይም፣ *እግዚአብሔር አምላካችን ነው፤ እግዚአብሔር አንድ ነው ወይም እግዚአብሔር አምላካችን ነው፤ እግዚአብሔር ብቻውን*

እንድትወርሳት፣ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት
ተስፋ የሰጣቸውን መልካሟንቱን ምድር ገብተህ
ቀናና መልካም የሆነውን አድርግ፤ 19*እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) በተናገረው መሠረትም ጠላቶ
ችህን ሁሉ ከፊትህ ታስወጣለህ። 20በሚ
መጡት ዘመናት ልጅህ፣ "*አምላካችን* እግዚ
አብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ያዘዛችሁ የመመሪያዎቹ፣
የሥርዐቶቹና የሕጎቹ ትርጕም ምንድነው?"
ብሎ በሚጠይቅህ ጊዜ፣ 21እንዲህ በለው፤
"እኛ በግብፅ የፈርዖን ባሮች ነበርን፤ *እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ግን በብርቱ እጅ ከግብፅ
አወጣን። 22እኛ በዐይናችን እያየን *እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ታላላቅና አስፈሪ የሆኑ ታም
ራዊ ምልክቶችና ድንቆችን በግብፅ፣ በፈር
ዖንና በመላው ቤተ ሰዎቹ ላይ አደረገ። 23እኛን
ግን ለአባቶቻችን በመሐላ ተስፋ ወደ ሰጣቸው
ምድር ሊያስገባንና ሊሰጠን ከዚያ አወጣን።
24ዛሬ እንደ ሆነው ሁሉ ምን ጊዜም መልካም
እንዲሆንልንና በሕይወት እንድንኖር ይህን
ሥርዐት ሁሉ እንድንፈጽም፣ *አምላካችንንም*
እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) እንድንፈራ *እግዚአ
ብሔር* (ያህዌ) አዘዘን። 25እንግዲህ ይህን ሁሉ
ሕግ እርሱ ባዘዘን መሠረት፣ *በአምላካችን*
በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ፊት ተጠንቅ ቀን ከጠ
በቅን፣ ያ ለእኛ ጽድቃችን ይሆናል።"

### አሕዛብን ማስወጣት

7 *አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ልትወርሳት
ወደምትገባባት ምድር በሚያመጣህና
ብዙዎችን፣ ከአንተ የሚበልጡ ታላላቆችና
ብርቱዎች የሆኑትን ሰባቱን አሕዛብ፦ ኬጢ
ያውያንን፤ ጌርጌሳውያንን፣ አሞራውያንን፣ ከነዓ
ናውያንን፣ ፌርዛውያንን፣ ኤዊያውያንንና ኢ
ያቡሳውያንን ከፊትህ በሚያስወጣቸው ጊዜ፣
2*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በእጅህ አሳልፎ
በሰጠህና አንተም ድል ባደረግሃቸው ጊዜ፣
ሁሉንም ፈጽመህ ደምስሳቸው[ነ]፤ ከእነርሱ
ጋር አትዋዋል፤ አትራራላቸውም። 3ከእነርሱ
ጋር ጋብቻ አታድርግ፤ ሴት ልጆችህን
ለወንድ ልጆቻቸው አትስጥ፤ ወይም
ለወንድ ልጆችህ ሴት ልጆቻቸውን
አታምጣ፤ 4ምክንያቱም እኔን ከመከተል
ልጆችህን መልሰው ሌሎችን አማልክት
እንዲያመልኩ ስለሚያደርጉና ከዚህም የተነሣ
*የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ቍጣ በላይህ ነዶ፣ ፈጥኖ
ስለሚያጠፋህ ነው። 5እንግዲህ በእነርሱ ላይ
የምታደርጉት ይህ ነው፤ መሠ ዊያዎቻቸውን
አፈራርሱ፤ የማምለኪያ ዐምዶቻ ቸውን[ኘ]
ሰባብሩ፤ የአሼራ ምስል ዐምዶቻቸውን ቍረጡ፤
ጣዖቶቻቸውንም በእሳት አቃጥሉ። 6አንተ
*ለአምላክህ* ለእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ቅዱስ
ሕዝብ ስለ ሆንህ፣ *አምላክህ* እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) የራሱ ሕዝብ፣ ርስትም እንድት
ሆንለት በምድር ላይ ከሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ
*መረጠህ*።
7*እግዚአብሔር* (ያህዌ) እናንተን የወደዳችሁና
የመረጣችሁ ከሌሎች ሕዝቦች በቍጥር
ስለ በዛችሁ አይደለም፤ ቍጥራችሁማ ከሕ
ዝቦች ሁሉ እጅግ አነስተኛ ነበር። 8ነገር
ግን እናንተን በብርቱ እጅ ያወጣችሁ፣
ከባርነት ምድርና ከግብፅ ንጉሥ ከፈርዖን
መዳፍ የተቤዣችሁ፣ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
እናንተን ስለ ወደዳችሁና ለአባቶቻችሁ የማ
ለላቸውን መሐላ ስለ ጠበቀ ነው። 9ስለዚ
ህም *አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) አምላክ
(ኤሎሂም) መሆኑን ዕወቅ፤ እርሱ ለሚወዱትና
ትእዛዞቹን ለሚጠብቁት የፍቅሩን ኪዳን
እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ የሚጠብቅ ታማኝ
አምላክ (ኤሎሂም) ነው። 10ነገር ግን፣ የሚጠ
ሉትን
ዐይናቸው እያየ ይበቀላቸዋል፤ የሚጠሉትን
ዐይናቸው እያየ ለመበቀል አይዘገይም።
11ስለዚህ በዛሬው ቀን የምሰጥህን ትእዛዙን፣
ሥርዐቱንና ሕግጋቱን ለመከተል ጥንቃቄ
አድርግ።
12እነዚህን ሕግጋት ብታዳምጥና በጥንቃቄ
ብትጠብቃቸው፣ *አምላክህ* እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ለአባቶችህ እንደ ማለላቸው ከአንተ
ጋር የገባውን የፍቅር ኪዳኑን ይጠብቃል።
13ይወ ድሃል፤ ይባርክሃል፤ ያበዛሃልም።
ለአንተ ለመስጠት ለአባቶችህ በ
ማለላቸው ምድር የማሕፀንህን ፍሬ፣
የምድርህን ሰብል፦ እህልህን፣ አዲሱን
ወይንና ዘይት፤ የከ ብት መንጋህን
ጥጆች፣ የበግና የፍየል መንጋህን
ግልገሎች ይባርካል። 14ከሕዝቦች ሁሉ
የበለጠ አንተ ትባረካለህ፤ ከአንተ ወይም
ከከብቶችህ መካከል የማይወልድ ወንድ ወይም
ሴት አይኖርም። 15*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ከማና
ቸውንም በሽታ ነጻ ያደርግሃል፤ በግብፅ የምታ
ውቃቸውን እነዚያን አሠቃቂ በሽታዎች
በሚጠሉህ ሁሉ ላይ እንጂ፣ በአንተ ላይ
አያመጣብህም። 16*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ
ኤሎሂም) በእጅህ አሳልፎ የሚሰጥህን ሕዝቦች
ሁሉ ማጥፋት አለብህ፤ አትዘንላቸው፤ ወጥ
መድ ስለሚሆኑብህም አማልክታቸውን አታ
ምልክ።
17"እነዚህ አሕዛብ ከእኛ ይልቅ ጠንካ
ሮች ስለ ሆኑ፣ እንዴት አድርገን እናስወ
ጣቸዋለን?" ብለህ በልብህ ታስብ ይሆናል።
18ነገር ግን አትፍራቸው፤ *አምላክህ* እግዚ
አብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በፈርዖንና በግብፅ ሁሉ ላይ

4፥9፤ኤር44፥10፤
6፥19 ዘፀ23፥27፤ ኢ
ሱ21፥44፤
መዝ78፥53፤107፥2፤1
36፥24
6፥20 ዘፀ10፥2
6፥21 ዘዳ4፥34
6፥24 ዘዳ10፥12፤
30፥6፤መዝ27፥12፤
41፥2፤86፥11፤
ኤር32፥39፤ሮሜ10፥5
6፥25 ዘዳ24፥13፤
መዝ103፥18፤119፥34፡
55፤ሮሜ9፥31
7፥1 ዘፍ10፥16፡
17፤13፥7፤15፥20፤
ዘሌ14፥34፤ዘዳ1፥7፤
4፥38፤20፥16-18፤
31፥3፤ኢሱ3፥10
7፥2 ቍ16፤
ዘፀ23፥32፤ዘኍ31፥17፤
ዘዳ2፥33፡34፤13፥8፤
19፥13፤25፥12፤
33፥27፤ኢሱ11፥11፤
7፥3 ዘፀ34፥15-16፤
ኢሱ22፥16፤ዳን9፥7
7፥4 ዘዳ4፥26፤
መሳ3፥6፤
7፥5 ዘፀ23፥24፤
34፥13ዘዳ16፥21፤
7፥6 ዘፍ17፥7፤
ዘፀ8፥22፤19፥6፤34፥9፤
ዘሌ27፥30፤ዘዳ14፥2፤2
6፥19፤1ነገ3፥8፤
መዝ30፥4፤37፥28፤
50፥5፤52፥9፤
ኢሳ41፥9፤43፥1፤
ሕዝ20፥5፤ሮሜ9፥4፤
ቲቶ2፥14
7፥7 ዘፍ22፥17፤
34፥30፤ ዘዳ4፥37፤
10፥22
7፥8 ዘፀ3፥20፤6፥6፤
13፥14፤32፥13፤
ዘኍ14፥8፤ዘዳ4፥37፤
1ነገ10፥9፤2ዜና2፥11፤
መዝ44፥3፤ሮሜ11፥28፤
7፥9 ቍ12፤
ዘፀ20፥6፤ዘዳ4፥35፤
5፥10፤1ነገ8፥23፤
2ዜና6፥14፤ነህ1፥5፤
9፥32፤መዝ18፥25፤
33፥4፤108፥4፤
145፥13፤146፥6፤
ኢሳ49፥7፤ኤር42፥5፤
ሆሴ11፥12፤1ቆሮ1፥9
7፥10 ዘሌ26፥28፤
ዘኍ10፥35፤ናሆ1፥2
7፥12 ዘሌ26፥3-13፤
ዘዳ28፥1-14፤
መዝ105፥8-9፤
ሚክ7፥20
7፥13 ዘፍ17፥6፤
27፥28፤49፥25፤ዘፀ
1፥7፤ዘዳ1፥10፤13፥17፤
28፥4፤
30፥5፤ዘኍ18፥12፤
መዝ11፥5፤107፥38፤1
46፥8፤ምሳ15፥9፤
ኢሳ51፥1፤ዮሐ14፥21
7፥14 ዘፀ23፥26
7፥15 ዘፀ9፥9፤
15፥26፤23፥25፤
ዘዳ30፥8-10

7፥16 ቍ2፤24፤ ቍ25፤ዘፀ10፥7፤ ኢሱ6፥2፤10፥26፤ መሳ3፥6፤
ዕዝ9፥1፤ መዝ106፥36፤ 7፥17 ዘኍ33፥53
7፥18 ዘኍ14፥9፤ ዘዳ1፥21፡29፤ መዝ105፥5፤119፥52

[ነ]2 በዚህና በቍጥር 26 ላይ የዕብራይስጡ ቃል አንድን ነገር ወይም አንድን ሰው ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠትን የሚያሳይ ነው።
[ኘ]5 በዚህ መጽሐፍም ሆነ በሌላ ስፍራ ይህ የአሼራን ምስል ዐምድ የሚያመለክት ነው።

ያደረገውን በሚገባ አስታውስ። 19 ታላላቅ
ፈተናዎችን፣ ታምራዊ ምልክቶችንና ድንቅ
ነገሮችን አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
አንተን ያወጣበትን ብርቱ እጅና የተዘረጋች
ክንድ በገዛ ዐይንህ አይተሃል። አምላክህ እግዚ
አብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) አሁን በምትፈራቸው ሕ
ዝቦች ሁሉ ላይ ያንኑ ያደርጋል። 20 ይልቀ
ንም አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በሕይወት
ተርፈው፣ ከአንተ የተደበቁት እንኳ እስኪጠፉ
ድረስ በመካከላቸው ተርብ ይሰድባቸዋል።
21 በመካከልህ ያለው አምላክህ እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ታላቅና የሚያስፈራ አምላክ (ኤሎሂም)
ስለ ሆነ አያስደንግጡህ። 22 አምላክህ እግዚአብሐ
ር (ያህዌ ኤሎሂም) እነዚህን ሕዝቦች ጥቂት
በጥቂት ከፊትህ ያስወጣቸዋል፤ የዱር አራዊቱ
ቍጥር በአካባቢህ እንዳይበራከት ሁሉንም
በአንድ ጊዜ ማጥፋት አይፈቀድልህም፤
23 አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ግን እስኪጠ
ፉ ድረስ ከባድ ትርምስ ፈጥሮባቸው
በእጅህ አሳልፎ ይሰጥሃል። 24 ነገሥታታቸውን
በእጅህ ይጥላቸዋል፤ ስማቸውንም ከሰማይ
በታች ታጠፋለህ። እስክ ትደመስሳቸው ድረስ፣
አንተን መቋቋም የሚችል አንድም ሰው የለም።
25 የአማልክታቸውን ምስ ሎች በእሳት
አቃጥል፤ በላያቸው የሚገኘውን ብርና ወርቅ
አትመኝ፤ ለራስህ አታድርግ፤ አለበለዚያ
በአምላክህ በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ዘንድ አስ
ጸያፊ ስለ ሆነ፣ ያሰናክልሃል። 26 አስጸያፊ
ነገርን ወደ ቤትህ ወይም ወደ ራስህ
አታምጣ፤ አለበለዚያ አንተም እንደ እርሱ
ለጥፋት ትዳረጋለህ፤ ፈጽመህ ጥላው፤ ተጸየፈ
ውም፤ ለጥፋት የተለየ ነውና።

## እግዚአብሔርን አትርሳ

8 በሕይወት እንድትኖሩ፣ እንድትበዙና እግዚ
አብሔር (ያህዌ) ለአባቶቻችሁ በመሐላ ተስፋ
የገባላቸውን ምድር ገብታችሁ እንድትወ
ርሱ፣ ዛሬ እኔ የምሰጥህን እያንዳንዱን ትእዛዝ
ለመከተል ጥንቃቄ አድርጉ። 2 አምላክህ እግ
ዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ትእዛዞቹን መጠበቅህ
ንና በልብህ ያለውን ለማወቅ፣ ትሑት ሊያደ
ርግህና ሊፈትንህ በእነዚህ አርባ ዓመታት
በዚህ ምድረ በዳ ጕዞህ ሁሉ እንዴት እንደ
መራህ አስታውስ። 3 ሰው ከእግዚአብሔር
(ያህዌ) አፍ በሚወጣው በእያንዳንዱ ቃል
እንጂ፣ በእንጀራ ብቻ እንደማይኖር ሊያስ
ተምርህ አስራበህ፤ አንተም ሆንህ አባቶችህ
የማታውቁትን መና መገበህ፤ 4 በእነዚህ አርባ
ዓመታት ውስጥ ልብስህ አላለቀም፤ እግ
ርህም አላበጠም። 5 ስለዚህ ሰው ልጁን እን
ደሚቀጣ፣ አምላክህ እግዚአብሔርም (ያህዌ ኤሎ
ሂም) አንተን እንደሚቀጣህ በልብህ ዕወቅ።
6 በመንገዶቹ በመሄድና እርሱንም በማክበር፣
የአምላክህን የእግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) ትእዛዞች
ጠብቅ። 7 አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
ጅረቶችና የኵሬ ውሃ ወዳለበት፣
ምንጮች ከየሸለቆውና ከየኰረብታው
ወደሚፈሱበት ወደ መልካሚቱ ምድር
ያገባል፤ 8 ስንዴና ገብስ፣ ወይንና የበለስ
ዛፎች፣ሮማን፣ የወይራ ዘይትና ማር
የሚገኝባት ምድር፤ 9 ምንም ነገር የ
ማይታጣባት፣ የዳቦም ዕጦት የሌለባት፣ ዐ
ለቶች ብረት የሆኑባት፣ ከኰረ ብቶቿም
መዳብ ቈፍረህ ልታወጣ የምትች ልባት
ምድር ናት።
10 በልተህ በምትጠግብበት ጊዜ እንዲህ
ያለች መልካም ምድር ስለ ሰጠህ አምላክህን
እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) ባርከው። 11 በዛሬዪቱ
ዕለት የምሰጥህን ትእዛዙን፣ ሕጉንና
ሥርዐቱን ባለመጠበቅ አምላክህን እግዚአብሔርን
(ያህዌ ኤሎሂም) እንዳትረሳው ተጠንቀቅ። 12 አለበ
ለዚያ በልተህ ስትጠግብና ጥሩ ጥሩ ቤቶችን
ሠርተህ መኖር ስትጀምር፣ 13 ደግሞም የከ
ብት፣ የበግና የፍየል መንጋህ ሲበዛ፣ ብር
ህና ወርቅህ ሲበረክት፣ ያለህም ሁሉ በላይ
በላዩ እየጨመረ ሲሄድ፣ 14 ልብህ ይታበይና
ከባርነት ምድር፣ ከግብፅ ያወጣህን አምላ
ክህን እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) ትረሳለህ። 15 በዚያ
ጭልጥ ባለና አስፈሪ ምድረ በዳ፣ በዚያ
በሚያስጠማና ውሃ በማይገኝበት ደረቅ
መሬት፣ መርዘኛ እባብና ጊንጥ ባለበት ምድረ
በዳ መራህ፤ ከጭኑ ዐለትም ውሃ
አፈለቀልህ። 16 በመጨረሻ መልካም እንዲ
ሆንልህ፣ አንተን ትሑት ለማድረግና
ለመፈተን፣ አባቶችህ ፈጽሞ የማያውቁትን
መና በምድረ በዳ መገበህ። 17 ምናልባትም፣
“ይህን ሀብት ያፈራሁት በጕልበቴና
በእጄ ብርታት ነው” ብለህ በልብህ ታስብ
ይሆናል። 18 ነገር ግን ሀብት እንድታፈራ
ችሎታ የሰጠህ፣ ለአባቶችህም በመሐላ
የገባውን ኪዳን ያጸናልህ እርሱ ስለ ሆነ፣
አምላክህን እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም)
አስበው።
19 አምላክህን እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም)
ብትረሳና ሌሎችን አማልክት ብትከተል፣ ብታ
መልክና ለእነርሱ ብትሰግድላቸው በእርግጥ
እንደምትጠፉ ዛሬ እመሰክርባችኋለሁ። 20 እግዚ
አብሔር (ያህዌ) ከፊታችሁ ያሉትን አሕዛብ
እንዳጠፋቸው ሁሉ፣ ለአምላካችሁ ለእግዚ
አብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ባለመታዘዛችሁ እናንተም
ትጠፋላችሁ።

7፥19 ዘዳ4፥34፤ መዝ136፥12፤
7፥20 ዘፀ23፥28
7፥21 ዘፍ17፥7፤ ዳን10፥17፤ ኢሱ3፥10፤ነህ1፥5፤ 9፥32፤መዝ47፥2፤ 66፥3፤68፥35፤ ኢሳ9፥6፤ዳን9፥4
7፥22 ዘፀ23፥28-30
7፥23 ዘፀ23፥27፤ ኢሱ10፥10
7፥24 ቊ16፤ ዘፀ23፥31፤ዘዳ11፥25፤ ኢሱ1፥5፤10፥8፡24፤ 21፥44፤23፥9፤ መዝ110፥5
7፥25 ቊ16፤ ዘፀ4፥14፤20፥17፤ 32፥20፤ዘዳ17፥1፤ ኢሱ7፥21፤
7፥26 ዘሌ27፥28-29
8፥1 ዘፀ19፥5፤ ዘዳ4፥1፤ኢዩ36፥11፤ መዝ16፥11፤ሕዝ20፥19
8፥2 ዘፍ22፥1፤ ዘዳ29፥5፤መዝ136፥16፤ አሞ2፥10፤
8፥3 ቊ9፤ ዘፍ3፥19፤ ዘፀ16፥2-3፡4፤ 1ነገ8፥36፤2ዜና36፥12፤ ኢዩ22፥22፤23፥12፤ መዝ25፥5፤44፥9፤ 94፥12፤104፥15፤ 119፥13፡171፤ 138፥4፤ምሳ18፥12፤ 28፥21፤ኢሳ2፥11፤ 51፥14፤ኤር42፥14፤ 44፥10፤ማቴ4፥4፤ ሉቃ4፥4
8፥4 ዘዳ29፥5፤ ነህ9፥21
8፥5 ዘዳ4፥36፤2 ሳሙ7፥14፤ኢዩ5፥17፤ 33፥19፥ምሳ3፥11-12፤ ዕብ12፥5-11፤ ራ እ3፥19
8፥6 ዘፀ33፥13፤ ዘዳ5፥33፤1ነገ3፥14፤ መዝ81፥13፤ 95፥10
8፥7 ዘዳ11፥9-12፤ መዝ106፥24፤ ኤር2፥7፤ 3፥19፤ ሕዝ20፥6፤
8፥8 ዘፍ49፥11፤ ዘፀ9፥31፤ዘኍ13፥23፤ ዘዳ32፥13፤ 1ነገ4፥25፤ መዝ81፥16
8፥9 ቊ3፤ መሳ18፥10፤ ኢዩ28፥2
8፥10 ዘዳ6፥10-12
8፥11 ዘዳ4፥9
8፥12 ምሳ30፥9፤ ሆሴ13፥6
8፥14 ቊ11፤ መዝ78፥7፤106፥21

8፥15 ዘፀ17፥6፤ ዘኍ21፥6፤ዘዳ1፥19፤32፥10፤32፥13፤ኢዩ28፥9፤ መዝ78፥15፤114፥8፤ኢሳ14፥29፤ 30፥6፤ 8፥16 ዘፍ22፥1፤ ዘፀ 16፥14፡15 8፥17 ዘዳ9፥4፡7፡24፤31፥27፤ መሳ7፥2፤መዝ44፥3፤ ኢሳ10፥13 8፥18 ዘፍ26፥13፤ ዘዳ26፥10፤ 28፥4፤ 1ሳሙ2፥7፤ መዝ25፥13፤112፥3፤ምሳ8፥18፤ 10፥22፤ መክ9፥11፤ ሆሴ2፥8፤
8፥19 ዘዳ6፥14፤ ዘዳ4፥26፤30፥18፤ መዝ16፥4፤ኤር7፥6፤13፥10፤25፥6
8፥20 2ነገ21፥2፤ መዝ10፥16፤ሕዝ5፥5-17

## የሕዝቡ አለመታዘዝ

**9** እስራኤል ሆይ፣ ስማ፤ ሰማይ ጠቀስ
ቅጥር ያላቸው ታላላቅ ከተሞች ያሏቸ
ውን፣ ከአንተ ይልቅ ታላቅና ብርቱ፣ የሆ
ኑትን አሕዛብ አስለቅቀህ ለመግባት ዮርዳ
ኖስን አሁን ትሻገራለህ። 2ዔናቃውያን
ብርቱና ቁመተ ረጃጅም ሕዝቦች ናቸው፤
ስለ እነርሱ ታውቃለህ፤ "ዔናቃውያንን ማን
ሊቋቋማቸው ይችላል?" ሲባልም ሰምተሃል።
3ይሁን እንጂ እንደሚባላ እሳት ከፊትህ
ቀድሞ የሚሻገረው *አምላክህ* እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) መሆኑን ዛሬ እርግጠኛ ሁን፤
እነርሱን ያጠፋቸዋል፤ በፊትህም ድል
ያደርጋቸዋል፤ አንተም *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
በሰጠህ ተስፋ መሠረት ታስወጣቸዋለህ፤
በፍጥነትም ትደመ ስሳቸዋለህ።
4*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) እነርሱን
ከፊትህ ካስወጣቸው በኋላ፣ "ይህችን ምድር
እንድወርስ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ወደዚህ ያመ
ጣኝ፣ ከጽድቄ የተነሣ ነው" ብለህ በልብህ
አታስብ። በዚህ አይደለም፤ እነዚህን አሕዛብ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ከፊትህ የሚያሳድዳቸው በክፉ
ታቸው ምክንያት ነው። 5ምድራቸውን ገብተህ
የምትወርሳት ከጽድቅህ ወይም ከልብህ ቅንነት
የተነሣ ሳይሆን፣ ለአባቶችህ ለአብርሃም፣
ለይስሐቅና ለያዕቆብ የማለላቸውን ቃል
ለመፈጸም *አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
እነዚህን አሕዛብ ከክፋታቸው የተነሣ ከፊትህ
ስለሚያባርራቸው ነው። 6ስለዚህ *አምላክህ*
እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ይህችን መልካም
ምድር እንድትወርሳት የሚሰጥህ ከጽድቅህ
የተነሣ አለመሆኑን አስተውል፤ አንተ ዐንገተ
ደንዳና ነህና።

## የወርቁ ጥጃ

7*አምላክህን* እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) በምድረ
በዳ እንዴት እንዳስቈጣኸው አስታውስ፤
ከቶም አትርሳ። ከግብፅ ከወጣህበት ዕለት
አንሥቶ እዚህ ቦታ እስከ ደረስህበት ጊዜ
*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ላይ እንዳመፅህ ነህ።
8በኮሬብ *እግዚአብሔርን* (ያህዌ) ለቍጣ አነ
ሣሣችሁት፤ እርሱም እናንተን ሊያጠ
ፋችሁ እጅግ ተቈጣ። 9እኔም የድንጋይ
ጽላቶቹን፣ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ከእናንተ ጋር
የገባውን የኪዳን ጽላቶች ለመቀበል ወደ ተ
ራራው በወጣሁ ጊዜ፣ እህል ሳልበላ፣ ውሃም
ሳልጠጣ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ቈየሁ፤
10*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ጣት የተጻፈባቸውን ሁለት
የድንጋይ ጽላቶች *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሰጠኝ፤
በተከበባችሁበት ዕለት *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ከተራራው ላይ፣ በእሳት ውስጥ ሆኖ
ለእናንተ የነገራችሁ ትእዛዛት ሁሉ በእነርሱ
ላይ ነበሩባቸው።
11አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከተፈጸመ በኋላ፣
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሁለቱን የድንጋይ
ጽላቶች ማለትም የኪዳኑን ጽላቶች ሰጠ
ኝ። 12ከዚያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ)፣ "ተነሣ፤
ከግብፅ ያወ ጣሃቸው ሕዝብህ ረክሰዋልና
ፈጥነህ ከዚህ ውረድ፤ እኔ ካዘዝኋቸው
ፈጥነው ፈቀቅ ብለዋል፤ ቀልጦ የተሠራ
ጣዖትም ለራሳቸው አበጅተዋል" ብሎ
ነገረኝ።
13ደግሞም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) እንዲህ
አለኝ፤ "ይህን ሕዝብ አይቼዋለሁ፤ በእርግጥ
ዐንገተ ደንዳና ሕዝብ ነው፣ 14አጠፋቸውና
ስማቸውንም ከሰማይ በታች እደመስሰው
ዘንድ ተወኝ፤ አንተንም ከእነርሱ ይልቅ
ብርቱና ብዙ ሕዝብ አደርግሃለሁ።"
15ስለዚህ ተራራው በእሳት እየተቀጣጠለ
ሳለ፣ ሁለቱን የቃል ኪዳን ጽላቶች በሁለተ
ም እጆቼ እንደያዝሁ[a] ከተራራው
ተመልሼ ወረድሁ። 16በእርግጥ
*በአምላካችሁ* በእግዚአ ብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ላይ
ኀጢአት ሠርታችሁ እንደ ነበር
ተመለከትሁ፤ ቀልጦ የተሠራ የጥጃ
ምስልም ለራሳችሁ አበጃችሁ፤ *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) እናንተን ካዘዛችሁ መንገድ በፍጥነት
ወጥታችሁ ነበር። 17ስለዚህ ሁለቱን ጽላቶች
ወስጄ ከእጆቼ አሽቀንጥሬ በፊታችሁ ሰባ
በርኋቸው።
18ከዚያም *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት
ክፉ ነገርን በመፈጸም ለቍጣ እንዲነሣሣ
የሚያደርገውን ኀጢአት ሁሉ ስለ ሠራ
ችሁ፣ እህል ውሃ ሳልቀምስ አርባ ቀንና
አርባ ሌሊት እንደ ገና *በእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ፊት በግምባሬ ተደፋሁ። 19እናንተን ሊያጠ
ፋችሁ ክፉኛ ተቈጥቶ ነበርና፣ እኔም *የእ
ግዚአብሔርን* (ያህዌ) ቍጣና መዓት ፈራሁ፤
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ግን እንደ ገና ሰማኝ።
20*እግዚአብሔር* (ያህዌ) አሮንን ሊያጠፋው
ክፉኛ ተቈጥቶ ነበር፤ በዚያን ጊዜ ለአሮንም
ጸለይሁ። 21ደግሞም ያን የኀጢአት ሥራችሁን፣
አበጅታችሁት የነበረውን ጥጃ ወስጄ፣ በእሳት
አቃጠልሁት፤ ከዚያም ሰባብሬ እንደ ትቢያ
ዱቄት እስኪሆን ድረስ ፈጭቼ ከተራራው
በሚወርደው ጅረት ውስጥ በተንሁት።
22በተቤራም፣ በማሳህና በቂብሮት ሐታአዋ
*እግዚአብሔርን* (ያህዌ) አስቈጣሁት።
23*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ከቃዴስ በርኔ ባስ
ወጣችሁ ጊዜ፣ "ውጡ፤ የሰጠኋችሁንም ምድር፣
ርስት አድርጋችሁ ውረሷት" አላችሁ። እናንተ
ግን *በአምላካችሁ* በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
ትእዛዝ ላይ ዐመፃችሁ፤ እርሱን አልታመና
ችሁበትም፤ አልታዘዛችሁትም።

[a]15 ወይም፣ *ሁለቱም የቃል ኪዳን ጽላቶች ከእኔ ጋር ነበሩ፤ አንዱም በአንዱ፣ ሌላውም በሌላው እጄ ነበር* ተብሎ መተርጐም ይችላል።

9፥1 ዘፍ11፥4፤ ዘኍ13፥28፤35፥10፤ ዘዳ4፥38፤
9፥2 ዘኍ13፥22፤ ኢ ሱ11፥22
9፥3 ዘፀ15፥7፤ 19፥18፤23፥31፤ ዘዳ31፥3፤ኢሱ3፥11፤ ዕብ12፥29
9፥4 ዘፀ23፥24፤ ዘዳ8፥17፤18፥9-14፤ ዘሌ18፥21፡24-30፤ 2ነገ16፥3፤17፥8፤ 21፥2፤ዕዝ9፥11፤
9፥5 ዘፍ12፥7፤ ዘዳ4፥38፤11፥23፤ ዘዳ18፥9፤ዘሌ18፥25፤ ሕዝ36፥32፤ኤፌ2፥9
9፥6 ዘፀ32፥9፤ ሐሥ7፥51
9፥7 ዘኍ11፥33፤ ዘፀ14፥11፤23፥21
9፥8 ዘፀ32፥7-10፤ ዘኍ16፥46፤ 1ሳሙ28፥18፤ ዕዝ9፥14፤ኢዩ20፥28፤ መዝ2፥12፤7፥11፤ 69፥24፤110፥5፤ ኢሳ9፥19፤ ሕዝ20፥13፤
9፥9 ዘፍ7፥4፤ ዘፀ24፥12፤ዘዳ4፥13፤
9፥10 ዘፀ31፥18፤ ዘዳ10፥4፤18፥16
9፥11 ዘፍ7፥4፤ ዘፀ24፥12
9፥12 ዘዳ4፥16፤ መሳ2፥17
9፥13 ቍ6፤ ዘዳ10፥16
9፥14 ዘፀ32፥10፤ ዘኍ14፥12፤ኤር7፥16
9፥15 ዘፀ32፥15
9፥16 ዘፀ32፥4
9፥18 ቍ9፤ ዘፀ32፥31፤ዘዳ34፥28
9፥19 ቍ26፤ ዘፀ32፥14፤34፥10፤ ዘኍ11፥2፤1ሳሙ7፥9፤ ኤር15፥1ዕብ12፥21፤
9፥21 ዘፀ32፥20፤ መዝ18፥42፤ ኢሳ2፥18፤29፥5፤ 40፥12፤ሚክ1፥7
9፥22 ዘፀ17፥7፤ ዘኍ1፥53፤11፥3፡34፤
9፥23 ዘኍ14፥9፤ ዘዳ1፥2፡21፡32፤ መዝ106፥24

24እኔ እናንተን ካወቅኋችሁ ጊዜ ጀምሮ፣
በእግዚአብሔር (ያህዌ) ላይ እንዳመፃችሁ ናችሁ።
25እግዚአብሔር (ያህዌ) እናንተን እንደሚ
ያጠፋችሁ ተናግሮ ስለ ነበር፣ በእነዚያ
አርባ ቀናትና አርባ ሌሊቶች በእግዚአብሐ
ር ፊት በግንባሬ ተደፋሁ፤ 26እንዲህም በ
ማለት ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ) ጸለይሁ፤
“ጌታ እግዚ አብሔር ሆይ (አዶናይ ያህዌ) በታላቅ
ኀይልህ የተቤ ዠኸውንና በኀያል ክንድህ
ከግብፅ ያወጣኸውን፣ ያንተ ርስት የሆነውን ሕ
ዝብህን አታጥፋ። 27ባሪያዎችህን አብርሃምን፣
ይስሐቅንና ያዕቆብን አስብ፤ የዚህን ሕዝብ
ልበ ደንዳናነት፣ ክፋትና ኀጢአት
አትመልከት። 28አለበለ ዚያ እኛን
ካመጣህበት ምድር ያሉ ሰዎች ‘እግዚአብሐ
ር (ያህዌ) ተስፋ ወደ ሰጣቸው ምድር ሊ
ያገባቸው ስላልቻለና ስለጠላቸው፤ በምድረ
በዳ ሊገድላቸው አወጣቸው ይላሉ።’ 29ነገር
ግን እነርሱ በታላቅ ኀይልህና በተዘረጋች
ክንድህ ያወጣሃቸው ሕዝብህና ርስትህ ናቸው።”

## በድጋሚ የተሰጡ የመጀመሪያዎቹ ዐይነት ጽላቶች

10 በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር (ያህዌ) እንዲህ
አለኝ፤ “እንደ መጀመሪያዎቹ ያሉ
ሁለት የድንጋይ ጽላቶች ቀርጸህ ወደ እኔ
ወደ ተራራው ላይ ውጣ፤ ታቦትም ከዕን
ጨት ሥራ። 2እኔም አንተ በሰበርሃቸው
በፊተኞቹ ጽላቶች ላይ የነበሩትን ቃላት
በእነዚህኞቹ ጽላቶች ላይ እጽፋቸዋለሁ፤ አን
ተም በታቦቱ ውስጥ ታኖራቸዋለህ።”
3ስለዚህ ከግራር ዕንጨት ታቦት ሠራሁ፤
እንደ ፊተኞቹ ያሉ ሁለት የድንጋይ
ጽላቶች ቀረጽሁ፤ ሁለቱንም ጽላቶች
በእጆቼ ይዤ ወደ ተራራው ወጣሁ።
4እግዚአብሔር (ያህዌ) በስብሰባው ቀን፣ በእሳት
ውስጥ ሆኖ ለእናንተ የተናገራቸውንና
ቀድሞ ጽፎአቸው የነበሩትን ዐሥሩን
ትእዛዛት በእነዚህ ጽላቶች ላይ ጻፋቸው።
እግዚአብሔርም (ያህዌ) እነርሱን ለእኔ ሰጠኝ።
5ከዚያም ከተራራው ተመልሼ ወረ ድሁ፤
እግዚአብሔር (ያህዌ) ባዘዘኝ መሠረት በሠራ
ሁት ታቦትም ውስጥ፣ ጽላቶቹን
አስቀመጥኋቸው፤ አሁንም እዚያ ናቸው።
6እስራኤላውያን ከብኤሮት ብኔያዕቃን፣
የያዕቃን ልጆች ከቈፈሯቸው የውሃ ጒድ
ጓዶች ተነሥተው ወደ ሞሴራ ተጓዙ፤
አሮንም በዚያ ቦታ ሞቶ ተቀበረ፤ ልጁ
አልዓዛር በእርሱ ምትክ ካህን ሆነ። 7ከዚ
ያም ተነሥተው ጒድጎዳ ወደተባለ ስፍራ፣
ቀጥሎም የውሃ ፈሳሾች ወዳሉባት ዮጥባታ
ወደምትባል ምድር ተጓዙ። 8በዚያን ጊዜ፣
ዛሬም እንደ ሚያደርገው ያገለግል ዘንድ፣
በእግዚአብሔርም (ያህዌ) ፊት እንዲቆምና
በስሙ እንዲባርክ የእግዚአብሔርንም (ያህዌ) የኪ
ዳኑን ታቦት እንዲሸከም እግዚአብሔር (ያህዌ)
የሌዊን ነገድ ለየ። 9ሌዋዊ በወንድሞቹ መካ
ከል ድርሻም ሆነ ርስት የሌለው ከዚህ የተ
ነሣ ነው፤ አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
በነገረው መሠረት ርስቱ እግዚአብሔር (ያህዌ)
ነው።
10እኔም በመጀመሪያው ጊዜ እንዳደረግ
ሁት፣ በተራራው ላይ አርባ ቀንና አርባ
ሌሊት ቈየሁ፤ በዚህ ጊዜም እግዚአብሔር
(ያህዌ) እንደ ገና ሰማኝ፤ እግዚአብሔር (ያህዌ)
አንተን ሊያጠፋ አልፈቀደም። 11ስለዚህም
እግዚአብሔር (ያህዌ)፣ “ሂድ፤ ለአባቶቻቸው
ለመስጠት ወደ ማልሁላቸው ምድር ገብተው
እንዲወርሱ ሕዝቡን ምራ” አለኝ።

## እግዚአብሔርን (ያህዌ) ፍራ

12አሁንም እስራኤል ሆይ፤ አምላክህ
እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ከአንተ የሚፈልገው
ምንድን ነው? አምላክህን እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም)
እንድትፈራው፣ በመንገዶቹ ሁሉ እንድትሄድ፣
እንድትወደው፣ በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም
ነፍስህ እንድታገለግለው፣ 13መልካም እን
ዲሆንልህና ዛሬ እኔ የምሰጥህን ትእዛዞችና
ሥርዐቶች እንድትጠብቅ አይደለምን?
14ሰማያት፣ ሰማየ ሰማያት፣ ምድርና
በእርሷም ያለው ሁሉ የአምላክህ የእግዚ
አብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ነው። 15ነገር ግን እግዚ
አብሔር (ያህዌ) አባቶችህን ስላፈቀረ፣ ወደ
ዳቸው፤ ዛሬም እንደ ሆነው የእነርሱ ዘር የሆና
ችሁትን እናንተን ከአሕዛብ ሁሉ ለይቶ መረ
ጣችሁ። 16ስለዚህ የልባችሁን ሸለፈት ግረ
ዙት፤ ከእንግዲህም ወዲያ ዐንገተ ደንዳና
አትሁኑ። 17አምላካችሁ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎ
ሂም) የአማልክት አምላክ (ኤሎሂም)፣ የጌቶች ጌታ
(አዶናይ) ታላቅ አምላክ (ኤሎሂም)፣ ኀያልና የሚያስፈራ
፣ አድ ልዎ የማያደርግ፣ መማለጃም የ
ማይቀበል ነውና። 18እርሱ አባት ለሌላቸውና
ለመበለቶች ይፈርዳል፤ መጻተኛውንም ምግብና
ልብስ በመስጠት ይወዳል። 19ስለዚህ
እናንተም በግ ብፅ ምድር መጻተኞች ነበራ
ችሁና መጻተኛን ውደዱ። 20አምላክህን እግዚ
አብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) ፍራ፤ አምልከውም፤
ከእርሱም ጋር ተጣበቅ፤ በስሙም ማል።
21እርሱ ውዳሴህ ነው፤ በገዛ ዐይኖችህ
ያየሃቸውን፣ እነዚያን ታላ ላቅና አስፈሪ
ነገሮች ያደረገልህ አምላክህ (ኤሎሂም) ነው።
22አባቶችህ ወደ ግብፅ ሲወ ርዱ ሰባ ነበሩ
፤ አሁን ግን አምላክህ እግዚ

9፥24 ዘዳ8፥17
9፥25 ቀኍ18፤
ዘፍ7፥4ዘፀ33፥17
9፥26 ቀኍ19፤
ዘፀ6፥6፤32፥11፤
33፥13፤34፥9፤
ዘዳ15፥15፤2ሳሙ7፥23፤
መዝ78፥35
9፥27 ቀኍ6፤
ዘፀ32፥9
9፥28 ዘፀ32፥12፤
ዘዳ1፥27፤32፥27፤
ኢ.ሱ7፥9
9፥29 ዘፀ33፥13፤
34፥9፤ዘዳ4፥34፤32፥9፤
ነህ1፥10፤ኤር27፥5፤
32፥17
10፥1 ዘፀ34፥1-2
10፥2 ዘፀ25፥16፡
21 2ዜና5፥10፤6፥11
10፥3 ዘፀ34፥4፤
37፥1-9
10፥4 ዘፀ24፥12፤
34፥28፤20፥1፤ዘዳ9፥10
10፥5 ዘፀ19፥11፤
25፥10፡21፤
1ሳሙ3፥3፤1ነገ8፥9
10፥6 ዘፀ6፥23፤
ዘኍ20፥20-28፤
27፥13፤33፥30
10፥7 ዘኍ33፥32-
34፤መዝ42፥1፤
መኃ5፥12፤ኢሳ32፥2
10፥8 ዘፍ48፥20፤
ዘኍ3፥6፤10፥33፤
16፥9፤1ዜና23፥26
10፥9 ዘኍ18፥20
10፥10 ዘፀ33፥17
10፥12 ዘፀ20፥20፤
ዘዳ5፥32፡33፤6፥5፡13፤11
፥13፤28፥47፤
1ነገ2፥3፤3፥3፤9፥4፤
ማቴ22፥37፤
1ጢሞ1፥5፤
መዝ100፥2፤119፥2፤
ሚክ6፥8፤
10፥13 ዘዳ4፥2፤
5፥33፤6፥24
10፥14 ዘፀ19፥5፤
ዘዳ33፥26፤ኢ.ሱ35፥5፤
1ነገ8፥27፤ነህ9፥6፤
ኢዮ35፥5፤መዝ8፥3፤
24፥1፤89፥11፤104፥3፤11
5፥16፤148፥4፤
ኢሳ19፥1፤ዕን3፥8፤
ሐሥ17፥24
10፥15 ዘኍ14፥8፤
ዘዳ4፥37፤መዝ105፥6፤1
35፥4፤ሮሜ11፥28፤
1ጴጥ2፥9
10፥16 ዘፍ17፥11፤
ዘፀ32፥9፥13፤
ዘሌ26፥41፤ዘዳ30፥6፤ኤ
ር32፥39
10፥17 ዘፀ23፥8፤
ዘሌ19፥16፤ዘዳ1፥17፤7
፥21፤ኢ.ሱ22፥22፤
መዝ135፥5፤136፥2፡3፤
ዳን2፥47፤11፥36፤
ሚል2፥9፤
1ጢሞ6፥15

10፥18 ዘፀ22፥21፡ 22-24፤23፥9፤ ዘሌ19፥33፤ዘኍ10፥32፤
ዘዳ27፥19፤ኢዮ29፥13፤ መዝ94፥6፤ ኢሳ10፥2፤ ኤር49፥11
10፥19 ዘፀ22፥21፤ዘሌ19፥34፤ዘዳ7፥12፤24፥19፤ሕዝ47፥22-23
10፥20 ዘፀ20፥7፤ ዘዳ11፥22፤13፥4፤30፥20፤ኢ.ሱ23፥8፤
ሩት1፥14፤ 2ነገ18፥6፤ መዝ119፥31፤ኢሳ38፥3፤ማቴ4፥10፤
10፥21 ዘፀ15፥2፤ 1ሳሙ12፥24፤ 2ሳሙ7፥23መዝ126፥2፤
10፥22 ዘፍ12፥2፤34፥30፤46፥26፤ ዘኍ10፥36፤ሐሥ7፥14፤

አብሔር (*ያህዌ ኤሎሂም*) እንደ ሰማይ ከዋክብት
አብዝቶሃል፡፡

### *እግዚአብሔርን ውደድ፤ ታዘዘውም*

11 እንግዲህ *አምላክህን* እግዚአብሔርን
(*ያህዌ ኤሎሂም*) ውደድ፤ ግዴታውን፣ ሥርዐ
ቱን፣
ሕጉንና ትእዛዙን ሁልጊዜ ጠብቅ፡፡ 2*የአምላካ
ችሁን* የእግዚአብሔርን (*ያህዌ ኤሎሂም*) ተግሣጽ ይኸ
ውም ግርማውን፣ ብርቱ እጁንና የተዘረጋች
ክንዱን ያዩትና የተለማመዱት ልጆቻችሁ
ሳይሆኑ እናንተ እንደ ሆናችሁ ዛሬ አስታ
ውሱ፤ 3በግብፅ መካከል፣ በግብፅ ንጉሥ
በፈር *ዖ*ንና በመላው አገሩ ላይ ያደረጋቸውን
ምል ክቶችና የሠራቸውን ነገሮች፣ 4በግብፃውያን
ሰራዊት፣ በፈረሶቻቸውና በሠረገሎቻቸው ላይ፣
እናንተን ባሳደዷችሁ ጊዜ በቀይ ባሕር[ከ]
ውሃ እንዴት እንዳሰጠማቸውና *እግዚአብሔር*
(*ያህዌ*) ፈጽሞ እንዴት እንዳጠፋቸው አስ
ታውሱ፤ 5ከምድረ በዳው አንሥቶ እዚህ እስከ
ምትደርሱ ድረስ፣ ለእናንተ ያደረገላችሁን
ያዩት ልጆቻችሁ አልነበሩም፤ 6የሮቤል ልጅ
የኤልያብ ልጆች የሆኑትን ዳታንና አቤሮንን
ከነቤተሰቦቻቸው፣ ከነድንኳናቸውና ከነእ
ንስሳታቸው በመላው እስራኤል መካከል
ምድር እንዴት አፏን ከፍታ እንደ ዋጠ
ቻቸው እነርሱ አላዩም፡፡ 7የእናንተ ዐይ
ኖች ግን *እግዚአብሔር* (*ያህዌ*) ያደረጋቸውን
ሥራዎች ሁሉ አይተዋል፡፡
8ስለዚህ ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ ወደምት
ወርሷት ምድር ለመግባትና ለመያዝ ብርታት
እንድታገኙ፣ ዛሬ እኔ የምሰጣችሁን ትእዛዞች
ሁሉ ጠብቁ፤ 9ለአባቶቻቸውና ለዘሮቻቸው
*እግዚአብሔር* (*ያህዌ*) ሊሰጣቸው በማለላቸው፣
በዚያች ማርና ወተት በምታፈሰው ምድር
ረጅም ዕድሜ ትኖሩ ዘንድ፣ 10የምትገባባት
ምድር እንደ ወጣህባትና ዘርህን ዘርተህባት
በእግርህ ውሃ እንዳጠጣሃት የአትክልት ቦታ
እንደ ግብፅ ምድር አይደለችም፡፡ 11ዮርዳኖስን
ተሻግረህ ልትወርሳት ያለችው ምድር
ግን፣ ከሰማይ ዝናብ የምትጠጣ፣ ተራሮችና
ሸለቆች ያሉባት ምድር ናት፡፡ 12ይህች ምድር
*አምላክህ* እግዚአብሔር (*ያህዌ ኤሎሂም*) የሚን
ከባከባት፣ ከዓመቱ መጀመሪያ እስከ ዓመቱ
መጨረሻ *የአምላክህ* የእግዚአብሔር (*ያህዌ ኤሎ
ሂም*) ዐይን ምንጊዜም የማይለያት ናት፡፡
13ዛሬ እኔ የምሰጣችሁን ትእዛዞች በታማኝነት
ብትጠብቁ፣ ይኸውም *አምላካችሁን* እግዚአ
ብሔርን (*ያህዌ ኤሎሂም*) ብትወዱና በፍጹም
ልባችሁ፣ በፍጹም ነፍሳችሁም እርሱን በ
ማገልገል፣ በታማኝነት ብትጠብቁ፣
14እህልህን፣ ወይንህንና ዘይትህን እንድትሰበስብ
የበልጉንና የክረምቱን ዝናብ በምድርህ ላይ
በየወቅቱ አዘንባለሁ፡፡ 15በሜዳ ላይ
ለከብቶችህ ሣር እሰጣለሁ፤ አንተም
ትበላለህ፤ ትጠግባለህም፡፡
16ተጠንቀቁ! አለበለዚያ ተታላችሁ ሌሎች
አማልክትን ታመልካላችሁ፤
ትሰግዳላችሁም፡፡ 17ከዚያም *የእግዚአብሔር*
(*ያህዌ*) ቍጣ በላያችሁ ይነዳል፤ እርሱም ዝናብ
እንዳይዘንብ፣ ምድሪ ቱም ፍሬ እንዳትሰጥ ሰ
ማያትን ይዘጋል፤ እናንተም *እግዚአብሔር* (*ያህዌ*)
ከሚሰጣችሁ ከመል ካሚቱ ምድር ወዲያውኑ
ትጠፋላችሁ፡፡ 18እነዚህን ቃሎቼን፣ በልባችሁና
በአእምሮአችሁ አኑሯቸው፤ በእጆቻችሁ ላይ
ምልክት አድር ጋችሁ እሰሯቸው፣ በግምባ
ራችሁም ላይ ይሁኑ፡፡ 19ልጆቻችሁንም
አስተምሯቸው፤ ቤት ስትቀመጥ፣ መንገድ
ስትሄድ፣ ስትተኛና ስት ነሣ ስለ እነዚሁ
አጫውታቸው፡፡ 20በቤ ትህ መቃኖችና
በግቢህ በሮች ላይ ጻፋ ቸው፤ 21ይህን
ካደረጋችሁ፣ *እግዚአብሔር* (*ያህዌ*)
ለአባቶቻችሁ ለመስጠት በማለላቸው
ምድር የእናንተና የልጆቻችሁ ዘመን ከም
ድር በላይ ያሉ ሰማያትን ርቀት ያህል
ይሆናል፡፡
22*አምላክህን* እግዚአብሔርን (*ያህዌ ኤሎሂም*)
ትወዱ ዘንድ፣ በመንገዶቹም ሁሉ ትሄዱና
ከእርሱም ጋር ትጣበቁ ዘንድ
እንድትከተሏቸው የምሰጣ ችሁን እነዚህን
ትእዛዞች ሁሉ በጥንቃቄ ብትጠብቁ፣
23ከዚያም *እግዚአብሔር* (*ያህዌ*) እነዚህን
አሕዛብ ሁሉ ከፊታችሁ ያስወጣ ቸዋል፤
እናንተም፣ ከእናንተ ይልቅ ታላላቅና ብርቱ
የሆኑትን አሕዛብ ታስለቅቃላችሁ፡፡ 24በእግ
ራችሁ የምትረግጡት ስፍራ ሁሉ የእናንተ
ይሆናል፤ ግዛታችሁም ከምድረ በዳው እስከ
ሊባኖስ፣ ከኤፍራጥስ ወንዝ አንሥቶ በስተ
ምዕራብ እስካለው ባሕር[ኸ] ይደርሳል፡፡
25ማንም ሰው ሊቋቋማችሁ አይችልም፤ *አም
ላካችሁ* እግዚአብሔር (*ያህዌ ኤሎሂም*) በሰጣችሁ ተስፋ
መሠረት ማስደንገጣችሁንና መፈራታችሁን
በምትሄዱበት በየትኛውም ምድር ሁሉ ላይ
ያሳድራል፡፡
26እነሆ፤ ዛሬ በረከትንና መርገምን በፊታ
ችሁ አኖራለሁ፤ 27በረከቱ ዛሬ የምሰጣች
ሁን *የአምላካችሁን* የእግዚአብሔርን (*ያህዌ ኤሎሂም*)
ትእዛዞች ስትፈጽሙ ሲሆን፣ 28መርገሙ
ደግሞ፣ *የአምላካችሁን* የእግዚአብሔርን (*ያህዌ ኤሎሂም*)
ትእዛዞች የማትፈጽሙ፣ የማታውቋቸውንም
ሌሎች አማልክት ለመከተል እኔ ከማዛችሁ
መንገድ የምትወጡ ከሆነ ነው፡፡ 29ልትወ
ርሳት ወደ ምትሄድባት ምድር *አምላክህ*
እግዚአብሔር (*ያህዌ ኤሎሂም*) በሚያስገባህ ጊዜ
በረከቱን በገሪዛን ተራራ፣ መርገሙን
ደግሞ በጌባል ተራራ ላይ ታሰማለህ፡፡

11፥1 ዘሌ8፥35፤ ዘዳ6፥5
11፥2 ዘዳ31፥13፤ ዘዳ3፥24፤5፥24፤31፥13፤ መዝ78፥6፤136፥12
11፥3 ዘፀ7፥8-21
11፥4 ዘፀ14፥27፤ 15፥1፤ዘኍ21፥4
11፥6 ዘኍ16፥1-35፤ መዝ106፥16-18፤ ኢሳ24፥19
11፥7 ዘዳ5፥3 11፥8 ዘዳ31፥6-7፡ 23፤ ኢሱ1፥7፤ዕዝ9፥10
11፥9 ዘፀ3፥8፤ ዘዳ5፥16፤9፥5፤
11፥10 ኢሳ11፥15፤ 37፥25
11፥11 ዘዳ8፥7፤ሕዝ36፥4፤ነህ9፥25
11፥12 1ነገ8፥29፤ 9፥3
11፥13 ዘዳ4፥29፤ 6፥17፤10፥12፤ኤር17፥24
11፥14 ዘሌ26፥4፤ መዝ147፥8፤ኤር3፥3፤5፥24፥ኢል2፥23፤ ሐሥ14፥17፤ያዕ5፥7
11፥15 ዘሌ26፥5፤ መዝ104፥14
11፥16 ዘዳ4፥19፤ 8፥19፤29፥18፤ ኢዮ31፥9፡27
11፥17 ዘሌ26፥20፤ ዘዳ4፥26፤6፥15፤9፥19፤ 28፥12፡24፤1ነገ17፥1፤ 2ዜና6፥26፤7፥13፤
11፥18 ዘፀ13፥9፤ ዘዳ6፥6-8
11፥19 ዘፀ12፥26፤ ዘዳ4፥9-10፤6፥7፤ መዝ145፥4፤ ኢሳ38፥19፤ ኤር32፥39፤
11፥20 ዘዳ6፥9
11፥21 ኢዮ5፥26፤ ምሳ3፥2፤4፥10፤9፥11
11፥22 ዘዳ6፥5፡17፤ 10፥20
11፥23 ዘፀ23፥28፤ ዘዳ9፥1፡5
11፥24 ዘፍ2፥14፤ 15፥18፤ዘዳ1፥36፤ 12፥20፤19፥8፤ ኢሱ1፥3፡14፥9
11፥25 ዘፀ23፥27፤ ዘዳ2፥25፤7፥24
11፥26 ዘሌ26፥14-17፤ ዘዳ27፥13-26፤30፥1፡ 15፡19፤መዝ24፥5፤ ሰቆ2፥17፤ዳን9፥11፤ሐጌ1፥11፤ ሚል2፥2፤3፥9፤4፥6
11፥27 ዘዳ28፥1-14፤ መዝ24፥5
11፥28 ዘዳ4፥28፤ 13፥6፡13፤29፥26፤ 1ሳሙ26፥19፤ 2ዜና24፥20፤
11፥29 ዘዳ27፥4፡ 12-13፤ኢሱ8፥30፡ 33፤መሳ9፥7፤ዮሐ4፥20

[ከ]4 ዕብራይስጡ፣ *ያም ሳውፍ ይለዋል*፤ ይኸውም የደንገል ባሕር ማለት ነው፡፡
[ኸ]24 የሜዲትራንያን ባሕር ነው፡፡

30እነዚህ ተራሮች የሚገኙት ከዮርዳኖስ
ማዶ[ሠ]
ፀሓይ በምትጠልቅበት አቅጣጫ ካለው
*መ*ንገድ በስተ ምዕራብ በዓረባ በሚኖሩ
የከነዓናውያን ምድር ውስጥ ከጌልገላ ፊት
ለፊት፣ በሞሬ ታላላቅ ዛፎች አጠገብ
አይደለምን? 31 *አምላካችሁ* እግዚአብሔር (ያህዌ
ኤሎሂም) በሚሰጣችሁ ምድር ትገቡባትና
ትወ ርሷት ዘንድ ዮርዳኖስን ልትሻገሩ ስለ
ሆነ፣ ምድሪቱን ወርሳችሁ በምትኖሩባት ጊ
ዜ፣ 32ዛሬ በፊታችሁ እኔ ያስቀመጥኋቸውን
ሥርዐቶችና ሕጎች ሁሉ ለመፈጸም ተጠንቀቁ።

## ብቸኛው የማምለኪያ ስፍራ

12 የአባቶቻችሁ *አምላክ* እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም)፣ እንድትወርሷት በሰጣችሁ
ምድር ላይ በምትኖሩበት ጊዜ ሁሉ፣ በጥንቃቄ
ልትከተሏቸው የሚገባችሁ ሥርዐቶችና ሕግጋት
እነዚህ ናቸው። 2ከምድራቸው የምታስለቅ
ቋቸው አሕዛብ በረጅሙ ተራሮች፣ በኰረ
ብቶችና በእያንዳንዱ ዛፍ ሥር አማልክታቸውን
የሚያመልኩባቸውን ስፍራዎች ሁሉ
ፈጽማችሁ አጥፉ። 3መሠዊያዎቻቸውን
አፍርሱ፤ የማምለኪያ ዐምዶቻቸውን ሰባብሩ፤
የአሼራ ምስል ዐምዶቻቸውን በእሳት አቃ
ጥሉ፤ የአማልክታቸውን ጣዖቶች ቈራርጣ
ችሁ ጣሉ፤ ስማቸውንም ከእነዚያ ስፍራዎች
ላይ አጥፉ።

4በእነርሱ መንገድ *አምላካችሁን* እግዚአብሔርን
(ያህዌ ኤሎሂም) አታምልኩ። 5ዳሩ ግን *አምላካችሁ*
እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ለስሙ ማደሪያ
እንዲ ሆነው፣ በነገዶቻችሁ መካከል
የሚመርጠውን
ስፍራ እሹ፤ ወደዚያም ስፍራ ሂዱ። 6ወደዚ
ያም የሚቃጠሉ መሥዋዕቶቻችሁንና ሌሎች
መሥዋዕቶቻችሁን፣ ዐሥራታችሁንና የእጃችሁን
ስጦታ፣ ስእለቶቻችሁንና የፈቃዳችሁን ስጦ
ታዎች፣ የቀንድ ከብት መንጋችሁን፣ የበግና
የፍየል መንጋዎቻችሁን በኵራት አምጡ።
7በዚያም *በአምላካችሁ* በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎ
ሂም) ፊት ትበላላችሁ፤ *አምላካችሁ* እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) እናንተን በባረከበት፣ በምታደ
ርጉት ሁሉ አንተና ቤተ ሰዎችህ ሐሤት
ታደርጋላችሁ።

8ዛሬ እንደምናደርገው ሁሉ፣ እያንዳንዱ
የሚመስለውን እንዳደረገ አታድርጉ፤ 9ምክንያ
ቱም ማረፊያ ወደ ሆነውና *አምላካችሁ* እግዚ
አብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ወደሚሰጣችሁ ርስት
ገና አልደረሳችሁም። 10ይሁን እንጂ ዮርዳኖስን
ስትሻገሩና *አምላካችሁ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
ርስት አድርጎ በሚሰጣችሁ ምድር ስትቀመጡ፣
ያለ ሥጋት እንድትኖሩ በዙሪያችሁ ካሉት
ጠላቶቻችሁ ሁሉ ያሳርፋችኋል። 11ከዚ
ያም *አምላካችሁ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
ለስሙ ማደሪያ እንዲሆን ወደሚመርጠው
ስፍራ፣ እኔ የማዝዛችሁን ሁሉ፦ የሚቃጠሉ
መሥ ዋዕቶቻችሁንና ሌሎች መሥዋዕ
ቶቻችሁን፣ ዐሥራቶቻችሁንና የእጃችሁን ስጦታ፣
እንዲሁም *ለእግዚአብሔር* (ያህዌ)
የተሳላችኋቸውን ምርጥ ነገሮች ሁሉ ወደዚ
ያ ታመጣላችሁ። 12እዚያም እናንተ፣
ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ፣ ወንዶችና ሴቶች
አገልጋዮቻችሁ፣ እንዲሁም የራሳቸው ድርሻ
ወይም ርስት የሌላቸው በየከተሞቻችሁ
የሚኖሩት ሌዋውያን በእግዚአብሔር
ፊት ሐሤት አድርጉ። 13የሚቃጠለውን
መሥዋዕትህን በፈለግኸው ስፍራ ሁሉ
እንዳታቀርብ ተጠንቀቅ። 14ከነገዶችህ መካከል
በአንዱ፣ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) በሚመርጠው
ስፍራ ብቻ የሚቃጠሉ መሥዋዕቶችህን አቅ
ርብ፤ እዚያም እኔ የማዝህን ሁሉ ጠብቅ፤
15ሆኖም *አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
በሚሰጥህ መጠን፣ በየትኛውም ከተማህ፣
እንስሳትህን ሚዳቋም ሆነ ድኵላ ዐርደህ
የምትፈልገውን ያህል ሥጋ ብላ፤ በሥርዐቱ
መሠረት ንጹሕ የሆነም ሆነ ያልሆነ ሰው
ከዚሁ ሥጋ ሊበላ ይችላል። 16ደሙን ግን
እንደ ውሃ መሬት ላይ አፍስሰው እንጂ
አትብላው። 17የእህልህን፣ የወይን ጠጅህንና
የዘይትህን ዐሥራት፣ ወይም የቀንድ ከብት፣
የበግና የፍየል መንጋህን በኵራት፣ ወይም
ለመስጠት የተሳልኸውን ወይም የፈቃድህን
ስጦታ፣ ወይም የእጅህን ስጦታ፣ በከተሞችህ
ውስጥ መብላት የለብህም። 18 *አምላክህ*
እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በሚመርጠው ስፍራ
አንተ፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆችህ፣ ወንድና
ሴት አገልጋዮችህ፤ በከተሞችህ የሚኖር
ሌዋዊም፣ *በአምላክህ* በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎ
ሂም) ፊት ትበሉታላችሁ፤ እጅህም በነካው ነገር
ሁሉ *በአምላክህ* በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
ፊት ደስ ይልሃል። 19በምድርም ላይ
በምትኖርበት ጊዜ ሁሉ ሌዋዊውን ቸል
እንዳትለው ተጠንቀቅ።

20 *አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በሰጠህ
ተስፋ መሠረት ግዛትህን ሲያሰፋልህ፣ ሥጋ
አምሮህ፣ "ሥጋ መብላት እፈልጋለሁ" በምት
ልበት ጊዜ፣ ያሰኘህን ያህል ሥጋ መብላት
ትችላለህ። 21ስሙን ለማኖር *አምላክህ* እግዚ
አብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) የመረጠው ስፍራ
ከአንተ እጅግ የራቀ ከሆነ፣ ባዘዝሁህ መ
ሠረት ከቀንድ ከብትህ፣ ከበግና ከፍየል
መንጋህ እንስሳት ማረድ ትችላለህ፤
በከተሞችህ ውስጥ የምትፈልገውን ያህል
መብላት ትችላለህ።

ኤር42፥13፤44፥16፤
11፥30 ዘፍ12፥6፤
ኢሱ4፥19፤5፥9፤9፥6፤
10፥6፤14፥6፤15፥7፤መ
ሳ2፥1፤2ነገ2፥1፤
ሚክ6፥5
11፥31 ዘኍ33፥53፤
ዘዳ12፥10፤ኢሱ11፥23
12፥1 ዘዳ4፥9-10፤
6፥5፤1ነገ8፥40፤
መዝ119፥5፤ሕዝ20፥19
12፥2 ዘኍ21፥28፤
1ነገ14፥23፤2ነገ17፥10፤
ኢሳ57፥5፤ኤር2፥20፤
3፥6፡13 12፥3 ዘፀ
23፥13፤32፥20፤34፥13
፤ነገ11፥18፤1ነገ14፥15፡2
3
12፥4 ቀኍ30፤
2ነገ17፥15፤ኤር10፥2
12፥5 ቀኍ11፡13፤ዘፀ
20፥24፤ ዘዳ14፥23፤
15፥20፤16፥2፡11፤
18፥6፤26፥2፤1ሳሙ2፥
29፤ 2ሳሙ7፥13፤
1ነገ5፥5፤ 8፥16፤9፥3፤
2ዜና2፡4፤6፡6፤7፥12፡16፤
ዕብ6፥12፤7፥15፤መዝ26፥
8፤ 78፥68፤ዘካ2፥12
12፥6 ዘፍ28፥20፤
ዘሌ27፥30፤ኢሱ22፥27፤
ኢሳ66፥20
12፥7 ዘፀ18፥12፤
ዘሌ23፥40፤መክ3፥12-
13፤ 5፥18-20፤
ኢሳ62፥9
12፥8 መሳ17፥6፤
21፥25
12፥9 ዘፀ33፥14፤
ዘዳ3፥20፤4፥21፤
መዝ95፥11፤ሚክ2፥10
12፥10 ዘፀ33፥14፤
ዘዳ11፥31፤
12፥11 ቀኍ5፤
ዘሌ1፥3፤ኢሱ22፥23
12፥12 ቀኍ7፤
ዘኍ18፥20፤ ዘዳ26፥1
1-13
12፥13 ቀኍ5
12፥14 ቀኍ11
12፥15 ቀኍ22፤
ዘዳ14፥5፤15፥22
12፥16 ቀኍ23-
24፤ዘፍ9፥4፤35፥14፤
ዘሌ17፥13፤ዘዳ15፥23፤
1ዜና11፥18፤ኤር7፥18፤
ዮሐ19፥34፤
ሐሥ15፥20፤
12፥17 ቀኍ26፤
ዘሌ27፥30፤ዘኍ18፥12፡
19፤ዘዳ14፥23፤15፥20
12፥18 ቀኍ5፡7፡12፤
ዘዳ14፥23፡26፤15፥20፤ነ
ህ8፥10፤መክ3፥12-13፤
5፥18-20
12፥19 ቀኍ12፤
ዘዳ14፥27፤
ነህ13፥10፤ሚል3፥8
12፥20 ዘፍ15፥8፤ዘፀ16፥3፤34፥24፤ ዘዳ11፥24
12፥21 ዘሌ17፥4፤ዘዳ14፥24፤

[ሠ]30 ወይም፣ *ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ*፡

22ሚዳቋ ወይም ድኵላ እንደሚበላ አድርገህ
ብላ፤ በሥርዐቱ መሠረት ንጹሕ የሆኑትና
ያልሆኑት ሊበሉ ይችላሉ። 23ደሙን ግን
እንዳትበላ ተጠንቀቅ፤ ደም ሕይወት ስለ ሆነ፣
ሥጋን ከነሕይወቱ አትብላ። 24ደሙን እንደ
ውሃ በመሬት ላይ አፍስሰው እንጂ አትብላው።
25በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ትክክል የሆነውን
ነገር ስለምታደርግ፣ ለአንተም ሆነ ከአንተ
በኋላ ለሚመጡት ልጆችህ መልካም እንዲ
ሆንላቸው አትብላው።
26ነገር ግን የተቀደሱ ነገሮችህን ለመስጠ
ት የተሳልሃቸውን ሁሉ ይዘህ እግዚአብሐ
ር (ያህዌ) ወደሚመርጠው ስፍራ ሂድ።
27የሚቃጠል
መሥዋዕትህን፣ ሥጋውንም ደሙንም
በአምላክህ በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) መሠዊያ
ላይ አቅርብ። የመሥዋዕትህ ደም
በአምላክህ በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) መ
ሠዊያ ላይ ይፍሰስ፤ ሥጋውን ግን
መብላት ትችላለህ። 28በአምላክህ በእግዚአብሐ
ር (ያህዌ ኤሎሂም) ፊት መልካምና ትክክል
የሆነውን ነገር ስለምታደርግ፣ ለአንተና
ከአንተም በኋላ ለሚመጡት ልጆችህ ለዘ
ላለም መልካም እንዲሆንላችሁ፣ እኔ የም
ሰጥህን እነዚህን ደንቦች ሁሉ በጥንቃቄ
ፈጽማቸው።
29የምትወርሯቸውንና የምታስለቅቋቸውን አሕ
ዛብ አምላካችሁ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ከፊ
ታችሁ ያስወግዳቸዋል፤ ባስወጣችኋቸውና
በምድራቸው በተቀመጣችሁ ጊዜ ግን፣ 30ከፊትህ
ከጠፉ በኋላ፣ "እነዚህ ሕዝቦች አማልክታቸውን
የሚያመልኩት እንዴት ነው? እኔም እንደ
እነርሱ አደርጋለሁ" ብለህ በመጠየቅ እንዳ
ትጠመድ ተጠንቀቅ። 31አምላክህን እግዚአብሔርን
(ያህዌ ኤሎሂም) በእነርሱ መንገድ ፈጽሞ አታምልክ፤
ምክንያቱም አማልክታቸውን ሲያመልኩ እግ
ዚአብሔር (ያህዌ) የሚጸየፈውን ሁሉንም ዐይ
ነት ነገር ያደርጋሉና፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻ
ቸውን እንኳ ለአማልክታቸው መሥዋዕት አድ
ርገው ያቃጥላሉ።
32እኔ ያዘዝሁህን ሁሉ ጠብቅ፤ አትጨምር
በት፤ አትቀንስለትም።

## ሌሎች አማልክትን ማምለክ

13 ነቢይ ወይም ሕልም ዐላሚ ከመ
ካከልህ ተነሥቶ ምልክት ወይም
ድንቅ አደርጋለሁ ቢልህ፣ 2የተናገረው ምል
ክት ወይም ድንቅ ቢፈጸም፣ "አንተ የማታው
ቃቸውን ሌሎች አማልክት እናምልካቸው"
ቢልህ፣ 3አምላካችሁ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
በፍጹም ልባችሁና በፍጹም ነፍሳችሁ ትወዱት
እንደ ሆነ ያውቅ ዘንድ ሊፈትናችሁ ነውና፣
የዚያን ነቢይ ቃል ወይም ሕልም ዐላሚውን
አትስማ። 4አምላካችሁን እግዚአብሔርን (ያህዌ
ኤሎሂም) ተከተሉት፤ ፍሩት፤ ትእዛዞቹንም
ጠብቁ፤ ታዘዙት፤ አገልግሉት፤ ከእርሱም
ጋር ተጣበቁ። 5ከግብፅ ባወጣችሁና ከባርነት
ምድር በዋጃችሁ በአምላካችሁ በእግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ላይ እንድ ታምፁ ተናግሮአልና፣
አምላካችሁ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) እንድት
ከተሉት ካዘዛችሁ መንገድ እንድትመለሱ
አድርጎአልና፣ ያ ነቢይ ወይም ሕልም አላሚ
ይገደል፤ ስለዚህ ክፉውን ከመካከልህ አስ
ወግድ። 6የእናትህ ልጅ ወንድምህ፣ ወንድ
ወይም ሴት ልጅህ፣ ወይም የምትወዳት
ሚስትህ ወይም የልብ ጓደኛህ፣ "ሄደን
ሌሎች አማልክትን እናምልክ" (አንተም ሆንክ
አባቶችህ የምታውቋቸውን አማልክት፣) ብሎ
በስውር ሊያስትህ ቢሞክር፣ 7በቅርብም ሆነ
በሩቅ፣ ከአንዱ የምድር ጫፍ እስከ ሌላው
ድረስ በዙሪያህ ያሉትን የአሕዛብ አማልክት
እናምልክ ቢልህ፣ 8እሺ አትበለው፤ ወይም
አታዳምጠው፤ አትራራለት፤ አትማረው፤
ወይም አትሸሽገው። 9ያለማመንታት ግደለው፤
እርሱንም ለመግደል በመጀመሪያ የአንተ እጅ፣
ከዚያም በኋላ የሕዝቡ ሁሉ እጅ ይነሣ።
10የባርነት ምድር ከሆነው ከግብፅ ካወጣህ
ከአምላክህ ከእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ሊ
ያርቅህ ፈልጎአልና እስኪሞት ድረስ
በድንጋይ ውገረው። 11ከዚያም እስራኤል
ሁሉ ሰምተው ይፈራሉ፤ ከመካከልህም
ማንም እንደዚህ ያለውን ክፉ ነገር ዳግም
አያደርግም።
12አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) እንድ
ትኖርባቸው ከሚሰጥህ ከተሞች ባንዲቱ
ውስጥ እንዲህ ሲባል ብትሰማ፣ 13ክፉ
ሰዎች ከመካከላችሁ ተነሥተው አንተ የማታ
ውቃቸውን፣ "ሌሎች አማልክትን ሄደን እና
ምልክ" በማለት የከተማቸውን ሕዝብ እያ
ሳቱ ቢሆን፣ 14ጉዳዩን አጣራ፤ መርምር፤ በሚ
ገባም ተከታተል፤ ነገሩ እውነት ሆኖ ከተገ
ኘና ይህ አስጸያፊ ነገር በመካከልህ መፈ
ጸሙ ከተረጋገጠ፣ 15በዚያች ከተማ
የሚኖሩትን ሁሉ በሰይፍ ግደላቸው፤ ከተ
ማዪቱን ከነሕዝቧና ከነቀንድ ከብቷ ፈጽሞ
ደም ስሳት[o]። 16በከተማዪቱ የተገኘውን
የምርኮ
ዕቃ ሁሉ በአደባባይዋ መካከል ላይ ሰብ
ስበህ፣ ከተማዪቱን ከነምርኮዋ እንዳለ
ለአምላክህ ለእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) የሚቀርብ
መሥዋዕት አድርገህ በሙሉ አቃጥል።
ለዘላለም እንደ ፈረሰች ትቅር፤ ተመልሳም
አትሠራ።
17እግዚአብሔር (ያህዌ) ከብርቱ ቍጣው ይመለስ
ዘንድ እርም ነገሮች በእጅህ አይገኙ[o]፤ እርሱ
ምሕረቱን ያሳይሃል፤ ይራራልሃል፤ ለአባቶችህ

12፥22 ቀ-15
12፥23 ዘሌ7፥26፤ ሕዝ33፥25
12፥24 ቀ-16
12፥25 ቀ-28፤ ዘፀ15፥26፤ዘዳ4፥40፤ 13፥18፤1ነገ11፥38፤ 2ነገ12፥2
12፥26 ቀ-17፤ ዘኍ5፥9-10
12፥27 ዘሌ1፥13፤ 3፥1-17
12፥28 ዘዳ4፥40፤ መክ8፥12
12፥29 ዘዳ6፥10፤ ኢሱ23፥4፤
12፥30 ቀ-4፤ ዘፀ10፥7፤
12፥31 ዘሌ18፥21፡ 25፤2ነገ3፥27
12፥32 ዘዳ4፥2፤ ራእ22፥18-19
13፥1 ዘፍ20፥3፤ ኤር23፥25፤27፥9፤ 29፥8፤ማቴ24፥24፤ ማር13፥22፤2ተሰ2፥9
13፥2 ዘዳ11፥28፤ 18፥22፤1ሳሙ2፥34፤10፥9፤2ነገ19፥29፤ 20፥9፤ኢሳ7፥11፤
13፥3 ዘፍ22፥1፤ ዘዳ6፥5፤1ሳሙ28፥6፡15፤1ነገ13፥18፤ 22፥22-23፤ ኤር29፥31፤43፥2፤ ሕዝ13፥9፤1ቆሮ11፥19፤ 2ጴጥ2፥1
13፥4 ዘዳ6፥13፤ 10፥20፤2ነገ23፥3፤ 2ዜና34፥31፤ መዝ5፥7፤2ዮሐ1፥6
13፥5 ቀ-10፤ ዘፀ21፥12፥12፤ 22፥20፤ዘዳ4፥19፤17፥7፡12፤19፥19፤24፥7፤ መሳ20፥13፤1ቆሮ5፥13
13፥6 ዘዳ11፥28፤ 17፥2-7፤29፥18
13፥8 ዘዳ7፥2፤ ምሳ1፥10
13፥9 ቀ-5፤ዘሌ24፥14
13፥10 ዘፀ20፥3
13፥11 ዘዳ17፥13፤ 19፥20፤21፥21፤ 1ጢሞ5፥20
13፥13 መሳ19፥22፤ 20፥13፤1ሳሙ2፥12፤10፥27፤11፥12፤ 25፥17፤1ነገ21፥10
13፥14 ዘዳ17፥4፤ መሳ20፥12
13፥15 ዘፀ22፥20፤ ኢሳ24፥6፤34፥5፤ 43፥28፥47፥6፤ ሰቆ2፥6፤ዳን9፥11፤ ዘካ8፥13፤ሚል4፥6፤
13፥16 ዘዳ7፥25፡ 26፤ኢሱ6፥24፤ 8፥28፤2ነገ25፥9፤ ኢሳ7፥16፤17፥1፤ 24፥10፤25፥2፤ 27፥10፤32፥14፤19፤37፥26፤ ኤር39፥8፤49፥2፤ 52፥13፤ሕዝ16፥41 ፤ ሚክ1፥6
13፥17 ዘፍ12፥2፤13፥14፤ 26፥24፤43፥14፤ዘፀ32፥12፤ ዘኍ25፥4፤ዘዳ7፥13፤30፥3፤

[o]15፥17 የዕብራይስጡ ቃል አንድን ነገር ወይም አንድን ሰው ሙሉ በሙሉ በማጥፋ ለእግዚአብሔር መስጠትን የሚያሳይ ነው።

በመሐላ ተስፋ በሰጠው መሠረት ቍጥርህን
ያበዛዋል፤ [18]ይህም የሚሆነው ዛሬ እኔ የምሰጥህን
ትእዛዞቹን ሁሉ በመጠበቅና መልካም የሆነ
ውን በአምላክህ በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ፊት በማ
ድረግ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ስለ
ታዘዝህለት ነው፡፡

## ንጹሕና ንጹሕ ያልሆነ ምግብ

14፥3-20 ተጓ ምብ - ዘሌ 11 1-23

**14** እናንተ የአምላካችሁ የእግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ልጆች ናችሁ፤ ለሞተ
ሰው ሰውነታችሁን አትቦጭቁ፤ ከግንባራችሁ
በላይ ያለውን ጠጕር አትላጩ፤ [2]ምክንያቱም
አንተ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ቅዱስ
ሕዝብ ነህ፤ ለራሱ የተለየ ሕዝብ እንድትሆ
ንለት እግዚአብሔር (ያህዌ) በምድር ላይ ከሚ
ኖሩ ሕዝቦች ሁሉ አንተን መርጦሃል፡፡
[3]ማናቸውንም ርኩስ ነገር አትብላ፡፡
[4]የምትበሏቸው እንስሳት እነዚህ ናቸው፤
በሬ፣ በግ፣ ፍየል፣ [5]ዋላ፣ ድኵላ፣ ሰስ፣
የበረሓ ፍየል፣ ዋሊያ፣ ሚዳቋ፣ አጋዘን[#]፡፡
[6]ሰኰናው ስንጥቅ የሆነውን፣ ለሁለት የተከ
ፈለውንና የሚያመሰኳ ማናቸውንም እንስሳ
ብላ፡፡ [7]ነገር ግን ከሚያመሰኩት ወይም
ሰኰናቸው ከተሰነጠቀ እንስሳት መካከል
ግመልን፣ ጥንቸልንና ሽኮኮን አትብሉ፤
እነርሱ ቢያመሰኩ እንኳ፣ ሰኰናቸው የተሰነጠ
ቀ ባለመሆኑ፣ በሥርዐቱ መሠረት በእናንተ
ዘንድ ርኩሶች ናቸው፡፡ [8]ዐሳማም እንደዚሁ
ርኩስ ነው፤ ምንም እንኳ ሰኰናው የተሰነጠ
ቀ ቢሆንም፣ ስለማያመሰኳ፣ እርሱ
ለእናንተ ንጹሕ አይ ደለም፤ የእነዚህን ሥጋ
አትብሉ፤ ጥም ባቸውንም አትንኩ፡፡
[9]በውሃ ውስጥ ከሚኖሩ ፍጡራን ሁሉ
ክንፍና ግልፋፊ ያለውን ማናቸውንም ብሉ፤
[10]ክንፍና ግልፋፊ የሌለውን ግን አትብሉ፤
ለእናንተ ርኩስ ነው፡፡
[11]ንጹሕ የሆነውን ወፍ ሁሉ መብላት
ትች ላላችሁ፡፡ [12]የሚከተሉትን ግን
አትበሉም፤ እነርሱም፦ ንስር፣ ገዴ፣ ዓሣ
አውጪ፣ [13]ጭል ፊት፣ ጭላት፣ ማናቸውም ዐ
ይነት አድኖ በል አሞራ፣ [14]ማናቸውም ዐ
ይነት ቁራ፣ [15]ሰጎን፣
ጠላቋ፣ ዝዪ፣ ማናቸውም ዐይነት በቋል፣
[16]ጕጕት፣ ጋጋኖ፣ የውሃ ዶሮ፣ [17]ይብራ፣ ጥንብ
አንሣ አሞራ፣ እርኩም፣ [18]ሽመላ፣ ማናቸውም
ዐይነት ሳቢሳ፣ ጅንጅላቴ ወፍና የሌሊት
ወፍ ናቸው፡፡
[19]ክንፍ ያላቸው ጥቃቅን ነፍሳት ሁሉ ለእና
ንተ ርኩስ ናቸው፤ እነርሱን አትብሏቸው፡፡
[20]ንጹሕ የሆነውን ማናቸውንም ክንፍ ያለውን
ፍጡር ግን ብሉ፡፡
[21]አንተ ግን ለአምላክህ ለእግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ቅዱስ ሕዝብ ነህና የሞተውን
ሁሉ አትብላ፤ ከከተሞችህ በአንዷቱ ለሚኖር
መጻተኛ ስጠው፤ ይብላውም፤ ለውጭ አገር
ሰው ሽጠው። የፍየልን ግልገል በእናቱ
ወተት አትቀቅል፡፡

## ዐሥራት

[22]በየዓመቱ ከእርሻህ ከምታገኘው ምርት
ከዐሥር አንዱን እጅ ለይተህ አስቀምጥ፡፡
[23]ምን ጊዜም አምላክህን እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎ
ሂም) ማክበር ትማር ዘንድ፣ የእሺሉን ወይን ጠ
ጅህንና የዘይትህን ዐሥራት፣ የቀንድ
ከብትህን፣ የበግና የፍየል መንጋህን በኵ
ራት ስሙ እንዲጠራበት በሚመርጠው ስፍ
ራ፣ በአም ላክህ በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ፊት
ብላ፡፡ [24]ነገር ግን አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ
ኤሎሂም) ባርኮህ ሳለ፣ መንገዱ ቢርቅብህና
እግዚአብሔር (ያህዌ) የስሙ ማደሪያ ይሆን
ዘንድ የሚመርጠው ስፍራ ከአንተ
እጅግ ከመራቁ የተነሣ
ዐሥራትህን ወደዚያ ቦታ ማድረስ ካልቻ
ልህ፣ [25]ዐሥራትህን በብር ለውጥ፤ ብሩንም
ይዘህ አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ወደ
ሚመርጠው ስፍራ ሂድ፡፡ [26]በብሩም ደስ
ያለህን ሁሉ ማለትም የቀንድ ከብት፣ በግ፣
የወይን ጠጅ ወይም ሌላ ብርቱ መጠጥ
ወይም የምትሻውን ሁሉ ግዛበት፡፡ ከዚያም
አንተና ቤተሰብህ በአምላክህ በእግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ፊት በዚያ ትበላላችሁ፤ ሐሤትም
ታደርጋላችሁ፡፡ [27]የራሱ ድርሻ ወይም ርስት
ስለሌለው በከተሞችህ የሚኖረውን ሌዋዊ
ቸል አትበለው፡፡
[28]በየሦስት ዓመቱ መጨረሻ የዚያን ዓመት
ሰብል ዐሥራት በሙሉ አውጥተህ በከተሞችህ
ውስጥ አከማች፡፡ [29]ይህን የምታደርገው የራ
ሱ ድርሻ ወይም ርስት የሌለው ሌዋዊና
መጻ ተኛ፣ በከተሞችህ የሚኖሩ አባት
የሌላቸውና መበለቶች መጥተው እንዲ
በሉና እንዲጠግቡ፣ አንተንም አምላክህ
እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በእጅህ ሥራ ሁሉ
እንዲባርክህ ነው፡፡

## ዕዳ የሚተውበት ዓመት

15፥1-11 ማመ - ዘሌ 25፥8-38

**15** በየሰባቱ ዓመት መጨረሻ የዕዳ ምሕ
ረት አድርግ፡፡ [2]አፈጻጸሙም እንደ
ሚከተለው ነው፤ እያንዳንዱ አበዳሪ ለእስ
ራኤላዊ ባልንጀራው ያበደረውን ይተውለት፤
እግዚአብሔር (ያህዌ) የዕዳ ምሕረት አውጆ
አልና፣ አበዳሪው፣ እስራኤላዊ ባልንጀራውን
ወይም ወንድሙን ዕዳውን እንዲከፍለው አይጠ
ይቀው። [3]ለባዕድ ያበደርኸውን መጠየቅ
ትች ላለህ፤ ወንድምህ ከአንተ የተበደረውን
ማናቸ ውንም ዕዳ ግን ተወው፡፡ [4]ይሁን እንጂ
አምላ ክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ትወርሳት
ዘንድ ርስት አድርጎ በሚሰጥህ ምድር ውስጥ
አብዝቶ

[#]5 በዚህ ስፍራ የተጠቀሱት አንዳንድ አዕዋፍና
እንስሳት ማንነታቸው በትክክል አይታወቅም፡፡

13፥18 ዘዳ12፥25
14፥1
ዮሐ1፥12፤ሮሜ8፥14፤
9፥8 14፥2
ዘፍ28፥14፤ዘፀ
8፥22፤22፥31፤ዘሌ20፥
26፤ዘዳ7፥6፤ኢሳ6፥13፤
ሚል2፥15፤ሮሜ12፥1፤
14፥3 ሕዝ4፥14
14፥4 ዘሌ7፥23፤
ሐሥ10፥14፤
14፥5 ዘዳ12፥15፤
ኢዮ39፥1፤መዝ104፥18
14፥8 ዘሌ5፤
14፥13 ዘፍ1፥11፤
ኢሳ34፥15
14፥14 ዘፍ8፥7
14፥17 መዝ102፥6፤
ኢሳ13፥21፤14፥23፤
34፥11፤ሶፎ2፥14
14፥20 ዘሌ20፥25
14፥21 ቆላ2፥
ዘፀ23፥19፤
ዘሌ11፥39፤
14፥22 ዘፍ14፥20፤
ዘኍ18፥21፤ዘሌ27፥30፤
14፥23 ዘዳ4፥10፤
12፥5፥17፥18፤1ነገ3፥2፤
መዝ4፥7፥22፥23፤
33፥8፤ሚል2፥5
14፥25 ማቴ21፥12፤
ዮሐ2፥14
14፥26 ዘሌ10፥9፤
23፥40፤ዘዳ12፥18፤መ
ክ10፥16-17
14፥27 ዘኍ18፥20፤
26፥62፤ዘዳ12፥19፤
18፥1-2
14፥28 ዘሌ27፥30፤
ዘዳ26፥12
14፥29 ዘፍ47፥22፤
ዘኍ26፥62፤ዘዳ6፥11፤
15፥10፤16፥11፤
24፥19-21፤መዝ41፥1፤
94፥6፤ ምሳ22፥9፤
ኢሳ1፥17፤58፥6፤
ሚል3፥10
15፥1 ዘዳ31፥10፤
ነህ10፥31
15፥3 ዘፍ31፥15፤
ዘዳ23፥20፤28፥12፤
ሩት2፥10
15፥4 ዘዳ 28፥8

ስለሚባርክህ፣ በመካከልህ ድኻ አይኖ
ርም፤ [5]ይህ የሚሆነውም *ለአምላክህ* ለእግዚ
አብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ፈጽመህ ስትታዘዝና ዛሬ
የምሰጥህን እነዚህን ትእዛዞች ሁሉ በጥንቃቄ
ስትከተል ብቻ ነው። [6]*አምላክህ* እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) በሰጠህ ተስፋ መሠረት ስለ ሚባር
ክህ፣ አንተ ለብዙ አሕዛብ ታበድራለህ
እንጂ ከማንም አትበደርም፤ ብዙ አሕ
ዛብን ትገዛለህ እንጂ ማንም አንተን አይገ
ዛህም።

[7]*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በሚ
ሰጥህ ምድር ላይ ካሉት ከተሞች ባንዲቱ
ውስጥ ድኻ ቢኖር፣ በድኻ ወንድምህ ላይ
ልብህን አታጨክንበት፤ ወይም እጅህን
ወደ ኋላ አትሰብስብበት። [8]ይልቁንስ እጅህን
ፍታለት፤ የሚያስፈልገውንም ሁሉ ቅር
ሳይልህ አበድረው። [9]“ዕዳ የሚሠረዝበት
ሰባተኛው ዓመት ተቃርቦአል” የሚል ክፉ
ሐሳብ አድሮብህ፣ በችግረኛ ወንድምህ ላይ
እንዳትጨክንና ምንም ሳትሰጠው እንዳት
ቀር፣ እርሱም በአንተ ላይ ወደ *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ጮኾ በደለኛ እንዳትሆን ተጠንቀቅ!
[10]በልግስና ስጠው፤ ስትሰጠውም ልብህ
አይጸጸት፤ ከዚህም የተነሣ *አምላክህ* እግዚ
አብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በሥራህ ሁሉና እጅህ
ባረፈበት በማናቸውም ነገር ይባርክሃል።
[11]በምድሪቱ ላይ ድኾች ምንጊዜም አይጠ
ፉም፤ ስለዚህ በዚያ ለሚኖሩ ወንድሞችህ፣
ለድኾችና ለችግረኞች እጅህን እንድትዘረጋ
አዝሃለሁ።

## አገልጋዮችን ዐርነት ማውጣት

15፥12-18 ተጓ ምብ - ዘፀ 21፥2-6
15፥12-18 ማመ - ዘሌ 25፥38-55

[12]ወገንህ የሆነ ዕብራዊ ወንድን ወይም
ሴትን ገዝተህ ስድስት ዓመት ካገለገለህ፣
በሰባተኛው ዓመት ዐርነት አውጣው። [13]በም
ታሰናብተውም ጊዜ ባዶ እጁን አትስደደው።
[14]ከመንጋህ፣ ከዐውድማህና ከወይን መጭመ
ቂያህ በልግስና ስጠው፤ *አምላክህ* እግዚአብሐ
ር (ያህዌ ኤሎሂም) በባረከህ መጠን ስጠው።
[15]አንተም ራስህ በግብፅ ባሪያ እንደ ነበርህና
*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) እንደ ተቤ
ዠህ አስታ ውስ፤ ይህን ትእዛዝ ዛሬ
የምሰጥህም በዚሁ ምክንያት ነው።

[16]ነገር ግን አገልጋይህ፣ አንተንና ቤተ ሰብህን
ከመውደዱና ከአንተም ጋር ደስተኛ ሆኖ
ከመኖሩ የተነሣ፣ “ከአንተ መለየት አልፈ
ልግም” ቢልህ፣ [17]ጆሮውን ከቤትህ መዝጊያ
ላይ በማስደገፍ በወስፌ ትበሳዋለህ፤ ከዚ
ያም ዕድሜ ልኩን አገልጋይህ ይሆናል።
በሴት አገልጋይህም ላይ እንደዚሁ አድርግ።

[18]አገልጋይህን ዐርነት ማውጣቱ ከባድ

15፥5 ዘፀ15፥26፤
ዘዳ7፥12፤28፥1
15፥6 ዘዳ28፥12-13፡
44
15፥7 ቀኍ11፤
ማቴ26፥11፤
1ዮሐ3፥17
15፥8 ማቴ5፥42፤
ሉቃ6፥34፤
ሐሥ24፥17
15፥9 ቀኍ1፤
ዘፀ22፥23፤ኢዩ5፥15፤
ማቴ20፥15፤ያዕ5፥4
15፥10 2ቆሮ9፥5፤
ዘዳ14፥29
15፥11 ቀኍ7፤
ማቴ26፥11፤
ማር14፥7፤ዮሐ12፥8
15፥12 ኤር34፥14
15፥14 ዘኍ18፥27
15፥15 ዘፀ13፥3፤
20፥2፤ ዘዳ4፥34፤
9፥26፤16፥12፤24፥18፤ኤ
ር16፥14፤23፥7፤
34፥13፤
15፥19 ዘፍ4፥4፤ ዘፀ
13፥2፤22፥30፤
ዘሌ27፥9
15፥20 ዘሌ7፥15-18፤
ዘዳ12፥5-7፥17፥18
15፥21 ዘፀ12፥5፤
ዘሌ22፥19-25፤
ዘዳ17፥1፤ሚል1፥8፥13
15፥22 ዘዳ12፥15
15፥23 ዘፍ9፥4፤
ዘዳ12፥16፤ሕዝ33፥25
16፥1 ዘፀ12፥2፥11፤
2ነገ23፥21፤
ማቴ26፥17-29
16፥2 ዘዳ12፥5፥26
16፥3 ዘፀ12፥8፡
11፥39፤34፥18፤
ዘዳ4፥9፤1ቆሮ5፥8፤
16፥4 ዘፀ12፥6፥8፤
ማር14፥12
16፥6 ዘፀ12፥42
16፥7 ዘፀ12፥8
16፥8 ዘሌ23፥8፤

መስሎ አይታይህ፤ የስድስት ዓመት አገል
ግሎቱ፣ አንድ የቅጥር ሠራተኛ የሚሰጠው
አገልግሎት ዕጥፍ ነውና። *አምላክህ* እግዚ
አብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በምታደርገው ነገር ሁሉ
ይባርክሃል።

## የእንስሳት በኵራት

[19]የቀንድ ከብት፣ የበግና የፍየል መን
ጋዎችህን ተባዕት በኵር ሁሉ *ለአምላክህ*
ለእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ቀድስ። የበሬህን
በኵር አትሥራበት፤ የበግህንም በኵር
አትሸልት፤ [20]እርሱ በሚመርጠው ስፍራ
አንተና ቤተ ሰብህ በየዓመቱ *በአምላክህ*
በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ፊት
ትበሉታላችሁ። [21]አንድ እንስሳ እንከን
ካለበት፣ አንካሳ ወይም ዕውር፣ ወይም
ደግሞ ማናቸውም
ዐይነት ከባድ ጕድለት ያለበት ከሆነ፣ *ለአ
ምላክህ* ለእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) አትሠዋው፤
[22]በየከተሞችህም ትበላዋለህ፤ በሥርዐቱ
መሠረት ንጹሕ የሆነውም ሆነ ያልሆነው
ሰው፣ እንደ ድኵላ እንደ ዋላ ይበላዋል።
[23]ደሙን ግን እንደ ውሃ መሬት ላይ አፍ
ስሰው እንጂ አትብላው።

## ፋሲካ

16፥18-ተጓ ምብ - ዘፀ 12፥14-20፤ ዘሌ 23 4-8፤ ዘኍ 28፥16-25

16 *አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በአቢ
ብ ወር ከግብፅ በሌሊት ስላወጣህ፣
የአቢብን ወር ጠብቅ፤ *የአምላክህን* የእግዚአብሔርን
(ያህዌ ኤሎሂም) ፋሲካ አክብርበት። [2]*እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ለስሙ ማደሪያ ይሆን ዘንድ በሚመርጠው
ስፍራ ከበግና ከፍየል ወይም ከመንጋህ
አንዱን እንስሳ *ለአምላክህ* ለእግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ፋሲካ አድርገህ ሠዋው። [3]ከቦካ
ቂጣ ጋር አትብላው፤ ከግብፅ የወጣኸው
በችኰላ ነውና ከግብፅ የወጣህበትን ጊዜ
በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ታስብ ዘንድ የመከራ
ቂጣ ሰባት ቀን ብላ። [4]በምድርህ ሁሉ ላይ
በአንተ ዘንድ ለሰባት ቀን እርሾ አይገኝ፤
በመጀመሪያው ዕለት ምሽት ከምትሠዋውም
ላይ ማናቸውንም ሥጋ ጧት ድረስ እንዲቈይ
አታድርግ።

[5]*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በሚሰ
ጥህ በማናቸውም ከተማ ፋሲካን መሠ
ዋት አይገባህም፤ [6]ነገር ግን ለስሙ ማደሪያ
ይሆን ዘንድ *አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
በሚመርጠው ስፍራ፣ ፀሐይ ስትጠልቅ
ምሽቱ[ሡ] ላይ ከግብፅ በወጣህበት ሰዓ
ት ዓመታዊ መታሰቢያ (በዚያ) ፋሲካን
ሠዋ። [7]ሥጋውንም ጠብሰህ *አምላክህ* እግዚ
አብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በሚመርጠው ስፍራ ብላ፤ ሲ
ነጋም ወደ ድንኳንህ ተመልሰህ ሂድ።

ሡ6 ወይም፣ *ፀሐይ ስትወጣ ንጋቱ ላይ*፡

[8]ስድስት ቀን ያልቦካ ቂጣ ብላ፤ በሰባተኛው
ቀን ለአምላክህ ለእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) የተ
ቀደሰ ጉባኤ አድርግ፤ ሥራም አትሥራበት።

## የመከር በዓል

16፥19-12 ተጓ ምብ - ዘሌ 23፥15- 22፤ ዘኍ 28፥26- 31

[9]እህልህን ማጨድ ከምትጀምርበት
ዕለት አንሥቶ ሰባት ሳምንት ቍጠር፤
[10]ከዚያም በኋላ አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
በባረከህ መጠን፣ በፈቃድህ የምታመጣውን
ስጦታ በማቅረብ የመከሩን በዓል አምላክህን
እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) አክብር። [11]አንተ፣
ወንዶችና ሴቶች ልጆችህ፣ ወንዶችና ሴቶች
አገልጋዮችህ፣ በከተሞችህ ያለ ሌዋዊና
መጻ ተኛ በመካከልህ የሚኖሩ አባት
የሌላቸውና መበለቶች አምላክህ እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ለስሙ ማደሪያ እንዲሆን
በሚመርጠው ስፍራ በአ ምላክህ በእግዚአብሐ
ር (ያህዌ ኤሎሂም) ፊት ደስ ይበላችሁ። [12]አንተም
በግብፅ ባሪያ እንደነ
በርህ አስታውስ፤ ይህንንም በጥንቃቄ ጠብቅ።

## የዳስ በዓል

16፥13-17 ተጓ ምብ ዘሌ 23፥33-43 ዘኍ 29፥12-39

[13]የእህልህን ምርት ከዐውድማህ፣ ወይንህ
ንም ከመጭመቂያህ ከሰበሰብህ በኋላ፣ የዳስን
በዓል ሰባት ቀን አክብር። [14]በበዓልህ አንተ፣
ወንድና ሴት ልጅህ፣ ወንድና ሴት አገልጋይህ፣
በከተማው ያለሌዋዊ፣ መጻተኛ፣ አባት አልባ
ውና መበለቲቱ ደስ ይበላችሁ። [15]እግዚ
አብሔር (ያህዌ) በመረጠው ስፍራ ለአምላክህ
ለእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በዓሉን ሰባት ቀን
አክብር፤ አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
በእ ህል ምርትህና በጅህ ሥራ ሁሉ
ይባርክሃል፤ ደስታህም ፍጹም ይሆናል።
[16]ወንዶችህ ሁሉ በዓመት ሦስት ጊዜ፣
በቂጣ በዓል፣ በመከር በዓልና በዳስ በዓል
ላይ፣ እርሱ በሚመርጠው ስፍራ በአምላክህ
በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ፊት ይቅረቡ፤ ማንም
ሰው በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ባዶ እጁን
አይቅረብ። [17]አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
በባረከህ መጠን እያንዳንዱ እንደ ችሎታው
ይስጥ።

## ስለ ፍርድ አሰጣጥ

[18]አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በሚሰጥህ
ከተሞች ሁሉ ለየነገዶችህ ዳኞችንና አለቆችን
ሹም፤ እነርሱም ሕዝቡን በቅን ፍርድ
ይዳኙ። [19]ፍርድ አታዛባ፤ አድልዎ አታድርግ፤
ጉቦም አትቀበል፤ ጉቦ የጠቢባንን ዐይን
ያሳውራል፤ የጻድቃንንም ቃል ያጣም
ማልና። [20]በሕይወት እንድትኖርና አምላክህ
እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) የሚሰጥህን ምድር
እንድትወርስ፣ ቅን ፍርድን ብቻ ተከተል።

## ሌሎችን አማልክት ስለ ማምለክ

ማቴ26፥17፤
ሉቃ2፥41፤22፥7፤
ዮሐ2፥13
16፥9 ዘፀ23፥16፤
ሐሥ2፥1
16፥11 ዘፀ20፥24፤
ዘዳ12፥7፤ዘዳ12፥12፤1
4፥29፤2ሳሙ7፥13፤ነህ
8፥10
16፥12 ዘዳ15፥15
16፥13 ዘፍ27፥37፤
ዘፀ23፥16ዘሌ2፥14፤
16፥14 ቀኍ11
16፥15 ኢዮ38፥7፤
መዝ4፥7፤28፥7፤30፥11
16፥16 ዘፀ12፥17፤
23፥14፥16፤34፥20፤
ዘዳ31፥11፤መዝ84፥7፤ዕ
ዝ3፥4
16፥18 ዘፍ31፥37፤
ዘፀ18፥21፥26፤
16፥19 ዘፀ18፥21፤
23፥2፤ዘሌ19፥15፤
1ሳሙ8፥3
16፥21 ዘፀ34፥13፤
ዘዳ7፥5፤1ነገ14፥15፤
2ነገ17፥16፤21፥3፤
2ዜና33፥3
16፥22 ዘፀ23፥24
17፥1 ዘፀ12፥5፤
ዘሌ22፥20፤ዘዳ7፥25፤1
5፥21
17፥2 ዘዳ13፥6-11
17፥3 ዘፍ1፥16፤
2፥1፤37፥9፤ዘፀ22፥20፤
ኤር7፥31
17፥4 ዘዳ22፥20፤
13፥12-14
17፥5 ዘሌ24፥14
17፥6 ዘኍ35፥30፤
ዘዳ19፥15፤ማቴ18፥16
17፥7 ዘሌ24፥14፤
ዘዳ13፥5፤ሐሥ7፥58፤
ዮሐ8፥7፤1ቆሮ5፥13
17፥8 ዘፀ21፥6፤
ዘዳ12፥5፤2ዜና19፥10፤
መዝ122፥3-5
17፥9 ዘፍ25፥22፤
ዘፀ21፥6፤ዘዳ19፥17፤
24፥8፤27፥9፤
ሕዝ44፥24፤ሐጌ2፥11
17፥11 ዘሌ10፥11፤
ዘዳ5፥32
17፥12 ቀኍ13፤
ዘፍ17፥14፤ዘኍ15፥30፤
16፥9፤ዘዳ13፥5፥11፤
18፥20፤19፥20፤
1ነገ18፥40፤ኤር14፥14፤ሆ
ሴ4፥4፤ዘካ13፥3

[21]ለአምላክህ ለእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
በምትሠራው መሠዊያ አጠገብ የኤሼራን
ምስል የዕንጨት ዐምድ አታቁም[የ]።
[22]አምላክህ
እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) የሚጠላውን ማምለኪ
ያ
ዐምድ ለአንተ አታቁም።

17 እንከን ወይም ጕድለት ያለበትን በሬ
ወይም በግ በእርሱ ዘንድ አስ
ጸያፊ ነውና ለአምላክህ ለእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎ
ሂም) አትሠዋ።
[2]እግዚአብሔር (ያህዌ) በሚሰጥህ ከተሞች በአ
ንዲቱ አብሮህ የሚኖር ወንድ ወይም ሴት
ኪዳኑን በማፍረስ በአምላክህ በእግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ፊት ክፉ ድርጊት ሲፈጽም ቢ
ገኝ፣ [3]ትእዛዜንም በመተላለፍ ባዕዳን አማ
ልክትን ያመለከ፣ ለእርሱም ማለትም ለፀ
ሓይ ወይም ለጨረቃ ወይም ለሰማይ
ከዋክብት የሰገደ፣ [4]አንተም ይህ መደረጉን
ብትሰማ፣ ነገሩን በጥንቃቄ መርምር፤
የተባለውም እውነት ከሆነና እንዲህ ያለው
አስጸያፊ ነገር በእስራኤል ዘንድ መፈጸሙ
ከተረጋገጠ፣ [5]ይህን ክፉ ድርጊት የፈ
ጸመውን ወንድ ወይም ሴት ወደ ከተማ
ደጅ ወስደህ፣ ያን ሰው እስኪሞት ድረስ
በድንጋይ ውገረው። [6]ሞት የሚገባው
ሰው፣ በሁለት ወይም በሦስት ሰዎች
ምስክርነት ይገደል፤ ነገር ግን በአንድ ሰው
ምስክርነት ብቻ ማንም ሰው አይገደል። [7]ሲ
ገደልም መጀመሪያ የምስክሮቹ እጅ፣
ቀጥሎም የሕዝቡ ሁሉ እጅ ይረፍበት፤
ክፉን ከመ ካከልህ አስወግድ።

## የፍርድ አደባባይ

[8]በአንድ የነፍስ ግድያ ዐይነትና በሌላ፣
በአንድ
ዐይነት ሕጋዊ ክርክርና በሌላ፣ ወይም በአ
ንድ የክስ ዐይነትና በሌላ መካከል ውሳኔ
የሚጠይቅ ማንኛውም ጕዳይ ቢነሣ፣ ከዐ
ቅምህ በላይ የሆነ ጕዳይ በከተሞችህ ውስጥ
ቢያጋጥምህ፣ ተነሥተህ አምላክህ እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ወደሚመርጠው ስፍራ ውጣ፤
[9]ካህናት ወደ ሆኑት ሌዋውያንና በዚያን ጊዜ
ዳኛ ወደ ሆነው ሰው ሄደህ፣ ስለ ጕዳዩ ጠይ
ቃቸው፤ እነርሱም ውሳኔውን ይነግሩሃል።
[10]አንተም እግዚአብሔር (ያህዌ) በሚመርጠው
ስፍራ እነርሱ በሚሰጡህ ውሳኔ መሠረት ፈ
ጽም፤ እንድትፈጽም የሚሰጡህን መመሪያ
ሁሉ በጥንቃቄ አድርግ። [11]በሚያስተምሩህ
ሕግና በሚሰጡህ መመሪያዎች መሠረት
ፈጽም። እነርሱ ከሚነግሩህ ቀኝም ግራም
አት በል። [12]አምላክህን እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም)
ለማ ገልገል በዚያ የሚቆመውን ካህን
ወይም ዳኛ

[የ]21 ወይም፣ ለአሼራ ብለህ ምንም ዐይነት ዛፍ አትትከል።

የሚንቅ ይገደል፤ ከእስራኤልም መካከል ክፉ
ውን አስወግድ:: 13ሕዝቡም ሁሉ ይህን ሲሰማ
ይፈራል፤ ከዚያ ወዲያም እንዲህ ያለውን
የንቀት ድርጊት አይደግመውም::

## ንጉሥን ስለማንገሥ

14*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ወደ ሚሰ
ጥህ ምድር ስትገባ፣ በምትወርሳትና በም
ትቀመጥባት ምድር፣ “በዙሪያዬ እንዳሉት
አሕዛብ ሁሉ፣ እኔም በላዬ ንጉሥ ላንግሥ”
ብትል፣ 15*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
የሚመርጠውን ንጉሥ በላይህ ታነግሣለህ፤
ከገዛ ወንድሞችህ መካከል እንጂ፣ እስራኤላዊ
ወንድምህ ያልሆነውን ባዕድ በላይህ
አታንግሥ:: 16ንጉሡም ብዙ ፈረሶችን
ለራሱ አያብዛ፤ ወይም ደግሞ የፈረሰኞችን
ቍጥር ለመጨመር ሕዝቡን ወደ ግብፅ
አይመልስ፤ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)፣ “በዚያ
መንገድ ፈጽሞ አትመለሱ” ብሎአችኋልና::
17ልቡ እንዳይስትም ብዙ ሚስቶችን አያግባ፤
ብዙ ብርና ወርቅም አያግበስብስ::
18በመንግሥቱ ዙፋን ላይ በሚቀመጥበትም
ጊዜ የዚህን ሕግ ቅጅ ከሌዋውያን ካህናት
ወስዶ በጥቅልል መጽሐፍ ለራሱ ይጻፍ::
19*አምላኩን* እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) ማክበር
ይማር ዘንድ፣ የዚህን ሕግ ቃል ሁሉና
ይህን ሥርዐት በጥንቃቄ ይከተል ዘንድ
ከእርሱ ጋር ይሁን፤ በሕይወቱ ዘመን ሁሉ
ያንብበው፤ 20እርሱና ዘሮቹ በእስራኤል ላይ
ረጅም ዘመን ይገዙ ዘንድ፣ ከሕጉ ቀኝም ግ
ራም አይበል፤ ራሱን ከሌሎች ወንድሞቹ
በላይ የተሻለ አድርጎ አይቍጠር::

## የካህናትና የሌዋውያን የመባ ድርሻ

18 ሌዋውያን ካህናት፣ የሌዊ ነገድም
ሁሉ ከእስራኤል ጋር የመሬት ድርሻ
ወይም ርስት አይኖራቸውም፤ *ለእግዚአብሔ
ር* (ያህዌ) በእሳት ከሚቀርበው መባ ይብሉ፣
ድር ሻቸው ነውና:: 2በወንድሞቻቸው መካከል
ርስት አይኖራቸውም፤ በሰጣቸው ተስፋ መ
ሠረት *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ርስታቸው ነው::
3ኮርማ ወይም በግ የሚሠዋው ሕዝብ
ለካህኑ የሚሰጠው ድርሻ ወርቹን፣ መንገጭላ
ውንና ሆድ ዕቃውን ነው:: 4የእህልህን፣
የአዲሱን ወይንህንና የዘይትህን በኵራት እንዲ
ሁም ከበጎችህ በመጀመሪያ የተሸለተውን
ጠጕር ትሰጣለህ፤ 5*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ስም
ቆሞ ለዘላለም ያገለግል ዘንድ *አምላክህ* እግ
ዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ከነገዶችህ ሁሉ
እርሱንና ዘሮቹን መርጦአል::
6አንድ ሌዋዊ ከሚኖርበት ከየትኛውም
በእስራኤል ካሉት ከተሞችህ መካከል በፍ
ጹም ፈቃድ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ወደሚመ

17፥13 ቍ12
17፥14 ዘኍ33፥53፤
ኢ.ሱ21፥43፤
1ሳሙ8፥5፤19-20፤
10፥19
17፥15 1ሳሙ16፥3፤
2ሳሙ5፥3፤
ኤር30፥21
17፥16 ዘፀ13፥17፤
1ሳሙ8፥11፤1ነገ4፥26፤9
፥19፤10፥26፡28፡29፤2ዜ
ና1፥14፤መዝ20፥7፤ኢ.
ሳ2፥7፤30፥16፤
31፥1፤ኤር42፥14፤ ሕ
ዝ17፥15፤
17፥17 ዘፀ34፥16፤
2ሳሙ5፥13፤12፥11፤1
ነገ10፥27፤11፥2፡3፤2ዜ
ና1፥11፤11፥21፤ምሳ3
1፥3፤ኢ.ሳ2፥7
17፥18 ዘዳ31፥22፡
24፤ኢ.ሱ24፥26፤
1ሳሙ10፥25፤
1ነገ1፥46፤1ዜና29፥23፤
2ዜና23፥11
17፥19 ዘዳ4፥9-10፤
11፥13፤ኢ.ሱ1፥8፤
1ነገ3፥3፤11፥38፤
2ነገ22፥2
17፥20 ዘዳ5፥32፤ ኢ.
ሱ23፥6፥12፤
1ሳሙ8፥5፤10፥25፤
1ነገ2፥3፤
9፥4፤1ዜና28፥8፤
መዝ119፥102
18፥1 ዘኍ18፥8፡20፤
ኤር33፥18፡21፤
1ቆሮ9፥13
18፥2 ዘኍ18፥20፤
ኢ.ሱ13፥14 18፥3
ዘፀ29፥27፤ዘሌ1፥5፤
7፥28-34፤ ዘኍ18፥12
18፥4 ዘፀ22፥29፤
ዘኍ18፥12
18፥5 ዘፀ28፥1፤
29፥9፤ዘዳ10፥8
18፥6 ዘኍ35፥2-3፤
ዘዳ12፥5
18፥7 ቍ19፤
1ነገ18፥32፤22፥16፤መ
ዝ118፥26
18፥8 ዘኍ18፥24፤
2ዜና31፥4፤ነህ12፥44፡
47፤13-12
18፥9 ዘሌ18፥3፤
ዘዳ9፥5፤12፥29-31፤
2ነገ21፥2፤2ዜና28፥3፤33
፥2፤34፥33፤
ዕዝ6፥21፤9፥11፤
ኤር44፥4
18፥10 ዘፀ7፥11፤
ዘሌ18፥21፤19፥31፤
1ሳሙ15፥23
18፥11 ዘፀ22፥18፤
1ሳሙ28፥13፤
ኢ.ሳ47፥9
18፥12 ዘሌ18፥24
18፥13 ዘፍ6፥9፤
መዝ119፥1፤ማቴ5፥48
18፥14 2ነገ21፥6

ርጠው ስፍራ ቢመጣ፣ 7*በእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ፊት ቆመው እንደሚያገለግሉት ሌዋውያን
ወንድሞቹ፣ እርሱም *በአምላኩ* በእግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ስም ያገልግል:: 8ከቤተ ሰቡ
ንብረት ሽያጭ ላይ ገንዘብ ቢቀበል እንኳ፣
ባልንጀሮቹ ከሚያገኙት ጥቅም እኩል ይካፈላል::

## አስጸያፊ ድርጊቶች

9*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
ወደሚሰጥህ ምድር በምትገባበት ጊዜ፣ በዚ
ያ የሚኖሩት አሕዛብ የሚፈጽሙትን አስ
ጸያፊ መንገድ አትከተል:: 10በመካከልህ
ወንድ ወይም ሴት ልጁን በእሳት የሚ
ሠዋ[ደ] ማርተኛ፣ ወይም መተተኛ፣ ሞራ
ገላጭ፣ ጠንቋይ 11ወይም በድግምት የሚጠ
ነቍል፤ መናፍስት ጠሪ ወይም ሙት
አነጋጋሪ በመካከልህ ከቶ አይገኝ:: 12እነዚ
ህን የሚያደርግ ሁሉ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ)
ዘንድ አስጸያፊ ነውና፣ ከእነዚህ አጸያፊ
ልምዶች የተነሣም *አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ
ኤሎሂም) እነዚያን አሕዛብ ከፊትህ ያባርራቸዋል::
13*በአምላክህ* በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ፊት
ነውር አልባ ሁን::

## ነቢይ ስለ መነሣቱ

14ምድራቸውን የምታስለቅቃቸው አሕዛብ፣
መተተኞችን ወይም ማርተኞችን ያዳምጣሉ፤
አንተ ግን ይህን እንድታደርግ *አምላክህ*
እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) አልፈቀደልህም:: 15*አምላክህ*
እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ከገዛ ወንድሞችህ መካ
ከል እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል፤
እርሱን አድምጥ:: 16በኮሬብ ጉባኤ በተደ ረገ
በት ዕለት፣ “እንዳልሞት *የአምላክህ* የእግዚአ
ብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) ድምፅ አልስማ፤ እንዲህ
ያለውንም አስፈሪ እሳት ደግሜ አልይ”
ብለህ *አምላክህን* እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎ
ሂም) የጠየቅኸው ይህን ነውና::
17*እግዚአብሔር* (ያህዌ) እንዲህ አለኝ፤ ‘የተናገሩ
ት መልካም ነው፤ 18ከወንድሞቻቸው
መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ
አስነሣላቸዋለሁ፤ ቃሌን በአፉ አደርጋለሁ፤
የማዝዘውንም ሁሉ ይነግራቸዋል:: 19ማንም
ሰው ነቢዩ በስሜ የሚናገረውን ቃሌን ባይሰ
ማ፣ እኔ ራሴ በተጠያቂነት እይዘዋለሁ:: 20ነገር
ግን እንዲናገር እኔ ያላዘዝሁትን ቃል
በድፍረት በስሜ የሚ ናገርም ሆነ በሌሎች
አማልክት ስም የሚና ገር ነቢይ ይገደል::”
21አንተም በልብህ፣ “*እግዚአብሔር* (ያህዌ)

18፥15 ማቴ21፥11፤ ሉቃ2፥25-35፤ ዮሐ1፥21፤ሐሥ3፥22፤ 7፥37
18፥16 ዘፀ20፥19፤ ዘዳ5፥23-27 18፥18 ዘፍ20፥7፤ዘፀ4፥12፤
ኢ.ሳ2፥3፤ 26፥8፤51፥4፤ ሚክ4፥2፤ ዮሐ4፥25-26፤ 14፥24፤
ሐሥ3፥22 18፥19 ቍ7፤ ዘፀ23፥21፤ ዘሌ19፥12፤2ነገ2፥24፤
ኢ.ሱ22፥23፤ሐሥ3፥23፤ዕ 12፥25 18፥20 ዘፀ23፥13፤ዘዳ13፥1-5፤
17፥12

[ደ]10 ወይም፣ *ወንድ ወይም ሴት ልጁን የሚገድል*::

ያልተነገረውን መልእክት እንዴት ማወቅ እንችላለን?” ብትል፣ 22ነቢዩ *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ስም የተናገረው ካልተፈጸመ ወይም እውነት ሆኖ ካልተገኘ፣ መልእክቱ *እግዚ አብሔር* (ያህዌ) የተናገረው አይደለም። ያ ነቢይ በድፍረት ተናግሮታልና እርሱን አትፍራው።

## መማጸኛ ከተሞች

19፥1–14 *ማመ* – *ዘኍ* 35፥6-34፤ *ዘዳ* 441-43፤ *ኢሱ* 2፥1-9

19 *አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ምድራቸውን ለአንተ የሚሰጥባቸውን አሕዛብ በሚደመስሳቸው ጊዜና አንተም እነርሱን አስለቅቀህ በከተሞቻቸውና በቤቶቻቸው በምትቀመጥበት ጊዜ፣ 2*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ርስት አድርጎ በሚሰጥህ ምድር አማካይ ስፍራ፣ ሦስት ከተሞችን ለራስህ ለይ። 3ሰው የገደለ ሁሉ እንዲሸሽባቸው *አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ርስት አድርጎ በሚሰጥህ ምድር መንገዶችን ሥርተህ፣ በሦስት ክፈላቸው።

4በተንኰል ሳይሆን ድንገት ሳያስበው ባልንጀራውን ገድሎ ሕይወቱን ለማትረፍ ለሚሸሽ ሰው መመሪያው የሚከተለው ነው። 5እነሆ፤ አንድ ሰው ከባልንጀራው ጋር እንጨት ለመቍረጥ ወደ ጫካ ቢሄድ፣ ዛፉን ለመጣል መጥረቢያውን በሚሰነዝርበት ጊዜ ብረቱ ከእጀታው ወልቆ ባልንጀራውን በመምታት ቢገድለው፣ ያ ሰው ከእነዚህ ከተሞች ወደ አንዱ በመሸሽ ሕይወቱን ማትረፍ ይችላል። 6አለበለዚያ በተንኰል ሳይሆን ድንገት ሳያስበው ባልንጀራውን ቢገድል፣ መንገዱ ረጅም ከሆነ ደም ተበቃዩ በንዴት ተከታትሎ ይደርስበትና፣ መገደል የማይገባውን ሰው ሊገድል ይችላል። 7ሦስት ከተሞችን ለራስህ እንድትለይ ያዘዝሁህ በዚሁ ምክንያት ነው።

8ለአባቶችህ በመሐላ በገባላቸው ቃል መሠረት *አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ወሰንህን ሲያሰፋ ውና ለእነርሱ በሰጣቸው መሠረት ምድሪቷን ሁሉ ሲሰጥህ፣ 9*አምላክህን* እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) እንድትወድና ምንጊዜም በመንገዱ እንድትሄድ ዛሬ የማዝህን እነዚህን ሕግጋት ሁሉ በጥንቃቄ የምትጠብቅ ከሆነ፣ በእነዚህ ላይ ሌሎች ሦስት ከተሞችን ትጨምራለህ። 10*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ርስት አድርጎ በሚሰጥህ ምድር የንጹሕ ሰው ደም እንዳይፈስና በሚፈሰውም ደም በደለኛ እንዳትሆን ይህን አድርግ።

11ይሁን እንጂ አንድ ሰው ባልንጀራውን ቢጠላው፣ አድፍጦ ጥቃት ቢያደርስበት፣ ቢገድለውና፣ ከእነዚህ ከተሞች ወደ አንዲቱ ቢሸሽ፣ 12የሚኖርባት ከተማ ሽማግሌዎች ሰው ልከው ከከተማው ያስመጡት፤ እንዲገድለውም ለደም ተበቃዩ አሳልፈው ይስጡት።

13አትራራለት፤ ነገር ግን መልካም እንዲሆንልህ የንጹሑን ደም በደል ከእስራኤል አስወግድ።

14*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) እንድትወርሳት በሚሰጥህ ምድር ውስጥ ለአንተ በሚተላለፍልህ ርስት ላይ የቀድሞ ሰዎች ያስቀመጡትን የባልጀራህን የድንበር ምልክት አታንሣ።

## ምስክሮች

15የማንኛውም ወንጀል ወይም ሕግ በመተላለፍ ሰውን ጥፋተኛ ለማድረግ፣ አንድ ምስክር አይበቃም፤ ጉዳዩ በሁለት ወይም በሦስት ሰዎች ምስክርነት መረጋገጥ አለበት።

16ተንኰለኛ የሆነ ምስክር አንድን ሰው በሐሰት ቢከስ፣ 17ክርክሩ የሚመለከታቸው ሁለቱ ሰዎች *በእግዚአብሐር* (ያህዌ) ፊት፣ በዚያ ወቅት በሚያገለግሉት ካህናትና ፈራጆች ፊት ይቁሙ። 18ፈራጆችም ጉዳዩን በጥልቅ ይመርምሩት፤ ያም ምስክሩ በወንድሙ ላይ በሐሰት የመሰከረ መሆኑ ከተረጋገጠ፣ 19በወንድሙ ላይ ለማድረግ ያሰበውን በእርሱ ላይ አድርጉበት፤ ክፉውን ከመካከልህ አስ ወግድ። 20የቀሩትም ሰዎች ይህን ሰምተው ይፈራሉ፤ እንዲህ ያለው ክፉ ነገርም ለወደፊቱ በመካከልህ ከቶ አይደገምም። 21ርኅራኄ አታድርግ፤ ሕይወት በሕይወት፣ ዐይን በዐይን፣ ጥርስ በጥርስ፣ እጅ በእጅ፣ እግር በእግር ይመለስ።

## ለጦርነት መውጣት

20 ጠላቶችህን ለመውጋት ወደ ጦርነት ስትሄድ፣ ሠረገሎችንና ፈረሶችን ከአንተ የሚበልጥ ሰራዊትንም በምታይበት ጊዜ አት ፍራቸው፤ ከግብፅ ያወጣህ *አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ከአንተ ጋር ነውና። 2ወደ ውጊያው ቦታ ስትቃረቡ፣ ካህኑ ወደ ፊት ወጣ ብሎ ለሰራዊቱ ይናገር፤ 3እንዲህም ይበል፤ “እስራኤል ሆይ ስማ፤ በዛሬው ቀን ጠላ ቶቻችሁን ለመግጠም ወደ ጦርነት ልትገቡ ነው፤ ልባችሁ አይባባ፤ አትፍሩ፤ አትደንግጡ፤ በጠላቶቻችሁ ፊት አትሸበሩ፤ 4ድልን ያቀዳጃችሁ ዘንድ ስለ እናንተ ጠላቶቻችሁን ሊወጋ አብሮአችሁ የሚወጣው *አምላካችሁ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎ ሂም) ነውና።”

5አለቆቹም ለሰራዊቱ እንዲህ ይበሉ፤ “አዲስ ቤት ሠርቶ ያላስመረቀ አለን? ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሂድ፤ ያለበለዚያ በጦርነቱ ላይ ይሞትና ቤቱን የሚያስመርቀው ሌላ ሰው ይሆናል። 6ወይን ተክሎ ገና ያልበላለት አለን? ወደ ቤቱ ይመለስ፤ ያለበለዚያ በጦርነቱ ላይ ይሞትና ወይኑን ሌላ ሰው ይበላዋል። 7ሚስት አጭቶ ያላገባት አለን? ወደ ቤቱ

18፥22 ቀኁ20፤ ዘዳ13፥2፤1ሳሙ3፥20፤1 ነገ22፥28፤ኤር28፥9
19፥1 ዘዳ6፥10-11
19፥6 ዘኍ35፥12
19፥8 ዘፍ15፥8፤ ዘፀ 34፥24፤ዘዳ11፥24
19፥9 ዘዳ6፥5
19፥10 ዘዳ21፥1-9፤ ምሳ6፥17፤ኤር7፥6፤ 26፥15
19፥11 ዘፀ21፥12፤ 1ዮሐ3፥15
19፥13 ዘዳ7፥2፤ 21፥9፤1ነገ2፥31
19፥14 ዘዳ27፥17፤ ኢዮ24፥2፤ ምሳ15፥25፤22፥28፤ 23፥10፤መዝ16፥6፤ ኢ ሳ1፥23፤ሆሴ5፥10
19፥15 ዘዳ17፥6፤ ማቴ18፥16፤26፥60፤2 ቆሮ13፥1
19፥16 ዘፀ23፥1፤ ምሳ6፥19
19፥17 ዘፀ21፥6
19፥18 ዘፀ23፥7
19፥19 ምሳ19፥5፡ 9፤1ቆሮ5፥13
19፥20 ዘዳ13፥11
19፥21 ቀኁ13፤ ዘፀ21፥24፤ማቴ5፥38
20፥1 ዘኍ14፥9፤ ዘዳ3፥22፤1ሳሙ17፥45፤ መዝ20፥7፤ኢሳ31፥1፤ 41፥10
20፥3 1ሳሙ17፥32፤ ኢዮ23፥16፤መዝ22፥14፤ ኢሳ7፥4፤35፥4፤ ኤር51፥46
20፥4 ዘፀ14፥14፤ 1ዜና5፥22፤ 2ዜና20፥14-22፤ ነህ4፥20፤መሳ12፥3፤ 15፥18፤መዝ44፥7፤ 144፥10
20፥5 ነህ12፥27
20፥6 ኤር31፥5፤ ሕዝ28፥26፤ ሚክ1፥6፤1ቆሮ9፥7
20፥7 ዘዳ24፥5፤ ምሳ5፥18

ይመለስ፤ ያለበለዚያ በጦርነቱ ይሞትና
ሌላ ሰው ያገባታል::” [8]ከዚያም አለቆቹ፣ “የሚ
ፈራ ወይም ልቡ የሚባባ ሰው አለን? የወን
ድሞቹም ልብ እንዳይባባ ወደ ቤቱ ይመለስ”
በማለት ጨምረው ይናገሩ::
[9]አለቆቹ ለሰራዊቱ ተናግረው ሲያበቁ፣
አዛዦችን በሰራዊቱ ላይ ይሹሙ::
[10]አንድን ከተማ ለመውጋት በምትዘም
ትበት ጊዜ፣ አስቀድመህ ለሕዝቧ የሰላም
ጥሪ አስተላልፍ፤ [11]ከተቀበሉህና ደጃቸውን
ከከፈቱልህ በከተማዋ ውስጥ ሕዝብ ሁሉ
ገባርህ ይሁን፤ ያገልግልህም:: [12]ዕርቀ ሰላምን
ባለመቀበል ውጊያን ከመረጡ፤ ከተማዪቱን
ክበባት:: [13]*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) አሳ
ልፎ በእጅህ በሰጠህ ጊዜ፣ በውስጧ
ያሉትን ወንዶች በሙሉ በሰይፍ ግደላቸው::
[14]ነገር ግን ሴቶቹን ሕፃናትን፣ እንስሳቱንና
በከተማዪቱ ውስጥ የሚገኘውን ማናቸውንም
ነገር በምርኮ ለራስህ አድርግ *አምላክህ* እግዚ
አብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ከጠላቶችህ የሚሰጥህን
ምርኮ ልትጠቀምበት ትችላለህ:: [15]እንግዲህ
የአካባቢህ አሕዛብ ከተሞች ባልሆኑትና
ከአንተ እጅግ ርቀው በሚገኙት ከተሞች
ሁሉ ላይ የምታደርገው ይኸው ነው::
[16]*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ርስት
አድርጎ በሚሰጥህ በአሕዛብ ከተሞች ውስጥ፣
እስትንፋስ ያለውን ነገር አታስተርፍ፤ [17]ኬጢ
ያዊውን፣ አሞራዊውን፣ ከነዓናዊውን፣
ፌርዛዊ ውን፣ ኤዊያዊውን፣ ኢያቡሳዊውን
*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ባዘዘህ መሠረት
ፈጽመህ ደምስሳቸው[ጀ]፤ [18]አለበለዚያ አ
ማልክታቸውን በሚያመልኩበት ጊዜ የሚፈ
ጽሟቸውን አስጸያፊ ተግባራት ሁሉ
ታደርግ ዘንድ ያስተ ምሩሃል፤ *በአምላክህ*
በእግዚአብሔርም (ያህዌ ኤሎሂም) ላይ ኀጢአት ትሠ
ራለህ::
[19]አንድን ከተማ ተዋግተህ ለመያዝ የረጅም
ጊዜ ከበባ ካደረግህ፣ ዛፎቹን በመጥረቢያ
ጨፍጭፈህ አታጥፋ፤ የእነርሱን ፍሬ
መብላት ትችላለህና አትቍረጣቸው፤ ከበህ
የምታጠፋቸው የሜዳ ዛፎች ሰዎች ናቸውን?[ገ]
[20]የሚበላ ፍሬ እንደማያፈራ የምታውቀውን
ዛፍ ግን ልትቈርጠውና ጦርነት የምታካ
ሄድባትን ከተማ በድል እስክትቈጣጠራት
ድረስ ለከበባው ምሽግ መሥሪያ ልትጠ
ቀምበት ትችላለህ::

**ገዳዩ ሳልታወቀ ሰው ስለሚቀርብ ማስተስረያ**

**21** *አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
እንድትወርሳት በሚሰጥህ ምድር
አንድ ሰው ተገድሎ ሜዳ ላይ ቢገኝና
ገዳዩም ማን እንደ ሆነ ባይታወቅ፣ [2]ሽማግ
ሌዎችህና ዳኞችህ ወጥተው ሬሳው ወድቆ
ከተገኘበት አንሥቶ በአቅራቢያው እስካሉት

20፥8 መሳ7፥3
20፥10 ዘዳ2፥26፤ ሉቃ14፥31-32
20፥11 ቀኍ15፤ 1ነገ9፥21፤2ነገ6፥22፤1 ዜና22፥2፤ኢሳ31፥8
20፥13 ዘኍ31፥7
20፥14 ዘኍ31፥11፡ 53፤ኢሱ8፥2፤22፥8
20፥15 ቀኍ11፤ ኢሱ9፥9
20፥16 ዘፀ23፥31-33፤ ዘኍ21፥2-3፤ ዘዳ7፥2፤ኢሱ6፥21፤ 10፥1፤11፥14
20፥18 ዘፀ10፥7፤ 34፥16
20፥20 ኤር6፥6
21፥1 ዘኍ25፥17
21፥3 ዘኍ19፥2
21፥5 ዘፍ48፥20፤ ዘፀ39፥43፤ዘዳ17፥8-11
21፥6 ማቴ27፥24
21፥8 ዘኍ35፥33-34
21፥9 ዘዳ19፥13
21፥10 ኢሱ21፥44፤ 1ነገ8፥46፤1ዜና9፥1፤ ዕዝ5፥12፤ኤር40፥1፤ ሕዝ1፥1፤17፥12፤ ዳን2፥25፤ሚክ4፥10
21፥11 ዘፍ6፥2፤ 34፥8
21፥12 ዘሌ14፥9፤ ዘኍ8፥7፤1ቆሮ11፥5
21፥13 መዝ45፥10
21፥14 ዘፍ34፥2
21፥15 ዘፍ4፥19፤ 29፥33
21፥16 1ዜና26፥10

ከተሞች ድረስ ያለውን ርቀት ይለኩ:: [3]ከዚ
ያም ሬሳው ወድቆ ከተገኘበት ስፍራ
በጣም ቅርብ የሆነችው ከተማ ሽማግሌዎች
ለሥራ ያልደረሰችና ቀንበር ያልተጫነባትን
ጊደር ይዘው፣ [4]ከዚያ በፊት ታርሶ ወይም
ተዘርቶበት ወደማይታወቅ ወራጅ ውሃ
ወዳለበት ሸለቆ ያምጡት:: በዚያ ሸለቆም የጊ
ደራቱን ዐንገት ይስበሩ፤ [5]እንዲያገለግሉና
*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ስም እንዲባርኩ፣ በማን
ኛውም የክርክርና የጥቃት ጉዳዮች ሁሉ
ላይ ውሳኔ እንዲሰጡ፣ *አምላክህ* እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) መርጦአቸዋልና የሌዊ ልጆች
ካህናቱ ወደ ፊት ይቅረቡ:: [6]ከዚያም
ሬሳው በተገኘበት አቅራቢያ ባለችው ከተ
ማ የሚ ኖሩ ሽማግሌዎች ሁሉ፣
በሸለቆው ውስጥ፣
ዐንገቷ በተሰበረው ጊደር ላይ እጃቸውን
ይታጠቡ:: [7]እንዲህም ብለው ይናገሩ፤ “እጆ
ቻችን ደም አላፈሰሱም፤ ድርጊቱ ሲፈጸምም
ዐይኖቻችን አላዩም:: [8]*እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ሆይ፤ ስለ ተቤዠኸው ሕዝብህ ስለ እስራ
ኤል ብለህ ይህን ስርየት ተቀበል፤ ሕዝብ
ህንም በፈሰሰው ንጹሕ ደም በደለኛ አታድ
ርግ::” ስለ ፈሰሰውም ደም ስርየት ይደረግ
ላቸዋል:: [9]አንተም *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ቀና
የሆነውን ስታደርግ፣ የንጹሑን ደም የማፍሰስ
በደልን ከመካከልህ ታስወግዳለህ::

**የተማረከች ሴት ስለ ማግባት**

[10]ከጠላቶችህ ጋር ጦርነት ልትገጥም ወጥተህ
*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) እነርሱን
በእጅህ አሳልፎ ሰጥቶህ በማረክህ ጊዜ፣
[11]ከምርኮኞቹ መካከል መልከ መልካም ሴት
አይተህ ብትማርክህ፣ ሚስትህ ልታደርጋት
ትችላለህ:: [12]ወደ ቤትህ ውሰዳት፤ ጠጕሯን
ትላጭ፤ ጥፍሯንም ትቍረጥ:: [13]ስትማረክ
የለበሰችውንም ልብስ ታውልቅ፤ እቤትህ
ተቀምጣ ለአባትና ለእናቷ ወር ሙሉ ካለቀ
ሰችላቸው በኋላ፣ ልትደርስባትና ባል ልትሆ
ናት፣ እርሷም ሚስት ልትሆንህ ትችላለች::
[14]በእርሷ ደስተኛ ባትሆን፣ ወደም ትፈልገው
አንድትሄድ ነጻነት ስጣት፤ ውርደት ላይ
ጥለሃታልና ልትሸጣት ወይም እንደ ባሪያ
ልትቈጥራት አይገባህም::

**የበኵር ልጅ መብት**

[15]አንድ ሰው ሁለት ሚስቶች ቢኖሩት፤
አንደኛዋን የሚወዳት፣ ሌላዋን ግን የሚጠ
ላት ቢሆን፣ ሁለቱም ወንዶች ልጆችን
ወልደውለት በኵር ልጁ ግን የተወለደው
ከማይወዳት ሚስቱ ቢሆን፣ [16]ንብረቱን ለልጆቹ
በሚያወርስበት ጊዜ፣ የብኵርናን መብት

[ጀ]17 የዕብራይጡ ቃል አንድን ነገር ወይም አንድን ሰው ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠትን የሚያሳይ ነው::
[ገ]19 ወይም፣ *ለመክበብ ወረደ፤ የዛፎቹ ፍሬ ለሰው ጥቅም ይዋሉ*

ከማይወዳት ሚስቱ ከወለደው በኵር ልጅ
ገፎ፣ ከሚወዳት ሚስቱ ለተወለደው ልጁ፣
በአድልዎ መስጠት አይገባውም፤ 17ይልቀ
ንም ከተጠላችው ሚስቱ ለተወለደው ልጅ
ካለው ሀብት ሁሉ ሁለት እጅ ድርሻውን
በመስጠት ብኵርናውን ያስታውቅ፤ ያ ልጅ
የአባቱ ኀይል መጀመሪያ ነውና፤ የብኵርና
መብት የራሱ ነው።

## የማይታዘዝ ልጅ

18አንድ ሰው፣ የአባቱን ወይም የእናቱን
ትእዛዝ የማይሰማ፣ ቢቀጡትም የማይታረም
እልከኛና ዐመፀኛ ልጅ ቢኖረው፣ 19አባትና
እናቱ ይዘው በሚኖሩበት ከተማ በር ወዳሉት
አለቆች ያምጡት፤ 20"ይህ ልጃችን እልከኛና
ዐመፀኛ ነው፤ አይታዘዘንም፤ አባካኝና ሰካራም
ነው" ብለው ለአለቆች ይንገሯቸው። 21ከዚ
ያም በኋላ የከተማዪቱ ሰዎች ሁሉ እስኪ
ሞት ድረስ በድንጋይ ይውገሩት፤
ክፉውንም ከመካከልህ አስወግድ፤ እስራ
ኤልም ሁሉ ይህን ሰምቶ ይፈራል።

## ልዩ ልዩ ሕጎች

22አንደ ሰው ለሞት የሚያበቃ በደል ፈጽሞ
ቢገደልና በድኑ በዕንጨት ላይ ቢሰቀል፤
23በድኑን በዕንጨት ላይ እንደ ተሰቀለ አታሳ
ድረው፤ ምክንያቱም በዕንጨት ላይ የተሰቀለ
*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ዘንድ የተረገመ ነውና፤
*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ርስት አድርጎ
የሚሰጥህን ምድር እንዳታረክስ፣ በዚያኑ
ዕለት ቅበረው።

22 የወንድምህ በሬ ወይም በግ ጠፍቶ
ሲባዝን ብታየው፣ ወደ እርሱ መልሰህ
አምጣለት እንጂ ዝም ብለህ አትለፈው፤ 2ወን
ድምህ በአቅራቢያህ ባይኖር፣ ወይም የማን
መሆኑን የማታውቅ ከሆነ፣ ባለቤቱ ፈልጎት
እስኪመጣ ድረስ፣ ወደ ቤትህ ወስደህ ከአ
ንተ ዘንድ አቈየው፤ ከዚያም መልሰህ ስጠው።
3የወንድምህን አህያ ወይም ልብስ ወይም
የጠፋብትን ማናቸውንም ነገር ስታገኝ እንደዚሁ
አድርግ፤ በቸልታ አትለፈው።
4የወንድምህ አህያ ወይም በሬ መንገድ ላይ
ወድቆ ብታየው፣ በእግሩ እንዲቆምለት ርዳው
እንጂ ዐልፈኸው አትሂድ።
5ሴት የወንድ ልብስ አትልበስ፤
ወንድም የሴት ልብስ አይልበስ፤ እንዲህ
የሚያደርገውን ሁሉ *አምላክህ* እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ይጸየ ፈዋልና።
6በመንገድ ስታልፍ፣ አንዲት ወፍ ጫጩቶቿን
ወይም ዕንቁላሎቿን የታቀፈችበትን ጎጆ
በዛፍ ወይም በመሬት ላይ ብታገኝ፣ እናቲተ
ን ከነጫ ጩቶቿ አትውሰድ፤ 7ጫጩቶቿን
መውሰድ ትችላለህ፤ እናቲቱን ግን መልካም
እንዲሆንልህና ዕድሜህም እንዲረዝም
ልቀቃት፤
8አዲስ ቤት በምትሠራበት ጊዜ፣ ከጣራ
ው ላይ ሰው ወድቆ በቤትህ ላይ የደም
በደል እንዳታመጣ፣ በጣራው ዙሪያ መከታ
አብጅለት።
9በወይን ተክል ቦታህ ውስጥ ሁለት ዐይ
ነት ዘር አትዝራ፤ ይህን ካደረግህ፣ የዘራኸው
ሰብል ብቻ ሳይሆን፣ የወይን ፍሬህም ይጠፋል።
10በሬና አህያ በአንድ ላይ ጠምደህ አትረስ።
11ሱፍና በፍታ አንድ ላይ ተፈትሎ የተ
ሠራ ልብስ አትልበስ።
12በምትለብሰው ልብስ ላይ በአራቱ ማእ
ዘኖች ዘርፍ አድርግ።

## ጋብቻን በንጽሕና ስለ መጠበቅ

13አንድ ወንድ ሚስት አግብቶ አብሮአት
ከተኛ በኋላ ቢጠላት፣ 14ስሟንም በማጥፋት፣
"ይህችን ሴት አገባኋት፤ ዳሩ ግን በደረስሁባት
ጊዜ ድንግልናዋን አላገኘሁም" ቢል፣ 15የልጂቱ
አባትና እናት ድንግልናዋን የሚያረጋግጥ
ማስረጃ ይዘው በከተማዪቱ በር ወዳሉት
አለቆች ይምጡ። 16የልጂቱም አባት ለአለቆቹ
እንዲህ ይበል፤ "ልጄን ለዚህ ሰው ዳርሁለት፤
እርሱ ግን ጠላት፤ 17ስሟንም በማጥፋት፣
'ልጅህን ከነድንግልናዋ አላገኘኋትም' ብሎኛል፤
ነገር ግን የልጄ ድንግልና ማረጋገጫ ይኸ
ውላችሁ፤" ከዚያም ወላጆቿ የደሙን ሸማ
በከተማዪቱ አለቆች ፊት ይዘርጉት።
18ከዚያም በኋላ አለቆቹ ሰውየውን ይዘው
ይቅጡት፤ 19ይህ ሰው የአንዲት እስራኤላዊት
ድንግል ስም አጥፍቶአልና አንድ መቶ ሰቅልጦ
ብር ያስከፍሉት፤ ገንዘቡንም ለልጂቱ አባት
ይስጡት፤ ሴቲቱም ሚስቱ ሆና ትኖራለች፤
በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ሊፈታት አይችልም።
20ሆኖም ክሱ እውነት ሆኖ ሴቲቱ ድንግል
ለመሆኗ ምንም ማረጋገጫ ማቅረብ ካልተቻለ፣
21ገና በአባቷ ቤት ሳለች በማመንዘር በእስ
ራኤል ውስጥ ወራዳ ተግባር ፈጽማለችና ወደ
አባቷ ቤት ደጃፍ ያምጧት፤ እዚያም
የከተማዋ ሰዎች እስክትሞት ድረስ
በድንጋይ ይውገሯት። ክፉውን ከመካከልህ
ማስወገድ አለብህ።
22አንድ ሰው፣ ከሌላ ሰው ሚስት ጋር
ተኝቶ ቢገኝ፣ አብሮአት የተኛው ሰውና ሴቲቱ
ሁለቱም ይገደሉ፤ ክፉውን ከእስራኤል ማስ
ወገድ አለብህ።
23አንድ ሰው የታጨች ድንግል በከተማ
ውስጥ አግኝቶ ከእርሷ ጋር ቢተኛ፣ 24ልጃ
ገረዲቱ በከተማ ውስጥ እያለች አስጥሉኝ
ብላ ስላልጮኸች፣ ሰውየውም የሌላን ሰው
ሚስት አስገድዶ ስለ ደፈረ፣ ሁለቱንም ወደ
ከተማ ደጃፍ ወስዳችሁ እስኪሞቱ ድረስ

21፥17 ዘፍ25፥31፤ 49፥3፤2ነገ2፥9፤ ኢሳ40፥2፤61፥7፤ ዘካ9፥12፤ሉቃ15፥12
21፥18 ዘፍ31፥35፤ ምሳ1፥8፤30፥17፤ መዝ78፥8፤ኢሳ30፥1፤ ኤር5፥23፤ሶፎ3፥1፤ ኤፌ6፥1-3
21፥21 ዘሌ20፥9፤ ዘዳ13፥11፤19፥19፤ 1ቆሮ5፥13
21፥22 ዘዳ22፥26፤ ማቴ26፥66፤ ማር14፥64፤ ሐሥ23፥29
21፥23 ዘሌ18፥25፤ ኢሱ8፥29፤10፥27፤ ዕዝ6፥11፤አስ2፥23፤ 7፥9፤8፥7፤9፥13፡25፤ኢሳ50፥11፤ ሕዝ39፥12፤ ዮሐ19፥31፤ገላ3፥13፤
22፥1 ዘፀ23፥4-5፤ ምሳ27፥10፤ዘካ7፥9
22፥4 ዘፀ23፥5፤ 1ቆሮ9፥9
22፥6 ዘሌ22፥28፤
22፥7 ዘሌ22፥28፤ ዘዳ5፥29
22፥8 ኢሱ2፥8፤ 1ሳሙ9፥25፤ 2ሳሙ11፥2
22፥9 ዘሌ19፥19
22፥10 2ቆሮ6፥14
22፥11 ዘሌ19፥19
22፥12 ዘኍ15፥37-41፤ማቴ23፥5
2፥13 ዘዳ24፥1
22፥15 ዘፍ23፥10
22፥18 ዘፀ18፥21፤ ዘዳ1፥9-18
22፥20 ዘዳ17፥4
22፥21 ዘፍ34፥7፤ 38፥24፤ዘሌ19፥29፤ ዘዳ23፥17- 18፤ 1ቆሮ5፥13
22፥22 ዘፍ38፥24፤ ዘፀ21፥12፤ 2ሳሙ11፥4፤ ማቴ5፥27-28፤ ዮሐ8፥5፤1ቆሮ6፥9፤ ዕብ13፥4
22፥24 1ቆሮ5፥13

ጦ19 ወደ አንድ ኪሎ ግራም ነው።

በድንጋይ ውገሯቸው:: ክፉውን ከመካ
ከልህ ማስወገድ አለብህ::
25ነገር ግን አንድ ሰው የታጨችውን
ልጃገረድ ከከተማ ውጭ አግኝቶ በማስገደድ
ቢደፍራት፣ ይህን ድርጊት የፈጸመው ሰው፣
ብቻ ይገደል:: 26በልጃገረዲቱ ላይ ግን ምንም
አታድርጉባት፤ ለሞት የሚያበቃ ኀጢአት
ምንም አልሠራችም፤ ይህ ዐይነቱ ጉዳይ፣ አደጋ
ጥሎ ባልንጀራውን ከሚገድል ሰው አድራ
ጎት ጋር የሚመሳሰል ነው:: 27ምክንያቱም
ሰውየው የታጨችውን ልጃገረድ ከከተማ
ውጭ ስላገኛትና ብትጮኽም እንኳ ለርዳታ
የደረሰላት ማንም ሰው ስላልነበር ነው::
28አንድ ሰው ያልታጨች ልጃገረድ አግኝቶ
በማስገደድ ቢደርስባትና ቢጋለጡ፣
29ሰውየው ለልጅቷ አባት አምሳ ሰቅል[ጨ]
ብር ይክፈል፤ ልጃገረዲቱን አስገድዶ
ደፍሮአታልና እርሷን
ማግባት አለበት፤ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ሊፈ
ታት አይችልም::
30አንድ ሰው የአባቱን ሚስት ማግባት
የለበትም፤ የአባቱንም መኝታ አያርክስ::

## ከእግዚአብሔር ጉባኤ መለየት

23 ብልቱ የተቀጠቀጠ ወይም የተቈረጠ
ማናቸውም ሰው ወደ *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ጉባኤ አይግባ::
2ዲቃላም ይሁን የዲቃላው ዘር የሆነ
ሁሉ፣ እስከ ዐሥር ትውልድ ድረስ እንኳን
ቢሆን ወደ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ጉባኤ አይግባ::
3አሞናዊም ሆነ ሞዓባዊ ወይም ማናቸውም
የእርሱ ዘር፣ እስከ ዐሥር ትውልድ እንኳ
ቢሆን ወደ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ጉባኤ አይ
ግባ:: 4ምክንያቱም ከግብፅ ከወጣችሁ
በኋላ በጉዞ ላይ በነበራችሁበት ጊዜ እህል
ውሃ ይዘው አልተቀበሏችሁም፤ በመስጴጦምያ
በምትገኘው በፐቶር[ጸ] ይኖር የነበረውን የቢ
ዖርን ልጅ በለዓምም አንተን እንዲረግም
በገንዘብ ገዙት:: 5ይሁን እንጂ *አምላክህ* እግዚ
አብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በለዓምን አልሰማውም፤
*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ስለሚወድህ
ርግማኑን በረከት አደረገልህ:: 6በሕይወት
ዘመንህ ሁሉ ሰላምን ለእነርሱ አትመኝ::
7ወንድምህ ስለ ሆነ ኤዶማዊውን አትጸየፈው፤
መጻተኛ ሆነህ በአገሩ ኖረሃልና ግብፃዊውን
አትጥላው:: 8ለእነርሱ የተወለዱላቸው የሦስ
ተኛው ትውልድ ልጆች ወደ *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ጉባኤ መግባት ይችላሉ::

## የጦር ሰፈር ንጽሕና አጠባበቅ

9ጠላትህን ለመውጋት ወጥተህ በሰፈርህ
ጊዜ፤ ከማናቸውም ርኵሰት ራስህን ጠብቅ::
10ከመካከላችሁ ሌሊት ዘር በማፍሰስ የረከሰ

22፥27 ዘፍ39፥14
22፥28 ዘፀ20፥7፤
34፥16
22፥30 ዘፍ29፥29፤
ዘሌ18፥8፤20፥9፤
1ቆሮ5፥1
23፥1 ዘሌ21፥20
23፥3 ቀኁ4፤
ዘፍ19፥38፤ነህ13፥2
23፥4 ቀኁ3፤
ዘፍ24፥10፤ዘኁ23፥7፤ዘ
ዳ2፥28፤2ጴጥ2፥15
23፥5 ዘኁ24፥10፤
ዘዳ4፥37፤
ኢሱ24፥10፤
ምሳ26፥2
23፥6 ዘኁ24፥17፤
ዕዝ9፥12፤
ኢሳ15፥1፤25፥10፤
ኤር25፥21፤27፥3፤
48፥1፤ሕዝ25፥8፤
ሶፎ2፥9፤ማቴ5፥43
23፥7 ዘፍ25፥26፡
30፤ዘሌ19፥34
23፥9 ዘሌ15፥1-33
23፥10 ዘሌ15፥16
23፥11 ዘሌ15፥16፤
1ሳሙ21፥5
23፥14 ዘፍ3፥8፤ ዘፀ
3፥5
23፥15 2ሳሙ22፥3፤
1ሳሙ30፥15፤
መዝ2፥12፤71፥1
23፥16 ዘፀ22፥21፤
23፥6
23፥17 ዘፍ38፥21፤
1ነገ14፥24፤15፥12፤
22፥46፤2ነገ23፥7፤
ኢዮ36፥14
23፥18 ዘፍ19፥5፤
ዘሌ20፥13፤
ራእ22፥15
23፥19 ዘሌ25፥35-
37፤ነህ5፥2-7
23፥20 ዘፍ31፥15፤
ዘዳ15፥3፡10
23፥21 ዘኁ6፥21፤
30፥1-2፤መሳ11፥35፤
ኢዩ22፥27፤
መዝ15፥4፤61፥8፤
65፥1፤76፥11፤
መክ5፥4-5፤
ኢሳ19፥21፤ማቴ5፥33፤
ሐሥ5፥3፤
23፥22 ሐሥ5፥4
23፥25 ማቴ 12፥1፤
ማር2፥23፤ሉቃ6፥1
24፥1 ቀኁ3፤
ዘዳ22፥13፤2ነገ17፥6፤
ኢሳ50፥1፤ኤር3፥8፤
ሚል2፥16፤
ማቴ1፥19፤5፥31፤
19፥7-9፤ማር10፥4-5

ሰው ቢኖር ከሰፈር ወጥቶ እዚያው ይቈይ::
11እየመሸ ሲመጣ ግን ገላውን ይታጠብ፤ ፀሓይ
ስትጠልቅም ወደ ሰፈሩ ይመለስ::
12ለመጸዳጃ የሚሆንህን ቦታ ከሰፈር ውጭ
አዘጋጅ:: 13ከትጥቅህም ጋር መቈፈሪያ ያዝ፤
በምትጸዳዳበት ጊዜ ዐፈር ቈፍረህ በዐይነ
ምድርህ ላይ መልስበት:: 14*አምላክህ* እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ሊጠብቅህ ጠላቶችህንም በእጅህ
አሳልፎ ሊሰጥህ በሰፈር ውስጥ ስለሚዘዋወር፣
በመካከልህ አንዳች ነውር አይቶ ከአንተ
እንዳይመለስ፣ ሰፈርህ የተቀደሰ ይሁን::

## ልዩ ልዩ ሕጎች

15አንድ ባሪያ ከአሳዳሪው ኰብልሎ ወደ
አንተ ቢመጣ፣ ለአሳዳሪው አሳልፈህ አትስጠው::
16ደስ በሚያሰኘው ቦታና ራሱ በመረጠው
ከተማ በመካከልህ ይኑር፤ አንተም አታስ
ጨንቀው::
17ወንድ ወይም ሴት እስራኤላዊ የቤተ
ጣዖት አመንዝራ አይሁን:: 18ለዝሙት አዳሪ
ሴት ወይም ለወንደቃ[ጸ] የተከፈለውን ዋጋ
ለማናቸውም ስእለት አድርገህ ለመስጠት
ወደ *አምላክህ* ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎ
ሂም) ቤት አታምጣ፤ *አምላክህ* እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ሁለቱንም ይጸየፋቸዋልና::
19የገንዘብ፣ የእህል ወይም የማንኛውንም
ነገር ወለድ ለማግኘት ለወንድምህ በወለድ
አታበድር:: 20ባዕድ ለሆነ ሰው ወለድ ማበደር
ትችላለህ፤ ነገር ግን ልትወርሳት በምትገ
ባባት ምድር እጅህ በሚነካው በማናቸውም
ነገር *አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) እንዲባርክህ
ለእስራኤላዊ ወንድምህ በወለድ አታበድረው::
21*ለአምላክህ* ለእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
ስእለት ከተሳልህ፣ *አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ
ኤሎሂም) አጥብቆ ከአንተ ይሻዋልና፣ ኀጢአት
እንዳ ይሆንብህ ለመክፈል አትዘግይ:: 22ሳትሳል
ብትቀር ግን በደለኛ አትሆንም:: 23በአንደበትህ
የተናገርኸውን ሁሉ ለመፈጸም ጠንቃቃ ሁን፤
*ለአምላክህ* ለእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በገዛ አንደ
በትህ ፈቅደህ ስእለት ተስለሃልና::
24ወደ ባልንጀራህ የወይን ተክል ቦታ በም
ትገባበት ጊዜ፣ ያሰኘህን ያህል መብላት
ትችላለህ፤ ነገር ግን አንዳችም በዕቃህ አትያዝ::
25ወደ ባልንጀራህ ዕርሻ በምትገባበት ጊዜ፣
እሸት መቅጠፍ ትችላለህ፤ በሰብሉ ላይ ግን
ማጭድ አታሳርፍበት::
24 አንድ ሰው አንዲት ሴት ካገባ
በኋላ፣ አሳፋሪ ነገር አግኝቶባት
ባይደሰትባት፣ የፍቺ ወረቀት ጽፎ በመ
ስጠት ከቤቱ አስወጥቶ ይስደዳት::

[ጨ]29 ወደ 0.6 ኪሎ ግራም ነው::
[ጸ]4 ይኸውም ሰሜን ምዕራብ መስጴጦምያ ነው::
[ጸ]18 ዕብራይስጡ፣ ውሻ ይላል::

[2]ከቤቱ ከወጣች በኋላ ሌላ ባል ብታገባ፣
[3]ሁለተኛ ባሏም እንደዚሁ ጠልቷት የፍቺ
ወረቀት በመስጠት ከቤቱ አስወጥቶ ቢሰ
ዳት ወይም ቢሞት፣ [4]ከዚያ በኋላ የፈታት
የመጀመሪያ ባሏ፣ የረከሰች በመሆኗ እንደ
ገና መልሶ ሊያገባት አይችልም፤ ይህ
*በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት አስጸያፊ ነው፡፡
*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ርስት
አድርጎ በሚሰ ጥህ ምድር ላይ ኀጢአት
አታምጣ፡፡
[5]አዲስ ሚስት በቅርብ ጊዜ ያገባ ሰው፣
ለጦርነት አይሂድ፤ ወይም ሌላ ሥራ እን
ዲሠራ አይገደድ፡፡ ለአንድ ዓመት ነጻ ሆኖ
እቤቱ ይቈይ፤ ያገባትን ሚስቱን ደስ ያሰኛት፡፡
[6]ወፍጮና መጁን ወይም መጁንም እንኳ
ቢሆን፣ የብድር መያዥ አድርገህ አትውሰድ፤
የሰውን ነፍስ መያዥ አድርጎ መውሰድ ይሆ
ናልና፡፡
[7]አንድ ሰው ከእስራኤላውያን ወንድሞቹ
አንዱን ፈንግሎ በመውሰድ ባሪያ ሲያደርገው
ወይም ሲሸጠው ቢገኝ፣ ፈንጋዩ ይሙት፡፡
ክፉውን ከመካከልህ አስወግድ፡፡
[8]የለምጽ ደዌን[θ] በተመለከተ ሌዋውያን
ካህናት የሚሰጡህን መመሪያ በትክክል ለመፈ
ጸም ጥንቃቄ አድርግ፡፡ እኔ ለእነርሱ
የሰጠሁትን ትእዛዝ በጥንቃቄ ተከተል፡፡
[9]ከግብፅ ከወጣችሁ በኋላ በመንገድ ላይ
ሳላችሁ *አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
በማርያም ላይ ያደረገባትን አስታውሱ፡፡
[10]ማናቸውንም ነገር ለባልንጀራህ
ስታበድር መያዥ አድርጎ የሚሰጥህን
ለመቀበል ወደ ቤቱ አትግባ፡፡ [11]አንተ
ከውጭ ሆነህ ጠብቅ፤ ያበደርኸውም ሰው
መያዥውን ከቤት ያምጣልህ፡፡ [12]ሰውየው
ድኻ ከሆነ፣ መያ ዥውን ከአንተ ዘንድ
አታሳድርበት፡፡ [13]መደ ረቢያውን ለብሶት
እንዲያደር ፀሐይ ሳትጠልቅ መልስለት፡፡ ከዚ
ያም ያመሰግንሃል፤ *አምላክህ* እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ፊትም የጽድቅ ሥራ ሆኖ ይቈጠ
ርልሃል፡፡
[14]ድኻና ችግረኛ የሆነውን የምንዳ ሠራተኛ
እስራኤላዊ ወንድምህም ሆነ፣ ከከተሞችህ
ባንዲቱ የሚኖረውን መጻተኛ አትበዝብዘው፤
[15]የሠራበትን ሒሣብ በዕለቱ፣ ፀሐይ ሳትጠ
ልቅ ክፈለው፤ ድኻ በመሆኑ በጒጒት ይጠ
ባበቀዋልና፡፡ ያለበለዚያ ወደ *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ይጮኽና ኀጢአት ይሆንብሃል፡፡
[16]አባቶች ስለ ልጆቻቸው፣ ልጆችም ስለ
አባቶቻቸው አይገደሉ፤ እያንዳንዱ በራሱ ኀጢ
አት አትገደል፡፡
[17]ለመጻተኛው ወይም አባት ለሌለው
ልጅ ፍትሕ አትንፈገው፤ የመበለቲቱንም
መደረቢያ መያዥ አታድርግ፡፡ [18]አንተም
በግብፅ ባሪያ እንደ ነበርህና *አምላክህ* እግዚ
አብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ከዚያ እንደ ተቤዠህ

24፥4 ኤር 3፥1
24፥5 ዘዳ20፥7
24፥6 ዘፀ22፥22
24፥7 ዘፀ21፥16፤ 1ቆሮ5፥13
24፥8 ዘሌ13፥1-46፤ 14፥2፤ዘዳ17፥9
24፥9 ዘኍ12፥10
24፥10 ዘፀ22፥25-27
24፥13 ዘፀ22፥26፡ 27፤ዘዳ6፥25፤ መዝ106፥31፤ዳን4፥27
24፥14 ዘሌ19፥13፤ 25፥35-43፤ ዘዳ15፥12-18፤ኢዩ24፥4፤ ምሳ14፥31፤19፥17፤ አሞ4፥1፤1ጢሞ5፥18
24፥15 ዘፀ22፥23፤ ዘሌ19፥13፤25፥35፤ ኢዩ12፥19፤ ማቴ20፥8፤ያዕ5፥4
24፥16 ዘኍ26፥11፤ ኤር31፥29-30
24፥17 ዘፀ22፥21፡ 22፤23፥2፤ዘዳ10፥18፤ ኢዮ6፥27፤24፥9፤ 29፥12፤መዝ10፥18፤8 2፥3፤ምሳ23፥10፤ ሕ ዝ22፥7፤
24፥18 ዘዳ15፥15
24፥19 ቀኍ20፤ ዘሌ19፥9፤ዘዳ10፥19፤1 4፥29፤27፥19፤ ምሳ19፥17፤28፥27፤መ ክ11፥1፤ ሕዝ47፥22፤ ዘካ7፥10፤ሚል3፥5
24፥20 ዘሌ19፥10
24፥22 ቀኍ18
25፥1 ዘፀ21፥6፤ 23፥7፤ዘዳ1፥16-17፤ 17፥8-13፤19፥17፤ 1ነገ8፥32፤ሐሥ23፥3
25፥2ምሳ10፥13፤ 19፥29፤ሉቃ12፥47-48
25፥3 ኤር20፥2፤ ማቴ27፥26፤ ዮሐ19፥1፤2ቆሮ11፥24
25፥4 ዘኍ22፥29፤ 1ቆሮ9፥9፤1ጢሞ5፥18
25፥5 ሩት4፥10፡ 13፤ማቴ22፥24፤ ማር12፥19፤ ሉቃ20፥28
25፥6 ዘፍ38፥9፤ ሩት4፥5፡10
25፥7 ዘፍ23፥10፤ ሩት1፥15፤4፥1-2፡5-6
25፥9 ዘኍ12፥14፤ ኢሱ24፥22፤ሩት4፥7-8፡ 11፤ኢዮ17፥6፤ 30፥10፤ኢሳ50፥6

አስታውስ፤ ይህን እንድታደርግ ያዘዝሁህ
ለዚህ ነው፡፡
[19]የዕርሻህን ሰብል በምታጭድበት ጊዜ፣
ተረስቶ የቀረ ነዶ ቢኖር፣ ያን ለመውሰድ
ተመልሰህ አትሂድ፡፡ *አምላክህ* እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) በእጅህ ሥራ ሁሉ እንዲባርክህ
ነዶ ውን ለመጻተኛው፣ አባት ለሌለውና
ለመ በለቲቱ ተወው፡፡ [20]የወይራ ዛፍህን
ፍሬ በምታራግፍበት ጊዜ በየቅርንጫፉ
ላይ የቀረውን ለመቃረም ተመልሰህ አትሂድ፤
ለመ ጻተኛው፣ አባት ለሌለውና ለመበለቲቱ
ተወው፡፡ [21]የወይን ተክልህን ፍሬ ስትሰበስብ
ቃርሚ ያውን ለመሰብሰብ አትመለስበት፤
የቀረውን ለመጻተኛው፣ አባት ለሌለውና
ለመበለቲቱ ተወው፡፡ [22]በግብፅ ባሪያ እንደ
ነበርህ አስታ ውስ፤ ይህን እንድታደርግ
ያዘዝሁህ ለዚህ ነው፡፡

25 በሰዎች መካከል ጠብ ቢነሣና ወደ
ፍርድ አደባባይ ቢሄዱ፣ ዳኞች
ተበዳይን ነጻ፣ በዳይን ግን ጥፋተኛ በማድ
ረግ የፍርድ ውሳኔ ይስጡ፡፡ [2]በደለኛው ሰው
መገረፍ የሚገባው ሆኖ ከተገኘ፣ ዳኛው
መሬት ላይ ያጋድመው፤ ለጥፋቱ ተመጣጣኝ
የሆነ ግርፋት እርሱ ባለበት ይገረፍ፡፡ [3]ሆኖም
ግርፋቱ ከአርባ የሚበልጥ አይሁን፤ ከዚህ
ካለፈ ግን፣ ወንድምህ በፊትህ የተዋረደ
ይሆናል፡፡
[4]እህል እያበራየ ያለውን በሬ አፉን አትሰር፡፡
[5]ወንድማማቾች በአንድነት ቢኖሩና ከእነርሱ
አንዱ ወንድ ልጅ ሳይወልድ ቢሞት፣
የሚቹ ሚስት ከቤተ ሰቡ ውጭ ባል
ማግባት የለባ ትም፡፡ የባሏ ወንድም
ይውሰዳትና ያግባት፤ የዋርሳነት ግዴታውንም
ይፈጽምላት፡፡ [6]በመጀ መሪያ የምትወልደውም
ልጅ ስሙ ከእስራኤል ፈጽሞ እንዳይጠፋ
በሚች ወንድሙ ስም ይጠራ፡፡
[7]ሆኖም ግን አንድ ሰው የወንድሙን
ሚስት ለማግባት ባይፈልግ፣ ሴትዮዋ በከተ
ማዋ በር ወዳሉት ሽማግሌዎች ሄዳ፣
"የባለቤቴ ወንድም የወንድሙን ስም በእስ
ራኤል ለማ ስጠራት አልፈለገም፤ የዋርሳነት
ግዴታውንም አልፈጸመልኝም" ትበላቸው፡፡
[8]ከዚያም የከተማው ሽማግሌዎችን
ሰው ጠርተው ያነጋ
ግሩት፤ እርሱም፣ "እርሷን ላገባት አልፈል
ግም" ብሎ በሐሳቡ ቢጸና፣ [9]የወንድሙም
ሚስት በሽማግሌዎች ፊት ወደ እርሱ ቀርባ፣
የአንድ እግሩን ጫማ በማውለቅ በፊቱ ላይ
ትትፋበትና "የወንድሙን ቤት በማይሠራ
ሰው ላይ እንዲህ ያለው ድርጊት ይፈጸምበ
ታል" ትበል፡፡ [10]የዚያም ሰው የዘር ሐረግ
በእስራኤል ዘንድ፣ "ጫማው የወለቀበት ቤት"
ተብሎ ይታወቃል፡፡

[θ]8 ዕብራይስጡ ለምጽን ብቻ ሳይሆን ቈዳን የሚያጠቁትን ማናቸውንም ዐይነት በሽታዎች ያመለክታል፡፡

11ሁለት ሰዎች ቢደባደቡ፣ የአንደኛው ሚስት
ባሏን ከደብዳቢው እጅ ለማስጣል መጥታ፣
እጇን ዘርግታ ብልቱን ብትይዘው፣ 12እጇን
ቍረጠው፤ አትራራላት።

13በከረጢትህ ውስጥ ከባድና ቀላል
የሆኑ ሁለት የተለያዩ ሚዛኖች አይኑሩህ።
14በቤትህም ውስጥ ትልቅና ትንሽ የሆኑ
ሁለት የተለያዩ መስፈሪያዎች አይኑሩህ።
15*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በሚሰጥህ
ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም፣ ትክክለኛና የታ
መነ ሚዛንና መስፈሪያ ይኑርህ። 16*አምላክህ*
እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) እንዲህ ያሉትን
ነገሮች የሚፈጽመውንና የሚያምታታውን
ሁሉ ይጸየ ፈዋልና።

17ከግብፅ በወጣህ ጊዜ፣ አማሌቅ በመንገድ
በአንተ ላይ ያደረገብህን አስታውስ፤ 18ደክመህና
ዝለህ በነበርህበት ጊዜ፣ በጕዞ ላይ አግኝተ
ውህ፣ ከኋላ ያዘግሙ የነበሩትን ሁሉ ገደሉ፤
እግዚአብሔርንም (ኤሎሂም) አልፈሩም። 19*አምላክህ*
እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ርስት አድርጎ
በሚሰጥህ ምድር ዙሪያ ካሉት ጠላቶችህ
ሁሉ ባሳረፈህ ጊዜ፣ ከሰማይ በታች
ያለውን የአማሌቅን መታሰቢያ ደምስስ፤
ከቶ እንዳትረሳ!

## ዐሥራትና በኵራት

26 *አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
ርስት አድርጎ ወደሚሰጥህ ምድር
ስትገባ፣ ስትወርሳትና ስትኖርባት፣ 2*አምላክህ*
እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ከሚሰጥህ ምድር
ከምትሰበስበው ሰብል ሁሉ፣ በኵራት
ወስደህ በቅርጫት ውስጥ አድርገው፤ ከዚያም
*አምላክህ*እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ለስሙ ማደሪያ
እንዲሆን ወደ ሚመርጠው ስፍራ ሂድ፤ 3በዚ
ያም ወቅት ለሚያገለግለው ካህን፣ "*እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ለእኛ ሊሰጠን ለአባቶቻችን
ወደ ማለላቸው ምድር እንደ ገባሁ ዛሬ
*በአምላክህ*በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ፊት እናገ
ራለሁ" በለው። 4ካህኑም ቅርጫቱን ከእጅህ
ተቀብሎ፣ *በአምላክህ* በእ ግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎ
ሂም) መሠዊያ ፊት ለፊት ያስቀምጠዋል።
5አንተም *በአምላክህ* በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
ፊት እንዲህ ብለህ ትናገራለህ፤ "አባቴ ዘላን
ሶርያዊ ነበር፤ ከጥቂት ሰዎችም ጋር ወደ
ግብፅ ወረደ፤ በዚያም ተቀ መጠ፤ ታላቅ፣
ኀያልና ቍጥሩ የበዛ ሕዝብ ሆነ። 6ግብፃውያን
ግን ከባድ ሥራ በማሠራት አንገላቱን፤ አ
ሠቃዩንም። 7ከዚያ በኋላ የአባ ቶቻችን
*አምላክ* (ያህዌ) ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር (ኤሎ
ሂም) ጮኽን፤ *እግዚአብሔርም* ጩኸ ታችንን ሰ
ማ፤ ጕስቍልናችንን፣ ድካማች ንንና የተፈ
ጸመብንን ግፍ ተመለከተ። 8ከዚህ የተነሣ *እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) በብርቱ እጅና በተ ዘረጋች
ክንድ፣ በታላቅ ድንጋጤ፣ በታምራዊ
ምልክትና በድንቅ ከግብፅ አወጣን። 9ወደዚህ
ስፍራ አመጣን፤ ማርና ወተት የምታፈ ሰውን
ይህችን ምድር ሰጠን፤ 10አሁንም *እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) ሆይ፤ "እነሆ፣ አንተ የሰጠኸኝን
የምድሪቱን በኵራት አምጥቻለሁ።" ቅርጫቱ
ንም *በአምላክህ* በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ፊት
አስ ቀምጠው፤ *በአምላክህ* በእግዚአብሔር (ያህዌ
ኤሎሂም) ፊት ስገድ። 11ከዚያም አንተ፣
ሌዋዊውና በመካከልህ የሚኖረው መጻተኛ፣
*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ለአንተና
ለቤትህ በሰጠው በጎ ነገር ሁሉ ደስ
ይበላችሁ።

12የዐሥራት ዓመት የሆነውን
የሦስተኛውን
ዓመት ምርት አንድ ዐሥረኛ ለይተህ ካወ
ጣህ በኋላ በየከተሞችህ ውስጥ በልተው
እንዲጠግቡ፣ ለሌዋዊው፣ ለመጻተኛው፣
አባት ለሌለውና ለመበለቲቱ ስጣቸው፣ 13ከዚያ
በኋላ *ለአምላክህ* ለእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) እንዲ
ህ በል፤ "በሰጠኸኝ ትእዛዝ መሠረት
የተቀደሰውን ክፍል ከቤቴ አውጥቼ
ለሌዋዊው፣ ለመጻ ተኛው፣ አባት ለሌለውና
ለመበለቲቱ ሰጥቻ ለሁ። ከትእዛዝህ
አልወጣሁም፤ አንዱንም አልረሳሁም። 14በሐ
ዘን ላይ ሳለሁ፣ ከተቀደሰው ክፍል ላይ
ምንም አልበላሁም፤ ባልነጻሁብ ትም ጊዜ
ከዚሁ ላይ ያነሣሁትም ሆነ ለሙ ታን
ያቀረብሁት ምንም ነገር የለም፤ *አምላኬን*
እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) ታዝዣለሁ፤ ያዘዝኸኝ
ንም ሁሉ ፈጽሜአለሁ። 15ከቅዱስ ማደሪያህ
ከሰማይ ተመልከት፤ ሕዝብህን እስራኤልንና
ለአባቶቻችን በመሐላ ቃል በገባኸው መሠ
ረት፣ ለእኛ የሰጠኸንን ይህችን ማርና ወተት
የምታፈሰውን ምድር ባርክ።"

## የእግዚአብሔርን ትእዛዞች ስለ መጠበቅ

16*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ይህን
ሥርዐትና ሕግ ትጠብቅ ዘንድ ዛሬ ያዝሃል፤
አንተም በፍጹም ልብህ፣ በፍጹምም ነፍስህ
ትፈጽመው ዘንድ ተጠንቀቅ። 17እግዚአብሔር
*አም ላክህ* (ኤሎሂም ያህዌ) እንደ ሆነ በመንገዱም
እንደ ምትሄድ፣ ሥርዐቱን፣ ትእዛዙንና ሕጉን
እንደ ምትጠብቅና እንደምትታዘዝለት
በዛሬዪቱ ዕለት ተናግረሃል። 18*እግዚአብሔር*
(ያህዌ) በሰጠህ ተስፋ መሠረት አንተ፣ ሕ
ዝቡና ርስቱ መሆንህን፣ ትእዛዙንም ሁሉ
እንደምትጠብቅ በዛሬው
ዕለት ተናግሮአል፤ 19ከፈጠራቸው ሕዝቦች
ሁሉ በላይ በምስጋና፣ በስም፣ በክብርም
ከፍ እንደሚያደርግህና በሰጠውም ተስፋ
መሠረት *ለአምላክህ* ለእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
ቅዱስ ሕዝብ እንደምትሆን ተናግሮአል።

## በጌባል ተራራ ላይ የቆመ መሠዊያ

27 ሙሴና የእስራኤል አለቆች ሕዝቡን
እንዲህ ብለው አዘዙ፤ "ዛሬ የማዛችሁን
እነዚህን ትእዛዞች ሁሉ ጠብቁ፤ 2*አምላክህ*
እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ወደሚሰጥህ ምድር

25፥12 ዘዳ7፥2
25፥13 ምሳ11፥1፤ 20፥23፤ሚክ6፥11
25፥15 ዘፀ20፥12
25፥16 ምሳ11፥1
25፥17 ዘፍ36፥12
25፥18 መዝ36፥1፤ ሮሜ3፥18
25፥19 ዘፍ36፥12፤ ዘፀ33፥14፤ኢስ9፥16፤ ዕብ3፥18-19
26፥2 ዘፀ20፥24፤ 22፥29፤ዘዳ12፥5
26፥5 ዘፍ12፥2፤ 20፥13፤25፥20፤ 34፥30፤43፥14
26፥6 ዘፀ1፥13፤ ዘኍ20፥15
26፥7 ዘፍ16፥11፤ 21፥17፤ዘፀ3፥9፤ 2ነገ13፥4፤14፥26፤ መዝ42፥9፤44፥24፤ 72፥14
26፥8 ዘኍ20፥16፤ ዘፀ3፥20፤ዘዳ4፥34፤ 34፥11-12
26፥9 ዘፀ3፥8
26፥10 ዘዳ8፥18
26፥11 ዘዳ12፥12፤ 16፥11
26፥12 ዘፍ14፥20፤ ዘኍ18፥24፤ ዘዳ14፥28-29፤ ዕብ7፥7፡9
26፥13 መዝ119፥141፡ 153፡176
26፥14 ዘሌ7፥20፤ ሆሴ9፥4
26፥15 ዘፀ39፥43፤ መዝ68፥5፤80፥14፤ 102፥19፤ኢሳ63፥15፤ ዘካ2፥13
26፥16 ዘዳ4፥29
26፥17 ዘፀ19፥8፤ መዝ48፥14
26፥18 ዘፀ6፥7፤ ዘዳ7፥6
26፥19 ዘዳ4፥7-8፤ 7፥6፤28፥1፡13፡44፤ 1ዜና14፥2፤ መዝ148፥14፤ ኢሳ40፥11፤62፥7፤ ሶፎ3፥20
27፥1 መዝ78፥7

*ለመግባት* ዮርዳኖስን በተሻገራችሁ ጊዜ፣
ጥቂት ትልልቅ ድንጋዮችን አቁምና በኖራ
ቅባቸው:: [3]የአባቶችህ *አምላክ* እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) በሰጠህ ተስፋ *መሠረት*፣ *ማርና*
ወተት ወደምታፈሰው *አምላክህ* እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ወደሚሰጥህ ምድር *ለመግባት*
ዮርዳኖስን ስትሻገር፣ የዚህን ሕግ ቃላት ሁሉ
ጻፍባቸው:: [4]ዮርዳኖስን እንደ ተሻገርህም፣
ዛሬ ባዘዝሁህ *መሠረት* እነዚህን ድንጋዮች
በጌባል ተራራ ላይ ትከላቸው፤ በኖራም ቅባቸው::
[5]እዚያም *ለአምላክህ* ለእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
የድንጋይ *መሠዊያ ሥራ*፤ በድንጋዮቹም ላይ
ማናቸውንም የብረት *መሣሪያ* አታሳርፍባቸው::
[6]*የአምላክህን* የእግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) *መሠ*
*ዊያ* ካልተጠረበ ድንጋይ *ሥራ*፤ በላዩም *ለአ*
*ምላክህ* ለእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) የሚቃጠ
ል *መሥዋዕት* አቅርብበት:: [7]በዚያም
የኅብረት *መሥዋዕት*[ሐ] *ሠዋ*፤ ብላም፣
*በአምላክህ* በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) *ፊት* ደስ
ይበልህ:: [8]በድን ጋዮቹ ላይ የዚህን ሕግ
ቃላት ሁሉ ግልጽ
አድርገህ ጻፍባቸው::"

## በጌባል ተራራ ላይ የተነገረ መርገም

[9]*ሙሴና* ሌዋውያን ካህናትም ለእስራ
ኤል ሁሉ እንዲህ አለ፤ "እስራኤል ሆይ፤ ጸጥ
ብለህ አድምጥ! አንተ ዛሬ *የአምላክህ* የእግ
ዚአብሔር (ያሀዌ ኤሎሂም) ሕዝብ ሆነሃል፤ [10]*አምላክህን*
እግዚ አብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) ታዘዝ፤ ዛሬ የምሰጥህን
ትእዛዙንና ሥርዐቱን ጠብቅ::"
[11]*ሙሴ* በዚያኑ ዕለት ሕዝቡን እንዲህ
ብሎ አዘዘ:-
[12]ዮርዳኖስን በተሻገራችሁ ጊዜ፣ ስምዖን፣
ሌዊ፣ ይሁዳ፣ ይሳኮር፣ ዮሴፍና ብንያም ሕ
ዝ ቡን ለመባረክ በገሪዛን ተራራ ላይ ይቀ
ሙ:: [13]ሮቤል፣ ጋድ፣ አሴር፣ ዛብሎን፣ ዳንና
ንፍታ ሌምም በጌባል ተራራ ላይ ለመርገም
ይቁሙ::
[14]ሌዋውያን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው
ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ እንዲህ ብለው ይናገሩ:-
[15]"የእጅ ጥበብ ባለ ሙያ የሠራውን፣ *በእግ*
*ዘአብሔር* (ያህዌ) ዘንድ አስጸያፊ የሆነውን
ምስል የሚቀርጽ ወይም ጣዖትን የሚያበጅ፣
በስውርም የሚያቆም ሰው የተረገመ ይሁን::"
ሕዝቡም ሁሉ፣ "አሜን!" ይበል::
[16]"አባቱን ወይም እናቱን የሚያቃልል
የተረገመ ይሁን::"
ሕዝቡም ሁሉ፣ "አሜን!" ይበል::
[17]"የባልንጀራውን የድንበር ድንጋይ
ከቦታው የሚያንቀሳቅስ የተረገመ ይሁን::"
ሕዝቡም ሁሉ፣ "አሜን!" ይበል::
[18]"ዐይነ ስውሩን በተሳሳተ መንገድ የሚመራ
፣ የተረገመ ይሁን::"
ሕዝቡም ሁሉ፣ "አሜን!" ይበል::

27፥2 ዘፀ24፥4፤ ኢሱ4፥1፤8፥31፤ 24፥26፤1ሳሙ7፥12
27፥3 ዘፀ3፥8
27፥4 ዘዳ11፥29
27፥5 ዘፀ20፥24፡25
27፥7 ዘፀ32፥6፤ ዘዳ16፥11፤ኢሱ8፥31
27፥8 ኢሱ8፥32፤ ኢሳ8፥1፤30፥8፤ ዕን2፥2
27፥9 ዘዳ17፥9፤ 26፥18
27፥12 ዘፍ30፥18፤ ዘዳ11፥29፤ኢሱ8፥35
27፥13 ዘዳ11፥29
27፥15 ዘፀ20፥4፤ ዘኍ5፥22፤1ነገ11፥5፡7 ፤2ነገ23፥13፤ ኢሳ44፥19፤66፥3፤ 1ቆሮ14፥16
27፥16 ዘፍ31፥35፤ ዘፀ21፥12፤ዘዳ5፥16
27፥17 ዘዳ19፥14
27፥18 ዘሌ19፥14
27፥19 ዘፀ22፥21፤ 23፥2፤ዘዳ10፥18፤ 24፥19
27፥20 ዘፍ34፥5፤ ዘሌ18፥7
27፥21 ዘፀ22፥19
27፥22 ዘሌ18፥9
27፥23 ዘሌ20፥14
27፥24 ዘፍ4፥23፤ ዘፀ21፥12
27፥25 ዘፀ23፥7-8፤ ዘሌ19፥16
27፥26 ዘሌ26፥14፤ ዘዳ28፥15፤ መዝ119፥21፤ ኤር11፥3፡5፤ገላ3፥10
28፥1 ዘሌ26፤3፤ ዘኍ24፥7፤ዘዳ15፥5፤2 6፥19
28፥2 ኤር32፥24፤ ዘካ1፥6
28፥3 ዘፍ39፥5፤ መዝ144፥15
28፥4 ዘፍ49፥25፤ ዘዳ8፥18
28፥6 መዝ121፥8
28፥7 ዘሌ26፥8፡ 17፤2ዜና6፥34፤
28፥8 ዘዳ15፥4

[19]"በመጻተኛው፣ አባት በሌለውና
በመበለቲቱ ላይ ፍትሕ የሚያዛባ የተረገመ
ይሁን::"
ሕዝቡም ሁሉ፣ "አሜን!" ይበል::
[20]"ከአባቱ ሚስት ጋር የሚተኛ
የተረገመ ይሁን፤ የአባቱን መኝታ
ያረክሳልና::"
ሕዝቡም ሁሉ፣ "አሜን!" ይበል::
[21]"ከማናቸውም እንስሳ ጋር የግብረ
ሥጋ ግንኙነት የሚያደርግ የተረገመ
ይሁን::
ሕዝቡም ሁሉ፣ "አሜን!" ይበል::
[22]"የአባቱ ወይም የእናቱ ልጅ
ከሆነችው እኅቱ ጋር የግብረ ሥጋ
ግንኙነት
የሚፈጽም የተረገመ ይሁን::"
ሕዝቡም ሁሉ፣ "አሜን!" ይበል::
[23]"ከዐማቱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት
የሚፈጽም የተረገመ ይሁን::"
ሕዝቡም ሁሉ፣ "አሜን!" ይበል::
[24]"በድብቅ ባልንጀራውን የሚገድል የተረገመ
ይሁን::"
ሕዝቡም ሁሉ፣ "አሜን!" ይበል::
[25]"ንጹሕን ሰው ለመግደል ጉቦ የሚቀበል
የተረገመ ይሁን::"
ሕዝቡም ሁሉ፣ "አሜን!" ይበል::
[26]"የዚህን ሕግ ቃሎች በመፈጸም የማይ
ጸና የተረገመ ይሁን::"
ሕዝቡም ሁሉ፣ "አሜን!" ይበል::

## በመታዘዝ የሚገኝ በረከት

**28** *ለአምላክህ* ለእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
በፍጹም ብትታዘዝና እኔ ዛሬ የምሰ
ጥህን ትእዛዙን ሁሉ በጥንቃቄ ብትከተል፣
*አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በምድር ላይ
ከሚኖሩ አሕዛብ ሁሉ በላይ ከፍ ያደርግሃል::
[2]*አምላክህን* እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) ብት
ታዘዝ፣ እነዚህ በረከቶች ሁሉ ያንተ ይሆናሉ፤
አይለዩህምም::
[3]በከተማ ትባረካለህ፣ በዕርሻህም ትባረካለህ::
[4]የማሕፀንህ ፍሬ፣ የምድርህ አዝመራ፣
የእንስሳትህ ግልገሎች፣ የከብትህ ጥጃ፣
የበግና የፍየል ግልገሎችህም ይባረካሉ::
[5]እንቅብህና ቡሓቃህ ይባረካሉ::
[6]ስትገባ ትባረካለህ፤ ስትወጣም ትባረካለህ::
[7]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) በአንተ ላይ የሚነሡ
ጠላቶችህን በፊትህ እንዲሸነፉ ያደርጋቸዋል፤
በአንድ አቅጣጫ ይመጡብሃል፤ በሰባት
አቅ ጣጫም ከአንተ ይሸሻሉ::
[8]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) በጐተራህና እጅህ
በነካው ሁሉ በረከቱን ይልካል:: *አምላክህ*

[ሐ] 7 በትውፊት የሰላም መሥዋዕት በመባል ይታወቃል

እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በሚሰጥህም ምድር ላይ
ይባርክሃል።
9የአምላክህን የእግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) ትእዛ
ዞች የምትጠብቅና በመንገዱ የምትሄድ
ከሆነ፣ በመሐላ በሰጠህ ተስፋ መሠረት
የተቀደሰ ሕዝቡ አድርጎ ያቆምሃል፤ 10ከዚያም
የምድር አሕዛብ ሁሉ በእግዚአብሔር (ያህዌ)
ስም መጠራትህን ያያሉ፤ ይፈሩሃልም። 11እግ
ዚአብሔርም (ያህዌ) ሊሰጥህ ለአባቶችህ በማ
ለላቸው ምድር በማሕፀንህ ፍሬ፣ በእንስ
ሳትህም ግልገል፣ በምድርህም ሰብል
የተት ረፈረፈ ብልጽግና ይሰጥሃል።
12እግዚአብሔር (ያህዌ) ለምድርህ በወቅቱ
ዝናብን ለመስጠትና የእጅህን ሥራ ሁሉ ለመ
ባረክ፣ መልካሙን መዝገብ ሰማዩን ይከፍ
ትልሃል፤ አንተም ለብዙ አሕዛብ ታበድራ
ለህ እንጂ ከአንዳቸውም አትበደርም።
13እግዚአብሔርም (ያህዌ) ራስ እንጂ ጅራት
አያደ ርግህም። ዛሬ የምሰጥህን የአምላክህን
የእግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) ትእዛዝ በጥንቃቄ
ብትጠብቅ መቼውንም ቢሆን አላይ እንጂ
ፈጽሞ እታች አትሆንም። 14ሌሎችን አ
ማልክት በመከተል እነርሱን በማገልገል
ዛሬ ከም ሰጥህ ትእዛዞች ቀኝም ግራም
አትበል።

## አለመታዘዝ የሚያስከትላቸው ርግማኖች

15ነገር ግን ለአምላክህ ለእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎ
ሂም) ባትታዘዝ በዛሬዋ ዕለት የምሰጥህን
ትእዛዙንና ሥርዐቱን ሁሉ በጥንቃቄ
ባትከተላቸው፣ እነዚህ ርግማኖች ሁሉ
ይደርሱብሃል፤ ያጥለቀልቁሃልም፦
16በከተማ ትረገማለህ፤ በዕርሻም ትረገማለህ።
17እንቅብህና ቡሓቃህ የተረገሙ ይሆናሉ።
18የማሕፀንህ ፍሬ፣ የዕርሻህ ሰብል፣ የመን
ጋህ ጥጆች፣ የበግና የፍየል ግልገሎችህ
ይረገማሉ።
19ስትገባ ትረገማለህ፤ ስትወጣም ትረገማለህ።
20እርሱንT በመተው ክፉ ድርጊት ከመ
ፈጸምህ የተነሣ፣ እስክትደመሰስ ፈጥነህም
እስክትጠፋ ድረስ እጅህ በነካው ሁሉ ላይ
እግዚአብሔር (ያህዌ) ርግማንን፣ መደናገርንና
ተግሣጽን ይሰድብሃል። 21እግዚአብሔር (ያህዌ)
ልትወርሳት ከምትገባባት ምድር ላይ እስኪያጠ
ፋህ ድረስም፣ በደዌ ይቀሥፍሃል። 22እግዚ
አብሔር (ያህዌ) እስክትጠፋ ድረስ በሚቀሥፍ
ደዌ፣ ትኩሳትና ዕባጭ፣ ኀይለኛ ሙቀትና
ድርቅ፣ ዋግና አረማሞ ይመታሃል። 23ከራስህ
በላይ ያለው ሰማይ ናስ፣ ከእግርህ በታች
ያለው ምድርም ብረት ይሆናል። 24እግዚ
አብሔር (ያህዌ) የምድርህን ዝናብ ወደ ዐቧራ
ነትና ወደ ትቢያነት ይለውጠዋል፤ ይህም
እስክትጠፋ ድረስ ከሰማይ ይወርድብሃል።
25እግዚአብሔር (ያህዌ) በጠላቶችህ ፊት
እንድትሸነፍ ያደርግሃል፤ በአንድ አቅጣጫ
ትመጣባቸዋለህ፤ ነገር ግን በሰባት አቅጣጫ
ከፊታቸው ትሸሻለህ፤ ለምድር መንግሥታትም
ሁሉ መሸማቀቂያ ትሆናለህ። 26ሬሳህ የሰ
ማይ አሞሮችና የምድር አራዊት ሲሳይ
ይሆናል፤ በማስፈራራትም የሚያባርራቸው
አይኖርም። 27እግዚአብሔር (ያህዌ) በ
ማትድንበት በግብፅ ብጉንጅ፣ በእባጭ፣
በሚመግል ቍስልና በዕከክ ያሠቃይሃል።
28እግዚአብሔር (ያህዌ) በእ ብደት በዕ
ውርነትና ግራ በማጋባት ያስጨ ንቅሃል።
29በእኩለ ቀን፣ በጨለማ እንዳለ
ዕውር በዳበሳ ትሄዳለህ። የምታደርገው ሁሉ
አይሳካልህም። በየዕለቱ ትጨቈናለህ፤ ትመዘ
በራለህም፤ የሚታደግህ አይኖርም።
30ሚስት ለማግባት ልጃገረድ ታጫለህ፤
ሌላው ግን ወስዶ ይደፍራታል። ቤት ትሠ
ራለህ፣ ግን አትኖርበትም። ወይን ትተክ
ላለህ፤ ፍሬውን ግን አትበላም። 31በሬህ ዐይንህ
እያየ ይታረዳል፤ ከሥጋውም አንዳች አት
ቀምስም። አህያህም በግድ ይወሰድብሃል፤
አይመለስልህም። በጎችህ ለጠላቶችህ ይሰጣሉ፤
የሚያስጥላቸውም አይኖርም። 32ወንዶችና
ሴቶች ልጆችህ ለባዕድ ሕዝብ ይሰጣሉ፤ እጅ
ህንም ለማንሣት ዐቅም ታጣለህ፤ ከዛሬ ነገ
ይመጣሉ፤ በማለትም ዐይኖችህ ሁልጊዜ
እነርሱን በመጠባበቅ ይደክማሉ። 33የምድ
ርህንና የድካምህን ፍሬ ሁሉ የማታውቀው ሕዝብ
ይበላዋል፤ ዕድሜ ልክህን በጭካኔና በጭቈና
ከመኖር በቀር የሚተርፍህ ነገር አይኖርም።
34የምታየው ሁሉ ያሳብድሃል። 35እግዚአ
ብሔር (ያህዌ) ከእግርህ ጥፍር እስከ ራስህ ጠጕር
በሚዛመት፣ ሊድን በማይችልና በሚያሠቃይ
ቍስል ጕልበትህንና እግርህን ይመታሃል።
36እግዚአብሔር (ያህዌ) አንተንና በላይህ
ያነገሥኸውን ንጉሥ፣ አንተና አባቶችህ
ወደማታውቁት ሕዝብ ይወስዳችኋል፤ ከዚ
ያም ከዕንጨትና ከድንጋይ የተሠሩ ሌሎች
አማልክትን ታመልካለህ። 37እግዚአብሔር
(ያህዌ) እንድትገባ በሚያደርግበት ምድር
ለአሕዛብ ሁሉ መሸማቀቂያ፣ ማላገጫና መዘ
ባበቻ ትሆናለህ።
38በዕርሻ ላይ ብዙ ዘር ትዘራለህ፤ አንበጣ
ስለሚበላው የምትሰበስበው ጥቂት
ይሆናል።

28፥9 ዘፀ19፥6፤ዘሌ26፥3
28፥10 ዘኍ6፥27፤ 1ነገ8፥43፤ኤር25፥29፤ ዳን9፥18
28፥11 ቍ4፤ ዘፍ30፥27፤ዘዳ30፥9
28፥12 ቍ44፤ ዘሌ25፥19፤26፥4፤ ዘዳ15፥3፡6፤ 1ነገ8፥35-36፤18፥1፤ ኢዮ38፥22፤ መዝ65፥11፤68፥10፤ 104፥13፤135፥7፤ ኢሳ5፥6፤30፥23፤ 32፥20፤61፥9፤65፥23፤ ኤር10፥13፤31፥12፤ 32፥38-41፤51፥16፤ ሕዝ34፥26፤ሚል3፥12
28፥13 ዘዳ26፥19፤ ኤር11፥6
28፥14 ዘዳ5፥32፤ ኢ ሱ1፥7
28፥15 ዘዳ27፥26፤ 29፥27፤ኢሱ23፥15፤ 1ነገ9፥6፤2ዜና7፥19፤ኤ ር12፥5፤ዳን9፥11፤ሚ ል2፥2
28፥16 ቍ3
28፥17 ቍ5
28፥18 ቍ4
28፥19 ቍ6
28፥20 ቍ8፡15፤ ዘፀ32፥22፤ዘሌ26፥16፤ ዘዳ4፥26፤መዝ39፥11፤7 6፥6፤80፥16፤ ኢሳ17፥13፤51፥20፤ 54፥9፤66፥15፤ ኤር42፥18፤ሕዝ5፥25፤ ሚል2፥2፤3፥9፤4፥6
28፥21 ዘሌ2625፤ ዘኍ14፥12፤ኤር24፥10፤2 8፥26 ዘፍ40፥19፤ መዝ79፥2፤ኢሳ18፥6፤ ኤር7፥33፤12፥9፤ 15፥2፤16፥4፤19፥7፤34፥ 20 አሞ4፥10
28፥22 ቍ48፤ ዘሌ26፥16፡25፤ ዘዳ4፥26፤32፥24፤ 2ነገ8፥1፤ኢዮ12፥15፤ መዝ105፥16፤ ኤር2፥17፤14፥1፤ አሞ4፥9፤ ሐጌ1፥11፤ሚል3፥9
28፥23 ዘሌ26፥19
28፥24 ዘሌ26፥19፤ ዘዳ11፥17፤1ነገ8፥35፤1 7፥1፤ኢሳ5፥6፤ ኤር14፥1፤ሐጌ1፥10
28፥25 ቍ37፤ ዘሌ26፥17፤ 1ሳሙ4፥10፤2ዜና29፥8፤3 0፥7፤ መዝ78፥62፤ ኤር15፥4፤24፥9፤ 26፥6፤29፥18፤44፥12፤ ሕዝ23፥46
28፥27 ዘዳ7፥15
28፥29 ዘፍ19፥11፤ ዘፀ10፥21፤መሳ3፥9፤ አስ4፥14፤2ነገ13፥5፤ ኢዮ5፥14፤12፥25፤
24፥13፤38፥15፤ኢሳ59፥10፤ኢሳ19፥20፤ 43፥11፤ ሆሴ13፥4፤ አብ1፥21 28፥30 ኢዮ31፥10፤ ኢሳ65፥22፤ኤር12፥13፤ አሞ5፥11
28፥32 ቍ41 28፥33 ኤር5፥15-17፤ 6፥6፤22፥17፤ሕዝ25፥4
28፥34 ቍ67 28፥35 ዘዳ7፥15፤ ኢዮ2፥7፤7፥5፤13፥28፤ 30፥17፡30፤ኢሳ1፥6፤ራእ16፥2 28፥36 ዘዳ4፥27፡ 28፤ 1ሳሙ12፥25፤ 2ነገ24፥14፤25፥7፡ 11፤2ዜና33፥11፤36፥21፤ዕዝ5፥12፤ኤር15፥14፤ 16፥13፤27፥20፤39፥1-9፤ 52፥28፤ሰቆ1፥3 28፥37 ቍ25፤ 1ነገ9፥7፤2ዜና7፥20፤ዕዝ9፥7፤መዝ22፥7፤ 39፥8፤44፥13፡14፤ 64፥8፤ኤር18፥16፤ 19፥8፤24፥9፤25፥9፡ 18፤29፥18፤42፥18፤ 44፥8፤48፥27፤ ሰቆ2፥15፤ሕዝ5፥15፤ ሚክ6፥16 28፥38 ዘፀ 10፥4፡15፤ ዘሌ26፥20፤ መዝ129፥7፤ ኢሳ5፥10፤ኤር12፥13፤ ሆሴ8፥7፤ሐጌ1፥6፡ 9፤2፥16፤ ሚክ6፥15

T20 ዕብራይስጡ፣ እኔን ይላል።

39ወይን ትተክላለህ፤ ትንከባከበዋለህ፤ ነገር
ግን ዘለላውን አትሰበስብም። 40በአገርህ ምድር
ሁሉ የወይራ ዛፍ ይኖርሃል፤ ፍሬው ስለሚ
ረግፍብህ ግን ዘይቱን አትጠቀምበትም።
41ወንዶችና ሴቶች ልጆች ትወልዳለህ፤ ነገር
ግን በምርኮ ስለሚወሰዱ፣ አብረውህ አይኖ
ሩም። 42ዛፍህንና የምድርህን ሰብል ሁሉ
የአንበጣ መንጋ ይወረዋል።
43በመካከልህ የሚኖር መጻተኛ ከአንተ
በላይ ከፍ ከፍ ሲል አንተ ግን ዝቅ ዝቅ
ትላለህ። 44እርሱ ያበድርሃል እንጂ አንተ አታ
በድረውም። እርሱ ራስ ይሆናል፤ አንተ
ግን ጅራት ትሆናለህ።
45እነዚህ ርግማኖች ሁሉ በአንተ ላይ ይመ
ጣሉ፤ *አምላክህን* እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) ስላል
ታዘዝህና የሰጠህን ትእዛዝና ሥርዐት ስላልጠ
በቅህ እስክትጠፋ ድረስ ይከተሉሃል፤ ይወ
ርዱብሃልም። 46ለአንተና ለዘርህ ለዘላለም
ምልክትና መገረም ይሆናሉ። 47በብልጽግና
ጊዜ *አምላክህን* እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) በደስ
ታና በሐሤት ስላላገለገልኸው፣ 48በራብና
በጥም፣ በእርዛትና በከፋ ድኽነት *እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) የሚያስነሣብህን ጠላቶችህን
ታገለግላለህ፤ እስኪያጠፉህም ድረስ በዐንገትህ
ላይ የብረት ቀንበር ይጭንብሃል።
49*እግዚአብሔር* (ያህዌ) እንደ ንስር ፈጥኖ
የሚወርድንና ቋንቋውን የማታውቀውን ሕዝብ
እጅግ ሩቅ ከሆነ፣ ከምድርም ዳርቻ ያስነ
ሣብሃል፤ 50ሽማግሌ የማያከብር፣ ለብላቴና
የማይራራ፣ ሲያዩት የሚያስፈራ ሕዝብ
ነው። 51እስክትጠፋም ድረስ የእንስሳትህን ግል
ገልና የምድርህን ሰብል ይበላል፤ እስኪያጠ
ፋህም ድረስ እህል፣ አዲስ የወይን ጠጅ
ሆነ ዘይት፣ የመንጋህን ጥጃ ሆነ፣ የበግና
ፍየል መንጋህን ግልገል አያስቀርልህም።
52የምትታመንባቸውን ታላላቅ የተመሸጉ ቅጥ
ሮች እስኪወድቁ ድረስ በመላው አገርህ ያሉ
ትን ከተሞችህን ሁሉ ይከባል፤ *አምላክህ*
እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በሚሰጥህ ምድር ያሉትን
ከተሞች በሙሉ ይወራቸዋል።
53ጠላቶችህ ከበው በሚያስጨንቁህ ጊዜ፣
ከሥቃይ የተነሣ፣ *አምላክህ* እግዚአብሔር (ያህዌ
ኤሎሂም) የሰጠህን፣ የወገብህ ፍሬ የሆኑትን
የወንዶችና የሴቶች ልጆችህን ሥጋ ትበላለህ።
54ሌላው ይቅርና በመካከልህ በጣም ደግና
ርኅሩኅ የሆነው ሰው እንኳ ለገዛ ወንድሙ
ወይም ለሚወዳት ሚስቱ ወይም ለተረፉት
ልጆቹ አይራራላቸውም። 55ከሚበላው ከልጆቹ
ሥጋ ላይም ቅንጣት ታህል እንኳ ከእነርሱ
ለአንዱ አያቀምስም፤ ከተሞችህ ሁሉ በመ
ከበባቸው ጠላቶችህ ከሚያደርሱብህ ሥቃይ
የተነሣ ለእርሱ የቀረለት ይህ ብቻ ነውና።
56በመካከልህ ተለሳልሳና ተቀማጥላ የምትኖር፣
ከልስላሴና ከቅምጥልነት የተነሣ፣ እግሯን
ዐፈር ነክቶት የማያውቅ ሴት፣ የምትወደውን
ባሏን፣ የገዛ ወንድ ወይም ሴት ልጇን
ትንቃለች። 57ከማሕፀኗ የወጣውን እንግዴ
ልጇንና የምትወልዳቸውን ሕፃናት ትጠየ
ፋለች፤ ይህን የምታደርገውም በመከራው ወቅት
ጠላቶችህ ከተሞችህን ከበው በሚያስጨንቀ
ህ ጊዜ፣ እነርሱን ደብቃ ለመብላት ስትል
ነው።
58በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የዚህን ሕግ
ቃሎች በጥንቃቄ ባትከተልና አስደናቂና
አስፈሪ የሆነውን *የአምላክህን* የእግዚአብሔርን
(ያህዌ ኤሎሂም) ስም ባታከብር፣ 59*እግዚአብሔር* (ያህዌ)
አስፈሪ መቅሠፍት፣ አስጨናቂና ለብዙ ጊዜ
የሚቈይ መዓት፣ አሠቃቂና በቀላሉ የማይወገድ
ደዌ በአንተና በዘሮችህ ላይ ይልክ
ባችኋል። 60የምትፈራቸውንም የግብፅ በሽ
ታዎች ሁሉ ያመጣብሃል፤ በአንተም ላይ ይጣ
በቃሉ። 61ደግሞም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) በዚህ
የሕግ መጽሐፍ ያልተጻፈውን ማንኛውንም ዐይነት
ደዌና መከራ እስክትጠፋ ድረስ ያመጣብሃል።
62*ለአምላካችሁ* ለእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ስላል
ታዘዛችሁ፣ እንደ ሰማይ ከዋክብት በዝታ
ችሁ የነበራችሁት እናንተ ጥቂት ብቻ ትቀራ
ላችሁ። 63*እግዚአብሔር* (ያህዌ)እናንተን በማበል
ጸግና ቍጥራችሁን በማብዛት ደስ እንዳተሰኘ፣
እናንተን በማጥፋትና በመደምሰስም ደስ
ይለዋል፤ ልትወርሷት ከምትገቡባት ምድር
ትነቀላላችሁ።
64ከዚያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ከአንዱ የምድር
ዳርቻ እስከ ሌላው ዳርቻ በሕዝቦች ሁሉ መካ
ከል ይበትንሃል። በዚያ አንተም ሆንህ አባቶችህ
የማታውቋቸውን ከዕንጨትና ከድንጋይ የተ
ሠሩ ሌሎች አማልክትን ታመልካለህ። 65በእ
ነዚያ ሕዝቦች መካከል ዕረፍት አታገኝም፤
ለእግርህም ጫማ ማረፊያ ቦታ አይኖርም። እዚ
ያም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) የሚጨነቅ
አእምሮ፣ በናፍቆት የሚደክም ዐይንና ተስፋ
የሚቈርጥ ልብ ይሰጥሃል። 66ቀንም ሆነ ሌሊት
በፍርሀት እንደ ተዋጥህ፣ ሕይወትህ ዋስትና
ሳታገኝ፣ ዘወትር በሥጋት ትኖራለህ። 67ልብህ
በፍርሀት ከመሞላቱና ዐይንህ ከሚያየው
የተነሣ፣ ሲነጋ፣ “ምነው አሁን በመሸ!” ሲመሽ
ደግሞ፣ “ምነው አሁን በነጋ!” ትላለህ።
68*ዳግመኛ* አትመለስ ባትም ባልሁህ
መንገድም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) በመርከብ ወደ
ግብፅ ይመልስሃል። እዚያም ወንዶችና
ሴቶች ባሮች እንድትሆኗቸው ለጠ
ላቶቻችሁ ለመሸጥ ራሳችሁን ታቀርባላችሁ፤
የሚገዛችሁ ግን አይኖርም።

28፥39 ዘሌ10፥9፤ ኢሳ5፥10፤17፥10-11፤ ኢል1፥4፤2፥25፤ ሰፎ1፥13፤ ሚል3፥11
28፥40 ኤር11፥16፤ ሚክ6፥15
28፥41 ቍ32
28፥42 ቍ12፥38፤ ዘዳ26፥19፤መሳ6፥5፤ 7፥12፤ኤር46፥23
28፥43 ቍ13
28፥44 ቍ12፤ ዘዳ26፥19
28፥45 ቍ15፤ ዘፀ 15፥9፤ዘዳ4፥25-26
28፥46 ዘኍ16፥38፤ መዝ71፥7፤ኢ ሳ8፥18፤20፥3፤ሕ ዝ5፥15፤ዘካ3፥8
28፥47 ዘሌ23፥40፤ ዘዳ10፥12፤ነህ9፥35
28፥48 ዘፍ49፥8፤ ኤር14፥3፤28፥13-14፤ ሰቆ1፥14፤4፥4
28፥49 ዘፍ11፥7፤ ዘሌ26፥44፤2ሳሙ1፥23፤ኢ ሳ5፥26-30፤ 7፥18-20፤39፥3፤ኤር4፥13፥1 6፤5፥15፤6፥22፤25፥32 ፤31፥8፤48፥40፤ 49፥22፤ ሰቆ4፥19፤ሕ ዝ17፥3፤ ሆሴ8፥1፤1ቆሮ14፥21፤ዕ ብ1፥6
28፥50 ኢ ሳ47፥6
28፥51 ቍ33፤ዘኍ18፥12፤መ ሳ6፥4፤መዝ4፥7፤ ኢ ሳ36፥17፤ሐጌ1፥11
28፥52 2ነገ6፥24፤ ኤር10፥18፤ሕዝ6፥10፤ ሶፎ1፥14-16፥17
28፥53 ቍ57፤ ዘሌ26፥29፤2ነገ6፥28-29፤ ሰቆ2፥20
28፥55 2ነገ6፥29
28፥56 ኢሳ47፥1፤ ሰቆ4፥10
28፥57 ቍ53
28፥58 ዘፀ3፥15፤ ዘዳ31፥24፤መዝ96፥4፤ኤ ር5፥22፤ሚል1፥14፤2፥5፤ 3፥5፥16፤4፥2፤ ኢ ሱ7፥9
28፥60 ዘፀ15፥26
28፥61 ዘዳ4፥25-26፤29፥21፤30፥10፤ 31፥26፤ኢሱ1፥8፤ 8፥34፤23፥6፤24፥26፤ 2ነገ14፥6፤22፥8፤ 2ዜና17፥9፤25፥4፤ ነህ8፥1፥18፤ሚል4፥4
28፥62 ዘፍ22፥17፤ ዘሌ26፥22፤ዘዳ4፥27፤1 0፥22
28፥63 ዘፍ6፥7፤ ዘዳ30፥9፤መዝ52፥5፤ ምሳ1፥26፤ኢሳ62፥5፤ 65፥19፤ኤር12፥14፤ 31፥28፤32፥41፤45፥4፤ሶ ፎ3፥17
28፥64 ዘዳ4፥27፥ 32፤11፥28፤32፥17፤
29፥1 ዘፀ3፥1፤

ዕዝ9፥7፤ነህ1፥8፤ መዝ44፥11፤ኢሳ6፥12፤ ኤር8፥19፤13፥24፤ 18፥17፤22፥22፤ 32፥23፤43፥11፤ 52፥27
28፥65 ዘሌ26፥16፥ 36፤ሰቆ1፥3፤ ኢዩ11፥20፤ሆሴ9፥17
28፥67 ቍ34 28፥68 ዘፀ13፥14

## የቃል ኪዳኑ መታደስ

29 *እግዚአብሔር* (ያህዌ) በኮሬብ ከገባው
ቃል ኪዳን በተጨማሪ በሞዓብ ምድር
ከእስራኤላውያን ጋር እንዲያደርግ ሙሴን
ያዘዘው የኪዳኑ ቃሎች እነዚህ ናቸው።
2ሙሴ እስራኤላውያንን ሁሉ ጠርቶ እንዲህ
አላቸው፦ "*እግዚአብሔር* (ያህዌ) በግብፅ፣ በፈርዖን፣
በሹማምንቱ ሁሉና በመላ አገሩ ላይ ያደረገውን
ሁሉ ዐይኖቻችሁ አይተዋል። 3እነዚያን
ከባድ ፈተናዎች፣ ታምራዊ ምልክቶችና
ታላላቅ ድንቆች በገዛ ዐይኖቻችሁ አይታ
ችኋል። 4ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ *እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) የሚያስተውል አእምሮ ወይም
የሚያይ ዐይን ወይም የሚሰማ ጆሮ አልሰ
ጣችሁም። 5በምድረ በዳ በመራኋችሁ በእ
ነዚያ አርባ ዓመታት ውስጥ ልብሳችሁ
አላረጀም፤ የእግራችሁም ጫማ አላለቀም።
6ቂጣ አልበላችሁም፤ የወይን ጠጅ ወይም
ሌላ የሚያሰክር መጠጥ አልጠጣችሁም፤ ይህን
ያደረግሁት እኔ *እግዚአብሔር* አምላካችሁ
(ያህዌ ኤሎሂም) እንደ ሆንሁ ታውቁ ዘንድ ነው።
7ወደዚህ ስፍራ በደረሳችሁ ጊዜ፣ የሐሴቦን
ንጉሥ ሴዎንና የባሳን ንጉሥ ዐግ ሊወጉን
መጡ፤ ሆኖም ድል አደረግናቸው። 8ምድ
ራቸውንም ወስደን፤ ለሮቤላውያን፣ ለጋዳውያንና
ለምናሴ ነገድ እኩሌታ ርስት አድርገን ሰጠን።
9እንግዲህ የምታደርጉት ሁሉ እንዲከናወ
ንላችሁ፣ የዚህን ኪዳን ቃሎች በጥንቃቄ
ተከተሉ። 10እናንተ ሁላችሁ *መሪዎቻችሁና*
አለቆቻችሁ፣ ሽማግሌዎቻችሁና ሹሞቻችሁ
እንዲሁም ሌሎች የእስራኤል ሰዎች ሁሉ ዛሬ
*በአምላካችሁ* በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ፊት
ቆማችኋል፤ 11ልጆቻችሁና ሚስቶቻችሁ እን
ጨትህን እየፈለጡ፣ ውሃህንም እየቀዱ በሰፈርህ
የሚኖሩ መጻተኞችም አብረውህ ቆመዋል። 12እዚ
ህ የቆምኸው *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ዛሬ
ከአንተ ጋር ወደሚያደርገውና በመሓላ
ወደሚያጸናው ኪዳን *ከአምላክህ* ከእግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ጋር ትገባ ዘንድ፣ 13ለአንተ በሰጠው
ተስፋና ለአባቶችህ ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና
ለያዕቆብ በማለላቸው መሠረት እርሱ
አምላክህ (ኤሎሂም) ይሆን ዘንድ፣ አንተም ሕዝቡ
መሆንህን፣ በዛሬው
ዕለት ለማረጋገጥ ነው። 14እኔም ይህን
የመሓላ ኪዳን የማደርገው ከእናንተ ጋር
ብቻ አይደለም፤ 15አብራችሁን *በአምላካችን*
በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ፊት እዚህ ከቆማች
ሁት ጋር ብቻ ሳይሆን፣ ዛሬ እዚህ ከሌ
ሉትም ጋር ነው።
16በግብፅ ምድር እንዴት እንደ ኖርንና ወደ
ዚህ ስንመጣም በየአገሮቹ ውስጥ እንዴት
እንዳለፍን ራሳችሁ ታውቃላችሁ። 17በመካከላ
ቸውም አስጸያፊ ምስሎቻቸውንና የዕ

ዘሌ7፥38
29፥2 ዘፀ19፥4
29፥3 ዘዳ4፥34
29፥4 ኢሳ6፥10፤
32፥3፤48፥8፤
ኤር5፥21፤ሕዝ12፥2፤
ማቴ13፥15፤ኤፌ4፥18፤
ሮሜ11፥8
29፥5 ዘዳ8፥2፡4
29፥6 ዘሌ10፥9፤
ዘዳ8፥3
29፥7 ዘኍ21፥21-24፡
25፡26፤33-35፤
ዘዳ2፥26-3፥11
29፥8 ዘኍ32፥33፤
ዘዳ3፥12-13፤
መዝ78፥55፤135፥12፤1
36፥22
29፥9 ዘፀ19፥5፤
ዘዳ4፥6፤ኢሱ1፥7፡8፤
2ዜና31፥21፤
መዝ25፥10፤103፥18
29፥11 ኢሱ9፥21፡
23፡27፤1ዜና20፥3
29፥13 ዘፍ6፥18፤
17፥7፤ዘፀ19፥6
29፥14 ዘፀ19፥5፤ ኢ
ሳ59፥21፤
ኤር31፥31፤32፥40፤
50፥5፤ሕዝ16፥62፤
37፥26፤ዕብ8፥7-8
29፥15 ዘፍ6፥18፤
ሐሥ2፥39
29፥17 ዘፀ20፥23፤
ዘዳ4፥28
29፥18 ዘዳ11፥16፤
13፥6፤ዕብ12፥15
29፥19 መዝ36፥2፤
72፥17፤ኢሳ65፥16
29፥20 ዘፀ23፥21፤
34፥14፤2ነገ13፥23፤
14፥27፤መዝ74፥1፤
79፥5፤80፥4፤
ሕዝ23፥25፤36፥5፤
ሶፎ1፥18፤ራእ3፥5
29፥21 ዘዳ28፥61፤
32፥23፤ሕዝ7፥26
29፥22 ኤር19፥8፤
49፥17፤50፥13
29፥23 ዘፍ13፥10፤
14፥8፤19፥24፡25፤
ኢሳ1፥7፤6፥11፤9፥18፤
64፥10፤ኤር12፥11፤
44፥2፡6፤ሕዝ47፥11፤
ሚክ5፥11፤ሶፎ2፥9
ማቴ10፥15፤
ሮሜ9፥29
29፥24 1ነገ9፥8፤
2ዜና36፥19፤
ኤር16፥10፤
22፥8-9፤52፥13
29፥25 2ነገ17፥23፤
2ዜና36፥21
29፥27 ዘዳ28፥15
29፥28 2ዜና7፥20፤
1ነገ14፥15፤መዝ7፥11
፤9፥6፤52፥5፤ምሳ2፥22፤
ኤር12፥14፤31፥28፥42
፤10፤ሕዝ19፥12

ንጨትና የድንጋይ፣ የብርና የወርቅ
ጣዖቶቻቸውን አይ ታችኋል። 18የእነዚ
ህን ሕዝቦች አማልክት ለማምለክ ልቡን
*ከአምላካችን* ከእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)
የሚመልስ ወንድም ሆነ ሴት ጐሣም ሆነ
ነገድ ዛሬ ከመካከላችሁ አለመገኘቱን አረ ጋግጡ፤
ከመካከልህ እንዲህ ያለውን መራራ መርዝ
የሚያወጣ ሥር እንዳይኖር ተጠንቀቁ።
19እንዲህ ያለው ሰው የዚህን መሐላ ቃል
በሚሰማበት ጊዜ፣ በልቡ ራሱን በመባረክ፣
"እንደ ልቤ ሐሳብ ብኖርም እንኳ ሰላም
አለኝ" ብሎ ያስባል። ይህም በለምለሙም
ሆነ በደረቁ መሬት ላይ ጥፋትን ያመጣል[ሀ]።
20*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ለዚያ ሰው ፈጽሞ ይቅርታ
አያደርግለትም፤ ቍጣውና ቅናቱ በእርሱ
ላይ ይነድበታል። በዚህ መጽሐፍ የተጻፈው
ርግማን ሁሉ ይወርድበታል፤ *እግዚአብሐ
ርም* (ያህዌ) ስሙን ከሰማይ በታች
ይደመስሰዋል። 21በዚህ የሕግ መጽሐፍ
በተጻፈው የኪዳኑ ርግማን መሠረት፣
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) እር ሱን ከእስራኤል
ነገዶች ሁሉ ለጥፋት ይለ የዋል።
22የሚቀጥለው ትውልድ ከእናንተ በኋላ
የሚተኩት ልጆቻችሁና ከሩቅ አገር የሚመጡ
እንግዶች በምድሪቱ የደረሰውን ታላቅ መቅሠ
ፍትና *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ያመጣባቸውን
በሽታዎች ያያሉ። 23ምድሪቱ በሙሉ የተቃጠለ
ጨውና ዲን ዐመድ ትሆናለች። አንዳች ነገር
አይተከልባትም፤ ምንም ነገር አያቈጠቍጥባ
ትም፤ የሚያድግ ተክል አይገኝባትም። የሚደር
ስባት ውድመት *እግዚአብሔር* (ያህዌ) በታላቅ
ቍጣ እንደ ገለባበጣቸው እንደ ሰዶምና
ገሞራ፣ እንደ አዳማና ሲባዮ ጥፋት ይሆናል።
24አሕዛብም ሁሉ፣ "*እግዚአብሔር* (ያህዌ) በዚች
ምድር ላይ ይህን ለምን አደረገባት? ይህ
አስፈሪና የሚነድ ቍጣስ ለምን መጣባት?"
ብለው ይጠይቃሉ።
25*መልሱም*፣ "የአባቶቻቸው አምላክ (ኤሎሂም)
ከግብፅ ምድር ባወጣቸው ጊዜ፣ ከእነርሱ
ጋር የገባውን ኪዳን ሕዝቡ ስለ ተዉ ነው።
26ወጥተውም የማያውቋቸውን፣ እርሱም
ያላዘዛቸውን ሌሎችን አማልክት አመለኩ፤
ሰገዱላቸውም። 27ስለዚህ በዚህ መጽሐፍ የተ
ጻፈውን ርግማን ሁሉ እስኪያመጣባት ድረስ፣
*የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ቍጣ በዚህች ምድር
ላይ ነደደ። 28በአስፈሪ ቍጣና በታላቅ መዓት
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ከምድራቸው ነቀላቸው፤
አሁን እንደ ሆነውም ወደ ሌላ ምድር
ጣላቸው" የሚል ይሆናል።
29ምስጢር የሆነው *ለአምላካችን* ለእግዚ
አብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ነው፤ የተገለጠው ግን የዚህን

29፥29 ሐሥ1፥7፤ 17፥11፤ዮሐ5፥39፤ 2ጢሞ3፥16

[ሀ]19 ወይም፣ *ለመርካት ስካርን ይጨምራል*።

ሕግ ቃል ሁሉ እንከተል ዘንድ ለዘላለም
የኛና የልጆቻችን ነው።

**ወደ እግዚአብሔር በመመለስ የሚገኝ በረከት**

30 በፊትህ ያስቀመጥሁት ይህ በረከትና
መርገም ሁሉ በአንተ ላይ ሲመጣና
አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) በትኖህ
በምትኖርበት አሕዛብ መካከል ሆነህ ወደ ልብህ
ተመልሰህ ነገሮቹን በምታስተውልበት ጊ
ዜ፣ 2እንዲሁም ዛሬ እኔ በማዝህ ሁሉ መ
ሠረት አንተና ልጆችህ ወደ አምላካችሁ
ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ተመልሳችሁ በፍ
ጹም ልባችሁና በፍጹም ነፍሳችሁ እርሱን
ስትታዘዙ፣
3አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ምርኮህን
ይመልስልሃል^፤ ይራራልሃልም፤ አንተን ከበተ
ነበት አሕዛብ መካከል እንደ ገና ይሰበስብሃል።
4ከሰማይ በታች እጅግ ሩቅ ወደ ሆነ ምድር
ብትጋዝ እንኳ፣ አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎ
ሂም)ከዚያ ይሰበስብሃል፤ መልሶም ያመጣሃል።
5የአባቶችህ ወደ ሆነችው ምድር ያመጣሃል፤
አንተም ትወርሳታለህ። ከአባቶችህ ይበልጥ ያበለ
ጽግሃል፤ ያበዛሃልም። 6አምላክህን እግዚአብሔርን
(ያህዌ ኤሎሂም) በፍጹም ልብህና በፍጹም ነፍስህ
እንድትወደው፣ በሕይወትም እንድትኖር፣
አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) የአንተንና
የዘርህን ልብ ይገርዛል። 7አምላክህ እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ይህን ርግማን ሁሉ በሚጠሉህና
በሚያሳድዱህ ጠላቶችህ ላይ ያደርገዋል። 8አን
ተም ተመልሰህ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) ትታዘዛ
ለህ፤ ዛሬ እኔ የማ ዝህን ትእዛዝ ሁሉ ትጠ
ብቃለህ። 9ከዚያም አምላክህ እግዚአብሔር (ያህዌ
ኤሎሂም) በእጅህ ሥራ ሁሉና በወገብህ ፍሬ፣ በእ
ንስሳትህ ግልገሎችና በምድርህ ሰብል እጅግ
ያበለጽግሃል። በአባቶችህ ደስ እንደ ተሰኘ
ሁሉ፣ እግዚአብሔር (ያህዌ) አንተንም በማበል
ጸግ ደስ ይለዋልና። 10ይህም የሚሆነው፣
አምላክህን እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) ከታዘዝህና
በዚህ የሕግ መጽሐፍ የተጻፉትን ትእዛዙንና
ሥርዐቱን በመጠበቅ፣ በፍጹም ልብህና በፍ
ጹም ነፍስህ ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ስትመለስ ነው።

**ሕይወትን ወይም ሞትን ስለ መምረጥ**

11በዛሬው ዕለት የምሰጥህ ትእዛዝ ይህን
ያህል አስቸጋሪ ወይም ከአንተ የራቀች አይ
ደለችም። 12"እንድንፈጽማት አምጥቶ ይነግረን
ዘንድ፣ ማን ወደ ሰማይ ይወጣል?" እንዳትል፣
በላይ በሰማይ አይደለችም። 13ደግሞም፣
"እንድናደርጋት አምጥቶ ይነግረን ዘንድ፣
ማን ባሕሩን ይሻገራል?" እንዳትልም፣ ከባሕር
ማዶ አይደለችም። 14ነገር ግን ቃሉ ለአንተ
በጣም ቅርብ ነው፤ ታደርገውም ዘንድ በአፍህና
በልብህ ውስጥ ነው።

30፥1 ዘሌ26፥40-45፤ ዘዳ4፥32፤11፥26፤ 29፥28
30፥2 ዘዳ4፥29፡30፤ መዝ119፥2
30፥3 ዘፍ11፥4፤ 48፥21፤ዘዳ4፥27፤ 13፥17፤መዝ14፥7፤ 53፥6፤85፥1፤126፥4፤ኢሳ11፥11፤ኤር12፥15፤ 16፥15፤24፥6፤29፥14፤30፥18፤33፥11፤48፥47፤49፥6፤ሕዝ16፥53፤ ኢል3፥1
30፥4 ነህ1፥8-9፤ መዝ19፥6፤ ኢሳ11፥12፤17፥6፤ 24፥13፤27፥12፤40፥11፤ 41፥5፤42፥10፤43፥6፤48፥20፤49፥5፤56፥8፤62፥11፤ኤር10፥50፥2፤29፥31፥8፤ሕዝ20፥34፡41፤34፥13
30፥5 ዘዳ7፥13፤ ኤር29፥14
30፥6 ዘዳ6፥5፡24፤ 10፥16
30፥7 ዘፍ12፥3፤ ዘዳ7፥15
30፥9 ዘዳ28፥63፤ ኤር1፥10፥24፥6፤ 31፥28፤34፥41፤ 42፥10፤45፥4
30፥10 ዘዳ5፥29፤ 28፥61
30፥11 መዝ19፥8፤ ኢሳ45፥19፡23፤63፥1
30፥12 ምሳ30፥4፤ ሮሜ10፥6
30፥13 ኢዮ28፥14፤ ሮሜ10፥7
30፥14 ዘዳ6፥6፤ ሮሜ10፥8
30፥15 ዘፍ2፥17፤ ዘዳ11፥26፤28፥11፤ ኢዮ36፥10፤ መዝ25፥13፤106፥5፤ ምሳ3፥1-2፤10፥16፤ 11፥19፤12፥28፤ኤር21፥8
30፥16 ቀኑ19፤ ዘዳ4፥1፤6፥5፤32፥47፤ነህ9፥29
30፥18 ዘዳ8፥19
30፥19 ዘዳ4፥26፤ 11፥26
30፥20 ዘፍ12፥7፤ ዘዳ4፥1፤6፥5፤8፥3፤ 32፥47፤ መዝ27፥137፥3፤ ምሳ3፥22፤ዮሐ5፥26፤ ሐሥ17፥28
31፥2 ዘፀ7፥7፤ ዘኍ27፥17፤ ዘዳ3፥23፡26፤1ነገ3፥7
31፥3 ዘኍ27፥18፤ ዘዳ3፥28፤7፥1፤9፥3
31፥4 ዘኍ21፥33
31፥5 ዘዳ2፥33 9፡18፤10፥25፤

15እነሆ፤ ዛሬ ሕይወትንና በረከትን፣ ሞትንና
ጥፋትን በፊትህ አኑሬአለሁ። 16አምላክህን
እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) እንድትወድ፣ በመንገዱም
እንድትሄድና ትእዛዙን፣ ሥርዐቱንና ሕጉን
እንድትጠብቅ አዝሃለሁ፤ ከዚያም በሕይወት
ትኖራለህ፤ ትበዛለህም፤ አምላክህም እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ትወርሳት ዘንድ በምትገባበት
ምድር ይባርክሃል።
17ዳሩ ግን ልብህ ወደ ኋላ ቢመለስና ባትታዘዝ፣
ለሌሎች አማልክት ለመስገድ ብትታለልና
ብታመልካቸው፣ 18በርግጥ እንደምትጠፉ
እኔ በዛሬው ዕለት እነግራችኋለሁ፤ ዮርዳኖስን
ተሻግረህ ትወርሳት ዘንድ በምትገባባት ምድር
ብዙ አትኖሩባትም።
19ሕይወትንና ሞትን፣ በረከትንና ርግማ
ንን በፊትህ እንዳስቀመጥሁ ዛሬ ሰማይንና
ምድርን ምስክር አድርጌ እጠራብሃለሁ።
እንግዲህ አንተና ልጆችህ በሕይወት እን
ድትኖሩ ሕይወትን ምረጥ፤ 20ይኸውም አምላ
ክህን እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) እንድትወድ፣
ቃሉን እንድታደምጥና ከእርሱ ጋር እንድ
ትጣበቅ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር
(ያህዌ) ሕይወትህ ነው፣ ለአባቶችህ፣ ለአብርሃም፣
ለይስሐቅና ለያዕቆብ ሊሰጣቸው በማለላቸው
ምድር ረጅም ዕድሜ ይሰጥሃል።

**ኢያሱ በሙሴ እግር መተካቱ**

31 ከዚያም ሙሴ ወጥቶ እነዚህን ቃሎች
ለእስራኤል ሁሉ ተናገረ፤ 2"እነሆ፤
መቶ ሃያ ዓመት ሆኖኛል፤ ከእንግዲህ ልወ
ጣና ልገባ አልችልም፤ እግዚአብሔርም (ያህዌ)
'ዮርዳኖስን አትሻገርም' ብሎኛል፤ 3አምላክህ
እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ራሱ በፊትህ ቀድሞ
ይሄዳል፤ እነዚህንም አሕዛብ ከፊትህ ያጠ
ፋቸዋል፤ አንተም ምድራቸውን ትወርሳለህ፤
እግዚአብሔር (ያህዌ) እንደ ተናገረው፣ ኢያ
ሱም አንተን ቀድሞ ይሻገራል። 4እግዚአብሔር
(ያህዌ) የአሞራውያንን ነገሥታት ሴዎንንና
ዐግን ከነምድራቸው እንዳጠፋቸው እነዚህንም
ያጠፋቸዋል። 5እግዚአብሔር (ያህዌ) እነርሱን
በፊ ታችሁ አሳልፎ ይሰጣችኋል፤ እናንተም
ያዘ ዝኋችሁን ሁሉ በእነርሱ ላይ
ታደርጋላችሁ። 6ብርቱና ደፋር ሁኑ፤
አትፍሯቸው ወይም
አትደንግጡላቸው። አምላክህ እግዚአብሔር
(ያህዌ ኤሎሂም) ካንተ ጋር ይሄዳልና፤
አይተውህም፤ አይጥልህምም።"
7ከዚያም ሙሴ ኢያሱን ጠርቶ በእስራ
ኤል ሁሉ ፊት እንዲህ አለው፤ "እግዚአብሔር
(ያህዌ) ለአባቶቻቸው ሊሰጥ ወደ ማለላቸው
ምድር

31፥6 ቀኑ7፥23፤ ዘፍ28፥15፤ዘዳ1፥29፤4፥31፤20፥4፤ኢሱ1፥6፡ 1ነገ6፥13፤1ዜና22፥13፤ 28፥20፤2ዜና32፥7፤መዝ56፥9፤94፥14፤ 118፥6፤ ኢሳ41፥17፤ ኤር1፥8፡17፤ሕዝ2፥6፤ ማቴ28፥20፤ዕብ13፥5
31፥7 ቀኑ23፤ ዘኍ27፥23፤ኢሱ1፥6

^3 ወይም፣ ከግዞት ይመልስሃል።

ከዚህ ሕዝብ ጋር አብረህ ስለምትገባ፣ ምድሪ
ቱን ርስታቸው አድርገህ ስለምታከፋፍል
በርታ፤ ደፋርም ሁን:: 8እግዚአብሔር (ያህዌ)
ራሱ በፊትህ ይሄዳል፤ ከአንተም ጋር ይሆናል፤
ፈጽሞ አይለይህም፤ አይተውህምም፤ አትፍራ
፤ ተስፋም አትቍረጥ::”

## ሕጉን ለማንበብ ትእዛዝ ስለ መስጠቱ

9ሙሴም ይህን ሕግ ጽፎ፣ የእግዚአብሔርን
(ያህዌ) የኪዳን ታቦት ለሚሸከሙ ለሌዊ ልጆች፣
ለካህናቱና ለእስራኤል አለቆች ሁሉ ሰጠ::
10ከዚያም በኋላ ሙሴ እንዲህ ሲል አዘዛቸው፤
“ዕዳ በሚተውበት፣ የዳስ በዓልም በሚከ
በርበት፣ በየሰባቱ ዓመት መጨረሻ፣ 11እስ
ራኤል ሁሉ እርሱ በሚመርጠው ስፍራ
በአምላክህ በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) ፊት ሲ
ታይ ይህን ሕግ በእነርሱ ፊት በጆሮአቸው
ታነብ ዋለህ:: 12ይሰሙና አምላካችሁን እግዚአብሐ
ብርን (ያህዌ ኤሎሂም) መፍራት ይማሩ ዘንድ፣ የዚ
ህን ሕግ ቃል ሁሉ በጥንቃቄ እንዲ
ከተሉ ሕዝቡን ይኸውም ወንዶችን፣
ሴቶችን፣ ልጆችንና በከተሞችህ
የሚኖረውንም መጻተኛ ሰብስብ::
13ዮርዳኖስን ተሻግረህ በምትወርሷት ምድር
በምትኖሩበት ዘመን ሁሉ ይህን ሕግ የማ
ያውቁት ልጆቻቸውም መስማትና አምላካችሁን
እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) መፍራት ሊማሩ ይገባቸዋል::

## የእስራኤል አለመታዘዝ አስቀድሞ ስለ መነገሩ

14እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን፣ “እነሆ የምት
ሞትበት ቀን ቀርቦአል፤ ትእዛዝ እንድሰጠው
ኢያሱን ጥራውና ወደ መገናኛው ድንኳን
ቅረቡ::” ሙሴና ኢያሱም ሄዱ፤ ወደ መገና
ኛው ድንኳንም ቀረቡ::
15እግዚአብሔርም (ያህዌ) በድንኳኑ ላይ
በደመና
ዐምድ ተገለጠ፤ የደመናውም ዐምድ ከድንኳኑ
ደጃፍ ላይ ቆመ:: 16እግዚአብሔርም (ያህዌ) ሙሴን
እንዲህ አለው:- “እነሆ፣ ከአባቶችህ ጋር
ልታርፍ ነው፤ ይህም ሕዝብ በሚገባበት
ምድር በሚ ገኙ ባዕዳን አማልክት ወዲያውኑ
ያመነዝራል:: እኔን ይተወኛል፤ ከእነርሱም
ጋር የገባሁትን ኪዳን ያፈርሳሉ:: 17በዚያች
ቀን እቈጣቸዋለሁ፤ እተዋቸዋለሁም፤ ፊቴን
ከእነርሱ እሰውራለሁ፤ እነርሱም ይጠፋሉ::
ብዙ ጥፋትና የከፋ ችግር ይደርስባቸዋል፤
በዚያችም ቀን፣ ‘ይህ ጥፋት የደረሰብን፣
አምላካችን (ኤሎሂም) ከእኛ ጋር ባለመሆኑ
አይደለምን?’ ይላሉ:: 18ወደ ባዕዳን አ
ማልክት በመዞር ከፈጸሙት ክፋታ ቸው
የተነሣ፣ በዚያች ቀን ፊቴን ከእነርሱ ፈጽሞ
እሰውራለሁ::
19“እንግዲህ ይህን መዝሙር ለራሳችሁ
ጻፉ፤ ለእስራኤል ልጆችም አስተምሩ፤ ስለ

31፥8 ዘፍ28፥15፤ ዘፀ13፥21፤ዘዳ4፥31
31፥9 ቍ25፤ ዘፀ17፥14፤1ዜና15፥2
31፥10 ዘፀ23፥16፤ ዘዳ15፥1፤16፥13
31፥11 ዘዳ12፥5፤ 16፥16፤ኢሱ8፥34-35፤ 2ነገ23፥2፤ነህ8፥2
31፥12 ዘዳ4፥10፤ ሐጌ1፥12፤ ሚል1፥6፤ 3፥5፥16
31፥13 ዘዳ11፥2
31፥14 ዘፍ25፥8፤ ዘፀ33፥9-11፤ ዘኍ27፥13፥19፥23፤ ዘዳ34፥9፤ኢሱ1፥1-9
31፥15 ዘፀ33፥9
31፥16 ዘፍ15፥15፤ ዘፀ34፥15፤ዘዳ4፥25-28፤ መሳ2፥12፤10፥6፥13፤1 ነገ9፥9፤18፥18፤ 19፥10፤ኤር2፥13፤ 5፥19፤19፥4
31፥17 ዘኍ14፥42፤ ዘዳ32፥16፥20፤ መሳ2፥14፥20፤6፥13፤1 0፥7፤2ነገ13፥3፤ 22፥13፤2ዜና15፥2፤ 24፥20፤ዕዝ8፥22፤ ኢ ዮ13፥24፤መዝ13፥1፤ 27፥9፤30፥7፤44፥9፤ 104፥29፤106፥29፥40፤ኢ ሳ1፥15፤2፥6፤ 45፥15፤50፥6፤53፥3፤5 4፥8፤ኤር4፥20፤7፥18፤ 21፥5፤33፥5፤36፥7፤ ሕ ዝ7፥26፤ሕዝ39፥29፤ ሆሴ9፥12፤ሚክ3፥4
31፥19 ቍ22፤ ዘፍ31፥50
31፥20 ቍ16፤ ዘፍ6፥10-12፤ ዘዳ6፥10-12፤ 8፥19፤11፥16-17፤ መዝ4፥2፤16፥4፤ 40፥4፤ኤር13፥25፤ ዳን3፥28፤አሞ2፥4
31፥21 ዘዳ4፥30፤ 1ዜና28፥9፤ሆሴ5፥3፤ዮ ሐ2፥24-25
31፥22 ቍ19
31፥23 ቍ7፤ኢ ሱ1፥6 31፥24 ዘዳ17፥18፤ 28፥582ነገ22፥8
31፥25 ቍ9
31፥26 ቍ19
31፥27 ዘፀ23፥21፤ ዘዳ9፥27
31፥28 ዘዳ4፥26፤ 30፥19፤32፥1፤ኢ ዮ20፥27፤ኢሳ26፥21
31፥29 ዘዳ4፥16፤1ነገ9፥9፤ 22፥23፤2ነገ22፥16፤ራ እ9፥20
32፥1 ዘዳ4፥26፤ መዝ49፥1፤ኤር2፥12፤ ሚክ1፥2

እኔ ምስክር ይሆንባቸው ዘንድ እንዲዘምሩ
አድርጉ:: 20ወተትና ማር ወደምታፈሰውና
ለአባቶቻቸው በመሐላ ቃል ወደ ገባሁላቸው
ምድር ባመጣኋቸው ጊዜ ከበሉና ከጠ
ገቡ፣ ከበለጸጉም በኋላ እኔን ንቀው ኪዳኔንም
አፍርሰው ወደ ባዕዳን አማልክት ይዞራሉ፤
እነርሱንም ያመልካሉ:: 21ብዙ ጥፋትና የከፋ
ችግር በደረሰባቸው ጊዜ ይህ መዝሙር
ምስክር ይሆንባቸዋል:: በዘራቸው የሚረሳ
አይደለምና:: ወደ ማልሁላቸው ምድር ሳላስገ
ባቸው በፊት ምን ለማድረግ እንደሚያስቡ
እንኳን አስቀድሜ ዐውቃለሁ::” 22ስለዚ
ህም ሙሴ ይህን መዝሙር በዚያች ቀን ጻፈ፤
ለእስራኤላውያንም አስተማራቸው::
23እግዚአብሔርም (ያህዌ) ለነዌ ልጅ ለኢያሱ፣
“በርታ፤ ደፋር ሁን፤ የእስራኤልን ልጆች
በመሐላ ቃል ወደ ገባሁላቸው ምድር ታስገ
ባቸዋለህና፤ እኔም ከአንተ ጋር እሆናለሁ”
በማለት ትእዛዝ ሰጠው::
24ሙሴ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የዚህን
ሕግ ቃል በመጽሐፍ ጽፎ እንዳበቃ፣ 25የእግዚ
አብሔርን (ያህዌ) የኪዳን ታቦት የሚሸከሙ ሌዋ
ውያንን እንዲህ ሲል አዘዛቸው፤ 26“በእናንተ
ላይ ምስክር ሆኖ በዚያ ይኖር ዘንድ በአም
ላካችሁ በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) የኪዳን ታቦት
አጠገብ አስቀምጡት፤ ይህም በእናንተ ላይ
ምስክር ሆኖ በዚያ ይኖራል፤ 27የቱን ያህል ዐ
መፀኞችና ዐንገተ ደንዳኖች እንደ ሆናችሁ ዐ
ው ቃለሁና:: እኔ በሕይወት ከእናንተ ጋር
እያለሁ እንደዚህ ካመፃችሁ፣ ከሞትሁ
በኋላማ የቱን ያህል ልታምፁ! 28ይህን ቃል
ይሰሙ ዘንድ እንድናገር፣ ሰማይንና ምድርን
ምስክር አድርጌ እንድጠራባቸው፣ የነገድ
አለቆቻችሁን በሙሉና ሹሞቻችሁን ሁሉ
በፊቴ ሰብስቡ:: 29እኔ ከሞትሁ በኋላ
ፈጽማችሁ እንደምትረክሱ፣ ካዘዝኋችሁም
መንገድ ዘወር እንደምትሉ ዐውቃለሁና::
በእግዚ አብሔር (ያህዌ) ፊት ክፉ ድርጊት
ስለም ትፈጽሙ፣ እጆቻችሁ በሠሯቸውም
ነገሮች እርሱን ለቍጣ ስለምታነሣሡት፣
በሚመጡት ዘመናት ጥፋት
ይደርስባችኋል::”

## የሙሴ መዝሙር

30ሙሴም የዚህን መዝሙር ቃል ከመጀመሪያ
እስከ መጨረሻ ድረስ፣ ለተሰበሰበው የእስራ
ኤል ሕዝብ ሁሉ በጆሮአቸው እንዲህ ሲል አሰማ:-

32 ሰማያት ሆይ፤ አድምጡ፤ እኔም እና
ገራለሁ፤
ምድር ሆይ፤ አንቺም የአፌን ቃል ስሚ::
2ትምህርቴ እንደ ዝናብ ትውረድ፤
ቃሌም እንደ ጤዛ ይንጠባጠብ፤

32፥2 2ሳሙ23፥4፤ መዝ65፥10፤68፥9፤ 72፥6፤107፥20፤ 147፥8፤ኢሳ9፥8፤ 55፥11፤ሚክ5፥7

በቡቃያ ሣር ላይ እንደ ካፊያ፣
ለጋ ተክልም ላይ እንደ ከባድ ዝናብ
ይውረድ::
3እኔ *የእግዚአብሔርን* (ያህዌ) ስም ዐውጃለሁ፤
የአምላካችንን (ኤሎሂም) ታላቅነት አወድሱ!
4እርሱ ዐለት፣ ሥራውም ፍጹም ነው፤
መንገዱም ሁሉ ትክክል ነው፤
የማይሳሳት ታማኝ አምላክ፣
ቀጥተኛና ጻድቅ አምላክም (ኤሎሂም) እርሱ
ነው::
5በእርሱ ላይ ክፋት ፈጽመዋል፤
ከነውራቸው የተነሣ ከእንግዲህ ልጆቹ
አይደሉም፤
ወልጋዳና ጠማማ ትውልዶች ናቸው[ሐ]::
6አንተ ተላላና ጥበብ የጐደለህ ሕዝብ፣
*ለእግዚአብሔር* (ለያህዌ) የምትመልስለት
በዚህ መንገድ ነውን?
አባትህ ፈጣሪህ[መ]፣
የሠራህና ያበጀህ እርሱ አይደለምን?
7የጥንቱን ዘመን አስታውስ፤
አባትህን ጠይቅ፤ ይነግርሃልም፤
ሽማግሌዎችህንም ጠይቅ፤ ያስረዱሃል::
8ልዑል ለአሕዛብ ርስታቸውን በሰጠ ጊዜ፣
የሰውንም ዘር በለያየ ጊዜ፣
በእስራኤል ልጆች[ሠ] ቍጥር ልክ፣
የአሕዛብን ርስት ድንበር ለየ፤
9*የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ድርሻ የገዛ ሕዝቡ፣
ያዕቆብ የተለየ ርስቱ ነውና::
10እርሱን በምድረ በዳ፣
ባዶና ጭው ባለ በረሓ ውስጥ አገኘው፤
ጋሻ ሆነው፤ ተጠነቀቀለትም፤
እንደ ዐይኑ ብሌን ጠበቀው::
11ንስር ጎጆዋን በትና፣
በጫጩቶቿም ላይ እንደምትረብብ፣
እነርሱን ለመያዝ ክንፎቿን እንደምትዘረጋ፣
በክንፎቿም እንደምትሸከማቸው፣
12*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ብቻ መራው፤
ምንም ባዕድ አምላክ አብሮት አልነበረም::
13በምድር ከፍታ ላይ አወጣው፤
የዕርሻንም ፍሬ መገበው፤
ከዐለት ድንጋይ ማር አበላው፤
ከባልጩትም ድንጋይ ዘይት መገበው::
14የላሙንና የበጉን መንጋ ቅቤና ወተት፣
የሰቡትን በጎችና ፍየሎች፣
የባሳንን ምርጥ አውራ በግ፣
መልካም የሆነውንም ስንዴ፣
ማለፊያውንም የወይን ጠጅ፣
15ይሹሩን[ረ] ወፈረ፤ ረገጠ፤
ጠገበ፤ ሰውነቱ ደነደነ፤ ለሰለሰ፤
የፈጠረውንም አምላክ (ኤሎሂም) ተወ፤
መጠጊያ ዐለት የሆነውን አዳኙንም ናቀ::
16በባዕዳን አማልክታቸው አስቀኑት፤
በአስጸያፊ ጣዖቶቻቸውም አስቈጡት::
17አምላክ ላልሆኑ አጋንንት:-
ላላወቋቸው አማልክት፣
ከጊዜ በኋላ ለተነሡ አማልክት፣
አባቶቻችሁ ላልፈሯቸው አማልክት ሠዉ::
18አባት የሆነህን ዐለት ከዳኸው፤
የወለደህን አምላክ (ኤሎሂም) ረሳኸው::
19*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ይህን አይቶ ናቃቸው፤
በወንድና በሴት ልጆቹ ተቈጥቶአልና::
20እርሱም፣ "ፊቴን ከእነርሱ እሰውራለሁ፤"
"መጨረሻቸው ምን እንደሚሆንም አያለሁ
አለ፤
ጠማማ ትውልድ፣
የማይታመኑም ልጆች ናቸውና::
21አምላክ ባልሆነው አስቀኑኝ፤
በከንቱ ጣዖቶቻቸው አስቈጡኝ::
እኔም ሕዝብ ባልሆነው አስቀናቸዋለሁ::
በማያስተውልም ሕዝብ
አስቈጣቸዋለሁ::
22በቍጣዬ እሳት ተቀጣጥሎአልና፤
እርሱ እስከ ሲኦል ዘልቆ ይነዳል::
ምድርን እስከ ሰብሏ ይበላል፤
የተራሮችንም መሠረት ያቀጣጥላል::
23"በመዓት ላይ መዓት አመጣባቸዋለሁ::
ፍላጻዬንም በእነርሱ ላይ እጨርሳለሁ::
24የሚያጠፉ ራብ፣
በልቶ የሚጨርስ ቸነፈርና ከባድ
መቅሠፍት እሰድባቸዋለሁ፤
የአራዊትን ሹል ጥርስ፣
በምድር የሚሳብ የእባብ መርዝም
እሰድባቸዋለሁ::
25ሰይፍ መንገድ ላይ ያስቀራቸዋል፤
ቤታቸውም ውስጥ ድንጋጤ ይነግሣል፤
ጐልማሳውና ልጃገረዷ፣
ሕፃኑና ሽማግሌው ይጠፋሉ::
26እበትናቸዋለሁ፤
ከሰዎችም መካከል መታሰቢያቸውን
አጠፋለሁ አልሁ፤

32፥4 ዘፍ18፥25፤ 49፥24፤ዘዳ4፥35፤ 2ሳሙ22፥31፤ መዝ18፥30፤19፥7፤ 92፥15
32፥5 ቍ20፤ ማቴ17፥17፤ሉቃ9፥41፤ ሐሥ2፥40
32፥6 ቍ15፥28፤ ዘፀ4፥22፤2ሳሙ7፥24፤ መዝ94፥8፤116፥12፤ኤር5፥21
32፥7 ዘፀ10፥2፤ ዘዳ4፥32፤ኢዮ8፥8፤ 15፥18፤20፥4፤ መዝ44፥1፤74፥2፤ 77፥5፤78፥4፤ ኢሳ46፥9፤
32፥8 ዘፍ11፥8፤ ዘኍ23፥9፤ዘዳ33፥12፥ 28፤መዝ7፥8፤74፥17፤ ኤር23፥6፤ሐሥ8፥1
32፥9 ዘዳ9፥29፤ 1ሳሙ26፥19፤ መዝ16፥5፤73፥26፤ 119፥57፤142፥5፤ ኤር10፥16
32፥10 ዘፀ19፥4፤ ዘዳ1፥19፤8፥15፤ ኢዮ12፥24፤መዝ17፥8፤ 32፥10፤107፥40፤ ምሳ7፥2፤ኤር31፥22፤ ሆሴ13፥5፤ዘካ2፥8
32፥11 ዘፀ19፥4፤ መዝ17፥8፤18፥10-19፤ 61፥4
32፥12 ቍ39፤ ዘዳ4፥35፤መሳ2፥12፤ መዝ18፥31፤81፥9፤ 106፥9፤ኢሳ43፥12፤ 45፥5፤63፥13፤ ኤር31፥32
32፥13 ዘዳ8፥8፤ 33፥24፥29፤ 2ሳሙ22፥34፤ ኢዮ29፥6፤መዝ18፥33፤ ኢሳ33፥16፤58፥14፤ ሕዝ36፥2፤ዕብ3፥19
32፥14 ዘፍ49፥11፤ ዘኍ21፥33፤መዝ65፥9፤ 81፥16፤147፥14
32፥15 ዘፍ49፥24፤ ዘዳ31፥20፥16፤ 33፥5፤ኢሳ1፥4፥ 28፤44፥2፤58፥2፤65፥11 ፤ኤር5፥28፤ 15፥6፤ሕዝ14፥5፤
32፥16 ዘኍ25፥11፤ ዘዳ31፥17፤ 1ነገ14፥9፤ 1ቆሮ10፥22
32፥17 ዘፀ32፥8፤ 22፥20፤ዘዳ28፥64፤ መሳ5፥8፤ 1ቆሮ 10፥20
32፥18 መሳ3፥7፤ 1ሳሙ12፥9፤ መዝ44፥17፥ 20፤ 06፥21፤ኤር2፥32፤ ሕዝ23፥35፤ሆሴ8፥14፤ 13፥6 ኢሳ10፥13፤ ኤር40፥2-3
32፥19 ዘሌ26፥30፤ መዝ78፥59፤ አሞ6፥8
32፥20 ቍ5፤ ዘዳ9፥23፤31፥17፥29፤ መዝ4፥6፤44፥24
32፥23 ቍ42፤ዘዳ29፥21፤ 2ሳሙ22፥15 ኢዮ6፥4፤ መዝ7፥13፤ 18፥14፤ 45፥5፤77፥17፤120፥4፤ኢሳ5፥28፤ 49፥2፤ሕዝ5፥16፤ዕን3፥9፥ 11
32፥24 ቍ33፤ ዘፍ26፥1፤37፥20፤ 41፥55፤42፥5፤ ዘዳ28፥22፤ 2ሳሙ24፥13፤ 1ዜና21፥12፤ኢዮ20፥16፤መዝ58፥4፤91፥6፤ ኤር8፥17፤ አሞ5፥18-19፤ ሚክ7፥17
32፥25 2ዜና36፥17፤ኢሳ13፥18፤24፥17፤ ኤር4፥31፤14፥18፤ ሰቆ1፥20፤2፥21፤ሕዝ7፥15፤2ቆሮ7፥5
32፥26 ዘኍ14፥12፤ ዘዳ4፥27፤ኢዮ18፥17፤ መዝ18፥17፤34፥16፤ 37፥28፤109፥15፤ኢሳ14፥20

[ሐ]5 ወይም *የተጣመሙት እነርሱ እንጂ የእርሱ ልጆች አይደሉም*::
[መ]6 ወይም *ያወጣህ አባትህ*::
[ሠ]8 የማሶሬቱ ቅጅ፣ የሙት ባሕር ጥቅል እንዲሁም የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም፣ *የእግዚአብሔር ልጆች* ይላሉ::
[ረ]15 ይሹሩን ማለት *ቅን* ወይም *ትክክለኛ* ማለት ሲሆን፣ ይኸውም እስራኤልን የሚያሳይ ነው::

27ነገር ግን ጠላቶቻቸው እንዳይታበዩ፣
 ‘ድል ያደረገችው እጃችን እንጂ፣
እግዚአብሔር (ያህዌ) ይህን ሁሉ አላደረገም
 እንዳይሉ፣’”
 የጠላትን መነሣሣት ሠጋሁ።
28አእምሮ የጐደላቸው፣
 ማስተዋልም የሌላቸው ናቸው።
29አስተዋዮች ቢሆኑ ኖሮ ይህን በተገነዘቡ፣
 መጨረሻቸውም ምን እንደሚሆን ባስተዋሉ
 ነበር።
30መጠጊያ ዐለታቸው ካልሸጣቸው፣
 እግዚአብሔር (ያህዌ) ካልተዋቸው በቀር፣
አንድ ሰው እንዴት ሺሁን ያሳድዳል?
 ሁለቱስ እንዴት ዐሥር ሺሁን እንዲ
 ሸሹ ያደርጋሉ?
31የእነርሱ መጠጊያ ዐለት እንደ እኛ መጠጊያ
 ዐለት አይደለምና፤
 ጠላቶቻችንም እንኳ ይህን አይክዱም።
32ወይናቸው ከሰዶም ወይን፣
 ከገሞራም እርሻ ይመጣል፤
የወይናቸው ፍሬ በመርዝ፣
 ዘለላቸውም በምሬት የተሞላ ነው።
33ወይናቸው የእባብ መርዝ፣
 የመራዥ እባብም መርዝ ነው።
34“ይህ በእኔ ዘንድ ተጠብቆ ያለ፣
 በመዝገቤስ የታተመ አይደለምን?
35በቀል የእኔ ነው፤ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ፤
 ጊዜው ሲደርስ እግራቸው ይሰናከላል፤
የመጥፊያቸው ቀን ቀርቦአል፤
 የሚመጣባቸውም ፍርድ
 ፈጥኖባቸዋል።”
36ነይላቸው መድከሙን፣
 ባሪያም ሆነ ነጻ ሰው አለመቅረቱን በሚያ
 ዩበት ጊዜ፣
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሕዝቡ ይፈርዳል፤
 ለአገልጋዮቹም ይራራል።
37እንዲህም ይላል፤ “መጠጊያ ዐለት የሆኗቸው፣
 እነዚያ አማልክታቸው የት አሉ?
38የመሥዋዕታቸውን ስብ የበሉ፣
 የመጠጥ ቍርባናቸውንም የወይን ጠጅ
 የጠጡ አማልክት ወዴት ናቸው?
እስቲ ይነሡና ይርዷችሁ!
 እስቲ መጠለያ ይስጧችሁ!
39“እኔ ራሴ እርሱ እንደ ሆንሁ እዩ፤
 ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም፤
እገድላለሁ፤ አድናለሁም፤
 አቈስላለሁ፤ እፈውሳለሁም፤
 ከእጄም የሚያስጥል ማንም የለም።
40እጄን ወደ ሰማይ አነሣለሁ፤
 ለዘላለምም ሕያው እንደ ሆንሁ እናገራለሁ፤
41የሚያብረቀርቅ ሰይፌን ስዬ፣
 እጄ ለፍርድ ስትይዘው፣
ባላጋራዎቼን እበቀላቸዋለሁ፤
 የሚጠሉኝንም እንደ ሥራቸው
 እከፍላቸዋለሁ።
42ሰይፌ ሥጋ በሚበላበት ጊዜ፣
 ፍላጾቼ በደም እንዲሰክሩ አደርጋለሁ፤
ደሙ የታረዱትና የምርኮኞች፣
 የጠላት አለቆችም ራስ ደም ነው።”
43አሕዛብ ሆይ፤ ከሕዝቡ ጋር ደስ
 ይበላችሁ[ሰሸ]፤
 እርሱ የአገልጋዮቹን ደም ይመልሳል፤
 ጠላቶቹንም ይበቀላል።
ምድሪቱንና ሕዝቡን ይቤዣቸዋልና።
44ሙሴም ከነዌ ልጅ ከኢያሱ ጋር መጥቶ
የዚህን መዝሙር ቃሎች በሕዝቡ ጆሮ
ተናገረ። 45ሙሴም እነዚህን ቃሎች ሁሉ
ለመላው እስራኤል ተናግሮ ከጨረሰ በኋላ፣
46እንዲህ አላቸው፤ የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ
በጥንቃቄ ይጠብቁ ዘንድ ልጆቻችሁን
እንድታዟቸው፣ እኔ ዛሬ በግልጥ የምነግራ
ችሁን ቃሎች ሁሉ በልባችሁ አኑሩ።
47ቃሎቹ ለእናንተ ሕይ ወታችሁ እንጂ
እንዲሁ ባዶ ቃሎች አይደሉም፤ በእነርሱ
ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ፤ በምትወር ሷትም
ምድር ረጅም ዘመን ትኖራላችሁ።

## ሙሴ በናባው ተራራ ላይ መሞቱ

48በዚያችም ዕለት እግዚአብሔር(ያህዌ) ሙሴን
እንዲህ አለው፤ 49ከኢያሪኮ ማዶ ባለው የሞዓብ
ምድር፣ ከዓባሪም ተራሮች አንዱ ወደ
ሆነው ወደ ናባው ተራራ ወጥተህ ለእስራ
ኤላውያን ርስት አድርጌ የምሰጣትን የከነዓ
ንን ምድር አሻግረህ ተመልከት። 50ወንድምህ
አሮን በሖር ተራራ ላይ እንደ ሞተና ወደ
ወገኖቹ እንደ ተሰበሰበ ሁሉ፣ አንተም
በወጣህበት በዚያ ተራራ ላይ ሙት፤ ወደ
ወገኖችህም ተሰብሰብ። 51ይህ የሚሆንበት
ምክንያት ሁለታችሁም በጺን ምድረ በዳ፣
በቃዴስ በመሪባ ውሃ አጠገብ በእኔ ላይ
መታመናችሁን በእስራኤላውያን ፊት ስላ
ጐደላችሁና ቅድስናዬንም በእስራኤላውያን
መካከል ስላላከበራችሁ ነው።

32፥27 ዘዳ9፥26-28፤መዝ140፥8፤
32፥28 ኢሳ1፥3፤5፥13፤27፥11፤ኤር8፥7
32፥29 ዘዳ5፥29፤መዝ81፥13፤ኢሳ47፥7፤ሰቆ1፥9
32፥30 ዘሌ26፥8፤ዘኍ21፥34፤1ሳሙ12፥9፤23፥7፤መሳ2፥14፤3፥8፤4፥2፤10፥7፤መዝ31፥8፤44፥12፤106፥41፤ኢሳ50፥1፤ 54፥6
32፥31 ዘፍ49፥24፤ዘፀ14፥25
32፥32 ዘዳ29፥18፤ኢዮ6፥4፤20፥16፤ኤር23፥14
32፥33 ቍ24
32፥34 ኢዮ14፥17፤ኤር2፥22፤ሆሴ13፥12
32፥35 ቍ41፤ዘፍ4፥24፤30፥2፤ዘፀ32፥34፤መዝ17፥5፤35፥6፤37፥31፤38፥16፤54፥5፤66፥9፤73፥2፥18፤94፥18፤121፥3፤ምሳ4፥19፤ኤር23፥12፤51፥6፤ሕዝ7፥8-9፤ሮሜ12፥19፤ዕብ10፥30
32፥36 ዘሌ26፥43-45፤ዘዳ30፥1-3፤መሳ2፥18፤1ነገ14፥10፤21፥21፤2ነገ9፥8፤መዝ90፥13፤102፥13፤103፥13፤106፥45፤135፥14፤ኢል2፥14፤አሞ7፥3፤ዕብ10፥30
32፥37 መሳ10፥14፤ኤር2፥28፤11፥12
32፥38 ዘኍ25፥1-2፤ኤር11፥12፤44፥8፥25
32፥39 ቍ12፤ዘፀ15፥26፤ዘዳ15፥26፤1ሳሙ2-6፤2ነገ 5፥7፤ኢዮ5፥18፤9፥12፤10፥7፤15፥11፤መዝ7፥2፤ 47፥3፤ 50፥22፤68፥20፤ኢሳ6፥10፤19፥22፤30፥26፤41፥4፤43፥10፥13፤ 44፥7፤46፥4፤ 48፥12፤ 53፥5፤57፥18፤ኤር33፥6፤ዳን4፥35፤ሆሴ5፥14፤6፥1፤ ሚል4፥2፤ዮሐ11፥25-26፤1ጴጥ2፥24
32፥40 ዘፍ14፥22፤21፥33፤ራእ1፥18
32፥41 ቍ35፤መሳ7፥20፤መዝ7፥12፤45፥3፤ 137፥8፤149፥7፤ኢሳ27፥1፤34፥6፤66፥16፤ኤር12፥12፤24፥56፤25፥14፤46፥10፤50፥29፤51፥24፥56፤ሕዝ21፥9-10፤ናሆ1፥2
32፥42 ቍ23፤2ሳሙ2፥26፤ኤር12፥12፤44፥1፤46፤10፥14 32፥43 2ነገ9፥7፤ መዝ65፥3፤79፥9፤ 137፥6፤ኢሳ1፥24፤25፥9፤ 65፥18፤66፥10፤33፥2 ዘፀ19፥18፤ዘኍ10፥12፤ኢሱ11፥17፤መሳ5፥4፤ መዝ50፥2፤68፥8፤ 80፥1፤89፥7፤94፥1፤ዳን4፥13፤ 7፥10፤8፥13፤ዘካ14፥5፤ ሐሥ7፥53፤ገላ3፥19፤ዕብ2፥2፤ራእ5፥11፤ኤር9፥9፤ሮሜ15፥10፤ራእ6፥10፤ 32፥44 ዘኍ13፥8፥ 16 32፥46 ዘዳ6፥6፥7፤ ዮሐ1፥17፤7፥19 32፥47 ዘፀ23፥26፤ዘዳ30፥20፤ 33፥25፤ ኢሳ65፥22 32፥48 ዘኍ27፥12 32፥49 ዘሌ14፥34፤ ዘኍ22፥1፤27፥12፤32፥3 32፥50 ዘፍ25፥8፤ዘኍ20፥22፥29፤ 27፥13 32፥51 ዘኍ13፥21፤ 20፥11-13፤27፥14፤ሕዝ47፥19

[ሰ]43 ወይም፣ *ሕዝቦች ሆይ፤ ደስ ይበላችሁ።*
[ሸ]43 የማሶሬቱ ቅጅ፣ የሙት ባሕር ጥቅል እንዲሁም የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም፣ *ሕዝቦች ሆይ፤ መላእክት ሁሉ ለእርሱ ይስገዱ* ይላሉ።

[52]ስለዚህ ምድሪቱን ከሩቅ ሆነህ ታያታለህ
እንጂ፣ ለእስራኤል ሕዝብ ወደምሰጣት ምድር
አትገባም።”

**ሙሴ የእስራኤልን ነገዶች ባረከ**
33፥1-29 *ማመ* - *ዘፍ* 49፥1-28

**33** *የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ሰው ሙሴ ከመ
ሞቱ በፊት ለእስራኤላውያን የሰጠው
ቃለ ቡራኬ ይህ ነው፤ [2]እንዲህም አለ፦
“*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ከሲና መጣ፤
በእነርሱም ላይ ከሴይር እንደ ማለዳ
ፀሓይ ወጣ፤
ከፋራን ተራራ አበራላቸው፤
ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር[+] መጣ፤
በስተቀኙ የሚነድ እሳት ነበር።
[3]በእርግጥ ሕዝቡን የምትወድ አንተ ነህ፤
ቅዱሳኑ ሁሉ በእጅህ ውስጥ ናቸው።
ከእግርህ ሥር ሁሉ ይሰግዳሉ፤
ከአንተ ትእዛዝ ይቀበላሉ፤
[4]ይህ ሙሴ የሰጠን ሕግ፣
የያዕቆብ ጉባኤ ርስት ነው።
[5]የሕዝቡ አለቆች ከእስራኤል ነገዶች ጋር
ሆነው፣
በአንድነት በተሰበሰቡ ጊዜ፣
እርሱ በይሹሩን[∩] ላይ ንጉሥ ነበር።
[6]“ሮቤል በሕይወት ይኑር፤ አይሙት፤
የወገኖቹ ቊጥርም አይጒደልበት።”
[7]ስለ ይሁዳ የተናገረው ይህ ነው፦
“*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሆይ፤ የይሁዳን ጩኸት
ስማ፤
ወደ ወገኖቹም አምጣው።
በገዛ እጆቹ ራሱን ይከላከላል፤
አቤቱ ከጠላቶቹ ጋር ሲዋጋ ረዳቱ ሁን!
[8]ስለ ሌዊም እንዲህ አለ፦
“ቱሚምህና ኡሪምህ፣
ለምትወደው ሰው ይሁን፤
ማሳህ በተባለው ቦታ ፈተንኸው፤
በመሪባም ውሃ ከእርሱ ጋር ተከራከርህ።
[9]ስለ አባቱና ስለ እናቱ ሲናገርም፣
‘ስለ እነርሱ ግድ የለኝም’ አለ።
ወንድሞቹን አልለያቸውም፤
ልጆቹንም አላወቃቸውም።
ለቃልህ ማን ጥንቃቄ አደረገ፤
ኪዳንህንም ጠበቀ።
[10]ሥርዐትህን ለያዕቆብ፣
ሕግህንም ለእስራኤል ያስተምራል።
ዕጣን በፊትህ፣
የሚቃጠለውን መሥዋዕት ሁሉ በመሠዊያህ
ላይ ያቀርባል።
[11]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሆይ፤ ኀይሉን ሁሉ
ባርክለት፤
በእጁ ሥራ ደስ ይበልህ፤
በእርሱ ላይ የሚነሡብትን ሽንጣቸውን ቊረጠው፤
ጠላቶቹንም እንዳያንሠራሩ አድርገህ
ምታቸው።”
[12]ስለ ብንያም እንዲህ አለ፦
“*የእግዚአብሔር* (ያህዌ) ወዳጅ የሆነ በእርሱ
ተጠብቆ በሰላም ይረፍ፤
ቀኑን ሙሉ ይጋርደዋልና፤
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) የሚወደውም ሰው በትከ
ሻዎቹ መካከል ያርፋል።”
[13]ስለ ዮሴፍ ደግሞ እንዲህ አለው፦
“*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ምድሩን ይባርክ፤
ድንቅ የሆነውን ጠል ከላይ ከሰማይ በማውረድ፣
ከታች የተንጣለለውን ጥልቅ ውሃ በመስጠ
ት፤
[14]ፀሓይ በምታስገኘው ምርጥ ፍሬ፣
ጨረቃም በምትሰጠው እጅግ መልካም
ነገር፤
[15]ከጥንት ተራሮች በተገኘ ምርጥ ስጦታ፣
በዘላለማዊ ኰረብቶች ፍሬያማነት፤
[16]ምድር በምታስገኘው ምርጥ ስጦታና
በሙላቷ፣
በሚቃጠለው ቊጥቋጦም ውስጥ
በነበረው በእርሱ ሞገስ።
እነዚህ ሁሉ በወንድሞቹ መካከል ገዥ በሆነው፣
በዮሴፍ ዐናት ላይ ይውረዱ።
[17]በግርማው እንደ በኵር ኰርማ ነው፤
ቀንዶቹም የጐሽ ቀንዶች ናቸው።
በእነርሱም ሕዝቦችን፣
በምድር ዳርቻ ላይ ያሉትን እንኳ
ሳይቀር ይወጋል፤
እነርሱም የኤፍሬም ዐሥር ሺዎቹ
ናቸው፤
የምናሴም ሺዎቹ እንደዚሁ ናቸው።”
[18]ስለ ዛብሎንም እንዲህ አለ፦
“ዛብሎን ሆይ፤ ወደ ውጭ በመውጣትህ፣
አንተም ይሳኮር በድንኳኖችህ ውስጥ
ደስ ይበልህ፤
[19]አሕዛብን ወደ ተራራው ይጠራሉ፤
በዚያም የጽድቅን መሥዋዕት
ያቀርባሉ።
በባሕሮች ውስጥ ያለውን በተትረፈረፈ
ብልጽግና፣
በአሸዋውም ውስጥ የተደበቀውን ሀብት
ይደሰቱበታል።”
[20]ስለ ጋድም እንዲህ አለ፦
“የጋድን ግዛት የሚያሰፋ የተመሰገነ ነው!
ክንድንና ራስን በመገነጣጠል፣
ጋድ እንደ አንበሳ በዚያ ይኖራል።
[21]ለም የሆነውን መሬት ለራሱ መረጠ፤
የአለቃም ድርሻ ለእርሱ ተጠ
ብቆለታል።
የሕዝቡ መሪዎች በተሰበሰቡ ጊዜ፣
*የእግዚአብሔርን* (ያህዌ) የቅን ፈቃድና፣

32፥52 *ዘዳ*3፥37፤ 34፥1-3
33፥1 *ዘፍ*27፥4፤ ኢ ሱ14፥6፤1ሳሙ2፥27፤ 9፥6፤1ነገ12፥22፤ 13፥1፤2ነገ1፥9-13፤ 5፥8፤ኤር35፥4
33፥3 *ዘዳ*4፥37፤ 7፥6፤ሉቃ10፥39፤ ራእ4፥10
33፥4 *ዘዳ*4፥2፤ ዮሐ1፥17፤7፥19፤ *መዝ*119፥11
33፥5 *ዘፀ*16፥8፤ *ዘኍ*23፥21፤*ዘዳ*32፥15፤1 ሳሙ10፥19፤ *መዝ*10፥16፤149፥2
33፥6 *ዘፍ*34፥5
33፥7 *ዘፍ*49፥10
33፥8 *ዘፍ*29፥34፤ *ዘፀ*17፥7፤28፥30፤ *ዘኍ*14፥22፤ *መዝ*106፥16
33፥9 *ዘፀ*32፥26-29፤ *መዝ*61፥5፤ሚል2፥5
33፥10 *ዘፀ*30፥7፤ *ዘሌ*10፥11፤16፥12-13፤ *ዘዳ*17፥8-11፤31፥9-13፤ ዕዝ7፥10፤ነህ8፥18፤ *መዝ*119፥151፤ ኤር23፥22፤ሚል2፥6፤ *መዝ*51፥19
33፥11 2ሳሙ24፥23፤ *መዝ*20፥3፤51፥19
33፥12 *ዘፍ*35፥18፤ *ዘፀ*19፥4፤28፥12፤ *ዘዳ*4፥37-38፤ 12፥10፤32፥8፤ *መዝ*60፥5፤127፥2፤ ኢ ሳ5፥1
33፥13 *ዘፍ*27፥28፤ 30፥24፤*መዝ*148፥7
33፥15 ዕን3፥6
33፥16 *ዘፍ*37፥8፤ *ዘፀ*3፥2
33፥17 *ዘፍ*41፥51፡ 52፤*ዘኍ*23፥22፤ 1ሳሙ2፥10፤ 2ሳሙ22፥3፤1ነገ22፥ 11፤*መዝ*44፥5፤ ሕዝ34፥21
33፥18 *ዘፍ*30፥18፡20
33፥19 *ዘፀ*15፥17፤ *መዝ*4፥5፤48፥1፤ 51፥19፤ኢሳ2፥3፤ 18፥7፤23፥18፤ 45፥14፤60፥5፡11፤ 61፥6፤65፥11፤66፥20፤ ኤር31፥6፤ሐጌ2፥7፤ *ዘካ*14፥14
33፥20 *ዘፍ*30፥11፤ *ዘዳ*3፥12-17
33፥21 *ዘኍ*32፥1-5፡ 31-32፤34፥14፤ ኢሳ22፥1-3

[+]2 ወይም *በአእላፋት ቅዱሳኑ*።
[∩]5 በዚህ ስፍራና በቍጥር 26 ላይ ይሹሩን ማለት፣ *ቅን* ወይም *ትክክለኛ* ማለት ሲሆን ይኸውም እስራኤልን የሚያሳይ ነው።

በእስራኤል ላይ የበየነውን ፍርዱን ፈጸመ።”
[22]ስለ ዳንም እንዲህ አለ፦
“ዳን ከባሳን ዘሎ የሚወጣ፣
የአንበሳ ደቦል ነው።”
[23]ስለ ንፍታሌምም እንዲህ አለ፦
“ንፍታሌም *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ሞገስ
ረክቶአል፤
በበረከቱም ተሞልቶአል፤
ባሕሩንና የደቡብን ምድር ይወርሳል።”
[24]ስለ አሴርም እንዲህ አለ፦
“አሴር ከሌሎች ልጆች ይልቅ የተባረከ
ነው፤
በወንድሞቹ ዘንድ ተወዳጅ ይሁን፤
እግሩንም በዘይት ውስጥ ያጥልቅ።
[25]የደጃፍህ መቀርቀሪያ ብረትና ናስ
ይሆናል፤
ኀይልህም በዘመንህ ሁሉ ይኖራል።
[26]አንተን ለመርዳት በሰማያት ላይ፣
በግርማው በደመናትም የሚገሠግሥ፣
እንደ ይሽሩን አምላክ (ኤሎሂም) ያለ ማንም
የለም።
[27]ዘላለማዊ አምላክ (ኤሎሂም) መኖርያህ ነው፤
የዘላለም ክንዶቹም ከሥርህ ናቸው፤
‘እርሱን አጥፋው!’ በማለት፣
ጠላትህን ከፊትህ ያስወግደዋል።
[28] ስለዚህ እስራኤል ብቻውን በሰላም
ይኖራል፤
የሰማያት ጠል በሚወርድበት፣
እህልና የወይን ጠጅ ባለበት ምድር፣
የያዕቆብ ምንጭ የሚነካው የለም።
[29]እስራኤል ሆይ፤ አንተ ቡሩክ ነህ፤
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ያዳነው ሕዝብ፣
እንዳንተ ያለ ማን አለ?
እርሱ ጋሻህና ረዳትህ፣
የክብርህም ሰይፍ ነው።
ጠላቶችህ በፍርሀት ከፊትህ
ያፈገፍጋሉ፤
አንተም የማምለኪያ ኩረብታቸውን መረ
ማመጃ ታደርጋለህ።

## የሙሴ መሞት

34 ሙሴ ከሞአብ ሜዳ ተነሥቶ ለኢ
ያሪኮ ትይዩ ወደ ሆነው ፈስጋ
ጫፍ፣ ወደ ናባው ተራራ ወጣ። በዚያም
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ምድሪቱን ሁሉ አሳየው፤
ይኸውም ከገለዓድ እስከ ዳን፣ [2]ንፍታሌምን
ሁሉ፣ የኤፍሬምንና የምናሴን ግዛት፣ እስከ
ምዕራብ ባሕር[†] ድረስ ያለውን የይሁዳን
ምድር ሁሉ፣ [3]ኔጌብንና የዘንባባ ከተማ
ከሆነችው ከኢያሪኮ ሸለቆ እስከ ዞዓር
ያለውን ምድር ሁሉ ነው። [4]ከዚያም በኋላ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን “ለአብርሃም፣
ለይስሐቅና ለያዕቆብ፣ ለዘሮቻችሁ እሰጣለሁ’
ብዬ በመሐላ ቃል የገባሁላቸው ምድር
ይህች ናት። በዐይንህ እንድታያት አድርጌአለሁ፤
ነገር ግን ወደዚያ አትሻገርም” አለው።
[5]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) እንደ ተናገረው *የእግ
ዚአብሔር* (ያህዌ) አገልጋይ ሙሴ በሞዓብ
ምድር ሞተ። [6]በሞዓብ ምድር በቤተ
ፌጎር ፊት ለፊት ባለው ሸለቆ ቀበረው[‡]፤
ይሁን እንጂ መቃብሩ የት እንደ ሆነ እስከ
ዛሬ ማንም አያውቅም። [7]ሙሴ በሞተ ጊዜ
ዕድሜው መቶ ሃያ ዓመት ነበር፤ ሆኖም
ዐይኑ አልፈዘዘም፤ ጕልበቱም አልደከመም።
[8]የልቅሶውና የሐዘኑ ጊዜ እስኪያበቃ ድረስ
እስራኤላውያን በሞዓብ ሜዳ ሠላሳ ቀን
አለቀሱለት።
[9]ሙሴ እጆቹን ጭኖበት ነበርና፣ የነዌ
ልጅ ኢያሱ በጥበብ መንፈስ ተሞላ። ስለዚህ
እስራኤላውያን አደመጡት፤ *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ሙሴን አዞት የነበረውንም ሁሉ
አደረጉ።
[10]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ለፊት
ያወቀው
እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ ከዚያ ወዲህ በእስ
ራኤል አልተነሣም። [11]*እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ልኮት፣ እነዚያን ታምራዊ ምልክቶችና
ድንቆች ሁሉ በግብፅ በፈርዖን፣ በሹ
ማምንቱና በምድሪቱ ሁሉ ላይ እንዲያደርግ
የላከውን ያደረገ ማንም ሰው አልነበረም።
[12]ሙሴ በእስራኤል ሁሉ ፊት ያሳየውን ታላቅ
ኀይል ያሳየ ወይም ያደ ረገውን አስፈሪ
ተግባር የፈጸመ ማንም ሰው የለም።

33፥22 ዘኍ1፥38፤ 49፥16
33፥23 ዘፍ30፥8
33፥24 ዘፍ30፥13፤ 49፥20፤ዘዳ32፥13
33፥25 ዘዳ32፥47፤ ነህ3፥3፤7፥3፤ መዝ147፥13
33፥26 ዘፀ15፥7፤ ዘዳ10፥14፤32፥15፤ 2ሳሙ22፥10፤ መዝ18፥9፡10፤68፥4፡33፤104፥3፤ዳን7፥13
33፥27 ዘፍ21፥33፤ ዘፀ15፥18፤34፥11፤ ዘዳ7፥2፤ኢሱ24፥18፤ መዝ9፥9፤84፥1፤ 90፥1፤91፥9፤ ኢሳ40፥28፤57፥15
33፥28 ቍ13፤ ዘፍ27፥28፤ዘፀ33፥16፤ ዘሌ25፥18፤ዘዳ32፥8፤ መዝ16፥9፤ምሳ1፥33፤ ኢሳ14፥30፤
33፥29 ዘፍ15፥1፤ ዘፀ18፥4፤ዘኍ33፥52፤ ዘዳ4፥7፤32፥13፤ 2ሳሙ22፥45፤ መዝ1፥1፤10፥14፤ 18፥1፡44፤27፥1፡9፤ 30፥10፤32፥1-2፤54፥4፤ 66፥3፤70፥5፤81፥15፤ 115፥9-11፤118፥7፤ 144፥15፤ኢሳ45፥24፤ ሆሴ13፥9፤ዕን3፥19
34፥1 ዘፍ14፥14፤ ዘኍ21፥20፤32፥3፤ ዘዳ32፥49፡52፤
34፥2 ዘፀ23፥31
34፥3 ዘፍ12፥9፤ 13፥10፤2ዜና28፥15፤ መሳ1፥16፤ 3፥13
34፥4 ዘፍ12፥7፤ 28፥13፤ዘዳ3፥23፤ ኢሱ21፥43
34፥5 ዘፍ25፥8፤ ዘኍ12፥7፤
34፥6 ዘዳ3፥29፤ ይሁ1፥9
34፥7 ዘፍ15፥15፤ 27፥1፤ዘፀ7፥7
34፥8 ዘፍ37፥34፤ ዘኍ21፥11፤ዘዳ1፥3፤ 2ሳሙ11፥27
34፥9 ዘፍ41፥38፤ ዘፀ28፥3፤ዘዳ31፥14፤ ኢሳ11፥2፤ሐሥ6፥6

34፥10 ዘፍ20፥7፤ ዘፀ33፥11፤ዘዳ18፥15፡18
34፥11 ዘፀ11፥3፤ ዘዳ4፥34 34፥12 ዘዳ4፥34፤ዕብ3፥1-6፤

[†]2 ይኸውም የሜዲትራንያን ባሕር ነው።
[‡]6 ወይም፣ *ተቀበረ* ተብሎ መተርጐም ይቻላል።

# መጽሐፈ ኢያሱ

## እግዚአብሔር ኢያሱን አዘዘ

**1** *የእግዚአብሔር* ባሪያ ሙሴ ከሞተ በኋላ፣ *እግዚአብሔር* የሙሴን አገልጋይ የነዌን ልጅ ኢያሱን እንዲህ አለው፤ 2“እነሆ፤ ባሪያዬ ሙሴ ሞቶአል፤ እንግዲህ አሁንም አንተና ይህ ሕዝብ ሁሉ ተነሡ፤ ለእስራኤላውያን ወደምሰጣቸው ምድር ለመግባት የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻገሩ። 3ለሙሴ በሰጠሁትም ተስፋ መሠረት፣ እግራችሁ የሚረግጠውን ቦታ ሁሉ እሰጣችኋለሁ። 4የርስታችሁ ዳርቻ ከምድረ በዳው እስከ ሊባኖስ፣ ከታላቁ ወንዝ ከኤፍራጥስ አንሥቶ፣ የኬጢያውያንን ምድር በሙሉ ይዞ፣ በምዕራብ በኩል እስከ ታላቁ ባሕር[ሀ] ይደርሳል። 5በሕይወት በምትኖርበት ዘመን ሁሉ ማንም አይቋቋምህም፤ ከሙሴ ጋር እንደ ነበርሁ ሁሉ ከአንተም ጋር እሆናለሁ፤ ከቶ አልጥልህም፤ አልተውህም።

6“ጽና፤ ለቀደሙት አባቶቻቸው እሰጣችኋለሁ ብዬ የማልሁላቸውን ምድር እንዲወርሱ፣ ይህን ሕዝብ የምትመራው አንተ ነህና በርታ። 7አይዞህ፤ ብቻ አንተ በርታ፤ ባሪያዬ ሙሴ የሰጠህን ትእዛዝ ሁሉ በጥንቃቄ ጠብቅ፤ በምትሄድበትም ሁሉ እንዲሳካልህ፣ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል። 8ይህ የሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፤ በውስጡ የተጻፈውን ሁሉ በጥንቃቄ እንድትፈጽመውም ቀንም ሆነ ሌት ከሐሳብህ አትለየው፤ ይህን ካደረግህ ያሰብኸው ይቃናል፤ ይሳካልም፤ 9በምትሄድበት ሁሉ *እግዚአብሔር* አምላክህ ከአንተ ጋር ነውና አይዞህ፤ በርታ፤ ጽና፤ አትፍራ፤ አትደንግጥ ብዬ አላዘዝሁህምን?”

10ኢያሱም የሕዝቡን አለቆች እንዲህ ሲል አዘዛቸው፤ 11“ወደ ሰፈር ግቡ፤ ለሕዝቡም፣ ‘ስንቃችሁን አዘጋጁ፤ ከአሁን ጀምሮ ባሉት ሦስት ቀናት ውስጥ ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ፣ *እግዚአብሔር* አምላካችሁ ርስት አድርጎ የሚሰጣችሁን ምድር ገብታችሁ ትወርሳላችሁ’ በሏቸው።”

12ኢያሱ የሮቤልን ነገድ፣ የጋድን ነገድና የምናሴን ነገድ እኩሌታ እንዲህ አላቸው፤ 13“*የእግዚአብሔር* ባሪያ ሙሴ እንዲህ ሲል የሰጣችሁን ትእዛዝ አስቡ፤ ‘*እግዚአብሔር* አምላካችሁ ያሳርፋችኋል፤ ይህችንም ምድር ይሰጣችኋል።’ 14ሚስቶቻችሁና ልጆቻችሁ እንዲሁም ከብቶቻችሁ ሙሴ በሰጣችሁ ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ባለው ምድር ይቆዩ፤ ነገር ግን ተዋጊዎቻችሁ ሁሉ፣ ከነሙሉ ትጥቃቸው፣ ከወንድሞቻችሁ ቀድመው ይሻገሩ፤ እናንተም ከወንድሞቻችሁ ጐን ተሰለፉ። 15ይህም፣ *እግዚአብሔር* እስኪያሳርፋቸውና ለእናንተም እንዳደረገው ሁሉ፣ እነርሱም *እግዚአብሔር* አምላካችሁ የሰጣቸውን ምድር እስኪወርሱ ድረስ ነው። ከዚህ በኋላ እናንተም ተመልሳችሁ *የእግዚአብሔር* ባሪያ ሙሴ የሰጣችሁን፣ በፀሓይ መውጫ ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ያለውን ምድር ትወርሳላችሁ።”

16እነርሱም ለኢያሱ እንዲህ ሲሉ መለሱለት፤ “ያዘዝኸንን ሁሉ እናደርጋለን፤ ወደምትልከንም ሁሉ እንሄዳለን። 17ለሙሴ ሙሉ በሙሉ እንደታዘዝን ሁሉ፣ ለአንተም እንታዘዛለን፤ ብቻ *እግዚአብሔር* አምላክህ ከሙሴ ጋር እንደ ነበረ፣ አሁንም ከአንተ ጋር ይሁን። 18በትእዛዝህ ላይ የሚያምፅና ለቃልህ የማይታዘዝ ሁሉ ይገደል፤ ብቻ አንተ ጽና፤ አይዞህ፤ በርታ።”

## ረዓብና እስራኤላውያን ሰላዮች

**2** ከዚያም የነዌ ልጅ ኢያሱ፣ “ሂዱና ምድሪቱን፣ በተለይም የኢያሪኮን ከተማ ሰልሉ” ብሎ ከሰጢም ሁለት ሰላዮች በስውር ላከ፤ ሰዎቹም ሄደው ረዓብ ከተባለች ጋለሞታ ቤት[ለ] ገቡ፤ በዚያም ዐደሩ።

2ለኢያሪኮም ንጉሥ፣ “እነሆ፤ ምድሪቱን ሊሰልሉ ጥቂት እስራኤላውያን በሌሊት ወደዚህ መጥተዋል” ተብሎ ተነገረው። 3የኢያሪኮም ንጉሥ፣ “ወደ አንቺ መጥተው ወደ ቤትሽ የገቡት ሰዎች ምድሪቱን በሙሉ ለመሰለል ስለሆነ፣ እንድታስወጪአቸው” የሚል መልእክት ወደ ረዓብ ላከ።

4ሴቲቱ ግን ሁለቱን ሰዎች ተቀብላ ሸሽጋቸው ስለ ነበር፣ እንዲህ አለች፤ “በእርግጥ ሰዎቹ ወደ እኔ መጥተዋል፤ ነገር ግን ከወዴት እንደ መጡ አላውቅም። 5ጨለሞ የቅጥሩ በር ከመዘጋቱ በፊት ወጥተው ሄደዋል፤ በየት በኩል እንደሄዱ ግን እኔ አላውቅም፤ ልትደርሱባቸው ትችላላችሁና ፈጥናችሁ ተከታተሏቸው።” 6ነገር ግን ሰዎቹን ጣራ ላይ አውጥታ በረበረበችው የተልባ እግር ውስጥ ደብቃቸው ነበር።

1፥1 ዘፀ14፥31፤17፥9 ዘዳ34፥5፤ራእ15፥3
1፥2 ዘፍ15፥14፤ ዘኍ13፥29፤35፥10፤ 12፥7፤ዘዳ1፥25
1፥3 ዘፍ50፥24፤ዘኍ 13፥2፤ዘዳ1፥8፤11፥24፤
1፥4 ዘፍ2፥14፤10፥ 15፤23፥10፤ዘፀ3፥8፤ ዘኍ34፥2-12፤ ዘዳ3፥25፤ዕዝ4፥20
1፥5 ቍ17፤ዘፍ26፥3፤ 28፥15፤ዘዳ4፥31፤7፥24፤ 39፥2፤መሳ6፥12፤1ሳሙ 10፥7፤ኤር1፥8፤30፥11
1፥6 ዘዳ1፥21፤31፥6፤ መሳ5፥21፤2ሳሙ2፥7፤ 1ነገ2፥2፤ኢሳ41፥6፤ ኤር 3፥18፤7፥7ኢል3፥9-10፤
1፥7 ቍ2፥9፥15፤ዘኍ 12፥7፤ዘዳ4፥2፤5፥3፤32፤ 11፥8፤29፥9፤ኢሱ11 ፥15፤23፥6፤1ነገ2፥3፤3፥ 3፤ዕዝ7፥26፤ኢዮ1፥8፤ 42፥7፤መዝ78፥10፤119 ፥136፤ኢሳ42፥24፤ኤር 26፥4-6፤32፥23፤44፥10
1፥8 ዘፍ24፥63፤ዘፀ 4፥15፤ዘዳ28፥61፤29፥9 ፤1ሳሙ18፥14፤ መዝ1፥1-3፤147፥19፤ ኢሳ52፥13፤53፥10፤ 59፥21፤ኤር23፥5
1፥9 ቍ7፤ዘዳ1፥21፤31፥ 6፥8፤ኢሱ10፥8፤ኢዮ 4፥5፤2ነገ19፥6፤ኢሳ 35፥5፤37፥6፤ኤር1፥8
1፥10 ዘዳ1፥15 1፥11 ዘፍ40፥13፤ ዘኍ 35፥10፤33፥53፤ ኢሱ3፥2፤1ሳሙ 17፥22፤ኢሳ10፥28
1፥12 ዘኍ 32፥33
1፥13 ዘፀ33፥14፤ መዝ55፥6፤ኢሳ11፥10፤ 28፥12፤30፥15፤32፥18፤ 40፥31፤ኤር6፥16፤45፥ 3፤ሰቆ5፥5
1፥14 ዘፀ13፥18፤ዘኍ 32፥26፤ዘዳ3፥19፤ኢሱ 4፥12
1፥15ዘኍ32፥20-22፤ ኢሱ22፥1-4
1፥16 ዘኍ27፥20፤ 32፥25
1፥17 ዘኍ27፥20
1፥18 ዘኍ32፥25፣ ዘዳ1፥21፤31፥6
2፥1 ቍ4፤ዘፍ42፥9፤ ዘኍ21፥32፤25፥1፤ 33፥48፤ኢሱ3፥1፤6፥ 17፥25፤መሳ18፥2፤ ኢል3፥18፤ዕብ11፥31
2፥3 ኢሱ6፥23
2፥4 ቍ1፤ኢሱ6፥ 17፥22
2፥5 መሳ5፥8፤9፥35፤ 16፥2፤ዕብ11፥31
2፥6 ዘፀ1፥19፤ኢሱ 6፥25፤መሳ15፥14፤2ሳሙ17፥19ምሳ31፥13፤ ኢሳ19፥9፤

ሀ4 *የሜድትራኒያን ባሕር* ለ1 ምናልባትም፣ “የሆቴል ቤት” ተጠቃሚ

7ሰዎቹም ሰላዮቹን በመከታተል ወደ ዮርዳ
ኖስ መሻገሪያ የሚወስደውን መንገድ ይዘው
ሄዱ፤ አሳዳጆቹ ወጥተው እንደሄዱም የቅ
ጥሩ በር ተዘጋ።
8ሰላዮቹ ከመተኛታቸው በፊት ሴቲቱ
ወደ ጣራው ወጥታ፤ 9እንዲህ አለቻቸው፤
“*እግዚአብሔር* ይህችን ምድር እንደሰጣችሁ፤
እናንተንም መፍራት እንዳደረብን፤ የዚ
ህች አገር ነዋሪዎች ሁሉ ልባቸው በፊታ
ችሁ መቅለጡንም ዐውቃለሁ። 10ከግብፅ
በወጣችሁ ጊዜ *እግዚአብሔር* ቀይ ባሕ
ርን[ሐ] በፊታችሁ እንዴት እንዳደረቀ፤ እናንተም
ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ፈጽሞ ያጠፋ
ችኋቸውን[መ] ሁለቱን የአሞራውያን ነገሥ
ታት፤ ሴዎንንና ዐግን ምን እንዳደረጋችኋ
ቸው ሰምተናል። 11ይህን በሰማን ጊዜ
ልባችን ቀለጠ፤ እናንተን ከመፍራት የተነ
ሣም ያልተሸበረ ሰው አልነበረም፤ *እግዚ
አብሔር* አምላካችሁ በላይም በሰማይ፤
በታ ችም በምድር እርሱ አምላክ ነውና።
12እን ግዲህ እኔ በጎነትን እንዳሳየኋችሁ
ሁሉ፤ እናንተም በጎነትን ለአባቴ ቤት
እንድታሳዩ *በእግዚአብሔር* ማሉልኝ፤ መተ
ማመኛ የሚ ሆን ምልክትም ስጡኝ፤
13የአባቴንና የእና ቴን፤ የወንድሞቼንና
የእኅቶቼን እንዲሁም የእነርሱ የሆነውን
ነፍስ ሁሉ እንድታ ተርፉልኝ፤ ከሞትም
አድኑን።”
14ሰዎቹም፤ “የእናንተን ሞት ለእኛ
ያድርገው! እኛ የምናደርገውን ሁሉ ካልተ
ናገራችሁ፤ *እግዚአብሔር* ምድሪቱን በሚሰጠን
ጊዜ፤ በጎነትና ታማኝነት እናሳይሻለን”
አሏት።
15መኖሪያ ቤቷ የከተማውን ቅጥር ተጠግቶ
የተሠራ ስለ ነበር፤ ሰዎቹን በመስኮት አሾ
ልካ በገመድ አወረደቻቸው። 16እርሷም፤
“የሚከታተሏችሁ ሰዎች እንዳያገኟችሁ፤ ወደ
ኰረብታዎቹ ሂዱ፤ እነርሱ እስኪመለሱም
ድረስ ሦስት ቀን በዚያ ተሸሸጉ፤ ከዚያ
በኋላ መንገዳችሁን ትቀጥላላችሁ” አለቻ
ቸው።
17ሰዎቹም እንዲህ አሏት፤ “ባማልሽን
በዚህ መሐላ የምንያዘው፤ 18ወደ ምድሪቱ
በገባን ጊዜ፤ ይህን ቀይ ፈትል እኛን
ባወረድሽበት መስኮት ላይ አስረሽ ካንጠ
ለጠልሽው፤ እንዲሁም አባትሽንና እናት
ሽን፤ ወንድሞችሽንና የአባትሽን ቤተ ሰዎች
ሁሉ ወደ ቤትሽ ካመጣሻቸው ብቻ ነው።
19ማንም ከቤትሽ ወጥቶ መንገድ ላይ ቢገኝ፤
ደሙ በራሱ ላይ ነው፤ እኛ አንጠየቅበ
ትም፤ ነገር ግን ከአንቺ ጋር እቤት
ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው ከተነካ የደሙ

2፥7 ቍ16፥22፤ዘኍ 22፥1፤መሳ3፥28፤7፥ 24፤12፥5፥6፤ኢሳ16፥2
2፥8 ዘዳ22፥8፤መሳ 16፥27፤2ሳሙ16፥22፤ ነህ8፥16፤ኢሳ15፥ 3፤22፥1፤ኤር32፥29
2፥9 ዘፍ35፥5፤ ዘፀ15፥14
2፥10 ዘፍ8፥1፤10፥ 16፤14፥7፤ዘፀ14፥ 21፤ዘኍ21፥2፥21፤ 23፥22፤ኢሱ3፥17፤ 9፥10፤መዝ74፥15
2፥11 ዘፍ14፥19፤ 42፥28፤ዘፀ15፥14፤ ዘኍ20፥14፤ዘዳ2፥25፤ ኢሱ5፥1፤7፥5፤2ሳሙ 4፥1፤2ነገ5፥15፤ 19፥15፤መዝ22፥14፤1 07፥26፤ኢሳ13፥7፤ 19፥1፤ኤር51፥30፤ዳን 6፥26፤ዮና1፥5 ናሆ2፥10፤
2፥12 ዘፍ24፥8፥12፥ 14፤47፥31፤ዘፀ3፥12፤ ኢሱ4፥6፤ሩት3፥10፤ 1ሳሙ2፥34፤2ነገ19፥29
2፥13 ቍ18፤ኢሱ 6፥23
2፥14 ዘፍ47፥29፤1ነገ 20፥39፥42፤2ነገ10፥24
2፥15 ቍ18፥21፤ዘፍ 26፥8፤መሳ5፥28፤ 1ሳሙ19፥12፤ኤር 38፥6፥11
2፥16 ቍ7፥22፤ዘፍ 14፥10፤ ዕብ11፥31
2፥17 ዘፍ24፥8
2፥18 ቍ13፥15፥21
2፥19 ዘሌ20፥9፤ ማቴ27፥25
2፥20 ዘፍ24፥8፤ 47፥31
2፥21 ቍ15፥18
2፥22 ቍ7፥16
2፥24 ዘፀ15፥15፤ኢሱ 10፥8፤11፥6፤መሳ3፥28 ፤7፥9፥14፤20፥28፤1ሳ ሙ14፥10
3፥1 ዘፍ13፥10፤ኢሱ 2፥1፤ኢዮ40፥23
3፥2 ዘፍ40፥13፤ዘዳ 1፥15፤ኢሱ1፥11፤2፥16
3፥3 ቍ8፥17፤ዘኍ 4፥15፤10፥33፤ዘዳ31፥9 ፤1ሳሙ6፥15፤ 1ነገ8፥3
3፥4 ዘኍ35፥5
3፥5 ዘፀ29፥1፤ዘሌ 11፥44፤መሳ6፥13፤ 1ዜና16፥9፥24፤መዝ2 6፥7፤75፥1
3፥6 ኢሱ1፥5፤4፥14፤ 1ዜና29፥25

ባለ ዕዳ እኛ እንሆናለን። 20እኛ የምናደርገ
ውን ብትናገሪ ግን፤ ካስማልሽን መሐላ
ነጻ እንሆናለን።”
21እርሷም፤ “ይሁን፤ ባላችሁት ተስማ
ምቻለሁ” ስትል መለሰች፤ ከዚያም ሰደደቻ
ቸው፤ እነርሱም ሄዱ፤ ቀይ ፈትሉንም
በመስኮቷ ላይ አንጠለጠለችው።
22እነርሱም ወጥተው ወደ ኰረብቶቹ
ሄዱ፤ የሚከታተሏቸውም ሰዎች በየመንገዱ
ሁሉ ላይ ፈልገውና አጥተው እስኪመለሱ
ድረስ፤ ሦስት ቀን በዚያው ተሸሸጉ።
23ሁለቱም ሰላዮች ተመለሱ፤ ከኰረብቶቹም
ወርደው ወንዙን በመሻገር፤ ወደ ነዌ ልጅ
ወደ ኢያሱ መጥተው ያጋጠማቸውን ነገር
ሁሉ ነገሩት። 24ለኢያሱም፤ “በእርግጥ *እግዚ
አብሔር* ምድሪቱን በሙሉ በእጃችን አሳ
ልፎ ሰጥቶናል፤ በዚያ የሚኖረውም ሕዝብ
ሁሉ እኛን ከመፍራቱ የተነሣ ልቡ
መቅለጡን አይተናል” አሉት።

## እስራኤላውያን ዮርዳኖስን ተሻገሩ

3 ኢያሱም ማልዶ ተነሣ፤ ከእስራኤላ
ውያንም ሁሉ ጋር ከሰጢም ወደ ዮር
ዳኖስ መጥተው፤ ወንዙን ከመሻገራቸው
በፊት በዚያ ሰፈሩ። 2ከሦስት ቀን በኋ
ላም የጦሩ አለቆች በሰፈር ውስጥ አለፉ፤
3ሕዝቡንም እንዲህ ሲሉ አዘዙ፤ “ሌዋውያን
ካህናቱ የአምላካችሁን *የእግዚአብሔርን* የቃል
ኪዳን ታቦት ተሸክመው ስታዩ፤ ከሰፈራ
ችሁ ተነሥታችሁ ታቦቱን ተከተሉ፤ 4ካሁን
በፊት በዚህ መንገድ ሄዳችሁ ስለማታውቁ፤
በየት በኩል መሄድ እንዳለባችሁ በዚህ ትረዳ
ላችሁ፤ ሆኖም በታቦቱና በእናንተ መካ
ከል የሁለት ሺህ ክንድ[ሠ] ያህል ርቀት
ይኑር፤ ወደ ታቦቱም አትቅረቡ።”
5ከዚያም ኢያሱ ሕዝቡን፤ “በነገው ዕለት
*እግዚአብሔር* በመካከላችሁ አስደናቂ ነገር
ስለሚያደርግ ራሳችሁን ቀድሱ” አላቸው።
6ኢያሱም ካህናቱን፤ “የቃል ኪዳኑን
ታቦት ተሸክማችሁ ሕዝቡን ቀድማችሁ
ሂዱ” አላቸው፤ እነርሱም ታቦቱን ተሸክ
መው ሕዝቡን ቀድመው ሄዱ።
7*እግዚአብሔርም* ኢያሱን እንዲህ አለው፤
“ከሙሴ ጋር እንደ ነበርሁ ሁሉ፤ ከአንተም
ጋር መሆኔን ያውቁ ዘንድ፤ በእስራኤል
ሁሉ ፊት አንተን ከፍ ከፍ ማድረጌን
በዛሬዋ ዕለት እጀምራለሁ። 8የቃል ኪዳ
ኑን ታቦት የሚሸከሙትንም ካህናት፤
‘ከዮርዳኖስ ውሃ ዳር ስትደርሱ፤ በወንዙ
ውስጥ ገብታችሁ ቁሙ’ በላቸው።”

[ሐ]10 ዕብራይስጡ፤ “ያም ስውፍ” ይላል፤ ይኸውም የደንገል ባሕር ማለት ነው። [መ]10 የዕብራይስጡ ቃል አንድን ሰው ወይም ነገር ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት ነው። [ሠ]4 የዕብራይስጡ ትርጒም 900 ሜትር፤ ይላል።

9ኢያሱ የእስራኤልን ሕዝብ “ወደዚህ
ቀርባችሁ፣ የአምላካችሁን *የእግዚአብሔርን* ቃል
ስሙ አላቸው፤ 10እንግዲህ ሕያው አምላክ
በመካከላችሁ መሆኑንና እርሱም በእርግጥ
ከነዓናውያንን፣ ኬጢያውያንን፣ ኤዊያውያንን፣
ፌርዛውያንን፣ ጌርጌሳውያንን፣ አሞራውያ
ንንና ኢያቡሳውያንን ከፊታችሁ እንዴት
አድርጎ እንደሚያሳድዳቸው የምታውቁት
በዚህ ነው። 11እነሆ፤ የምድር ሁሉ ጌታ የቃል
ኪዳኑ ታቦት ቀድሞአችሁ ወደ ዮርዳኖስ
ይገባል። 12እንግዲህ ከእስራኤል ነገዶች ዐሥራ
ሁለት ሰው ምረጡ፤ ከየነገዱም አንዳንድ
ሰው ይሁን። 13የምድርን ሁሉ ጌታ
*የእግዚአብሔርን* ታቦት የተሸከሙት
ካህናት ገና እግራቸውን በዮርዳኖስ ውሃ
ውስጥ እንዳስገቡ፣ ቊልቊል የሚወርደው
ውሃ ወዲያውኑ ይቋረጣል፤ እንደ ክምርም
ሆኖ ይቆማል።”

14ስለዚህ ሕዝቡ ዮርዳኖስን ለመሻገር ሰፈሩን
ለቀው ሲወጡ፣ የቃል ኪዳኑን ታቦት
የተሸከሙት ካህናት ከፊታቸው ቀድመው
ሄዱ። 15ወቅቱም የመከር ጊዜ በመሆኑ፣
የዮርዳኖስ ወንዝ ሞልቶ ነበር፤ ታቦቱን
የተሸከሙት ካህናት ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ
በደረሱ ጊዜ እግራቸው ውሃውን እንደ
ነካ፣ 16ከላይ የሚወርደው ውሃ ቆመ፤
በጻርታን አጠገብ “አዳም” ተብላ እስከም
ትጠራው ሩቅ ከተማ ድረስ በመከማቸት
እንደ ክምር ተቈለለ፤ ቊልቊል ወደ ዓረባ
ጨው ባሕር[ሐ] የሚወርደውም ውሃ ፈጽሞ
ተቋረጠ፤ ሕዝቡም ከኢያሪኮ ትይዩ ባለው
አቅጣጫ ተሻገሩ። 17*የእግዚአብሔርን* የቃል
ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙት ካህናትም፣ ሕዝቡ
ሁሉ ማለት እስራኤል በሙሉ ፈጽመው እስ
ኪሻገሩ ድረስ፣ በዮርዳኖስ ወንዝ መካከል
በደረቁ ምድር ላይ ቀጥ ብለው ቆመው
ነበር።

4 ሕዝቡ ሁሉ ዮርዳኖስን ከተሻገረ
በኋላ፣ *እግዚአብሔር* ኢያሱን እንዲህ
አለው፤ 2“ከሕዝቡ መካከል ከየነገዱ
አንዳንድ ሰው፣ በድምሩ ዐሥራ ሁለት
ሰው ምረጥ፤ 3እንዲሁም ከዮርዳኖስ ወንዝ
መካከል ልክ ካህናቱ ከቆሙበት ስፍራ ዐሥራ
ሁለት ድንጋይ አንሥተው በመሸከም ከእ
ናንተ ጋር እንዲሻገሩና ዛሬ በምታድሩ
በት ቦታ እንዲያኖሯቸው ንገራቸው።”

4ስለዚህ ኢያሱ ከእያንዳንዱ የእስራኤል
ነገድ የሾማቸውን ዐሥራ ሁለት ሰዎች ጠራ፤
5እንዲህም አላቸው፤ “ከአምላካችሁ *ከእግዚአብሔ
ር* ታቦት ፊት ቀድማችሁ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ
መካከል ዕለፉ፤ እያንዳንዳችሁም በእስራኤል
ነገድ ቍጥር አንዳንድ ድንጋይ በትከሻችሁ ተሸ
ከሙ፤ 6ይህም በመካከላችሁ ምልክት እንዲ
ሆናችሁ ነው። ወደ ፊት ልጆቻችሁ፣ ‘እነ
ዚህ ድንጋዮች ምንድን ናቸው?’ ብለው
ቢጠይቋችሁ፣ 7የዮርዳኖስ ወንዝ *በእግዚ
አብሔር* የቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት መቆ
ሙን፤ እንዲሁም ታቦቱ ዮርዳኖስን በሚሻ
ገርበት ጊዜ፣ የዮርዳኖስ ወንዝ ውሃ መቆ
ሙን፣ እነዚህ ድንጋዮች ለእስራኤል ሕዝብ
የዘላለም መታሰቢያ መሆናቸውን ንገሯ
ቸው።”

8እስራኤላውያንም ኢያሱ እንዳዘዛቸው
አደረጉ፤ *እግዚአብሔር* ለኢያሱ በነገረ
ውም መሠረት፣ በእስራኤል ነገዶች ቍጥር
ልክ ዐሥራ ሁለት ድንጋዮች ከዮርዳኖስ
ወንዝ መካከል አነሡ፤ ወደ ሰፈራቸውም
ይዘው በመሻገር በዚያ አኖሯቸው። 9ኢያ
ሱም የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙት
ካህናት ቆመውበት በነበረው በዮርዳኖስ
ወንዝ መካከል ሌሎች ዐሥራ ሁለት
ድንጋዮችን አቆመ፤ እነዚህም ድንጋዮች
እስከ ዛሬ ድረስ[ሰ] በዚሁ ስፍራ ይገኛሉ።

10ሙሴ ለኢያሱ በሰጠው መመሪያ መሠ
ረት፣ *እግዚእብሔር* ለሕዝቡ እንዲነግር ኢያ
ሱን ያዘዘው እስኪፈጸም ድረስ፣ ታቦቱን
የተሸከሙት ካህናት በዮርዳኖስ መካከል
ቆመው ቈዩ፤ ሕዝቡም ፈጥነው ተሻገሩ፤
11ሕዝቡ ሁሉ ተሻግረው እንዳበቁ፣ *የእግዚ
አብሔር* ታቦትና ካህናቱ፣ ሕዝቡ እያዩአ
ቸው ተሻገሩ። 12የሮቤል ነገድና የጋድ ነገድ፣
የምናሴም ነገድ እኩሌታ ሙሴ ባዘዛቸው
መሠረት፣ የጦር መሣሪያቸውን ይዘው
ከእስራኤላውያን ፊት ቀድመው ተሻገሩ።
13አርባ ሺህ ያህሉ ጦርና ጋሻቸውን ይዘው፣
ለውጊያ ዝግጁ ሆነው፣ *በእግዚአብሔር*
ፊት ወደ ኢያሪኮ ሜዳ ተሻገሩ።

14በዚያች ዕለት *እግዚአብሔር* ኢያሱን
በእስራኤል ሁሉ ፊት ከፍ ከፍ አደረገው፤
ሕዝቡ ሙሴን እንዳከበሩት ሁሉ፣ ኢያሱ
ንም በሕይወት ዘመኑ ሁሉ አከበሩት።

15ከዚያም *እግዚአብሔር* ኢያሱን እንዲህ
አለው፤ 16“የምስክሩን ታቦት የተሸከሙ
ትን ካህናት ከዮርዳኖስ ወንዝ እንዲወጡ
እዘዛቸው።”

17ኢያሱም ካህናቱን “ከዮርዳኖስ ውጡ”
ብሎ አዘዛቸው።

18ካህናቱ *የእግዚአብሔርን* የቃል ኪዳን
ታቦት ተሸክመው ከውሃው በመውጣት
እግራቸው ደረቁን መሬት ልክ ሲነካ
የዮርዳኖስ ውሃ ወደ ስፍራው ተመለሰ፤
እንደቀድሞው ሁሉ ሞልቶ በዳሩ ሁሉ ይፈስ
ጀመር።

[ሐ]16 የሙት ባሕር ነው። [ሰ]9 ወይም “ዐሥራ ሁለት ድንጋ
ዮች አቆመ”

3፥8 ቊ3
3፥10 ዘፍ26፥34፤ዘፀ3፥8፤23፥23፤ዘዳ5፥26፤7፥1፡21፤ኢሱ9፥1፤11፥3፤12፥8፤17፥15፤24፥11፤መሳ1፥4፤3፥5፤19፥11፤1ሳሙ17፥26፡36፤2ነገ19፥4፡16፤1ዜና11፥4፤መዝ18፥46፤42፥2፤84፥2፤ኢሳ37፥4፡17፤ኤር10፥10፤23፥36፤ዳን6፥26፤ሆሴ1፥10፤ማቴ16፥16፤
3፥11 ቊ13፤ዘፀ19፥5፤ዘዳ9፥3፤10፥14፤ ኢዮ9፥10፤28፥24፤41፥11፤መዝ50፥12፤97፥5፤ዘካ6፥5
3፥12 ኢሱ4፥2፡4
3፥13 ቊ11፡16፤ዘፀ14፥22፤ኢሱ4፥7፤ኢሳ11፥15
3፥14መዝ132፥8፤ ሐሥ7፥44-45
3፥15 ዘፍ8፥22፤ኢሱ4፥18፤2ነገ2፥6፤1ዜና12፥15፤ኢሳ8፥7፤
3፥16 ቊ13፤ዘፍ14፥3፤8፥1፤ዘፀ14፥22፤ዘዳ1፥1፤ኢዮ 38፥37፤1ነገ4፥12፤7፥46፤2ነገ2፥4፤መዝ33፥7፤66፥6፤74፥15፤114፥3
3፥17 ቊ3፤ዘፀ14፥22፤ኢሱ2፥10፤4፥3፡5፡8፡9፡10
4፥1 ዘዳ27፥2
4፥2 ኢሱ3፥12
4፥3 ቊ19፡20፤ኢሱ 3፥17
4፥4 ኢሱ3፥12
4፥5 ኢሱ3፥17
4፥6 ቊ21፤ዘፀ10፥2፤12፥26፤13፥14፤ኢሱ2፥12
4፥7 ዘፀ28፥12፤ ኢሱ3፥13
4፥8 ቊ20፤ዘፀ28፥21፤ኢሱ3፥17
4፥9 ዘፍ28፥18፤35፥20፤ኢሱ24፥26፤1ሳሙ7፥12፤
4፥12 ዘፍ29፥32፤30፥11፤41፥51፤ዘኍ32፥27፡29
4፥13 ዘፀ13፥18፤ዘኍ32፥17
4፥14 ኢሱ3፥7
4፥16 ዘፀ25፥22
4፥18 ዘፀ14፥27፤ኢሱ3፥15

19የመጀመሪያው ወር በገባ በዐሥረኛው
ቀን ሕዝቡ ዮርዳኖስን ተሻግሮ በኢያሪኮ
ምሥራቃዊ ዳርቻ በጌልገላ ሰፈረ። 20ኢያ
ሱም ከዮርዳኖስ ወንዝ ያወጧቸውን ዐሥራ
ሁለት ድንጋዮች በጌልገላ ተከላቸው፤
21እስራኤላውያንንም እንዲህ አላቸው፤
“ልጆቻችሁ ወደ ፊት፣ ‘እነዚህ ድንጋዮች
ምንድን ናቸው?’ ብለው አባቶቻቸውን
ቢጠይቁ፣ 22‘እስራኤል ይህን ዮርዳኖስ
በደረቅ ምድር ተሻገረ’ ብላችሁ ንገሯ
ቸው፤ 23አኛ እስክንሻገር ድረስ አምላካችሁ
እግዚአብሔር ቀይ ባሕርን[ሽ] እንዳደረቀው
ሁሉ እናንተም እስክትሻገሩ ድረስ አምላካ
ችሁ እግዚአብሔር የዮርዳኖስን ወንዝ
በፊታ ችሁ አደረቀው። 24ይህን
ያደረገውም፣ የእግዚአብሔር ክንድ ብርቱ
መሆኑን የምድር ሕዝቦች ሁሉ እንዲ
ያውቁና እናን ተም አምላካችሁን እግዚአብሐ
ሔርን ለዘላለም እን ድትፈሩ ነው።”

## በጌልገላ የተደረገ ግዝረት

5 በዚህ ጊዜ ከዮርዳኖስ ማዶ በምዕራብ
በኩል ያሉት የአሞራውያን ነገሥታት
ሁሉ፣ በባሕሩም ዳርቻ ያሉ የከነዓ
ናውያን ነገሥታት በሙሉ እግዚአብሔር
ዮርዳኖስን እስክንሻገር ወንዙን በእስራኤላ
ውያን ፊት እንዴት እንዳደረቀው በሰሙ
ጊዜ፣ ልባቸው በፍርሃት ቀለጠ፤ እስራኤላ
ውያንንም ለመቋቋም ድፍረት አጡ።
2በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ኢያሱን፣
“የባልጩት መቊረጫ አዘጋጅተህ፣ ያልተ
ገረዙትን እስራኤላውያንን ለሁለተኛ ጊዜ
ግረዛቸው” አለው። 3ስለዚህ ኢያሱ የባል
ጩት መቍረጫ አዘጋጅቶ በጊብዓዝ ዓረ
ሎት[ቀ] በተባለ ስፍራ እስራኤላውያንን
ገረዛቸው።
4እንግዲህ ኢያሱ እስራኤላውያንን የገረዘ
በት ምክንያት ይህ ነው፤ ዕድሜያቸው
መሣሪያ ለመያዝ የደረሱ ወንዶች ሁሉ
ከግብፅ ከወጡ በኋላ በመንገድ ላይ ሳሉ
በምድረ በዳ ሞቱ። 5ከዚያ የወጡት
ሰዎች ሁሉ ተገርዘው ነበር፤ ከግብፅ ከወጡ
በኋላ በምድረ በዳ በጕዞ ላይ ሳሉ የተወለ
ዱት ግን በሙሉ አልተገረዙም ነበር።
6ግብፅን ለቀው በወጡ ጊዜ መሣሪያ ለመያዝ
የደረሱ ወንዶች ሁሉ ለእግዚአብሔር ስላል
ታዘዙ፣ እነርሱ ሞተው እስኪያልቁ ድረስ፣
እስራኤላውያን በምድረ በዳ አርባ ዓመት
ይንከራተቱ ነበር። እግዚአብሔር ለእኛ
ይሰጠን ዘንድ ለአባቶቻቸው ቃል የገባላቸ
ውን ያችን ማርና ወተት የምታፈስ ምድር
እንደማያዩአት ምሎአልና። 7ስለዚህ በእነርሱ
ምትክ ወንዶች ልጆቻቸውን አስነሣ፤ እንግዲህ

4፥19 ዘጸ11፥30
4፥20 ቀኍ3፥8
4፥21 ቀኍ6
4፥22 ዘፀ14፥22
4፥23 ዘፀ14፥19-22
4፥24 ዘፀ14፥31፤ 15፥16፤1ነገ8፥60፤18፥36፤2ነገ5፥15፤1ዜና29፥12፤መዝ44፥3፤67፥2፤83፥18፤89፥13፤98፥1፤106፥8፤118፥15-16፤ ኢሳ37፥20፤ 52፥10
5፥1 ዘፍ42፥28፤ ዘኍ13፥29
5፥2 ዘፍ17፥10፥12፥14፤ዘፀ4፥25
5፥4 ዘኍ1፥3፤ዘዳ 2፥14
5፥6 ዘፀ3፥8፤16፥35፤ ዘኍ14፥23፥29-35፤ 32፥13፤ ዘዳ2፥14፤ኢሱ 14፥10፤መዝ107፥4
5፥8 ዘፍ34፥25
5፥9 ዘጸ11፥30
5፥10 ዘፀ12፥6፥11
5፥11 ዘፀ12፥15፤ ዘሌ 23፥14፤ ዘኍ15፥19
5፥12 ዘፀ16፥35
5፥13 ዘፍ18፥2፤ ዘኍ22፥23
5፥14 ዘፍ17፥3፤ 19፥1
5፥15 ዘፍ28፥17፤ዘፀ 3፥5፤ሐሥ7፥33
6፥1 ኢሱ24፥11
6፥2 ቀኍ16፤ዘዳ7፥24፤ ኢሱ 8፥1
6፥4 ዘፀ19፥13፤ዘሌ 25፥9

ኢያሱ የገረዛቸው እነዚህን ነበር፤ በጕዞ
ላይ ሳሉ ባለመገረዛቸው ከነሸለፈታቸው
ነበሩና። 8ሕዝቡ ሁሉ ከተገረዙ በኋላ
ቍስሉ እስኪሽር ድረስ እዚያው በሰፈሩ
በት ቦታ ቈዩ።
9ከዚያም እግዚአብሔር ኢያሱን፣ “እነሆ፤
ዛሬ የግብፅን ነውር ከእናንተ ላይ አንከባል
ያለሁ” አለው፤ ከዚህም የተነሣ የዚያ ቦታ
ስም እስከ ዛሬ ድረስ ጌልገላ[በ] ተባለ።
10እስራኤላውያን በኢያሪኮ ሜዳ በጌል
ገላ ሰፍረው ሳሉ፣ ወሩ በገባ በዐሥራ አራ
ተኛው ቀን ምሽት የፋሲካን በዓል አከበሩ።
11ከፋሲካም በኋላ በዚያኑ ዕለት የምድሪቱን
ፍሬ ማለት ያልቦካ ቂጣና የተጠበሰ እሸት
በሉ። 12የምድሪቱ ፍሬ በበሉበት ቀን[ተ]
መናው መውረዱ ቀረ፤ ከዚያ በኋላ ለእስ
ራኤላውያን መና አልወረደላቸውም፤ ነገር
ግን በዚያኑ ዓመት የከነዓንን ምድር ፍሬ
በሉ።

## የኢያሪኮ መውደቅ

13ኢያሱ በኢያሪኮ አጠገብ ሳለ፣ ቀና
ብሎ ሲመለከት የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ
የያዘ አንድ ሰው ከፊቱ ቆሞ አየ፤ ኢያ
ሱም ወደ እርሱ ቀርቦ፤ “ከእኛ ወገን ነህ
ወይስ ከጠላቶቻችን?” ሲል ጠየቀው። 14እር
ሱም፣ “አይደለሁም፤ ነገር ግን የእግዚ
አብሔር ሰራዊት አለቃ በመሆኔ እነሆ፤
መጥቻለሁ” ሲል መለሰለት፤ ኢያሱም በግ
ንባሩ ተደፍቶ ሰገደና፣ “ጌታዬ ለባሪያው
የሚነግረው ምንድን ነው?” አለው።
15የእግዚአብሔር ሰራዊት አለቃም ኢያ
ሱን፣ “ጫማህን ከእግርህ አውልቅ፤ የቆ
ምህባት ምድር የተቀደሰች ናትና” አለው፤
ኢያሱም እንደታዘዘው አደረገ።

6 በዚህ ጊዜ እስራኤላውያንን ከመፍራት
የተነሣ፣ ኢያሪኮ ፈጽማ ተዘግታ ነበር፤
ወደ ውጭ የሚወጣም ሆነ ወደ ውስጥ የሚገባ
አልነበረም።
2እግዚአብሔርም ኢያሱን እንዲህ አለው፤
“እነሆ፤ ኢያሪኮን ከንጉሥዋና ከተዋጊዎቿ
ጋር አሳልፌ በእጅህ ሰጥቻለሁ። 3ከተማዪቱን
ከተዋጊዎቻችሁ ጋር አንድ ጊዜ ዙሩ፤ ይህ
ንም ስድስት ቀን አድርጉ። 4ሰባት ካህናት፣
ሰባት ቀንደ መለከት ተሸክመው በታቦቱ
ፊት ይውጡ፤ በሰባተኛውም ቀን ካህናቱ
መለከት እየነፉ ከተማይቱን ሰባት ጊዜ ይዙሩ።

[ሽ]23 ዕብራይስጡ፣ “ያም ስውፍ” ይላል፤ ይኸውም የደንገል ባሕር ማለት ነው።
[ቀ]3 ትርጓሜውም የሸለፈት ኰረብታ ማለት ነው።
[በ]9 በዕብራይስጡ ጌልጌላ የሚለው የቃል ድምፅ መንከባለል ከሚለው ቃል ጋር አንድ ዐይነት ነው።
[ተ]12 ወይም በበሉበት ጊዜ ተብሎ መተርጐም ይቻላል።

[5]የማያቋርጥ የመለከት ድምፅ ሲነፋ በም
ትሰሙበት ጊዜ፣ ሕዝቡ ሁሉ ከፍ ያለ
ጩኸት ያሰማ፤ ከዚያም የከተማዪቱ ቅጥር
ይፈርሳል፤ ሕዝቡም ወደ ላይ ይወጣል፤
እያንዳንዱም ሰው በቀጥታ ይገባል።”
[6]ስለዚህ የነዌ ልጅ ኢያሱ ካህናቱን ጠርቶ፣
“የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸከሙ፤ ሰባት
ካህናትም ሰባት ቀንደ መለከት ይዘው
በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ይሂዱ” አላ
ቸው። [7]ሕዝቡንም፣ “ወደ ፊት ሂዱ፤ ከተ
ማዋን ዙሩ፤ የታጠቁ ተዋጊዎችም በእግዚ
አብሔር ታቦት ፊት ቀድመው ይሂዱ፤
ከተማዪቱንም ዙሩ” ሲል አዘዛቸው።
[8]ኢያሱም ለሕዝቡ ከተናገረ በኋላ፣
ሰባቱ ካህናት በእግዚአብሔር ፊት ሰባት
ቀንደ መለከት ይዘው መለከታቸውን
እየነፉ ወደ ፊት ቀደሙ፤ የእግዚአብሔር
የቃል ኪዳን ታቦትም ተከተላቸው። [9]የታጠቁ
ተዋጊዎችም መለከት ከሚነፉት ካህናት
ፊት ቀድመው ሲሄዱ፣ ደጀን የሆኑት ጠባ
ቂዎች ደግሞ ታቦቱን ተከተሉ፤ በዚህ ጊዜ
ሁሉ መለከቶቹ ባለማቋረጥ ይነፉ ነበር።
[10]ኢያሱ ሕዝቡን፣ “የማሽበሪያ ጩኸት
አታሰሙ፤ ድምፃችሁ ከፍ ብሎ አይሰማ፤
ጩኹ እስከምላችሁም ቀን ድረስ ከአፋችሁ
አንዲት ቃል አትውጣ፤ የምትጮኹት ከዚያ
በኋላ ነው” ሲል አዘዛቸው።
[11]ስለዚህ ኢያሱ የእግዚአብሔርን ታቦት
ተሸክመው፣ ከተማዪቱን አንድ ጊዜ እን
ዲዞሩ አደረገ። ከዚያም ሕዝቡ ወደ ሰፈር
ተመልሰው ዐደሩ።
[12]ኢያሱ በማግሥቱ ማልዶ ተነሣ፤ ካህናቱም
የእግዚአብሔርን ታቦት ተሸከሙ። [13]ሰባቱም
ካህናት ሰባት ቀንደ መለከት ይዘው በእግዚ
አብሔር ታቦት ፊት እየሄዱ፣ መለከቱን
ባለማቋረጥ ይነፉ ጀመር፤ የታጠቁ ተዋጊ
ዎችም እነዚህን በመቅደም ሲሄዱ፣ የደ
ጀን ጠባቂዎቹ ደግሞ የእግዚአብሔርን
ታቦት ይከተሉ ነበር፤ ካህናቱም ሳያቋርጡ
መለከት ይነፉ ነበር። [14]በሁለተኛውም ቀን
ከተማዪቱን አንድ ጊዜ ከዞሩ በኋላ ወደ ሰፈር
ተመለሱ፤ ስድስት ቀን ሙሉም እንዲሁ
አደረጉ።
[15]በሰባተኛው ቀን ገና ጎሕ ሲቀድ ተነሡ፤
እንደ በፊቱም ከተማይቱን ሰባት ጊዜ ዞሩ፤
ከተማዪቱን ሰባት ጊዜ የዞሯትም በዚያን
ቀን ብቻ ነው። [16]በሰባተኛው ዙር ላይ
ካህናቱ መለከቱን ሲነፉ፣ ኢያሱ ሕዝቡን
እንዲህ ሲል አዘዘ፤ “እግዚአብሔር ይህ
ችን ከተማ ሰጥቶአችኋልና ጩኹ! [17]ከተማዪ
ቱና በውስጧ ያለው ሁሉ ለእግዚአብሔር
የተለየ ስለ ሆነ ፈጽማችሁ አጥፉ[*]፣ እኛ
የላክናቸውን ሰላዮች ስለሸሸገች ጋለሞታዪቱ[ⁱ]
ረዓብ ብቻና ከእርሷ ጋር በቤቷ ውስጥ
ያሉት ሁሉ ይትረፉ። [18]እናንተ ግን እርም
ከሆኑት ነገሮች አንዳች በመውሰድ በራ
ሳችሁ ላይ ጥፋት እንዳታመጡ እጃችሁን
ሰብስቡ፤ ያለዚያ የእስራኤልን ሰፈር ለጥ
ፋት ትዳርጋላችሁ፤ ክፉ ነገር እንዲደርስ
በትም ታደርጋላችሁ፤ [19]ብሩና ወርቁ
እንዲሁም የናሱና የብረቱ ዕቃ ሁሉ ለእግ
ዚአብሔር የተቀደሰ ስለ ሆነ፣ ወደ እግዚ
አብሔር ግምጃ ቤት ይግባ።”
[20]መለከቱ ሲነፋ ሕዝቡ ጮኸ፤ የመለ
ከቱ ድምፅ ተሰምቶ፣ ሕዝቡ በኀይል ሲጮኽ
ቅጥሩ ፈረሰ፤ እያንዳንዱ ሰው ስተት
ብሎ ገባ፤ ከተማዪቱም በእጃቸው ወደ
ቀች። [21]በከተማዪቱ ውስጥ ያለውን ሁሉ
ማለትም ወንዱንና ሴቱን፣ ወጣቱንና ሽማ
ግሌውን፣ ከብቱንና በጉን እንዲሁም አህ
ያውን በሰይፍ ስለት ፈጽመው አጠፉ።
[22]ኢያሱ ምድሪቱን የሰለሉትን ሁለቱን
ሰዎች፣ “ወደ ጋለሞታዪቱ ቤት ሂዱ፤ በማ
ላችሁላትም መሠረት እርስዋንና የእርሷ
የሆነውን ሁሉ ከዚያ አውጡ” አላቸው።
[23]ስለዚህ ሁለቱ ወጣት ሰላዮች ገብተው
ረዓብን፣ አባቷንና እናቷን፣ ወንድሞቿንና
የእርሷ የሆኑትን ሁሉ ከዚያ አወጧቸው።
ቤተ ዘመዶቿንም ሁሉ አውጥተው ከእስራ
ኤል ሰፈር ውጭ አስቀመጧቸው።
[24]ከዚያም ከተማዪቱን በሙሉ፣ በውስጧ
ያለውንም ሁሉ አቃጠሉ፤ ብሩንና ወርቁን፣
የናሱንና የብረቱን ዕቃ ግን በእግዚአብሔር
ግምጃ ቤት አኖሩ። [25]ኢያሪኮን እንዲሰልሉ
ኢያሱ የላካቸውን ሰዎች ስለ ደበቀች፣
ጋለሞታዪቱን ረዓብን፣ ቤተ ሰቧንና የእርሷ
የሆኑትን ሁሉ አዳናቸው፤ እርሷም እስከ
ዛሬ ድረስ በእስራኤላውያን መካከል ትኖራ
ለች።
[26]በዚያን ጊዜም ኢያሱ፣ እንዲህ ሲል
ማለ፤ “ይህችን ከተማ መልሶ የሚሠራት ሰው
በእግዚአብሔር ፊት የተረገመ ይሁን፤

“መሠረቷን ሲጥል፣
የበኵር ልጁ ይጥፋ፤
ቅጥሮቿንም ሲያቆም፣
የመጨረሻ ልጁ ይጥፋ” ብሎ ማለ።

[27]ስለዚህ እግዚአብሔር ከኢያሱ ጋር ነበር፤
ዝናውም በምድሪቱ ሁሉ ላይ ወጣ።

6፥5 ቊ20፤ዘፀ19፥13፤1ሳሙ4፥5፤2ሳሙ6፥15፤ዕዝ3፥11፤10፥12፤መዝ42፥4፤95፥1፤ኢሳ8፥9፤42፥13
6፥6 ቊ4
6፥7 ዘፀ14፥15፤ዘኍ10፥35፤1ሳሙ4፥3፤7፥1
6፥9 ቊ13፤ዘኍ2፥31፤ ኢሳ52፥12
6፥10 ቊ20፤1ሳሙ4፥5፤ዕዝ3፥11
6፥15 1ነገ18፥44፤2ነገ4፥35፤5፥14
6፥16 ቊ2
6፥17 ቊ21፡25፤ዘሌ27፥28፤ዘዳ20፥17፤ኢሱ2፥1፡4፤ኢሳ13፥5፤24፥1፤34፥2፡5፤ሚል4፥6
6፥18 ኢሱ7፥1፡12፡25፡26፤1ዜና2፥7፤
6፥19 ቊ24፤ዘኍ31፥22
6፥20 ቊ5፡10ዘሌ25፥9፤መሳ6፥34፤7፥22፤1ነገ1፥41፤ኢሳ18፥3፤27፥13፤ኤር4፥21፤42፥14፤አሞ2፥2፤ዕብ11፥30
6፥21 ቊ17፤ዘዳ20፥16
6፥22 ዘፍ42፥9፤ዘኍ21፥32፤ኢሱ2፥4፡14፤ዕብ11፥31
6፥23 ኢሱ2፥13
6፥24 ቊ19፤ዘኍ31፥10፤ዘዳ13፥16
6፥25 ቊ17፤ኢሱ2፥1፡6፤መሳ1፥25
6፥26 ዘኍ5፥21፤1ሳሙ14፥24፤1ነገ16፥34
6፥27 ዘፍ39፥2፤ዘኍ14፥43፤ኢሱ9፥1፤1ዜና14፥17

[*]17 የዕብራይስጡ ቃል አንድን ሰው ወይም ነገር ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት ነው።
[ⁱ]17 በዚህም ሆነ በቍጥር 22 እና 25 ላይ፣ “የሆቴል ቤት ተጠቃሚ” ተብሎ ሊተረጐም ይችላል።

## የአካን ኀጢአት

7 እስራኤላውያን ግን እርም የሆነውን ነገር[ነ]
ባለማጥፋታቸው በደሉ፤ ይህም ከይሁዳ
ነገድ የሆነው አካን የከርሚ ልጅ፣ የዘንበሪ[ኘ]
ልጅ፣ የዛራ ልጅ እርም ከሆነው ነገር ስለ
ወሰደ *የእግዚአብሔር* ቊጣ በእስራኤል
ልጆች ላይ ነደደ፡፡
[2]ኢያሱ ከቤቴል በስተ ምሥራቅ ካለችው
ከቤትአዌን አጠገብ ወደምትገኘው ወደ
ጋይ ከኢያሪኮ ሰዎችን ልኮ፣ "ወደዚያ
ውጡ፤ አገሪቱንም ሰልሉ" አላቸው፤ ሰዎቹም
ወጥተው ጋይን ሰለሉ፡፡
[3]ወደ ኢያሱም ተመልሰው፣ "ጋይን
ለመውጋት ሕዝቡ ሁሉ መሄድ አያስፈልገ
ውም፤ በዚያ ያለው ሕዝብ ጥቂት ስለ
ሆነ፣ ከተማዪቱን ለመውጋት ሁለት
ወይም ሦስት ሺህ ሰው ስለሚበቃ ሕዝቡ
ሁሉ ወደዚያ በመሄድ አይድከም" አሉት፡፡
[4]ስለዚህ ሦስት ሺህ ያህል ሰው ወጣ፤ ከጋ
ይም ሰዎች ፊት ሸሸ፤ [5]የጋይም ሰዎች እስ
ራኤላውያንንም ከከተማዪቱ ቅጥር በር
ጀምሮ እስከ ሽባሪም[አ] ድረስ በማባረር
ቊልቊለቱ ላይ መቷቸው፤ ከእነርሱም
ሠላሳ ስድስት ያህል ሰው ገደሉባቸው፡፡
ከዚህ የተነሣም የሕዝቡ ልብ ቀለጠ፤
እንደ ውሃም ፈሰሰ፡፡
[6]በዚህ ጊዜ ኢያሱ ልብሱን ቀደደ፤ *በእግ
ዚአብሔርም* ታቦት ፊት በግንባሩ ተደፋ፤
የእስራኤል ሽማግሌዎችም እንደዚሁ አደ
ረጉ፤ በራሳቸውም ላይ ትቢያ ነሰነሱ፡፡ [7]ኢያ
ሱም እንዲህ አለ፤ "ወዮ! ልዑል *እግዚአ
ብሔርሆይ*፤ ዮርዳኖስን አሻግረህ ይህን ሕዝብ
ወደ ዚህ ያመጣኸው ለአሞራውያን አሳልፈህ
በመስጠት እንዲያጠፉን ነውን? ምነው
ሳንሻገር እዚያው ማዶ በቀረን ኖሮ! [8]ጌታ
ሆይ፤ እስራኤል በጠላቱ ፊት ሲሸሽ እኔ
ምን ልበል? [9]ከነዓናውያንና ሌሎቹ የምድ
ሪቱ ነዋሪዎች ሁሉ ይህን ሲሰሙ ይከቡ
ናል፤ ስማችንንም ከምድር ገጽ ያጠፉታል፤
እንግዲህ ስለ ታላቁ ስምህ ስትል የምታደር
ገው ምንድን ነው?"
[10]*እግዚአብሔር* ኢያሱን እንዲህ አለው፤
"ተነሥ! ለምን በግንባርህ ተደፋህ? [11]እስራ
ኤል በድሎአል፤ እንዲጠብቁ ያዘዝኋቸ
ውን ቃል ኪዳኔን ጥሰዋል፤ እርም የሆነውን
ነገር ወስደዋል፤ ሰርቀዋል፤ ዋሽተዋል፤ የወ
ሰዱትንም ከራሳቸው ንብረት ጋር ደባልቀ
ዋል፡፡ [12]እንግዲህ እስራኤላውያን ጠላቶቻ
ቸውን ለመቋቋም ያልቻሉት በዚህ ምክንያት
ነው፡፡ ጀርባቸውን አዙረው የሸሹትም ለጥ
ፋት በመዳረጋቸው ነው፡፡ እርም የሆነውን
ነገር ከመካከላችሁ ካላጠፋችሁ፣ ከዚህ

7፥1 ቊ18፥26፤ዘፀ 4፥14፤32፥20፤ዘሌ10፥6፤ዘኍ1፥4፤ኢሱ6፥18፤22፥20፤ 1ዜና2፥7
7፥2 ዘፍ12፥8፤ዘኍ 21፥32፤ኢሱ8፥1፡28፤12፥16፤16፥1፤18፥12፤መሳ1፥22፤1ሳሙ13፥5፤14፥23፤30፥27፤2ነገ23፥15፤ኤር48፥13፤ሆሴ4፥15፤5፥8፤10፥5፤አሞ3፥14፤4፥4፤5፥5-6፤7፥10፡13
7፥4 ዘሌ26፥17፤ዘዳ 28፥25
7፥5 ዘፍ42፥28፤ኢሱ 22፥7መዝ22፥14፤ኢሳ 13፥7፤ሕዝ21፥7፤ናሆ 2፥10
7፥6 ዘፍ17፥3፤37፥29፤ኢሱ8፥10፤9፥11፤20፥4፤23፥2፤መሳ20፥23፤1ሳሙ4፥12፤2ሳሙ 13፥19፤15፥32፤1ዜና21፥16፤ነህ9፥1፤ኢዮ2፥12፤ሰቆ2፥10፤ሕዝ9፥8፤27፥30፤ራእ18፥19
7፥7 ዘፀ5፥22፤ዘኍ 14፥16፤1ሳሙ4፥3
7፥9 ዘፀ32፥12፤ዘዳ 9፥28፤28፥58፤1ሳሙ12፥22፤መዝ48፥10፤106፥8፤ኤር14፥21
7፥11 ቊ15፥21፤ዘፀ 9፥27፤ዘዳ29፥27፤ኢሱ 6፥17-19፤23፥16፤24፥16-27፤መሳ2፥20፤1ሳሙ15፥24፤2ነገ17፥7፤መዝ78፥10፤ሆሴ 10፥9፤ሐሥ5፥1-2፤
7፥12ዘሌ26፥17፡37፤ኢሱ6፥18፤መዝ18፥40፤21፥12፤44፥9፤60፥10
7፥13 ዘሌ11፥44
7፥14 1ሳሙ10፥19፤ምሳ16፥33
7፥15 ቊ11፤ዘፍ 34፥7፤ዘዳ7፥25፤ኢሱ 6፥18፤1ሳሙ14፥39፤2ነገ25፥9፤1ዜና14፥12፤ኢሳ37፥19፤ኤር 43፥12፤ሕዝ30፥16
7፥17 ዘኍ26፥20
7፥18 ቊ1፤ዘሌ24፥11፤ዮና1፥7
7፥19 ዘፀ14፥17፤ዘሌ5፥5፤1ሳሙ6፥5፤14፥43፤መዝ96፥8፤ኢሳ42፥12፤ኤር13፥16፤ዮሐ9፥24
7፥21 ዘፍ34፥29፤

በኋላ ከእናንተ ጋር አልሆንም፡፡
[13]"ተነሣ፤ ሕዝቡን ቀድስ፤ እንዲህም በላ
ቸው፤ 'እስራኤል ሆይ፤ እርም የሆነ ነገር
በመካከላችሁ ስላለ፣ ይህን ካላስወገዳ
ችሁ ጠላቶቻችሁን ለመቋቋም እንደማት
ችሉ፣ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር
ተናግሮአልና፣ ለነገ ራሳችሁን ለማዘጋጀት
ሰውነታችሁን ቀድሱ፡፡
[14]" 'ማለዳ በየነገድ በየነገዳችሁ ሆናችሁ
ቅረቡ፤ እግዚአብሔር የሚለየው ነገድ በየ
ጐሣ በየጐሣው ሆኖ ከሕዝቡ መካከል ወደ
ፊት ይወጣል፤ እንዲሁም *እግዚአብሔር*
የሚለየው ጐሣ በየቤተሰቡ ሆኖ ወደ ፊት
ይወጣል፤ *እግዚአብሔር* የሚለየው ቤተ
ሰብ ደግሞ በግለሰብ በግለሰብ ሆኖ ወደ
ፊት ይወጣል፡፡ [15]እርሙ የተገኘበት ሰው፣
እርሱና ያለው ሁሉ በእሳት ይቃጠላል፤
*የእግዚአብሔርን* ቃል ኪዳን አፍርሶአል፤
በእስራኤልም ዘንድ አሳፋሪ ተግባር ፈጽሞ
አልና፡፡"
[16]በማግሥቱ ጥዋት ኢያሱ ማልዶ
ተነሣ፤ እስራኤልንም በየነገድ በየነገዳቸው
ሆነው እንዲቀርቡ አደረገ፤ ከዚያም የይ
ሁዳ ነገድ ተለየ፤ [17]የይሁዳንም ጐሣዎች
ወደ ፊት አቀረበ፤ ከእነዚህም የዛራን ጐሣ
ለየ፤ እነዚህን ደግሞ በየቤተሰባቸው እንዲ
ወጡ አደረገ፤ ከእነዚህም ዘንበሪ ተለየ፡፡
[18]ኢያሱ የዘንበሪን ቤተ ሰብ አባላት አንድ
በአንድ ወደፊት እንዲቀርቡ አደረገ፤ ከዚ
ያም ከይሁዳ ነገድ የሆነውም የዛራ ልጅ፣
የዘንበሪ ልጅ፣ የከርሚ ልጅ አካን ለብቻው
ተለየ፡፡
[19]ኢያሱም አካንን፣ "ልጄ ሆይ፤ ለእስራ
ኤል አምላክ[ከ] *ለእግዚአብሔር* ክብርን
ስጥ፤ ለእርሱም ተናዘዝ፤ ያደረግኸውን
ሳትደ ብቅ ንገረኝ" አለው፡፡
[20]አካንም መልሶ ኢያሱን እንዲህ
አለው፤ "እውነት ነው! የእስራኤልን አምላክ
*እግዚአብሔርን* በድያለሁ፤ ያደረግሁትም ይህ
ነው፤ [21]ከምርኮው ዕቃ መካከል ከሰናዖር[ኸ]
የመጣ አንድ የሚያምር ካባ፣ ሁለት መቶ
ሰቅል[ወ] ብርና[ዐ] ክብደቱ አምሳ ሰቅል
የሚሆን የወርቅ ቡችላ አይቼ ጐመጀሁ፤
ወሰድኋቸውም፤ ዕቃውም ብሩ ከታች
ሆኖ፣ በድንኳኔ ውስጥ መሬት ተቀብሮ
አል፡፡"

[ነ]1 በዚህም ሆነ በቍጥር 11:12:13 እና 15 ላይ የዕብራይስጡ ቃል አንድን ሰው ወይም ነገር ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት ነው፡፡ [ኘ]1 1ዜና 2፥6 እና የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ይመ፤ በዚህም ሆነ በቍጥር 17 እና 18 ላይ ዕብራይስጡ "ዘብዴ" ይላል፡፡ [አ]5 ወይም እስከ "ድንጋይ መፍለጫው" ተብሎ መተርጐም ይችላል፡፡
[ከ]19 እውነትን ለመናገር የሚደረግ መሐላ ነው፡፡ [ኸ]21 አንዳንድ ቅጂዎች "ባቢሎን" ይላሉ፡፡ [ወ]21 2.3 ኪሎ ግራም ያህል ነው፡፡ [ዐ]21 0.6 ኪሎ ግራም ያህል ነው፡፡

[22]በዚህ ጊዜ ኢያሱ መልእክተኞች ላከ፤
እነርሱም ወደ ድንኳኑ ሮጡ፤ በዚያም
ብሩ ከታች ሆኖ ዕቃው እንደ ተቀበረ
አገኙ። [23]ከድንኳኑም አውጥተው፣ ኢያ
ሱና እስራኤላውያን ሁሉ ወዳሉበት አምጥ
ተው *በእግዚአብሔር* ፊት አኖሩ።
[24]ኢያሱም ከመላው እስራኤል ጋር
ሆኖ፣ የዛራን ልጅ አካንን፣ ብሩን፣ ካባ
ውን፣ የወርቁን ቡችላ፣ ወንዶችና ሴቶች
ልጆቹን፣ የከብቱን መንጋ፣ አህዮቹንና
በጎቹን እንዲሁም ድንኳኑንና የእርሱ
የሆነውን ሁሉ ወደ አኮር ሸለቆ አስወሰደ።
[25]ኢያሱም፣ “እንዲህ ያለውን መከራ ለምን
አመጣብህን? እነሆ፤ ዛሬ በአንተም ላይ
*እግዚአብሔር* መከራ ያመጣብሃል” አለው፤
ከዚያም እስራኤል በሙሉ በድንጋይ ወገሩት፤
የቀሩትንም እንደዚሁ ከወገሩ በኋላ በእ
ሳት አቃጠሏቸው። [26]በአካንም ላይ እስከ
ዛሬ ድረስ የሚታየውን ታላቅ የድንጋይ
ቍልል ከመሩበት፤ ከዚያም *እግዚአብሔር*
ከአስፈሪ ቍጣው ተመለሰ፤ ስለዚህ ከዚያን
ጊዜ ጀምሮ ያ ስፍራ የአኮር" ሸለቆ ተባለ።

## የጋይ ከተማ ተደመሰሰ

8 ከዚያም *እግዚአብሔር* ኢያሱን እንዲህ
አለው፤ “አትፍራ፤ አትደንግጥ፤ ሰራ
ዊቱን ሁሉ ይዘህ በመውጣት ጋይን ውጋ፤
የጋይን ንጉሥ፣ ሕዝቡን፣ ከተማውንና
ምድሩን አሳልፌ በእጅህ ሰጥቼሃለሁና።
[2]በኢያሪኮና በንጉሥዋ ላይ ያደረግኸውንም
ሁሉ፣ በጋይና በንጉሥዋ ላይ ትደግመዋለህ፤
በዚህ ጊዜ ግን ምርኮውንና ከብቱን ለራ
ሳችሁ ታደርጉታላችሁ፤ ታዲያ ከከተማ
ዪቱ በስተጀርባ የደፈጣ ጦር አዘጋጅ።”
[3]ስለዚህ ኢያሱና ሰራዊቱ በሙሉ ጋይን
ለመውጋት ወጡ፤ ኢያሱም ምርጥ ከሆኑት
ተዋጊዎቹ ሠላሳ ሺህ ጦር አዘጋጅቶ በሌሊት
ላካቸው፤ [4]እንዲህ የሚል ትእዛዝም ሰጣቸው፤
“እነሆ፤ ከከተማዪቱ በስተጀርባ ታደፍጣላ
ችሁ፤ ከከተማዪቱ አትራቁ፤ ሁላችሁም
ነቅታችሁ ተጠባበቁ፤ [5]እኔና አብረውኝ
ያሉት ሁሉ ወደ ከተማዪቱ እንጠጋለን፤
ሰዎቹ ከዚህ በፊት እንዳደረጉት ሊወጉን
ወደኛ ሲመጡ፤ እኛ ደግሞ እንሸሻለን፤
[6]እነርሱም፣ ‘ከዚህ ቀደም እንዳደረጉት
አሁንም ከእኛ በመሸሽ ላይ ናቸው’ በማ
ለት ከከተማዪቱ እስክናርቃቸው ድረስ
ይከታተሉናል፤ በዚህ ሁኔታ እኛም እንሸ
ሻለን፣ [7]እናንተም ከተደበቃችሁበት ትወ
ጡና ከተማዪቱን ትይዛላችሁ፤ አምላካችሁ
*እግዚአብሔር* ከተማዪቱን በእጃችሁ አሳ
ልፎ ይሰጣችኋልና። [8]ከተማዪቱን ስትይ
ዙም በእሳት አቃጥሏት፤ *እግዚአብሔር*
ያዘዘውንም አድርጉ፤ እነሆ አዝዣችኋለሁ።”
[9]ከዚያም ኢያሱ ሰዎቹን ላካቸው፤ እነር
ሱም ሄደው ከጋይ በስተ ምዕራብ በቤቴ
ልና በጋይ መካከል ባለው ቦታ አደፈጡ፤
ኢያሱ ግን እዚያው ከሕዝቡ ጋር ዐደረ።
[10]በማግስቱ ጧት ኢያሱ ማልዶ በመነ
ሣት ወንዶቹን ሰበሰበ፤ እርሱና የእስራ
ኤል አለቆችም ከፊት ሆነው እየመሯቸው
ወደ ጋይ ወጡ፤ [11]ከእርሱ ጋር የነበሩትም
ተዋጊዎች በሙሉ ወጥተው ወደ ከተማ
ዪቱ በመጠጋት ከፊት ለፊቷ ደረሱ፤ ከዚ
ያም ከጋይ በስተ ሰሜን መካከል ካለው
ሸለቆ ማዶ ሰፈሩ። [12]ኢያሱ ቀደም ብሎ
አምስት ሺህ ሰው ያህል በመውሰድ ከከተ
ማዪቱ በስተ ምዕራብ፣ በቤቴልና በጋይ
መካከል እንዲያደፍጡ አድርጎ ነበር።
[13]ከከተማዪቱ በስተ ሰሜን የነበሩትንም፣
ከከተማዪቱ በስተ ምዕራብ የሸመቁትንም
ወታደሮች ሁሉ ስፍራ ስፍራቸውን እንዲ
ይዙ አደረጋቸው፤ በዚያችም ሌሊት ኢያሱ
ወደ ሸለቆው ሄደ።
[14]የጋይ ንጉሥ ይህን ባየ ጊዜ እርሱና
የከተማዪቱ ወንዶች ሁሉ ማልደው በመገ
ሥገሥ፣ እስራኤልን ለመውጋት ከዓረባ
ፊት ለፊት ወደሚገኘው ስፍራ መጡ፤ ንጉሡ
ግን ከከተማዪቱ በስተ ጀርባ ያደፈጠ
ኀይል የሚጠባበቀው መሆኑን አያውቅም
ነበር። [15]ኢያሱና እስራኤል በሙሉ ድል
የተመቱ መስለው በመታየት፣ ወደ
ምድረ በዳው ሸሹ። [16]የጋይ ሰዎች በሙሉ
እንዲያሳድዷቸው ተጠሩ፤ ኢያሱንም አሳደ
ዱት፤ በዚህ ሁኔታም የጋይ ሰዎች
ከከተማዪቱ እንዲርቁ ተደረገ። [17]እስራ
ኤልን ለማሳደድ ከጋይና ከቤቴል ያልወጣ
ወንድ አልነበረም፤ ከተማዪቱንም ከፍተው
ትተው እስራኤልን ማሳደድ ያዙ።
[18]*እግዚአብሔርም* ኢያሱን፣ “ከተ
ማዪቱን በእጅህ አሳልፌ እሰጥሃለሁ፣
የያዝኸውን ጦር ወደ ጋይ አነጣጥር”
አለው፤ ኢያሱም ጦሩን ወደ ጋይ አነጣ
ጠረ። [19]ይህን እንዳደረገም ያደፈጡት
ሰዎች ከተደበቁበት ስፍራ በፍጥነት
ወጥተው ወደ ፊት ሮጡ፤ ገብተው ከተማ
ዪቱን ያዟት፤ ወዲያውኑም በእሳት
አቃጠሏት።
[20]የጋይ ሰዎች ወደ ኋላ ዞረው ሲመ
ለከቱ የከተማዪቱ ጢስ ወደ ሰማይ ሲወጣ
አዩ፤ ወደ ምድረ በዳ ይሸሹ የነበሩት እስ
ራኤላውያን ፊታቸውን ስላዞሩባቸውም፣
በየትኛውም በኩል ማምለጫ መንገድ
አልነበራቸውም። [21]ኢያሱና እስራኤል

49፥27፤ዘዳ7፥25፤ ኤፌ5፥5፤1ጢሞ 6፥10
7፥24 ቍ26፤ዘኍ 16፥27፤ኢሱ15፥7፤ ኢሳ65፥10፤ሆሴ2፥15
7፥25 ዘፍ38፥24፤ ዘሌ20፥2፤ዘዳ17፥5፤ ኢሱ6፥18፤1ነገ12፥ 18፤2ዜና10፥18፤24፥2 1፤ነህ9፥26፤
7፥26 ቍ24፤ዘፍ 5፥20፤ዘኍ25፥4፤ 2ሳሙ18፥17
8፥1 ዘፍ26፥24፤ዘኍ 14፥9፤ዘዳ1፥21፤31፥6፤ ኢሱ6፥2፤7፥2፤9፥3፤ 10፥1፡7፤12፥9፤6፥2
8፥2 ቍ4፡12፡27፤ ዘፍ49፥27፤ዘዳ20፥ 14፤መሳ9፥43፤20፥29
8፥7 መሳ7፥7፤ 1ሳሙ 23፥4
8፥8 ቍ19፤መሳ20፥ 29-38
8፥9 2ዜና13፥13
8፥10 ዘፍ22፥3፤ ኢሱ7፥6
8፥14 ዘዳ1፥1፤ መሳ20፥34
8፥15 ኢሱ15፥61፤ 16፥1፤18፥12፤ መሳ20፥36
8፥16 መሳ20፥31
8፥18 ቍ26፤ዘፀ4፥ 2፤17፥9-12፤ኢዮ41፥ 26፤መዝ 35፥3
8፥19 ቍ8፤መሳ 20፥33
8፥20 መሳ20፥40

"26 “አኮር” ማለት ችግር ወይም መከራ ማለት ነው።

ሁሉ ያደፈጠው ጦር ከተማዪቱን መያዙ
ንና ጢሱ ወደ ላይ መውጣቱን ሲያዩ፣
ወደ ኋላ ተመልሰው በጋይ ሰዎች ላይ
አደጋ ጣሉባቸው፤ 22ያደፈጡትም ሰዎች
እንደዚሁ ከከተማዪቱ ወጥተው መጡባ
ቸው፤ ስለዚህ እስራኤላውያን በዚያም በዚ
ህም ስለ ከበቧቸው የጋይን ሰዎች ከመካ
ከል አደረጓቸው፤ እስራኤላውያንም ሰዎቹን
ፈጇቸው፤ አንድ እንኳ የተረፈ ወይም
ያመለጠ አልነበረም፤ 23ነገር ግን የጋይን
ንጉሥ ከነሕይወቱ ይዘው ወደ ኢያሱ
አመጡት።

24እስራኤላውያን የጋይን ወንዶች ሁሉ
ባሳደዷቸው ሜዳና ምደረ በዳ ከጨረሷቸ
ውና እያንዳንዳቸውንም በሰይፍ ከፈጁ በኋላ፣
ወደ ከተማዪቱ ተመልሰው በዚያ ያገኙትን
ሁሉ ገደሉ። 25በዚያች ዕለት የጋይ ሰዎች
ሁሉ አለቁ፤ የወንዶቹና የሴቶቹም ብዛት ዐሥራ
ሁለት ሺህ ነበር። 26ኢያሱ በጋይ የሚኖሩ
ትን ሰዎች ሁሉ ፈጽሞ እስኪያጠፋቸው[ሀ]
ድረስ ጦር ያነጣጠረባትን እጁን አላጠ
ፈም ነበር። 27እስራኤላውያንም እግዚአብሔር
ኢያሱን ባዘዘው መሠረት፣ በከተማዪቱ ያገኙ
ትን እንስሳትና ምርኮ ብቻ ለራሳቸው
አደረጉ።

28ስለዚህ ኢያሱ ጋይን አቃጠላት፣
እስከ ዛሬ እንደሚታየውም ለዘላለም የዐ
መድ ቍልልና ባድማ አደረጋት። 29የጋይንም
ንጉሥ በዛፍ ላይ ሰቀለው፤ ሬሳውንም እስኪ
መሸ ድረስ እዚያው እንዳለ ተወው፤ ፀሓይ
ስትጠልቅም፣ ኢያሱ ሬሳውን እንዲያወር
ዱትና በከተማው በር ላይ እንዲጥሉት
አዘዘ፤ የትልልቅ ድንጋይ ቍልልም ከመሩ
በት፤ ይህም እስከ ዛሬ ድረስ እዚያው
ይገኛል።

## ቃል ኪዳኑ በጌባል ተራራ ታደሰ

30ከዚያም ኢያሱ በጌባል ተራራ ላይ
ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር መሠዊ
ያን ሠራ። 31መሠዊያዉንም የሠራው የእ
ግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ፣ እስራኤላውያ
ንን ባዘዛቸው መሠረት ሲሆን፣ ይህንም የሠ
ራው በሙሴ የሕግ መጽሐፍ እንደ ተጻ
ፈው ባልተጠረበና የብረት መሣሪያ ባል
ነካው ድንጋይ ነው፤ በዚህም ላይ የሚ
ቃጠል መሥዋዕት አቀረቡ፤ የኅብረት
መሥዋዕትም[ለ] ሠው። 32ኢያሱም ሙሴ
የጻፈውን የሕግ መጽሐፍ እስራኤላውያን
እያዩ በድንጋዮች ላይ ቀረጸው። 33እስራ
ኤል በሙሉ መጻተኛውም ሆነ ተወላጁ፣
ሽማግሌዎቻቸውም ሆኑ ሹማምንታቸው እን
ዲሁም ዳኞቻቸው የእግዚአብሔርን የቃል
ኪዳን ታቦት ወደ ተሸከሙት ሌዋውያን

8፥22 ዘጸ7፥2፤ ኢሱ10፥1
8፥23 1ሳሙ15፥8
8፥25 ዘዳ20፥16-18
8፥26 ቍ18፤ ዘፀ17፥12፤ዘኍ21፥2
8፥27 ቍ2
8፥28 ዘፍ35፥20፤ ዘኍ31፥10፤ዘዳ13፥16፤ ኢሱ7፥2፤10፥1፤ኤር 49፥3
8፥29 ዘዳ21፥23፤ 2ሳሙ18፥17፤ዮሐ 19፥31
8፥30 ቍ33፤ዘፀ 20፥24፤ዘዳ11፥29
8፥31 ዘፀ20፥25፤ ዘዳ27፥6-7
8፥32 ዘዳ27፥8
8፥33 ዘሌ16፥29፤ ዘዳ፤11፥29፤31፥12 ዮሐ4፥20
8፥34 ዘዳ28፥61፤ 31፥11
8፥35 ዘፀ12፥38፤ ዘዳ31፥12
9፥1 ቍ7፤ዘፍ13፥7፤ ዘኍ13፥17፤34፥6፤ዘዳ 3፥25፤ኢሱ3፥10፤ 11፥19
9፥3 ቍ17፤ዘፍ12፥ 8፤ኢሱ8፥1፤10፥10፤ 11፥19፤18፥25፤21፥17 ፤2ሳሙ2፥12፤5፥25፤2 0፥8፤1ነገ3፥4፤9፥2 1ዜና8፥29፤14፥16፤16 ፥39፤21፥29፤2ዜና1፥3፤ ነህ3፥7፤ኢሳ28፥ 21፤ኤር28፥1፤41፥12
9፥6 ቍ22፤ዘፍ26፥ 28፤ዘዳ11፥30
9፥7 ቍ1፤ዘፀ23፥ 32፤1ነገ5፥12
9፥8 2ነገ10፥5
9፥9 ቍ24፤ዘዳ20፥ 15፤ዘኍ23፥22

ካህናት ፊታቸውን አዙረው፣ በታቦቱ ግራና
ቀኝ ቆመው ነበር። የእግዚአብሔር ባሪያ
ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ እንዲባርኩ
መመሪያ በሰጠ ጊዜ፣ አስቀድሞ ባዘዘው
መሠረት፣ ግማሹ ሕዝብ በገሪዛን ተራራ፣
ግማሹ ደግሞ በጌባል ተራራ ፊት ለፊት
ቆመ።

34ከዚህ በኋላ ኢያሱ፣ የሕጉን ቃላት
በሙሉ ማለትም በረከቱንና መርገሙን ሁሉ፣
ልክ በሕጉ መጽሐፍ እንደተጻፈው አነበበ።
35ኢያሱ በመላው የእስራኤል ጉባኤ ፊት
ሴቶች፣ ሕፃናትና በመካከላቸው የኖሩ
መጻተኞች ባሉበት ያነበበው፣ አንድም
ሳይቀር ሙሴ ያዘዘውን ቃል ሙሉ በሙሉ
ነበር።

## የገባዖን ሰዎች የፈጸሙት ማታለል

9 በዮርዳኖስ ምዕራብ ባለው በተራራ
ማው አገር፣ በቈላማው ምድር እንዲ
ሁም እስከ ሊባኖስ በሚደርሰው በመላው
በታላቁ ባሕር[ሐ] ዳርቻ የነበሩት የኬጢ
ያውያን፣ የአሞራው ያን፣ የከነዓናውያን፣
የፌርዛውያን፣ የኤዊያውያን፣ የኢያቡሳውያን
ነገሥታት ይህን በሰሙ ጊዜ፣ 2ኢያሱንና
እስራኤልን ለመውጋት በአንድነት መጡ።

3የገባዖን ሰዎች ግን ኢያሱ በኢ
ያሪኮና በጋይ ላይ ያደረገውን በሰሙ ጊዜ፣
4ለማታለል ፈለጉ፤ ስለዚህም ያረጀ ስል
ቻና የተጣፈ አሮጌ የወይን ጠጅ አቍማዳ
በአህያ የጫኑ[መ] መልእክተኛ መስለው
ሄዱ። 5ሰዎቹም ያረጀና የተጠጋገነ ነጠላ
ጫማ አድርገዋል፤ አሮጌ ልብስ ለብሰዋል፤
ለስንቅ የያዙት እንጀራም በሙሉ የደ
ረቀና የሻገተ ነበር። 6ከዚያም ኢያሱ ወደ
ሰፈረበት ወደ ጌልገላ ሄደው ኢያሱንና የእስ
ራኤልን ሰዎች፣ "የመጣነው ከሩቅ አገር
ነው፤ ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን ግቡ"
አሏቸው።

7የእስራኤልም ሰዎች ለኤዊያውያኑ፣ "እናንተ
የምትኖሩት እዚሁ ቅርብ ቢሆንስ? ታዲያ
ከእናንተ ጋር እንዴት ቃል ኪዳን እንገባ
ለን?" አሏቸው።

8እነርሱም ኢያሱን፣ "እኛ ባሪያዎችህ ነን"
አሉት።

ኢያሱ ግን፣ "እናንተ እነማን ናችሁ?
የመጣችሁትስ ከየት ነው?" ሲል ጠየቃቸው።

9እነርሱም እንዲህ ብለው መለሱለት፤ "እኛ

[ሀ]26 የዕብራይስጡ ቃል አንድን ሰው ወይም ነገር ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት ነው። [ለ]31 በትውፊት የሰላም መሥዋዕት ይባላል። [ሐ]1 የሜድትራኒያን ባሕር ነው። [መ]4 አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጂዎች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ነገር ግን አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጂዎች፣ የቩልጌት፣ የሱርስቱ ትርጒም እንዲሁም የሰብዓ ሊቃ ናት ቅጂ፣ "የሚያስፈልጋቸውን ነገር አዘጋጁ፤ በአህዮቻቸውም ላይ ጫኑ" ይላሉ።

ባሪያዎችህ የአምላካህን *የእግዚአብሔርን*
ዝና ሰምተን፣ እጅግ ሩቅ ከሆነ አገር
መጥተናል፤ ዝናውንና በግብፅ ያደረገውንም
ሁሉ ሰምተናል፤ 10እንዲሁም ከዮርዳኖስ
ማዶ ባሉት በሁለቱ የአሞራውያን ነገሥ
ታት ማለትም በሐሴቦን ንጉሥ በሴዎን፣
አስታሮትን ይገዛ በነበረው በባሳን ንጉሥ
በዐግ ያደረገውን ሁሉ ነው። 11ሽማግሌ
ዎቻችንና በአገራችን የሚኖሩት ሁሉ፣
'ለመንገዳችሁ የሚሆን ስንቅ ያዙ፤ ሄዳች
ሁም ተገናኟቸው፤ እኛ ባሮቻችሁ እንሆና
ለን፤ ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን ግቡ በሉአ
ቸው' አሉን። 12ይህ የያዝነው እንጀራ
ወደ እናንተ ለመምጣት ከቤታችን በተነሣ
ንበት ቀን ትኩስ ነበር፤ አሁን ግን እን
ዴት እንደ ደረቀና እንደ ሻገተ ተመል
ከቱ። 13እነዚህ የወይን ጠጅ አቍማዳዎቻ
ችን ያን ጊዜ ስንሞላቸው አዲስ ነበሩ፤
አሁን ግን እንዴት እንደተቀዳደዱ ተመ
ልከቱ፤ ልብሳችንና ጫማችንም ብዙ መን
ገድ በመጓዛችን አልቀዋል።"

14የእስራኤልም ሰዎች ከስንቃቸው ላይ
ጥቂት ወሰዱ፤ ስለ ጕዳዩ ግን *እግዚአብሔ
ርን* አልጠየቁም ነበር። 15ኢያሱም በሰላም
ለመኖር የሚያስችላቸውን ቃል ኪዳን
ከእነርሱ ጋር አደረገ፤ የጉባኤውም መሪዎች
ይህንኑ በመሐላ አጸኑላቸው።

16እስራኤላውያን ከገባዖን ሰዎች ጋር ቃል
ኪዳኑን ካደረጉ ከሦስት ቀን በኋላ፣ ሰዎቹ
እዚያው አጠገባቸው የሚኖሩ ጎረቤቶቻቸው
መሆናቸውን ሰሙ። 17ስለዚህ እስራኤላው
ያን ተጕዘው በሦስተኛው ቀን ገባዖን፣ ከፊራ፣
ብኤሮትና ቂርያትይዓይሪም ወደ ተባሉት
የገባዖን ሰዎች ወደሚኖሩባቸው ከተሞች
መጡ። 18ሆኖም እስራኤላውያን አልወጓቸ
ውም፤ የጉባዔው መሪዎች በእስራኤል
አምላክ *በእግዚአብሔር* ስም ምለውላቸው
ነበርና። ማኅበሩም ሁሉ በመሪዎቹ ላይ
አጕረመረመ፤ 19ነገር ግን መሪዎቹ ሁሉ ለማ
ኅበሩ እንዲህ ሲሉ መለሱ፤ "በእስራኤል
አምላክ *በእግዚአብሔር* ስም ስለ
ማልንላቸው፣ አሁን ጕዳት ልናደርስባቸው
አንችልም፤ 20እንዲህ እናደርግላቸዋለን፤
የገባንላቸውን መሐላ በማፍረስ ቍጣ
እንዳይደርስብን፣ በሕይወት እንዲኖሩ እንዲ
ሁ እንተዋቸዋለን፤ 21ነገር ግን ለማኅበረ
ሰቡ በሙሉ ዕንጨት እየቈረጡ ውሃ
እየቀዱ ይኑሩ።" ስለዚህ መሪዎቹ
የገቡላቸው ቃል ተጠበቀ።

22ከዚያም ኢያሱ የገባዖንን ሰዎች ጠርቶ
እንዲህ አላቸው፤ "እዚሁ አጠገባችን መኖ
ራችሁ የታወቀ ሆኖ ሳለ፣ 'የምንኖረው ከእ
ናንተ በራቀ ስፍራ ነው' ብላችሁ ያታለላችሁን
ለምንድን ነው? 23ስለዚህ አሁን የተረገማችሁ
ናችሁ፤ ጥቂቶቻችሁም ለአምላኬ ቤት ምን
ጊዜም ዕንጨት ቈራጭ፣ ውሃ ቀጂ
ባሮች ትሆናላችሁ።"

24እነርሱም ለኢያሱ እንዲህ ብለው
መለሱለት፤ "አምላክህ *እግዚአብሔር* ባሪያ
ውን ሙሴን እንዳዘዘው፣ ምድሪቱን በሙሉ
ለእናንተ እንደሚሰጣችሁና ነዋሪዎቿንም
ከፊታችሁ እንደሚያጠፋቸው በእርግጥ
ለእኛ ለባሪያዎችህ ተነግሮናል፤ ስለዚህ
ከእናንተ የተነሣ ለሕይወታችን በመሥ
ጋት ይህን አድርገናል። 25እነሆ፤ አሁን
በእጅህ ውስጥ ነን፤ በጎና ትክክል መስሎ
የታየህን ነገር ሁሉ አድርግብን።"

26ስለዚህ ኢያሱ የገባዖንን ሰዎች ከእስራ
ኤላውያን እጅ አዳናቸው፤ እነርሱም አል
ገደሏቸውም። 27በዚያችም ዕለት ኢያሱ የገባዖንን
ሰዎች ለማኅበረ ሰቡና *እግዚአብሔር* በሚመ
ርጠው ስፍራ ለሚቆመው *የእግዚአብሔር*
ለሆነው መሠዊያ እስከ ዛሬ ድረስ ዕን
ጨት ቈራጮችና ውሃ ቀጂዎች አደረ
ጋቸው።

## ፀሓይ ቆመች

10 የኢየሩሳሌም ንጉሥ አዶኒጼዴቅ፣
ኢያሱ ጋይን ይዞ እንደ ደመሰሳት[ገ1]፣
እንደዚሁም በኢያሪኮና በንጉሥዋ ላይ
ያደረገውን ሁሉ፣ በጋይና በንጉሥዋ ላይ
ማድረጉን፣ የገባዖን ሰዎችም ከእስራኤል
ጋር የሰላም ውል አድርገው በአጠገባቸው
መኖራቸውን ሰማ፤ 2በዚህም እርሱና ሕዝቡ
ደነገጡ፤ ምክንያቱም ገባዖን እንደ ነገሥ
ታቱ ከተማ ሁሉ ታላቅ ከተማ፣ በስፋ
ቷም ከጋይ የምትበልጥ፣ ሰዎቿም ብርቱ
ተዋጊዎች ነበሩ። 3ስለዚህ የኢየሩሳሌም
ንጉሥ አዶኒጼዴቅ፣ ሆሃም ወደ ተባለው
የኬብሮን ንጉሥ ጲርአም ወደ ተባለው
የየርሙት ንጉሥ፣ ያፊዓ ወደ ተባለው
የለኪሶ ንጉሥና ዳቤር ወደተባለው የዔግ
ሎን ንጉሥ በመላክ፣ 4"ወደዚህ ወጥታችሁ
አግዙኝ፤ ከኢያሱና ከእስራኤላውያን ጋር
ሰላምን መሥርታለችና ገባዖንን እንምታ"
አላቸው።

5ከዚያም አምስቱ የአሞራውያን ነገሥ
ታት ማለት የኢየሩሳሌም ንጉሥ፣ የኬብሮን
ንጉሥ፣ የያርሙት ንጉሥ፣ የለኪሶ
ንጉሥና የዔግሎን ንጉሥ ያላቸውን አስተ
ባብረው፣ ሰራዊታቸውንም ሁሉ ይዘው በመ
ውጣት ገባዖንን ወጓት።

6የገባዖንም ሰዎች በጌልገላ ወደ ሰፈረው

9፥10 ዘኍ21፥24፡25፡33፡35፤21፥24፡35፤ኢሱ2፥10
9፥14 ዘፀ16፥28፤ዘኍ27፥21
9፥15 ቍ3፡7፡21፤ኢሱ10፥1፡4፤11፥19፤መሳ1፥21፤2ሳሙ21፥2፤24፥1፤መዝ106፥34
9፥16 ቍ22
9፥17 ኢሱ15፥9፡60፤18፥14፡15፡25፤መሳ18፥12፤1ሳሙ6፥21፤7፥2፤2ሳሙ4፥2፤23፥37፤መዝ132፥6፤ኤር26፥20
9፥18 ቍ15፤ዘፀ15፥24፤መሳ21፥1፡7፡18፤1ሳሙ20፥17፤መዝ15፥4
9፥20 ዘፍ24፥8
9፥21 ቍ15፤ዘዳ29፥11
9፥22 ቍ6፡16
9፥23 ዘፍ9፥25
9፥24 ቍ9
9፥25 ዘፍ16፥6፤ኤር26፥14
9፥27 ዘፀ1፥11፤ዘዳ12፥5፤29፥11
10፥1 ቍ3፤ዘዳ20፥16፤ኢሱ8፥1፡22፤9፥3፡15፤12፥10፤15፥8፡63፤18፥28፤መሳ1፥7
10፥3 ቍ5፡23፡31፡34፡36፡38፤ዘፍ13፥18፤ኢሱ11፥21፤12፥11-13፤13፡26፤15፥7፡35፡39፡49፤21፥15፡29፤መሳ1፥11፤2ነገ14፥19፤1ዜና6፥58፤2ዜና11፥9፤25፥27፤32፥9፤ነህ11፥29፡30፤ኢሳ36፥2፤37፥8፤ኤር34፥7፤ሚክ1፥13፤9፥3፡15፤12፥10፤15፥8፡63፤18፥28፤መሳ1፥7፤
10፥4 ኢሱ9፥15
10፥5 ቍ16፤ዘኍ13፥29፤ዘዳ1፥7
10፥6 ዘዳ11፥30

[ገ1] የዕብራይስጡ ቃል በዚህም ሆነ በቍጥር 28፡35፡37፡39 እና 40 ላይ ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት ነው።

ወደ ኢያሱ፣ “በተራራማው አገር የሚ
ኖሩ የአሞራውያን ነገሥታት ኀይላቸውን
አስተባብረው ተሰልፈውብናል፤ እኛን ባሮ
ችህን አትተወን፤ ርዳን፤ ፈጥነህ በመድረስም
አድነን” ሲሉ ላኩበት።
7ስለዚህ ኢያሱ ምርጥ የሆኑትን ተዋጊ
ዎች ሁሉ ጨምሮ ሰራዊቱን በሙሉ ይዞ
ከጌልገላ ወጣ። 8*እግዚአብሔርም* ኢያ
ሱን፣ “አትፍራቸው፤ ሁሉንም አሳልፌ
በእጅህ ሰጥቻቸዋለሁ፤ አንዳቸውም እንኳ
ሊቋቋሙህ አይችሉም” አለው።
9ኢያሱ ከጌልገላ ሌሊቱን ሁሉ ሲገሠግሥ
አድሮ ድንገት ወረራቸው። 10*እግዚአብሔርም*
የአሞራውያንን ነገሥታት በእስራኤል
ፊት አሸበራቸው፤ በገባዖን እጅግ መታቸው፤
ወደ ቤትሖሮን በሚያስወጣውም መንገድ
ሽቅብ ተከተላቸው፤ እስከ ዓዜቅና እስከ
መቄዳም ድረስ አሳድዶ መታቸው።
11ከቤትሖሮን ወደ ዓዜቃ ቍልቍል በሚ
ወስደው መንገድ ላይ፣ ከእስራኤላውያን
ፊት በሚሸሹበት ጊዜ፣ *እግዚአብሔር* ከሰ
ማይ ትልልቅ የበረዶ ድንጋይ አወረደባ
ቸው፤ በእስራኤላውያን ሰይፍ ካለቁት
ይልቅ በወረደው የበረዶ ድንጋይ ያለቁት
በልጠው ተገኙ።
12*እግዚአብሔር* አሞራውያንን ለእስራኤል
አሳልፎ በሰጠባት ዕለት፣ ኢያሱ *እግዚአ
ብሔርን* በእስራኤል ፊት እንዲህ አለው፤

“ፀሓይ ሆይ፤ በገባዖን ላይ ቁሚ፤
ጨረቃም ሆይ፤ በኤሎን ሸለቆ ላይ ቀጥ
በዪ፤
13ስለዚህ ሕዝቡ ጠላቶቹን እስኪበቀል
ድረስ[ጣ]፣
ፀሓይ ባለችበት ቆመች፤
ጨረቃም አልተንቀሳቀሰችም።
ይህም በያሻር መጽሐፍ ተጽፎ ይገኛል።
ፀሓይ በሰማዩ መካከል ቆመች፤ ለመጥለ
ቅም ሙሉ ቀን ፈጀባት። 14*እግዚአብሔር*
የሰውን ቃል የሰማበት እንደዚያ ያለ ዕለት
ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ አልነበረም፤
*እግዚአብሔር* ለእስራኤል ተዋግቶ ነበርና።
15ከዚያም ኢያሱ ከመላው እስራኤል ጋር
ጌልገላ ወዳለው ሰፈር ተመለሰ።

## አምስቱ የአሞራውያን ነገሥታት ተገደሉ

16በዚህ ጊዜ አምስቱ የአሞራውያን
ነገሥታት ሸሽተው በመቄዳ ዋሻ ተደብቀው
ነበር። 17ኢያሱም አምስቱ ነገሥታት በመ
ቄዳ ዋሻ ውስጥ ተደብቀው መገኘታቸውን
ሰማ፣ 18እንዲህም አለ፤ “ትልልቅ ድንጋዮች
ወደ ዋሻው አፍ አንከባሉ፤ ጠባቂ ሰዎችንም
በዚያ አቁሙ፤ 19ጠላቶቻችሁን አሳዱአቸው

10÷7 ኢሱ8÷1
10÷8 ዘዳ3÷2፤7÷24፤ኢሱ1÷9፤2÷24
10÷10 ቍ16፥17፥21፤ዘፀ14÷24፤ዘዳ7÷23፤ኢሱ9÷3፤12÷16፤15÷35፥41፤16÷3፥5፤18÷13፥14፤21÷22፤1ሳሙ13÷18፤17÷1፤1ነገ9÷17፤1ዜና6÷68፤7÷24፤2ዜና8÷5፤11÷9፤25÷13፤ነህ11÷30፤ኤር34÷7
10÷11 ዘፀ9÷18፤መሳ5÷20፤መዝ18÷12፤ኢሳ28÷2፥17፤32÷19፤ሕዝ13÷11፥13
10÷12 ኢሱ19÷42፤21÷24፤መሳ1÷35፤12÷12፤1ሳሙ14÷31፤1ዜና 6÷69፤8÷13፤2ዜና11÷10፤28÷18፤አሞ2÷9፤
10÷13 2ሳሙ1÷18፤ኢሳ38÷8፤ዕን3÷11
10÷14 ቍ42፤ዘፀ14÷14፤መዝ106÷43፤136÷24፤ኢሳ63÷10፤ኤር21÷5
10÷15 ቍ43
10÷16 መዝ68÷12
10÷20 ዘዳ20÷16፤2ዜና11÷10፤ኤር4÷5፤5÷17፤8÷14፤35÷11
10÷24 ዘዳ7÷24፤2ሳሙ22÷40፤መዝ110÷1፤ኢሳ51÷23፤ሚል4÷3
10÷25 ዘዳ31÷6
10÷27 ዘፍ35÷20፤ዘዳ21÷23
10÷28 ቍ30፥32፥35፥39፤ዘዳ20÷16፤ኢሱ6÷21
10÷29 ዘኍ33÷20

እንጂ ችላ አትበሉ፤ ከበስተ ኋላ ሆናችሁም
አደጋ ጣሉባቸው፤ ወደ ከተሞቻቸው
እንዳይገቡ ከልክሏቸው፤ እነሆ፤ *እግዚ
አብሔር* አምላካችሁ በእጃችሁ አሳልፎ
ሰጥቶአቸዋልና።”
20ስለዚህ ኢያሱና እስራኤላውያን እስከ
መጨረሻው ደመሰሷቸው፤ የተረፉት ጥቂ
ቶቹ ግን ወደ ተመሸጉት ከተሞቻቸው
ለመድረስ ቻሉ። 21ከዚያም ሰራዊቱ ሁሉ
በደኅና ተመልሶ፣ ኢያሱ ወደ ሰፈረበት
ወደ መቄዳ መጣ፤ በእስራኤላውያንም
ላይ አንዲት ቃል የተናገረ ሰው አልነ
በረም።
22ኢያሱም፤ “ዋሻውን ከፍታችሁ እነዚ
ያን አምስቱን ነገሥታት አውጥታችሁ
አምጡልኝ” አላቸው። 23እነርሱም አምስቱን
ነገሥታት ማለትም የኢየሩሳሌምን ንጉሥ፣
የኬብሮንን ንጉሥ፣ የያርሙትን ንጉሥ፣
የለኪሶን ንጉሥ የዔግሎንን ንጉሥ አውጥ
ተው አመጡለት። 24እነዚህን ነገሥታት
ባመጡለትም ጊዜ፣ ኢያሱ መላውን የእስ
ራኤልን ወንዶች ከጠራ በኋላ አብረውት
የመጡትን የጦር አዛዦች፣ “ወደዚህ
ቅረቡና እግሮቻችሁን በእነዚህ ነገሥታት
አንገት ላይ አድርጉ” አላቸው፤ እነርሱም
ወደ ፊት ቀርበው እግራቸውን በነገሥታቱ
አንገት ላይ አሳረፉ።
25ኢያሱም፣ “አትፍሩ፤ አትደንግጡ፤ በርቱ፤
ጽኑ፤ እንግዲህ በምትወጓቸው ጠላቶች
ሁሉ ላይ *እግዚአብሔር* እንደዚሁ ያደርጋ
ልና” አላቸው። 26ከዚያም ኢያሱ ነገሥታ
ቱን መትቶ ገደላቸው፤ በአምስትም ዛፎች
ላይ ሰቀላቸው፤ ሬሳቸውም እስኪመሽ
ድረስ አልወረደም ነበር።
27ፀሓይ ለመጥለቅ በማዘቅዘቅ ላይ
ሳለች ኢያሱ ትእዛዝ ሰጠ፤ ከዚያም የነገ
ሥታቱን ሬሳ ከዛፎቹ ላይ አውርደው
ቀድሞ ተደብቀው ወደነበሩበት ዋሻ ውስጥ
ጣሏቸው። በዋሻውም አፍ ትልልቅ ድንጋ
ዮች አኖሩ፤ ድንጋዮቹም እስከ ዛሬ ድረስ
በዚያ ይገኛሉ።
28በዚያች ዕለት ኢያሱ መቄዳን ያዘ፤
ከተማዪቱንና ንጉሥዋንም በሰይፍ ስለት
መታ፤ አንድም ሰው ሳያስቀር በውስጧ
ያለውን ሁሉ ፈጽሞ ደመሰሰ፤ በኢያሪኮ
ንጉሥ ላይ ያደረገውንም ሁሉ፣ በመቄዳ
ንጉሥ ላይ አደረገ።

## የደቡብ ከተሞች መያዝ

29ከዚያም ኢያሱና ከእርሱ ጋር የነበሩት
እስራኤላውያን በሙሉ ከመቄዳ ወደ ልብና
አለፉ፤ ወጓትም። 30እንዲሁም እግዚአብሔር

[ጣ]13 ወይም “ሕዝቡ እስኪያሸንፍ ድረስ”

ከተማዪቱንና ንጉሥዋን በእስራኤል እጅ
አሳልፎ ሰጣቸው፤ ኢያሱ ከተማዪቱንና
በውስጧ ያለውን ሁሉ በሰይፍ ስለት አጠፋ፤
አንድም ሰው አላስተረፈም፤ በኢያሪኮ ንጉሥ
ላይ ያደረገውንም በልብና ንጉሥ ላይ ደገ
መው።

31ከዚያም ኢያሱና ከእርሱ ጋር የነበሩት
እስራኤላውያን በሙሉ ከልብና ወደ ለኪሶ
አለፉ፤ ወጓትም። 32እግዚአብሔር ለኪሶን
አሳልፎ ለእስራኤል ሰጠ፤ ኢያሱም በሁለ
ተኛው ቀን ያዛት፤ በልብና እንዳደረገው
ሁሉ እዚህም ከተማዪቱንና በውስጧ ያሉ
ትን ሁሉ በሰይፍ ስለት ፈጃቸው። 33በዚህ
ጊዜ የጌዝር ንጉሥ ሆራም ለኪሶን ለመር
ዳት መጣ፤ ኢያሱ ግን አንድ እንኳ ሳያስ
ተርፍ ንጉሡንና ሕዝቡን መታቸው።

34ከዚያም ኢያሱና ከእርሱ ጋር የነበሩት
እስራኤላውያን በሙሉ ከለኪሶ ወደ ዔግ
ሎን አለፉ፤ ወጓትም። 35በዚያኑ ዕለት
ያዟት፤ በሰይፍም ስለት አጠፏት፤ በለኪሶ
እንዳደረጉት ሁሉ እዚህም በውስጧ የሚገ
ኙትን ፈጽመው ደመሰሷቸው።

36ከዚያም ኢያሱና ከእርሱ ጋር የነበሩት
እስራኤላውያን በሙሉ ከዔግሎን ወደ
ኬብሮን ወጡ፤ ወጓትም። 37ከተማዪቱንም
ከንጉሥዋ፣ ከመንደሮቿና በውስጧ ካሉት
ጋር ሁሉ አንድም ሰው ሳያስቀሩ በሰይፍ
ስለት ፈጇቸው፤ በዔግሎን እንዳደረጉት
ሁሉ እዚህም ከተማዪቱንና በውስጧ
ያለውን ሁሉ ፈጽመው ደመሰሱ።

38ከዚያም ኢያሱና ከእርሱ ጋር የነበሩት
እስራኤላውያን በሙሉ ወደ ኋላ ተመል
ሰው ዳቤርን ወጓት። 39ከተማዪቱን፣ ንጉ
ሥዋንና መንደሮቿን ይዘው በሰይፍ ስለት
ፈጇቸው፤ በውስጧ ያለውንም ሁሉ
አንድም ሳያስቀሩ ደመሰሱ፤ በልብናና
በንጉሥዋ እንዲሁም በኬብሮን ያደረጉትን
ሁሉ እዚህም በዳቤርና በንጉሥዋ ላይ
ደገሙት።

40በዚህ ሁኔታም ኢያሱ ተራራማውን አገር
ኔጌብን፣ የምዕራቡን ቈላና የተራራውን
ሽንተረሮች ጨምሮ ምድሪቱን በሙሉ
ከነገሥታቷ ጋር ያዘ፤ የእስራኤል አምላክ
እግዚአብሔር ባዘዘውም መሠረት፣ እስት
ንፋስ ያላቸውን ሁሉ ፈጽሞ ደመሰሰ፤
ማንንም በሕይወት አላስቀረም፤ 41ኢያሱም
ከቃዴስ በርኔ እስከ ጋዛ እንዲሁም
የጎሶምን ምድር ሁሉ እስከ ገባዖን ድረስ
በሙሉ ያዘ። 42ኢያሱ እነዚህን ሁሉ ነገሥታ
ትና ምድራቸውን ያሸነፈው በአንድ ዘመቻ
ብቻ ነበር፤ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር
ለእስራኤላው ያን ተዋግቶላቸዋልና።

43ከዚህ በኋላ ኢያሱ ከመላው እስራኤላው
ያን ጋር ጌልገላ ወዳለው ሰፈር ተመለሰ።

## የሰሜን ነገሥታት ድል መሆን

11 የአሦር ንጉሥ ኢያቢስ ይህን በሰማ
ጊዜ፣ ወደ ማዶን ንጉሥ፣ ወደ
ዮባብ ንጉሥ፣ ወደ ሺምሮን ንጉሥ፣ ወደ
አዚፍ ንጉሥ ላከ፤ 2እንዲሁም በተራራማው
አገር ከኪኔሬት ደቡብ በዓረባ፣ በምዕራቡ
ቈላ አገርና ከዶር ኰረብታ[ጨ] በስተ ምዕራብ
ወዳሉት ነገሥታት ላከ፤ 3ደግሞም በምሥ
ራቅና በምዕራብ ወደሚገኙት ወደ ከነዓ
ናውያን፣ ወደ አሞራውያን፣ ወደ ኬጢ
ያውያን፣ ወደ ፌርዛውያንና በኰረብታ
ማው አገር ወደሚኖሩት ወደ ኢያቡሳው
ያን፣ እንዲሁም ደግሞ በምጽጳ ምድር
በአርሞንዔም ተራራ ግርጌ ወዳሉት ወደ
ኤዊያውያን ነገሥታት መልእክት ላከ።
4እነዚህም ሰራዊታቸውን ሁሉ እጅግ ብዙ
ከሆኑ ፈረሶችና ሠረገሎች ጋር ይዘው
ወጡ፤ የሰራዊቱም ብዛት በባሕር ዳር እን
ዳለ አሸዋ ነበር። 5እነዚህ ሁሉ ነገሥታት
እስራኤልን ለመውጋት ኀይላቸውን አስተ
ባብረው በማሮን ውሃ አጠገብ በአንድ
ነት ሰፈሩ።

6እግዚአብሔር ኢያሱን፣ "እነዚህን ሁሉ
ነገ በዚች ሰዓት እንደ ሙት አድርጌ፣
በእስራኤል እጅ አሳልፌ ስለምሰጣቸው
አትፍራቸው፤ የፈረሶቻቸውን ቋንጃ ትቈ
ርጣለህ፤ ሠረገሎቻቸውንም ታቃጥላለህ"
አለው።

7ስለዚህ ኢያሱና ሰራዊቱ ሁሉ በድንገት
ወደ ማሮን ውሃ መጥተው ወጓቸው። 8እግዚ
አብሔርም በእስራኤል እጅ አሳልፎ ስለ
ሰጣቸው ድል አደረጓቸው፤ በታላቂቱ ሲዶና
መንገድ መጨረሻ እስከ ማስሮን፣ በስተ
ምሥራቅም እስከ ምጽጳ ሸለቆ ድረስ አሳደ
ዷቸው፤ ከእነርሱም በሕይወት የተረፈ አን
ድም ሰው አልነበረም። 9ኢያሱ እግዚአብሔር
ባዘዘው መሠረት የፈረሶቻቸውን ቋንጃ
ቈረጠ፤ ሠረገሎቻቸውንም አቃጠለ።

10በዚያን ጊዜም ኢያሱ ወደ ኋላ ተመ
ልሶ አጾርን ያዘ፤ ንጉሥዋንም በሰይፍ ገደ
ለው፤ አጾርም ቀድሞ በእነዚህ ሁሉ
መንግሥታት ላይ የበላይነት ነበራት።
11በውስጧ ያሉትን ሁሉ በሰይፍ ስለት
ገደሉ፤ እስትንፋስ ካለው ፍጡር አንድ
እንኳ ሳያስቀሩ ሁሉንም ደመሰሱ[ጸ]፤ ራሷን
አሦርንም በእሳት አቃጠሏት።

12ኢያሱ እነዚህን የነገሥታት ከተሞች
በሙሉና ነገሥታታቸውን ሁሉ ያዘ፤ በሰይ

10፥31 ቍ3
10፥33 ኢሱ12፥12፤16፥3፡10፤21፥21፤መሳ1፥29፤2ሳሙ5፥25፤1ነገ9፥15፤1ዜና6፥67
10፥34 ቍ3
10፥36 ዘፍ13፥18፤ኢሱ14፥13፤15፥13፤20፥7፤21፥11፤መሳ16፥3
10፥37 ቍ28
10፥38 ቍ3
10፥39 ቍ28
10፥40 ዘፍ12፥9፤ዘዳ1፥7፤7፥24፤20፥16-17፤ኢሱ12፥8፤15፥19፡21፤18፥25፤19፥8፤1ሳሙ30፥27
10፥41 ዘፍ14፥7፤10፥19፤ኢሱ11፥16፤15፥51
10፥42 ቍ14
10፥43 ቍ15፤ኢሱ5፥9፤1ሳሙ7፥16፤10፥8፤11፥14፤13፥12
11፥1 ቍ10፤ኢሱ12፥19፡20፤15፥23፡25፤19፥15፡25፡36፤መሳ4፥2፡7፡17፡23፤1ሳሙ12፥9፤1ነገ4፥15፤2ነገ15፥29፤ነህ11፥33፤መዝ83፥9፤ኤር49፥28፡33
11፥2 ቍ16፤ዘኍ34፥11፤ዘዳ1፥1፤3፥17፤ኢሱ12፥1፡23፤17፥11፤18፥18፤19፥35፤መሳ1፥27፤1ነገ15፥20፤4፥11፤1ዜና7፥29
11፥3 ኢሱ3፥10፤ዘኍ13፥17፤ዘፀ3፥8፤ዘዳ7፥1፤መሳ3፥3፡5፤1ነገ9፥20፤ዘዳ3፥8፤ቍ8፤ዘፍ31፥49፤ኢሱ15፥38፤18፥26፤መሳ11፥11፤20፥1፤21፥1፤1ሳሙ7፥5፡6፤1ነገ15፥22፤2ነገ25፥23
11፥4 ዘፍ12፥2፤ መሳ7፥12፤1ሳሙ13፥5
11፥5 ቍ7፤መሳ5፥19
11፥6 ቍ9፤ዘፍ49፥6፤ኢሱ2፥24
11፥8 ዘፍ10፥15፤ኢሱ13፥6፤መሳ18፥7
11፥10 ኢሳ3፥25፤ኤር41፥2፤44፥18
11፥11 ዘኍ31፥10፤ዘዳ7፥2፤20፥16-17
11፥12 ዘኍ33፥50-52፤ዘዳ7፥2

ጨ2 ወይም "ከዶር ከፍታማ ስፍራ"
ጸ11 የዕብራይስጡ ቃል በዚህም ሆነ በቍጥር 12፡20 እና 21 ላይ አንድን ሰው ወይም ነገር ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት ነው።

ፍም ስለት ፈጃቸው፤ የእግዚአብሔር ባሪያ
ሙሴ ባዘዘውም መሠረት ፈጽሞ ደመሰሳ
ቸው። 13ያም ሆኖ ግን ኢያሱ ካቃጠላት
ከአጾር በስተቀር፣ እስራኤላውያን በየተራ
ራው ላይ ያሉትን ከተሞች አላቃጠሉም
ነበር። 14እስራኤላውያን ምርኮውን በሙሉ፣
ከእነዚህም ከተሞች የተገኙትን እንስሳት
ለራሳቸው ወሰዱ፤ ሕዝቡን ግን በሙሉ
በሰይፍ ስለት ፈጁት፤ እስትንፋስ ካለው
ፍጡር አንድም ሳያስቀሩ ፈጽመው ደመ
ሰሱት። 15እግዚአብሔር ባሪያውን ሙሴን
እንዳዘዘው ሁሉ፣ ሙሴም ኢያሱን አዘ
ዘው፤ ኢያሱም እንዲሁ አደረገ፤ እግዚ
አብሔር ሙሴን ካዘዘው ሁሉ እርሱ ያልፈ
ጸመው አንዳች ነገር አልነበረም።

16ኢያሱ ያንን ምድር በሙሉ ማለት ተራ
ራማውን አገር፣ ኔጌብን ሁሉ፣ የጎሶምን
ምድር በሙሉ፣ የምዕራቡን ቈላ፣ ዓረባን
እንዲሁም የእስራኤልን አገር ደጋውንና
ቈላውን ጠቅልሎ ያዘ፤ 17እንዲሁም እስከ
ሴይር በሚደርሰው ከሐላቅ ተራራ አን
ሥቶ ከአርሞንዔም ተራራ በታች በሊባ
ኖስ ሸለቆ ውስጥ እስካለው እስከ በኣል
ጋድ ድረስ ያለውን ምድር በሙሉ ያዘ፤
ነገሥታታቸውንም ሁሉ ያዘ፤ መትቶም
ገደላቸው። 18ኢያሱ ከእነዚህ ነገሥታት
ጋር ብዙ ዘመን የፈጀ ጦርነት አደረገ።
19በገባዖን ከሚኖሩ ከኤዊያውያን በስተ
ቀር፣ ከእስራኤላውያን ጋር የሰላም ውል
ያደረገ አንድም ከተማ አልነበረም፤ ሁሉ
ንም የያዙት በጦርነት ነው። 20እግዚአ
ብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት፣ ያለ አን
ዳች ርኅራኄ ፈጽሞ ይደመስሳቸው ዘንድ
እስራኤልን እንዲወጉ ልባቸውን ያደነደ
ነው ራሱ እግዚአብሔር ነውና።

21በዚያን ጊዜ ኢያሱ ሄዶ በተራራማው
አገር ማለት በኬብሮን፣ በዳቤርና በአናብ
እንዲሁም በመላው የይሁዳና የእስራኤል
ተራራማ አገሮች ያሉትን የዔናቅን ዘሮች
ከነከተሞቻቸው በሙሉ ደመሰሳቸው፤
22ከእነዚህም ጥቂቶቹ ብቻ በጋዛ፣ በጌትና
በአሽዶድ ሲቀሩ፣ በእስራኤል የቀሩ የዔ
ናቅ ዘሮች ግን አልነበሩም። 23ስለዚህ ኢያሱ
እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት ምድ
ሪቱን በሙሉ ያዘ፤ እንደ ነገዳቸው አከፋ
ፈል በመመደብም ርስት አድርጎ ለእስራ
ኤላውያን ሰጣቸው።

ከዚያም ምድሪቱ ከጦርነት ዐረፈች።

## የተሸነፉ ነገሥታት ስም ዝርዝር

12 እንግዲህ እስራኤላውያን ድል
ያደረጓቸውና ከዮርዳኖስ ማዶ
በስተ ምሥራቅ የሚገኘውን የዓረባን ክፍል
በሙሉ ይዞ፣ ከአርኖን ሸለቆ እስከ
አርሞንዔም ተራራ የሚዘልቀውን ግዛታ
ቸውን የወሰዱባቸው ነገሥታት እነዚህ
ናቸው፤

2መቀመጫውን በሐሴቦን አድርጎ የገዛው
የአሞራውያን ንጉሥ ሴዎን፣ ከአርኖን
ሸለቆ ዳርቻ ላይ ካለችው ከአሮዔር ማለት
ከሸለቆው መካከል አንሥቶ፣ የአሞናውያን
ወሰን እስከ ሆነው እስከ ያቦቅ ወንዝ
ድረስ ገዝቶአል፤ ይህም የገለዓድን
እኩሌታ ይጨምራል። 3እንዲሁም ከኪ
ኔሬት… ባሕር[θ] እስከ ሙት[ፊ] ባሕር
ያለውን ምሥራቃዊውን ዓረባ፣ እስከ
ቤት የሺሞትና ከዚያም በስተ ደቡብ
እስከ ፈስጋ ተራራ ግርጌ ድረስ ገዝቶአል።

4መቀመጫውን በአስታሮትና በኤድራይ
አድርጎ የገዛውና ከመጨረሻዎቹ ከራፋ
ይም ዘሮች አንዱ የሆነው የባሳን
ንጉሥ ዖግ፣ 5የአርሞንዔምን ተራራ፣
ሰልካንን፣ ባሳንን ሁሉ እስከ ጌሹራ
ውያንና እስከ ማዕካታውያን ድንበሮች
እንዲሁም ከገለዓድ እኩሌታ እስከ ሐሴ
ቦን ንጉሥ እስከ ሴዎን ወሰን ድረስ
ገዝቶአል።

6የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴና እስራ
ኤላውያን እነዚህን ድል አደረጉ፤ የእግዚ
አብሔር ባሪያ ሙሴም ምድራቸውን ለሮ
ቤል፣ ለጋድና ለምናሴ ነገድ እኩሌታ
ርስት አድርጎ ሰጣቸው።

7እንግዲህ ኢያሱና እስራኤላውያን
ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ ድል ያደረጓ
ቸው የምድሪቱ ነገሥታት እነዚህ ናቸው፤
ግዛታቸውም በሊባኖስ ሸለቆ ውስጥ ካለው
ከበኣልጋድ ተነሥቶ በምዕራብ ሴይር
እስካለው እስከ ሐላቅ ተራራ ይደርሳል፤
ኢያሱም የእነዚህን ነገሥታት ምድር
እንደ ነገዳቸው አከፋፈል ለእስራኤላውያን
በማከፋፈል ርስት አድርጎ ሰጣቸው፤ 8ይህም
ተራራማው አገር፤ በስተ ምዕራብ ያለው
የኰረብታ ግርጌ፣ ዓረባ፣ የተራራው ሸንተረ
ሮች፣ ምድረ በዳውና ነጌብ ማለት የኬጢ
ያውያን፣ የአሞራውያን፣ የከነዓናውያን፣
የፌርዛውያን፣ የኤዊያውያንና የኢያቡሳውያን
ምድር ነው፤ ነገሥታቱም እነዚህ ናቸው፤

| | |
|---|---|
| 9የኢያሪኮ ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| ቤቴል አጠገብ ያለችው የጋይ ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| 10የኢየሩሳሌም ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| የኬብሮን ንጉሥ፣ | አንድ፤ |
| 11የየርሙት ንጉሥ፣ | አንድ፤ |

[θ]3 "ገሊላ" ናት። [ፊ]3 የሙት ባሕር፣ የጨው ባሕርም ይባላል።

11፥14 ዘጸ20፥16
11፥15 ዘፀ34፥11፤ ዘዳ7፥2፤ኢሱ1፥7
11፥16 ዘኍ13፥17፤ ዘዳ1፥7፤ኢሱ10፥41
11፥17 ዘፍ14፥6፤ ዘኍ24፥18፤ዘዳ3፥25፤ ዘዳ3፥9፡25፤7፥24፤33፥2፤ኢሱ12፥7፡8፤ 13፥5
11፥19 ኢሱ9፥1፡3፡15
11፥20 ዘፀ4፥21፤ 14፥17፤ዘዳ7፥16፤መሳ 14፥4፤ሮሜ9፥18፤
11፥21 ዘኍ13፥22፡33፤ኢሱ10፥3፤15፥50
11፥22 ዘፍ10፥19፤ ኢሱ12፥17፤15፥47፤ 19፥13፤1ሳሙ5፥1፡8፤ 17፥4፤1ነገ2፥39፤2ነገ1 4፥25፤1ዜና8፥13፤ ኢሳ20፥1፤አሞ6፥2
11፥23 ዘፀ33፥14፤ ዘኍ26፥53፤ዘዳ1፥38፤ 12፥9-10፤25፥19፤ኢሱ 13፥7፤14፥15፤21፥43-45፤ ነህ9፥24፤መዝ105፥44
12፥1 ዘኍ32፥19፤ 21፥13፤ዘዳ3፥8፤ኢሱ 11፥2፤መዝ136፥21፤
12፥2 ቍ5፤ዘፍ19፥38፤31፥21፤32፥22፡26፤፤ዘኍ21፥21፡25፤32፥26፡34፤ዘዳ2፥36፤3፥15፤ኢሱ13፥10፡11፡16፡25፤171፤20፥8፤21፥38፤መሳ5፥17፤7፥3፤10፥8፤11፥19
12፥3 ዘፍ14፥3፤ዘኍ 21፥20፤33፥49፤ኢሱ 11፥2፤13፥20
12፥4 ዘፍ14፥5፤ዘኍ 21፥21፡33፤ዘዳ1፥4፤ ኢሱ13፥30
12፥5 ቍ2፤ዘኍ32፥33፤ዘዳ3፥10፡14፤ኢሱ 17፥1፤20፥8፤21፥27፤22፥7፤13፥2፡13፤ 1ሳሙ 27፥8
12፥6 ዘኍ32፥29፡33፤ዘዳ3፥8፤ኢሱ13፥8
12፥7 ኢሱ11፥17
12፥8 ዘዳ1፥7፤ኢሱ 3፥10፤11፥17፤ዕዝ9፥1
12፥9 ዘፍ12፥8፤ዘኍ 33፥48፤ኢሱ8፥1፤ 7፥2፤8፥9፤18፥13፤ መሳ1፥23፤4፥5፤20፥18፤21፥2፤ነህ11፥31
12፥10 ኢሱ10፥1
12፥11 ኢሱ10፥3

የለኪሶ ንጉሥ፣ አንድ፤
12የዔግሎን ንጉሥ፣ አንድ፤
የጌዝር ንጉሥ፣ አንድ፤
13የዳቤር ንጉሥ፣ አንድ፤
የጌድር ንጉሥ፣ አንድ፤
14የሔርማ ንጉሥ፣ አንድ፤
የዓራድ ንጉሥ፣ አንድ፤
15የልብና ንጉሥ፣ አንድ፤
የዓዶላም ንጉሥ፣ አንድ፤
16የመቄዳ ንጉሥ፤ አንድ፣
የቤቴል ንጉሥ፣ አንድ፤
17የታጱዋ ንጉሥ፣ አንድ፤
የኦፌር ንጉሥ፣ አንድ፤
18የአፌቅ ንጉሥ፣ አንድ፤
የለሽሮን ንጉሥ፣ አንድ፤
19የማዶን ንጉሥ፣ አንድ፤
የሐጾር ንጉሥ፣ አንድ፤
20የሺምሮን ሚሮን ንጉሥ፣ አንድ፤
የአዚፍ ንጉሥ፣ አንድ፤
21የታዕናክ ንጉሥ፣ አንድ፤
የመጊዶ ንጉሥ፣ አንድ፤
22የቃዴስ ንጉሥ፣ አንድ፤
በቀርሜሎስ የሚገኘው
የዮቅንዓም ንጉሥ፣ አንድ፤
23በዶር ኰረብታ[T] የሚገኘው
የዶር ንጉሥ፣ አንድ፤
በጌልገላ የሚገኘው የጎይም
ንጉሥ፣ አንድ፤
24የቲርሳ ንጉሥ፣ አንድ፤
እነዚህ በድምሩ ሠላሳ አንድ ነገሥታት
ናቸው።

## ወደ ፊት የሚያዝ ምድር

13 ኢያሱ በሸመገለና ዕድሜው በገፋ ጊዜ፣
እግዚአብሔር እንዲህ አለው፤ "እነሆ
አርጅተሃል፤ ዕድሜህም ገፍቶአል፤ ነገር
ግን መያዝ ያለበት እጅግ በጣም ሰፊ ምድር
ገና አለ።
2"የሚቀረውም ምድር ይህ ነው፤ እር
ሱም የፍልስጥኤማውያንና የጌሹራውያን
አገር ሁሉ ነው፤ 3ከግብፅ በስተ ምሥራቅ
ከሚገኘው ከሺሖር ወንዝ አንሥቶ፣
በሰሜን እስከ አቃሮን ወሰን ያለው
አገር፣ ሁሉም እንደ ከነዓናውያን ምድር
ይቈጠራል፤ ይኸውም በጋዛ፣ በአሽ
ዶድ፣ በአስቀሎና፣ በጌትና በአቃሮን
የሚኖሩትን የአምስቱን የፍልስጥኤማው
ያን ገዦች ምድር የሚያካትት ሲሆን፣
ይህም የኤዋውያን ምድር ነበር። 4በደ
ቡብ በኩል የከነዓናውያን ምድር ሁሉና
የሲዶናውያን ይዞታ ከሆነችው ከመዓራ
አንሥቶ እስከ አፌቅ ያለው የአሞራ
ውያን ግዛት፣ 5የጌባላውያንም ምድር[ሀ]፤
በምሥራቅም ከበኣልጋድ አንሥቶ በአር
ሞንዔም ተራራ ግርጌ አልፎ፣ እስከ ሐማት
መተላለፊያ[ለ] ያለው የሊባኖስ ምድር
ሁሉ ነው።
6"ከሊባኖስ እስከ ማሴሮን ባለው ተራራማ
ምድር ላይ የሚኖሩትን ሁሉ፣ ሲዶናውያ
ንንም ጭምር እኔው ራሴ ከእስራኤላውያን
ፊት አሳድጄ አስወጣቸዋለሁ። ብቻ አንተ
ባዘዝሁህ መሠረት ምድሪቱን ርስት አድር
ገህ ለእስራኤላውያን አካፍል። 7ይህንንም
ለዘጠኙ ነገድና ለምናሴ ነገድ እኩሌታ ርስት
አድርገህ አካፍል።"

## ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ያለው ምድር አከፋፈል

8ሌላው የምናሴ ነገድ እኩሌታ፣ የሮቤል
ነገድና የጋድ ነገድ *የእግዚአብሔር* ባሪያ
ሙሴ ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ እንደየ
ድርሻቸው ከፋፍሎ በመደበላቸው መሠረት፣
ራሱ ሙሴ የሰጣቸውን ርስት ተቀበሉ።
9ይህም ከአርኖን ሸለቆ ዳርቻ ካለው
ከአሮዔርና በሸለቆው መካከል ካለችው
ከተማ አንሥቶ እስከ ዲቦን የሚደር
ሰውን የሜድባን ደጋማ ምድር በሙሉ
ይይዛል፤ 10እንዲሁም በሐሴቦን ተቀ
ምጦ እስከ አሞናውያን ዳርቻ የገዛውን
የአሞራውያንን ንጉሥ የሴዎንን ከተ
ሞች ሁሉ ያጠቃልላል፤ 11በተጨማሪም
ገለዓድን፣ የጌሹራውያንንና የማዕካታ
ውያንን ግዛት ሁሉ፣ የአርሞንዔምን
ተራራ በሙሉ፣ ባሳንንም ሁሉ እስከ
ሰልካ ድረስ ይይዛል፤ 12ይህም በአስታ
ሮትና በኤድራይ ሆኖ የገዛውን በባሳን
ያለውን የዐግን መንግሥት በሙሉ
ያጠቃልላል፤ ዐግም በሕይወት ከቀሩት
ከመጨረሻዎቹ ከራፋይም ዘሮች አንዱ
ነበር፤ እነዚህንም ሙሴ ድል አደረጋ
ቸው፤ ምድራቸውንም ያዘ፤ 13ነገር ግን
እስራኤላውያን የጌሹርንና የማዕካ
ትን ሕዝብ ስላላስወጡ፣ እስከ ዛሬ
ድረስ በመካከላቸው ይኖራሉ።
14ለሌዊ ነገድ ግን ርስት አልሰጠም፤ ለእስራ
ኤል አምላክ *ለእግዚአብሔር* በእሳት የሚቀር
በው ቍርባን፣ በተሰጣቸው ተስፋ መሠረት
ርስታቸው ነውና።
15ሙሴ በየጐሣቸው መድቦ ለሮቤል ነገድ
የሰጠው ርስት ይህ ነው፤

12፥12 ኢሱ10፥3፡33
12፥13 ኢ.ሱ10፥3
12፥14 ዘኍ14፥45፤ 21፥1
12፥15 ዘፍ38፥1፤ ዘኍ 33፥20፤ኢ.ሱ15፥35፤ሚክ1፥15
12፥16 ኢ.ሱ7፥2፤ 10፥10
12፥17 ኢ.ሱ11፥22፤ 15፥34፤16፥8፤17፥8፤1ነገ4፥10
12፥18 ኢ.ሱ13፥4፤ 19፥30፤መሳ1፥31፤ 1ሳሙ4፥1፤29፥1
12፥19 ኢ.ሱ11፥1
12፥22 ኢ.ሱ15፥23፡55፤19፥11፡26፡37፤ 20፥7፤21፥32፡34 መሳ4፥6፡9፤1ሳሙ15፥12፤2ሳሙ23፥35
12፥20 ኢ.ሱ11፥1
12፥21 ኢ.ሱ17፥11፤ 21፥25፤መሳ1፥27፤ 5፥19፤1ነገ4፥12
12፥23 ኢ.ሱ11፥2
12፥24 1ነገ14፥17፤ 15፥33፤16፥8፡23፤መሓ 6፥4፤መዝ135፥11፤ 136፥18
13፥1 ዘፍ 24፥1፤ኢ.ሱ 14፥10፤23፥1፡2፤1ነገ1፥1
13፥2 ዘፍ10፥14፤ ኢ.ሱ12፥5፤መሳ3፥31
13፥3 ዘዳ2፥23፤ኢ.ሱ 11፥22፤15፥11፡45፤19፥43፤መሳ1፥18፤3፥3፤14፥19፤16፥5፡18፤ 1ሳሙ5፥10፤6፥4፡17፤ 7፥14፤2ሳሙ1፥20፤1ዜና13፥5፤ኢ.ሳ23፥3፤ 14፥29፤ኤር2፥18፤ 25፥20፤ሕዝ25፥15፤ አሞ3፥9
13፥4 ዘፍ14፥7፤15፥16፤ኢ.ሱ12፥18፤ አሞ2፥10
13፥5 ዘኍ13፥21፤ 34፥8፤ዘዳ3፥8፤1ነገ5፥18፤ኢ.ሱ11፥17፤መሳ 3፥3፤መዝ83፥7፤ሕዝ 27፥9
13፥6 ዘኍ33፥54፤ 34፥13፤ኢ.ሱ11፥8፤ መዝ80፥8
13፥7 ኢ.ሱ11፥23፤ መዝ78፥55
13፥8 ኢ.ሱ12፥6፤8፥7
13፥9 ቀኍ16፥17፡21፤ዘኍ21፥30፤32፥3፡34፤ዘዳ2፥36፤መሳ 11፥26፤2ሳሙ24፥5፤ኢ.ሳ15፥2፤ኤር48፥8፡18፡21፡22
13፥10 ዘኍ21፥24፤ ኢ.ሱ12፥2
13፥11 ኢ.ሱ12፥2፡5
13፥12 ዘፍ14፥5፤ ዘኍ21፥33፤ዘዳ1፥4፤ 3፥8፤ኢ.ሱ12፥4
13፥13 ዘዳ3፥12፡14፤ኢ.ሱ12፥5
13፥14 ቀኍ33፤ዘዳ 18፥1-2፤ኢ.ሱ14፥3

[T]23 ወይም፣ "ናፎት ዳር" ማለት ነው። [ሀ]5 የቢብሎስ አካባቢ ነው።
[ለ]5 ወይም፣ "እስከ ሌቦ ሐማት"

16ድንበራቸው ከአርኖን ሸለቆ ዳርቻ ካለው
ከአሮዔርና ከሸለቆው መካከል ካለችው
ከተማ አንሥቶ ያለው ግዛት ሲሆን፣ ሜድባ
አጠገብ ያለውን ደጋውን አገር በሙሉ፣
17ሐሴቦንና በደጋው ላይ ያሉትን ከተሞ
ችዋን በሙሉ፣ እንዲሁም ዲቦንን፣ ባሞ
ትባኣልን፣ ቤትበኣልምዖን፣ 18ያህጽን፣
ቅዴሞትን፣ ሜፍዓትን፣ 19ቂርያታያምን፣
ሴባማን፣ በሸለቆው ኰረብታ ላይ ያለች
ውን ዜሬትሻሐርን፣ 20ቤተፌጎርን፣ የፊ
ስጋን ሽንተረሮችና ቤትየሺሞትን፣

21ማለት በደጋው አገር የሚገኙት ከተሞች
ሁሉና መቀመጫውን በሐሴቦን አድርጎ
የገዛውን የአሞራውያንን ንጉሥ የሴዎንን
ግዛት በሙሉ ያካትታል። ሙሴ ሴዎ
ንንና በዚያው ምድር ተቀማጭ የነበሩ
ትን መሳፍንት፤ አዊ፣ ሮቆም፣
ሱር፣ ሑርና ሪባ የተባሉትን የምድ
ያም አለቆች ድል አደረጋቸው። 22በጦር
ሜዳ ከሞቱት ሌላ እስራኤላውያን
የቢዖርን ልጅ ምዋርተኛውን በለዓምን
በሰይፍ መትተው ገደሉት። 23የሮቤል
ነገድ ወሰን የዮርዳኖስ ወንዝ ነው፤ የሮ
ቤል ነገድ በየጐሣቸው የወረሷቸው
ከተሞችና መንደሮቻቸው እነዚህ ነበሩ፤
24ሙሴ በየጐሣቸው መድቦ ለጋድ ነገድ
የሰጠው ርስት ይህ ነው፤

25ድንበራቸው ኢያዜር፣ የገለዓድን ከተ
ሞች በሙሉ በረባት አጠገብ እስካለው
እስከ አሮዔር የሚደርሰውን የአሞናውያን
አገር እኩሌታ፣ 26ከሐሴቦን እስከ ራማት
ምጽጴና ከዚያም እስከ ብጦኒም፣ ከመሃ
ናይም እስከ ደቤር ግዛት ያለውን፣
27በሸለቆው ውስጥ ደግሞ ቤትሀራምን፣
ቤትኒምራን፣ ሱኮትን፣ ጻፎንንና እስከ
ኪኔሬት[ሐ] ባሕር ጫፍ የሚደርሰውን
ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ያለውን ቀሪ
ውን የሐሴቦን ንጉሥ የሴዎንን ግዛት ያካ
ትታል፤ 28የጋድ ነገድ በየጐሣቸው የወ
ረሷቸው ከተሞችና መንደሮቻቸው እነ
ዚህ ነበሩ።

29ሙሴ ለምናሴ ነገድ እኩሌታ ማለት
ለገሚሱ የምናሴ ቤተሰብ ዘሮች በየጐሣቸው
የሰጣቸው ርስት ይህ ነው፤

30ድንበራቸው ከመሃናይም አንሥቶ ባሳ
ንን በሙሉ ይጨምርና፣ በባሳን ያሉ
ትን ሥልሳ የኢያዕር ከተሞች ሁሉ ይዞ
የባሳን ንጉሥ የዐግን ግዛት ሁሉ የሚያካ
ትት ሲሆን፣ 31የገለዓድን እኩሌታ፣ በባ
ሳን የዐግ መንግሥት ዋና ከተማ የሆኑትን
አስታሮትንና ኤድራይን ይጨምራል፤ እነዚህ
ለምናሴ ልጅ ለማኪር ዘሮች የተሰጡ

13፥16 ቀኍ9፤ዘኍ 21፥30፤ኢሱ12፥2፤ 1ሳሙ30፥28፤ ኢሳ15፥2
13፥17 ቀኍ9፤ዘኍ 32፥3፤22፥41፤1ዜና 5፥8፤ኤር48፥23፤ ሕዝ25፥9
13፥18 ዘኍ21፥23፤ ዘዳ2፥26፤ኢሱ21፥37፤ ኤር48፥21
13፥19 ዘኍ32፥3፡ 37 13፥20 ዘዳ3፥29
13፥21 ቀኍ9፤ዘፍ25፥ 2፤ ዘኍ25፥15፤31፥8
13፥22 ዘፍ30፥27፤ ዘኍ22፥5፤23፥23
13፥23 1ዜና5፥7
13፥25 ዘኍ21፥32፤ ዘዳ3፥11፤ኢሱ 21፥39፤ 12፥2
13፥26 ዘፍ32፥2፤ ዘኍ21፥25፤ኢሱ 10፥3፤ኤር49፥3
13፥27 ዘፍ33፥17፤ ዘኍ32፥3፤34፥11፤ መሳ12፥1፤መዝ48፥2
13፥28 ዘፍ46፥16፤ ዘኍ32፥33፤ሕዝ48፥27
13፥30 ዘፍ32፥2፤ ዘኍ21፥33፤32፥41፤ ኢሱ12፥4፤
13፥31 ዘፍ50፥23፤ ዘኍ21፥33፤ኢሱ17፥5
13፥32 ዘኍ26፥3፤ 22፥1
13፥33 ቀኍ14፤ዘኍ 26፥62፤18፥20፤ኢሱ 18፥7፤ሕዝ44፥28
14፥1 ዘፀ6፥23፤ዘኍ 26፥53፤34፥17-18፤ ኢሱ11፥23፤19፥51፤ 21፥1፤መዝ16፥6፤136፥ 21
14፥2 ዘሌ16፥8፤ ዘኍ34፥13
14፥3 ዘኍ32፥33፤ 34፥14፤35፥2፤ኢሱ 13፥14
14፥4 ዘፍ41፥52፤ ዘኍ35፥2-3፤ኢሱ 21፥2፣መሳ1፥29
14፥5 ዘኍ34፥13
14፥6 ዘኍ13፥6፥26፤ 14፥30፥38፤ዘዳ11፥30፤ 33፥1
14፥7 ዘኍ1317፥30፤ 14፥6-9፤ኢሱ 15፥3
14፥8 ዘኍ13፥31፤ 14፥24፤32፥12
14፥9 ዘኍ14፥24፤ ዘዳ11፥24
14፥10 ዘኍ11፥28፤ 14፥30፤ኢሱ5፥6፤ 13፥1

ሲሆን፣ ይህም ለግማሾቹ የማኪር ልጆች
በየጐሣቸው የተሰጡ ናቸው።

32ሙሴ ከኢያሪኮ በስተ ምሥራቅ፣ ከዮር
ዳኖስ ማዶ በሞዓብ ሜዳ ሳለ የሰጣቸው
ርስት ይህ ነበር። 33ለሌዊ ነገድ ግን
ሙሴ ርስት አልሰጠም፤ የእስራኤል
አምላክ እግዚአብሔር እንደ ተናገራቸው
እርሱ ራሱ ርስታቸው ነውና።

### ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ ስላለው ምድር አከፋፈል

14 ካህኑ አልዓዛር፣ የነዌ ልጅ ኢያ
ሱና የእስራኤል የየነገዱ ጐሣ
አባቶች የደለደሉላቸው፣ እስራኤላውያንም
በከነዓን ምድር የወረሱት ርስት ይህ
ነው። 2ርስታቸውም እግዚአብሔር በሙሴ
አማካይነት በሰጠው ትእዛዝ መሠረት፣
ለዘጠኙ ነገድና ለእኩሌታው ነገድ በዕጣ
ተከፋፈለ። 3ሙሴ ለሁለቱ ነገድና ለእኩሌ
ታው፣ የዮርዳኖስን ምሥራቅ ክፍል ርስት
አድርጎ ሰጣቸው፤ ሌዋውያኑ ግን አብረዋ
ቸው እንዲካፈሉ አላደረገም፤ 4የዮሴፍ
ልጆች ምናሴና ኤፍሬም ሁለት ነገዶች
ሆነው ነበርና፤ ለሌዋውያኑ ግን ከሚኖሩ
ባቸው ከተሞች እንዲሁም ለበግ፣ ለፍየልና
ለከብት መንጎቻቸው መሰማሪያ እንዲሆን
አብሮ የተከለለላቸውን ምድር ብቻ እንጂ
ሌላ አልሰጣቸውም፤ 5ስለዚህ እስራኤላውያን
እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት፣
ምድሪቱን ተካፈሉ።

### ኬብሮን ለካሌብ ተሰጠች

6የይሁዳም ሰዎች በጌልገላ ወደ ኢያሱ
ቀረቡ፤ ከዚያም የቄኔዛዊው የዮፎኒ ልጅ
ካሌብ እንዲህ አለው፤ "እግዚአብሔር
በቃዴስ በርኔ ስለ አንተና ስለ እኔ፣
የአም ላክ ሰው ለሆነው ለሙሴ
የተናገረውን ታውቃለህ። 7የእግዚአብሔር
ባሪያ ሙሴ ምድሪቱን እንድሰልል ከቃዴስ
በርኔ በላ ከኝ ጊዜ የአርባ ዓመት ሰው
ነበርሁ፤ እኔም ትክክለኛውን ማስረጃ ይዠ
ለት መጣሁ፤ 8አብረውኝ ወደዚያ የወጠ
ት ወንድሞቼ ግን፣ የሕዝቡ ልብ
በፍርሃት እንዲቀልጥ አደረጉ፤ ሆኖም እኔ
አምላኬን እግዚአብሔ ርን በፍጹም ልቤ
ተከተልሁት። 9ስለዚህም ሙሴ በዚያች ዕ
ለት፣ 'አምላኬን እግዚአብሔ ርን በፍጹም
ልብህ ተከትለኸዋልና እግርህ የረገጣት
ምድር ለዘላለም የአንተና የዘርህ ርስት
ትሆናለች'[መ] ብሎ ማለልኝ።

10"አሁንም እነሆ፤ ልክ እግዚአብሔር
እንዳለው ይህን ለሙሴ ከተናገረበት ጊዜ

[ሐ]27 የገሊላ ባሕር ነው። [መ]9 ዘዳ 1፥36 ይመ።

አንሥቶ እስራኤል በምድረ በዳ ሲንከራ
ተት እኔን አርባ አምስት ዓመት በሕ
ይወት ጠብቆ አኑሮኛል፤ ይኸው ዛሬ ሰማንያ
አምስት ዓመት ሆነኝ። 11ሙሴ በላከኝ ጊዜ
የነበረኝ ብርታት ዛሬም አብሮኝ አለ፤
ልክ እንደዚያን ጊዜ ሁሉ አሁንም ወደ
ጦርነት ለመሄድ ኀይሉም ብርታቱም
አለኝ። 12አሁንም እግዚአብሔር በዚ
ያች ዕለት ቃል የገባልኝን ይህችን ኰረብ
ታማ አገር ሰጠኝ። ዔናቃውያን በዚያ
እንደ ነበሩና ከተሞቻቸውም ታላላቅና
የተመሸጉ እንደሆኑ ያን ጊዜ አንተው
ራስህ ሰምተሃል፤ ሆኖም ልክ እርሱ እንዳ
ለው *በእግዚአብሔር* እርዳታ አሳድጄ አወ
ጣቸዋለሁ።”
13ከዚያም ኢያሱ የዮፎኒን ልጅ ካሌብን
ባረከው፤ ኬብሮንንም ርስት አድርጎ ሰጠው።
14ስለዚህም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኬብሮን
የቄኔዛዊው የዮፎኒ ልጅ የካሌብ ርስት
ሆነች፤ የእስራኤልን አምላክ *እግዚአብሔ
ርን* በፍጹም ልቡ ተከትሎአልና። 15ኬብ
ሮን ቀድሞ ከዔናቃውያን ሁሉ ታላቅ በሆ
ነው በአርባቅ ስም ቂርያትአርባቅ ተብላ
ትጠራ ነበር።
ከዚያም ምድሪቱ ከጦርነት ዐረፈች።

## ለይሁዳ ነገድ የተመደበው ድርሻ

15፥15-19ተን ምብ-መሳ 1፥11-15

15 ለይሁዳ ነገድ በየጐሣቸው በዕጣ
የተመደበው ድርሻ እስከ ኤዶም
ምድር የሚወርድ ሲሆን፣ በስተ ደቡብ
መጨረሻ እስከ ጺን ምድረ በዳ ድረስ
ይዘልቃል።

2የደቡብ ወሰናቸው፣ ከጨው
ባሕር[ሠ] ደቡባዊ ጫፍ ካለው የባሕር
ወሽመጥ ይነሣል፤ 3ከዚያም የአቅረቢ
ምን መተላለፊያ በማቋረጥ በጺን
በኩል እስከ ቃዴስ በርኔ ደቡባዊ
ክፍል ይደርሳል፤ ደግሞም ሐጽሮንን
አልፎ ወደ አዳር ይወጣና ወደ ቀርቃ
ይታጠፋል፤ 4በአድሞን በኩል
አድርጎም ወደ ግብፅ ደረቅ ወንዝ
ይገባና መቆሚያው ባሕሩ ይሆናል፤
እንግዲህ በደቡብ በኩል ያለው
ወሰናቸው[ረ] ይህ ነው።

5በምሥራቅ በኩል ያለው ወሰና
ቸው ደግሞ የጨው ባሕር ሲሆን፣
ይህም የዮርዳኖስ ወንዝ እስከሚሠርግ
በት ይደርሳል።

በሰሜን በኩል ያለው ወሰንም
የዮርዳኖስ ወንዝ ከሚሠርግበት የባሕር
ወሽመጥ ይነሣና 6ሽቅብ ወደ ቤትሖ
ግላ ይወጣል፤ ከዚያም በሰሜናዊው
ቤትዓረባ በኩል አድርጎ የሮቤል ልጅ
የቦሀን ድንጋይ እስካለበት ይደርሳል።
7ከዚያም ድንበሩ ከአኮር ሸለቆ ወደ
ዳቤር ይወጣና ከወንዙ በስተ ደቡብ
ባለው በአዱሚም መተላለፊያ ፊት
ለፊት አድርጎ በስተ ሰሜን ወደ
ጌልገላ ይታጠፋል፤ በዓይንሳሚስ
ምንጭ በኩል አልፎም ወደ ዓይንሮ
ጌል ይወጣል። 8እንደዚሁም የሄኖምን
ልጅ ሸለቆ አልፎ ይሄድና የኢ
ያቡሳውያን ከተማ እስከ ሆነችው እስከ
ኢየሩሳሌም ደበብዊ ተረተር በመዝ
ለቅ፣ በራፋይም ሸለቆ ሰሜን ጫፍ
በኩል አድርጎ ከሄኖም ሸለቆ በስተ
ምዕራብ ካለው ከጳረብታ አናት
ላይ ይደርሳል። 9ከዚያም በመቀጠ
ል ከተራራው አናት ተነሥቶ ወደ
ኔፍቶ ምንጮች በማምራት፣ በዔፍሮን
ተራራ ላይ ያሉትን ከተሞች አልፎ
ይወጣና ቂርያትይዓሪም ተብሎ ወደ
ሚጠራው ወደ በኣላ ቍልቍል
ይወርዳል፤ 10ከዚያም ከበኣላ በምዕራብ
በኩል አድርጎ ወደ ሴይር ይታጠፍና
ክሳሎን ተብሎ በሚጠራው በይዓሪም
ኰረብታ ሰሜ ናዊ ተረተር አልፎ
ቍልቍል ወደ ቤት ሳሚስ በመውረድ
ወደ ተምና ይሻገራል። 11ደግሞም
በአቃሮን ሰሜናዊ ተረተር አድርጎ
ወደ ሽክሮን ይታጠፍና በበኣላ ተራራ
ላይ አልፎ እስከ የብኒኤል ይደርሳል፤
ከዚህ በኋላ ወሰኑ ባሕሩ ላይ ይቆማል።

12የምድሪቱ ምዕራባዊ ወሰን የታ
ላቁ ባሕር[ሰ] ጠረፍ ነው፤
እንግዲህ በየጐሣው የተደለደለውን የይሁ
ዳን ሕዝብ በዙሪያው የከበቡት ወሰኖቹ
እነዚሁ ናቸው።
13ኢያሱ *እግዚአብሔር* ባዘዘው መሠ
ረት፣ ከይሁዳ ድርሻ ላይ ከፍሎ ኬብሮን
የተባለችውን ቂርያትአርባቅን ለዮፎኒ
ልጅ ለካሌብ ሰጠው፤ አርባቅም የዔናቅ
አባት ነበረ። 14ካሌብም ሦስቱን የዔናቅን
ዘሮች ሴሲንን፣ አኪመንንና ተላሚንን
ከኬብሮን አሳደዳቸው፤ 15ከዚያም በዳ
ቤር ሕዝብ ላይ ዘመተ፤ ዳቤር ቀድሞ
ቂርያትሤፍር ትባል ነበር። 16ካሌብ፣
“ቂርያትሤፍርን ወግቶ ለሚይዝ ሰው
ልጄን ዓክሳን እድርለታለሁ” አለ። 17ስለዚህ
የካሌብ ወንድም የቄኔዝ ልጅ ጎቶንያል
ከተማዪቱን ያዛት፤ ካሌብም ልጁን ዓክሳን
ዳረለት።

14፥11 ዘፍ15፥15፤ ዘዳ34፥7
14፥12 ዘኍ13፥28፡33፤14፥24
14፥13 ዘፍ23፥19፤ ኢሱ10፥36፤22፥6፡7፤ መሳ1፥20፤1ሳሙ25፥3፤30፥14፤1ዜና6፥56
14፥14 ዘኍ14፥24
14፥15 ዘፍ23፥2፤ ኢሱ11፥23፤15፥13፤መሳ3፥11፤1ነገ4፥24፤5፥4፤1ዜና22፥9
15፥1 ዘኍ34፥3፤13፥21፤ኢሱ18፥5
15፥2 ዘፍ14፥3
15፥3 ዘኍ34፥4፤ ዘዳ1፥2
15፥4 ዘፍ15፥18፤ ዘኍ34፥4
15፥5 ዘፍ14፥3፤ዘኍ34፥10፤ኢሱ18፥15-19
15፥6 ቍ61፤ኢሱ18፥17-19፡21
15፥7 ዘዳ11፥30፤ ኢሱ7፥24፤10፥3፤18፥16፡17፤2ሳሙ17፥17፤1ነገ1፥9
15፥8 ቍ63፤ኢሱ10፥1፤18፥16፡28፤መሳ1፥21፤19፥10፤2ሳሙ5፥6፡18፡22፤2ነገ23፥10፤1ዜና11፥4፤14፥9፤2ዜና28፥3፤ዕዝ9፥1፤ኢሳ17፥5፤ኤር7፥31፤19፥2፡6
15፥9 ቍ10፡11፡29፤ኢሱ9፥17፤18፥15፤2ሳሙ6፥2፤1ዜና13፥6
15፥10 ቍ9፤ዘፍ38፥12፤ዘኍ24፥18፤ኢሱ19፥22፡38፤21፥16፤መሳ1፥33፤1ሳሙ6፥9፤1ነገ4፥9፤2ነገ14፥11
15፥11 ቍ9፤ኢሱ13፥3፤19፥33
15፥12 ዘኍ34፥6
15፥13 ዘፍ23፥2፤ ዘኍ13፥22፤ኢሱ10፥36፤21፥12፤1ሳሙ25፥3፤30፥14፤1ዜና6፥56
15፥14 ዘኍ13፥22፡33፤መሳ1፥10፡20
15፥16 1ዜና2፥49
15፥17 መሳ3፥9፡11፤1ዜና4፥13፤27፥15

[ሠ]2 በዚህና በቍጥር 5 ላይ የሙት ባሕር ማለት ነው። [ረ]4 ዕብ ራይስጡ ወሰናችሁ ይላል። [ሰ]12 በዚህና በቍጥር 47 ላይ የተጠቀሰው የሜድትራንያን ባሕር ነው።

[18]ዓክሳ ወደ ጎቶንያል በመጣች ጊዜም፣
ከአባትዋ ላይ የእርሻ መሬት እንዲለምን
አጥብቃ ነገረችው::[ሸ] ከአህያዋ ላይ እንደ
ወረደች ካሌብ፣ “ምን እንዳደርግልሽ ትፈ
ልጊያለሽ?” ሲል ጠየቃት::

[19]እርስዋም፣ “እባክህ፤ በጎ ነገር አድርግ
ልኝ፤ በኔጌብ መሬት እንደ ሰጠኸኝ ሁሉ፣
አሁንም የውሃ ምንጭ ጉድጓዶች ስጠኝ”
አለችው፤ ካሌብም የላይኛውንና የታችኛ
ውን ምንጮች ሰጣት::

[20]ለይሁዳ ነገድ በየጐሣቸው የተሰጣ
ቸው ርስት ይህ ነው፤

[21]በኔጌብ አካባቢ በኤዶም ድንበር ላይ
በወሰኑ ጫፍ የሚገኙት የይሁዳ ነገድ ደቡ
ባዊ ከተሞች እነዚህ ነበሩ፤

ቀብስኤል፣ ዔዴር፣ ያጉር፣ [22]ቂና፣
ዲሞና፣ ዓድዓዳ፣ [23]ቃዴስ፣ ሐጾር፤
ዩትናን፣ [24]ዚፍ፣ ጤሌም፣ በዓሎት፣
[25]ሐጾርሐዳታ፣ ሐጾር የምትባለው ቂርያ
ትሐጾር [26]አማም፣ ሽማዕ፣ ሞላዳ፣
[27]ሐጻርጋዳ፣ ሐሽሞን፣ ቤትጳሌጥ፣
[28]ሐጸር ሹዓል፣ ቤርሳቤህ፣ ቢዝዮ
ትያ [29]በኣላ፣ ዒዩም፣ ዓጼም፣
[30]ኤልቶላድ፣ ኪሲል፣ ሔርማ፣ [31]ጺቅ
ላግ፣ ማድማና፣ ሳንሳና [32]ልባዎት፣
ሺልሂም፣ ዓይንና ሪሞን ናቸው፤ ባጠ
ቃላይም ከተሞቹና መንደሮቻቸው
ሃያ ዘጠኝ ናቸው::

[33]በምዕራቡ በኰረብታዎች ግርጌ ያሉት
ደግሞ እነዚህ ናቸው፤ ኤሽታኦል፤
ጾርዓ፣ አሽና [34]ዛኖዋ፣ ዓይንገኒም፣
ታጱዋ፣ ዓይናም፣ [35]የርሙት፣ ዓዶላም፣
ሰኰት፣ ዓዜቃ፣ [36]ሽዓራይም፣ ዓዲ
ታይም፣ ግዴራ፣ ግዴሮታይም ናቸው፤
ከተሞቹም ከነመንደሮቻቸው ዐሥራ
አራት ናቸው::

[37]ጽናን፣ ሐዳሻ፣ ሚግዳልጋድ፣
[38]ዲልዓን፣ ምጽጳ፣ ዮቅትኤል፣
[39]ለኪሶ፣ ቦጽቃት፣ ዔግሎን፣ [40]ከቦን፣
ለሕማስ፣ ኪትሊሽ፣ [41]ግዴሮት፣
ቤት ዳጎን፣ ናዕማና መቄዳ ናቸው፤
ከተሞቹም ከነመንደሮቻቸው ዐሥራ
ስድስት ናቸው::

[42]ልብና፣ ዔትር፣ ዓሻን [43]ይፍታሕ፣
አሽና፣ ንጺብ፣ [44]ቅዒላ፣ አክዚብና
መሪሳ ናቸው፤ ከተሞቹም ከነመንደ
ሮቻቸው ዘጠኝ ናቸው::

[45]አቃሮን በዙሪያዋ ካሉ ሰፈሮ
ችና መንደሮቿ ጋር፣ [46]እንዲሁም
ከአቃሮን በስተ ምዕራብ በአሽዶድ
አካባቢ ያሉ ሰፈሮችና መንደሮቻቸው
ሁሉ፣ [47]አሽዶድ በዙሪያዋ ካሉ ሰፈሮ
ችና መንደሮች ጋር፣ ጋዛ እስከ
ግብፅ ደረቅ ወንዝና እስከ ታላቁ ባሕር
ጠረፍ በመለስ ካሉት ሰፈሮቿና
መንደሮቿ ጋር::

[48]በኰረብታማዋም አገር የሚገኙ ከተሞች
ደግሞ እነዚህ ናቸው፤ ሳምር፣ የቲር፣
ሶኮ [49]ደና፣ ዳቤር የምትባለው ቂርያ
ትስና [50]ዓናብ፣ ኤሽትሞዓ፣ ዓኒም፣
[51]ጎሶም፣ ሖሎንና ጊሎ፤ እነዚህም ዐሥራ
አንዱ ከተሞችና መንደሮቻቸው ናቸው::

[52]አራብ፣ ዱማ፣ ኤሽዓን፣ [53]ያኒም፣
ቤትታጱዋ፣ አፌቃ [54]ሑምጣ፣
ኬብሮን የተባለችው ቂርያትአርባቅና ጺዖር
ናቸው፤ እነዚህም ዘጠኝ ከተሞችና
መንደሮቻቸው ናቸው::

[55]ማዖን፣ ቀርሜሎስ፣ ዚፍ፣ ዩጣ
[56]ኢይዝራኤል፣ ዮቅድዓም፣ ዛኖዋሕ፣
[57]ቃይን፣ ጊብዓና ተምና ናቸው፤ እነ
ዚህም ዐሥር ከተሞችና መንደሮቻቸው
ናቸው::

[58]ሐልሑል፣ ቤትጹር፣ ጌዶር፣ [59]ማዕ
ራት፣ ቤትዓኖትና ኤልትቆን ናቸው፤
እነዚህም ስድስት ከተሞችና መንደሮቻ
ቸው ናቸው::

[60]ቂርያትይዓሪም የተባለችው ቂርያ
ትበኣልና ረባት፤ እነዚህም ሁለት ከተሞ
ችና መንደሮቻቸው ናቸው::

[61]በምድረ በዳው ደግሞ እነዚህ ናቸው፤
ቤትዓረባ፣ ሚዲን፣ ስካካ፣ [62]ኒብሻን፣
የጨው ከተማና ዓይንጋዲ፤ እነዚህም
ስድስት ከተሞችና መንደሮቻቸው
ናቸው::

[63]ነገር ግን የይሁዳ ዘሮች በኢየሩሳሌም
የሚኖሩትን ኢያቡሳውያን ከቦታቸው ሊያስ
ለቅቋቸው አልቻሉም፤ ኢያቡሳውያንም እስከ
ዛሬ ድረስ ከይሁዳ ሕዝብ ጋር በኢየሩሳሌም
አብረው ይኖራሉ::

## ለኤፍሬምና ለምናሴ ነገድ የተመደበው ድርሻ

**16** ለዮሴፍ ዝርያዎች የተመደበው
ድርሻ፣ ከዮርዳኖስ ኢያሪኮ[ቀ] ማለት
ከኢያሪኮ ምንጮች በስተ ምሥራቅ ይነ
ሣና፣ ምድረ በዳውን በማቋረጥ በኰረብ
ታማው አገር አድርጎ ወደ ቤቴል ይወጣል::

15፥19 ዘፍ36፥24፤ ኢሱ10፥40
15፥21 ዘፍ35፥21፤ ኢሱ10፥40፤2ሳሙ23፥20፤1ዜና11፥22
15፥23 ኢሱ11፥1፤ 12፥22
15፥24 ቁ55፤1ሳሙ23፥14፤2ዜና11፥8
15፥25 ኢሱ11፥1
15፥26 ኢሱ19፥2፤ 1ዜና4፥28፤ነህ11፥26
15፥28 ዘፍ21፥14፤ ኢሱ19፥3፤1ዜና4፥28
15፥29 ቁ9፤ኢሱ19፥3፤1ዜና4፥29
15፥30 ዘኍ14፥45፤ ኢሱ 19፥4
15፥31 ኢሱ19፥5፤1ሳሙ27፥6፤1ዜና2፥49፤4፥30፤12፥1፤ ነህ11፥28
15፥32 ዘኍ34፥11፤ ኢሱ19፥7፤መሳ20፥45፤21፥13፤ዘካ14፥10
15፥33 ቁ43፤ኢሱ19፥41፤መሳ13፥2፡25፤16፥31፤18፥2፡11፤2ዜና11፥10፤ነህ11፥29
15፥34 ቁ56፤ኢሱ12፥17፤19፥21፤21፥29፤1ዜና4፥18፤ነህ3፥13፤11፥30
15፥35 ቁ48፤ዘፍ38፥1፤ኢሱ10፥3፡10፤ 1ነገ4፥10
15፥36 1ሳሙ17፥52፤1ዜና4፥31፤12፥4
15፥38 ኢሱ11፥3፤ 2ነገ14፥7
15፥39 ኢሱ10፥3፤ 2ነገ22፥1
15፥41 ኢሱ10፥10፤ 19፥27፤2ዜና28፥18
15፥42 ዘኍ33፥20፤ ኢሱ19፥7፤1ሳሙ30፥30፤1ዜና4፥32፤6፥59
15፥43 ቁ33
15፥44 ኢሱ19፥29፤ መሳ1፥31፤1ሳሙ23፥1-2፤1ዜና4፥19፤ ነህ3፥17፡18፤ሚክ1፥14፡15
15፥45 ኢሱ13፥3
15፥46 ኢሱ11፥22
15፥47 ዘፍ15፥18፤ ዘኍ34፥6፤ኢሱ11፥22
15፥48 ቁ35፤ኢሱ21፥14፤መሳ10፥1፤1ሳሙ30፥27፤1ዜና6፥57
15፥49 ኢሱ10፥3
15፥50 ኢሱ11፥21፤ 21፥14፤1ሳሙ30፥28
15፥51 ኢሱ10፥41፤ 21፥15፤2ሳሙ15፥12፤ ኤር48፥21 15፥52 ዘፍ25፥14
15፥54 ዘፍ35፥27
15፥55 ኢ-12፥22፤ 1፥16፤መሳ10፥12፤1ሳሙ23፥24፡25፤25፥1፡2፤ 1ዜና2፥45
15፥56 ቁ34፤ኢሱ17፥16፤19፥18፤መሳ 6፥33፤1ሳሙ25፥43፤ ነገ18፥45፤ 1ዜና3፥1፤ ሆሴ1፥5 15፥57 ዘፍ38፥12፤ ኢሱ18፥28፤24፥33፤ መሳ19፥12፤20፥4፤2ሳሙ 23፥29፤ 1ዜና11፥31 15፥58 1ዜና2፥45፤4፥39፤ 12፥7፤2ዜና11፥7፤ ነህ3፥16 15፥60 ቁ9፤ዘዳ 3፥11፤ኢሱ9፥17 15፥61 ቁ6፤ኢሱ 8፥15 15፥62 1ሳሙ23፥ 29፤24፥1፤ሕዝ 47፥10 15፥63 ቁ8፤ ኢሱ 10፥1፤16፥10፤17፥12፤መሳ1፥21፤ 1ነገ9፥21፤ሕዝ48፥7 16፥1 ኢሱ8፥15፤12፥9

[ሸ]18 ዕብራይስጥና አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ብዙ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች ግን ዱመሳ 1፥14 ይመዕ አጥብቆ ነገራት ያላሉ:: [ቀ]1 ምናልባት፣ ዮርዳኖስ ዘኢያሪኮ የዮርዳኖስ ወንዝ የጥንት መጠሪያ ሊሆን ይችላል::

2ሎዛ ከምትባለው ከቤቴል ይነሣና በአጣ
ሮት ወደሚገኘው ወደ አርካውያን ግዛት
ይሻገራል፣ 3በዚያም በምዕራብ በኩል
ቍልቍል ወደ የፍሌጣውያን ግዛት እስከ
ታችኛው ቤትሖሮን ምድር ይወርድና
ወደ ጌዝር ዘልቆ ባሕሩ ላይ ይቆማል፡፡
4ስለዚህ የዮሴፍ ዘሮች ምናሴና ኤፍሬም
ርስታቸውን ተቀበሉ፡፡
5ለኤፍሬም ወገን በየጐሣ በየጐሣቸው
የተሰጣቸው ድርሻ ይህ ነው፤

ድንበሩ በምሥራቅ በኩል ከአጣ
ሮት አዳር ተነሥቶ እስከ ላይኛው
ቤትሖሮን ይወጣና፣ 6እስከ ባሕሩ ይዘ
ልቃል፡፡ በስተ ሰሜን ደግሞ ከሚ
ክምታት ተነሥቶ በምሥራቅ በኩል
ወደ ተአናት ሴሎ ይታጠፍና ከዚያ
በማለፍ እስከ ኢያኖክ ምሥራቅ
ይዘልቃል፤ 7ከኢያኖክም በመነሣት
ወደ አጣሮትና ወደ ነዓራት ቍልቍል
ይወርድና በኢያሪኮ በኩል አድርጎ
ዮርዳኖስ ላይ ብቅ ይላል፡፡ 8ድንበሩ
አሁንም ከታጱዋ በምዕራብ በኩል
አድርጎ ወደ ቃና ወንዝ ይወርድና
ከባሕሩ ላይ ይቆማል፡፡ እንግዲህ
የኤፍሬም ነገድ በየጐሣ በየጐሣ
ቸው የተካፈሉት ርስት ይህ ነበር፡፡
9ይህም በምናሴ ነገድ ርስት ውስጥ
ለኤፍሬም ዘሮች የተመደቡትን ከተ
ሞች በሙሉና መንደሮቻቸውን የሚ
ያጠቃልል ነው፡፡
10ይህ ሁሉ ሆኖ የኤፍሬም ዘሮች በጌ
ዝር የሚኖሩትን ከነዓናውያን ከዚያ
አላባረሯቸውም ነበር፤ ከነዓናውያን እስከ
ዛሬ ድረስ ከኤፍሬም ዘሮች ጋር አብ
ረው ይኖራሉ፤ ይሁን እንጂ የጕልበት
ሥራ እንዲሠሩ ይገደዳሉ፡፡

17 ምናሴ የዮሴፍ የበኵር ልጅ
እንደ መሆኑ መጠን፣ ለነገዱ
የተመደበለት ድርሻ ይህ ነበር፤ የምናሴ
የበኵር ልጅ ማኪር፣ የገለዓዳውያን አባት
ብርቱ ጦረኛ ስለነበር ገለዓድና ባሳን ድር
ሻው ሆኑ፡፡ 2ስለዚህ ይህ ርስት ለተቀሩት
የምናሴ ዘሮች ማለትም ለአቢዔዝር፣ ለኬ
ሌግ፣ ለእሥራኤል፣ ለሴኬም፣ ለኦፌር፣
ለሸሚዳ ጐሣዎች የተሰጠ ነው፤ እነዚህ በየ
ጐሣዎቻቸው የዮሴፍ ልጅ የምናሴ ሌሎች
ወንዶች ዝርያዎች ናቸው፡፡
3ሰለጰዓድ የአፌር ልጅ፣ የገለዓድ
ልጅ፣ የማኪር ልጅ፣ የምናሴ ልጅ ነው፡፡
እርሱም ሴቶች ልጆች እንጂ ወንዶች ልጆች
አልነበሩትም፡፡ የሴቶች ልጆቹም ስም
ማህለህ፣ ኑዓ፣ ዔግላ፣ ሚልካ፣ ቲርጻ
ይባላል፡፡ 4እነርሱም ወደ ካህኑ ወደ
አልዓዛር፣ ወደ ነዌ ልጅ ወደ ኢያሱና
ወደ መሪዎቹ ቀርበው፣ “ከወንድሞቻችን
ጋር ርስት እንድንካፈል እግዚአብሔር
ሙሴን አዞታል” አሏቸው፡፡ ስለዚህ ኢያሱ
እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት፣ ከአባታ
ቸው ወንድሞች ጋር ርስት ሰጣቸው፡፡
5ምናሴም ከገለዓድና ከባሳን ምድር ሌላ፣
ዐሥር ቦታ የሚደለደል የመሬት ክፍል
በዮርዳኖስ ምሥራቅ ነበረው፤ 6የምናሴ
ነገድ ሴት ልጆች ከወንዶቹ ጋር ርስት
ተካፍለዋልና፤ የገለዓድ ምድር ግን ለቀሩት
የምናሴ ዘሮች ተሰጠ፡፡

7የምናሴ ርስት ከአሴር አንሥቶ
ከሴኬም በስተ ምሥራቅ እስካለችው
እስከ ሚክምታት ይደርሳል፤ ድን
በሩም ወደ ደቡብ በመዝለቅ በዓ
ይንታጱዋ የሚኖረውን ሕዝብ ይጨ
ምራል፡፡ 8የታጱዋ ምድር የምናሴ
ይዞታ ነበር፤ ይሁን እንጂ በድን
በሩ ላይ የምትገኘው የታጱዋ ከተማ
የኤፍሬም ዘሮች ይዞታ ነበረች፤
9ከዚያም በመቀጠል ድንበሩ በደ
ቡብ በኩል ወደ ቃና ወንዝ ይደር
ሳል፡፡ በምናሴ ከተሞችም መካከል
የኤፍሬም ከተሞች ነበሩ፤ ያም
ሆኖ የምናሴ ድንበር የወንዙ ሰሜናዊ
ክፍል ሲሆን፣ እስከ ባሕሩ ይዘል
ቃል፡፡ 10በደቡብ በኩል ያለው ምድር
የኤፍሬም ሲሆን፣ በሰሜን በኩል
ያለው ደግሞ የምናሴ ነበር፤ የም
ናሴ ግዛት እስከ ባሕሩ የሚደርስ
ሲሆን፣ ሰሜናዊ ድንበሩ አሴር፣
ምሥራቃዊ ድንበሩ ደግሞ ይሳኮር
ነው፡፡

11እንዲሁም በይሳኮርና በአሴር
ውስጥ፤ ቤትሳን፣ ይብልዓም፣ የዶር
ሕዝብ፣ ዓይንዶር፣ ታዕናክና መጊዶ
በዙሪያቸው ካሉ ሰፈሮቻቸው ጋር
የምናሴ ነበሩ፤ ሦስተኛውም ናፎት
ነው[ሀ]፡፡
12ይሁን እንጂ የምናሴ ዘሮች እነዚ
ህን ከተሞች መያዝ አልቻሉም፤ ከነዓ
ናውያን የያዙትን ላለመልቀቅ ቍርጥ
ሐሳብ አድርገው ነበርና፡፡ 13እስራኤላው
ያን በበረቱ ጊዜ ግን ከነዓናውያንን
የጕልበት ሥራ እንዲሠሩ አስገደዷቸው፣
እንጂ ከዚያ ፈጽመው አላባረሯቸውም
ነበር፡፡
14የዮሴፍ ዘሮች ኢያሱን፣ “ቍጥራችን
ብዙ ነው፤ እግዚአብሔርም አብዝቶ ባርኮ

16፥2 ቍ5፤ዘፍ28፥19፤ዘኍ32፥3፤2ሳሙ15፥32
16፥3 ኢሱ10፥10፥33
16፥4 ኢሱ18፥5
16፥5 ቍ2፤ኢሱ10፥10፤18፥13
16፥6 ቍ7፤ኢሱ17፥7፤2ነገ15፥29
16፥7 ቍ6፤ዘኍ32፥3
16፥8 ኢሱ12፥17፤17፥9፤19፥28
16፥9 ሕዝ48፥5
16፥10 ኢሱ15፥63፤17፥13፤መሳ1፥28-29፤1ነገ9፥16
17፥1 ዘፍ41፥51፤50፥23፤ዘኍ1፥34፤ኢሱ12፥2፥5፤1ዜና7፥14
17፥2 ዘኍ26፥30፤27፥1፤ ኢሱ22፥7፤መሳ6፥ 11፥34፤8፥2፤1ዜና7፥14፥18፥19
17፥3 ዘኍ27፥1፤26፥33
17፥4 ዘኍ27፥5-7
17፥5 ኢሱ13፥30-31
17፥7 ቍ10፤ዘፍ12፥6፤ኢሱ16፥6፤19፥24፥31፤21፥6፥30፤21፥21፤24፥25፤መሳ1፥31፤5፥17፤6፥35፤7፥23፤9፥1
17፥8 ኢሱ12፥17
17፥9 ኢሱ16፥8
17፥10 ቍ7፤ዘፍ30፥18፤ሕዝ48፥5
17፥11 ቍ10፥16፤ኢሱ11፥2፤12፥21፤መሳ1፥27፤1ሳሙ28፥7፤31፥10፤2ሳሙ21፥12፤1ነገ4፥12፤9፥15፤2ነገ9፥27፤1ዜና7፥29፤መዝ83፥10፤ሕዝ 48፥4
17፥12 ኢሱ15፥63
17፥13 መሳ1፥27-28
17፥14 ዘኍ26፥28-37

[ሀ]11 ይኸውም ናፎት ዶር ነው፡፡

ናል፤ ታዲያ እንዴት ርስታችን አንድ ዕጣና
አንድ ድርሻ ብቻ ሆነ?” አሉት።
15ኢያሱም መልሶ፣ “ቍጥራችሁ ይህን
ያህል በዝቶ ኰረብታማው የኤፍሬም ምድር
እስከዚህ የሚጠባችሁ ከሆነ፣ ወደ ፌሪዛ
ውያንና ወደ ራፋይም ምድር ወጥታችሁ
ደኑን ለራሳችሁ መንጥሩ” አላቸው።
16የዮሴፍም ዘሮች፣ “ኰረብታማው አገር
አይበቃንም፤ ደግሞም በሜዳው ላይ
ያሉት በቤትሳንና በሰፈሮችዋ፣ እንዲሁም
በኢይዝራኤል ሸለቆ የሚኖሩት ከነዓ
ናውያን ሁሉ የብረት ሠረገሎች አሏቸው”
አሉት።
17ኢያሱ ግን ለዮሴፍ ዘሮች ለኤፍሬምና
ለምናሴ እንዲህ አላቸው፤ “እናንተ ቍጥ
ራችሁ ብዙ፣ እጅግም ኀያል እንደመሆና
ችሁ ድርሻችሁ አንድ ብቻ አይሆንም፤
18ነገር ግን ደን የለበሰው ኮረብታማው
አገር የእናንተ ነው፤ ሄዳችሁ መንጥሩት፣
ዳር ድንበሩ ሁሉ የእናንተ ይሆናል፤ ከነዓ
ናውያን የብረት ሠረገላ ቢኖራቸውና
ብርቱዎች ቢሆኑም እንኳ ከዚያ ታስወጧቸ
ዋላችሁ።”

## የቀሪው ምድር መከፋፈል

18 መላው የእስራኤላውያን ማኅበር
በሴሎ ተሰበሰቡ፣ የመገናኛው
ንም ድንኳን እዚያው ተከሉ፤ ምድሪቱም
ጸጥ ብላ ተገዛችላቸው። 2ዳሩ ግን ርስት ገና
ያልተሰጣቸው ሰባት የእስራኤል ነገዶች
ነበሩ።
3ስለዚህ ኢያሱ እስራኤላውያንን እንዲህ
አላቸው፤ “የአባቶቻችሁ አምላክ እግዚ
አብ
ሔር የሰጣችሁን ምድር ለመውረስ ቸል
የምትሉት እስከ መቼ ነው? 4አሁንም ከእ
ያንዳንዱ ነገድ ሦስት ሦስት ሰው ምረጡ፤
እኔም ምድሪቱን ተዘዋውረው እንዲያጠ
ኑና እያንዳንዱም ነገድ መውረስ የሚገባ
ውን ድርሻ ዝርዝር መግለጫ ጽፈው እን
ዲያመጡ እልካቸዋለሁ፤ ከዚያም ወደ እኔ
ይመለሳሉ። 5ምድሪቱንም ሰባት ቦታ ይከ
ፍሏታል፤ ይሁዳ በደቡብ፣ የዮሴፍ ዘሮች
በሰሜን በኩል የተመደበላቸውን ርስት
ይዘው ይኖራሉ። 6የሰባቱን የመሬት ክፍ
ፍል ዝርዝር መግለጫ ጽፋችሁ ወደኔ
ታመጡና በአምላካችን በእግዚአብሔር
ፊት ዕጣ እጥልላችኋለሁ። 7ሌዋውያኑ
ግን ለእግዚአብሔር የሚሰጡት የክህነት
አገልግሎት ርስታቸው ስለ ሆነ በእናንተ
መካከል ድርሻ አይኖራቸውም፤ ጋድ፣
ሮቤልና የምናሴ ነገድ እኩሌታም የእግዚ
አብሔር ባሪያ ሙሴ በምሥራቅ ዮርዳኖስ
የሰጣቸውን ርስት ቀደም አድርገው
ወስደዋል።”
8ሰዎቹ የምድሪቱን ሁኔታ ለማጥናትና
ለመመዝገብ ጕዞ ሲጀምሩ ኢያሱ፣ “ሄዳ
ችሁ የምድሪቱን ሁኔታ አጥኑና በዝርዝር
ከጻፋችሁ በኋላ ወደ እኔ ተመለሱ፤ እኔም
እዚሁ ሴሎ በእግዚአብሔር ፊት ዕጣ እጥ
ላላችኋለሁ” አላቸው። 9ስለዚህም ሰዎቹ
ሄደው ምድሪቱን ተዘዋውረው አዩ፤ ከነከተ
ሞቿም ሰባት ቦታ ከፍለው በጥቅልል ብራና
ላይ በዝርዝር ጻፉ፤ ከዚያም በሴሎ ሰፈር
ወዳለው ወደ ኢያሱ ተመለሱ። 10ኢያሱም
በሴሎ በእግዚአብሔር ፊት ዕጣ ጣለላቸው፤
ምድሪቱንም እንደየነገዱ ደልድሎ ለእስራ
ኤላውያን አከፋፈላቸው።

## ለብንያም ነገድ የተመደበው ድርሻ

11ለብንያም ነገድ የሆነው የመጀመሪ
ያው ዕጣ በየጐሣ በየጐሣው ወጣ፤ በዕጣ
የደረሳቸውም ምድር የሚገኘው በይሁዳና
በዮሴፍ ነገዶች ርስት መካከል ሲሆን
እንደሚከተለው ነው፤
12በሰሜን ያለው ድንበራቸው ከዮ
ርዳኖስ ይነሣና የኢያሪኮን ሰሜናዊ
ተረተር አልፎ፣ በስተ ምዕራብ ወዳ
ለው ኰረብታማ ምድር በማምራት፣
እስከ ቤትአዌን ምድረ በዳ ይዘል
ቃል። 13ከዚያ ደግሞ ወደ ደቡብ
ሎዛ ማለት ወደ ቤቴል ተረተር ይሻ
ገርና በታችኛው ቤትሖሮን በስተ
ደቡብ ባለው ተራራ በኩል አድርጎ
ወደ አጣሮት አዳር ይወርዳል።
14በስተ ደቡብ ያለው ድንበር ከቤት
ሖሮን ትይዩ ካለው ኰረብታ ተነ
ሥቶ፣ በምዕራብ በኩል ወደ ደቡብ
በመታጠፍ፣ የይሁዳ ነገድ ከተማ
ወደ ሆነችው ወደ ቂርያትበኣል ማለት
ወደ ቂርያትይዓሪም ያልፋል፤ ይህ
እንግዲህ በምዕራብ በኩል ያለው
ድንበር ነው።
15በስተ ደቡብ ያለው ድንበር ደግሞ
በምዕራብ በኩል ከቂርያትይዓሪም
ጥግ ይነሣና እስከ ነፍቶ ውሃ ምንጭ
ይዘልቃል፤ 16ይኸው ድንበር ከራፋ
ይም ሸለቆ በስተ ሰሜን ባለው በሄ
ኖም ሸለቆ ትይዩ ቍልቍል ወደ
ኰረብታው ግርጌ ይወርዳል፤ ከዚ
ያም ከኢያቡሳውያን ከተማ በደ
ቡብ በኩል ባለው ተረተር አድርጎ
ወደ ሄኖም ሸለቆ በመውረድ እስከ
ዓይንሮጌል ይዘልቃል። 17ደግሞም
ወደ ሰሜን ይታጠፍና በቤትሳሚስ
በኩል አድርጎ እስከ ጌሊሎት ይዘ

17፥15 ዘፍ14፥5፤ ኢሱ3፥10፤15፥8፤ 18፥16፤2ሳሙ5፥18፤18፥6፤23፥13፤ኢሳ 15፥8፤17፥5
17፥16 ቊ11፥18፤ ኢሱ15፥56፤መሳ1፥19፤4፥3፥13፤1ሳሙ 29፥1
17፥17 ሕዝ48፥5
17፥18 ቊ16፤ 1ሳሙ1፥1
18፥1 ቊ10፥89፤ዘፀ 27፥21፤40፥2፤ኢሱ19፥51፤21፥2፤መሳ18፥31፤21፥12፥19፤1ሳሙ 1፥3፤3፥21፤4፥3፤1ነገ14፥2፤መዝ78፥60፤ኤር7፥12፤26፥6፤40፥2፤41፥5፤ሐሥ 7፥45
18፥4 ቊ8፤ሚክ 2፥5
18፥5 ኢሱ15፥1፤ 16፥1-4
18፥6 ዘሌ16፥8
18፥7 ኢሱ13፥8፥33
18፥8 ቊ1፥4
18፥10 ቊ1፤ዘኍ 33፥54፤34፥13፤ኢሱ 19፥51፤ኤር7፥12
18፥12 ኢሱ7፥2፤ 8፥15
18፥13 ዘፍ28፥19፤ ዘኍ32፥3፤ኢሱ 12፥9፤16፥5
18፥14 ኢሱ9፥ 17፤10፥10
18፥15 ኢሱ15፥9
18፥16 ኢሱ15፥7፥ 8፤17፥15
18፥17 ኢሱ፤15፥6፥ 7፤22፥10

ልቃል፤ ከዚያም በአዱሚም
መተላለፊያ ትይዩ እስካለው እስከ
ሮቤል ልጅ እስከ ቦሀን ድንጋይ
ይወርዳል። 18ወደ ቤትዓረባ ሰሜ
ናዊ ተረተር በመቀጠል ቍልቍል
ወደ ዐረባ ይወርዳል። 19ከዚያም ሰሜ
ናዊን የቤትሖግላንን ተረተር አልፎ
ይሄድና በስተ ደቡብ የዮርዳኖስ
ወንዝ እስከሚገባበት እስከ ሙት
የባሕር ወሽመጥ ይዘልቃል፤ ይህም
ደቡባዊ ድንበሩ ነው።
20በምሥራቅ በኩል ያለው ድንበር፣
ራሱ የዮርዳኖስ ወንዝ ነው።
ይህ እንግዲህ የብንያም ነገድ ጐሣዎች
በርስትነት የወረሷት ምድር ዳር ድንበ
ሮቿ ሁሉ እነዚህ ነበሩ።

21የብንያም ነገድ በየጐሣቸው የያዟቸው ከተ
ሞች እነዚህ ናቸው፤
ኢያሪኮ፣ ቤትሖግላ፣ ዓመቀጺጽ፣
22ቤትዓረባ፣ ዘማራይም፣ ቤቴል፣ 23ዓዊም፣
ፋራ፣ ኤፍራታ፣ 24ክፌርዓሞናይ፣ ዖፍኒ
እንዲሁም ጋባ ናቸው፤ እነዚህም ከነ
መንደሮቻቸው ዐሥራ ሁለት ከተሞች
ናቸው።
25ገባዖን፣ ራማ፣ ብኤሮት፣ 26ምጽጳ፣
ከፊራ፣ አሞቂ፣ 27ሬቄም፣ ይርጵኤል፣
ተርአላ፣ 28ጼላ፣ ኤሌፍ፣ የኢያቡሳው
ያን ከተማ ኢየሩሳሌም፣ ጊብዓ እንዲ
ሁም ቂርያት ነበሩ፤ እነዚህም ከነመንደ
ሮቻቸው ዐሥራ አራት ከተሞች ናቸው።
እንግዲህ የብንያም ነገድ በየጐሣቸው
የወረሱት ይህ ነበር።

## ለስምዖን ነገድ የተመደበው ድርሻ

19፥2-10 ተጓ ምብ-1 ዜና 4፥28-33

19 ሁለተኛው ዕጣ ለስምዖን ነገድ በየ
ጐሣ በየጐሣው ወጣ፤ ርስታቸውም
ዙሪያውን በይሁዳ ነገድ ርስት የተከበበ
ነበር፤ 2ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፤
ቤርሳቤህ፣ ሼባ፣ ሞላዳ፣ 3ሐጸር
ሹዓል፣ ባላ፣ ዔጼም፣ 4ኤልቶላድ፣
በቱል፣ ሔርማ፣ 5ጺቅላግ፣ ቤት
ማርካ ቦት፣ ሐጸርሱሳ፣ 6ቤተለባኦትና
ሻሩሔን ነበሩ፤ እነዚህ ዐሥራ ሦስት
ከተሞችና መንደሮቻቸው ናቸው።
7ዓይን፣ ሪሞን፣ ዔቴርና ዓሻን የተባ
ሉት አራት ከተሞቻቸውና መንደሮቻ
ቸው፣ 8ደግሞም እስከ ባዕላትብኤር ወይም
ኔጌብ ውስጥ እስካለው እስከ ራማት
ድረስ ባሉት ከተሞች ዙሪያ የሚገኙት
መንደሮች ሁሉ ከእነዚሁ ጋር ይጠ
ቃለላሉ።
እንግዲህ በየጐሣው የተደለደለው የስም
ዖን ነገድ ርስት ይህ ነበር። 9የይሁዳ ነገድ

18፥18 ኢሱ11፥2፤ 15፥6
18፥19 ዘፍ14፥3፤ ኢሱ15፥6
18፥20 1ሳሙ9፥1
18፥21 ኢሱ15፥6
18፥22 ኢሱ15፥6፤ 16፥1፤2ዜና13፥4
18፥23 ዘዳ2፥23፤መሳ 6፥11፡24፤8፥27፡32፤9፥ 5፤1ሳሙ13፥17
18፥24 ኢሱ21፥17፤ 1ሳሙ13፥3፡16፤ 14፥5፤1ነገ15፥22፤ 2ነገ23፥8፤ኢሳ10፥29
18፥25 ኢሱ9፥3፡ 17፤10፥40፤መሳ4፥5፤1 9፥13፤1ሳሙ1፥1፡19፤ 2፥11፤7፥17፤25፥1፤ 1ነገ15፥17፡21፤ዕዝ 2፥25፡26፤ነህ7፥29፤11 ፥33፤ኢሳ10፥29፤ ኤር31፥15፤40፥1
18፥26 ኢሱ9፥17፤ 11፥3፤ዕዝ 2፥25፤ ነህ7፥29
18፥28 ኢሱ9፥17፤ 10፥1፤15፥8፡57፤2ሳሙ 21፥14፤ሕዝ 48፥23
19፥1 ዘፍ49፥7
19፥2 ዘፍ21፥14፤ ኢሱ15፥26፤1ነገ19፥3
19፥3 ኢሱ15፥28፡29
19፥4 ዘኍ14፥ 45፤ኢሱ15፥30
19፥5 ኢሱ15፥31
19፥7 ኢሱ15፥32፡42
19፥8 ኢሱ10፥40
19፥9 ዘፍ49፥7፤ሕዝ 48፥24
19፥10 ቍ12፥16፡ 27፡34፤ኢሱ21፥7፡34፤
19፥11 ኢሱ12፥22
19፥12 ቍ10፤ኢሱ 21፥28፤1ዜና6፥72
19፥13 ኢሱ11፥22፤ 15፥32
19፥14 ቍ27
19፥15 ዘፍ35፥19፤ ኢሱ11፥1፤21፥35
19፥16 ቍ10፤ሕዝ 48፥26
19፥17 ዘፍ30፥18
19፥18 ኢሱ15፥56፤ 1ሳሙ28፥4፤1ነገ1፥3፤ 2ነገ4፥8
19፥20 ኢሱ21፥28
19፥21 ኢሱ15፥34
19፥22 ኢሱ15፥10፤ መሳ4፥6፡12፤8፥18፤መ ዝ89፥12፤ኤር46፥18
19፥23 ዘፍ49፥15፤ ኢሱ17፥10፤ሕዝ48፥ 25
19፥24 ኢሱ17፥7
19፥25 ኢሱ11፥1

የያዘው ርስት እጅግ ሰፊ ስለ ነበር፣ ከይ
ሁዳ ነገድ ድርሻ ተከፍሎ ለስምዖን ነገድ
በርስትነት ተሰጠ ፤ ከዚህ የተነሣም የስም
ዖን ነገድ በይሁዳ ነገድ ድርሻ ርስት ሊካ
ፈል ቻለ።

## ለዛብሎን ነገድ የተመደበው ድርሻ

10ሦስተኛው ዕጣ ለዛብሎን ነገድ በየጐሣ
በየጐሣው ወጣ፤
የርስታቸውም ድንበር እስከ ሣሪድ
ይደርሳል፤ 11ወደ ምዕራብም በመሄድ
በመርዓላ በኩል ያልፋል፤ ደባሼትን
ተጠግቶም በዮቅንዓም አጠገብ እስካ
ለው ወንዝ ድረስ ይዘልቃል። 12ከሣሪ
ድም ወደ ምሥራቅ በመታጠፍ፣ የፀ
ሓይ መውጫ ወደ ሆነው አገር ወደ
ኪስሎትታቦር በመዝለቅ እስከ ዳብራት
ሄዶ ወደ ያፊዓ ያቀናል፤ 13ከዚያም
ወደ ምሥራቅ በመቀጠል፤ ወደ
ጋትሔ ፍርና ወደ ዒትቃጺን ይዘል
ቃል፤ ከዚያ ደግሞ ወደ ሪሞን
በመሄድ፣ ወደ ኒዓ ይታጠፋል።
14በስተ ሰሜንም በኩል ወደ ሐናቶን
ይዞርና በይፍታሕኤል ሸለቆ ላይ
ይቆማል። 15ደግሞም ቀጣትን፣
ነህላልን፣ ሺምሮንን፣ ይዳላንና
ቤተልሔምን ይጨምራል፤ እነዚ
ህም ከነመንደሮቻቸው ዐሥራ ሁለት
ከተሞች ናቸው።
16እነዚህ ሁሉ ለዛብሎን ነገድ ርስት
ሆነው ለየጐሣ ለየጐሣው የተደለደሉ
ከተሞችና መንደሮቻቸው ነበሩ።

## ለይሳኮር ነገድ የተመደበው ድርሻ

17አራተኛው ዕጣ ለይሳኮር ነገድ በየጐሣ
በየጐሣው ወጣ፤ 18ምድራቸውም የሚከ
ተሉትን ያካትታል፤
ኢይዝራኤል፣ ከስሎት፣ ሱነም፣
19ሐፍራይም፣ ሺኦን፣ አናሐራት፣
20ረቢት፣ ቂሶን፣ አቤጽ፣ 21ሬሜት፣
ዐይንጋኒም፣ ዐይንሐዳ እንዲሁም
ቤትጳጼጽ። 22ድንበራቸውም ታቦ
ርና፣ ሻሕጹማን፣ ቤትሳሚስን ይነ
ካና በዮርዳኖስ ላይ ያቆማል፤ እነዚህ
ከነመንደሮቻቸው ዐሥራ ስድስት
ከተሞች ናቸው።
23እነዚህ ለይሳኮር ነገድ ርስት ሆነው
ለየጐሣ ለየጐሣው የተደለደሉ ከተሞ
ችና መንደሮቻቸው ነበሩ።

## ለአሴር ነገድ የተመደበው ድርሻ

24አምስተኛ ዕጣ ለአሴር ነገድ በየጐሣ
በየጐሣው ወጣ፤ 25ምድራቸውም የሚከተ
ሉትን ያካትታል፤

ሔልቃት፣ ሐሊ፤ ቤጤን፣ አዚፍ፣
[26]አላሜሌክ፣ ዓምዓድ እንዲሁም
ሚሽአል። ድንበሩ በስተ ምዕራብ
ቀርሜሌስንና ሺሖርሊብናትን ይነ
ካል፣ [27]ከዚያም በምሥራቅ በኩል
ወደ ቤትዳጎን ይመለስና ዛብሎን
ንና የይፍታሕኤልን ሸለቆ ይዞ ካቡ
ልን በስተ ግራ በመተው በሰሜን
በኩል ወደ ቤትዔሜቅና ወደ ንዒ
ኤል ይቃናል። [28]በመቀጠልም ወደ
ዔብሮን[ቸ]፣ ወደ ረአብ፣ እንዲሁም
ወደ ሐሞንና ወደ ቃና ሽቅብ ወጥቶ
እስከ ታላቁ ሲዶና ይደርሳል።
[29]ድንበሩ ወደ ራማ ከዞረ በኋላ ወደ
ተመሸገው ወደ ጢሮስ ከተማ ታጥፎ
ወደ ሖሳ ይመለስና በአክዚብ በኩል
ሜድትራኒያን ባሕር ደርሶ ይቆማል፤
[30]ይህም የዑማን፣ የአፌቅንና የረ
አብን ምድር ይጨምራል። በዚ
ህም ሃያ ሁለት ከተሞችና መንደ
ሮቻቸው ይገኛሉ።
[31]እነዚህ ለአሴር ነገድ ሆነው በየጐ
ሣው የተደለደሉ ከተሞችና መንደሮቻ
ቸው ነበሩ።

## ለንፍታሌም ነገድ የተመደበው ድርሻ

[32]ስድስተኛው ዕጣ ለንፍታሌም ነገድ በየ
ጐሣ በየጐሣው ወጣ፤
[33]ድንበራቸውም ከሔሌፍና በጸዕነ
ኒም ካለው ከትልቁ የወርካ ዛፍ ይነ
ሣና በአዳሚኔቄብና በየብኒኤል አልፎ
ወደ ለቁም በመምጣት ዮርዳኖስ ላይ
ይቆማል፤ [34]ድንበሩ በአዝኖት ታቦር
ያልፍና ወደ ምዕራብ በመታጠፍ ሑቆቅ
ላይ ይቆማል፤ ይኸው ድንበር በደ
ቡብ ዛብሎንን፣ በምዕራብ አሴርን፣
በምሥራቅ ዮርዳኖስን ይነካል[ኀ]።
[35]የተመሸጉትም ከተሞች እነዚህ ናቸው፤
ጺዲም፣ ጼር፣ ሐማት፣ ረቃት፣ ኬኔሬት፣
[36]አዳማ፣ ራማ፣ አሶር፣ [37]ቃዴስ፣ ኤድራይ፣
ዐይንሐጾር፣ [38]ይርኦን፣ ሚግዳልኤል፣
ሖሬም፣ ቤትዓናትና ቤትሳሚስ። እነዚህ
ከነመንደሮቻቸው ዐሥራ ዘጠኝ ከተሞች
ናቸው።
[39]እነዚህ ለንፍታሌም ነገድ ርስት ሆነው በየ
ጐሣው የተደለደሉ ከተሞችና መንደሮች
ነበሩ።

## ለዳን ነገድ የተመደበው ድርሻ

[40]ሰባተኛው ዕጣ ለዳን ነገድ በየጐሣው
ወጣ፤ [41]የወረሱትም ምድር የሚከተሉ
ትን ያካትታል፤
ጾርዓ፣ ኤሽታኦል፣ ዒርሼሜሽ፣
[42]ሸዕለቢን፣ ኤሎን፣ ይትላ፣ [43]ኤሎን፣
ተምና፣ አቃሮን፣ [44]ኢልተቄ፣ ገባ
ቶን፣ ባዕላት፣ [45]ይሁድ፣ ብኔብረቅ፣
ጋትሪሞን፣ [46]ሜያርቆንና በኢዮጴ
ፊት ለፊት ያለው ርቆን።
[47]ነገር ግን የዳን ዘሮች ርስታቸው አል
በቃቸውም፣ ወደ ሌሼም ወጥተው አደጋ
በመጣል ያዟት፤ ሰዎቹንም በሰይፍ ስለት
ፈጅተው ይዞታቸው አደረጓት፤ በዚያው
ሰፈሩ፤ ስሟንም ለውጠው በአባታቸው
ስም ዳን አሏት።
[48]እነዚህ ለዳን ነገድ ርስት ሆነው በየጐ
ሣው የተደለደሉ ከተሞችና መንደሮች
ነበሩ።

## ለኢያሱ የተመደበው ድርሻ

[49]እስራኤላውያን ድርሻ ድርሻቸውን ከያዙ
በኋላ፣ ለነዌ ልጅ ለኢያሱ በመካከላቸው
ርስት ሰጡት፤ [50]*እግዚአብሔር* ባዘዘውም
መሠረት በኰረብታማው የኤፍሬም ምድር
የምትገኘውን ተምናሴራ የምትባለውን
የፈለጋትን ከተማ ሰጡት፤ እርሱም ከተ
ማዪቱን ሠራ፤ መኖሪያውም አደረጋት።
[51]እንግዲህ ካህኑ አልዓዛር፣ የነዌ ልጅ ኢያ
ሱና የእስራኤል ነገድ የየጐሣ መሪዎች ሴሎ
ላይ በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ፣ *በእግዚ
አብሔር* ፊት ዕጣ ያደላደሉት ርስት ይህ
ነው፤ የምድሪቱንም አከፋፈል በዚህ ሁኔታ
ፈጸሙ።

## የመማጠኛ ከተሞች

20፥1-9ማመ-ዘኍ35፥9-34፤ዘዳ4፥41-43፤19፥1-14

20 ከዚያም *እግዚአብሔር* ኢያሱን
እንዲህ አለው፤ [2]“በሙሴ በኩል
በነገርኋችሁ መሠረት የመማጠኛ ከተሞች
እንዲለዩ ለእስራኤላውያን ንገራቸው፤
[3]ሳያስበው ድንገት ሰው የገደለ ማንኛውም
ሰው ወደዚያ በመሸሽ ከደም ተበቃዩ እን
ዲያመልጥ ከተማዪቱ መጠለያ ትሁን።
[4]“ገዳዩ ከነዚህ ከተሞች ወደ አንዲቱ
በሚሸሽበት ጊዜ፣ በከተማዪቱ መግቢያ
በር ላይ ቆሞ ጕዳዩን ለከተማዪቱ ሽማግ
ሌዎች ይንገራቸው፤ ከዚያም እነርሱ ወደ
ከተማቸው አስገብተው የሚኖሩበትን ስፍራ
ሰጥተውት አብሮአቸው ይቀመጥ። [5]ደም
ተበቃዩ ተከታትሎት ቢመጣ፣ ሆን ብሎና
በክፋት ተነሣሥቶ ወንድሙን የገደለው
ባለ መሆኑ፣ ሰዎቹ ነፍሰ ገዳዩን አሳል
ፈው አይስጡት። [6]በማኅበሩ ፊት ለፍርድ

19፥26 ኢሱ12፥22፤ 21፥30፤1ነገ18፥19፤ 2ነገ2፥25
19፥27 ቀኍ10፥14፤ ኢሱ15፥41፤1ነገ9፥13
19፥28 ቀኍ30፤ዘፍ 10፥19፤ዘኍ13፥21፤ኢሱ 16፥8፤21፥30፤መሳ1፥ 31፤1ዜና6፥74፥76
19፥29 ኢሱ15፥44፤ 18፥25፤መሳ5፥17፤ 2ሳሙ5፥11፤24፥7፤ ዕዝ3፥7፤መዝ45፥ 12፤ኢሳ23፥1፤ኤር 25፥22፤ሕዝ26፥2
19፥30 ቀኍ28፤ኢሱ 12፥18
19፥31 ዘፍ30፥13፤ ኢሱ17፥7፤ሕዝ48፥2
19፥33 ኢሱ15፥11፤ መሳ4፥11
19፥34 ቀኍ10፤1ዜና 6፥75
19፥35 ኢሱ11፥2፤ 1ዜና2፥55
19፥36 ኢሱ11፥ 1፤18፥25
19፥37 ዘኍ21፥33፤ ኢሱ12፥22
19፥38 ኢሱ15፥10፤ መሳ1፥33
19፥39 ሕዝ48፥3
19፥41 ኢሱ15፥33
19፥42 ኢሱ10፥12
19፥43 ዘፍ38፥12፤ ኢሱ13፥3
19፥44 ኢሱ21፥23፤ 1ነገ9፥18፤15፥27፤16፥ 15፤2ዜና8፥6
19፥45 ኢሱ21፥24፤ 1ዜና6፥69
19፥46 2ዜና2፥ 16፤ዕዝ3፥7፤ዮና 1፥3፤ሐሥ9፥36
19፥47 ዘዳ3፥14፤መ ሳ 18፥1፥7፥14፥27፥29
19፥48 ዘፍ30፥6
19፥50 ኢሱ24፥30፤ መሳ2፥9
19፥51 ኢሱ14፥1፤ 18፥10፤23፥10፤ ሐሥ13፥19
20፥3 ዘሌ4፥2፤ ዘኍ35፥12
20፥4 ዘፍ23፥10፤ ኢሱ7፥6፤ኤር38፥7
20፥6 ዘኍ35፥12

[ቸ]28 አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጂዎች ከዚህ ጋር ይስማ ማሉ፤ ነገር ግን ጥቂት ቅጂዎች ኢሱ21፡30 ይመ፣ አብዩን ይላሉ። [ኀ]34 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ነገር ግን የዕብራይስጡ ቅጂ በምስራቅ ይሁዳንና ዮርዳኖስን ይከባል ይላል።

እስኪቀርብና በዚያ ጊዜ የሚያገለግለው
ሊቀ ካህናት እስኪሞት ድረስ በዚያች
ከተማ ይቆይ፡፡ ከዚያም ወደ ቤቱ፣ ሸሽቶ
ወደ መጣበት ከተማ ሊመለስ ይችላል፡፡”
7ስለዚህም በኰረብታማው በንፍታሌም
ምድር በገሊላ ቃዴስን፣ በኰረብታማው
በኤፍሬም ምድር ሴኬምን፣ በኰረብታ
ማው በይሁዳ ምድር ኬብሮን የምትባለ
ውን ቂርያትአርባቅን ለዩ፡፡ 8እንደዚሁም
ከዮርዳኖስ ማዶ ከኢያሪኮ' በስተምስራቅ
በሮቤል ነገድ ይዞታ ውስጥ ከፍታ ባለው
ምድረ በዳ ያለችውን ቦሶርን፣ በጋድ
ነገድ ይዞታ ውስጥ ባለችው በገለዓድ
የምትገኘውን ራሞትንና በምናሴ ነገድ
ይዞታ ውስጥ በባሳን የምትገኘውን ጎላንን
ለዩ፡፡ 9ሳያስበው በድንገት ሰው የገደለ
ማንኛውም እስራኤላዊ ወይም በመካከላ
ቸው የሚኖር ማንኛውም መጻተኛ ወደ
ተለዩት ከተሞች መሸሽ ይችላል፤ በማ
ኅበሩ ፊት ከመቆሙ አስቀድሞም ደም
ተበቃዩ መገደል የለበትም፡፡

## ለሌዋውያን የተመደቡ ከተሞች

21፥4-39 ተጓ ማብ-1ዜና 6፥54-80

21 የሌዋውያን ቤተሰብ አለቆች ወደ
ካህኑ ወደ አልዓዛር፣ ወደ ነዌ
ልጅ ወደ ኢያሱና ወደ ሌሎቹ የእስራ
ኤል ነገድ አባቶች ዘንድ ቀረቡ፤ 2በከነዓን
ምድር በሴሎም፣ “እግዚአብሔር የምንኖ
ርባቸውን ከተሞች፣ ከብቶቻችን ከሚሰ
ማሩባቸው ቦታዎች እንድትሰጡን በሙሴ
በኩል አዞልን ነበር” አላቸው፡፡ 3ስለዚህ
እስራኤላውያን ከወረሱት ምድር ላይ
የሚከተሉትን ከተሞችና መሰማሪያዎች
እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት ለሌዋው
ያኑ ሰጡ፤
4የመጀመሪያው ዕጣ ለቀዓት ዘሮች
በየጐሣቸው ወጣ፤ የካህኑ የአሮን ዝርያዎች
ለሆኑት ሌዋውያን ከይሁዳ፣ ከስምዖንና
ከብንያም ነገዶች ዐሥራ ሦስት ከተሞች
በዕጣ ተመደቡላቸው፡፡ 5ለቀሩት ለቀዓት
ዘሮች ደግሞ ከኤፍሬምና ከዳን ነገድ
ጐሣዎች፣ እንዲሁም ከምናሴ ነገድ እኩ
ሌታ ጐሣዎች ዐሥር ከተሞች በዕጣ
ተመደቡላቸው፡፡
6ለጌርሶን ዝርያዎች ከይሳኮር፣ ከአ
ሴር፣ ከንፍታሌም ነገድ ጐሣዎችና ባሳን
ውስጥ ካለው ከምናሴ ነገድ እኩሌታ
ጐሣዎች ዐሥራ ሦስት ከተሞች ተመደ
ቡላቸው፡፡
7ለሜራሪ ዝርያዎች በየጐሣቸው ከሮ
ቤል፣ ከጋድና ከዛብሎን ነገዶች ዐሥር
ከተሞች ተመደቡላቸው፡፡

8ስለዚህ እስራኤላውያን እግዚአብሔር
በሙሴ በኩል ባዘዘው መሠረት፣ እነዚ
ህን ከተሞችና መሰማሪያቸውን ለሌዋው
ያኑ በዕጣ መደቡላቸው፡፡

9ከይሁዳና ከስምዖን ነገዶች ደግሞ ከዚህ
በታች በስም የተጠቀሱትን ከተሞች በዕጣ
መደቡላቸው፡፡ 10እነዚህም ከተሞች የሌዊ
ልጆች፣ የቀዓት ጐሣዎች ለሆኑት ለአ
ሮን ዝርያዎች ተመደቡ፤ ይህም የሆ
ነው የመጀመሪያው ዕጣ ለእነርሱ ስለ
ወጣላቸው ነበር፤
11እነርሱም በተራራማው የይሁዳ
ምድር ያለችውን ኬብሮን የተባ
ለችውን ቂርያት አርባቅን በዙሪ
ያዋ ካለው መሰማሪያ ጋር ሰጧቸው፤
አርባቅ የዔናቅ አባት ነበረ፡፡ 12ይሁን
እንጂ በከተማዪቱ ዙሪያ ያሉትን
ዕርሻዎችና መንደሮች ለዮፎኒ ልጅ
ለካሌብ ርስት አድርገው ሰጡት፡፡
13እንደዚሁም ለነፍስ ገዳይ መማጠኛ
የሆነችውን ኬብሮንንና ልብናን
ከነማሰማሪያቸው ለካህኑ ለአሮን ልጆች
ሰጧቸው፤ 14ደግሞም የቲርን፣
ኤሽትሞዓን፣ 15ሖሎንን፣ ዳቤርን፣
16ዐይንን፣ ዮጣንና ቤትሳሚስን ከነ
ማሰማሪያቸው ሰጧቸው፤ እነዚህ
ዘጠኙ ከተሞች ከሁሉ ነገዶች ይዞታ
ላይ ተከፍለው የተሰጡ ናቸው፡፡
17ከብንያም ነገድ ገባዖን፣ ጌባዕ፣
18ዓናቶትና አልሞን የተባሉትን አራት
ከተሞች ከነማሰማሪያዎቻቸው ሰጧቸው፡፡
19ለካህናቱ ለአሮን ዝርያዎች ከነማሰማሪያ
ቸው የተሰጧቸው ከተሞች ዐሥራ ሦስት
ነበሩ፡፡
20የሌዊ ልጅ የቀዓት ጐሣዎች ለሆኑት
ለሌሎቹ ደግሞ ከኤፍሬም ነገድ ላይ
ተከፍለው የሚከተሉት ከተሞች በዕጣ
ተመደቡላቸው፡፡
21በተራራማው በኤፍሬም ምድ
ርም ለነፍሰ ገዳይ መማጠኛ የሆ
ነችው ሴኬምና ጌዝር፣ 22ቂጠ
ብጻይሞና ቤትሖሮን ከነመሠማሪ
ያዎቻቸው አራት ከተሞች ተሰጡ
አቸው፡፡
23እንዲሁም ከዳን ነገድ ኤልተ
ቄን፣ ገባቶን፤ 24ኤሎንና ጋትሪ
ሞን ከነመሰማሪያዎቻቸው አራት
ከተሞች ተሰጧቸው፡፡
25ከምናሴ ነገድ እኩሌታ ደግሞ
ታዕናክና ጋትሪሞን ከነማሰማሪያ
ዎቻቸው ሁለት ከተሞች ተሰጧቸው፡፡

20፥7 ዘፍ12፥6፤35፥27፤ኢሱ10፥36፤12፥22፤ሉቃ1፥39
20፥8 ኢሱ12፥2፡5፤21፥36፤1ዜና6፥71፡78፡80
20፥9 ዘፀ21፥13፤ዘሌ4፥2
21፥1 ኢሱ14፥1
21፥2 ዘሌ25፥32፤ዘኍ35፥2-3፤ኢሱ14፥4፤18፥1
21፥4 ቊ19፤ዘኍ3፥17
21፥5 ቊ26
21፥6 ዘፍ30፥18፤ዘኍ3፥17፤ኢሱ17፥7
21፥7 ቊ40፤ዘፀ6፥16፤ኢሱ19፥10
21፥11 ዘፍ23፥2፤ኢሱ10፥36
21፥12 ኢሱ15፥13
21፥13 ዘኍ33፥20፤35፥6
21፥14 ኢሱ15፥48፡50
21፥16 ዘኍ34፥11፤ኢሱ15፥10፡55
21፥17 ኢሱ9፥3፤18፥24፤ነህ11፥31
21፥18 2ሳሙ23፥27፤1ነገ2፥26፤ዕዝ2፥23፤ነህ7፥27፤11፥32፤ኢሳ10፥30፤ኤር1፥1፤11፥21፤32፥7
21፥19 ቊ4፤2ዜና31፥15
21፥21 ኢሱ10፥33፤17፥7
21፥22 ኢሱ10፥10፤1ሳሙ1፥1
21፥23 ኢሱ19፥44
21፥24 ኢሱ10፥12፤19፥45
21፥25 ኢሱ12፥21

'8 ምናልባት፣ ዮርዳኖስ ዘኢያሪኮ የዮርዳኖስ ወንዝ የጥንት
መጠሪያ ሊሆን ይችላል፡፡

26እነዚህ ዐሥር ከተሞች ሁሉ ከነማሰ
ማሪያዎቻቸው ለተቀሩት የቀዓት ጐሣ
ዎች ተሰጧቸው።

27የጌርሶን ወገኖች ለሆኑት ለሌሎቹ
የሌዋ ጐሳዎች የተሰጧቸው የሚከተ
ሉት ናቸው፤

ከምናሴ ነገድ እኩሌታ በባሳን
ውስጥ ለነፍሰ ገዳይ መማጠኛ የሆ
ነችው ከተማ ጎላንና በኤሽትራ
እነዚህ ሁለት ከተሞች ከነመሰማሪ
ያዎቻቸው፤

28ከይሳኮር ነገድ፣
ቂሶን፣ ዳብራት፣ 29የርሙትና ዓይን
ጋኒም፣ እነዚህ አራት ከተሞች
ከነመሰማሪያዎቻቸው፤

30ከአሴር ነገድ፣
ሚሽአል፣ ዓብዶን፣ 31ሔልቃትና
ረአብ እነዚህ አራት ከተሞች ከነ
መሰማሪያዎቻቸው፤

32ከንፍታሌም ነገድ፣
በገሊላ ውስጥ ለነፍሰ ገዳይ መማ
ጠኛ የሆነችው ከተማ ቃዴስ፣ ሐሞ
ትዶርና ቀርታን እነዚህ ሦስት
ከተሞች ከነመሰማሪያዎቻቸው፤

33ለጌድሶናውያን ጐሣዎች የተመደ
ቡት ከተሞች ሁሉ ከነማሰማሪያዎቻ
ቸው ዐሥራ ሦስት ነበሩ።

34የሜራሪ ጐሣዎች ለሆኑት ለተቀሩት
ሌዋውያን የተሰጧቸው የሚከተሉት
ናቸው፤

ከዛብሎን ነገድ ዮቅንዓም፣ ቀርታ፣
35ዲሞናና ነህላል፣ እነዚህ አራት
ከተሞች ከነመሰማሪያዎቻቸው፤

36ከሮቤል ነገድ፣
ቦሶር፣ ያህጽ፣ 37ቅዴሞትና ሜፍዓት፣
እነዚህ አራት ከተሞች ከነመሰማሪያዎ
ቻቸው፤

38ከጋድ ነገድ፣
በገለዓድ ውስጥ ለነፍሰ ገዳይ መማጠኛ
የሆነችው ከተማ ራሞት መሃና
ይም፣ 39ሐሴቦንና ኢያዜር፣ እነዚህ
አራት ከተሞች ከነመሰማሪያዎቻ
ቸው፡-

40የሜራሪ ጐሣዎች ለሆኑት ለተቀሩት
ሌዋውያን የተመደቡት ከተሞች ሁሉ ዐሥራ
ሁለት ነበሩ።

41እንግዲህ እስራኤላውያን ርስት አድር
ገው ከያዙት ምድር ለሌዋውያኑ የተሰጧ
ቸው ከተሞች ከነማሰማሪያዎቻቸው ባጠ
ቃላይ አርባ ስምንት ነበሩ። 42እነዚህም
ከተሞች እያንዳንዳቸው በዙሪያቸው ማሰ
ማሪያዎች ነበሯቸው፤ ማሰማሪያ የሌለው
ከተማ አልነበረም።

43ስለዚህ እግዚአብሔር ለቀድሞ አባቶ
ቻቸው ይሰጣቸው ዘንድ የማለላቸውን
ምድር ሁሉ ለእስራኤል ሰጠ፤ እነርሱም
ምድሪቱን ወረሱ፣ መኖሪያቸውም አደረ
ጓት። 44እግዚአብሔር ለቀድሞ አባቶቻ
ቸው እንደ ማለላቸው በዙሪያቸው ካሉት
አሳረፋቸው፤ አንድም ጠላት ሊቋቋማቸው
አልቻለም፤ እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን
ሁሉ አሳልፎ በእጃቸው ሰጥቶአቸዋልና።
45እግዚአብሔር ለእስራኤል ቤት ከሰጠው
መልካም የተስፋ ቃል አንዳችም አልቀ
ረም፤ ሁሉም ተፈጽሞአል።

## ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ርስት ያገኙ ነገዶች ወደ ቤታቸው ተመለሱ

22 በዚህ ጊዜ ኢያሱ የሮቤልንና የጋ
ድን ነገዶች፣ እንዲሁም የምና
ሴን ነገድ እኩሌታ ጠርቶ፣ 2እንዲህ አላ
ቸው፤ "የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ ያዘዘ
ውን ሁሉ ጠብቃችኋል፤ እኔም ያዘዝኋች
ሁን በሙሉ ፈጽማችኋል፤ 3ከረጅም ጊዜ
ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ወንድሞቻችሁን
አልተዋችሁም፤ አምላካችሁ እግዚአብሔር
የሰጣችሁን ተልእኮ በሚገባ ተወጥታች
ኋል። 4አሁንም አምላካችሁ እግዚአብሔር
በሰጣችሁ ተስፋ መሠረት ወንድሞቻች
ሁን አሳርፎአቸዋል፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር
ባሪያ ሙሴ ከዮርዳኖስ ማዶ ርስት አድ
ርጎ በሰጣችሁ ምድር ወዳለው ቤታችሁ
ተመለሱ። 5የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ፣
አምላካችሁን እግዚአብሔርን
እንድትወዱ፣ በመንገዱ ሁሉ
እንድትሄዱ፣ ትእዛዙን እንድትፈጽሙ፣
እርሱም አጥብቃችሁ እን ድትይዙት
እንዲሁም በፍጹም ልባችሁ፣ በፍጹም
ነፍሳችሁ እንድታገለግሉት የሰጣችሁን
ትእዛዙንና ሕጉን ነቅታችሁ
ጠብቁ።"

6ከዚያም ኢያሱ መርቆ አሰናበታቸው፤
እነርሱም ወደ ቤታቸው ተመለሱ። 7ሙሴ
ለምናሴ ነገድ እኩሌታ በባሳን ምድር
ርስት ሰጥቶአቸው ነበር፤ ለቀረው እኩሌታ
ደግሞ ኢያሱ ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ
ከወንድሞቻቸው ጋር ርስት ሰጣቸው።
ኢያሱ ወደ ቤታቸው እንዲገቡ ባሰናበ
ታቸው ጊዜ መረቃቸው፤ 8እንዲህም
አላቸው፤ "ብዙ ሀብት ይዛችሁ ማለትም
አያሌ የከብት መንጋ፣ ብርና ወርቅ፣
ናስና ብረት እንዲሁም ቍጥሩ እጅግ
የበዛ ልብስ ይዛችሁ ወደ ቤታችሁ
ተመለሱ፤ ከጠላት የተገኘውንም ይህን
ምርኮ ከወንድሞቻችሁ ጋር ተካፈሉት"
አላቸው።

21፥26 ቍ5
21፥27 ዘኍ35፥6፤ ኢሱ12፥5
21፥28 ዘፍ30፥18፤ ኢሱ19፥12፡20
21፥29 ኢሱ10፥3፤ 15፥34
21፥30 ኢሱ17፥7፤ 19፥26፡28
21፥31 ኢሱ19፥28
21፥32 ዘኍ35፥6፤ ኢሱ 12፥22
21፥33 ቍ6
21፥34 ኢሱ12፥22፤ 19፥10
21፥35 ኢሱ19፥15
21፥36 ዘኍ21፥23፤ ዘዳ2፥32፤ኢሱ20፥8፤ መሳ11፥20
21፥37 ኢሱ13፥18
21፥38 ዘፍ32፥2፤ ዘዳ4፥43፤ኢሱ12፥2
21፥39 ኢሱ13፥25
21፥40 ቍ7
21፥41 ዘኍ35፥7
21፥43 ዘዳ11፥31፤ 17፥14፤34፥4
21፥44 ዘፀ23፥31፤ 33፥14፤ዘዳ6፥19፤ 21፥10
21፥45 ኢሱ23፥14፤ ነህ9፥8
22፥2 ዘኍ32፥25
22፥4 ዘፀ33፥14፤ ዘኍ32፥18፡22፤ዘዳ3፥20፤ኢሱ1፥13-15
22፥5 ዘዳ5፥29፤6፥5፤ኢሱ23፥11፤ኢሳ 43፥22፤ ሚል3፥14
22፥6 ዘፍ24፥60፤ ዘፀ39፥43
22፥7 ዘኍ32፥19፤ኢሱ12፥5፤14፥13፤17፥2፤ሉቃ24፥50
22፥8 ዘፍ49፥27፤ ዘኍ31፥22፡27፤ዘዳ20፥14፤1ሳሙ30፥16፤ 2ሳሙ1፥1፤ኢሳ9፥3

9ስለዚህ የሮቤልና የጋድ ነገዶች እንዲ
ሁም የምናሴ ነገድ እኩሌታ እስራኤላው
ያንን ከነዓን ውስጥ ባለችው በሴሎ
ትተው፣ በእግዚአብሔር ትእዛዝ በሙሴ አማ
ካይነት ወደ ተቀበሏት ርስታቸው፣ ወደ
ገለዓድ ምድር ተመለሱ።
10የሮቤልና የጋድ እንዲሁም የምናሴ
ነገድ እኩሌታ በከነዓን ምድር ወዳለችው፣
ዮርዳኖስ አጠገብ ወደምትገኘው ገሊሎት
ወደ ተባለች ስፍራ ሲደርሱ በወንዙ አጠ
ገብ ግዙፍ መሠዊያ ሠሩ። 11የእስራኤላው
ያን ይዞታ በሆነችው በከነዓናውያን ምድር
ወሰን በገሊሎት ላይ መሠዊያ መሥራ
ታቸውን፣ ሌሎቹ እስራኤላውያን በሰሙ
ጊዜ፣ 12በእነርሱ ላይ ለመዝመት፣ የእስራ
ኤል ማኅበር ሁሉ በሴሎ ተሰበሰቡ።
13ስለዚህም እስራኤላውያን የካህኑ የአ
ልዓዛርን ልጅ ፊንሐስን በገለዓድ ምድር
ወደ ሚኖሩት ወደ ሮቤልና ወደ ጋድ እን
ዲሁም ወደ ምናሴ ነገድ እኩሌታ ላኩ፤
14ከእርሱም ጋር እያንዳንዱን የእስራኤልን
ነገድ የሚወክሉ ዐሥር አለቆች አብረው
ላኩ፤ እነዚህም እያንዳንዳቸው ከእስራኤላ
ውያን ጐሣዎች የተውጣጡ የየቤተ ሰቡ
አለቆች ነበሩ።
15እነርሱም በገለዓድ ምድር ወዳሉት
ወደ ሮቤላውያን፣ ወደ ጋዳውያንና ወደ
ምናሴ ነገድ እኩሌታ ሄደው እንዲህ
አሏቸው፤ 16"መላው የእግዚአብሔር ጉባኤ
እንዲህ ይላል፤ 'በእስራኤል አምላክ ላይ
እንዲህ ያለ ክህደት የፈጸማችሁት ለምን
ድን ነው? እግዚአብሔርን ከመከተልስ
እንዴት ወደ ኋላ ትላላችሁ? እንዴትስ
ዛሬ በእግዚአብሔር ላይ ዐምፃችሁ ለራ
ሳችሁ መሠዊያ ትሠራላችሁ? 17በፌጎር
የተሠራው ኀጢአት አይበቃንምን? ምንም
እንኳ በእግዚአብሔር ጉባኤ ላይ መቅሠ
ፍት ቢወርድም፣ እስከ ዛሬዪቱ ዕለት
ድረስ ራሳችንን ከዚያች ኀጢአት አላነጻ
ንም። 18እናንተ፣ አሁንም እግዚአብሔርን
ከመከተል ወደ ኋላ ትላላችሁን?
"'ዛሬ እናንተ በእግዚአብሔር ላይ
ብታምፁ፣ እርሱ ደግሞ ነገ በመላው እስ
ራኤል ጉባኤ ላይ ይቈጣል። 19የወረሳ
ችኋት ምድር ረክሳ እንደ ሆነ፣ የእግዚ
አብሔር ማደሪያ ወደ ተተከለበት ወደ
እግዚአብሔር ምድር መጥታችሁ ከእኛ
ጋር ርስት ተካፈሉ፤ ነገር ግን ከአምላካችን
ከእግዚአብሔር መሠዊያ በስተቀር ሌላ መሠ
ዊያ ሠርታችሁ በእግዚአብሔርም ሆነ
በእኛ ላይ አታምፁ። 20የዛራ ልጅ አካን፣
እርም የሆነውን ነገር በመውሰድ ኀጢአት
ስለ ሠራ፣ በመላው የእስራኤል ጉባኤ ላይ
ቍጣ አልመጣምን? በሠራው ኀጢአት
የሞተውም[ኘ] እርሱ ብቻ አልነበረም።"
21ከዚያም የሮቤልና የጋድ ነገዶች
እንዲሁም የምናሴ ነገድ እኩሌታ ለእስራ
ኤልጐሣ መሪዎች እንዲህ ሲሉ መለሱላ
ቸው፤ 22"ኀያሉ አምላክ፣ እግዚአብሔር!
ኀያሉ አምላክ፤ እግዚአብሔር! እርሱ
ያውቃል! እስራኤልም ይህን ይወቅ! ይህ
የተደረገው በማመፅ ወይም ለእግዚአብሔር
ባለመታዘዝ ከሆነ፣ ዛሬ አትማሩን! 23መሠ
ዊያውን የሠራነው እግዚአብሔርን ከመከ
ተል ወደ ኋላ ለማለት፣ የሚቃጠል መሥ
ዋዕትና የእህል ቍርባን ልናሳርግበት
ወይም የኅብረት መሥዋዕት[ኦ] ልናቀር
ብበት አስበን ከሆነ፣ ራሱ እግዚአብሔር
ይበቀለን።
24"እኛማ ይህን ያደረግነው፣ ወደፊት
ዘሮቻችሁ ለዘሮቻችን እንዲህ እንዳይ
ሏቸው ፈርተን ነው፤ 'ከእስራኤል አምላክ
ከእግዚአብሔር ጋር ምን ግንኙነት አላ
ችሁ? 25እናንት የሮቤልና የጋድ ልጆች፤
እግዚአብሔር ዮርዳኖስን በመካከላችን
መለያ ድንበር ስላደረገው፣ ከእግዚአብሔር
ዘንድ ድርሻ የላችሁም።' ስለዚህ ዘሮቻችሁ፣
የእኛ ዘር እግዚአብሔርን እንዳይፈራ ሊያ
ደርጉ ይችላሉ።
26"እኛም 'እንነሣና መሠዊያ እንሥራ፤
የምንሠራው መሠዊያ ግን ለሚቃጠል
መሥዋዕት ወይም ለሌላ መሥዋዕት ማቅ
ረቢያ አይውልም' ያልነው ለዚህ ነው።
27በሌላም በኩል የሚቃጠል መሥዋዕታ
ችንን፣ ሌላውን ቍርባናችንንና የኅብረት
መሥዋዕታችንን ይዘን በተቀደሰው ስፍራ
እግዚአብሔርን እንደምናመልክ መሠዊ
ያው በእኛና በእናንተ እንዲሁም በሚቀ
ጥሉት ትውልዶች መካከል ምስክር ይሆ
ናል። ስለዚህ ወደፊት ዘሮቻችሁ ዘሮቻች
ንን፣ 'ከእግዚአብሔር ዘንድ ድርሻ የላች
ሁም' ሊሏቸው አይችሉም።
28"እኛም፣ 'ወደ ፊት እኛንም ሆነ ዘሮቻ
ችንን እንዲህ የሚሉ ከሆነ፣ "እነሆ፤ አባቶቻ
ችን የሠሩትን የእግዚአብሔርን መሠዊያ
ምሳሌ ተመልከቱ፤ ይህ በእኛና በእናንተ
መካከል ምስክር እንዲሆን እንጂ፣ ለሚቃጠል
መሥዋዕትና ለሌላ መሥዋዕት ማቅረቢያ
አይደለም ብለን እንመልሳለን' አልን።
29"በማደሪያው ድንኳን ፊት ካለው ከእግዚ
አብሔር መሠዊያ ሌላ፣ ለሚቃጠል መሥዋዕት
ወይም ለእህል ቍርባን እንዲሁም ለሌላ

[ኘ]20 የዕብራይስጡ ቃል አንድን ሰው ወይም ነገር ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠት ማለት ነው። [ኦ]23 በዚህና በቍጥር 27 ላይ በትውፊት የሰላም መሥዋዕት በመባል ይታወቃል።

22፥9 ዘኍ32፥26፤ ኢሱ18፥1
22፥10 ቀኍ19፥26-27፤ኢሱ18፥17፤ ኢሳ19፥19፤56፥7
22፥12 ኢሱ18፥1
22፥13 ዘኍ3፥32፤ 25፥7፤ኢሱ24፥33
22፥14 ቀኍ32፤ ዘኍ1፥4
22፥16 ዘዳ7፥3፤ 12፥13-14፤1ሳሙ13፥13፤15፥11
22፥17 ዘኍ23፥28፤ 25፥1-9
22፥18 ዘሌ10፥6
22፥19 ቀኍ10፤ዘፀ 26፥1
22፥20 ዘሌ10፥6፤ኢሱ7፥1፡5፤መዝ7፥11
22፥22 ዘዳ10፥17፤ 1ሳሙ2፥3፤16፥7፤1ነገ 8፥39፤1ዜና28፥9፤መዝ 11፥4፤40፥9፤44፥21፤50፥1፤139፥4፤ኤር17፥10
22፥23 ዘዳ12፥11፤ 18፥19፤1ሳሙ20፥16፤ኤር41፥5
22፥27 ዘፍ21፥30፤ ዘዳ12፥6፤ኢሱ24፥27፤ ኢሳ19፥20
22፥28 ዘፍ21፥30
22፥29 ዘፀ26፥1፤ ኢሱ24፥16

መሥዋዕት ማቅረቢያ የሚሆን መሠዊያ
በመሥራት ዛሬ በእግዚአብሔር ላይ እናምፅን?
እርሱን ማምለካችንንም እንተውን? ይህ ከእኛ
ይራቅ!”
30ካህኑ ፊንሐስና የእስራኤላውያን የጐሣ
መሪዎች የነበሩት የማኅበረ ሰቡ አለቆች
የሮቤል፣ የጋድና የምናሴ ወገኖች ያሉትን
በሰሙ ጊዜ ተደሰቱ። 31የካህኑ የአልዓዛር
ልጅ ፊንሐስም፣ የሮቤልን የጋድንና የምና
ሴን ወገኖች “በዚህ ነገር እግዚአብሔርን
አልበደላችሁምና፣ እግዚአብሔር ከእኛ
ጋር መሆኑን ዛሬ ዐውቀናል፤ እነሆ እስራ
ኤላውያንን ከእግዚአብሔር እጅ አድናች
ኋል” አላቸው።
32ከዚያም የካህኑ የአልዓዛር ልጅ ፊንሐ
ስና መሪዎቹ፣ ከሮቤልና ከጋድ ወገኖች
ጋር በገለዓድ ምድር ከተነጋገሩ በኋላ፣
ወደ ከነዓን ተመልሰው፣ ሁኔታውን ለእስ
ራኤላውያን ነገሩ። 33እስራኤላውያንም
ይህን ሲሰሙ ደስ ብሎአቸው እግዚአብሔ
ርን አመሰገኑ፤ ከዚያም የሮቤልና የጋድ
ወገኖች የሚኖሩበትን አገር በጦርነት ለማ
ጥፋት የመሄድን ነገር አላነሡም።
34የሮቤልና የጋድ ወገኖችም፣ እግዚ
አብሔር አምላክ ለመሆኑ፣ ይህ በመካከላ
ችን ምስክር ነው፤ በማለት መሠዊያውን
“ምስክር” ብለው ጠሩት።

## ኢያሱ ለመሪዎች የተናገረው የመሰናበቻ ቃል

23 እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በዙ
ሪያቸው ካሉት ጠላቶቻቸው ሁሉ
ካሳረፋቸው እነሆ፣ ብዙ ዘመን አለፈ፤ በዚህ
ጊዜ ኢያሱ በጣም አርጅቶ፣ ዕድሜውም
ገፍቶ ነበር፤ 2ኢያሱ እስራኤልን ሁሉ አለ
ቆቻቸውን፣ መሪዎቻቸውን፣ ፈራጆቻቸው
ንና ሹማምንታቸውን በሙሉ ጠርቶ እንዲህ
አላቸው፤ “እኔ አርጅቻለሁ፤ ዕድሜዬም
ገፍቶአል። 3አምላካችሁ እግዚአብሔር ስለ
እናንተ ሲል በእነዚህ ሕዝቦች ሁሉ ላይ
ያደረገውን ማናቸውንም ነገር እናንተው ራሳ
ችሁ አይታችኋል፤ ስለ እናንተ የተዋጋ
ላችሁ ራሱ አምላካችሁ እግዚአብሔር ነው።
4ከዮርዳኖስ አንሥቶ በስተ ምዕራብ እስካ
ለው እስከ ታላቁ ባሕር[ከ] ድረስ በሙሉ ካሸነ
ፍኋቸው ሕዝቦች ያልወረሳችሁትን ቀሪ ምድር
ርስት እንዲሆን ለየነገዶቻችሁ እንዴት
አድርጌ በዕጣ እንዳከፋፈልኋችሁ አስታ
ውሱ። 5ራሱ አምላካችሁ እግዚአብሔር
ከፊ ታችሁ ያስወግዳቸዋል፤ ከፊታችሁም
ያሉብትን ስፍራ ያስለቅቃቸዋል፤ አምላካችሁ
እግዚአብሔር በሰጣችሁም ተስፋ መሠ
ረት ምድራቸውን ትወርሳላችሁ።
6“በርቱ፤ ወደ ግራም ወደ ቀኝም ሳትሉ

22፥31 2ዜና15፥2
22፥32 ቀኍ14
22፥33 1ዜና29፥20፤ ዳን2፥19፤ሉቃ2፥28
22፥34 ዘፍ21፥30
23፥1 ዘዳ12፥9፤ኢሱ 13፥1፤21፥44
23፥2 ኢሱ7፥6፤13፥ 1፤24፥1
23፥3 ዘፀ14፥14፤ ዘዳ20፥4
23፥4 ዘኍ34፥2፡ 6፤ኢሱ19፥51፤መዝ 78፥55
23፥5 ቀኍ13፤ዘፀ 23፥30፤መሳ2፥21፤መዝ 44፥5፤ኤር46፥15
23፥6 ዘዳ17፥20፤ 28፥61፤ኢሱ1፥7
23፥7 ዘፀ20፥5፤23፥ 13፤ኤር5፥7፤12፥16
23፥8 ዘዳ10፥20
23፥9 ዘዳ7፥24፤ 11፥23
23፥10 ዘፀ14፥14፤ ዘሌ26፥8፤መሳ3፥31
23፥11 ዘዳ4፥15፤ ኢሱ22፥5
23፥12 ዘፍ34፥9፣ ዘፀ34፥16፤መዝ 106፥34-35
23፥13 ቀኍ5፤ዘፀ10፥ 7፤ዘኍ33፥55፤ዘዳ1፥8፤ 1ነገ9፥7፤2ነገ25፥21
23፥14 ኢሱ21፥45፤ 1ነገ2፥2፤መዝ119፥ 140፤145፥13
23፥15 ዘሌ26፥17፤ ዘዳ28፥15፤ኢሱ24፥20፤ 1ነገ8፥56፤14፥10፤2ነገ 22፥16፤ኢሳ24፥6፤34፥ 5፤43፥28፤ኤር6፥19፤ 11፥8፤33፥14፤35፥17፤ 39፥16፤40፥2፤ሚል4፥6
24፥1 ዘፍ12፥6፤ 49፥2፤ኢሱ7፥6፤23፥2፤ 1ሳሙ12፥7፤1ነገ8፥14
24፥2 ዘፍ11፥26፡32

በሙሴ የሕግ መጽሐፍ የተጻፈውን ሁሉ
ለመጠበቅና ለማድረግ እጅግ በርቱ።
7በመካከላችሁ ከቀሩት ከእነዚህ ሕዝቦች
ጋር አትተባበሩ፤ የአማልክቶቻቸውን ስም
አትጥሩ፤ አትማሉባቸው፤ አታገልግሏ
ቸው፤ አትስገዱላቸውም፤ 8ነገር ግን እስካ
ሁን እንዳደረጋችሁት ሁሉ አምላካችሁን
እግዚአብሔርን አጥብቃችሁ ያዙ።
9“እግዚአብሔር ታላላቅና ኀያላን ሕዝቦ
ችን ከፊታችሁ አሳድዶ አስወጥቶአቸዋል፤
እስከ ዛሬም ድረስ ማንም ሊቋቋማችሁ
አልቻለም። 10አምላካችሁ እግዚአብሔር
በሰጣችሁ ተስፋ መሠረት የሚዋጋላችሁ
ስለ ሆነ፣ ከእናንተ አንዱ ሰው ሺውን
ያሳድዳል። 11ስለዚህ አምላካችሁን እግዚ
አብሔርን ለመውደድ ተጠንቀቁ።
12ነገር ግን ከእርሱ ተመልሳችሁ ተር
ፈው በመካከላችሁ ከሚገኙት ከእነዚህ ሕዝ
ቦች ጋር ብትተባበሩ፣ በጋብቻም ብትተሳ
ሰሩና ብትቀላቀሉ፣ 13አምላካችሁ እግዚአ
ብሔር ከእንግዲህ ከፊታችሁ እንደማያወ
ጣቸው ይህን ልታውቁ ይገባል፤ አምላካ
ችሁ እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ከዚህች መል
ካም ምድር እስክትጠፉ ድረስም ወጥመ
ድና አሽክላ፣ ለጀርባችሁ ጅራፍ፣ ለዐይኖ
ቻችሁም እሾኽ ይሆኑባችኋል።
14“እነሆ፤ አሁን የምድርን ሁሉ መንገድ
ልሄድ ነው፤ አምላካችሁ እግዚአብሔር
ከሰ ጣችሁ መልካም ተስፋ ሁሉ አንዲተ
ን እንኳ እንዳላስቀረባችሁ፣ በፍጹም
ልባችሁ በፍጹም ነፍሳችሁ ታውቃላችሁ፤
አንዱም ሳይቀር ሁሉም ተፈጽሞአል።
15ነገር ግን አምላካችሁ እግዚአብሔር
የሰጣችሁ መል ካሙ ተስፋ በሙሉ እንደ
ተፈጸመ ሁሉ፣ እንደዚሁም አምላካችሁ
እግዚአብሔር ከሰ ጣችሁ ከመልካሚቱ
ምድር እስኪያጠፋ ችሁ ድረስ ክፉውን
ነገር ያመጣባችኋል። 16አምላካችሁ እግዚ
አብሔር ያዘዛችሁን ኪዳን ብታፈርሱ፣
ሄዳችሁም ሌሎችን አማልክት ብታገለግሉና
ብትሰግዱላቸው የእግዚአብሔር ቍጣ
በላያችሁ ይነዳል፤ ከሰጣችሁም ከመ
ልካሚቱ ምድር በፍጥነት ትጠፋላችሁ።”

## ቃል ኪዳኑ በሴኬም ታደሰ

24 ከዚያም ኢያሱ የእስራኤልን ነገ
ዶች ሁሉ በሴኬም ሰበሰበ፤ የእስ
ራኤልንም ሽማግሌዎች፣ መሪዎች፣ ፈራጆ
ችና ሹማምንት ጠራ፤ እነርሱም በእግዚአ
ብሔር ፊት ቆሙ።
2ኢያሱም ሕዝቡን ሁሉ እንዲህ አላቸው፤
“የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲ
ህ ይላል፤ ‘የቀድሞ አባቶቻችሁ፣
የአብርሃም

[ከ]4 የሜድትራንያን ባሕር ነው።

ንና የናኮርን አባት ታራን ጨምሮ ከብዙ
ዘመን በፊት ከወንዙ ማዶ ኖሩ[ኸ]፤ ሌሎች
ንም አማልክት አመለኩ:: 3እኔ ግን አባታ
ችሁን አብርሃምን ከወንዙ ማዶ ካለው ምድር
አምጥቼ፣ በከነዓን ምድር ሁሉ መራሁት፤
ዘሮቹን አበዛሁለት፤ ይስሐቅንም ሰጠሁት::
4ለይስሐቅ ያዕቆብንና ዔሳውን ሰጠሁት፤
ለዔሳውም ኰረብታማውን የሴይርን ምድር
ርስት አድርጌ ሰጠሁት፤ ያዕቆብና ልጆቹ
ግን ወደ ግብፅ ወረዱ::
5 “‘ከዚያም ሙሴንና አሮንን ላክሁ፤ ባመ
ጣሁት መቅሰፍት ግብፃውያንን አስጨ
ንቄ፣ እናንተን ከዚያ አወጣኋችሁ::
6አባቶቻችሁን ከግብፅ ባወጣኋቸው ጊዜ፣
ወደ ባሕሩ መጣችሁ፤ ግብፃውያንም በሠ
ረገሎችና[ሠ] በፈረሰኞች እስከ ቀይ ባሕር[ዐ]
ድረስ ተከታተሏቸው:: 7እነርሱ ግን ወደ
*እግዚአብሔር* ጮኹ፤ እርሱም በእናንተ ና
በግብፃውያን መካከል ጨለማ እንዲሆን
አደረገ:: ባሕሩን በላያቸው አመጣ፤ አሰጠ
ማቸውም:: በግብፃውያን ላይ ያደረግሁት
ንም ራሳችሁ በዐይናችሁ አያችሁ፤ በምድረ
በዳም ብዙ ጊዜ ኖራችሁ::
8“ ‘በምሥራቅ ዮርዳኖስ ወደሚኖሩት
ወደ አሞራውያን ምድር አመጣኋችሁ፤
እነርሱ ወጓችሁ፤ እኔ ግን አሳልፌ በእ
ጃችሁ ሰጠኋቸው፤ ከፊታችሁ አጠፋኋ
ቸው፤ እናንተም ምድራቸውን ወረሳ
ችሁ:: 9የሞዓብ ንጉሥ የሴፎር ልጅ
ባላቅ፣ እስራኤልን ለመውጋት ተነሣ፣
እናንተንም መጥቶ ይረግማችሁ ዘንድ
ወደ ቢዖር ልጅ ወደ በለዓም መልእክ
ተኛ ላከ፤ 10እኔ ግን በለዓምን ልሰማው
አልፈለግሁም፤ ስለዚህ ደግሞ ደጋግሞ
መረቃችሁ፤ እኔም፤ ከባላቅ እጅ ታደ
ግኋችሁ::
11“ ‘ከዚያም ዮርዳኖስን ተሻገራችሁ ወደ
ኢያሪኮ መጣችሁ፤ አሞራውያን፣ ፌርዛ
ውያን፣ ከነዓናውያን፣ ኬጢያውያን፣ ጌርጌ
ሳውያን፣ ኤዊያውያንና ኢያቡሳውያን እንደ
ወጓችሁ ሁሉ፤ የኢያሪኮም ነዋሪዎች ወጓ
ችሁ:: 12በፊታችሁ ተርብ ላክሁ፤ ይህም
እነርሱንና ሁለቱን የአሞራውያን ነገሥ
ታት ጭምር ከፊታችሁ አሳደደ፤ ይህ ደግሞ
በራሳችሁ ሰይፍና ቀስት ያደረጋችሁት
አይደለም:: 13ስለዚህ ያልደከማችሁበትን
ምድርና ያልሠራችኋቸውን ከተሞች ሰጠ
ኋችሁ፤ እነሆ፤ በከተሞቹ ትኖራላችሁ፤
ካልተከላችሁት የወይን ተክልና የወይራ
ዛፍ ትበላላችሁ::’
14“አሁንም *እግዚአብሔርን* ፍሩ፤ በፍ
ጹም ታማኝነትም ተገዙለት:: የቀድሞ
አባቶቻችሁ ከወንዙ ማዶና በግብፅ ያመ
ለኳቸውን አማልክት ከእናንተ አርቁ፤
*እግዚአብሔርን* ብቻ አምልኩ:: 15*እግዚአ
ብሔርን* ማምለክ የማያስፈልግ መስሎ
ከታያችሁ ግን፣ የቀድሞ አባቶቻችሁ
ከወንዙ ማዶ ካመለኳቸው አማልክት ወይም
በምድራቸው የምትኖሩባቸው አሞራውያን
ከሚያመልኳቸው አማልክት ታመልኩ እንደ
ሆነ የምታመልኩትን ዛሬውኑ ምረጡ፤
እኔና ቤቴ ግን *እግዚአብሔርን* እናመል
ካለን::”
16ከዚያም ሕዝቡ እንዲህ ሲል መለሰ፤
“ሌሎችን አማልእክት ለማምለክ ብለን
እግዚአብሔርን መተው ከእኛ ይራቅ::
17እኛንና የቀደሙ አባቶቻችንን ከዚያ
ከጦርነት ምድር ከግብፅ ያወጣን፣ በፊታ
ችንም እነዚያን ታላላቅ ምልክቶች ያደረገ
ማነው? ራሱ አምላካችን *እግዚአብሔር*
አይደለምን? በጕዞአችን ላይና ባለፍንባ
ቸውም ሕዝቦች ሁሉ ዘንድ የጠበቀን
እርሱ ነው:: 18እንዲሁም *እግዚአብሔር*
በምድሪቱ የሚኖሩትን አሞራውያንን
ጨምሮ ሕዝቦችን ሁሉ ከፊታችን አሳ
ደደ፤ ስለዚህ እኛም *እግዚአብሔርን* እናመ
ልካለን፤ አምላካችን ነውና::”
19ኢያሱም ሕዝቡን እንዲህ አለ፤ “እግዚ
አብሔርን ማምለክ አትችሉም፤ እርሱ
ቅዱስ አምላክና፤ ቀናተኛም አምላክ ነው፤ ዐ
መ ፃችሁን ወይም ኀጢአታችሁን ይቅር
አይ ልም:: 20*እግዚአብሔርን* ትታችሁ ባዕዳን
አማ ልክትን የምታመልኩ ከሆነ፣
መልካም ነገር ካደረገላችሁ በኋላ ተመልሶ
ክፉ ነገር ያደርግባችኋል፤ ያጠ
ፋችኋልም::”
21ሕዝቡ ግን ኢያሱን፣ “የለም! እኛ *እግ
ዚአብሔርን* እናመልካለን” አሉት::
22ከዚያም ኢያሱ፣ “እንግዲህ *እግዚአብሔርን*
ለማምለክ መርጣችኋልና በራሳችሁ ላይ ምስክ
ሮች ናችሁ” አላቸው:: እነርሱም፣ “አዎን
ምስ ክሮች ነን” ሲሉ መለሱ::
23ኢያሱም፣ “እንግዲህ በመካከላችሁ
ያሉትን ባዕዳን አማልክት አስወግዱ፤
ልባችሁንም ወደ እስራኤል አምላክ ወደ
*እግዚአብሔር* መልሱ” አላቸው::
24ሕዝቡም ኢያሱን፣ “እኛ አምላካችንን
*እግዚአብሔርን* እናመልካለን፤ እንታዘዝለ
ታለንም” አሉት::
25በዚያን ቀን ኢያሱ ከሕዝቡ ጋር ቃል
ኪዳን አደረገ፤ የሚመሩበትንም ደንብና
ሥርዐት እዚያው ሴኬም ሰጣቸው:: 26ኢያ
ሱም እነዚህን ቃሎች *በእግዚአብሔር* የሕግ

24፥3 ዘፍ1፥28፤12፥1፡2፤21፥3
24፥4 ዘፍ14፥6፤25፥26፤46፥5-6፤ዘኍ24፥18
24፥5 ዘፀ3፥10፤12፥51
24፥6 ዘፀ14፥9፡22፡23
24፥7 ዘፀ14፥10፡20፡28፤19፥4፤ዘዳ1፥46
24፥8 ዘፀ23፥23፤ዘኍ21፥31
24፥9 ዘኍ22፥2፡6፤23፥7
24፥10 ዘኍ23፥11፤ዘዳ23፥5
24፥11 ዘፍ15፥18-21፤ዘፀ14፥29፤23፥23፤ዘዳ7፥1፤ኢሱ3፥10፤6፥1
24፥12 ዘፀ23፥28፡31፤መዝ44፥3፡ 6-7፤135፥11
24፥13 ዘፀ6፥8፤ዘዳ6፥10-11
24፥14 ቀኊ23፤ዘፍ31፥19፤ዘፀ12፥12፤18፥11፤20፥3፤ዘኍ25፥2፤ዘዳ10፥12፤11፥28፤18፥13፤መሳ10፥16፤ሩት1፥ 15፤1ሳሙ12፥14፡24፤ኢዮ23፥15፤መዝ19፥9፤119፥120፤ኢሳ55፥7፤ሕዝ23፥3፤ 2ቆሮ1፥12
24፥15 ዘፍ35፥2፤መሳ6፥10፤ሩት1፥15፡16፤2፥12፤1ነገ18፥21፤ዳን3፥18
24፥16 ኢሱ22፥29
24፥17 ዘፀ10፥1፤መሳ6፥8
24፥18 ዘፍ28፥21፤ዘፀ23፥31፤ዘዳ33፥27፤ሐሥ7፥45
24፥19 ዘፀ20፥5፤23፥21፤34፥7፤ዘሌ11፥44፤20፥26
24፥20 ኢሱ23፥15፤1ሳሙ12፥25፤1ዜና28፥9፡20፤2ዜና24፥18፤ሆሴ13፥1፤ሐሥ7፥42
24፥22 ቀኊ27፤ዘዳ25፥9፤ሩት4፥10፤መዝ119፥30፡173፤ኢሳ8፥2፤43፥10፤44፥8፤ኤር42፥5፤ሚል2፥14
24፥23 ቀኊ14፤1ነገ8፥58፤መዝ119፥36፤141፥4፤ኤር31፥33
24፥24 ዘፀ19፥8፤ኤር42፥6
24፥25 ዘፀ15፥25፤24፥8፤ኢሱ17፥7
24፥26 ዘፍ12፥6፤28፥18፤ዘዳ17፥18፤27፥2፤28፥61፤31፥24፤መሳ4፥11

[ኸ]2 በዚህ እንዲሁም ቍጥር 3፡14 እና 15 ላይ የተጠቀሰው የኤፍራጥስ ወንዝ ነው:: [ሠ]6 ወይም *ሠረገለኞች* ተብሎ መተርጐም ይቻላል። [ዐ]6 ዕብራይስጡ *ያም ሳውፍ* ይላል፤ ይኸውም የደንገል ባሕር ማለት ነው::

መጽሐፍ ጻፋቸው፤ ትልቅ ድንጋይም
ወስዶ በባሉጥ ዛፍ ሥር፣ በተቀደሰው *በእግ
ዚአብሔር* ስፍራ አጠገብ አቆመው፡፡
27ኢያሱም ሕዝቡን ሁሉ፣ "እነሆ፤ ይህ
ድንጋይ፣ *እግዚአብሔር* የተናገረንን ሁሉ
ሰምቶአል፣ በእኛም ይመሰክርብናል፤ እና
ንተም በአምላካችሁ ዘንድ እውነተኞች
ሆና ችሁ ባትገኙ ምስክር ይሆንባችኋል"
አላቸው፡፡

## ኢያሱ በተሰፋዪቱ ምድር ተቀበረ

24፥29-31ተጓ ምብ-መሳ 2፥6-9

28ከዚያም ኢያሱ ሕዝቡን ሁሉ ወደየ
ርስቱ እንዲሄድ አሰናበተ፡፡
29ከዚህ በኋላ *የእግዚአብሔር* ባሪያ የነዌ
ልጅ ኢያሱ በመቶ ዐሥር ዓመቱ ሞተ፡፡
30በኩረብታማው በኤፍሬም አገር በምትገ
ኘው፣ ከገዓስ ተራራ በስተ ሰሜን ባለችው
በራሱ ርስት በተምናሴራ ቀበሩት፡፡

24፥27 ቊ22፤ዘፍ 21፥30፤28፥18፤ዘኍ 11፥20፤ኢሱ7፥11፤ 22፥27፤ምሳ30፥9፤ ዕን2፥11
24፥28 መሳ21፥ 23፥24
24፥29 ዘፍ50፥22፤ መሳ1፥1
24፥30 ኢሱ19፥50፤ 2ሳሙ23፥30
24፥31 ኢሱ7፥6
24፥32 ዘፍ33፥19፤ 47፥29-30፤ዮሐ4፥5፤ ሐሥ7፥16፤ዕብ11፥22
24፥33 ዘፀ6፥25፤ኢሱ 15፥57፤22፥13፤1ሳሙ 9፥4፤1ነገ4፥8

31ኢያሱ በሕይወት በነበረበት ዘመን
ሁሉ፣ ከኢያሱም በኋላ በሕይወት በኖሩ
ትና *እግዚአብሔር* ለእስራኤል ያደረገ
ውን ሁሉ በሚያውቁት ሽማግሌዎች
ዘመን ሁሉ እስራኤላውያን *እግዚአብሔ
ርን* አመለኩ፡፡
32እስራኤላውያን ከግብፅ ያወጡት የዮ
ሴፍ ዐፅም፣ ያዕቆብ ከሰኬም አባት ከኤ
ሞር በመቶ ሰቅል" ብር በገዛው በሴኬም
ምድር ተቀበረ፤ ይህችም የዮሴፍ ዘሮች
ርስት ሆነች፡፡
33እንዲሁም የአሮን ልጅ አልዓዛር
ሞተ፤ እርሱም በኩረብታማው በኤፍሬም
አገር በሚገኘው ለልጁ ለፊንሐስ በዕጣ
በደረሰው በጊብዓ ምድር ተቀበረ፡፡

"32 *ዕብራይስጡ እንድ መቶ ከሲታሃስ ይላል፤ ክብደቱና ዋጋው በትክክል የማይታወቅ የገንዘብ ዐይነት ነው፡፡*

# መጽሐፈ መሳፍንት

## እስራኤላውያን ከቀሩት ከነዓናውያን ጋር ያደረጉት ውጊያ

1 ኢያሱ ከሞተ በኋላ እስራኤላውያን፣
“ከነዓናውያንን ለመውጋት ማን ቀድሞ
ይውጣልን?” ብለው *እግዚአብሔርን* ጠየቁ።
2*እግዚአብሔርም*፣ “ይሁዳ ቀድሞ ይውጣ፤
እነሆ ምድሪቱን በእጁ አሳልፌ ሰጥቼዋለሁ”
በማለት መለሰ።
3የይሁዳም ሰዎች ወንድሞቻቸውን የስም
ዖንን ልጆች፣ “ከነዓናውያንን ለመውጋት
ድርሻችን ወደ ሆነው ምድር አብረን እንውጣ፤
እኛም እንደዚሁ ድርሻችሁ ወደ ሆነው ምድር
አብረናችሁ እንወጣለን” አሏቸው፤ ስለዚ
ህም የስምዖን ሰዎች አብረዋቸው ሄዱ።
4ይሁዳ በከነዓናውያንና በፌርዛውያን
ላይ ወጣ፤ *እግዚአብሔርም* በእጃቸው አሳ
ልፎ ሰጣቸው፤ ቤዜቅ በተባለውም ስፍራ
ዐሥር ሺህ ሰው ገደሉ። 5በዚህም አዶኒ
ቤዜቅን አግኝተው ተዋጉት፤ ከነዓናውያ
ንንና ፌርዛውያንን ድል አደረጉ። 6አዶኒ
ቤዜቅም ከዚያ ሸሸ፤ እነርሱ ግን አሳደው
ያዙት፤ የእጆቹንና የእግሮቹንም አውራ
ጣቶች ቈረጡ።
7ከዚያም አዶኒቤዜቅ፣ “የእጃቸውና የእግ
ራቸው አውራ ጣቶች የተቈረጡባቸው ሰባ
ነገሥታት ከገበታዬ ሥር የወደቀ ፍርፋሪ
ይለቃቅሙ ነበር፤ አሁን ግን እግዚአብሔር
በእነርሱ ላይ የፈጸምሁትን አመጣብኝ”
አለ፤ እነርሱም ወደ ኢየሩሳሌም አመጡት፤
በዚያም ሞተ።
8የይሁዳ ሰዎች ኢየሩሳሌምን ወግተው
ያዟት፤ ከተማዪቱንም በሰይፍ ስለት
መተው፣ በእሳት አቃጠሏት።
9ከዚያም በኋላ የይሁዳ ሰዎች በኰረብ
ታማው አገር፣ በኔጌብና በምዕራቡ ኮረ
ብታ ግርጌ የሚኖሩትን ከነዓናውያንን ለመ
ውጋት ወረዱ፤ 10ቀደም ሲል ቂርያት አር
ባቅ ተብላ በምትጠራው በኬብሮን በሚኖ
ሩት ከነዓናውያን ላይ ዘመቱ፤ ሴሲንን፣ አኪ
መንንና ተላሚንን ድል አደረጉ።
11ከዚያም ቀደም ሲል ቅርያትሤፍር
ተብላ በምትጠራው በዳቤር በሚኖሩት
ሰዎች ላይ ዘመቱ። 12ካሌብም፣ “ቅርያት
ሤፍርን ወግቶ ለሚይዛት ሰው ልጄን ዓክሳ
ንን እድርለታለሁ” አለ። 13በዚህ ጊዜ የካ
ሌብ ወንድም የቄኔዝ ልጅ ጎቶንያል ከተ
ማዪቱን ያዘ፤ ካሌብም ልጁን ዓክሳንን
ዳረለት።
14እርሷም ወደ ጎቶንያል በመጣች ጊዜ፣
አባቷ የዕርሻ መሬት እንዲሰጠው ይለምነው
ዘንድ አጥብቃ ነገረችው፤[ሀ] ካሌብም እርሷ
ከአህያዋ ላይ እንደወረደች “ምን እንዳደር
ግልሽ ትፈልጊያለሽ?” ሲል ጠየቃት።
15እርሷም፣ “እባክህ አንድ ነገር አድር
ግልኝ፤ በኔጌብ መሬት እንደ ሰጠኸኝ ሁሉ፣
አሁንም የውሃ ምንጭ ስጠኝ” አለችው፤
ካሌብም የላይኛውንና የታችኛውን ምን
ጮች ሰጣት።
16የቄናዊው የሙሴ ዐማት ዝርያዎች
ከዓራድ አጠገብ በኔጌብ ውስጥ በይሁዳ
ምድረ በዳ ካሉት ሕዝቦች ጋር አብረው
ለመኖር፣ ከይሁዳ ሰዎች ጋር በመሆን
ከባለ ዘንባባዋ ከተማ ከኢያሪኮ ወጡ።
17የይሁዳ ሰዎች ከወንድሞቻቸው ከስም
ዖን ልጆች ጋር ሆነው በጻፋት በሚኖሩት
ከነዓናውያን ላይ ዘመቱ፤ ከተማዪቱንም ፈጽሞ
ደመሰሷት[ለ]፤ ስለዚህ ከተማዪቱ ሔርማ[ሐ] ተብላ
ተጠራች። 18ደግሞም የይሁዳ ሰዎች ጋዛ፣
አስቀሎና፣ አቃሮን የተባሉትን ከተ ሞች
ከነግዛቶቻቸው ያዙ[መ]።
19*እግዚአብሔር* ከይሁዳ ሰዎች ጋር
ነበር፤ ስለዚህ ኰረብታማውን አገር ያዙ፤
ነገር ግን በረባዳው ምድር የሚኖሩት
ሰዎች ከብረት የተሠሩ ሠረገሎች ስለ
ነበሯቸው ከዚያ አሳደው ሊያስወጧቸው
አልቻሉም። 20ሙሴ ባዘዘው መሠረት
ኬብሮን ለካሌብ ተሰጠች፤ እርሱም ሦስቱን
የዔናቅ ልጆች ከውስጧ አሳደደ። 21የብን
ያም ልጆች በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን ኢያ
ቡሳውያንን ከዚያ ሊያሰወጧቸው አልቻ
ሉም፤ ስለዚህ ኢያቡሳውያን እስከ ዛሬ ድረስ
ከብንያማውያን ጋር በዚያ አብረው ይኖራሉ።
22የዮሴፍ ወገን ደግሞ ቤቴልን ወጉ፤
*እግዚአብሔርም* ከእነርሱ ጋር ነበር።
23እነርሱም ቀደም ሲል ሎዛ ትባል ወደ
ነበረችው ወደ ቤቴል ሰላዮችን በላኩ
ጊዜ፣ 24ሰላዮቹም አንድ ሰው ከከተማዪቱ
ሲወጣ አይተው፤ “የከተማዪቱን መግቢያ
አሳየን፤ እኛም ምሕረት እናደርግልሃለን”

1፥1 ቍ27፤ዘፍ10፥18፤ዘኍ2፥3-9፤ ኢሱ24፥29፤ መሳ3፥1-6፤20፥18፤ 1ነገ20፥14
1፥2 ቍ4፤ዘፍ 49፥10፤ መሳ3፥ 28፤4፥7፡14፤ 7፥9
1፥3 ቍ17
1፥4 ዘፍ13፥7፤ ኢሱ 3፥10፤ 1ሳሙ11፥8
1፥5 ቍ6፡7
1፥7 ዘሌ24፥19፤ ኢሱ 10፥1፤ ኤር25፥12
1፥8 ቍ21፤ ኢሱ 15፥63፤ 2ሳሙ5፥6
1፥9 ዘፍ12፥9፤ ዘኍ13፥17፤21፥1፤ ኢሳ30፥6
1፥10 ቍ20፤ ዘፍ13፥18፤35፥27፤ ዘኍ13፥22፤ ኢሱ 15፥14
1፥11 ኢሱ10፥38
1፥15 ዘኍ13፥6
1፥16 ዘፍ15፥19፤ ዘኍ10፥29፤21፥1፤ ዘዳ34፥3፤ኢሱ 12፥14፤ መሳ3፥13፤ 2ዜና28፥15
1፥17 ቍ3፤ ዘኍ14፥45
1፥18 ኢሱ11፥22፤ 13፥3
1፥19 ዘኍ13፥ 17፤14፥43፤ ኢሱ17፥16
1፥20 ቍ10፤ ኢሱ10፥36፤14፥13
1፥21 ቍ8፤ ኢሱ9፥15፤15፥63
1፥22 ኢያሱ7፥2፤ መሳ10፥9
1፥23 ዘፍ28፥19
1፥24 ዘፍ47፥29
1፥25 ኢሱ6፥25

[ሀ]14 ዕብራይስጡ፣ሰብዓ ሊቃናትና ቩልጌት *አጥብቆ ነገረው* ይላሉ።
[ለ]17 የዕብራይስጡ ቃል አንድን ነገር ወይም ሰው ሙሉ ለሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠትን የሚያሳይ ነው
[ሐ]17 *ሔርማ* ማለት *ጥፋት* ማለት ነው
[መ]18 ዕብራይስጡና የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም *አልያዙም* ይላሉ።

አሉት። 25እርሱም አሳያቸው፤ እነርሱም
ከሰውየውና ከቤተ ሰቡ በስተቀር የከተማ
ዪቱን ሕዝብ በሰይፍ ስለት ፈጁ። 26ሰው
የውም ወደ ኬጢያውያን ምድር ሄዶ ከተማ
ሠራ፤ ስሟንም ሎዛ ብሎ ጠራት፤ እስከ
ዛሬም የምትጠራው በዚሁ ስም ነው።
27የምናሴ ነገድ ግን በቤትሳን፣ በታዕናክ፣
በዶር፣ በይብለዓም፣ በመጊዶንና በየአካባ
ቢያቸው ያሉት መንደሮች ነዋሪውን ሕዝብ
ስላላስወጡ፣ ከነዓናውያን ኑሮአቸውን በዚ
ያው ለማድረግ ወሰኑ። 28እስራኤላውያን
በበረቱ ጊዜ ግን ከነዓናውያንን የጕልበት
ሥራ እንዲሠሩ አስገደዷቸው እንጂ ፈጽሞ
አላስወጧቸውም። 29እንደዚሁም የኤፍሬም
ወገኖች በጌዝር የሚኖሩትን ከነዓናውያንን
ማስወጣት አልቻሉም፤ ስለዚህ ከነዓናው
ያን በመካከላቸው እዚያው መኖርን ቀጠሉ።
30ዛብሎንም እንደዚሁ በቂድሮንና በነህሎል
የነበሩትን በመካከለቸው የቀሩትን ከነዓ
ናውያንን አላስወጣም፤ ነገር ግን የጕልበት
ሥራ እንዲሠሩ አስገደዳቸው። 31አሴርም
በዓኮ፣ በሲዶን፣ በአሕላብ፣ በአክዚብ፣
በሒልባ፣ በአፌቅና በረአብ የሚኖሩትን
ሕዝብ በምድሪቱ ካሉት ከነዓናውያን
ጋር አብረው ኖሩ። 33ንፍታሌምም በቤ
ትሳ ሚስና በቤትዓናት የሚኖሩትን አላስ
ወጣም፤ ስለዚህ የንፍታሌም ነገድ በምድሪቱ
ከሚኖሩት ከነዓናውያን ጋር አብረው ኖሩ፤
ይሁን እንጂ በቤትሳሚስና በቤትዓናት
የሚኖሩት ለእነርሱ የጕልበት ሥራ ተገ
ደው ይሠሩ ነበር። 34የዳን ነገድ በኰረብታ
ማው ምድር ብቻ እንዲወሰን እንጂ
ወደ ሜዳማው አገር እንዲወርድ አሞራ
ውያን አልፈቀዱለትም። 35አሞራውያንም በሐ
ሬስ ተራራ፣ በኤሎንና በሸዓልቢም
ኑሯቸውን ቀጠሉ፤ ይሁን እንጂ የዮሴፍ
ወገን በበረታ ጊዜ ተገደው የጕልበት ሥራ
ከመ ሥራት አላመለጡም። 36የአሞራውያን
ድንበር አቅራቢያም መተላለፊያ እስከ ሴላዕ
ና ከዚያም የሚያልፍ ነበር።

## የእግዚአብሔር መልአክ በቦኪም

2 የእግዚአብሔር መልአክ ከጌልገላ
ወደ ቦኪም ወጥቶ እንዲህ አለ፤ “ከግ
ብፅ ምድር አወጣራችሁ፤ ለቀደሙትም
አባቶቻችሁ ልሰጣቸው ወደ ማልሁላቸው
ምድር አመጣኋችሁ፤ እንዲህም አልሁ፤
ከእናንተ ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳኔን
አላፈርስም፤ 2እናንተም ከዚህች ምድር
ነዋሪዎች ጋር ቃል ኪዳን አታድርጉ፤ መሠዊ
ያቸውንም አፍርሱ፤ እናንተ ግን አልታዘ
ዛችሁኝም፤ ይህን ያደረጋችሁት ለምንድ
ነው? 3ስለዚህ አሁንም ከፊታችሁ አሳድጄ
እንደማላስወጣቸው እነግራችኋለሁ፤ ነገር
ግን እነርሱ የጐን ውጋት፣ አማልክቶቻቸ
ውም ወጥመድ ይሆኑባችኋል።”
4የእግዚአብሔርም መልአክ ይህን ቃል
ለእስራኤላውያን ሁሉ በተናገረ ጊዜ፣ ሕዝቡ
ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ፤
5ያንን ስፍራ ቦኪም[ሠ] ብለው ጠሩት፤
በዚያም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀ
ረቡ።

## ያለመታዘዝ ውጤት

6ኢያሱ ሕዝቡን ካሰናበተ በኋላ እያንዳንዱ
የእስራኤል ነገድ ምድሪቱን ለመውረስ
ወደ የርስቱ ሄደ። 7ኢያሱ በሕይወት
በነበረበት ዘመን ሁሉ እንዲሁም ከእርሱ
በኋላ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገውን
ታላላቅ ነገሮች ሁሉ ያዩ አለቆች በነበሩ
በት ዘመን ሁሉ ሕዝቡ እግዚአብሔርን
አመለከ።
8የእግዚአብሔር አገልጋይ የነዌ ልጅ
ኢያሱ በመቶ ዐሥር ዓመቱ ሞተ። 9እነርሱም
በኰረብ ታማው በኤፍሬም አገር በምትገኘው
ከገዓስ ተራራ በስተ ሰሜን ባለችው በራሱ
ርስት ላይ በተምናሔሬስ ቀበሩት።
10ያ ሁሉ ትውልድ ወደ አባቶቹ ከተከ
ማቸ በኋላ እግዚአብሔርንም ሆነ እርሱ
ለእስራኤል ሕዝብ ያደረገውን ነገር የማያ
ውቅ ሌላ ትውልድ ተነሣ ። 11ከዚያም
እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ፊት ክፉ
ነገር አደረጉ፤ የበኣል አማልክትንም አመ
ለኩ። 12ከግብፅ ምድር ያወጣቸውን የአባቶ
ቻቸውን አምላክ እግዚአብሔርን ተው፤ በዙ
ሪያቸው ያሉት ሕዝቦች የሚያመልኳቸውን
አማልክት ተከተሉ፤ ሰገዱላቸውም። እግዚ
አብሔርንም አስቈጡት፤ 13እርሱን ትተው
በኣልንና አስታሮትን አምልከዋልና 14እግ
ዚአብሔር በእስራኤል ላይ በመቈጣቱ
ለሚዘርፏቸው አሳልፎ ሰጣቸው፤ በዙሪያቸው
ላሉ ጠላቶቻቸው ሸጣቸው። 15እስራኤላውያን
ለውጊያ በሚወጡበት ጊዜ ሁሉ እግዚ
አብሔር አስቀድሞ በእርሱ ላይ እንደ
ተናገረውና እንደ ማለው ይሸነፉ ዘንድ
የእግዚአብሔር እጅ ትከፋባቸው ነበር፤ ከዚ
ህም የተነሣ እጅግ ተጨነቁ።
16እግዚአብሔርም ከእነዚህ ወራሪዎች
የሚያድኗቸውን መሳፍንት[ረ] አስነሣ፤ 17እስ
ራኤላውያን ግን ሌሎችን አማልክት

1፥26 ዘፍ28፥19፤ ዘዳ7፥1፤ሕዝ16፥3
1፥27 ቀኈ1፤ ኢሱ11፥2፤12፥21፤ 17፥11፣1ነገ9፥21
1፥28 ኢሱ17፥12-13
1፥29 ኢሱ10፥33፤ 14፥4፤16፥10፤ መሳ5፥14
1፥31 ዘፍ49፥13፤ ዘኍ13፥21፤ ኢሱ12፥18፤ 15፥44፤17፥7
1፥33 ኢሱ15፥10፤ 19፥38
1፥34 ዘፍ30፥6፤ ዘኍ13፥29፤ መሳ10፥11፤18፥1፤ 1ሳሙ7፥14
1፥35 ኢሱ19፥42፤ መሳ8፥13፤1ነገ4፥9
1፥36 ኢሱ15፥3፤ 2ነገ14፥7፤መዝ106፥34፤ ኢሳ16፥1፤42፥11
2፥1 ቀኈ5፤ ዘፍ16፥7፤ 17፥8፤ ዘፀ20፥2፤ ዘሌ26፥42-44፤ ዘዳ7፥9፤11፥30፤ መሳ6፥8
2፥2 ዘፀ23፥24፥2፤ 3 4፥12፥13፤ ዘዳ7፥2፥5፤2ዜና14፥3፤ ኤር7፥28
2፥3 ዘፀ10፥7፤ ዘኍ33፥55፤ ኢሱ 23፥13
2፥4 ዘፍ27፥38፤ ዘ25፥6፤2ነገ17፥13
2፥5 ቀኈ1
2፥7 ቀኈ17
2፥8 ኢሱ1፥1
2፥9 ኢሱ19፥50
2፥10 ዘፀ5፥2፤ ገላ4፥8
2፥11 መሳ3፥7፥12፤ 4፥1፤6፥1፤ 8፥33፤ 10፥6፤1ነገ15፥26፤ 16፥31፤22፥53፤ 2ነገ10፥18፤17፥16
2፥12 ዘኍ11፥33፤ ዘዳ4፥25፤31፥16፤ 32፥12፤መሳ10፥6፤ መዝ78፥58፤106፥36፥ 40
2፥13 መሳ3፥ 7፤ 5፥8፤6፥25፤8፥ 33፤10፥6፤1ሳሙ7፥3፤ 31፥10፤1ነገ11፥5፥33፤ 2ነገ23፥13፤ነህ9፥26፤ መዝ78፥56፤ ኤር 11፥10
2፥14 ዘዳ28፥25፤ 31፥17፤32፥30፤ መሳ3፥8፤ነህ9፥27፤ መዝ44፥10፤89፥41፤ 106፥41፤ሕዝ34፥8
2፥15 ዘፍ35፥3፤ሩት1፥13፤2ሳሙ22፥7፤2ዜና15፥4፤ኢዮ5፥5፤ 19፥21፤20፥22፤ መዝ4፥1፤18፥6፤32፥4
2፥16 ሩት1፥1፤ 1ሳሙ4፥18፤ 7፥6፥15፤11፥3፤2ሳሙ7፥11፤1ዜና17፥10፤ መዝ106፥46፤ ሐሥ13፥20፤ዘዳ9፥12፤ነህ9፥28
2፥17 ቀኈ7፤ዘፀ34፥15፤ዘኍ15፥39መዝ4፥2፤106፥36

ሠ5 ቦኪም ማለት አልቃሽ ማለት ነው።
ረ16 በዚህም ከ17—19 ባለው ክፍልመሪ ተብሎ ሊተረጐም ይችላል።

ተከትለው አመነዘሩ፤ ሰገዱላቸውም እንጂ
መሳፍንታቸውን አልሰሙም:: አባቶቻቸው
እግዚአብሔርን በመታዘዘ በሄዱበት
መንገድ ሳይሆን፣ አባቶቻቸው የእግዚአብሐ
ሬርን ሕግ በመከተል ከሄዱበት መንገድ
ፈጥነው ፈቀቅ አሉ:: [18]እግዚአብሔር
መሳፍንትን ባስነሣላቸው ቍጥር ከመስፍኑ
ጋር ስለ ሚሆን፣ እርሱ በሕይወት እስካለ
ድረስ እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው
ያድናቸው ነበር፤ ከጠላቶቻቸው ሥቃይና
መከራ ሲደርስባ ቸው በሚጮኹበት ጊዜ
እግዚአብሔር ይራራላቸው ነበር:: [19]መስፍኑ
ከሞተ በራላ ግን ሕዝቡ ሌሎችን አ
ማልክት በመከተል፣ እነርሱን በማገልገልና በ
ማምለክ ከአባቶ ቻቸው ይልቅ ወደ ክፉ
መንገድ ተመለሱ፤ ክፉ ሥራቸውንና
የእልኸኝነት መንገዳቸው ንም አይተውም
ነበር::

[20]ስለዚህ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ
እጅግ ተቈጣ፤ እንዲህም አለ፤ "ይህ ሕዝብ
ለቀደሙ አባቶቹ የሰጠሁትን ቃል ኪዳን
ስለተላለፈ፣ እኔንም ስላልሰማ፣ [21]ኢያሱ
በሞተ ጊዜ ከተዋቸው በምድሪቱ ከነ
በሩት ሕዝቦች አንዳቸውንም እንኳ በፊታ
ቸው አሳድጄ አላስወጣም:: [22]ይህን የሚያ
ደርገውም አባቶቻቸው እንዳደረጉት ሁሉ፣
እስራኤላውያን የእግዚአሔርን መንገድ
የሚጠብቁ መሆን አለመሆናቸውን ለማወቅ
እፈትናቸው ዘንድ እነርሱን መሣሪያ ለማ
ድረግ ነው::" [23]ስለዚህ እግዚአብሔር እነ
ዚያን ሕዝቦች በዚያው እንዲኖሩ አደረገ፤
በኢያሱ እጅ አሳልፎ በመስጠት ወዲያውኑ
አሳዶ አላስወጣቸውም::

3 በዚህ ጊዜ በከነዓን ላይ በተደረጉት
ጦርነቶች ተሳትፈው የማያውቁትን
እስራኤላውያን ለመፈተን፣ እግዚአብሔር
ባሉበት የተዋቸው ሕዝቦች እነዚህ ናቸው፤
[2]ይህን ማድረጉ ቀደም ሲል በጦር ሜዳ
ውለው የማያውቁትን የእስራኤል ልጆች
የጦርነት ልምድ እንዲያገኙ ለማድረግ ብቻ
ነው፤ [3]እነዚህም አሕዛብ አምስቱ የፍልስ
ጥኤም ገዞች፣ ከነዓናውያን በሙሉ፣ ሲዶና
ውያንና ከበኣል አርሞንዔም ተራራ
እስከ ሐማትስ መግቢያ ባሉት የሊባኖስ ተራ
ሮች የሚኖሩ ኤዊያውያን ነበሩ:: [4]እነዚህ፣
እግዚአብሔር በሙሴ በኵል ለቀደሙ
አባቶቻቸው የሰጠውን ትእዛዛት ማክበር
አለማክበራቸውን ለማወቅ መፈተኛ እንዲ
ሆኑ እዚያው የቀሩ ነበሩ::

[5]ስለዚህ እስራኤላውያን ከከነዓናውያን፣
ከኬጢያውያን፣ ከአሞራውያን፣ ከፌርዛ
ውያን፣ ከኤዊያውያንና ከኢያቡሳውያን ጋር
አብረው ኖሩ:: [6]እስራኤላውያን የእነዚህን
ሴቶች ልጆች አገቡ፤ የራሳቸውንም ሴቶች
ልጆች ለእነርሱ ወንዶች ልጆች ዳሩ፤ አማ
ልክቶቻቸውንም አመለኩ::

## ጎቶንያል

[7]እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ፊት
ክፉ ድርጊት ፈጸሙ፤ እግዚአብሔር
አምላካ ቸውንም ረሱ፤ የበኣልንና
የአስታሮትን አማልክት አመለኩ::
[8]እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ እጅግ
ተቈጣ፤ ስለዚህ ለመ ስጴጦምያ[ሽ] ንጉሥ
ለኵስርስቴም አሳልፎ ሰጣቸው፤ እስራ
ኤላውያንም ስምንት ዓመት በባርነት
ተገዙለት:: [9]እስራኤላውያን ወደ እግዚ
አብሔር በጮኹ ጊዜ ግን የካሌብን
ታናሽ ወንድም የቄኔዝን ልጅ ጎቶንያልን
ታዳጊ አድርጎ አስነሣላቸው:: [10]የእግዚ
አብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ ወረደ፤
የእስራኤል መስፍን[ቀ] ሆኖ ወደ ጦርነትም
ወጣ:: እግዚአብሔር የመስጴጦምያን ንጉሥ
ኵስርስቴምን አሳልፎ ስለ ሰጠው ድል
አደረገ:: [11]የቄኔዝ ልጅ ጎቶንያል እስከሞ
ተበት ጊዜ ድረስ ምድሪቱ ለአርባ ዓመት
ሰላም አገኘች::

## ናዖድ

[12]እስራኤላውያን እንደ ገና በእግዚ
አብሔር ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸሙ፤
ይህን በማድረጋቸውም እግዚአብሔር የሞዓብ
ንጉሥ ዔግሎን በእስራኤል ላይ እንዲበረ
ታባቸው አደረገ:: [13]እርሱም አሞናውያንንና
አማሌቃውያንን ካስተባበረ በኋላ እስራ
ኤልን ወግቶ የዘንባባ ዛፎች[በ] ከተማ የሆነ
ችውን ኢያሪኮን ያዙ:: [14]እስራኤላውያንም
ለሞዓብ ንጉሥ ለዔግሎን ዐሥራ ስም
ንት ዓመት ተገዘሉት::

[15]እስራኤላውያን እንደ ገና ወደ እግዚ
አብሔር ጮኹ፤ እግዚአብሔርም ብንያማ
ዊውን የጌራን ልጅ ግራኙን ናዖድን ነጻ
እንዲያወጣቸው አስነሣው:: እስራኤላው
ያን ናዖድን ግብር አስይዘው ወደ ሞዓብ
ንጉሥ ወደ ዔግሎን ላኩት:: [16]እርሱም
በሁለት በኩል ስለታም የሆነና አንድ
ክንድ ተኩል ርዝመት[ተ] ያለው ሰይፍ
አዘጋጅቶ በልብሱ ውስጥ በቀኝ ጭኑ ላይ
አሰረው:: [17]ግብሩንም ወፍራም ለነበረው
ለሞዓብ ንጉሥ ለዔግሎን አቀረበ፤ [18]ናዖድም
ግብሩን ካቀረበ በኋላ፣ ግብር ተሸክመው

2፥18 ዘፀ2፥23፤ ዘኍ10፥9፤ዘዳ32፥36፤ 1ሳሙ7፥3፤2ነገ13፥5፤ ኢሳ19፥20፤ 43፥3፡11፤45፥15፡21፤ 49፥26፤60፥16፤63፥8
2፥19 ዘፍ6፥11፤ ዘፀ32፥9፤ ዘዳ4፥16፤32፥17፤ መሳ4፥1፤8፥33፤ ነህ9፥2፤መዝ78፥57፤ ኤር 44፥3፡9
2፥20 ዘዳ31፥17፤ ኢሱ7፥11፤23፥16፤ 2ነገ17፥15
2፥21 ኢሱ23፥5
2፥22 ዘፍ 22፥1፤ ዘፀ15፥25
2፥23 መሳ1፥1
3፥1 ዘፀ15፥25
3፥3 ዘፍ 10፥14፡ 17፤ ዘኍ13፥21፤ ዘፀ፥8፤ ዘሌ13፥21፤ ዘዳ3፥8፤ ኢሱ13፥3
3፥4 ዘፀ15፥25
3፥5 ኢሱ3፥10፤ 11፥3፤ ዕዝ9፥1፤ መዝ106፥35
3፥6 ዘፀ34፥16፤ ዘዳ7፥3-4፡16፤ ዕዝ10፥18፤ ነህ13፥23፤ሚል2፥11
3፥7 ዘፀ34፥13፤ ዘዳ4፥9፤32፥18፤ መሳ2፥11፡13፤8፥34፤1ነገ16፥33፤2ዜና34፥7፤ መዝ78፥11፡42፤106፥7፤ኢሳ178፤ ኤር23፥27
3፥8 ቍ10፤ ዘፍ24፥10፤መሳ2፥14፤ መዝ44፥12፤ ኢሳ 50፥1፤52፥3
3፥9 ቍ15፤ ዘዳ 28፥29፤ ኢሱ15፥17፤ መሳ6፥6፡7፤10፥10፤ 1ሳሙ12፥10ነህ9፥27፤ መዝ106፥44፤107፥13
3፥10 ቍ8፤ ዘፍ10፥22፤ዘኍ11፥25፤መሳ6፥34፤11፥29፤13፥25፤14፥6፡19፤ 15፥14፤1ሳሙ11፥6፤ 16፥13፤1ነገ18፥46፤ 1ዜና12፥18፤ 2ዜና24፥20፤ ኢሳ11፥2
3፥12 መሳ2፥11፤1ሳሙ12፥9
3፥13 ዘፍ14፥7፤ 19፥38፤መሳ1፥16፤ 10፥11
3፥14 ኤር48፥1
3፥15 ቍ9፥16፡
3፥16 ቍ15
3፥17 ቍ15፤ኢዮ 15፥27፤መዝ73፥417፡18፤መሳ4፥1፤20፥16፤ 2ሳሙ8፥2፡6፤1ነገ4፥21፤ 2ነገ17፥3፤1ዜና12፥2አስ10፥1፤መዝ68፥29፤ 72፥10፤89፥22፤መክ2፥8፤ኢሳ 60፥5፤ ሆሴ10፥6

[ሰ]3 ወይም *እስከ መግቢያው ድርስ* ተብሎ ሊተረጐም ይችላል::

[ሽ]8 ስሜን ምዕራብ መሴጴጦንያ ነው::
[ቀ]10 ወይም *መሪ* ተብሎ ሊተረጐም ይችላል::
[በ]13 ኢያሪኮ ነች
[ተ]16 0.5 ሜትር ያህል ነው

የመጡት ሰዎች ተመልሰው እንዲሄዱ አደ
ረገ። 19እርሱ ራሱ ግን ጌልጌላ አጠገብ
ድንጋዮች[ቸ] ተጠርበው ከሚወጡበት አካ
ባቢ ሲደርስ ወደ ኋላ በመመለስ ወደ
ንጉሡ ሄዶ፣ “ንጉሥ ሆይ፤ በምስጢር የምነ
ግርህ ነገር አለኝ” አለው።

ንጉሡም፣ “ጸጥታ” ሲል፤ አጠገቡ የነበሩት
አገልጋዮች በሙሉ ትተውት ወጡ።

20ንጉሡ ሰገነት ላይ ባለው ነፋሻ ዕል
ፍኝ፤ ውስጥ ብቻውን ተቀምጦ ሳለ ናዖድ
ቀረብ ብሎ፣ “ከእግዚአብሔር ዘንድ ለአንተ
ያመጣሁት መልእክት አለኝ” አለው፤ ንጉሡም
ከዙፋኑ ተነሣ። 21ናዖድ ግራ እጁን ሰደድ በማ
ድረግ ሰይፉን ከደበቀበት ከቀኝ ጭኑ
መዝዞ በንጉሡ ሆድ ሻጠው። 22እጀታው
ሳይቀር ሰይፉ እንዳለ ሆዱ ውስጥ ገባ፤
ስለቱም በጀርባው ወጣ፤ ሞራም ስለቱን
ሸፈነው፤ ናዖድ ሰይፉን ስላልነቀለው አን
ጀቱ ተዘረገፈ። 23ከዚያም በኋላ ናዖድ በዕ
ልፍኙ[ነ] መግቢያ ወጣ፤ የዕልፍኙንም በር
በንጉሡ ላይ ዘግቶ ቈለፈው።

24ናዖድ ከሄደ በኋላ፣ የንጉሡ
አገልጋዮች ሲመጡ፣ የዕልፍኙ በር
ተቈልፎ አገኙት፤ እነርሱም፣ “በውስጠኛው
ክፍል እየተጸዳዳ ይሆ ናል” አሉ፤ 25እስኪደክ
ማቸውም ድረስ ጠበቁ፤ ነገር ግን ንጉሡ
የእልፍኙን በሮች ባለመክ ፈቱ ቍልፍ
ወስደው ከፈቱ፤ በዚያም ጌታ ቸው ሞቶ፣
በወለሉም ላይ ተዘርግቶ አገ ኙት።

26የንጉሡ አገልጋዮች በዕልፍኙ በር
ላይ ቆመው ሲጠባበቁ ናዖድ ርቆ ሄደ፤
ድንጋዮች ተጠርበው በሚወጡበት በኩል ወደ
ሴርታ ይም አመለጠ። 27እዚያም እንደ ደረሰ፣
በኰረ ብታማው በኤፍሬም ምድር ቀንደ
መለከቱን ነፋ፤ እስራኤላውያንም በእርሱ
መሪነት ከኰ ረብታው ላይ አብረውት
ወረዱ።

28እርሱም፣ “ጠላታችሁን ሞዓብን እግዚ
አብሔር በእጃችሁ አሳልፎ ስለ ሰጣችሁ
ተከተሉኝ” በማለት አዘዛቸው፤ እነርሱም
ተከትለውት ወረዱ፤ ከዚያም ከዮርዳኖስ
ወደ ሞዓብ የሚያሻግሩትን መልካዎች
በመያዝ አንድም ሰው እንዳያልፍ ከለከሉ።
29በዚያን ጊዜ ብርቱና ፤ይለኛ የሆኑ ዐሥር
ሺህ ሞዓባውያንን ገደሉ፤ አንድም ሰው
አላመለጠም። 30በዚያን ቀን ሞዓብ በእስ
ራኤል ድል ሆነች፤ ምድሪቱም ለሰማንያ ዓ
መት ሰላም አገኘች።

## ሰሜጋር

31ከናዖድ በኋላ ስድስት መቶ
ፍልስጥኤማውያንን በበሬ መንጃ የገደለው
የዓናት ልጅ ሰሜጋር ተነሣ፤ እርሱም

3፥20 ነህ8፥5፤ አሞ3፥15
3፥21 2ሳሙ2፥16፤ 3፥27፤20፥10
3፥24 1ሳሙ24፥3
3፥25 2ነገ2፥17፤ 8፥11
3፥27 ዘሌ25፥9፤ መሳ6፥34፤7፥18፤ 2ሳሙ2፥28፤ ኢሳ18፥3፤ኤር42፥14
3፥28 ዘፍ19፥37፤ ዘኍ13፥29፤ኢሱ2፥7፡ 24፤መሳ1፥2
3፥30 ቍ11፤ ዘፍ36፥35
3፥31 ኢሱ13፥2፤ 23፥10፤መሳ5፥6፤ 10፥11፤13፥1፤ 1ሳሙ5፥1፤31፥1፤ 2ሳሙ8፥1፤ ኤር25፥20፤47፥1
4፥1 መሳ2፥11፡ 19፤3፥15
4፥2 ዘጻ32፥30፤ ኢሱ11፥1፤ 1ሳሙ12፥9፤ መዝ83፥9
4፥3 ኢሱ17፥16፤ መሳ10፥12፤ መዝ106፥42
4፥4 ዘፀ15፥20፤ መሳ5፥1፡7፡12፡15
4፥5 ኢሱ12፥9፤ 18፥25፤1ሳሙ14፥2፤ 22፥6
4፥6 ዘፍ30፥8፤ ኢሱ12፥22፤ 19፥22፤መሳ5፥1፡12፡ 15፡18፤6፥35፤ 1ሳሙ12፥11፤ ዕብ11፥32
4፥7 ቍ13፤ ኢሱ11፥1፤ መሳ1፥2፤5፥21፤ 1ነገ18፥40፤መዝ83፥9
4፥9 ኢሱ12፥22
4፥10 2ዜና 36፥3፤ ዕዝ1፥2፤ኢሳ4 1፥2፤ 42፥6፤ 45፥3፤ 46፥11፤48፥15
4፥11 ዘፍ15፥19፤ ዘኍ10፥29፤ ኢሱ19፥33፤24፥26፤ መሳ9፥6

እን ደዚሁ ደግሞ እስራኤልን አዳነ።

## ዲቦራ

4 ናዖድ ከሞተ በኋላ እስራኤላውያን እንደ
ገና በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ድርጊት
ፈጸሙ። 2ስለዚህም እግዚአብሔር በሐጾር
ሆኖ ይገዛ ለነበረው ለከነዓን ንጉሥ ለኢ
ያቢስ አሳልፎ ሸጣቸው። የኢያቢስ ሰራዊት
አዛዥ፣ በሐሮሼትሐጎይም የሚኖረው ሲሣራ
ነበረ፤ 3እርሱም ዘጠኝ መቶ የብረት ሠረገ
ሎች ስለ ነበሩት እስራኤላውያንን ሃያ
ዓመት እጅግ አስጨነቃቸው፤ እነርሱም
ይረ ዳቸው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ
ሉ።

4በዚያን ጊዜ የለፊዶት ሚስት ነቢዩቱ
ዲቦራ በእስራኤል ላይ ፈራጅ[ኘ] ነበረች።
5እርሷም በኰረብታማው በኤፍሬም
ምድር፣ በራማና በቤቴል መካከል ካለው
የዲቦራ ዘንባባ ዛፍ ሥር ተቀምጣ ትፈ
ርድ ነበር፤ እስራኤላውያንም ለፍርድ ወደ
እርሷ ይመጡ ነበር። 6ዲቦራ፣ በንፍታሌም
ውስጥ ቃዴስ በተባለች ከተማ ይኖር
የነበረውን የአቢኒኤምን ልጅ ባራቅን አስጠ
ርታ እንዲህ አለችው፤ “የእስራኤል አም
ላክ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ያዝሃል፤
“ተነሣ፤ ከንፍታሌምና ከዛብሎን ዐሥር ሺህ
ሰዎች ይዘህ ወደ ታቦር ተራራ ውጣ፤
7እኔም የኢያቢስን ሰራዊት አዛዥ ሲሣ
ራን ከሠረገሎቹና ከሰራዊቱ ጋር ቂሶን
ወንዝ እንዲመጣ አነሣሣ ዋለሁ፤ በእጅህም
አሳልፌ እሰጥሃለሁ።”

8ባርቅም፣ “አብረሽኝ የምትሄጂ
ከሆነ እሄዳለሁ፤ አብረሽኝ የማትሄጂ ከሆነ
ግን አልሄድም” አላት።

9ዲቦራ መልሳ፣ “ይሁን እሺ፤ መሄዱን
አብሬህ[አ] እሄዳለሁ፤ በዚህ ሁኔታ የምጠ
ትሄድ ከሆነ ግን ክብሩ ለአንተ አይሆ
ንም፤ እግዚአብሔር ሲሣራን ለሴት አሳ
ልፎ ይሰጣልና” አለችው። ስለዚህ ዲቦራ
ከባርቅ ጋር ወደ ቃዴስ ሄደች፤ 10በዚያም
ባርቅ ለዛብሎንና ለንፍታሌም ሰዎች ጥሪ
አስተላለፈ፤ ዐሥር ሺህ ሰዎች ተከተሉት፤
ዲቦራም አብራው ሄደች።

11በዚያን ጊዜ ቄናዊው ሔቤር፣ ዐማች
የአባብ ልጆች ከሆኑት ከሌሎቹ ቄናውያን
ተለይቶ በቃዴስ አጠገብ ጻዕናይም ከተባለ
ቦታ ከሚገኘው ትልቅ ወርካ ጥግ ድንኳ
ኑን ተክሎ ነበር።

[ቸ]19 በዚህና በቍጥር26 ላይ ጣዖት ተብሎ ሊተረጐም ይችላል።
[ነ]20 የዕብራይስጡ ሐረግ ትርጒም በትክክል አይታወቅም።
[ነ]23 የዕብራስጡ ቃል ትርጒም በትክክል አይታወቅም።
[ኘ]4 በትውፊት መሳፍንት ማለት ነው
[አ]9 ወይም፣ ነገር ግን ልትሄድ ወደ ዐቀድክበት ስፍራ

[12]የአቢኒዔም ልጅ ባርቅ ወደ ታቦር ተራራ
መሄዱን ሲሣራ በሰማ ጊዜ፣ [13]ዘጠኝ መቶ
የብረት ሠረገሎችንና ከአሪሶት ሐጎይም እስከ
ቂሶን ወንዝ ያለውን ሰራዊቱን በሙሉ
አሰባሰበ።
[14]በዚህ ጊዜ ዲቦራ ባርቅን፣ "ተነሣ!
*እግዚአብሔር* ሲሣራን በእጅህ አሳልፎ
የሰጠባት ቀን ይህች ናት፤ እነሆ *እግዚ
አብሔር* በፊትህ ቀድሞ ወጥቶአል" አላ
ቸው። ስለዚህ ባርቅ ዐሥር ሺህ ሰዎችን
አስከትሎ ከታቦር ተራራ ወረደ። [15]*እግዚ
አብሔር* ሲሣራንና ሠረገሎቹን ሁሉ በባርቅ
ፊት በሰይፍ ስለት እጅግ ተሸንፈው ወደ
ኋላ እንዲያፈገፍጉ አደረገ፤ ሲሣራም ከሠ
ረገላው ወርዶ በእግሩ ሸሸ፤ [16]ባርቅ ግን የሲሣ
ራን ሠረገሎችና ሰራዊቱን እስከ አሪሶት ሐጎ
ይም ድረስ አሳደዳቸው፤ የሲሣራ ሰራዊት
በሙሉ በሰይፍ ወደቀ፤ በሕይወት የተረፈ
አንድም ሰው አልነበረም።
[17]በሐጾር ንጉሥ በኢያቡስና በቄናዊው
በሔቤር ጐሣ መካከል መልካም ግንኙነት
ስለ ነበር ሲሣራ በእግሩ ሸሽቶ የቄናዊው
የሔቤር ሚስት ወደ ሆነችው ወደ ኢያዔል
ድንኳን ሮጠ።
[18]ኢያዔልም ወጥታ ሲሣራን ተቀበ
ለችውና፣ "ጌታዬ፤ ወደ ውስጥ ግባ፤ ፈ
ጽሞ አትፍራ" አለችው፤ ሲሣራም ወደ
ድንኳኗ ገባ፤ እርሷም በልብስ ሸፍና
ደበቀችው።
[19]ሲሣራም፣ "ጠምቶኛልና እባክሽን ውሃ
አጠጪኝ" አላት፤ እርሷም የወተት ሎጫውን
ከፍታ የሚጠጣውን ሰጠችው፤ እንደ
ገናም ሸፈነችው።
[20]እርሱም፣ "በድንኳኑ በር ላይ ቁሚ፤
ማንም ሰው መጥቶ፣ 'እዚህ ሰው አለ?'
ቢልሽ፣ "የለም በይ" አላት።
[21]የሔቤር ሚስት ኢያዔል ግን ሲሣራ
ደክሞ፣ ከባድ እንቅልፍም ወስዶት ሳለ፣
የድንኳን ካስማና መዶሻ ይዛ በቀስታ ወደ
እርሱ ቀረበች፤ ከዚያም ካስማውን በመ
ዶሻ ጆሮ ግንዱ ላይ መትታ ከመሬት ጋር
ሰፋችው፤ እርሱም ሞተ።
[22]ባርቅ ሲሣራን በመከታተል ላይ ስለ
ነበር ከዚያ ሲደርስ፣ ኢያዔል ከድንኳኗ
ወጥታ "ና፤ የምትፈልገውን ሰው አሳይ
ሃለሁ" አለችው፤ ስለዚህ ከእርሷ ጋር ወደ
ድንኳንዋ ገባ፤ ሲሣራም በጆሮ ግንዱ ላይ
ካስማ እንደተመታበት ሞቶ ተዘርሮ
ነበረ።
[23]በዚያች ዕለት እግዚአብሔር የከነዓንን
ንጉሥ ኢያቢስን በእስራኤላውያን ፊት
እንዲሸነፍ አደረገው፤ [24]የከነዓናዊውን

4፥12 ኢሱ19፥22
4፥13 ቀኍ7፤
ኢሱ17፥16፤መሳ5፥19
4፥14 ዘዳ9፥3፤
መሳ1፥2፤1ሳሙ8፥20፤
2ሳሙ5፥24፤
መዝ68፥7
4፥15 ዘፀ14፥24፤
መዝ18፥14 4፥16
ዘፀ14፥28፤ መዝ83፥9
4፥17 ቀኍ18፥21፡
22፤ ዘፍ15፥19፤
ኢሱ11፥1፤
መሳ5፥6፡24 4፥18
ቀኍ17 4፥19
ዘፍ18፥8
4፥21 ቀኍ17፤
ዘፍ2፥21፤15፥12፤
መሳ5፥26፤
1ሳሙ26፥12፤
ኢሳ29፥10፤ ዮና1፥5
4፥22 ቀኍ17፤
መሳ5፥27
4፥23 ኢሱ11፥1፤
ነህ9፥24፤መዝ18፥47፤
44፥2፤47፥3፤
144፥2
4፥24 መዝ83፥9፤
106፥43
5፥1 ዘፀ15፥1፤
መሳ4፥4፡6፤
መዝ32፥7
5፥2 ቀኍ9፤
2ዜና17፥16፤
መዝ110፥3
5፥3 ዘፀ15፥1፤
መዝ27፥6
5፥4 ዘፀ13፥21፤
ዘኍ24፥18፤ዘዳ33፥2፤
2ሳሙ22፥8፤መዝ18፥7፤
68፥8፤77፥17፡1፤
82፥5፤ኢሳ2፥19፡
21፤13፥13፤24፥18፤
64፥3፤ኤር10፥10፤
50፥46፤51፥29፤
ኢል3፥16፤ ናሆ1፥5፤ዕ
ን3፥6 5፥5 ዘፀ
19፥18፤
መዝ29፥6፤46፥3፤
77፥18፤114፥4፤ ኢ
ሳ64፥3 5፥6
ዘሌ26፥22፤
መሳ3፥31፤4፥17፤
መዝ125፥5፤
ኢሳ33፥8፤59፥8
5፥7 መሳ4፥4
5፥8 ቀኍ11፤
ዘኍ 5፥7፤ዘዳ32፥17፤
ኢሱ2፥5፤መሳ2፥13
5፥9 ቀኍ2
5፥10 ዘፍ49፥11፤
መሳ12፥14 5፥11
ቀኍ8
1ሳሙ 12፥7፤
ዳን9፥16፤ሚክ6፥5

ንጉሥ ኢያቢስን እስኪደመስሱ ድረስ
የእስራኤላውያን ክንድ እየበረታ ሄደ።

## የዲቦራ መዝሙር

**5** በዚያን ዕለት ዲቦራና የአቢኒኤም
ልጅ ባርቅ ይህን ቅኔ ተቀኙ፤

[2]"በእስራኤል ያሉ መሳፍንት ሲመሩ፣
ሕዝቡም በፈቃዱ ራሱን ሲያስገዛ፣
*እግዚአብሔርን* አመስግኑ

[3]"እናንት ነገሥታት ይህን ስሙ፤
ገዦችም አድምጡ፤
*ለእግዚአብሔር* እዘምራለሁ፤ ደግሜም
ለእስራኤል አምላክ *ለእግዚአብሔር*
እቀኛለሁ።

[4]"*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ከሴይር በወጣህ ጊ
ዜ፣
ከኤዶም ምድርም በተነሣህ ጊዜ፣
ምድር ተንቀጠቀጠች፤ ሰማያትም ዝናብ
አዘነቡ፤
ደመናዎችም ውሃ አፈሰሱ።

[5]ተራሮች በሲና አምላክ *በእግዚአብሔር*
ፊት፣
በእስራኤልም አምላክ *በእግዚአብሔር*
ፊት ተናወጡ።

[6]"በዓናት ልጅ በሰሜጋር ዘመን፣
በኢያዔል ጊዜ መንገዶች ባድማ ሆኑ፤
ተጓዦችም በጠመዝማዛ መንገድ ሄዱ።

[7]ለእስራኤል እናት ሆኜ
እኔ ዲቦራ እስክነሣ ድረስ
በእስራኤል ያለው የከተማ ኑሮ
አበቃለት፤
[8]አዳዲስ አማልክትን በተከተሉ ጊዜ፣
ጦርነት እስከ ከተማው በር መጣ፤
ጋሻም ሆነ ጦር፣
በአርባ ሺህ እስራኤላውያን መካከል
አልተገኘም።
[9]ልቤ ከእስራኤል መሳፍንት፣
ፈቃደኞችም ከሆኑ ሰዎች ጋር ነው፤
*እግዚአብሔር* ይመስገን።

[10]"እናንት በነጫጭ አህዮች የምትጋልቡ፣
በባለ ግላስ ኮርቻ ላይ የምትቀመጡ፣
በመንገድ ላይ የምትጓዙ፣
በውሃ ምንጮች ዙሪያ ያለውን፣
[11]የዝማሬ ድምፅ[ወ] ስሙ።
ይህም *የእግዚአብሔር* የጽድቅ ሥራ፣
ጦረኞቹም በእስራኤል ያደረጉትን
ያስታውሳል።

"ከዚያም *የእግዚአብሔር* ሕዝቦች፣
ወደ ከተማዪቱ[0] በሮች ወረዱ፤

[ከ]3 ወይም *ከምዘምረው ዝማሬ ጋር* ተብሎ ሊተረጐም ይችላል
[ከ]7 ወይም *አንቺ* ተብሎ ሊተረጐም ይችላል።
[ወ]11 ወይም *ቀስተኞች* ተብሎ ሊተረጐም ይችላል።

[0]11 ወይም *ወደመንደሮቹ* ተብሎ መተርጐም ይቻላል፡፡

12‘ዲቦራ ሆይ፤ ንቂ፤ ንቂ፤
ንቂ፤ ንቂ፤ ቅኔም ተቀኚ፤
የአቢኒኤል ልጅ ባራቅ ሆይ፤ ተነሣ፤
ምርኮኞችህንም ማርከህ ውሰድ’ አሉ፡፡

13የቀሩትም ሰዎች፣
ወደ መኳንንቱ ወረዱ፤
*የእግዚአብሔር* ሕዝብ፣
እንደ ፤ያል ጦረኛ ወደ እኔ መጣ፡፡
14መሠረታቸው ከአማሌቅ የሆነ አንዳንዶች
ከኤፍሬም መጡ፤
ብንያም አንተን ከተከተሉ ሰዎች ጋር
ነበር፤
የጦር አዛዦች ከማኪር፣
የሥልጣን በትር የያዙም ከዛብሎን
ወረዱ፡፡

15የይሳኮር መሳፍንት ከዲቦራ ጋር ነበሩ፤
ይሳኮርም ራሱ ወደ ሸለቆው ከራዋላ
በመከተል፣ ከባርቅ ጋር ነበረ፡፡
በሮቤል አውራጃዎች፣ ብዙ የልብ
ምርምር ነበር፡፡
16በበጎች ጒረኖ[॥] መካከል ለምን ተቀመጥህ?
መንጎችን የሚጠራውን ፉጨት ለመስማት
ነውን?
በሮቤል አውራጃዎች፣ ብዙ የልብ
ምርምር ነበር፡፡
17ገለዓድ ከዮርዳኖስ ማዶ ተቀመጠ፤
ዳን ለምን በመርከብ ውስጥ ዘገየ?
አሴር በጠረፍ ቀረ፤
በባሕሩ ዳርቻም ተቀመጠ፡፡
18ይዛብሎን ሰዎች ሕይወታቸውን
አሳልፈው ሰጡ
የንፍታሌም ሰዎች እንደዚሁ በምድሪቱ
ኰረብታዎች አደረጉ፡፡

19“ነገሥታት መጡ፤ ተዋጉም፤
የከነዓን ነገሥታት፣ በመጊዶ ውኃዎች”
አጠገብ በታዕናክ ተዋጉ፤
ብርም ሆነ ሌላ ምርኮ ተሸክመው
አልሄዱም፡፡
20ከሰማያት ከዋክብት ተዋጉ፤
በአካሄዳቸውም ሲሣራን ገጠሙት፡፡
21ጥንታዊው ወንዝ፣ የቂሶን ወንዝ፣
የቂሶን ወንዝ ጠርጐ ወሰዳቸው፤
ነፍሴ ሆይ፤ በ፤ይል ገሥግሺ፤
22የፈረሶች ኮቴ ድምፅ በ፤ይል ተሰማ፤
ጋለቡ፤ በ፤ይልም ፈጥነው ጋለቡ፡፡
23*የእግዚአብሔር* መልአክ፣ ‘ሜሮዝን
ርገሙ፤’
‘ሕዝቧንም አብራችሁ ርገሙ፤
ከ፤ያላን ሰልፍ *እግዚአብሔርን*
ለመርዳት፣
በእግዚአብሔርም ጐን ለመቆም አልመ
ጡምና’ አለ፡፡

24‘የቄናዊው የሔቤር ሚስት ኢያዔል፣
ከሴቶች ሁሉ የተባረከች ትሁን፤
በድንኳን ከሚኖሩ ሴቶች ሁሉ
የተባረከች ትሁን፡፡
25ውሃ ለመነ፤ ወተት ሰጠችው፤
ለመኳንንት በሚገባ ዕቃ፣ እርጎ
አቀረበችለት፡፡
26እጇዋ ካስማ ያዘ፤
ቀኝ እጇም የሠራተኛ መዶሻ ጨበጠ፤
ሲሣራን መታችው፤ ራሱንም ተረከከችው፤
ክፉኛ ወጋችው፤ ጆሮ ግንዱን በሳችው፡፡
27በእግሯ ሥር ተደፋ፤ ወደቀ፤
በዚያም ተዘረረ፤ በእግሯ ሥር ተደፋ፤
ወደቀ፤ በተደፋበት በዚያ ወደቀ፤
ሞተም፡፡
28“የሲሣራ እናት በመስኮት ተመለከተች፤
በዐይነ ርግቡ ቀዳዳም ጮኻ ተጣራች፤
‘ለምን ሠረገላው ሳይመጣ ዘገየ?
የሠረገሎቹስ ድምፅ ለምን ጠፋ?’ አለች፡፡
29ብልሃተኞች ወይዛዝርቷም መለሱላት፤
እርሷ ግን ለራሷ እንዲህ አለች፤
30‘ምርኮ አግኝተው እየተከፋፈሉ፣
እያንዳንዱም ሰው አንዲት ወይም
ሁለት ልጃገረዶች እየወሰደ
አይደለምን?
ይህ ሁሉ ምርኮ፣ በቀለም ያጌጡ ልብሶች
ለሲሣራ ደርሰውት፣
በጌጣጌጥ የተጠለፉ ልብሶች ለአንገቴ
ይዞልኝ እየመጣ አይደለምን?’

31“እግዚአብሔር ሆይ፤ ጠላቶችህ ሁሉ ይጥፉ፤
አንተን የሚወዱህ ግን፣ የንጋት ፀሐይ
በ፤ይል እንደሚወጣ እንዲያ
ይሁኑ፡፡”

ከዚያም በራላ ምድሪቱ ለአርባ ዓመት
ሰላም አገኘች፡፡

**ጌዴዎን**

6 እንደ ገና እስራኤላውያን *በእግዚአብ
ሔር ፊት* ክፉ ድርጊት ፈጸሙ፤ *እግ
ዚአብሔርም* ለምድያማውያን አሳልፎ ሰጣ
ቸው፤ እነርሱም ሰባት ዓመት ገዟቸው፡፡
2እስራኤላውያን የምድያማውያን ፤ይል
ስለበረታ ባቸው በየዋሻውና በየምሽጉ፣ በየተ
ራራው ጥግ መሸሸጊያ ስፍራ አበጁ፡፡ 3እስራ
ኤላው ያን ዘር በሚዘሩበት ጊዜ ሁሉ
ምድያማ ው ያን፣ አማሌቃውያንና
ሌሎች የምሥራቅ ሕዝቦች መጥተው አገሩን
ይወሩ ነበር፡፡ 4እነርሱም በምድሪቱ ላይ
ሰፍረው እስከ ጋዛ ያለውን ሰብል በማጥፋት
አንዳችም የእህል

[॥]16 ወይም *በኮርቻ ላይ* ተብሎ መተርጐም ይቻላል፡፡

5፥12 መሳ4፥4:6፤ መዝ44፥23፤57፥8፤ 68፥18፤ ኢሳ51፥9:17፤ ኤፌ4፥8
5፥14 ዘፍ41፥52፤ 50፥23፤ ዘኁ34፥21፤ መሳ1፥2 9፤3፥13
5፥15 ዘፍ30፥18፤ መሳ4፥4:6
5፥16 ዘፍ49፥14፤ ዘኁ32፥1
5፥17 ኢሱ12፥2፤ 17፥7፤19፥29
5፥18 ዘፍ30፥ 8:20፤መሳ4፥6፤ መዝ68፥27
5፥19 ቀኁ30፤ ኢሱ11፥5፤ 12፥21፤መሳ4፥13፤ ራእ16፥16
5፥20 ኢሱ10፥11
5፥21 መሳ4፥7፤ ኢሱ1፥6
5፥22 ኤር8፥16
5፥24 ዘፍ15፥19፤ መሳ4፥17፤ሉቃ1፥42
5፥25 ዘፍ18፥8
5፥26 መሳ4፥21
5፥27 መሳ4፥22
5፥28 ኢሱ2፥15፤ ምሳ7፥6
5፥30 ቀኁ19፤ ዘፀ5፥9፤ 1ሳሙ30፥24፤ 2ሳሙ1፥24፤ መዝ45፥14፤68፥12፤ ሕዝ16፥10
5፥31 ዘኁ10፥35፤ መሳ3፥11፤ 2ሳሙ18፥32፤ 23፥4፤ኢዮ37፥21፤ መዝ19፥4፤89፥36፤ ኢሳ18፥4
6፥1 ዘፍ25፥2፤ መሳ2፥11
6፥2 1ሳሙ13፥6፤ ኢዮ24፥8፤ኢሳ2፥19፤ 5፥30፤8፥21፤26፥16፤ 37፥3፤ኤር41፥9፤ 48፥28፤49፥8:30፤ ዕብ11፥38
6፥3 ዘፍ25፥6፤ ዘኁ13፥29፤ ኢሳ 11፥14፤ ኤር49፥28
6፥4 ዘፍ10፥19፤ ዘሌ26፥16፤ዘዳ28፥30: 51፤ኢሳ10፥6፤ 39፥6፤ 42፥22

ዘር አያስተርፉም፣ የበግም ሆነ የከብት ወይም
የአህያ መንጋ አይተዉም ነበር። 5ከብቶቻ
ቸውንና ድንኳኖቻቸውን ይዘው ሲመጡ ልክ
የአንበጣ መንጋ ይመስሉ ነበር፤ ሰዎቹንም
ሆነ ግመሎቻቸውን ለመቍጠር አዳጋች ሲሆን፣
የሚመጡትም ምድሪቱን ለማጥፋት ነበር።
6ምድያማውያን እስራኤላውያንን ችግር
ላይ ስለጣሏቸው፣ ይረዳቸው ዘንድ ወደ
*እግዚአብሔር* ጮኹ።
7ከምድያማውያን ጥቃት የተነሣ እስራ
ኤላውያን ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፤ 8*እግዚ
አብሔር* አንድ ነቢይ ላከላቸው፤ እርሱም
እንዲህ አለ፤ "የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር*
እንዲህ ይላል፤ ከባርነት ቤት ከግብፅ ምድር
ያወጣኋችሁ እኔ ነኝ። 9ከግብፃውያን እጅ
ታደግኋችሁ፤ ከሚያስጨንቋችሁ ሁሉ አዳ
ንኋችሁ፤ እነርሱንም ከፊታችሁ አሳድጄ
አስወጣኋቸው፤ ምድራቸውንም ሰጠኋችሁ።
10እናንተንም፣ 'እኔ *እግዚአብሔር* አምላካችሁ
ነኝ፤ በምድራቸው ላይ የምትኖሩባቸው የአ
ሞራውያንን አማልክት አታምልኩ' አልኋ
ችሁ፤ እናንተ ግን አላዳመጣችሁኝም።"
*11የእግዚአብሔር መልአክ ዖፍራ* ወደ
ምትባል መንደር መጥቶ፣ በአቢዔዝራ
ዊው በኢዮአስ ዕርሻ ውስጥ በሚገኝ በአ
ንድ የባሉጥ ዛፍ *ሥር* ተቀመጠ፤ የኢ
ዮአስም ልጅ ጌዴዎን፣ ምድያማውያን
እንዳያዩበት ደብቆ በወይን *መጭመቂያው*
ስፍራ ስንዴውን ይወቃ ነበር። *12የእግዚ
አብሔር መልአክ* ተገልጦ፣ "አንተ ፤ያል
ጦረኛ! እነሆ፤ *እግ ዚአብሔር* ከአንተ ጋር
ነው" አለው።
13ጌዴዎን *መልሶ*፣ "ጌታዬ ሆይ፤ *እግ
ዚአብሔር* ከእኛ ጋር ከሆነ ይህ ሁሉ እን
ዴት ሊደርስብን ቻለ? '*እግዚአብሔር* ከግ
ብፅ ምድር አውጥቶናል' በማለት አባቶቻ
ችን የነገሩን ታምራት የት አለ? አሁን ግን
*እግዚአብሔር* ትቶናል፤ በምድያማውያንም
እጅ አሳልፎ ሰጥቶናል" አለው።
14በዚህ ጊዜ *እግዚአብሔር* ወደ እርሱ
ዘወር ብሎ፣ "ሂድ፤ ባለህ ኀይል እስራኤላ
ውያንን ከምድያማውያን እጅ ነጻ እንድ
ታወጣ የምልክህ እኔ አይደለሁምን?
አለው"።
15ጌዴዎንም፣ "ጌታ ሆይ፤ የእኔ ጐሣ ከም
ናሴ ነገድ እጅግ ደካማ ነው፤ ከቤተሰቤም እኔ
የመጨረሻ ነኝ፤ ታዲያ እንዴት እኔ እስራ
ኤልን ላድን እችላለሁ?" አለ።
*16እግዚአብሔርም*፣ "በእርግጥ እኔ ከአንተ
ጋር እሆናለሁ፤ ምድያማውያንንም እንደ
አንድ ሰው አድርገህ ትመታቸዋለህ"
አለው።

17ጌዴዎን እንዲህ ብሎ መለሰ፤
"አሁን በፊትህ ሞገስ አግኝቼ ከሆነ
በእርግጥ የምታነጋግረኝ አንተ ራስህ ለመ
ሆንህ ምልክት ስጠኝ፤ 18*ተመልሼ* እስክ
*መጣ፣ መሥዋዕቴንም* አምጥቼ በፊትህ
እስካቀርብ ድረስ እባክህ አትሂድ።"
*እግዚአብሔርም*፣ "እስክትመለስ እጠ
ብቅሃለሁ" አለው።
19ጌዴዎን ወደ ቤቱ ሄደ፤ የፍየል ጠቦ
ትም ዐረደ፤ አንድ ኢፍ *መስፈሪያ*[ዡ]
ዱቄት ወስዶ እርሾ ያልገባበት ቂጣ
ጋገረ። *ሥጋውን* በቅርጫት፣ *መረቁን*
በምንቸት ይዞ በመምጣት በባሉጥ *ሥር*
ለተቀመጠው አቀረበለት።
20 *የእግዚአብሔር መልአክ*፣ "*ሥጋውንና*
ዕርሾ ያልገባበትን ቂጣ ወስደህ፣ በዚያ
ዐለት ላይ አኑር፤ *መረቁንም* በ*ሥጋውና*
በቂጣው ላይ አፍስስ" አለው፤ ጌዴዎንም
እንደ ታዘዘው አደረገ። 21*መልአኩም*
በያዘው በትር ጫፍ *ሥጋውንና* ቂጣውን
ነካ፤ ከዐለቱም እሳት ወጥቶ *ሥጋውንና*
ቂጣውን በላ፤ ከዚያም *የእግዚአብሔር*
*መልአክ* ተሰወረ። 22ጌዴዎን ያየው *የእግዚ
አብሔር መልአክ* መሆኑን ባወቀ ጊዜ፣ "ልዑ
ል *እግዚአብሔር* ሆይ፤ *የእግዚአብሔ ርን*
*መልአክ* ፊት ለፊት አይቻለሁና ወዮልኝ"
አለ።
*23እግዚአብሔርም*፣ "ሰላም ለአንተ
ይሁን፤ አትፍራ፤ አትሞትም" አለው።
24ጌዴዎንም በዚያ *ለእግዚአብሔር* መሠ
ዊያ ሠራ፤ ስሙንም "*እግዚአብሔር* ሰላም
ነው" ብሎ ጠራው፤ ይህ መሠዊያ የአቢዔዝ
ራውያን ይዞታ በሆነው በ*ዖፍራ* ዛሬም ቆሞ
ይታያል።
25በዚያች ሌሊት *እግዚአብሔር* ጌዴ
ዎንን እንዲህ አለው፤ "ከአባትህ መንጋ
ሰባት ዓመት የሆነውን[የ] ሁለተኛውን ወይ
ፈን ውሰድ፤ አባትህ ለበኣል የሠራውን
መሠዊያ አፍርስ፤ በአጠገቡ የአሼራን
ዐምድ[ዶ] ሰባብረህ ጣል። 26በዚህ ፍርስራሽ
ጕብታ ላይ ለአምላክህ *ለእግዚአብሔር* የሚ
ገባውን *መሠዊያ*[ጀ] *ሥራ*። ሰባብረህ በጣ
ልኸው የአሼራ ምስል ዐምድ ሁለተኛውን[ገ]
ወይፈን ወስደህ የሚቃጠል *መሥዋዕት*
አድርገህ አቅርበው።"
27ጌዴዎን ከአገ ልጋዮቹ ዐሥር ሰዎች
ወስዶ *እግዚአብሔር* እንዳዘዘው አደረገ፤

6፥5 ዘዳ28፥42፤ መሳ8፥10፤ኢሳ21፥7፤ 60፥6፤ኤር49፥32
6፥6 መሳ3፥9
6፥7 መሳ3፥9
6፥8 ዘጸ18፥15፤ ኢሱ24፥17፤ መሳ2፥1፤1ነገ20፥13፡ 22፤2ነገ17፥13፡23፤ ነህ9፥29፤ኢዮ36፥10፤ ኤር25፥5፤ሕዝ18፥3 0 ኛ31
6፥9 ዘኍ10፥9፤ መዝ44፥2፤136፥24
6፥10 ዘፀ20፥5፤ ኢሱ24፥15
6፥11 ቀኍ29፤ ዘፍ6፥7 ፤ዘኍ26፥30፤ ኢሱ18፥23፤ መሳ7፥1፡14፤8፥1፡13፡ 29 ፤ሩት2፥173፥2፤ 1ሳሙ23፥1፤ 1ዜና 21፥20፤ ነህ13፥ 15፤ ኢሳ16፥10፤ 63፥3፤ ሰቆ1፥15፤ ኢል3፥13፤ዕዝ11፥ 32
6፥12 ሉ1፥5፤ መሳ11፥1፤ሩት2፥4፤ 1ሳሙ10፥7፤ መዝ 129፥8
6፥13 ዘዳ31፥17፤ ኢሱ3፥5፤2ሳሙ7፥ 22፤ መዝ44፥1፤ 78፥3
6፥14 ቀኍ36፤ መሳ10፥1፤2ነገ14፥2 7፤ዕብ11፥34
6፥15 1ሳሙ9፥21፤ ኢሳ60፥22
6፥16 ዘፀ3፥12፤ ዘኍ14፥43፤ኢሱ1፥5
6፥17 ቀኍ36ኛ37፤ ዘፍ24፥14፤ዘፀ3፥12፤ 4፥8
6፥19 ዘፍ18፥7ኛ8፤ ዘሌ19፥36፤ መሳ13፥15
6፥20 መሳ13፥19
6፥21 ዘፀ4፥2፤ ዘሌ9፥24
6፥22 ዘፍ32፥30፤ መሳ13፥16፡21፡22
6፥23 ዘፍ16፥13፤ ዘዳ5፥26፤ዳን10፥19
6፥24 ዘፍ22፥14፤ ኢሱ18፥23
6፥25 ቀኍ26፡ 28፡30፤ዘፀ34፥13፤ መሳ2፥13
6፥26 ዘፍ8፥20

[ዡ]19 22 ሊትር ያህል ነው።
[የ]25 ወይም፣ *ከአባትህ መንጋ በደንብ ያደገውን ኮርማ ውሰድ*
[ዶ]25 በዚህም ሆነ በመጽሐፉ ክፍሎች ሁሉ የአሼራን ምስል ጣዖት የሚያመለክት ነው።
[ጀ]26 ወይም፣ *የድንጋይ ካብ*
[ገ]26 ወይም፣ *የደረሰ*

ቤተ ሰቡንና የከተማውን ሰው ስለ ፈራ ይህን ያደረገው ቀን ሳይሆን ሌሊት ነበር።

28ሌሊቱ ነግቶ የከተማው ሕዝብ ከመኝታው ሲነሣ፣ የበኣል መሠዊያ ፈርሶ በአጠገቡ የቆመው የአሼራ ምስል ተሰባብሮ፣ አዲስ በተሠራው መሠዊያ ላይ ሁለተኛው ወይፈን ተሠውቶ ነበር።

29እነርሱም፣ “ይህን ያደረገ ማን ነው?” በማለት እርስ በርሳቸው ተጠያየቁ።

ነገሩን በጥብቅ ሲከታተሉም፣ “የኢዮአስ ልጅ ጌዴዎን መሆኑን ደረሱበት።”

30የከተማዪቱም ሰዎች ኢዮአስን፣ “የበኣልን መሠዊያ ያፈረሰና በአጠገቡ የቆመውን የአሼራን ምስል ዐምድ የሰበረው ልጅህ በመሆኑ መሞት ስላለበት አውጣልን አሉት።”

31በዚህ ጊዜ ኢዮአስ በቍጣ ለገነፈለውና በዙሪያው ለነበረው ሕዝብ እንዲህ አለ፤ “ለበኣል ትሟገቱለታላችሁን? ልታድኑትስ ትሞክራላችሁን? ለእርሱ የሚሟገትለት ቢኖር እስከ ጠዋት ይሙት! እንግዲህ በኣል በእርግጥ አምላክ ከሆነ መሠዊያውን ሲያፈርሱበት ራሱን ሊከላከል ይችላል።” 32ስለ ዚህም፣ “መሠዊያውን አፍርሶበታልና ራሱ በኣል ይሟገተው” ሲሉ በዚያ ዕለት ጌዴዎንን፣ “ይሩበኣል”[ጠ] ብለው ጠሩት።

33በዚህ ጊዜ ምድያማውያን ሁሉ፣ አማሌቃውያንና ሌሎች የምሥራቅ ሕዝቦች ፤ይላቸውን አስተባብረው የዮርዳኖስን ወንዝ በመሻገር በኢይዝራኤል ሸለቆ ሰፈሩ። 34ከዚያም የእግዚአብሔር መንፈስ በጌዴዎን ላይ ወረደ፤ እርሱም መለከት ነፋ፤ አቢዓ ˏዝራውያን እንዲከተሉት ጠራቸው። 35እንዲሁም በመላው የምናሴ ምድር መልእክተ ኞቹን ልኮ እንዲከተሉት ጥሪ አደረገ፤ ደግሞም የአሴር፣ የዛብሎንና የንፍታሌም ሰዎች ወጥ ተው እንዲገጥሟቸው መልእክተኛ ላከባቸው።

36ጌዴዎን እግዚአብሔርን እንዲህ አለው፤ “በተናገርኸው መሠረት እስራኤላውያንን በእጄ የምታድናቸው ከሆነ፣ 37እነሆ፤ የበግ ጠጕር ባዘቶ በዐውድማው ላይ አኖ ራለሁ። ምድሩ በሙሉ ደረቅ ሆኖ ባዝቶው ላይ ብቻ ጤዛ ቢኖር፣ እንዳልኸው እስራ ኤላውያንን በእኔ እጅ እንደምታድናቸው ዐውቃለሁ።” 38እንደዚሁ ሆነ፤ ጌዴዎን በማግስቱ ጠዋት ማልዶ ተነሣ፤ ባዘቶውንም ሲጨምቅ የወጣው ውሃ አንድ ቈሬ ሞላ።

39ከዚያም ጌዴዎን እግዚአብሔርን እንዲህ አለው፤ “እባክህ አትቈጣኝ፤ አንዲት ጥያቄ እንደ ገና ልጠይቅ። በጠጕሩ ባዘቶ ላይ ሌላ ሙከራ እንዳደርግ ፍቀድልኝ፤ በዚህ ጊዜ ምድሩ ሁሉ በጤዛ ተሸፍኖ ባዘቶው ደረቅ ይሁን።” 40በዚያች ሌሊት እግዚአብሔር እንደ ተጠየቀው አደረገ፤ ምድሩ በሙሉ በጤዛ ሲሸፈን፣ ባዘቶው ብቻ ደረቅ ሆነ።

6፥28 ቍ30፤ 1ነገ16፥32፤ 2ነገ21፥3
6፥29 ቍ11
6፥30 ቍ28
6፥31 ሳሙ24፥15፤ መዝ43፥1፤ ኤር30፥13
6፥32 መሳ7፥1፤ 8፥29፡35፤9፥1፤ 1ሳሙ12፥11
6፥33 ዘፍ25፥6፤ ዘኍ13፥29፤ ኢሱ15፥56፤ ሕዝ25፥4፤ሆሴ1፥5
6፥34 ኢሱ6፥20፤ 17፥2፤መሳ3፥10፡ 27
6፥35 ኢሱ17፥7፤ መሳ4፥6፤7፥23
6፥36 ቍ14
6፥37 ዘፍ24፥14፤ ዘኍ18፥27፤2ሳሙ6፥6፤24፥16፤ ኢዮ31፥20
6፥39 ዘፍ18፥32
6፥40 ዘፀ4፥3ኛ7፤ ኢሳ38፥7

## ጌዴዎን ምድያማውያንን ድል አደረገ

7 ይሩበኣል የተባለው ጌዴዎን፣ ከእርሱም ጋር የነበሩት ሰዎች ሁሉ በጠዋት ተነሥተው በሐሮድ ምንጭ አጠገብ ሰፈሩ። የምድያማውያንም ሰፈር እስራኤላውያን ከሰፈሩበት በስተ ሰሜን በኩል፣ በሞሬ ኰረብታ አጠገብ በሸለቆው ውስጥ ነበር። 2እግዚአብሔር ጌዴዎንን እንዲህ አለው፤ “ምድያማውያንን በእጃቸው አሳልፌ እንዳልሰጥ አብረውህ ያሉት ሰዎች በጣም ብዙ ናቸው፤ እስራኤላውያን የገዛ ፤ይላቸው እንዳዳናቸው በመቍጠር እንዳይታበዩብኝ፣ 3‘ማንም የፈራ ቢኖር የገለዓድን ተራራ ትቶ ወደ መጣበት ይመለስ’ ብለህ ለሕዝቡ ዐውጅ።” ስለዚህ ሃያ ሁለቱ ሺህ ሲመለሱ ዐሥሩ ሺህ ብቻ ቀሩ።

4እግዚአብሔር ጌዴዎንን እንዲህ አለው፤ “አሁንም ሰዎቹ ብዙ ናቸው፤ ወደ ወንዝ ይዘሃቸው ውረድ፤ በዚያም እለይልሃለሁ። ‘ይህ ከአንተ ጋር ይሂድ’ የምለው፣ ከአንተ ጋር ይሄዳል፤ ነገር ግን፣ ‘ይህ ከአንተ ጋር አይሂድ’ የምለው፣ ከአንተ ጋር አይሄድም።”

5ስለዚህ ጌዴዎን ሰዎቹን ወደ ወንዝ ይዞአቸው ወረደ፤ እዚያም እግዚአብሔር፤ “ውሻ በምላሱ እየጨለፈ እንደሚጠጣ ሁሉ፣ በምላሳቸው የሚጠጡትን፣ በጕልበታቸው ተንበርክከው ከሚጠጡት ለይ” አለው። 6ሦስት መቶ ሰዎች ውሃውን በእጃቸው እያፈሱ ጠጡ፤ የቀሩት ሁሉ ግን ለመጠጣት በጕልበታቸው ተንበረከኩ።

7እግዚአብሔርም ጌዴዎንን፣ “ውሃውን በእጃቸው እያፈሱ በጠጡት ሦስት መቶ ሰዎች አድናችኋለሁ፤ ምድያማውያንንም በእጃችሁ አሳልፌ እሰጣችራለሁ፤ የቀሩት በሙሉ ወደየመጡበት ይመለሱ” አለው። 8ጌዴዎንም የቀሩትን እስራኤላውያን በሙሉ ወደየድንኳናቸው እንዲመለሱ አደረገ፤ ሦስት መቶውን ግን አስቀራቸው፤ እነርሱም የሚመለሱትን ሰዎች ስንቅና መለከት ወሰዱ።

በዚህ ጊዜ የምድያማውያኑ ሰፈር ከእነርሱ በታች በሸለቆአማው ውስጥ ነበር። 9በዚያች ሌሊት እግዚአብሔር ጌዴዎንን እንዲህ አለው፤ “ተነሥ፤ በሰፈሩም ላይ ውረድ፤ በእጅህ አሳልፌ ሰጥቼሃለሁና። 10አደጋ ለመጣል የምትፈራ ከሆነ ግን፣ ፉራ ከተባለው አገልጋይህ ጋር ወደ ሰፈሩ

7፥1 ዘፍ12፥6፤ 25፥2፤መሳ6፥11፡32፤ 2ሳሙ23፥25
7፥2 ዘዳ8፥17፤ 2ቆሮ4፥7
7፥3 ዘዳ20፥8፤ ኢሱ12፥2
7፥4 1ሳሙ14፥6
7፥6 ዘፍ14፥14
7፥7 ኢሱ8፥7፤ 1ሳሙ14፥6
7፥9 ቍ13ኛ15፤ ኢሱ2፥24፤መሳ1፥2

[ጠ]32 ይሩበኣል ማለት በኣል ይጋፈጠው ማለት ነው።

ውረድ፤ 11የሚሉትንም አድምጥ፤ ከዚያ በኋላ
በሰፈሩ ላይ አደጋ ለመጣል ድፍረት ታገኛ
ለህ፤” ስለዚህም ጌዴዎን አገልጋዩን ፉራን
አስከትሎ እስከ ሰፈሩ ዳርቻ ወረደ።
12ብዛታቸው እንደ አንበጣ መንጋ የሆነ
ምድያማውያን፣ አማሌቃውያንና ሌሎ
ችም የምሥራቅ ሕዝቦች በሸለቆው ውስጥ
ሰፍረው ነበር፤ የግመሎቻቸውም ብዛት
በባሕር ዳርቻ እንዳለ አሸዋ ስፍር ቍጥር
አልነበረውም።

13አንድ ሰው ያየውን ሕልም ለጓደኛው
በሚነግርበት ጊዜ ጌዴዎን እዚያ ደረሰ።
ያም ሰው፣ “በሕልሜ ክብ የሆነ አንድ
የገብስ ቂጣ ከላይ ተንከባሎ በምድያ
ማውያን ሰፈር ላይ ሲወርድ፣ ድንኳኑንም
ሲመታው ከአመታቱም ኀይለኛነት የተነሣ
ድንኳኑ ተገልብጦ ሲፈራርስ አየሁ” በ
ማለት ይነግረው ነበር።

14ጓደኛውም መልሶ፣ “ይህ የእስራኤላዊው
የኢዮአስ ልጅ የጌዴዎን ሰይፍ እንጂ ሌላ
ነገር ሊሆን አይችልም፤ እነሆ፤ *እግዚአብሔር*
ምድያማውያንንና ሰፈሩን በሙሉ በእጁ
አሳልፎ ሰጥቶታልና” አለው።

15ጌዴዎንም ሕልሙንና ፍቺውን በሰማ
ጊዜ *ለእግዚአብሔር* ሰገደ፤ ከዚያም ወደ እስ
ራኤላውያን ሰፈር ወጥቶ፣ “*እግዚአብሔር*
የምድያማውያንን ሰፈር በእጃችሁ አሳልፎ
ሰጥቶአልና ተነሡ” አላቸው። 16ሦስቱን
መቶ ሰዎች በሦስት ቡድን ከፍሎ፣ እያን
ዳንዱን ሰው ቀንደ መለከትና በውስጡ ችቦ
ያለበት ባዶ ማሰሮ በእጁ እንዲይዝ አደረገ።

17ጌዴዎንም እንዲህ አላቸው፤ እኔን ተመ
ልከቱ፤ የማደርገውንም አድርጉ፤ በሰፈሩ ዳርቻ
ስደርስ እኔ የማደርገውን አይታችሁ ልክ
እንደዚያው አድርጉ። 18እኔና አብረውኝ
ያሉት ሁሉ ቀንደ መለከቶቻችንን በምንነ
ፋበት ጊዜ እናንተም በሰፈሩ ዙሪያ ሁሉ
ቀንደ መለከቶቻችሁን እየነፋችሁ፣ ‘*ለእግዚ
አብሔርና* ለጌዴዎን’ ብላችሁ ጩኹ።”

19ዘቦቹ ተቀያይረው የእኩለ ሌሊቱን
ጥበቃ በጀመሩበት ጊዜ፣ ጌዴዎንና አብረ
ውት የነበሩት መቶ ሰዎች በሰፈሩ ዳርቻ
ደረሱ፤ እነርሱም ቀንደ መለከቶቻቸውን ነፉ፤
የያዟቸውንም ማሰሮች ሰበሩ። 20በሦስት
ቡድን የተከፈሉት ሰዎች ቀንደ መለከቶ
ቻቸውን ነፉ፤ ማሰሮቻቸውንም ሰበሩ፤
ችቦዎቻቸውን በግራ እጆቻቸው፣ የሚነፏ
ቸውንም ቀንደ መለከቶች በቀኝ እጆቻቸው
ይዘው፣ “*የእግዚአብሔርና የጌዴዎን ሰይፍ*” በማ
ለት ጮኹ። 21እያንዳንዱ ሰው በሰፈሩ
ዙሪያ የተመደበበትን ቦታ እንደያዘም ምድ
ያማውያኑ እየጮኹ ሸሹ።

7፥12 ዘኍ13፥29፤
ዘዳ28፥42፤ኢሱ11፥4፤
ኤር46፥23፤
49፥29
7፥14 መሳ6፥11
7፥15 ቍ9፤
1ሳሙ15፥31
7፥16 ቍ19፤
ዘፍ14፥15፤15፥17፤
24፥14፤ዘሌ25፥9፤
መሳ9፥43፤
1ሳሙ11፥11፤
2ሳሙ18፥2
ሳ3፥27
7፥19 ቍ16
7፥20 ዘፍ15፥17፤
ዘዳ32፥41
7፥21 2ነገ7፥7
7፥22 ኢሱ6፥20፤
1ሳሙ14፥20፤
18፥19፤1ነገ4፥12፤
19፥16፤2ዜና20፥23፤
ኢሳ9፥21፤19፥2
ሕዝ 8፥21፤ዕን3፥14፤
ሐጌ2፥22፤ዘካ14፥13
7፥23 ኢሱ17፥7፤
መሳ6፥35፤
መዝ83፥9
7፥24 ኢያ2፥7
7፥25 መሳ8፥3፡4፤
መዝ83፥11፤106፥43፤
ኢሳ9፥4፤10፥26
8፥1 ዘፍ25፥2፤
መሳ6፥11፤12፥1፤
2ሳሙ19፥41
8፥2 ዘኍ26፥30
8፥3 መሳ7፥25
8፥4 መሳ7፥25
8፥5 ቍ7፡12፤
ዘፍ33፥17፤ኢዮ16፥
7፤መዝ6፥6፤
83፥11፤ ኤር45፥3
8፥6 ቍ14፡15፤
1ሳሙ25፥11
8፥7 ቍ5

22የሦስት መቶው ቀንደ መለከት ድምፅ
እንደተሰማም *እግዚአብሔር* በሰፈሩ ውስጥ
ያለው ሰው አንዱ በሌላው ላይ ሰይፉን
እንዲመዝበት አደረገ፤ ሰራዊቱ በጽሬራ
አቅጣጫ ወደ ቤት ሺጣ፣ ከዚያም አል
ፈው በጠባት አጠገብ እስካለው እስከ
አቤላሞሖላ ድንበር ድረስ ሸሽተው ሄዱ።
23በንፍታሌም፣ በአሴርና በመላው የምናሴ
ምድር የሚገኙ እስራኤላውያን ተጠርተው
ወጡ፤ ምድያማውያንንም አሳደዱ። 24ጌዴ
ዎንም በኤፍሬም ኰረብታማ አገር ለሚ
ኖሩት ሁሉ፣ “በምድያማውያን ላይ ውረዱ፤
እስከ ቤትባራ ድረስ ያለውንም የዮርዳኖስ
ወንዝ ቀድማችሁ ያዙ” አላቸው።

ስለዚህ የኤፍሬም ሰዎች ሁሉ ተጠርተው
ወጡ፤ እስከ ቤትባራ ድረስ ያለውንም የዮ
ርዳኖስን ወንዝ ያዙ። 25እንዲሁም ሔሬብና
ዜብ የተባሉትን ሁለቱን የምድያም መሪዎች
ያዙ። ሔሬብን በሔሬብ ዐለት አጠገብ፣
ዜብን ደግሞ በዜብ የወይን መጭመቂያ
ላይ ገደሏቸው፤ ምድያማውያንንም አሳ
ደዱ፤ የሔሬብንና የዜብን ራስ ቈርጠው
ጌዴዎን ወዳለበት ወደ ዮርዳኖስ ይዘው
መጡ።

## ዛብሄልና ስልማና

8 በዚህ ጊዜ የኤፍሬም ሰዎች፣ “ምድያ
ማውያንን ለመውጋት ስትሄድ ለምን
አልጠራኸንም? ለምንስ እንዲህ ያለ ነገር
አደረግህ?” በማለት ጌዴዎንን እጅግ ነቀፉት።

2ጌዴዎን ግን፣ “እናንተ ካደረጋችሁት
ጋር ሲነጻጸር የእኔ ከምን ይቈጠራል? የኤ
ፍሬም የወይን ቃርሚያ ተጠቃሎ ከገባው
ከአቢዔ ዝር የወይን መከር አይበልጥምን?
3እግዚአብሔር የምድያማውያንን መሪዎች ሔሬ
ብንና ዜብን በእጃችሁ አሳልፎ ሰጣችሁ፤
ታዲያ እናንተ ከፈጸማችሁት ጋር የሚወ
ዳደር ምን ማድረግ እችል ነበር?” ይህን ሲሰሙ
ቍጣቸው በረደ።

4ጌዴዎንና ሦስት መቶዎቹ ሰዎች ዮርዳ
ኖስን ተሻገሩ፤ ምንም እንኳ ድካም ቢሰ
ማቸውም ጠላቶቻቸውን ያሳድዱ ነበር።
5የሱ ኮትንም ሰዎች፣ “የምድያምንም
ነገሥታት ዛብሄልንና ስልማናን በማሳደድ
ላይ ስለ ሆንሁ የተከተሉኝም ሰዎች ስለ
ደከሙ ብኝ እባካችሁ የሚበሉትን እንጀ
ራ ስጧቸው” አላቸው።

6የሱኮት ሹማምንት ግን፣ “ለተከተሉህ
ሰዎች እንጀራ እንሰጥ ዘንድ ዛብሄልና
ስልማና በእጅህ ገብተዋልን?” አሉት።

7ጌዴዎንም መልሶ፣ “ደህና፤ *እግዚብሔር*
ዛብሄልንና ስልማናን በእጄ አሳልፎ በሚ

ሰጥበት ጊዜ በምድረ በዳ እሾኽና አሜከላ ሥጋችሁን እተለትላለሁ” አላቸው::

8ከዚያም ወደ ጵኒኤል ሰዎች ሄዶ ያንኑ ጥያቄ አቀረበላቸው፤ የእነርሱም መልስ የሱኮት ሰዎች ከሰጡት መልስ ጋር አንድ ዐይነት ነበር። 9እርሱም የጵኒኤልን ሰዎች፣ “በድል አድራጊነት በሰላም ስመለስ ከተ ማችሁን የምትጠብቁበትን ይህን ግንብ አፈርሰዋለሁ” አላቸው::

10በዚህ ጊዜ ዛብሄልና ስልማና ዐሥራ አምስት ሺህ ከሆነ ሰራዊታቸው ጋር ቀርቀር በተባለ ስፍራ ነበሩ፤ ይህም ከምሥራቅ ሕዝቦች ከተውጣጣውና በጦር ሜዳ ከወደ ቀው መቶ ሃያ ሺህ ሰይፍ ታጣቂ ሰራዊት የተረፈው ነበር:: 11ከዚያም ጌዴዎን ተነሣ፤ ከኖባህና ከዮግብሃ በስተ ምሥራቅ የሚ ኖሩ ዘላኖች የሚሄዱበትን መንገድ ተከ ትሎ በጠላት ሰራዊት ላይ በድንገት አደጋ ጣለ:: 12ሁለቱ የምድያም ነገሥታት ዛብሄ ልና ስልማና ሸሹ፤ ጌዴዎን ግን አሳዶ ያዛ ቸው፤ መላ ሰራዊታቸውንም እጅግ በታተ ነው::

13ከዚህ በኋላ የኢዮአስ ልጅ ጌዴዎን በሐሬስ መተላለፊያ በኩል አድርጎ ከጦርነቱ ተመለሰ፤ 14እርሱም የሱኮት ሰው የሆነ አንድ ወጣት ማረከ፤ መረመረውም፤ ወጣተ ም የሰባ ሰባት የሱኮት ሹማምንትና የከተ ማዪቱ ንም አለቆች ስም ጻፈለት:: 15ከዚ ያም ጌዴ ዎን ወደ ሱኮት ሰዎች መጥቶ እንዲህ አላ ቸው፤ “‘ለደከሙት ሰዎችህ እንጀራ እንሰጥ ዘንድ ዛብሄልና ስልማና በእጅህ ገብተዋልን’ በማለት ያላገጣችሁብኝ ዛብሄልና ስልማና እነዚሁላችሁ::” 16ጌዴዎን የከተማዪቱን አለ ቆች ወሰደ፤ በምድረ በዳ እሾኽና አሜኬላ በመቅጣት የሱኮትን ሰዎች ትምህርት ሰጣ ቸው:: 17እንዲሁም በጵኒ ኤል ያለውን የከ ተማ መጠበቂያ ግንብ አፈረሰ፤ የከተማዪቱ ንም ሰዎች ገደለ::

18ዛብሄልና ስልማናንም፣ “በታቦር ላይ የገደላችኋቸው ሰዎች እንዴት ያሉ ነበሩ?” በማለት ጠየቃቸው::

እነርሱም፣ “ሁሉም እንዲህ እንዳንተ ያሉ የንጉሥ ልጆች የሚመስሉ ናቸው” አሉት::

19ጌዴዎንም፣ “እነርሱ የእናቴ ልጆች ወንድሞቼ ናቸው፤ ባትገድሏቸው ኖሮ እኔም እንደማልገድላችሁ በሕያው *እግዚ አብሔር* ስም አረጋግጥላችሁ ነበር::” ብሎ መለሰላቸው:: 20ከዚያም ወደ በኵር ልጁ ወደ ዮቴር ዞወር ብሎ፣ “ግደላቸው” አለው፤ ዮቴር ግን ትንሽ ልጅ ነበርና ስለ ፈራ ሰይፉን አልመዘዘም::

21ዛብሄልና ስልማናም፣ “የሰው ጕልበቱ እንደ ሰውነቱ መጠን ነውና አንተው ራስህ ግደለን አሉት፤ ጌዴዎንም ተነሥቶ ገደላቸው፤ በግመሎቻቸው አንገት ላይ የነበሩትንም ጌጦች ወሰደ::

### የጌዴዎን ኤፉድ

22እስራኤላውያንም ጌዴዎንን፣ “ከም ድያማውያን እጅ ታድገኸናልና አንተ፣ ልጅህና የልጅ ልጅህ ግዙን” አሉት::

23ጌዴዎን ግን መልሶ፣ “እኔም ሆንሁ ልጄ አንገዛችሁም፤ የሚገዛችሁ *እግዚአብሔር* ነው” አላቸው:: 24እርሱም፣ “አንድ የምጠ ይቃችሁ ነገር አለኝ፤ ይኸውም እያንዳንዳ ችሁ ከምርኮ ካገኛችሁት ውስጥ የጆሮ ጕትቻችሁን እንድትሰጡኝ ነው” አላቸው፤ የወርቅ ጕትቻ ማድረግ የእስማኤላውያን ባህል ነበርና።

25እነርሱም መልሰው፤ “ደስ እያለን እንሰጥሃለን” አሉት፤ ወዲያው ልብስ አነጠፉ፤ በላዩም ላይ እያንዳንዳቸው ከማረኩት ውስጥ የጆሮ ጕትቻ ጣል ጣል አደረጉለት:: 26ሌሎቹን ጌጣ ጌጦች ይኸውም የዐንገት ሐብሉን ከነእንጥልጥሉ፣ የምድያም ነገሥታት ይለብሱት የነበረውን ሐምራዊ ልብስ ወይም በግመሎቻቸው ዐንገት ላይ ያሉትን ጌጦች ሳይጨምር ጌዴዎን በጠየቃቸው መሠረት የሰጡት የወርቅ ጕትቻ ክብደት ሺህ ሰባት መቶ ሰቅል[ጨ] ያህል መዘነ::

27ጌዴዎን በወርቁ ኤፉድ ሠራ፤ በተወለደበትም ከተማ በዖፍራ አኖረው:: እስራኤልም በሙሉ ኤፉዱን በማምለክ ስላመነዘሩ፣ ኤፉዱ ለጌዴዎንና ለቤተ ሰቡ ወጥመድ ሆነ::

### የጌዴዎን መሞት

28ስለዚህ ምድያማውያን በእስራኤላ ውያን ተሸነፉ፤ ዳግመኛም ራሳቸውን ከፍ ከፍ አላደረጉም:: ጌዴዎን በሕይወት እስ ካለ ጊዜ ድረስ ምድሪቱ አርባ ዓመት ሰላም አገኘች::

29የኢዮአስ ልጅ ይሩባኣል ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ በዚያም ተቀመጠ፤ 30ብዙ ሚስ ቶች ስላገባ ሰባ ልጆች ነበሩት፤ 31በሴኬም የምትኖረው ቁባቱም እንደዚሁ ወንድ ልጅ ወለደችለት፤ ስሙንም አቤሜሌክ አለው:: 32የኢዮአስ ልጅ ጌዴዎን ዕድሜ ጠግቦ ሞተ፤ በአቢዔዝራውያን ምድር ባለችው በዖፍራ፣ በአባቱ በኢዮአስ መቃብር ተቀበረ::

33ጌዴዎን ሞቶ ብዙም ሳይቈይ እስ ራኤላውያን የበኣልን አማልክት በማምለክ

8፥8 ቀኍ9:17፤ ዘፍ32፥30፤ 1ነገ12፥25
8፥9 ቀኍ17
8፥10 መሳ6፥5፤ ኢሳ9፥4
8፥11 ዘኍ32፥35፡42
8፥13 መሳ1፥3 5፤6፥11
8፥14 ቀኍ6፤ ዘፀ3፥16
8፥15 ቀኍ6
8፥16 ሳሙ14፥12
8፥17 ቀኍ8:9
8፥18 ኢሱ19፥22
8፥19 ዘኍ14፥21
8፥21 ቀኍ26፤ ኢሳ3፥18
8፥23 ዘፀ16፥8፤ ዘኍ11፥20፤ 1ሳሙ12፥12
8፥24 ዘፍ16፥11፤ 35፥4፤49፥27
8፥26 ቀኍ21
8፥27 ዘፀ10፥7፤ 25፥7፤32፥2፤ ኢሱ18፥23፤ መሳ17፥5፤18፥14
8፥28 መሳ3፥11፤ መዝ83፥2
8፥29 መሳ6፥11፡ 32
8፥30 መሳ9፥2፡5፡ 18፡24፤12፥14፤ 2ነገ10፥1፤
8፥31 ዘፍ22፥24፤ መሳ9፥1፤10፥1፤ 2ሳሙ11፥21
8፥32 ዘፍ15፥15
8፥33 መሳ2፥11፡ 13፡19፤9፥4፡27፡46

[ጨ]26 19.5 ኪሎ ግራም ያህል ነው::

አመነዘሩ፤ በኣልብሪትንም አምላካቸው
አደረጉ፤ [34]በዙሪያቸው ከነበሩት ጠላቶቻ
ቸው እጅ የታደጋቸውን እግዚአብሔር
አምላካቸውን አላሰቡትም፡፡ [35]እንዲሁም ይሩ
ባኣል የተባለው ጌዴዎን ያደረገላቸውን
በጎ ነገር ሁሉ አስበው ለቤተ ሰቡ ውለታ
መላሽ ሆነው አልተገኙም፡፡

## አቤሜሌክ

9 የይሩባኣል ልጅ አቤሜሌክ ወደ
እናቱ ወንድሞች ወደ ሴኬም ሄደ፡፡
እነርሱንና የእናቱን ጐሣዎች በሙሉ እን
ዲህ አላቸው፤ [2]“የሴኬምን ነዋሪዎች ሁሉ
እንዲህ ብላችሁ ጠይቋቸው፤ ‘ሰባዎቹ የይሩ
ባኣል ልጆች ቢገዟችሁ ይሻላል ወይስ
አንድ ሰው ብቻ?’ የሥጋችሁ ቍራጭ፣
ያጥንታችሁ ፍላጭ መሆኔን ልብ በሉ፡፡”
[3]የእናቱ ዘመዶች ስለ እርሱ ሆነው
እነዚህን ቃሎች ሁሉ ለሴኬም ነዋሪዎች
በሙሉ ነገሩ፤ አቤሜሌክንም ለመከተል ልባ
ቸው ዳዳ፤ “እርሱማ ወንድማችን አይደል
ብለዋልና”፡፡ [4]እነርሱም በኣልብሪት ቤተ
ጣዖት ሰባ ሰቅል* ናስ ሰጡት፤ አቤሜሌክም
በዚያ ወሮበሎችንና ምናምንቴዎችን ቀጠ
ረበት፤ እነርሱም ተከተሉት። [5]ከዚያም ዖፍራ
ወደ ሚገኘው ወደ አባቱ ቤት ሄደ፤ ሰባ
ውን የይሩበኣልን ልጆች ወንድሞቹን በአ
ንድ ድንጋይ ላይ ዐረዳቸው፤ የይሩበኣል
የመጨረሻ ልጅ ኢዮአታም ግን ተሸሽጎ
ስለነበር አመለጠ፡፡ [6]የሴኬምና የቤት
ሚሎ ነዋሪዎች በሙሉ አቤሜሌክን ለማ
ንገሥ ሴኬም ውስጥ በዐምዱ አጠገብ
ካለው የባሉጥ ዛፍ ሥር ተሰበሰቡ፡፡
[7]ኢዮአታም ይህ በተነገረው ጊዜ፣ በገሪዛን
ተራራ ጫፍ ላይ ወጥቶ ድምፁን ከፍ በማ
ድረግ እንዲህ አላቸው፤ የሴኬም ነዋሪዎች
ሆይ፤ እግዚአብሔር ይሰማችሁ ዘንድ እኔን ስሙኝ፤
[8]ከዕለታት አንድ ቀን ዛፎች የሚ ያነግ
ሡትን ለመቀባት ወጡ፤ ወይራንም፣
‘አንተ ንጉሣ ችን ሁን’ አሉት፡፡
[9]የወይራ ዛፍም፣ “ከዛፎች በላይ ለመወ
ዛወዝ ስል፣ እግዚአብሔርና ሰዎች የሚከ
በሩበትን ዘይቴን መስጠት ልተውን?” አለ፡፡
[10]“ቀጥሎም ዛፎቹ በለስን፣ ‘መጥተህ
ንጉሣችን ሁን’ አሉት፡፡
[11]“በለስ ግን፣ ‘ከዛፎች በላይ
ለመወ ዛወዝ ስል፣ እጅግ ጣፋጭና
መልካም የሆ ነውን ፍሬዬን መስጠት
ልተውን?’ አለ፡፡
[12]“ከዚያም ዛፎቹ የወይን ተክልን፣
‘መጥተህ ንጉሣችን ሁን’ አሉት፡፡
[13] “የወይን ተክሉም፣ ‘ከዛፎች በላይ
ለመወዛወዝ ስል፣ አማልክትንና ሰዎችን
ደስ የሚያሰኘውን የወይን ጠጄን መስጠት
ልተውን? አለ፡፡
[14]በመጨረሻም ዛፎቹ በሙሉ የእሾኽ
ቍጥቋጦን፣ ‘መጥተህ ንጉሣችን ሁን’
አሉት፡፡
[15]“የእሾኽ ቍጥቋጠውም ዛፎቹን፣ ‘በእ
ርግጥ ቀብታችሁ በላያችሁ የምታነግሡኝ
ከሆነ መጥታችሁ በጥላዬ ሥር ተጠለሉ፤
ይህን ባታደርጉ ግን እሳት ከእሾ ቍጥ
ቋጠው ይነሣ፥ የሊባኖስንም ዝግባዎች
ይብላ’ አላቸው፡፡
[16]“እንግዲህ አቤሜሌክን ስታነግሡት
በቅንነትና በእውነት አድርጋችሁት ከሆነ፣
ይሩበኣልንና ቤተ ሰቡን በበጎ ዐይን
ተመል ክታችሁ ላደረገው የሚገባውን
አይታች ሁለት ከሆነ፣ [17]አባቴ ለእናንተ
መዋጋቱን፣ ከምድያማውያን እጅ ሊያድ
ናችሁ ሕይወቱን መስጠቱን አሰባችሁ
ማለት ነው፡፡ [18]ነገር ግን እናንተ ዛሬ
በአባቴ ቤተ ሰብ ላይ ዐመፃችሁ፤ ሰባ
ልጆቹን በአንዲት ድንጋይ ላይ ዐረዳችሁ፤
ዘመዳችሁ ስለ ሆነም አባቴ ከባሪያው
የወለደውን ልጅ አቤሜሌክን በሴኬም
ነዋሪዎች ላይ አነገሣችሁት፡፡ [19]እንግዲህ
ዛሬ በይሩበኣልና በቤተ ሰቡ ላይ ያደረ
ጋችሁት በእውነትና በቅንነት ከሆነ እና
ንተ በአቤሜሌክ ደስ ይበላችሁ፤ እርሱም
በእናንተ ደስ ይበለው፥ [20]ይህ ካልሆነ ግን
እሳት ከአቤሜሌክ ትውጣና እናንተን፣
የሴኬምንና የቤትሚሎን ነዋሪዎች ትብላ፤
እንዲሁም እሳት ከእናንተ፣ ከሴኬምና
ከቤትሚሎን ነዋሪዎች ትውጣና አቤሜሌክን
ትብላ፡፡”
[21]ከዚህ በኋላ ኢዮአታም ሸሽቶ አመለጠ፤
ብኤር ወደ ተባለች ቦታም መጣ፤ ወንድ
ሙንም አቤሜሌክን ፈርቶ ስለ ነበር እዚ
ያው ይኖር ጀመር፡፡
[22]አቤሜሌክ እስራኤልን ሦስት ዓመት
ከገዛ በኋላ፣ [23]እግዚአብሔር በአቤሜሌክና
በሴኬም ነዋሪዎች መካከል ክፉ መንፈስ
ሰደደ፤ ስለዚህም የሴኬም ሰዎች አቤሜሌክን
ከዱት፡፡ [24]እግዚአብሔር ይህን ያደረገውም፣
በሰባው የይሩበኣል ልጆች ላይ ስለ ተፈ
ጸመው ግፍና ስለ ፈሰሰው ደማቸው፣ ወንድ
ማቸውን አቤሜሌክና ወንድሞቹን እንዲ
ገድል የረዱትን የሴኬም ሰዎች ለመበቀል
ነው፡፡ [25]የሴኬም ነዋሪዎችም አቤሜሌክን
ሸምቀው የሚጠባበቁትን ሰዎች መደቡ፤
ሰዎቹም እርሱን በመጠባበቅ ላይ ሳሉ
በዚያ የሚያልፈውን ሁሉ ዘረፉ፤ ወሬውም
ለአቤሜሌክ ደረሰው፡፡

*4. 0.8 ኪሎ ግራም ያህል ነው

8፥34 መሳ3፥7፤ ነህ9፥17
8፥35 መሳ6፥32፤ 9፥16
9፥1 መሳ6፥32፤ 8፥31
9፥2 ዘፍ29፥14
9፥4 መሳ8፥33፤ 11፥3፤1ሳሙ25፥25፤ 2ዜና13፥7፤ ኢዮ30፥8
9፥5 ቍ7፡21፡ 57፤መሳ8፥30፤ 2ነገ11፥2፤2ዜና22፥9
9፥6 ቍ20፤ ዘፍ12፥6፤መሳ4፥11፤ 2ነገ12፥20
9፥7 ቍ5፤ ዘዳ11፥29፤ዮሐ4፥20
9፥13 ዘፍ14፥18፤ መክ2፥3፤መኀ4፥10
9፥15 ቍ20፤ ዘዳ3፥25፤1ነገ5፥6፤ መዝ29፥5፤92፥12፤ ኢሳ2፥13፤30፥2
9፥17 መሳ12፥3፤ 1ሳሙ19፥5፤28፥21፤ ኢዮ13፥14፤ መዝ119፥109
9፥18 መሳ8፥30
9፥19 ቍ16
9፥20 ቍ6፡15፡45
9፥21 ቍ5፤ ዘኍ2 1፥16
9፥23 1ሳሙ16፥14፡ 23፤18፥10፤19፥9፤ 1ነገ22፥22
9፥24 ቍ56-57፤ ዘፍ9፥6፤ዘሌ35፥33፤ ዘዳ27፥25፤መሳ8፥30፤ 1ነገ2፥32

26በዚህ ጊዜ የአቤድ ልጅ ገዓል ከወን
ድሞቹ ጋር ወደ ሴኬም መጣ፤ የሴኬምም
ሰዎች ተማመኑበት። 27ወደ ዕርሻ ወጥ
ተው ወይናቸውን ለቅመው ከጨመቁ
በኋላ በአምላካቸው ቤት የደስታ በዓል
አደረጉ፤ በዚያም እየበሉና እየጠጡ
አቤሜሌክን ሰደቡ። 28የአቤድ ልጅ ገዓል
እንዲህ አለ፤ "እንገዛለት ዘንድ አቤሜሌክ
ማን ነው? ሴኬምስ ምንድን ናት? እርሱ
የይሩበኣል ልጅ አይደለምን? ዜቡልስ
የእርሱ ረዳት ሹም አይደለምን? ለሴኬም
አባት ለኤሞር ሰዎች ተገዙ፤ ለምን
ለአቤሜሌክ እንገዛለን? 29ምነው ይህን
ሕዝብ የማዘው እኔ በሆንሁ ኖሮ"
አቤሜሌክን አስወግ ደው ነበር፤ 'ሰራ
ዊትህን አብዝተህ ውጣ*! እለው ነበር። ' "
30የከተማዪቱ ገዥ ዜቡል፣ የአቤድ
ልጅ ገዓል ያለውን በሰማ ጊዜ እጅግ
ተቈጣ፤ 31ወደ አቤሜልክም መልእክተ
ኞች በምስጢር ልኮ እንዲህ አለ፤ "እነሆ፤
የአቤድ ልጅ ገዓልና ወንድሞቹ ወደ ሴኬም
መጥተው ከተማዪቱ እንድትሸፍትብህ
አድርገዋል። 32ስለዚህ በሌሊት ሰዎችህን
ይዘህ ወጥተህ ሜዳው ላይ ማድፈጥ አለ
ብህ፤ 33ጠዋት ፀሓይ ስትወጣም ወደ ከተ
ማዪቱ ገሥግሥ፤ ገዓልና ሰዎቹ ሊገጥሙህ
በሚወጡበት ጊዜ እጅህ ማድረግ የሚችለ
ውን ሁሉ አድርግ።
34ስለዚህ አቤሜሌክና ሰዎቹ በሙሉ
በሌሊት ወጡ፤ በአራት ምድብ ሆነውም
በሴኬም አጠገብ አደፈጡ። 35የአቤድ ልጅ
ገዓል ከከተማዪቱ ወጥቶ በመግቢያው በር
ላይ ሲቆም፣ አቤሜሌክና ሰዎቹ ካደፈጡ
በት ወጡ።
36ገዓል ባያቸው ጊዜ ዜቡልን፣ "ተመ
ልከት፤ ከተራራው ጫፍ ሕዝብ እየወረደ ነው"
አለው።
ዜቡልም መልሶ፣ "የተራሮች ጥላ
ሰዎች መስሎ ተሳስተህ "ነው። አለው።
37ገዓልም፣ "ተመልከት እንጂ ሕዝብ
እኮ ከተራራው ወገብ ላይ እየደረሰ ነው፤
አንዱ ክፍልም በቃላተኞች ዛፍ በኩል
አድርጎ እየመጣ ነው" ብሎ እንደ ገና
ተናገረ።
38ከዚያም ዜቡል፣ "እንገዛለት ዘንድ
አቤሜልክ ማን ነው? ብለህ የደነፋኸው
አሁን የት አለ? ያቃለልህቸውስ ሰዎች እነዚህ
አይደሉምን? በል ውጣና ግጠማቸው"
አለው።
39ገዓል የሴኬምን ሰዎች መርቶ በመውጣት
አቤሜሌክን ተዋጋው፤ 40ሆኖም አቤሜሌክ
አሳደደው፤ እስከ መግቢያው በር ድረስ

9፥26 ቍ28፥31፡ 41
9፥27 መሳ8፥33፤ ኢሳ16፥10፤አሞ5፥11፡ 9፥13
9፥28 ቍ26፤ ዘፍ33፥19፤ 1ሳሙ25፥10
9፥29 ቍ38፤ 2ሳሙ15፥4
9፥32 ኢሱ8፥2
9፥33 1ሳሙ10፥7
9፥34 ኢሱ2፥5፤ መዝ32፥7፤ ኢሳ28፥15፥17፤ ኤር49፥10
9፥38 ቍ28-29

9፥43 ኢሱ8፥2፤ መሳ7፥16
9፥45 ቍ20፤ ኤር48፥9
9፥46 መሳ8፥33
9፥48 መዝ68፥14
9፥50 2ሳሙ11፥21
9፥53 2ሳሙ11፥21
9፥54 1ሳሙ31፥4፤ 2ሳሙ1፥9

ባለው መንገድ ሲሸሹም ብዙ ሰዎች ቈስለው
ወደቁ። 41አቤሜሌክ በአሩማ ተቀመጠ፤
ዜቡልም ገዓልንና ወንድሞቹን ከሴኬም
አስወጣቸው።
42በማግስቱ የሴኬም ሕዝብ ወደ ዕርሻ
ወጡ፤ ይህም ለአቤሜሌክ ተነገረው፤
43እርሱም ሰዎቹን አስከትሎ ወጣ፤ ከዚያም
ሰዎቹን ሦስት ቦታ መድቦ በዕርሻዎቹ
ውስጥ አድፍጠው እንዲጠባበቁ አደረገ።
አቤሜሌክ የሴኬም ሰዎች ከከተማዪቱ መው
ጣታቸውን እንዳየም ካደፈጠበት ሊወጋቸው
ተነሣ። 44ከዚያም አቤሜሌክና አብረውት
የነበሩ ምድቦች ቦታ ለመያዝ በፍጥነት
ወደ ከተማዪቱ መግቢያ በሚሮጡበት ጊዜ፣
ሌሎቹ ሁለት ምድቦች ደግሞ እየሮጡ
ሄደው በዕርሻው ያሉትን ሁሉ ፈጇቸው።
45በዚያን ዕለት አቤሜሌክ ቀኑን ሙሉ
ከተማዪቱን ሲወጋ ውሎ በመጨረሻ
ያዛት፤ ሕዝቧን ፈጀ፤ ከተማዪቱንም
አጠፋ፤ በላይዋም ጨው ዘራባት።
46በሴኬም ግምብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች
ይህን እንደ ሰሙ፤ በኤልበሪት ቤተ መቅደስ
ወዳለው ምሽግ ውስጥ ገቡ። 47አቤሜሌ
ክም በዚያ መመሸጋቸውን ሲሰማ፣ 48እር
ሱና ሰዎቹ ሁሉ ወደ ሰልሞን ተራራ
ወጡ፤ አቤሜሌክም መጥረቢያ ወስዶ
ጥቂት የዛፍ ቅርንጫፍ ቈረጠ፤ በትከሻውም
ላይ አደረገ። የተከተሉትንም ሰዎች፣
"ፍጠኑ፤ እኔ ሳደርግ ያያችሁትን አድርጉ"
ሲል አዘዛቸው። 49ሰዎቹም ሁሉ ቅርን
ጫፎች ቈርጠው አቤሜሌክን ተከተሉት፤
ቅርንጫፎቹንም ምሽጉ ላይ አስደግፈው
በመከመር ሰዎቹ በውስጡ እንዳሉ በእሳት
አቃጠሏቸው። ስለዚህ በሴኬም ምሽግ
ውስጥ የነበሩት አንድ ሺህ ያህል ወንዶ
ችና ሴቶች ሞቱ።
50ከዚያም አቤሜሌክ ወደ ቴመስ በመ
ሄድ ከተማዪቱን ከቦ ያዛት። 51ሆኖም በከተ
ማይቱ ውስጥ ብርቱ ግንብ ስለ ነበር፣
የከተማዪቱ ሕዝብ በሙሉ ወንድ ሴት
ሳይባል ወደዚያ ሸሹ፤ ደጁንም በውስጥ
ዘግተው ወደ ግንቡ ጣሪያ ወጡ። 52አቤሜ
ሌክም ተዋግቶ ግንቡን ያዘ፤ ይሁን እንጂ
እሳት ለመለኮስ ወደ ግንቡ መግቢያ
አጠገብ እንደ ደረሰ፣ 53አንዲት ሴት ከላይ
የወፍጮ መጅ በራሱ ላይ ለቀቀችበት፤
ጭንቅላቱንም አፈረሰችው።
54ወዲያውም ጋሻ ጃግሬውን ጠርቶ፣
"'ሴት ገደለችው' እንዳይሉ እባክህ ሰይ
ፍህን መዘህ ግደለኝ' አለው። ስለዚህ አገ
ልጋዩ ወጋው፤ እርሱም ሞተ። 55እስራኤላ

*29. ዕብርይስጡ *አቤሜሌክን እንዲህ አለው ሰራዊትህን ሁሉ ጥራ ! ይላል።*

ውያንም አቤሜሌክ መሞቱን ሲያዩ ወደ
የቤታቸው ተመለሱ።
56አቤሜሌክ ሰባ ወንድሞቹን በመግደል፣
በአባቱ ላይ ስላደረሰው በደል እግዚአብሔር
የእጁን ከፈለው። 57በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር
የሴኬምን ሰዎች ክፋት ሁሉ በራሳቸው
ላይ መለሰው፤ የይሩበኣል ልጅ የኢዮአታም
ርግማን ደረሰባቸው።

## ቶላ

10 ከአቤሜሌክ በኋላ ከይሳኮር ነገድ
የሆነ የዱዲ ልጅ፣ የፎሖ ልጅ
ቶላ እስራኤልን ለማዳን ተነሣ፤ እርሱም
በኰረብታማው በኤፍሬም አገር ሳምር
በምትባል መንደር ይኖር ነበር። 2ቶላ
በእስራኤል ላይ ሃያ ሦስት ዓመት በፈራ
ጅነት ከተቀመጠ በኋላ ሞተ፤ በሳምርም
ተቀበረ።

## ኢያዕር

3ከቶላ ቀጥሎ ገለዓዳዊው ኢያዕር ተነሣ፤
እርሱም በእስራኤል ላይ ሃያ ሁለት ዓ
መት በፈራጅነት[θ] ተቀመጠ። 4ኢያዕር በሠላሳ
አህዮች የሚጋልቡ ሠላሳ ወንዶች ልጆች ነበ
ሩት፤ ልጆቹም እስከ ዛሬ ድረስ የኢያዕር
መንደሮች ተብለው የሚጠሩ ሠላሳ ከተ
ሞች በገለዓድ ምድር ነበሯቸው። 5ኢያዕር
ሞተ፤ በቃሞንም ተቀበረ።

## ዮፍታሔ

6እስራኤላውያን እንደ ገና *በእግዚአብሔር*
ላይ ክፉ ድርጊት ፈጸሙ፤ በኣልንና
አስታ ሮትን እንዲሁም የሶሪያን፣ የሲ
ዶናን፣ የሞዓብን፣ የአሞንንና የፍልስጥኤ
ማውያ ንን አማልክት አመለኩ፤ እስራ
ኤላውያን *እግዚአብሔርን* ስለተዉና
ስላላገለገሉት፣ 7ተቈጣቸው፤ በፍልስጤ
ማውያንና በአሞ ናውያን እጅ ሸጣቸው፤
8እነርሱም በዚያን ዓመት ሰበሯቸው፤
አደቀቋቸውም፤ እስራኤላውያንን ሁሉ
ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ባለው በገለዓድ
ምድር፣ 9በአሞራውያን አገር ዐሥራ
ስምንት ዓመት እን ዲሁም አሞናውያን
ይሁዳን፣ ብንያምንና የኤፍሬምን ቤት
ለመውጋት ዮርዳኖስን ስለ ተሻገሩ እስራ
ኤላውያን እጅግ ተጨነቁ። 10ከዚያም እስ
ራኤላውያን አንተን አምላካ ችንን
በመተው የበኣልን አማልክት በማ
ምለካችን አንተን በድለናል" ብለው ወደ
*እግዚአብሔር* ጮኹ።
11*እግዚአብሔርም* መልሶ እንዲህ አላቸው፤
"ግብፃውያን፣ አሞራውያን፣ አሞናውያን፣
ፍልስጥኤማውያን፣ 12ሲዶናውያን፣ አማሌቃ
ውያንና ማዖናውያን[ፊ] አሠቃዩአችሁ፤ እናን

9፥57 ቀኍ5፥24፤ መዝ94፥23
10፥1 ዘፍ30፥18፤ 46፥13፤ኢሱ15፥48፤ መሳ6፥14፤8፥31
10፥3 ዘኍ32፥41
10፥4 ዘፍ49፥11፤ ዘሌ32፥41፤1ነገ1፥33
10፥5 ዘኍ32፥41
10፥6 ዘፍ10፥15፤ 19፥38፤26፥1፤ ዘኍ21፥29፤ ዘዳ32፥15፤መኣ2፥11፡ 12፡13፤ሕዝ27፥16
10፥7 ዘዳ31፥17፤ 32፥30
10፥8 ኢሱ12፥2
10፥9 ቀኍ17፤ መሳ1፥22፤11፥4
10፥10 ዘፀ9፥27፤ መሳ3፥9፤መዝ32፥5፤ኢ ር2፥27፤3፥25፤8፥14፤1 4፥20
10፥11 ዘፍ14፥7፤ ዘፀ14፥30፤ መሳ3፥13 31
10፥12 ዘፍ14፥7፤ ኢሱ15፥55፤ መሳ4፥3
10፥13 ዘዳ32፥15፤ ኤር11፥10፤13፥10
10፥14 ኢሳ32፥37፤ ኢሳ44፥17፤ 57፥13፤ኤር2፥28፤ 11፥12፤ዕን2፥18
10፥15 1ሳሙ3፥18፤ 2ሳሙ10፥ 12፤ 15፥26፤ኢዮ1፥21፤ ኢሳ39፥8
10፥16 ዘዳ32፥36፤ ኢሱ24፥23፤ ኢሳ63፥9፤ኤር18፥8
10፥17 ዘፍ31፥49፤ መሳ11፥29
10፥18 ሳ11፥8፡9
11፥1 ዘፍ38፥15፤ ዘኍ26፥29፤መሳ6፥12፤ 12፥1፤1ሳሙ12፥11፤ ዕብ11፥32
11፥3 ቀኍ5፤ መሳ11፥8፡9
11፥4 መሳ10፥9
11፥7 ዘፍ26፥16
11፥8 መሳ10፥18
11፥10 ዘፍ31፥50፤ ኢሳ1፥2
11፥11 ዘፀ19፥9፤ ኢ

ተም እንድረዳችሁ ወደ እኔ ጮኻችሁ፤
ታዲያ እኔ ከእጃቸው አላዳንኋችሁምን?
13እናንተ ግን እኔን ትታችሁ ሌሎች አማ
ልክትን አመለካችሁ፤ ስለዚህ ከእንግዲህ
ወዲያ አላድናችሁም፤ 14ሂዱና ወደ መረ
ጣችኋቸው አማልክት ጩኹ፤ መከራ
በሚያገኛችሁ ጊዜ እስቲ ያድኗችሁ"
15እስራኤላውያንም *እግዚአብሔርን*፣
"፤ጢአት ሠርተናል፤ መልካም መስሎ የታ
የህን አድርግብን፤ እባክህን የዛሬን ብቻ
አድነን" አሉት። 16ከዚያም በመካከላቸው
ያሉትን ባዕዳን አማልክት አስወገዱ፤
*እግዚአብሔርንም* አመለኩ፤ *እግዚአብሔርም*
የእስራኤልን ጐስቍልና ሊታገሠው የማ
ይቻለው ሆነ።
17አሞናውያን ለጦርነት ዝግጁ ሆነው
በገለዓድ በሰፈሩ ጊዜ፣ እስራኤላውያንም
እን ደዚሁ ተሰብስበው በምጽጳ ሰፈሩ።
18የገለ
ዓድ ሕዝብ አለቆችም እርስ በእርሳቸው፣
"በአሞናውያን ላይ ጦርነቱን የሚጀምር ሰው
በገለዓድ ነዋሪዎች ሁሉ ላይ አለቃ ይሆናል"
ተባባሉ።

11 ገለዓዳዊው ዮፍታሔ ፤ያል ጦረኛ
ነበረ፤ አባቱ ገለዓድ ነበር፤ እናቱም
ጋለሞታ ነበረች። 2እንደዚሁም የገለዓድ
ሚስት ለገለዓድ ወንዶች ልጆች ወለደች
ለት፤ እነርሱም ባደጉ ጊዜ ዮፍታሔን፣
"ከሌላ ሴት ስለ ተወለድህ ከቤተ ሰባችን
ምንም ዐይነት ውርስ አይገባህም" በማለት
አሳደዱት። 3ስለዚህም ዮፍታሔ ከወን
ድሞቹ ሸሽቶ መኖሪያውን ጦብ በተባለች
ምድር አደረገ፤ እዚያም ወሮበሎች ተሰ
ባስበው ተከተሉት።
4ከጥቂት ጊዜ በኋላም አሞናውያን በእ
ስራኤል ላይ ጦርነት ባደረጉ ጊዜ፣ 5የገለዓድ
አለቆች ዮፍታሔን ለማምጣት ወደ ጦብ
ምድር ሄዱ። 6እነርሱም፣ "ከአሞናውያን
ጋር መዋጋት እንችል ዘንድ መጥተህ
ምራን " አሉት።
7ዮፍታሔም፣ "ምነው ጠልታችሁኝ ከአ
ባቴ ቤት አሳዳችሁኝ አልነበረምን? ታዲያ
አሁን ችግር ሲገጥማችሁ ነው የምትፈ
ልጉኝ?" አላቸው።
8የገለዓድ አለቆችም፣ "እንግዲህ አሁን
ወደ አንተ መጥተናል፤ አሞናውያንን እን
ድንወጋ በል ተነሥና አብረን እንሂድ፤
በገለዓድ በምንኖረው በሁላችንም ላይ አለቃ
ትሆናለህ" አሉት።
9ዮፍታሔም፣ "አሞናውያንን ለመውጋት

[θ]2 በዚህና በቍጥር 3 ላይ በትውፊት *መሳፍንት* ይባላል።
[ፊ]12. አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች *ምድያማውያን* ይላሉ።

ወደ አገሬ ብትመልሱኝና *እግዚአብሔር* በእጄ አሳልፎ ቢሰጣቸው በእርግጥ አለቃችሁ እሆናለሁ?” ሲል ጠየቃቸው።

10የገለዓድ አለቆችም፣ “*እግዚአብሔር* ምስክራችን ነው፤ ያልከውንም በእርግጥ እናደርጋለን” አሉት። 11ስለዚህ ዮፍታሔ ከገለዓድ አለቆች ጋር ሄደ፤ ሕዝቡም በላያቸው ላይ አለቃና አዛዥ አደረጉት፤ ዮፍታሔም የተናገረውን ቃል ሁሉ ምጽጳ ላይ *በእግዚአብሔር* ፊት ደገመው።

12ከዚያም ዮፍታሔ ወደ አሞናውያን ንጉሥ፣ “ከእኔ ጋር ምን ጠብ ቢኖርህ ነው መጥተህ አገሬን የወጋኸው?” በማለት መልእክተኞች ላከ።

13የአሞናውያንም ንጉሥ ለዮፍታሔ መልእክተኞች፣ “ይህን ያደረግሁት እስራኤል ከግብፅ በወጣ ጊዜ በአርኖንና በያቦቅ ወንዞች መካከል ያለውንና እስከ ዮርዳኖስ ያለውን አገሬን ስለ ወሰዱብኝ ነው፤ አሁንም በሰላም መልሱልኝ” አላቸው።

14ዮፍታሔም መልእክተኞቹን እንደ ገና ወደ አሞናውያን ንጉሥ ላካቸው፤ 15እንዲህም አላቸው፤ “ዮፍታሔ እንዲህ ይላል፤ እስራኤል የሞዓብንም ሆነ የአሞና ውያንን ምድር አልወሰደም። 16እስራኤል ከግብፅ በወጣ ጊዜ በምድረ በዳ አድርጎ ወደ ቀይ ባሕር[ፐ] ከዚያም ወደ ቃዴስ ሄደ። 17እስራኤልም ወደ ኤዶም ንጉሥ፣ ‘በአገርህ እንዳልፍ እባክህ ፍቀድልኝ’ በማ ለት መልእክተኞችን ላከበት፤ የኤዶም ንጉሥ ግን አልሰማውም። ለሞዓብ ንጉሥም እንደዚሁ ላከበት፤ እርሱም አልተቀበለውም፤ ስለዚህ እስራኤል በቃዴስ ተቀመጠ።

18“ቀጥሎም የኤዶምንና የሞዓብን ምድር በመዞር፣ በምድረ በዳው ተጕዞ ከሞዓብ በስተ ምሥራቅ በኩል በማለፍ ከአርኖን ማዶ ሰፈረ፤ የሞዓብም ድንበር አርኖን ስለ ነበር ወደ ሞዓብ ክልል አልገባም።

19“ከዚያም እስራኤል በሐሴቦን ወዳለው ወደ አሞራውያን ንጉሥ ወደ ሴዎን መልእክተኞች ልኮ፣ ‘ወደ ገዛ ስፍራችን ለመሄድ በአገርህ እንዳልፍ ፍቀድልኝ’ አለው። 20ሴዎን ግን በግዛቱ እንዲያልፍ ለመፍቀድ እስራኤልን አላመነውም[ሀ]፤ ሰራዊቱንም ሰብስቦ በያሃድ ከሰፈረ በኋላ ከእስራኤል ጋር ተዋጋ።

21“ከዚያም የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር* ሴዎንንና ሕዝቡን ሁሉ በእስራኤል እጅ አሳልፎ ሰጣቸው፤ አሸነፏቸውም፤ እስራኤልም በዚያ አገር የሚኖሩትን የአሞራውያንን ምድር በሙሉ ወረሰ፤ 22ከአርኖን እስከ ያቦቅ፣ ከምድረ በዳው እስከ ዮርዳኖስ ድረስ ያለውን ምድር በሙሉ ወረሱ።

23“እንግዲህ የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር* አሞራውያንን ከሕዝቡ ከእስራኤል ፊት አሳዶ ካስወጣቸው፣ አንተ ለመውሰድ ምን መብት አለህ? 24አምላክህ ካሞሽ የሰጠህን ይዞ ማቈየቱ ያንተ ፈንታ ነው፤ እኛም እንደዚሁ አምላካችን *እግዚአብሔር* የሰጠንን ሁሉ ርስት አድርገን እንወርሳለን። 25አንተ ከሞዓብ ንጉሥ ከሴፎር ልጅ ከባላቅ ትበልጣለህን? ለመሆኑ እርሱ ከእስራኤል ጋር ተጣልቶአልን? ወይስ ተዋግቶአልን? 26እስራኤልም በሐሴቦንና በመንደሮቿ፣ በአሮዔርና በመንደሮቿ፣ በአርኖንም አቅ ራቢያ ባሉት ከተሞች ሁሉ ሦስት መቶ

ዓመት ተቀምጦ በነበረበት በዚያን ጊዜ ስለ ምን አልወሰዳችኋቸውም ነበር? 27እኔ አልበደልሁህም፤ አንተ ግን በእኔ ላይ ዘምተህ በድለኸኛል፤ እንግዲህማ ፈራጁ[ለ] *እግዚአብሔር* በእስራኤላውያንና በአሞናውያን መካከል ዛሬ ይፍረድ።”

28የአሞን ንጉሥ ግን ዮፍታሔ የላከውን መልእክት ከምንም አልቈጠረውም።

29ከዚያም *የእግዚአብሔር* መንፈስ በዮፍታሔ ላይ ወረደ፤ ተነሥቶም ገለዓድንና ምናሴን አቋርጦ ሄደ፤ ገለዓድ ባለችው በምጽጳ በኩል አድርጎም በአሞናውያን ላይ ዘመተ ባቸው። 30ዮፍታሔም እንዲህ ሲል *ለእግዚአብሔር* ተሳለ፤ “አሞናውያንን በእጄ አሳልፈህ ብትሰጠኝ፣ 31አሞናውያንን ድል አድርጌ በምመለስበት ጊዜ በመጀመሪያ ሊቀበለኝ ከቤቴ ደጅ የሚወጣው ማንኛውም ሰው *ለእግዚአብሔር* ይሆናል፤ እኔም የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጌ አቀርበዋለሁ።”

32ከዚያም ዮፍታሔ አሞናውያንን ለመውጋት ወጣ፤ እግዚአብሔርም እርሱን በእጁ አሳልፎ ሰጠው። 33ከአሮዔር አንሥቶ እስከ ሚኒት አካባቢ ከዚያም አልፎ እስከ ክራሚም የሚገኙትን ሃያ ከተሞች ፈጽሞ አጠፋቸው፤ አሞናውያንም ለእስራኤል ተገዙ።

34ዮፍታሔ ምጽጳ ወዳለው ቤቱ ተመለሰ፤ እነሆ፤ ልጁ አታሞ እየደለቀች በመዝፈን ልትቀበለው ወጣች፤ እርሷም አንዲት ልጁ ብቻ ነበረች፤ ከእርሷ በቀር ወንድም ሆነ ሴት ልጅ አልነበረውም።

ሱ11፥3፤1ሳሙ8፥4፡ 21፤2ሳሙ3፥17
11፥13 ዘኍ21፥13-24
11፥15 ዘዳ2፥9፡ 19
11፥16 ዘፍ14፥7፤ ዘኍ14፥25፤ዘዳ1፥40
11፥17 ቍ19፤ ዘፍ32፥3፤ዘኍ20፥14፡ 17፤ኢሱ24፥9፤ ኤር48፥1
11፥18 ዘኍ20፥21፤ 21፥13፤ዘዳ2፥8
11፥19 ቍ17፤ ዘኍ21፥21-22፤ ኢሱ12፥2
11፥20 ዘኍ21፥23
11፥22 ዘኍ21፥ 21-26፤ ዘዳ2፥26
11፥24 ዘዳ2፥36፤ ኢሱ3፥10፤ ዘኍ21፥29
11፥25 ዘኍ22፥2፤ ኢሱ24፥9
11፥26 ዘኍ21፥ 25፤ 32፥34፤ኢሱ13፥9
11፥27 ዘፍ16፥5፤ 18፥25፤ 2ዜና20፥12
11፥29 ዘፍ31፥49፤ መሳ3፥10፤ መሳ10፥17
11፥30 ዘፍ28፥20፤ ዘኍ30፥10፤1ሳሙ1፥21፤ ምሳ31፥2
11፥31 ዘፍ8፥20፤ 28፥21፤ዘሌ1፥3፤ መሳ13፥16
11፥33 ሕዝ27፥17
11፥34 ዘፍ31፥27፤ ዘፀ15፥20፤ዘካ12፥10

[ፐ]16. ዕብራይስጡ *ያም ሶውፍ* ይላል ይህም የደንኤል ባሕር ማለት ነው።
[ሀ]20. ወይም *ከእስራኤል ጋር አልተስማማም*
[ለ]27. ወይም *መሪው*

35ባያትም ጊዜ ልብሱን በመቅደድ፣
“ወይኔ ልጄ ጉድ አደረግሽኝኄ
ጭንቅም ላይ ጣልሺኝ፤ ማስቀረት የ
ማልችለውን ስእለት ለእግዚአብሔር
ተስያለሁና” ብሎ በኀዘን ጮኸ፡፡
36እርሷም እንዲህ አለች፤ “አባቴ ሆይ፤
መቼም አንዴ ለእግዚአብሔር ቃል
ገብተሃል፤ ጠላቶችህን አሞናውያንን አሁን
እግዚአብሔር ተበቅሎልሃልና ቃል የገባኸ
ውን ፈጽምብኝ፡፡ 37ነገር ግን አንድ ነገር
ብቻ እንድትፈቅድልኝ እለምንሃለሁ፤ ከእን
ግዲህ ባል ስለማላገባ ከባልንጀሮቼ ጋር
ወደ ተራሮች ወጥቼ እየዞርሁ ሁለት ወር
እንዳለቅስ አሰናብተኝ፡፡”
38እርሱም፣ “በይ ሂጂ” ብሎ ለሁለት
ወር አሰናበታት፤ እርሷም ከእንግዲህ ባል
ስለማታገባ ከልጃገረድ ጓደኞቿ ጋር ወደ
ተራሮች ሄደው አለቀሱ፡፡ 39ከሁለት ወር
በኋላ ወደ አባቷ ተመለሰች፤ እርሱም
የተሳለውን አደረገ፤ ድንግልም ነበረች፡፡
ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ በእስራኤል
ልማድ ሆኖ፣ 40የእስራኤል ወጣት ሴቶች
የገለዓዳዊውን የዮፍታሔን ልጅ በማሰብ
በየዓመቱ እየወጡ የአራት ቀን ኀዘን ያደር
ጉላታል፡፡

### ዮፍታሔና ኤፍሬም

12 የኤፍሬም ሰዎች ፤ይላቸውን
አሰባስበው ወደ ጻፎን በመሻገር
ዮፍታሔን፣ አሞናውያንን ለመውጋት
ስትወጣ አብረንህ እንድንሄድ ያልጠራኸን
ለምንድን ነው? ቤትህን በላይህ ላይ እናቃ
ጥለዋለን አሉት፡፡”
2ዮፍታሔም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
“እኔና ሕዝቤ ከአሞናውያን ጋር ከፍተኛ
ትግል ገጥመን በነበረበት ጊዜ ጠርቼያ
ችሁ ከእጃቸው አላዳናችሁኝም፤ 3እኔም
እንደማትረዱኝ በተረዳሁ ጊዜ በሕይወቴ
ቈርጬ አሞናውያንን ለመውጋት ተሻገ
ርሁ፤ እግዚአብሔርም ድሉን ሰጠኝ፤ ታዲ
ያ ዛሬ እኔን ለመውጋት የመጣችሁት
ለምንድን ነው?”
4ከዚያም ዮፍታሔ የገለዓድን ሰዎች አሰ
ባስቦ ከኤፍሬም ጋር ተዋጋ፡፡ ኤፍሬማውያን
ገለዓዳውያንን፣ “እናንተ ገለዓዳውያን ከኤ
ፍሬምና ከምናሴ የከዳችሁ ናችሁ” ይሏ
ቸው ስለ ነበር በብርቱ መቷቸው፡፡ 5ገለዓ
ዳውያን ወደ ኤፍሬም የሚያሻግሩትን
የዮርዳኖስን መልካዎች ያዙ፤ ታድያ አም
ልጦ የሚሸሽ አንድ ኤፍሬማዊ ለመሻገር
በሚጠይቃቸው ጊዜ፣ የገለዓድ ሰዎች
“አንተ ኤፍሬማዊ ነህ?” ብለው ይጠይቁ

11፥35 ዘኍ14፥6፤ 30፥2፤ዘዳ23፥21፤ መክ5፥2፡4፡5
11፥36 ዘኍ31፥3፤ 2ሳሙ18፥19፤ ሉቃ1፥38
12፥1 ኢሱ13፥27፤ መሳ8፥1፤11፥1
12፥3 ዘዳ20፥4፤ መሳ9፥17
12፥4 ዘፍ46፥20፤ 1ነገ17፥1፤ኢሳ9፥21፤ 19፥2
12፥5 ኢሱ2፥7
12፥8 ዘፍ35፥19
12፥12 ኢሱ10፥12
12፥13 ቊ15፤ 2ሳሙ23፥30፤ 1ዜና11፥31፤27፥14
12፥14 መሳ5፥10፤ 8፥30
12፥15 መሳ5፥14
13፥1 መሳ3፥31፤ 14፥4
13፥2 ቊ8፤ ዘፍ11፥30፤30፥6፤ ኢሱ15፥33፤ መሳ16፥31
13፥3 ቊ10፤ ዘፍ16፥7፤ ኢሳ7፥14፤ ሉቃ1፥13
13፥4 ቊ14፤ ዘሌ10፥9፤ዘኍ6፥2-4፤ ሉቃ1፥15
13፥5 ዘፍ3፥15፤

ታል፤ ያም ሰው፣ “አይደለሁም” ብሎ
ከመለሰላቸው፣ 6እስቲ “ሺቦሌት” በል
ይሉታል፤ ታዲያ ቃሉን በትክክል ማለት
ሳይችል ቀርቶ “ሲቦሊት” ካለ ይዘው እዚ
ያው እመልካው ላይ ይገድሉታል፤ በዚያ
ጊዜም አርባ ሁለት ሺህ ኤፍሬማውያን
ተገደሉ፡፡
7ዮፍታሔ በእስራኤል ላይ ለስድ
ስት ዓመት ፈራጅ[ሐ] ሆነ፡፡ ገለዓዳዊው ዮፍ
ታሔ ሞተ፤ ከገለዓድም ከተሞች በአንዲቱ
ተቀበረ፡፡

### ኢብጻን፣ ኤሎም፣ ዔብዶን

8ከዮፍታሔ ቀጥሎ የቤተ ልሔሙ ኢብ
ጻን በእስራኤል ላይ ፈራጅ ሆነ፡፡ 9እርሱም
ሠላሳ ወንዶችና ሠላሳ ሴቶች ልጆች
ነበሩት፡፡ ሴቶች ልጆቹንም ከጐሣው ውጭ
ለሆኑ ሰዎች ዳራቸው፤ ጐሣው ውጭ የሆኑ
ሠላሳ ልጃገረዶች አምጥቶ ከወን ዶች
ልጆቹ ጋር አጋባቸው፡፡ ኢብጻን በእ ስራ
ኤል ላይ ሰባት ዓመት ፈራጅ ሆነ፡፡ 10ኢ
ብጻን ሞተ፤ በቤተ ልሔምም ተቀበረ፡፡
11ከእርሱም በኋላ ዛብሎናዊው ኤሎም
በእስራኤል ላይ ዐሥር ዓመት ፈራጅ
ሆነ፡፡ 12ከዚያም ኤሎም ሞተ፤ በዛብሎን
ምድር በኢያሎን ተቀበረ፡፡
13ከኤሎም ቀጥሎ የጺርዓቶናዊው የሂ
ሌል ልጅ ዓብዶን በእስራኤል ፈራጅ
ሆነ፡፡ 14እርሱም በሰባ አህዮች ላይ የሚቀ
መጡ አርባ ወንዶች ልጆችና ሠላሳ
ወንዶች የልጅ ልጆች ነበሩት፤ በእስራ
ኤልም ላይ ስምንት ዓመት ፈራጅ ሆነ፡፡
15ከዚያም የሂ ሌል ልጅ ዓብዶን ሞተ፤
ኰረብታማ በሆ ነው በአማሌቃውያን አገር
በኤፍሬም ምድር በጺርዓቶን ተቀበረ፡፡

### የሳምሶን መወለድ

13 እስራኤላውያን እንደ ገና በእግዚ
አብሔር ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸሙ፤
ስለዚህም እግዚአብሔር በፍልስጥኤማውያን
እጅ አርባ ዓመት እንዲገዙ አሳልፎ ሰጣቸው፡፡
2ማኑሄ የተባለ ከዳን ወገን የተወለደ
አንድ የጾርዓ ሰው ነበረ፤ ሚስቱ መካን
ስለ ነበረች ልጅ አልወለደችም፡፡ 3የእግ
ዚአብሔርም መልአክ ለሴቲቱ ተገልጦ
እንዲህ አላት፤ “እነሆ፤ አንቺ መካን ነሽ፤
ልጅም አልወለድሽም፤ ነገር ግን ትፀን
ሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፡፡ 4እን
ግዲህ ተጠንቀቂ፤ የወይን ጠጅም ሆነ ሌላ
የሚያሰክር መጠጥ አትጠጪ፤ ርኵስ ነገ

[ሐ]7. በዚህ እንዲሁም በቍጥር 8-14 ላይ ባለው ክፍል በትውፊት መሳፍንት ይባላል፡፡

ርም አትብዪ፤ 5ምክንያቱም ትፀንሻለሽ፤
ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ። በራሱ ላይ
ምላጭ አይድረስበት፤ ልጁ ከእናቱ ማሕፀን
ጀምሮ ናዝራዊ በመሆን ለእግዚአብሔር
የተለየ ይሆናልና፤ እስራኤልንም ከፍልስጥኤ
ማውያን እጅ መታደግ ይጀምራል።"
6ከዚያም ሴቲቱ ወደ ባሏ ሄዳ እንዲህ አለ
ችው፤ "የእግዚአብሔር ሰው ወደ እኔ መጣ፤
የእግዚአብሔር መልአክ የሚመስልና እጅግ
የሚያስደነግጥ ነበር። ከየት እንደ መጣ
አልጠየቅሁትም፤ እርሱም ስሙን አልነገረ
ኝም፤ 7ነገር ግን፣ 'ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅም
ትወልጃለሽ፤ ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲያ
የወይን ጠጅም ሆነ ሌላ የሚያሰክር መጠጥ
አትጠጪ፤ ርኩስ ነገር አትብዪ፤ ልጁም
ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ እስኪ ሞት ድረስ
ናዝራዊ በመሆን ለእግዚአብሔር የተለየ ይሆና
ልና' ብሎኛል።"
8ከዚያም ማኑሄ፣ "ጌታ ሆይ፤
የሚወለደውን ልጅ እንዴት አድርገን
ማሳደግ አንዳለ ብን እንዲያስተምረን ያ
ወደ እኛ የላክ
ኸው የእግዚአብሔር ሰው እንደ ገና እንዲ
መጣ ታደርግ ዘንድ እለምንሃለሁ"። ብሎ
ወደ *እግዚአብሔር* ጸለየ።
9እግዚአብሔርም የማኑሄን ጸሎት ሰማ፤
የእግዚአብሔርም መልአክ ሴቲቱ በዕርሻ ውስጥ
ሳለች ተገለጠላት፤ በዚህ ጊዜ ግን ባሏ ማኑሄ
አብሮአት አልነበረም። 10እርሷም ለባሏ ለመ
ንገር ፈጥና በመሄድ፣ "ባለፈው ጊዜ የተገ
ለጠልኝ ሰው ዛሬም ተገለጠልኝ" አለ
ችው።
11ማኑሄም ተነሥቶ ሚስቱን ተከተ
ላት፤ ሰውየው እንደ ደረሰም፣ "ከሚስቴ ጋር
ተነጋግረህ የነበርኸው አንተ ነህ?" ሲል ጠየ
ቀው።
እርሱም፤ "አዎን እኔ ነኝ" አለው።
12ማኑሄም፣ "ያልኸው በሚፈጸምበት
ጊዜ የልጁ ሕይወት የሚመራው እንዴት
ነው? እኛስ ምን ማድረግ አለብን?" ሲል
ጠየቀው።
*13የእግዚአብሔርም* መልአክ እንዲህ
አለው፤ "ሚስትህ የነገርኋትን ሁሉ ታድርግ።
14ከወይን ተክል የሚገኝ ማንኛውንም ነገር
አትብላ፤ የወይን ጠጅም ሆነ ሌላ የሚ
ያሰክር መጠጥ አትጠጣ፤ ርኩስ ነገር
አትብላ፤ ያዘዝኋትንም ሁሉ ታድርግ።"
15ከዚያም ማኑሄ *የእግዚአብሔርን* መል
አክ፣ "የፍየል ጠቦት ዐርደን እስክናዘጋጅልህ
ድረስ እባክህ ቈይ" አለው።
*16የእግዚአብሔርም* መልአክ፣ "የግድ
ብታቈየኝ እንኳ የምታቀርበውን ማንኛውንም

ዘኍ6፥2 ፡13፤1
ሳሙ1፥11፤7፥13፤
አሞ2፥11 ፡12
13፥6 ቀኍ8፤
ዘኍ22፥22፤
1ሳሙ2፥27፤9፥6፤
1ነገ13፥1፤17፥18፤
መዝ66፥5
13፥7 ዘሌ10፥9፤
1ሳሙ1፥11፡
28፤ኤር35፥6
13፥8 ቀኍ2፥6
13፥10 ቀኍ3
13፥14 ቀኍ4፤
ዘሌ10፥9
13፥15 መሳ6፥19
13፥16 መሳ6፥22፤
11፥31
13፥17 ዘፍ32፥29
13፥18 ዘፍ32፥29
13፥19 መሳ6፥20
13፥20 ዘፍ17፥3፤
ዘሌ9፥24
13፥21 መሳ6፥22
13፥22 ዘፍ16፥13፤
ዘፀ3፥6፤24፥10፤
ዘኍ17፥12፤ዘዳ5፥26
13፥23 መዝ25፥14
13፥24 መሳ14፥1፤
15፥1፤
16፥1ሳሙ2፥21፡
26፥3፥19፤ሉቃ1፥80፤
ዕብ11፥32
13፥25 መሳ3፥10፤
18፥12
14፥1 ዘፍ38፥12፤
መሳ13፥24
14፥2 ዘፍ21፥21
14፥3 ዘፍ24፥4፤
34፥14፤
ዘፀ4፥16፤1ሳሙ14፥6
14፥4 ዘዳ2፥30፤ ኢ
ሱ11፥20፤
መሳ13፥1፤15፥11

ምግብ አልበላም፤ ነገር ግን የሚቃጠል መሥ
ዋዕት የምታዘጋጅ ከሆነ እርሱን *ለእግዚአብሔር*
አቅርበው" አለው። *የሚያነጋግረው የእግዚአ
ብሔር* መልአክ መሆኑን አላወቀም ነበር።
17ማኑሄ *የእግዚአብሔርን* መልአክ፣ "የተና
ገርኸው ሲፈጸም እንድናከብርህ ስምህ ማን
ነው"? በማለት ጠየቀው።
18እርሱም፣ "ስሜ ድንቅ[መ] ስለ ሆነ፣
ለምን ትጠይቀኛለህ?" አለው። 19ማኑሄም
የፍየሉን ጠቦት ከእህል ቍርባኑ ጋር ወስዶ
በዐለት ላይ *ለእግዚአብሔር* ሠዋው። ማኑ
ሄና ሚስቱ እያዩ *እግዚአብሔር* አስደናቂ
ነገር አደረገ፤ 20ይኸውም የእሳቱ ነበልባል
ከመሠዊያው ወደ ሰማይ ሲወጣ፣ *የእግዚ
አብሔር* መልአክ በነበልባሉ ውስጥ ዐረገ።
ማኑሄና ሚስቱ ይህን ሲመለከቱ በግንባራ
ቸው መሬት ላይ ተደፉ። *21የእግዚአብሐ
ርም* መልአክ ለማኑሄና ለሚስቱ ዳግመኛ
ባለመገለጡ፣ ቀደም ሲል የተገለጠላቸው
*የእግዚአብሔር* መልአክ መሆኑን ማኑሄ ዐ
ወቀ።
22ሚስቱንም፣ "እግዚአብሔርን ስላየን
ያለ ጥርጥር እንሞታለን" አላት።
23ሚስቱ ግን መልሳ እንዲህ አለ
ችው፣ "*እግዚአብሔር* ሊገድለን ቢፈልግ ኖሮ፣
የሚቃጠለውን መሥዋትና የእህል ቍር
ባኑን ከእጃችን ባልተቀበለን፤ ደግሞም
ይህን ነገር ሁሉ ባላሳየንና እንዲህ
ያለውንም ነገር በዚህ ጊዜ ባልነገረን
ነበር።"
24ሴቲቱ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙንም
ሳምሶን ብላ ጠራችው፤ ልጁ አደገ፤ *እግዚ
አብሔርም* ባረከው፤ *25የእግዚአብሔርም*
መን ፈስ በጾርዓና በኤሽታኦል መካከል
ባለው በዳን ሰፈር ሳለ ያነቃቃው
ጀመር።

### የሳምሶን ጋብቻ

14 ሳምሶን ወደ ተምና ወረደ፤ እዚ
ያም አንዲት ወጣት ፍልስጥኤ
ማዊት አየ። 2እንደተመለሰም አባቱንና
እናቱን፣ "በተምና አንዲት ወጣት
ፍልስጥኤማዊት አይቻለሁና አሁኑኑ
አጋቡኝ" አላቸው።
3አባቱና እናቱም፣ "ከዘመዶችህ ወይም
ከሕዝባችን ሁሉ መካከል ለአንተ የምት
ሆን ሴት መች ታጣችና ነው ወደ አልተ
ገረዙት አሕዛብ ዘንድ ሚስት ፍለጋ የሄ
ድኸው?" አሉት።
ሳምሶንም አባቱን፣ "ልቤን የማረከችው
እርሷ ናትና እርሷን አጋባኝ" አለው።
4በዚያን ጊዜ በእስራኤል ላይ ገዦቹ ፍል
ስጥኤማውያን ስለ ነበሩ፣ ከፍልስጥኤ

[መ]18 ወይም *ድንቁ*

ማውያን ጋር ጠብ እንዲፈጠር እግዚ
አብሔር ሆን ብሎ ያደረገው ነገር መሆኑን
አባቱና እናቱ አላወቁም ነበር። [5]ከዚያም
ሳምሶን ከአባቱና ከእናንቱ ጋር ወደ
ተምና ወረደ፤ በዚያም ከአንድ የወይን
አትክልት ቦታ እንደ ደረሱ፣ ድንገት
አንድ የአንበሳ ደቦል እያገሣ መጣበት።
[6]በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ በ፤ይል
ወረደበት፤ ስለዚህ የፍየል ጠቦት እንደ
ሚገነጣጠል አንበሳውን ያለ ምንም መሣሪያ
በባዶ እጁ ገነጣጠለው፤ ያደርገውን ግን
ለአባቱም ሆነ ለእናቱ አልነገራቸውም ነበር።
[7]ወደ ሴቲቱም ወረደ፤ ከእርሷም ጋር ተነ
ጋገረ፤ እጅግም ወደዳት።

[8]ከጥቂት ቀን በኋላም ሊያገባት ተመለሰ፤
የአንበሳውንም በድን ለማየት ከመንገድ
ዘወር አለ፤ በበድኑም ውስጥ የንብ መንጋ
ሰፍሮ ተመለከተ፤ ማርም ነበረበት፤ [9]በእጁ
ወስዶም መንገድ ለመንገድ እየበላ ሄደ፤
ከወላጆቹም ጋር እንደተገናኘም ከማሩ
ሰጣቸው፤ እነርሱም በሉ። ነገር ግን ማሩን
የወሰደው ከአንበሳ በድን መሆኑን አልነገ
ራቸውም ነበር።

[10]የሳምሶን አባት ልጅቱን ሊያይ ወረደ፤
ሳምሶንም በነበረው የሙሽራ ወግ መሠ
ረት በዚያ ግብዣ አደረገ። [11]እርሱም
ለፍልስጥኤማውያን በታየ ጊዜ፣ ሠላሳ
አጃቢዎች ሰጡት።

[12]ሳምሶን እንዲህ አላቸው፤ እንድ እንቈ
ቅልሽ እነግራችኋለሁ፤ ታዲያ ፍቺውን በሰ
ርጉ በዓል ሰባት ቀኖች ውስጥ ከሰጣች
ሁኝ፣ ሠላሳ የቀጭን ፈትል በፍታ ቀሚ
ስና ሠላሳ የክት ልብስ እሰጣችኋለሁ።
[13]እንቈቅልሹን ካልፈታችሁልኝ ግን ሠላሳ
የቀጭኔ ፈትል በፍታ ቀሚስና ሠላሳውን
የክት ልብስ እናንተ ትሰጡኛላችሁ።"

እነርሱም፣ "በል እንቈቅልሽህን ንገረ
ንና እንስማው" አሉት።
[14]ሳምሶንም፣
"ከበላተኛው መብል፣
ከብርቱም ጣፋጭ ነገር ወጣ" አላቸው።

እነርሱም እስከ ሦስት ቀን ድረስ እን
ቈቅልሹን መፍታት አልቻሉም ነበር።
[15]በአራተኛው[ሠ] ቀን የሳምሶንን ሚስት፣
"የእንቈቅልሹን ፍች እንዲነግረን ባልሽን
እስቲ አግባቢልን፤ ያለዚያ አንቺንም የአባ
ትሽንም ቤተ ሰብ በእሳት እናቃጥላችኋ
ለን፤ ጠርታችሁ የጋበዛችሁን ልትዘርፉን ነው?"
አሏት።

[16]ከዚያ የሳምሶን ሚስት ተንሰቅስቃ
እያለቀሰች ከፊቱ በመቅረብ፣ "ለካስ ትጠላ
ኛለህ፤ በእርግጥ አትወደኝም" አለችው።
እርሱም፣ "ይህን ለአባቴም ሆነ ለእናቴ
አልነገርኋቸውም፤ ታዲያ ለአንቺ ለምን
እነግርሻለሁ?" አላት። [17]ሚስቱም በሰርጉ
በዓል ሰባት ቀን ሙሉ እያለቀሰች ጨቀጨ
ቀችው፤ አጥብቃ ስለ ነዘነዘችውም በመ
ጨረሻ በሰባተኛው ቀን ነገራት፤ እርሷም
በበኩሏ የእንቈቅልሹን ፍች ለሕዝቧ
ነገረች።

[18]በሰባተኛው ቀን ፀሓይ ከመጥለቋ
በፊት የከተማው ሰዎች፣

"ከማር የጣፈጠ ምን ተገኝቶ?
ከአንበሳስ ወዲያ ብርቱ ከየት መጥቶዬ
አሉት።
ሳምሶንም መልሶ፣
"በጊደሬ ባላረሳችሁ፣
እንቈቅልሼንም ባልፈታችሁ"አላቸው።

[19]ከዚያም የእግዚአብሔር መንፈስ በሳ
ምሶን ላይ በ፤ይል ወረደበት፤ ወደ አስቀ
ሎናም ወርዶ ከሰዎቻቸው መካከል ሠላሳ
ውን ገደለ፤ ያላቸውንም ከገፈፈ በኋላ
ልብሶቻቸውን አምጥቶ እንቈቅልሹን ለፈ
ቱት ሰዎች ሰጣቸው። በቍጣ እንደነደ
ደም ተነሥቶ ወደ አባቱ ቤት ወጣ።
[20]የሳምሶንም ሚስት ለሚዜው ተዳረች።

## ሳምሶን ፍልስጥኤማውያንን ተበቀለ

15 ከጥቂት ጊዜ በኋላ በስንዴ መከር
ወራት ሳምሶን አንድ የፍየል
ጠቦት ይዞ ሚስቱን ለማየት ሄደ፤ እር
ሱም፣ "ሚስቴ ወዳለችበት ጫጉላው ቤት
ልግባ" አለ፤ አባቷ ግን እንዲገባ አልፈቀደ
ለትም።

[2]አባትየውም፣ ፈጽሞ የጠላሃት መሆ
ንህን ስለ ተረዳሁ ለሚዜህ ድሬለታለሁ፤
ታናሽ እኅቷ ከእርሷ ይልቅ ውብ
አይደለችምን? እርሷን አግባት" አለው።

[3]ሳምሶንም መልሶ፣ "ከእንግዲህ በፍል
ስጥኤማውያን ላይ በሚደርሰው ጕዳት
ተጠያቂ አልሆንም" አላቸው። [4]ከዚያም
ወጥቶ በመሄድ ሦስት መቶ ቀበሮች ያዘ፤
የሁለት ሁለቱን ጭራ አንድ ላይ ካሰረ በኋላ
ችቦ ወስዶ ጥንድ ሆኖ ከተያያዘው ጭራ
ጋር አሰረው። [5]ችቦውን በእሳት አቀጣጥሎ
ቀበሮቹን በፍልስጥኤማውያን የእህል አዝ መ
ራ ላይ ለቀቃቸው፤ ነዶውንና የቆመውን
አዝመራ እንዲሁም የወይኑንና የወይራውን
ተክል አቃጠለ።

[6]ፍልስጥኤማውያን፣ "ይህን ያደረገው ማን
ነው?" ብለው ሲጠይቁ፣ "ሚስቱ ለሚዜው

14፥6 መሳ3፥10፤ 1ሳሙ17፥35
14፥10 ዘፍ29፥22
14፥12 ዘፍ29፥27፤ 45፥22፤ዘኍ12፥8፤ 2 ነገ5፥5ሕዝ17፥2፤ 20፥49፤24፥3፤ሆሴ12፥1
14፥14 ቍ18
14፥15 ዘሌ20፥14፤ መሳ15፥6፤16፥5፤ መክ7፥26
14፥16 መሳ16፥15
14፥17 አስ1፥5
14፥18 ቍ14
14፥19ኢሱ13፥3፤ መሳ3፥10፤ 1ሳሙ11፥6
14፥20 መሳ15፥2፡ 6፤ዮሐ3፥35
15፥1 ዘፍ29፥21፤ 30፥14፤38፥17፤ መሳ13፥24
15፥2 መሳ14፥20
15፥4 ዘፍ15፥17፤ መኃ2፥15
15፥5 ዘፍ15፥17፤ ዘፀ22፥6፤ 2ሳሙ14፥30-31
15፥6 ዘፍ38፥24፤

[ሠ]15. አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞችና የሱርስቱ ትርጕም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን ሰባተኛ ይላል።

ስለ ተሰጠችበት የተምናዊው ዐማች ሳምሶን
ነው” የሚል መልስ አገኙ፡፡
ስለዚህም ፍልስጥኤማውያን ወጥተው
ሴቲቱንና አባቷን በእሳት አቃጥለው ገደ
ሏቸው፡፡ 7ሳምሶንም፣ “እንግዲህ እናንተ
ይህን ካደረጋችሁ እኔ ደግሞ ሳልበቀላችሁ
አልመለስም” አለ፡፡ 8ክፉኛ መታቸው፤
ከነርሱም ብዙዎችን ገደለ፤ ከዚያም ወርዶ
በኢታም ዐለት ዋሻ ተቀመጠ፡፡
9ፍልስጥኤማውያን ወጥተው በይሁዳ ሰፈሩ፤
ከዚያም በሌሒ አጠገብ ተበታትነው አደ
ፈጡ፡፡ 10የይሁዳም ሰዎች፣ “ልትወጉን የመ
ጣችሁት ለምንድን ነው?” ሲሉ ጠየቋ
ቸው፡፡
እነርሱም “እኛ የመጣነው ሳምሶንን ልና
ስርና ያደረገብንን ልናደርግበት ነው”
ብለው መለሱላቸው፡፡
11ከዚያም ሦስት ሺህ ሰዎች ከይሁዳ ተነ
ሥተው በኤታም ዐለት ወዳለው ዋሻ ወር
ደው ሳምሶንን፣ “ፍልስጥኤማውያን ገዦቻችን
መሆናቸውን አታውቅምን? ያደረግህብንስ ነገር
ምንድን ነው?” ብለው ጠየቁት፡፡
ሳምሶንም፣ “ያደረግሁት እነርሱ ያደረ
ጉብኝን ነው” በማለት መለሰላቸው፡፡
12እነርሱም፣ “አስረን ለፍልስጥኤ
ማውያን ልንሰጥህ ይኸው መጥተናል”
አሉት፡፡
ሳምሶንም፣ “እናንተ ራሳችሁ ላትገድሉኝ
ማሉልኝ” አላቸው፡፡
13እነርሱም፣ “አስረን ብቻ ለእነርሱ
አሳልፈን እንሰጥሃለን እንጂ ራሳችን አንገድል
ህም” አሉት፤ ከዚያ በሁለት አዳዲስ ገመድ
አስረው ከዐለቱ ዋሻ አወጡት፡፡ 14ሳምሶን
ሌሒ እንደ ደረሰም ፍልስጥኤማውያን እየ
ጮኹ ወደ እርሱ መጡ፤ በዚህ ጊዜ *የእግዚ
አብሔር* መንፈስ በሳምሶን ላይ በ፤ይል
ወረደበት፡፡ እጆቹ የታሰሩበትም ገመድ እሳት
ውስጥ እንደ ገባ የተልባ እግር ፈትል
ሆኖ ከእጆቹ ላይ ወደቀ፡፡ 15ከዚያም በቅርቡ
የሞተ የአንድ የአህያ መንጋጋ አይቶ
ከመሬት አነሣ፤ በዚያም አንድ ሺህ ሰው
ገደለ፡፡

16ሳምሶንም፣

“በአንድ የአህያ መንጋጋ፣
ሺህ ሰው ዘራሪ፤
በአንድ የአህያ መንጋጋ፣
ሺህ ሬሳ አነባባሪ[ሎ]፡ ብሎ ፎከረ፡፡

17ይህን ተናግሮ እንዳበቃ የአህያውን
መንጋጋ ከእጁ ወዲያ ወረወረው፤ የዚያም
ቦታ ስም ራማት ሌሒ[ሰ] ተብሎ ተጠራ፡፡
18እጅግ ተጠምቶ ስለ ነበር፤ “እነሆ፤ ለአገ

መሳ14፥5 ፡20
15፥8 ቀኁ11፤
ኢሳ2፥21
15፥9 ቀኁ14፡
17፡19
15፥11 መሳ14፥4፤
መዝ106፥40-42
15፥12 ዘፍ47፥31
15፥13 መሳ16፥11፡12
15፥14 ቀኁ9፤
ኢሱ2፥6፤መሳ3፥10
15፥15 ዘሌ26፥8
15፥16 ኤር22፥9
15፥17 ቀኁ9
15፥18 ዘጸ20፥4፤
መሳ16፥28
15፥19 ዘፍ45፥27፤
ዘፀ17፥6፤
1ሳሙ30፥12፤
ኢሳ40፥29
15፥20 መሳ16፥31

16፥1 ዘፍ10፥19፤
38፥15፤መሳ13፥24
16፥2 ኢሱ2፥5፤
1ሳሙ19፥11
16፥3 ኢስ10፥36
16፥4 ቀኁ6፤
ዘፍ24፥67፤34፥3
16፥5 ቀኁ6 ፡15፡
18፤ዘፀ10፥7፤
ኢሱ13፥3፤
መሳ14፥15
16፥6 ቀኁ4

ልጋይህ ይህን ታላቅ ድል አጐናጽፈሃል፤ ታዲያ
አሁን በውሃ ጥም ልሙት? እንዴትስ በእነ
ዚህ ባልተገረዙ ፍልስጥኤማውያን እጅ
ልውደቅ? በማለት ወደ *እግዚአብሔር* ጮኸ፡፡
19እግዚአብሔርም በሌሒ ዐለት ሰነጠ
ቀለት፤ ከዚያም ውኃ ወጣ፤ ሳምሶንም ያን
ሲጠጣ በረታ፤ መንፈሱም ታደሰ፡፡ ስለዚህ
ያ ምንጭ
ዓይንሀቆሬ[ሸ] ተባለ፤ እስከ ዛሬም ድረስ
በዚያው በሌሒ ይገኛል፡፡
20ሳምሶንም በፍልስጥኤማውያን ዘመን
በእስራኤል ላይ ለሃያ ዓመት ፈራጅ[ቀ]
ሆነ፡፡

## ሳምሶንና ደሊላ

16 አንድ ቀን ሳምሶን ወደ ጋዛ ሄደ፤
እዚያም አንዲት ዝሙት አዳሪ አየ፤
አብሮአት ለማደርም ገባ፡፡ 2የጋዛ ሰዎች፣
“ሳምሶን እዚህ ነው!” የሚል ወሬ
ደረሳቸው፤ ስለዚህም ሰዎቹ ቦታውን
ከበው፤ ሌሊቱን በሙሉ በከተማዪቱ ቅጥር
በር ላይ አድፍጠው ጠበቁት፤ “በማለዳ
እንገ ድለዋለን” በማለትም ሌሊቱን በሙሉ
እንዳ ደፈጡ አደሩ፡፡
3ነገር ግን ሳምሶን እዚያ የተኛው
እስከ እኩለ ሌሊት ብቻ ነበር፤ ተነሥቶም
የከተማዪቱን ቅጥር በር ከሁለት መቃኖቹ
ጋር መወርወሪያውንና ማያያዣውን ጭምር
በሙሉ ነቅሎ በትከሻው ላይ ካደረገ በኋላ፣
በኬብሮን ፊት ለፊት እስካለው ኰረብታ
ጫፍ ድረስ ተሸክሞት ወጣ፡፡
4ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሳምሶን በሶሬቅ
ሸለቆ የምትኖር ደሊላ የምትባል አንዲት
ሴት ወደደ፡፡ 5የፍልስጥኤማውያን ገዦች
ወደ እርሷ ሄደው፣ “እርሱን አስረን በቊጥ
ጥራችን ሥር በማዋል ልናሸንፈው እን
ዴት እንደምንችልና የብርታቱ ታላቅነት
ምስጢር ምን እንደ ሆነ እንዲያሳይሽ
እስቲ አባብዪው፤ ይህን ካደረግሽ እያን
ዳንዳችን አንድ ሺህ አንድ መቶ ሰቅል[በ] ጥሬ
ብር እንሰጥሻለን” አሏት፡፡
6ስለዚህም ደሊላ ሳምሶንን፣ “የብር
ታትህን ታላቅነት ምስጢርና ታስረህ
በቊጥጥር ሥር የምትውለው እንዴት እንደ
ሆነ እባክህ ንገረኝ” አለችው፡፡
7ሳምሶንም፣ “ማንም ባለደረቁ ሰባት
እርጥብ ጠፍ ሮች[ተ] ቢያስረኝ እንደ
ማንኛውም ሰው ደካማ እሆናለሁ”

[ሎ]16. በዕብራይስጡ አህያ የሚለው ቃል *ፍም ከመረ* ወይም *አነባበረ* ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡
[ሰ]17.ራማት ሌሒ ማለት *የመንጋጋ ኰረብታ ክምር* ማለት ነው፡፡
[ሸ]19.*ዓይንሀቆሬ* ማለት የጠሪዎች ምንጭ ማለት ነው
[ቀ]20. በትውፊት *መሳፍንት* ይባላል፡፡
[በ]5. 13 ኪሎ ግራም ያህል ነው፡፡
[ተ]7. በዚህ እንዲሁም በቍጥር 8 እና 9 ላይ *የቀስት አውታር*

አላት።
[8]ከዚያም የፍልስጥኤማውያን ገዦች
ያልደረቁ ሰባት እርጥብ ጠፍሮች አመጡ
ላት፤ እርሷም አሰረችው። [9]ሰዎች በጓዳ ውስጥ
ተደብቀው ነበር፤ እርሷም፣ “ሳምሶን! ፍልስ
ጥኤማውያን መጡብህ” አለችው፤ ሳምሶን ግን
ፈትል እሳት ሲነካው እንደሚበጣጠስ ጠፍ
ሮቹን በቀላሉ በጣጠሳቸው፤ ስለዚህ የብር
ታቱ ምስጢር ምን እንደ ሆነ ሊታወቅ
አልቻለም።
[10]ደሊላም ሳምሶንን፣ “አሞኘተኸኛል፤
ዋሽተኸኛል፤ እባክህ አሁንም አንተን
እንዴት ማሰር እንደሚቻል ንገረኝ” አለ
ችው።
[11]እርሱም፣ *ሥራ* ላይ ባልዋሉ አዳዲስ
ገመዶች ቢያስሩኝ እንደ ማንኛውም ሰው
ደካማ እሆናለሁ” አላት።
[12]ደሊላም አዳዲስ ገመዶች ወስዳ
አሰረችው፤ ሰዎች በጓዳ ውስጥ ተደብቀው
ነበር፤ እርሷም፣ “ሳምሶንሄ ፍልስጥኤማውያን
መጡብህ” አለችው። እርሱ ግን ክንዱ
የታ ሰረባቸውን ገመዶች እንደ ፈትል ክር
በጣጠሳቸው።
[13]ደግሞም ደሊላ ሳምሶንን፣ “እስካሁን
አሞኘተኸኛል፤ ዋሽተኸኛል። እባክህን አን
ተን ማሰር የሚቻለው እንዴት እንደ ሆነ
ንገረኝ” አለችው።
እርሱም መልሶ፣ “የራስ ጠጕሬን
ሰባት ቈንዳላዎች ከድር ጋር ጐንጕነሽ
በችካል ብትቸክዪው፣ እንደ ማንኛውም ሰው
ደካማ እሆናለሁ” አላት። ደሊላም መተኛቱን
አይታ ሰባቱን ቈንዳላዎቹን ከድር ጋር
ጐነጐነችው፤ [14]ከችካልም ጋር ቸከለችው።
እንደ ገናም፣ “ሳምሶንሄ ፍልስጥኤማውያን
መጡብህ” አለችው። ሳምሶን ከእንቅልፉ
ነቃ፤ ችካሉን ከነድሩ፣ ከነቈንዳላው
ነቀለው።
[15]ከዚያም፣ “ሳታምነኝ እንዴት ‘እወድሻ
ለሁ’ ትለኛለህ? ስታታልለኝና የ፤ይልህንም
ታላቅነት ምስጢር ስትደብቀኝ ይህ ሦስተኛ
ጊዜህ ነው” አለችው። [16]በሕይወት መኖሩ
ን እስኪ ጠላ ድረስ ዕለት ዕለት
በመጨቅጨቅ አሰለቸችው።
[17]ስለዚህ ሁሉንም ነገር ነገራት፤ እንዲ
ህም አለ፤ “ከተወለድሁ ጀምሮ ናዝራዊ
በመሆን *ለእግዚአብሔር* የተለየሁ ስለ ሆንሁ
ራሴን ምላጭ ነክቶት አያውቅም፤ የራሴ
ጠጕር ቢላጭ ግን ፤ይሌ ተለይቶኝ እንደ
ማንኛውም ሰው ደካማ እሆናለሁ” አላት።
[18]ደሊላ ሁሉንም ነገር እንደ ነገራት
በተረዳች ጊዜ፣ ለፍልስጥኤማውያን ገዦች
“ሁሉንም ነገር ነግሮኛልና ተመልሳችሁ
ኑ” ብላ ላከችባቸው፤ የፍልስጥኤማውያን ገዦ
ችም ብሩን ይዘው ተመልሰው መጡ።
[19]ደሊላ፣ ሳምሶንን በጭኗ ላይ አስተኝታ
እንቅልፍ እንዲወስደው ካደረገች በኋላ
አንድ ሰው ጠርታ ሰባቱን የጠጕር ቈንዳ
ላዎቹን አስላጨቻቸው፤ እርሷም ታስጨ
ንቀው[፻] ጀመር፤ ፤ይሉም ተለየው።
[20]እርሷም፣ “ሳምሶን፤ ፍልስጥኤማውያን
መጡብህሄ” አለችው።
ሳምሶን ከእንቅልፉ ነቅቶ፣ “እንደ ወትሮው
አደርጋለሁ” አለ፤ ነገር ግን *እግዚአብሔር*
እንደ ተወው አላወቀም ነበር።
[21]ከዚያም ፍልስጥኤማውያን ያዙት፤
ዐይኖቹን አውጥተው ወደ ጋዛ ይዘውት ወረዱ፤
በናስ ሰንሰለት አስረውም እስር ቤት
ውስጥ እህል እንዲፈጭ አደረጉት፤ [22]ነገር
ግን ከተላጨ በኋላ ጠጕሩ እንደ ገና ማደግ
ጀመረ።

## የሳምሶን አሟሟት

[23]በዚህ ጊዜ የፍልስጥኤማውያን ገዦች፣
“አምላካችን ዳጎን፣ ጠላታችን ሳምሶንን
በእጃችን አሳልፎ ሰጥቶናል” ብለው በመ
ደሰት ለአምላካቸው ለዳጎን ታላቅ መሥዋዕት
ለማ ቅረብ ተሰበሰቡ።
[24]ሕዝቡም ሳምሶንን ባዩት ጊዜ፣
አምላካቸውን ዳጎንን በማመስገን፣

“ምድራችንን ያጠፋውን፣
ብዙ ሰው የገደለብንን፣ጠላታችንን፣
አምላካችን በእጃችን አሳልፎ ሰጠን” አሉ።
[25]እጅግ ደስ ባላቸው ጊዜ፣ “እንዲያዝ
ናናን ሳምሶንን አምጡት” አሉ፤ ስለዚህ
ሳምሶንን ከእስር ቤት ጠርተው አስመጡት፤
በፊታቸውም ተጫወተ።
በምሶሶዎቹ መካከል ባቆሙት ጊዜ፣
[26]ሳምሶን እጁን ይዞ የሚመራውን ልጅ፣
“ቤተ ጣዖቱ ደግፈው ወደ ያዙት ምሰሶዎች
አስጠጋኝና ልደገፋቸው” አለው። [27]በዚህ ጊ
ዜ ወንዶችና ሴቶች ቤተ ጣዖቱን ሞልተ
ውት ነበር፤ የፍልስጥኤማውያን ገዦችም
በሙሉ በዚያ ነበሩ፤ ሳምሶን ሲጫወት ለማ
የት ሦስት ሺህ ያህል ወንዶችና ሴቶች
በጣራው ላይ ነበሩ። [28]ሳምሶንም ወደ
*እግዚአብሔር* እንዲህ ሲል ጸለየ፤ “ልዑል
*እግ ዚአብሔር* ሆይ፤ አስበኝ፤ አምላክ
ሆይ፤ እባክህን አንድ ጊዜ ብቻ ብርታት
ስጠኝና ስለ ጠፉት ዐይኖቼ ፍልስጥኤ
ማውያ ንን አንዴ ልበቀላቸው።” [29]ከዚ
ያም ቤተ

16፥9 ቀኍ12፤ቀኍ14
16፥10 ቀኍ13
16፥11 መሳ15፥13
16፥12 ቀኍ14
16፥14 ቀኍ9 ፡20
16፥15 ቀኍ5፤ ዘኁ24፥10፤ መሳ14፥16
16፥17 ቀኍ18፤ ዘኁ6፥2፤ ሚክ7፥5
16፥18 ቀኍ5፤ ኢሱ13፥3፤1ሳሙ5፥8
16፥19ምሳ7፥26-27
16፥20 ቀኍ14፤ ዘኁ 14፥42፤ ኢሱ7፥12፤ 1ሳሙ16፥14፤18፥12፤ 28፥15
16፥21 ዘፍ10፥19፤ ዘኁ16፥14፤ ኢዮ31፥10፤ ኢሳ47፥2፤ኤር47፥1
16፥23 1ሳሙ5፥2፤ 1ዜና10፥10
16፥24 1ሳሙ 1፥9፤ ዜና10፥9፤ ዳን5፥4
16፥25 መሳ9፥27፤ 19፥6፡9፡22፤ ሩት3፥7፤ አስ1፥10
16፥27 ኢሱ2፥8
16፥28 ሳ15፥18፤ ኤር15፥15

[፻]19. ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ሲስማማ እንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች ግን *ታዳክመው ጀመር* ይላሉ

ጣዖቱን መካከል ላይ ደግፈው የያዙትን
ሁለት ምሰሶዎች አንዱን በቀኙ፣ አንዱን
በግራ እጁ አቅፎ በመያዝ፣ 30“ከፍልስጥ
ኤማውያን ጋር አብሬ ልሙት” በማለት
ባለ ፤ይሉ ሲገፋው፣ ቤተ ጣዖቱ በገዦቹና
በውስጡ በነበሩት በሌሎቹ ሰዎች ሁሉ ላይ
ወደቀባቸው፤ ስለዚህ በሕይወት ከኖረበት
ጊዜ ይልቅ በሞቱ ጊዜ ብዙ ሰው ገደለ።
31ወንድሞቹና መላው የአባቱ ቤተ
ሰብ ሬሳውን ለማምጣት ወደዚያ ወረዱ፤
አምጥተውም የአባቱ የማኑሄ መቃብር
ባለበት በጾርዓና በኤሽታኦል መካከል
ቀበሩት። ሳምሶን በእስራኤል ላይ
ሃያ ዓመት ፈራጅ[ጎ] ሆነ ።

## ሚካ ያሠራቸው ጣዖታት

17 ሚካ የተባለ በኰረብታማው
በኤ ፍሬም አገር የሚኖር ሰው
ነበር። 2እናቱን፣ “አንድ ሺህ አንድ መቶ
ሰቅል[ነ] ብር ተሰርቆብሽ፣ የሰረቀውን ሰው
ስትራገሚ ሰምቼሽ ነበር፤ ብሩ ከእኔ
ዘንድ ይገኛል፤ የወሰድሁት እኔ ነኝ”
አላት።
ከዚያም እናቱ፣ “ልጄ፤ *እግዚአብሔር*
ይባርክህ” አለችው።
3አንድ ሺህ አንድ መቶውን ሰቅል
ብር በመለሰላት ጊዜ፣ እናቱ “ብሬን
የተቀረጸ ምስልና ቀልጦ የተሠራ ጣዖት
ለማበጀት ስለ ልጄን *ለእግዚአብሔር* እቀድ
ሰዋለሁ፤ አሁንም ለአንተው መልሼ
እሰጥሃለሁ” አለችው።
4ስለዚህ ብሩን ለእናቱ መለሰላት፤ እና
ቱም ከላዩ ሁለት መቶ[ኘ] ጥሬ ብር ወስዳ
ለብር አንጥረኛ ሰጠች፤ አንጥረኛውም
የተቀረጸ ምስልና ቀልጦ የተሠራ ጣዖት
አደረገው፤ ምስሎቹም በሚካ ቤት ተቀ
መጡ።
5ሚካ የተባለው ይህ ሰው የአምልኮ ስፍራ
ነበረው፤ አንድ ኤፉድና ተራፊም ሠርቶ
ከልጆቹ አንዱን ካህን ሆኖ እንዲ
ያገለግለው አደረገ። 6በዚያን ዘመን በእስ
ራኤል ንጉሥ አልነበረም፤ እያንዳንዱ ሰው
ለራሱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ
ነበር። 7በይሁዳ ምድር፣ በይሁዳ ነገድ
መካከል በቤተ ልሔም የሚኖር አንድ
ሌዋዊ ወጣት ነበር። 8ይህም ሰው ሌላ
መኖሪያ ስፍራ ለመፈለግ ከተማዪቱን ለቆ
ሄደ። በሚጓዘበትም[ኦ] ጊዜ በኰረብታማው
በኤፍሬም አገር ወዳለው ወደ ሚካ ቤት
መጣ።
9ሚካም፣ “የየት አገር ሰው ነህ?” ሲል
ጠየቀው።

16፥31 መሳ13፥2፤ 15፥20፤ሩት1፥1፤1 ሳሙ4፥18፤7፥6
17፥1 መሳ18፥2፡ 13
17፥2 ሩት2፥20፤ 3፥10፤1ሳሙ15፥13፤ 23፥21፤2ሳሙ2፥5
17፥3 ዘፀ20፥4
17፥4 ዘፀ32፥4፤ ኢ ሳ17፥8
17፥5 ዘፍ31፥19፤ ዘፀ29፥9፤ ዘኍ16፥10፤ መሳ8፥27፤ ኢሳ44፥13፤ ሕዝ8፥ 10
17፥6 ዘዳ12፥8፤ መሳ18፥1፤ 19፥1፤21፥25
17፥7 ዘፍ35፥19፤ መሳ18፥3፤ማቴ2፥1
17፥9 ሩት1፥1
17፥10 ዘፍ45፥8፤ መሳ18፥19
17፥12 ኍ16፥10፤ መሳ18፥4
17፥13 ዘኍ18፥7
18፥1 ኢሱ19፥47፤ መሳ1፥34፤17፥6
18፥2 ቀኁ17፤ ዘፍ30፥6፤ዘኍ21፥32፤ ኢሱ2፥1፤መሳ17፥1
18፥3 መሳ17፥7
18፥4 መሳ17፥12
18፥5 ዘፍ25፥22፤ መሳ20፥18፡23፡ 27፤1ሳሙ14፥18፤ 2ሳሙ5፥19፤ 2ነገ1፥2፤8፥8
18፥6 1ነገ22፥6
18፥7 ቀኁ17፡28፤ ዘፍ34፥25፤

እርሱም፣ “እኔ በይሁዳ ምድር ከምትገኝ
ከቤተ ልሔም የመጣሁ ሌዋዊ ነኝ፤ መኖ
ሪያ ስፍራ እፈልጋለሁ” አለው።
10ሚካም፣ “እንግዲያውስ” አብረኸኝ
ተቀመጥ፤ አባትም ካህንም ሁነኝ፤ እኔም
በዓመት ዐሥር ሰቅል[ከ] ብር እንዲሁም
ልብስና ምግብ እሰጥሃለሁ”አለው። 11ስለዚህ
ሌዋዊው አብሮት ለመኖር ተስማማ፤ ወጣ
ቱም ለሚካ ከልጆቹ እንደ አንዱ ሆነ
ለት። 12ሚካም ሌዋዊውን ካህን አድርጎ
አስቀመጠው፤ ወጣቱም ካህኑ ሆነ፤ በቤቱም
ኖረ። 13ሚካም፤ “ይህ ሌዋዊ ካህን ለሆነ
ልኝ፣ *እግዚአብሔር* በጎ ነገር እንደሚያደር
ግልኝ አሁን ተረዳሁ” አለ።

## ዳናውያን ሰዎች በላይሽ ሰፈሩ

18 በዚያን ዘመን በእስራኤል ንጉሥ
አልነበረም፤ የዳን ነገድም በእስራ
ኤል ነገዶች መካከል ርስተ ድርሻውን ገና
ስላልወሰደ፣ የሚሰፍርበትን የራሱን ርስት
ይፈልግ ነበር። 2ስለዚህ ዳናውያን ምድሪ
ቱን እንዲሰልሉና እንዲ መረምሩ አም
ስት ፤ያላን ሰዎች ከጾርዓና ከኤሽታኦል
ከተሞች ወደዚያ ላኩ፤ እነዚህም ነገዶቻ
ቸውን ሁሉ የሚወክሉ ነበሩ። የላኳቸውም
ሰዎች፣ “ሂዱ፤ ምድሪቱን ሰልሉ” አሏ
ቸው።
መልእክተኞቹም ወደ ኰረብታማው
የኤፍሬም አገር ገቡ፤ ወደሚያድሩበትም ወደ
ሚካ ቤት መጡ። 3በሚካ ቤት አጠገብ እንደ
ደረሱም የወጣቱን ሌዋዊ ድምፅ ዐወቁ፤
ስለዚህ ወደዚያ ጐራ ብለው፣ “ወደዚህ ያመ
ጣህ ማን ነው? እዚህ ምን ትሠራለህ? የመ
ጣኸውስ ለምንድን ነው?”። ሲሉ ጠየ
ቁት።
4እርሱም፣ “ሚካ ይህን ይህን አደረ
ገልኝ ቀጠረኝ፤ ካህኑም ሆንሁ” አላቸው።
5እነርሱም፣ “መንገዳችን መቃናት አለ
መቃናቱን እንድናውቅ እባክህ *እግዚአብሔ
ርን* ጠይቅልን” አሉት።
6ካህኑም፣ “በሰላም ሂዱ፤ መንገዳችሁን
*እግዚአብሔር* አቃንቶላችኋል” ብሎ መለሰ
ቸው።
7ስለዚህ አምስቱ ሰዎች ከዚያ ተነሥ
ተው ወደ ላይሽ መጡ፤ ሲዶናውያን ያለ
ስጋት በጸጥታ[ኸ] እንደሚኖሩ ሁሉ፣ በዚ
ያም የሚኖረው ሕዝብ በሰላም እንደሚ

[ጎ]31. በትውፊት *መሳፍንት* ይባላል።
[ነ]2. 13 ኪሎ ግራም ያህል ነው።
[ኘ]4 2. 3 ኪሎ ግራም ያህል ነው፡
[ኦ]8. ወይም *የዕለት ምግባሩ እያከናወነ ሳለ*
[ከ]10. 110 ግራም ያህል ነው።
[ኸ]7. በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጉም በትክክል አይታወቅም

ኖር አዩ:: ምድሪቱ አንዳች የሚጐድላት
ነገር ባለ መኖሩ ሕዝቡ ባለጸጋ ነበር::
እንዲሁም ከሲዶናውያን ርቆ የሚኖር ሲ
ሆን፣ ከማንኛውም ሕዝብ ጋር[ሠ] ግንኙነት
አልነበረውም::
[8]ወደ ጾርዓና ወደ ኤሽታኦል እንደ
ተመለሱ ወገኖቻቸው፣ "የሄዳችሁበት ጕዳይ
እንዴት ሆነ?" በማለት ጠየቋቸው::
[9]መልእክተኞቹም እንዲህ አሏቸው፤
"ምድሪቱ እጅግ መልካም መሆኗን አይተ
ናል፤ እንግዲህ ተነሡ፤ ሄደን እንዋጋቸው፤
ተነሡ እንጂ ዝም ትላላችሁን? ወደዚያው
ሄዳችሁ ምድሪቱን ለመያዝ አታመንቱ
[10]እዚያ ስትደርሱም ያለ ሥጋት የሚ
ኖር ሕዝብ፣ *እግዚአብሔር* በእጃችሁ የሚሰ
ጣችሁን አንዳች ነገር ያልጐደላትን ሰፊ
ምድር ታገኛላችሁ::"
[11]ከዚያ በኋላም ከዳን ወገን ለጦርነት
ዝግጁ የሆኑ ስድስት መቶ ሰዎች ከጾርዓና
ከኤሽታኦል ተነሡ:: [12]ወጥተውም በይሁዳ
ምድር ባለችው በቂርያትይዓሪም ሰፈሩ፤
እንግዲህ ከቂርያትይዓሪም በስተ ምዕራብ
ያለው ስፍራ እስከ ዛሬ ድረስ የዳን ሰፈር
መባሉ ከዚሁ የተነሣ ነው:: [13]ከዚያም
ተጕዘው ወደ ኰረብታማው የኤፍሬም
አገር በመሄድ ወደ ሚካ ቤት መጡ::
[14]የላይሽን ምድር ሰልለው የነበሩት
አምስቱ ሰዎች ለወንድሞቻቸው፣ "ከእነዚሁ
ቤቶች በአንዱ ኤፉድ፣ ተራፊም፣ የተቀረጸ
ምስልና ቀልጦ የተሠራ ጣዖት እንዳለ
ታውቃላችሁን? እንግዲህ ምን ማድረግ
እንዳለባችሁ ዕወቁበት" አሏቸው:: [15]ስለዚህ
ወጣቱ ሌዋዊ ወደሚኖርበት ወደ ሚካ
ቤት ጎራ ብለው ሰላምታ አቀረቡለት ::
[16]ለጦርነት ተዘጋጅተው የመጡት ስድስት
መቶ የዳን ሰዎች በቅጥሩ በር መግቢያ
ላይ ቆመው ነበር:: [17]ካህኑ ለጦርነት ከተዘጋ
ጁት ስድስት መቶ ሰዎች ጋር በቅጥሩ
በር ላይ ቆሞ ሳለ፣ ምድሪቱን ለመሰለል
መጥተው የነበሩትን አምስት ሰዎች ወደ
ቤቱ ውስጥ በመግባት የተቀረጸውን ምስ
ልና ኤፉዱን፣ ተራፊሙንና ቀልጦ የተሠ
ራውን ምስል ወሰዱ::
[18]እነዚህ ሰዎች ወደ ሚካ ቤት ገብተው
የተቀረጸውን ምስልና ኤፉዱን፣ ተራፊሙንና
ቀልጦ የተሠራውን ምስል በሚወስዱበት
ጊዜ ካህኑ፣ "ምን ማድረጋችሁ ነው?" አላቸው::
[19]እነርሱም፣ "ዝም በልሄ አንዲት ቃል
እንዳትተነፍስ፤ ከእኛ ጋር ሁን፤ አባትም
ካህንም ሁነን፤ ለአንተስ የአንድ ቤተ ሰብ
ካህን ከመሆን ይልቅ በእስራኤል የአንዱ
ነገድና ጐሣ ካህን ሆነህ ማገልገሉ አይሻል

ኢሱ11፥8፤19፥47
18፥9 ዘኍ13፥30፤
1ነገ22፥3
18፥10 ዘዳ8፥9፤
1ዜና4፥40
18፥11 ቀኍ16፥17፤
መሳ13፥2
18፥12 ኢሱ9፥17፤
መሳ13፥25
18፥13 መሳ17፥1
18፥14 ዘፍ31፥19፤
ኢሱ19፥47፤
መሳ8፥27
18፥16 ቀኍ11
18፥17 ቀኍ11፤
ዘፍ31፥19፤ሚክ5፥13
18፥18 ቀኍ24፤
ዘፍ31፥19፤
ኢሳ46፥2፤
ኤር43፥11፤48፥7፤
49፥3፤ሆሴ10፥5
18፥19 ዘኍ26፥ 42፤
መሳ17፥10፤
ኢዮ13፥5፤
21፥5፤29፥9፤40፥4፤ ኢ
ሳ52፥15፤ ሚክ7፥16

18፥24 ቀኍ17-18
18፥26 2ሳሙ3፥39 ፤
መዝ18፥17፤ 35፥10
18፥27 ዘፍ34፥25፤
49፥47፤ዘኍ31፥10፤
ኢሱ19፥47
18፥28 ቀኍ7፤
ዘፍ10፥19፤
ዘኍ13፥21
18፥29 ዘፍ14፥14፤
ኢሱ19፥47፤
1ነገ15፥20
18፥30 ዘፀ2፥22
18፥31 ቀኍ17፤
ኢሱ18፥1፤
መሳ19፥18፤
20፥18፤ኤር7፥14

ህምን?" አሉት:: [20]ይህም ካህኑን ደስ አሰ
ኘው፤ እርሱም ኤፉዱን፣ ተራፊሙንና
የተቀረጸውን ምስል ይዞ ከሕዝቡ ጋር
ሄደ:: [21]እነርሱም ሕፃናታቸውን፣ የከብቶ
ቻቸውን መንጋና ሀብታቸውን ሁሉ ወደ
ፊት በማስቀደም ተመልሰው ሄዱ::
[22]ከሚካ ቤት ጥቂት ራቅ እንዳሉም፣
የሚካ ጎረቤቶች ለርዳታ ተጠርተው ተሰ
በሰቡ፤ የዳን ሰዎችንም ተከታትለው
ደረሱ ባቸው:: [23]ከበስተ ኋላቸው ሆነው ሲ
ጮኹባ ቸውም፣ የዳን ሰዎች ወደ
ኋላቸው ዞረው ሚካን፣ "ሰዎችህን ለውጊ
ያ አሰባስበህ መምጣትህ ምን ሆንህና
ነው?" አሉት::
[24]እርሱም፣ "እንዴት፣ 'ምን ሆንህ' ብላ
ችሁ ትጠይቁኛላችሁ? የሠራኋቸውን አማል
ክቴንና ካህኔን ወስዳችሁ ሄዳችኋል፤ ምን
የቀረኝ ነገር አለ?" አላቸው::
[25]የዳን ሰዎች፣ "አትሚገተን፤ ያለዚያ
የተቈጡ ሰዎች ጉዳት ላይ ይጥሉሃል፤ አን
ተም ቤተ ሰብህም ሕይወታችሁን ታጣላ
ችሁ" አሉት:: [26]የዳን ሰዎች ይህን ብለው
መንገዳቸውን ቀጠሉ፤ ሚካም የማይች
ላቸው መሆኑን በማየት ተመልሶ ወደ
ቤቱ ሄደ::
[27]ከዚያም ሚካ የሠራውን ጣዖትና ካህኑን
ወስደው ወደ ላይሽ በመሄድ፣ በሰላምና
ያለ ስጋት ይኖር የነበረውን ሕዝብ በሰ
ይፍ መቱት፤ ከተማይቱንም በእሳት
አቃጠሏት:: [28]የሚኖሩት ከሲዶና በጣም
ርቀው ስለ ነበርና ከማንም ጋር ግንኙነት
ስላልነበራቸው የሚታደጋቸው አንድም
አልነበረም፤ ከተማዪቱም የምትገኘው በቤ
ትሮዓብ አጠገብ ነበረ::
የዳንም ሰዎች ከተማዪቱን እንደ ገና
ሠርተው መኖሪያቸው አደረጓት:: [29]ከተ
ማዪቱንም ከእስራኤል በተወለደው በአባ
ታቸው በዳን ስም ዳን ብለው ጠሯት፤
ቀድሞ ግን ስሟ ላይሽ ይባል ነበር:: [30]እዚ
ያም የዳን ሰዎች ለራሳቸው ጣዖታት አቆሙ፤
የሙሴ ልጅ፣[0] የጌርሳም ልጅ ዮናታንና የእ
ርሱም ልጆች ምድሪቱ እስከ ተማረከች
በት ጊዜ ድረስ ለዳን ነገድ ካህናት ሆኗ
ቸው፤ [31]ስለዚህም ሚካ የሠራቸውን ጣዖ
ታት፣ *የእግዚአብሔር* ቤት በሴሎ
በነበረበት ጊዜ ሁሉ ባለማቋረጥ
አመለኳቸው::

[ሠ]7. በዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ሲስማማ የስብዓ ሊቃናት ትርጕም ግን *ከአራም ሰዎች ጋር* ይላል::
30.ጥንታዊው የዕብራውያን ጸሓፍት ትውፊት፣ አንዳንድ የስብዓ ሊቃናት ትርጕም እንዲሁም የሱርስቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የማሶሬቱ ቅጂ ግን *ምናሴ* ይላል::

## አንድ ሌዋዊና ቁባቱ

19 በዚያን ዘመን በእስራኤል ንጉሥ
አልነበረም፤ በዚሁ ጊዜም በኰረብ
ታማው በኤፍሬም አገር የሚኖር አንድ ሌዋዊ
ከይሁዳ ምድር ከቤተ ልሔም አንዲቱን
ሴት ቁባት አድርጎ ወሰዳት።
2ሴቲቱ ግን በታማኝነት አልጸናችም፤ ትታ
ውም በይሁዳ ምድር ወደሚገኘው ወደ
አባቷ ቤት ወደቤተ ልሔም ሄደች፤ እዚ
ያም አራት ወር ከቈየች በኋላ፣ 3ባሏ ታርቆ
ሊመልሳት ወደ እርሷ ሄደ፤ ሲሄድም አሽ
ከሩንና ሁለት አህዮችን ይዞ ነበር፤ ሴቲቱም
ወደ አባቷ ቤት አስገባችው፤ አባቷም ባየው
ጊዜ በደስታ ተቀበለው። 4የልጂቱ አባ
ትም እዚያው እንዲቈይ አጥብቆ ለመነው፤
ስለዚህ እየበላ እየጠጣ ሦስት ቀን አብሮት
ተቀመጠ።
5በአራተኛው ቀን ማልደው ተነሡ፤
እንግዳውም ለመሄድ ተዘጋጀ፤ የልጂቱ
አባት ግን፣ “እንድትበረታ እህል ቅመስ፤
ከዚያም መሄድ ትችላለህ” አለው። 6ስለዚህ
ሁለቱ ለመብላትና ለመጠጣት አብረው
ተቀመጡ። የልጂቷም አባት፣ “እባክህ
ዛሬም እዚሁ አድረህ ተደሰት” አለው።
7ሰውየው ለመሄድ ሲነሣም ዐማቱ እንዲ
ያድር ለመነውና እዚያው አደረ። 8በአም
ስተኛውም ቀን ጠዋት ሌዋዊው ለመሄድ
ሲነሣ፣ የልጂቱ አባት “ሰውነትህን አበ
ርታ፤ ጥላው እስኪበርድም ድረስ በዚሁ
ቈይ” አለው፤ ስለዚህ ሁለቱም አብረው
በሉ።
9ሰውየውም ከቁባቱና ከአገልጋዩ ጋር
ለመሄድ በተነሣ ጊዜ፣ የልጅቱ አባት ዐማቱ
“እነሆ ጊዜው እየመሸ ነው፤ እዚሁ እደሩ፤
ቀኑ እየተገባደደ ነው፤ እዚሁ አድራችሁ
ተደሰቱ፤ ነገ ጠዋት ማልዳችሁ በመነሣት
መንገዳችሁን ትሄዳላችሁ” አለው። 10ሌዋዊው
ግን በዚያች ሌሊት በዚያ ለማደር ስላል
ፈለገ ተነሥቶ የተጫኑትን ሁለቱን አህዮ
ቹንና ቁባቱን ይዞ ኢየሩሳሌም ወደ
ተባለችው ወደ ኢያቡስ ሄደ።
11ወደ ኢያቡስ እንደ ቀረቡም ጊዜው
እየመሸ ስለ ነበር አገልጋዩ ጌታውን፣
“እንግዲህ ወደዚህች ወደ ኢያቡሳውያን
ከተማ ጐራ ብለን እንደር” አለው።
12ጌታውም፣ “አይሆንም፤ ሕዝቧ እስራ
ኤላዊ ወዳልሆነ ወደ ባዕድ ከተማ አንገባም፤
ወደ ጊብዓ አልፈን እንሂድ” አለው። 13ቀጥ
ሎም፣ “በልና፤ ወደ ጊብዓ ወይም ወደ ራማ
ለመድረስ እንሞክርና ከዚያ በአንዱ ስፍራ
እናድራለን” አለው። 14ስለዚህም መንገዳቸውን
ቀጠሉ፤ የብንያም ነገድ ወደ ሆነችው
ወደ ጊብዓ እንደ ደረሱም ፀሓይ ጠ
ለቀች። 15ለማ ደርም ወደዚያው ጎራ አሉ፤
ሄደ ውም በከተማዪቱ አደባባይ ተቀመጡ፤
ሆኖም በቤቱ ለማሳደር ማንም
አልተቀበላቸውም ነበር።
16በዚያች ምሽት ከኰረብታማው ከኤ
ፍሬም አገር መጥቶ በጊብዓ የሚኖር
አንድ መጻተኛ ሽማግሌ ከዕርሻ ሥራው
መጣ፤ የዚያ አገር ሰዎች ግን ብንያማውያን
ነበሩ። 17ሽማግሌው ቀና ብሎ መንገደኛ
ውን በከተማዪቱ አደባባይ ላይ ባየው
ጊዜ፣ “ከወዴት መጣህ? ወዴትስ ትሄዳ
ለህ?” ሲል ጠየቀው።
18ሰውየውም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “እኛ
የመጣነው ከይሁዳ ቤተ ልሔም ርቆ ከሚገኘው
ከኰረብታማው ከኤፍሬም አገር ነው፤
ከይሁዳ ቤተ ልሔም ነበርሁ፤ አሁን ወደ
*እግዚአብሔር* ቤት እሄዳለሁ፤ ወደ ቤቱ
የሚወስደኝ ሰው አላገኘሁም። 19ለአህዮቻችን
ገለባና ገፈራ አለን፤ እኛ ባሮችህ ለእኔም
ሆነ ለገረድህ፣ አብሮን ላለውም ወጣት
እንጀራና የወይን ጠጅ ይዘናል፤ ሌላ ምንም
ነገር አያስፈልገንም።”
20ሽማግሌውም፣ “ኑ ግቡ በቤቴም እደሩ፤
የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አቀርባለሁ፤ በዐደ
ባባይ ግን አትደሩ” አለው። 21ስለዚህ ወደ
ቤቱ አስገብቶት ለአህዮቹ ገፈራ ሰጣቸው፤
እንግዶቹም እግራቸውን ታጠቡ፤ በሉ፤
ጠጡም።
22በግብዣው ላይ እየተደሰቱ ሳለ፣ ጥቂት
የከተማዪቱ ወስላቶች ቤቱን ከበቡ፤ በሩ
ንም እየደበደቡ፣ “ዝሙት እንድንፈጽም
በት ቤትህ የገባውን ሰው አውጣው” በማ
ለት የቤቱ ባለቤት በሆነው ሽማግሌ ላይ
ጮኹበት።
23የቤቱም ባለቤት ወደ ውጭ ወጥቶ
እንዲህ አላቸው፤ “የለም ወዳጆቼ፤ እንዲህ
አትሁኑ፤ ሰውየው እንግዳዬ ስለ ሆነ ይህን
አሳፋሪ ድርጊት አትፈጽሙ። 24እነሆ
ድንግል የሆነች ልጄና የሰውየው ቍባት
አሉ፤ እነርሱን አሁኑኑ ላውጣላችሁና
አስነውሯቸው፤ ያሻችሁንም አድርጉባቸው፤
በዚህ ሰው ላይ ግን እንዲህ ያለውን አሳፋሪ
ድርጊት አትፈጽሙበት።”
25ሆኖም ሰዎቹ ሊሰሙት አልፈለጉም፤
ስለዚህ ሌዋዊው ቁባቱን ወደ ውጭ
አወጣላቸው፤ ሰዎቹም አመነዘሩባት፤ ሌሊቱን
ሙሉ ሲፈራረቁባት አድረው ጎሕ ሲቀድ
ለቀቋት። 26በነጋም ጊዜ ሴቲቱ ጌታዋ
ወዳለበት ቤት ተመልሳ ሄደች። ደጃፉ
ላይ ወድቃ ፀሓይ እስክትወጣ ድረስ እዚ

19፥1 ቀኁ16፡ 18፤ሩት1፥1
19፥4 ቀኁ6፡8፤ ዘፀ32፥6
19፥5 ቀኁ8፤ ዘፍ18፥5
19፥6 መሳ16፥25
19፥10 ዘፍ10፥16፤ ኢሱ15፥8
19፥11 ዘፍ10፥16፤ ኢሱ3፥10
19፥13 ኢሱ18፥25
19፥14 ኢሱ 15፥57፤ 1ሳሙ 10፥29
19፥15 ዘፍ19፥2፤ 24፥23
19፥16 ቀኁ1፤ መዝ104፥23
19፥17 ዘፍ29፥4
19፥18 መሳ18፥31
19፥19 ዘፍ14፥18፤ 24፥25፤42፥27
19፥21 ዘፍ24፥32-33፤ ሉቃ7፥44
19፥22 ዘፍ19፥4-5፤ ዘዳ13፥13፤መሳ16፥25፤ 20፥5፤ ሮሜ1፥26-27
19፥23 ዘፍ19፥6፤ 34፥7፤ዘሌ19፥29፤ ኢሱ7፥15፤ መሳ20፥6፤ሮሜ1፥27
19፥24 ዘፍ19፥8
19፥25 መሳ20፥5፤ 1ሳሙ31፥4

ያው ተዘረረች።
27ጌታዋ በጠዋት ተነሥቶ በሩን በመ
ክፈት መንገዱን ለመቀጠል ሲወጣ፣ ቁባቱ
እጅዋን ከደጃፉ መድረክ ላይ እንደ
ዘረጋች ከቤቱ በራፍ ላይ ተዘርራ ወድቃ
አገኛት። 28ሌዋዊውም፣ “በዪ ተነሺና እን
ሂድ” አላት፤ ነገር ግን መልስ አልነበረም።
ከዚያም በአህያው ላይ ከጫናት በኋላ ወደ
ቤቱ ጒዞውን ቀጠለ።
29ቤቱ እንደ ደረሰም ቢላዋ አንሥቶ
ቁባቱን ዐሥራ ሁለት ቦታ በመቈራረጥ
ወደ እስራኤል ምድር ሁሉ ሰደደ።
30ያየም ሁሉ፣ “እስራኤላውያን ከግብፅ
ከወጡ ጀምሮ እንዲህ ያለ ነገር ከቶ አል
ታየም፤ አልተደረገም፤ ምን ማድረግ
እንዳለብንም በነገሩ አስቡበት፤ ተመካከሩ
በት” ተባባሉ።

## እስራኤላውያን ከብንያማውያን ጋር ተዋጉ

20 ከዚያም ከዳን እስከ ቤርሳቤህ
ያሉ እንዲሁም በገለዓድ ምድር
የሚገኙ እስራኤላውያን ሁሉ እንደ አንድ
ሰው ሆነው ወጡ፤ በምጽጳም *በእግዚአብሔር*
*ፊት* ተሰበሰቡ። 2የእስራኤል ሕዝብ ነገ
ዶች ሁሉ ቍጥራቸው አራት መቶ ሺህ
በሚሆን፣ ሰይፍ በሚመዙ እግረኞች
ወታደሮች በሆኑ *በእግዚአብሔር* ሕዝብ
ጉባኤ መካከል ተገኙ። 3በዚህ ጊዜ ብንያ
ማውያን፣ እስራኤላውያን ወደ ምጽጳ መው
ጣታቸውን ሰሙ፤ ከዚያም እስራኤላውያን፣
“ይህ ክፉ ድርጊት እንዴት እንደ ተፈጸመ
እስቲ ንገሩን” ተባባሉ።
4ስለዚህ የተገደለችው ሴት ባል ሌዋዊ
እንዲህ ሲል መለሰ፤ “እኔና ቍባቴ በዚያ
ለማደር በብንያም ወደምትገኘው ወደ ጊብዓ
መጣን። 5የጊብዓም ሰዎች በሌሊት ሊገ
ድሉኝ ያደርኩበትን ቤት ከበቡት፤ ከዚ
ያም በቁባቴ ላይ ስለ አመነዘሩባት
ሞተች። 6የቁባቴንም ሬሳ ከቈራረጥሁ በኋላ
እያንዳንዱን ቍራጭ፣ እያንዳንዱ የእስራ
ኤል ርስት ወዳለበት አገር ሰደድሁ፤ ይህን
ያደረግሁትም ሰዎቹ በእስራኤል ዘንድ አሠ
ቃቂና አስነዋሪ ድርጊት ስለፈጸሙ ነው።
7አሁንም እናንተ እስራኤላውያን ሁሉ
በጒዳዩ ላይ ተወያዩበት፤ ፍርዳችሁንም
ስጡ።”
8ከዚያም ሕዝቡ እንደ አንድ ሰው
ሆነው በመነሣት እንዲህ አሉ፤ “ከእኛ
ማንም ሰው ወደ ድንኳኑ አይሄድም፤
ማንኛችንም ወደ ቤታችን አንመለስም።
9ነገር ግን በጊብዓ ላይ የምናደርገው ይህ
ነው፤ በዕጣው መሠረት እንዘምትበታለን።
10ከመላው የእስራኤል ነገዶችም ለሰራዊቱ
ስንቅ እንዲይዙ፣ ከመቶው ዐሥር፣ ከሺው
አንድ መቶ፣ ከዐሥር ሺው ደግሞ አንድ
ሺህ ሰው እንወስዳለን። ከዚያም ሰራዊቱ
በብንያም ወደምትገኘው ጊብዓ
በሚደርስበት ጊዜ፣ ነዋሪዎችዋ በእስራኤል
ላይ ለፈጸሙት አስነዋሪ ድርጊት ተገቢ
ውን ቅጣት ይሰጣቸዋል።” 11ስለዚህ
የእስራኤል ሰዎች ሁሉ እንደ አንድ ሰው
ሆነው በመተባበር በከተማዪቱ ላይ ዘመቱባት።
12የእስራኤል ነገዶች ለመላው የብጠ
ንያም ነገድ እንዲህ በማለት መልእክተ
ኞች ላኩ፣ “በመካከላችሁ የተፈጸመው ይህ
ክፉ ድርጊት ምንድነው? 13አሁንም እነርሱን
ገድለን ይህን ክፉ ድርጊት ከእስራኤል
እንድናስወግድ፣ እነዚያን የጊብዓን ወስላ
ቶች አሳልፋችሁ ስጡን።”
ብንያማውያን ግን ወገኖቻቸውን እስራኤላው
ያንን አልሰሟቸውም ነበር፤ 14ስለዚህ እስራ
ኤላውያንን ለመውጋት ከየከተሞቻቸው
በአንድነት ወደ ጊብዓ መጡ። 15ብንያማው
ያንም ከመላው የጊብዓ ነዋሪዎች መካከል
ከተመረጡት ሰባት መቶ ሰዎች ሌላ፣
ሰይፍ የታጠቁ ሃያ ስድስት ሺህ ሰዎች
በአንድ አፍታ ከየከተሞቻቸው በተጨማሪ
አሰባሰቡ። 16በእነዚህም ሁሉ መካከል
እያንዳንዳቸው ድንጋይ ወንጭፈው ጠጕር
እንኳ የማይስቱ ሰባት መቶ ምርጥ ግራ
ኞች ነበሩ።
17እስራኤላውያን፣ ብንያማውያንን ሳይ
ጨምር፣ ሰይፍ የታጠቁ አራት መቶ ሺህ
ተዋጊዎች አሰባሰቡ ።
18እስራኤላውያን ወደ ቤቴል″ ወጡ፤
*እግዚአብሔርንም*፣ “ብንያማውያንን ለመውጋት
ከመካከላችን ማን ቀድሞ ይውጣ?” ሲሉ
ጠየቁ።
*እግዚአብሔርም*፣ “ይሁዳ ቀድሞ ይውጣ”
ብሎ መለሰ።
19በማግሥቱ ጧት እስራኤላዋያን ተነሥተው
በጊብዓ አጠገብ ሰፈሩ፤ 20የእስራኤል ሰዎች
ብንያማውያንን ለመውጋት ሄዱ፤ በጊብዓ
ለሚያደርጉትም ውጊያ ቦታ ቦታቸውን ያዙ።
21ብንያማውያን ከጊብዓ ወጡ፤ በዚያችም
ዕለት ከእስራኤላውያን ሃያ ሁለት ሺህ
ሰዎች ገደሉ። 22ይሁን እንጂ እስራኤላውያን
እርስ በርሳቸው ተበረታትተው በመጀመሪያው
ቀን ተሰልፈው በነበረበት ስፍራ ላይ
እንደገና ቦታ ቦታቸውን ያዙ። 23እስራ
ኤላውያን ወጥተው እስኪመሽ ድረስ *በእግዚ*
*አብሔር ፊት* አለቀሱ፤ “ወንድሞቻችንን
ብንያማውያንን ለመግጠም እንደገና እንው

19፥29 ዘፍ22፥6፤ መሳ20፥6፤ 1ሳሙ11፥7
19፥30 መሳ20፥7፤ ምሳ13፥10፤ ሆሴ9፥9
20፥1 ቍ11፤ ዘፍ21፥14፤ ኢ.ሱ11፥3፤ መሳ21፥5፤1ሳሙ3፥20፤ 7፥5፤ 11፥7፤ 2ሳሙ3፥10፤17፥11፤ 24፥15፤1ነገ4፥25፤ 2ዜና30፥5
20፥2 1ሳሙ11፥8
20፥4 ዘፍ24፥23፤ ኢ.ሱ15፥57
20፥5 መሳ19፥22፡ 25-26
20፥6 መሳ19፥23፡ 29፤2ሳሙ13፥12
20፥7 መሳ19፥30
20፥9 ዘሌ16፥8
20፥11 ቍ1
20፥12 ዘዳ13፥14
20፥13 ዘዳ13፥5፡13፤ 1ቆሮ5፥13
20፥16 መሳ3፥15
20፥18 ቍ23፡28፤ ዘፍ49፥10፤ ኢ.ሱ12፥9፤መሳ1፥1፤ 18፥5፡31
20፥23 ቍ18፤ ዘኍ14፥1፤ ኢ.ሱ7፥6፤መሳ18፥5

ጣን?” ብለው እግዚአብሔርን ጠየቁ።
እግዚአብሔርም፣ “አዎን፤ ውጡና
ግጠሟቸው” ብሎ መለሰላቸው።
24በሁለተኛው ቀን እስራኤላውያን ወደ
ብንያማውያን ተጠጉ። 25በዚሁ ጊዜም
ብንያማውያን፣ እስራኤላውያንን ሊወጉ
ከጊብዓ ወጡ፤ እንደገናም በሙሉ ሰይፍ
የታጠቁ ዐሥራ ስምንት ሺህ ሰዎች
ገደሉ።
26የእስራኤልም ሕዝብ ሁሉ ወደ ቤቴል
ወጡ፤ እዚያም እያለቀሱ በእግዚአብሔር
ፊት ተቀመጡ፤ በዚያን ቀን እስኪመሽ ድረስ
ጾሙ፤ በእግዚአብሔር ፊት የሚቃጠል
መሥዋትና የኅብረት መሥዋዕት[ዠ]
አቀረቡ። 27እስራኤላውያንም የእግዚአብሐ
ሔርን ፈቃድ ጠየቁ፤ በዚያን ጊዜ የእግዚ
አብሔር የኪዳኑ ታቦት እዚያው ነበር፤
28የአሮን ልጅ፤ የአልዓዛር ልጅ ፊንሐስም
በፊቱ ይቆም ነበር። እስራኤላውያንም፣
“ወንድ ሞቻችንን ብንያማውያንን እንደ
ገና ሄደን ጦርነት እንግጠማቸው ወይስ
ይቅር?” ሲሉ ጠየቁ።
እግዚአብሔርም፣ “ሂዱ፤ በነገው ዕለት
በእጃችሁ እሳልፌ እሰጣችኋለሁ” አላቸው።
29ከዚያም እስራኤላውያን በጊብዓ
ዙሪያ ድብቅ ጦር አኖሩ። 30በሦስተኛውም
ቀን ብንያማውያንን ለመውጋት ወጡ፤
ከዚህ በፊት እንዳደረጉት ሁሉ ጊብዓን ለመ
ውጋት ቦታ ቦታቸውን ያዙ። 31ብንያ
ማውያንም ሊገጥሟቸው ወጡ፤ ከከተማዪ
ቱም ርቀው እንዲሄዱ ተደረጉ፤ እንደ
በፊቱም እስራኤላውያንን ይገድሉ ጀመር።
ከዚህ የተነሣም በሜዳው እንዲሁም ወደ
ቤቴልና ወደ ጊብዓ በሚወስደው መንገዶች
ላይ ሠላሳ ያህል ሰዎች ወድቀው ነበር።
32ብንያማውያኑ፣ “እንደ በፊቱ ይኸው
ድል እያደረግናቸው ነው” አሉ፣ እስራኤላው
ያንም በበኩላቸው፣ “ወደ ኋላ እያፈገፈ
ግን ከከተማዪቱ ወደ መንገዶቹ እንዲርቁ
እናድርጋቸው” ይሉ ነበር።
33የእስራኤል ሰዎች በሙሉ ከነበሩበት
ቦታ አፈግፍገው በበኣልታማር ስፍራ ስፍ
ራቸውን ያዙ። ሽምቆ ይጠባበቅ የነበረው
የእስራኤል ጦር ደግሞ ካደፈጠበት ከጊ
ብዓ በስተ ምዕራብ[የ] ካለው ቦታ ወጣ።
34ከዚያም ከመላው እስራኤል የተውጣ
ጣው ዐሥር ሺህ ጦር በጊብዓ ላይ ፊት
ለፊት አደጋ ጣለ። ውጊያው ከመበርታቱ
የተነሣም፣ ብንያማውያን መጥፊያቸው
እየቀረበ መምጣቱን ገና አላወቁም ነበር።
35እግዚአብሔር ብንያምን በእስራኤል
ፊት መታው፤ በዚያችም ዕለት እስራ
ኤላውያን በሙሉ ሰይፍ የታጠቁ ሃያ
አምስት ሺህ አንድ መቶ ብንያማውያንን
ገደሉ። 36ከዚህ የተነሣ ብንያማውያን ድል
መሆናቸውን ተረዱ።
በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን ጊብዓ ላይ
ባኖሩት ድብቅ ጦር ስለ ተማመኑ የተሸነፉ
በመምሰል ለብንያማውያን ቦታ ለቀቁ።
37ከዚያም ሽምቀው የነበሩት ሰዎች በድ
ንገት እየተወረወሩ ወደ ጊብዓ ገቡ፤ በየቦ
ታው ተሰራጭተውም መላዪቱን ከተማ
በሰይፍ መቱ። 38የእስራኤል ሰዎች ያሸመ
ቀው ጦር በከተማዪቱ ውስጥ ከባድ የጢስ
ደመና ምልክት እንዲያሳዩ ተስማሙ፤
39እስራኤላውያንም ወዲያውኑ እንዲያፈገ
ፍጉ ነበር።
ብንያማውያንን ማጥቃት እንደ ጀመሩ
፣ሠላሳ እስራኤላውያንን ስለ ገደሉ፣
“እንደ መጀመሪያው የጦርነት ጊዜ
እያሸነፍና ቸው ነው” አሉ። 40ነገር
ግን የጢሱ
ዐምድ ከከተማዪቱ መሦት በጀመረ ጊዜ፣
ብንያማውያን ወደ ኋላቸው ዞረው የመላ
ዪቱ ከተማ ጢስ ወደ ሰማይ ሲወጣ አዩ።
41ከዚያም እስራኤላውያን ዞረው አጠ
ቋቸው፤ በዚህ ጊዜ ብንያማውያን ጥፋት
እንደ ደረሰባቸው ስላ ወቁ እጅግ ደነገጡ።
42ስለዚህም ጀርባቸውን አዙረው ከእስራ
ኤላውያን ፊት ወደ ምድረ በዳው ሸሹ፤
ሆኖም ከጦርነት ማምለጥ አልቻሉም፤
ከየከተሞቹ የወጡ እስራኤላውያንም በዚ
ያው ገደሏቸው። 43ብንያማውያንንም ከበ
ቧቸው፤ አሳደዷቸው፤ ከጊብዓ በስተ ምሥ
ራቅ ትይዩ ባለውም ስፍራ በቀላሉ[ደ] አሸ
ነፏቸው፤ 44በጦርነቱም ላይ ዐሥራ ስምንት
ሺህ ብንያማውያን ወደቁ፤ ሁሉም ምርጥ
ተዋጊዎች ነበሩ። 45ብንያማውያን ጀርባ
ቸውን አዙረው በምድረ በዳው በኩል
ወደ ሬሞን ዐለት በሚሸሹበት ጊዜ፣ እስ
ራኤላውያን በመንገድ ላይ አምስት ሺህ ሰው
ገደሉባቸው፤ እስከ ጊድአምም ድረስ ተከ
ታትለው ሁለት ሺህ ሰዎች በተጨማሪ ገደሉ።
46በዚያች ዕለት ሰይፍ የታጠቁ ሃያ
አምስት ሺህ ብንያማውያን በጦር ሜዳ
ወደቁ፤ ሁሉም ምርጥ ተዋጊዎች ነበሩ።
47ነገር ግን ስድስት መቶ ሰዎች ጀርባ
ቸውን አዙረው በምድረ በዳው ውስጥ
ወዳለው ወደ ሬሞን ዐለት ሸሹ፤ በዚ
ያም አራት ወር ተቀመጡ። 48ከዚያም
እስራኤላውያን ወደ ብንያም ምድር
ተመልሰው

20፥25 ቊ21
20፥26 ዘፀ32፥6፤ ዘሌ1፥3፤ዘኊ14፥1፤መሳ21፥4፤ 2ሳሙ12፥21
20፥27 ዘኊ10፥33፤ መሳ18፥5
20፥28 ዘኊ25፥7፤ ዘዳ18፥5፤ ኢሱ2፥24
20፥29 ኢሱ8፥2
20፥31 ኢሱ8፥16፤ 16፥1
20፥32 ቊ39
20፥33 ኢሱ8፥19
20፥34 ቊ41፤ ኢሱ8፥14
20፥35 1ሳሙ9፥21
20፥36 ኢሱ8፥2፡ 15
20፥37 ኢሱ8፥19
20፥38 ኢሱ8፥4-8፡ 20
20፥39 ቊ32፤ መዝ78፥9
20፥40 ኢሱ8፥20
20፥41 ቊ34፤ ኢሱ8፥21
20፥44 1ሳሙ10፥26፤ መዝ76፥5
20፥45 ኢሱ15፥32
20፥46 1ሳሙ9፥21
20፥48 መሳ21፥23

[ዠ]26 በትውፊት የሰላም መስዋዕት ይባላል።
[የ]33. አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች ቩልጌት ከዚህ ጋር ይስማማሉ ነገር ግን የዕብራይስጡ ቃል ትርጒም በትክክል አይታወቅም።
[ደ]43. የዕብርይስጡ ቃል ትርጒም በትክክል አይታወቅም።

ከተሞቻቸውን በሙሉ እንዲሁም እንስሳቱ
ንና በዚያ ያገኙትን ሁሉ በሰይፍ መቱ፤
በመንገዳቸው ያገኙትን ከተማ ሁሉ በእ
ሳት አቃጠሉ።

## ለብንያማውያን ሚስት ስለ ማግኘት

21 እስራኤላውያን በምጽጳ፣ "ከእኛ አን
ድም ሰው ሴት ልጁን ቢጋብቻ
ለብንያማውያን መዳር የለበትም" በማለት
ተማምለው ነበር።
2ሕዝቡ ወደ ቤቴል[፳] ሄደው በዚያም
እስከ ማታ ድረስ *በእግዚአብሔር* ፊት ተቀ
መጡ፤ ድምፃቸውንም ከፍ በማድረግ
አምርረው አለቀሱ፤ 3እንዲህም አሉ፤ "የእ
ስራኤል *አምላክ እግዚአብሔር* ሆይ፤ ይህ
ለምን በእስራኤል ላይ ሆነ? ዛሬ ከእስራ
ኤል አንድ ነገድ እንዴት ይታጣ?"
4በማግሥቱ ጠዋት ሕዝቡ መሠዊያ
ሠሩ፤ የሚቃጠል መሥዋዕትና የኅብረት
መሥዋዕት[፯] አቀረቡ።
5በምጽጳ፣ *በእግዚአብሔር* ጉባኤ ፊት
ያልተገኘ ማንኛውም ሰው መገደል አለ
በት ብለው እስራኤላውያን ተማምለው ስለ
ነበር፣ "ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ *በእግዚ
አብሔር* ፊት ሳይወጣ የቀረ ማን አለ?" ሲሉ
ጠየቁ።
6በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን ስለ ወንድ
ሞቻቸው ስለ ብንያማውያን በማዘን እንዲህ
አሉ፤ "ዛሬ ከእስራኤል ነገዶች አንዱ ታጥ
ቷል፤ 7ሴቶች ልጆቻችንን ለእነዚህ ብንያ
ማውያን በጋብቻ ላንሰጥ *በእግዚአብሔር* ስለ
ማልን ለተረፉት እንዴት ሚስት ልናገኝላ
ቸው እንችላለን?" 8ከዚያም፣ "ከእስራኤል
ነገዶች ምጽጳ ላይ *በእግዚአብሔር* ጉባኤ
ፊት ሳይወጣ የቀረ ማን ነው" ሲሉ ጠየቀ
ሉ፤ ታዲያ ከኢያብስ ገለዓድ አንድም ሰው
ለጉባኤው ወደ ሰፈሩ አለመምጣቱን ተረዱ፤
9ሕዝቡን ሲቈጥሩም ከኢያቢስ ገለዓድ
ሰዎች አንድም ሰው አልነበረምና።
10ስለዚህ ዐሥራ ሁለት ሺህ ተዋጊዎች
ወደ ኢያቢስ ገለዓድ ሄደው በእዚያ የሚኖሩ
ትን በሙሉ ሴቶቹንና ሕፃናቱን ጭምር
በሰይፍ እንዲፈጁቸው ጉባኤው መመሪያ
ሰጥቶ ላካቸው። 11እነርሱም፣ "እንግዲህ የምታ
ደርጉት ይህ ነው፤ ወንዱን በሙሉ እንዲሁም
ድንግል ያልሆኑትን ሴቶች ሁሉ ግደሉ"
አሏቸው። 12በኢያቢስ ገለዓድ ከሚኖረው ሕዝብ
መካከል ወንድ ያልደረሰባቸው አራት መቶ
ደናግል አገኙ፤ በከነዓን ምድር በሴሎ
ወደሚገኘውም ሰፈር አመጧቸው።
13ከዚያም ጉባኤው በሙሉ በሬሞን
ዐለት ወዳሉት ብንያማውያን የሰላም ጥሪ
አስተላለፈ። 14ስለዚህ በዚህን ጊዜ ብንያ
ማውያን ተመለሱ፤ ከመገደል የተረፉ
ትንም የኢያቢስ ገለዓድ ሴቶች ሰጧቸው፤
ይሁን እንጂ የሴቶቹ ቍጥር ለሁሉም
የሚበቃ አልነበረም። 15*እግዚአብሔር* በእ
ስራኤል ነገዶች መካከል አስደንጋጭ ስብ
ራት ስላደረገ የእግዚአብሔር ሕዝብ
ለብንያማውያን አዘነ። 16የጉባኤውም መሪ
ዎች እንዲህ አሉ፤ "እነሆ፤ የብንያም ሴቶች
አልቀዋል፤ ታዲያ ለቀሩት ወንዶች ሚስት
የምናገኝላቸው እንዴት ነው? 17ከእስራ
ኤል ነገዶች አንዱ የሆነው እንዳይጠፋ
አሁን በሕይወት ያሉት ብንያማውያን
ወራሽ የሚሆን ዘር ሊኖራቸው ይገባል።
18'ልጁን ለብንያማዊ የሚድር ርጉም
ይሁን' ብለን እኛ እስራኤላውያን ስለ
ተማማልን እንግዲህ ልጆቻችንን ልንድርላ
ቸው አንችልም፤ 19ይሁን እንጂ ከቤቴል
በስተ ሰሜንና ከቤቴል ወደ ሴኬም
በሚወስደው መንገድ በስተ ምሥራቅ
እንዲሁም ከለቦና በስተ ደቡብ ባለችው
በሴሎ የእግዚአብሔር በዓል በየዓመቱ
ይከበራል።"
20ስለዚህም ለብንያማውያን እንዲህ ሲ
ሉ መመሪያ ሰጧቸው፤ "ሂዳችሁ በወይኑ
የአ ትክልት ስፍራ ተደበቁ፤
21አድፍጣችሁ ተጠባበቁ። የሴሎ ልጃገረዶች
ለጭፈራ ወደ ዚያ በሚወጡበት ጊዜ፣
ከወይኑ አትክ ልት ቦታ ወጥታችሁ
ከልጃገረዶቹ ለየራሳችሁ ሚስት ጥለፉ፤
ወደ ብንያምም ምድር ሂዱ።
22አባቶቻቸውም ሆኑ ወንድ ሞቻቸው
ቢቃወሙ፣ 'በጦርነት ጊዜ ለእያ
ንዳንዳቸው የሚሆኑ ሚስቶች ስላላገኘን
ነውና እነርሱን በመርዳት ምሕረት አድ
ርጉልን፤ እናንተም ደግሞ ልጆቻችሁን
ፈቅዳችሁ ያልዳራችሁ በመሆናችሁ በደለኞች
አትሆኑም' እንላቸዋለን።"
23ብንያማውያን እንደ ተባሉት አደረጉ፤
ልጃገረዶቹ በሚጨፍሩበትም ጊዜ እያንዳንዱ
ሰው አንዳንድ እየጠለፈ ሚስት እንድትሆነው
ይዞ ሄደ፤ ከዚያም ወደ ርስታቸው ተመለሱ፤
ከተሞቻቸውንም አድሰው በዚያ ኖሩ።
24በዚያን ጊዜ እስራኤላውያን ያን
ቦታ ትተው ወደየቤታቸው፣
ወደየርስታቸው፣ ወደ የጐሣቸውና
ወደየነገዳቸው ሄዱ።
25በዚያን ዘመን በእስራኤል ንጉሥ
አልነበረም፤ እያንዳንዱም ሰው መልካም
መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር።

21፥1 ቊ18፡22፤ ኢ.ሱ9፥18፤11፥3
21፥2 ቊ6፥17
21፥4 መሳ20፥26
21፥5 መሳ20፥1
21፥7 ኢ.ሱ9፥18
21፥8 1ሳሙ11፥1፤ 31፥11፤2ሳሙ2፥4፤ 21፥12፤1ዜና10፥11
21፥11 ዘኍ31፥7፡ 17-18
21፥12 ኢ.ሱ18፥1
21፥13 ዘዳ2፥26፤ ኢ.ሱ15፥32
21፥15 ቊ6
21፥17 ቊ3
21፥18 ቊ1፤ ኢ.ሱ9፥18
21፥19 ኢ.ሱ16፥1፤ 17፥7፤18፥1
21፥21 ዘፀ15፥20
21፥22 ቊ1
21፥23 ቊ21፤ ኢ.ሱ24፥28፤ መሳ20፥48
21፥25 ዘዳ12፥8

[፳]2. ወይም ወደ እግዚአብሔር ቤት ተብሎ መተርጐም ይቻላል
[፯]4. በትውፊት የሰላም መሥዋዕት ይባላል ።

# መጽሐፈ ሩት

## ኑኃሚንና ሩት

1 መሳፍንት[ሀ] በሚገዙበት ዘመን፣ በምድሪቱ
ላይ ራብ ሆነ፤ አንድ ሰው በይሁዳ
ከምትገኘው ከቤተ ልሔም ሚስቱንና ሁለ
ቱን ወንዶች ልጆቹን ይዞ፣ ለተወሰነ ጊዜ
ለመኖር ወደ ሞዓብ አገር ሄደ። 2የሰውየው
ስም አቤሜሌክ፣ የሚስቱ ኑኃሚን፣ የሁለ
ቱም ወንዶች ልጆቹ ስሞች መሐሎንና
ኬሌዎን ነበሩ። እነርሱም የይሁዳ ቤተ
ልሔም ኤፍራታውያን ሲሆኑ፣ ወደ ሞዓብ
አገር ሄደው በዚያ ኖሩ።
3የኑኃሚን ባል አቤሜሌክ ሞተ፤ ኑኃ
ሚንም፣ ከሁለት ልጆቿ ጋር ብቻዋን
ቀረች። 4ልጆቿም ዖርፋና ሩት የተባሉ
የሞዓብ ሴቶችን አገቡ፤ በዚያም ዐሥር ዓመት
ያህል ከኖሩ በኋላ፣ 5መሐሎንና ኬሌዎን
ሁለቱም ሞቱ፤ ኑኃሚንም ሁለት ልጆቿ
ንና ባሏን አጥታ ብቻዋን ቀረች።
6እርሷም በሞዓብ ሳለች እግዚአብሔር ሕዝ
ቡን እንደ ጐበኘና እህል እንደ ሰጣቸው
በሰማች ጊዜ፣ ሁለቱን ምራቶቿን ይዛ
ወደ አገሯ ለመመለስ ከዚያ ተነሣች።
7የኖረችበትን ስፍራ ትታ ከሁለቱ ምራቶቿ
ጋር ወደ ይሁዳ ምድር የሚመልሳቸውን
መንገድ ይዘው ጕዞአቸውን ቀጠሉ።
8ከዚያም ኑኃሚን ሁለቱን ምራቶቿን
እንዲህ አለቻቸው፤ "እያንዳንዳችሁ ወደ
እናቶቻችሁ ቤት ተመለሱ፤ ለሞቱ ባሎቻች
ሁና ለእኔ በጎ ነገር እንዳደረጋችሁ፣ ለእ
ናንተም እግዚአብሔር እንደዚሁ ያድ
ርግላችሁ፤ 9እያንዳንዳችሁ በምታገቡት
ባል ቤት፣ እግዚአብሔር ያሳርፋችሁ።"
ከዚያም ሳመቻቸው፤ እነርሱም ድምፃ
ቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ፤
10ቀጥለውም፣ "አይሆንም! ከአንቺ ጋር
ተመልሰን ወደ ወገኖችሽ እንሄዳለን"
አሏት።
11ኑኃሚን ግን እንዲህ አለቻቸው፤ "ልጆቼ
ሆይ፤ ወደየቤታችሁ ተመለሱ፤ ከእኔ ጋር
ለምን ትሄዳላችሁ? ባል የሚሆኗችሁ
ሌሎች ልጆች ከእንግዲህ የምወልድ
ይመስላችኋልን? 12ወደየቤታችሁ ተመለሱ
ልጆቼ፤ ሌላ ባል እንዳላገባ እጅግ
አርጅቻለሁ፤ አሁንም ተስፋ አለኝ ብል፣
ዛሬ ማታ አግብቼ ከዚያም ልጆች
ብወልድ፣ 13እስኪያድጉ ድረስ ትጠ
ብቃላችሁን? እነርሱን በመጠበቅ እስከዚያ
ሳታገቡ ትቈያላችሁን? ልጆቼ ሆይ፤ እንዲህ
አይሆንም፤ ሁኔታው ከእናንተ ይልቅ
ለእኔ እጅግ መራራ ነው፤ የእግዚአብሔር
እጅ በእኔ ላይ ወጥቶአልና።"
14እነርሱም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው
እንደ ገና አለቀሱ፤ ከዚያም ዖርፋ አማ
ቷን ስማ ተሰናበተቻት፤ ሩት ግን ልትለ
ያት ስላልፈለገች ተጠመጠመችባት።
15ኑኃሚን መልሳ፣ "እነሆ የባልሽ ወንድም
ሚስት ወደ ወገኖቿና ወደ አማልክቷ ተመል
ሳለች፤ አብረሻት ተመለሽ" አለቻት።
16ሩት ግን እንዲህ አለች፤ "ተለይቼሽ
እንድቀር ወይም እንድመለስ አትለማመጭኝ፤
ወደምትሄጂበት እሄዳለሁ፤ በምትኖሪበትም
እኖራለሁ፤ ሕዝብሽ ሕዝቤ፤ አምላክሽ
አምላኬ ይሆናል። 17በምትሞቺበት
እሞታለሁ፤ እዚ ያው እቀበራለሁ።
ከእንግዲህ ሞት ከሚ ለየን በቀር ብለይሽ
እግዚአብሔር ይፍረ ድብኝ፤ ከዚህም የከፋ
ያድርግብኝ።" 18ሩት አብራት ለመሄድ
መቍረጧን በተረዳች ጊዜ፣ ኑኃሚን
መጐትጐቷን ተወች።
19ከዚያም ሁለቱ ሴቶች እስከ ቤተ ልሔም
ድረስ ተጓዙ፤ ቤተ ልሔም እንደ ደረሱም፣
በእነርሱ ምክንያት ከተማው በሙሉ ተተረ
ማመሰ፤ ሴቶቹም፣ "ይህች ኑኃሚን ናትን?"
በማለት ተገረሙ።
20እርሷም እንዲህ አለች፤ "ሁሉን የሚችል
አምላክ[ለ] ሕይወቴን እጅግ መራራ አድርጎ
ታልና ማራ[ሐ] በሉኝ እንጂ፣ ኑኃሚን[መ] ብላችሁ
አትጥሩኝ። 21በሙላት ወጣሁ፤ ነገር ግን
እግዚአብሔር ባዶዬን መለሰኝ፤ እግዚአብሔር
አስጨንቆኝ[ሠ]፣ ሁሉን የሚችል አምላክ መከ
ራ አምጥቶብኝ ሳለ እንዴት ኑኃሚን
ብላችሁ ትጠሩኛላችሁ?" አለቻቸው።
22ስለዚህ ኑኃሚን ከምራቷ ከሞዓባዊቷ ሩት
ጋር በመሆን ከሞዓብ ተመለሰች፤ ቤተልሔም
የደረሱትም የገብስ አዝመራ በሚሰበሰብበት
ወቅት መጀመሪያ ላይ ነበር።

## ሩት በቦዔዝ ዕርሻ

2 ኑኃሚን፤ ከአቤሜሌክ ጐሣ የሆነ ቦዔዝ
የሚባል ባለጸጋ የባል ዘመድ ነበራት።
2ሞዓባዊቷ ሩትም ኑኃሚንን፣ "በፊቱ ሞገስ
አገኝቼ ቃርሚያ የሚያስቃርመኝ ሰው ባገኝ
እስቲ ወደ እህል አዝመራው ልሂድ" አለቻት።

[ሀ]1 በትውፊት *ፈራጆች* ተብሎአል።
[ለ]20 በዚህና በቍጥር 21 ላይ ዕብራይስጡ፣ *ሻዳይ* ይላል።
[ሐ]20 *ማራ* ማለት *መራራ* ማለት ነው። [መ]20 በዚህና በቍጥር 21 ላይ፣ *ኑኃሚን* ማለት *ደስተኛ* ማለት ነው። [ሠ]21 ወይም *እግዚአብሔር ፈተነኝ*

1፥1 ዘፍ12፥10፤ 35፥19፤36፥35፤ 47፥4፤መሳ2፥16-18፤ 2ነገ6፥25፤ መዝ105፥16፤ሐጌ1፥11
1፥2 ቍ3፡5፤ ዘፍ35፥16፡19፤ ሩት2፥1፤4፥3፤ 1ሳሙ16፥18
1፥4 ቍ14፤ ሩት4፥13፤1ነገ11፥1፤ 2ዜና24፥26፤ዕዝ9፥2፤ ነህ13፥23፤ማቴ1፥5
1፥5 ቍ2፡8፤ ሩት2፥11
1፥6 ዘፍ11፥31፤ 36፥35፤38፥16፤ 50፥24፤ዘፀ4፥31፤ መዝ132፥15፤ ኤር29፥10፤ሶፎ2፥7፤ ማቴ6፥11
1፥8 ቍ5፤ዘፍ19፥19፤ 38፥11፤2ጢሞ1፥16
1፥9 ዘፍ27፥27፡38፤ 29፥11፤ዘኍ25፥6፤ ሩት3፥1
1፥11 ዘፍ38፥11፤ ዘዳ25፥5
1፥13 ቍ20፤ ዘፍ38፥11፤ዘፀ1፥14፤ 15፥ 23፤መሳ2፥15፤ 1ሳሙ30፥6፤ኢዮ4፥5
1፥14 ቍ9፤ ዘፍ31፥28፤ዘዳ10፥20፤ ሩት2፥11፤3፥1፤ ሚክ7፥6
1፥15 ዘዳ25፥7፤ ኢሱ24፥14
1፥16 ዘፍ24፥58፤ ኢሱ24፥15፤ 2ነገ2፥2፤መዝ45፥10
1፥17 1ሳሙ3፥17፤ 14፥44፤20፥13፤ 25፥22፤2ሳሙ3፥9፡ 35፤15፥21፤19፥13፤ 1ነገ2፥23፤19፥2፤ 20፥10፤2ነገ6፥31
1፥18 ሐሥ21፥14
1፥19 መሳ17፥7፤ ማቴ21፥10
1፥20 ቍ13፤ ዘፍ15፥1፤17፥1፤ መዝ91፥1
1፥21 ኢዮ1፥21፤ 30፥11፤መዝ88፥7፤ ኢሳ53፥4
1፥22 ዘፍ11፥31፤ ዘፀ9፥31፤ዘሌ19፥9፤ ሩት2፥2፡6፡21፤4፥5፡ 10፤2ሳሙ21፥9
2፥1 ሩት1፥2፤3፥2፤ 4፥21፤1ሳሙ9፥1፤ 1ነገ11፥28፤ 1ዜና2፥12፤ምሳ7፥4፤ ማቴ1፥5፤ሉቃ3፥32
2፥2 ዘፍ6፥8፤18፥3፤

ዘሌ19፥9፤23፥22፤ሩት1፥22

ኑኃሚንም፣ "ልጄ ሆይ፤ ይሁን ሂጂ"
አለቻት። 3ስለዚህ እርሷም ወጣች፤ ከአ
ጫጆች ኋላ ኋላ እየተከታተለችም ከአዝ
መራው ቦታ ትቃርም ጀመር፤ እንዲጋጣሚ
ትቃርምበት የነበረው አዝመራ ከአቤሜ
ሌክ ጐሣ የሆነው የቦዔዝ ነበር።
4በዚሁ ጊዜ ቦዔዝ ከቤተ ልሔም መጣ፤
አጫጆቹንም፣ "*እግዚአብሔር* ከእናንተ ጋር
ይሁን" ብሎ ሰላምታ ሰጣቸው።
እነርሱም፣ "*እግዚአብሔር ይባርክህ*" ብለው
መለሱለት።
5ከዚያም ቦዔዝ የአጫጆቹን አለቃ፣ "ይህች
ወጣት ሴት የማን ናት?" ሲል ጠየቀው።
6የአጫጆቹም አለቃ እንዲህ ሲል መለሰ፤
"ከኑኃሚን ጋር ከሞዓብ ምድር ተመልሳ
የመጣች ሞዓባዊት ናት። 7እርሷም፣ 'አጫጆቹን
እየተከተልሁ በነዶው መካከል እንድቃርም
እባክህ ፍቀድልኝ' አለችኝ። ለጥቂት ጊዜ
በመጠለያው ከማረፏ በስተቀር፣ ወደ አዝ
መራው ቦታ ገብታ ከጥዋት አንሥቶ እስ
ካሁን ያለማቋረጥ ስትቃርም ቈይታለች።"
8ስለዚህም ቦዔዝ ሩትን፣ "ልጄ ሆይ ስሚኝ፤
ከእንግዲህ ወደ ሌላ አዝመራ ሄደሽ አት
ቃርሚ፤ ከዚህም አትራቂ፤ ከሴቶች ልጆቼ
ጋር እዚሁ ሁኚ። 9ወንዶቹ የሚያጭዱበ
ትን ዕርሻ ልብ እያልሽ ልጃገረዶቹን ተከተዪ፤
ወንዶቹ እንዳያስቸግሩሽም አስጠንቅቄአ
ቸዋለሁ፤ ውሃ ሲጠማሽ ደግሞ፣ እየሄድሽ
ወንዶቹ ሞልተው ካስቀመጡት እንስራ
ቀድተሽ ጠጪ።"
10በዚህ ጊዜ ወደ መሬት ዝቅ ብላ እጅ
ነሣችው። እርሷም፣ "ባይተዋር የሆንሁትን
እኔን ታስበኝ ዘንድ በፊትህ ሞገስ ለማግ
ኘት የበቃሁት እንዴት ነው?" አለችው።
11ቦዔዝም መልሶ እንዲህ አላት፤ "ባልሽ
ከሞተ ጀምሮ ለዐማትሽ ያደረግሽላትን ሁሉ፣
አባት እናትሽን እንዲሁም የተወለድሽበትን
አገር ትተሽ ቀድሞ ከማታውቂው ሕዝብ
ጋር ለመኖር እንዴት እንደመጣሽ ነግረውኛል።
12ስላደረግሽው ሁሉ *እግዚአብሔር* ዋጋሽን
ይክፈልሽ፤ በክንፉ ጥላ ሥር ለመጠለል
የመ ጣሽበት የእስራኤል አምላክ *እግዚ
አብሔር* ብድራትሽን አትረፍርፎ
ይመልስልሽ።
13እርሷም መልሳ፣ "ጌታዬ ሆይ፤ ምንም
እንኳ፣ ከሴት ሠራተኞችህ እንደ አንዲቱ
መቈጠር የማይገባኝ ብሆንም፣ እንድጽናና
አድርገኸኛል፤ እንዲሁም እኔን አገልጋይህን
በመልካም ንግግር ደስ አሰኝተኸኛል፤ ስለዚህ
ሞገስህ እንዳይለየኝ እለምንሃለሁ"
አለችው።
14በምሳ ሰዓት ቦዔዝ፣ "ወደዚህ ቀረብ
በዪ፤ እንጀራም ወስደሽ በወይን ሆምጣጤው

2፥3 ቀኍ1፥14፤ 2ነገ4፥18፤ኤር9፥22፤ አሞ9፥13
2፥4 ዘፍ28፥3፤ ዘኍ6፥24፤መሳ6፥12፤ ሉቃ1፥28፤2ተሰ3፥16
2፥6 ሩት1፥22
2፥7 ዘፍ37፥7፤ ዘሌ19፥9፤2ሳሙ4፥5
2፥10 ቀኍ19፤ ዘፍ19፥1፤31፥15፤ ዘዳ15፥3፤1ሳሙ20፥41
2፥11 ሩት1፥5፤14፡ 16-17፤ኢሳ55፥5
2፥12 ኢሱ24፥15፤ 1ሳሙ24፥19፤ 26፥23፤25፤ መዝ17፥8፤18፥20፤ 36፥7፤57፥1፤61፥4፤ 63፥7፤71፥1፤91፥4፤ምሳ 25፥22፤ኤር31፥16
2፥13 ዘፍ18፥3
2፥14 ቀኍ3፥18፤ ዘፍ3፥19፤ዘሌ23፥14
2፥15 ዘፍ37፥7፤ ዘሌ19፥9
2፥16 ዘፍ37፥10
2፥17 ዘሌ19፥36፤ መሳ6፥11
2፥18 ቀኍ14
2፥19 ቀኍ10
2፥20 ዘፍ11፥31፤ 19፥19፤ዘሌ25፥25፤ መሳ17፥2፤ሩት3፥9፡ 12፤4፥1፤14፤ 1ሳሙ23፥21
2፥21 ሩት1፥22
2፥23 ዘፍ30፥14፤ ዘፀ9፥31፤1ሳሙ6፥13
3፥1 ሩት1፥9፤14
3፥2 ዘሌ2፥14፤ ዘኍ18፥27፤ መሳ6፥11፤ሩት2፥1

አጥቅሽ" አላት።
እርሷም ከአጫጆች አጠገብ እንደ ተቀ
መጠች፣ ቦዔዝ የተጠበሰ እሸት ሰጣት፤
የቻለችውንም ያህል በልታ ጥቂት
ተረፋት። 15ለመቃረም ስትነሣም፣ ቦዔዝ
ጐበዛዝቱን እንዲህ ብሎ አዘዛቸው፤
"በነዶው መካከል እንኳ ብትቃርም ክፉ
አትናገሯት፤ 16ይልቁንም ከየታሰረው ነዶ
ላይ ጥቂት ጥቂቱን ዘለላ እየመዘዛችሁ
በመጣል እንድታነሣው ተዉላት፤
አታስቀይሚት።"
17ስለዚህ ሩት እስኪመሽ ድረስ ከአዝመ
ራው ላይ ቃረመች፤ ከዚያም የሰበሰበችውን
ገብስ ወቃች፤ አንድ የኢፍ መስፈሪያም[ረ]
ያህል ሆነ። 18ያንንም ይዛ ወደ ከተማ
ሄደች፤ አማቷም የሰበሰበችው ምን ያህል
እንደ ሆነም አየች፤ እንዲሁም ሩት የሚበ
ቃትን ያህል ከበላች በኋላ አስተርፋ የነበ
ረውን አውጥታ ለእርሷ ሰጠቻት።
19አማቷም፣ "ዛሬ የቃረምሽው ከየት ነው?
የትስ ቦታ ስትሠሪ ዋልሽ? መልካም ነገር
ያደረገልሽ ሰው የተባረከ ይሁን" አለቻት።
ከዚያም ሩት ስትሠራ ስለዋለችበት ስፍ
ራ ባለቤት ለአማቷ ነገረቻት፤ እርሷም፣
"ዛሬ ስቃርም የዋልሁበት አዝመራ
ባለቤት፣ ስሙ ቦዔዝ ይባላል" አለቻት።
20ኑኃሚንም ምራቷን፣ "በጎነቱን ለሕ
ያዋንም ሆነ ለሙታን ማድረጉን ያልተወ
*እግዚአብሔር* ይባርከው" አለቻት፤ ቀጥላም፣
"ሰውየው እኮ የሥጋ ዘመዳችን ነው፤
የመቤዠት ግዴታ
ካለባቸው ዘመዶቻችን አንዱ እርሱ ነው"
አለቻት።
21ከዚያም ሞዓባዊቷ ሩት፣ "ደግሞም፣
'እህሌን ሁሉ አጭደው እስኪጨርሱ ድረስ
ከሠራተኞቼ አትለዪ! ብሎኛል" አለቻት።
22ኑኃሚንም ምራቷን ሩትን፣ "የኔ ልጅ፤
እንዲህ ካልሽማ ከሴት ሠራተኞቹ ጋር አብሮ
መሄድ ይሻልሻል፤ ወደ ሌላ ሰው አዝመራ
ብትሄጂ ጉዳት ሊያገኝሽ ይችላልና" አለቻት።
23ስለዚህ የገብሱና የስንዴው አዝመራ
ተሰብስቦ እስኪያበቃ ድረስ፣ ሩት የቦዔዝን
ሴቶች ሠራተኞች ተጠግታ ቃረመች፣ ከአ
ማቷም ጋር ኖረች።

## ቦዔዝና ሩት በእህል ዐውድማው ላይ

3 ከዚህ በኋላ አማቷ ኑኃሚን ሩትን
እንዲህ አለቻት፤ "ልጄ ሆይ፤ የሚመ
ችሽን ቤት[ሰ] እንድፈልግልሽ አይገባኝምን?
2ከሴቶች ሠራተኞቹ ጋር አብረሽ የነበር
ሽበት ቦዔዝ፣ ዘመዳችን አይደለምን? ዛሬ
ማታ በዐውድማው ላይ ገብስ ያበራያል፤

[ረ]17 22 ሊትር ያህል ነው።
[ሰ]1 *ወይም የምታርፍበትን*

3ተጣጠቢ፤ ሽቶ ተቀቢ፤ እንዲሁም የክት
ልብስሽን ልበሺ፤ ከዚያም ወደ ዐውድማው
ውረጂ፤ ይሁን እንጂ በልቶና ጠጥቶ
እስኪያበቃ ድረስ፣ እዚያ መሆንሽን እንዳ
ያውቅ ይሁን። 4በተኛም ጊዜ፣ የሚተኛ
በትን ቦታ ልብ ብለሽ እዪና ሄደሽ እግሩን
ገልጠሽ ተኚ፤ ከዚያም የምታደርጊውን ራሱ
ይነግርሻል።”

5ሩትም፣ “ያልሽውን ሁሉ አደርጋለሁ”
አለቻት። 6ስለዚህ ተነሥታ ወደ ዐውድ
ማው ወረደች፤ አማቷ አድርጊ ያለቻትንም
ሁሉ አደረገች።

7ቦዔዝ በልቶ ጠጥቶ ከጨረሰና ደስም
ከተሰኘ በኋላ፣ ራቅ ካለው የእህል ክምር
አጠገብ ለመተኛት ሄደ። ሩት በቀስታ ከአጠ
ገቡ ደረሰች፤ እግሩንም ገልጣ ተኛች።
8እኩለ ሌሊት ላይ ሰውዬውን አንዳች ነገር
አስደነ ገጠው፤ ገልበጥ ሲልም አንዲት ሴት
እግርጌው ተኝታ አገኘ።

9እርሱም፣ “አንቺ ማነሽ?” ሲል ጠየቀ።
እርሷም፣ “እኔ አገልጋይህ ሩት ነኝ፤ መቤዠት
የሚገባህ ቅርብ የሥጋ ዘመድ አንተ ነህና
ልብስህን ጣል አድርግብኝ” አለችው።

10እርሱም መልሶ እንዲህ አላት፤ “ልጄ
ሆይ፤ *እግዚአብሔር* ይባርክሽ፤ ከዚህ በፊት
ካደረግሽው ይልቅ ያሁኑ በጎነትሽ ይበልጣል፤
ባለጠጋም ሆነ ድኻ፣ ወጣት ወንድ ፈልገሽ
አልሄድሽምና። 11አሁንም ልጄ ሆይ፤ አትፍሪ፤
የምትጠይቂውን ሁሉ አደርግልሻለሁ፤
አንቺ ምግባረ መልካም ሴት መሆንሽንም
የአገሬ ሰው ሁሉ ያውቀዋል። 12ምንም እንኳ
እኔ ቅርብ የሥጋ ዘመድ መሆኔ የተረጋገጠ
ቢሆንም፣ ከእኔ ይልቅ መቤዠት የሚገባው
ቅርብ የሥጋ ዘመድ አለ። 13ከዚህ ዕደሪ፤
ሲነጋም ሰውየው ሊቤዥሽ ከፈለገ፣ መልካም
ነው ይቤዥሽ፤ የማይፈልግ ከሆነ ግን በሕያው
*እግዚአብሔር* እምላለሁ፤ እኔ እቤዥሻለሁ፤
እስኪነጋም ድረስ እዚሁ ተኚ።”

14ስለዚህም ሩት እስኪነጋ ድረስ እግርጌው
ተኛች፤ ዳሩ ግን ማንም ሰው ተለይቶ ሊታ
ወቅ በማይችልበት ሰዓት ቀደም ብላ ተነ
ሣች፤ እርሱም፣ “ሴት ወደዚህ ዐውድማ መም
ጣቷ እንዳይታወቅ” አላት።

15እንዲሁም፣ “በላይሽ የደረብሽውን ልብስ
አቅርቢልኝ፤ ዘርግተሽም ያዢው” አላት፤
ዘርግታ እንደ ያዘችም፤ ስድስት መስፈሪያ ገብስ
ሰፍሮ አሸከማት፤ ከዚያም ወደ ከተማ
ተመለሰች[ሻ]።

16ሩት ወደ አማቷ እንደ ተመለሰች፣
ኑኃሚን፣ “ልጄ ሆይ፤ የሄድሽበት ጉዳይ
እንዴት ሆነ?” ብላ ጠየቀቻት።

ሩትም ቦዔዝ ያደረገላትን ሁሉ ነገረቻት፤

3፥3 ዘፍ41፥14፤
ዘፀ32፥6፤
2ሳሙ12፥20፤14፥2፤
2ነገ5፥10፤መዝ26፥6፤
51፥2፤መክ2፥3፤
ኢሳ1፥16፤61፥3፤
ኤር4፥14፤15፥17፤
ሕዝ16፥9
3፥5 ኤፌ6፥1፤
ቈላ3፥20
3፥6 ዘኍ18፥27
3፥7 መሳ19፥6፡22፤
1ሳሙ25፥36፤
2ሳሙ13፥28፤
1ነገ21፥7፤2ዜና31፥6፤
አስ1፥10፤
ማሕ7፥2፤ኤር5፥26፤
ሐጌ2፥16
3፥9 ሩት2፥20፤
ሕዝ16፥8
3፥10 ኢሱ2፥12፤
መሳ17፥2
3፥11 ምሳ12፥4፤
14፥1፤31፥10
3፥12 ሩት2፥20፤
4፥1
3፥13 ዘኍ14፥21፤
ዘዳ25፥5፤ሩት4፥5፡6፤
ሆሴ4፥15፤ማቴ22፥24
3፥14 ዘኍ18፥27፤
ሮሜ14፥16፤
2ቆሮ8፥21
3፥15 ኢሳ3፥22
3፥18 መዝ37፥3-5
4፥1 ዘፍ18፥1፤
23፥10፤ሩት2፥20፤
3፥12
4፥2 ዘፀ3፥16፤
ዘዳ25፥7
4፥3 ዘሌ25፥25፤
ሩት1፥2
4፥4 ዘሌ25፥25፤
ኤር32፥7-8
4፥5 ዘፍ38፥8፤
ሩት1፥22፤3፥13
4፥6 ዘሌ25፥25፤
ዘዳ25፥7፤ሩት3፥13
4፥7 ቀኍ8፤
ዘሌ25፥24፤
ዘዳ25፥7-9፤
ኢሳ8፥1-2፡16፡20
4፥8 ዘዳ25፥9
4፥9 ኢሳ8፥2፤
ኤር32፥10፡44
4፥10 ዘዳ25፥5፡6፤
ኢሱ24፥22፤
ሩት1፥22

17ቀጥላም፣ “‘ወደ አማትሽ ባዶ እጅሽን
አትመለሺ’ በማለት ይህን ስድስት መስፈሪያ
ገብስ ሰጠኝ” አለቻት።

18ኑኃሚንም፣ “ልጄ ሆይ፤ የሚሆነውን
ነገር እስክታውቂ ድረስ ታገሺ፤ ጉዳዩ
ዛሬውኑ እልባት ካላገኘ ሰውየው አያርፍም”
አለቻት።

## ቦዔዝ ሩትን አገባ

4 ቦዔዝም ወደ ከተማዪቱ በር አደባ
ባይ ወጥቶ ተቀመጠ፤ እርሱም የመቤ
ዠት ቅድሚያ ያለው የቅርብ ዘመድ በመጣ
ጊዜ፣ “ወዳጄ ሆይ፤ ወደዚህ ና፣ አጠገቤም ተቀ
መጥ” አለው፤ ስለዚህም ሰውየው ሄዶ ተቀመጠ።

2ቦዔዝ ከከተማዪቱ ሽማግሌዎች ዐሥሩን
ጠርቶ፣ “እዚህ ተቀመጡ” አላቸው፤ እነር
ሱም ተቀመጡ። 3ከዚያም የመቤዠት ቅድ
ሚያ ያለውን ቅርብ የሥጋ ዘመድ እን
ዲህ አለው፤ “ከሞዓብ የተመለሰችው ኑኃሚን፣
የወንድማችንን የአቤሜሌክን ጢንጦ መሬት
ልትሸጥ ነው። 4አንተም ይህንኑ ጉዳይ ማወቅ
አለብህ ብዬ ስላሰብሁ፣ አሁን እዚህ በተቀ
መጡትና በሕዝቤም ሽማግሌዎች ፊት እን
ድትገዛው ላሳስብህ ወደድሁ፤ አሁንም ራስህ
የምትቤዠው ከሆነ ልትቤዠው ትችላለህ፤
ለዚህ ከአንተ ቅድሚያ የሚኖረው የለም፤
ይህን የማታደርግ ከሆነ ግን ከአንተ ቀጥሎ
የሚገባኝ ስለሆንሁ፣ ንገረኝና ልወቀው።” ሰው
የውም “እኔ እቤዠዋለሁ” አለ።

5ከዚያም ቦዔዝ፣ “እንግዲህ መሬቱን
ከኑኃሚንና ከሞዓባዊቷ ከሩት ላይ በም
ትገዛበት ዕለት የሟቹን ስም በርስቱ
ለማስጠራት ሚስቱንም አብረህ መውሰድ
አለብህ” አለው።

6ያም ቅርብ የሥጋ ዘመድ፣ “እንዲህ
ከሆነማ የራሴን ርስት አደጋ ላይ ልጥል
ስለምችል፣ እኔ ልቤዠው አልችልም፤
አንተው ራስህ ተቤዠው” አለው።

7በጥንት ዘመን በእስራኤል የመቤዠትም
ሆነ ንብረት የማስተላለፍ ጉዳይ የሚጸናው
አንዱ ወገን ጫማውን አውልቆ ለሌላው
ወገን ሲሰጠው ነው፤ በእስራኤል ዘንድ
መሸጥም ሆነ መግዛት ሕጋዊነት የሚኖረው
በዚህ ሁኔታ ነበር።

8ቅድሚያ ያለው ቅርብ የሥጋ ዘመድም
ቦዔዝን፣ “እንግዲህ አንተው ራስህ ግዛው”
ብሎ ጫማውን አወለቀ።

9ቦዔዝም ለሽማግሌዎቹና ለሕዝቡ ሁሉ
እንዲህ አለ፤ “የአቤሜሌክን፣ የኬሌዎንንና
የመሐሎንን ንብረት በሙሉ ከኑኃሚን ላይ
ለመግዛቴ፣ በዛሬው ዕለት እናንተ ምስክሮች

[ሻ]15 አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ ቩልጌትና ሱርስተ ከዚ
ህ ጋር ይስማማሉ፤ አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን
ይነገረኝና ይላሉ።

ናችሁ፤ 10እንዲሁም የሚቱ ስም ከወንድ
ሞቹ መካከልና ከአገሩ ደጅ እንዳይጠፋ፣
የሚቱን ስም በርስቱ ላይ ለማስጠራት
የመሐሎን ሚስት የነበረችው ሞዓባዊት ሩትን
አግብቼአታለሁ፤ እናንተም ዛሬ ምስክሮች
ናችሁ።”
11ከዚያም ሽማግሌዎቹና በከተማዪቱ በር
አደባባይ የነበሩት ሁሉ እንዲህ አሉ፤
“እኛ ምስክሮች ነን፤ እግዚአብሔር ይህችን
ወደ ቤትህ የምትገባውን ሴት፣ የእስራ
ኤልን ቤት በአንድነት እንደሠሩ እንደ
ራሔልና እንደልያ ያድርጋት፤ አንተም
በኤፍራታ የበ ረታህ ሁን፤ ስምህም በቤተ
ልሔም የተጠራ ይሁን። 12እግዚአብሔር
ከዚህች ወጣት ሴት በሚሰጥህ ዘር አ
ማካይነት፣ ቤተ ሰብህን ትዕማር ለይሁዳ
እንደ ወለደችው እንደ ፋሬስ ቤተሰብ
ያድርገው።”

## የዳዊት የትውልድ ሐረግ

4፥18 ተጓ ምብ - 1ዜና 2፥5-15፤ ማቴ 1፥3- 6፤ ሉቃ 3፥31- 33

13ስለዚህ ቦዔዝ ሩትን ወሰዳት፤ ሚስቱም
ሆነች። ከዚያም ወደ እርሷ ገባ፤ እግዚ
አብሔር እንድትፀንስ አደረጋት፤ ወንድ
ልጅም ወለደች። 14ሴቶቹም ኑኃሚንን እንዲህ
አሏት፤ “ዛሬ የሚቤዥ ቅርብ የሥጋ ዘመድ
ያላሳጣሽ እግዚአብሔር ይባረክ፤ በመላው
እስራኤልም ስሙ ይግነን። 15ልጁ ሕይ
ወትሽን ያድሳታል፤ በእርጅና ዘመንሽም

4፥11 ዘፍ4፥19፤ 23፥10፤29፥16፤ 35፥16፤ዘዳ25፥9፤ ሩት1፥19
4፥12 ዘፍ38፥6፡24፡ 29
4፥13 ዘፍ8፥1፤ 29፥ 31፡32፤30፥6፤ ሉቃ1፥57
4፥14 ዘፍ24፥27፤ ሩት2፥20፤ሉቃ1፥58
4፥15 ዘፍ11፥31፤ 1ሳሙ1፥8፤2፥5፤ ኢዮ1፥2
4፥17 ቀኁ22፤1ሳሙ 16፥1፡13፡18፤17፥12፡ 58፤1ዜና2፥12፡13፡ 15፤መዝ72፥20
4፥18 ዘፍ38፥29፤ ዘኁ26፥21
4፥19 ዘፀ6፥23
4፥20 ዘኁ7፥12
4፥21 ሩት2፥1

ይጦርሻል፤ የምትወድሽና ከሰባት ወንዶች
ልጆች የምትበልጥብሽ ምራትሽ ወልዳዋለችና።”
16ከዚያም ኑኃሚን ሕፃኑን ተቀብላ ታቀ
ፈችው፤ ሞግዚትም ሆነችው። 17ጎረቤቶቿ
የሆኑ ሴቶችም፣ “ለኑኃሚን ወንድ ልጅ
ተወለደላት” አሉ። ስሙንም ኢዮቤድ ብለው
ጠሩት፤ እርሱም የዳዊት አባት የሆነው
የእሴይ አባት ነበር።
18እንግዲህ የፋሬስ ቤተ ሰብ ትውልድ ይህ
ነው፦

ፋሬስ ኤስሮምን ወለደ፤
19ኤስሮምም አራምን ወለደ፤
አራምም አሚናዳብን ወለደ፤
20አሚናዳብም ነአሶንን ወለደ፤
ነአሶን ሰልሞንን[ቀ] ወለደ፤
21ሰልሞንም ቦዔዝን ወለደ፤
ቦዔዝም ኢዮቤድን ወለደ፤
22ኢዮቤድም እሴይን ወለደ፤
እሴይም ዳዊትን ወለደ።

[ቀ]20 ጥቂት የዕብራይስጥ ቅጆች፣ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናትና ቩልጌት (እንዲሁም ቍጥር 21 እና ከሰብዓ ሊቃናት 1ዜና 2፥11 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን ሳልማ ይላሉ።

# መጽሐፈ ሳሙኤል -አንደኛ

## የሳሙኤል መወለድ

1 በተራራማው በኤፍሬም አገር በአር
ማቴም መሴፋ የሚኖር ሕልቃና የተባለ
አንድ ሰው ነበረ፤ እርሱም ኤፍሬማዊ ሲሆን፣
የኤያሬምኤል ልጅ፣ የኢሊዩ ልጅ፣
የቶሑ ልጅ፣ የናሲብ ልጅ፣ ነበረ። 2እርሱም
አንዲቱ ሐና፣ ሌላዪቱ ፍናና የተባሉ ሁለት
ሚስቶች ነበሩት፤ ፍናና ልጆች ሲኖሯት፣
ሐና ግን ምንም ልጅ አልነበራትም።
3ያም ሰው ሁሉን ቻይ ለሆነው ለእግዚ
አብሔር ለመስገድና መሥዋዕት ለመሠ
ዋት በየዓመቱ ከሚኖርበት ከተማ ወደ
ሴሎ ይወጣ ነበር። በዚያም ሁለቱ የዔሊ
ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ የእግዚአብሔር
ካህናት ነበሩ። 4ሕልቃና ወደ ሴሎ ሄዶ
መሥዋዕት የሚሠዋበት ወቅት በደረሰ ጊዜ
ሁሉ፣ ለሚስቱ ለፍናና እንዲሁም ለወን
ዶችና ለሴቶች ልጆቿ ሁሉ ከሥጋው ድር
ሻቸውን ይሰጣቸው ነበር። 5ሐናን ግን ይወ
ዳት ስለ ነበር፣ ዕጥፍ ድርሻ ይሰጣት ነበር፤
ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ማሕፀኗን ዘግቶት
ነበር። 6እግዚአብሔር ማሕፀኗን ስለ ዘጋም
ጣውንቷ ታስቈጣት፣ ታበሳጫትም ነበር።
7ይህም በየዓመቱ ይደጋገም ነበር፤ ሐና ወደ
እግዚአብሔር ቤት በምትወጣበት ጊዜ
ሁሉ፣ እስክታለቅስና መብላት እስኪ
ያቅታት ድረስ ጣውንቷ ታበሳጫት ነበር።
8ባሏ ሕልቃናም እርሷን፣ "ሐና ሆይ፤ ለምን
ታለቅሻለሽ? ለምንስ አትበዪም? ልብሽስ
ለምን ያዝናል? ከዐሥር ወንዶች ልጆች
እኔ አልበልጥብሽምን?" ይላት ነበር።
9አንድ ጊዜ በሴሎ ሳሉ ከበሉና ከጠጡ
በኋላ ሐና ተነሥታ ቆመች፤ በዚያ ጊዜ
ካህኑ ዔሊ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ[ሀ]
መቃን አጠገብ በወንበር ላይ ተቀምጦ
ነበር። 10ሐናም በነፍሷ ተመርራ አብ
ዝታ በማልቀስ ወደ እግዚአብሔር ጸለ
የች። 11እንዲህም ብላ ስእለት ተሳለች፤
"የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፤ የአገ
ልጋይህን መዋረድ ተመልክተህ ብታስበ
ኝና አገልጋይህን ሳትረሳት ወንድ ልጅ
ብትሰጣት፣ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ለእ
ግዚአብሔር እሰጠዋለሁ፤ ምላጭም በራሱ
ላይ አይደርስም።"
12ሐና ባለማቋረጥ ወደ እግዚአብሔር በጸለ
የች ጊዜ፣ ዔሊ አፏን ይመለከት ነበር።
13እርሷም በልቧ ትጸልይ ስለ ነበር፤
ከንፈሯ ይንቀሳቀስ እንጂ ድምጿ አይሰ

1፥1 ኢሱ 17፥17-18፤
25፤21፤20-22
1ሳሙ 9፥5፤
1ዜና 6፥27፡34
1፥2 ዘፍ 4፥19
1፥3 ቀኍ21፤
ዘፀ23፥14፤
ዘዳ12፥5-7፤
ኢሱ18፥1፤
1ሳሙ 2፥19፤31፤
14፥3፤20፥6፡29፤
ሉቃ2፥41
1፥4 ዘፍ29፥34፤
ዘሌ7፥15-18፤
ዘዳ12፥17-18
1፥5 ዘፍ11፥30፤
29፥31፤37፥3
1፥6 ዘፍ16፥4
1፥7 2ሳሙ12፥17፤
መዝ102፥4
1፥8 ሩት4፥15
1፥9 1ሳሙ3፥3
1፥10 ኢዮ3፥20፤
7፥11፤10፥1፤21፥25፤2
3፥2፤27፥2፤ ኢ
ሳ38፥15፤ ኤር
20፥18
1፥11 ዘፍ 8፥1፤
17፥1፤ዘኍ6፥1-21፤
መሳ11፥30፤13፥5፡7፤
መዝ24፥10፤46፥7፤
ኢሳ 1፥9፤ሉቃ1፥15
1፥15 2ነገ4፥27፤
መዝ42፥4፤
62፥8፤ሰቆ2፥19
1፥16 መዝ 55፥2
1፥17ዘፍ25፥20፡21፤
ዘኍ 6፥26፤1ሳሙ
20፥42፤2ነገ5፥19፤
መዝ20፥3-5፤
ሐሥ15፥33
1፥18 ዘፍ18፥3፤
ሩት2፥13፤ሮሜ15፥13
1፥19 ዘፍ8፥1፤
29፥31፤ኢሱ18፥25
1፥20 ዘፍ17፥19፤
29፥32፤30፥6፤ ዘፀ
2፥10፤
1ሳሙ7፥5፤12፥23፤
1ዘና6፥27፤ኤር15፥1፤
ማቴ1፥21፤
ዕብ11፥32
1፥21 ቀኁ3፤
ዘፍ28፥20፤ ዘኍ
30፥2፤ ዘዳ12፥11
1፥22 ዘፀ13፥2፤
ሉቃ2፥22
1፥23 ዘፍ21፥8፤
25፥21

ማም ነበር፤ ዔሊም እንደ ሰከረች አድርጎ
ቈጠራት 14እርሱም "ስካሩ የማይለቅሽ እስከ
መቼ ድረስ ነው? የወይን ጠጅሽን ከአንቺ
አስወግጂው" አላት።
15ሐናም እንዲህ ብላ መለሰችለት፤
"ጌታዬ ሆይ፤ ሰክሬ አይደለም፤ እኔ ልቧ
ክፉኛ የታወከባት ሴት ነኝ፤ ልቤን በእግዚ
አብሔር ፊት አፈሰስሁ እንጂ፣
የወይን ጠጅም ሆነ ሌላ የሚያሰክር መጠ
ጥ አልጠጣሁም። 16ይህን ያህል ጊዜ የ
ጸለይሁት ከባድ ከሆነው ጭንቀቴና ሐ
ዘኔ የተነሣ ስለ ሆነ፣ አገልጋይህን እንደ
ምናምንቴ ሴት አትቍጠረኝ።"
17ዔሊም፣ "በሰላም ሂጂ፤ የእስራ
ኤል አምላክ የለመንሺውን ይስጥሽ" ሲ
ል መለሰላት።
18እርሷም፣ "አገልጋይህ በፊትህ ሞገስ
ታግኝ" አለች፤ ከዚያም መንገዷን ሄደች፤
ምግብም በላች፤ ከዚያም በኋላ በፊቷ
ላይ ሐዘን አልታየም።
19በማግስቱ ጠዋት ተነሥተው በእግዚ
አብሔር ፊት ሰገዱ፤ ከዚያም በራማ
ወደ ሚገኘው ቤታቸው ሄዱ። ሕልቃና
ከሚስቱ ከሐና ጋር ተኛ፤ እግዚአብሔርም
አሰባት፤ 20ስለዚህ ሐና ፀነሰች፤ የእርግዝ
ናዋ ወራት በተፈጸመ ጊዜም ወንድ ልጅ
ወለደች፤ ስሙንም፤ "ከእግዚአብሔር ለም
ኜዋለሁ" ስትል ሳሙኤል[ሰ] አለችው።

## ሐና ሳሙኤልን ለእግዚአብሔር ሰጠች

21ሰውየውም ሕልቃና ለእግዚአብሔር
ዓመታዊውን መሥዋዕት ለመሠዋት ስእለ
ቱን ለማድረስ ቤተሰቡን ሁሉ ይዞ
ወደ ሴሎ ወጣ። 22ሐና ግን
አልሄደችም፤ እርሷም ባሏን፣ "ሕፃኑ ጡት
ከተወ በኋላ፣ ወስጄ በእግዚአብሔር ፊት
አቀርበዋለሁ፤ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜም በዚያ
ይኖራል" አለችው።
23ባሏ ሕልቃናም፣ "መልካም መስሎ
የታየሽን አድርጊ፤ ጡት እስክታስጥዪው
ድረስ እዚሁ ቆዪ፤ ብቻ እግዚአብሔር ቃሉን[ሐ]
ያጽናልሽ" አላት። ስለዚህ ሐና ሕፃኑን ጡት
እስክታስጥለው ድረስ እያጠባችው በቤቷ
ተቀመጠች።

[ሀ]9 የማደሪያ ድንኳን ማለት ነው ።
[ሰ]20 በዕብራይስጡ ሳሙኤል የሚለው ቃል ድምፅ እግዚአብሔር ሰማ ከሚለው ሐረግ ጋር ይመሳሰላል።
[ሐ]23 የሙት ባሕር ጥቅል፣ የሰብዓ ሊቃናትና የሱርስቱ ትርጒም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የማሶሬቱ ቅጅ ግን ቃልሽን ይላል።

[24]ልጁ ጡት በተወ ጊዜ ከእርሱ ጋር አንድ
የሦስት ዓመት ወይፈን[ሙ]፣ አንድየኢፍ መስ
ፈሪያ[ሡ] ዱቄትና አንድ አቍማዳ የወይን ጠጅ
ወስዳ፣ በሴሎ ወዳለው ወደ *እግዚአብሔር*
ቤት አመጣችው፣ ልጁም ገና ሕፃን ነበረ።
[25]ወይፈኑን ካረዱ በኋላም ልጁን ወደ ዔሊ
አቀረቡት። [26]ሐናም ዔሊን እንዲህ አለችው፤
“ጌታዬ ሆይ፤ በነፍስህ እምላለሁ፤ እዚህ
ቦታ ላይ በአጠገብህ ቆማ ወደ *እግዚአ*
*ብሔር* ስትጸልይ የነበረች ያች ሴት እኔ ነኝ።
[27]ይህን ልጅ እንዲሰጠኝ ጸለይሁ፤ *እግዚ*
*አብሔርም* የለመንሁትን ሰጠኝ። [28]ስለዚህ
እኔም *ለእግዚአብሔር* እሰጠዋለሁ፤ በሕ
ይወት ዘመኑም ሁሉ *ለእግዚአብሔር* የተሰጠ
ይሆናል።” እርሱም በዚያ *ለእግዚአብሔር* ሰገደ።

### የሐና የምስጋና ጸሎት

2 ሐናም እንዲህ ብላ ጸለየች፤
“ልቤ *በእግዚአብሔር* ጸና፤
ቀንዴም[ሩ] *በእግዚአብሔር* ከፍ ከፍ አለ፤
አፌ በጠላቶቼ ላይ ተከፈተ፤
በማዳንህ ደስ ይለኛልና።

[2]“እንደ *እግዚአብሔር* ያለ ቅዱስ[ሰ] ማንም
የለም፤
ከአንተም በቀር ሌላ የለም፤
እንደ አምላካችን ያለ ዐለት የለም።
[3]“ይህን ያህል በመታበይ አትናገሩ፤
እንዲህ ያለውም የእብሪት ቃል
ከአፋችሁ አይውጣ፤
*እግዚአብሔር* አምላክ ዐዋቂ ነውና፤
ሥራም ሁሉ በእርሱ ይመዘናል።
[4]“የኀያላን ቀስቶች ተሰባብረዋል፤
ደካሞች ግን በኀይል ታጥቀዋል።
[5]ጠግበው የነበሩ ለእንጀራ ሲሉ ተገዙ፤
ተርበው የነበሩ ግን እንጀራ ጠገቡ፤
መካኒቱ ሰባት ልጆች ወልዳለች፤
ብዙ ወንዶች ልጆች ወልዳ የነበረችው
ግን መከነች።
[6]“*እግዚአብሔር* ይገድላል፤ ያድናልም፤
ወደ መቃብር[ሸ] ያወርዳል፤ ያወጣልም።
[7]*እግዚአብሔር* ያደኸያል፤ ያበለጽጋልም፤
ያዋርዳል፤ ከፍ ከፍም ያደርጋል።
[8]እርሱ ድኻውን ከትቢያ ያነሣል፤
ምስኪኑንም ከጕድፍ ከፍ ከፍ ያደርጋል፤
ከመኳንንቱ ጋር ያስቀምጣቸዋል፤
የክብር ዙፋንም ያወርሳቸዋል።

“የምድር መሠረቶች *የእግዚአብሔር* ናቸውና፣
ዓለምን በእነርሱ ላይ አድርጎአል።
[9]እርሱ የቅዱሳኑን እግር ይጠብቃል፤
ክፉዎች ግን በጨለማ ውስጥ ይጣላሉ፤

“ሰው በኀይሉ ድል አያደርግም፤
*[10]ከእግዚአብሔር ጋር የሚጣሉ ይደቃሉ፤*
እርሱ ከሰማይ ያንጐደጕድባቸዋል፤
*እግዚአብሔር* እስከ ምድር ዳርቻ ይፈርዳል።

“ለንጉሡ ኀይልን ይሰጣል፤
የመሲሑንም ቀንድ ከፍ ከፍ ያደርጋል።”

[11]ከዚያ በኋላ ሕልቃና ወደ ቤቱ ወደ ራ
ማ ሄደ፤ ብላቴናው ግን በካህኑ በዔሊ ፊት
እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር።

### የዔሊ ልጆች ክፉ ድርጊት

[12]የዔሊ ልጆች ምናምንቴዎች ነበሩ፤
*እግዚአብሔርንም* አይፈሩም ነበር። [13]በዚ
ያን ጊዜ ካህናቱ ከሕዝቡ ጋር ባላቸው
ግንኙነት የሚፈጽሙት ወግ ነበር፤ ይኸ
ውም ማንም ሰው መሥዋዕት በሚያቀር
ብበት ጊዜ፣ ሥጋው እየተቀቀለ ሳለ የካህኑ
አገልጋይ ሦስት ጣት ያለውን ሜንጦ ይዞ
ይመጣል፤ [14]ወደ ድስቱ ወይም ወደ
ቶፋው ወይም ወደ አፍላሉ፣ ወይም ወደ
ምንቸቱ ይሰደዋል። ከዚያም ካህኑ ሜን
ጦው ያወጣውን ማናቸውንም ሥጋ ለራሱ
ይወስደዋል። ወደ ሴሎ የሚመጡትን እስራ
ኤላውያን ሁሉ የሚያስተናግዱት በዚህ ዐይ
ነት ነበር። [15]ነገር ግን ሥቡ ገና ከመቃጠሉ
በፊት የካህኑ አገልጋይ መጥቶ መሥዋዕት
የሚያቀርበውን ሰው፣ “ካህኑ ጥሬውን
እንጂ የተቀቀለውን ሥጋ ከአንተ ስለ
ማይቀበል፣ ለካህኑ የሚጠበስ ሥጋ ስጠኝ”
ይለው ነበር።
[16]ሰውየውም፣ “በመጀመሪያ ሥቡ ይቃጠል፤
ከዚያ በኋላ የምትፈለገውን ትወስዳለህ”
ቢለው እንኳ አገልጋዩ፣ “አይሆንም፤ አሁኑኑ
ስጠኝ፤ ያለዚያ በግድ እወስዳለሁ” ይለው
ነበር።
[17]*ለእግዚአብሔር* የሚቀርበውን መሥዋዕት
ይንቁ ስለ ነበር[ቀ]፣ ይህ የወጣቶቹ ኀጢአት
*በእግዚአብሔር* ፊት እጅግ ታላቅ ነበረ።
[18]ብላቴናው ሳሙኤል ግን ከበፍታ የሠራ
ኤፉድ ለብሶ *በእግዚአብሔር* ፊት ያገለግል
ነበር። [19]እናቱም ከባሏ ጋር ዓመታዊ
መሥዋዕት ለማቅረብ በምትሄድበት ጊዜ
ሁሉ ትንሽ መደረቢያ እየሠራች ይዛለት

**1፥24** ዘኍ15፥8-10
**1፥27** 1ሳሙ2፥20፤ መዝ66፥19-20
**1፥28** መሳ13፥7
**2፥1** ዘኍ10፥35፤ መዝ6፥8፥10፤13፥5፤1፤ 18፥2፤33፥21፤89፥17፥ 24፤148፥14፤ዘካ10፥7፤ ሉቃ1፥46-55
**2፥2** ዘፍ49፥24፤ ዘፀ 8፥10፤15፥11፤ 33፥22፤ ዘሌ11፥44፤ ዘዳ32፥37፤2ሳሙ22፥2፥ 32፤23፥3፤መዝ31፥3፤7 1፥3፤ኢሳ40፥25፤ 46፥5
**2፥3** ኢሳ22፥22፤ 1ሳሙ16፥7፤1ነገ8፥39 ፤1ዜና28፥9፤ 2ዜና6፥30፤ መዝ17፥10፤31፥18፤7 3፥8፤75፥4፤94፥4፤ ምሳ15፥11፤ 16፥2፤ 24፥11-12፣ ኤር11፥20፤17፥10
**2፥4** 2ሳሙ1፥27፤ መዝ37፥15፤46፥9፤ 76፥3፤ኢዮ17፥9፤ ኢሳ40፥31፤41፥1፤ 52፥1፤57፥10
**2፥5** መዝ113፥9፤ ኢሳ54፥1፤ኤር15፥9፣ ሉቃ1፥53
**2፥6** ዘዳ32፥39፤ ኢሳ 26፥19፤ ሕዝ37፥3፥12
**2፥7** ዘዳ8፥18፤ ኢዮ 5፥11፤40፥12፤ መዝ 75፥7፤ ኢሳ2፥12፤ 13፥11፤22፥19፤ ዳን4፥37
**2፥8** 2ሳሙ7፥8፤ 1ነገ16፥2፤ኢዮ15፥7፤ 36፥7፤38፥4፤መዝ 72፥12፤ 104፥5፤ 107፥41፤113፥7-8፤ 145፥14፤146፥8፤ ምሳ8፥29፤ኢሳ22፥23፤ 40፥12፤ኤር10፥12፤ ሕዝ21፥26፤ ያዕ2፥5
**2፥9** 1ሳሙ17፥47፤ ኢዮ10፥22፤ መዝ 33፥16- 17፤91፥12፤121፥3፤ ዘዳ18፥316፤ 7፥29- 34፤ምሳ2፥8፤ 3፥26፤ ኢሳ5፥30፤ 8፥22፤ 59፥9፤60፥2 ኤር13፥16፤አሞ5፥18፥ 20፤ሰፎ1፥14-15፤ ዘካ4፥6፤ማቴ8፥12
**2፥10** ዘፀ15፥6፤ 19፥16፤ዘዳ33፥17፤ 1ሳሙ7፥10፤12፥17፤ 2ሳሙ22፥14፤ ኢዮ 37፥4፥5፤8፥1፤ መዝ18፥1፤13፥21፥1፤2 9፥3፤59፥16፤89፥24፤9 6፥13፤98፥9፤ ኢ. ሳ66፥6፤ማቴ25፥ 31- 32፤ሉቃ
1ሳሙ3፥1 **2፥12** ኤር2፥8፤9፥6 **2፥13** ዘሌ7፥35-36፤
**2፥16** ዘሌ3፥3፥14-16፤ 7፥35-36፤ **2፥17** ቍ22፥29፤
ዘኍ16፥14፥11፤ኤር 7፥21፤ሕዝ22፥26፤ሚል2፥7-9**2፥18**
ቍ11፥28፤ 1ሳሙ22፥18፤23፥9፤2ሳሙ6፥14፤
1ዜና15፥27 **2፥19** 1ሳሙ1፥3 **2፥20** 1ሳሙ 1፥27

[ሙ]24 የሙት ባሕር ጥቅልል፤ የሰብዓ ሊቃናትና የሱርቱ ትርጕም ከዚህ፤ ጋር ይስማማል የማስሬቱ ቅጅ ግን *ሦስት ወይፈን* ይላል።
[ሡ]24 22 ሊትር ያህል ነው።
[ሩ]1 በዚህ ስፍራና በቍጥር 10 ላይ *ቀንድ* የጥንካሬ ምልክት ነው
[ሰ]2 ወይም *አንድ* ቅዱስ
[ሸ]6 ዕብራይስጡ *ሲኦል* ይላል
[ቀ]17 ወይም የሚንቁ ሰዎች ስለነበሩ።

ትሄድ ነበር። [20]ዔሊም፣ "በጸሎት
ባገኘ ችውና ለእግዚአብሔር በሰጠችው
ልጅ ምትክ እግዚአብሔር ከዚህችው ሴት
ዘር ይስጥህ" እያለ ሕልቃናንና ሚስቱን
ይመ ርቃቸው ነበር፤ ከዚያ በኋላ ወደ
ቤታቸው ይመለሱ ነበር። [21]እግዚአብሐ
ሔርም ሐናን ባረካት፤ ፀነሰችም፤ ሦስት
ወንዶች፣ ሁለት ሴቶች ልጆችም ወለደች።
ብላቴናውም ሳሙኤል በእግዚአብሔር
ፊት አደገ።
[22]በዚህ ጊዜ ዔሊ እጅግ አርጅቶ ነበር፤
ልጆቹም በመላው እስራኤል ያደርጉ የነበ
ረውን፣ በመገናኛውም ድንኳን ደጃፍ
ከሚያገለግሉ ሴቶች ጋር ዝሙት መፈ
ጸማቸውን ሰማ። [23]ስለዚህም እንዲህ
አላቸው፤ "ስለምትፈጽሙት ክፉ ድርጊት
ከመላው ሕዝብ እሰማለሁ፤ ለምን እንዲህ
ያለ ነገር ታደርጋላችሁ? [24]ልጆቼ ሆይ፤
ትክክል አይደላችሁም፤ በእግዚአብሔር ሕዝብ
መካከል ተሠራጭቶ የምሰማባችሁ ወሬ
ጥሩ አይደለም። [25]አንድ ሰው ሌላውን
ቢበድል፣ እግዚአብሔር[a] ጣልቃ ገብቶ ይፈ
ርዳል፤ ነገር ግን ሰው እግዚአብሔርን ቢበድል፣
ማን ይማልድለታል?" ይሁን እንጂ እግዚ
አብሔር ሊያጠፋቸው ስለ ፈለገ፣ ልጆቹ
የአባታቸውን ተግሣጽ አልሰሙም።
[26]ብላቴናውም ሳሙኤል በአካልና በሞገስ
በእግዚአብሔርና በሰው ፊት እያደገ ሄደ።

## በዔሊ ቤተ ሰብ ላይ የተነገረ ትንቢት

[27]በዚህ ጊዜ አንድ የእግዚአብሔር ሰው ወደ
ዔሊ መጥቶ እንዲህ አለው፤ "እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤ 'የአባትህ ቤት በግብፅ ምድር
በፈርዖን እጅ በነበረ ጊዜ ራሴን ገለጥሁ
ለት? [28]የእኔ ካህን እንዲሆን፣ ወደ መሠ
ዊያዬ እንዲወጣ፣ ዕጣን እንዲያጥን፣
በፊቴም ኤፉድ እንዲለብስ ከእስራኤል
ነገዶች ሁሉ አባትህን መረጥሁት። ደግ
ሞም እስራኤላውያን በእሳት የሚያቀር
ቡትን ቊርባን ሁሉ ለአባትህ ቤት
ሰጠሁ። [29]ታዲያ በማደሪያዬ እንዲቀርብ
ያዘዝሁትን መሥዋዕትና ቊርባን የናቃ
ችሁ ለምንድን ነው? አንተና ልጆችህ ሕዝቤ
እስራኤል ካቀረበው ቊርባን ሁሉ ምርጥ
ምርጡን በልታችሁ ራሳችሁን በማወ
ፈር ከእኔ ይልቅ ልጆችህን የምታከብራቸው
ስለ ምንድን ነው?"
[30]"ስለዚህ የእስራኤል አምላክ እግዚ
አብሔር እንዲህ ይላል፤ 'ቤትህና የአባትህ
ቤት በፊቴ ለዘላለም ያገለግሉኝ ዘንድ
ተስፋ ሰጥቼ ነበር፤' አሁን ግን እግዚ
አብሔር እንዲህ ይላል፤ 'ይህን ከእንግዲህ
አላደርገውም፤ የሚያከብሩኝን አከብራለሁ፤

1፥69 2፥11 ቊ18፤
ዘኍ16፥9፤
ኢሱ18፥25፤
2፥21 ዘፍ21፥1፤
መሳ13፥24፤
ሉቃ1፥80፤ 2፥40
2፥22 ቊ17፤
ዘፀ 38፥8
2፥25 ዘፀ4፥21፤
32፥10፤ዘኍ11፥2፤ ኢ
ሱ11፥20፤1ሳሙ
3፥14፤1ነገ13፥6፤
ኢዮ9፥33፤
መዝ106፥30፤
ኢሳ1፥18፤ 22፥14፤
ኤር15፥1፤
ዕብ10፥26
2፥26 መሳ13፥24፤
ምሳ3፥4፤ሉቃ2፥5
2፥27 ዘዳ33፥1፤
መሳ13፥6
2፥28 ዘፀ28፥1፤
30፥7፤ዘሌ7፥35-
36፤1ሳሙ22፥18፤
23፥6፥9፤30፥7
2፥29 ቊ12-17፤
ዘዳ 12፥5
2፥30 ዘፀ29፥9፤
መዝ50፥23፤91፥15፤
ምሳ8፥17፤ኢሳ53፥3፤
ኤር18፥10፤ናሆ3፥6፤
ሚል2፥9
2፥31 1ሳሙ4፥11-18፤
22፥16
2፥32 1ሳሙ4፥3፤
22፥17-20፤
1ነገ 2፥26-27፤
ኤር 7፥12፥14
2፥33 ኤር29፥32፤
ሚል2፥12
2፥34 ዘዳ13፥2፤
1ሳሙ 4፥11፤
1ነገ13፥3
2፥35 1ሳሙ9፥16፤
10፥1፤16፥13፤
2ሳሙ 2፥4፤8፥17፤
12፥7፤20፥25፤
23፥1፤1ነገ
1፥8፥32፥34፤2፥35፤
4፥4፤1ዜና16፥39፤
29፥22፤መዝ89፥20፤
ሕዝ 44፥15-16
2፥36 1ሳሙ3፥12፤
1ነገ2፥27፤
ሕዝ 44፥10-14
3፥1 1ሳሙ2፥11፤
መዝ74፥9ሰቆ2፥9፤
ሕዝ7፥26፤አሞ8፥11
3፥2 ዘፍ27፥1፤
1ሳሙ4፥15
3፥3 ዘፀ25፥31-38፤
ዘሌ24፥1-4፤
ዘዳ10፥ 1-5፤
1ሳሙ1፥9፤
1ነገ 6፥19፤8፥1
3፥4 ዘፍ22፥1፤
ዘፀ3፥4

የሚንቁኝም ፈጽሞ ይናቃሉ። [31]እነሆ፤ በዘርህ
ሽማግሌ እንዳይገኝ ያንተን ኀይልና የአ
ባትህን ቤተ ሰብ ኀይል የምሰብርበት ጊዜ
ይመጣል፤ [32]በማደሪያዬም መከራ ታያለህ፤
ምንም እንኳ ለእስራኤል በጐ ነገር ቢደ
ረግም፣ በቤተ ሰብህ ውስጥ ሽማግሌ ፈጽሞ
አይገኝም። [33]ከመሠዊያዬ የማላስወግዳቸው
ዘሮችህ በሕይወት የሚተርፉትም ዐይኖች
ህን በእንባ ለማፍዘዝ፣ ልብህን በሐዘን
ለማደንዘዝ ብቻ ነው፣ ሌሎቹ ዘሮችህ
ግን በሙሉ በለጋነታቸው ባጭር ይቀጫሉ።
[34]"በሁለቱ ልጆችህ በአፍኒንና በፊንሐስ
ላይ የሚደርሰው ላንተ ምልክት ይሆንሃል፣
ሁለቱም በአንድ ቀን ይሞታሉ። [35]እንደ
ልቤና እንደ አሳቤ የሚያገለግል የታመነ
ካህን ለራሴ አስነሣለሁ፤ ቤቱን አጽንቼ
አቆማለሁ፣ እርሱም በቀባሁት ፊት ለዘላለም
ያገለግላል። [36]ከዘሮችህም መካከል የተ
ረፈው ማንኛውም ሰው፣ ለአንዲት ጥሬ
ብርና ለቍራሽ እንጀራ ሲል በፊቱ ወድቆ
ይሰግዳል፤ 'የዕለት ጕርሴን እንዳገኝ
እባክህ በማንኛውም የክህነት ሥራ ላይ
መድበኝ' በማለት ይለምናል።" '

## እግዚአብሔር ሳሙኤልን ጠራው

3 ብላቴናው ሳሙኤል ከዔሊ በታች
ሆኖ እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር።
በዚያም ዘመን የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ
ነበረ፤ ራእይም አይታይም ነበር።
[2]ዐይኖቹ ከመድከማቸው የተነሣ ማየት
የተሳነው ዔሊ አንድ ሌሊት በስፍራው
ተኝቶ ነበር። [3]ሳሙኤልም ደግሞ የእግ
ዚአብሔር ታቦት ባለበት፣ በእግዚአብሐ
ሔር ቤተ መቅደስ[+] ውስጥ ተኝቶ ነበር፤
የእግ ዚአብሔር መብራትም ገና አልጠፋም
ነበር። [4]እግዚአብሔርም ሳሙኤልን ጠራ
ው፤
ሳሙኤልም፣ " እነሆኝ " አለ፤
[5]ወደ ዔሊም ሮጦ በመሄድ፣ "እነሆኝ
የጠራኸኝ " አለው።
ዔሊ ግን፣ "እኔ አልተጣራሁም፤
ተመልሰህ ተኛ" አለው፤ እርሱም ሄዶ
ተኛ።
[6]ደግሞም እግዚአብሔር፣ "ሳሙኤል!"
ብሎ ጠራው።
ሳሙኤልም ተነሣና ወደ ዔሊ ሄዶ፣
"እነ ሆኝ የጠራኸኝ" አለው።
ዔሊም መልሶ፣ "ልጄ ሆይ፤ እኔ አልተጣራ
ሁም፤ ተመልሰህ ተኛ" አለው።
[7]በዚያም ጊዜ ሳሙኤል እግዚአብሔ
ርን ገና አላወቀም ነበር፤ የእግዚአብሔርም
ቃል ገና አልተገለጠለትም ነበር።

[a]25 ወይም መሳፍንት
[+]3 የማደሪያው ድንኳን ነው

8 *እግዚአብሔር* ሳሙኤልን ለሦስተኛ
ጊዜ ጠራው፤ አሁንም ሳሙኤል ተነሥቶ
ወደ ዔሊ በመሄድ፣ "እነሆኝ የጠራኸኝ" አለው።
ዔሊ በዚህ ጊዜ ብላቴናውን ይጠራ የነ
በረው *እግዚአብሔር* መሆኑን ተረዳ። 9 በዚያ
ጊዜ ዔሊ ሳሙኤልን፣ "ሂድና ተኛ፤ ከእንግዲህ
ቢጠራህ ግን፣ '*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ባሪያህ
ይሰማልና ተናገር' በል" አለው። ስለዚህም
ሳሙኤል ወደ ስፍራው ተመልሶ ተኛ።
10 *እግዚአብሔርም* መጥቶ በዚያ ቆመ፤
ቀደም ሲል እንዳደረገው ሁሉ "ሳሙኤል!
ሳሙኤል!" ብሎ ጠራው። ሳሙኤልም፣
"ባሪ ያህ ይሰማልና ተናገር" አለ።
11 *እግዚአብሔርም* ሳሙኤልን እንዲህ አለው፤
"እነሆ፤ የሰሚውን ሁሉ ጆሮ ጭው
የሚያደርግ አንድ ነገር በእስራኤል ላይ
አደርጋለሁ። 12 በዚያም ቀን ከመጀመሪያ
እስከ መጨረሻ በዔሊና በቤተ ሰቡ ላይ
የተናገርሁትን ሁሉ እፈጽማለሁ። 13 ዔሊ
በሚያውቀው ኀጢአት ምክንያት በቤተ
ሰቡ ላይ ለዘላለም እንደምፈርድ ነግሬው
ነበር ልጆቹ አስጸያፊ ነገር አድርገዋል[*]፤
እርሱ ግን አልከለከላቸውም። 14 ስለዚህ
'የዔሊ ቤት በደል በመሥዋዕትም ሆነ
በቍርባን ፈጽሞ አይሰረይም' ብዬ በዔሊ
ቤት ላይ ምያለሁ።"
15 ሳሙኤል እስኪነጋ ድረስ ተኛ፤ ከዚያም
ተነሥቶ የእግዚአብሔርን ቤት በሮች
ከፈተ፤ ራእዩንም ለዔሊ መንገር ፈራ፤ 16 ዔሊ
ግን ሳሙኤልን፣ "ልጄ ሳሙኤል ሆይ"
ሲል
ጠራው።
ሳሙኤልም፣ "እነሆኝ" ሲል መለሰ።
17 ዔሊም፣ "*እግዚአብሔር* የነገረህ ነገር
ምን ድነው? አትደብቀኝ፤ ከነገረህ ውስጥ አንዲ
ቱን እንኳ ብትደብቀኝ እግዚአብሔር እንደዚ
ያው ያድርግብህ፤ ከዚያ ለከፋም ይዳርግህ"
አለው። 18 ስለዚህ ሳሙኤል ምንም ነገር
ሳይደብቅ ሁሉንም ነገረው። ዔሊም፣
"እርሱ *እግዚአብሔር* ነው፤ መልካም
መስሎ የታየውን ያድርግ" አለ።
19 ሳሙኤል እያደገ ሄደ፤ *እግዚአብሔ
ርም* ከእርሱ ጋር ስለ ነበረ፣ ከሚናገረው
ቃል አንዳች በምድር አይወድቅም ነበር።
20 ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ያሉ እስራኤላ
ውያን በሙሉ ሳሙኤል በእርግጥ *የእግዚ
አብሔር* ነቢይ መሆኑን ዐወቁ። 21 *እግዚ
አብሔር* በሴሎ ይገለጥ ነበር፤ በዚያም
በቃሉ አማካይነት ራሱን ለሳሙኤል ገለጠ።

4 የሳሙኤልም ቃል ወደ እስራኤል
ሁሉ ደረሰ።

3፥7 ዘኍ2፥6፤
1ሳሙ2፥12፤
ኤር1፥2፤አሞ3፥7
3፥10 ዘፀ3፥4
3፥11 2ነገ21፥12፤
ኢዮ15፥21፤ኤር19፥3
3፥12 1ሳሙ2፥27-36
3፥13 1ነገ1፥6
3፥14 1ሳሙ2፥25
3፥17 ሩት 1፥17፤
1ነገ22፥14፤
ኤር 23፥28፤38፥14፤
42፥4
3፥18 መሳ10፥15
3፥19 ዘፍ21፥22፤
ዘኍ14፤43፤
መሳ13፥24፤
1ሳሙ9፥6
3፥20 ዘዳ18፥22፤
መሳ20፥1፤
ሕዝ33፥33
3፥21 ዘኍ12፥6

4፥1 ኢሱ12፥18፤
1ሳሙ5፥1፤29፥2፤
1ነገ20፥26
4፥3 ኢሱ6፥7፤7፥7፤
18፥1፤1ሳሙ2፥32፤
2 ዜና13፥8
4፥4 ዘፍ3፥24፤
ዘፀ25፥22
4፥5 ኢሱ 6፥5፡10
4፥6 ዘፍ 14፡13
4፥7 ዘፀ 15፥14
4፥8 ዘፀ12፥30፤
1ሳሙ5፥12፤
ራእ11፥6
4፥9 መሳ13፥1
4፥10 ዘዳ 28፥25
4፥11 መዝ78፥64፤
ኤር7፥12

## ታቦቱ በፍልስጥኤማውያን ተማረከ

በዚያ ዘመን እስራኤላውያን ፍልስጥኤማ
ውያንን ሊወጉ ወጡ፤ እስራኤላውያን በአ
ቤንኤዘር፣ ፍልስጥኤማውያን ደግሞ በአፌቅ
ሰፈሩ። 2 ፍልስጥኤማውያን እስራኤልን ለመ
ግጠም ሰራዊታቸውን አሰለፉ፤ ጦርነቱ
እንደ ተፋፋመም፣ እስራኤላውያን በፍል
ስጥ ኤማውያን ተሸነፉ፤ በጦርነቱም ላይ አ
ራት ሺህ ያህል እስራኤላውያን ተገደሉ።
3 ሰራዊቱ ወደ ሰፈር በተመለሰ ጊዜ የእስራ
ኤል አለቆች፣ ዛሬ *እግዚአብሔር*
በፍልስጥኤማውያን እንድንሸነፍ ያደረገን
ለምንድን ነው? አብሮን እንዲወጣ፣ ከጠ
ላቶቻችንም እጅ እንዲያድነን *የእግዚ
አብሔርን* የኪዳኑን ታቦት ከሴሎ እናምጣ"
አሉ።
4 ስለዚህ ሕዝቡ ሰዎችን ወደ ሴሎ ላከው፣
በኪሩቤል መካከል በዙፋኑ ላይ የተቀ
መጠውን የሰራዊት ጌታ *የእግዚእብሔርን*
የኪዳን ታቦት አስመጡ፤ ሁለቱ የዔሊ
ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ ከኪዳኑ ታቦት
ጋር በዚያ ነበሩ።
5 *የእግዚአብሔር* የኪዳኑ ታቦት ወደ
ሰፈር በገባ ጊዜ፣ ምድሪቱ እስክትናወጥ
ድረስ እስራኤላውያን ሁሉ ታላቅ የደስታ
ጩኸት አሰሙ። 6 ፍልስጥኤማውያንም
ይህን ታላቅ ጩኸት ሲሰሙ፣ "በዕብራ
ውያን ሰፈር የምንሰማው ይህ ሁሉ
ጩኸት ምንድ ነው?" ሲሉ ጠየቁ።
*የእግዚአብሔር ታቦት* ወደ ሰፈር መምጣቱን
በተረዱ ጊዜ ፤ 7 ፍልስጥኤማውያንም ፈርተው
እንዲህ አሉ፤ "አምላክ ወደ ሰፈሩ መጥቶአል፤
ወዮልን! እንዲህ ዐይነት ነገር ገጥሞን
አያውቅም። 8 ወዮልን! ከእነዚህ ኀያላን አማ
ልክት እጅ ማን ያድነናል? ግብፃውያንን
በምድረ በዳ በልዩ ልዩ መቅሠፍት የመቱ
እነዚሁ አማልክት ናቸው፤ 9 ፍልስጥኤማውያን
ሆይ፤ በርቱ! ወንድነታችሁም ይታይ፤ ያለዚ
ያ ባሪያ እንዳደረጋችኋቸው ሁሉ፣ ዕብራ
ውያን እናንተን መልሰው ባሪያ
ያደርጓችኋል። ወንድነታችሁ ይታይ፤
ተዋጉ! "
10 ስለዚህ ፍልስጥኤማውያን ተዋጉ፤
እስራኤላውያንም ስለ ተሸነፉ እያንዳንዱ
ወደየድንኳኑ ሸሸ። ታላቅ እልቂት ሆነ፤
ከእስራኤልም ሠላሳ ሺህ እግረኛ ወታ
ድሮች ወደቁ። 11 የእግዚአብሔር ታቦት
ተማረከ፤ ሁለቱም የዔሊ ልጆች አፍኒንና
ፊንሐስ ተገደሉ።

## የዔሊ መሞት

12 በዚያች ዕለት አንድ ብንያማዊ ልብሱን

[*]13 የማሶሬቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ነገር ግን ጥንታዊው የዕብራይስጡ ጸሓፍት ትውፊት እንዲሁም የሰብዓ ሊቃ ናት፣ *ልጆቹ እግዚአብሔርን ተዳፍረዋል* ይላል።

ቀዶ፣ በራሱም ላይ ትቢያ ነስንሶ፣ ከጦሩ ሜዳ እየበረረ ወደ ሴሎ መጣ። 13እዚያ እንደ ደረሰም፣ ዔሊ ስለ እግዚአብሔር ታቦት ልቡ ስለ ተጨነቀ፣ በመንገድ ዳር ወንበሩ ላይ ተቀምጦ ይጠባበቅ ነበር። ሰውየውም ወደ ከተማው ገብቶ የሆነውን ሁሉ ባወራ ጊዜ፣ ከተማው ሁሉ በጩኸት ተናወጠ።

14ዔሊም ጩኸቱን በሰማ ጊዜ፣ "የምን ጩኸት ነው?" ሲል ጠየቀ።

ሰውየውም ፈጥኖ መጣና ለዔሊ ነገረው፤ 15ዔሊ የዘጠና ስምንት ዓመት ሽማግሌ ስለ ነበር
ዐይኖቹ ደክመው ማየት ተስኖአቸው ነበር። 16ሰውየውም ዔሊን፣ "ከጦሩ ሜዳ ገና አሁን መምጣቴ ነው፤ ከጦርነቱ አምልጬ የወጣሁትም ዛሬ ውኑ ነው" ብሎ ነገረው።

ዔሊም፣ "ልጄ ሆይ፤ ታዲያ እንዴት ሆነ?" ሲል ጠየቀ።

17ወሬውን ያመጣውም ሰው፣ "እስራኤል ከፍልስጥኤማውያን ፊት ሸሸ፤ ሰራዊቱም ከፍተኛ እልቂት ደርሶበታል፤ እንዲሁም ሁለቱ ልጆችህ አፍኒንና ፊንሐስ ሞተዋል፤ የእግዚአብሔርም የኪዳኑ ታቦት ተማርኮአል" ብሎ መለሰለት።

18ሰውየው ስለ እግዚአብሔር ታቦት በተናገረ ጊዜ፣ ዔሊ በቅጥሩ በር አጠገብ ከተቀመጠበት ወንበር ላይ በጀርባው ወደቀ፤ እርሱም ያረጀና ሰውነቱም የሚከብድ ስለ ነበር፣ ዐንገቱ ተሰብሮ ሞተ። እርሱም ለአርባ ዓመት በእስራኤል ላይ ፈራጅ[ጎ] ነበር።

19በዚያን ጊዜ ምራቱ የፊንሐስ ሚስት፣ ነፍሰ ጡር ነበረች፤ የምትወልድበትም ጊዜ ተቃርቦ ነበር፣ የእግዚአብሔርን ታቦት መማረክ፣ የዐማቷንና የባሏንም መሞት በሰማች ጊዜ ምጡ ስለ ጠናባት ተንበርክካ ወለደች። 20ለመሞትም በምታጣጥርበት ጊዜ፣ በአጠገቧ የነበሩት ሴቶች፣ "አይዞሽ፤ ወንድ ልጅ ወልደሻልና በርቺ" አሏት። እርሷ ግን መልስ አልሰጠችም፤ ልብ ብላም አላዳመጠችም።

21የእግዚአብሔር ታቦት ስለ ተማረከ፣
ዐማቷና ባሏም ስለ ሞቱ፣ "ክብር ከእስራኤል ተለይቶአል" ስትል የሕፃኑን ስም ኢካቦድ[ነ] አለችው። 22ከዚያም፣ "የእግዚአብሔር ታቦት ተማርኮአልና ክብር ከእስራኤል ተለይቶአል" አለች።

## ታቦቱ ወደ አሽዶድና ወደ አቃሮን ተወሰደ

5 ፍልስጥኤማውያን የእግዚአብሔርን ታቦት ከማረኩ በኋላ፣ ከአቤንኤዘር ወደ አሽዶድ ወሰዱት። 2ከዚያም ወደ ዳጎን ቤተ ጣዖት አግብተው፣ በዳጎን አጠገብ አኖሩት።

4፥12 ኢሱ7፥6፤ 2ሳሙ1፥2፤ ሕዝ24፥26፤33፥21
4፥13 ቍ18
4፥15 1ሳሙ3፥2
4፥17 1ሳሙ22፥18፤ መዝ78፥61፡64
4፥18 መሳ2፥16፤ 16፥31፤1ሳሙ 2፥31
4፥21 ዘፍ35፥18፤ ዘፀ24፥16፤ መዝ106፥20፤ ኤር2፥11፤ ሕዝ 1፥28፤ 9፥3፤10፥18
4፥22 ዘፀ24፥16፤ መዝ78፥61፤ ኤር7፥12
5፥1 ኢሱ11፥22፤ 13፥3፤1ሳሙ 4፥1
5፥2 መሳ16፥23፤ ኢሳ2፥18፤19፥1፤ 46፥1
5፥3 ኢሳ40፥20፤ 41፥7፤46፥7፤ ኤር10፥4
5፥4 ሕዝ 6፥6፤ ሚክ 1፥7
5፥5 ሰፎ1፥9
5፥6 ዘፀ 9፥3፤ 15፥26፤1ሳሙ6፥5፤ 2ሳሙ 6፥7፤ መዝ 78፥66፤ ሐሥ13፥11
5፥8 ኢሱ11፥22፤ መሳ16፥18
5፥9 ዘፀ14፥24
5፥10 ኢሱ 13፥3
5፥11 ቍ 8
5፥12 1ሳሙ 4፥8

3የአሽዶድም ሰዎች በማግስቱ ማለዳ ተነሥተው ሲመለከቱ እነሆ፣ ዳጎን በእግዚአብሔር ታቦት ፊት መሬት ላይ በግንባሩ ተደፍቶ አገኙት። ከዚያም አንሥተው ወደ ቦታው መለሱት። 4በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ተነሥተው ሲመለከቱ፣ ዳጎን *በእግዚአብሔር* ታቦት ፊት፣ መሬት ላይ በግንባሩ ተደፍቶ ነበር፤ ራሱና እጆቹ ተሰባብረው በደጃፉ ላይ የወደቁ ሲሆን፣ የቀረው ሌላው አካሉ ብቻ ነበር። 5የዳጎን ካህናትም ሆኑ ሌሎች በአሽዶድ ወዳለው የዳጎን ቤተ ጣዖት የሚገቡ ሁሉ እስከ ዛሬ ድረስ እግራቸው ደጃፉን እንዳይረግጥ ተራምደው የሚያልፉት በዚሁ ምክንያት ነው።

6*የእግዚአብሔር* እጅ በአሽዶድ ሕዝብና በአካባቢዋ ላይ ጠነከረ፤ እርሱም ጥፋት አመጣባቸው፤ በዕባጭም መታቸው[ኘ]። 7የአሽዶድ ሰዎች ይህን ባዩ ጊዜ፣ "እጁ በእኛና በአምላካችን በዳጎን ላይ ጠንክሮአልና የእስራኤል አምላክ ታቦት በእኛ ዘንድ መቈየት የለበትም" አሉ። 8ከዚህ በኋላ የፍልስጥኤማውያንን ገዦች በሙሉ ጠርተው፣ "የእስራኤልን አምላክ ታቦት ምን እናድርገው?" ሲሉ ጠየቁ።

እነርሱም፣ "የእስራኤልን አምላክ ታቦት ወደ ጌት ውሰዱት" አሏቸው። ስለዚህ የእስራኤልን አምላክ ታቦት ወሰዱት።

9ነገር ግን ታቦቱን ወደዚያ ከወሰዱት በኋላ *የእግዚአብሔር* እጅ በከተማዪቱ ላይ ሆነ፤ ታላቅ መሸበርም አመጣባቸው፤ ሕፃን ሽማግሌ ሳይል ሕዝቡን በእባጭ መታ[ኦ]። 10ስለዚህ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ አቃሮን ሰደዱት።

የእግዚአብሔር ታቦት እዚያ ሲገባም፣ የአቃሮን ሕዝብ፣ "የእስራኤልን አምላክ ታቦት ያመጡብን እኛንና ሕዝባችንን ለማስፈጀት ነው" በማለት ጮኹ። 11የእግዚአብሔር እጅ በርትቶባቸው ስለ ነበር፣ ሞት ከተማዪቱን እጅግ አስደንግጦአት ነበርና ሕዝቡ የፍልስጥኤማውያንን ገዦች በሙሉ ጠርተው፣ "የእስራኤልን አምላክ ታቦት ከዚህ አርቁልን፤ ወደ ገዛ ስፍራው ይመለስ፤ ያለዚያ እኛንም ሕዝባችንንም ይፈጃል" አሉ። 12ያልሞቱትን ደግሞ ዕባጩ ያሠቃያቸው ስለ ነበር፣ የከተማዪቱ ጩኸት እስከ ሰማይ ወጣ።

[ጎ]18 ወይም *እስራኤል መርቶ ነበር*
[ነ]21 *ኢካቦድ* ማለት *ክብር የለም* ማለት ነው።
[ኘ]6 ዕብርይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት የሹልጊት ትርጒም ግን *በምድራቸው ላይ ዐይጥ መታየት ጀመረ፤እንዲሁም ሞትና ጥፋት በከተማዪቱ ዙሪያ ነበር* ይላል።
[ኦ]9 ወይም *ብልታቸውን አሳበጠባቸው*

## የታቦቱ ወደ እስራኤል መመለስ

6 *የእግዚአብሔር* ታቦት በፍልስጥኤማውያን
ግዛት ሰባት ወር ቈየ። [2]ፍልስጥኤ
ማውያን ካህናትንና ጠንቋዮችን ጠርተው፣
“*የእግዚአብሔርን* ታቦት ምን እናድርገው?
ወደ ስፍራው እንዴት መመለስ እንደሚገ
ባን ንገሩን” አሏቸው።
[3]እነርሱም፣ “የእስራኤልን አምላክ ታቦት
የምትመልሱ ከሆነ ከበደል መሥዋዕት ጋር
ስደዱት እንጂ ባዶውን አትስደዱት፤ በዚያ
ጊዜ ትፈወሳላችሁ፤ እጁም ከእናንተ ላይ ለምን
እንዳልተነሣ ታውቃላችሁ” አሏቸው።
[4]ፍልስጥኤማውያንም፣ “የምንልከው የበ
ደል መሥዋዕት ምን መሆን አለበት?” ሲሉ
ጠየቁ።
እነርሱም እንዲህ ሲሉ መለሱ፤ “እናን
ተንም ሆነ አለቆቻችሁን የመታው መቅ
ሠፍት አንድ ዐይነት በመሆኑ፣ በፍልስ
ጥኤማውያን ገዦች ቍጥር ልክ አምስት
የወርቅ ዕባጮችና አምስት የወርቅ ዐይ
ጦች ላኩ። [5]አገሩን በማጥፋት ላይ ባሉት
ዕባ ጮችና ዐይጦች ዐይነት ምስሎችን
ሥርታችሁ፤ ለእስራኤል አምላክ ክብር
ስጡ። ይህን ካደረጋችሁ እጁን ከእናንተ፣
ከአማልክታችሁና ከምድራችሁ ላይ ያነሣ
ይሆናል። [6]እንደ ግብፃውያንና እንደ ፈርዖን
ልባችሁን የምታደነድኑት ለምንድን ነው?
እነርሱም እስራኤላውያንን የለቀቋቸው እግዚ
አብሔር በጽኑ ከቀጣቸው በኋላ አይ
ደለምን?
[7]“ስለዚህ አዲስ ሠረገላና ቀንበር ያል
ተጫነባቸው ሁለት የሚያጠቡ ላሞች አዘ
ጋጁ። ላሞቹን በሠረገላው ጥመዷቸው፤
እንቦሶቻቸውን ግን ወደ ቤት መልሷቸው።
[8]*የእግዚአብሔርን* ታቦት ወስዳችሁ በሠ
ረገላው ላይ አኑሩ፤ በታቦቱም አጠገብ
ባለው ሣጥን ውስጥ ለበደል መሥዋዕት
የምትልኩትን የወርቅ ምስሎች አስቀምጡ፤
በፈለገውም መንገድ እንዲሄድ ልቀቁት፤
[9]ነገር ግን ወዴት እንደሚሄድ ተመልከቱ፤
ወደ ቤትሳሚስ አቅጣጫ ወደ ገዛ አገሩ
የሚሄድ ከሆነ፣ ይህን ታላቅ መከራ ያመጣ
ብን *እግዚአብሔር* ነው። ወደዚያ ካልሄደ
ግን፣ መከራው በአጋጣሚ የደረሰብን እንጂ
የእርሱ እጅ እንዳልመታን እናውቃለን።”
[10]እነርሱም እንደዚሁ አደረጉ። ሁለቱን
ላሞች ወስደው በሠረገላው ጠመዷቸው፤
እንቦሶቻቸውንም በቤት ውስጥ ዘጉባቸው።
[11]*የእግዚአብሔርንም* ታቦት፣ የወርቁን
ዐይጦችና የዕባጮቹን ምስሎች በሠረ
ገላው ላይ ጫኑ። [12]ከዚያም ላሞቹ መንገ
ዳቸውን ይዘው እምቧ! እምቧ! እያሉ ቀጥ

6፥2 ዘፀ7፥11፤ ኢሳ44፥25
6፥3 ቀኍ9፤ ዘፀ 22፥29፤34፥20፤ ዘሌ5፥15
6፥4 ኢሱ13፥3፤ 2ሳሙ24፥25
6፥5 ኢሱ7፥19፤ 1ሳሙ5፥6፤ራእ14፥7
6፥6 ዘፀ4፥21፤ 10፥2፤12፥33
6፥7 ዘኍ19፥2፤ 2ሳሙ6፥3፤ 1ዜና13፥7
6፥9 ኢሱ15፥10፤ 21፥16
6፥13 ዘፍ30፥14፤ ሩት2፥23፤ 1ሳሙ12፥17
6፥14 1ሳሙ11፥7፤ 2ሳሙ 24፥22፤ 1ነገ19፥21
6፥15 ቀኍ18፤ ኢሱ3፥3፤21፥16
6፥17 ኢሱ13፥3
6፥19 ዘፀ19፥21፤ 2ሳሙ6፥7
6፥20 ዘሌ11፥45፤ 2ሳሙ6፥9፤ መዝ 130፥3፤ ሚል3፥2፤ራእ6፥17
6፥21 ኢሱ 9፥17
7፥1 ኢሱ6፥7፤ 2ሳሙ6፥3፤1ዜና13፥7

ብለው ወደ ቤት ሳሚስ አመሩ። የፍል
ስጥኤም ገዦችም እስከ ቤትሳሚስ ድንበር
ተከተሏቸው።
[13]በዚህ ጊዜ የቤትሳሚስ ሰዎች በሸለ
ቆው ውስጥ ስንዴአቸውን ያጭዱ ነበር፤
ቀና ብለው ሲመለከቱም ታቦቱን በ
ማየታቸው በጣም ደስ አላቸው። [14]
ሠረገላውም ወደ ቤትሳሚስ ወደ ኢ
ያሱ ዕርሻ መጥቶ በአንድ ትልቅ ቋጥኝ
አጠገብ ቆመ። ሕዝቡም የሠረገላውን ዕ
ንጨት ፈልጠው፣ ሁለቱን ላሞች
የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገው *ለእግዚ
አብሔር* አቀረቡ። [15]ሌዋውያኑም *የእግ ዚ
እብሔርን* ታቦት፣ የወርቅ ዕቃዎቹን ከያ ዘው
ሣጥን ጋር አውርደው በትልቁ ድንጋይ ላይ
አኖሩ። በዚያችም ዕለት የቤትሳሚስ
ሕዝብ *ለእግዚአብሔር* የሚቃጠል መሥዋዕት
አቀረቡ፤ መሥዋዕቶችንም ሠዉ፡ [16]አምስቱ
የፍልስጥኤም ገዦችም ይህን ሁሉ ካዩ
በኋላ በዚያኑ ዕለት ወደ አቃሮን ተመለሱ።
[17]ፍልስጥኤማውያን ስለ በደል መሥዋዕ
ት *ለእግዚአብሔር* የላኳቸው የወርቅ ዕ
ባጮች አንዱ ስለ አሽዶድ፣ አንዱ ስለ
ጋዛ፣ አንዱ ስለ አስቀሎና፣ አንዱ ስለ
ጌትና አንዱ ስለ አቃሮን የቀረቡ ናቸው፤
[18]የወርቅ ዐይጦቹም ቍጥር፣ አምስቱ
የፍልስጥኤም ገዦች በሚ ያስተዳድሯቸው
የተመሸጉ ከተሞችና ከእ ነዚህ ውጭ
ባሉት መንደሮቻቸው ቍጥር ልክ ነው።
በቤትሳሚሳዊው በኢያሱ ዕርሻ ውስጥ
*የእግዚአብሔርን* ታቦት ያስቀመጡ በት ያ
ትልቅ ድንጋይ እስከ ዛሬ ምስክር ነው።
[19]ነገር ግን እግዚአብሔር ከቤትሳሚስ ሰዎች
ጥቂቱን መታ፤ ወደ *እግዚአብሔር* ታቦት
ውስጥ ተመልክተዋልና ከመካከላቸው ሰባ[ሀ]
ሰዎችን ገደለ፤ *እግዚአብሔር* እጅግ ስለ
መታቸውም ሕዝቡ አለቀሰ። [20]የቤትሳሚስም
ሰዎች፣ “ታዲያ በዚህ ቅዱስ አምላክ
*በእግ ዚአብሔር* ፊት ማን መቆም ይችላል?
ታቦቱስ ከዚህ ወጥቶ ወደ ማን ይሂድ?”
አሉ።
[21]ከዚያም ወደ ቂርያትይዓሪም ሰዎች
መልእክተኞች ልከው፣ “ፍልስጥኤማውያን
*የእግዚአብሔርን* ታቦት መልሰውልናል፤
ውረዱና ይዛችሁ ወደ ስፈራችሁ ውጡ”
አሏቸው።

7 የቂርያትይዓሪም ሰዎችም መጥተው
*የእግዚአብሔርን* ታቦት ይዘው ወጡ፤
ከዚያም በኰረብታው ላይ ወዳለው ወደ
አሚና ዳብ ቤት ወሰዱት። *የእግዚአብሔርን*
ታቦት እንዲጠብቅም ልጁን አልዓዛርን ቀደ
ሱት።

[ሀ] 19 ጥቂት የዕብራይስጥ ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆችና የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ግን *አምሳ ሺህ ሰባ* ይላል።

## የፍልስጥኤማውያን መሸነፍ

[2]ታቦቱ በቂርያትይዓሪም ከተቀመጠ ረዥም
ጊዜ ሆነው፤ በአጠቃላይ ሃያ ዓመት ቈየ።
የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ አዘነ፤ እግዚአብሔ
ርንም ፈለገ። [3]ሳሙኤልም የእስራኤልን
ቤት ሁሉ፣ "በፍጹም ልባችሁ ወደ እግዚአ
ብሔር የምትመለሱ ከሆነ፣ ሌሎችን አማል
ክትና አስታሮትን ከመካከላችሁ አስወ
ግዱ፤ ራሳችሁንም ለእግዚአብሔር አሳል
ፋችሁ ስጡ፤ እርሱንም ብቻ አምልኩ፤
እርሱም ከፍልስጥኤማውያን እጅ ይታደጋች
ኋል።" አላቸው። [4]ስለዚህ እስራኤላውያን
የበኣልንና የአስታሮትን አማልክት አስወ
ግደው፣ እግዚአብሔርን ብቻ አመለኩ።
[5]ከዚያ በኋላ ሳሙኤል፣ "እስራኤልን ሁሉ
በምጽጳ ሰብስቡ፤ እኔም ስለ እናንተ ወደ
እግዚአብሔር እጸልያለሁ" አለ። [6]እስራ
ኤላውያን በምጽጳ በተሰበሰቡ ጊዜ፣ ውሃ
ቀድተው በእግዚአብሔር ፊት አፈሰሱ፤
በዚያች ዕለት ጾሙ፤ በዚያም "እግዚአብሔርን
በድለናል" ብለው ተናዘዙ። ሳሙኤልም በምጽጳ
እስራኤልን ይፈርድ ነበር።
[7]እስራኤል በምጽጳ መሰብሰባቸውን ፍልስ
ጥኤማውያን በሰሙ ጊዜ፣ የፍልስጥኤማውያን
ገዦች ሊወጓቸው ወጡ፤ እስራኤላውያንም
ይህን ሲሰሙ፣ ፍልስጥኤማውያንን ፈሩ፤
[8]ሳሙኤልንም፣ "አምላካችን እግዚአብሔር
ከፍልስጥኤማውያን እጅ ያድነን ዘንድ ስለ
እኛ ወደ እርሱ መጸለይህን አታቋርጥ" አሉት።
[9]ሳሙኤልም አንድ የሚጠባ የበግ ግልገል
ወስዶ ሙሉ ለሙሉ የሚቃጠል መሥዋዕ
ት በማድረግ ለእግዚአብሔር አቀረበው፤
ስለ እስራኤልም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤
እግዚአብሔርም መለሰለት።
[10]ሳሙኤል የሚቃጠለውን መሥዋዕት
በሚያሳርግበት ጊዜ፣ ፍልስጥኤማውያን እስ
ራኤልን ለመውጋት ቀረቡ። ይሁን እንጂ
በዚያ ዕለት እግዚአብሔር በፍልስጥኤማውያን
ላይ ከባድ የነጐድጓድ ድምፅ ስላንጐዳጐ
ደባቸው እጅግ ተሸበሩ፤ ድልም ተመተው
ከእስራኤላውያን ፊት ሸሹ። [11]እስራኤላ
ውያንም ከምጽጳ ወጥተው ፍልስጥኤማ
ውያንን በየመንገዱ እየገደሉ ከቤትካር በታች
እስካለው ስፍራ ድረስ አሳደዷቸው።
[12]ከዚህ በኋላ ሳሙኤል አንድ ድንጋይ
ወስዶ በምጽጳና በሼን መካከል አቆመው፤
ስሙንም "እግዚአብሔር እስከ አሁን ድረስ
ረድቶናል" ሲል "አቤንኤዘር[ኸ]" ብሎ ጠራው።
[13]በዚህ ሁኔታ ፍልስጥኤማውያን ድል ስለ
ተመቱ፣ የእስራኤልን ምድር ዳግመኛ አል
ወረሩም።
ሳሙኤል በሕይወት በነበረበት ዘመን ሁሉ፣
የእግዚአብሔር እጅ በፍልስጥኤማውያን ላይ
ከብዳ ነበር። [14]ፍልስጥኤማውያን ከእስራኤል
የወሰዷቸው ከአቃሮን እስከ ጌት የነበሩ
ከተሞች ለእስራኤል ተመለሱላት፤ ግዛታ
ቸውም ከፍልስጥኤማውያን እጅ ነፃ ወጣች፤
በእስራኤልና በአሞራውያንም መካከል ሰላም
ነበረ።
[15]ሳሙኤል በሕይወት በነበረበት ዘመን
ሁሉ፣ እስራኤልን ይዳኝ ነበር። [16]በየዓ
መቱ በቤቴል፣ በጌልገላና በምጽጳ እየተ
ዘዋወረ፣ በእነዚህ ቦታዎች ሁሉ በእስራኤል
ላይ ይፈርድ ነበር። [17]ከዚያም በአርማቴም
ወዳለው ቤቱ ይመለስ ነበር፤ በዚያም ደግሞ
በእስራኤል ላይ ይፈርድ ነበር። በዚያም
ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ።

## እስራኤል ንጉሥ ለማንገሥ መጠየቁ

8 ሳሙኤል በሸመገለ ጊዜ፣ ልጆቹን ፈራጆች
አድርጎ በእስራኤል ላይ ሾማቸው። [2]የበ
ኵር ልጁ ኢዮኤል ሲሆን፣ ሁለተኛው ልጁ
አብያ ነበረ፤ እነርሱም በቤርሳቤህ ይፈርዱ
ነበር። [3]ነገር ግን ልጆቹ የአባታቸውን ፈለግ
አልተከተሉም፤ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማ
ግኘት ሲሉ ከመንገዱ ወጡ፤ ጉቦ ተቀ
በሉ፤ ፍርድም አጣመሙ።
[4]ስለዚህ የእስራኤል ሽማግሌዎች ሁሉ
በአንድነት ተሰብስበው ሳሙኤል ወዳለበት
ወደ አርማቴም መጡ። [5]እነርሱም፣ "አንተ
አርጅተሃል፤ ልጆችህ ያንተን ፈለግ አይከ
ተሉም፤ ስለዚህ ሌሎች ሕዝቦች እንደሚያ
ደርጉት ሁሉ የሚመራን[ሠ] ንጉሥ አንግሥ
ልን" አሉት።
[6]ነገር ግን፣ "የሚመራን ንጉሥ አንግሥ
ልን" ማለታቸው ሳሙኤልን አላስደሰተውም፤
ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ [7]እግዚ
አብሔርም ሳሙኤልን እንዲህ አለው፤ "ንጉ
ሣቸው እንዳልሆን የናቁት እኔን እንጂ
አንተን አይደለምና ሕዝቡ የሚሉህን ሁሉ
አድምጥ። [8]ከግብፅ ምድር ካወጣኋቸው
ዕለት አንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ እኔን ትተው
ሌሎች አማልክትን በማምለክ ያደረጉትን
ሁሉ በአንተም ላይ እያደረጉ ነው። አንተ
ግን [9]የሚሉህን አድምጣቸው፤ በላያቸው
የሚነግሠው ንጉሥ ምን እንደሚፈጽምባቸውም
አሳውቃቸው፤ በሚገባም አስጠንቅቃቸው።"
[10]ሳሙኤልም የእግዚአብሔርን ቃል
ሁሉ፣ ንጉሥ እንዲነግሥላቸው ለጠየቀ
ት ሕዝብ ተናገረ።

7፥2 1ዜና13፥3፡5፤ መዝ 132፥6
7፥3 ዘፍ31፥19፤ ዘዳ 6፥13፤30፥10፤ ኢሱ 24፥14፤ መሳ2፥12-13፡ 18፤1ሳሙ12፥10፤ 31፥10፤2ነገ18፥5፤ 23፥25፤ ኤር24፥7፤ ኢል2፥12፤ ማቴ 4፥10፤ሉቃ4፥8
7፥5 ቀኍ8፤ ዘፍ20፥7፤ ዘዳ9፥19፤ ኢሱ11፥3፤ መሳ21፥5፤ 1ሳሙ1፥20፤10፥17፤ መዝ99፥6፤ኤር15፥1
7፥6 ኢሱ11፥3፤ መሳ2፥16፤16፥31፤ ሰቆ2፥19
7፥7 1ሳሙ17፥11
7፥8 ቀኍ5፤ ዘፀ32፥30፤ዘኍ21፥7፤ 1ሳሙ12፥19፡23፤ 1ነገ18፥24፤ኢሳ37፥4፤ ኤር15፥1፤27፥18
7፥9 ዘፀ32፥11፤ ዘዳ9፥19፤መዝ99፥6
7፥10 ዘፍ35፥5፤ ዘፀ9፥23፤14፥24፤1 ሳሙ2፥10
7፥12 ዘፍ28፥22፤ ዘዳ27፥2፤ኢሱ4፥9፤ 1ሳሙ4፥1
7፥13 መሳ13፥5
7፥14 ኢሱ13፥3፤ መሳ1፥34
7፥15 ቀኍ6፤ መሳ 2፥16፡18፤ 1ሳሙ 12፥11
7፥16 ቀኍ6፤ ዘፍ12፥8፤ኢሱ10፥43፤ 1ሳሙ10፥8፤አሞ5፥5፤ ሐሥ13፥20
7፥17 ቀኍ6፤ ኢሱ 18፥25፤ 1ሳሙ8፥4፤ 9፥12፤14፥35፤15፥34፤ 19፥18፤20፥6፤25፥1፤2 8፥3፤2ሳሙ24፥25
8፥1 ዘዳ16፥18-19
8፥2 ዘፍ22፥19፤ 1ነገ19፥3፤1ዜና6፥28፤ አሞ5፥4-5
8፥3 ዘፀ23፥2፡8፤ 1ሳሙ2፥12፤12፥3፤ ነህ9፥29፤ኢዮ8፥22፤ 34፥27፤መዝ14፥3፤ 58፥3፤ምሳ17፥23፤ ኢሳ53፥6
8፥4 መሳ11፥11፤ 1ሳሙ 7፥17፤11፥3
8፥5 ቀኍ19፡20፤ ዘዳ 17፥14-20፤ 1ሳሙ3፥20፤10፥19፤ 12፥2፡12፡13፤ ሆሴ13፥11
8፥6 1ሳሙ12፥17፤ 15፥11፤16፥1፤ ሆሴ13፥10
8፥7 ቀኍ22፤
ዘፀ 16፥8፤ዘኍ11፥20፤1ሳሙ12፥1 8፥8 1ሳሙ12፥10፤ 2ነገ21፥22፤ኤር2፥17 8፥9 ቀኍ11-18፤ ዘዳ17፥14-20፤1ሳሙ 10፥25 8፥10 ዘፀ19፥7 ማሕ3፥7፤9፥25

[ኸ]12 አቤኔዘር ማለት የርዳታ ድንጋይ ማለት ነው
[ሠ]5 በዚም ሆነ በቍጥር 6 እና 20 ላይ በትውፊት መሳፍንት ይባላል

11እንዲያም አለ፤ “በላያችሁ የሚነግሠው ንጉሥ
የሚያደርግባችሁ ይህ ነው፤ ወንዶች ልጆ
ቻችሁን ወስዶ ሠረገለኞችና ፈረሰኞች
ያደርጋቸዋል፤ በሠረገሎቹም ፊት
ይሮጣሉ:: 12አንዳንዶቹን ሻለቆችና አምሳ
አለቆች ያደርጋቸዋል፤ ሌሎቹን መሬቱን
እንዲያርሱና እህሉን እንዲያጭዱ፣ የቀሩትን
ደግሞ የጦር መሣሪያና ለሠረገላ
የሚሆኑትን ዕቃዎች እንዲሠሩ ያደርጋቸዋል፤
13ሴቶች ልጆቻችሁን ወስዶ ሽቶ ቀማሚ፣
ወጥ ሠሪዎችና እንጀራ ጋጋሪዎች
ያደርጋቸዋል:: 14ከእርሻችሁ፣ ከወይንና
ከወይራ ተክል ቦታዎቻችሁ ምርጥ
ምርጡን ወስዶ ለባለሟሎቹ ይሰ
ጣቸዋል:: 15ከእህላችሁና ከወይናችሁ ከዐ
ሥር አንዱን ወስዶ ለሹማምቱና ለባለሟ
ሎቹ ይሰጣቸዋል:: 16ወንድና ሴት አሽከሮ
ቻችሁን እንዲሁም ምርጥ ከብቶቻችሁንና°
አህዮቻችሁን ለራሱ ያደርጋቸዋል:: 17ከበግና
ከፍየል መንጎቻችሁ አንድ ዐሥረኛውን ለራሱ
ይወስዳል፤ እናንተ ራሳችሁም ባሪያዎቹ
ትሆናላችሁ:: 18ያም ቀን በደረሰ ጊዜ፣ ወዳችሁ
ከመረጣችሁት ንጉሥ የተነሣ ትጮኻላችሁ፤
ነገር ግን በዚያ ቀን እግዚአብሔር አይመልስ
ላችሁም::”

19ሕዝቡ ግን ሳሙኤልን መስማት እምቢ
በማለት፤ እንዲህ አሉ፤ “አይሆንም፤ ንጉሥ
እንዲነግሥልን እንፈልጋለን፤ 20እኛም እንደ
ሌሎቹ ሕዝቦች የሚመራንና ከፊታችን
የሚሄድ፣ ጦርነታችንንም የሚዋጋልን ንጉሥ
ያለን ሕዝቦች እንሆናለን::”

21ሳሙኤልም ሕዝቡ ያለውን ሁሉ ሰማ፤
ያንኑ በእግዚአብሔር ፊት ተናገረው:: 22እግ
ዚአብሔርም፣ “አድምጣቸው፤ ንጉሥም አን
ግሥላቸው” አለው::

ከዚያም ሳሙኤል የእስራኤልን ሰዎች፣
“እያንዳንዳችሁ ወደ ከተማችሁ ተመለሱ”
አላቸው::

## ሳሙኤል ሳኦልን ለንጉሥነት ቀባው

9 ቂስ የተባለ አንድ ታዋቂ ብንያማዊ
ሰው ነበረ፤ እርሱም የአቢኤል ልጅ፣
የጽሮር ልጅ፣ የብኮራት ልጅ፣ የብንያ
ማዊው የአፌቅ ልጅ ነበር:: 2ቂስም ከእስ
ራኤል ልጆች መካከል በመልከ ቀናነቱ
ተወዳዳሪ የማይገኝለት፣ ቁመቱም ከሌሎቹ
ሁሉ ይልቅ ከትከሻው በላይ ዘለግ ያለ፣
ሳኦል የተባለ ወጣት ልጅ ነበረው::

3በዚያም ጊዜ የሳኦል አባት የቂስ አህዮች
ጠፍተው ነበር፤ ቂስም ልጁን ሳኦልን፣
“ከአገልጋዮቹ መካከል አንዱን ይዘህ ሂድና
አህዮቹን ፈልግ” አለው:: 4ስለዚህ በኰረብ
ታማው በኤፍሬም አገርና በሻሊሻ አካባቢ

8፥12 ዘዳ1፥15
8፥14 1ነገ21፥7፡
15፤2ነገ22፡12፤
ሕዝ46፥18፤ሚክ2፥2
8፥11 ዘፍ41፥46፤
ዘዳ17፥16፤1ሳሙ14፥5
2፤2ሳሙ15፥1፤
1ነገ1፥5፤2ዜና1፥14፤1
ሳሙ17፥25
8፥15 ዘፍ41፥34፤
8፥18 1ሳሙ10፥25፤
28፥6፤1ነገ12፥4፤
ኢዮ27፥9፤35፥12፡13
፤መዝ18፥41፤66፥18፤
ምሳ1፥28፤ኢሳ1፥15፤
58፥4፤59፥2፤
ኤር 14፥12፤
ሕዝ8፥18፤ ሚክ3፥4
8፥19 ቁ.5፤
ምሳ 1፥24፤
ኢሳ50፥2፤ 66፥4፤
ኤር7፥13፤8፥12፤13፥10፤
44፥16፤ሐሥ13፥21
8፥20 ቁ.5
8፥21 መሳ11፥11
8፥22 ቁ.7
9፥1 ኢሱ18፥11-20፤
ሩት2፥1፤
1ሳሙ 14፥51፤
1ዜና8፥33፤
9፥39፤አስ2፥5፤
ሐሥ 13፥21
9፥2 ዘፍ39፥6፤
1ሳሙ10፥23፡24
9፥3 ቁ.20፤
1ሳሙ10፥14፡16
9፥4 ኢሱ 24፥33፤
1ሳሙ10፥2፤
2ነገ4፥42
9፥5 1ሳሙ1፥1፤
10፥2
9፥6 ዘዳ33፥1፤
መሳ13፥6፤1ሳሙ3፥19
9፥7 ዘፍ 32፥20፤
1ነገ13፥7፤14፥3፤
2ነገ4፥42፤5፥5፡15፤
ኤር40፥5
9፥9 ዘፍ25፥22፤
2ሳሙ15፥27፤
24፥11 2ነገ17፥13፤
1ዜና9፥22፤21፥9፤
26፥28፤ 29፥29፤
2ዜና19፥2፤
ኢሳ29፥10፤30፥10፤
አሞ7፥12
9፥11 ዘፍ24፥11፡13
9፥12 ዘሌ26፥30፤
ዘኍ28፥11-15፤
1ሳሙ7፥17
9፥13 ማቴ14፥19፤
1ቆሮ10፥16፤
1ጢሞ4፥3-5

ባለው ስፍራ ሁሉ ተዘዋወረ፤ ሆኖም አህዮ
ቹን አላገኙም:: ወደ ሻዕሊምም ግዛት ዘል
ቀው ገቡ፤ አህዮቹ ግን በዚያም አልነበሩ
ም:: እንዲሁም በብንያም ግዛት በኩል ዐ
ለፉ፤ ሆኖም አላገኟቸውም::

5ወደ ጹፍ ግዛት በደረሱ ጊዜ ሳኦል አብ
ሮት የነበረውን አገልጋይ፣ “አባቴ ይህን ጊ
ዜ ስለ አህዮቹ ማሰቡን ትቶ ስለ እኛ
መጨ ነቅ ስለሚጀምር፣ ና እንመለስ”
አለው::

6አገልጋዩ ግን፣ “እነሆ፤ በዚህች ከተማ አንድ
የእግዚአብሔር ሰው አለ፤ እርሱም በጣም
የተከበረ ነው፤ የሚናገረውም ሁሉ በትክክል
ይፈጸማል፤ በየትኛው መንገድ መሄድ እን
ዳለብን ይነግረን ይሆናልና ወደዚያ እን
ሂድ” ሲል መለሰለት::

7ሳኦልም አገልጋዩን፣ “መሄዱን እንሂድ፤
ነገር ግን ለሰውየው ምን እንሰጠዋለን? በስ
ልቻዎቻችን የያዝነው ስንቅ አልቆአል::
ለእግዚአብሔር ሰው የምናበረክተውም
ስጦታ የለንም፤ ታዲያ ምን አለን?”
አለው::

8አገልጋዩ፣ “እኔ የአንድ ሰቅል ጥሬ ብር
ሩብ″ አለኝ፤ በየትኛው መንገድ መሄድ
እንዳለብን ይነግረን ዘንድ ገንዘቡን ለእግዚ
አብሔር ሰው እሰጠዋለሁ” ሲል በድጋሚ
መለሰለት:: 9ቀደም ሲል በእስራኤል ዘንድ
አንድ ሰው እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ሲሄድ፣
“ኑ ወደ ባለ ራእዩ እንሂድ” ይል ነበር፤
ዛሬ ነቢይ የሚባለው በዚያ ጊዜ ባለ ራእይ
ይባል ነበርና::

10ሳኦልም፣ “መልካም፤ ና እንሂድ” አለው::
ስለዚህ የእግዚአብሔር ሰው ወዳለበት ከተማ
ሄዱ::

11በከተማዪቱ መዳረሻ ያለውን
ኰረብታ በመውጣት ላይ ሳሉ፣ ውሃ
ለመቅዳት የሚ ወጡ ልጃገረዶችን
አግኝተው፣ “ባለ ራእዩ እዚህ ነውን?” ሲ
ሉ ጠየቁ::

12እነርሱም እንዲህ ሲሉ መለሱላቸው፤
“አዎን አለ፤ እነሆ፤ ከፊታችሁ ነው፤ ፈጠን
በሉ፤ ሕዝቡ በማምለኪያው ኰረብታ ላይ
መሥዋዕት ስለሚያቀርብ፣ ወደ ከተማችን
ገና ዛሬ መምጣቱ ነው፤ 13ወደ ከተማዪቱም
በገባችሁ ጊዜ፣ ለመብላት ወደ ማምለኪ
ያው ኰረብታ ከመውጣቱ በፊት ታገኙታላ
ችሁ:: መሥዋዕቱን እርሱ መባረክ
ስላለበት፣ እርሱ እስኪመጣ ድረስ ሕዝቡ
መብላት አይጀምርም፤ ከዚያ በኋላ
የተጋበዘው ሕዝብ ይበላል፤ አሁኑኑ ውጡ፤
ወዲያው ታገኙ ታላችሁ::”

°16 የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራ
ይስጡ ግን ወጣቶችን ይላል::
″8 ሦስት ግራም ያህል ነው::

14እነርሱም ወደ ከተማዪቱ ወጡ፤ ወደ
ከተማዪቱም በመግባት ላይ ሳሉ፣ እነሆ፤
ሳሙኤል ወደ ማምለኪያው ኰረብታ
ለመውጣት እነርሱ ወዳሉበት አቅጣጫ መጣ።
15ሳኦል ከመምጣቱ ከአንድ ቀን በፊት
*እግዚአብሔር* ለሳሙኤል ይህንን እንዲህ
ሲል ገልጦለት ነበር፤ 16"ነገ በዚህ ጊዜ
ከብንያም ምድር አንድ ሰው ወደ አንተ
እልካለሁ፤ በሕዝቤ በእስራኤል ላይ መሪ
እንዲሆን ቅባው፤ እርሱም ሕዝቤን ከፍል
ስጥኤማውያን እጅ ይታደጋል። እነሆ፤
ሕዝቤን ከላይ ተመልክቻለሁ፤ ጩኸቱ ከእኔ
ዘንድ ደርሶአልና።"
17ሳሙኤል ሳኦልን ባየው ጊዜ *እግዚ
አብሔር*፣ "ያ የነገርሁህ ሰው እነሆ፤ እር
ሱም ሕዝቤን ይገዛል" አለው።
18ሳኦልም በቅጥሩ በር ላይ ወደ ሳሙ
ኤል ቀረብ ብሎ፣ "የባለ ራእዩ ቤት የት
እንደ ሆነ ትነግረኛለህ?" ሲል ጠየቀው።
19ሳሙኤልም እንዲህ ሲል መለሰለት፤
"ባለ ራእዩ እኔ ነኝ፤ ዛሬ ከእኔ ጋር ስለ
ምትበሉ፤ ከፊቴ ቀድማችሁ ወደ ማምለኪ
ያው ኰረብታ ውጡ፤ ነገ ጠዋት አሰና
ብትሃለሁ፤ በልብህ ያለውንም እነግርሃለሁ።
20ከሦስት ቀን በፊት ስለ ጠፉብህ አህዮች
አትጨነቅ፤ ተገኝተዋልና። የእስራኤል
ምኞት ሁሉ ያዘነበለው ወደ አንተና ወደ
አባትህ ቤተ ሰብ ሁሉ አይደለምን?"
21ሳኦልም፣ "እኔ ከእስራኤል ነገዶች ውስጥ
በጣም አነስተኛ ከሆነው ከብንያም ወገን
አይደለሁምን? ጐሣዬስ ከብንያም ነገድ
ጐሣዎች ሁሉ የሚያንስ አይደለምን? ታዲያ
እንዲህ ያለውን ነገር ስለ ምን ትነግረኛ
ለህ?" ብሎ መለሰለት።
22ከዚያም ሳሙኤል ሳኦልንና አገልጋዩን
ወደ አዳራሹ አመጣ፤ ከተጋበዙትም ሠላሳ
ያህል ሰዎች ሁሉ በላይ አስቀመጣቸው።
23ሳሙኤልም ወጥ ቤቱን፣ "ለይተህ አስቀምጥ
ብዬ የሰጠሁህን የሥጋ ብልት አምጣው"
አለው።
24ወጥ ቤቱም የጭኑን ሥጋ እንዳለ
አም ጥቶ በሳኦል ፊት አስቀመጠው።
ሳሙ ኤልም፣ " ይህ፣ 'እንግዶችን
ጋብዣለሁ' ካልሁበት ጊዜ ጀምሮ እስከ
ተወሰነው ጊዜ ድረስ ለአንተ ተለይቶ
የተቀመጠልህ ስለ ሆነ ብላው" አለው።
ሳኦልም በዚያች ዕለት ከሳሙኤል ጋር
አብሮ በላ።
25ከማምለኪያው ኰረብታ ወደ ከተማዪቱ
ከወረዱ በኋላ ሳሙኤል በቤቱ ሰገነት ላይ
ከሳኦል ጋር ተነጋገረ። 26በማለዳ ተነሡ፤
ሳሙኤል ሳኦልን ከሰገነቱ ላይ ጠርቶ፣

9፥16 ዘፍ 16፥11፤
ዘፀ3፥8፤30፥25፤
1ሳሙ2፥35፤12፥3፤
15፥1፤23፥4፤26፥9፤
2ሳሙ3፥18፤7፥8፤
1ነገ8፥16፤2ነገ11፥12 ፤
1ዜና5፥2፤መዝ2፥2፤
102፥1
9፥17 1ሳሙ16፥12
9፥20 ቍ3፤
1ሳሙ 12፥13፤
ዕዝ6፥8፤ኢሳ 60፥4-9፤
ዳን2፥44፤ሐጌ2፥7፤
ሚል3፥1
9፥21 ዘፀ3፥11፤
መሳ6፥15፤20፥35፡
46፤1ሳሙ18፥18፤
መዝ 68፥27፤
ማቴ2፥6፤ ቆሮ15፥9
9፥24 ዘሌ7፥34
9፥25 ዘዳ22፥8፤
ኢሱ 2፥8፤
ማቴ24፥17፤
ሉቃ5፥19

10፥1 ዘፀ29፥7፤
34፥9፤1ሳሙ9፥16፤
16፥1፤2ሳሙ20፥19፤
1ነገ1፥39፤2ነገ9፥1፤
መዝ78፥62፡71
10፥2 ዘፍ35፥20፤
1ሳሙ9፥4፡5
10፥3 ዘፍ35፥8
10፥4 ቍ27፤
1ሳሙ 16፥20፤
ምሳ18፥16
10፥5 ቍ10፡26፤
ዘፍ31፥27፤
ዘሌ 26፥30፤
ዘኍ11፥29፤
1ሳሙ11፥4፤13፥3፤
15፥34፤16፥16፤
18፥10፤ 19፥9፡20፤
1ነገ1፥40፤20፥35፤
2ነገ 2፥3፡15፤3፥15፤
4፥1፤6፥1፤9፥1፤
1ዜና25፥1፤መዝ92፥3፤
ኢሳ 30፥29፤ኤር31፥4፤
አሞ7፥14፤1ቆሮ14፥1
10፥6 ቍ9፤
ዘኍ 11፥25
10፥7 ኢሱ1፥5፤
መሳ9፥33፤
2ሳሙ7፥3፤1ነገ8፥17፤
1ዜና22፥7፤28፥2፤2
ዜና6፥7፤መክ9፥10፤
ሉቃ1፥28፤ዕብ13፥5
10፥8 ኢሱ4፥20፤
10፥43፤1ሳሙ7፥16፤
11፥14፤13፥8

"ላሰናብትህ ስለ ሆነ ተዘጋጅ" አለው።
ሳኦልም ተዘጋጅቶ እንዳበቃ፣ ከሳሙኤል
ጋር ተያይዘው ወደ ውጭ ወጡ። 27ወደ
ከተማዪቱ ዳርቻ እየወረዱ ሳለ፣ ሳሙኤል
ሳኦልን፣ "አገልጋይህ ወደ ፊት ቀድሞን
እንዲሄድ ንገረው" አለው፤ አገልጋዩም እንደ
ተነገረው አደረገ፤ ከዚህ በኋላ ሳሙኤል፣
"አንተ ግን ከእግዚአብሔር የተላከ
መልእክት እነግርህ ዘንድ ለጥቂት ጊዜ
እዚህ ቈይ" አለው።

10 ከዚያም ሳሙኤል የዘይቱን ብርሌ
ወስዶ፣ ዘይቱን በሳኦል ራስ ላይ ካፈ
ሰሰ በኋላ እንዲህ ሲል ሳመው፤ "በርስቱ
ላይ ገዥ ትሆን ዘንድ *እግዚአብሔር* ቀብ
ቶህ የለምን[ሠ]? 2ዛሬ ከእኔ ተለይተህ ስት
ሄድ፣ በብንያም ወሰን ላይ በምትገኘው
ጼልጻህ በተባለች ስፍራ በራሔል መቃ
ብር አጠገብ ሁለት ሰዎች ታገኛለህ። እነር
ሱም፣ 'የምትፈልጋቸው አህዮች ተገኝተዋል፤
አሁን አባትህ ስለ አህዮቹ ማሰቡን ትቶ፣
"ስለ ልጄ ምን ባደርግ ይሻለኛል?" እያለ
በመጨነቅ ላይ ነው' ይሉሃል።
3"አንተም ጕዞህን በመቀጠል በታቦር
እስካለው እስከ ትልቁ ዛፍ ድረስ ትሄዳለህ፤
እዚያም ሦስት ሰዎች፣ አንዱ ሦስት የፍ
የል ግልገል፣ ሌላው ሦስት ዳቦ፣ ሌላው
ደግሞ የወይን ጠጅ የተሞላበት አቁማዳ
ይዘው ወደ እግዚአብሔር ወደ ቤቴል ሲወጡ
ያገኙሃል። 4እነርሱም ሰላም ይሉሃል፤
ሁለት ዳቦ ይሰጡሃል፤ አንተም ትቀበላቸዋለህ።
5"ከዚያ በኋላ የፍልስጥኤማውያን ጦር
ወዳለበት ወደ እግዚአብሔር ተራራ ወደ ጊብዓ
ትሄዳለህ። ወደ ከተማዪቱ እንደ ደረስ
ህም የነቢያት ጉባኤ በመሰንቆ፣ በከበሮ፣
በእምቢልታና በበገና ታጅበው ትንቢት
እየተናገሩ ከማምለኪያው ኰረብታ ላይ ሲወርዱ
ታገኛቸዋለህ። 6*የእግዚአብሔር መንፈስ* በኀይል
ይወርድብሃል፤ ከእነርሱ ጋር ትንቢት ትናገ
ራለህ፤ እንደ ሌላ ሰውም ሆነህ ትለወጣለህ።
7እነዚህ ምልክቶች በተፈጸሙ ጊዜ እጅህ
ማድረግ የምትችለውን ሁሉ አድርግ፤ እግዚ
አብሔር ከአንተ ጋር ነውና።
8"ከፊቴ ቀድመህ ወደ ጌልገላ ውረድ፤
እኔም የሚቃጠለውን *መሥዋዕት*ና የኅብረት
*መሥዋዕቱ*ን ለማቅረብ ወደ አንተ እመጣለሁ፤
ነገር ግን ወደ አንተ መጥቼ ምን ማድረግ
እንዳለብህ እስክነግርህ ድረስ ሰባት ቀን
መቆየት አለብህ።"

[ሠ]1 የዕራይስጥ ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ የሰብዓ ሊቃናትና የቩልጌት ትርጕም ግን፣ *የእግዚአብሔርን ሕዝብ ትገዛለህ ከከበቡት ጠላቶቹም እጅ ታድነዋለህ፤ አግዚአብሔር ለርስቱ ገዥ አድርጐ የሾመህ ምልክቱ ይህ ነው* የሚለውን ይጨምራሉ።
[የ]8 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል።

## ሳኦል ነገሠ

9ሳኦል ከሳሙኤል ተለይቶ ለመሄድ ፊቱን
በመለሰ ጊዜ፣ እግዚአብሔር የሳኦልን ልብ
ለወጠው፤ ምልክቱም ሁሉ በዚያ ዕለት
ተፈጸመ:: 10ጊብዓ በደረሱ ጊዜ የነቢያቱ
ጉባኤ አገኙት፤ የእግዚአብሔር መንፈስ በኀ
ይል ወረደበት፤ ከእነርሱም ጋር ትንቢት
ተናገረ:: 11ቀድሞ የሚያውቁት ሁሉ
ከነቢያቱ ጋር ትንቢት ሲናገር ባዩት ጊዜ፣
እርስ በርሳቸው፣ "የቂስን ልጅ ምን ነካው?
ሳኦልም ከነቢያት ወገን ነውን?" ሲሉ ተጠ
ያየቁ::
12በዚያ ነዋሪ የሆነ አንድ ሰው፣ "የእነርሱስ
አባት ማን ነው?" ብሎ መለሰ:: ስለዚህ፣
"ሳኦልም ከነቢያት ወገን ነውን?" የሚል
ምሳሌያዊ አነጋገር ሆነ:: 13ሳኦል ትንቢት
መናገሩን ከፈጸመ በኋላ ወደ ማምለኪ
ያው ኰረብታ ሄደ::
14በዚህ ጊዜ የሳኦል አጎት እርሱንና
አገልጋዩን፣ "የት ነበራችሁ?" ሲል ጠየቃቸው።
እርሱም፣ "አህዮቹን ፍለጋ ሄደን ነበር፤
እንደማይገኙ በተረዳን ጊዜ ግን ወደ ሳሙ
ኤል ሄድን" አለው::
15የሳኦል አጎትም፣ "እባክህ፣ ሳሙኤል
ያለህን ንገረኝ" አለው::
16ሳኦልም መልሶ፣ "አህዮቹ መገኘታቸውን
ገልጦ ነገረን" አለው። ይሁን እንጂ ስለ መንግሡ
ሳሙኤል የነገረውን ለአጎቱ አልተናገረም::
17ሳሙኤል የእስራኤልን ሕዝብ ወደ ም
ጽጳ ወደ *እግዚአብሔር ፊት* ጠርቶ፣
18እንዲህ አላቸው፤ "የእስራኤል አምላክ
*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ 'እስራኤልን
ከግብፅ አወጣ ሁት፤ ከግብፃውያን እጅ
ይጨቁኗችሁ ከነበሩት ከሌሎቹ
*መንግሥታት* ሁሉ እጅ *ታደግኋችሁ::"*
19ዛሬ ግን ከመከራችሁና ከጭ
ንቀ ችሁ ሁሉ የሚያድናችሁን
አምላካችሁን ንቃችሁ፤ 'የለም፤ ንጉሥ
አንግሥልን' አላ ችሁ:: ስለዚህ
በየነገዳችሁና በየጐሣችሁ ሆናችሁ *በእግዚ
አብሔር ፊት* ቅረቡ::
20ሳሙኤል የእስራኤልን ነገዶች ሁሉ
ባቀረበ ጊዜ፣ የብንያም ነገድ ተመረጠ::
21ከዚያም የብንያምን ነገድ በየጐሣው ወደ
ፊት አቀረበ፤ የማጥሪ ጐሣም ተመረጠ::
በመጨረሻም የቂስ ልጅ ሳኦል ተመረጠ::
እርሱ ግን ተፈልጎ አልተገኘም:: 22ሰዎቹም፣
"ሰውየው መጥቶአልን?' ሲሉ *እግዚአብሔ
ርን* ጠየቁ::
*እግዚአብሔርም፣* "አዎን፤ ነገር ግን በዕቃ
መካከል ተሸሽጎአል" አለ::
23እነርሱም ሮጠው ከተደበቀበት አመጡት፤

10፥9 ቀኁ6፡7፤ ዘጻ 13፥2
10፥10 ቀኁ5፤ ዘኍ 11፥25፤ 1ሳሙ11፥6
10፥11 ቀኁ12፤ 1ሳሙ19፥24፤ 2ነገ9፥11፤ኤር29፥26፤ ሆሴ9፥7፤ ማቴ 13፥54፤ ዮሐ7፥15
10፥12 ቀኁ 11
10፥13 1ሳሙ19፥23
10፥14 1ሳሙ9፥3፤ 14፥50
10፥16 1ሳሙ9፥3
10፥17 1ሳሙ 7፥5
10፥18 ዘፀ1፥14፤ ዘኍ 10፥9
10፥19 ዘኍ11፥20፤ ዘጸ 17፥14፤33፥5፤ ኢሱ7፥14፤1ሳሙ8፥5፤ መዝ7፥10፤18፥48፤ 68፥20፤145፥19
10፥21 አስ 3፥7፤ ምሳ16፥33
10፥22 ዘፍ25፥22፤ መሳ18፥5
10፥23 1ሳሙ 9፥2
10፥24 ዘዳ17፥15፤ 1ሳሙ9፥2፤2ሳሙ21፥6፤ 1ነገ1፥25፡34፡39፤ 2ነገ11፥12
10፥25 ዘዳ17፥14-20፤ 1ሳሙ8፥9፡11-18፤ 11፥14፤2ነገ11፥12
10፥26 ቀኁ5፤ መሳ19፥14፤20፥44
10፥27 ቀኁ4፤ ዘጻ 13፥13፤ 1ሳሙ 20፥7፤ 1ነገ10፥25፤ 2ዜና17፥5፤32፥23፤ መዝ68፥29
11፥1 ዘፍ19፥38፤ ዘፀ23፥32፤መሳ21፥8፤ 1ሳሙ12፥12፤31፥11፤ 2ሳሙ2፥4፡5፤10፥2፤ 17፥27፤21፥12፤ 1ዜና19፥1፤ኤር37፥1
11፥2 ዘፍ34፥15፤ ዘኍ 16፥14፤ 1ሳሙ 17፥26
11፥3 ቀኁ10፤ መሳ2፥16፤1ሳሙ8፥4
11፥4 ዘፍ27፥38፤ ዘኍ25፥6፤1ሳሙ 10፥5፡26
11፥6 መሳ3፥10
11፥7 መሳ19፥29፤ 20፥1፤21፥5፤ 1ሳሙ6፥14
11፥8 መሳ1፥4፤20፥2
11፥10 ቀኁ3

በሕዝቡ መካከል በቆመ ጊዜም ቁመቱ ከሌ
ሎቹ ሁሉ ይልቅ ከትከሻው በላይ ዘለግ
ያለ ነበር:: 24ሳሙኤልም መላውን ሕዝብ፣
"*እግዚአብሔር* የመረጠውን ሰው አያችሁን?
ከሕዝቡ ሁሉ የሚስተካከለው ማንም የለም"
አለ::
ከዚያም ሕዝቡ፣ "ንጉሡ ለዘላለም
ይኑር!" ብሎ ጮኸ::
25ሳሙኤልም ለንጉሥ የሚገባውን ወግና
ሥርዐት ለሕዝቡ ገልጦ ካስረዳ በኋላ በመ
ጽሐፍጽፎ *በእግዚአብሔር ፊት* አኖረው::
ከዚህ በኋላ ሳሙኤል እያንዳንዱን ሰው
ወደየቤቱ አሰናበተ::
26ሳኦልም ጊብዓ ወዳለው ቤቱ ሄደ፤
*እግዚአብሔርም* ልባቸውን የነካው ኀያላን
ሰዎች አብረውት ሄዱ:: 27አንዳንድ ምና
ምንቴ ሰዎች ግን፣ "እንዲህ ያለ ሰው እንዴት
ሊያድነን ይችላል?" በማለት ናቁት፤ ስጦታም
አላመጡለትም:: ሳኦል ግን ዝም አለ::

## ሳኦል የኢያቢስን ከተማ ታደገ

11 አሞናዊው ናዖስ ወጥቶ ኢያቢስ
ገለዓድን ከበባት፤ የኢያቢስም
ሰዎች ሁሉ፣ "ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን አድ
ርግ፣ እኛም እንገዛልሃለን" አሉት::
2አሞናዊው ናዖስ፣ "ከእናንተ ጋር ቃል
ኪዳን የማደርገው የእያንዳንዳችሁን ቀኝ
ዐይን አውጥቼ እስራኤልን ሁሉ ካዋረድሁ
በኋላ ብቻ ነው" ሲል መለሰ::
3የኢያቢስም ሽማግሌዎች፣ "ወደ መላው
እስራኤል መልእክተኞችን እንድንልክ የሰ
ባት ቀን ጊዜ ሰጠን፤ ሊታደገን የሚመጣ ሰው
ከሌለ፣ ለአንተ እንገዛለን" አሉት::
4መልእክተኞቹም ሳኦል ወዳለበት ወደ
ጊብዓ መጥተው ይህን ለሕዝቡ በተናገሩ
ጊዜ፣ ሕዝቡ ሁሉ ድምፃቸውን ከፍ አድ
ርገው አለቀሱ፤ 5በዚህ ጊዜ፣ ሳኦል በሬዎ
ቹን እየነዳ ከዕርሻ ተመለሰ፤ እርሱም፣
"ሕዝቡ የሚያለቅሰው ምን ሆኖ ነው?" ሲል
ጠየቀ:: እነርሱም የኢያቢስ ሰዎች ያሏቸውን
ነገሩት::
6ሳኦል ይህን በሰማ ጊዜ የእግዚአብሔር
መንፈስ በኀይል ወረደበት፤ እጅግ ተቈጣ::
7ጥንድ በሬዎች ወስዶ ቈራረጠ፤ *ሥጋቸውንም*
በመልእክተኞች እጅ ልኮ፣ "ሳኦልንና
ሳሙኤልን የማይከተል ሰው በሬው እንደዚህ
ይቈራረጣል" ሲል በመላው እስራኤል
አስነገረ:: ታላቅ ፍርሀት *ከእግዚአብሔር*
ዘንድ በሕዝቡ ላይ ወደቀ፤ ሕዝቡም እንደ
አንድ ሰው ሆኖ ወጣ:: 8ሳኦል ቤዜቅ በተባለ
ስፍራ ሰራዊቱን በሰበሰበ ጊዜ፤ ቍጥራቸው
ከእስራኤል ሦስት መቶ ሺህ፣ ከይሁዳም
ሠላሳ ሺህ ነበር::

9ከዚያ ለመጡትም መልእክተኞች፣ “ለኢ
ያቢስ ገለዓድ ሰዎች፣ ‘ነገ ፀሓይ ሞቅ
በሚልበት ጊዜ ነጻ ትሆናላችሁ’ ብላችሁ
ንገሯቸው” አሏቸው። መልእክተኞቹም
ሄደው ለኢያቢስ ሰዎች ይህንኑ በነገሯ
ቸው ጊዜ በደስታ ፈነደቁ። 10ለአሞናውያ
ንም፣ “እኛ ነገ እጃችንን እንሰጣችኋለን፤
እናንተም መልካም መስሎ የታያችሁን ሁሉ
ልታደርጉብን ትችላላችሁ” አሏቸው።
11በማግስቱ ሳኦል ሰራዊቱን ከሦስት
ቦታ ከፈለው፤ ሊነጋጋ ሲል፣ የአሞናውያንን
ሰፈር ጥሰው በመግባት ፀሓይ ሞቅ እስኪል
ድረስ ፈጇቸው። በሕይወት የተረፉትም
ሁለት እንኳን ሆነው በአንድ ላይ ሊሆኑ
እስከማይችሉ ድረስ ተበታተኑ።

## የሳኦል ንጉሥነት ተረጋገጠ

12ሕዝቡ ሳሙኤልን፣ “ሳኦል እንዴት ሊገ
ዛን ይችላልሄ’ ያሉት እነማን ነበሩ? እነዚህን
ሰዎች እንገድላቸው ዘንድ አምጣቸው” አሉት።
13ሳኦል ግን፣ “ይህ ዕለት እግዚአብሔር
እስራኤልን የታደገበት ቀን ስለሆነ ፣በዛ
ሬው ዕለት ማንም ሰው አይገደልም” አለ።
14ከዚያም ሳሙኤል ሕዝቡን፣ “ኑና ወደ
ጌልገላ እንሂድ፤ ንግሥናውን እናጽና” አለ።
15ሕዝቡ ሁሉ ወደ ጌልገላ ሄደ፤ የሳኦልንም
ንጉሥነት በእግዚአብሔር ፊት አጸና። በዚ
ያም ሕዝቡ የኅብረት መሥዋዕት[ደ] በእግዚ
አብሔር ፊት አቀረበ፤ ሳኦልና እስራኤላ
ውያንም ሁሉ ታላቅ በዓል አደረጉ።

## ሳሙኤል ያደረገው የመሰነባበቻ ንግግር

12 ሳሙኤል ለመላው እስራኤል እን
ዲህ አለ፤ “እነሆ፤ ያላችሁኝን ሁሉ
ሰምቼ ንጉሥ አንግሼላችኋለሁ። 2ንጉሥ
ሆኖ የሚመራችሁንም ሰው እነሆ፤ አግኝታ
ችኋል። እኔም ዕድሜዬ ገፍቶአል፤ ጠ
ጕሬም ሸብቶአል፤ ልጆቼም አብረዋችሁ
አሉ፤ ከወጣትነት ጊዜዬ ጀምሮ እስከ አሁን
ድረስ ስመራችሁ ቈይቻለሁ። 3እነሆ፤
ከፊታችሁ ቆሜአለሁ፤ በእግዚአብሔርና
እርሱ በቀባው ፊት መስክሩብኝ፤ የማንን
በሬ ወሰድሁ? የማንን አህያ ወሰድሁ?
ማንን አታለልሁ? በማንስ ላይ ግፍ ሠራ
ሁ? አይቶ እንዳላየ ለመሆንስ ከማን እጅ
ጉቦ ተቀበልሁ? ከእ ነዚህ ሁሉ አንዱን
እንኳ አድርጌ ከሆነ እመልስላችኋለሁ።”
4እነርሱም፣ “አላታለልኸንም ወይም
ግፍ አልሠራህብንም፤ ከማንም እጅ አንዳች
ነገር አልተቀበልህም” ብለው
መለሱለት።
5ሳሙኤልም፣ “በእጄ ምንም እንዳላገኛችሁ
እግዚአብሔርና እርሱ የቀባው ዛሬ በእና
ንተ ላይ ምስክሮች ናቸው” አላቸው።

11፥11 ዘፍ19፥38፤ መሳ7፥16
11፥12 ዘዳ13፥13፤ ሉቃ19፥27
11፥13 1ሳሙ19፥5 ፤ 2ሳሙ19፥22፤ 1ዜና11፥14
11፥14 ኢሳ10፥43፤ 1ሳሙ10፥8፡25
11፥15 ኢሱ5፥9፤ 1ሳሙ12፥1፡ 2ሳሙ19፥15
12፥1 1ሳሙ8፥7፤ 11፥15
12፥2 1ሳሙ8፥3፡5
12፥3 ዘፀ18፥21፤ 20፥17፤ዘሌ25፥14፤ ዘኍ16፥15፤1ሳሙ8፥3 ፤9፥16፤24፥6፤26፥9፡ 11፤2ሳሙ1፥14፤ 19፥21፤መዝ105፥15፤ ሐሥ20፥33
12፥5 ዘፍ31፥50፤ ዘፀ22፥4፤ሐሥ23፥9፤ 24፥20
2፥6 ዘፀ3፥10፤ ሚክ 6፥4
12፥7 ኢሱ24፥1፤ መሳ5፥11ኢሳ1፥18፤ 3፥14፤ኤር2፥9፤ 25፥31፤ሕዝ17፥20፤ 20፥35፤ሚክ 6፥1-5
12፥8 ዘፍ46፥6፤ ዘፀ2፥23፤3፥10፤4፥16
12፥9 ዘዳ32፥18፡ 30፤ኢሱ11፥1፤ መሳ 3፥7፡12፤4፥2፤10፥7
12፥10 መሳ3፥9 1ሳሙ7፥3፤8፥8
12፥11 መሳ4፥6፤ 6፥32፤11፥1፤1ሳሙ7፥15
12፥12 1ሳሙ8፥5፤ 11፥1፤25፥30፤2ሳሙ 5፥2፤1ዜና5፥2
12፥13 1ሳሙ8፥5፤ 9፥20
12፥14 ኢሱ24፥14 ኤር4፥17፤ሰቆ1፥18
12፥15 ዘሌ26፥16፤ ኢሱ24፥20፤ኢሳ 1፥20፤ ኤር4፥17፤ 26፥4
12፥16 ዘፀ14፥13፡14
12፥17 ዘፍ7፥12፤ 30፥14፤ዘፀ9፥18፡23፤ 1ሳሙ2፥10፤6፥13፤ 8፥6፤1ነገ18፥42፤ ኢዮ37፥13፤ምሳ26፥1፤ ያዕ5፥18
12፥18 ዘፍ3፥10፤

እነርሱም፣ “እርሱ ምስክር ነው” አሉ።
6ከዚያም ሳሙኤል ለሕዝቡ እንዲህ
አለ፤ “ሙሴንና አሮንን የመረጠ፣ የቀድሞ
አባቶቻችሁንም ከግብፅ ያወጣ እግዚአብሔር
ነው። 7አሁንም ለእናንተና ለአባ ቶቻችሁ
እግዚአብሔር ስላደረገው የጽድቅ ሥራ
ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ስለ ምሟገታችሁ
በዚህ ቁሙ።
8“ያዕቆብ ወደ ግብፅ ከገባ በኋላ፣ አባቶ
ቻችሁ እግዚአብሔር እንዲረዳቸው ወደ
እርሱ ጮኹ፤ እግዚአብሔርም የቀድሞ
አባቶቻችሁን ከግብፅ ምድር አውጥተው
በዚህ ስፍራ እንዲኖሩ ያደረጉትን ሙሴንና
አሮንን ላከላቸው።
9“እነርሱ ግን አምላካቸውን እግዚአብሔ
ርን ረሱት፤ ስለዚህ ለሐጾር የጦር አዛዥ
ለሲሣራ፣ ለፍልስጥኤማውያንና ለሞዓብ
ንጉሥ አሳልፎ ሸጣቸው። 10እነርሱም፣ ‘ኀጢአት
ሠርተናል፤ እግዚአብሔርን ትተን በአሊ
ምንና አስታሮትን አምልከናል። አሁን
ግን ከጠላቶቻችን እጅ ታደገን፤ እኛም
አንተን እናመልካለን’ ሲሉ ወደ እግዚአብሔር
ጮኹ። 11ከዚያም እግዚአብሔር ይሩብኣልን[ጀ]፣
ባርቅን[ገ]፣ ዮፍታሔንና ሳሙኤልን[ጠ] ልኮ
በሰላም ትኖሩ ዘንድ በዙሪያችሁ ካሉት ጠላቶ
ቻችሁ እጅ ታደጋችሁ።
12የአሞናውያን ንጉሥ ናዖስ እንደ መጣ
ባችሁ ባያችሁ ጊዜ ግን፣ ምንም እንኳ
አምላካችሁ እግዚአብሔር ንጉሣችሁ ቢ
ሆንም፣ ‘አይሆንም፤ የሚገዛን ንጉሥ
እንፈልጋለን’ አላችሁ። 13“አሁንም የጠ
የቃችሁትና የመረ ጣችሁት ንጉሥ ይኸ
ው፤ እነሆ፣ እግዚአ ብሔር በላያችሁ
ንጉሥ አንግሦአል። 14እግ ዚአብሔርን
የምትፈሩና የምታመልኩ፣ የም ትታዘዙትና
በትእዛዛቱ ላይ የማታምፁ ከሆነ፣ እንዲሁም
እናንተና በእናንተ ላይ የነገሠው ንጉሥ
አምላካችሁን እግዚአብሔርን ከተከተላችሁ
መልካም ይሆንላችኋል። 15እግዚአብሔርን የ
ማትታዘዙና በትእዛዛቱም ላይ የምታምፁ
ከሆነ ግን፣ እጁ በአባቶቻችሁ ላይ እንደ
ነበረች ሁሉ በእናንተም ላይ ትሆናለች።
16“ስለዚህ ጸንታችሁ ቁሙ፤ እግዚአብሔር
በዐይናችሁ ፊት የሚያደርገውንም ይህን ታላቅ
ነገር ተመልከቱሄ 17አሁን የስንዴ መከር ጊ
ዜ አይደለምን? እኔ ነጐድጓድና ዝናብ
እንዲልክ ወደ እግዚአብሔር እጮኻለሁ፤
እናን ተም ንጉሥ እንዲነግሥላችሁ በመጠ
የቃችሁ

[ጀ]11 ጌድዎን በመባል ይታወቃል።
[ገ]11 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት የሱርስት ቅጆች ከዚህ ጋር ይስ ማማሉ፤ ዕብርይስጡ ግን፣ ቢዳን ይላል
[ጠ]11 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት የሱርስቱ ቅጅ ግን ሳንሶ ይላሉ።

*በእግዚአብሔር* ፊት የቱን ያህል የከፋ
ድርጊት እንደፈጸማችሁ ያን ጊዜ ታውቃላ
ችሁ፡፡”
[18]ከዚህ በኋላ ሳሙኤል ወደ *እግዚአብሔር*
ጮኸ፤ በዚያኑ ዕለት *እግዚአብሔር* ነጐድ
ጓድና ዝናብ ላከ፡፡ ስለዚህ ሕዝቡ ሁሉ
*እግዚአብሔርን*ና ሳሙኤልን እጅግ ፈሩ፡፡
[19]ሕዝቡም ሁሉ ሳሙኤልን፣ “ሌላው በደ
ላችን ሳያንስ፣ ንጉሥ እንዲነግሥልን በመጠ
የቃችን ተጨማሪ ክፋት ስላደረግን እንዳን
ሞት፣ ለአገልጋዮችህ ወደ አምላክህ ወደ
*እግዚአብሔር* ጸልይልን” አሉት፡፡
[20]ሳሙኤልም እንዲህ ብሎ መለሰ፤ “አት
ፍሩ፤ ይህን ሁሉ ክፋት አድርጋችኋል፤ ሆኖም
*እግዚአብሔርን* በፍጹም ልባችሁ አምል
ኩት እንጂ *እግዚአብሔርን* ከመከተል ፈቀቅ
አትበሉ፡፡ [21]ሊጠቅሟችሁ ወይም ሊያድኗችሁ
የማይችሉ ምናምንቴ ነገሮችን አትከተሉ፤
ከንቱ ናቸውና፡፡ [22]*እግዚአብሔር* የራሱ
ሕዝብ ያደርጋችሁ ዘንድ ስለ ወደደ፣ ስለ
ታላቅ ስሙ ሲል *እግዚአብሔር* ሕዝቡን
አይተውም፡፡ [23]ከዚህም በላይ እኔ ለእናንተ
ከመጸለይ ወደ ኋላ በማለት *እግዚአብሔ
ርን* መበደል ከእኔ ይራቅ፤ እኔ መልካምና
ቅን የሆነውን መንገድ አስተምራችኋለሁ፡፡
[24]ብቻ *እግዚአብሔርን* ፍሩ፤ በፍጹም ልባችሁ
በታማኝነት አምልኩት፤ ያደረገላችሁንም
ታላላቅ ነገሮች አትርሱ፡፡ [25]በክፉ ሥራችሁ
ብትጸኑ ግን፣ እናንተም ንጉሣችሁም ትጠ
ፋላችሁ፡፡”

## ሳሙኤል ሳኦልን መገሠጹ

# 13

ሳኦል በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሠላሳ[ጨ]
ዓመት ነበረ፤ እስራኤልንም አርባ[ጸ]
ሁለት ዓመት ገዛ፡፡
[2]ሳኦል[ጸ] ከእስራኤል ሦስት ሺህ ሰዎች
መረጠ፡፡ ሁለቱ ሺህ በማክማስና በኰረብታ
ማው አገር በቤቴል ከሳኦል ጋር፣ አንዱ
ሺህ ደግሞ በብንያም ግዛት በጊብዓ ከዮና
ታን ጋር ነበሩ፡፡ የቀሩትን ሰዎች ግን ወደ
የቤታቸው እንዲሄዱ አሰናበተ፡፡
[3]ዮናታን ጊብዓ የነበረውን የፍልስጥኤማ
ውያን ጦር ሰፈር መታ፤ ፍልስጥኤማውያ
ንም ይህን ሰሙ፡፡ ሳኦልም፣ “ዕብራውያን ይስ
ሙትሄ” በማለት በምድሪቱ ሁሉ መለከት
አስነፋ፡፡ [4]ስለዚህ እስራኤላውያን ሁሉ፣
“ሳኦል የፍልስጥኤማውያንን ጦር ሰፈር መታ፤
እስራኤልም በፍልስጥኤማውያን ዘንድ እንደ
ርኩስ ተቈጥራ ተጠላች” የሚለውን ወሬ
ሰሙ፤ ሕዝቡም ሳኦልን ለመከተል ወደ
ጌልገላ ተሰበሰቡ፡፡
[5]ፍልስጥኤማውያን ሦስት[ፀ] ሺህ
ሠረገሎች፣ ስድስት ሺህ ፈረሰኞች ቍጥሩ
እንደ ባሕር አሸዋ የበዛ ሰራዊት ይዘው እስራ
ኤልን ለመ ውጋት ተሰበሰቡ፤ ወጥተውም
ከቤት አዌን በስተ ምሥራቅ ባለችው በ
ማክማስ ሰፈሩ፡፡ [6]እስራኤላውያን፣ ያሉበት
ሁኔታ እጅግ የሚያሠጋ መሆኑንና ሰራ
ዊታቸውም በከባድ ጭንቀት ውስጥ
መግባቱን ባዩ ጊዜ፣ በየዋ ሻውና
በየቍጥቋጦው፣ በየዐለቱ መካከ ልና
በየገደሉ እንዲሁም በየጕድጓዱ ሁሉ
ተደበቁ፡፡ [7]ከዕብራውያንም አንዳንዶቹ ዮር
ዳኖስን ተሻግረው ወደ ጋድና ወደ ገለዓድ
ምድር ሄዱ፡፡
ሳኦል ግን በጌልገላ ቈየ፣ አብሮት የነ
በረውም ሰራዊት ሁሉ በፍርሀት ይንቀጠ
ቀጥ ነበር፡፡ [8]እርሱም ሳሙኤል በሰጠው ቀጠሮ
መሠረት ሰባት ቀን ጠበቀው፡፡ ነገር ግን
ሳሙኤል ወደ ጌልገላ አልመጣም፤ የሳ
ኦልም ሰራዊት መበታተን ጀመረ፡፡ [9]በዚህ
ጊዜ ሳኦል፣ “የሚቃጠለውን መሥዋዕትና
የኅብረት መሥዋዕቱን[ፈ] አምጡልኝ” አለ፡፡
ከዚያም የሚቃጠለውን መሥዋዕት አቀረበ፡፡
[10]ልክ መሥዋዕቱን አቅርቦ እንዳበቃ፣
ወዲያውኑ ሳሙኤል መጣ፤ ሳኦልም ሊ
ቀበለው ወጣ፡፡
[11]ሳሙኤልም፣ “ያደረግኸው ምንድን
ነው?” ሲል ጠየቀው፡፡
ሳኦልም እንዲህ ሲል መለሰ፤ ሰራዊቱ
መበታተኑን፣ አንተም በቀጠርኸው ጊዜ
አለመምጣትህን፣ ፍልስጥኤማውያንም በማ
ክማስ መሰብሰባቸውን አየሁ፤ [12]‘ስለዚህ ፍል
ስጥኤማውያን ወርደው ወደ ጌልገላ ይመጡ
ብኛል፤ እኔም *የእግዚአብሔርን* ሞገስ አልለ
መንሁም’ ብዬ አሰብሁ፡፡ ስለዚህ የሚቃጠል
መሥዋዕት ማቅረብ ግድ ሆነብኝ፡፡”
[13]ሳሙኤልም እንዲህ አለ፤ “የማይገባህን
አደረግህ፤ አምላክህ *እግዚአብሔር* የሰጠ
ህን ትእዛዝ አልጠበቅህም፤ ጠብቀኸው
ቢሆን
ኖሮ፣ መንግሥትህን በእስራኤል ላይ
ለዘላለም ባጸናልህ ነበር፤ [14]አሁን ግን
መንግሥትህ አይጸናም፤ እነሆ፣ *እግዚ
አብሔር* እንደ ልቡ የሚሆንለትን ሰው
አግኝቶአል፤ አንተ *የእግዚአብሔርን* ትእዛዝ
ባለመጠበቅህም፣ እርሱን የሕዝቡ መሪ
አድርጎ መርጦታል፡፡”

ዘፀ14፥31፤መዝ99፥6
**12፥19** ዘፀ8፥8፤
ዘዳ9፥19፤1ሳሙ7፥8፤
ኤር37፥3፤ያዕ5፥18፤
1ዮሐ5፥16
**12፥20** ዘፀ32፥30
**12፥21** ዘዳ11፥16፤
ኢሳ40፥20፤41፥24፡
29፤44፥9፤ኤር2፥5፡
11፤14፥22፤16፥16፤
ዕን2፥18፤ዮሐ2፥8፤
ሐሥ14፥15
**12፥22** ዘሌ26፥11፤
ዘዳ7፥7፤31፥6፤
ኢሱ7፥9፤2ሳሙ7፥23፤
መዝ25፥11፤106፥8
ኢሳ48፥9፡11፤
ኤር14፥7፤ዳን9፥19፤
ዮሐ 7፥12፤1ጴጥ2፥9
**12፥23** ዘኍ11፥2፤
1ሳሙ1፥20፤7፥8፤
1ነገ8፥36፤መዝ25፥4፤
34፥11፤86፥11፤
94፥12፤ምሳ4፥11፤
ሮሜ1፥10
**12፥24** ዘዳ6፥2፡5፤
10፥21፤ኢሱ24፥14፤
ኢዮ34፥27፤መክ12፥3፤
ኢሳ5፥12፤
22፥11፤26፥10
**12፥25** ዘዳ28፥36፤
ኢሱ24፥20፤1ሳሙ
31፥1-5፤1ነገ14፥10
**13፥2** ቀኍ5፥11፡
15፡23፤መሳ19፥14፤
ነህ11፥31፡ኢሳ10፥28
**13፥3** ዘሌ25፥9፤ኢሱ
18፥24፤መሳ3፥27፤
1ሳሙ10፥5
**13፥4** ዘፍ34፥30
**13፥5** ቀኍ2፡ኢሱ
7፥2፤11፥4፤1ሳሙ
17፥1፤ራእ20፥8
**13፥6** መሳ6፥2፤
1ሳሙ14፥11፡22፤
ሕዝ 33፥27
**13፥7** ዘፍ35፥5፤ዘፀ
19፥16፤ዘኍ32፥33
**13፥8** 1ሳሙ10፥8
**13፥9** ዘዳ12፥5-
14፤2ሳሙ24፥25፤
1ነገ3፥4
**13፥10** 1ሳሙ15
፥13፤ 25፥14
**13፥11** ቀኍ2
**13፥12** ዘዳ4፥29፤
ኢሱ10፥43፤
መዝ 119፥58፤
ኤር26፥19
**13፥13** ቀኍ14፤ኢሱ
22፥16፤1ሳሙ15፥23፡
24፤2ሳሙ7፥15፤
1ዜና10፥13፤16፥9፤
መዝ72፥5
**13፥14** 1ሳሙ15፥26፡
28፤16፥1፤18፥8፤
24፥20፤25፥30፤
2ሳሙ 5፥2፤6፥21፤
12፥9፤1ነገ13፥21፤
1ዜና10፥14፤
መዝ 18፥43፤
ኢሳ16፥5፤
55፥4፤ኤር30፥9፤

[ጨ]1 ጥንታዊ ያልሆኑ ጥቂት የሰብዓ ሊቃናት ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን *ሠላሳ* የሚለውን አይጨምርም
[ጸ]1 የዐሥር ብዜት የሆኑት ቍጥሮች በተመለከተ በሐሥ13፥21 ይመ፤ ዕብራይስጡ ግን *አርባ* የሚለውን አይጨምርም፡፡
[ጸ]1፡2 ወይም እርሱ በእስራኤል ላይ ለሁለት ዓመት ከነገሠ በኋላ
[ፀ]5 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞችና የሱርስቱ ቅጅ ከዚህ ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን *ሠላሳ ሺህ* ይላል፡፡

[ፊ]9 በትውፊት የሰላም መሥዋዕት ይባላል።

15ከዚያ በኋላ ሳሙኤል ከጌልገላ ተነ
ሥቶ[ፐ] በብንያም ግዛት ወዳለው ወደ ጊብዓ
ወጣ። ሳኦልም አብረውት የነበሩትን ሰዎች
ቈጠራቸው፤ ብዛታቸውም ስድስት መቶ
ያህል ነበረ።

### እስራኤል ያለ ጦር መሣሪያ

16ፍልስጥኤማውያን በማክማስ ሰፍረው
በነበረበት ጊዜ ሳኦል፣ ልጁ ዮናታንና አብ
ረዋቸው የነበሩት ሰዎች በብንያም ግዛት
በምትገኘው በጊብዓ ነበሩ። 17በሦስት
ምድብ የተከፈሉ ወራሪዎች ከፍልስጥኤ
ማውያን ሰፈር ወጡ፤ አንዱ ምድብ
በሦጋል ግዛት ወደሚገኘው ወደ ዖፍራ
አቀና፤ 18ሌላው ወደ ቤትሖሮን፣
ሦስተኛው ደግሞ በምድረ በዳው ትይዩ
ካለው ከስቦይም ሸለቆ ቍል ቍል
ወደሚያሳየው ድንበር ዞረ።
19ፍልስጥኤማውያን፣ “ዕብራውያን ሰይፍ
ወይም ጦር ለራሳቸው አይሥሩ” ብለው ስለ
ነበር፣ በመላው የእስራኤል ምድር ብረት
ቀጥቃጭ አልተገኘም። 20ስለዚህ እስራኤ
ላውያን ሁሉ፣ ማረሻቸውንና ዶማቸውን
ለማሾል፣ ጠገራቸውንና ማጭዳቸውን ለማሳል
ወደ ፍልስጥኤማውያን ይወርዱ ነበር። 21
ማረሻና ዶማ ለማሾል የሚከፈለው ዋጋ
ሁለት ሦስተኛ ሰቅል[ሀ] ሲሆን፣ መንሽና ጠ
ገራ እንዲሁም የበሬ መንጃ ለማሾል ደግሞ
አንድ ሦስተኛ ሰቅል[ለ] ነበር።
22ስለዚህ ጦርነቱ በተደረገበት ዕለት ከሳ
ኦልና ከልጁ ከዮናታን በስተቀር፣ አብረዋ
ቸው ከነበሩት ወታደሮች መካከል ሰይፍ
ወይም ጦር የያዘ አንድም ሰው
አልነበረም።

### ዮናታን በፍልስጥኤማውያን ላይ አደጋ መጣሉ

23በዚያ ጊዜ አንድ የፍልስጥኤማውያን
ጭፍራ ወደ ማክማስ መተላለፊያ ወጥቶ ነበር።

14 አንድ ቀን የሳኦል ልጅ ዮናታን
ወጣት ጋሻ ጃግሬውን፣ “ና በሌላ
በኩል ወዳለው የፍልስጥኤማውያን ጦር ሰፈር
እንሻገር” አለው። ይህን ግን ለአባቱ አልነ
ገረውም ነበር።
2ሳኦልም በጊብዓ ዳርቻ መጌዶን በተባለ
ስፍራ ከአንድ የሮማን ዛፍ ሥር ሰፍሮ ነበር፤
ስድስት መቶ ያህል ሰዎችም አብረውት
ነበሩ፤ 3ኤፉድ ይለብስ የነበረውም አኪያ
በመካከላቸው ነበር። እርሱም በሴሎ የእግ
ዚአብሔር ካህን የነበረው የዔሊ ልጅ፣
የፊንሐስ ልጅ የኢካቦድ ወንድም የአኪ
ጦብ ልጅ ነበር። ዮናታን አለመኖሩን ግን
ያወቀ ሰው አልነበረም።

ሕዝ34፥23-24፤ 37፥24፤ዳን9፥25፤ ሆሴ3፥5፤13፥11፤ ሚክ5፥2፤ ሐሥ7፥46፤13፥22
13፥15 ቈላ2፤ 1ሳሙ14፥2
13፥16 ኢሱ18፥24
13፥17 ኢሱ18፥23 ፤1ሳሙ14፥15
13፥18 ኢሱ10፥10፤ ነህ11፥34
13፥19 ዘፍ4፥22፤ ዘኊ25፥7
13፥22 ዘኊ25፥7፤ 1ሳሙ14፥6፤17፥47፤1 ዜና9፥39፤ዘካ4፥6
13፥23 ቈላ2፤ 1ሳሙ14፥4
14፥2 ዘፀ28፥33፤ መሳ4፥5፤1ሳሙ 13፥15፤ኢሳ10፥28
14፥3 ዘፍ35፥18፤ 1ሳሙ1፥3፤22፥11፡ 20፤መዝ78፥60
14፥4 1ሳሙ13፥23
14፥5 ኢሱ18፥24
14፥6 መሳ7፥4፤ 14፥3፤1ሳሙ13፥22፤ 17፥26፡36፤31፥4፤ 1ነገ 19፥12፤መዝ 33፥16፤ኤር9፥26፤ ሕዝ28፥10፤ማቴ 19፥26፤ዕብ11፥34
14፥10 ዘፍ24፥14፤ ኢሱ2፥24
14፥11ዘፍ14፥13፤1ሳ ሙ13፥6
14፥12 መሳ8፥16፤ 1ሳሙ17፥46፤ 2ሳሙ5፥24
14፥15 ዘፍ 35፥5፤ ዘፀ14፥24፤19፥16፤ 1ሳሙ13፥17፤2ነገ 7፥5-7

4ዮናታን ወደ ፍልስጥኤማውያን ጦር
ሰፈር ለመሻገር በፈለገበት መተላለፊያ ግራና
ቀኝ አንዱ ቦጼጽ ሌላው ሴኔ የተባሉ ሁለት
ሾጣጣ ዐለቶች ነበሩ። 5አንዱ ዐለት በስተ
ሰሜን በኩል በማክማስ አንጻር፣ ሌላው
ደግሞ በስተ ደቡብ በኩል በጊብዓ አንጻር
ይገኝ ነበር።
6ዮናታን ወጣት ጋሻ ጃግሬውን፣ “ና፤
ወደነዚያ ሸለፈታሞች ጦር ሰፈር እንሻገር፤
ምናልባትም እግዚአብሔር ይዋጋልን ይሆ
ናል፤ በብዙም ሆነ በጥቂት ለማዳን እግዚአ
ብሔርን የሚያግደው የለምና” አለው።
7ወጣቱም ጋሻ ጃግሬ፣ “በልብህ ያሰብኸ
ውን ሁሉ አድርግ፤ ወደ ኋላም አትበል፤
እኔም በሙሉ ልብ ካንተው ጋር ነኝ” አለው።
8ዮናታንም እንዲህ አለው፣ “እንግዲያውስ
ና፤ ወደ ሰዎቹ እንሻገርና እንታያቸው።
9እነርሱም፣ ‘ወደ እናንተ እስክንመጣ እዚ
ያው ጠብቁን’ ካሉን፣ ባለንበት ሆነን
እንጠብቃቸዋለን፤ ወደ እነርሱም አንወጣም።
10ነገር ግን፣ ‘ወደ እኛ ውጡ’ ካሉን፣ እግ
ዚአብሔር እነርሱን በእጃችን አሳልፎ
የሰጠን ለመሆኑ ምልክቱ ይህ ስለ ሆነ፣
ወደ እነርሱ እንወጣለን።”
11ሁለቱም ለፍልስጥኤማውያን ጭፍራ
በታዩ ጊዜ፣ ፍልስጥኤማውያን፣ “እነሆ፤ ዕብ
ራውያን ከተደበቁባቸው ጕድጓዶች እየወጡ
ነው” አሉ። 12የፍልስጥኤም ጦር ሰፈር ሰዎ
ችም፣ “ኑ ወደ እኛ ውጡ፤ አንድ ነገር እናሳ
ያችሁ” ሲሉ በዮናታንና በጋሻ ጃግሬው ላይ
ጮኹባቸው።
ስለዚህ ዮናታን ጋሻ ጃግሬውን፣ “ተከ
ትለኸኝ ውጣ፤ እግዚአብሔር በእስራኤላ
ውያን እጅ አሳልፎ ሰጥቶአቸዋልና” አለው።
13ዮናታን በእጁና በእግሩ ተፍጨርጭሮ፣
ጋሻ ጃግሬውን በማስከተል ወጣ። ፍልስጥ
ኤማውያንም በዮናታን እጅ ወደቁ፤ ጋሻ
ጃግሬውም ከበስተኋላው እየተከተለ ገደላቸው።
14ዮናታንና ጋሻ ጃግሬው በመጀመሪያው ቀን
ባደረጉት ግዳይ አንድ ጥማድ በምታውል
የዕርሻ ቦታ[ሐ] ላይ ሃያ ያህል ሰዎች ገደሉ።

### የፍስጥኤማውያን መሸነፍ

15በሰፈር በዕርሻ ላይና በሕዝብ ሁሉ
መካከል ሽብር ሆነ፤ ከተማ ጠባቂዎችና አደ
ጋጣዮችም ሁሉ ተቀጠቀጡ፤ ምድሪቱም ተና
ወጠች፤ ሽብሩም ከእግዚአብሔር ዘንድ
የተላከ ነበር[መ]።

[ፐ]15 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ግን፣ *ከጌልገላ ተነሥተው ወደ መንገድ ሄዱ፤ ከጦሩ ጋር ለመገናኘት የተቀረው ሕዝብ ሳኦልን ተከተለ፤ ከጌልገላም ወጥቶ ሄደ* ይላል።
[ሀ]21 በዕብራይስጡ፣ *ፒም* ይባላል፤ 8ግራም ያህል ነው
[ለ]21 4 ግራም ያህል ነው።
[ሐ]14 ዕብራይስጡ ግማሽ ቀንበር ይላል፤ ይኸውም በጥማድ በሬ በአንድ ቀን የሚታረሰውን መሬት የሚያሳይ ነው
[መ]15 ወይም ከፍተኛ የሆነ

[16]በብንያም ግዛት በጊብዓ የነበሩ የሳኦል
ዘቦች፣ የፍልስጥኤም ሰራዊት በየአቅጣ
ጫው መበታተኑን አዩ። [17]ሳኦልም አብረ
ውት የነበሩትን ሰዎች፣ "እስኪ፣ ሰራዊቱን
ቍጠሩና ማን ከዚህ እንደ ሄደ እዩ" አላ
ቸው። ይህን ባደረጉ ጊዜም ዮናታንና ጋሻ
ጃግሬው በዚያ አልነበሩም።
[18]ሳኦልም አኪያን፣ "የእግዚአብሔርን ታቦት
ወደዚህ አምጣ" አለው፤ በዚያን ጊዜ ታቦቱ
በእስራኤላውያን ዘንድ ነበር[ሠ]። [19]ሳኦል
ለካህኑ በመናገር ላይ ሳለ፣ በፍልስጥኤ
ማውያን ሰፈር ሁካታው እየጨመረ ሄደ።
ስለዚህ ሳኦል ካህኑን፣ "እጅህን መልስ"
አለው።
[20]ከዚያም ሳኦልና ሰዎቹ ተሰብስበው
ወደ ውጊያው ሄዱ። እነርሱም ፍልስጥኤ
ማውያን በሰይፋቸው እየተጨፋጨፉ በታላቅ
ትርምስ ላይ ሆነው አገኟቸው። [21]እነዚያ
ቀድሞ ከፍልስጥኤማውያን ጐን ተሰልፈው
የነበሩትና አብረዋቸውም ወደ ሰፈራቸው
የወጡት ዕብራውያን ከሳኦልና ከዮናታን
ጋር ወደ ነበሩት እስራኤላውያን ገቡ።
[22]በኰረብታማው የኤፍሬም አገር ተሸሽገው
የነበሩት እስራኤላውያን ሁሉ ፍልስጥኤ
ማውያኑ በሽሽት ላይ መሆናቸውን በሰሙ ጊዜ፣
አጥብቀው በመከታተል አሳደዷቸው። [23]በዚያ
ቀን *እግዚአብሔር* እስራኤልን ታደገው፤
ጦርነቱም ከቤትአዌን ዘልቆ ሄደ።

### ዮናታን ማር በላ

[24]ሳኦል፣ "ዛሬ ጠላቶቼን ከመበቀሌ በፊት
እስከ ማታ ድረስ እህል የሚበላ ሰው የተረገመ
ይሁን" ብሎ ሕዝቡን አምሎ ስለ ነበር፣ በዚ
ያች ዕለት የእስራኤል ሰዎች ተጨንቀው
ዋሉ፤ ስለዚህ ከሕዝቡ አንድም እህል የቀ
መሰ አልነበረም።
[25]ሰራዊቱ[ረ] ሁሉ ወደ ጫካ ሲገባ፣ ማር
በመሬቱ ላይ ይታይ ነበር። [26]ሕዝቡ ወደ
ጫካው በገባ ጊዜ፣ የማሩ ወለላ እየተንጠ
ባጠበ መውረዱን አየ፤ ሆኖም መሓላውን
ፈርቶ ስለ ነበር፣ እጁን ወደ አፉ የዘረጋ
ማንም አልነበረም። [27]ነገር ግን ዮናታን
አባቱ ሕዝቡን በመሐላ ማሰሩን አልሰማም
ነበር። ስለዚህ በእጁ የያዘውን ዘንግ ጫፍ
በማሩ ወለላ ውስጥ በማስገባት እጁን ወደ
አፉ አደረገ፤ ዐይኑም በራ። [28]ከዚያም አንዱ
ወታደር፣ "አባትህ ሰራዊቱን፣ 'ዛሬ እህል
የሚቀምስ ማናቸውም ሰው የተረገመ
ይሁን!' በማለት በጽኑ መሓላ አስሮአል።
ሰው ሁሉ የተዳከመው በዚሁ ምክንያት
ነው" አለው።
[29]ዮናታንም እንዲህ አለ፤ "አባቴ በምድሪቱ
ላይ ችግር ፈጥሮአል፤ ከዚህ ማር ጥቂት
በቀመስሁ ጊዜ ዐይኔ እንዴት እንደ በራ
ተመልከቱ![ሰ] [30]ሕዝቡ ከጠላቶቻቸው እጅ
ከወሰዱት ምርኮ ዛሬ በልተው ቢሆን ኖሮ
ምንኛ በተሻለ ነበር፤ የተገደሉትም ፍልስ
ጥኤማውያን ቍጥር ከዚህ በበለጠ ነበር።"
[31]በዚያች ዕለት እስራኤላውያን ፍልስጥ
ኤማውያንን ከማክማስ እስከ ኤሎን ድረስ
ከመቷቸው በኋላ እጅግ ዝለው ነበር።
[32]በምርኮው ላይ ተረባርበው በጉን፣ በሬ
ውንና ጥጃውን በመውሰድ በመሬት ላይ ዐ
ር ደው ሥጋውን ከነደሙ በሉት። [33]ከዚ
ያም ለሳኦል፣ "እነሆ፤ ሕዝቡ ሥጋውን
ከነደሙ በመብላት *እግዚአብሔርን*
እየበደለ ነው" ተብሎ ተነገረው።
ሳኦልም፣ "ሕግ ተላልፋችኋል፤ በሉ አንድ
ትልቅ ድንጋይ አንከባላችሁ አቅርቡልኝ"
አለ። [34]እርሱም፣ "በሕዝቡ መካከል እየዞራ
ችሁ፣ 'እያንዳንዳችሁ በሬዎቻችሁንና በጎቻ
ችሁን አምጡ፤ እዚሁ ዐርዳችሁ ብሉ፤ ነገር
ግን ሥጋውን ከነደሙ በመብላት *እግዚ
አብሔርን* አትበድሉ' በሏቸው" አለ።
ስለዚህ በዚያች ሌሊት እያንዳንዱ ሰው
በሬውን አምጥቶ በዚያ ዐረደው። [35]ሳኦልም
*ለእግዚአብሔር* መሠዊያ ሠራ፤ መሠዊያ
ሲሠራም ይህ የመጀመሪያ ጊዜው ነበር።
[36]ሳኦልም፣ "ፍልስጥኤማውያንን ተከትለን
በሌሊት እንውረድና እስኪነጋ ድረስ እንበ
ዝብዛቸው፤ አንድም ሰው በሕይወት አናስ
ቀርላቸው" አለ። እነርሱም፣ "መልካም መስሎ
የታየህን ሁሉ አድርግ" ብለው መለሱለት።
ካህኑ ግን፣ "እዚሁ እግዚአብሔርን እንጠይቅ" አለ።
[37]በዚህ ጊዜ ሳኦል፣ "ፍልስጥኤማውያንን
ተከትዬ ልውረድን? በእስራኤላውያንስ እጅ
አሳልፈህ ትሰጣቸዋለህን?" ሲል እግዚአ
ብሔርን ጠየቀ። ነገር ግን እግዚአብሔር
በዚያች ቀን አልመለሰለትም።
[38]ስለዚህ ሳኦል እንዲህ አለ፤ "የሰራዊቱ
መሪዎች ሁላችሁም ወደዚህ ቅረቡ፤ ዛሬ
ምን ኀጢአት እንደ ተሠራ እንወቅ። [39]እስራ
ኤልን የታደገ ሕያው እግዚአብሔርን! አድራጊው
ልጄ ዮናታን እንኳ ቢሆን መሞት አለበት።"
ነገር ግን ከሕዝቡ መካከል የመለሰለት አንድም
አልነበረም።
[40]ሳኦልም እስራኤላውያንን ሁሉ፣
"እናንተ በዚያ በኩል ቁሙ፤ እኔና ልጄ
ዮናታን ደግሞ በዚህ በኩል እንቆማለን"
አላቸው።
ሰዎቹም፣ "መልካም መስሎ የታየህን አድርግ"

14፥16 2ሳሙ 18፥24፤2ነገ9፥17፤ ኢሳ52፥8፤ሕዝ33፥2
14፥18 መሳ18፥5፤ 1ሳሙ30፥7
14፥19 ዘኍ27፥21
14፥20 መሳ7፥22፤ ሕዝ38፥21፤ ዘካ14፥13
14፥21 1ሳሙ29፥4
14፥22 1ሳሙ13፥6
14፥23 ዘፀ14፥30፤ ኢሱ7፥2
14፥24 ኢሱ6፥26
14፥27 ቍ43፤ መዝ19፥10፤ ምሳ 16፥24፤24፥13
14፥29 ኢሱ7፥25፤ 1ነገ18፥18
14፥31 ቍ5፤ ኢሱ10፥12
14፥32 ዘፍ9፥4፤ 1ሳሙ15፥19፤ አስ9፥10
14፥33 ዘፍ9፥4
14፥34 ዘሌ19፥26
14፥35 1ሳሙ7፥17
14፥36 ዘፍ25፥22፤ መሳ18፥5
14፥37 1ሳሙ28፥6 ፡ 15፤2ሳሙ 22፥42፤ መዝ 18፥41
14፥38 ኢሱ 7፥11
14፥39 ቍ44፤ ዘኍ14፥21፤ኢሱ 7፥15፤2ሳሙ12፥5፤ ኢዮ19፥25፤ መዝ 18፥46፤42፥2፤

[ሠ]18 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ግን ኤፉዱን ወደዚህ አምጣ፤ በዚያ ጊዜ እርሱ ኤፉዱን በእስራኤል ፊት ለብሶት ነበር ይላል።
[ረ]25 ወይም *አሁን የምድሩ ነዋሪዎች* በሙሉ
[ሰ]29 ወይም *ኀይሌ እንዴት እንደ ታደሰ*

ብለው መለሱለት፡፡
[41]ከዚያ በኋላ ሳኦል፣ “ትክክለኛውን መልስ
ስጠኝ”[ሸ] ሲል ወደ እስራኤል አምላክ ወደ
*እግ ዚአብሔር* ጸለየ፤ ዕጣው በሳኦልና
በዮናታን ላይ ወደቀ፤ ሕዝቡም ነጻ ሆነ፡፡
[42]ሳኦልም በእኔና በልጄ በዮናታን
መካከልም ዕጣ ጣሉ” አላቸው፡፡ ዕጣውም
በዮናታን ላይ ወደቀ፡፡
[43]ከዚያም ሳኦል ዮናታንን፣ “እስቲ ያደ
ረግኸውን ንገረኝ” አለው፡፡
ዮናታንም፣ “በዘንጌ ጫፍ ጥቂት ማር ቀም
ሻለሁ፤ እነሆ፤ ለመሞት ዝግጁ ነኝ” አለው፡፡
[44]ሳኦልም፣ “ዮናታን፣ አንተ ካልተገደልህ
እግዚአብሔር ይፍረድብኝ፣ የከፋም ነገር
ያም ጣብኝ” አለ፡፡
[45]ሕዝቡ ግን ሳኦልን፣ “ለእስራኤል ይህን
ታላቅ ድል ያስገኘ ዮናታን መሞት ይገባ
ዋልን? አይደረግምሄ ዛሬ ይህን ያደረገው
*በእግዚአብሔር* ርዳታ ስለ ሆነ፣ ሕያው
እግዚአብሔርንሄ ከራስ ጠጕሩ አንዲቱ እንኳ
መሬት ላይ አትወድቅም” አሉት፡፡ ስለዚህ
ሰዎቹ ዮናታንን ታደጉት፤ እርሱም ከመ
ሞት ዳነ፡፡
[46]ሳኦል ፍልስጥኤማውያንን ከማሳደድ
ተመለሰ፤ እነርሱም ወደ አገራቸው ተመለሱ፡፡
[47]ሳኦል በእስራኤል ላይ በትረ መንግሥ
ቱን ከጨበጠ በኋላ፣ በዙሪያው ያሉትን
ጠላቶቹን ማለትም ሞዓብን፣ አሞናውያንን፣
ኤዶምን፣ የሱባን ነገሥታትና[ቀ] ፍልስጥኤ
ማውያንን ወጋቸው፡፡ በሄደበት ሁሉ ድል
ይነሣ[በ] ነበር፡፡ [48]በጀግንነት ተዋግቶ አማሌቃ
ውያንን አሸነፈ፤ እስራኤልንም ይዘርፏቸው
ከነበሩት እጅ ታደጋቸው፡፡

## የሳኦል ቤተ ሰብ

[49]የሳኦል ወንዶች ልጆች ዮናታን፣ የሱዊ፣
ሜልኪሳ ነበሩ፤ ሴቶች ልጆቹም ትልቋ ሜሮብ፣
ትንሿ ሜልኮል ይባሉ ነበር፡፡ [50]የሳኦል ሚስት
አኪናሆም የምትባል የአኪማአስ ልጅ ነበረች፤
የሰራዊቱም አዛዥ አበኔር የሚባል የአጎቱ
የኔር ልጅ ነበረ፡፡ [51]የሳኦል አባት ቂስና የአበኔር
አባት ኔር ሁለቱም የአቢኤል ልጆች
ነበሩ፡፡
[52]በሳኦል ዘመን ሁሉ ከፍልስጥኤማ
ውያን ጋር ከባድ ጦርነት ነበረ፤ ስለዚህ
ሳኦል ብርቱ ወይም ጀግና ሰው ባየ ቊጥር
ወደ ራሱ ወስዶ እንዲያገለግለው ያደርግ
ነበር፡፡

## እግዚአብሔር የሳኦልን ንጉሥነት መናቁ

15 ሳሙኤል ሳኦልን እንዲህ አለው፤
“በሕዝቡ በእስራኤል ላይ ቀብቼ
እንዳነግሥህ፣ *እግዚአብሔር* የላከው እኔን
ነው፤ ስለዚህ *ከእግዚአብሔር* የመጣውን
መልእክት አድምጥ፡፡ [2]የሰራዊት ጌታ *እግ*
*ዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ ‘እስራኤል ከግ
ብፅ በወጣ ጊዜ፣ አማሌቃውያን በመንገድ
ላይ ስለ ተቃወሙት እቀጣቸዋለሁ፡፡ [3]አሁ
ንም ሂድ፤ አማሌቃውያንን ውጋ፤ ያላቸ
ውንም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋ፤ አንዱንም
አታስቀር፤ ወንዱንና ሴቱን፣ ልጁንና ሕፃ
ኑን፣ የቀንድ ከብቱንና በጉን፣ ግመሉንና
አህያውን ግደል፡፡” ’[ተ]
[4]ስለዚህ ሳኦል ሰዎቹን ጥላኢም በተባለ
ቦታ ሰብስቦ ቈጠራቸው፤ እነርሱም ሁለት
መቶ ሺህ እግረኛ ወታደሮችና ከይሁዳም
ዐሥር ሺህ ሰዎች ነበሩ፤ [5]ሳኦልም ወደ
አማሌቅ ከተማ ሄዶ በአንዲት ሸለቆ ውስጥ
አደፈጠ፡፡ [6]እርሱም፣ ቄናውያንን፣ “ከእ
ነርሱ ጋር እንዳላጠፋችሁ ከአማሌቃውያን
ራቁ፤ ተለዩአቸውም፤ እስራኤላውያን
ከግብፅ ምድር በወጡ ጊዜ፣ ቸርነት አድርጋ
ችሁላቸዋልና” ’ አላቸው፡፡ ስለዚህ ቄናውያን
ከአማሌቃውያን ተለዩ፡፡
[7]ከዚያም ሳኦል አማሌቃውያንን ከኤው
ላጥ አንሥቶ በምሥራቅ ግብፅ እስካለው
እስከ ሱር ድረስ ወጋቸው፡፡ [8]የአማሌቃው
ያንን ንጉሥ አጋግን ከነሕይወቱ ማረከው፤
ሕዝቡን ሁሉ በሰይፍ ስለት ፈጽሞ አጠ
ፋቸው፡፡ [9]ነገር ግን ሳኦልና ሰራዊቱ አጋግን፣
ምርጥ ምርጡን በግና የቀንድ ከብት፣
የሰባውን ጥጃና[ቸ] ጠቦት፣ መልካም የሆነውን
ሁሉ ሳይገድሉ ተውት፡፡ እነዚህን ፈጽመው
ለማጥፋት ፈቃደኞች አልነበሩም፤ ነገር
ግን የተናቀውንና የማይጠቅመውን ሁሉ
አጠፉ፡፡
[10]ከዚህ በኋላ *የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ
ሲል ወደ ሳሙኤል መጣ፤ [11]“ሳኦልን በማ
ንገሤ ተጸጽቻለሁ፤ እኔን ከመከተል ተመልሶ
አልና፣ ትእዛዜንም አልፈጸመምና፡፡” ሳሙኤ
ልም እጅግ ተጨንቆ፣ ሌሊቱን ሁሉ ወደ
*እግዚአብሔር* ጮኸ፡፡
[12]ሳሙኤልም ጠዋት ተነሥቶ በማለዳ
ሳኦልን ለመገናኘት ሄደ፤ ነገር ግን፣
“ሳኦል ወደ ቀርሜሎስ ሄዶአል፤ ለራሱ

14፥41 ምሳ16፥33፤ ሐሥ1፥24
14፥42 ዮና1፥7
14፥43 ቊ27፤ ኢሱ7፥19
14፥44 ቊ39፤ ሩት1፥17
14፥45 2ሳሙ14፥11፤ 1ነገ1፥52፤ ማቴ10፥30
14፥47 ዘፍ19፥37፡ 38፤1ሳሙ21፥7፤ 2ሳሙ8፥3፤10፥6፤ 12፥31፤23፥36
14፥48 ዘፍ36፥12፤ ዘኍ13፥29፤ መሳ3፥13፤ 1ሳሙ15፥2፥7፤ 27፥8፤28፥18፤ 30፥13፤2ሳሙ1፥13፤ 1ዜና 4፥43
14፥49 ዘፍ29፥26፤ 1ሳሙ31፥2፤ 1ዜና 8፥33
14፥50 1ሳሙ 10፥14፤2ሳሙ2፥8፤ 3፥6፤1ነገ2፥5
14፥51 1ሳሙ9፥1
14፥52 1ሳሙ8፥11
15፥1 1ሳሙ9፥16
15፥2 ዘፍ 14፥7፤ 1ሳሙ14፥48፤ 2ሳሙ1፥8
15፥3 ቊ9፡19፤ ዘፍ14፥23፤ ኢሱ 6፥17፤ 1ሳሙ22፥19፤ 27፥9፤28፥18፤ አስ3፥13፤9፥5
15፥6 ዘፍ15፡19፤ ዘኍ24፥22፤መሳ 1፥16፤1ሳሙ30፥29
15፥7 ዘፍ16፥7፤ ን1ሳሙ14፥48
15፥8 ዘፀ17፥8-16፤ ዘኍ24፥7፤ኢሱ8፥23
15፥9 ቊ3
15፥11 ቊ35፤ ዘፍ6፥6፤ዘፀ32፥14፤ ኢሱ22፥16፤ 1ሳሙ 8፥6፤ ኢዮ21፥14፤ 34፥27፤መዝ28፥5፤ ኢሳ5፥12፤53፥6፤ ኤር48፥10፤ ሕዝ18፥24
15፥12 ዘኍ32፥42፤ ኢሱ15፥55

[ሸ]41 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት ትር
ጒም ግን *ዛሬ ለባሪያህ ያልመለስህለት ለምንድን ነው ጥፋቱ*
*በእኔና በልጄ በዮናታን ላይ ከሆነ በኡሪም መልስልን፤ነገር ግን*
*ጥፋቱ በእስራኤል ሰዎች ላይ ከሆነ በቱሚም መልስ* ይላል፡፡
[ቀ]47 የማሶሬ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሙት ባሕር ጥቅልና የሰብዓ
ሊቃናት ትርጒም ግን *ንጉሥ* ይላል፡፡
[በ]47 ዕብራይስጡ *ያሠቃያቸው ነበር* ሲል፣የሰብዓ ሊቃናት
ትርጒም ደግሞ *ድል ይነሣቸው ነበር* ይላል፡፡
[ተ]3 በዚህም ሆነ በቍጥር 8፡9፡15፡18፡20 እና 21 ላይ የዕብራይስጡ
ቃል አንድን ሰው ወይም ነገር ሙሉ በሙሉ በማጥፋት
ለእግዚአብሔር መስጠትን የሚያሳይ ነው፡፡
[ቸ]9 ወይም ያደገ ጥጃ የዚህ ሐረግ የዕብራይስጡ ትርጒም
በትክክል አይታወቅም

ክብር የመታሰቢያ ሐውልት በዚያ ካቆመ
በኋላ ተመልሶ ወደ ጌልገላ ወርዶአል” ተብሎ
ተነገረው፡፡
13ሳሙኤል ባገኘው ጊዜ ሳኦል፣ “እግዚአ
ብሔር ይባርክህ፤ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ
ፈጽሜለሁ” አለው፡፡
14ሳሙኤል ግን፣ “ታዲያ ይህ በጆሮዬ
የምሰማው የበጎች ጩኸትና የበሬዎች ግሣት
ምንድን ነው?” ሲል ጠየቀ፡፡
15ሳኦልም፣ “ሰራዊቱ ከአማሌቃውያን ማርከው
ያመጧቸው ናቸው፤ ምርጥ ምርጦቹ በጎችና
በሬዎች ለእግዚአብሔር ለአምላክህ መሥዋዕት
እንዲሆኑ ሳይገድሉ የተዉአቸው ናቸው፤
የቀሩትን ግን በሙሉ አጥፍተናል” ብሎ
መለሰ፡፡
16ሳሙኤልም ሳኦልን፣ “ስማኼ ትናንት
ማታ እግዚአብሔር የነገረኝን ልንገርህ?”
አለው፡፡
ሳኦልም፣ “ንገረኝ” ሲል መለሰለት፡፡
17ሳሙኤልም እንዲህ አለው፤ “በዐይንህ
ፊት ታናሽ የነበርህ ብትሆንም፣ የእስራኤል
ነገዶች መሪ ሆነህ የለምን? እግዚአብሔ
ርም በእስራኤል ላይ ቀብቶ አንግሦሃል፡፡
18እግዚአብሔርም፣ ‘ሄደህ እነዚያን ኀጢአ
ተኞቹን አማሌቃውያንን ፈጽመህ አጥፋ
ቸው፤ ጨርሰህ እስኪታጠፉቸውም ድረስ
ውጋቸው’ ብሎ ልኮህ ነበር፡፡ 19ታዲያ እግዚ
አብሔርን ለምን አልታዘዝህም? ለምርኮ
ውስ ተስገብግበህ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ
የሆነውን ነገር ለምን አደረግህ?”
20ሳኦልም መልሶ እንዲህ አለ፤ “እግዚአ
ብሔር ታዝዣለሁ፤ እግዚአብሔር በላከኝ መሠ
ረት ሄጃለሁ፤ አማሌቃውያንን በሙሉ አጥ
ፍቼ ንጉሣቸውን አጋግን አምጥቻለሁ፡፡ 21ሰ
ራዊቱ ግን ከምርኮው ለእግዚአብሔር
ከተለዩት መካከል፣ ምርጥ ምርጡን በግና
በሬ፣ በጌ ልገላ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር
ይሠዉ ዘንድ ወስደዋል፡፡”
22ሳሙኤልም እንዲህ አለ፤
“ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ደስ
የሚለውን ያህል፣ እግዚአብሔር፣ በሚቃ
ጠል ቍርባንና መሥዋዕት ደስ ይለዋልን?

እነሆ፤ መታዘዝ ከመሥዋዕት፣
ማዳመጥም ከአውራ በግ ሥብ
ይበልጣል፡፡
23ዐመፅ እንደ ጥንቈላ ያለ ኀጢአት፣
እልኸኛነትም እንደ ጣዖት አምልኮ ያለ
ክፉ ነገር ነው፤ አንተ የእግዚአብሔርን ቃል
ስለ ናቅህ፣ እርሱም ንጉሥ እንዳትሆን ንቆ
ሃል፡፡”
24ከዚያም ሳኦል ሳሙኤልን እንዲህ አለው፤
“ኀጢአት ሠርቻለሁ፤ የእግዚአብሔርን ትእ
ዛዝና የአንተን መመሪያ ጥሻለሁ፤ ሕዝቡን
ፈርቼ ስለ ነበር፣ የጠየቁኝን ታዝዣለሁ፡፡
25አሁንም፣ ኀጢአቴን ይቅር እንድትለኝ፣
ለእግዚአብሔርም እሰግድ ዘንድ አብረኸኝ
እንድትመለስ እለምንሃለሁ፡፡”
26ሳሙኤል ግን፣ “ከአንተ ጋር አልመለ
ስም፤ አንተ የእግዚአብሔርን ቃል ንቀሃል፤
እግዚአብሔርም በእስራኤል ላይ ንጉሥ እን
ዳትሆን ንቆሃል” አለው፡፡
27ሳሙኤል ለመሄድ ዘወር ባለ ጊዜ፣ ሳኦል
የልብሱን ጫፍ ያዘ፤ ተቀደደም፡፡ 28ሳሙኤልም
እንዲህ አለው፤ “እግዚአብሔር የእስራኤልን
መንግሥት ዛሬ ከአንተ ቀዶታል፤ ከአንተም
ለሚሻል ለጎረቤትህ አሳልፎ ሰጥቶታል፡፡
29የእስራኤል ክብር የሆነው እግዚአብሔር
አይዋሽም፤ አይጸጸትምም፤ እርሱ ይጸጸት
ዘንድ ሰው አይደለምና፡፡”
30ሳኦልም መልሶ፣ “ኀጢአት ሠርቻለሁ፤
ነገር ግን በሕዝቤ አለቆች ፊትና በእስራ
ኤል ፊት አክብረኝ፤ ለአምላክህ ለእግዚ
አብሔር እሰግድ ዘንድ እባክህ አብረኸኝ
ተመለስ” አለው፡፡ 31ስለዚህ ሳሙኤል
አብሮት ተመ ለሰ፤ ሳኦልም ለእግዚአብሐ
ር ሰገደ፡፡
32ከዚያም ሳሙኤል፣ “የአማሌቃውያንን
ንጉሥ አጋግን አምጡልኝ” አለ፡፡
አጋግም፣ “በውኑ ሞት እንዲህ መራራ
ነውን? በማለት እየተንቀጠቀጠ መጣ፡፡
33ሳሙኤልም፣
“ሰይፍህ ሴቶችን ልጅ አልባ እንዳደረገ
ቻቸው፣ እናትህም በሴቶች መካከል ልጅ
አልባ ትሆናለች”
ሲል አጋግን ጌልገላ ላይ በእግዚአብሔር
ፊት ቈራረጠው፡፡
34ከዚያም ሳሙኤል ወደ አርማቴም ሄደ፡፡
ሳኦል ግን ወደ ቤቱ ወደ ሳኦል ጊብዓ
ወጣ፡፡ 35ሳሙኤል ለሳኦል ቢያለቅስለትም
እንኳ እስከ ሞተበት ዕለት ድረስ ዳግመኛ
ሊያየው አልሄደም፤ እግዚአብሔርም ሳኦልን
በእስራኤል ላይ በማንገሡ ተጸጸተ፡፡

### ሳሙኤል ዳዊትን መቀባቱ

16 እግዚአብሔር ሳሙኤልን፣ “በእስ
ራኤል ላይ እንዳይነግሥ ለናቅሁት
ለሳኦል የምታለቅስለት እስከ መቼ ነው?
ወደ ቤተ ልሔሙ ሰው ወደ እሴይ ስለምልክህ፣
ዘይት በቀንድ ሞልተህ ሂድ፤ ከልጆቹ አንዱ
ንጉሥ ይሆን ዘንድ መርጬዋለሁ” አለው፡፡
2ሳሙኤል ግን፣ “ሳኦል ከሰማ ስለሚገድ
ለኝ እንዴት መሄድ እችላለሁ?” አለ፡፡
እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፤ “አን
ዲት ጊደር ይዘህ ሂድና፣ ‘ለእግዚአብሔር

15፥17 ዘፀ3፥11
15፥19 ዘፍ14፥23፤ 1ሳሙ14፥32
15፥20 1ሳሙ28፥18
15፥22 መዝ40፥6-8፤ 51፥16፤ምሳ21፥3፤ ኢሳ1፥11-15፤ ኤር 7፥22፤ሆሴ6፥6፤ አሞ 5፥25፤ ሚክ6፥6-8፤ ማር12፥33
15፥23 ዘዳ18፥10፤ 1ሳሙ13፥13
15፥24 ዘፀ9፥27፤ ዘኍ22፥34፤ 1ሳሙ 13፥13፤ መዝ51፥4፤ ምሳ29፥25፤ ኢሳ51፥ 12-13፤ ኤር42፥11
15፥25 ዘፀ10፥17
15፥26 ዘኍ15፥31፤ 1ሳሙ13፥14፤ 1ነገ14፥10
15፥27 1ሳሙ28፥14፤ 1ነገ11፥11፡31፤14፥8፤ 2ነገ17፥21
15፥28 1ሳሙ13፥14፤ 28፥17፤2ሳሙ6፥21፤ 7፥15
15፥29 ዘኍ23፥19፤ ቲቶ1፥2፤ዕብ7፥21
15፥30 ዘኍ22፥34፤ ኢሳ29፥13፤ ዮሐ12፥43
15፥33 አስ9፥7-10፤ ኤር18፥21
15፥34 መሳ19፥14፤ 1ሳሙ7፥17፤10፥5
15፥35 ቀኍ11፤ ዘፍ6፥6፤1ሳሙ16፥1፤1 9፥24
16፥1 ሩት4፥17፤ 1ሳሙ8፥6፤10፥1፤ 13፥14፤15፥35፤ 2ሳሙ5፥2፤7፥8፤ 1ነገ 8፥16፤ 1ዜና 12፥23፤ መዝ78፥70፤ ሐሥ13፥22

ልሠዋ መጥቻለሁ’ በል:: 3እሴይን ወደ
መሥዋዕቱ ጥራው፤ ከዚያም የምታደርገውን
አሳይሃለሁ፤ የምነግርህንም ሰው ትቀባል
ኛለህ::”
4ሳሙኤል *እግዚአብሔር* ያለውን ነገር
አደረገ:: ቤተልሔም እንደ ደረሰም፣ የከተ
ማዪቱ ሽማግሌዎች እየተንቀጠቀጡ ሊገ
ናኙት መጡ፣ እነርሱም “አመጣጥህ ለሰላም
ነውን?” ብለው ጠየቁት::
5ሳሙኤልም፣ “አዎን፤ ለሰላም ነው፤ የመጣ
ሁትም *ለእግዚአብሔር* መሥዋዕት ላቀርብ
ነው፤ እናንተም ራሳችሁን ቀድሳችሁ ከእኔ
ጋር ወደ መሥዋዕቱ ኑ” ሲል መለሰላቸው::
ከዚያም እሴይንና ልጆቹን ቀደሳቸው፤ ወደ
መሥዋዕቱም እንዲመጡ ጠራቸው::
6እዚያ በደረሱ ጊዜም፣ ሳሙኤል ኤል
ያብን አይቶ፣ “በእርግጥ *እግዚአብሔር* የቀ
ባው ሰው እነሆ፤ *በእግዚአብሔር ፊት ቆሞአል*”
ብሎ አሰበ::
7*እግዚአብሔር* ግን ሳሙኤልን፣ “መል
ኩን ወይም ቁመቱን አትይ፤ እኔ ንቄዋለ
ሁና:: *እግዚአብሔር* የሚያየው፣ ሰው እንደሚ
ያየው አይደለም:: ሰው የውጭውን ገጽታ
ያያል፤ *እግዚአብሔር* ግን ልብን ያያል” አለው::
8ከዚያም እሴይ አሚናዳብን ጠርቶ በሳ
ሙኤል ፊት እንዲያልፍ አደረገ፤ ሳሙኤል
ግን፣ “*እግዚአብሔር* ይህንንም አልመረጠውም”
አለው:: 9እሴይም ሣማን አሳለፈ፤ ሳሙኤልም፣
“እርሱንም *እግዚአብሔር* አልመረጠውም” አለ::
10እሴይም ሰባቱን ልጆቹን በሳሙኤል ፊት
እንዲያልፉ አደረገ፤ ሳሙኤል ግን፣
“*እግዚአብሔር* እነዚህንም አልመረጣቸውም”
አለው:: 11ቀጥሎም እሴይን፣ “ልጆችህ እነዚ
ሁ ብቻ[ነ] ናቸውን?” ሲል ጠየቀው::
እሴይም፣ “የሁሉም ታናሽ ገና አልመጣም፤
ነገር ግን በጎች እየጠበቀ ነው” ብሎ መለሰ::
ሳሙኤልም፣ “በል ልከህ አስመጣው፤
እስኪመጣ ድረስ አንቀመጥምና[ነ]” አለው::
12ስለዚህ ልኮ አስመጣው፤ እርሱም ደም
ግባት ያለው፣ ዐይኑ የሚያምርና መልከ
መልካም ነበረ::
*እግዚአብሔርም*፣ “የመረጥሁት ይህ
ነውና ተነሥተህ ቅባው” አለው::
13ሳሙኤልም የዘይቱን ቀንድ ወስዶ በወን
ድሞቹ ፊት ቀባው:: ከዚያ ቀን ጀምሮ *የእግ
ዚአብሔር* መንፈስ በዳዊት ላይ በኀይል
መጣ፤ ሳሙኤልም ወደ አርማቴም ሄደ::

## ዳዊት ሳኦልን ማገልገሉ

14*የእግዚአብሔር* መንፈስ ከሳኦል ስለ ራቀ፤
*ከእግዚአብሔር* ዘንድ የታዘዘ ክፉ[ነ] መንፈስ
ያሠቃየው ነበር::

16፥3 ዘፀ4፥15፤ ዘዳ17፥15
16፥4 ዘፍ48፥7፤ 1ሳሙ21፥1፤ 1ነገ2፥13፤2ነገ9፥17፤ሉቃ2፥4
16፥5 ዘፀ19፥10፡22
16፥6 1ሳሙ17፥13፤ 1ዜና2፥13
16፥7 1ሳሙ2፥3፤ 2ሳሙ7፥20፤ መዝ44፥21፤139፥23፤ 147፥10፤ሮእ2፥23
16፥8 1ሳሙ17፥13
16፥9 1ሳሙ17፥13፤ 2ሳሙ13፥3፤21፥21
16፥11 ዘፍ37፥2፤ 1ሳሙ 17፥12፤ 2ሳሙ7፥8
16፥12 ዘፍ39፥6፤ 1ሳሙ9፥17
16፥13 1ሳሙ2፥35፤ 11፥6፤18፥12፣ 2ሳሙ22፥51
16፥14 ቀኍ23፤ መሳ9፥23፤1፤16፥20፤1 ሳሙ18፥10፤ 2ሳሙ7፥15
16፥16 ቀኍ23፤ 1ሳሙ10፥5፡6፤ 2ዜና29፥26-27፤ መዝ49፥4
16፥18 ዘፍ39፥2፤ ሩት4፥17፤ 1ሳሙ 17፥37፤ 20፥13፤ 2ሳሙ17፥8፤ 1ዜና 22፥11፤ ማቴ1፥23
16፥19 1ሳሙ17፥15
16፥20 ዘፍ32፥13፤ 1ሳሙ10፥4
16፥21 ዘፍ41፥46
16፥23 ቀኍ14፤ መሳ9፥23
17፥1 ኢሱ10፥10፡ 11፤15፥35፤ 1ሳሙ 13፥5፤ 2ዜና28፥18
17፥2 1ሳሙ21፥9
17፥4 1ሳሙ21፥9፤ 2ሳሙ21፥19

15የሳኦል አገልጋዮችም እንዲህ አሉት፤
“እነሆ፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ የታዘዘ ክፉ
መንፈስ እያሠቃየህ ነው:: 16እንግዲህ በገና
መደርደር የሚችል ሰው እንዲፈልጉ፣ ጌታ
ችን በፊቱ የሚቆሙትን አገልጋዮቹን ይዘዝ፤
ከዚያም ከእግዚአብሔር የታዘዘው ክፉ መንፈስ
ባንተ ላይ በሚመጣ ጊዜ በገና ይደረድርል
ሃል፤ ደኅናም ትሆናለህ::”
17ስለዚህ ሳኦል አገልጋዮቹን፣ “መልካም
አድርጎ በገና መደርደር የሚችል ሰው
ፈልጋችሁ አምጡልኝ” አላቸው::
18ከአገልጋዮቹም አንዱ፣ “መልካም አድርጎ
በገና መደርደር የሚችለውን የቤተልሔሙን
የእሴይን ልጅ አይቻለሁ፣ እርሱም ጀግናና
ተዋጊ ነው፤ በአነጋገሩ አስተዋይና የደስ
ደስ ያለው ነው፤ *እግዚአብሔርም* ከእርሱ
ጋር ነው” ብሎ መለሰ::
19ከዚያም ሳኦል፣ “ከበጎች ጋር ያለውን
ልጅህን ዳዊትን ላክልኝ” ሲል መልክተኞ
ችን ወደ እሴይ ላከ:: 20እሴይም እንጀራና
በወይን ጠጅ የተሞላ አቁማዳ በአህያ
አስጭኖ፣ የፍየል ጠቦትም አስይዞ ልጁን
ዳዊትን ወደ ሳኦል ላከው::
21ዳዊት ወደ ሳኦል መጥቶ አገልግሎቱን
ጀመረ፤ ሳኦልም እጅግ ወደደው፣ እርሱም
የሳኦል ጋሻ ጃግሬ ሆነ:: 22ከዚያም ሳኦል፣
“ዳዊትን ወድጄዋለሁና ከእኔ ዘንድ ሆኖ
እንዲያገለግለኝ ፍቀድልኝ” ብሎ ወደ እሴይ
ላከ::
23ክፉው መንፈስ ከእግዚአብሔር ዘንድ
በሳ ኦል ላይ በሚመጣበት ጊዜ፣ ዳዊት
በገናውን ይዞ ይደረድር ነበር፤ ሳኦልም
ይሻለው ነበር፤ ክፉውም መንፈስ ከእርሱ
ይርቅ ነበር::

## ዳዊትና ጎልያድ

17 ፍልስጥኤማውያን ሰራዊታቸውን
ለጦርነት አሰባሰበው፣ በይሁዳ
ምድር በሰኰት ላይ አከማቹ፤ እነርሱም
በሰኰትና በዓዜቃ መካከል ባለው በኤፌሰደ
ሚም ሰፈሩ:: 2ሳኦልና እስራኤላውያን ተሰብስ
በው፣ በዔላ ሸለቆ ሰፈሩ፤ ፍልስጥኤማውያ
ንንም ለመግጠም ቦታ ቦታቸውን ያዙ::
3ሸለቆ በመካከላቸው ሆኖ ፍልስጥኤማውያን
አንዱን ኰረብታ እስራኤላውያን ደግሞ፣
ሌላውን ኰረብታ ያዙ::
4ከጌት የመጣ ቁመቱ ከዘጠኝ ጫማ በላይ
የሆነ፣ ጎልያድ የተባለ አንድ ጀግና ከፍልስ
ጥኤማውያን ሰፈር ወጣ:: 5እርሱም ከናስ
የተሠራ የራስ ቍር ደፍቶ፣ ክብደቱ አምስት

[ነ]11 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች ከዚህ ጋር ይስማ
ማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን *አንሰበስብምና* ይላል::
[ነ]14 በዚህ እንዲሁም በቍጥር 15፥16 እና 23 ላይ *ጐጂ*

ሺህ ሰቅል የሆነ የናስ ጥሩር ለብሶ ነበር።
6በእግሮቹ ላይ የናስ ገምባሌ አድርጎ፣
በጫንቃው ላይ ደግሞ የናስ ጭሬ ይዞ
ነበር። 7የጦሩም ዘንግ እንደ ሸማኔ መጠ
ቅለያ የወፈረ፣ የጦሩም ብረት ስድስት
መቶ ሰቅል ያህል የሚመዝን ነበር፤ ጋሻ
ጃግሬውም ከፊት ከፊቱ ይሄድ ነበር።
8ጎልያድ ቆሞ ለተሰለፈው የእስራኤል
ሰራዊት እንዲህ ሲል ጮኾ ተናገረ፤
“ለው ጊያ ተሰልፋችሁ መውጣታችሁ ስለ
ምንድን ነው? እኔ ፍልስጥኤማዊ፣
እናንተም የሳኦል አገልጋዮች
አይደላችሁምን? አንድ ሰው ምረ
ጡና እኔ ወደ አለሁበት ይውረድ፤ 9ከእኔ
ጋር ሊዋጋና ሊገድለኝ ከቻለ፣ እኛ ባሪያ
ዎቻችሁ እንሆናለን፤ እኔ ባሸንፈውና
ብገድለው ግን እናንተ ባሪያዎቻችን ትሆና
ላችሁ፤ ትገዙልናላችሁ።” 10ከዚያም ፍልስጥኤ
ማዊው፣ “ዛሬ የእስራኤልን ሰራዊት እገዳደራ
ለሁ፤ እንዋጋ ዘንድ ሰው ስጡኝ” አለ። 11ሳኦልና
እስራኤላውያን ሁሉ የፍልስጥኤማዊውን ቃል
በሰሙ ጊዜ እጅግ ፈሩ፤ ደነገጡም።
12ዳዊት በይሁዳ የቤተልሔሙ ሰው የኤ
ፍራታዊው የእሴይ ልጅ ነበር። እሴይ
ስምንት ወንዶች ልጆች ነበሩት፤ በሳኦልም
ዘመን ያረጀና ዕድሜው የገፋ ሰው ነበር።
13ሦስቱ የእሴይ ታላላቅ ልጆች ሳኦልን
ተከትለው ወደ ጦርነት ሄደው ነበር፤ እነ
ርሱም ታላቁ ኤልያብ፣ ሁለተኛው አሚና
ዳብ፣ ሦስተኛውም ሣማ ይባላሉ፤ 14ዳዊት
የሁሉም ታናሽ ነበር። ሦስቱ ታላላቅ ወንድ
ሞቹ ሳኦልን ተከትለው ሄዱ፤ 15ዳዊት ግን
የአባቱን በጎች ለመጠበቅ ከሳኦል ዘንድ
ወደ ቤተልሔም ይመላለስ ነበር።
16ፍልስጥኤማዊውም አርባ ቀን ሙሉ ጠዋ
ትና ማታ ፊት ለፊት ብቅ እያለ ቆሞ ይታ
ያቸው ነበር።
17በዚህ ጊዜ እሴይ ልጁን ዳዊትን እንዲህ
አለው፤ “ይህን ዐሥር ኪሎ የተጠበሰ
እሸትና
ዐሥር እንጀራ ለወንድሞችህ ይዘህ ወዳ
ሉበት የጦር ሰፈር በቶሎ ድረስ። 18ይህ
ንም ዐሥር የአይብ ጥፍጥፍ ለክፍል አዛዥ
ቸው[ኘ] አብረህ ውሰድ፤ ወንድሞችህም እን
ዴት እንደሆኑ አይተህ፣ ደኅንነታቸውን
የሚያረጋግጥ ምልክት ከእነርሱ ዘንድ
አምጣልኝ። 19እነርሱ ከሳኦልና ከእስራኤል
ሰዎች ሁሉ ጋር ሆነው በዔላ ሸለቆ ከፍል
ስጥኤማውያን ጋር እየተዋጉ ናቸው።”
20ዳዊት በማለዳ በጎቹን ለጠባቂ ትቶ፣
እሴይ እንዳዘዘው ዕቃውን ይዞ ጕዞ ጀመረ።
ልክ ሰራዊቱ እየፎከረ ለውጊያ ቦታ ቦታ
ውን ለመያዝ በሚወጣበት ጊዜ ከጦሩ ሰፈር
ደረሰ። 21እስራኤልና ፍልስጥኤማውያን ቦታ
ቦታቸውን ይዘው ፊት ለፊት ተፋጠው
ይጠባበቁ ነበር። 22ዳዊት ዕቃውን ከስንቅ
ጠባቂው ዘንድ አስቀምጦ ወደ ጦሩ ግንባር
ሮጠ፤ ወንድሞቹንም አግኝቶ
ደኅንነታቸውን
ጠየቀ። 23ከእነርሱም ጋር በሚነጋገርበት ጊ
ዜ፣ ከጌት የመጣው ፍልስጥኤማዊው ጀግና
ጎል ያድ ከሰልፉ መካከል ወጥቶ እንደ
ለመደው ሲደነፋ፤ ዳዊት ሰማ። 24እስራ
ኤላውያንም ሰውየውን ባዩት ጊዜ ሁሉም
በታላቅ ፍር ሀት ከፊቱ ሸሹ።
25እስራኤላውያንም እርስ በርሳቸው “ይህ
ሰው በየቀኑ እየመጣ እስራኤልን እንደሚገ
ዳደር ታያላችሁ? ይህን ሰው ለሚገድል፣
ንጉሡ ብዙ ሀብት ይሰጠዋል፤ ሴት ልጁን
ይድርለታል፣ የአባቱንም ቤት በእስራኤል
ዘንድ ከግብር ነጻ ያደርገዋል” ይባባሉ
ነበር።
26ዳዊት በአጠገቡ የቆሙትን ሰዎች፣
“ለመሆኑ ይህን ፍልስጥኤማዊ ገድሎ እን
ዲህ ያለውን ውርደት ከእስራኤል ለሚያ
ስወግድ ሰው ምን ይደረግለታል? ደግሞስ
የሕያው እግዚአብሔርን ሰራዊት ይገዳደር
ዘንድ ይህ ያልተገረዘ ፍልስጥኤማዊ እርሱ
ማነው?” ሲል ጠየቀ።
27እነርሱም፣ “ለሚገድለው ሰው የሚደረግ
ለትማ ይህ ነው” ሲሉ አስቀድመው ያሉትን
ደግመው ነገሩት።
28ታላቅ ወንድሙ ኤልያብ፣ ዳዊት ከሰ
ዎች ጋር ሲነጋገር በሰማ ጊዜ እጅግ ተቈ
ጥቶ፣ “ለምን ወደዚህ ወረድህ? እነዚያንስ
ጥቂት በጎች በምድረ በዳ ለማን ተውሃ
ቸው? ትዕቢትህንና የልብህን ክፋት ዐው
ቃለሁ፤ የመጣኸው ጦርነቱን ለማየት ብቻ
ነው” አለው።
29ዳዊትም፣ “ታዲያ ምን አደረግሁ?
መጠ የቅ እንኳ አልችልም?” አለ። 30ከዚ
ያም ወደ ሌላ ሰው ዘወር ብሎ፣ ያንኑ
ጥያቄ ጠየቀ፤ ሰዎቹም እንደ ቀድሞው
መለሱለት፤ 31ዳዊት የተናገረው ነገር ወደ
ሳኦል ጆሮ ደረሰ፤ ሳኦልም ልኮ አስጠራ
ው።
32ዳዊትም ሳኦልን፣ “ከዚህ ፍልስጥኤ
ማዊ የተነሣ የማንም ሰው ልብ አይሸበር፤
ባሪያህ ሄዶ ይዋጋዋል” አለው።
33ሳኦልም መልሶ “አንተ ገና አንድ
ፍሬ ልጅ ነህ፣ ሰውየው ግን ከልጅነቱ
ጀምሮ ውጊያ የተለማመደ ስለ ሆነ፣
ወጥተህ ይህን ፍልስጥኤማዊ ልተገጥመው
አትችልም” አለው።
34ዳዊት ግን ሳኦልን እንዲህ አለው፣ “አገ
ልጋይህ የአባቱን በጎች በሚጠብቅበት ጊዜ፤
አንበሳ ወይም ድብ መጥቶ ከመንጋው አንድ

17፥6 ቀኍ45፤ 1ሳሙ18፥10
17፥7 ቀኍ41፤ 2ሳሙ21፥19፤ 1ዜና11፥23፤20፥5
17፥8 2ሳሙ2፥12-17
17፥10 ቀኍ23፡26፡ 45፤2ሳሙ21፥21
17፥12ዘፍ35፥16፡ 19፤48፥7፤ሩት4፥17፤ 1ሳሙ16፥11፤ መዝ 132፥6
17፥13 1ሳሙ16፥6፡ 8፡9
17፥15 ዘፍ37፥2፤ 1ሳሙ16፥19
17፥17 ዘሌ19፥36፤ 23፥14፤1ሳሙ25፥18
17፥18 ዘፍ37፥14
17፥22 ኢሱ 1፥11
17፥23 ቀኍ8-10
17፥25 1ሳሙ8፥15፤ 18፥17
17፥26 ቀኍ10፤ ዘዳ5፥26፤ኢሱ3፥10፤ 1ሳሙ11፥2፤ 14፥6፤2ነገ18፥35
17፥28 ዘፍ27፥41፤ ምሳ18፥19
17፥32 ዘዳ20፥3፤ መዝ18፥45፤ ኢሳ7፥4፤ኤር4፥9፤ 38፥4፤ዳን11፥30
17፥33 ዘኍ13፥31
17፥34 ኢዮ10፥16፤ ኢሳ31፥4፤ ኤር49፥19፤ሆሴ13፥8፤ አሞ3፥12
17፥35 መሳ14፥6
17፥36 1ዜና11፥22

ኘ18 ዕብራይስጡ ሻለቃ ይላል።

በግ ነጥቆ ሲሄድ፣ 35ተከትዬ በመሄድ እመታ
ውና ከአፉ አስጥል ነበር፤ ፊቱን ወደ እኔ
በሚያዞርበትም ጊዜ ጕሮሮውን ይዤ
በመምታት እገድለው ነበር። 36ባሪያህ አን
በሳውንም ድቡንም ገድሎአል፤ ይህም ያለ
ተገረዘ ፍልስጥኤማዊ የሕያው እግዚአብሔርን
ሰራዊት ተገዳድሮአልና መጨረሻው ከእነርሱ
እንደ አንዱ ይሆናል። 37ከአንበሳ መዳፍና
ከድብ መንጋጋ ያዳነኝ እግዚአብሔር አሁንም
ከዚህ ፍልስጥኤማዊ እጅ ያድነኛል።"

ሳኦልም፣ "ሂድ፤ እግዚአብሔር ካንተ ጋር
ይሁን" አለው።

38ከዚያም ሳኦል ለዳዊት የገዛ ራሱን የጦር
ልብስ አለበሰው፤ ጥሩር አጠለቀለት፤ ከናስ
የተሠራ ቍርም ደፋለት። 39ዳዊትም ይህን ዐይ
ነት ልብስ ለብሶ ስለማያውቅ፣ ሰይፉን
በጦር ልብሱ ላይ ታጥቆ ለመራመድ
ሞከረ፤

እርሱም ሳኦልን፣ "ያልተለማመድሁት ስለ
ሆነ እንደዚህ ሆኜ መራመድ አልችልም"
አለው። ስለዚህ ሁሉንም አወለቀው። 40ከዚ
ያም በትሩን በእጁ ያዘ፤ አምስት ድቡል
ቡል ድንጋዮች ከወንዝ መርጦ በእረኛ ኮረ
ጆው ከጨመረ በኋላ፣ ወንጭፉን በእጁ
ይዞ፣ ወደ ፍልስጥኤማዊው ቀረበ።

41ፍልስጥኤማዊውም፣ ጋሻ ጃግሬውን እፊት
እፊቱ በማስቀደም፣ ወደ ዳዊት እየቀረበ
መጣ። 42እርሱም ዳዊትን ትኵር ብሎ
ሲያየው፣ ደም ግባት ያለው፣ መልከ መል
ካምና አንድ ፍሬ ልጅ ነበር፤ ስለዚህ ናቀው።
43ፍልስጥኤማዊውም ዳዊትን፣ "በትር ይዘህ
የምትመጣብኝ እኔ ውሻ ነኝን?" አለው፤ በአ
ማልክቱም ስም ረገመው። እርሱም፣ "እስቲ
ወደኔ ና! ሥጋህን ለሰማይ አሞሮችና፣ ለምድር
አራዊት እሰጣለሁ" አለው።

45ዳዊትም ፍልስጥኤማዊውን እንዲህ
አለው፤ "አንተ ሰይፍ፣ ጦርና ጭሬ ይዘህ
ትመጣብኛለህ፤ እኔ ግን አንተ በተገዳደ
ርኸው የእስራኤል ሰራዊት አምላክ በሆ
ነው፣ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር ስም
እመጣብሃለሁ። 46እግዚአብሔር ዛሬ አንተን
በእጄ አሳልፎ ይሰጣል፤ እኔ መትቼ እጥ
ልሃለሁ፤ ራስህንም እቈርጠዋለሁ። በዚህች
ዕለት የፍልስጥኤማውያንን ሰራዊት ሬሣ
ለሰማይ አሞሮችና ለምድር አራዊት እሰ
ጣለሁ፣ ዓለምም ሁሉ በእስራኤል ዘንድ
አምላክ መኖሩን ያውቃል። 47እዚህ የተሰ
በሰቡትም ሁሉ፣ እግዚአብሔር የሚያድነው
በሰይፍ ወይም በጦር እንዳልሆነ ያውቃሉ፤
ሰልፉ የእግዚአሔር ስለ ሆነም ሁላችሁን
በእጃችን አሳልፎ ይሰጣል።"

48ፍልስጥኤማዊው ሊመታው በቀረበ ጊ
ዜ፣ ዳዊትም ሊገጥመው ወደ ውጊያው ሜ
ዳ በፍ ጥነት ሮጠ። 49እጁንም ወደ ኮሮጆው
በመስ ደድ አንድ ድንጋይ አውጥቶ
ወነጨፈው፤ ፍልስጥኤማዊውንም ግንባሩ
ላይ መታው። ድንጋዩም ግንባሩ ውስጥ
ገብቶ ተቀረቀረ፤ ፍልስጥኤማዊውም
በግምባሩ ተደፋ።

50በዚህ ሁኔታ ዳዊት በወንጭፍና በድ
ንጋይ ብቻ ፍልስጥኤማዊውን አሸነፈው፤
በእጁም ሰይፍ ሳይዝ ፍልስጥኤማዊውን
መታው፤ ገደለውም።

51ዳዊት ሮጦ በላዩ ላይ ቆመ፤ ከዚያም
የፍልስጥኤማዊውን ሰይፍ ከሰገባው መዞ
አወጣው፤ እርሱንም ከገደለው በኋላ ራሱን
በሰይፍ ቈረጠው።

ፍልስጥኤማውያንም ጀግናቸው መሞቱን
ባዩ ጊዜ ሸሹ። 52ከዚህ በኋላ የእስራኤልና
የይሁዳ ሰዎች ተነሥተው እየፎከሩ ፍልስጥኤ
ማውያንን እስከ ጌት መግቢያና እስከ ዔቅ
ሮን በሮች ድረስ አሳደዷቸው። የፍልስጥ
ኤማውያንም ሬሳ ከሸዓይራይም አንሥቶ እስከ
ጌት[ሀ] ከዚያም እስከ ዔቅሮን በሮች ባለው
መንገድ ላይ ወድቆ ነበር። 53እስራኤላውያን
ፍልስጥኤማውያንን ከማሳደድ ተመለሱ፤ ሰፈ
ራቸውንም በዘበዙ። 54ዳዊትም የፍልስጥኤ
ማዊውን ራስ ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም አመ
ጣው፤ ነገር ግን የፍልስጥኤማዊውን የጦር መሣ
ሪያዎች በራሱ ድንኳን ውስጥ አስቀመጠ።

55ዳዊት ፍልስጥኤማዊውን ለመግጠም በሚ
ሄድበት ጊዜ ሳኦል ተመልክቶ የሰራዊቱን
አዛዥ አበኔርን፣ "አበኔር ሆይ፤ ይህ ልጅ
የማን ነው?" ሲል ጠየቀው።

አበኔርም፣ "ንጉሥ ሆይ፤ በሕያው ነፍ
ስህ እምላለሁ፤ አላውቅም" ብሎ መለሰለት።

56ንጉሡም፣ "እንግዲህ ወጣቱ የማን ልጅ
እንደ ሆነ ተከታትለህ ድረስበት" አለው።

57ዳዊት ፍልስጥኤማዊውን ገድሎ እንደ
ተመለሰ፣ አበኔር ይዞ ንጉሡ ዘንድ አቀ
ረበው። በዚህ ጊዜ ዳዊት የጎልያድን ራስ
በእጁ ይዞ ነበር።

58ሳኦልም፣ "አንተ ወጣት፣ የማን ልጅ ነህ?"
ሲል ጠየቀው።

ዳዊትም፣ "እኔ የአገልጋይህ የቤተልሔሙ
ሰው የእሴይ ልጅ ነኝ" ሲል መለሰ።

## ሳኦል በዳዊት ቀና

18 ዳዊት ከሳኦል ጋር የሚያደርገውን
ንግግር እንዳበቃ፤ የዮናታን ነፍስ
ከዳዊት ነፍስ ጋር ተቈራኘች፤ እንደራሱም
አድርጎ ወደደው። 2ከዚያች ዕለት አንሥቶ
ሳኦል ዳዊትን አብሮት እንዲኖር አደረገ፤
ወደ አባቱም ቤት እንዲመለስ አላሰናበተውም።
3ዮናታን እንደ ራሱ አድርጎ ስለ ወደደው፣

[ሀ]52 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራ ይስጡ ግን ሸለቆ ይላል።

17፥37 1ሳሙ16፥18፤ 18፥12፤2ቆሮ 1፥10፤ 2ጢሞ4፥17
17፥38 ዘፍ41፥42
17፥41 ቊ7
17፥42 1ሳሙ16፥12፤ መዝ123፥3-4፤ ምሳ16፥18
17፥43 1ሳሙ24፥14፤ 2ሳሙ3፥8፤9፥8፤ 2ነገ8፥13
17፥44 ዘፍ40፥19፤ 2ሳሙ21፥10፤ ኤር 34፥20፤ ራእ19፥17
17፥45 ቊ6፥10፤ ዘዳ20፥1፤2ዜና13፥12፤ 14፥11፤32፥8፤ መዝ 20፥7-8፤ 124፥8፤ ዕብ11፥32-34
17፥46 ዘዳ28፥26፤ ኢሱ4፥24፤ 1ሳሙ 14፥12፤ 1ነገ18፥36፤ 2ነገ5፥8፤19፥19፤ ኢሳ 11፥9፤37፥20፤
17፥47 ዘፀ14፥14፤ ዘኍ21፥14፤ 1ሳሙ2፥9፤14፥6፤ 2ዜና14፥11፤20፥15፤ መዝ44፥6-7፤ ኤር39፥18፤ ሆሴ1፥7
17፥50 1ሳሙ25፥29
17፥51 1ሳሙ21፥9፤ 22፥10፤ዕብ11፥34
17፥52 ኢሱ15፥11፣ 36
17፥55 1ሳሙ 16፥21፤ 26፥5
17፥58 ሩት4፥17
18፥1 ዘፍ44፥30፤ 1ሳሙ19፥1፤20፥16፤3 1፥2፤2ሳሙ1፥26፤ 4፥4
18፥3 1ሳሙ20፥8 ፤ 16፥17፥42፤22፥8፤ 23፥18፤24፥21፤ 2ሳሙ21፥7

ከዳዊት ጋር ኪዳን አደረገ፤ 4ዮናታን
የለበሰውን ካባ አውልቆ ከነጦር ልብሱ፣
በተጨማሪም ሰይፉን፣ ቀስቱንና መታጠ
ቂያውን ሰጠው፡፡
5ሳኦል በሚልከው በማናቸውም ስፍራ፣
ዳዊት ተልእኮውን በሚገባ[ሀ] ይፈጽም ስለ
ነበር፣ በሰራዊቱ ላይ ሾመው፤ ይህም ሕዝ
ቡን በሙሉ፣ የሳኦልንም የጦር ሹማምንት
ደስ አሰኘ፡፡
6ዳዊት ፍልስጥኤማዊውን ከገደለ በኋላ፣
ሰዎቹ ወደየቤታቸው በሚመለሱበት ጊዜ፣
ሴቶች ከበሮና መሰንቆ ይዘው እየዘፈኑ፣
እየጨፈሩና እልል እያሉ ንጉሥ ሳኦልን
ለመቀበል ከእስራኤል ከተሞች ሁሉ ወጡ፡፡
7ሴቶቹም እንዲህ ሲሉ በመቀባበል ዘፈኑ፤

"ሳኦል ሺህ ገደለ፤
ዳዊት ግን ዐሥር ሺህ ገደለ፡፡"

8ሳኦል እጅግ ተቈጣ፤ ይህም ነገር አላስ
ደሰተውም፡፡ እርሱም፣ "ለዳዊት ዐሥር ሺህ
አሉለት፤ ለእኔ ግን ሺህ ብቻ! እንግዲህ
መንግሥት እንጂ ሌላ ምን ቀረው" አለ፡፡
9ከዚያች ዕለት አንሥቶ ሳኦል ዳዊትን
በቅናት ዐይን ይመለከተው ጀመር፡፡
10በማግስቱም ከእግዚአብሔር የታዘዘ ክፉ[ሸ]
መንፈስ በሳኦል ላይ በኀይል መጣበት፣
በዚህ ጊዜ ዳዊት ወትሮ እንደሚያደርገው
ሁሉ በገና ሲደረድር፣ ሳኦል በቤቱ ሆኖ
ትንቢት ይናገር ነበር፡፡ ሳኦል በእጁ ጦር
ይዞ ነበር፤ 11እርሱም፣ "ዳዊትን ከግድግዳው
ጋር አጣብቀዋለሁ" ብሎ በማሰብ ጦሩን
ወረወረበት፤ ዳዊት ግን ሁለት ጊዜ ከፊቱ
ዘወር አለ፡፡
12*እግዚአብሔር* ከእርሱ ተለይቶ ከዳዊት
ጋር ስለ ሆነ፣ ሳኦል ዳዊትን ፈራው፡፡ 13ስለ
ዚህ ዳዊትን ከአጠገቡ በማራቅ የሺህ አለቃ
አደረገው፡፡ ዳዊትም ሰራዊቱን እየመራ
በፊታቸው ይወጣና ይገባ ነበር፡፡ 14*እግዚ
አብሔር* ከእርሱ ጋር ስለ ነበር
የሚያደርገው ነገር ሁሉ ይሳካለት[ወ] ነበር፡፡
15ሳኦልም፣ ዳዊት እንደ ተሳካለት[ዐ] ባየ ጊ
ዜ ፈራው፤ 16መላው እስራኤልና ይሁዳ
ግን ዳዊትን ወደዱት፤ በፊታቸው እየጠ
ወጣና እየገባ የሚመራቸው እርሱ ነበርና፡፡
17ሳኦል ዳዊትን፣ "ታላቋ ልጄ ሜሮብ
እነኋት፤ እርሷን እድርልሃለሁ፤ አንተ ግን
በጀግንነት አገልግለኝ፤ *የእግዚአብሔርንም*
ጦርነቶች ተዋጋ" አለው፤ ሳኦል በልቡ፣ "ፍል
ስጥኤማውያን እጃቸውን ያንሡበት እንጂ
እኔ በእርሱ ላይ እጄን አላነሣም" ብሎ
ነበርና፡፡
18ዳዊት ግን ሳኦልን፣ "የንጉሥ ዐማች
እሆን ዘንድ እኔ ማን ነኝ? ቤተ ሰቤም ሆነ
የአባቴ ጐሣስ በእስራኤል ዘንድ ምንድን
ነው?" አለው፡፡ 19ይሁን እንጂ[ዘ] የሳኦል
ልጅ ሜሮብ ለዳዊት የምትዳርበት ጊዜ
ሲደርስ ለመሓላታዊው ለኤስድሪኤል ተዳረች፡፡
20በዚህ ጊዜ የሳኦል ልጅ ሜልኮል ዳዊ
ትን ወደደችው፤ ሳኦልም ይህን ሲሰማ
ደስ አለው፡፡ 21ሳኦልም በልቡ፣ "ወጥመድ
እንድ ትሆነው፣ በፍልስጥኤማውያንም እጅ
እንዲጠፋ እርሷን እድርለታለሁ" ሲል አሰበ፡፡
ስለዚህ ሳኦል ዳዊትን፣ "እነሆ፤ ዛሬ ለሁለተኛ
ጊዜ ዐማቼ ትሆናለህ" አለው፡፡
22ከዚያም ሳኦል ባለሟሎቹን፣ "ለዳዊት፣
'እነሆ፤ ንጉሡ በአንተ ደስ ብሎታል፤ ባለ
ሟሎቹም ሁሉ ይወዱሃል፤ ስለዚህ ዐማቹ
ሁንለት' ብላችሁ በምስጢር ንገሩት" ብሎ
አዘዛቸው፡፡
23እነርሱም ይህንኑ ለዳዊት ደግመው
ነገሩት፤ ዳዊት ግን "ለመሆኑ የንጉሥ አማች
መሆንን እስከዚህ ትንሽ ነገር አድርጋችሁ
ትቈጥራላችሁን? እኔ አንድ ምስኪን ድኻና
እምብዛም የማልታወቅ ሰው ነኝ" አላቸው፡፡
24የሳኦል ባለሟሎችም ዳዊት ያላቸውን
በነገሩት ጊዜ፣ 25ሳኦል፣ "ዳዊትን፣ 'ንጉ
ሡስ ለልጅቱ ካንተ የሚፈልገው ጥሎሽ ጠ
ላ ቶቹን ለመበቀል የመቶ ፍልስጥኤ
ማውያ ንን ሸለፈት እንጂ ሌላ አይደለም
ብላችሁ ንገሩት' " አላቸው፡፡ ሳኦል ይህን
ያቀደው ዳዊት በፍልስጥኤማውያን እጅ
እንዲወድቅ ነበር፡፡
26ባለሟሎቹ ይህን ለዳዊት በነገሩት ጊዜ
የንጉሥ ዐማች መሆኑ ደስ አሰኘው፡፡
ስለዚህ የተወሰነው ጊዜ ከማለፉ በፊት፣
27ዳዊትና አብረውት የነበሩት ሰዎቹ ሄደው
ሁለት መቶ ፍልስጥኤማውያንን ገደሉ፤
ለንጉሡ ዐማች ይሆን ዘንድ፣ ሸለፈታቸውን
አምጥቶ በቍጥራቸው ልክ ለንጉሡ አቀረበ፤
ከዚያም ሳኦል ልጁን ሜልኮልን ለዳዊት
ዳረለት፡፡
28ሳኦል *እግዚአብሔር* ከዳዊት ጋር እንደ
ሆነና ልጁ ሜልኮልም እንደወደደችው
በተረዳ ጊዜ፣ 29ሳኦል ከቀድሞው ይልቅ
ፈራው፤ እስከ ዕድሜውም ፍጻሜ
ድረስ
ጠላቱ ሆነ፡፡ 30የፍልስጥኤማውያን ጦር
አዛዦች እንደ ወትሮው ሁሉ፣ ለጦርነት
ይወጡ ነበር፤ ዳዊትም ከቀሩት የሳኦል
መኳንንት የበለጠ ድል አገኘ[ዠ]፤ ስሙም
የታወቀ ሆነ፡፡

18÷4 ዘፍ41÷42፤ 2ሳሙ18÷11
18÷5 ቁ30፤ 2ሳሙ 5÷2
18÷6 ዘፀ15÷20፤ 2ሳሙ1÷20፤ መዝ68÷25
18÷7 ዘፀ15÷21፤ 1ሳሙ21÷11፤29÷5፤2 ሳሙ18÷3
18÷8 1ሳሙ13÷14
18÷9 1ሳሙ19÷1
18÷10 መሳ9÷23፤ 1ሳሙ10÷5፤16÷14፡ 21፤17÷6፤19÷7
18÷11 ቁ25፤ 1ሳሙ 20÷7ል33፤ 19÷10፤መዝ132÷1
18÷12 ቁ29፤ ኢሱ1÷5፤ መሳ 16÷20፤ 1ሳሙ16÷13፤17÷37፤ 20÷13፤ 1ዜና22÷11
18÷13 ዘኍ27÷17፤ 2ሳሙ5÷2
18÷14 ዘፍ39÷2፡3፤ ዘኍ14÷43፤ 2ሳሙ 7÷9
18÷16 2ሳሙ5÷2
18÷17 ቁ25፤ ዘፍ29÷26፤ ዘኍ 21÷14፤ 1ሳሙ 17÷25፤ 20÷33
18÷18 ቁ23፤ ዘፀ3÷11፤ 1ሳሙ9÷21
18÷19 መሳ7÷22፤ 2ሳሙ21÷8
18÷20 ቁ28፡29፤ ዘፍ29÷26
18÷21 ዘፀ10÷7፤ ዘዳ7÷16
18÷23 ቁ18
18÷25 ቁ11፡17፤ ዘፍ34÷12፤ መዝ8÷2፤44÷16፤ ኤር20÷10
18÷27 2ሳሙ3÷14፤6 ÷16
18÷28 ቁ20
18÷29 ቁ 12
18÷30 ቁ5

[ሀ]5 ወይም *በብልኀት*
[ሸ]10 ወይም *የሚጐዳ*
[ወ]14 ወይም *እጅግ ብልኀ ነበር*
[ዐ]15 ወይም *ብልኀ እንደሆነ*
[ዘ]19 ወይም *ስለዚህ ተብሎ*
[ዠ]30 ወይም *ዳዊት....የበለጠ በብልኀት አደረገ*

### ሳኦል ዳዊትን ለመግደል ያደረገው ሙከራ

19 ሳኦል ዳዊትን እንዲገድሉት ለልጁ
ለዮናታንና ለባልሟሎቹ ነገራቸው፡፡
ዮናታን ግን ዳዊትን እጅግ ይወደው
ነበር፣ 2እንዲህ ሲል አስጠነቀቀው፤ “አባቴ
ሳኦል ሊገድልህ አጋጣሚ እየፈለገ ነው፤
ነገ ጠዋት ተጠንቀቅ፤ ወደ አንድ መደበ
ቂያ ቦታም ሂድ፤ በዚያም ቈይ፡፡ 3እኔም
እወጣና አንተ ባለህበት ዕርሻ ከአባቴ አጠ
ገብ እቆማለሁ፤ ስለ አንተም አነጋግ
ረዋለሁ፤ የተረዳሁትንም እነግርሃለሁ፡፡”
4ዮናታን ለአባቱ ለሳኦል ስለ ዳዊት እን
ዲህ ሲል መልካም ነገር ተናገረ፣ “ንጉሥ
በአገልጋዩ በዳዊት ላይ ክፉ ነገር አያድ
ርግ፤ እርሱ አልበደለህም፤ ያደረገውም ነገር
በእጅጉ ጠቅሞሃል፡፡ 5ዳዊት ፍልስጥኤማዊ
ውን የገደለው በገዛ ሕይወቱ ቈርጦ ነው፡፡
*እግዚአብሔር* ለመላው እስራኤል ታላቅ
ድልን አቀዳጀ፤ አንተም አይተህ ደስ
አለህ፡፡ ታዲያ እርሱን በከንቱ በመግደል
ዳዊትን በመሰለ ንጹሕ ሰው ላይ ለምን በደል
ትፈጽማለህ?”
6ሳኦልም ዮናታንን ካዳመጠው በኋላ፣
“ሕያው *እግዚአብሔርን*! ዳዊት አይገደልም”
ብሎ ማለ፡፡
7ስለዚህም ዮናታን ዳዊትን ጠርቶ የተባ
ባሉትን ሁሉ ነገረው፤ ወደ ሳኦልም አመ
ጣው፤ ዳዊትም እንደ ቀድሞው በፊቱ
ቆመ፡፡
8እንደ ገና ሌላ ጦርነት ተነሣ፤ ዳዊትም
ወጥቶ ፍልስጥኤማውያንን ወጋቸው፤ ከፊ
ቱም እስኪሸሹ ድረስ እጅግ መታቸው፡፡
9ነገር ግን ሳኦል ጦሩን ይዞ በቤቱ ተቀ
ምጦ ሳለ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ክፉ[የ] መን
ፈስ መጣበት፤ ዳዊት በገናውን ይደረድር
ነበር፣ 10ሳኦልም ከግድግዳው ጋር ሊያጣብ
ቀው ጦሩን ወረወረበት፤ ነገር ግን ዳዊት
ዘወር በማለቱ ሳኦል የወረወረው ጦር እግድ
ግዳው ላይ ተሰካ፡፡ በዚያች ሌሊት ዳዊት ሸሽቶ
አመለጠ፡፡
11ሳኦልም የዳዊትን ቤት ከበው በማለዳ
እንዲገድሉት ሰዎችን ላከ፡፡ የዳዊት ሚስት
ሜልኮል ግን፣ “ሕይወትህን ለማትረፍ በዚ
ህች ሌሊት ካልሸሸህ፣ በነገው ቀን ትገደላ
ለህ” ብላ አስጠነቀቀችው፡፡ 12ሜልኮልም ዳዊትን
በመስኮት አሾልካ አወረደችው፣ እርሱም
ሸሽቶ አመለጠ፡፡ 13ከዚያም ሜልኮል የጣዖት[ዶ]
ምስል ወስዳ በዐልጋው ላይ አጋደመችው፤
በራስጌውም የፍየል ጠጕር አኖረች፤
በልብስም ሸፈነችው፡፡
14ሳኦል ዳዊትን እንዲይዙት ሰዎች
በላከ ጊዜ ሜልኮል፣ “እርሱ ታሞአል”

19፥1 1ሳሙ18፥1፡9
19፥2 1ሳሙ20፥5፡
19
19፥3 1ሳሙ20፥12
19፥4 1ሳሙ20፥32፤
22፥14፤25፥21፤
ምሳ17፥13፤31፥8፡
9፤ኤር18፥20
19፥5 ዘፍ31፥36፤
ዘዳ10፥10፥10-13፤
መሳ9፥17፤12፥3፤
1ሳሙ11፥13
19፥7 1ሳሙ18፥10
19፥9 መሳ9፥23፤
1ሳሙ10፥5
19፥10 1ሳሙ18፥11
19፥11 መሳ16፥2፤
መዝ59
19፥12 ኢሱ2፥15፤
ሐሥ9፥25፤
2ቆሮ11፥33
19፥13 ዘፍ31፥19
19፥14 ዘፀ1፥19፤
ኢሱ 2፥4
19፥18 1ሳሙ7፥17
19፥20 ዘኍ11፥25፡
29፤1ሳሙ10፥5
19፥23 1ሳሙ10፥13
19፥24 1ሳሙ10፥11፤
15፥35፤2ሳሙ6፥20፤ኢ
ሳ20፥2
20፥1 1ሳሙ22፥23፤2
3፥15፤24፥9፡11፤
25፥29፤መዝ40፥14፤5
4፥3፤63፥9፤70፥2

አለቻቸው፡፡
15ሳኦልም ሰዎቹ ዳዊትን እንዲያዩት መልሶ
ላካቸው፤ እርሱም፣ “እገድለው ዘንድ ከነዐል
ጋው አምጡልኝ” አላቸው፡፡ 16የተላኩትም
ሰዎች በገቡ ጊዜ እነሆ፤ የጣዖት ምስሉ
በዐልጋው ላይ ተጋድሞ በራስጌውም የፍ
የል ጠጕር ተደርጎለት ነበር፡፡
17ሳኦልም ሜልኮልን፣ “እንዲህ አድርገሽ
ያታለልሽኝ፣ ጠላቴ እንዲያመልጥ ያሰደድ
ሽው ለምንድን ነው?” ሲል ጠየቃት፡፡
ሜልኮልም፣ “ ‘እንዳመልጥ እርዳኝ፤
ያለዚያ እገድልሻለሁ’ አለኝ” ብላ መለሰች
ለት፡፡
18ዳዊት ሸሽቶ ካመለጠ በኋላ፣ ወደ
አርማቴም ወደ ሳሙኤል ሄደ፣ ሳኦል
ያደረገበትን ሁሉ ነገረው፡፡ ከዚያም እርሱና
ሳሙኤል ወደ ነዋት ሄደው ተቀመጡ፡፡
19ለሳኦልም፣ “እነሆ፤ ዳዊት በአርማቴም
በምትገኘው በነዋት ተቀምጦአል” ብለው
ነገሩት፡፡ 20ስለዚህ ዳዊትን እንዲይዙ
ሰዎችን ላከ፤ ይሁን እንጂ፣ የነቢያትም
ጉባኤ በሳሙኤል መሪነት ትንቢት ሲናገሩ
ባዩ ጊዜ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በሳኦል ሰዎች
ላይ ወረደ፤ እነርሱም እንደዚሁ ትንቢት
ተናገሩ፡፡
21ሳኦልም ይህ በተነገረው ጊዜ ሌሎች
ሰዎች ላከ፤ እነርሱም ትንቢት ተናገሩ፤
ሳኦል ለሦስተኛ ጊዜ ሰዎች ላከ፣ እነርሱም
ደግሞ ትንቢት ተናገሩ፡፡ 22በመጨረሻም፣
እርሱ ራሱ ወደ አርማቴም ሄደ፤ ከዚያም
በሤኩ ወዳለው ትልቅ የውሃ ማጠራቀሚያ
ጕድጓድ እንደ ደረሰ፣ “ሳሙኤልና ዳዊት
የትናቸው?” ሲል ጠየቀ፡፡
አንድ ሰውም “በአርማቴም በምትገኘው
በነዋት ዘራማ ናቸው” ብሎ ነገረው፡፡
23ስለዚህ ሳኦል በአርማቴም ወደምትገ
ኘው ወደ ነዋት ዘራማ ሄደ፤ የእግዚአብሔር
መንፈስ በእርሱም ላይ ደግሞ ወረደ፤
ወደ ነዋት እስኪደርስ ድረስም ትንቢት
እየተ ናገረ ተጓዘ፡፡ 24እርሱም ልብሱን
አውልቆ፣ በሳሙኤልም ፊት ደግሞ ትንቢ
ት ተናገረ፤ በዚህ ሁኔታም ቀኑንና ሌሊቱን
በሙሉ ራቁቱን ተጋደመ፡፡ ሕዝቡ፣
“ሳኦልም ደግሞ ከነቢያት እንደ አንዱ ሆኖ
ተቈጠረ?” ያለው በዚህ ምክንያት ነው፡፡

### ዳዊትና ዮናታን

20 ከዚህ በኋላ ዳዊት በአርማቴም
ካለችው ከነዋት ዘራማ ሸሽቶ
ወደ ዮናታን በመሄድ፣ “ምን አድርጌአለሁ?
ምን በደልስ ፈጸምሁ? አባትህ ሕይወቴን ለማ

[የ]9 ወይም የሚጐዳ
[ዶ]13 በዚህና በቍጥር 13 ላይ ዕብራይስጡ *ተራፊም* ይላል፡፡

ጥፋት የሚፈልገውስ በፊቱ ምን ተገኝቶብኝ
ነው?” ሲል ጠየቀው፡፡
[2]ዮናታንም፣ “ይህስ ከቶ አይሁንብህ፤ አት
ሞትም! እነሆ፤ አባቴ ትልቅም ይሁን ትንሽ
ማናቸውንም ነገር አስቀድሞ ሳይነግረኝ አያ
ደርገውም፡፡ ታዲያ አባቴ ይህን ለምን
ይደብቀኛል? ነገሩ እንዲህ አይደለም!”
ብሎ መለሰለት፡፡
[3]ዳዊት ግን፣ “በፊትህ ሞገስ ማግኘቴን
አባትህ በሚገባ ያውቃል፤ እርሱም በልቡ፤
‘ዮናታን እንዳያዝን ይህን ማወቅ የለበ
ትም’ ብሎአል፤ ነገር ግን ሕያው *እግዚአ
ብሔርን!* በነፍስህ እምላለሁ! በእኔና
በሞት መካከል አንድ እርምጃ ብቻ ቀርቶአል”
ብሎ ማለ፡፡
[4]ዮናታንም ዳዊትን፣ “እንዳደርግልህ የም
ትፈልገውን ማናቸውንም ነገር አደርግልሃ
ለሁ” አለው፡፡
[5]ስለዚህ ዳዊት እንዲህ አለ፤ ‘እነሆ፤ ነገ
የወር መባቻ በዓል ስለ ሆነ፣ ከንጉሡ ጋር
ምሳ መብላት ይጠበቅብኛል፤ ነገር ግን
እስከ ከነገ ወዲያ ማታ ድረስ ከዱር ልደ
በቅ፤ [6]አባትህ ከፈለገኝ፣ ‘ለቤተ ዘመዶቹ
ሁሉ ዓመታዊ መሥዋዕት የሚቀርብ ስለ
ሆነ፣ ዳዊት ወደ መኖሪያ ከተማው ወደ
ቤተልሔም ቶሎ ለመሄድ አጥብቆ ፈቃድ
ጠየቀኝ’ ብለህ ንገረው፡፡ [7]እርሱም ‘መልካም
ነው’ ካለ፣ አገልጋይህን የሚያሰጋው የለም፤
ከተቈጣ ግን፣ ክፉ ነገር እንዳሰበብኝ ታረ
ጋግጣለህ፡፡ [8]አንተ ግን፤ ለአገልጋይህ በጎነትን
አሳይ፣ ከአገልጋይህ ጋር *በእግዚአብሔር*
*ፊት* ቃል ኪዳን ገብታችኋልና፡፡ እኔ
በደለኛ ከሆንሁ፣ አንተው ራስህ ግደለኝ፤
ለምንስ ለአባትህ አሳልፈህ ትሰጠኛለህ!”
[9]ዮናታንም፣ “ይህ ከአንተ ይራቅ! አባቴ
ክፉ ነገር እንዳሰበብህ ባውቅ ኖሮ እንዴት
ሳልነግርህ እቀራለሁ?” አለው፡፡
[10]ዳዊትም፣ “አባትህ ክፉ ቃል ቢመል
ስልህ ማን ይነግረኛል?” ብሎ ጠየቀው፡፡
[11]ዮናታን፣ “በል ና፤ ወደ ሜዳ እንውጣ”
አለው፤ ተያይዘውም ወጡ፡፡
[12]ከዚያም ዮናታን ዳዊትን እንዲህ አለው፤
“የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር* ምስክር
ይሁንብኝ፤ አባቴን ነገ መርምሬ ነገ ወይም
ከነገ ወዲያ በዚህ ሰዓት እልክብሃለሁ፤ ስለ
አንተ ያለው አመለካከት በጎ ከሆነም አሳው
ቅሃለሁ፡፡ [13]ነገር ግን አባቴ ክፉ አስቦብህ፣
ይህን ሳላሳውቅህ ብቀርና በሰላም እንድት
ሄድ ባላደርግ፣ *እግዚአብሔር* ክፉ ያድርግ
ብኝ፤ ከዚያም የባሰ ያምጣብኝ፡፡ *እግዚአ
ብሔር* ከአባቴ ጋር እንደ ነበር እንደዚሁ
ከአንተም ጋር ይሁን፡፡ [14]አንተም እኔ በሕ
ይወት እስካለሁ ድረስ እንዳልገደል
*የእግዚአብሔርን* በጎነት አድርግልኝ፡፡ [15]*እግዚ
አብሔር* የዳዊትን ጠላቶች ሁሉ ከምድረ ገ
ጽ በሚደ መስሰበት ጊዜ እንኳ የበጎነት
ሥራህ ከቤተ ሰቤ በፍጹም አይቋረጥ፡፡
[16]ስለዚህ ዮናታን፣ “የዳዊትን ጠላቶች *እግ
ዚአብሔር* ይፋረዳቸው” በማለት ከዳዊት
ቤት ጋር ቃል ኪዳን አደረገ፡፡ [17]ዮናታን
ከፍቅሩ የተነሣ ዳዊት እንደ ገና እንዲምል
ለት አደረገ፤ ዳዊትን የሚወደውም እንደ
ራሱ አድርጎ ነበርና፡፡
[18]ከዚያም ዮናታን ዳዊትን እንዲህ አለው፤
“ነገ የወር መባቻ በዓል ነው፤ መቀመጫህ
ባዶ ስለሚሆን፣ አለመኖርህ ይታወቃል፡፡
[19]ከነገ ወዲያ ምሽት ላይ ይህ ችግር በተ
ፈጠረ ዕለት ወደ ተደበቅህበት ስፍራ ሂድና
ኤዜል በተባለው ድንጋይ አጠገብ ቈይ፡፡
[20]እኔም በአንድ ዒላማ ላይ እንደሚያነጣጥር
ሰው ወደ ድንጋዩ አጠገብ ሦስት ፍላጻ
እወረውራለሁ፤ [21]ከዚያም፣ ‘ሂድና ፍላጻቹን
አምጣቸው’ ብዬ አንድ ልጅ እልካለሁ፤ ል
ጁ ንም፣ ‘እነሆ፤ ፍላጻቹ ያሉት፣ ከአንተ
ወደ ዚህ ነው፤ ሄደህ አምጣቸው’ ያልሁት
እንደ ሆነ፣ ሕያው እግዚአብሔርን! ክፉ
ነገር አያገኝህም፤ አደጋም የለም፤ ውጣና ና፡፡
[22]ነገር ግን ልጁን፣ ‘እነሆ፤ ፍላጻቹ ያሉት
ከአንተ ወዲያ ዐልፎ ነው’ ያልሁት እንደ
ሆነ እግዚአብሔር እንድትሄድ ፈቅዶአልና
ሂድ፡፡ [23]አንተና እኔ ስለ ተነጋገርነው ነገር
እነሆ፤ *እግዚአብሔር* በመካከላችን ለዘላለም
ምስክር ነው፡፡”
[24]ስለዚህም ዳዊት በዱር ተደበቀ፤ የወር
መባቻ በዓል በተከበረበት ጊዜ፣ ንጉሡ
ግብር ለመብላት ተቀመጠ፤ [25]ንጉሡ እንደ
ወትሮው በግድግዳው[፳] አጠገብ ተቀመጠ፤
ዮናታን ከፊት ለፊቱ፣ አበኔር ደግሞ ከአጠ
ገቡ ተቀመጡ፤ የዳዊት መቀመጫ ግን ባዶ
ነበር፡፡ [26]ሳኦልም፣ “ዳዊት በሥርዐቱ መሠ
ረት እንዳይነጻ የሚያደርገው አንድ ነገር
ገጥሞታል፤ በእርግጥም አልነጻም” ብሎ
ስላሰበ፣ በዚያ ቀን ምንም አልተናገረም፡፡
[27]በማግስቱም፣ ወር በገባ በሁለተኛው ቀን
የዳዊት መቀመጫ ባዶ ነበር፤ ከዚያም
ሳኦል ልጁን ዮናታንን፣ “የእሴይ ልጅ
ትናንትናም፣ ዛሬም ግብር ላይ ያልተገኘው
ለምንድን ነው?” ሲል ጠየቀው፡፡
[28]ዮናታንም እንዲህ ብሎ መለሰለት፤
“ዳዊት ወደ ቤተ ልሔም እንዲሄድ እፈቅ
ድለት ዘንድ አጥብቆ ለመነኝ፡፡ [29]እርሱም

[፳]25 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራ ይስጡ *ዮናታን ሲነሣ* ይላል፡፡

20፥3 ዘዳ6፥13
20፥5 ዘኍ10፥10፤ 1ሳሙ19፥2
20፥6 ቊ28፤ 1ሳሙ1፥3፤17፥58
20፥7 1ሳሙ10፥27፤ 18፥11፤25፥17
20፥8 1ሳሙ18፥3፤ 2ሳሙ14፥32
20፥12 1ሳሙ19፥3
20፥13 ሩት1፥17፤ 1ሳሙ16፥18፤ 18፥12
20፥14 ዘፍ40፥14
20፥15 1ሳሙ24፥21፤ 2ሳሙ9፥7
20፥16 ኢሱ2፥23፤ 1ሳሙ 18፥1፡3
20፥17 ኢሱ9፥18፤ 1ሳሙ18፥3
20፥18 ቊ25
20፥19 1ሳሙ19፥2
20፥20 2ነገ13፥15
20፥22 ቊ37
20፥23 ዘፍ31፥50
20፥24 ዘኍ10፥10
20፥25 ቊ18
20፥26 ዘሌ7፥20-21
20፥28 ቊ6
20፥29 ዘፍ 8፥20

‘ቤተ ሰባችን በከተማዪቱ ውስጥ *መሥዋዕት*
ስለሚያደርግ በዚያ እንድገኝ ወንድሜ አዞ
ኛልና ልሂድ፤ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እን
ደሆነ ወንድሞቼን ለማየት እንድሄድ አሰ
ናብተኝ’ አለኝ፡፡ በንጉሡ ግብር ላይ ሳይ
ገኝ የቀረውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡”
30ሳኦል በዮናታን ላይ እጅግ ተቈጣ፤ እንዲ
ህም አለው፤ “አንተ የዚያች ጠማማና ዐመፀኛ
ሴት ልጅ! ለአንተው ለራስህ ውርደት፣
ለወላጅ እናትህም ዕፍረት ከሚሆነው ከእ
ሴይ ልጅ ጋር መግጠምህን የማላውቅ መሰ
ለህ? 31የእሴይ ልጅ በምድር ላይ በሕይ
ወት እስካለ ድረስ አንተም ሆንህ *መንግሥትህ*
አትጸኑም፡፡ *መሞት* ስለሚገባው፣ ሰው ላክና
አስመጣልኝ!”
32ዮናታንም፣ “ለምን ይገደላል? ጥፋቱስ
ምንድን ነው?” ሲል አባቱን ጠየቀ፡፡ 33ሳኦ
ልም ዮናታንን ለመግደል ጦሩን ወረወረበት፡፡
ስለዚህ ዮናታን፣ አባቱ ዳዊትን ለመግደል
ቈርጦ መነሣቱን ዐወቀ፡፡
34ዮናታንም በታላቅ ቍጣ ከግብሩ ላይ
ተነሣ፤ አባቱም ዳዊትን ስላዋረደው ወሩ
በገባ በሁለተኛው ቀን ምግብ አልበላም፡፡
35በማግስቱ ጠዋት ዮናታን አንድ ትንሽ
ልጅ አስከትሎ፣ ከዳዊት ጋር ወደ ተቃጠ
ረበት ቦታ ሄደ፤ 36ልጁንም፣ “ሩጥ! የምሰዳ
ቸውን ፍላጻዎች ፈልጋቸው” አለው፤ ልጁም
በሮጠ ጊዜ፣ ከእርሱ አሳልፎ አንድ ፍላጻ
ወረወረ፡፡ 37ልጁም የዮናታን ፍላጻ ባረፈበት
ስፍራ እንደ ደረሰ፤ ዮናታን ጠራውና፣
“ፍላጻው ካንተ ወዲያ ዐልፎ የለምን?”
አለው፡፡ 38እርሱም “ቶሎ በል! ፍጠን! አት
ቁም!” ሲል ጮኸበት፤ ልጁም ፍላጻዎቹን
ሰብስቦ ወደ ጌታው ተመለሰ፡፡ 39ከዮናታ
ንና ከዳዊት በስተቀር ልጁ ስለዚህ ነገር
የሚያውቀው አንዳች አልነበረም፡፡ 40ከዚያም
ዮናታን የጦር መሣሪያውን ለልጁ ሰጥቶ፣
“ይዘህ ወደ ከተማ ተመለስ” አለው፡፡
41ልጁ ከሄደ በኋላ፣ ዳዊት ከድንጋዩ
በስተ ደቡብ ከተደበቀበት ቦታ ወጥቶ
በዮናታን ፊት ሦስት ጊዜ በምድር ላይ ተደ
ፍቶ ሰገደለት፤ ከዚያም ተሳሳሙ፤ ተላቀ
ሱም፤ በይበልጥ ያለቀሰው ግን ዳዊት
ነበር፡፡
42ዮናታንም ዳዊትን፤ “ ‘በአንተና
በእኔ፣ በዘሮችህና በዘሮቼ መካከል *እግዚ
አብሔር* ለዘላለም ምስክር ነው’ ተባብለን
ወዳጅነ ታችን እንዲጸና በእግዚአብሔር
ስም ስለ ተማማልን እንግዲህ በሰላም ሂድ”
አለው፡፡ ከዚያም ዳዊት ተነሥቶ ሄደ፤
ዮናታንም ወደ ከተማ ተመለሰ፡፡

20፥31 1ሳሙ23፥17፤ 24፥20
20፥32 ዘፍ31፥36፤ 1ሳሙ19፥4፤ ማቴ27፥23
20፥33 1ሳሙ18፥11፥17
20፥37 ቍ22
20፥41 ዘፍ33፥3፤ ሩት2፥10፤ 1ሳሙ24፥8፤25፥23፤ 2ሳሙ1፥2
20፥42 ዘፍ31፥50 ፤ 40፥14፤1ሳሙ1፥17፤18፥3፤ 2ሳሙ1፥26፥9፥1፤ ምሳ18፥24፤ ኢሳ 48፥1፤ ሐሥ15፥33
21፥1 1ሳሙ16፥4፤ 22፥9፤19ነህ11፥32፤ ኢሳ10፥32
21፥4 ዘፀ19፥15፤ ዘሌ15፥18፤24፥8-9፤ ማቴ12፥4
21፥5 ዘዳ23፥9-11፤ ኢሱ3፥5፤ 2ሳሙ11፥11፤ 1ተሰ 4፥4
21፥6 ዘፀ25፥30፤ 1ሳሙ22፥10፤ ማቴ12፥3-4፤ ማር2፥25-28፤ ሉቃ6፥1-5
21፥7 1ሳሙ14፥47፤ 22፥9፡22፤መዝ52
21፥9 1ሳሙ17፥2፡ 4፡51
21፥10 1ሳሙ25፥13፤ 27፥2

### ዳዊት ወደ ኖብ ሄደ

21 ዳዊትም ካህኑ አቢሜሌክ ወዳ
ለበት ወደ ኖብ ሄደ፡፡ አቢሜሌክም
እየተንቀጠቀጠ ዳዊትን ሊገናኘው መጣና፣
“ምነው ብቻህን? ሰውስ ለምን አብሮህ
የለም?” ሲል ጠየቀው፡፡
2ዳዊት፣ ካህኑን አቢሜሌክን እንዲህ አለው፤
“ንጉሡ፣ ‘ስለ ላክሁህ ነገርና ስለ ሰጠሁህ
*መመሪያ* ማንም ሰው ምንም ነገር አይ
ወቅ’ ብሎ አዞኛል፡፡ ሰዎቼንም የት እን
ደምንገናኝ ነግሬያቸዋለሁ፡፡ 3ታዲያ አሁን
በእጅህ ምን አለ? አምስት እንጀራ ወይም
የተገኘውን ማንኛውንም ነገር ስጠኝ፡፡”
4ካህኑም፣ “ሰው ሁሉ የሚበላው እንጀራ
የለኝም፤ ነገር ግን ሰዎቹ በቅርቡ ከሴት
የተጠበቁ ከሆነ፣ የተቀደሰ እንጀራ በዚህ
አለ” አለው፡፡
5ዳዊትም “እንደተለመደው ሁሉ ከወጣሁ
ጊዜ ጀምሮ ሴቶች ከእኛ ተጠብቀዋል፤ ባል
ተቀደሰ ተልእኮ ውስጥ እንኳ የሰዎቹ ዕቃዎች[1]
የተቀደሱ ናቸው፤ ታዲያ ዛሬማ እንዴታ!”
ሲል መለሰ፡፡ 6ስለዚህ ካህኑ የተቀደሰውን
እንጀራ ለዳዊት ሰጠው፤ *ከእግዚአብሔር*
ፊት ተነሥቶ በትኩስ እንጀራ ከተተካው
ከኅብስተ ገጹ በስተቀር በዚያ ሌላ እንጀራ
አልነበረምና፡፡
7በዚያችም ዕለት ከሳኦል አገልጋዮች
አንዱና የእረኞቹ አለቃ የሆነው ኤዶማዊው
ዶይቅ እዚያው *በእግዚአብሔር* ፊት እንዲ
ቈይ ተገዶ ነበር፡፡
8ዳዊት አቢሜሌክን፣ “የንጉሡ ጕዳይ ስላ
ስቸኮለኝ፣ ሰይፌንም ሆነ ሌላ የጦር *መሣ
ሪያ* አላመጣሁም፤ እዚህ ካንተ ዘንድ ጦር
ወይም ሰይፍ አይገኝምን?” ሲል ጠየቀው፡፡
9ካህኑም፣ “በኤላ ሸለቆ አንተ የገደልኸው
የፍልስጥኤማዊው የጎልያድ ሰይፍ እዚህ
አለ፤ ከኤፉዱ በስተኋላ በጨርቅ ተጠቅል
ሎአል ከፈለግህ ውሰደው፤ ከእርሱ በስ
ተቀር ሌላ ሰይፍ እዚህ የለም” ብሎ መለ
ሰለት፡፡
ዳዊትም “እንደ እርሱ ያለ የለምና
እርሱኑ ስጠኝ” አለው፡፡

### ዳዊት ወደ ጌት ሄደ

10በዚያች ዕለት ዳዊት ከሳኦል ሸሽቶ
ወደ ጌት ንጉሥ ወደ አንኩስ ሄደ፡፡ 11የአ
ንኩስ አገልጋዮችም፣ “የምድሪቱ ንጉሥ
ዳዊት ይህ አይደለምን? ደግሞስ

‘ሳኦል ሺህ ገደለ፤
ዳዊት ግን ዐሥር ሺህ ገደለ’

[1]5 *ወይም አካል*

ብለው በጭፈራቸው የዘፈኑለትስ እርሱ
አይደለምን?” አሉት፡፡
12ዳዊት ነገሩን በልቡ አኖረ፤ የጌትን
ንጉሥ አንኩስንም እጅግ ፈራው፡፡ 13ስለዚህ
በፊታቸው አእምሮውን እንደሳተ ሰው
ሆነ፤ በያዙትም ጊዜ የከተማዪቱን ቅጥሮች
እየቦጫጨረ፣ ልጋጉንም በጺሙ ላይ እያዝረ
በረበ እንደ እብድ ሆነ፡፡
14አንኩስም አገልጋዮቹን እንዲህ አላቸው፤
ሰውየውን እስቲ ተመልከቱት፤ እብድ እኮ
ነው! ታዲያ ወደ እኔ ያመጣችሁት ለምንድን
ነው? 15በፊቴ እንዲህ ይሆን ዘንድ ይህን ሰው
እዚህ ያመጣችሁት እብድ አጥቼ ነውን?
እንዲህ ያለውስ ሰው ወደ ቤቴ መግባት
ይገባዋልን?”

### ዳዊት በዓዱላምና በምጽጳ

22 ዳዊት ከጌት ወደ ዓዱላም ዋሻ
ሸሸ፤ ወንድሞቹና የአባቱ ቤተ
ሰቦች ይህን በሰሙ ጊዜ፣ እርሱ ወዳለበት
ወደዚያው ወረዱ፡፡ 2የተጨነቁ፣ ዕዳ ያለባ
ቸውና የተከፉ አራት መቶ ያህል ሰዎች፣
ወደ እርሱ ተሰባሰቡ፤ መሪያቸውም ሆነ፡፡
3ዳዊት ከዚያ ተነሥቶ፣ በሞዓብ
ምድር ወዳለችው ወደ ምጽጳ ሄደ፤ ለሞዓብ
ንጉሥ፣ እግዚአብሔር የሚያደርግልኝን እስካ
ውቅ ድረስ፣ አባቴና እናቴ መጥተው ካንተ
ዘንድ እንዲቀመጡ ፈቃድህ ነውን?” አለው፡፡
4እርሱም በሞዓብ ንጉሥ ዘንድ አስቀመጣ
ቸው፤ ዳዊት በዐምባ ውስጥ እስከ ቈየበ
ትም ጊዜ ድረስ ከንጉሡ ዘንድ ተቀመጡ፡፡
5ይሁን እንጂ ነቢዩ ጋድ ዳዊትን፣ “በዐ
ምባው ውስጥ አትቈይ፤ ሂድና ወደ ይሁዳ
ምድር ግባ” አለው፡፡ ስለዚህ ዳዊት ተነ
ሥቶ ወደ ሔሬት ጫካ ገባ፡፡

### ሳኦል የኖብን ካህናት መግደሉ

6ሳኦልም፣ ዳዊትና ከእርሱ ጋር የነበሩ
ሰዎች መገኘታቸውን በሰማ ጊዜ፣ በጊብዓ
ኰረብታ ላይ በአጣጥ ዛፍ ሥር፣ ጦሩን በእጁ
ይዞ ተቀምጦ ነበር፤ ሹማምንቱም ሁሉ
በዙሪያው ቆመው ነበር፡፡ 7ሳኦልም እንዲህ
አላቸው፤ “እናንት የብንያም ሰዎች ስሙ!
በውኑ የእሴይ ልጅ ዕርሻና የወይን ቦታ
ለሁላችሁ ይሰጣችኋልን? ሁላችሁንስ ሻለቆ
ችና የመቶ አለቆች ያደርጋችኋልን?
8በእኔ ላይ የዶለታችሁት ለዚህ ነውን? ልጄ
ከእሴይ ልጅ ጋር ቃል ኪዳን ሲያደርግ
ማንም አልነገረኝም፤ ዛሬ እንደሚያደርገው
ሁሉ፣ ልጄ አገልጋዬን በእኔ ላይ እንዲያ
ደባብኝ ማነሣሣቱን ከእናንተ ስለ እኔ
ተቈርቍሮ የነገረኝ ማንም የለም፡፡”
9ነገር ግን እዚያ ከነበሩት የሳኦል ሹማም

21፥11 1ሳሙ18፥7
21፥13 መዝ34
22፥1 ዘፍ38፥1፤ መዝ57፤142
22፥2 1ሳሙ23፥13፤ 25፥13፤ 2ሳሙ 15፥20
22፥4 ዘፍ19፥37
22፥5 2ሳሙ23፥14፤ 24፥11፤1ዜና21፥9፤ 29፥25፡29
22፥6 ዘፍ21፥33፤ መሳ4፥5
22፥7 ዘዳ1፥15
22፥8 ቀኁ13፤ 1ሳሙ18፥3፤ 23፥21፤2ሳሙ20፥1
22፥9 1ሳሙ14፥3፤ 21፥1፡7
22፥10 ዘፍ25፥22፤ 1ሳሙ17፥51፤21፥6፤23፥2
22፥13 ቀኁ8
22፥14 1ሳሙ19፥4
22፥16 1ሳሙ2፥31
22፥17 ዘፀ1፥17
22፥18 1ሳሙ2፥18፤4፥17
22፥19 1ሳሙ15፥3፤ 21፥1
22፥20 1ሳሙ2፥32፤ 14፥3፤23፥6፡9፤30፥7፤ 2ሳሙ15፥24፤20፥25፤ 1ነገ1፥7፤2፥22፡ 26፡27፡4፥4፤ 1ዜና15፥11፤27፥34

ንት ጋር ቆሞ የነበረው ኤዶማዊው ዶይቅ
እንዲህ አለ፣ “የእሴይ ልጅ በኖብ ወዳለው
ወደ አኬጦብ ልጅ ወደ አቢሜሌክ ሲመጣ
አይቻለሁ፡፡ 10አቢሜሌክም *እግዚአብሔርን*
ጠየቀለት፤ እንዲሁም ስንቅና የፍልስጥኤ
ማዊውን የጎልያድን ሰይፍ ሰጠው፡፡”
11ከዚያም ንጉሡ፣ የአኪጦብን ልጅ ካህ
ኑን አቢሜሌክን፣ በኖብ ካህናት የነበሩ
ትን የአባቱን ቤተ ሰብ በሙሉ ልኮ አስጠ
ራቸው፤ ሁሉም ወደ ንጉሡ መጡ፡፡
12ሳኦልም፤ “የአኪጦብ ልጅ ሆይ፤ እንግዲህ ስ
ማ” አለው፡፡
አቢሜሌክም፣ “እሺ ጌታዬ” ብሎ
መለሰ፡፡
13ሳኦልም፤ “ዛሬ እንደሚያደርገው ሁሉ፣
በእኔ ላይ እንዲያምፅብኝና እንዲያደባብኝ፣
እንጀራና ሰይፍ በመስጠት፣ እግዚአብሔርን
ስለ እርሱ በመጠየቅ ከእሴይ ልጅ ጋር
ለምን ዶለታችሁብኝ?” አለው፡፡
14አቢሜሌክም ለንጉሡ እንዲህ ሲል መለሰ፤
“የንጉሥ ዐማች፣ የክብር ዘቦችህ አዛዥና
በቤተ ሰብህ ዘንድ እጅግ የተከበረው ዳዊ
ትን የመሰለ ታማኝ ከአገልጋዮችህ ሁሉ
ማን አለ? 15ስለ እርሱ እግዚአብሔርን ስጠይ
ቅስ ያ ቀን የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበርን?
ፈጽሞ አልነበረም፤ ይህን ጕዳይ በተመለከተ
አገልጋይህ የሚያውቀው ምንም ነገር ስለ
ሌለ ንጉሥ እኔን አገልጋዩን ወይም ከአባቴ
ቤተ ሰብ ማንንም ጥፋተኛ አያድርግ፡፡”
16ንጉሡ ግን፣ “አቢሜሌክ ሆይ፤ አንተም
የአባትህም ቤተሰብ በሙሉ በእርግጥ ትሞ
ታላችሁ” አለው፡፡
17ከዚያም ንጉሡ በአጠገቡ የቆሙትን
ዘቦች፣ “እነዚህም *የእግዚአብሔር* ካህናት
ከዳዊት ጋር ስላበሩ፣ ዳዊት መኰብለሉንም
እያወቁ ስላልነገሩኝ ዙሩና ግደሏቸው” ሲል
አዘዛቸው፡፡
የንጉሡ ሹማምንት ግን እጃቸውን አን
ሥተው *የእግዚአብሔርን* ካህናት ለመም
ታት ፈቃደኞች አልሆኑም፡፡
18ንጉሡም ዶይቅን፣ “እንግዲያውስ አን
ተው ዙርና ካህናቱን ግደላቸው” ብሎ
አዘዘው፡፡ ኤዶማዊው ዶይቅም ዞረና ገደላ
ቸው፡፡ በዚያች ዕለት ሰማንያ አምስት የበ
ፍታ ኤፉድ የለበሱ ካህናትን ገደለ፡፡ 19የካ
ህናቱንም ከተማ ኖብን በሰይፍ መታት፣
በዚያ የሚኖሩትንም ወንዶችንና ሴቶችን፣
ልጆችንና ጡት የሚጠቡ ሕፃናትን፣
እንዲሁም በሬዎችንና አህያዎችን፣ በጎችንም
ሁሉ በሰይፍ ስለት ፈጃቸው፡፡
20የአኪጦብ ልጅ፣ የአቢሜሌክ ልጅ
አብያታር ግን አምልጦ ዳዊት ወዳለበት
ሸሸ፡፡ 21እርሱም ሳኦል *የእግዚአብሔርን*

ካህናት እንደ ገደላቸው ለዳዊት ነገረው።
22ዳዊትም አብያታርን እንዲህ አለው፤ “ያን
ዕለት ኤዶማዊው ዶይቅ እዚያ ስለ ነበር፣
ነገሩን በትክክል ለሳኦል እንደሚናገር አው
ቄአለሁ፤ ለመላው የአባትህ ቤተሰብ ዕል
ቂት ተጠያቂው እኔ ነኝ። 23አሁንም ከእኔ
ጋር ቈይ፤ አትፍራ፤ የአንተን ሕይወት
የሚፈልግ የእኔን ሕይወት የሚፈልግ ነውና።
አብረኸኝ በሰላም ትኖራለህ።”

## ዳዊት ቅዒላን መታደጉ

23 ከዚህ በኋላ “እነሆ፤ ፍልስጥኤማ
ውያን በቅዒላ ላይ ጦርነት ከፍ
ተው፣ ዐውድማውን እየዘረፉት ነው” ብለው
ለዳዊት ነገሩት። 2እርሱም፣ “እነዚህን ፍልስ
ኤማውያን ሄጄ ልምታን?” ሲል *እግዚአ
ብሔርን* ጠየቀ።

*እግዚአብሔርም*፣ “ሂድ፤ ፍልስጥኤማው
ያንን ምታ፤ ቅዒላንም አድናት” ብሎ መለ
ሰለት።

3የዳዊት ሰዎች ግን፣ “እዚሁ በይሁዳ
ምድር እያለን እየፈራን ነው፤ የፍልስጥኤ
ማውያንን ሰራዊት ለመውጋት ወደ ቅዒላ
የምንሄድ ከሆነማ ምን ያህል የሚያስፈራ
ነው?” አሉት።

4ዳዊት እንደ ገና *እግዚአብሔርን* ጠየቀ፤
*እግዚአብሔርም*፣ “ፍልስጥኤማውያንን በእጅህ
አሳልፌ ስለምሰጥ፣ ወደ ቅዒላ ውረድ” አለው።
5ስለዚህ ዳዊትና ሰዎቹ ወደ ቅዒላ ሄደው፣
ፍልስጥኤማውያንን ወጉ፤ እንስሶቻቸውን
ማርከው ወሰዱ፤ በፍልስጥኤማውያን ላይ
ከባድ ጕዳት አደረሱ፤ ዳዊትም የቅዒ
ላን
ሕዝብ ታደገ። 6የአቢሜሌክ ልጅ አብያታር
ወደ ቅዒላ ወደ ዳዊት በሸሸ ጊዜ፣ ኤፉዱን
ይዞ ወርዶ ነበር።

## ሳኦል ዳዊትን ማሳደዱ

7ሳኦል የዳዊትን ወደ ቅዒላ መሄድ በሰማ
ጊዜ፣ “ዳዊት መዝጊያና የብረት መወርወ
ሪያ ወዳላት ከተማ መግባቱ፣ ራሱን
በራሱ እንደ ማሰር ስለ ሆነ፣ ይህን ሰው
እግዚአብሔር በእጄ አሳልፎ ሰጥቶኛል” አለ።
8ሳኦልም፣ ወደ ቅዒላ ወርደው ዳዊትንና
ሰዎቹን እንዲከቡ፣ ሰራዊቱን በሙሉ
ለጦርነት ጠራ።

9ዳዊትም ሳኦል ክፉ እንዳሰበበት ባወቀ
ጊዜ፣ ካህኑን አብያታርን፣ “ኤፉዱን
አምጣ” አለው። 10ከዚያም ዳዊት እንዲህ
አለ፤ “የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር*
ሆይ፤ ሳኦል ወደ ቅዒላ መጥቶ፣ በእኔ
ምክንያት ከተማዪቱን ለማጥፋት ማሰቡን
ባሪያህ በት ክክል ሰምቶአል። 11የቅዒላ
ሰዎች አሳል ፈው ይሰጡኝ ይሆን? ባሪያህ

22፥22 1ሳሙ21፥7
22፥23 1ሳሙ20፥1
23፥1 ዘኍ18፥27፤ ኢሱ15፥44፤መሳ6፥11
23፥2 ቍ4፥12፤ 1ሳሙ22፥10፤30፥8፤2 ሳሙ2፥1፤5፥19፤ መዝ50፥15
23፥4 ቍ2፤ ኢሱ 8፥7፤ 1ሳሙ9፥16
23፥6 1ሳሙ2፥28፤ 22፥20
23፥7 ዘዳ32፥30፤ መዝ31፥21
23፥9 1ሳሙ2፥18፤ 22፥20
23፥12 ቍ20
23፥13 1ሳሙ22፥2
23፥14 ኢሱ15፥24፤ መዝ32፥7፤54፥3-4፤ 55፥7
23፥15 1ሳሙ20፥1
23፥16 1ሳሙ30፥6፤ መዝ18፥2፤27፥14
23፥17 1ሳሙ20፥31
23፥18 1ሳሙ18፥3 ፤ 2ሳሙ9፥1
23፥19 1ሳሙ26፥1፡ 3፤መዝ54
23፥20 ቍ12
23፥21 ሩት2፥20፤ 1ሳሙ22፥8፤ 2ሳሙ2፥5
23፥23 ዘፍ31፥36
23፥24 ኢሱ15፥55፤ 1ሳሙ26፥1

እንደሰማውም ሳኦል ወደዚህ ይወርድ
ይሆን? የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር*
ሆይ፤ ለባሪያህ እንድ ትነግረው
እለምንሃለሁ።”

*እግዚአብሔርም*፣ “አዎን ይወርዳል” አለው።

12ዳዊትም እንደ ገና፣ “የቅዒላ ነዋሪዎች
እኔንና ሰዎቼን ለሳኦል አሳልፈው ይሰጡ
ናል?” ሲል ጠየቀ።

*እግዚአብሔርም*፣ “አዎን አሳልፈው ይሰጡ
አችኋል” አለው።

13ስለዚህ ዳዊትና ስድስት መቶ
የሚሆኑ ሰዎቹ ከቅዒላ ተነሥተው መሄድ
ወደ ሚች ሉበት ቦታ ሁሉ ሄዱ፤ ዳዊት
ከቅዒላ መሸሹን በሰማ ጊዜ፣ ሳኦል ወደዚያ
መሄዱን ተወ።

14ዳዊት በምድረ በዳ ባሉ ምሽጎችና በዚፍ
ምድረ በዳ ኰረብታዎች ተቀመጠ፤ ሳኦ
ልም በየዕለቱ ይከታተለው ነበር፤ ነገር ግን
እግዚአብሔር ዳዊትን አሳልፎ አልሰጠ
ውም።

15ዳዊት በዚፍ ምድረ በዳ ሖሬሽ በተባለ
ቦታ ሳለ፣ ሳኦል ሊገድለው መምጣቱን
አየ። 16የሳኦል ልጅ ዮናታንም ዳዊት
ወዳለበት ወደ ሖሬሽ ሄዶ፣ በእግዚአብሔር
ስም አበረታ ታው፤ 17እርሱም፣ “አትፍራ፤
አባቴ ሳኦል እጁን በአንተ ላይ አያሳርፍም፤
በእስራኤል ላይ ትነግሣለህ፤ እኔም ካንተ
ቀጥዬ ሁለተኛ ሰው እሆናለሁ፤ ይህንም
አባቴ ሳኦል እንኳ ያውቀዋል” አለው።
18ሁለቱም *በእግዚአብሔር ፊት* ቃል ኪዳን
አደረጉ። ከዚያም ዮናታን ወደ ቤቱ ሄደ፤
ዳዊት ግን እዚያው ሖሬሽ ተቀመጠ።

19የዚፍ ሰዎች ወደ ጊብዓ ወደ ሳኦል
ወጥተው እንዲህ አሉ፤ “እነሆ፤ ዳዊት ከየሴ
ሞን በስተደቡብ በኤኬላ ኰረብታ ላይ
በሖሬሽ ምሽጎች ውስጥ በመካከላችን ተደ
ብቆ የለምን? 20አሁንም ንጉሥ ሆይ፤
አንተ ደስ ባለህ ጊዜ ና እንጂ፣ እርሱን
ለንጉሡ አሳልፎ ለመስጠት እኛ አለን።”

21ሳኦል እንዲህ ሲል መለሰ፤ “ለእኔ ስለ
ተቈረቈራችሁ *እግዚአብሔር* ይባርካችሁ፤
22አሁንም ሂዱና አጣሩ ዘወትር የት
እንደ ሆነና በዚያ ያየውን ሰው
ለይታችሁ ዕወቁ፤ እጅግ ተንኰለኛ
መሆኑን ሰምቻለሁና። 23የሚደበቅባቸውን
ቦታዎች ሁሉ ካያችሁ በኋላ ግልጽ መረጃ
ይዛችሁ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም አብሬችሁ
እሄዳለሁ፤ ብቻ በዚያ አገር ይገኝ እንጂ
በይሁዳ ነገዶች ሁሉ መካከል ከገባበት
ጕድጓድ ገብቼ አወጣዋ ለሁ።”

24ስለዚህ ሰዎቹ ለመሄድ ተነሥተው ከሳ
ኦል በፊት ወደ ዚፍ ሄዱ፤ በዚህ ጊዜ
ዳዊትና ሰዎቹ ከየሴሞን በስተ ደቡብ በዓ
ረባ ውስጥ ባለው በማዖን ምድረ በዳ ነበሩ።

25ሳኦልና ሰዎቹም ዳዊትን ሊፈልጉት
ሄዱ፤ እርሱም ይህን በሰማ ጊዜ፣ ወደ ዐለቱ
ወርዶ በማዖን ምድረ በዳ ተቀመጠ። ሳኦልም
ይህን እንደሰማ፣ ዳዊትን በማሳደድ ወደ
ማዖን ምድረ በዳ ዘልቆ ገባ።
26ሳኦል በተራራው በአንዱ በኩል ሆኖ ሲያ
ሳድድ፣ ዳዊትና ሰዎቹ ደግሞ በተራራው
በሌላ በኩል ከሳኦል ለማምለጥ ይጣደፉ
ነበር። ሳኦልና ወታደሮቹ ዳዊትንና ሰዎቹን
ከበው ለመያዝ ተቃርበው ሳሉ፣ 27አንድ
መልእክተኛ ወደ ሳኦል መጥቶ፣
"ፍልስጥኤማውያን አገሩን ወረውታልና
ቶሎ ድረስ!" አለው። 28ከዚያም ሳኦል
ዳዊትን ማሳደዱን ትቶ፣ ከፍልስጥኤ
ማውያን ጋር ሊዋጋ ሄደ። ከዚህ የተነሣም
የዚያን ቦታ ስም "የመለ ያያ ዐለት"
ብለው ጠሩት። 29ዳዊትም ከዚያ ወደ ላይ
ወጥቶ በዐይንጋዲ ምሽጎች ተቀ መጠ።

## ዳዊት ሳኦልን ከመግደል ታቀበ

24 ሳኦል ፍልስጥኤማውያንን ከማሳ
ደድ ከተመለሰ በኋላ፣ "እነሆ፤
ዳዊት በዓይንጋዲ ምድረ በዳ አለ" ብለው
ነገሩት። 2ስለዚህ ሳኦል ከመላው እስራኤል
የተመረጡ ሦስት ሺህ ሰዎችን ይዞ ዳዊትንና
ሰዎቹን ለመፈለግ "የሚዳ ፍየሎች ዐለት"
ወደ ተባለው ቦታ አቅራቢያ ሄደ።
3ሳኦልም በመንገድ ዳር ወዳለው ወደ
አንድ የበጎች ማደሪያ በደረሰ ጊዜ፣ ዋሻ
አግኝቶ ወገቡን ሊሞክር ወደዚያ ገባ። ዳዊትና
ሰዎቹም ከዋሻው በውስጠኛው ቦታ ተቀምጠው
ነበር። 4የዳዊት ሰዎችም ዳዊትን፣ "*እግዚ
አብሔር*፣ 'የወደድኸውን ታደርግበት ዘንድ
ጠላትህን በእጅህ አሳልፌ እሰጥሃለሁ' ብሎ
ለአንተ የተናገረው ቀን ዛሬ ነው" አሉት።
ዳዊትም በልቡ እየተሳበ ሄዶ የሳኦልን ልብስ
ጫፍ ማንም ሳያውቅ ቈርጦ ወሰደ።
5ዳዊት የሳኦልን ልብስ ጫፍ በመቍረጡ
ልቡ በሐዘን ተመታ። 6ለሰዎቹም፣ "*እግዚ
አብሔር* በቀባው በጌታዬ ላይ እንዲህ
ያለውን ነገር ከማድረግና *እግዚአብሔር*
የቀባው ስለ ሆነም እጄን በእርሱ ላይ ከማን
ሣት *እግዚአብሔር* ይጠብቀኝ" አላቸው።
7ዳዊት ሰዎቹን በዚህ ቃል ገሠጻቸው፤ በሳ
ኦል ላይ አደጋ እንዲያደርሱበትም አልፈቀ
ደላቸውም። ሳኦልም ከዋሻው ወጥቶ ሄደ።
8ከዚያም ዳዊት ከዋሻው ወጥቶ ሳኦልን፣
"ጌታዬ ንጉሥ ሆይ!" ብሎ ጠራው። ሳኦ
ልም ወደ ኋላው ዞር ባለ ጊዜ፣ ዳዊት ወደ
መሬት ጐንበስ ብሎ እጅ ሲነሣው ተመ
ለከተ፤ 9ዳዊትም ሳኦልን እንዲህ አለው፤
"ሰዎች፣ 'እነሆ፤ ዳዊት ክፉ ነገር ሊያደር
ግብህ ይፈልጋል' ሲሉ ለምን ትቀበላቸዋ
ለህ? 10በዛሬው ዕለት በዋሻው ውስጥ *እግዚ
አብሔር* አንተን እንዴት አድርጎ በእጄ
ላይ እንደ ጣለህ እነሆ፤ በገዛ ዐይንህ አይ
ተሃል፤ አንዳንዶች እንድገድልህ ገፋፍተ
ውኝ ነበር፤ እኔ ግን፣ '*እግዚአብሔር* በቀባው
በጌታዬ ላይ እጄን አላነሣም' በማለት ራራ
ሁልህ። 11አባቴ ሆይ፤ የልብስህ ቍራጭ
ይኸው በእጄ ላይ ተመልከተው! የልብስህን
ጫፍ ቈረጥሁ እንጂ አንተን አልገደል
ሁህም። አሁንም ክፋት ወይም ዐመፅ
አለመፈጸሜን ዕወቅልኝ፤ ተረዳልኝም፤ እኔ
ክፉ አልሠራሁብህም፤ አንተ ግን ሕይወ
ቴን ለማጥፋት እያሳደድኸኝ ነው። 12*እግዚ
አብሔር* በአንተና በእኔ መካከል ይፍረድ።
ክፉ ስላደረግህብኝ *እግዚአብሔር* ይበቀልህ
እንጂ፣ እጄስ በአንተ ላይ አትሆንም፤ 13በጥንት
አባባል፣ 'ለክፉ አድራጊዎች ክፉ ድርጊት
ይወጣል' እንደ ተባለ፤ አሁንም እጄ በአንተ
ላይ አትሆንም።
14 "የእስራኤል ንጉሥ የወጣው በማን ላይ
ነው? አንተስ የምታሳድደው ማንን ነው?
የሞተ ውሻን? ወይስ ቁንጫ? 15አሁንም
*እግዚአብሔር* ዳኛ ሆኖ በመካከላችን ይፍ
ረድ፤ ጉዳዬን ተመልክቶ እርሱው ይሟ
ገትልኝ፤ እኔንም ከእጅህ ነጻ በማውጣት
እውነተኛ መሆኔን ይግለጠው።"
16ዳዊት ይህን ተናግሮ ሲያበቃ ሳኦል፣
"ልጄ ዳዊት ሆይ፤ ይህ የአንተ ድምፅ ነውን?"
ሲል ጠየቀው፤ ጮኾም አለቀሰ። 17እንዲ
ህም አለ፤ "ክፉ ሳደርግብህ፣ በጎ
መልሰህልኛልና፣ አንተ ከእኔ ይልቅ ጻድቅ
ነህ። 18ያደረግ ህልኝን በጎ ነገር ይኸው
ነግረኸኛል፤ *እግዚአብሔር* እኔን በእጅህ
ጥሎኝ ነበር፤ አንተ ግን አልገደልኸኝም።
19ለመሆኑ ጠላቱን አግኝቶ ጉዳት
ሳያደርስበት የሚለቀው ማን ነው? ዛሬ
ስላደረግህልኝ ቸርነት *እግ ዚአብሔር*
ይመልስልህ። 20እነሆ፤ አንተ በእርግጥ
እንደምትነግሥና የእስራኤል መን ግሥት
በእጅህ እንደምትጸና ዐውቃለሁ።
21ዘሮቼን እንዳታጠፋ ስሜንም ከአባቴ ቤት
እንዳትደመስስ አሁን *በእግዚአብሔር* ማልልኝ።"
22ዳዊትም ለሳኦል ማለለት፤ ከዚያም
ሳኦል ወደ ቤቱ ተመለሰ። ዳዊትና ሰዎቹ
ግን ወደ ዐምባው ወጡ።

## ዳዊት፣ ናባልና አቢግያ

25 ሳሙኤልም ሞተ፤ እስራኤል ሁሉ
ተሰብስበው አለቀሱለት፤ አርማቴም
ባለው ቤቱም ቀበሩት።
ከዚያም ዳዊት ተነሥቶ ወደ ማዖን ምድረ
በዳ ወረደ። 2በማዖን ምድር በቀርሜሎስ

23፥26 መዝ17፥9
23፥29 ኢሱ15፥62፤ 1ሳሙ24፥22፤ 2ዜና 20፥2፤ ማሕ1፥14፤
24፥1 ኢሱ15፥62
24፥2 1ሳሙ26፥2
24፥3 መሳ3፥24፤ መዝ57፤142
24፥4 ቀኑ10፡11፤ 1ሳሙ25፥28-30፤ 2ሳሙ4፥8
24፥5 1ሳሙ24፥10፤ 26፥9
24፥6 ዘፍ26፥11፤ 1ሳሙ12፥3
24፥8 1ሳሙ20፥41
24፥9 1ሳሙ26፥9፤ 2ሳሙ24፥10
24፥10 ቀኑ4
24፥11 ቀኑ4፤ ዘፍ 31፥36፤ 1ሳሙ20፥1፤ 25፥28፤26፥20፤ መዝ7፥3፤35፥7
24፥12 ዘፍ16፥5፤ ዘኍ31፥3፤ 1ሳሙ 25፥38፤ ኢዮ9፥15
24፥13 ማቴ 7፥20
24፥14 1ሳሙ17፥43፤ 26፥20
24፥15 ቀኑ12፤ ዘፍ16፥5፤መዝ26፥1፤ 35፥1፡23፡24፤43፥1፤ 50፥4፤54፥1፤119፥13፤ 4፡154፤135፥14፤ ኢሳ49፥25
24፥16 1ሳሙ26፥17
24፥17 ዘፍ38፥26፤ ዘዳ9፥27፤ማቴ 5፥44
24፥18 1ሳሙ26፥23
24፥19 ሩት2፥12፤ 2ዜና15፥7
24፥20 1ሳሙ13፥14፤ 20፥31
24፥21 ዘፍ21፥23፤ 47፥31፤1ሳሙ18፥3፤20፥14-15፤ 2ሳሙ21፥1-9
24፥22 1ሳሙ23፥29
25፥1 ዘሌ10፥6፤ ዘዳ34፥8፤ 1ሳሙ7፥17፤28፥3

ንብረት ያለው አንድ ባለጸጋ ሰው ነበረ፤
እርሱም አንድ ሺህ ፍየሎችና በቀርሜሎስ
የሚሸልታቸው ሦስት ሺህ በጎች ነበሩት፡፡
3የሰውየው ስም ናባል፣ የሚስቱም ስም
አቢግያ ነበረ፡፡ እርሷም አስተዋይና ውብ
ነበረች፤ ባሏ ግን ባለጌና ምግባረ ብልሹ
ሰው ነበረ፤ እርሱም ከካሌብ ወገን ነበር፡፡
4ዳዊት በምድረ በዳ ሳለ ናባል በጎቹን
እንደሚሸልት ሰማ፡፡ 5እርሱም ዐሥር ወጣ
ቶችን እንዲህ ሲል ላካቸው፤ “ወደ ቀርሜ
ሎስ ወደ ናባል ውጡ፤ በስሜም ሰላምታ
አቅርቡለት፡፡ 6እንዲህም በሉት፤ ‘ዕድሜህ
ይርዘም! ሰላም ለአንተ ይሁን፤ ሰላም ለቤ
ተሰብህና የአንተ ለሆነው ሁሉ ይሁን፡፡
7“በዚህ ጊዜ በጎች እንደምትሸልት ሰምቻ
ለሁ፤ እረኞችህ ከእኛ ጋር በነበሩበት ጊዜ፣
ያደረስንባቸው ጉዳት የለም፤ ቀርሜሎስ
በነበሩበት ጊዜ ሁሉ፣ የጠፋባቸው አንዳች
ነገር አልነበረም፡፡ 8የገዛ አገልጋዮችህን ጠይቅ፤
እነርሱም ይነግሩሃል፡፡ ስለዚህ አመጣጣችን
በጥሩ ቀን በመሆኑ፣ እነዚህ ወጣቶቼ በፊትህ
ሞገስ ያግኙ፡፡ እባክህን ለአገልጋዮችህና
ለልጅህ ለዳዊት የምትችለውን ያህል ስጥ፡፡” ’
9የዳዊት ሰዎች ከዚያ እንደ ደረሱም፣
በዳዊት ስም ይህንኑ መልእክት ለናባል
ከተናገሩ በኋላ ምላሹን ይጠባበቁ ጀመር፡፡
10ናባልም ለዳዊት አገልጋዮች እንዲህ
ሲል መለሰ፤ “ለመሆኑ ይህ ዳዊት ማነው?
የእሴይስ ልጅ ማን ነው? በአሁኑ ጊዜ ከጌቶ
ቻቸው የሚኰበልሉ አገልጋዮች ብዙ ናቸው፡፡
11ታዲያ እንጀራዬንና ውሃዬን እንዲሁም
በጎቼን ለሚሸልቱልኝ ሰዎች ያረድሁትን
ፍሪዳ ከየት እንደመጡ ለማይታወቁ ሰዎች
የምሰጠውስ ለምንድን ነው?”
12የዳዊት ሰዎችም ወደ መጡበት ተመ
ለሱ፤ እዚያም እንደ ደረሱ የተባሉትን ሁሉ
ነገሩት፡፡ 13ዳዊትም ሰዎቹን፣ “በሉ ሁላች
ሁም ሰይፋችሁን ታጠቁ” አላቸው፡፡ ስለዚህ
ሁሉም ሰይፋቸውን ታጠቁ፤ ዳዊትም የራ
ሱን ታጠቀ፡፡ አራት መቶ ያህል ሰዎች ከዳ
ዊት ጋር ሲወጡ መቶ ያህሉ ግን ጓዝ
ለመጠበቅ ቀሩ፡፡
14ከአገልጋዮቹ አንዱ ለናባል ሚስት ለአ
ቢግያ እንዲህ አላት፤ “እነሆ፤ ዳዊት ሰላም
ታውን እንዲያቀርቡለት ከምድረ በዳ ወደ
ጌታችን መልእክተኞች ልኮ ነበር፤ እርሱ
ግን የስድብ ናዳ አወረደባቸው፡፡ 15እነዚህ
ሰዎች ግን እጅግ መልካም ነበሩ፤ ጉዳትም
አላደረሱብንም፤ በዱር አብረናቸው በነበር
ንበት ጊዜም ሁሉ፣ ምንም ነገር አልጠፋ
ብንም፡፡ 16በጎቻችንን እየጠበቅን አብረናቸው
ባሳለፍነው ጊዜ ሁሉ፣ ቀንም ሆነ ሌሊት

25፥2 ዘፍ31፥19፤ ኢሱ15፥55፤ 2ሳሙ19፥32
25፥3 15፥13፤ ምሳ31፥10
25፥6 1ዜና12፥18፤ መዝ122፥7፤ ማቴ10፥12
25፥7 ቀኁ15
25፥8 ነህ8፥10
25፥10 መሳ9፥28
25፥11 መሳ8፥6
25፥13 ዘኍ31፥27፤ 1ሳሙ21፥10፤22፥2
25፥14 1ሳሙ13፥10
25፥15 ቀኁ7፡21
25፥16 ዘፀ14፥22፤ ኢዮ1፥10፤ መዝ139፥5
25፥17 ዘዳ13፥13፤ 1ሳሙ20፥7
25፥18 ዘፍ42፥26፤ ዘሌ23፥14፤ 1ሳሙ 17፥17፤ 2ሳሙ16፥1፤ 1ዜና12፥40፤ ኢሳ 30፥6
25፥19 ቀኁ36፤ ዘፍ32፥20
25፥21 ቀኁ15፤ 1ሳሙ19፥4፤ መዝ109፥5
25፥22 ሩት1፥17፤ 1ነገ14፥10፤21፥21፤ 2ነገ9፥8
25፥23 ዘፍ19፥1፤ 1ሳሙ20፥41
25፥24 2ሳሙ14፥9
25፥25 ምሳ12፥16፤ 14፥16፥17፥12፤20፥3፤ ኢሳ32፥5፡34፤ 2ሳሙ 18፥32፤ ዕብ10፥30
25፥27 ዘፍ33፥11
25፥28 ቀኁ24፤ 1ሳሙ18፥17፤24፥11፤ 2ሳሙ7፥11፡ዕ26፤ 14፥9

በዙሪያችን ዐጥር ሆነውን ነበር፡፡ 17አሁንም
በጌታችንና በመላው ቤተ ሰቡ ላይ መከራ
እያንዣበበ ስለሆነ፣ አስቢበትና የምታደርጊ
ውን አድርጊ፤ እርሱ እንደ ሆነ እንዲህ
ያለ ባለጌ ሰው ስለሆነ፣ ደፍሮ የሚነግረው
አንድም ሰው የለም፡፡
18አቢግያም ጊዜ አላጠፋችም፤ ሁለት
መቶ እንጀራ፣ ሁለት አቁማዳ የወይን ጠጅ፣
አምስት የተሰናዱ በጎች፣ አምስት መስፈ
ሪያ የተጠበሰ[ጣ] እሸት፣ መቶ የወይን ዘለላና
ዘቢብ፣ ሁለት መቶ ጥፍጥፍ የበለስ ፍሬ
ወስዳ በአህዮች ላይ ጫነች፡፡ 19ከዚያም
አገልጋዮቿን፣ “ቀድማችሁኝ ሂዱ፤ እኔም
እከተላችኋለሁ” አለቻቸው፤ ለባሏ ለናባል
ግን አልነገረችውም፡፡
20እርሷም በአህያዋ ላይ ተቀምጣ ወደ
ሸለቆው በምትወርድበት ጊዜ ዳዊትና ሰዎቹ
ወደ እርሷ ወረዱ፤ እርሷም አገኘቻቸው፡፡
21ዳዊትም እንዲህ ብሎ ነበር፤ “ምንም ነገር
እንዳይጠፋበት የዚህን ሰው ሀብት
በምድረ በዳ ያን ያህል መጠበቄ ለካ
በከንቱ ኖሮ አል፤ ደግ በሠራሁ ይኸው
ክፉ መለሰልኝ፡፡ 22ነገ ጠዋት የእርሱ
ከሆነው ሁሉ አንድ ወንድ እንኳ በሕ
ይወት ባስቀር እግዚአብሔር በዳዊት ላይ[ጨ]
እንዲህ ያለውን ነገር ያድርግ ግበት፣ ከዚ
ህም የከፋ ይጨምርበት!”
23አቢግያም ዳዊትን ባየች ጊዜ ወዲ
ያው ከአህያዋ ወርዳ፣ በዳዊትም ፊት
በግምባርዋ ተደፍታ እጅ ነሣች፡፡ 24በእግሩም
ላይ ወድቃ እንዲህ አለች፤ “ጌታዬ ሆይ፤
በደሉ በእኔ ላይ ብቻ ይሁን፤ እባክህ አገልጋይህ
ታናግርህ፤ የምትልህንም ስማ፡፡ 25ጌታዬ፣
ያን ባለጌ ሰው ናባልን ከቁም ነገር አይቍጠ
ረው፤ ስሙ ራሱ ጅል ማለት ስለሆነ፣
ሰውየውም ልክ እንደ ስሙ ነው፤ ጅልነትም
አብሮት የኖረ ነው፡፡ እኔ አገልጋይህ ግን
ጌታዬ የላካቸውን ጕልማሶች አላየኋቸውም፡፡
26“ጌታዬ ሆይ፤ ሕያው *እግዚአብሔርን!*
በሕያው ነፍስህም እምላለሁ፤ ደም ከማፍሰ
ስና በገዛ እጅህ ከመበቀል የጠበቀህ *እግዚ
አብሔር* ነው፤ አሁንም ጠላቶችህና ጌታዬን
ሊጐዱ የሚፈልጉ ሁሉ እንደ ናባል ይሁኑ፤
27አገልጋይህም ለጌታዬ ያመጣችው ይህ
ስጦታ አንተን ለሚከተሉ ጕልማሶች ይሰጥ፡፡
28ጌታዬ *የእግዚአብሔርን* ጦርነት ስለሚዋጋ
*እግዚአብሔርም* ለጌታዬ ሥርወ መንግሥቱን
በእርግጥ ለዘላለም የሚያጸናለት በመሆኑ፣
እባክህ የእኔን የአገልጋይህን በደል ይቅር
በል፤ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ ክፋት
አይገኝብህ፡፡

[ጣ]18 37 ሊትር ያህል ነው፡፡
[ጨ]22 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች ከዚህ ጋር ይስማ
ማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን *በዳዊት ጠላቶች ላይ* ይላል፡፡

29ማንም ሰው ሕይወትህን ለማጥፋት ቢያ
ሳድድህ እንኳ፣ የጌታዬ ሕይወት በሕያዋን
አንድነት እስራት ውስጥ በአምላክህ በእግዚ
አብሔር ዘንድ በሰላም ትጠበቃለች፤ የጠ
ላቶችህን ሕይወት ግን፣ እንደ ወንጭፍ
ድንጋይ ይወነጭፋል። 30እግዚአብሔር ለጌታዬ
በሰጠው ተስፋ መሠረት በጎውን ነገር ሁሉ
ባደረገለትና በእስራኤልም ላይ ባነገሠው ጊዜ፣
31ጌታዬ የምታዝንበት ምክንያት ወይም
የኅሊና ጸጸት አይኖርህም፤ በከንቱ ያፈሰስኸ
ውም ደም ሆነ በገዛ እጅህ የተበቀልኸው
የለምና። እግዚአብሔር በጎ ነገር ባደረገልህ ጊዜ
እኔን አገልጋይህን አስበኝ።"

32ዳዊትም አቢግያን እንዲህ አላት፤ "ዛሬ
እንድታገኚኝ ወደ እኔ የላከሽ፣ የእስራኤል
አምላክ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን።
33ደም እንዳላፈስና በገዛ እጄ እንዳልበቀል
ዛሬ ስለ ጠበቅሽኝ ስለ በጎ ሐሳብሽ
አንቺም የተባረክሽ ሁኚ። 34ጕዳት
እንዳላደርስብሽ የጠበቀኝ የእስራኤል
አምላክ ሕያው እግዚአብሔርን! እንዲህ
በቶሎ መጥተሽ ባታገ ኚኝ ኖሮ፣ እስኪነጋ
ድረስ ለናባል አንድ ወንድ እንኳ ባልተረፈ
ነበር።"

35ከዚያም ዳዊት ያመጣችለትን ከእጇ
ተቀብሎ፣ "በሰላም ወደ ቤትሽ ሂጂ፤ እነሆ፤
ቃልሽን ሰምቻለሁ፤ የጠየቅሽኝንም ተቀብ
ያለሁ" አላት።

36አቢግያም ወደ ናባል በተመለሰች ጊዜ፣
እነሆ፤ በቤቱ እንደ ንጉሥ ግብዣ ትልቅ
ግብዣ አድርጎ አገኘችው፤ ክፉኛም ሰክሮ
ልቡ በደስታ ተሞልቶ ነበር። ስለዚህ እስ
ኪነጋ ድረስ ምንም አልነገረችውም። 37ንጋቶ
የወይን ጠጁ ስካር ካለፈለት በኋላ የሆነ
ውን ሁሉ ስትነግረው ልቡ ቀጥ አለ፤
ሰውነቱም እንደ ድንጋይ በድን ሆነ። 38ዐሥር
ቀን ያህል ካለፈ በኋላ፣ እግዚአብሔር ናባልን
ቀሠፈው፤ እርሱም ሞተ።

39ዳዊትም ናባል መሞቱን በሰማ ጊዜ፣
"የናባልን ስድብ የተበቀለልኝና እኔን አገ
ልጋዩን ክፉ ከማድረግ የጠበቀኝ እግዚአ
ብሔር ይመስገን፤ ናባል የሠራውንም ክፉ
ነገር በራሱ ላይ መለሰበት" አለ።

ዳዊትም አቢግያ ሚስት ትሆነው ዘንድ
በመጠየቅ መልእክት ላከባት። 40አገልጋዮ
ቹም ወደ ቀርሜሎስ ሄደው አቢግያን፣
"ሚስት ትሆኚው ዘንድ እንድንወስድሽ ዳዊት
ወደ አንቺ ልኮናል" አሏት።

41እርሷም ተነሥታ በግምባሯ በመደፋት
እጅ ከነሣች በኋላ፣ "እነሆ፤ እኔ ገረድህ
አንተን ለማገልገል፣ የጌታዬንም አገልጋዮች
እግር ለማጠብ ዝግጁ ነኝ" አለች። 42አቢ
ግያም ወዲያውኑ በአህያ ላይ ተቀምጣ
አምስት አገልጋዮቿን በማስከተል፣ ከዳዊት
መልእክተኞች ጋር ሄደች፤ ለዳዊትም ሚስት
ሆነችው። 43እንዲሁም ዳዊት ኢይዝራ
ኤላዊቷን አኪናሆምን አገባ፣ ሁለቱም ሚስ
ቶቹ ሆኑ። 44ሳኦል ግን የዳዊት ሚስት የነ
በረችውን ልጁን ሜልኮልን፣ ለጋሊም ተወ
ላጅ ለሌሳ ልጅ ለፈልጢ ሰጥቶ ነበር።

## ዳዊት ለሁለተኛ ጊዜ ሳኦልን ከመግደል ታቀበ

26 የዚፍ ሰዎች ሳኦል ወዳለበት ወደ
ጊብዓ መጥተው፣ "እነሆ፤ ዳዊት
በየሴሞን ትይዩ በሚገኘው በኤኬላ ኰረብታ
ተደብቆአል" ብለው ነገሩት።

2ስለዚህ ሳኦል ተነሣ፤ ከእስራኤል የተመ
ረጡትን ሦስት ሺህ ሰዎችን ይዞ፣ ዳዊትን
ፍለጋ ወደ ዚፍ ምድረ በዳ ወረደ። 3ሳኦ
ልም በየሴሞን ትይዩ በሚገኘው በኤኬላ
ኰረብታ ላይ በመንገድ ዳር ሰፈረ፤ ዳዊት
ግን በምድረ በዳ ነበር። ዳዊትም ሳኦል
እዚያ ድረስ እንደ ተከተለው ባወቀ ጊዜ፣
4ሰላዮች ልኮ በትክክል ሳኦል መምጣቱን
አረጋገጠ።

5ዳዊትም ተነሥቶ ሳኦል ወደ ሰፈረበት
ቦታ ሄደ፤ ሳኦልና የሰራዊቱ አለቃ፣ የኔር
ልጅ አበኔር የተኙበትን ስፍራ አየ። ሳኦል
በሰፈሩ መካከል ተኝቶ ሳለ፣ ሰራዊቱ በዙ
ሪያው ሰፍሮ ነበር።

6ዳዊትም ኬጢያዊውን አቢሜሌክንና
የጽሩያን ልጅ የኢዮአብን ወንድም አቢ
ሳን፣ "ወደ ሳኦል ሰፈር አብሮኝ የሚወርድ
ማነው?" ሲል ጠየቃቸው።

አቢሳም፣ "እኔ አብሬህ እወርዳለሁ" አለ።

7ስለዚህ ዳዊትና አቢሳ በሌሊት ሰራዊተ
ወዳለበት ሄዱ። እነሆ፤ ሳኦል በሰፈሩ
ውስጥ ተኝቶ ጦሩም ራስጌው አጠገብ
በመሬት ላይ ተተክሎ ነበር፤ አበኔርና
ወታደሮቹም በዙሪያው ተኝተው ነበር።

8አቢሳም ዳዊትን፣ "ዛሬ እግዚአብሔር ጠ
ላ ትህን በእጅህ ላይ ጥሎታል፤ አሁንም
እኔ አንድ ጊዜ በጦር ወግቼ ከመሬት ጋር
ላጣ ብቀው፤ መድገምም አያስፈልገኝም"
አለው።

9ዳዊት ግን አቢሳን እንዲህ አለው፤ "አት
ግደለው! እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጁን
አንሥቶ ከበደል ነጻ የሚሆን ማን ነው? 10ሕ
ያው እግዚአብሔርን ! እግዚአብሔር ራሱ
ይቀሥ ፈዋል፤ ወይም ቀኑ ደርሶ
ይሞታል፤ ወይም በጦርነት ይሞታል።
11እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጄን ከ
ማንሣት እግዚአብሔር ይጠብቀኝ! ነገር ግን
በራስጌው አጠገብ ያለውን ጦርና የውሃ
መያዣውን ያዝና እንሂድ።"

12ስለዚህ ዳዊት በሳኦል ራስጌ አጠገብ

25፥29 1ሳሙ17፥50፤ 20፥1፤2ሳሙ4፥8፤ ኤር10፥18፤22፥26
25፥30 1ሳሙ12፥12፤ 13፥14
25፥31 ዘፍ40፥14፤ 2ሳሙ3፥10
25፥32 ዘፍ24፥27
25፥33 ቀኍ26
25፥34 ቀኍ26
25፥35 ዘፍ19፥21
25፥36 ቀኍ19፤ ሩት 3፥7፤ምሳ20፥1፤ መክ 10፥17፤ ኢሳ5፥11፡ 22፤22፥13፤28፥7፤ 56፥12፤ሆሴ4፥11
25፥37 ዘፀ15፥16
25፥38 ዘዳ32፥35፤ 1ሳሙ24፥12፤26፥10፤ 2ሳሙ 6፥7፤12፥15
25፥42 2ሳሙ2፥2፤ 3፥3፤1ዜና3፥1
25፥43 1ሳሙ27፥3፤ 30፥5፤2ሳሙ2፥2፤ 3፥2፤1ዜና3፥1
25፥44 2ሳሙ3፥15፤ ኢሳ10፥30
26፥1 1ሳሙ23፥19፡ 24፤መዝ54
26፥2 1ሳሙ24፥2
26፥3 1ሳሙ23፥19
26፥5 1ሳሙ17፥55
26፥6 ዘፍ10፥15፤ 2ሳሙ2፥18፤10፥10፤16፥9፤18፥2፤19፥21፤23፥18፤1ዜና2፥16፤ 11፥20፤19፥11
26፥9 ቀኍ16፤ ዘፍ 26፥11፤ 1ሳሙ9፥16፤ 24፥5፤ሳሙ1፥14፤ 19፥21፤ሰቆ4፥20
26፥10 ዘፍ16፥5፤ ዘዳ31፥14፤ 1ሳሙ 25፥38፤31፥6፤ 2ሳሙ 1፥1፤ መዝ37፥13፤ ሮሜ12፥19
26፥12 መሳ 4፥21

የነበረውን ጦርና የውሃውን መያዣ ወሰደ፤
ከዚያም ሄዱ፤ ይህን ያየም ሆነ ያወቀ ወይም
የነቃ ማንም አልነበረም፡፡ *ከእግዚአብሔር*
ዘንድ ከባድ እንቅልፍ ስለ ወደ ቀባቸው
ሁሉም ተኝተው ነበርና፡፡
[13]ከዚህ በኋላ ዳዊት ወደ ማዶ ተሻግሮ
በኰረብታው ጫፍ ላይ ራቅ ብሎ ቆመ፤
በመካከላቸውም ሰፊ ርቀት ነበር፡፡ [14]ዳዊት
ሰራዊቱንና የኔርን ልጅ አብኔርን፣ "አበኔር
ሆይ፣ አትመልስልኝምን?" ሲል ተጣራ፡፡
አበኔርም፣ "በንጉሡ ላይ የምትጮኽ አንተ
ማነህ?" በማለት መለሰ፡፡
[15]ዳዊትም እንዲህ አለ፤ "አንተ ብርቱ
ሰው ነህ? በእስራኤልስ ዘንድ አንተን የሚመስል
ማን ነው? እነሆ፤ አንድ ሰው ንጉሡን ጌታህን
ለመግደል መጥቶ ነበር፤ ታዲያ አንተ
ንጉሥ ጌታህን ያልጠበቅኸው ስለ ምንድን
ነው? [16]ያደረግኸው መልካም አይደለም፤
ሕያው *እግዚአብሔርን*! አንተና ሰዎችህ
ሞት ይገባችኋል፤ *እግዚአብሔር* የቀባውን
ጌታችሁን አልጠበቃችሁምና፡፡ እስቲ ተመ
ልከት፤ በራስጌው የነበሩት የንጉሡ ጦርና
የውሃ መያዣ የት አሉ?"
[17]ሳኦል የዳዊትን ድምፅ ለይቶ ስላወቀ፣
"ልጄ ዳዊት ሆይ፤ ይህ ድምፅህ ነውን?"
አለው፡፡ ዳዊትም፣ "ንጉሥ ጌታዬ ሆይ፤ አዎን
ድምፄ ነው" ሲል መለሰ፤ [18]በመቀጠልም፣
"ጌታዬ አገልጋዩን የሚያሳድደው ስለምን
ድን ነው? ምን አደረግሁ? ምን በደልስ
ፈጸምሁ? [19]አሁንም ንጉሥ ጌታዬ የባሪያ
ውን ቃል ያድምጥ፤ *እግዚአብሔር* በእኔ
ላይ አነሣሥቶህ እንደ ሆነ፣ ቍርባን
ይቀበል፤ ነገር ግን ይህን ያደረጉት ሰዎች
ከሆኑ፣ *በእ ግዚአብሔር* ፊት የተረገሙ
ይሁኑ፤ 'ሂድ ሌሎችን አማልክት አምልክ'
ብለው *በእግ ዚአብሔር* ርስት ድርሻ
እንዳይኖረኝ ዛሬ አሳደውኛልና፡፡ [20]አንድ
ሰው በተራራ ላይ ቆቅ እንደሚያድን የእስራ
ኤልም ንጉሥ ቍንጫ ለመፈለግ ስለ ወጣ፣
ደሜ *ከእግዚአብሔር* ፊት ርቆ በምድር
ላይ እንዲፈስ አታድርግ፡፡"
[21]ሳኦልም፣ "በድያለሁ፤ ልጄ ዳዊት
ሆይ፤ ተመለስ፤ ዛሬ ነፍሴ በፊትህ ስለ
ከበረች፣ ከእንግዲህ ወዲያ አልጐዳህም፤
በእርግጥ የሞኝ ሥራ ሠርቻለሁ፤ እጅግ ሲ
በዛም ተሳስቻለሁ" አለ፡፡
[22]ዳዊትም እንዲህ ሲል መለሰ፤ "የንጉሥ
ጦር እነሆ፤ ከወጣቶችህ አንዱ መጥቶ
ይውሰዳት፡፡ [23]*እግዚአብሔር* ለእያንዳንዱ ሰው
እንደ ጽድቁና እንደ ታማኝነቱ ይክፈለው፡፡
እኔ ግን ዛሬ *እግዚአብሔር* አንተን በእጄ

26፥17 1ሳሙ24፥16
26፥18 ኢዮ13፥23፤ ኤር37፥18
26፥19 ዘዳ4፥28፤ 11፥28፤20፥16፤ 32፥9፤1ሳሙ24፥9፤ 2ሳሙ14፥16፤16፥11፤ 20፥9፤21፥3
26፥20 1ሳሙ24፥11፡ 14፤ኤር4፥29፤ 16፥16፤አሞ 9፥3
26፥21 ዘፀ9፥27፤ መዝ72፥14
26፥23 ዘፍ16፥5፤ ሩት2፥12፤ 1ሳሙ 24፥18፤ 2ሳሙ22፥21፡ 25፤መዝ7፥8፤ 18፥20፡24፤62፥12
26፥24 መዝ54፥7
26፥25 ሩት2፥12
27፥2 1ሳሙ21፥10፤ 30፥9፤2ሳሙ2፥3፤ 1ነገ2፥39
27፥3 1ሳሙ25፥43
27፥6 ኢሱ15፥31፤ 19፥5፤1ሳሙ30፥1፤ 1ዜና12፥20፤ ነህ11፥28
27፥7 1ሳሙ29፥3
27፥8 ዘፍ16፥7 ዘፀ17፥14፤ኢሱ12፥5፤ 1ሳሙ14፥48፤30፥1፤2 ሳሙ1፥8፤8፥12

አሳልፎ ሰጥቶኝ ሳለ *እግዚአብሔር* በቀባው
ላይ እጄን አላነሣሁም፡፡ [24]እነሆ፤ ዛሬ ሕይ
ወትህ በፊቴ እንደ ከበረች ሁሉ፣ የእኔም
ሕይወት *በእግዚአብሔር* ዘንድ የከበረች
ትሁን፤ ከመከራም ሁሉ ያድነኝ፡፡"
[25]ከዚያም ሳኦል ዳዊትን፣ "ልጄ ዳዊት
ሆይ፤ የተባረክህ ሁን፤ ታላቅ ነገር ታደር
ጋለህ፤ በእርግጥም ይከናወንልሃል" አለው፡፡
ስለዚህም ዳዊት ወደሚሄድበት ሄደ፤
ሳኦልም ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡

### ዳዊት በፍልስጥኤማውያን መካከል መኖሩ

27 ዳዊት ግን በልቡ፣ "ከእነዚህ ቀናት
በአንዱ በሳኦል እጅ መገደሌ ስለ
ማይቀር፣ የሚበጀኝ ወደ ፍልስጥኤማውያን
ምድር መሸሽ ብቻ ነው፤ ከዚያ በኋላም
ሳኦል በእስራኤል ሁሉ እኔን ማሳደዱን
ይተዋል፤ እኔም ከእጁ አመልጣለሁ" ብሎ
አሰበ፡፡
[2]ስለዚህ ዳዊትና አብረውት ያሉት ስድ
ስት መቶ ሰዎች ተነሥተው የጌት ንጉሥ
ወደ ሆነው ወደ አሜህ ልጅ ወደ አንኩስ
ሄዱ፡፡ [3]ዳዊትና ሰዎቹ በጌት በአንኩስ
ዘንድ ተቀመጡ፤ እያንዳንዱ ሰው ከቤተሰቡ
ጋር ነበረ፤ ዳዊትም ከሁለቱ ሚስቶቹ ጋር፣
ከኢይዝራኤላዊቷ ከአኪናሆምና የናባል
ሚስት ከነበረችው ከቀርሜሎሳዊቷ አቢ
ግያ ጋር ነበር፡፡ [4]ሳኦልም፣ ዳዊት ወደ ጌት
እንደ ሸሸ በሰማ ጊዜ፣ እርሱን ማሳደዱን
ተወ፡፡
[5]ከዚያም ዳዊት አንኩስን፣ "በፊትህ ሞገስ
አግኝቼ እንደሆነ፣ በአገሪቱ ካሉት ከተሞች
በአንዲቱ እኖር ዘንድ ስፍራ ይሰጠኝ፤ ስለ
ምን አገልጋይህ ካንተ ጋር በንጉሥ ከተማ
ይቀመጣል?" አለው፡፡
[6]ስለዚህ በዚያ ዕለት አንኩስ ጺቅላግን
ሰጠው፤ ጺቅላግም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የይ
ሁዳ ነገሥታት ይዞታ ሆነች፡፡ [7]ዳዊት በፍ
ልስጥኤማውያን ምድር አንድ ዓመት ከአ
ራት ወር ተቀመጠ፡፡
[8]በዚያ ጊዜም ዳዊትና ሰዎቹ ወጥተው
ጌሹራውያንን፣ ጌርዛውያንንና አማሌቃው
ያንን ወረሩ፡፡ እነዚህ ሕዝቦች ከጥንት
ጀምሮ፣ እስከ ሱርና እስከ ግብፅ ባለው
ምድር ላይ ይኖሩ ነበር፡፡ [9]ዳዊትም ምድሪ
ቱን በመታበት ጊዜ፣ ወንድም ሆነ ሴት
በሕይወት አላስቀረም፤ ነገር ግን በጎችንና
ላሞችን፣ አህዮችንና ግመሎችን እንዲሁም
ልብሶችን ወሰደ፤ ወደ አንኩስም ተመለሰ፡፡
[10]አንኩስም፣ "ዛሬ በማን ላይ ዘመታችሁ?"
ሲል በጠየቀው ጊዜ ዳዊት፣ "የዘመትነው
በይሁዳ ደቡብ፣ ወይም በይረሕምኤላውያን
ደቡብ፣ ወይም በቄናውያን ደቡብ ላይ

ነው” በማለት ይመልስ ነበር::” [11]ዳዊት
“‘እርሱ እንዲህ አድርጎአል’ ብለው ይነግሩ
ብናል” ብሎ ስላሰበ፣ ወንድም ሆነ ሴት
በሕይወት አስቀርቶ ወደ ጌት አላመጣም::
በፍልስጥኤም ግዛት በኖረበት ዘመን ሁሉ፣
እንዲህ ማድረጉ የተለመደ ነበር:: [12]አንኩስም
በልቡ፣ “እርሱ ራሱ የገዛ ሕዝቡ የሆኑት
እስራኤላውያን እጅግ እንዲጠሉት ስላደረገ፣
ለዘላለም አገልጋዬ ይሆናል” ብሎ ስላሰበ
ዳዊትን አመነው::

## ሳኦልና የዓይንዶር ነዋሪዋ ሙታን ጠሪ

28 በዚያን ዘመን ፍልስጥኤማውያን፣
እስራኤልን ለመውጋት ሰራዊታቸ
ውን ሰበሰቡ:: አንኩስም ዳዊትን፣ “አንተና
ሰዎችህ አብራችሁኝ ለጦርነት መውጣት
እን ዳለባችሁ” አለው::

[2]ዳዊትም፣ “አገልጋይህ ምን እንደሚያ
ደርግ ያን ጊዜ አንተው ራስህ ታያለህ”
አለው::

አንኩስም፣ “መልካም፤ በዘመኔ ሁሉ የራሴ
የክብር ዘብ አደርግሃለሁ” ሲል መለሰለት::

[3]በዚህ ጊዜ ሳሙኤል ሞቶ ነበር፤ እስራ
ኤላውያንም ሁሉ በገዛ ከተማው በአር
ማቴም አልቅሰው ቀበሩት:: ሳኦል ሙታን
ሳቢዎችንና መናፍስት ጠሪዎችን ከምድሪቱ
አባሮአቸው ነበር::

[4]ፍልስኤማውያን ተሰብስበው በመም
ጣት በሱነም ሲሰፍሩ፣ ሳኦል ደግሞ እስራ
ኤላውያንን ሁሉ ሰብስቦ በጊልቦዓ ተራራ ላይ
ሰፈረ:: [5]ሳኦል የፍልስጥኤማውያንን ሰራዊት
ባየ ጊዜ ፈራ፤ ልቡም እጅግ ተሸበረ::
[6]እርሱም *እግዚአብሔርን* ጠየቀ፤ *እግዚ
አብሔር* ግን በሕልምም ሆነ በኡሪም ወይም
በነቢያት አልመለሰለትም:: [7]ሳኦልም አገል
ጋዮቹን፣ “እስቲ ሙታን ሳቢ ሴት ፈልጉልኝና
ሂጄ ልጠይቃት” አላቸው::

እነርሱም፣ “እነሆ፤ ሙታን የምትስብ ሴት
በዓይንዶር አለች” አሉት::

[8]ስለዚህ ሳኦል ሌላ ልብስ በመልበስ መል
ኩን ለውጦ ከሁለት ሰዎች ጋር በሌሊት
ወደ ሴቲቱ ሄደ:: እርሱም፣ “እባክሽ፣
መናፍስትን ጠይቂልኝ፤ የምነግርሽንም ሰው
አስነሺልኝ” አላት::

[9]ሴትዮዋ ግን፣ “እነሆ፤ ሳኦል ሙታን ሳቢ
ዎችንና መናፍስት ጠሪዎችን ከምድሪቱ እን
ዴት እንዳጠፋና ያደረገባቸውን ታውቃለህ፤
ታዲያ፣ ታስገድለኝ ዘንድ በሕይወቴ ላይ
ወጥመድ የዘረጋኸው ለምንድን ነው?” አለችው::

[10]ሳኦልም፣ “ሕያው *እግዚአብሔርን*! በዚህ
ነገር ቅጣት አያገኝሽም” ሲል *በእግዚአብሐ*

27፥9 1ሳሙ15፥3
27፥10 መሳ1፥16 ፤ 1ሳሙ30፥29
27፥12 ዘፍ34፥30፤ 1ሳሙ29፥6
28፥1 1ሳሙ29፥1
28፥2 1ሳሙ29፥2
28፥3 ቀኁ9፤ ዘፀ22፥18፤1ሳሙ 7፥17፤25፥1
28፥4 ኢሱ19፥18፤ 1ሳሙ31፥1፡3፤ 2ሳሙ1፥6፡21፥12
28፥5 ዘፀ19፥16
28፥6 ዘፀ28፥30፤ ዘሌ8፥8፤ዘዳ13፥3፤ 1ሳሙ8፥18፤14፥37፤ሕ ዝ20፥3፤ አሞ 8፥11፤ ሚክ 3፥7
28፥7 ኢሱ17፥11፤ 1ዜና10፥13፤ መዝ 83፥10፤ ሐሥ16፥16
28፥8 2ዜና18፥29፤ 35፥22፤1ነገ22፥30፤ 2ነገ1፥3፤ኢሳ8፥19
28፥9 ቀኁ3፤ ኢዮ 18፥10፤ መዝ31፥4፤ 69፥22፤ኢ ሳ8፥14
28፥12 ዘፍ27፥36፤ 1ነገ14፥6
28፥13 ቀኁ15፤ ዘሌ 19፥31፤ 2ዜና33፥6
28፥14 1ሳሙ15፥27
28፥15 ዘዳ13፥3፤ መሳ16፥20፤ 1ሳሙ14፥37
28፥17 1ሳሙ15፥28
28፥18 ዘፍ14፥7፤ ዘዳ9፥8፤1ሳሙ14፥48፤ 15፥3፡20
28፥19 1ሳሙ31፥2፤ 1ዜና8፥33

*ር* ስም ማለላት::
[11]ሴትዮዋም፣ “ማንን ላስነሣልህ?” ብላ
ጠየቀችው::

እርሱም፣ “ሳሙኤልን አስነሺልኝ” አላት::
[12]ሴትዮዋም ሳሙኤልን ባየችው ጊዜ በታልቅ
ድምፅ ጮኸች፤ ሳኦልንም፣ “አንተ ሳኦል
ሆነህ ሳለ፣ ለምን አታለልኸኝ?” አለችው::
[13]ንጉሡም፣ “አትፍሪ፤ ለመሆኑ ምን እያየሽ
ነው?” አላት::

ሴትዮዋም፣ “አንድ መንፈስ[a] ከምድር
ሲወጣ አያለሁ” አለችው::

[14]እርሱም፣ “መልኩ ምን ይመስላል?”
ሲል ጠየቃት:: እርሷም፣ “ካባ የለበሰ አንድ
ሽማግሌ ሰው እየወጣ ነው” አለችው::

ሳኦልም ሴትዮዋ ያየችው ሳሙኤል መሆ
ኑን ዐወቀ፤ በመሬትም ላይ ተደፍቶ እጅ
ነሣ::

[15]ሳሙኤልም ሳኦልን፣ “አስነሥተህ የምታ
ውከኝ ለምንድነው?” አለው’

ሳኦልም፣ “እጅግ ተጨንቄአለሁ፤ ፍልስ
ጥኤማውያን እየወጉኝ ነው፤ እግዚአብሔርም
ከእኔ ርቆአል፤ በነቢያትም ሆነ በሕልም
አልመለሰልኝም፤ ስለዚህ ምን ማድረግ እን
ደሚገባኝ እንድትነግረኝ ጠራሁህ” አለው::

[16]ሳሙኤልም እንዲህ አለ፤ “ታዲያ *እግዚ
አብሔር* ከራቀህ፣ ጠላትም ከሆነህ ለምን
ትጠይቀኛለህ? [17]*እግዚአብሔር* በእኔ የተ
ናገረውን አድርጎአል፤ *እግዚአብሔር* መን
ግሥትህን ከእጅህ ነጥቆ ለጎረቤትህ ለዳዊት
ሰጥቶታል። [18]*ለእግዚአብሔር* ስላልታዘዝህ፣ ታላቅ
ቍጣውንም በአማሌቃውያን ላይ ስላልፈ
ጸምህ *እግዚአብሔር* ዛሬ ይህን አድርጎብ
ሃል:: [19]*እግዚአብሔር* አንተንና እስራኤልን
ለፍልስጥኤማውያን አሳልፎ ይሰጣል፤ አን
ተና ልጆችህም ነገ ከእኔ ጋር ትሆናላችሁ፤
እንዲሁም *እግዚአብሔር* የእስራኤልን ሰራ
ዊት ለፍልስጥኤማውያን አሳልፎ ይሰጣል::”

[20]ሳሙኤል ከተናገረው ቃል የተነሣ፣ ሳኦል
በፍርሀት ተውጦ ወዲያውኑ በቁመቱ ሙሉ
መሬት ላይ ወደቀ፤ ቀኑንና ሌሊቱን ሁሉ
እህል ስላልቀመሰ ጕልበቱ ዝሎ ነበር::

[21]ሴትዮዋ ወደ ሳኦል መጥታ እጅግ መደ
ንገጡን ባየች ጊዜ እንዲህ አለችው፤ “እነሆ፤
አገልጋይህ ቃልህን ሰምቻለሁ፤ በነፍሴም
ቈርጬ የነገርኸኝን ፈጽሜአለሁ:: [22]አሁ
ንም እባክህ አገልጋይህ የምትልህን ስማ፤
ብርታት አግኝተህ መሄድ እንድትችል፣
ጥቂት ምግብ ላቅርብልህና ብላ::”

[23]እርሱም፣ “አልበላም” በማለት እምቢ
አለ:: ነገር ግን የራሱ ሰዎች ከሴትዮዋ

[a]13 ወይም *መናፍስት* ወይም *አማልክት*

ጋር ሆነው አጥበቀው ስለ ለመኑት ቃላቸውን
ሰማ፤ ከመሬትም ተነሥቶ በዐልጋ ላይ
ተቀመጠ፡፡
24ሴትዮዋም በቤቷ የሠባ ጥጃ ስለነበራት፣
ፈጥና ዐረደችው፤ ዱቄት ወስዳ ለወሰች፣
እርሾ የሌለው እንጀራም ጋገረች፡፡ 25ከዚ
ያም ለሳኦልና ለሰዎቹ አቀረበችላቸው፤
እነርሱም በሉ፤ በዚያም ሌሊት ተነሥተው
ሄዱ፡፡

## አንኩስ ዳዊትን ወደ ጺቅላግ መልሶ መላኩ

29 ፍልስጥኤማውያን ሰራዊታቸውን
ሁሉ በአፌቅ ሰበሰቡ፤ እስራኤላ
ውያንም በኢይዝራኤል ሸለቆ ባለው ምንጭ
አጠገብ ሰፈሩ፤ 2የፍልስጥኤማውያን ገዦች
በመቶና በሺህ ሆነው ሲዘምቱ፣ ዳዊትና
ሰዎቹም ከአንኩስ ጋር ደጀን ሆነው ይከተሉ
ነበር፡፡ 3የፍልስጥኤም አዛዦችም፣ "እነዚህ
ዕብራውያን እዚህ ምን እያደረጉ ነው?"
ብለው ጠየቁ፡፡
አንኩስም፣ "ይህ የእስራኤል ንጉሥ የሳኦል
አገልጋይ የነበረው ዳዊት አይደለምን?" ከእኔ
ጋር መኖር ከጀመረ እነሆ ዓመት አለፈው፤
እኔን ከተጠጋበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን
ድረስ ምንም በደል አላገኘሁበትም" አላቸው፡፡
4የፍልስጥኤማውያን አዛዦች ግን በአን
ኩስ ላይ ተቈጥተው እንዲህ አሉ፤ "ይህን
ሰው ወደዚያው ወደ ሰጠኸው ቦታ ይመ
ለስ ዘንድ ስደደው፤ በውጊያው ጊዜ በእኛ
ላይ ተመልሶ ጠላት እንዳይሆን፣ አብሮን
ወደ ጦርነቱ መሄድ የለበትም፤ የእኛን
ሰዎች ራስ ቈርጦ ካልወሰደ ከጌታው ጋር
እንዴት ሊታረቅ ይችላል? 5በዘፈን እየተ
ቀባበሉ፣

'ሳኦል ሺህ ገደለ፤
ዳዊት ግን ዐሥር ሺህ'
ብለው የዘመሩለት ይኸው ዳዊት አይደለ
ምን?"
6ስለዚህ አንኩስ ዳዊትን ጠርቶ እንዲህ
አለው፤ "ሕያው *እግዚአብሔርን*! አንተ
ታማኝ ነህ፤ ወደ እኔ እዚህ ከመጣህበት
ቀን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ምንም ጥፋት
ያላገኘሁብህ ስለሆነ፣ አብረኸኝ ብትዘምት
በበኩሌ ደስተኛ ነበርሁ፤ ነገር ግን ገዦቹ
አልተቀበሉህም፤ 7እንግዲህ ተመልሰህ
በሰላም ሂድ፤ የፍልስጥኤማውያንን ገዦች
ደስ የማያሰኝ ምንም ነገር አታድርግ"
8ዳዊትም፣ "ለመሆኑ ምን አደረግሁ? እዚህ
ከመጣሁበት ዕለት ጀምሮ እስካሁን ድረስ፣
በአገልጋይህ ላይ ምን አገኘህበት? ታዲያ፣
ከንጉሡ ከጌታዬ ጠላቶች ጋር የማልዋጋው
ስለ ምንድን ነው?" ብሎ ጠየቀው፡፡

28፥21 መሳ9፥17፤ 12፥3
28፥23 1ነገ21፥4
28፥24 ዘፍ18፥7
29፥1 ኢሱ17፥16፤ 1ሳሙ4፥1፤28፥1፤ 1ነገ18፥45፤21፥1፡23፤ 2ነገ9፥30፤ኤር50፥5፤ ሆሴ1፥4፡5፡11፤2፥22
29፥2 1ሳሙ28፥2
29፥3 1ሳሙ27፥7፤ 1ዜና12፥19
29፥4 1ሳሙ14፥21፤ 1ዜና12፥19
29፥5 1ሳሙ18፥7
29፥6 ቀኁ3፤ 1ሳሙ27፥8-12
29፥9 ቀኁ4፤ 2ሳሙ 14፥17፡20፤ 19፥27
29፥10 1ዜና12፥19
30፥1 ቀኁ14፤ 1ሳሙ27፥6፡8
30፥3 ዘፍ31፥26
30፥4 ዘፍ27፥38
30፥5 1ሳሙ25፥43
30፥6 ዘፀ17፥4፤ ሩት1፥13፤ 1ሳሙ 23፥16፤ ዮሐ8፥59፤ ሮሜ 4፥20
30፥7 1ሳሙ2፥28፤ 2፥20
30፥8 ዘፍ14፥16፤ ዘፀ2፥17፤ 1ሳሙ23፥2
30፥9 1ሳሙ27፥2

9አንኩስም እንዲህ አለው፤ "በእኔ ዘንድ
እንደ እግዚአብሔር መልአክ መልካም እንደ
ሆንህ ዐውቃለሁ፤ የፍልስጥኤማውያን አዛ
ዦች ግን፣ 'አብሮን ለጦርነት መውጣት
የለበትም' ብለዋል፡፡ 10አሁንም አብረውህ ከመ
ጡት ከጌታህ አገልጋዮች ጋር ማለዳ ተነ
ሡ፤ በጥዋት ፀሐይ እንደ ወጣችም ሂዱ"
አለው፡፡
11ስለዚህ ዳዊትና ሰዎቹ ወደ ፍልስጥኤ
ማውያን ምድር ለመመለስ በማለዳ ተነ
ሡ፤ ፍልስጥኤማውያንም ወደ ኢይዝራኤል
ወጡ፡፡

## ዳዊት አማሌቃውያንን አጠፋ

30 በሦስተኛው ቀን ዳዊትና ሰዎቹ
ጺቅላግ ደረሱ፤ በዚህ ጊዜ አማሌ
ቃውያን ደቡቡን አገርና ጺቅላግን ወረው
ነበር፤ ጺቅላግንም ወግተው አቃጥለው ነበር፡፡
2ሴቶቹን፣ በዚያ የነበሩትን ወጣቶችና ሽ
ማግ ሌዎቹን ሁሉ ማርከው ወሰዱ፤ የ
ማረኩት ንም ይዘው ከመሄድ በስተቀር
አንዱንም አልገደሉም ነበር፡፡
3ዳዊትና ሰዎቹ ወደ ጺቅላግ እንደ ደረ
ሱም፣ እነሆ፤ ከተማዪቱ በእሳት ጋይታ፣
ሚስቶቻቸው፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው
ተማርከው አገኙ፡፡ 4በዚህ ጊዜ ዳዊትና
ሰዎቹ ማልቀስ እስከሚያቅታቸው ድረስ
ድምፃቸ ውን ከፍ አድርገው አለቀሱ፤
5ሁለቱ የዳ ዊት ሚስቶች ማለትም ኢይዝ
ራኤላዊቷ አኪናሆምና የቀርሜሎሳዊው
የናባል ሚስት የነበረችው አቢግያም ተ
ማርከው ነበር፡፡ 6ሰዎቹ ስለ ወንዶችና
ሴቶች ልጆቻቸው ነፍሳቸው ተመራ ሊ
ወግሩት ስለ ተመካከሩ ዳዊት በጣም
ተጨነቀ፤ ነገር ግን ዳዊት በአምላኩ
*በእግዚአብሔር* በረታ፡፡
7ከዚያም ዳዊት የአቢማሌክን ልጅ ካህ
ኑን አብያታርን፣ "ኤፉዱን አምጣልኝ" አለው፤
አብያታርም አመጣለት፤ 8ዳዊትም፣ "ይህን
ወራሪ ሰራዊት ልከተለውን?' እደርስባቸዋ
ለሁን?" ሲል *እግዚአብሔርን* ጠየቀ፡፡
*እግዚአብሔርም*፣ "በእርግጥ ትደርስባቸዋ
ለህ፤ ምርኮውንም ትመልሳለህ፤ ተከተል" ሲል
መለሰለት፡፡
9ስለዚህ ዳዊትና አብረውት የነበሩት
ስድስት መቶ ሰዎች ወደ ቦሦር ወንዝ መጡ፤
ጥቂቶቹም በቦሦር ወንዝ ቈዩ፤ 10ሁለት
መቶዎቹ እጅግ ዝለው ስለ ነበር ወንዙን
መሻገር አልቻሉምና፡፡ ነገር ግን ዳዊትና
አራት መቶ ሰዎች መከታተላቸውን ቀጠሉ፡፡
11እነርሱም በምድረ በዳ አንድ ግብፃዊ
አገኙ፤ ወደ ዳዊትም አመጡት፤ የሚጠ

ጣውን ውሃና የሚበላውን ምግብ ሰጡት::
12እንደዚሁም የበለስ ጥፍጥፍ ቊራሽና
ሁለት ደረቅ የወይን ዘለላዎች ሰጡት::
ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ምንም እህል
ስላልበላ፣ ውሃም ስላልጠጣ ይህን ከበላ
በኋላ ነፍሱ ተመለሰች::
13ዳዊትም፣ “አንተ የማን ነህ? የመጣኸ
ውስ ከየት ነው?” ብሎ ጠየቀው:: እርሱም
እንዲህ አለው፤ “እኔ ግብፃዊ ስሆን፣ የአ
ንድ አማሌቃዊ ባሪያ ነኝ፤ ከሦስት ቀን
በፊት ታምሜ በነበረበት ጊዜ ጌታዬ ጥሎኝ
ሄደ:: 14የከሊታውያንን ደቡብ፣ የይሁዳን
ግዛትና የካሌብን ደቡብ ወረርን፤ ጺቅላግ
ንም በእሳት አጋየናት::”
15ዳዊትም፣ “ታዲያ ወራሪው ሰራዊት
ወዳለበት መርተህ ታደርሰኛለህ?” ሲል
ጠየቀው:: እርሱም፣ “እንደማትገድለኝ ወይም
ለጌታዬ አሳልፈህ እንደማትሰጠኝ በእግዚአ
ብሔር ማልልኝ እንጂ እነዚህ ወራሪዎች
ወዳሉበት አደርስሃለሁ” አለው::
16ዳዊትን ወደታች መርቶ ባደረሰው
ጊዜም፣ ወራሪዎቹ ከፍልስጥኤማውያንና ከይ
ሁዳ ምድር ከወሰዱት ታላቅ ምርኮ የተነሣ
በየቦታው ተበታትነው ይበሉ፣ ይጠጡና ይዘ
ፍኑ፣ ይጨፍሩም ነበር:: 17ዳዊት፣ ከዚያች
ዕለት ማታ ጀምሮ እስከ ማግሥቱ ምሽት
ድረስ ወጋቸው፤ በግመል ተቀምጠው ከሸሹት
አራት መቶ ወጣቶች በስተቀር፣ ከመካከላ
ቸው ያመለጠ አንድም አልነበረም:: 18ዳዊት
አማሌቃውያን የወሰዱትን ሁሉ አስጣለ፣
ሁለቱንም ሚስቶቹን አስመለሰ:: 19ትንሽም
ሆነ ትልቅ፣ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ልጆች፣
ምርኮም ሆነ ሌላ፣ አማሌቃውያን ከወሰ
ዱት ነገር ምንም የጐደለ አልነበረም፤
ዳዊት ሁሉንም አስመለሰ:: 20እንዲሁም
ዳዊት የበጉን፣ የፍየሉንና የላሙን መንጋ
ሁሉ ወሰደ፤ ሰዎቹም “ይህ የዳዊት ምርኮ
ነው’ እያሉ መንጋውን ከሌሎች ከብቶች
ፊት ለፊት ይነዱ ነበር::
21ከዚያም ዳዊት፣ እጅግ በመድከ
ማቸው ምክንያት ሊከተሉት ወዳልቻሉት
በቦሦር ወንዝ ቀርተው ወደ ነበሩት ወደ
ሁለቱ መቶ ሰዎች መጣ፤ እነርሱም
ዳዊትንና አብረውት የነበሩትን ሰዎች
ለመቀበል ወጡ:: ዳዊትና ሰዎቹ ወደ
እነርሱ እንደ ቀረቡም ዳዊት ሰላምታ
ሰጣቸው:: 22ከዳዊት ተከታዮች ክፉዎቹና
ምናምንቴዎቹ ሁሉ ግን፣ “አብረውን
ስላልዘመቱ ካመጣነው ምርኮ አናካፍላቸውም፤
ነገር ግን እያንዳንዱ ሚስ ቱንና ልጆቹን
ይዞ መሄድ ይችላል” አሉ::
23ዳዊትም እንዲህ አለ፤ “ወንድሞቼ ሆይ፤
የጠበቀን፣ የመጣብንንም ወራሪ በእጃችን
የጣለልን *እግዚአብሔር* ነው፤ እርሱ በሰጠን
ነገር፣ ይህን ማድረግ አይገባችሁም:: 24የም
ትሉትን ማን ይቀበላችኋል? ከጓዝ ጋር
የቀረው ሰው ድርሻ ለጦርነት ከወጣው ሰው
ድርሻ ጋር አይበላለጥም፤ ሁሉም እኩል
ይካፈላሉ::” 25ዳዊትም ከዚያ ቀን ጀምሮ
እስከ ዛሬ ድረስ ይህን ለእስራኤል ደንብና
ሥርዐት አደረገው::
26ዳዊት ወደ ጺቅላግ በመጣ ጊዜ፣ ወዳ
ጆቹ ለሆኑት ለይሁዳ ሽማግሌዎች፣ “*ከእግ
ዚአብሔር* ጠላቶች የተገኘ ስጦታ እነሆ፤”
በማለት ከምርኮው ላይ ከፍሎ ላከላቸው::
27ይህንም፣ በቤቴል፣ በደቡብ ራሞትና
በየቲር ለነበሩ፣ 28በአሮዔር፣ በሢፍሞት፣
በኤሽትሞዓና 29በራካል እንዲሁም በይረሕ
ምኤላውያንና በቄናውያን ከተሞች ለሚ
ኖሩ፣ 30በሔርማ፣ በቦራሣን፣ በዓታክ፣ 31በኬ
ብሮን እንዲሁም ዳዊትና ሰዎቹ በተዘዋ
ወሩባቸው ስፍራዎች ሁሉ ለነበሩት ላከላቸው::

### የሳኦል መሞት

31፥1-13 ተጓ ምብ-2ሳሙ1፥4-12፤ 1ዜና10፥1-12

31 በዚህ ጊዜ ፍልስጥኤማውያን እስ
ራኤልን ወጉ፤ እስራኤላውያን ከፊ
ታቸው ሸሹ፤ ብዙዎቹም በጊልቦዓ ተራራ
ላይ ተወግተው ወደቁ:: 2ፍልስጥኤማውያን
ሳኦልንና ልጆቹን አጥብቀው ተከታተሉ፤
የሳኦልንም ልጆች ዮናታንን፣ አሚናዳ
ብንና ሜልኪሳን ገደሉ:: 3ውጊያው በሳኦል
ላይ በረታበት፤ ቀስተኞችም ደርሰው እጅግ
አቈሰሉት::
4ሳኦልም ጋሻ ጃግሬውን፣ “እነዚህ ያል
ተገረዙ ሰዎች መጥተው እንዳይወጉኝ፣
እንዳ ያዋርዱኝ፣ አንተው ሰይፍህን መዘህ
ውጋኝ” አለው::
ጋሻ ጃግሬው ግን እጅግ ፈርቶ ስለ ነበር፣
እምቢ አለው:: ስለዚህ ሳኦል የራሱን ሰይፍ
ወስዶ በላዩ ላይ ወደቀበት:: 5ጋሻ ጃግሬውም
ሳኦል መሞቱን ባየ ጊዜ፣ እርሱም እንደዚሁ
በሰይፉ ላይ ወድቆ አብሮት ሞተ:: 6ሳኦልና
ሦስቱ ልጆቹ፣ አብረውት የነበሩ ሰዎች
ሁሉና ጋሻ ጃግሬው የሞቱት በዚያኑ ቀን
ነበር::
7በሸለቆው ማዶና ከዮርዳኖስ ባሻገር
ያሉ እስራኤላውያን የእስራኤል ሰራዊት
መሸሹን፣ ሳኦልና ልጆቹም መሞታቸውን
ባዩ ጊዜ ከተሞቻቸውን ለቀው ሸሹ፤ ፍል
ስጥኤማውያንም መጥተው ተቀመጡባቸው::
8በማግስቱ ፍልስጥኤማውያን የሞቱትን
ሰዎች ለመግፈፍ ሲመጡ፣ ሳኦልና ሦስቱ
ልጆቹ በጊልቦዓ ተራራ ላይ ወድቀው
አገኟቸው:: 9ከዚያም የሳኦልን ራስ ቈርጠው፣
የጦር መሣሪያውንም ገፈው፣ የምሥራቹን
በየቤተ ጣዖቶቻቸውና በሕዝባቸው መካከል

30፥10 ቊ21
30፥12 መሳ15፥19
30፥13 1ሳሙ14፥48
30፥14 ቊ1፤ ኢሱ14፥13፤15፥13፤ 2ሳሙ8፥18፥15፥18፤20፥7፡23፤1ነገ1፥38፡44፤1ዜና18፥17፤ ሕዝ25፥16፤ሰፎ2፥5
30፥15 ዘዳ 23፥15
30፥16 ቊ7፤ ኢሱ22፥8፤ ሉቃ12፥19
30፥17 ቊ16፤ 1ሳሙ11፥11፤ 2ሳሙ1፥1፡8
30፥18 ዘፍ14፥16
30፥21 ቊ10
30፥24 ዘኍ31፥27፤ መሳ5፥30
30፥26 ዘፍ33፥11
30፥27 ኢሱ7፥2፤ ኢሱ10፥40፤15፥48
30፥28 ዘኍ32፥34፤ ኢሱ13፥16፤ 15፥50፤1ዜና27፥27
30፥29 1ሳሙ15፥6፤ 27፥10
30፥30 ዘኍ14፥45፤ 21፥3፤ኢሱ15፥42
30፥31 ዘኍ13፥22፤ ኢሱ10፥36፤ 2ሳሙ 2፥1፡4
31፥1 1ሳሙ28፥4
31፥2 1ሳሙ14፥49፤ 18፥1፤28፥19
31፥3 1ሳሙ28፥4
31፥4 ዘፍ34፥14፤ መሳ9፥54፤ 1ሳሙ14፥6
31፥6 1ሳሙ26፥10
31፥8 2ሳሙ1፥20

እንዲናገሩ ወደ ፍልስጥኤም ምድር ሁሉ
መልክተኞች ላኩ። [10]የጦር መሣሪያውን
በአስታሮት ቤተ ጣዖት ውስጥ አኖሩት፤
ሬሳውን ደግሞ በቤትሳን ግንብ ላይ አንጠ
ለጠሉት።
[11]የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ፍልስጥኤማው
ያን በሳኦል ላይ ያደረጉትን በሰሙ ጊዜ፣

31፥9 መሳ16፥24፤ 2ሳሙ1፥20፤4፥4
31፥10 ኢሱ17፥11፤ መሳ2፥12-13፤1ሳሙ7፥3
31፥11 መሳ21፥8፤ 1ሳሙ11፥1
31፥12 ዘፍ38፥24፤ መዝ76፥5፤ አሞ 6፥10

[12]ጀግኖቻቸው ሁሉ በሌሊት ወደ ቤትሳን
ሄዱ። የሳኦልንና የልጆቹን ሬሳ ከግንቡ ላይ
አውርደው ወደ ኢያቢስ አምጥተው
አቃጠሉ። [13]ከዚያም ዐጥንቶቻቸውን ወስ
ደው በኢያቢስ ባለው የአጣጥ ዛፍ ሥር
ቀበሩ፤ ሰባት ቀንም ጾሙ።

31፥13 ዘፍ21፥33፤2ሳሙ21፥12-14

# መጽሐፈ ሳሙኤል - ሁለተኛ

## ዳዊት የሳኦልን ሞት ሰማ

1፥4-12 ተጓ ምብ - 1ሳሙ 31፥1-13፤ 1ዜና10፥1-12

1 ሳኦል ከሞተ በኋላ፣ ዳዊት አማሌ
ቃውያንን ድል አድርጎ በመመለስ፣
በጺቅላግ ሁለት ቀን ቈየ፡፡ 2በሦስተኛውም
ቀን የተቀደደ ልብስ የለበሰ፣ በራሱም ላይ
ትቢያ የነሰነሰ አንድ ሰው ከሳኦል ሰፈር
መጣ፡፡ ወደ ዳዊት እንደደረሰም፣ ወደ መሬት
ለጥ ብሎ በአክብሮት እጅ ነሣ፡፡

3ዳዊትም፣ "ከወዴት መጣህ?" ሲል ጠየ
ቀው፡፡

እርሱም፣ "ከእስራኤላውያን ሰፈር ሸሽቼ
መምጣቴ ነው" በማለት መለሰለት፡፡

4ዳዊትም፣ "ምን ነገር ተፈጠረ?" ሲል ጠየ
ቀው፡፡

እርሱም "ሰዎቹ ከጦርነቱ ሸሽተዋል፤ ብዙ
ዎቹ ወድቀዋል፤ ሞተዋል፤ ሳኦልና ልጁ ዮና
ታንም ሞተዋል" አለ፡፡

5ከዚያም ዳዊት ወሬውን የነገረውን ወጣት፣
"ሳኦልና ልጁ ዮናታን መሞታቸውን እን
ዴት አወቅህ?" ሲል ጠየቀው፡፡

6ወሬ ነጋሪው ወጣትም እንዲህ አለ፤ "ድን
ገት ወደ ጊልቦዓ ተራራ ወጥቼ ነበር፤ እዚያም
ሳኦል ጦሩን ተደግፎ ሳለ፣ ሠረገሎችና
ፈረሰ ኞች ተከታትለው ደረሱበት፤ 7ወደ
ኋላውም ዞር ሲል እኔን ስላየ ጠራኝ፤
እኔም፣ 'ምን ልታዘዝ' አልሁ፡፡

8"እርሱም፣ 'አንተ ማን ነህ?' ሲል ጠየቀኝ፤
"እኔም 'አማሌቃዊ ነኝ' ብዬ መለስሁለት፡፡

9"ከዚያም፣ 'እኔ በሞት ጣር ውስጥ እገኛለሁ፤
ነፍሴ ግን አልወጣችም፤ እባክህ በላዬ ቆመህ
ግደለኝ' አለኝ፡፡

10"መቼም ከወደቀ በኋላ እንደማይተርፍ
ስላወቅሁ፣ በላዩ ቆሜ ገደልሁት፤ በራሱ ላይ
የነበረውን ዘውድና የክንዱን አንባር ወስጄ
እነሆ፤ ለጌታዬ አምጥቻለሁ፡፡"

11ከዚያም ዳዊትና አብረውት የነበሩት
ሰዎች ሁሉ ልብሳቸውን ቀደዱ፡፡ 12ለሳኦልና
ለልጁ ለዮናታን፣ ለእግዚአብሔር ሰራዊትና
ለእስራኤል ቤት አዘኑ፤ አለቀሱ፤ እስከ ማታም
ድረስ ጾሙ፤ የወደቁት በሰይፍ ነበርና፡፡

13ዳዊትም ወሬውን ያመጣለትን ወጣት፣
"ከየት ነው የመጣኸው?" ብሎ ጠየቀው፡፡

እርሱም፣ "እኔ የአንድ መጻተኛ አማሌቃዊ
ልጅ ነኝ" ብሎ መለሰ፡፡

14ዳዊትም፣ "ታዲያ እግዚአብሔር የቀባውን
ለማጥፋት እጅህን ስታነሣ እንዴት አልፈራ
ህም?" ሲል ጠየቀው፡፡

15ዳዊትም ከጒልማሶቹ አንዱን ጠርቶ፣
"በል ቀረብና ውደቅበት" አለው፡፡ እር
ሱም መታው፤ ሞተም፡፡ 16ዳዊትም፣ "እግ
ዚአብሔር የቀባውን ገድያለሁ' ስትል
የገዛ አፍህ መስክሮብሃልና፣ ደምህ በራስህ
ላይ ይሁን" አለው፡፡

## ዳዊት ለሳኦልና ለዮናታን የተቀኘው የሐዘን እንጒርጒሮ

17ዳዊትም በሳኦልና በልጁ በዮናታን
ሞት ምክንያት ይህን የሐዘን እንጒርጒሮ
እየተቀኘ አለቀሰ፤ 18እንዲሁም የቀስት
እን ጒርጒሮ የተባለውን ለይሁዳ ሕዝብ
እንዲያስተምሩ አዘዘ፤ ይህም በያሻር መ
ጽሐፍ ተጽፎአል፡፡

19"እስራኤል ሆይ፤ ክብርህ በኰረብቶችህ
ላይ ተወግቶ ሞቶአል፤
ኀያላኑ እንዴት እንደዚህ ይውደቁ!

20"ይህን በጌት አትናገሩ፤
በአስቀሎናም መንገዶች አታውጁት፤
የፍልስጥኤም ቈነጃጅት አይደሰቱ፤
ያልተገረዙት ሴቶች ልጆች እልል አይበሉ፡፡

21"እናንተ የጊልቦዓ ተራሮች ሆይ፤
ጠል አያረስርሳችሁ፤
ዝናብም አይውረድባችሁ፤
የቍርባን እህል የሚያበቅሉም ዕርሻዎች
አይኑራቸው፤
በዚያ የኀያሉ ሰው ጋሻ ረክሶአልና፤
የሳኦል ጋሻ ከእንግዲህ በዘይት
አይወለወልም፡፡

22ከሞቱት ሰዎች ደም፣
ከኀያላኑም ሥብ፣
የዮናታን ቀስት ተመልሳ አልመጣችም፤
የሳኦልም ሰይፍ በከንቱ አልተመለሰችም፡፡

23"ሳኦልና ዮናታን በሕይወት እያሉ፣
የሚዋደዱና የሚስማሙ ነበሩ፤
ሲሞቱም አልተለያዩም፤
ከንስርም ይልቅ ፈጣኖች፣
ከአንበሳም ይልቅ ብርቱዎች ነበሩ፡፡

24"እናንት የእስራኤል ቈነጃጅት ሆይ፤
ሐምራዊ ቀሚስና ቀጭን ፈትል ላለበሳችሁ፣
ልብሶቻችሁንም በወርቅ ዘቦ ላስጌጠላችሁ፣
ለሳኦል አልቅሱለት፡፡

25"ኀያላን እንዴት እንዲህ በጦርነት ወደቁ!
ዮናታን በኰረብቶችህ ላይ ተወግቶ ሞቶአል፡፡

1፥1 ዘፍ14፥7፤ዘኍ 13፥29፤ኢሱ22፥8፤ 1ሳሙ26፥10፤30፥ 17፤1ዜና10፥13
1፥2 ዘፍ37፥7፤ 1ሳሙ4፥12፤20፥41፤2 ሳሙ4፥10፤ኢዮ2፥12 ፤ሕዝ27፥30
1፥6 ቀኍ21፤1ሳሙ 28፥4
1፥8 ቀኍ13፤1ሳሙ 15፥2፤27፥8፤30፥13 ፡17
1፥9 መሳ9፥54
1፥10 2ነገ11፥12
1፥11 ዘፍ37፥29፤ ዘኍ14፥6
1፥13 ቀኍ8፤1ሳሙ 14፥48
1፥14 1ሳሙ12፥3፤ 26፥9
1፥15 2ሳሙ4፥ 10፥12
1፥16 ዘሌ20፥9፤ ማቴ27፥24-25፤ ሐሥ18፥6
1፥17 ቀኍ26፤ዘፍ 50፥10፤ሕዝ32፥2
1፥18 ኢሱ10፥13
1፥19 2ሳሙ3፥38፤ 23፥8፤መዝ29፥1፤ 45፥3
1፥20 ኢሱ13፥3፤ 1ሳሙ18፥6፤31፥8፤ ሚክ1፥10
1፥21 ቀኍ6፤ዘፍ 27፥28፤ዘዳ11፥17፤ 1ነገ8፥35፤17፥1፤ 18፥1፤2ዜና6፥26፤ ኢዮ36፥27፤38፥28፤ መዝ65፥10፤147፥8፤ ኢሳ5፥6፤18፥4፤ 21፥5፤ኤር5፥24፤ 12፥4፤14፥4፤ሕዝ 31፥15፤አሞ1፥12
1፥22 ዘዳ32፥42፤ ኢሳ34፥3፡7፤49፥26
1፥23 ዘዳ28፥49፤ መሳ14፥18
1፥24 መሳ5፥30

26ወንድሜ ዮናታን ሆይ፤ እኔ ስለ አንተ
አዘንሁ፤
አንተ ለእኔ እጅግ ውድ ነበርህ፤
ፍቅርህ ለእኔ ድንቅ ነበረ፤
ከሴት ፍቅርም ይልቅ ግሩም ነበር፡፡
27"ኀያላኑ እንዴት ወደቁ!
የጦር መሣሪያዎቹስ እንዴት ከንቱ ይሁኑ!"

### ዳዊት የይሁዳ ንጉሥ ሆነ

2 ከዚህ በኋላ ዳዊት፣ "ከይሁዳ ከተሞች ወደ
አንዲቱ ልውጣን?" ብሎ እግዚአብሔ
ርን ጠየቀ፡፡
*እግዚአብሔርም*፣ "አዎን ውጣ" አለው፡፡
ዳዊትም፣ "ወደ የትኛዪቱ ልሂድ?" ሲል
ጠየቀ፡፡
*እግዚአብሔርም*፣ "ወደ ኬብሮን" ብሎ መለ
ሰለት፡፡
2ስለዚህ ዳዊት ከሁለቱ ሚስቶቹ ከኢይ
ዝራኤላዊቷ ከአኪናሆምና የቀርሜሎሳዊው
የናባል ሚስት ከነበረችው ከአቢግያ ጋር ወደ
ዚያ ወጣ፡፡ 3እንዲሁም ዳዊት አብረውት
የነበሩትን ሰዎች ከነቤተ ሰቦቻቸው አመ
ጣቸው፤ እነርሱም በኬብሮን ከተሞች ተቀ
መጡ፡፡ 4የይሁዳም ሰዎች ወደ ኬብሮን
መጡ፤ በዚያም ዳዊትን ቀብተው በይሁዳ
ቤት ላይ አነገሡት፡፡
ሳኦልን የቀበሩት የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች
መሆናቸውን ለዳዊት በነገሩት ጊዜ፣ 5እር
ሱም የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ይህን እንዲ
ነግሩ መልእክተኞች ላከ፤ "በእንዲህ ዐይነት
ሁኔታ ጌታችሁን ሳኦልን በመቅበር በጎነት
አሳይታችኋልና *እግዚአብሔር* ይባርካችሁ፤
6አሁንም *እግዚአብሔር* ጽኑ ፍቅሩንና ታማኝነ
ቱን ይግለጥላችሁ፤ እናንተ ይህን ስላደረጋ
ችሁ፣ እኔም እንደዚሁ በጎ ነገር አደርግ
ላችኋለሁ፤ 7እንግዲህ ጠንክሩ፤ በርቱ ጌታ
ችሁ ሳኦል ሞቶአልና፤ የይሁዳ ቤትም
እኔን ቀብተው በላያቸው አንግሠውኛል፡፡"

### በዳዊት ቤትና በሳኦል ቤት መካከል የተደረገ ጦርነት

3፥2-5 ተጓ ምብ - 1ዜና 3፥1-4

8በዚህ ጊዜ የሳኦል ሰራዊት አዛዥ የኔር
ልጅ አበኔር፣ የሳኦልን ልጅ ኢያቡስቴን ወስዶ
ወደ መሃናይም አሻገረው፤ 9እርሱንም በገለዓ
ድ፣ በአሴር፣ በኢይዝራኤል፣ በኤፍሬ ምና
በብንያም እንዲሁም በእስራኤል ሁሉ ላይ
አነገሠው፡፡
10የሳኦል ልጅ ኢያቡስቴ በእስራኤል
ላይ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው አርባ ዓመት
ነበረ፤ ሁለት ዓመትም ገዛ፡፡ የይሁዳ ቤት
ግን ዳዊትን ተከተለ፡፡ 11ዳዊት በኬብሮን
ንጉሥ ሆኖ እስራኤልን የገዛው ሰባት ዓመት

1፥26 ቀኁ17፤1ሳሙ 18፥1፤20፥42፤ ኤር22፥18፤34፥5
1፥27 1ሳሙ2፥4
2፥1 ዘፍ13፥18፤ 23፥19፤1ሳሙ23፥2፡ 11-12
2፥2 1ሳሙ25፥42 ፡43
2፥3 ዘፍ13፥18፤ 23፥2፤37፥14፤1ሳሙ 27፥2፤1ዜና12፥22
2፥4 መሳ21፥8፤ 1ሳሙ2፥35፤11፥1፤ 30፥31፤2ሳሙ5፥3-5፤ 1ዜና12፥23-40
2፥5 መሳ17፥2፤ 1ሳሙ23፥21፤ 2ጢሞ1፥16
2፥6 ዘፀ34፥6
2፥7 ኢሱ1፥6፤ መሳ5፥21
2፥8 ዘፍ32፥2፤ 1ሳሙ14፥50፤2ሳሙ 3፥27፤4፥5፤1ዜና8፥33፤ 9፥39
2፥9 ዘኍ32፥26፤ ኢሱ19፥24-31፤ 1ዜና12፥29
2፥11 2ሳሙ5፥5
2፥12 ኢሱ9፥3
2፥13 2ሳሙ8፥16፤ 19፥13፤1ነገ1፥17፤ 1ዜና2፥16፤11፥6፤ 27፥34
2፥16 መሳ3፥21
2፥17 1ሳሙ17፥8፤ 2ሳሙ3፥1
2፥18 1ሳሙ26፥6፤ 2ሳሙ3፥30፡39፤10፥7 ፤11፥1፤14፥1፤16፥10፤ 18፥14፤19፥22፤ 20፥8፤23፥24፤ 24፥3፤1ነገ1፥7፤ 2፥5፡34፤1ዜና2፥16፤ 11፥26፤12፥8፤27፥7፤ ምሳ6፥5፤ማሕ2፥9
2፥22 2ሳሙ3፥27
2፥23 2ሳሙ3፥27፤ 4፥6፤20፥12

ከስድስት ወር ነበረ፡፡
12የኔር ልጅ አበኔር፣ ከሳኦል ልጅ ከኢያ
ቡስቴ አገልጋዮች ጋር ሆኖ ከመሃናይም ተነ
ሥተው ወደ ገባዖን ሄዱ፡፡ 13እነርሱንም የጽ
ሩያ ልጅ ኢዮአብና የዳዊት ሰዎች ወጥተው
በገባዖን ኵሬ አጠገብ ተገናኟቸው፤ አንዱ
ወገን በኵሬው ወዲህ ማዶ፣ ሌላው ወገን
ደግሞ በኵሬው ወዲያ ማዶ ተቀመጠ፡፡
14ከዚያም አበኔር፣ ኢዮአብን፣ "ከእናን
ተም ከእኛም ጕልማሶች ይነሡና በፊታችን
በጨበጣ ውጊያ ይጋጠሙ" አለው፡፡
ኢዮአብም፣ "ይሁን እሺ ይጋጠሙ" ብሎ
መለሰ፡፡
15ስለዚህ ከብንያም ለሳኦል ልጅ ለኢያቡ
ስቴ ዐሥራ ሁለት፣ ለዳዊት ደግሞ ዐሥራ
ሁለት ሰዎች ተነሥተው ተቈጠሩ፡፡ 16ከዚያም
እያንዳንዱ ሰው የባለጋራውን ራስ በመያዝ
ሰይፉን በጐኑ እየሻጠበት ተያይዘው ወደቁ፡፡
ስለዚህም በገባዖን የሚገኘው ያ ቦታ "የሰይፍ
ምድር"ሀ ተባለ፡፡
17የዚያን ዕለቱ ጦርነት እጅግ ከባድ
ነበር፤ አበኔርና የእስራኤል ሰዎች በዳዊት
ሰዎች ድል ሆኑ፡፡
18ሦስቱ የጽሩያ ወንዶች ልጆች ኢዮአብ፣
አቢሳና አሣሄል እዚያው ነበሩ፡፡ አሣሄል
እንደ ዱር ሚዳቋ በሩጫ ፈጣን ነበረ፤ 19ወደ
ቀኝ ወይም ወደ ግራ ሳይል አበኔርን ተከ
ታተለው፡፡ 20አበኔርም ወደ ኋላው ዘወር ብሎ
በመመልከት፣ "አሣሄል! አንተ ነህ?" ሲል
ጠየቀው፡፡
እርሱም፣ "አዎን እኔ ነኝ" ብሎ መለ
ሰለት፡፡
21ከዚያም አበኔር፣ "ወደ ቀኝህ ወይም ወደ
ግራህ ዘወር በልና አንዱን ጕልማሳ ይዘህ
መሣሪያውን ንጠቀው" አለው፡፡ አሣሄል ግን
እርሱን መከታተሉን አልተወም ነበር፡፡
22እንደ ገናም አበኔር፣ "እኔን መከታተል
ብትተው ይሻልሃል፤ እኔስ ለምን ከመሬት
ጋር ላጣብቅህ? ከዚያስ የወንድምህን የኢዮአብን
ፊት ቀና ብዬ እንዴት አያለሁ?" አለው፡፡
23አሣሄል ግን መከታተሉን አልተወም፤
ስለዚህ አበኔር በጦሩ ጫፍ ሆዱን ወጋው፣
ጦሩም በጀርባው ዘልቆ ወጣ፤ አሣሄልም
እዚያው ወደቀ፤ ወዲያው ሞተ፡፡ እያንዳን
ዱም ሰው አሣሄል ወድቆ ወደ ሞተበት
ስፍራ ሲደርስ ይቆም ነበር፡፡
24ኢዮአብና አቢሳ ግን አበኔርን ተከታተሉት፤
እየሳደዱም ወደ ገባዖን ምድረ በዳ በሚወስደው
መንገድ ከጋይ አጠገብ ወዳለው ወደ አማ
ኩረብታ ሲደርሱ ፀሓይ ጠለቀች፡፡ 25ከዚያም

ሀ16 ዕብራይስጡ፤ *ሔልቃዝ ሀዙሪም* ይባላል፤ ትርጕሙም፣ *የመሻሻጥ ምድር* ወይም *የጥላቻ ምድር* ማለት ነው፡፡

የብንያም ሰዎች ወደ አበኔር ተሰብስበው
ግንባር በመፍጠር በኰረብታው ጫፍ ላይ
ተሰለፉ።
26አበኔር ኢዮአብን ጠርቶ፣ “ይህ ሰይፍ
ዘላለም ማጥፋት አለበትን? ውጤቱ መራራ
መሆኑን አንተስ ሳታውቀው ቀርተህ ነውን?
ሰዎችህ ወንድሞቻቸውን ማሳደዱን እንዲ
ያቆሙ ትእዛዝ የማትሰጣቸውስ እስከ መቼ
ድረስ ነው?” አለው።
27ኢዮአብም፣ “ሕያው *እግዚአብሔርን*!
ይህን ባትናገር ኖሮ፣ ሰዎቹ እስኪነጋ
ድረስ ወንድሞቻቸውን ማሳደዱን ባላቆሙም
ነበር”[ለ] ብሎ መለሰ።
28ስለዚህ ኢዮአብ ቀንደ መለከቱን ነፋ፤
ከዚያም በኋላ ሰዎቹ በሙሉ እስራኤልን
ማሳደዱን ተው፤ ውጊያውም በዚሁ አበቃ።
29አበኔርና ሰዎቹም ሌሊቱን ዓረባን አል
ፈው ሄዱ፤ ከዚያም ዮርዳኖስን በመሻገር ቢት
ሮንን[ሐ] ሁሉ ዐልፈው ወደ መሃናይም መጡ።
30ከዚያም ኢዮአብ አበኔርን ማሳደዱን
ትቶ ተመለሰ፤ ሰዎቹንም ሁሉ አንድ ላይ
በሰበሰባቸው ጊዜ፣ ከዳዊት ሰዎች አሣሄ
ልን ሳይጨምር፣ ዐሥራ ዘጠኝ ሰዎች መጥ
ፋታቸው ታወቀ። 31የዳዊት ሰዎች ግን
ከአበኔር ጋር ከነበሩት ሦስት መቶ ሥልሳ
ብንያማውያን ገደሉ። 32አሣሄልንም ከወደ
ቀበት አንሥተው በቤተልሔም በአባቱ
መቃብር ቀበሩት። ከዚያም ኢዮአብና
ሰዎቹ ሌሊቱን ሁሉ ሲገሠግሡ አድረው፣
ሲነጋ ኬብሮን ደረሱ።

3 በዳዊት ቤትና በሳኦል ቤት መካከል የነበ
ረው ጦርነት ብዙ ጊዜ ቈየ፤ ዳዊት እየበ
ረታ ሲሄድ፣ የሳኦል ቤት ግን እየተዳከመ መጣ።
2ዳዊት በኬብሮን ሳለ፣ ስድስት ወንዶች
ልጆች ተወለዱለት፤
የበኵር ልጁ፣ ከኢይዝራኤላዊቷ ከአ
ኪናሆም የተወለደው አምኖን፣
3ሁለተኛው፣ የቀርሜሎሳዊው የናባል ሚስት
ከነበረችው ከአቢግያ የተወለደው ኪልአብ፣
ሦስተኛው፣ ተልማይ ከተባለው ከጌሹር ንጉሥ
ልጅ ከመዓካ የተወለደው አቤሴሎም፣
4አራተኛው፣ ከአጊት የተወለደው አዶንያስ፤
አምስተኛው፣ ከአቢጣል የተወለደው ሰፋጥያ፣
5ስድስተኛው፣ ከዳዊት ሚስት ከዔግላ የተ
ወለደው ይትረኃም ነበር፤ እነዚህ ዳዊት
በኬብሮን ሳለ የተወለዱለት ናቸው።

## አበኔር ከዳዊት ጋር ተባበረ

6የሳኦል ቤትና የዳዊት ቤት በጦርነት ላይ
በነበሩበት ጊዜ፣ አበኔር በሳኦል ቤት ላይ
ኀይሉን ያጠናክር ነበር። 7ሳኦልም የኢ
ዮሄልን ልጅ ሪጽፋን በቁባትነት

2፥26 ዘጸ32፥42፤ ኤር46፥10፡14፤ናሆ 2፥13፤3፥15
2፥28 መሳ3፥27፤ 2ሳሙ18፥16፤20፥23
2፥29 ዘፍ32፥2፤ ዘጸ3፥17
2፥32 ዘፍ49፥29
3፥1 2ሳሙ2፥17፤ 5፥10፤22፥44፤1ነገ 14፥30፤አስ9፥4
3፥2 1ሳሙ25፥43፤ 2ሳሙ13፥1
3፥3 1ሳሙ25፥42፤ 2ሳሙ13፥1፡28፡37፤ 14፥32፤15፥8
3፥4 1ነገ1፥5፡11፤ 2፥13፡22
3፥6 1ሳሙ14፥50
3፥7 ዘፍ22፥24፤ 2ሳሙ16፥21-22፤ 21፥8-11፤1ነገ1፥3
3፥8 1ሳሙ17፥43፤ 2ሳሙ9፥8፤16፥9፤ 2ነገ8፥13
3፥9 1ሳሙ15፥28
3፥10 መሳ20፥1፤ 1ሳሙ25፥28-31፤ 2ሳሙ24፥2
3፥13 ዘፍ43፥5
3፥14 1ሳሙ18፥27
3፥15 ዘጸ24፥1-4፤ 25፥44
3፥16 2ሳሙ16፥5፤ 17፥18
3፥17 መሳ11፥11
3፥18 1ሳሙ9፥16፤ 2ሳሙ8፥6

አስቀምጦአት ነበር፤ ኢያቡስቴም አበኔርን፣
“ለምንድን ነው ከአ ባቴ ቁባት ጋር የተኛኸ
ው?” አለው።
8አበኔርም በኢያቡስቴ ንግግር እጅግ
ስለ ተቈጣ እንዲህ አለ፤ “እኔ ለይሁዳ
የምወግን የውሻ ጭንቅላት ነኝን? ለአ
ባትህ ለሳኦል ቤት ለወንድሞቹና ለዘመ
ዶቹ ታማኝነቴን እስከ ዛሬ ድረስ አላጓ
ደልሁም፤ አንተንም አሳልፌ ለዳዊት አል
ሰጠሁም፤ አሁን ግን አንተ ከዚህች ሴት
ጋር በፈጸምሁት ነገር ትከሰኛለህን? 9*እግ
ዚአብሔር* ለዳዊት በመሐላ የሰጠውን ተስፋ
እዳር እንዲደርስ ሳላደርግ ብቀር *እግዚአብሔር*
በአበኔር ላይ ክፉ ያድርግበት፤ ከዚያ የባሰም
ያምጣበት፤ 10የማለለትም መንግሥትን ከሳኦል
ቤት አውጥቶ፣ ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ባለው
በእስራኤልና በይሁዳ ምድር ላይ የዳዊትን
ዙፋን ለመመሥረት የሰጠው ተስፋ ነው።”
11ኢያቡስቴም አበኔርን አጥብቆ ፈርቶት
ስለ ነበር፣ እንደ ገና አንዲት ቃል እንኳ ሊመ
ልስለት አልደፈረም።
12ከዚያም አበኔር ለዳዊት፣ “ምድሪቱ የማን
ናት? ከእኔ ጋር ተስማማ፤ እነሆ እስራኤል
ሁሉ ወደ አንተ እንዲመለስ እኔ እረዳሃለሁ”
ብለው ለዳዊት እንዲነግሩለት መልክተኞች
ላከ።
13ዳዊትም፣ “ይሁን እሺ፣ ከአንተ ጋር ስም
ምነቱን አደርጋለሁ፣ ነገር ግን ከአንተ
አንዲት ነገር እሻለሁ፤ ይኸውም ወደ እኔ
ስትመጣ በመጀመሪያ የሳኦልን ሴት
ልጅ ሜልኮልን ይዘህልኝ እንድትመጣ ነው፤
ያለዚያ ግን ወደ እኔ እንዳትመጣ” አለ።
14ከዚያም ዳዊት፣ “የመቶ ፍልስጥኤማውያን
ሸለፈት ማጫ የከፈልሁባትን ሚስቴን ሜል
ኮልን ስጠኝ” ብሎ ወደ ሳኦል ልጅ ወደ
ኢያቡስቴ መልክተኞች ላከበት።
15ስለዚህም ኢያቡስቴ መልክተኛ ልኮ፣ ሜል
ኮልን ከባሏ ከሌሳ ልጅ ከፈልጢኤል ወሰ
ዳት። 16ባሏም እስከ ብራቂም ከተማ
ድረስ እያለቀሰ ተከትሎአት ሄደ፤ ከዚያም
አበኔር፣ “በል በቃህ! ወደ ቤትህ ተመለስ”
አለው። ስለዚህም ተመለሰ።
17አበኔር ከእስራኤል ሽማግሌዎች ጋር
ተመካከረ፤ እንዲህም አለ፤ “ባለፈው ጊዜ
ዳዊት በላያችሁ እንዲነግሥ ፈልጋችሁ ነበር፤
18*እግዚአብሔር* ለዳዊት፣ ‘በባሪያዬ በዳዊት ሕዝ
ቤን እስራኤልን ከፍልስጥኤማውያን እጅና
ከጠላቶቻቸው እጅ እታደጋቸዋለሁ’ ብሎ
ተስፋ ስለ ሰጠው፣ ይህን አሁኑኑ አድርጉት።”

[ለ]27 ወይም፣ *በዚህ ማለዳ ይህንን ብትናገር ኖሮ ሰዎቹ ወንድ ሞቻቸውን ማሳደዱን ባቆሙ ነበር* ወይም፣ *ይህንን ብትናገር ኖሮ ሰዎቹ እስኪነጋ ድረስ ወንድሞቻቸውን ማሳደዱን ባቆሙ ነበር*
[ሐ]29 ወይም *ማለዳ* ወይም *ሸለቆ* የዕብራይስጡ ቃል ትርጉም በትክክል አይታወቅም።

19እንዲሁም አበኔር ለብንያማውያን ራሱ
ሄዶ ይህንኑ ነገራቸው፤ ከዚያም እስራ
ኤልና መላው የብንያም ቤት ለማድረግ
የፈለጉትን ሁሉ ለዳዊት ለመንገር ወደ
ኬብሮን ሄደ። 20አበኔር ከሃያ ሰዎች ጋር ዳዊት
ወዳለበት ወደ ኬብሮን መጣ፤ ዳዊትም
ለአበኔርና አብረውት ለነበሩት ሰዎች ግብዣ
አደረገላቸው። 21ከዚያም አበኔር ዳዊትን፤
"ከአንተ ጋር ቃል ኪዳን እንዲያደርጉ፣
ልብህ እንደተመኘውም ሁሉን እንድትገዛ
ፈጥኜ ሄጄ፣ ለጌታዬ ለንጉሡ መላውን እስ
ራኤልን ልሰብስብ" አለው። ስለዚህ ዳዊት
አበኔርን አሰናበተው፤ በሰላምም ሄደ።

## ኢዮአብ አበኔርን ገደለው

22የዳዊትና የኢዮአብ ሰዎች በዚያኑ ጊዜ
ብዙ ምርኮ ይዘው ከዘመቻ ተመለሱ። አበ
ኔር ግን ዳዊት በሰላም አሰናብቶት ስለ ሄደ፣
በኬብሮን አልነበረም። 23ኢዮአብና አብ
ሮት የነበረው ሰራዊት ሁሉ እዚያ እንደ
ደረሱ፣ የኔር ልጅ አበኔር ወደ ንጉሡ
መምጣቱን፣ ንጉሡ እንዳሰናበተውና እርሱም
በሰላም እንደ ሄደ፣ ኢዮአብ ሰማ።
24ስለዚህ ኢዮአብ ወደ ንጉሡ ገብቶ
እንዲህ አለ፤ "ምን ማድረግህ ነው? እነሆ
አበኔር መጥቶልህ እንዴት በሰላም እንዲ
ሄድ አሰናበትኸው? 25የኔርን ልጅ አበ
ኔርን ታውቀዋለህ፤ የመጣው ሊያታልልህ፣
መውጣት መግባትህን ለማወቅና የምታደርገውን
ሁሉ ሊሰልል ነው።"
26ከዚያም ኢዮአብ ከዳዊት ዘንድ ወጣ፤ አበ
ኔርን እንዲያመጡትም መልክተኞች ላከ፤ መል
ክተኞቹም ከሴይር የውሃ ጕድጓድ አጠገብ መለ
ሱት። ዳዊት ግን ይህን አላወቀም ነበር። 27አበ
ኔር ወደ ኬብሮን በተመለሰ ጊዜ፣ ኢዮአብ
በቈይታ የሚያነጋግረው በመምሰል ዞር
አድርጎ ወደ ቅጽሩ በር ይዞት ሄደ፤ እዚያም
የወንድሙን የአሣሄልን ደም ለመበቀል ሲል፣
ሆዱ ላይ ወግቶ ገደለው።
28ዳዊት ይህን ነገር ቈይቶ በሰማ ጊዜ እን
ዲህ አለ፤ "እኔም ሆንሁ መንግሥቴ ከኔር
ልጅ ከአበኔር ደም *በእግዚአብሔር* ፊት
ለዘላለም ንጹሕ ነን፤ 29ደሙ በኢዮአብ ራስና
በአባቱ ቤት ሁሉ ላይ ይሁን፤ ፈሳሽ ነገር
የሚወጣው ወይም አሠቃቂ የቈዳ በሽታ[መ]
ያለበት፣ በምርኵዝ የሚሄድ አንካሳ፣
ወይም በሰይፍ ተመቶ የሚወድቅ ወይም
የሚበላው ያጣ ራብተኛ ከኢዮአብ ቤት
አይታጣ።"
30አበኔር ገባዖን ላይ በተደረገው ጦርነት
የኢዮአብንና የአቢሳን ወንድም አሣሄልን ገድ
ሎት ስለ ነበር፣ እነርሱም አበኔርን ገደሉት።
31ከዚያም ዳዊት ለኢዮአብና አብሮት ለነበ

3፥19 1ዜና12፥2፤ 16፥29
3፥20 1ዜና12፥39
3፥21 2ሳሙ5፥3፤ 1ነገ11፥37
3፥27 ዘፀ21፥14፤ መሳ3፥21፤2ሳሙ2፥8፡22፡23፤4፥1፤1ነገ2፥5፡32
3፥28 ቀኍ37፤ ዘዳ21፥9
3፥29 ዘሌ15፥2፤ 20፥9፤1ነገ2፥31-33
3፥31 ዘፍ37፥34፤ መዝ30፥11፤35፥13፤ 69፥11፤ኢሳ20፥2
3፥32 ዘኍ14፥1፤ ምሳ24፥17
3፥33 ዘፍ50፥10
3፥34 ኢዮ36፥8፤ መዝ2፥3፤149፥8፤ ኢሳ45፥14፤ናሆ3፥10
3፥35 ሩት1፥17፤ 1ሳሙ31፥13፤2ሳሙ12፥17፤ኤር16፥7
3፥37 ቀኍ28
3፥38 2ሳሙ1፥19
3፥39 መሳ18፥26፤ 2ሳሙ2፥18፤16፥9፤ 18፥11፤1ነገ2፥32፤ መዝ41፥10፤101፥8
4፥1 2ሳሙ3፥27
4፥2 ኢሱ9፥17
4፥3 ነህ11፥33
4፥4 ዘሌ21፥18፤ 1ሳሙ18፥1፤31፥9፤ 2ሳሙ9፥8፡12፤ 16፥1-4፤19፥24፤ 21፥7-8፤1ዜና 8፥34፤9፥40

ረው ሕዝብ ሁሉ፣ "ልብሳችሁን ቀዳችሁ፣
ማቅ ለብሳችሁ በአበኔር ፊት አልቅሱ" አላቸው፤
ራሱ ንጉሥ ዳዊትም አስከሬኑን አጀበ። 32ከዚ
ያም አበኔርን በኬብሮን ቀበሩት፤ ንጉሡም
በአበኔር መቃብር ላይ ጮኾ አለቀሰ፤ ሕዝ
ቡም ሁሉ እንደዚሁ አለቀሱ።
33ንጉሡም ለአበኔር ይህን የሐዘን እንጉ
ርጕሮ ተቀኘ፤

"አበኔር እንደ ተራ ሰው ይሙት?
34እጆችህ አልታሰሩም፤
እግሮችህ በእግር ብረት አልገቡም፤
ሰው በክፉ ሰዎች ፊት እንደሚወድቅ
አንተም እንደዚሁ ወደቅህ።"

ሕዝቡም ሁሉ እንደ ገና አለቀሱለት።
35ከዚያም ሕዝቡ ሁሉ እህል በሚቀምስ
በት ሰዓት ወደ ዳዊት መጥተው ምግብ
እንዲበላ አጥብቀው ለመኑት። ዳዊት ግን፣
"ፀሓይ ከመጥለቋ በፊት እንጀራ ወይም ሌላ
ነገር ብቀምስ፣ *እግዚአብሔር* ክፉ ያድርግብኝ
ከዚያም የባሰ ያምጣብኝ" ብሎ ማለ።
36ሕዝቡም ሁሉ ይህንኑ ተመለከቱ፤ ደስም
አላቸው፤ በእርግጥ ንጉሡ ያደረገው ሁሉ ሕዝ
ቡን ደስ አሰኛቸው። 37እንዲሁም በዚያን ዕ
ለት
ሕዝቡ ሁሉና እስራኤል በሙሉ ንጉሡ የኔር
ልጅ በአበኔር ሞት እጁ እንዳልገባበት ዐወቀ።
38ከዚያም ንጉሡ ለራሱ ሰዎች እንዲህ አለ፤
"በዛሬይቱ ዕለት በእስራኤል መስፍንና ታላቅ
ሰው መውደቁን አላወቃችሁምን? 39ምንም
እንኳ ዛሬ የተቀባሁ ንጉሥ ብሆንም፣ እኔ ደካማ
ሰው ነኝ፤ እነዚህ የጽሩያ ልጆች እጅግ
በርትተውብኛል። *እግዚአብሔር* ለክፉ አድራጊ
የእጁን ይስጠው።"

## ኢያቡስቴ ተገደለ

4 አበኔር በኬብሮን መሞቱን የሳኦል
ልጅ ኢያቡስቴ በሰማ ጊዜ ወኔ ከዳው፤
መላው እስራኤልም ደነገጠ። 2በዚህ ጊዜ
የሳኦል ልጅ ኢያቡስቴ የወራሪ ጭፍራ
ቡድን መሪዎች የሆኑ ሁለት ሰዎች ነበሩት፤
አንዱ በዓና ሌላው ደግሞ ሬካብ ይባሉ
ነበር። እነርሱም ከብንያም ነገድ የብኤሮት
ተወላጅ የሆነው የሬሞን ልጆች ነበሩ፤
ብኤሮት ከብንያም ክፍል እንደ አንዱ
ትቈጠራለች። 3የብኤሮት ሕዝብ ወደ
ጌቴም በመሸሽ እስከ ዛሬም በመጻተኛነት
እዚያው ይኖራሉና።
4የሳኦል ልጅ ዮናታን ሁለት እግሮቹ ሽባ
የሆኑ አንድ ልጅ ነበረው። እርሱም የሳኦ
ልና የዮናታን አሟሟት ወሬ ከኢይዝራኤል
በመጣ ጊዜ የአምስት ዓመት ልጅ ነበረ።

[መ]29 የዕብራይስጡ ቃል ማናቸውንም ዐይነት የቈዳ በሽታ
የሚያመለክት ነው።

ሽባ የሆነውንም በዚህ ጊዜ ሞግዚቱ አን
ሥታው በጥድፊያ ስትሸሽ በመውደቁ
ነው። ስሙም ሜምፊቦስቴ ይባል ነበር።
5በዚህ ጊዜ የብኤሮታዊው የሬሞን ልጆች
ሬካብና በዓና ወደ ኢያቡስቴ ቤት ለመ
ሄድ ተነሡ፤ እርሱም የቀትር ጊዜ ዕረፍት
ለማድረግ ዐልጋው ላይ ተኝቶ ሳለ፣
ሙቀት ሲሆን እኩለ ቀን ላይ ደረሱ፤
6ስንዴ እንደሚፈልግም ሰው ሆነው ወደ
ቤቱ ውስጥ ዘልቀው በመግባት ሆዱ ላይ
ወጉት። ከዚያም ሬካብና ወንድሙ በዓና
ሹልክ ብለው ወጡ።
7ወደ ቤቱ ውስጥ የገቡት ኢያቡስቴ በመ
ኝታ ክፍሉ ውስጥ ተኝቶ ሳለ ነበር፤ ወግተው
ከገደሉትም በኋላ ራሱን ቈርጠው በመው
ሰድ፣ ሌሊቱን ሁሉ በዓረባ መንገድ ተጓዙ።
8የኢያቡስቴንም ራስ ወደ ኬብሮን ዳዊት ዘንድ
አምጥተው ንጉሡን፣ “አንተን ሊገድል ይፈልግ
የነበረው የጠላትህ የሳኦል ልጅ የኢያቡስቴ ራስ
ይኸውልህ፤ እነሆ *እግዚአብሔር* በዛሬው ቀን ስለ
ጌታዬ ስለ ንጉሡ ሳኦልንና ዘሩን ተበቅሎአል”
አሉት።
9ዳዊትም ለብኤሮታዊው ለሬሞን ልጆች
ለሬካብና ለወንድሙ ለበዓና እንዲህ ሲል መለሰ
ላቸው፤ ‘ከመከራ ሁሉ ያዳነኝ ሕያው *እግዚ
አብሔርን*፣ 10የምሥራች ያመጣልኝ መስሎት፣
‘እነሆ ሳኦል ሞተ’ ብሎ የነገረኝን ሰው ይዤ ጺቅ
ላግ ላይ ገደልሁት፤ እንግዲህ ለዚያ ሰው
ስላመጣው ምሥራች የሸለምሁት ይህን ነበር።
11ታዲያ በገዛ ቤቱ፣ በገዛ ዐልጋው ላይ ዐርፎ
የተኛውን ንጹሕ ሰው የገደሉትን ክፉ ሰዎች
እንዴት የባሰ ቅጣት አይገባቸውም? ደሙን
ከእጃችሁ መፈለግ፣ እናንተን ከምድሪቱ ማጥ
ፋት የለብኝምን?”
12ስለዚህም ዳዊት የራሱን ሰዎች አዘዘ፤ እነርሱ
ንም ገደሏአቸው፤ እጅና እግራቸውንም ቈርጠ
ው በኬብሮን ካለው ኵሬ አጠገብ ሰቀሏቸው።
ነገር ግን የኢያቡስቴን ራስ ወስደው ኬብሮን
በሚገ ኘው በአበኔር መቃብር አጠገብ ቀበሩት።

## ዳዊት በእስራኤል ላይ ነገሠ

5፥1-3 ተጓ ምብ - 1ዜና 11፥1-3

5 የእስራኤል ነገዶች በሙሉ ወደ ኬብሮን
ወደ ዳዊት መጥተው እንዲህ አሉ፤ “እነሆ፤
እኛ የዐጥንትህ ፍላጭ፣ የሥጋህ ቍራጭ ነን፤
2ባለፈው ሳኦል በእኛ ላይ ነግሦ በነበረ ጊዜ፣ እስ
ራኤልን በጦርነት የምትመራቸው አንተ ነበርህ፤
*እግዚአብሔርም*፣ ‘ሕዝቤን እስራኤልን ትጠብ
ቃለህ፤ መሪያቸውም ትሆናለህ’ ብሎህ ነበር።”
3ስለዚህም የእስራኤል ሽማግሌዎች
በሙሉ ወደ ኬብሮን መጡ፤ ንጉሥ ዳዊትም
ኬብ ሮን ላይ *በእግዚአብሔር ፊት* ከእነርሱ
ጋር ቃል ኪዳን አደረገ፤ እነርሱም ዳዊትን
ቀብ ተው በእስራኤል ላይ አነገሡት።
4ዳዊት በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሠላሳ ዓመት
ነበረ፤ አርባ ዓመትም ገዛ። 5በኬብሮን ተቀ
ምጦ በይሁዳ ላይ ሰባት ዓመት ከስድስት ወር፣
ኢየሩሳሌም ሆኖም በመላው እስራኤልና በይ
ሁዳ ላይ ሠላሳ ሦስት ዓመት ነገሠ።

## ዳዊት ኢየሩሳሌምን ድል አደረገ

5፥6-10 ተጓ ምብ - 1ዜና 11፥4-9
5፥11-16 ተጓ ምብ - 1ዜና 3፥5-9፤ 14፥1-7

6ንጉሡና ሰዎቹ በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን ኢያ
ቡሳውያንን ለመውጋት ወደዚያ ሄዱ። ኢያቡሳ
ውያንም፣ “ዳዊት እዚህ ሊገባ አይችልም”
ብለው ስላሰቡ ዳዊትን፣ “ዕውሮችና አንካሶች
እንኳ ይከለክሉሃልና ወደዚህች አትገባም”
አሉት። 7ይሁን እንጂ ዳዊት የጽዮንን ዐምባ
ያዘ፤ ይህችም የዳዊት ከተማ የተባለችው ናት።
8በዚያም ዕለት ዳዊት፣ “ኢያቡሳውያንን
ድል ማድረግ የሚፈልግ፣ የዳዊት ጠላቶች[ረ]
ወደሚሆኑ፣ ‘አንካሶችና ዕውሮች’ ለመድረስ
በውሃ መተላለፊያው[ሠ] ሽቅብ መውጣት አለ
በት” አለ። እንግዲህ፣ “‘አንካሶችና ዕውሮች’
ወደ ቤተ መንግሥት አይገቡም” ያሉት ለዚህ
ነው።
9ከዚያም ዳዊት መኖሪያውን በዐምባዪቱ
ላይ አደረገ፤ የዳዊት ከተማም ብሎ ጠራት።
ዳዊትም ከሚሎ አንሥቶ ወደ ውስጥ ዙሪ
ያዋን ገነባት። 10የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር
ከእ ርሱ ጋር ስለ ነበር፣ ዳዊት ከዕለት ወደ ዕ
ለት እየበረታ ሄደ።
11በዚህ ጊዜ የጢሮስ ንጉሥ ኪራም ወደ
ዳዊት መልክተኞችን ላከ፤ እንዲሁም የዝግባ ዕ
ን ጨት፣ አናጢዎችንና ድንጋይ ጠራቢዎችን
አብሮ ሰደደ፤ እነርሱም ለዳዊት ቤተ መን
ግሥት ሠሩለት። 12*እግዚአብሔር* በእስራኤል
ላይ ንጉሥነቱን እንዳጸናለት፣ ስለ ሕዝቡ ስለ
እስራኤልም መንግሥቱን እንዳስፋለት ዳዊት
ዐወቀ።
13ዳዊት ከኬብሮን ከሄደ በኋላ፣ ከበፊቶቹ
በተጨማሪ በኢየሩሳሌም ሌሎች ቁባቶች አስ
ቀመጠ፤ ሚስቶችም አገባ፤ ሌሎች ወንዶችና
ሴቶች ልጆችም ተወለዱለት። 14በኢየሩሳሌም የተ
ወለዱለትም ልጆች ሳሙስ፣ ሶባብ፣ ናታን፣
ሰሎሞን፣ 15ኢያቤሐር፣ ኤሊሱዔ፣ ናፌቅ፣
ናፍያ፣ 16ኤሊሳማ፣ ኤሊዳሄ፣ ኤሊፋላት ይባ
ላሉ።

## ዳዊት ፍልስጥኤማውያንን ድል አደረገ

5፥17-25 ተጓ ምብ - 1ዜና 14፥8-17

17ዳዊት በእስራኤል ላይ ንጉሥ ሆኖ መቀባቱን
ፍልስጥኤማውያን በሰሙ ጊዜ፣ እርሱን ለመ
ፈለግ በሙሉ ኀይላቸው ወጡ፤ ዳዊት ግን

[ሠ]8 ወይም *ማንጠልጠያ ኵላቦች*
[ረ]8 ወይም *በዳዊት የተጠላ*

4፥5 ሩት2፥7፤ 2ሳሙ2፥8
4፥6 2ሳሙ2፥23
4፥7 ዘጸ3፥17
4፥8 ዘኍ31፥3፤ 1ሳሙ24፥4፤25፥29፤2 ሳሙ20፥21፤ 2ነገ10፥7
4፥9 ዘፍ48፥16፤ 1ነገ1፥29
4፥10 2ሳሙ1፥2-16
4፥11 ዘፍ4፥10፤ 9፥5፤መዝ9፥12፤ 72፥14
4፥12 2ሳሙ1፥15
5፥1 ዘፍ29፥14፤ 35፥26፤2ሳሙ19፥43
5፥2 ዘፍ48፥15፤ 1ሳሙ11፥6፤12፥12፤ 13፥14፤16፥1፤18፥5፡ 13፡16፤2ሳሙ6፥21፤ 7፥7፤ማቴ2፥6፤ ዮሐ21፥16
5፥3 ዘጸ17፥15፤ 2ሳሙ2፥4፤3፥21
5፥4 ዘፍ37፥2፤ 1ነገ2፥11፤1ዜና3፥4፤ 26፥31፤ሉቃ3፥23
5፥5 2ሳሙ2፥11፤ 1ነገ2፥11፤1ዜና3፥4
5፥6 ኢሱ15፥8፤ መሳ1፥8
5፥7 2ሳሙ6፥12፡ 16፤1ነገ2፥10፤8፥1፤ መዝ76፥2፤ኢሳ29፥1፤ ኤር21፥13፤25፥29
5፥8 2ነገ20፥20፤ 32፥30፤ማቴ21፥14
5፥9 1ነገ9፥15፡24
5፥10 2ሳሙ3፥1፤ 7፥9፤መዝ24፥10
5፥11 1ነገ5፥1፡18፤ 2ዜና2፥3
5፥12 ዘኍ24፥7
5፥13 ዘዳ17፥17
5፥14 1ዜና3፥5፤ ሉቃ3፥31
5፥17 2ሳሙ23፥14 ፤1ዜና11፥16

ይህን ሰምቶ ወደ ምሽጉ ወረደ። 18በዚህ
ጊዜም ፍልስጥኤማውያን መጥተው በራ
ፋይም ሸለቆ ተበታትነው ሰፈሩ። 19ስለዚ
ህም ዳዊት እግዚአብሔርን፣ “ፍልስጥኤ
ማውያንን ወጥቼ ልውጋቸው? በእጄስ
አሳልፈህ ትሰጠኛለህ?” ሲል ጠየቀ።

እግዚአብሔርም፣ “አዎን ሂድ፤ በእርግጥ
ፍልስጥኤማውያንን በእጅህ አሳልፌ እሰጥሃ
ለሁ” አለው።

20ስለዚህም ዳዊት ወደ በአልፐራሲም[ሰ] ሄዶ
ፍልስጥኤማውያንን ድል አደረጋቸው። እር
ሱም “የጐርፍ ውሃ ጥሶ በመውጣት እንደ
ሚያፈራርስ፣ እግዚአብሔርም ጠላቶቼን በፊቴ
አፈራረሳቸው” አለ። ከዚህ የተነሣም የዚያ
ቦታ ስም በአልፐራሲም ተባለ። 21ፍልስጥኤ
ማውያንም ጣዖቶቻቸውን ትተው ሸሽተው
ስለ ነበር፣ ዳዊትና ሰዎቹ ወስደው አቃጠ
ሏቸው።

22ፍልስጥኤማውያን እንደ ገና መጥተው
በራፋይም ሸለቆ ተበታትነው ሰፈሩ።
23ስለዚህም ዳዊት እግዚአብሔርን ጠየቀ፤
እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፤ “በስተ
ኋላቸው በኩል በመክበብ በበለሳኑ ፊት
ለፊት ግጠማቸው እንጂ በቀጥታ ወዳሉ
በት አትውጣ፤ 24በበለሳኑ ዛፎች ጫፍ ላይ
የሰልፍ ጒዞ ድምፅ ስትሰማም፣ እግዚአ
ብሔር የፍልስጥኤማውያንን ሰራዊት ለመ
ምታት ቀድሞህ ወጥቶአል ማለት ነውና
በዚያን ጊዜ በፍጥነት ወደ ፊት ሂድ።”
25ስለዚህም ዳዊት እግዚአብሔር እንዳዘ
ዘው አደረገ፤ ፍልስጥኤማውያንንም ከገባ
ዖን[ሸ] እስከ ጌዝር ድረስ እያሳደደ መታ
ቸው።

## ታቦቱ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ

6፥1-11 ተጓ ምብ - 1ዜና 13፥1-14
6፥12-19 ተጓ ምብ - 1ዜና 15፥25-16፥3

6 ዳዊት እንደ ገና ከእስራኤል የተመረጡ
በአጠቃላይ ሠላሳ ሺህ ሰዎች ሰበሰበ።
2እርሱና አብረውት ያሉት ሰዎች ሁሉ በታ
ቦቱ ላይ ባለው ኪሩቤል ላይ በተቀመጠው
በሰራዊት ጌታ በእግዚአብሔርም ስም[ቀ] የተጠ
ራውን የእግዚአብሔርን ታቦት ከዚያ ለማምጣት
በይሁዳ ወዳለችው ወደ በአል ሄዱ። 3የእግዚ
አብሔርንም ታቦት በአዲስ ሠረገላ ላይ አኑ
ረው፣ በኰረብታ ላይ ካለው ከአሚናዳብ ቤት
አውጥተው አመጡ፤ ሠረገላውን ይነዱ የነበሩ
ትም የአሚናዳብ ልጆች ዖዛና አሒዮ ሲሆኑ፣
4የእግዚአብሔርም ታቦት በሠረገላው ላይ ሆኖ[በ]፣
አሒዮ ፊት ፊት ይሄድ ነበር። 5ዳዊትና የእስራ
ኤል ቤት በሙሉ በዝማሬ፣ በበገና፣ በመሰንቆ፣
በከበሮ፣ በጸናጽልና በቃጭል ባለ ኀይላቸው
ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ያሸበሽቡ ነበር።

5፥18 ኢሱ15፥8፤ 17፥15
5፥19 መሳ18፥5፤ 1ሳሙ23፥2
5፥20 ዘፍ38፥29
5፥21 ዘዳ7፥5፤ኢሳ 46፥2
5፥24 ዘፀ14፥24፤ መሳ4፥14
5፥25 ኢሱ10፥33፤ 2ሳሙ8፥12፤21፥15፤ኢሳ28፥21
6፥2 ዘፍ3፥24፤ዘፀ 25፥22፤ዘሌ24፥16፤ ዘዳ28፥10፤ኢሱ 15፥9፤1ሳሙ4፥4፤ 7፥1፤መዝ99፥1፤ 132፥14፤ኢሳ63፥14
6፥3 ቀኍ7፤ዘኁ 7፥4-9፤1ሳሙ6፥7፤ 2ሳሙ7፥1
6፥5 ዘፀ15፥20፤ ዕዝ3፥10፤ነህ12፥27፤ መዝ150፥5
6፥6 ዘኁ4፥15፡ 19-20
6፥7 ዘፀ19፥22፤ 1ሳሙ5፥6፤6፥19፤25፥ 38፤1ዜና15፥13-15
6፥8 ዘፍ38፥29፤ መዝ7፥11
6፥9 1ሳሙ6፥20
6፥10 1ዜና15፥18፤ 26፥4-5
6፥11 ዘፍ30፥27፤ 39፥5
6፥12 1ነገ8፥1
6፥13 1ነገ8፥5፡62፤ ዕዝ6፥17
6፥14 ዘፀ15፥20፤ 19፥6፤1ሳሙ2፥18
6፥15 ኢሱ6፥5፤ መዝ47፥5፤98፥6
6፥16 1ሳሙ18፥27 ፤2ሳሙ5፥7
6፥17 ዘሌ1፥1-17፤ 1ነገ8፥6፡62-64፤ 1ዜና15፥1፤2ዜና1፥4

6ወደ ናኮን ዐውድማ ሲደርሱም በሬዎቹ
ስለ ተደናቀፉ፣ ዖዛ እጁን ዘርግቶ የእስራ
ኤልን ታቦት ያዘ። 7ዖዛ በድፍረት ይህን
ስላደረገ፣ የእግዚአብሔር ቍጣ በላዩ ላይ
ነደደ፤ ስለዚህም እግዚአብሔር ቀሠፈው፤
እርሱም በእግዚአብሔር ታቦት አጠገብ እዚ
ያው ሞተ።

8የእግዚአብሔር ቍጣ ዖዛን ስለ ሰበረው፣
ዳዊት ተከፋ፤ አዘነም፤ ያም ቦታ እስከ
ዛሬ ድረስ ፔሬዝ ዖዛ[ተ] ተብሎ ይጠራል።

9ዳዊት በዚያን ቀን እግዚአብሔርን ስለ
ፈራ “የእግዚአብሔር ታቦት እንዴት ወደ
እኔ ይመጣል?” አለ። 10ስለዚህ ዳዊት የእ
ግዚአብሔር ታቦት አብሮት እንዲሆን ወደ
ዳዊት ከተማ ይዞት ለመሄድ አልፈለገም፤
በዚህ ፈንታ አቅጣጫ ለውጦ የጌት ሰው
ወደ ሆነው ወደ አቢዳራ ቤት ወሰደው።
11የእግዚአብሔርም ታቦት የጌት ሰው በሆነው
በአቢዳራ ቤት ሦስት ወር ተቀመጠ፤ እግዚ
አብሔርም አቢዳራንና ቤተ ሰውን ሁሉ ባረከ።

12በዚህ ጊዜ፣ “በእግዚአብሔር ታቦት ምክንያት
የአቢዳራን ቤተ ሰውና ያለውን ሁሉ እግዚአብሔር
ባረከለት” ብለው ለዳዊት ነገሩት። ስለዚህ ዳዊት
ወደዚያው ወርዶ፣ የእግዚአብሔርን ታቦት ከአ
ቢዳራ ቤት ወደ ዳዊት ከተማ በታላቅ ደስታ
አመጣው። 13እነዚያ የእግዚአብሔርን ታቦት
ተሸክመው የነበሩት ሰዎች ስድስት ርምጃ
በሄዱ ቍጥር፣ አንድ በሬና አንድ የሰባ ጥጃ
ይሠዋ ነበር። 14ዳዊትም የበፍታ ኤፉድ
በወገቡ ታጥቆ በሙሉ ኀይሉ በእግዚአብሔር
ፊት ይጨፍር ነበር። 15እንዲህ ባለ ሁኔታም
ዳዊ ትና መላው የእስራኤል ቤት ሆ!
እያሉና ቀንደ መለከቱን እየነፉ የእግዚአብሔርን
ታቦት ወደ ላይ አመጡ።

16የእግዚአብሔር ታቦት ወደ ዳዊት ከተማ
ሲገባ፣ የሳኦል ልጅ ሜልኮል በመስኮት ሆና
ትመለከት ነበር፤ ንጉሥ ዳዊት በእግዚአብሔር
ፊት ሲዘልና ሲያሸበሽብ ባየችው ጊዜ በልቧ
ናቀችው።

17ከዚያም የእግዚአብሔርን ታቦት አምጥተው፣
ዳዊት በተከለለት ድንኳን ውስጥ አግብተው
በተዘጋጀለት ስፍራ አኖሩት፤ ዳዊትም የሚ
ቃጠል መሥዋዕትና የኅብረት መሥዋዕት[ቸ]

[ሰ]20 በአልፐራሲም ማለት የሰባበረ ጌታ ማለት ነው።
[ሸ]25 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ከዚህ ጋር ይስማማል (1ዜና 14፥16 ይመ)፤ ዕብራይስጡ ግን፣ ጊባ ይላል።
[ቀ]2 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ግን፣ ስም የሚለውን አይጨምርም።
[በ]4 የሙት ባሕር ጥቅልና አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ የማሶሬቲኩ ቅጅ ግን፣ ኰረብታው ላይ ካለው ከአቢናዳብ ቤት ከእግዚአብሔር ታቦት ጋር አመጡት ይላል።
[ተ]8 ፔሬዝ ዖዛ ማለት ዖዛን ማሰባበር ማለት ነው
[ቸ]17 በትውፊት የሰላም መሥዋዕት ይባላል።

በእግዚአብሔር ፊት አቀረበ። [18]ዳዊት የሚ
ቃጠለውን መሥዋዕትና የኅብረቱን መሥዋዕት
ካቀረበ በኋላ ሕዝቡን በሰራዊት ጌታ በእግዚ
አብሔር ስም ባረከ። [19]የእስራኤል ወገን ለሆ
ነው ለሕዝቡ ሁሉ፣ ለወንዱም ለሴቱም ለእያን
ዳንዱ ሰው አንዳንድ እንጀራ፣ አንዳንድ ሙዳ
ሥጋና አንዳንድ የዘቢብ ጥፍጥፍ ሰጠ፤ ከዚህ
በኋላ ሁሉም ወደየቤቱ ሄደ።
[20]ዳዊት ቤተ ሰውን ለመመረቅ ወደ ቤቱ በተ
መለሰ ጊዜ፣ የሳኦል ልጅ ሜልኮል ልትቀበለው
ወጥታ፣ "ዛሬ የእስራኤል ንጉሥ በመኳንንቱ ገረ
ዶች ፊት እንደ አንድ ተራ ሰው ራቍቱን መታ
የቱ ክብሩ ሆኖ ነው!" አለችው።
[21]ዳዊትም እንዲህ አላት፤ "አዎን ከአባትሽና
በቤቱ ካሉት ሁሉ አስበልጦ በእግዚአብሔር
ሕዝብ በእስራኤል ላይ ገዥ አድርጎ በመረጠኝ
በእግዚአብሔር ፊት አሸብሽቤአለሁ፤ አሁንም
አሸበሽባለሁ። [22]እንዲያውም ከዚህ ይልቅ
ራሴን በፊቱ ዝቅ አደርጋለሁ፤ ከዚህም የባሰ
የተናቅሁ እሆናለሁ፤ ነገር ግን በጠቀስሻቸው
ገረዶች ፊት እከብራለሁ።"
[23]የሳኦልም ልጅ ሜልኮል እስከሞተችበት
ጊዜ ድረስ ልጅ አልወለደችም ነበር።

## እግዚአብሔር ለዳዊት የሰጠው ተስፋ

7፥1-17 ተጓ ምብ - 1ዜና 17፥1-15

7 ንጉሡ በቤተ መንግሥቱ ተደላድሎ ከተ
ቀመጠና እግዚአብሔርም በዙሪያው
ካሉት ጠላቶቹ ሁሉ ካሳረፈው በኋላ፣ [2]ነቢ
ዩን ናታንን፣ "እነሆ፤ እኔ ከዝግባ በተሠራ
ቤተ መንግሥት ውስጥ እኖራለሁ፤ የእግዚአብሔር
ታቦት ግን በድንኳን ውስጥ ይኖራል" አለው።
[3]ናታንም፣ "እግዚአብሔር ካንተ ጋር ስለ
ሆነ፣ ያሰብኸውን ሁሉ አድርግ" አለው።
[4]በዚያች ሌሊት የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ
ሲል ወደ ናታን መጣ፤

[5]"ሂድና ባሪያዬን ዳዊትን፣ 'እግዚአብሐ
ር እንዲህ ይላል፤ የምኖርበትን ቤት
የምትሠራልኝ አንተ አይደለህም፤ [6]እስራኤላ
ውያንን ከግብፅ ምድር ካወጣሁበት ቀን
አንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ ድንኳንን ማደ
ሪያዬ አድርጌ ከቦታ ወደ ቦታ ተጓዝሁ
እንጂ በቤት ውስጥ አልተቀመጥሁም።
[7]ከእስራኤላውያን ሁሉ ጋር በተጓዝሁ
በት ስፍራ ሁሉ ሕዝቤን እስራኤልን እን
ዲጠብቁ ካዘዝኋቸው መሪዎቻቸው አን
ዱን፣ "ከዝግባ ዕንጨት ለምን ቤት አልሠ
ራህልኝም?" ያልሁት አለን?
[8]"አሁንም ባሪያዬን ዳዊትን እንዲህ
በለው፤ 'የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤ በሕዝቤ በእስራኤል
ላይ ገዥ እንድትሆን ከሜዳ አነሣሁህ፤
ከበግ ጥበቃም ወሰድሁህ፤ [9]በሄድህበት
ሁሉ እኔ ከአንተ ጋር ነበርሁ፤ ጠላቶ
ችህንም ሁሉ ከፊትህ አጠፋሁልህ፤
አሁንም ስማቸው በምድር ላይ ከገነ
ነው እጅግ ታላላቅ ሰዎች እንደ አንዱ
ስምህን ገናና አደርገዋለሁ፤ [10]የራሱ
የሆነ መኖሪያ እንዲኖረውና ከእንግዲህ
ወዲያ እንዳይናወጥ፣ ለሕዝቤ ለእስራኤል
ቦታ እሰጠዋለሁ፤ አጸናዋለሁም። ከዚህ
በፊት እንደሆነውም ከእንግዲህ ወዲህ
ክፉ ሕዝብ አይጨቍነውም፤ [11]ለሕዝቤ
ለእስራኤልም መሪዎች[a] ከሾምሁለት ጊዜ
አንሥቶ እን ዳደረጉበት ሁሉ ከእንግዲህ
አያደርጉብ ትም፤ እንዲሁም ከጠላቶችህ
ሁሉ እጠብ ቅሃለሁ። " 'እግዚአብሔር ራ
ሱ ቤት እን ደሚሠራልህ ይነግርሃል፤ [12]ዕ
ድሜህን ጨር ሰህ ከአባቶችህ ጋር
በምታንቀላፋበት ጊዜ፣ በእግርህ እንዲተካ
ከአብራክህ የተከፈለ ዘር አስነሣልሃለሁ፤
መንግሥቱንም አጸና ለሁ። [13]ለስሜ ቤት
የሚሠራ እርሱ ነው፤ እኔም
የመንግሥቱን ዙፋን ለዘላለም አ
ጸናለሁ። [14]አባት እሆነዋለሁ፤ እርሱም
ልጄ ይሆናል። በደል ቢፈጽም ግን ሰዎች
በሚቀጡበት በትር እቀጣዋለሁ፤ የሰው
ልጆችም በዐለንጋ እንደሚገረፉ እገርፈ
ዋለሁ። [15]ምሕረቴን ከአንተ በፊት ካስወገ
ድሁት ከሳኦል እንዳራቅሁ ሁሉ ከእርሱ
አላርቅም። [16]ቤትህና መንግሥትህ በፊቴ[b]
ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል፤ ዙፋንህም እን
ደዚሁ ለዘላለም የጸና ይሆናል።' "
[17]ናታንም የዚህን የጠቅላላውን ራእይ ቃል
በሙሉ፣ ለዳዊት ነገረው።

## የዳዊት ጸሎት

7፥18-29 ተጓ ምብ - 1ዜና 17፥16-27

[18]ከዚያም ንጉሥ ዳዊት ገባ፤ በእግዚአብሔር
ፊት ተቀምጦ እንዲህ አለ፤
"ልዑል እግዚአብሔር ሆይ፤ እስከዚህ
ያደረስኸኝ እኔ ማን ነኝ? ቤቴስ
ምንድን ነው? [19]ልዑል እግዚአብሔር
ሆይ፤ ይህ በፊትህ ጥቂት ሆኖ ሳለ፤
አንተ ግን ስለ ወደፊቱ የባሪያህ ቤት
ተናገርህ፤ ልዑል እግዚአብሔር ሆይ፤
ከሰው ጋር የምታደርገው ግንኙነት ለካ
እንዲህ ነው?

6፥18 ዘፀ39፥43፤ 1ነገ8፥22
6፥19 ዘዳ26፥13፤ ነህ8፥10፤ሆሴ3፥1
6፥20 1ሳሙ19፥24
6፥21 1ሳሙ13፥14፤15፥28፤2ሳሙ5፥2፤7፥8፤1ዜና5፥2፤17፥7፤ሚክ5፥2
7፥1 ቀኍ11፤2ሳሙ6፥3፤1ዜና22፥18
7፥2 ዘፀ26፥1፤2ሳሙ5፥11፤12፥1፤1ነገ1፥8፡22፤3፥1፤7፥1፡2፡7፤9፥1፤1ዜና29፥29፤2ዜና8፥1፤9፥29፤መዝ132፥3፤ኤር22፥14፤ሐጌ1፥4፤ሐሥ7፥45-46
7፥3 1ሳሙ10፥7፤መዝ132፥1-5
7፥5 1ነገ5፥3-5፤8፥19፤1ዜና22፥8፤28፥3
7፥6 ዘፀ40፥18፡34፤ኢሱ18፥1፤1ነገ8፥16፤ሐሥ7፥45
7፥7 ዘሌ26፥11-12፤ዘዳ23፥14፤2ሳሙ5፥2፤1ነገ8፥27፤ኢሳ66፥1
7፥8 1ሳሙ2፥7-8፤9፥16፤16፥1፡11፤2ሳሙ6፥21፤1ዜና21፥17፤መዝ74፥1፤78፥70-72፤አሞ7፥15፤2ቆሮ6፥18
7፥9 ዘፀ11፥3፤1ሳሙ18፥14፤2ሳሙ5፥10፤መዝ18፥37-42
7፥10 ዘፀ15፥17፤2ነገ21፥8፤2ዜና33፥8፤መዝ89፥22-23፤147፥14፤ኢሳ5፥1-7፤54፥14፤60፥18
7፥11 ቀኍ1፤ዘፀ1፥21፤መሳ2፥16፤1ሳሙ12፥9-11፤25፥28፤1ነገ2፥24፤መዝ89፥35-37፤ኢሳ7፥2፤ማቴ1፥1፤ሉቃ1፥32-33፤ሐሥ13፥22-23፤2ጢሞ2፥8
7፥12 ዘፍ15፥15፤1ነገ2፥1፤8፥20፤2ዜና23፥3፤መዝ132፥11-12፤ኤር30፥21፤33፥15፤ሐሥ13፥36
7፥13 ቀኍ16፤ዘፍ16፥11፤2ሳሙ22፥51፤1ነገ2፥4፡45፤5፥5፤6፥12፤8፥19፡29፤2ነገ21፥4፡7፤1ዜና22፥10፤28፥6፤2ዜና6፥16፤7፥18፤13፥5፤21፥7፤መዝ89፥3-4፡29፡35-37ምሳ25፥5፤ኢሳ9፥7፤16፥5፤ኤር17፥25፤33፥17፡21፤ዳን7፥27
7፥14 ዘዳ8፥5፤1ነገ11፥34፤1ዜና22፥10፤መዝ2፥7፤89፥26፡30-33፤ምሳ13፥24፤ኤር3፥19፤ማቴ3፥17፤
ዮሐ1፥49፤2ቆሮ6፥18፤ዕብ1፥5፤12፥7፤ራእ21፥7 7፥15 ቀኍ25፤1ሳሙ13፥13፤15፥28፤16፥14፤1ነገ2፥4፤6፥12፤8፥25፤9፥5፤11፥13፡32፤2ነገ19፥34፤2ዜና6፥16፤7፥18፤21፥7፤መዝ89፥24፡33፤ኤር33፥17 7፥16 ቀኍ13፤መዝ 9፥7፤89፥36-37፤93፥2፤103፥19፤ሉቃ1፥33፤9፥16፤ዘዳ12፥5፤ 7፥18 ዘፀ3፥11 7፥19 ኢሳ55፥8-9

[a]11 በትውፊት፣ መሳፍንት ይባላል
[b]16 አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆችና የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ በፊትህ ይላሉ

20"ዳዊት ከዚህ በላይ ምን ሊልህ ይች
ላል? ልዑል *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ባሪያ
ህን አንተ ታውቀዋለህና! 21ስለ ቃልህና
እንደ ልብህ ሐሳብ ይህን ታላቅ ነገር
አድርገሃል፤ ባሪያህም እንዲያውቀው ገል
ጸህለታል።
22ልዑል *እግዚአብሔር* ሆይ፤ እንዴት
ታላቅ ነህ! ከቶ የሚመስልህ ማንም የለም፤
በጆሮአችን እንደሰማነው ሁሉ፣ ከአንተ
በቀር አምላክ የለም።
23ለራሱ ሕዝብ ይሆን ዘንድ ሊታደገው፣
*እግዚአብሔር* በፊቱ እንደሄደለት ሕዝብ፣
ለራሱም ስም ያደርግ ዘንድ አሕዛብንና አ
ማ ልክቶቻቸውን ከፊቱ አሳዶ ታላቅና
አስፈሪ ታምራት እንዳደረገለትና ከግብፅም
እንደ ተቤዠው እንደ ሕዝብህ እንደ እስራ
ኤል ያለ በምድር ላይ ማን አለ? 24ሕ
ዝብህን እስራኤልን ለዘላለሙ ያንተው
የራስህ ሕዝብ አድርገህ አጽንተኸዋል፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተም አምላክ
ሆነኸዋል።
25"አሁንም *እግዚአብሔር* አምላክ
ሆይ፤ ለባሪያህና ለቤቱ የሰጠኸውን ተስፋ
ለዘላ ለም ጠብቅለት፤ እንደተናገርኸ
ውም ፈጽም፤ 26ስለዚህ ስምህ ለዘላለም
ታላቅ ይሆናል፤ ሰዎችም፣ 'የሰራዊት
ጌታ *እግ ዚአብሔር* የእስራኤል አምላክ
ነው!' ይላሉ። የባሪያህ የዳዊትም ቤት
በፊትህ የጸና ይሆናል።
27"አቤቱ የእስራኤል አምላክ የሰራዊት
ጌታ *እግዚአብሔር* ሆይ፤ 'እኔ ለአንተ ቤት
እሠራልሃለሁ' ብለህ ይህን ለባሪያህ ገል
ጸህለታል። ስለዚህ ባሪያህ ይህችን ጸሎት
ወደ አንተ ለማቅረብ በልቡ ደፈረ። 28ልዑል
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ አምላክ ነህ፤ ቃል
ህም የታመነ ነው፤ ይህንንም መልካም ነገር
ለማድረግ ለባሪያህ ተስፋ ሰጥተኸዋል፤
29በፊትህ ለዘላለም ጸንቶ እንዲኖር፣ አሁ
ንም የባሪያህን ቤት እባክህ ባርክ። ልዑል
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ይህን አንተው ራስህ
ተናግረሃል፤ በበረከትህም የባሪያህ ቤት
ለዘላለም ይባረካል።

## ዳዊት የተቀዳጃቸው ድሎች

8፥1-14 ተጓ ምብ - 1ዜና 18፥1-13

8 ከዚህ በኋላ ዳዊት ፍልስጥኤማውያንን
ድል አደረጋቸው፤ በቍጥጥሩም ሥር
አዋላቸው፣ ሜቴግ አማ የተባለችውንም
ከተማ ከፍልስጥኤማውያን ቍጥጥር ነጻ አደ
ረጋት።
2እንዲሁም ዳዊት ሞዓባውያንን ድል አደረገ፤
በመሬት ላይ አጋድሞ በገመድ ለካቸው፤ በገ
መድ ከተለኩትም ሁለት እጅ ሲገድል፣ አንድ

**7፥20** 1ሳሙ16፥7፤ ኢሳ38፥15፤ዮሐ21፥17
**7፥22** ዘፀ8፥10፤ 9፥14፤10፥2፤20፥4፤ ዘዳ3፥24፤መሳ6፥13፤ መዝ44፥1፤48፥1፤ 77፥13፤86፥10፤ ኤር10፥6
**7፥23** ዘኍ6፥27፤ ዘዳ4፥32-38፤7፥7-8፤ 9፥26፤10፥21፤33፥29፤ 1ሳሙ12፥22
**7፥24** ዘፀ6፥6-7፤ ዘዳ26፥18፤መዝ 48፥14
**7፥25** ቍ15፤ዘኍ 23፥19፤2ዜና1፥9
**7፥26** ዘፀ6፥3፤ነህ 9፥5፤1ሳሙ25፥28፤ መዝ72፥19፤96፥8፤ ማቴ6፥9
**7፥28** ዘፀ34፥6፤ ዮሐ17፥17
**7፥29** ዘኍ6፥23-27
**8፥1** መዝ60፥8፤ 87፥4፤108፥9፤ ዕብ11፥32-33
**8፥2** ዘፍ19፥37፤ ዘኍ21፥29፤መሳ 3፥15፤ኢሳ45፥14
**8፥3** ዘፍ2፥14፤1ሳሙ 14፥47፤2ሳሙ10፥ 16፥19፤1ነገ11፥23
**8፥4** ዘፍ49፥6፤ኢሱ 11፥9
**8፥5** ዘፍ14፥15፤ 2ሳሙ10፥6፤1ነገ11፥ 24፤2ነገ8፥7፤14፥28
**8፥6** 2ሳሙ3፥18፤ 10፥19፤1ነገ20፥34
**8፥7** 1ነገ10፥16፤ 14፥26፤2ነገ11፥10
**8፥8** ሕዝ47፥16
**8፥9** 1ነገ8፥65፤ 2ነገ14፥28፤2ዜና8፥ 4፤ሉቃ14፥31-32
**8፥11** ቍ12፤1ነገ 7፥51፤15፥15፤1ዜና 26፥26፤2ዜና5፥1
**8፥12** ቍ2፤ዘኍ24፥ 18፥20፤1ሳሙ27፥8፤ 2ሳሙ5፥25፤10፥14
**8፥13** 2ሳሙ7፥9፤ 2ነገ14፥7፤1ዜና18፥ 12፤መዝ60 ርዕስ
**8፥14** ዘፍ27፥29፡ 37-40፤ዘኍ24፥17- 18፤2ሳሙ22፥44፤ መዝ108፥9፤144፥10፤ ኢሳ34፥5፤63፥1፤ ኤር49፥7፤ሕዝ25፥12

እጅ ግን በሕይወት ይተው ነበር። ስለዚህ ሞዓ
ባውያን የዳዊት ተገዦች ሆኑ፤ ገበሩለትም።
3ከዚህም በቀር ዳዊት በኤፍራጥስ ወንዝ
አጠገብ ያለውን ግዛት መልሶ ለመያዝ በሄደ
ጊዜ፣ የሱባን ንጉሥ የረአብን ልጅ አድርአዛርን
ወጋው። 4ዳዊትም አንድ ሺህ ሠረገሎች፣ ሰባት
ሺህ ፈረሰኞችና[ኘ] ሃያ ሺህ እግረኞች ማረከበት።
ቍጥራቸው መቶ የሆነ የሠረገላ ፈረሶች ብቻ
ሲቀሩ ሌሎቹን በሙሉ ቋንጃቸውን ቈረጠ።
5የደማስቆዎቹ ሶርያውያን የሱባን ንጉሥ
አድርአዛርን ለመርዳት በመጡ ጊዜ ዳዊት
ሃያ ሁለት ሺህ ሰው ገደለባቸው። 6ከዚ
ያም የደማስቆ ክፍል በሆነው የሶርያውያን
ግዛት የጦር ሰፈሮችን አቋቋመ። ሶርያ
ውያን ተገዙለት፤ ገበሩለትም። *እግዚአብሔ
ር*ም ዳዊት በሄደበት ሁሉ ድልን ሰጠው።
7ዳዊት የአድርአዛር ሹማምንት ያነገቧ
ቸውን የወርቅ ጋሻዎች ወስዶ ወደ ኢየሩ
ሳሌም አመጣቸው። 8ንጉሡ ዳዊት ቤጣ
ህና[ኣ] ቤሮታይ ከተባሉ ከአድርአዛር ከተሞ
ችም እጅግ ብዙ ናስ አጋዘ።
9የሐማት ንጉሥ ቶዑ ዳዊት መላውን የአድ
ርአዛርን ሰራዊት ማሸነፉን በሰማ ጊዜ፣ 10ቶዑ
ከአድርአዛር ጋር ሁልጊዜ ይዋጋ ስለ ነበር፣
ሰላ ምታና በአድርአዛር ላይ ሰለ ተቀዳጀውም
ድል የደስታ መግለጫ እንዲያቀርብለት፣ ል
ጁን ዮራምን ወደ ንጉሥ ዳዊት ላከው፤
እርሱም የብር፣ የወርቅና የናስ ዕቃ ይዞ መጣ።
11ንጉሥ ዳዊትም፣ ቀድሞ ካስገበራቸው መን
ግሥታት ሁሉ በገባለት ብርና ወርቅ እንዳደ
ረገው እነዚህንም ዕቃዎች ለ*እግዚአብሔር* ቀደ
ሳቸው። 12የገበሩትም መንግሥታት ኤዶ
ምና[ከ] ሞዓብ፣ አሞናውያን፣ ፍልስጥኤማ
ውያንና አማሌቃውያን ነበሩ። እንዲሁም
ከሱባ ንጉሥ ከረአብ ልጅ ከአድርአዛር የወ
ሰደውን ምርኮ ለ*እግዚአብሔር* ቀደሰ።
13ዳዊት የጨው ሸለቆ በተባለው ስፍራ
ዐሥራ ስምንት ሺህ ኤዶማውያንን[ኸ] ገድሎ
ከተመለሰ በኋላ ስሙ ገነነ።
14በመላው ኤዶም የጦር ሰፈሮችን
አቋቋመ፤ ኤዶማውያን ሁሉ ለዳዊት ተገዙ፤
*እግዚአብሔ ር*ም ዳዊት በሄደበት ስፍራ ሁሉ
ድልን ሰጠው።

[ኘ]4 የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም (እንዲሁም የሙት ባሕር ጥቅልና 1ዜና 18፥4 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ የማሶሬቱ ቅጅ ግን፣ *ሰባት መቶ ሠረገለኞቹን* ይላል።
[ኣ]8 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃ ናት ትርጕሞች (እንዲሁም 1ዜና 18፥8 ይመ)፤ አብዛኞቹ የዕ ብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *ቴባ* ይላሉ።
[ከ]12 አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ የሰብዓ ሊቃናት ትር ጕምና የሱርስቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማል (እንዲሁም 1ዜና 18፥11 ይመ)፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *አራም* ይላሉ።
[ኸ]13 ጥቂት የዕብራይስጥ ቅጆች፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕምና የሱርስቱ ቅጅ (እንዲሁም 1ዜና 18፥11 ይመ)፤ ከዚህ ጋር ይስ ማማል አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *አራም* ይላሉ።

## የዳዊት ሹማምት
8፥15-18 ተጓ ምብ - 1ዜና 18፥14-17

[15]ዳዊት በመላው እስራኤል ላይ ነገሠ፤
ለሕዝቡም ሁሉ ፍትሕና ርትዕ አሰፈነላቸው።
[16]የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ የሰራዊቱ አለቃ ሲሆን፣
የአሒሉድ ልጅ ኢዮሣፍጥም ታሪክ ጸሓፊ
ነበረ። [17]እንዲሁም የአኪጦብ ልጅ ሳዶቅና
የአብያታር ልጅ አቢሜሌክ ካህናት ሲሆኑ፣
ሠራያ ጸሓፊ ነበረ፤ [18]የዮዳሔ ልጅ በናያስ
የከሪታውያንና የፈሊታውያን አለቃ ሲሆን፣
የዳዊት ወንዶች ልጆች ደግሞ የቤተ መንግ
ሥት አማካሪዎች[ሠ] ነበሩ።

## ዳዊትና ሜምፊቦስቴ

9 ዳዊትም፣ "ስለ ዮናታን ስል ቸርነት
አደርግለት ዘንድ ከሳኦል ቤት የቀረ
ሰው ይኖር ይሆን?" በማለት ጠየቀ።
[2]በዚያን ጊዜ ከሳኦል ቤት ሲባ የሚባል
አንድ አገልጋይ ስለ ነበር፣ ወደ ዳዊት እንዲ
ሄድ ነገሩት። ንጉሡም፣ "ሲባ የምትባለው
አንተ ነህን?" ሲል ጠየቀው።
እርሱም፣ "አዎን እኔ አገልጋይህ ነኝ"
አለ።
[3]ንጉሡም፣ "*የእግዚአብሔርን* ቸርነት እን
ዳደርግለት ከሳኦል ቤት የቀረ ሰው የለምን?"
ሲል ጠየቀው።
ሲባም ለንጉሡ፣ "እግሮቹ ሽባ የሆኑ አንድ
የዮናታን ልጅ አለ" ብሎ መለሰለት።
[4]ንጉሡም፣ "የት ነው ያለው?" ብሎ ጠየቀ።
ሲባም፣ "ሎዶባር በተባለ ስፍራ በዓሚ
ኤል ልጅ በማኪር ቤት ይገኛል" ብሎ መለ
ሰለት።
[5]ስለዚህም ንጉሥ ዳዊት፣ ሜምፊቦስቴን ከዓ
ሚኤል ከማኪር ቤት ከሎደባር ልኮ አስ
መጣው።
[6]የሳኦል ልጅ፣ የዮናታን ልጅ ሜምፊቦስቴ
ወደ ዳዊት በመጣ ጊዜ፣ አክብሮቱን ለመ
ግለጥ ለጥ ብሎ እጅ ነሣ።
ዳዊትም፣ "ሜምፊቦስቴ!" ብሎ ጠራው።
እርሱም፣ "እነሆ፤ አገልጋይህ" አለ።
[7]ዳዊትም፣ "አትፍራ፤ ስለ አባትህ ስለ ዮና
ታን ስል በእርግጥ ቸርነት አደርግልሃለሁና።
የአባትህን የሳኦልን ምድር በሙሉ እመ
ልስልሃለሁ፤ ዘወትርም ከማዕዴ ትበላለህ"
አለው።
[8]ሜምፊቦስቴ ለጥ ብሎ እጅ ነሣና፣ "እንደ
ሞተ ውሻ ለምቈጠር ለእኔ ይህን ያህል
የምታደርግልኝ አገልጋይህ ኧረ ማን ነኝ?"
አለ።
[9]ከዚያም ንጉሡ የሳኦልን አገልጋይ ሲባን
ጠርቶ እንዲህ አለው፤ "የሳኦልና የቤተ ሰቡ
የሆነውን ሁሉ ለጌታህ የልጅ ልጅ ሰጥቼዋለሁ።

8፥15 ዘፍ18፥19፤ 1ነገ11፥38፤14፥8፤ 15፥11፤22፥43፤2ነገ 12፥2፤ኢዮ29፥14፤ መዝ5፥12፤119፥121 ፤ዕብ11፥33
8፥16 2ሳሙ2፥13፤ 20፥24፤1ነገ4፥3፤ ኢሳ36፥3፡22
8፥17 1ሳሙ2፥35፤ 2ሳሙ15፥24፡29፤ 4፥3፡4፤2ነገ12፥10፤19፥ 2፤22፥3፤1ዜና6፥8፡53፤ 16፥39፤24፥3፤27፥17፤ 2ዜና31፥10፤ኢሳ36፥3፤ኤር36፥12፤ሕዝ40፥46፤43፥19፤44፥15፤48፥11፤ማር2፥26 20፥25፤1ነገ1፥8፤
8፥18 1ሳሙ30፥14፤ 2ሳሙ20፥23፤23፥20፤ 1ነገ1፥8፡38፤2፥25፡35፡ 46፤4፥4
9፥1 1ሳሙ20፥ 14-17፡42፤23፥18
9፥2 2ሳሙ16፥1-4 ፤19፥17፡26፡29
9፥3 ዘሌ21፥18፤ 1ዜና8፥34
9፥4 2ሳሙ17፥27- 29
9፥6 ዘፍ37፥7
9፥7 ቊ13፤1ሳሙ 20፥14-15፤2ሳሙ 19፥28፤21፥7፤1ነገ 2፥7፤2ነገ25፥29፤ ኤር52፥33
9፥8 2ሳሙ3፥8፤4፥4
9፥10 2ሳሙ16፥3
9፥11 ኢዮ36፥7፤ መዝ113፥8
9፥12 2ሳሙ4፥4
10፥2 1ሳሙ11፥1
10፥3 ዘኍ21፥32
10፥4 ዘሌ19፥27፤ ኢሳ7፥20፤15፥2፤ 20፥4፤50፥6፤52፥14፤ኤር48፥37፤ሕዝ5፥1
10፥6 ዘፍ34፥30፤ ዘኍ13፥21፤ዘዳ3፥14፤ መሳ11፥3-5፤1ሳሙ 14፥47፤2ሳሙ8፥5
10፥7 2ሳሙ2፥18

[10]አንተ፣ ልጆችህና አገልጋዮችህ የጌታችሁ
የልጅ ልጅ የሚበላውን እንዲያገኝ መሬቱን
እረሱለት፣ ምርቱንም አግቡለት። የጌታህ
የልጅ ልጅ ሜምፊቦስቴ ግን ምን ጊዜም
ከማእዴ ይበላል።" በዚያን ጊዜ ሲባ ዐሥራ
አምስት ወንዶች ልጆችና ሃያ አገልጋዮች
ነበሩት።
[11]ከዚያም ሲባ ንጉሡን፣ "ጌታዬ ንጉሥ፣
አገልጋዩን ያዘዘውን ሁሉ፣ አገልጋይህም ይፈ
ጽመዋል" አለው። ስለዚህም ሜምፊቦስቴ
ከንጉሡ ልጆች እንደ አንዱ ሆኖ ከዳዊት[ዐ]
ማእድ ይበላ ነበር።
[12]ሜምፊቦስቴ ሚካ የተባለ አንድ ትንሽ ልጅ
ነበረው፤ የሲባ ቤተ ሰዎች በሙሉ ሜምፊቦስ
ቴን ያገለግሉት ነበር። [13]ሜምፊቦስቴም ሁል
ጊዜ ከንጉሥ ማእድ ስለሚበላ ይኖር የነበ
ረው በኢየሩሳሌም ነው፤ ሁለት እግሮቹም ሽባ
ነበሩ።

## ዳዊት አሞናውያንን ድል አደረገ
10፥1-19 ተጓ ምብ - 1ዜና 19፥1-19

10 ከዚህ በኋላ የአሞናውያን ንጉሥ ሞተ፤
ልጁ ሐኖንም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።
[2]ዳዊትም፣ "አባቱ ቸርነትን እንዳደረገልኝ
ሁሉ፣ እኔም ለናዖስ ልጅ ለሐኖን
ወሮታውን ልክፈል" ሲል አሰበ። ስለዚህ
ስለ አባቱ ሞት የተሰማውን ሐዘን እንዲ
ገልጹለት ዳዊት መልክተኞችን ላከ።
የዳዊት ሰዎች ወደ አሞናውያን ምድር
በደረሱ ጊዜ፣ [3]የአሞናውያን መኳንንት ጌታ
ቸውን ሐኖንን፣ "ዳዊት የተሰማውን ሐዘን
ለመግለጽ ሰዎች መላኩ አባትህን ለማክበር
አስቦ ይመስልሃል? የላካቸው ሰዎች ከተማ
ዪቱን እንዲመረምሩ፣ እንዲሰልሉና እን
ዲያጠፏት አይደለምን?" አሉት። [4]ስለ
ዚህ ሐኖን የዳዊትን ሰዎች ይዞ፣ የእያን
ዳንዳቸውን ጢም በከፊል ላጨ፣ ልበሳቸ
ውንም ወገባቸው ድረስ አሳጥሮ በመቀሕረጥ
መልሶ ሰደዳቸው።
[5]ዳዊት ይህን በሰማ ጊዜ፣ ሰዎቹ እጅግ ዐፍ
ረው ስለ ነበር መልክተኞቹን ላከባቸው፤ ንጉ
ሡም፣ "ጢማችሁ እስኪያድግ በኢያሪኮ
ቈዩና ከዚያ በኋላ ተመለሱ" አላቸው።
[6]አሞናውያን፣ ዳዊት እንደ ጠላቻው ባወቁ
ጊዜ፣ ከቤትሮዖብና ከሱባ ሃያ ሺህ ሶርያውያን
እግረኛ ወታደሮችን እንዲሁም ንጉሥ መዓካን
ከአንድ ሺህ ሰዎቹ ጋር ደግሞም ከጦብ ዐሥ
ራ ሁለት ሺህ ሰዎች ቀጠሩ።
[7]ዳዊት ይህን ሲሰማ፣ ኢዮአብን ከመላው ተዋጊ
ሰራዊት ጋር ላከው። [8]አሞናውያን ወጥተው

[ሠ]18 ወይም *ካህናት* ተብሎ መተርጐም ይችላል።
[ዐ]11 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን፣ *ከእኔ* ይላል።

በከተማቸው መግቢያ በር ላይ ተሰለፉ፤
የሱባና የረአብ ሶርያውያን እንዲሁም የጦብና
የመዓካ ሰዎች ለብቻ ሜዳው ላይ ተሰለፉ።
9ኢዮአብም ከፊትና ከኋላው ጦር እንደ
ከበበው ባየ ጊዜ፣ በእስራኤል ጀግንነታቸው
ከታወቀው ጥቂቶቹን መርጦ በሶርያውያን
ግንባር አሰለፋቸው። 10የቀሩትን ሰዎች ደግሞ
በወንድሙ በአቢሳ ሥር መድቦ በአሞናው
ያን ግንባር አሰለፋቸው።
11ኢዮአብም እንዲህ አለ፤ ሶርያውያን የሚያይ
ሉብኝ ከሆን አንተ መጥተህ ትረዳኛለህ፤ አሞ
ናውያን የሚያይሉብህ ከሆነ እኔ መጥቼ
እረዳሃለሁ። 12እንግዲህ በርታ፤ ለሕዝባ
ችንና ለአምላካችን ከተሞች በጀግንነት
እን ዋጋ፤ እግዚአብሔርም በፊቱ መልካም
መስሎ የታየውን ያድርግ።
13ከዚያም ኢዮአብና አብሮት የነበረው ሰራ
ዊት ሶርያውያንን ለመውጋት ወደፊት ገሠገሠ፤
ሶርያውያንም ከፊቱ ሸሹ። 14ሶርያውያን መሸ
ሻቸውን አሞናውያን ባዩ ጊዜ፣ እነርሱም ከአቢ
ሳ ፊት ሸሽተው ወደ ከተማዪቱ ውስጥ ገቡ።
ስለዚህም ኢዮአብ አሞናውያንን መውጋቱን
አቁሞ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ።
15ሶርያውያን በእስራኤላውያን እንደ ተሸ
ነፉ ባዩ ጊዜ፣ እንደ ገና ተሰባሰቡ። 16አድ
ርአዛር መልክተኞችን ሰዶ ከወንዙ[″] ማዶ
ያሉትን ሶርያውያን አስመጣ፤ እነርሱም በአ
ድርአዛር ሰራዊት አዛዥ በሶባክ መሪነት
ወደ ኤላም ሄዱ።
17ዳዊት ይህን በሰማ ጊዜ፣ መላውን
እስራኤልን ሰበሰበ፤ ከዚያም ዮርዳኖስን
ተሻግሮ ወደ ዔላም ሄደ። ሶርያውያንም
ለጦርነት ተሰልፈው ዳዊትን በግንባር ገጠ
ሙት፤ 18ይሁን እንጂ ከእስራኤል ፊት ሸሹ፤
ዳዊትም ሰባት መቶ ሠረገለኞችንና አርባ ሺ
ህ እግረኛ ወታ ደሮች[‴] ገደለባቸው። እንዲ
ሁም የሰራዊታ ቸውን አዛዥ ሶባክን
አቍስሎት ስለ ነበር፣ እዚያው ሞተ።
19በአድርአዛር ሥር የነበሩት ነገሥታት
ሁሉ በእስራኤል መሸነፋቸውን ባዩ ጊዜ
ከእስራኤላውያን ጋር ሰላም መሠ ረቱ፤
ተገዙላቸውም።
ስለዚህም ሶርያውያን ከዚያ በኋላ አሞ
ናውያንን መርዳት ፈሩ።

## ዳዊትና ቤርሳቤህ

11 ነገሥታት ለጦርነት በሚወጡበት፣
በጸደይ ወራት ዳዊት ኢዮአብን
ከንጉሡ ሰዎችና ከመላው የእስራኤል ሰራ
ዊት ጋር አዘመተው፤ እነርሱም አሞናው
ያንን አጠፉ፤ ረባት የተባለችውንም ከተማ
ከበቡ፤ በዚህ ጊዜ ግን ዳዊት በኢየሩሳ
ሌም ቀርቶ ነበር።
2አንድ ቀን ማታ፣ ዳዊት ከዐልጋው
ተነ ሥቶ በቤተ መንግሥቱ ሰገነት ወዲያና
ወዲህ ይመላለስ ነበር፤ ከሰገነቱ ላይ
እንዳለም፣ አን ዲት ሴት ገላዋን ስትታጠብ
አየ፤ ሴቲቱም እጅግ በጣም ውብ ነበረች።
3ዳዊትም ሰው ልኮ ስለ ሴቲቱ አጠያየቀ።
ሰውየውም፣ "ይህች የኤልያብ ልጅ፣
የኬጢያዊው የኦ ርዮን ሚስት ቤርሳቤህ
አይደለችምን?" አለ። 4ከዚያም ዳዊት
መልእክተኞች ልኮ አስመ ጣት፤ እርሱ
ወዳለበት ገባች፤ አብሮአትም ተኛ። በዚህም
ጊዜ ወርሐዊ የመንጻት ጊዜ ዋን ፈጽማ
ነበር። ከዚያም ተመልሳ ወደ ቤቷ ሄደች።
5ሴቲቱ ፀነሰች፤ ለዳዊትም፣ "አርግዤለሁ"
ብላ ላከችበት።
6ስለዚህም ዳዊት ለኢዮአብ፣ "ኬጢያዊ
ውን ኦርዮንን ወደ እኔ ስደደው" ሲል
ላከበት፤ ኢዮአብም ወደ ዳዊት ላከው።
7ኦርዮን በመጣ ጊዜም፣ ዳዊት የኢዮአብ
ንና የሰራዊቱን ሁሉ ደኅንነት እንዲሁም
ጦርነቱ እንዴት እየተካሄደ እንዳለ ጠየ
ቀው። 8ከዚያም ዳዊት ኦርዮንን፣ "በል እን
ግዲህ ወደ ቤትህ ወርደህ እግርህን ታጠብ"
አለው። ኦርዮን ከቤተ መንግሥት ተሰና
ብቶ ወጣ፤ ንጉሡም ማለፊያ ምግብ አስ
ከትሎ ላከለት። 9ነገር ግን ኦርዮን ከጌታው
አገልጋዮች ሁሉ ጋር በቤተ መንግሥቱ
ቅጽር በር ተኛ እንጂ፣ ወደ ቤቱ አልወረ
ደም ነበር።
10ዳዊት፣ "ኦርዮ ወደ ቤቱ አልሄደም"
መባሉን ሲሰማ ኦርዮንን፣ "ከመንገድ ገና
አሁን መግባትህ አይደለምን? ወደ ቤትህ
ያልሄድኸው ለምንድን ነው?" ሲል ጠየ
ቀው።
11ኦርዮም ዳዊትን፣ "ታቦቱ፣ እስራኤ
ልና ይሁዳ በድንኳን ሆነው፣ ጌታዬ ኢዮ
አብና የጌታዬም ሰዎች አውላላ ሜዳ ላይ
ሰፍረው፣ ለመብላትና ለመጠጣት እንዲ
ሁም ከሚስቴ ጋር ለመተኛት እንዴት ወደ
ቤቴ እሄዳለሁ? እንዲህ ያለውን ነገር እንደ
ማላደርገው በነፍስህ እምላለሁ" አለው።
12ከዚያም ዳዊት፣ "እንግዲያውስ ዛሬ እዚህ
እደርና ነገ አሰናብትሃለሁ" አለው። ስለዚህ
ኦርዮ በዚያ ዕለትና በማግስቱ እዚያው ኢየሩ
ሳሌም ቈየ። 13በማግስቱም ዳዊት ራሱ ባለ
በት ግብዣ አድርጎለት በላ፤ ጠጣ፤ አሰከረ
ውም፤ ሲመሽም ኦርዮ በምንጣፉ ላይ ለመ
ተኛት የጌታው አሽከሮች ወዳሉበት ወጥቶ
ሄደ እንጂ ወደ ቤቱ አልወረደም።
14ሲነጋም ዳዊት ለኢዮአብ ደብዳቤ ጽፎ
በኦርዮን እጅ ላከለት፤ 15በደብዳቤውም ላይ፣

10፥10 1ሳሙ 26፥6
10፥12 ዘዳ 1፥21፤ 31፥6፤ መሳ 10፥15፤ ነህ 4፥14፤ ኤፌ 6፥10
10፥14 2ሳሙ 8፥12
10፥19 2ሳሙ 8፥6፤ 1ነገ 11፥25፤ 22፥31፤ 2ነገ 5፥1
11፥1 ዘዳ 3፥11፤ 2ሳሙ 2፥18፤ 1ነገ 20፥22፡26፤ 1ዜና 20፥1
11፥2 ዘዳ 22፥8፤ ኢሱ 2፥8፤ ማቴ 5፥28
11፥3 2ሳሙ 23፥34፡ 39፤ 1ዜና 3፥5
11፥4 ዘሌ 15፥25-30፤ 20፥10፤ ዘዳ 22፥22፤ መዝ 51 ርእስ፤ ያዕ 1፥14-15
11፥6 1ዜና 11፥41
11፥8 ዘፍ 18፥4
11፥11 1ሳሙ 21፥5፤ 2ሳሙ 7፥2
11፥14 1ነገ 21፥8

[″]16 የኤፍራጥስ ወንዝ ነው።
[‴]18 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም እንዲሁም (1ዜና 19፥18 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የዕብራይስጡ፣ *ፈረሰኞች* ይላል።

"ኦርዮን ውጊያው በተፋፋመበት ግንባር መድ
በው፤ ከዚያም ተወግቶ እንዲሞት ትታችሁት
ሽሹ" ብሎ ጻፈ።
16ስለዚህም ኢዮአብ ከተማዪቱን በከበ
ባት ጊዜ፣ እጅግ ጠንካራ ተከላካዮች እን
ዳሉበት በሚያውቀው ግንባር ኦርዮንን መደ
በው። 17የከተማዪቱም ሰዎች ወጥተው
ከኢዮአብ ጋር ጦርነት ገጠሙ፤ ከዳዊት ሰራ
ዊት ውስጥ ጥቂቶቹ ወደቁ፤ እንዲሁም ኬጢ
ያዊው ኦርዮንም ሞተ።
18ኢዮአብም በጦርነቱ የሆነውን ሁሉ ለዳ
ዊት ላከ። 19መልእክተኛውንም እንዲህ አለው፤
"ይህን የጦርነቱን ወሬ ለንጉሡ ከነገርኸው
በኋላ፣ 20ንጉሡ በቍጣ ቱግ ብሎ 'ለመዋ
ጋት ስትሉ ይህን ያህል ወደ ከተማዪቱ
የተጠጋችሁት ስለምንድን ነው? ከግንቡ
ቅጥር በላይ ፍላጻ እንደሚሰዱባችሁ አታ
ውቁም ኖሯል? 21የይሩቤሼትን ልጅ አቤሜ
ሌክን የገደለው ማነው? በቴቤስ ከግንብ ቅጥር
የወፍጮ መጅ ለቃበት የገደለችው አንዲት
ሴት አይደለችምን? ታዲያ እናንተስ ወደ ግንቡ
ቅጥር ይህን ያህል የተጠጋችሁት ለምንድን
ነው?' በማለት ቢጠይቅህ፣ አንተም መልሰህ፣
'አገልጋይህ ኬጢያዊው ኦርዮም ሞቶአል' ብለህ
ንገረው።"
22ስለዚህ መልእክተኛው ተነሥቶ ሄደ፤
እዚያ እንደ ደረሰም፣ ከኢዮአብ የተቀበለ
ውን መልእክት በሙሉ ለዳዊት ነገረው።
23መልእክተኛውም ለዳዊት እንዲህ አለው፤
"ሰዎቹ አየሉብን፤ እኛንም ለመውጋት ወጥ
ተው እስከ ሜዳው ድረስ መጡ፤ እኛ ግን
እስከ ከተማዪቱ ቅጽር መግቢያ ድረስ
አሳደን መለስናቸው። 24ከዚያም ባለ ፍላጻ
ዎቹ ከግንቡ ላይ ሆነው በእኛ በአገልጋ
ዮችህ ላይ ቀስት ስለ ለቀቁ፣ ከንጉሡ አገ
ልጋዮች ጥቂቶቹን ገደሉ፤ አገልጋይህ ኬጢ
ያዊው ኦርዮም ሞተ።"
25ዳዊትም፣ መልእክተኛውን፣ "እንግዲ
ህ እንዲህ ብለህ ይህን ለኢዮአብ ንገረው፤
'መቼም ሰይፍ አንድ ጊዜ ይህን፣ ሌላ ጊዜም
ሌላውን ትበላለችና በዚህ አትዘን'" አለው።
26የኦርዮ ሚስት ባሏ መሞቱን በሰማች ጊዜ
አዘነች፤ አለቀሰችለትም። 27የሐዘኑ ጊዜ ካበቃ
በኋላም፣ ዳዊት ልኮ ቤርሳቤህን ወደ ቤቱ
አስመጣት፤ ሚስቱ ሆነች፤ ወንድ ልጅም
ወለደችለት፤ ነገር ግን ዳዊት የሠራው ሥራ
*እግዚአብሔርን* አላስደሰተውም ነበር።

## ናታን ዳዊትን ገሠጸው

11፥1፤ 12፥29-31 ተጓ ምብ - 1ዜና 20፥1-3

12 *እግዚአብሔር* ናታንን ወደ ዳዊት
ላከው፤ እርሱም ወደ ዳዊት
መጥቶ እንዲህ አለው፤ "በአንድ ከተማ
የሚኖሩ ሁለት ሰዎች ነበሩ፤ ከእነርሱም
አንዱ ባለ ጠጋ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ድኻ
ነበረ። 2ባለ ጠጋው እጅግ ብዙ በጎችና
የቀንድ ከብቶች ነበሩት፤ 3ድኻው ግን ከገ
ዛት ከአንዲት ጠቦት በግ በስተቀር ሌላ
አልነበረውም። ተንከባከባት፤ አብራውም
ከልጆቹ ጋር አደገች፤ አብራው ትበላ፤
ከጽዋው ትጠጣ እንዲሁም በዕቅፉ ትተኛ
ነበር፤ ልክ እንደ ገዛ ልጁ ነበረች።
4ወደ ባለ ጠጋውም ቤት እንግዳ መጣ፤
ባለ ጠጋው ግን ከራሱ በጎች ወይም
ቀንድ ከብቶች ወስዶ ለመጣበት እንግዳ
ምግብ ማዘጋጀት አልፈለገም፤ ከዚህ ይልቅ
የድኻውን እንስት ጠቦት በግ ወስዶ ቤቱ
ለመጣው እንግዳ አዘጋጀው።
5ዳዊት በዚያ ሰው ላይ እጅግ ተቈጥቶ
ናታንን እንዲህ አለው፤ "ሕያው *እግዚአ
ብሔርን* ይህን ያደረገው ሰው ሞት ይገባ
ዋል! 6እንዲህ ያለውን ነገር በማድረጉና
ባለ ማዘኑም ስለ በጊቱ አራት ዕጥፍ መክ
ፈል አለበት።"
7ከዚያም ናታን፣ ዳዊትን እንዲህ አለው፤
"ያ ሰው አንተ ነህ፤ የእስራኤል አምላክ
*እግዚአብሔር* የሚለው ይህን ነው፤ በእስ
ራኤል ላይ ንጉሥ ትሆን ዘንድ ቀባሁህ፤
ከሳኦልም እጅ ታደግሁህ፤ 8የጌታህን ቤት
ሰጠሁህ፣ የጌታህንም ሚስቶች በብብትህ
አስታቀፍሁህ፤ የእስራኤልንና የይሁዳን ቤት
ሰጠሁህ፤ ይህም ሁሉ አንሶህ ቢሆን ኖሮ፤
ከዚህ በላይ ጨምሬ በሰጠሁህ ነበር።
9ታዲያ በፊቱ ክፉ ነገር በማድረግ፣ *የእግዚ
አብሔርን* ቃል ያቃለልኸው ስለምንድን
ነው? ኬጢያዊውን ኦርዮን በሰይፍ መታህ፤
ሚስት እንድትሆንህም ሚስቱን ወሰድ
ሃት፤ እርሱንም በአሞናውያን ሰይፍ ገደ
ልኸው። 10ስለዚህ ሰይፍ ለዘላለም ከቤትህ
አይርቅም፤ እኔን አቃለኸኛል፤ ሚስት እን
ድትሆንህም የኬጢያዊውን የኦርዮን ሚስት
ወስደሃታልና።'
11"*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ 'እነሆ ከራ
ስህ ቤት ክፉ ነገር አስነሣብሃለሁ፤ ዐይንህ
እያየም ሚስቶችህን ወስጄ ለአንተ ቅርብ
ለሆነ ሰው ለአንዱ እሰጣለሁ፤ እርሱም በቀን
ብርሃን ከሚስቶችህ ጋር ይተኛል። 12አንተ
ይህን በስውር አድርገኸዋል፤ እኔ ግን ይህ
ንኑ ነገር በቀን ብርሃን በእስራኤል ሁሉ
ፊት እገልጠዋለሁ።'"
13ከዚያም ዳዊት ለናታን፣ "*እግዚአብሔ
ርን* በጣም በድያለሁ" አለው።

11፥15 ቀኍ14-17፤
2ሳሙ12፥9፡12
11፥21 መሳ8፥31፤
9፥50-54
11፥27 ዘዳ34፥8፤
2ሳሙ12፥9፤
መዝ51፥4-5
12፥1 2ሳሙ7፥2፤
14፥4፤መዝ51ርእስ
12፥5 ዘፍ34፥7፤
1ሳሙ14፥39፤
1ነገ20፥40፤ሮሜ2፥1
12፥6 ዘፀ22፥1
12፥7 1ሳሙ2፥35፤
2ሳሙ14፥13፤1ነገ
20፥42፤ዳን4፥22
12፥8 2ሳሙ9፥7
12፥9 ዘኍ15፥31፤
1ሳሙ13፥14፤
2ሳሙ11፥15፤1ነገ
15፥5፤መዝ26፥9፤
51፥14
12፥10 2ሳሙ13፥
28፤18፥14-15፤
1ነገ2፥25
12፥11 ዘዳ17፥17፤
28፥30፤2ሳሙ16፥
11፡21-22
12፥12 2ሳሙ
11፥4-15፤16፥22
12፥13 ዘፍ13፥13፤
20፥6፡ዘሌ20፥10፤
24፥17፤ዘኍ22፥34፤
መዝ32፥1-5፤51፥1፡9፤
103፥12፤ምሳ28፥13፤
ኢሳ43፥25፤44፥22፤
ኤር2፥35፤ሚክ
7፥18-19፤ዘካ3፥4፡9

[ሀ]21 ጌዴዎን፣ *ይሩበአል* በመባልም ይታወቃል።

ናታንም እንዲህ አለው፣ “እግዚአብሔር
ኀጢአትህን አስወግዶልሃል፡፡ አንተ አትሞ
ትም፤ [14]ይህን በመፈጸምህ ግን፣ የእግዚአ
ብሔር ጠላቶች እጅግ እንዲያቃልሉት[ደ]
ስላደረግህ፣ የተወለደልህ ልጅ ይሞታል፡፡”
[15]ናታን ወደ ቤቱ ከሄደ በኋላ፣
የኦርዮን ሚስት ለዳዊት
የወለደችለትን ሕፃን እግ ዚአብሔር
ከባድ ሕመም ላይ ጣለው፡፡ [16]ዳዊት ስለ ሕፃኑ
እግዚአብሔርን ለመነ፤ ጾመም፤ ከዚያም
ወደ ክፍሉ ገብቶ በተከታታይ ሌሊቱን
መሬት ላይ ተኝቶ ዐደረ፡፡ [17]የቤተ ሰው ሽ
ማግሌዎችም ከመሬት ሊያስነሡት በአጠ
ገቡ ቆሙ፤ እርሱ ግን እምቢ አለ፤
አብሮአቸውም አንዳች ነገር አልበላም፡፡
[18]በሰባተኛው ቀን ሕፃኑ ሞተ፤ የዳዊት
አገልጋዮችም፣ “እነሆ ሕፃኑ በሕይወት እያለ
የነገርነውን ዳዊት አልሰማንም ታዲያ አሁን
የሕፃኑን መሞት እንዴት አድርገን ልንነ
ግረው እንችላለን? በራሱ ላይ ጒዳት ሊያ
ደርስ ይችላል” ብለው መንገሩን ፈሩ፡፡
[19]ዳዊት አገልጋዮቹ በሹክሹክታ ሲነጋ
ገሩ አይቶ፣ ሕፃኑ መሞቱን ዐወቀ፤ ስለዚህ፣
“ሕፃኑ ሞተ?” ብሎ ጠየቃቸው፡፡
እነርሱም፣ “አዎን ሞቶአል” ብለው መለ
ሱለት፡፡
[20]በዚህ ጊዜ ዳዊት ከመሬት ተነሣ፤
ከታጠበ፣ ከተቀባና ልብሱን ከለወጠ በኋላ
ወደ እግዚአብሔርም ቤት ሄዶ ሰገደ፡፡
ከዚያም ወደ ክፍሉ ገባ፤ በራሱም ጥያቄ
ምግብ አቅርበውለት በላ፡፡
[21]አገልጋዮቹም፣ “እንደዚህ ያደረግኸው
ለምንድን ነው? ሕፃኑ በሕይወት እያለ ጾምህ፤
አለቀስህ፤ ሕፃኑ ከሞተ በኋላ ግን ተነሥ
ተህ በላህ” ብለው ጠየቁት፡፡
[22]እርሱም እንዲህ አለ፤ “በእርግጥ ሕፃኑ
በሕይወት እያለ፣ ‘እግዚአብሔር ይቅር
ብሎኝ ሕፃኑን በሕይወት ያኖረው ይሆ
ናል’ ብዬ ጾምሁ፤ አለቀስሁ፡፡ [23]አሁን
ግን ሕፃኑ ስለ ሞተ፣ የምጾመው ለምንድን
ነው? መልሼ ላመጣው እችላለሁን? እኔ
ወደ እርሱ እሄዳ ለሁ እንጂ፣ እርሱ ወደ
እኔ አይመለስ!”
[24]ከዚያም ዳዊት ሚስቱን ቤርሳቤህን አጽ
ናናት፤ ወደ እርሷም ገብቶ አብሮአት ተኛ፤
ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙንም ሰሎሞን
አለው፡፡ እግዚአብሔርም ወደደው፤ [25]እግ
ዚአብሔር ሕፃኑን ስለ ወደደም ስሙ
ይዲድያ[ጀ] ተብሎ እንዲጠራ በነቢዩ በና
ታን በኩል ቃል ላከ፡፡
[26]በዚያን ጊዜም ኢዮአብ የአሞናውያንን
ከተማ ረባትን ወግቶ የቤተ መንግሥቱን
ምሽግ ያዘ፡፡ [27]ከዚያም ኢዮአብ እንዲህ በማ

12፥14 ኢሳ52፥5፤ ሮሜ2፥24
12፥15 1ሳሙ 25፥38
12፥16 መዝ5፥7፤ 95፥6
12፥17 ዘፍ37፥35፤ 1ሳሙ1፥7፤2ሳሙ 3፥35፤ዳን6፥18
12፥20 ዘፍ41፥14፤ ማቴ6፥17
12፥21 መሳ20፥26
12፥22 ኢሳ 38፥1-5፤ዮና3፥9
12፥23 ዘፍ37፥35፤ 1ሳሙ31፥13፤2ሳሙ 13፥39፤ኢዮ7፥10፤ 10፥21
12፥24 1ነገ1፥10፡ 11፤1ዜና22፥9፤ 28፥5፤ማቴ1፥6
12፥25 ነህ13፥26
12፥26 ዘዳ3፥11
12፥30 አስ8፥15፤ መዝ21፥3፤132፥18
12፥31 1ሳሙ 14፥47
13፥1 2ሳሙ3፥2፡3፤ 14፥27፤1ዜና3፥9
13፥3 1ሳሙ16፥9

ለት ወደ ዳዊት መልክተኞችን ላከ፤ “ረባ
ትን ወግቼ የውሃውን ከተማ ይገኜአለሁ፤
[28]እንግዲህ የቀረውን ሰራዊት አሰባስበህ
ከተማዪቱን ክበብና ያዛት፤ ያለበለዚያ
እኔ ከተማዪቱን እይዛትና በስሜ መጠራቷ
ነው፡፡”
[29]ስለዚህ ዳዊት መላውን ሰራዊት አሰባ
ስቦ ወደ ረባት በመሄድ ወግቶ ያዛት፡፡
[30]የንጉሣቸውንም ዘውድ ከራሱ ላይ ወሰደ፤
የዘውዱ ክብደት የሚመዝን አንድ መክሊት
ወርቅ ሲሆን፣ በከበረ ዕንቍም ያጌጠ ነበር፤
ይህም በዳዊት ራስ ላይ ተጫነ፡፡ ዳዊትም
ከከተማዪቱ እጅግ ብዙ ምርኮ ወሰደ፤
[31]እዚያ የነበሩትንም ሕዝብ አውጥቶ መጋዝ፣
የብረት መቈፈሪያና መጥረቢያ ተጠቅ
መው ሥራ እንዲሠሩ አደረጋቸው፣ እን
ዲሁም የሸክላ ጡብ አሠራቸው[ገ]፡፡ እንዲህ
ያለውም ሥራ በሌሎቹ የአሞናውያን ከተ
ሞች ሁሉ እንዲፈጸም አደረገ፡፡ ከዚያም
ዳዊትና ሰራዊቱ በሙሉ ወደ ኢየሩሳሌም
ተመለሱ፡፡

## አምኖን ትዕማርን ደፈረ

13 የዳዊት ልጅ አቤሴሎም ትዕማር የም
ትባል ቈንጆ እኅት ነበረችው፤
እርሷንም የዳዊት ልጅ አምኖን ወደዳት፡፡
[2]አምኖን እኅቱን ትዕማርን ከማፍቀሩ
የተነሣ እስኪታመም ድረስ ተጨነቀ፤ ድን
ግል ስለ ሆነች እርሷን ማግኘት የማይቻል
ሆኖ አግኝቶታልና፡፡
[3]አምኖን ኢዮናዳብ የተባለ ወዳጅ ነበረው፤
እርሱም የዳዊት ወንድም የሳምዓ ልጅ ነው፡፡
ኢዮናዳብ እጅግ ተንኰለኛ ሰው ነበር፡፡ [4]አም
ኖንንም፣ “የንጉሥ ልጅ ሆይ፤ ሰውነትህ
ቀን በቀን የሚከሳበትን ምክንያት ለምን
አትነግረኝም?” ሲል ጠየቀው፡፡
አምኖንም፣ “የወንድሜን የአቤሴሎምን
እኅት ትዕማርን አፍቅሬ ነው” አለው፡፡
[5]ኢዮናዳብም፣ “እንግዲያው ‘ታምሜአለሁ’
ብለህ ዐልጋ ላይ ተኛ፤ አባትህ ሊጠይቅህ
ሲመጣም፣ ‘እኅቴ ትዕማር መጥታ የም
በላውን ነገር ብትሰጠኝ ደስ ይለኛል፤
መብሉንም እዚሁ አጠገቤ ሆና እያየሁ
አዘጋጅታ በእጇ እንድታጐርሰኝ እባክህ ፍቀ
ድልኝ ብለህ ንገረው” አለው፡፡
[6]ስለዚህ አምኖን የታመመ ሰው መስሎ
ተኛ፤ ንጉሡም ሊጠይቀው መጣ፤ አምኖ
ንም፣ “እኅቴ ትዕማር መጥታ፣ እያየሁ ሁለት

[ደ]14 የማሶሬቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ጥንታዊው የዕብራ ይስጥ የጸሓፍት ትውፊት ግን፤ *በዚህም እግዚአብሔርን እጅግ ስላቃለልህ* ይላል፡፡
[ጀ]25 *ይዲድያ* ማለት *በእግዚአብሔር (ያህዌ) የተወደደ* ማለት ነው
[ገ]31 በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጒም በትክክል አይታ ወቅም፡፡

እንጀራ ጋግራ በእጇ እንድታጕርሰኝ እለ
ምንሃለሁ” ብሎ ጠየቀው።
7ዳዊትም፣ “ወንድምሽ አምኖን ቤት ሂደሽ
ምግብ እንድታዘጋጂለት” በማለት ለትዕማር
እንዲነግሯት ወደ ቤተ መንግሥቱ ላከ።
8ስለዚህም ትዕማር ወንድሟ አምኖን ወደ
ተኛበት ቤት ሄደች፤ ጥቂት ሊጥ ወስዳ ካቦ
ካች በኋላ እያየ አዘጋጅታ ጋገረችው፤ 9ከዚ
ያም መጋገሪያውን አውጥታ እንጀራውን አቀ
ረበችለት፤ እርሱ ግን መብላት አልፈለገም።
አምኖንም፣ “ሰውን ሁሉ ከዚህ አስወጡ
ልኝ” አለ፤ ያለውም ሰው ሁሉ ትቶት ወጣ።
10ከዚያም አምኖን ትዕማርን፣ “እንድታጕ
ርሺኝ ምግቡን እዚሁ መኝታ ክፍሌ አም
ጪልኝ” አላት። ትዕማርም ያዘጋጀችውን
እንጀራ ይዛ ወንድሟ አምኖን ወዳለበት
መኝታ ክፍል ገባች። 11ነገር ግን ምግቡን
ስታቀርብለት አፈፍ አድርጎ ያዛትና፣ “እህቴ
ነዪ አብረን እንተኛ” አላት።
12እርሷም እንዲህ አለችው፤ “እባክህ ወን
ድሜ ተው አይሆንም! አታስገድደኝ፤ እንዲ
ህ ያለው ነገር በእስራኤል ተደርጎ አያው
ቅም፤ ይህን አሳፋሪ ድርጊት አታድርግ።
13እኔስ እንዴት እሆናለሁ? ነውሬንስ ተሸ
ክሜ የት እገባለሁ? አንተስ ብትሆን በእስ
ራኤል ከወራዳዎቹ እንደ አንዱ መቈጠ
ርህ አይደለምን? እባክህ ለንጉሡ ንገረው፤
እንዳላገባህም አይከለክለኝም።” 14እርሱ ግን
ሊሰማት አልፈለገም፤ ከእርሷ ይልቅ ብርቱ
ስለ ነበር፣ በግድ አስነወራት፤ ከእርሷም
ጋር ተኛ።
15ከዚያም አምኖን እጅግ ጠላት፤ እንዲ
ያውም ቀድሞ ካፈቀራት የበለጠ ጠላት።
አምኖንም፣ “ተነሽ ውጭልኝ!” አላት።
16እርሷም፣ “ይህ አይሆንም! እኔን አስወ
ጥቶ መስደድ፣ አስቀድመህ ካደረስህብኝ በደል
የባሰ መፈጸምህ ነው” አለችው። እርሱ ግን
አልተቀበላትም፤ 17በግል የሚያገለግለውን
ወጣት ጠርቶ፣ “ይህቺን ሴት ከዚህ አስወ
ጣና በሩን ዝጋባት” አለው። 18ስለዚህም
አገልጋዩ አስወጥቶ በሩን ዘጋባት፤ ጌጠኛ[ጠ]
የሆነና በዚያን ጊዜ ድንግል የሆኑት የንጉሥ
ልጆች የሚለብሱትን ዐይነት ልብስ ለብሳ
ነበር። 19ትዕማርም በራሷ ላይ ዐመድ ነሰነ
ሰች፤ ጌጠኛ[ጨ] ልብሷን ቀደደች፤ ከዚያም
እጇን በራሷ ላይ አድርጋ እያለቀሰች ሄደ
ች።
20ወንድሟ አቤሴሎምም፣ “ያ
ወንድምሽ አምኖን ካንቺ ጋር ነበርን? እኅቴ
ሆይ፣ በይ አሁን ዝም በዪ፤ ወንድምሽ ስለ
ሆነ፤ ነገሩን በልብሽ አትያዢው” አላት።
ትዕማርም በወ ንድሟ በአቤሴሎም ቤት

13፥9 ዘፍ45፥1
13፥11 ዘፍ38፥16፤
39፥12
13፥12 ዘፍ34፥7፤
ዘሌ20፥17
13፥13 ዘሌ18፥9፤
ዘዳ22፥21፡23-24
13፥14 ዘፍ34፥2፤
ሕዝ22፥11
13፥18 ዘፍ37፥23
13፥19 ኢሱ7፥6፤
አስ4፥1፤ዳን9፥3

13፥21 ዘፍ34፥7
13፥22 ዘፍ31፥24፤
ዘሌ19፥17-18፤
1ዮሐ2፥9-11
13፥23 1ሳሙ25፥7
13፥28 ሩት3፥7፤
2ሳሙ3፥3፤12፥10
13፥31 ዘኍ14፥6

ብቸኛ ሴት ሆና ኖረች።
21ንጉሥ ዳዊት ይህን ሁሉ በሰማ ጊዜ
እጅግ ተቈጣ፤ 22አቤሴሎም አምኖንን ክፉም
ሆነ ደግ አንዳች ቃል አልተናገረውም፤ ምክ
ንያቱም አምኖን እኅቱን ትዕማርን ስላ
ስነወራት ጠልቶት ነበር።

## አቤሴሎም አምኖንን ገደለው

23ከሁለት ዓመት በኋላ አቤሴሎም በኤ
ፍሬም ድንበር አቅራቢያ ባለችው በቤ
ላሶር ከተማ በጎቹን ይሸልት ነበር፤ በዚህን
ጊዜ የንጉሡን ወንዶች ልጆች ሁሉ በዚያ
እንዲገኙለት ጋበዛቸው። 24አቤሴሎምም ወደ
ንጉሡ ሄዶ፣ “እነሆ፤ ባሪያህ በጎቹን እየሸለተ
ነው፤ ታዲያ ንጉሡና ሹማምንቱ ፈቃ
ዳቸው ሆኖ እባክህ ይገኙልኝ?” ሲል ጠየ
ቀው።
25ንጉሡም፣ “ልጄ ሆይ፣ ሁላችንም መሄድ
የለብንም፤ ሸክም እንሆንብሃለን” ሲል መለ
ሰለት። አቤሴሎም አጥብቆ ቢለምነውም
ንጉሡ መሄድ አልፈለገም፤ ነገር ግን መርቆ
አሰናበተው።
26አቤሴሎምም፣ “እንግዲያውስ ወንድሜ
አምኖን አብሮን ይሂድ” አለው።
ንጉሡም፣ “አብሮአችሁ የሚሄደው ስለ
ምንድን ነው?” ሲል ጠየቀው። 27ነገር
ግን አቤሴሎም አጥብቆ ስለ ለመነው፣
አምኖንና ሌሎቹ የንጉሡ ወንዶች ልጆች
ሁሉ አብረውት እንዲሄዱ አደረገ።
28አቤሴሎምም አገልጋዮቹን፣ “አምኖን የወ
ይን ጠጅ ጠጥቶ መንፈሱ መለወጡን ተጠ
ባበቁ፤ ከዚያም እኔ አምኖንን፣ ‘ምቱት’ ስላ
ችሁ ግደሉት፤ ያዘዝኋችሁ እኔ ነኝ አት
ፍሩ፤ በርቱ፤ ጠንክሩ” ብሎ አዘዛቸው።
29የአቤሴሎምም አገልጋዮች ጌታቸው ያዘ
ዛቸውን በአምኖን ላይ ፈጸሙ። ከዚያም
የንጉሡ ልጆች በሙሉ ተነሥተው በየበ
ቅሎዎቻቸው ላይ ተቀምጠው ሸሹ።
30እነርሱ በመንገድ ላይ ሳሉም፣ “አቤሴ
ሎም የንጉሡን ልጆች በሙሉ ፈጃቸው፤
አንድም የተረፈ የለም” የሚል ወሬ ለዳ
ዊት ደረሰው። 31ንጉሡም ተነሥቶ ቆመ፤
ልብሱን ቀደደ፤ በመሬትም ላይ ተዘረረ፤
በአጠገቡ ቆመው የነበሩት አገልጋዮቹም
ሁሉ ልብሳቸውን ቀደዱ።
32የዳዊት ወንድም የሳምዓ ልጅ ኢዮና
ዳብ ግን እንዲህ አለ፤ “የንጉሡን ልጆች
በሙሉ እንደ ፈጇቸው አድርጎ ጌታዬ
አያስብ፤ እኅቱን ትዕማርን በግድ ካስነወራት
ጊዜ አንሥቶ አቤሴሎም ቈርጦ የተነሣበት

[ጠ]18 በዕብራይስጡ የዚህ ሐርግ ትርጕም በትክክል አይታወቅም።
[ጨ]19 በዕብራይስጡ የዚህ ሐርግ ትርጕም በትክክል አይታወቅም።

ጕዳይ ስለ ሆነ፣ የሞተው አምኖን ብቻ
ነው። 33እንግዲህ የሞተው አምኖን ብቻ ስለ
ሆነ፣ ‘የንጉሡ ልጆች በሙሉ ተገደሉ’ ተብሎ
የተነገረውን ንጉሥ ጌታዬ ማመን የለበትም።”
34አቤሴሎምም ፈጥኖ ሸሸ።
ለዘብ ጥበቃ የቆመውም ሰው ቀና ብሎ
ሲመለከት፣ ከእርሱ በስተ ምዕራብ ካለው
መንገድ ብዙ ሰዎች በተራራው ጥግ ቍል
ቍል ሲወርዱ አየ፤ ዘብ ጠባቂውም ሄዶ
ለንጉሡ፣ “ከበስተ ሖሮናይም አቅጣጫ
በኰረብታው ጥግ ላይ ሰዎች ቍልቍል
ሲወርዱ አያለሁ”[ጸ] ብሎ ነገረው።
35ኢዮናዳብም ዳዊትን፣ “እነሆ፣ የንጉሡ
ልጆች መጥተዋል፤ አገልጋይህም እንዳለው
ሆኖአል” አለው።
36ገና ተናግሮ ሳይጨርስ፣ የንጉሡ ልጆች
ጮኸው እየተላቀሱ ገቡ፤ እንደዚሁም ንጉ
ሡና አገልጋዮቹ ሁሉ እጅግ አለቀሱ።
37አቤሴሎም ኰብልሎ የጌሹር ንጉሥ
ወደ ሆነው ወደ ዓሚሁድ ልጅ ወደ ተልማይ
ሄደ፤ ነገር ግን ዳዊት ስለ ሞተው ልጁ
ዘወትር ያለቅስ ነበር።
38አቤሴሎም ሸሽቶ ወደ ጌሹር ከሄደ
በኋላ፣ በዚያ ሦስት ዓመት ተቀመጠ።
39ንጉሥ ዳዊት በልጁ በአምኖን ሞት ከደ
ረሰበት ሐዘን ከተጽናና በኋላ፣ ወደ አቤሴ
ሎም ለመሄድ መንፈሱ ተነሣሣ[ጸ]።

## አቤሴሎም ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ

14 የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ የንጉሡ ልብ
አቤሴሎምን እንደ ናፈቀ ተረዳ።
2ስለዚህም ኢዮአብ ወደ ቴቁሔ፤ ሰው
ልኮ አንዲት ብልኅ የሆነች ሴት አስ
መጣ፤ እንዲህም አላት፤ “ሐዘንተኛ በመ
ምሰል የሐዘን ልብስ ልበሺ፤ ዘይት አት
ቀቢ፤ ለሞተ ሰው ብዙ ጊዜ እንዳዘነች
ሴት መስለሽም ታዪ። 3ከዚያም ወደ ንጉሡ
ሄደሽ እንዲህ በዪው።” ከዚያም ኢዮአብ
የምትናገራቸውን ቃላት ነገራት።
4የቴቁሔዪቱም ሴት ወደ ንጉሡ ገብታ፣[θ]
በንጉሡ ፊት ወደ መሬት በግምባሯ ተደፍታ
እጅ በመንሣት አክብሮቷን ከገለጠች በኋላ፣
“ንጉሥ ሆይ! እርዳኝ” አለች።
5ንጉሡም፣ “ችግርሽ ምንድን ነው?”
ብሎ
ጠየቃት።
እርሷም እንዲህ አለች፤ “እኔ በእርግጥ
ባሌ የሞተብኝ መበለት ነኝ፤ 6እኔ አገልጋ
ይህ ሁለት ወንዶች ልጆች ነበሩኝ፤ ሜዳ
ላይ እርስ በርሳቸው ተጣሉ፤ ገላጋይም ስላ
ልነበረ፣ አንዱ ሌላውን መትቶ ገደለው።
7እነሆ ቤተ ዘመዱ ሁሉ በባሪያህ ላይ ተነ
ሥተው፣ ‘ወንድሙን ስለ ገደለ እንገድለ
ዋለንና ወንድሙን የገደለውን ሰው አሳል
ፈሽ ስጪን፣ ከዚያም ወራሽ አልባ ትሆኛ
ለሽ’ ይሉኛል፤ ስለዚህ የቀረኝን አንዱን
መብራቴን አጥፍተው፣ ባሌን በምድር ላይ
ያለ ስምና ያለ ዘር ሊያስቀሩት ነው።”
8ንጉሡም ሴቲቱን፣ “አንቺ ወደ ቤትሽ
ሂጂ፤ ስለ ጕዳይሽ አስፈላጊውን ትእዛዝ እሰ
ጣለሁ” አላት። 9ነገር ግን የቴቁሔዪቱም
ሴት፣ “ንጉሥ ጌታዬ፣ በደሉ በእኔና በአ
ባቴ ቤተ ሰብ ላይ ይሁን፤ ንጉሡና ዙፋኑ
ከበደል የነጹ ይሁኑ” አለች።
10ንጉሡም፣ “ማንም ሰው አንዳች ነገር
ቢናገርሽ እኔ ዘንድ አምጪው፤ ዳግም
አያስቸግርሽም” ሲል መለሰላት።
11እርሷም፣ “ደም ተበቃዮቹ ልጄን በማ
ጥፋት የባሰ ጕዳት እንዳያደርሱ፣ ንጉሡ አም
ላኩን *እግዚአብሔርን* ይለምን” አለች።
ንጉሡም፣ “ሕያው *እግዚአብሔርን!* ከል
ጅሽ ራስ ላይ አንዲት ጠጕር እንኳ አት
ነካም” አላት።
12ከዚያም ሴቲቱ፣ “እኔ አገልጋይህ ለጌ
ታዬ ለንጉሡ አንዲት ቃል እንድናገር ፍቀ
ድልኝ” አለችው። እርሱም፣ “እሺ ተና
ገሪ” አላት።
13ሴቲቱም መልሳ እንዲህ አለችው፣ “እን
ዲህ ያለውን ነገር *በእግዚአብሔር* ሕዝብ ላይ
ያሰብሽው ለምንድን ነው? ንጉሡ ከአገር የተ
ሰደደውን ልጁን አልመለሰውም፤ ታዲያ ይህን
ሲናገር በራሱ ላይ መፍረዱ አይደለምን?
14በመሬት ላይ የፈሰሰ ውሃ እንደማይ
ታፈስ ሁሉ፣ እኛም እንደዚሁ እንሞታ
ለን፤ *እግዚአብሔር* ግን ከአገር የተሰደደ
ሰው ከእርሱ እንደ ራቀ በዚያው እንዳ
ይቀር የሚመለስበትን ሁኔታ ያመቻቻል
እንጂ ሕይወቱ እንድትጠፋ አይፈቅድም።
15“አሁንም ወደዚህ የመጣሁት ሕዝቡ
ስላስፈራኝ ይህንኑ ለንጉሥ ጌታዬ ለመንገር
ነው። እኔም አገልጋይህ ይህን አሰብሁ፤
‘ለንጉሡ እነግረዋለሁ፤ ምናልባትም አገል
ጋዩ የጠየቀችውን ይፈጽምላት ይሆናል፤
16*እግዚአብሔር* ከሰጠን ርስት እኔንም
ልጄ ንም ሊነቅለን ከተነሣው ሰው እጅ
ንጉሡ አገልጋዩን ሊታደግ ይፈቅድ
ይሆናል።’
17“አሁንም አገልጋይህ፤ ‘ንጉሥ ጌታዬ በጎ
ውንና ክፋውን በመለየት እንደ *እግዚአብሔር*

13፥37 2ሳሙ3፥3
13፥39 2ሳሙ 12፥19-23፤14፥13
14፥1 2ሳሙ2፥18
14፥2 ሩት3፥3፤ 2ሳሙ20፥16፤ነህ 3፥5፤ኢሳ1፥6፤ ኤር6፥1፤አሞ1፥1
14፥3 ቍ19
14፥7 ዘኍ35፥19፤ ዘዳ19፥10-13፤ ማቴ21፥38
14፥8 1ሳሙ25፥35
14፥9 1ሳሙ25፥24፡ 28፤ማቴ27፥25
14፥11 ዘኍ35፥12፡ 21፤1ሳሙ14፥45፤ ማቴ10፥30
14፥13 2ሳሙ 12፥7፤13፥38-39፤ 1ነገ20፥40
14፥14 ዘኍ35፥15፡ 25-28፤ኢዮ10፥8፤ 14፥11፤17፥13፤ 30፥23፤መዝ22፥15፤ 58፥7፤ኢሳ19፥5፤ ዕብ9፥27
14፥16 ዘፀ34፥9፤ 1ሳሙ26፥19
14፥17 1ሳሙ 29፥9፤1ነገ3፥9፤ ዳን2፥21

[ጸ]34 የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራ ይስጡ ግን ይህን ዐረፍተ ነገር አይጨምርም።
[ጸ]39 የሙት ባሕር ጥቅልና አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ የማሶሬቱ ቅጅ ግን፣ *የንጉሥ ዳዊት መንፈስ ተነሣሣ* ይላል።
[θ]4 ብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ የሰብዓ ሊቃናት፣ የቩልጌትና የሱርስት ትርጕሞች፣ *ሄዳ* ይላሉ፤ አብዛኞቹ ቅጆች ግን፣ *ለንጉሡ ተናገረች* ይላሉ።

መልአክ ስለ ሆነ፣ የጌታዬ የንጉሡ ቃል
ያጽናናኝ፤ *እግዚአብሔር* አምላክህም ካንተው
ጋር ይሁን’ ትላለች።”
18ከዚያም ንጉሡ ሴቲቱን፣ “እኔም ለምጠ
ይቅሽ ነገር አንቺም መልሱን አትደብ
ቂኝ” አላት።
ሴቲቱም፣ “ንጉሥ ጌታዬ፤ እሺ ይና
ገር” አለችው።
19ንጉሡም፣ “በዚህ ሁሉ የኢዮአብ እጅ
የለበትምን?” ሲል ጠየቃት።
ሴቲቱም መልሳ እንዲህ አለች፤ “ንጉሥ
ጌታዬ ሆይ በሕያው ነፍስህ እምላለሁ፤ ንጉሥ
ጌታዬ ከተናገረው ሁሉ ወደ ቀኝም ወደ
ግራም የሚል ማንም የለም። አዎን ይህን
እንዳደርግ ያዘዘኝና ይህም ሁሉ ቃል
በእኔ በአገልጋይህ አንደበት እንዲነገር የላ
ከኝ አገልጋይህ ኢዮአብ ነው። 20አገልጋይህ
ኢዮአብ ይህን ያደረገውም ያለውን ሁኔታ
ለመለወጥ ሲል ነው፤ ነገር ግን ጌታዬ *የእግዚ
አብሔርን* መልአክ ጥበብ የመሰለ ጥበብ
ስላለው፣ በምድሪቱ ላይ የሚሆነውን ነገር ሁሉ
ያውቃል።”
21ንጉሡም ኢዮአብን፣ “መልካም ነው፤
ፈቅጃለሁ፤ ሂድና ወጣቱን አቤሴሎምን መል
ሰህ አምጣው” አለው።
22ኢዮአብም አክብሮቱን ለንጉሡ ለመግ
ለጥ ወደ መሬት በግምባሩ ተደፍቶ እጅ ነሣ፤
ንጉሡንም ባረከ፣ ኢዮአብም በመቀጠል፣
“ንጉሡ የአገልጋዩን ልመና ስለ ተቀበ
ለው፣ ባሪያህ በፊትህ ሞገስ ማግኘቱን ዛሬ
ለማወቅ ችሎአል” አለ።
23ከዚያም ኢዮአብ ወደ ጌሹር ሄዶ አቤ
ሴሎምን ወደ ኢየሩሳሌም መልሶ አመጣው።
24ንጉሡ ግን፣ “እዚያው እቤቱ ይሂድ፤ ዐይ
ኔን ማየት የለበትም” አለ። ስለዚህም አቤ
ሴሎም ወደ ቤቱ ሄደ፤ የንጉሡንም ፊት
አላየም።
25መቼም በመልኩ ማማር አቤሴሎምን
የሚያህል አንድም ሰው በመላው እስራ
ኤል አልነበረም፤ ከራስ ጠጕሩ እስከ እግር
ጥፍሩ የሚወጣለት እንከን አልነበረም።
26የራስ ጠጕሩ ሲከብደው በዓመት አንድ
ጊዜ ይቈርጠው ነበር፤ የተቈረጠውን በሚ
መዝነው ጊዜ ክብደቱ በቤተ መንግሥቱ
ሚዛን ሁለት መቶ ሰቅል[ፊ] ይሆን ነበር።
27አቤሴሎም ሦስት ወንዶች ልጆችና ትዕ
ማር የተባለች አንዲት ሴት ልጅ ተወለ
ዱለት፤ ሴት ልጁም በጣም ውብ ነበረች።
28አቤሴሎም የንጉሡን ዐይን ሳያይ
ሁለት
ዓመት በኢየሩሳሌም ኖረ። 29ከዚያም አቤ
ሴሎም ወደ ንጉሡ እንዲሄድለት ኢዮአ
ብን አስጠራው፤ ኢዮአብ ግን ወደ እርሱ
መምጣት አልፈለገም፤ ለሁለተኛ ጊዜም
ላከበት፤ ኢዮአብ አሁንም መምጣት አል
ፈለገም። 30ከዚያም አቤሴሎም ለአገል
ጋዮቹ “ተመልከቱ የኢዮአብ ዕርሻ የሚገኘው
ከእኔ ዕርሻ አጠገብ ነው፤ በዕርሻው ላይ
የገብስ አዝመራ አለው፤ ሂዱችሁም እሳት
ልቀቁበት” አላቸው። ስለዚህ የአቤሴሎም
አገልጋዮች ሄደው የኢዮአብን ዕርሻ በእ
ሳት አቃጠሉት።
31ከዚያም ኢዮአብ ወደ አቤሴሎም
ቤት ሄደ፣ “አገልጋዮችህ ለምንድን ነው ዕር
ሻዬን ያቃጠሉት?” ብሎ ጠየቀው።
32አቤሴሎምም፣ ኢዮአብን፣ “ከጌሹር ለምን
መጣሁ? ለእኔ እስካሁንም እዚያው ብሆን
ይሻለኝ ነበር ብሎአል ብለህ እንድ ትነግ
ርልኝ ‘ወደ ንጉሡ እልክህ ዘንድ ወደ እኔ
ና’ ብዬ አስጠራሁህ፤ አሁንም ቢሆን፤ የን
ጉሡን ዐይን ማየት እፈልጋለሁ፤ ምንም ዐይ
ነት በደል ከተገኘብኝ ይግደለኝ” አለው።
33ኢዮአብም ወደ ንጉሡ ሄዶ ይህንኑ
ነገረው። ከዚያም ንጉሡ አቤሴሎምን አስጠ
ራው፤ እርሱም መጥቶ በንጉሡ ፊት በግ
ምባሩ ተደፍቶ እጅ ነሣ፤ ንጉሡም አቤ
ሴሎምን ሳመው።

### የአቤሴሎም ዐመፅ

15 ከዚህ በኋላ አቤሴሎም ሠረገላና
ፈረሶች እንዲሁም ፊት ፊቱ የሚ
ሮጡ አምሳ ሰዎች ለራሱ አዘጋጀ። 2አቤ
ሴሎምም በማለዳ ተነሥቶ ወደ ከተማዪቱ
መግቢያ በር በሚወስደው መንገድ ዳር ሆን
ብሎ ይቆም ነበር። ማናቸውም ባለ ጕዳይ
አቤቱታውን ለንጉሡ አቅርቦ ለማስወሰን
በሚመጣበት ጊዜ ሁሉ፣ አቤሴሎም ወደ
እርሱ እየጠራ፣ “አንተ ከየትኛው ከተማ
ነው የመጣኸው? በማለት ይጠይቀዋል፤ ያም
ሰው፣ “አገልጋይህ ከአንዱ የእስራኤል ነገ
ዶች ነው” ብሎ ይመልስለታል። 3ከዚያም
አቤሴሎም፣ “ተመልከት! ጕዳይህማ ትክ
ክልና ተገቢም ነው፤ የትኛው የንጉሥ እን
ደራሴ ነው ታዲያ የሚያይልህ?” ይለዋል።
4ቀጠል አድርጎም፣ “ምነው ዳኛ ሆኜ በም
ድሪቱ ላይ በተሾምሁ! አቤቱታ ወይም
ክስ ያለበት ሁሉ ወደ እኔ እየመጣ ፍትሕ
እንዲያገኝ አደርገው ነበር” ይል ነበር።
5እንዲሁም ማናቸውም ሰው ወደ እርሱ
ቀርቦ እጅ በሚነሣው ጊዜ፣ አቤሴሎም እጁን
ዘርግቶ ይይዘውና ይስመው ነበር። 6አቤሴ
ሎም ፍትሕ ለማግኘት ወደ ንጉሡ የሚ
መጣውን እስራኤላዊ ሁሉ የሚቀርበው

14፥19 ቀኍ3
14፥20 2ሳሙ 18፥13፤1ነገ3፥12፡28፤ 10፥23-24፤ኢሳ28፥6
14፥22 ዘፍ47፥7
14፥26 2ሳሙ18፥9
14፥27 2ሳሙ 13፥1፤18፥18
14፥30 ዘፀ9፥31
14፥31 መሳ15፥5
14፥32 1ሳሙ 20፥8፤2ሳሙ3፥3
14፥33 ሉቃ15፥20
15፥1 1ሳሙ8፥11፤ 2ሳሙ12፥11
15፥2 ዘፍ23፥10፤ 2ሳሙ19፥8
15፥3 ምሳ12፥2
15፥4 መሳ9፥29
15፥6 ሮሜ16፥18

ፊ26 2.3 ኪሎ ግራም ያህል ነው።

በዚህ መንገድ ስለ ነበር፣ የእስራኤልን
ሰዎች ልብ ሰረቀ።
7ከአራት ዓመት[ፐ] በኋላም አቤሴሎም ንጉ
ሡን እንዲህ አለው፤ “*ለእግዚአብሔር* የተ
ሳልሁትን ስእለት ለማድረስ ወደ ኬብሮን
እንድሄድ ፍቀድልኝ፤ 8እኔ አገልጋይህ በሶ
ርያ ምድር በጌሹር ሳለሁ ‘*እግዚአብሔር*
ወደ ኢየሩሳሌም የመለሰኝ እንደ ሆነ፣ በኬ
ብሮን[ሀ] *ለእግዚአብሔር* እሰግዳለሁ’ ብዬ ተስ
ያለሁ።”
9ንጉሡም፣ “በሰላም ሂድ” አለው፤ ስለዚህ
አቤሴሎም ወደ ኬብሮን ሄደ።
10ከዚያም አቤሴሎም፣ “የቀንደ መለ
ከት ድምፅ ስትሰሙ፣ ‘አቤሴሎም በኬብሮን
ነገሠ በሉ” የሚሉ የምስጢር ሠራተኞችን
በመላው የእስራኤል ነገዶች አሰማራ። 11ከኢ
የሩሳሌምም ሁለት መቶ ሰዎች አብረ
ውት ሄዱ፤ በእንግድነት ተጋብዘው በየዋ
ህነት ከመሄዳቸው በስተቀር፣ ስለ ጕዳዩ
የሚያውቁት አንዳችም ነገር አልነበረም።
12አቤሴሎም መሥዋዕት በሚያቀርብበት ጊዜ
የዳዊት አማካሪ የሆነው ጊሎአዊው አኪጦ
ፌል ከአገሩ ከጊሎ ወደ እርሱ እንዲመጣ
ላከበት፤ ስለዚህ ሤራው ጥንካሬ አገኘ፤
የአቤሴሎምም ተከታዮች ቍጥር እየጨመረ
መጣ።

## የዳዊት ሽሽት

13መልእክተኛም መጥቶ፣ “የእስራኤል ሰዎች
ልብ ከአቤሴሎም ጋር ሆኖአል” ብሎ ለዳ
ዊት ነገረው።
14ከዚያም ዳዊት በኢየሩሳሌም ላሉት ሹ
ማ ምንቱ ሁሉ፣ “ተነሡ እንሽሽ፤
ያለበለዚያ አንዳችንም ከአቤሴሎም እጅ
ማምለጥ አንችልም፤ አሁኑኑ ከዚህ
መውጣት አለ ብን፤ ካልሆነ ገሥግሦ
መጥቶ ከያዘን እኛን ያጠፋናል፤ ከተማዪቱ
ንም በሰይፍ ይመታ ታል” አላቸው።
15የንጉሡ ሹማምንትም፣ “ጌታችን ንጉሡ
የመረጠውን ሁሉ ለማድረግ እኛ አገልጋ
ዮችህ ዝግጁ ነን” ብለው መለሱለት።
16ንጉሡ ከመላው ቤተ ሰቡ ጋር ወጣ፤ ቤተ
መንግሥቱንም እንዲጠብቁ ዐሥር ቁባ
ቶች አስቀረ። 17ስለዚህ ንጉሡ መላውን
ሕዝብ አስከትሎ ወጣ፤ ጥቂት ርቀው
ከሄዱ በኋላም በአንዲት ቦታ ቆሙ። 18ሰዎቹ
ሁሉ፣ ከሊታውያን፣ ፈሊታውያን እንዲሁም
ከጌት አብረውት የመጡትን ስድስት መቶ
ጌታውያንን ሁሉ ጨምሮ ተሰልፈው በንጉሡ
ፊት ዐለፉ።
19ንጉሡም ጌታውን ኢታይን እንዲህ
አለው፤ “ከእኛ ጋር የመጣኸው ለምንድን
ነው? ተመለስና ከንጉሡ ከአቤሴሎም ጋር
ተቀመጥ፤ አንተ ለራስህ ከአገርህ ተወስ
ደህ የመጣህ እንግዳ ነህ፤ 20የመጣኸውም
ገና ትናንት ነው፤ ታዲያ የት
እንደምሄድ የማላውቅ ሰው እንዴት ዛሬ
ከእኛ ጋር እንድትንከራተት ላድርግ? በል
አሁንም ሰዎችህን ይዘህ ተመለስ፤ በጎነትና
ታማኝ ነትም ከአንተ ጋር ይሁን”
አለው።
21ኢታይ ግን፣ “ሕያው *እግዚአብሔርን*!
እንዲሁም በጌታዬ በንጉሡ እምላለሁ፤ ሕይ
ወትም ይሁን ሞት በየትም ቦታ ንጉሥ
ጌታዬ የሚሆነውን ሁሉ አገልጋይህም እን
ደዚያው ይሆናል” ብሎ መለሰለት።
22ዳዊትም ኢታይን፣ “በል እንግዲያው
ቅደምና ሂድ” አለው። ስለዚህ ጌታዊው ኢታይ
ሰዎቹን ሁሉና አብረውት የነበሩትን ቤተ
ሰቦቹን ይዞ ሄደ።
23ሕዝቡ ሁሉ በሚያልፍበትም ጊዜ ባላ
ገሩ በሙሉ እየጮኸ አለቀሰ፤ ንጉሡም
የቄድሮንን ሸለቆ ተሻገረ፤ ሕዝቡም ሁሉ
ተሻግሮ ወደ ምድረ በዳው ተጓዘ።
24ሳዶቅም በዚያ ነበር፤ አብረውት የነ
በሩትም ሌዋውያን ሁሉ የእግዚአብብሔርን
የኪዳኑን ታቦት ተሸክመው ነበር። እነር
ሱም የእግዚአብሔርን ታቦት ዐሳረፉ፤ አብያ
ታርም ሕዝቡ በሙሉ ከከተማዪቱ ለቆ
እስኪወጣ ድረስ መሥዋዕት አቀረበ[ሰ]።
25ከዚያም ንጉሡ ሳዶቅን እንዲህ አለው፤
“አንተ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ከተማ
ዪቱ ይዘህ ተመለስ፤ *በእግዚአብሔር* ፊት
ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ፣ እርሱ እኔንም
መልሶ ታቦቱንና ማደሪያውን እንደ ገና
ለማየት ያበቃኛል፤ 26ነገር ግን እርሱ፣
‘ባንተ አልተደሰትሁም’ የሚል ከሆነ፣ መል
ካም መስሎ የታየውን ነገር ያድርግብኝ፤
እኔም ለመቀበል ዝግጁ ነኝ።”
27እንዲሁም ንጉሡ ካህኑን ሳዶቅን እንዲህ
አለው፤ “አንተ ነቢይ አይደለህምን? እንግ
ዲህ አንተም ልጅህን አኪማአስን፣ የአብያ
ታርን ልጅ ዮናታንን ይዘህ በሰላም ወደ
ከተማዪቱ ተመለስ። አንተና አብያታር ሁለ
ቱን ልጆቻችሁን ይዛችሁ ሂዱ። 28እኔም
ከአንተ ዘንድ ወሬ እስካገኝ ድረስ
በምድረ በዳው በሚገኘው በወንዙ መሻገሪያ
እቈያለሁ” 29ስለዚህ ሳዶቅና አብያታር የእ
ግዚአብሔርን ታቦት ይዘው ወደ ኢየሩ
ሳሌም በመመለስ እዚያው ቈዩ።

**15፥8** ዘፍ28፥20፤ 2ሳሙ3፥3
**15፥10** 1ነገ1፥34፡39፤2ነገ9፥13
**15፥12** ቀኍ31፡34፤ ኢሱ15፥51፤2ሳሙ 16፥15፡23፤17፥14፤ 23፥34፤1ዜና27፥33፤ኢዮ19፥14፤መዝ 3፥1፤41፥9፤55፥13፤ ኤር9፥4
**15፥14** 2ሳሙ 19፥9፤1ነገ2፥26፤ መዝ3 ርእስ፤132፥1
**15፥16** 2ሳሙ16፥21-22፤20፥3
**15፥18** 1ሳሙ30፥14፤2ሳሙ20፥7፡23፤ 1ነገ1፥38፡44፤ 1ዜና18፥17
**15፥19** ዘፍ31፥15፤ 2ሳሙ18፥2
**15፥20** 1ሳሙ 22፥2፤2ሳሙ2፥6
**15፥21** ሩት1፥16-17፤ምሳ17፥17
**15፥23** 1ሳሙ 11፥4፤1ነገ2፥37፤2ነገ 23፥12፤2ዜና15፥16፤2 9፥16፤30፥14፤ ኢዮ2፥12፤ኤር 31፥40፤ዮሐ18፥1
**15፥24** ዘኍ4፥15፤ 10፥33፤1ሳሙ 22፥20፤2ሳሙ8፥17፤ 19፥11
**15፥25** ዘፀ15፥13፤ ዘሌ15፥31፤መዝ 43፥3፤46፥4፤84፥1፤ 132፥7
**15፥26** መሳ10፥15፤ 2ሳሙ22፥20
**15፥27** ቀኍ36፤ 1ሳሙ9፥9፤2ሳሙ 17፥17፤1ነገ1፥42
**15፥28** 2ሳሙ 17፥16

[ፐ]7 የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም፣ የሱርስቱ ቅጅና የአይሁዳዊው የታሪክ ጸሓፊ የዮሴፍ ወልደ ኮሪዮን ጽሑፎች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ *አርባ* ይላል።
[ሀ]8 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ *ኬብሮን* የሚለውን ቃል አይጨርም።
[ሰ]24 ወይም *አብያታር ሄዶ*

[30]ዳዊት ግን እያለቀሰ የደብረ ዘይትን ተራራ
ሽቅብ ወጣ፤ ራሱን ተከናንቦ፣ ባዶ እግሩን
ነበር፤ አብሮት ያለውም ሕዝብ ሁሉ እንደ
ዚሁ ራሱን ተከናንቦ እያለቀሰ ሽቅብ
ይወጣ ነበር። [31]በዚህ ጊዜ፣ "ከአቤሴሎም
ጋር ካሤሩት መካከል አንዱ አኪጦፌል
ነው" ብለው ለዳዊት ነገሩት። ስለዚህ
ዳዊት፣ "*እግዚአብሔር* ሆይ፤ እባክህን የአ
ኪጦፌልን ምክር ወደ ከንቱነት ለውጠው"
ብሎ ጸለየ።

[32]ዳዊትም ሕዝቡ *እግዚአብሔርን* ወደ
ሚያመልክበት ወደ ተራራው ጫፍ ሲደ
ርስ፣ አርካዊው ኩሲ ልብሱን ቀዶ ትቢያ
በራሱ ላይ ነስንሶ ሊገናኘው መጣ።

[33]ከዚያም ዳዊት እንዲህ አለው፤ "አብ
ረኸኝ ብትሄድ ሸክም ትሆንብኛለህ፤ [34]ነገር
ግን ወደ ከተማዪቱ ተመልሰህ አቤሴሎምን፣
'ንጉሥ ሆይ፤ አገልጋይህ እሆናለሁ፤ ቀድሞ
የአባትህ አገልጋይ እንደ ነበርሁ ሁሉ፣ ዛሬም
አንተን አገለግልሃለሁ' ብትለው የአኪጦፌ
ልን ምክር በማፍረስ ትረዳኛለህ። [35]ካህ
ናቱ ሳዶቅና አብያታር እዚያው ከአንተው
ጋር ይሆኑ የለምን? ከቤተ መንግሥቱ
የምትሰማትን ሁሉ ንገራቸው። [36]የሳዶቅ
ልጅ አኪማአስና የአብያታር ልጅ ዮና
ታን፣ ሁለቱ ወንዶች ልጆቻቸው እዚያው
አብረዋቸው ይገኛሉ። የምትሰማትን ሁሉ
በእነርሱ ላክልኝ።"

[37]ስለዚህ የዳዊት ወዳጅ ኩሲ ልክ አቤ
ሴሎም ኢየሩሳሌም በገባበት ሰዓት እዚ
ያው ደረሰ።

## ዳዊትና ሲባ

16 ዳዊት ከተራራው ጫፍ ባሻገር ጥቂት
እልፍ ብሎ እንደ ሄደ፣ ሲባ የተ
ባለው የሜምፊቦስቴ አገልጋይ፣ ሁለት
መቶ እንጀራ፣ አንድ መቶ ጥፍጥፍ ዘቢብ፣
አንድ መቶ ጥፍጥፍ በለስና አንድ አቍ
ማዳ የወይን ጠጅ የተጫኑ ሁለት አህዮች
እየነዳ ሊገናኘው መጣ።

[2]ንጉሡም ሲባን፣ "ይህን ሁሉ ያመጣኸው
ለምንድን ነው?" ሲል ጠየቀው።

ሲባም "አህዮቹን የንጉሡ ቤተ ሰዎች እን
ዲቀመጡባቸው፣ እንጀራውንና በለሱን ወጣ
ቶቹ እንዲበሉት፣ የወይን ጠጁን ደግሞ በም
ድረ በዳ የደከሙት እንዲጠጡት
ነው"
አለው።

[3]ከዚያም ንጉሡ፣ "የጌታህ ልጅ የት ነው?"
ሲል ጠየቀው።

ሲባም፣ "'የእስራኤል ቤት ዛሬ የአባ
ቴን መንግሥት ይመልስልኛል' ብሎ ስለ
ሚያስብ፣ በኢየሩሳሌም ተቀምጦአል" አለው።

[4]ከዚያም ንጉሡ ሲባን፣ "የሜምፊቦስቴ የነ
በረው ሁሉ ከእንግዲህ ያንተ ነው" አለው።

ሲባም፣ "በታላቅ ትሕትና በግንባሬ ተደ
ፍቼ እጅ እነሣለሁ፤ ንጉሥ ጌታዬ ሆይ፤
በፊትህ ሞገስ ላግኝ" አለው።

## ሳሚ ንጉሥ ዳዊትን ረገመ

[5]ንጉሥ ዳዊት ወደ ብራቂም ሲደርስ፣ ከሳ
ኦል ቤተ ሰብ ነገድ የሆነ አንድ ሰው ብቅ
አለ፤ እርሱም የጌራ ልጅ ሳሚ ነው፤ እየ
ተራገመም ወጣ። [6]የንጉሡ ወታደሮችና
የክብር ዘቦቹ ሁሉ በዳዊት ግራና ቀኝ
ቢኖሩም እንኳ፣ በዳዊትና በሹማምንቱ
ላይ ሁሉ ድንጋይ ይወረውርባቸው ነበር።
[7]ሳሚም እንዲህ ብሎ ይራገም ነበር፤
"ውጣ! ከዚህ ውጣ! አንተ የደም ሰው፤
አንተ ክፉ ሰው፤ [8]መንግሥቱን የወሰድክ
በትን የሳኦልን ቤተ ሰው ደም ሁሉ *እግዚ
አብሔር* ወደ አንተው እየመለሰው ነው።
*እግዚአብሔር* መንግሥትህን ለልጅህ ለአ
ቤሴሎም አሳልፎ ሰጥቶታል፤ አንተ የደም
ሰው ስለ ሆንህ እነሆ፣ መከራ መጥቶ
ብሃል።"

[9]ከዚያም የጽሩያ ልጅ አቢሳ ንጉሡን፤
"ይህ የሞተ ውሻ፣ ንጉሥ ጌታዬን እን
ዴት ይራገማል? ልሻገርና ራሱን ልቍረጠው"
አለ።

[10]ንጉሡ ግን፣ "እናንት የጽሩያ ልጆች እና
ንተንና እኔን የሚያገናኘን ምን ነገር አለ?
*እግዚአብሔር*፣ 'ዳዊትን ርገመው' ብሎት
የሚረግመኝ ከሆነ፣ 'ይህን ለምን አደ
ረግህ' ብሎ ማን ሊጠይቀው ይችላል?"
አለው።

[11]ከዚያም ዳዊት አቢሳንና ሹማምንቱን
ሁሉ እንዲህ አላቸው፤ "ከአብራኬ የወ
ጣው ልጄ ሕይወቴን ሊያጠፋት ከፈለገ፣ ይህ
ብንያማዊ ቢያደርገው ምን ያስደንቃል?
ስለዚህ ተዉት፤ *እግዚአብሔር* በል ብሎት
ነውና ይራገም፤ [12]ምናልባትም *እግዚአ
ብሔር* ሐዘኔን አይቶ በዛሬውም ርግማን
ፈንታ በጎ ነገር ያደርግልኝ ይሆናል።"

[13]ስለዚህም ዳዊትና ሰዎቹ
መንገዳቸውን ቀጠሉ፤ ሳሚም በአንጻሩ
ባለው ኰረብታ ጥግ ጥግ እየሄደ ይራ
ገም፣ ድንጋይ ይወረ ውርበትና ዐፈር
ይበትንበት ነበር። [14]ንጉሡና አብረውት
የነበሩት ሰዎች ሁሉ ለመ ሄድ ወዳሰቡበት
ስፍራ ደረሱ፤ በጣም ደክ ሞአቸው ስለ
ነበር በዚያ ዐረፉ።

## የኩሲና የአኪጦፌል ምክር

[15]በዚህን ጊዜ አቤሴሎምና የእስራኤል
ሰዎች ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ፤ አኪ

15፥30 ዘኍ25፥6፤ አስ6፥12፤መዝ30፥5
15፥31 ቀኍ12
15፥32 ቀኍ37፤ኢሱ 7፥6፤16፥2፤2ሳሙ 16፥16፤17፥5፤ 1ነገ4፥16
15፥33 2ሳሙ 19፥35
15፥34 2ሳሙ 16፥19፤17፥14፤ ምሳ11፥14
15፥35 2ሳሙ 17፥15-16
15፥36 ቀኍ27፤ 2ሳሙ17፥17፤ 18፥19፤1ነገ1፥42
15፥37 2ሳሙ 16፥15፤1ዜና27፥33
16፥1 1ሳሙ 25፥18፤2ሳሙ9፥1-13 ፤1ዜና12፥40
16፥2 2ሳሙ 17፥27-29
16፥3 2ሳሙ9፥2፡ 9-10
16፥4 2ሳሙ4፥4
16፥5 ዘፀ22፥28፤ 2ሳሙ3፥16፤ 19፥16-23፤ 1ነገ2፥8-9፡36፡44
16፥8 2ሳሙ19፥19፡ 28፤21፥9፤መዝ55፥3
16፥9 1ሳሙ26፥6፤ 2ሳሙ3፥8፡39፤ ሉቃ9፥54
16፥10 2ሳሙ 2፥18፤19፥22፤ ሮሜ9፥20
16፥11 ዘፍ45፥5፤ 1ሳሙ26፥19፤ 2ሳሙ12፥11
16፥12 ዘዳ23፥5፤ መዝ4፥1፤25፥18፤ 109፥28፤ሮሜ8፥28
16፥14 2ሳሙ17፥2
16፥15 2ሳሙ 15፥12፡37
16፥16 2ሳሙ 15፥32
16፥17 2ሳሙ 19፥25
16፥19 2ሳሙ 15፥34
16፥22 2ሳሙ3፥7፤ 12፥11-12፤15፥16

ጦፌልም አብሮት ነበር። 16የዳዊት ወዳጅ
አርካዊው ኩሲም ወደ አቤሴሎም መጥቶ
“ንጉሥ ሆይ፤ ለዘላለም ንገሥ፤ ንጉሥ ሆይ፤
ለዘላለም ንገሥ” አለው።

17አቤሴሎምም፣ ኩሲን፣ “ለወዳጅህ ያለህ
ታማኝነት እስከዚህ ድረስ ነው? ለምን
ከወዳጅህ ጋር አልሄድህም?” ሲል ጠየቀው።

18ኩሲም፣ አቤሴሎምን እንዲህ አለው፤
“ይህንንስ አላደርገውም! እኔ *በእግዚአብሔር*፣
በዚህ ሕዝብና በእስራኤል ሰዎች ሁሉ
ለተመረጠው ለእርሱ እሆናለሁ፤ አብሬ
ውም እኖራለሁ፤ 19እንግዲህ ልጁን ካላገለ
ገልሁ ማንን ላገለግል ነው? አባትህን እንዳገ
ለገልሁ ሁሉ፤ አንተንም አገለግላለሁ።”

20አቤሴሎምም አኪጦፌልን፤ “እስቲ ምክር
አምጣ፤ ምን እናድርግ?” አለው።

21አኪጦፌልም መልሶ፣ “ቤተ መንግሥተ
-ን እንዲጠብቁ አባትህ ከተዋቸው ቁባቶቹ
ጋር ግባና ተኛ፤ ከዚያም አንተ፣ አባትህን
እጅግ የጠላህ መሆንህን መላው እስራኤል
ይሰማና አብሮህ ያለው ሁሉ ክንዱ ይበረታል”
አለው። 22ስለዚህ ለአቤሴሎም በሰገነቱ ላይ
ድን ኳን ተከሉለት፤ እዚያም መላው እስ
ራኤል እያየው ከአባቱ ቁባቶች ጋር
ተኛ።

23በዚያም ጊዜ አኪጦፌል የሚሰጠው ምክር
ሁሉ *የእግዚአብሔርን* ቃል እንደ መጠ
የቅ ይቈጠር ነበር፤ ዳዊትም ሆነ አቤሴሎም
የአኪጦፌልን ምክር የሚቀበሉት በዚህ
ሁኔታ ነበር።

17 አኪጦፌልም፣ አቤሴሎምን እንዲህ
አለው፤ “ዐሥራ ሁለት ሺህ ሰው
መርጬ[ሐ]፣ በዛሬዪቱ ሌሊት አባትህን አሳድ
ደዋለሁ፤ 2በደከመውና ዐቅም ባነሰው ጊዜም
አደጋ እጥልበታለሁ፤ ሽብር እለቅበታለሁ፤
ከዚያም አብሮት ያለው ሕዝብ ሁሉ ትቶት
ይሸሻል፤ ንጉሡን ብቻ እመታዋለሁ፣ 3ሕዝ
ቡን ሁሉ ወደ አንተ እመልሳለሁ፣ አንተ
የምትፈልገው የአንድ ሰው ብቻ መሞት
ሁሉም እንዲመለሱ ያደርጋል። ከዚያም ሕዝቡ
ሁሉ በሰላም ይኖራል።” 4ምክሩም አቤሴ
ሎምንና አብረውት የነበሩትን የእስራኤ
ልን ሽማግሌዎች ሁሉ ደስ አሰኘ።

5አቤሴሎም ግን፣ “እስቲ ደግሞ አርካዊ
ውን ኩሲን ጥሩትና የሚለውን እንስማ”
አለ። 6ኩሲ ወደ እርሱ በመጣ ጊዜ አቤሴ
ሎም፣ “አኪጦፌል ይህን ምክር አቅርቦአል፤
ታዲያ እርሱ ያለውን እናድርግ? ካልሆ
ነም እስቲ የአንተን ሐሳብ ንገረን” አለው።

7ኩሲም አቤሴሎምን እንዲህ አለው፤ “አኪ
ጦፌል የሰጠው ምክር በዚህ ጊዜ የሚያዋጣ
አይደለም፤ 8አባትህና ሰዎቹ የማይበገሩ ተዋ
ጊዎችና ግልገሎቿም እንደ ተነጠቀባት የዱር
ድብ አስፈሪ መሆናቸውን አንተም ታው
ቃለህ፤ በተጨማሪም አባትህ በቂ ልምድ
ያለው ነው፤ ሌሊቱን ከሰራዊቱ ጋር አያ
ድርም፤ 9እነሆ፤ አሁን እንኳ በአንዱ ዋሻ
ወይም በሌላ ቦታ ተደብቆ ይሆናል። እርሱ
ቀድሞ አደጋ በመጣል ከሰዎችህ ጥቂት
ቢሞቱ[መ] ይህን የሰማ ሁሉ፣ ‘አቤሴሎምን
የተከተለው ሰራዊት አለቀ’ ብሎ ያወራል።
10አባትህ ታላቅ ጦረኛ፣ አብረውት ያሉትም
ጀግኖች መሆናቸውን እስራኤል ሁሉ ስለ
ሚያውቅ፣ ልቡ እንደ አንበሳ ልብ ነው የተ
ባለው ደፋሩ ወታደር እንኳ በፍርሀት
ይርዳል።

11“እንግዲህ እኔ የምመክርህ ይህ ነው፤
ቍጥሩ እንደ ባሕር ዳር አሸዋ የበዛው፣
ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ያለው እስራኤል
ሁሉ ወዳንተ ይሰብሰብና አንተው ራስህ ወደ
ጦርነቱ ምራው፤ 12ከዚያም እርሱ እገባበት
ቦታ ሁሉ ገብተን አደጋ እንጥልበታለን፣
ጤዛ በመሬት ላይ እንደሚወርድ እንወር
ድበታለን፤ እርሱም ሆነ ሰዎቹ አንድ
እንኳ አይተርፉም፤ 13ከአንዲቱ ከተማ ቢገባ፣
እስራኤል ሁሉ ገመድ አምጥቶ አንድ
ድንጋይ እንኳ እስከማይቀር ድረስ፣ ከተማ
ዪቱን ወደ ሸለቆ ስበን እንከታታለን።”

14አቤሴሎምና የእስራኤል ሰዎች ሁሉ፣
“ከአኪጦፌል ምክር ይልቅ የአርካዊው የኩሲ
ምክር ይሻላል” አሉ፤ *እግዚአብሔር* በአቤ
ሴሎም ላይ ጥፋት ለማምጣት ሲል መል
ካም የነበረው የአኪጦፌል ምክር ተቀባይነት
እንዲያጣ አድርጎአልና።

15ኩሲም ካህናቱን ሳዶቅንና አብያታርን
እንዲህ አላቸው፤ “አኪጦፌል አቤሴሎም
ንና የእስራኤልን ሽማግሌዎች ምን ምን
ማድረግ እንዳለባቸው መክሮአቸው ነበር፤
እኔ ግን እንዲህ እንዲህ አድርጉ ብዬ
መክሬአቸዋለሁ። 16አሁንም በፍጥነት
ላኩና፣ ‘በምድረ በዳው ባለው የወንዙ
መሻገሪያ እንዳታድር፤ ሳትዘገይ ፈጥነህ
መሻገር አለ ብህ፤ ያለዚያ ግን ንጉሡና
አብሮት ያለው
ሕዝብ በሙሉ ትዋጣላችሁ’ ብላችሁ ለዳዊት
ንገሩት።”

17በዚህ ጊዜ ዮናታንና አኪማአስ ወደ ከተ
ማዪቱ ከገቡ ስለሚታዩ በዓይንሮጌል ይጠ
ባበቁ ነበር፤ አንዲት ልጃገረድ አገልጋይ
ወደዚያ እየሄደች በምትነግራቸው ጊዜ፣ እነ
ርሱ ደግሞ ይህንኑ ወስደው ለንጉሥ
ዳዊት ይነግሩት ነበር። 18ሆኖም አንድ
ወጣት አያቸውና ለአቤሴሎም ነገረው፤

[ሐ]1 ወይም፣ *ልምረጥ*
[መ]9 ወይም *በመጀመሪያው ጥቃት አንዳንድ ሰዎች ቢወድቁ*

16፥23 2ሳሙ15፥12፤17፥14፡23፡23
17፥2 2ሳሙ16፥14፤1ነገ22፥31፤ዘካ13፥7
17፥5 2ሳሙ15፥32
17፥8 1ሳሙ16፥18፤ሆሴ13፥8
17፥9 ኤር41፥9
17፥10 ኢሱ2፥9፡11፤2ሳሙ23፥8፤1ዜና11፥11፤12፥8፤ሕዝ21፥15
17፥11 ዘፍ12፥2፤ኢሱ11፥4፤መሳ20፥1
17፥13 ሚክ1፥6
17፥14 2ሳሙ15፥12፡34፤16፥23፤2ዜና10፥8፤ነህ4፥15፤መዝ9፥16
17፥16 2ሳሙ15፥28፡35
17፥17 ኢሱ15፥7፤18፥16፤2ሳሙ15፥27፡36፤1ነገ1፥9
17፥18 2ሳሙ3፥16

ስለ ዚህ ሁለቱም በፍጥነት ተነሥተው በብራ
ቂም ወደሚገኝ ወደ አንድ ሰው ቤት ሄዱ፤
ሰውየው በግቢው ውስጥ ጒድጓድ ስለ
ነበረው ወደዚያው ወረዱ። 19ሚስቱም በጒ
ድጓዱ አፍ ላይ የስጥ ማስጫ ዘርግታ እህል
አሰጣች፤ ማንም ይህን አላወቀም ነበር።
20የአቤሴሎም ሰዎች እዚያ ቤት ወደ ሴቲተ
ዘንድ መጥተው፣ “አኪማአስና ዮናታን
የት አሉ?” ብለው ጠየቁ።
ሴቲቱም፣ “ወንዙን ተሻግረው ሄደዋል”[ሠ]
ብላ መለሰችላቸው፤ እነርሱም ፈልገው ስላ
ጧቸው፣ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ።
21ሰዎቹ ከሄዱ በኋላ እነዚህ ሁለቱ ከጒ
ድጓዱ ወጥተው ሄዱ፤ ለንጉሥ ዳዊትም፣
“አኪጦፌል በአንተ ላይ እንዲህ እንዲህ ብሎ
ስለ መከረብህ ተነሥተህ በፍጥነት ወንዙን
ተሻገር” አሉት። 22ስለዚህ ዳዊትና አብ
ሮት ያለው ሕዝብ በሙሉ ተነሥቶ ዮር
ዳኖስን ተሻገረ፤ ሲነጋም ዮርዳኖስን ሳይሻ
ገር የቀረ አንድም ሰው አልነበረም።
23አኪጦፌልም ምክሩን
እንዳልተከተሉት ባየ ጊዜ፣ አህያውን
ጭኖ ቤቱ ወደሚገኝ በት ወደ መኖሪያ
ከተማው ሄደ፤ ቤቱንም መልክ መልክ
ካስያዘ በኋላ በገዛ እጁ ታንቆ ሞተ። በዚህ
ሁኔታም ሞቶ በአባቱ መቃ ብር
ተቀበረ።
24አቤሴሎም ከመላው የእስራኤል ሰዎች
ጋር ዮርዳኖስን ሲሻገር፣ ዳዊት ግን መሃና
ይም ደርሶ ነበር። 25አቤሴሎምም በኢዮ
አብ ምትክ አሜሳይን በሰራዊቱ ላይ
ሾመ፤ አሜሳይ የእስማኤላዊው[ረ] የዮቴር
ልጅ ነበረ፤ ዮቴርም የኢዮአብን እናት፣ የ
ጽሩያን እኅት፣ የናዖስን ልጅ አቢግያን[ሰ]
አግብቶ ነበር። 26እስራኤላውያንና አቤሴሎም
በገለዓድ ምድር ሰፈሩ።
27ዳዊት መሃናይም ሲደርስ፣ ከአሞናው
ያን ከተማ ከራባ የመጣው፣ የናዖስ ልጅ
ሾቢ፣ ከሎዶባር የመጣው የዓሚኤል ልጅ
ማኪርና ከሮግሊም የመጣው ገለዓዳዊው ቤር
ዜሊ 28መተኛ ምንጣፎች፣ ወጭቶችና የሸ
ክላ ዕቃዎች ይዘው መጡ፤ እንዲሁም ስን
ዴና ገብስ፣ ዱቄትና የተጠበሰ እሸት፣ ባቄ
ላና ምስር[ሸ]፣ 29ማር፣ እርጎ፣ በጎችና የላም
አይብ እንዲበሉ ለዳዊትና ለሕዝቡ አመጡ
ላቸው፤ ይህን ያደረጉትም፣ “ሕዝቡ በም
ድረ በዳ ተርቦአል፤ ደክሞአል፤ ተጠምቶአል”
በማለት ነው።

## የአቤሴሎም መሞት

18 ዳዊት አብሮት የነበረውን ሕዝብ
ቈጠረ፤ የሻለቆችንና የመቶ አለቆ
ችን ሾመላቸው። 2ዳዊትም ሰራዊቱን ሲሦ
ውን በኢዮአብ፣ ሲሦውን በኢዮአብ ወን
ድም በጽሩያ ልጅ በአቢሳ፣ ሲሦውን ደግሞ
በጌታዊው በኢታይ አዛዥነት ሥር ላካቸው።
ንጉሡም ለሰራዊቱ፣ “እኔ ራሴም አብሬአ
ችሁ በእርግጥ እወጣለሁ” አላቸው።
3ሰዎቹ ግን፣ “አንተ መውጣት የለብህም፤
እንድንሸሽ ብንገደድ፣ ሰዎቹ ከቁም ነገር
አይቈጥሩንም፤ ግማሾቻችን እንኳ ብን
ሞት ደንታቸው አይደለም፣ አንተ ግን
ብቻህን ከእኛ ከዐሥሩ ሺህ ትበልጣለህ[ቀ]፤
ስለዚህ በከተማ ሆነህ ብትረዳን ይሻላል”
አሉት።
4ንጉሡም፣ “መልካም መስሎ የታያች
ሁን ሁሉ አደርጋለሁ” አላቸው። ስለዚህ
ሕዝቡ ሁሉ በመቶና በሺህ እየሆነ ተሰልፎ
ሲወጣ፣ ንጉሡ በቅጥሩ በር ቆሞ ነበር።
5ንጉሡም ኢዮአብን፣ አቢሳንና ኢታይን፣
“ለእኔ ስትሉ በወጣቱ ልጄ በአቤሴሎም ላይ
ጒዳት እንዳ ታደርሱበት” ብሎ አዘዛቸው።
ንጉሡ ልጁን አቤሴሎምን አስመልክቶ ለእ
ያንዳንዱ አዛዥ ትእዛዝ ሲሰጥ ሰራዊቱ
ሁሉ ሰማ።
6ሰራዊቱ እስራኤልን ለመውጋት ተሰ
ልፎ ወደ ሜዳ ወጣ፤ ጦርነቱም
በኤፍሬም ደን ውስጥ ሆነ። 7እዚያም የእስ
ራኤል ሰራ ዊት በዳዊት ሰዎች ተመታ፤
በዚያም ቀን ታላቅ እልቂት ሆነ፤ ሃያ ሺ
ህም ሰው ተገደለ። 8ውጊያው በገጠሩ
ሁሉ ተስፋፋ፤ በዚያን ቀን ሰይፍ
ከጨረሰው ይልቅ ጫካ ውጦ ያስቀረው ሰው
በለጠ።
9በዚህ ጊዜ አቤሴሎም ከዳዊት ሰዎች ጋር
ድንገት ተገናኘ፤ አቤሴሎም በበቅሎ ተቀ
ምጦ ይሄድ ስለ ነበር፣ በቅሎዋ ጥቅጥቅ ያለ
ቅርንጫፍ ባለው ትልቅ ወርካ ሥር በም
ታልፍበት ጊዜ፣ የአቤሴሎም ራስ በዛፉ
ቅርንጫፍ ተያዘ፤ የተቀመጠበትም በቅሎ
በሥሩ ስታልፍ፣ እርሱ በሰማይና በምድር
መካከል ተንጠልጥሎ ቀረ።
10አንድ ሰው ይህን አይቶ ለኢዮአብ፣
“እነሆ፤ አቤሴሎም በባሉጥ ዛፍ ላይ ተንጠል
ጥሎ አየሁት” አለው።
11ኢዮአብም ይህን የነገረውን ሰው፣ “ምን
አልህ! ካየኸው ታዲያ ለምንድን ነው ያኔ
ውኑ መተህ መሬት ላይ ያልጣልኸው?

[ሠ]20 ወይም፣ *በበጎች ጒረኖ አድርገው ወደ ውሃው ተሻገሩ*
[ረ]25 ዕብራይስጡና አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች፣ ***እስ
ራኤላዊ*** ይላሉ፤ አብዛኞቹ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች ግን፣
***እስማኤላዊ*** ወይም ***ይዝራኢላዊ*** ይላሉ (1ዜና 2፥17 ይመ)።
[ሰ]25 በዕብራይስጥ፣ ***አቢግያ*** ማለትና፣ ***አቢጋኤል*** ማለት አንድ ነው።
[ሸ]28 አብዛኞቹ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞችና የሱርስቱ ቅጅ ከዚህ
ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን፣ ***ምስርና የተቈላ ባቄላ*** ይላል።
[ቀ]3 ሁለት የዕብራይስጥ ቅጆች፣ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒ
ሞች እንዲሁም ቩልጌት ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ
ትርጒሞች ግን፣ ***አሁን እንደኛ የሆኑ ዐሥር ሺህ አሉ*** ይላል።

17፥19 ኢሱ2፥6
17፥20 ዘፀ1፥19
17፥23 2ሳሙ 16፥23፤2ነገ20፥1
17፥24 ዘፍ32፥2
17፥25 2ሳሙ 19፥13፤20፥4፡9-12፤ 1ነገ2፥5፡32፤1ዜና 2፥13-17፤12፥18
17፥27 ዘዳ3፥11፤ 1ሳሙ11፥1፤2ሳሙ 9፥4፤19፥31-39፤ 1ነገ2፥7፤ዕዝ2፥61
17፥29 2ሳሙ 16፥2፤1ዜና12፥40፤ ሮሜ12፥13
18፥2 መሳ7፥16፤ 1ሳሙ11፥11፤26፥6፤ 2ሳሙ15፥19
18፥3 1ሳሙ18፥7፤ 2ሳሙ21፥17
18፥6 ኢሱ17፥15
18፥9 2ሳሙ14፥26
18፥11 1ሳሙ 18፥4፤2ሳሙ3፥39

ይህን አድርገህ ቢሆን ኖሮ፣ ዐሥር ሰቅል[ሀ]
ጥሬ ብርና የጀግና ሰው ቀበቶም እሸልምህ
ነበር” አለው።
[12]ሰውየው ግን እንዲህ አለ፤ “እኛ እየሰ
ማን ንጉሡ፣ ‘ወጣቱ አቤሴሎም ጒዳት
እንዳያ ገኘው ስለ እኔ ብላችሁ ጠብቀ
ት’[ተ] ብሎ አንተን፣ አቢሳንና ኢታይን
ያዘዛችሁ ስለ ሆነ፣ አንድ ሺህ ሰቅል[ቸ]
ጥሬ ብር በእጄ ላይ ቢመዘንልኝ እንኳ፣
በንጉሡ ልጅ ላይ እጄን አላነሣም።
[13]በሌላ በኩል ደግሞ በነፍሴ ቈርጬ ሕ
ይወቱን ባጠፋው ኖሮ[ኀ]፣ ከንጉሡ ተደብቆ
የሚቀር ነገር ስለ ሌለ፣ አንተም ራስህ
አትቀርበኝም ነበር” ብሎ መለሰለት።
[14]ኢዮአብም፣ “ከእንግዲህ በዚህ ሁኔታ
ከአንተ ጋር ጊዜ ማጥፋት አልችልም” አለው፤
ስለዚህ በእጁ ሦስት ጦር ይዞ ሄደና አቤ
ሴሎም እዛፉ ላይ ተንጠልጥሎ ገና በሕይ
ወት እያለ፣ ወርውሮ በልቡ ላይ ተከላቸው።
[15]እንዲሁም ከኢዮአብ ጋሻ ጃግሬዎች ዐሥሩ
አቤሴሎምን በመክበብ ወግተው ገደሉት።
[16]ከዚያም ኢዮአብ ቀንደ መለከት
ነፍቶ ስለ ከለከላቸው፣ ሰራዊቱ እስራ
ኤልን ማሳ ደዱን አቆመ። [17]አቤሴሎምን
ጫካ ወስ ደው በትልቅ ጒድጓድ ውስጥ
ወርውረው ጣሉት፤ በላዩም ትልልቅ
ድንጋይ ከመሩበት። በዚህ ጊዜ እስራ
ኤላውያን ሁሉ ወደ የቤታቸው ሸሹ።
[18]አቤሴሎም፣ “ስሜን የሚያስጠራ ልጅ
የለኝም” በማለት መታሰቢያ እንዲሆነው
በሕ ይወት እያለ የንጉሥ ሸለቆ በተባለው
ስፍራ በራሱ ስም ሐውልት አቁሞ ስለ ነበር፣
እስከ ዛሬ ድረስ የአቤሴሎም ሐውልት
ተብሎ ይጠራል።

## የዳዊት ሐዘን

[19]በዚህ ጊዜ የሳዶቅ ልጅ አኪማአስ፣ “*እግ
ዚአብሔር* ጠላቶቹን የተበቀለለት መሆ
ኑን ሮጬ ሄጄ ለንጉሡ የምሥራች ልን
ገረው” አለ።
[20]ኢዮአብም፣ “ዛሬ የምሥራቹን ወሬ የም
ትወስድለት አንተ አይደለህም፤ የንጉሡ ልጅ
ስለ ሞተ፣ ዛሬ ሳይሆን፣ የምሥራቹን ሌላ
ጊዜ ታደርስለታለህ” አለው።
[21]ከዚያም ኢዮአብ ለኢትዮጵያዊው፣ “ሂድና
ያየኸውን ለንጉሡ ንገር” አለው፤ ኢትዮጵ
ያዊውም ኢዮአብን እጅ ነሥቶ እየሮጠ
ሄደ።
[22]የሳዶቅ ልጅ አኪማአስም እንደ ገና ኢዮ
አብን፣ “የመጣው ይምጣ፤ እባክህ ኢትዮ
ጵያዊውን ተከትየው ልሩጥ” አለው።
ኢዮአብ ግን፣ “ልጄ ሆይ፣ መሂድ ለምን

18፥13 2ሳሙ 14፥19-20
18፥14 2ሳሙ 2፥18
18፥15 2ሳሙ 12፥10
18፥16 2ሳሙ 2፥28
18፥17 ኢሱ 7፥26፤ 8፥29
18፥18 ዘፍ 14፥17፤ 50፥5፤ ዘኍ 32፥42፤ 2ሳሙ 14፥27
18፥19 መሳ 11፥36፤ 2ሳሙ 15፥36
18፥24 1ሳሙ 14፥16፤ ኤር 51፥12
18፥26 1ነገ 1፥42፤ ኢሳ 52፥7፤ 61፥1
18፥27 2ነገ 9፥20
18፥32 መሳ 5፥31፤ 1ሳሙ 25፥26

አስፈለገህ? ሽልማት የሚያስጥህ ምን የም
ሥራች ይዘህ ነው?” ብሎ መለሰለት።
[23]አኪማአስም፣ “የመጣው ይምጣ፤ መሄድ
እፈልጋለሁ” አለ።
ስለዚህም ኢዮአብ፣ “እንግዲያውማ ሩ
ጥ!” አለው። ከዚያም አኪማአስ በሜዳው
መን ገድ[ነ] ሮጦ ኢትዮጵያዊውን ቀድሞት
ሄደ።
[24]ዳዊት በውስጠኛውና በውጭኛው በሮች
መካከል ተቀምጦ ሳለ፣ ጠባቂው ቅጥሩ
ላይ ወዳለው ወደ በሩ ሰገነት ጣራ ወጥቶ
ወደ ውጭ ሲመለከት አንድ ሰው ብቻ
ውን ሲሮጥ አየ። [25]ጠባቂውም ተጣራና
ይህንኑ ለንጉሡ ነገረው፤
ንጉሡም፣ “ብቻውን ከሆነ መልካም
ወሬ ይዞ የመጣ መሆን አለበት” አለ።
ሰውየውም እየቀረበ መጣ።
[26]ከዚያም ጠባቂው ሌላ ሰው ሲሮጥ አይቶ፣
ዘበኛውን ተጣራና፣ “እነሆ ሌላም ሰው ብቻ
ውን እየሮጠ በመምጣት ላይ ነው!” አለ።
ንጉሡም፣ “ይኸኛውም መልካም ወሬ ይዞ
የመጣ መሆን አለበት” አለ።
[27]ጠባቂውም፣ “የመጀመሪያው ሰው ሩጫ
የሳዶቅን ልጅ የአኪማአስን ሩጫ ይመስለ
ኛል” አለ።
ንጉሡም፣ “እርሱማ ጥሩ ሰው ነው፤ የም
ሥራች ሳይዝ አይመጣም” አለ።
[28]አኪማአስም ጮኾ ንጉሡን፣ “ሁሉም ነገር
ተሳክቶአል” አለ፤ ከዚያም ወደ መሬት ለጥ
ብሎ በንጉሡ ፊት እጅ ነሣና፣ “በጌታዬ
በንጉሡ ላይ እጃቸውን ያነሡትን ሰዎች አሳ
ልፎ የሰጠ አምላክ *እግዚአብሔር* የተመሰ
ገነ ይሁን!” አለ።
[29]ንጉሡም፣ “ብላቴናው አቤሴሎም ደኅና
ነውን?” ሲል ጠየቀ።
አኪማአስም፣ “ኢዮአብ የንጉሡን አገል
ጋይና እኔንም ባሪያህን ሊልክ ሲል፣ ትልቅ
ሁካታ አይቻለሁ፤ ምን እንደ ሆነ ግን
አላወቅሁም” ብሎ መለሰ።
[30]ንጉሡም፣ “እልፍ በልና ቁም”
አለው፤ ስለዚህ እልፍ ብሎ ቆመ።
[31]ከዚያም ኢትዮጵያዊው ደርሶ፣
“ንጉሥ ጌታዬ ሆይ፤ የምሥራች! ዛሬ *እግዚ
አብሔር* ከተነሡብህ ጠላቶችህ ሁሉ ታድጎ
ሃል” አለው።
[32]ንጉሡም ኢትዮጵያዊውን፣ “ብላቴናው
አቤሴሎም ደኅና ነውን?” ሲል ጠየቀው።

[ሀ]11 115 ግራም ያህል ነው።
[ተ]12 አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ የሰብዓ ሊቃናት፣ የቩልጌትና የሱርስት ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አብዛኞቹን የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ ***አቤሴሎም ምንም ዐይነት ሰው ብትሆን*** ይላሉ።
[ቸ]12 11 ኪሎ ግራም ያህል ነው።
[ኀ]13 ወይም፣ ***ወይም እርሱን ባታልለው ኖሮ***
[ነ]23 ይህ የዮርዳኖስ ሜዳማ ስፍራ ነው።

ኢትዮጵያዊውም፣ “የጌታዬ የንጉሡ ጠላቶ
ችና ሊጐዱህ የሚነሡብህ ሁሉ እንደዚያ
ወጣት ይሁኑ” ሲል መለሰ።
33ንጉሡም እጅግ አዘነ፤ በቅጽር በሩ ዐናት
ላይ ወዳለችው ቤት ወጥቶ አለቀሰ፤ ሲሄ
ድም፣ “ልጄ አቤሴሎም ሆይ! ልጄ አቤሴ
ሎም! በአንተ ፈንታ ምነው እኔ በሞትሁ
ኖሮ! አቤሴሎም ሆይ፣ ልጄን፣ ወየው ልጄን!”
ይል ነበር።

19 ለኢዮአብ፣ “ንጉሡ ዳዊት ስለ ልጁ
ስለ አቤሴሎም እያለቀሰ እያዘነ ነው”
ተብሎ ተነገረው። 2ንጉሡ፣ “ስለ ልጁ
አዝኖአል” መባሉን በዚያ ቀን ሰራዊቱ
ሰምቶ ስለ ነበር፣ የዚያ ዕለት ድል በመ
ላው ሰራዊት ዘንድ ወደ ሐዘን ተለውጦ
ዋለ። 3በዚያችም ዕለት ከጦርነት ሸሽቶ
በኀፍረት እየተሸማቀቀ ወደ ከተማ እንደሚገባ
ሰው ሕዝቡም ተሸማቆ ወደ ከተማ ገባ።
4ንጉሡ ፊቱን ሸፍኖ፣ “ልጄ አቤሴሎም
ሆይ፤ ልጄን! ወየው ልጄን!” እያለ ጮኸ።
5ከዚያም ኢዮአብ ወደ ንጉሡ ቤት ገብቶ
እንዲህ አለው፤ “የአንተን፣ የወንዶችን የሴ
ቶች ልጆችህን፣ የሚስቶችህንና የቁባቶች
ህን ሕይወት ያተረፉትን ሰዎች ሁሉ ዛሬ
አሳፍረሃቸዋል። 6የሚጠሉህን ትወዳለህ፤ የሚ
ወዱህን ትጠላለህ፤ የጦር አዛዦችህና ወታደ
ሮቻቸው ለአንተ ምንህም እንዳይደሉ ይኸው
ዛሬ ግልጽ አድርገሃል፤ ዛሬ አቤሴሎም
በሕይወት ኖሮ እኛ ሁላችን አልቀን ቢ
ሆን ደስ እንደሚልህ በዛሬው ዕለት ለ
ማየት በቅቻለሁ። 7በል አሁን ተነሥተህ
ውጣና ሰዎ ችህን አበረታታ፤ ባትወጣ ግን
በዚች ሌሊት አንድም ሰው አብሮህ እንደ
ማይ ሆን በእግዚአብሔር እምላለሁ፤ ይህ
ደግሞ ከልጅነትህ ጀምሮ እስካሁን ድረስ
ከደረሰ ብህ ክፉ ነገር ሁሉ የባሰ መከራ
ያስከት ልብሃል።” 8ስለዚህ ንጉሡ ተነሥቶ
በበሩ አጠገብ ተቀመጠ፤ ለሕዝቡም፣ “እነሆ
ንጉሡ በበሩ አጠገብ ተቀምጦአል” ተብሎ
በተነ ገረ ጊዜ ሕዝቡ በሙሉ ወደ ንጉሡ
መጣ።

## ዳዊት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ

በዚያን ጊዜ እስራኤላውያን በሙሉ ወደ
የቤታቸው ሸሽተው ነበር።
9በመላው የእስራኤል ነገዶችም፣ ሕዝቡ
እንዲህ እያለ እርስ በርሱ ይከራከር ነበር፤
“ንጉሡ ከጠላቶቻችን እጅ አውጥቶናል፤ ከፍ
ልስጥኤማውያንም እጅ የታደገን እርሱ ነው፤
አሁን ግን በአቤሴሎም ምክንያት ከአገር
ሸሽቶ ሄዶአል፤ 10በላያችን ሆኖ እንዲገዛን
የቀባነው አቤሴሎም ደግሞ በጦርነት ሞቶ
አል፤ ታዲያ ንጉሡን የመመለሱን ጉዳይ
ለምንድን ነው ዝም የምትሉት?”
11ንጉሥ ዳዊት ወደ ካህናቱ ወደ ሳዶ
ቅና ወደ አብያታር እንዲህ ሲል መልእክት
ላከ፤ “የእስራኤል ሽማግሌዎችን እንዲህ
በኋቸው አለ፤ ‘በመላው እስራኤል የሚባ
ለው ሁሉ ለንጉሡ ባለበት የደረሰው ስለ
ሆነ፣ ንጉሡን ወደ ቤተ መንግሥቱ ለመ
መለስ እንዴት የመጨረሻ ሰዎች ትሆናላ
ችሁ? 12እናንተ የዐጥንቴ ፍላጭ፣ የሥጋዬ
ቊራጭ ወንድሞቼ ናችሁ፤ ታዲያ ንጉ
ሡን ለመመለስ እንዴት የመጨረሻ ሰዎች
ትሆናላችሁ?’ 13አሜሳይንም፣ ‘አንተስ የዐ
ጥንቴ ፍላጭ፣ የሥጋዬ ቊራጭ አይደለህ
ምን? ከአሁን ጀምሮ እስከ ሕይወትህ ፍጻሜ
በኢዮአብ ምትክ የሰራዊቴ አዛዥ ባላደ
ርግህ፣ እግዚአብሔር ክፉ ያድርግብኝ፣
ከዚህ የባሰም ያምጣብኝ’ ብላችሁ ንገሩት።”
14እርሱም የይሁዳን ሰዎች ልብ ሁሉ እንደ
አንድ ሰው ልብ አድርጎ ማረከው፤ እነር
ሱም “አንተም ሰዎችህም ሁሉ ተመለሱ”
ብለው ላኩበት። 15ከዚያም ንጉሡ ተመ
ልሶ እስከ ዮርዳኖስ ድረስ መጣ።
በዚህ ጊዜ የይሁዳ ሰዎች ንጉሡን ተቀ
ብለው ዮርዳኖስን ለማሻገር እስከ ጌልገላ
ድረስ መጥተው ነበር። 16የብራቂም ሰው
የሆነው የጌራ ልጅ ብንያማዊው ሳሚ ከይ
ሁዳ ሰዎች ጋር ሆኖ ንጉሥ ዳዊትን ለመ
ቀበል ፈጥኖ ወረደ። 17ከእርሱም ጋር አንድ
ሺህ ብንያማውያን፣ እንዲሁም የሳኦል
ቤተ ሰብ አገልጋይ ሲባ ከዐሥራ አምስት
ወንዶች ልጆቹና ከሃያ አሽከሮቹ ጋር ሆኖ
አብረውት ነበሩ። ከዚያም ንጉሡ ወዳለ
በት ወደ ዮርዳኖስ በጥድፊያ ወረዱ።
18የንጉሡን ቤተ ሰው ለማምጣትና እርሱ
የሚፈልገውንም ሁሉ ለማድረግ በመልካው
ተሻገሩ።
የጌራ ልጅ ሳሚ ዮርዳኖስን ተሻገረ፤
በንጉሡም ፊት ተደፍቶ፣ 19እንዲህ አለ፤
“ጌታዬ በደሌን አይቊጠርብኝ፤ ንጉሥ
ጌታዬ ከኢየሩሳሌም በወጣህባት ዕለት
የፈጸምሁትን ስሕተት እርሳው፤ ከአእምሮ
ህም አውጣው። 20እኔ አገልጋይህ ኀጢአት
መሥራቴን አውቃለሁና፤ ዛሬ ግን ጌታ
ዬን ንጉሡን ለመቀበል ከዮሴፍ ቤት ሁሉ
የመጀመሪያ ሆኜ እነሆ መጥቻለሁ።”
21ከዚያም የጽሩያ ልጅ አቢሳ፣ “ሳሚ
በእግዚአብሔር የተቀባውን የረገመ ስለ
ሆነ፣ መሞት አይገባውምን?” አለ።
22ዳዊትም፣ “እናንት የጽሩያ ልጆች፣ እና
ንተንና እኔን ምን የሚያገናኘን ነገር አለ?
ዛሬ ጠላት ሆናችሁኛል! ማንስ ቢሆን ዛሬ

18፥33 ዘፍ43፥14፤ ዘፀ32፥32፤2ሳሙ 19፥4
19፥7 ምሳ14፥28
19፥8 2ሳሙ15፥2
19፥9 2ሳሙ8፥1-14 ፤15፥14
19፥11 2ሳሙ 15፥24
19፥13 ዘፍ29፥14፤ ሩት1፥17፤ 2ሳሙ2፥13፤17፥25
19፥15 1ሳሙ 11፥15
19፥16 2ሳሙ 16፥5-13
19፥17 ዘፍ43፥16፤ 2ሳሙ9፥2
19፥19 2ሳሙ 16፥6-8
19፥21 ዘፀ22፥28፤ 1ሳሙ12፥3፤26፥6፥9
19፥22 1ሳሙ 11፥13፤2ሳሙ2፥18፤ 16፥10

በእስራኤል ዘንድ ሰው መሞት አለበት? እኔ
በእስራኤል ላይ ንጉሥ መሆኔን ያወቅሁበት
ቀን አይደለምን?" ብሎ መለሰ። 23ስለዚህ
ንጉሡ ሳሚን፣ "አትሞትም" አለው፤ ይህንንም
ንጉሡ በመሐላ አጸናለት።

24የሳኦል ልጅ ሜምፊቦስቴም ንጉሡን
ለመቀበል ወረደ። ንጉሡ ከተሰደደበት ጊዜ
ጀምሮ እስከ ተመለሰበት ዕለት ድረስ ለእ
ግሩ ተገቢውን ጥንቃቄ አላደረገም፤ ጢሙን
አልተላጨም፤ ልብሱንም አላጠበም ነበር።
25እርሱም ንጉሡን ለመቀበል ከኢየሩሳ
ሌም በመጣ ጊዜ ንጉሡ፣ "ሜምፊቦስቴ፣
አብረኸኝ ያልሄድኸው ለምንድን ነው?"
ሲል ጠየቀው።

26እርሱም እንዲህ አለው፤ "ጌታዬ ንጉሥ
ሆይ፤ እኔ አገልጋይህ ሽባ በመሆኔ፣ 'ከንጉ
ሡ ጋር መሄድ እንድችል አህያዬ
ይጫንል ኝና ልቀመጥበት' ብዬ ነበር፤
ይሁን እንጂ አገልጋዬ ሲባ አታለለኝ።
27በጌታዬ በንጉሡ ፊትም የእኔን
የባሪያህን ስም አጥፍቶአል፤ መቼም
ንጉሥ ጌታዬ እንደ እግዚአብሔር
መልአክ ስለ ሆንህ ደስ ያለህን ሁሉ
አድርግ። 28የአባቴ ቤት ሁሉ ከንጉሥ
ጌታዬ ሞት እንጂ ሌላ የሚ ገባው
አልነበረም፤ አንተ ግን ባሪያህን በማ እድህ
ከሚካፈሉት ጋር አስቀመጥኸው፤ ከዚህ
በላይ ይደረግልኝ ብዬ ንጉሡን ለመጠየቅ
ምን መብት አለኝ?"

29ንጉሡም፣ "ነገርህን ለምን ታበዛለህ?
አንተና ሲባ ዕርሻውን ሁሉ እንድትካፈሉ
አዝዣለሁ" አለው።

30ሜምፊቦስቴም ንጉሡን፣ "ንጉሥ ጌታዬ
እንኳን በደኅና ተመለሰ እንጂ፣ እርሱ
ሁሉንም ይውሰደው" አለው።

31እንዲሁም ገለዓዳዊው ቤርዜሊ ከሮግ
ሊም ወረደ፤ ንጉሡን ለመሸኘትም አብ
ሮት ዮርዳኖስን ተሻገረ። 32በዚያን ጊዜ
ቤርዜሊ በዕድሜ የገፋ የሰማንያ ዓመት
ሽማግሌ ነበር፤ እጅግ ባለ ጸጋ ስለ ነበረም
ንጉሡ በመሃናይም ሳለ የሚመገበውን
አምጥቶለት ነበር። 33ንጉሡም ቤርዜሊን፣
"ከእኔ ጋር ተሻገርና በኢየሩሳሌም አብ
ረኸኝ ኑር፤ እኔ እመግብሃለሁ" አለው።

34ቤርዜሊ ግን ለንጉሡ እንዲህ ሲል መለ
ሰለት፤ "ከንጉሡ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም
የም ሄደው ለየትኛው ዕድሜዬ ብዬ ነው?
35እኔ አሁን የሰማንያ ዓመት ሽማግሌ ነኝ፤
ታዲያ ደግና ክፉውን መለየት እችላለሁ?
ከእንግዲህ አገልጋይህ የሚበላውንና የሚጠ
ጣውን ጣዕሙን መለየት ይችላል? የሚዘ
ፍኑትን የወንዶችና የሴቶችን ድምፅ አሁ

19፥23 1ነገ2፥8፡42
19፥24 2ሳሙ4፥4
19፥25 2ሳሙ 16፥17
19፥26 ዘሌ21፥28፤ 2ሳሙ9፥2
19፥27 1ሳሙ29፥9
19፥28 2ሳሙ9፥7፡ 13፤16፥8
19፥31 2ሳሙ17፥ 27-29፤1ነገ2፥7
19፥32 1ሳሙ25፥2
19፥35 2ዜና35፥ 25፤ዕዝ2፥65፤ መዝ90፥10፤መክ2፥8፤ 12፥1
19፥37 ዘፍ49፥29፤ ኤር41፥17
19፥39 ዘፍ47፥7
19፥41 መሳ8፥1፤ 12፥1
19፥43 2ሳሙ5፥1
20፥1 ዘፍ29፥14፤ 31፥14፤1ሳሙ 22፥7-8፤1ነገ12፥16
20፥3 2ሳሙ15፥16
20፥4 2ሳሙ17፥25

ንም መስማት እችላለሁ? ታዲያ አገልጋይህ
ለንጉሥ ጌታዬ ለምን ተጨማሪ ሸክም
ይሆናል? 36አገልጋይህ ዮርዳኖስን ተሻግሮ
ከንጉሡ ጋር ጥቂት መንገድ ይሄዳል፤ ነገር
ግን ንጉሡ በዚህ ሁኔታ ወሮታ የሚመልስ
ልኝ ለምንድን ነው? 37በገዛ ከተማዬ ሞቼ
በአባቴና በእናቴ መቃብር አጠገብ እቀ
በር ዘንድ፣ አገልጋይህን አሰናብተውና
ይመለስ፤ ነገር ግን አገልጋይህ ከመዓም
እነሆ፤ ከጌታዬ ከንጉሡ ጋር ይሻገር፤ ደስ
ያለህንም ነገር አድርግለት።"

38ንጉሡም፣ "ከመዓም ከእኔ ጋር ይሻገራል፤
አንተን ደስ የሚያሰኝህንም ሁሉ አደርግለ
ታለሁ፤ ከእኔ የምትፈልገውን ማናቸው
ንም ነገር ለአንተም አደርግልሃለሁ" አለው።

39ስለዚህም ሕዝቡ በሙሉ ዮርዳኖስን
ተሻገረ፤ ከዚያ በኋላም ንጉሡ ተሻገረ።
ንጉሡ ቤርዜሊን ስሞ መረቀው፤ ቤርዜሊም
ወደ ቤቱ ተመለሰ።

40ንጉሡ ወደ ጌልገላ ሲሄድ፣ ከመዓም
አብሮት ሄደ። የይሁዳ ሰራዊት በሙሉ
እንዲሁም ግማሹ የእስራኤል ሰራዊት ንጉ
ሡን አጅበው አሻገሩት።

41ወዲያውም የእስራኤል ሰዎች ሁሉ
ወደ ንጉሡ መጥተው፣ "ወንድሞቻችን
የይሁዳ ሰዎች ንጉሡን በሹልክታ ለብቻ
ቸው ይዘው እርሱንና ቤተ ሰውን ከተከታ
ዮቹ ጋር ዮርዳኖስን ለምን አሻገሩ?"
አሉት።

42የይሁዳም ሰዎች ሁሉ፣ ለእስራኤል ሰዎች፣
"ይህን ያደረግነው ንጉሡ የቅርብ ዘመዳ
ችን ስለሆነ ነው፤ ታዲያ ይህ እናንተን
የሚያስቈጣ ነው? እኛ ከንጉሡ ተቀብለን
አንዳች በልተናልን? ለራሳችንስ ምን የወ
ሰድነው ነገር አለ?" አሉአቸው።

43ከዚያም የእስራኤል ሰዎች ለይሁዳ ሰዎች፣
"እኛ እኮ ከንጉሡ ዐሥር እጅ ድርሻ አለን፤
ከዚህም በተጨማሪ በዳዊት ላይ ከእናንተ
ይልቅ እኛ የበለጠ መብት አለን፤ ታዲያ
እኛን የናቃችሁን ስለ ምንድን ነው? ንጉ
ሣችን እንዲመለስ በመጀመሪያ የጠየቅ
ነው እኛ አይደለንምን?" አሉ።

ነገር ግን የይሁዳ ሰዎች የሰጡት መልስ
የእስራኤል ሰዎች ከሰጡት መልስ ይልቅ
እጅግ የከረረ ነበር።

## ሳቤዔ በዳዊት ላይ ዐመፀ

20 በዚህ ጊዜ የቢክሪ ልጅ ስሙ ሳቤዔ
የተባለ አንድ ምናምንቴ ብንያማዊ
በዚያ ነበረ፤ እርሱም መለከት ነፍቶ እንዲህ
ሲል ጮኸ፤ "እኛ ከዳዊት ድርሻ የለንም፤
ከእሴይም ልጅ ርስት የለንም፤ እስራኤል
ሆይ፤ እያንዳንድህ ወደ ድንኳንህ ተመለስ!"

[2]ስለዚህ የእስራኤል ሰው ሁሉ ዳዊትን
ከድቶ የቢክሪን ልጅ ሳቤዔን ተከተለ።
የይሁዳ ሰዎች ግን ከዮርዳኖስ አንሥቶ
እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ ከንጉሣቸው ሳይ
ለዩ አብረውት ሄዱ።
[3]ዳዊት ኢየሩሳሌም ወዳለው ቤተ መን
ግሥቱ በተመለሰ ጊዜ፤ ቤተ መንግሥቱን
እንዲጠብቁ ትቶአቸው የሄደውን ዐሥሩን
ቁባቶቹን ወሰደ፤ በአንድ ቤትም ውስጥ
እንዲጠበቁ አደረገ። ቀለብ ሰጣቸው፤
ይሁን እንጂ ወደ እነርሱ አልገባም ነበር፤
እነርሱም እስከ ሞቱበት ጊዜ ድረስ መበ
ለት ሆነው፣ ለብቻቸው ተገልለው ተቀ
መጡ።
[4]ከዚያም ንጉሡ አሜሳይን፣ “የይሁዳ
ሰዎች ሁሉ በሦስት ቀን ውስጥ፣ ወደ እኔ
እንዲመጡ ጥራልኝ፤ አንተ ራስህም ተገኝ”
አለው። [5]አሜሳይ ይሁዳን ለመጥራት ሄደ፤
ነገር ግን ንጉሡ ከወሰነው ጊዜ በላይ ቈየ።
[6]ዳዊትም አቢሳን፣ “ከአቤሴሎም ይልቅ
አሁን የቢክሪ ልጅ ሳቤዔ የበለጠ ጕዳት ሊ
ያ ደርስብን ስለ ሆነ የጌታህን ሰዎች
ይዘህ አሳደው፤ ያለዚያ የተመሸገ ከተማ
አግኝቶ ያመልጠናል” አለው። [7]ስለዚህ
የኢዮአብ ሰዎች፣ ከሊታውያን፣ ፈሊ
ታውያን እንዲሁም ሌሎች ኀያላን ጦረኞች
በሙሉ በአቢሳ አዛዥነት ወጡ፤ ከኢየሩ
ሳሌም የወጡትም የቢክሪ ልጅ ሳቤዔን ለ
ማሳደድ ነበር።
[8]በገባዖን ከታላቁ ቋጥኝ አጠገብ ሳሉ፣
አሜሳይ ሊገናኛቸው መጣ፤ ኢዮአብ የጦር
ሜዳ ልብሱን ለብሶ ሰይፉን ከሰገባው በወ
ገቡ ላይ ታጥቆ ነበር፤ ወደ ፊት ራመድ
እንዳለም ሰይፉ ከሰገባው ወጥቶ ወደቀ።
[9]ኢዮአብም አሜሳይን፣ “ወንድሜ ሆይ፤
እንደምንድን ነህ?” አለው፤ ከዚያም አሜሳይን
የሚስም መስሎ በቀኝ እጁ ጢሙን ያዘው።
[10]አሜሳይ ግን በኢዮአብ እጅ ሰይፍ መኖሩን
ልብ ስላላለ ጥንቃቄ አላደረገም፤ ስለዚህ
ኢዮአብ ሰይፉን ሆዱ ላይ ሻጠበት፤ አንጀ
ቱም መሬት ላይ ተዘረገፈ፤ ከዚያም ኢዮአብ
መድገም ሳያስፈልገው፣ አሜሳይ በዚያው
ሞተ። ከዚህ በኋላ ኢዮአብና ወንድሙ አቢሳ፣
የቢክሪን ልጅ ሳቤዔን ማሳደድ ጀመሩ።
[11]በአሜሳይ ሬሳ አጠገብ ከቆሙት ከኢ
ዮአብ ሰዎች አንዱ፤ “ኢዮአብን የሚወድ፣
የዳዊትም የሆነ ሁሉ ኢዮአብን ይከተል!”
አለ። [12]በዚህን ጊዜ የአሜሳይ ሬሳ በደም
ተጨማልቆ በመንገዱ መካከል ወድቆ ነበር፤
በዚያ የሚያልፈው ሰራዊት ሁሉ መቆ
ሙን ያ ሰው አየ፤ ወደ ሬሳው የደረሰው
ሰራዊት ሁሉ መቆሙን በተረዳ ጊዜም፣
የአሜሳይን ሬሳ ከመንገድ ወደ ዕርሻ ፈቀቅ

20፥6 2ሳሙ 21፥17
20፥7 1ሳሙ 30፥14፤2ሳሙ 15፥18
20፥8 ኢሱ 9፥3፤2ሳሙ 2፥18
20፥10 መሳ 3፥21፤1ነገ 2፥5
20፥12 2ሳሙ 2፥23
20፥14 ዘኍ 21፥16
20፥15 1ነገ 15፥20፤2ነገ 15፥29፤ኢሳ 37፥33፤ኤር 6፥6፤32፥24
20፥16 2ሳሙ 14፥2
20፥19 ዘዳ 2፥26፤1ሳሙ 26፥19
20፥21 2ሳሙ 4፥8
20፥22 መክ 9፥13
20፥23 2ሳሙ 2፥28፤8፥16-18፤24፥2

አድርጎ ልብስ ጣል አደረገበት። [13]የአሜ
ሳይ ሬሳ ከመንገድ ላይ ከተነሣ በኋላ ሕ
ዝቡ ሁሉ ኢዮአብን ተከትሎ የቢክሪን
ልጅ ሳቤዔን ሊያሳድድ ሄደ።
[14]ሳቤዔም በእስራኤል ነገዶች ሁሉ መካ
ከል ዐልፎ ወደ አቤል ቤትማዓካና ወደ
መላው የቢክሪያውያን ግዛት መጣ፤ የቢ
ክሪ ሰዎችም ተሰብስበው ተከተሉት። [15]ከኢ
ዮአብ ጋር ያለውም ሰራዊት መጥቶ
ሳቤዔን በአቤል ቤትመዓካ በከል ከበበው፤
በስተ ውጭም እስከ ከተማዪቱ ግንብ
ጫፍ ድረስ ዙሪያውን የዐፈር ድልድል
ሠሩ፤ ግንቡን ለመናድ በኀይል በሚደበ
ድቡበት ጊዜ፣ [16]አንዲት ብልኅ ሴት ድምፅ
ዋን ከፍ አድርጋ፣ “ስሙ! ስሙ! ለኢዮአብ
የምነግረው ነገር ስላለ ወደዚህ እንዲመጣ
ንገሩት” አለቻቸው። [17]ኢዮአብ ወደ እርሷ
ሄደ፤ እርሷም፣ “ኢዮአብ አንተ ነህ?’ ስትል
ጠየቀችው።
እርሱም፣ “አዎን እኔ ነኝ” ብሎ መለሰ
ላት።
እርሷም፣ “እንግዲህ አገልጋይህ የምትለ
ውን አድምጥ” አለችው።
እርሱም፣ “እሺ፣ አደምጣለሁ” አላት።
[18]ከዚያ በመቀጠልም እንዲህ አለች፤ “በቀ
ድሞው ጊዜ ሰዎች፣ ‘ምክርን ከአቤል ጠይቁ’
ይሉ ነበር፤ ታዲያ እንዳሉትም ይፈጸም
ነበር፤ [19]በእስራኤል ሰላማዊና ታማኝ ከሆኑ
ሰዎች መካከል አንዷ እኔ ነኝ፤ አንተ በእ
ስራኤል እናት የሆነችውን ከተማ ለማጥ
ፋት ትሻለህ፤ *የእግዚአብሔርን* ርስት ለመ
ዋጥ የፈለግኸው ለምንድን ነው?”
[20]ኢዮአብም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “ይህስ
ከእኔ ይራቅ! መዋጡና ማጥፋቱ አሁንም
ከእኔ ይራቅ! [21]ነገሩስ እንዲህ አይደለም፤
የኰረብታማው የኤፍሬሙ አገር ሰው፣
የቢክሪ ልጅ ሳቤዔ እጁን በንጉሡ በዳዊት
ላይ አንሥቶአል፤ እናንተ ይህን ሰው ብቻ
ስጡኝ እንጂ እኔ ከተማዪቱን ትቼ እሄዳለሁ”
አላት።
ሴቲቱም ኢዮአብን፣ “የሰውየው ራስ ተቈ
ርጦ በግንቡ ላይ ይወረወርልሃል” አለችው።
[22]ከዚህም በኋላ ሴቲቱ ብልኀነት የተሞ
ላበት ምክሯን ይዛ ወደ ሕዝቡ ሁሉ ሄደች፤
እነርሱም የቢክሪን ልጅ የሳቤዔን ራስ ቈርጠው
ለኢዮአብ ወረወሩለት፤ ስለዚህ ኢዮአብ
መለከቱን ነፋ፤ ሰዎቹም ከከተማዪቱ ርቀው
በየአቅጣጫው ተበታተኑ፤ እያንዳንዳቸውም
ወደየቤታቸው ሄዱ፤ ኢዮአብም ወደ ንጉሡ
ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ።
[23]ኢዮአብ በእስራኤል ሰራዊት ሁሉ

ላይ የበላይ ሆነ፤ የዮዳሄ ልጅ በናያስ
ደግሞ በከሊታውያንና በፈሊያታውያን ላይ
አለቃ ሆነ። 24አዶኒራም[ኘ] በግዳጅ ሥራ ላይ
ለተሰማሩት ሰዎች አለቃ ሆነ፤ የአሒሉድ
ልጅ ኢዮሣ ፍጥ ደግሞ ታሪክ ጸሓፊ
ሆነ፤ 25ሱሳ ጸሓፊ፣ ሳዶቅና አብያታር
ካህናት ነበሩ፤ 26እንዲሁም የኢያዕር
ሰው ዒራስ የዳዊት አማካሪ ነበር።

## የገባዖናውያን ብቀላ

21 በዳዊት ዘመነ መንግሥት፣ በተ
ከታታይ ለሦስት ዓመት ራብ ሆነ፤
ስለዚህ ዳዊት እግዚአብሔርን ጠየቀ፤ እግዚ
አብሔርም፣ ሳኦል ገባዖናውያንን ስለ
ገደለ፣ እርሱና ቤቱ የደም ዕዳ አለባቸው”
አለ።

2ንጉሡ ገባዖናውያንን ጠርቶ አነጋገራቸው።
ገባዖናውያን ከአሞራውያን የተረፉ እንጂ
ከእስራኤል ወገን አልነበሩም፤ እስራኤላው
ያን ሊጠብቋቸው ቢምሉላቸውም፣ ሳኦል
ግን ለእስራኤልና ለይሁዳ ካለው ቅናት የተ
ነሣ ሙሉ በሙሉ ሊያጠፋቸው ፈልጎ ነበር፤
3ዳዊትም ገባዖናውያንን፣ “ምን ላድርግላችሁ?
የእግዚአብሔርን ርስት ትባርኩ ዘንድ ማስ
ተሰረያውን ምን ማድረግ አለብኝ?” ሲል ጠየ
ቃቸው።

4ገባዖናውያንም፣ “ከሳኦልም ሆነ ከቤተ ሰቡ
ብር ወይም ወርቅ የመጠየቅ መብት የለንም፤
እንዲሁም ከእስራኤል ማንንም ለመግደል
መብት የለንም” ብለው መለሱለት።

ዳዊትም፣ “ታዲያ ምን ላድርግላችሁ?”
ሲል ጠየቃቸው።

5እነርሱም፣ “እንድንፈራርስና በእስራኤ
ልም ውስጥ በየትኛውም ስፍራ እንዳንኖር
ካጠፋንና ደባ ከፈጸመብን ሰው 6ከእርሱ
ዘሮች ሰባት ወንዶች ልጆች ይሰጠን፤ እኛም
ከእግዚአብሔር በተመረጠው በሳኦል አገር
በጊብዓ በእግዚአብሔር ፊት እንሰቅላቸው”
ብለው መለሱለት።

ስለዚህ ንጉሡ፣ “እሺ እሰጣችኋለሁ” አለ።

7ንጉሥ ዳዊት በራሱና በሳኦል ልጅ በዮ
ናታን መካከል በእግዚአብሔር ፊት ስላደ
ረጉት መሐላ ሲል የሳኦልን ልጅ፣ የዮና
ታንን ልጅ ሜምፊቦስቴን ከሞት አተረፈ።
8ነገር ግን ንጉሡ የኢዮሄል ልጅ ሪጽፋ
ለሳኦል የወለደቻቸውን ሁለቱን ወንዶች
ልጆች ሄርሞንንና ሜምፊቦስቴን፤ የሳ
ኦል ልጅ ሜሮብ[ኦ] ለምሓላታዊው
ለቤርዜሊ ልጅ ለኤስድሪኤል
የወለደችለትን አምስት ወንዶች ልጆች
ጭምር ወሰደ፤ 9ለገባዖና ውያን አሳልፎ
ሰጣቸው፤ እነርሱም ገድ ለው በኰረብታው
ላይ በእግዚአብሔር ፊት ሰቀሏቸው። ሰባተ
ም በአንድነት ወደቁ፤ የተገደሉትም
በመከሩ ወራት የመጀመሪያ ቀኖች፣
የገብስ ዐጨዳ በተጀመረበት ዕለት ነበር።

10የኢዮሄል ልጅ ሪጽፋ ማቅ ወስዳ፣ በቋ
ጥኝ ላይ ለራሷ አነጠፈች፤ ከመከር ወቅት
መጀመሪያ አንሥቶ ዝናብ ከሰማይ በሬሳ
ዎቹ ላይ እስከ ወረደ ጊዜ ድረስ ቀን የሰ
ማይ ወፎች ሌሊት የዱር አራዊት እንዲ
ነኳቸው አልፈቀደችም፤ 11የሳኦል ቁባት
የኢዮሄል ልጅ ሪጽፋ ያደረገችውን ዳዊት
በሰማ ጊዜ፣ 12ሄዶ የሳኦልንና የልጁን የዮ
ናታንን ዐፅም ከኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች
ወሰደ፤ የኢያቢስ ሰዎች፣ ፍልስጥኤማው
ያን ሳኦልን በጊልቦዓ ከገደሉ በኋላ እነ
ርሱን ከሰቀሉት ከቤትሳን አደባባይ በድ
ብቅ ወስደዋቸው ነበር። 13ዳዊትም የሳኦ
ልንና የልጁን የዮናታንን ዐፅም ከዚያ
አመጣ፤ እንዲሁም የእነዚያን የተገደሉትን
ሰዎች ዐፅም ሰበሰቡ።

14የሳኦልንና የልጁን የዮናታንን ዐፅም በብ
ንያም አገር ጼላ በተባለ ስፍራ በሳኦል አባት
በቂስ መቃብር ቀበሩት፤ ንጉሡ ያዘዘውንም
ሁሉ አደረጉ። ከዚያ በኋላም ስለ ምድሪቱ
የቀረበውን ጸሎት እግዚአብሔር ሰማ።

## በፍልስጥኤማውያን ላይ የተደረገ ጦርነት

21÷15-22 ተጓ ምብ - 1ዜና 20÷4-8

15እንደ ገና በፍልስጥኤማውያንና በእስ
ራኤል መካከል ጦርነት ተደረገ። ዳዊትም
ከሰዎቹ ጋር ሆኖ ፍልስጥኤማውያንን
ለመውጋት ወረደ፤ በዚያም ደከመው። 16ከራ
ፋይም ዘሮች አንዱ የሆነ ይሽቢብኖብ
የተባለ፣ የናስ ጦሩ ሦስት መቶ ሰቅል[ከ]
የሚመዝንና አዲስ ሰይፍ የታጠቀ ሰው
ነበረ፤ እርሱም ዳዊትን ለመግደል አሰበ።
17የጽሩያ ልጅ አቢሳ ግን ዳዊትን ለመ
ታደግ መጣ፤ ፍልስጥኤማዊውንም ወግቶ
ገደለው። ከዚያም የዳዊት ሰዎች፣ “የእስ
ራኤል መብራት እንዳይጠፋ ከእንግዲህ
አንተ ከእኛ ጋር ወደ ጦርነት መውጣት
የለብህም” ብለው ማሉለት።

18ከዚህ በኋላ ጎብ በተባለ ስፍራ ከፍልስ
ጥኤማውያን ጋር ሌላ ጦርነት ተደረገ። በዚ
ያን ጊዜም ኩሳታዊው ሴቦካይ፣ ከራፋ
ይም ዘሮች አንዱ የሆነውን፣ ሳፍን ገደ
ለው።

20÷24 2ሳሙ 8÷16፤1ነገ4÷6፤5÷14፤12÷18፤2ዜና10÷18
20÷25 1ሳሙ 2÷35፤2ሳሙ8÷17
21÷1 ዘፍ12÷10፤ዘፀ32÷11፤ዘዳ32÷24
21÷2 ኢሱ9÷15
21÷3 1ሳሙ26÷19
21÷4 ዘኍ 35÷33-34
21÷6 ዘኍ25÷4፤1ሳሙ10÷24
21÷7 1ሳሙ18÷3፤2ሳሙ4÷4፤9÷7
21÷8 1ሳሙ 18÷19፤2ሳሙ3÷7
21÷9 ሩት1÷22፤2ሳሙ16÷8
21÷10 ዘፍ40÷19፤1ሳሙ17÷44
21÷12 ኢሱ17÷11፤መሳ21÷8፤1ሳሙ 11÷1፤28÷4፤31÷10፡11-13
21÷14 ኢሱ7÷26፤18÷28፤2ሳሙ24÷25፤1ዜና8÷34
21÷15 2ሳሙ5÷25
21÷17 2ሳሙ18÷3፤20÷6፤1ነገ11÷36፤15÷4፤2ነገ8÷19፤2ዜና 21÷7፤መዝ132÷17
21÷18 1ዜና11÷29፤27÷11

[ኘ]24 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ቅጆች (እንዲሁም 1ነገ 4÷6 እና 5÷14 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ ***አይራም*** ይላል።
[ኦ]8 ሁለት የዕብራይስጥ ቅጆች፤ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናትና የሱርስት ትርጕሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ (እንዲሁም 1ሳሙ 18÷19 ይመ)፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥና የሰብዓ ሊቃናት ቅጆች ግን፣ ***ሜልኮል*** ይላሉ።
[ከ]16 3.5 ኪሎ ግራም ያህል ነው።

[19]ጎብ ላይ ከፍልስጥኤማውያን ጋር በተ
ደረገ ሌላ ጦርነትም፣ የቤተልሔሙ የየዓ
ሬዓርጊም[ኸ] ልጅ ኤልያናን፣ የጦሩ ዘንግ
እንደ ሸማኔ መጠቅለያ የሆነውን የጌት
ሰው ጎልያድን ገደለ[ወ]፡፡
[20]እንደ ገና ጌት ላይ በተደረገው ጦር
ነት በእያንዳንዱ እጁና በእያንዳንዱ
እግሩ ስድስት ስድስት ጣቶች ባጠቃላይ
ሃያ አራት ጣቶች የነበሩት አንድ ግዙፍ
ሰው ነበረ፤ እርሱም ደግሞ ከራፋይም ዘር
ነበረ፡፡ [21]ይህም ሰው እስራኤልን በተገዳደረ
ጊዜ፣ የዳዊት ወንድም የሣማ ልጅ
ዮናታን ገደ ለው፡፡
[22]እነዚህ አራቱ በጌት የራፋይም ዘሮች
የነበሩ ናቸው፤ እነርሱም በዳዊትና በሰዎቹ
እጅ ወደቁ፡፡

### የዳዊት የምስጋና መዝሙር

22፥1-51 ተጓ ምብ - መዝ 18፥1-50

22 *እግዚአብሔር* ከጠላቶቹ ሁሉና
ከሳ ኦልም እጅ በታደገው ጊዜ፣
ዳዊት የዚህን መዝሙር ቃል *ለእግዚአብሔር*
ዘመረ፤ [2]እንዲህም አለ፤

"*እግዚአብሔር* ዐለቴ ዐምባዬና ታዳጊዬ ነው፤
[3]አምላኬ፣ የምጠጋበት ዐለቴ፣
ጋሻዬና የድነቴ ቀንድ[ዐ] ነው፡፡
እርሱም ጠንካራ ምሽጌ፣ መጠጊያና አዳኜ
ነው፤
ከኀይለኞች ሰዎች ታድነኛለህ፡፡
[4]ምስጋና የሚገባውን *እግዚአብሔርን*
እጠራለሁ፤
ከጠላቶቼም እድናለሁ፡፡

[5]"የሞት ማዕበል ከበበኝ፤
የጥፋትም ጐርፍ አሰጠመኝ፡፡
[6]የሲኦል ገመድ ተጠመጠመብኝ፤
የሞትም ወጥመድ ተጋረጠብኝ፡፡
[7]በጨነቀኝ ጊዜ *እግዚአብሔርን* ጠራሁት፤
ወደ አምላኬም ጮኽሁ፡፡
እርሱም ከመቅደሱ ድምፄን ሰማ፤
ጩኸቴም ከጆሮው ደረሰ፡፡

[8]"ምድር ተንቀጠቀጠች፤ ተናወጠችም፤
የሰማያትም መሠረቶች[ዘ] ተናጉ፤
እርሱ ተቈጥቶአልና ራዱ፡፡
[9]ከአፍንጫው የቍጣ ጢስ ወጣ፤
ከአፉ የሚባላ እሳት ነደደ፤
ከውስጡም ፍሙ ጋለ፡፡
[10]ሰማያትን ሰንጥቆ ወረደ፤
ከእግሩም በታች ጥቅጥቅ ያለ ደመና
ነበረ፡፡
[11]በኪሩቤል ላይ ተቀምጦ በረረ፤
በነፋስም ክንፍ መጠቀ፡፡[ዠ]
[12]ጨለማው በዙሪያው እንዲከበው፣
ጥቅጥቅ ያለውም የሰማይ ዝናም ደመና
እንዲሰውረው አደረገ፡፡
[13]በእርሱ ፊት ካለው ብርሃን፣
የመብረቅ ብልጭታ ወጣ፡፡
[14]*እግዚአብሔር* ከሰማያት አንጐደጐደ፤
የልዑልም ድምፅ አስተጋባ፡፡
[15]ፍላጻውን ሰድዶ ጠላቶቹን በተናቸው፤
መብረቆቹንም ልኮ አወካቸው፡፡
[16]*ከእግዚአብሔር* ተግሣጽ፣ ከአፍንጫው
ከሚወጣው፣ ከእስትንፋሱ ቍጣ የተነሣ፣
የባሕር ሸለቆዎች ታዩ፤ የምድር
መሠረቶችም ተገለጡ፡፡

[17]"ከላይ እጁን ዘርግቶ ያዘኝ፤
ከጥልቅ ውሆችም ውስጥ አወጣኝ፡፡
[18]ከብርቱ ጠላቶቼ፣
ከማልቋቋማቸውም ባለጋሮቼ ታደገኝ፡፡
[19]በመከራዬ ቀን መጡብኝ፤
*እግዚአብሔር* ግን ደገፈኝ፡፡
[20]ሰፊ ወደ ሆነ ስፍራ አወጣኝ፤
በእኔ ደስ ስለ ተሰኘም አዳነኝ፡፡

[21]"*እግዚአብሔር* እንደ ጽድቄ መለሰልኝ፤
እንደ እጄም ንጹሕነት ብድራትን ከፈለኝ፤
[22]*የእግዚአብሔርን* መንገድ ጠብቄአለሁና፤
ከአምላኬም ዘወር ብዬ ክፉ ነገር
አላደረግሁም፡፡
[23]ሕጉ ሁሉ በፊቴ ነው፤
ከሥርዐቱም ዘወር አላልሁም፡፡
[24]በፊቱ ያለ ነውር ነበርሁ፤
ራሴንም ከኀጢአት ጠብቄአለሁ፡፡
[25]*እግዚአብሔር* እንደ ጽድቄ፣
በፊቱም እንዳለኝ ንጽሕና[የ] ብድራትን
ከፈለኝ፡፡

[26]"ለታማኝ ሰው አንተም ታማኝ መሆንህን፣
ለቅን ሰው አንተም ቅን መሆንህን
ታሳያለህ፡፡
[27]ለንጹሕ ሰው አንተም ንጹሕ መሆንህን፣
ለጠማማ ሰው ግን አንተም ጠማማ
መሆንህን ታሳያለህ፡፡
[28]አንተ የተጠቃውን ሕዝብ ታድናለህ፤
ዐይንህ ግን ያዋርዳቸው ዘንድ፣
ትዕቢተኞችን ይመለከታል፡፡

21፥19 1ሳሙ 17፥4፡
21፥21 1ሳሙ 16፥9፤ 17፥10
22፥1 ዘፀ 15፥1
22፥2 1ሳሙ 2፥2፤ መዝ 31፥3፤91፥2፤ መዝ 144፥2
22፥3 ዘፍ 15፥1፤ ዘዳ 23፥15፤32፥37፤ 33፥17፤መዝ 9፥9፤14፥6፤31፥2፤52፥7፤59፥16፤ 71፥7፤91፥2፤94፥22፤ ምሳ 10፥29፤ኢሳ 25፥4፤ ኤር 16፥19፤ኢል 3፥16፤ ሉቃ 1፥69
22፥4 መዝ 48፥1፤ 96፥4፤145፥3
22፥5 መዝ 69፥14-15፤ ዮና 2፥3
22፥6 መዝ 116፥3፤ ሐሥ 2፥24
22፥7 ዘፍ 35፥3፤ መሳ 2፥15፤2ዜና 15፥4፤ መዝ 4፥1፤34፥6፥15፤ 77፥2፤116፥4፤120፥1፤ኢሳ 26፥16
22፥8 ዘፀ 19፥18፤ መሳ 5፥4፤ኢዮ 9፥6፤ 26፥11፤መዝ 68፥8፤ 75፥3፤77፥18፤97፥4፤ ኤር 10፥10
22፥9 መዝ 50፥3፤ 97፥3፤ኢሳ 6፥6፤ሕዝ 1፥13፤10፥2፤ዕብ 12፥29፤ራእ 11፥5
22፥10 ዘፀ 19፥9፤ ዘሌ 16፥2፤ዘዳ 33፥26፤1 ነገ 8፥12፤ኢዮ 26፥9፤ መዝ 104፥3፤ኢሳ 19፥1፤ኤር 4፥13፤ናሆ 1፥3
22፥11 ዘፍ 3፥24፤ ዘፀ 25፥22፤መዝ 104፥3
22፥12 ዘፀ 19፥9
22፥13 ኢዮ 37፥3፤ መዝ 77፥18
22፥14 1ሳሙ 2፥10
22፥15 ዘዳ 32፥23
22፥16 ዘፀ 14፥21፤ መዝ 6፥1፤50፥8፡21፤ 106፥9፤ኢሳ 30፥33፤ 40፥24፤ናሆ 1፥4
22፥17 ዘፀ 2፥10፤ መዝ 144፥7
22፥18 ሉቃ 1፥71
22፥19 መዝ 23፥4
22፥20 2ሳሙ 15፥26፤ኢዮ 36፥16፤መዝ 22፥8፤31፥8፤118፥5፤ ኢሳ 42፥1፤ማቴ 12፥18
22፥21 1ሳሙ 26፥23፤ኢዮ 17፥9፤22፥30፤ 42፥7-8፤መዝ 24፥4፤ 26፥6
22፥22 ዘፍ 18፥19፤ መዝ 128፥1፤ምሳ 8፥32
22፥23 ዘዳ 6፥4-9፤ መዝ 119፥30-32፡102

22፥24 ዘፍ 6፥9፤ኤፌ 1፥4 22፥25 1ሳሙ 26፥23 22፥27 ዘሌ 26፥23-24፤ማቴ 5፥8 22፥28 ዘፀ 3፥8፤1ሳሙ 2፥8-9፤መዝ 72፥12-13፤ 131፥1፤ምሳ 30፥13፤ኢሳ 2፥12፡17፤5፥15፤ዳን 4፥31፤ሶፎ 3፥11፤ ሉቃ 1፥51

[ኸ]19 ወይም፣ *የሸማኔው የይዔር ልጅ*
[ወ]19 ዕብራይስጡና የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች ከዚህ ጋር ይስ ማማሉ፤ ነገር ግን 1ዜና 20፥5 ላይ ያለው ከዚህ የተለየ ነው፡፡
[ዐ]3 *ቀንድ* የጥንካሬ ወይም የኀይል ምልክት ነው፡፡
[ዘ]8 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ቩልጌትና ሱርስቱ ግን (እንዲሁም መዝ 18፥7 ይመ) *ተራሮች* ይላሉ፡፡
[ዠ]11 አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች (እንዲሁም መዝ 18፥10 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ እጅግ ብዙ የሆኑ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *ተገለጠ* ይላሉ፡፡
[የ]25 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናትና የቩልጌት ትርጕሞች (እንዲሁም መዝ 18፥24 ይመ) ግን፣ *እንደ እጄም ንጽሕ* ይላሉ፡፡

29*እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ መብራቴ ነህ፤*
*እግዚአብሔርም* ጨለማዬን ያበራል።
30በአንተ ርዳታ በጠላት ሰራዊት ላይ ወደ
ፊት ገፍቼ እሄዳለሁ[ጸ]፤
በአምላኬም ኀይል ቅጥሩን እዘላለሁ።
31"የአምላክ *መንገዱ* ፍጹም ነው፤
*የእግዚአብሔርም* ቃል የነጠረ ነው፤
*ለሚታመኑበትም* ሁሉ ጋሻ ነው፤
32*ከእግዚአብሔር* በቀር አምላክ ማን
አለና፤
ከአምላካችንስ በቀር ዐለት ማን ነው?
33ኀይልን የሚያስታጥቀኝ[ጀ]፣
*መንገዴንም* የሚያቀና እርሱ አምላኬ ነው።
34እግሮቼን እንደ ብሆር እግር ያበረታል፤
በከፍታዎችም ላይ አጽንቶ ያቆመኛል።
35እጆቼን ለጦርነት ያሰለጥናል፤
ክንዶቼም የናስ ቀስት ይገትራሉ።
36የማዳንህን ጋሻ ሰጥተኸኛል፤
ድጋፍህ ታላቅ አድርጎኛል።
37እርምጃዬን አሰፋህ፤
እግሮቼም አልተሰነካከሉም።

38"ጠላቶቼን አሳደድሁ፤ አጠፋኋቸውም፤
እስኪደመሰሱም ድረስ ወደ ኋላ
አልተመለስሁም።
39*ፈጽሜ* አጠፋኋቸው፤ *ተመልሰውም*
*መቆም* አልቻሉም፤
ከእግሬም *ሥር* ወድቀዋል።
40ለጦርነት ኀይልን አስታጠቅኸኝ፣
*ተቃዋሚዎቼንም* ከእግሬ *ሥር*
አንበረከካቸው።
41ጠላቶቼ *ፊታቸውን* አዙረው እንዲሸሹ
አደረግሃቸው።
ባላንጣዎቼንም ደመሰስኋቸው።
42ለርዳታ ጮኹ፤ ያዳናቸው ግን አልነበረም፤
ወደ *እግዚአብሔር* ጮኹ፤ እርሱ ግን
አልመለሰላቸውም።
43በምድር ላይ እንዳለ ትቢያ አድቅቄ
ፈጨኋቸው፤
በመንገድም ላይ እንዳለ ጭቃ
ወቀጥኋቸው፤ ረገጥኋቸውም።

44"በሕዝቤ ከተቃጣብኝ አደጋ አዳንኸኝ፤
የመንግሥታትም ራስ አደረግኸኝ።
የማላውቀው ሕዝብ ተገዛልኝ፤
45ባዕዳን ሊለማመጡኝ መጡ፤
እንደ ሰሙኝም ወዲያውኑ ይታዘዙኛል።
46ባዕዳን ፈሩ፤
ከምሽጋቸውም እየተንቀጠቀጡ ወጡ[ገ]።

47"*እግዚአብሔር* ሕያው ነው፤ ዐለቴ
የተባረከ ይሁን፤
የድነቴ ዐለት አምላኬ ከፍ ከፍ ይበል።
48የሚበቀልልኝ አምላክ፣
*መንግሥታትንም* ከሥሬ የሚያስገዛልኝ
እርሱ ነው፤
49እርሱ ከጠላቶቼ እጅ ነጻ ያወጣኛል።
አንተ ከጠላቶቼ በላይ ከፍ ከፍ
አደረግኸኝ፤
ከጨካኝ ሰዎችም እጅ ታደግኸኝ።
50ስለዚህ *እግዚአብሔር* ሆይ፤
በመንግሥታት መካከል አመሰግንሃለሁ፤
ለስምህም ምስጋና እዘምራለሁ።
51ለንጉሡ ታላቅ ድል ይሰጠዋል፤
ለቀባው ለዳዊትና ለዘሩ፣
ለዘላለም የማይለወጥ ፍቅሩን ያሳየዋል።"

## የዳዊት የመጨረሻ ቃል

23 የዳዊት የመጨረሻ ቃሉ ይህ ነው፤
"በያዕቆብ አምላክ የተቀባው፣
ልዑል ከፍ ከፍ ያደረገው ሰው፣
የእስራኤል ተወዳጁ ዘማሪ፣
የእሴይ ልጅ የዳዊት የትንቢት
ቃል ይህ ነው፤

2"*የእግዚአብሔር መንፈስ* በእኔ ተናገረ፤
ቃሉ በአንደበቴ ላይ ነበረ።
3የእስራኤል አምላክ ተናገረ፤
የእስራኤልም ዐለት እንዲህ አለኝ፤
ሰዎችን በጽድቅ የሚገዛ፣
በፈሪሀ *እግዚአብሔርም* የሚያስተዳድር፣
4እርሱ፣ ደመና በሌለበት፣
በማለዳ ፀሓይ በምትወጣበት ጊዜ፣
እንዳለው ብርሃን ነው፤
በምድር ላይ ሣርን እንደሚያበቅለው፣
ከዝናብም በኋላ እንዳለው የብርሃን
ጸዳል ነው።'

5"የእኔስ ቤት *በእግዚአብሔር* ዘንድ ትክክል
አይደለምን?
ሁሉንም ነገር አዘጋጅቶና ጠብቆ፣
ከእኔ ጋር ዘላለማዊ ኪዳን ያደረገ አይደለምን?
ድነቴን ከፍጻሜ የሚያደርሰው፣
መሻቴን ሁሉ የሚሰጠኝ እርሱ
አይደለምን?
6ነገር ግን ክፉ ሰዎች ሁሉ፣
በእጅ እንደማይሰበሰብ እንደ እሾኽ
ይጣላሉ።
7እሾኽ የሚነካ ሁሉ፣
የብረት መሣሪያ ወይም የጦር ዘንግ
ይይዛል፤
ባሉበትም ቦታ ፈጽመው በእሳት
ይቃጠላሉ።

22፥29 መዝ27፥1፤ ኢሳ2፥5፤ሚክ7፥8፤ ራእ21፥23፤22፥5
22፥31 ዘፍ15፥1፤ ዘዳ32፥4፤መዝ12፥6፤119፥140፤ምሳ30፥5-6፤ ማቴ5፥48
22፥32 1ሳሙ2፥2፤ 2ሳሙ7፥22
22፥34 ዘዳ32፥13፤ ኢሳ35፥6፤ዕን3፥19
22፥35 መዝ7፥12፤ 11፥2፤144፥1፤ዘካ9፥13
22፥36 ኤፌ6፥16
22፥37 ምሳ4፥11
22፥39 መዝ44፥5፤ 110፥6፤ሚል4፥3
22፥40 ኢሱ10፥ 24፤1ነገ5፥3
22፥41 ዘፀ23፥27
22፥42 1ሳሙ 14፥37፤መዝ50፥22፤ ኢሳ1፥15
22፥43 1ነገ20፥10፤ 2ነገ13፥7፤መዝ7፥5፤ ኢሳ5፥25፤10፥6፤22፥ 5፤41፥2፥25፤አሞ1፥3 ፤ሚክ7፥10፤ዘካ7፥10
22፥44 ዘፀ11፥3፤ ዘዳ28፥13፤2ሳሙ3፥1፤ 8፥1-14፤ኢሳ55፥3-5
22፥45 ዘዳ33፥29፤ መዝ66፥3፤81፥15
22፥46 ሚክ7፥17
22፥47 ዘፀ15፥2፤ ዘዳ 32፥15፤መዝ 18፥31፤89፥26፤95፥1
22፥48 ዘኍ31፥3፤ መዝ144፥2
22፥49 መዝ27፥6፤ 140፥1
22፥50 መዝ9፥11፤ 47፥6፤68፥4፤ሮሜ15፥9
22፥51 1ሳሙ16፥ 13፤2ሳሙ7፥13፤መዝ 21፥1፤መዝ89፥20፥24፥ 29፤144፥9-10፤ሐሥ 13፥23
23፥1 ዘፀ11፥3፤ 1ሳሙ2፥10፥35፤መዝ 18፥50፤20፥6፤78፥70- 71፤84፥9፤ኢሳ45፥1 ፤ዕን3፥13
23፥2 ማቴ22፥43፤ ማር12፥36፤2ጴጥ1፥21
23፥3 ዘፍ42፥18፤ ዘዳ32፥4፤1ሳሙ2፥2፤ መዝ18፥31፤72፥3፤ ኢሳ11፥1-5
23፥4 ዘዳ32፥2፤ መሳ5፥31፤መዝ 119፥147፤130፥6፤ ምሳ4፥18፤ ማቴ13፥43፤ዮሐ1፥5
23፥5 ዘፍ9፥16፤ መዝ89፥29
23፥6 ኢሳ5፥6፤ 9፥18፤10፥17፤27፥4፤ 33፥12፤ሚክ7፥4፤ናሆ1 ፥10፤ማቴ13፥40-41

[ጸ]30 ወይም *በጋሬጣዎች ውስጥ እሮጣለሁ*
[ጀ]33 የሙት ባሕር ጥቅል፣ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች፣ የቩልጌትና የሱርስት ቅጆች (እንዲሁም መዝ 18፥32 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ የማሶሬቱ ቅጅ ግን፣ *ጠንካራ መሸሸጊያ የሚሆነኝ* ይላል።
[ገ]46 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞችና የቩልጌቱ ቅጅ (እንዲሁም መዝ 18፥32 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ማሶሬቱ ግን *ራሳቸውን ጐዱ* ይላል።

### የኀያላኑ የዳዊት ሰዎች ጀብዱ

23፥8-39 ተጓ ምብ - 1ዜና 11፥10-41

[8]የዳዊት ኀያላን ሰዎች ስም የሚከተለው ነው፤ የታሕክሞን[ጠ] ሰው ዮሴብ በሴትቤት[ጨ] የሦስቱ አለቆች አለቃ ሲሆን፣ እርሱም ጦሩን ሰብቆ በአንድ ውጊያ ላይ ስምንት መቶ ሰው የገደለ ነው።[ጸ]

[9]ከእርሱ ቀጥሎ የአሆሃዊው የዱዲ ልጅ ኤልዔዘር ነበረ፤ እርሱም ለጦርነት አንድ ላይ ተሰብስበው[ጸ] የነበሩትን ፍልስጥኤማውያንን በተገዳደሩ ጊዜ፣ ከዳዊት ጋር ከነበሩት ከሦስቱ ኀያላን ሰዎች አንዱ ነበር። ከዚያም የእስራኤል ሰዎች ሸሹ። [10]እርሱ ግን የቆመበትን ስፍራ አለቀቀም፤ እጁ እስኪዝልና ከሰይፉ ጋር እስኪጣበቅ ድረስ ፍልስጥኤማውያንን ወጋ፤ በዚያችም ዕለት *እግዚአብሔር* ታላቅ ድልን ሰጠ። የሸሸውም ሰራዊት ወደ ኤልዔዘር የተመለሰው የተገደሉትን ሰዎች ለመግፈፍ ብቻ ነበር።

[11]ከእርሱም ቀጥሎ የአሮዳዊው የአጌ ልጅ ሣማ ነበር፤ ፍልስጥኤማውያንም ሌሒ በተባለ ስፍራ ምስር በሞላበት አንድ ዕርሻ ላይ፣ በአንድነት ተሰብስበው ሳሉ፣ የእስራ ኤል ሰራዊት ከፍልስጥኤማውያን ፊት ሸሹ፤ [12]ሣማ ግን የቆመበትን ስፍራ አለቀቀም፤ ጦርነቱንም ተቋቁሞ ፍልስጥኤማውያንን ገደለ፤ በዚያችም ዕለት *እግዚአብሔር* ታላቅ ድል ሰጠ።

[13]በመከር ወራት፣ የፍልስጥኤም ሰራ ዊት በራፋይም ሸለቆ ሰፍሮ ሳለ፣ ከሠላሳዎቹ አለቆች ሦስቱ ዳዊት ወዳለበት ወደ ዓዶ ላም ዋሻ መጡ። [14]በዚያም ጊዜ ዳዊት በምሽግ ውስጥ ነበረ፤ የፍልስጥኤማውያንም ሰራዊት በቤተልሔም ነበረ፤ [15]ዳዊ ትም በናፍቆት፣ “በቤተልሔም በር አጠ ገብ ካለችው ጕድጓድ ውሃ ማን ባመጣ ልኝ!” አለ። [16]ስለዚህ ሦስቱ ኀያላን በፍል ስጥኤማውያን ሰራዊት መካከል ሰንጥቀው በማለፍ፣ በቤተልሔም በር አጠገብ ካለ ችው ጕድጓድ ውሃ ቀድተው ለዳዊት አመጡለት። እርሱ ግን አልጠጣውም፤ ይልቁን *በእግዚአብሔር* ፊት መሥዋዕት አድርጎ አፈሰሰው፤ [17]“እርሱም፣ *እግዚአ ብሔር* ሆይ፤ እንዲህ ያለውን ነገር ላደ ርግ? ይህስ ከእኔ ይራቅ! ይህ በነፍሳቸው ቈርጠው የሄዱ ሰዎች ደም አይደለምን?” አለ፤ ዳዊትም ሊጠጣው አልፈለገም። እን ግዲህ ሦስቱ ኀያላን ሰዎች ያደረጉት ጀብዱ እንዲህ ነበር።

[18]የጽሩያ ልጅ የኢዮአብ ወንድም አቢሳ የሦስቱ[θ] ኀያላን አለቃ ነበረ። በሦስት መቶ ሰዎች ላይ ጦሩን ሰብቆ የገደላቸውና እንደ ሦስቱ ኀያላን ሁሉ እርሱም ዝናን ያተረፈ ሰው ነበረ። [19]አቢሳ ከሦስቱ ይልቅ እጅግ የከበረ አልነበረምን? ከእነርሱ እንደ አንዱ ባይሆንም አለቃቸው ነበረ።

[20]የቀብጽኤል አገር ሰው የሆነው የዮዳሄ ልጅ በናያስ ታላቅ ጀብዱ የሠራ ሌላው ጐበዝ ተዋጊ ነበረ፤ እርሱም ሁለት በጣም የታወቁ የሞዓብን ሰዎች ገደለ፤ እንዲሁም በረዶ በጣለበት ዕለት በጕድጓድ ውስጥ ገብቶ አንበሳ ገድሎአል፤ [21]ደግሞም አንድ ግዙፍ ግብፃዊ ገድሎአል፤ ግብፃዊው በእጁ ጦር የያዘ ቢሆንም፣ በናያስ ግን ሊገጥመው በትር ይዞ ወደ እርሱ ሄደ፤ ከግብፃዊውም እጅ ጦሩን በመንጠቅ በገዛ ጦሩ ገደለው።

[22]የዮዳሄ ልጅ የበናያስ ጀግንነት እንደዚህ ያለ ነበረ፤ እርሱም እንደ ሦስቱ ኀያላን ሁሉ ዝናን ያተረፈ ሲሆን፣ [23]ከሠላሳዎቹ ሁሉ በላይ የከበረ ሰው ነበረ፤ ነገር ግን ከሦስቱ እንደ አንዱ አልነበረም። ዳዊትም የክብር ዘበኞቹ አለቃ አድርጎ ሾመው።

[24]ከሠላሳዎቹ መካከል የሚከተሉት ይገኙ
ባቸዋል፤
የኢዮአብ ወንድም አሣሄል፣
የቤተልሔሙ ሰው የዱዲ ልጅ
ኤልያናን፣
[25]አሮዳዊው ሣማ፣
አሮዳዊው ኤሊቃ፣
[26]ፈሊጣዊው ሴሌስ፣
የቴቁሐዊው የዒስካ ልጅ ዒራስ፣
[27]ዓናቶታዊው አቢዔዜር፤
ኩሳታዊው ምቡናይ[ፊ]፣
[28]አሆሃዊው ጸልሞን፣
ነጦፋዊው ማህራይ፣
[29]የነጦፋዊው የበዓና ልጅ ሔሌብ[ፐ]፣
ከብንያም ወገን የጊብዓ ሰው የሆነው
የሪባይ ልጅ ኢታይ፣
[30]ጲርዓቶናዊው በናያስ፣
የገዓስ ሸለቆ ሰው ሂዳይ[ሀ]፣

23፥8 2ሳሙ17፥10፤ 1ዜና27፥2
23፥9 1ዜና8፥4፤ 27፥4
23፥13 ዘፍ38፥1፤ ኢሱ12፥15፤17፥15
23፥14 ሩት1፥19፤ 1ሳሙ22፥4-5፤ 2ሳሙ5፥17
23፥16 ዘፍ35፥14
23፥17 ዘሌ17፥10-12
23፥18 1ሳሙ26፥6
23፥20 ኢሱ15፥21፤2ሳሙ8፥18፤ 1ዜና27፥5
23፥24 2ሳሙ2፥18
23፥25 መሳ7፥1
23፥26 1ዜና 27፥9፡10
23፥27 ኢሱ21፥18፤1ዜና27፥12
23፥28 2ነገ25፥23፤ 1ዜና27፥13፤ዕዝ 2፥22፤ነህ7፥26፤ ኤር40፥8
23፥29 ኢሱ15፥57፤ 1ዜና27፥15
23፥30 ኢሱ24፥30፤ መሳ12፥13

[ጠ]8 *የታሕክሞን ሰው* ማለት *ሐክሞናዊ* ማለት ሊሆን ይችላል። (1ዜና 11፥11 ይመ)።

[ጨ]8 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች ግን፣ *ኢያሱስቴ* ይላሉ፣ ይኸውም፣ *ያሾብዓም* ነው (1ዜና 11፥11 ይመ)።

[ጸ]8 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ (1ዜና 11፥11 ይመ)፤ ዕብራይስጡና አብዛኞቹ የሰብዓ ሊቃናት ትር ጕሞች ግን *ስምንት መቶ ሰዎችን የገደለው አዜናዊው አዲኖ ነበር* ይላሉ።

[ጸ]9 1ዜና 11፥13 ይመ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ *በዚያ ተሰበሰቡ* ይላል

[θ]18 አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች (እንዲሁም 1ዜና 11፥20 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ሁለት የዕብራይስጥ ቅጆችና የሱርስቱ ትርጕም፣ *ሠላሳ* ይላሉ።

[ፊ]27 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች (እንዲሁም 1ዜና 11፥29 ይመ) ግን፣ *ሲባካይ* ይላሉ።

[ፐ]29 አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆችና ቩልጌት (እንዲሁም 1ዜና 11፥30 ይመ) ግን፣ *ሔሌድ* ይላሉ።

[ሀ]30 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች (እንዲሁም 1ዜና 11፥32 ይመ) ግን፣ *ሁራይ* ይላሉ።

31ዓረባዊው አቢዓልቦን፣
በርሑማዊው ዓዝሞት፣
32ሸዓልቦናዊው ኤሊያሕባ፣
የአሳን ልጆች፤
ዮናታን የተባለው፣
33የአሮዳዊው የሣማ ልጅ[ለ]፣
የአሮዳዊው የሻራር[ሐ] ልጅ አሒአም፤
34የማዕካታዊው የአሐሰባይ ልጅ ኤሌፋላት፣
የጊሎናዊው የአኪጦፌል ልጅ ኤሊአም፣
35ቀርሜሎሳዊው ሐጽሮ፤
አርባዊው ፈዓራይ፣
36የሱባ ሰው የሆነው የናታን ልጅ ይግዓል፣
37አሞናዊው ጻሌቅ፣
የጽሩያ ልጅ የኢዮአብ ጦር መሣሪያ ያዥ
የነበረው ብኤሮታዊው ነሃራይ፣
38ይትራዊው ዒራስ፣
ይትራዊው ጋሬብ፣
39እንዲሁም ኬጢያዊው ኦርዮ፤
በጠቅላላው ሠላሳ ሰባት ነበሩ።

## ዳዊት ተዋጊዎቹን ቈጠረ

22፥1-51 ተጓ ምብ - መዝ 18፥1-50

24 እንደ ገናም እግዚአብሔር በእስራ
ኤል ላይ እጅግ ተቈጣ፤ ዳዊ
ትንም በእነርሱ ላይ በማስነሣት፣ “ሂድ
እስራኤልንና ይሁዳን ቊጠር” አለው።
2ስለዚህም ንጉሡ ኢዮአብንና አብረ
ውት ያሉትን የጦር አዛዦች[መ]፣ “ከዳን
እስከ ቤርሳቤህ ወዳሉት የእስራኤል ነገዶች
ሁሉ ሂዱ፤ ብዛታቸው ምን ያህል እንደ ሆነ
ለማወቅ እንድችልም ተዋጊዎቹን መዝግቡ”
አላቸው።
3ኢዮአብ ግን ንጉሡን፣ “አምላክህ እግዚአ
ብሔር ሰራዊቱን መቶ ዕጥፍ ያድርገው፤
የጌታዬ የንጉሡ ዐይን ይህን ለማየት ይብቃ፤
ንጉሡ ጌታዬ ግን ይህን ለማድረግ የፈለ
ገው ለምንድን ነው?” ሲል መለሰለት።
4ሆኖም የንጉሡ ቃል ኢዮአብንና የሰራዊቱን
አዛዦች ስላሸነፋቸው፣ የእስራኤልን ሰራዊት
ለመመዝገብ ከፊቱ ወጥተው ሄዱ።
5ዮርዳኖስን ከተሻገሩ በኋላ፣ በሸለቆው
ውስጥ ካለችው ከተማ በስተ ደቡብ በምት
ገኘው በአሮዔር አጠገብ ሰፈሩ፤ ከዚያም
በጋድ በኩል አድርገው ወደ ኢያዜር ሄዱ፤
6እንዲሁም ወደ ገለዓድና ወደ ተባሶን አዳ
ሰይ፣ ቀጥሎም ወደ ዳንየዓን ከዚያም ዞረው
ወደ ሲዶና ሄዱ። 7ደግሞም ወደ ጢሮስ
ምሽግ፣ ወደ ኤዊያውያንና ወደ ከነዓና
ውያን ከተሞች፣ በመጨረሻም በይሁዳ
ደቡብ ወዳለችው ወደ ቤር ሳቤህ ሄዱ።
8ምድሪቱን ሁሉ ዞረው ከዘጠኝ ወር
ከሃያ ቀን በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ።
9ኢዮአብም የተዋጊዎቹን ጠቅላላ ቊጥር

23፥31 2ሳሙ3፥16
23፥34 ዘዳ3፥14፤ 2ሳሙ11፥3፤15፥12
23፥35 ኢሱ12፥22
23፥36 1ሳሙ14፥47
23፥37 ኢሱ9፥17
23፥38 1ዜና2፥53
23፥39 2ሳሙ11፥3
24፥1 ዘፀ30፥12፤ ኢሱ9፥15፤1ዜና27፥23፤ኢዮ1፥6፤ ዘካ3፥1
24፥2 2ሳሙ3፥10፤ 20፥23፤2ዜና2፥17፤ 17፥14፤25፥5
24፥3 ዘዳ1፥11፤ 2ሳሙ2፥18
24፥5 ዘኍ21፥32፤ ኢሱ13፥9
24፥6 ዘፍ10፥19፤ መሳ1፥31
24፥7 ዘፍ21፥31፤ ዘፀ3፥8፤ዘዳ1፥7፤ ኢሱ19፥29
24፥9 ዘኍ1፥44-46
24፥10 ዘኍ12፥11፤ 22፥34፤1ሳሙ24፥5
24፥11 1ሳሙ9፥9፤ 22፥5
24፥13 ዘፀ5፥3፤ 30፥12፤ዘሌ26፥25፤ ዘዳ28፥21-22፤27-28-35፤28፥38-42፤48፤ 32፥24፤ሕዝ14፥21
24፥14 ነህ9፥28፤ መዝ4፥1፤51፥1፤86፥5፤103፥8፤13፤119፥132፤130፥4፤ኢሳ54፥7፤ 55፥7፤ኤር33፥8፤ 42፥12፤ዳን9፥9
24፥15 1ዜና27፥24
24፥16 ዘፍ6፥6፤ 16፥7፤19፥13፤ዘፀ12፥23፤ሐሥ12፥23
24፥17 ዘፍ18፥23፤ መዝ74፥1፤100፥3፤ ኤር49፥20፤ዮና1፥12

ለንጉሡ አሳወቀ፤ በእስራኤል ስምንት
መቶ ሺህ፣ በይሁዳ አምስት መቶ ሺህ ሰይፍ
መምዘዝ የሚችሉ ብቃት ያላቸው ሰዎች
ተገኙ።
10ዳዊት ተዋጊዎቹን ከቈጠረ በኋላ ኅሊ
ናው ስለ ወቀሰው፣ “ባደረግሁት ነገር ታላቅ
ኀጢአት ሠርቻለሁ፤ አሁንም እግዚአብሔር
ሆይ፤ የአገልጋይህን በደል እንድታርቅ
እለምንሃለሁ፤ የፈጸምሁት ታላቅ የስን
ፍና ሥራ ነውና” አለ።
11በማግስቱ ጠዋት ዳዊት ከመነሣቱ በፊት
የእግዚአብሔር ቃል የዳዊት ባለ ራእይ ወደ
ሆነው ወደ ነቢዩ ወደ ጋድ መጣ፤
12እንዲህም አለው፤ “ሂድና ዳዊትን፣ ‘እግዚ
አብሔር እንዲህ ይላል፤ ሦስት ነገሮችን
ለምርጫ አቅርቤልሃለሁ፤ በአንተ ላይ
አደርግብህ ዘንድ አንዱን ምረጥ’
በለው።”
13ስለዚህም ጋድ ወደ ዳዊት ሄዶ፣ “በም
ድርህ የሦስት[ሠ] ዓመት ራብ ይምጣብህ?
ወይስ ጠላቶችህ እያሳደዱህ ሦስት ወር
ትሸሽ? ወይስ ደግሞ በምድርህ ላይ የሦ
ስት ቀን ቸነፈር ይምጣ? እንግዲህ አሁን
ለላከኝ ምን መልስ እንደምሰጥ አስበህበት
ወስን” አለው።
14ዳዊትም ጋድን፣ “እጅግ ተጨንቄአለሁ፤
ምሕረቱ ታላቅ ስለሆነ በእግዚአብሔር
እጅ እንውደቅ፤ በሰው እጅ ግን አልውደቅ”
አለው። 15ስለዚህም እግዚአብሔር ከዚያች
ዕለት ጥዋት አንሥቶ እስከ ተወሰነው ቀን
ድረስ በእስራኤል ላይ ቸነፈር ላከ፤ በዚ
ህም ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ድረስ ሰባ ሺህ
ሰው አለቀ። 16የእግዚአብሔር መልአክ
ኢየሩሳሌምን ለማጥፋት እጁን በዘረጋ ጊዜ፣
የደረሰው ጒዳት እግዚአብሔርን ስላሳዘ
ነው፣ ሕዝቡን የሚቀሥፈውን መልአክ
“በቃ! እጅህን መልስ” አለው። በዚያን ጊዜ
የእግዚአብሔር መልአክ በኢያቡሳዊው በኦ
ርና ዐውድማ አጠገብ ቆሞ ነበር።
17ዳዊት ሕዝቡን የሚቀሥፈውን መል
አክ ባየ ጊዜ እግዚአብሔርን፦ “እነሆ ኀጢ
አት የሠራሁም የተሳሳትሁም እኔ ነኝ፤ እነ
ዚህ ግን በጎች ናቸው፤ ምን አጠፉ? እጅህ
በእኔና በአባቴ ቤት ላይ ትሁን” አለ።

[ለ]33 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች (እንዲሁም 1ዜና 11፥34 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን ***ልጅ*** የሚለውን አይጨምርም።
[ሐ]33 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች (እንዲሁም 1ዜና 11፥35 ይመ) ግን፣ ***ሳካር*** ይላሉ።
[መ]2 የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም -እንዲሁም ቍጥር 4 እና 1ዜና 21፥2 ይመ? ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን፣ ***የጦር አዛዡ ኢዮአብ*** ይላል።
[ሠ]13 የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም (እንዲሁም 1ዜና 21፥12 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን፣ ***ሰባት*** ይላል።

## *ዳዊት መሠዊያ ሠራ*

24፥18-25 ተጓ ምብ - 1ዜና 21፥18-26

18በዚያን ቀን ጋድ ወደ ዳዊት ዘንድ
ሄዶ፣ "ውጣና በኢያቡሳዊው በኦርና ዐው
ድማ ላይ *ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሥራ*"
አለው። 19ስለዚህ ዳዊት፣ *እግዚአብሔር*
በጋድ በኩል ባዘዘው *መሠረት* ወጣ።
20ኦርናም ቍልቍል ሲመለከት፣ ንጉሡና
ሰዎቹ ወደ እርሱ ሲመጡ አየ፤ ከዚያም
ወጥቶ ወደ መሬት ለጥ ብሎ ለንጉሡ
እጅ ነሣ።
21ኦርናም፣ "ንጉሥ ጌታዬ ወደ አገል
ጋዩ የመጣው ለምንድን ነው?" አለ።
ዳዊትም መልሶ፣ "መቅሠፍቱ ከሕዝቡ
እንዲከለከል *ለእግዚአብሔር* መሠዊያ እን
ድሠራ ዐውድማህን ልገዛ ነው" አለው።
22ኦርናም ዳዊትን እንዲህ አለ፤ "ንጉሥ
ጌታዬ ደስ ያለውን ወስዶ መሥዋዕቱን ያቅርብ፤
ለሚቃጠል መሥዋዕት በሬዎች አሉ፤

24፥18 ዘፍ22፥2፤
2ዜና3፥1
24፥21 ዘኍ16፥
44-50
24፥22 1ሳሙ6፥14
24፥23 ዘፍ23፥11
24፥24 ዘፍ23፥16፤
ሚል1፥13-14
24፥25 1ሳሙ
7፥17፤2ሳሙ21፥14

ለሚነደውም ዕንጨት፣ የመውቂያው ዕቃና
የበሬ ቀንበር አለ። 23ንጉሥ ሆይ፣ ይህን
ሁሉ ኦርና ለንጉሡ ይሰጣል።" እንዲሁም
ኦርና፣ "*እግዚአብሔር* አምላክህ ይቀበልህ"
አለው።
24ንጉሡ ግን ኦርናን፣ "እንዲህማ አይሆ
ንም፤ ዋጋውን ሳንተ መክፈል አለብኝ፤
ለአ ምላኬም *ለእግዚአብሔር* የሚቃጠል
መሥ ዋዕት ያለ ዋጋ አላቀርብም"
አለው።
ስለዚህም ዳዊት ዐውድማውንና በሬዎቹን
በአምሳ ሰቅል[ሩ] ብር ገዛ፤ 25በዚያም ዳዊት
*ለእግዚአብሔር* መሠዊያ ሠራ፤ የሚቃጠል
መሥዋዕትና የኅብረት መሥዋዕት[ሰ] አቀረበ።
ከዚያም *እግዚአብሔር* ስለ ምድሪቱ የቀረ
በውን ጸሎት ሰማ፤ በእስራኤል ላይ የመ
ጣውም ቸነፈር ቆመ።

[ሩ]24 0.6 ኪሎ ግራም ያህል ነው።
[ሰ]25 በትውፊት፣ *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል።

# መጽሐፈ ነገሥት - አንደኛ

## አዶንያስ ለመንገሥ እንደ ፈለገ

**1** ንጉሥ ዳዊት እየሸመገለና ዕድሜው በጣም እየገፋ ሲሄድ፣ ልብስ ቢደራርቡለትም እንኳ ሊሞቀው አልቻለም:: [2]ስለዚህ አገልጋዮቹ፣ “ንጉሡን የምትንከባከብና የምታገለግል ወጣት ድንግል እንፈልግ፤ እርሷም ጌታችን ንጉሡ እንዲሞቀው በጐኑ ትተኛለች” አሉት::

[3]ከዚያም በመላው እስራኤል ቈንጆ ልጃገረድ ፈልገው ሱነማዊቷን አቢሳን አገኙ፤ ለንጉሡም አመጡለት:: [4]ልጃገረዲቱ እጅግ ቈንጆ ነበረች፤ ንጉሡንም ትንከባከበውና ታገለግለው ነበር፤ ንጉሡ ግን ከእርሷ ጋር ግንኙነት አልነበረውም::

[5]በዚህ ጊዜ ከአጊት የተወለደው አዶንያስ፣ “እነግሣለሁ” ብሎ ተነሣ፤ ስለዚህ ሠረገሎችንና[ሀ] ፈረሶችን እንዲሁም ከፊት ከፊቱ የሚሄዱ አምሳ ሰዎችን አዘጋጀ:: [6]አባቱም፣ “ለምን እንዲህ ታደርጋለህ?” ብሎ ገሥጾት አያውቅም ነበር፤ አዶንያስም እጅግ መልከ መልካምና የአቤሴሎም ታናሽ ወንድም ነበር::

[7]አዶንያስ ከጽሩያ ልጅ ከኢዮአብና ከካህኑ ከአብያታር ጋር ተመካከረ፤ እነርሱም ድጋፋቸውን ሰጡት:: [8]ነገር ግን ካህኑ ሳዶቅ፣ የዮዳሄ ልጅ በናያስ፣ ነቢዩ ናታን፣ ሳሚ፣ ሬሲና[ለ] የዳዊት የክብር ዘበኞች ከአዶንያስ ጋር አልተባበሩም::

[9]ከዚያም አዶንያስ በዓይንሮጌል አቅራቢያ ባለው የዞሔልት ድንጋይ አጠገብ በጎችን፣ በሬዎችንና የሰቡ ጥጆችን ሠዋ፤ ወንድሞቹን ሁሉ፣ የንጉሡን ልጆች እንዲሁም የቤተ መንግሥቱ ሹማምት የነበሩትን የይሁዳ ሰዎች ሁሉ ጠራ፤ [10]ይሁን እንጂ ነቢዩ ናታንንም ሆነ በናያስን፣ የክብር ዘበኞቹ ንም ሆነ ወንድሙን ሰሎሞንን አልጠራም::

[11]ከዚያም ናታን የሰሎሞንን እናት ቤርሳቤህን እንዲህ አላት፤ “ጌታችን ዳዊት ሳያውቅ የአጊት ልጅ አዶንያስ መንገሡን አልሰማሽምን? [12]አሁንም የራስሽንና የልጅሽን የሰሎሞንን ሕይወት እንዴት ማዳን እንደምትችዪ ልምከርሽ፤ [13]ወደ ንጉሥ ዳዊት ሂጂና፣ ‘ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፤ ልጅሽ ሰሎሞን ከእኔ ቀጥሎ ይነግሣል፤ በዙፋኔም ይቀመጣል’ ብለህ ‘ለእኔ ለአገልጋይህ አልማልህልኝም ነበር? ታዲያ አዶንያስ የነገሠው ስለ ምንድን ነው?’ በዪው፤ [14]አንቺ እዚያው ሆነሽ ይህን በምትነግሪው ጊዜ እኔ እገባና ያልሽው ትክክል መሆኑን አረጋግጣለሁ::”

[15]ስለዚህ ቤርሳቤህ፣ ሱነማዊቷ አቢሳ በምታገለግልበት ክፍል እርጅና የተጫጫነውን ንጉሥ ለማነጋገር ሄደች:: [16]ቤርሳቤህም ለጥ ብላ እጅ ከነሣች በኋላ እፊቱ በጕልበቷ ተንበረከከች::

ንጉሡም፣ “ምን ትፈልጊያለሽ?” ሲል ጠየቃት::

[17]እርሷም እንዲህ አለችው፣ “ጌታዬ ሆይ፤ ‘ልጅሽ ሰሎሞን ከእኔ ቀጥሎ ይነግሣል፤ በዙፋኔም ይቀመጣል’ ብለህ አንተው ራስህ ለአገልጋይህ በአምላክህ *በእግዚአብሔር* ምለህልኝ ነበር:: [18]እነሆ፤ አሁንም አዶንያስ ነግሦአል፤ ንጉሥ ጌታዬ አንተ ግን ስለዚህ ነገር አታውቅም:: [19]እርሱ በሬዎችን፣ ኮርማዎችንና በጎችን በብዛት ሠውቶአል፤ የንጉሡን ልጆች በሙሉ፣ ካህኑን አብያታርንና የሰራዊቱን አዛዥ ኢዮአብን ጠርቶአል፤ አገልጋይህን ሰሎሞንን ግን አልጠራውም:: [20]ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፤ ከአንተ ቀጥሎ በጌታዬ በንጉሡ ዙፋን ላይ ማን መቀመጥ እንዳለበት እንድታሳውቀው የእስራኤል ዐይን ሁሉ አንተን ይመለከታል:: [21]ያለበለዚያ ግን ንጉሥ ጌታዬ ከአባቶቹ ጋር በሚያንቀላፋበት ጊዜ እኔና ልጄ ሰሎሞን እንደ ወንጀለኞች እንቈጠራለን::”

[22]እርሷ ከንጉሡ ጋር በመነጋገር ላይ ሳለች ነቢዩ ናታን ገባ:: [23]ለንጉሡም፣ “ነቢዩ ናታን መጥቶአል” ብለው ነገሩት፤ እርሱም ንጉሡ ፊት ቀርቦ ለጥ ብሎ እጅ ነሣ::

[24]ናታንም እንዲህ አለው፤ “ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፤ ለመሆኑ አዶንያስ ከአንተ ቀጥሎ እንደሚነግሥ፣ በዙፋንህም እንደሚቀመጥ አስታውቀሃልን? [25]በዛሬው ቀን ታች ወርዶ ብዙ በሬዎች፣ ኮርማዎችና በጎች ሠውቶአል፤ የንጉሡን ልጆች በሙሉ፣ የሰራዊቱን አዛዦችና ካህኑን አብያታርንም ጠርቶአል፤ እነሆ፤ አሁን፣ ‘አዶንያስ ለዘላለም ይኑር’ እያሉ ከእርሱ ጋር በመብላትና በመጠጣት ላይ ናቸው:: [26]ነገር ግን እኔን አገልጋይህን፣ ካህኑን ሳዶቅን፣ የዮዳሄን

1፥3 ቍ15ኢሱ19፥18፤2ሳሙ37፤1ነገ2፥17፡22
1፥5 1ሳሙ8፥11፤2ሳሙ3፥4
1፥6 1ሳሙ3፥13
1፥7 1ሳሙ22፥20፤2ሳሙ2፥13፡18
1፥8 1ሳሙ2፥35፤2ሳሙ7፥2፤8፥17፡18፤23፥8፤1ነገ4፥18
1፥9 2ሳሙ17፥17፤1ዜና29፥24
1፥10 ቍ26፤2ሳሙ12፥24
1፥11 2ሳሙ3፥4፤12፥24
1፥12 ምሳ15፥22
1፥13 ቍ17፡30
1፥15 ቍ3
1፥17 ቍ13
1፥19 ቍ9
1፥21 ዘፍ15፥15፤1ነገ2፥10
1፥26 ቍ10

[ሀ]5 ወይም *ሠረገለኞች* ተብሎ ሊተረጐም ይችላል::
[ለ]8 ወይም *እና ጓደኞቹ* ተብሎ ሊተረጐም ይችላል::

ልጅ በናያስንና አገልጋይህን ሰሎሞንን
አልጠራም፤ 27ታዲያ ከእርሱ ቀጥሎ በን
ጉሥ ጌታዬ ዙፋን ላይ የሚቀመጠውን
አገልጋዮቹን ሳያሳውቅ ይህ እንዲሆን ንጉሡ
ፈቅዶአልን?”

## ዳዊት ሰሎሞን እንዲነግሥ አደረገ

1፥28-53 ተጓ ምብ - 1ዜና 29፥21-25

28ከዚያም ንጉሥ ዳዊት፣ “ቤርሳቤህን
ጥሩልኝ” አለ፤ እርሷም ንጉሡ ወዳለበት
ገብታ በፊቱ ቆመች፡፡
29ከዚያም ንጉሡ እንዲህ ሲል ማለ፤
“ነፍሴን ከመከራ ሁሉ ያዳናት ሕያው
*እግዚአብሔርን*! 30‘ልጅሽ ሰሎሞን ከእኔ
ቀጥሎ ይነግሣል፤ በእኔም ምትክ በዙፋኔ
ይቀመጣል’ ብዬ በእስራኤል አምላክ *በእግዚ
አብሔር* የማልሁልሽን ዛሬ በእውነት እፈ
ጽማለሁ”
31ቤርሳቤህም ለጥ ብላ እጅ ከነሣች በኋላ፣
በንጉሡ ፊት ተንበርክካ፣ “ጌታዬ ንጉሥ
ዳዊት ለዘላለም ይኑር!” አለች፡፡
32ንጉሥ ዳዊትም፣ “ካህኑን ሳዶቅን፣
ነቢዩን ናታንንና የዮዳሄን ልጅ በናያስን
ጥሩልኝ” አለ፡፡ እነርሱም ንጉሡ ፊት በቀ
ረቡ ጊዜ፣ 33እንዲህ አላቸው፤ “የጌታች
ሁን አገልጋዮች ይዛችሁ በመሄድ ልጄን
ሰሎሞንን በራሴ በቅሎ ላይ አስቀምጡት፤
ወደ ግዮንም ይዛችሁት ውረዱ፡፡ 34በዚ
ያም ካህኑ ሳዶቅና ነቢዩ ናታን ቀብተው
በእስራኤል ላይ ያንግሡት፤ ቀንደ መለ
ከት ነፍታችሁም፣ ‘ንጉሥ ሰሎሞን ለዘ
ላለም ይኑር!’ ብላችሁ ጩኹ፡፡ 35አጅባ
ችሁት ወደ ላይ ውጡ፤ ከዚያም መጥቶ
በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ፤ በእኔም ምትክ
ይግዛ፤ በእስራኤልና በይሁዳ ላይ ሾሜ
ዋለሁ፡፡”
36የዮዳሄ ልጅ በናያስም ለንጉሡ እንዲህ
ሲል መለሰ፤ “አሜን! የጌታዬ የንጉሡ
አምላክ *እግዚአብሔር* ይህንኑ ያጽናው፡፡
37*እግዚአብሔር* ከጌታዬ ከንጉሡ ጋር እንደ
ነበረ ሁሉ፣ ከሰሎሞንም ጋር ይሁን፤
ዙፋኑንም ከጌታዬ ከንጉሥ ዳዊት ዙፋን
የበለጠ ያድርገው፡፡”
38ስለዚህ ካህኑ ሳዶቅ፣ ነቢዩ ናታን፣
የዮዳሄ ልጅ በናያስ፣ ከሊታውያንና ፈሊ
ታውያን ወርደው ሰሎሞንን በንጉሥ
ዳዊት በቅሎ አስቀምጠው በማጀብ ወደ
ግዮን አመጡት፡፡ 39ካህኑ ሳዶቅም የዘይቱን
ቀንድ ከመገናኛው ድንኳን ወስዶ ሰሎሞንን
ቀባው፤ ከዚያም ቀንደ መለከቱን ነፉ፤ ሕዝ
ቡም በሙሉ፣ “ንጉሥ ሰሎሞን ለዘላለም
ይኑር!” በማለት ዳር እስከ ዳር አስተ

1፥29 2ሳሙ4፥9
1፥30 ቍ13፤1ዜና 23፥1
1፥32 1ሳሙ2፥35
1፥33 ቍ38፤መሳ 10፥4፤2ዜና32፥30፤ 33፥14፤ዘካ9፥9
1፥34 1ሳሙ2፥35፤ 10፥1፤2ሳሙ15፥10
1፥37 ቍ47፤ኢሱ 1፥5፡17
1፥38 ቍ8፡33፤ 1ሳሙ30፥14፤2ሳሙ 15፥18
1፥39 ቍ34፤ዘፀ 26፥1፤27፥21፤29፥7፤ዘ ኍ23፥21፤1ሳሙ 10፥1፤2ሳሙ15፥10፤ 2ነገ11፥12፡14፤መዝ 47፥5፤89፥20፤ ዘካ9፥9
1፥40 1ሳሙ10፥5
1፥41 2ዜና23፥ 12፡13
1፥42 2ሳሙ15፥ 27፡36፤18፥26
1፥45 ቍ40
1፥46 ዘዳ17፥18
1፥47 ቍ37
1፥48 ነገ3፥6
1፥50 ዘፀ27፥2
1፥52 1ሳሙ14፥45

ጋቡ፡፡ 40ሕዝቡ ሁሉ እንቢልታ እየነፉና
እጅግ እየተደሰተ አጀበው፤ ከድምፁ የተ
ነሣም ምድሪቱ ተናወጠች፡፡
41አዶንያስና የተጠሩት እንግዶች ሁሉ
ግብዣውን በማገባደድ ላይ ሳሉ፣ ይህንኑ
ሰሙ፤ ኢዮአብም የመለከቱን ድምፅ ሲሰማ፣
“ይህ በከተማዪቱ ውስጥ የሚሰማው ድምፅ
ምንድን ነው?” ሲል ጠየቀ፡፡
42ኢዮአብ ገና ተናግሮ ሳይጨርስ፣ የካ
ህኑ የአብያታር ልጅ ዮናታን ደረሰ፤ አዶ
ንያስም፣ “እንዳንተ ያለ ታማኝ ሰው መል
ካም ዜና ሳይዝ አይመጣምና ግባ” አለው፡፡
43ዮናታንም እንዲህ ሲል መለሰ፣ “ነገሩ
ከቶ እንዲህ አይደለም! ጌታችን ንጉሥ
ዳዊት ሰሎሞንን አንግሦታል፡፡ 44ንጉሡ
ካህኑ ሳዶቅ፣ ነቢዩ ናታን፣ የዮዳሄ ልጅ
በናያስ፣ ከሊታውያንና ፈሊታውያን አብ
ረውት እንዲሄዱ አድርጎአል፤ እነርሱም
በንጉሡ በቅሎ አስቀመጡት፡፡ 45ካህኑ
ሳዶቅና ነቢዩ ናታን በግዮን ቀብተው አን
ግሠውታል፡፡ ከዚያም ደስ ብሎአቸው ወጥ
ተዋል፤ ከተማዪቱም ይህንኑ አስተጋብታ
ለች፤ እንግዲህ የሰማችሁት ድምፅ ይኸው
ነው፡፡ 46ከዚህም ሌላ ሰሎሞን በመንግሥቱ
ዙፋን ላይ ተቀምጦአል፡፡ 47የመንግሥቱ
ሹማምትም ወደ ጌታችን ወደ ንጉሥ
ዳዊት መጥተው፣ ‘አምላክህ የሰሎሞንን
ስም ከአንተ ስም የላቀ፣ ዙፋኑንም ከአ
ንተ ዙፋን የበለጠ ያድርገው’ በማለት
መልካም ምኞታቸውን ገልጸውለታል፡፡
ንጉሡም ዐልጋው ላይ ሆኖ በመስገድ፣
48‘ዛሬ በዙፋኔ ላይ የሚቀመጠውን ወራሽ
ዐይኔ እንዲያይ የፈቀደ፣ የእስራኤል
አምላክ *እግዚአብሔር*፣ ምስጋና
ይድረሰው’ አለ፡፡”
49በዚህም አዶንያስና የጠራቸው እንግዶች
በሙሉ ደንግጠው ተነሡ፤ በየአቅጣጫ
ውም ተበታተኑ፡፡ 50አዶንያስ ግን ሰሎሞ
ንን በመፍራት ሄዶ፣ የመሠዊያውን ቀንድ
ያዘ፡፡ 51ከዚያም፣ ለሰሎሞን፣ “አዶንያስ
እነሆ፣ ንጉሥ ሰሎሞንን በመፍራት የመ
ሠዊያውን ቀንድ ይዞ ተማጥኖአል፤ እር
ሱም፣ ‘ባሪያውን በሰይፍ እንዳይገድለው
ንጉሡ ሰሎሞን ዛሬውኑ ይማልልኝ’ ብሎ
አል” ብለው ነገሩት፡፡
52ሰሎሞንም፣ “አካሄዱን ካሳመረ ከራስ
ጠጕሩ አንዲቱ እንኳ መሬት ላይ አትወ
ድቅም፤ ጥፋት ከተገኘበት ግን ይሞታል”
ሲል መለሰ፡፡ 53ከዚያም ንጉሥ ሰሎሞን
ሰዎች ልከ ከመሠዊያው ላይ አወረዱት፡፡
አዶንያስም መጥቶ ለንጉሥ ሰሎሞን
አጐንብሶ እጅ ነሣ፤ ሰሎሞንም፣ “በል ወደ
ቤትህ ሂድ” አለው፡፡

### ዳዊት ለሰሎሞን የሰጠው መመሪያ
2፥10-12 ተጓ ምብ - 1ዜና 29፥26-28

2 ዳዊት የሚሞትበት ጊዜ እንደ ተቃ
ረበም፣ ልጁን ሰሎሞንን እንዲህ ሲል
አዘዘው፤
2"እነሆ፤ እኔ የምድሩን ሁሉ መንገድ ልሄድ
ነው፤ እንግዲህ በርታ፤ ሰውም ሁን፡፡ 3የአ
ምላክህን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቅ፤
የምታደርገው ሁሉ እንዲከናወንልህ፣ በም
ትሄድበትም ሁሉ እንዲሳካልህ፣ በሙሴ
ሕግ እንደ ተጻፈው በመንገዶቹ ተመላለስ፣
ሥርዐቶቹንና ትእዛዛቱን፣ ሕጋጋቱንና ደን ቦቸ
-ን ጠብቅ፤ 4እግዚአብሔርም፣ 'ዘሮችህ
መንገዳቸውን ቢጠብቁ፣ እንዲሁም በፍጹም
ልባቸው፣ በፍጹም ነፍሳቸው በታማኝነት
በፊቴ ቢመላለሱ፣ በእስራኤል ዙፋን የሚ
ቀመጥ ሰው ከዘርህ አላሳጣህም' ሲል
የሰጠኝን ተስፋ ይፈጽምልኛል፡፡
5የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ በእኔ ላይ ያደረ
ገውን፣ እንዲሁም በእስራኤል ሰራዊት
አዛዦች በኔር ልጅ በአበኔርና በዬቴሩ
ልጅ በአሜሳይ ላይ የፈጸመውን አንተው
ራስህ ታውቃለህ፤ ጦርነት ሳይኖር በሰ
ላሙ ጊዜ ደማቸውን አፍሶአል፤ በዚህም
ደም ወገቡ ላይ የታጠቀውን ቀበቶና በእ
ግሩ ላይ ያደረገውን ጫማ በክሎአል፡፡
6መደረግ ያለበትን በጥበብህ አድርግ፤
ከነሽበቱ በሰላም ወደ መቃብር[ሐ] እንዲ
ወርድ አታድርግ፡፡
7"ከወንድምህ ከአቤሴሎም በሸሸሁ ጊዜ
መልካም ነገር አድርገውልኛልና ለገለዓዳ
ዊው ለቤርዜሊ ልጆች ግን በጎ ነገር አድ
ርግላቸው፤ ማእድህን ከሚካፈሉ ሰዎችም
ጋር አብረው ይብሉ፡፡
8"ወደ መሃናይም በሄድሁ ጊዜ፣ ክፉኛ
የረገመኝ የባሑሪም ሰው የብንያማዊው የጌራ
ልጅ ሳሚ እነሆ፤ ከአንተ ዘንድ ይገኛል፤ ሊቀ
በለኝ ወደ ዮርዳኖስ ሲወርድ፣ 'በሰይፍ
አልገድልህም' ብዬ በእግዚአብሔር ስም
ምዬለታለሁ፤ 9አሁን ግን በደል እንደ
ሌለበት ሰው አትተወው፤ ጥበበኛ ነህና
መደረግ ያለበትን ታውቃለህ፤ ሽበቱን
በደም ወደ መቃብር አውርድ፡፡"
10ከዚያም ዳዊት ከአባቶቹ ጋር አንቀ
ላፋ፤ በዳዊትም ከተማ ተቀበረ፡፡ 11ዳዊት
በኬብሮን ሰባት ዓመት፣ በኢየሩሳሌም
ሠላሳ ሦስት ዓመት ባጠቃላይ አርባ ዓመት
በእስራኤል ላይ ነገሠ፡፡ 12ስለዚህ ሰሎሞን
በአባቱ በዳዊት ዙፋን ተቀመጠ፤ መንግ
ሥቱም እጅግ የጸና ሆነ፡፡

### የሰሎሞን መንግሥት መጽናት

2፥1 ዘፍ27፥2፤ ዘኍ27፥13
2፥2 ኢሱ1፥6፤ 23፥14
2፥3 ዘዳ4፥6፤10፥12፤17፥1420፤ኢሱ 1፥7፤1ዜና22፥13
2፥4 2ሳሙ7፥13፡ 15፤2ነገ18፥36፤20፥3፤ 2ዜና23፥3፤መዝ26፥ 13፤132፥12
2፥5 1ሳሙ14፥50፤ 2ሳሙ2፥18፤3፥27፤ 17፥25
2፥6 ቍ9
2፥7 ዘፍ40፥14፤ 2ሳሙ9፥7፤17፥27፤ 19፥3139
2፥8 ቍ36-46፤ ዘፍ32፥2፤2ሳሙ16፥ 5-13፤19፥18-23
2፥9 ቍ6
2፥10 2ሳሙ5፥7፤ ሐሥ2፥29
2፥11 2ሳሙ5፥4፡5
2፥12 ቍ46፤1ዜና 17፥14፤29፥23፤2ዜና1 ፥1፤9፥8፤12፥13፤ 17፥1፤21፥4
2፥13 1ሳሙ16፥4፤ 2ሳሙ3፥4
2፥17 1ነገ1፥3
2፥19 1ነገ15፥13፤ 2ነገ10፥13፤24፥15፤ 2ዜና15፥16፤መዝ45፥ 9፤ኤር13፥18፤22፥26፤ 29፥2
2፥21 1ነገ1፥3
2፥22 ዘፍ22፥24፤ 1ሳሙ22፥20፤1ነገ1፥3 ፤1ዜና3፥2
2፥23 ሩት1፥17
2፥24 2ሳሙ7፥11
2፥25 2ሳሙ8፥18፤ 12፥10
2፥26 ኢሱ21፥18፤ 1ሳሙ22፥20፤2ሳሙ 15፥14፡24

13በዚህ ጊዜ የአጊት ልጅ አዶንያስ ወደ
ሰሎሞን እናት ወደ ቤርሳቤህ ሄደ፤ ቤርሳ
ቤህም፣ "የመጣኸው በሰላም ነውን?"
ስትል ጠየቀችው፤
እርሱም፣ "አዎን በሰላም ነው" ብሎ
መለሰ፡፡ 14ከዚያም፣ "የምነግርሽ ጉዳይ አለኝ"
አላት፡፡
እርሷም፣ "እሺ ተናገር" ብላ መለሰች፡፡
15እርሱም፣ "መንግሥቱ የእኔ እንደ ነበ
ረና እስራኤልም ሁሉ እኔ እንድነግሥ ዐይ
ናቸውን ጥለውብኝ እንደ ነበር አንቺ ራስሽ
ታውቂአለሽ፤ ሆኖም ነገሩ ከእግዚአብሔር
የተቈረጠለት ሆነና ሁኔታዎች ተለዋውጠው፣
መንግሥቱ ለወንድሜ ተላለፈ፡፡ 16አሁንም
አንዲት ነገር እለምንሻለሁ፤ አታሳፍሪኝ"
አላት፡፡
እርሷም፣ "በል እሺ ተናገር" አለችው፡፡
17እርሱም፣ "ንጉሥ ሰሎሞን መቼም እምቢ
አይልሽምና ሱነማዊቷን አቢሳን እንዲድር
ልኝ ለምኚልኝ" አላት፡፡
18ቤርሳቤህም፣ "መልካም ነው፤ ይህንኑ
ለንጉሡ እነግርልሃለሁ" ብላ መለሰች፡፡
19ስለዚህም ቤርሳቤህ የአዶንያስን ጉዳይ
ልትነግረው ወደ ንጉሥ ሰሎሞን ሄደች፤
ንጉሡም ሊቀበላት ተነሣ፤ እጅ ከነሣትም
በኋላ በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ፤ ንጉሡም
ለእናቱ ሌላ ዙፋን አስመጥቶ በቀኙ አስ
ቀመጣት፡፡
20እርሷም፣ "የምለምንህ አንዲት ነገር አለ
ችኝና እባክህ እሺ በለኝ" አለችው፡፡
ንጉሡም፣ "እናቴ ሆይ፤ አላሳፍርሽምና
ንገሪኝ" ሲል መለሰላት፡፡
21ስለዚህም፣ "ሱነማዊቷን አቢሳን ወንድ
ምህ አዶንያስ ቢያገባትስ?" አለችው፡፡
22ንጉሥ ሰሎሞንም እናቱን፣ "ስለምን
ሱነማዊቷን አቢሳን ብቻ ለአዶንያስ ትጠ
ይቂለታለሽ? ታላቅ ወንድሜ ስለ ሆነ
መንግሥቱንም ጠይቂለት እንጂ፤ ለእርሱ
ብቻ ሳይሆን እንዲሁም ለካህኑ ለአብ
ያታርና ለጽሩያ ልጅ ለኢዮአብ ጠይቂ
ላቸው" አላት፡፡
23ከዚያም ንጉሥ ሰሎሞን በእግዚአብሔር
ስም እንዲህ ሲል ማለ፤ "አዶንያስ ይህን
ስለ ጠየቀ በሞት ሳይቀጣ ቢቀር፣ እግዚአ
ብሔር ይፍረድብኝ፤ ከዚህ የባሰም ያምጣ
ብኝ፤ 24አሁንም በሚገባ ያጸናኝ፤ በአባቴ
በዳዊት ዙፋን ያስቀመጠኝና በሰጠውም
ተስፋ መሠረት ሥርወ መንግሥትን የመ
ሠረተልኝ ሕያው እግዚአብሔርን አዶንያስ

[ሐ]6 በዚህ ስፍራና በቍጥር 9 ላይ ዕብራይስጡ ሲኦል ይላል፡፡

ዛሬ ይሞታል!” 25ስለዚህም አዶንያስን እን
ዲገድለው ንጉሥ ሰሎሞን፣ የዮዳሄን ልጅ
በናያስን አዘዘው፤ በናያስም አዶንያስን
መቶ ገደለው፡፡
26ንጉሡም ካህኑን አብያታርን፣ “ሞት
የሚገባህ ሰው ነበርህ፤ ነገር ግን ልዑል
*እግዚአብሔርን* ታቦት በአባቴ በዳዊት ፊት
ስለ ተሸከምህ፣ አባቴ የተቀበለውንም መከራ
ሁሉ አብረኸው ስለ ተቀበልህ፣ እኔ አሁን
አልገድልህም፤ ዓናቶት ወዳለው ዕርሻህ
ሂድ” አለው፡፡ 27ስለዚህ *እግዚአብሔር* ስለ
ዔሊ ቤት በሴሎ የተናገረውን ቃል ለመ
ፈጸም፣ ሰሎሞን አብያታርን *ከእግዚአብሔር*
ክህነት አስወገደው፡፡
28ከአቤሴሎም ጋር ሳይሆን ከአዶንያስ
ጋር አሢሮ የነበረው ኢዮአብም ይህን በሰማ
ጊዜ፣ ወደ *እግዚአብሔር* ድንኳን ሸሽቶ
የመሠዊያውን ቀንድ ያዘ፡፡ 29ኢዮአብ ወደ
*እግዚአብሔር* ድንኳን ሸሽቶ መሄዱንና
በመሠዊያው አጠገብ መሆኑን ንጉሥ ሰሎ
ሞን በሰማ ጊዜ፣ የዮዳሄን ልጅ በናያስን፣
“ሂድና ግደለው!” ብሎ አዘዘው፡፡
30ስለዚህም በናያስ ወደ *እግዚአብሔር*
ድንኳን ገብቶ ኢዮአብን፣ “ንጉሡ፣ ‘ከዚህ
ውጣ’ ይልሃል” አለው፡፡
እርሱ ግን “አልወጣም፣ እዚሁ እሞታ
ለሁ” አለው፡፡
በናያስም፣ “ኢዮአብ የሰጠኝ መልስ
ይህ ነው” በማለት ለንጉሡ ተናገረ፡፡
31ንጉሡም በናያስን እንዲህ ሲል አዘ
ዘው፤ “በል እንዳለው አድርግ፤ ግደልና ቅበ
ረው፤ ኢዮአብ በከንቱ ካፈሰሰው ንጹሕ
ደምም እኔንና የአባቴን ቤት አንጻን፡፡
32አባቴ ዳዊት ሳያውቅ ኢዮአብ በሁለቱ
ሰዎች ላይ አደጋ ጥሎ በሰይፍ ገድሎአቸ
ዋልና ስላፈሰሰው ደም *እግዚአብሔር* ይበ
ቀለዋል፡፡ የእስራኤል ሰራዊት አዛዥ የኔር
ልጅ አበኔርና የይሁዳ ሰራዊት አዛዥ
የዬቴሩ ልጅ አሜሳይ ሁለቱም ከእርሱ
የተሻሉና ይበልጥ ትክክለኛ ሰዎች ነበሩ፡፡
33የደማቸውም ዕዳ ለዘላለም በኢዮአብና
በዘሩ ራስ ላይ ይሁን፡፡ ነገር ግን በዳዊትና
በዘሩ፣ በቤቱና በዙፋኑ ላይ *የእግዚአብሔር*
ሰላም ለዘላለም ጸንቶ ይኑር፡፡”
34ስለዚህም የዮዳሄ ልጅ በናያስ ወጣ፤
ኢዮአብንም መቶ ገደለው፤ እርሱም በም
ድረ በዳ ባለው በገዛ ምድሩ[መ] ተቀበረ፡፡
35ንጉሡም በኢዮአብ ቦታ የዮዳሄን ልጅ
በናያስን በሰራዊቱ ላይ ሾመ፤ በአብያታ
ርም ቦታ ካህኑን ሳዶቅን ተካ፡፡
36ከዚያም ንጉሡ ሳሚን አስጠርቶ እንዲህ
አለው፤ “በኢየሩሳሌም ቤት ሠርተህ እዚያው

2፥27 1ሳሙ2፥27-36
2፥28 ዘፀ27፥2
2፥29 ቀኍ25፤ዘፀ21፥14
2፥30 ዘፀ21፥14፤2ነገ11፥15
2፥31 ዘዳ19፥13
2፥32 ዘፍ4፥14፤መሳ9፥24፡57፤2ሳሙ17፥25፤2ዜና21፥13
2፥34 ቀኍ25፤2ሳሙ2፥18
2፥35 1ሳሙ2፥35፤2ሳሙ8፥18
2፥36 2ሳሙ16፥5
2፥37 ዘሌ20፥9፤2ሳሙ15፥23፤ዮሐ18፥1
2፥39 1ሳሙ27፥2
2፥42 2ሳሙ19፥23
2፥44 2ሳሙ16፥5-13
2፥45 2ሳሙ7፥13
2፥46 ቀኍ8፡12፤2ሳሙ818
3፥1 2ሳሙ5፥7፤7፥2፤1ነገ2፥10፤7፥8፤9፥10፡24፤11፥113፤2ዜና8፥11
3፥2 ዘሌ17፥35፤26፥30፤ዘዳ12፥14፤14፥23፤1ነገ15፥14፤22፥43

ተቀመጥ፤ ከዚያ ግን የትም እንዳትሄድ፤
37ነገር ግን ከዚያ ወጥተህ የቄድሮንን ሸለቆ
ከተሻገርህ እንደምትሞት ዕወቅ፤ ደምህም
በራስህ ላይ ይሆናል፡፡”
38ሳሚም መልሶ ንጉሡን፣ “መልካም፤
ባሪያህ ጌታዬ ንጉሡ ያለውን ይፈጽማል”
አለው፤ እርሱም በኢየሩሳሌም ብዙ ጊዜ
ተቀመጠ፡፡
39ከሦስት ዓመት በኋላ ግን፣ ከሳሚ አገ
ልጋዮች ሁለቱ ወደ ጌት ንጉሥ፣ ወደ
መዓካ ልጅ ወደ አንኩስ ኰበለሉ፤ ለሳሚም፣
“እነሆ፣ አገልጋዮችህ በጌት ናቸው” ተብሎ
ተነገረው፡፡ 40ሳሚ ይህን ሲሰማም አህዮቹን
ጭኖ አገልጋዮቹን ለመፈለግ ጌት ወዳ
ለው ወደ አንኩስ ሄደ፤ አገልጋዮቹንም
ከጌት መልሶ አመጣቸው፡፡
41ሳሚ ከኢየሩሳሌም ወደ ጌት ሄዶ መመ
ለሱን ሰሎሞን በሰማ ጊዜ፣ 42ንጉሡ
ሳሚን አስጠርቶ እንዲህ አለው፤ “ ‘ወደ
ሌላ ቦታ የሄድህ ዕለት እንደምትሞት ዕወቅ’
ብዬ *በእግዚአብሔር* ስም አስምዬ አስጠን
ቅቄህ አልነበረምን? በዚያን ጊዜ አን
ተም፣ ‘መልካም ነው፤ እኔም እታዘዛለሁ’
ብለኸኝ ነበር፤ 43ታዲያ *ለእግዚአብሔር* የማ
ልኸውን መሐላ ያልጠበቅኸውና እኔም
የሰጠሁህን ትእዛዝ ያልፈጸምኸው ለምን
ድን ነው?”
44ንጉሡም መልሶ ሳሚን እንዲህ አለው፤
“በአባቴ በዳዊት ላይ ያደረግህበትን ክፉ
ነገር ሁሉ ልብህ ያውቀዋል፤ ስለዚህ *እግ*
*ዚአብሔር* ስለ ክፉ ሥራህ ብድሩን ይከ
ፍልሃል፡፡ 45ንጉሥ ሰሎሞን ግን ይባረካል፤
የዳዊትም ዙፋን *በእግዚአብሔር* ፊት ለዘ
ላለም ጸንቶ ይኖራል፡፡”
46ከዚያም ንጉሡ የዮዳሄን ልጅ በናያስን
አዘዘው፤ በናያስም ወጣ፤ ሳሚንም መቶ
ገደለው፡፡
በዚህ ጊዜም መንግሥቱ በሰሎሞን እጅ
ጸና፡፡

## ሰሎሞን ጥበብን ከእግዚአብሔር መለመኑ

3፥4-15 ተጓ ምብ - 2ዜና 1፥2-13

3 ሰሎሞን የግብፅ ንጉሥ የፈርዖን
ወዳጅ ሆነ፤ የፈርዖንንም ልጅ አገባ፡፡
እርሱም ቤተ መንግሥቱን፣ *የእግዚአብሔ*
*ርን* ቤተ መቅደስና የኢየሩሳሌምን ዙሪያ
ቅጥር ሠርቶ እስኪጨርስ ድረስ በዳዊት
ከተማ አስቀመጣት፡፡
2በዚያን ጊዜ *ለእግዚአብሔር* ስም ገና
ቤተ መቅደስ ስላልተሠራ፣ ሕዝቡ አሁንም
መሥዋዕት የሚያቀርበው በማምለኪያ
ኰረብታ

[መ]34 ወይም *በገዛ መቃብሩ* ተብሎ ሊተረጐም ይችላል

ላይ ነበር። [3]ሰሎሞን እግዚአብሔርን ይወድ
ነበር፤ በአባቱ በዳዊት ሥርዐትም ይሄድ
ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ በኰረብታዎች ላይ
መሥዋዕት ይሠዋና ዕጣን ያጥን ነበር።
[4]ከሁሉ የሚበልጠው የማምለኪያ ኰረብታ
ገባዖን ስለ ነበረ፣ ንጉሡ መሥዋዕት ለማ
ቅረብ ወደዚያ ሄደ። ሰሎሞን በዚያ መሠ
ዊያ ላይ አንድ ሺህ የሚቃጠል መሥዋዕት
አቀረበ። [5]በገባዖንም እግዚአብሔር ለሰሎ
ሞን ሌሊት በሕልም ተገለጠለት፤
አምላክም፣ "እንድሰጥህ የምትፈልገውን
ሁሉ ለምን" አለው።
[6]ሰሎሞን እንዲህ ሲል መለሰ፤ "አባቴ
ዳዊት በእውነት፣ በጽድቅና በቅን ልቦና
በፊትህ ስለ ተመላለሰ፣ ለባሪያህ ታላቅ ቸር
ነትን አሳይተኸዋል፤ ይህ ታላቅ ቸርነት እን
ዲቀጥል በማድረግ ዛሬም በዙፋኑ ላይ
የሚቀመጥ ልጅ ሰጥተኸዋል።
[7]"እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤ ባሪያህ
በአባቴ በዳዊት እግር ተተክቼ
እንድነግሥ አድርገሃል፤ እኔ ግን ገና
ትንሽ ልጅ ስለ ሆንሁ፣ መውጫና መግቢ
ያዬን አላውቅም። [8]ባሪያህ አንተ
በመረጥኸው ሕዝብ፣ ከብዛቱም የተነሣ ሊ
ቈጠር በማይችል ታላቅ
ሕዝብ መካከል ይገኛል። [9]ስለዚህ መልካ
ሙንና ክፉውን በመለየት ሕዝብህን ማስ
ተዳደር እንዲችል ለባሪያህ አስተዋይ ልብ
ስጠው፤ አለዚያማ ይህን ታላቅ ሕዝብህን
ማን ሊያስተዳድር ይችላል?"
[10]ሰሎሞን ይህን በመለመኑ ጌታ ደስ
አለው፤ [11]ስለዚህ እንዲህ አለው፤ "ለራስህ
ረጅም ዕድሜ፣ ብልጽግና እንድታገኝ
ወይም ጠላ ቶችህ እንዲጠፉልህ ሳይሆን፣
በትክክል ማስተዳደር እንድትችል
ማስተዋልን ስለ ጠየ ቅህ፣ [12]ይህንኑ
አደርግልሃለሁ፤ ከአንተ በፊት ማንም
ያልነበረውን፣ ከአንተም በኋላ ማንም የ
ማያገኘውን ጥበብና አስተዋይ ልቡና እሰ
ጥሃለሁ፤ [13]ከዚህም በላይ አንተ ያልጠ
የቅኸውን ብልጽግናና ክብር እሰጥሃለሁ፤
ይኸውም በሕይወት ዘመንህ የሚተካከልህ
ማንም ንጉሥ እንዳይኖር ነው። [14]አባትህ
ዳዊት እንዳደረገው በመንገዴ ብትሄድ፣
ሥርዐቴንና ትእዛዜን ብትጠብቅ ዕድሜ
ህን አረዝመዋለሁ።" [15]ሰሎሞንም ከእንቅ
ልፉ ነቃ፤ እነሆ ሕልም መሆኑን ተረዳ።
ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ፣
በጌታ ኪዳን ታቦት ፊት ቆመ፤ የሚቃጠል
መሥ ዋዕትና የኅብረት መሥዋዕት[ሠ]
አቀረበ፤ ለሹማምቱም ሁሉ ግብዣ
አደረገ።

## ጥበብን የተሞላ ፍትሕ

[16]በዚህን ጊዜ ሁለት ዝሙት አዳሪዎች
ወደ ንጉሡ መጥተው ከፊቱ ቆሙ።
[17]ከእነርሱም አንዲቱ እንዲህ አለች፣
"ጌታዬ ሆይ፤ ይህች ሴትና እኔ በአንድ
ቤት አብረን እንኖራለን፤ አብራኝ እያለ
ችም እኔ ልጅ ወለድሁ፤ [18]እኔ ከወለድሁ
ከሦስት ቀን በኋላም፣ ይህች ሴት ወለ
ደች፤ ያለነው እኛ ብቻ ነን፤ ከሁለታችን
በቀር በዚያ ቤት ማንም አልነበረም።
[19]"የዚህች ሴት ሕፃን ልጅ ስለ ተኛችበት
ሌሊት ሞተ። [20]ስለዚህም በእኩለ ሌሊት
ተነሥታ፣ እኔ አገልጋይህ ተኝቼ ሳለሁ
ልጄን ከአጠገቤ ወሰደችው፤ ከዚያም የእ
ኔን ልጅ ራሷ ታቅፋ፣ የሞተ ልጇን አም
ጥታ በዕቅፌ አደረገችው። [21]በማግሥቱ
ልጄን ላጠባ ስነሣ እነሆ ሞቶአል፤ ነገር
ግን በማለዳ ብርሃን ትክ ብዬ ስመለከ
ተው እኔ የወለድሁት ልጅ አለመሆኑን
ተገነዘብሁ።
[22]ሌላዪቱም ሴት፣ "ነገሩ አንቺ እንደ
ምትዪው አይደለም፤ የሞተው የአንቺ፣ በሕ
ይወት ያለውም የእኔ ነው" አለች።
የመጀመሪያዋ ሴት ግን አጠንክራ፣ "አይ
ደለም! የሞተው የአንቺ፣ በሕይወት ያለው
ግን የእኔ ልጅ ነው" አለች፤ በዚህ ሁኔ
ታም በንጉሡ ፊት ተከራከሩ።
[23]ንጉሡም፣ "ይህችኛዪቱ፣ 'የእኔ ልጅ
በሕይወት ያለው ነው፣ የአንቺ የሞተው
ነው' ትላለች፤ ያችኛዪቱ ደግሞ፣ 'አይደለም
የአንቺ ልጅ ሞቶአል፣ በሕይወት ያለው
የእኔ ነው' ትላለች" አለ።
[24]ከዚያም ንጉሡ፣ "እንግዲያውስ ሰይፍ
አምጡልኝ" አለ፤ ለንጉሡም ሰይፍ አመጡ
ለት። [25]በዚህ ጊዜ ንጉሡ፣ "በሉ በሕ
ይወት ያለውን ልጅ ከሁለት ክፈሉና
ለአንዷ ግማሹን፣ ለሌላዪቱም ግማሹን ስጡ"
ብሎ አዘዘ።
[26]በሕይወት ያለው ልጅ እናት ለልጇ
እጅግ ስለ ራራች ንጉሡን፣ "ጌታዬ ሆይ፤
እባክህ በሕይወት ያለውን ሕፃን ለእርሷ
ስጣት፤ አትግደለው" አለች።
ሌላዪቱ ግን፣ "ለእኔም ሆነ ለአንቺ
አይሰጥም፤ ሁለት ላይ ይከፈል!" አለች።
[27]ከዚህ በኋላ ንጉሡ፣ "በሉ በሕይወት
ያለውን ሕፃን ለመጀመሪያዪቱ ሴት ስጧት፤
አትግደሉት፤ እናቱ እርሷ ናት" አለ።
[28]እስራኤላውያን ሁሉ ንጉሡ የሰጠውን
ፍርድ ሲሰሙ ፈሩት፤ ፍትሕ ለመስጠት
የአምላክን ጥበብ የታደለ መሆኑን አይተዋጠ
ልና።

## የሰሎሞን ሹማምት

4 ንጉሥ ሰሎሞን በእስራኤል ሁሉ ላይ
ነገሠ፤ [2]ዋና ዋናዎቹ ሹማምቱም እነዚህ

3÷3 ቀኍ2፤ዘሌ17÷35፤ዘዳ6÷5፤10÷12፤17÷19፤ኢሱ1÷7፤1ነገ14÷8፤2ነገ12÷3፤15÷4፥35፤16÷4፤21÷3፤መዝ31÷23፤145÷20
3÷4 ኢሱ9÷3
3÷5 1ነገ9÷2፤11÷9፤ማቴ7÷7፤27÷9
3÷6 ዘፍ17÷1፤1ነገ1÷48
3÷7 ዘኍ27÷17፤1ዜና22÷5፤29÷1፤ኤር1÷6
3÷8 ዘፍ12÷2፤ዘዳ7÷6፤1ዜና27÷23
3÷9 ዘዳ1÷16፤2ሳሙ14÷17፤2ቆሮ2÷16፤ዕብ5÷14፤ያዕ1÷5
3÷11 1ዜና22÷12፤ያዕ4÷3
3÷12 2ሳሙ14÷20፤1ነገ4÷29፥30፥31፤5÷12፤10÷23፤መክ1÷16፤1ዮሐ5÷1415
3÷13 1ነገ10÷23፤2ዜና9÷22፤ነህ13÷26፤ምሳ3÷12፥16፤8÷18፤ማቴ6÷33፤ኤፌ3÷20
3÷14 1ነገ9÷4፤መዝ25÷13፤61÷6፤101÷2፤128÷1፤ምሳ3÷12፥16
3÷15 ቀኍ5፤ዘፍ28÷16፤ዘሌ6÷813፤7÷11-21፤አስ1÷3፥9፤2÷18፤5÷8፤6÷14፤9÷17፤ዳን5÷1
3÷26 መዝ102÷13፤ኢሳ49÷15፤63÷15፤ኤር3÷12፤31÷20፤ሆሴ11÷8
3÷28 2ሳሙ14÷20፤ቈላ2÷3

[ሠ]15 በትውፊት የሰላም መሥዋዕት ይባላል

ነበሩ፤

የሳዶቅ ልጅ ዓዛርያስ፣ ካህን፤
3የሺሻ ልጆች ኤሊሖሬፍና
አኪያ፣ ጸሓፊዎች፤
የአሒሉድ ልጅ ኢዮሣፍጥ፣ ታሪክ
ጸሓፊ፤
4የዮዳሄ ልጅ በናያስ፣ የሰራዊቱ ዋና
አዛዥ፤
ሳዶቅና አብያታር፣ ካህናት፤
5የናታን ልጅ ዓዛርያስ፣ የአውራጃ
ገዦች የበላይ ኀላፊ፤
የናታን ልጅ ዛቡድ፣ ካህንና የንጉሡ
የቅርብ አማካሪ፤
6አሒሳር፣ የቤተ መንግሥቱ አዛዥ፤
የዓብዳ ልጅ አዶኒራም የግዳጅ ሥራ
ተቈጣጣሪ።

7እንዲሁም ሰሎሞን ለንጉሡና ለንጉሡ
ቤት የሚሆነውን ቀለብ ከመላው እስራ
ኤል የሚሰበስቡ ዐሥራ ሁለት የአውራጃ
ገዦች ነበሩት፤ እነዚህም እያንዳንዳቸው
በዓመት ውስጥ የወር ቀለብ የሚያቀርቡ
ነበሩ። 8ስማቸውም እንደሚከተለው ነው፤

ቤንሑር፣ በኰረብታማው በኤፍሬም
ምድር፤
9ቤንዴቄር፣ በማቃጽ፣ በሻዓልቢም፣
በቤትሳሚስ፣ በኤሎንቤትሐናን፤
10ቤንሔሴድ፣ በአሩቦት ውስጥ
የሚገኙት ሰኮትና የኦፌር አገር
በሙሉ የእርሱ ነበር፤
11ቤን አሚናዳብ፤ በናፎት[ረ] ዶር፣
እርሱም የሰሎሞንን ልጅ ጣፊትን
አግብቶ የነበረ ነው፤
12የአሒሉድ ልጅ በዓና፣ በታዕናክና
በመጊዶ እንዲሁም ከጻርታን ቀጥሎ
ቍልቍል እስከ ኢይዝራኤል ባለው
በቤትሳን ሁሉ፣ ከዚያም ዮቅምዓምን
ተሻግሮ እስከ አቤልምሖላና ድረስ፣
13ቤንጌበር፣ በገለዓድ ራሞት ከተማ
እዚያው ገለዓድ ውስጥ የምናሴ
ልጅ የኢያዕር መንደሮች፣ በባሳንም
የአርጎብ አውራጃ እንዲሁም በሮቻ
ቸው የናስ መወርወሪያ በሆኑ ሥልሳ
ባለ ቅጥር ታላላቅ ከተሞች፤
14የዒዶ ልጅ አሒናዳብ፤ በማሃናይም፣
15አኪማአስ በንፍታሌም፣ እርሱም
የሰሎሞንን ልጅ ባስማትን አግብቶ
የነበረ ነው፤
16የኩሲ ልጅ በዓና፤ በአሴርና በበዓ
ሎት፣
17የፋሩዋ ልጅ ኢዮሣፍጥ በይሳኮር፣
18የኤላ ልጅ ሳሚ በብንያም፣
19የኡሪ ልጅ ጌበር፤
በአሞራውያን ንጉሥ በሴዎን ምድር፣
በባሳን ንጉሥ በዐግ አገር፣ እርሱም
የአውራጃው ብቸኛ ገዥ ነበር።

## ለሰሎሞን በየቀኑ የሚገባለት ቀለብ

20የይሁዳና የእስራኤል ሕዝቦች ብዛታቸው
እንደ ባሕር ዳር አሸዋ ሆነ፤ ይበሉ፣
ይጠጡና ይደሰቱም ነበር። 21ሰሎሞንም
ከወንዙ[ሰ] አንሥቶ እስከ ፍልስጥኤማውያን
ምድር፣ ከዚያም እስከ ግብፅ ዳርቻ ያሉትን
መንግሥታት ሁሉ ገዛ፤ እነዚህም አገሮች
ግብር አመጡለት፤ በሕይወት ዘመኑም ሁሉ
ተገዙለት።

22ለሰሎሞን በየቀኑ የሚገባለትም ቀለብ
ይህ ነበር፤ ሠላሳ ኮር[ሸ] ማለፊያ ዱቄት፣
ሥልሳ ኮር[ቀ] መናኛ ዱቄት፣ 23ዐሥር ቅልብ
ሰንጋዎች፣ ሃያ ግጦሽ መሬት ላይ የሚውሉ
በሬዎች፣ መቶ በግና ፍየል እንዲሁም ዋሊያ፣
ሚዳቋ፣ የበረሓ ፍየልና ምርጥ አዕዋፍ።
24ከወንዙ በስተ ምዕራብ፣ ከቲፍሳ እስከ
ጋዛ ያሉትን መንግሥታት ስለ ገዛ፣ በሁ
ሉም አቅጣጫ ሰላም ሆኖለት ነበር። 25በሰ
ሎሞን ዘመን ሁሉ ከዳን አንሥቶ እስከ
ቤርሳቤህ ያለው ይሁዳና እስራኤል፣ እያ
ንዳንዱ ሰው ከወይኑና ከበለሱ ጥላ ሥር
በሰላም ለመኖር በቃ።

26ሰሎሞን ሠረገላ የሚጐትቱ ፈረሶች የሚ
ያድሩበት አራት ሺህ ጋጣና ዐሥራ ሁለት
ሺህ ፈረሶች[በ] ነበሩት[ተ]።

27የየአውራጃው ሹማምትም በየወር ተራ
ቸው ንጉሡን ሰሎሞንንና ወደ ንጉሡ ማእድ
የሚቀርቡትን ሁሉ ምንም ሳያጓድሉ ይቀ
ልቡ ነበር፤ 28እንዲሁም ለሠረገላ ፈረሶችና
ለፈጣን ፈረሶች የተመደበውን ገብስና ጭድ
ከተፈለገው ቦታ ድረስ ያመጡ ነበር።

## የሰሎሞን ጥበብ

29አምላክ ለሰሎሞን ጥበብንና እጅግ
ታላቅ ማስተዋልን እንዲሁም በባሕር ዳር
እንዳለ አሸዋ የልብ ስፋትን ሰጠው።
30የሰሎሞን ጥበብ ከምሥራቅ ሰዎች ሁሉ
ጥበብ በጣም የላቀ ከግብፅም ጥበብ ሁሉ
የበለጠ ነበር፤ 31እርሱም ከማንም ሰው ይልቅ
ጥበበኛ ነበር፣ ከኢይዝራኤላዊው ከኤታን፣
ከማሖል ልጆች ከሄማንና ከከልቀድ
ደግሞም ከደራል ይልቅ ጥበበኛ ነበር፤
ዝናውም በዙሪያው ባሉት አሕዛብ ሁሉ
ተሰማ። 32እርሱም ሦስት ሺህ ምሳሌዎችን
ተናገረ፤ የመሓልዩም ቍጥር ሺህ አምስት
ነበር።

4፥2 1ነገ12፥6፤ 1ዜና6፥10፤2ዜና26፥17፤ኢዩ12፥12
4፥3 2ሳሙ8፥16፥17
4፥4 2ሳሙ8፥17፥18
4፥6 ዘፍ41፥40፤ 49፥15፤2ሳሙ20፥24
4፥7 ቍ27
4፥8 ኢሱ24፥33
4፥9 ኢሱ15፥10፤ መሳ1፥35
4፥10 ኢሱ12፥17፤ 15፥35
4፥11 ኢሱ11፥2
4፥12 ኢሱ3፥16፤ 17፥11፤መሳ7፥22፤ 1ዜና6፥68
4፥13 ዘኍ32፥40፥ 41፤ዘዳ3፥4
4፥14 ኢሱ13፥26
4፥15 2ሳሙ15፥27
4፥16 2ሳሙ15፥32
4፥18 1ነገ1፥8
4፥19 ዘዳ3፥810፤ ኢሱ12፥2፥4
4፥20 ዘፍ12፥2፤ 32፥12፤1ዜና22፥9
4፥21 ዘፍ2፥14፤ዘፀ 23፥31፤መሳ3፥15፤ 2ዜና9፥26፤ዕዝ4፥20፤ መዝ72፥8፥11፤ሰቆ 1፥1፤ሕዝ16፥13
4፥22 1ነገ10፥5
4፥23 ነህ5፥18
4፥24 ኢሱ14፥15፤ 2ነገ15፥16
4፥25 ዘዳ8፥8፤መሳ 20፥1፤2ነገ18፥31፤ 1ዜና22፥9፤መዝ105፥ 33፤ኢሳ36፥16፤ኤር 5፥17፤23፥6፤ሕዝ28፥ 26፤39፥26፤ኢል2፥ 22፤ሚክ4፥4፤ዘካ3፥10
4፥26 ዘዳ17፥16
4፥27 ቍ7
4፥29 ዘፍ32፥12፤ 1ነገ3፥12
4፥30 ዘፍ25፥6፤ መሳ6፥3፤ኢሳ19፥11፤ ዳን1፥20፤ማቴ2፥1፤ ሐሥ7፥22
4፥31 1ነገ3፥12
4፥32 መዝ78፥63፤ ምሳ1፥1፤10፥1፤25፥1፤ መክ12፥9፤ማሕ1፥1፤ሕ ዝ33፥32

[ረ]11 ወይም *በናፎት ቆመት* ተብሎ ሊተረጐም ይችላል
[ሰ]21 በዚህና በቍ 24 ላይ የተጠቀሰው የኤፍራጥስ ወንዝ ነው።
[ሸ]22 6.6 ኪሎ ግራም ያህል ነው።
[ቀ]22 13.2 ኪሎ ግራም ያህል ነው።
[በ]26 ዕብራይስጡና አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች *አርባ* ይላሉ።
[ተ]26 ወይም *ሠረገለኞች* ተብሎ መተርጐም ይችላል።

33ከሊባኖስ ዝግባ አንሥቶ በቅጥር ግንብ
ላይ እስከሚበቅለው ሂሶጵ ስለ ዕፀዋት
ተናግሮአል፤ እንዲሁም ስለ እንስሳት፣ ስለ
ወፎች፣ በሆዳቸው ስለሚሳቡ እንስሳትና
ስለ ዓሦችም ተናግሮአል፤ 34ጥበቡን ከሰ
ሙት ከዓለም ነገሥታት ሁሉ የተላኩ፣
የየአገሩ ሰዎች ሁሉ የሰሎሞንን ጥበብ ለማ
ድመጥ መጡ።

## ቤተ መቅደሱን ለመሥራት የተደረገ ዝግጅት

5፥1-16 ተጓ ምብ - 2ዜና 2፥1-18

5 የጢሮስ ንጉሥ ኪራም በዘመኑ ሁሉ
ለዳዊት ወዳጅ ስለ ነበር፣ ሰሎሞን
በአባቱ እግር ለመተካት መቀባቱን በሰማ
ጊዜ፣ መልእክተኞቹን ወደ ሰሎሞን ላከ።
2ሰሎሞንም እንዲህ የሚል መልእክት ወደ
ኪራም መልሶ ላከ፤

3"አባቴ ዳዊት በዙሪያው ሁሉ ከገጠ
መው ጦርነት የተነሣ፣ *እግዚአብሔር*
ጠላቶቹን ከእግሩ በታች እስኪጥል
ለት ድረስ ለአምላኩ *ለእግዚአብሔር*
ስም ቤተ መቅደስ መሥራት እንዳ
ልቻለ ታውቃለህ። 4አሁን ግን አም
ላኬ *እግዚአብሔር* በዙሪያዬ ሁሉ
ሰላም ሰጥቶኛል፤ ጠላትም የለብኝም።
5እነሆ፣ *እግዚአብሔር* ለአባቴ ለዳ
ዊት፣ 'ለስሜ ቤተ መቅደስ የሚሠራ
ልኝ ከአንተ ቀጥሎ በዙፋንህ የማስ
ቀምጠው ልጅህ ነው' ብሎ እንደ
ነገረው፣ ለአምላኬ *ለእግዚአብሔር*
ስም ቤተ መቅደስ ለመሥራት
አስቤአለሁ።

6"ስለዚህ የሊባኖስ ዝግባ እንዲቈረ
ጥልኝ ትእዛዝ ስጥ፤ ሰዎቼ ከሰዎችህ
ጋር አብረው ይሠራሉ፤ የሰዎችህንም
ደመወዝ አንተ በወሰንኸው እከፍልሃ
ለሁ፤ ከሰዎቼ መካከል እንደ ሲዶናው
ያን ዕንጨት በመቍረጥ እስከዚህ የሠ
ለጠነ ሰው አለመኖሩን ራስህም ታው
ቃለህና።"

7ኪራም የሰሎሞን መልእክት በደረሰው
ጊዜ እጅግ ደስ ስላለው፣ "ይህን ታላቅ ሕዝብ
እንዲመራ ለዳዊት ጥበበኛ ልጅ ሰጥቶታ
ልና ዛሬ ምስጋና *ለእግዚአብሔር* ይግባው"
አለ።

8ስለዚህ ኪራም፣ ለሰሎሞን እንዲህ ሲል
ላከበት፤

"የላክኸው መልእክት ደርሶኛል፤
የዝግባውንና የጥዱን ግንድ በማቅረብ
ረገድ የምትፈልገውን ሁሉ ለማድረግ
ዝግጁ ነኝ፤ 9ሰዎቼ ግንዱን ከሊባኖስ
እስከ ባሕሩ ድረስ ጐትተው ያወርዳሉ፤
እኔም ግንዱ ሁሉ ታስሮ አንተ እስከ
ወሰንኸው ስፍራ በባሕር ተንሳፎ
እንዲደርስ አደርጋለሁ፤ እዚያም እኔ
እፈታዋለሁ፣ አንተም ትወስደዋለህ፤
አንተም ለቤተ ሰቤ ቀለብ በመስጠት
ፍላጎቴን ታሟላ ለህ።"

10በዚህ ሁኔታ ኪራም ለሰሎሞን የሚያ
ስፈልገውን የዝግባና የጥድ ግንድ በሙሉ
ያቀርብለት ጀመር፤ 11ሰሎሞን ደግሞ ለኪ
ራም ቤተ ሰው ቀለብ እንዲሆን ሃያ ሺህ
የቆሮስ መስፈሪያ[ቸ] ስንዴ፣ ሃያ ሺህ ኮር[ነ] ንጹሕ[ነ]
የወይራ ዘይት ሰጠው፤ ይህን ባለ ማቋረጥ
በያመቱ ለኪራም ይሰጥ ነበር። 12*እግዚአብሔ
ርም* በገባለት ተስፋ መሠረት ለሰሎ
ሞን ጥበብን ሰጠው፤ በኪራምና በሰሎሞን
መካከልም መልካም ግንኙነት ነበር፤ ሁለ
ቱም ቃል ኪዳን አደረጉ።

13ንጉሥ ሰሎሞን ከመላው እስራኤል
የጒልበት ሠራተኞችን መለመለ፤ ቍጥራ
ቸውም ሠላሳ ሺህ ነበር። 14እነዚህንም
አንድ ወር በሊባኖስ እንዲሠሩ፣ ሁለት
ወር በቤታቸው እንዲያርፉ በማድረግ፣
ዐሥር ዐሥር ሺውን ወር ተራ አግብቶ
ላካቸው። የጒልበት ሠራተኞቹም አለቃ
አዶኒራም ነበር። 15ሰሎሞንም በኰረብታ
ማው አገር ሰባ ሺህ ተሸካሚዎችና ሰማ
ንያ ሺህ ድንጋይ ጠራቢዎች ነበሩት፤
16እንዲሁም ሥራውን የሚቈጣጠሩ ሦስት
ሺህ ሦስት መቶ[ኘ] ኀላፊዎች ነበሩ። 17እነ
ርሱም በንጉሡ ትእዛዝ ለቤተ መቅደሱ
መሠረት የሚሆን ታላላቅና ምርጥ ድንጋይ
ፈልፍለው በማውጣት የተጠረበ ድንጋይ
አዘጋጁ። 18የሰሎሞንና የኪራም የእጅ
ባለሙያዎች እንዲሁም የጌባል ሰዎች[አ] ለቤተ
መቅደሱ የሚያስፈልገውን ዕንጨትና ድን
ጋይ ፈልጠው አዘጋጁ።

## ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን መሥራት ጀመረ

6፥1-29 ተጓ ምብ - 2ዜና 3፥1-14

6 እስራኤላውያን ከግብፅ በወጡ በአራት
መቶ ሰማንያ[ከ] ዓመት፣ ሰሎሞን በእስ
ራኤል ላይ በነገሠ በአራተኛው ዓመት፣
ዚፍ በተባለው በሁለተኛው ወር ሰሎሞን
*የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስ መሥራት
ጀመረ።

2ንጉሥ ሰሎሞን *ለእግዚአብሔር* የሠራው
ቤተ መቅደስ ርዝመቱ ሥልሳ ክንድ፣ ወርዱ
ሃያ ክንድ፣ ቁመቱ ሠላሳ ክንድ[ኸ] ነበር።

[ቸ]11 4400 ኪሎ ሊትር ያህል ነው።
[ነ]11 ዕብራይስጡና የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ሃያ ኮር ይላሉ (2ዜና 2፥10 ይመ) [ነ]11 440 ኪሎ ሊትር ያህል ነው።
[ኘ]16 ዕብራይስጡና አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም *ሦስት ሺህ ስድስት መቶ* ይላሉ
[አ]18 ይኸውም ቢብሎስ የተባለው ስፍራ ነው
[ከ]1 ዕብራይስጡና የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም *አራት መቶ አርባ* ይላሉ
[ኸ]2 ርዝመቱ 27 ሜትር፣ ወርዱ 9 ሜትር እንዲሁም ቁመቱ 13.5 ሜትር ያህል ነው

4፥33 ዘሌ14፥49
4፥34 2ዜና9፥23
5፥1 2ሳሙ5፥11
5፥3 2ሳሙ7፥5፤ 22፥40፤1ዜና22፥8፤ 28፥3፤መዝ8፥6፤ 110፥1፤ማቴ22፥44፤ 1ቆሮ15፥25
5፥4 ኢሱ14፥15፤ 1ነገ11፥14፡23፤1ዜና 22፥9፤ሉቃ2፥14
5፥5 ዘዳ12፥5፤ 2ሳሙ7፥13፤1ዜና17፥ 12፤1ቆሮ3፥16፤ራእ 21፥22
5፥6 1ዜና14፥1፤ 22፥4
5፥7 1ነገ10፥9፤ ኢሳ 60፥6
5፥9 ቍ11፤ ዕዝ3፥7፤ሕዝ 27፥17፤ሐሥ12፥20
5፥11 ቍ9
5፥12 ኢሱ9፥7፤ 1ነገ3፥12፤15፥19፤ አሞ1፥9
5፥13 ዘፍ49፥15፤ ዘሌ25፥39፤1ነገ9፥15
5፥14 2ሳሙ20፥24፤1ነገ4፥6 ፤2ዜና10፥18
5፥16 1ነገ9፥23
5፥17 1ነገ6፥7፤ 1ዜና22፥2
5፥18 ኢሱ13፥5፤ 2ሳሙ5፥11
6፥1 ዕዝ3፥8፤5፥11
6፥2 ዘፀ26፥1

3በቤተ መቅደሱ ዋነኛ አዳራሽ ፊት ለፊት
ያለው በረንዳ ወርዱ እንደ ቤተ መቅደሱ
ወርድ ሁሉ ሃያ ክንድ[ሠ] ሲሆን፣ ርዝ
መቱ ዐሥር ክንድ[ዐ] ወደ ውጭ የወጣ
ነበር። 4ለቤተ መቅደሱም ባለ ዐይነ ርግብ
መስኮቶች አበጀ። 5በዋናው ቤተ መቅደ
ስና በቅድስተ ቅዱሳኑ ግድግዳ ዙሪያ ልዩ
ክፍሎች ያሉት ተቀጥላ ግንብ ሠራ።
6የምድር ቤቱ ወርድ አምስት ክንድ፣[ዘ]
የመካከለኛው ፎቅ ስድስት ክንድ፣[ዠ] የሦ
ስተኛው ፎቅ ሰባት ክንድ[የ] ነበር፤ የቤተ
መቅደሱን ግድግዳ ዘልቆ እንዳይገባም፣
ከቤተ መቅደሱ ግንብ ውጭ ዙሪያውን
እርከኖች አደረገ።
7ቤተ መቅደሱ የተሠራው እዚያው ድን
ጋዩ ተቈፍሮ ከወጣበት ቦታ በተዘጋጀ
ድንጋይ በመሆኑ የመራጃ፣ የመሮ ወይም
የሌላ ብረት ነክ መሣሪያ ድምፅ በቤተ
መቅደሱ አካባቢ አልተሰማም ነበር።
8የምድር[ደ] ቤቱ መግቢያ በስተ ደቡብ
በኩል ባለው የቤተ መቅደሱ ጐን ሲሆን ወደ
መካከለኛውና ከዚያም ወደ መጨረሻው
ፎቅ የሚያስወጣ ደረጃ ነበረው። 9ቤተ መቅ
ደሱንም በዚሁ ሁኔታ ሠርቶ ጨረሰ፤ ለጣ
ራው ተሸካሚ አደረገለት፤ በዝግባ ሳን
ቃም ከደነው። 10በቤተ መቅደሱም ዙሪያ
በሙሉ፣ ቁመታቸው አምስት አምስት ክንድ
የሆነ ክፍሎች ሠራ፤ እነዚህንም ከቤተ
መቅደሱ ጋር በዝግባ አግዳሚ ዕንጨቶች
አያያዛቸው።
11የእግዚአብሔርም ቃል እንዲህ ሲል
ወደ ሰሎሞን መጣ፤ 12"ስለምትሠራው ስለዚህ
ቤተ መቅደስ ሥርዐቴን ብትከተል፣ ፍር
ዴን በተግባር ብትገልጸው፣ ትእዛዛቴን ብትጠ
ብቅና ብትመላለስባቸው ለአባትህ ለዳዊት
የሰጠሁትን ተስፋ በአንተ እፈጽመዋለሁ፤
13በእስራኤላውያን መካከል እኖራለሁ፤
ሕዝቤን እስራኤልንም አልተወውም።"
14ስለዚህ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ሠርቶ
ፈጸመ፤ 15የውስጡን ግድግዳ ከቤተ መቅደሱ
ወለል እስከ ጣራው ድረስ በዝግባ ሳንቃ ለበጠ፤
የቤተ መቅደሱንም ወለል የጥድ ሳንቃ
አለበሰው። 16በቤተ መቅደሱም ውስጥ
በስተ ኋላ በኩል፣ ሃያውን ክንድ ቅድስተ
ቅዱ ሳን እንዲሆን፣ ከወለሉ አንሥቶ
እስከ ጣራው ድረስ በዝግባ ሳንቃዎች
ጋረደው፤ 17በቅድስተ ቅዱሳኑ ፊት ለፊት
ያለው ዋና አዳራሽ ርዝመቱ አርባ ክንድ[ጀ]
ነበር። 18የቤተ መቅደሱም፣ ውስጡ
በሙሉ በዝ ግባ የተለበጠ ሲሆን፣ ይህም
በእንቡጥ አበ ቦችና በፈኩ አበቦች ቅር
ጽ የተጌጠ ነበር፤ በሙሉ ዝግባ እንጂ
የሚታይ ድንጋይ አልነበረም።

6፥3 ሕዝ40፥49
6፥4 ሕዝ41፥16
6፥5 ኤር35፥2፤ ሕዝ41፥56
6፥7 ዘፀ20፥25፤ ዘዳ27፥5
6፥9 ማሕ1፥17
6፥11 1ነገ12፥22፤ 13፥20፤16፥1፡7፤17፥2፤ 21፥17፤ኤር40፥1
6፥12 2ሳሙ7፥12-16፤1ነገ9፥5፤11፥10
6፥13 ዘሌ26፥11፤ ዘዳ31፥6፤ዮሐ14፥18፤ ዕብ13፥5
6፥14 1ዜና28፥20፤ 2ዜና5፥1፤ሐሥ7፥47
6፥15 1ነገ7፥7፤ ሕዝ41፥1516
6፥16 ዘ26፥33
6፥18 ቍ29፤መዝ 74፥6፤ሕዝ41፥18
6፥19 ዘፀ25፥10፤ 1ሳሙ3፥3፤1ነገ8፥6
6፥20 ዘፀ30፥1፤ ሕዝ41፥34
6፥23 ዘፀ37፥7
6፥27 ዘፍ3፥24፤ ዘፀ25፥18
6፥29 ቍ18፡32፡ 35፤ሕዝ41፥18፡25
6፥32 ሕዝ41፥23

19በቤተ መቅደሱም ውስጠኛ ክፍል የእ
ግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት የሚቀመ
ጥበትን ቅድስተ ቅዱሳን ሠራ። 20ቅድስተ
ቅዱሳኑም ርዝመቱ ሃያ ክንድ፣ ወርዱ
ሃያ ክንድ፣ ቁመቱም ሃያ ክንድ[ገ] ነበር፤
ውስጡን በንጹሕ ወርቅ ለበጠው፤ ከዝግባ
የተሠራውንም መሠዊያ በወርቅ ለበጠው።
21ሰሎሞንም ቤተ መቅደሱን በውስጥ
በኩል በንጹሕ ወርቅ ለበጠው፤ በወርቅ በተ
ለበጠው ቅድስተ ቅዱሳን ፊት ለፊትም
የወርቅ ሰንሰለቶች ዘረጋ። 22ስለዚህ ውስጡን
በሙሉ በወርቅ ለበጠው፤ በቅድስተ ቅዱ
ሳኑ ውስጥ ያለውን መሠዊያም እንደዚሁ
በወርቅ ለበጠው።
23በቅድስተ ቅዱሳኑም ውስጥ ቁመታቸው
ዐሥር ክንድ[ጠ] የሆነ ሁለት የኪሩቤል ቅርጽ
ከወይራ ዕንጨት ሠራ፤ 24የአንደኛው ኪሩብ
አንዱ ክንፍ አምስት ክንድ ሲሆን፣ ሌላ
ውም ክንፉ እንደዚሁ አምስት ክንድ
ነበር፤ ይህም ከአንዱ ክንፍ ጫፍ እስከ ሌላው
ክንፍ ጫፍ ዐሥር ክንድ ማለት ነው።
25የሁለተኛውም ኪሩብ ክንፍ እንደዚ
ሁ
ዐሥር ክንድ ሆነ፣ ሁለቱ ኪሩቤል
በመጠንና በቅርጽ አንድ ዐይነት ነበሩና።
26የእያንዳንዱም ኪሩብ ቁመት ዐሥር
ክንድ ነበር። 27ክንፎቻቸው እንደ ተዘረጋ፣
ኪሩቤልን ወስዶ በቅድስተ ቅዱሳኑ አኖራ
ቸው፤ የአንዱ ኪሩብ ክንፍ አንዱን ግድግዳ
ሲነካ፣ የሌላው ኪሩብ ክንፍ ደግሞ ሌላ
ውን ግድግዳ ይነካ ነበር፤ ሌሎቹ ክንፎቻ
ቸውም በቅድስተ ቅዱሳኑ መካከል እርስ
በርሳቸው ይነካኩ ነበር። 28ኪሩቤልንም
በወርቅ ለበጣቸው።
29በመቅደሱ ግድግዳ ዙሪያ ላይ ሁሉ
በውስጥም በውጭም ኪሩቤልን፣ ከዘንባባ
ዛፎችና ከፈነዱ አበቦች ጋር ቀረጸ። 30እን
ዲሁም የቅድስተ ቅዱሳኑንና የመቅደሱን
ወለል በሙሉ በወርቅ ለበጠ።
31ለቅድስተ ቅዱሳኑም መግቢያ የወይራ ዕን
ጨት ደጃፎች ሠራ፤ መቃኖቻቸውንና መድ
ረኮቻቸውን ባለ አምስት ማእዘን አደረገ።
32በሁለቱ የወይራ ዕንጨት መዝጊያዎችም
ላይ ኪሩቤልን፣ የዘንባባ ዛፎችንና የፈነዱ
አበቦችን ቀረጸ፤ በወርቅም ለበጣቸው። 33እን
ዲሁም ለዋናው አዳራሽ መግቢያ ባለ አራት

[ሠ]3 16.9 ሜትር ያህል ነው
[ዐ]3 4.5 ሜትር ያህል ነው
[ዘ]6 በዚህ እንዲሁም በቍ10 እና 24 ላይ 2.3 ሜትር ያህል ነው [ዠ]6 2.7 ሜትር ያህል ነው
[የ]6 3.1 ሜትር ያህል ነው
[ደ]8 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም እንዲሁም ዕብራይስጡ፤ *የመካከለኛ* ይላሉ
[ጀ]17 18 ሜትር ያህል ነው
[ገ]20 ርዝመቱ፣ ወርዱና ቁመቱ 9 ሜትር ያህል ነው
[ጠ]23 4.5 ሜትር ያህል ነው

ማእዘን የወይራ ዕንጨት መቃን ሠራ፤ [34]እያን
ዳንዳቸው በማጠፊያ የተያያዙ ሁለት ሁለት
ሳንቃዎች ያሏቸው ሁለት መዝጊያዎች አበጀ።
[35]ኪሩቤልን፣ የዘንባባ ዛፎችንና የፈኩ
አበቦችንም ቀረጸባቸው፤ ቅርጹን ሠራ፤ ጥሩ
አድርጎም በወርቅ ለበጠው።

[36]የውስጠኛውን አደባባይ በሦስት
ረድፍ ጥርብ ድንጋይና በአንድ ረድፍ
የዝግባ ሳንቃ ሠራው።

[37]የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስም በአራ
ተኛው ዓመት ዚፍ በተባለው ወር መሠ
ረቱ ተጣለ፤ [38]በዐሥራ አንደኛው ዓመት
ቡል በተባለውም በስምንተኛው ወር ቤተ
መቅደሱ በዝርዝር ጥናቱ መሠረት እንደ
ታቀደው ተፈጸመ፤ ሠርቶ የጨረሰውም በሰ
ባት ዓመት ጊዜ ውስጥ ነበር።

## ሰሎሞን ቤተ መንግሥቱን ሠራ

**7** ሰሎሞን የራሱን ቤተ መንግሥት
ሠርቶ ለመጨረስ ዐሥራ ሦስት ዓ
መት ወስ ዶበታል፤ [2]የሊባኖስ ዱር
የተባለ ቤተ መንግሥት ሠራ፤ ይህም
ርዝመቱ መቶ ክንድ፣ ወርዱ አምሳ
ክንድ፣ ቁመቱ ሠላሳ ክንድ ሲሆን፣ በአራ
ት ረድፍ የቆሙ የዝ ግባ ምሰሶዎች
ደግፈው የያዟቸው አግዳሚ የዝግባ
ተሸካሚዎች ነበሩት። [3]ቤቱ ከምሰ ሶዎቹ
ላይ ያረፉ አግዳሚ ተሸካሚዎች አሉት፤
በእያንዳንዱ ዐምድ ላይ ዐሥራ አምስት፣
በድምሩ አርባ አምስት ተሸጋጋ ሪዎች ሲ
ኖሩ፣ ከእነዚህም ተሸጋጋሪዎች በላይ
ከዝግባ የተሠራ የጣሪያ ክዳን ነበር።
[4]መስኮቶቹም ከፍ ብለው የተሠሩ በሦስት
ምድብ የተከፈሉና ትይዩ ነበሩ። [5]በሮቹ
በሙሉ ባለ አራት ማእዘን መቃኖች ያሏ
ቸው፣ በሦስት ምድብ የተከፈሉና ትይዩ[ጸ]
ነበሩ።

[6]ሰሎሞን፣ “ባለ ብዙ ምሰሶ አዳራሽ”
የተባለ ቤት ሠራ፤ የዚህም ርዝመቱ አምሳ
ክንድ፣ ወርዱ ሠላሳ ክንድ፣[ጸ] ነበር፤ በስተ
ፊት በኩልም ጣራ ያለውና በአዕማድ የተ
ደገፈ መመላለሻ ነበረው።

[7]ዳኝነት የሚያይበትንም የዙፋን ችሎት
አዳራሽ ሠራ፤ ይኸውም የፍትሕ አዳራሽ
የተባለው ነው፤ ይህንንም ከወለሉ አንሥቶ
እስከ ጣራው[ፀ] ድረስ በዝግባ ሳንቃ ሸፈ
ነው። [8]ከአዳራሹ በስተ ጀርባ ባለው አደባ
ባይ መኖሪያው እንዲሆን የተሠራው ቤተ
መንግሥትም የዚሁ ተመሳሳይ ነበር።
ሰሎሞን ላገባት ለፈርዖን ልጅ ይህንኑ
ቤተ መንግሥት የመሰለ አዳራሽ ሠራ።

[9]ከውጭ አንሥቶ እስከ ትልቁ አደባ
ባይ፣ ከመሠረቱ አንሥቶ እስከ ድምድማቱ
ያለው የሕንጻ ሥራ በሙሉ፣ በውስጥም

6፥36 1ነገ7፥12፤
2ዜና4፥9፤ዕዝ6፥4
6፥38 ዘፀ25፥9፤
1ዜና28፥19፤ዕብ8፥5
7፥1 2ሳሙ7፥2
7፥2 2ሳሙ7፥2፤
1ነገ10፥17፤2ዜና
9፥16፤ኢሳ22፥8፤
37፥24፤ኤር22፥6፡23
7፥7 1ሳሙ7፥15፤
1ነገ6፥15፤መዝ122፥5
፤ምሳ20፥8
7፥8 1ነገ3፥1
7፥12 1ነገ6፥36
7፥13 ቍ45፤
2ዜና2፥13፤4፥16
7፥14 ዘ31፥25፤
35፥31፤2ዜና4፥11
7፥15 2ነገ11፥14፤
23፥3፤25፥17፤2ዜና
3፥15፤23፥13፤
34፥31፤ኤር27፥19፤52
፥17፡21፤ሕዝ40፥49
7፥16 ቍ20፡42፤
2ነገ25፥17፤
ኤር52፥22
7፥20 ቍ18፤
2ዜና3፥16፤4፥13
7፥21 2ዜና3፥17

በውጭም በልክ በልኩ በተቈረጠና አምሮ
በተስተካከለ ምርጥ ድንጋይ የተሠራ ነበር።
[10]መሠረቱም ዐሥርና[ፈ] ስምንት ክንድ[ፐ]
ርዝመት ባላቸውና ምርጥ በሆኑ ታላላቅ
ድንጋዮች የተሠራ ነበር። [11]በላዩም ላይ
ምርጥ የሆኑ፣ በልክ በልኩ የተቈረጡ
ድንጋዮችና የዝግባ ሳንቃዎች ነበሩ።
[12]የእ ግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጠኛ
አደባ ባይ ከመመላለሻ በረንዳው ጭምር
እንደ ትልቁ አደባባይ አምሮ በተጠረበ
ሦስት ረድፍ ድንጋይና ተስተካክሎ
በተከረከመ በአንድ ረድፍ የዝግባ ሳንቃ
የታጠረ ነበር።

## የቤተ መቅደሱ ዕቃዎች

7፥23-26 ተጓ ምብ - 2ዜና 4፥2-5
7፥38-51 ተጓ ምብ - 2ዜና 4፥6፤10-5፥1

[13]ንጉሥ ሰሎሞንም መልእክተኛ
ልኮ ኪራም[ሀ] የተባለውን ሰው ከጢሮስ
አስ መጣ፤ [14]የኪራም እናት ከንፍታሌም
ነገድ ስትሆን፣ እርሷም መበለት ነበረች፤
አባቱ የጢሮስ ሰው ሲሆን፣ የናስ ሥራ
ባለሙያ ነበር። ኪራም በማናቸውም የናስ
ሥራ ጥበብን፣ ማስተዋልንና ዕውቀትን
የተሞላ ሰው ነበር፤ እርሱም ወደ ንጉሥ
ሰሎሞን መጥቶ የተመደበለትን ሥራ
ሁሉ አከና ወነ።

[15]ኪራም የእያንዳንዱ ቁመት ዐሥራ
ስምንት ክንድ፣ ዙሪያው ዐሥራ ሁለት
ክንድ[ለ] የሆነ፣ ሁለት የናስ ምሰሶዎች ሠራ።
[16]እንዲሁም በምሰሶዎቹ አናት ላይ የሚሆኑ፣
ሁለት ጕልላት ከቀለጠ ናስ ሠራ፤ የእያን
ዳንዱም ጕልላት ቁመት አምስት ክንድ[ሐ]
ነበር። [17]በምሰሶዎቹ አናት ላይ ላሉት ጕል
ላቶችም ጌጥ እንዲሆኑ፣ ለእያንዳንዳቸው
ሰባት የመረብ ሰንሰለት አበጀ፤ [18]ደግሞም
በምሰሶዎቹ ላይ ያሉትን ጕልላቶች ለማ
ስጌጥ የእያንዳንዱን መረብ ዙሪያ የሚከቡ
ሮማኖች በሁለት ረድፍ[መ] ሠራ፤ ለሁለቱም
ጕልላቶች[ሠ] ያደረገው ተመሳሳይ ነበር።
[19]በመመላለሻው ምሰሶዎች አናት ላይ ያሉት
ጕልላቶች ቁመታቸው አራት ክንድ[ረ] ሲሆን፣
የሱፍ አበባ ቅርጽ ነበራቸው። [20]በሁለቱም
የምሰሶ ጕልላቶችና ከመርከቡ ቀጥሎ ባለው
የክብ ቅርጽ ላይ ዙሪያውን በሙሉ ሁለት
መቶ ሮማኖች በተርታ ነበሩ። [21]ምሰሶዎቹ
ንም በቤተ መቅደሱ መመላለሻ ላይ አቆመ፤

[ጨ]2 ርዝመቱ 46 ሜትር፣ ወርዱ 23 ሜትር እንዲሁም ቁመቱ 13.5 ሜትር ያህል ነው
[ጸ]5 በዕብራይስጥ የክፍሉ መልእክት በትክክል አይታወቅም።
[ጸ]6 ርዝመቱ 23 ሜትር፣ ወርዱ 13.5 ሜትር ያህል ነው።
[ፀ]7 ቩልጌትና የሱርስቱ ትርጕም ከዚህ ጋር ሲስማሙ ዕብራይስጡ ግን፣ ወለል ይላል
[ፈ]10 4.5 ሜትር ያህል ነው። [ፐ]10 3.6 ሜትር ያህል ነው።
[ሀ]13 በዚህ ስፍራ እንዲሁም በቍ 40 እና 45 ላይ ኪራም የሚለው ዕብራይስጡ ሂራም ይለዋል።

[ለ]15 ቁመቱ 8.1 ሜትር፣ ዙሪያው 5.4 ሜትር ያህል ነው።

በስተ ደቡብ ያቆመውን ምሰሶ ያቁም፣[ሰ]
በስተ ሰሜን በኩል ያለውንም ቦዔዝ[ሸ] ብሎ ጠ
ራው። 22አናቱ ላይ ያሉት ጕልላቶች የሱፍ
አበባ ቅርጽ ነበራቸው። የምሰሶዎቹም ሥራ
በዚህ ሁኔታ ተፈጸመ።

23ቅርጹ ክብ፣ ስፋቱ ከዳር እስከ
ዳር ዐሥር ክንድ፣[ቀ] ቁመቱ አምስት ክንድ
የሆነ ክብ ገንዳ ከቀለጠ ብረት ሠራ፤ ዙሪ
ያውም ሲለካ ሠላሳ ክንድ[በ] ሆነ። 24ከከ
ንፈሩም ዝቅ ብሎ፣ በእያንዳንዱ ክንድ
ላይ እንደ ቅል ያሉ ዐሥር ቅርጾች ዙሪያ
ውን በሁለት ረድፍ ከበውታል፤ እነዚህም
ከገንዳው ጋር አንድ ወጥ ሆነው በሁለት
ረድፍ ተሠርተው ነበር።

25ገንዳውም፣ ሦስቱ ፊታቸውን ወደ ሰሜን፣
ሦስቱ ወደ ደቡብ፣ ሦስቱ ወደ ምዕራብ፣
ሦስቱ ወደ ምሥራቅ ባዞሩ የዐሥራ ሁለት
በሬዎች ምስሎች ላይ የተቀመጠ ሲሆን፣
ገንዳው በላያቸው ሆኖ የሁሉም የኋላ
አካል በመካከል ላይ የገጠመ ነበር። 26የገ
ንዳው ውፍረት አንድ ጋት[ተ] ሲሆን፣ የከን
ፈሩ ጠርዝ ደግሞ እንደ አበባ ቅርጽ ሆኖ፣
የጽዋ ከንፈር የመሰለ ነው፤ ይህም አርባ
ሁለት ሺህ ሊትር[ቸ] ያህል ውሃ የሚይዝ
ነበር።

27እንዲሁም ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱ ዐሥር
ባለ መንኰራኵር የዕቃ ማስቀመጫዎች
ከመዳብ ሠራ፤ የእያንዳንዱም ርዝመት አራት
ክንድ፣ ወርድ አራት ክንድ፣ ቁመትም
ሦስት ክንድ[ኀ] ነበር። 28የዕቃ ማስቀመጫዎቹ
የተሠሩት እንደዚህ ነው፤ እነዚህም ቀጥ
ብለው ከቆሙ ደጋፊዎች ጋር የተያያዙ ባለ
አራት ማእዘን ጠፍጣፋ ናሶች ነበሯቸው።
29ዳርና ዳር ባሉት ድጋፎች መካከል በሚ
ገኙት ጠፍጣፋ ናሶች ላይ የአንበሶችን፣
የኮርማዎችንና የኪሩቤልን ምስል አደረገ፤
በድጋፎቹም ላይ እንደዚሁ አደረገ። ከአንበ
ሶቹና ከኮርማዎቹ በላይና በታች በኩል
ደግሞ የአበባ ጕንጕን የሚመስሉ ተቀጥ
ቅጠው የተሠሩ ቅርጾች ነበሩ። 30እያንዳ
ንዱ የዕቃ ማስቀመጫ አራት የናስ መን
ኰራኵርና መንኰራኵሮቹ የሚሽከረከሩ
ባቸው የናስ ወስከምቶች እንዲሁም እያንዳን
ዳቸው በአራቱም ማእዘን ገጽ ላይ የአበባ
ጕንጕን ቀልጦ የተሠራባቸው የመታጠቢያ
ገንዳ መደገፊያዎች ነበረው። 31በዕቃ ማስ
ቀመጫወቹም ውስጥ ጥልቀቱ አንድ ክንድ[ነ]
የሆነ ባለ ክብ ክፍተት ነበር፤ ይህም ክፍ
ተት ድቡልቡል ሆኖ ከታች ከመቆሚያው
በኩል ደግሞ አንድ ክንድ ተኩል[ኘ] ወርድ
ሲኖረው፣ በክፍተቱም ዙሪያ ቅርጾች ነበሩ፤
ክፈፎቹ ግን ባለ አራት ማእዘን እንጂ ክብ
አልነበሩም። 32አራቱ መንኰራኵሮች በዕቃ
ማስቀመጫው ጠፍጣፋ ናስ ሥር ሲሆኑ፣
የመንኰራኵሮቹ ወስከምቶች ደግሞ ከዕቃ
ማስቀመጫዎቹ ጋር የተያያዙ ነበሩ፤ የእ
ያንዳንዱም መንኰራኵር ስፋት አንድ
ክንድ ተኩል ነበር። 33መንኰራኵሮቹ የሠ
ረገላ መንኰራኵር መሰል ሲሆኑ፣ ወስከምቶቹ
የመንኰራኵሮቹ ክፈፎችና ዐቃፊዎቻቸው እን
ዲሁም ወስከምቶቹ የሚገቡባቸው ቧምቧዎች
በሙሉ ከቀለጠ ብረት የተሠሩ ነበሩ።

34እያንዳንዱ የዕቃ ማስቀመጫ አራት ወጣ
ያለእጀታ ነበረው። 35በዕቃ ማስቀመጫው
ጫፍ ላይ ግማሽ ክንድ[አ] የሆነ ዙሪያ ክብ
ነበረበት፤ ድጋፎቹና ጠፍጣፋ ናሶቹ ከዕቃ
ማስቀመጫው አናት ጋር የተያያዙ ነበሩ።
36እርሱም በድጋፎቹና በጠፍጣፋ ናሶቹ
ላይ ባለው ቦታ ሁሉ፣ ዙሪያውን የአበባ
ጕንጕን እያደረገ ኪሩቤልን፣ አንበሶችንና
የዘንባባ ዛፎችን ቀረጸ። 37ዐሥሩም የዕቃ
ተሸካሚዎች የተሠሩት በዚህ ሁኔታ ነበር፤
ሁሉም ከአንድ ቅርጽ ቀልጠው የወጡ ስለ
ሆነ፣ በመጠንና በቅርጽ ፍጹም ተመሳሳይ
ነበሩ።

38ከዚያም ለእያንዳንዱ የዕቃ ማስቀ
መጫ የሚሆን፣ እያንዳንዱ ስምንት መቶ
ሰማንያ ሊትር የሚይዝ ዐሥር የናስ መታጠቢያ
ገንዳ ሠራ፤ ስፋቱም አራት ክንድ ነበር።
39ከዕቃ ማስቀመጫዎቹም አምስቱን ከመ
ቅደሱ በስተ ደቡብ፣ አምስቱን በስተ ሰሜን
በኩል አኖረ፤ ገንዳውንም ከቤተ መቅደሱ
በደቡብ ምሥራቅ ጫፍ ላይ በስተ ደቡብ
አኖረው። 40እንዲሁም ምንቸቶችን፣
መጫ ሪያዎችንና ድስቶችን ሠራ፤

ኪራምም በዚህ ሁኔታ ለንጉሥ ሰሎ
ሞን የሠራውን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅ
ደስ ሥራ እንደሚከተለው ፈጸመ፤

41ሁለቱን ምሰሶዎች፣
በምሰሶዎቹ አናት ላይ

በክብ ቅርጽ የተሠሩ ሁለት
ጕልላቶችን፤

7፥22 2ነገ25፥17
7፥23 ቍ47፤2ነገ 25፥13፤1ዜና18፥8፤ 2ዜና4፥18፤ኤር31፥ 39፤52፥17፤ዘካ2፥1፤ ራእ4፥6
7፥25 ኤር52፥20
7፥27 2ነገ16፥17
7፥30 2ነገ16፥17
7፥38 ዘፀ30፥18
7፥40 ዘፀ27፥3፤ ኤር52፥18
7፥42 ቍ16

[ሐ]16 በዚህና በቍ 23 ላይ 2.3 ሜትር ያህል ነው።
[መ]18 ሁለት የዕብራይስጥ ቅጆችና የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ከዚህ ጋር ሲስማሙ፣ አብዛኞዎቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *በሁለት ረድፍ አዕማዶች ሥራ* ይላሉ።
[ሠ]18 ብዙ የዕብራይስጥ ቅጆችና የሱርስቱ ትርጕም ከዚህ ጋር ሲስ ማሙ፣ አብዛኞዎቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን *ሮማኖች* ይላሉ።
[ረ]19 በዚህና በቍ 38 ላይ 1.8 ሜትር ይላል።
[ሰ]21 ምናልባት *አነጸ* ማለት ሊሆን ይችላል።
[ሸ]21 ምናልባት *በእርሱ ዘንድ ጥንካሬ አለ* ማለት ሊሆን ይችላል
[ቀ]23 4.5 ሜትር ያህል ነው።
[በ]23 13.5 ሜትር ያህል ነው።
[ተ]26 8 ሴንቲ ሜትር ያህል ነው።
[ቸ]26 44 ኪሎ ሊትር ያህል ነው። የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ይህን ዐረፍተ ነገር አይጨምርም።
[ኀ]27 ርዝመቱና ወርዱ 1.8 ሜትር ያህል ሲሆን ቁመቱ 1.3 ሜትር ያህል ነው።
[ነ]31 0.5 ሜትር ያህል ነው።
[ኘ]31 በዚህና በቍ 32 ላይ 0.7 ሜትር ያህል ነው።
[አ]35 0.2 ሜትር ያህል ነው።

በምሰሶዎቹ ላይ ያሉትን በክብ
ቅርጽ የተሠሩትን ሁለት
ጕልላት ያስጌጡትን ሁለት መረቦች፤
42በምሰሶዎቹ አናት ላይ ያሉትንና
ክብ ቅርጽ የያዙትን፣
በሁለት ረድፍ የተቀረጹትን መረቦች፣
የሚያስጌጡትን አራት መቶ ሮማኖች፤
43ዐሥሩን የዕቃ ማስቀመጫዎች፣
ከዐሥር መታጠቢያ ገንዳዎቻቸው ጋር፤
44ገንዳውንና በሥሩ ያሉትን ዐሥራ
ሁለት በሬዎች፤
45ድስቶችን፣ መጫሪያዎችንና ጐድጓዳ
ሳሕኖችን።

ኪራም *ለእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ አገ
ልግሎት እንዲውሉ እነዚህን ዕቃዎች ሁሉ
ለንጉሥ ሰሎሞን የሠራለት ከተወለወለና
ከሚብረቀረቅ ናስ ነበር። 46ንጉሡም እነዚ
ህን በማቅለጥ በሸክላ ቅርጽ ውስጥ ፈሰው
እንዲወጡ ያደረገው በሱኮትና በጻርታን
መካከል ባለው በዮርዳኖስ ሸለቆ ነበር።
47ሰሎሞን ከብዛታቸው የተነሣ እነዚህ ሁሉ
ዕቃዎች እንዲመዘኑ አላደረገም፣ ስለዚ
ህም የናሱ ክብደት ምን ያህል እንደ ነበረ
አልታወቀም።
48እንዲሁም ሰሎሞን *ለእግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስ አግልግሎት እንዲውሉ ከዚህ
የሚከተሉትን ዕቃዎች ሁሉ ሠራ፤

የወርቅ መሠዊያን፣
ገጸ ኅብስቱ የሚቀመጥበትን
የወርቅ ጠረጴዛ፤
49በቅድስተ ቅዱሳኑ ፊት ለፊት
አምስቱ በቀኝ፣ አምስቱ
በግራ የሚቀመጡ፣ ከንጹሕ
ወርቅ የተሠሩ መቅረዞችን፣ ከወርቅ
የተሠሩ
አበቦችን፣ የመብራት ቀንዲሎችንና
መቈስቈሻዎችን፤
50የንጹሕ ወርቅ ሳሕኖችን፣ የመብራት
መኰስተሪያዎችን፣
ለመርጫ የሚሆኑ ጐድጓዳ ሳሕኖችንና
ጭልፋዎችን፣
የዕጣን ማቅረቢያ ዕቃዎችን፣
ለውስጠኛው ክፍል ለቅድስተ
ቅዱሳኑ በሮችና እንዲሁም ለቤተ
መቅደሱ በሮች የሚሆኑ የወርቅ
ማጠፊያዎችን።

51ንጉሥ ሰሎሞን *የእግዚአብሔርን* ቤተ
መቅደስ ሥራ ሁሉ ከፈጸመ በኋላ አባቱ
ዳዊት *ለእግዚአብሔር* የለየውን ብሩንና
ወርቁን እንዲሁም ዕቃውን አምጥቶ *በእግ
ዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ግምጃ ቤት አኖረ።

**7፥45** ቍ13፤ዘፀ 27፥3፤ኤር52፥18
**7፥46** ዘፍ13፥10፤ 33፥17፤ኢሱ3፥16
**7፥47** ቍ23፤ዘፀ 36፥57፤1ዜና22፥3፤ ኤር52፥20
**7፥48** ዘፀ25፥23፡ 30፤39፥32-43
**7፥49** ዘፀ25፥31
**7፥50** ዘኍ7፥14፤ 2ነገ25፥13፤ኤር52፥19
**7፥51** 2ሳሙ8፥11፤ 2ነገ12፥13፤24፥13፤ ኤር27፥19

**8፥1** ዘኍ7፥2፤1ሳሙ 3፥3፤2ሳሙ5፥7፤ ራእ11፥19
**8፥2** ቍ65፤ዘሌ23፥ 34፡36፤ዘኍ29፥12፤ ነህ8፥17
**8፥3** ኢሱ3፥3
**8፥4** ዘሌ17፥4፤ 1ዜና15፥13
**8፥5** 2ሳሙ6፥13፤ 2ዜና30፥24
**8፥6** ዘፍ3፥24፤ዘፀ 25፥18፤26፥33፤2ሳሙ 6፥17፤ራእ11፥19
**8፥7** ዘፀ25፥20
**8፥8** ዘፀ25፥13-15
**8፥9** ዘፀ16፥34፤ 25፥16፤ዕብ9፥4
**8፥10** ዘፀ16፥10፤ ዘሌ16፥2፤ራእ15፥8
**8፥11** ዘፀ16፥7፤ 29፥43፤2ዜና7፥2፤ ራእ15፥8
**8፥12** ዘፀ40፥34፤ 2ሳሙ22፥10
**8፥13** ዘፀ15፥17፤ መዝ132፥13፤135፥ 21፤ማቴ23፥21
**8፥14** ዘፀ39፥43
**8፥15** 1ዜና16፥36፤ ሉቃ1፥68

## ታቦቱ ወደ ቤተ መቅደሱ ገባ

8፥1-21ተጓ ምብ - 2ዜና 5፥2-6፥11

8 ከዚያም ንጉሥ ሰሎሞን *የእግዚአብሔ
ርን* የኪዳኑን ታቦት ከዳዊት ከተማ
ከጽዮን ለማምጣት፣ የእስራኤልን ሽማግሌ
ዎች፣ የእስራኤልን ነገድ አለቆችና የእስራ
ኤልን ጐሣዎች ሹማምት ሁሉ እርሱ ወዳ
ለበት ወደ ኢየሩሳሌም ጠራቸው። 2በዓሉ
በሚከበርበት ኤታኒም በተባለው በሰባተኛው
ወር፣ የእስራኤል ወንዶች ሁሉ ንጉሥ
ሰሎሞን ወዳለበት ተሰበሰቡ።
3የእስራኤል ሽማግሌዎች ሁሉ በመጡ
ጊዜም ካህናቱ ታቦቱን አነሡ፤ 4*የእግዚአ
ብሔርን* ታቦት፣ የመገናኛውን ድንኳንና
በውስጡ ያሉትን ንዋያተ ቅድሳት ሁሉ
አመጡ፤ ካህናቱና ሌዋውያኑም ይህን
ሁሉ ተሸከሙ። 5ንጉሥ ሰሎሞንና አብሮት
በዚያ የተሰበሰበው መላው የእስራኤል ጉባ
ኤም በታቦቱ ፊት በመሆን ስፍር ቍጥር
የሌለው በግና በሬ ሠዋ።
6ከዚያም ካህናቱ *የእግዚአብሔርን* የኪ
ዳኑን ታቦት አምጥተው በቤተ መቅደሱ
ውስጥ ወዳለው ማደሪያው፣ ወደ ቅድስተ
ቅዱሳኑ በማስገባት ከኪሩቤል ክንፍ በታች
አኖሩት። 7ኪሩቤልም ታቦቱ ባለበት ቦታ
ላይ ክንፋ ቸውን ዘርግተው፣ ታቦቱንና
መሎጊያዎቹን ጋረዱ። 8መሎጊያዎቹ
ከመርዘማቸው የተ ነሣ ጫፎቻቸው
ከቅድስተ ቅዱሳኑ ፊት ለፊት ካለው
ከመቅደሱ ሆኖ ይታዩ ነበር፤ ከመቅደሱ
ወዲያ ላለ ሰው ግን አይታዩም ነበር፤
እስከ ዛሬም ድረስ እዚያው ይገኛሉ። 9የእስ
ራኤል ልጆች ከግብፅ ምድር በወጡ ጊዜ
*እግዚአብሔር* ከእስራኤል ጋር ኪዳን
በገባበት በኮሬብ፣ ሙሴ በታቦቱ ውስጥ
ካስቀመጣቸው ሁለት የድንጋይ ጽላቶች
በቀር በታቦቱ ውስጥ ምንም አልነበረም።
10ካህናቱ ከቤተ መቅደሱ በወጡ ጊዜ፣
ደመና *የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስ ሞላው።
11*የእግዚአብሔር* ክብር ቤተ መቅደሱን ሞል
ቶት ስለ ነበር፣ ካህናቱ በደመናው ምክን
ያት አገልግሎታቸውን ማከናወን አልቻሉም
ነበር።
12ከዚያም ሰሎሞን እንዲህ አለ፤ "*እግዚ
አብሔር* ጥቅጥቅ ባለ ደመና ውስጥ እንደ
ሚኖር ተናግሮአል፤ 13እነሆ፣ እኔም
ለዘላለም የምትኖርበትን ታላቅ ቤተ
መቅደስ ሠር ቼልሃለሁ።"
14መላው የእስራኤል ጉባኤ በዚያ ቆሞ
ሳለ፣ ንጉሡ ፊቱን ወደ እነርሱ መልሶ
ጉባኤውን ባረከ። 15ከዚያም እንዲህ አለ፤

"ለአባቴ ለዳዊት በገዛ አፉ ተናግሮ
የሰጠውን ተስፋ፣ እርሱ ራሱ በእጁ

የፈጸመ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔ
ር የተመሰገነ ይሁን፤ እርሱም እንዲህ
ብሎ ነበርና፤ [16]‘ሕዝቤን እስራኤልን
ከግብፅ ምድር ካወጣሁበት ዕለት አን
ሥቶ፣ ስሜ በዚያ እንዲጠራና ቤተ
መቅደስ እንዲሠራበት ከመላው የእስ
ራኤል ነገድ አንድም ከተማ አልመረ
ጥሁም፤ ሕዝቤን እስራኤልን እንዲመራ
ግን ዳዊትን መረጥሁት።’
[17]“አባቴ ዳዊት ለእስራኤል አምላክ
ለእግዚአብሔር ስም ቤተ መቅደስ ለመሥ
ራት በልቡ አስቦ ነበር፤ [18]እግዚአብሔር
ግን አባቴን ዳዊትን እንዲህ አለው፤
‘ለስሜ ቤተ መቅደስ ለመሥራት አስ
በሃልና፣ ይህን በልብህ ማሰብህ መል
ካም ነው፤ [19]ይሁን እንጂ ቤተ መቅደ
ሱን የምትሠራው አንተ ሳትሆን፣
ከአንተ የሚወለደው ልጅህ ነው፤ አዎን
ለስሜ ቤተ መቅደስ የሚሠራው
እርሱ ነው።’
[20]“እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ
ፈጽሞአል፤ እግዚአብሔር በሰጠው ተስፋ
መሠረት በአባቴ በዳዊት እግር ተተ
ክቻለሁ፤ በእስራኤል ዙፋን ተቀምጫለሁ፤
እንዲሁም ለእስራኤል አምላክ ለእግዚ
አብሔር ስም ቤተ መቅደስ ሠርቻለሁ።
[21]ከግብፅ ባወጣቸው ጊዜ ከአባቶቻችን
ጋር የገባው የእግዚአብሔር ኪዳን በው
ስጡ ላለበት ታቦት መኖሪያ ስፍራ
በዚያ አዘጋጅቻለሁ።”

### ሰሎሞን በምረቃው ላይ ያቀረበው ጸሎት

8፥22-53 ተጓ ምብ - 2ዜና 6፥12-40

[22]ከዚያም ሰሎሞን መላው የእስራኤል
ጉባኤ ባለበት በእግዚአብሔር መሠዊያ ፊት
ቆመ፤ እጆቹንም ወደ ሰማይ ዘርግቶ፣
[23]እንዲህ አለ፤
“የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤
በፊትህ በፍጹም ልባቸው ጸንተው ለሚ
ኖሩ አገልጋዮችህ ኪዳንህን የምትጠ
ብቅ፣ ጽኑ ፍቅርህን የምትገልጥ አንተ
ነህ፤ በላይ በሰማይ፣ በታችም በምድር
እንዳንተ ያለ አምላክ ከቶ የለም፤ [24]ለባ
ሪያህ ለአባቴ ለዳዊት የሰጠኸውን
ተስፋ ጠብቀሃል፤ በአፍህ ተናገርህ፤ ይህ
ንኑም በዛሬው ዕለት በእጅህ ፈጸምኸው።
[25]“አሁንም የእስራኤል አምላክ
እግዚአብሔር ሆይ ለአባቴ ለባሪያህ
ለዳዊት፣ ‘አንተ እንዳደረግኸው ሁሉ፣
ልጆችህ በፊቴ ለመመላለስ
በሚያደርጉት ሁሉ ይጠንቀቁ ብቻ
እንጂ በእስራኤል ዙፋን ላይ በፊቴ
የሚቀመጥ ሰው አታጣም’ ስትል የሰጠ
ኸውን ተስፋ ፈጽምለት። [26]አሁንም
የእስራኤል አምላክ ሆይ፤ ለባሪያህ
ለአባቴ ለዳዊት የሰጠኸው የተስፋ
ቃል ይፈጸም።
[27]“ነገር ግን አምላክ በእርግጥ በም
ድር ላይ ይኖራልን? እነሆ፤ ሰማይ፣
ከሰማያትም በላይ ያለው ሰማይ እንኳ
ይይዝህ ዘንድ አይችልም፤ ታዲያ እኔ
የሠራሁት ይህ ቤተ መቅደስማ ምኑ
ሊበቃ! [28]አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ፤
ይህም ሆኖ የባሪያህን ጸሎትና ልመና
ስማ፤ በዛሬው ዕለት ባሪያህ በፊትህ
የሚያቀርበውን ጩኸትና ልመና አድ
ምጥ። [29]ባሪያህ ወደዚህ ቦታ የሚያቀር
በውን ጸሎት ትሰማ ዘንድ፣ ‘ስሜ በዚያ
ይሆናል’ ወዳልኸው በዚህ ስፍራ ወዳ
ለው ቤተ መቅደስ ዐይኖችህ ሌትና
ቀን የተከፈቱ ይሁኑ። [30]ባሪያህና ሕዝ
ብህ እስራኤል ወደዚህ ስፍራ ጸሎት
በሚያቀርቡበት ጊዜ፣ ልመናቸውን
ተቀበል፤ መኖሪያህ በሆነው በሰማይ
ስማ፤ ሰምተህም ይቅር በል።
[31]“አንድ ሰው ባልንጀራውን በድሎ
መማል ኖሮበት ቢመጣና በዚህ ቤተ
መቅደስ ውስጥ በመሠዊያህ ፊት ቢምል፣
[32]ይህን በሰማይ ሆነህ ስማ፤ አድር
ግም፤ በባሪያዎችህ መካከል ፍረድ፤
ለበደለኛው ስለ አድራጎቱ የእጁን
ክፈል፤ ከበደል ነጻ ለሆነውም ንጽሕ
ናውን ይፋ በማድረግ ይህንኑ አረጋግ
ጥለት።
[33]ሕዝብህ እስራኤል አንተን ከመ
በደላቸው የተነሣ፣ በጠላቶቻቸው ድል
በሚሆኑበት ጊዜ፣ ወደ አንተም ተመ
ልሰው ስምህን ቢጠሩ፣ በዚህም ቤተ
መቅደስ ወደ አንተ ቢጸልዩና ልመና
ቸውን ቢያቀርቡ፣ [34]በሰማይ ሆነህ
ስማ፤ የሕዝብህ የእስራኤልን ኀጢአት
ይቅር በል፤ ለአባቶቻቸው ወደ ሰጠ
ሃቸውም ምድር መልሰህ አግባቸው።
[35]“ሕዝቡም አንተን ከመበደላቸው የተ
ነሣ፣ ሰማዩ ተዘግቶ ዝናብ ሳይዘንብ
ቢቀር፣ ወደዚህ ስፍራ ቢጸልዩና ስም
ህን ቢጠሩ፣ ስላስጨነቅሃቸውም ከበደ
ላቸው ቢመለሱ፣ [36]በሰማይ ሆነህ ስማ፤
የባሪያዎችህን የሕዝብህን የእስራኤልን
ኀጢአት ይቅር በል፤ የሚሄዱበትን ቀና
ውን መንገድ አስተምራቸው፤ ርስት
አድርገህ ለሕዝብህ ለሰጠሃትም ምድር
ዝናብ አውርድ።
[37]“በምድሪቱ ላይ ራብ ወይም ቸነ
ፈር በሚመጣበት፣ ዋግ ወይም አረማሞ

8፥16 ዘፀ3፥10፤ ዘዳ12፥5፤1ሳሙ9፥16፤ 16፥1፤መዝ89፥34
8፥17 1ሳሙ 10፥7፤2ሳሙ7፥27፤ 1ዜና22፥7፤መዝ 26፥8፤132፥5፤ሐሥ 7፥46
8፥19 2ሳሙ7፥5፡13
8፥20 2ሳሙ7፥12፤ 1ዜና28፥6
8፥22 ዘፀ9፥29
8፥23 ዘፀ9፥14፤ ዘዳ7፥9፡12፤ነህ1፥5፤ 9፥32፤ዳን9፥4
8፥25 2ሳሙ7፥15፤ 1ዜና17፥23፤2ዜና1፥9
8፥26 2ሳሙ7፥25
8፥27 ዘዳ10፥14፤ 2ዜና2፥6፤መዝ139፥ 7ጠ16፤ኢሳ66፥1፤ኤር 23፥24፤ሐሥ7፥48፤ 17፥24
8፥29 ቀኍ52፤ዘዳ 11፥12፤12፥11፤2ሳሙ 7፥13፤2ነገ19፥16፤ 2ዜና7፥15፤ነህ1፥6፤ መዝ5፥1፤28፥2፤31፥ 2፤102፥17፤130፥2፤ 138፥2፤ኢሳ37፥17፤ ዳን6፥10
8፥30 ቀኍ39፡47፤ ዘፀ34፥7፡9፤ዘሌ26፥ 40ጠ42፤ነህ1፥6፤መዝ 34፥6፤85፥2፤ኤር 29፥12፤ዳን9፥4
8፥31 ዘፀ22፥11
8፥32 ዘዳ25፥1፤ ሕዝ18፥20
8፥33 ዘሌ26፥17፡ 39፤ኢሳ37፥1፡14፡38
8፥35 ዘዳ28፥24፤ 2ሳሙ1፥21፤ኤር5፥25
8፥36 ቀኍ35፤ዘዳ 8፥3፤1ሳሙ12፥23፤ 1ነገ17፥1፤18፥1፡45፤ መዝ5፥8፤27፥11፤ 107፥7፤ምሳ11፥5፤ ኢሳ45፥13፤ኤር5፥24 ፤6፥16፤7፥23፤10፥3፤ 14፥22፤31፥21፤ዘካ 10፥1
8፥37 ዘፀ10፥13፤ 30፥12፤ዘሌ26፥25፡26 ፤ዘዳ28፥22፤መዝ 105፥34

በሚከሡትበት፣ አንበጣ ወይም ኵብ
ኵባ በሚወርድበት ወይም በምድራቸው
ውስጥ ባሉት ከተሞቻቸው ጠላት ቢከ
ባቸው እንዲሁም ማንኛውም ዐይነት ጥፋት
ወይም በሽታ በሚመጣባቸው ጊዜ፣
[38]ከሕዝብህ ከእስራኤል ማንኛውም ሰው
የልቡን ጭንቀት ዐውቆ እጆቹን ወደዚ
ህ ቤት በመዘርጋት ጸሎትና ልመና
በሚ ያቀርብበት ጊዜ ሁሉ፣ [39]በ
ማደሪያህ በሰማይ ሆነህ ስማ፤ ይቅር
በል፤ አድ ርግም። አንተ ብቻ
የሰውን ሁሉ ልብ የምታውቅ ስለ
ሆንህ ልቡን ለምታው ቀው
ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ሥራው ሁሉ
ክፈለው፤ [40]ይህም እነርሱ ለአባ
ቶቻችን በሰጠሃቸው ምድር በሚኖሩ
በት ጊዜ ሁሉ፣ አንተን እንዲፈሩ
ነው።

[41]“ከሕዝብህ ከእስራኤል ወገን ያል
ሆነ፣ ግን ከስምህ ታላቅነት የተነሣ
ከሩቅ የመጣ የባዕድ አገር ሰው ቢኖር፣
[42]ሰዎች ከሩቅ የሚመጡት ስለ ታላቁ
ስምህ፣ ስለ ጠንካራዪቱ እጅህ፣ ስለ
ተዘረጋችው ክንድህ ሰምተው ነውና፤
እንግዳው መጥቶ ወደዚህ ቤተ መቅ
ደስ ቢጸልይ፣ [43]አንተ በማደሪያህ በሰ
ማይ ሆነህ ስማ፤ የጠየቀህንም ሁሉ
ፈጽምለት፤ ይኸውም የምድር ሕዝ
ቦች ሁሉ ስምህን ዐውቀው፣ ሕዝብህ
እስራኤል አንተን እንደሚፈሩት ሁሉ
እንዲፈሩህ፣ እኔ የሠራሁትም ይህ ቤት
በስምህ መጠራቱን እንዲያውቁ ነው።

[44]“ሕዝብህ ጠላታቸውን ለመውጋት
አንተ ወደምትልካቸው ወደ የትኛውም
ቦታ ለጦርነት በሚወጡበት ጊዜ፣ አንተ
ወደ መረጥሃት ከተማና እኔ ለስምህ
ወደ ሠራሁት ቤተ መቅደስ ፊታቸውን
መልሰው *ለእግዚአብሔር* ቢጸልዩ፣ [45]ጸሎ
ትና ልመናቸውን በሰማይ ሆነህ ስማ፤
ርዳቸውም።

[46]“*መቼም ኀጢአት የማይሠራ የለ*
ምና ሕዝብህ በአንተ ላይ ኀጢአት ቢሠሩ
አንተም ተቈጥተህ ሩቅ ወይም ቅርብ
ወደ ሆነው ምድሩ ማርኮ ለሚወስደው
ጠላት አሳልፈህ ብትሰጣቸው፣ [47]ተማ
ርከው በሚኖሩበት አገር ሳሉ ልባ
ቸው ቢመለስ፣ በተማረኩበትም ምድር
ሆነው ንስሓ ቢገቡና ‘ኀጢአት ሠርተ
ናል፤ በድለናል፤ ክፉ ድርጊትም ፈጽመ
ናል’ ብለው ቢለምኑህ፣ [48]እንዲሁም
ማርከው በወሰዷቸው ጠላቶቹ ምድር
ሳሉ በፍጹም ልባቸውና በፍጹም ነፍሳ
ቸው ወደ አንተ ቢመለሱ፣ ለአባቶ
ቻቸው ወደ ሰጠሃት ወደዚህች ምድር
ወደ መረጥሃትም ወደዚህች ከተማና
እኔም ለስምህ ወደ ሠራሁት ቤተ መቅ
ደስ ፊታቸውን መልሰው ቢጸልዩ፣
[49]ከማደሪያህ ከሰማይ ሆነህ ጸሎታቸ
ውን ስማ፤ ልመናቸውንም ተቀበል፤
ርዳቸውም። [50]በአንተ ላይ ስለ ሠሩት
ኀጢአት፣ አንተንም ስለ በደሉህ በደል
ሁሉ ሕዝብህን ይቅር በል፤ የማረኳቸ
ውም እንዲራሩላቸው አድርግ። [51]ከዚያች
እንደ ብረት ማቅለጫ እቶን እሳት ከሆነ
ችው፣ ከግብፅ ምድር ያወጣሃቸው ሕዝ
ብህም ርስትህም ናቸውና።

[52]“አሁንም ዐይኖችህ ለባሪያህና ለሕ
ዝብህ ለእስራኤል ልመና የተከፈቱ
ይሁኑ፤ ወደ አንተ በሚጮኹበትም ጊዜ
ሁሉ ስማቸው፤ [53]አምላኬ *እግዚአብሔር*
ሆይ፤ አባቶቻችንን ከግብፅ ባወጣህ
ጊዜ፣ በባሪያህ በሙሴ አማካኝነት እንደ
ተናገርኸው ሁሉ፣ ርስትህ ይሆኑ ዘንድ
ከምድር ሕዝቦች ሁሉ ለይተሃቸዋልና።”

[54]ሰሎሞንም ይህን ሁሉ ጸሎትና ልመና
*ለእግዚአብሔር* አቅርቦ ከፈጸመ በኋላ፣
እጆቹን ወደ ሰማይ በመዘርጋት፣ በጒል
በቱ ተንበርክኮ ከነበረበት *ከእግዚአብሔር*
*መሠዊያ* ፊት ተነሣ። [55]ከዚያም ቆሞ
መላውን የእስራኤልን ጉባኤ ከፍ ባለ
ድምፅ እንዲህ ሲል መረቀ፤

[56]“በሰጠው ተስፋ መሠረት ለሕ
ዝቡ ለእስራኤል ዕረፍትን ለሰጠ *እግዚ*
*አብሔር* ምስጋና ይግባው፤ በባሪያው
በሙሴ አማ ካይነት ከተሰጠው መልካም
ተስፋ ሁሉ አንድም ቃል አልቀረምና።
[57]አምላካችን *እግዚአብሔር*
ከአባቶቻችን ጋር እንደ ነበረ ሁሉ፣
ከእኛም ጋር ይሁን፤ አይ ተወን፤
አይጣለንም። [58]በመንገዱም ሁሉ
እንድንሄድ፣ ለአባቶቻችን የሰጣቸውን
ትእዛዞች፣ ሥርዐቶችና ደንቦች እንድንጠ
ብቅ ልባችንን ወደ እርሱ ይመልስ።
[59]በየዕለቱም ባሪያውንና ሕዝቡን እስራ
ኤልን በሚያስፈልጋቸው ሁሉ እንዲ
ረዳቸው፣ ይህች *በእግዚአብሔር* ፊት
ያቀረብኋት የራሴ ልመና በቀንና በሌ
ሊት ወደ አምላካችን ወደ *እግዚአብሐ*
*ር* ፊት ትቅረብ። [60]ይኸውም
የምድር ሕዝ ቦች ሁሉ *እግዚአብሔር*
ብቻ አምላክ እንደ ሆነና ከእርሱ
በቀር ሌላ እንደ ሌለ ያውቁ ዘንድ
ነው። [61]ስለዚህ እንደ ዛሬው ዕለት ሁሉ፣
በሥርዐቱ እንድት ኖሩና ትእዛዙን
እንድትጠብቁ ልባችሁ ለአምላካችሁ
*ለእግዚአብሔር* የተገዛ ይሁን።”

**8፥38** ዘ9፥29
**8፥39** ቀኍ30፤ኢሱ 22፥22፤መዝ44፥21፤130፥4፤ዮሐ2፥24፤ራእ2፥23
**8፥40** ቀኍ3940፤ዘዳ 6፥13፤12፥1፤መዝ 103፥11፤130፥4
**8፥41** ዘፍ31፥15፤ ኢሳ56፥3፡6፤61፥5
**8፥42** ዘዳ3፥24፤ 1ነገ10፥1፤ኢሳ 60፥3፤ሐሥ8፥27
**8፥43** ዘዳ28፥10፤ ኢሱ4፥24፤1ሳሙ 17፥46፤መዝ102፥15
**8፥44** 1ዜና5፥20፤ 2ዜና14፥11
**8፥45** መዝ9፥4፤ 140፥12
**8፥46** ዘሌ26፥33-39፤ዘዳ4፥27፤21፥10፤28፥64፤2ነገ25፥21፤መዝ130፥3፤143፥2፤ምሳ 20፥9፤ሮሜ3፥9
**8፥47** ቀኍ30፤ዘሌ 5፥5፤ዕዝ9፥7፡15፤ ነህ1፥6፤መዝ106፥6፤ ኤር3፥25፤14፥20
**8፥48** ዘዳ4፥29፡30፤ 12፥11ጠ14፤ነህ1፥9፤ መዝ5፥7፤11፥4፤ኤር 23፥3፤31፥8፤ዮና2፥4፤1 ዮሐ1፥810
**8፥50** 2ነገ25፥28፤ 2ዜና30፥9፤መዝ106፥ 46፤ዳን1፥9
**8፥51** ዘፀ1፥13፤ 34፥9፤ዘዳ9፥29፤ኢሳ 48፥10፤ኤር11፥4
**8፥52** ቀኍ29፤ኢዮ 30፥20፤መዝ3፥4፤22፥2፤77፥1፤142፥1
**8፥53** ዘ19፥5፤34፥9
**8፥55** ዘፀ39፥43፤ ዘኍ6፥23
**8፥56** ዘፀ33፥14፤ዘዳ 12፥10፤ኢሱ23፥15፤ ኤር29፥10፤ዕብ4፥8
**8፥57** ዘዳ4፥31፤ 31፥6፤ማቴ28፥20፤ ዕብ13፥5
**8፥58** ኢሱ24፥23
**8፥60** ዘዳ4፥35፤ኢሱ 4፥24
**8፥61** ዘዳ6፥5፤1ነገ 9፥4፤11፥4፤15፥3፡14፤22፥43፤2ነገ20፥3፤ 1ዜና28፥9፤29፥19፤ 2ዜና16፥9፤17፥6፤ 25፥2፤መዝ119፥80፤ ኢሳ38፥3

### የቤተ መቅደሱ መመረቅ
8፥62-66 ተጓ ምብ - 2ዜና 7፥1-10

62ከዚያም ንጉሡና ከእርሱ ጋር ያሉት
እስራኤል ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት መሥ
ዋዕት አቀረቡ። 63ሰሎሞንም ሃያ ሁለት ሺህ
በሬ፣ መቶ ሃያ ሺህ በግና ፍየል የኅ
ብረት መሥዋዕት[ከ] አድርጎ ለእግዚአብሔር
አቀረበ፤ ንጉሡና እስራኤላውያንም ሁሉ
የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ በዚህ ሁኔታ
ቀደሱ።
64በዚያኑ ዕለትም ንጉሡ በእግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ ፊት ለፊት ያለውን የአደባ
ባዩን መካከለኛ ክፍል ቀደሰ፤ በዚያም የሚ
ቃጠለውን መሥዋዕት፣ የእህል ቍርባንና
የኅብረት መሥዋዕቱን ስብ አቀረበ፤ ይህን
ያደረገውም በእግዚአብሔር ፊት የነበረው የናስ
መሠዊያ ከትንሽነቱ የተነሣ የሚቃጠለ
ውን መሥዋዕት የእህሉን ቍርባንና የኅ
ብረት መሥዋዕቱን ስብ መያዝ ባለመ
ቻሉ ነበር።
65በዚያን ጊዜም ሰሎሞን አብረውት
ካሉት የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ጋር፣ ማለ
ትም ከሐማት መተላለፊያ እስከ ግብፅ
ደረቅ ወንዝ[ኸ] ካለው ምድር ከተሰበሰበው
ታላቅ ጉባኤ ጋር በዓሉን አከበረ። እነር
ሱም ሰባት ቀን፣ በተጨማሪም ሌላ ሰባት
ቀን በድምሩ ዐሥራ አራት ቀን በአምላካ
ችን በእግዚአብሔር ፊት በዓሉን አከበሩ።
66በሚቀጥለው ቀን ሕዝቡን አሰናበተ፤ ሕዝ
ቡም ንጉሡን መረቁ፤ እግዚአብሔር ለባሪ
ያው ለዳዊትና ለሕዝቡ ለእስራኤል ባደረ
ገው በጎ ነገር ሁሉ ከልብ ተደስተው ሐሤት
በማድረግ ወደየቤታቸው ተመለሱ።

### እግዚአብሔር ለሰሎሞን ዳግመኛ ተገለጠ
9፥1-9 ተጓ ምብ - 2ዜና 7፥11-22

9 ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደ
ስና የራሱን ቤተ መንግሥት ሠርቶ
ከጨረሰና ለመሥራት የፈለገውንም ሁሉ
ካከናወነ በኋላ፣ 2እግዚአብሔር ለሰሎሞን
በገባዖን ተገልጦለት እንደ ነበረ ሁሉ ዳግም
ተገለጠለት። 3እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፤
"በፊቴ ያቀረብኸውን ጸሎትና ልመና
ሰምቻለሁ፤ ይህን የሠራኸውንም ቤተ
መቅደስ ስሜን በዚያ ለዘላለም እንዲኖር
በማድረግ ቀድሼዋለሁ፤ ዐይኖቼና ልቤ
ምን ጊዜም በዚያ ይሆናሉ።
4"አንተም አባትህ ዳዊት እንዳደረገው፣
በልበ ቅንነትና በትክክለኛነት ብትሄድ፣
የማዝህን ሁሉ ብትፈጽም፣ ሥርዐቴንና
ሕጌን ብትጠብቅ፣ 5ለአባትህ ለዳ
ዊት፣ 'በእስራኤል ዙፋን ላይ የሚቀ
መጥ ከዘርህ ሰው አታጣም' በማለት
በሰጠሁት ተስፋ መሠረት ዙፋንህን
በእስራኤል ላይ ለዘላለም አጸናለሁ።
6"ነገር ግን አንተም[ወ] ሆንህ ልጆችህ
እኔን ከመከተል ወደ ኋላ ብትመ
ለሱ፣ የሰጠኋችሁን ትእዛዞችና ሥርዐ
ቶች ሳትጠብቁ ብትቀሩ፣ ሄዳችሁም
ሌሎችን አማልክት ብታመልኩና ብት
ሰግዱላቸው፣ 7እኔም እስራኤልን ከሰጠ
ኋቸው ምድር እነቅላቸዋለሁ፤ ስለ
ስሜ የቀደስሁትን ይህን ቤተ መቅደ
ስም እተወዋለሁ፤ ከዚያም እስራኤል
በሕዝቦች ሁሉ ዘንድ መተረቻና መዘ
ባበቻ ይሆናሉ፤ 8ይህ ቤተ መቅደስ
አሁን የሚያስገርም ቢሆንም እንኳ፣
የፍርስራሽ ክምር ይሆናል፤ ዐላፊ አግዳ
ሚውም ሁሉ ይገረማል፤ እያፌዘም፣
'እግዚአብሔር በዚህች ምድርና በዚህ
ቤተ መቅደስ ላይ እንዲህ ያለውን
ነገር ያደረገው ስለምን ይሆን?' ይላል፤
9ራሱ መልሶም፣ 'አዎን እግዚአብሔር
ይህን ሁሉ ጥፋት ያመጣባቸው አባቶቻ
ቸውን ከግብፅ ምድር ያወጣውን አምላካ
ቸውን እግዚአብሔርን ትተው ሌሎች አማ
ልክትን በመከተል ስለ ሰገዱላቸውና
ስላመለኳቸው ነው' ይላል።"

### ሰሎሞን ያከናወናቸው ሌሎች ሥራዎች
9፥10-28 ተጓ ምብ - 2ዜና 8፥1-18

10ሰሎሞን ሁለቱን ሕንጻዎች፣ ማለትም
የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስና የንጉሡን
ቤተ መንግሥት ሠርቶ በፈጸመ በሃያኛው
ዓመት መጨረሻ፣ 11ንጉሥ ሰሎሞን በገሊላ
የሚገኙትን ሃያ ከተሞች ለጢሮስ ንጉሥ
ለኪራም ሰጠው፤ ንጉሡ ይህን ያደረገውም፣
የሚያስፈልገውን ሁሉ ዝግባ፣ ጥድና ወርቅ
ኪራም ሰጥቶት ስለ ነበር ነው፤ 12ይሁን እንጂ
ኪራም ከጢሮስ ተነሥቶ ሰሎሞን የሰጠ
ውን ከተሞች ለማየት በሄደ ጊዜ አል
ተደሰተባቸውም፤ 13እርሱም፣ "ወንድሜ ሆይ፤
እነዚህ የሰጠኸኝ ከተሞች ምንድን ናቸው?"
አለ፤ እነዚህንም 'ከቡል[ዐ] ምድር' አላቸው፤
እስከ ዛሬም በዚሁ ስም ይጠራሉ። 14በዚያን
ጊዜ ኪራም ለንጉሡ መቶ ሃያ መክሊት[ዘ]
ወርቅ ልኮለት ነበር።
15ንጉሥ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተ
መቅደስ፣ የራሱን ቤተ መንግሥት፣ ሚሎን፣
የኢየሩሳሌምን ቅጥር፣ ሐጾርን፣ መጊዶንና
ጌዝርን ለመሥራት የጕልበት ሠራተኞች

8፥62 2ሳሙ6፥13፤ 1ዜና29፥21፤ ሕዝ45፥17
8፥63 ዕዝ6፥16
8፥64 ዘፀ27፥1፤ 29፥13፤2ሳሙ6፥17፤ 2ነገ16፥14፤2ዜና4፥1፤ 8፥12፤15፥8፤ ሕዝ43፥13-17
8፥65 ቍ2፤ዘፍ 15፥18፤ዘኍ13፥21
8፥66 ዘፀ18፥9
9፥1 2ሳሙ7፥2
9፥2 1ነገ3፥5
9፥3 ዘፀ20፥24፤ዘዳ 11፥12፤12፥5፤1ሳሙ 9፥16፤2ነገ19፥20፤ 20፥5፤መዝ10፥17፤ 34፥17
9፥4 ዘፍ17፥1፤ዘዳ 17፥20፤1ነገ3፥14፤ 14፥8፤15፥5፤1ዜና28፥ 9፤ምሳ4፥4
9፥5 2ሳሙ7፥15፤ 1ዜና22፥10
9፥6 ዘዳ28፥15፤ 2ሳሙ7፥14፤1ነገ11፥ 10፤2ነገ18፥12፤ኤር 17፥27፤26፥4፤32፥23፤ 44፥23
9፥7 ዘሌ18፥24-28፤ ዘዳ4፥26፤12፥5፤28፥ 37፤ኢሱ23፥13፤2ነገ 17፥23፤ኢዮ17፥6፤ መዝ44፥14፤ኤር7፥14 ፤24፥9፡10፤ሕዝ5፥15፤ ኢል2፥17
9፥8 ዘሌ26፥32፤ ዘዳ29፥24፤ኤር7፥4- 15፤ማቴ23፥38
9፥9 ዘኍ25፥3፤ዘዳ 29፥25፤31፥29፤2ነገ 22፥17፤ኤር5፥19፤ 13፥22፤16፥11፡13፤ 22፥9፤40፥3፤44፥23፤ሰ ቆ4፥12
9፥11 ቍ14
9፥13 ኢሱ19፥27
9፥14 ቍ11
9፥15 ኢሱ10፥33፤ 11፥1011፤2ሳሙ5፥9፤ 1ነገ5፥13

[ከ]63 በዚህና በቍ 64 ላይ በትውፊት፣ የሰላም መሥዋዕት ይባላል።
[ኸ]65 ወይም ከመግቢያው ጀምሮ ተብሎ መተርጐም ይችላል።
[ወ]6 የዕብራይስጡ ትርጕም የብዙ ቍጥርን ያመለክታል
[ዐ]13 ከቡል የሚለው የዕብራይስጥ ቃል፣ የመልካም ነገር ተምሳሌት ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር ተመሳሳይ የሆነ ድምፅ አለው።
[ዘ]14 4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው

መልምሎ ነበር። [16]የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን
ወጥቶ በጌዝር ላይ አደጋ ጥሎ ያዛት፤
አቃጠላትም፤ ነዋሪዎቿን ከነዓናውያንን ገድሎ
ለልጁ ለሰሎሞን ሚስት መዳሪያ አድርጎ
ሰጥቶአት ነበር፤ [17]ሰሎሞንም ጌዝርን መልሶ
ሠራት፤ እንዲሁም የታችኛውን ቤትሖሮ
ንን፣ [18]ባዕላትን፣ በይሁዳ ምድር በምድረ
በዳው የምትገኘውን ተድሞርን[ዠ] ሠራ፤
[19]ደግሞም ማናቸውንም በኢየሩሳሌም፣ በሊ
ባኖስና በሌሎች ግዛቶቹ ሁሉ ለመሥራት
የፈለገውን፣ ሥንቅ የሚከማችባቸውን፣ ሠረ
ገሎች[የ] የሚጠበቁባቸውን እንዲሁም ፈረ
ሰኞች የሚቀመጡባቸውን ከተሞችና መን
ደሮች ሁሉ ሠራ።
[20]ከእስራኤል ሕዝብ ያልሆኑትን ከአሞ
ራውያን፣ ከኬጢያውያን፣ ከፌርዛውያን፣
ከኤውያውንና ከኢያቡሳውያን ሕዝቦች
ሁሉ የተረፉትን፣ [21]እስራኤላውያን ዘሮቻ
ቸውን ለማጥፋት[ደ] ያልቻሉትንና በምድ
ሪቱ የቀሩትን እነዚህን እስከ ዛሬ እንደሚ
ደረገው ሁሉ፣ ሰሎሞን ለግዳጅ ሥራ መለመ
ላቸው። [22]ይሁን እንጂ ሰሎሞን ከእስራ
ኤላውያን ማንንም ባሪያ አላደረገም፤ እነ
ርሱ ወታደሮቹ፣ ሹማምቱ፣ የጦር አለቆቹ፣
ሻምበሎቹ፣ ባልደራሶቹ ነበሩ። [23]እነዚህም
ሰሎሞን የሚያሠራውን የሕንጻ ሥራ የሚ
ያከናውኑትን ሠራተኞች የሚቈጣጠሩ
ናቸው፤ ቍጥራቸውም አምስት መቶ
አምሳ ነበር።
[24]የፈርዖን ልጅ ከዳዊት ከተማ ሰሎሞን
ወዳሠራላት ቤተ መንግሥት ከመጣች በኋላ
ሰሎሞን ሚሎንን ሠራ።
[25]ሰሎሞንም *ለእግዚአብሔር* ባሠራው መሠ
ዊያ ላይ በዓመት ሦስት ጊዜ የሚቃጠል
መሥዋዕትና የኅብረት መሥዋዕት[ጀ] በማቅ
ረብ፣ ከዚሁ ጋር *በእግዚአብሔር* ፊት ዕጣን
ያሳርግ ነበር፤ በዚህ ሁኔታም የቤተ መቅ
ደሱን ግዳጅ ተወጣ።
[26]እንዲሁም ንጉሡ ሰሎሞን በኤዶምያስ
ምድር፣ በኤሎት አጠገብ፣ በቀይ ባሕር[ገ]
ዳርቻ ላይ ባለችው በዔጽዮንጋብር መር
ከቦችን ሠራ። [27]በመርከቦቹም ላይ ከሰሎ
ሞን ሰዎች ጋር አብረው እንዲሠሩ፣ ኪራም
ባሕሩን የሚያውቁ የራሱን መርከበኞች ላከ።
[28]እነዚያም ወደ ኦፊር ሄደው አራት መቶ
ሃያ መክሊት[ጠ] ወርቅ ይዘው ተመለሱ፤
ይህንም ለንጉሥ ሰሎሞን ሰጡት።

## ንግሥተ ሳባ ሰሎሞንን እንደ ጐበኘች

10፥1-13 ተጓ ምብ - 2ዜና 9፥1-12

**10** ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን ዝና እና
*ከእግዚአብሔር* ስም ጋር ያለውን
ግንኙነት በሰማች ጊዜ፣ አስቸጋሪ በሆኑ

9፥16 1ነገ3፥1፤መዝ 45፥12፤68፥29፤ 72፥10
9፥17 ኢያሱ10፥10
9፥18 ኢያሱ19፥44
9፥19 ዘፀ1፥11፤ዘዳ 17፥16፤1ነገ4፥26፤ 2ዜና1፥14፤9፥25
9፥20 ዘኍ13፥29፤ ኢያሱ11፥3
9፥21 ዘፍ9፥2526፤ 49፥15፤ዘፀ1፥11፤ ዘዳ20፥11፤ኢያሱ15፥63
9፥22 ዘሌ25፥39
9፥23 1ነገ5፥16
9፥24 2ሳሙ5፥9፤ 1ነገ3፥1፤11፥27
9፥25 ዘፀ23፥14
9፥26 ዘኍ33፥35፤ 1ነገ10፥22፤22፥48፤2 ነገ14፥22፤16፥6፤2ዜና 20፥37፤ኢሳ2፥16
9፥27 ሕዝ27፥8
9፥28 ቍ14፤ዘፍ 10፥29፤1ነገ10፥10፡ 11፡14፡21፤2ዜና1፥15 ፤መክ2፥8
10፥1 ዘፍ10፥7፡28፤ 25፥3፤ዘኍ12፥8፤መሳ 14፥12፤ሕዝ16፥14፤ ማቴ12፥42፤ሉቃ 11፥31
10፥2 ዘፍ24፥10
10፥5 1ነገ4፥22
10፥7 ዘፍ45፥26፤ 1ዜና29፥25
10፥8 ምሳ8፥34
10፥9 ዘዳ7፥8፤1ነገ 5፥7፤መዝ11፥7፤33፥5፤ 72፥2፤99፥4፤103፥6፤ኢ ሳ42፥10
10፥10 1ነገ9፥28፤ ኢሳ60፥6
10፥11 ዘፍ10፥29

ጥያቄዎች ልትፈትነው መጣች። [2]ታላቅ
አጀብ አስከትላ ሽቶ፣ እጅግ ብዙ ወርቅና
የከበሩ ዕንቆች በግመል አስጭና ኢየሩሳሌም
ከደረሰች በኋላ፣ ወደ ሰሎሞን ገብታ
በልቧ ያለውን ጥያቄ ሁሉ አቀረበችለት።
[3]ሰሎሞንም የጠየቀችውን ሁሉ መለሰላት፤
ንጉሡ አቅቶት የቀረ አንዳች ጥያቄ
አልነበረም። [4]ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን
ጥበብ ሁሉ፣ የሠራውንም ቤተ መንግሥት
ስትመለከት [5]እንዲሁም በገበታው ላይ የሚ
ቀርበውን መብል፣ የሹማምቱን አቀማ
መጥ፣ አሳላፊዎቹን ከነደንብ ልብሳቸው፣
ጠጅ አሳላፊዎቹን፣ ደግሞም *በእግዚአብሔር*
ቤተ መቅደስ ያቀረበውን የሚቃጠል መሥ
ዋዕት[ጨ] ስታይ እጅግ ተደነቀች።
[6]ንጉሡንም እንዲህ አለችው፤ "ስላከናወ
ንኸው ሥራና ስለ ጥበብህ ባገሬ ሳለሁ
የሰማሁት ትክክል ነው፤ [7]ይሁን እንጂ፣
ራሴ መጥቼ እነዚህን ነገሮች በዐይኔ እስ
ካይ ድረስ አላመንሁም ነበር፤ በእርግጥ ግማ
ሹን እንኳ አልነገሩኝም፤ ጥበብህና ብል
ጽግናህ ከሰማሁት በላይ ነው። [8]ሰዎችህ
እንዴት ያሉ ዕድለኞች ናቸው! ሁል ጊዜ
በፊትህ ቆመው ጥበብህን የሚሰሙ ሹማ
ምትህስ እንዴት የታደሉ ናቸው! [9]በአንተ
ደስ ተሰኝቶ በእስራኤል ዙፋን ላይ ያስቀ
መጠህ *እግዚአብሔር* አምላክህ የተመሰገነ
ይሁን፤ *እግዚአብሔር* በዘላላም ፍቅሩም
እስራኤልን ከመውደዱ የተነሣ፣ ፍትሕና
ጽድቅ እንዲሰፍን አንተን ንጉሥ አድርጎ
አስነሣህ።"
[10]ለንጉሡም መቶ ሃያ መክሊት[ጸ] ወርቅ፣
እጅግ ብዙ ሽቶና የከበረ ድንጋይ ሰጠችው፤
ንግሥተ ሳባ ለንጉሥ ሰሎሞን ያበረከተ
ችለትን ያን ያህል ብዛት ያለው ሽቶ ከዚያ
በኋላ ከቶ አልመጣም።
[11]ከኦፊር ወርቅ ያመጡት የኪራም መር
ከቦች፣ እጅግ ብዙ የሰንደል ዕንጨትና[ጸ]
የከበሩ ዕንቆችም አመጡ። [12]ንጉሡም የሰ
ንደሉን ዕንጨት *ለእግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስና ለቤተ መንግሥቱ መደገፊያ፣ ለበ
ገናና ለመሰንቆ መሥሪያ አዋለው። ይህን ያህል
ብዛት ያለው የሰንደል ዕንጨት እስከ ዛሬ
ድረስ ከቶ አልመጣም፤ አልታየምም።

[ዠ]18 በዕብራይስጥ *ታማር* ተብሎ ይነበባል
[የ]19 ወይም *ሠረገለኞች* ተብሎ መተርጐም ይችላል
[ደ]21 የዕብራይስጡ ቃል ሰውን ወይም ቍስን ፈጽሞ በማጥ
ፋት ለእግዚአብሔር መስጠት የሚለውን ያመለክታል
[ጀ]25 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል
[ገ]26 የዕብራይስጡ *ያም ሰውፍ* ይለዋል፤ ይኸውም የደንገል ባሕር
ማለት ነው
[ጠ]28 14.5 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
[ጨ]5 ወይም *ወደ ላይ የሚወጣባቸው ደረጃዎች* ተብሎ መተር
ጐም ይችላል
[ጸ]10 4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
[ጸ]11 በዚህና በቍ 12 ላይ፣ *የአልጉም ዕንጨት* ከሚባለው ጋር
ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል።

13 ንጉሥ ሰሎሞንም ለንግሥተ ሳባ
ከቤተ መንግሥቱ በልግስና ከሚሰጣት
ሌላ፣ የፈለገችውንና የጠየቀችውን ሁሉ
ሰጣት፤ ከዚያም ከአጃቢዎቿ ጋር ወደ አገሯ
ተመለሰች።

### የሰሎሞን ብልጽግናና ክብር

10፥14-29 ተጓ ምብ - 2ዜና 1፥14-17፤ 9፥13-28

14 ለሰሎሞን በየዓመቱ የሚገባለት ስድ
ስት መቶ ሥልሳ ስድስት መክሊት ወርቅ
ነበር። 15 ይህም ከንግድና ከሌላ ገቢ ላይ
የሚከፈለውን ቀረጥ፣ የዐረብ ነገሥታት
ሁሉ የሚያገቡትንና አገረ ገዦች የሚሰበስ
ቡትን ግብር ሳይጨምር ነው።
16 ንጉሥ ሰሎሞን ከተጠፈጠፈ ወርቅ ሁለት
መቶ ታላላቅ ጋሻ አሠራ፤ በእያንዳንዱም
ጋሻ የገባው ሦስት መቶ ሰቅል[ፈ] ወርቅ ነበር።
17 እንዲሁም ከተጠፈጠፈ ወርቅ ሦስት መቶ
ትንንሽ ጋሻ አሠራ፤ በእያንዳንዱ ጋሻ የገ
ባው ደግሞ ሦስት ምናን[ፐ] ወርቅ ነው።
ንጉሡም እነዚህን የሊባኖስ ዱር በተባለው
ቤተ መንግሥት አኖረ።
18 ከዚያም ንጉሡ ከዝሆን ጥርስ ትልቅ
ዙፋን አሠርቶ በንጹሕ ወርቅ አስለበጠው።
19 ዙፋኑ ባለ ስድስት ደረጃ ነው፤ በስተ
ኋላውም ዐናቱ ላይ ክብ ቅርጽ ሲኖረው፣
ግራና ቀኙ ባለመደገፊያ ነው፤ በመደገፊያ
ዎቹም አጠገብ ሁለት አንበሶች ቆመዋል።
20 በስድስቱም ደረጃ ጫፍ ላይ ግራና ቀኝ
ስድስት ስድስት አንበሶች ቆመዋል።
ይህን የመሰለም ዙፋን በየትኛውም አገር
መንግሥት ከቶ ተሠርቶ አያውቅም።
21 ንጉሥ ሰሎሞን የሚጠጣበት ዋንጫ ሁሉ
የወርቅ ሲሆን፣ የሊባኖስ ዱር በተባለው
ቤተ መንግሥት ውስጥ የነበረው ዕቃ
በሙሉ ከንጹሕ ወርቅ የተሠራ ነበር፤ በሰ
ሎሞን ዘመነ መንግሥት ብር ይህን ያህል
ዋጋ ስላልነበረው፣ ከብር የተሠራ ዕቃ
ፈጽሞ አልነበረም። 22 ንጉሡ ከኪራም
መርከቦች ጋር አብረው በባሕር ላይ
የሚጓዙ የተርሴስ የንግድ መርከቦች[ሀ] ነበሩት።
እነዚህም በየሦስት ዓመቱ አንድ ጊዜ
ወርቅ፣ ብርና የዝሆን ጥርስ፣ ጦጣዎችና
ዝንጀሮዎች ያመጡ ነበር።
23 ንጉሥ ሰሎሞንም በሀብትና በጥበብ
ከምድር ነገሥታት ሁሉ ይበልጥ ነበር።
24 ዓለሙ ሁሉ እግዚአብሔር በሰሎሞን ልብ
ያኖረውን ጥበብ ለመስማት ወደ እርሱ
መምጣት ይፈልግ ነበር። 25 በየዓመቱም
የሚመጣውን ሰው ሁሉ የብርና የወ
ርቅ ዕቃ፣ ልብስ፣ የጦር መሣሪያ፣ ሽቶ፣
ፈረስና በቅሎ ስጦታ አድርጎ ያመጣለት
ነበር።
26 ሰሎሞን ሠረገሎችና[ለ] ፈረሶች ሰበሰበ፤
አንድ ሺህ አራት መቶ ሠረገሎችና ዐሥራ
ሁለት ሺህ ፈረሶች ነበሩት። እነዚህንም
ሁሉ ሠረገሎች በሚያኖርበት ከተሞችና
ራሱ በሚኖርበት በኢየሩሳሌም እንዲሆኑ አደ
ረገ። 27 ንጉሡም ብሩን በየቦታው እንደሚገኝ
ድንጋይ አደረገ፤ የዝግባውም ዕንጨት
ብዛት በቈላ እንደሚበቅል ሾላ ሆነ። 28 የሰ
ሎሞን ፈረሶች የመጡት ከግብፅና[ሐ] ከቀዌ[መ]
ሲሆን፣ እነዚህንም ከቀዌ ገዝተው ያመጧ
ቸው የቤተ መንግሥቱ ንግድ ሰዎች ነበሩ።
29 አንዱን ሠረገላ ከግብፅ የሚያመጡት በስ
ድስት መቶ ሰቅል[ሠ] ብር ሲሆን፣ ፈረሱን
ደግሞ በመቶ አምሳ ሰቅል[ረ] ብር ያመጡ
ነበር፤ ለኬጢያውያንና ለሶርያ ነገሥታትም
አምጥተው ይሸጡላቸው ነበር።

### የሰሎሞን ሚስቶች

11 ንጉሥ ሰሎሞን ከፈርዖን ልጅ
ሌላ ብዙ የባዕድ አገር ሴቶችን
ማለትም ሞዓባውያትን፣ አሞናውያትን፣
ኤዶማውያትን፣ ሲዶናውያትን፣ ኬጢያውያ
ትን አፈቀረ። 2 እነዚህም *እግዚአብሔር* እስ
ራኤላውያንን፣ "ልባችሁን ወደ አማልክታ
ቸው በእርግጥ ይመልሱታልና ከእነርሱ
ጋር መጋባት የለባችሁም" ካላቸው አሕዛብ
ወገን ነበሩ፤ ሆኖም ሰሎሞን ከእነዚሁ ጋር
ፍቅሩ ጠና። 3 እርሱም ከነገሥታት የተወ
ለዱ ሰባት መቶ ሚስቶችና ሦስት መቶ
ቁባቶች ነበሩት፤ ሚስቶቹም ልቡ ወደ
ሌላ እንዲያዘነብል አደረጉት። 4 ሰሎሞን
በሸመገለ ጊዜ ሚስቶቹ ልቡን ወደ ሌሎች
አማልክት መለሱት፤ የአባቱ የዳዊት ልብ
እንደ ተገዛ ሁሉ፣ በፍጹም ልቡ ለአምላኩ
*ለእግዚአብሔር* አልተገዛም። 5 ሰሎሞንም
የሲዶናውያንን ሴት አምላክ አስታሮትን፣
አስጸያፊውን የአሞናውያንን አምላክ ሚል
ኮምን ተከተለ። 6 ስለዚህ ሰሎሞን *በእግዚ
አብሔር* ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸመ፤ እንደ
አባቱ እንደ ዳዊትም *እግዚአብሔርን* እስከ
መጨረሻው አልተከተለም።
7 ሰሎሞን ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ
ባለው ተራራ ላይ ለአስጸያፊው የሞዓብ አም
ላክ ለካሞሽ እንዲሁም አስጸያፊ ለሆነው
ለአሞናውያን አምላክ ለሞሎክ ማምለኪያ
ኮረብታ ሠራ። 8 ለአማልክቶቻቸው ዕጣን

10፥14 1ነገ9፥28
10፥16 2ሳሙ8፥7
10፥17 1ነገ7፥2
10፥21 ኢሳ60፥17
10፥22 1ነገ9፥26፡ 27፤መዝ48፥7፤ኢሳ 2፥16፤23፥1፡14፤ 60፥6፡9
10፥23 1ነገ3፥12፡ 13፤ማቴ6፥29፤12፥42
10፥24 2ሳሙ 14፥20
10፥25 1ሳሙ 10፥27
10፥26 ዘዳ17፥16
10፥27 ዘዳ17፥17፤ 1ዜና27፥28፤ኢዮ 27፥16፤ኢሳ60፥17፤ አሞ7፥14
10፥29 ዘኍ13፥29
11፥1 ቍ3፤ዘፀ34፥ 16፤1ነገ14፥21፡31
11፥2 ዘፀ34፥16፤ 1ነገ16፥31
11፥3 ቍ1፤ዘፍ 22፥24፤ዘዳ17፥17፤ ነህ13፥26፤አስ2፥14፤ ምሳ31፥3
11፥4 ዘፀ34፥16፤ 1ነገ8፥61፤1ዜና 29፥19
11፥5 ቍ7፤ዘሌ 18፥21፤መሳ2፥13፤ ኢሳ57፥9፤ሰፎ1፥5
11፥6 ዘዳ4፥25
11፥7 ዘሌ18፥21፤ 20፥25፤ዘኍ21፥29፤ 2ነገ23፥13፤ ሐሥ7፥43

[ፀ]14 23 *ሜትሪክ ቶን ያህል ነው*
[ፈ]16 3.5 ኪሎ *ግራም ያህል ነው*
[ፐ]17 1.7 ኪሎ *ግራም ያህል ነው*
[ሀ]22 *ዕብራይስጡ* ***የተርሴስ መርከቦች*** *ይላል*
[ለ]26 *ወይም* ***ሠረገለኞች*** ተብሎ መተርጐም ይችላል
[ሐ]28 በዚህና በቍ 29 ላይ ምናልባት በቂልቂያ የምትገኘዋ ***ሙዝር*** ልትሆን ትችላለች
[መ]28 ምናልባትም ***ኪልቂያ*** ልትሆን ትችላለች
[ሠ]29 7 ኪሎ *ግራም ያህል ነው*
[ረ]29 1.7 ኪሎ *ግራም ያህል ነው*

ለሚያጥኑና መሥዋዕት ለሚያቀርቡ ለሌሎቹ
ሚስቶቹም ሁሉ በዚሁ ዐይነት ሠራላቸው።
9ሰሎሞን ሁለት ጊዜ ከተገለጠለት ከእስ
ራኤል አምላክ ከእግዚአብሔር ልቡ
ስለ ሸፈተ፥ እግዚአብሔር ተቈጣው።
10ምንም እንኳ ሌሎች አማልክትን
እንዳይከተል ሰሎ ሞንን ቢከለክለውም፥
ሰሎሞን የእግዚአ ብሔርን ትእዛዝ አልጠ
በቀም፤ 11ስለዚህ እግዚአብሔር ሰሎሞንን
እንዲህ አለው፤ "ይህን በማድረግህ
ያዘዝሁህን ኪዳኔንና ሥርዐቴንም ባለመጠ
በቅህ፥ መንግሥትህን ከአንተ ወስጄ
ከአገልጋዮችህ ለአንዱ እሰጠዋለሁ፤ 12ይህን
ግን ስለ አባትህ ስለ ዳዊት ስል በዘመንህ
አላደርገውም፤ መን ግሥትህን የምቀዳት
ከልጅህ እጅ ነው። 13ይህም ሆኖ
መንግሥቱን በሙሉ አልነ ጥቀውም፤ ነገር
ግን ስለ ባሪያዬ ስለ ዳዊትና ስለ
መረጥኋት ስለ ኢየሩሳሌም ስል ለልጅህ
አንድ ነገድ እሰጠዋለሁ።"

### የሰሎሞን ጠላቶች

14እግዚአብሔር ከኤዶም ንጉሣዊ ቤተ
ሰብ ኤዶማዊውን ሃዳድን በሰሎሞን ላይ
አስነሣው። 15ከዚያ በፊት ዳዊት ከኤዶም
ጋር በተዋጋ ጊዜ፥ የሞቱትን ለመቅበር
መጥቶ የነበረው የሰራዊቱ አዛዥ ኢዮአብ
የኤዶምን ሰዎች ሁሉ ፈጅቶ ነበር። 16ኢዮ
አብና እስራኤላውያን ሁሉ፥ በኤዶም ያሉትን
ወንዶች በሙሉ እስኪያጠፉ ድረስ፥ እዚ
ያው ስድስት ወር ቈይተው ነበርና። 17ሃዳድ
ግን ገና በልጅነቱ አባቱን ካገለገሉ ጥቂት
ኤዶማውያን ጋር ወደ ግብፅ ሸሸ፤ 18እነር
ሱም ከምድያም ተነሥተው ወደ ፋራን ሄዱ፤
ከፋራንም ሰዎች ይዘው ወደ ግብፅ በመም
ጣት፥ ወደ ግብፅ ንጉሥ ወደ ፈርዖን
ገቡ። ንጉሡም ለሃዳድ ቤትና መሬት
ሰጠው፤ ቀለብም አዘዘለት።
19ፈርዖንም ሃዳድን እጅግ ወደደው፤ ስለ
ዚህም ከሚስቱ ከንግሥት ጣፍኔስ እኅት
ጋር አጋባው። 20የጣፍኔስም እኅት ጌንባት
የተባለውን ልጅ ወለደችለት፤ ጣፍኔስ በፈ
ርዖን ቤት አሳደገችው፤ ጌንባትም ከፈ
ርዖን ልጆች ጋር አደገ።
21ሃዳድ በግብፅ ሳለ ዳዊት ከአባቶቹ
ጋር ማንቀላፋቱን፥ የሰራዊቱ አዛዥ ኢዮ
አብም መሞቱን ሰማ። ሃዳድም ፈርዖንን፥
"ወደ አገሬ እንድመለስ አሰናብተኝ" አለው።
22ፈርዖንም፥ "እዚህ ምን ጐደለብህና
ነው ወደ አገርህ ለመግባት የፈለግኸው?"
ሲል ጠየቀው።
ሃዳድም፥ "ምንም የጐደለብኝ የለም፥ ብቻ
እንድሄድ ፍቀድልኝ" አለ።

11፥9 1ነገ3፥5
11፥10 1ነገ6፥12፤ 9፥6
11፥11 ቍ31፤ዘሌ 18፥4፤1ሳሙ15፥27፤ 2ነገ17፥21፤ ማቴ21፥43
11፥12 መዝ89፥33
11፥13 ዘዳ12፥11፤ 2ሳሙ7፥151ነገ 12፥20
11፥14 1ነገ5፥4
11፥15 1ዜና18፥12
11፥18 ዘኍ10፥12
11፥23 2ሳሙ8፥3፤ 1ነገ5፥4
11፥24 2ሳሙ8፥5
11፥25 ዘፍ10፥22፤ 2ሳሙ10፥19
11፥26 2ዜና13፥6
11፥27 1ነገ9፥24
11፥28 ዘፍ39፥4፤ ሩት2፥1፤ምሳ22፥29
11፥29 1ነገ12፥15፤ 14፥2፤2ዜና9፥29፤ 10፥15
11፥30 1ሳሙ 15፥27
11፥31 ቍ11፤ 1ሳሙ15፥27
11፥32 2ሳሙ7፥15
11፥33 መሳ2፥13፤ 1ነገ3፥3፤2ነገ21፥22

23እግዚአብሔርም ከጌታው ከሱባ ንጉሥ
ከሆብ ልሎ የነበረውን የኤልያዳን ልጅ
ሬዞንን ሌላ
ጠላት አድርጎ በሰሎሞን ላይ አስነሣው፤
24ዳዊት የሱባን ኀይል በደመሰሰ[ሰ] ጊዜ፥ ሬዞን
ሰዎቹን በዙሪያው አሰባስቦ የወንበዴ አለቃ
ሆነ፤ ሰዎቹም ወደ ደማስቆ ሄደው ተቀመጡ፤
በዚያም አነገሡት። 25ሃዳድ ካስከተለበት
ችግር ሌላ ሬዞን በሰሎሞን ዘመን ሁሉ ሌላው
የእስራኤል ተቃዋሚ ሆነ፤ ሬዞን ሶርያን
ገዛ፤ እስራኤልንም ይጠላ ነበር።

### ኢዮርብዓም በሰሎሞን ላይ ዐመፀ

26እንዲሁም ከሰሎሞን ሹማምት አንዱ
የሆነው የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም በንጉሡ
ላይ ዐመፀ፤ እርሱም ከጽሬዳ የመጣ ኤፍ
ሬማዊ ሲሆን፥ እናቱ ጽሩዓ የተባለች
መበለት ነበረች።
27በንጉሡ ላይ ያመፀበትም ምክንያት እን
ዲህ ነው፤ ሰሎሞን ድጋፍ የሚሆኑ እርከ
ኖች በመሥራት የአባቱን የዳዊትን ከተማ
ቅጥር ይጠግን ነበር። 28ኢዮርብዓም ከፍተኛ
ችሎታ ያለው ሰው ነበር፤ ሰሎሞንም ወጣቱ
ሥራውን እንዴት በሚገባ እንደሚያከና
ውን ባየ ጊዜ፥ በዮሴፍ ነገድ ለሚሠራው
የጕልበት ሥራ ሁሉ ኀላፊ አደረገው።
29በዚያ ጊዜም ኢዮርብዓም ከኢየሩሳሌም
ሲወጣ፥ የሴሎው ነቢይ አኪያ በመንገድ ላይ
ተገናኘው፤ አኪያም አዲስ መጐናጸፊያ ለብሶ
ነበር፤ ሁለቱ ብቻቸውን ሳሉ፥ 30አኪያ የለ
በሰውን አዲስ መጐናጸፊያ ይዞ ዐሥራ ሁለት
ቦታ ቀደደው። 31ከዚያም ኢዮርብዓምን እን
ዲህ አለው፤ "ዐሥሩን ቍራጭ ለራስህ ውሰድ፤
የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላልና፤ 'እነሆ፤ መንግሥቱን ከሰሎሞን እጅ
እቀዳለሁ፤ ዐሥሩን ነገድ ለአንተ እሰጣ
ለሁ፤ 32ነገር ግን ስለ ባሪያዬ ስለ ዳዊትና
ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ ስለ መረጥኋት
ስለ ኢየሩሳሌም ስል አንድ ነገድ ይቀርለ
ታል፤ 33ይህን የማደርገውም እኔን ትተው[ሸ]
የሲዶናውያንን አምላክ አስታሮትን፥ የሞዓ
ብን አምላክ ካሞሽን፥ የአሞናውያንን
አምላክ ሚልኮምን ስላመለኩ እንዲሁም
አባቱ ዳዊት እንዳደረገው በመንገዴ ስላ
ልሄዱ በፊቴ ትክክለኛውን ነገር ስላላደ
ረጉ፥ ሥርዐቴንና ሕጌን ስላልጠበቁ ነው።
34" 'ይሁን እንጂ መንግሥቱን በሙሉ
ከእጁ አልወስድበትም፤ ስለ መረጥሁት፥
ትእዛዜንና ሥርዐቴን ስለ ጠበቀው ስለ
ባሪያዬ ስለ ዳዊት ስል በሕይወት ዘመኑ
ሁሉ እንዲገዛ አድርጌዋለሁ። 35መንግሥትን
ከልጁ እጅ እወስዳለሁ፤ ለአንተም ዐሥሩን

[ሰ]24 ዕብራይስጡ በደመሰሳቸው ጊዜ ይላል።
[ሸ]33 የዕብራይስጡ፥ የሰብዓ ሊቃናት፥ የቩልጌትና የሱርስት ትርጒሞች፥ እኔን ስለ ተወ ይላሉ።

ነገድ እሰጥሃለሁ። [36]ስሜ እንዲኖርባት በመ
ረጥኋት በዚያች በኢየሩሳሌም ከተማ
ለባሪያዬ ለዳዊት ምን ጊዜም በፊቴ መብ
ራት እንዲኖረው፣ ለልጁ አንድ ነገድ እሰ
ጣለሁ። [37]አንተን ግን እኔ እወስድሃለሁ፤
ልብህ በወደደው ሁሉ ላይ ትነግሣለህ፤
የእስራኤልም ንጉሥ ትሆናለህ። [38]ባሪያዬ
ዳዊት እንዳደረገው ሁሉ አንተም ያዘዝ
ሁህን ሁሉ ብትፈጽም፣ በመንገዴ ብት
ሄድ፣ ሥርዐቴንና ትእዛዜን በመጠበቅ
ትክክል የሆነውን ነገር በፊቴ ብታደርግ፣
ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ የዳዊትን ሥርወ
መንግሥት እንዳጸናሁ፣ ለአንተም እንዲሁ እስከ
ዘላለም የሚኖር ሥርወ መንግሥት አጸና
ለሁ፤ እስራኤልንም ለአንተ እሰጣለሁ።
[39]ከዚህ የተነሣም የዳዊትን ቤት አዋርዳ
ለሁ፤ ነገር ግን ለዘላለም አይደለም።' ”
[40]ሰሎሞን ኢዮርብዓምን ለመግደል ፈለገ፤
ኢዮርብዓም ግን ወደ ግብፅ ሸሸ፤ ወደ ንጉ
ሡ ወደ ሺሻቅ ሄዶ፣ ሰሎሞን እስኪሞት
ድረስ በዚያው ተቀመጠ።

### የሰሎሞን መሞት

11፥41-43 ተጓ ምብ – 2ዜና 9፥29-31

[41]የቀረው በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት የተ
ከናወነው፣ የሠራውም ሁሉ፣ ጥበቡም በሰ
ሎሞን የታሪክ መጽሐፍ ተጽፎ የለምን?
[42]ሰሎሞን በመላው እስራኤል ላይ በኢየሩ
ሳሌም የነገሠው አርባ ዓመት ነው። [43]ከአ
ባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በአባቱ በዳዊት ከተማ
ተቀበረ፤ ልጁም ሮብዓም በእግሩ ተተክቶ
ነገሠ።

### እስራኤል በሮብዓም ላይ ዐመፀ

12፥1-24 ተጓ ምብ - 2ዜና 10፥1-11፥4

12 እስራኤላውያን ሁሉ ሊያነግሡት
ወደ ሴኬም ስለ ሄዱ፣ ሮብዓም
ወደዚያው ሄደ።[ቀ] [2]የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም
ይህን በሰማ ጊዜ፣ ከንጉሥ ሰሎሞን ሸሽቶ
ከሚኖርበት ከግብፅ ተመልሶ መጣ። [3]ስለ
ዚህም ወደ ኢዮርብዓም ላኩበት፤ እርሱና
መላው የእስራኤል ጉባኤም ወደ ሮብዓም
መጥተው፣ [4]“አባትህ ከባድ ቀንበር ጫነ
ብን፤ አንተ ግን አሁን የአባትህን የጭካኔ
አገዛዝ የጫነብንንም ከባድ ቀንበር ብታ
ቀልልን እንገዛልሃለን” አሉት።
[5]ሮብዓምም፣ “እንግዲያውስ ሂዱ፤ ከሦስት
ቀን በኋላ ተመልሳችሁ ወደ እኔ ኑ” አላ
ቸው። ስለዚህ ሕዝቡ ሄዱ።
[6]ከዚያም ሮብዓም አባቱ ሰሎሞን በሕይ
ወቱ ሳለ ካገለገሉት ሽማግሌዎች ጋር ተማ
ከረ፤ “ለዚህ ሕዝብ ምን መልስ እንድሰጥ
ትመክሩኛላችሁ?” አላቸው።

[7]እነርሱም፣ “ዛሬ አንተ ለዚህ ሕዝብ
አገልጋይ ብትሆን፣ ብትገዛለትና ደስ የሚ
ያሰኝ መልስ ብትሰጠው፣ ምን ጊዜም የአ
ንተ አገልጋይ ይሆናል” ብለው መለሱለት።
[8]ሮብዓም ግን ሽማግሌዎቹ የሰጡትን ምክር
ንቆ፣ አብሮ አደግ የሆኑትንና እርሱን
የሚያገለግሉትን ወጣቶች፣ [9]“ሐሳብ ለማግ
ኘት፣ የእናንተስ ምክር ምንድን ነው?
‘አባትህ የጫነብንን ቀንበር አቅልልን’
ለሚሉኝ ለእነዚህ ሰዎች ምን መልስ እን
ስጥ?” ሲል ጠየቃቸው።
[10]ወጣት አብሮ አደጎቹም፣ እንዲህ አሉት፣
“ ‘አባትህ ከባድ ቀንበር ጫነብን፣ አንተ
ግን ቀንበራችንን አቅልልን’ ላሉህ ለእነዚህ
ሰዎች፣ ‘ትንሿ ጣቴ ከአባቴ ወገብ ይልቅ
ትወፍራለች፤ [11]አባቴ ከባድ ቀንበር ጫነባ
ችሁ፤ እኔ ግን ከዚያ ይብስ አከብደዋለሁ፤
አባቴ በዐለንጋ ገረፋችሁ፤ እኔ ግን በጊ
ንጥ እገርፋችኋለሁ’ በላቸው!” አሉ።
[12]ንጉሡ፣ “በሦስተኛው ቀን ተመልሳችሁ
ኑ” ብሎአቸው ስለ ነበር፣ ኢዮርብዓምና
ሕዝቡ ሁሉ በሦስተኛው ቀን ወደ ሮብዓም
ተመልሰው መጡ። [13]ንጉሡም በሽማግሌ
ዎቹ የተሰጠውን ምክር ትቶ፣ ሕዝቡን
የሚያስከፋ መልስ ሰጣቸው፤ [14]ወጣቶቹ
የሰጡትን ምክርም ተቀብሎ፣ “አባቴ ቀን
በራችሁን አከበደባችሁ፤ እኔ ደግሞ ከዚያ
ይብስ አከብደዋለሁ፤ አባቴ በአለንጋ ገረ
ፋችሁ፣ እኔ ደግሞ በጊንጥ እገርፋችኋለሁ”
አላቸው። [15]*እግዚአብሔር* በሴሎናዊው
በአኪያ አማካይነት ስለ ናባጥ ልጅ ስለ
ኢዮርብዓም የተናገረው ቀድሞውኑ *እግዚአ
ብሔር* የወሰነው ስለ ሆነ፣ መፈጸም ነበረብ
ትና ንጉሡ ሕዝቡን አልሰማም።
[16]እስራኤልም ሁሉ ንጉሡ ሊሰማቸው
አለመፈለጉን በተረዱ ጊዜ፣ ለንጉሡ እንዲህ
በማለት መለሱ፤

“ከዳዊት ምን ድርሻ አለን?
ከእሴይስ ልጅ ምን የምናገኘው አለ?
እስራኤል ሆይ፤ ወደየድንኳንህ ተመለስ፤
ዳዊት ሆይ፤ እንግዲህ የገዛ
ቤትህን ጠብቅ!

ስለዚህም እስራኤላውያን ወደ ድንኳኖቻቸው
ተመለሱ። [17]ሮብዓምም በይሁዳ ምድር በሚ
ኖሩት እስራኤላውያን ላይ ገዥ ሆነ።
[18]ንጉሥ ሮብዓም የጉልበት ሠራተኞች
አለቃ የነበረውን አዶኒራምን[በ] ላከው፤
ነገር ግን እስራኤል ሁሉ በድንጋይ ወግ
ረው ገደሉት። ንጉሡ ሮብዓም ግን እንደ

11፥36 2ሳሙ 21፥17፤1ነገ12፥17
11፥37 2ሳሙ 3፥21፤1ነገ14፥7
11፥38 ዘፀ1፥21፤ ዘዳ12፥25፤17፥19፤ 2ሳሙ8፥15
11፥40 1ነገ12፥2፤ 2ዜና10፥2፤12፥2
11፥43 ማቴ1፥7
12፥1 ቀኍ25፤ዘፍ 12፥6፤ኢሱ24፥32
12፥2 1ነገ11፥40
12፥4 1ሳሙ8፥11-18፤1ነገ4፥2028
12፥6 1ነገ4፥2
12፥7 ምሳ15፥1
12፥8 ዘሌ19፥32
12፥14 ዘፀ1፥14
12፥15 ዘዳ2፥30፤ 1ነገ11፥29፤2ዜና 25፥20
12፥16 ዘፍ31፥14፤ 2ሳሙ20፥1፤ኢሳ7፥17
12፥17 1ነገ 11፥13፣36
12፥18 ኢሱ7፥25፤ 2ሳሙ20፥24

[ቀ]2 ወይም በግብፅ ቀረ ተብሎ መተርጐም ይችላል።
[በ]18 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ቅጆችና የሱርስት ትርጕሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ (1ነገ4፥6፤ 5፥14 ይመ) ዕብራይስጡ፣ *አዶራም* ይላል

ምንም ብሎ ሠረገላው ላይ በመውጣት
ወደ ኢየሩሳሌም ሸሸ። [19]ስለዚህ ሕዝቡ
በዳዊት ቤት ላይ እስከ ዛሬ ድረስ እንዳ
መፀ ነው።
[20]ኢዮርብዓም መመለሱን እስራኤላው
ያን ሁሉ በሰሙ ጊዜ፣ ወደ ጉባኤያቸው
በማስጠራት በመላው እስራኤል ላይ አነገ
ሡት። ለዳዊት ቤት በታማኝነት ጸንቶ
የተገኘው የይሁዳ ቤት ብቻ ነው።
[21]ሮብዓም ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ፣
የእስራኤልን ቤት ወግተው መንግሥቱን
ለሰሎሞን ልጅ ለሮብዓም እንዲመልሱ መላ
ውን የይሁዳ ቤትና የብንያምን ነገድ
ሰበሰበ፤ የሰራዊቱም ቊጥር አንድ መቶ ሰ
ማ ንያ ሺህ ነበር።
[22]ነገር ግን ይህ የአምላክ ቃል፣ የእግዚአብሐ
ር ሰው ወደ ሆነው ወደ ሳማያ መጣ፤
[23]"ለይ ሁዳ ንጉሥ ለሰሎሞን ልጅ ለሮብዓ
ም፣ ለመ ላው የይሁዳ ቤትና ለብንያም
ነገድ፣ ለቀ ረውም ሕዝብ ሁሉ እንዲህ
በል፤ [24]'እግዚ አብሔር የሚለው ይህ ነው፤
ይህ ነገር ከእኔ የሆነ ነውና ወንድሞቻችሁን
እስራኤላውያ ንን ለመውጋት አትውጡ፤
እያንዳንዳችሁ ወደየቤታችሁ ተመለሱ።'
ስለዚህ እግዚአ ብሔር እንዳዘዘው የእግዚ
አብሔርን ቃል ሰሙ፤ ወደየቤታቸውም
ተመለሱ።

### በቤቴልና በዳን የቆሙ የወርቅ ጥጆች

[25]ከዚያም ኢዮርብዓም በኰረብታው አገር
በኤፍሬም የምትገኘውን ሴኬምን ምሽግ አድ
ርጎ ሠራ፤ በዚያም ተቀመጠ። ደግሞም ያንን
ትቶ በመውጣት የጵኒኤልን† ምሽግ ሠራ።
[26]ኢዮርብዓም በልቡ እንዲህ ሲል አሰበ፤
"መንግሥቱ ለዳዊት ቤት የሚመለስ ይመ
ስላል፤ [27]ይህ ሕዝብ መሥዋዕት ለማቅ
ረብ ኢየሩሳሌም ወዳለው ወደ እግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ የሚወጣ ከሆነ፣ እንደ ገና
ልቡን ወደ ጌታው ወደ ይሁዳ ንጉሥ ወደ
ሮብዓም ሊያዞር ነው። ከዚያም እኔን
ይገድለኛል፤ ወደ ንጉሡም ወደ ሮብዓም
ይመለሳል።"
[28]ንጉሡ ከመከረበት በኋላ ሁለት የወ
ርቅ ጥጆች አሠርቶ ሕዝቡን፣ "እስራኤል
ሆይ፤ ወደ ኢየሩሳሌም እስካሁን የወጣኸው
ይበቃል፤ ከግብፅ ምድር ያወጡህ አማል
ክትህ እነዚህ ናቸው" አለ። [29]አንዱን በቤ
ቴል ሌላውንም በዳን አቆመው። [30]ይህም
አድራጎት ኀጢአት ሆነ፤ ሕዝቡም በዚያ
ላለው ለመስገድ እስከ ዳን ድረስ ርቆ
ሄደ።
[31]ኢዮርብዓም በማምለኪያ ኰረብቶች ላይ
አብያተ ጣዖታትን ሠራ፤ ከሕዝቡ የተለ
ያዩ ክፍሎች ሁሉ፣ ሌዋውያን ካልሆኑት
ካህናትን ሾመ። [32]በይሁዳ እንደሚደረገው
ሁሉ እርሱም በስምንተኛው ወር ዐሥራ
አምስተኛው ቀን በዓል እንዲሆን ወሰነ፤ በመ
ሠዊያውም ላይ መሥዋዕት አቀረበ። ለሠ
ራቸው ጥጆች መሥዋዕት በማቅረብም
እንዲህ ያለውን ድርጊት በቤቴል ፈጸመ።
በማምለኪያ ኰረብቶች ላይ ላሠራቸው
አብያተ ጣዖታት በቤቴል ካህናቱን መደበ።
[33]ራሱ በመረጠው በስምንተኛው ወር፣ በዐሥራ
አምስተኛው ቀን በቤቴል ባቆመው መሠ
ዊያ ላይ መሥዋዕት አቀረበ፤ ስለዚህ ለእ
ስራኤላውያን በዓል ወሰነላቸው፤ ዕጣንም
ለማቅረብ ወደ መሠዊያው ወጣ።

### ከይሁዳ የመጣ የእግዚአብሔር ሰው

13 ኢዮርብዓም መሥዋዕት ለማቅረብ
በመሠዊያው አጠገብ ቆሞ ሳለ፣ በእ
ግዚአብሔር ቃል ታዞ አንድ የእግዚአብሔር
ሰው ከይሁዳ ወደ ቤቴል መጣ። [2]መሠዊ
ያውንም በእግዚአብሔር ቃል በመቃወም
እንዲህ አለ፤ "አንተ መሠዊያ ሆይ! እንግ
ዲህ እግዚአብሔር የሚለው ይህ ነው፤ 'እነሆ፤
ኢዮስያስ የተባለ ለዳዊት ቤት ይወለዳል፤
እርሱም አሁን እዚህ መሥዋዕት የሚያቀ
ርቡትን የኰረብታ ማምለኪያ ካህናት በላ
ይህ ይሠዋቸዋል፤ የሰዎችም ዐጥንት በአንተ
ላይ ይነዳል።'" [3]በዚያች ዕለት ያ የእግዚአ
ብሔር ሰው፣ እንዲህ ሲል ምልክት ሰጠ፤
"እግዚአብሔር የሰጠውም ምልክት፣
'እነሆ፣ መሠዊያው ይሰነጠቃል፤ በላዩም
ላይ ያለው
ዐመድ ይፈሳል'" የሚል ነው።
[4]ንጉሥ ኢዮርብዓምም ያ የእግዚአብሔር ሰው
በቤቴል መሠዊያ ላይ ጮኾ የተናገረውን
ሲሰማ፣ እጁን መሠዊያው ካለበት በመዘር
ጋት፣ "ያዙት!" አለ፤ ነገር ግን ያች የዘረ
ጋት እጁ ደርቃ ቀረች፤ ሊመልሳትም አል
ቻለም [5]እንዲሁም ያ የእግዚአብሔር ሰው
በእግዚአብሔር ቃል ተመርቶ በሰጠው
ምልክት መሠረት መሠዊያው ተሰነጠቀ፤
ዐመዱም ፈሰሰ።
[6]ከዚያም ንጉሡ የእግዚአብሔርን ሰው፣ "እጄ
ወደ ቦታዋ እንድትመለስ ወደ አምላክህ
ወደ እግዚአብሔር ለምንልኝ፤ ጸልይልኝም"
አለው፤ ስለዚህም የእግዚአብሔር ሰው እግዚ
አብሔርን ለመነ፤ የንጉሡ እጅ ወደ
ቦታዋ ተመለ ሰች፤ እንደ ቀድሞዋም
ሆነች።
[7]ንጉሡም የእግዚአብሔርን ሰው፣ "አብ
ረኸኝ ወደ ቤት እንሂድ፤ አንድ ነገር
ቅመስ፤ ስጦታም አደርግልሃለሁ" አለው።

12፥19 2ነገ17፥21
12፥20 1ነገ11፥13፡32፤ሕዝ37፥16
12፥21 1ነገ14፥30፤15፥6፡16፤2ዜና11፥1
12፥22 ዘጸ33፥1፤2ነገ4፥7፤2ዜና12፥57
12፥25 ቊ1፤መሳ8፥8
12፥27 ዘጸ12፥56
12፥28 ዘፀ32፥4፡8፤2ዜና11፥15
12፥29 ዘፍ12፥8፤ኢሱ7፥2፤መሳ18፥27-31፤አሞ8፥14
12፥30 1ነገ13፥34፤14፥16፤15፥26፡30፤16፥2፤2ነገ3፥3፤10፥29፤13፥2፤ 17፥21
12፥31 ዘፀ29፥9፤ዘሌ26፥30፤1ነገ13፥32፡33፤2ነገ17፥29፡32፤2ዜና11፥1415፤13፥9
12፥32 ዘኍ29፥12፤2ነገ10፥29
12፥33 2ነገ23፥15፤አሞ7፥13
13፥1 ዘጸ33፥1፤መሳ13፥6፤አሞ7፥13
13፥2 ዘሌ26፥30፤2ነገ23፥1516፡20፤2ዜና34፥5
13፥3 ዘፍ24፥14፤ዘ4፥8፤ዮሐ2፥11
13፥6 ዘፍ20፥7፤ዘኍ11፥2፤ኤር37፥3፤ሐሥ8፥24
13፥7 1ሳሙ9፥7

†25 ዕብራይስጡ ጵኑኤል ይለዋል

8የእግዚአብሔር ሰው ግን ለንጉሡ እንዲህ
ሲል መለሰለት፤ “ግማሽ ሀብትህን ብትሰጠ
ኝ እንኳ፣ አብሬህ አልሄድም፤ እዚህ፣ እንጀ
ራ አልበላም፤ ውሃም አልጠጣም፡፡ 9በእግዚ
አ ብሔር ቃል፤ ‘እንጀራ እንዳትበላ፣
ውሃም እንዳትጠጣ፣ በሄድህበትም
መንገድ እንዳ ትመለስ’ ተብዬ
ታዝዣለሁና፡፡” 10ስለዚህም በመጣበት
ሳይሆን በሌላ መንገድ ወደ ቤቴል ተመለሰ፡፡
11በዚያን ጊዜ በቤቴል የሚኖር አንድ ሽ
ማ ግሌ ነቢይ ነበር፤ ልጆቹም መጥተው
በዚያች ዕለት የእግዚአብሔር ሰው እዚያ
ያደረገ ውን ሁሉና ንጉሡንም ምን
እንዳለው ለአባታቸው ነገሩት፡፡
12አባታቸውም፣ “ለመ ሆኑ የተመለሰው
በየትኛው መንገድ ነው?” በማለት ጠ
የቃቸው፤ ልጆቹም ከይሁዳ የመጣው
የእግዚአብሔር ሰው የተመለሰበትን መንገድ
ለአባታቸው አሳዩት፡፡ 13ስለዚህም ልጆቹ
ን፣ “በሉ አህያውን ጫኑልኝ” አላ ቸው፡፡
እነርሱም አህያውን ጫኑለትና ተቀ
ምጦበት 14እየጋለበ ያን የእግዚአብሔር ሰው
ተከተለው፡፡ ከዚያም በአንድ የወርካ ዛፍ
ሥር ተቀምጦ አገኘውና፣ “ከይሁዳ የመ
ጣኸው የእግዚአብሔር ሰው አንተ ነህን?” ሲል
ጠየቀው፡፡
እርሱም፣ “አዎን እኔ ነኝ” ብሎ መለሰለት፡፡
15ስለዚህ ነቢዩ፣ “አብረን ወደ ቤት እን
ሂድና ምግብ ብላ” አለው፡፡
16የእግዚአብሔርም ሰው እንዲህ ሲል መለ
ሰለት፤ “ተመልሼ ከአንተ ጋር አልሄድም፤
በዚህ ቦታም አብሬህ እንጀራ አልበላም፤
ውሃም አልተጣም፤ 17‘እዚያ እንጀራ እንዳ
ትበላ፣ ውሃም እንዳትጠጣ፣ በሄድህበትም
መንገድ እንዳትመለስ’ ተብዬ በእግዚአብሔር
ቃል ታዝዣለሁና” አለው፡፡
18ሽማግሌው ነቢይ ግን፣ “እኔም እኮ እንዳ
ንተው ነቢይ ነኝ፤ መልአክ በእግዚአብሔር
ቃል፣ ‘እንጀራ እንዲበላና ውሃ እንዲጠጣ
መልሰህ ወደ ቤትህ አምጣው’ ብሎኛል
ነው” አለው፤ ነገር ግን ውሸቱን ነበር፡፡
19ስለዚህ የእግዚአብሔርም ሰው አብሮት
ተመ ልሶ በቤቱ በላ፤ ጠጣም፡፡
20በማእድ ተቀምጠው ሳለ፣ የእግዚአብሔር
ቃል መልሶ ወደ አመጣው ወደ ሽማግሌው
ነቢይ መጣ፤ 21ከይሁዳ ለመጣውም የእግዚአ
ብሔር ሰው፣ “እግዚአብሔር የሚለው ይህ
ነው፣ ‘የእግዚአብሔርን ቃል አቃለሃል፤
አምላክህ እግዚአብሔር የሰጠህንም ትእዛዛት
አልጠ በቅህም፤ 22ተመልሰህ በመምጣት
እንዳትበ ላና እንዳትጠጣ በነገረህ ቦታ
እንጀራ በላህ፤ ውሃም ጠጣህ፡፡ ስለዚህ

13፥8 ቍ16፤ ዘኍ22፥18
13፥16 ቍ8
13፥18 ዘፍ19፥14፤ ዘዳ13፥3፤1ነገ22፥6፡ 12፤2ዜና35፥21፤ ኢሳ36፥10
13፥21 ቍ26፤ 1ሳሙ13፥14፤1ነገ 20፥35
13፥24 1ነገ20፥36
13፥26 ቍ21
13፥30 2ነገ23፥17፤ ኤር22፥18
13፥32 ዘሌ26፥30፤ 1ነገ12፥31፤16፥24፡ 28፤20፥1፤2ነገ10፥1፤ 15፥13፤23፥16
13፥33 1ነገ12፥31፤ 15፥26
13፥34 1ነገ12፥30፤ 14፥10፤15፥29፤2ነገ 9፥9፤ኤር35፥17፤ አሞ7፥9
14፥2 1ነገ11፥29

ሬሳህ በአባቶችህ መቃብር አይቀበርም’” ሲ
ል ጮኾ ተናገረው፡፡
23የእግዚአብሔርም ሰው በልቶና ጠጥቶ
ካበቃ በኋላ፣ ያ መልሶ ያመጣው ነቢይ
አህያ ውን ጫነለት፡፡ 24ሲሄድ ሳለም አንበሳ
መን ገድ ላይ አግኝቶ ገደለው፤ ሬሳውም
በመን ገድ ላይ ተጋደመ፤ አህያውና
አንበሳውም አጠገቡ ቆመው ነበር፡፡ 25በዚ
ያ ያለፉ ሰዎች ሬሳው በመንገድ ላይ
ተጋድሞ፣ አንበሳውም አጠገቡ ቆሞ ስላዩ፣
ሽማግሌው ነቢይ ወዳለበት ከተማ ሄደው
ይህንኑ ተናገሩ፡፡
26ያም ከመንገድ የመለሰው ነቢይ ይህን
ሲሰማ፣ “ይህ የእግዚአብሔርን ቃል ያቃ
ለለው ያ የእግዚአብሔር ሰው ነው፤ እግዚአ
ብሔር ባስጠነቀቀው ቃል መሠረት አሳ
ልፎ ሰጥቶት አንበሳ ሰብሮ ገድሎታል”
አለ፡፡
27ከዚያም ነቢዩ ልጆቹን፣ “በሉ አህያ
ጫኑልኝ” አላቸውና ጫኑለት፡፡ 28ከዚያም ሄዶ
ሬሳው መንገድ ላይ ተጋድሞ አንበሳውና
አህያው በአጠገቡ ቆመው አገኘ፤ አንበሳው
ሬሳውን አልበላውም፤ አህያውንም አልሰበ
ረውም፡፡ 29ስለዚህ፣ ነቢዩ የዚያን የእግዚአብሐ
ር ሰው ሬሳ አንሥቶ በአህያው ላይ ጫነ፤
አልቅሶ ለመቅበርም ራሱ ወደሚኖርበት
ከተማ አመጣው፡፡ 30ከዚያም ሬሳውን በራሱ
መቃብር ቀበረው፤ “አወይ ወንድሜ”
እያሉም አለቀሱለት፡፡
31ከቀበሩትም በኋላ ልጆቹን እንዲህ
አላ ቸው፤ “እኔም በምሞትበት ጊዜ የእግዚ
አብሔር ሰው በተቀበረበት መቃብር
ቅበሩኝ፤ ዐጥ ንቶቼንም በዐጥንቶቹ አጠ
ገብ አኑሩ፡፡ 32በቤቴል ባለው መሠዊያ፣
በሰማርያ ከተ ሞችና በየኰረብታው ባሉ
ማምለኪያ ስፍራዎች ላይ በእግዚአብሔር
ቃል ጮኾ ያሰማው መልእክት በትክክል
የሚፈጸም ነውና፡፡”
33ይህም ሁሉ ሆኖ ኢዮርብዓም ከክፉ
መንገዱ አልተመለሰም፤ ይልቁንም በኰረ
ብታ ማምለኪያዎች ከየትኛውም ክፍል እንደ
ገና ካህናትን ይሾም ጀመር፤ ካህን ለመ
ሆን የሚፈልገውንም ሁሉ ለየኰረብታ
ማምለኪያዎቹ ለየ፡፡ 34ይህም ኀጢአት የኢ
ዮርብዓም ቤት እንዲወድቅና ከምድር
ገጽም እንዲደመሰስ ምክንያት ሆነ፡፡

## አኪያ በኢዮርብዓም ላይ የተናገረው ትንቢት

14 በዚያን ጊዜ የኢዮርብዓም ልጅ
አብያ ታመመ፤ 2ኢዮርብዓም
ሚስቱን እንዲህ አላት፤ “ተነሺ፣ የኢዮር
ብዓም ሚስት መሆንሽ እንዳይታወቅብሽ

ሆነሽ፣ ወደ ሴሎ ሂጂ፤ በዚህ ሕዝብ ላይ
እንደምነግሥ የነገረኝ ነቢይ አኪያ እነሆ፤
በዚያ ይገኛል። 3ስትሄጂም ዐሥር እንጀራ፣
ጥቂት ሙልሙል ዳቦ እና አንድ እንስራ
ማር ይዘሽ ሂጂ፤ እርሱም በልጁ ላይ የሚ
ደርሰውን ይነግርሻል።" 4ስለዚህ የኢዮር
ብዓም ሚስት ያላትን አድርጋ በሴሎ ወደ
ሚገኘው ወደ አኪያ ቤት ሄደች።
በዚህ ጊዜ አኪያ ከማርጀቱ የተነሣ ዐይ
ኖቹ ፈዘው ነበር። 5*እግዚአብሔር* ግን ለአ
ኪያ፣ "እነሆ፤ የኢዮርብዓም ሚስት ስለ ታመ
መው ልጇ ልትጠይቅህ ሌላ ሴት መስላ
ትመጣለችና እንዲህ ብለህ መልሳት" ብሎ
ነገረው።
6አኪያም የእግሯን ኰቴ ድምፅ እበሩ
ላይ እንደ ሰማ እንዲህ አላት፤ "የኢዮር
ብዓም ሚስት ሆይ ግቢ፤ ግን ለምንድን
ነው ሌላ ሴት መስለሽ ለመታየት የፈለግ
ሽው? ለአንቺ ከባድ ነገር እንድነግርሽ
ተልኬአለሁ። 7አሁንም ሂጂና ኢዮርብዓ
ምን የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር*
የሚለው ይህ ነው ብለሽ ንገሪው፤ 'ከሕዝቡ
መካከል አንሥቼ የሕዝቤ የእስራኤል መሪ
አደረግሁህ፤ 8ከዳዊት ቤት መንግሥቱን
ቀድጄ ለአንተ ሰጠሁህ፤ አንተ ግን በፊቴ
መልካም ነገር በማድረግ ብቻ ትእዛዜን
እንደ ጠበቀው፣ በፍጹም ልቡም እንደ ተከ
ተለኝ እንደ ባሪያዬ እንደ ዳዊት አልሆ
ንህም። 9ከአንተ በፊት ከነበሩት ሁሉ ይልቅ
አንተ የከፋ ሥራ ሠራህ፤ ለራስህም ከቀለጠ
ብረት ሌሎች አማልክትን ሠራህ፤ ቍጣዬን
አነሣሣህ፤ ወደ ኋላህም ጣልኸኝ።
10" 'ስለዚህ እኔም በኢዮርብዓም ቤት ላይ
ጥፋትን አመጣለሁ፤ ባሪያም ይሁን ነጻ ዜጋ
የኢዮርብዓምን ወንድ ልጅ ሁሉ ከእስራኤል
አስወግዳለሁ፤ ኩበትም ዐመድ እስኪሆን
ድረስ እንደሚቃጠል፣ እኔም የኢዮርብዓምን
ቤት እንዲሁ አቃጥላለሁ። 11ከኢዮርብዓም
ወገን በከተማ የሞተውን ውሾች፣ በባላገር
የሞተውን ደግሞ የሰማይ አሞሮች ይበሉ
ታል፤ *እግዚአብሔር* ተናግሮአልና!'
12"እንግዲህ አንቺም ወደ ቤትሽ ሂጂ፤
የምትኖሪበትን ከተማ እግርሽ እንደ ረገጠ፣
ልጁ ይሞታል፤ 13እስራኤልም ሁሉ አልቅ
ሰው ይቀብሩታል። የእስራኤል አምላክ *እግ
ዚአብሔር* ከኢዮርብዓም ቤት ሁሉ መል
ካም ነገር ያገኘበት እርሱ ብቻ ስለ ሆነ፣
በወግ በማዕረግ የሚቀበር እርሱ ብቻ
ነው።
14"ከዚህም በላይ፣ *እግዚአብሔር* የኢ
ዮር ብዓምን ቤተ ሰብ የሚያስወግድ
ንጉሥ በእስራኤል ላይ ለራሱ ያስነሣል፤

14፥3 1ሳሙ·9፥7
14፥6 1ሳሙ·28፥12
14፥7 1ነገ11፥37፤
15፥29
14፥8 1ሳሙ·
15፥27፤2ሳሙ·8፥15፤
1ነገ3፥3፤15፥5፤2ነገ
14፥3፤15፥3፡34፤16፥2፤
18፥3፤20፥3፤22፥2
14፥9 ዘፀ20፥4፤
32፥4፤ዘዳ32፥16፤1ነገ1
6፥2፡30፡33፤21፥25፤2
ነገ21፥9፡11፤24፥3፤
2ዜና11፥15፤ነህ9፥26፤
መዝ50፥17፤78፥58፤ኤ
ር2፥27፤7፥18፤
8፥19፤32፥32፡33፤
44፥3፤ሕዝ8፥17፤
16፥26፤23፥35
14፥10 ዘዳ32፥36፤
ኢሱ23፥15፤1ሳሙ·
12፥25፤15፥26፤1ነገ
13፥34፤15፥29፤2ነገ
9፥89፤ሆሴ13፥11
14፥11 ዘፍ40፥19፤
ዘዳ28፥26፤1ነገ16፥4፤2
1፥24
14፥13 2ዜና
12፥12፤19፥3
14፥15 ዘዳ12፥3፤
29፥28፤2ዜና7፥20፤
ኤር44፥3
14፥16 1ነገ12፥30፤
15፥26
14፥17 ኢሱ12፥24፤
1ነገ15፥33
14፥21 1ነገ11፥1
14፥22 ዘዳ32፥21፤
2ነገ17፥19፤2ዜና12፥1
፤መዝ78፥58፤ኤር
44፥3፤1ቆሮ10፥22
14፥23 ዘፀ23፥24፤
ዘዳ12፥2፡3፤16፥22፤
ሕዝ6፥13፤ሆሴ10፥1፤
14፥24 ዘዳ23፥17፤
1ነገ11፥57፤2ነገ21፥2፤
ዕዝ9፥11፤ምሳ
21፥27፤ ኢሳ1፥13፤
ኤር16፥18፤32፥35፤
44፥4
14፥25 2ዜና12፥2
14፥26 2ሳሙ·8፥7፤
1ነገ15፥15፡18

ይህም ዛሬ፣ አሁኑኑ ይሆናል።[ቸ] 15*እግዚ
አብሔር* እስራኤልን በውሃ ውስጥ
እንደሚንቀጠቀጥ ሸንበቆ ያንቀጠቅጠ
ዋል፤ የአሼራን ምስል
ዐምድ[ኀ] በመሥራት *እግዚአብሔርን* ለቍጣ
ያነሣሡት ስለ ሆነ፣ *እግዚአብሔር* ለቀ
ድሞ አባቶቻቸው ከሰጣቸው ከዚህች ከመ
ልካሚቱ ምድር እስራኤልን ይነቅላቸዋል፤
ከወንዙም ማዶ[ነ] ይበትናቸዋል። 16ኢዮርብዓም
ኀጢአት ሠርቶ፣ እስራኤልንም እንዲሠሩ
በማድረጉ፣ *እግዚአብሔር* እስራኤልን ይተ
ዋቸዋል።
17የኢዮርብዓም ሚስትም ተነሥታ ወደ
ቴርሳ ሄደች፤ የቤቱን መድረክ ወዲያው
እንደ ተራመደች ልጁ ሞተ፤ 18ከዚያም
ቀበሩት፤ *እግዚአብሔር* በባሪያው በአኪያ
አማካይነት እንደ ተናገረ፣ እስራኤል ሁሉ
አለቀሱለት።
19የቀረው የኢዮርብዓም ታሪክ፣ ያደረገው
ጦርነትና አገዛዙም ሁሉ በእስራኤል ነገሥ
ታት ታሪክ ተጽፎአል። 20እርሱም ሃያ
ሁለት ዓመት ነግሦ ከአባቶቹ ጋር አንቀ
ላፉ፤ ልጁ ናዳብም በእግሩ ተተክቶ ነገ
ሠ።

## የይሁዳ ንጉሥ ሮብዓም

14፥21:25-31 ተጓ ምብ - 2ዜና 12፥9-16

21የሰሎሞን ልጅ ሮብዓም በይሁዳ ነገ
ሠ፤ በነገሠም ጊዜ ዕድሜው አርባ አንድ ዓ
መት ነበር፤ እርሱም *እግዚአብሔር* ለስሙ
መጠሪያ እንድትሆን ከእስራኤል ነገድ ሁሉ
በመ ረጣት በኢየሩሳሌም ዐሥራ ሰባት ዓ
መት ገዛ። እናቱ ናዕማ የተባለች
አሞናዊት ነበረች።
22ይሁዳ *በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ ነገር
አደረገ፤ ከአባቶቻቸው ይልቅ እነርሱ በሠሩት
ኀጢአት ይበልጥ የቅናት ቍጣውን አነሣ
ሡ፤ 23እንዲሁም በእያንዳንዱ ኰረብታና
በየት ልልቁ ዛፍ ጥላ ሥር የማምለኪያ
ኰረብ ቶችን አዕማደ ጣዖታት፣ የአሼራን
ምስል
ዐምድ ለራሳቸው አቆሙ። 24ከዚያም ይልቅ፣
የቤተ ጣዖት ወንደቃዎች በምድሪቱ ላይ
ነበሩ፤ *እግዚአብሔር* ከእስራኤላውያን ፊት
አሳዶ ያስወጣቸው አሕዛብ የፈጸሙትን አስ
ጸያፊ ድርጊት ሁሉ እነዚህም ፈጸሙ።
25ሮብዓም በነገሠ በአምስተኛው ዓመት
የግብፅ ንጉሥ ሺሻቅ በኢየሩሳሌም ላይ
አደጋ ጣለ፤ 26*የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደ
ስና የቤተ መንግሥቱን ሀብት ወሰደ፤ ሰሎ
ሞን ያሠራቸው የወርቅ ጋሻዎች እንኳን

[ቸ]14 በዕብራይስጡ የዚህ ዐረፍተ ነገር ትርጒም በትክክል አይታወቅም
[ኀ]15 በዚህም ሆነ በሌሎቹም የመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ክፍሎች፣ የአሼራ ጣዖት አምላክ ምስል ነው
[ነ]15 የኤፍራጥስ ወንዝ ነው

ሳይቀሩ ሁሉንም ነገር አጋዘ። 27ስለዚህ ንጉሥ
ሮብዓም እነዚህን ለመተካት ሲል፣ የናስ
ጋሻዎች አሠርቶ የቤተ መንግሥቱን በር
የሚጠብቁት ዘበኞች አዛዦች እንዲይዙ
አደረገ። 28ንጉሡ ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስ በሚሄድበት ጊዜ ሁሉ፣ ዘቦቹ
ጋሻዎቹን ያነግባሉ፤ ከዚያም በዘብ ጥበ
ቃው ክፍል መልሰው ያስቀምጡ ነበር።
29የቀረው የሮብዓም አገዛዝ፣ ያደረገ
ውም ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ
የሚገኝ አይደለምን? 30በሮብዓምና በኢዮር
ብዓም መካከል ያላቋረጠ ጦርነት ተደርጎ
ነበር። 31ሮብዓምም ከአባቶቹ ጋር አንቀ
ላፋ፤ እነርሱ በተቀበሩበትም በዳዊት ከተማ
ተቀበረ። እናቱ ናዓማ የተባለች አሞና
ዊት ነበረች። ልጁ አብያም[ኘ] በእግሩ ተተ
ክቶ ነገሠ።

### የይሁዳ ንጉሥ አብያ

15፥12:6-8 ተጓ ምብ - 2ዜና 13፥1-2:22-14፥1

15 የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም በነገሠ
በዐሥራ ስምንተኛው ዓመት አብያ[ኣ]
በይሁዳ ነገሠ፤ 2በኢየሩሳሌም ሆኖ ሦስት
ዓመት ገዛ፤ እናቱ መዓካ የተባለች የአቤ
ሴሎም ልጅ ነበረች።
3እርሱም አባቱ ከእርሱ በፊት የሠራ
ውን ኀጢአት ሁሉ ሠራ፤ እንደ አባቱ
እንደ ዳዊትም በፍጹም ልቡ በታማኝነት
*ለእግዚአብሔር* አልተገዛም። 4ነገር ግን
ከእርሱ ቀጥሎ እንዲነግሥና ኢየሩሳሌምን
እንዲያጸናት፣ አምላክ *እግዚአብሔር* ስለ
ዳዊት ሲል በኢየሩሳሌም መብራት ሰጠው።
5ዳዊት በኬጢያዊው በኦርዮ ላይ ካደረሰው
በደል በቀር፣ *በእግዚአብሔር* ፊት ትክ
ክል የሆነውን ነገር አድርጓል፤ በሕይወት
ዘመኑም ሁሉ *ከእግዚአብሔር* ትእዛዝ
ፈቀቅ ያለበት ጊዜ አልነበረም።
6አብያም[ከ] በሕይወት በነበረበት ዘመን ሁሉ
በሮብዓምና በኢዮርብዓም መካከል ጦርነት
ነበር። 7ሌላው አብያ በዘመኑ የፈጸመውና
ያደረገው ሁሉ፣ በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ
ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን? በአብያና በኢ
ዮርብዓም መካከልም ጦርነት ነበር። 8አብ
ያም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በዳዊትም ከተማ
ተቀበረ። ልጁም አሳ በእግሩ ተተክቶ ነገ
ሠ።

### የይሁዳ ንጉሥ አሳ

15፥9-22 ተጓ ምብ - 2ዜና 14፥2-3፤ 15፥16-16፥6
15፥23-24 ተጓ ምብ - 2ዜና 16፥11-17፥1

9የእስራኤል ንጉሥ ኢዮርብዓም በነገሠ
በሃያኛው ዓመት፣ አሳ የይሁዳ ንጉሥ
ሆነ፤ 10በኢየሩሳሌምም አርባ አንድ ዓመት
ነገሠ፤ አያቱ መዓካ ትባላለች፤ እርሷም
የአቤሴሎም ልጅ ነበረች።

11አሳ አባቱ ዳዊት እንዳደረገው ሁሉ፣
*በእግዚአብሔር* ፊት መልካም የሆነውን
ነገር አደረገ። 12የቤተ ጣዖት ወንደቃዎ
ችን ከምድሪቱ አባረረ፤ አባቶቹ የሠሯቸ
ውን ጣዖታት ሁሉ አስወገደ። 13አስ
ጸያፊውን የአሼራ ምስል ዐምድ በማቆሟ፣
አያቱን መዓካን ከእቴጌነቷ ሻራት፤
ጣዖቷንም ሰባ ብሮ በቄድሮን ሸለቆ አቃጠ
ለው። 14አሳ የማ ምለኪያ ኰረብታዎችን
ፈጽሞ ባያስወግ ድም እንኳ በሕይወት
ዘመኑ ሁሉ፣ ልቡ *ለእግዚአብሔር* የተገዛ
ነበር። 15አባቱና እርሱ *ለእግዚአብሔር*
የቀደሱትን ብርና ወርቅ እንዲ
ሁም ዕቃዎችን አምጥቶ ወደ *እግዚአብሔር*
ቤት አስገባ።
16አሳና የእስራኤል ንጉሥ ባኦስ ዘመነ
መንግሥታቸውን ያሳለፉት፣ እርስ በርስ
በመዋጋት ነበር። 17የእስራኤል ንጉሥ
ባኦስ ይሁዳን ለመውጋት ወጣ፤ ከዚያም ወደ
ይሁዳ ንጉሥ ወደ አሳ ግዛት ማንም እንዳ
ይገባና እንዳይወጣ ለመቈጣጠር ራማን
ምሽግ አድርጎ ሠራት።
18አሳም *በእግዚአብሔር* ቤትና በቤተ
መንግሥቱ ግምጃ ቤት የቀረውን ብርና
ወርቅ በሙሉ ወሰደ፤ ከዚያም በታማኝ ሹማ
ምቱ እጅ በደማስቆ ይገዛ ለነበረው፣ ለጠብ
ሪሞን ልጅ፣ የአዚን የልጅ ልጅ ለሆነው
ለሶርያ ንጉሥ ለቤን ሀዳድ ላከው። 19እን
ዲህም አለ፤ "በአባቴና በአባትህ መካከል
የስምምነት ውል እንደ ነበረ ሁሉ፣ አሁ
ንም በእኔና በአንተ መካከል ይኑር፤ እነሆ፣
የብርና የወርቅ ገጸ በረከት ልኬልሃለሁ።
አሁንም የእስራኤል ንጉሥ ባኦስ ወደ
መጣበት እንዲመለስ፣ ሄደህ ከእርሱ ጋር
ያደረግኸውን የስምምነት ውል አፍርስ።"
20ቤን ሀዳድም የንጉሥ አሳን ሐሳብ
ተቀብሎ፣ የጦር አዛዦቹን በእስራኤል
ከተሞች ላይ አዘመተ፤ ዒዮንን፣ ዳንን፣
አቤልቤት ማዕካን እንዲሁም ንፍታሌምን
ጨምሮ ጌንሳሬጥን በሙሉ ድል አደረገ።
21ባኦስም ይህን ሲሰማ፣ በራማ የጀመረውን
የምሽግ ሥራ አቁሞ ወደ ቴርሳ ተመ
ለሰ። 22ንጉሥ አሳ አንድም ሰው እንዳይቀር
በይሁዳ ሁሉ ዐዋጅ አስነገረ፤ ከዚ
ያም
ሕዝቡ ባኦስ በራማ አስቀምጦት የነበረውን
ድንጋይና ዕንጨት አጋዘ፤ ንጉሡም በዚሁ
ምጽጳንና በብንያም ውስጥ ጌባን ሠራ።

14፥27 1ነገ11፥5
14፥30 2ሳሙ3፥1፤ 1ነገ12፥21
14፥31 1ነገ11፥1
15፥2 ቀኍ10፡13፤ 2ዜና11፥20
15፥3 1ነገ8፥61
15፥4 2ሳሙ21፥17
15፥5 ዘጸ5፥32፤ 2ሳሙ11፥2-7፤12፥9፤ 1ነገ9፥4
15፥6 ቀኍ16፡32፤ 1ነገ12፥21፤2ዜና 16፥9
15፥10 ቀኍ2
15፥11 1ነገ9፥4
15፥12 ነገ14፥24፤ 2ዜና15፥8
15፥13 ቀኍ2፤ዘፀ 34፥13፤1ነገ2፥19
15፥14 1ነገ8፥61፤ 2ዜና14፥5፤17፥6
15፥15 2ሳሙ8፥11
15፥16 ቀኍ6፤ 1ነገ12፥21
15፥17 ኢሱ18፥25
15፥18 ቀኍ18-20፤ 1ነገ14፥26፤20፥1፤ 2ነገ6፥24፤12፥18፤ 13፥3፤16፥8፤18፥14-16፥15፤ኤር49፥27፤ ኢል3፥5
15፥19 ዘፀ23፥32፤ 1ነገ5፥12
15፥20 1ነገ20፥34
15፥21 ኢሱ18፥25፤ 1ነገ16፥15-17
15፥22 ቀኍ924፤ ኢሱ11፥3፤18፥24፤ 2ነገ23፥8፤ኤር41፥9

[ኘ]31 አንዳንድ የዕብራይስጥና የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ትርጕሞች ግን፣ ***አቢጃም*** ይላሉ
[ኣ]1 በዚህ ስፍራና በቍ 7 እና 8 ላይ እንዳንድ የዕብራይስጥና የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አብዛኞቹ የዕብርይስጥ ትርጕሞች ግን፤ ***አቢጃም*** ይላሉ
[ከ]6 አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ አንዳንድ የዕብራይስጥና የሱርስት ትርጕሞች ግን፣ ***አቢጃም*** ይላሉ

23በአሳ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው
ሌላው ነገር በሙሉ፣ ያደረገውም ሁሉና የ
ሠ ራቸውም ከተሞች በይሁዳ ነገሥታት
ታሪክ ተጽፈው የሚገኙ አይደሉምን?
ንጉሥ አሳ በሸመገለ ጊዜ ግን እግሮቹ
ታመሙ:: 24አሳ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤
እነርሱ በተቀበሩበትም በአባቱ በዳዊት ከተ
ማ ተቀበረ፤ ልጁ ኢዮሣፍጥም በእግሩ
ተተ ክቶ ነገሠ::

## የእስራኤል ንጉሥ ናዳብ

25በይሁዳ ንጉሥ በአሳ ዘመነ
መንግሥት በሁለተኛው ዓመት የኢዮርብዓም
ልጅ ናዳብ በእስራኤል ላይ ነገሠ፤ ሁለት ዓ
መትም ገዛ:: 26እርሱም በአባቱ መንገድ
በመሄድ፣ አባቱ የሠራውንና እስራኤልም
እንዲሠሩ ያደረገውን ኀጢአት በመሥራ
ት በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ድርጊት ፈ
ጸመ::
27ናዳብና መላው እስራኤል በፍልስጥ
ኤም የምትገኘውን የገባቶንን ከተማ ከበው
ሳሉ፣ ከይሳኮር ነገድ የተወለደው የአኪያ
ልጅ ባኦስ ዐምፆ በመነሣት ናዳብን በገባ
ቶን ገደለው:: 28ባኦስ ናዳብን የገደለውና
በእግሩ ተተክቶ የነገሠው፣ የይሁዳ ንጉሥ
አሳ በነገሠ በሦስተኛው ዓመት ነው::
29ወዲያውኑ እንደ ነገሠም የኢዮርብዓምን
ቤተ ሰብ በሙሉ ፈጀ:: እግዚአብሔር
በሴሎናዊው ባሪያው በአኪያ በኩል እንደ
ተናገረው፣ ከኢዮርብዓም ቤተ ሰብ አን
ድም ሰው በሕይወት ሳያስቀር፣ ሁሉንም
አጠፋቸው፤ 30ይህም የሆነው ኢዮርብዓም
በሠራው ኀጢአትና እስራኤልም እንዲሠሩ
በማድረጉ ምክንያት፣ የእስራኤል አምላክ
እግዚአብሔርን ለቍጣ በማነሣሣቱ ነው::
31ሌላው በናዳብ ዘመነ መንግሥት የተ
ከናወነው፣ እርሱም ያደረገው ሁሉ በእስራ
ኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይ
ደለምን? 32አሳና የእስራኤል ንጉሥ ባኦስ
ዘመነ መንግሥታቸውን ያሳለፉት እርስ
በርስ በመዋጋት ነበር::

## የእስራኤል ንጉሥ ባኦስ

33የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሦስተኛው
ዓመት የአኪያ ልጅ ባኦስ በቴርሳ ከተማ፣
በእስራኤል ሁሉ ላይ ነገሠ፤ ሃያ አራት ዓመ
ትም ገዛ:: 34በኢዮርብዓም መንገድ በመሄ
ድና እስራኤልም እንዲሠሩ ያደረገውን ኀጠ
አት በመፈጸም በእግዚአብሔር ፊት
ክፉ ሥራ ሠራ::

16 ከዚያም የእግዚአብሔር ቃል በባ
ኦስ ላይ እንዲህ ሲል ወደ አናኒ
ልጅ ወደ ኢዩ መጣ፤ 2“ከትቢያ አን
ሥቼ፣ የሕዝቤ የእስራኤል መሪ አደረግ
ሁህ፤ አንተ ግን በኢዮርብዓም መንገድ
ሄድህ፤ ሕዝቤ እስራኤል ኀጢአት እንዲሠራ፣
በኀጢአቱም ለቍጣ እንዲያነሣሣኝ አሳሳ
ትኸው:: 3ስለዚህ ባኦስንና ቤቱን ፈጽሜ
አጠፋለሁ፤ ቤትህንም እንደ ናባጥ ልጅ
እንደ ኢዮርብዓም ቤት አደርገዋለሁ::
4በከተማዪቱ ውስጥ የሚሞቱትን የባኦስን
ወገኖች ሁሉ ውሾች ይበሏቸዋል፤ በገጠር
የሚሞቱትንም ሁሉ የሰማይ አሞሮች
ይቀራመቷቸዋል::”
5በባኦስ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው፣
ሌላው ያደረገው ሥራው በሙሉ በእስራኤል
ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
6ባኦስ፣ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በቴርሳም
ተቀበረ:: ልጁም ኤላ በእግሩ ተተክቶ ነገ
ሠ::
7ከዚህም በቀር የእግዚአብሔር ቃል በነ
ቢዩ ኢዩ አማካይነት በባኦስና በቤቱ ላይ
የመጣበት ምክንያት፣ በእጁ ሥራ ያስቈጣው
ዘንድ እንደ ኢዮርብዓም ቤት ሁሉ
በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራን ሁሉ በ
ማድረጉና ኢዮርብዓምን በማጥፋቱም
ጭምር ነው::

## የእስራኤል ንጉሥ ኤላ

8የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሃያ ስድስ
ተኛው ዓመት የባኦስ ልጅ ኤላ በእስራ
ኤል ላይ ነገሠ፤ በቴርሳ ተቀምጦም ሁለት
ዓመት ገዛ::
9ከሹማምቱ አንዱና የግማሽ ሠረገሎቹ
አዛዥ የሆነው ዘምሪ ዐምፆ ተነሣበት፤ በዚ
ያን ጊዜ ኤላ በቴርሳ ከተማ የቤተ መንግ
ሥቱ ኀላፊ በሆነው በአርጻ ቤት ጠጥቶ
ሰክሮ ነበር፤ 10ዘምሪም ገብቶ ኤላን ገደ
ለው፤ እርሱም በኤላ እግር ተተክቶ፣ የይ
ሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሃያ ሰባተኛው
ዓመት ነገሠ::
11ዘምሪ ወዲያው እንደ ነገሠና በዙፋን
እንደ ተቀመጠ፣ የባኦስን ቤተ ሰብ በሙሉ
ገደለ፤ የሥጋ ዘመድም ሆነ ወዳጅ አን
ድም ወንድ አላስቀረም:: 12በዚህ ሁኔታም
በነቢዩ በኢዩ አማካይነት በባኦስ ላይ
በተነገረው በእግዚአብሔር ቃል መሠረት፣
የባኦስን ቤተ ሰብ ሁሉ ፈጀ::
13ይህም የሆነው ባኦስና ልጁ ኤላ፣ በማ
ይረቡ ጣዖቶቻቸው ምክንያት የእስራ
ኤልን አምላክ እግዚአብሔርን ያስቈጡት
ዘንድ በሠሩት ኀጢአት ሁሉና፣ እስራኤ
ልም እንዲሠሩ በማድረጉ ነበር::
14ሌላው ኤላ በዘመኑ የፈጸመውና ያደ
ረገው ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ
ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?

15፥24 ማቴ1፥8
15፥26 ዘዳ4፥25፤ 1ነገ12፥30
15፥27 ኢሱ19፥44፤ 1ነገ14፥14
15፥29 1ነገ13፥34
15፥30 1ነገ12፥30፤16፥26፤2ነገ3፥3፤14፥24፤15፥28፤21፥16
15፥31 1ነገ11፥41
15፥32 ቍ6
15፥33 1ነገ14፥17፤16፥6፡23፤ 2ነገ15፥14፤ማሕ6፥4
15፥34 ቍ26
16፥1 ቍ7፤2ዜና 16፥7፤19፥2፤20፥34
16፥2 1ሳሙ2፥8፤ 1ነገ12፥30፤14፥79
16፥3 ቍ11፤ 1ነገ21፥22፤2ነገ9፥9
16፥4 ዘፍ40፥19፤ 1ነገ14፥11
16፥5 1ነገ15፥31
16፥6 1ነገ15፥33
16፥7 ቍ1፤ 1ነገ6፥11
16፥9 1ነገ18፥3፤ 1ነገ20፥12፡16፤ ምሳ31፥45
16፥10 2ነገ9፥31
16፥11 ቍ3
16፥13 ዘዳ32፥21

ኸ24 70 ኪሎ ግራም ያህል ነው

## የእስራኤል ንጉሥ ዘምሪ

15የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሃያ ሰባተ
ኛው ዓመት ዘምሪ በቴርሳ ሆኖ ሰባት
ቀን ብቻ ገዛ:: በዚህ ጊዜ ሰራዊቱ የፍል
ስጥኤማውያን ከተማ የሆነችውን ገባቶንን
ከቦ ሰፍሮ ነበር:: 16በዚያም ሰፈር የነበሩ
እስራኤላውያን ዘምሪ ዐምፆ ንጉሡን
መግደሉን እንደ ሰሙ፣ የሰራዊቱን አዛዥ
ዖምሪን በዚያኑ ዕለት እዚያው ሰፈር
ውስጥ በእስራኤል ላይ ማንገሣቸውን ዐወጁ::
17ከዚያም ዖምሪና አብረውት ያሉት እስራ
ኤላውያን ሁሉ ከገባቶን ወደ ላይ ወጥ
ተው ቴርሳን ከበቡ:: 18ዘምሪ ከተማዪቱ
መያዟን ሲያይ፣ ቤተ መንግሥቱ ውስጥ
ወዳለው ግንብ ገብቶ በቤተ መንግሥቱ ላይ
እሳት ለቀቀበትና በዚሁ ሞተ:: 19ይህ
የሆነውም *በእግዚአብሔር ፊት* የተጠላ ክፉ
ሥራ በመሥራትና በኢዮርብዓም መን
ገድ በመሄድ፣ እንዲሁም ራሱ በሠራው
ኀጢአትና እስራኤልም እንዲሠሩ ባደረ
ገው ኀጢአት ምክንያት ነው::
20ሌላው ዘምሪ በዘመኑ የፈጸመው ድር
ጊትና ያካሄደውም ዐመፅ በእስራኤል ነገ
ሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አደለምን?

## የእስራኤል ነጉሥ ዖምሪ

21ከዚያም የእስራኤል ሕዝብ ከሁለት ተከ
ፈለ፣ ይህም ግማሹ የጎናትን ልጅ ታምኒን
ለማንገሥ ሲሆን፣ የቀረው ደግሞ ዖምሪን
በመደገፍ ነበር:: 22ሆኖም የዖምሪ ተከታዮች
ከጎናት ልጅ ከታምኒ ተከታዮች ይልቅ በረቱ፤
ስለዚህ ታምኒ ሞተ፤ ዖምሪም ነገሠ::
23የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሠላሳ አን
ደኛው ዓመት፣ ዖምሪ በእስራኤል ላይ ነገሠ፤
ዐሥራ ሁለት ዓመትም ገዛ፤ ከዚህም
ውስጥ ስድስቱን ዓመት የገዛው በቴርሳ ሆኖ
ነው:: 24እርሱም የሰማርያን ኰረብታ
በሁለት መክሊት[ኸ] ጥሬ ብር ከሳምር ላይ
ገዝቶ ከተማ ሠራባት፤ ስሟንም በቀድሞው
የተራራዋ ባለ ቤት በሳምር ስም ሰማርያ
ብሎ ጠራት::
25ይሁን እንጂ ዖምሪ *በእግዚአብሔር ፊት*
ክፉ ድርጊት ፈጸመ፤ ከእርሱ አስቀድሞ
ከነበሩትም ይልቅ የበለጠ ኀጢአት ሠራ::
26እርሱም እስራኤል በማይረቡ ጣዖቶቻቸው፣
የእስራኤልን አምላክ *እግዚአብሔርን* ለቍጣ
እንዲያነሣሡት ባደረገው በናባጥ ልጅ
በኢዮርብዓም መንገድ ሁሉና እርሱም
ኀጢአት ሠርቶ እስራኤልም እንዲሠሩ ባደ
ረገው ኀጢአት ተመላለሰ::
27ሌላው ዖምሪ በዘመኑ የፈጸመው፣ ያደ
ረገውና ያከናወነው ሁሉ በእስራኤል የነገ
ሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለ
ምን? 28ዖምሪ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤
በሰማርያም ተቀበረ፤ ልጁም አክዓብ በእ
ግሩ ተተክቶ ነገሠ::

## አክዓብ የእስራኤል ንጉሥ ሆነ

29የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሠላሳ
ስምንተኛው ዓመት፣ የዖምሪ ልጅ አክዓብ
በእስራኤል ላይ ነገሠ፣ በሰማርያም ሆኖ
እስራኤልን ሃያ ሁለት ዓመት ገዛ::
30የዖምሪ ልጅ አክዓብ ከእርሱ አስቀድሞ
ከነበሩት ሁሉ ይልቅ፣ *በእግዚአብሔር ፊት*
ክፉ ነገር አደረገ:: 31የናባጥን ልጅ የኢ
ዮርብዓምን ኀጢአት እንደ ቀላል ነገር
ከመቍጠሩም በላይ የሲዶናውያንን ንጉሥ
የኤትበኣልን ልጅ ኤልዛቤልን አገባ፤ ሄዶም
በኣልን አመለከ፤ ሰገደለትም:: 32ሰማርያ ላይ
በሠራውም የበኣል ቤተ ጣዖት ለበኣል መሠ
ዊያ አቆመለት:: 33ደግሞም አክዓብ
የአሼራን ምስል ዐምድ በማቆም ከእርሱ
በፊት ከነበሩት የእስራኤል ነገሥታት
ይልቅ የእስራኤልን አምላክ *እግዚአብሐ
ሔርን* ለቍጣ የሚያነሣሣ ድርጊት ፈጸመ::
34የቤቴል ሰው አኪኤል፣ በአክዓብ ዘመን
ኢያሪኮን መልሶ ሠራት:: *እግዚአብሔር*
በነዌ ልጅ በኢያሱ አማካይነት የተናገረው
ቃል ይፈጸም ዘንድ መሠረቷን ሲያኖር
በኵር ልጁ አቢሮን ሞተ፤ የቅጽር በሮቿ
ንም በሚሠራበት ጊዜ የመጨረሻው ልጁ
ሠጉብ ሞተ::

## ኤልያስን ቍራዎች መገቡት

17 በዚህ ጊዜ ከገለዓድ ነዋሪዎች
አንዱ የሆነው ቴስብያዊው ኤል
ያስ አክዓብን፣ "የማመልከው ሕያው *እግዚ
አብሔርን፣* በእኔ ቃል ካልሆነ በቀር፣ በሚቀ
ጥሉት ዓመታት ዝናብ ወይም ጠል አይ
ኖርም" አለው::
2ከዚያም እንዲህ የሚል *የእግዚአብሔር*
ቃል ለኤልያስ መጣለት፤ 3"ከዚህ ተነሥ
ተህ ወደ ምሥራቅ ሂድ፤ ከዮርዳኖስ
በስተ ምሥራቅ ባለው በኮራት ወንዝ
ተሸሸግ:: 4ውሃ ከወንዙ ትጠጣለህ፤ ቍራ
ዎችም እዚያው እንዲመግቡህ አዝዣለሁ::"
5ስለዚህ *እግዚአብሔር* ያዘዘውን ፈጸመ፤
ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ወዳለው
ወደ ኮራት ወንዝ ሄዶ በዚያ ተቀመጠ::
6ቍራዎችም ጧትና ማታ እንጀራና ሥጋ
ያመጡለት ነበር፤ ውሃም ከወንዙ ይጠጣ
ነበር::

## የሰራፕታዪቱ መበለት

7በምድሪቱ ላይ ዝናብ ባለመጣሉ ከጥቂት
ጊዜ በኋላ ወንዙ ደረቀ:: 8ከዚያም እንዲህ

16፥15 ኢሱ19፥44
16፥23 ኢሱ12፥24፤ 1ነገ15፥33
16፥24 1ነገ13፥32፤ ማቴ10፥5
16፥25 ዑ25-26፤ ዘዳ4፥25ሚክ6፥16
16፥26 ዘዳ32፥21፤ 1ነገ15፥30
16፥28 1ነገ13፥32
16፥30 1ነገ14፥9
16፥31 መሳ2፥11፤ 3፥6፤1ነገ11፥2ነገ 9፥34
16፥32 መሳ6፥28፤ 2ነገ10፥27፤11፥18፤ ኤር43፥12
16፥33 መሳ3፥7፤ 1ነገ14፥9፤21፥25፤ 2ነገ13፥6
16፥34 ኢሱ6፥26
17፥1 ዘዳ11፥17፤ 28፥24፤መሳ12፥4፤ 2ሳሙ1፥21፤1ነገ8፥36 ፤ኢዮ12፥15ሚል4፥5፤ ማቴ11፥14፤17፥3፤ ሉቃ4፥25
17፥3 1ነገ18፥4፡ 10፤ኤር36፥19፥26
17፥4 ዘፍ8፥7

የሚል የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤልያስ
መጣ፤ 9“ተነሥና ሲዶና ውስጥ ወዳለችው
ወደ ሰራፕታ ሄደህ ተቀመጥ፤ በዚያም
አንዲት መበለት እንድትመግብህ አዝዣ
ለሁ።” 10ስለዚህ ተነሥቶ ወደ ሰራፕታ
ሄደ። ወደ ከተማዪቱ በር እንደ ደረሰም፣
አንዲት መበለት ጭራሮ ስትለቃቅም አገ
ኛት፤ ጠርቶም፣ “የምጠጣው ውሃ በዕቃ
ታመጪልኛለሽን?” ሲል ለመናት። 11ልታ
መጣለት ስትሄድ አሁንም ጠራትና፣ “እባ
ክሽን፣ ቍራሽ እንጀራም ይዘሽልኝ ነይ”
አላት።
12እርሷም መልሳ፣ “አምላክህን ሕያው እግ
ዚአብሔርን! በማድጋ ካለው ዕፍኝ ዱቄ
ትና በማሰሮ ካለው ጥቂት ዘይት በቀር
ምንም የለኝም። እነሆ፤ ለራሴና ለልጄ ምግብ
አዘጋጅቼ በልተን እንድንሞት ጭራሮ
ለቃቅሜ ወደ ቤት ልወስድ ነው” አለ
ችው።
13ኤልያስም መልሶ እንዲህ አላት፤ “አይ
ዞሽ አትፍሪ፤ ወደ ቤት ገብተሽ እንዳል
ሽው አድርጊ፤ በመጀመሪያ ግን ከዚያ
ችው ካለችሽ ትንሽ እንጎቻ ጋግረሽ አም
ጪልኝ፤ ከዚያም ለራስሽና ለልጅሽ ጋግሪ፤
14የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲ
ህ ይላል፤ ‘እግዚአብሔር ለምድሪቱ ዝናብ
እስከሚሰጥበት ዕለት ድረስ፤ ከማድጋው
ዱቄት አይጠፋም፤ ከማሰሮውም ዘይት አያ
ልቅም።’ ”
15እርሷም ሄዳ ኤልያስ እንደ ነገራት
አደረገች፤ በዚህ ሁኔታም ኤልያስ፣ መበ
ለቲቱና ቤተ ሰቧ ብዙ ቀን ተመገቡ፤
16በኤልያስ በተነገረው የእግዚአብሔር ቃል
መሠረት ከማድጋው ዱቄት አልጠፋም፤
ከማሰሮውም ዘይት አላለቀም ነበርና።
17ከጥቂት ጊዜ በኋላም የባለቤቲቱ ልጅ
ታመመ፤ ሕመሙ እየጠናበት ሄደ፣ በመ
ጨረሻም ትንፋሹ ቀጥ አለ። 18እርሷም ኤል
ያስን፤ “የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፤ እኔ ምን
አደረግሁህ? እዚህ የመጣኸው ኀጢአቴን
አስታውሰህ ልጄን ለመግደል ነውን?” አለ
ችው።
19ኤልያስም መልሶ፣ “ልጅሽን ስጪኝ”
አላት፤ ልጁንም ከዕቅፏ ወስዶ እርሱ ወደ
ሚኖርበት ሰገነት በማውጣት በዐልጋው
ላይ አስተኛው። 20ከዚያም፣ “አምላኬ
እግዚአብሔር ሆይ፤ ልጇን እንዲሞት በማ
ድረግ ተቀብላ በምታስተናግደኝ በዚህች
መበለት ላይም መከራ ታመጣባታለህን?”
ብሎ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ። 21በልጁም
ላይ ሦስት ጊዜ ተዘርግቶ፣ “አምላኬ እግዚ
አብሔር ሆይ፤ የዚህ ልጅ ነፍስ ትመለስ

17፥6 ዘፀ16፥8
17፥9 አብ1፥20፤ ሉቃ4፥26
17፥10 ዘፍ24፥17፤ ዮሐ4፥7
17፥12 2ነገ4፥2
17፥14 ቍ1
17፥18 ሉቃ5፥8
17፥20 2ነገ4፥33
17፥21 2ነገ4፥34፤ ሐሥ20፥10
17፥23 ዕብ11፥35
17፥24 ቍ18፤1ነገ 22፥16፤መዝ119፥43፤ ዮሐ16፥30፤17፥7
18፥1 ቍ15፤ዘዳ 28፥12፤1ነገ17፥1፤ ሉቃ4፥25
18፥2 ዘሌ26፥26
18፥3 1ነገ16፥9፤ ነህ7፥2
18፥4 1ነገ17፥3፤ 21፥23፤2ነገ9፥7፤ ኢሳ16፥3፤25፥4፤ 32፥2፤ኤር26፥24፤ አብ1፥14
18፥5 ዘፍ47፥4፤ ኤር14፥3
18፥7 2ነገ1፥8፤ ዘካ13፥4
18፥10 1ነገ17፥3

ለት” ብሎ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ።
22እግዚአብሔርም የኤልያስን ጩኸት ሰማ፤
የልጁም ነፍስ ተመለሰችለት፤ እርሱም ዳነ።
23ከዚያም ኤልያስ ልጁን አስነሥቶ ከሰገ
ነቱ ወደ ምድር ቤት አወረደው፤ ለእናቱም
ልጅሽ ይኸውልሽ፤ ድኖልሻል!” ብሎ ሰጣት።
24ከዚያም ሴቲቱ ኤልያስን፣ “አሁን የእ
ግዚአብሔር ሰው መሆንህን፣ ከአንደበትህም
የወጣው የእግዚአብሔር ቃል እውነት መሆ
ኑን ዐወቅሁ” አለችው።

## ኤልያስና አብድዩ

18 ከብዙ ጊዜ በኋላም በሦስተኛው
ዓመት እንዲህ የሚል የእግዚአብሔር
ቃል ለኤልያስ መጣለት፤ “ሄደህ ለአክዓብ
ተገለጥ፤ እኔም በምድሪቱ ላይ ዝናብ አዘ
ንባለሁ።” 2ስለዚህም ኤልያስ ራሱን በአ
ክዓብ ፊት ለመግለጥ ሄደ።
በዚህ ጊዜ ራብ በሰማርያ ክፉኛ ጸንቶ
ነበር። 3አክዓብም የቤተ መንግሥቱን አዛዥ
አብድዩን ጠራው፤ አብድዩም እግዚአብሔ
ርን በጣም የሚፈራ ሰው ነበር። 4ኤልዛ
ቤል የእግዚአብሔርን ነቢያት እያስገደ
ለች በነበረበት ጊዜ፣ አብድዩ መቶውን ነቢ
ያት ወስዶ አምሳ አምሳውን በሁለት ዋሻ
ውስጥ ሸሽጎ እንጀራና ውሃ ይሰጣቸው
ነበር። 5አክዓብም አብድዩን፣ “ተነሣና በአ
ገሪቱ ውስጥ ወዳሉት ምንጮችና ሸለቆ
ዎች ሂድ፤ ፈረሶቻችንና በቅሎዎቻችን
እንዳይሞቱ በሕይወት እንዲቈዩ ምናል
ባት ሣር እናገኝ ይሆናል።” አለው። 6ስለ
ዚህ የሚሄዱበትን ምድር ተከፋፈሉ፤ አክዓብ
በአንድ በኩል፣ አብድዩም በሌላ በኩል
ሄደ።
7አብድዩ በመንገድ ላይ ሳለም ኤል
ያስን አገኘው። አብድዩም ዐወቀው፤ ወደ
መሬት ለጥ ብሎ እጅ በመንሣት፣ “ጌታዬ
ኤልያስ ሆይ፤ በእርግጥ አንተ ነህን?”
አለው።
8እርሱም፣ “አዎን እኔ ነኝ፤ ሂድና ለጌ
ታህ፣ ‘ኤልያስ እዚሁ አለልህ’ ብለህ ንገ
ረው” ሲል መለሰለት።
9አብድዩም እንዲህ አለው፤ “ምነው ምን
አጠፋሁና ነው ባሪያህ እንዲሞት ለአክዓብ
አሳልፈህ የምትሰጠው? 10አምላክህን ሕ
ያው እግዚአብሔርን! ጌታዬ አንተን
ለመፈለግ መልእክተኛ ያላከበት ሕዝብና
መንግሥት የለም፤ የትኛውም ሕዝብ ሆነ
መንግሥት አንተ በዚያ አለመኖርህን
ባስታወቀው ጊዜ ሁሉ አንተን አለማግኘተ
ን ለማረጋገጥ ያስ ምለው ነበር። 11አሁን
ግን አንተ ወደ ጌታዬ ሂጄ፣ ‘ኤልያስ እዚ

ህ አለልህ’ እንድለው ትፈልጋለህ፤
12ተለይቼህ ስሄድ የእግዚአ ብሔር
መንፈስ የት እንደሚወስድህ አላ ውቅም፤
ታዲያ ሄጄ ለአክዓብ ከነገርሁት በኋላ
ሳያገኝህ ቢቀር እኔን ይገድለኛል፤ ነገር
ግን እኔ ባሪያህ ከጕልማሳነቴ ጀምሮ
እግዚአብሔርን አመልካለሁ። 13ጌታዬ ሆይ፤
ኤልዛቤል የእግዚአብሔርን ነቢያት ባሰገደ
ለች ጊዜ ምን እንዳደረግሁ አልሰማህምን?
መቶውን የእግዚአብሔር ነቢያት ወስጄ አምሳ
አምሳውን በሁለት ዋሻ በመሸሸግ እህልና
ውሃ ሰጠኋቸው። 14ታዲያ አንተ ሄጄ ለጌታዬ፤
‘ኤልያስ እዚህ አለልህ’ እንድለው ትፈል
ጋለህ፤ እርሱም ይገድለኛል!”
15ኤልያስም፣ “በፊቱ የቆምሁት ሁሉን
የሚገዛ ጌታ እግዚአብሔርን፣ ዛሬ አክዓብ
ፊት በእርግጥ እገለጣለሁ” አለ።

## ኤልያስ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ

16ስለዚህ አብድዩ ሄዶ ይህንኑ ለአክዓብ
ነገረው፤ አክዓብም ኤልያስን ለማግኘት ሄደ።
17ኤልያስንም ባየው ጊዜ፤ “እስራኤልን የም
ታውክ አንተ ነህን?’ አለው።
18ኤልያስም መልሶ እንዲህ አለ፤ “አን
ተና የአባትህ ቤት እንጂ እኔ እስራኤልን
አላወክሁም። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተዋ
ችሁ፣ እነ በኣልንም ተከተላችሁ። 19አሁ
ንም ሕዝቡ በቀርሜሎስ ተራራ እንዲገናኘኝ
ለመላው እስራኤል ጥሪ አድርግ። ኤልዛ
ቤል ማእድ የሚቀለቡትን አራት መቶ
አምሳውን የበኣል ነቢያት፣ አራት መቶ
ውንም የአሼራ ነቢያት አምጣቸው።”
20ስለዚህ አክዓብ በመላው እስራኤል
ጥሪ አደረገ፣ ነቢያቱንም በቀርሜሎስ ተራራ
ሰበሰበ። 21ኤልያስም በሕዝቡ ፊት ቀርቦ፣
“በሁለት ሐሳብ የምትዋልሉት እስከ መቼ
ድረስ ነው? አምላክ እግዚአብሔር ከሆነ
እግዚአብሔርን ተከተሉ፤ በኣል አምላክ
ከሆነም በኣልን ተከተሉ” አለ።
ሕዝቡ ግን አንዲት ቃል አልመለሱም።
22ከዚያም ኤልያስ እንዲህ አላቸው፤
“ከእግዚአብሔር ነቢያት የተረፍሁ እኔ ብቻ
ነኝ፤ በኣል ግን አራት መቶ አምሳ ነቢያት
አሉት። 23ሁለት ወይፈኖች ስጡን፤ እነ
ርሱም አንዱን መርጠው ይውሰዱ፤ በየብ
ልቱም ቈራርጠው፣ በዕንጨት ላይ ያኑሩት፤
ግን እሳት አያንድዱበት፤ እኔም ሁለተኛ
ውን ወይፈን አዘጋጃለሁ፤ በዕንጨትም
ላይ አኖረዋለሁ፤ እሳት አላነድበትም። 24ከዚያ
እናንተ የአምላካችሁን ስም ጥሩ፤ እኔም
የእግዚአብሔርን ስም እጠራለሁ፤ ሰምቶ
በእሳት የሚመልሰውም እርሱ እውነተኛ
አምላክ ነው።”
ከዚያም ሕዝቡ ሁሉ፣ “ያልኸው መልካም
ነው” አሉ።
25ኤልያስም ለበኣል ነቢያት፣ “እናንተ ብዙ
ስለ ሆናችሁ በመጀመሪያ አንዱን ወይፈን
መርጣችሁ አዘጋጁ፤ የአምላካችሁን ስም
ጥሩ፤ ግን እሳት አታንድዱበት”
አላቸው። 26ስለዚህ የተሰጣቸውን ወይፈን
ወስደው አዘ ጋጁት።
ከዚያም ከጧት እስከ እኩለ ቀን የበኣልን
ስም ጠሩ፤ “በኣል ሆይ ስማን” እያሉ ጮኹ
፤ ድምፅ ግን የለም፤ የሚመልስ
አልነበረም፤ በሠሩት መሠዊያ ዙሪያም
ጨፈሩ።
27እኩለ ቀንም ላይ ኤልያስ፣ “ድምፃች
ሁን ከፍ አድርጋችሁ ጩኹ እንጂ! አምላክ
አይደለም እንዴ! ምናልባት በሐሳብ ተውጦ
ወይም ሥራ በዝቶበት፣ አልያም በጕዞ
ላይ ይሆናል፤ ተኝቶም ከሆነ ቀስቅሱት”
እያለ ያፌዝባቸው ጀመር። 28ስለዚህ እየ
ጮኹ እንደ ልማዳቸው ደማቸው እስኪ
ፈስ ድረስ ሰውነታቸውን በሰይፍና በጩቤ
ያቈስሉ ነበር። 29እኩለ ቀን ዐለፈ፤
እነርሱም የሠርክ መሥዋዕት እስኪቀርብ
ድረስ እየተራወጡ ይዘላብዱ ነበር፤ አሁንም
ድምፅ የለም፤ የመለሰና ከቁም ነገር የቈጠ
ረውም አልነበረም።
30ከዚያም ኤልያስ ሕዝቡን በሙሉ፣ “ወደ
እኔ ቅረቡ” አላቸው፤ ሕዝቡም ሁሉ ወደ
እርሱ ቀረቡ፤ እርሱም ፈርሶ የነበረውን
የእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ። 31ከዚያም
ኤልያስ፣ “ስምህ እስራኤል ይባላል” ተብሎ
የእግዚአብሔር ቃል በመጣለት በያዕቆብ
ልጆች ነገድ ቍጥር ልክ ዐሥራ ሁለት
ድንጋይ ወስዶ፤ 32በድንጋዮቹም ለእግዚ
አብሔር ስም መሠዊያ ሠራ፤ በመሠዊ
ያውም ዙሪያ ዐሥራ አምስት ሊትር ውሃ[ሠ]
የሚይዝ ጕድጓድ ቈፈረ፤ 33ዕንጨቱን ረበ
ረበ፤ የወይፈኑንም ሥጋ በየብልቱ ከቈ
ረጠ በኋላ በዕንጨቱ ላይ አኖረው። ከዚ
ያም፣ “ውሃ በአራት ጋን ሞልታችሁ፣
በመሥዋዕቱና በዕንጨቱ ላይ አፍስሱ”
አላቸው።
34ደግሞም፣ “እንደ ገና ጨምሩበት”
አላቸው፤ እነርሱም ጨመሩበት።
“ሦስተኛም ጨምሩበት” ሲል አዘዛቸው፤
እነርሱም ለሦስተኛ ጊዜ ጨመሩበት።
35ውሃ ውም በመሠዊያው ዙሪያ ፈሰሰ፤
ጕድጓዱ ንም ሞላው።
36የሠርክ መሥዋዕት በሚቀርብበትም ጊ
ዜ ኤልያስ ወደ መሠዊያው ቀረብ ብሎ
እን ዲህ ሲል ጸለየ፤ “የአብርሃም፣ የይስሐ
ቅና

[ሠ]32 15 ሊትር ያህል ነው

18፥12 2ነገ2፥16፤ሕዝ3፥14፤ሐሥ8፥39
18፥15 ቍ1
18፥17 ኢሱ7፥25፤1ሳሙ14፥29፤1ነገ21፥20፤ኤር38፥4
18፥18 ዘዳ31፥16፤1ነገ16፥33፤21፥25
18፥19 ኢሱ19፥26፤2ነገ9፥22፤10፥19
18፥20 2ነገ2፥25፤4፥25
18፥21 ቍ39፤ኢሱ24፥15፤2ነገ17፥41፤መዝ100፥3፤118፥27፤119፥113፤ማቴ6፥24
18፥22 1ነገ19፥10፤ኤር2፥8፤23፥13
18፥24 ቍ38፤ዘፍ4፥26፤ዘፀ19፥18፤ዘሌ9፥24፤1ሳሙ7፥8
18፥26 መዝ115፥45፤135፥16፤ኢሳ41፥26፡28፤44፥17፤45፥20፤46፥7፤ኤር10፥5፤1ቆሮ8፥4፤12፥2
18፥27 ዕን2፥19
18፥28 ዘሌ19፥28
18፥29 ዘፀ29፥41፤2ነገ19፥12፤ኢሳ16፥12፤ኤር10፥5
18፥30 1ነገ19፥10
18፥31 ዘፍ17፥5፤2ነገ17፥34
18፥32 ዘዳ18፥7፤ቆላ3፥17
18፥33 ዘፍ22፥9
18፥36 ዘፍ24፥12፤ዘፀ4፥5፤29፥39፡41፤ዘኍ16፥28፤ኢሱ4፥24፤1ሳሙ17፥46፤መዝ46፥10፤ማቴ22፥32

የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ
የእስራኤል አምላክ መሆንህ፣ እኔም የአ
ንተ አገልጋይ መሆኔና ይህን ሁሉ በት
እዛዝህ እንዳደረግሁ ዛሬ ይታወቅ። 37ይህ
ሕዝብ፣ አንተ አምላክ እግዚአብሔር
እውነ ተኛ መሆንህንና ልባቸውን
የመለስኸው አንተ መሆንህን ያውቁ
ዘንድ እባክህ ስማኝ፤ እግዚአብሔር ሆይ፤
እባክህ መል ስልኝ።”
38ከዚያም የእግዚአብሔር እሳት ወርዳ
መሥዋዕቱን፣ ዕንጨቱን፣ ድንጋዩንና ዐፈሩን
ፈጽማ በላች፤ በጒድጓዱ ውስጥ ያለውንም
ውሃ ላሰች።
39ሕዝቡም ሁሉ ይህን ሲያዩ፣ በግንባራ
ቸው ተደፍተው፣ “አምላክ እግዚአብሔር እርሱ
እውነተኛ ነው! እግዚአብሔር እርሱ እው
ነተኛ አምላክ ነው!” አሉ።
40ከዚያም ኤልያስ፣ “የበአልን ነቢያት
ያዟቸው! አንድም ሰው እንዳያመልጥ” ሲል
አዘዘ፤ ሕዝቡም ያዟቸው፤ ኤልያስም ወደ
ቂሶን ወንዝ አውርዶ አሳረዳቸው።
41ኤልያስም አክዓብን፣ “የከባድ ዝናብ
ድምፅ ይሰማልና ሂድና ብላ፤ ጠጣም” አለው።
42ስለዚህ አክዓብ ሊበላና ሊጠጣ ሄደ፤
ኤልያስ ግን ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ጫፍ
ወጣ፤ ፊቱንም በጒልበቶቹ መካከል አድ
ርጎ ወደ መሬት አቀረቀረ።
43አገልጋዩንም፣ “ውጣና ወደ ባሕሩ ተመ
ልከት” አለው።
አገልጋዩም ሂዶ ተመለከተና፤ “በዚያ ምንም
የለም” አለው።
ኤልያስ ሰባት ጊዜ፣ “እንደ ገና ሂድ”
አለው።
44በሰባተኛው ጊዜ አገልጋዩ፣ “እነሆ፤
የሰው እጅ የምታህል ትንሽ ደመና ከባሕሩ
እየወጣች ነው” አለው።
ኤልያስም፣ “ሂድና አክዓብን፣ ‘ዝናቡ
ሳያግድህ፣ ሠረገላህን ጭነህ ውረድ’ ብለህ
ንገረው” አለው።
45ወዲያውኑም ሰማዩ በጥቁር ደመና
ተሸፈነ፤ ነፋሱ ነፈሰ፤ ከባድ ዝናብ ጣለ፤
አክዓብም በሠረገላ ተቀምጦ ወደ ኢይዝራ
ኤል ሄደ። 46የእግዚአብሔርም ኀይል በኤ
ልያስ ላይ ወረደ፤ ኤልያስም ልብሱን ከፍ
አድርጎ በቀበቶው ካጠበቀ በኋላ እስከ ኢይ
ዝራኤል ድረስ በአክዓብ ፊት ሮጠ።

### ኤልያስ ወደ ኮሬብ ኰበለለ

19 አክዓብ በዚህ ጊዜ፣ ኤልያስ ያደ
ረገውን በሙሉ፣ ነቢያቱንም ሁሉ
እንዴት በሰይፍ እንዳስገደላቸው ለኤልዛ
ቤል ነገራት። 2ስለዚህም እርሷ፣ “ነገ በዚህ

18፥37 ኢሱ4፥24
18፥38 ቊ24፤ዘፀ 19፥18፤ዘሌ9፥24፤2ነገ 1፥10፤1ዜና21፥26፤ 2ዜና7፥1፤ኢዮ1፥16
18፥39 ቊ21፤ዘሌ 9፥24፤መዝ46፥10
18፥40 ዘፀ22፥20፤ ዘዳ17፥12፤መሳ4፥7፤2 ነገ11፥18
18፥42 1ሳሙ 12፥ 17፤ያዕ5፥18
18፥44 ኢሱ6፥15፤ ሉቃ12፥54
18፥45 1ሳሙ 29፥1፤1ነገ8፥36፤ ኢዮ37፥13፤ሆሴ1፥4
18፥46 መሳ3፥10፤ 1ሳሙ11፥6፤2ነገ 4፥29፤9፥1፤ ሉቃ1፥35፤4፥14
19፥1 ዘፀ22፥20፤ 1ነገ16፥31
19፥2 ሩት1፥17፤ መዝ13፥4፤ኤር 20፥10፤26፥21፤ 36፥26
19፥3 ዘፍ19፥17፤ 31፥21፤ኢሱ19፥2
19፥4 ዘኍ11፥15፤ ኢዮ6፥9፤7፥16፤ 10፥1፤30፥4፤መዝ69፥1 9፤ኤር20፥18፤ ዮና4፥18
19፥5 ዘፍ16፥7፤ 28፥11
19፥8 ዘፀ3፥1፤ 24፥18፤ማቴ4፥2
19፥9 ዘፍ3፥9፤ ዘፀ33፥22
19፥10 ዘኍ25፥13፤ ዘዳ31፥16፤1ነገ18፥22፥ 30፤ኤር5፥11፤9፥2፤ሐ ሥ22፥3፤ሮሜ 11፥13፤ገላ4፥18
19፥11 ዘፀ14፥21፤ 33፥19፤34፥2፤2ነገ 2፥1፤ናሆ1፥6፤ ማቴ17፥13
19፥12 ቊ11፤ዘፀ 3፥2፤1ሳሙ14፥6፤ ኢዮ4፥16፤ዘካ4፥6፤ 2ቆሮ12፥9

ሰዓት ያንተንም ነፍስ ከእነዚያ እንደ
አንዱ ነፍስ ሳላደርጋት ብቀር አማልክት
እንዲህ ያድርጉብኝ፤ ከዚህ የባሰም ያምጡ
ብኝ” ስትል ወደ ኤልያስ መልእክተኛ
ላከች።
3ኤልያስም ፈርቶ[0] ስለ ነበር፣ ሕይወተ
ን ለማትረፍ ሲል ሸሸ። በይሁዳ ምድር
ወዳ ለችው ወደ ቤርሳቤህ እንደ መጣም
አገ ልጋዩን በዚያ ተወው፤ 4በምድረ
በዳም ውስጥ የአንድ ቀን መንገድ ተጓዘ፤
ወደ አንድ ክትክታ ዛፍ እንደ መጣም፣
ከሥሩ ተቀምጦ፣ ይሞት ዘንድ “እግዚ
አብሔር ሆይ፤ በቅቶኛል፤ እኔ ከቀደሙት
አባቶቼ አልበልጥምና ነፍሴን ውሰዳት”
ብሎ ጸለየ። 5ከዚያም ከዛፍ ሥር ተጋደመ፤
እንቅልፍም ወሰደው።
በድንገትም አንድ መልአክ ነካ አደረገ
ውና፣ “ተነሥና ብላ” አለው። 6ዘወር ብሎ
ሲመለከትም፣ እነሆ፣ በፍም የተጋገረ እን
ጎቻና አንድ ገንቦ ውሃ ከራስጌው አገኘ፤
ከበላና ከጠጣም በኋላ ተመልሶ ተኛ።
7የእግዚአብሔርም መልአክ እንደ ገና
መጥቶ ነካ አደረገውና፣ “ሩቅ መንገድ
ስለምትሄድ ተነሥና ብላ” አለው። 8ስለዚ
ህም ተነሥቶ በላ፤ ጠጣም፤ በምግቡም
ብርታት አግኝቶ ወደ እግዚአብሔር ተራራ
ወደ ኮሬብ እስኪደርስ አርባ ቀንና አርባ
ሌሊት ተጓዘ፤ 9በዚያም ወደ አንዲት ዋሻ
ገብቶ ዐደረ።

### እግዚአብሔር ለኤልያስ ተገለጠለት

የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እርሱ መጣ፤
“ኤልያስ ሆይ፤ እዚህ ምን ታደርጋለህ?”
አለው።
10እርሱም፣ “እኔ ለሰራዊት ጌታ ለእግ
ዚአብሔር እጅግ ቀንቻለሁ፤ እስራኤላው
ያን ኪዳንህን ትተዋል፤ መሠዊያዎችህን
አፍርሰዋል፤ ነቢያትህንም በሰይፍ
ገድለ
ዋልና። የቀረሁት እኔ ብቻ ነኝ፤ አሁንም
እኔን ለመግደል ይፈልጋሉ” አለ።
11እግዚአብሔርም፣ “እግዚአብሔር በዚያ
ያልፋልና ወደ ተራራው ወጥተህ በእግዚአ
ብሔር ፊት ቁም” አለው።
ከዚያም ታላቅና ኀይለኛ ነፋስ ተራሮቹን
ሰነጣጠቀ፤ አለቶችንም በእግዚአብሔር
ፊት ብትንትናቸውን አወጣ፤ እግዚአብሔር
ግን በነፋሱ ውስጥ አልነበረም፤ ከነፋሱም
ቀጥሎ የምድር መነዋወጥ ሆነ፤ እግዚአ
ብሔር ግን በምድር መነዋወጡ ውስጥ አል
ነበረም። 12ከምድር መነዋወጡም ቀጥሎ
እሳት መጣ፤ እግዚአብሔር ግን በእሳቱ

[0]3 ወይም ኤልያስ አይቶ ተብሎ ሊተረጐም ይችላል

ውስጥ አልነበረም፤ ከእሳቱም ቀጥሎ ለስ
ለስ ያለ ድምፅ ተሰማ። [13]ኤልያስም ይህን
ሲሰማ፣ ፊቱን በመጐናጸፊያው ሸፍኖ ወጣና
በዋሻው ደጃፍ ቆመ።
ከዚያም፣ “ኤልያስ ሆይ፤ እዚህ ምን
ታደርጋለህ?” የሚል ድምፅ ሰማ።
[14]እርሱም፣ “እኔ ሁሉን ለሚችል ጌታ
*ለእግ ዚአብሔር* እጅግ ቀንቻለሁ፤ እስራ
ኤላውያን ኪዳንህን ትተዋል፤ መ
ሠዊያዎችህን አፍር ሰዋል፤ ነቢያትህንም
በሰይፍ ገድለዋልና። የቀረሁት እኔ ብቻ
ነኝ፤ አሁንም እኔን ለመግደል ይፈልጋሉ”
አለ።
[15]*እግዚአብሔርም* እንዲህ አለው፤ “በመ
ጣህበት መንገድ ተመልሰህ ወደ ደማስቆ
ምድረ በዳ ሂድ፤ እዚያ ስትደርስም አዛሄ
ልን በሶርያ ላይ እንዲነግሥ ቅባው።
[16]እንዲሁም የናሜሲን ልጅ ኢዩን በእስራ
ኤል ላይ እንዲነግሥ ቅባው፤ ደግሞም ነቢይ
ሆኖ በእግርህ እንዲተካ የአቤል ምሖላን
ሰው የሣፋጥን ልጅ ኤልሳዕን ቅባው።
[17]ከአ ዛሄል ሰይፍ ያመለጠውን ኢዩ
ይገድለ ዋል፤ ከኢዩ ሰይፍ ያመለጠውን
ደግሞ ኤልሳዕ ይገድለዋል። [18]እኔም
ጕልበታ ቸው ለበኣል ያልተንበረከ
ከውንና አፋቸው ምስሉን ያልሳመውን ሰባት
ሺህ ሰዎች በእስራኤል አስቀራለሁ።”

### የኤልሳዕ መጠራት

[19]ስለዚህ ኤልያስ ከዚያ ተነሥቶ ሲሄድ
የሣፋጥን ልጅ ኤልሳዕን ዐሥራ ሁለት ጥማድ
በሬ አውጥቶ ራሱ በዐሥራ ሁለተኛው ጥማድ
በሬ ሲያርስ አገኘው። ኤልያስም ወደ እርሱ
ወጥቶ መጐናጸፊያውን በላዩ ጣለበት። [20]ከዚ
ያም ኤልሳዕ በሬዎቹን ትቶ ኤልያስን
ተከትሎ እየሮጠ፣ “አባቴንና እናቴን ስሜ
እንድሰናበታቸው ፍቀድልኝ፤ ከዚያም እከ
ተልሃለሁ” አለው።
ኤልያስም መልሶ፣ “እኔ ምን ያደረግ
ሁህ ነገር አለ? ልትመለስ ትችላለህ”
አለው።
[21]ስለዚህም ኤልሳዕ ትቶት ተመለሰ። ሁለ
ቱን በሬዎቹን ወስዶ ዐረደ፤ የዕርሻ ዕቃውን
አንድዶ ሥጋቸውን በመቀቀል ለሕዝቡ
ሰጠ፤ እነርሱም በሉ። ከዚያም ኤልያስን
ለመከተል ሄደ፤ ረዳቱም ሆነ።

### ቤን ሀዳድ ሰማርያን ወጋ

20 በዚህ ጊዜ የሶርያ ንጉሥ ቤን ሀዳድ
መላ ሰራዊቱን በአንድነት አሰባ
ሰበ፤ ከእርሱም ጋር ሠላሳ ሁለት ነገ
ሥታት ከነፈረሶቻቸውና ከነሠረገሎቻቸው
አብረውት ነበሩ፤ ወጥቶም ሰማርያን ከበ
ወጋት። [2]ወደ ከተማዪቱም መልእክተኞች
በመላክ የእስራኤልን ንጉሥ አክዓብን እንዲህ
አለው፤ “ቤን ሀዳድ እንዲህ ይላል፤
[3]‘ብርና ወርቅህ የእኔ ነው፤ የሚያማምሩት
ሚስቶችህና ልጆችህም የእኔ ናቸው።’ ”
[4]የእስራኤልም ንጉሥ፣ “ንጉሥ ጌታዬ
ሆይ፤ ልክ እንዳልኸው ነው እኔም ሆንሁ
የእኔ የሆነው ሁሉ የአንተ ነው” ሲል መለ
ሰለት።
[5]መልክተኞቹም እንደ ገና መጥተው
እንዲህ አሉት፤ “ቤን ሀዳድ የሚለው ይህ
ነው፤ ‘ብርህንና ወርቅህን፣ ሚስቶችህንና
ልጆችህን እንድትሰጠኝ ልኬብህ ነበር፤
[6]ሆኖም ነገ በዚሁ ጊዜ ቤተ መንግሥትህንና
የሹማምትህን ቤቶች እንዲበረብሩ፣ ሹማ
ምቴን እልካቸዋለሁ። እነርሱም ማናቸ
ውንም ለአንተ ዋጋ ያለውን ሁሉ በእጃ
ቸው በማስገባት ይወስዱታል።’ ”
[7]የእስራኤልም ንጉሥ የአገሩን ሽማግሌ
ዎች ሁሉ ጠርቶ፣ “ይህ ሰው እንዴት ጠብ
እንደሚፈልግ ታያላችሁ! ሚስቶቼንና ልጆ
ቼን፣ ብሬንና ወርቄን እንዳስረክበው በጠ
የቀኝ ጊዜ አልከለከልሁትም” አላቸው።
[8]ሽማግሌዎቹና ሕዝቡም ሁሉ፣ “የሚልህን
አትቀበለው፤ የጠየቀህንም እሺ አትበለው”
አሉት።
[9]ስለዚህ ለቤን ሀዳድ መልእክተኞች፣ “ለጌ
ታዬ ለንጉሡ፣ ‘እኔ ባሪያህ በመጀመሪያ
ያልኸኝን ሁሉ አደርጋለሁ፤ ያሁኑን ጥያቄ
ህን ግን ልፈጽመው አልችልም’ ብላችሁ
ንገሩት” አላቸው። መልእክተኞቹም ይህ
ንኑ ይዘው ተመለሱ።
[10]ከዚያም ቤን ሀዳድ፣ “ለሚከተለኝ
ሰው ሁሉ የሰማርያ ዐፈር አንዳንድ ዕፍኝ
የሚዳረስ ሳይሆን ቢቀር፣ አማልክት ይህን
ያድርጉብኝ፤ ከዚህ የባሰም ያምጡብኝ”
ሲል ሌሎች መልክተኞችን ወደ አክዓብ
ላከ።
[11]የእስራኤልም ንጉሥ፣ “ ‘ታጥቆ ለጦር
ነት የሚወጣ ሰው የጦር ትጥቁን እንደ ፈታ
ሰው መደንፋት የለበትም’ ብላችሁ ንገሩት”
አላቸው።
[12]ቤን ሀዳድ ይህን መልእክት የሰማው
አብረውት የነበሩት ነገሥታት በድንኳኖቻ
ቸው[a] ውስጥ ሆነው በሚጠጡበት ጊዜ ነበር፤
ቤን ሀዳድ ሰዎቹን፣ “በሉ ለጦርነት ተዘጋ
ጁ” አላቸው፤ ስለዚህ ከተማዪቱን
ለመውጋት ተዘጋጁ።

### አክዓብ ቤን ሀዳድን ድል አደረገ

[13]በዚያን ጊዜ አንድ ነቢይ ወደ እስራኤል

[a]12 ወይም *ሱኮት* ተብሎ ሊተረጐም ይችላል፤ በቍ 16 ላይም
እንደዚሁ

19፥13 ዘፀ3፥6
19፥14 1ነገ
18፥22፤ሮሜ11፥3
19፥15 2ነገ8፥7-15
19፥16 ቀኍ21፤
መሳ7፥22፤2ነገ2፥1፤
3፥11፤9፥6
19፥17 2ነገ8፥12፡
29፤10፥32፤12፥17፤
13፥3፡7፡22፤ኤር
48፥44፤አሞ1፥4
19፥18 ሆሴ13፥2፤
ሮሜ11፥4
19፥19 ዘፍ41፥42፤
2ነገ2፥8፡14፤
19፥20 ሉቃ9፥61
19፥21 ቀኍ16፤
1ሳሙ6፥14
20፥1 1ነገ13፥32፤
15፥18
20፥7 1ሳሙ11፥3፤
2ነገ5፥7
20፥10 2ሳሙ
22፥43
20፥11 ምሳ27፥1፤
ኤር9፥23፤አሞ2፥14
20፥12 1ነገ16፥9
20፥13 ዘፀ6፥7፤
መሳ6፥8

ንጉሥ ወደ አክዓብ መጥቶ፣ “እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤ ‘ይህን ብዙ ሰራዊት ታያለ
ህን? ዛሬ በእጅህ አሳልፌ እሰጥሃለሁ፤ ከዚ
ያም እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቃ
ለህ’ ” አለው።
[14]አክዓብም፣ “ይህን የሚያደርገው ማን
ነው?” ሲል ጠየቀ።
ነቢዩም፣ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
‘ይህን የሚያደርጉት የየአውራጃው አዛዥ
የሆኑ ወጣት መኰንኖች ናቸው’ ” አለው።
“ታዲያ ጦርነቱን የሚጀምረው ማን ነው?”
ሲል ጠየቀ።
ነቢዩም፣ “አንተው ትጀምራለህ” ብሎ
መለሰ።
[15]ስለዚህ አክዓብ የየአውራጃው አዛዥ
የሆኑትን ሁለት መቶ ሠላሳ ሁለት ወጣት
መኰንኖች ጠራ፤ ከዚያም የቀሩትን እስራ
ኤላውያን ሰበሰበ፤ እነዚህም በአጠቃላይ
ሰባት ሺህ ነበሩ። [16]እነርሱም ቤን ሀዳድና
ከእርሱ ጋር ተባብረው የነበሩት ሠላሳ
ሁለቱ ነገሥታት በድንኳኖቻቸው ውስጥ
ሰክረው ሳለ እኩለ ቀን ላይ መጡ። [17]በግ
ንባር ቀደምትነት የወጡት ግን፣ የየአውራ
ጃው አዛዥ የሆኑት ወጣት መኰንኖች
ነበሩ።
በዚህ ጊዜ ቤን ሀዳድ ሰላዮች ልኮ ነበርና
እነርሱም፣ “ሰዎች ከሰማርያ ወጥተው
ወደዚህ በመምጣት ላይ ናቸው” ብለው
ነገሩት።
[18]እርሱም፣ “አመጣጣቸው ለሰላምም ይሁን
ለጦርነት ከነሕይወታቸው ይዛችሁ አምጧ
ቸው” አለ።
[19]የየአውራጃው አዛዥ የሆኑ ወጣት መኰ
ንኖችም ሰራዊቱን አስከትለው ከከተማ
ዪቱ ወጡ፤ [20]እያንዳንዱም በፊቱ የገጠ
መውን ጠላት ገደለ፤ ሶርያውያን ሸሹ፤
እስራኤላውያንም ያሳድዷቸው ጀመር። የሶ
ርያ ንጉሥ ቤን ሀዳድ ግን በፈረሱ ላይ
ሆኖ ከጥቂት ፈረሰኞቹ ጋር አመለጠ። [21]የእ
ስራኤል ንጉሥ አክዓብም ወደ ፊት በመግ
ፋት ፈረሶችንና ሠረገሎችን ማረከ፤ በሶርያ
ውያንም ላይ ከባድ ጒዳት አደረሰባቸው።
[22]ከዚያም በኋላ ነቢዩ ወደ እስራኤል ንጉሥ
መጥቶ፣ “በሚመጣው የጸደይ ወራት የሶ
ርያ ንጉሥ ተመልሶ ይመጣብሃልና በርታ፤
ምን ማድረግ እንዳለብህም ዕወቅ” አለው።
[23]በዚያኑ ጊዜም የሶርያ ንጉሥ ሹማምት
እንዲህ ሲሉ መከሩት፤ “አማልክታቸው
የኰረብታ አማልክት ናቸው፤ ያየሉብንም
ከዚህ የተነሣ ነው። በሜዳ ላይ ብንገጥማ
ቸው ግን እኛ እንደምናይልባቸው አያጠራ
ጥርም። [24]እንግዲህ እንዲህ አድርግ፤ ነገሥ
ታቱን በሙሉ ከአዛዥነታቸው አስነሣ፤
በቦታቸውም ሌሎች ሹማምት አድርግ።
[25]ከእስራኤል ጋር በሜዳው ላይ እንዲጋጠም
በፈረሱ ፈንታ ፈረስ፣ በሠረገላው ፈንታ
ሠረገላ በመተካት፣ እንደ ተደመሰሰው ያለ
ሰራዊት አቋቁም፤ ከዚያ በኋላ ከእነርሱ
ይበልጥ እኛ እንደምንበረታ አያጠራጥርም።”
ንጉሡም ባቀረቡት ሐሳብ ተስማማ፤ እን
ዳሉትም አደረገ።
[26]በተከታዩም የጸደይ ወራት ቤን ሀዳድ
ሶርያውያንን አሰባስቦ እስራኤልን ለመው
ጋት ወደ አፌቅ ወጣ። [27]እስራኤላውያ
ንም እንደዚሁ ተሰብስበው ስንቅ ከተሰጣ
ቸው በኋላ ሊገጥሟቸው ተሰልፈው ወጡ።
ሶርያውያን አገር ምድሩን ሞልተውት
ሳለ፣ እስራኤላውያን ግን እንደ ሁለት
ትናንሽ የፍየል መንጋ ሆነው ከፊት ለፊታ
ቸው ሰፈሩ።
[28]የእግዚአብሔርም ሰው ወጥቶ ለእስራኤል
ንጉሥ፣ “እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ‘ሶር
ያውያን እግዚአብሔር የኰረብታ እንጂ የሸ
ለቆ አምላክ አይደለም ብለዋልና ይህን ስፍር
ቍጥር የሌለው ሰራዊት በእጅህ አሳልፌ
እሰጥሃለሁ፤ አንተም እኔ እግዚአብሔር
መሆ ኔን ታውቃለህ’ ” አለው።
[29]በየሰፈሩበትም ቦታ ሰባት ቀን ከተፋጠጡ
በኋላ በሰባተኛው ቀን ጦርነት ገጠሙ። እስ
ራኤላውያንም በአንዲት ጀምበር ከሶርያ
ውያን ሰራዊት መቶ ሺህ እግረኛ ገደሉ።
[30]የቀሩት ወደ አፌቅ ከተማ ሸሹ፤ በዚ
ያም በሃያ ሰባቱ ሺህ ላይ ቅጥሩ ተንዶ
ወደቀባቸው። ቤን ሀዳድም ወደ ከተማ
ዪቱ ሸሽቶ በመሄድ ወደ አንዲት እልፍኝ
ገብቶ ተደበቀ።
[31]ሹማምቱም፣ “የእስራኤል ቤት ነገሥ
ታት መሓሪዎች መሆናቸውን ሰምተናል፤
አሁንም እንነሣና በወገባችን ላይ ማቅ
ታጥቀን፣ በራሳችን ላይ ገመድ ጠምጥመን
ወደ እስራኤል ንጉሥ እንሂድ፤
ምናልባትም
ሕይወትህን ያተርፋት ይሆናል” አሉት።
[32]እነርሱም በወገባቸው ላይ ማቅ ታጥቀው፣
በራሳቸው ላይ ገመድ ጠምጥመው ወደ እስ
ራኤል ንጉሥ በመሄድ፣ “አገልጋይህ ቤን
ሀዳድ፣
‘እባክህ በሕይወት እንድኖር ፍቀድልኝ’
ብሎ ይለምንሃል” አሉት።
ንጉሡም፣ “እስካሁን በሕይወት አለን?
ወንድሜ እኮ ነው” አለ።
[33]ሰዎቹም ይህን በደግ በመተርጐም ቃሉን
ከአፉ ቀበል አድርገው፤ “አዎን ቤን ሀዳድ

20፥14 መሳ1፥1
20፥16 1ነገ16፥9
20፥22 መሳ6፥8፤ 2ሳሙ11፥1
20፥23 ቊ28፤ኢሳ 36፥20፤ሮሜ1፥21-23
20፥26 ቊ30፤ 1ሳሙ4፥1፤2ሳሙ 11፥1፤2ነገ13፥17
20፥27 መሳ6፥6፤ 1ሳሙ13፥6
20፥28 ቊ23፤ዘፀ 6፥7፤ኤር16፥19-21
20፥30 ቊ26፤ 1ነገ22፥25፤መዝ62፥4 ፤ኢሳ26፥21፤30፥13
20፥31 ዘፍ37፥34፤ ኢዩ41፥3

ወንድምህ ነው” አሉት።
ንጉሡም፣ “በሉ ሂዱና አምጡት” አላ
ቸው፤ ቤን ሀዳድም በመጣ ጊዜ፣ አክዓብ
ሠረገላው ላይ እንዲወጣ አደረገው።
34ቤን ሀዳድም፣ “አባቴ ከአባትህ የወሰዳ
ቸውን ከተሞች እመልሳለሁ፤ አባቴ በሰማ
ርያ እንዳደረገው ሁሉ፣ አንተም በደማስቆ
የራስህን ገበያ ማቋቋም ትችላለህ” አለው።
አክዓብም፣ “እንግዲያውስ ስምምነት አድ
ርገን በነጻ እለቅሃለሁ” አለው፤ ስለዚህም ከእ
ርሱ ጋር የውል ስምምነት አድርጎ ለቀቀው።

### አንድ ነቢይ በአክዓብ ላይ ፈረደ

35ከነቢያት ልጆች አንዱ ጓደኛውን *በእ
ግዚአብሔር* ቃል ታዞ፣ “ምታኝ” አለው፤
ሰውየው ግን ፈቃደኛ አልሆነም።
36ስለዚህም ነቢዩ፣ “*ለእግዚአብሔር* ባለ
መታዘዝህ፣ ከእኔ ተለይተህ እንደ ሄድህ
አንበሳ ይገድልሃል” አለው። ሰውየው ከሄደ
በኋላ አንበሳ አግኝቶ ገደለው።
37ነቢዩም ሌላ ሰው አግኝቶ፣ “እባክህ
ምታኝ” አለው። ስለዚህ ያ ሰው መትቶ
አቈሰለው። 38ከዚያም ነቢዩ ሄዶ ከመ
ንገድ ዳር በመቆም፣ ንጉሡን ይጠባበቅ
ጀመር። የራሱን መጠምጠሚያ ወደ ታች
አውርዶ ዐይኖቹን በመሸፈንም፣ ማንነቱ
እንዳይታወቅ አደረገ። 39ንጉሡ በዚያ
በሚያልፍበትም ጊዜ፣ ነቢዩ ጠርቶት
እንዲህ አለው፤ “እኔ አገልጋይህ በተፋፋ
መው ጦርነት መካከል ገብቼ ሳለሁ፣
አንድ ሰው ምርኮኛ ይዞ መጥቶ ‘ይህን
ሰው ጠብቅ፤ ቢያመልጥ በገመዱ ትገባለህ
ወይም አንድ መክሊት[ሦ] ብር ትከፍላለህ’
አለኝ። 40‘ታዲያ እኔ አገልጋይህ ሥራ በዝ
ቶብኝ ወዲያ ወዲህ ስል ሰውየው አምልጦ
ሄደ።’ ”
የእስራኤልም ንጉሥ፣“ራስህ ፈርደሃል፤
ይኸው ይፈጸምብሃል” አለው።
41ከዚያም ነቢዩ መጠምጠሚያውን በፍ
ጥነት ከዐይኑ ላይ አነሣ፤ የእስራኤልም
ንጉሥ ያ ሰው ከነቢያት አንዱ መሆኑን
ዐወቀ። 42ነቢዩም ንጉሡን አለው፤ “*እግዚአ
ብሔር* እንዲህ ይላል፤ ‘እኔ ፈጽሞ ይገደል[የ]
ያልሁትን ሰው ለቀኸዋልና በገመዱ ትገ
ባለህ፤ በሕዝቡም ፈንታ ያንተ ሕዝብ
በገመዱ ይገባል።’” 43የእስራኤልም ንጉሥ
ተበሳጭቶና ተቈጥቶ ሰማርያ ወዳለው
ቤተ መንግሥቱ ሄደ።

### የናቡቴ የወይን ተክል ቦታ

21 ከጥቂት ጊዜ በኋላ በኢይዝራኤላዊው
በናቡቴ የወይን ተክል ቦታ ላይ አንድ

20፥34 ዘፍ10፥22፤ 14፥15፤ዘፀ23፥32፤ 2ሳሙ8፥6፤1ነገ15፥20 ፤ኤር49፥23-27
20፥35 1ሳሙ 10፥5፤1ነገ13፥21፤ አሞ7፥14
20፥36 1ነገ13፥24
20፥39 ኢሱ2፥14
20፥40 2ሳሙ 12፥5፤14፥13
20፥42 ኢሱ2፥14፤ 2ሳሙ12፥7፤ኤር 48፥10
20፥43 1ነገ21፥4
21፥1 1ሳሙ 29፥1፤2ነገ9፥21፤ 10፥1
21፥3 ዘሌ25፥23
21፥4 1ሳሙ 28፥23፤1ነገ20፥43
21፥7 1ሳሙ8፥14
21፥8 ዘፍ38፥18፤ 2ሳሙ11፥14
21፥10 ዘፀ22፥28፤ ዘሌ24፥1516፤ዘዳ13፥ 13፤ሐሥ6፥11
21፥12 ኢሳ58፥4
21፥13 ዘሌ24፥16

ነገር ደረሰ፤ ቦታውም በኢይዝራኤል ውስጥ
ከሰማርያ ንጉሥ ከአክዓብ ቤተ መንግ
ሥት አጠገብ ነበር። 2አክዓብም ናቡ
ቴን፣ “የወይን ተክል ቦታህ ከቤተ መን
ግሥቴ አጠገብ ስለ ሆነ፣ የአትክልት ቦታ
እንዳደርገው ልቀቅልኝ፤ በምትኩ ከዚህ
የበለጠ የወይን ተክል ቦታ እሰጥሃለሁ፤
የተሻለ ሆኖ ከታየህም የሚያወጣውን ገንዘብ
እከፍልሃለሁ” አለው።
3ናቡቴ ግን፣ “ዐፅመ ርስቴን እለቅልህ
ዘንድ *እግዚአብሔር* አይበለው” ሲል መለ
ሰለት።
4ኢይዝራኤላዊው ናቡቴ፣ “ዐፅመ ርስ
ቴን አልለቅልህም” ስላለው፣ አክዓብ ተበ
ሳጭቶና ተቈጥቶ ወደ ቤቱ ገባ፤ አኰ
ርፎም በዐልጋው ላይ ተኛ፤ ምግብም
መብላት ተወ።
5ሚስቱ ኤልዛቤልም ወደ እርሱ ገብታ፣
“እስከዚህ የተበሳጨኸው፣ ምግብስ የማት
በላው ለምንድን ነው?” ብላ ጠየቀችው።
6እርሱም፣ “ኢይዝራኤላዊውን ናቡቴን፣
‘የወይን ተክል ቦታህን ሽጥልኝ፤ ከፈለ
ግህም በምትኩ ሌላ የወይን ቦታ እሰጥ
ሃለሁ’ አልሁት፤ እርሱ ግን፣ ‘የወይን
ተክል ቦታዬን አልለቅልህም’ ስላለኝ ነው”
አላት።
7ሚስቱ ኤልዛቤልም፣ “አንተ አሁን የእ
ስራኤል ንጉሥ ትባላለህ? በል ተነሥና እህል
ቅመስ፤ ደስም ይበልህ፤ የኢይዝራኤላዊ
ውን የናቡቴን የወይን ተክል ቦታ እኔ እን
ድታገኝ አደርግሃለሁ” አለችው።
8ስለዚህ በአክዓብ ስም ደብዳቤዎች ጻፈች፤
በገዛ ማኅተሙም አትማ በናቡቴ ከተማ
አብረውት ለሚኖሩ ሽማግሌዎችና መኳን
ንት ላከች። 9በደብዳቤዎቹም ላይ እንዲህ
ስትል ጻፈች፤

“የአንድ ቀን ጾም ዐውጁ፤ ናቡቴንም
በሕዝቡ መካከል ከፍ ባለ ቦታ ላይ አስ
ቀምጡት። 10እንዲሁም ሁለት የሐ
ሰት ምስክሮች ከፊት ለፊቱ አስቀምጡና፣
‘እግዚአብሔርንም ንጉሡንም ሰድቦአል’
ብለው ይመስክሩበት፤ ከዚያም አውጥ
ታችሁ በድንጋይ ወግራችሁ ግደሉት።”

11ስለዚህ በናቡቴ ከተማ የሚኖሩ ሽማግ
ሌዎችና መኳንንት በደብዳቤዎቹ ላይ እንደ
ጻፈችላቸው አደረጉ። 12የአንድ ቀን ጾም ዐወጁ፤
ናቡቴንም በሕዝቡ መካከል ከፍ ባለ ቦታ
ላይ አስቀመጡት። 13ከዚያም ሁለት የሐ
ሰት

[ሦ]39 34 ኪሎ ግራም ያህል ነው
[የ]42 የዕብራይስጡ ቃል ሰውን ወይም ቍስን ፈጽሞ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠት የሚለውን ያመለክታል

ምስክሮች መጥተው ከፊት ለፊቱ ተቀመጡ፤
በሕዝቡም ፊት፣ “ናቡቴ እግዚአብሔርንና
ንጉሡን ሰድቦአል” ብለው መሰከሩበት። ስለ
ዚህ ከከተማዪቱ ውጭ ወስደው በድንጋይ
ወግረው ገደሉት። 14ከዚያም ለኤልዛቤል፣
“ናቡቴ በድንጋይ ተወግሮ ሞቶአል” ብለው
ላኩባት።

15ኤልዛቤልም በድንጋይ ተወግሮ መሞተ
ን ወዲያው እንደ ሰማች አክዓብን፣
“ናቡቴ በድንጋይ ተወግሮ ሞቶአል፤ በል
ተነሣና ኢይዝራኤላዊው ናቡቴ ሊሸጥልህ
ያል ፈለገውን የወይን ተክል ቦታ
በርስትነት ውሰደው” አለችው። 16አክዓብ
የናቡቴን ሞት ሲሰማ የናቡቴን የወይን
ተክል ቦታ በርስትነት ለመያዝ ተነሥቶ
ወረደ።

17ከዚያም *የእግዚአብሔር* ቃል ወደ
ቴስብያዊው ወደ ኤልያስ እንዲህ ሲል
መጣ፤ 18“ተነሣና በሰማርያ ሆኖ የሚገ
ዛውን የእስራኤልን ንጉሥ አክዓብን ትገ
ናኝ ዘንድ ውረድ፤ የናቡቴን የወይን
ተክል ቦታ በርስትነት ለመያዝ ሄዶ አሁን
እዚያው ይገኛል። 19እንዲህም በለው፤
‘*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ ሰውየውን
ገደልኸው፤ ደግሞ ርስቱን ልትወስድ? ከዚ
ያም እንዲህ በለው፤ ‘*እግዚአብሔር* እንዲ
ህ ይላል፤ ውሾች የናቡቴን ደም በላሱበት
ቦታ የአን ተንም ደም ውሾች እንዲሁ
ይልሱታል!’ ”

20አክዓብም ኤልያስን፣ “ጠላቴ ሆይ አገ
ኘኸኝን?” አለው።

ኤልያስም መልሶ እንዲህ አለው፤ “*በእ
ግዚአብሔር* ፊት የተጠላውን ነገር ለማ
ድረግ ራስህን ሸጠሃልና አዎን አግኝቼሃለሁ።
21‘እነሆ ክፉ ነገር አመጣብሃለሁ፤ ዘርህን
ፈጽሜ አጠፋለሁ፤ ባሪያም ይሁን ነጻ
እያንዳንዱን የአክዓብን የመጨረሻ ወንድ
ልጅ ከእስራኤል እጠርጋለሁ። 22ለቍጣ
ስላነሣሣኸኝና እስራኤልንም ስላሳትሃቸው
ቤትህን እንደ ናባጥ ልጅ እንደ ኢዮርብዓም
ቤት፣ እንደ አኪያም ልጅ እንደ ባኦስ ቤት
አደርገዋለሁ።’

23“ስለ ኤልዛቤልም *እግዚአብሔር*፣ ‘በኢ
ይዝራኤል ቅጥር አጠገብ[ደ] ውሾች ኤልዛቤ
ልን ይበሏታል’ ይላል።

24“ደግሞም ከአክዓብ ወገን ሆኖ በከተማ
የሞተውን ውሾች ይበሉታል፤ በገጠር የሞ
ተውንም የሰማይ አሞሮች ይበሉታል።”

25በሚስቱ በኤልዛቤል ተገፋፍቶ *በእግዚ
አብሔር* ፊት ክፉ ለማድረግ ራሱን የሸጠ
እንደ አክዓብ ያለ ሰው ከቶ አልነበረም።
26*እግዚአብሔር* ከእስራኤል ፊት ያሳደዳ
ቸው አሞራውያን እንዳደረጉት ሁሉ፣ እር
ሱም ጣዖታትን በማምለክ እጅግ የሚያስ
ጸይፍ ርኵሰት ፈጸመ።

27አክዓብም ይህን ቃል ሲሰማ ልብሱን
ቀደደ፤ ማቅ ለብሶ፤ ጾመ፤ በማቅ ላይ
ተኛ በሐዘን ኵርምት ብሎም ይሄድ
ነበር።

28ከዚያም እንዲህ የሚል *የእግዚአብሔር*
ቃል ወደ ቴስብያዊው ወደ ኤልያስ
መጣ፤ 29አክዓብ ራሱን በፊቴ እንዴት
እንዳዋረደ አየህን? ራሱን ስላዋረደ ይህን
መከራ በዘመኑ አላመጣበትም፤ ነገር ግን
ይህን በቤቱ ላይ የማመጣው በልጁ ዘመን
ነው።”

21፥15 1ሳሙ8፥14
21፥19 1ነገ22፥38፤ 2ነገ9፥26፤ኢዮ 24፥6፤ 31፥39፤ መዝ9፥12፤68፥23፤ ኢሳ14፥20፤ኤር15፥3
21፥20 1ነገ18፥17፤ 2ነገ17፥17፤ሮሜ7፥14
21፥21 ዘዳ32፥36፤ መሳ9፥5፤2ነገ10፥7
21፥22 1ነገ12፥30፤ 16፥3
21፥23 1ነገ9፥10፤ 34፥36
21፥24 ዘፍ40፥19፤ ዘዳ28፥26፤1ነገ14፥11
21፥25 1ነገ14፥9፤ 16፥33
21፥26 ዘፍ15፥16
21፥27 ዘፍ37፥34፤ ኢሳ38፥15፤ኤር4፥8
21፥29 ዘፀ10፥3፤ 20፥5፤32፥14፤2ነገ 9፥26፤10፥6-10፤ 22፥20
22፥3 ዘዳ4፥43
22፥4 2ነገ3፥7
22፥5 ዘፀ33፥7፤ 2ነገ3፥11፤ኢዮ38፥2፤ መዝ32፥8፤73፥24፤ 107፥11
22፥6 መሳ18፥6፤ 1ነገ13፥18
22፥7 ዘኍ27፥21፤ ዘዳ18፥15፤1ነገ3፥11፤5፥8
22፥8 ቀኍ13፤ኢሳ 5፥20፤30፥10፤ኤር 23፥17፤አሞ5፥10

## ሚክያስ በአክዓብ ላይ ትንቢት ተናገረ
22፥1-28 ተጓ ምብ - 2ዜና 18፥1-27

22 በሶርያና በእስራኤል መካከል ለሦ
ስት ዓመት ጦርነት አልነበረም።
2በሦስተኛው ዓመት ግን የይሁዳ ንጉሥ ኢ
ዮ ሣፍጥ የእስራኤልን ንጉሥ
ለመጐብኘት ወረደ። 3የእስራኤልም
ንጉሥ ሹማምቱን፣ “በገለዓድ የምትገኘው ሬ
ማት የእኛ ሆና ሳለች፣ ከሶርያው ንጉሥ
እጅ ለመመለስ ምንም እንዳላደረግን
አታውቁምን?” አላቸው።

4ስለዚህ ኢዮሣፍጥን፣ “በገለዓድ የምትገ
ኘው ሬማት ላይ ለመዝመት አብረኸኝ
ለመሄድ ትፈቅዳለህን?” ሲል ጠየቀው።

ኢዮሣፍጥም፣ “እኔ ያው እንደ አን
ተው ነኝ፤ ሕዝቤ እንደ ሕዝብህ፣ ፈረሶቼም
እንደ ፈረሶችህ ናቸው” አለ። 5ኢዮሣ
ፍጥም የእስራኤልን ንጉሥ፣ “በመጀመ
ሪያ ግን *የእግዚአብሔርን* ሐሳብ ጠይቅ”
አለው።

6ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ አራት መቶ
ነቢያትን በአንድነት ሰብስቦ፣ “በገለዓድ
በምትገኘው ሬማት ላይ ልዝመት ወይስ
ልተው?” ሲል ጠየቃቸው።

እነርሱም፣ “*እግዚአብሔር* በንጉሡ እጅ
አሳልፎ ይሰጣታልና ዝመትባት” አሉት።

7ኢዮሣፍጥ ግን፣ “የምንጠይቀው *የእግ
ዚአብሔር* ነቢይ እዚህ የለምን?” አለ።

8የእስራኤልም ንጉሥ ለኢዮሣፍጥ፣ “መኖ
ሩንማ በእርሱ አማካይነት *የእግዚአብሔ
ርን* ፈቃድ የምንጠይቀው አንድ ሰው
አሁንም አለ፤ ነገር ግን ምን ጊዜም ቢሆን
ስለ እኔ ክፉ እንጂ አንዳችም መልካም
ትንቢት ተናግሮ ስለማያውቅ እጠላዋለሁ፤
ይህም ሰው የይምላ ልጅ ሚክያስ ነው”
አለ።

[ደ]23 አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ነገር ግን አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ ቩልጌትና የሱርስቱ ትርጒም (2ነገ9፥26 ይመ)፣ *በዕርሻው ማሳ ላይ ይላሉ*

ኢዮሣፍጥም፣ “ንጉሡ እንዲህ ማለት አይ
ገባውም” ሲል መለሰ።
[9]ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ ከሹማምቱ
አንዱን ጠርቶ፣ “በል የይምላን ልጅ ሚክ
ያስን በፍጥነት አምጣው” አለው።
[10]የእስራኤል ንጉሥና የይሁዳ ንጉሥ ኢዮ
ሣፍጥ አልባሰ መንግሥታቸውን ለብሰው፣
በሰማርያ ቅጥር በር አጠገብ ባለው አውድ
ማ ላይ በየዙፋናቸው ተቀምጠው ሳለ፣
ነቢያቱ ሁሉ በፊታቸው ትንቢት ይናገሩ
ነበር።
[11]በዚህ ጊዜ ሴዴቅያስ የተባለው የክንዓና
ልጅ የብረት ቀንዶች አበጅቶ፣ “እግዚአብሐ
ር
እንዲህ ይላል፤ ‘ሶርያውያን እስኪጠፉ ድረስ
የምትወጋቸው በእነዚህ ነው’” አለው።
[12]የቀሩትም ነቢያት ሁሉ፣ “እግዚአብሔር
በንጉሡ እጅ አሳልፎ ይሰጣታልና በገለዓድ
የምትገኘውን ሬማትን ወግተህ ድል አድ
ርግ” በማለት በአንድ ቃል ትንቢት ይና
ገሩ ነበር።
[13]ከዚያም ሚክያስን ሊጠራ የሄደው መል
እክተኛ፣ “እነሆ፤ ሌሎቹ ነቢያት ንጉሡ
ድል እንደሚያደርግ በአንድ ቃል ትንቢት
እየተናገሩለት ነውና ያንተም ቃል ከእነ
ርሱ ጋር አንድ እንዲሆን እባክህ መልካም
ነገር ተናገር” አለው።
[14]ሚክያስ ግን፣ “ሕያው እግዚአብሔ
ር! ለእርሱ የምነግረው እግዚአብሔር
የነገረኝን ብቻ ነው” አለ።
[15]እዚያም እንደ ደረሰ ንጉሡ፣ “ሚክ
ያስ ሆይ፤ በገለዓድ በምትገኘው ሬማት
ላይ እንዝመትባት ወይስ እንተው?” ሲል
ጠየቀው።
እርሱም፣ “እግዚአብሔር በንጉሡ እጅ
አሳልፎ ይሰጣታልና ዘምተህ ድል አድርጋት”
ብሎ መለሰለት።
[16]ንጉሡም፣ “ከእውነት በቀር በእግዚአ
ብሔር ስም አንዳች ነገር እንዳትነግረኝ የማ
ምልህ ስንት ጊዜ ነው?” አለው።
[17]ከዚያም ሚክያስ እንዲህ ሲል መለሰ፣
“እስራኤል ሁሉ ጠባቂ እንደሌላቸው በጎች
በየተራራው ላይ ተበትነው አየሁ፣ እግዚ
አብሔርም፣ ‘ይህ ሕዝብ ጌታ የለውም፤
እያንዳንዱ በሰላም ወደየቤቱ ይሂድ’ አለ።”
[18]የእስራኤልም ንጉሥ ለኢዮሣፍጥ፣
“ስለ እኔ ክፉ ብቻ እንጂ ከቶ መልካም
ትንቢት አይናገርም አላልሁህምን?” አለው።
[19]ከዚያም ሚክያስ እንዲህ አለ፤ “እንግዲህ
የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን ስማ፤
‘እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ፣ የሰ

22፥11 ቍ24፤ ዘዳ33፥17፤ኤር27፥2፤ 28፥10፤ዘካ1፥8-21
22፥13 ቍ8
22፥14 ዘኍ22፥18፤ 1ሳሙ3፥17
22፥17 ዘፍ11፥4፤ ዘኍ27፥17፤ኢሳ 13፥14፤ናሆ3፥18፤ ማቴ9፥36
22፥19 ኢዮ1፥6፤ 15፥8፤38፥7፤መዝ 47፥8፤103፥20-21፤ 148፥2፤ኢሳ6፥1፤ 63፥15፤ኤር23፥18፡ 22፤ሕዝ1፥26፤ ዳን7፥9፤ሉቃ2፥13
22፥22 መሳ9፥23፤ 2ተሰ2፥11
22፥23 ዘዳ13፥3፤ 31፥29፤ሕዝ14፥9
22፥24 ቍ11፤ ኢዮ26፥4፤ሐሥ23፥2
22፥25 1ነገ20፥30
22፥27 2ዜና 16፥10፤ኤር20፥2፤ 26፥21፤37፥15፤ ዕብ11፥36
22፥28 ዘዳ18፥22
22፥30 1ሳሙ28፥8
22፥31 ዘፍ10፥22፤ 2ሳሙ10፥19፤17፥2

ማይ ሰራዊት ሁሉ በቀኙና በግራው ቆመው
አየሁ፤ [20]እግዚአብሔርም፣ “በገለዓድ በም
ትገኘው ሬማት ላይ ዘምቶ እዚያው እን
ዲሞት፣ አክዓብን ማን ያስተው?” አለ።’
“ታዲያ አንዱ ይህን፣ ሌላውም ያን አለ፤
[21]በመጨረሻም፣ ‘አንድ መንፈስ ወጣ፤ ከዚ
ያም በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ፣ “እኔ አስ
ተዋለሁ” አለ።’
[22]እግዚአብሔርም፣ ‘እንዴት አድርገህ?’
ሲል ጠየቀው።
“እርሱም፣ ‘እኔ እወጣለሁ፤ በገዛ ነቢያቱም
አፍ ሁሉ የሐሰት መንፈስ እሆናለሁ’ አለ።
እግዚአብሔርም፣ “በል እንግዲያው ውጣና
አስተው፤ ይሳካልሃል” አለው።
[23]“ስለዚህ እነሆ እግዚአብሔር በእነዚህ
ሁሉ ነቢያትህ አፍ የሐሰት መንፈስ
አኖረ፤ በአንተም ላይ መዓቱን እንደሚያ
መጣብህ ተናገረ።”
[24]ከዚያም የክንዓና ልጅ ሴዴቅያስ
ወጥቶ ሚክያስን በጥፊ መታውና፣ “ለመ
ሆኑ የእግዚአብሔር መንፈስ ከእኔ በየት
በኩል ዐልፎ ነው አንተን መጥቶ ያና
ገረህ?” ሲል ጠየቀው።
[25]ሚክያስም፤ “ይህንማ ለመደበቅ ወደ
አንዲት እልፍኝ በሄድህ ዕለት ታውቀዋለህ”
አለው።
[26]ከዚያም የእስራኤል ንጉሥ እንዲህ ሲል
አዘዘ፤ “በሉ ሚክያስን ይዛችሁ ወደ ከተ
ማዪቱ ገዥ ወደ አሞንና ወደ ንጉሡ
ልጅ ወደ ኢዮአስ መልሱት፤ [27]ከዚያም፣
‘ንጉሡ፣ “በደኅና እስክመለስ ድረስ፣
ይህን ሰው በእስር ቤት አቈዩት፤ ከደረቅ
እንጀራና ከውሃ በስተቀር ሌላ እንዳትሰጡ
ት” ብሎአል በሉት’ አለ።
[28]ሚክያስም፣ “አንተ በደኅና ከተመለ
ስህ እግዚአብሔር በእኔ አልተናገረማ!”
አለ፤ ከዚያም በመቀጠል፣ “በዚህ ያለኸው
ሕዝብ ሁሉ ይህን ቃሌን ልብ ብለህ
ያዘው፤” አለ።

### አክዓብ በገለዓድ በምትገኘው በሬማት ተገደለ

22፥29-36 ተጓ ምብ - 2ዜና 18፥28-34

[29]ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥና የይሁዳ ንጉሥ
ኢዮሣፍጥ በገለዓድ ወደምትገኘው ሬማት
ወጡ። [30]የእስራኤል ንጉሥ ኢዮሣፍጥን፣
“እንዳልታወቅ እኔ ልብስ ለውጬና ሌላ
ሰው መስዬ እገባለሁ፤ አንተ ግን ልብሰ
መንግሥትህን ልበስ” አለው። ስለዚህ
የእስራኤል ንጉሥ ራሱን ደብቆ ወደ ጦር
ነቱ ገባ።
[31]በዚህ ጊዜ የሶርያ ንጉሥ ሠላሳ ሁለቱን

የሠረገላ አዛዦች፣ “ከራሱ ከእስራኤል ንጉሥ
በቀር ትንሽም ይሁን ትልቅ ከማንም ጋር
እንዳትገጥሙ” ሲል አዞአቸው ነበር፤ 32የ
ሠረገላ አዛዦቹ ኢዮሣፍጥን ሲያዩት፣
“ያለ ጥርጥር ይህ የእስራኤል ንጉሥ
ነው” አሉ፤ ስለዚህ አደጋ ሊጥሉበት
ከበቡት፤ ኢዮሣፍጥ ሲጮህ ግን 33የሠረገላ
አዛዦቹ እርሱ የእስራኤል ንጉሥ አለ
መሆኑን አውቀው መከታተሉን ተዉት።
34ነገር ግን አንዱ ቀስቱን ሳያልም እንዲ
ሁ ሲያስፈነጥር በጦር ልብሱ መጋጠሚያ
ላይ የእስራኤልን ንጉሥ ወጋው፤ ንጉሡም
ሠረገላ ነጂውን፣ “ቄስያለሁና ወደ ኋላ
አዙረህ ከጦሩ ሜዳ አውጣኝ” አለው።
35ጦርነቱም ቀኑን ሙሉ ተፋፍሞ ዋለ፤
በዚህ ጊዜም ንጉሡ በሶርያውያን ፊት
ለፊት ሠረገላው ላይ ቀና ብሎ እንደ
ተደገፈ ነበር፤ የቈስሉ ደም በሠረገላው
ወለል ላይ ይወርድ ነበር፤ በዚያኑ ዕለት
ማታም ንጉሡ ሞተ። 36ፀሓይ ስትጠ
ልቅም በሰራዊቱ መካከል፣ “እያንዳንዱ
ሰው ወደ ቤቱ፣ እያንዳንዱም ወደ ሀገሩ
ይሂድ!” የሚል ጩኸት አስተጋባ።
37ንጉሡ ስለ ሞተም ወደ ሰማርያ አም
ጥተውት እዚያው ተቀበረ። 38ሠረገላው
ንም አመንዝሮች በታጠቡበት በሰማርያ[ጀ]
ኵሬ አጠቡት፤ *እግዚአብሔርም* እንደ
ተናገረው ቃል ደሙን ውሾች ላሱት።
39ሌላው በአክዓብ ዘመነ መንግሥት
የተፈጸመውና ያደረገው ሁሉ፣ ቤተ መን
ግሥቱን መሥራቱና በዝሆን ጥርስ መለ
በጡ እንዲሁም የሠራቸው የምሽግ ከተ
ሞች በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ የተጻፈ
አይደለምን? 40አክዓብም ከአባቶቹ ጋር
አንቀላፋ፤ ልጁ አካዝያስም በእግሩ ተተ
ክቶ ነገሠ።

### የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ

22፥41-50 ተጓ ምብ - 2ዜና 20፥31-21፥1

41የእስራኤል ንጉሥ አክዓብ በነገሠ በአ
ራተኛው ዓመት የአሳ ልጅ ኢዮሣፍጥ
በይሁዳ ነገሠ። 42ኢዮሣፍጥ ሲነግሥ ዕድሜው
ሠላሳ አምስት ዓመት ነበር፤ እርሱም በኢ
የሩሳሌም ሃያ አምስት ዓመት ገዛ። እናቱ
ዓዙባ ትባላለች፤ እርሷም የሺልሒ ልጅ
ነበረች። 43በአካሄዱም ሁሉ የአባቱን

22፥34 2ነገ9፥24፤ 2ዜና35፥23
22፥36 2ነገ14፥12
22፥38 1ነገ21፥19
22፥39 2ዜና 9፥17፤መዝ45፥8፤ አሞ3፥15

22፥43 1ነገ3፥2፤ 8፥61፤2ዜና17፥3
22፥46 ዘዳ23፥17
22፥47 1ነገ11፥14-18፤2ነገ3፥9፤8፥20
22፥48 ዘኍ33፥35፤ 1ነገ9፥26
22፥52 1ነገ15፥26
22፥53 መሳ2፥11፤ 1ነገ21፥25

የአሳን መንገድ ተከተለ፤ ከዚያች ፈቀቅ
አላለም፤ *በእግዚአብሔርም* ፊት መልካም
የሆነውን አደረገ፤ ይሁን እንጂ በየኰረ
ብታው ላይ ያሉትን የማምለኪያ ቦታዎች
አላጠፋም፤ ሕዝቡም በዚያ መሥዋዕት
ይሠዋ፣ ዕጣንም ያጥን ነበር። 44እንዲሁም
ኢዮሣፍጥ ከእስራኤል ንጉሥ ጋር በሰላም
ኖረ።
45ሌላውም ኢዮሣፍጥ በዘመነ መንግ
ሥቱ የፈጸመው፣ ያከናወነውና ያደረገው
ጦርነት ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ የተ
ጻፈ አይደለምን? 46ከአባቱ ከአሳ ዘመን
በኋላ እንኳ ተርፈው በጣዖት ማምለኪያ
ቦታዎች የነበሩትን የወንደቃ ቅሬታዎች
ከምድሪቱ አስወገደ። 47በዚያን ጊዜ ኤዶም
ንጉሥ አልነበራትም፤ የሚገዛት እንደራሴ
ነበር።
48ኢዮሣፍጥ ወርቅ ለማምጣት ወደ
ኦፊር የሚሄዱ የንግድ መርከቦች[ገ] አሠርቶ
ነበር፤ ይሁን እንጂ በዔጽዮንጋብር ስለ
ተሰበሩ ከቶ ወደዚያ መሄድ አልቻሉም
ነበር። 49በዚያን ጊዜም የአክዓብ ልጅ አካ
ዝያስ ኢዮሣፍጥን “ሰዎቼ ከሰዎችህ ጋር
በመርከብ ይሂዱ” ሲል ጠይቆት ነበር፤
ኢዮሣፍጥ ግን እሺ አላለውም።
50ኢዮሣፍጥ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤
እነርሱ በተቀበሩበት በአባቱ በዳዊት ከተማ
ተቀበረ። ልጁ ኢዮራምም በእግሩ ተተ
ክቶ ነገሠ።

### የእስራኤል ንጉሥ አካዝያስ

51የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ በነገሠ በዐሥ
ራ ሰባተኛው ዓመት የአክዓብ ልጅ
አካዝያስ የእስራኤል ንጉሥ ሆኖ በሰማርያ
ነገሠ፤ እስራኤልንም ሁለት ዓመት ገዛ።
52እር ሱም የአባቱንና የእናቱን፣ እንዲ
ሁም እስራኤልን ያሳተውን የናባጥን ልጅ
የኢዮርብዓምን መንገድ በመከተሉ፣
*በእግዚአብሔር* ፊት የተጠላ ክፉ ሥራ
ሠራ። 53አባቱ እንዳደረገው ሁሉ፣
እርሱም በኣ ልን አመለከ፤ ሰገደለትም።
በዚህም የእስራኤልን አምላክ *እግዚአብሐ
ጌርን* ለቍጣ እንዲነሣሣ አደረገ።

[ጀ]38 ወይም፣ *የጦር መሣሪያ በሚታጠብበት በሰማርያ* ተብሎ መተርጐም ይችላል
[ገ]48 ዕብራይስጡ *የተርሴስ መርከቦች* ይላል

## የእግዚአብሔር ፍርድ በአካዝያስ ላይ

1 አክዓብ ከሞተ በኋላ ሞዓብ በእስራ
ኤል ላይ ዐመፀ። 2በዚህ ጊዜ አካ
ዝያስ በሰማርያ ካለው እልፍኝ ሰገነቱ ላይ
ሳለ፣ ከዐይነ ርግቡ ሾልኮ ወድቆ ነበርና
ታመመ፤ ስለዚህ፣ “ሄዳችሁ ከዚህ ሕመም
እድን እንደሆነ የአቃሮንን አምላክ ብዔል
ዜቡልን ጠይቁ” ሲል መልእክተኞች ላከ።
3*የእግዚአብሔር* መልአክ ግን ቴስብያዊ
ውን ኤልያስን እንዲህ አለው፤ “ተነሥተህ
የሰማርያን ንጉሥ መልእክተኞች ለመገና
ኘት ውጣና፣ ‘የአቃሮንን አምላክ ብዔልዜ
ቡልን ለመጠየቅ የምትሄዱ በእስራኤል
አምላክ ስለሌለ ነውን?’ ብለህ ጠይቃቸው።
4ስለዚህ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ ‘ከተ
ኛህበት ዐልጋ አትነሣም፤ በእርግጥ ትሞ
ታለህ።’ ” ከዚያም ኤልያስ ሄደ።
5መልእክተኞቹ ወደ ንጉሡ ሲመለሱ
እርሱም፣ “ለምን ተመልሳችሁ መጣችሁ?”
ሲል ጠየቃቸው።
6እነርሱም እንዲህ ሲሉ መለሱለት፤
“አንድ ሰው ሊገናኘን መጥቶ፣ ‘ወደ ላካ
ችሁ ንጉሥ ተመልሳችሁ ሂዱና፣ “*እግዚ
አብሔር* እንዲህ ይላል፤ ‘የአቃሮንን አም
ላክ ብዔል ዜቡልን ለመጠየቅ ሰዎች የም
ትልከው በእስራኤል አምላክ ስለሌለ ነውን?
ስለዚህ ከተኛህበት ዐልጋ አትነሣም፤ በእር
ግጥ ትሞታለህ።’”’
7ንጉሡም፣ “ለመሆኑ ሊገናኛችሁ መጥቶ
እንዲህ ያላችሁ ሰው እንዴት ያለ ነው?”
ሲል ጠየቃቸው።
8እነርሱም “ሰውየው ጠጕራም ልብስ የለ
በሰ ነው፤ በወገቡም ላይ ጠፍር ታጥቆ
አል” አሉት።
ንጉሡም፣ “ዐወቅሁት፤ ቴስብያዊው ኤል
ያስ ነው” አላቸው።
9ከዚያም ንጉሡ አንድ የአምሳ አለቃ
ከአምሳ ወታደሮቹ ጋር ወደ ኤልያስ ላከ።
የአምሳ አለቃውም ኤልያስ ወደ ተቀመጠ
በት ኰረብታ ጫፍ ወጥቶ፣ “አንተ የእግዚ
አብሔር ሰው፤ ንጉሡ፣ ‘ና ውረድ’ ይል
ሃል” አለው።
10ኤልያስም መልሶ የአምሳ አለቃ
ውን፣ “እኔ የእግዚአብሔር ሰው ከሆንሁ፣
እሳት ከሰማይ ወርዳ፣ አንተንና አምሳውን
ሰዎችህን ትብላ!” አለው። ከዚያም እሳት
ከሰማይ ወርዳ የአምሳ አለቃውንና ሰዎቹን

1፥1 ዘፍ19፥37፤
2ነገ3፥5
1፥2 ቍ16፤መሳ
18፥5፤ 1ሳሙ6፥2፤ኢሳ
2፥6፤14፥29፤ማር3፥22
1፥3 ቍ15፤1ሳሙ
28፥8፤1ነገ17፥1
1፥4 ቍ6፥16፤
መዝ41፥8
1፥6 ቍ4
1፥8 1ነገ18፥7፤
ማቴ3፥4፤ማር1፥6
1፥9 ዘፀ18፥25፤
2ነገ6፥14፤ኢሳ3፥3
1፥10 1ነገ18፥38፤
ራእ11፥5፤13፥13

1፥13 መዝ72፥14
1፥15 ቍ3፤ኢሳ
51፥12፤57፥11፤
ኤር1፥17፤ሕዝ2፥6
1፥16 ቍ2፥4
1፥17 2ነገ3፥1፤
8፥15፥16፤ኤር
20፥6፤28፥17
2፥1 ቍ11፤ዘፍ
5፥24፤ዘዳ11፥30፤
1ነገ19፥11፥16፥21፤2ነ
ገ4፥38፤ኢሳ5፥28፤
66፥15፤ኤር4፥13፤
ናሆ1፥3
2፥2 ቍ6፤ሩት
1፥16

ፈጽማ በላች።
11እንደገናም ንጉሡ ሌላ የአምሳ አለቃ
ከአምሳ ሰዎቹ ጋር ላከ፤ የአምሳ አለቃ
ውም፣ “አንተ የእግዚአብሔር ሰው፤ ንጉሡ፣
‘አሁኑኑ ና ውረድ’ ይልሃል” አለው።
12ኤልያስም መልሶ፣ “እኔ የእግዚአብሔ
ር ሰው ከሆንሁ እሳት ከሰማይ ወርዳ
አንተ ንና ሃምሳውን ሰዎችህን ትብላ!”
አለው፤ ከዚያም እሳት ከሰማይ ወርዳ
እርሱንና ሰዎቹን ፈጽማ በላች።
13ስለዚህም ንጉሡ ሦስተኛውን የአምሳ
አለቃ ከአምሳ ሰዎቹ ጋር ላከ። ይህም
ሦስተኛው የአምሳ አለቃ ወጥቶ፣ በኤል
ያስ ፊት በጕልበቱ ተንበርክኮ እንዲህ ሲል
ለመነ፤ “አንተ የእግዚአብሔር ሰው፤ እባክህ
የእኔና የእነዚህ የአምሳዎቹ አገልጋዮችህ
ነፍስ በፊትህ የከበረች ትሁን። 14እነሆ፤
እሳት ከሰማይ ወርዳ፣ የፊተኞቹን ሁለት
አምሳ አለቆችና ሰዎቻቸውን ሁሉ በላች፤
አሁን ግን ሕይወቴ በፊትህ የከበረች
ትሁን።”
15*የእግዚአብሔርም* መልአክ ኤልያስን፣
“አብረኸው ውረድ፤ ደግሞም አትፍራው”
አለው። ስለዚህ ኤልያስ ተነሣ፤ አብሮ
ትም ወደ ንጉሡ ወረደ።
16ንጉሡንም፣ “*እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤ ‘ለመሆኑ የአቃሮንን አምላክ ብዔል
ዜቡልን ስለራስህ ለመጠየቅ መልእክተ
ኞች የላክኸው በእስራኤል አምላክ ስለ
ሌለ ነውን? ይህን በማድረግህም ከተኛህ
በት ዐልጋ ፈጽሞ አትነሣም፤ በእርግጥ
ትሞታለህ’ ” ብሎ ነገረው። 17ስለዚህ አካዝ
ያስ ኤልያስ እንደ ተናገረው እንደ *እግዚ
አብሔር* ቃል ሞተ።
አካዝያስ ወንድ ልጅ ስላልነበረው፣
የኢዮሣፍጥ ልጅ ኢዮራም በይሁዳ በነገሠ
በሁለተኛው ዓመት ወንድሙ ኢዮራም
በእግሩ ተተክቶ ነገሠ። 18ሌላው አካዝያስ
በዘመኑ ያከናወናቸውና የፈጸማቸው ሥራ
ዎች ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ
የተጻፉ አይደለምን?

## ኤልያስ ወደ ሰማይ ዐረገ

2 *እግዚአብሔር* ኤልያስን በዐውሎ
ነፋስ ወደ ሰማይ የሚወስድበት ጊዜ
ሲደርስ፣ ኤልያስና ኤልሳዕ ከጌልገላ ተነ
ሥተው ይጓዙ ነበር። 2ኤልያስም ኤልሳ
ዕን፣ “*እግዚአብሔር* እኔን ወደ ቤቴል ልኮ

ኛልና አንተ በዚሁ ቈይ” አለው::
ኤልሳዕ ግን፣ “ሕያው፣ እግዚአብሔ
ርን፣ በሕያው ነፍስህም እምላለሁ ካንተ
አልለይም” አለው:: ስለዚህ አብረው ወደ
ቤቴል ወረዱ::
3በቤቴል የነበሩ የነቢያት ማኅበር ወደ
ኤልሳዕ ወጥተው፣ “እግዚአብሔር፣ ጌታ
ህን ኤልያስን ዛሬ ከአንተ ነጥሎ እንደ
ሚወስደው አውቀሃልን?” አሉት::
ኤልሳዕም፣ “አዎን ዐውቄአለሁ፤ እና
ንተ ግን ዝም በሉ” አለ::
4ከዚያም ኤልያስ፣ “ኤልሳዕ ሆይ፤
እግ ዚአብሔር እኔን ወደ ኢያሪኮ
ልኮኛልና አንተ በዚሁ ቈይ” አለው::
እርሱም፤ “ሕያው እግዚአብሔርን፣
በሕያው ነፍስህም እምላለሁ፤ ከአንተ አል
ለይም” ሲል መለሰ:: ስለዚህ አብረው ወደ
ኢያሪኮ ሄዱ::
5በኢያሪኮ የነበሩትም የነቢያት ማኅ
በር ወደ ኤልሳዕ ወጥተው፣ “ለመሆኑ እግ
ዚአብሔር ፣ ጌታህን ኤልያስን ዛሬ ከአ
ንተ ነጥሎ እንደሚወስደው ዐውቀሃልን?”
አሉት::
እርሱም፣ “አዎን ዐውቄአለሁ፤ እናንተ
ግን ዝም በሉ” ሲል መለሰ::
6ከዚያም ኤልያስ፣ “እግዚአብሔር እኔን
ወደ ዮርዳኖስ ልኮኛልና አንተ እዚሁ ቈይ”
አለው::
እርሱም፣ “ሕያው እግዚአብሔርን፤ በሕ
ያው ነፍስህም እምላለሁ፤ ከአንተ አልለ
ይም” ሲል መለሰ:: ስለዚህ ሁለቱም አብ
ረው ሄዱ::
7ከነቢያትም ማኅበር አምሳው ሄደው፣
ኤልያስና ኤልሳዕ ከቆሙበት ከዮርዳኖስ
ትይዩ ራቅ ብለው ቆሙ:: 8ኤልያስም ካባ
ውን አውልቆ ጠቀለለውና ውሃውን መታ
በት፤ ከዚያም ውሃው ግራና ቀኝ ተከፈለ፤
ሁለቱም በደረቅ ምድር ተሻገሩ::
9ከተሻገሩ በኋላም ኤልያስ ኤልሳዕን፤
“ከአንተ ከመወሰዴ በፊት ምን ላደርግልህ
እንደምትፈልግ ንገረኝ” አለው::
ኤልሳዕም፣ “መንፈስህ በዕጥፍ እንዲ
ያድርብኝ እለምንሃለሁ” ብሎ መለሰ::
10ኤልያስም፣ “አስቸጋሪ ነገር ጠይቀ
ሃል፤ ይሁን እንጂ እኔ ከአንተ ስወሰድ
ብታየኝ፣ እንዳልከው ይሆንልሃል፤ ያለበለ
ዚያ ግን አይሆንም” አለው::
11እያዘገሙም ሲነጋገሩ ሳለ፣ የእሳት
ሠረገላና የእሳት ፈረሶች ድንገት በመካ
ከላቸው ገብተው ሁለቱን ለዩአቸው፤ ኤል
ያስም በዐውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ዐረገ::

2፥3 1ሳሙ10፥5
2፥4 ኢሱ3፥16
2፥5 ቊ3
2፥6 ቊ2፤ኢሱ
3፥15፤ሩት1፥16
2፥8
ቊ14፤ዘፀ14፥21፡22፡
29፤1ነገ19፥19
2፥9 ዘኍ11፥17፤
ዘዳ21፥17
2፥11 ቊ1፤ዘፍ
5፥24፤2ነገ6፥17፤
መዝ68፥17፤104፥3፡4፤
ኢሳ66፥15፤
ዕን3፥8፤ዘካ6፥1
2፥12 ዘፍ37፥29፤
2ነገ6፥17፤13፥14
2፥14 ቊ8፤1ነገ
19፥19
2፥15 ዘኍ11፥17፤
1ሳሙ10፥5
2፥16 1ነገ18፥12፤
ሐሥ8፥39
2፥17 መሳ3፥25
2፥21 ዘፀ15፥25፤
2ነገ4፥41፤6፥6
2፥22 ዘፀ15፥25
2፥23 ዘፀ22፥28፤
2ዜና30፥10፤36፥16፤ኢ
ዮ19፥18፤መዝ
31፥18

12ኤልሳዕም ይህን አይቶ፣ “አባቴ! አባቴ!
የእስራኤል ሠረገሎችና ፈረሰኞች!” ብሎ
ጮኸ፤ ዳግመኛም ኤልያስን አላየውም፤
ከዚያም የገዛ ልብሱን ይዞ ከሁለት ቦታ
ቀደደ:: 13እርሱም ከኤልያስ የወደቀውን
ካባ አነሣ፤ ተመልሶም በዮርዳኖስ ወንዝ
ዳር ቆመ:: 14ከኤልያስ፣ የወደቀውንም
ካባ ይዞ ውሃውን መታና፣ “የኤልያስ አም
ላክ እግዚአብሔር ወዴት ነው?” አለ::
ውሃውን ሲመታውም በግራና በቀኝ ተከ
ፍሎለት ተሻገረ:: 15ከኢያሪኮም መጥተው
ይህን ያዩ የነበሩት የነቢያት ወገኖች፣
“የኤልያስ መንፈስ በኤልሳዕ ላይ ዐርፎ
አል” አሉ፤ ሊያገኙትም ሄደው በፊቱ ወደ
መሬት ዝቅ ብለው እጅ ነሡ:: 16ከዚ
ያም፣ “እነሆ እኛ አገልጋዮችህ እዚህ አምሳ
ጠንካራ ሰዎች አሉን፤ ምናልባትም የእግ
ዚአብሔር መንፈስ ጌታህን አንሥቶ ከአ
ንዱ ተራራ ላይ አስቀምጦት ወይም ከአ
ንዱ ሸለቆ አግብቶት ይሆናልና እስቲ
ሄደው ይፈልጉት” አሉት:: ኤልሳዕም፣ “አይ
ሆንም፤ አትላሞቸው” አለ::
17አይሆንም ለማለት ዕፍረት እስኪሰ
ማው ድረስ ግድ አሉት፤ ስለዚህ፣ “በሉ
እንግዲያው ላኳቸው” አለ:: እነርሱም አምሳ
ሰዎች ላኩ፤ ሰዎቹም ሦስት ቀን ሙሉ
ፈልገው ሳያገኙት ቀሩ:: 18በኢያሪኮ ቈይቶ
ወደ ነበረው ወደ ኤልሳዕ በተመለሱም
ጊዜ፣ “ቀድሞውንስ ቢሆን አትሂዱ ብያ
ችሁ አልነበረምን?” አላቸው::

## የውሃው መፈወስ

19የከተማዪቱም ሰዎች ኤልሳዕን፣ “እነሆ
ጌታችን፤ እንደምታያት ይህች ከተማ ለኑሮ
የተመቸች ናት፤ ይሁን እንጂ ውሃው
መጥፎ ሲሆን ምድሪቱም ፍሬ የማትሰጥ
ናት” አሉት::
20እርሱም፣ “እስቲ በአዲስ ማሰሮ
ጨው ጨምራችሁ አምጡልኝ” አለ፤
እንዳለውም አመጡለት:: 21ከዚያም ወደ
ውሃው ምንጭ ሄዶ ጨው ጣለበትና
“እግዚአብሔር እን ዲህ ይላል፤ ‘ይህን
ውሃ ፈውሸዋለሁ፤ ከእ ንግዲህ ወዲያ
ለሞት ምክንያት አይሆ ንም፤ ምድሪተ
ንም ፍሬ እንዳትሰጥ አያደ ርጋትም’
አለ::” 22ኤልሳዕ እንደ ተናገረ ውም
ውሃው እስከ ዛሬ ድረስ የተፈወሰ ነው::

## በኤልሳዕ ላይ አፌዙበት

23ኤልሳዕም ከዚያ ተነሥቶ ወደ ቤቴል
ወጣ፤ በመንገድ ላይ ሲሄድ ሳለም ልጆች
ከከተማ ወጥተው፣ “አንተ መላጣ፤ ውጣ!

አንተ መላጣ ውጣ!” እያሉ አፌዙበት።
24ኤልሳዕም ዘወር ብሎ ተመለከታቸውና
በእግዚአብሔር ስም ረገማቸው፤ ከዚያም
ሁለት እንስት ድቦች ከዱር ወጥተው ከል
ጆቹ አርባ ሁለቱን ሰባበሯቸው። 25እር
ሱም ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ሄደ፤ ከዚ
ያም ወደ ሰማርያ ተመለሰ።

### ሞዓብ ዐመፀ

3 የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ በነገሠ በዐ
ሥራ ስምንተኛው ዓመት፤ የአክአብ
ልጅ ኢዮራም በእስራኤል ላይ በሰማርያ
ነገሠ ዐሥራ ሁለት ዓመትም ገዛ። 2እር
ሱም በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ክፉ
ድርጊት ፈጸመ፤ ክፉ ድርጊቱ ግን አባ
ትና እናቱ እንደ ፈጸሙት ዐይነት አልነ
በረም፤ አባቱ ያሠራውንም የበኣልን ሐው
ልት አስወገደ። 3ነገር ግን የናባጥ ልጅ ኢዮ
ርብዓም እስራኤልን ባሳተበት ኀጢአት
ተያዘ፤ ከዚያም አልተላቀቀም።
4በዚህ ጊዜ የሞዓብ ንጉሥ ሞሳ በግ
ያረባ ነበር፤ እርሱም መቶ ሺህ ጠቦትና
የመቶ ሺህ አውራ በግ ጠጕር ለእስራኤል
ንጉሥ ይገብር ነበር። 5አክዓብ ከሞተ
በኋላ ግን የሞዓብ ንጉሥ በእስራኤል
ንጉሥ ላይ ዐመፀ። 6ስለዚህ በዚያኑ ጊዜ
ንጉሥ ኢዮራም ከሰማርያ ተነሥቶ በመ
ሄድ እስራኤልን ሁሉ አሰባሰበ። 7ለይሁዳ
ንጉሥ ለኢዮሣፍጥ፣ “የሞዓብ ንጉሥ ስለ
ዐመፀብኝ አብረኸኝ ትዘምታለህን?” ሲል
መልእክት ላከበት።
እርሱም፣ “አዎን አብሬህ እዘምታለሁ፤
እኔ እንደ አንተው ነኝ፤ ሕዝቤ እንደ ሕዝ
ብህ፤ ፈረሶቼም እንደ ፈረሶችህ ናቸው”
በማለት መለሰለት።
8ኢዮሣፍጥም፣ “የምንዘምተው በየትኛው
መንገድ ነው” ብሎ ጠየቀው፤
ኢዮራምም “በኤዶም ምድረ በዳ አል
ፈን ነው” ሲል መለሰለት።
9ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ ከይሁዳ ንጉ
ሥና ከኤዶም ንጉሥ ጋር ለመዝመት
ተነሣ። ሰባት ቀን ከዞሩም በኋላ ለሰራዊ
ቱም ሆነ ለእንስሶቻቸው የተረፈ ውሃ
አልነበረም።
10የእስራኤልም ንጉሥ፣ “ወዮ! እግዚአ
ብሔር እኛን ሦስት ነገሥታት የጠራን
ለሞዓብ አሳልፎ ሊሰጠን ነውን?” አለ።
11ኢዮሣፍጥ ግን፣ “በእርሱ አማካይነት
እግዚአብሔርን ለመጠየቅ እንድንችል፣
የእግዚአብሔር ነቢይ እዚህ የለምን?” በማ
ለት ጠየቀ።
ከእስራኤል ንጉሥ የጦር አለቆችም
አንዱ፣ “ቀድሞ የኤልያስን እጅ ያስታጥብ
የነበረው፤[ሀ] የሣፋጥ ልጅ ኤልሳዕ በዚህ
አለ” ብሎ መለሰለት።
12ኢዮሣፍጥም፣ “የእግዚአብሔር ቃል ከእ
ርሱ ዘንድ ይገኛል” አለ፤ ስለዚህ የእስራ
ኤል ንጉሥ፣ ኢዮሣፍጥና የኤዶም ንጉሥ
አብረው ወደ እርሱ ወረዱ።
13ኤልሳዕም የእስራኤልን ንጉሥ፤ “ከአ
ንተ ጋር ምን የሚያገናኘን ጕዳይ አለና
መጣህ፤ አሁን የአባትህና የእናትህ ነቢ
ያት ወዳሉበት ሂድ” አለው።
የእስራኤልም ንጉሥ መልሶ፣ “ይህማ
አይሆንም፤ በሞዓብ እጅ አሳልፎ ሊሰጠን
እኛን ሦስት ነገሥታት አንድ ላይ የጠ
ራን እግዚአብሔር ነው” አለ።
14ኤልሳዕን እንዲህ አለው፤ “የማገለግ
ለው ሕያው እግዚአብሔርን ፣ የይሁዳን
ንጉሥ ኢዮሣፍጥን ባላከብር ኖሮ፣ አንተን
አላይም ወይም ጕዳዬ አልልህም ነበር።
15አሁንም ባለ በገና አምጡልኝ።”
ታዲያ ባለ በገናው በሚደረድርበት
ጊዜ፣ የእግዚአብሔር እጅ በኤልሳዕ ላይ
መጣ፤ 16እንዲህም አለ፤ “እግዚአብሔር
የሚለው እንዲህ ነው፤ ‘በዚህ ሸለቆ ብዙ
ጕድጓዶች ቈፍሩ። 17እግዚአብሔር እን
ዲህ ይላልና፤ ‘ነፋስም ሆነ ዝናብ አታ
ዩም፤ ሸለቆው ግን በውሃ ይሞላል፤ እና
ንተ፣ የቀንድ ከብቶቻችሁና ሌሎች እንስ
ሶቻችሁም ትጠጣላችሁ። 18ይህ በእግዚአ
ብሔር ፊት ቀላል ነገር ነው። ሞዓብንም
በእጃችሁ አሳልፎ ይሰጣችኋል።
19የተመሸጉትን ከተሞችና ያማሩትን
ከተሞቻቸውን ሁሉ ድል ታደርጋላችሁ።
ውብ ዛፎቻቸውን ሁሉ ትቈርጣላችሁ፤
ምንጮቻቸውን በሙሉ ትደፍናላችሁ፤
መልካሙንም ዕርሻ በድንጋይ ታበላሹታ
ላችሁ።”
20በማግስቱ መሥዋዕት በሚቀርብበት
ጊዜ፣ እነሆ፤ ከኤዶም በኩል ውሃ እየጐረፈ
መጣ፤ ምድሪቱም ውሃ በውሃ ሆነች።
2በዚህ ጊዜ ነገሥታቱ ሊወጓቸው መም
ጣታቸውን ሞዓባውያን ሁሉ ሰምተው ነበ
ርና፣ ልጅም ሆነ ሽማግሌ፣ መሣሪያ መያዝ
የቻለ ሁሉ ተጠርቶ በመውጣት በጠረፉ
ላይ ይጠባበቅ ጀመር። 22በማግስቱ ጠዋት
ማልደው ሲነሡም፣ ፀሓይ በውሃው ላይ
ታንጸባርቅ ነበር። ማዶ ላሉት ሞዓባውያ
ንም፣ ውሃው እንደ ደም ቀልቶ ታያቸው።
23ስለዚህ፣ “ያ እኮ ደም ነው! ያለ ጥር
ጥር ነገሥታቱ እርስ በርስ ተዋግተው ተራ
ርደዋል። እንግዲህ ሞዓብ ወደ ምርኮህ

[ሀ]11 የኤልያስ አገልጋይ ነው።

2፥24 ዘፍ4፥11፤ ዘዳ18፥19
2፥25 1ነገ18፥20
3፥1 2ነገ1፥17
3፥2 ዘፀ23፥24፤ 1ነገ15፥26፤16፥30
3፥3 1ነገ12፥30
3፥4 ዘፍ19፥37፤ 2ነገ1፥1፤ዕዝ 7፥17፤ኢ ሳ16፥1
3፥5 2ነገ1፥1
3፥7 1ነገ22፥4
3፥9 1ነገ22፥47
3፥11 ዘፍ20፥7፤ 25፥22፤1ነገ19፥ 16፤22፥5
3፥12 ዘኍ11፥17
3፥15 1ሳሙ10፥5፤ ኤር15፥17፤ሕዝ1፥3
3፥17 መዝ107፥ 35፤ ኢሳ12፥3፤ 32፥2፤35፥6፤ 41፥18፤65፥13
3፥18 ዘፍ18፥14፤ 2ነገ20፥10፤ኢሳ 49፥6፤ኤር32፥17፥27፤ ማር10፥27
3፥20 ዘፀ17፥6፤ 29፥41

ዙር!" ተባባሉ።
24ሞዓባውያን ወደ እስራኤል ሰፈር ሲወ
ጡም፣ እስራኤላውያን ተነሥተው ወጓ
ቸው፤ ሞዓባውያንም ከፊታቸው ሸሹ።
ከዚያም እስራኤላውያን ምድሪቱን ወረው
ሞዓባውያንን ፈጇቸው። 25ከተሞቹን ደመ
ሰሱ፤ መልካሙን የዕርሻ መሬት ሁሉ
እስኪሸፍነው ድረስ፤ እያንዳንዱ ሰው አን
ዳንድ ድንጋይ ጣለበት፤ ምንጮቹን በሙሉ
ደፈኑ፤ ጥሩ ጥሩውንም ዛፍ ሁሉ ቈርጠው
ጣሉ። ቂርሐራሴት ብቻ ከነድንጋይዋ
ቀርታ ነበር፤ እርሷም ቢሆን ባለ ወንጭፉ
ሰራዊት ከቦ አደጋ ጣለባት።
26የሞዓባውያን ንጉሥ በጦርነቱ መሸነ
ፉን እንዳወቀ፣ ሰይፍ የታጠቁ ሰባት
መቶ ሰዎች ይዞ የኤዶም ንጉሥ ወዳለበት
ጥሶ ለመግባት ሞከረ፤ ነገር ግን አልተሳካ
ላቸውም። 27ከዚያም በእግሩ ተተክቶ የሚ
ነግሠውን፣ የበኵር ልጁን ወስዶ በከተ
ማዪቱ ቅጥር ላይ የሚቃጠል መሥዋዕት
አድርጎ አቀረበው። በእስራኤልም ላይ
ታላቅ ቍጣ ሆነ፤ ከዚያም ለቀው ወደ ገዛ
ምድራቸው ተመለሱ።

## የመበለቲቱ ዘይት

4 የነቢያት ማኅበር ወገን ከሆነው የአን
ደኛው ሚስት፣ "አገልጋይህ ባሌ ሞቶ
አል፤ እርሱም እግዚአብሔርን የሚፈራ
ሰው እንደ ነበር አንተ ታውቃለህ፤ አሁን
ግን ባለ ዕዳ ሁለት ወንዶች ልጆቼን ባሪያ
አድርጎ ሊወስዳቸው መጥቶአል" ስትል
ወደ ኤልሳዕ ጮኸች።
2ኤልሳዕም፣ "ታዲያ እኔ ምን እንዳደ
ርግልሽ ትፈልጊያለሽ? በቤትሽ ምን እን
ዳለ ንገሪኝ" አላት።
እርሷም፣ "አገልጋይህ ከጥቂት ዘይት
በቀር በቤቷ ምንም ነገር የላትም"
አለች።
3ኤልሳዕም እንዲህ አላት፤ "እንግዲያው
ሂጂና ከጎረቤቶችሽ ሁሉ ጥቂት ሳይሆን
ብዙ ማድጋ ተዋሺ፤ 4ገብተሽም መዝጊያ
ውን ባንቺና በልጆችሽ ላይ የኋሊት ዝጊው፤
ዘይቱንም በማድጋዎቹ ሁሉ ጨምሪ፤ እያ
ንዳንዱ ማድጋ ሲሞላም ወደ አንድ በኩል
አኑሪው።"
5ስለዚህ ትታው ሄዳ መዝጊያውን በራ
ሷና በልጆቿ ላይ የኋሊት ዘጋችው። ማድ
ጎቹን እያቀረቡላትም እርሷ ትሞላ ጀመር።
6ማድጋዎቹ ሁሉ ከሞሉ በኋላ ልጇን፣
"ሌላ ማድጋ አምጣ" አለችው።
እርሱ ግን፣ "ምንም የቀረ ማድጋ የለም"
ሲል መለሰላት። ከዚያም ዘይቱ መውረ

3፥25 ኢሳ15፥1፤
16፥7፤ኤር48፥31፥36
3፥27 ዘዳ12፥31፤
2ነገ16፥3፤21፥6፤
2ዜና28፥3፤መዝ
106፥38፤ኤር19፥45፤
ሚክ6፥7
4፥1 ዘፀ22፥26፤
ዘሌ25፥3943፤1ሳሙ
10፥5፤ነህ5፥35፤
ኢዩ22፥6፤24፥9
4፥2 1ነገ17፥12
4፥7 1ነገ12፥22
4፥8 ኢሱ19፥18
4፥10 ማቴ
10፥41፤ሮሜ12፥13
4፥12 2ነገ8፥1
4፥16 ዘፍ18፥10
4፥18 ሩት2፥3

ዱን አቆመ።
7እርሷም ሄዳ ይህንኑ ለእግዚአብሔር ሰው
ነገረችው። እርሱም፣ "ሂደሽ ዘይቱን በመ
ሸጥ ዕዳሽን ክፈይ፤ የተረፈውም ለአንቺና
ለልጆችሽ መተዳደሪያ ይሁን" አላት።

## የሱነማዪቱ ልጅ ከሞት ተነሣ

8አንድ ቀን ኤልሳዕ ወደ ሱነም ሄደ።
በዚያም አንዲት ሀብታም ሴት ነበረች፤
እርስዋም ምግብ እንዲበላ አጥብቃ ለመነ
ችው፤ በዚያም ባለፈ ቍጥር ምግብ ለመ
ብላት ወደ ቤቷ ይገባ ነበር። 9ሴቲቱም
ባልዋን እንዲህ አለችው፤ "ይህ አዘውትሮ
በደጃችን የሚያልፍ ሰው፣ ቅዱስ የእግዚ
አብሔር ሰው መሆኑን ዐውቃለሁ፤ 10ስለዚህ
በሰገነቱ ላይ አንዲት ትንሽ ክፍል ቤት
ሠርተን ዐልጋና ጠረጴዛ፣ ወንበርና ፋኖስ
እናስገባለን፤ ከዚያም ወደ እኛ በሚመ
ጣበት ጊዜ ሁሉ ማረፊያ ትሆነዋለች።"
11አንድ ቀን ኤልሳዕ ወደዚያው መጥቶ
ወደ ማረፊያ ክፍሉ በመውጣት ጋደም
አለ። 12አገልጋዩን ግያዝንም፣ "ሱነማዪ
ቱን ጥራት" አለው፤ በጠራትም ጊዜ መጥታ
በፊቱ ቆመች። 13ኤልሳዕም፣ "'ለእኛ ስትይ
በጣም ተቸግረሻል፣ ምን እንዲደረግልሽ
ትፈልጊአለሽ? ለንጉሡ ወይስ ለሰራዊቱ
አዛዥ የምን ነግርልሽ ጕዳይ አለን?'
ብለህ ጠይቃት" አለው።
ሴቲቱም መልሳ፣ "እኔ እኮ የምኖረው
በገዛ ወገኖቼ መካከል ነው" አለችው።
14ኤልሳዕም፣ "ታዲያ ምን ይደረግላት"
ሲል ጠየቀ።
ግያዝም፣ "ልጅ እኮ የላትም፤ ባሏም
ሸምግ ሎአል" አለ።
15ኤልሳዕም፣ "በል እንግዲያው ጥራት"
አለው፤ እርሱም ጠርቶአት መጥታ እበራፉ
ላይ ቆመች። 16ኤልሳዕም የዛሬ ዓመት
በዚሁ ጊዜ ወንድ ልጅ ትታቀፊያለሽ"
አላት፤
እርሷም፣ "አይደለም ጌታዬ፣ ኋላ አገ
ልጋይህን መዋሸት እንዳይሆንብህ? አንተ
የእግዚአብሔር ሰው" አለችው።
17ሴትዮዋም ፀነሰች፤ ኤልሳዕ እንደ ነገ
ራትም በተባለው ጊዜ ወንድ ልጅ ወለ
ደች።
18ሕፃኑ አደገ፤ አንድ ቀንም አባቱ ከዐ
ጫጆች ጋር ወደነበረበት ቦታ ሄደ። 19አባ
ቱንም፣ "ራሴን! ራሴን!" አለው።
አባቱም አገልጋዩን፣ "ተሸክመህ ወደ
እናቱ አድርሰው" አለው።
20አገልጋዩም አንሥቶ እናቱ ዘንድ አደ
ረሰው፤ ልጁም እስከ እኩለ ቀን ድረስ

በእ ናቱ ጭን ላይ ተቀመጠ፤ ከዚያም
ሞተ። 21ወደ ላይ ወጥታም በእግዚአብሔር
ሰው ዐልጋ ላይ አስተኛችው፤ በሩንም
ዘግታበት ወጣች።
22ከዚያም ባሏን ጠርታ፣ “ወደ እግዚአብሔር
ሰው በፍጥነት ደርሼ እንድመለስ አንድ
አገልጋይና አንድ አህያ ላክልኝ” አለችው።
23ባሏም፣ “ዛሬ ወደ እርሱ መሄድ
ለምን አስፈለገሽ? መባቻ ወይም ሰንበት
አይደል” አላት።
እርሷም፣ “ምንም አይደል፤ ልሂድ” አለ
ችው።
24ከዚያም አህያውን ጭና አገልጋይዋን፣
“ቶሎ ቶሎ ንዳ፤ እኔ ካልነገርኩህ በቀር
ለእኔ ብለህ አታዝግም” አለችው። 25ስለዚህ
ተነሥታ የእግዚአብሔር ሰው ወዳለበት ወደ
ቀርሜሎስ ተራራ ሄደች።
የእግዚአብሔር ሰው በሩቁ ሲያያት
አገል ጋዩን ግያዝን እንዲህ አለው፤
“ሱነማዪ ቱን አየሃት፤ ያቻትና!
26በል ሩጠህ ሂድና፣ ምነው ደኅና
አይደለሽምን? ባልሽ ደኅና አይደለምን?
ልጅሽስ ደህና አይደለምን? ብለህ ጠ
ይቃት።”
እርሷ፣ “ሁሉ ነገር ደህና ነው” አለች።
27የእግዚአብሔር ሰው ወዳለበት ተራራ ስት
ደርስም እግሩ ላይ ተጠመጠመች፤ ግያዝ
ሊያስለቅቃት ሲመጣ፣ የእግዚአብሔር ሰው
ግን፣ “እጅግ አዝናለችና ተዋት! *እግዚአ
ብሔር* ይህን ለምን ከእኔ እንደሰወረውና
እንዳልነገረኝ አልገባኝም” አለ።
28እርሷም፣ “ጌታዬ፤ ለመሆኑ እኔ ልጅ
እንድትሰጠኝ ጠይቄህ ነበርን? ‘አጕል
ተስፋ እንዳትሰጠኝ’ አላልሁህምን?”
አለችው።
29ኤልሳዕም ግያዝን፣ “እንግዲህ ወገብ
ህን ታጠቅ፤ በትሬን ያዝና ሩጥ፤ መንገድ
ላይ ሰው ብታገኝ ሰላም አትበል፤ ማንም
ሰው ሰላም ቢልህ መልስ አትስጥ፤ በትሬ
ንም በልጁ ፊት ላይ አድርግ” አለው።
30የልጁ እናት ግን፣ “ሕያው *እግዚአ
ብሔርን* ፤ በሕያው ነፍስህም እምላለሁ፣
ፈጽሞ ትቼህ አልሄድም” አለችው፤ ስለዚህ
ተነሥቶ ተከተላት።
31ግያዝም ቀድሞአቸው ሄዶ በትሩን
በልጁ ፊት ላይ አደረገ፤ ነገር ግን ድም
ፅም፣ ምላሽም አልነበረም። ስለዚህ ግያዝ
ወደ ኤልሳዕ ተመልሶ፣ “ልጁ አልነቃም”
አለው።
32ኤልሳዕ ወደ ቤት ሲገባም ልጁ ሞቶ
በዐልጋው ላይ ተጋድሞ ነበር። 33ወደ ውስ
ጥም ገባ፤ ከዚያም በሩን በራሱና በልጁ
ላይ ዘግቶ ወደ *እግዚአብሔር* ጸለየ።
34በዐልጋው ላይ ወጥቶም በልጁ ላይ ተጋ
ደመና አፉን በአፉ፣ ዐይኑን በዐይኑ፣ እጁን
በእጁ ላይ አደረገ። ሙሉ በሙሉ እንደተ
ዘረጋበትም፣ የልጁ ሰውነት መሞቅ ጀመረ።
35ኤልሳዕም ተነሥቶ በቤቱ ውስጥ ወዲ
ያና ወዲህ ከሄደ በኋላ ወደ ዐልጋው
ወጥቶ እንደ ገና በልጁ ላይ ሙሉ ለሙሉ
ተዘረጋበት፤ ልጁም ሰባት ጊዜ አስነጠሰ
ውና ዐይኖቹን ከፈተ።
36ኤልሳዕም ግያዝን ጠርቶ፣ “ሱነማዪ
ቱን ጥራት፤” አለው፤ እርሱም ጠራት። እንደ
መጣችም፣ “በይ ልጅሽን ውሰጂ” አላት።
37እርሷም ገብታ በእግሩ ላይ ወደቀች፤
በምድርም ላይ ተደፋች፤ ልጇንም ይዛ
ወጣች።

### መርዛሙ ወጥ

38ኤልሳዕ ወደ ጌልገላ ተመለሰ፤ በዚ
ያም አገር ራብ ነበረ። የነቢያት ማኅበር
በፊቱ ተቀምጠው ሳለ አገልጋዩን፣
“ትልቁን ምንቸት ጣድና ለእነዚህ ሰዎች
ወጥ ሥራ ላቸው” አለው።
39ከእነርሱም አንዱ ቅጠላ ቅጠል ለማም
ጣት ወደ ሜዳ ወጥቶ፤ ዱር በቀል ሐረግ
አገኘ፤ ከሐረጉም ላይ የቅል ፍሬ ለቅሞ
በልብሱ ሙሉ ይዞ ተመለሰና ቈራርጦ
በወጡ ምንቸት ውስጥ ጨመረው፤ ምን
እንደሆን ግን ማንም አላወቀም። 40ሰዎቹ
እንዲመገቡትም ወጡ ወጣ፤ ገና አንደ
ቀመሱትም፣ “የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፤ በም
ንቸቱ ውስጥ የሚገድል መርዝ አለ!”
ብለው ጮኹ፤ ሊመገቡትም አልቻሉም።
41ኤልሳዕም፣ “እስቲ ዱቄት አምጡልኝ”
አለ። ያንንም በምንቸቱ ውስጥ ጨምሮ፣
“እንዲመገቡት ለሰዎቹ አቅርቡላቸው” አለ።
በምንቸቱም ውስጥ ጕዳት የሚያስከትል
ነገር አልተገኘም።

### አንድ መቶ ሰው ተመገበ

42አንድ ሰው ከበኵራቱ ፍሬ የተጋገረ
ሃያ የገብስ ሙልሙልና ጥቂት የእሸት
ዛላ ዎች በአቀሚማዳ ይዞ ከበኣልሻሊሻ ወደ
እግዚአብሔር ሰው መጣ። ኤልሳዕም አገልጋ
ዩን፣ “ሰዎቹ እንዲበሉት ስጣቸው” አለው።
43አገልጋዩም፣ “ይህን እንዴት አድርጌ ለመቶ
ሰው አቀርባለሁ?” ሲል ጠየቀ፤
ኤልሳዕ ግን፣ “እንዲበሉት ለሰዎቹ ስጣ
ቸው፤ *እግዚአብሔር*፣ ‘በልተው ይተርፋቸ
ዋል’ ይላልና” አለው። 44ከዚያም አቀረበላ
ቸው፤ *እግዚአብሔር* እንደ ተናገረውም
በልተው ተረፋቸው።

4፥21 ቍ32
4፥23 ዘኍ10፥10፤ 1ዜና23፥31፤መዝ81፥3
4፥25 1ነገ18፥20
4፥27 1ሳሙ1፥15
4፥29 ዘፀ4፥2፤1ነገ 18፥46
4፥32 ቍ21
4፥33 1ነገ17፥20፤ ማቴ6፥6
4፥34 1ነገ17፥21፤ ሐሥ20፥10
4፥35 ኢሱ6፥15፤ 2ነገ8፥5
4፥36 ዕብ11፥35
4፥38 ዘሌ26፥26፤ 2ነገ2፥1፤8፥1
4፥41 ዘፀ15፥25፤ 2ነገ2፥21
4፥42 1ሳሙ9፥4፥7፤ ማቴ14፥17፤ 15፥36
4፥43 ማቴ14፥20፤ ሉቃ9፥13፤ዮሐ6፥12

## ንዕማን ከለምጽ ተፈወሰ

5 በዚህ ጊዜ ንዕማን የሶርያ ንጉሥ ጦር
አዛዥ ነበረ፤ *እግዚአብሔር* በዚህ ሰው
አማካይነት፣ ሶርያ ድልን እንድትጐናጸፍ
ስላደረጋት በጌታው ዘንድ ታላቅና የተከ
በረ ሰው ነበር። ጀግና ወታደር ቢሆንም
ነገር ግን ለምጽ[ለ] ወጥቶበት ነበር።
2አደጋ ጣዮች ከሶርያ ወጥተው፣ ከእስራ
ኤል ምድር አንዲት ልጃገረድ ማረኩ፤
እርሷም የንዕማንን ሚስት ታገለግላት
ነበር። 3እመቤቷንም፣ “ጌታዬ በሰማርያ
ያለውን ነቢይ ሄዶ ቢያገኘው እኮ ከዚህ
ለምጹ ይፈውሰው ነበር” አለቻት።
4ንዕማንም ወደ ጌታው ሄዶ ከእስራኤል
የመጣችው ልጃገረድ ያለችውን ነገረው።
5የሶርያም ንጉሥ፣ “በል እንግዲያው አሁ
ኑኑ ሂድ፤ እኔም ለእስራኤል ንጉሥ ደብ
ዳቤ እጽፋለሁ” አለው፤ ስለዚህ ንዕማን
ዐሥር መክሊት[ሐ] ብር፣ ስድስት ሺህ ሰቅል[መ]
ወርቅና ዐሥር ሙሉ ልብስ ይዞ ሄደ።
6ለእስራኤልም ንጉሥ የያዘው ደብዳቤ፣
“ከአሠቃቂ የቆዳ በሽታው እንድትፈው
ሰው ይህን ደብዳቤ አስይዤ አገልጋዬን
ንዕማንን ወዳንተ ልኬዋለሁ” የሚል ነው።
7የእስራኤልም ንጉሥ ደብዳቤውን ወዲ
ያው እንደአነበበ ልብሱን ቀዶ፣ “ለምጽ
እንድፈውሰው ይህን ሰው ወደ እኔ መላኩ
እኔ ገድዬ ማዳን የምችል አምላክ ሆኜ
ነውን? እንግዲህ ጠብ ሲፈልገኝ እዩ!”
አለ።
8የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ፣ የእስራኤል
ንጉሥ ልብሱን መቅደዱን በሰማ ጊዜ እን
ዲህ ሲል ላከበት፤ “ልብስህን ለምን ቀደ
ድህ? ሰውየው ወደ እኔ ይምጣ፤ ከዚያም
በእስራኤል ነቢይ መኖሩን ያውቃል።”
9ስለዚህ ንዕማን በፈረሶቹና በሠረገሎቹው
ሆኖ በኤልሳዕ ቤት ደጃፍ ሲደርስ ቆመ።
10ኤልሳዕም፣ “ሂድና በዮርዳኖስ ሰባት ጊ
ዜ ታጠብ፤ ሥጋህ ይፈወሳል፤ አንተም
ትነጻ ለህ” ብሎ እንዲነግረው
መልእክተኛ ላከ በት።
11ንዕማን ግን ተቈጥቶ እንዲህ በማለት
ሄደ፤ ‘እኔ እኮ በእርግጥ ወደ እኔ መጥቶ
በመቆም የአምላኩን *የእግዚአብሔርን* ስም
የሚጠራ፣ በእጁም ዳሶ ለምጽ በሽታዬ የሚ
ፈውሰኝ መስሎኝ ነበር። 12ለዚህ ለዚህ
የደማስቆ ወንዞች አባናና ፋርፋር ከየትኞ
ቹም የእስራኤል ውሆች አይሻሉምን?
ለመታጠብ ለመታጠብማ በእነርሱ ታጥቤ
መንጻት አልችልምን?” ስለዚህ በቍጣ ተመ
ለሰ።

5፥1 ዘፍ10፥22፤ ዘፀ4፥6፤ዘኍ12፥10፤ 2ሳሙ10፥19፤ ሉቃ4፥27
5፥2 2ነገ6፥23፤ 13፥20፤24፥2
5፥3 ዘፍ20፥7
5፥5 ቊ22፤ዘፍ 24፥53፤መሳ14፥12፤1 ሳሙ9፥7
5፥7 ዘፍ30፥2፤ዘዳ 32፥39፤1ነገ20፥7፤2ነገ 19፥14
5፥8 1ነገ22፥7
5፥10 ዘፍ33፥3፤ ዘሌ14፥7፤ዩሐ9፥7
5፥11 ዘፀ7፥19
5፥12 ምሳ14፥17፡ 29፤19፥11፤29፥11፤ ኢሳ8፥6
5፥13 2ነገ6፥21፤ 13፥14
5፥14 ዘፍ33፥3፤ ዘፀ4፥7፤ዘሌ14፥7፤ ኢሱ6፥15፤ ኢዮ33፥25
5፥15 ኢሱ2፥11፤ 4፥24፤1ሳሙ9፥7፤ 17፥46
5፥16 ቊ20፡26፤ ዘፍ14፥23፤ዳን5፥17
5፥17 ዘፀ20፥24
5፥18 2ነገ7፥2
5፥19 1ሳሙ1፥17፤ ሐሥ15፥33
5፥20 ዘፀ20፥7
5፥22 ቊ5፤ዘፍ 45፥22

13የንዕማን አገልጋዮች ግን ወደ እርሱ
ቀርበው፣ “አባት ሆይ፤ ነቢዩ ከዚህ ከበድ
ያለ ነገር እንድታደርግ ቢነግርህ ኖሮ አታ
ደርገውም ነበርን? ታዲያ፣ ‘ታጠብና ንጻ’
ቢልህ ምኑ አስቸገረህ?” አሉት። 14ስለዚህ
ንዕማን ወረደ፤ የእግዚአብሔር ሰው እንደ
ነገረውም በዮርዳኖስ ሰባት ጊዜ ብቅ ጥልቅ
አለ፤ ሥጋውም እንደ ትንሽ ልጅ ሥጋ
ሆነ፤ ነጻም።
15ከዚያም ንዕማን ከጭፍሮቹ ሁሉ ጋር
ወደ እግዚአብሔር ሰው ተመልሶ ሄደ፤ በፊ
ቱም ቆሞ፣ “እነሆ በእስራኤል አገር እንጂ
በዓለም ሁሉ ሌላ አምላክ አለመኖሩን ተረ
ድቻለሁ፤ ስለዚህ አሁንም ከአገልጋይህ
ስጦታ እንድ ትቀበል እለምንሃለሁ” አለው።
16ነቢዩም፣ “የማገለግለውን ሕያው *እግዚአ
ብሔርን*፣ ምንም ነገር አልቀበልም” ሲል
መለሰ። ምንም እንኳ ንዕማን አስጨንቆ
ቢለምነውም አልተቀበለም። 17ንዕማንም
እንዲህ አለው፤ “ስጦታውን የማትቀበል
ከሆነ፣ ለማንኛውም አምላክ የሚቃጠል
ወይም ሌላ መሥዋዕት ስለማላቀርብ፣ ሁለት
የበቅሎ ጭነት ዐፈር እንድወስድ ትፈቅድ
ልኝ ዘንድ እለምንሃለሁ። 18ነገር ግን *እግ
ዚአብሔር* ስለ አንድ ነገር ብቻ አገልጋይ
ህን ይቅር ይበለው፤ ይኸውም ጌታዬ ለመ
ስገድ ወደ ሬሞን ቤተ ጣዖት በሚገባበት
ጊዜ ክንዴን ሲደገፍ እኔም እንደ እርሱ
በዚያ ብሰግድ፣ በሬሞን ቤተ ጣዖት በመ
ስገዴ *እግዚአብሔር* አገልጋይህን ይቅር
ይበለው።”
19ኤልሳዕም፣ “በሰላም ሂድ” አለው። ንዕ
ማን ጥቂት ራቅ ብሎ እንደ ሄደ፣ 20የእግ
ዚአብሔር ሰው አገልጋይ ግያዝ፣ “ጌታዬ፣
ይህ ሶርያዊ ንዕማን ያመጣውን አለመቀ
በሉ ደግም አይደል፤ ሕያው *እግዚአብሔ
ርን*! ተከትዬ ሂጄ ከእርሱ አንድ ነገር
ማግኘት አለብኝ” ብሎ አሰበ።
21ስለዚህ ግያዝ ንዕማንን ተከተለው፤ ንዕ
ማንም ግያዝ እየሮጠ ወደ እርሱ መም
ጣቱን ባየ ጊዜ፣ ሊገናኘው ከሠረገላው
ወርዶ፣ “ምነው፤ በደኅና መጣህን?” ሲል ጠየ
ቀው።
22ግያዝም፣ “ሁሉም ደኅና ነው፤ ግን
ጌታዬ፣ ‘ከነቢያት ማኅበር ሁለት ወጣ
ቶች ከኰረብታማው አገር ከኤፍሬም ወደ
እኔ አሁን በድንገት ስለመጡ፣ ‘እባክህ

[ለ]1 በዚህ ስፍራ እንዲሁም በቍጥር 3፡6፡7፡11 እና 12 ላይ የዕብራይስጡ ቃል ቆዳን የሚያጠቁ በሽታዎች ሁሉ የሚያሳይ ነው።
[ሐ]5 340 ኪሎ ግራም ያህል ነው።
[መ]5 70 ኪሎ ግራም ያህል ነው።

አንድ መክሊት[ሠ] ብርና ሁለት ሙሉ ልብስ
ስጣቸው ብለህ ንገር’ ብሎ ልኮኛል’ አለው።
[23]ንዕማንም፣ “እባክህ ሁለት መክሊት
ውሰድ” በማለት ግያዝን አስጨንቆ ለመ
ነው። ከዚያም ሁለቱን መክሊት ብር፣
በሁለት ከረጢት ውስጥ አስሮ ሁለት ሙሉ
ልብስ ጨምሮ ለሁለት አገልጋዮቹ አስ
ያዘ፤ እነርሱም ያን ተሸክመው ከግያዝ
ፊት ፊት ሄዱ። [24]ግያዝም ወደ ኰረብ
ታው እንደ ደረሰ፣ ዕቃዎቹን ከአገልጋ
ዮቹ ተቀብሎ በቤቱ ውስጥ አስቀመጠ፤
ሰዎቹንም አሰናብቶአቸው ሄዱ። [25]ከዚ
ያም ገብቶ በጌታው በኤልሳዕ ፊት ቆመ።
ኤልሳዕም፣ “ግያዝ ሆይ፤ የት ነበርህ?”
ሲል ጠየቀው።
ግያዝም፣ “አገልጋይህ የትም አልሄ
ደም” ብሎ መለሰ።
[26]ኤልሳዕ ግን እንዲህ አለው፤ “ያ ሰው
ሊገናኝህ ከሠረገላው ሲወርድ መንፈሴ
ከአንተ ጋር አልሄደምን? እንዲያው ለመ
ሆኑ ጊዜው ገንዘብና ልብስ፣ የወይራ ዘይት
ተክልና የወይን ተክል ቦታ፣ የበግና የከ
ብት መንጋ፣ ወንድና ሴት አገልጋይ የሚ
ቀበሉበት ነውን? [27]ስለዚህ የንዕማን ለምጽ
በአንተ ላይ ይጣበቃል፤ ለዘላለምም ወደ
ዘርህ ይተላለፋል።” ከዚያም ግያዝ ከኤል
ሳዕ ፊት ወጣ፤ እንደ በረዶ እስኪነጣም
ድረስ ለምጻም ሆኖ ወጣ።

### መጥረቢያው ተንሳፈፈ

6 የነቢያት ማኅበር ኤልሳዕን እንዲህ
አሉት፤ “እነሆ፣ በፊትህ የምንቀመጥ
በት ስፍራ ጠቦናል፤ [2]ስለዚህ ወደ ዮርዳ
ኖስ ሄደን፣ እያንዳንዳችን ምሰሶ ቈርጠን
እናምጣ፣ በዚያም የምንቀመጥበትን መኖ
ሪያ እንሥራ።”
እርሱም፣ “ይሁን ሂዱ” አላቸው።
[3]ከመካከላቸውም አንዱ፣ “አንተስ ከአገ
ልጋዮችህ ጋር አትመጣምን?”አለው።
ኤልሳዕም፣ “እሺ እሄዳለሁ” አለ፤ [4]አብ
ሮአቸውም ሄደ። ወደ ዮርዳኖስም ሄደው
ዛፎች መቈረጥ ጀመሩ። [5]ከእነርሱም
አንዱ ዛፍ እየቈረጠ ሳለ፣ መጥረቢያው
በሮ ከውሃው ውስጥ ወደቀ፤ እርሱም፣
“አየ ጕድ ጌታዬ፤ የተውሶ መጥረቢያ እኮ
ነው!” ብሎ ጮኸ።
[6]የእግዚአብሔርም ሰው፣ “በየት በኩል
ነው የወደቀው?” ሲል ጠየቀ። ቦታውን
ባሳየ ውም ጊዜ ኤልሳዕ እንጨት ቈርጦ
ወደ ውሃው ውስጥ በመጣል መጥረቢያውን
እን ዲንሳፈፍ አደረገው። [7]ከዚያም፣ “በል
አው ጣና ውሰደው” አለው፤ ሰውየውም እ
ጁን ዘርግቶ ወሰደው።

### ኤልሳዕ ሶርያውያንን አሳወረ

[8]በዚህ ጊዜ የሶርያ ንጉሥ ከእስራኤል
ጋር ይዋጋ ነበር፤ ከጦር አለቆቹ ጋር
ከተመካከረ በኋላም፣ “በዚህ፣ በዚህ ቦታ
እሰፍራለሁ” አለ።
[9]የእግዚአብሔርም ሰው፣ “ሶርያውያን በዚያ
ታች ወርደዋልና በዚያ በኩል እንዳታልፍ
ተጠንቀቅ” ሲል ለእስራኤል ንጉሥ ላከ
በት።
[10]ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ የእግዚአብሔር
ሰው የነገረውን ቦታ አስቃኘ፤ ኤልሳዕም
ንጉሡን እንደዚህ ካሉት ቦታዎች ራሱን
እንዲጠብቅ ከአንድ ሁለት ጊዜ በላይ
አስጠነቀቀው።
[11]ይህም የሶርያን ንጉሥ እጅግ ስላበሳ
ጨው፣ የጦር አለቆቹን ጠርቶ፣ “ከመካከ
ላችን ከእስራኤል ንጉሥ ጋር የተወዳጀ
እንዳለ ለምን አትነግሩኝም?” ሲል ጠየቃ
ቸው።
[12]ከጦር አለቆቹም አንዱ፣ “ንጉሥ ጌታዬ
ሆይ፤ ከእኛ በኩል ማንም ሰው የለም፤
ነገር ግን አንተ በእልፍኝህ ሆነህ እንኳ
የምትናገረውን አንዲቱም ሳትቀር ለእስራ
ኤል ንጉሥ የሚነግረው በእስራኤል ያለው
ነቢዩ ኤልሳዕ ነው” አለው።
[13]ንጉሡም፣ “ሰዎች ልኬ እንዳስይዘው፣
የት እንደሚገኝ ፈልጉ” ሲል አዘዘ። ከዚ
ያም፣ “በዶታይን ይገኛል”የሚል ዜና ደረ
ሰው። [14]ስለዚህ ፈረሶችና ሠረገሎች እንዲ
ሁም ብዙ ሰራዊት ወደዚያ ላከ። እነር
ሱም በሌሊት ደርሰው ከተማዪቱን ከበቡ።
[15]የእግዚአብሔር ሰው አገልጋይ በማለዳ
ተነሥቶ ወደ ውጭ ሲወጣ፣ በፈረሶችና
በሠረገሎች የተጠናከረ ሰራዊት ከተማዪ
ቱን ከቧት ነበር። አገልጋዩም “ጌታዬ
ሆይ፤ ምን ማድረግ ይሻለናል?” ሲል ጠየቀ።
[16]ነቢዩም፣ “ከእኛ ጋር ያሉት ከእነርሱ
ጋር ካሉት ይበልጣሉና አትፍራ” አለው።
[17]ኤልሳዕም፣ “ *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ያይ
ዘንድ እባክህ ዐይኖቹን ክፈትለት” ብሎ
ጸለየ፤ *እግዚአብሔርም* የአገልጋዩን ዐይ
ኖች ከፈተለት፤ ሲመለከትም፤ የእሳት
ፈረሶችና ሠረገሎች በኤልሳዕ ዙሪያ ተራ
ራውን ሞልተውት አየ።
[18]ሶርያውያንም ወርደው ወደ እርሱ
ሲመጡ ኤልሳዕ፣ “ይህን ሕዝብ ዕውር
አድርገው” ብሎ ወደ *እግዚአብሔር* ጸለየ።
ስለዚህ ኤልሳዕ በጠየቀው መሠረት እግዚ
አብሔር ዕውር አደረጋቸው።

5፥26 ቍ16፤ ኤር45፥5
5፥27 ዘፀ4፥6፤ ዘኍ12፥10፤ቈላ3፥5
6፥1 1ሳሙ10፥5
6፥6 ዘፀ15፥25፤ 2ነገ2፥21
6፥9 ቍ12
6፥10 ኤር11፥18
6፥12 ቍ9
6፥13 ዘፍ37፥17
6፥14 2ነገ1፥9
6፥16 ዘፍ15፥1፤ 2ዜና32፥7፤መዝ 55፥18፤1ዮሐ4፥4፤ ሮሜ8፥31
6፥17 2ነገ2፥11፡12
6፥18 ዘፍ19፥11፤ ሐሥ 13፥11

[ሠ] 22 34 ኪሎ ግራም ያህል ነው።

19ኤልሳዕም፣ “መንገዱ በዚህ
አይደለም፤ ከተማዪቱም ይህች
አይደለችም፤ ወደ ምት ፈልጉት ሰው
መርቼ እንዳደርሳ ችሁም እኔን
ተከተሉኝ” አላቸው፡፡ ከዚያም መርቶ ወደ
ሰማርያ ወሰዳቸው፡፡
20ወደ ከተማዪቱም ከገቡ በኋላ ኤል
ሳዕ፣ “*እግዚአብሔር* ሆይ፤ እንዲያዩ የእነ
ዚህን ሰዎች ዐይን ክፈት” አለ፡፡ *እግዚአ
ብሔርም* ዐይኖቻቸውን ከፈተ፡፡ እነርሱም
በሰማርያ ውስጥ መሆናቸውን አዩ፡፡
21የእስራኤልም ንጉሥ ባያቸው ጊዜ፣
“አባቴ ሆይ፤ ልግደላቸውን? ልፍጃቸውን”
ብሎ ኤልሳዕን ጠየቀው፡፡ 22እርሱም፣
“አትግደላቸው፤ ለመሆኑ በሰይፍህና በቀስ
ትህ የማረክሃቸውን ትገድላቸው ዘንድ ይገ
ባሃልን? አሁንም የሚበሉትንና የሚጠጡ
ትን አስቀርብላቸው፤ በልተው ጠጥተ
ውም ወደ ጌታቸውም ይሂዱ” አለው፡፡
23ስለዚህ ታላቅ ግብዣ አዘጋጅቶላቸው ከበ
ሉና ከጠጡ በኋላ አሰናብቶአቸው ወደ
ጌታቸው ሄዱ፡፡ የሶርያ አደጋ ጣዮችም
የእስራኤልን ምድር ለመውረር ከዚያ
በኋላ አልተመለሱም፡፡

## በተከበበችው ሰማርያ የተከሠተ ራብ

24ከጥቂት ጊዜ በኋላም የሶርያ ንጉሥ
ቤንሐዳድ ሰራዊቱን ሁሉ ሰበሰበ፤ ወጥቶም
ሰማርያን ከበባት፡፡ 25ከተማዪቱን እንደ
ከበባትም የአንድ አህያ ጭንቅላት በሰማ
ኒያ ሰቅል[ረ] ብር፣ የጎሞር አንድ ስምንተኛ[ሰ]
የርግብ ኵስ[ሸ] በአምስት ሰቅል[ቀ] ብር እስኪ
ሸጥ ድረስ ታላቅ ራብ ሆነ፡፡
26የእስራኤልም ንጉሥ በቅጥሩ ላይ
በሚ መላለስበት ጊዜ አንዲት ሴት
ድምፅዋን ከፍ አድርጋ “ጌታዬ፣ ንጉሥ
ሆይ፤ እባ ክህ ርዳኝ!” አለች፡፡
27ንጉሡም፣ “*እግዚአብሔር* ካልረዳሽ እኔ
እንዴት ልረዳሽ እችላለሁ? ከዐውድማው
ነው ወይስ ከወይን መጥመቂያው የምረ
ዳሽ?” ሲል መለሰላት፡፡ 28ከዚያም፣ “ለመ
ሆኑ ችግርሽ ምንድነው?” ሲል ጠየቃት፡፡
እርሷም እንዲህ ስትል መለሰችለት፤
“ይህች ሴት፣ ‘ዛሬ እንድንበላው ልጅሽን
አምጪው፤ ነገ ደግሞ የእኔን ልጅ እን
በላዋለን’ አለችኝ፡፡ 29ስለዚህ ልጄን ቀቅ
ለን በላ ነው፡፡ በማግሥቱም፣ ‘እንድንበ
ላው ልጅሽን አምጪው’ አልኋት፤ እርታ
ግን ደበቀችው፡፡”
30ንጉሡም ሴቲቱ ያለችውን ሲሰማ ልብ
ሱን ቀደደ፤ በቅጥሩ ላይ በሚመላለስ
በትም ጊዜ በውስጥ ማቅ መልበሱን ሕዝቡ
አየ፡፡ 31ንጉሡም፣ “የሣፋጥ ልጅ የኤልሳዕ

6፥21 2ነገ5፥13
6፥22 ዘዳ20፥11፤ 2ዜና28፥8-15
6፥23 2ነገ5፥2
6፥24 ዘዳ28፥52፤ 1ነገ15፥18፤2ነገ 8፥7
6፥25 ዘሌ26፥26፤ ሩት1፥1፤ኢሳ 36፥12
6፥29 ዘሌ26፥29፤ ዘዳ28፥53-55
6፥30 ዘፍ37፥34፤ 2ነገ18፥37፤ኢሳ 22፥15
6፥32 ቀኊ31፤1ነገ 18፥4፤ሕዝ8፥1፤ 14፥1፤20፥1
6፥33 ዘሌ24፥11፤ ኢዩ 2፥9፤ 14፥14፤ ኢሳ 40፥31
7፥1 ቀኊ16
7፥2 ቀኊ17፥19፤ ዘፍ7፥11፤2ነገ5፥18፤ መዝ78፥23፤ ሚል3፥10
7፥3 ዘሌ13፥45-46፤ ዘኊ5፥14
7፥6 ዘፀ14፥24፤ ዘኊ13፥29፤2ሳሙ 10፥6፤ኤር46፥21፤ ሕዝ1፥24

ራስ ዛሬ በዕንገቱ ላይ ካደረ፣ እግዚአብሔር
ይህን ያድርግብኝ፤ ከዚህም የባሰ ያምጣ
ብኝ” ብሎ ዛተ፡፡
32በዚህ ጊዜ ኤልሳዕ በቤቱ ተቀምጦ
ነበር፤ ሽማግሌዎችም አብረውት ተቀምጠው
ነበር፡፡ ንጉሡም መልእክተኛ ቀድሞት እን
ዲሄድ አደረገ፡፡ የተላከውም ሰው ከመድ
ረሱ በፊት ኤልሳዕ ለሽማግሌዎቹ፣ “ይህ
ነፍሰ ገዳይ ራሴን ለመቊረጥ ሰው መላ
ኩን ታያላችሁ? እነሆ፤ አሁንም መልእክ
ተኛው ሲደርስ በሩን ዘግታችሁ እንዳይገባ
አድርጉ፡፡ የጌታው የእግሩ ኮቴ ከኋላው
ይሰማ የለምን?” አላቸው፡፡
33ኤልሳዕ ከሽማግሌዎቹ ጋር በመነጋገር
ላይ ሳለም፣ መልእክተኛው ወደ እርሱ
ወረደ፡፡ ንጉሡም ደርሶ፣ “ይህ ጥፋት የመ
ጣው *ከእግዚአብሔር* ነው፤ ታዲያ እኔ
*ከእግዚአብሔር* ምን እጠብቃለሁ?” አለ፡፡

7 ኤልሳዕም፣ “እንግዲህ *የእግዚአብሔ
ርን* ቃል ስማ፤ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤ ‘በነገው ዕለት በዚሁ ሰዓት፣ በሰማ
ርያ በር አንድ መስፈሪያ ማለፊያ ዱቄት
በአንድ ሰቅል፣ ሁለት መስፈሪያ ገብስም
በአንድ ሰቅል ይሸጣል’”አለ፡፡
2ንጉሡ በክንዱ ላይ የተደገፈውም የጦር
አለቃ፣ የእግዚአብሔርን ሰው፣ “እንዲያው
ለመሆኑ፣ *እግዚአብሔር* የሰማያትን መስ
ኮቶች ቢከፍት እንኳ ይህ ሊሆን ይችላ
ልን?” ሲል ጠየቀው፡፡
ኤልሳዕም፣ “ይህን አንተው ራስህ በዐ
ይንህ ታየዋለህ፤ ይሁን እንጂ ከዚያ አን
ዳች አትቀምስም” አለው፡፡

## ከበባው ተወገደ

3በዚህ ጊዜ የሚያሠቅቅ የቆዳ በሽታ
የያዛቸው አራት ሰዎች በከተማዪቱ መግ
ቢያ በር አጠገብ ነበሩ፤ እነርሱም እርስ
በርሳቸው እንዲህ ተባባሉ፤ “እስክንሞት
ድረስ በዚህ የምንቆየው ለምንድን ነው?
4ታዲያ፣ ‘ወደ ከተማዪቱ እንግባ ብንል’
በዚያም ራብ ስላለ እንሞታለን፤ በዚሁም
ብንሆን ያው መሞታችን እንደሁ አልቀ
ረም፤ ስለዚህ ወደ ሶርያውያኑ ሰፈር ዝም
ብለን እንሂድ፤ ዝም ካሉን ሕይወታችን
ትተርፋለች፤ ከገደሉንም ያው ሞቶ መገላ
ገል ነው፡፡”
5ከዚያም መሸትሸት ሲል ተነሥተው
ወደ ሶርያውያን ሰፈር ሄዱ፤ ወደ ሰፈሩ
ጥግ ሲደርሱም አንድም ሰው በዚያ አል
ነበረም፡፡ 6ይህ የሆነበትም ምክንያት
እግዚ

[ረ]25 1 ኪሎ ግራም ያህል ነው፡፡ [ሰ]25 0.3 ሊትር ያህል ነው፡፡
[ሸ]25 ወይም፣ *ጥሬ* [ቀ]25 55 ግራም ያህል ነው፡፡

አብሔር የሠረገሎችንና የፈረሶችን እንዲ
ሁም የብዙ ሰራዊት ድምፅ ሶርያውያን
እንዲሰሙ አድርጎ ስለነበር ነው፤ እርስ
በእርሳቸው፣ “እነሆ፣ የእስራኤል ንጉሥ
በእኛ ላይ አደጋ ለመጣል፣ የኬጢያውያን
ንና የግብፃውያንን ነገሥታት ቀጥሮ አም
ጥቶብናል” ተባባሉ:: 7ከዚያም መሸትሸት
ሲል ተነሥተው ሸሹ፤ ድንኳኖቻቸውን፣
ፈረሶቻቸውንና አህዮቻቸውንም አልወሰ
ዱም ነፍሳቸውን ብቻ ለማዳን ሲሉ ሰፈሩን
እንዲሁ እንዳለ ትተው ሄዱ::
8ለምጽ ያለባቸውም ሰዎች ወደ ሰፈሩ
አጠገብ ከደረሱ በኋላ፣ ከድንኳኖቹ ወደ
አንዱ ገብተው በሉ፤ ጠጡም፤ ከዚያም
ብር፣ ወርቅና ልብስ ይዘው በመሄድ ደበ
ቁት:: ተመልሰው በመምጣትም ወደ
ሌላው ድንኳን ገብተው ሌሎች ነገሮችን
በመውሰድ እንደዚሁ ደበቁ::
9እርስ በርሳቸውም፣ “ያደረግነው ትክ
ክል አይደለም፤ ዕለቱ የምሥራች ቀን
ነው፤ እኛ ግን የራሳችን ብቻ አደረግነው፤
እስኪነጋም ከቈየን በደለኞች እንሆናለን፤
ስለዚህ ወደ ቤተ መንግሥት በፍጥነት
ሄደን እንንገር” ተባባሉ::
10ስለዚህ ሄደው የከተማዪቱን መግቢያ
በር ጠባቂዎች ጮኸው በመጥራት፣ “ወደ
ሶርያውያን ሰፈር ገባን፤ እዚያም ከታሰሩ
ፈረሶችና አህዮች በቀር አንድም ሰው
አልነበረም፤ የማንም ድምፅ አልተሰማም፤
ድንኳኖቹም እንዳሉ ናቸው” ብለው
ነገ ሯአቸው:: 11የበሩ ጠባቂዎችም
ይህንኑ አስተጋቡ፤ ዜናውም በቤተ
መንግሥቱ ተሰማ::
12ንጉሡም በሌሊት ተነሥቶ ለጦር አለ
ቆቹ እንዲህ አላቸው፤ “ሶርያውያን ያደረ
ጉብንን እነግራችኋለሁ፤ መራባችንን ስለ
ሚያውቁ፣ ‘መቼም መውጣታቸው አይቀ
ርም፤ ከዚያም ከነሕይወታቸው እንማርካ
ቸዋለን፤ እኛም ሰተት ብለን ወደ ከተማ
ዪቱ እንገባለን’ በማለት በገጠር ለመደበቅ
ከሰፈራቸው ወጥተዋል::”
13ከጦር አለቆቹም አንዱ እንዲህ አለ፤
“ጥቂት ሰዎች በከተማዪቱ ውስጥ ከተረ
ፉት ፈረሶች አምስቱን ይዘው ይሂዱ፤ ዕጣ
ፈንታቸውም በዚህ ከቀሩት እስራኤላው
ያን ሁሉ ዕድል ጋር አንድ ነው፤ የሚጠ
ብቃቸው ቢኖር በዚህ በሙሉ እንዳለቁት
እስራኤላውያን መሆን ብቻ ነው፤ ስለዚህ
እንላካቸውና የሆነውን እንይ::”
14ስለዚህ ሁለት ሠረገሎች ከነፈረሶቻ
ቸው መረጡ፤ ንጉሡም፣ “ሂዱና የሆነውን
ነገር እዩ” ብሎ ከሶርያውያን ሰራዊት
በኋላ እንዲሄዱ ላካቸው:: 15እነርሱም እስከ
ዮርዳኖስ ድረስ ተከተሏቸው:: ሶርያው
ያን በጥድፊያ ሲሸሹ፣ የጣሉትንም ልብ
ስና ዕቃ በየመንገዱ ላይ ተበታትኖ አገኙ፤
መልክተኞቹም ተመልሰው ይህንኑ ለንጉሡ
ነገሩት:: 16ከዚያም ሕዝቡ ወጥቶ የሶርያ
ውያንን ሰፈር በዘበዘ፤ ስለዚህ *እግዚአብሔር*
እንደ ተናገረው አንድ መስፈሪያ ማለፊያ
ዱቄት በአንድ ሰቅል፣ ሁለት መስፈሪያ
ገብስም በአንድ ሰቅል ተሸጠ::
17በዚህ ጊዜ ንጉሡ እጁን ይደግፈው
የነበረውን የጦር አለቃ፣ የቅጥሩ በር
ኀላፊ አድርጎት ነበርና በበራፉ መተላለ
ፊያ ላይ ሕዝቡ ሲጋፋ ረጋገጠው፤ ያ የእግ
ዚአብሔር ሰው ንጉሡ ወደ እርሱ በመጣ
ጊዜ አስቀድሞ እንደተናገረውም የጦር
አለቃው ሞተ:: 18እንዲሁም የእግዚአብሔር
ሰው ለንጉሡ፣ “ነገ በዚሁ ሰዓት በሰማርያ
በር ላይ አንድ መስፈሪያ ዱቄት በአንድ
ሰቅል፣ ሁለት መስፈሪያ ገብስም በአንድ
ሰቅል ይሸጣል” ያለውም ተፈጸመ::
19የጦር አለቃው *ለእግዚአብሔር* ሰው፣
“እግዚአብሔር የሰማይን መስኮቶች ቢከፍት
እንኳ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?” ብሎት
ስለነበር፣ *የእግዚአብሔር* ሰው፣ “ይህን
አንተው ራስህ ታያለህ፤ ከዚህ ግን አንዳች
አትበላም” ሲል መልሶለት ነበር:: 20በበሩ
መተላለፊያ ላይ ሕዝቡ ረጋግጦት ስለሞ
ተም፣ የተነገረበት በትክክል ደረሰ::

## የሱነማዪቱ ርስት ተመለሰ

8 በዚህ ጊዜ ኤልሳዕ፣ ልጇ ከሞት ያስነ
ሣላትን ሴት፣ “*እግዚአብሔር* በምድ
ሪቱ ላይ የሰባት ዓመት ራብ ስለ ወሰነ፣
ተነሺና ለጊዜው መቈየት ወደምትችዪ
በት ቦታ ከቤተሰብሽ ጋር ሂጂ” አላት::
2ሴቲቱም ተነሥታ የእግዚአብሔር ሰው እንደ
ነገራት አደረገች፤ ከነቤተሰቧም ሄዳ፣ በፍ
ልስጥኤም ምድር ሰባት ዓመት ተቀመጠች::
3ከሰባት ዓመት በኋላም፣ ከፍልስጥኤም
ምድር ተመልሳ መጣች፤ ስለ ቤቷና ስለ
መሬቷ አቤቱታ ለማቅረብ፣ ወደ ንጉሡ
ሄደች:: 4በዚህ ጊዜ ንጉሡ የእግዚአብሔርን
ሰው አገልጋይ ግያዝን፣ “ኤልሳዕ ያደረ
ጋቸውን ታላላቅ ሥራዎች ሁሉ እስቲ
ንገረኝ” እያለው ነበር:: 5ኤልሳዕ ልጇን
ከሞት ያስነሣላት ሴት ስለ ቤቷና ስለ

7፥7 መሳ7፥21፤ መዝ48፥46፤ምሳ28፥1፤ ኢሳ30፥17
7፥8 ኢሳ33፥23፤ 35፥6
7፥12 ኢሱ8፥4
7፥15 ኢዮ27፥22
7፥16 ቍ1፤ኢሳ 33፥4፡23
7፥17 ቍ2
7፥19 ቍ2
8፥1 ዘፍ12፥10፤ ዘሌ26፥26፤ዘዳ 28፥22፤ሩት1፥1፤ 2ነገ4፥8-37
8፥5 2ነገ4፥35

ሀ1 በዚህ እንዲሁም በቍጥር 16 እና 18 ላይ 7.3 ሊትር ያህል ነው::
ተ1 በዚህ እንዲሁም በቍጥር 16 እና 18 ላይ 11 ግራም ያህል ነው
ቶ1 በዚህ እንዲሁም በቍጥር 16 እና 18 ላይ 15 ሊትር ያህል ነው
ኀ3 በዚህ እና በቍጥር 8 ላይ የዕብራይስጡ ቃል ቆዳን የሚያጠቁን በሽታዎች ሁሉ የሚያሳይ ነው::

መሬቷ ለማመልከት ወደ ንጉሡ ዘንድ
የቀረበችውም፣ ኤልሳዕ የሞተውን ልጅ
እንዴት እንዳስ ነሣ፣ ግያዝ ለንጉሡ በሚ
ነግርበት ወቅት ነበር።
ግያዝም፣ "ንጉሥ ጌታዬ ሆይ፤ ሴቲቱ
ይህች ናት፤ ኤልሳዕ ከሞት ያስነሣው
ልጇም ይህ ነው" አለ። 6ንጉሡም ስለዚሁ
ጒዳይ ጠየቃትና ነገረችው።
ከዚያም ንጉሡ፣ "የነበራትን ሁሉ እን
ዲሁም ትታ ከሄደችበት ጊዜ አንሥቶ
እስካሁን ድረስ ያለውን የዕርሻዋን ሰብል
በሙሉ እንድትመልስላት" ሲል አንድ ሹም
አዘዘላት።

## አዛሄል ቤንሃዳድን ገደለ

7ኤልሳዕ ወደ ደማስቆ ሄደ፤ በዚያን
ጊዜም የሶርያ ንጉሥ ቤንሃዳድ ታሞ ነበር፤
ለንጉሡም፣ "የእግዚአብሔር ሰው ወደዚህ
መጥ ቶአል ብለው ነገሩት። 8እርሱም
አዛሄ ልን፣ "ገጸበረከት ይዘህ ሂድና የእግዚ
አብሔ ርን ሰው ተገናኘው። በእርሱም አ
ማካይ ነት፣ 'ከዚህ በሽታ እድናለሁን?'
ብለህ *እግዚአብሔርን* ጠይቅ" አለው።
9አዛሄልም ደማስቆ ካፈራቻቸው ምርጥ
ነገሮች ሁሉ የአርባ ግመል ጭነት ገ
ጸ በረ ከት ይዞ ኤልሳዕን ለመገናኘት ሄደ።
ሄዶም እፊቱ ቆመና፣ "የሶርያ ንጉሥ
ልጅህ ቤን ሃዳድ፣ 'ከዚህ በሽታ
እድናለሁን?' ሲል ወደ አንተ ልኮኛል"
አለው። 10ኤልሳዕም፣ "ሂድና፣
'*መዳኑንስ በእርግጥ ትድናለህ*' በለው፤
*ነገር ግን እንደሚሞት እግዚአብሔር
ገልጦልኛል*'" ሲል መለሰለት። 11እስኪያ
ፍር ድረስም፣ አዛሄልን ትኵር ብሎ ተመ
ለከተው፤ ከዚያም የእግዚአብሔር ሰው እንባ
ውን አፈሰሰ።
12አዛሄልም፣ "ጌታዬ የሚያለቅሰው ለም
ንድን ነው?"ሲል ጠየቀ።
ኤልሳዕም መልሶ፣ "በእስራኤላውያን
ላይ የምታደርሰውን ጒዳት ስለማውቅ
ነው፤ ምሽጎቻቸውን በእሳት ታቃጥላለህ፤
ጐልማሶቻቸውን በሰይፍ ትገድላለህ፤
ሕፃናታቸውን በምድር ላይ ትፈጠፍጣለህ፤
ያረገዙ ሴቶቻቸውንም ሆድ ትቀድዳለህ"
አለው።
13አዛሄልም፣ "ለመሆኑ እንደ ውሻ የሚ
ቈጠር አገልጋይህ ይህን ጀብዱ መፈጸም
እንዴት ይችላል?" አለ።
ኤልሳዕም መልሶ፣ "መቼም አንተ በሶ
ርያ ላይ እንደምትነግሥ *እግዚአብሔር*
አሳይቶኛል" አለው።
14ከዚያም አዛሄል ከኤልሳዕ ዘንድ ወጥቶ

8፥7 2ሳሙ8፥5፤ 2ነገ6፥24
8፥8 ዘፍ32፥20፤ መሳ18፥5፤1ሳሙ9፥7፤ 1ነገ19፥15
8፥10 ኢሳ38፥1
8፥11 መሳ3፥25፤ ሉቃ19፥41
8፥12 ዘፍ34፥29፤ 1ነገ19፥17፤2ነገ 15፥16፤መዝ137፥9፤ ኢሳ13፥16፤ ሆሴ13፥16፤አሞ 1፥13፤ናሆ3፥10፤ ሉቃ19፥44
8፥13 1ሳሙ 17፥43፤2ሳሙ3፥8፤ 1ነገ19፥15
8፥15 2ነገ1፥17
8፥16 2ነገ1፥17፤ 2ዜና21፥14
8፥18 ቊ26፤ 2ነገ11፥1
8፥19 ዘፍ6፥13፤ 2ሳሙ21፥17፤ ራእ21፥23
8፥20 1ነገ22፥47
8፥22 ዘፍ27፥40፤ ዘኍ33፥20፤ ኢሱ21፥13፤ 2ነገ19፥8
8፥25 2ነገ9፥29
8፥26 ቊ18፤1ነገ 16፥23
8፥27 1ነገ15፥26፤ 16፥30

ወደ ጌታው ተመለሰ፤ ቤንሀዳድም፣ "ለመ
ሆኑ ኤልሳዕ ምን አለህ?" ሲል ጠየቀው፤
አዛሄልም፣ "በእርግጥ ከበሽታህ እንደም
ትድን ነግሮኛል" አለው። 15በማግስቱ ግን
ወፍራም ልብስ ወስዶ በውሃ ከነከረ በኋላ
የንጉሡን ፊት ሸፈነው፤ ንጉሡም በዚሁ
ሞተ፤ ከዚያም አዛሄል በእግሩ ተተክቶ
ነገሠ።

## የይሁዳ ንጉሥ ኢዮራም

8፥16-24 ተጓ-ምብ 2ዜና21፥5-10፡20

16የእስራኤል ንጉሥ የአክዓብ ልጅ ኢዮ
ሆራም በነገሠ በአምስተኛው ዓመት፣ የኢ
ዮሣፍጥ ልጅ ኢዮራም በይሁዳ ነገሠ።
17እርሱም ሲነግሥ ዕድሜው ሠላሳ ሁለት
ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም
ስምንት ዓመት ገዛ። 18ያገባት የአክዓብ
ልጅ ስለ ነበረች የአክዓብ ቤት እንዳደ
ረገው ሁሉ፣ እርሱም የእስራኤልን ነገሥ
ታት መንገድ ተከተለ፤ *በእግዚአብሔርም*
ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸመ። 19ይሁን እንጂ
ስለ ባሪያው ስለ ዳዊት ሲል፣ *እግዚአብሔር*
ይሁዳን ሊያጠፋ አልፈለገም፤ ምክንያቱም
ለዳዊትና ለዘሩ መብራት እንደማያሳጣ
ተስፋ ሰጥቶ ነበርና።
20በኢዮራም ዘመነ መንግሥት፣ ኤዶም
ያስ በይሁዳ ላይ ዐምፆ የራሱን ንጉሥ
አነገሠ። 21ስለዚህም ኢዮራም ሠረገሎቹን
ሁሉ አሰልፎ ወደ ጸዒር ዘመተ። ኤዶ
ማውያንም እርሱንና የሠረገላ አዛዦቹን
ከበቡ፤ እርሱና የሠረገላ አዛዦቹ ግን
በሌሊት ተነሥተው ከበባውን ጥሰው ወጡ፤
ሰራዊቱም ሸሽቶ ተመለሰ። 22ኤዶምያስም
እስከ ዛሬ ድረስ በይሁዳ ላይ እንደ ዐመፀ
ነው፤ ልብናም በዚሁ ጊዜ ዐምፆ ነበር።
23በኢዮራም ዘመነ መንግሥት የተከናወ
ነው ሌላው ነገር ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት
ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን? 24ኢዮ
ራምም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ እንደ
እነርሱም ሁሉ በዳዊት ከተማ ተቀበረ።
ልጁ አካዝያስም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

## የይሁዳ ንጉሥ አካዝያስ

8፥25-29 ተጓ ምብ - 2ዜና22፥1-6

25የእስራኤል ንጉሥ የአክዓብ ልጅ ኢዮ
ራም በነገሠ በዐሥራ ሁለተኛው ዓመት፣
የኢዮሆራም ልጅ አካዝያስ በይሁዳ ነገሠ።
26አካዝያስ ሲነግሥ ዕድሜው ሀያ
ሁለት
ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም
አንድ ዓመት ገዛ። እናቱ ጎቶልያ ትባላ
ለች፤ እርሷም የእስራኤል ንጉሥ የዖምሪ
የልጅ ልጅ ነበረች። 27አካዝያስ ከአክዓብ

ነ10 ዕብራይስጡ እንዲህም "ሂድና፣ *በእርግጥ አትድንም*በለው
እንደሚሞት እግዚአብሔር ገልጦልኛል"

ቤተ ሰብ ጋር በጋብቻ የተሳሰረ ስለ
ነበር፣ የአክዓብ ቤት እንዳደረገው ሁሉ፣
እርሱም በአክዓብ ቤት መንገድ ሄደ፤
*በእግዚአብሔርም* ፊት ክፉ ነገር አደረገ።
28አካዝያስም ከአክዓብ ልጅ ከኢዮራም
ጋር ሆኖ በሶርያ ንጉሥ በአዛሄል ላይ
ለመዝመት ወደ ሬማት ዘገለዓድ ሄደ፤
ሶርያውያንም በዚያ ኢዮራምን አቈሰ
ሉት። 29ስለዚህ ንጉሥ ኢዮራም፣ በሬ
ማት ከአዛሄል ጋር ባደረገው ጦርነት ሶር
ያውያን ካደረሱበት ቍስል ለማገገም ወደ
ኢይዝራኤል ተመለሰ።
ከዚያም የአክዓብ ልጅ ኢዮራም ስለ
ታመመ የይሁዳ ንጉሥ የኢዮራሆም ልጅ
አካዝያስ ሊጠይቀው ወደ ኢይዝራኤል
ወረደ።

### ኢዩ ተቀብቶ በእስራኤል ላይ ነገሠ

9 ነቢዩ ኤልሳዕ ከነቢያት ማኅበር አን
ዱን ጠርቶ እንዲህ አለው፤ “ወገብህን
ታጥቀህ፣ ይህን የዘይት ማሰሮ በመያዝ
በሬማት ወደምትገኘው ገለዓድ ሂድ።
2በዚያም ስትደርስ የናሜሲን የልጅ ልጅ፣
የኢዮሣፍጥን ልጅ ኢዩን ፈልገው። ወደ
እርሱም ቀርበህ ከጓደኞቹ ለብቻ ከነጠል
ኸው በኋላ፣ ወደ እልፍኝ አስገባው። 3ከዚ
ያም ማሰሮውን ይዘህ ዘይቱን በራሱ ላይ
አፍስስና፣ ‘*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“እነሆ፤ እኔ በእስራኤል ላይ እንድትነግሥ
ቀባሁህ”’ ብለህ ዐውጅ። ከዚያም በሩን
ከፍተህ ሩጥ፤ ፈጽሞ አትዘግይ።”
4ስለዚህ ጐልማሳው ነቢይ በሬማት ወደ
ምትገኘው ገለዓድ ሄደ። 5በዚያ እንደደረ
ሰም፣ የሰራዊቱ ጦር መኰንኖች በአንድ
ነት ተቀምጠው ነበር፤ እርሱም “መኰንን
ሆይ፤ ወደ አንተ ተልኬአለሁ” አለ።
ኢዩም፣ “ለማንኛችን ነው?” ሲል ጠየቀ።
እርሱም፣ “መኰንን ሆይ፤ ለአንተ ነው”
ብሎ መለሰ።
6ኢዩም ተነሥቶ ወደ ቤት ገባ፤ ከዚ
ያም ነቢዩ ዘይቱን በኢዩ ላይ አፈሰሰና
እንዲህ አለ፤ “የእስራኤል አምላክ እግዚአ
ብሔር እንዲህ ይላል፤ ‘*በእግዚአብሔር* ሕ
ዝብ በእስራኤል ላይ እንድትነግሥ
ቀብቼሃ ለሁ። 7የአገልጋዮቼን የነቢያትን
ደም እን ዲሁም *የእግዚአብሔርን*
አገልጋዮች ደም ሁሉ ከኤልዛቤል እጅ
እበቀል ዘንድ አንተ የጌታህን የአክዓብን
ቤት ትመታለህ። 8የአክዓብ ቤት በሙሉ
ይጠፋል፤ ባሪያም ይሁን ተወላጅ፣ በእስራ
ኤል የሚገኘውን የመጨረሻ ወንድ ልጅ
ሁሉ ከአክዓብ እቈርጣለሁ። 9ከእንግዲህ

8፥28 ዘዳ4፥43፤ 2ነገ9፥1፥14
8፥29 1ነገ19፥15፡ 17፥21፥29፤2ነገ9፥21፤ 10፥13
9፥1 1ሳሙ10፥1፡ 5፤1ነገ18፥46፤2ነገ 8፥28
9፥3 1ነገ19፥16
9፥6 1ነገ19፥16
9፥7 ዘፍ4፥24፤ዘዳ 32፥43፤1ነገ18፥4፤ ራእ6፥10
9፥8 1ሳሙ25፥22፤ 2ነገ10፥17
9፥9 1ነገ13፥34፤ 14፥10፤16፥3
9፥10 1ነገ21፥23
9፥11 1ሳሙ10፥ 11፤ዮሐ10፥20
9፥13 2ሳሙ15፥ 10፤ ማቴ21፥8፤ ሉቃ19፥36
9፥14 ዘዳ4፥43፤ 2ነገ8፥28
9፥15 2ነገ8፥29
9፥16 2ዜና22፥7
9፥17 1ሳሙ 14፥16፤16፥4፤ ኢሳ21፥6

የአክዓብን ቤት፣ እንደ ናባጥ ልጅ እንደ
ኢዮርብዓም ቤት፣ እንደ አኪያም ልጅ
እንደ ባኦስ ቤት አደርገዋለሁ።
10ኤልዛቤልን ግን በኢይዝራኤል ዕርሻ
ውሾች ይበሏታል፤ የሚቀብራትም
አይኖርም።’” ይህን ተናግሮም መዝ ጊ
ያውን ከፍቶ ሮጠ።
11ኢዩ ወጥቶ የጦር አለቆች ወደሆኑት
ጓደኞቹ እንደ ደረሰ፣ ከመካከላቸው አንዱ
“ሁሉም ነገር ሰላም ነው? ይህ እብድ ወደ
አንተ የመጣው ለምንድን ነው?” ሲል ጠየ
ቀው።
ኢዩም “ሰውየውንም ሆነ የሚናገረውን
እናንተም ታውቃላችሁ” ሲል መለሰ።
12እነርሱም፣ “ይህማ ትክክል አይደለም
ይልቅስ እውነቱን ንገረን” አሉት።
ኢዩም እንዲህ አለ፤ “እርሱ የነገረኝማ
ይህ ነው፤ ‘*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“የእስራኤል ንጉሥ እንድትሆን ቀብቼሃ
ለሁ።’ ”
13ከዚያ ሁሉም ቶሎ ብለው ልበሳቸ
ውን እያወለቁ በሚራመድበት ደረጃ ላይ
አነጠፉ፤ ከዚያም መለከት ነፍተው፣ “ኢዩ
ነግሦአል” አሉ።

### ኢዩ ኢዮራምንና አካዝያስን ገደለ

9፥21-29 ተጓ ምብ - 2ዜና22፥7-9

14ስለዚህ የናሜሲ የልጅ ልጅ፣ የኢዮሣ
ፍጥ ልጅ ኢዩ በኢዮራም ላይ አሤረ።
በዚህ ጊዜ ኢዮራምና እስራኤል ሁሉ በሬ
ማት የምትገኘውን ገለዓድን ከሶርያ
ንጉሥ ከአዛሄል ጥቃት ለማዳን ይጠብቁ
ነበር። 15ንጉሥ ኢዮራም ግን የሶርያን
ንጉሥ አዛሄልን ጦርነት በገጠመው ጊዜ፣
ሶርያውያን ካደረሱበት ቍስል ለማገገም
ወደ ኢይዝራኤል ተመልሶ ነበር። ኢዩም፣
“እንግዲህ ሐሳባችሁ እንዲህ ከሆነ፣ ይህን
ነገር ወደ ኢይዝራኤል ሄዶ እንዳይናገር፣
ማንም ሰው ከዚህች ከተማ ሾልኮ እንዳይ
ወጣ ጠብቁ” አለ። 16ከዚያም በሠረገላው
ተቀምጦ ወደ ኢይዝራኤል ገሠገሠ፤ ይህን
ያደረገውም ኢዮራም በዚያ ስለተኛና
የይሁዳ ንጉሥ አካዝያስም እርሱን ለመጠ
የቅ ወደዚያው ስለወረደ ነው።
17በኢይዝራኤል ግንብ ማማ ላይ የቆመው
ጠባቂ የኢዩ ወታደሮች መቅረባቸውን
አይቶ፣ “እረ ወታደሮች መጡ!” በማለት
ጮኾ ተናገረ።
ኢዮራምም፣ “አንድ ፈረሰኛ ተጠርቶ፤
እንዲገናኛቸው ላኩትና፣ ‘የመጣችሁት በሰ
ላም ነውን?’ ብሎ ይጠይቅ” ሲል አዘዘ።
18ፈረሰኛውም ኢዩን ለመገናኘት ጋልቦ
ሄደና፣ “ንጉሡ፣ ‘የመጣችሁት በሰላም

ነውን?' ብሎአል" አለው፡፡
ኢዩም፣ "ስለ ሰላም መጨነቅ የአንተ
ጕዳይ አይደለም! ይልቅስ ወደ ኋላ እለ
ፍና ተከተለኝ" አለው፡፡
ጠባቂውም፣ "መልእክተኛው ከእነርሱ
ዘንድ ደርሶአል፤ ነገር ግን ተመልሶ አል
መጣም" ብሎ አሳወቀ፡፡
19ስለዚህ ንጉሡ ሌላ ፈረሰኛ ላከ፤ ወደ
እነርሱ ዘንድ እንደ ደረሰም፣ "ንጉሡ፣
'የመጣችሁት በሰላም ነውን?' ይላል" አለው፡፡
ኢዩም "ስለ ሰላም መጨነቅ የአንተ
ጕዳይ አይደለም! ይልቅስ ወደ ኋላ እለ
ፍና ተከተለኝ" አለው፡፡
20ጠባቂው፣ "መልእክተኛው ከእነርሱ ዘንድ
ደርሶአል፤ ነገር ግን ይህም ተመልሶ አል
መጣም፤ የወታደሮቹ መሪ ሠረገላ አነዳዱ
ልክ እንደ ናሜሲ ልጅ እንደ ኢዩ አነዳድ
ነው፤ ሲነዳም እንደ እብድ ነው" ሲል
አሳወቀ፡፡
21ኢዮራምም፣ "በሉ ሠረገላዬን አዘጋጁ"
ብሎ አዘዘ፡፡ ሠረገላው እንደ ተዘጋጀም፣
የእስራኤል ንጉሥ ኢዮራምና የይሁዳ ንጉሥ
አካዝያስ በየሠረገሎቻቸው ሆነው ኢዩን
ለመገናኘት ሄዱ፤ የኢይዝራኤላዊው የና
ቡቴ ርስት በነበረው ዕርሻ ላይም ተገና
ኙት፡፡ 22ኢዮራምም ኢዩን ገና ሲያየው፣
"ኢዩ፣ የመጣኸው በሰላም ነውን?" ሲ
ል
ጠየቀው፡፡
ኢዩም፣ "የእናትህ የኤልዛቤል የጣዖት
አምልኮና መተት እንዲህ በዝቶ እያለ
ምን ሰላም አለ!" ሲል መለሰ፡፡
23ኢዮራምም ሠረገላውን አዙሮ በመ
ሸሽ፣ "አካዝያስ ሆይ፤ ይህ ክዳት ነው!"
አለ፡፡
24ከዚያም ኢዩ ቀስቱን በማስፈንጠር
ኢዮራምን በትከሻና ትከሻው መካከል
ወጋው፤ ፍላጻውም ዘልቆ ልቡን ስለ ወጋው፣
ሠረገላው ውስጥ ዘፍ ብሎ
ወደቀ፡፡
25ኢዩም የሠረገላ ኀላፊውን ቢድቃርን
እንዲህ አለው፤ "አንሣውና በኢይዝራኤላ
ዊው በናቡቴ ዕርሻ ላይ ጣለው፤ አንተና
እኔ አባቱን አክዓብን በየሠረገሎቻችን
ሆነን ተከትለነው ስንሄድ፣ *እግዚአብሔር*
ይህን ትንቢት እንዲህ ሲል እንደ ተናገረ
በት አስታውስ፤ 26'ትናንት የናቡቴንና የል
ጆቹን ደም አይቻለሁ፤ ይላል *እግዚአብሔር*፤
ይህንንም በዚሁ ዕርሻ ላይ በእርግጥ አን
ተው እንድትከፍል አደርግሃለሁ፤ ይላል
እግዚአብሔር፤'[ኀ] አሁንም *በእግ ዚአብሔር*
ቃል በተነገረው መሠረት አንሣውና በዚሁ
ዕርሻ ውስጥ ጣለው፡፡"

9፥20 2ሳሙ18፥27
9፥21 1ነገ21፥17፡
15-19
9፥22 1ነገ18፥19፤
ራእ2፥20
9፥23 2ነገ11፥14
9፥24 1ነገ22፥34
9፥25 1ነገ21፥19-22
9፥26 1ነገ21፥19-29
9፥27 መሳ1፥27፤
2ነገ23፥29
9፥28 2ነገ14፥20፤
23፥30
9፥29 2ነገ8፥25
9፥30 ኤር4፥30፤
ሕዝ23፥40
9፥31 1ነገ16፥9-10
9፥33 መዝ7፥5
9፥34 1ነገ16፥31
9፥36 1ነገ21፥23፤
መዝ68፥23፤ኤር
15፥3
9፥37 መዝ83፥10፤
ኢሳ 5፥25፤ኤር
8፥2፤9፥22፤16፥4፤
25፥33፤ስፎ1፥17
10፥1 ቆ5፤መሳ
8፥30፤1ነገ13፥32፤
21፥1

27የይሁዳ ንጉሥ አካዝያስም ይህን
ሲያይ፣ ወደ ቤት ሀጋን በሚያወጣው መን
ገድ ሸሸ፤[ኣ]ኢዩም እያሳደደ ድምፁን ከፍ
አድርጎ፣ "እርሱንም ግደሉት!" አለ፡፡ እነ
ርሱም በይብለዓም ከተማ አጠገብ
በጉር
ዐቀበት መንገድ ላይ በሠረገላው ውስጥ
እንዳለ አቈሰሉት፤ እርሱ ግን ወደ መጊዶ
ሸሽቶ፤ እዚያው ሞተ፡፡ 28አገልጋዮቹም በሠ
ረገላ አድርገው ወደ ኢየሩሳሌም ወሰ
ዱት፤ በዳዊትም ከተማ ከአባቶቹ ጋር
በመቃብሩ ቀበሩት፡፡ 29አካዝያስ በይሁዳ
የነገሠው፣ የአክዓብ ልጅ ኢዮራም በነገሠ
በዐሥራ አንደኛው ዓመት ነበር፡፡

## ኤልዛቤል ተገደለች

30ከዚያም ኢዩ ወደ ኢይዝራኤል ሄደ፤
ኤልዛቤልም ይህን በሰማች ጊዜ ዐይኗን
ተኳኰላ፣ ጠጕሯንም አሰማምራ በመስ
ኮት ትመለከት ነበር፡፡ 31ኢዩ የቅጥሩን በር
አልፎ ሲገባ፣ "ጌታህን የገደልህ አንተ
ዘምሪ የመጣኸው በሰላም ነውን?"[ከ] ስትል
ጠየቀችው፡፡
32ቀና ብሎ ወደ መስኮቱ ተመለከ
ተና፣ "ማነህ አንተ? ማነው የሚተባበረኝ
ሲል ጮኾ ተጣራ፡፡ ሁለት ሦስት ጃንደረ
ቦችም ቍልቍል ወደ እርሱ ተመለከቱ፤
33ኢዩም፣ "ወደ ታች ወርውሩአት!" አለ፡፡
እነርሱም ወረወሯት፡፡ ፈረሶቹ ሲረጋግ
ጧትም ደሟ በግንቡና በፈረሶቹ ላይ
ተረጨ፡፡
34ኢዩም ገብቶ በላ፤ ጠጣም፡፡ ከዚያም፣
"ምንም ቢሆን የንጉሥ ልጅ ናትና ይህ
ችን የተረገመች ሴት በሚገባ ቅበሯት"
አለ፡፡ 35ሊቀብሯት ሲወጡ ግን ከራስ
ቅሏ፣ ከእግሯና ከእጇ በቀር ሌላ ያገኙት
አልነበረም፡፡ 36ተመልሰውም ይህን ሲ
ነግ
ሩት፣ ኢዩ እንዲህ አለ፤ "*እግዚአብሔር*
ለባሪያው ለቴስቢያዊው ለኤልያስ፣ 'በኢ
ይዝራኤል ምድር ዕርሻ ውስጥ ውሾች
የኤልዛቤልን ሥጋ ይበሉታል፤[ኸ] 37ሥጋዋም
በኢይዝራኤል ምድር ዕርሻ ውስጥ እንደ
ፍግ ስለሚሆን፣ ማንም ሰው፣ 'ይህች ኤል
ዛቤል ናት' ሊል አይችልም ብሎ የተናገ
ረው ቃል ይህ ነው፡፡"

## የአክዓብ ቤተሰቦች ተገደሉ

10 በዚህ ጊዜ አክዓብ በሰማርያ ሰባ
ወንዶች ልጆች ነበሩት፤ ስለዚህ
ኢዩ ደብዳቤ ጽፎ ለኢይዝራኤል ሹማም

[ኀ]26 1ነገ2፥19 *ይመ* [ኣ]27 *ወይም በአትክልቱ ስፍራ በሚገኘው በኩል ሸሸ*
[ከ]31 ወይም፣ *ጌታውን የገደለው ዘምሪ ሰላም አለውን?*
[ኸ]36 1ነገ 21፥23 *ይመ*

ንት፣[ሠ] ለሽማግሌዎችና የአክዓብን ልጆች
ለሚያሳድጉ ሞግዚቶች ወደ ሰማርያ ላከ፤
መልእክቱም እንዲህ የሚል ነበር፤ [2]“የጌ
ታችሁ ልጆች ከእናንተ ጋር ስለሆኑ፣
ሠረገሎችና ፈረሶች፣ የተመሸገች ከተማና
መሣሪያም ስላላችሁ፣ ይህ ደብዳቤ እንደ
ደረሳችሁ ወዲያውኑ [3]ከጌታችሁ ልጆች
መካከል ብልጫ ያለውንና ተገቢ ነው
የምትሉትን መርጣችሁ በአባቱ ዙፋን
አስቀምጡት። ከዚያም ስለ ጌታችሁ ቤት
ተዋጉ።”

[4]እነርሱ ግን እጅግ ፈርተው ነበርና፣
“ሁለት ነገሥታት ሊቋቋሙት ያልቻሉ
ትን ሰው እኛ እንዴት ልንቋቋመው እን
ችላለን?” አሉ።

[5]ስለዚህ የቤተ መንግሥቱ አዛዥ፣ የከተ
ማዪቱ ገዥ፣ ሽማግሌዎችና የልጆቹ ሞግ
ዚቶች፣ “እኛ ያንተው አገልጋዮች ነን፤
ትእዛዝህን ሁሉ እንፈጽማለን፤ እኛ ማን
ንም አናነግሥም፤ ደስ የሚያሰኝህን ሁሉ
አንተው አድርግ” በማለት ይህን መልእ
ክት ለኢዩ ላኩ። [6]ከዚያም ኢዩ፣ “እንግ
ዲህ የእኔ ወገን ከሆናችሁና ከታዘዛችሁኝ
የጌታችሁን ልጆች ራስ ቈርጣችሁ ነገ
በዚህ ሰዓት ይዛችሁልኝ ወደ ኢይዝራኤል
እንድትመጡ” ሲል ደግሞ ጻፈላቸው።

በዚህም ጊዜ ሰባው የንጉሡ ልጆች
በከተማዪቱ ውስጥ ታዋቂ በሆኑ አሳዳጊ
ዎቻቸው ዘንድ ነበሩ። [7]ደብዳቤውም
በደረ ሳቸው ጊዜ፣ ሰዎቹ ሰባውን ልዑላን
በሙሉ ወስደው ገደሏቸው። ራሳቸውንም
በቅርጫት አድርገው ኢዩ ዘንድ ወደ ኢይ
ዝራኤል ላኩ። [8]መልእክተኛው እንደ ደረ
ሰም፣ ለኢዩ፣ “የንጉሡን ልጆች ራስ አም
ጥተዋል” ብሎ ነገረው። ከዚያም ኢዩ፣ “በከ
ተማዪቱ መግቢያ በር ላይ ሁለት ቦታ
ከምራችሁ እስከ ነገ ጧት ድረስ አቈዩአ
ቸው” ብሎ አዘዘ።

[9]በማግስቱም ጧት ኢዩ ወጥቶ በሕዝቡ
ሁሉ ፊት በመቆም እንዲህ አለ፤ “እናንተ
ንጹሐን ናችሁ፤ ጌታዬን ያሤርሁበትና
የገደልሁት እኔ ነኝ። እነዚህን ሁሉ ግን
የፈጀቻቸው ማን ነው?

[10]እንግዲህ እግዚአብሔር በአክዓብ ቤት
ላይ ከተናገረው ቃል አንዲቱ እንኳ በም
ድር ላይ ወድቃ እንደ ማትቀር ዕወቁ።
እግዚአብሔር በባሪያው በኤልያስ የተናገረ
ውን ፈጽሞአል።” [11]ስለዚህ ኢዩ ከአክዓብ
ቤት የቀረውን ሁሉ፣ ታላላቆቹን ሰዎች
በሙሉ፣ የቅርብ ወዳጆቹንና ካህናቱን አን
ድም ሳይቀር በኢይዝራኤል ገደላቸው።

[12]ከዚያም ኢዩ ተነሥቶ ወደ ሰማርያ
ሄደ፤ ቤትኤከድ ወደተባለው የበግ ጠባቂ
ዎችም ቤት ሲደርስ፣ [13]ከይሁዳ ንጉሥ
ከአካዝያስ ሥጋ ዘመዶች ጥቂቶቹን አግ
ኝቶ፣ “እናንተ እነማን ናችሁ?” ሲል ጠየ
ቃቸው፤

እነርሱም፣ “እኛ የአካዝያስ ሥጋ ዘመ
ዶች ነን፤ ንጉሣዊውን ቤተሰብና የእቴጌ
ይቱን ልጆች ለመጠየቅ ወደዚህ ወርደን
መጥተናል” አሉ።

[14]እርሱም፣ “ከነሕይወታቸው ያዟቸው!”
ሲል አዘዘ፤ ስለዚህ ከነሕይወታቸው ወስ
ደው በቤት ኤከድ ጕድጓድ አጠገብ አርባ
ሁለቱን ሰዎች ገደሏቸው፤ አንድ እንኳ
አላስቀ ረም።

[15]ከዚያም ተነሥቶ ሲሄድ የሬካብ ልጅ
ኢዮናዳብ ወደ እርሱ ሲመጣ መንገድ
ላይ አገኘው። ኢዩም ሰላምታ ሰጥቶት
“ልቤ ለልብህ ታማኝ የሆነውን ያህል ያን
ተስ ልብ ለልቤ እንዲሁ ታማኝ ነውን?”
ሲል ጠየቀው።

ኢዮናዳብም፣ “አዎን፤ ነው!” ብሎ መለሰ።

ኢዩም፣ “እንግዲያውስ እጅህን ስጠኝ”
አለው። እጁንም ሰጠው፤ ከዚያም ኢዩ
ደግፎ ወደ ሠረገላው አወጣው።

[16]ኢዩም፣ “በል አብረን እንሂድና ለእግ
ዚአብሔር ያለኝን ቅናት እይልኝ” አለው፤
ከዚያም በሠረገላው ይዞት ሄደ።

[17]ኢዩ ወደ ሰማርያ በደረሰ ጊዜ፣ ከአ
ክዓብ ቤተሰብ በዚያ የቀረውን ሁሉ
ገደለ። ለነቢዩ ለኤልያስ በተነገረውም የእ
ግዚአብሔር ቃል መሠረት አጠፋቸው።

## የበኣል አገልጋዮች ተገደሉ

[18]ከዚያም ኢዩ ሕዝቡን ሁሉ በአንድነት
ሰብስቦ እንዲህ አለ፤ “አክዓብ በኣልን ያገ
ለገለው በጥቂቱ ነው፤ ኢዩ ግን ይበልጥ
ያገለግለዋል። [19]አሁንም የበኣልን ነቢያት
ሁሉ አገልጋዮቹንና ካህናቱንም በሙሉ
ጥሩልኝ። ለባኣል ትልቅ መሥዋዕት ስለ
ማቀርብ አንድ ሰው እንኳ እንዳይቀር።
የማይመጣ ሰው ቢኖር ግን በሕይወት
አይኖርም፤ ኢዩ ግን ይህን ማድረጉ የበ
ኣልን አገልጋዮች ለማጥፋት ተንኰል
መፍጠሩ ነበር።

[20]ኢዩም፣ “ለበኣል ክብር ጉባኤ ጥሩ”
አለ፤ እነርሱም ይህንኑ ለሕዝቡ አስታወቁ።
[21]ከዚያም በመላው እስራኤል መልእክት
ላከ፤ የበኣል አገልጋዮች በሙሉ መጡ፤
ማንም አልቀረም፤ ሁሉም ወደ በኣል ቤተ

10፥5 ኢሱ9፥8
10፥7 2ሳሙ4፥8፤ 1ነገ21፥21
10፥10 1ነገ 21፥29፤2ነገ9፥7-10
10፥11 ቀኊ14፤ ኢዮ18፥19፤ ሆሴ1፥4፤ሚል4፥1
10፥13 1ነገ 2፥19፤2ነገ8፥29፤ 2ዜና22፥8
10፥14 ቀኊ11
10፥15 1ዜና2፥55 ፤ዕዝ 10፥19፤ ኤር35፥2፤6፤14-19 ፤ሕዝ17፥18
10፥16 ዘኍ25፥13
10፥17 2ነገ9፥8
10፥18 መሳ2፥11
10፥19 1ነገ18፥19
10፥20 ዘፀ32፥5

[ሠ]1 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ነገር ግን አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞችና የቩልጌት ቅጂ፣ “የከተማዪቱ” ይላሉ።

ጣዖት ገቡ፤ የበኣል ቤተ ጣዖት ዳር እስከ
ዳር ሞላ። [22]ኢዩም የልብስ ቤቱን ኀላፊ፣
“ለበኣል አገልጋዮች ሁሉ አልባሳት አውጣ”
አለው፤ እርሱም አልባሳቱን አወጣላቸው።
[23]ከዚያም ኢዩ ከሬካብ ልጅ ከኢዮናዳብ
ጋር ወደ በኣል ቤተ ጣዖት ገባ። የበኣ
ልንም አገልጋዮች፣ “እንግዲህ የበኣል አገ
ልጋዮች ብቻ እንጂ *የእግዚአብሔር* አገል
ጋዮች እዚህ አብረዋችሁ አለመኖራቸውን
አረጋግጡ” አላቸው። [24]ከዚያም የሚቃጠል
መሥዋዕትና ሌላም መሥዋዕት ለማቅረብ
ገቡ። በዚህ ጊዜም ኢዩ፣ “በእጃችሁ አሳ
ልፌ ከሰጠኋችሁ ሰዎች አንድ እንኳ እን
ዲያመልጥ ያደረገ በገመዱ ይገባበታል”
ብሎ በማስጠንቀቅ ውጭ ሰማንያ ሰዎች
አዘጋጅቶ ነበር።
[25]ኢዩ የሚቃጠለውን መሥዋዕት አቅ
ርቦ እንዳበቃ ጠባቂዎቹንና የጦር አለቆ
ቹን፣ “ግቡና ግደሏቸው፤ ማንም እንዳያ
መልጥ” ሲል አዘዘ። እነርሱም በሰይፍ
ፈጇቸው፤ ጠባቂዎቹና የጦር ሹማምን
ቱም ሬሳውን በሙሉ ወደ ውጭ አውጥ
ተው ጣሉ። ከዚያም ወደ ውስጠኛው የበ
ኣል ቤተ ጣዖት ገቡ። [26]ከድንጋይ የተሠሩ
ትንም ማምለኪያ ምስሎች ከበኣል ቤተ
ጣዖት አውጥተው አቃጠሉ። [27]የበኣልን
ማምለኪያ ምስል ቀጠቀጡ፤ የበኣልንም
ቤተ አምልኮ አፈረሱ፤ ይህንንም ሕዝቡ
እስከ ዛሬ ድረስ የኵስ መጣያው አድር
ጎታል።
[28]በዚህ ሁኔታም ኢዩ የበኣልን አምልኮ
ከእስራኤል አስወገደ። [29]ይሁን እንጂ ኢዩ
የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም፣ በቤቴልና በዳን
የወርቅ ጥጃዎች እንዲያመልኩ እስራኤ
ልን ካሳተበት ኀጢአት አልራቀም።
[30]*እግዚአብሔርም* ኢዩን፣ “በፊቴ መል
ካም የሆነውን ነገር ስላደረግህና በአክዓ
ብም ቤት ላይ እንዲደርስ በልቤ ያለውን
ሁሉ ስለፈጸምህ፤ ዘርህ እስከ አራት
ትውልድ ድረስ በእስራኤል ዙፋን ላይ
ይቀመጣል” አለው።
[31]ነገር ግን ኢዩ የእስራኤልን አምላክ
*የእግዚአብሔርን* ሕግ በፍጹም ልቡ ለመ
ጠበቅ ጥንቃቄ አላደረገም፤ ኢዮርብዓም፣
እስራኤልን ካሳተበት ኀጢአት አልራቀ
ምና።
[32]በዚያ ዘመን *እግዚአብሔር* የእስራ
ኤልን ምድር መቀናነስ ጀመረ።
አዛሄልም እስራኤልን ዳር እስከ ዳር
መታ። [33]ይኸውም ከዮርዳኖስ በስተ ምሥ
ራቅ ያለውን የገለዓድን ምድር ሁሉ ሲ
ሆን፣ ይህም በአርኖን ወንዝ አጠገብ
ካለው ከአሮዔር አንሥቶ የጋድን፣

10፥24 ኢሱ2፥14
10፥25 ዘፀ22፥20፤ 1ነገ18፥40፤2ነገ 11፥18
10፥26 ዘፀ23፥24
10፥27 1ነገ16፥32
10፥28 1ነገ19፥17
10፥29 ዘፀ32፥4፤ 1ነገ12፥30፡32
10፥30 2ነገ15፥12
10፥31 ዘዳ4፥9፤ 1ነገ12፥30፤ምሳ4፥23
10፥32 1ነገ 19፥17፤2ነገ13፥25፤ መዝ107፥39
10፥33 ዘኁ21፥13፤ 32፥34፤ዘዳ2፥36፤ መሳ11፥26፤ኢሳ17፥2
10፥34 1ነገ15፥31
11፥1 2ነገ8፥18
11፥2 መሳ9፥5፤ 2ነገ12፥1
11፥4 ቀኁ19
11፥5 1ነገ14፥27፤ 1ዜና9፥25

የሮቤልንና የምናሴን አገር ገለዓድንና
ባሳንን ነበር።
[34]የቀረው በኢዩ ዘመነ መንግሥት የሆ
ነው፣ ያደረገውም ሁሉ፣ ያከናወነውም ሥራ
በሙሉ በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ
የሚገኝ አይደለምን?
[35]ኢዩ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በሰ
ማርያ ቀበሩት። ልጁ ኢዮአካዝም በእግሩ
ተተክቶ ነገሠ። [36]ኢዩ በሰማርያ ተቀምጦ
በእስራኤል ላይ የነገሠው ሃያ ስምንት ዓመት
ነበር።

## ጎቶልያና ኢዮአስ

11፥1-21 ተጓ ምብ - 2ዜና10-23፡21

11 የአካዝያስ እናት ጎቶልያ ልጇ መሞ
ቱን በሰማች ጊዜ፣ ንጉሣዊውን
ቤተ ሰብ በሙሉ አጠፋች። [2]የንጉሥ ኢዮ
ራም ልጅ፣ የአካዝያስ እኅት ዮሳቤት ግን
የአካዝያስን ልጅ ኢዮአስን ሊገደሉ ከነበ
ሩት ልዑላን መካከል ሰርቃ ወሰደችው።
እንዳይገድሉትም ከጎቶልያ በመደበቅ
እርሱንና ሞግዚቱን በአንድ እልፍኝ ሸሸገ
ቻቸው። [3]ጎቶልያ አገሩን በምትገዛበት
ጊዜም ከሞግዚቱ ጋር ስድስት ዓመት *በእ
ግዚአብሔር* ቤት ተሸሸገ።
[4]በሰባተኛውም ዓመት ዮዳሄ ልኮ ካራ
ውያንንና ዘብ ጠባቂዎቹን የሚያዙትን
የመቶ አለቆች እርሱ ወዳለበት ወደ *እግ
ዚአብሔር* ቤተ መቅደስ እንዲመጡ አደ
ረገ። ከእነርሱም ጋር ቃል ኪዳን በማድ
ረግ *በእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ውስጥ
አስማላቸው፤ ከዚያም የንጉሡን ልጅ አሳ
ያቸው። [5]እንዲህም ሲል አዘዛቸው፤ “እና
ንተ የምታደርጉት ይህ ነው፤ በሦስት
ምድብ ሆናችሁ በሰንበት ዕለት ዘብ ከም
ትጠብቁት መካከል አንዱ እጅ ቤተ መን
ግሥቱን ይጠብቅ፤ [6]ሌላው ከሦስት አንዱ
የሱርን በር ይጠብቅ፤ የቀረው ሌላው
አንድ ሦስተኛው እጅ ደግሞ ቤተ መቅ
ደሱን ተራ ገብቶ ከሚጠብቀው ከዘብ ጥበ
ቃው ኋላ ያለውን በር ይጠብቅ። [7]እናንተ
እንደ ተለመደው በሰንበት ዕለት ከዘብ
ጥበቃ ነጻ የምትሆኑት ሁለት ሦስተኛው
እጅ ግን ንጉሡ ያለበትን ቤተ መቅ
ደስ ጠብቁ። [8]ሁላችሁም መሣሪያችሁን
ይዛችሁ በንጉሡ ዙሪያ ሁኑ፤ የሚቀርባ
ችሁ ቢኖር⁰ ግን ይገደል። ንጉሡ በሚወ
ጣበትም ሆነ በሚገባበት ጊዜ ሁሉ አት
ለዩት።”
[9]የመቶ አለቆቹም ካህኑ ዮዳሄ ያዘዘውን
ሁሉ አደረጉ፤ እያንዳንዳቸውም
በሰንበት ዕለት ለዘብ ጥበቃ የሚገቡትንና
ከዘብ ጥበቃ የሚወጡትን ጭፍሮቻቸውን
ይዘው ወደ ካህኑ ወደ ዮዳሄ መጡ።

[10]ካህኑም *በእግዚአብሔር* ቤት የነበረውን
የንጉሥ ዳዊትን ጦርና ጋሻ ለመቶ
አለቆቹ ሰጣ ቸው፡፡ [11]ወታደሮቹም
እያንዳንዳቸው መሣ ሪያቸውን ይዘው፣
ከቤተ መቅደሱ በስተ ደቡብ አንሥቶ
እስከ ሰሜን ድረስ በመሠዊያውና በቤተ
መቅደሱ አጠገብ በን ጉሡ ዙሪያ
ቆሙ፡፡
[12]ዮዳሄም የንጉሡን ልጅ አውጥቶ
ዘው ዱን ጫነለት፤ የኪዳኑንም መጽሐፍ
ሰጠው፣ መንገሡን ዐወጀ፤ ኢዮአስም
ተቀብቶ ነገሠ፡፡ ከዚያም ሕዝቡ፣ "ንጉ
ሡ ሺህ ዓመት ይንገሥ" እያሉ በ
ማጨብጨብ ደስታቸ ውን ከፍ ባለ
ድምፅ ገለጹ፡፡
[13]ጎቶልያም የሰራዊቱንና የሕዝቡን
ጩኸት በሰማች ጊዜ ሕዝቡ ወዳለበት
ወደ ቤተ መቅደሱ ሄደች፡፡ [14]እነሆ፤ በወጉ
መሠረት ንጉሡ በዐምዱ አጠገብ ቆሞ፣
ሹማምንቱና መለከት ነፊዎቹ ከአጠገቡ
ሆነው አየች፡፡ የአገሩም ሕዝብ ሁሉ ይፈነ
ጥዝ፣ መለከትም ይነፋ ነበር፡፡ ጎቶልያም
ልብሷን ቀዳ፣ "ይህ ክዳት ነው! ክዳት
ነው!" በማለት ጮኸች፡፡
[15]ካህኑ ዮዳሄም ጭፍሮቹን የሚያዙትን
የመቶ አለቆች፣ "በረድፍ በተሰለፉት ጭፍ
ሮች መካከል አውጧት፤‖ የሚከተላትንም
ሁሉ በሰይፍ በሉት" ሲል አዘዘ፤ ይህ የሆ
ነውም ካህኑ አስቀድሞ፣ "*በእግዚአብሔር*
ቤት መገደል የለባትም" በማለቱ ነበር፡፡
[16]ስለዚህ ፈረሶች ወደ ቤተ መንግሥቱ
በሚገቡበት ስፍራ ስትደርስ፣ ይዘው እዚ
ያው ገደሏት፡፡
[17]ዮዳሄም *የእግዚአብሔር* ሕዝብ ይሆኑ
ዘንድ *በእግዚአብሔርና* በንጉሡ በሕዝቡም
መካከል ቃል ኪዳን እንዲኖር አደረገ፤
እንደዚሁም በንጉሡና በሕዝቡ
መካከል ቃል ኪዳን መሠረተ፡፡ [18]የአገሩ
ም ሕዝብ ሁሉ ወደ በኣል ቤተ ጣዖት
ሄደው አፈራረሱት፤ መሠዊያዎቹንና
ምስሎቹን ሁሉ ሰባበሩ፤ የበኣልን ካህን
ማታንንም በመሠዊያዎቹ ፊት ለፊት
ገደሉት፡፡
ከዚያም ካህኑ ዮዳሄ *የእግዚአብሔርን*
ቤተ መቅደስ የሚጠብቁ ዘበኞችን መደበ፡፡
[19]ከዚያም መቶ አለቆቹን፣ ካራውያንንና
ዘበኞቹን እንዲሁም የአገሩን ሕዝብ በሙሉ
በመያዝ ሁሉም በአንድነት ሆነው፣ ንጉ
ሡን *ከእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ወስ
ደው በዘብ ጠባቂዎች ቅጥር በር በኩል
ታች ወዳለው ቤተ መንግሥት ይዘውት
ገቡ፤ ንጉሡም በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ፤
[20]የአገሩም ሕዝብ ሁሉ ደስ አለው፤ ጎቶ
ልያ ቤተ መንግሥቱ ውስጥ በሰይፍ ተገ
ድላ ስለ ነበር፣ ከተማዪቱ ጸጥ አለች፡፡
[21]ኢዮአስ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሰባት ዓመት
ነበር፡፡

## ኢዮአስ ቤተ መቅደሱን አደሰ

12፥1-21 ተጓ ምብ - 2ዜና24፥1-14፤24፥23-27

12 ኢዩ በነገሠ በሰባተኛው ዓመት
ኢዮ አስ ነገሠ፤ በኢየሩሳሌም
ተቀምጦም አርባ ዓመት ገዛ፡፡ እናቱ ሳብያ
የተባለች፤ የቤርሳቤህ ከተማ ተወላጅ ነበ
ረች፡፡ [2]ካህኑ ዮዳሄ ያስተምረው በነበረበት
ዘመን ሁሉ፣ ኢዮአስ *በእግዚአብሔር* ፊት
መልካም ነገር አደረገ፡፡ [3]ይሁን እንጂ
የኰረብታ ማምለኪያ ስፍራዎች አልተወ
ገዱም፤ ሕዝቡም በእነዚህ ቦታዎች መሠ
ዋቱንና ማጠኑን እንደ ቀጠለ ነበር፡፡
[4]ኢዮአስ ካህናቱን እንዲህ አላቸው፤
"ከሕዝብ ቈጠራ የተገኘውንና በስእለት
የገባውን እንዲሁም በራስ ፈቃድ ለቤተ
መቅደሱ የተሰጠውን የተቀደሰ ገንዘብ
በሙሉ ሰብስቡ፡፡ [5]እያንዳንዱም ካህን ገንዘ
ቡን ከገንዘብ ያዡ እጅ ይቀበል፤ እንደ
አስፈላጊነቱም በቤተ መቅደሱ ውስጥ የፈ
ረሰውን ለማደስ ይዋል፡፡"
[6]ይሁን እንጂ እስከ ሃያ ሦስተኛው የኢ
ዮአስ ዘመነ መንግሥት ካህናቱ በቤተ
መቅደሱ ውስጥ የፈረሰውን አላደሱም
ነበር፡፡ [7]ስለዚህ ኢዮአስ ካህኑን ዮዳሄንና
ሌሎቹን ካህናት ጠርቶ፣ "በቤተ መቅደሱ
ውስጥ የፈረሰውን ያላደሳችሁት ለምንድን
ነው?" ሲል ጠየቃቸው፤ ቀጥሎም፣ "ከእን
ግዲህ ወዲያ ገንዘቡ በቤተ መቅደሱ
ውስጥ የፈረሰውን ለማደስ ይዋል እንጂ
ከገንዘብ ያዦች አትቀበሉ" አላቸው፡፡ [8]ካህ
ናቱም ከእንግዲህ ከሕዝቡ ገንዘብ ላለመ
ሰብሰብና ቤተ መቅደሱንም ራሳቸው ላለ
ማደስ ተስማሙ፡፡
[9]ከዚያም ካህኑ ዮዳሄ አንድ ሣጥን
ወስዶ በመክደኛው ላይ ቀዳዳ አበጀለት፤
ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ በሚያስ
ገባው በስተቀኝ በኩል በመሠዊያው አጠ
ገብ አኖረው፡፡ በራፉን የሚጠብቁት ካህና
ትም ወደ *እግዚአብሔር* ቤት የሚመጣ
ውን ገንዘብ በሙሉ በሣጥኑ ውስጥ ያስ
ገቡ ነበር፡፡ [10]በሣጥኑም ውስጥ ብዙ ገንዘብ
መኖሩን በሚያዩበት ጊዜ ሁሉ፣ የንጉሡ
ጸሐፊና ሊቀ ካህናቱ መጥተው ወደ *እግ
ዚአብሔር* ቤተ መቅደስ የገባውን ገንዘብ
ቈጥረው በየከረጢቱ በማስገባት ቋጥረው
ያኖሩት ነበር፡፡ [11]የገንዘቡ ልክም ተመዝኖ
ከታወቀ በኋላ፣ የቤተ መቅደሱን ሥራ

°8 ወይም፣ *ወደ ቅጥራችሁ የሚደርስ ቢኖር*
‖15 ወይም፣ *ከቅጥራችሁ መካከል*

11፥10 2ሳሙ8፥7
11፥12 ዘፀ25፥16፤ 1ሳሙ9፥16፤10፥24፤1ነገ1፥39፤2ነገ23፥3፤መዝ47፥1፤98፥8፤ ኢሳ55፥12
11፥14 ዘፍ37፥29፤ 1ነገ1፥39፤7፥15፤ 2ነገ9፥23
11፥15 1ነገ2፥30
11፥16 ዘፍ4፥14፤ ነህ3፥28፤ኤር31፥40
11፥17 ዘፀ24፥8፤ 2ሳሙ5፥3፤2ነገ23፥3፤2ዜና15፥12፤23፥3፤29፥10፤34፥31፤ዕዝ10፥3፤ ኤር34፥8
11፥18 ዘዳ12፥3፤ 1ነገ16፥32፤18፥40፤2ነገ10፥25፤23፥20
11፥19 ቍ4
11፥20 ምሳ 11፥10፤28፥12፤ 29፥2
12፥1 2ነገ11፥2
12፥2 ዘዳ12፥25፤ 2ሳሙ8፥15
12፥3 1ነገ3፥3፤ 2ነገ18፥4
12፥4 ዘፀ25፥2፤ 30፥12፤35፥29፤ዘኍ18፥19፤2ነገ22፥4
12፥5 2ነገ22፥5
12፥9 2ነገ25፥18፤ ኤር35፥4፤52፥24፤ ማር12፥41፤ ሉቃ21፥1
12፥10 2ሳሙ8፥17

በኀላፊነት እንዲያሠሩ ለተመደቡት ሰዎች
ገንዘቡን ያስረክቧቸዋል፤ ይህም የእግዚአ
ብሔርን ቤተ መቅደስ ለሚሠሩ አናጢዎ
ችና ግንበኞች፣ [12]ለድንጋይ ጠራቢዎችና
ለድንጋይ ቅርጽ አውጭዎች የሚከፈል
እንዲሁም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
ለሚታደስበት ዕንጨትና ጥርብ ድንጋይ
መግዣ የሚውል ነበር።
[13]ለቤተ መቅደሱ ከገባው ገንዘብ ግን
ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ግልጋሎት
ለሚውሉ የብር ጽዋዎች፣ መኰስተሪያ
ዎች፣ ድስቶች፣ መለከቶችና ወይም ለሌ
ሎች የወርቅም ሆነ የብር ዕቃዎች መሥ
ሪያ አልዋለም፤ [14]የተከፈለው ግን ቤተ
መቅደሱን ለሚያድሱ ሠራተኞች ብቻ
ነበር። [15]ለሠራተኞቹ እንዲከፍሉ ገንዘቡ
የተሰጣቸው ሰዎች ፍጹም ታማኞች በመ
ሆናቸው ተቈጣጣሪ ማድረግ አላስፈለጋቸ
ውም ነበር። [16]ስለ በደል መሥዋዕትና ስለ
ኀጢአት መሥዋዕት የሚቀርበው ገንዘብ
ግን የካህናቱ በመሆኑ ወደ እግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ አይገባም ነበር።
[17]በዚህ ጊዜ የሶርያ ንጉሥ አዛሄል
ወጣ፤ ጌትንም አደጋ ጥሎ ያዛት። ከዚ
ያም በኢየሩሳሌም ላይ አደጋ ለመጣል
ፊቱን አዞረ። [18]የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአስ ግን
አባቶቹ የይ ሁዳ ነገሥታት ኢዮሣፍጥ፣
ኢዮሆራም፣ አካዝያስ ለእግዚአብሔር
ቀድሰው የለዩአ ቸውን የተቀደሱ ዕቃዎች
በሙሉ፣ እርሱ ራሱ የቀደሳቸው
ስጦታዎች እንዲሁም በእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስና በቤተ መንግሥቱ ዕቃ ቤቶች
የተገኘውን ወርቅ ሁሉ ሰብስቦ ለሶርያ
ንጉሥ ለአዛሄል ላከ ለት፤ አዛሄልም ከኢ
የሩሳሌም ተመለሰ።
[19]ኢዮአስ በዘመነ መንግሥቱ ያከናወ
ነው ሌላው ተግባርና የፈጸመው ሥራ
ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚ
ገኝ አይደለምን? [20]ሹማምንቱም በእርሱ
ላይ ዐመፁበት፤ ቊልቊል ወደ ሲላ በሚ
ወስደው መንገድ ላይ በቤት ሚሎ ገደ
ሉት። [21]ገዳዮቹ ሹማምትም የሰምዓት
ልጅ ዮዛካርና የሾሜር ልጅ ዮዛባት ነበሩ።
እርሱም ሞተ፤ እንደ አባቶቹም ሁሉ በዳ
ዊት ከተማ ተቀበረ። ልጁ አሜስያስም
በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

## የእስራኤል ንጉሥ ኢዮአካዝ

13 የይሁዳ ንጉሥ የአካዝያስ ልጅ
ኢዮአስ በነገሠ በሃያ ሦስተኛው
ዓመት፣ የኢዩ ልጅ ኢዮአካዝ በሰማርያ
ከተማ በእስራኤል ላይ ነገሠ፤ ዐሥራ ሰባት
ዓመትም ገዛ። [2]እርሱም የናባጥ ልጅ ኢዮ
ርብዓም እስራኤልን ያሳተበትን ኀጢአት
በመከተል በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ
ሠራ፤ ከዚህ ድርጊቱም አልተመለሰም።
[3]የእግዚአብሔር ቊጣ በእስራኤል ላይ
ነደደ፤ ስለዚህ የሶርያ ንጉሥ አዛሄልና
ልጁ ቤንሃዳድ በነበሩበት ዘመን ሁሉ አሳ
ልፎ በእጃቸው ሰጣቸው።
[4]ከዚያም ኢዮአካዝ እግዚአብሔርን
ለመነ፤ እግዚአብሔርም የሶርያ ንጉሥ እስ
ራኤልን እንዴት አድርጎ እንዳስጨነቀ
አይቶአልና ልመናውን ሰማው። [5]ስለዚህ
እግዚአብሔር ለእስራኤል የሚታደጋቸ
ውን ሰው ሰጠ፤ እነርሱም ከሶርያውያን
ጭቍና ተላቀቁ፤ እንደ ቀድሞውም በየድ
ንኳናቸው መኖር ጀመሩ፤ [6]ይሁን እንጂ
እስራኤልን ካሳተው ከኢዮርብዓም ቤት
ኀጢአት አልተመለሱም፤ በዚያው ገፉ
በት። የአሼራም ምስል ዐምድ[ዣ] በሰማርያ
መመለኩ ቀጠለ።
[7]ከኢዮአካዝ ሰራዊት የተረፈው አምሳ
ፈረሰኞች፣ ዐሥር ሠረገሎችና ዐሥር ሺህ
እግረኛ ወታደር ብቻ ነው፤ ይህ የሆነበ
ትም ምክንያት የሶርያ ንጉሥ የቀረውን
ስለ አጠፋውና እንደ ዐውድማ ብናኝ ስለ
አደረገው ነበር።
[8]ኢዮአካዝ በዘመነ መንግሥቱ ያከናወ
ነው ሌላው ሥራ፣ ያደረገውና የፈጸመ
ውም ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ
ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን? [9]ኢዮአካዝ
ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በሰማርያም ተቀ
በረ። ልጁ ዮአስም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

## የእስራኤል ንጉሥ ዮአስ።

[10]በይሁዳ ንጉሥ በኢዮአስ ዘመን፣ በሠ
ላሳ ሰባተኛው ዓመት፣ የኢዮአካዝ ልጅ
ዮአስ በሰማርያ ከተማ በእስራኤል ላይ ነገሠ፤
ዐሥራ ስድስት ዓመትም ገዛ። [11]እርሱም
በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ሠራ፤ የና
ባጥ ልጅ ኢዮርብዓም እስራኤልን ካሳተ
በት ኀጢአት ሁሉ አልራቀም፤ በዚያው
ገፋበት።
[12]ዮአስ በዘመነ መንግሥቱ ያከናወነው
ሌላ ሥራ፣ ያደረገውና የፈጸመው ሁሉ
እንዲሁም በይሁዳ ንጉሥ በአሜስያስ ላይ
ያካሄደው ጦርነት ጭምር በእስራኤል ነገ
ሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለ
ምን?። [13]ዮአስም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤
ኢዮርብዓም በእግሩ ተተክቶ በዙፋኑ
ተቀመጠ። ዮአስም በሰማርያ ከእስራኤል
ነገሥታት ጋር ተቀበረ።
[14]በዚህ ጊዜ ኤልሳዕ ለሞት ባደረሰው
ሕመም ታሞ ያጣጥር ነበር። የእስራኤልም

12፥12 2ነገ22፥5-6
12፥13 1ነገ7፥51
12፥15 2ነገ22፥7፤1ቆሮ4፥2
12፥16 ዘሌ4፥1-35፤5፥14-19፤7፥7
12፥17 2ነገ8፥12
12፥18 1ነገ15፥18፡21፤2ነገ15፥20፤19፡36፤2ዜና21፥16-17
12፥20 መሳ9፥6፤2ነገ14፥5፡19፤15፥10፡14፡25፡30፤21፥23፤25፥25
13፥2 1ነገ12፥26-33
13፥3 ቊ24፤ዘዳ31፥17፤1ነገ19፥17
13፥4 ዘኁ10፥9፤ዘጸ4፥29፤26፥7፤2ሳሙ7፥10
13፥5 ዘፍ45፥7፤ዘጸ28፥29፤መሳ2፥18
13፥6 1ነገ12፥30፤16፥33
13፥7 2ሳሙ22፥43፤2ነገ10፥32-33
13፥12 1ነገ15፥31፤2ነገ14፥15
13፥13 2ነገ 14፥23፤ሆሴ1፥1
13፥14 2ነገ2፥12

[ዣ]6 በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሁሉ ይህ የአሼራን ሴት ጣዖት የሚያመለክት ነው

ንጉሥ ዮአስ ሊጠይቀው ወርዶ አለቀሰ
ለት፤ "ወየው አባቴን! ወየው አባቴን!
ወየው የእስራኤል ሠረገሎችና ፈረሰኞች!"
እያለም ጮኸ።
15ኤልሳዕም፣ "አንድ ቀስትና ፍላጾች
አምጣ" አለው፤ እርሱም አመጣ፤ 16የእስራ
ኤልንም ንጉሥ፣ "ቀስቱን በእጅህ ያዘው"
አለው፤ ቀስቱን በያዘውም ጊዜ ኤልሳዕ
እጆቹን በንጉሡ እጆች ላይ አኖረ።
17ቀጥሎም፣ "የምሥራቁን መስኮት
ክፈት" አለው፤ ከፈተውም፤ ኤልሳዕም፣
"በል አስፈንጥረው" አለው፤ አስፈነጠረ
ውም፤ ከዚያም፣ "*የእግዚአብሔር* የድል
ቀስት! ሶርያ ድል የምትሆንበት ቀስት!"
አለ። ኤልሳዕም እንደገና "ሶርያውያንንም
አፌቅ ላይ ፈጽመህ ድል ታደርጋቸዋለህ"
አለው።
18ቀጥሎም፣ "በል ቀስቶቹን ውሰድ"
አለው፤ ንጉሡም ወሰደ። ኤልሳዕም፣ "መሬ
ቱን ውጋ" አለው። እርሱም ሦስት ጊዜ
ወግቶ አቆመ።
19የእግዚአብሔርም ሰው ተቈጣውና፣ "መሬ
ቱን አምስት ወይም ስድስት ጊዜ መው
ጋት ነበረብህ፤ እንዲህ ብታደርግ ኖሮ
ሶርያን ታሸንፍና ፈጽመህ ትደመስሳት
ነበር፤ አሁን ግን የምታሸንፈው ሦስት ጊዜ
ብቻ ነው" አለው።
20ኤልሳዕ ሞተ፤ ቀበሩትም። በዚህም
ጊዜ ሞዓባውያን አደጋ ጣዮች በየዓመቱ
በጸደይ ወራት ወደ እስራኤል ምድር እየ
ሰረጉ ይገቡ ነበር።
21አንድ ጊዜ እስራኤላውያን ሰው ሞቶ
ሲቀብሩ፣ አንድ የአደጋ ጣይ ቡድን በድን
ገት አዩ፤ ስለዚህ የሞተውን ሰው ሬሳ
ኤልሳዕ መቃብር ውስጥ ጣሉት፤ ሬሳው
የኤልሳዕን ዐፅም እንደ ነካም ወዲያውኑ
ሰውየው ድኖ በእግሩ ቆመ።
22በኢዮአካዝ ዘመነ መንግሥት ሁሉ፣
የሶርያ ንጉሥ አዛሄል፣ እስራኤልን ያስጨ
ንቃቸው ነበር። 23*እግዚአብሔር* ግን ራራ
ላቸው፤ አዘነላቸው፤ ፊቱን መለሰላቸው፤
ይህም ከአብርሃም፣ ከይስሐቅና ከያዕቆብ
ጋር ስለ ገባው ኪዳን ሲል ነው፤ እስከ
ዛሬ ድረስ ሊያጠፋቸው አልፈለገም፤ ከፊ
ቱም አላስወገዳቸውም።
24የሶርያ ንጉሥ አዛሄል ሞተ፤ ልጁ ቤን
ሃዳድም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ። 25ከዚያም
የኢዮአካዝ ልጅ ዮአስ፣ አዛሄል ከአባቱ
ከኢዮአካዝ እጅ በጦርነት የወሰዳቸውን
ከተሞች ከአዛሄል ልጅ ከቤንሃዳድ አስመ
ልሶ ያዘ። ዮአስ ሦስት ጊዜ ድል አደረ
ገው፤ የእስራኤልንም ከተሞች በዚህ ሁኔታ

13፥15 1ሳሙ 20፥20
13፥17 ኢሱ8፥18፤ 1ነገ20፥26
13፥19 ቍ25
13፥20 2ነገ5፥2
13፥21 ማቴ27፥52
13፥22 1ነገ19፥17
13፥23 ዘፀ2፥24፤ 33፥15፤ዘዳ29፥20፤ 2ነገ17፥18፤24፥3፡20
13፥24 ቍ3
13፥25 ቍ2ነገ 10፥32

14፥4 2ነገ12፥3
14፥5 2ነገ12፥20፤ 21፥24
14፥6 ዘኁ26፥11፤ ዘዳ28፥61፤ ኢዮ21፥20፤ ኤር31፥30፤44፡3፤ ሕዝ18፥4፡20
14፥7 መሳ1፥36፤ 2ሳሙ8፥13
14፥9 መሳ9፥8-15
14፥10 2ዜና26፥16፤ 32፥25
14፥11 ኢሱ15፥10

መልሶ ያዘ።

## የይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ

14፥1-7 ተጓ ምብ - 2ዜና25፥1-4፤11-12
14፥8-22 ተጓ ምብ - 2ዜና25፥17- 26፥2

14 የእስራኤል ንጉሥ የኢዮአካዝ ልጅ
ዮአስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት፣
የይሁዳ ንጉሥ የኢዮአስ ልጅ አሜስያስ
ነገሠ። 2በነገሠም ጊዜ ዕድሜው ሃያ አም
ስት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀም
ጦም ሃያ ዘጠኝ ዓመት ገዛ። እናቱም ዮዓ
ዳን የተባለች የኢየሩሳሌም ሴት ነበረች።
3እርሱም *በእግዚአብሔር* ፊት መልካም
ነገር አደረገ፤ ነገር ግን አባቱ ዳዊት
እንደ አደረገው ዐይነት አልነበረም፤ በ
ማና ቸውም ረገድ የአባቱን የኢዮአስን
ፈለግ ተከተለ። 4በየኰረብታው ላይ
ያሉት ማም ለኪያዎች አልተወገዱም፤ ሕ
ዝቡም በየኰረ ብታው ላይ መሥዋዕት
ማቅረቡንና ዕጣን ማጤሱን እንደ ቀጠለ
ነበር።
5አሜስያስ መንግሥቱን አጽንቶ ከያዘ
በኋላ፣ ንጉሥ አባቱን የገደሉትን ሹማም
ንት ገደላቸው፤ 6ይሁን እንጂ በሙሴ
የሕግ መጽሐፍ *እግዚአብሔር*፣ "እያንዳ
ንዱ በራሱ ኀጢአት ይገደል እንጂ አባ
ቶች በልጆቻቸው፣ ልጆችም በአባቶቻቸው
ኀጢአት አይገደሉ"[የ] ሲል ያዘዘ በመሆኑ፣
የነፍሰ ገዳዩን ልጆች አልገደላቸውም።
7የጨው ሸለቆ በተባለው ቦታ ዐሥር
ሺህ ኤዶማውያንን ድል ያደረገ፣ ሴላን
በጦርነት የያዘና እስከ ዛሬም ድረስ ዮቅት
ኤል ተብላ የምትጠራበትን ስም ያወጣ
ላት አሜስያስ ነው።
8ከዚያም አሜስያስ የኢዩ የልጅ ልጅ፣
የኢዮአካዝ ልጅ ወደ ሆነው ወደ እስራ
ኤል ንጉሥ ወደ ዮአስ፣ "ናና ፊት ለፊት
ይዋጣልን" ሲል መልእክተኞች ላከበት።
9የእስራኤል ንጉሥ ዮአስ ግን ለይሁዳ
ንጉሥ ለአሜስያስ እንዲህ ሲል ላከበት፤
"አንድ የሊባኖስ ኵርንችት፣ ለአንድ የሊ
ባኖስ ዝግባ፣ 'ሴት ልጅህን ለልጄ በሚ
ስትነት ስጠው' አለው፤ ከዚያም አንድ
የሊባኖስ ዱር አውሬ መጥቶ ኵርንችቱን
በእግሩ ረገጠው። 10በእርግጥ ኤዶምን
ድል አድርገሃል፤ ታዲያ ልብህ አለመጠን
አይኵራራ። ድል በማድረግህ አትንጠራራ፤
አርፈህ ተቀመጥ! ጠብ በመጫር የራስህ
ንስ፣ የይሁዳንስ ውድቀት ለምን ትሻ
ለህ?"
11አሜስያስ ግን አልሰማም፤ ስለዚህ የእ
ስራኤል ንጉሥ ዮአስ ወጣ፤ እርሱና የይ
ሁዳ ንጉሥ አሜስያስም በይሁዳ ምድር

በቤትሳሚስ ፊት ለፊት ጦርነት ገጠሙ።
12ይሁዳ በእስራኤል ድል ሆነ፤ እያንዳን
ዱም ወደ ድንኳኑ ሸሸ። 13የእስራኤል
ንጉሥ ዮአስም የአካዝያስን የልጅ ልጅ፣
የኢዮአስን ልጅ የይሁዳን ንጉሥ አሜ
ስያስን ቤትሳሚስ ላይ ማረከው። ከዚያም
ዮአስ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ፤ ከኤፍሬም
ቅጥር በር አንሥቶ የማእዘን ቅጥር በር
እስከተባለው ድረስ ርዝመቱ አራት መቶ
ክንድ[ዶ] የሆነውን ቅጥር አፈረሰ። 14*በእግዚ
አብሔር* ቤተ መቅደስና በቤተ መንግ
ሥቱ ግምጃ ቤቶች ያለውን ወርቅና ብር
በሙሉ በዚያም የተገኘውን ዕቃ ሁሉ በመ
ውሰድ ምርኮኞችንም ይዞ ወደ ሰማርያ
ተመለሰ። 15በዮአስ ዘመነ መንግሥት የተ
ከናወነው ሌላው ነገር፣ ያደረገውና የፈ
ጸመው ሁሉ በይሁዳ ንጉሥ በአሜስያስ
ላይ ያደረገው ጦርነት ጭምር በእስራኤል
ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለ
ምን? 16ዮአስ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በሰ
ማርያም ከእስራኤል ነገሥታት ጋር ተቀ
በረ፤ ልጁ ኢዮርብዓምም በእግሩ ተተክቶ
ነገሠ። 17የኢዮአስ ልጅ የይሁዳ ንጉሥ
አሜስያስም የእስራኤል ንጉሥ የኢዮአካዝ
ልጅ ዮአስ ከሞተ በኋላ ዐሥራ አም
ስት ዓመት ኖረ። 18በአሜስያስ ዘመነ መን
ግሥት የተከናወነው ሌላው ነገር በይሁዳ
ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለ
ምን?
19አሜስያስ በኢየሩሳሌም ሴራ ስለጠነሰ
ሱበት ሸሽቶ ወደ ላኪሶ ሄደ፤ እነርሱ ግን
የሚከታተሉት ሰዎች ወደዚያው ልከው
አስገደሉት፤ 20ሬሳውም በፈረስ ተጭኖ
መጥቶ በዳዊት ከተማ ከአባቶቹ ጋር በኢ
የሩሳሌም ተቀበረ።
21ከዚያም የይሁዳ ሕዝብ በሙሉ ዕድሜው
ዐሥራ ስድስት ዓመት የሆነውን ዓዛርያስን
ወስደው በአባቱ በአሜስያስ ፋንታ አነገ
ሡት። 22አሜስያስ ከአባቶቹ ጋር
ካንቀላፋ በኋላ ኤላትን እንደገና ሠርቶ
ወደ ይሁዳ የመለሳት ይኸው ዓዛርያስ[ጀ]
ነበር።

## የእስራኤል ንጉሥ ዳግማዊ ኢዮርብዓም

23የኢዮስያስ ልጅ አሜስያስ በይሁዳ በነ
ገሠ በዐሥራ አምስተኛው ዓመት፣ የእስራ
ኤል ንጉሥ የዮአስ ልጅ ኢዮርብዓም በሰ
ማርያ ነገሠ፤ አርባ አንድ ዓመትም ገዛ።
24*በእግዚአብሔርም* ፊት ክፉ ነገር አደ
ረገ፤ የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም እስራኤልን
ካሳተበት ኀጢአት አልተመለሰም። 25የእስ
ራኤል አምላክ *እግዚአብሔር* በጋትሔፌር
ነቢይ፣ በአማቴ ልጅ በባሪያው በዮናስ
አማካይነት እንደ ተናገረው፣ ከሐማት መተ

14፥12 1ነገ22፥36
14፥13 1ነገ3፥1፤ 2ዜና26፥9፤33፥14፤36፥19፤ነህ8፥16፤12፥39፤ ኤር31፥38፤39፥2፤ዘካ14፥10
14፥15 2ነገ13፥12
14፥19 ኢሱ10፥3፤ 2ነገ12፥20
14፥20 2ነገ9፥28
14፥21 2ነገ15፥1፤ 2ዜና26፥23፤ ኢሳ1፥1፤ ሆሴ1፥1፤አሞ1፥1
14፥22 1ነገ9፥26
14፥23 2ነገ13፥13፤ 1ዜና5፥17፤አሞ1፥1፤7፥10
14፥24 1ነገ15፥30
14፥25 ዘኁ13፥21፤ ዘዳ3፥17፤ዮና1፥1፤ ማቴ12፥39
14፥26 ዘዳ32፥36፤ 2ነገ13፥4፤መዝ18፥41፤22፥11፤ 72፥12፤107፥12፤ ኢሳ63፥5፤ስቆ1፥7
14፥27 ዘዳ29፥20፤መሳ6፥14
14፥28 2ሳሙ8፥5፥9፤1ነገ15፥31
15፥1 ቍ32፤2ነገ14፥21
15፥3 1ነገ14፥8
15፥5 ቍ7፥32፤ ዘፍ12፥17፥41፥40፤ ዘሌ13፥46፤2ዜና27፥1፤ሚክ1፥1
15፥7 ቍ5፤ኢሳ6፥1፤14፥28

ላሊፈያ[ገ] አንሥቶ እስከ ሙት ባሕር[ጠ] ድረስ
የነበረውን የእስራኤልን ድንበር ያስመለሰ
ኢዮርብዓም ነው።
26ባሪያም ይሁን ነጻ ዜጋ፣ በእስራኤል
የሚኖር ሁሉ እንዴት እጅግ ይሠቃይ
እንደ ነበር *እግዚአብሔር* አየ፤ የሚረዳቸ
ውም አልነበረም። 27ይሁን እንጂ *እግዚአ
ብሔር* የእስራኤልን ስም ከምድረ ገጽ
እንደሚያጠፋ ስላልተናገረ፣ በዮአስ ልጅ
በኢዮርብዓም አማካይነት ታደጋቸው።
28በኢዮርብዓም ዘመነ መንግሥት የተ
ከናወነው ሌላው ነገር፣ የፈጸመው ሁሉና ያደ
ረጋቸው ጦርነቶች እንዲሁም የይሁዳ
ግዛት የነበሩትን ደማስቆንና ሐማትን እን
ዴት ለእስራኤል እንዳስመለሰ በእስራኤል
ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለ
ምን? 29ኢዮርብዓም ከአባቶቹ ከእስራኤል
ነገሥታት ጋር አንቀላፋ፤ ልጁ ዘካርያስም
በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

## የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ

15፥1-7 ተጓ ምብ - 2ዜና26፥3-4፤21-23

15 የእስራኤል ንጉሥ ኢዮርብዓም በነ
ገሠ በሃያ ሰባተኛው ዓመት የይ
ሁዳ ንጉሥ የአሜስያስ ልጅ ዓዛርያስ ነገሠ።
2ሲነግሥም ዕድሜው ዐሥራ ስድስት
ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦ
አምሳ ሁለት ዓመት ገዛ። እናቱም ይኮ
ልያ የተባለች የኢየሩሳሌም ሴት ነበረች።
3አባቱ አሜስያስ እንዳደረገው ሁሉ ዓዛር
ያስም *በእግዚአብሔር* ፊት መልካም ነገር
አደረገ። 4ይሁን እንጂ በየኰረብታው ላይ
ያሉት የማምለኪያ ስፍራዎች አልተወገ
ዱም፤ ሕዝቡም በዚያ መሥዋዕት ማቅረቡ
ንና እጣን ማጤሱን እንደ ቀጠለ ነበር።
5*እግዚአብሔርም* ንጉሡን እስከሚሞት
በት ቀን ድረስ በለምጽ[ጩ] መታው፤ በተ
ለየቤትም ይኖር ነበር። በዚያን ጊዜ ቤተ
መንግሥቱን በኀላፊነት የሚመራውና የአ
ገሩንም ሕዝብ የሚያስተዳድረው የንጉሡ
ልጅ ኢዮአታም ነበር።
6በዓዛርያስ ዘመነ መንግሥት የተከናወ
ነው ሌላው ሥራ፣ የፈጸመውም ሁሉ በይ
ሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይ
ደለምን? 7ዓዛርያስ ከአባቶቹ ጋር አንቀ
ላፋ፤ በዳዊትም ከተማ በአባቶቹ መቃብር
አጠገብ ቀበሩት። ልጁ ኢዮአታምም በእ
ግሩ ተተክቶ ነገሠ።

## የእስራኤል ንጉሥ ዘካርያስ

8የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ በነገሠ በሠላሳ
ስምንተኛው ዓመት፣ የኢዮርብዓም ልጅ

[የ]6 ዘዳ 24፥16 ይመ። [ዶ]13 ዕብራይስጡ 180 ሜትር ይላል
[ጀ]21 *ኢዩስያስ* [ገ]5 *ሊቦ* [ጠ]25 *የዓረባ ባሕር*

ዘካርያስ በሰማርያ ከተማ በእስራኤል ላይ
ነገሠ፤ ስድስት ወርም ገዛ። 9አባቱ እንዳደ
ረገው ሁሉ፣ እርሱም *በእግዚአብሔር* ፊት
ክፉ አደረገ፤ የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም እስ
ራኤልን ካሳተበት ኀጢአት አልተመለ
ሰም።
10የያቤስ ልጅ ሰሎም በዘካርያስ ላይ
አሤረበት፤ በሕዝቡ[ጰ] ፊት አደጋ ጥሎ ገደ
ለው፤ በእግሩም ተተክቶ ነገሠ። 11በዘካር
ያስ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው ሌላው
ሥራ በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተመዝ
ግቦአል። 12በዚህም *እግዚአብሔር* ለኢዩ፣
“ልጆችህ እስከ አራት ትውልድ ድረስ
በእስራኤል ዙፋን ላይ ይቀመጣሉ”[ጸ] ሲል
የተናገረው ቃል ተፈጸመ።

### የእስራኤል ንጉሥ ሰሎም

13የይሁዳ ንጉሥ ዖዝያን በነገሠ በሠላሳ
ዘጠነኛው ዓመት የኢያቤስ ልጅ ሰሎም
በእስራኤል ላይ ነገሠ። በሰማርያ ተቀምጦ
አንድ ወር ገዛ። 14የጋዲ ልጅ ምናሔም
ከቴርሳ ወጥቶ ወደ ሰማርያ በመሄድ አደጋ
ጥሎ የኢያቤስን ልጅ ሰሎምን ገደለው፤
ከዚያም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።
15በሰሎም ዘመነ መንግሥት የተከናወ
ነው ሌላው ሥራና የጠነሰሰውም ሤራ በእ
ስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎአል።
16በዚያን ጊዜም ምናሔም ከቴርሳ
ወጥቶ በቲፍሳና በከተማዪቱ ነዋሪዎች
ላይ ሁሉ፣ በአካባቢዋም ጭምር አደጋ ጣለ፤
ይህን ያደረገውም የከተማዪቱን በሮች
ለመክፈት ፈቃደኞች ባለመሆናቸው ነበር፤
ቲፍሳን መታት፤ የነፍሰጡሮችንም ሆድ
ሁሉ ቀደደ።

### የእስራኤል ንጉሥ ምናሔም

17የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ በነገሠ በሠላሳ
ዘጠነኛው ዓመት፣ የጋዲ ልጅ ምናሔም
በእስራኤል ላይ ነገሠ፤ በሰማርያ ተቀም
ጦም ዐሥር ዓመት ገዛ። 18*በእግዚአብሔር*
ፊት ክፉ ነገር አደረገ፤ በዘመኑም ሁሉ
የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም እስራኤልን ካሳ
ተበት ኀጢአት አልተመለሰም።
19ከዚያም የአሦር ንጉሥ ቴልጌልቴልፌ
ልሶር[ፀ] ምድሪቱን ወረረ፤ ምናሔም ርዳታ
ውን ለማግኘትና በመንግሥቱ ላይ ያለ
ውን ይዞታ ለማጽናት ሲል፣ አንድ ሺህ
መክሊት[ፈ] ብር ሰጠው። 20ምናሔም ገን
ዘቡ እንዲዋጣ ያደረገው ከእስራኤል ሲሆን፣
ይህንንም ያደረገው ለአሦር ንጉሥ ይሰጥ
ዘንድ እያንዳንዱ ሀብታም አምሳ፣ አምሳ
ሰቅል[ፐ] ብር እንዲያዋጣ በማስገደድ
ነበር። ስለዚህ የአሦር ንጉሥ በዚያች

15፥9 1ነገ15፥26
15፥10 2ነገ12፥20
15፥11 1ነገ15፥31
15፥12 2ነገ10፥30
15፥13 1ነገ13፥32
15፥14 1ነገ5፥33፤ 2ነገ12፥20
15፥15 1ነገ15፥31
15፥16 1ነገ4፥24፤ 2ነገ8፥12፤ሆሴ13፥16
15፥18 1ነገ15፥26
15፥19 1ዜና5፥6፡26
15፥20 2ነገ12፥18
15፥24 1ነገ15፥26
15፥25 2ነገ12፥20፤2ዜና28፥6፤ኢሳ7፥1
15፥27 2ዜና 28፥6፤ኢሳ7፥1፡4
15፥29 1ነገ 15፥20፤2ነገ16፥7፡9፤ 17፥6፡24፤24፥14,16፤ 1ዜና5፥22፡26፤2ዜና 16፥4፤28፥20፤ኢሳ 7፥9፤9፥1፤10፥9፡10፤ 14፥6፡17፤28፥1፤36፥1 7፡19፤37፥18፤45፥13፤ ኤር50፥17
15፥30 2ነገ 12፥20፤17፥1
15፥31 1ነገ15፥31

አገር አል ቈየም፤ ተመልሶ ሄደ።
21በምናሔም ዘመነ መንግሥት የተከና
ወነው ሌላው ሥራ የፈጸመውም ሁሉ በእ
ስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ
አይደለምን? 22ምናሔም ከአባቶቹ ጋር
አንቀላፋ፤ ልጁ ፋቂስያስም በእግሩ ተተ
ክቶ ነገሠ።

### የእስራኤል ንጉሥ ፋቂስያስ

23የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ በነገሠ በአም
ሳኛው ዓመት፣ የምናሔም ልጅ ፋቂስያስ
በሰማርያ ከተማ የእስራኤል ንጉሥ ሆነ፤
ሁለት ዓመትም ገዛ። 24ፋቂስያስ *በእግዚአ
ብሔር* ፊት ክፉ ነገር አደረገ፤ የናባጥ
ልጅ ኢዮርብዓም፣ እስራኤልን ካሳተበት
ኀጢአት አልተመለሰም። 25ከጦር አለቆቹ
አንዱ የሆነው የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ
አሤረበት፤ አምሳ የገለዓድ ሰዎች ይዞ
በመሄድ፣ ሰማርያ ቤተ መንግሥት ባለው
ምሽግ ፋቂስያስን ከአርጎብና ከአርያ ጋር
ገደለው፤ በእግሩም ተተክቶ ነገሠ።
26በፋቂስያስ ዘመነ መንግሥት የተከና
ወነው ሌላው ሥራ የፈጸመውም ሁሉ
በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎአል።

### የእስራኤል ንጉሥ ፋቁሔ

27የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ በነገሠ
በአምሳ ሁለተኛው ዓመት የሮሜልዩ ልጅ
ፋቁሔ በሰማርያ ከተማ፣ በእስራኤል ላይ
ነገሠ፤ ሃያ ዓመትም ገዛ። 28እርሱም
*በእግዚአ ብሔር* ፊት ክፉ ነገር አደረገ፤
የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም እስራኤልን
ካሳተበት ኀጢአት አልተመለሰም።
29በእስራኤል ንጉሥ በፋቁሔ ዘመን፣
የአሦር ንጉሥ ቴልጌልቴልፌልሶር መጥቶ
ዒዮንን፣ አቤልቤትመዓካን፣ ያኖዋን፣ ቃዴ
ስንና ሐጾርን፣ ገለዓድንና ገሊላን፣ የንፍታሌ
ምንም ምድር ጭምር ያዘ። ሕዝቡንም
ማርኮ ወደ አሦር ወሰደው። 30ከዚያም
የኤላ ልጅ ሆሴዕ በሮሜልዩ ልጅ በፋቁሔ
ላይ አሤረበት፤ አደጋ ጥሎም ገደለው፤ የዖዝ
ያን ልጅ ኢዮአታም በነገሠ በሃያኛው
ዓመትም ሆሴዕ በፋቁሔ እግር ተተክቶ
ነገሠ። 31በፋቁሔ ዘመነ መንግሥት የተከ
ናወነው ሌላው ሥራ የፈጸማቸውም ሁሉ
በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚ
ገኝ አይደለምን?

[ጨ]5 የዕብራይስጡ ቃል ቈዳን የሚያጠቁትን ማንኛውንም ዐይነት በሽታዎች ያመለክታል። [ጰ]10 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማምል። አንዳንድ የስብዓ ሊቃናት ትርጒሞች ግን፣ “በኢብላም” ይላሉ [ጸ]12 2ነገ 10፥30 ይመ።
[ፀ]19 *ቲግላት ፐሌሴርም* ይባላል።
[ፈ]19 34 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
[ፐ]20 0.6 ኪሎ ግራም ያህል ነው።

### የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአታም

15፥33-38 ተጓ ምብ - 2ዜና27፥1-4፤7-9

32የእስራኤል ንጉሥ የሮሜልዩ ልጅ
ፋቁሔ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት፣ የይ
ሁዳ ንጉሥ የዖዝያን ልጅ ኢዮአታም ነገሠ።
33ሲነግሥም ዕድሜው ሃያ አምስት ዓመት
ነበር፤ ኢየሩሳሌም ተቀምጦም ዐሥራ ስድ
ስት ዓመት ገዛ፤ እናቱም የሳዶቅ ልጅ
ስትሆን፤ ኢየሩሳ ትባል ነበር። 34አባቱ
ዖዝያን እንዳደረገው ሁሉ እርሱም *በእግዚ
አብሔር* ፊት መልካም ነገር አደረገ።
35ይሁን እንጂ በየ ኰረብታው ላይ ያሉት
የማምለኪያ ስፍራዎች አልተወገዱም፤ ሕዝ
ቡም በዚያ መሥዋዕት ማቅረቡንና ዕጣን
ማጤሱን እንደ ቀጠለ ነበር። ኢዮአታም
*የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስ የላይኛውን
በር መልሶ ሠራ።

36በኢዮአታም ዘመነ መንግሥት የተከና
ወነው ሌላው ሥራ፣ የፈጸመውም ሁሉ
በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ
አይደለምን? 37በዚያን ጊዜ *እግዚአብሔር*
የሶርያ ንጉሥ ረአሶንና የሮሜልዩ ልጅ
ፋቁሔን ይሁዳን እንዲወጉ አደረገ። 38ኢዮ
አታምም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ አባቶቹ
በተቀበሩበትም፤ በአባቱ በዳዊት ከተማ
ተቀበረ። ልጁ አካዝም በእግሩ ተተክቶ
ነገሠ።

### የይሁዳ ንጉሥ አካዝ

16፥1-20 ተጓ ምብ - 2ዜና28፥1-27

16 የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ በነገሠ
በዐሥራ ሰባተኛው ዓመት፣ የይ
ሁዳ ንጉሥ፣ የኢዮአታም ልጅ አካዝ ነገሠ።
2አካዝ ሲነግሥ ዕድሜው ሃያ ዓመት ነበር፤
በኢየሩሳሌም ተቀምጦም ዐሥራ ስድ
ስት ዓመት ገዛ። አባቱ ዳዊት ያደረገውን
መልካም ነገር በአምላኩ *በእግዚአብሔር*
ፊት አላደረገም። 3እርሱም የእስራኤልን
ነገሥታት መንገድ ተከተለ፤ ይልቁንም
*እግዚአብሔር* ከእስራኤላውያን ፊት ያሳ
ደዳቸውን የአሕዛብን ርኵሰት ተከትሎ፣
ልጁን በእሳት የሚቃጠል መሥዋዕት አድ
ርጎ አቀረበ።[ሀ] 4እንዲሁም ኰረብታ ላይ
ባሉ ማምለኪያ ስፍራዎች፣ በኰረብታ
አናቶችና ቅጠሉ በተንሰራፋው ዛፍ ሥር
ሁሉ ሠዋ፤ ዕጣንም አጤሰ።

5የሶርያ ንጉሥ ረአሶንና የእስራኤል
ንጉሥ የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ ኢየሩሳሌ
ምን ለመውጋትና አካዝን ለመክበብ ወጡ፤
ይሁን እንጂ ሊያሸንፉት አልቻሉም።
6በዚያን ጊዜም የሶርያ ንጉሥ ረአሶን የይ
ሁዳን ሰዎች አሳዶ፣ ኤላትን ወደ ሶርያ
ግዛት መለሰ፤ ከዚያም ኤዶማውያን ወደ
ኤላት መጥተው እስከ ዛሬ በዚያ ይኖራሉ።

7ከዚህ የተነሣም አካዝ፣ ወደ አሦር
ንጉሥ ወደ ቴልጌልቴልፌልሶር፣ “እኔ አገ
ልጋይህም ልጅህም ነኝ፤ ስለዚህ መጥተህ
ከሚወጉኝ ከሶርያ ንጉሥና ከእስራኤል
ንጉሥ እጅ አድነኝ” ሲል መልእክተኞች
ላከበት። 8አካዝም *በእግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስና በቤተ መንግሥቱ ግምጃ ቤቶች
የሚገኘውን ብርና ወርቅ አውጥቶ ለአሦር
ንጉሥ ገጸ በረከት ላከለት። 9የአሦር ንጉ
ሥም፣ የአካዝን ልመና በመቀበል፤ ደማስ
ቆን አጥቅቶ ያዛት፤ ሕዝቧን ማርኮ ወደ
ቂር አፈለሳቸው፤ ረአሶንንም ገደለው።

10ከዚያም ንጉሥ አካዝ የአሦርን ንጉሥ
ቴልጌልቴልፌልሶርን ለመገናኘት ወደ ደማ
ስቆ ሄደ። በደማስቆም ያለውን መሠዊያ
አይቶ፣ ንድፉን ከዝርዝር ጥናቱ ጋር
ለካህኑ ለኦርያ ላከለት። 11ካህኑ ኦርያም
ንጉሥ አካዝ ከደማስቆ በላከለት ዝርዝር
ጥናት መሠረት መሠዊያ ሠራ፤ ንጉሡ
አካዝ ከመመለሱም በፊት አጠናቀቀው።
12ንጉሡ ከደማስቆ ተመልሶ በመጣ ጊዜ፣
መሠዊያውን አየ፤ ቀርቦም በመሠዊያው
ላይ ወጣ፤ 13ከዚያም የሚቃጠል መሥዋዕ
ቱንና የእህል ቍርባኑን በመሠዊያው ላይ
አቀረበ፤ የመጠጥ ቍርባኑን አፈሰሰ፤ የኅ
ብረት መሥዋዕቱንም[ለ] ደም በመሠዊያው
ላይ ረጨ። 14በአዲሱ መሠዊያና *በእግዚ
አብሔር* ቤተ መቅደስ መካከል፣ *በእግዚ
አብሔር* ፊት ቆሞ የነበረውን የናስ መሠ
ዊያ፣ ከቦታው አሥነስቶ ከአዲሱ መሠ
ዊያ በስተ ሰሜን በኩል አኖረው።

15ከዚያም ንጉሥ አካዝ፣ ካህኑን ኦርያን
እንዲህ ሲል አዘዘው፤ “በዚህ በትልቁ
አዲስ መሠዊያ ላይ የጧቱን የሚቃጠል
መሥዋዕትና የማታውን የእህል ቍርባን፣
የንጉሡን የሚቃጠል መሥዋዕትና የእህ
ሉን ቍርባን እንዲሁም የመላውን የአገሬ
ቱን ሕዝብ የሚቃጠል መሥዋዕት፣ የእህ
ልና የመጠጥ ቍርባናቸውን አቅርብ፤ የሚ
ቃጠለውን መሥዋዕት ደምና የሌላውን
መሥዋዕት ደም ሁሉ በመሠዊያው ላይ
እርጨው፤ የናሱ መሠዊያ ግን እኔ መመ
ሪያ ለመጠየቅ የምጠቀምበት ይሆናል።”
16ካህኑ ኦርያም ንጉሡ አካዝ እንዳዘዘው
ሁሉ እንዲሁ አደረገ።

17ንጉሡ አካዝም የጐንና የጐን ሳንቃ
ዎቹን ነቅሎ ወሰደ፤ በተንቀሳቃሹ መቆ
ሚያ ላይ ያሉትን የመታጠቢያ ሳሕኖች
አስወገደ። የውሃ ማጠራቀሚያውን ክብ
ገንዳ ከታች ተሸክመው ከያዙት ከዐሥራ

[ሀ]3 ወይም፣ *ልጁን ገደለ* [ለ]13 በትውፊት፣ *የሰላም መሥዋዕት*

15፥32 ቈላ1፥5፤ 1ዜና5፥17፤ኢሳ 1፥1፤ሆሴ1፥1
15፥34 1ነገ14፥8
15፥35 ዘፍ23፥10፤ 2ነገ12፥3፤2ዜና 23፥20
15፥37 2ነገ16፥5፤ ኢሳ7፥1፤8፥6፤ 9፥11
16፥1 ኢሳ1፥1፤ 7፥1፤14፥28፤ሆሴ1፥1፤ ሚክ1፥1
16፥2 1ነገ14፥8
16፥3 ዘሌ18፥3፡ 21፤ ዘዳ9፥4፤2ነገ 3፥27፤17፥19፤
16፥4 ዘዳ12፥2፤ 2ነገ22፥17፤23፥5፤ ሕዝ6፥13
16፥5 2ነገ15፥37
16፥6 1ነገ9፥26፤ ኢሳ9፥12
16፥7 2ነገ15፥29፤ ኢሳ 2፥6፤10፥20፤ ኤር2፥18፤3፥1፤ ሕዝ16፥28፤ 23፥5፤ሆሴ10፥6
16፥8 1ነገ15፥18፤ 2ነገ12፥18
16፥9 ዘፍ 14፥15፤2ነገ15፥29፤ ኢሳ22፥6፤ አሞ1፥5፤9፥7
16፥10 ቈላ11፡ 15፡16፤ኢሳ8፥2
16፥12 2ዜና 26፥16
16፥13 ዘፀ29፥40፤ ዘሌ6፥813፡14-23፤ 7፥11-21
16፥14 ዘፀ20፥24፤ 40፥6፤1ነገ8፥64
16፥15 ዘፀ29፥38-41፤1ሳሙ9፥9
16፥17 1ነገ7፥27
16፥18 ሕዝ16፥28

ሁለቱ የናስ ቅርጽ ኮርማዎች ላይ አውርዶ
በጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ አስቀመጠው።
18የአሦርንም ንጉሥ ለማስደሰት ሲል፣ በዕ
ለተ ሰንበት ንጉሣዊ ዙፋን[ሐ] እንዲዘረጋ
በት በቤተ መቅደሱ ውስጥ የተሠራውን
ከፍ ያለ ስፍራና ነገሥታቱ ወደ እግዚአ
ብሔር ቤተ መቅደስ የሚገቡበትን በውጭ
ያለውን መግቢያ አነሣ።
19በአካዝ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው
ሌላው ሥራ፣ የፈጸመውም ሁሉ በይሁዳ
ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለ
ምን? 20አካዝም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤
ከእነርሱ ጋር በዳዊት ከተማ ተቀበረ። ልጁ
ሕዝቅያስም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

## ሆሴዕ የመጨረሻው የእስራኤል ንጉሥ

17፥3-7 ተጓ ምብ - 2ነገ18፥9-12

17 የይሁዳ ንጉሥ አካዝ በነገሠ በዐ
ሥራ ሁለተኛው ዓመት፣ የኤላ
ልጅ ሆሴዕ በሰማርያ ከተማ በእስራኤል
ላይ ነገሠ፤ ዘጠኝ ዓመትም ገዛ። 2እርሱም
በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር አደረገ፤
ክፉ ሥራው ግን ከእርሱ አስቀድሞ የነ
በሩት የእስራኤል ነገሥታት የፈጸሙትን
ያህል አልነበረም። 3የአሦር ንጉሥ ሰልም
ናሶር ሊወጋው መጣ፤ ሆሴዕም ተገዛለት፤
ገበረለትም። 4የአሦር ንጉሥ ግን ሆሴዕ
እንደ ከዳው ተገነዘበ፤ ምክንያቱም ወደ
ግብፅ ንጉሥ ወደ ሲኦር መልክተኞች
ስለላከና በየመቱም ያደርግ እንደነበረው
ለአሦር ንጉሥ ስላልገበረ ነው፤ ከዚህም
የተነሣ ስልምናሶር ይዞ ወህኒ ቤት አስገ
ባው። 5የአሦርም ንጉሥ አገሩን በሙሉ
ወረረ፤ ወደ ሰማርያም ገሥግሦ ሦስት ዓመት
ከበባት። 6በሆሴዕ ዘመነ መንግሥት በዘጠ
ነኛው ዓመት፣ የአሦር ንጉሥ ሰማርያን
ያዘ፤ እስራኤላውያንንም በምርኮ ወደ
አሦር አፈለሳቸው። እነዚህም በአላሔ፣
ጎዛን ውስጥ በአቦር ወንዝ አጠገብ እንዲ
ሁም በሜዶን ከተሞች እንዲሰፍሩ አደ
ረገ።

## እስራኤላውያን በኀጢአታቸው ምክንያት ተማረኩ

7እንግዲህ እስራኤላውያን ይህ ሁሉ ሊደ
ርስባቸው የቻለው፣ ከግብፅ ምድር ከፈር
ዖን አገዛዝ ከግብፅ ንጉሥ ያወጣቸውን
አምላካቸውን እግዚአብሔርን ስለ በደሉት
ነው፤ እንዲሁም ሌሎች አማልክትን በማ
ምለክ፣ 8እግዚአብሔር ከፊታቸው አሳዶ
ያወጣቸውን የአሕዛብንና የእስራኤልም
ነገሥታት ወደ ምድሪቱ ያገቡትን አጸያፊ
ልማድ ስለ ተከተሉ ነበር።
9እስራኤላውያን በአምላካቸው በእግዚ
አብሔር ላይ ትክክል ያልሆነ ነገር በስ
ውር አደረጉ፤ ከቃፊር መጠባበቂያ ማማ
አንሥቶ እስከ ተመሸገው ከተማ ባሉት
መኖሪያዎቻቸው ሁሉ በሚገኙት ኰረብ
ቶች ላይ ማምለኪያ ስፍራዎችን ሠሩ።
10በእያንዳንዱ ኰረብታ ላይና በእያንዳን
ዱም የተንሰራፋ ዛፍ ሥር ዐምደ ጣዖትና
የአሼራን ምስል ዐምዶች አቆሙ። 11እግዚ
አብሔር ከፊታቸው አሳዶ ያስወጣቸው
አሕዛብ እንዳደረጉትም ሁሉ፣ በየኰረብ
ታው ላይ ዕጣን አጤሱ፤ እግዚአብሔር
ንም የሚያስቈጣ ክፉ ነገር አደረጉ። 12እግ
ዚአብሔር፣ "ይህን ማድረግ አይገባች
ሁም"[መ] ቢላቸውም እንኳ እነርሱ
ጣዖታ ትን አመለኩ። 13ይህም ሆኖ እግዚ
አብሔር፣ "ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ፤
አባቶቻችሁ እንዲፈጽሙት ባዘዝኋቸው ሕ
ግ ሁሉ መሠ ረት እንዲሁም በአገልጋዮቼ
በነቢያት አማ ካይነት ለእናንተ
ባስተላለፍሁት ሕግ መሠረት፣
ትእዛዜንና ሥርዐቴን ጠብቁ" ብሎ በነቢ
ያቱና በባለ ራእዮች ሁሉ እስራኤልንና
ይሁዳን አስጠንቅቆ ነበር።
14ይሁን እንጂ እነዚህም አልሰሙም፤
እግዚአብሔር አምላካቸውን እንዳልታመኑ
በት እንደ አባቶቻቸው ዐንገታቸውን አደነ
ደኑ። 15ሥርዐቱንና ከአባቶቻቸው ጋር የገ
ባውን ኪዳን፣ ለእነርሱም የሰጣቸውን ማስ
ጠንቀቂያ ናቁ፤ ከንቱ ጣዖታትን ተከት
ለው ራሳቸውም ከንቱ ሆኑ፤ እግዚአብሔር፣
"እነርሱ የሚያደርጉትን እንዳታደርጉ" ብሎ
ቢያዛቸው እንኳ በዙሪያቸው ያሉትን አሕ
ዛብ ተከተሉ፤ እግዚአብሔር እንዳያደርጉ
የከለከላቸውንም ፈጸሙ እንጂ አልተዉም።
አምላካቸው እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ሁሉ
አልፈጸሙም፤ አቅልጠውም ሁለት የጥጃ
ምስልና የአሼራን ምስል ዐምድ ሠሩ፤ ለሰ
ማይ ከዋክብት ሰገዱ፤ በኣልን አመለኩ፤
17እንዲሁም ወንዶችንና ሴቶች ልጆቻቸ
ውን በእሳት የሚቃጠል መሥዋዕት አድ
ርገው አቀረቡ።[ሠ] ጥንቈላና መተት አደ
ረጉ፤ በእግዚአብሔርም ፊት ክፉ ነገር ለማ
ድረግ ራሳቸውን ሸጡ፤ ለቍጣም አነሣ
ሡት። 18ስለዚህ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ
እጅግ ተቈጣ፤ የይሁዳ ነገድ ብቻ ሲቀር
እስራኤልን ከፊቱ አራቀ። 19ይሁዳም
ቢሆን ከእስራኤል የተቀበለውን ልማድ
ተከተለ እንጂ የአምላኩን የእግዚአብሔ
ርን ትእዛዝ አልጠበቀም። 20ስለዚህ እግዚ
አብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ሁሉ ተዋ
ቸው፤ አስጨነቃቸው፤ ከፊቱ እስኪያስወግ

16፥20 ኢሳ14፥28
17፥1 2ነገ15፥30
17፥2 ዘዳ4፥25
17፥3 መሳ3፥15፤ ሆሴ10፥14
17፥4 መዝ146፥3፤ ኢሳ30፥1፡7፤36፥6፤ ኤር2፥36፤ሆሴ12፥1፤13፥10
17፥5 ሆሴ13፥16
17፥6 ቀኊ20፤ ዘዳ4፥27፤24፥1፤2ነገ15፥29፤1ዜና5፥26፤ ኢሳ10፥9፤42፥24፤ አሞ7፥17
17፥7 ዘፀ14፥15-31፤ኢሱ7፥11
17፥8 ዘፀ34፥15፤ ዘሌ18፥3፤ዘዳ9፥4
17፥9 2ነገ18፥8
17፥10 ዘፀ23፥24፤ 34፥13፤ዘዳ12፥2፤ኢሳ 17፥8፤ሚክ5፥14
17፥12 ዘፀ20፥4
17፥13 መሳ6፥8፤ 1ሳሙ9፥9፤2ዜና7፥14፤ ኢዮ34፥33፤ኤር4፥1፤ 18፥11፤23፥22፤25፥5፤ 35፥15፤36፥3፤ሕዝ3፥17-19፤ ዘካ1፥4፤ማቴ 23፥34
17፥14 ዘፀ32፥9፤ ሐሥ7፥51
17፥15 ዘሌ26፥11፤ ዘዳ12፥4፤29፥25፤32፥21፤መሳ2፥20፤1ነገ 11፥11፤2ነገ18፥12፤ መዝ78፥10፤ኤር2፥5፤ ሕዝ5፥6፤ ሆሴ11፥2፤ ሚል2፥10፤ሮሜ1፥21-23
17፥16 ዘፍ2፥1፤ዘፀ 32፥4፤ዘዳ16፥21፤ መሳ2፥11፤ኢሳ 40፥26፤ኤር 19፥13
17፥17 ዘሌ19፥26፤ ዘዳ12፥31፤18፥10-12፤ 1ነገ21፥20፤2ነገ16፥3፤ ሕዝ16፥21፤ሮሜ7፥14
17፥18 ዘፍ4፥14፤ ዘፀ33፥15፤2ነገ13፥23፤ 2ተስ1፥9
17፥19 2ነገ16፥3፤ ኤር3፥6-10፤ሕዝ 23፥13፤
17፥20 ቀኊ6፤ኤር 7፥15፤15፥1፤

[ሐ]18 የሰብዓ ሊቃናት መሥዋዕት ትርጒም፣ የዙፋኑ ሰሌዳ ይላል።
[መ]12 ዘፀ 20፥4-5 [ሠ]17 ወይም ልጆቻቸው ገድሉ

ዳቸውም ድረስ በማራኪዎቻቸው እጅ አሳ
ልፎ ሰጣቸው።
21እስራኤልን ከዳዊት ቤት ከለየ በኋላ፣
እነርሱ የናባጥን ልጅ ኢዮርብዓምን አነገሡ፤
ኢዮርብዓምም እስራኤል *እግዚአብሔርን*
እንዳይከተል በማሳት ትልቅ ኀጢአት እን
ዲሠራ አደረገ። 22እስራኤላውያንም በኢዮ
ርብዓም ኀጢአት ሁሉ ጸኑ፤ ከዚያም አል
ተመለሱም። 23*እግዚአብሔር* በባሪያዎቹ
በነቢያት ሁሉ አማካይነት ባስጠነቀቃቸው
መሠረት፣ ከፊቱ እስኪያስወግዳቸው ድረስ
በዚያው ቀጠሉበት፤ ስለዚህ የእስራ
ኤል
ሕዝብ ከሀገሩ ተማርኮ ወደ አሦር ተወ
ሰደ፤ አሁንም በዚያው ይገኛል።

## *አሦራውያን በሰማርያ ሰፈሩ*

24የአሦርም ንጉሥ ሕዝቡን ከባቢሎን፣
ከኩታ፣ ከአዋና ከሐማት፣ ከሴፈርዋይም
ከተሞች አምጥቶ በእስራኤላውያን ቦታ
እንዲገቡ በሰማርያ ከተሞች አሰፈራቸው፤
እነርሱም ሰማርያን ወርሰው በከተሞቿ ይኖሩ
ጀመር። 25በዚያ መኖር እንደ ጀመሩም
*እግዚአብሔርን* አላመለኩም፤ ስለዚህ *እግ
ዚአብሔር* አንበሶች ሰደደባቸው፤ ከእነር
ሱም ጥቂቶቹን ሰብረው ገደሉ። 26ለአሦ
ርም ንጉሥ፣ “ወደ ሰማርያ ከተሞች ወስ
ደህ ያስፈርኸው ሕዝብ የዚያ አገር አም
ላክ የሚፈልገውን አላወቀም፤ ከዚህም የተ
ነሣ *እግዚአብሔር* ሰብሮ የሚገድል አንበሳ
ላከበት” የሚል ወሬ ደረሰው።
27ከዚያም የአሦር ንጉሥ፣ “ከሰ
ማርያ ማርካችሁ ካመጣችኋቸው ካህናት
አን ዱን፣ በእዚያው እንዲኖር መልሳችሁ
ውሰ ዱትና የአገሩ አምላክ ምን
እንደሚፈ ልግ ሕዝቡን ያስተምር” ሲል
አዘዘ። 28ስለ ዚህ ከሰማርያ ማርከው
ከወሰዷቸው ካህ ናት አንዱ ወደ ቤቴል
ተመልሶ *እግዚአ ብሔርን* እንዴት
ማምለክ እንደሚገባቸው አስተማራቸው።
29ያም ሆኖ ግን እያንዳ ንዱ ወገን
በየሰፈረበት ከተማ የራሱን አምላክ ሠ
ራ፤ ያንንም ቀድሞ የሰማርያ
ሕዝብ በኰረብታው ላይ በሠራው ማምለ
ኪያ እየወሰደ አቆመ። 30ከባቢሎን የመጡት
ሱኮትበኖትን፣ ከኩታ የመጡት ኔርጋ
ልን፣ ከሐማት የመጡት አስማትን ሠሩ፤
31አዋውያንም ኤልባዝርንና ተርታቅ የተባ
ሉትን አማልክት ሲሠሩ፣ ከሴፈርዋይም
የመጡት ደግሞ አድራሜሌክና አናሜሌክ
ለተባሉት አማልክታቸው ልጆቻቸውን የሚ
ቃጠል መሥዋዕት አድርገው አቀረቡ። 32*እግ
ዚአብሔርን* አመለኩ፤ ይሁን እንጂ እያን
ዳንዱ ወገን የመጣበትን ሕዝብ ልማድ

17፥21 1ሳሙ15፥27፤ 1ነገ11፥11፤12፥20፡30፤
17፥23 መሳ6፥8፤1ነገ 9፥7፤ሕዝ39፥23-24፤
17፥24 ቍ31፤2ነገ 15፥29፤18፥34፤19፥37፤ዕዝ4፥2፡10፤ኢሳ 36፥19፤37፥13፡38፤አሞ 6፥2
17፥25 ዘፍ37፥20፤ ኢሳ5፥29፤15፥9፤ ኤር50፥17
17፥29 ዘሌ26፥30፤ 1ነገ12፥31፤ኤር 2፥28፤11፥13፤ ሚክ4፥5
17፥31 ቍ24፤ 2ነገ19፥37
17፥32 1ነገ12፥31
17፥34 ዘፍ17፥5፤ 1ነገ18፥31
17፥35 ዘፀ20፥3፡5
17፥36 ዘፀ3፥20፤ መዝ136፥12
17፥37 ዘሌ19፥37፤ ዘዳ5፥32
17፥38 ዘዳ6፥12
17፥41 1ነገ18፥21፤ ዕዝ4፥2፤ማቴ6፥24
18፥1 ኢሳ1፥1፤ ሆሴ1፥1፤ሚክ1፥1
18፥2 ቍ13፤ኢሳ 38፥5
18፥3 1ነገ14፥8፤ ኢሳ38፥5
18፥4 ዘፀ23፥24፤ ዘኍ21፥9፤2ነገ12፥3፤21፥3፤2ዜና31፥1፤ኢሳ 36፥7

ተከተሉ፣ በየኰረብታው ባሉት ቤተ ጣዖ
ታት የሚያገለግሉትን ካህናት ሾመ። 33በአ
ንድ በኩል *እግዚአብሔርን* ሲያመልኩ፣
በሌላ በኩል ግን እንደየአገራቸው ልማድ
የየራሳቸውን አማልክት ያመልኩ ነበር።
34ይህንንም ልማዳቸውን እስከ ዛሬ ድረስ
አልተውትም፤ *እግዚአብሔርን* በአግባቡ አያ
መልኩም፤ እንዲሁም እስራኤል ብሎ ለጠ
ራው ለያዕቆብ ዘሮች የሰጣቸውን ሥርዐ
ቶችና ደንቦች፣ ሕጎችና ትእዛዞችን አይከ
ተሉም። 35*እግዚአብሔር* ከእስራኤላውያን
ጋር ኪዳን ሲገባ እንዲህ ሲል አዞአቸው
ነበር፤ “ሌሎችን አማልክት አታምልኳ
ቸው፤ አትስገዱላቸው፤ አታገልግሏቸው፤
አትሠውላቸውም፤ 36ማምለክ የሚገባችሁ
ግን በታላቅ ኀይልና በተዘረጋች ክንድ
ከግብፅ ምድር ያወጣችሁን *እግዚአብሔ
ርን* ብቻ ነው። ለእርሱ ስገዱ፤ ለእርሱም
መሥዋዕት አቅርቡ። 37የጻፈላችሁን ሥርዐ
ቶችና ደንቦች፣ ሕጎችና ትእዛዞች ምን
ጊዜም ተግታችሁ ጠብቁ። ሌሎች አማል
ክትን አታምልኩ። 38ከእናንተ ጋር የገባሁ
ትን ኪዳን አትርሱ፤ ሌሎች አማልክትም
አታምልኩ። 39ይልቅስ አምላካችሁን *እግዚ
አብሔርን* አምልኩ፤ ከጠላቶቻችሁ ሁሉ
እጅ የሚታደጋችሁ እርሱ ነውና።”
40ነገር ግን በቀደመው ልማዳቸው ጸኑ
እንጂ አልተመለሱም። 41እነዚህ ሕዝቦች
ምንም እንኳ በአንድ ወገን *እግዚአብሔ
ርን* ቢያመልኩት የተቀረጹ ምስሎቻቸው
ንም ያገለግሉ ነበር። ልጆቻቸውና የልጅ
ልጆቻቸውም አባቶቻቸው ያደረጉትን ዛሬም
እንደ ቀጠሉበት ነው።

## *የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ*

18፥2-4 ተጓ ምብ - 2ዜና29፥1- 2፤31፥1
18፥5-7 ተጓ ምብ - 2ዜና31፥20-21
18፥9-12 ተጓ ምብ - 2ነገ17፥3ኛ7

18 የእስራኤል ንጉሥ የኤላ ልጅ
ሆሼዕ በነገሠ በሦስተኛው ዓመት
የይሁዳ ንጉሥ የአካዝ ልጅ ሕዝቅያስ ነገሠ።
2በነገሠም ጊዜ ዕድሜው ሃያ አምስት
ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም
ሃያ ዘጠኝ ዓመት ገዛ። እናቱ የዘካርያስ
ልጅ ስትሆን ስሟ አብያ ይባል ነበር።
3አባቱ ዳዊት እንዳደረገው ሁሉ፣ እርሱም
*በእግዚአብሔር* ፊት መልካም ነገር አደ
ረገ። 4በየኰረብታው ላይ ያሉትን ማምለ
ኪያዎች አስወገደ፤ አዕማደ ጣዖታትን ሰባ
በረ፤ የአሼራን ምስል ዐምዶች ቈራረጠ፤
ሙሴ የሠራውን የናስ እባብ፣ እስራኤ
ላውያን እስከዚያች ጊዜ ድረስ ዕጣን ያጤ
ሱለት ስለነበር ሰባበረው፤ ይህም ነሑሽ

‘2 በዕብራይስጡ *አብያ* ማለት *አብግያ* ማለት ነው።

ታን[ሰ] ይባል ነበር።
5ሕዝቅያስም በእስራኤል አምላክ
*በእግዚአብሔር* *ታመነ*፤ ከእርሱ በፊትም
ሆነ ከእርሱ በኋላ ከይሁዳ ነገሥታት
ሁሉ፣ እንደ እርሱ ያለ አልነበረም።
6*ከእግዚአ ብሔር* ጋር ተጣበቀ፤ እርሱን
ከመከተል ወደ ኋላ አላለም፤ *እግዚአብሔ*
*ር* ለሙሴ የሰጠውንም ትእዛዞች ጠበቀ።
7*እግዚአ ብሔር* ከእርሱ ጋር ስለ ነበር
የሚያደርገው ሁሉ ተከናወነለት።
በአሦር ንጉሥ ላይ ዐመፀ፤ ግብር መገበሩ
ንም ተወ። 8እስከ ጋዛና እስከ ግዛቷ ዳርቻ
በመዝለቅ ፍልስጤማውያንን ከመጠበቂያ
ማማ እስከ ተመሸገችው ከተማ ድረስ
ድል አደረጋ ቸው።
9ሕዝቅያስ በነገሠ በአራተኛው ዓመት፣
የእስራኤልም ንጉሥ የኤላ ልጅ ሆሴዕ
በነገሠ በሰባተኛው ዓመት፣ የአሦር ንጉሥ
ስልምናሶር ወደ ሰማርያ ገሥግሦ ከተ
ማይቱን ከበባት፤ 10በሦስተኛውም ዓመት
መጨረሻ ያዛት። ሰማርያ የተያዘችውም
ሕዝቅያስ በነገሠ በስድስተኛው ዓመት፣
ሆሴዕ በእስራኤል ላይ በነገሠ በዘጠ
ነኛው ዓመት ነበር። 11የአሦር ንጉሥ እስ
ራኤልን ማርኮ ወደ አሦር በማፍለስ በአ
ላሔ፣ በጎዛን ውስጥ በአቦር ወንዝ አጠገ
ብና በሜዶን ከተሞች አሰፈራቸው። 12ይህ
የደረሰባቸውም *የእግዚአብሔር* ባሪያ ሙሴ
ያዘዘውን የአምላካቸውን *የእግዚአብሔርን*
ቃል ሁሉ ከመስማት ይልቅ ኪዳኑን ስላፈ
ረሱ ነበር፤ ትእዛዞቹን አላደመጡም፤ ደግ
ሞም አልፈጸሙም።
13ሕዝቅያስ በነገሠ በዐሥራ አራ
ተኛው
ዓመት፣ የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም የተመሸ
ጉትን የይሁዳን ከተሞች ሁሉ አደጋ ጥሎ
ያዛቸው። 14ስለዚህ የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅ
ያስ፣ "በደለኛው እኔ ነኝ፤ ተመለስልኝ፤
እኔም የምትጠይቀኝን ሁሉ እከፍላለሁ፤"
ሲል በለኪሶ ወደ ሰፈረው ወደ አሦር ንጉሥ
ይህን መልእክት ላከ። የአሦርም ንጉሥ፣
የይሁዳን ንጉሥ ሕዝቅያስን ሦስት መቶ
መክሊት[ሸ] ብርና ሠላሳ መክሊት[ቀ] ወርቅ
እንዲያገባለት ጠየቀው።
15ስለዚህ ሕዝቅያስ *በእግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስና በቤተ መንግሥቱ ግምጃ ቤቶች
የሚገኘውን ብር ሁሉ ሰጠው።
16በዚህ ጊዜም የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅ
ያስ፣ *በእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ መዝ
ጊያዎችና መቃኖች ላይ የለበጠውን ወርቅ
ነቃ ቅሎ ለአሦር ንጉሥ ሰጠው።

18፥5 ቍ19፤ 1ሳሙ7፥3፤2ነገ 19፥10፤መዝ21፥7፤125፥1፤ምሳ3፥26
18፥6 ዘዳ6፥18፤ 10፥20
18፥7 ዘፍ39፥3፤ 2ነገ24፥1፤ዕዝ 4፥19፤ኢዮ 22፥25፤ ኢሳ36፥5
18፥8 2ነገ17፥9
18፥9 ኢሳ1፥1፤ 36፥1
18፥11 ኢሳ 37፥12፤ሕዝ 16፥39፤23፥9
18፥12 1ነገ9፥6፤ 2ነገ17፥15፤21፥8፤ ዳን9፥6፥10
18፥13 ቍ2፤ኢሳ 1፥7፤ሚክ1፥9
18፥14 2ነገ19፥8፤ ኢሳ24፥5፤33፥8
18፥15 1ነገ 15፥18፤ኢሳ39፥2
18፥16 2ዜና29፥3
18፥17 2ነገ 20፥20፤ 2ዜና32፥4፡ 30፤ነህ2፥14፤ኢሳ 20፥1፤22፥9
18፥18 ቍ26፡37፤ 2ነገ19፥2፤ኢሳ 22፥15፤22፥20፤ 6፥36፥3፡11፡22፤ 37፥2
18፥19 ቍ5፤ኢዮ 4፥6
18፥21 2ነገ24፥7፤ ኢሳ20፥5፡6፤ 30፥5፡7፤31፥1፤ ኤር25፥19፤37፥7፤ 46፥2፤ሕዝ29፥6
18፥24 ኢሳ10፥8
18፥25 2ነገ19፥6፡ 22፤24፥3፤2ዜና 35፥21
18፥26 ዕዝ4፥7

## ሰናክሬም ኢየሩሳሌምን አስፈራራ

18፥13፤17-37 ተጓ ምብ - ኢሳ36፥1-22
18፥17- 35 ተጓ ምብ - 2ዜና32፥9-19

17የአሦርም ንጉሥ ከለኪሶ የጦሩን ጠቅ
ላይ አዛዥ፣ ዋና አዛዡንና የጦር መሪውን
ከታላቅ ሰራዊት ጋር የይሁዳ ንጉሥ ወዳለ
በት ወደ ኢየሩሳሌም ላከ፤ እነርሱም ወደ
ኢየሩሳሌም መጥተው፣ ወደ ልብስ አጣቢው
ዕርሻ በሚወስደው መንገድ ላይ የሚገኘው
የላይኛው ኵሬ ውሃ በመስኖ የሚወርድበ
ትን ስፍራ ያዙ። 18ወደ ንጉሡም
ላኩበት፤ ከዚያም የቤተ መንግሥቱ አዛዥ
የሆነው የኬልቅያስ ልጅ ኤልያቄም፣
ጸሓፊው ሳም ናስ እንዲሁም ታሪክ ጸሐ
ፊው የአሳፍ ልጅ ዮአስ ወደ እነርሱ
ሄደ። 19የጦር መሪውም እንዲህ አላቸው፤
"ሕዝቅያስን እንዲህ በሉት፤
"'ታላቁ የአሦር ንጉሥ የሚለው ይህ
ነው፤ "ለመሆኑ እንዲህ የልብ ልብ እንድ
ታገኝ ያደረገህ ምንድነው? 20የጦር ስል
ትና ኀይል አለኝ ትላለህ፤ ነገር ግን ወሬ
ብቻ ነው። በእኔ ላይ እንዲህ ያመፅኸውስ
በማን ተመክተህ ነው? 21እነሆ፤ እንዲህ
የምትመካባት ግብጽ፤ የሚደገፍባትን ሰው
እጅ ወግታ የምታቈስል የተቀጠቀጠች
ሸንበቆ ናት። የግብጽ ንጉሥ ፈርዖንም
ለሚመኩበት ሁሉ እንደዚሁ ነው። 22ደግ
ሞም፣ "የምንመካው በአምላካችን *በእግዚአ*
*ብሔር* ነው" የምትለኝ ከሆነም፣ ሕዝቅያስ
ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን፣ "ማምለክ ያለባ
ችሁ ኢየሩሳሌም ባለው በዚህ መሠዊያ
ፊት ነው" ብሎ የኰረብታ ላይ መመለኪ
ያዎቹንና መሠዊያዎቹን ያስፈረሰ በት
እርሱ አይደለምን? 23"'ከሆነልህ ከጌታዬ
ከአሦር ንጉሥ ጋር ውርርድ ግጠም፤ የሚ
ጋልቢቸው ሰዎች ማግኘት የምትችል
ከሆነ፣ ሁለት ሺህ ፈረሶች እሰጥሃለሁ።
24የምትመካው በግብጽ ሠረገሎችና[በ] ፈረ
ሶች ሆኖ ሳለ ከጌታዬ የበታች የጦር ሹማ
ምንት እንኳ አንዱን እንዴት መመለስ
ትችላለህ? 25ከዚህም በቀር አደጋ ጥዬ ይህ
ችን ስፍራ ለማጥፋት የመጣሁት፣ ያለ
*እግዚአብሔር* ፈቃድ ይመስልሃል? በዚች
አገር ላይ ዘምቼ እንዳጠፋት የነገረኝ ራሱ
*እግዚአብሔር* ነው።'"
26ከዚያም የኬልቅያስ ልጅ ኤልያቄም
ሳምናስና ዮአስ የጦር መሪውን፣ "እኛ አገ
ልጋዮችህ ስለምንሰማ፣ እባክህን በሶርያ
ቋንቋ ተናገር፤ በቅጥሩ ላይ ያሉት ሰዎች

[ሰ]4 *ነሑሽታን* የሚለው ቃል ድምፅ *ነሐስ*፣ እባብ እንዲሁም ርኩስ ነገር ከሚለው የቃል ድምፅ ጋር አንድ ዐይነት ነው።
[ሸ]14 10ሜትሪክ ቶን ያህል ነው። [ቀ]14 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው። [በ]24 ወይም፣ *ሠረገለኞች*

በሚሰሙት በዕብራይስጥ አትናገረን” አሉት።
27የጦር አዛዡም፣ “ለመሆኑ ጌታዬ ይህን
እንድናገር የላከኝ፣ ለጌታችሁና ለእናንተ
ብቻ ነውን? እነርሱም እንደ እናንተው
ገና ኵሳቸውን ይበሉ ዘንድ፣ ሽንታቸው
ንም ይጠጡ ዘንድ በቅጥሩ ላይ ለተቀ
መጡት ጭምር አይደለምን?”
28ከዚያም የጦር አዛዡ ቆሞ ድምፁን
ከፍ በማድረግ በዕብራውያን ቋንቋ እንዲህ
ሲል ተናገረ፤ “እንግዲህ የታላቁን የአሦ
ርን ንጉሥ ቃል ስሙ! 29ንጉሡ የሚለውም
ይህ ነው፤ ‘ከእጄ ሊያድናችሁ አይችልምና
ሕዝቅያስ እንዳያታልላችሁ፤ 30ደግሞም
ሕዝቅያስ፣ “*እግዚአብሔር* ያለ ጥርጥር
ያድነናል፤ ይህችም ከተማ ለአሦር ንጉሥ
አልፋ አትሰጥም’ በማለት *በእግዚአብሔር*
እንድት ታመኑ የሚነግራችሁን አትቀ
በሉ።” ’
31“ሕዝቅያስንም አትስሙት፤ የአሦር
ንጉሥ የሚለው ይህ ነው፤ ‘ከእኔ ጋር
ሰላም መሥርቱ፤ እጃችሁን ስጡ፤ ከዚያም
ከእናንተ እያንዳንዱ ከገዛ ወይኑና ከገዛ
በለሱ ይበላል፤ ከገዛ ጕድጓዱም ውሃ ይጠ
ጣል፤ 32ይህም የሚሆነው የእናንተኑ ወደ
ምትመስለው ምድር እህልና የወይን ጠጅ፣
ዳቦና የወይን ተክል፣ የወይራ ዛፍና ማር
ወዳለበት እስካገባችሁ ድረስ ነው፤ እናን
ተም ሞትን ሳይሆን ሕይወትን ምረጡ።’
“ሕዝቅያስ፣ ‘*እግዚአብሔር* ይታደገናል’
በማለት ስለሚያሳስታችሁ አትስሙት።
33ለመሆኑ ከአሕዛብ አማልክት ምድሩን
ከአሦር ንጉሥ እጅ የታደገ ማን አለ?
34የሐማትና የአርፋድ አማልክት እስቲ የት
አሉ? የሴፈርዋይም፣ የሄናና የዒዋም አማ
ልክት ታዲያ የት ደረሱ? ሰማርያን ከእጄ
አድነዋታልን? 35ከእነዚህ አገሮች አማል
ክት ሁሉ አገሩን ከእኔ ለማዳን የቻለ ማን
አለ? ታዲያ *እግዚአብሔር* ኢየሩሳሌምን
ከእጄ ሊታደጋት እንዴት ይችላል?”
36ነገር ግን ሕዝቡ ዝም አለ፤ ምንም መልስ
አልሰጠም፤ ንጉሡ፣ “መልስ እንዳትሰጡ”
ሲል አዝዞ ነበርና።
37ከዚያም የቤተ መንግሥቱ አዛዥ የኬ
ልቅያስ ልጅ፤ ኤልያቄም፣ ጸሓፊው ሳም
ናስ እንዲሁም ታሪክ ጸሓፊው የአሳፍ
ልጅ ዮአስ ልብሳቸውን ቀደዱ፤ ወደ ሕዝ
ቅያስም መጥተው የጦር አዛዡ ያላቸውን
ነገሩት።

18፥29 2ነገ19፥10
18፥31 ዘኍ13፥23፤ 1ነገ4፥25፤ኤር14፥3፤ ስቆ4፥4
18፥32 ዘዳ30፥19
18፥33 2ነገ19፥12
18፥34 2ነገ 17፥24፤ኢሳ 10፥9፤ኤር49፥23
18፥35 መዝ2፥12
18፥37 ቍ18፤ 2ነገ6፥30፤ኢሳ33፥7፤ 36፥3፥22

19፥1 ዘፍ37፥34፤ ዘኍ14፥6
19፥2 ዘፍ37፥34፤ 2ነገ18፥18፤ኢሳ 1፥1፤ኤር19፥1
19፥3 ሆሴ13፥13
19፥4 ዘፍ45፥7፤ 1ሳሙ17፥26፤ 2ሳሙ16፥12፤ኤር 37፥3
19፥6 ዘዳ3፥2፤ኢሱ 1፥9፤2ነገ18፥25
19፥7 ቍ37፤ ዘፀ14፥24፤2ዜና32፥21፤ኢሳ10፥12፤ ኤር51፥46
19፥8 ዘኍ33፥20፤ 2ነገ8፥22፤18፥14
19፥10 2ነገ18፥5፡29
19፥12 ዘፍ11፥31፤ 2ነገ17፥6፤18፥33፤ 2ዜና32፥17
19፥13 ኢሳ10፥9-11፤ኤር49፥23

## ኢየሩሳሌም ከጠላት እጅ እንደምትድን አስቀድሞ መነገሩ

19፥1-13 ተጓ ምብ - ኢሳ37፥1-13

19 ንጉሥ ሕዝቅያስ ይህን ሲሰማ
ልብሱን ቀደደ፤ ማቅ ለብሶም
ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ገባ። 2ከዚ
ያም የቤተ መንግሥቱን አዛዥ ኤልያቄ
ምን፣ ጸሓፊውን ሳምናስንና ዋና ዋናዎቹን
ካህናት ማቅ ለብሰው ወደ አሞጽ ልጅ
ወደ ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲሄዱ ሁሉንም
ላካቸው። 3እነርሱም እንዲህ አሉት፤ “ሕዝ
ቅያስ የሚለው ይህ ነው፤ ‘እንግዲህ
ይህች ዕለት የመከራ፣ የዘለፋና የውርደት
ቀን ናት፤ ይህችም ቀን ልጆች ሊወለዱ
ምጥ እንዳፋፋመበት፣ ነገር ግን ለመገላ
ገል ዐቅም እንደ ታጣበት ሰዓት ናት።
4ሕያው እግዚአብሔርን ያንቋሽሽ ዘንድ በጌ
ታው በአሦር ንጉሥ የተላከውን የጦር
አዛዡን ቃል ሁሉ *እግዚአብሔር* አምላክህ
ሰምቶ ይሆናልና፣ ስለሰማውም ቃል *እግ
ዚአብሔር* እንዲገሥጸው በሕይወት ስለተ
ረፉት ወገኖቻችን እባክህ ጸልይ።”
5የንጉሥ ሕዝቅያስ ሹማምንት ወደ ኢሳ
ይያስ በመጡ ጊዜ፣ 6ኢሳይያስ እንዲህ
አላቸው፤ “ለጌታችሁ እንዲህ ብላችሁ ንገ
ሩት፤ ‘እንግዲህ *እግዚአብሔር* የሚለው
ይህ ነው፤ “የአሦር ንጉሥ አገልጋዮች በእኔ
ላይ የወረወሯቸውን የስድብ ቃላት በመስ
ማትህ አትፍራ። 7እነሆ፣ አንድ ዐይነት
መንፈስ አሳድርበታለሁ፤ የሆነ ወሬም ሲሰማ
ወደ አገሩ ይመለሳል፤ እዚያም በሰይፍ
እንዲወድቅ አደርገዋለሁ።’ ”
8የጦር አዛዡም የአሦር ንጉሥ ለኪሶን
ትቶ መሄዱን ሲሰማ ተመለሰ፤ ንጉሡንም
ልብናን ሲወጋ አገኘው።
9በዚህም ጊዜ የግብጽ ንጉሥ ኢትዮጵያ
ዊው ቲርሐቅ፣ ሊወጋው በመገሥገሥ ላይ
መሆኑን ሰናክሬም ሰማ፤ ስለዚህ ወደ ሕዝ
ቅያስ እንደ ገና እንዲህ ሲል መልእክተ
ኞች ላከ፤ 10“ሂዱና ለይሁዳ ንጉሥ ለሕዝ
ቅያስ እንዲህ በሉት፤ ‘የምትመካበት አም
ላክ፣ “ኢየሩሳሌም በአሦር ንጉሥ እጅ
አትወድቅም” በማለት እንዳያታልልህ።
11መቼም የአሦር ነገሥታት በአገሮች ሁሉ
ላይ ምን እንዳደረጉ ሰምተሃል፤ ፈጽሞ
አጥፍተዋቸዋል፤ ታዲያ አንተስ ከዚህ የም
ታመልጥ ይመስልሃልን? 12የቀድሞ አባ
ቶቼ ያጠፏቸውን ሕዝቦች ማለትም ጎዛ
ንን፣ ካራንን፣ ራፊስን እንዲሁም በተላሳር
የነበሩትን የዔድንን ሰዎች አማልክታቸው
አድነዋቸዋልን? 13ለመሆኑ የሐማትና የአ
ርፋድ ነገሥታት የት አሉ? የሴፈርዋይም

ከተማ ንጉሥስ የት አለ? ደግሞስ የሄና
ወይም የዒዋ ነገሥታት የት አሉ?

## የሕዝቅያስ ጸሎት

19፥14-19 ተጓ ምብ - ኢሳ37፥14-20

14ሕዝቅያስም ደብዳቤውን ከመልእክተ
ኞቹ ተቀብሎ አነበበው፤ ከዚያም ወደ እግ
ዚአብሔር ቤተ መቅደስ ወጥቶ ደብዳቤ
ውን *በእግዚአብሔር* ፊት ዘረጋው፡፡ 15ከዚ
ያም ሕዝቅያስ እንዲህ ሲል ወደ *እግዚ
አብሔር* ጸለየ፤ "በኪሩቤል ላይ በዙፋንህ
የተቀመጥህ የእስራኤል አምላክ *እግዚአ
ብሔር* ሆይ፤ በምድር ነገሥታት ሁሉ ላይ
አምላክ አንተ ብቻ ነህ፤ ሰማይንና ምድ
ርን የፈጠርህም አንተ ነህ፡፡ 16*እግዚአብሔር*
ሆይ፤ አሁንም ጆሮህን አዘንብልና ስማ፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ዐይንህንም ክፈትና
እይ፤ ሰናክሬም ሕያው *እግዚአብሔርን*
ይሰድብ ዘንድ የላከውንም ቃል አድምጥ፡፡
17"*እግዚአብሔር* ሆይ፤ የአሦር ነገሥ
ታት እነዚህን አሕዛብንና ምድራቸውን በእ
ርግጥ አጥፍተዋል፡፡ 18አማልክቶቻቸውን
በእሳት ውስጥ ጥለው አቃጥለዋቸዋል፤ በሰው
እጅ የተሠሩ ዕንጨትና ደንጊያ ብቻ
እንጂ አማልክት አልነበሩምና፡፡ 19አሁንም
*እግዚአብሔር* አምላካችን ሆይ፤ የምድር
መንግሥታት ሁሉ *እግዚአብሔር* አንተ
ብቻ አምላክ መሆንህን እንዲያውቁ፣ ከእጁ
አድነን፡፡"

## ኢሳይያስ ስለ ሰናክሬም መውደቅ ትንቢት ተናገረ

19፥20-37 ተጓ ምብ - ኢሳ37፥21-38
19፥35-37 ተጓ ምብ - 2ዜና32፥20-21

20ከዚያም የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ ወደ
ሕዝቅያስ እንዲህ ሲል መልእክት ላከ፤
"የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር* የሚለው
ይህ ነው፤ 'በአሦር ንጉሥ በሰናክሬም ላይ
ወደ እኔ ያቀረብኸውን ልመና ሰምቻ
ለሁ፡፡ 21እንግዲህ *እግዚአብሔር* በእርሱ
ላይ የተናገረው ቃል ይህ ነው፤

" 'ድንግሊቱ የጽዮን ልጅ፣
ትንቅሃለች፤ ታቃልልሃለችም፤
የኢየሩሳሌም ልጅ፣
አንተ በላይዋ ስትበር ራሷን
ትነቀንቅብሃለች፡፡
22ለመሆኑ የሰደብኸውና ያቃለልኸው
ማንን ነው?
ድምፅህንስ ከፍ ያደረግኸው?
ዐይንህንስ በኵራት ያነሣኸው በማን ላይ
ነው?
በእስራኤል ቅዱስ ላይ ነው እንዴ?
23በመልእክተኞችህ አማካይነት፣
በአምላክ ላይ የስድብ መዓት
አውርደሃል፤
እንዲህም ብለሃል፤
"በብዙ ሠረገሎቼ፣
የተራሮቹን ከፍታ፣
የሊባኖስንንም የመጨረሻ ጫፍ
ወጥቻለሁ፤
ረጃጅም ዝግባዎቹን፣
ምርጥ የሆኑ ጥዶቹንም ቈርጫለሁ፤
ወደ ሩቅ ዳርቻዎቹ፣
ወደ ውብ ደኖቹም ደርሻለሁ፡፡"
24"በሌሎች አገሮችም የውሃ ጕድጓዶች
ቈፍሬአለሁ፤
በዚያም ውሃ ጠጥቻለሁ፤
በእግሬ ጫማዎችም፣
የግብፅን ምንጮች ሁሉ ረግጬ
አድርቄአለሁ፡፡"

25" 'ከብዙ ጊዜ በፊት፣
ይህን እኔ እንዳደረግሁት አልሰማህም
ነበርን?
ዕቅዱን ገና ድሮ አውጥቼ፣
አሁን ግን እንዲፈጸም አደረግሁት፤
ይህም የተመሸጉትን ከተሞች፣
አንተ የድንጋይ ክምር ማድረግህ ነው፡፡
26የሚኖሩባቸውም ሰዎች ኀይላቸው
ተሟጦ አልቆአል፤
ደንግጠውም የኀፍረት ማቅ ለብሰዋል፤
ሜዳ ላይ እንደ በቀለ ተክል፣
ገና እንዳልጠነከረ የቡቃያ ሥር፣
በቤት ጣራ ላይ በቅሎ፣
ገና ሳያድግ እንደ ጠወለገ ሣርም
ሆነዋል፡፡

27" 'የት እንደምትቀመጥ፣
መቼ መጥተህ መቼ እንደምትሄድ፣
በእኔም ላይ የተቈጣኸውን ቍጣ
ዐውቃለሁ፡፡
28በእኔ ላይ በመቈጣትህ፣
ንቀትህም ወደ ጆሮዬ ስለ ደረሰ፣
ስናጋዬን በአፍንጫህ አደርጋለሁ፤
ልጓሜን በአፍህ አገባለሁ፤
በመጣህበትም መንገድ
እንድትመለስ አደርጋለሁ፡፡'

29"ሕዝቅያስ ሆይ፤ ምልክቱ ይህ ነው፤

"በዚህ ዓመት በገዛ እጁ የበቀለውን፣
በሚመጣው ዓመት ደግሞ የገበውን እህል
ትበላላችሁ፤
በሦስተኛው ዓመት ግን ትዘራላችሁ፤
ታጭዳላችሁ፤
ወይንም ትተክላላችሁ፤ ፍሬውንም
ትበላላችሁ፡፡
30አሁንም ከዳዊት ቤት የተረፉት፣

19፥14 2ነገ5፥7
19፥15 ዘፍ1፥1፤ 3፥24፤ዘፀ25፥22፤ ኢሱ2፥11
19፥16 ዘፀ3፥16፤ 1ነገ8፥29፤መዝ 31፥2፤71፥2፤88፥2፤ 102፥2
19፥18 ዘዳ4፥28፤ መዝ115፥4፤ኢሳ 44፥911፤ኤር10፥3-10፤ ሐሥ17፥29
19፥19 ኢሱ 4፥24፤1ሳሙ12፥10፤17፥46፤1ነገ8፥43፤ 1ዜና16፥8፤ ኢዮ6፥23፤ መዝ3፥7፤71፥4
19፥20 1ነገ9፥3
19፥21 ኢዩ16፥4፤ መዝ44፥14፤53፥5፤64፥8፤109፡፡25፤ምሳ1፥26፤3፥34፤ኢሳ10፥5፤ 33፥1፤ 47፥1፤ ኤር14፥17፤18፥13፥16፤31፥4፤46፥11፤ሰቆ2፥13፤አሞ5፥2
19፥22 ዘሌ19፥2፤ 1ሳሙ2፥2፤2ነገ18፥25፤ኢዮ 6፥10፤ መዝ16፥10፤ 22፥3፤71፥22፤78፥41፤ 89፥18፤ኢሳ1፥4፤ 6፥3፤57፥15፤ሆሴ 11፥9
19፥23 መዝ20፥7፤ ኢሳ10፥18፥34፤ 14፥8፤33፥9፤ኤር21፥14፤50፥37፤ሕዝ 20፥47፤31፥3
19፥25ኢሳ 22፥11፤ 40፥21፥28፤ሚክ 1፥6
19፥26 ኢዩ8፥12፤ መዝ6፥10፤37፥2፤ 71፥24፤83፥17፤ 129፥6፤ኢሳ4፥2፤ 11፥1፤13፥7፤ 41፥23፤53፥2፤ኤር 8፥9፤23፥5፤ሕዝ 7፥17፤ሰፎ3፥16፤
19፥27 መዝ 139፥14፤
19፥28 ቆላ33፤ 2ዜና33፥11፤ኢሳ 30፥28፤ሕዝ19፥9፤ 29፥4፤38፥4፤ አሞ4፥2፤
19፥29 ዘፀ7፥9፤ ዘሌ25፥5፤ዘዳ13፥2፤መ ዝ107፥37፤ኢሳ 65፥21፤ አሞ9፥14፤ ሉቃ2፥12
19፥30 ዘፍ45፥7፤ ኢሳ5፥24፤11፥1፤ 27፥6፤ሕዝ17፥22፤ አሞ2፥9

ሥራቸውን ወደ ታች ይሰዳሉ፤ ወደ
ላይም ፍሬ ያፈራሉ።
[31]ከኢየሩሳሌም በሕይወት የተረፉት፣
ከጽዮን ተራራም ከሞት ያመለጡት
ይወጣሉና።

የእግዚአብሔር ቅናት ይህን ታደርጋለች።

[32]“እንግዲህ እግዚአብሔር ስለ አሦር
ንጉሥ የሚለው ይህ ነው፤
“ወደዚች ከተማ ፈጽሞ አይገባም፤
አንዲትም ፍላጻ አይወረውርባትም፤
ጋሻ አንግቦ ወደ እርሷ አይቀርብም፤
በዐፈርም ቍልል አይከባትም።
[33]በመጣበት መንገድ ተመልሶ ይሄዳል፤
ተመልሶ ይሄዳታል እንጂ ወደዚች
ከተማ ፈጽሞ አይገባም፤
ይላል እግዚአብሔር ።
[34]ስለ ራሴና ስለ ባሪያዬም ስለ ዳዊት
ስል፣
ይህችን ከተማ አድናት ዘንድ
እጋርዳታለሁ።

[35]በዚያችም ሌሊት የእግዚአብሔር መል
አክ ወጥቶ ከአሦራውያን ሰፈር መቶ ሰማ
ንያ አምስት ሺህ ሰው ገደለ። በማግስ
ቱም ሰዎቹ ሲነቁ ቦታው ሬሳ በሬሳ ሆኖ
ተገኘ። [36]የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም ከዚያ
ተነሥቶ ሄደ፤ ወደ ነነዌም ተመልሶ በዚያ
ተቀመጠ።
[37]አንድ ቀንም ናሳራክ በተባለው አም
ላኩ ቤተ ጣዖት ገብቶ በመስገድ ላይ ሳለ፣
አድራሜሌክና ሳራሳር የተባሉ ልጆቹ በሰ
ይፍ ገደሉት፤ ከዚያም አምልጠው ወደ አራ
ራት ሸሹ። ልጁ አስራዶንም በእግሩ ተተ
ክቶ ነገሠ።

### የሕዝቅያስ መታመም

20፥1-11 ተጓ ምብ - 2ዜና32፥24-26፤ኢሳ38፥1-8

20 በዚያ ጊዜ ሕዝቅያስ በጠና ታሞ
ሊሞት ተቃርቦ ነበር። የአሞጽ
ልጅ ነቢዩ ኢሳይያስም ወደ እርሱ ሄዶ፣
“እግዚአብሔር፣ ‘ትሞታለህ ከእንግዲህ
በሕይወት አትኖርምና ቤትህን አስተካ
ክል’ ብሎሃል” አለው።
[2]ሕዝቅያስም ፊቱን ወደ ግድግዳው
መልሶ እንዲህ ሲል ወደ እግዚአብሔር
ጸለየ፤ [3]“እግዚአብሔር ሆይ፤ በታማኝነትና
በፍጹም ልብ በፊትህ እንደ ሄድሁ፣ አን
ተን ደስ የሚያሰኝህንም እንዳደረግሁ አስብ፤”
ሕዝቅያስም ምርር ብሎ አለቀሰ።
[4]ኢሳይያስ የመካከለኛውን አደባባይ አልፎ
ከመሄዱ በፊት የእግዚአብሔር ቃል እን
ዲህ ሲል ወደ እርሱ መጣ፤ [5]“ተመለስና
የሕዝቤን አለቃ ሕዝቅያስን እንዲህ በለው፤

19፥31 ዘፍ45፥7፤ ኢሳ9፥7፤66፥19፤ ሶፎ2፥9፤ዘካ14፥16
19፥33 ቍ28
19፥34 2ሳሙ 7፥15፤2ነገ20፥6
19፥35 ዘፍ19፥13፤ ዘፀ12፥23፤ኢዩ24፥ 24፤ኢሳ17፥14፤ 41፥12፤ናሆ3፥3
19፥36 ዘፍ10፥11፤ 2ነገ12፥18
19፥37 ቍ7፤ዘፍ 8፥4፤2ነገ17፥24፡31
20፥3 ዘፍ5፥22፤ 8፥1፤1ነገ2፥4፤2ዜና 31፥20፤ነህ1፥8፤5፥19፤ 13፥14
20፥5 2ነገ9፥3፤ መዝ6፥6፡8፤39፥12፤56 ፥8
20፥6 2ነገ19፥34፤ 1ዜና17፥19
20፥7 ዘፀ9፥9
20፥9 ዘዳ13፥2፤ ኤር44፥29
20፥10 2ነገ3፥18
20፥11 ኢሱ 10፥13፤2ዜና32፥31

‘የአባትህ የዳዊት አምላክ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤ “ጸሎትህን ሰምቻለሁ፤ እን
ባህንም አይቻለሁ፤ እነሆ፣ እፈውስሃለሁ።
ከዛሬ ሦስት ቀን በኋላ ወደ እግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ ትወጣለህ፤ [6]በዕድሜህ ላይ
ዐሥራ አምስት ዓመት እጨምርልሃለሁ፤
አንተንና ይህችንም ከተማ ከአሦር ንጉሥ
እጅ እታደጋለሁ፤ ስለ እኔ ስለ ራሴና ስለ
ባሪያዬ ስለ ዳዊት ስል ይህችን ከተማ
እከላከልላታለሁ።’ ”
[7]ከዚያም ኢሳይያስ፣ “ትኵስ የበለስ ጥፍ
ጥፍ አዘጋጁ” አላቸው፤ እነርሱም አዘጋ
ጅተው ዕባጩ ላይ አደረጉለት፤ ተፈወ
ሰም።
[8]ሕዝቅያስም፣ “እግዚአብሔር እኔን ስለ
መፈወሱ፣ ከሦስት ቀን በኋላም ወደ እግ
ዚአብሔር ቤተ መቅደስ ስለ መውጣቴ
ምልክቱ ምንድን ነው?” ሲል ኢሳይያ
ስን ጠየቀው።
[9]ኢሳይያስም፣ “እግዚአብሔር የሰጠውን
ተስፋ እንደሚፈጽም ምልክቱ ይህ ነው፤
ጥላው ዐሥር ደረጃ ወደ ፊት ይቅደምን?
ወይስ ዐሥር ደረጃ ወደ ኋላ ይመለስ?”
ሲል ጠየቀው።
[10]ሕዝቅያስም መልሶ፣ “ጥላው ዐሥር
ደረጃ ወደ ፊት መሄዱ ቀላል ነገር ነው፤
ይልቁን ዐሥር ደረጃ ወደ ኋላ ይመለስ”
አለ።
[11]ከዚያም ነቢዩ ኢሳይያስ ወደ እግዚ
አብሔር ጮኸ፤ እግዚአብሔርም አካዝ በሠ
ራው ደረጃ ላይ የወረደውን ጥላ ዐሥር
ደረጃ ወደ ኋላው እንዲመለስ አደረገ።

### ከባቢሎን የመጡ መልእክተኞች

20፥12-19 ተጓ ምብ - ኢሳ39፥1-8
20፥20-21 ተጓ ምብ - 2ዜና32፥32-33

[12]በዚያን ጊዜ የባቢሎን ንጉሥ የባልዳን
ልጅ መሮዳክ ባልዳን የሕዝቅያስን መታ
መም ሰምቶ ስለነበር፣ ደብዳቤና ገጸ በረ
ከት ለሕዝቅያስ ላከለት። [13]ሕዝቅያስም
መልክተኞቹን ተቀብሎ በዕቃ ቤቱ ያለ
ውን ሁሉ ብሩን፣ ወርቁን ቅመማ ቅመ
ሙንና ከፍ ያለ ዋጋ ያለውን ዘይት የጦር
መሣሪያ ግምጃ ቤቱንና በቀረውም ግምጃ
ቤት ያለውን በሙሉ አሳያቸው። በቤተ
መንግሥቱም ሆነ በመላው ግዛቱ ሕዝቅ
ያስ ሳያሳያቸው የቀረ ምንም ነገር አልነበ
ረም።
[14]ከዚያም ነቢዩ ኢሳይያስ ወደ ሕዝቅ
ያስ ሄዶ፣ “እነዚያ ሰዎች ምን አሉህ?
የመጡትስ ከወዴት ነው?” ሲል ጠየቀው።
ሕዝቅያስም መልሶ፣ “የመጡት ከሩቅ
አገር ከባቢሎን ነው” አለው።

[15]ነቢዩም፣ “በቤተ *መንግሥት*ህ ምን ምን
አዩ?” ሲል ጠየቀው፡፡
ሕዝቅያስም፣ “በቤተ *መንግሥ*ቴ ያለ
ውን ሁሉ አይተዋል፤ በግምጃ ቤቶቼ ሳላ
ሳያቸው የቀረ ምንም ነገር የለም”አለ፡፡
[16]ከዚያም ኢሳይያስ ሕዝቅያስን እንዲህ
አለው፤ “*የእግዚአብሔርን ቃ*ል ስማ፤ [17]በቤተ
*መንግሥ*ትህ ያለው ሁሉ አባቶችህም እስከ
ዛሬ ድረስ ያከማቹት በሙሉ ወደ ባቢ
ሎን የሚወሰድበት ጊዜ በእርግጥ ይመ
ጣል፤ አንዳች የሚቀር ነገር የለም ይላል
*እግዚአብሔር*፡፡ [18]*የሥጋ*ህ ቁራጭ የዐጥን
ትህ ፍላጭ ከሚሆኑት፣ ከምትወልዳቸው
ልጆችህ አንዳንዶቹ በምርኮ ይወሰዳሉ፤
በባቢሎንም ቤተ *መንግሥት* ጃንደረቦች
ይሆናሉ፡፡” [19]ሕዝቅያስም፣ “የተናገርኸው
*የእግዚአብሔር ቃ*ል መልካም ነው”ሲል
መለሰ፤ “እኔ እስካለሁ ድረስ ሰላምና ጸጥታ
ከተገኘ የሆነው ይሁን” ብሎ አሰቦአልና፡፡
[20] በሕዝቅያስ *ዘመነ መንግሥት* የተከና
ወነው ሌላው *ሥራ*፣ የፈጸመውም ሁሉ
ኵሬውንና ውሃውን ወደ ከተማዪቱ ያመ
ጣበትን የመሬት ለመሬት ቦይ እንዴት
አድርጎ እንደ ሠራው በይሁዳ ነገሥታት
ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን? [21]ሕዝ
ቅያስም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ ልጁ
ምናሴም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ፡፡

## የይሁዳ ንጉሥ ምናሴ

21፥1-10 ተጓ ምብ - 2ዜና33፥1-10
21፥17-18 ተጓ ምብ - 2ዜና33፥18-20

21 ምናሴ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ዐሥራ
ሁለት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም
ተቀምጦም አምሳ አምስት ዓመት ገዛ፤
እናቱም ሐፍሴባ ትባል ነበር፡፡ [2]ምናሴ
*እግዚአብሔር* ከእስራኤላውያን ፊት አሳዶ
ያወጣቸውን የአሕዛብን አስጸያፊ ልማድ
በመከተል *በእግዚአብሔር ፊት* ክፉ ድር
ጊት *ፈጸመ*፡፡ [3]አባቱ ሕዝቅያስ
ያፈረሰውን የየኰረብታውን ማምለኪያ
ስፍራ መልሶ *ሠራ*፤ የእስራኤል ንጉሥ
አክዓብ እንዳደ ረገው ሁሉ፣ እርሱም
ለበኣል *መሠዊያዎ* ችን አቆመ፤ የአሼራ
ንም ምስል ዐምድ *ሠራ*፡፡ እንዲሁም
ለሰማይ ከዋክብት ሰራዊት ሁሉ ሰገደ፤
አመለካቸውም፡፡ [4]*እግዚአ ብሔር*፣ “ስሜን
በኢየሩሳሌም አኖራለሁ” ባለበት *በእግዚ
አብሔር* ቤተ መቅደስ *መሠ ዊያዎ*ችን *ሠ
ራ*፡፡ [5]በሁለቱም *የእግዚአ ብሔር* ቤተ
መቅደስ አደባባዮች ለሰማይ ከዋክብት ሰ
ራዊት ሁሉ *መሠዊያ ሠራ*፡፡ [6]የገዛ ልጁን
የሚቃጠል *መሥዋዕት* አድ ርጎ አቀረበ[†]፤
*መተተኛና* ጠንቋይ *ሆነ*፤ ሙታን
*አነጋጋሪዎችንና መናፍስት* ጠሪ ዎችን

20፥17 2ነገ
24፥13፤2ዜና36፥10፤
ኤር20፥5፤27፥22፤
52፥17-23
20፥18 2ነገ
24፥15፤ዳን1፥3፤
ሚክ4፥10
20፥20 2ሳሙ5፥8፤
2ነገ18፥17
21፥1 ኢሳ62፥4
21፥2 ቍ16፤ዘዳ
4፥25፤9፥4፤18፥9፤
1ነገ14፥24፤2ነገ
16፥3፤ኤር15፥4
21፥3 ዘፍ2፥1፤ዘዳ
16፥21፤17፥3፤
መሳ6፥28፤1ነገ
3፥3፤2ነገ18፥4፤
ኤር19፥13
21፥4 ዘፀ20፥24፤
2ሳሙ7፥13፤
ኢሳ66፥4፤ኤር4፥1፤
7፥30፤23፥11፤
32፥34፤ሕዝ 23፥39
21፥5 1ነገ7፥12፤
2ነገ23፥12
21፥6 ዘሌ18፥21፤
19፥31፤ዘዳ18፥10፡14፤
2ነገ3፥27፤
23፥26
21፥7 ዘፀ20፥24፤
ዘሌ15፥31፤ዘዳ
16፥21፤2ሳሙ
7፥13፤2ነገ23፥4
21፥8 2ሳሙ7፥10፤
2ነገ18፥12
21፥9 ዘዳ9፥4፤
1ነገ14፥9፤ሕዝ5፥7
21፥11 ዘፍ15፥16፤
1ነገ14፥9፤ሕዝ 18፥12
21፥12 1ሳሙ
3፥11፤2ነገ23፥26፤
24፥3፤ኤር15፥4፤ሕዝ
7፥5
21፥13 2ነገ
23፥27፤ኢሳ28፥17፤
34፥11፤ሰቆ2፥8፤
አሞ7፥79
21፥14 2ነገ19፥4፤
ዕዝ9፥8፤ነህ1፥2፤መዝ
78፥60፤ኢሳ1፥9፤
10፥21፤ኤር6፥9፤
12፥7፤21፥22፤
23፥33፤40፥15፤42፥2፤
44፥7፡28፤50፥20፤
ሚክ2፥12-21
21፥15 ዘፀ32፥22፤
ኤር25፥7
21፥16 ቍ2፡11፤
2ነገ24፥4፤ኢዮ
22፥14፤መዝ10፥11፤9
4፥7፤106፥38፤ኢሳ
29፥15፤47፥10፤
59፥3፡7፤ኤር2፥34፤
7፥6፤19፥4፤22፥17፤
ሰቆ4፥13፤ሕዝ7፥23፤
8፥12፤9፥9፤23፥34፤
ሆሴ4፥2፤ሰፎ1፥12፤
21፥18 ቍ26፤
አስ1፥5፤7፥7
21፥20 1ነገ15፥26

ምክር ጠየቀ፤ *እግዚአብሔርን* ለቍጣ
*የሚያነሣሣውን* ክፉ ድርጊት በፊቱ *ፈጸመ*፡፡
[7]*የሠራውን* የአሼራን የተቀረጸ ምስል
ዐምድ ወስዶ በቤተ *መቅደሱ* ውስጥ አስ
*ቀመጠ*፤ ይህም *እግዚአብሔር* ለዳዊትና
ለልጁ ለሰሎሞን፣ “በዚህ ቤተ *መቅደስ*ና
ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ በ*መረጥ*ኋት በኢ
የሩሳሌም ስሜን ለዘላለም አኖራለሁ” ያለው
ስፍራ ነው፡፡ [8]እንዲሁም፤ “ብቻ ያዘዝኋቸ
ውን ሁሉ ተጠንቅቀው በ*መፈጸ*ምና ባሪ
ያዬ ሙሴ የሰጣቸውንም ሕግ በሙሉ
በ*መ*ጠበቅ ይጽኑ እንጂ ከእንግዲህ የእስራ
ኤላውያን እግር፣ ለአባቶቻቸው ከሰጠ
ኋቸው ምድር ወጥቶ እንዲንከራተት አላ
ደርግም” ያለው ስለዚሁ ስፍራ ነው፡፡ [9]ሕዝቡ
ግን አልሰሙም፤ *እግዚአብሔር* በእስራኤላ
ውያን ፊት ካጠፋቸው አሕዛብ ይልቅ
ክፉ ድርጊት እንዲፈጽሙ ምናሴ አሳታ
ቸው፡፡
[10]*እግዚአብሔር* በባሪያዎቹ በነቢያት አማ
ካይነት እንዲህ ሲል ተናገረ፤ [11]“የይሁዳ
ንጉሥ ምናሴ ይህን ሁሉ አስጸያፊ ኀጢ
አት ሠርቶአል፤ ከእርሱ በፊት ከነበሩት
አሞራውያን ይልቅ ክፉ ድርጊት ፈጽሞ
አል፤ ይሁዳንም በጣዖታቱ አስቶአል፡፡ [12]ስለ
ዚህ የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር*
የሚለው ይህ ነው፤ ‘ለሚሰማ ሁሉ ጆሮ
ዎቹ ጭው እንዲሉ የሚያደርግ ክፉ መከራ
በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ላይ አመጣለሁ፡፡
[13]በሰማርያ ላይ ያዘጋጀሁትን መለኪያ ገመድ፣
የአክዓብንም ቤት የለካሁበትን ቱንቢ በኢ
የሩሳሌም ላይ እዘረጋለሁ፤ አንድ ሰው
ሳሕን እንደሚወለውል ከወለወለም በኋላ
እንደሚገለብጠው እኔም ኢየሩሳሌምን
ወልውዬ እገለብጣታለሁ፡፡
[14]የርስቴንም ቅሬታ እተዋቸዋለሁ፤ ለጠ
ላቶቻቸው አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ፤ ለጠ
ላቶቻቸውም ሁሉ ብዝበዛና ምርኮ
ይሆናሉ፡፡ [15]ይህን የማደ ርገውም የቀድሞ
አባቶቻቸው ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ
አንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ በፊቴ ክፉ
ድርጊት ስለ ፈጸሙና ለቍጣ ስላነሣሡኝ
ነው፡፡”
[16]ይልቁንም ምናሴ፣ *በእግዚአብሔር ፊት*
ክፉ ድርጊት እንዲፈጽም ይሁዳን ካሳተ
በት ኀጢአት ሌላ፣ ኢየሩሳሌምን ከዳር
እስከ ዳር እስኪሞላት ድረስ ብዙ ንጹሕ
ደም አፈሰሰ፡፡
[17]በምናሴ *ዘመነ መንግሥት* የተከናወ
ነው ሌላው *ሥራ*፣ የሠራውን ኀጢአት
ጨምሮ የፈጸመው ድርጊት ሁሉ በይሁዳ
*ነገሥታት ታሪክ* ተጽፎ የሚገኝ አይደለ

[†]6 ወይም፣ የራሱን ልጅ በዚህ ውስጥ እንዲያልፍ አደረገ፡፡

ምን? [18]ምናሴም ከአባቶቹ ጋር አንቀ
ላፋ፤ "የዖዛ አትክልት" በሚባለው በቤተ
መንግሥቱ አትክልት ውስጥ ተቀበረ። ልጁ
አሞንም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

## የይሁዳ ንጉሥ አሞን

21፥19-24 ተጓ ምብ - 2ዜና33፥21-25

[19]አሞን ሲነግሥ ዕድሜው ሃያ ሁለት ዓመት
ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም ሁለት
ዓመት ገዛ፤ እናቱ ሜሶላም ትባላለች፤
እርሷም የዮጥባ አገር ሰው የሐሩስ ልጅ
ነበረች። [20]አባቱ ምናሴ እንዳደረገው ሁሉ
እርሱም *በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ ድርጊት
ፈጸመ። [21]አባቱ በሄደበት መንገድ ሁሉ
ሄደ፤ አባቱ ያመለካቸውን አማልክት አመ
ለከ፤ ሰገደላቸውም። [22]የአባቶቹን አምላክ
*እግዚአብሔርን* ተወ፤ *በእግዚአብሔርም*
መንገድ አልሄደም።

[23]የአሞንም ሹማምንት ዐመፁ፤ ንጉሡ
ንም በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ገደሉት።
[24]ከዚያም የአገሩ ሕዝብ በንጉሥ አሞን
ላይ ያመፁትን ሁሉ ገደሉ፤ ልጁን ኢዮስ
ያስንም በእግሩ ተክተው አነገሡት።

[25]በአሞን ዘመነ መንግሥት የተከናወ
ነው ሌላው ሥራ፣ የፈጸመውም ድርጊት
ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚ
ገኝ አይደለምን? [26]እርሱም በዖዛ አትክ
ልት ውስጥ ባለው መቃብሩ ተቀበረ፤ ልጁ
ኢዮስያስም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

## የሕጉ መጽሐፍ ተገኘ

22፥1-20 ተጓ ምብ - 2ዜና34፥1-2፤8-28

**22** ኢዮስያስ ሲነግሥ ዕድሜው ገና
ስምንት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳ
ሌም ተቀምጦም ሠላሳ አንድ ዓመት ገዛ።
እናቱም የባሱሮት አገር ሰው የአዳያ ልጅ
ይዲዳ ነበረች። [2]ኢዮስያስም *በእግዚአብሔር*
ፊት መልካም ነገር አደረገ፤ ወደ ቀኝም
ወደ ግራም አላለም፤ አባቱ ዳዊት በሄደ
በት መንገድ ሁሉ ሄደ።

[3]በዘመነ መንግሥቱ በዐሥራ ስምንተኛ
ውምዓመት ኢዮስያስ የሜሶላምን የልጅ
ልጅ የኤዜልያስን ልጅ ጸሓፊውን ሳፋንን
ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ላከው፤
እንዲህም አለው፤ [4]"ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ
ኬልቅያስ ውጣ፤ የበር ጠባቂዎች ከሕዝቡ
ሰብስበው ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ መቅ
ደስ የገባው ገንዘብ ምን ያህል እንደ ሆነ
ራሱ እንዲቈጥረው አድርግ፤ [5]ይህም የቤተ
መቅደሱን ሥራ እንዲቈጣጠሩ ለተሾሙት
ሰዎች ይሰጥ፤ እነርሱም *የእግዚአብሔርን*
ቤተ መቅደስ ለሚያድሱት ይከፈሏቸው፤
[6]የሚከፍሉትም ለአናጺዎች፣ ለግንበኞችና
ለድንጋይ ጠራቢዎች ነው። እንዲሁም ለቤተ

21፥22 1ሳሙ8፥8፤ 1ነገ11፥33
21፥23 2ነገ12፥20
21፥24 2ነገ14፥5፤ 2ዜና33፥21፤ስፎ1፥1
21፥26 ቍ18
22፥1 ኢሱ15፥39፤ ኤር1፥2፤25፥3
22፥2 ዘዳ5፥32፤ 17፥19፤1ነገ14፥8
22፥3 2ዜና34፥20፤ ኤር39፥14
22፥4 2ነገ12፥45፤ ዕዝ7፥1
22፥5 2ነገ12፥5
22፥6 2ነገ12፥11-12
22፥7 2ነገ12፥15
22፥8 ዘዳ28፥61፤ 31፥24፤ገላ3፥10
22፥10 ኤር36፥21
22፥11 ቍ28
22፥12 1ሳሙ 8፥14፤2ነገ25፥22፤ ኤር26፥24፤39፥14
22፥13 ዘፍ25፥22፤ ዘዳ29፥24-28፤31፥17፤ 1ሳሙ9፥9፤ኢሳ5፥25፤ 42፥25፤አሞ2፥4
22፥14 ዘፀ15፥20
22፥16 ዘዳ31፥29፤ ኢሱ23፥15፤ኤር 6፥19፤11፥11፤ 18፥11፤35፥17፤ ዳን9፥11
22፥17 1ነገ9፥9
22፥18 ኤር 21፥2፤37፥3፡7
22፥19 ዘፀ10፥3፤ ዘሌ26፥31፤ኢሳ 57፥15፤61፥1፤ኤር24፥ 9፤25፥18፤26፥6፤ ሚክ6፥8

መቅደሱ እድሳት ሥራ የሚሆኑ ሳንቃዎ
ችና የተጠረቡ ድንጋዮች ይግዙበት።
[7]ሰዎቹ ታማኞች ስለሆኑም የተሰጣቸውን
ገንዘብ መቈጣጠር አያስፈልግም።"

[8]ሊቀ ካህናቱ ኬልቅያስ ጸሓፊውን ሳፋ
ንን፣ "የሕጉን መጽሐፍ እኮ *በእግዚአብሔር*
ቤተ መቅደስ ውስጥ አገኘሁት" ብሎ ሰጠው፤
እርሱም ተቀብሎ አነበበው። [9]ከዚያም
ጸሓፊው ሳፋን ሄዶ ለንጉሡ፣ "ሹማምን
ትህ *በእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ውስጥ
የነበረውን ገንዘብ አውጥተዋል፤ ቤተ መቅ
ደሱን እየተቈጣጠሩ ለሚያሠሩትም አስረ
ክበዋል" አለው። [10]ከዚያም ጸሓፊው
ሳፋን ለንጉሡ፣ "ሊቀ ካህናቱ ኬልቅያስ መ
ጽሐፍ ሰጥቶኛል" ብሎ ነገረው። ሳፋንም
ለንጉሡ ከመጽሐፉ አነበበለት።

[11]ንጉሡም የሕጉን መጽሐፍ ቃል ሲሰማ
ልብሱን ቀደደ። [12]ከዚያም ካህኑን ኬል
ቅያስን፣ የሳፋን ልጅ አኪቃምን፣ የሚክያ
ስን ልጅ ዓክቦርን፣ ጸሓፊውን ሳፋንንና
የንጉሡን የቅርብ አገልጋይ ዓሳያን እንዲህ
ሲል አዘዛቸው፤ [13]"ሂዱና ስለ እኔ፣ ስለ
ሕዝቡና ስለ ይሁዳም ሁሉ በተገኘው በዚህ
መጽሐፍ የተጻፈው ምን እንደ ሆነ *እግዚ
አብሔርን* ጠይቁ፤ ምክንያቱም አባቶቻ
ችን ለዚህ መጽሐፍ ቃል ባለመታዘዛቸው፣
እኛን በተመለከተም በዚሁ ላይ የተጻፈ
ውን ሁሉ ባለመፈጸማቸው፣ በእኛ ላይ
የሚነደው *የእግዚአብሔር* ቍጣ ታላቅ
ነውና።"

[14]ካህኑ ኬልቅያስ፣ አኪቃም፣ ዓክቦርና፣
ሳፋን፣ ዓሳያም የሐርሐስ የልጅ ልጅ፣
የቲቁዋ ልጅ የአልባሳት ጠባቂውን የሴሌ
ምን ሚስት ነቢዪቱን ሕልዳናን ለመጠ
የቅ ሄዱ። እርሷም የምትኖረው ኢየሩሳ
ሌም ውስጥ በሁለተኛው ሰፈር ነበር።

[15]ነቢዪቱም፣ "የእስራኤል አምላክ *እግ
ዚአብሔር* የሚለው ይህ ነው፤ ወደ እኔ
ለላካችሁ ሰው እንዲህ ብላችሁ ንገሩት፤
[16]"*እግዚአብሔር* የሚለው ይህ ነው፤ የይ
ሁዳ ንጉሥ ባነበበው መጽሐፍ የተጻፈውን
ሁሉ በዚህ ቦታና በሕዝቡ ላይ አመጣ
ለሁ። [17]እኔን ስለተውኝና ለሌሎች አማ
ልክት ዕጣን ስላጠኑ፣ እጆቻቸው በሠሯቸ
ውም አማልክት ሁሉ* ስላስቈጡኝ፣
ቍጣዬ በዚህ ቦታ ላይ ይነዳል፣ አይጠፋ
ምም።' " [18]*እግዚአብሔርን* እንድትጠይቁ
ወደዚህ ቦታ ለላካችሁ ለይሁዳ ንጉሥ
ይህን ንገሩት፣ 'ስለ ሰማኸው ነገር የእስራ
ኤል አምላክ *እግዚአብሔር* የሚለው ይህ
ነው፤ [19]"ርግማንና ለጥፋት የተዳረጉ ስለ
መሆናቸው በዚህ ቦታና በሕዝቡ ላይ

የተናገርኩትን ስትሰማ ልብህ ስለተነካና
ራስህን በእግዚአብሔር ፊት ስላዋረድህ፣
ልብስህንም ቀደህ በፊቴ ስላለቀስህ እግዚ
አብሔር ሰምቼሃለሁ ብሏል። [20]ስለዚህ
ወደ አባቶችህ እሰበስብሃለሁ፤ ወደ መቃ
ብር በሰላም ትወርዳለህ፤ በዚህ ቦታም
የማመጣውን መከራ ሁሉ ዐይኖችህ አያ
ዩም።' " ሰዎቹም መልሱን ለንጉሡ ይዘ
ውለት ሄዱ።

## ኢዮስያስ ኪዳኑን ዐደሰ

23፥1-3 ተጓ ምብ - 2ዜና34፥29-32
23፥4-20 ተጓ ምብ - 2ዜና34፥3-7፤33
23፥21-23 ተጓ ምብ - 2ዜና35፥1፤18-19
23፥28-30 ተጓ ምብ - 2ዜና35፥20-36፥1

23 ከዚያም ንጉሡ የይሁዳንና የኢየሩ
ሳሌምን ሽማግሌዎች ሁሉ ጠራ።
[2]የይሁዳን ሰዎች ሁሉ፣ የኢየሩሳሌምን
ከተማ ነዋሪዎች በሙሉ፣ ካህናቱንና ነቢያ
ቱን ሁሉ ከልጅ እስከ ዐዋቂ አንድም ሰው
ሳይቀር ይዞአቸው ወደ እግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ መጣ። በእግዚአብሔር ቤተ መቅ
ደስ የተገኘውንም የኪዳኑን መጽሐፍ ቃል
በጆሮአቸው እንዲሰሙት በሙሉ አነበበላ
ቸው። [3]ንጉሡም በዐምደ ወርቁ አጠገብ
በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ እግዚአብሔርን
እንደሚከተል ትእዛዞቹን፣ ደንቦቹን፣ ሥር
ዐቶቹን በፍጹም ልቡ፣ በፍጹምም ነፍሱ
እንደሚጠብቅ፣ በዚህም መጽሐፍ የተጻፈ
ውን ኪዳን እንደሚያጸና በእግዚአብሔር
ፊት ኪዳኑን አደሰ፤ ከዚያም ሕዝቡ ሁሉ
ለኪዳኑ ያላቸውን ታማኝነት አረጋገጡ።
[4]ንጉሡም ለበኣል፣ ለአሼራና ለሰማይ
ከዋክብት ሰራዊት ሁሉ የተሠሩትን የመገ
ልገያ ዕቃዎች በሙሉ፣ ከእግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ እንዲያወጡ ሊቀ ካህናቱን
ኬልቅያስን በሁለተኛ ማዕረግ ያሉትን
ካህናትና የቤተ መቅደሱን በር ጠባቂዎች
አዘዘ። ዕቃዎቹንም ከኢየሩሳሌም ውጭ
በቄድሮን ሸለቆ ሜዳ ላይ አቃጠላቸው፤
ዐመዱንም ወደ ቤቴል ወሰደው። [5]በይሁዳ
ከተሞችና በኢየሩሳሌም ዙሪያ በሚገኙ
ኰረብቶች ላይ ዕጣን እንዲያጥኑ የይሁዳ
ነገሥታት የሾሙአቸውን የጣዖት ካህናት
አባረረ እንዲሁም ለበኣል፣ ለፀሓይና
ለጨረቃ፣ ለስብስብ ከዋክብትና ለመላው
የሰማይ ከዋክብት ሰራዊት የሚያጥኑትን
አስወገደ። [6]የአሼራንም ምስል ዐምድ ከእ
ግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አውጥቶ ከኢ
የሩሳሌም ውጭ ወዳለው ወደ ቄድሮን
ሸለቆ ወስዶ አቃጠለው፤ አድቅቆ ፈጭ
ቶም በሕዝቡ መቃብር ላይ በተነው። [7]እን
ዲሁም ስለ አምልኮ ባዕድ ሥርዐት በእግ
ዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ የቤተ
ጣዖት ወንደቃዎችን ክፍሎችና ሴቶች ለአ
ሼራ መጋረጃ የሚፈትሉባቸውን ክፍሎች
አፈረሰ።
[8]ኢዮስያስ የቤተ ጣዖት ካህናትን ሁሉ
ከይሁዳ ከተማ ወደ ኢየሩሳሌም አወጣ
ቸው፤ ከጌባ ጀምሮ እስከ ቤርሳቤህ ድረስ፣
ካህናቱ ዕጣን ያጥኑባቸው የነበሩትን የኰ
ረብታ ማምለኪያ ስፍራዎችን አረከሰ።
ከከተማዪቱ በር በስተግራ በኩል፣ በከተ
ማዪቱ ገዥ በኢያሱ በር መግቢያ አጠ
ገብ የነበሩትን የበሮቹን ማምለኪያ ስፍራ
ዎች[ጎ] አፈረሰ። [9]የየኰረብታው ማምለኪያ
ካህናት ኢየሩሳሌም ባለው በእግዚአብሔር
መሠዊያ ላይ ባያገለግሉም እንኳ ከካህናት
ወንድሞቻቸው ጋር እርሾ ያልነካው ቂጣ
ይበሉ ነበር።
[10]በሄኖም ሸለቆ የነበረውን ቶፌት የተ
ባለውን ማምለኪያ አረከሰ፤ ይኸውም
ማንም ሰው ወንድ ወይም ሴት ልጁን
ለሞሎክ በእሳት የሚቃጠል መሥዋዕት
አድርጎ እንዳያቀርብበት[ነ] ነው። [11]የይሁዳ
ነገሥታት ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅ
ደስ መግቢያ ላይ ለፀሓይ አምልኮ የሰጡ
አቸውን ፈረሶች ከዚያ አስወገደ። እነዚ
ህም ናታን ሜሌክ በተባለ በአንድ ሹም
ቤት አጠገብ በአደባባዩ ላይ ነበሩ። ኢዮስ
ያስም ለፀሐይ አምልኮ የተሰጡትን ሠረገ
ሎች አቃጠለ።
[12]የይሁዳ ነገሥታት በላይኛው የአካዝ
እልፍኝ አጠገብ በሰገነቱ ላይ ያቆሟቸውን
መሠዊያዎች፣ ምናሴም በሁለቱ የእግዚ
አብሔር ቤተ መቅደስ አደባባዮች ላይ ያሠ
ራቸውን መሠዊያዎች አስወገደ፤ ስብርብ
ራቸውን አወጣ፤ ድቃቂውንም አንሥቶ
ወደ ቄድሮን ሸለቆ ጣለው። [13]እንዲሁም
ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ ከርኩሰት
ኰረብታ በስተ ደቡብ የነበሩትን የእስራ
ኤል ንጉሥ ሰሎሞን ለሲዶናውያን የርኩ
ሰት አምላክ ለአስታሮት፣ ለሞዓብ ሕዝ
ቦች የርኩሰት አምላክ ለካሞሽ፣ ለአ
ሞን ሕዝቦች የርኩሰት አምላክ ለሞሎክ
ያሠራቸውን የኰረብታ ላይ ማምለኪያ
ዎች ንጉሡ አረከሰ። [14]አሁንም ኢዮስያስ
ማምለኪያ የድንጋይ ሐውልቶችን ሰባበረ፤
የአሼራን ምስል ዐምዶች ቈራረጠ፤ ስፍራ
ውንም በሙታን ዐጥንት ሞላው።
[15]እስራኤልን ባሳተው በናባጥ ልጅ በኢ
ዮርብዓም የተሠራውን መሠዊያ፣ በቤቴል
የነበረውን ያን የኰረብታ ማምለኪያ ስፍራ፣
መሠዊያው ያለበትን ያን የኰረብታ ማም

22፥20 1ነገ21፥29፤ ኢሳ47፥11፤ 57፥1፤ኤር18፥11
23፥2 ዘፀ24፥7፤ ዘዳ31፥11
23፥3 ዘዳ13፥4፤ 1ነገ7፥15፤2ነገ11፥12
23፥4 2ነገ21፥7፤ 25፥18፤ኤር35፥4
23፥5 2ነገ16፥4፤ ኤር8፥2፤ኤር43፥13
23፥6 ዘፀ32፥20፤ ዘኍ19፥16፤ኤር 26፥23፤31፥40
23፥7 ዘፍ38፥21፤ 1ነገ14፥24፤ሕዝ 16፥16
23፥8 ኢሱ18፥24፤ 1ነገ15፥22
23፥9ሕዝ44፥10-14
23፥10 ዘሌ 18፥21፤ዘዳ18፥10፤ ኢሱ15፥8፤ኢሳ 30፥33፤ኤር7፥31፡32፤ 19፥6
23፥11 ቍ5፡19፤ ዘዳ4፥19፤ነህ9፥34፤ ኤር44፥9
23፥12 2ሳሙ 15፥23፤2ነገ21፥5፤ 2ዜና33፥15፤ኤር 19፥13፤ሰፎ1፥5
23፥13 ዘዳ27፥15፤ 1ነገ11፥7፤ኤር11፥13
23፥14 ዘፀ23፥24፤ ዘኍ19፥16፤መዝ 53፥5
23፥15 ኢሱ7፥2፤ 1ነገ12፥33፤13፥13

[ተ]17 ወይም፣ በሠሩት ሥራ ሁሉ
[ጎ]8 ወይም፣ ከፍተኛ ቦታዎች
[ነ]10 ወይም ወንድ ወይም ሴት ልጁን የገደለ

ለኪያ ስፍራ እንኳ እንደዚሁ አፈረሰ፤ ድን
ጋዮቹን ሰባበረ፤ እንደ ዱቄትም አደቀቃ
ቸው፤ የአሼራንም ምስል ዐምድ አቃጠለ።
16ኢዮስያስ ዘወር ሲል በኰረብታው ላይ
የነበሩትን መቃብሮች አየ፤ ዐፅሞቹንም
ከየ መቃብሩ አስወጣ፤ ያ የእግዚአብሔር
ሰው አስቀድሞ እንደ ተናገረው፣ *የእግዚአ
ብሔር* ቃል ይፈጸም ዘንድ፣ መሠዊያውን
ለማርከስ ሲል ዐፅሞቹን በላዩ ላይ አቃጠ
ለበት።

17ንጉሡም፣ "ያ የማየው የመቃብር ሐው
ልት የማን ነው?" ሲል ጠየቀ የከተማ
ዪቱም ሰዎች፣ "ከይሁዳ መጥቶ አሁን
አንተ ያደረግኸውን ነገር ሁሉ በቤቴል
መሠዊያ ላይ እንደሚደርስ የተናገረ የዚ
ያ የእግዚአብሔር ሰው መቃብር ነው"
አሉት።

18ኢዮስያስም፣ "በሉ እንዳለ ተዉት፤
ዐፅሙን ማንም ሰው ከቦታው እንዳያንቀ
ሳቅሰው" አለ፤ ስለዚህ የእርሱንና ከሰማርያ
የመጣውን ነቢይ ዐፅም ሳይነኩ እንዳለ
ተውት። 19ኢዮስያስም በቤቴል እንዳደረ
ገው ሁሉ በሰማርያም ከተሞች ኰረብቶች
ላይ የእስራኤል ነገሥታት አሠርተዋቸው
የነበሩትንና *እግዚአብሔርን* ያስቈጡበትን
ቤተ ጣዖቶች ሁሉ አስወገደ፤ አረከሳቸ
ውም። 20ኢዮስያስ እነዚያን የየኰረብታ
ውን ማምለኪያ ቦታ ካህናትን ሁሉ፣ በየ
መሠዊያው ላይ ዐረዳቸው፤ በመሠዊያዎቹ
ላይ የሰው ዐፅም አቃጠለ፣ ከዚያም ወደ
ኢየሩሳሌም ተመለሰ።

21ንጉሡም መላውን ሕዝብ፣ "በዚህ በኪ
ዳኑመጽሐፍ በተጻፈው መሠረት የአምላካ
ችሁን *የእግዚአብሔርን* ፋሲካ አክብሩ"
ብሎ አዘዘ። 22እስራኤልን ከመሩ ከመሳፍ
ንት ዘመን ጀምሮ፣ በእስራኤልና በይሁዳ
ነገሥታት ዘመን ሁሉ፣ እንደዚህ ያለ
ፋሲካ መቼም ተከብሮ አያውቅም። 23በኢ
ዮስያስ ዘመነ መንግሥት በዐሥራ ስምን
ተኛው ዓመት ግን ይህ ፋሲካ በኢየሩሳ
ሌም *ለእግዚአብሔር* ተከበረ። 24ከዚህም
በቀር ኢዮስያስ ሙታን አነጋጋሪዎችንና
መናፍስት ጠሪዎችን፣ የየቤተ ሰውን አማ
ልክት፣ ጣዖታትን እንዲሁም በይሁዳና
በኢየሩሳሌም የተገኙትን ሌሎች አስጸያፊ
ነገሮች ሁሉ አስወገደ፤ ይህን ያደረገውም
ካህኑ ኬልቅያስ *ከእግዚአብሔር* ቤተ መቅ
ደስ ባገኘው መጽሐፍ የተጻፈው የሕጉ
ቃል ተፈጻሚነት እንዲኖረው ለማድረግ
ነው። 25በሙሴ ሕግ በተጻፈው መሠረት
በፍጹም ልቡ፣ በፍጹም ነፍሱ፣ በፍጹም
ኀይሉ ወደ *እግዚአብሔር* የተመለሰ፣ እንደ
ኢዮስያስ ያለ ንጉሥ፣ ከእርሱ በፊትም
ሆነ ከእርሱ በኋላ ፈጽሞ አልተነሣም።
26ይህም ሆኖ እንኳ ለቍጣ እንዲነሣሣ
ምናሴ ካደረጋቸው ነገሮች ሁሉ የተነሣ፣
*እግዚአብሔር* በይሁዳ ላይ ከነደደው ከአ
ስፈሪው ቍጣው ገና አልበረደም ነበር።
27ስለዚህ *እግዚአብሔር*፣ "እስራኤልን እን
ዳስወገድሁ ሁሉ ይሁዳንም ከፊቴ አስወግ
ዳለሁ የመረጥኋትን ከተማ ኢየሩሳሌም
ንና፣ 'ስሜ በዚያ ይሆናል'[ኘ] ብዬ የተናገር
ሁለትን ይህን ቤተ መቅደስ እተዋለሁ"
አለ።

28በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት የተከናወ
ነው ሌላው ሥራ፣ የፈጸመውም ሁሉ በይ
ሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይ
ደለምን?

29ኢዮስያስ ንጉሥ በነበረበት ዘመን የግ
ብፅ ንጉሥ ፈርዖን ኒካው የአሦርን ንጉሥ
ለመርዳት ወደ ኤፍራጥስ ወንዝ ወጥቶ
ነበር፤ ንጉሥ ኢዮስያስም ጦርነት ሊገጥ
መው ወጣ፤ ሆኖም ፈርዖን ኒካው ፊት
ለፊት ገጥሞት መጊዶ ላይ ገደለው። 30የኢ
ዮስያስም አገልጋዮች ከመጊዶ ሬሳውን በሠ
ረገላ ወደ ኢየሩሳሌም አምጥተው በገዛ
መቃብሩ ቀበሩት። የአገሩም ሰዎች የኢ
ዮስያስን ልጅ ኢዮአክስን ወሰዱት፤ ቀብተ
ውም በአባቱ እግር አነገሡት።

## የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአክስ

23፥31-34 ተጓ ምብ - 2ዜና36፥2-4

31ኢዮአክስ ሲነግሥ ዕድሜው ሃያ ሦስት
ዓመት ነበር፤ እርሱም በኢየሩሳሌም ተቀ
ምጦ ሦስት ወር ገዛ። እናቱ አሚጣል
ትባላለች፤ እርሷም የልብና ሰው የኤርም
ያስ ልጅ ነበረች። 32አባቶቹ እንዳደረጉ
ሁሉ፣ እርሱም *በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ
አደረገ። 33በኢየሩሳሌም ተቀምጦ እንዳ
ይገዛም ፈርዖን ኒካው በሐማት ምድር ሪብላ
በምትባል ቦታ በሰንሰለት አሰረው[አ]፤ በይ
ሁዳም ላይ መቶ መክሊት[ከ] ብርና አንድ
መክሊት[ኸ] ወርቅ ግብር ጣለበት። 34ፈር
ዖን ኒካው የኢዮስያስን ልጅ ኤልያቄምን
በአባቱ በኢዮስያስ እግር አነገሠው፤ ኤል
ያቄም የተባለ ስሙንም ኢዮአቄም ብሎ
ለወጠው። ነገር ግን ኢዮአክስን በምርኮ
ወደ ግብፅ ወሰደው፤ እርሱም በዚያ ሞተ።
35ኢዮአቄምም ፈርዖን ኒካው የጠየቀውን
ብርና ወርቅ ከፈለ፤ ይህን ለማድረግም
የመሬት ግብር ጣለ፤ የአገሩም ሰዎች እንደ

23፥16 1ነገ 13፥2፤32
23፥18 1ነገ 13፥29፤31
23፥20 ዘፀ22፥20፤ 1ነገ13፥2፤2ነገ11፥18
23፥21 ዘፀ12፥11፤ 24፥7፤ዘዳ16፥18
23፥23 ዘፀ12፥11፤ ዘኍ28፥16
23፥24 ዘፍ31፥19፤ ዘሌ19፥31፤ዘዳ7፥26፤18፥11፤2ነገ16፥3
23፥25 1ሳሙ7፥3፤ኤር 22፥15
23፥26 2ነገ21፥6፡ 12፤ኤር23፥20፤ 30፥24
23፥27 ዘፀ33፥15፤ 2ነገ21፥13፤24፥3፤ ኤር27፥10፤ 32፥31
23፥29 ቀኍ33-35፤ 2ነገ9፥27፤ኤር46፥2
23፥30 2ነገ9፥28
23፥31 2ነገ 24፥18፤1ዜና3፥15፤ ኤር22፥11
23፥32 1ነገ15፥26
23፥33 ዘኍ34፥11፤ 1ነገ8፥65
23፥34 2ነገ24፥6፤1ዜና3፥15፤ 2ዜና36፥5-8፤ ኤር1፥3፤22፥12
23፥35 ኤር2፥16

[ኘ]27 1ነገ8፥29 ይመ።

[አ]33 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ግን ዱ2ዜና 36፥3 ይመዕ፣ ኒካው በሐማት ምድር ሪብላ በምትባል ላይ አስወገደው

[ከ]33 3.4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው። [ኸ]33 34 ኪሎ ግራም ያህል ነው።

ገቢው መጠን ብሩንና ወርቁን እንዲከፍሉ አደረገ።

## ኢዮአቄም የይሁዳ ንጉሥ

23፥36-24 ተጓ ምብ - 2ዜና36፥5-8

36ኢዮአቄም ሲነግሥ *ዕድሜው ሃያ* አምስት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም ዐሥራ አንድ ዓመት ገዛ። እናቱ ዘቢዳ ትባላለች፤ እርሷም የሩማ ተወላጅ የፈዳያ ልጅ ነበረች። 37ኢዮአቄም አባቶቹ እንደ አደረጉት ሁሉ፣ እርሱም *በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ ነገር አደረገ።

24 በኢዮአቄም ዘመነ መንግሥት የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ምድሪቱን ወረረ፤ ኢዮአቄምም ሦስት ዓመት ገበረለት፤ ከዚያ በኋላ ግን ሐሳቡን ለውጦ በናቡከደነፆር ላይ ዐመፀ። 2*እግዚአብሔርም* በኢዮአቄም ላይ ባቢሎናውያን[ሠ]፣ ሶርያውያን፣ ሞዓባውያንና አሞናውያን አደጋ ጣዮችን ላከበት፤ በአገልጋዮቹ በነቢያቱ አማካይነት በተነገረው *በእግዚአብሔር* ቃል መሠረት ይሁዳን ያጠፉ ዘንድ እነዚህን ላከ። 3ከፊቱ ያርቃቸው ዘንድ እነዚህ ነገሮች ሁሉ *እግዚአብሔር* ባዘዘው መሠረት በይሁዳ ላይ በትክክል ሊፈጸሙ ችለዋል፤ ይህም ምናሴ ስለ ሠራው ኀጢአትና ስለ ፈጸመውም ሁሉ፣ 4እንዲሁም ንጹሕ ደም ስላፈሰሰ ነው። ኢየሩሳሌምም በንጹሕ ደም እንድትጥለቀለቅ በማድረጉ፤ *እግዚአብሔር* ይቅርታ ለማድረግ አልፈለገም።

5በኢዮአቄም ዘመነ መንግሥት የተከናወነው ሌላው *ሥራ* የፈጸመውም ድርጊት ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን? 6ኢዮአቄምም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ ልጁ ዮአኪንም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

7የባቢሎንም ንጉሥ ከግብፅ ደረቅ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ የነበረውን ግዛቱን ሁሉ ወስዶበት ስለ ነበር፣ የግብፅ ንጉሥ ከአገሩ ዳግም ለዘመቻ አልወጣም።

## የይሁዳ ንጉሥ ዮአኪን

24፥8-17 ተጓ ምብ - 2ዜና36፥9-10

8ዮአኪን ሲነግሥ *ዕድሜው* ዐሥራ ስምንት ዓመት ነበር፤ እርሱም በኢየሩሳሌም ተቀምጦ ሦስት ወር ገዛ። እናቱ ኔስታ ትባላለች፤ እርሷም የኢየሩሳሌም ሰው የኤልናታንልጅ ነበረች። 9አባቱ እንዳደረገው ሁሉ እርሱም *በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ አደረገ።

10በዚያን ጊዜ የባቢሎን ንጉሥ የናቡከደነፆር ጦር አለቆች ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው ከበቧት፤ 11የጦር አለቆቹ ከበባ በሚያደርጉበትም ሰዓት ናቡከደነፆር ራሱ ወደ ከተማዪቱ መጣ። 12የይሁዳ ንጉሥ ዮአኪን፣ እናቱ፣ የክብር አጃቢዎቹ፣ መሳፍንቱና ሹማምንቱ ሁሉ እጃቸውን ለባቢሎን ንጉሥ ሰጡ። የባቢሎን ንጉሥ በነገሠ በስምንተኛው ዓመት ዮአኪንን ማርኮ ወሰደው። 13*እግዚአብሔር* አስቀድሞ እንደ ተናገረው፣ ናቡከደነፆር *የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስና የቤተ መንግሥቱን ሀብት በሙሉ አጋዘ፤ የእስራኤል ንጉሥ ሰሎሞን *ለእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ያሠራቸውንም የወርቅ ዕቃዎች ሁሉ ወሰደ። 14ደግሞም የኢየሩሳሌምን ሕዝብ እንዳለ የጦር አለቆቹንና ተዋጊዎቹን በሙሉ፣ የእጅ ባለሙያዎችንና ቀጥቃጮችን ሁሉ ጨምሮ ባጠቃላይ ዐሥር ሺህ ሰው በምርኮ ወደ አገሩ ወሰደ። በዚያ የቀሩት የመጨረሻዎቹ ያገሪቱ ድኾች ብቻ ነበሩ።

15ናቡከደነፆር ዮአኪንን ማርኮ ወደ ባቢሎን ወሰደው እንዲሁም የንጉሡን እናት፣ ሚስቶቹን፣ ሹማምንቱንና በአገር የታወቁትን ታላላቅ ሰዎችም ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢሎን ወሰደ። 16ደግሞም የባቢሎን ንጉሥ በአጠቃላይ ብርቱ የሆኑትንና ለጦርነት ብቃት ያላቸውን ሰባት ሺህ ተዋጊዎች አንድ ሺህ የእጅ ባለሙያዎችንና ቀጥቃጮችን በምርኮ ወደ ባቢሎን ወሰደ። 17ከዚያም የዮአኪንን አጎት ማታንያን በምትኩ አነገሠው፤ ስሙንም ሴዴቅያስ አለው።

## የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ

24፥18-20 ተጓ ምብ - 2ዜና36፥11-16፤ኤር52፥1-3

18ሴዴቅያስ ሲነግሥ *ዕድሜው ሃያ* አንድ ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም ዐሥራ አንድ ዓመት ገዛ። እናቱ አሚጣል ትባላለች፤ እርሷም የልብና ሰው የኤርምያስ ልጅ ነበረች። 19ኢዮአቄም እንዳደረገው ሁሉ፣ እርሱም *በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ ነገር አደረገ። 20እንግዲህ ይህ ሁሉ በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ላይ ሊደርስ የቻለው *ከእግዚአብሔር* ቍጣ የተነሣ ነበር፤ በመጨረሻም ከፊቱ አራቃቸው።

## የኢየሩሳሌም መውደቅ

25፥1-12 ተጓ ምብ - ኤር39፥1-10
25፥1-21 ተጓ ምብ - 2ዜና36፥17-20፤ኤር52፥27
25፥22-26 ተጓ ምብ - ኤር40፥7- 9፤41፥1-3፤16-18

በዚህ ጊዜ ሴዴቅያስ በባቢሎን ንጉሥ ላይ ዐመፀ።

25 በይሁዳ ንጉሥ በሴዴቅያስ ዘመነ መንግሥት በዘጠነኛው ዓመት በዐሥረኛው ወር፣ ከወሩም በዐሥረኛው ቀን የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር መላ

[ሠ]2 ወይም *ከለዳውያን*

23፥36 ኤር26፥1
23፥37 1ነገ15፥26
24፥1 ቆ10፤2ነገ 18፥7፤25፥11፤ዕዝ 5፥12፤ኤር4፥7፤ 25፥1፥9፤35፥11፤ 39፥1፤40፥1፤50፥17፤52፥15፤ሕዝ 32፥2፤ ዳን1፥1፤7፥4
24፥2 2ነገ5፥2፤ኢሳ 28፥1819፤ኤር5፥15፤12፥79፤25፥1፤26፥1፤35፥11፤36፥1፤ሕዝ 23፥23፤ ዳን1፥2፤ ዕን1፥6
24፥3 1ነገ14፥9፤ 2ነገ13፥23፤18፥25፤21፥12፤ኤር15፥4
24፥4 ዘፀ23፥21፤ 2ነገ21፥16፤ኤር 22፥3፤ሰቆ3፥42
24፥5 ኤር22፥18-19
24፥6 1ዜና3፥16፤ ኤር22፥19፡24፡28፤ 36፥30፤ሕዝ19፥1
24፥7 ዘፍ15፥18፤ 2ነገ18፥21፤ኤር1፥14፤ 25፥9፤46፥24፡25
24፥8 ቆ15፤1ዜና 3፥16፤ኤር13፥18፤ 22፥24፡26፤29፥2፤ 37፥1
24፥9 1ነገ15፥26፤
24፥10 ቆ1፤
24፥12 2ነገ 25፥27፤ ኤር13፥18፤22፥24-30፤24፥1፤ 29፥2፤
24፥13 1ነገ7፥51፤ 2ነገ20፥17፤25፥14፡15፤ ዕዝ 1፥7፤ኢሳ39፥6፤ 42፥22፤ኤር15፥13፤17፥3፤ 20፥5፤27፥16፤ 28፥3፤ሕዝ7፥21፤ዳን 1፥2፤5፥2፡23፤ሰፎ1፥13
24፥14 ዘዳ15፥11፤ 28፥36፤2ነገ25፥12፤2ዜና36፥20፤ኢዮ5፥16፤ መዝ9፥18፤ኢሳ3፥13፤ ኤር40፥7፤52፥16፤ ማቴ1፥11
24፥15 ቆ8፤1ነገ 2፥19፤2ነገ20፥18፤አስ 2፥6፤ኢሳ39፥7፤ሰቆ2፥9፤ሕዝ1፥2፤17፥12-14፤ 19፥9፤ ዳን1፥3
24፥16 ዕዝ 2፥1፤ኤር24፥1
24፥17 1ዜና3፥15፤ 2ዜና36፥11፤ኤር1፥3፤ 37፥1፤52፥1፤ሕዝ 17፥13
24፥18 2ነገ23፥31፤ 1ዜና3፥16፤ኤር39፥1
24፥19 1ነገ15፥26፤ ኤር37፥2
24፥20 ዘፀ33፥15፤ ዘዳ4፥26፤29፥27፤2ነገ13፥23
25፥1 ኢሳ23፥13፤ 29፥3፤ኤር4፥16-17፤ 21፥2፤32፥1፡2፤33፥4፤

ሰራዊቱን ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ዘመተ፤
ከከተማዪቱ ቅጥር ውጭ ሰፈረ፤ ዙሪያው
ንም በሙሉ በዕርድ ከበባት። [2]ከተማዪ
ቱም እስከ ሴዴቅያስ ዘመነ
መንግሥት
ዐሥራ አንደኛ ዓመት ድረስ እንዲሁ
እንደ ተከበበች ቈየች። [3]በአራተኛው[ሀ]
ወር በዘጠነኛው ቀን በከተማዪቱ ውስጥ
የተከሠተው ራብ ጸንቶ ስለነበር ሕዝቡ
የሚቀምሰው አጣ። [4]ምንም እንኳ ባቢሎና
ውያን[ለ] ከተማዪቱን እንደ ከበቧት ቢሆ
ንም የከተማዪቱ ቅጥር ተጣሰ፤ ሰራዊቱም
ሁሉ በንጉሡ አትክልት አጠገብ ባሉት
በሁለቱ ቅጥሮች መካከል በሚገኘው በር
አልፎ በሌሊት ሸሸ፤ ሸሽቱም ወደ ዮርዳ
ኖስ ሸለቆ[ሐ] ነበር። [5]ይሁን እንጂ የባቢ
ሎን[መ] ሰራዊት ንጉሡን ተከታትሎ በኢያ
ሪኮ ሜዳ ላይ ደረሰበት። ወታደሮቹ ሁሉ
ተለይተውት ተበታትነው ነበር። [6]እርሱም
ተያዘ፤ በዚያን ጊዜ ሪብላ ወደ ነበረው
ወደ ባቢሎን ንጉሥ አመጡት፤ ቅጣትም
ተፈረደበት። [7]ሴዴቅያስ ዐይኑ እያየም
የገዛ ልጆቹን ገደሉበት፤ ከዚያም ሁለት ዐይ
ኖቹን በማውጣት በናስ ሰንሰለት አስረው
ወደ ባቢሎን ወሰዱት።
[8]የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር በነገሠ
በዐሥራ ዘጠነኛው ዓመት፣ በአምስተኛው
ወር ከወሩም በሰባተኛው ቀን የክብር ዘቡ
ሰራዊት አዛዥና የባቢሎን ንጉሥ ከፍተኛ
ባለ ሥልጣን የሆነው ናቡዘረዳን ወደ ኢየሩሳ
ሌም መጣ። [9]*የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅ
ደስ፣ ቤተ *መንግሥቱንና* በኢየሩሳሌም
የሚገኙትን ቤቶች ሁሉ አቃጠለ፤ እያንዳ
ንዱንም ታላላቅ ሕንጻ ለእሳት ዳረገው።
[10]በክብር ዘቡ አዛዥ የተመራው መላው
የባቢሎን ሰራዊትም በኢየሩሳሌም ዙሪያ
የነበረውን ቅጥር አፈረሰው። [11]የክብር ዘቡ
አዛዥም በከተማዪቱ ቀርቶ የነበረውን፣
ከድቶም በዚያ የተገኘውን ሰው ሁሉ ወደ
ባቢሎን ንጉሥ የገባውን ጭምር በምርኮ
ወደ ባቢሎን ወሰደው። [12]ሆኖም አዛዡ
ከአገሬው ሰዎች ምንም የሌላቸውን ድኾች
ወይን እንዲተክሉ፣ ዕርሻም እንዲያርሱ
እዚያው ተዋቸው። [13]ባቢሎናውያን
የናስ
ዐምዶቹን፣ በቤተ መቅደሱ ውስጥ የነበሩ
ትን ተንቀሳቃሽ የዕቃ ማስቀመጫዎችንና
ከናስ የተሠራውን የውሃ ማጠራቀሚያ
ክብ በርሜል ሰባብረው ናሱን ወደ ባቢ
ሎን ወሰዱ። [14]እንዲሁም ምንቸቶቹን፣
*መጫሪያዎቹን*፣ *መኰስተሪያዎቹን*፣ ጭል
ፋዎቹን፣ ባጠቃላይም ከናስ የተሠሩትን
የቤተ *መቅደሱን መገልገያ* ዕቃዎች ሁሉ
ወሰዱ። [15]የክብር ዘቡ አዛዥም ከንጹሕ

34÷1-7፤ሕዝ21÷22፤
24÷2
25÷3 ዘሌ26÷26፤ ኢ
ሳ22÷2፤ኤር14÷18፤
37÷21፤ሰቆ2÷20፤4÷9
25÷4 ኢዩ30÷14፤
መዝ144÷14፤ኤር4÷1
7፤6÷3፤50÷15፤
51÷44፡58፤ሕዝ
33÷21
25÷5 ዘሌ26÷36፤ ሕዝ
12÷14፤ 17÷21
25÷6 ዘኍ34÷11፤
ኢሳ22÷3፤ኤር38÷23
25÷7 ዘዳ28÷36፤
ኤር21÷7፤32÷45፤
34÷3፡21፤ሕዝ
12÷11፤19÷9፤40÷1
25÷9 ዘዳ13÷16፤
ነህ1÷3፤መዝ74÷38፤7
9÷1፤ኢሳ ነህ1÷3፤
60÷7፤63÷15፡18፤
64÷11፤ኤር2÷15፤
17÷27፤21÷10፤26÷6፡
18፤ሰቆ4÷11፤አሞ
2÷5፤ሚክ3÷12
25÷10 ኤር50÷15
25÷11 ዘሌ26÷44፤
ዘዳ28÷36፤2ነገ24÷1
25÷12 2ነገ24÷14
25÷13 1ነገ7÷50
25÷14 ዘኍ7÷14፤
2ነገ24÷13፤ዕዝ1÷7
25÷15 2ነገ
24÷13፤ኤር15÷13፤
20÷5፤27÷16-22
25÷17 1ነገ7÷15-22
25÷18 ቀኍ1821፤
2ነገ12÷9፤23÷4፤1ዜና
6÷14፤ ዕዝ7÷1፤
ነህ11÷11፤ኤር21÷1፤
29÷25፤37÷3
25÷21 ዘፍ12÷7፤
ዘኍ34÷11፤ኢሱ
23÷13፤1ነገ8÷46፤
ኤር34÷21፤
25÷22 2ነገ22÷12፤
ኤር39÷14፤
40÷5፡7፤41÷18፤
25÷25 2ነገ12÷20፤
ዘካ7÷5፤

ወርቅና ብር የተሠሩትን ጽናዎችና የመ
ርጫ ወጭቶችን ወሰደ።
[16]ሰሎሞን *ለእግዚአብሔር* ቤተ *መቅደስ*
*መገልገያ* ብሎ ከናስ *ያሠራቸው* ሁለት ዐም
ዶች፣ የውሃ ማጠራቀሚያው ክብ በርሜ
ልና ተንቀሳቃሽ የዕቃ ማስቀመጫዎቹ ክብ
ደታቸው ከሚዛን በላይ ነበር። [17]እያንዳ
ንዱ ዐምድ ዐሥራ ስምንት ክንድ[ሠ] ሲሆን፣
የናስ ጕልላት ነበረው፤ የጕልላቱ ርዝ
መት ሦስት ክንድ[ረ] ሆኖ፣ ዙሪያውን በሙሉ
የናስ መርበብና የሮማን ፍሬዎች ቅርጽ
ነበረው፤ ሌላውም ዐምድ ከነቅርጾቹ ከዚሁ
ጋር ተመሳሳይ ነበር።
[18]የክብር ዘብ አዛዡም ሊቀ ካህኑን ሠራ
ያን፣ በማዕረግ ከእርሱ ቀጥሎ ያለውን ካህ
ኑን ሶፎንያስንና ሦስቱን የበር ጠባቂዎች
እስረኛ አድርጎ ወሰዳቸው። [19]እስከዚያች
ጊዜ ድረስ በከተማዪቱ ውስጥ ከቀሩትም
የተዋጊዎቹን አለቃና አምስት የንጉሡን
አማካሪዎች ወሰዳቸው። ደግሞም የአገሩን
ሕዝብ ለውትድርና የሚመለምለውን ዋና
የጦር አለቃ የነበረውን ጸሓፊውንና በከተ
ማዪቱ ውስጥ የተገኙትን የጸሓፊውን ሥልሳ
ሰዎች ወሰዳቸው። [20]አዛዡ ናቡዘረዳንም
እነዚህን ሁሉ ይዞ ልብና ወዳለው ወደ
ባቢሎን ንጉሥ አመጣቸው። [21]ንጉሡም
ሰዎቹን በሐማት ምድር እዚያው ልብና
ውስጥ አስገደላቸው። ይሁዳም ከምድሩ
በዚህ ሁኔታ ተማርኮ ሄደ።
[22]የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር፣ የሳፋን
የልጅ ልጅ የሆነውን የአኪቃምን ልጅ
ጎዶልያስን እዚያው በቀረው በይሁዳ ሕዝብ
ላይ አለቃ አድርጎ ሾመው። [23]መላው የሰ
ራዊቱ ጦር አለቆችና ሰዎቻቸው የባቢሎን
ንጉሥ፣ አገረ ገዥ አድርጎ ጎዶልያስን መሾ
ሙን ሲሰሙ፣ እርሱ ወዳለበት ወደ ምጽጳ
መጡ፤ እነርሱም የናታንያ ልጅ እስማ
ኤል፣ የቃሬያም ልጅ ዮሐናን፣ የነጦፋ
ዊው የተንሑሜት ልጅ ሠራያ የማዕካታ
ዊው ልጅ ያእዛንያና ሰዎቻቸው ነበሩ።
[24]ጎዶልያስም፣ "የባቢሎናውያንን ሹማም
ንት አትፍሩ፤ እዚሁ አገር ኑሩ፤ የባቢሎ
ንን ንጉሥ አገልግሉ፤ ሁሉም ነገር ይሳካላ
ችኋል" ሲል ይህንኑ በቃለ መሐላ አረጋገ
ቸው። [25]ነገር ግን በሰባተኛው ወር ንጉ
ሣዊ ዝርያ የነበረው የኤሊሳማ የልጅ ልጅ
የሆነው የናታንያ ልጅ እስማኤል ዐሥር
ሰዎች ይዞ መጥቶ ጎዶልያስንና በምጽጳ
አብረውት የነበሩትን የይሁዳን ሰዎችና

[ሀ]3 ኤር52÷6 ይመ።
[ለ]4 በዚህና በቍጥር 13፡25 እንዲሁም 26 ላይ፣ *ከለዳውያን*
[ሐ]4 ወይም፣ *በዓረባም* [መ]5 በዚህም ሆነ በቍጥር 10 እና 24
ላይ፣ ከለዳውያን
[ሠ]17 8. 1 ሜትር ያህል ነው። [ረ]17 1.3 ሜትር ያህል ነው።
[ሰ]27 *አሜል ማርዶክ* ይባላል።

ባቢሎናውያንን ገደለ። [26]ባቢሎናውያንን
ከመፍራታቸው የተነሣም ትንሽ ትልቅ
ሳይባል ሕዝቡ ሁሉ ከሰራዊቱ የጦር አለ
ቆች ጋር ወደ ግብፅ ሸሹ።

## ዮአኪን ከእስራት ተፈታ

25፥27-30 ተጓ ምብ - ኤር52፥31-34

[27]የይሁዳ ንጉሥ ዮአኪን በተማረከ በሠ
ላሳ ሰባተኛው ዓመት፣ በዐሥራ ሁለተ
ኛው ወር ከወሩም በሃያ ሰባተኛው ቀን
ዮርማሮዴቅ[ገ] በባቢሎን በነገሠ በዓመቱ
ዮአኪንን ከእስራቱ ፈታው። [28]በርኅራኄም
መንፈስ አነጋገረው፤ በባቢሎን አብረውት
ከነበሩት ነገሥታት ይልቅ ከፍ ያለውን
የክብር ቦታ ሰጠው። [29]ዮአኪንም የእስር
ቤት ልብሱን ጣለ፤ እስከ ዕድሜው ፍጻሜ
ድረስ ከንጉሡ ማዕድ ዘወትር ይመገብ
ጀመር፤ [30]ንጉሡም ለዮአኪን እስከ ዕድሜው
ፍጻሜ ድረስ የዕለት ቀለቡን ይሰጠው ነበር።

25፥26 ኢሳ30፥2፤ ኤር43፥7፤
25፥27 2ነገ24፥12
25፥28 1ነገ8፥50፤ ዕዝ5፥5፤7፥6፡28፤ 9፥9፤ነህ2፥1፤ዳን 2፥48
25፥29 2ሳሙ9፥7
25፥30 ዘፍ43፥34፤ አስ2፥9፤9፥22፤ ኤር28፥4

# መጽሐፈ ዜና መዋዕል - አንደኛ

## *ከአዳም እስከ አብርሃም ያለው የትውልድ ሐረግ*

1፥1 ዘፍ5፥1-32፤ ሉቃ 3፥36-38
1፥2 ዘፍ5፥9፡12፡15
1፥3 ዘፍ5፥18፡21፡ 25፡29፤ይሁ1፥14
1፥4 ዘፍ5፥32፤ 6፥10፤10፥1

### እስከ ኖኅ ልጆች

1 አዳም፣ ሴት፣ ሄኖስ፣ [2]ቃይናን፣ መላ
ልኤል፣ ያሬድ፣ [3]ሄኖክ፣ ማቱሳላ፣
ላሜሕ፣ ኖኅ።
[4]የኖኅ ወንዶች ልጆች[ሀ]፤
ሴም፣ ካም፣ ያፌት።

### *ያፌታውያን*

1፥5-7 ተጓ ምብ - ዘፍ10፥2-5

[5]የያፌት ወንዶች ልጆች፤[ለ]
ጋሜር፣ ማጎግ፣ ማዴ፣ያዋን፣
ቶቤል፣ ሞሳሕ፣ ቴራስ።
[6]የጋሜር ወንዶች ልጆች፤
አስከናዝ፣ ሪፋት፣ ቴርጋማ።
[7]የያዋን ወንዶች ልጆች፤
ኤሊሳ፣ ተርሴስ፣ ኪቲም፣ ሮድኢ።

### *ካማውያን*

1፥8-16 ተጓ ምብ - ዘፍ 10፥6-20

[8]የካም ወንዶች ልጆች፤
ኩሽ፣ ምጽራይም፣[ሐ] ፉጥ፣ ከነዓን።
[9]የኩሽ ወንዶች ልጆች፤
ሳባ፣ ኤውላጥ፣ ሰብታ፣ ራዕማ፣
ሰብቃታ።
የራዕማ ወንዶች ልጆች፤
ሳባ፣ ድዳን።
[10]ኩሽ ናምሩድን ወለደ፤
እርሱም በምድር ላይ የመጀመሪያው
ኀያል ጦረኛ ሆነ።
[11]ምጽራይም የሉዲማውያን፣ የዐናማው
ያን፣ የላህባማውያን፣ የነፍተሂማው
ያን፣ [12]የፈትሩሲማውያን፣ የፍልስጥ
ኤማውያን ቅድመ አባቶች የሆኑት
የከስሉሂማውያንና የከፍቶሪማውያን
ነገዶች አባት[መ] ነው።
[13]ከነዓን የበኵር ልጁ የሆነው የሲዶን
እንዲሁም የኬጢያውያን፣ [14]የኢያቡሳ
ውያን፣ የአሞራውያን፣ የጌርጌሳው
ያን፣ [15]የኤዊያውያን፣ የዐርካውያን፣
የሲኒውያን፣ [16]የአራዴዎያውያን፣ የሰ
ማርያውያን፣ የአማቲያውያን አባት
ነው።

### *ሴማውያን*

1፥17-23 ተጓ ምብ – ዘፍ 10፥21-31፤11፥10-27

1፥24 ዘፍ10፥21-25፤ ሉቃ3፥34-36

[17]የሴም ወንዶች ልጆች፤
ኤላም፣ አሦር፣ አርፋክስድ፣ ሉድ፣ አ
ራም።
የአራም ወንዶች ልጆች፤[ሠ]
ዑፅ፣ ሁል፣ ጌቴር፣ ሞሳሕ።
[18]አርፋክስድ ሳላን ወለደ፤
ሳላም ዔቦርን ወለደ።
[19]ዔቦር ሁለት ወንዶች ልጆች ወለደ፤
በዘመኑ ምድር ስለተከፈለች፣
የአንደኛው ስም ፋሌቅ[ረ] ተብሎ ተጠራ፤
ወንድሙም ዮቅጣን ተባለ።
[20]ዮቅጣንም፡
አልሞዳድን፣ ሣሌፍን፣ ሐስረሞትን፣
ያራሕን፣[21]ሀዶራምን፣አውዛልን፣
ደቅላን፣
[22]ዖባልን፣[ሰ] አቢማኤልን፣ ሳባን፣
[23]ኦፊርን፣ ኤውላጥን፣ ዮባብን ወለደ፤
እነዚህ ሁሉ የዮቅጣን ወንዶች ልጆች
ናቸው።
[24]ሴም፣ አርፋክስድ[ሸ]፣ሳላ፣
[25]ዔቦር፣ ፋሌቅ፣ ራግው፣
[26]ሴሮሕ፣ ናኮር፣ ታራ፣
[27]እንዲሁም በኋላ አብርሃም የተባለው
አብራም።

### የአብርሃም ቤተ ሰብ

[28]የአብርሃም ወንዶች ልጆች፤
ይስሐቅ፣ እስማኤል።

### የአጋር ዘሮች

1፥29-31 ተጓ ምብ - ዘፍ 25፥12-16

[29]የእነዚህ ዘሮች የሚከተሉት ናቸው፤
የእስማኤል በኵር ልጅ ነባዮት፣
ቄዳር፣ ነብ ዳኤል፣ መብሳም፣ [30]ማስ
ማዕ፣ ዱማ፣ ማሣ፣ ኩዳን፣ ቴማን፣
[31]ኢጡር፣ ናፌስ፣ ቄድማ፤ እነዚህ የእ
ስማኤል ወንዶች ልጆች ናቸው።

[ሀ]4 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን፣ *የኖኅ ወንዶች ልጆች* የሚለውን አይጨምርም።
[ለ]5 *ወንዶች ልጆች* ማለት ዘር ወይም ሕዝብ ማለት ነው፤ እንዲሁም ቍ 6-10፤ 17 እና 20
[ሐ]8 *ግብፅ* ናት፤ እንዲሁም ቍ 11
[መ]12 *አባት* ማለት *ቅድመ አያት ወይም እንጅላት ወይም መሥረት* ማለት ነው፤ እንዲሁም ቍ 16
[ሠ]13 ወይም፣ *የሲዶናውያን አለቃ*
[ረ]19 ፋሌቅ ማለት *መከፈል* ማለት ነው
[ሰ]22 አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆችና የሱርስቱ ትርጒም (እንዲሁም ዘፍ 10፥28 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *ዒባል* ይላሉ።
[ሸ]24 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ቅጆች ግን፣ *አርፋክስድ፣ ቃይንም* ይላሉ (የዘፍ 11፥10 ማብ ይመ)።

## የኬጡራ ዘሮች

1፥32-33 ተጓ ምብ - ዘፍ 25፥1-4

32የአብርሃም ቁባት ኬጡራ የወለደቻ
ቸው ወንዶች ልጆች ዘምራን፣ ዮቅ
ሳን፣ ሜዳን፣ ምድያም፣ የስቦቅና፣
ስዌሕ ናቸው፡፡
የዮቅሳን ወንዶች ልጆች፤
ሳባ፣ ድዳን፡፡
33የምድያም ወንዶች ልጆች፤
ጌፌር፣ ዔፌር፣ ሄኖኅ፣ አቢዳዕ፣
ኤልዳዓ፤
እነዚህ ሁሉ የኬጡራ ዘሮች ናቸው፡፡

## የሣራ ዘሮች

1፥35-37 ተጓ ምብ - ዘፍ 36፥10-14

34አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፡፡
የይስሐቅ ወንዶች ልጆች፤
ዔሳው፣ እስራኤል፡፡

## የዔሳው ወንዶች ልጆች

35የዔሳው ወንዶች ልጆች፤
ኤልፋዝ፣ ራጉኤል፣የዑስ፣ የዕላም፣
ቆሬ፡፡
36የኤልፋዝ ወንዶች ልጆች፤
ቴማን፣ አማር፣ ስፎ[ቀ]፣ ጎቶም፣
ቄኔዝ፣ ቲምናዕ፣ አማሌቅ፡፡
37የራጉኤል ወንዶች ልጆች፤
ናሖት፣ ዛራ፣ ሣማ፣ ሚዛህ፡፡

## በኤዶም የሚኖሩ የሴይር ሰዎች

1፥38-42 ተጓ ምብ - ዘፍ 36፥20-28

38የሴይር ወንዶች ልጆች፤
ሎጣን፣ ሦባል፣ ጽብዖን፣ ዓና፣
ዲሶን፣ ኤጽር፣ ዲሳን፡፡
39የሎጣን ወንዶች ልጆች፤
ሖሪ፣ ሄማም፤ ቲሞናዕ የሎጣን እኅት
ነበረች፡፡
40የሦባል ወንዶች ልጆች፤
ዓልዋን፣ ማኔሐት፣ ዔባል፣ ስፎ፣ አው
ናም፡፡
የጽብዖን ወንዶች ልጆች፤
አያ፣ ዓና፡፡
41የዓና ወንድ ልጅ፤
ዲሶን፡፡
የዲሶን ወንዶች ልጆች፤
ሔምዳን[በ]፣ ኤስባን፣ ይትራን፣ ክራን፡፡
42የኤጽር ወንዶች ልጆች፤
ቢልሐን፣ዛዕዋን፣ ዓቃን፡፡
የዲሳን ወንዶች ልጆች፤
ዑፅ፣ አራን፡፡

## የኤዶምያስ ነገሥታት

1፥43-54 ተጓ ምብ - ዘፍ 36፥31-43

43በእስራኤል አንድም ንጉሥ ገና ሳይነ
ግሥ[ተ] በኤዶም ምድር የነገሡ ነገሥ
ታት እነዚህ ናቸው፤ የቢዖር ልጅ ባላቅ፤
ከተማዪቱም ዲንሃባ ትባል ነበር፡፡
44ባላቅ ሲሞትም የባሶራ ሰው የሆነው
የዛራ ልጅ ኢዮባብ በእግሩ ተተክቶ
ነገሠ፡፡
45ኢዮባብ ሲሞት የቴማን አገር ሰው
የሆነው ሑሳም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ፡፡
46ሑሳም ሲሞት በሞዓብ ምድር ምድያ
ምን ድል ያደረገው የባዳድ ልጅ
በእግሩ ተተክቶ ነገሠ፡፡ የከተማዪቱም
ስም ዓዊት ተባለ፡፡
47ሃዳድም ሲሞት የመሥሬቃ ሰው የሆ
ነው ሠምላ በእግሩ ተተክቶ ነገሠ፡፡
48ሠምላም ሲሞት በወንዙ[ቸ] አጠገብ ያለ
ችው የረሆቦት ሰው የሆነው ሳኡል
በእግሩ ተተክቶ ነገሠ፡፡
49ሳኡልም ሲሞት የዓክቦር ልጅ የሆነው
በኣልሐናንም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ፡፡
50በኣልሐናን ሲሞት ሀዳድ በእግሩ ተተ
ክቶ ነገሠ፡፡ ከተማውም ፋዑ ትባል
ነበር፤ ሚስቱ መሄጣብኤል ትባላ
ለች፤ እርሷም የሜዛሃብ ልጅ የመ
ጥሬድ ልጅ ነበረች፡፡ 51ሀዳድም ሞተ፡፡

ዋና ዋናዎቹ የኤዶም ሕዝብ አለቆች
እነዚህ ነበሩ፤
ቲምናዕ፣ ዓልዋ፣ የቴት፣ 52አህሊባማ፣
ኤላ፣ ፊኖን፣ 53ቄኔዝ፣ ቴማን፣ ሚብ
ሳር፣ 54መግዲኤል፣ዒራም፡፡ እነዚህ
የኤዶም አለቆች ነበሩ፡፡

## የእስራኤል ወንዶች ልጆች

2፥1-2 ተጓ ምብ - ዘፍ 35፥23-26

2 የእስራኤል ወንዶች ልጆች እነዚህ
ነበሩ፤ ሮቤል፣ ስምዖን፣ ሌዊ፣ ይሁዳ፣
ይሳኮር፣ ዛብሎን፣ 2ዳን፣ ዮሴፍ፣ ብን
ያም፣ ንፍታሌም፣ ጋድ፣ አሴር፡፡

## ይሁዳ

2፥5-15 ተጓ ምብ - ሩት 4፥18-22፤ ማቴ 1፥3-6

## እስከ ኤስሮን ወንዶች ልጆች

3የይሁዳ ወንዶች ልጆች፤
ዔር፣ አውናን፣ ሴሎም፤ እነዚህን
ሦስቱን ከከነዓናዊት ሚስቱ ከሴዋ
ወለደ፡፡ የበኵር ልጁ ዔር *በእግዚ*

1፥32 ዘፍ10፥7፤22፥24
1፥34 ዘፍ17፥5፤ ማቴ 1፥2፤ ሉቃ3፥34፤ሐሥ 7፥8
1፥35 ዘፍ36፥4፡19
1፥36 ዘፀ17፥14
1፥37 ዘፍ36፥17
1፥40 ዘፍ36፥2
1፥45 ዘፍ36፥11
2፥3 ዘፍ29፥35፤ 38፥2-10፤ ዘኍ26፥19

[ቀ]36 ብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞችና የሱርስቱ ቅጅ (እንዲሁም ዘፍ 36፥11 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አያሌ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *ጸፊ* ይላሉ

[በ]41 ብዙ የዕብራይስጥና አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች (እንዲሁም ዘፍ 36፥26) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አያሌ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *ሐምራን* ይላሉ፡፡

[ተ]43 ወይም፣ *እስራኤላዊ የሆነ ንጉሥ ገና በእነርሱ ላይ ከመንገሡ በፊት*

[ቸ]48 ምናልባት *ኤፍራጥስን* ነው፡፡

እግዚአብሔር ፊት ክፉ ሰው ሆነ፤ እግዚ
አብሔርም ቀሠፈው። [4]የልጁም
ሚስት የነበረችው ትዕማር ፋሬስ
ንና ዛራን ወለደችለት፤ ይሁዳም ባጠ
ቃላይ አምስት ወንዶች ልጆች
ነበሩት።
[5]የፋሬስ ወንዶች ልጆች፤
ኤስሮም፣ ሐሙል።
[6]የዛራ ወንዶች ልጆች፤
ዘምሪ፣ ኤታን፣ ሄማን፣ ከልኮል፣ ዳራ[ጎ]፤
ባጠቃላይ አምስት ናቸው።
[7]የከርሚ ወንድ ልጅ አካን[ነ]፤
እርሱም ፈጽሞ መደምሰስ የነበረበትን
ነገር ሰርቆ በእስራኤል ላይ ጥፋት[ኘ]
እንዲመጣ ያደረገ ነው።
[8]የኤታን ወንድ ልጅ፤
አዛርያ።
[9]የኤስሮም ወንዶች ልጆች፤
ይረሕምኤል፣ አራም፣ ካሌብ።[አ]

### ከኤስሮም ልጅ ከአራም ጀምሮ ያለው የትውልድ ሐረግ

[10]አራም አሚናዳብን ወለደ፤
አሚናዳብም የይሁዳ ሕዝብ መሪ
የሆነውን
ነአሶንን ወለደ፤[11]ነአሶን ሰልሞንን[ከ]
ወለደ፤ ሰልሞን ቦዔዝን ወለደ። [12]ቦዔዝ
ኢዮቤድን ወለደ፤ ኢዮቤድ እሴይን
ወለደ።
[13]የእሴይ ወንዶች ልጆች፤
የበኩር ልጁ ኤልያብ፣ ሁለተኛ ልጁ
አሚናዳብ፣ ሦስተኛ ልጁ ሣማ፣ [14]አ
ራተኛ ልጁ ናትናኤል፣ አምስተኛ
ልጁ ራዳይ፣ [15]ስድስተኛ ልጁ አሳም፣
ሰባተኛ ልጁ ዳዊት። [16]እኅቶቻቸውም
ጽሩያና አቢግያ ነበሩ። የጽሩያ
ሦስት ወንዶች ልጆች አቢሳ፣ኢዮ
አብና አሣኤል ነበሩ። [17]አቢግያ
አሜሳይን ወለደች፤ አባቱም ዬቴር
የተባለ እስማኤላዊ ነበረ።

### የኤስሮም ልጅ ካሌብ

[18]የኤስሮም ልጅ ካሌብ ከሚስቱ ከዓዙ
ባና እንዲሁም ከይሪዖት ወንዶች
ልጆች ወለደ፤ ከዓዙባ የተወለዱት
ወንዶች ልጆች እነዚህ ናቸው፤
ያሳር፣ ሶባብ፣ አርዶን። [19]ዓዙባ
ስትሞት፣ ካሌብ ኤፍራታን አገባ፤
እርሷም ሆርን ወለደችለት። [20]ሆር
ኡሪን ወለደ፤ ኡሪም ባስልኤልን
ወለደ።
[21]ከዚያም በኋላ ኤስሮም ሥልሳ ዓመት
ሲሆነው የገለዓድን አባት የማኪርን
ልጅ አገባ፤ እርሷም ሠጉብን ወለደ
ችለት። [22]ሠጉብም ኢያዕርን ወለደ፤
እርሱም በገለዓድ ምድር ሃያ ሦስት
ከተሞች ያስተዳድር ነበር። [23]ይሁን
እንጂ ጌሹርና አራም፣ ቄናትንና
በዙሪያዋ የሚገኙትን ሥልሳ መን
ደሮች ጨምሮ የኢያዕርን ከተሞች
ነጠቁት[ኸ]። እነዚህ ሁሉ የገለዓድ
አባት የማኪር ዘሮች ነበሩ። [24]ኤስ
ሮም በካሌብ ኤፍራታ ከሞተ በኋላ፣
ሚስቱ አቢያ የቴቁሔን አባት[ወ] አሽሑ
ርን ወለደችለት።

### የኤስሮም ልጅ ይረሕምኤል

[25]የኤስሮም የበኵር ልጅ የይረሕምኤል
ወንዶች ልጆች፤ የበኵር ልጁ ራም፣
ቡናህ፣ ኦሬን፣ ኦጼም፣ አኪያ። [26]ይረ
ሕምኤል ዓጣራ የተባለች ሌላ ሚስት
ነበረችው፤ እርሷም የኦናምን እናት
ነበረች።
[27]የይረሕምኤል የበኵር ልጁ የራም
ወንዶች፤
መዓስ፣ ያሚን፣ ዔቄር።
[28]የኦናም ወንዶች ልጆች፤
ሸማይና ያዳ።
የሸማይ ወንዶች ልጆች፤
ናዳብና አቢሱር።
[29]የአቢሱር ሚስት አቢካኢል ትባላለች፤
እርሷም አሕባንንና ሞሊድ የተባሉ
ልጆች ወለደችለት።
[30]የናባድ ወንዶች ልጆች፤
ሴሌድ፣ አፋይም፤ ሴሌድ ወንድ
ልጅ ሳይወልድ ሞተ።
[31]የአፋይም ወንድ ልጅ፤
ይሽዒ። ይሽዒም ሶሳን ወለደ።
ሶሳን አሕላይን ወለደ።
[32]የሸማይ ወንድም የያዳ ወንዶች
ልጆች፤ ዬቴር፣ ዮናታን፤ ዬቴርም
ልጅ ሳይወልድ ሞተ።
[33]የዮናታን ወንዶች ልጆች፤
ፌሌት፣ ዛዛ።
እነዚህ የይረሕምኤል ዘሮች ነበሩ።

2፥5 ዘፍ46፥12፤ ዘኍ26፥21
2፥7 ኢሱ6፥18፤7፥1
2፥9 ዘኍ26፥21
2፥10 ዘፀ6፥23፤ ዘኍ1፥7፤ሉቃ3፥32-33
2፥12 ሩት2፥1፤4፥ 17
2፥13ሩት4፥17፤ 1ሳሙ16፥6
2፥16 1ሳሙ 26፥6 ሳሙ2፥13፥18
2፥17 2ሳሙ17፥25
2፥19 ቀኍ42፡50
2፥20 ዘፀ31፥2
2፥21 ዘኍ27፥1
2፥23 ዘኍ32፥41፡ 42፤ዘዳ3፥14
2፥24 1ዜና4፥5

[ጎ]6 አያሌ የዕብራይስጥ ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አንዳንድ የዕብራይስጥ፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞችና የሱርስቱ ቅጆች (እንዲሁም 1ነገ 4፥31 ይመ) ግን፣ ***ዳርዳ*** ይላሉ።
[ነ]7 ***አካን*** ማለት፣ ***ችግር*** ወይም፣ ***መከራ*** ማለት ነው።
[ኘ]7 የዕብራይስጡ ቃል አንድን ሰው ወይም ነገር ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠትን ያመለክታል።
[አ]9 ዕብራይስጡ፣ ***ከሉባይ*** ይላል፤ ይኸውም፣ ***ካሌብ*** ማለት ነው።
[ከ]11 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም (እንዲሁም ሩት 4፥21) ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን፣ ***ሳልማ***
[ኸ]23 ወይም፣ ***የኢያሶርን መኖሪያ ነጠቁ***
[ወ]24 በዚህም ሆነ በቍጥር 42፡45፡ 49 - 52 ላይ፣ ***አባት*** ማለት፣ ***የአገር ሽማግሌ*** ወይም፣ ***የጦር መሪ*** ማለት ነው።

34ሶሳን ሴቶች ልጆች እንጂ ወንዶች
ልጆች አልነበሩትም:: እርሱም ኢዮ
ሄል የተባለ ግብፃዊ አገልጋይ ነበ
ረው:: 35ሶሳን ልጁን ለአገልጋዩ ለኢ
ዮሄል ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠው፤
እርሷም ዓታይ የተባለ ወንድ ልጅ
ወለደችለት::
36ዓታይ ናታንን ወለደ፤
ናታንም ዛባድን ወለደ፤
37ዛባድ ኤፍላልን ወለደ፤
ኤፍላል ዖቤድን ወለደ፤
38ዖቤድ ኢዩን ወለደ፤
ኢዩ ዓዛርያስን ወለደ፤
39ዓዛርያስ ኬሌስን ወለደ፤
ኬሌስ ኤልዓሣን ወለደ፤
40ኤልዓሣ ሲስማይን ወለደ፤
ሲስማይ ሰሎምን ወለደ፤
41ሰሎም የቃምያን ወለደ፤
የቃምያም ኤሊሳማን ወለደ::

## የካሌብ ጐሣዎች

42የይረሕምኤል ወንድም የካሌብ ወን
ዶች ልጆች፤
የበኵር ልጁ ሞሳ ሲሆን፣ እርሱም
ዚፍን ወለደ፤ ዚፍም መሪሳን[0] ወለደ፤
መሪ ሳም ኬብሮንን ወለደ::
43የኬብሮን ወንዶች ልጆች፤
ቆሬ፣ ተፉዋ፣ ሬቄም፣ ሽማዕ:: 44ሽማዕ
ረሐምን ወለደ፤ ረሐምም ዮርቅዓምን
ወለደ:: ሬቄም ሸማይን ወለደ፤ 45ሸማ
ይም ማዖንን ወለደ፤ ማዖንም ቤት
ጹርን ወለደ::
46የካሌብ ቁባት ዔፉ ሐራንን፣ ሞጻን፣
ጋዜዝን ወለደች:: ሐራንም ጋዜዝን
ወለደ::
47የያህዳይ ወንዶች ልጆች፤
ሬጌም፣ኢዮታም፣ ጌሻን፣ ፋሌጥ፣ ዔፉ፣
ሸዓፍ::
48የካሌብ ቁባት ማዕካ ሼቤርን፣ ቲርሐ
ናን ወለደችለት:: 49እንዲሁም የመድ
ማናን አባት ሸዓፍን፣ የመክቢናንና
የጊብዓን አባት ሱሳን ወለደች:: ካሌብ
ዓክሳ የተባለች ልጅ ነበረችው:: 50እነ
ዚህ ሁሉ የካሌብ ዘሮች ነበሩ::

የኤፍራታ የበኵር ልጅ የሑር ወንዶች
ልጆች፤
ሦባል የቂርያትይዓሪም አባት፤ 51ሰልሞን
የቤተልሔም አባት፤ ሐሬፍ የቤት
ጋዴር አባት::
52 የቂርያትይዓሪም አባት የሦባል ዘሮች፤
የመናሕታውያን ነዋሪዎች እኵሌታ፣
ሀሮኤ፤

2፥36 1ዜና11፥41
2፥45 ኢሱ 15፥55፡ 58
2፥49 ኢሱ15፥16፡31
2፥50
ቀኍ19፤ 1ዜና 4፥4

2፥53 2ሳሙ23፥38
2፥54 ዕዝ2፥22፤
ነህ 7፥26፤12፥28
2፥55 ዘፍ15፥19፤
ኢሱ19፥35፤መሳ4፥11፤
2ነገ10፥15፡23፤
ኤር35፥2-9
3፥1ኢሱ15፥56፤
1ሳሙ25፥42፡43፤
1ዜና14፥3፤28፥5
3፥2 1ነገ2፥22
3፥4 2ሳሙ5፥4፡5፤
1ዜና29፥27
3፥5 2ሳሙ11፥3
3፥9 2ሳሙ13፥1፤
1ዜና14፥4
3፥10 1ነገ14፥21-
31፤15፥1-8፡9-24፤
2ዜና12፥16፤13፥1፤17
፥1-21

53እንዲሁም የቂርያትይዓሪም ጐሣዎች፤
ይትራውያን፣ ፉታውያን፣ ሹማታው
ያን፣ ሚሽራውያን፣ ጾርዓውያንና ኤሽ
ታኦላውያን ከእነዚህ የመጡ ጐሣዎች
ነበሩ::
54የሰልሞን ዘሮች፤
ቤተልሔም፣ ነጦፋውያን፣ ዓጣሮት
ቤት ዮአብ፣ የመናሕታውያን እኵ
ሌታ፣ ጾርዓውያን:: 55በያቤጽ የሚኖሩ
የጸሐፍት ጐሣዎች[″] ቲርዓውያን፣
ሺምዓታውያን፣ ሡካታውያን:: እነዚህ
ከሬካብ ቤት አባት ከሐማት የመጡ
ቄናውያን ናቸው::

## የዳዊት ወንዶች ልጆች

3፥1-4 ተጓ ምብ - 2ሳሙ 3፥2-5
3፥5-8 ተጓ ምብ - 2 ሳሙ 5፥14 -16፤1ዜና 14፥4-7

3 ዳዊት በኬብሮን ሳለ የወለዳቸው
ወንዶች ልጆች እነዚህ ነበሩ፤
ከኢይዝራኤላዊቷ ከአኪናሆም የተወ
ለደው የበኵር ልጁ አምኖን፣ ሁለተ
ኛው ከቀርሜሎሳዊቷ ከአቢግያ የተ
ወለደው ዳንኤል፣
2ሦስተኛው ከጌሹር ንጉሥ ከተልማይ
ልጅ ከመዓካ የተወለደው አቤሴሎም፣
አራተኛው የአጊት ልጅ አዶንያስ፣
3አምስተኛው የአቢጣል ልጅ ሰፋጥ
ያስ፣ ስድስተኛው ከሚስቱ ከዔግላ
የተወለደው ይትረኃም::
4እነዚህ ስድስቱ የተወለዱት ዳዊት
በኬብሮን ሆኖ ሰባት ዓመት ተኩል
በገዛበት ጊዜ ነበር::
ዳዊት በኢየሩሳሌም ሠላሳ ሦስት ዓመት
ነገሠ፤ 5በዚያም የወለዳቸው ልጆች እነ
ዚህ ነበሩ፤
ሳሙስ፣[‴] ሶባብ፣ ናታን፣ ሰሎሞን፤ እነዚህ
አራት ወንዶች ልጆች ከዓሚኤል ልጅ
ከቤርሳቤህ የተወለዱ ናቸው:: 6እንዲሁም
ሌሎች ወንዶች ልጆች ነበሩት፤ ስማቸ
ውም ኢያቤሐር፣ ኤሊሱዔ፣ ኤሊፋላት፣
7ኖጋ፣ ናፌቅ፣ ያፍያ፣ 8ኤሊሳማ፣ ኤሊ
ዳሄ፣ ኤሊፋላት ይባላል፤ ባጠቃላይ ዘጠ
ኝ ነበሩ:: 9ከቁባቶቹ ከወለዳቸው ወንዶች
ልጆች ሌላ እነዚህ ሁሉ ልጆቹ ነበሩ፤
እነዚህም ትዕማር የምትባል እኅት ነበ
ረቻቸው::

## የይሁዳ ነገሥታት

10የሰሎሞን ልጅ ሮብዓም ነበረ፤
የሮብዓም ልጅ አቢያ፣
የአቢያ ልጅ አሳ፣

[0]42 የዚህ ቃል የዕብራይስጡ ትርጒም በትክክል አይታወቅም::
[″]55 ወይም፣ ሶፍራውያን
[‴]5 ዕብራይስጡ፣ ሺማ ይላል፤ ሻሙአ ከሚለው ጋር አንድ ነው::

የአሳ ልጅ ኢዮሣፍጥ፣
11የኢዮሣፍጥ ልጅ ኢዮራም፣
የኢዮራም ልጅ አካዝያስ፣
የአካዝያስ ልጅ ኢዮአስ፣
12የኢዮአስ ልጅ አሜስያስ፣
የአሜስያስ ልጅ ዓዛርያስ፣
የዓዛርያስ ልጅ ኢዮአታም፣
13የኢዮአታም ልጅ አካዝ፣
የአካዝ ልጅ ሕዝቅያስ፣
የሕዝቅያስ ልጅ ምናሴ፣
14የምናሴ ልጅ አሞጽ፣
የአሞጽ ልጅ ኢዮስያስ።
15የኢዮስያስ ወንዶች ልጆች፤
በኵሩ ዮሐናን፣
ሁለተኛ ልጁ ኢዮአቄም፣
ሦስተኛ ልጁ ሴዴቅያስ፣
አራተኛ ልጁ ሰሎም።
16የኢዮአቄም ዘሮች፤
ልጁ ኢኮንያ፣ ልጁ ሴዴቅያስ።

## ከምርኮ በኋላ የነበረው የነገሥታቱ የትውልድ ሐረግ

17የምርኮኛው የኢኮንያን ዘሮች፤
ልጁ ሰላትያል፣ 18መልኪራም፣
ፈዳያ፣ ሼናጻር፣ ይቃምያ፣ ሆሻማ፣
ነዳብያ።
19የፈዳያ ወንዶች ልጆች፤
ዘሩባቤል፣ ሰሜኢ።
የዘሩባቤል ወንዶች ልጆች፤
ሜሱላም፣ ሐናንያ፤
እኅታቸው ሰሎሚት ትባላለች።
20ሌሎችም አምስት ልጆች ነበሩ፤
እነርሱም ሐሹባ፣ ኦሄል፣ በራክያ፣
ሐሳድያ፣ ዮሻብሒሴድ።
21የሐናንያ ዘሮች፤
ፈላጥያ፣ የሻያ፤ እንዲሁም የረፋያ፣
የአርናን፣ የአብድዩና የሴኬንያ
ወንዶች ልጆች።
22የሴኬንያ ዘሮች፤
ሸማያና ወንዶች ልጆቹ፤
ሐጡስ፣ ይግአል፣ ባሪያሕ፣ ነዓርያ፣
ሻፋጥ፤ ባጠቃላይ ስድስት ነበሩ።
23የነዓርያ ወንዶች ልጆች፤
ኤልዮዔናይ፣ ሕዝቅያስ፣ ዓዝሪቃም፤
ባጠቃላይ ሦስት ነበሩ።
24የኤልዮዔናይም ወንዶች ልጆች፤
ሆዳይዋ፣ ኤልያሴብ፣ ፌልያ፣ ዓቁብ፣
ዮሐናን፣ ደላያ፣ ዓናኒ፤ ባጠቃላይ
ሰባት ናቸው።

## ሌሎቹ የይሁዳ ጐሣዎች

4 የይሁዳ ዘሮች፤
ፋሬስ፣ ኤስሮም፣ ከርሚ፣ ሆር፣ ሦባል።
2የሦባል ልጅ ራያ ኢኤትን ወለደ፤ ኢኤት
ደግሞ አሑማይንና ላሀድን ወለደ፤ እነ
ዚህም የጸርዓውያን ጐሣዎች ናቸው።
3የኤጣም ወንዶች ልጆች[የ] እነዚህ ናቸው፤
ኢይዝራኤል፣ ይሽማ፣ ይደባሽ። እኅ
ታቸው ሃጽሌልፎኒ ትባላለች። 4ፋኑ
ኤልጌዶርን ወለደ፤ ኤጽር ደግሞ ሑሻ
ምን ወለደ[ደ]። እነዚህ የኤፍራታ የበ
ኵር ልጅና የቤተልሔም አባት የሆ
ነው የሆር ዘሮች ናቸው።
5የቴቁሔ አባት አሽሑር፣ ሔላና ነዕራ
የተባሉ ሁለት ሚስቶች ነበሩት።
6ነዕራም አሑዛምን፣ ኦፌርን፣ ቴምኒን፣
አሐሽታሪን ወለደችለት፤ የነዕራ ዘሮች
እነዚህ ነበሩ።
7የሔላ ወንዶች ልጆች፤
ዴሬት፣ ይጽሐር፣ ኤትናን ናቸው።
8የቆጽ ወንዶች ልጆች ደግሞም ዓኑብ፣
ጾቤባና፣ የሃሩም ናቸው።
9ያቤጽ ከወንድሞቹ ይልቅ የተከበረ ሰው
ነበረ፤ እናቱም "በጣር የወለድሁት" ስትል
ስሙን ያቤጽ አለችው። 10ያቤጽም ወደ
እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ጮኸ፤ "አቤቱ፤
እንድትባርከኝና ግዛቴንም እንድታሰፋ
እለምንሃለሁ። እጅህ በእኔ ላይ ትሁን፤
ከሥቃይና ከጕዳትም ጠብቀኝ እግዚአብሔ
ርም የለመነውን ሰጠው።
11የሹሐ ወንድም ክሉብ ምሒርን ወለደ፤
ምሒርም ኤሽቶን ወለደ። 12ኤሽቶን
ቤትራፋንና ፋሴሐን ወለደ፤ የዒር
ናሐሽን ከተሞች የቈረቈረ እርሱ
ነው[ጀ]። እነዚህ የሬካ ሰዎች ናቸው።
13የቄኔዝ ወንዶች ልጆች፤
ጎቶንያል፣ ሠራያ።
የጎቶንያል ወንዶች ልጆች፤
ሐታት፣ መዖኖታይ[ገ]። 14መዖኖታይ ደግሞ
ዖፍራን ወለደ።
ሠራያ የኢዮአብ አባት ሲሆን፣ ኢዮአብ
ጌሐራሺምን[ጠ] ወለደ፤ የእደ ጥበብ ባለ
ሙያዎች
ስለ ነበሩ ይህ ስም ተሰጣቸው።
15የዮፎኔ ልጅ የካሌብ ወንዶች ልጆች፤
ዒሩ፣ ኤላ፣ ነዓም።
የኤላ ልጅ፤
ቄኔዝ።

3፥11 2ነገ8፥16-25፤10፥14፤11፥1-12፤12፥21፤2ዜና21፥1፤22፥1-10፤11-24፡27
3፥13 2ነገ16፥1-20፤18፥1-20፥21፤21፥1-18፤ 2ዜና29፥1፤33፥1፤ኢሳ1፥1፤ኤር26፥19፤ሆሴ1፥1፤ሚክ1፥1
3፥14 2ነገ21፥19-26፤22፥1፤2ዜና33፥21፤34፥1፤ኤር1፥2፤3፥6፤25፥3፤ሶፎ1፥1
3፥15 2ነገ23፥31፡34፤ኤር37፥1
3፥16 2ነገ24፥6፡ 8፡18
3፥17 ዕዝ32
3፥18 ዕዝ1፥8፤ 5፥14፤ኤር 22፥30
3፥19 ዕዝ2፥2፤3፥2፤5፥2፤ነህ7፥7
3፥22 ዕዝ8፥2-3
4፥1 ዘፍ29፥35፤ዘኍ26፥21፤1ዜና 2፥3
4፥4 ሩት 1፥19፤1ዜና2፥50
4፥5 1ዜና2፥24
4፥13 ኢሱ15፥17

[የ]3 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ቅጆች (እንዲሁም ቩልጌት ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡን ግን፣ *አባት* ይላል
[ደ]4 ቃል በቃል ሲተረጐም *አባት ሆነ* ማለት ነው፤ ይህም ምናልባት፣ *አባት* ማለት፣ የጐሣው፣ *እንዝላት፣ እንጅላት* ወይም፣ *መሠረት* መሆኑን የሚያመለክት ነው
[ጀ]12 ወይም፣ *የዒር ናሐሽ አባት ነው*
[ገ]13 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞችና የቩልጌት ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ መዖኖታይ የሚለውን አይጨምርም።
[ጠ]14 *ጌሐራሺም* ማለት *የእደ ጥበብ ሸለቆ* ማለት ነው።

16የይሃሌልኤል ወንዶች ልጆች፤
ዚፍ፣ ዚፋ፣ ቲርያ፣ አሣርኤል።
17የዕዝራ ወንዶች ልጆች፤
ዬቴር፣ ሜሬድ፣ ዔፌር፣ ያሎን።
ከሜሬድ ሚስቶች አንዲቱ ማርያ
ምን፣ ሽማይንና የኤሽትምዓን አባት
ይሽባን ወለደች። 18አይሁዳዊት ሚስ
ቱም የጌዶርን አባት ዮሬድን፣ የሦ
ኮን አባት ሔቤርን፣ የዛኖዋን አባት
ይቁቲኤልን ወለደች፤ እነዚህም ሜሬድ
ያገባት የፈርዖን ልጅ የቢትያ ልጆች
ናቸው።
19የሆዲያ ሚስት የነሐም እኅት ወን
ዶች ልጆች፤
የገርሚው የቅዒላ አባት፣ ማዕካታ
ዊው ኤሽትሞዓ።
20የሺሞን ወንዶች ልጆች፤
አምኖን፣ ሪና፣ ቤንሐናን፣ ቲሎን።
የይሽዒ ዘሮች፤ ዞሔትና ቤንዞሔት።
21የይሁዳ ልጅ የሴሎም ወንዶች ልጆች፤
የሌካ አባት ዔር፣ የመሪሳና በቤት
አሽቤዓ የበፍታ ጨርቅ ሠሪ የሆኑት
ጐሣዎች አባት ለዓዳ፣ 22ዮቂም፣
የኮዜባ ሰዎች፣ ኢዮአስ፣ ሞዓብን
የገዛ ሣራፍና ያሹቢሌሔም። ታሪካቸ
ውም ጥንታዊነት ያለው ነው። 23ሰዎቹ
በነጣዒምና በጋዴራ የሚቀመጡ
ሸክላ ሠሪዎች ነበሩ፤ በዚያ በመቀ
ምጥ እየኖሩ ለንጉሡ ሸክላ ይሠሩ
ለት ነበር።

## ስምዖን

4፥28-33 ተጓ – ምብ ኢሱ 19፥2-10

24የስምዖን ዘሮች፤
ነሙኤል፣ ያሚን፣ ያሪን፣ ዛራ፣ ሳኡል፤
25ሰሎም የሳኡል ልጅ ነው፤ መብሳም
የሰሎም ልጅ ነው፤
ማስማዕ ደግሞ የመብሳም ልጅ ነው።
26የማስማዕ ዘሮች
ልጁ ሃሙኤል፣ ልጁ ዘኩር፣ ልጁ
ሰሜኢ።
27ሰሜኢ ዐሥራ ስድስት ወንዶችና ስድስት
ሴቶች ልጆች ነበሩት፤ ወንድሞቹ ግን ብዙ
ልጆች አልነበሯቸውም፤ ስለዚህ ጐሣቸው
በሙሉ እንደ ይሁዳ ሕዝብ ብዙ አልነ
በረም። 28የኖሩባቸውም ቦታዎች እነ ዚህ
ናቸው፤ ቤርሳቤህ፣ ሞላደ፣ ሐጻርሹዓል፣ 29ቢ
ልሃ፣ ዔጼም፣ ቶላድ፣ 30ቤቱኤል፣ ሔርማ፣ ጺቅ
ላግ፣ 31ቤትማርካቦት፣ ሐጻርሱሲም፣ ቤት
ቢሪ፣ ሸዓራይም፤ እስከ ዳዊት ዘመነ መን
ግሥት ድረስ የኖሩት በእነዚህ ከተሞች
ነው። 32በአካባቢያቸው የሚገኙት መንደ
ሮች ደግሞ ኤጣም፣ ዓይን፣ ሬሞን፣ ቶኬን፣
ዓሻን የተባሉ አምስት ከተሞች ናቸው፤
33በእነዚህም ከተሞች ዙሪያ እስከ በኣል
የሚዘልቁ መንደሮች ነበሩ፤ መኖሪ ያቸው
በዚሁ ሲሆን፣ የትውልድ መዝገ ብም
አላቸው።
34ሞሾባብ፣ የምሌክ፣ የአሜስያስ ልጅ ኢዮ
ስያስ፣ 35ኢዮኤል፣ የዮሺብያ ልጅ፣
የሠራያ ልጅ፣ የዓሢኤል ልጅ ኢዩ
36እንዲሁም ኤልዩዔናይ፣ ያዕቆባ፣
የሾሐያ፣ ዓሣያ፣ ዓዲዔል፣ ዩሲምኤል፣
በናያስ፣ 37የሺፊ ልጅ ዚዛ፣ የአሎን
ልጅ፣ የይዳያ ልጅ፣ የሺምሪ ልጅ፣
የሸማያ ልጅ፤
38እነዚህ ስማቸው ከላይ የተዘረዘረው
ሰዎች የየጐሣቸው መሪዎች ነበሩ፤ የየቤተ
ሰባቸውም ብዛት እጅግ በጣም እየጨመረ
ሄደ፤ 39እነርሱም ለከብቶቻቸው ግጦሽ
ፍለጋ ከሸለቆው በስተምሥራቅ እስካለው
እስከ ጌደር መግቢያ ድረስ ዘልቀው
ሄዱ። 40በዚያም ለምለምና ያማረ የግጦሽ
ቦታ አገኙ፤ ምድሪቱም ሰፊ፣ ሰላምና
ጸጥታ የሰፈነባት ነበረች። በቀድሞ ዘመን
በዚህ ምድር ይኖሩ የነበሩት አንዳንድ
የካም ዘሮች ናቸው።
41እነዚህ ስማቸው ከላይ የተዘረዘረው
ወደዚህ ቦታ የመጡት በይሁዳ ንጉሥ
በሕዝቅያስ ዘመን ነበረ፤ እነርሱም በድን
ኳኖቻቸው ውስጥ በነበሩት በካም ወገ
ኖችና በምዑናውያን ላይ አደጋ በመጣል
ፈጽመው አጠፉአቸው[ጨ]፤ ይህም እስከ
ዛሬ ድረስ በግልጽ ይታያል።
ለመንጎቻቸው በቂ የግጦሽ ቦታ
ስላገኙም፣ በዚያ መኖር ጀመሩ። 42ከእነዚ
ሁ አምስት መቶ የሚ ሆኑ የስምዖን
ወገኖች በይሽዒ ልጆች በፈላጥያ፣ በነዓ
ርያ፣ በረፋያና በዑዝኤል ተመርተው
የሴይርን ኰረብታማ አገር ወረሩ።
43አምልጠው የቀሩትን አማሌቃ ውያን
ፈጅተው እስከ ዛሬ በዚያው ይኖራሉ።

## ሮቤል

5 የእስራኤል የበኵር ልጅ የሮቤል ልጆች፤
ሮቤል የበኵር ልጅ ቢሆንም፣ የአባቱን
መኝታ ስላረከሰ፣ የብኵርና መብቱ ለእስ
ራኤል ልጅ ለዮሴፍ ልጆች ተሰጥቶ
አል። ከዚህም የተነሣ ትውልዱ የበኵርነ
ቱን ተራ ይዞ ሊቈጠር አልቻለም። 2ይሁዳ
ከወንድሞቹ ይልቅ ብርቱ ነበረ፤ ገዥ የወ
ጣው ከእርሱ ቢሆንም፣ የብኵርና መብቱ
የተላለፈው ለዮሴፍ ነበረ። 3የእስራኤል
የበኵር ልጅ የሮቤል ወንዶች ልጆች፤
ሄኖኅ፣ ፋሉሶ፣ አስሮን፣ ከርሚ።

[ጨ]41 የዕብራይስጡ ቃል አንድን ሰው ወይም ነገር ሙሉ
በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠትን ያመለክታል።

4፥17 ዘፀ15፥20
4፥18 ኢሱ15፥34
4፥19 ዘዳ3፥14፤
ኢሱ15፥44
4፥21 ዘፍ38፥5
4፥24 ዘፍ29፥33፤
ዘኍ 26፥12
4፥28 ዘፍ1፥14፤
ኢሱ 15፥26
4፥29 ኢሱ15፥29
4፥30 ዘኍ14፥45፤
ኢሱ15፥31
4፥31 ኢሱ15፥36
4፥32 ዘኍ 34፥11፤
ኢሱ15፥42
4፥39 ኢሱ15፥58
4፥40 መሳ18፥7-10
4፥41
2ዜና20፥1፤ 26፥7
4፥42 ዘፍ14፥6
4፥43 ዘፍ14፥7፤
አስ3፥1፤9፥16
5፥1
ዘፍ29፥32፤35፥22፤
48፥5፡16፤49፥4፡26፤1
ዜና 26፥10
5፥2 ዘፍ25፥31፤
49፥10፡12፤1ሳሙ9፥1
6፤12፥12፤
2ሳሙ6፥21፤
1ዜና11፥2፤
2ዜና7፥18፤ማቴ 2፥6
5፥3 ዘፍ29፥32፤
46፥9፤ዘፀ6፥14፤
ዘኍ26፥5-11

[4]የኢዩኤል ዘሮች
ልጁ ሽማያ፣ ልጁ ጎግ፣ ልጁ
ሰሜኢ፣ [5]ልጁ ሚካ፣
ልጁ ራያ ፣ ልጁ ቢኤል፣
[6]የአሦር ንጉሥ ቴልጌልቴልፌልሶር
ማርኮ የወሰደው ልጁ ብኤራ።
[7]የቤተ ሰቡ የዘር ትውልድ በየጐሣ በየጐሣው
ሲቈጠር እንደሚከተለው ነው፤
የጐሣ አለቃ የሆነው ኢዮኤል፣ ዘካር
ያስ፣ [8]የኢዮኤል ልጅ፣ የሽማዕ ልጅ፣
የያዛዝ ልጅ ቤላ፣ እነዚህ ከአሮዔር
እስከ ናባውና እስከ በኣልሜዎን ድረስ
በሚገኘው ምድር ላይ ሰፈሩ። [9]ከብ
ቶቻቸው በገለዓድ ምድር በዝተው ስለ
ነበር በምሥራቅ በኩል ወደ ኤፍራጥስ
ወንዝ እስከ ምድረ በዳው ዳርቻ ድረስ
የሚገኘውን ምድር ያዙ።
[10]በሳኦልም ዘመነ መንግሥት በእ
ጃቸው ተመትተው ድል ከተደረጉት
አጋራውያን ጋር ተዋጉ፤ በመላው የገ
ለዓድ ምሥራቃዊ ክፍል የሚገኙትን
መኖሪያዎቻቸውን ያዙ።

## ጋድ

[11]የጋድ ነገድ ደግሞ ከእነርሱ ቀጥሎ
እስከ ሰልካ ድረስ በሚገኘው በባሳን
ምድር ኖሩ፤
[12]አለቃው ኢዮኤል፣ ሁለተኛው ሳፋም
ከዚያም ያናይና ሰፋጥ ሆነው በባሳን
ተቀመጡ። [13]ቤተ ዘመዶቻቸውም
በየቤተ ሰቡ እነዚህ ነበሩ፤ ሚካ
ኤል፣ ሜሱ ላም፣ ሳባ፣ ዮራይ፣ ያካን፣
ዙኤ፣ ኦቤድ፤ ባጠቃላይ ሰባት ነበሩ።
[14]እነዚህ ደግሞ የቡዝ ልጅ፣ የዬዳይ
ልጅ፣ የኢዬሳይ ልጅ፣ የሚካኤል
ልጅ፣ የገለዓድ ልጅ፣ የኢዳይ ልጅ፣
የዑሪ ልጅ፣ የሑሪ ልጅ፣ የአ ቢካኢ
ል ልጆች ናቸው።
[15]የቤተ ሰባቸውም አለቃ የጉኒ ልጅ፣
የአብዲኤል ልጅ አሒ ነበረ።
[16]ጋዳውያንም በገለዓድ፣ በባሳንና እስከ
ዳርቻዋ በሚገኙት መንደሮች እንዲ
ሁም በሳሮን በሚገኙ የግጦሽ ስፍራ
ዎች ሁሉና ከዚያም ወዲያ አልፈው
ተቀመጡ።
[17]እነዚህ ሁሉ በትውልድ መዝገብ የሰ
ፈሩት በይሁዳ ንጉሥ በኢዮአታምና በእስ
ራኤል ንጉሥ በኢዮርብዓም ዘመነ መንግ
ሥት ነው።
[18]የሮቤል፣ የጋድና የምናሴ ነገድ እኩ
ሌታ አርባ አራት ሺህ ሰባት መቶ ሥልሳ
ብቁ የጦር ሰዎች ነበሩአቸው። እነርሱም
ጋሻ መያዝ፣ ሰይፍ መምዘዝና ቀስት

5፥6 ቍ26፤
2ነገ 15፥19፤
16፥10፤2ዜና28፥20
5፥7 ኢሱ13፥15-23
5፥8 ዘኍ32፥3፡34፤
ኢሱ13፥17፤ መሳ 1
1፥26
5፥9 ዘፍ2፥14፤
ዘኍ 32፥26
5፥10
ቍ22፤1ዜና 27፥31
5፥11 ዘፍ30፥11፤
ዘኍ1፥25፤
ዘዳ3፥10፤
ኢሱ13፥24-28
5፥17
2ነገ4፥23፤ 15፥32
5፥18 ዘኍ1፥3
5፥19 ዘፍ25፥15
5፥20
ነገ8፥44፤2ዜና6፥34፤1
3፥14፤14፥11፤
መዝ20፥7-9፤22፥5፤
26፥1፤ 37፥40፤46፥5
54፥4፤107፥6፤
ኢሳ26፥3፤ዳን6፥23
5፥22 ቍ10፤ ዘዳ
20፥4፤2ነገ15፥29፤
2ዜና32፥8
5፥23 ዘዳ3፥8፡9፤
4፥8፤1ዜና7፥14
5፥25 ዘፀ34፥15፤
ዘሌ18፥3፤ዘዳ32፥15-
18፤1ዜና9፥1፤10፥13፤
2ዜና፤12፥2፤26፥16፤28፥
19፤29፥6፤30፥7፤36፥14
5፥26
ቍ6፤2ነገ15፥19፡29፤
17፥6፤ኢሳ37፥7
6፥1
ዘፍ29፥34፤
ዘኍ3፥17
6፥2 ዘፀ6፥18
6፥3
ዘፀ6፥23፤15፥20፤
ዘሌ10፥1-20
6፥4 ዕዝ7፥5

መሳብ የሚችሉ ጠንካራና በውጊያ የሠ
ለጠኑ ናቸው። [19]እነዚህም በአጋራውያን፣
በኢጡር፣ በናፌስ፣ በናዳብ ላይ ዘመቱ።
[20]በጦርነቱም ላይ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ
ው ስለ ነበር፣ በውጊያው ረዳቸው፤ አጋራ
ውያንንና የጦር አጋሮቻቸውን ሁሉ አሳ
ልፎ ሰጣቸው፤ ስለ ታመኑበትም ጸሎታ
ቸውን ሰማ። [21]የአጋራውያንንም እንስ
ሶች ማረኩ፤ እነዚህም አምሳ ሺህ ግመ
ሎች፣ ሁለት መቶ አምሳ ሺህ በጎችና
ሁለት ሺህ አህዮች ነበሩ። እንዲሁም
አንድ መቶ ሺህ ሰው ማረኩ። [22]ውጊያው
የእግዚአብሔር ስለ ነበር ሌሎችም ብዙ
ሰዎች ተገደሉ። እስከ ምርኮ ጊዜ ድረስ
ምድሪቱ በእጃቸው ነበረች።

## እኩሌታው የምናሴ ነገድ

[23]የምናሴ ነገድ እኩሌታ ሕዝብ ቍጥር
ብዙ ነበረ፤ እነርሱም ከባሳን ጀምሮ እስከ
በኣልአርሞንዔም ድረስ ባለው ምድር ሰፈሩ፤
ይህም እስከ ሳኔር አርሞንዔም ተራራ ድረስ
ማለት ነው።
[24]የየቤተ ሰቡም አለቆች እነዚህ ነበሩ፤
ዔፌር፤ ይሽዒ፣ ኤሊኤል፣ ዓዝርኤል፣
ኤርምያ፣ ሆዳይዋ፣ ኢየድኤ፤ እነዚህ
ጀግና ተዋጊዎች፣ የታወቁ ሰዎችና የየ
ቤተ ሰባቸው አለቆች ነበሩ። [25]ይሁን
እንጂ ለአባቶቻቸው አምላክ ታማኞች
አልሆኑም፤ እግዚአብሔር ከፊታቸው ያጠፋ
ቸውን የምድሪቱን አሕዛብ አማልክት በማ
ምለክ አመነዘሩ። [26]ስለዚህ የእስራኤል
አምላክ የአሦርን ንጉሥ የፎሐን መንፈስ
ይኸውም የቴልጌልቴልፌልሶርን መንፈስ
አነሣሥቶ የሮቤልን፣ የጋድንና፣ የምናሴን
ነገድ እኩሌታ ማርኮ እንዲወስድ አደረገ።
እነዚህንም ወደ ኣላሔ፣ ወደ አቦር፣ ወደ
ሃራና ወደ ጎዛን ወንዝ ዳርቻ አፈለሳቸው፤
እነርሱም እስከ ዛሬ ድረስ በዚያ ይገኛሉ።

## ሌዊ

6 የሌዊ ወንዶች ልጆች፤
ጌድሶን፣ ቀዓት፣ ሜራሪ።
[2]የቀዓት ወንዶች ልጆች፤ እንበረም፣
ይስዓር፣ ኬብሮን፣ ዑዝኤል።
[3]የእምበረም ልጆች፤
አሮን፣ ሙሴ፣ ማርያም።
የአሮን ወንዶች ልጆች፤
ናዳብ፣ አብዮድ፣ አልዓዛር፣
ኢታምር።
[4]አልዓዛር ፊንሐስን ወለደ፤
ፊንሐስ አቢሱን ወለደ፤
[5]አቢሱ ቡቂን ወለደ፤
ቡቂ ኦዚን ወለደ፤

6ኦዚ ዘራእያን ወለደ፤
ዘራእያ መራዮትን ወለደ፤
7መራዮት አማርያን ወለደ፤
አማርያ አኪጦብን ወለደ፤
8አኪጦብ ሳዶቅን ወለደ፤
9ሳዶቅ አኪማአስን ወለደ፤
አኪማአስ ዓዛርያስን ወለደ፤
ዓዛርያስ ዮሐናን ወለደ፤
10ዮሐናን ዓዛርያስን ወለደ፤
እርሱም ሰሎሞን በኢየሩሳሌም ባሠራው
ቤተ መቅደስ በክህነት ያገለገለ ነበር፤
11ዓዛርያስ አማርያን ወለደ፤
አማርያም አኪጦብን ወለደ፤
12አኪጦብ ሳዶቅን ወለደ፤
ሳዶቅ ሰሎምን ወለደ፤
13ሰሎም ኬልቅያስን ወለደ፤
ኬልቅያስ ዓዛርያስን ወለደ፤
14ዓዛርያስ ሠራያን ወለደ፤
ሠራያ ኢዮሴዴቅን ወለደ።
15*እግዚአብሔር* የይሁዳና የኢየሩሳሌም
ሕዝብ በናቡከደነፆር እጅ ተማርከው
እንዲወሰዱ ባደረገ ጊዜ ኢዮሴዴቅም
አብሮ ተማርኮ ሄደ።
16የሌዊ ወንዶች ልጆች፤
ጌድሶን፣ ቀዓት፣ ሜራሪ።
17የጌድሶን ወንዶች ልጆች፤
ሎቤኒ፣ ሰሜኢ።
18የቀሃት ወንዶች ልጆች፤
እምበረም፣ ይስዓር፣ ኬብሮን፣
ዑዝኤል።
19የሜራሪ ወንዶች ልጆች፤
ሞሖሊ፣ ሙሲ።
በየአባቶቻቸው ቤተ ሰብ የተቈጠሩት
የሌዊ ጐሣዎች የሚከተሉት ናቸው፤
20ከጌርሶን፤
ልጁ ሎቤኒ፣ ልጁ ኢኤት፣
ልጁ ዛማት፣ 21ልጁ ዮአክ፣
ልጁ አዶ፣ ልጁ ዛራ፣ ልጁ ያትራ
ይ።
22የቀዓት ዘሮች፤
ልጁ አሚናዳብ፣ ልጁ ቆሬ፣ ልጁ
አሴር፣ 23ልጁ ሕልቃና፣ ልጁ አቢ
ሳፍ፣ ልጁ አሴር፣ 24ልጁ ኢኢት፣
ልጁ ኡርኤል፣ ልጁ ዖዝያ፣ ልጁ
ሳውል።
25የሕልቃና ዘሮች፤
አማሢ፣ አኪሞት።
26ልጁ ሕልቃና፣[ጰ] ልጁ ሱፊ፣ ልጁ
ናሐት፣
27ልጁ ኤልያብ፣ ልጁ ይሮሐም፣
ልጁ ሕልቃና፣ ልጁ ሳሙኤል[ጰ]።
28የሳሙኤል ወንዶች ልጆች፤
የበኵር ልጁ ኢዮኤል[θ]፣

6፥8 2ሳሙ8፥17፤ 1ዜና12፥28፤ዕዝ7፥2
6፥10 1ነገ4፥2
6፥13 2ነገ22፥1-20፤2ዜና34፥9፤35፥8
6፥14 2ነገ25፥18፤ዕዝ2፥2
6፥15 ነህ12፥1፤ ሐጌ1፥1፥14፤ 2፥2፥4፤ዘካ6፥11
6፥16 ዘፍ29፥34፤ ዘኍ3፥17-20፤26፥57
6፥17 ዘፀ6፥17
6፥18 ዘፀ6፥18
6፥19 ዘፍ46፥11፤ ዘፀ6፥19፤1ዜና23፥21፤ 24፥26
6፥22 ዘፀ6፥24
6፥24 1ዜና15፥5
6፥27 1ሳሙ1፥1፥20
6፥28 ቍ33፤1ሳሙ8፥2
6፥31 1ዜና9፥33፤15፥19፤25፥1፤2ዜና29፥25-26፤ዕዝ3፥10፤ነህ 12፥45፤መዝ68፥25
6፥33 ቍ28፤ 1ነገ 4፥31፤1ዜና15፥17፤25፥1
6፥34 1ሳሙ1፥1
6፥37 ዘፀ6፥24
6፥38 ዘፀ6፥21
6፥39 1ዜና15፥17፤ 25፥1፥9፤2ዜና29፥13፤ ነህ11፥17
6፥44 1ዜና15፥17

ሁለተኛው ልጁ አብያ።
29የሜራሪ ዘሮች፤
ሞሖሊ፣ ልጁ ሎቤኒ፣ ልጁ ሰሜኢ፣
ልጁ ዖዛ፣
30ልጁ ሳምዓ፣ ልጁ ሐግያ፣ ልጁ ዓሣያ።

## የቤተ መቅደሱ መዘምራን

6፥54-80 ተጓ ምብ - ኢሱ21፥4-39

31ታቦቱ ከገባ በኋላ፣ ዳዊት የመዘምራን
አለቃ አድርጎ *በእግዚአብሔር* ቤት የሾማ
ቸው ሰዎች እነዚህ ናቸው፤ 32እነርሱም
ሰሎሞን *የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስ
በኢየሩሳሌም እስኪሠራ ድረስ፣ በማደሪ
ያው ድንኳን በመገናኛው ድንኳን ፊት
ሆነው እየዘመሩ ያገለግሉ ነበር፤ አገልግ
ሎታቸውንም የሚያከናውኑት በወጣላቸው
ደንብ መሠረት ነው።
33ከወንዶች ልጆቻቸው ጋር ሆነው ያገለ
ገሉ ሰዎች እነዚህ ናቸው፤
ከቀዓታውያን ልጆች፤ ዘማሪው ኤማን፣
የኢዮኤል ልጅ፣ የሳሙኤል ልጅ፣
34የሕልቃና ልጅ፣ የይሮሐም ልጅ፣
የኤሊኤል ልጅ፣ የቶዋ ልጅ
35የሱፍ ልጅ፣ የሕልቃና ልጅ፣ የመሐት
ልጅ፣ የአማሢ ልጅ፣
36የሕልቃና ልጅ፣ የኢዮኤል ልጅ፣ የዓ
ዛርያስ ልጅ፣ የሶፎንያስ ልጅ፣
37የታሐት ልጅ፣ የአሴር ልጅ፣ የአብያ
ሳፍ ልጅ፣ የቆሬ ልጅ፣
38የይስዓር ልጅ፣ የቀዓት ልጅ፣ የሌዊ
ልጅ፣ የእስራኤል ልጅ።
39እንዲሁም የሔማን ወንድም አሳፍ
በስተቀኙ ሆኖ ያገለግል ነበር፤
አሳፍ የበራክያ ልጅ፣ የሳምዓ ልጅ፣
40የሚካኤል ልጅ፣ የበዓሤያ ልጅ፣
የመልክያ ልጅ፣ 41የኤትኒ ልጅ፣
የዛራ ልጅ፣ የዓዳያ ልጅ፣
42የኤታን ልጅ፣ የዛማት ልጅ፣
የሰሜኢ ልጅ፣ 43የኢኤት ልጅ፣
የጌድሶን ልጅ፣ የሌዊ ልጅ፤
44በስተግራቸው በኩል አብረዋቸው
ያሉት የሜራሪ ልጆች፤ የቂሳ ልጅ
ኤታን፣ የአብዲ ልጅ፣ የማሎክ
ልጅ፣ 45የሐሸብያ ልጅ፣ የአሜስያስ

[ጰ]26 አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕምና የሱርስቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *ኪሞትና 26 ሕልቃና፤ የሕልቃና ወንዶች ልጆች፤*
[ጰ]27 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች (እንዲሁም 1ሳሙ 19፥20 እና 1 ዜና 6፥33፥34 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራ ይስጡ ግን፣ ***ልጁ ሳሙኤል*** የሚለውን ሐረግ አይጨምርም
[θ]28 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞችና ሱርስቱ (እንዲሁም 1 ሳሙ8፥2 እና 1 ዜና 6፥33 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራ ይስጡ ግን፣ ***ኢዮኤል*** የሚለውን ስም አይጨምርም።

ልጅ፣ የኬልቅያስ ልጅ፣ [46]የአማሲ
ልጅ፣ የባኒ ልጅ፣ የሴሜር ልጅ፣
[47]የሞሖሊ ልጅ፣ የሙሲ ልጅ የሜራሪ
ልጅ፣ የሌዊ ልጅ፣
[48]ሌዋውያን ወንድሞቻቸው ግን የእግዚ
አብሔርን ቤት የማደሪያ ድንኳን ተግባር
እንዲያከናውኑ ተመድበው ነበር። [49]የእግዚ
አብሔር ባሪያ ሙሴ ባዘዘው መሠረት ስለ
እስራኤል ማስተስረያ በቅድስተ ቅዱሳኑ
ውስጥ የሚከናወነውን ተግባር ሁሉ፣ በመ
ሠዊያው ላይ የሚቃጠል መሥዋዕትና በዕ
ጣኑ መሠዊያ ላይ የሚቀርበውን መሥዋዕት
የሚያቀርቡት ግን አሮንና ዘሮቹ ብቻ
ነበሩ።
[50]የአሮን ዘሮች እነዚሁ ነበሩ፤
ልጁ አልዓዛር፣ ልጁ ፊንሐስ፣ ልጁ
አቢሱ [51]ልጁ ቡቂ፣ ልጁ ኦዚ፣ ልጁ
ዘራእያ፣
[52]ልጁ መራዮት፣ ልጁ አማርያ፣ልጁ አኪ
ጦብ፣ [53]ልጁ ሳዶቅ፣ ልጁ አኪማአስ።
[54]መኖሪያዎቻቸው እንዲሆኑ የተመደቡ
ላቸው ቦታዎች እነዚህ ናቸው፤ የመጀመሪ
ያው ዕጣ የእነርሱ ስለ ሆነ፣ ከቀዓት ጐሣ
ለሆኑት ለአሮን ዘሮች የተመደቡላቸው
መኖሪያዎች እነዚህ ነበሩ።
[55]ለእነርሱም በይሁዳ ምድር የም
ትገኘው ኬብሮንና በዙሪያዋ ያለው
የግጦሽ ቦታ ተሰጠ፤ [56]በኬብሮን
ዙሪያ የሚገኙት የዕርሻ ቦታዎችና
መንደሮች ግን ለዮፎኒ ልጅ ለካሌብ
ተሰጡ።
[57]ለአሮን ዘሮች የመማፀኛ ከተሞች
የሆኑትን ኬብሮንን፣ ልብናን፣ የቲ
ርን፣ ኤሽትሞዓን፣ [58]ሖሎንን፣ ዳቤ
ርን፣ [59]ዓሳንን፣ ዮታን[ፊ]፣ ቤትሳሚስን
ከነመሰማሪያዎቻቸው ሰጡ። [60]ከብ
ንያም ነገድ ድርሻ ላይ ገባዮንን፣[ፐ]
ጌባን፣ ጋሌማን፣ ዓናቶትን ከነመሳሪያ
ዎቻቸው ሰጡ። ለቀዓት ዘሮች የተከ
ፋፈሉት እነዚህ ከተሞች ባጠቃላይ
ዐሥራ ሦስት ናቸው።
[61]ለቀሩት የቀዓት ዘሮች ደግሞ ከም
ናሴ ነገድ እኩሌታ ድርሻ ዐሥር ከተሞች
ተሰጧቸው።
[62]ለጌድሶን ነገድ በየጐሣቸው ከይሳኮር፣
ከአሴር፣ ከንፍታሌምና በባሳን ከሚገኘው
ከምናሴ ነገድ ድርሻ ላይ ዐሥራ ሦስት
ከተሞች ተመደቡላቸው።
[63]ለሜራሪ ዘሮች በየጐሣቸው ከሮቤል፣
ከጋድና ከዛብሎን ድርሻ ላይ ዐሥራ ሁለት
ከተሞች ተመደቡላቸው።
[64]እስራኤላውያንም ከተሞቹን በዚሁ

6፥48 1ዜና23፥32
6፥49 ዘፀ27፥1-8፤30፥7፤2ዜና26፥18
6፥53 2ሳሙ8፥17
6፥54 ዘኍ31፥10
6፥56 ኢሱ14፥13፤15፥13
6፥57 ዘኍ33፥20፤ ኢሱ15፥48
6፥58 ኢሱ10፥3
6፥59 ኢሱ15፥42
6፥60 ኤር1፥1
6፥64 ዘኍ35፥1-8
6፥67 ኢሱ10፥33
6፥68 ኢሱ10፥10፤ 1ነገ4፥12
6፥69 ኢሱ10፥12፤ ኢሱ19፥45
6፥71 ኢሱ20፥8፤1ዜና23፥7
6፥72 ኢሱ19፥12
6፥74 ኢሱ19፥28
6፥75 ዘኍ13፥21፤ ኢሱ19፥34
6፥76 ዘኍ32፥37፤ ኢሱ 19፥28
6፥78 ኢሱ20፥8
6፥79 ዘዳ2፥26
6፥80 ዘፍ32፥2፤ ኢሱ20፥8
6፥81 ዘኍ21፥32፤ 2ዜና11፥14

ሁኔታ መድበው ከነመሰማሪያዎቻቸው ለሌ
ዋውያኑ ሰጧቸው። [65]ቀደም ብለው የተጠ
ቀሱትንም ከተሞች ከይሁዳ፣ ከስምዖንና
ከብንያም ነገድ ላይ ወስደው መደቡላ
ቸው።
[66]ለአንዳንድ የቀዓት ጐሣዎችም ከኤፍ
ሬም ነገድ ድርሻ ላይ የሚኖሩበት ቦታ
ተሰጣቸው።
[67]በኰረብታማው በኤፍሬም ምድር
የሚገኙትን የመማፀኛ ከተሞች ሴኬ
ምን፣ ጌዝርን፣ [68]ዮቅምዓምን፣ ቤትሖ
ሮን፣ [69]ኤሎንንና ጋትሪሞን ከነመሰ
ማሪያዎቻቸው ሰጧቸው።
[70]እንዲሁም እስራኤላውያን ከምናሴ
ነገድ እኩሌታ ድርሻ ላይ ዓኔርና ቢል
ዓም የተባሉትን ከተሞች ከነመሰ
ማሪያዎቻቸው ወስደው ለቀሩት
የቀዓት ጐሣዎች ሰጧቸው።
[71]ጌድሶናውያን ከዚህ የሚከተሉትን
ከተሞች ወሰዱ፤
ከምናሴ ነገድ እኩሌታ፣
በባሳን የሚገኘውን ጎላንና አስታሮትን
ከነመሰማሪያዎቻቸው ወሰዱ፤
[72]ከይሳኮርም ነገድ፣
ቃዴስን፣ ዳብራትን [73]ራሞትንና ዓኔ
ምናን ከነመሰማሪያዎቻቸው ወሰዱ፤
[74]ከአሴር ነገድ
መዓሳልን፣ ዓብዶን፣ [75]ሑቆቅንና፣ ረአ
ብን ከነመሰማሪያዎቻቸው ወሰዱ፤
[76]ከንፍታሌም ነገድ
በገሊላ የሚገኘውን ቃዴስን፣
ሐሞንንና፣ ቂርያታይምን ከነመሰማሪ
ያዎቻቸው ወሰዱ።
[77]ከሌዋውያን የቀሩት የሜራሪ ጐሣዎች
ደግሞ ከዚህ የሚከተለውን ወሰዱ፤
ከዛብሎን ነገድ ዮቅኒዓምን፣ ቀርታ
ህን፣[ሀ] ሬሞንና፣ታቦርን ከነመሰማሪያ
ዎቻቸው ወሰዱ።
[78]ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ ኪኢያሪኮ በስተ
ምሥራቅ ከሚገኘው ከሮቤል ነገድ፣
በምድረ በዳ የሚገኘውን ቦሶርን፣ ያሳን፣
[79]ቅዴሞትንና ሜፍዓትን ከነመሰማሪ
ያዎቻቸው ወሰዱ፤
[80]ከጋድ ነገድ በገለዓድ የምትገኘውን ሬማ
ትን፣መሃናይምን፣[81]ሐሴቦንና ኢያዜርን
ከነመሰማሪያዎቻቸው ወሰዱ።

[ፊ]59 የሱርስቱ ቅጅ (እንዲሁም የሰብዓ ሊቃናትና ኢሱ 21፥16) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ *ዮታን* የሚለውን ስም አይጨምርም።
[ፐ]60 ኢሱ 21፥17 ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን *ገባዮን* የሚለውን ስም አይጨምርም።
[ሀ]77 የሰብዓ ሊቃናት ትርጕምንና ኢሱ 21፥34 ይመ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ *ዮቅኒዓምን፣ ቀርታህን* የሚለውን አይጨምርም።

### ይሳኮር

7 የይሳኮር ወንዶች ልጆች፤
ቶላ፣ ፉዋ፣ ያሱብ፣ ሺምሮን፤ ባጠ
ቃላይ አራት ናቸው።
2የቶላ ወንዶች ልጆች፤
ኦዚ፣ ረፋያ፣ ይሪኤል፣ የሕማይ፣
ይብሣም፣ ሽሙኤል፤ እነዚህ የየቤተ
ሰባቸው አለቆች ናቸው፤ በዳዊት
ዘመነ መንግሥት ከቶላ ዘሮች፣
በየትውልድ ሐረጋቸው የተቈጠሩት
የቶላ ዘሮች ብርቱ ተዋጊዎች ነበሩ፤
ቍጥራቸውም ሃያ ሁለት ሺህ ስድ
ስት መቶ ነበረ።
3የኦዚ ወንድ ልጅ፤
ይዝረሕያ።
የይዝረሕያ ወንዶች ልጆች፤
ሚካኤል፣ አብድዩ፣ ኢዩኤል፣ ይሺያ፤
አምስቱም አለቆች ነበሩ። 4ብዙ ሚስ
ቶችና ልጆች ስለ ነበሩአቸው፣ ከቤተ
ሰባቸው የትውልድ ሐረግ ለውጊያ
ብቁ የሆኑ ሠላሳ ስድስት ሺህ ሰዎች
ነበሩአቸው።
5ከይሳኮር ጐሣዎች ሁሉ የተመዘገቡት
ተዋጊዎች የቤተ ሰቦቹ ትውልድ ቍጥር
ባጠቃላይ ሰማንያ ሰባት ሺህ ነበሩ።

### ብንያም

6ሦስቱ የብንያም ወንዶች ልጆች፤
ቤላ፣ቤኬር፣ ይዲኤል።
7የቤላ ወንዶች ልጆች፤
ኤሴቦን፣ ኦዚ፣ ዑዝኤል፣ ኢያሪሙት፣
ዒሪ፤ ባጠቃላይ አምስት ሲሆኑ፣
የቤተ ሰብ አለቆች ናቸው፤ በትው
ልድ ሐረግ መዝገባቸው ሃያ ሁለት
ሺህ ሠላሳ አራት ተዋጊ ሰዎች ተመ
ዝግበዋል።
8የቤኬር ወንዶች ልጆች፤
ዝሚራ፣ ኢዮአስ፣ አልዓዛር፣ ኤልዮዔ
ናይ፣ ያምሪ፣ ኢያሪሙት፣ አብያ፣ ዓ
ናቶት፣ ዓሌሜት፤ እነዚህ ሁሉ የቤ
ኬር ልጆች ነበሩ። 9በትውልድ ሐ
ረግ መዝገባቸውም ውስጥ የየቤተ
ሰባ ቸው አለቆችና ሃያ ሺህ ሁለት
መቶ ተዋጊዎች ተመዝግበዋል።
10የይዲኤል ልጅ፤
ቢልሐን።
የቢልሐን ወንዶች ልጆች፤
የዑስ፣ ብንያም፣ ኤሁድ፣ ክንዓና፣ ዜታን፣
ተርሴስ፣ አኪሳኦር፤ 11እነዚህ ሁሉ
የይዲኤል ልጆች የየቤተ ሰቡ አለ
ቆች ነበሩ፤ እነርሱም ለውጊያ ብቁ
የሆኑ ዐሥራ ሰባት ሺህ ተዋጊዎች
ነበሯቸው።

7፥1 ዘፍ30፥18፤46፥13
7፥6 ዘኍ26፥38
7፥13 ዘፍ30፥8
7፥14 ዘፍ41፥51፤ዘኍ26፥30፤ ኢሱ17፥1፤ 1ዜና 5፥23
7፥15 ዘኍ26፥33፤ 36፥1-12
7፥17 ዘኍ26፥30
7፥18 ኢሱ17፥2
7፥19 ኢሱ17፥2
7፥20 ዘፍ41፥52፤ዘኍ1፥33
7፥24 ኢሱ10፥10

12ሳፊንና ሑፊም የዒር ዘሮች ሲሆኑ፣
ሑሺም ደግሞ የአሔር ዘር ነው።

### ንፍታሌም

13የንፍታሌም ወንዶች ልጆች፤
ያሕጽሔል፣ ጉኒ፣ ዬጽር፣ ሺሌም፤ እነ
ዚህ የባላ ዘሮች ናቸው።

### ምናሴ

14የምናሴ ዘሮች፤
ሶርያዊት ቁባቱ የወለደችለት ልጁ
አሥርኤል ነው። እርሷም የገለዓድን
አባት ማኪርን የወለደች ናት፤ 15ማኪ
ርም ከሑፊምና ከሳፊም ወገኖች ሚስት
አገባ። እኅቱም መዓካ ትባል ነበር።
ሌላው ዘሩ ሰለጰዓድ ሲሆን፣ እር
ሱም ሴቶች ልጆች ብቻ ነበሩት።
16የማኪር ሚስት መዓካ ወንድ ልጅ
ወለደች፤ ስሙንም ፋሬስ አለችው።
የወንድሙም ስም ሱሮስ ይባላል፤ ወን
ዶች ልጆቹም ኡላምና ራቄም ነበሩ።
17የኡላም ወንድ ልጅ፤
ባዳን፤
እነዚህ የምናሴ ልጅ፣ የማኪር ልጅ፣
የገለዓድ ወንዶች ልጆች ናቸው፤
18እኅቱ መለኬት ኢሱድን፣ አቢዓ
ዝርንና መሕላን ወለደች።
19የሸሚዳ ወንዶች ልጆች ደግሞ እነዚህ
ነበሩ፤
አሒያን፣ ሴኬም፣ ሊቅሒ፣ አኒዓም።

### ኤፍሬም

20የኤፍሬም ዘሮች፤
ሹቱላ፣ ልጁ ባሬድ፣ ልጁ ታሐት፣
ልጁ ኤልዓዳ፣ ልጁ ታሐት፣21 ልጁ
ዛባድ፣ ልጁ ሹቱላ። ኤድርና ኤልዓ
ድ ከብቶች ለመስረቅ በወረዱ ጊዜ፣
የአገሩ ተወላጆች በሆኑት በጌት
ሰዎች ተገደሉ። 22አባታቸውም
ኤፍሬም ብዙ ቀን አለቀሰላቸው፤
ዘመዶቹም መጥተው አጽናኑት።
23ከዚያም ወደ ሚስቱ ገብቶ ተኛ፤
እርሷም ፀነሰች፤ ወንድ ልጅም
ወለደች፤ በቤተ ሰቡ ላይ ከደረሰው
መከራ የተነሣ ስሙን በሪዓ አለው።
24ሴት ልጁ ስሟ ሲአራ ይባላል፤
እርሷም የታችኛውንና የላይኛውን
ቤት ሖሮንንና ኡዜን ሼራን የተባሉ
ትን ከተሞች የቈረቈረች ናት።
25ልጁ ፋፌ፣ ልጁ^ ሬሴፍ፣ ልጁ ቴላ፣
ልጁ ታሐን፣ 26ልጁ ለአዳን፣ ልጁ ዓሚ

^25 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች ከዚህ ጋር ይስማ
ማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ ልጁ የሚለውን ቃል አይጨምርም

ሁድ፣ ልጁ ኤሊሳማ፣ 27ልጁ ነዌ፣
ልጁ ኢያሱ።
28ምድራቸውና መኖሪያቸው ቤቴልንና
በዙሪያዋ የሚገኙትን ከተሞች፣ በስተምሥ
ራቅ ነዓራን፣ በስተ ምዕራብ ጌዝርንና
መንደሮቿን፣ እንዲሁም ሴኬምንና መን
ደሮቿን፣ ከዚያም አልፎ ዓያንና መንደ
ሮቿን በሙሉ ያጠቃልል ነበር። 29በምና
ሴም ወሰን ላይ ቤትሳን፣ ታዕናክ፣ መጊ
ዶና ዶር ከነመንደሮቻቸው ነበሩ። በእነዚ
ህም መንደሮች የእስራኤል ልጅ የዮሴፍ
ዘሮች ይኖሩ ነበር።

## አሴር

30የአሴር ወንዶች ልጆች፤
ዪምና፣ የሱዋ፣ የሱዊ፣ በሪዓ፤ እኅታቸ
ውም ሤራሕ ትባል ነበር።
31የበሪዓ ወንዶች ልጆች፤
ሐቤርና የቢርዛዊት አባት መልኪ
ኤል።
32ሔቤርም ያፍሌጥን፣ ሳሜርን፣ ኮታም
ንና እኅታቸውን ሶላን ወለደ።
33የያፍሌጥ ወንዶች ልጆች፤
ፋሴክ፣ ቢምሃል፣ ዓሲት፤
የያፍሌጥ ወንዶች ልጆች እነዚህ
ነበሩ።
34የሳሜር ወንዶች ልጆች፤
አኪ፣ ሮኦጋ፣[ሐ] ይሑባ፣ አራም።
35የወንድሙ የኤላም ወንዶች ልጆች፤
ጾፋ፣ ይምና፣ ሰሌስ፣ ዓማል።
36የጻፋ ወንዶች ልጆች፤
ሱዋ፣ ሐርኔፍር፣ ሦጋል፣ ቤሪ፣ ይምራ፣
37ቤጼር፣ ሆድ፣ ሳማ፣ ሰሊሳ፣ ይትራን፣
ብኤራ።
38የዬቴር ወንዶች ልጆች፤
ዮሮኒ፣ ፊስጳ፣ አራ።
39የዑላ ወንዶች ልጆች፤
ኤራ፣ ሐኒኤል፣ ሪጽያ።
40እነዚህ ሁሉ የአሴር ዘሮች ናቸው፤
እነ ርሱም የቤተ ሰብ አለቆች፣ ምርጥ
ሰዎች፣ ብርቱ ተዋጊዎችና ድንቅ
መሪዎች ነበሩ። በትውልድ መዝገባቸው
እንደተጻፈው ለውጊያ ብቁ የሆኑት
ወንዶች ቍጥር ሃያ ስድስት ሺህ ነበር።

## የብንያማዊው የሳኦል ትውልድ ሐረግ

8፥28-38 ተጓ ምብ – 1 ዜና 9፥34-44

8 ብንያም የበኵር ልጁን ቤላን፣
ሁለተኛ ልጁን አስቤልን፣
ሦስተኛ ልጁን አሐራን፣ 2አራተኛ ልጁን
ኖሐን፣ አምስተኛ ልጁን ራፋን
ወለደ።
3የቤላ ወንዶች ልጆች እነዚህ ነበሩ፤
አዳር፣ ጌራ፣ አቢሁድ፣[መ] 4አቢሱ፣ ናዕ
ማን፣ አሖዋ፣ 5ጌራ፣ ሰፉፋ፣ ሒራም።
6በጌባ ይኖሩ የነበሩትና በኋላም በምርኮ
ወደ መናሐት የተወሰዱት የኤሁድ
ዘሮች እነዚህ ናቸው፤ 7ናዕማን፣ አኪያ፣
ጌራ፤ በምርኮ ጊዜ እየመራ የወሰዳ
ቸው የያዛና የአሒሑድ አባት ጌራ
ነበረ።
8ሸሐራይም ሚስቶቹን ሑሺምንና በዕራን
ከፈታ በኋላ በሞዓብ ምድር ወንዶች
ልጆች ወለደ። 9ከሚስቱ ከሖዴሽ ዮባ
ብን፣ ዲብያን፣ ማሴን፣ ማልካምን፣
10ይዑጽን፣ ሻክያንና ሚርማን ወለደ፤
እነዚህም የቤተ ሰብ አለቆች የነበሩ
ልጆቹ ናቸው። 11ሑሺም ከተባለች
ሚስቱ አቢጡብና ኤልፍዓል የተባሉ
ወንዶች ልጆች ነበሩት።
12የኤልፍዓል ወንዶች ልጆች፤
ዔቤር፣ ሚሻም እንዲሁም ኦኖንና ሎድ
የተባሉ ከተሞችን ከነመንደሮቻቸው
የቈረቈረ ሻሜድ፣ 13በኤሎን ይኖሩ
ለነበሩ ቤተ ሰቦች አለቆችና የጋት
ነዋሪዎችን አስወጥተው ያሳደዱ በሪዓና
ሽማዕ።
14አሒዮ፣ ሻሻቅ፣ ይሬምት፣ 15ዝባድያ፣
ዓራድ፣ ዔድር፣ 16ሚካኤል፣ ይሽጳና
ዮሐ የበሪዓ ወንዶች ልጆች ነበሩ።
17ዝባድያ፣ ሜሱላም፣ ሕዝቂ፣ ሔቤር፣
18ይሽምራይ፣ ይዝሊያና ዮባብ የኤል
ፍዓል ወንዶች ልጆች ነበሩ።
19ያቂም፣ ዝክሪ፣ ዘብዲ፣ 20ኤሊዔናይ፣
ጺልታይ፣ ኤሊኤል፣ 21ዓዳያ፣ ብራያና፣
ሺምራት የሰሜኢ ወንዶች ልጆች
ነበሩ።
22ይሽጳን፣ ዔቤር፣ ኤሊኤል፣ 23ዓብዶን፣
ዝክሪ፣ ሐናን፣ 24ሐናንያ፣ ኤላም፣ ዓን
ቶትያ 25ይፍዴያና ፋኑኤል የሶሴቅ
ወንዶች ልጆች ነበሩ።
26ሽምሽራይ፣ ሽሃሪያ፣ ጎቶልያ፣ 27ያሬ
ሽያ፣ ኤልያስና፣ ዝክሪ የይሮሐም ወን
ዶች ልጆች ነበሩ።
28እነዚህ ሁሉ በየትውልድ ሐረጋቸው
የተቈጠሩ አለቆችና የቤተ ሰብ መሪዎች
ሲሆኑ፣ የሚኖሩትም በኢየሩሳሌም ነበረ።
29የገባዖን አባት[ሠ] ይዒኤል[ረ] በገባዖን
ኖረ፤ ሚስቱ መዓካ ትባል ነበር።
30የበኵር ልጁም አብዶን ይባል
ነበር፤ የእርሱም ተከታዮች ዱር፣ ቂስ፣

7፥28 ኢሱ10፥33
7፥29
ኢሱ11፥2፤17፥11
7፥30 ዘኍ1፥40
8፥1 ዘፍ46፥21
8፥3 ዘፍ46፥21
8፥4 2ሳሙ23፥9

8፥6 መሳ3፥12-30
8፥12 ዕዝ2፥33፤
ነህ6፥2፤7፥37፤11፥35
8፥13
ኢሱ10፥12፤11፥22
8፥29 ኢሱ9፥3

[ሐ]34 ወይም፣ *ወንድሙ ሳሜር፤ ሮኦጋ*
[መ]3 ወይም፣ *የሁድ አባት ጌራ*
[ሠ]29 *አባት* ማለት፣ *የማኅበረሰብ መሪ* ወይም *የጦር መሪ*
ማለት ነው።
[ረ]29 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች (1 ዜና 9፥35
ይመ') ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን *ይዒኤል*
የሚለውን አይጨምርም

በኣል፣ ኔር፣[ሰ] ናዳብ፣ [31]ጌዶር፣ አሒዮ፣
ዛኩርና [32]የሺምዓ አባት ሚቅሎት
ነበሩ። እነዚህም ከሥጋ ዘመዶቻቸው
ጋር በኢየሩሳሌም ከተማ አቅራቢያ
ይኖሩ ነበር።
[33]ኔር ቂስን ወለደ፤ ቂስ ሳኦልን ወለደ፤
ሳኦልም ዮናታንን፣ ሜልኪሳን፣ አሚ
ናዳብን፣ አስበኣልን[ሸ] ወለደ።
[34]የዮናታን ወንድ ልጅ
መሪበኣል[ቀ]፤ እርሱም ሚካን ወለደ።
[35]የሚካ ወንዶች ልጆች፤
ፒቶን፣ ሜሌክ፣ ታሬዓ፣ አካዝ።
[36]አካዝ ይሆዓዳን ወለደ፤ ይሆዓዳም ዓሌ
ሜትን፣ ዓዝሞትን፣ ዘምሪን ወለደ፤
ዘምሪም ሞጻን ወለደ። [37]ሞጻ ቢንዓን
ወለደ፤ ቢንዓ ረፋያን ወለደ፤ ረፋያ
ኤልዓሣን ወለደ፤ ኤልዓሣም ኤሴልን
ወለደ።
[38]ኤሴል ስድስት ወንዶች ልጆች ነበሩት፤
ስማቸውም፦
ዓዝሪቃም፣ ቦክሩ፣ እስማኤል፣ ሸዓ
ርያ፣ አብድዩ፣ ሐናን ይባላል፤ እነዚህ
ሁሉ የኤሴል ልጆች ነበሩ።
[39]የወንድሙ የኤሴቅ ወንዶች ልጆች፤
የበኵር ልጁ ኡላም፣ ሁለተኛ ልጁ
ኢያስ፣ ሦስተኛ ልጁ ኤሊፋላት።
[40]የኡላም ልጆች በቀስት መንደፍ
የሚችሉ ብርቱ ተዋጊዎች ነበሩ፤ እነ
ርሱም ባጠቃላይ ቍጥራቸው አንድ
መቶ ሃምሳ ወንዶች ልጆችና የልጅ
ልጆች ነበሩአቸው፤ እነዚህ ሁሉ የብ
ንያም ትውልዶች ነበሩ።
9 እስራኤል ሁሉ በየትውልድ ሐረጋ
ቸው ተቈጥረው ስማቸው በእስራኤል
ነገሥታት መዝገብ ላይ ሰፈረ።

## የኢየሩሳሌም ከተማ ሕዝብ

9፥1-17 ተጓ ምብ - ነህ 11፥3-19

የይሁዳ ሕዝብ ከፈጸሙት በደል የተ
ነሣ ተማርከው ወደ ባቢሎን ተወሰዱ።
[2]በመጀመሪያ በየርስታቸውና በየከተሞ
ቻቸው ተመልሰው የሰፈሩት ጥቂት እስራ
ኤላውያን፣ ካህናት፣ ሌዋውያንና በቤተ
መቅደሱ ውስጥ የጉልበት ሥራ የሚሠሩ
አገልጋዮች ነበሩ።
[3]በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ የይሁዳ፣
የብንያም፣ የኤፍሬምና የምናሴ ነገዶች
የሚከተሉት ናቸው፤
[4]ከይሁዳ ልጅ፣ ከፋሬስ ዘሮች፣ የባኒ
ልጅ፣ የአምሪ ልጅ፣ የዖምሪ ልጅ፣
የዓሚሁድ ልጅ ዑታይ።
[5]ከሴሎናውያን፦
የበኵር ልጁ ዓሣያና ወንዶች ልጆቹ።
[6]ከዛራውያን፦
ይዑኤል፤
የሕዝቡ ቍጥር ስድስት መቶ ዘጠና
ነበረ።
ከይሁዳ ነገድ የሰው ቊጥር ስድስት
መቶ ዘጠና ነበር።
[7]ከብንያማውያን፦
የሐስኑአ ልጅ፣ የሆዳይዋ ልጅ፣ የሜ
ሱላም ልጅ ሰሉ። [8]የይሮሐም ልጅ
ብኔያ፤ የሚክሪ ልጅ፣ የኦዚ ልጅ
ኤላ፤ የይብንያ ልጅ፣ የራጉኤል
ልጅ፣ የሰፋ ጥያ ልጅ ሜሱላም።
[9]በትውልድ ሐረግ መዝገቡ ላይ በተ
ጻፈው መሠረት ከብንያም ነገድ የሕ
ዝቡ ቍጥር ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ስድ
ስት ነበረ፤ እነዚህ ሁሉ ወንዶች
የቤተ ሰብ አለቆች ነበሩ።
[10]ከካህናቱ፦
ዮዳኤ፣ ዮአሪብ፣ ያኪን፤
[11]የእግዚአብሔር ቤት አለቃ የሆነው
የአኪጦብ ልጅ፣ የመራዮት ልጅ፣
የሳዶቅ ልጅ፣ የሜሱላም ልጅ፣
የኬልቅያስ ልጅ ዓዛርያስ።
[12]የመልክያ ልጅ፣ የጳስኮር ልጅ፣ የይ
ሮሐም ልጅ ዓዳያ፤ የኢሜር ልጅ፣
የምሺላሚት ልጅ፣ የሜሱላም ልጅ፣
የየሕዜራ ልጅ፣ የዓዲኤል ልጅ መዕሣይ።
[13]የቤተ ሰብ አለቃ የነበሩት ካህናት
ቍጥር አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሥልሳ
ነበረ፤ እነዚህም በእግዚአብሔር ቤት
ለሚከናወነው አገልግሎት ብቁ ሰዎች
ነበሩ።
[14]ከሌዋውያን ወገን፦
ከሜራሪ ዘሮች የአሳብያ ልጅ፣ የዓ
ዝሪቃም ልጅ፣ የአሱብ ልጅ ሸማያ፣
[15]በቅበቃር፣ ኤሬስ፣ ጋላልና የአሳፍ
ልጅ፣ የዝክሪ ልጅ፣ የሚካ ልጅ
መታንያ። [16]የኤዶታም ልጅ፣ የጋ
ላል ልጅ፣ የሰሙስ ልጅ አብድያ።
እንዲሁም በነ ጦፋውያን ከተሞች
የኖረው የሕልቃና ልጅ፣
የአሳ ልጅ በራክያ።
[17]የቤተ መቅደሱ በር ጠባቂዎች፦
ሰሎም፣ ዓቁብ፣ ጤልሞን፣ አሒማ
ንና ወንድሞቻቸው፤ አለቃቸውም
ሰሎም ነበረ፤ [18]እርሱም በስተ ምሥ
ራቅ በሚገኘው በንጉሡ በር እስካሁን

**8፥33** 1ሳሙ9፥1፤14፥49፤ 28፥19፤2ሳሙ2፥8
**8፥34** 2ሳሙ4፥4፤9፥12፤ 21፥7-14
**8፥40** ዘኍ26፥38
**9፥1** ዘጸ21፥10፤1ዜና5፥25፤1 1፥1፡10፤12፥38፤ 14፥8፤15፥3፡28፤18፥1 4፤1917፤215፤284፡8 ፤2921፡23፤ 2ዜና1፥2፤5፥3፤7፥8፤10 ፥3፡16፤12፥1፤13፥4፡15 ፤18፥16፤24፥5፤ 28፥23፤29፥24፤30፥1
**9፥2** ኢሱ9፥27፤ ዕዝ2፥43፡ 58፡70፤ 8፥20፤ነህ7፥60
**9፥4** ዘፍ38፥29፤46፥12
**9፥12** ዕዝ2፥38፤10፥22፤ ነህ10፥3፤ኤር21፥1፤38፥1
**9፥15** 2ዜና20፥14፤ነህ11፥22
**9፥16** ነህ12፥28
**9፥17** ቊ22፤1ዜና26፥1፤ 2ዜና8፥14፤31፥14፤ ዕዝ2፥42፤ነህ7፥45
**9፥18** 1ዜና26፥14፤ ሕዝ43፥1፤46፥1

[ሰ]30 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች (እንዲሁም 1ዜና 9፥36 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ "**ኔር**" የሚለውን ስም አይጨምርም
[ሸ]33 ***ኢሽ ቦሼት*** በመባልም ይታወቃል
[ቀ]34 ***ሜፊቦስቴ*** በመባልም ይታወቃል

ድረስ ተመድቦአል። እነዚህም የሌ
ዋውያኑ ሰፈር በር ጠባቂዎች ነበሩ።
19የቆሬ ልጅ የአብያሳፍ ልጅ፣ የቆሬ
ልጅ ሰሎምና ከእርሱም ቤተ ሰብ
የሆኑት ቆሬያውያን ወደ *እግዚአብሔር*
ማደሪያ[በ] የሚያስገባውን በር ይጠብቁ
እንደ ነበር ሁሉ፣ እነዚህም ወደ ቤተ
መቅደሱ የሚያስገባውን በር ይጠብቁ
ነበር። 20በቀድሞ ጊዜ የበር ጠባቂ
ዎቹ አለቃ የአልዓዛር ልጅ ፊንሐስ
ነበረ፤ *እግዚአብሔርም* ከእርሱ ጋር
ነበረ። 21ወደ መገናኛው ድንኳን የሚ
ያስገባውን በር የሚጠብቀው ደግሞ
የሜሱላም ልጅ ዘካርያስ ነበረ።
22መግቢያ በሮቹን እንዲጠብቁ የተመ
ረጡት ባጠቃላይ ሁለት መቶ ዐሥራ
ሁለት ነበሩ። እነርሱም በትውልድ ሐረ
ጋቸው መሠረት በሚኖሩባቸው መንደ
ሮች ተቈጥረው ተመዘገቡ፤ በር ጠባቂዎቹን
በዚያ ቦታ ላይ የመደቡአቸው ዳዊትና
ባለ ራእዩ ሳሙኤል ነበሩ። 23የማደሪያ
ውን ድንኳን ማለትም *የእግዚአብሔርን*
ቤት የሚጠብቁትም እነርሱና ዘሮቻቸው
ነበሩ። 24በር ጠባቂዎቹም በምሥራቅ፣
በምዕራብ፣ በሰሜንና፣ በደቡብ በሚገኙት
በአራቱም ማዕዘኖች ላይ ነበሩ። 25ወንድ
ሞቻቸውም በየመንደሮቻቸው ሆነው በየጊ
ዜው እየወጡ የጥበቃውን ሥራ ሰባት
ሰባት ቀን ያግዙአቸው ነበር። 26ሌዋውያን
የነበሩት አራቱ የበር ጠባቂ አለቆች ግን
በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የሚገኙትን
ክፍ ሎችና ግምጃ ቤቶች በኀላፊነት ይጠ
ብቁ ነበር። 27የጥበቃውን ሥራ
የሚያከናውኑት እነርሱ በመሆናቸው
የሚያድሩትም በዚያው በእግዚአብሔር ቤት
አካባቢ ነበረ፤ ጠዋት
ጠዋትም ደጆቹን የሚከፍቱት እነርሱ
ነበሩ። 28ከእነርሱም አንዳንዶቹ ለቤተ
መቅደሱ አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎችን
በኀላፊነት ይጠብቁ ነበር፤ ዕቃዎቹም በሚ
ገቡበትና በሚወጡበት ጊዜ ሁሉ ይቈጥሩ
ነበር፤ 29ሌሎቹ ሌዋውያን ደግሞ ዕቃዎቹንና
የቤተ መቅደሱን ንዋያተ ቅድሳት፣ ዱቄ
ቱን፣ የወይን ጠጁን፣ የወይራ ዘይቱን፣ ዕ
ጣኑን፣ የሽቱውን ቅመማ ቅመም እንዲጠ
ብቁ ተመድበው ነበር። 30ከካህናቱም አን
ዳንዶቹ የሽቱውን ቅመማ ቅመም ይለው
ሱና ያዘጋጁ ነበር። 31የቆሬያዊው የሰ
ሎም በኵር ልጅ ሌዋዊው ማቲትያ የቍ
ርባኑን እንጀራ የመጋገር ኀላፊነት ተሰ
ጥቶት ነበር። 32በየሰንበቱ ለሚዘጋጀው ገጸ
ኅብስትም ኀላፊነቱ የተሰጠው ከቀዓታው
ያን ወንድሞቻቸው መካከል ለአንዳንዶቹ

9፥19 ኤር35፥4
9፥20 ዘኍ25፥11
9፥21 1ዜና26፥2፡14
9፥22 ቀኍ17፤1ሳሙ9፥9
9፥25 2ነገ11፥5
9፥26 1ዜና26፥22
9፥27 ዘኍ3፥38፤ ኢሳ22፥22
9፥29 ዘኍ3፥28፤ 1ዜና23፥29
9፥30 ዘፀ30፥25
9፥32 ዘሌ24፥5-8፤1ዜና23፥29፤ 2ዜና13፥11
9፥33 1ዜና6፥31፤25፥1-31፤2ዜና5፥12፤ መዝ134፥1
9፥35 1ዜና8፥29
9፥39 1ሳሙ9፥1፤ 13፥22፤ 2ሳሙ2፥8፤1ዜና8፥33
9፥40 2ሳሙ4፥4

ነበር።
33የሌዋውያን ቤተ ሰብ አለቆች የነበሩት
መዘምራኑ ደግሞ በቤተ መቅደሱ ክፍሎች
ውስጥ እንዲኖሩና ከሌላው ሥራ ሁሉ ነጻ
እንዲሆኑ ተደርጎ ነበር፤ ምክንያቱም
ቀንና ሌሊት የሚሠሩት ሥራ ነበራቸው።
34እነዚህ ሁሉ የሌዋውያን ቤተ ሰብ አለ
ቆች ሲሆኑ፣ በትውልድ ሐረጋቸው መሠ
ረት ተመዘገቡ፤ የሚኖሩትም በኢየሩሳ
ሌም ነበረ።

## የሳኦል ትውልድ ሐረግ

9፥34-44 ተጓ ምብ - 1 ዜና 8፥28-38

35የገባዖን አባት[ተ] ይዒኤል የሚኖረው
በገባዖን ነበረ፤
የሚስቱም ስም መዓካ ይባላል። 36የበ
ኵር ልጁ ዓብዶን ሲሆን፣ የእርሱም
ተከታዮች ዱር፣ ቂስ፣ በኣል፣ ኔር፣
ናዳብ፣ 37ጌዶር፣ አሒዮ፣ ዛኩር፣
ሚቅሎት ነበሩ። 38ሚቅሎት ሳምአን
ወለደ፤ እነርሱም ከዘመዶቻቸው ጋር
በኢየሩሳሌም አቅራቢያ ይኖሩ ነበር።
39ኔር ቂስን ወለደ፤ ቂስ ሳኦልን ወለደ፤
ሳኦል ዮናታን፣ ሜልኪሳን፣ አሚናዳ
ብን፣ አስበኣልን[ቸ] ወለደ።
40የዮናታን ወንድ ልጅ፤
መሪበኣል[ኀ] ነው፤ መሪበኣል ሚካን
ወለደ።
41የሚካ ወንዶች ልጆች፤
ፒቶን፣ ሜሌክ፣ ታሬዓ፣ አካዝ።
42አካዝ የዕራን ወለደ፤ የዕራም ናሌሜ
ትን፣ ዓዝሞትን፣ ዘምሪን ወለደ፤
ዘምሪም ሞጻን ወለደ። 43ሞጻም ቢን
ዓን ወለደ፤ ልጁ ረፋያ ነበረ፤ ልጁ
ኤልዓሣ፣ ልጁ ኤሴል።
44ኤሴል ስድስት ወንዶች ልጆች ነበሩት፤
ስማቸውም፦
ዓዝሪቃም፣ ቦክሩ፣ እስማኤል፣ ሸዓርያ፣
አብድዩ፣ ሐናን እነዚህ የኤሴል
ወንዶች ልጆች ናቸው።

## ሳኦል ራሱን ገደለ

10፥1-12 ተጓ ምብ - 1ሳሙ 31፥1-13፤ 2ሳሙ 1፥4-12

10 ከዚህ በኋላ ፍልስጥኤማውያን
እስራኤልን መውጋት ጀመሩ፤
እስራኤላውያንም ከፊታቸው ሸሹ፤ ብዙዎች
በጊልቦዓ ተራራ ላይ ሞቱ። 2ፍልስጥኤ
ማውያን ሳኦልንና ልጆቹን ይበልጥ አሳደዱ

[በ]19 በዚህ በቍጥር 21 እና 23 ላይ ቤተ መቅደሱን ያመለክታል።
[ተ]35 *አባት* ማለት፣ *የማኅበረሰብ መሪ* ወይም፣ *የጦር መሪ* ማለት ነው።
[ቸ]39 *ኢሽጠቦሼት* በመባልም ይታወቃል።
[ኀ]40 *ሜፊቦስቴ* በመባልም ይታወቃል።

አቸው፤ የሳኦልንም ልጆች ዮናታንን፣ አሚ
ናዳብንና ሜልኪሳን ገደሉ፤ [3]ሳኦል በተ
ሰለፈበት ግንባር ውጊያው በረታ፤ ቀስተኞ
ችም አግኝተው አቈሰሉት።
[4]ሳኦል ጋሻ ጃግሬውን፣ "እነዚህ ሸለፈታ
ሞች መሳለቂያ እንዳያደርጉኝ ሰይፍህን
መዝዘህ ውጋኝ" አለው።
ጋሻ ጃግሬው ግን እጅግ ፈርቶ ስለ ነበር
አልደፈረም፤ ስለዚህ ሳኦል በገዛ ሰይፉ
ላይ ወድቆ ሞተ። [5]ጋሻ ጃግሬውም ሳኦል
መሞቱን ሲያይ፣ እርሱም በሰይፉ ላይ
ወድቆ ሞተ። [6]ስለዚህ ሳዖልና ሦስት
ልጆቹ ሞቱ፤ ቤተ ሰዎቹም ሁሉ አብረው
ሞቱ።
[7]በሸለቆው ውስጥ የነበሩት እስራኤላው
ያን ሁሉ ሰራዊቱ እንደ ሸሸ፣ ሳኦልና ልጆ
ቹም እንደ ሞቱ ባዩ ጊዜ ከተሞቻቸውን
ለቀው ሸሹ፤ ፍልስጥኤማውያንም መጥ
ተው ከተሞቹን ያዙ።
[8]በማግሥቱ ፍልስጥኤማውያን የሞቱ
ትን ለመግፈፍ ሲመጡ፣ ሳኦልና ልጆቹ
በጊልቦዓ ተራራ ላይ ወድቀው አገኙአ
ቸው። [9]ሳኦልን ከገፈፉ፣ ራሱን ከቈረጡና
መሣሪያውንም ከወሰዱ በኋላ፣ ለአማልክ
ቶቻቸውና ለሕዝቡ የምሥራቹን እንዲ
ነግሩ ወደ መላው የፍልስጥኤም ምድር
መልክተኞችን ላኩ። [10]ከዚያም መሣሪያ
ውን በአማልክቶቻቸው ቤተ ጣዖት አኖሩ፤
ራሱንም በዳጎን ቤተ ጣዖት ውስጥ አንጠ
ለጠሉት።
[11]የኢያቢስ ገለዓድ ነዋሪዎች ሁሉ ፍልስ
ጥኤማውያን በሳኦል ላይ ያደረጉትን በሰሙ
ጊዜ፣ [12]ብርቱ የሆኑ ሰዎች ሄደው የሳኦል
ንና የልጆቹን ሬሳ አንሥተው ወደ ኢያቢስ
አመጡ፤ ዐጽማቸውንም ኢያቢስ ውስጥ
በሚገኘው ትልቁ ዛፍ ሥር ቀበሩ፤ ከዚ
ያም ሰባት ቀን ጾሙ።
[13]ሳኦል *እግዚአብሔርን* ስላልታዘዘ ሞተ፤
*የእግዚአብሔርን* ቃል አልጠበቀም፤ ይል
ቁንም ከሙታን ጠሪ ምክርን ጠየቀ፤
[14]ይህን *ከእግዚአብሔር* አልጠየቀም፤ ስለዚህ
*እግዚአብሔር* ገደለው፤ መንግሥቱንም
ወደ እሴይ ልጅ ወደ ዳዊት እንዲተላለፍ
አደረገ።

## ዳዊት በእስራኤል ላይ ነገሠ

11፥1-3 ተጓ ምብ - 2ሳሙ 5፥1-3

11 እስራኤል ሁሉ በኬብሮን ወደ
ዳዊት መጥተው እንዲህ አሉት፤"
እነሆ፤ እኛ የገዛ ሥጋህና ደምህ ነን፤ [2]በቀ
ደመው ዘመን ሳኦል ንጉሥ ሆኖ ሳለ እስ
ራኤልን ወደ ጦርነት የምትመራ አንተ

10፥10 መሳ16፥23
10፥11 መሳ21፥8
10፥13
ዘሌ19፥31፤20፥6፤
ዘዳ18፥9-14፤
1ሳሙ 13፥13፤
2ሳሙ1፥1፤1
ዜና5፥25
10፥14
1ሳሙ13፥14፤
1ዜና12፥23
11፥1
ዘፍ13፥18፤23፥19፤
1ዜና9፥1
11፥2
1ሳሙ18፥5፡16፤1ዜና
5፥2፤መዝ78፥1፤
ማቴ2፥6
11፥3
1ሳሙ16፥1-13
11፥4
ዘፍ10፥16፤15፥18-
21፤ኢሱ3፥10፤15፥8
11፥6 2ሳሙ2፥13
11፥8
2ሳሙ5፥9፤2ዜና32፥5
11፥9
አስ 9፥4
11፥10
ቀኑ1፤1ዜና12፥23
11፥11
2ሳሙ17፥10
11፥14 ዘፀ14፥30፤
1ሳሙ 1113

ነበርህ፤ *እግዚአብሔር* አምላክህም፣ 'ሕዝ
ቤን እስራኤልን የምትጠብቅ አንተ ነህ፤
ንጉሣቸውም ትሆናለህ' ብሎሃል"።
[3]የእስራኤል ሽማግሌዎች ሁሉ ንጉሥ
ዳዊት ወዳለበት ወደ ኬብሮን መጡ፤ ዳዊ
ትም በኬብሮን *በእግዚአብሔር ፊት* ከእነ
ርሱ ጋር ቃል ኪዳን ገባ። *እግዚአብሔር*
በሳሙኤል አማካይነት በሰጠው ተስፋ መሠ
ረት ዳዊትን ቀብተው በእስራኤል ላይ
አነገሡት።

## ዳዊት ኢየሩሳሌምን ድል አደረገ

11፥4-9 ተጓ ምብ - 2ሳሙ 5፥6-10

[4]ዳዊትና እስራኤላውያን ሁሉ ኢያቡስ
ወደምትባለው ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ።
በዚያም የሚኖሩ ኢያቡሳውያን [5]ዳዊትን
"ወደዚህ ፈጽሞ አትገባም" አሉት፤ ዳዊት
ግን የጽዮንን ምሽግ ያዘ፤ እርሷም የዳዊት
ከተማ ናት።
[6]ዳዊትም፣ "ኢያቡሳዊያንን ቀድሞ የሚ
ወጋ ሰው የሰራዊቱ አዛዥ ይሆናል" አለ፤
ስለዚህ የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ በመጀመሪያ
ወጣ፤ እርሱም አዛዥ ለመሆን በቃ።
[7]ከዚያም ዳዊት መኖሪያውን በዐምባ
ዩቱ ውስጥ አደረገ፤ ከዚህም የተነሣ የዳ
ዊት ከተማ ተባለች። [8]ዳዊትም ከሚሎ
ጀምሮ የከተማዪቱን ዙሪያ ቅጥር ሠራ፤
ኢዮአብ ደግሞ የቀረውን የከተማዪቱን
ክፍል መልሶ ሠራ። [9]*እግዚአብሔር ጸባ
ኦት* ከእርሱ ጋር ስለ ነበር ዳዊት በየጊ
ዜው እየበረታ ሄደ።

## የዳዊት ኀያላን ሰዎች

11፥10-41 ተጓ ምብ - 2 ሳሙ 23፥8-39

[10]የዳዊት ኀያላን ሰዎች አለቆች እነዚህ
ናቸው፤ እነርሱም *እግዚአብሔር* በሰጠው
ተስፋ መሠረት መንግሥቱ በምድሪቱ
ሁሉ ትሰፋ ዘንድ ከሌሎቹ እስራኤላውያን
ጋር ሆነው ለመንግሥቱ ብርቱ ድጋፍ
ሰጡ። [11]የዳዊት ኀያላን ሰዎች ስም ዝር
ዝር ይህ ነው፤
ሐክሞናዊው ያሾብዓም የጦር መኮንኖቹ
አለቃ' ነበረ፤ እርሱም ጦሩን አንሥቶ
በአንድ ጊዜ ሦስት መቶ ሰው ገደለ።
[12]ከእርሱም ቀጥሎ ከሦስቱ ኀያላን አንዱ
የሆነው የአሆሃዊው የዱዲ ልጅ አልዓዛር
ነው፤ [13]እርሱም ፍልስጥኤማውያን ለጦር
ነት በተሰበሰቡ ጊዜ በፈስደሚም ከዳዊት
ጋር አብሮ ነበረ፤ ገብስ በሞላበት የእርሻ
ቦታ ወታደሮቹ ከፍልስጥኤማውያን ፊት
ሸሹ፤ [14]ይሁን እንጂ በእርሻው መካከል ቦታ
ይዘው ስለ ነበረ ፍልስጥኤማውያንን ገደሉ፤

'11 *ሠላሳ* ወይም እንደ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት
ትርጒሞች፣ *ሦስት* (እንዲሁም 2ሳሙ 23፥8 ይመ) ይላሉ

*እግዚአብሔርም* ታላቅ ድል ሰጣቸው።
[15]ከፍልስጥኤማውያን ሰራዊት ጥቂቱ
በራፋይም ሸለቆ ሰፍሮ ሳለ፣ ከሠላሳዎቹ
አለቆች ሦስቱ ዳዊትን ለመገናኘት በዓ
ዶላም ዋሻ አጠገብ ወደሚገኘው ወደ ዐለቱ
ወረዱ። [16]በዚያን ጊዜ ዳዊት በምሽጉ
ውስጥ ነበረ፤ የፍልስጥኤማውያን ሰራዊት
ደግሞ በቤተልሔም ነበረ። [17]ዳዊትም
ውሃ ፈልጎ ነበርና፣ "ከቤተ ልሔም በር
አቅራቢያ ከሚገኘው ጕድጓድ የምጠጣው
ውሃ ማን ባመጣልኝ!" አለ። [18]በዚህ ጊዜ
ሦስቱ የፍልስጥኤማውያንን ሰራዊት ጥሰው በ
ማለፍ በቤተልሔም በር አጠገብ ከሚገ
ኘው ጕድጓድ ውሃ ቀድተው ለዳዊት
አመጡለት፤ እርሱ ግን ሊጠጣው ስላልፈለገ
*በእግዚአብሔር* ፊት አፈሰሰው፤ [19]ከዚያም
"ይህን ከማድረግ እግዚአብሔር ይጠብቀኝ፤
ይህ በሕይወታቸው ቈርጠው የሄዱትን
የእነዚህን ሰዎች ደም እንደ መጠጣት
አይደለምን?" አለ። ይህን ለማምጣት በሕ
ይወታቸው ቈርጠው ስለ ነበር፣ ዳዊት
ሊጠጣው አልፈለገም።
ሦስቱ ኀያላን ሰዎች የሠሩት ይህንን
ነበር።
[20]የኢዮአብ ወንድም አቢሳ የሦስቱ
አለቃ ነበረ። እርሱም ጦሩን አንሥቶ
ሦስት መቶ ሰዎች ገደለ፤ ከዚህም የተነሣ
እንደ ሦስቱ ሁሉ ዝነኛ ሆነ። [21]ከሦስቱ
አንዱ ሆኖ ባይቈጠርም እንኳ፣ እጥፍ
ክብር አገኘ፤ አዛዣቸውም ሆነ።
[22]ከቀብስኤል የመጣውና ታላቅ ጀብዱ
የሠራው የዮዳሄ ልጅ በናያስ ብርቱ ተዋጊ
ነበረ። እርሱም እጅግ የታወቁ ሁለት የሞ
አብ ሰዎችን ገደለ። እንዲያውም አንድ
ጊዜ በረዶ ምድርን በሸፈነበት ቀን ወደ
አንድ ጕድጓድ ወርዶ አንበሳ ገደለ።
[23]ደግሞም ቁመቱ አምስት ክንድ[ኘ] የሆነ
አንድ ግብፃዊ ገደለ፤ ግብፃዊው የሸማኔ
መጠቅለያ የመሰለ ጦር በእጁ ቢይዝም፣
በናያስ ግን ቆመጥ ይዞ ገጠመው፤ ከግብ
ፃዊው እጅ ጦሩን ነጥቆ በገዛ ጦሩ ገደ
ለው። [24]የዮዳሄ ልጅ በናያስ የፈጸመው
ጀብዱ ይህ ነበር፤ እርሱም እንደ ሦስቱ
ኀያላን ዝነኛ ሆነ። [25]ከሠላሳዎቹም ይልቅ
የበለጠ ክብር ተጐናጸፈ፤ ይሁን እንጂ
ከሦስቱ አንዱ አልነበረም፤ ዳዊትም
የክብር ዘቡ አዣዥ አደረገው።
[26]ኀያላኑም እነዚህ ነበሩ፤
የኢዮአብ ወንድም አሣሄል፣
የቤተልሔሙ የዱዲ ልጅ ኤልያናን፣
[27]ሃሮራዊው ሳሞት፣ፈሎናዊው ሴሌድ፣
[28]የቴቆሑሔ ሰው የሆነው የዒስካ ልጅ፣

11፥15
1ዜና14፥9፤
ኢሳ 17፥5
11፥16 2ሳሙ5፥17
11፥18 ዘጸ12፥16
11፥20 1ሳሙ26፥6
11፥22
ኢሱ15፥21፤ 1ሳሙ
17፥36
11፥23 1ሳሙ17፥7
11፥26 2ሳሙ2፥18
11፥27 1ዜና27፥8
11፥28 1ዜና27፥12
11፥29 ሳሙ21፥18
11፥31
መሳ12፥13፤1ዜና27፥14
11፥41
2ሳሙ11፥6፤1ዜና2፥36
11፥44 ዘጸ1፥4
12፥1 ኢሱ15፥31
12፥2
መሳ3፥15፤2ሳሙ3፥19

ዒራስ፣የዓናቶቱ ሰው አቢዔዜር፣
[29]ኩሳታዊው ሴቤካይ፣
አሆሃዊው ዔላይ፣
[30]ነጦፋዊው ማህራይ፣
የነጦፋዊው የበዓና ልጅ ሔሌድ፣
[31]ከብንያም ወገን የጊብዓ ሰው የሆ
ነው የሪባይ ልጅ ኤታይ፣
ጲርዓቶናዊው በናያስ፣
[32]የገዓስ ሸለቆዎች ሰው የሆነው ኡሪ፣
ዓረባዊው አቢኤል፣
[33]ባሕሩማዊው ዓዝሞት፣
ሰዓልቦናዊው ኤሊያሕባ፣
[34]የጊዞናዊው የአሳን ልጆች፣
የሃራራዊው የሻጌ ልጅ ዮናታን፣
[35]የሃራራዊው የሳኮር ልጅ አሒአም፣
የኡር ልጅ ኤሊፋል፣
[36]ምኬራታዊው ኦፌር፣
ፍሎናዊው አኪያ፣
[37]ቀርሜሎሳዊው ሐጽሮ፣
የኤዝባይ ልጅ ነዕራይ፤
[38]የናታን ወንድም ኢዮኤል፣
የሃግሪ ልጅ ሚብሐር፣
[39]አሞናዊው ጼሌቅ፣
የጽሩያ ልጅ የኢዮአብ ጋሻ ጃግሬ
ቤሮ ታዊው ነሃራይ፣
[40]ይትራዊው ዒራስ፣
ይትራዊው ጋሬብ፣
[41]ኬጢያዊው ኦርዮ፣
የአሕላይ ልጅ ዛባድ፣
[42]የሮቤላዊው የሺዛ ልጅ ዓዲና፤
እርሱም የሮቤላውያንና አብረውት
ለነበሩት የሠላሳ ሰዎች አለቃ ነበረ።
[43]የማዕካ ልጅ ሐናን፣
ሚትናዊው ኢዮሣፍጥ፣
[44]አስታሮታዊው ዖዝያ፣ የአሮዔራዊው
የኮታም ልጆች ሻማና ይዒኤል፣
[45]የሺምሪ ልጅ ይዲኤል፣
ወንድሙም ቴጻዊው ዮሐ፣
[46]መሐዋዊው ኤሊኤል፣
የኤልነዓም ልጆች ይሪባይና ዮሻውያ፣
ሞዓባዊው ይትማ፣
[47]ኤሊኤል፣ ዖቤድና ምጾባዊው
የዕሢኤል።

## ከዳዊት ጋር የተቀላቀሉ ተዋጊዎች

12 ዳዊት ከቂስ ልጅ ከሳኦል ፊት
ሸሽቶ በጺቅላግ ሳለ ወደ እርሱ
የመጡት ሰዎች እነዚህ ናቸው፤ እነርሱም
በጦርነቱ ላይ ከረዱት ተዋጊዎች መካከል
ነበሩ። [2]ሰዎቹ ቀስተኞች ሲሆኑ፣ በቀኝም
ሆነ በግራ እጃቸው ፍላጻ መወርወርና
ድንጋይ መወንጨፍ የሚችሉ ነበሩ፤

[ኘ]23 2.3 ሜትር ያህል ነው።

እነርሱም ከብንያም ነገድ የሆነው የሳኦል
ሥጋ ዘመዶች ነበሩ፤
3አለቃቸው አሒዔዝር ነበረ፤ ከእር
ሱም በኋላ ኢዮአስ ነበረ፤ ሁለቱም
የጊብዓዊው የሸማዓ ልጆች ነበሩ፤ የዓዝ
ሞት ልጆች ይዝኤልና ፋሌጥ፤ በራኪ
ያ፣ ዓናቶታዊው ኢዩ፤ 4ገባዖናዊው ሰ
ማያስ ከሠላሳዎቹ መካከል ኀያልና የ
ሠላሳዎቹም መሪ ነበረ፤ ኤርምያስ፣
የሕዚኤል፣ ዮሐናን፣ ገድሮታዊው
ዮዛባት፣ 5ኤሉዛይ፣ ኢያሪሙት፣ በዓ
ልያ፣ ሰማራያ፣
ሐሩፋዊው ሰፋጥያስ፣ 6ቆሬያውያኑ
ሕልቃና፣ ይሺያ፣ ዓዘርኤል፣ ዮዛር፣
ያሾብዓም፤ 7የጌዶር ሰው ከሆነው ደግሞ
የይሮሐም ልጆች ዮዔላና ዝባድያ።

8ዳዊት በምድረ በዳ በሚገኘው ምሽጉ
ውስጥ ሳለ፣ ከጋድ ነገድ የሆኑ ሰዎች
መጥተው የእርሱን ሰራዊት ተቀላቀሉ፤
እነርሱም ለውጊያ የተዘጋጁ ጋሻና ጦር
ለመያዝ የሚችሉ ብርቱ ተዋጊዎች ነበሩ፤
ፊታቸው እንደ አንበሳ ፊት የሚያስፈራና
በየተራራውም ላይ እንደሚዘል ሚዳቋ ፈጣ
ኖች ነበሩ።
9የእነዚህም አለቃ ዔጼር ነበረ፤
ሁለተኛው አዛኽ አብድዩ፣ ሦስተኛው
ኤልያብ፣
10አራተኛው መስመና፣ አምስተኛው
ኤርምያስ፣
11ስድስተኛው ዓታይ፣ ሰባተኛው ኢሊ
ኤል፣
12ስምንተኛው ዮሐናን፣
ዘጠነኛው ኤልዛባድ፣
13ዐሥረኛው ኤርምያስ፣ ዐሥራ አንደ
ኛው መክበናይ።
14እነዚህ ጋዳውያን የጦር አዛዦች ነበሩ፣
ከእነርሱ ታናሽ የሆነው እንደ መቶ፣
ታላቅ የሆነው ደግሞ እንደ ሺህ አለቃ
ይቈጠር ነበር። 15በመጀመሪያው ወር
የዮርዳኖስ ወንዝ ከአፍ እስከ ገደፍ ሞልቶ
ሳለ፣ ወንዙን ተሻግረው በስተ ምሥራቅና
በስተ ምዕራብ ሸለቆዎች ይኖሩ የነበሩትን
ሁሉ ከዚያ ያባረሩት እነዚህ ሰዎች ነበሩ።
16ሌሎች ከብንያምና ከይሁዳም ወገን
የሆኑ ሰዎች ዳዊት ወደሚገኝበት ምሽግ
መጡ። 17ዳዊትም እነዚህን ሰዎች ሊቀበል
ወጥቶ እንዲህ አላቸው፤ የመጣችሁት
ልትረዱኝና በሰላም ከሆነ፣ ከእኔ ጋር እን
ድትሰለፉ ልቀበላችሁ ዝግጁ ነኝ፤ ነገር
ግን እጄ ከበደል ንጹሕ ሆኖ ሳለ፣ ለጠላ
ቶቼ አሳልፋችሁ ልትሰጡኝ ከሆነ፣ የአባ
ቶቻችን አምላክ ይመልከተው፤ ይፈረድ

12፥4 ኢሱ15፥36
12፥7 ኢሱ15፥58
12፥8 ዘፍ30፥11፤2ሳሙ2፥18፤17፥10
12፥14 ዘሌ26፥8፤ ዘዳ32፥30
12፥15 ኢሱ3፥15
12፥16 2ሳሙ3፥19
12፥18 መሳ3፥10፤1ሳሙ25፥5-6፤2ሳሙ17፥25፤1ዜና28፥12፤2ዜና15፥1፤20፥14፤24፥20
12፥19 1ሳሙ29፥2-11
12፥20 1ሳሙ27፥6
12፥23 1ሳሙ16፥1፤ 2ሳሙ3፥4፤ 1ዜና10፥14፤11፥10
12፥28 1ዜና6፥8፤15፥11፤16፥39፤27፥17
12፥29 2ሳሙ2፥8-9፤3፥19

ውም"።
18ከዚያም የእግዚአብሔር መንፈስ በ
ሠላ ሳዎቹ አለቃ በዓማሣይ ላይ ወረደ፤
እር ሱም እንዲህ አለ፤
"ዳዊት ሆይ፤ እኛ የአንተ ነን፤
የእሴይ ልጅ ሆይ፤ እኛ ከአንተ ጋር ነን፤
ሰላም ፍጹም ሰላም ለአንተ ይሁን፤
አንተን ለሚረዱም ሁሉ ሰላም ይሁን፤
አምላክህ ይረዳሃልና"።
ስለዚህ ዳዊት ተቀበላቸው፤ የሰራዊቱም
አለቃ አደረጋቸው።
19ዳዊት ከፍልስጥኤማውያን ጋር ተባ
ብሮ ሳኦልን ለመውጋት በሄደ ጊዜ፣ ከም
ናሴ ነገድ የሆኑ ጥቂት ሰዎች ከድተው
ከዳዊት ሰራዊት ጋር ተቀላቀሉ። እርሱ
ግን ርዳታ አላደረገላቸውም፤ ምክንያቱም
የፍልስጥኤማውያን ገዦች ምክር ካደረጉ
በኋላ እንዲህ ሲሉ ልከውት ነበር፤ "ከድቶ
ወደ ጌታው ወደ ሳኦል ቢሄድ እኛን ያስ
ጨርሰናል"። 20ዳዊት ወደ ጺቅላግ በሄደ
ጊዜ ከድተው ወደ እርሱ የተቀላቀሉ የም
ናሴ ነገድ ሰዎች እነዚህ ነበሩ፤ ዓድና፣
ዮዛባት፣ ይዲኤል፣ ሚካኤል፣ ዮዛባት፣
ኤሊሁ፣ ጺልታይ፤ እነዚህ በምናሴ ግዛት
ሳሉ የሻለቆች ነበሩ። 21ሁሉም ብርቱ ተዋ
ጊዎችና በዳዊትም ሰራዊት ውስጥ አዛ
ዦች ስለ ነበሩ፣ አደጋ ጣዮችን በመ
ውጋት ረዱት። 22ሰራዊቱም እንደ እግዚአብሐ
ር ሰራዊት[ኣ] እስኪሆን ድረስ፣ ዳዊትን
ለመር ዳት በየዕለቱ ብዙ ሰዎች ይጎርፉ
ነበር።

**ሌሎችም በኬብሮን የዳዊትን ሰራዊት ተቀላቀሉ**

23እግዚአብሔር ለዳዊት በገባለት ቃል
ኪዳን መሠረት የሳኦልን መንግሥት አን
ሥተው ለእርሱ ለመስጠት ዳዊት ወደ
ሚገኝበት ወደ ኬብሮን የመጡት ሰዎች
ቍጥር ይህ ነው፤
24ጋሻና ጦር አንግበው ለጦርነት የተዘጋ
ጁት የይሁዳ ሰዎች ስድስት ሺህ
ስምንት መቶ፤
25ከስምዖን ነገድ ለጦርነት ዝግጁ የሆኑ
ሰባት ሺህ አንድ መቶ።
26ከሌዊ ነገድ አራት ሺህ ስድስት
መቶ፤ 27የአሮን ቤተ ሰብ መሪ የሆ
ነውን ዮዳሄን ጨምሮ ሦስት ሺህ
ሰባት መቶ ሰዎች፤ 28ወጣቱ ብርቱ
ተዋጊ ጻዶቅና ከቤተ ሰቡ ሃያ ሁለት
የጦር አለቆች፤
29የሳኦል ሥጋ ዘመድ የሆኑ የብንያም
ሰዎች ሦስት ሺህ፤ ከእነዚህም አብዛ

[ኣ]22 ወይም፣ *ታላቅና ኀያል ሰራዊት*

ኞቹ እስከዚያች ጊዜ ድረስ ለሳኦል
ቤት ታማኝ ነበሩ፤
30ከኤፍሬም ሰዎች በጐሣዎቻቸው ዘንድ
ታዋቂ የሆኑ ብርቱ ተዋጊዎች ሃያ
ሺህ ስምንት መቶ፤
31ከምናሴ ነገድ እኩሌታ ዐሥራ ስም
ንት ሺህ ሰዎች፤ እነርሱም ዳዊትን
ለማንገሥ በየስማቸው ተጽፈው የመጡ
ነበሩ፡፡
32ዘመኑን የተረዱና እስራኤላውያንም
ምን ማድረግ እንደሚገባቸው የተገነ
ዘቡ የይሳኮር ሰዎች ሁለት መቶ አለ
ቆች፤ በእነርሱም ሥር ሆነው የሚ
ታዘዙ ዘመዶቻቸው፡፡
33ልምድ ያላቸው፣ በሁሉም ዐይነት
መሣሪያ ለመዋጋት የተዘጋጁና ዳዊ
ትን ለመርዳት የመጡት መንታ
ልብ የሌላቸው የዛብሎን ሰዎች ሃምሳ
ሺህ፤
34ከንፍታሌም ሰዎች አንድ ሺህ የጦር
አለቆች፤ ከእነርሱም ጋር ጋሻና ጦር
የያዙ ሠላሳ ሰባት ሺህ ሰዎች፤
35ከዳን ሰዎች ለጦርነት የተዘጋጁ ሃያ
ስምንት ሺህ ስድስት መቶ፤
36ከአሴር ሰዎች ልምድ ያላቸውና ለጦ
ርነት የተዘጋጁ ወታደሮች አርባ ሺህ፤
37ከምሥራቅ ዮርዳኖስ ከሮቤል፣
ከጋድና ከምናሴ ነገድ እኩሌታ ልዩ
ልዩ ዐይ ነት መሣሪያ የታጠቁ
አንድ መቶ ሃያ ሺህ ሰዎች፡፡
38እነዚህ ሁሉ በሰራዊቱ ውስጥ ለማገ
ልገልገል ፈቃደኞች የሆኑ ተዋጊዎች
ናቸው፤ ወደ ኬብሮን የመጡትም ዳዊ
ትን በእስራኤል ሁሉ ላይ ለማንገሥ ወስ
ነው ስለ ነበር ነው፡፡ የቀሩትም እስራኤላ
ውያን ሁሉ ዳዊትን ለማንገሥ በአ
ንድ ሐሳብ ጸኑ፡፡ 39የሚያስፈልጋቸውንም
ቤተ ሰቦቻቸው አዘጋጅተውላቸው ስለ
ነበር፣ ሰዎቹ እየበሉና እየጠጡ ከዳዊት
ጋር ሦስት ቀን ቈዩ፡፡ 40እንዲሁም ሩቅ
ከሆነው ከይሳኮር፣ ከዛብሎንና ከንፍታ
ሌም አገር ሳይቀር ጎረቤቶቻቸው በአ
ህያ፣ በግመል፣ በበቅሎና በበሬ ጭነው
ምግብ አመጡላቸው፤ በእስራኤል ታላቅ
ደስታ ስለ ሆነ ዱቄት፣ የበለስና የዘቢብ
ጥፍጥፍ፣ የወይን ጠጅ፣ የወይራ ዘይት፣
የቀንድ ከብትና በጎች በገፍ ቀርበው
ነበር፡፡

### የታቦቱ መመለስ

13፥1-14 ተጓ ምብ - 2 ሳሙ6፥1-11

13 ዳዊትም ሻለቆችና መቶ አለቆች
ከሆኑት የጦር ሹማምቱ ሁሉ ጋር

12፥32 አስ1፥13
12፥38 1ዜና9፥1
12፥39
2ሳሙ3፥20፤
ኢሳ25፥6-8
12፥40
1ሳሙ25፥18፤
2ሳሙ16፥1፤17፥29፤
1ዜና29፥22

13፥3
1ሳሙ7፥1-2፤
2ዜና 1፥5
13፥5ዘኊ13፥21፤
ኢሱ13፥3፤1ሳሙ7፥2፤
1ዜና11፥1፤15፥3
13፥6 ዘፀ25፥22፤
ኢሱ15፥9፤2ነገ19፥15
13፥7 1ሳሙ7፥1
13፥8
1ዜና15፥16፡19፡24፤2
ዜና5፥12፤መዝ92፥3
13፥10
ዘሌ10፥2፤1ዜና15፥13
13፥11
1ዜና15፥13፤መዝ7፥11
13፥13
1ዜና15፥18፡24፤
16፥38፤26፥4-5፡15
13፥14 2ሳሙ6፥11

ተማከረ፡፡ 2ከዚያም ለመላው የእስራኤል
ማኅበር እንዲህ አለ፤ “እንግዲህ ነገሩ
መልካም መስሎ ከታያችሁና የአምላካችን
የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ፣ በእስራኤል
ግዛት ሁሉ ለሚኖሩ በሩቅም ሆነ በቅርብ
ላሉት ለቀሩት ወንድሞቻችን እንዲሁም
በየራሳቸው ከተሞችና መሰማሪያዎች የሚ
ኖሩ ካህናትና ሌዋውያን መጥተው ከእኛ
ጋር እንዲሰባሰቡ እንላክባቸው፡፡ 3በሳኦል
ዘመነ መንግሥት ሳንፈልገው[ሀ] የነበረውን
የአምላካችንን ታቦት መልሰን ወደ እኛ
እና ምጣ”፡፡ 4ነገሩም በሕዝቡ ሁሉ ዘንድ
ተቀ ባይነት ስላገኘ መላው ማኅበር ይህንኑ
ለማ
ድረግ ተስማማ፡፡
5ስለዚህ ዳዊት የእግዚአብሔርን ታቦት
ከቂ ርያትይዓሪም ለማምጣት ከግብፅ
ወንዝ ከሺሖር ጀምሮ እስከ ሐማት
መተላለፊያ[ሁ] ድረስ የሰፈሩትን እስራ
ኤላውያን ሁሉ ሰበ ሰበ፡፡ 6ዳዊትና እስራ
ኤላውያን ሁሉ በኪሩብና በኪሩብ
መካከል የተቀመጠውን ስሙም በእርሱ
የተጠራውን፣ የእግዚአ ብሔር አምላክን
ታቦት ከዚያ ለማምጣት በይሁዳ
ወዳለችው ቂርያትይዓሪም ወደ ተባለችው
ወደ በኣላ ሄዱ፡፡
7የእግዚአብሔርንም ታቦት ከአሚናዳብ
ቤት በአዲስ ሠረገላ ላይ አድርገው
አመጡት፤ ሠረገላውን ይነዱ የነበሩትም
ዖዛና አሒዮ ነበሩ፡፡ 8ዳዊትና እስራ
ኤላውያን ሁሉ በእግ ዚአብሔር ፊት ሆነው
በቅኔና በበገና፣ በመ ሰንቆና በከበሮ፣ በ
ጸናጽልና በመለከት በሙሉ ኀይላቸው በዓ
ሉን በደስታ ያከብሩ ነበር፡፡
9ወደ ኪዶን ዐውድማ በደረሱ ጊዜ በሬ
ዎቹ አደናቅፏቸው ስለ ነበር፣ ዖዛ ታቦቱን
ለመደገፍ እጁን ዘረጋ፡፡ 10ታቦቱን በእጁ
ስለ ነካ፣ የእግዚአብሔር ቍጣ በዖዛ ላይ
ነደደ፤ ስለዚህም በዚያው በእግዚአብሔር
ፊት ሞተ፡፡
11የእግዚአብሔር ቍጣ ዖዛን በድንገት
ስለ ቀሠፈው ዳዊት አዘነ፤ ያም ቦታ እስከ
ዛሬ ድረስ የዖዛ ስብራት[ሠ] ተብሎ ይጠራል፡፡
12ዳዊት በዚያን ዕለት እግዚአብሔርን ስለ
ፈራ፣ “ታዲያ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ
እኔ እንዴት ማምጣት እችላለሁ?” አለ፡፡
13ስለዚህ ታቦቱን ወደ ዳዊት ከተማ በመ
ውሰድ ፈንታ የጋት ሰው ወደ ሆነው ወደ
አቢዳራ ቤት ወሰደው፡፡ 14የእግዚአብሔርም
ታቦት በአቢዳራ ቤት ከቤተ ሰቡ ጋር
ሦስት ወር ተቀመጠ፤ እግዚአብሔርም
ቤተ ሰቡንና ያለውንም ሁሉ ባረከ፡፡

[ሀ]3 ወይም፣ ቸላ ብለን
[ሁ]5 ወይም፣ እስከ ሌቦ ሐመት
[ሠ]11 ወይም፣ ፔሬዝ ዖዛ

## የዳዊት ቤትና ቤተ ሰቡ

14፥1-7 ተጓ ምብ - 2ሳሙ 5፥11-16 1ዜና3፥5-8

14 በዚህ ጊዜ የጢሮስ ንጉሥ ኪራም
ለዳዊት ቤተ መንግሥት እንዲ
ሠሩ መልክተኞችን፣ ድንጋይ ጠራቢዎ
ችንና አናጢዎችን ከዝግባ ዕንጨት ጋር
ላከ። 2ዳዊትም *እግዚአብሔር* በእስራኤል
ላይ አንግሦ እንዳጸናውና ስለ ሕዝቡም
ስለ እስራኤል ሲል *መንግሥቱን* ከፍ ከፍ
እንዳደረገለት አስተዋለ።
3ዳዊትም በኢየሩሳሌም ብዙ ሚስቶች
አገባ፤ ከእነርሱም ወንዶችንና ሴቶች ልጆ
ችን ወለደ። 4በዚያ ሳለ የወለዳቸው የል
ጆቹ ስም ይህ ነው፤ ሳሙስ፣ ሶባብ፣
ናታን፣ ሰሎሞን፣ 5ኢያቤሐር፣ ኤሊሱዔ፣
ኤሊፉላት፣ 6ኖጋ፣ ናፌቅ፣ ያፍያ፣ 7ኤሊሳማ፣
ኤሊዳሄ፣ ኤሊፉላት።

## ዳዊት ፍልስጥኤማውያንን ድል አደረገ

14፥8-17 ተጓ ምብ - 2 ሳሙ 5፥17-25

8ዳዊት በእስራኤል ሁሉ ላይ ተቀብቶ
*መንገሡን* ፍልስጥኤማውያን በሰሙ ጊዜ፣
እርሱን ፍለጋ በሙሉ ኀይላቸው ወጡ፤
ዳዊት ይህን ሰምቶ ስለ ነበር ሊገጥማቸው
ወጣ። 9በዚህ ጊዜ ፍልስጥኤማውያን መጥ
ተው የራፋይምን ሸለቆ ወረሩ። 10ስለዚህ
ዳዊት፣ "ወጥቼ በፍልስጥኤማውያን ላይ
አደጋ ልጣልን? አንተስ በእጄ አሳልፈህ
ትሰጣቸዋለህን? ሲል እግዚአብሔርን ጠየቀ።
*እግዚአብሔርም*፣ "አዎን ውጣ! በእጅህ
አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ" ብሎ መለሰለት።
11ስለዚህ ዳዊትና ሰዎቹ ወደ በኣልፐራሲም
ወጡ፤ በዚያም ድል አደረጋቸው። ዳዊትም፣
"ውሃ ነድሎ እንደሚወጣ ሁሉ እግዚአብሔ
ርም ጠላቶቼን በእጄ አፈረሳቸው" አለ፤
ከዚህም የተነሣ ያን ቦታ "በኣልፐራሲም"
ብለው ሰየሙት። 12ፍልስጥኤማውያን አማ
ልክቶቻቸውን በዚያው ጥለዋቸው ስለ ነበር፣
ዳዊት በእሳት እንዲያቃጥሏቸው አዘዘ።
13ፍልስጥኤማውያን ሸለቆውን እንደ ገና
ወረሩ፤ 14ዳዊትም እንደ ገና እግዚአብሔ
ርን ጠየቀ። እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል
መለሰለት "ዙሪያውን ከበህ በሾላው ዛፍ ፊት
ለፊት አደጋ ጣልባቸው እንጂ በቀጥታ
ወደ ላይ አትውጣ፤ 15በሾላው ዐናት ላይ
የሰልፍ ድምፅ ስትሰማ ወዲያውኑ ለጦር
ነት ውጣ፤ ይህም የፍልስጥኤማውያንን ሰራ
ዊት ለመምታት እግዚአብሔር በፊትህ
መጥቶአል ማለት ነውና።"16ስለዚህ ዳዊት
እግዚአብሔር እንዳለው አደረገ፤ ከገባዖን
ጀምሮ እስከ ጌዝር ድረስ ፍልስጥኤማው
ያንን መቷቸው።

14፥1
1ነገ5፥6፤
1ዜና17፥6፤22፥4፤
2ዜና2፥3፤
ዕዝ3፥7፤ሐጌ1፥8
14፥2
ዘኍ24፥7፤ዘዳ26፥19
14፥3 1ዜና3፥1
14፥4 1ዜና3፥9
14፥8 1ዜና11፥1
14፥9 ቍ13፤
ኢሱ15፥8፤
1ዜና11፥15
14፥11
መዝ94፥16፤
ኢሳ 28፥21
14፥12
ዘፀ32፥20፤ኢሱ7፥15
14፥13 ቍ9
14፥16
ኢሱ9፥3፤10፥33
14፥17 ዘፀ15፥14-
16፤ዘዳ2፥25፤
ኢሱ6፥27፤
መዝ2፥1-12
15፥1
2ሳሙ6፥17፤1ዜና16፥
1፤17፥1፤መዝ132፥1-18
15፥2
ዘኍ3፥6፤4፥15፤
ዘዳ 10፥8፤31፥9፥25፤
1ዜና16፥4፤23፥13፤
2ዜና5፥5፤29፥11፤
31፥2፤ መዝ134፥1፤
135፥2
15፥3 1ዜና13፥5
15፥4 ዘኍ3፥17-20
15፥5 1ዜና6፥24
15፥8 ዘፀ6፥22
15፥9 ዘፀ6፥18
15፥11
1ሳሙ22፥20፤ዜና12፥28
15፥12 ዘፀ29፥1፤
30፥19-21፤30፤
40፥31-32፤ዘሌ11፥44
15፥13
ዘሌ5፥10፤1ነገ8፥4፤
1ዜና13፥11
15፥15
ዘፀ25፥14፤2ሳሙ6፥7

17ከዚህም የተነሣ የዳዊት ዝና በየአገሩ
ሁሉ ተሰማ፤ *እግዚአብሔርም መንግሥ
ታት* ሁሉ እንዲፈሩት አደረገ።

## ታቦቱ ወደ ኢየሩሳሌም ተወሰደ

15፥25-16፥3 ተጓ ምብ - 2ሳሙ 6፥12-19

15 ዳዊት በስሙ በተጠራችው ከተማ
ለራሱ ቤቶችን ሠራ፤ ለእግዚአብሐ
ር ታቦት ቦታ አዘጋጅቶ ድንኳን ተከለ።
2ከዚያም ዳዊት፣ "የእግዚአብሔርን ታቦት
እንዲሸከሙና ለዘላለም በፊቱ እንዲያገለ
ግሉ እግዚአብሔር ከመረጣቸው ከሌዋውያን
በቀር፣ *የእግዚአብሔርን* ታቦት ማንም አይ
ሸከም" ሲል አዘዘ።
3ዳዊት *የእግዚአብሔርን* ታቦት ወዳዘጋ
ጀለት ስፍራ እንዲያመጡ እስራኤልን ሁሉ
በኢየሩሳሌም ሰበሰበ። 4የአሮንን ዘሮችና
ሌዋውያኑንም በአንድነት ሰበሰበ፤
5ከቀዓት ዘሮች፣
አለቃውን ኡርኤልንና አንድ መቶ
ሃያ የሥጋ ዘመዶቹን፤
6ከሜራሪ ዘሮች፣
አለቃውን ዓሣያንና ሁለት መቶ ሃያ
የሥጋ ዘመዶቹን፤
7ከጌድሶን ዘሮች፣
አለቃውን ኢዮኤልንና አንድ መቶ
ሠላሳ የሥጋ ዘመዶቹን፤
8ከኤሊጻፋን ዘሮች፣
አለቃውን ሸማያንና ሁለት መቶ
የሥጋ ዘመዶቹን፤
9ከኬብሮን ዘሮች፣
አለቃውን ኤሊኤልንና ሰማንያ የሥጋ
ዘመዶቹን፤
10ከዑዝኤል ዘሮች፣
አለቃውን አሚናዳብንና አንድ መቶ
ዐሥራ ሁለት የሥጋ ዘመዶቹን።
11ከዚያም ዳዊት ካህናቱን ሳዶቅንና
አብያታርን፣ ሌዋውያኑን ኡርኤልን፣ ዓሣ
ያን፣ ኢዩኤልን፣ ሸማያን፣ ኤሊኤልንና
አሚናዳብን ጠርቶ፣ 12እንዲህ አላቸው፤
"እንግዲህ እናንተ የሌዋውያን ቤተ ሰብ
አለቆች ስለ ሆናችሁ፣ እናንተና ወንድሞ
ቻችሁ ሌዋውያን ራሳችሁን ቀድሱ፤ ከዚ
ያም የእስራኤልን አምላክ *የእግዚአብሐ
ርን* ታቦት ወዳዘጋጀሁለት ቦታ አምጡ።
13የአ ምላካችን *የእግዚአብሔር* ቍጣ
በላያችን ላይ እንዲህ የነደደው እናንተ
ሌዋውያኑ ቀድሞም ስላላመጣችሁት ነው፤
እኛም ብንሆን ምን ማድረግ እንዳለብን
በታዘ ዘው መሠረት አልጠ
የቅነውም።"14ስለዚህ ካህናቱና ሌዋውያኑ
የእስራኤልን አምላክ *የእግዚአብሔርን*
ታቦት ለማምጣት ራሳቸ ውን ቀደሱ።
15ሙሴ በእግዚአብሔር ቃል እን ዳዘዘው፣

ሌዋውያኑ የእግዚአብሔርን ታቦት
በትከሻቸው ላይ በመሎጊያዎች አድርገው
ተሸከሙ፡፡
16ዳዊትም በዜማ መሣሪያ ማለትም
በመሰንቆ፣ በበገናና በጸናጽል እየታጀቡ
የደስታ ዜማዎችን የሚያዜሙ መዘምራ
ንን ከወንድሞቻቸው መካከል እንዲሾሙ
ለሌዋውያኑ መሪዎች ነገራቸው፡፡
17ስለዚህ ሌዋውያኑ የኢዮኤልን ልጅ
ኤማንን ሾሙ፤ ከወንድሞቹም የበራክያን
ልጅ አሳፍን፣ ከወንድሞቻቸው ከሜራሪ
ዘሮች የቂሳን ልጅ ኤታንን ሾሙ፤ 18ከእነ
ርሱም ጋር ወንድሞቻቸው በደረጃ ተሾሙ፤
እነርሱም ዘካርያስ[ዐ]፣ ያዝኤል፣ ሰሚራ
ሞት፣ ይሒኤል፣ ዑኒን፣ ኤልያብ፣ በና
ያስ፣ መዕሤያን፣ መቲትያ፣ ኤሊፍሌሁ፣
ሚቅኔያ፣ ደግሞም በር ጠባቂዎቹ ዖቤድ
ኤዶምና ይዒኤል[ዘ] ነበሩ፡፡
19መዘምራኑ ኤማን፣ አሳፍና ኤታን በናስ
ጸናጽል ድምፁን ከፍ አድርገው እንዲያ
ሰሙ ተሾሙ፤ 20ዘካርያስ፣ ዓዝኤል፣ ሰሚ
ራሞት፣ ይሒኤል፣ ዑኒ፣ ኤልያብ፣ መዕ
ሤያና በናያስ ደግሞ በአላሞት[ዠ] ቅኝት
መሰንቆ ይገርፉ ነበር፡፡ 21እንዲሁም መቲ
ትያ፣ ኤሊፍሌሁ፣ ሚቅኔያ፣ ዖቤድኤ
ዶም፣ ይዒኤል፣ ዓዛዝያ፣ በሺሚኒት[ዠ]
ቅኝት በገና ይደረድሩ ነበር፡፡ 22የዝ
ማሬው ኀላፊ ሌዋዊው አለቃ ክናንያ
ነበረ፤ ይህን ኀላፊነት የወሰደው በዝማሬ
የተካነ ስለ ነበር ነው፡፡
23በራክያና ሕልቃና የታቦቱ በር ጠባ
ቂዎች ነበሩ፤ 24ካህናቱ ሰበኒያ፣ ኢዮሣፍጥ፣
ናትናኤል፣ ዓማሣይ፣ ዘካርያስ፣ በናያስና
አልዓዛር በእግዚአብሔር ታቦት ፊት
መለከት ይነፉ ነበር፡፡ ዖቤድኤዶምና ይሒ
ያ ደግሞ የታቦቱ በር ጠባቂዎች ነበሩ፡፡
25ስለዚህ ዳዊት የእስራኤል ሽማግሌዎ
ችና የሻለቃው አዛዦች የእግዚአብሔርን
የቃል ኪዳኑን ታቦት ከዖቤድኤዶም ቤት
በደስታ ለማምጣት ሄዱ፡፡ 26የእግዚአብሔርን
የቃል ኪዳን ታቦት የተሸከሙትን ሌዋ
ውያን እግዚአብሔር ረድቶአቸው ስለ ነበር፣
ሰባት ኮርማዎችና ሰባት አውራ በጎች
ሠዉ፡፡ 27ታቦቱን የተሸከሙት ሌዋውያን
ሁሉ፣ መዘምራኑና የመዘምራኑ አለቃ
ከናንያ የለበሱትን ዐይነት ከቀጭን በፍታ
የተሠራ ልብስ ዳዊትም ለብሶ ነበር፤
እንዲሁም ከበፍታ የተሠራ ኤፉድ ለብሶ
ነበር፡፡ 28በዚህ ሁኔታ መላው የእስራ
ኤል ሕዝብ በሆታ ቀንደ መለከትና እም
ቢልታ እየተነፋ፣ ጸናጽል እየጸነጸሉ፣ መሰ
ንቆና በገና እየደረደሩ የእግዚአብሔርን
የኪዳኑን ታቦት አመጡ፡፡

15፥16 1ዜና6፥31፤13፥8፤23፥5፤2ዜና7፥6፤29፥26፤ዕዝ2፥41፤ነህ11፥23፤12፥27፡36፤ኢዮ21፥12፤መዝ68፥25፤150፥5፤አሞ6፥5
15፥17 1ዜና6፥33፡39፡44
15፥18 2ሳሙ6፥10፤1ዜና26፥4-5
15፥19 1ዜና16፥41፤25፥6
15፥24 2ዜና5፥12፤7፥6፤29፥26
15፥25 2ዜና1፥4፤5፥2፤ኤር3፥16
15፥26 ዘኁ23፥1-4፡29
15፥27 1ሳሙ2፥18
15፥28 ዘፀ19፥13፤1ነገ1፥39፤1ዜና9፥1፤ዘካ4፥7
16፥1 1ዜና15፥1
16፥2 ዘፀ39፥43፤ዘኁ6፥23-27
16፥3 ኢሳ16፥7
16፥4 1ዜና15፥2
16፥7 መዝ47፥7
16፥8 ቍ34፤2ነገ19፥19፤መዝ107፥1፤118፥1፤136፥1
16፥9 ዘፀ15፥1፤ መዝ7፥17
16፥10 መዝ8፥1፤29፥2፤66፥2
16፥11 ቍ10፤1ዜና28፥9፤2ዜና7፥14፤14፥4፤15፥2፡12፤1612፤18፥4፤20፥4፤34፥3 መዝ24፥6፤27፥8፤105፥4፤119፥2፡58፤ምሳ 8፥17

29የእግዚአብሔር የኪዳኑ ታቦት ወደ
ዳዊት ከተማ ሲገባ የሳኦል ልጅ ሚልኮል
በመስኮት ሆና ተመለከተች፤ ንጉሡ ዳዊት
ደስ ብሎት ሲያሸበሽብ አይታ በልቧ ናቀ
ችው፡፡

16 ከዚያም የእግዚአብሔርን ታቦት
አምጥተው ዳዊት በተከለለት
ድንኳን ውስጥ አኖሩት፤ የሚቃጠል መሥ
ዋዕትና የኅብረት መሥዋዕትም[የ] በእግዚአብ
ሔር ፊት አቀረቡ፡፡ 2ዳዊት የሚቃጠለ
ውን መሥዋዕትና የኅብረቱን መሥዋዕት
ከሠዋ በኋላ፣ ሕዝቡን በእግዚአብሔር
ስም ባረከ፡፡ 3ከዚያም ለእስራኤል ሁሉ
ለወንዱም ለሴቱም አንዳንድ ሙልሙል
ዳቦ፣ አንዳንድ ጥፍጥፍ ተምር፣ ሙዳ
ሙዳ ሥጋና አንዳንድ ጥፍጥፍ ዘቢብ ሰጠ
፡፡
4በእግዚአብሔር ታቦት ፊት እንዲያገለ
ግሉና ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር
ልመና፣ ምስጋናና ውዳሴ እንዲያቀርቡ
ከሌዋውያን ሰዎች ሾመ፤ 5አለቃው አሳፍ
ነበረ፤ ከእርሱ ቀጥሎ ዘካርያስ ሁለተኛ
ሆኖ ተሾመ፤ ከዚያም ይዒኤል፣ ሰሚራ
ሞት፣ ይሒኤል፣ መቲትያ፣ ኤልያብ፣
በናያስ፣ ዖቤድኤዶም፣ ይዒኤል ተሾሙ፤
እነርሱም በመሰንቆና በበገና ይዘምሩ
ነበር፤ አሳፍ ደግሞ ጸናጽል የሚጸነጽል ሆኖ
ተመደበ፡፡ 6እንዲሁም ካህናቱ በናያስና
የሕዚኤል ዘወትር በእግዚአ ብሔር የኪዳኑ
ታቦት ፊት መለከት እንዲነፉ ተመደቡ፡፡

## የዳዊት የምስጋና መዝሙር

16፥8-22 ተጓ ምብ - መዝ 105፥1-15
16፥23-33 ተጓ ምብ - መዝ 96፥1-13
16፥34-36 ተጓ ምብ - 106፥ 1፡47-48

7በዚያም ቀን ዳዊት በመጀመሪያ ለአ
ሳፍና ለሥራ ጓደኞቹ ይህን የእግዚአብሔር
ምስጋና መዝሙር ሰጠ፤

8ለእግዚአብሔር ምስጋና አቅርቡ፤
ስሙንም ጥሩ፤
ለአሕዛብ ያደረገውን ሁሉ ንገሩ፤
9ዘምሩለት፤ ውዳሴም አቅርቡለት፤
ድንቅ ሥራውን ሁሉ ንገሩ፤
10በቅዱስ ስሙ ተጓደዱ፤
እግዚአብሔርን የሚፈልጉ ሁሉ፣
ልባቸው ሐሤት ያድርግ፡፡
11ወደ እግዚአብሔርና ወደ ኀይሉ
ተመልከቱ፤

[ዐ]18 ሦስት የዕብራይስጥ ቅጆችና በርካታ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች (እንዲሁም ቍ20 እና 1ዜና 165 ይመ)፤ በርካታ የዕብራይስጥ ቅጆች *የዘካርያስ ልጅ ወይም ዘካርያስ፣ ቤን* ይላሉ፡፡
[ዘ]18 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም (እንዲሁም ቍ21) ግን *ይዒኤልና ዓዛዝያ* ይላል፡፡
[ዠ]21፤22 ምናልባት የዜማ ስም ነው፡፡
[የ]1 በዚህና በቍጥር 2 ላይ በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል፡፡

ዘወትር ፊቱን ፈልጉ፡፡
12ያደረጋቸውን ድንቅ ሥራዎች፣
ታምራቱንና የሰጠውንም ፍርድ አስታውሱ፤
13እናንተ የባሪያው የእስራኤል ዘሮች፣
እናንተ የተመረጣችሁ የያዕቆብ ልጆች፡፡
14እርሱ እግዚአብሔር አምላካችን ነው፤
ፍርዱም በምድር ሁሉ ላይ ነው፤
15ኪዳኑን እስከ ዘላለም፣
ያዘዘውንም ቃል እስከ ሺህ ትውልድ
ያስባል፡፡
16ከአብርሃም ጋር የገባውን ቃል ኪዳን፣
ለይስሐቅ የማለውን መሐላ፡፡
17ይህንንም ለያዕቆብ ሥርዐት አድርጎ
አጸና፤
ለእስራኤልም የዘላለም ኪዳን
አደረገ፤
18እንዲህ ሲል፣ "የምትወርሰው ርስት
እንዲሆን፣
የከነዓንን ምድር ለአንተ እሰጣለሁ፡፡"
19ቍጥራቸው ገና ጥቂት ሳለ፣
በእርግጥ ጥቂትና መጻተኞች ሳሉ፣
20ከአንዱ ሕዝብ ወደ ሌላው ሕዝብ፣
ከአንዱም መንግሥት ወደ ሌላው
መንግሥት ተንከራተቱ፡፡
21ማንም እንዲጨቍናቸው
አልፈቀደም፤
ስለ እነርሱም ነገሥታትን ገሠጸ፤
22እንዲህ ሲል፤ "የቀባኋቸውን
አትንኩ፤
በነቢያቴ ላይ ክፉ አታድርጉ፡፡
23ምድር ሁሉ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤
ማዳኑንም ዕለት ዕለት ዐወጁ፡፡
24ክብሩን ለአሕዛብ ተናገሩ፤
ድንቅ ሥራዎቹን ለሕዝቦች ሁሉ ንገሩ፡፡
25እግዚአብሔር ታላቅ ነው፤
ምስጋናውም ብዙ ነው፤
ከአማልክትም ሁሉ በላይ ሊፈራ የሚገ
ባው ነው፡፡
26የአሕዛብ ሁሉ አማልክት ጣዖታት
ናቸው፤
እግዚአብሔር ግን ሰማያትን ሠራ፡፡
27በፊቱ ክብርና ሞገስ አለ፤
ብርታትና ደስታም በማደሪያው ስፍራ፡፡
28የአሕዛብ ወገኖች ለእግዚአብሔር ስጡ፤
ክብርና ኀይልን ለእግዚአብሔር
አምጡ፡፡
29ለስሙ የሚገባውን ክብር ለእግዚአብሔር
ስጡ፤
መባ ይዛችሁ በፊቱ ቅረቡ፤
በቅድስናውም ክብሩ ለእግዚአብሔር[ዶ]
ስገዱ፡፡
30ምድር ሁሉ በፊቱ ትንቀጥቀጥ፤
ዓለም በጽኑ ተመሥርታለች፤
አትናወጥምም፡፡
31ሰማያት ደስ ይበላቸው፤ ምድር ሐሤት
ታድርግ፤
በአሕዛብም መካከል፤ "እግዚአብሔር
ነገሠ!" ይበሉ፡፡
32ባሕርና በውስጧ ያለው ሁሉ ይናወጥ፤
ሜዳዎችና በእርሷ ላይ ያሉ ሁሉ
ሐሤት ያድርጉ፡፡
33ያን ጊዜ የዱር ዛፎች በእግዚአብሔር
ፊት ደስ ይላቸዋል፤
በደስታ ይዘምራሉ፤
በምድረ በዳ ላይ ሊፈርድ ይመጣልና፡፡
34ቸር ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ፤
ፍቅሩም ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል፡፡
35 "አዳኛችን እግዚአብሔር ሆይ ታደገን፤
ለቅዱስ ስምህ ምስጋና እንድናቀርብ፣
በምስጋናህም እንድንከብር ሰብስበን፤
ከአሕዛብም መካከል ታደገን"
ብላችሁ ጩኹ፡፡
36ከዘላለም እስከ ዘላለም፣
ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር
ምስጋና ይሁን፡፡
ከዚያም ሕዝቡ ሁሉ፣ "አሜን፤ እግዚአ
ብሔር ይመስገን" አሉ፡፡
37ዳዊትም ለእያንዳንዱ ቀን በተመደ
በው መሠረት ዘወትር እንዲያገለግሉ አሳ
ፍንና የሥራ ባልደረቦቹን በዚያው በእግዚ
አብሔር ቃል ኪዳን ታቦት ፊት ተዋቸው፡፡
38እንዲሁም ዖቤድኤዶምና ሥልሳ ስም
ንቱ የሥራ ባልደረቦቹ አብረዋቸው እንዲ
ያገለግሉ በዚያው ተዋቸው፡፡ የኤዶታም
ልጅ ዖቤድኤዶምና ሖሳ የቅጥሩ በር ጠባ
ቂዎች ሆኑ፡፡
39ዳዊት ካህኑን ሳዶቅንና የሥራ ባልደረ
ቦቹን ካህናት በገባዖን ከፍተኛ ቦታ ላይ
በሚገኘው በእግዚአብሔር ድንኳን ተዋ
ቸው፤ 40የተዋቸውም ለእስራኤል በተሰጠው
ትእዛዝ መሠረት በእግዚአብሔር ሕግ
እንደ ተጻፈው ሁሉ በመሠዊያው ላይ
የሚቀርበውን የሚቃጠል መሥዋዕት ጧትና
ማታ በየጊዜው እንዲያቀርቡ ነው፡፡ 41እን
ዲሁም "ፍቅሩ ለዘላለም ነውና" እያሉ እን
ዲያቀርቡ ኤማንና ኤዶታም እንዲሁም
ተመርጠውና ስማቸው ተመዝግቦ የተመ
ደቡ ሌሎችም አብረዋቸው ነበሩ፡፡
42ድምፀ መለከቱንና ጸናጽሉን ለማሰ
ማት፣ደግሞም መንፈሳዊ መዝሙር ሲዘመር
ለሚጠቀሙ ባቸው ሌሎች መሣሪያዎች
ኀላፊዎቹ ኤማ

16፥12 ዘጸ4፥34፤መዝ77፥11፤78፥43
16፥14 ኢሳ4፥4፤26፥9
16፥15 ዘፍ8፥1፤መዝ98፥3፤111፥5፤115፥12፤136፥23
16፥16 ዘፍ12፥7፤15፥18፤22፥16-18
16፥17 ዘፍ35፥9-12
16፥18 ዘፍ13፥14-17
16፥19 ዘጻ7፥7
16፥20 ዘፍ20፥13
16፥21 ዘፍ12፥17፤20፥3፤ዘፀ7፥15-18፤መዝ9፥5
16፥22 ዘፍ20፥7
16፥24 ኢሳ42፥12፤66፥19
16፥25 ዘፀ18፥11፤ዘዳ 32፥39፤2 ዜና 2፥5፤መዝ18፥3፤48፥1፤76፥7፤89፥7፤135፥5፤ኢሳ40፥25
16፥26 መዝ8፥3፤102፥25
16፥28 መዝ29፥1-2
16፥29 2ዜና20፥21፤መዝ8፥1፤29፥1-2
16፥30 መዝ2፥11፤33፥8፤76፥8፤93፥1፤99፥1፤114፥7
16፥31 መዝ9፥7፤47፥8፤93፥1፤97፥1፤99፥1፤146፥10፤ኢሳ44፥23፤49፥13፤52፥7፤ሰቆ5፥19
16፥32 ዘፀ20፥11፤ኢሳ42፥10
16፥33 1ሳሙ2፥10፤መዝ7፥8፤96፥10፤98፥9፤110፥6፤ኢሳ2፥4፤14፥8፤55፥12
16፥34 ቀኊ8፤2ዜና 5፥13፤7፥3፤ዕዝ3፥11፤መዝ 25፥7፤ 34፥8፤100፥5፤105፥1፤135፥3 136፥1-26፤145፥9፤ኢሳ12፥4፤ኤር33፥11፤ናሆ1፥7
16፥35 ዘጻ32፥15፤መዝ18፥46፤38፥22፤ሚክ7፥7
16፥36 1ነገ8፥15፤መዝ72፥18-19
16፥37 2ዜና8፥14
16፥38 1ዜና13፥13፤26፥4-5፡10፤
16፥39 ኢሱ9፥3፤1ሳሙ2፥35፤2ሳሙ8፥17፤1ዜና12፥28፤2ዜና1፥3
16፥40 ዘፀ29፥38፤ዘኍ28፥1-8
16፥41 1ዜና15፥19
16፥42 1ዜና25፥3፤2ዜና7፥6

ዶ29 ወይም፣ ከክብሩ ጋር ለእግዚአብሔር

ንና ኤዶታም ነበሩ፤ የኤዶታምም ልጆች
በሩን እንዲጠብቁ ተመድበው ነበር።
43ከዚያም ሕዝቡ ተነሣ፤ እያንዳንዱም
ወደየቤቱ ሄደ። ዳዊትም ቤተ ሰቡን ለመ
ባረክ ወደ ቤቱ ተመለሰ።

**እግዚአብሔር ለዳዊት የሰጠው ተስፋ**

17፥1-15 ተጓ ምብ - 2 ሳሙ 7፥1-17

17 ዳዊት በቤተ መንግሥቱ ተደላ
ድሎ በተቀመጠበት ጊዜ፣ ነቢዩ
ናታንን “እነሆ እኔ ከዝግባ በተሠራ ቤት
ውስጥ እኖራለሁ፤ የእግዚአብሔር የኪዳኑ
ታቦት ግን በድንኳን ውስጥ ይኖራል” አለው።
2ናታንም ለዳዊት፣ “እግዚአብሔር ከአንተ
ጋር ስለ ሆነ፣ ያሰብከውን ሁሉ አድርግ” ሲል
መለሰለት።
3በዚያም ሌሊት የእግዚአብሔር ቃል ወደ
ናታን መጥቶ እንዲህ አለው፤
4“ሂድና ለባሪያዬ ለዳዊት እንዲህ
ብለህ ንገረው፤ ‘እግዚአብሔር የሚ
ለው ይህን ነው፤ እኔ የምኖርበትን
ቤት የምትሠራልኝ አንተ አይደለ
ህም። 5እስራኤልን ከግብፅ ካወጣሁ
በት ቀን ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ፣
ከአንዱ ድንኳን ወደ ሌላው ድንኳን፣
ከአንዱ ማደሪያ ወደ ሌላው ማደሪያ
እሄድ ነበር እንጂ፣ በቤት ውስጥ
አልኖርሁም። 6ከእስራኤላውያን ጋር
በሄድሁባቸው ቦታዎች ሁሉ፣ ሕዝ
ቤን እንዲጠብቁ ላዘዝኋቸው መሪዎ
ቻቸው[፳] ከቶ፣ “ለምን ከዝግባ ዕን
ጨት ቤት አልሠራችሁልኝም ያለሁ
በት ጊዜ አለን?”
7“እንግዲህ አሁንም ለባሪያዬ ለዳ
ዊት እንዲህ ብለህ ንገረው፤ “የሰራ
ዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚለው
ይህን ነው፤ ‘የሕዝቤ የእስራኤል ገዥ
እንድትሆን በጎችን ከመጠበቅና ከመ
ከተል አንሥቼ ወሰድሁህ። 8በሄድህ
በት ሁሉ ከአንተ አልተለየሁም፤ ጠላ
ቶችህንም ሁሉ ከፊትህ አጠፋሁልህ፤
አሁንም ስምህን እንደ ምድር ታላላቅ
ሰዎች ስም ገናና አደርገዋለሁ። 9ለሕ
ዝቤ ለእስራኤል መኖሪያ ስፍራ
እሰጠዋለሁ፤ የራሳቸውም መኖሪያ
ስፍራ እንዲኖራቸው ከእንግዲህም
በኋላ እንዳይናወጡ አደርጋቸዋለሁ።
ክፉ ሰዎች በመጀመሪያ እንዳደረጉት
ሁሉ፣ ከእንግዲህ አይጨቁኗቸ
ውም፤ 10ከዚህ ቀደም በሕዝቤ በእስራ
ኤል ላይ መሪዎች በሾምሁ ጊዜ
ጨቋኞቹ ያደረጉትን ዛሬ አያደርጉ

17፥1 1ዜና15፥1
17፥2 1ዜና22፥7፤
28፥2፤2ዜና6፥7
17፥4
1ዜና22፥10፤28፥3
17፥6 1ዜና14፥1
17፥7 2ሳሙ6፥21

17፥10 መሳ2፥16
17፥12
1ነገ5፥5፤1ዜና22፥10፤
2ዜና7፥18፤13፥5
17፥13
1ዜና28፥6፤
ሉቃ1፥32፤
2ቆሮ6፥18፤ዕብ1፥5
17፥14
1ነገ2፥12፤1ዜና28፥5፤
29፥23፤2ዜና9፥8፤
መዝ132፥11፤
ኤር33፥17
17፥19
2ሳሙ7፥16-17፥25፤
2ነገ20፥6፤ኢሳ9፥7፤
37፥35፤55፥3
17፥20 ዘፀ8፥10፤
9፥14፤15፥11፤
ኢሳ44፥6፤46፥9
17፥21 ዘፀ6፥6
17፥22 ዘፀ19፥5-6

ትም፤ ጠላቶቻችሁን ሁሉ አዋርዳ
ቸዋለሁ።
“ ‘እግዚአብሔር ቤት እንደሚሠ
ራልህ በግልጽ እነግርሃለሁ፤ 11ዘመን
ህን ጨርሰህ ወደ አባቶችህ በምትሄ
ድበት ጊዜ፣ ከአብራክህ ከተከፈሉት
ልጆችህ አንዱ በእግርህ እንዲተካ
አደርጋለሁ፤ መንግሥቱንም አጸናለታ
ለሁ፤ 12ቤት የሚሠራልኝም እርሱ
ነው፤ እኔም ዙፋኑን ለዘላለም አጸና
ለሁ። 13አባት እሆነዋለሁ፤ እርሱም
ልጅ ይሆነኛል፤ ጽኑ ፍቅሬን ከአንተ
በፊት ከነበረው ላይ እንደወሰድሁ፣
ከእርሱ ላይ ከቶ አልወስድም። 14በቤ
ቴና በመንግሥቴ ላይ ለዘላለም አኖ
ረዋለሁ፤ ዙፋኑም ለዘላለም ይጸናል።” ’
15ናታንም የዚህን ሁሉ ራእይ ቃል ለዳ
ዊት ነገረው።

**የዳዊት ጸሎት**

17፥16-27 ተጓ ምብ - 2 ሳሙ 7፥18-29

16ከዚያም ንጉሥ ዳዊት ገባ፤ በእግዚአ
ብሔር ፊት ተቀምጦም እንዲህ አለ፤

“እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፤ ለመሆኑ
እስከዚህ ያደረስኸኝ እኔ ማን ነኝ?
ቤተ ሰቤስ ምንድን ነው? 17አምላክ
ሆይ፤ ይህ በፊትህ በቂ እንዳልሆነ
ቈጥረህ ስለ ወደፊቱ የባሪያህ ቤት
ተናገርህ። እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፤
እኔንም ከሰዎች ሁሉ እጅግ የከበረ
ሰው አድርገህ ተመለከትኸኝ።
18“ባሪያህን ስላከበርኸው፣ ዳዊት
ከዚህ በላይ ምን ማለት ይችላል? ባሪ
ያህን እኮ ታውቀዋለህ፤ 19እግዚአብሔር
ሆይ፤ ስለ ባሪያህ ብለህና እንደ ፈቃ
ድህም መሠረት ይህን ታላቅ ነገር
አድርገሃል፤ እነዚህም ታላላቅ ተስፋ
ዎች ሁሉ እንዲታወቁ አደረግህ።
20 “አቤቱ፤ እንደ አንተ ያለ የለም፤
በጆሮአችን እንደ ሰማነው ሁሉ ከአ
ንተ በቀር አምላክ የለም’ 21ከግብፅ
ተቤዥተህ እንዳወጣኸው እንደ ሕዝ
ብህ እንደ እስራኤል ያለ ማን አለ?
እነርሱ እግዚአብሔር ለራሱ ሊቤዣ
ቸው ከምድር ሕዝቦች መካከል የመረ
ጣቸው ናቸው፤ በሕዝብህም ፊት ታላ
ላቅና አስፈሪ ነገሮችን በማድረግ መን
ግሥታትን በፊታቸው አሳደድህ።
22ሕዝብህንም እስራኤልን ለዘላለም የ
ራስህ ሕዝብ አደረግኸው፤ እግዚአ
ብሔር ሆይ፤ አንተም አምላክ ሆንህለት።

[፳]በዚህና በቍጥር 10 ላይ በትውፊት፣ መሳፍንት ይባላል

23“እግዚአብሔር ሆይ፤ አሁንም ስለ
ባሪያህና ስለ ቤቱ የሰጠኸው ተስፋ
ለዘላለም የጸና ይሁን፤ የሰጠኸውንም
ተስፋ ፈጽም፤ 24ይህም ስምህ ጸንቶ
እንዲኖርና ለዘላለምም ታላቅ እንዲ
ሆን ነው። ከዚያም ሰዎች “የእስራ
ኤል አምላክ የሰራዊት ጌታ እግዚ
አብሔር በእውነት የእስራኤል አምላክ
ነው!” ይላሉ፤ የባሪያህ የዳዊትም ቤት
በፊትህ የጸና ይሆናል።
25“አምላኬ ሆይ፤ ቤት እንደምትሠ
ራለት ለባሪያህ ገልጸህለታል፤ ስለዚህ
ባሪያህ ወደ አንተ ለመጸለይ ድፍረት
አገኘ። 26እግዚአብሔር ሆይ፤ በእውነት
አንተ አምላክ ነህ፤ ይህንንም መልካም
ተስፋ ለባሪያህ ሰጥተሃል። 27በፊትህ
ለዘላለም እንዲኖር አሁንም የባሪያህን
ቤት ልትባርክ ወደሃል፤ እግዚአብሔር
ሆይ፤ የባረክኸው አንተ ስለ ሆንህ፣
ለዘላለም የተባረከ ይሆናል።”

## ዳዊት የተቀዳጃቸው ድሎች

18፥1-13 ተጓ ምብ - 2 ሳሙ 8፥1-14

18 ከዚህ በኋላ ዳዊት ፍልስጥኤማው
ያንን ድል መትቶ ተገዢ አደ
ረጋቸው፤ ጌትንና በዙሪያዋም የሚገኙትን
መንደሮች ከፍልስጥኤማውያን እጅ ወሰደ።
2እንዲሁም ዳዊት ሞዓባውያንን ድል
አደረጋቸው፤ እነርሱም ገባሮቹ ሆኑ፤ ግብ
ርም አመጡለት።
3ከዚህም በላይ ዳዊት በኤፍራጥስ ወንዝ
አጠገብ የነበረውን ግዛት ለመቈጣጠር
በሄደ ጊዜ፣ የሱባን ንጉሥ አድርአዛርን
እስከ ሐማት ድረስ ዘልቆ ወጋው። 4ዳዊ
ትም አንድ ሺህ ሠረገላ፣ ሰባት ሺህ ፈረ
ሰኞና ሃያ ሺህ እግረኛ ወታደር ማረከ፤
አንድ መቶ የሠረገላ ፈረሶች ብቻ አስ
ቀርቶ የቀሩትን ቋንጃቸውን ቈረጠ።
5ሶርያውያንም የሱባን ንጉሥ አድርአዛ
ርን ለመርዳት ከደማስቆ በመጡ ጊዜ፣
ከእነርሱ ሃያ ሁለት ሺህ ሰው ገደለ። 6ከዚ
ያም በሶርያ ግዛት ውስጥ ባለችው በደ
ማስቆ የጦር ሰፈር አቋቋመ፤ ሶርያውያን
ገባሮቹ ሆኑ፤ ግብርም አመጡለት። እግዚ
አብሔርም ዳዊትን በሄደበት ሁሉ ድል
አጐናጸፈው።
7ዳዊትም የአድርአዛር ጦር አለቆች ያነ
ገቡትን የወርቅ ጋሻ ወሰደ፤ ወደ ኢየሩሳሌ
ምም አመጣው። 8ዳዊት ከአድርአዛር ከተ
ሞች ከጢብሐትና ከኩን እጅግ ብዙ ናስ
ወሰደ፤ ሰሎሞን የናሱን ባሕር፣ ዐምዶቹ
ንና ልዩ ልዩ የናስ ዕቃዎቹን የሠራው

17፥23 1ነገ8፥25
17፥27
መዝ16፥11፤21፥6
18፥2 ዘኍ21፥29
18፥3
ዘፍ2፥14፤1ዜና19፥6
18፥4 ዘፍ49፥6
18፥5 2ነገ16፥9
18፥8
1ነገ7፥23፤2ዜና4፥2-5
18፥11
ዘኍ24፥18፡20
18፥12 1ነገ11፥15
18፥14
1ዜና11፥1፤29፥26
18፥15 2ሳሙ5፥6-8
18፥16
1ዜና6፥8፤24፥6
18፥17 1ሳሙ30፥14፤
2ሳሙ15፥18
19፥1
ዘፍ19፥38፤መሳ10፥17
፤11፥33፤2ዜና20፥1-
2፤ሶፎ2፥8-11
19፥3 ዘኍ21፥32

በዚሁ ነበር።
9የሐማት ንጉሥ ቶዑ ዳዊት የሱባን
ንጉሥ የአድርአዛርን ሰራዊት ሁሉ ድል
እንደ መታ ሲሰማ፣ 10እጅ እንዲነሣውና
ደስታውንም እንዲገልጥለት ልጁን አዶራ
ምን ወደ ንጉሥ ዳዊት ላከው፤ ቶዑ ከአ
ድርአዛር ጋር ብዙ ጊዜ ጦርነት ገጥሞ
ነበር። አዶራምም ከወርቅ፣ ከብርና ከናስ
የተሠሩ ልዩ ልዩ ዕቃዎች አመጣለት።
11ንጉሥ ዳዊት ከኤዶም፣ ከሞዓብ፣
ከአሞናውያን፣ ከፍልስጥኤማውያንና ከአ
ማሌቃውያን ከእነዚህ ሁሉ መንግሥታት
የማረከውን ወርቅና ብር ከዚህ ቀደም እን
ዳደረገው ሁሉ፣ እነዚህንም ዕቃዎች ለእግ
ዚአብሔር ቀደሰ።
12የጽሩያ ልጅ አቢሳ በጨው ሸለቆ ዐሥራ
ስምንት ሺህ ኤዶማውያን ገደለ። 13እር
ሱም በኤዶም የጦር ሰፈሮች አቋቋመ፤
ኤዶማውያንም ሁሉ ለንጉሥ ዳዊት ገባ
ሮች ሆኑ። እግዚአብሔርም ዳዊትን በሄ
ደበት ሁሉ ድል አጐናጸፈው።

## የዳዊት ሹማምት

18፥14-17 ተጓ ምብ - 2ሳሙ 8፥15-18

14ዳዊት በመላው እስራኤል ላይ ነገሠ፤
ለሕዝቡም ሁሉ ፍትሕንና ጽድቅን አሰ
ፈነላቸው። 15የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ የሰራ
ዊቱ አዛዥ ነበረ፤ የአሒሉድ ልጅ ኢዮሣ
ፍጥ ደግሞ የቤተ መዛግብቱ ኀላፊ ነበረ።
16የአኪጦብ ልጅ ሳዶቅና የአቤሜሌክ
ልጅ አብያታር ካህናት ነበሩ፤ ሱሳ ደግሞ
ጸሓፊ ነበረ። 17የዮዳሄ ልጅ በናያስ የከሊ
ታውያንና የፈሊታውያን አዛዥ ነበረ።
የዳዊት ወንዶች ልጆቹ ደግሞ ከንጉሡ
ቀጥሎ የበላይ ሹማምት ነበሩ።

## ከአሞናውያን ጋር የተደረገ ጦርነት

19፥1-19 ተጓ ምብ - 2 ሳሙ 10፥1-19

19 ከዚህ በኋላ የአሞናውያን ንጉሥ
ናዖስ ሞተ፤ ልጁም በእግሩ
ተተክቶ ነገሠ። 2ዳዊትም፣ “አባቱ ለእኔ
በጎ ነገር እንዳደረገልኝ እስቲ እኔም ለና
ዖስ ልጅ ለሐኖን በጎ ነገር ላድርግለት”
ብሎ አሰበ። ስለዚህ ዳዊት ስለ አባቱ
ሞት ሐዘኑን ለመግለጽ ወደ ሐኖን መል
ክተኞችን ላከ።
የዳዊት ሰዎች ሐዘናቸውን ለመግለጽ
ሐኖን ወደሚኖርበት ወደ አሞናውያን
ምድር በመጡ ጊዜ፣ 3የአሞናውያን መኳ
ንንት ለሐኖን “ዳዊት ሐዘኑን ለመግለጽ
ሰዎችን ወደ አንተ የላከው አባትህን
አክብሮ ይመስልሃልን? ሰዎቹ ወደ አንተ
የመጡት አገሪቱን ለመመርመር፣ ለመ

ሰለልና ለመያዝ አይደለምን?" አሉት።
4ስለዚህ ሐኖን የዳዊትን ሰዎች ይዞ ላጫ
ቸው፤ ልብሳቸውንም እስከ መቀመጫቸው
ድረስ መኻል ለመኻል ቀዶ ሰደዳቸው።
5በሰዎቹ ላይ የደረሰባቸውን ዳዊት በሰማ
ጊዜ እጅግ ዐፍረው ስለ ነበር፣ ወደ እነ
ርሱ መልክተኞችን ላከ፤ ንጉሡም፣ "ጢማ
ችሁ እስኪያድግ ድረስ በኢያሪኮ ቈዩና
ከዚያ በኋላ ትመጣለችሁ" አለ።
6አሞናውያን በዳዊት ዘንድ እንደ ተጠሉ
ባወቁ ጊዜ፣ ሐኖንና አሞናውያን ከመስ
ጴጦምያ[ገ]፣ ከአራምመዓካና ከሱባ ሠረገሎ
ችንና ፈረሰኞችን ለመከራየት አንድ ሺህ
መክሊት[ጠ] ብር ላኩ፤ 7ከዚያም ሠላሳ
ሁለት ሺህ ሠረገሎችንና ፈረሰኞችን እን
ዲሁም የመዓካን ንጉሥና ወታደሮች በገ
ንዘብ ቀጠሩ፤ እነርሱም መጥተው በሜ
ድባ አጠገብ ሲሰፍሩ፣ አሞናውያን ደግሞ
ከየከተሞቻቸው ተሰብስበው ለጦርነት ወጡ።
8ዳዊት ይህን ሲሰማ ኢዮአብንና መላ
ውን ተዋጊ ሰራዊት ላከ። 9አሞናውያንም
መጥተው ወደ ከተማቸው በሚያስገባው
በር ላይ ለጦርነት ተሰለፉ፤ የመጡት ነገ
ሥታት ደግሞ ብቻቸውን በሜዳው ላይ
ነበሩ።
10ኢዮአብም ከፊቱና ከኋላው ጦር
መኖሩን አየ፤ ስለዚህ በእስራኤል የታወቁ
ትን ጀግኖች መርጦ ሶርያውያንን እንዲ
ገጥሙ አሰለፋቸው። 11የቀሩትም ሰዎች
በወንድሙ በአቢሳ ሥር ሆነው አሞናው
ያንን እንዲገጥሙ አሰለፋቸው። 12ኢዮአ
ብም እንዲህ አለ፤ "ሶርያውያን ከበረቱ
ብኝ አንተ ትረዳኛለህ፤ አሞናውያን ከበረ
ቱብኝ ደግሞ እኔ እረዳሃለሁ። 13እንግዲህ
በርቱ፤ ስለ ሕዝባችንና ስለ አምላካችን
ከተሞች ብለን በጀግንነት እንዋጋ፤ እግዚ
አብሔርም ደስ ያሰኘውን ያድርግ።"
14ከዚያም ኢዮአብና አብረውት ያሉት
ወታደሮች ሶርያውያንን ለመውጋት ወደ
ፊት ገሠገሡ፤ ሶርያውያንም ከፊታቸው
ሸሹ። 15አሞናውያንም ሶርያውያን መሸሻ
ቸውን ሲያዩ፣ እነርሱም ከወንድሙ ከአ
ቢሳ ፊት ሸሽተው ወደ ከተማዪቱ ገቡ፤
ስለዚህ ኢዮአብ ወደ ኢየሩሳሌም ተመ
ለሰ።
16ሶርያውያን በእስራኤል መሸነፋቸውን
ሲያዩ፣ መልክተኞችን ልከው ከኤፍራጥስ
ወንዝ ማዶ ያሉትን ሶርያውያን አስመጡ፤
እነዚህንም የሚመራቸው የአድርአዛር ሰራ
ዊት አዛዥ ሾፋክ ነበረ።
17ዳዊት ይህን ሲሰማ፣ እስራኤልን ሁሉ
ሰብስቦ ዮርዳኖስን ተሻገረ፤ ወደፊት በመገ

19፥6 ዘፍ34፥30፤1ዜና18፥3
19፥7 ዘኍ21፥30
19፥11 1ሳሙ26፥6
19፥17 1ዜና9፥1
20፥1 ዘዳ3፥11፤ አሞ1፥13-15
20፥3 ዘዳ29፥11
20፥4 ዘፍ14፥5፤ ኢሱ10፥33
20፥5 1ሳሙ17፥7

ሥገሥም ከፊት ለፊታቸው የውጊያ
መሥመሩን ያዘ። ዳዊትም ሶርያውያንን
ጦርነት ለመግጠም ወታደሮቹን አሰለፈ፤
እነርሱም ተዋጉት። 18ይሁን እንጂ ከእስራ
ኤል ፊት ሸሹ። ዳዊትም ሰባት ሺህ ሠረ
ገለኞችና አርባ ሺህ እግረኛ ወታደሮች
ገደለ። የሠራዊታቸው አዛዥ ሾፋክም በጦ
ርነቱ ላይ ሞተ።
19የአድአዛርም ሹማምት በእስራኤል
መሸነፋቸውን ሲያዩ፣ ከዳዊት ጋር ታረቁ፤
ገባሮቹም ሆኑ።
ስለዚህ ሶርያውያን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ
አሞናውያንን ለመርዳት ፈቃደኞች አልሆ
ኑም።

### የራባ ከተማ መያዝ

20፥1-3 ተጓ ምብ - 2 ሳሙ 11፥1፤12፥29-31

20 ነገሥታት ለጦርነት በሚሄዱበት
በጸደይ ወራት፣ ኢዮአብ የጦር ሰ
ራዊቱን እየመራ ሄዶ የአሞናውያንን
አገር አጠፋ፤ ወደ ራባትም ሄዶ ከበባት፤
ዳዊት ግን ኢየሩሳሌም ቀርቶ ነበር። ኢዮ
አብም ራባትን ወግቶ አፈራረሳት፤ 2ዳዊት
የንጉሣቸውን ዘውድ ከራሱ ላይ ወሰደ፤
ክብደቱም አንድ መክሊት[ጨ] ወርቅ ነበረ፤
ይህንንም በዳዊት ራስ ላይ ጫኑለት፤ እን
ዲሁም ከከተማዪቱ እጅግ ብዙ ምርኮ
ወሰደ። 3በዚያ የነበረውንም ሕዝብ አው
ጥቶ መጋዝ፣ ዶማና መጥረቢያ ይዘው
እንዲሠሩ አደረጋቸው። ዳዊት በሌሎቹም
የአሞን ከተሞች ሁሉ ይህንኑ አደረገ።
ከዚያም ዳዊትና መላው ሰራዊቱ ወደ ኢየሩ
ሳሌም ተመለሱ።

### ከፍልስጥኤማውያን ጋር የተደረገ ጦርነት

2፥4-8 ተጓ ምብ - 2ሳሙ 21፥15-22

4ከዚያም በኋላ ከፍልስጥኤማውያን ጋር
በጌዝር ጦርነት ተደረገ፤ በዚያ ጊዜ ኩሳ
ታዊው ሴቦካይ የራፋይም ዘር የሆነውን
ሲፋይን ገደለ፤ ፍልስጥኤማውያንም ድል
ተመቱ።
5ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሌላ ጦርነት
ተደረገ፤ የያዒር ልጅ ኤልያናን የጦሩ የቦ
ውፍረቱ እንደ ሸማኔ መጠቅለያ የሚ
ያህለውን የጌት ተወላጅ የሆነውን የጎል
ያድን ወንድም ላሕሚን ገደለ።
6ደግሞም ጌት ላይ በተደረገ ሌላ ጦርነት፣
በእጆቹና በእግሮቹ ላይ ስድስት ስድስት
ጣት በድምሩ ሃያ አራት ጣት የነበሩት
አንድ ግዙፍ ሰው ነበረ፤ ይህም እንደዚሁ

[ገ]6ሰሜን ምዕራብ ባሕር መስጴጦምያ ነው
[ጠ]6 34 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
[ጨ]2 34 ኪሎ ግራም ያህል ነው

ከራፋይም ዘር ነበረ። 7እርሱም እስራ
ኤልን በተገዳደረ ጊዜ የዳዊት ወንድም
የሳምዓ ልጅ ዮናታን ገደለው።
8በጌት የነበሩ የራፋይም ዘሮች እነዚህ
ናቸው፤ እነርሱም በዳዊትና በሰዎቹ እጅ
ወደቁ።

## ዳዊት ተዋጊ ሰራዊቱን ቈጠረ

21፥1-26 ተጓ ምብ - 2 ሳሙ 24፥1-25

21 ሰይጣን በእስራኤል ላይ ተነሥቶ
ዳዊት የእስራኤልን ሕዝብ እንዲ
ቈጥር አነሣሣው። 2ዳዊትም ኢዮአብንና
የሰራዊቱን አዛዦች፣ “ሄዳችሁ ከቤርሳቤህ
እስከ ዳን ያሉትን እስራኤላውያን ቍጠሩ፤
ከዚያም ምን ያህል እንደ ሆኑ አውቅ ዘንድ
ንገሩኝ” አላቸው።
3ኢዮአብ ግን፣ “*እግዚአብሔር* የእስራኤ
ልን ሰራዊት አሁን ካለው በላይ በመቶ
እጥፍ ያብዛው፤ ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፤
ሁሉስ ቢሆኑ የጌታዬ ተገዦዎች አይደ
ሉምን? ታዲያ ጌታዬ ይህን ማድረግ
ለምን አስፈለገው? ለምንስ በእስራኤል
ላይ በደል ያመጣል?” አለ።
4ይሁን እንጂ የንጉሡ ቃል ኢዮአብን
አሸነፈው፤ ስለዚህ ኢዮአብ ወጣ፤ በመላው
እስራኤል ከተዘዋወረ በኋላ ወደ ኢየሩሳ
ሌም ተመለሰ። 5ኢዮአብም የተዋጊዎቹን
ሰዎች ቍጥር ለዳዊት አቀረበ፤ እነዚህም
በመላው እስራኤል አንድ ሚሊዮን አንድ
መቶ ሺህ፣ በይሁዳ ደግሞ አራት መቶ
ሰባ ሺህ ሲሆኑ፣ ሁሉም ሰይፍ መምዘዝ
የሚችሉ ነበሩ።
6ኢዮአብ ግን የንጉሡ ትእዛዝ አስጸያፊ
ነበረና፣ የሌዊንና የብንያምን ነገድ ጨምሮ
አልቈጠረም። 7ይህ ትእዛዝ በእግዚአብሔር
ዘንድ የተጠላ ነበር፤ ስለዚህ እግዚአብሔር
እስራኤልን ቀጣ።
8ከዚያም ዳዊት እግዚአብሔርን፣ “ይህን በማ
ድረጌ እጅግ በድያለሁ፤ የፈጸምሁትም
የስ ንፍና ሥራ ስለ ሆነ፣ የባሪያህን በደል
አን ድታስወግድ እለምንሃለሁ” አለ።
9*እግዚአብሔርም* የዳዊት ባለ ራእይ
የሆነውን ጋድን እንዲህ አለው፤ 10“ሂድና
ለዳዊት እንዲህ ብለው ንገረው፤ ‘*እግዚ
አብሔር* የሚለው ይህን ነው፤ እነሆ፣
ሦስት ምርጫ ሰጥቼሃለሁ፤ በአንተ ላይ
እንዳደርስብህ አንዱን ምረጥ”
11ስለዚህ ጋድ ወደ ዳዊት ሄዶ እንዲህ
አለው፤ “*እግዚአብሔር* የሚለው ይህን
ነው፤ ‘በል እንግዲህ አንዱን ምረጥ፤
12የሦስት ዓመት ራብ ወይስ ሦስት ወር
በጠላቶችህ እጅ መጥፋት ወይስ ሦስት

21፥1
2ዜና14፥8፤18፥21፤25
፥5፤መዝ109፥6
21፥2
1ዜና27፥23-24
21፥3 ዘዳ1፥11
21፥5 1ዜና9፥1
21፥9
1ሳሙ9፥9፤22፥5
21፥12
ዘፍ19፥13፤ዘዳ32፥24፤
ሕዝ30፥25
21፥13 መዝ6፥4፤
86፥15፤130፥4፡7
21፥14 1ዜና27፥24
21፥15
ዘፍ6፥6፤19፥13፤
32፥1፤ዘፀ32፥14፤
መዝ 125፥2
21፥16
ኢሱ7፥6፤ዘኍ14፥5
21፥17
2ሳሙ7፥8፤ዮና1፥12
21፥18 2ዜና3፥1
21፥20 መሳ6፥11

ቀን *የእግዚአብሔር* ሰይፍ መቅሠፍት
በምድሪቱ ላይ ወርዶ *የእግዚአብሔር*
መልአክ እስራኤልን ሁሉ ያጥፋ?’ ለላከኝ
ምን እንደምመልስ ቍርጡን ንገረኝ።”
13ዳዊትም ጋድን፣ “እጅግ ተጨንቄ
አለሁ፤ ኅሕረቱ ታላቅ ስለሆነ *በእግዚአ
ብሔር* እጅ መውደቅ ይሻለኛል፤ በሰው
እጅስ አልውደቅ” አለ።
14ስለዚህ *እግዚአብሔር* በእስራኤል ላይ
መቅሠፍት ላከ፤ ከእስራኤልም ሰባ ሺህ
ሰው ዐለቀ። 15እንዲሁም እግዚአብሔር ኢየሩ
ሳሌምን እንዲያጠፉ መልአክ ላከ፤ መል
አኩ ሊያጠፉትም ሲል *እግዚአብሔር*
አይቶ ስለሚደርሰው ጥፋት አዘነ፤ ሕዝ
ቡን የሚያጠፋውንም መልአክ፣ "እጅህን
መልስ” አለው። *የእግዚአብሔርም* መል
አክ በኢያቡሳዊው በኦርና ዐውድማ አጠ
ገብ ቆሞ ነበር።
16ዳዊት ቀና ብሎ ሲመለከት፣ *የእግዚ
አ ብሔር* መልአክ በሰማይና በምድር
መካ ከል ቆሞ አየ፤ መልአኩም በኢየሩ
ሳሌም ላይ የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ ይዞ
ነበር፤ ከዚያም ዳዊትና ሽማግሌዎቹ ማቅ
እንደ ለበሱ በግምባራቸው ተደፉ።
17ዳዊት እግዚአብሔርን፣ “ተዋጊዎቹ
እንዲቈጠሩ ያዘዝሁ እኔ አይደለሁምን?
ኀጢአት የሠራሁትም ሆነ የበደልሁት እኔ
ነኝ፤ እነ ዚህ እኮ በጎች ናቸው፤ ታዲያ
እነርሱ ምን አደረጉ? *እግዚአብሔር*
አምላኬ ሆይ፤ እጅህ በእኔና በአባቴ ቤት
ላይ ትሁን እንጂ፣ መቅሠፍቱ በሕዝብህ
ላይ አይው ረድ” አለ።
18ከዚያም *የእግዚአብሔር* መልአክ ዳዊት
ወጥቶ በኢያቡሳዊው በኦርና ዐውድማ ላይ
*ለእግዚአብሔር* መሠዊያ ይሠራ ዘንድ
እንዲነግረው ጋድን አዘዘው። 19ዳዊትም
ጋድ *በእግዚአብሔር* ስም በነገረው ቃል
መሠረት ለመፈጸም ወጣ።
20ኦርና ስንዴ በመውቃት ላይ ሳለ
ዘወር ሲል መልአኩን አየ፤ አብረውት የነ
በሩት አራት ወንዶች ልጆቹም ተሸሸጉ።
21ዳዊት ወደ እርሱ እየቀረበ መጣ፤ ኦርና
ቀና ብሎ ሲመለከት፣ ዳዊትን አየው፤ ከዐ
ውድማውም ወጥቶ መሬት ላይ ለጥ ብሎ
በመደፋት ለዳዊት እጅ ነሣ።
22ዳዊትም፣ “በሕዝቡ ላይ የወረደው መቅ
ሠፍት እንዲወገድ *ለእግዚአብሔር* መሠ
ዊያ እሠራ ዘንድ ዐውድማህን ልውሰደው፤
ሙሉውን ዋጋ እከፍልሃለሁ” አለው።
23ኦርናም ዳዊትን፣ “እንዲሁ ውሰደው፤
ጌታዬ ንጉሥ ደስ ያለውን ያድርግ፤
እነሆ፤ ለሚቃጠል መሥዋዕት በሬዎቹን፣

መውቂያ በትሮቹን ለማቀጣጠያ ዕንጨት፣
ስንዴውን ደግሞ ለእህል ቍርባን እንዲሆን
እሰጣለሁ፤ ሁሉንም እኔ እሰጣለሁ።” አለ።
[24]ንጉሥ ዳዊት ግን ለኦርና “አይደረ
ግም፤ ሙሉውን ዋጋ እኔ እከፍላለሁ፤ የአ
ንተ የሆነውን ለእግዚአብሔር ለማቅረብ
አልፈልግም፤ ዋጋ ያልከፈልሁበትንም የሚ
ቃጠል መሥዋዕት አድርጌ አላቀርብም”
ሲል መለሰለት።
[25]ስለዚህ ዳዊት ለኦርና የቦታውን ዋጋ
ስድስት መቶ ሰቅል[ጰ] ወርቅ ከፈለ። [26]ዳዊ
ትም በዚያ ለእግዚአብሔር መሠዊያ
ሠርቶ የሚቃጠል መሥዋዕትና የኅብረት
መሥዋዕት[ጰ] አቀረበ። እግዚአብሔርንም ጠራ፤
እግዚአብሔርም የሚቃጠል መሥዋዕት
በሚቀርብበት መሠዊያ ላይ ከሰማይ በእ
ሳት መለሰለት።
[27]ከዚያም እግዚአብሔር ለመልአኩ ተና
ገረ፤ መልአኩም ሰይፉን ወደ አፎቱ መለሰ።
[28]በዚያን ጊዜ ዳዊት፣ እግዚአብሔር በኢ
ያቡሳዊው በኦርና ዐውድማ ላይ እንደ
መለሰለት ሲያይ፣ በዚያው ቦታ መሥዋዕት
ማቅረብ ጀመረ። [29]ሙሴ በምድረ በዳ የሠ
ራው የእግዚአብሔር ማደሪያ ድንኳንና
የሚቃጠል መሥዋዕት የሚቀርብበት
መሠዊያ በዚያ ጊዜ በገባዖን ኮረብታ ላይ
ነበረ። [30]ዳዊት የእግዚአብሔርን መልአክ
ሰይፍ ስለ ፈራ ወደዚያ ሄዶ እግዚአብሔርን
ለመጠየቅ አልቻለም።

22 ከዚያም ዳዊት፣ “ከእንግዲህ የእ
ግዚአብሔር አምላክ ቤት በዚህ
ይሆናል፤ እንዲሁም ስለ እስራኤል የሚ
ቃጠል መሥዋዕት የሚቀርብበት መሠ
ዊያ በዚሁ ይቆማል” አለ።

## ቤተ መቅደሱን ለመሥራት የተደረገ ዝግጅት

[2]ስለዚህ ዳዊት በእስራኤል የሚኖሩ
መጻተኞች እንዲሰበሰቡ አዘዘ፤ ከመካከላ
ቸውም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሚ
ሠራበትን ጥርብ ድንጋይ እንዲያዘጋጁ ጠ
ራቢዎችን መደበ። [3]ለቅጥር በሮቹ ምስማ
ርና ማጠፊያ የሚሆን ብዙ ብረትና ከብ
ዛቱ የተነሣ ሊመዘን የማይቻል ናስ አዘ
ጋጀ። [4]እንዲሁም ሲዶናውያንና ጢሮሳ
ውያን በብዛት አምጥተውለት ስለ ነበር፣
ስፍር ቍጥር የሌለው የዝግባ ዕንጨት
አሰናዳ።
[5]ዳዊትም፣ “ልጄ ሰሎሞን ወጣት ነው፤
ልምዱም የለውም፤ ለእግዚአብሔር የሚሠ
ራው ቤተ መቅደስ ደግሞ እጅግ የሚያ
ምር፣ በአሕዛብም ሁሉ ዘንድ ዝናው የተ
ሰማና እጅግ የተዋበ መሆን አለበት፤ ስለ

21፥26 መሳ19፥18፤መሳ6፥21
21፥29 ኢሱ9፥3
22፥1 ዘፍ28፥17
22፥2 ዘፀ፥11፤ ዘዳ20፥11፤ 1ነገ5፥17-18፤2ዜና8፥10፤ ዕዝ3፥7፤ኢሳ56፥6
22፥3 1ነገ7፥47፤1ዜና29፥2-5
22፥4 1ነገ5፥6
22፥5 1ነገ3፥7፤ 1ዜና29፥1፤2ዜና2፥5
22፥6 ሐሥ7፥47
22፥7 ዘዳ12፥5፡11፤1ነገ8፥17፤1ዜና17፥2
22፥8 1ነገ5፥3፤1ዜና28፥3
22፥9 ቍ18፤ኢሱ14፥15፤ 2ሳሙ12፥24፤1ነገ4፥20፤ 5፥4፤1ዜና23፥1፡25፤ 2ዜና14፥6፥7፤15፥15፤ 20፥30፤36፥21
22፥10 2ሳሙ7፥13፡14፤ 1ነገ9፥5፤1ዜና17፥4፡12፤2ዜና6፥15
22፥11 1ሳሙ16፥18፤18፥12
22፥12 1ነገ3፥11
22፥13 ዘዳ31፥6፤ 1ነገ2፥3፤1ዜና28፥7
22፥14 1ዜና29፥2-5፡19
22፥15 ዕዝ3፥7
22፥16 2ዜና2፥7
22፥17 1ዜና28፥1

ዚህ ሁሉንም እኔ አዘጋጃለሁ” አለ። እን
ዳለውም ዳዊት ከመሞቱ በፊት በብዛት
አዘጋጀ።
[6]ከዚያም ልጁን ሰሎሞንን ጠርቶ ለእስ
ራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ቤት እንዲ
ሠራ አዘዘው።
[7]ዳዊትም ሰሎሞንን እንዲህ አለው፤
“ልጄ ሆይ፤ ለአምላኬ ለእግዚአብሔር
ስም ቤት ለመሥራት በልቤ አስብ ነበር፤
[8]ነገር ግን ከእግዚአብሔር እንዲህ የሚል
ቃል መጣልኝ፤ “አንተ ብዙ ደም
አፍስሰሃል፤ ብዙ ጦርነትም አድርገሃል፤
በፊቴ በም ድር ላይ ብዙ ደም ያፈሰስህ
ስለ ሆነ አንተ ለስሜ ቤት አትሠራ
ልኝም፤ [9]ነገር ግን የሰላምና የዕረፍት ሰው
የሆነ ልጅ ትወልዳለህ፤ በየአቅጣጫው
ካሉ ጠላቶቹ ዐሳ
ርፈዋለሁ፤ ስሙም ሰሎሞን ይባላል። በዘ
መኑም ለእስራኤል ሰላምንና ጸጥታን እሰ
ጣለሁ። [10]ለስሜ ቤት የሚሠራልኝ እርሱ
ነው። እርሱ ልጅ ይሆነኛል፤ እኔም አባት
እሆነዋለሁ። ዙፋኑንም በእስራኤል ላይ
ለዘላለም አጸናለሁ።
[11]“አሁንም ልጄ ሆይ፤ እግዚአብሔር
ከአንተ ጋር ይሁን፤ እንድትፈጽመው በተ
ናገረውም መሠረት፣ ተሳክቶልህ የአምላ
ክህን የእግዚአብሔርን ቤት ለመሥራት
ያብቃህ። [12]በእስራኤል ላይ አለቃ ባደረ
ገህ ጊዜ፣ የአምላክህን የእግዚአብሔርን
ትእዛዝ ትፈጽም ዘንድ እግዚአብሔር ጥበ
ብንና ማስተዋልን ይስጥህ። [13]እግዚአብሔር
በሙሴ አማካይነት ለእስራኤል የሰጠ
ውን ሕጉንና ሥርዐቱን ተጠንቅቀህ ብትጠ
ብቅ ይሳካልሃል፤ አይዞህ ጠንክር፤ በርታ፤
ተስፋም አትቍረጥ።
[14]“ለእግዚአብሔር ቤት እንዲሆንም
አንድ ሺህ መክሊት[ፈ] ወርቅ፣ አንድ ሚሊ
ዮን መክሊት[ፐ] ብር፣ ከብዛቱ የተነሣ ሊመ
ዘን የማይቻል ናስና ብረት ለማዘጋጀት
በተቻለኝ ሁሉ ጥሬአለሁ። በተረፈ አንተ
ጨምርበት። [15]ድንጋይ ጠራቢዎች፣ ግን
በኞች፣ አናጢዎች የሆኑ ብዙ ሠራተኞች፣
እንዲሁም በልዩ ልዩ ሙያ የተጠበቡ
ሰዎች አሉህ፤ [16]እነዚህም ቍጥራቸው
እጅግ የበዛ የወርቅ፣ የብር፣ የናስና የብ
ረት ሠራተኞች ናቸው። በል ሥራህን ጀምር፤
እግዚአብሔርም ከአንተ ጋር ይሁን።”
[17]ከዚያም ዳዊት የእስራኤል መሪዎች
ሁሉ ልጁን ሰሎሞንን እንዲረዱት አዘዘ፤

[ጰ]25 7 ኪሎ ግራም ያህል ነው
[ጰ]26 በትውፊት፣ የሰላም መሥዋዕት ይባላል
[ፈ]14 3,450 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
[ፐ]14 34,500 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው

18እንዲህም አለ፤ “*እግዚአብሔር*
አምላካችሁ እስካሁን ከእናንተ ጋር
አይደለምን? በየ አቅጣጫውስ ዕረፍትን
ሰጥቷችሁ የለምን? የምድሪቱን ነዋሪዎች
በእጄ አሳልፎ ሰጥ ቶኛል፤ ምድሪቱም
*ለእግዚአብሔርና* ለሕዝቡ ተገዝታለች።
19አሁንም *እግዚአብሔር* አምላካችሁን
ለመፈለግ ልባችሁንና ነፍሳች ሁን
ሰብስቡ። *የእግዚአብሔርን* የኪዳኑን
ታቦትና ንዋያተ ቅድሳቱን ለእግዚአብሔር
ስም ወደ ሚሠራቸው ቤተ መቅደስ አም
ጥታችሁ የአምላክን *የእግዚአብሔርን* መቅ
ደስ ሥሩ።”

## ሌዋውያን

23 ዳዊት በሸመገለና ዕድሜው በገፋ
ጊዜ፣ ልጁን ሰሎሞንን በእስራ
ኤል ላይ አነገሠው።
2እንዲሁም መላውን የእስራኤልን መሪ
ዎች፣ ካህናቱንና ሌዋውያኑን ሁሉ በአን
ድነት ሰበሰበ። 3ዕድሜያቸው ሠላሳና ከዚያ
በላይ የሆኑ ወንዶች ሁሉ ተቈጠሩ፤ ቍጥ
ራቸውም በጠቅላላው ሠላሳ ስምንት ሺህ
ነበረ። 4ዳዊትም እንዲህ አለ፤ “ከእነዚህ
መካከል ሃያ አራቱ ሺህ *የእግዚአብሔርን*
ቤተ መቅደስ ሥራ ይቈጣጠሩ፤ ስድስቱ ሺህ
ደግሞ ሹሞችና ዳኞች ይሁኑ፤ 5አራቱ ሺህ
የቅጥሩ በር ጠባቂዎች ይሁኑ፤ አራቱ ሺህ
ደግሞ ለዚሁ ብዬ ባዘጋጀሁት የዜማ
መሣሪያ *እግዚአብሔርን* ያመስግኑ”።
6ዳዊትም ሌዋውያኑን በሌዊ ልጆች በጌ
ድሶን፣ በቀዓትና በሜራሪ በየጐሣቸው
መደባቸው።

## ጌድሶናውያን

7ከጌድሶናውያን ወገን፤
ለአዳን፣ ሰሜኢ።
8የለአዳን ወንዶች ልጆች፤
የመጀመሪያው ይሒኤል፣ ዜቶም፣
ኢዮኤል፤ ባጠቃላይ ሦስት ናቸው።
9የሰሜኢ ወንዶች ልጆች፤
ሰሎሚት፣ ሐዝኤል፣ ሐራን፤ ባጠቃ
ላይ ሦስት ናቸው። እነዚህ የለአዳን
ቤተ ሰብ አለቆች ናቸው።
10የሰሜኢ ወንዶች ልጆች፤
ኢኢት፣ ዚዛ፣ የዑስ፣ በሪዓ፤ እነዚህ
አራቱ የሰሜኢ ልጆች ናቸው።
11የመጀመሪያው ኢኢት፣ ሁለተኛው
ደግሞ ዚዛ[ሀ] ነበረ፤ የዑስና በሪዓ ግን
ብዙ ወንዶች ልጆች አልነበሯቸውም፤
ስለዚህ የተቈጠሩት በሥራ መደብ
እንደ አንድ ቤተ ሰብ ሆነው ነው።

22፥18 ቀኍ9፤2ሳሙ7፥1
22፥19 2ዜና7፥14
23፥1 1ነገ1፥30፤1ዜና22፥9፤28፥5፤29፥28፤2ዜና1፥8
23፥3 ዘኍ4፥3-49፤8፥24፤1ዜና21፥7
23፥4 1ዜና26፥29፤2ዜና19፥8፤34፥13፤ ዕዝ3፥8፤ነህ4፥10፤ ሕዝ44፥24
23፥5 1ዜና15፥16፤ነህ12፥45፤መዝ92፥3
23፥6 ዘኍ3፥17፤ 1ዜና24፥20፤2ዜና8፥14፤23፥18፥18፤29፥25
23፥7 1ዜና6፥71
23፥12 ዘፍ46፥11፤ዘፀ6፥18
23፥13 ዘፀ6፥20፤30፥7-10፤ዘኍ6፥23፤ 1ዜና15፥2
23፥14 ዘዳ33፥1
23፥15 ዘፀ18፥4
23፥16 1ዜና26፥24-28
23፥17 1ዜና24፥21
23፥18 1ዜና26፥25
23፥19 1ዜና24፥23፤26፥31
23፥21 ዘፀ6፥19፤ 1ዜና6፥19
23፥22 ዘኍ36፥8
23፥24 ዘኍ4፥3

## ቀዓታውያን

12የቀዓት ወንዶች ልጆች፤
እንበረም፣ ይስዓር፣ ኬብሮን፣
ዑዝኤል፤ ባጠቃላይ አራት ናቸው።
13የእንበረም ወንዶች ልጆች፤
አሮን፣ ሙሴ።
አሮን የተቀደሰ እንዲሆን ተለየ፤ እር
ሱና ዘሮቹ ለዘላለም ቅዱስ የሆኑትን
ነገሮች እንዲቀድሱ፣ *በእግዚአብሔር*
ፊት መሥዋዕት እንዲያቀርቡ፣ በፊቱ
እንዲያገለግሉና በስሙም ለዘላለም
እንዲባርኩ ተለዩ። 14የእግዚአብሔር ሰው
የሙሴ ወንዶች ልጆችም እንደ ሌዊ
ነገድ ሆነው ተቈጠሩ።
15የሙሴ ወንዶች ልጆች፤
ጌርሳም፣ አልዓዛር።
16የጌርሳም ዘሮች፤
ሱባኤል።
17የአልዓዛር ዘሮች፤
የመጀመሪያው ረዓብያ ነበረ።
አልዓዛር ሌሎች ወንዶች ልጆች አል
ነበሩትም፤
የረዓብያ ወንዶች ልጆች ግን እጅግ
ብዙ ነበሩ።
18የይስዓር ወንዶች ልጆች፤
የመጀመሪያው ሰሎሚት።
19የኬብሮን ወንዶች ልጆች፤
የመጀመሪያው ይሪያ፣ ሁለተኛው አማ
ርያ፣ ሦስተኛው የሕዚኤል፣ አራተ
ኛው ይቅምዓም ነበሩ።
20የዑዝኤል ወንዶች ልጆች፤
የመጀመሪያው ሚካ፣ ሁለተኛው
ይሺያ ነበሩ።

## ሜራሪያውያን

21የሜራሪ ወንዶች ልጆች፤
ሞሖሊ፣ ሙሲ።
የሞሖሊ ወንዶች ልጆች፤
አልዓዛርና ቂስ ነበሩ።
22አልዓዛር ወንድ ልጅ ሳይወልድ ሞተ፤
ልጆቹ ሴቶች ብቻ ነበሩ፤ እነርሱንም
የአጎታቸው የቂስ ልጆች አገቡአቸው።
23የሙሲ ወንዶች ልጆች፤
ሞሖሊ፣ ዔደር፣ ኢያሪሙት ባጠ
ቃላይ ሦስት ናቸው።
24እንግዲህ እነዚህ የቤተ ሰቡ አለቆች
ሆነው እያንዳንዳቸው በየስማቸው ተመ
ዝግበው የተቈጠሩት የሌዊ ዘሮች ናቸው፤
ዕድሜአቸውም ሃያና ከዚያ በላይ የሆና

[ሀ]11 አንድ የዕብራይስጥ ቅጅ፣ የሰብዓ ሊቃናትና የቩልጌት ትርጕሞች (እንዲሁም ቍጥር 11 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማ ማሉ፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *ዚና* ይላሉ።

ቸው *በእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ውስጥ
የሚያገለግሉ ነበሩ። 25ዳዊት እንዲህ ብሎ
ነበርና፣ “የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር
ለሕዝቡ ዕረፍት ሰጥቷል፤ በኢየሩሳሌ
ምም ለዘላለም ለመኖር መጥቷል፤ 26ሌዋ
ውያን ከእንግዲህ ወዲህ ድንኳኑን ወይም
የመገልገያ ዕቃውን ሁሉ መሸከም የለባቸ
ውም።”

27ዳዊት በሰጠው የመጨረሻ መመሪያ
መሠረት የተቈጠሩት ሌዋውያን ዕድሜያ
ቸው ሃያና ከዚያ በላይ ነበረ።

28የሌዋውያኑ ተግባር *በእግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስ አገልግሎት የአሮንን ዘሮች መር
ዳት፣ የቤተ መቅደሱን ቅጥር ግቢና ክፍ
ሎች መንከባከብ፣ የተቀደሱ ዕቃዎችን
ሁሉ ማንጻትና በእግዚአብሔር ቤት ያሉትን
ሌሎች ተግባሮች ማከናወን ነበር። 29እንዲ
ሁም መባ ሆኖ የሚቀርበውን ኅብስተ ገጽ፣
የእህል ቍርባኑን ዱቄት፣ ያለ እርሾ የሚ
ጋገረውን ቂጣ የሚጋግሩ፣ የሚያቦኩና
የሚሰፈረውንም ሆነ የሚለካውን ሁሉ በኀ
ላፊነት የሚቈጣጠሩ እነርሱ ነበሩ። 30በየዕ
ለቱም *እግዚአብሔርን* ለማመስገንና ለመ
ወደስ ጠዋት ጠዋት ይቆሙ ነበር፤ ይህን
ንም ማታ ማታ 31እንዲሁም በየሰንበቱ፣
በወር መባቻ በዓልና በተደነገጉት በዓላት
ሁሉ ይፈጽሙ ነበር፤ በተወሰነላቸው ቍጥ
ርና በተሰጠውም *መመሪያ መሠረት* ዘወ
ትር *በእግዚአብሔር* ፊት ያገለግሉ ነበር።

32ስለዚህ ሌዋውያኑ ለመገናኛው ድንኳ
ንና ለመቅደሱ እንዲሁም በወንድሞቻቸው
በአሮን ዘሮች ሥር ሆነው *ለእግዚአብሔር*
ቤተ መቅደስ ያለባቸውን ኀላፊነት ያከና
ውኑ ነበር።

## የካህናት አመዳደብ

24 የአሮን ልጆች አመዳደብ እንደ
ሚከተለው ነበረ፤

የአሮን ልጆች ናዳብ፣ አብዩድ፣ አልዓ
ዛር፣ ኢታምር ነበሩ። 2ናዳብና አብዩድ
ግን ዘር ሳይተኩ ከአባታቸው በፊት ሞቱ፤
ስለዚህ አልዓዛርና ኢታምር ካህናት ሆነው
ያገለግሉ ነበር። 3ዳዊትም የአልዓዛር ዘር
የሆነው ሳዶቅና የኢታምር ዘር የሆነው
አቢሜሌክ እየረዱት እንደየአገልግሎታ
ቸው ሥርዐት እየለየ መደባቸው። 4ከኢ
ታምር ይልቅ በአልዓዛር ዘሮች መካከል
ብዙ መሪዎች ተገኙ፤ አከፋፈላቸውም እን
ደሚከተለው ነበር፤ ከአልዓዛር ዘሮች ዐሥራ
ስድስት የቤተ ሰብ አለቆች፤ ከኢታምርም
ዘሮች ስምንት የቤተ ሰብ አለቆች። 5ከአ
ልዓዛርና ከኢታምር ዘሮች መካከል የመቅ
ደሱ ሹማምትና የእግዚአብሔር ሹማምት
ስለ ነበሩ፣ ያለ አድልዎ በዕጣ ለዩአቸው።

6የሌዋዊው የናትናኤል ልጅ ጸሓፊው
ሸማያ በንጉሡና በሹማምቱ፣ በካህኑ በሳ
ዶቅ፣ በአብያታር ልጅ በአቤሜሌክ እንዲ
ሁም በካህናቱና በሌዋውያኑ ቤተ ሰብ
አለቆች ፊት ስማቸውን ጻፈ፤ የጻፈውም
አንዱን ቤተ ሰብ ከአልዓዛር ሌላውን
ደግሞ ከኢታምር በመውሰድ ነው፤

7የመጀመሪያው ዕጣ ለዮአሪብ፣ ሁለተኛ
ውም ዕጣ ለዮዳሄ ወጣ፤
8ሦስተኛው ለካሪም፣ አራተኛው ለሥ
ዖሪም፣
9አምስተኛው ለመልክያ፣ ስድስተኛው
ለሚያሚን፣
10ሰባተኛው ለአቆስ፣ ስምንተኛው ለአ
ብያ፣
11ዘጠነኛው ለኢያሱ፣ ዐሥረኛው
ለሴኬንያ፣
12ዐሥራ አንደኛው ለኤሊያሴብ፣ ዐሥራ
ሁለተኛው ለያቂም፣
13ዐሥራ ሦስተኛው ለኦፓ፣ ዐሥራ አራ
ተኛው ለየሼብአብ፣
14ዐሥራ አምስተኛው ለቢልጋ፣ ዐሥራ
ስድስተኛው ለኢሜር፣
15ዐሥራ ሰባተኛው ለኤዚር፣ ዐሥራ
ስምንተኛው ለሃፌጼጽ፣
16ዐሥራ ዘጠነኛው ለፈታያ፣ ሃያኛው
ለኤዜቄል፣
17ሃያ አንደኛው ለያኪን፣ ሃያ ሁለተኛው
ለጋሙል፣
18ሃያ ሦስተኛው ለድላያ፣ ሃያ አራተኛ
ለመዓዝያ ወጣ።

19የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር*
ባዘዘ ውና ከቀድሞ አባታቸው ከአሮን
በተሰጣ ቸው *መመሪያ መሠረት* ወደ *እግዚ
አብሔር* ቤተ መቅደስ በሚገቡበት ጊዜ፣
የተወሰነላ ቸው ሥርዐት ይህ ነበር።

## የተቀሩት ሌዋውያን

20ከቀሩት የሌዊ ዘሮች ደግሞ፦
ከእንበረም ወንዶች ልጆች፤ ሱባኤል፤
ከሱባኤል ወንዶች ልጆች፤ ዬሕድያ።
21ከረዓብያ ወንዶች ልጆች፤ አለቃው
ይሺያ።
22ከይስዓራውያን ወገን፤ ሰሎሚት
ከሰሎሚት ወንዶች ልጆች፤ ያሐት።
23የኬብሮን ወንዶች ልጆች፤ የመጀመሪ
ያው ይሪያ^፣ ሁለተኛው አማርያ፣
ሦስተኛው የሕዚኤል፣አራተኛው ይቀ
ምዓም።

^23 ሁለት የዕብራይስጥ ቅጆችና ጥቂት የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች (እንዲሁም 1 ዜና23፥19 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማ ማሉ፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *የይሪያ ወንዶች ልጆች* ይላሉ

23፥25 1ዜና22፥9
23፥26 ዘኍ4፥5፡15፤ 7፥9፤ዘዳ10፥8
23፥28 2ዜና29፥15፤ነህ13፥9፤ሚል3፥3
23፥29 ዘፀ25፥30፤ዘሌ2፥4-7፤6፥20-23፤19፥35-36፤1ዜና19፥29፡32
23፥30 1ዜና9፥33፤መዝ134፥1
23፥31 ዘኍ28፥9-29፡39፤2ነገ4፥23፤ ኢሳ1፥13-14፤ ቈላ2፥16
23፥32 ዘኍ3፥6-8፡38፤1ዜና6፥48፤ 2ዜና23፥18፤31፥2፤ ሕዝ44፥14
24፥1 ዘፀ6፥23፤ዘኍ3፥2-4፤1ዜና23፥6፤28፥13፤ 2ዜና5፥11፤8፥14፤23፥8፤31፥2 35፥4፡5፤ዕዝ6፥18
24፥2 ዘሌ10፥1-2
24፥3 2ሳሙ8፥17
24፥5 ቍ31፤ 1ዜና25፥8፤26፥13
24፥6 1ዜና18፥16
24፥7 ዕዝ2፥36፤ነህ12፥6
24፥8 ዕዝ2፥39፤ 10፥21፤ነህ10፥5
24፥10 ነህ12፥4፡17፤ሉቃ1፥5
24፥14 ዕዝ2፥37፤ 10፥20፤ኤር20፥1
24፥15 ነህ10፥20
24፥20 1ዜና23፥6
24፥21 1ዜና23፥17
24፥23 1ዜና23፥19
24፥26 1ዜና6፥19

24የዑዝኤል ልጅ፤ ሚካ፡፡
ከሚካ ወንዶች ልጆች ሻሚር፡፡
25የሚካ ወንድም ይሺያ፤
ከይሺያ ወንዶች ልጆች ዘካርያስ፡፡
26የሜራሪ ወንዶች ልጆች፤
ሞሖሊ፣ሙሲ፡፡
የያዝያ ወንድ ልጅ በኖ፡፡
27የሜራሪ ወንዶች ልጆች፤
ከያዝያ በኖ፣ ሾሃም፣
ዘኩር፣ ዔብሪ፡፡
28ከሞሖሊ፤ አልዓዛር፤ ይህ ሰው ወንዶች
ልጆች አልነበሩትም፡፡
29ከቂስ፤ የቂስ ወንድ ልጅ፤
ይረሕምኤል፡፡
30የሙሲ ወንዶች ልጆች፤ ሞሖሊ፣
ዔዳር፣ኢያሪሙት፡፡
እነዚህ እንግዲህ እንደየቤተ ሰባቸው
የተቈጠሩ ሌዋውያን ነበሩ፡፡ 31ወንድሞ
ቻቸው የአሮን ዘሮች እንዳደረጉት ሁሉ፣
እነዚህም በንጉሥ ዳዊት፣ በሳዶቅ፣ በአ
ቢሜሌክ እንዲሁም የካህናቱና የሌዋውያኑ
ቤተ ሰብ አለቆች ባሉበት ዕጣ ተጣጣሉ፤
የበኵሩም ቤተ ሰቦች እንደ ትንሹ ውነ
ድም ቤተ ሰብ እኩል ዕጣ ተጣለላቸው፡፡

## የቤተ መቅደሱ መዘምራን

25 ዳዊት ከሰራዊቱ አለቆች ጋር ሆኖ በመሰንቆ፣ በበገናና በጸናጽል ድምፅ እየታጀቡ ትንቢት የሚናገሩትን ከአሳፍ፣ ከኤማንና ከኤዶታም ቤተ ሰብ መካከል መርጦ መደበ፤ ይህን አገልግሎት የሚያከናውኑትም ሰዎች ዝርዝር እንደ ሚከተለው ነው፤
2ከአሳፍ ወንዶች ልጆች፤
ዘኩር፣ ዮሴፍ፣ ነታንያ፣ አሼርኤላ፡፡
የአሳፍ ልጆች በአሳፍ አመራር ሥር
ነበሩ፤ አሳፍም በንጉሡ አመራር
ሥር ነበረ፡፡
3ከኤዶታም ወንዶች ልጆች፤
ጎዶልያስ፣ ጽሪ፣ የሻያ፣ ሰሜኢ[ሐ]፣
ሐሸብያ፣ መቲትያ፡፡ እነዚህ ስድስቱ
በመሰንቆ *እግዚአብሔርን* እያመሰገ
ነና እየወደሰ ትንቢት በተናገረው
አባታቸው በኤዶታም አመራር ሥር
ነበሩ፡፡
4ከኤማን ወንዶች ልጆች፤
ቡቅያ፣ መታንያ፣ ዓዛርዔል፣ ሱባ
ኤል፣ ኢያሪሙት፣ ሐናንያ፣ ሐናኒ፣
ኤልያታ፣ ጊዶልቲ፣ ሮማንቲዔዘር፣
ዮሽብቃሻ፣ መሎቲ፣ ሆቲር፣ መሐ
ዝዮት፡፡ 5እነዚህም ሁሉ የንጉሡ ባለ
ራእይ የኤማን ልጆች ነበሩ፡፡ እርሱን
ከፍ ከፍ እንዲያደርጉትም እግዚአብሐ
ር በገባለት ቃል መሠረት ሰጡት[መ]፡፡
እግዚአብሔር ለኤማን ዐሥራ አራት ወን
ዶችና ሦስት ሴቶች ልጆች ሰጠው፡፡
6እነዚህ ሁሉ *በእግዚአብሔር* ቤተ መቅ
ደስ በጸናጽል፣በመሰንቆና በበገና ድምፅ
ለሚቀርበው የእግዚአብሔር ቤት
አገልግሎት በአባቶቻቸው አመራር ሥር
ነበሩ፡፡ አሳፍ፣ ኤዶታምና ኤማን ደግሞ
በንጉሡ የበላይ አመራር ሥር ነበሩ፡፡
7እነዚህም ከቤተ ዘመዶቻቸው ጋር
በመሆን ሁሉም ወደ *እግዚአብሔር*
በሚቀርበው ዜማ የሠለጠኑና የተካኑ
ነበሩ፤ ቍጥራቸውም ሁለት መቶ ሰማንያ
ስምንት ነበረ፡፡ 8የሥራ ድር ሻቸውንም
ለመወሰን ወጣት፣ ሽማግሌ፣ መምህርም
ሆነ ደቀ መዝሙር ሳይባል እኩል ዕጣ
ተጣጣሉ፡፡
9የመጀመሪያው ዕጣ ከአሳፍ ወገን
ለሆነው ለዮሴፍ ወንዶች ልጆቹና
ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ[ሠ]፤
ቍጥራቸውም 12[ረ]
ሁለተኛው ለጎዶልያስ ወጣ፤ እርሱን
ጨምሮ ለቤተ ዘመዶቹና ለወንዶች
ልጆቹ፤
ቍጥራቸውም 12
10ሦስተኛው ለዛኩር፣ ለወንዶች ልጆቹና
ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቍጥራቸውም 12
11አራተኛው ላይጽሪ፣ ለወንዶች ልጆቹና
ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቍጥራቸውም 12
12አምስተኛው ለነታንያ ለወንዶች ልጆ
ቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቍጥራቸውም 12
13ስድስተኛው ለቡቅያ፣ ለወንዶች ልጆ
ቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቍጥራቸውም 12
14ሰባተኛው ለይሽርኤል፣ ለወንዶች
ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቁጥራቸውም 12
15ስምንተኛው ለየሻያ፣ ለወንዶች ልጆቹና
ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቁጥራቸውም 12
16ዘጠነኛው ለመታንያ፣ ለወንዶች ልጆ
ቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቁጥራቸውም 12

24፥31 ቍ5
25፥1 1ሳሙ10፥5፤2ነገ3፥15፤1ዜና6፥31፡33፤15፥16፤16፥41፡42፤2ዜና5፥12፤8፥14፤34፥12፤35፥15፤ዕዝ3፥10፤ነህ11፥17
25፥3 ዘፍ4፥21፤1ዜና16፥41-42፤መዝ33፥2
25፥6 1ዜና15፥16፡19፤2ዜና23፥18፤29፥25
25፥8 1ዜና26፥13
25፥9 1ዜና6፥39

[ሐ]3 አንድ የዕብራይስጥ ቅጅና ጥቂት የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች (እንዲሁም ቍጥር17 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን *ስሜኢ* የሚለውን አይጨምሩም
[መ]5 ዕብራይስጡ፤ *ቀንዱ ከፍ ከፍ አለ* ይላል
[ሠ]9 የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን፣ *ለወንዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ* የሚለውን አይጨምርም
[ረ]9 ድምሩን በተመለከተ ቍጥር 7 ይመ፤ ዕብራይስጡ፣ “12” የሚለውን አይጨምርም

17 ዐሥረኛው ለሰሜኢ፣ ወጣ፤ ለወንዶች
ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቊጥራቸውም 12
18 ዐሥራ አንደኛው ለዓዛርኤል፣ ለወን
ዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቊጥራቸውም 12
19 ዐሥራ ሁለተኛው ለሐሻብያ ለወንዶች
ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቊጥራቸውም 12
20 ዐሥራ ሦስተኛው ለሱባኤል፣ ለወን
ዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቊጥራቸውም 12
21 ዐሥራ አራተኛው ለመቲትያ፣ ለወን
ዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቊጥራቸውም 12
22 ዐሥራ አምስተኛው ለኢያሪሙት፣ ለወ
ንዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቊጥራቸውም 12
23 ዐሥራ ስድስተኛው ለሐናንያ፣ ለወን
ዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቊጥራቸውም 12
24 ዐሥራ ሰባተኛው ለዮሽብቃሻ፣ ለወን
ዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቊጥራቸውም 12
25 ዐሥራ ስምንተኛው ለሐናኒ፣ ለወን
ዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቊጥራቸውም 12
26 ዐሥራ ዘጠነኛው ለመሎቲ፣ ለወንዶች
ልጆቹና ለቤተ ዘምዶቹ ወጣ፤
ቊጥራቸውም 12
27 ሃያኛው ለኤልያታ፣ ለወንዶች ልጆቹና
ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቊጥራቸውም 12
28 ሃያ አንደኛው ለሆቲር፣ ለወንዶች ልጆ
ቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቊጥራቸውም 12
29 ሃያ ሁለተኛው ለጊዶልቲ፣ ለወንዶች
ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቊጥራቸውም 12
30 ሃያ ሦስተኛው ለመሐዝዮት፣ ለወን
ዶች ልጆቹ ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቊጥራቸውም 12
31 ሃያ አራተኛው ለሮማንቲዔዘር፣ ለወን
ዶች ልጆቹና ለቤተ ዘመዶቹ ወጣ፤
ቊጥራቸውም 12

## የቤተ መቅደሱ በር ጠባቂዎች

**26** የቤተ መቅደሱ በር ጠባቂዎች
አመዳደብ፤

ከቆሬያውያን ወገን፤ ከአሳፍ ወንዶች
ልጆች አንዱ የሆነው የቆሬ ወንድ
ልጅ ሜሱላም።
2 ሜሱላም ወንዶች ልጆች ነበሩት፤
የመጀመሪያው ዘካሪያስ፣
ሁለተኛው ይዲኤል፣
ሦስተኛው ዮዛባት፣
አራተኛው የትኒኤል፣
3 አምስተኛው ኤላም፣
ስድስተኛው ይሆሐናን፣
ሰባተኛው ኤሊሆዔናይ።
4 ዖቤድኤዶምም እንደዚሁ ወንዶች
ልጆች ነበሩት፤
የመጀመሪያው ሸማያ፣
ሁለተኛው ዮዛባት፣
ሦስተኛው ኢዮአስ፣
አራተኛው ሣካር፣
አምስተኛው ናትናኤል፣
5 ስድስተኛው ዓሚኤል፣
ሰባተኛው ይሳኮር፣
ስምንተኛው ፒላቲ፤
እግዚአብሔር ዖቤድኤዶምን ባርኮታልና።
6 እንዲሁም ልጁ ሸማያ ወንዶች ልጆች
ነበሩት፤ እነርሱም በቂ ችሎታ ስለ
ነበራቸው የአባታቸው ቤት መሪዎች
ሆነው ነበር። 7 የሸማያ ወንዶች ልጆች፤
ዖትኒ፣ ራፋኤል፣ ዖቤድ፣ ኤልዛባድ፤
ዘመዶቹ ኤሊሁና ሰማክያም እንደዚሁ
በቂ ችሎታ ነበራቸው። 8 እነዚህ ሁሉ
የዖቤድኤዶም ዘሮች ሲሆኑ፣ እነ ር
ሱም ሆኑ ወንዶች ልጆቻቸውና ቤተ
ዘመዶቻቸው ሥራውን ለመሥራት
በቂ ችሎታ ነበራቸው። የዖቤድኤ
ዶም ዘሮች ባጠቃላይ ሥልሳ ሁለት
ነበሩ።
9 ሜሱላም በቂ ችሎታ ያላቸው ወንዶች
ልጆችና ቤተ ዘመዶች ነበሩት፤ ቊጥ
ራቸውም ባጠቃላይ ዐሥራ ስም ንት
ነበረ።
10 ከሜራሪ ወገን የሆነው ሖሳ ወንዶች
ልጆች ነበሩት፤ የመጀመሪያው ሽምሪ
ነበረ፤ የበኵር ልጅ ባይሆንም እንኳ፣
አባቱ ቀዳሚ አድርጎት ነበር። 11 ሁለ
ተኛው ኬልቅያስ፣ ሦስተኛው ጥበ
ልያ፣ አራተኛው ዘካርያስ፤ የሖሳ
ወንዶች ልጆችና ቤተ ዘመዶቹ ባጠ
ቃላይ ዐሥራ ሦስት ነበሩ።
12 የቤተ መቅደሱም ጠባቂዎች በአለቆቻ
ቸው ሥር ተመድበው ልክ እንደ ቤተ
ዘመዶቻቸው ሁሉ *የእግዚአብሔርን* ቤተ
መቅደስ ሥራ ለማከናወን ምድብ ተራ
ነበራቸው። 13 ለእያንዳንዱም በር ወጣት
ሽማግሌ ሳይባል ለሁሉም እኩል ዕጣ
ተጣለ።
14 የምሥራቁ በር ዕጣ ለሴሌምያ ወጣ።
ከዚያም ምክር ዐዋቂ ለሆነው ለልጁ ለዘ
ካርያስ ዕጣ ጣሉ፤ እርሱም የሰሜኑ በር

25፥31 1ዜና9፥33
26፥1 1ዜና9፥17
26፥2 1ዜና9፥21
26፥5
2ሳሙ6፥10፤1ዜና13፥1
3፤16፥38
26፥10
ዘጸ21፥16፤1ዜና5፥1
26፥12 1ዜና9፥22
26፥13 1ዜና24፥5
26፥14
1ዜና9፥18፡21

ደረሰው። 15የደቡቡ በር ዕጣ ለዖቤድኤ
ዶም ሲወጣ፣ የግምጃ ቤቱ ዕጣ ደግሞ
ለልጆቹ ወጣ። 16የምዕራቡ በርና በላይ
ኛው መንገድ ላይ የሚገኘው የሽሌኬት
በር ዕጣዎች ለሰፊንና ለሖሳ ወጣ።
17በአንዱ ዘብ ጥበቃ ትይዩ ሌላ ዘብ
ጥበቃ ነበረ፤ በየቀኑም በምሥራቅ በኩል
ስድስት፣ በሰሜን በኩል አራት፣ በደቡብ
በኩል አራት፣ በዕቃ ቤቱ በኩል በአንድ
ጊዜ ሁለት ሌዋውያን ይጠብቁ ነበር።
18በምዕራቡ በኩል የሚገኘውን አደባባይ
ደግሞ በመንገዱ ላይ አራት፣ በአደባባዩ
ላይ ደግሞ ሁለት ሆነው ይጠብቁ ነበር።
19እንግዲህ የቆሬና የሜራሪ ዘሮች የሆ
ኑት በር ጠባቂዎች ድልድል ይህ ነበር።

### የግምጃ ቤት ኀላፊዎችና ሌሎች ሹማምት

20ከሌዋውያን መካከል አኪያ የእግዚአብሔር
ቤት ግምጃ ቤትና የተቀደሱት ዕቃዎች
የሚቀመጡበት ግምጃ ቤት ኀላፊ ነበረ።
21የለአዳን ዘሮች፣ በለአዳን በኩል ጌድሶ
ናውያን የሆኑትና ለጌድሶናዊው ለለአዳን
ቤተ ሰቦች አለቆች የሆኑት የለአዳን
ዘሮች እነዚህ ነበሩ፤ ይሒኤሊ፣ 22የይሒ
ኤሊ ወንዶች ልጆች፣ ዜቶምና ወንድሙ
ኢዩኤል። እነዚህም *የእግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስ ግምጃ ቤት ኀላፊዎች ነበሩ።
23ከእንበረማውያን፣ከይስዓራውያን፣ ከኬ
ብሮናውያን፣ ከዑዝኤላውያን፤
24የሙሴ ልጅ የጌርሳም ዘር የሆነው
ሱባኤል የግምጃ ቤቱ የበላይ ኀላፊ
ነበረ። 25በአልዓዛር በኩል የሚዛመ
ዱት፤ ልጁ ረዓብያ፣ ልጁ የሻያ፣ ልጁ
ኢዮራም፣ ልጁ ዝክሪ፣ ልጁ ሰሎ
ሚት። 26ሰሎሚትና የሥጋ ዘመዶቹ
ንጉሥ ዳዊት፣ የቤተ ሰቡ ኀላፊዎች፣
የሻለቆችና የመቶ አለቆች እንዲሁም
ሌሎች የሰራዊቱ አዛዦች ቀድሰው
ላቀረቧቸው ንዋያተ ቅድሳት ኀላ
ፊዎች ነበሩ። 27በጦርነት ከተገኘውም
ምርኮ ከፊሉን *ለእግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስ ማደሻ እንዲሆን ቀደሱት።
28ባለ ራእዩ ሳሙኤል፣ የቂስ ልጅ
ሳኦል፣ የኔር ልጅ አበኔር፣ የጽሩያ
ልጅ ኢዮአብ የቀደሱትን ሁሉና እን
ዲሁም ሌሎቹን ንዋያተ ቅድሳት
ሰሎሚናትና ቤተ ዘመዶቹ ይጠብቁ
ነበር።
29ከይስዓራውያን፤ ከናንያና ወንዶች
ልጆቹ ከቤተ መቅደሱ ውጭ ባለው
ሥራ በእስራኤል ላይ ሹማምትና
ዳኞች ሆነው ተመደቡ።
30ከኬብሮናውያን፤ ሐሸብያ፣ ጠንካራና

26፥15 1ዜና13፥13፤ 2ዜና25፥24
26፥19 2ዜና35፥15፤ነህ7፥1፤ ሕዝ44፥11
26፥20 1ዜና28፥12፤2ዜና24፥5
26፥21 1ዜና23፥7፤29፥8
26፥22 1ዜና9፥26
26፥23 ዘኍ3፥27
26፥24 1ዜና23፥18
26፥25 1ዜና 23፥18
26፥26 2ሳሙ8፥11
26፥28 1ሳሙ9፥9
26፥29 ዘዳ17፥8-13፤1ዜና23፥4
26፥30 1ዜና27፥17
26፥31 2ሳሙ5፥4፤1ዜና23፥19
27፥2 2ሳሙ23፥8
27፥4 2ሳሙ23፥9
27፥5 2ሳሙ23፥20
27፥7 2ሳሙ2፥18
27፥8 1ዜና11፥27

ጉበዝ የሆኑ አንድ ሺህ ሰባት መቶ
ሰዎች ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ በሚ
ገኘው የእስራኤል ምድር ላለው *የእግ
ዚአብሔር* ሥራና ለንጉሡም አገል
ግሎት ኀላፊዎች ሆነው ተመደቡ።
31በኬብሮናውያን በኩል በቤተ ሰቦቻ
ቸው የትውልድ መዝገብ መሠረት
ይሪያ አለቃቸው ነበረ። በዳዊት
ዘመነ መንግሥት በአርባኛው ዓመት
መዛግብቱ ተመርምረው ስለ ነበር፣
በገለዓድ ውስጥ ኢያዜር በተባለ ቦታ
ከኬብሮናውያን መካከል ጠንካራ
ሰዎች ሊገኙ ችለዋል። 32ይሪያም ጠን
ካሮችና የቤተ ሰባቸው አለቆች የሆኑ
ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ሥጋ ዘመ
ዶች ነበሩት። ንጉሥ ዳዊትም እነዚ
ህን የእግዚአብሔር ለሆነውና የንጉሡም
በሆነው ጉዳይ ላይ ሮቤልን፣ ጋድንና
የምናሴን ነገድ እኵሌታ ኀላፊ አድ
ርጎ ሾማቸው።

### የሰራዊቱ ዋና ዋና ክፍሎች

27 የእስራኤል የቤተ ሰቡ አለቆች፣
የሻለቆች፣ የመቶ አለቆች እንዲ
ሁም ዓመቱን ሙሉ በየወሩ የሚመደ
ቡትን ዋና ዋና ክፍሎች በተመለከተ ንጉ
ሡን ያገለገሉ አለቆቻቸው ዝርዝር ይህ
ነው። እያንዳንዱ ዋና ክፍል ሃያ አራት
ሺህ ሰው ነበረው።
2በመጀመሪያው ወር የመጀመሪያው ዋና
ክፍል የበላይ የዘብድኤል ልጅ ያሾ
ብዓም ሲሆን፣ በሥሩ የሚታዘዙ ሃያ
አራት ሺህ ሰዎች ነበሩ። 3እርሱም
የፋሬስ ዘር ሲሆን፣ በመጀመሪያው
ወር የሰራዊቱ ሹማምት ሁሉ የበላይ
ነበር።
4በሁለተኛው ወር የክፍለ ጦሩ የበላይ
አዛዥ አሆሃዊው ዱዲ ሲሆን፣ የዚሁ
ክፍል መሪ ደግሞ ሚቅሎት ነው፤
በሥሩም ሃያ አራት ሺህ ሰው ነበረ።
5በሦስተኛውም ወር የሦስተኛው ክፍለ
ጦር የበላይ አዛዥ የካህኑ የዮዳሄ
ልጅ በናያስ ነበረ፤ ዋናው እርሱ ሲሆን፣
በሥሩ ሃያ አራት ሺህ ሰው ነበረ።
6ይህም ከሠላሳዎቹ ይልቅ ኀያል ሲሆን፣
የሠላሳዎቹ የበላይ ነበረ፤ ልጁ ዓሚዛ
ባድም የክፍሉ ሰራዊት አዛዥ ነበረ።
7በአራተኛው ወር አራተኛው የበላይ
አዛዥ የኢዮአብ ወንድም አሣሄል ሲሆን፣
በእግሩ የተተካውም ልጁ ዝባድያ ነው፤
በሥሩም ሃያ አራት ሺህ ሰው ነበረ።
8በአምስተኛው ወር አምስተኛው የበላይ
አዛዥ ይዝራዊው ሸምሁት ሲሆን፣

በሥሩም ሃያ አራት ሺህ ሰው ነበረ።
9በስድስተኛ ወር ስድስተኛው የበላይ
አዛዥ የቴቁሐዊው የዒስካ ልጅ ዒራስ
ሲሆን፣ በሥሩም ሃያ አራት ሺህ ሰው
ነበረ።
10በሰባተኛው ወር ሰባተኛው የበላይ
አዛዥ የኤፍሬም ወገን የሆነው ፍሎ
ናዊው ሴሌስ ሲሆን፣ በሥሩም ሃያ
አራት ሺህ ሰው ነበረ።
11በስምንተኛው ወር ስምንተኛው የበላይ
አዛዥ ከካዛራውያን ወገን የሆነው
ኩሳታዊው ሲቦካይ ሲሆን፣ በሥሩም
ሃያ አራት ሺህ ሰው ነበረ።
12በዘጠነኛው ወር ዘጠነኛው የበላይ አዛዥ
ከብንያም ወገን የሆነው ዓናቶታዊው
አቢዔዜር ሲሆን፣ በሥሩም ሃያ አራት
ሺህ ሰው ነበረ።
13በዐሥረኛው ወር ዐሥረኛው የበላይ
አዛዥ ከከዛራውያን ወገን የሆነው
ነጦፋዊው ኖኤሬ ሲሆን፣ በሥሩም
ሃያ አራት ሺህ ሰው ነበረ።
14በዐሥራ አንደኛው ወር ዐሥራ አንደ
ኛው የበላይ አዛዥ ከኤፍሬም ወገን
የሆነው ጲርዓቶናዊው በናያስ ሲሆን፣
በሥሩም ሃያ አራት ሺህ ሰው ነበረ።
15በዐሥራ ሁለተኛው ወር ዐሥራ ሁለ
ተኛው የበላይ አዛዥ ከጎቶንያል ቤተ
ሰብ የሆነው ነጦፋዊው ሔልዳይ ነበረ።

## የየነገዱ የጦር ሹማምት

16የየነገዱ የእስራኤል የጦር ሹማምት፤

በሮቤል ነገድ ላይ የተሾመው፣ የዝክሪ
ልጅ አልዓዛር፤
በስምዖን ነገድ ላይ የተሾመው፣ የመዓካ
ልጅ ሰፋጥያስ።
17በሌዊ ነገድ ላይ የተሾመው የቀሙኤል
ልጅ ሐሸብያ፤
በአሮን ነገድ ላይ የተሾመው፣ ሳዶቅ።
18በይሁዳ ነገድ ላይ የተሾመው፣
የዳዊት ወንድም ኤሊሁ፤
በይሳኮር ነገድ ላይ የተሾመው፣የሚካ
ኤል ልጅ ያምሪ።
19በዛብሎን ነገድ ላይ የተሾመው፣
የአብድዩ ልጅ ይሽማያ፤
በንፍታሌም ነገድ ላይ የተሾመው፣
የዓዝሪኤል ልጅ ኢያሪሙት።
20በኤፍሬም ነገድ ላይ የተሾመው፣ የዓዛ
ዝያ ልጅ ሆሴዕ፤
በምናሴ ነገድ እኵሌታ ላይ የተሾ
መው፣ የፈዳያ ልጅ ኢዩኤል።
21በገለዓድ ባለው የምናሴ ነገድ እኵ
ሌታ ላይ የተሾመው፣ የዘካርያስ ልጅ
አዶ፤ በብንያም ነገድ ላይ የተሾመው፣
የአበኔር ልጅ የዕሢኤል።
22በዳን ነገድ ላይ የተሾመው፣ የይሮሐም
ልጅ ዓዛርኤል፤ እንግዲህ የእስራኤል
ነገድ አለቆች እነዚህ ነበሩ።
23እግዚአብሔር እስራኤልን እንደ ሰማይ
ከዋክብት እንደሚያበዛቸው ተስፋ ሰጥቶ
ስለ ነበር፣ ዳዊት ዕድሜያቸው ሃያና ከዚያ
በታች የሆነውን አልቈጠረም ነበር። 24የጽ
ሩያ ልጅ ኢዮአብ መቍጠር ጀመረ፤
ሆኖም አልፈጸመውም፤ መቈጠራቸው በእ
ስራኤል ላይ ቍጣ ስላመጣ፣ የተቈጠረ
ውም በንጉሡ ዳዊት መዝገብ አልገባም።

## ንጉሡ የሾማቸው የበላይ ተቈጣጣሪዎች

25የዓዲኤል ልጅ ዓዝሞት የቤተ መንግ
ሥቱ ዕቃ ቤት ኀላፊ ነበረ፤
የዖዚያ ልጅ ዮናታን በየአውራጃው
በየከተማው፣ በየመንደሩና በየቃፊር መጠ
በቂያው ላሉት ዕቃ ቤቶች ኀላፊ ነበረ።
26የክሉብ ልጅ ዔዝሪ ምድሪቱን ለሚ
ያርሱት ገበሬዎች ኀላፊ ነበረ።
27ራማታዊው ሰሜኢ የወይን ተክል
ቦታዎች ኀላፊ ነበረ፤ ሸፋማዊው ዘብዲ
የወይን ጠጅ ዕቃ ቤት ኀላፊ ነበረ።
28ጌድራዊው በአልሐናን በምራባዊው
ኰረብታዎች ግርጌ ለሚገኙት የወይንና
የወርካ ዛፎች ጥበቃ ኀላፊ ነበረ።
29ሳሮናዊው ሰጥራይ በሳሮን ለሚሰማሩት
የከብት መንጋዎች ኀላፊ ነበረ፤
የዓድላይ ልጅ ሻፋጥ በሸለቆው ውስጥ
ላሉት የከብት መንጋዎች ኀላፊ ነበረ።
30እስማኤላዊው ኡቢያስ የግመሎች ኀላፊ
ነበረ።
ሜሮኖታዊው ዬሕድያ የአህዮች ኀላፊ
ነበረ።
31አጋራዊው ያዚዝ የበግና የፍየል
መንጋዎች ኀላፊ ነበረ።
እነዚህ ሁሉ የንጉሥ ዳዊት ንብረት
ኀላፊዎች ነበሩ።
32አስተዋይ የሆነው የዳዊት አጎት ዮና
ታን አማካሪና ጸሓፊ ነበረ፤ የሐክሞኒም
ልጅ ይሒኤል ደግሞ የንጉሡ ልጆች
ሞግዚት ነበረ።
33አኪጦፌል የንጉሡ አማካሪ ሲሆን፣
አርካዊው ኩሲ ደግሞ የንጉሡ ወዳጅ
ነበረ። 34የበናያስ ልጅ ዮዳሄና አብያታር
በአኪጦፌል እግር ተተኩ።
ኢዮአብም የንጉሡ የክብር ዘብ አዛዥ ሆነ።

## ዳዊት ስለ ቤተ መቅደሱ ያወጣው ዕቅድ

28 ዳዊት በኢየሩሳሌም እንዲሰበሰቡ
የነገዱን የጦር አለቆች፣ ንጉሡን

27፥9 2ሳሙ23፥26
27፥10 2ሳሙ23፥26
27፥11 2ሳሙ21፥18
27፥12 2ሳሙ23፥27
27፥13 2ሳሙ23፥28
27፥14 1ዜና11፥31
27፥15 ኢሱ15፥17፤2ሳሙ23፥29
27፥17 2ሳሙ8፥17፤1ዜና12፥28፤26፥30
27፥23 ዘፍ12፥2፤2ሳሙ24፥1፤1ዜና21፥2-5
27፥24 2ሳሙ24፥15፤1ዜና21፥14
27፥28 1ነገ10፥27
27፥29 መሐ2፥1፤ኢሳ33፥9፤35፥2፤65፥10
27፥31 1ዜና5፥10
27፥33 2ሳሙ15፥12፡37
27፥34 1ሳሙ22፥20፤2ሳሙ2፥13
28፥1 1ዜና22፥17፤1ዜና27፥1-31፤29፥6

የሚያገለግሉትን የከፍለ ጦር አዛዦች፣
የሻለቆቹን፣ የመቶ አለቆቹን፣ የንጉሡና
የልጆቹ ንብረትና ከብት ሁሉ ኀላፊ የሆ
ኑትን፣ እንዲሁም የቤተ መንግሥቱን ሹማ
ምት፣ ኀያላንና ጀግና ተዋጊዎቹን፣ በአጠ
ቃላይ የእስራኤልን ሹማምት ሁሉ ጠራ።
2ከዚያም ንጉሥ ዳዊት በእግሩ ቆሞ
እንዲህ አላቸው፤ "ወንድሞቼና ወገኖቼ
ሆይ፤ እስቲ አድምጡኝ፤ ለእግዚአብሔር
ለቃል ኪዳኑ ታቦት ማደሪያና
ለአምላካችን እግር ማረፊያ የሚሆን ቤት
ለመሥራት
ዐስቤ ዕቅድ አውጥቼ ነበር። 3እግዚአብሔር
ግን እንዲህ አለኝ፤ 'ጦረኛ ሰው ስለሆን
ህና ደምም ስላፈሰስህ፣ አንተ ለስሜ ቤት
አትሠራም'።
4"ነገር ግን የእስራኤል አምላክ እግዚአ
ብሔር በእስራኤል ላይ ለዘላለም እንድ
ነግሥ ከቤተ ሰቤ ሁሉ እኔን መረጠ፤
መሪ እንዲሆንም ይሁዳን መረጠ፤ ከይሁ
ዳም ቤት የእኔን ቤተ ሰብ መረጠ፤ ከአ
ባቴ ልጆች መካከል ደግሞ በመላው እስ
ራኤል ላይ እንድነግሥ ፈቃዱ ሆነ። 5እግ
ዚአብሔር ብዙ ልጆች ሰጥቶኛል፤ ከወን
ዶቹ ልጆቼ ሁሉ በእግዚአብሔር መንግ
ሥት ዙፋን ላይ ተቀምጦ በእስራኤል ሁሉ
ላይ እንዲነግሥ ደግሞ ልጄን ሰሎሞንን
መርጦታል። 6እንዲህም አለኝ፤ 'ቤቴንና
አደባባዮቼን የሚሠራልኝ ልጅህ ሰሎሞን
ነው፤ ምክንያቱም ልጄ እንዲሆን መርጬዋ
ለሁ፤ እኔም አባት እሆነዋለሁ። 7አሁን
እንደሚያደርገው ሁሉ፣ ትእዛዞቼንና ሕጎ
ቼን ምንጊዜም ሳያወላውል የሚፈጽም
ከሆነ፣ መንግሥቱን ለዘላለም አጸናታለሁ'።
8"እንግዲህ አሁንም ይህቺን መልካሚቱን
ምድር እንድትወርሱና ለልጆቻችሁም የዘ
ላለም ርስት አድርጋችሁ እንድታወርሱአ
ቸው፣ የእግዚአብሔርንም ትእዛዝ ሁሉ በጥን
ቃቄ እንድታከብሩ በእስራኤል ሁሉ ፊት፣
በእግዚአብሔር ጉባኤና እግዚአብሔርም እየሰ
ማ አዛችኋለሁ።
9"አንተም ልጄ ሰሎሞን ሆይ፤ እግዚአብሔር
ልብን ሁሉ ስለሚመረምርና ሐሳብን ሁሉ
ስለሚያውቅ፣ የአባትህን አምላክ ዕወቅ፤
በፍጹም ልብና በበጎ ፈቃድ አገልግለው።
ከፈለግኸው ታገኘዋለህ፤ ከተውከው ግን
እርሱም ለዘላለም ይተውሃል። 10ለመቅደስ
የሚሆን ቤት እንድትሠራ እግዚአብሔር
የመረጠህ መሆኑን አሁንም ዐስብ፤ በርት
ተህም ሥራ።
11ከዚያም ዳዊት የቤተ መቅደሱን
መመላለሻ፣ የሕንጻውን፣ የዕቃ ቤቶቹን፣
የፎቁንና የውስጥ ክፍሎቹን እንዲሁም

28፥2 1ሳሙ10፥7፤ 1ዜና17፥2፤2ዜና6፥41፤መዝ99፥5፤132፥1-5፡7፤ኢሳ60፥13
28፥3 2ሳሙ7፥5፤1ነገ5፥3፤1ዜና17፥4፤22፥8
28፥4 ዘፍ49፥10፤ ዘኍ24፥17-19፤1ሳሙ16፥1-13፤1ዜና11፥1፤2ዜና6፥6
28፥5 2ሳሙ12፥24፤1ዜና3፥1፤17፥14፤23፥1
28፥6 2ሳሙ7፥13፤1ነገ8፥20፤1ዜና17፥13
28፥7 1ዜና22፥13
28፥8 ዘዳ4፥1፤6፥1፤17፥14-20፤1 ዜና9፥1
28፥9 ዘዳ4፥31፤ኢሱ24፥20፤1ሳሙ2፥3፤1ነገ9፥7፤1ዜና16፥11፤1ዜና29፥19 2ዜና6፥30፤7፥19፤15፥2፤መዝ7፥9፤40፥16፤44፥23፤74፥1፤77፥7
28፥11 ዘፀ25፥9፤ሐሥ7፥44፤ዕብ8፥5
28፥12 1ዜና12፥18፤26፥20
28፥13 1ዜና24፥1
28፥15 ዘፀ25፥31
28፥16 ዘፀ25፥23
28፥17 ዘፀ27፥3
28፥18 ዘፀ25፥20፡22፤30፥1-10
28፥19 ዘፀ25፥9፤1ነገ6፥38
28፥20 ዘዳ4፥31፤31፥6፤ኢሱ24፥20፤1ነገ6፥14፤1ዜና22፥13፤2ዜና7፥11፤19፥11፤ሐጌ2፥4
28፥21 ዘፀ35፥25-36፤36፥5
29፥1 1ነገ3፥7፤1ዜና22፥5፤2ዜና13፥7

የማስተስረያውን ቦታ ንድፍ ለልጁ ለሰሎ
ሞን ሰጠው። 12ደግሞም መንፈስ ቅዱስ
በልቡ ያሳደረውን የእግዚአብሔርን ቤተ
መቅደስ አደባባይ፣ በዙሪያው ያሉትን
ክፍሎች ሁሉ፣ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅ
ደስ ዕቃ ቤቶችና የንዋየ ቅድሳቱን ግምጃ
ቤቶች ንድፍ ሁሉ ሰጠው፤ 13እንዲሁም
የካህናቱንና የሌዋውያኑን አመዳደብ፣
በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አገልግ
ሎት ሥራና ለአገልግሎቱ ስለሚጠቀምባ
ቸው ዕቃዎች ሁሉ መመሪያ ሰጠው።
14ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውሉትን የወ
ርቅ ዕቃዎች ሁሉ መጠን፣ ለልዩ ልዩ
አገልግሎት የሚውሉትን የብር ዕቃዎች
ሁሉ መጠን አሳወቀው፤ 15እንደየመቅረዙ
አገልግሎት ዐይነት ለወርቁ መቅረዞችና
ለቀንዲሎቻቸው የሚሆነውን የእያንዳንዳ
ቸውን የወርቅ መጠን፣ ለብሩ መቅረዞችና
ለቀንዲሎቻቸው የሚያስፈልገውን የእያ
ንዳንዳቸውን የብር መጠን፣ 16ለያንዳንዱ፣
ኅብስተ ገጽ ጠረጴዛ የሚያስፈልገውን የወ
ርቅ መጠን፣ ለእያንዳንዱም የብር ጠረጴዛ
የሚያስፈልገውን የብር መጠን፣ 17ለሹካ
ዎቹ፣ ለጐድጓዳ ሳሕኖቹ፣ ለማንቆርቆሪ
ያዎቹ የሚያስፈልገውን ንጹሕ የወርቅ
መጠን፣ ለእያንዳንዱ የብር ሳሕን የሚያ
ስፈልገውን የብር መጠን፣ 18ለዕጣኑ መሠ
ዊያ የሚሆነውን የጠራ ወርቅ መጠን እን
ዲሁም ክንፎቻቸውን ዘርግተው የእግዚአ
ብሔርን የቃል ኪዳኑን ታቦት የሚሸፍኑ
ትን ከወርቅ የተሠሩትን የኪሩቤል ሠረገ
ሎች ማለት፣ ንድፍ ሰጠው።
19ዳዊትም፣ "ይህ ሁሉ፣ በእኔ ላይ ባለው
በእግዚአብሔር እጅ በጽሑፍ ተገለጠልኝ፤
የንድፉንም ዝርዝር እንድረዳ ማስተዋልን
ሰጠኝ" አለ።
20ደግሞም ዳዊት ልጁን ሰሎሞንን እን
ዲህ አለው፤ "እንግዲህ በል በርታ፤ ጠን
ክር፤ ሥራውንም ጀምር። አትፍራ፤ ተስ
ፋም አትቍረጥ፤ እግዚአብሔር አምላኬ
ከአንተ ጋር ነውና፤ እርሱም የእግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ አገልግሎት ሥራ እስኪፈ
ጸም ድረስ አይተውህም፤ አይጥልህም።
21ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሥራ ሁሉ
የሚያስፈልጉት ካህናትና ሌዋውያን ምድ
ብም ዝግጁ ነው። በሁሉም የእጅ ሙያ የሠ
ለጠኑ ፈቃደኛ ሰዎች በሥራው ሁሉ
ይረዱሃል። ሹማምቱና ሕዝቡ ሁሉ ትእዛ
ዝህን ይፈጽማሉ።"

## ቤተ መቅደሱን ለመሥራት የቀረቡ ስጦታዎች

29 ከዚያም ንጉሥ ዳዊት ለመላው
ጉባኤ እንዲህ አለ፤ "እግዚአብሔር

የመረጠው ልጄ ሰሎሞን ገና ወጣትና
ልምድም የሌለው ነው:: ይህ ታላቅ ሕንጻ
የሚሠራው ለሰው ሳይሆን ለእግዚአብሔር
አምላክ በመሆኑ፣ ሥራው ከባድ ነው:: 2እኔም
ያለኝን ሀብት ለአምላኬ ቤተ መቅደስ ለወ
ርቁ ሥራ ወርቁን፣ ለብሩ ሥራ ብሩን፣
ለናሱ ሥራ ናሱን፣ ለብረቱ ሥራ ብረቱን፣
ለዕንጨቱ ሥራ ዕንጨቱን እንዲሁም ለፈ
ርጥ የሚሆነውን መረግድ፣ ኬልቄዶን[ሀ]፣
ልዩ ልዩ ኅብር ያላቸውን የከበሩ ድንጋ
ዮች፣ ማናቸውንም ዐይነት የሚያምር
ድንጋይና ዕብነበረድ፣ ይህን ሁሉ በብዛት
አዘጋጅቻለሁ:: 3ከዚህም በቀር ለአምላኬ
ቤት ካለኝ ፍቅር የተነሣ ለዚህ ለተቀደሰ
ቤት ከዚህ በፊት ከሰጠሁት በተጨማሪ
ለዚሁ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የግል
ሀብቴ የሆነውን ወርቅና ብር እሰጣለሁ፤
4ይህም ሦስት ሺህ መክሊት[ሸ] የኦፊር ወር
ቅና ሰባት ሺህ መክሊት[ቀ] ንጹሕ ብር
ለቤተ መቅደሱ የግድግዳ ግንብ ማስጌጫ
5እንዲሁም ለወርቁ ሥራ፣ ለብሩ ሥራ፣
በባለሙያዎች ለሚሠራው ሥራ ሁሉ የሚ
ሆን ነው:: ታዲያ ዛሬ ራሱን ለእግዚአብሔር
ለመቀደስ ፈቃደኛ የሚሆን ማን ነው?”

6ከዚያም የቤተ ሰቡ መሪዎች፣ የነገዱ
የእስራኤል ሹማምት፣ የሻለቆችና የመቶ
አለቆች እንዲሁም በንጉሡ ሥራ ላይ የተ
መደቡ ሹማምት በፈቃዳቸው ሰጡ፤ 7ለእግ
ዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሥራ የሰጡትም
አምስት ሺህ መክሊት[በ] ወርቅ፣ ዐሥር ሺህ
ዳሪክ[ተ] ወርቅ፣ ዐሥር ሺህ መክሊት[ቸ]
ብር፣
ዐሥራ ስምንት ሺህ መክሊት[ኀ] ናስ አንድ
መቶ ሺህ መክሊት[ነ] ብረት ነው:: 8የከበሩ
ድንጋዮች ያለውም ሁሉ፣ በጌድሶናዊው
በይሒኤል አማካይነት ወደ እግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ ግምጃ ቤት አስገባ::
9ስጦታው በገዛ ፈቃድና በፍጹም ልብ
የቀረበ በመሆኑ፣ አለቆቹ ስላደረጉት የበጎ
ፈቃድ ስጦታ ሕዝቡ ደስ አለው፤ ንጉሥ
ዳዊትም እንደዚሁ እጅግ ደስ አለው::

## የዳዊት ጸሎት

10ዳዊትም በመላው ጉባኤ ፊት እግዚአ
ብሔርን እንዲህ ሲል አመሰገነ፤

“የአባታችን የእስራኤል አምላክ እግዚአ
ብሔር ሆይ፤
ከዘላለም እስከ ዘላለም ለአንተ ምስጋና
ይሁን::
11እግዚአብሔር ሆይ፤ በሰማይና
በምድር ያለው ሁሉ የአንተ ነውና፤
ታላቅነት፣ ኀይል፣ ክብርና ግርማ የአንተ
ነው::
እግዚአብሔር ሆይ፤መንግሥትም የአንተ
ነው፤
አንተም እንደ ራስ ከሁሉ በላይ ከፍ ከፍ
ያልህ ነህ::
12ባለጠግነትና ክብር የሚገኘው ከአንተ ነው፤
አንተም የሁሉ ገዢ ነህ፤
ከፍ ከፍ ለማድረግ፣ ለሁሉም ብርታትን
ለመስጠት፣
ብርታትና ኀይል በእጅህ ነው::
13አምላካችን ሆይ፤ አሁንም እናመሰግንሃለን፤
ለከበረው ስምህም ውዳሴ እናቀርባለን::

14”ሁሉ የተገኘው ከአንተ ነው፤ ለአን
ተም የሰጠንህ ከእጅህ የተቀበልነውን ብቻ
ነው:: ታዲያ እንዲህ ያለ ቸርነት እና
ድርግ ዘንድ እኔ ማነኝ? ሕዝቤስ ማነው?
15እኛም እንደ ቀድሞ አባቶቻችን በፊትህ
መጻተኞችና እንግዶች ነን፤ ዘመናችንም
በምድር ላይ እንደ ጥላ ነው፤ ተስፋ ቢስም
ነው:: 16እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ፤
ለተቀደሰው ስምህ ቤተ መቅደስ እንሠራ
ልህ ዘንድ ይህ በብዛት ያዘጋጀነው ሁሉ፣
ከእጅህ የተገኘና ሁሉም የአንተ ነው::
17አምላኬ ሆይ፤ ልብን እንደምትመረ
ምርና ቅንነትን እንደምትወድ ዐውቃ
ለሁ፤ እኔም ይህን ሁሉ የሰጠሁት በበጎ
ፈቃድና በቀና መንፈስ ነው:: አሁንም
በዚህ ያለው ሕዝብህ በበጎ ፈቃዱ እን
ዴት እንደ ሰጠ አይቻለሁ:: 18የአባቶቻ
ችን የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የእስራኤል
አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤ ይህን ዐሳብ
ለዘላለም በሕዝብህ ልብ ጠብቀው፤ ልባ
ቸውንም ለአንተ ታማኝ አድርገው:: 19ትእ
ዛዞችህን፣ ደንብህንና ሥርዐትህን እንዲጠ
ብቅ፣ እኔ ባዘጋጀሁለት ነገሮች ታላቅ ሕንጻ
ለመሥራት እንዲችል፣ ለልጄ ለሰሎሞን
ፍጹም ፈቃደኝነት ስጠው::

20ከዚያም ዳዊት ለመላው ጉባኤ፣
“አምላካችሁን እግዚአብሔርን ወድሱት”
አላ
ቸው:: ስለዚህ የአባቶቻቸውን አምላክ እግ
ዚአብሔርን ወደሱ፤ በእግዚአብሔር በን
ጉሡም ፊት ተደፍተው ሰገዱ::

## ሰሎሞን ንጉሥ መሆኑ በይፋ ታወቀ

29÷21-25 ተጓ ምብ-1ነገ 1÷28-53

21በማግስቱም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት
ሠው፤ የሚቃጠል መሥዋዕትም አቀረቡ፤
ይህም አንድ ሺህ ወይፈን፣ አንድ ሺህ

29÷2 ቀኍ7፥14፥16፤1ዜና22÷2-5፤ዕዝ1÷4፤6÷5፤ኢሳ54÷11፤ሐጌ2÷8
29÷3 2ዜና24÷10፤31÷3፤35÷8
29÷4 ዘፍ10÷29፤1ዜና22÷14
29÷6 ቀኍ9፤ዘፀ25÷1-8፤35÷20-29፤36÷2፤2ዜና24÷10፤1ዜና27÷1፤28÷1፤ዕዝ7÷15
29÷7 ዘፀ25÷2፤ነህ7÷70-71
29÷8 ዘፀ35÷27፤1ዜና26÷21
29÷9 1ነገ8÷61
29÷11 መዝ24÷8፤59÷17፤62÷11፤89÷11፤ራእ5÷12-13
29÷12 2ዜና1÷12፤20÷6፤32÷27፤ዕዝ7÷27፤ መክ5÷19
29÷14 ቀኍ2፤መዝ8÷4፤144÷3
29÷15 ዘፍ17÷8፤23÷4፤ኢዮ7÷6፤ 8÷9፤14÷2፤32÷7፤መዝ39÷12፤102÷11፤144÷4፤መክ6÷12፤ዕብ11÷13
29÷17 1ዜና28÷9፤መዝ15÷1-5፤139÷23፤ምሳ11÷20፤15÷11፤17÷3፤ኤር11÷20፤17÷10
29÷19 1ነገ8÷61፤11÷4፤1ዜና22÷14፤28÷9፤መዝ72÷1፤ኢሳ38÷3
29÷21 1ነገ8÷62፤1ዜና12÷40

[ሀ]2 የዕብራይስጥ የዚህ ቃል ትርጒም በትክክል አይታወቅም
[ሸ]4 100 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
[ቀ]4 240 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
[በ]7 170 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
[ተ]7 84 ኪሎ ግራም ያህል ነው
[ቸ]7 345 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
[ኀ]7 610 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
[ነ]7 345 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው

አውራ በግ፣ አንድ ሺህ የበግ ጠቦት ሲሆን፣
ከመጠጥ ቍርባኖቻቸውና ከሌሎች መሥ
ዋዕቶች ጋር ስለ እስራኤል ሁሉ በብዛት
አቀረቡ። 22በዚያችም ዕለት *በእግዚአብሔር*
ፊት በታላቅ ደስታ በሉ፤ ጠጡም።

ከዚያም የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ንጉሥ
መሆኑን ለሁለተኛ ጊዜ በይፋ ዐወቁ፤ ገዥ
እንዲሆንም *በእግዚአብሔር* ፊት ቀቡት፤
ሳዶቅንም ካህናቸው እንዲሆን ቀቡት።
23ሰሎሞንም ነግሦ በአባቱ በዳዊት ምትክ
*በእግዚአብሔር* ዙፋን ላይ ተቀመጠ፤ ተከ
ናወነለት፤ እስራኤልም ሁሉ ታዘዙለት።
24የጦር አለቆቹና ኀያላኑ ሁሉ እንዲሁም
የንጉሡ የዳዊት ወንዶች ልጆች በሙሉ
ታማኝነታቸውን ለንጉሥ ሰሎሞን አረጋ
ገጡለት።

25*እግዚአብሔርም* ሰሎሞንን በእስራኤል
ሕዝብ ዘንድ ሁሉ እጅግ ከፍ ከፍ አደረ
ገው፤ ከእርሱ በፊት ለነበሩት የእስራኤል
ነገሥታት ያላጐናጸፋቸውን ንጉሣዊ ክብር
ሁሉ ሰጠው።

29፥22 1ሳሙ2፥35፤ 1ዜና12፥40
29፥23 ዘዳ17፥18፤1ነገ2፥12፤1 ዜና17፥14
29፥24 1ነገ1፥9
29፥25 ኢሱ3፥7፤1ነገ10፥7፤ 2ዜና1፥1፡12፤መክ2፥9
29፥26 1ዜና11፥1፤18፥14
29፥27 ዘፍ23፥19፤ 2ሳሙ5፥4-5፤1ዜና 3፥4
29፥28 ዘፍ15፥15፤ 1ዜና23፥1፤ ሐሥ13፥36
29፥29 1ሳሙ9፥9፤ 22፥5፤2ሳሙ7፥2

### የዳዊት መሞት

29፥26-28 ተጓ ምብ - 1 ነገ 2፥10-12

26የእሴይ ልጅ ዳዊት በእስራኤል ሁሉ
ላይ ነግሦ ነበር። 27እርሱም በኬብሮን
ሰባት ዓመት፣ በኢየሩሳሌም ሠላሳ ሦስት
ዓመት፣ በአጠቃላይ አርባ ዓመት ነገሠ።
28ብዙ ዘመን ባለጠግነትና ክብር ሳይጐድ
ልበት ዕድሜ ጠግቦ ሞተ፤ ልጁ ሰሎሞ
ንም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

29በንጉሥ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ከመ
ጀመሪያ እስከ መጨረሻ የተከናወነው
ድርጊት በባለ ራእዩ በሳሙኤል የታሪክ
መጽሐፍ፣ በነቢዩ በናታን የታሪክ መጽሐፍ፣
በባለ ራእዩ በጋድ የታሪክ መጽሐፍ ተጽ
ፎአል። 30የተጻፈውም በሥልጣን ላይ በነ
በረበት ጊዜ ከፈጸማቸው ዝርዝር ጉዳዮ
ችና በዙሪያው ከከበቡት፣ ከእስራኤልና
ከሌሎች አገር መንግሥታት ታሪክ ጋር
ነው።

## ሰሎሞን ጥበብ እንዲሰጠው ጠየቀ

1፥2-13 ተጓ ምብ-3፥4-15
1፥14-17 ተጓ ምብ—10፥26-29፣ 2ዜና9፥25-28

1 አምላኩ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለ
ነበር፣ እጅግም ስላገነነው፣ የዳዊት ልጅ
ሰሎሞን በመንግሥቱ ላይ ተደላድሎ ተቀመጠ
።
2ከዚያም ሰሎሞን ለመላው እስራኤል፣
ለሻለቆች፣ ለመቶ አለቆች፣ ለዳኞች፣
ለእስራኤል መሪዎች ሁሉ እንዲሁም ለየቤተ
ሰቡ አለቆች ተናገረ። 3የእግዚአብሔር ባሪያ
ሙሴ በምድረ በዳ የሠራው የአምላክ
የመገናኛ ድንኳን በዚያ ስለ ነበር፣ ሰሎሞንና
መላው ጉባኤ በገባዖን ወዳለው ኰረብታ ሄዱ።
4በዚያ ጊዜ ዳዊት የአምላክን ታቦት
ከቂሪ ያት ይዓሪም በኢየሩሳሌም ድንኳን
ተክሎ ወዳ ዘጋጀለት ስፍራ አምጥቶት ነበር፤
5ይሁን እንጂ የሆር ልጅ፣ የኡሪ ልጅ
ባስልኤል የሠራው መሠዊያ በገባዖን
በእግዚአብሔር ማደሪያ ድንኳን ፊት
ለፊት ይገኝ ነበር፤ ስለዚህ ሰሎሞንና
ጉባኤው ይህንኑ ፈለጉ። 6ሰሎሞንም
በእግዚአብሔር ፊት በመገናኛው ድንኳን
ውስጥ ወዳለው ወደ ናሱ መሠዊያ ወጥቶ
በላዩ ላይ አንድ ሺህ የሚቃጠል መሥዋዕት
አቀረበ።
7በዚያ ሌሊት እግዚአብሔር ለሰሎሞን
ተገለጠ፣ "እንድሰጥህ የምትፈልገውን ሁሉ
ጠይቀኝ" አለው።
8ሰሎሞን እግዚአብሔርን እንዲህ አለው፤
"ለአባቴ ለዳዊት ታላቅ በጎነት አድርገህለ
ታል፤ እኔንም በእግሩ ተክተህ አንግሠኸኛል።
9አሁንም እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፤
ያነገሥኸኝ ብዛቱ እንደ ትቢያ በሆነ ሕዝብ
ላይ ስለ ሆነ፣ ለአባቴ ለዳዊት የሰጠኸው
ተስፋ ይጽና። 10ይህን ሕዝብ ለመምራት
እንድችል፣ ጥበብና ዕውቀትን ስጠኝ፤
ይህ ካልሆነ ይህን ታላቅ ሕዝብህን ማን
ሊገዛ ይችላል?"
11እግዚአብሔርም ሰሎሞንን እንዲህ አለው፤
"የልብህ መሻት ይህ ስለ ሆነ፣ ብልጥግናና
ሀብት ወይም የጠላቶችህን ነፍስ ወይም
ረጅም ዕድሜ ስላልጠየቅህ፣ ነገር ግን ባነ
ገሥሁህ ሕዝቤ ላይ የምትገዛበትን ጥበብና
ዕውቀት ስለ ጠየቅህ፣ 12ጥበብና ዕውቀት
ይሰጥሃል፤ እንዲሁም ከአንተ በፊት የነበረ
ማንኛውም ንጉሥ ያላገኘውን፣ ከአንተ በኋላም
የሚነሣው የማያገኘውን ብልጽግና፣ ሀብትና

1፥1 ዘፍ21፥22፤ 39፥2፤ ዘኍ14፥43፤ 1ነገ2፥12፤1ዜና29፥25፤2ዜና12፥1
1፥2 1ዜና9፥1
1፥3 ዘፀ40፥18፤ ዘሌ17፥4፤ኢሱ9፥3
1፥4 2ሳሙ6፥17፤ 1ዜና15፥25
1፥5 ዘፀ31፥2፤ 38፥2፤1ዜና13፥3
1፥7 2ዜና7፥12
1፥8 1ዜና23፥1
1፥9 ዘፍ12፥2፤ 2ሳሙ7፥25፤ 1ነገ8፥25 27፥17፤ 2ሳሙ5፥2፤ ምሳ8፥15-16
1፥11 ዘዳ17፥17
1፥12 1ዜና29፥12፡ 25፤ 2ዜና9፥22፤ ነህ13፥26
1፥14 1ሳሙ8፥11፤ 1ነገ9፥19
1፥15 1ነገ9፥28፤ ኢሳ60፥5
2፥1 ዘዳ12፥5፤ መክ2፥4
2፥2 2ዜና10፥4
2፥3 2ሳሙ5፥11፤ 1ዜና14፥1
2፥4 ዘፀ25፥30፤ 29፥42፤30፥7፤ ዘሌ23፥38፤ዘኍ28፥14፤ዘዳ12፥5፤2ዜና13፥11፤29፥28
2፥5 ዘፀ12፥12፤ 1ዜና16፥25፤22፥5

ክብር እሰጥሃለሁ።"
13ሰሎሞንም የመገናኛው ድንኳን ካለበት
ከገባዖን ኰረብታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ፤
በእስራኤልም ላይ ነገሠ።
14ሰሎሞን ሠረገሎችንና[ሀ] ፈረሶችን ሰበሰበ፤
እርሱም አንድ ሺህ አራት መቶ ሠረገ
ሎችና ዐሥራ ሁለት ሺህ ፈረሶች ነበሩት፤
እነርሱንም በሠረገላ ከተሞችና እርሱ ባለበት
በኢየሩሳሌም ከተማ አኖራቸው። 15ንጉሡም
ወርቁና ብሩ በኢየሩሳሌም እንደ ተራ ድንጋይ
እንዲበዛ፣ ዝግባውም በየኰረብታው ግርጌ
እንደሚገኝ የሾላ ዛፍ እንዲበዛ አደረገ።
16የሰሎሞንም ፈረሶች የመጡት ከግብፅና[ለ]
ከቀዌ ነበር፤ ከቀዌ[ሐ] የገዟቸውም የንጉሡ
ነጋዴዎች ነበሩ። 17ከግብፅ ያስገ ቧቸውም
አንዱን ሠረገላ በስድስት መቶ ሰቅል[መ] ብር፣
አንዱን ፈረስ በአንድ መቶ አምሳ ሰቅል[ሠ]
ብር ገዝተው ነው። እነዚህንም ደግሞ ለኬጢ
ያዊያንና ለሦርያውያን ነገሥታት ሁሉ
ይሸጡላቸው ነበር።

## ቤተ መቅደሱን ለመሥራት የተደረገ ዝግጅት

2፥1-18ተጓ ምብ-1ነገ5፥1-16

2 ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ስም ቤተ
መቅደስ፣ ለራሱም ቤተ መንግሥት
እንዲሠራ አዘዘ። እርሱም፣ የሚሸከሙ ሰባ
ሺህ፣ ከኰረብታ ላይ ድንጋይ የሚፈልጡ
ሰማንያ ሺህ ሰዎችና ሦስት ሺህ ስድስት
መቶ የሥራ ተቈጣጣሪዎች አሰማራ።
3ከዚህ በኋላ፣ ሰሎሞን ለጢሮስ ንጉሥ
ለኪራም የሚከተለውን ይህን መልእክት ላከ፤
"አባቴ ዳዊት የሚኖርበትን ቤተ መንግ
ሥት ሲሠራ እንደ ላክህለት ሁሉ፣ ለእኔም
የዝግባ እንጨት ላክልኝ። 4ሽታው ደስ
የሚያሰኝ ዕጣን በፊቱ የሚታጠንበትን፣
የተቀደሰ እንጀራ በየጊዜው የሚቀር
ብበትን፣ በየጧቱና በየማታው፣ በየሰ
ንበቱና በየመባቻው እንዲሁም በተወሰኑት
በአምላካችን በእግዚአብሔር በዓላት የሚቃጠ
ል መሥዋዕት የሚቀርብበትን ቤተ
መቅደስ ለአምላኬ ለእግዚአብሔር ስም
ሠርቼ እቀድስ ዘንድ አስቤአለሁ። ይህም
ለእስራኤል የዘላለም ሥርዓት ነው።
5"አምላካችን ከሌሎች አማልክት ሁሉ
ይበልጥ ታላቅ ስለ ሆነ፣ የምሠራውም ቤተ
መቅደስ ታላቅ ይሆናል።

[ሀ]14 ወይም ሠረገለኞች ተብሎ መተርጐም ይቻላል።
[ለ]16 በዚህና በቍጥር 17 ላይ የተጠቀሰችው በኪልቂያ አውራጃ የምትገኘው ሙዙር ልትሆን ትችላለች።
[ሐ]16 ምናልባት ኪልቂያ ናት።
[መ]17 7 ኪሎ ግራም ያህል ነው።
[ሠ]17 1.7 ኪሎ ግራም ነው።

[6]ነገር ግን ሰማይና ከሰማያት በላይ ያለው
ሰማይ እንኳን እርሱን ይይዘው ዘንድ
አይችልምና፣ ቤተ መቅደስ ሊሠራለት
የሚችል ማነው? በፊቱ ዕጣን የሚታጠ
ንበትን እንጂ ቤተ መቅደስ እሠራለት
ዘንድ እኔ ማን ነኝ?
[7]"ስለዚህ አንተ በወርቅና በብር፣ በናስና
በብረት፣ በሐምራዊና በደማቅ ቀይ፣
በሰማያዊም ግምጃ *ሥራ* ዕውቀት
ያለውን እንዲሁም አባቴ ዳዊት ካዘጋ
ጃቸው ከእኔ የእጅ ባለሙያዎች ጋር
በይሁዳና በኢየሩሳሌም የቅርጻ ቅርጽ
ጥበብ *ሥራ* የሚሠራ ሰው ላክልኝ።
[8]ሰዎችህ ከሊባኖስ እንጨት በመቍረጥ
*ሥራ* ዐዋቂዎች መሆናቸውን ስለማውቅ፣
ከሊባኖስ የዝግባ፣ የጥድና የሰንደል ዕን
ጨትም ላክልኝ፤ ሰዎቼም ከሰዎችህ ጋር
አብረው ይሠራሉ። [9]የምሠራው ቤተ
መቅደስ ትልቅና እጅግ ውብ መሆን
ስላለበት፣ ብዙ ጠርብ ያዘጋጁልኛልና።
[10]ዕንጨቱን ለሚቈርጡ አገልጋዮችህ
ሃያ ሺህ የቆሮስ መስፈሪያ[ሬ] ስንዴ ዱቄት፣
ሃያ ሺህ የባዶስ[ሰ] መስፈሪያ ወይን ጠጅና
ሃያ ሺህ የባዶስ መስፈሪያ ዘይት እሰጣለሁ።"
[11]የጢሮስ ንጉሥ ኪራምም ለሰሎሞን እንዲህ
ሲል በደብዳቤ መለሰለት፤
"*እግዚአብሔር* ሕዝቡን ስለሚወድድ
አንተን በእነርሱ ላይ አነገሠህ፤ "
[12]ኪራምም በመቀጠል እንዲህ አለ፤
"ሰማይንና ምድርን የፈጠረ የእስራ
ኤል አምላክ *እግዚአብሔር* ይባረክ! *ለእግዚ
አብሔር* ቤተ መቅደስን፣ ለራሱም ቤተ
መንግሥትን የሚሠራ፣ ብልኅነትንና
ማስተዋልን የተሞላ ጥበበኛ ልጅ ለንጉሥ
ዳዊት ሰጥቶአልና።
[13]"እጅግ ብልሃተኛ የሆነውን ኪራምአቢ
ን ልኬልሃለሁ፤ [14]እርሱም እናቱ ከዳን
ወገን፣ አባቱም የጢሮስ አገር ሰው ነው፤
በወርቅና በብር፣ በናስና በብረት፣ በድን
ጋይና በዕንጨት፤ እንዲሁም በሐምራ
ዊና በሰማያዊ፣ በቀይ ግምጃና በቀጭን
በፍታ *ሥራ* የሠለጠነ ሲሆን፣ በልዩ
ልዩ ቅርጻ ቅርጽ *ሥራ* ልምድ ያካበተና
የተሰጠውን ማናቸውንም ንድፍ በ*ሥራ*
መተርጐም የሚችል ባለሙያ ነው።
እርሱም ከአንተ የእጅ *ሥራ* ባለሙያዎችና
ከጌታዬ ከአባትህ የእጅ *ሥራ* ባለሙያዎች
ጋር አብሮ ይሠራል።
[15]"አሁንም ጌታዬ በሰጠው ተስፋ
መሠረት ስንዴውንና ገብሱን፣ የወይራ
ዘይቱንና የወይን ጠጁን ለአገልጋዮቹ
ይላክ፤ [16]እኛም የሚያስፈልግህን ግንድ

2፥6 ዘፀ3፥11፤ 1ነገ8፥27፤ኤር23፥24
2፥7 ዘፀ35፥31፤ 1ዜና22፥16
2፥10 ዕዝ3፥7
2፥11 1ነገ10፥9፤ 2ዜና9፥8
2፥12 ነህ9፥6፤ መዝ8፥3፤ 33፥6፤96፥5፤102፥25፤ 146፥6
2፥13 1ነገ7፥13
2፥14 ዘፀ31፥6፤ 35፥31፡35
2፥15 ዕዝ3፥7
2፥16 ኢሱ19፥46፤ ዮና1፥3
2፥17 2ሳሙ24፥2፤ 1ዜና22፥2
2፥18 1ዜና22፥2፤ 2ዜና8፥8

3፥1 ዘፍ28፥7፤ 2ሳሙ24፥18፤ ሐሥ7፥47
3፥2 ዕዝ5፥11
3፥3 ሕዝ41፥2
3፥5 ሕዝ40፥16
3፥7 ዘፍ3፥24፤ ሕዝ41፥18
3፥8 ዘፀ26፥33
3፥9 ዘፀ26፥32

ሁሉ ከሊባኖስ ቈርጠንና አስረን እስከ
ኢዮጴ ድረስ ቍልቍል በማንሳፈፍ እን
ሰድልሃለን፤ አንተም ወደ ኢየሩሳሌም
ታስወስደዋለህ።"
[17]ሰሎሞን አባቱ ዳዊት ካደረገው ቈጠራ
በኋላ፣ በእስራኤል ምድር የነበሩትን መጻ
ተኞች ሁሉ ቈጠረ፤ ቍጥራቸውም አንድ
መቶ አምሳ ሦስት ሺህ ስድስት መቶ
ሆነ። [18]ከእነዚህም ሰባ ሺውን ተሸካሚዎች፣
ሰማንያ ሺውን በኰረብታው ላይ ድንጋይ
ፈላጮች፣ ሦስት ሺህ ስድስት መቶውን
ደግሞ የሥራው ተቈጣጣሪዎች ሆነው
ሰዎቹን እንዲያሠሩ መደበ።

**ሰሎሞን ቤተ መቅደስ ሠራ**

3፥1-14 ተጓ ምብ —1ነገ6፥1-29

**3** ሰሎሞንም በኢየሩሳሌም *እግዚአብሔር*
ለአባቱ ለዳዊት በተገለጠበት በሞሪያ
ተራራ ላይ በኢያቡሳዊው በኦርና ዐውድማ
ዳዊት ባዘጋጀው ቦታ *የእግዚአብሔርን* ቤተ
መቅደስ *መሥራት* ጀ*መረ*። [2]በነገሠም
በአራተኛው ዓመት፣ በሁለተኛው ወር፣
በሁለተኛው ቀን ቤተ መቅደሱን *መሥራት*
ጀ*መረ*።
[3]ሰሎሞን ለሕንጻው የጣለው መሠረት
በቀድሞው ስፍር ልክ ርዝመቱ ስድሳ ክንድ፣
ወርዱም ሃያ ክንድ[ሸ] ነበር። [4]በቤተ መቅደሱ
መግቢያ በር ላይ ያለው በረንዳ[ቀ]
ርዝመቱ በቤተ መቅደሱ ወርድ ልክ
ሃያ ክንድ ሲሆን፣ ከፍታውም ሃያ[በ] ክንድ
ነበር።
ውስጡንም በንጹሕ ወርቅ ለበጠው።
[5]የቤተ መቅደሱን ዋና ክፍል በጥድ እንጨት
አልብሶ በተጣራ ወርቅ ለበጠው፤ የዘን
ባባና የሰንሰለት አምሳልም ቀረጸበት። [6]ቤተ
መቅደሱን በከበረ ድንጋይ አስጌጠው፤ የተጠ
ቀመበትም ወርቅ የፈርዋይም ወርቅ ነበር።
[7]የጣራውን ተሸካሚዎች፣ መቃኖችን፣ የቤተ
መቅደሱን ግድግዳና መዝጊያዎች በወርቅ
ለበጠ፤ በግድግዳዎቹም ላይ የኪሩቤልን ምስል
ቀረጸ።
[8]እንደዚሁም ቅድስተ ቅዱሳኑን ሠራ፤
ርዝመቱ ከቤተ መቅደሱ ወርድ ጋር እኩል
ሲሆን፣ ርዝመቱ ሃያ ክንድ፣ ስፋቱም ሃያ
ክንድ ነበር፤ ውስጡንም በስድስት መቶ[ተ]
መክሊት የተጣራ ወርቅ ለበጠው። [9]የወርቅ
ምስማሮቹም አምሳ[ቸ] ሰቅል ይመዝኑ ነበር፤
የላይኛውንም ክፍሎች እንደዚሁ በወርቅ
ለበጠ።

[ሬ]10 4,400,000 ኪሎ ሊትር ያህል ነው።
[ሰ]10 440,000 ኪሎ ሊትር ያህል ነው።
[ሸ]3 ርዝመቱ 27 ሜትር ወርዱ 9 ሜትር ያህል ነው።
[ቀ]4 በዚህና በቍጥር 8፡11 እንዲሁም 13 ላይ 9 ሜትር ያህል ነው።
[በ]4 አንዳንድ የሰበዓ ሊቃናት ትርጒሞችና የሱርስቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን *አንድ መቶ ሃያ* ይላል።
[ተ]8 21 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው።
[ቸ]9 0.6 ኪሎ ግራም ያህል ነው።

[10]በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ የሁለት ኪሩቤል
ምስል አስቀርጾ በወርቅ ለበጣቸው።
[11]ከዳር እስከ ዳር ገጥሞ የተዘረጋው የኪሩ
ቤል ክንፍ በጠቅላላው ሃያ ክንድ ነበር፤
የመጀመሪያው ኪሩብ አንዱ ክንፍ አምስት
ክንድ[ኀ] ሆኖ የቤተ መቅደሱን ግድግዳ ሲነካ፣
ሌላው አምስት ክንድ የሆነው ክንፉ
ደግሞ የሁለተኛውን ኪሩብ ክንፍ ይነካ
ነበር። [12]እንደዚሁም የሁለተኛው ኪሩብ
አንዱ ክንፍ አምስት ክንድ ሆኖ በአንጻሩ
ያለውን የቤተ መቅደስ ግድግዳ ሲነካ፣
አምስት ክንድ የሆነው ሌላው ክንፉ
ደግሞ የመጀመሪ ያውን ኪሩብ ክንፍ ይነካ
ነበር። [13]የተዘረጋው የእነዚህ ኪሩቤል ክንፍ
ሃያ ክንድ ሲሆን፣ ፊታቸውን ወደ ቤተ
መቅደሱ ዋና ክፍል አዙረው[ነ] በእግራቸው
ቆመዋል።
[14]ደግሞም ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊ፣ ከደ
ማቅ ቀይ ፈትልና ከቀጭን በፍታ መጋ
ረጃ ሠርቶ፣ የኪሩቤልን ምስል በጥልፍ
ጠለፈበት።
[15]በቤተ መቅደሱም ፊት ለፊት በአን
ድነት ቁመቱ ሠላሳ አምስት ክንድ[ኘ]
የሆነ፣ በእያንዳንዱም ላይ አምስት ክንድ
ጒልላት ያለው ሁለት ዐምድ ሠራ። [16]እርስ
በርሳቸው የተጠላለፉ ሰንሰለቶች ሠርቶ[አ] ከዐ
ምዶቹ ጫፍ ጋር አገናኛቸው፤ ከዚያም
መቶ የሮማን ፍሬዎች ሠርቶ ከሰንሰለቶቹ
ጋር አያያዛቸው።
[17]ዐምዶቹንም አንዱን በደቡብ፣
ሌላውን በሰሜን አድርጎ በቤተ
መቅደሱ ፊት ለፊት አቆማቸው፤ በደቡብ
በኩል ያለውን፤ "ያኪን"፣[ከ] በሰሜን በኩል
ያለውንም "ቦዔዝ"[ኸ] ብሎ ጠራቸው።

## የቤተ መቅደሱ ዕቃዎች መሟላት

4፥2-6፥10-5፥1ተጓ ምብ—1ነገ 7፥23-26፡38-51

4 ርዝመቱ ሃያ ክንድ፣ ወርዱ ሃያ
ክንድ፣ ቁመቱ ዐሥር ክንድ[ወ] የሆነ የናስ
መሠዊያ ሠራ። [2]እንዲሁም የጐኑ ስፋት
ከጠርዝ እስከ ጠርዝ ዐሥር ክንድ፣ ቁመቱ
አምስት[ዘ] ክንድ የሆነ ክብ በርሜል ቀልጦ
ከፈሰሰ ብረት ሠራ፤ ዙሪያውም ሲለካ
ሠላሳ ክንድ[ዠ] ሆነ። [3]ከበርሜሉ ከንፈር
በታችም በእያንዳንዱ ክንድ ርቀት ላይ
ዙሪያውን
ዐሥር የኮርማ ቅርጾች[የ] ነበሩበት፤ ኮር
ማዎቹም ከበርሜሉ ጋር አንድ ወጥ ሆነው
በሁለት ረድፍ ቀልጠው ተሠርተው ነበር።
[4]በርሜሉ በዐሥራ ሁለት ኮርማዎች ላይ
የቆመ ሲሆን፣ ኮርማዎቹም ሦስቱ ወደ
ሰሜን፣ ሦስቱ ወደ ምዕራብ፣ ሦስቱ ወደ
ደቡብ፣ ሦስቱ ወደ ምሥራቅ ይመለከቱ
ነበር። በርሜሉ በእነዚህ ላይ ያረፈ ሲሆን፣

3፥10 ዘፀ25፥18
3፥13 ዘፀ25፥18
3፥14 ዘፍ3፥24፤
ዘፀ26፥31፡33
3፥15 1ነገ7፥15፡
22፤ ራእ3፥12
3፥16 1ነገ7፥17፡29
4፥1 ዘፀ20፥24፤
40፥6፤1ነገ8፥64
4፥2 ራእ4፥6፤15፥2
4፥4 ዘኁ2፥3-5፤
ሕዝ48፥30-34፤
ራእ21፥13
4፥6 ዘፀ30፥18፤
ነህ13፥5፡9፤
ሕዝ40፥38
4፥7 ዘፀ25፥31፡40
4፥8 ዘፀ25፥23፤
ዘኁ4፥14
4፥9 1ነገ6፥36፤
2ዜና33፥5
4፥11 1ነገ7፥14
4፥14 1ነገ7፥27-30

የሁሉም ጀርባ ወደ መካከል የዞረ ነበር።
[5]የበርሜሉ ውፍረት አንድ ስንዝር፣[ደ] ከንፈሩ
ደግሞ የጽዋ ከንፈር ወይም የሱፍ አበባ
ይመስል ነበር፤ ይህም ሦስት ሺህ የባዶስ
መስፈሪያ[ጀ] የሚይዝ ነበር።
[6]እንዲሁም ዐሥር የመታጠቢያ ገንዳዎች
አሠርቶ አምስቱን በደቡብ፣ አምስቱን ደግሞ
በሰሜን በኩል አስቀመጠ፤ ገንዳዎች ለሚ
ቃጠል መሥዋዕት የሚቀርቡት ነገሮች የሚ
ታጠቡባቸው ሲሆኑ፣ በርሜሉ ግን ለካህ
ናት መታጠቢያ የሚያገለግል ነበር።
[7]በተሰጠው የአሠራር መመሪያ መሠረት፣
ዐሥር የወርቅ መቅረዞች ሠርቶ ወደ ቤተ
መቅደሱ በማስገባት፣ አምስቱን
በስተደቡብ፣ አምስቱን በስተሰሜን አኖራ
ቸው።
[8]ዐሥር ጠረጴዛ ሠርቶም ወደ ቤተ መቅደሱ
በማስገባት አምስቱን በስተ ደቡብ፣ አምስ
ቱን ደግሞ በስተ ሰሜን በኩል አኖራቸው፤
ደግሞም አንድ መቶ ጐድጓዳ የወርቅ ሳሕ
ኖች ሠራ።
[9]የካህናቱንም አደባባይ ሠራ፣ እንዲሁም
ታላቁን አደባባይና በሮቹን ከሠራ በኋላ
በናስ ለበጣቸው። [10]በርሜሉንም ከቤተ መቅ
ደሱ በስተደቡብ ምሥራቅ ባለው ማዕዘን
በቀኝ በኩል አኖረው።
[11]እንዲሁም ምንቸቱን፣ መጫሪያዎችንና
ጐድጓዳ ሳሕኖችን ሠራ። ኪራምም ለቤተ
መቅደሱ አገልግሎት የሚውሉትን ዕቃዎች
ለንጉሥ ሰሎሞን ሠርቶ ጨረሰ፤ እነዚህም
[12]ሁለቱ ዐምዶች፣
በአዕማዱ ጫፍ ላይ ያሉት
ሁለት ባለ ሳሕን ቅርጽ ጒልላት
በዐምዶቹ ላይ ያሉትን ሁለቱን፣
ባለ ሳሕን ቅርጽ ጒልላት
የሚያስጌጡ ሁለት ዙር መርበቦች፤
[13]በዐምዶቹ ላይ ያሉትን ሁለቱን፣
ባለሳሕን ቅርጽ ጒልላት እንዲያስጌጡ
ለያንዳንዱ መርበብ ሁለት ዙር ሮማኖች
ለሁለቱም ዙር መርበቦች
በድምሩ አራት መቶ ሮማኖች፤
[14]መቆሚያዎች ከነመታጠቢያ ሳሕኖቻቸው፤

[ኀ]11 በዚህና በቍጥር 15 ላይ 2.3 ሜትር ያህል ነው።
[ነ]13 ወይም፣ *ወደ ቤተ መቅደሱ እያዩ* ተብሎ መተርጐም ይቻላል።
[ኘ]15 16 ሜትር ያህል ነው።
[አ]16 ወይም፣ *በቤተ መቅደሱ ውስጥ ሰንሰለት ሠርቶ* ተብሎ መተርጐም ይችላል፤ በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጒም በትክክል አይታወቅም።
[ከ]17ምናልባት *ያኪን* ማለት፣ *እርሱ አነጻ* ማለት ሊሆን ይችላል።
[ኸ]17ምናልባት *ቦዔዝ* ማለት *ብርታት በእርሱ ውስጥ ነው* ማለት ሊሆን ይችላል።
[ወ]1ርዝመቱና ወርዱ 9 ሜትር ቍመቱ 4.5 ሜትር ያህል ነው።
[ዘ]2 2.3 ሜትር ያህል ነው።
[ዠ]2 13.5 ሜትር ይህል ነው።
[የ]3 0.5 ሜትር ያህል ነው።
[ደ]5 8 ሳንቲ ሜትር ያህል ነው።
[ጀ]5 66 ኪሎ ሊትር ያህል ነው።

15በርሜሉና እርሱን የተሸከሙት ዐሥራ
ሁለት ኮርማዎች፤
16ምንቸቶችና መጫሪያዎች፣
ሜንጦዎችና ከነዚሁም ጋር
የተያያዙ ዕቃዎች።
ኪራምአቢ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
መገልገያ እንዲሆን ለሰሎሞን የሠራቸው ዕቃዎች
በሙሉ ከተወለወለ ናስ የተሠሩ ነበሩ።
17ንጉሡም እነዚህ ዕቃዎች በዮርዳኖስ ሸለቆ፣
በሱኮትና በጽሬዳ መካከል ባለው በሸክላ ዐፈር
ቦታ ቀልጠው በሸክላ ቅርጽ ተሠርተው እንዲ
ወጡ አደረገ። 18እነዚህ ሰሎሞን ያሠራቸው
ነገሮች ሁሉ እጅግ ብዙዎች ስለ ሆኑ የናሱ
ክብደት ምን ያህል እንደሆነ አልታወቀም
ነበር።
19እንደዚሁም ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ መገልገያ የሚሆኑትን ዕቃዎች ሠራ
፤
እነዚህም፦
የወርቅ መሠዊያ፣
የገጸ ኅብስቱ ጠረጴዛ፣
20በተሰጠው መመሪያ መሠረት፣ በቅድስተ
ቅዱሳኑ ፊት ለፊት እንዲነድዱ፣ ከንጹሕ
ወርቅ የተሠሩ መቅረዞች ከነቀንዲሎቻቸው፣
21የወርቅ አበባ ቅርጽ ሥራዎች፣
ቀንዲሎችና መኮስተሪያዎች ከንጹሕ ወርቅ
የተሠሩ ነበሩ።
22ከንጹሕ ወርቅ የተሠሩ የመብራት ማጥፊ
ያዎች፣ ለመርጨት የሚያገለግሉ ጐድጓዳ
ሳሕኖች፣ ጭልፋዎችና ጥናዎች፣ እንደ
ዚሁም የቤተ መቅድሱ የወርቅ መዝጊ
ያዎች፣ ይኸውም የቅድስተ ቅዱሳኑ
የውስጠኛው መዝጊያዎችና የቤተ
መቅደሱ ዋናው አዳራሽ መዝጊያዎች ከን
ጹሕ ወርቅ የተሠሩ ነበሩ።

5 ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
የሠራው ሥራ ሁሉ ከተጠናቀቀ በኋላ፣
አባቱ ዳዊት የቀደሰውን ብሩንና ወር
ቁን፣ ዕቃዎቹንም ሁሉ አምጥቶ በእግዚአ
ብሔር ቤተ መቅደስ ግምጃ ቤት አኖራቸው።

## ታቦቱ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ

5፥2-6፥11 ተጓ ምብ— 1ነገ 8፥1-21

2ከዚያ በኋላ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን
የኪዳን ታቦት ከዳዊት ከተማ ከጽዮን እንዲ
ያመጡ፣ የእስራኤልን ሽማግሌዎች፣ የየነ
ገዱን መሪዎች ሁሉና የእስራኤላውያንን የቤ
ተሰብ አለቆች በኢየሩሳሌም ሰበሰበ። 3የእስ
ራኤልም ሰዎች ሁሉ የሰባተኛው ወር በዓ
ል በሚከበርበት ጊዜ፣ በንጉሡ ፊት
ተሰበሰቡ።
4የእስራኤል ሽማግሌዎች በተሰበሰቡም
ጊዜ ሌዋውያኑ ታቦቱን አነሡት፤ 5ታቦቱን፣
የመገናኛ ድንኳኑንና በውስጡ ያሉትን

4፥16 1ነገ7፥13
4፥17 ዘፍ33፥17
4፥18 1ነገ7፥23
4፥19 ዘፀ25፥23
4፥20 ዘፀ25፥31
4፥22 ዘሌ10፥1፤ ዘኍ7፥14
5፥1 2ሳሙ8፥11፤ 1ነገ6፥14
5፥2 ዘኍ3፥31፤ 1ዜና15፥25
5፥3 1ዜና9፥1
5፥5 ዘኍ3፥31፤ 1ዜና15፥2
5፥7 ራእ11፥19
5፥8 ዘፍ3፥24
5፥10 ዘፀ16፥34፤ ዘዳ10፥2፤ዕብ9፥4
5፥11 1ዜና24፥1
5፥12 1ነገ10፥12፤ 1ዜና9፥33፤13፥8፤፣25፥1፤መዝ68፥25
5፥13 ዘፀ40፥34፤ 1ዜና16፥34፤2ዜና7፥3፤20፥21፤ዕዝ3፥11፤ መዝ100፥5 106፥1፤107፥1፤118፥1፤136፥1፤ኤር33፥11
5፥14 ዘፀ19፥16፤ 29፥43፤ 40፥35፤ ራእ15፥8
6፥1 ዘፀ19፥9
6፥2 ዕዝ6፥12፤ 7፥15፤መዝ135፥21

የተቀደሱ ዕቃዎች ሁሉ ይዘው ወደ ላይ ወጡ፤
ሌዋውያን የሆኑ ካህናትም ተሸከሟቸው።
6ንጉሥ ሰሎሞንና በአጠገቡ የተሰበሰበው
መላው የእስራኤል ጉባኤ ስፍር ቍጥር
የሌላቸውን በጎችና በሬዎች በታቦቱ ፊት
ሠዉ።
7ካህናቱም የእግዚአብሔርን የኪዳኑን
ታቦት የቤተ መቅደሱ ውስጠኛ ክፍል ወደ
ሆነው ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ አግብተው
ከኪሩቤል ክንፍ በታች ባለው ስፍራው
አኖሩት። 8ኪሩቤልም ክንፎቻቸውን
ከታቦቱ በላይ ባለው ስፍራ ላይ ዘርግተው፣
ታቦቱንና መሎጊያ ዎቹን ሸፈኑ። 9መሎጊ
ያዎቹም በጣም ረጃጅም ከመሆናቸው
የተነሣ፣ ታቦቱ እስካለበት ድረስ ያሉት
ጫፎቻቸው ከቅድስተ ቅዱሳኑ ፊት ለፊት
ይታዩ ነበር፤ ከመቅደሱ ውጭ ግን አይታዩም
ነበር፤ ዛሬም እዚያው ቦታ ይገኛሉ። 10እስራ
ኤላውያን ከግብፅ ከወጡ በኋላ ከእነርሱ
ጋር ኪዳን ባደረገ ጊዜ፣ ሙሴ በኮሬብ ተራራ
በውስጡ ካስቀመጣቸው ከሁለቱ ጽላቶች
በቀር በታቦቱ ውስጥ ምንም አልነበረም።
11ካህናቱም ከቤተ መቅደሱ ወጡ፤ እዚያ
የነበሩት ካህናት በምድባቸው መሰረት
ባይሆንም፣ ሁሉም ራሳቸውን ቀድሰው ነበር።
12መዘምራን የነበሩት ሌዋውያን ሁሉ፣
አሳፍ፣ ኤማን፣ ሄማንና ኤዶታም፣ ወንዶች
ልጆቻቸውና የሥጋ ዘመዶቻቸው ሁሉ
ያማረ ቀጭን በፍታ ለብሰው፣ ከመሠዊያው
በስተ ምሥራቅ በኩል ቆመው ጸናጽል ይጸነ
ጽሉ፣ በገና ይደረድሩና መሰንቆ ይመቱ
ነበር፤ እነርሱም መለከት በሚነፉ አንድ
መቶ ሃያ ካህናት ታጅበው ነበር፡ 13መለ
ከት ነፊዎችና ዘማሪዎችም በአንድነት አንድ
ድምፅ ሆነው ለእግዚአብሔር ውዳሴና ምስጋና
አቀረቡ፤ በመለከት፣ በጸናጽልና በሌሎች
መሣሪያዎች ታጅበውም ድምፃቸውን ከፍ
በማድረግ እግዚአብሔርን እያወደሱ፣
"እርሱ ቸር ነው፣
ፍቅሩም ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።"
እያሉ ዘመሩ።
ከዚያም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
በደመና ተሞላ። 14የእግዚአብሔር ክብር
የአምላክን ቤተ መቅደስ ሞልቶት ስለነበር፣
ከደመናው የተነሣ ካህናቱ አገልግሎታቸውን
ማከናወን አልቻሉም።

6 ከዚያም ሰሎሞን እንዲህ አለ፤ "እግ
ዚአብሔር ጥቅጥቅ ባለ ደመና ውስጥ
እንደሚኖር ተናግሮአል፤ 2እኔም አንተ
ለዘላለም ትኖርበት ዘንድ፣ ይህን ታላቅና
ድንቅ ቤተ መቅደስ ሠራሁልህ።"
3መላው የእስራኤል ጉባኤ እዚያው
ቆመው ሳሉ፣ ንጉሡ ዘወር ብሎ
ባረካቸው፤ 4እንዲህም አለ፤

“ለአባቴ ለዳዊት በቃሉ የሰጠውን ተስፋ
በእጁ የፈጸመ የእስራኤል *አምላክ* እግዚ
አብሔር ይመስገን፤ እንዲህ ብሏልና፤
5 ‘ሕዝቤን ከግብፅ ካወጣሁበት ጊዜ
ጀምሮ፣ ስሜ የሚጠራበት ቤተ መቅ
ደስ ይሠራበት ዘንድ ከማናቸውም የእስ
ራኤል ነገድ ከተሞች አንድም አልመ
ረጥሁም፤ ወይም የሕዝቤ የእስራኤል
መሪ ይሆን ዘንድ ማንንም አልመረጥሁም።
6አሁን ግን ስሜ በዚያ እንዲሆን ኢየሩ
ሳሌምን፣ ሕዝቤን እስራኤልን እንዲ
ገዛም ዳዊትን መርጫለሁ።”
7“አባቴ ዳዊት፣ ለእስራኤል አምላክ
*ለእግ ዚአብሔር ስም* ቤተ መቅደስ
*ለመሥራት* በልቡ አስቦ ነበር፤ *8እግዚ
አብሔር ግን*፣ ለአባቴ ለዳዊት እንዲህ
አለው፤ ‘ለስሜ ቤተ መቅደስ *ለመሥራ
ት* በልብህ አስበህ ነበር፤ ይህን በልብህ
በማሰብህ መልካም አድርገሃል፤ 9ይሁን
እንጂ ቤተ መቅደሱን የምትሠራው
አንተ አይደለህም፤ ለስሜ ቤተ መቅደስ
የሚሠራልኝ ከአብራክህ የሚከፈለው፣
የገዛ ልጅህ ነው።’
*10“እግዚአብሔርም የተናገረውን ቃል ፈ
ጽሞ አል*፤ እኔም *እግዚአብሔር* በሰጠው
ተስፋ *መሠረት* በአባቴ በዳዊት እግር
ተተክቼ፣ በእስራኤል ዙፋን ላይ
ተቀምጫለሁ፤ ለእስራኤል አምላክ
*ለእግዚአብሔርም* ስም ቤተ መቅደስ
ሠርቻለሁ። 11በዚያም *እግዚአብሔር* ከእስ
ራኤል ሕዝብ ጋር ያደ ረገው ኪዳን
ያለበትን ታቦት አኑሬአለሁ።”

## ሰሎሞን በምረቃው ጊዜ ያቀረበው ጸሎት

6፥12-40ተጓ ምብ—1ነገ8፥22-53
6፥41-42ተጓ ምብ—መዝ132፥8-10

12ከዚህ በኋላ ሰሎሞን መላው የእስራ
ኤል ጉባኤ ባሉበት *በእግዚአብሔር መ
ሠዊያ* ፊት እጆቹን ዘርግቶ ቆመ።
13ሰሎሞንም ርዝመቱ አምስት ክንድ፣[ገ]
ወርዱ አምስት ክንድ፣ ከፍታውም ሦስት
ክንድ[ጠ] የሆነ የናስ መድረክ በውጭው
አደባባይ መካከል አሠ ርቶ ነበር፤
በመድረኩም ላይ ወጥቶ በመ ቆም
በመላው የእስራኤል ጉባኤ ፊት
ተንበርክኮ እጆቹን ወደ ሰማይ ዘረጋ፣
14እንዲህም አለ፤
“የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር*
ሆይ፤ በፍጹም ልባቸው በመንገድህ
ከሚሄዱት ባሪያዎችህ ጋር የፍቅር ኪዳንህን
የምትጠብቅ በሰማይም ሆነ በምድር
እንደ አንተ ያለ አምላክ የለም፤ 15ለባሪያህ
ለአባቴ ለዳዊት የሰጠኸውን ተስፋ አ
ጽንተሃል፤ በአፍህ የተናገርኸውን ዛሬም
እንደ ሆነው በእጅህ ፈጽመኸው።

6፥6 ዘፀ20፥24፤ ዘዳ12፥5፤1ዜና28፥4፤ ኢሳ14፥1
6፥7 1ሳሙ10፥7፤ 1ዜና17፥2፤ ሐሥ7፥46
6፥11 ዘዳ10፥2፤ መዝ25፥10፤50፥5
6፥13 ነህ8፥4፤ መዝ95፥6
6፥14 ዘፀ8፥10፤ 15፥11፤ዘዳ7፥9
6፥15 1ዜና22፥10
6፥16 2ሳሙ7፥13፡ 15፤2ዜና23፥3፤ መዝ132፥12
6፥18 መዝ11፥4፤ ኢሳ40፥22፤66፥1፤ ራእ21፥3
6፥20 ዘፀ3፥16፤ ዘዳ12፥11፤2ዜና7፥14፤ 30፥20፤መዝ34፥15
6፥21 መዝ51፥1፤ ኢሳ33፥24፤ 40፥2፤43፥25፤44፥22፤ 55፥7፤ሚክ7፥18
6፥22 ዘፀ22፥11
6፥23 ኢሳ3፥11፤ 65፥6፤ማቴ16፥27
6፥24 ዘሌ26፥17
6፥26 ዘሌ26፥19፤ ዘዳ11፥17፤28፥24፤2ሳሙ1፥21
6፥27 ቀኍ30፥39፤ 2ዜና7፥14

16“አሁንም የእስራኤል *አምላክ* እግዚአብሐ
ር ሆይ፤ ለባሪያህ ለአባቴ ለዳዊት፣
‘ልጆችህ ‘አንተ እንደ አደረግኸው ሁሉ
በሚያደርጉት ሁሉ ሕጌን በመጠበቅ
በፊቴ ቢመላለሱ፣ በእስራኤል ዙፋን ላይ
በፊቴ የሚቀመጥ ሰው ከቶ አታጣም’
ብለህ የሰጠኸውን ተስፋ አጽናለት።
17እንግዲህ የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሐ
ር* ሆይ፤ ለባሪያህ ለዳዊት የሰጠኸው
የተስፋ ቃል ይፈጸም።
18“በውኑ እግዚአብሔር ከሰው ጋር
በምድር ላይ ይኖራልን? እነሆ፤ ሰ
ማያትና ሰማየሰማያት እንኳ አንተን ሊ
ይዙህ አይችሉም፤ ታዲያ እኔ የሠራሁት
ይህ ቤተ መቅደስማ
ምንኛ ያንስ! 19ይሁን እንጂ እግዚአብሔር
*አምላኬ* ሆይ፤ የባሪያህን ጸሎትና ስለ ምሕ
ረት ያቀረበውን ልመና አድምጥ፤ ባሪያህ
በፊትህ የሚያቀርበውን ጩኸትና ጸሎት
ስማ። 20ስምህ እንደሚጠራበት ወደ
ተናገርኸው ወደዚህ ቤተ መቅደስ ዓይ
ኖችህ በቀንም በሌሊትም የተገለጡ ይሁኑ፤
ባሪያህ ወደዚህ ስፍራ የሚጸልየውንም ጸሎት
ስማ። 21ባሪያህና ሕዝብህ እስራኤል ወደዚህ
ስፍራ በሚጸልዩበትም ጊዜ ልመናቸውን
ስማ፤ ከማደሪያህ ከሰማይ ስማ፤ ሰምተህም
ይቅር በል።
22አንድ ሰው ባልንጀራውን ቢበድልና
እንዲምል ቢጠየቅ፣ እርሱም መጥቶ በቤተ
መቅደሱ በመሠዊያህ ፊት ቢምል፣ 23ከሰ
ማይ ሆነህ ስማ፤ አድርግም። በደለኛውን፣
በደሉን በራሱ ላይ አድርገህ እንደ ሥራው
በመክፈል በባሪያዎችህ መካከል ፍረድ።
ንጹሑም በደለኛ አለመሆኑን አስታውቅ፤
እንደ ንጽሕናውም ክፈለው።
24“ሕዝብህ እስራኤል አንተን ከመበደላቸው
የተነሣ በጠላቶቻቸው ፊት ድል ቢሆኑ፣
ወደ አንተ ተመልሰውም በዚህ ቤተ
መቅደስ ውስጥ በፊትህ በመጸለይና
ልመናቸውን በማቅረብ ስምህን ቢጠሩ፣
25በሰማይ ሆነህ ስማ፤ የሕዝብህን የእስራ
ኤልን ኀጢአት
ይቅር በል፤ ለእነርሱና ለአባቶቻቸው ወደ
ሰጠሃቸውም ምድር መልሳቸው።
26“ሕዝብህ አንተን ከመበደላቸው የተነሣ፣
ሰማያት ተዘግተው ዝናብ ባይዘንብ፣ አንተ
ስለ አስጨነቅሃቸው ወደዚህ ስፍራ ቢጸልዩ፣
ስምህን ቢጠሩና ከኀጢአታቸው ቢመለሱ፣
27በሰማይ ሆነህ ስማ፤ የባሪያዎችህን የሕዝብህን
የእስራኤልን ኀጢአት ይቅር በል፤ የሚኖሩ
በትን ቀናውን መንገድ አስተምራቸው፤
ለሕዝብህ ርስት አድርገህ በሰጠኸውም
ምድር ላይ ዝናብን ላክ።

[ገ]13 2.3 ሜትር ይህል ነው።
[ጠ]13 1.3 ሜትር ይህል ነው።

28“በምድሪቱ ላይ ራብ ወይም ቸነፈር
ወይም ዋግ ወይም አረማሞ ወይም
አንበጣ ወይም ኩብኩባ በሚወርድባት
ጊዜ፣ ወይም ደግሞ በየትኛውም ከተ
ማቸው ሳሉ ጠላት በሚከባቸው ጊዜ፣
ወይም ማና ቸውም አደጋ ወይም ደዌ
በሚደርስባቸው
ጊዜ፣ 29ከሕዝብህ ከእስራኤል ማንም
ሰው ጭንቀቱና ሕመሙ ተሰምቶት፣ እጁን
ወደዚህ ቤተ መቅደስ በመዘርጋት
ጸሎትና ልመና ቢያቀርብ፣ 30በሰማይ
በማደሪያህ ሆነህ ስማ፤ ይቅርም በል፤
የሰውን ልብ የምታውቅ አንተ ብቻ ስለ
ሆንህ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው መጠን
ክፈለው፤ 31ይህም ለአባቶቻችን በሰጠ
ሃቸው ምድር በሚኖሩበት ጊዜ ሁሉ
አንተን እንዲፈሩህና በመንገዶችህ
እንዲሄዱ ነው፡፡
32“ከሕዝብህ ከእስራኤል ወገን ያልሆነ
ባዕድ ሰው ስለ ታላቁ ስምህ፣ ስለ
ኀያሉ እጅህና ስለ ተዘረጋው ክንድህ
ሰምቶ ከሩቅ አገር በመምጣት ወደዚህ
ቤተ መቅደስ በሚጸልይበት ጊዜ፣ 33በሰ
ማይ በማደሪያህ ሆነህ ስማ፤ የምድር
ሕዝቦች ሁሉ እንደገዛ ሕዝብህ እንደ
እስራኤል፣ ስምህን በማወቅ እንዲፈሩ
ህ፣ የሠራሁትም ይህ ቤት ስምህ
የሚጠራብት ቤት መሆኑን እንዲያውቁ
ባዕዱ ሰው የሚጠይቅህን ሁሉ አድርግ፡፡
34“ሕዝብህ አንተ በምትልካቸው ቦታ
ሁሉ
ጠላቶቻቸውን ለመውጋት በሚወጡበት
ጊዜ፣ አንተ ወደ መረጥኻት ወደዚህች
ከተማ፣ እኔም ለስምህ ወደ ሠራሁት
ወደዚህ ቤተ መቅደስ ወደ አንተ ቢጸልዩ፣
35ጸሎታቸውንና ልመናቸውን በሰማይ
ስማ፤ የጠየቁህንም አድርግላቸው፡፡
36“መቼም የማይበድል ሰው የለምና፣
አንተን በበደሉህ ጊዜ፣ ተቈጥተሃቸው ሩቅ
ወይም ቅርብ ወደ ሆነ አገር በምርኮ
ለሚወስዳቸው ጠላት አሳልፈህ ብትሰ
ጣቸው፣ 37በተማረኩበት አገር ሆነው
የልብ ጸጸት ተሰምቶአቸው ንስሐ ቢገቡና
በምርኮ ሳሉ፣ ‘ኀጢአት ሠርተናል፤
በድለናል፤ ክፉ ድርጊትም ፈጽመናል’ ቢሉ፣
38ተማርከው በሚኖሩብትም ምድር ሆነው
በፍጹም ልባቸው፣ በፍጹምም ነፍሳቸው
ቢመለሱና ለአባቶቻቸው ወደ ሰጠሃቸው
ምድር፣ አንተም ወደ መረጥኻት ከተማና
እኔም ለስምህ ወደ ሠራሁት ቤተ መቅደስ
ቢጸልዩ፣ 39ጸሎታቸውንና ልመናቸውን
በሰማይ በማደሪያህ ስማ፤ የጠየቁህንም
አድርግላቸው፡፡ የበደሉህንም የሕዝብህን
ኀጢአት ይቅር በል፡፡

6፥28 2ዜና20፥9
6፥30 ቀኍ27፤ 1ሳሙ2፥3፤መዝ7፥9፤44፥21፤ምሳ16፥2፤17፥3
6፥31 ዘዳ6፥13፤ መዝ34፥7፡9፤103፥11፡13፤ምሳ8፥13
6፥32 ዘፀ3፥19፡20፤2ዜና9፥6
6፥33 ዘፀ12፥43
6፥34 ዘዳ28፥7፤ 1ዜና5፥20
6፥36 ዘሌ26፥44፤ 1ነገ8፥46፤ ኢዮ11፥12፤ 15፥14፤መዝ143፥2፤ መክ7፥20፤ኤር9፥5፤13፥23፤17፥9፤ ሮሜ3፥9፤ኤፌ2፥3
6፥37 1ነገ8፥48፤ 2ዜና7፥14፤12፥6፡12፤30፥11፤33፥12፡19፡23፤34፥27፤ 36፥12፤ኢሳ58፥3፤ ኤር24፥7፤29፥13
6፥39 ቀኍ27፤ 2ዜና30፥9
6፥40 1ነገ8፥29፡52፤ 2ዜና7፥15፤ ነህ1፥6፡11፤መዝ17፥6፤ 116፥1፤130፥2፤ ኢሳ37፥17
6፥41 1ዜና28፥2፤ መዝ3፥7፤7፥6፤13፥6፤27፥13፤59፥4፤116፥12፤ 132፥16፤142፥7፤ ኢሳ33፥10
6፥42 መዝ2፥2፤ 89፡24፡2
7፥1 ዘፀ16፥10፤ 19፥18፤ዘሌ9፥24፤ 1ነገ18፥38፤ መዝ26፥8
7፥2 ዘፀ29፥43፤ 40፥35፤1ነገ8፥11
7፥3 1ዜና16፥34፤ 2ዜና5፥13፤ዕዝ3፥11
7፥6 1ዜና15፥16፡ 24
7፥7 ዘፀ29፥13
7፥8 ዘፍ15፥18፤ ዘኍ13፥21፤1ዜና9፥1፤ 2ዜና30፥26፤ ነህ8፥17

40አሁንም አምላኬ ሆይ፤ በዚህ ስፍራ
ወደ ቀረበው ጸሎት ዓይኖችህ የተገለጡ፣
ጆሮ ዎችህም የሚያደምጡ ይሁኑ፡፡
41“አሁንም እግዚአብሔር *አምላክ* ሆይ
ተነሥ፣ ከኀይልህ ታቦት ጋር ወደ
ማረፊያ ቦታህ ግባ፡፡ *እግዚአብሔር* አምላክ
ሆይ፤ ካህናትህ ድነትን ይልበሱ፤
ቅዱሳንህም በቸርነትህ ደስ ይበላቸው፡፡
42*እግዚአብሔር* አምላክ ሆይ፤ የቀባኸውን
አትተወው፤ ለባሪያህ ለዳዊት ቃል
የገባህለትን ጽኑ ፍቅር አስብ፡፡

### የቤተ መቅደሱ መመረቅ

7፥1-10ተጓ ምብ— 1ነገ8፥62-66

7 ሰሎሞን ጸሎቱን በፈጸመ ጊዜ እሳት
ከሰማይ ወርዶ የሚቃጠለውን መሥዋዕ
ትና ሌላውንም መሥዋዕት በላ፤ *የእግዚ
አብሔርም* ክብር ቤተ መቅደሱን ሞላው፡፡
2*የእግዚአብሔርም* ክብር *የእግዚአብሔር*
ክብር ቤተ መቅደስ ስለ ሞላው ካህናቱ ወደዚያ
መግባት አልቻሉም፡፡ 3እስራኤላውያንም
ሁሉ እሳቱ ሲወርድ፣ *የእግዚአብሔርንም*
ክብር ከቤተ መቅደሱ በላይ ሲያዩ፣
በመተሳለ ፈያው ወለል ላይ ተንበረከኩ፤
በግንባራቸውም ወደ መሬት ተደፍተው
ሰገዱ፤ እንዲህ እያሉም *ለእግዚአብሔር*
ምስጋና አቀረቡ፤
“እርሱ ቸር ነውና፤
ፍቅሩም ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል፡፡”
እያሉም *እግዚአብሔርን* አመሰገኑ፡፡
4ከዚህ በኋላ ንጉሡና ሕዝቡ ሁሉ
*በእግዚአብሔር ፊት መሥዋዕት* አቀረቡ፡፡
5*ንጉሥ* ሰሎሞንም *ሃያ* ሁለት ሺህ በሬ፣ *መቶ*
*ሃያ* ሺህ በግና ፍየል *ሠዋ*፤ ንጉሡና ሕዝቡም
ሁሉ በዚህ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ
ቀደሱ፡፡ 6ካህናቱም እንደ ሌዋውያኑ፣ *ንጉሥ*
*ዳዊት እግዚአብሔር* እንዲወደስበት *የሠራውንና*
“ፍቅሩ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል” በማለት *እግዚ
አብሔርን* ባመሰገነ ጊዜ የተቀመጠበትን
*የእግዚአብሔርን* የዜማ *መሣሪያ* ይዘው በተመደ
በላቸው ስፍራ ቆሙ፡፡ ካህናቱ በሌዋውያኑ
ትይዩ ሆነው መለከቶቻቸውን ሲነፉም እስራ
ኤላውያን ሁሉ ቆመው ነበር፡፡
7ሰሎሞን የሠራው የናስ *መሠዊያ የሚቃጠ*
*ለውን መሥዋዕት*፣ የእህሉን ቍርባንና ስቡን
*መያዝ* ስላልቻሉ *ከእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ
*ፊት ለፊት ያለውን የመካከለኛውን*
አደባባይ ክፍል ቀድሰው፤ *የሚቃጠለውን*
*መሥዋዕትና የኅብረት መሥዋዕቱን*[ጫ] ስብ በዚያ
አቃጠለ፡፡
8በዚያን ጊዜ ሰሎሞን ከእስራኤል ሕዝብ
ሁሉ ጋር ለሰባት ቀን በዓሉን አከበረ፤ ሕዝ
ቡም ከሐማት መግቢያ እስከ ግብፅ ወንዝ
ድረስ ካለው ምድር የመጣ እጅግ ታላቅ

[ጫ]7 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል

ጉባኤ ነበር። 9*መሠዊያውን* ለሰባት ቀን ስለ
ቀደሱና የሰባት ቀን በዓል በተጨማሪ ስላከ
በሩ፣ በስምንተኛው ቀን የተቀደሰ ጉባኤ
አደረጉ። 10ሰሎሞንም በሰባተኛው ወር፣
በሃያ ሦስተኛው ቀን ወደየቤታቸው እንዲ
ሄዱ ሕዝቡን አሰናበተ፤ ሕዝቡም *እግዚ
አብሔር* ለዳዊትና ለሰሎሞን እንዲሁም
ለሕዝቡ ለእስራኤል ስላደረገው በጎ ነገር
ሁሉ በልባቸው ደስ እያላቸውና ሐሤት
እያደረጉ ሄዱ።

### *እግዚአብሔር* ለሰሎሞን ተገለጠለት

7፥11-22ተጓ ምብ— 1ነገ9፥1-9

11ሰሎሞን *የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስና
የቤተ መንግሥቱን ሥራ ጨረሰ፤ ለ*እግዚ
አብሔር* ቤተ መቅደስና ለራሱ ቤተ መን
ግሥት ያደርግ ዘንድ በልቡ ያሰበውን ሁሉ
ካከናወነ በኋላ፣ 12*እግዚአብሔር* በሌሊት
ተገልጦለት እንዲህ አለው፤

"ጸሎትህን ሰምቻለሁ፤ ይህንንም ስፍራ
መሥዋዕት የሚቀርብበት ቤተ መቅደስ
እንዲሆን ለራሴ መርጬዋለሁ።

13"ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማያትን በምዘጋ
በት ጊዜ ወይም ምድሪቱን እንዲበላ አንበጣ
በማዝበት ጊዜ፣ ወይም በሕዝቤ ላይ ቸነ
ፈር በምሰድበት ጊዜ፣ 14በስሜ የተጠራው
ሕዝቤ ራሱን አዋርዶ ቢጸልይ፣ ፊቴን ቢፈ
ልግና ከክፉ መንገዱ ቢመለስ፣ ከሰማይ
እሰማዋለሁ፤ ኀጢአቱን ይቅር እላለሁ፤
ምድሩንም እፈውሳለሁ። 15አሁንም በዚህ
ስፍራ ወደሚጸለየው ጸሎት ዓይኖቼ
ይገለጣሉ፤ ጆሮዎቼም ያዳምጣሉ። 16ስሜ
ለዘላለም በዚያ ይኖር ዘንድ ይህን ቤተ
መቅደስ መርጫለሁ፤ ቀድሼዋለሁም። ዓይ
ኖቼም ልቤም ዘወትር በዚያ ይሆናሉ።

17"አንተም ደግሞ አባትህ ዳዊት እንዳ
ደረገው ሁሉ በፊቴ ብትሄድ፣ ያዘዝሁህን
ሁሉ ብትፈጽም፣ ሥርዐቶቼንና ሕግጋቴን
ብትጠብቅ፣ 18ለአባትህ ለዳዊት፣ 'ከዘርህ
እስራኤልን የሚገዛ አታጣም' ብዬ
በገባሁለት ቃል ኪዳን መሠረት የመንግ
ሥትህን ዙፋን አጸናለሁ።

19"እናንተ ግን እኔን ከመከተል ተመል
ሳችሁ የሰጠኋችሁን ሥርዐቴንና ትእዛዜን
ብትተው፣ ሄዳችሁም ሌሎችን አማልክት
ብታገለግሉና ብታመልኩ፣ 20በዚያን ጊዜ
እስራኤልን ከሰጠኋቸው ምድሬ እነቅላ
ቸዋለሁ፤ ለስሜ የቀደስሁትን ይህን ቤተ
መቅደስ እተዋለሁ፤ በሕዝቦችም ሁሉ ዘንድ
መተረቻና መዘባበቻ አደርገዋለሁ። 21ይህ
ቤተ መቅደስ አሁን እጅግ የሚያስደንቅ
ቢሆንም በአጠገቡ የሚያልፉ ሁሉ በመ
ገረም፤ '*እግዚአብሔር* በዚህች ምድርና
በዚህ ቤተ መቅደስ ላይ እንዲህ ያለውን
ነገር ያመጣው ከቶ ለምን ይሆን?' ይላሉ፤
22ሕዝቡም፣ 'ይህን ሁሉ ጥፋት ያመ
ጣባቸው፣ ከግብፅ ምድር ያወጣቸውን
የአባቶቻቸውን *አምላክ* እግዚአብሔርን
ትተው ሌሎችን አማልክት ስለ ተከተሉ፣
ስላመለኳቸውና ስላገለገሏቸው ነው' ብለው
ይመልሳሉ።"

### ሰሎሞን ያከናወናቸው ሌሎች ሥራዎች

8፥1-18ተጓ ምብ— 1ነገ9፥10-28

8 ሰሎሞን *የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስና
የራሱን ቤተ መንግሥት የሠራባቸው
ሃያ ዓመት ከተፈጸመ በኋላ፣ 2ኪራም የሰጠ
ውን ከተሞች አድሶ እስራኤላውያን እንዲ
ሰፍሩባቸው አደረገ። 3ከዚያም ሰሎሞን ወደ
ሐማት ሱባ ዘመተ፤ ያዛትም። 4በምድረ
በዳውም ውስጥ ተድሞርንና ቀድሞ በሐማት
ሠርቶአቸው የነበሩትን የዕቃ ቤት ከተሞች
ሁሉ ሠራ። 5እንዲሁም የላይኛውን ቤት
ሖሮንና የታችኛውን ቤትሖሮን የተመሸጉ
ከተሞች አድርጎ ከቅጥሮቻቸው፣ ከበሮቻ
ቸውና ከመዝጊያዎቻቸው ጋር ሠራ። 6ደግ
ሞም ባዕላትንና የዕቃ ቤት ከተሞቹን ሁሉ፣
ሠረገሎችና* ፈረሶች የሚኖሩባቸውን ከተሞች
ሁሉ፣ ባጠቃላይ በኢየሩሳሌም፣ በሊባኖስና
በግዛቱ ሁሉ ለመሥራት የፈለጋቸውን ነገሮች
ሁሉ ሠራ።

7እስራኤላውያን ያልሆኑ ግን ከኬጢ
ያውያን፣ ከአሞራውያን፣ ከፌርዜያውያን፣
ከኤዊያውያንና ከኢያቡሳውያን የቀሩ
ት
ሕዝቦች ሁሉ፣ 8እስራኤላውያን ያላጠፏ
ቸውን፣ በምድሪቱ የቀሩ ዘሮቻቸውን የጕልበት
ሥራ ይሠሩ ዘንድ ሰሎሞን መለመላቸው፤
እስከ ዛሬም ይሠራሉ። 9ይሁን እንጂ ሰሎሞን
ማንም እስራኤላዊ ባሪያ ሆኖ በግዳጅ ሥራ
ውን እንዲሠራ አላደረገም፤ እነርሱ ተዋጊ
ዎች፣ የሻምበል አዛዦች፣ የሠረገሎችና
የሠረገላ ነጂዎች አዛዦች ነበሩና። 10ከእነዚ
ህም ሁለት መቶ አምሳዎቹ የንጉሥ
ሰሎሞን ሹማምንት ሰዎቹን የሚቈጣጠሩ
ነበሩ።

11ሰሎሞንም፣ "*የእግዚአብሔር* ታቦት የገ
ባበት ቦታ ሁሉ ቅዱስ ስለሆነ፣ ሚስቴ
በእስራኤል ንጉሥ በዳዊት ቤተ መንግ
ሥት መኖር አይገባትም" በማለት የፈርዖንን
ልጅ ከዳዊት ከተማ እርሱ ወደሠራላት ቤተ
መንግሥት አመጣት።

12ሰሎሞንም በቤተ መቅደሱ መመላለሻ
ፊት ለፊት ባሠራው *የእግዚአብሔር* መሠዊያ
ላይ የሚቃጠል መሥዋዕት ለ*እግዚአብሔር*

7፥9 ዘሌ23፥26፤ 2ዜና30፥23
7፥11 1ዜና28፥20
7፥12 ዘዳ12፥5፡11፤ 2ዜና1፥7
7፥13 ዘዳ11፥7፤ አሞ4፥7
7፥14 ዘፀ10፥3፤ 15፥26፤ዘሌ26፥41፤ ዘኍ6፥27፡2ነገ17፥13፤ 1ዜና16፥11፤2ዜና6፥20፡27፡37፤30፥20፤ መዝ60፥2፤ ኢሳ30፥26፤ 53፥5፤55፥7፤57፥18፤ኤር33፥6፤ ሕዝ18፥32፤ ዘካ1፥4፤ሚል4፥2
7፥15 1ነገ8፥29፤ 2ዜና6፥40፤ነህ1፥6
7፥16 ዘዳ12፥5፤ 2ዜና33፥7
7፥17 ዘሌ19፥37፤ 1ነገ9፥4
7፥18 2ሳሙ7፥13፤ 1ዜና5፥2፤17፥12፤ 2ዜና13፥5፤23፥3፤ ኢሳ9፥7፤55፥4፤ ኤር33፥17፡21፤ ሚክ5፥2
7፥19 ዘዳ28፥15፤ 1ዜና28፥9፤2ዜና12፥1፤24፥18፤ኤር9፥13፤11፥8
7፥20 ዘዳ28፥37፤ 29፥28፤1ነገ14፥15፤ ኤር12፥14፤16፥13፤50፥11
7፥21 ዘዳ29፥24፤ ኤር19፥8
7፥22 ኤር16፥11
8፥1 2ሳሙ7፥2
8፥4 2ሳሙ8፥9
8፥5 ኢሱ10፥10
8፥6 ኢሱ19፥44
8፥7 ዘፍ10፥16፤ 15፥18-21፤ዕዝ9፥1
8፥8 2ዜና2፥18
8፥11 1ነገ3፥1
8፥12 1ነገ8፥64፤ 2ዜና15፥8

*6 ወይም *ሠረገለኞች* ተብሎ መተርጐም ይቻላል።
*8 ወይም *ከሌቦ ሐማት* ተብሎ መተርጐም ይቻላል።

አቀረበ። [13]ሙሴ ስለ መሥዋዕት አቀራረብ ባዘዘው መሠረት በእያንዳንዱ የበዓል ቀን ይኸውም በየሰንበቱ፣ በየወሩ መባቻና በሦስቱ የዓመት በዓላት ማለትም በቂጣ በዓል፣ በመከር በዓልና በዳስ በዓል ጊዜ የሚቃጠለውን መሥዋዕት *ለእግዚአብሔር* አቀረበ። [14]የአባቱን የዳዊትን ሥርዐት በመከተልም፣ ካህናቱን በየአገልግሎት ክፍላቸው ሌዋውያኑንም ምስጋናውን እንዲመሩና በየዕለቱ ሥራቸው ካህናቱን እንዲረዱ መደባቸው። ደግሞም የእግዚአብሔር ሰው ዳዊት ባዘዘው መሠረት የቤተ መቅደሱን በር ጠባቂዎች በልዩ ልዩ በሮች ጥበቃ ላይ በየክፍላቸው መደባቸው። [15]እነርሱም ንጉሡ ግምጃ ቤቱን ጨምሮ ስለ ማናቸውም ነገር ለካህናቱና ለሌዋውያኑ የሰጠውን ትእዛዝ አልተላለፉም ነበር።

[16]*የእግዚአብሔ ቤተ መቅደስ መሠረት* ከተጣለበት ዕለት አንሥቶ እስከ ፍጻሜው ድረስ ያለው የሰሎሞን ሥራ ሁሉ ተከናወነለት፤ በዚሁ ሁኔታም *የእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ሥራ ከፍጻሜ ደረሰ።

[17]ከዚያም ሰሎሞን የኤዶም የባሕር ጠረፍ ወደ ሆኑት ወደ ዔዮንጋብርና ወደ ኤሎት ሄደ። [18]ኪራምም ባሕሩን በሚያውቀት በራሱ መኮንኖች የሚታዘዙ መርከቦችን ላከለት፤ እነዚህም ከሰሎሞን ሰዎች ጋር በመሆን ወደ ኦፊር ተጓዙ፤ ከዚያም አራት መቶ አምሳ መክሊት[ፀ] ወርቅ አምጥተው ለንጉሥ ሰሎሞን ሰጡት።

## የሳባ ንግሥት ሰሎሞንን ጐበኘች

9፥1-12ተጓ ምብ— 1ነገ10፥1-13

**9** የሳባ ንግሥት የሰሎሞንን ዝና በሰማች ጊዜ አስቸጋሪ በሆኑ ጥያቄዎች ልትፈትነው ወደ ኢየሩሳሌም መጣች። ቅመማ ቅመም፣ እጅግ ብዙ ወርቅና የከበሩ ድንጋዮችን በግመሎች አስጭና ከታላቅ ጓዝ ጋር ደረሰች፤ ወደ ሰሎሞንም ቀርባ በልቧ ያለውን ሁሉ አጫወተችው። [2]ሰሎሞንም የጠየቀችውን ሁሉ መለሰላት፤ ሊመልስላት የተሳነው አንዳች ነገር አልነበረም። [3]የሳባ ንግሥት የሰሎሞንን ጥበብና የሠራውን ቤተ መንግሥት፣ [4]በገበታው ላይ የሚቀርበውን መብል፣ የሹማምቱን አቀማመጥ፣ አስተናባሪዎቹንና አለባበሳቸውን፣ ጠጅ አሳላፊዎቹንና አለባበሳቸውን እንዲሁም በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ያቀረባቸውን የሚቃጠሉ መሥዋዕቶች[ፈ] ባየች ጊዜ እጅግ ተደነቀች።

[5]ንጉሡንም እንዲህ አለችው፤ “ስለ ሥራህና ስለ ጥበብህ በአገሬ ሳለሁ የሰማሁት ሁሉ እውነት ነው። [6]ነገር ግን መጥቼ በዓይኔ እስካየሁ ጊዜ ድረስ የነገሩኝን አላመንሁም ነበር፤ በእርግጥም የጥበብህ እኩሌታ እንኳ አልተነገረኝም፤ አኔ ከሰማሁት ዝና እጅግ ትልቃለህ። [7]ሰዎችህ ምንኛ ታድለዋል፤ ዘወትር በፊትህ ቆመው ጥበብህን የሚሰሙ ሹማምትህስ ምንኛ ታድለዋል፤ [8]ለአምላክህ *ለእግዚአብሔር* ንጉሥ ሆነህ እን ድትገዛ፣ በአንተ ደስ የተሰኘውና በዙፋኑ ላይ ያስቀመጠህ *አምላክህ* እግዚአብሔር ብሩክ ይሁን፤ አምላክህ ለእስራኤል ካለው ፍቅርና ለዘላለም ሊያጸናቸው ካለው ፍላጎት የተ ነሣ፣ ፍትሕና ጽድቅ እንዲሰፍን ታደርግ ዘንድ አንተን በላያቸው ላይ አንግሦሃልና ።”

[9]ከዚያም ለንጉሡ አንድ መቶ ሃያ መክሊት[ፐ] ወርቅ፣ እጅግ ብዙ ቅመማ ቅመምና የከበሩ
ድንጋዮች ሰጠችው፤ የሳባ ንግሥት ለንጉሥ ሰሎሞን እንደሰጠችው ዐይነት ቅመማ ቅመም ያለ ከቶ አልነበረም።

[10]የኪራም ሰዎችና የሰሎሞን ሰዎች ወርቅ ከኦፊር እንደዚሁም ሰንደልና[ሀ] የከበሩ ድንጋዮች አመጡ። [11]ንጉሡም የሰንደሉን እንጨት *ለእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስና ለቤተ መንግሥቱ ደረጃ መሥሪያ እንደዚሁም ለመዘምራኑ የመሰንቆና የበገና መሥሪያ አደረገው፤ ይህን የመሰለ ነገር በይሁዳ ምድር ከቶ አልታየም።

[12]ንጉሥ ሰሎሞን ለሳባ ንግሥት የፈለገችውንና የጠየቀችውን ሁሉ ሰጣት፤ ስጦታውም እርስዋ ካመጣችለት በላይ ነበር። ከዚያም ከአጃቢዎቿ ጋር ወደ አገሯ ተመለሰች።

## የሰሎሞን ብልጽግና

9፥13-28ተጓ ምብ—1ነገ10፥14-29፡2ዜና1፥14-17

[13]ሰሎሞን በየዓመቱ የሚቀበለው ወርቅ ክብደቱ ስድስት መቶ ሥልሳ ስድስት መክሊት[ለ] ነበር። [14]ይህም ከታላላቅና ከተራ ነጋዴዎች ከሚገባው ቀረጥ ሌላ ነበር፤ እንዲሁም መላው የዐረብ ነገሥታትና የገዛ ምድሩ አገረ ገዦች ለሰሎሞን ወርቅና ብር ያመጡለት ነበር።

[15]ንጉሥ ሰሎሞን ሁለት መቶ ከጥፍጥፍ ወርቅ የተሠራ ታላላቅ ጋሻዎች አበጀ፤ በእያንዳንዱም ጋሻ የገባው ጥፍጥፍ ወርቅ ስድስት መቶ ሰቅል[ሐ] ነበር። [16]እንዲሁም ሦስት መቶ ትንንሽ ጋሻዎች በጥፍጥፍ ወርቅ ሠራ፤ በእነዚህም በእያንዳንዳቸው የገባው ጥፍጥፍ ወርቅ ሦስት መቶ ሰቅል[መ] ነበር። ንጉሡም ጋሻዎቹን “የሊባኖስ ደን” በተባለው ቤተ መንግሥት ውስጥ አኖራቸው።

[17]ከዚያም ንጉሡ በዝሆን ጥርስ ያጌጠና በንጹሕ ወርቅ የተለበጠ ትልቅ ዙፋን ሠራ ።

8፥13 ዘፀ12፥17፤ 23፥14፡16፤29፥38፤ ዘኍ10፥10፤28፥9፡16-25፤29፥12-38፤ነህ8፥17
8፥14 1ዜና9፥17፤ 23፥6፤24፥1፤25፥1፤ ነህ12፥24፡36፡45
8፥18 2ዜና9፥9
9፥1 ዘፍ10፥7፤ ሕዝ23፥42፤ ማቴ12፥42፤ ሉቃ11፥31
9፥3 1ነገ5፥12
9፥6 2ዜና6፥32
9፥8 1ነገ2፥12፤ 1ዜና17፥14፤ 2ዜና2፥11፤13፥8
9፥9 2ዜና8፥18
9፥10 2ዜና8፥18
9፥14 2ዜና17፥11፤ ኢሳ21፥13፤ ኤር25፥24፤ ሕዝ27፥21፤30፥5
9፥16 1ነገ7፥2፤ 2ዜና12፥9
9፥17 1ነገ22፥39

[ፀ]18 ዐሥራ ስድስት ሜትሪክ ቶን ያህል ነው።
[ፈ]4 ወይም *ወደላይ የሚመጣባቸውን ደረጃዎች* ተብሎ መተርጐም ይቻላል።
[ፐ]9 4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው።
[ሀ]10 *የአልሙግ እንጨት* ሊሆን ይቻላል
[ለ]13 23 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው።
[ሐ]15 3.5 ኪሎ ግራም ያህል ነው።
[መ]16 1.7 ኪሎ ግራም ይህል ነው

18ዙፋኑ ስድስት መውጫ መውረጃ ደረጃ
ዎች ሲኖሩት፣ ከዙፋኑ ጋር የተያያዘ ከወርቅ
የተሠራ የእግር መርገጫ ነበረው፡፡ መቀመ
ጫውም ግራና ቀኙ መደገፊያ ያለው ሆኖም
ከመደገፊያዎቹም አጠገብ አንዳንድ አንበሳ
ቆሞ ነበር፡፡ 19እንዲሁም በስድስቱ ደረጃዎች
ዳርና ዳር ላይ አንዳንድ አንበሳ፣ ባጠቃላይ
አሥራ ሁለት አንበሶች ቆመው ነበር፤ ይህን
የመሰለ ዙፋን በየትኛውም አገር ተሠርቶ
አያውቅም፡፡ 20ንጉሥ ሰሎሞን የሚጠጣ
ባቸው ዕቃዎች በሙሉ ከወርቅ የተሠሩ
ነበሩ፤ "የሊባኖስ ደን" ተብሎ በሚጠራው
ቤተ መንግሥት ውስጥ የነበሩትም ዕቃዎች
ሁሉ ከንጹሕ ወርቅ የተሠሩ ነበሩ፤ በሰ
ሎሞን ዘመን ብር ዋጋ እንደ ሌለው ስለ
ሚቈጠር ከብር የተሠራ አንድም ነገር አል
ነበረም፡፡ 21ንጉሡ በኪራም ሰዎች የሚነዱ
የንግድ መርከቦች ነበሩት፤[ሠ] እነዚህም በየ
ሦስት ዓመቱ አንድ ጊዜ ወርቅ፣ ብር፣ የዝ
ሆን ጥርስ፣ ጦጣዎችና ዝንጀሮዎች እየያዙ
ይመለሱ ነበር፡፡

22ንጉሥ ሰሎሞን በሀብትም ሆነ በጥበብ
ከምድር ነገሥታት ሁሉ የበለጠ ነበር፡፡
23የምድር ነገሥታት ሁሉ እግዚአብሔር በልቡ
ያኖረውን ጥበብ ለመስማት ከሰሎሞን ጋር
መገናኘት ይፈልጉ ነበር፡፡ 24በየዓመቱ ወደ
እርሱ የሚመጡትም ሁሉ የብርና የወርቅ ዕቃ፣
የልብስ፣ የጦር መሣሪያና የቅመማ ቅመም
እንደዚሁም የፈረስና የበቅሎ ገጸ በረከት
ያመጡለት ነበር፡፡

25ሰሎሞን አራት ሺ የፈረሶችና የሠረገሎች[ረ]
ጋጥ ነበረው፤ እንዲሁም በሚኖርበት በኢ
የሩሳሌምና በሰረገላ ከተሞች አሥራ ሁለት
ሺህ ፈረሶች ነበሩት፡፡ 26እርሱም ከኤፍራጥስ
ወንዝ[ሰ] እስከ ፍልስጥኤም ምድርና እስከ
ግብፅ ዳርቻ ድረስ ባሉት ነገሥታት ሁሉ
ላይ ገዛ፡፡ 27ንጉሡ በኢየሩሳሌም ብሩን እንደ
ማንኛውም ድንጋይ፣ የዝግባውንም ዕንጨት
ብዛት በየኰረብታው ግርጌ እንደሚበቅል
ሾላ አደረገው፡፡ 28ለሰሎሞን ከግብፅና[ሸ] ከሌ
ሎች አገሮች ሁሉ ፈረሶች ያመጡለት ነበር፡፡

## የሰሎሞን መሞት

9፥29-31ተጓ ምብ—1ዜና11፥41-43

29ሰሎሞን በዘመነ መንግሥቱ የሠራው
ሌላው ነገር በነቢዩ በናታን ታሪክና በሴ
ሎናዊው በአሒያ ትንቢት እንዲሁም ባለ
ራእዩ አዶ ስለናባጥ ልጅ ስለ ኢዮርብዓም
ባየው ራእይ ውስጥ የተጻፈ አይደለምን?
30ሰሎሞን በኢየሩሳሌም ተቀምጦ በእስራኤል
ሁሉ ላይ አርባ ዓመት ነገሠ፡፡ 31ከዚያም
እንደ አባቶቹ አንቀላፋ፤ በአባቱም በዳዊት
ከተማ ተቀበረ፡፡ ልጁም ሮብዓም በእርሱ ፋንታ

9፥22 1ነገ3፥13፤ 2ዜና1፥12
9፥23 1ነገ4፥34
9፥24 2ዜና32፥23፤ መዝ45፥12፤68፥29፤72፥10፤ኢሳ18፥7
9፥25 1ሳሙ8፥11
9፥26 ዘፍ15፥18-21፤1ነገ4፥21፤ መዝ72፥8-9
9፥29 2ሳሙ7፥2፤ 1ነገ11፥29፤ 2ዜና10፥2
9፥31 1ነገ2፥10

10፥2 1ነገ11፥40፤ 2ዜና9፥29
10፥3 1ዜና9፥1
10፥4 2ዜና2፥2
10፥6 ኢዮ8፥8-9፤12፥12፤15፥10፤32፥7
10፥7 ምሳ15፥1
10፥8 2ሳሙ17፥14፤ ምሳ13፥20

ነገሠ፡፡

## እስራኤል በሮብዓም ላይ ዐመፀ

10፥1-11፥4ተጓ ምብ—1ዜና12፥1-24

10 እስራኤላውያን ሁሉ ሊያነግሡት
ወደዚያ ሄደው ስለነበር፣ ሮብዓም
ወደ ሴኬም ሄደ፡፡ 2ከንጉሥ ሰሎሞን ሸሽቶ
በግብፅ ይኖር የነበረው የናባጥ ልጅ ኢዮርብ
ዓም ይህን ሲሰማ፣ ከግብፅ ተመልሶ መጣ፡፡
3እርሱንም ልከው አስጠሩት፤ ከዚያም እርሱና
እስራኤል ሁሉ ወደ ሮብዓም ሄደው እንዲህ
አሉት፤ 4"አባትህ በላያችን ከባድ ቀንበር
ጫነብን፤ አንተ ግን አስጨናቂውን ሥራና
በላያችን የጫነብንን ከባድ ቀንበር አቅልልን፤
እኛም እንገዛልሃለን፡፡"

5ሮብዓምም፣ "ከሦስት ቀን በኋላ ተመል
ሳችሁ ወደ እኔ ኑ" አላቸው፤ ስለዚህ ሰዎቹ
ወጥተው ሄዱ፡፡

6ከዚያም ንጉሥ ሮብዓም፣ "ለዚህ ሕዝብ
ምን እንድመልስለት ትመክሩኛላችሁ?"
በማለት አባቱ ሰሎሞን በሕይወት ሳለ ያገለ
ገሉትን የእስራኤልን ሽማግሌዎች ጠየቃቸው፡፡
7እነርሱም፣ "ለእዚህ ሕዝብ ደግ ከሆን
ህለት፣ ደስ ካሰኘኸውና የሚስማማው መልስ
ከሰጠኸው ምን ጊዜም ይገዛልሃል" አሉት፡፡
8ሮብዓም ግን ሽማግሌዎች የሰጡትን
ምክር ትቶ፣ አብሮ አደጎቹና አገልጋዮቹ
ከሆኑት ወጣቶች ምክር ጠየቀ፤ 9እንዲህም
አላቸው፤ " 'አባትህ የጫነብንን ቀንበር አቅል
ልልን' ለሚሉኝ ለእነዚህ ሰዎች የምትሰጡኝ
ምክር ምንድነው? ምንስ ብለን እንመልስላ
ቸው?"

10አብሮ አደጎቹም ወጣቶች እንዲህ ሲሉ
መለሱለት፤ "ለጠየቁህ ሕዝብ፤ 'አባትህ በላ
ያችን ከባድ ቀንበር ጫነብን፤ አንተ ግን
ቀንበራችንን አቅልልልን' ለሚሉህ እንዲህ
በላቸው፤ 'ትንሿ ጣቴ ከአባቴ ወገብ ይልቅ
ትወፍራለች፤ 11አባቴ ከባድ ቀንበር ጫነባችሁ፤
እኔ ግን የባሰ አከብደዋለሁ፤ አባቴ በዐለንጋ
ገረፋችሁ፤ እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለሁ፡፡"

12ንጉሡ፣ "ከሦስት ቀን በኋላ ተመል
ሳችሁ ኑ" ባላቸው መሠረት ኢዮርብዓምና
ሕዝቡ ሁሉ ከሦስት ቀን በኋላ ወደ ሮብዓም
ተመለሱ፡፡ 13ንጉሡም የሽማግሌዎችን ምክር
በመናቅ፣ አመናጭቆ መለሰላቸው፤ 14እርሱም
የወጣቶቹን ምክር በመቀበል፣ "አባቴ ቀንበ
ራችሁን አከበደ፤ እኔ ደግሞ የባሰ አከብደ
ዋለሁ፤ አባቴ በአለንጋ ገረፋችሁ፤ እኔ ደግሞ
በጊንጥ እገርፋችኋለሁ" አላቸው፡፡

[ሠ] 21 ዕብራይስጡ፣ ወደ ተርሴስ ሊሄዱ የሚችሉ መርከቦች ይላል፡፡
[ረ] 25 ወይም፣ ሠረገለኞች ተብሎ መተርጐም ይቻላል፡፡
[ሰ] 26 የኤፍራጥስ ወንዝ ነው፤ ነገር ግን አንዳንድ ቅጅዎች ኤፍራጥስ የሚለውን ቃል አይጨምሩም
[ሸ] 28 በኪልቂያ የምትገኘው ሙዙር ነች፡፡

15እግዚአብሔር በሴሎናዊው በአሒያ አማካይነት
ለናባጥ ልጅ ለኢዮርብዓም የተናገረው ቃል
ይፈጸም ዘንድ፣ ወስኖ ስለነበር፣ ንጉሡ ሕ
ዝቡን አላዳመጠም።
16መላው እስራኤልም ንጉሡ ሊሰማቸው
አለመፈለጉን በተረዱ ጊዜ፣ እንዲህ ሲሉ
መለሱለት፤

"ከዳዊት ምን ድርሻ አለን? ከእሴይስ
ልጅ ምን ክፍል አለን? እስራኤል፣ ሆይ፤
ወደ ድንኳንህ ተመለስ፤ ዳዊት ሆይ፤
አንተም የገዛ ቤትህን ጠብቅ።"

ስለዚህ እስራኤላውያን ሁሉ ወደ የቤ
ታቸው ተመለሱ። 17ይሁን እንጂ በይሁዳ
ከተሞች የሚኖሩትን እስራኤላውያን አሁንም
የሚገዛቸው ሮብዓም ነበር።
18ንጉሥ ሮብዓም የገባሮች ኀላፊ የነበረውን
አዶራምን ላከው፤ እስራኤላውያን ግን በድን
ጋይ ወግረው ገደሉት። ንጉሥ ሮብዓም
ግን እንደምንም ብሎ ሰረገላው ላይ በመ
ውጣት ወደ ኢየሩሳሌም ሸሽቶ አመለጠ።
19ስለዚህ እስራኤል እስከ ዛሬ ድረስ በዳዊት
ቤት ላይ እንደ ዐመፀ ነው።

11 ሮብዓም ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ፣
እስራኤልን ወግተው መንግሥቱን
ወደ ሮብዓም እንዲመልሱ ከይሁዳና ከብ
ንያም ቤት አንድ መቶ ሰማንያ ሺህ ወታ
ደሮች ሰበሰበ።
2ነገር ግን *የእግዚአብሔር* ቃል ወደ እግ
ዚአብሔር ሰው ወደ ሸማያ እንዲህ ሲል
መጣ፤ 3"ለይሁዳ ንጉሥ ለሰሎሞን ልጅ
ለሮብዓምና በይሁዳና በብንያም ላሉ እስራ
ኤላው ያን ሁሉ እንዲህ በል፤ 4'*እግዚ
አብሔር* እንዲህ ይላል፤ ይህ ነገር ከእኔ
ዘንድ ስለ ሆነ፣ ወንድሞቻችሁን ለመውጋት
ወደዚያ አትውጡ፤ እያንዳንዳችሁም ወደ
የቤታችሁ ሂዱ" አላቸው። ስለዚህ *ለእግዚ
አብሔር* ቃል በመታዘዝ በኢዮርብዓም ላይ
መዝመቱን ትተው ተመለሱ።

## ሮብዓም የይሁዳን ከተሞች መሸገ

5ሮብዓም መኖሪያውን በኢየሩሳሌም በማ
ድረግ ለመከላከያ የሚሆኑ ከተሞችን በይ
ሁዳ ሠራ፤ እነዚህም 6ቤተ ልሔም፣ ኤጣም፣
ቴቁሔ፣ 7ቤትጹር፣ ሦኮ፣ ዓዶላም፣ 8ጌት፣
መሪሳ፣ ዚፍ፣ 9አዶራይም፣ ለኪሶ፣ ዓዜቃ፣
10ጾርዓ፣ ኤሎን፣ ኬብሮን ናቸው። በይሁዳና
በብንያም ውስጥ የተመሸጉት ከተሞች እነዚህ
ነበሩ። 11እነዚህንም ምሽጎቻቸውን አጠ
ንክሮ፣ አዛዦችን ሾመባቸው፤ ምግብ፣
ዘይትና የወይን ጠጅ አከማቸባቸው።
12በየከተሞቹም ሁሉ ጋሻና ጦር አከማችቶ
ይበልጥ አጠናከራቸው። በዚህ ዓይነት
ይሁዳንና ቢንያምን የራሱ አደረገ።

**10፥15** 1ነገ11፥29፤ 2ዜና11፥4፤ 25፥16-20
**10፥16** 2ሳሙ20፥1፤ 1ዜና9፥1
**10፥18** 2ሳሙ20፥24፤ 1ነገ5፥14
**11፥1** 1ነገ12፥21
**11፥2** 1ነገ12፥22፤ 2ዜና12፥5-7፡15
**11፥4** 2ዜና28፥8-11
**11፥10** ኢሱ10፥20፤ 2ዜና12፥4፤17፥2፡19፤ 21፥3
**11፥14** ዘኁ35፥2-5፤1ዜና6፥81
**11፥15** ዘሌ17፥7፤ 1ነገ12፥28፡31፤13፥33፤2ዜና13፥8
**11፥16** 2ዜና15፥9
**11፥17** 2ዜና12፥1
**11፥20** 1ነገ15፥2፤ 2ዜና12፥16፤13፥2
**11፥21** ዘዳ17፥17
**11፥22** ዘዳ21፥15-17
**11፥23** 2ዜና21፥3
**12፥1** ቀኍ13፤ 1ዜና9፥1፤2ዜና1፥1፤7፥19፤11፥17
**12፥2** 1ነገ11፥40፤ 14፥22-24፤ 1ዜና5፥25
**12፥3** ዘፍ10፥6፤ 2ዜና14፥9፤16፥8፤ኢሳ18፥2፤ዳን11፥43፤አሞ9፥7፤ናሆ3፥9

13በመላው እስራኤል ያሉት ካህናትና
ሌዋውያን ከየክልላቸው ሁሉ ወደ እርሱ
ተሰበሰቡ። 14ኢዮርብዓምና ልጆቹ ሌዋውያኑን
*ከእግዚአብሔር* የክህነት አገልግሎት ስላባረ
ሯቸው ሌዋውያኑ ማሰማሪያ ቦታቸውንና
ንብረታቸውን ሁሉ ትተው ወደ ይሁዳና ወደ
ኢየሩሳሌም መጡ፤ 15እርሱም ለየኰረብታው
መስገጃ እንዲሁም ለሠራቸው የፍየልና
የጥጃ ምስሎች የራሱን ካህናት ሾመ።
16ከእያ ንዳንዱም የእስራኤል ነገድ
ከልባቸው የእ ስራኤልን *አምላክ* እግዚአብሐ
ሔርን የሚፈልጉ ሁሉ፣ ለአባቶቻቸው *አምላክ*
ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ያቀርቡ ዘንድ፣
ሌዋውያኑን ተከት ለው ወደ ኢየሩሳሌም
ሄዱ። 17በዚሁ ሁኔታ የዳዊትንና የሰሎሞንን
መንገድ በመከተል፣ ለሦስት ዓመት የይሁዳን
መንግሥት አበረቱ፤ የሰሎሞንን ልጅ ሮብዓ
ምንም ረዱ።

## የሮብዓም ቤተሰብ

18ሮብዓም መሐላትን አገባ፤ አባቷ የዳዊት
ልጅ ኢያሪሙት ሲሆን፣ እናቷም አቢካኢል
የተባለች፣ የእሴይ የልጅ ልጅ የኤልያብ
ልጅ ነበረች። 19እርስዋም የዑስ፣ ሰማርያና
ዛሃም የተባሉ ወንዶች ልጆች ወለደችለት።
20ከዚያም የአቤሴሎምን ልጅ መዓካን አገባ፤
እርሷም አብያ፣ ዓታይ፣ ዚዛ፣ ሰሎሚት
የተባሉትን ወለደችለት። 21ሮብዓም መዓካን
ከሌሎቹ ሚስቶቹና ቁባቶቹ ይልቅ አብ
ልጦ ወደዳት። ባጠቃላይ ዐሥራ ስምንት
ሚስትና ስልሣ ቁባት፣ ሃያ ስምንት ወንድና
ሥልሳ ሴት ልጆች ነበሩት።
22ሮብዓም የማዕካን ልጅ አቢያን ሊያ
ነግሠው ስለፈለገ ከልዑላን ወንድሞቹ
አልቆ ዋና አደረገው። 23ከወንዶች ልጆቹም
ጥቂቱን በይሁዳና በብንያም አውራጃዎች
እንዲሁም በተመሸጉት ከተሞች ስለ ሾማ
ቸው፣ ዘዴኛነቱን አሳይቶአል። የሚያስ
ፈልጋቸውን በብዛት ሰጣቸው፤ ብዙ ሚስ
ቶችም አጋባቸው።

## ሺሻቅ በኢየሩሳሌም ላይ ዘመተ

12፥9-16ተጓ ምብ— 1ዜና14፥21፡25-31

12 ሮብዓም መንግሥቱን ከመሠረተና ካ
ጸና በኋላ እርሱና እስራኤል[ቀ] ሁሉ
*የእግዚአብሔርን* ሕግ ተዉ። 2*እግዚአብሔርን*
ከመበደላቸው የተነሣም፣ ሮብዓም በነገሠ
በአምስተኛው ዓመት የግብፅ ንጉሥ ሺ
ሻቅ በኢየሩሳሌም ላይ ዘመተ። 3ከግብፅ
አብረውት የመጡትን ዐሥራ ሁለት ሺህ
ሠረገላዎች፣ ስድሳ ሺ ፈረሰኞችና ስፍር
ቍጥር የሌላቸውን የሊብያ፣ የሱኪምና

[ቀ]1በዜና ካልዕ መጽሐፍ ተደጋግሞ እንደተጠቀሰው ይህ የይሁዳ
ክፍል ነው

የኢትዮጵያ ወታደሮች ይዞ፣ [4]የተመሸጉትን
የይሁዳ ከተሞች በቁጥጥሩ ሥር በማድረግ
እስከ ኢየሩሳሌም ዘለቀ።
[5]ከዚህ በኋላ ነቢዩ ሸማያ ወደ ሮብዓምና
ሺሻቅን ፈርተው በኢየሩሳሌም ወደ ተሰበ
ሰቡት ወደ እስራኤል መሪዎች መጥቶ፣
*"እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ 'እናንተ
ትታችሁኛል፤ ስለዚህ እኔም በሺሻቅ እጅ
ትቼአችኋለሁ' " አላቸው።
[6]የእስራኤል መሪዎችና ንጉሡ ራሳቸ
ውን በማዋረድ፣ "*እግዚአብሔር* ጻድቅ ነው"
አሉ።
[7]*እግዚአብሔርም* ራሳቸውን እንዳዋረዱ
ባየ ጊዜ፣ *የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል
ወደ ሸማያ መጣ፤ "ራሳቸውን ዝቅ አድርገው
ስላዋረዱ እታደጋቸዋለሁ እንጂ አላጠፋቸ
ውም፤ ቍጣዬም በሺሻቅ እጅ በኢየሩ
ሳሌም ላይ አይፈስስም። [8]ይሁን እንጂ
እኔን በማገልገልና የሌሎችን አገሮች
ነገሥታት በማገልገል መካከል ያለውን
ልዩነት ያውቁ ዘንድ፣ ለእርሱ ይገዛሉ።"
[9]የግብፅ ንጉሥ ሺሻቅ ኢየሩሳሌምን በወረረ
ጊዜ፣ የቤተ መቅደሱን ንብረትና የቤተ
መንግሥቱን ንብረት ዘርፎ ወሰደ፤ ሰሎሞን
ያሠራው የወርቅ ጋሻ ሳይቀር፣ እንዳለ ሁለ
ንም አጋዘው። [10]ንጉሥ ሮብዓምም በተወሰ
ዱት ፈንታ የናስ ጋሻዎች ሠርቶ፣ የቤተ
መንግሥቱን ቅጥር በሮች ለሚጠብቁ የዘብ
አለቆች በኀላፊነት ሰጠ። [11]ንጉሡ ወደ *እግዚ
አብሔር* ቤተ መቅደስ በሚሄድበት ጊዜ
ሁሉ፣ ዘበኞቹ ጋሻዎቹን አንግበው ያጅቡት
ነበር፤ ከዚያም በኋላ ጋሻዎቹን ወደ ዘበኞች
ክፍል ይመልሱ ነበር።
[12]ሮብዓም ራሱን ዝቅ አድርጎ ስላዋረደ
*የእግዚአብሔር* ቍጣ ከእርሱ ተመለሰ፤ ፈጽሞም
አላጠፋውም፤ በይሁዳም ደግሞ በጥቂቱም
ቢሆን መልካም ነገር ተገኝቶ ነበር።
[13]ንጉሥ ሮብዓም በሚገባ ተደላድሎ
በኢየሩሳሌም በንጉሥነቱ ቀጠለ፣ ሲነ
ግሥ ዕድሜው አርባ አንድ ዓመት ነበር፤
*እግዚአብሔር* ስሙን በዚያ ለማኖር ከእስ
ራኤል ነገዶች ሁሉ በመረጣት በኢየሩ
ሳሌም ከተማ ተቀምጦም፣ ዐሥራ ሰባት
ዓመት ገዛ፤ እናቱም ናዕማ የምትባል
አሞናዊት ነበረች። [14]*እግዚአብሔርን* ይሻ
ዘንድ ልቡን ስላላዘጋጀ ክፉ ነገር አደረገ።
[15]ሮብዓም በዘመነ መንግሥቱ ያከናወናቸው
ተግባሮች ሁሉ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ
ድረስ ነቢዩ ሸማያ በጻፈው የታሪክ መዝገብና
በባለ ራእዩ አዶ በዘገበው የትውልድ ሐረግ
ታሪክ የሚገኝ አይደለምን? በሮብዓምና በኢ
ዮርብዓም መካከል የማያቋርጥ ጦርነት

12፥4 2ዜና11፥10
12፥5 ዘዳ28፥15፤ 2ዜና11፥2
12፥6 ዘፀ9፥27፤ ዘሌ26፥41፤2ዜና6፥37፤ዕዝ9፥15፤ መዝ11፥7፤116፥5፤ ዳን9፥14
12፥7 ዘዳ9፥19፤ መዝ69፥24፤78፥38፤ኤር7፥20፤42፥18፤ ሕዝ5፥13
12፥8 ዘዳ8፥48
12፥9 2ዜና9፥16
12፥12 1ነገ14፥13፤ 2ዜና6፥37፤19፥3
12፥13 ቍ1፤ዘፀ 20፥24፤ዘዳ12፥5፤ 1ነገ2፥12
12፥15 2ዜና11፥2
12፥16 1ዜና3፥10፤ 2ዜና11፥20
13፥2 1ነገ15፥6፤ 2ዜና11፥20፤15፥16
13፥4 ኢያ18፥22፤ 1ዜና11፥1
13፥5 ዘሌ2፥13፤8 2ሳሙ7፥13፤ 1ዜና17፥12
13፥6 1ነገ11፥26
13፥7 መሳ9፥4፤ 1ዜና29፥1
13፥8 ዘፀ32፥4፤ 1ሳሙ4፥3፤2ዜና9፥8፤ 11፥15
13፥9 ዘፀ29፥31፡ 35-36፤1ነገ12፥31፤ 2ዜና11፥14-15፤ ኤር2፥11፤ገላ4፥
13፥11 ዘፀ25፥6፡ 37፤29፥39፤1ዜና9፥32 ፤2ዜና2፥4

ነበር። [16]ሮብዓም እንደ አባቶቹ ሁሉ አን
ቀላፋ፤ በዳዊትም ከተማ ተቀበረ፤ ልጁ አብያም
በእርሱ ፈንታ ነገሠ።

## የይሁዳ ንጉሥ አብያ

13፥1-2፡22-14፥1 ተጓ ምብ—1ዜና15፥1-2፡6-8

13 ኢዮርብዓም በነገሠ በዐሥራ ስምን
ተኛው ዓመት አብያ በይሁዳ ነገሠ።
[2]በኢየሩሳሌም ተቀምጦም ሦስት ዓመት ገዛ።
እናቱ ሚካያ[a] ትባላለች፤ እርሷም የገብዓ
ተወላጅ የኡርኤል ልጅ ነበረች።
በአብያና በኢዮርብዓምም መካከል
ጦርነት ነበር። [3]አብያ አራት መቶ ሺህ
ብርቱ ተዋጊዎች ይዞ ዘመተ፤ ኢዮርብዓምም
ስምንት መቶ ሺህ ብርቱ ተዋጊዎች ይዞ
በመውጣት
ጠበቀው።
[4]አብያ በኰረብታማው በኤፍሬም አገር
በጽማራይም ተራራ ላይ ቆሞ፣ እንዲህ አለ፤
"ኢዮርብዓምና እስራኤል ሁሉ አድምጡኝ!
[5]የእስራኤል *አምላክ* እግዚአብሔር ዳዊትና
ዘሮቹ በእስራኤል ላይ ለዘላለም እንዲነግሡ
በጨው ኪዳን የሰጣቸው መሆኑን
አታውቁምን? [6]የዳዊት ልጅ የሰሎሞን ባሪያ
የነበረው የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ግን
በጌታው ላይ ዐመፀ። [7]የሰሎሞን ልጅ
ሮብዓም ገና ሕፃን ሳለ፣ ምንም ማድረግ
በማይችልበትና እነር ሱንም ለመቋቋም
አቅሙ በማይፈቅድለት ጊዜ የማይረቡ
ጥቂት ወሮበሎች በዙሪ ያው
ተሰበሰቡበት፣ በረቱበትም።
[8]"አሁንም እናንተ በዳዊት ዘርዐ-ትው
ልድ እጅ ያለውን *የእግዚአብሔርን* መን
ግሥት ልትቋቋሙ አስባችኋል። በእር
ግጥም በሰራዊት ረገድ እጅግ ብዙ ናችሁ፤
አማልክቶቻችሁ ይሆኑ ዘንድ ኢዮርብዓም
የሠራቸውንም የወርቅ ጥጆች ይዛችኋል።
[9]ደግሞስ የአሮን ልጆች የሆኑትን ካህናትና
ሌዋውያን አባርራችሁ፣ ሌሎች ሕዝቦች
እንደሚያደርጉት ሁሉ፣ እናንተም የራ
ሳችሁን ካህናት አልሾማችሁምን? አንድ
ኮርማና ሰባት አውራ በግ ይዞ ራሱን ለመ
ቀደስ የሚመጣ ማናቸውም ሰው አማልክት
ላልሆኑ ለእነዚያ ጣዖታት ካህን ይሆናል።
[10]"ለእኛ ግን አምላካችን እግዚአብሔር
ነው፤ እርሱንም አልተውነውም፤ *እግዚአብሔርን* በ
ማገልገል ላይ ያሉት ካህናት የአሮን ልጆች
ሲሆኑ፣ ረዳቶቻቸውም ሌዋውያኑ ናቸው።
[11]እነርሱም በየጧቱና በየማታው የሚቃጠል
*መሥዋዕትና* ሽታው ደስ የሚያሰኝ ዕጣን *ለእግ
ዚአብሔር* ያቀርባሉ፤ የገጹን ኅብስት
በሥርዐቱ መሠረት በንጻው ጠረጴዛ ላይ ያኖ
ራሉ፤ በየማታውም በወርቁ መቅረዝ ላይ

[a]2 ብዙ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች የሱርስቱ ቅጂ (እንዲሁም 2ዜና 11፥20 እና 1ነገ15፥2) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ *ሚካያ* ይላል።

ያሉትን ቀንዲሎች ያበራሉ፤ እኛም
*የአምላካችንን* የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንፈ
ጽማለን፤ እናንተ ግን ትታችሁታል። 12እግዚ
አብሔር ከእኛ ጋር ነው፤ መሪአችንም እርሱ
ነው። መለከት የያዙ ካህናቱም የጦርነቱን
ድምፅ በእናንተ ላይ ያሰማሉ። እናንተ የእስ
ራኤል ሰዎች ሆይ፤ አይቀናችሁምና፣ ከአ
ባቶቻችሁ *አምላክ* ከእግዚአብሔር ጋር
አትዋጉ።”

13በዚህ ጊዜ ኢዮርብዓም ከሰራዊቱ
ከፊሉን ከይሁዳ ሰራዊት በስተ ጀርባ እንዲ
ያደፍጡ ላከ፤ የቀረውም ሰራዊት ከእርሱ
ጋር የይሁዳን ሰራዊት ፊት ለፊት እንዲ
ገጥሙ አደረገ። 14የይሁዳም ሰዎች
ዙሪያቸውን ሲመለከቱ ከፊትና ከኋላ
መከበባቸውን አዩ፤ ወደ *እግዚአብሔርም*
ጮኹ፤ ካህናቱም መለ ከታቸውን ነፉ።
15የይሁዳም ሰዎች በፉከራ የጦርነት ድምፅ
አሰሙ፤ እግዚአብሔር ኢዮርብዓምንና እስራ
ኤልን ሁሉ በአብያና በይሁዳ ፊት ፊጽሞ
መታቸው። 16እስራኤላውያን ከይሁዳ ፊት
ሸሹ፤ እግዚአብሔርም በእጃቸው አሳልፎ
ሰጣቸው። 17አብያና ሰዎቹም ከባድ ጉዳት
አደረሱባቸው፤ ከዚህ የተነሣም ከእስራኤል
ብርቱ ተዋጊዎች መካከል አምስት መቶ ሺህ
ሰዎች ተገደሉ። 18በጦርነቱም የእስራኤል
ሰዎች ተዋረዱ፣ የይሁዳ ሰዎች ግን በአባቶ
ቻቸው *አምላክ* በእግዚአብሔር ታምነዋልና ድል
ነሡ።

19አብያም ኢዮርብዓምን አሳድዶ የቤ
ቴልን፣ የይሻናንና የዔፍሮንን ከተሞች
ከነመንደሮቻቸው ወሰደበት። 20ኢዮርብዓም
በአብያ ዘመን እንደ ገና ሊያንሠራራ አል
ቻለም፤ ከዚያም *እግዚአብሔር* ስለ ቀሠፈው
ሞተ።

21አብያ ግን ይበልጥ እየበረታ ሄደ፤ ዐሥራ
አራት ሚስቶች አግብቶም ሃያ ሁለት ወን
ዶችና ዐሥራ ስድስት ሴቶች ልጆች ነበሩት።

22በአብያ ዘመን የተከናወነው ተግባር፣
እርሱ የፈጸመውና የተናገረው ሁሉ በነቢ
ዩ በአዶ የታሪክ መዛግብት ተጽፎአል።

14 አብያ እንደ አባቶቹ ሁሉ አንቀላፋ፤
በዳዊትም ከተማ ተቀበረ፤ ልጁም
አሳ በእርሱ ፈንታ ነገሠ፤ በዘመኑም በም
ድሪቱ ለዐሥር ዓመት ሰላም ሆነ።

### የይሁዳ ንጉሥ አሳ

14፥2-3ተጓ ምብ—1ዜና15፥11-12

2አሳ *በአምላኩ* በእግዚአብሔር ፊት መልካ
ምና ቅን የሆነውን ነገር አደረገ፤ 3ባዕዳን
መሠዊያዎችንና ማምለኪያ ኰረብታዎችን
አስወገደ፤ ማምለኪያ ዐምዶችን አፈረሰ፤
አሼራ ለተባለች ጣዖት አምላክ የቆሙ የዕን
ጨት ቅርጽ ምስሎችንም[†] ቈራረጠ፤ 4የአባ
ቶቻቸውን *አምላክ* እግዚአብሔርን እንዲፈልጉ፣
ሕጉንና ትእዛዙንም እንዲፈጽሙ የይሁ
ዳን ሕዝብ አዘዘ። 5ከእያንዳንዱም የይሁዳ
ከተሞች የየኰረብታውን መስገጃ ስፍራ
ዎችንና የዕጣን መሠዊያዎችን አስወገደ፤
መንግሥቱም በእርሱ አገዛዝ ዘመን ሰላም
አገኘች። 6በምድሪቱ ሰላም ስለ ሰፈነ፣
በይሁዳ የተመሸጉ ከተሞችን ሠራ። *እግዚ
አብሔር* ዕረፍት ስለ ሰጠውም፣ በዘመኑ
የተዋጋው ማንም አልነበረም።

7እርሱም ለይሁዳ ሕዝብ እንዲህ አላቸው፤
“እነዚህን ከተሞች እንሥራ፤ ማማ፣ መዝጊያና
መወርወሪያ ያላቸውን ቅጥሮች በዙሪያቸው
እናብጅ። *አምላካችንን* እግዚአብሔርን ስለ
ፈለግነው ምድሪቱ አሁንም የኛው ናት፤
እኛ ፈለግነው፤ እርሱም በሁሉም አቅጣጫ
ዕረፍት ሰጠን” እነርሱም ሠሩ፤ ተከናወነላ
ቸውም።

8አሳ ታላላቅ ጋሻና ጦር የያዙ ሦስት
መቶ ሺህ የይሁዳ ሰዎች እንዲሁም ጋሻና
ቀስት የያዙ ሁለት መቶ ሰማንያ ሺህ የብ
ንያም ሰዎች ነበሩት፤ እነዚህ ሁሉ ብርቱ
ተዋጊዎች ነበሩ።

9ኢትዮጰያዊው ዝሪ አንድ ሚሊዮን[‡] ሰራ
ዊትና ሦስት መቶ ሠረገላ ይዞ በመውጣት
እስከ መሪሳ ድረስ መጣባቸው። 10አሳም ሊ
ገ ጥመው ወጣ፤ መሪሳ አጠገብ ባለው በ
ጽፉታ ሸለቆም የውጊያ ቦታ ቦታቸውን
ያዙ።

11በዚህ ጊዜ አሳ ወደ *አምላኩ* ወደ
እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ጮኸ፤ “*እግዚ
አብሔር* ሆይ፤ ደካሞችን ከኀይለኞች
የሚታደግ እንደ አንተ ያለ ማንም የለም፤
አምላካችን *እግዚአብሔር* ሆይ፤ በአንተ
ታምነናልና፣ ይህን ታላቅ ሰራዊት በስምህ
እንገጥመዋለን፤ እግዚአብሔር ሆይ፤
አምላካችን አንተ ነህ፤ ሰውም
አያሸንፍህም።”

12*እግዚአብሔርም* ኢትዮጲያውያንን በአሳና
በይሁዳ ፊት መታቸው፤ ኢትዮጲያውያኑም
ሸሹ፤ 13አሳና ሰራዊቱም እስከ ጌራራ ድረስ
አሳደዷቸው፤ እጅግ ብዙ ቊጥር ያላቸው
ኢትዮጲያውያን ስለወደቁም፣ ሊያንሰራሩ
አልቻሉም፤ በሰራዊቱም ፊት ተደመሰሱ።
የይሁዳም ሰዎች እጅግ ብዙ ምርኮ ወሰዱ።
14በጌራራ ዙሪያ ባሉት ከተሞች ሁሉ ላይ
ታላቅ ድንጋጤ *ከእግዚአብሔር* ዘንድ ስለ
ወደቀባቸው ከተሞቹን ሁሉ አጠፏቸው፤
እጅግ ብዙ ምርኮም በዚያ ስለ ነበር፣ በዘ
በዟቸው። 15እንዲሁም በእረኞች ሰፈር ላይ
አደጋ ጥለው እጅግ ብዙ በጎች፣ ፍየሎችና
ግመሎች ማረኩ ወደ ኢየሩሳሌምም ተመለሱ።

13፥12 ዘኍ10፥8-9፤መሳ2፥15፤ ኢዮ9፥4፤ ምሳ21፥30፤29፥1፤ ሐሥ5፥39
13፥13 ኢሱ8፥9፤ 2ዜና20፥22
13፥14 1ዜና5፥20፤ 2ዜና14፥11፤18፥31
13፥15 1ዜና9፥1
13፥16 2ዜና16፥8
13፥18 2ዜና14፥11፤ 16፥7፤ መዝ22፥5
14፥2 2ዜና21፥12
14፥3 ዘፀ23፥24፤ 34፥13፤መሳ2፥2
14፥4 1ዜና16፥11
14፥5 1ነገ15፥14፤ ኢሳ27፥9፤ሕዝ6፥4
14፥6 1ዜና22፥9
14፥7 1ዜና22፥9
14፥8 1ዜና21፥1
14፥9 ዘፍ10፥8-9፤2ዜና11፥8፤12፥3፤24፥24
14፥11 1ሳሙ17፥45፤ 1ነገ8፥44፤ 2ዜና13፥14፡18፤ 25፥8፤ መዝ9፥19፤60፥11-12፤79፥9
14፥12 1ነገ8፥45
14፥13 ዘፍ10፥19፤ 2ሳሙ22፥38፤2ዜና15፥11፡18፤ነህ9፥24፤ መዝ44፥2፡19፤ 135፥10
14፥14 ዘፍ35፥5፤ ዘዳ2፥25፤11፥25

[†]3 በሁለተኛው የዜና መዋዕል መጽሐፍ ተደጋግሞ እንደተጠቀሰው ይህ አሼራ የምትባለው ጣዖት አምላክ ምስል ነው።
[‡]9 ዕብራይስጡ ***አእላፍ*** ወይም ***እልፍ ጊዜ እልፍ*** ይላል።

## ንጉሥ አሳ ያደረገው ተሐድሶ

15፥16-19ተጓ ምብ—1ዜና15፥13-16

15 የእግዚአብሔር መንፈስ በዖዴድ
ልጅ በአዛርያስ ላይ መጣ።
2እርሱም አሳን ሊገናኘው ወጣ፤ እንዲህም
አለው፤ አሳ፣ እናንተም ይሁዳና ብንያም ሁሉ
ሆይ፤ አድምጡኝ፤ እናንተ ከእግዚአብሔር
ጋር ስትሆኑ፣ እርሱም ከእናንተ ጋር ይሆናል፤
ብትፈልጉት ይገኝላችኋል፤ ብትተዉት ግን፣
ይተዋችኋል። 3እስራኤል ያለ እውነተኛ
አምላክ፣ ያለ አስተማሪ ካህንና ያለ ሕግ
ብዙ ዘመን አሳልፈዋል። 4በመከራቸው ጊዜ
ግን፣ ወደ እስራኤል አምላክ ወደ እግዚአብሐ
ር ተመልሰው ፈለጉት፤ እርሱም ተገኘላቸው።
5በዚያን ዘመን በምድር ነዋሪዎች ሁሉ
ዘንድ ታላቅ ሁከት ስለ ነበር፣ በሰላም
ወጥቶ መግባት አስተማማኝ አልነ በረም።
6እግዚአብሔር በተለያየ መከራ ያስጨንቃቸው
ስለ ነበር፣ አንዱ መንግሥት በሌላው
መንግሥት፣ አንዱም ከተማ በሌላው ከተማ
ይደመሰስ ነበር። 7እናንተ ግን የድካማ
ችሁን ዋጋ ስለምታገኙ በርቱ፤ እጃችሁም
አይላላ።"

8አሳ ይህን ቃልና የነቢዩን የዖዴድን
ልጅ[a] የዓዛርያስን ትንቢት በሰማ ጊዜ
በረታ። ከመላው ይሁዳና ከብንያም ምድር፣
በኤፍ ሬምም ኰረብታዎች ላይ ከያዛቸው
ከተሞች አስጸያፊዎቹን ጣዖታት አስወገደ።
ከእግዚአብሔር መቅደስ ሰበሰበ ፊት ለፊት
የነበረ ውንም የእግዚአብሔር መሠዊያ
አደሰ።

9አምላኩ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መሆ
ኑን ባዩ ጊዜ፣ ከእስራኤል ብዙ ሰዎች እር
ሱን ተጠግተው ነበር፤ እርሱም ይሁዳንና ብን
ያምን እንዲሁም ከኤፍሬም፣ ከምናሴና
ከስምዖን መጥተው ከእነርሱ ጋር የተቀመጡትን
ሰበሰበ።

10እነርሱም በአሳ ዘመነ መንግሥት በዐሥራ
አምስተኛው ዓመት፣ በሦስተኛው ወር
በኢየሩሳሌም ተሰበሰቡ። 11በዚያን ጊዜ
በምርኮ ካመጡት ውስጥ ሰባት መቶ በሬ፣
ሰባት ሺ በግና ፍየል ለእግዚአብሔር ሠዉ።
12የአባቶቻቸውንም አምላክ እግዚአብሔርን
በፍጹም ልባቸውና በፍጹም ነፍሳቸው ይሹ
ዘንድ ቃል ኪዳን አደረጉ። 13የእስራኤልን
አምላክ እግዚአብሔርን የማይፈልግ ሁሉ ግን፣
ትንሽም ሆነ ትልቅ፣ ወንድም ሆነ ሴት
እንዲገደል አደረጉ። 14ይህንንም በታላቅ ድምፅ
፣ በእልልታ፣ በእምቢልታና በመለከት
ድምፅ ለእግዚአብሔር ማሉ። 15በፍጹም
ልባቸው ስለማሉም የይሁዳ ሕዝብ በመሐ
ላው ደስ ተሰኙ። እግዚአብሔርን ከልብ
ፈለጉት፤ እርሱም ተገኘላቸው፤ ስለዚህ
እግዚአብሔር በሁሉም አቅጣጫ ዕረፍት
ሰጣቸው።

16እንዲሁም ንጉሥ አሳ አያቱን ማዓካን
ለአስጸያፊዋ የአሼራ ጣዖት ዐምድ ስላቆመች
ከእቴጌነት ክብሯ ሻራት። አሳም ዐምዱን
ቈርጦ በመሰባበር በቄድሮን ሸለቆ አቃጠ
ለው። 17ምንም እንኳ ማምለኪያ ኰረብታ
ዎችን ሙሉ በሙሉ ከእስራኤል ባያስወግ
ድም፣ የአሳ ልብ በዘመኑ ሁሉ ፈጽሞ
ለእግዚአብሔር የተገዛ ነበር። 18እርሱና
አባቱ የቀደሱትን ብሩን፣ ወርቁንና ልዩ
ልዩ ዕቃ ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
አገባ።

19እስከ ሠላሳ አምስተኛው የአሳ ዘመነ
መንግሥት ድረስ ምንም ዓይነት ጦርነት
አልነበረም።

## የአሳ የመጨረሻ ዓመታት

16፥1-6ተጓ ምብ—ዜና15፥17-22
16፥11-17፥1ተጓ ምብ —1ዜና15፥23-24

16 አሳ በነገሠ በሠላሳ ስድስተኛው
ዓመት፣ የእስራኤል ንጉሥ ባኦስ
በይሁዳ ላይ ዘምቶ፣ ከእስራኤል ንጉሥ
ከአሳ ግዛት ማንም እንዳይወጣ፣ ወደዚያም
ማንም እንዳይገባ ለመከልከል ራማን መሸገ።

2አሳም ከእግዚአብሔር ቤተ መቅደስና
ከራሱም ቤተ መንግሥት ግምጃ ቤቶች
ብርና ወርቅ ወስዶ በደማስቆ ተቀምጦ
ይገዛ ለነበረው ለሶርያ ንጉሥ ለወልደ አዴር
ላከ፤ 3ከዚያም "ቀድሞ በአባቴና በአባትህ
መካከል እንደ ነበረው ሁሉ፣ ዛሬም በእኔና
በአንተ መካከል የስምምነት ውል ይኑረን፤
እነሆ፤ ብርና ወርቅ ልኬልሃለሁ፤ ከእኔ
ተመልሶ ይሄድ ዘንድ ከባኦስ ጋር ያደረ
ግኸውን የስምምነት ውል አፍርስ" አለው።

4ወልደአዴር የንጉሥ አሳን ሐሳብ ተቀበለ፤
የጦር አዛዦቹንም በእስራኤል ከተሞች ላይ
አዘመተ። እነርሱ ዒዮንን፣ ዳንን፣ አቤል
ማይምንና የንፍታሌምን የዕቃ ግምጃ
ቤት ከተሞች ሁሉ ድል አድርገው ያዙ።
5ባኦስ ይህን በሰማ ጊዜ ራማን መገንባቱን
አቆመ፤ ሥራውንም አቋረጠ። 6ንጉሥ አሳም
የይሁዳን ሰዎች ሁሉ አመጣቸው፤ እነርሱም
ባኦስ ይሠራበት የነበረውን ድንጋይና
እንጨት ወሰዱ፤ አሳም ጌባንና ምጽጳን ሠ
ራባት።

7በዚያን ጊዜም ባለ ራእዩ አናኒ ወደ
ይሁዳ ንጉሥ ወደ አሳ መጥቶ እንዲህ አለው፤
"በአምላክህ በእግዚአብሔር ሳይሆን በሶርያ
ንጉሥ ስለ ታመንህ፣ የሶርያ ንጉሥ ሰራ
ዊት ከእጅህ አምልጦአል። 8ኢ
ትዮጵያውያንና ሊቢያውያን ብዙ ቍጥር
ካላቸው ሠረገላ ዎቻቸውና[b] ፈረሶቻቸው
ጋር ኀያል ሰራዊት

15፥1 ዘኍ11፥25፥26
15፥2 ዘዳ31፥17፤ 1ዜና28፥9፤2ዜና7፥14፤20፥17፤ መዝ78፥34፤ ኢሳ45፥19፤ 55፥6፤ኤር29፥13፤ ሆሴ3፥5፤ያዕ4፥8
15፥3 ዘሌ10፥11፤ ሰቆ2፥9፤አሞ8፥11
15፥4 ዘዳ4፥29
15፥5 መሳ5፥6፤ 19፥20፤ዘካ8፥10
15፥6 ኢሳ19፥2፤ ማቴ24፥7፤ማር13፥8፤ ሉቃ21፥10
15፥7 ኢሱ1፥7፥9፤1ሳሙ24፥19፤ መዝ18፥20፤58፥11፤ ምሳ14፥14፤ ኤር31፥16
15፥8 1ነገ8፥64፤ 15፥12፤2ዜና8፥12፤ 17፥2
15፥9 2ዜና11፥16-17
15፥10 ዘሌ23፥15-21
15፥11 2ዜና 14፥13
15፥12 2ነገ11፥17፤1ዜና16፥11
15፥13 ዘፀ22፥20፤ ዘዳ13፥9-16
15፥15 ዘዳ4፥29፤ 1ዜና22፥9
15፥16 ዘፀ34፥13፤ 2ሳሙ15፥23፤ 1ነገ2፥19፤2ዜና13፥2
15፥18 2ዜና14፥ 13
16፥1 2ነገ9፥9፤ ኤር41፥9
16፥2 2ዜና19፥1-20፥37፤22፥1-9
16፥3 2ዜና20፥35፤ 25፥7
16፥4 2ነገ15፥29
16፥6 ኤር41፥9
16፥7 1ነገ16፥1፤ 2ዜና13፥18
16፥8 ዘፍ10፥6፥8-9፤2ዜና12፥3፤13፥16፤ 24፥24
16፥9 1ሳሙ13፥13፤ 1ነገ15፥6፤ 2ዜና19፥2፤25፥7፤28፥16-21፤ኢዮ24፥23፤ መዝ33፥13-15፤ ምሳ15፥3፤ኤር16፥17፤ዘካ3፥9፤4፥10

[a]8 የቩልጌትና የሱርስቱ ቅጅ (እንዲሁም ቍጥር1) ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን የዖዴድን ልጅ የሚለውን አይ ጨምርም።
[b]8 ወይም ሠረገለኞች

አልነበሩምን? ይሁን እንጂ *በእግዚአብሔር*
ስለ ታመንህ በእጅህ አሳልፎ ሰጠህ፤ [9]በፍ
ጹም ልባቸው የሚታመኑበትን ለማበርታት
*የእግ ዚአብሔር* ዐይኖች በምድር ሁሉ
ላይ ይመለከታሉና። የሞኝነት ሥራ ስለ
ሠራህ ከእንግዲህ ወዲያ ጦርነት
አይለይህም።
[10]ከዚህ የተነሣም አሳ ባለ ራእዩን ተቈጣው፤
በጣም ስለ ተናደደም እስር ቤት አስገባው።
በዚያን ጊዜም አሳ አንዳንድ ሰዎችን ክፉኛ
አስጨነቃቸው።
[11]በአሳ ዘመነ መንግሥት ከመጀመሪያ
እስከ መጨረሻ የተከናወነው ሥራ በይሁዳና
በእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መዛግብት
ተጽፎአል። [12]አሳ በነገሠ በሠላሳ ዘጠነኛው
ዓመት እግሮቹን ክፉኛ ታመመ፤ ሕመሙ
ቢጸናበትም እንኳ፣ በዚያ ሁሉ ሕመም የባለ
መድኃኒቶችን እንጂ *የእግዚአብሔርን* ርዳታ
አልፈለገም። [13]አሳም በነገሠ በአርባ አንደ
ኛው ዓመት ሞተ፤ እንደ አባቶቹም ሁሉ
አንቀላፋ። [14]በዳዊት ከተማ ከዐለት
አስፈልፍሎ ለራሱ ባሠራውም መቃብር
ቀበሩት። በቅ መማ ቅመምና በልዩ ልዩ
ጣፋጭ ሽቱዎች በተሞላ ቃሬዛ ላይ አኖሩ
ት፤ ስለ ክብሩም ትልቅ እሳት አነደዱ።

## የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ

17 ልጁ ኢዮሣፍጥ በእርሱ ፈንታ ነገሠ፤
በእስራኤል ላይ በረታ። [2]እርሱም
በተመሸጉት የይሁዳ ከተሞች ሁሉ ውስጥ
ወታደር አኖረ፤ እንዲሁም በይሁዳ ምድርና
አባቱ አሳ በያዛቸው በኤፍሬም መንደሮች
ዘበኞች አስቀመጠ።
[3]በለጋነት ዕድሜው አባቱ ዳዊት በሄደበት
መንገድ ስለሄደ፣ *እግዚአብሔር* ከኢዮሣፍጥ
ጋር ነበር፤ የበኣልንም አማልክት አልጠ
የቀም፤ [4]ነገር ግን ከእስራኤል ድርጊት ይልቅ፣
የአባቱን አምላክ ፈለገ፤ ትእዛዛቱንም ተከተለ።
[5]*እግዚአብሔርም* መንግሥቱን በእጁ አጸናለት፤
መላው ይሁዳም ስጦታ አመጣለት፤ ከዚህ
የተነሣም ታላቅ ብልጽግናና ክብር አገኘ።
[6]ልቡም *በእግዚአብሔር* መንገድ የጸና ነበር፤
እንደዚሁም ማምለኪያ ኰረብታዎችንና የአ
ሼራ ዐምዶችን ከይሁዳ አስወገደ።
[7]በነገሠ በሦስተኛው ዓመት በይሁዳ ከተ
ሞች ያስተምሩ ዘንድ ሹማምቱን ማለትም
ቤን ኀይልን፣ አብድያስን፣ ዘካርያስን፣ ናትና
ኤልንና ሚካያን ላካቸው። [8]ከእነዚህም
ጋር ጥቂት ሌዋውያን ነበሩ፤ ስማቸውም፦ ሸ
ማያ፣ ነታንያ፣ ዝባድያ፣ አሣሄል፣ ሰሚራሞት፣
ዮናታን፣ አዶንያስ፣ ጦብያና ጦባዶንያ
ነበር። ካህናቱ ደግሞ ኢሊሳማና ኢዮራም
ነበሩ። [9]እነርሱም *የእግዚአብሔርን* የሕጉን
መጽሐፍ ይዘው በመሄድ በይሁዳ ሁሉ

16፥10 1ነገ22፥27
16፥12 2ዜና7፥14፤ 21፥18፤26፥19፤ መዝ103፥3፤ኤር17፥5 -6
16፥14 ዘፍ50፥2፡ 5፤2ዜና21፥19፤ ኤር34፥5
17፥1 1ነገ2፥12
17፥2 2ዜና11፥10፤ 2ዜና15፥8
17፥3 1ነገ22፥43
17፥4 2ዜና22፥9
17፥5 1ሳሙ10፥ 27፤ 2ዜና18፥1
17፥6 ዘፀ34፥13፤ 1ነገ 8፥61፤ 15፥14፤2ዜና19፥3፤20፥3 3፤21፥12
17፥7 ዘሌ10፥11፤ ዘዳ6፥4-9፤2ዜና 19፥4-11፤35፥3፤ ነህ8፥7፤ሚል2፥7
17፥8 2ዜና19፥8፤ ነህ8፥7-8፤ሆሴ4፥6
17፥9 ዘዳ28፥61
17፥10 ዘፍ35፥5፤ ዘዳ2፥25
17፥11 2ዜና9፥14፤ 21፥16
17፥14 2ሳሙ24፥2
17፥16 መሳ5፥9
17፥17 ዘኍ1፥36
17፥19 2ዜና11፥ 10 ፤25፥5
18፥1 2ዜና17፥5፤ 19፥1-3፤21፥6፤22፥3

ላለው ሕዝብ አስተማሩ፤ በይሁዳ ከተሞች
ሁሉ በመዘዋወርም ሕዝቡን አስተማሩ።
[10]በይሁዳ ዙሪያ ባሉ ነገሥታት ሁሉ ላይ
*ከእግዚአብሔር* ዘንድ ፍርሀት ስለወደቀባቸው
ኢዮሣፍጥን አልተዋጉትም። [11]ከፍልስጥኤ
ማውያንም አንዳንዶቹ እጅ መንሻ አመጠ
ሉት፤ ጥሬ ብርም ገበሩለት፤ ዐረቦችም
ሰባት ሺህ ሰባት መቶ አውራ በግና ሰባት
ሺህ ሰባት መቶ አውራ ፍየል መንጋ
አመጡለት።
[12]ኢዮሣፍጥም እያየለ ሄደ፤ በይሁዳም
ምሽጎችና የዕቃ ማከማቻ ከተሞች ሠራ።
[13]በይሁዳም ከተሞች እጅግ ብዙ ስንቅና ትጥቅ
ነበረው። ደግሞም በቂ ልምድ ያላቸውን
ተዋጊዎች በኢየሩሳሌም አስቀመጠ። [14]እነ
ርሱም በየቤተ ሰቦቻቸው ሲመዘገቡ እንደ
ሚከተለው ነው፤ ከይሁዳ የየሻለቃው አዛዦች፣
አዛዡ ዓድና ከሦስት መቶ ሺ ተዋጊዎች
ጋር፤ [15]ከእርሱ ቀጥሎም አዛዡ የሆሐ
ናን ከሁለት መቶ ሰማንያ ሺህ ጋር፤
[16]ከዚያ ቀጥሎም *ለእግዚአብሔር* አገልግሎት
በፈቃደኝነት ራሱን የሰጠው የዝክሪ ልጅ
ዓማስያ ከሁለት መቶ ሺህ ተዋጊዎች ጋር፤
[17]ከብንያምም ጀግናው ወታደር ኤሊዳሄ
ቀስትና ጋሻ ከያዙ ከሁለት መቶ ሺ ሰዎች ጋር፤
[18]ቀጥሎም ዮዛባት ለጦርነት ዝግጁ ከሆኑ
ከአንድ መቶ ሰማንያ ሺህ ሰዎች ጋር፤
[19]እነዚህ እንግዲህ በመላው ይሁዳ በተመሸጉት
ከተሞች ካስቀመጣቸው ሌላ፣ ንጉሡን ያገለግሉ
የነበሩ ሰዎች ናቸው።

## ሚካያ በአክዓብ ላይ ትንቢት ተናገረ

18፥1-27ተጓ ምብ—1ዜና22፥1-28

18 ኢዮሣፍጥ ታላቅ ሀብትና ክብር
ባገኘ ጊዜ ከአክዓብ ጋር በጋብቻ
ተሳሰረ። [2]ከጥቂት ዓመታት በኋላም አክዓ
ብን ሊጎበኝ ወደ ሰማርያ ወረደ። አክዓብም
ለእርሱና አብሮት ለነበረው ሕዝብ ብዙ በግና በሬ
ዐረደ፤ ከዚያም በሬማት ዘገለዓድ ላይ አደጋ
እንዲጥል አግባባው። [3]የእስራኤል ንጉሥ አክዓ
ብም የይሁዳን ንጉሥ ኢዮሣፍጥን፣ “ሬማት
ዘገለዓድን ለመውጋት አብረኸኝ ትሄዳለህን?” ሲ
ል ጠየቀው።
ኢዮሣፍጥም፣ “እኔ እንደ አንተው ነኝ፤ ሕዝ
ቤም እንደ ሕዝብህ ነው፤ በጦርነቱ አብረ
ናችሁ እንሰለፋለን” ሲል መለሰለት። [4]ደግ
ሞም ኢዮሣፍጥ የእስራኤልን ንጉሥ፣ “አስ
ቀድመህ ግን *የእግዚአብሔርን* ፈቃድ ጠይቅ”
አለው።
[5]ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ አራት መቶ
ነቢያትን በአንድነት ሰብስቦ፣ “ሬማት ዘገለዓ
ድን ለመውጋት ልሂድን ወይስ ልቅር?” ሲል
ጠየቃቸው።
እነርሱም፣ “እግዚአብሔር በንጉሡ እጅ

አሳልፎ ይሰጣታልና ሂድ” ብለው መለሱለት።
6ኢዮሣፍጥ ግን፣ “እንጠይቀው ዘንድ ሌላ
የእግዚአብሔር ነቢይ እዚህ የለምን?” አለ።
7የእስራኤልም ንጉሥ ለኢዮሣፍጥ፣ “መኖሩ
ንማ በእርሱ አማካይነት የእግዚአብሔርን
ፈቃድ የምንጠይቅበት አንድ ሰው አሁንም
አለ፤ ነገር ግን ምን ጊዜም ቢሆን ስለ እኔ
ክፉ እንጂ ደግ ትንቢት ስለማይናገር እጠ
ላዋለሁ፤ እርሱም የይምላ ልጅ ሚካያ ነው”
ሲል መለሰ።
ኢዮሳፍጥም፣ “ንጉሥ እንዲህ ማለት አይገ
ባውም” አለው።
8የእስራኤልም ንጉሥ ከሹማምንቱ አን
ዱን ጠርቶ “ሂድና የይምላን ልጅ ሚካያን
በፍጥነት አምጣው” አለው።
9የእስራኤል ንጉሥና የይሁዳ ንጉሥ ኢዮ
ሣፍጥ ልብሰ መንግሥታቸውን ለብሰው፣
በሰማርያ ቅጥር በር መግቢያ አጠገብ
ባለው ዐውድማ ላይ በየዙፋናቸው ተቀ
ምጠው፣ ነቢያቱ ሁሉ በፊታቸው ትንቢት
ይናገሩ ነበር። 10የክንዓና ልጅ ሴዴቅያስም
የብረት ቀንዶች ሠርቶ፣ “እግዚአብሔር እን
ዲህ ይላል፤ ‘ሶርያውያን እስኪጠፉ ድረስ
በእነዚህ ትወጋቸዋለህ” አለ።
11ሌሎቹ ነቢያት ሁሉ፣ “እግዚአብሔር
በንጉሡ እጅ አሳልፎ ይሰጣታልና፣ በሬ
ማት ገለዓድ ላይ አደጋ ጣልባት” በማለት
ተመሳሳይ ትንቢት ይናገሩ ነበር።
12ሚካያን ሊጠራ ሄዶ የነበረውም መል
እክተኛ፣ “እነሆ፣ ሌሎቹ ነቢያት በአንድ
አፍ ሆነው፣ ንጉሡ ድል እንደሚያደርግ
እየተ ነበዩ ነው፤ ያንተም ቃል እንደቃላቸው
ይሁን፤ ንጉሡን ደስ የሚያሰኘውን ተናገር”
አለው።
13ሚካያ ግን፣ “ሕያው እግዚአብሔርን!
አምላኬ የሚለውን ብቻ እናገራለሁ” አለ።
14እዚያ በደረሰም ጊዜ ንጉሡ፣ “ሚካያ
ሆይ፤ ሬማት ዘገለዓድን ለመውጋት እንሂድ
ወይስ ልቅር?” ሲል ጠየቀው።
እርሱም መልሶ፣ “ሂዱና ድል አድርጉ፤
በእጃችሁ አልፈው ይሰጣሉና” አለው።
15ንጉሡም፣ “ከእውነት በቀር ምንም ነገር
በእግዚአብሔር ስም እንዳትነግረኝ ስንት
ጊዜ አምለሃለሁ?” አለው።
16ከዚያም ሚካያ “እስራኤል ሁሉ
እረኛ እንደሌላቸው በጎች በተራሮች ላይ
ተበታትነው አየሁ፤ እግዚአብሔርም፣ ‘እነዚህ
ሰዎች ጌታ የላቸውም፤ እያንዳንዱም በሰላም
ወደ የቤቱ ይመለስ’ ብሎአል” ሲል መለሰ።
17የእስራኤልም ንጉሥ ኢዮሣፍጥን፣ “ስለ
እኔ ክፉ ብቻ እንጂ፣ ደግ ትንቢት እንደማይ
ናገር አልነገርሁህምን?” አለው።

18፥11 2ዜና22፥5
18፥13 ዘኍ22፥18፡20፡35
18፥16 ዘኍ27፥17፤ 1ዜና9፥1
18፥18 ዳን 7፥9
18፥21 1ዜና21፥1፤ ኢዮ1፥6፤ ዘካ3፥1፤ ዮሐ8፥44
18፥22 ኢዮ12፥16፤ ሕዝ14፥9
18፥23 ሐሥ23፥2
18፥26 ዕብ11፥36
18፥29 1ሳሙ28፥8

18ሚካያም በመቀጠል እንዲህ አለ፤
“እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቃል ስማ፤
እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ፣ የሰማይም
ሰራዊት ሁሉ በቀኙና በግራው ቆመው
አየሁ። 19እግዚአብሔርም፣ ‘የእስራኤል ንጉሥ
አክዓብ በሬማት ገለዓድ ላይ ዘምቶ እዚ
ያው እንዲሞት ማን ያሳስተው?’ አለ።
“አንዱ አንድ ሐሳብ፣ ሌላውም ሌላ ሐሳብ
አቀረበ። 20በመጨረሻም አንድ መንፈስ
ወደ ፊት ወጥቶ፣ በእግዚአብሔር ፊት
በመቆም፣ ‘እኔ አሳስተዋለሁ’ አለ።
“እግዚአብሔርም፣ ‘እንዴት አድርገህ?’
ሲል ጠየቀው።
21“እርሱም፣ ‘እሄድና በነቢያቱ ሁሉ
አፍ የሐሰት መንፈስ እሆናለሁ’ አለ።
“እግዚአብሔርም፣ ‘እንግዲያውስ ሂደህ
አሳስተው፤ ይሳካልሃልም’ አለው።
22“አሁንም እነሆ፣ እግዚአብሔር በእነዚህ
ነቢያትህ አፍ የሐሰት መንፈስ አኖረ፤ እግዚ
አብሔርም ጥፋት አዞብሃል”።
23ከዚያም የክንዓናም ልጅ ሴዴቅያስ ወጥቶ
ሚካያን በጥፊ መታውና፣ “ለመሆኑ የእግ
ዚአብሔር መንፈስ አንተን ያነጋገረህ፣
በየት በኩል አልፎኝ ነው?” አለው።
24ሚካያም፣ “ለመሸሸግ ወደ እልፍኝህ
በምትሄድበት በዚያ ዕለት ታገኘዋለህ”
አለው።
25ከዚያም የእስራኤል ንጉሥ እንዲህ
ሲል አዘዘ፤ “ሚካያን ይዛችሁ ወደ ከተ
ማዪቱ ገዥ ወደ አሞንና ወደ ንጉሡ ልጅ
ወደ ኢዮአስ መልሳችሁ ላኩት፤ 26እነር
ሱንም፣ ‘ንጉሡ፣ ይህን ሰው እስር ቤት
አስገቡት፤ በደህና እስክመለስም ድረስ
ከደረቅ ቂጣና ከውሃ በስተቀር ምንም
አትስጡት ብሎአል’ በሏቸው።”
27ሚካያም፣ “አንተ በደህና ከተመለስክማ
እግዚአብሔር በእኔ አልተናገረም ማለት
ነው!” አለ፤ ቀጥሎም፣ “እናንተ ሕዝብ
ሁላችሁ ስሙኝ” አለ።

## አክዓብ በሬማት ገለዓድ ተገደለ

18፥28-34ተጓ ምብ—1ዜና22፥29-36

28ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥና የይሁዳ
ንጉሥ ኢዮሣፍጥ ወደ ሬማት ገለዓድ ወጡ።
29የእስራኤልም ንጉሥ ኢዮሣፍጥን፣ “እኔ
ልብሴን ለውጬ ወደ ጦርነቱ እገባለሁ፤
አንተ ግን ልብሰ መንግሥትህን ልበስ”
አለው። ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ ልብሱን
ለውጦ ሌላ ሰው መስሎ ወደ ጦርነቱ ገባ።
30በዚህ ጊዜ የሶርያ ንጉሥ የሠረገላ አዛ
ዦቹን፣ “ከእስራኤል ንጉሥ በቀር፣ ትንሽም

ሆነ ትልቅ ከሌላ ከማንም ጋር አትዋጉ” ብሎ አዘዛቸው። 31የሠረገላው አዛዦችም ኢዮሣፍጥን ባዩ ጊዜ፣ “የእስራኤል ንጉሥ ይህ ነው” ብለው አሰቡ፤ ሊወጉትም ከበቡት፤ ኢዮሣፍጥ ግን ጮኸ፤ እግዚአብሔርም ረዳው፤ አምላክም ከእርሱ መለሳቸው፤ 32የሠረገላ አዛዦቹም የእስራኤል ንጉሥ አለመሆኑን በተረዱ ጊዜ እርሱን ከማሳደድ ተመለሱ።

33ይሁን እንጂ ቀስቱን በነሲብ ቢያስፈ ነጥረው በጥሩሩ መጋጠሚያዎች መካከል አልፎ የእስራኤልን ንጉሥ ወጋው። ንጉሡም ሠረገላ ነጂውን “ተመለስና ከጦርነቱ አውጣኝ፤ ቈስያለሁና” አለው። 34ጦርነቱ ቀኑን ሙሉ እንደ ተፋፋመ ዋለ፤ የእስራኤልም ንጉሥ በሶርያውያን ፊት ለፊት በሠረ ገላው ላይ እስከ ምሽት ድረስ ተደግፎ ነበር፤ ፀሐይ ስትጠልቅም ሞተ።

19 የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሳፍጥ ኢየሩሳሌም ወዳለው ቤተ መንግሥቱ በደኅና በተመለሰ ጊዜ፣ 2ባለ ራእዩ የአናኒ ልጅ ኢዩ ሊገናኘው ወጣ፤ እንዲህም አለው፣ “አንተ ክፉውን መርዳትህና እግዚአብሔርን የሚጠ ሉትን ማፍቀርህ[ኘ] ተገቢ ነውን? ስለዚህ የእግዚ አብሔር ቍጣ ባንተ ላይ ነው፤ 3ይሁን እንጂ የአሼራን ዐምዶች ከምድሪቱ ስላስወገድህና እግዚአብሔርን ለመፈለግ ልብህን ስላዘጋጀህ፣ መልካም ነገር ተገኝቶብሃል”።

## ኢዮሣፍጥ ዳኞችን ሾመ

4ኢዮሣፍጥ በኢየሩሳሌም ተቀመጠ፤ ከቤርሳቤህ እስከ ኰረብታማው አገር እስከ ኤፍሬም ድረስ እንደገና በመውጣት ወደ ሕዝቡ መካከል ገብቶ ወደ አባቶቻቸው አምላክ ወደ እግዚአብሔር መለሳቸው። 5በምድሪቱም ላይ በተመሸጉት የይሁዳ ከተሞች ሁሉ ዳኞችን ሾመ፤ 6እንዲህም አላቸው፤ “እናንተ የምትፈርዱት ለሰው ሳይሆን፣ ፍርድ በምት ሰጡበት ጊዜ ሁሉ ከእናንተ ጋር ለሆነው ለእግዚአብሔር ስለሆነ፣ በምትሰጡት ውሳኔ ሁሉ ብርቱ ጥንቃቄ አድርጉ፤ 7አሁንም እግዚአብሔርን መፍራት በእናንተ ላይ ይሁን፤ በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ ፍርድ ማጣመም፣ አድልዎ ማድረግና መማለጃ መቀበል ስለሌለ ተጠንቅቃችሁ ፍረዱ።”

8ኢዮሳፍጥም በኢየሩሳሌም የእግዚአብሔ ርን ሕግ እንዲያስፈጽሙና ለሚነሡ ክርክ ሮችም እልባት እንዲሰጡ ከሌዋውያን፣ ከካህ ናትና ከእስራኤል ቤት አለቆች ጥቂት ሰዎች ሾመ፤ እነርሱም መኖሪያቸው በኢ የሩሳሌም ሆነ። 9እነርሱንም እንዲህ ብሎ አዘዛቸው፤ “እግዚአብሔርን በመፍራት፣ በታ ማኝነትና በፍጹም ልብ አገልግሉ። 10በየከተ ማው ከሚኖሩት ወገኖቻችሁ ስለ ደም መፋሰስ ወይም ሕግን፣ ትእዛዛትን፣ ደን ብንና ሥርዐትን ስለ መተላለፍ በሚቀ ርብላችሁ በማናቸውም ጕዳይ እግዚ አብሔርን እንዳይበድሉ አስጠንቅቋቸው፤ ያለዚያ ግን ቍጣው በእናንተና በወንድ ሞቻችሁ ላይ ይመጣል፤ ይህን ብታደርጉ በደለኞች አትሆኑም።

11“የእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ ላይ የካህናቱ አለቃ አማርያ፣ የንጉሡ በሆነው ነገር ሁሉ ላይ የይሁዳ ነገድ መሪ የሆነው የእስማኤል ልጅ ዝባድያ በላያችሁ ተሾመዋል፤ ሌዋውያኑ ደግሞ በፊታችሁ አለቆች ሆነው ያገለግላሉ፤ በርትታችሁ ሥሩ፤ እግዚአብሔርም መልካም ከሚያደርጉ ጋር ይሁን።”

## ኢዮሣፍጥ ሞዓብንና አሞንን ድል ማድረጉ

20 ከዚህ በኋላ ሞዓባውያንና አሞና ውያን ከጥቂት ምዑናውያን[ኣ] ጋር ሆነው ኢዮሣፍጥን ለመውጋት መጡ።

2ሰዎችም መጥተው ኢዮሣፍጥን፣ “ግዙፍ ሰራዊት ሊወጋህ ከሙት[ኸ]ባሕር ወዲያ ካለው ከኤዶም[ከ] መጥቶብሃል፤ እነሆም፣ ሐሴሶን ታማር በተባለው በዓይንጋዲ ናቸው” አሉት። 3ኢዮሣፍጥም እጅግ ስለ ፈራ እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ወሰነ፤ በይሁዳም ሁሉ ጾም ዐወጀ። 4የይሁዳ ሕዝብም የእግዚአብሔን ርዳታ ይሻ ዘንድ በአንድነት ተሰበሰበ፤ ከይሁዳ ከተሞች ሁሉም እግዚአብሔርን ለመፈለግ መጡ። 5ኢዮሣፍጥም በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ፣ ከአዲሱ አደባባይ ፊት ለፊት በይሁዳና በኢየሩሳሌም ጉባኤ መካከል ቆመ፤ 6እንዲህም አለ፤

“የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ በሰማይ የምትኖር አምላክ አይደለህ ምን? የምድር ሕዝቦችን መንግሥታት ሁሉ የምትገዛ አንተ ነህ፤ ኀይልና ሥልጣን በእጅህ ነው፤ ሊቋቋምህም የሚችል ማንም የለም። 7አምላካችን ሆይ፤ የዚህችን ምድር ነዋሪዎች ከሕዝብህ ከእስራኤል ፊት አሳ ድደህ ያስወጣህና ለወዳጅህ ለአብርሃም ዘሮች ለዘላለም የሰጠሃቸው አንተ አይ ደለህምን? 8እነርሱም ተቀመጡባት፤ ለስ ምህ መቅደስ ሠሩባት፤ እንዲህም አሉ፤ 9‘የፍርድ ሰይፍም ሆነ የቸነፈር ወይም የራብ መከራ ቢደርስብን ስምህ በተጠራበት በዚህ

18፥31 2ዜና13፥14
18፥34 2ዜና22፥5
19፥2 1ነገ16፥1፤ 2ዜና16፥2-9፤ 24፥18፤32፥25፤ መዝ7፥11፤ 139፥21-22
19፥3 1ነገ14፥13፤ 2ዜና17፥6፤18፥1፤20፥35፤25፥7
19፥5 ዘፍ47፥6፤ ዘፀ18፥26
19፥6 ዘሌ19፥15፤ ዘዳ16፥18-20፤ 17፥8-13
19፥7 ዘፍ18፥25፤ ዘፀ18፥16፤ ዘዳ10፥17፤ኢዮ8፥3፤ 13፥10፤32፥21፤ 34፥19
19፥8 1ዜና23፥4፤ 2ዜና17፥8-9፤ ሕዝ44፥24
19፥10 ዘዳ17፥8-13
19፥11 1ዜና28፥20
20፥1 1ዜና4፥41፤ መዝ83፥6
20፥2 ዘፍ14፥7፤ 1ሳሙ23፥29፤2ዜና24፥24፤መኃ1፥14
20፥3 1ሳሙ7፥6፤ ዕዝ8፥23፤ ነህ1፥4፤አስ4፥16፤ ኢሳ58፥6፤ ኤር36፥9፤ዳን9፥3፤ ኢል1፥14፤ 2፥15፤ዮና3፥5፥7
20፥4 ኤር36፥6
20፥6 ዘዳ4፥39፤ 1ዜና29፥11-12፤2ዜና25፥8፤ ኢዮ25፥2፤ 41፥10፤42፥2፤ ኢሳ14፥27፤ ኤር32፥27፤49፥19፤ ማቴ6፥9
20፥7 ዘፍ12፥7፤ ኢሳ41፥8፤ያዕ2፥23
20፥8 2ዜና6፥20
20፥9 2ዜና6፥28

[ኘ]2 ወይም፣ *ከሚጠሉት ጋር መተባበርህ*
[ኣ]1 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች ከዚህ ጋር ይስማ ማሉ፤ ነገር ግን ዕብራይስጡ ***ምዲያማውያን*** ይላል።
[ከ]2 አንድ የዕብራይስጥ ቅጂ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን ***አራም*** ይላል።
[ኸ]2 ምንም እንኳ ***የሙት ባሕር*** መሆኑን ግልጽ ቢሆንም አንዳንድ ቅጆች ***ሙት*** የሚለውን ቃል አይጨምሩም ።

ፊት ለፊት፣ በፊትህ ቆመን በጭንቀታ
ችን ወደ አንተ እንጮሃለን፤ አንተም ትሰ
ማናለህ፤ ታድነናለህም።’
[10]እስራኤል ከግብፅ በወጡ ጊዜ፣ ግዛታ
ቸውን እንዳይወርሩባቸው በማድረግህ
ከእነርሱ ተመልሰው ሳያጠፏቸው የቀሩት
የአሞን፣ የሞዓብና የሴይር ተራራ ሰዎች
እነሆ እዚህ አሉ። [11]እነሆ፣ አንተ ርስት
አድርገህ ከሰጠኸን ምድር እኛን በማፈናቀል
ወሮታ ሊመልሱልን መጥተዋል። [12]አምላካችን
ሆይ፤ አንተ አትፈርድባቸውምን? የመ
ጣብንን ይህን ታላቅ ሰራዊት እንቋቋም
ዘንድ አቅም የለንምና የምናደርገውን
አናውቅም ነገር ግን ዓይኖቻችን ወዳንተ
ናቸው።
[13]የይሁዳ ሰዎች ሁሉ ከሚስቶቻቸው፣
ከልጆቻቸውና ከሕፃኖቻቸው ጋር *በእግዚ
አብሔር* ፊት ቆመው ነበር።
[14]በዚህ ጊዜ የአሳፍ ዘር በሆነው በሌዋዊው
በዘካሪያስ ልጅ፣ በየሕዚኤል ላይ *የእግዚ
አብሔር* መንፈስ መጣ። ዘካርያስም የበናያስ
ልጅ ሲሆን፣ በናያስም የማታንን ልጅ የሆነው
የይዒኤል ልጅ ነው።
[15]እርሱም እንዲህ አለ፤ “ንጉሥ ኢ
ዮሣ ፍጥ፣ እናንተም በይሁዳና በኢየሩ
ሳሌም የምትኖሩ ሁሉ አድምጡ! *እግዚ
አብሔር* እንዲህ ይላችኋል፤ ‘ውጊያው
*የእግዚአብሔር* እንጂ የእናንተ አይ
ደለምና፣ ከዚህ ታላቅ ሰራዊት የተነሣ
አትፍሩ፣ አትደንግጡ፣ [16]ነገ በእነርሱ
ላይ ውረዱ፤ እነርሱ በጺ
ጽ መተላለፊያ ሽቅብ ይወጣሉ፣ እናን
ተም በይሩኤል ምድረ በዳ ውስጥ በሸ
ለቆው መጨረሻ ላይ ታገኟቸዋላችሁ። [17]ይህን
ጦርነት የምትዋጉት እናንተ አይደላችሁም፤
ይሁዳና ኢየሩሳሌም ሆይ፤ ቦታ ቦታችሁን
ያዙ፤ ጸንታችሁ ቁሙ፤ *እግዚአብሔር*
የሚሰጣችሁንም ማዳን እዩ። አትፍሩ፤
አትደንግጡም፤ ነገውኑ ውጡና ግጠ
ሙ አቸው፤ *እግዚአብሔርም* ከእናንተ
ጋር ይሆናል።’ ”
[18]ኢዮሣፍጥ በግምባሩ ወደ መሬት ተደፋ፤
የይሁዳና የኢየሩሳሌምም ሕዝብ ሁሉ
*በእግዚአብሔር* ፊት ወደቁ፤ ሰገዱም። [19]ከቀዓ
ትና ከቆሬ ወገኖች ጥቂት ሌዋውያንም
ቆመው፣ እጅግ ከፍ ባለ ድምፅ የእስራ
ኤልን *አምላክ* እግዚአብሔርን አመሰገኑ።
[20]በማግሥቱ ጠዋት በማለዳ ተነሥተው
ወደ ቴቁሔ ምድረ በዳ ሄዱ። መንገድ እንደ
ጀመሩም ኢዮሣፍጥ ቆሞ፣ “ይሁዳና የኢ
የሩሳሌም ሕዝብ ሆይ፣ አድምጡኝ! *በአም
ላካችሁ* በእግዚአብሔር እመኑ፤ ትጸኑ
ማላችሁ። በነቢያቱም እመኑ፤ ይሳካላችሁ
ማል” አላቸው። [21]ከሕዝቡም ጋር

20፥10 ዘኍ20፥14-21፤ዘዳ2፥4-6፥9፥18-19
20፥11 መዝ83፥1-12
20፥12 መሳ11፥27፤ መዝ25፥15፤ ኢሳ30፥15፤ 45፥22፤ሚክ7፥7
20፥14 1ዜና9፥15፤ 12፥18
20፥15 1ሳሙ17፥47፤ 2ዜና32፥7፤ መዝ91፥8
20፥17 ዘፀ14፥13
20፥18 ዘፍ24፥26፤ 2ዜና29፥29
20፥20 ዘፍ39፥3፤ ምሳ16፥3፤ኢሳ7፥9
20፥21 1ዜና16፥29፤ 2ዜና5፥13፤ መዝ136፥1
20፥22 2ዜና13፥13
20፥23 ዘፍ19፥38፤ መሳ7፥22፤1ሳሙ14፥20፤2ዜና21፥8፤ሕዝ38፥21
20፥29 ዘፍ35፥5፤ ዘፀ14፥14፤ዘዳ2፥25
20፥30 1ዜና22፥9
20፥33 2ዜና17፥6

ከተመካከረ በኋላ ከሠራዊቱ ፊት ቀድመው
በመሄድ፣
“*እግዚአብሔርን* አመስግኑ፣ ፍቅሩ ለዘላለም
ጸንቶ ይኖራልና” እያሉ *ለእግዚአብሔር*
የሚዘምሩና ስለ ቅድስናውም ክብር
የሚያወድሱ ሰዎችን መደበ።
[22]መዘመርና ማወደስ እንደ ጀመሩም፣
*እግዚአብሔር* ይሁዳን በወረሩት በአሞን፣
በሞዓብና በሴይር ተራራ ሰዎች ላይ ድብቅ
ጦር አመጣባቸው፤ ተሸነፉም። [23]የአሞንና
የሞዓብ ሰዎችም የሴይርን ተራራ ሰዎች ለማ
ጥፋትና ለመደምሰስ ተነሡባቸው። ከሴይር
የመጡትን ሰዎች ካጠፉ በኋላም፣ እርስ በርስ
ተጠፋፉ።
[24]የይሁዳ ሰዎች ምድረ በዳውን
ቍልቍል ወደሚያሳየው ቦታ መጥተው
ግዙፉን ሰራዊት ሲመለከቱ፣ መሬቱ ሬሳ
በሬሳ ሆኖ አዩ፤ አንድም ሰው አላመለጠ
ም። [25]ኢዮ ሣፍጥና ሰዎቹም ምርኮአቸውን
ለማጋዝ ሄዱ፤ በዚያም መካከል እጅግ ብዙ
መሣሪያና ልብስ፣ [ᵚ]ሊሸከሙ ከሚችሉትም
በላይ ውድ ዕቃዎችን አገኙ። ምርኮውም
ከመብዛቱ የተነሣ ለመሰብሰብ ሦስት ቀን
ፈጀ። [26]በአራተኛውም ቀን *እግዚአብሐ
ሔርን* ባመሰ ገኑበት በበረከት[ᵒ] ሸለቆ
ተሰበሰቡ፤ ያም ስፍራ እስከ ዛሬ ድረስ
የበረከት ሸለቆ ተብሎ የተጠራው ከዚህ
የተነሣ ነው።
[27]*እግዚአብሔር* በጠላቶቻቸው ላይ እን
ዲደሰቱ ስላደረጋቸው፣ የይሁዳና የኢየሩ
ሳሌም ሰዎች ሁሉ በኢዮሳፍጥ እየተመሩ፣
በታላቅ ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ።
[28]ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ እንደገቡም በበ
ገና፣ በመሰንቆና በመለከት ድምፅ ታጅበው
ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ አመሩ።
[29]እግዚአብሔር የእስራኤልን ጠላቶች እንዴት
እንደተዋጋቸው በሰሙ *መንግሥታት* ሁሉ
ላይ *ከእግዚአብሔር* ዘንድ ፍርሀት ወደቀባቸው።
[30]አምላኩ በየአቅጣጫው ዕረፍት
ስለ ሰጠው፣ የኢዮሣፍጥ *መንግሥት*
ሰላም አግኝቶ ነበር።

### የኢዮሣፍጥ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ

20፥31-21፥1 ተጓ ምብ —1ዜና22፥41-50

[31]ኢዮሣፍጥ በይሁዳ ላይ ነገሠ። *መንገሥ*
በጀመረ ጊዜም ዕድሜው ሠላሳ አምስት ዓመት
ሲሆን፣ በኢየሩሳሌም ተቀምጦ ሃያ አምስት
ዓመት ገዛ። እናቱም የሺልሒ ልጅ ዓዙባ
ነበረች። [32]እርሱም በአባቱ በአሳ መንገድ
ሄደ፤ ከዚያም ፈቀቅ አላለም፤ *በእግዚ
አብሔርም* ፊት መልካም የሆነውን ነገር
አደረገ። [33]ያም ሆኖ ግን ማምለኪያ ኰረብታዎች

ᵚ25 አንዳንድ የዕብራይስጥና የቡልጌት ቅጆች ከዚህ ጋር ይስ
ማማሉ ፤ ነገር ግን አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች *ሬሳ* ይላል።
ᵒ26 በዕብራይስጡ፣ *በራካ* ማለት *በረከት* ማለት ነው።

ሙሉ በሙሉ አልተወገዱም፤ ሕዝቡም ገና
ልቡን በአባቶቹ አምላክ ላይ አልጣለም
ነበር።
34በኢዮሣፍጥ ዘመነ መንግሥት ከመጀመሪያ
እስከ፣ መጨረሻ የተከናወኑት ሌሎች ተግባ
ራት የአናኒ ልጅ ኢዩ በዘገበው የእስራ
ኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ ተመዝ
ግቦአል።
35ከዚህ በኋላ የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ
ሥራው እጅግ ክፉ ከሆነው ከእስራኤል
ንጉሥ ከአካዝያስ ጋር የስምምነት ውል
አደረገ፤ 36የንግድ መርከብ[ዘ] ለመሥራትም
ተስማሙ፤ መርከቦቹንም በዔጽዮንጋብር
አሠሩ። 37የመሪሳ ሰው የሆነው የዶዳያ ልጅ
አልዓዛር በኢዮሣፍጥ ላይ፣ "ከአካዝያስ ጋር
የስምምነት ውል ስለ አደረግህ፣ *እግዚአብሔር*
*ሥራህን ያፈርሰዋል*" ሲል ትንቢት ተናገረበት፤
መርከቦቹም ተሰበሩ፤ ለንግዱም ሥራ መን
ቀሳቀስ አልቻሉም።[ዠ]

21 ኢዮሣፍጥ እንደ አባቶቹ ሁሉ
አንቀላፋ፤ እነርሱ በተቀበሩበትም በዳ
ዊት ከተማ ተቀበረ። ልጁ ኢዮራምም በእርሱ
ፈንታ ነገሠ። 2የኢዮራም ወንድሞች
የሆኑት የኢዮሣፍጥ ልጆችም ዓዛርያስ፣
ይሒኤል፣ ዘካርያስ፣ዔዛርያስ፣
ሚካኤልና ሰፋጥያስ ይባላሉ። እነዚህ
ሁሉ የእስራኤል[የ] ንጉሥ የኢዮሣፍጥ
ልጆች ነበሩ። 3አባታቸውም ብዙ የብርና
የወርቅ፣ የውድ ዕቃዎችም ስጦታ እንዲ
ሁም በይሁዳ ያሉትን የተመሸጉ ከተሞች
ሰጣቸው፤ ነገር ግን መንግሥቱን ለኢዮራም
ሰጠ፤ የበኵር ልጁ ነበርና።

### የይሁዳ ንጉሥ ኢዮራም

21፥5-10፡20ተጓ ምብ —2ዜና8፥16-24

4ኢዮራም በአባቱ መንግሥት ላይ ተደላ
ድሎ ከተቀመጠ በኋላ ወንድሞቹን በሙሉ
ከጥቂት የእስራኤል አለቆች ጋር በሰይፍ
ገደለ።
5ኢዮራም በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሰላሳ
ሁለት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም
ስምንት ዓመት ገዛ። 6እርሱም የአክዓብን
ልጅ አግብቶ ስለ ነበር የአክዓብ ቤት
እንደ አደረገው ሁሉ የእስራኤል ነገሥ
ታት የሄዱበትን መንገድ ተከተለ፤ በእግዚ
አብሔርም ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸመ። 7ይሁን
እንጂ *እግዚአብሔር* ከዳዊት ጋር ካደረገው
ኪዳን የተነሣ፣ የዳዊትን ቤት ማጥፋት አል
ፈለገም፤ ለዳዊትና ለዘሩ ለዘላለም የሚጸና
መብራት እንዲኖር ለማድረግ ተስፋ
ሰጥቶ ነበርና።
8በኢዮራም ዘመነ መንግሥት ኤዶም
በይሁዳ ላይ ዐምፆ፣ የራሱን ንጉሥ አነገሠ።
9ስለዚህ ኢዮራም የጦር ሹማምንቱንና
ሰረገላዎቹን ሁሉ ይዞ ወደዚያው ሄደ።

20፥34 1ነገ16፥1
20፥35 2ዜና16፥3፤ 19፥1-3
20፥37 1ነገ9፥26
21፥1 1ዜና3፥11
21፥3 2ዜና11፥10፡ 23
21፥4 መሳ9፥5፤ 1ነገ2፥12
21፥6 1ነገ12፥28-30፤2ዜና18፥1፤22፥3
21፥7 2ሳሙ7፥13፡ 15፤21፥17፤23፥3
21፥8 2ዜና20፥22፥23
21፥10 ዘኍ33፥20
21፥12 2ነገ1፥16-17፤2ዜና14፥2፤ 17፥3-6
21፥13 1ነገ2፥32፤ 16፥29-33
21፥15 ዘኍ12፥10
21፥16 2ዜና17፥ 10-11፤22፥1፤26፥7
21፥17 2ነገ12፥18፤ 2ዜና22፥1፤ኢል3፥5
21፥19 2ዜና16፥ 14
21፥20 2ዜና24፥2 5፤ 28፥27፤33፥20

ኤዶማውያንም እርሱንና የሰረገላ አዛዦቹን
ሁሉ ከበቡ፤ እርሱ ግን በሌሊት ተነሥቶ
የከበቧቸውን መታ። 10ኤዶምም እስከ ዛሬ
ድረስ በይሁዳ ላይ እንደ ዐመፀ ነው።
ኢዮራም የአባቶቹን *አምላክ* እግዚአብሔርን
ስለ ተወ፣ የልብና ከተማ በዚያኑ ጊዜ
ዐመፀችበት።
11ከዚህም በላይ በይሁዳ ኰረብቶች ላይ
መስገጃ ስፍራዎች ሠርቶ የኢየሩሳሌም ሕዝብ
በዚያ እንዲያመነዝር አደረገ፤ ይሁዳንም
አሳተ።
12ከነቢዩ ከኤልያስ እንዲህ የሚል
ደብዳቤ ለኢዮራም መጣ፤
"የአባትህ የዳዊት *አምላክ* እግዚአብሔር
እን ዲህ ይላል፤ 'አንተ በአባትህ በኢዮሣፍጥ
ወይም በይሁዳ ንጉሥ በአሳ መንገድ
አልሄድህም፤ 13ነገር ግን በእስራኤል
ነገሥታት መንገድ ሄደሃል፤ የአክዓብ ቤት
የእስራኤልን ሕዝብ እንዲያመነዝር
እንዳደረገ ሁሉ፣ አንተም ይሁዳና የኢየሩ
ሳሌም ሕዝብ እንዲያመነ ዝሩ
አሳሳትሃቸው፤ እንዲሁም ካንተ
የሚሻሉትን፣ የገዛ ወንድሞችህንና የአባ
ትህን ቤተ ሰብ አባላት ገደልሃቸው፤
14ስለዚህ እነሆ፤ *እግዚአብሔር ሕዝብህን*፣
ልጆችህን፣ ሚስቶችህንና ያለህን ሁሉ በታላቅ
መቅሠፍት ይመታል። 15አንተም ራስህ
በየዕለቱ እየባሰ በሚሄድ የአንጀት በሽታ
ክፉኛ ትታመማለህ፤ በመጨረሻም
ሕመሙ አንጀትህን ወደ ውጭ ያወጣዋል።'"
16*እግዚአብሔርም* ፍልስጥኤማውያንንና በኢ
ትዮጵያውያን አጠገብ የሚኖሩ ዐረቦችን በኢ
ዮራም ላይ በጠላትነት እንዲነሡ አደረገ።
17እነርሱም በይሁዳ ላይ ወጡ፤ ወረሯትም።
በንጉሡ ቤተ መንግሥት የሚገኘውን ዕቃ ሁሉ፣
ከወንዶች ልጆቹና ከሚስቶቹ ጋር ወሰዱ፤
ከመጨረሻ ልጁ ከአካዝያስ[ደ] በስተቀር አንድም
ልጅ አልቀረለትም።
18ከዚህ ሁሉ በኋላ *እግዚአብሔር* ሊድን
በማይችል የአንጀት በሽታ ኢዮራምን
ቀሠፈው። 19ሕመሙም ሲያሠቃየው ከቈየ
በኋላ፣ በሁለተኛው ዓመት መጨረሻ ላይ
በዚሁ ሳቢያ አንጀቱ ወጥቶ በከባድ ሥቃይ
ሞተ። ሕዝቡም ለአባቶቹ ክብር እሳት
ያነድዱ ነበር፤ ለእርሱ ግን አላነደዱለትም።
20ኢዮራም ሲነግሥ ዕድሜው ሠላሳ
ሁለት
ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም
ስምንት ዓመት ገዛ። በሞተ ጊዜም ማንም
አላዘነለትም፤ በዳዊትም ከተማ እንጂ ብነገ
ሥታቱ መቃብር አልቀበሩትም።

[ዘ]36 ዕብራይስጡ፣ *ወደ ተርሴስ ሊሄዱ የሚችሉ መርከቦች* ይላል።
[ዠ]37 ዕብራይስጡ፣ *ወደ ተርሴስ መሄድ አልቻሉም* ይላል።
[የ]2 በሁለተኛው የዜና መዋልዕ መጽሐፍ ተደጋግሞ እንደተጠቀሰው ይህ ይሁዳ ነው።
[ደ]17 በዕብራይስጥ *አካዝ* እና *ኢዮአስ* አንድ ናቸው።

## የይሁዳ ንጉሥ አካዝያስ

22፥1-6ተጓ ምብ —2ዜና8፥25-29
22፥7-9ተጓ ምብ —2ዜና9፥21- 29

22 ከዐረቦች ጋር ወደ ሰፈር የመጡት
ወራሪዎች፣ ታላላቅ ወንድሞቹን ሁሉ
ገድለዋቸው ስለ ነበር፣ የኢየሩሳሌም ሕዝብ የኢዮ
ራምን የመጨረሻ ልጅ አካዝያስን በአባቱ
ምትክ አነገሡት። ስለዚህ የይሁዳ ንጉሥ
የኢዮራም ልጅ አካዝያስ መግዛት ጀመረ።
2አካዝያስ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሃያ ሁለት[፳]
ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም አንድ
ዓመት ገዛ። እናቱም ጎቶልያ የተባለች
የዘንበሪ የልጅ ልጅ ነበረች።
3እናቱ ክፋትን እንዲያደርግ
ትመክረው ስለ ነበር፣ እርሱም በአክዓብ
ቤት መንገድ ሄደ። 4ከአባቱ ሞት በኋላ
የአክዓብ ቤት አማካሪዎቹ በመሆን ወደ
ጥፋት ስለ መሩት፣ የአክዓብ ቤት
እንዳደረገው ሁሉ እርሱም *በእግዚአብሔር*
*ፊት* ክፉ ነገር አደረገ። 5እን ዲሁም የእስራ
ኤል ንጉሥ የአክዓብ ልጅ ኢዮራም
የሶርያን ንጉሥ አዛሄል ለመውጋት ወደ ሬ
ማት ገለዓድ በሄደ ጊዜ የእነዚህኑ ሰዎች
ምክር ተከትሎ ከኢዮራም ጋር አብ ሮት
ሄደ፣ ሶርያውያንም ኢዮራምን አቈሰሉት።
6ስለዚህ ከሶርያ ንጉሥ ከአዛሄል ጋር
ባደረገው ጦርነት ሬማት[ገ] ላይ ከደረሰበት
ቊስል ለመዳን ወደ ኢይዝራኤል ተመለሰ።
የአክዓብ ልጅ ኢዮራም በመቊሰሉም
የይ ሁዳ ንጉሥ የኢዮራም ልጅ አካዝያስ
ሊጠይቀው ወደ ኢይዝራኤል ወረደ።
7አካዝያስ ኢዮራምን ለመጠየቅ መሄዱን፣
እግዚአብሔር ለአካዝያስ መውደቅ ምክንያት
አደረገው፤ አካዝያስ እንደ ደረሰም የናሜሲ
ን ልጅ ኢዩን ለመቀበል ከኢዮራም ጋር
ወጣ፤ ኢዩም የአክዓብን ቤት እንዲያጠፋ
*እግዚአብሔር* የቀባው ሰው ነበር። 8ኢዩ
በአ ክዓብ ቤት ላይ ፍርድ በሚፈጽምበት
ጊዜ፣ አካዝያስን ያጅቡ የነበሩትን
የይሁዳን መሳፍንትና የዘመዶቹን ወንዶች
ልጆች አግኝቶ ገደላቸው። 9ከዚያም አካዝያስን
ለመፈለግ ሄደ፤ የእርሱም ሰዎች አካዝያስን
በሰማርያ ከተደበቀበት አግኝተው ያዙት፤
ወደ ኢዩም አምጥተው ገደሉት።
"*እግዚአብሔርን* በፍጹም ልቡ የፈለገው
የኢዮሣፍጥ ልጅ ነው" በማለት ቀበሩት።
ስለዚህ ከአካዝያስ ቤት የመንግሥቱን
ሥልጣን ይይዝ ዘንድ የሚችል ሰው
አልነበረም።

## ጎቶልያና ኢዮአስ

22፥10-23፥21ተጓ ምብ—2ዜና11፥1-21

10የአካዝያስ እናት ጎቶልያ ልጇዋ መሞቱን
ባየች ጊዜ፣ የይሁዳን ንጉሣውያን ቤተ
ሰብ በሙሉ አጠፋች፤ 11የንጉሥ ኢዮራም
ልጅ ዮሳቤት ግን፣ ከሚገደሉት መሳፍንት
መካከል ኢዮአስን ደብቃ ወሰደችው፣ ከሞ
ግዚቱም ጋር በእልፍኝ ሸሸገችው። የኢዮ
ራም ልጅ የካህኑ የዮዳሄ ሚስት ዮሳቤት፣
የአካዝያስ እኅት በመሆኗ፣ ሕፃኑን የደበ
ቀችው ጎቶልያ እንዳትገድለው ነበር።
12እርሱም ጎቶልያ ምድሪቱን በገዛችበት ጊዜ
ሁሉ፣ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
ተደብቆ ስድስት ዓመት አብሮአቸው
ኖረ።

23 በሰባተኛው ዓመት ዮዳሄ በረታ፤
የመቶ አለቆች ከሆኑት ከይሮሐም
ልጅ ከዓዛርያስ፣ ከይሆሐናን ልጅ ከይስ
ማኤል፣ ከዖቤድ ልጅ ከዓዛርያስ፣ ከዓዳያ
ልጅ ከማዕሤያ፣ ከዝክሪ ልጅ ከኤሊሳፋጥ ጋር
ቃል ኪዳን አደረገ።2እነርሱም ወደ መላው
ይሁዳ ሄደው፣ ሌዋውያንንና የእስራኤል
ቤት አለቆችን ከየከተማው ሁሉ ሰበሰቡ።
ወደ ኢየሩሳሌም በመጡ ጊዜም፣ 3ጉባኤው
ሁሉ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ ከንጉ
ሡ ጋር ቃል ኪዳን አደረጉ።
ዮዳሄም እንዲህ አላቸው፤ "*እግዚአብሔር*
ለዳዊት ዘር በሰጠው ተስፋ መሠረት እነሆ፣
የንጉሡ ልጅ ይነግሣል። 4እንግዲህ እናንተ
የምታደርጉት ይህ ነው፤ በሰንበት ዕለት
ተረኛ ከሆናችሁት ከእናንተ ከካህናቱና
ከሌዋውያኑ አንድ ሦስተኛው በሮቹን ጠብቁ፤
5አንድ ሦስተኛው ቤተ መንግሥቱን፣ አንድ
ሦስተኛው "የመሠረት ቅጽር በር" የተባለውን
ጠብቁ፤ የቀሩት ሰዎች በሙሉ *በእግዚ*
*አብሔር* ቤተ መቅደስ አደባባይ ይሁኑ።
6ተረኛ ከሆኑት ካህናትና ሌዋውያን በቀር
ማንም ሰው ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ መቅ
ደስ አይግባ፤ እነርሱ የተቀደሱ ስለሆኑ
ይግቡ፤ የቀሩት ሰዎች በሙሉ ግን፣ ወደ
ቤተ መቅደሱ እንዳይገቡ *እግዚአብሔር* ያዘ
ዘውን ይጠብቁ[ጣ]። 7ሌዋውያኑም የጦር
መሣሪያቸውን በእጃቸው ይዘው በንጉሡ
ዙሪያ ይቁሙ፤ ወደ ቤተ መቅደሱ
የሚገባ ማንኛውም ሰው ይገደል፤ ንጉሡ
በሚሄ ድበትም ቦታ ሁሉ አብረውት
ይሁኑ።"
8ሌዋውያኑና ይሁዳ ሁሉ ልክ ካህኑ ዮዳሄ
እንዳዘዘው አደረጉ፤ ካህኑ ዮዳሄ ከጥበቃ ክፍ
ሎች የትኛውንም አላሰናበተም ነበርና፣
እያንዳንዱ በሰንበት ቀን በሥራ ላይ የሚሰማሩ
ትንና ከሥራ የሚወጡትን የራሱን ሰዎች
ወሰደ፤ 9ከዚያም በቤተ መቅደሱ የነበሩትን
የንጉሥ ዳዊት ጦሮች፣ ታላላቅና ታናናሽ
ጋሻዎች ለመቶ አለቆቹ ሰጣቸው።

22፥1 2ዜና21፥16-17፤23፥20-21፤26፥1፤33፥25፤36፥1
22፥3 2ዜና18፥1፤21፥6
22፥5 2ዜና18፥11፥ 34
22፥6 1ነገ19፥15፤2ነገ8፥13-15
22፥7 2ነገ9፥16
22፥8 2ነገ10፥13
22፥9 መሳ9፥5፤2ዜና17፥4
23፥2 ዘኍ35፥2-5
23፥3 2ሳሙ7፥12፤1ነገ2፥4፤2ነገ11፥17፤2ዜና6፥16፤7፥18፤21፥7
23፥6 ዘካ3፥7
23፥8 2ነገ11፥9፤1ዜና24፥1

[፳]2 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናትና የሱርስቱ ቅጆች (እንዲሁም 2ነገ8፥26 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን ***አርባ አራት*** ይላል።
[ጣ]6 ወይም ***አይግባ የሚለውን የእግዚአብሔር ትእዛዝ ይጠብቁ***
[ገ]6 ጥቂት የዕብራይስጥ ቅጆች የሰብዓ ሊቃናት፣ የቩልጌትና የሱርስቱ ትርጉም (2ነገ8፥29) ከዚህ ጋር ይስማማሉ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ ***አዛርያ*** ይላሉ።

[10]ሰዎቹም ሁሉ እያንዳንዳቸው መሣሪያቸውን
በእጃቸው እንደ ያዙ ከቤተ መቅደሱ
ደቡብ አንሥቶ እስከ ሰሜን ድረስ በመ
ሠዊያውና በቤተ መቅደሱ አጠገብ በንጉሡ
ዙሪያ እንዲቆሙ አደረገ።
[11]ዮዳሄና ወንዶች ልጆቹ የንጉሡን ልጅ
አምጥተው ዘውድ ጫኑለት፤ የኪዳኑንም
መጽሐፍ ሰጥተውት አነገሡት፤
ቀብተውትም፣ "ንጉሡ ለዘላለም ይኑር!"
እያሉ ጮኹ።
[12]ጎቶልያም የሚሯሯጠውንና ደስታውን
ለንጉሡ የሚገልጠውን ሕዝብ ሁካታ ስትሰማ፣
ሕዝቡ ወዳለበት ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስ ሄደች። [13]ንጉሡ በመግቢያው
ላይ ባለው በዐምዱ አጠገብ ቆሞ አየች፣
የጦር መኰንኖችና መለከት ነፊዎችም በንጉሡ
አጠገቡ ነበሩ፤ የምድሪቱ ሕዝብ ሁሉ
ይደሰቱ፣ መለከትም ይነፉ ነበር፤ መዘምራ
ንም በዜማ ዕቃ ታጅበው የበዓሉን ዝማሬ
ይመሩ ነበር፤ ጎቶልያም ልብሷን ቀድዳ፣
ይህ ዐመፅ ነው! ይህ ዐመፅ ነው!" ብላ ጮኸች።
[14]ካህኑ ዮዳሄም የወታደር አዛዥ ወደ ሆኑት
ወደ መቶ አለቆቹ፣ "በሰልፉ መካከል
አውጥታችሁ አምጧት[ጨ]፤ የሚከተላት ካለም
በሰይፍ ግደሉት' ሲል ላከባቸው። ካህኑም፣
"*በእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ አትግደሏት"
ብሎ ነበርና። [15]እርሷም በቤተ መንግሥቱ ግቢ
የፈረስ መግቢያ በር ወደ ተባለው ቦታ
እንደ ደረሰች ያዟት፤ በዚያም ገደሏት።
[16]ዮዳሄም ራሱ፣ ሕዝቡና ንጉሡ *የእግዚ
አብሔር* ሕዝብ እንደሚሆኑ ቃል ኪዳን ገቡ[ጰ]።
[17]ከዚህ በኋላ ሕዝቡ በሙሉ ሄዶ የበአልን
ቤተ ጣዖት አፈረሰው፤ መሠዊያዎቹንና ጣዖ
ታቱን አደቀቀ፤ የበኣልን ካህን ማታንንም
በመሠዊያዎቹ ፊት ለፊት ገደሉት። [18]ዮዳሄ
በሙሴ ሕግ እንደተጻፈውና ዳዊትም እንዳዘዘው፣
በደስታና በመዝሙር የሚቃጠለውን *የእግዚ
አብሔርን* መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ዳዊት
ለመደባቸው ካህናትና ሌዋውያን *የእግዚአብሐ
ርን* ቤተ መቅደስ ኀላፊነት ሰጣቸው።
[19]እን ዲሁም በማንኛውም ነገር የረከሰ
ሰው እን ዳይገባ፣ በቤተ መቅደሱ ቅጥር
በሮች ላይ
ጠባቆች አቆመ። [20]የመቶ አለቆቹን፣ መኳ
ንንቱን፣ የሕዝቡን ገዦችና የአገሩን ሕዝብ
ሁሉ ይዞ ንጉሡን ከላይ ከቤተ መቅደሱ
ወደታች አመጣው። በላይኛውም መግቢያ
በኩል ወደ ቤተ መንግሥቱ ገብተው ንጉ
ሡን በመንግሥቱ ዙፋኑን ላይ አስቀመጡት።
[21]መላውም የአገሩ ሕዝብ ተደሰተ፤ ጎቶልያ
ስለ ተገደለችም ከተማዪቱ ሰላም አግኝታ
ነበር።

## ኢዮአስ ቤተ መቅደሱን ማደሱ

24፥1-14ጠተጓ ምብ 2ነገ —12፥1-16

24፥23-27ተጓ ምብ —2ነገ12፥17-21

24 ኢዮአስ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሰባት
ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀ
ምጦም አርባ ዓመት ገዛ። እናቱ ሳብያ
የተባለች የቤርሳቤህ ሴት ነበረች። [2]ካህኑ
ዮዳሄ በሕይወት በነበረበት ዘመን ሁሉ፣ ኢ
ዮ አስ *እግዚአብሔርን* ደስ የሚያሰኝ ነገር
አደረገ። [3]ዮዳሄ ሁለት ሚስቶች መረጠለት፤
ወንዶችና ሴቶች ልጆችም ወለደ።
[4]ከጥቂት ጊዜ በኋላ ኢዮአስ *የእግዚአብሔ
ርን* ቤተ መቅደስ ለማደስ ወሰነ። [5]ካህናቱ
ንና ሌዋውያኑን ሰብስቦም፣ "ወደ ይሁዳ
ከተ ሞች ሄዳችሁ የእግዚአብሔርን ቤተ
መቅደስ በየዓመቱ ለማደስ የሚሆን
ገንዘብ ከእስራኤል ሁሉ ሰብስቡ፤
ይህንንም አሁኑኑ አድ ርጉት" አላቸው
ሌዋውያኑ ግን ቸል አሉ።
[6]ስለዚህ ንጉሡ ሊቀ ካህኑን ዮዳሄን ጠርቶ፣
"*የእግዚአብሔር* ባሪያ ሙሴና የእስራኤል
ጉባኤ ለምስክሩ ድንኳን እንዲወጣ የወሰ
ኑትን ግብር ከይሁዳና ከኢየሩሳሌም እን
ዲያመጡ ሌዋውያኑን ያላተጋሃቸው ለምን
ድን ነው?" አለው።
[7]በዚህ ጊዜ የዚያች ክፉ የጎቶልያ ልጆች
የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ሰብረው በመ
ግባት የተቀደሱ ዕቃዎች እንኳ ሳይቀሩ፣
ለበኣል ጣዖታት አገልግሎት እንዲውሉ አድርገው
ነበር።
[8]በንጉሡም ትእዛዝ የገንዘብ መሰብሰቢ
ያ ሣጥን ሠርተው *በእግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስ መግቢያ በር አጠገብ በውጭ በኩል
አኖሩት። [9]ከዚህ በኋላ እስራኤል በምድረ
በዳ ሳሉ *የእግዚአብሔር* ባሪያ ሙሴ
ያዘዘውን ግብር ለእግዚአብሔር እንዲያመጡ
በይሁዳና በኢየሩሳሌም ዐዋጅ ተነገረ።
[10]ሹማምንቱ ሁሉ፣ ሕዝቡም ሁሉ ግብሩን
በደስታ አመጡ፤ እስኪሞላም ድረስ በሣጥኑ
ውስጥ ጨመሩ። [11]ሣጥኑ በሌዋውያኑ እጅ
ወደ ንጉሡ ሹማምንት በሚደርስበት
ጊዜ፣ እነርሱም በውስጡ ብዙ ገንዘብ
መኖሩን በሚያዩበት ጊዜ ሁሉ፣ የቤተ
መንግሥቱ ጸሓፊና የሊቀ ካህናቱ ሹም
ይመጡና ሣጥኑን አጋብተው ወደ ቦታው
ይመልሱት ነበር። ይህን በየ ቀኑ በ
ማድረግ እጅግ ብዙ ገንዘብ ሰበሰቡ። [12]ንጉ
ሡና ዮዳሄም *የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅ ደስ
ሥራ እንዲያሠሩ ለተመደቡት ሰዎች
ገንዘቡን አስረከቧቸው፤ እነርሱም *የእግዚአብሔ
ርን* ቤተ መቅደስ ለማደስ ድንጋይ ጠራቢ
ዎችንና ዐናጢዎችን እንዲሁም ቤተ መቅ
ደሱን ለመጠገን የብረትና የናስ ሠራተኞችን
ቀጠሩ።

23፥11 ዘጸ17፥18
23፥13 1ነገ1፥41፤ 7፥15
23፥15 ኤር31፥40
23፥16 ዜና29፥10፤ 34፥31፤ነህ9፥38
23፥17 ዘጸ13፥6-9
23፥18 1ዜና23፥6፡ 28-32፤25፥6
23፥19 1ዜና9፥22
23፥20 2ነገ15፥35
23፥21 2ዜና22፥1
24፥2 2ዜና25፥2፤ 26፥5
24፥5 ዘፀ30፥16፤ 1ዜና11፥1፤26፥20፤ ነህ10፥32-33፤ ማቴ17፥24
24፥6 ዘፀ38፥21
24፥10 ዘፀ25፥2፤ 1ዜና29፥3፡6፡9
24፥12 2ዜና34፥11

[ጨ]14 ወይም *ከቅጥሩ ውስጥ አውጥታችሁ አምጡአት* ተብሎ
[ጰ]16 ወይም *በእግዚአብሔር በሕዝቡና በንጉሡ መካከል የተደረገው ቃል ኪዳን* ....

[13]በሥራው ላይ የተሰማሩት ሰዎች ትጉሃን
ስለ ነበሩ፣ ሥራው በእጃቸው ተከናወነ፤ የእግዚ
አብሔርንም ቤተ መቅደስ ቀደም ሲል በነበ
ረው ዓይነት መሠረት አደሱት፤ አጠ
ናከሩትም። [14]ከጨረሱም በኋላ ቀሪውን
ገንዘብ ወደ ንጉሡና ወደ ዮዳሄ አመጡ፤
በገንዘቡም የእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ ዕቃዎች ማለትም ለአገልግሎትና
ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚ ውሉ ዕቃዎች
እንደዚሁም ጭልፋዎችና ሌሎች
የወርቅና የብር ዕቃዎችም ተሠሩ። ዮዳሄ
በሕይወት በነበረበት ዘመን ሁሉ በእግዚ
አብሔር ቤተ መቅደስ የሚቃጠል
መሥዋዕት ዘወትር ይቀርብ ነበር።
[15]ዮዳሄ ሸምግሎ ዕድሜ ከጠገበ በኋላ
በመቶ ሠላሳ ዓመቱ ሞተ። [16]እርሱም በእስራኤል
ውስጥ ለእግዚአብሔርና ለቤተ መቅደሱ
መልካም ሥር ቶአልና በዳዊት ከተማ
በነገሥታቱ መቃብር ተቀበረ።

## የኢዮአስ ክፋት

[17]ከዮዳሄ ሞት በኋላ የይሁዳ ሹማምንት
መጥተው ለንጉሡ ታማኝነታቸውን ገለጡ፤
ንጉሡም አዳመጣቸው። [18]እነርሱም የአባ
ቶቻቸውን አምላክ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ
ትተው፣ የአሼራን ዐምዶችና ጣዖታትን
አመለኩ፤ በበደላቸውም ምክንያት የእግዚ
አብሔር ቍጣ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ
መጣ። [19]ወደ እግዚአብሔር ይመልሷቸው ዘንድ
እርሱ ነቢያቱን ወደ ሕዝቡ ሰደደ፤ ነቢያቱም
መሰ ከሩባቸው፤ እነርሱ ግን አላዳመጠ
ዉም።
[20]የእግዚአብሔርም መንፈስ በካህኑ በዮዳሄ
ልጅ በዘካርያስ ላይ መጣ፤ እርሱም በሕዝቡ
ፊት ቆሞ፣ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለምን
ትተላለፋላችሁ? አይሳካላችሁም፤ እናንተ
እግዚአብሔርን ስለ ተዋችሁት እርሱም
ትቶአችኋል" አላቸው።
[21]እነርሱ ግን አሤሩበት፤ በንጉሡም ትእዛዝ
በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አደባባይ ላይ
በድንጋይ ወግረው ገደሉት።
[22]ንጉሥ ኢዮአስ የዘካርያስ አባት ዮዳሄ
ያደረገለትን ቸርነት አላሰበም፤ በዚህ ፈንታ
ልጁን ገደለው፤ በሚሞትበትም ጊዜ፣
"እግዚ አብሔር ይየው፤ እርሱው
ይበቀልህ" አለ።
[23]በዓመቱም መጨረሻ[ጸ]፣ የሶርያ ሰራዊት
በኢዮአስ ላይ ዘመተ፤ ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን
ወሮም የሕዝቡን መሪዎች ሁሉ ደመሰሰ፤
ምርኮው ንም ሁሉ ወደ ንጉሡ ወደ ደማስቆ ላከ።
[24]የሶርያ ሰራዊት ሰዎች ጥቂት ቢሆኑም እንኳ
እግዚአብሔር በጣም የሚበልጠውን ሰራ
ዊት በእጃቸው አሳልፎ ሰጠ፤ ይሁዳ
የአባቶቹን አምላክ እግዚአብሔርን ስለ ተወ፣ በኢ

24፥18 ዘፀ34፥13፤ ኢሱ24፥20፤ 2ዜና7፥19፤19፥2፤33፥3፤ኤር17፥2
24፥19 ዘኍ11፥29፤ ኤር7፥25፤ዘካ1፥4
24፥20 ዘኍ14፥41፤ ዘዳ31፥17፤ መሳ3፥10፤1ዜና12፥18፤ማቴ23፥35፤ ሉቃ11፥51
24፥21 ኢሱ7፥25፤ ኤር20፥2፤26፥21
24፥22 ዘፍ9፥5
24፥23 2ነገ12፥17-18
24፥24 ዘሌ26፥23-25፤ዘዳ28፥25፤2ዜና14፥9፤16፥8፤20፥2፥12
24፥25 2ዜና21፥20
24፥26 ሩት1፥4፤ 2ነገ12፥21
25፥2 1ነገ8፥61፤ 2ዜና24፥2
25፥4 ዘኍ26፥11፤ ዘዳ28፥61
25፥5 ዘፀ30፥14፤ 2ሳሙ24፥2፤1ዜና21፥1፤2ዜና17፥14-19
25፥7 2ዜና16፥2-9፤19፥1-3
25፥8 2ዜና14፥11፤ 20፥6
25፥9 ዘዳ8፥18፤ ምሳ10፥22

ዮአስ ላይ ተፈረደበት። [25]ሶርያውያንም በወጡ
ጊዜ ኢዮ አስን ክፉኛ አቍስለው፣
ጥለውት ሄዱ፤ የካህኑን የዮዳሄን ልጅ ስለ
ገደለም፣ ሹማ ምንቱ አሢረውበት በዐልጋው
ላይ እንዳለ ገደሉት። በዚህ ሁኔታም ሞቶ
በዳዊት ከተማ ተቀበረ እንጂ በነገሥታቱ
መቃብር አልተቀ በረም።
[26]በእርሱ ላይ ያሤሩትም የአሞናዊቱ የሰ
ምዓት ልጅ ዛባድና የሞዓባዊቱ የሰማሪት
ልጅ ዮዛባት ነበሩ። [27]የወንዶች ልጆቹ
ታሪክ፣ ስለ እርሱ የተነገሩት ብዙ ትንቢ
ቶችና የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መታደስ
በነገ ሥታቱ የታሪክ መዛግብት ተጽፈዋል።
ልጁ አሜስያስም በእርሱ ፈንታ ነገሠ።

## የይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ

25፥1-4 ተጓ ምብ —2ዜና14፥1-6
25፥11-12ተጓ ምብ —14፥7
25፥17-28ተጓ ምብ 2ዜና14፥8-20

25 አሜስያስ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው
ሃያ አምስት ዓመት ነበር፤ በኢየሩ
ሳሌም ተቀምጦም ሃያ ዘጠኝ ዓመት ገዛ።
እናቱም ዮዓዳን የተባለች የኢየሩሳሌም ሴት
ነበረች። [2]እርሱም በእግዚአብሔር ፊት መል
ካም ነገር አደረገ፤ ነገር ግን በፍጹም ልቡ
አልነበረም። [3]መንግሥቱን በቍጥጥር ሥር
ካጸና በኋላ፣ ንጉሥ የነበረውን አባቱን የገደ
ሉትን ሹማምንት በሞት ቀጣቸው። [4]እግዚአ
ብሔር በሙሴ መጽሐፍ በተጻፈው ሕግ "ሰው
ሁሉ በገዛ ኀጢአቱ ይሙት እንጂ ወላጆች ስለ
ልጆቻቸው አይገደሉ፤ ልጆችም ስለ
ወላጆቻቸው አይገደሉ"[ፀ] ብሎ ባዘዘው መሠረት
አደረገ እንጂ ልጆቻቸውን አልገደለም።
[5]አሜስያስ የይሁዳን ሕዝብ በአንድነት
ሰብስቦ፣ እንደየቤተሰቡ በሻለቆችና በመቶ
አለቆች በመደልደል በመላው ይሁዳና በብን
ያም መደባቸው። ከዚያም ዕድሜያቸው ሃያና
ከሃያ በላይ የሆናቸውን ሰብስቦ፣ ለውትድርና
አገልግሎት ብቁ ሆነው ጋሻና ጦር መያዝ
የሚችሉ ሦስት መቶ ሺህ ሰዎች አገኘ። [6]እንዲ
ሁም በመቶ መክሊት[ፊ] ጥሬ ብር አንድ መቶ
ሺህ ተዋጊዎች ከእስራኤል ቀጠረ።
[7]ነገር ግን አንድ የእግዚአብሔር ሰው ወደ
እርሱ መጥቶ እንዲህ አለው፤ "ንጉሥ ሆይ፤
እግዚአብሔር ከእስራኤልም ሆነ ከማናቸውም
የኤፍሬም ሕዝብ ጋር አይደለምና፣ እነዚህ
የእስራኤል ወታደሮች ከአንተ ጋር አይዝመቱ።
[8]ሄደህ ጦርነቱን በቈራጥነት ብትዋጋም እንኳ፣
የመርዳትና የመጣል ኀይል ከእግዚአብሔር
ዘንድ ስለ ሆነ እግዚአብሔር በጠላቶችህ ፊት
ይጥልሃል።"
[9]አሜስያስም የእግዚአብሔርን ሰው፣ "ታዲያ
ለእነዚህ ለእስራኤል ወታደሮች የከፈልኩት
መቶ መክሊት እንዴት ይሁን?" ሲል ጠየቀው

[ጸ]23 ምናልባት መስከረም፣ ጥቅምትና ኅዳር
[ፀ]4 ዘዳ 24፥16
[ፊ]6 በዚህና በቍጥር 9 ላይ 3.4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው

የእግዚአብሔርም ሰው፣ *“እግዚአብሔር* ከዚህ
አብልጦ ሊሰጥህ ይችላል” ሲል መለሰለት።
10ስለዚህ አሜስያስ ከኤፍሬም ወደ
እርሱ የመጡትን ወታደሮች ወደየመኖሪያ
ስፍራቸው አሰናበታቸው። እነርሱም በይሁዳ
ላይ ክፉኛ ተበሳጭተው ነበርና በታላቅ ቍጣ
ወደ መኖሪያ ስፍራቸው ተመለሱ።
11አሜስያስም ኃይሉን በሚገባ አደራጅቶ
ሰራዊቱን ወደ ጨው ሸለቆ መራ፤ በዚያም
ዐሥር ሺህ የሴይር ወታደሮችን ገደለ። 12የይሁዳ
ሰራዊት ሌሎች ዐሥር ሺህ ሰዎች ማረኩ፤
ወደ አንድ ዓለት ዐናት ላይም አውጥተው
ቍልቍል ለቀቁአቸው፤ ሁሉም ተፈጠፈጡ።

13በዚያኑ ጊዜ አሜስያስ ያሰናበታቸውና
በጦርነቱ እንዳይካፈሉ የከለከላቸው ወታደሮች፤
ከሰማርያ እስከ ቤትሖሮን ያሉትን የይሁዳ
ከተሞች ወረሩ፤ ሦስት ሺህ ሰው ገደሉ፤
እጅግ ብዙ ምርኮም ወሰዱ።
14አሜስያስም ኤዶማያውያንን ደምስሶ በተ
መለሰ ጊዜ፣ የሴይርን ሕዝብ አማልክት
ይዞ መጣ፤ ለራሱም አማልክት አድርጎ በማቆም
ሰገደላቸው፤ መሥዋዕትም አቀረበላቸው። 15*የእግዚ
አብሔርም* ቍጣ በአሜስያስ ላይ ነደደ፤ ነቢ
ይንም ላከበት፤ ነቢዩም፣ “የገዛ ሕዝባቸውን
ከእጅህ ማዳን ያልቻሉትን የአሕዛብን አማ
ልክት ርዳታ የጠየቅኸው ለምንድን ነው?”
አለው።
16እርሱም በመናገር ላይ ሳለ፣ ንጉሡ፣ “ለመሆኑ
አንተን የንጉሥ አማካሪ አድርገን ሾመነሃልን?
ዝም አትልም እንዴ! መሞት ትፈልጋለህ?”
አለው።
ነቢዩም ዝም አለ፤ ሆኖም፣ “ይህን አድር
ገሃልና ምክሬንም አልሰማህምና፤ እግዚአብሔር
ሊያጠፋህ እንደወሰነ ዐውቃለሁ” አለ።
17የይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ አማካሪዎቹን
ካማከረ በኋላ፣ የእስራኤል ንጉሥ የኢዩ የልጅ
ልጅ፣ የኢዮአካዝ ልጅ ወደ ሆነው ወደ
ኢዮአስ፣ “እስቲ ናና ፊት ለፊት እንጋጠም”
ሲል ላከበት።
18የእስራኤል ንጉሥ ኢዮአስ ግን፣ ለይሁዳ
ንጉሥ ለአሜስያስ እንዲህ ሲል መለሰለት፤
“አንድ የሊባኖስ ኵርንችት፣ ‘ሚስት እንድ
ትሆነው ሴት ልጅህን ለልጄ ስጠው’ ሲል
ወደ ሊባኖስ ዝግባ ላከበት። ከዚያም የዱር
አውሬ ከሊባኖስ ወጥቶ ኵርንችቱን ረገጠው።
19ኤዶምን አሸንፌአለሁ ብለህ ራስህን በትዕ
ቢት ክበኸዋል፤ ኮርተሃልም፤ ግን ዐርፈህ
እቤትህ ተቀመጥ! በራስህና በይሁዳ ላይ ውድቀት
ታመጣ ዘንድ ችግር የምትጠራው ስለ ምንድን
ነው?”
20የኤዶምን አማልክት ማምለክ በመፈ
ለጋቸው፣ እግዚአብሔር በጠላቶቻቸው እጅ

25፥10 ቍ13
25፥12 መዝ141፥6፤ አብ1፥3
25፥14 ዘፀ20፥3፤ 2ዜና28፥23፤ ኢሳ44፥15
25፥15 ኢሳ36፥20
25፥18 መሳ9፥8-15
25፥20 2ዜና10፥15
25፥23 2ነገ14፥13፤ 2ዜና26፥9፤ነህ8፥16፤12፥39፤ኤር31፥38
25፥24 1ዜና26፥15
25፥27 ኢሱ10፥3
26፥1 2ዜና22፥1
26፥5 2ዜና24፥2፤ 27፥6

አሳልፎ ሊሰጣቸው ወስኖአልና፣ አሜስያስ
አላዳመጣቸውም። 21ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ
ኢዮአስ አደጋ ጣለ። እርሱና የይሁዳ ንጉሥ
አሜስያስ በይሁዳ ውስጥ ቤትሳሚስ በተባለ
ስፍራ ፊት ለፊት ተጋጠሙ። 22ይሁዳ በእስ
ራኤል ክፉኛ ተመታ፤ እያንዳንዱም ሰው
ወደየመኖሪያው ሸሸ። 23የእስራስል ንጉሥ
ኢዮአስም የአካዝያስን የልጅ ልጅ የኢ
ዮአስን ልጅ አሜስያስን ቤትሳሚስ ላይ
ማርኮ ወደ ኢየሩሳሌም አመጣው፤ ከኤፍሬም
በር እስከ ማዕዘኑ በር ድረስ አንድ መቶ ሰማ
ንያ ሜትር[T] ያህል ርዝመት ያለውንም
የኢየሩሳሌምን ቅጥር አፈረሰ። 24እርሱም
በዖቤድኤዶም ጥበቃ ሥር የነበረውንና በቤተ
መቅደሱ የተገኘውን ወርቅ፣ ጥሬ ብርና ዕቃ
በሙሉ፣ ከቤተ መንግሥቱም ንብረትና በመያዣ
ከያዛቸው ሰዎች ጭምር ወስዶ ወደ ሰማ
ርያ ተመለሰ።
25የይሁዳ ንጉሥ የኢዮአስ ልጅ አሜስያስ፣
የእስራኤል ንጉሥ የኢዮአካዝ ልጅ ኢዮ
አስ ከሞተ በኋላ አሥራ አምስት ዓመት ኖረ።
26በአሜስያስ ዘመነ መንግሥት ከመጀመሪያው
እስከ መጨረሻው የተከናወነው ሌላው
ተግባር ሁሉ በይሁዳና በእስራኤል
ነገሥታት የተጻፈ አይደለምን? 27አሜ
ስያስ *እግዚአብሔርን* መከተል ከተወ
በኋላ፣ በኢየሩሳሌም ስላመፁበት ወደ ለኪሶ
ሸሸ፤ ነገር ግን የሚከታተሉትን ሰዎች
ከኋላው ልከው በዚያው በለኪሶ ገደሉት።
28በፈረስ ተጭኖ ከመጣ በኋላም፣ እንደ
አባቶቹ ሁሉ በይሁዳ ከተማ ተቀበረ።

### የይሁዳ ንጉሥ ዖዝያን

26፥1-4ተጓ ምብ —2ዜና14፥21-22፤15፥1-3
26፥1-23ተጓ ምብ —2ዜና15፥5-7

26 ከዚህ በኋላ የይሁዳ ሕዝብ በሙሉ
ዕድሜው ዐሥራ ስድስት ዓመት
የነበረውን ዖዝያንን ወስደው በአባቱ በአሜ
ስያስ ፈንታ አነገሡት። 2አሜስያስ እንደ
አባቶቹ ሁሉ ካንቀላፋ በኋላ፣ ኤላትን እንደገና
የሠራት፣ ወደ ይሁዳም የመለሳት ዖዝያን
ነበር።
3ዖዝያን በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ዐሥራ
ስድስት ዓመት ሲሆን፣ በኢየሩሳሌም ተቀምጦ[ሀ]
አምሳ ሁለት ዓመት ገዛ። እናቱ ይኮልያ
የተባለች የኢየሩሳሌም ሴት ነበረች። 4እርሱም
አባቱ አሜስያስ እንደ አደረገው ሁሉ
*በእግዚአብሔር* ፊት ቅን ነገር አደረገ።
5እግዚአብሔርን መፍራት ባስተማረው በዘካርያስ

[T]23 ዕብራይስጡ፣ *80 ሜትር ያህል ነው ይላል፤ አንዳንድ ቅጂዎች ግን ስድስት መቶ ጫማ ይላሉ።*
[ሀ]3 ብዙ የዕብራይስጥ ትርጉሞች፣ የሰብዓ ሊቃናትና የሱርስቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አንዳንድ የዕብራስጥ ቅጆች ግን *እንደ እግዚአብሔር ራእይ ባስተማረው*

ዘመን እግዚአብሔርን ፈለገ፤ እግዚአብሔርን
በፈለገ መጠንም አምላክ ነገሮችን
አከናወነለት፡፡
[6]በፍልስጥኤማውያን ላይ ዘምቶ የጌትን፣
የየብናንና የአዛጦንን ቅጥሮች አፈረሰ፡፡
ከዚያም በአዛጦን አጠገብና በቀሩትም
የፍልስጥኤም ግዛቶች ውስጥ ከተሞችን
እንደ ገና ሠራ። [7]እግዚአብሔርም በፍልስጥኤማ
ውያን፣ በጉርበኣል በሚኖሩ ዐረቦችና በምዑ
ናውያን ላይ ድልን አቀዳጀው፡፡ [8]አሞናውያን
ለዖዝያን ግብር ገበሩለት፤ ኀይሉ ስለ ገነነም
ዝናው እስከ ግብፅ ዳርቻ ወጣ፡፡
[9]ዖዝያንም በኢየሩሳሌም በማዕዘኑ በር፣
በሸለቆው በርና በቅጥሩ ማዕዘን ማማዎች ሠርቶ
መሸጋቸው፡፡ [10]እንዲሁም በየኰረብታው ግር
ጌና በየሜዳው ላይ ብዙ የቀንድ ከብት ስለ
ነበረው፣ በምድረ በዳ የግንብ ማማዎች ሠራ፤
ብዙ የውሃ ጕድጓዶችም ቈፈረ። ግብርና ይወ
ድድ ስለ ነበረም በኰረብታዎችና ለም በሆኑ
መሬቶች ላይ ዕርሻ የሚያርሱና ወይን የሚ
ተክሉ ሰራተኞች ነበሩት፡፡
[11]ዖዝያን ከንጉሡ ሹማምንት አንዱ በሆነው
በሐናንያ መሪነት፣ በጸሓፊው በይዒኤልና
በአለቃው በመዕሤያ አማካይነት ተሰብስቦ
በተቈጠረው መሠረት በየምድቡ ለጦርነት
ዝግጁ ሆኖ የሚወጣ፣ በሚገባ የሠለጠነ ሰራ
ዊት ነበረው፡፡ [12]በተዋጊዎቹ ላይ የተሾሙት
የየቤተሰቡ መሪዎች ጠቅላላ ቍጥር
ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ነበር። [13]በእነዚህም
የሚመራ ሦስት መቶ ሰባት ሺህ አምስት መቶ
ሰው ያለው ሰራዊት አለ፤ ይህም ንጉሡ
በጠላቶቹ ላይ በሚያደርገው ዘመቻ
ለመሰለፍ የሚበቃ ጠንካራ ኃይል ነበር፡፡
[14]ዖዝያን ለሰራዊቱ ሁሉ ጋሻ፣ ጦር፣ የራስ
ቁር፣ ጥሩር፣ የቀስት ማስፈንጠሪያ
ደጋንና የሚወነጨፍ ድንጋይ አደለ፡፡
[15]በኢየሩሳሌምም፣ ንድፎ ቻቸው በባለ
ሙያዎች የተዘጋጁ፣ በመጠበቂያ የግንብ
ማማዎችና በየማዕዘኑ መከላ ከያዎች ላይ
ፍላጻ የሚስፈነጠርባቸውንና ትል ልቅ
ድንጋዮች የሚወረወርባቸውን መሣሪያዎች አሠ
ራ፡፡ እስኪበረታም ድረስ በሚያስደንቅ ሁኔታ
ስለ ታገዘ፣ ዝናው በርቀትና በስፋት ተሰማ።
[16]ዖዝያን ከበረታ በኋላ ግን ዕብሪቱ ለውድ
ቀት ዳረገው፡፡ በዕጣን መሠዊያው ላይ ዕጣን
ለማጠን ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
በመግባቱ እግዚአብሔርን በደለ፤ [17]ካህኑም ዓዛር
ያስ ቈራጥ ከሆኑ ከሌሎች ሰማንያ የእግዚ
አብሔር ካህናት ጋር ተከትሎት ገባ። [18]እነ
ርሱም ፊት ለፊት በመጋፈጥ፣ “ዖዝያን ሆይ፤
ለእግዚአብሔር ማጠን ለተለዩትና የአሮን ዘሮች
ለሆኑት ለካህናቱ እንጂ ለአንተ የተገባ
አይደለም፤ እግዚአብሔርን በድለሃልና ከመ

26፥6 ኢሳ2፥6፤ 11፥14፤14፥29፤ኤር25፥20፤አሞ1፥8፤3፥9
26፥7 2ዜና20፥1፤ 21፥16
26፥8 ዘፍ19፥38
26፥9 2ነገ14፥13፤ 2ዜና25፥23፤ነህ2፥13፤ 3፥13
26፥14 ኤር46፥4
26፥16 ዘዳ32፥5፤ 2ነገ14፥10፤16፥12፤1ዘ ና5፥25
26፥17 1ነገ4፥2
26፥18 ዘፀ30፥7፤ ዘኍ16፥39፤18፥1-7፤1ዜና6፥49
26፥19 ዘኍ12፥10
26፥21 ዘፀ4፥6፤ ዘሌ13፥46፤14፥8፤ ዘኍ5፥2፤19፥12
26፥22 2ነገ15፥1፤ ኢሳ1፥1፤6፥1
26፥23 2ነገ14፥21፤ ኢሳ1፥1፤6፥1፤ አሞ1፥1
27፥1 2ነገ15፥5፡ 32፤1ዜና3፥12
27፥3 2ዜና33፥14፤ ነህ3፥26
27፥5 ዘፍ19፥38
27፥6 2ዜና26፥5

ቅደሱ ውጣ፤ ከእግዚአብሔር አምላክ ዘንድም
ክብር አይሆንልህምና” አሉት፡፡
[19]ጥና በእጁ ይዞ ዕጣን ለማጠን ዝግጁ
የነበረው ዖዝያን ተቈጣ፤ በእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ ውስጥ በዕጣን መሠዊያው ፊት ሆኖ
ካህናቱ ላይ እየተቈጣ ሳለ፣ በግንባሩ ላይ ለም
ጽ[ሰ] ወጣበት፡፡ [20]ሊቀካህናቱ ዓዛርያስና
ሌሎቹ ካህናት ሁሉ በተመለከቱት ጊዜ፣
በግንባሩ ላይ ለምጽ እንደ ወጣበት አዩ፡፡
ስለዚህ አጣድፈው አስወጡት፤ በእርግጥ
እርሱም ራሱ ለመውጣት ቸኵሎ ነበር፤
እግዚአብሔር አስጨንቆታልና፡፡
[21]ንጉሥ ዖዝያን እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ
ለምጻም ነበረ። ለምጻም በመሆኑም ከቤተ
መቅደስ ተወግዶ ነበርና በተለየ ቤት ተቀ
መጠ[ሐ]፡፡ ከዚያም ልጁ ኢዮአታም የቤተ መን
ግሥቱን አስተዳደር በኀላፊነት ተረክቦ የአገሩን
ሕዝብ ይመራ ጀመር፡፡
[22]በዖዝያን ዘመነ መንግሥት ከመጀመሪያው
እስከ መጨረሻው የተከናወነውን ሌላውን
ተግባር ሁሉ የአሞጽ ልጅ ነቢዩ ኢሳይያስ
ጽፎታል፡፡ [23]ዖዝያንም እንደ አባቶቹ ሁሉ
አንቀላፋ፡፡ ሕዝቡም “ለምጽ አለበት” ብለው
የነገሥታቱ በሆነው መቃብር አጠገብ ባለው
ቦታ ቀበሩት፤ ልጁም ኢዮአታም በእርሱ ፈንታ
ነገሠ፡፡

## የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአታም

27፥1-4፡7-9ተጓ ምብ —2ዜና15፥33-38

27 ኢዮአታም በነገሠ ጊዜ ዕድሜው
ሃያ አምስት ዓመት ሲሆን፣ በኢየሩ
ሳሌም ተቀምጦ ዐሥራ ስድስት ዓመት ገዛ፡፡
እናቱም ኢየሩሳ የተባለች የሳዶቅ ልጅ
ነበረች፡፡ [2]አባቱ ዖዝያን እንዳደረገው ሁሉ
በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገር አደረገ፤ ይሁን
እንጂ እንደ አባቱ ወደ እግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ አልገባም፡፡ ሕዝቡም በበደሉ እንደ
ገፉበት ነበር፡፡ [3]ኢዮአታም የእግዚአብሔርን
ቤተ መቅደስ የላይኛውን በር እንደገና ሠራው፤
በዖፌልም በኩል ባለው ቅጥር ላይ፣ አያሌ
የማሻሻል ተግባር አከናወነ፡፡ [4]በይሁዳ ኰረ
ብታዎች ላይ ከተሞችን፣ ደን በለበሱ ስፍ
ራዎችም ምሽጎችንና ማማዎችን ሠራ፡፡
[5]ኢዮአታም የአሞናውያንን ንጉሥ ወግቶ
ድል አደረጋቸው፡፡ በዚያ ዓመትም አሞና
ውያን አንድ መቶ መክሊት[መ] ጥሬ ብር፣ ዐሥር ሺ
ህ ቆሮስ[ሠ] ስንዴና ዐሥር ሺህ ቆሮስ ገብስ
ገበሩለት፡፡ አሞናውያን በሁለተኛውና በሦስ
ተኛው ዓመት ይህንኑ ግብር አመጡለት፡፡
[6]ኢዮአታም በአምላኩ በእግዚአብሔር ፊት
በታማኝነት ስለ ተመላለሰ፣ እየበረታ ሄደ፡፡

[ሰ]19 የዕብራይስጡ ቃል በዚህም ሆነ በቍጥር 20፡21 እና 23
ላይ ማንኛውንም ዐይነት የቈዳ በሽታ የሚያመልክት ነው፡፡
[ሐ]21 ወይም *ከኀላፊነቱ በሚርቅበት ቤት* ተብሎ መተርጐም ይቻላል።
[መ]5 3.4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው፡፡
[ሠ]5 2, 200 ኪሎ ሊትር ያህል ነው፡፡

7በኢዮአታም ዘመነ መንግሥት የተከናወነው
ሌላው ተግባር፣ ያደረጋቸው ጦርነቶችና የ
ሠራቸው ነገሮች በሙሉ በእስራኤልና
በይሁዳነገሥታት መጽሐፍ ተጽፎአል።
8እርሱም በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሃያ አምስት ዓ
መት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም ዐሥራ
ስድስት ዓመት ገዛ። 9ኢዮአታም እንደ አባቶቹ
ሁሉ አንቀላፋ፤ በዳዊት ከተማ ተቀበረ፤ ልጁ
አካዝም በእርሱ ፈንታ ነገሠ።

## የይሁዳ ንጉሥ አካዝ

28፥1-27ተጓ ምብ 2ዜና16፥10-20

28 አካዝ መንገሥ በጀመረ ጊዜ ዕድሜው
ሃያ ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀም
ጦም ዐሥራ ስድስት ዓመት ገዛ። እርሱም *በእግ
ዚአብሔር* ፊት ቅን ነገር አንዳደረገው እንደ
አባቱ እንደ ዳዊት አላደረገም። 2በእስራ
ኤል ነገሥታት መንገድ ሄደ፤ በኣሊምን
ለማምለክም የተቀረጹ ጣዖታትን ሠራ። 3*እግዚ
አብሔር* ከእስራኤላውያን ፊት ያሰወገዳ
ቸውን አሕዛብ ልማድ በመከተል፣ በሄኖም
ልጅ ሸለቆ ዐጠነ፤ ወንዶች ልጆቹንም የሚቃጠል
መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ። 4በኰረብታ መስ
ገጃዎችና በተራሮች አናት ላይ፣ በየዛፉም
ጥላ ሥር መሥዋዕት አቀረበ፤ ዕጣንም ዐጠነ።
5ስለዚህ *አምላኩ* እግዚአብሔር ለሶርያ ንጉሥ
አሳልፎ ሰጠው፤ ሶርያውያንም ድል አደረጉት፤
ከሕዝቡም ብዙዎቹን ምርኮኞች አድርገው
ወደ ደማስቆ ወሰዷቸው።
ደግሞም ለእስራኤል ንጉሥ አልፎ ተሰጠ
፤ እርሱም ከባድ ጉዳት አደረሰበት።
6ይሁዳ የአባቶቹን *አምላክ* እግዚአብሔርን
ስለ ተወ፣ የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ በአንድ
ቀን ከይሁዳ መቶ ሃያ ሺህ ወታደሮች
ገደለ። 7ጠረኛው ኤፍሬማዊ ዝክሪም የንጉ
ሡን ልጅ መዕሤ ያን፣ የቤተ መንግሥቱ
ኀላፊ የሆነውን
ዓዝሪቃምንና ለንጉሡ በማዕረግ ሁለተኛ
ሰው የሆነውን ሕልቃናን ገደለ። 8እስራኤላ
ውያንም ከገዛ ወገኖቻቸው ሁለት መቶ ሺ
ባለ ትዳር ሴቶችን፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆችን
ማረኩ፤ እንዲሁም እጅግ ብዙ ምርኮ ይዘው
ወደ ሰማርያ ተመለሱ።
9*ዖዴድ* የተባለ *የእግዚአብሔር* ነቢይ በዚ
ያ ስለ ነበር፣ ሰራዊቱ ወደ ሰማርያ በተመለሰ
ጊዜ ለመቀበል ወጣ፤ እንዲህም አላቸው፤
"የአባቶ ቻችሁ *አምላክ* እግዚአብሔር ይሁዳን
ስለ ተቈጣ በእጃችሁ አሳልፎ ሰጣችሁ፤ እናንተ
ግን እስከ ሰማይ በሚደርስ ቍጣ ፈጃችኋቸው።
10አሁንም የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ወንዶችና
ሴቶች፣ ባሪያዎቻችሁ ልታደርጓቸው
ትፈልጋላችሁ፤ እናን ተስ ብትሆኑ ኀጢአት
ሠርታችሁ *አምላካችሁን* እግዚአብሔርን
አልበደላችሁምን? 11እንግዲህ ስሙኝ፤ *የእግዚ
አብሔር* አስፈሪ ቍጣ በእናንተ ላይ
ነዶአልና፣ በምርኮ ያመጣችኋቸውን ወገኖቻችሁን
መልሷቸው።"
12ከዚያም ከኤፍሬም መሪዎች ጥቂቶቹ
የዮሐናን ልጅ ዓዛርያስ፣ የምሺሌሞት ልጅ
በራክያ፣ የሰሎም ልጅ ይሒዝቅያ፣ የሐድላይ
ልጅ ዓሜሳይ ከጦርነቱ የተመለሱትን በመ
ቃወም፣ 13"እነዚህን ምርኮኞች እዚህ ማምጣት
አልነበረባችሁም፤ ያለዚያ እኛ *በእግዚአብሔር*
ፊት በደለኞች እንሆናለን፤ በኀጢአታችንና
በበደላችን ላይ ሌላ ልትጨምሩ ታስባላችሁን?
በደላችንማ ቀድሞውኑ በዝቶአል፤ ቍጣውም
በእስራኤል ላይ ነውና" አሉ።
14ስለዚህ ወታደሮቹ በሹማምንቱና በጉ
ባኤው ሁሉ ፊት ምርኮኞቹን ለቀቁ፤ የተ
ማረከውንም ዕቃ መለሱ። 15በስም የተጠቀሱ
ሰዎችም ምርኮኞቹን ተረክበው ዕራቁታቸውን
ለቀሩት ሁሉ ከምርኮው አለበሷቸው፤ ልብስና
ጫማ፣ ምግብና መጠጥ ሰጧቸው፣ በቅባትም
ቀቧቸው፤ የደከሙትንም ሁሉ በአህያ ላይ አስቀ
መጧቸው። ከዚያም ወገኖቻቸው ወደሚገ
ኙባት የዘንባባ ከተማ ተብላ ወደምትጠራው
ወደ ኢያሪኮ ወስደዋቸው፣ ወደ ሰማርያ ተመ
ለሱ።
16በዚያን ጊዜ ንጉሡ አካዝ ወደ አሦር
ንጉሥ ልኮ ርዳታ ጠየቀ፤ 17ኤዶማውያን እንደ
ገና መጥተው በይሁዳ ላይ አደጋ በመጣል
ምርኮኞችን ወስደው ነበርና። 18ፍልስጥኤማውያን
ደግሞ በየኰረብታው ግርጌና በይሁዳ ደቡብ
ያሉትን ከተሞች በመውረር ቤት ሳሚስን፣
ኤሎንን፣ ግዴሮትን፣ ሦኮን፣ ተምናን፣ ጊምዞ
ንና በአካባቢአቸው የሚገኙትን መንደሮች ሁሉ
ያዙ፤ ተቀመጡባቸውም። 19የእስራኤል[ሰ]
ንጉሥ አካዝ ክፉትን በይሁዳ ምድር
ስላስፋፋና *ለእግዚአብሔርም* የነበረውን ታ
ማኝነት በከ ፍተኛ ደረጃ ስላጓደለ፣ *እግዚ
አብሔር* ይሁዳን አዋረደ። 20የአሦር ንጉሥ
ቴልጌልቴልፌልሶር ወደ እርሱ መጥቶ ነበር፤
ሆኖም ችግር ፈጠረበት እንጂ አልረዳውጠ
ም። 21አካዝ *ከእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ፣
ከቤተ መንግሥቱና ከመሳፍንቱ
ጥቂት ዕቃዎች ወስዶ ለአሦር ንጉሥ ሰጥቶ
ነበር፤ ይህም አልረዳው።
22ንጉሥ አካዝ በተጨነቀ ጊዜም፣ *ለእግ
ዚአብሔር* የነበረውን ታማኝነቱን ከምን ጊዜ
ውም ይበልጥ አጓደለ፤ 23እርሱም "የሶርያ
ነገሥታት አማልክት እነርሱን ስለ ረዷቸው፣
እኔንም ይረዱኝ ዘንድ እሠዋላቸዋለሁ" ሲል
እርሱን ላሸነፉት የደማስቆ አማልክት መሥዋዕት
አቀረበ።

28፥1 1ዜና3፥13፤ ኢሳ1፥1
28፥2 ዘፀ34፥17
28፥3 ዘሌ18፥21፤ ዘዳ18፥9፤ኢሱ15፥8፤ 2ነገ3፥27፤2ዜና33፥2፤ ሕዝ20፥26
28፥5 ኢሳ7፥1
28፥6 ቀኍ8፤ 2ነገ15፥25፡27፤ ኢሳ9፥21፤11፥13
28፥8 ዘዳ28፥25-41፤2ዜና29፥9
28፥9 ዕዝ9፥6፤ ኢሳ10፥6፤ 47፥6፤ዘካ1፥15፤ ራእ18፥5
28፥10 ዘሌ25፥39-46
28፥11 2ዜና11፥4
28፥15 ዘዳ34፥3፤ መሳ1፥16፤2ነገ6፥22፤ ምሳ25፥21-22፤ሉቃ10፥25-37
28፥16 2ነገ16፥7፤ ሕዝ23፥12
28፥17 2ዜና29፥9፤ መዝ137፥7፤ ኢሳ34፥5፤ 63፥1፤ ኤር25፥21፤ ሕዝ16፥57፤ 25፥12፤ አሞ1፥11
28፥18 ዘፍ38፥12፤ ኢሱ10፥12፤ 15፥41፤1ሳሙ17፥1፤አ ሳ9፥12፤11፥14፤ ኤር25፥20፤ ሕዝ 16፥27፡ 57፤25፥15
28፥19 1ዜና5፥25
28፥20 2ነገ15፥29፤ 16፥7፤1ዜና5፥6፤ ኢሳ7፥17፤8፥7፤10፥5-6 ፡20፤36፥1
28፥21 2ዜና16፥2-9፤ኤር2፥36
28፥22 ኤር5፥3፤ 15፥7፤17፥23
28፥23 1ዜና11፥1፤ 2ዜና25፥14፤ ኢሳ10፥20፤ ኤር18፥5፤44፥17-18
28፥24 2ነገ16፥18፤

ʻ16 አንድ የዕብራይስጥ ቅጅ፣ የሰብዓ ሊቃናትና የሱርስቱ ቅጅ እንዲሁም (2ነገ16፥7) ከዚህ ጋር ይስማማል፤ አብዛኞቹ የዕብ ራይስጥ ትርጒሞች ግን ነገሥታት ይላሉ።
[ሰ]19 በዜና ካልዕ መጽሐፍ ተደጋግሞ እንደተጠቀሰው ይህ ይሁዳ ነው።

24አካዝ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ዕቃዎች ሁሉ አንድ ላይ ሰብስቦ ወሰደ[ሸ]፤ *የእግዚአብሔ ርን* ቤተ መቅደስ በሮች ዘጋ፤ በኢየሩሳሌምም በየአውራ ጎዳናው ማዕዘን ላይ መሠዊያ አቆመ። 25በይሁዳ ከተሞች ሁሉ ለሌሎች አማልክት መሥዋዕት የሚያቃጥልባቸውን የኰረብታ መስገጃዎች ሠራ፤ በዚህም የአባቶቹን *አምላክ* እግዚአብሔርን ለቍጣ አነሣሣው።

26በአካዝ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው ሌላው ተግባርና አካሄዱ ሁሉ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው በይሁዳና በእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ ተጽፎአል። 27አካዝ እንደ አባቶቹ ሁሉ አንቀላፋ፤ በኢየሩሳሌምም ከተማ ተቀበረ፤ የተቀበረው ግን በእስራኤል ነገሥታት መካነ መቃብር አልነበረም። ልጁ ሕዝቅያስም በእርሱ ፈንታ ነገሠ።

## ሕዝቅያስ ቤተ መቅደሱን አነጻ

29፥1-2 ተጓ ምብ —1ዜና18፥2-3

29 ሕዝቅያስ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሃያ አምስት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም ሃያ ዘጠኝ ዓመት ገዛ። እናቱም አቡ የተባለች፤ የዘካርያስ ልጅ ነበረች። 2አባቱ ዳዊት እንዳደረገው ሁሉ፣ እርሱም *በእግዚአብሔር* ፊት ቅን ነገር አደረገ።

3በዘመነ መንግሥቱ በመጀመሪያው ዓመት፣ በመጀመሪያው ወር *የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስ በሮች ከፈተ፤ አደሳቸው። 4ካህናቱንና ሌዋውያኑን አስገብቶ በምሥራቅ በኩል ባለው አደባባይ ላይ በመሰብሰብ፣ 5እንዲህ አላቸው፤ ‘እናንተ ሌዋውያን፤ ስሙኝ! ራሳችሁን አሁኑኑ ቀድሱ፤ የአባቶቻችሁን *አምላክ* የእግዚአብሔርንም ቤተ መቅደስ ቀድሱ። ርኩስ ነገርንም ሁሉ ከመቅደሱ አስወግዱ። 6አባቶቻችን ታማኞች አልነበሩም፣ *በአምላካችን* በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸሙ፤ ተውትም። *ከእግዚአብሔር* ማደሪያ ፊታቸውን መለሱ፤ ጀርባቸውንም አዞሩበት። 7የሰበሰቡንም በሮች ዘጉ፤ መብራቶቹንም አጠፉ። ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ዕጣን አላጠኑም፤ በመቅደሱም የሚቃጠል መሥዋዕት አላቀረቡም። 8ስለዚህ *የእግዚአብሔር* ቍጣ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ ወርዶአል፤ እናንተ በገዛ ዓይናችሁ እንደ ምታዩት ለድንጋጤ፣ ለመደነቂያና ለመዘበቻ አሳልፎ ሰጣቸው። 9በዚህ ምክንያት አባቶ ቻችን በሰይፍ ወደቁ፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችን፣ ሚስቶቻችንም ተማረኩ። 10አሁንም አስፈሪ ቍጣው ከእኛ እንዲመለስ፣ ከእስራኤል *አምላክ* ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ለመግባት አስቤአለሁ። 11ልጆቼ ሆይ፤ እንግዲህ ቸል አትበሉ፤ በፊቱ እንድትቆሙና እንድ ታገለግሉት፣ በፊቱም አገልጋዮቹ እንድት ሆኑና ዕጣን እንድ ታጥኑለት *እግዚአብሔር* መርጦአችኋልና።”

12ከዚያም እነዚሁ ሌዋውያን በሥራው ላይ ተሰማሩ፤ ከቀዓት ዘሮች የአማሢ ልጅ መሐትና የዓዛርያስ ልጅ ኢዮኤል፤
ከሜራሪ ዘሮች፣
የአብዲ ልጅ ቂስና የይሃሌልኤል
ልጅ ዓዛርያስ፤
ከጌድሶን ዘሮች፣
የዛማት ልጅ ዮአክና የዮአክ ልጅ ዔድን፤
13ከኤሊጻፉን ዘሮች፣
ሺምሪና ይዒኤል፤
ከአሳፍ ዘሮች፣
ዘካርያስና መታንያ፤
14ከኤማን ዘሮች፣
ይሒኤልና ሰሜኢ፣
ከኤዶታም ዘሮች፣
ሸማያና ዑዝኤል።

15ወንድሞቻቸውን ከሰበሰቡና ራሳቸውን ከቀደሱ በኋላ፣ ንጉሡ *የእግዚአብሔርን* ቃል ተከትሎ ባዘዘው መሠረት *የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስ ለማንጻት ገቡ። 16ካህናቱ *የእግዚ አብሔርን* መቅደስ ለማንጻት ወደ ውስጡ ገቡ። *በእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ውስጥ ያገኙ ትንም ማናቸውንም የረከሰ ነገር ወደ *እግዚ አብሔር* ቤተ መቅደስ አደባባይ አወጡት። ሌዋውያኑም ተሸክመው በመውሰድ በቄድሮን ሸለቆ ውስጥ ጣሉት። 17ማንጻቱንም በመጀመ ሪያው ወር፣ በመጀመሪያው ቀን ጀምረው በዚያኑ ወር በስምንተኛው ቀን እስከ መቅደስ ሰበሰብ ደረሱ፤ በሚቀጥሉትም ስምንት ቀናት *የእግ ዚአብሔርን* ቤተ መቅደስ ቀደሱ፤ የመቀደሱም ሥራ በመጀመሪያው ወር በዐሥራ ስድስተኛው ቀን ተጠናቀቀ።

18ከዚያም ወደ ንጉሡ ወደ ሕዝቅያስ ገብተው እንዲህ አሉ፤ “*የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስ በሙሉ፣ የሚቃጠል መሥዋዕት የሚቀርብበትን መሠዊያ ከዕቃዎቹ ሁሉ፣ ገጸ ኅብስቱ የሚቀ መጥበትን ጠረጴዛ፣ ከነዕቃዎቹ አንጽተናል። 19ንጉሥ አካዝ ነግሦ ሳለ ታማኝነቱን ትቶ፣ ከቦታቸው ያነሣቸውን ዕቃዎች ሁሉ አዘጋጅተን ቀድሰናቸዋል፤ እነሆ፤ ዕቃዎቹ *በእግዚአ ብሔር* ቤተ መቅደስ መሠዊያ ፊት ለፊት ናቸው።”

20በማግስቱም ጧት በማለዳ፣ ንጉሥ ሕዝቅያስ የከተማዪቱን ሹማምንት በአንድነት ሰብስቦ፣ ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ወጣ፤ 21እነርሱም ስለ መንግሥቱ፣ ስለ መቅደሱና ስለ ይሁዳ ሰባት ወይፈኖች፣ ሰባት አውራ በጎች፣ ሰባት ተባዕት የበግ ጠቦቶችና ሰባት ተባዕት የፍየል ጠቦቶች ለኀጢአት መሥዋዕት አቀረቧቸው፤ ንጉሡም እነዚህን *በእግዚአብሔር* መሠዊያ ላይ እንዲያቀርቡ የአሮንን ዘሮች ካህናቱን አዘዘ።

2ዜና29፥19፤30፥14፤ ሚል1፥10
28፥27 2ዜና21፥20፤ ኢሳ14፥28-32
29፥1 1ዜና3፥13
29፥2 2ዜና34፥2
29፥3 2ነገ18፥16
29፥5 ዘሌ11፥44፤ ነህ13፥9
29፥6 1ዜና5፥25፤ ዕዝ9፥7፤መዝ106፥6-47፤ኤር2፥27፤18፥17፤ ሕዝ23፥35፤ዳን9፥5-6
29፥7 ዘፀ30፥7
29፥8 ዘሌ26፥32፤ ዘዳ28፥25፤ኤር18፥16፤19፥8፤25፥9፡18
29፥9 2ዜና28፥5-8፡17
29፥10 ዘኍ25፥4፤ 2ነገ11፥17፤2ዜና23፥16፤30፥8፤ዕዝ10፥14
29፥11 ዘኍ3፥6፤ 8፥6፡14፤1ዜና15፥2
29፥12 ዘኍ3፥17-20፤2ዜና31፥15
29፥13 ዘፀ6፥22፤ 1ዜና6፥39
29፥15 1ዜና23፥28፤ ኢሳ1፥25
29፥16 2ሳሙ15፥23
29፥19 2ዜና28፥24
29፥21 ዘሌ4፥13-14፤ዕዝ6፥17፤8፥35

[ሸ]24 ወይም *ሰበረ* ተብሎ መተርጐም ይቻላል።

22ካህናቱም ወይፈኖቹን ዐርደው ደሙን በመ
ውሰድ በመሠዊያው ላይ ረጩት፤ አውራ በጎ
ቹንም ዐርደው ደሙን በመሠዊያው ላይ
ረጩት፤ እንደዚሁም ጠቦቶቹን ዐርደው
ደሙን በመሠዊያው ላይ ረጩት። 23ለኀጢአት
መሥዋዕት የሚሆኑትን ፍየሎች በንጉሡና
በጉባኤው ፊት አቀረቡ፤ እነርሱም እጆ
ቻቸውን ጫኑባቸው፡፡ 24ንጉሡ የሚቃጠል
መሥዋዕትና የኀጢአት መሥዋዕት ስለ እስ
ራኤል ሁሉ እንዲቀርብ አዞ ስለ ነበር፣
ካህናቱ ፍየሎቹን ዐርደው ስለ እስራኤል
ሁሉ ማስተስረያ እንዲሆን የኀጢአት መሥዋዕት
በማድረግ ደሙን በመሠዊያው ላይ አቀረቡ፡፡
25ንጉሥ ሕዝቅያስም በዳዊት፣ በንጉሡ
ባለ ራእይ በጋድና በነቢዩ በናታን በተሰጠ
ው መመሪያ መሠረት ሌዋውያኑን ጸና
ጽል፣ በገናና መሰንቆ አስይዞ በእግዚአብሐ
ር ቤተ መቅደስ መደባቸው፤ ይህም በነቢ
ያት አማካ ይነት ከእግዚአብሔር የተሰጠ
ትእዛዝ ነበር። 26ስለዚህ ሌዋውያኑ የዳዊትን
የዜማ ዕቃዎች፣ ካህናቱም መለከቶቻቸውን
ይዘው ዝግጁ በመሆን ቆሙ፡፡
27ከዚህ በኋላ ሕዝቅያስ የሚቃጠለው መሥ
ዋዕት በመሠዊያው ላይ እንዲቀርብ አዘዘ።
መሥዋዕቱ ማረግ በጀመረ ጊዜም፣ በእስራ
ኤል ንጉሥ በዳዊት የዜማ ዕቃዎችና በመለከት
የታጀበ ዝማሬም ጀመረ፡፡ 28መዘምራኑ
በሚዘምሩበትና መለከተኞቹም በሚነፉበት
ጊዜም መላው ጉባኤ አጎንብሰው ሰገዱ፤
የሚቃጠለው መሥዋዕት እስኪጠናቀቅ ድረ
ስም ይህ ሁሉ ቀጠለ፡፡
29መሥዋዕቱ ሁሉ ቀርቦ ካበቃ በኋላ፣
ንጉሡና አብረውት የነበሩት ሁሉ ተንበ
ርክከው ሰገዱ፡፡ 30ንጉሥ ሕዝቅያስና ሹማ
ምንቱ፣ ሌዋውያኑ በዳዊትና በባለ ራእዩ
በአሳፍ ቃል እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ
አዘዙ፡፡ እነርሱም ውዳሴውን በደስታ ዘመሩ፤
ራሳቸውንም አጎንብሰው ሰገዱ፡፡
31ከዚያም ሕዝቅያስ፣ “እነሆ፤ ራሳችሁን
ለእግዚአብሔር ቀድሳችኋል፤ አሁንም ቅረቡ፤
መሥዋዕትና የምስጋና ስጦታ ወደ እግዚ
አብሔር ቤተ መቅደስ አምጡ” አላቸው፡፡
ስለዚህ ጉባኤው መሥዋዕትና የምስጋና ስጦታ
አመጡ፤ ልባቸው የፈቀደ ሁሉም የሚቃጠ
ል መሥዋዕት አመጡ፡፡
32ጉባኤውም ያመጣው የሚቃጠለው መሥ
ዋዕት ብዛት ሰባ ወይፈኖች፣ መቶ አውራ
በጎችና ሁለት መቶ ተባዕት የበግ ጠቦቶች
ናቸው፤ ሁሉም የሚቃጠል መሥዋዕት ሆነው
ለእግዚአብሔር የሚቀርቡ ነበሩ፡፡ 33ለመሥዋዕት
የተቀደሱት እንስሳት ባጠቃላይ ስድስት
መቶ ወይፈን፣ ሦስት ሺህ በጎችና ፍየሎች
ነበሩ፡፡ 34ይሁን እንጂ ካህናቱ የሚቃጠለውን
መሥዋዕት ቈዳ ሁሉ ለመገፈፍ ቍጥራቸው

29፥22 ዘሌ4፥18፤ ዘኍ18፥17
29፥23 ዘሌ4፥15፤ 16፥5
29፥24 ዘፀ29፥36፤ ዘሌ4፥26፤1ዜና11፥1፤ ዕዝ8፥35
29፥25 1ሳሙ 22፥5፤ 1ዜና25፥6፤ 28፥19
29፥26 1ዜና15፥ 16፥24
29፥27 1ሳሙ16፥16
29፥28 2ዜና2፥4
29፥29 2ዜና20፥18
29፥31 ዘፀ25፥2፤ 35፥22፤ ዕብ13፥15-16
29፥32 ዘሌ1፥1-17
29፥34 2ዜና30፥3፡ 15፤ሕዝ44፥11
29፥35 ዘፍ4፥4፤ 35፥14፤ዘፀ29፥13፤ ዘሌ7፥11-21
29፥36 2ዜና35፥8
30፥1 ዘፍ41፥52፤ ዘፀ12፥11፤ ዘኍ28፥16፤1ዜና9፥1
30፥2 ዘኍ9፥10
30፥3 ዘኍ9፥6-13፤2ዜና29፥34
30፥5 መሳ20፥1
30፥7 ዘዳ28፥25፤ 1ዜና5፥25፤መዝ78፥8፡ 57፤106፥6፤ ኤር11፥10፤ ሕዝ20፥18
30፥8 ዘፀ32፥9፤ ዘኍ25፥4፤ 2ዜና29፥10
30፥9 ዘፀ3፥21፤ 22፥27፤ዘዳ4፥31፤ 30፥2-5፤ 1ነገ8፥ 50፤2ዜና6፥39፤ ኢሳ1፥16፤55፥7፤ ኤር25፥5፤ ሕዝ33፥11፤ ሚክ7፥18

እጅግ ጥቂት ነበር፤ ስለዚህ ወገኖቻቸው
የሆኑት ሌዋውያን ሥራው እስኪያልቅና
ሌሎች ካህናት እስኪቀደሱ ድረስ ረዷቸው፤
ሌዋው ያኑም ራሳቸውን ለመቀደስ ከካህናቱ
ይልቅ
ጠንቃቆች ነበሩና፡፡ 35ከሚቃጠለው መሥዋዕ
ት ጋር የሚቀርበውን የኅብረት መሥዋዕት*
ስብና የመጠጡን ቍርባን ጨምሮ የሚ
ቃጠለው መሥዋዕት እጅግ ብዙ ነበር። በዚህ
ሁኔታም የእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት
እንደገና ተደራጀ፡፡ 36ሕዝቅያስና ሕዝቡ
ነገሩ ሁሉ እንዲህ በተፋጠነ ሁኔታ እንዲ
ከናወን እግዚአብሔር ስለረዳቸው ሐሴት
አደረጉ፡፡

## ሕዝቅያስ ፋሲካን ማክበሩ

30 ሕዝቅያስ የእስራኤልን አምላክ የእግ
ዚአብሔርን ፋሲካ ለማክበር በኢየሩ
ሳሌም ወዳለው ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
እንዲመጡ፣ ለመላው እስራኤልና ለይሁዳ
መልእክት ላከ፤ ለኤፍሬምና ለምናሴም ደብዳቤ
ጻፈ፡፡ 2ንጉሡ፣ ሹማምንቱና መላው የኢየሩሳ
ሌም ጉባኤ የፋሲካውን በዓል በሁለተኛው ወር
ለማክበር ተስማሙ፡፡ 3በቂ ካህናት ራሳቸውን
ስላልቀደሱና ሕዝቡም ገና በኢየሩሳሌም
ስላልተሰበሰቡ፣ በዓሉን በወቅቱ ለማክበር
አልቻሉም ነበር፡፡ 4ንጉሡና መላው ጉባኤም
ዕቅዱ ትክክል ሆኖ አገኙት፡፡ 5ስለዚህ
የእስራኤልን አምላክ የእግዚአብሔን ፋሲካ ለ
ማ ክበር ሕዝቡ እንዲመጣ፣ ከቤርሳቤህ እስከ
ዳን ድረስ ዐዋጅ እንዲነገር ወሰኑ፤
በተጻፈው መሠረት በዓሉ ብዛት ባለው ሕ
ዝብ ተከብሮ አያውቅም ነበርና፡፡
6መልእክተኞችም በንጉሡ ትእዛዝ፣ የንጉ
ሡንና የሹማምንቱን ደብዳቤ ይዘው ወደ
እስራኤልና ወደ ይሁዳ ሁሉ ሄዱ፤ ደብ
ዳቤውም እንዲህ የሚል ነበር፤
“የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፤ እርሱ ወደ
ተረፋችሁት፣ ከአሦር ነገሥታትም እጅ
ወዳመለጣችሁት ወደ እናንተ እንዲመለስ፣
እናንተም የአብርሃም፣ የይስሐቅና የእስ
ራኤል አምላክ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር
ተመለሱ፡፡ 7እንደምታዩት ሁሉ መሣለቂያ
እንስኪያደርጋቸው ድረስ፣ ለአባቶቻቸው
አምላክ ለእግዚአብሔር እንዳልታመኑ እንደ
አባቶቻችሁና እንደ ወንድሞቻችሁ አትሁኑ፡፡
8እንደ አባቶቻችሁም አንገተ ደንዳኖች አትሁኑ፤
ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ እርሱ ለዘላለም
ወደ ቀደሰውም መቅደስ ኑ፡፡ አስፈሪ ቍጣው
ከእናንተ እንዲመለስም፣ እግዚአብሔር አምላ
ካችሁን አገልግሉ፡፡ 9እናንተ ወደ እግዚአብሐ
ር ብትመለሱ አምላካችሁ እግዚአብሔር
ቸርና

*35 በትውፊት የሰላም መሥዋዕት ይባላል፡፡

ርኅሩኅ ስለሆነ ወንድሞቻችሁና ልጆቻችሁን
በማረኳቸው ዘንድ ምሕረትን ያገኛሉ፤
ወደ ዚህች ምድር ይመለሳሉ። እናንተ
ወደእርሱ ብትመለሱ፣ እርሱም ፊቱን
ከእናንተ አይ መልስም።
10መልእክተኞቹም በኤፍሬምና በምናሴ
ምድር ካንዱ ከተማ ወደ ሌላው ከተማ
በመዘዋወር እስከ ዛብሎን ድረስ ሄዱ፤ ሕዝቡ
ግን አንቋሸ ሻቸው፤ ተሣለቀባቸውም።
11ሆኖም ከአሴር፣ ከምናሴና ከዛብሎን
ጥቂት ሰዎች ራሳቸውን ዝቅ አድርገው
ወደ ኢየሩሳሌም መጡ። 12እንዲሁም ንጉ
ሡና ሹማምንቱ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት
ያዘዙትን እንዲፈጽሙ አንድ ልብ
ይሰጣቸው ዘንድ የእግዚአብሔር እጅ
በይሁዳ ላይ ነበር።
13በሁለተኛው ወር የቂጣን በዓል ለማክበር
እጅግ ብዙ ሕዝብ በኢየሩሳሌም ተሰበሰበ።
14በኢየሩሳሌም የነበሩትን መሠዊያዎች ነቃ
ቅለው፣ የዕጣን መሠዊያዎችንም ከስፍራው
አንሥተው ወደ ቄድሮን ሸለቆ ጣሉ።
15በሁለተኛው ወር በዐሥራ አራተኛው ቀን
የፋሲካውን በግ ዐረዱ። ካህናቱና ሌዋውያኑ
አፍረው ስለ ነበር ራሳቸውን ቀደሱ፤ የሚ
ቃጠል መሥዋዕትንም ወደ እግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ አመጡ። 16ከዚያም በእግዚአ
ብሔር ሰው በሙሴ ሕግ እንደ ታዘዘው መደበኛ
ቦታቸውን ያዙ። ካህናቱም ከሌዋውያኑ እጅ
የተቀበሉትን ደም ረጩ። 17ከጉባኤው መካከል
አብዛኞዎቹ ራሳቸውን ያልቀደሱ ስለ ነበሩ፣
ሌዋውያኑ በሥርዐቱ መሠረት ራሳቸውን
ላላነጹትና ጠቦቶቻቸውን ለእግዚአብሔር መቀደስ
ላልቻሉት ሁሉ የፋሲካውን በጎች ማረድ
ነበረባቸው። 18ምንም እንኳ ከኤፍሬም፣ ከምናሴ፣
ከይሳኮርና ከዛብሎን ከመጡት አብዛኞዎቹ
ራሳቸውን ያላነጹ ቢሆንም ከተጻፈው ትእዛዝ
ውጭ ፋሲካውን በሉ። ሕዝቅያስ ግን እንዲህ
ሲል ጸለየ፤ “ቸሩ እግዚአብሔር ሆይ፤ ይቅር
በላቸው፤ 19ምንም እንኳ በመቅደሱ ሥርዐት
መሠረት የነጹ ሆነው ባይገኙም የአባቶቻቸው
አምላክ የሆነውን እግዚአብሔር አምላካቸውን
ለመ ፈለግ ልባቸውን የሚያዘጋጁትን ሁሉ
ይቅር በላቸው።” 20እግዚአብሔርም ሕዝቅያስን
ሰማው፤
ሕዝቡንም ፈወሰ።
21ሌዋውያኑና ካህናቱ በእግዚአብሔር የዜማ
ዕቃ ታጅበው፣ በየዕለቱ ለእግዚአብሔር እየዘ
መሩ[ቦ]፣ በኢየሩሳሌም የነበሩት እስራኤላው
ያን የቂጣን በዓል በታላቅ ደስታ ለሰባት ቀን
አከበሩ፤
22ሕዝቅያስም በእግዚአብሔር አገልግሎት
አስተዋዮች የነበሩትን ሌዋውያን ሁሉ በን
ግግሩ አበረታታ። ሰባቱንም ቀን የተወሰነላ
ቸውን ድርሻ እየበሉና የኅብረት መሥዋዕቱንም[†]
እያቀረቡ የአባቶቻቸውን አምላክ እግዚአብሔርን
አመሰገኑ።
23ጉባዔውም ሁሉ በተከታዩ ሰባት ቀን
በዓሉን እንደገና ለማክበር ተስማሙ፣ ስለዚህ
በዓሉን ለሰባት ተጨማሪ ቀን በታላቅ ደስታ
አከበሩ። 24የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ አንድ
ሺህ ወይፈን፣ ሰባት ሺህ በግና ፍየል ለጉ
ባኤው ሰጠ፤ ሹማምንቱም እንደዚሁ አንድ
ሺህ ወይፈን፣ ዐሥር ሺህ በግና ፍየል ሰጡ።
እጅግ ብዙ ካህናትም ራሳቸውን ቀደሱ።
25መላው የይሁዳ ጉባኤ፣ ካህናቱና ሌዋውያኑ፣
ከእስራኤል የተሰበሰበው ጉባኤ ሁሉ፣ እን
ዲሁም ከእስራኤል የመጡ መጻተኞችና
በይሁዳ የሚኖሩ መጻተኞች ደስ አላቸው።
26ከእስራኤል ንጉሥ ከዳዊት ልጅ ከሰሎሞን
ጊዜ አንሥቶ በኢየሩሳሌም እንዲህ ያለ በዓል
ተደርጎ ስለማያውቅ፣ በኢየሩሳሌም ታላቅ
ደስታ ሆነ። 27ከዚያም ካህናቱና ሌዋውያኑ
ተነሥተው ሕዝቡን ባረኩ፤ እግዚአብሐ
ሔርም ሰማቸው፤ ጸሎታቸውም ወደ ሰማይ
ወደ ቅዱሱ ማደሪያው ደረሰ።

31 ይህ ሁሉ ከተፈጸመ በኋላ፣ በዚያ
የነበሩት እስራኤላውያን ወደ ይሁዳ
ከተሞች ወጥተው፣ የማምለኪያ ድንጋዮችን
ሰባበሩ፤ የአሼራ ምስል ዐምዶች ቈረጡ፤
እንዲሁም በመላው ይሁዳና በብንያም፣ በኤፍ
ሬምና በምናሴ የነበሩትን የኰረብታ መስገ
ጃዎችና መሠዊያዎች አጠፉ፤ እስራኤላውያን
እነዚህን ሁሉ ካጠፉ በኋላ ወደየከተሞቻቸውና
ወደ የርስታቸው ተመለሱ።

### ለካህናት የተደረገ ስጦታ

31፥20-21 ተጓ ምብ —1ዜና18፥5-7

2ሕዝቅያስ ካህናቱና ሌዋውያኑ የሚቃጠል
መሥዋዕትና የኅብረት መሥዋዕት[‡] እንዲ
ያቀርቡ፣ እንዲያገለግሉና እንዲያመሰግኑ እንዲሁም
በእግዚአብሔር ማደሪያ ደጆች ውዳሴውን
እንዲዘምሩ፣ ካህናትንም ሆኑ ሌዋውያንን
እያንዳንዳቸውን እንደየተግባራቸው በየክፍሉ
መደባቸው። 3በእግዚአብሔር ሕግ እንደተጻፈው
ንጉሡ ጠዋትና ማታ እንደዚሁም በየሰንበቱ፣
በየወሩ መባቻውና በተወሰኑ በዓላት፣ የሚ
ቃጠለውን መሥዋዕት ከራሱ ንብረት ሰጠ።
4ካህናቱና ሌዋውያኑም ሙሉ ጊዜአቸውን ለእግዚ
አብሔር ሕግ አገልግሎት ማዋል ይችሉ ዘንድ፣
በኢየሩሳሌም የሚኖረው ሕዝብ ተገቢውን
ድርሻ እንዲሰጣቸው አዘዘ። 5ትእዛዙ እንደ
ወጣ እስራኤላውያን ወዲያውኑ የእህሉንና
የአዲሱን ወይን ጠጅ፣ የዘይቱንና የማሩን እንዲ
ሁም የዕርሻውን ፍሬ ሁሉ በኵራት በልግሥና

30፥10 2ዜና36፥16
30፥11 ቀኁ25፤ 2ዜና6፥37
30፥12 ኤር32፥39፤ሕዝ11፥19
30፥13 ዘኍ28፥16
30፥14 2ሳሙ15፥ 23፤ 2ዜና28፥24
30፥15 2ዜና29፥34
30፥16 2ዜና 35፥10
30፥17 2ዜና35፥11፤ ዕዝ6፥20
30፥18 ዘፀ12፥43-49፤ዘኍ9፥6-10
30፥20 2ዜና6፥20፤ 7፥14፤ሚል4፥2፤ ያዕ5፥16
30፥21 ዘፀ12፥15፡ 17፤13፥6
30፥23 2ዜና7፥9
30፥24 1ነገ8፥5፤ 2ዜና35፥7፤ ዕዝ6፥17፤8፥35
30፥25 ቀኁ11
30፥26 2ዜና7፥8
30፥27 ዘፀ39፥43
31፥1 2ነገ18፥4፤ 2ዜና32፥12፤ ኢሳ36፥7
31፥2 1ዜና15፥2፤ 23፥28-32፤24፥1፤ 2ዜና29፥9፤መዝ7፥17፤ 9፥2፤47፥6፤71፥22
31፥3 ዘኍ28፥1-29፥40፤1ዜና29፥3፤2ዜና35፥7፤ሕዝ45፥17
31፥4 ዘኍ18፥8፤ ዘዳ18፥8፤ነህ13፥10
31፥5 ዘኍ18፥12፡ 24፤ዘዳ12፥17፤ነህ13፥12፤ሕዝ44፥30
31፥6 ዘሌ27፥30፤

[ቦ]21 ወይም *ሌዋውያንና ካህናቱ በእግዚአብሔር የዜማ ዕቃ ታጅበው በየዕለቱ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር*
[†] 22 በትውፊት፣ *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል።
[‡] 2 በትውፊት፣ *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል።

ሰጡ፤ ካላቸው ከማንኛውም ነገር ሁሉ ላይ
እጅግ ብዙ የሆነ ዐሥራት አውጥተው አመጡ።
6በይሁዳ ከተሞች ይኖሩ የነበሩት የእስራ
ኤልና የይሁዳ ሰዎችም ከከብቶቻቸው፣ ከበግና
ከፍየል መንጎቻቸውና ለአምላካቸው ለእግዚ
አብሔር ከለዩአቸው የተቀደሱ ነገሮች ዐሥራት
አውጥተው አመጡ፤ ከመሩትም። 7ይህንም
በሦስተኛው ወር ጀምረው፣ በሰባተኛው ወር
አጠናቀቁ። 8ሕዝቅያስና ሹማምንቱም መጥተው
ክምሩን ባዩ ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፤
ሕዝቡን እስራኤልንም ባረኩ።
9ሕዝቅያስም ካህናቱንና ሌዋውያኑን ስለ
ክምሩ ጠየቃቸው፤ 10ከሳዶቅ ቤተሰብ የሆነው
ሊቀ ካህናቱ ዓዛርያስም፣ "ሕዝቡ ስጦታውን
ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ማምጣት
ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ በቂ ምግብ አግኝ
ተናል፤ ብዙም ተርፎናል፤ እግዚአብሔር ሕዝ
ቡን ስለባረከም ይህን ያህል ብዛት ያለው
ሊተርፍ ችሎአል" አለ።
11ሕዝቅያስም በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
ውስጥ ጎተራ እንዲያዘጋጅ አዘዛቸው፤ እነ
ርሱም አዘጋጁ። 12ከዚያም ስጦታውን፣ ዐሥራ
ቱንና የተቀደሱ ስጦታዎቹን በታማኝነት
አምጥተው አስገቡ። ሌዋዊው ኮናንያ የእነ
ዚሁ ዕቃዎች ኀላፊ ሲሆን ወንድሙ ስሜኢ
ደግሞ በማዕረግ ሁለተኛ ነበር። 13ይሒዒል፣
ዓዛዝያ፣ ናሖት፣ አሣሄል፣ ይሬሞት፣ የዛባት፣
ኤሊኤል፣ ሰማኪያ፣ መሐትና በናያስ በንጉሡ
ሕዝቅያስና በእግዚአብሔር ቤት ኀላፊ በዓዛርያስ
ተሹመው በኮናንያና በወንድሙ በስሜኢ
ሥር ሆነው ተቈጣጣሪዎች ነበሩ።
14የምሥራቁ በር ጠባቂ የሆነው የሌዋዊው
የይምና ልጅ፣ ቆሬ ደግሞ በበጎ ፈቃድ፣
ለእግዚአብሔር በቀረበው ስጦታ ላይ የእግዚ
አብሔርን መባና የተቀደሱትንም ነገሮች
ለማከፋፈል፣ ኀላፊ ነበረ። 15ዔድን፣ ሚንያ
ሚን፣ ኢያሱ፣ ሸማያ፣ አማርያና ሴኬንያ በካህናቱ
ከተሞች ተገኝተው፣ ለካህናት ወገኖቻቸው
ለታላላቆቹም ሆነ ለታናናሾቹ፣ እንደየምድ
ባቸው፣ በማከፋፈሉ ረገድ በታማኝነት ረዱት።
16በተጨማሪም፣ ስማቸው በትውልድ መዝገቡ
ውስጥ የነበረና የየዕለቱ ልዩ ልዩ ተግባራ
ቸውን እንደየኀላፊነታቸው መጠንና እንደ
የምድብ ሥራቸው ለማከናወን ወደ እግዚ
አብሔር ቤተ መቅደስ መግባት
ለሚችሉት፣
ዕድሜአቸው ሦስት ዓመትና ከዚያም በላይ
ለሆናቸው ወንዶች ልጆች እንደዚሁ አከፋ
ፈሉ። 17በትውልድ መዝገብ በየቤተ ሰባቸው
ተቈጥረው ለገቡት ካህናት፣ ዕድሜአቸው
ሃያ ዓመትና ከዚያም በላይ ለሆናቸው ሌዋውያን
እንደየኀላፊነታቸው መጠንና እንደየምድብ
ሥራቸው አካፈሏቸው። 18በዚህ የትውልድ

ሩት3፥7፤ነህ13፥10-12
31፥7 ዘፀ23፥16
31፥8 መዝ144፥13-15
31፥10 ዘፀ36፥5፤ 2ሳሙ8፥17፤ ሕዝ44፥30፤ ሚል3፥10-12
31፥12 2ዜና35፥9
31፥13 2ዜና35፥9
31፥15 ኢሱ21፥9-19፤2ዜና29፥12
31፥16 1ዜና23፥3
31፥19 ዘኊ35፥2-5
31፥20 2ነገ20፥3
31፥21 ዘዳ29፥9
32፥1 ኢሳ36፥1፤ 37፥9፡17፡37
32፥2 ኢሳ22፥7፤ ኤር1፥15
32፥4 2ነገ18፥17፤ ኢሳ22፥9፡11፤ናሆ 3፥14
32፥5 1ዜና11፥8፤ ኢሳ22፥8፡10
32፥7 ዘኊ14፥9፤ ዘዳ31፥6፤2ነገ6፥16፤2ዘ ና20፥15
32፥8 ዘዳ3፥22፤1 ሳሙ17፥45፤1ዜና5፥2 2፤ኢዮ40፥9፤ መዝ20፥7፤ ኢሳ28፥6፤52፥10 ኤር17፥5፤32፥21
32፥9 ኢሱ10፥3፡ 31

መዝገብ ላይ የተዘረዘሩትን መላውን የማኅበ
ረሰቡን ሕፃናት፣ ሚስቶችን፣ ወንዶችና ሴቶች
ልጆች ጨመሯቸው፤ ራሳቸውን በመቀደስ
ታማኞች ነበሩና።
19በከተሞቻቸው ዙሪያ ባሉት የዕርሻ ቦታዎች፣
ወይም በሌሎች ከተሞች ሁሉ ለሚኖሩት
ለካህናቱ ለአሮን ዘሮች፣ በመካከላቸው ላሉት
ወንዶችና በሌዋውያን የትውልድ መዝገብ
ለተመዘገቡት ሁሉ እንዲያከፋፍሉ በየስማቸው
የተጻፉ ሰዎች ነበሩ።
20ሕዝቅያስ በአምላኩ በእግዚአብሔር ፊት
መልካም፣ ቅንና ታማኝ ሆኖ በመገኘት
በመላው ይሁዳ የፈጸመው ተግባር ይህ ነው።
21የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ በማገልገልም
ሆነ፣ ለእግዚአብሔር
ሕግና ትእዛዝ በመገዛት አንጻር ያደረገውን
ሁሉ በፍጹም ልቡ አምላኩን በመፈለግ አከናወነ፤
ተሳካለትም።

## ሰናክሬም በኢየሩሳሌም ላይ ዛተ

32፥9-19ተጓ ምብ —2ዜና18፥17-35፤ኢሳ36፥2-20
32፥20-21ተጓ ምብ -2ዜና19፥35፤ኢሳ37፥36-38

32 ሕዝቅያስ እንዲህ ባለ ታማኝነት
ነገሮችን ሁሉ ካከናወነ በኋላ፣ የአሦር
ንጉሥ ሰናክሬም መጥቶ ይሁዳን ወረረ። ድል
አድርጎ የራሱ ሊያደርጋቸው በማሰብም የተመ
ሸጉትን ከተሞች ከበበ።
2ሕዝቅያስም ሰናክሬም መምጣቱንና ኢየሩ
ሳሌምንም ለመውጋት ማሰቡን ባወቀ ጊዜ፣ 3ከከተ
ማዪቱ ውጭ ያሉት የውሃ ምንጮች እንዲ
ዘጉ ከሹማምንቱና ከጦር አለቆቹ ጋር ተማከረ፤
እነርሱም ረዱት። 4ብዙ ሰዎችም ተሰብስበው
"የአሦር ነገሥታት[ጎ] መጥተው ስለምን ብዙ
ውሃ ያገኛሉ?" በማለት ምንጮቹን ሁሉና
በምድር ውስጥ ለውስጥ ይተላለፍ የነበረውን
ውሃ ዘጉ። 5ከዚህ በኋላም ንጉሡ ጠንክሮ
በመሥራት፣ ከቅጥሩ የፈራረሱትን ሁሉ ጠገነ፤
በላዩም ማማ ሠራበት፤ በውጭ በኩልም ሌላ
ቅጥር በመገንባት የዳዊትን ከተማ ድጋፍ እርከን
አጠናከረ፤ እንደዚሁም ብዙ የጦር መሣሪያዎ
ችንና ጋሻዎችን ሠራ።
6የጦር መኮንኖችንም በሕዝቡ ላይ ሾሞ
በከተማዪቱ በር አደባባይ ላይ በፊቱ ከሰበሰበ
በኋላ እንዲህ ሲል አበረታታቸው፤ 7"በርቱ፤
ጠንክሩ፤ ከእኛ ጋር ያለው ከእርሱ ጋር ካለው
ስለሚበልጥ፣ የአሦርን ንጉሥና አብሮት ያለውን
ብዙ ሰራዊት አትፍሩ፤ አትደንግጡም። 8ከእነርሱ
ጋር ያለው የሥጋ ክንድ ሲሆን፣ ከእኛ ጋር
ያለው ግን የሚረዳንና ጦላታችንን የሚዋጋልን
አምላካችን እግዚአብሔር ነው።" ሕዝቡም
የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ በተናገረው ቃል
ተበረታታ።
9ከዚህ በኋላ ሰናክሬም ከሰራዊቱ ሁሉ

ጎ4 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል የሰብዓ ሊቃናትና የሱርስቱ ትርጉም ግን፣ ንጉሥ ይላል።

ጋር ለኪሶን ከቦ ሳለ፣ የሚከተለውን መልእክት
በጦር መኮንኖቹ አማካይነት፣ ለሕዝቅያስና
ከእርሱ ጋር በኢየሩሳሌም ለነበሩት ለይሁዳ
ሕዝብ ላከ፤
[10]“የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም የሚለው
ይህ ነው፤ በተከበበችው በኢየሩሳሌም
እስከዚህ የቈያችሁት በማን ተማምናችሁ
ነው? [11]ሕዝቅያስ፣ *‘አምላካችን* እግዚአብሔር
ከአሦር ንጉሥ እጅ ያድነናል’ ማለቱስ በራ
ብና በጥማት እንድትሞቱ ሊያስታችሁ
አይደለምን? [12]ለይሁዳና ለኢየሩሳሌም፣
‘በአንድ *መሠዊያ* ፊት ሰገዱ፤ በላዩም
*መሥዋዕት* አቃጥሉ’ በማለት የራሱን
አምላክ የኰረብታ መስገጃ ስፍራዎችንና
*መሠዊያዎችን* ያስወገደስ
ሕዝቅያስ አይደለምን?
[13]“እኔና አባቶቼ በሌሎች አገሮች ሕዝቦች
ሁሉ ላይ ያደረግነውን አታውቁምን? ታዲያ
የእነዚያ መንግሥታት አማልክት ምድ
ራቸውን ከእጄ ለማዳን ችለዋልን? [14]አባቶቼ
ካጠፏቸው ከእነዚህ የመንግሥታት አማል
ክት ሁሉ፣ ሕዝቡን ከእጄ ሊያድን የቻለ
ከእነዚህ አምላክ የትኛው ነው? ታዲያ
አምላካችሁ እንዴት ከእጄ ሊያድናችሁ
ይችላል? [15]አሁንም ሕዝቅያስ በዚህ ዐይነት
አያታልላችሁ፤ አያስታችሁም። የየትኛውም
አገር ሕዝብ ወይም መንግሥት አምላክ
ሕዝቡን ከእጄ ወይም ከአባቶቼ እጅ
መታደግ የቻለ ስለሌለ አትመኑት። የእናንተ
አምላክማ ከእጄ ያድናችሁ ዘንድ ምንኛ
ያንስ!”
[16]የሰናክሬም ሹማምንትም *በእግዚአብሔር*
*አምላክና* በባሪያው በሕዝቅያስ ላይ ከዚህ የከፋ
ብዙ ነገር ተናገሩ። [17]ንጉሡም እንደዚሁ
የእስራኤልን *አምላክ* እግዚአብሔርን
በመሳደብ፣ “የሌሎቹ አገሮች ሕዝቦች አ
ማልክት፣ ከእጄ እንዳልታደጉ ሁሉ፣ የሕ
ዝቅያስም አምላክ
ሕዝቡን ከእጄ ሊታደግ አይችልም” ሲል በእ
ርሱ ላይ ደብዳቤ ጻፈ። [18]ከዚያም በማስደን
ገጥና በማስፈራራት ከተማዪቱን ለመያዝ ሲሉ
በቅጥሩ ላይ ወደተቀመጠው ወደ ኢየሩሳሌም
ሕዝብ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በዕብራ
ይስጥ ቋንቋ ጮኹ፤ [19]የሰው እጅ በሠራቸው
በሌሎች የምድር አሕዛብ አማልክት ላይ እንደ
ተናገሩት ሁሉ፣ በኢየሩሳሌም *አምላክ* ላይም
ተናገሩ።
[20]ንጉሥ ሕዝቅያስና የአሞጽ ልጅ ነቢዩ
ኢሳይያስም ስለዚህ ጒዳይ በጸሎት ወደ ሰማይ
ጮኹ። [21]*እግዚአብሔርም* መልአክ ልኮ በአሦር
ንጉሥ ሰፈር ተዋጊዎችን፣ መሪዎችንና የጦር
መኮንኖችን እንዲያጠፋቸው አደረገ። ስለዚህ
ንጉሡ በውርደት ወደ ገዛ አገሩ ተመለሰ። ወደ
አምላኩ ቤተ ጣዖት እንደገባም፣ የገዛ ወንዶች
ልጆቹ በሰይፍ ገደሉት።
[22]*እግዚአብሔርም* ሕዝቅያስንና የኢየሩ
ሳሌምን ሕዝብ ከአሦር ንጉሥ ከሰናክሬምና
ከሌሎችም እጅ ሁሉ አዳናቸው፤ በዙሪያቸው
ካሉትም ሁሉ ጠበቃቸው[ነ]፤ [23]ብዙዎችም *ለእግ*
*ዚአብሔር* መባ ይዘው ወደ ኢየሩሳሌም መጠ
፤ ለይሁዳ ንጉሥ ለሕዝቅያስም ውድ
የሆኑ ገጸ በረከቶች አመጡለት፤ ከዚያን ጊዜ
ጀምሮም
በአሕዛብ ሁሉ ፊት ከፍ ከፍ አለ።

### የሕዝቅያስ ዕብሪት፣ ያከናወናቸው ተግባሮችና ሞቱ

32፥24-33 ተጓ ምብ —2ዜና20፥1-21፤ኢሳ37፥21-38፤38፥1-8

[24]በዚያ ጊዜ ሕዝቅያስ ታሞ ሊሞት ተቃርቦ
ነበር፤ ወደ *እግዚአብሔርም* ጸለየ፤ እርሱም
መለሰለት፤ ምልክትም ሰጠው። [25]የሕዝቅያስ
ልብ ግን ታበየ እንጂ ስለ ተደረገለት በጎ ነገር
ተገቢ ምላሽ አልሰጠም፤ በዚህ ምክንያት *የእግዚ*
*አብሔር* ቍጣ በእርሱ፣ በይሁዳና በኢየሩሳሌም
ላይ ወረደ። [26]ይሁን እንጂ ሕዝቅያስና የኢየሩ
ሳሌም ሕዝብ ስለ ልባቸው ትዕቢት ራሳ
ቸውን አዋረዱ፤ ስለዚህ *የእግዚአብሔር* ቍጣ
በዘመነ መንግሥቱ አልመጣባቸውም።
[27]ሕዝቅያስ እጅግ ብዙ ሀብትና ክብር
ነበረው፤ ከዚህ የተነሣም ለብሩ፣ ለወርቁ፣
ለከበሩት ዕንቈዎቹ፣ ለቅመማ ቅመሞቹ፣
ለጋሻዎቹና ለተለያዩ ውድ ዕቃዎቹ ሁሉ ግምጃ
ቤቶችን ሠራ። [28]እንደዚሁም ለእህሉ፣ ለወይን
ጠጁና ለዘይቱ ማከማቻ የሚሆኑ ግምጃ ቤቶች
ለተለያዩ እንስሳት በረት ለበግና ለፍየል መንጋም
በረት ሠራ። [29]እግዚአብሔር ታላቅ ብልጽግና ስለ
ሰጠው፤ ብዙ የበግና የፍየል፣ የእንስሳትም
መንጋ ሰበሰበ፤ መንደሮችንም ሠራ።
[30]የላይኛውን የግዮንን ምንጭ መውጫ
ገድቦ፣ ውሃውን በቦይ ቍልቍል ወደ ምዕራብ
የዳዊት ከተማ እንዲወርድ ያደረገም ይኸ
ው
ሕዝቅያስ ነበር፤ ሥራውም ሁሉ ተከናወነለት።
[31]ነገር ግን በምድሪቱ ላይ ስለ ተፈጸመው
ታምራዊ ምልክት እንዲጠይቁት፣ የባቢሎን
ገዦች መልእክተኞችን በላኩ ጊዜ፣ እግዚአብሔር
ሊፈትነውና በልቡ ያለውን ሁሉ ሊያውቅ
ስለፈለገ ተወው።
[32]በሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው
ሌላው ሥራና ቸርነቱ በአሞጽ ልጅ በነቢዩ
በኢሳይያስ ራእይ፣ በይሁዳና በእስራኤል ነገ
ሥታት መጽሐፍ ተጽፎአል። [33]ሕዝቅያስም እንደ
አባቶቹ ሁሉ አንቀላፋ፤ የዳዊት ዘሮች መካነ
መቃብር በሆነው ኰረብታም ተቀበረ። በሞተም
ጊዜ ይሁዳ ሁሉና የኢየሩሳሌም ሕዝብ በሙሉ
አከበሩት። ልጁ ምናሴም በእርሱ ፈንታ ነገ
ሠ።

32፥10 ሕዝ29፥16
32፥11 ኢሳ37፥10
32፥12 2ዜና31፥1
32፥13 ቍ15
2፥15 ዘፀ5፥2፤ኢሳ37፥10፤ዳን3፥15
32፥17 2ነገ19፥12፤ መዝ74፥22፤ ኢሳ37፥4፡14፡17
32፥19 መዝ115፥4-8፤ኢሳ2፥8፤17፥8፤37፥19፤ኤር1፥16
32፥20 ኢሳ1፥15፤37፥15
32፥21 ዘፍ19፥13፤2ነገ19፥7፤ኢሳ37፥7፡38፤ኤር41፥2
32፥23 1ሳሙ10፥27፤2ዜና9፥24፤መዝ68፥18፡29፤76፥11፤ኢሳ16፥1፤ 18፥7፤45፥14፤ሶፎ3፥10፤ዘካ14፥16-17
32፥24 ቍ31
32፥25 2ነገ 14፥10፤2ዜና19፥2
32፥26 2ዜና34፥27፡28፤ኢሳ39፥8፤ኤር26፥18-19
32፥27 1ዜና29፥12፤2ዜና9፥24
32፥29 ኢሳ39፥2
32፥30 2ሳሙ5፥8፤1ነገ1፥33፤2ነገ18፥17
32፥31 ቍ24፤ዘፍ22፥1፤ዘዳ8፥16፤ኢሳ13፥1፤ 38፥7፤39፥1

ነ22 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል የሰብዓ ሊቃናት የቩልጌት ቅጆች ግን *አሳረፋቸው* ይላል።

## የይሁዳ ንጉሥ ምናሴ

33፥1-10 ተጓ ምብ —2ዜና21፥1-10
33፥18-20 ተጓ ምብ 2ዜና21፥17-18

33 ምናሴ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ዐሥራ ሁለት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም አምሳ አምስት ዓመት ገዛ። 2*እግዚአብሔር* ከእስራኤላውያን ፊት አሳዶ ያስወጣቸውን ሕዝቦች አስጸያፊ ልማድ በመከተል*ም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸመ*። 3አባቱ ሕዝቅያስ ያጠፋቸውን የኰረብታ *መ*ስገጃ ስፍራዎች *መልሶ ሠራ*፤ ለበአሊም *መሠዊያዎችን አቆመ*፤ የአሼራንም ዐምዶች *ሠራ*፤ ለሰማይ ከዋክብት ሰራዊትም ሰገደ፤ *አመለካቸውም*። 4*እግዚአብሔር*፡ "ስሜ ለዘላለም በኢየሩሳሌም *ይኖራል*" ባለበት *በእግዚአብሔር* ቤተ *መቀደስ መሠዊያዎችን ሠራ*። 5በሁለቱም የእግዚአብሔር ቤተ *መቅደስ* አደባባዮች ላይ፣ ለሁሉም የሰማይ ከዋክብት ሰራዊት *መሠዊያዎችን ሠራ*። 6በሄኖም ልጅ ሸለቆ ወንዶች ልጆቹን በእሳት *ሠዋ*[ኘ]፤ አስማት፣ *መተትና* ጥንቈላ *አደረገ*፤ *ሙታን ጠሪዎችንና መናፍስት* ሳቢዎችን ጠየቀ። ለቍጣ *ያነሣሣው* ዘንድ *በእግዚአብሔር ፊት* እጅግ ክፉ *ነገር አደረገ*።

7*ያበጀውን* የተጠረበ ምስል ወስዶም በእግዚአብሔር ቤተ *መቅደስ* አኖረ፤ ስለዚህም ቤተ *መቅደስ* እግዚአብሔር ለዳዊትና ለልጁ ለሰሎሞን እንዲህ ብሎ ነበር፤ "በዚህ ቤተ *መቅደስ*ና ከእስራኤል ነገድ ሁሉ በመረጥኋት በኢየሩሳሌም ስሜን ለዘላለም አኖራለሁ፤ 8በሙሴ አማካይነት *ያዘዝኋቸውን ሕግጋቴን*፣ *ደንቦቼንና ሥርዓ*ቶቼን ሁሉ በጥንቃቄ *ይፈጽሙ* እንጂ፣ ለቀድሞ አባቶቻችሁ ከሰጠኋቸው ምድር የእስራኤላውያን እግር ከእንግዲህ ለቆ እንዲወጣ *አላደርግም*።" 9*ምናሴ ግን እግዚአብሔር* በእስራኤላውያን *ፊት* ካጠፋቸው አሕዛብ የባሰ ክፉ ድርጊት *ይፈጽሙ* ዘንድ፣ የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ሕዝብ አሳተ።

10*እግዚአብሔር* ለምናሴና ለሕዝቡ ተናገረ፤ እነርሱ *ግን መ*ስማት *አልፈለጉም*። 11ስለዚህ *እግዚአብሔር* የአሦርን *ንጉሥ* ሰራዊት አዛዦች *አመጣባቸው*፤ እነርሱም በምናሴ አፍንጫ *መንጠቆ* አገቡበት፤ በናስ ሰንሰለት አስረውም ወደ ባቢሎን ወሰዱት። 12በተጨነቀም ጊዜ *የአምላኩን* የእግዚአብሔርን በጎነት *ፈለገ*፤ በአ ባቶቹም አምላክ *ፊት* ራሱን እጅግ *አዋረደ*። 13ወደ እርሱም በጸለየ ጊዜ፣ በጭንቀት ልመናው ራርቶለት *እግዚአብሔር* ጸሎቱን ሰማው፤
ስለዚህ ወደ ኢየሩሳሌም፣ ወደ *መንግሥቱም መ*ለሰው፤ ምናሴም *እግዚአብሔር* አምላክ *መሆኑን*
ዐወቀ።

14ከዚህ በኋላ በሸለቆው ውስጥ ከሚገኘው ከግዮን ምንጭ ምዕራብ *አንሥቶ* እስከ ዓሣ በር *መግቢያ* ድረስ ያለውን የዳዊትን ከተማ የውጭውን ቅጥር፣ *የዖፌል*ን ኰረብታ እንዲከብ በማድረግ፣ ይበልጥ ከፍ አድርጎ እንደ ገና *ሠራው*። በተመሸጉትም የይሁዳ ከተሞች ሁሉ የጦር አዛዦችን አኖረ።

15እንግዶች አማልክትንና ጣዖታቱን *ከእግዚአብሔር* ቤተ *መቅደስ* አስወገደ፤ በቤተ *መቅደሱ* ኰረብታና በኢየሩሳሌም *የሠራቸውንም መሠ*ዊያዎች ሁሉ አራቀ፤ ከከተማዪቱም ውጭ ጣላቸው። 16ከዚያም *የእግዚአብሔርን መሠዊያ* አደሰ፤ በላዩም የኅብረት *መሥዋዕትና* የምስጋና *መሥዋዕት* አቀረበ፤ ይሁዳም የእስራኤልን *አምላክ* እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ አዘዘ። 17ሕዝቡ *ግን* በኰረብታ *መ*ስገጃ ስፍራዎች *መሠዋቱን* ቢቀጥልም፣ *የሚሠዋው ግን* ለአንዱ *አምላክ* ለእግዚአብሔር ብቻ ነበር።

18በምናሴ *ዘመነ መንግሥት* የተከናወነው ሌላው *ተግባር*፣ ወደ አምላኩ *ያቀረበው* ጸሎትና ባለራእዮች በእስራኤል *አምላክ* በእግዚአብሔር ስም የነገሩት ቃል በእስራኤል[አ] *ነገሥታት ታሪክ ተጽፎአል*። 19ጸሎቱና እግዚአብሔር ራርቶ ልመናውን እንዴት እንደ ተቀበለው፣ *ኀጢአቱ* ሁሉና *ታማኝነቱን ማጕደሉ*፣ እንደዚሁም ራሱን ከማዋረዱ በፊት *ያሠራቸው* የኰረብታ *መ*ስገጃ ስፍራዎች፣ *ያቆማቸው* የአሼራ ምስል ዐምዶችና ጣዖታት ሁሉ በባለ ራእዮች *መዛግብት ተጽፈዋል*። 20ምናሴም እንደ አባቶቹ ሁሉ አንቀላፋ፤ በቤተ *መንግሥቱም* ተቀበረ። ልጁም አሞጽ በእርሱ ፈንታ ነገሠ።

## የይሁዳ ንጉሥ አሞጽ

21አሞጽ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው *ሃያ* ሁለት ዓመት ነበር፤ እርሱም በኢየሩሳሌም ተቀምጦ ሁለት ዓመት ገዛ። 22አባቱ ምናሴ እንዳደረገው ሁሉ እርሱም *በእግዚአብሔር ፊት* ክፉ ድርጊት *ፈጸመ*፤ አሞጽም ምናሴ *ያሠራቸውን* ጣዖታት ሁሉ *አመለከ*፤ *መሥዋዕትም* አቀረበላቸው። 23አሞጽ *በእግዚአብሔር ፊት* ራሱን እንዳዋረደ እንደ አባቱ እንደ ምናሴ ራሱን አላዋረደም፤ ነገር ግን በበደል ላይ በደል እየጨመረ ሄደ።

24የአሞጽ ሹማምንት በእርሱ ላይ አሢረው በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ገደሉት። 25ከዚያም *ያገሩ* ሕዝብ በንጉሡ አሞጽ ላይ *ያሤሩትን* ሁሉ ገደሉ፤ ልጁን ኢዮስያስንም በእርሱ *ፈንታ* አነገሡት።

## ኢዮስያስ ያደረገው ተሐድሶ

34፥1-2ተጓ ምብ —2ዜና22፥1-2
34፥3-7ተጓ ምብ —2ዜና23፥4-20
34፥8-13ተጓ ምብ —2ዜና22፥3-7

34 ኢዮስያስ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ስምንት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም ሠላሳ አንድ ዓመት ገዛ።

33፥1 1ዜና3፥13
33፥2 ዘዳ18፥9፤ ኤር15፥4
33፥3 ዘዳ16፥21-22፤17፥3፤2ዜና24፥18
33፥4 2ዜና7፥16
33፥5 2ዜና4፥9
33፥6 ዘፀ22፥18፤ ዘሌ18፥21፤19፥31፤ ዘዳ18፥10፤ 1ሳሙ28፥13
33፥7 2ዜና7፥16
33፥8 2ሳሙ7፥10
33፥9 ኤር15፥4፤ ሕዝ5፥7
33፥11 ዘዳ28፥36፤ 2ነገ19፥28፤መዝ149፥8፤ኢሳ37፥29፤ሕዝ29፥4፤38፥4፤አሞ4፥2
33፥12 2ዜና6፥37
33፥14 1ነገ1፥33፤ 2ዜና27፥3፤ነህ3፥3፡26፤12፥39፤ሶፎ1፥10
33፥15 2ነገ23፥12
33፥16 ዘሌ7፥11-18
33፥19 2ነገ21፥21፥17፤2ዜና6፥37
33፥20 2ነገ21፥18፤ 2ዜና21፥20
33፥21 1ዜና3፥14
33፥23 ዘፀ10፥3፤ 2ዜና7፥14፤መዝ18፥27፤147፥6፤ምሳ3፥34
33፥25 2ዜና22፥1
34፥1 1ዜና3፥14፤ ሶፎ1፥1

[ኘ]6 ወይም ወንዶች ልጆቹቹን ገደለ
[አ]18 በዜና መዋዕሉ መጽሐፍ ተደጋግሞ እንደተጠቀሰው ይህ ይሁዳ ነው።

2እርሱም *በእግዚአብሔር ፊት* መልካም
የሆነውን ነገር አደረገ፤ ወደ ቀኝም ወደ ግራም
ሳይል፣ በአባቱ በዳዊት መንገድ ሄደ፡፡
3በዘመነ መንግሥቱ በስምንተኛው ዓመት
ገና ወጣት ሳለ፣ የአባቱን የዳዊትን አምላክ
መፈለግ ጀመረ፤ በዐሥራ ሁለተኛውም
ዓመት ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን ከኰረብታ
መስገጃ ስፍራዎች፣ ከአሼራ፣ ምስል ዐምዶች፣
ከተቀረጹ ጣዖታትና ቀልጠው ከተሠሩ
ምስሎች አነጻ፡፡ 4በእርሱም ትእዛዝ የበኣሊም
መሠዊያዎችን አፈራረሱ፤ እርሱም ከበላያቸው
የነበሩትን የዕጣን መሠዊያዎችን አደቀቀ፤
የአሼራን ምስል ዓምዶችን፣ ጣዖታቱንና ምስሎቹን
ሰባብሮ ከፈጫቸው በኋላ ይሠዉላቸው በነበሩት
ሰዎች መቃብር ላይ በተነ፡፡ 5የካህናቱን ዐጥንት
በመሠዊያዎቻቸው ላይ አቃጠለ፤ በዚህ
ዐይነትም ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን አነጻ፡፡ 6እስከ
ንፍታሌም ባሉ በምናሴ፣ በኤፍሬምና በስ
ምዖን ከተሞች እንዲሁም በዙሪያቸው ባሉ
የፈራረሱ አካባቢዎች፣ 7መሠዊያዎችንና
የአሼራ ምስል ዐምዶችን አፈራረሰ፤ ጣዖታቱን
እንደ ዱቄት አደቀቀ፤ በመላው እስራኤል
የሚገኙትንም የዕጣን መሠዊያዎች አነካከተ፤
ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ፡፡
8ኢዮስያስ በነገሠ በዐሥራ ስምንተኛው
ዓመት፣ ምድሪቱንና ቤተ መቅደሱን ካነጻ
በኋላ፣ የኤዜልያስን ልጅ ሳፋንን፣ የከተማ
ዩቱን ገዥ መዕሤያንና የጸሓፊውን የኢዮ
አካዝን ልጅ ኢዮአክን *የአምላኩን* የእግዚአ
ብሔርን ቤተ መቅደስ ይጠግኑ ዘንድ ላካቸው፡፡
9እነርሱም ወደ ሊቀ ካህኑ ወደ ኬልቅያስ
ሄደው፣ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የመጣውን
ገንዘብ ሰጡት፤ ገንዘቡም በር ጠባቂዎች
የነበሩት ሌዋውያን፣ ከምናሴ፣ ከኤፍሬምና
ከመላው የእስራኤል ቅሬታዎች እንደዚሁም
ከመላው ይሁዳና ከብንያም፣ ከኢየሩሳሌምም
ነዋሪዎች የሰበሰቡት ነበር፡፡ 10እነርሱም *የእግ
ዚአብሔርን* ቤተ መቅደስ ሥራ እየተቈጣጠሩ
እንዲያሠሩ ለተሾሙት ሰዎች ዐደራ ሰጡ፤
እነዚህም ሰዎች ገንዘቡን ቤተ መቅደሱን ለጠ
ገኑትና ላደሱት ሰዎች ከፈሉ፡፡ 11እንዲ
ሁም የይሁዳ ነገሥታት እንዲፈርሱ
ላደረጓቸው
ሕንጻዎች ጥርብ ድንጋዮችን፣ ሠረገላዎችንና
ማገጣጠሚያ ዕንጨቶችን እንዲገዙ ለዐናጢ
ዎችና ለግንበኞች ገንዘብ ሰጡ፡፡
12ሰዎቹም ሥራውን በታማኝነት አከናወኑ፡፡
የበላይ ሆነው አመራር የሚሰጧቸውም ከሜራሪ
ጐሣ የሆኑት ሌዋውያን፣ ኢኤትና አብድዩ፣
ከቀዓት ጐሣ ዘካርያስና ሜሱላም ነበሩ፡፡ በዜማ
ዕቃ የላቀ ችሎታ የነበራቸው ሌዋውያን ሁሉ፣
13የጕልበት ሠራተኞች ኀላፊ በመሆን፣ በየሥራው
ላይ የተመደቡትን ሠራተኞች ይቈጣጠሩ ነበር፡፡

34፥2 2ዜና29፥2
34፥3 1ዜና16፥11
34፥4 ዘፀ32፥20፤ 34፥13፤ዘሌ26፥30፤2ነገ23፥11፤ሚክ1፥5
34፥5 1ነገ13፥2
34፥7 ዘፀ32፥20
34፥9 1ዜና6፥13
34፥11 2ዜና24፥12፤33፥4-7
34፥12 2ነገ12፥15፤ 1ዜና25፥1
34፥13 1ዜና23፥4
34፥15 2ነገ22፥8፤ ዕዝ7፥6፤ነህ8፥1
34፥19 ዘዳ28፥3-68፤ኢሳ36፥22፤37፥1
34፥20 2ነገ22፥3
34፥21 ሰቆ2፥4፤ 4፥11፤ሕዝ36፥18
34፥22 ዘፀ15፥20፤ ነህ6፥14
34፥24 ዘዳ28፥15-68፤2ዜና36፥14-20፤ምሳ16፥4፤ኢሳ3፥9፤ኤር40፥2፤42፥10፤44፥2፥11
34፥25 2ዜና33፥3-6፤ኤር22፥9

ጥቂቶቹ ሌዋውያን ደግሞ ኀላፊዎች፣ ጸሓፊዎችና
በር ጠባቂዎች ነበሩ፡፡

### የሙሴ ሕግ መጽሐፍ መገኘት

34፥14-28ተጓ ምብ —2ዜና22፥8-20
34፥29-32ተጓ ምብ —2ዜና23፥1-3

14ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ የገባውን
ገንዘብ በሚያወጡበት ጊዜ፣ ካህኑ ኬልቅያስ
በሙሴ አማካይነት የተሰጠውን *የእግዚአ
ብሔርን* ሕግ መጽሐፍ አገኘ፡፡ 15ኬልቅያስም
ጸሓፊውን ሳፋንን፣ “የሕጉን መጽሐፍ *በእግዚ
አብሔር* ቤተ መቅደስ ውስጥ አገኘሁት” አለው፤
ከዚያም መጽሐፉን ለሳፋን ሰጠው፡፡
16ሳፋንም መጽሐፉን ወደ ንጉሡ ወስዶ
እንዲህ አለው፤ “ሹማምንትህ የታዘዙትን ሁሉ
በመፈጸም ላይ ናቸው፤ 17*በእግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስ የነበረውንም ገንዘብ አውጥተው ለተ
ቈጣጣሪዎቹና ለሠራተኞቹ አስረክበዋል፡፡”
18ከዚያም ጸሓፊው ሳፋን ንጉሡን፣ “ካህኑ
ኬልቅያስ መጽሐፍ ሰጥቶኛል” አለው፡፡ ሳፋንም
መጽሐፉን ለንጉሡ አነበበለት፡፡
19ንጉሡም የሕጉን ቃል በሰማ ጊዜ ልብሱን
ቀደደ፡፡ 20እርሱም ለኬልቅያስ፣ ለሳፋን ልጅ
ለአኪቃም፣ ለሚክያስ ልጅ ለዓብዶን፣
ለጸሓፊው ለሳፋንና ለንጉሡ የቅርብ አገል
ጋይ ለዓሳያ ይህን ትእዛዝ ሰጠ፤ 21“ሄዳችሁ
ስለ እኔ እንደዚሁም በእስራኤልና በይሁዳ
ስላሉት ቅሬታዎች በተገኘው መጽሐፍ ውስጥ
ስለ ተጻፈው ነገር *እግዚአብሔርን* ጠይቁ፡፡
አባቶቻችን *የእግዚአብሔርን* ቃል ስላልጠ
በቁ በላያችን ላይ ታላቅ *የእግዚአብሔርን*
ቍጣ ፈስሶአል፤ በዚህ መጽሐፍ በተጻፈው
መሠረት አልተመላለሱምና፡፡”
22ኬልቅያስና ንጉሡ ከእርሱ ጋር የላካቸው[ካ]
ሰዎች የአልባሳት ጠባቂ የነበረው የሐስራ
ልጅ፣ የቲቁዋ ልጅ የሴሌም ሚስት ወደ
ሆነችው ወደ ነቢይቱ ወደ ሕልዳና ሄደው
ነገሯት፡፡ እርሷም በኢየሩሳሌም ውስጥ በሁለ
ተኛው ክፍለ ከተማ ትኖር ነበር፡፡
23ነቢይቱም እንዲህ አለቻቸው፤ “የእስ
ራኤል *አምላክ* እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
ወደ እኔ ለላካችሁ ሰው እንዲህ ብላችሁ
ንገሩት፤ 24‘*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ በይ
ሁዳ ንጉሥ ፊት በተነበበው መጽሐፍ በተ
ጻፈው ርግማን ሁሉ መሠረት፣ በዚህ ስፍራና
በሕዝቡ ላይ ጥፋትን አመጣለሁ፡፡ 25እኔን
ትተውኝ ለሌሎች አማልክት ዕጣን ስላጠኑና
እጃቸው በሠራው ነገር ሁሉ[ኸ] ለቍጣ ስላነሣ
ሡኝ፣ ቍጣዬ በዚህ ስፍራ ይነድዳል፤ አይጠ
ፋምም፡፡’ 26*እግዚአብሔርን* ለመጠየቅ

[ካ]22 አንድ የዕብራይስጥ ቅጅ እንዲሁም ቩልጌትና የሱርስት ትርጒሞች በዚህ ሲስማሙ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን *ከእርሱ ጋር የላካቸው* የሚለውን አይጨምሩም፡፡
[ኸ]25 ወይም *ባደረጉት ነገር ሁሉ*

የላካችሁን የይሁዳን ንጉሥ እንዲህ
በሉት፤ ‘ስለ ሰማኸው ቃል የእስራኤል አም
ላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ 27በዚህ
ስፍራና በሕዝቡ ላይ የተናገረውን በሰማህ
ጊዜ፣ ልብህ ስለ ተነካና በእግዚአብሔርም
ፊት ራስህን ስለ አዋረድህ፣ እንዲሁም በእኔ
ፊት ራስህን ዝቅ ስላደረግህ፣ ልብስህንም
በመቅደድ በፊቴ ስለ አለቀስህ፣ ሰምቼሃለሁ
ይላል እግዚአብሔር። 28እነሆ፤ ወደ አባቶችህ
እሰበስብሃለሁ፤ በሰላምም ትቀበራለህ፤ በዚህ
ቦታና በነዋሪዎቹ ላይ የማመጣውን መከራ ሁሉ
በዓይንህ አታይም።’ ” መልሷንም ይዘው
ወደ ንጉሡ ሄዱ።

29ከዚያም ንጉሡ የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን
ሽማግሌዎች ሁሉ በአንድ ላይ ሰበሰበ። 30እርሱም
ከትንሽ እስከ ትልቅ ካሉት ከይሁዳ ሰዎች፣
ከኢየሩሳሌም ሕዝብ፣ ከካህናትና ከሌዋውያን
ጋር ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ወጣ።
በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የተገኘውንም የኪ
ዳኑን መጽሐፍ ቃል ሁሉ ለሕዝቡ
አነበበላቸው 31ንጉሥም በዐምዱ አጠገብ
ቆሞ፣ እግዚአብሔ ርን ይከተል ዘንድ በፍጹም
ልቡና በፍጹም ነፍሱ ትእዛዛቱን፣ ሕግጋቱንና
ሥርዐቱን ለመጠበቅ፣ በዚህ መጽሐፍ
ለተጻፈውም የኪዳን ቃል ለመታዘዝ በእግዚ
አብሔር ፊት ኪዳኑን አደሰ።

32ከዚህ በኋላ በኢየሩሳሌምና በብንያም የሚ
ኖረው ሁሉ በዚህ ነገር ቃል እንዲገባ አደረገ፤
የኢየሩሳሌምም ሕዝብ የአባቶቹ አምላክ ባዘዘው
የአምላክ ቃል ኪዳን መሠረት ፈጸሙ።

33ኢዮስያስም አስጸያፊ ጣዖታትን ሁሉ
ከመላው የእስራኤል ግዛት አስወገደ፤
በእስራኤል የነበሩትም ሁሉ አምላካቸውን
እግዚአ ብሔርን እንዲያመልኩ አደረገ፤
እርሱ በሕይወት እያለም የአባቶቻቸውን
አምላክ እግዚአብሔርን ከመከተል ወደ ኋላ
አላሉም።

## ኢዮስያስ ፋሲካን ማክበሩ

35፥1፡18-19ተጓ— ምብ 2ዜና 23፥21-23

35 ኢዮስያስ በኢየሩሳሌም ለእግዚአብሔር
ፋሲካን አደረገ፤ በመጀመሪያውም
ወር በዐሥራ አራተኛው ቀን የፋሲካው በግ
ታረደ። 2ካህናቱን በየአገልግሎታቸው መደበ፤
በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አገልግሎትም
እንዲተጉ አበረታታቸው። 3እስራኤልን ሁሉ
ያስተምሩ ለነበሩትና ራሳቸውን ለእግዚአብሔር
ለቀደሱት ሌዋውያን እንዲህ አላቸው፤ “የእግዚ
አብሔርን ታቦት የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ባሠራው
ቤተ መቅደስ አኑሩ፤ በእናንተ ትከሻ አት
ሸከሙት፤ አሁንም አምላካችሁን እግዚአብሐ
ሔርንና ሕዝቡን እስራኤልን አገልግሉ። 4በእስ
ራኤል ንጉሥ በዳዊትና በልጁ በሰሎሞን

34፥27 ዘፀ10፥3፤ 2ዜና6፥37፤32፥26
34፥28 2ዜና32፥26፤ 35፥20-35
34፥30 2ነገ23፥2
34፥31 ዘዳ13፥4፤ 1ነገ7፥15፤2ነገ11፥17፤ 2ዜና23፥16
34፥33 ዘዳ18፥9
35፥1 ዘፀ12፥1-30፤ዘኍ28፥16
35፥3 2ዜና17፥7
35፥4 ቊ10፤ 1ዜና24፥1፤ዕዝ6፥18
35፥6 ዘሌ11፥44
35፥7 2ዜና30፥24፤ 31፥3
35፥8 1ዜና6፥13፤ 29፥3፤2ዜና29፥31-36
35፥9 2ዜና31፥12፡ 13
35፥10 ቊ4፤ 2ዜና30፥16
35፥11 2ዜና30፥17
35፥13 ዘፀ12፥2-11
35፥14 ዘፀ29፥13
35፥15 1ዜና25፥1፤ 26፥12-19፤2ዜና29፥30፤ነህ12፥46፤መዝ68፥25

በተጻፈው
መመሪያ መሠረት፣ እንደየቤተሰባችሁ በክፍል
በክፍላችሁ ራሳችሁን አዘጋጁ።

5“ሌዋውያን ባልሆኑ ወንድሞቻችሁ
አንጻር እንደየቤተ ሰቡ ምድብ በተቀደሰው ስፍ
ራ ቁሙ፤ ለእያንዳንዱም የቤተ ሰብ ምድብ
ሌዋውያን ይኑሩት። 6ከዚያም የፋሲካውን
በጎች እረዱ፤ ራሳችሁን ቀድሱ፤ እግዚአብሔር
በሙሴ አማ ካይነት ባዘዘውም መሠረት ዕርዶቹ
ን ለወንድሞ ቻችሁ አዘጋጁ።”

7ኢዮስያስም እዚያ ለነበሩት ሕዝብ ሁሉ
ለፋሲካው መሥዋዕት እንዲሆኑ ባጠቃላይ
ሠላሳ ሺህ በግና ፍየል እንዲሁም ሦስት ሺ
ህ ወይፈን ከራሱ ሃብት ሰጠ።

8ሹማምንቱም ለሕዝቡ፣ ለካህናቱና ለሌዋ
ውያኑ በገዛ ፈቃዳቸው አዋጥተው ሰጡ።
የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አለቆች የሆኑት ኬል
ቅያስ፣ ዘካርያስና ይሒኤልም ለፋሲካ መሥዋዕት
የሚቀርቡ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ በግ
እንዲሁም ሦስት መቶ ወይፈን ሰጡ። 9ደግሞም
ኮናንያ፣ ወንድሞቹ ሸማያና ናትናኤል እንደዚ
ሁም የሌዋውያኑ መሪዎች ሐሸቢያ፣ ይዔኤልና
ዮዛባት ለፋሲካ መሥዋዕት እንዲሆኑ አምስት
ሺህ በግና ፍየል አምስት መቶም በሬ ለሌዋውያኑ
ሰጧቸው።

10የአገልግሎቱ ዝግጅት በተጠናቀቀ ጊዜ፣
ንጉሡ ባዘዘው መሠረት ካህናቱ በየክፍላቸው
ከተመደቡት ሌዋውያን ጋር ቦታ ቦታቸውን
ይዘው ቆሙ። 11የፋሲካው በጎች ታረዱ፤ ካህ
ናቱ የተቀበሉትን ደም ረጩ፤ ሌዋውያኑም
የበጎቹን ቈዳ ገፈፉ። 12በሙሴ ሕግ እንደ ተጻፈው
ለእግዚአብሔር እንዲያቀርቡም፣ እንደ የቤተ
ሰቡና እንደየምድቡ ለሕዝቡ ለመስጠት
የሚቃጠለውን መሥዋዕት ለዩ፤ ወይፈኖቹንም
እንደዚሁ አደረጉ። 13እነርሱም የፋሲካውን
መሥዋዕት በሥርዐቱ መሠረት ጠበሱ፤
የተቀደሰውንም ቍርባን በምንቸት፣ በሰታቴና
በድስት ቀቀሉ፤ ወዲያውኑም ለሕዝቡ አደሉ።
14ከዚህ በኋላ ለራሳቸውና ለካህናቱ ዝግጅት
አደረጉ፤ ምክንያቱም ካህናቱ የአሮን ልጆች
የሚቃጠለውን መሥዋዕትና ስቡን እስከ
ሌሊት ድረስ ያቀርቡ ስለ ነበር ነው።
ስለዚህ ሌዋውያኑ ለራሳቸውና ለካህናቱ
ለአሮን ልጆች ዝግጅት አደረጉ።

15መዘምራኑ የአሳፍ ዘሮች በዳዊት፣ በአሳፍ፣
በኤማንና በንጉሡ ባለ ራእይ በኤዶታም በተ
ሰጠው መመሪያ መሠረት በቦታቸው ነበሩ።
በእያንዳንዱ በር ላይ የነበሩት በር ጠባቂዎችም
ሌዋውያን ወገኖቻቸው ስላዘጋጁላቸው፣
ከጥበቃ ቦታቸው መለየት አያስፈልጋቸውም
ነበር።

16በዚህ ዓይነት የፋሲካን በዓል በማክበርና
የሚቃጠል መሥዋዕት በእግዚአብሔር መ
ሠዊያ ላይ በማቅረብ የእግዚአብሔር

አገልግሎት ሁሉ ንጉሥ ኢዮስያስ ባዘዘው መ
ሠረት በዚያኑ ቀን ተከናወነ። 17በዚያን ጊዜ
በስፍራው የተገኙ እስራኤላውያን የፋሲካን
በዓል አከበሩ፤ የቂ ጣንም በዓል እንደዚሁ
ሰባት ቀን አከበሩ። 18ከነቢዩ ከሳሙኤል
ዘመን ወዲህ እንዲህ ያለ ፋሲካ በእስራ
ኤል ዘንድ ተከብሮ አያ ውቅም፤ ኢ
ዮስያስ ከካህናቱ፣ ከሌዋውያኑ፣ ከመላው
ይሁዳና ከእስራኤል፣ በዚያ ከነበሩትም ከኢ
የሩሳሌም ሰዎች ጋር እንዳከበረው አድርጎ
ያከበረ አንድም የእስራኤል ንጉሥ የለም።
19ይህ ፋሲካ የተከበረው በኢዮስያስ ዘመነ
መንግሥት በዐሥራ ስምንኛው ዓመት
ነበር።

## የኢዮስያስ መሞት

35፥20-36፥1ተጓ ምብ —2ዜና23፥28-30

20ከዚህ ሁሉ በኋላ ኢዮስያስ ቤተ መቅደሱን
አደራጅቶ ባጠናቀቀ ጊዜ፣ የግብፅ ንጉሥ
ኒካዑ በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ፣ በከር
ከሚሽ ላይ ለመዋጋት ወጣ፤ ኢዮስያስም ጦር
ነት ሊገጥመው ወጣ። 21ኒካዑ ግን፣ "የይሁዳ
ንጉሥ ሆይ፤ አንተንና እኔን የሚያጣላን ምን
ድነው? ጦርነት ከገጠምሁት ቤት ጋር
እንጂ በአሁኑ ጊዜ አንተን የምወጋህ
አይደለሁም፤ እግዚአብሔር እንድፈጥን አዞኛል፤
ስለዚህ ከእኔ ጋር ያለውን እግዚአብሔርን
መቃወምህን ተው፤ ያለዚያ ያጠፋሃል"
አለው።
22ኢዮስያስ ግን ሌላ ሰው መስሎ በጦርነት
ሊገጥመው ወጣ እንጂ ወደ ኋላ አልተመለሰም፤
በመጊዶ ሜዳ ላይ ሊዋጋው ሄደ እንጂ ኒካዐ
ከእግዚአብሔር ታዞ የነገረውን ሊሰማ
አልፈለገም።
23ቀስተኞች ንጉሥ ኢዮስያስን ወጉት፤
እርሱም የጦር መኰንኖቹን፣ 'ክፉኛ ቈስያለሁና
ከዚህ አውጡኝ" አላቸው። 24ስለዚህ ከሠረገላው
አውርደው በራሱ ሠረገላ ላይ አስቀምጠውት
ወደ ኢየሩሳሌም ወሰዱት፤ እዚያም ሞተ፤
በአባቶቹ መካነ መቃብር ተቀበረ፤ የይሁዳና
የኢየሩሳሌም ሕዝብ ሁሉ አለቀሱለት።
25ኤርምያስ ለኢዮስያስ የሐዘን እንጕርጕሮ
ግጥም ጻፈለት፤ ወንዶችና ሴቶች ሙሾ አው
ራጆች ሁሉ እስከ ዛሬ ድረስ በዚህ ግጥም
ኢዮስያስን ያስታውሱታል፤ ይህም በእስራ
ኤል የተለመደ ሆኖ በልቅሶ ግጥም መጽሐፍ
ተጽፎአል።
26በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት የተከና
ወነው ሌላው ድርጊትና *በእግዚአብሔር* የሕግ
መጽሐፍ በተጻፈው መሠረት ያከናወነው መን
ፈሳዊ ተግባር፣ 27ከመጀመሪያው እስከ
መጨረሻው ያደረገው ሁሉ በይሁዳና በእስ
ራኤል ነገሥታት መጽሐፍ ተጽፎአል።

36 የአገሩም ሰዎች የኢዮስያስን ልጅ
ኢዮአሐዝን ወስደው በአባቱ ፈንታ
በኢየሩሳሌም አነገሡት።

35፥20 ዘፍ2፥14፤ ኢሳ10፥9፤ኤር46፥2
35፥21 1ነገ13፥18፤ 2ነገ18፥25
35፥22 1ሳሙ28፥8
35፥23 1ነገ22፥34
35፥25 ዘፍ50፥10፤ 2ዜና34፥28፤ኤር22፥10፡15፡16
36፥1 2ዜና22፥1
36፥4 ኤር22፥10-12፤ሕዝ19፥4
36፥5 ኤር22፥18፤ 25፥1፤26፥1፤35፥1፤36፥1፤45፥1፤46፥2
36፥6 ኤር25፥9፤ 27፥6፤ሕዝ19፥9፤ 29፥18፤ዳን1፥1
36፥7 ቀኑ18፤ዕዝ 1፥7፤ ኤር27፥16፤ ዳን1፥2
36፥9 ኤር22፥24-28፤24፥1፤27፥20፤29፥21፤52፥31
36፥10 ቀኑ18፤ 2ነገ20፥17፤ ዕዝ1፥7፤ኢሳ52፥11፤ ኤር14፥18፤21፥7፤ 22፥25፤24፥1፤ 27፥16፡20፡22፤ 29፥1፤34፥21፤40፥1፤ሕዝ17፥12፤ዳን5፥2
36፥11 2ነገ24፥17፤ ኤር27፥1፤28፥1፤34፥2፤37፥1፤39፥1
36፥12 ዘዳ8፥3፤ 2ዜና7፥14፤ኤር37፥1፤ 39፥18፤44፥10

## የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአሐዝ

36፥2-4ተጓ ምብ —2ዜና23፥31-34

2ኢዮአሐዝ በነገሠ ጊዜ፣ ዕድሜው ሃያ
ሦስት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም
ሦስት ወር ገዛ። 3ከዚያም የግብፅ ንጉሥ በኢ
የሩሳሌም ካለው ዙፋኑ አወረደው፣ በአገሩም
ላይ አንድ መቶ መክሊት[ሠ] ብርና አንድ
መክሊት[ዐ] ወርቅ ግብር ጣለበት። 4የግብፅም
ንጉሥ የኢዮአሐዝን ወንድም ኤልያቄምን
በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ አነገሠው፤
ስሙንም ለውጦ ኢዮአቄም አለው። ኒካዑም
የኤልያቄምን ወንድም ኢዮአሐዝን ይዞ ወደ
ግብፅ ወሰደው።

## የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም

36፥5-8ተጓ ምብ —2ዜና23፥36-24፥6

5ኢዮአቄም በነገሠ ጊዜ፣ ዕድሜው ሃያ
አምስት ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም
ዐሥራ አንድ ዓመት ገዛ። *በአምላኩም* በእግዚ
አብሔር ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸመ። 6የባቢ
ሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር በእርሱ ላይ ዘመተ፤
ወደ ባቢሎንም ይወስደው ዘንድ በናስ
ሰንሰለት አሰረው። 7እንደዚሁም ናቡከደነፆር
*የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስ ዕቃ ወስዶ፣
ባቢሎን ባለው በራሱ ቤተ ጣዖት[ዘ]
አኖረው።
8በኢዮአቄም ዘመነ መንግሥት የተጠ
ከናወነው ሌላው ተግባሩ የፈጸመው አስጸያፊ
ድርጊትና በእርሱ ላይ የተገኘበት ሁሉ
በእስራኤልና በይሁዳ ነገሥታት መጽሐፍ ተ
ጽፎአል። ልጁ ዮአኪንም በእርሱ ፈንታ ነገ
ሠ።

## የይሁዳ ንጉሥ ዮአኪን

36፥9-10ተጓ ምብ —2ዜና24፥8-17

9ዮአኪን በነገሠ ጊዜ፣ ዕድሜው ዐሥራ
ስምንት[ዠ] ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም
ተቀምጦም ሦስት ወር ከዐሥር ቀን ገዛ፤
እርሱም *በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ ድርጊት ፈ
ጸመ። 10በጸደይም ወራት ንጉሡ
ናቡከደነፆር ልኮ *በእግዚአ ብሔር* ቤተ
መቅደስ ውስጥ ከፍተኛ ዋጋ
ካላቸው ዕቃዎች ጋር ወደ ባቢሎን ወሰደው።
የዮአኪንንም አጎት[የ] ሴዴቅያስን በይሁዳና
በኢየሩሳሌም ላይ አነገሠው።

## የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ

36፥11-16ተጓ ምብ—2ዜና24፥18፤ኤር52፥1-3

11ሴዴቅያስ በነገሠ ጊዜ፣ ዕድሜው ሃያ
አንድ ዓመት ነበር፤ በኢየሩሳሌም ተቀምጦም
ዐሥራ አንድ ዓመት ገዛ። 12እርሱም በአምላኩ
*በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ ድርጊት ፈ
ጸመ፤ የእግዚአብሔን ቃል በተናገረው በነቢዩ
በኤርምያስ

[ሠ]3 3.4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው።
[ዐ]3 34 ኪሎ ግራም ይህል ነው።
[ዘ]7 ወይም **ቤተ መንግሥት** ተብሎ መተርጐም ይቻላል።
[ዠ]9 አንድ የዕብራይስጥ ቅጂ ጥቂት የሰብዓ ሊቃናትና የሱርስት ትርጒሞች (እንዲሁም 2ነገ24፥8) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ብዙ የዕብራይስጥ ቅጅዎች ግን **ስምንት** ይላሉ።
[የ]10 ዕብራይስጡ **ወንድም** ይላል (እንዲሁም 2ነገ24፥17 ይመ) ።

ፊትም ራሱን ዝቅ አላደረገም። 13እንደዚሁም
በእግዚአብሔር ስም አምሎት በነበረው በንጉሥ
ናቡከደነፆር ላይ ዐመፀ፤ አንገቱን አደነደነ፤
ልቡንም አጠነከረ እንጂ ወደ እስራኤል
አምላክ ወደ *እግዚአብሔር* አልተመለሰም።
14ከዚህም ላይ የካህናቱና የሕዝቡ መሪዎች
ሁሉ፣ አስጸያፊ የሆኑትን የአሕዛብን ል
ማዶች በመከተልና በኢየሩሳሌም
የተቀደሰውን *የእግዚአብሔርን* ቤተ
መቅደስ በማርከስ፣ ባለመታመናቸው ከጊዜ
ወደ ጊዜ እየባሱ ሄዱ።

## የኢየሩሳሌም መውደቅ

36፥17-20 ተጓ ምብ —2ዜና25፥1-21፡ኤር52፥4-7
36፥22-23 ተጓ ምብ — ዕዝራ1፥1-3

15የአባቶቻቸው *አምላክ* እግዚአብሔር ለሕ
ዝቡና ለማደሪያው ስላዘነ፣ መልእክተኞቹን
ይልክ ነበር፤ 16እነርሱ ግን የእግዚአብሔር ቍጣ
በሕዝቡ ላይ እስኪነሣሣና ፈውስም እስከ
ማይገኝላቸው ድረስ በእግዚአብሔር
መልእክተኞች ላይ ተሳለቁ፤ ቃሉን ናቁ፤ ነቢ
ያቱንም አቃለሉ። 17ስለዚህ የባቢ
ሎናውያንን[ዶ] ንጉሥ አመጣባቸው፤
እርሱም ወጣቶቻቸውን በቤተ መቅደሱ
ውስጥ በሰይፍ ፈጀ፤ ወጣቱንም ሆነ ወጣ
ቲቱን፣ ሽማግሌውንም ሆነ በዕድሜ የገ
ፋውን አላስቀረም፤ እግዚአብሔር ሁሉንም
ለናቡከደናፆር አሳልፎ ሰጠው። 18እርሱም
ትልልቁንም ሆነ ትንንሹን የእግዚአብሔርን
ቤተ መቅደስ ዕቃ በሙሉ፣ እንዲሁም የእግዚ
አብሔርን ቤተ መቅደስ ሀብት፣ የንጉሡንና
የሹማምንቱን ሀብት ሁሉ ወደ ባቢሎን
አጋዘ።

19የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ በእሳት አቃጠ
ሉ፤ የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች አፈረሱ፤ ቤተ
መንግሥቶቹን በሙሉ አቃጠሉ፤ በዚያ
የነበረውንም የከበረ ዕቃ በሙሉ አጠፉ።
20ከሰይፍ የተረፉትን ቅሬታዎች በምርኮ
ወደ ባቢሎን ወሰዳቸው፤ እስከ ፋርስ መን
ግሥት መነሣትም ድረስ የእርሱና የል
ጆቹ አገልጋዮች ሆኑ። 21ምድሪቱም የሰ
ንበት ዕረፍት አገኘች፤ በኤርምያስ የተነ
ገረው *የእግዚአብሔር* ቃል ይፈጸም ዘንድ፣
ሰባው ዓመት እስኪያበቃ ድረስ፣ ባድማ
በነበረችበት ዘመን ሁሉ ዐረፈች።

22በኤርምያስ የተነገረው *የእግዚአብሔር*
ቃል ይፈጸም ዘንድ፣ በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ
ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ ዓመት፣ በግዛቱ
ሁሉ ዐዋጅ እንዲያስነግርና ይህም እንዲጻፍ
*እግዚአብሔር* የፋርስን ንጉሥ የቂሮስን
መንፈስ አነሣሣ፤ እርሱም እንዲህ አለ፤
23 "የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ እንዲህ ይላል፤
" 'የሰማይ *አምላክ* እግዚአብሔር የምድርን
መንግሥታት ሁሉ ሰጥቶኛል፤ በይሁዳ
በምትገኘው በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ
እሠራለት ዘንድ አዝዞኛል፤ ከሕዝቡ በመ
ካከላችሁ የሚገኝ ማናቸውም ሰው፣
*እግዚአብሔር* አምላኩ ከእርሱ ጋር
ይሁን፤ እርሱም ወደዚያው ይውጣ።'
"

36፥13 ዘፀ32፥9፤ ዘዳ9፥27፤ሕዝ17፥13
36፥14 1ዜና5፥25
36፥15 ኢሳ5፥4፤ 44፥26፤ኤር7፥13፡25፤ 11፥7፤25፥3-4፤ 35፥14፡15፤44፥4-6 ሐጌ1፥13፤ዘካ1፥4፤ ሚል2፥7፤3፥1፤ ማቴ5፥12
36፥16 2ነገ2፥23፤ ዕዝ5፥12፤ነህ9፥30፤ ኢዮ8፥2፤ምሳ1፥30-31፤29፥1፤ ኢሳ28፥14፡22፤ 29፥20፤57፥4፤ ኤር5፥13፤7፥26፤ 20፥8፤25፥4፤30፥12፤43፥2፤44፥3፤ዳን9፥6፤ሚክ2፥11፤ዘካ1፥2
36፥17 ዘፍ10፥10፤ ዘዳ32፥25፤ዕዝ5፥12፤ኤር6፥11፤9፥21፤18፥21፤32፥28፤ 44፥7፤ 51፥22፤ ሰቆ2፥21፤ ሕዝ9፥6፤23፥47
36፥18 ቍ7፡10፤ ኤር27፥20
36፥19 1ነገ9፥8-9፤2ነገ14፥13፤ መዝ79፥1-3፤ ኤር11፥16፤17፥27፤ 21፥10፤14፤22፥7፤ 32፥29፤39፥8፤ ሰቆ2፥6፤4፥11፤ ሕዝ20፥47፤ አሞ2፥5፤ዘካ11፥1
36፥20 ዘሌ26፥44፤ 2ነገ24፥14፤ዕዝ2፥1፤ ነህ7፥6፤ኤር27፥7
36፥21 ዘሌ25፥4፤ 1ዜና22፥9፤ ኤር1፥1፤ 25፥11፤27፥22፤ 29፥10፤40፥1፤ ዳን9፥2፤ዘካ1፥12፤7፥5
36፥22 ኢሳ44፥28፤ 45፥1፡13፤ዳን1፥21፤6፥28፤10፥1

[ዶ]17 ወይም *ከለዳውያን*

# መጽሐፈ ዕዝራ

### ቂሮስ ምርኮኞቹ እንዲመለሱ ፈቀደ

1፥1-3 ተጓ ምብ 2ዜና 36፥22-23

1 ቂሮስ የፋርስ ንጉሥ በሆነ በመጀመሪ
ያው ዓመት እግዚአብሔር የቂሮስን
መንፈስ አነሣሥቶ በመንግሥቱ ሁሉ ዐዋጅ
እንዲያስነግርና ይህም በጽሑፍ እንዲሰፍር
አደረገ፤ ይህ የሆነው በኤርምያስ አፍ
የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል ይፈጸም
ዘንድ ነው።
2የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ የሚለው ይህ ነው፤
" 'የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር የምድርን
መንግ ሥታት ሁሉ ሰጥቶኛል፤ በይሁዳ
ምድር በም ትገኘው በኢየሩሳሌምም ለእርሱ
ቤተ መቅደስ እንድሠራ አዞኛል። 3ከሕዝቡ
መካከል በእናንተ ዘንድ የሚኖር ማናቸ
ውም ሰው አምላኩ ከእርሱ ጋር ይሁን፤ በይሁዳ
ወደምትገኘው ወደ ኢየሩሳሌም ይውጣና በዚያ
ለሚኖረው አምላክ፣ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚ
አብሔር ቤተ መቅደስ ይሥራ፤ 4ባለብት ስፍራ
የሚቀሩ በየትኛውም አገር የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ
በኢየሩሳሌም ለሚገኘው የእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ ስጦታ እንዲሆን በበጎ ፈቃድ ከሚያ
ቀርቡት መባ በተጨማሪ ብርና ወርቅ፣
ዕቃና እንስሳ በመስጠት ይርዷቸው' "
5ከዚያም እግዚአብሔር መንፈሳቸውን
ያነሣሣው የይሁዳና የብንያም ቤተ ሰብ አለ
ቆች እንዲሁም ካህናቱና ሌዋውያኑ ሁሉ
ለመሄድና በኢየሩሳሌም የሚገኘውን የእግዚ
አብሔርን ቤተ መቅደስ ለመሥራት ተዘጋጁ።
6ጎረቤቶቻቸውም ሁሉ በበጎ ፈቃድ ከሰጡት
መባ በተጨማሪ ከብርና ከወርቅ የተሠሩ
ዕቃዎችን፣ ቍሳቍስን፣ እንስሶችንና ሌሎች
ጠቃሚ የሆኑ ስጦታዎችንም በመለገስ ረዷ
ቸው። 7ከዚህም በላይ ንጉሡ ቂሮስ፣ ናቡከደነፆር
ከኢየሩሳሌም ወስዶ በአማልክቱ ቤተ ጣዖት[ሀ]
ያኖራቸውን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ
ንዋየተ ቅድሳት አወጣ። 8የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ
በግምጃ ቤቱ ኀላፊ በሚትሪዳጡ አማካይ
ነት ንዋየተ ቅድሳቱ እንዲመጡና በይሁዳው
ገዢ በሰሳብሳር ፊት እንዲቈጠሩ አደረገ።
9የዕቃው ዝርዝር ይህ ነበር፤

| | |
|---|---|
| የወርቅ ሳሕን | 30 |
| የብር ሳሕን | 1,000 |
| ዝርግ የብር ሳሕን[ለ] | 29 |
| 10ጐድጓዳ የወርቅ ሳሕን | 30 |
| ባለ ግጣም የብር ጐድጓዳ ሳሕን | 410 |
| ሌሎች ቍሳቍስ | 1000 |

11ባጠቃላይ አምስት ሺህ አራት መቶ
የወርቅና የብር ዕቃዎች ነበሩ። ሰሳብሳር ምር
ኮኞቹ ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም ሲመ
ለሱ ይህን ሁሉ ዕቃ ይዞ ወጣ።

### ወደ አገራቸው የተመለሱ ምርኮኞች ዝርዝር

2፥1-70 ተጓ ምብ ነህ 7፥6-73

2 የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ወደ ባቢ
ሎን ማርኮ ከወሰዳቸው መካከል ከምርኮ
ተመልሰው ወደየራሳቸው ከተሞች ወደ
ይሁዳና ወደ ኢየሩሳሌም የመጡት የአገሩ ልጆች
እነዚህ ናቸው፤ 2የመጡትም ከዘሩባቤል፣ ከኢ
ያሱ፣ ከነህምያ፣ ከሠራያ፣ ከረዕላያ፣ ከመር
ዶክዮስ፣ ከበላሳን፣ ከመሴፋር፣ ከበጉዋይ፣
ከሬሁም፣ ከበዓና ጋር ነበር።
የተመለሱት የእስራኤል ሰዎች ዝርዝር
የሚከተለው ነው፤

| | |
|---|---|
| 3የፋሮስ ዘሮች | 2,172 |
| 4የሰፋጥያስ ዘሮች | 372 |
| 5የኤራ ዘሮች | 775 |
| 6ከኢያሱና ከኢዮአብ ዘር የሆኑት የፈሐት ሞዓብ ዘሮች | 2,812 |
| 7የኤላም ዘሮች | 1,254 |
| 8የዛቱዕ ዘሮች | 945 |
| 9የዘካይ ዘሮች | 760 |
| 10የባኒ ዘሮች | 642 |
| 11የቤባይ ዘሮች | 623 |
| 12የዓዝጋድ ዘሮች | 1,222 |
| 13የአዶኒቃም ዘሮች | 666 |
| 14የበጉዋይ ዘሮች | 2,056 |
| 15የዓዲን ዘሮች | 454 |
| 16የሕዝቅያስ ልጅ የአጤር ዘሮች | 98 |
| 17የቤሳይ ዘሮች | 323 |
| 18የዮራ ዘሮች | 112 |
| 19የሐሱም ዘሮች | 223 |
| 20የጋቤር ዘሮች | 95 |
| 21የቤተ ልሔም ሰዎች[ሐ] | 123 |
| 22የነጦፋ ሰዎች | 56 |
| 23የዓናቶት ሰዎች | 128 |
| 24የዓዝሞት ዘሮች | 42 |
| 25የቂርያትይዓሪም[መ]፣ | |

1፥1 ዕዝ6፥22፤7፥27፤ ኤር25፥11ኛ12፤ 29፥ 10ኛ14፤ዘካ1፥12ኛ16
1፥2 መሳ4፥10፤ መዝ72፥11ኢሳ41፥2፡ 25፤44፥28፤45፥13፤ 46፥11፤49፥ 7ኛ23፤ 60፥3፡10፤ ሐጌ1፥2
1፥4 ዘፀ3፥22፤ ዘኍ15፥3፤ዕ3፥7፤ ዕዝ 4፥3፤ 5፥13፤6፥3፡14፤ መዝ50፥14፤54፥6፤ 116፥17፤72፥8ኛ11፤ ኢሳ10፥20ኛ22፤ ራእ21፥24
1፥5 ቍ1፤ ዘዳ35፥20ኛ22፤2ዜና11፥1፡ 3፡10፡12፡23፤15፥2፡8ኛ9፤ 25፥5፤31፥1፤34፥9፤ 36፥22፤ዕዝ4፥1፤10፥9፤ ነህ11፥4፤12፥34፤ መዝ127፥1፤ሐጌ1፥14፤ ፊል2፥13
1፥6 ዘፀ3፥22
1፥7 2ነገ24፥13፤ 2ዜና36፥7፡10፤ዕዝ5፥14፤ 6፥5፤ ኤር52፥17ኛ19
1፥8 1ዜና3፥18
2፥1 ቍ70፤ 2ነገ24፥16፤25፥12፤ 1ዜና9፥2፤2ዜና36፥20፤ ነህ7፥73፤11፥3
2፥2 1ዜና3፥19፤ 6፥14፤ዕዝ3፥2፤5፥2፤ 10፥18፤ነህ10፥2፤ 11፥11፤12፥1፡8፤ ሐጌ1፥1፡12፤2፥4፤ ዘካ3፥1ኛ10፤ 6፥9ኛ15፤ ማቴ1፥12፤ሉቃ3፥27
2፥3 ዕዝ8፥3፤ 10፥25፤ ነህ3፥25
2፥13 ዕዝ8፥13
2፥21 ሚክ5፥2

[ሀ]7 ወይም፣ አምላኩ
[ለ]9 በዕብራይስጡ የዚህ ቃል ትርጒም በትክክል አይታወቅም።
[ሐ]21 ወይም ልጆች፣ ዘሮች
[መ]25 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም (እንዲሁም ነህ 7፥29 ይመ)፤ ዕብራይስጡ ግን፣ ቂሪያት አሪም ይላል።

የከፊራና የብኤሮት ዘሮች 743
26የራማና የጌባ ዘሮች 621
27የማክማስ ሰዎች 122
28የቤቴልና የጋይ ሰዎች 223
29የናባው ዘሮች 52
30የመጌብስ ዘሮች 156
31የሌላው ኤላም ዘሮች 1,254
32የካሪም ዘሮች 320
33የሎድ፣ የሐዲድና
የኦኖም ዘሮች 725
34የኢያሪኮ ሰዎች 345
35የሴናዓ ዘሮች 3,630
36ካህናቱ፡-
ከኢያሱ ቤተ ሰብ
የዮዳኤ ዘሮች 973
37የኢሜር ዘሮች 1,052
38የፋስኮር ዘሮች 1,247
39የካሪም ዘሮች 1,017
40ሌዋውያኑ፡-
በሆዳይዋ በኩል የኢያሱና
የቀድምኤል ዘሮች 74
41መዘምራኑ፡-
የአሳፍ ዘሮች 128
42የቤተ መቅደሱ በረኞች፡-
የሰሎም፣
የአጤር፣ የጤልሞን፣
የዓቁብ፣ የሐጢጣና
የሶባይ ዘሮች 139
43የቤተ መቅደሱ አገልጋዮች፡-
የሲሐ፣ የሐሡፋና የጠብዖት ዘሮች፤
44የኬራስ፣ የሲዓ፣ የፋዶን ዘሮች፤
45የልባና፣ የአጋባ፣ የዓቁብ ዘሮች፤
46የአጋብ፣ የሰምላይ፣ የሐናን ዘሮች፤
47የጌዴል፣ የጋሐር፣ የራያ ዘሮች፤
48የረአሶን፣ የኔቆዳ፣ የጋሴም ዘሮች፤
49የዖዛ፣ የፋሴሐ፣ የቤሳይ ዘሮች፤
50የአስና፣ የምዑናውያን፣ የንፉሰሲም
ዘሮች፤
51የበቅቡቅ፣ የሐቁፋ፣ የሐርሑር
ዘሮች፤
52የበስሎት፣ የምሒዳ፣ የሐርሳ ዘሮች፤
53የበርቆስ፣ የሲሣራ፣ የቴማ ዘሮች፤
54የንስያና የሐጢፋ ዘሮች፤
55የሰሎሞን አገልጋዮች ዘሮች፡-
የሶጣይ፣ የሶፌሬት፣ የፍሩዳ ዘሮች፤
56የየዕላ፣ የደርቆን፣ የጌዴል ዘሮች፤
57የሰፋጥያስ፣ የሐጢል፣ የፌክራት፣የሐፂ
ቦይም፣ የአሚ ዘሮች፤
58የቤተ መቅደሱ አገልጋዮችና የሰሎሞን
አገልጋዮች ዘሮች 392
59ከዚህ የሚከተሉት ደግሞ ከቴልሜላ፣
ከቴላሬሳ፣ ከክሩብ፣ ከአዳንና ከኢሜር ከተ
ሞች የመጡ ናቸው፤ ነገር ግን ቤተ ሰቦቻ
ቸው የእስራኤል ዘር መሆናቸውን ማስረዳት
አልቻሉም፤
60የዳላያ፣ የጦብያና የኔቆዳ፣ ዘሮች 652
61ከካህናቱ መካከል የኤብያ፣ የአቆስና
የቤርዜሊ ዘሮች፤ ቤርዜሊ በዚህ ስም ሊጠራ
የቻለው የገለዓዳዊውን የቤርዜሊን ልጅ አግ
ብቶ ስለ ነበር ነው።
62እነዚህ በትውልድ መዝገቡ ውስጥ የቤተ
ሰባቸውን ዝርዝር ፈለጉ፤ ነገር ግን ማግኘት
አልቻሉም፤ ስለዚህ እንዳልነጹ ተቈጥ
ረው፣ ከክህነት አገልግሎት ተገለሉ። 63አገረ
ገዡውም በኡሪምና በቱሚም እግዚአብሔርን
የሚጠይቅ ካህን እስኪነሣ ድረስ፣ እጅግ
ከተቀደሰው ምግብ እንዳይበሉ አዘዛቸው።
64ከምርኮ የተመለሱት ሰዎች ብዛት
42,360 ነበረ፤ 65ይህም 7,337 ከሚሆኑት
ከወንዶችና ከሴቶች አገልጋዮቻቸው በተጨ
ማሪ ነው፤ 200 ወንድና ሴት ዘማሪዎችም
ነበሯቸው። 66736 ፈረሶች፣ 245 በቅሎዎች፣
67435 ግመሎችና 6,720 አህዮች ነበሯ
ቸው።
68በኢየሩሳሌም ወደሚገኘው ወደ *እግዚ
አብሔር* ቤት በደረሱ ጊዜ፣ አንዳንድ የቤተ
ሰብ መሪዎች በቀድሞው ቦታ እንደ ገና
ለሚሠራው የእግዚአብሔር ቤት በበጎ ፈቃድ
61,000 የወርቅ ዳሪክ[ሠ]፣ 5,000 ምናን[ረ] ብር፣
100 ልብሰ ተክህኖ ለግምጃ ቤቱ ሰጡ።
70ካህናቱ፣ ሌዋውያኑ፣ መዘምራኑ፣ በር ጠባ
ቂዎቹና የቤተ መቅደስ አገልጋዮቹ፣ ከሌ
ሎች ሰዎች ጋር በየራሳቸው ከተሞች ሰፈሩ፤
የቀሩት እስራኤላውያንም በየከተሞቻቸው
ተቀመጡ።

### *መሠዊያው እንደ ገና ተሠራ*

3 ሰባተኛው ወር በደረሰ ጊዜ፣ እስራ
ኤላውያን በየከተሞቻቸው ሳሉ፣ ሕዝቡ
እንደ አንድ ሰው ሆነው በኢየሩሳሌም
ተሰበሰቡ። 2ከዚያም የኢዮሴዴቅ ልጅ ኢያ
ሱና ካህናት ዘመዶቹ እንዲሁም የሰላትያል
ልጅ ዘሩባቤልና የሥራ ባልደረቦቹ፣ በእግዚአብሐ
ር ሰው በሙሴ ሕግ በተጻፈው መሠረት የሚ
ቃጠል መሥዋዕት ለማቅረብ፣ የእስራኤልን
አምላክ መሠዊያ መሥራት ጀመሩ። 3በዙ
ሪያቸው ካሉት አሕዛብ የተነሣ ፍር
ሀት ቢያድርባቸውም፣ መሠዊያውን በቀድ
ሞው መሠረት ላይ ሠሩ፤ በመሠዊያውም
ላይ ጠዋትና ማታ የሚቀርበውን የሚቃጠ
ል መሥዋዕት *ለእግዚአብሔር* አቀረቡ። 4ከዚ
ያም ለእያንዳንዱ ቀን እንደታዘዘው፣
በሚያስፈልገው

2፥26 ኢሱ18፥25
2፥28 ዘፍ12፥8
2፥34 1ነገ16፥34፤ 2ዜና28፥15
2፥36 1ዜና24፥7
2፥37 1ዜና24፥14
2፥38 1ዜና9፥12
2፥39 1ዜና24፥8
2፥40 ዘፍ29፥34፤ ዘኍ3፥9፤ዘዳ18፥6ኛ7፤ 1ዜና16፥4፤ዕዝ7፥7፤ 3፥9፤8፥15፤ነህ12፥24
2፥41 1ዜና15፥16
2፥42 1ሳሙ3፥15፤ 1ዜና9፥17
2፥43 1ዜና9፥2፤ ነህ11፥21
2፥58 1ዜና9፥2
2፥59 ዘኍ1፥18
2፥61 2ሳሙ17፥27
2፥62 ዘኍ3፥10፤ 16፥39ኛ40
2፥63 ዘፀ28፥30፤ ዘሌ2፥3፡10
2፥65 2ሳሙ19፥35
2፥66 ኢሳ66፥20
2፥68 ዘፀ25፥2
2፥70 ቊ1፤ 1ዜና9፥2፤ ነህ11፥3ኛ4
3፥1 ዘሌ23፥24፤ ነህ7፥73
3፥2 ዘፀ20፥24፤ ዘዳ12፥5ኛ6፤1ዜና3፥17፤ ዕዝ2፥2፤ሐጌ1፥1፤ ዘካ6፥11
3፥3 ዘፀ29፥39፤ ዘኍ28፥1ኛ8፤ዕዝ4፥4፤ ዳን9፥25
3፥4 ዘፀ23፥16፤ ዘኍ29፥12ኛ38፤ነህ8፥ 14ኛ18፤ዘካ14፥16ኛ19

[ሠ]69 500 ኪሎ ግራም ያህል ነው።
[ረ]69 2.9 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው።

ቊጥር ልክ የሚቃጠል መሥዋዕት በ
ማቅረብ የዳስ በዓልን በተጻፈው መሠረት
አከበሩ። 5ከዚያም በኋላ መደበኛውን የሚቃጠል
መሥዋዕት፣ የወር መባቻን መሥዋዕት፣
በተቀደሱት የእ ግዚአብሔር በዓላት
የሚቀርበውን መሥዋዕትና በበጎ ፈቃድ
ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን መባ አቀረቡ።
6የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መሠረት ገና
ያልተጣለ ቢሆንም፣ በሰባተኛው ወር
በመጀመሪያው ቀን ለእግዚአብሔር የሚቃጠ
ል መሥዋዕት አቀረቡ።

## ቤተ መቅደሱ እንደገና ተሠራ

7ከዚያም ለድንጋይ ጠራቢዎችና ለዐናጢ
ዎች ገንዘብ ሰጡ፤ ከፋርስ ንጉሥ ከቂሮስ
በተፈቀደው መሠረት የዝግባ ዛፎች ከሊባኖስ
ወደ ኢዮጴ በባሕር እንዲያመጡላቸው፣ ለሲ
ዶናና ለጢሮስ ሰዎችም ምግብ፣ መጠጥና
ዘይት ሰጡ።
8ኢየሩሳሌም ወደሚገኘው ወደ እግዚአ
ብሔር ቤት በደረሱ በሁለተኛው ዓመት
በሁለተኛው ወር፣ የሰላትያል ልጅ ዘሩ
ባቤልና የኢዮሴዴቅ ልጅ ኢያሱ እንዲ
ሁም የቀሩት ወንድሞቻቸው (ካህናቱ፣
ሌዋውያኑ፣ ከምርኮ ወደ ኢየሩሳሌም የተ
መለሱት ሁሉ) ሃያ ዓመትና ከዚያም በላይ
የሆናቸው ሌዋውያን የእግዚአብሔርን ቤት ሕ
ንጻ ሥራ እንዲቈጣጠሩ ሾሟቸው፤ ሥራውንም
ጀመሩ። 9ኢያሱ፣ ወንዶች ልጆቹና ወንድሞቹ፣
የዮሐዳያ[ሰ] ዘሮች ቀድምኤልና ወንዶች
ልጆቹ፣ የኤንሐዳድ ወንዶች ልጆች፣ ልጆቻቸ
ውና ወንድሞቻቸው፣ ሌዋውያኑም ሁሉ የእግዚ
አብሔርን ቤት የሚሠሩትን ሰዎች ለመቈጣጠር
በአንድ ላይ ሆኑ።
10ግንበኞቹ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ
መሠረት በጣሉ ጊዜ፣ ካህናቱ ልብሰ ተክህኖአ
ቸውን ለብሰውና መለከታቸውን ይዘው፣ ሌዋ
ውያኑ የአሳፍ ልጆች ደግሞ ጸናጽል ይዘው፣
በእስራኤል ንጉሥ በዳዊት መመሪያ መሠረት
እግ ዚአብሔርን ለመወደስ ስፍራቸውን ያዙ።
11በውዳሴና በምስጋናም ለእግዚአብሔር እንዲህ
ሲሉ ዘመሩ፤
"ቸር ነውና፤ ለእስራኤልም ምሕረቱ ለዘላ
ለም ነውና።" የእግዚአብሔር ቤት መሠረት ስለ
ተጣለ፣ ሕዝቡ ሁሉ በታላቅ ድምፅ እልል
እያሉ፣ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረቡ።
12የቀድሞውን ቤተ መቅደስ ያዩ በዕድሜ
የሸመገሉ ብዙ ካህናት፣ ሌዋውያንና የቤተ
ሰብ አለቆች የዚህ ቤተ መቅደስ መሠረት
ሲጣል ባዩ ጊዜ፣ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው
አለቀሱ፤ ሌሎቹ ግን የደስታ ጩኸት
አሰሙ። 13የሕዝቡ ጩኸት ድብልቅልቅ
ያለ ስለ ነበር፣ የደስታውን እልልታ
ከልቅሶው ጩኸት መለየት የሚችል ማንም
አልነበረም፤ ድምፁም ከሩቅ ይሰማ ነበር።

## ቤተ መቅደሱ እንዳይሠራ የተነሣ ተቃውሞ

4 የይሁዳና የብንያም ጠላቶች ከምርኮ
የተመለሱት ሰዎች የእስራኤልን አምላክ
የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ በመሥራት
ላይ መሆናቸውን ሲሰሙ፣ 2ወደ ዘሩባቤልና
ወደ ቤተ ሰቡ አለቆች መጥተው፣ "እኛም
እንደ እናንተ አምላካችሁን የምንፈልግ ነን፤
የአሦር ንጉሥ አስራዶን ወደዚህ ካመጣን ጊዜ
ጀምሮ ለእርሱ ስንሠዋለት ቈይተናል፤ ስለዚህ
አብረን ከእናንተ ጋር እንሥራ" አሏቸው።
3ዘሩባቤል፣ ኢያሱና ሌሎቹ የእስራኤል
ቤተ ሰቦች አለቆች ግን፣ "ለአምላካችን ቤተ
መቅ ደስ እንድትሠሩ ከእኛ ጋር
የሚያገናኛችሁ ምንም ነገር የለም። የፋርስ
ንጉሥ ቂሮስ ባዘዘን መሠረት ለእስራኤል
አምላክ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የምን
ሠራው እኛ ብቻ ነን" ሲሉ መለሱላቸው።
4ከዚያም የምድሪቱ ነዋሪዎች የይሁ
ዳን ሕዝብ ተስፋ ማስቈረጥና ሥራውንም
እንዳይቀጥሉ ማስፈራራት ጀመሩ[ሸ]። 5ከፋርስ
ንጉሥ ከቂሮስ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ እስከ
ፋርስ ንጉሥ እስከ ዳርዮስ ዘመነ መንግሥት
ድረስ ዕቅዶቻቸውን የሚያሰናክሉ መካሪዎችን
በገንዘብ ገዙባቸው።

## በጠረክሲስና በአርጤክስስ ዘመን የተደረገ ሌላው ተቃውሞ

6በአርጤክስስ ዘመነ መንግሥት መጀመ
ሪያ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ላይ
የጽሑፍ ክስ መሠረቱባቸው።
7በፋርስ ንጉሥ በአርጤክስስ ዘመን ቢሽ
ላም፣ ሚትሪዳጡ፣ ጣብኤልና ተባባሪዎቹ
ወደ አርጤክስስ ደብዳቤ ጻፉ። ደብዳቤው
የተጻፈው በአረማይስጥ ፊደል፣ በአረማይ
ስጥ ቋንቋ ነበረ[ቀቀ]።
8አገረ ገዡ ሬሁምና ጸሓፊው ሲምሳይ
በኢየሩሳሌም ላይ ለንጉሡ ለአርጤክስስ እን
ዲህ የሚል ደብዳቤ ጻፉ፤
9ደብዳቤው የተጻፈው፣ ከአገረ ገዡ
ሬሁም፣ ከጸሓፊው ሲምሳይ በትሪፖሊስ፣
በፋርስ፣ በአ ርክ፣ በባቢሎን፣ እንዲሁም በሱሳ
ማለትም በኤላማውያን ላይ ዳኞችና ገዦች
ከሆኑት ከተባባሪዎቻቸው፣ 10ደግሞም ታላቁና
ኀያሉ አስናፈር[በ] አፍልሶ በሰማርያ ከተማና
ከኤፍራጥስ

3፥5 ዘሌ23፥1ኛ44፤ ዘኍ28፥14፤29፥39፤ ሐሳ2፥16
3፥7 1ዜና14፥1፤ 22፥15፤ዕዝ1፥2ኛ4፤ ኢሳ35፥2፤60፥13
3፥8 ዘኍ4፥3፤ 1ዜና6፥1፤ዘካ4፥9
3፥9 ዕዝ2፥40
3፥10 ዘኍ10፥2፤ 2ሳሙ6፥5፤1ዜና6፥31፤ 16፥6፤25፥1፤2ዜና5፥13፤ ዕዝ5፥16፤6፥3፤ነህ12፥35፤ ሐጌ2፥15፤ዘካ6፥12
3፥11 ኢሱ6፥5፡10፤ 1ዜና16፥34፡41፤ 2ዜና7፥3፤መዝ30፥5፤107፥1፤118፥1፤138፥8፤ ሐጌ2፥18፤ዘካ4፥9፤8፥9
3፥12 ኤር31፥9፤ 50፥4፤ሐጌ2፥3፡9
3፥13 አዩ8፥21፤ 33፥26፤ መዝ27፥6፤ 42፥4፤ኢሳ16፥9፤ ኤር48፥33
4፥1 ነህ2፥20
4፥2 2ነገ17፥24፡41
4፥3 ዕዝ1፥1ኛ4
4፥4 ዕዝ3፥3
4፥6 አስ1፥1፤3፥13፤ 9፥5፤ዳን9፥1
4፥7 2ነገ18፥26፤ ዕዝ7፥1፤ነህ2፥1፤ ኢሳ36፥11፤ዳን1፥4፤2፥4
4፥9 ቍ23፤ ዘፍ10፥10፤ዕዝ5፥6፤ 6፥6፡13፤ነህ1፥1፤ አስ1፥2፤ዳን8፥2
4፥10 ቍ17፤ 2ነገ17፥24፤ነህ4፥2

[ሰ]9 ዕብራይስጡ፣ ይሁዳ ይላል፤ ምናልባት ከዮሐዳያ ጋር ተመሳሳይ ነው።
[ሸ]4 ወይም፣ ቤተ መቅደሱን ለመሥራት ሲነሡ አወኳቸው።
[ቀ]7 ወይም፣ በአረማይስጥ ቋንቋ ተጽፎ በዚያው ቋንቋ የተተረጐመ።
[ቀ]7 ዕዝ 4፥8-6፥18 ያለው ክፍል የተጻፈው በአረማይስጥ ቋንቋ ነው።
[በ]10 በአረማይስጥ ቋንቋ "አሹርባኒጳል" ማለት ነው።

ወንዝ ማዶ እንዲሰፍሩ ካደረጋቸው ሌሎች ሕዝ
ቦች ነው።
11የላኩለት ደብዳቤ ቅጅ ይህ ነው፤

ለንጉሥ አርጤክስስ፣

በኤፍራጥስ ወንዝ ማዶ ከሚኖሩት አገልጋ
ዮችህ የተላከ፤
12ከአንተ ዘንድ ወደ እኛ የመጡት አይሁ
ዳውያን ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ዐመፀኛና
ርኩስ ከተማ እንደ ገና በመሥራት ላይ ናቸው፤
ቅጥሮቿንም እንደ ገና በመሥራትና መሠ
ረቶቿንም በመጠገን ላይ መሆናቸው በንጉሡ
ዘንድ የታወቀ ይሁን።
13ከዚህም በላይ ይህች ከተማ ከተሠራች፣
ቅጥሮቿም እንደ ገና ከተገነቡ፣ ቀረጥና እጅ
መንሻ ወይም ግብር እንደማይከፍሉ፣ የቤተ
መንግሥቱም ገቢ እንደሚቀንስ በንጉሡ
ዘንድ የታወቀ ይሁን። 14አሁንም እኛ ስለ
ቤተ መን ግሥቱ ስለሚገደን፣ የንጉሡም
ክብር ሲነካ ዝም ብሎ ማየት ተገቢ ሆኖ
ስላላገኘነው፣ ይህ ነገር በንጉሡ ዘንድ
የታወቀ እንዲሆን ይህን መልእክት ልከናል፤
15ስለዚህ በአባቶችህ ቤተ መዛግብት ምርመራ
ይደረግ፤ በእነዚህ መዛግብት ውስጥ ይህች
ከተማ ዐመፀኛ ከተማ እንደ ሆነች፣
ነገሥታትንና አውራጃዎችን የጐዳችና
ከጥንት ጀምሮ የዐመፅ ጐሬ ስለ መሆኗ
ማስረጃ ታገኛለህ፤ እንግዲህ ከተማዪቱ
የተደመሰሰችው በዚህ ምክንያት ነው።
16ይህች ከተማ ተመልሳ የምትሠራና
ቅጥሮቿም እንደ ገና የሚገነቡ ከሆነ፣ ከኤፍራ
ጥስ ማዶ ምንም ነገር እንደማይኖርህ ንጉሥ
ታውቅ ዘንድ እንወዳለን።
17ንጉሡም ይህን መልስ ላከ፤
ለአገረ ገዡ ሬሁም፣ ለጸሓፊው ሲም
ሳይ፣ በሰማርያና በኤፍራጥስ ማዶ ለሚ
ኖሩ ተባባሪዎቻቸው፤

ሰላም ለእናንተ ይሁን፤

18የላካችሁልኝ ደብዳቤ በፊቴ ተተርጕሞ
ተነቧል። 19እኔም ትእዛዝ ሰጥቼ ምርመራ
ተደርጎአል፤ በምርመራውም መሠረት ይህች
ከተማ ከጥንት ጀምሮ በነገሥታት ላይ ስታምፅ
የኖረች የዐመፅና የወንጀል መናኸሪያ
እንደ ሆነች ማስረጃ ተገኝቶአል። 20ኢየሩ
ሳሌም ከኤፍራጥስ ማዶ ያለውን አገር ሁሉ
የገዙ፣ ቀረጥ፣ ግብርና እጅ መንሻም ይቀበሉ
የነበሩ ኀያላን ነገሥታት ነበሯት። 21አሁንም
እኔ ትእዛዝ እስከምሰጥበት ድረስ ይህች ከተማ
እንደ ገና እንዳትሠራ ሥራውን ያቆሙ ዘንድ
ለእነዚህ ሰዎች ትእዛዝ አስተላልፉ።
22ይህን ነገር ቸል እንዳትሉ ተጠንቀቁ፤
በነገሥታቱ ላይ የሚደርሰው ኪሣራ ለምን
እየበዛ ይሄዳል?

23የንጉሡ የአርጤክስስ ደብዳቤ ቅጅ በሬ
ሁም፣ በጸሓፊው በሲምሳይና በተባባሪዎ
ቻቸው ፊት እንደ ተነበበ፣ ወዲያውኑ
በኢየሩሳሌም ወደሚገኙት አይሁድ ሄደው
ሥራውን እንዲያቆሙ አስገደዷቸው።
24ስለዚህም በኢየሩሳሌም የሚሠራው
የእግዚአብሔር ቤት ሥራ እስከ ፋርስ ንጉሥ
እስከ ዳርዮስ ዘመነ መንግሥት ሁለተኛ
ዓመት ድረስ ተቋረጠ።

### *ለዳርዮስ የተላከ የተንትናይ ደብዳቤ*

5 በዚያን ጊዜ ነቢዩ ሐጌና የአዶ ልጅ
ነቢዩ ዘካርያስ፣ በይሁዳና በኢየሩሳሌም
ለሚኖሩ አይሁድ ከእነርሱ በላይ በሆነው
በእስራኤል አምላክ ስም ትንቢት ተናገሩ
ላቸው። 2ከዚያም የሰላትያል ልጅ ዘሩ
ባቤልና የኢዮሴዴቅ ልጅ ኢያሱ በኢየሩ
ሳሌም ያለውን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እንደ
ገና ለመሥራት ተነሡ፤ የሚያግዟቸውም *የእግዚ
አብሔር ነቢያት* አብረዋቸው ነበሩ።
3በዚህ ጊዜ በኤፍራጥስ ማዶ ገዥ
የነበረው ተንትናይ፣ ሰተርቡዝናይና ተባባሪዎ
ቻቸው ሄደው፣ "ይህን ቤተ መቅደስ እንደገና
ለመሥራትና ውቅሩንም ለመጠገን የፈቀደ
ላችሁ ማን ነው?" ሲሉ ጠየቋቸው።
4ደግሞም፣ "ይህን ሕንጻ የሚገነቡት ሰዎች ስም
ማን ይባላል?" በማለት ጠየቋቸው[†]።
5የአምላካቸው
ዐይን ግን በአይሁድ መሪዎች ላይ ነበረ፤
ነገሩ ወደ ዳርዮስ ደርሶ የጽሑፍ መልስ
እስኪያገኙ ድረስ አልተከለከሉም።
6በኤፍራጥስ ማዶ ገዥ የነበረው ተንትናይ፣
ሰተርቡዝናይ፣ ተባባሪዎቻቸውና በኤፍራጥስ
ማዶ የነበሩ ሹማምንት ለንጉሥ ዳርዮስ
የላኩት ደብዳቤ ቅጅ ይህ ነው፤ 7የላኩትም
ደብዳቤ
እንዲህ የሚል ነበር፤

ለንጉሥ ዳርዮስ፣

የከበረ ሰላምታ እናቀርባለን።

8የታላቁ አምላክ ቤተ መቅደስ ወደሚገኝበት
ወደ ይሁዳ አውራጃ ሄደን እንደ ነበር በንጉሡ
ዘንድ የታወቀ ይሁን። ሕዝቡ ቤተ
መቅደሱን በታላላቅ ድንጋዮች እየገነቡና
ቅጥሩንም በወፍራም ምሰሶዎች እየሠሩ ነው፤
ሥራው በትጋት በመከናወንና በእነርሱም
አመራር በመፋጠን ላይ ይገኛል።
9እኛም መሪዎቹን፣ "ይህን ቤተ መቅ
ደስ እንደ ገና ለመሥራትና ይህንም ውቅር
ለመጠገን የፈቀደላችሁ ማን ነው?" ብለን
ጠየቅናቸው። 10የመሪዎቻቸውን ስም በጽ
ሑፍ እናሳውቅህ ዘንድ ስማቸውን ደግሞ
ጠየቅን።

4፥12 ዕዝ5፥3፡9
4፥13 ዕዝ7፥24፤
ነህ5፥4
4፥15 ዕዝ5፥17፤
6፥1፤አስ3፥8
4፥17 ቀኍ10
4፥19 2ነገ18፥7
4፥20 ዘፍ15፥18ኛ21፤
ዙ23፥31፤ኢሱ1፥4፤
1ነገ4፥21፤1ዜና18፥3፤
መዝ72፥8ኛ11
4፥22 ዳን6፥2
4፥23 ቀኍ9
4፥24 ነህ2፥1ኛ8፤
ዳን9፥25፤ሐጌ1፥1፡15፤
ዘካ1፥1
5፥1 ዕዝ6፥14፤
ሐጌ1፥1፡3፡12፡14፤
2፥1፡9፡10፡20፤ዘካ1፥1፤
4፥9ኛ10፤7፥1፤8፥9
5፥2 ቀኍ8 1ዜና3፥19፤
ዕዝ2፥2፤ሐጌ1፥14፤
2፥2፤5፡21፤ዘካ4፥6ኛ10
5፥3 ዕዝ4፥12፤6፥6
5፥5 2ነገ25፥28፤
ዕዝ7፥6፡9፡28፤8፥18፡
22፡31፤ነህ2፥8፡18፤
መዝ33፥18፤ኢሳ66፥14
5፥8 ቀኍ2
5፥9 ዕዝ4፥12

[†]4 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ይመ፤ የአረማይስጡ ትርጒም
እንዲህ ይላል፣ *ይህን ሕንጻ የሚገነቡትን ሰዎች ስም ነገር ናቸው።*

11የሰጡን መልስ ይህ ነው፤
“እኛ የሰማይና የምድር አምላክ
አገልጋዮች ነን፤ አሁንም እንደ ገና የምንሠራ
ው ቤተ መቅደስ፣ ከብዙ ዘመናት በፊት
ታላቁ የእስራኤል ንጉሥ ሠርቶ
የጨረሰውን ነው። 12ነገር ግን አባቶቻችን
የሰማይን አምላክ አስቈጥተውት ስለ ነበር፣
ለባቢሎኑ ንጉሥ ለከለዳዊው ናቡከደነፆር
አሳልፎ ሰጣቸው፤ እርሱም ይህን ቤተ
መቅደስ አፈራርሶ ሕዝቡን ወደ ባቢሎን አፈለሰ።
13“ይሁንና ቂሮስ፣ የባቢሎን ንጉሥ በሆነ
በመጀመሪያው ዓመት ይህን የእግዚአብሔር ቤት
እንደ ገና እንዲሠሩ ንጉሥ ቂሮስ ትእዛዝ ሰጠ።
14ናቡከደነፆር ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ
አውጥቶ ባቢሎን በሚገኘው ቤተ መቅደስ[ቶ]
ውስጥ ያኖራቸውን የእግዚአብሔርን ቤት
የወርቅና የብር
ዕቃዎች ከባቢሎን ቤተ መቅደስ አስመጣ።
‘ከዚያም ንጉሥ ቂሮስ፣ አገረ ገዥ አድርጎ
ለሾመውና ሰሳብሳር ተብሎ ለሚጠራው ሰው
ሰጠው፤ 15‘ቀጥሎም እነዚህን ዕቃዎች ይዘህ
ሂድና በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ
አኑራቸው፤ የእግዚአሔር ቤት ቀድሞ
በነበረበት ቦታ እንደ ገና ይሠራ አለው። 16ስለ
ዚህ ይህ ሰሳብሳር መጥቶ በኢየሩሳሌም
የሚገኘውን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ
መሠረት ጣለ፤ ከዚያን ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ
ድረስ እነሆ በመሠራት ላይ ነው፤ ሆኖም
ገና አላለቀም።
17አሁንም ንጉሡን ደስ የሚያሰኘው ቢሆን፣
ይህ የእግዚአብሔር ቤት በኢየሩሳሌም እንዲሠራ
ንጉሥ ቂሮስ በእርግጥ ትእዛዝ ሰጥቶ
እንደ ሆነ በባቢሎን ቤተ መንግሥት
ግምጃ ቤት የተቀመጡት መዛግብት
እንዲመረመሩ ያድርግ፤ ከዚያም ንጉሡ
ስለዚህ ጉዳይ የወሰነውን ይላክልን።”

### *የዳርዮስ ዐዋጅ*

6 ከዚያም ንጉሥ ዳርዮስ በባቢሎን
ግምጃ ቤት የተቀመጡት መዛግብት
እንዲመረመሩ ትእዛዝ ሰጠ። 2በሜዶን አውራጃ
በሚገኘው በአሕምታ ከተማ አንድ ጥቅልል
ብራና ተገኘ፤ በውስጡም እንዲህ የሚል
ቃል ተጽፎበት ነበር፤

ማስታወሻ፤

3በንጉሥ ቂሮስ የመጀመሪያው ዓመት
በኢየሩሳሌም ስለሚገኘው የእግዚእብሔር
ቤተ መቅደስ ንጉሡ የሰጠው ትእዛዝ ይህ
ነው፤

ቤተ መቅደሱ መሥዋዕት የሚቀርብበት
ቦታ ሆኖ እንደ ገና ይሠራ፤ መሠረቱም ይጣል፤
ቁመቱ ሥልሳ ክንድ[ጎ]፣ ወርዱም ሥልሳ ክንድ
ይሁን፤ 4በሦስት ዙር ታላላቅ ድንጋዮችና

5፥11 1ነገ6፥1፤ 2ዜና3፥1ኛ2
5፥12 ዘዳ21፥10፤ 28፥36፤2ነገ24፥1፤ 2ዜና36፥16፤ኤር1፥3
5፥13 ዕዝ1፥2ኛ4
5፥14 1ዜና3፥18፤ ዕዝ1፥7
5፥16 ዕዝ3፥10
5፥17 ዕዝ4፥15
6፥1 ዕዝ4፥15
6፥3 ዕዝ3፥10፤ ሐጌ2፥3
6፥4 ቊ8፤ 1ነገ6፥36፤ዕዝ7፥20
6፥5 1ዜና29፥2፤ ዕዝ1፥7
6፥6 ዕዝ5፥3
6፥8 ቊ4፤ሳሙ9፥20
6፥9 ዘሌ1፥3፡10
6፥10 ዕዝ7፥23፤ 1ጢሞ2፥1ኛ2
6፥11 ዘዳ21፥22ኛ23፤ አስ2፥23፤5፥14፤ 9፥14፤ዕዝ7፥26፤ ዳን2፥5፤3፥29፤
6፥12 ቊ14፤ ዘ20፥24፤ዘዳ12፥5፤ 2ዜና6፥2
6፥13 ዕዝ4፥9
6፥14 ቊ12፤ ዕዝ1፥2ኛ4፤5፥1፤ 7፥1፤ ነህ2፥1

በአንድ ዙር ዕንጨት ይሠራ፤ ውጪም ከቤተ
መንግሥቱ ግምጃ ቤት ይከፈል። 5እንዲሁም
ናቡከደነፆር በኢየሩሳሌም ከሚገኘው ቤተ
መቅ ደስ አውጥቶ ወደ ባቢሎን የወሰዳቸው
የእግዚአብሔር ቤት የወርቅና የብር ዕቃዎች፣
በኢየሩሳሌም ወዳለው ቦታቸው ወደ ቤተ
መቅደሱ እንዲመለሱ ይሁን፤ በእግዚአብሔርም
ቤት ይቀመጡ።

6አሁንም በኤፍራጥስ ማዶ አገረ ገዥ
የሆንኸው ተንትናይ፣ ሰተርቡዝናይና እናን
ተም በዚያ አውራጃ የምትገኙ ተባባሪዎ
ቻቸው ሁሉ ወደዚያ አትድረሱ። 7በዚህም
በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሥራ ጣልቃ አት
ግቡ፤ ይህን የእግዚአብሔርን ቤት የአይሁድ
አገረ ገዥና የአይሁድ መሪዎች በቀድሞው
ቦታ ላይ መልሰው ይሥሩት።

8በተጨማሪም የአይሁድ መሪዎች ይህን
የእግዚአብሔር ቤት እንደ ገና ሲሠሩ፣ እናንተ
ምን እንደ ምታደርጉላቸው ይህን ትእዛዝ
ሰጥቻለሁ፤ ሥራውም እንዳይቋረጥ የእነዚህ
ሰዎች ወጪ በሙሉ ከመንግሥት ግምጃ
ቤትና ከኤፍራጥስ ማዶ ከሚገኘው ገቢ ላይ
ይከፈል። 9ለሰማይ አምላክ የሚቃጠል መሥ
ዋዕት ይሆን ዘንድ የሚያስፈልጋቸውን ነገር፣
ማለት ወይፈኖችን፣ አውራ በጎችንና ተባዕት
ጠቦቶችን ስጧቸው፤ እንዲሁም ስንዴው፣
ጨው፣ የወይን ጠጁና ዘይቱ በኢየሩሳሌም
ያሉት ካህናት በሚጠይቋችሁ መሠረት ያለ
ማቋረጥ በየቀኑ ይሰጣቸው። 10ይህ የሚሆነው
የሰማይ አምላክን ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት
እንዲያቀርቡ፣ ለንጉሡና ለወንድ ልጆቹም
ደኅን ነት እንዲጸልዩ ነው።

11ደግሞም ይህን ትእዛዝ የሚለውጥ
ማንም ሰው ቢኖር፣ ከቤቱ ምሰሶ ተነቅሎ
በምሰሶው ላይ እንዲሰቀል፣ ስለ ወንጀሉም
ቤቱ የቈሻሻ መጣያ እንዲሆን አዝዣለሁ።
12ይህን ትእዛዝ ለማፍረስ ወይም በኢየሩሳሌም
የሚገኘውን ቤተ መቅደስ ለማጥፋት እጁን
የሚያነሣ ማንኛውንም ንጉሥ ወይም ሕዝብ፣
ስሙን በዚያ እንዲኖር ያደረገ አምላክ ያጥፋው።

እኔ ዳርዮስ በትጋት እንዲፈጸም ይህን
ትእዛዝ ሰጥቻለሁ።

### *የቤተ መቅደሱ ሥራ ፍጻሜና ምረቃ*

13ከዚያም ንጉሡ ዳርዮስ ባዘዘው መሠ
ረት በኤፍራጥስ ማዶ አገረ ገዥ የነበረው
ተንትናይ፣ ሰተርቡዝናይና ተባባሪዎቻቸው
ሥራው በትጋት እንዲፈጸም አደረጉ።
14ስለዚህ የአይሁድ መሪዎች በነቢዩ በሐ
ጌና በአዶ ልጅ በዘካርያስ ትንቢት እየተ
ጽናኑ ሥራውን ቀጠሉ፤ የቤተ መቅደሱንም
ሥራ በእስራኤል አምላክ ትእዛዝ እንዲሁም

[ጎ]3 27 ሜትር ያህል ነው።
[ቶ]14 ወይም፣ *ቤተ መንግሥት*

የፋርስ ነገሥታት ቂሮስ፣ ዳርዮስና አርጤክስስ በሰጡት ትእዛዝ መሠ ረት ሠርተው ጨረሱ። 15ይህም ቤተ መቅደስ ንጉሥ ዳርዮስ በነገሠ በስድስተኛው ዓመት አዳር ተብሎ በሚጠራው ወር በሦስተኛው ቀን ተጠ ናቀቀ።

16ከዚያም የእስራኤል ሕዝብ፣ ካህናቱ፣ ሌዋውያኑና የቀሩትም ምርኮኞች የእግዚአብሔርን ቤት ምረቃ በዓል በደስታ አከበሩ። 17ለዚህ ለእግዚአብሔር ቤት ምረቃም አንድ መቶ ወይፈ ኖችን፣ ሁለት መቶ አውራ በጎችንና አራት መቶ ተባዕት ጠቦቶችን ሰጡ፤ ለመላው እስራኤል የኀጢአት መሥዋዕትም ዐሥራ ሁለት ተባ ዕት ፍየሎችን በእያንዳንዱ የእስራኤል ነገድ ልክ አቀረቡ። 18በሙሴ መጽሐፍ በተጻፈው መሠረት በኢየሩሳሌም ላለው ለእግዚአብሔር አገልግሎት ካህናቱን በየማዕረጋቸው፣ ሌዋ ውያኑንም በየክፍላቸው መደቧቸው።

*የፋሲካ በዓል*

19ምርኮኞቹ በመጀመሪያው ወር በዐሥራ አራተኛው ቀን የፋሲካን በዓል አከበሩ። 20ካህናቱና ሌዋውያኑ ራሳቸውን አነጹ፤ ሁሉም በሥርዐቱ መሠረት ነጽተው ነበር። ሌዋውያ ኑም የፋሲካውን በግ ለምርኮኞቹ ሁሉ፣ ለካህናት ወንድሞቻቸውና ለራሳቸው ዐረዱ። 21ስለዚህ ከምርኮ የተመለሱት እስራኤላውያን የእስራ ኤልን አምላክ *እግዚአብሔርን* በአምልኮ ይፈል ጉት ዘንድ ራሳቸውን ከአረማውያን ጎረቤቶቻ ቸው ርኩሰት ከለዩት ሁሉ ጋር በሉ። 22*እግዚ አብሔር* ደስ እንዲሰኙ ስላደረጋቸው የቂጣን በዓል ሰባት ቀን በደስታ አከበሩ፤ ምክንያቱም *እግዚአብሔር* የአሦርን ንጉሥ ልብ ለውጦ በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ቤት ሥራ እንዲያግዛቸው አድርጎ ነበር።

*ዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ*

7 ከእነዚህም ነገሮች በኋላ በፋርስ ንጉሥ በአርጤክስስ ዘመነ መንግ ሥት፣ ዕዝራ የሠራያ ልጅ፣ የዓዛርያስ ልጅ፣ የኬልቅያስ ልጅ 2የሰሎም ልጅ፣ የሳዶቅ ልጅ፣ የአኪጦብ ልጅ፣ 3የአማርያ ልጅ፣ የዓዛርያስ ልጅ፣ የመራዮት ልጅ፣ 4የዘ ራእያ ልጅ፣ የኦዚ ልጅ፣ የቡቂ ልጅ፣ 5የአ ቢሱ ልጅ፣ የፊንሐስ ልጅ፣ የአልዓዛር ልጅ፣ የታላቁ ካህን የአሮን ልጅ፣ 6ይህ ዕዝራ ከባቢሎን መጣ። እርሱም የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር* ለሙሴ የሰጠውን ሕ ግ በሚ ገባ የሚያውቅ የሕግ መምህር ነበር። የአምላኩ *የእግዚአብሔር* እጅ በእርሱ ላይ ስለ ነበ ረች፣ የጠየቀውን ሁሉ ንጉሡ ፈቀደለት። 7እንደዚሁም አንዳንድ እስራ ኤላውያን፣ ከካ ህናት፣ ከሌዋውያን፣ ከመዘም ራን፣ ከበር ጠባ ቂዎችና ከቤተ መቅደሱ

6፥15 ዘካ1፥1፤4፥9
6፥16 1ነገ8፥63
6፥17 2ሳሙ6፥13፤ 2ዜና29፥21፤30፥24
6፥18 ዘኍ3፥6ኛ9፤ 8፥9ኛ11፤18፥1ኛ32፤ 1ዜና24፥1፤ 2ዜና35፥4፤ሉቃ1፥5
6፥19 ዘ12፥11፤ ዘኍ28፥16
6፥20 2ዜና30፥17
6፥21 ዘዳ18፥9፤ 1ዜና22፥19፤ዕዝ9፥1፤ ነህ9፥2፤መዝ14፥2፤ ሕዝ36፥25
6፥22 ዘ12፥17፤ ዕዝ1፥1
7፥1 2ነገ22፥4፤ 25፥18፤ ዕዝ4፥7፤6፥14
7፥2 1ነገ1፥8፤ 2፥35፤1ዜና6፥8፤ ነህ11፥11፤ሕዝ40፥46፤ 43፥19፤44፥15
7፥5 1ዜና6፥4
7፥6 2ነገ25፥28፤ ዕዝ5፥5፤ነህ12፥36፤ ኢሳ41፥20
7፥7 ዕዝ8፥1
7፥9 ቀኍ6
7፥10 ዘዳ33፥10
7፥12 ሕዝ26፥7፤ ዳን2፥37
7፥14 አስ1፥14
7፥15 ዘዳ12፥5፤ 1ዜና29፥6፤2ዜና6፥2
7፥16 ዘ3፥22፤ ዘካ6፥10
7፥17 ዘኍ15፥5ኛ12፤ ዘዳ12፥5ኛ11፤ 2ነገ3፥4
7፥19 ዕዝ5፥14፤ ኤር27፥22
7፥20 ዕዝ6፥4

አገልጋዮች ጋር በመሆን በንጉሡ በአርጠ ክስስ ዘመነ መን ግሥት በሰባተኛው ዓ መት ወደ ኢየሩሳሌም መጡ።

8ዕዝራ በንጉሡ ሰባተኛ ዓመት በአምስተ ኛው ወር ኢየሩሳሌም ደረሰ። 9መልካሚቱ የእግዚአብሔር እጅ በእርሱ ላይ ስለ ነበረች፣ ከባቢሎን በመጀመሪያው ወር በመጀመ ሪያው ቀን ተነሥቶ በአምስተኛው ወር በመ ጀመሪያው ቀን ኢየሩሳሌም ደረሰ። 10ዕዝራ የእግዚአብሔርን ሕግ በማጥናትና በ ማድረግ፣ ለእስራኤልም ሥርዐቱንና ሕጉን በ ማስተማር ራሱን ፈጽሞ ሰጥቶ ነበር።

*ንጉሥ አርጤክስስ ለዕዝራ የሰጠው ደብዳቤ*

11እግዚአብሔር ለእስራኤል የሰጠ ውን ሕግና ትእዛዝ ዐዋቂ ለነበረው ለካህኑና ለመምህሩ ዕዝራ ንጉሥ አርጤክስስ የሰጠው የደብዳቤ ቅጅ ይህ ነው፤

12ከንጉሠ ነገሥት አርጤክስስ'፤ ለሰ ማይ አምላክ ሕግ መምህር ለሆነው ለካህኑ ለዕዝራ፤

ሰላም ለአንተ ይሁን፤

13ካህናቱንና ሌዋውያኑን ጨምሮ በመንግ ሥቴ ውስጥ የሚኖርና ከአንተ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ የሚፈልግ ማንኛ ውም እስራኤላዊ መሄድ እንዲችል ይህን ትእዛዝ ሰጥቻለሁ። 14በእጅህ በሚገኘው በአ ምላክህ ሕግ መሠረት፣ ስለ ይሁዳና ስለ ኢየ ሩሳሌም እንድትመረምር በንጉሡና በሰባት አማካሪዎቹ ተልከሃል። 15ከዚህም በላይ፣ ንጉሡና አማካሪዎቹ መኖሪያው በኢየሩሳ ሌም ለሆነው ለእስራኤል አምላክ በፈቃዳ ቸው የሰጡትን ብርና ወርቅ ይዘህ ሂድ፤ 16እንዲሁም ከመላው ባቢሎን አውራጃ የም ታገኘውን ብርና ወርቅ በሙሉ፣ ሕዝቡና ካህናቱም በኢየሩሳሌም ላለው ለአምላካቸው ቤተ መቅደስ በፈቃዳቸው የሚሰጡትን መባ ሁሉ ይዘህ ሂድ። 17በዚህም ገንዘብ ወይፈ ኖችን፣ አውራ በጎችንና ጠቦቶችን፣ ከእህል ቍርባኖቻቸውና ከመጠጥ ቍርባኖቻቸው ጋር መግዛት እንዳለብህ አትርሳ፤ እነዚ ህንም በኢየሩሳሌም በሚገኘው በአምላካችሁ ቤተ መቅደስ መሠዊያ ላይ አቅርብ። 18ከዚህ የሚቀረውንም ብርና ወርቅ አንተና ወንድሞ ችህ አይሁድ እንደ አምላካችሁ ፈቃድ ደስ ለሚላችሁ ነገር ሁሉ አውሉት። 19ለአምላክህ ቤተ መቅደስ በዐደራ የተሰጠ ህንም ዕቃ ሁሉ በኢየሩሳሌም አምላክ ፊት አቅርብ። 20ከዚህም

'12 በዕዝ 7፥12ኛ26 ላይ የሚገኘው ክፍል የተጻፈው በአረማይስጥ ቋንቋ ነው።

በላይ ለአምላክህ ቤተ መቅደስ ለመስጠት
የምትፈ ልገውን ነገር ሁሉ ከንጉሡ ግምጃ ቤት
መውሰድ ትችላለህ።
21በኤፍራጥስ ማዶ የምትገኙ በጅሮን
ዶች ሁሉ፣ የሰማይ አምላክ ሕግ መምህር
የሆነው ካህኑ ዕዝራ የሚጠይቃችሁን ሁሉ
በትጋት እንድትሰጡት እኔ ንጉሥ አርጤ
ክስስ እነሆ አዝዣለሁ፤ 22እስከ አንድ
መቶ መክሊት[ኘ] ብር፣ እስከ አንድ መቶ ቆሮሶ
ስንዴ፣ እስከ አንድ መቶ ባዶስ[ከ] መስፈሪያ
ወይን ጠጅ፣ እስከ አንድ መቶ ባዶስ የወይራ
ዘይትና የሚፈለገውን ያህል ጨው ስጡት።
23የሰማይ አምላክ የሚያዘው ሁሉ፣ ለሰማይ
አምላክ ቤተ መቅደስ በፍጹም ትጋት ይደ
ረግ፤ በንጉሡና በልጆቹ መንግሥት ላይ
ለምን ቍጣ ይውረድ? 24ደግሞም በካህናቱ፣
በሌዋውያኑ፣ በመዘምራኑ፣ በበር ጠባቂዎቹ፣
በቤተ መቅደሱ አገልጋዮች ወይም በሌ
ሎቹ በዚህ በእግዚአብሔር ቤት ሠራተኞች ላይ
ቀረጥ፣ ግብርና እጅ መንሻ ለመጣል ሥልጣን
እንደ ሌላችሁ ይህን ዕወቁ።
25አንተም ዕዝራ ከአምላክህ እንደ ተሰጠህ
ጥበብ መጠን፣ ከኤፍራጥስ ማዶ ለሚገ
ኙት ሕዝቦች ሁሉ የአምላክህን ሕግ የሚያ
ውቁ ዳኞችንና ፈራጆችን ሹምላቸው፤ ሕጉን
የማያውቅ ሰው ቢኖር፣ አንተ ራስህ አስተ
ምረው። 26ለአምላክህ ሕግና ለንጉሡ ሕግ የማ
ይታዘዝ ማንኛውም ሰው፣ የሞት ወይም
የስደት ወይም የንብረት መወረስ ወይም
የእስራት ቅጣት ይፈጸምበት።
27በኢየሩሳሌም የሚገኘው *የእግዚአብሔር*
ቤት በዚህ ሁኔታ እንዲከበር ይህን በንጉሡ
ልብ ያኖረ የአባቶቻችን አምላክ *እግዚአብሔር*
ቡሩክ ይሁን፤ 28እንዲሁም በንጉሡ፣ በአ
ማ ካሪዎቹና በኀያላን ሹሞቹ ፊት ሁሉ
ሞገ ስን የሰጠኝ አምላክ የተመሰገነ ይሁን፤
የአም ላኬ *የእግዚአብሔር* እጅ በእኔ ላይ ስለ
ነበረች፣ አብረውኝ እንዲሄዱ ከእስራኤል
መካከል የታወቁ ሰዎችን ለመሰብሰብ ብር
ታት አገኘሁ።

### *ከዕዝራ ጋር የተመለሱት የየቤተ ሰቡ አለቆች ስም ዝርዝር*

8 በንጉሡ በአርጤክስስ ዘመነ መንግ
ሥት ከባቢሎን አብረውኝ የወጡት
የየቤተ ሰቡ አለቆችና አብረዋቸው የተመ
ዘገቡት እነዚህ ናቸው፤
2ከፊንሐስ ዘሮች ጌርሶን፤
ከኢታምር ዘሮች ዳንኤል፤
ከዳዊት ዘሮች ሐጡስ፤ 3እርሱም ከሴኬንያ
ዘሮች ነው፤
ከፋሮስ ዘሮች ዘካርያስና ከእርሱም
ጋር 150 ወንዶች ተመዝግበው ነበር፤

7፥23 ዕዝ6፥10
7፥24 ዕዝ4፥13፤ 8፥36
7፥25 ዘፀ18፥21፡26፤ ዘሌ10፥11
7፥26 ዕዝ6፥11
7፥27 ዕዝ1፥1፤ 1ዜና29፥12
7፥28 2ነገ25፥28፤ ዕዝ5፥5
8፥1 ዕዝ7፥7
8፥3 1ዜና3፥22፤ ዕዝ2፥3
8፥4 ዕዝ2፥6
8፥6 ዕዝ2፥15፤ ነህ7፥20፤10፥16
8፥13 ዕዝ2፥13
8፥15 ቀኍ21፡31፤ ዕዝ2፥40
8፥17 ዕዝ2፥43
8፥18 ቀኍ24፤ዕዝ5፥5

4ከፋሐት ሞዓብ ዘሮች የዘራእያ ልጅ
ኤሊሆዔናይና ከእርሱም ጋር 200 ወንዶች፤
5ከዛቱ[ኸ] ዘሮች የየሕዚኤል ልጅ ሴኬንያና
ከእርሱም ጋር 300 ወንዶች፤
6ከዓዲን ዘሮች የዮናታን ልጅ ዔቤ
ድና ከእርሱም ጋር 50 ወንዶች፤
7ከኤላም ዘሮች የጎቶልያ ልጅ የሻያና
ከእርሱም ጋር 70 ወንዶች፤
8ከሰፋጥያስ ዘሮች፣ የሚካኤል ልጅ
ዝባድያ፣ ከ80 ወንዶች ጋር፤
9ከኢዮአብ ዘሮች የይሒኤል ልጅ አብ
ድዩና ከእርሱ ጋር 218 ወንዶች፤
10ከባኒ[ወ] ዘሮች የዮሲፍያ ልጅ ሰሎ
ሚትና ከእርሱም ጋር 160 ወንዶች፤
11ከቤባይ ዘሮች የቤባይ ልጅ ዘካርያስ
ከእርሱም ጋር 28 ወንዶች፤
12ከዓዝጋድ ዘሮች የሃቃጣን ልጅ ዮሐ
ናንና ከእርሱም ጋር 110 ወንዶች፤
13ከአዶኒቃም ዘሮች፣ የመጨረሻዎቹ ስ
ማ ቸው ይህ ነው፤ ኤሊፋላት፣ ይዑኤልና ሸ
ማያ፣
ከእነርሱም ጋር 60 ወንዶች፤
14ከበጉዋይ ዘሮች ዑታይና ዘቡድ፣ ከእነ
ርሱም ጋር 70 ወንዶች።

### *ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ*

15እኔም ወደ አኅዋ በሚፈሰው ወንዝ
አጠገብ ሰዎቹን ሰበሰብኋቸው፤ በዚያም ሦስት
ቀን ቈየን፤ ሕዝቡንና ካህናቱን ስመለከት፣
ከሌዊ ወገን የሆነ አንድም ሰው በዚያ
አላገኘሁም። 16ስለዚህ መራሕያኑን አልዓ
ዛርን፣ አርኤልን፣ ሸማያን፣ ኤልናታ ንን፣
ያሪብን፣ ኤልናታንን፣ ናታንን፣ ዘካርያስ
ንና ሜሱላምን እንዲሁም መምህራኑን
ዮያሪብንና ኤልናታንን አስጠራኋቸው፤ 17እነ
ርሱንም ካሲፍያ በሚባል ስፍራ አለቃ
ወደ ሆነው ወደ አዶ ላክኋቸው፤ በአምላካ
ችን ቤት የሚያገለግሉ ሰዎችን ያመጡልን
ዘንድ በካሲፍያ የቤተ መቅደስ አገልጋዮች
ለሆኑት ለአዶና ለሥጋ ዘመዶቹ የሚናገሩ
ትን አስታወቅኋቸው። 18መልካሚቱ
የአምላ ካችን እጅ በእኛ ላይ ስለነበረች፣
ከሞሖሊ ዘሮች የእስራኤል ልጅ የሌዊ ልጅ
የሆነ ውን ሰራብያ ተብሎ የሚጠራውን
አስተዋይ ሰው፣ ከእርሱም ጋር ዐሥራ
ስምንት የሚ ሆኑ ወንዶች ልጆቹንና
ወንድሞቹን አመጡ ልን፤ 19እንዲሁም ሐ
ሸብያንና ከሜራሪ ዘሮች የሻያን፣

[ኘ]22 3.4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው።
[እ]22 22 ኪሎ ሊትር ያህል ነው።
[ከ]22 2.2 ኪሎ ሊትር ያህል ነው።
[ኸ]5 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች (እንዲሁም መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል 8፥22) ይህን ስም ይጨምራሉ፤ ዕብራይስጡ ግን ዛቱ የሚለውን አይጨምርም።
[ወ]10 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች (እንዲሁም መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል 8፥36) ይህን ስም ይጨምራሉ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ ባኒ የሚለውን አይጨምርም።

ከወንድሞቹና ከአጎቶቹ ወንዶች ልጆች ጋር
20 ወንዶችን አመጡልን። 20በተጨማሪም
ዳዊትና ሹማምቱ ሌዋውያኑን እንዲረዳ
ካቋቋሙት ከቤተ መቅደሱ አገልጋዮች ቡድን
220 አመጡ፤ እነዚህም ሁሉ በየስማቸው
ተመዘገቡ።

21ራሳችንን በአምላካችን ፊት ዝቅ
እንድናደርግ፣ ጕዞውም ለእኛና ለልጆቻችን፣
ለንብረታችንም ሁሉ የተቃና እንዲሆንልን፣
እዚያው በአኅዋ ወንዝ አጠገብ ጾም ዐወ
ጅሁ። 22"መልካሚቱ የአምላካችን እጅ
በሚፈልጉት ሁሉ ላይ ናት፤ እርሱን በሚ
ተዉ ሁሉ ላይ ግን ቍጣው ትወርድባ
ቸዋለች" ብለን ለንጉሡ ነግረነው ስለ ነበር፣
በመንገድ ላይ ከጠላት የሚጠብቁን ወታደ
ሮችንና ፈረሰኞችን እንዲሰጠን ንጉሡን
ለመጠየቅ ዐፍሬ ነበር። 23ስለዚህ ጾምን፤ ወደ
አምላካችንም ስለዚህ ነገር ልመና አቀረብን፤
እርሱም ጸሎታችንን ሰማ።

24እኔም ከዋና ዋናዎቹ ካህናትም ዐሥራ
ሁለት ሰዎችን፣ ከእነርሱም ጋር ሰራ
ብያን፣ ሐሸቢያንና ከወንድሞቻቸውም መካ
ከል ዐሥር ሰዎችን ለየሁ፤ 25ንጉሡ፣
አማካሪዎቹ፣ ሹሞቹና በዚያ የነበሩ እስራ
ኤል ሁሉ ለአምላካችን ቤት የሰጡትን ብር፣
ወርቅና ዕቃ ሁሉ መዝኜ ሰጠኋቸው።
26ስድስት መቶ አምሳ መክሊት[o] ብር፣
አንድ መቶ መክሊት የብር ዕቃዎች፣ አንድ
መቶ መክሊት ወርቅ፣ 27አንድ ሺህ ዳሪክ
[ፕ] የሚያወጡ ሃያ የወርቅ ወጭቶችና እንደ
ወርቅ ነጥረው ከሚያብረቀርቅ ናስ የተሠሩ
ሁለት ዕቃዎችን መዝኜ በእጃቸው አስረከ
ብኋቸው።

28እንዲህም አልኋቸው፤ "እናንተና እነ
ዚህ ዕቃዎች ለእግዚአብሔር ተቀድሳችኋል፤
ብሩና ወርቁ ለአባቶቻችሁ አምላክ ለእግዚ
አብሔር በበጎ ፈቃድ የቀረበ መባ ነው።
29ኢየሩሳሌም በሚገኘው በእግዚአብሔር
ቤት ክፍሎች ውስጥ በዋና ዋናዎቹ
ካህናት፣ በሌዋውያኑና በየቤተ ሰቡ የእስራ
ኤል አለ ቆች ፊት እስክትመዝኗቸው
ድረስ በጥን ቃቄ ጠብቋቸው።" 30ከዚያም
ካህናቱና ሌዋውያኑ ኢየሩሳሌም
ወደሚገኘው ወደ አምላካችን ቤት እንዲ
ሄድ የተመዘነውን ብር፣ ወርቅና ንዋያተ
ቅድሳት ተረከቡ።

31እኛም በመጀመሪያው ወር ዐሥራ
ሁለተኛው ቀን ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ
ከአኅዋ ወንዝ ተነሣን። የአምላካችን እጅ
በላያ ችን ነበረች፤ እርሱም ከጠላቶቻችንና
በመ ንገድ ላይ ከሚሸምቁ አዳነን። 32ኢየሩ
ሳሌምም ደረስን፤ በዚያም ሦስት ቀን ዐረ
ፍን።

8፥20 1ዜና9፥2
8፥21 ቍ15፤መዝ5፥8፤27፥11፤107፥7
8፥22 ዘዳ31፥17፤ዕዝ5፥5፤ነህ2፥9፤ኤር41፥16
8፥23 2ዜና20፥3፤ሐሥ14፥23
8፥24 ቍ18
8፥25 ቍ33
8፥28 ዘሌ21፥6፤22፥2ኛ3
8፥31 ቍ15፤ዕዝ5፥5
8፥32 ዘፍ40፥13
8፥33 ቍ25፤ነህ3፥4፡21፡24፤11፥16
8፥35 ዘሌ1፥3፤2ዜና29፥21፡24፤30፥24፡
8፥36 ዕዝ7፥21ኛ24፤ነህ2፥7፤አስ9፥3
9፥1 ዘፍ10፥16፤19፥37፡38፤ዙ13፥5፤23፥28፤ዘዳ20፥17፤ኢሱ3፥10፤15፥8፤መሳ3፥5፤1ነገ9፥20፤2ዜና8፥7፤ዕዝ6፥21፤ነህ9፥8
9፥2 ዙ22፥31፤34፥16፤ዘሌ27፥30፤ዘዳ14፥2፤ሩት1፥4፤ዕዝ10፥2፤መዝ106፥35
9፥3 ዙ32፥19፤33፥4፤ዘኍ14፥6
9፥4 ዕዝ10፥3፤ኢህ1፥4፤መዝ119፥120፡136፤ኢሳ66፥2፡5፤ዳን10፥2
9፥5 ዘ29፥41፤ ኢህ8፥6፤መዝ28፥2፤134፥2
9፥6 2ዜና28፥9፤ኢዮ42፥6፤መዝ38፥4፤ኢሳ59፥12፤ ኤር3፥25፤14፥20፤31፥19፤ራእ18፥5

33በአራተኛው ቀን ብሩን፣ ወርቁንና
ንዋያተ ቅድሳቱን በአምላካችን ቤት መዝ
ነን ለኦሪዮ ልጅ ለካህኑ ለሜሪሞት በእጁ
አስረ ከብነው፤ ከእርሱም ጋር የፊንሐስ
ልጅ አልዓዛር፣ ሌዋውያኑ የኢያሱ ልጅ
ዮዛባ ትና የቢንዊ ልጅ ኖዓድያ ነበሩ።
34ሁሉም ነገር ተቈጠረ፤ ተመዘነም፤
የተመዘነውም ሁሉ በዚያኑ ጊዜ
ተመዘገበ።

35ከዚያም ከምርኮ የተመለሱት፣ ለእስ
ራኤል ሁሉ ዐሥራ ሁለት ወይፈኖችን፣ ዘጠና
ስድስት አውራ በጎችን፣ ሰባ ሰባት ተባዕት
ጠቦቶችን፣ ለእስራኤል አምላክ የሚቃጠል
መሥዋዕት አቀረቡ፤ ለኀጢአት መሥዋዕት
ደግሞ ዐሥራ ሁለት ተባዕት ፍየሎችን
አቀረቡ፤ ይህም ሁሉ ለእግዚአብሔር የቀ
ረበ የሚቃጠል መሥዋዕት ነበር። 36የንጉ
ሡንም ትእዛዝ ለንጉሡ እንደራሴዎችና
በኤፍራጥስ ማዶ ለሚገኙት አገረ ገዦች
ሰጡ፤ እነርሱም ሕዝቡንና የእግዚአብሔርን
ቤት ረዱ።

### *ከባዕዳን ጋር ስለተደረገው ጋብቻ የዕዝራ ጸሎት*

9 እነዚህ ነገሮች ከተፈጸሙ በኋላ መሪዎቹ
ወደ እኔ መጥተው እንዲህ አሉኝ፤ "ካህና
ቱንና ሌዋውያኑን ጨምሮ የእስራኤል ሕዝብ
ከጎረቤቶቻቸው ከከነዓናውያን፣ ከኬጢያው
ያን፣ ከፌርዛውያን፣ ከኢያቡሳውያን፣ ከአሞና
ውያን ርኩሰት ራሳቸውን አልለዩም። 2ሴቶ
ቻቸውን ለራሳቸውና ለልጆቻቸው ሚስት
አድርገው ወስደዋል፤ የተቀደሰውንም ዘር
ከምድር ሕዝቦች ጋር ደባልቀዋል፤ በዚህ
በደል ዋነኛ የሆኑትም መሪዎቹና ሹማምቱ
ናቸው።

3እኔም ይህን በሰማሁ ጊዜ፣ መጐናጸፊያ
ዬንና ካባዬን ቀደድሁ፤ የራሴን ጠጕ
ርና ጢሜን ነጨሁ፤ እጅግ ደንግጬም
ተቀመጥሁ። 4በደል ከፈጸሙት ምርኮኞች የተነ
ሣም በእስራኤል አምላክ ቃል የተንቀጠ
ቀጡት ሁሉ በዙሪያዬ ተሰበሰቡ፤ እኔም
እስከ ሠርክ መሥዋዕት ድረስ እጅግ እንደ
ደነገጥሁ በዚያው ተቀመጥሁ።

5ከዚያም፣ የሠርክ መሥዋዕት በሚቀር
ብበት ጊዜ፣ የተቀደደውን መጐናጸፊያ
ዬንና ካባዬን እንደለበስሁ በሐዘን ከተቀ
መጥሁበት ተነሣሁ፤ በጕልበቴም ተንበ
ርክኬ ወደ አምላኬ ወደ እግዚአብሔር እጆ
ቼን በመዘርጋት፣ 6እንዲህ ስል ጸለይሁ፤

"አምላኬ ሆይ፤ ኀጢአታችን ከራሳችን በላይ
ሆኖአል፤ በደላችንም እስከ ሰማያት ደርሶአል፤

[o]26 22 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው።
["]26 3.4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው።
[ፕ]26 8.5 ኪሎ ግራም ያህል ነው።

አምላኬ ሆይ፤ ፊቴን ወደ አንተ ቀና ለማ
ድረግ ፈራሁ፤ እጅግም ፈራሁ። 7ከአባቶቻችን
ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በደላችን
ታላቅ ነው። ከኀጢአታችንም የተነሣ፣ ዛሬ እንደ
ሆነው ሁሉ እኛምሆንን፣ ነገሥታቶቻችንና
ካህናቶቻችን በባዕዳን ነገሥታት እጅ ወድ
ቀን ለሰይፍ፣ ለምርኮ፣ ለብዝበዛና ለውር
ደት ተዳርገናል። 8"አሁን ግን እግዚአ
ብሔር አምላካችን ቅሬታ ይተውልን ዘንድ፣
በመቅደሱም ውስጥ ጽኑ ስፍራ ይሰጠን
ዘንድ፣ ለጥቂት ጊዜ ቸርነቱን አሳይቶናል፤
ስለዚህ አምላካችን ለዐይናችን ብርሃን ሰጠ
ን፤ በባርነትም ሳለን ለጥቂት ጊዜ ዕረፍት
ሰጠን። 9ባሮች ብንሆንም፣ አምላካችን
ግን ባሮች ሆነን እንድንቀር አልተወ
ንም፤ ነገር ግን በፋርስ ነገሥታት ፊት
ቸርነቱን አሳየን፤ የአምላካችንን ቤት እንደ
ገና እንድንሠራና ፍርስራሾቿን እንድንጠ
ግን አዲስ ሕይወት ሰጠን፤ በይሁዳና በኢ
የሩሳሌምም የመከላከያ ቅጥር ሰጠን።
10አሁን ግን አምላካችን ሆይ፤ ከዚህ
በኋላ ምን እንላለን? ትእዛዞችህን አቃለናልና፤
11ያቃለ ልነውም በባሮችህ በነቢያት አ
ማካይነት፣ 'ለመውረስ የምትገቡባት
ምድር በሕዝቦቿ ርኵሰት ተበክላለች፤
ከዳር እስከ ዳርም በአስ ጸያፊ ድርጊ
ታቸውና በርኵሰታቸው ተሞል ታለች'፣
12ስለዚህ ሴቶች ልጆቻችሁን ለወንዶች
ልጆቻቸው አትስጡ፤ ሴቶች ልጆቻቸውንም
ለወንዶች ልጆቻችሁ አትውሰዱ። ብርቱዎች
እንድትሆኑ፣ የምድሪቱን መልካም ነገር
እንድትበሉና ለልጆቻችሁም የዘላለም ርስት
እንድታወርሱ ከእነርሱ ጋር ምንም ዐይነት
ውል አታድርጉ' ብለህ የሰጠኸውን ትእዛዝ
ነው።
13"ይህ ሁሉ የደረሰብን በክፉ ሥራች
ንና በብዙ በደላችን ምክንያት ነው፤ አምላ
ካችን ሆይ፤ አንተ ግን እንደ በደላችን
ብዛት አልቀጣኸንም፤ ይልቁንም ቅሬታን
ተውህልን። 14ታዲያ ትእዛዞችህን እንደ ገና
ተላልፈን እንዲህ ያለውን አስጸያፊ ድርጊት
ከሚፈጽሙ ሕዝቦች ጋር መጋባት ተገቢ
ነውን? አንተስ ቅሬታ እስከማይኖር ወይም፣
አንድም ሰው እስከማይድን ድረስ ተቈጥ
ተህ አታጠፋንምን? 15የእስራኤል አምላክ
እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ጻድቅ ነህ፤ እኛም
በዚህ
ዕለት ተርፈን በሕይወት አለን። እነሆ በፊ
ትህ ከነበደላችን ቀርበናል፤ ከበደላችን የተ
ነሣ ግን በፊትህ ሊቆም የሚችል ማንም
የለም።

### ሕዝቡ ኀጢአቱን ተናዘዘ

10 ዕዝራ በእግዚአብሔር ቤት ፊት ወድቆ
በሚጸልይበት፣ በሚናዘዝበትና በሚ
ያለቅስበት ጊዜ ወንዶች፣ ሴቶችና ልጆች
የሚገኙበት እጅግ ብዙ የእስራኤል ማኅ
በር በዙሪያው ተሰበሰበ፤ እነርሱም እንደዚሁ
አምርረው አለቀሱ። 2ከዚያም ከኤላም ዘሮች
አንዱ የሆነው የይሒኤል ልጅ ሴኬንያ ዕዝራን
እንዲህ አለው፤ በዙሪያችን ካሉት አሕዛብ፣
ባዕዳን ሴቶችን በማግባታችን ለአምላካችን
ታማኞች ሆነን አልተገኘንም፤ ይህም ሆኖ
አሁንም ለእስራኤል ተስፋ አለ። 3አሁንም
እንደ ጌታዬ ምክርና የአምላካችንን ትእዛዝ
እንደሚፈሩ ሰዎች እነዚህን ሴቶችና
ልጆቻቸውን ለመስደድ በአምላካችን ፊት
ቃል ኪዳን እንግባ፤ በሕጉም መሠረት ይፈ
ጸም። 4ዕዝራ፣ ነገሩ በእጅህ ነው፤ ተነሥ!
እኛም እንደግፍሃለን፤ በርትተህም፤
አድርገው።
5ዕዝራም ተነሥቶ ዋና ዋናዎቹ
ካህናት፣ ሌዋውያንና እስራኤል ሁሉ
የቀረበውን ሐሳብ እንዲፈጽሙ አስማላቸው፤
እነርሱም ማሉ። 6ከዚያም ዕዝራ ከእግዚአብሔር
ቤት ፊት ተነ ሥቶ ወደ ኤልያሴብ ልጅ
ወደ ዮሐናን ክፍል ገባ፤ ምርኮኞቹ ታ
ማኞች ሆነው ባለመገኘታቸው ያለቅስ
ነበር፤ በዚያም ምግብ አልቀመሰም፤
ውሃም አልጠጣም።
7ከዚያም ምርኮኞቹ ሁሉ በኢየሩሳ
ሌም እንዲሰበሰቡ በይሁዳና በኢየሩሳ
ሌም ዐዋጅ ተነገረ፤ 8ዐዋጁም በሦስት ቀን
ውስጥ ያልመጣ ማንም ሰው በሹማምቱና በሽ
ማግሌዎቹ ውሳኔ መሠረት ንብረቱ ሁሉ
እንዲወረስ፣ ራሱም ከምርኮኞቹ ጉባኤ እን
ዲወገድ የሚያዝ ነበር።
9ስለዚህ በሦስት ቀን ውስጥ የይሁዳና
የብንያም ሰዎች ሁሉ፣ በኢየሩሳሌም ተሰ
በሰቡ፤ በዘጠነኛው ወር በሃያኛውም ቀን
ሕዝቡ ሁሉ ስለ ወቅቱ ጕዳይና ስለ ከባዱ
ዝናብ በመጨነቅ በእግዚአብሔር ቤት ፊት
ባለው አደባባይ ተቀምጠው ነበር። 10ከዚ
ያም ካህኑ ዕዝራ ተነሥቶ እንዲህ አላቸው፤
"እናንተ ታማኞች አልነበራችሁም፤ በእስራ
ኤል በደል ላይ በደል በመጨመር ባዕዳን
ሴቶችን አገባችሁ። 11አሁንም ለአባቶቻችሁ
አምላክ ለእግዚአብሔር ተናዘዙ፤ ፈቃዱን
ፈጽሙ፤ በዙሪያችሁ ካሉት አሕዛብና ከባዕ
ዳን ሚስቶቻችሁ ተለዩ።"
12ጉባኤውም ሁሉ እንዲህ ሲሉ በታላቅ
ድምፅ መለሱ፤ "እውነት ብለሃል፤ ያልኸ
ውን መፈጸም ይገባናል። 13ይሁን እንጂ በዚህ
የተሰበሰበው ሕዝብ ብዙ ነው፤ ወቅቱም
ክረምት ነው፤ ስለዚህ ውጭ መቆም አንችልም፤
ከዚህም በላይ በዚህ ነገር ብዙ ኀጢአት ስለ
ሠራን፣ ይህ ጕዳይ በአንድና በሁለት ቀን
የሚያልቅ አይደለም። 14ስለዚህ ሹሞቻችን

9፥7 ዘዳ28፥37፥64፤ 2ዜና29፥6፤ሕዝ21፥1ኛ32
9፥8 ዘፍ45፥7፤ መዝ13፥3፤19፥8፤ 25፥16፤67፥1፤ 119፥58፤መክ12፥11፤ ኢሳ22፥23፤33፥2
9፥9 ዘፀ1፥14፤ 2ነገ25፥28፤ነህ9፥36፤ መዝ69፥35፤106፥46፤ኢሳ43፥1፤ 44፥26፤ 48፥20፤52፥9፤63፥9፤ኤር32፥44፤ ዘካ1፥16ኛ17
9፥10 ዘዳ11፥8፤ ኢሳ1፥19ኛ20
9፥11 ዘሌ18፥25ኛ28፤ ዘዳ4፥5፤9፥4፤18፥9፤ 1ነገ14፥24
9፥12 ዘፍ45፥18፤ ዘፀ34፥15፤ዘዳ11፥8፤መዝ103፥17፤ሕዝ37፥25፤ ኢል3፥20
9፥13 ዘፀ32፥22፤ ኢዮ11፥6፤15፥5፤22፥5፤ 33፥27፤መዝ103፥10
9፥14 ዘዳ9፥8፥14፤ ነህ13፥27
9፥15 ዘፍ18፥25፤ 1ነገ8፥47፤2ዜና12፥6፤ ነህ9፥8፤መዝ51፥4፤ 76፥7፤129፥4፤130፥3፤ 145፥17፤ኢሳ24፥16፤ ኤር12፥1፤23፥6፤33፥16፤ ሰቆ1፥18፤ዳን9፥7ሰፎ3፥5፤ ሚል3፥2
10፥2 ቍ26፤ ዘዳ30፥8ኛ10፤ዕዝ9፥2
10፥3 ዘፀ34፥16፤ 2ነገ11፥17
10፥5 ነህ5፥12፤13፥25
10፥6 ዘፀ34፥28፤ ዘዳ9፥18፤መዝ102፥4፤ ዮና3፥7
10፥9 ዕዝ1፥5
10፥10 2ዜና28፥13፤ ዕዝ7፥21
10፥11 ዘዳ24፥1፤ ነህ9፥2፤ሚል2፥10ኛ16
10፥12 ኢሱ6፥5
10፥14 ዘኍ25፥4፤ ዘዳ16፥18፤2ዜና29፥10

በማኅበሩ ሁሉ ምትክ መደረግ ያለበትን
ያድርጉ። ከዚያም በዚህ የተነሣ የመጣው
የአምላካችን ብርቱ ቍጣ ከእኛ እስኪ
መለስ ድረስ፣ በየከተሞቻችን ያሉ ባዕዳን
ሴቶችን ያገቡ ሁሉ በየከተማው ካሉት ሽ
ማግሌዎችና ዳኞች ጋር በተወሰነው ቀን ይምጠ
ሩ።” 15ይህ ንንም ነገር የተቃወሙት ከሜ
ሱላምና ከሌዋ ዊው ከሳባታይ ድጋፍ ያገኙት
የአሣሄል ልጅ ዮናታንና የቴቁዋ ልጅ የሕ
ዝያ ብቻ ናቸው።

16ስለዚህ ምርኮኞቹ እንደ ተባለው
አደረጉ፤ ካህኑ ዕዝራም ከእያንዳንዱ የቤተ
ሰብ ምድብ አንዳንድ የቤተ ሰብ ኀላፊ የሆነ
ሰው መረጠ፤ ሁሉም በየስማቸው ተመዘ
ገቡ። ከዚያም በዐሥረኛው ወር በመጀ
መሪያው ቀን ጉዳዩን ለመመርመር ተቀ
መጡ፤ 17በመጀመሪያው ወር በመጀመ
ሪያው ቀን ባዕዳን ሴቶችን ያገቡትን ወን
ዶች ሁሉ አጣርተው ጨረሱ።

## ከባዕዳን ሴቶች ጋር የተጋቡት ሰዎች

18ከካህናት ዘሮች መካከል ባዕዳን ሴቶ
ችን ያገቡት ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፤
ከኢዮሴዴቅ ልጅ ከኢያሱ ዘሮችና ከወንድ
ሞቹ መካከል፤ መዕሤያ፣ አልዓዛር፣ ያሪብና
ጎዶልያስ። 19እነዚህ ሁሉ ሚስቶቻቸውን
ለመፍታት ቃል በመግባት እጃቸውን ሰጡ፤
ስለ በደላቸውም እያንዳንዳቸው ከመንጋው
አንዳንድ አውራ በግ ለበደል መሥዋዕት
አቀረቡ።

20ከኢሜር ዘሮች፤
አናኒና ዝባድያ።
21 ከካሪም ዘሮች፤
መዕሤያ፣ ኤልያስ፣ ሸማያ፣ ይሒኤ
ልና ዖዝያ።
22ከፋስኩር ዘሮች፤
ኤልዮዔናይ፣ መዕሤያ፣ ይስ
ማኤል፣
ናትናኤል፣ ዮዛባትና ኤልዓሣ።
23ከሌዋውያኑም መካከል፤
ዮዛባት፣ ሰሜኢ፣ ቆሊጣስ የሚባል
ቆልያ፣ ፈታያ፣ ይሁዳ፣ አልዓዛር።
24ከመዘምራኑም መካከል፤
ኤልያሴብ። ከበር ጠባቂቹም፣
ሰሎም፣ ጤሌም፣ ኡሪ።
25ከሌሎቹ እስራኤላውያን መካከል፤

10፥15 ነህ11፥16
10፥18 መኅ3፥6፤ዕዝ2፥2
10፥19 ዘሌ5፥15፤
6፥6፤2ነገ10፥15
10፥20 1ዜና24፥14
10፥21 1ዜና24፥8
10፥22 1ዜና9፥12
10፥23 ነህ8፥7፤9፥4
10፥24 ነህ3፥1፤
12፥10፤13፥7፡28
10፥25 ዕዝ2፥3
10፥26 ቊ28፥3
1ዜና3፥22፤ዕዝ2፥3

ከፋሮስ ዘሮች፤ ራምያ፣ ይዝያ፣
መልክያ፣
ሚያሚን፣ አልዓዛር፣ መልክያና በናያስ።
26ከኤላም ዘሮች፤
መታንያ፣ ዘካርያስ፣ ይሒኤል፣ አብዲ፣
ይሬሞትና ኤልያ።
27ከዛቱዕ ዘሮች፤
ዒሊዮዔናይ፣ ኢልያሴብ፣ መታንያ፣
ይሬሞት፣ ዛባድና ዓዚዛ።
28ከቤባይ ዘሮች፤
ይሆሐናን፣ ሐናንያ፣ ዛባይና
አጥላይ።
29ከባኒ ዘሮች፤
ሜሱላም፣ መሉክ፣ ዓዳያ፣ ያሱብ፣
ሸዓልና ራሞት።
30ከፈሐት ሞዓብ ዘሮች፤
ዓድና፣ ክላል፣ በናያስ፣ መዕሤያ፣
መታንያ፣ ባስልኤል፣ ቢንዊና
ምናሴ።
31ከካሪም ዘሮች፤
አልዓዛር፣ ይሺያ፣ መልክያ፣ ሸማያ፣
ስምዖን፣ 32ብንያም፣ መሉክና
ሰማራያ።
33ከሐሱም ዘሮች፤
መትናይ፣ መተታ፣ ዛባድ፣ ኤሊፋላት፣
ይሬማይ፣ ምናሴና ሰሜኢ።
34ከባኒ ዘሮች፤
መዕዳይ፣ ዓምራም፣ ኡኤል፣
35በናያስ፣
ቤድያ፣ ኬልቅያ፣ 36ወንያ፣ ሜሪሞት፣
ኤልያሴብ፣ 37መታንያ፣ መትናይና
የዕሡ።
38ከቢንዊ ዘሮች፤
ሰሜኢ[የ]፣ 39ሰሌምያ፣ ናታን፣ ዓዳያ፣
40መክነድባይ፣ ሴሴይ፣ ሽራይ፣ 41ኤዝር
ኤል፣ ሰሌምያ፣ ሰማራያ፣ 42ሰሎም፣
አማርያና ዮሴፍ።
43ከናባው ዘሮች፤
ይዒኤል፣ መቲትያ፣ ዛባድ፣ ዘቢና፣
ያዳይ፣ ኢዮኤልና በናያስ።
44እነዚህ ሁሉ ባዕዳን ሴቶችን ያገቡ
ናቸው፤ ከእነርሱም ጥቂቶቹ ከእነዚህ ሴቶች
ልጆችን ወልደው ነበር።

[የ]37፡38 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ( እንዲሁም መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል 9፣34) ይመ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ *የዕሡ፣ ባኒና ቤኑዊ* ይላል።
[ዶ]44 ወይም *ከልጆቻቸው ጋር ላኩአቸው*

# መጽሐፈ ነህምያ

### *የነህምያ ጸሎት*

**1** የሐካልያ ልጅ የነህምያ ቃል፤
በሃያኛው ዓመት ካሴሉ በተባለው ወር
በሱሳ ግንብ ሳለሁ፣ 2ከወንድሞቼ አንዱ
የሆነው አናኒ፣ ከሌሎች ጥቂት ሰዎች
ጋር ከይሁዳ መጣ፤ እኔም ከምርኮ ስለ ተረ
ፉት የአይሁድ ቅሬታዎችና ስለ ኢየሩሳ
ሌም ጠየቅኋቸው።
3እነርሱም በሕይወት ተርፈው "ከምርኮ
ወደ አገራቸው የተመለሱት ሰዎች በታላቅ
መከራና ውርደት ላይ ይገኛሉ፤ የኢየሩሳሌም
ቅጥር ፈራርሶአል፤ በሮቿም በእሳት ተቃጥ
ለዋል" አሉኝ።
4ይህን ነገር በሰማሁ ጊዜ አያሌ
ቀናት ዐዘንሁ፤ ጾምሁ፤ ጸለይሁም። 5ከዚያም
እንዲህ አልሁ፤
"ለሚወዱህና ትእዛዝህን ለሚያከብሩ የፍ
ቅርህን ቃል ኪዳን የምትጠብቅ ታላቅና የተፈ
ራህ አምላክ፣ የሰማይ አምላክ *እግዚአብሐ
ር* ሆይ፤ 6ባሪያህ ስለ አገልጋዮችህ ስለ እስራ
ኤል ሕዝብ ቀንና ሌሊት በፊትህ የሚጸል
የውን ጸሎት ለመስማት ጆሮህ ይንቃ፤ ዐይ
ንህም ይከፈት። እኔንና የአባቴን ቤት
ጨምሮ እኛ እስራኤላውያን አንተን በመበ
ደል የሠራነውን ኀጢአት እናዘዛለሁ። 7በአንተ
ላይ እጅግ ክፉ ሥራ ሠርተናል፤ ለባሪያህም
ለሙሴ የሰጠኸውን ትእዛዝ፣ ሥርዐትና ሕግ
አልጠበቅንም።
8"ለባሪያህ ለሙሴ እንዲህ ስትል የሰጠ
ኸውን ቃል አስብ፤ 'ታማኞች ካልሆናችሁ፣
በአሕዛብ መካከል እበትናችኋለሁ፤ 9ወደ እኔ
ብትመለሱና ትእዛዞቼን ብትፈጽሙ፣ የተ
ሰደዱት ወገኖቻችሁ እስከ ምድር ዳርቻ
ድረስ እንኳ ቢበተኑ፣ ከዚያ እሰበስባቸ
ዋለሁ፤ ለስሜም ማደሪያ ወደ መረጥሁት
ስፍራ አመጣቸዋለሁ።'
10"እነዚህም በታላቁ ኀይልህና በብርቱ
እጅህ የተቤዠሃቸው ባሪያዎችህና ሕዝብህ
ናቸው። 11*እግዚአብሔር ሆይ*፤ የባሪያህን
ጸሎት፣ ስምህን በመፍራት ደስ
የሚሰኙትን የባሪያ ዎችህንም ጸሎት ጆሮህ
ታድምጥ። በዚህ ሰው ፊት ሞገስን
አድርገህለት ዛሬ ለባሪያህ መከናወንን ስጠ
ው።" በዚያን ጊዜ እኔ የንጉሡ ጠጅ
አሳላፊ ነበርሁ።

1፥1 ዕዝ4፥9፤
አስ2፥8፤ዘካ2፥1
1፥2 2ነገ21፥14፤
ነህ7፥2፡6፤ኤር52፥28
1፥3 ዘሌ26፥31፤
2ነገ25፥10ነህ፤2፥3፡
13፡17፤ኢሳ22፥9፤
ኤር39፥8፤52፥14፤
ሰቆ2፥9
1፥4 2ዜና20፥3፤
ዕዝ9፥4፤ መዝ137፥1፤
ዳን9፥3
1፥5 ዘዳ7፥9፡21፤
1ነገ8፥23፤ነህ4፥14፤
ዳን9፥3
1፥6 1ነገ8፥29፡3፤
47፤2ዜና7፥15
1፥7 መዝ106፥6
1፥8 ዘፍ8፥1፤
ዘሌ26፥33፤2ነገ20፥3፤
ነህ4፥14፤5፥19፤
6፥14፤13፥22፡29፡31
1፥9 ዘዳ 30፥4፤
1ነገ 8፥48፤
መዝ 106፥47፤ 107፥3፤
ኢሳ 11፥12፤ 56፥8፤
ኤር 29፥14፤ 42፥12፤
ሕዝ 11፥17፥20፥34-38፤
36፥24-38፤
ሚክ 2፥12
1፥10 ዘፀ 32፥11፤
ኢሳ 51፥9-11 1፥11
ዘፍ 40፥1፤ ዘፀ ፥21፤
2ዜና6፥40
1፥9 ዘዳ 30፥4፤
1ነገ 8፥48፤
መዝ 106፥47፤ 107፥3፤
ኢሳ 11፥12፤ 56፥8፤
ኤር 29፥14፤ 2፥12፤
ሕዝ 11፥17፥20፥34-38፤
36፥24-38፤
ሚክ 2፥12
1፥10 ዘፀ 32፥11፤
ኢሳ 51፥9-11
1፥11 ዘፍ 40፥1፤
ዘፀ ፥21፤ 2ዜና6፥40

2፥1 ዕዝ4፥7፤6፥14
2፥3 1ነገ1፥31፤
ነህ1፥3፤ መዝ137፥6፤
ዳን2፥4፤ 3፥9፤
5፥10፤6፥6፡21
2፥6 ነህ5፥14፤13፥6
2፥7 ዕዝ8፥36፤
ዕዝ 4፥24፤5፥5፤ ነህ7፥2
2፥9 ዕዝ8፥22
2፥10 ቍ19፥ነህ4፥1፡
3፡7፤6፥1-2፡5፡12፡
14፤13፥4-7፡28፤
አስ10፥3

### አርጤክስስ ነህምያን ወደ ኢየሩሳሌም እንዲ ሄድ ፈቀደለት

**2** በንጉሡ በአርጤክስስ ዘመነ መንግ
ሥት በሃያኛው ዓመት ኒሳን ተብሎ
በሚጠራው ወር የወይን ጠጅ በመጣለት
ጊዜ፣ የወይን ጠጁን አንሥቼ ለንጉሡ
ሰጠሁት። ቀድሞ በፊቱ ዐዝኜ አላውቅም
ነበር፤ 2ስለዚህ ንጉሡ፣ "ሳትታመም ፊትህ
ለምን እንዲህ ዐዘነ? መቼም ይህ የልብ
ሐዘን እንጂ ሌላ አይደለም" አለኝ።
እኔም በጣም ፈርቼ ነበር፤ 3ለንጉሡም
"ንጉሡ ለዘላለም ይኑር፤ አባቶቼ የተቀ
በሩባት ከተማ ስትፈርስ፣ በሮቿም በእሳት
ሲቃጠሉ ለምን ፊቴ አይዘን?" አልሁት።
4ንጉሡም፣ "ታዲያ ምን ትፈልጋለህ?"
አለኝ። ከዚያም ወደ ሰማይ አምላክ
ጸለይሁ፤ 5ለንጉሡም፣ "ንጉሡን ደስ
የሚያሰኘው ቢሆ ንና ባሪያህ በፊትህ ሞገስ
ቢያገኝ፣ እንደ ገና እንድሠራት አባቶቼ
ወደ ተቀበሩባት ወደ ይሁዳ ከተማ
እንድሄድ ይፈቀድልኝ" አልሁት።
6ከዚያም ንጉሡ አጠገቡ ከተቀመጠ
ችው ንግሥት ጋር በመሆን፣ "ጕዞህ ምን
ያህል ቀን ይፈጃል? መቼ ስ
ትመለሳለህ?" ሲል
ጠየቀኝ። ንጉሡም እኔን ለመስደድ ደስ
አለው፤ እኔም ጊዜውን ወሰንሁ።
7ደግሞም እንዲህ አልሁት፤ "ንጉሡን
ደስ የሚያሰኘው ቢሆን፣ ይሁዳ እስክደርስ
ድረስ በደኅና እንዲያሳልፉኝ ከኤፍራጥስ
ማዶ ላሉት አገረ ገዥዎች ደብዳቤ ይሰጠኝ፤
8እንዲሁም ለንጉሡ ደን ጠባቂ ለአሳፍ፣
በቤተ መቅደሱ አጠገብ ላለው ግምብ
በሮች፣ ለከተማዪቱ ቅጥርና እኔም ለምገ
ባበት ቤት ሠረገላ የሚሆን እንጨት እንዲ
ሰጠኝ ደብዳቤ ይጻፍልኝ፤" መልካሚቱ የአም
ላኬ እጅ በእኔ ላይ ነበረችና ንጉሡም
ፈቀደ ልኝ። 9ስለዚህ በኤፍራጥስ ማዶ
ወደሚገ ኙት አገረ ገዥዎች ሄጄ የንጉሡን
ደብዳ ቤዎች ሰጠኋቸው፤ ንጉሡም የጦር
አለቆችና ፈረሰኞች አብረውኝ እንዲሄዱ
አድርጎ ነበር።
10ሖሮናዊው ሰንባላጥና አሞናዊው ሹም
ጦብያ ይህን በሰሙ ጊዜ ስለ እስራኤላውያን
ደኅንነት የሚቈረቈር ሰው በመምጣቱ እጅግ
ተበሳጩ።

## *ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች ተዘዋውሮ ተመለከተ*

11እኔም ወደ ኢየሩሳሌም ሄድሁ፤ በዚያም
ሦስት ቀን ከቈየሁ በኋላ፣ 12ከጥቂት ሰዎች
ጋር በሌሊት ወጣሁ። ለኢየሩሳሌም አደር
ገው ዘንድ እግዚአብሔር በልቤ ያኖረውን ነገር
ለማንም አልነገርሁም፤ ከተቀመጥሁበት
እንስሳ በቀር ከእኔ ጋር ሌሎች እንስሳት
አልነበሩም።
13በሌሊትም ወጥቼ በሸለቆው በር በኩል
አድርጌ ወደ ዘንዶው[ሀ] የውሃ ጕድጓድና
ወደ ቆሻሻ መድፊያው በር ሄድሁ፤
የፈረሱትንም የኢየሩሳሌምን ቅጥሮችና
በእሳት የወደሙትን በሮች ተመለከትሁ።
14ከዚያም ወደ ውሃ ምንጭ በርና ወደ ንጉ
ሡ ኵሬ ሄድሁ፤ ይሁን እንጂ
የተቀመጥሁበትን እንስሳ ማሳለፍ
የሚያስችል በቂ ቦታ አልነበ ረም። 15ስለዚ
ህ ቅጥሩን እየተመለከትሁ ሌሊቱን
ሸለቆውን ዐልፌ ወደ ላይ ወጣሁ፤
በመጨረሻም ተመልሼ በሸለቆው በር በኩል
ገባሁ። 16ለአይሁድ ወይም ለካህናቱ ወይም
ለመኳንንቱ ወይም ለሹማምቱ ወይም
ሥራውን ለሚሠሩት ሰዎች ገና ምንም
የተናገርሁት ነገር ስላልነበረ፣ ወዴት እንደ
ሄድሁ ወይም ምን እንዳደረግሁ ሹማምቱ
አላወቁም።
17ከዚያም፣ "ያለንበትን ችግር ይኸው
ታያላችሁ፤ ኢየሩሳሌም ፈርሳለች፤ በሮቿም
በእሳት ጋይተዋል፤ አሁንም ኑና የኢየሩ
ሳሌምን ቅጥር እንደ ገና እንሥራ፤ ከእን
ግዲህስ መሣለቂያ አንሆንም" አልኋቸው።
18እንዲሁም መልካሚቱ የአምላኬ እጅ በእኔ
ላይ እንደ ነበረችና ንጉሡም ምን እንዳለኝ
ነገርኋቸው።
እነርሱም፣ "እንደ ገና መሥራቱን
እንጀምር!" ካሉ በኋላ ይህን መልካም ሥራ
ጀመሩ።
19ነገር ግን ሖሮናዊው ሰንባላጥ፣ አሞና
ዊው ሹም ጦብያና ዐረባዊው ጌሳም ይህን
ሲሰሙ አፌዙብን፤ አንቋሸሹንም፤ እንዲ
ሁም፣ "የምታደርጉት ይህ ምንድን ነው?
በንጉሡ ላይ ልታምፁ ትፈልጋላችሁን?"
አሉ።
20እኔም፣ "የሰማይ አምላክ ያከናውንል
ናል፤ እኛ ባሪያዎቹ እንደ ገና ሥራውን እን
ጀምራለን፤ እናንተ ግን በኢየሩሳሌም ድርሻ
ወይም ይገባናል የምትሉት ወይም
የታሪክ መታሰቢያ የላችሁም" ስል
መለስሁላቸው።

## *የቅጥሩ ሠራተኞች*

3 ሊቀ ካህናቱ ኤልያሴብና ወንድሞቹ
ካህናት ለሥራ ተነሡ፤ የበጎች በር
የተባለውንም እንደ ገና ሠሩ። ቀደሱት፤
መዝጊያዎቹንም በየቦታቸው ላይ አቆሙ።
መቶ ማማ እስከሚባለው ግንብና ሐና
ንኤል ማማ ተብሎ እስከ ሚጠራው ድረስ
ሠርተው ቀደሱት፤ 2ቀጥሎ ያለውንም የኢ
ያሪኮ ሰዎች ሠሩ፤ እነርሱ ከሠሩት ቀጥሎ
ደግሞ የአምሪ ልጅ ዘኩር ሠራ።
3የዓሣ በሩን የሃስናአ ልጆች ሠሩ፤ እነር
ሱም ምሰሶዎቹን አቁመው መዝጊያዎ
ቹን፣ መቀርቀሪያዎቹንና መወርወሪያዎቹን
በየቦታቸው አኖሩ።
4የአቆስ ልጅ የኦርዮ ልጅ ሜሪሞት ከዚያ
ቀጥሎ ያለውን ክፍል መልሶ ሠራ። ከእርሱ
ቀጥሎ ያለውን የሜሴዜቤል ልጅ የበራክያ
ልጅ ሜሱላም መልሶ ሠራ። ከእርሱ ቀጥሎ
ያለውን የበዓና ልጅ ሳዶቅ መልሶ ሠራ፤
5የሚቀጥለውን ክፍል የቴቁሐ ሰዎች
መልሰው ሠሩ፤ መኳንንቶቻቸው ግን በተቈ
ጣጣሪ አሠሪዎቻቸው[ለ] ሥር ሆነው በሥራው
መጠመድ አልፈለጉም።
6አሮጌውን[ሐ] በር የፋሴሐ ልጅ ዮዳሄና
የበሶድያ ልጅ ሜሱላም መልሰው ሠሩ፤
እነርሱም ምሰሶዎቹን አቁመው መዝጊያዎ
ቹን፣ ማያያዣዎቹንና መወርወሪያዎቹን
በየቦታቸው አኖሩ። 7ከእነርሱም ቀጥሎ
የዕድሳቱ ሥራ የተከናወነው በኤፍራጥስ
ማዶ በሚገኘው አገረ ገዥ ሥልጣን ሥር
ባሉት በገባዖንና በምጽጳ ሰዎች በገባዖ
ናዊው በመልጥያና በሜሮኖታዊው
በያዶን ነበር። 8ከወርቅ አንጥረኞች አንዱ
የሆነው የሐርሃያ ልጅ ዑዝኤል
የሚቀጥለውን ክፍል ሠራ፤ ከሽቱ ቀ
ማሚዎች አንዱ የሆ ነው ሐናንያ ደግሞ
ከዚያ ቀጥሎ ያለ ውን መልሶ ሠራ።
እነርሱም "ሰፊው ቅጥር" ተብሎ እስከሚጠ
ራው ድረስ ኢየሩሳሌምን መልሰው ሠሩ።
9ከዚያ የሚቀጥለ ውን ክፍል የኢየሩ
ሳሌም አውራጃ እኩ ሌታ ገዥ የሆነው
የሆር ልጅ ረፋያ መልሶ ሠራ። 10የኤርማፍ
ልጅ ይዳያ ከቤቱ ፊት ለፊት ያለውን
ክፍል መልሶ ሠራ፤ የአሰ በንያ
ልጅ ሐጡስ ደግሞ ከእርሱ ቀጥሎ ያለውን
መልሶ ሠራ። 11የካሪም ልጅ መል ክያና
የፈሐት ሞዓብ ልጅ አሱብ ሌላውን ክፍልና
"የእቶን ግንብ" ተብሎ የሚጠራውን
መልሰው ሠሩ። 12የኢየሩሳሌም አውራጃ
እኩሌታ ገዥ የሆነው የአሎኤስ ልጅ
ሰሎም ከሴት ልጆቹ ጋር በመሆን ቀጥሎ
ያለውን ክፍል መልሶ ሠራ።
13"የሸለቆ በር" ተብሎ የሚጠራውን
የሐኖንና የዛኖ ነዋሪዎች ዐደሱት፤ መልሰው

2፥11 ዘፍ40፥13
2፥13 2ዜና26፥9፤ ነህ1፥3፤3፥13፤12፥31
2፥14 2ነገ18፥17፤ ነህ3፥15፤12፥37
2፥17 ነህ1፥3፤ መዝ10216፤ ኢሳ30፥13፤58፥12፤ ሕዝ5፥14
2፥18 ዕዝ5፥5
2፥19 ቍ10፤ ነህ6፥1፡2፡6፤ መዝ44፥13-16
2፥20 ዕዝ4፥1፡3፤ ሐሥ8፥21
3፥1 ቍ32፤ ዕዝ10፥24፤ ነህ12፥39፤ መዝ48፥12፤ ኢሳ58፥12፤ ኤር31፥38፤ ዘካ14፥10፤ዮሐ5፥2
3፥2 ነህ7፥36
3፥3 2ዜና33፥14
3፥4 ዕዝ8፥33
3፥5 ቍ27፥2ሳሙ14፥2
3፥6 ነህ12፥39
3፥7 ኢሳ9፥3
3፥8 ነህ12፥38
3፥11 ነህ12፥38
3፥13 ኢሱ 15፥34፤ 2ዜና26፥9፤ነህ2፥13

[ሀ]13 ወይም *ቀበሮ ወይም በለሱ*
[ለ]5 *ጌቶቻቸው፤ ወይም ገዦቻቸው*
[ሐ]6 ወይም *የይሻናን*

ሠሩት፤ ከሠሩትም በኋላ መዝጊያዎቹን
በየ ቦታቸው አኖሩ፤ መወርወሪያዎቹንና
መቀ ርቀሪያዎቹንም አበጁ። እንዲሁም
“የቆሻሻ መጣያ በር” ተብሎ እስከሚጠራ
ው ድረስ ያለውን አንድ ሺህ ክንድ[መ] ቅጥር
መልሰው ሠሩ።
14“የቈሻሻ መጣያ በር” ተብሎ የሚጠራ
ው የቤት ሐካሪም አውራጃ ገዥ የሆነው
የሬካብ ልጅ መልክያ መልሶ ሠራ፤ መልሶ
ከሠራ
በኋላም መዝጊያዎቹን፣ መቀርቀሪያዎቹንና
መወርወሪያዎቹን በየቦታቸው አኖረ።
15የምጽጳ አውራጃ የኮልሖዜ ልጅ
ሰሎም “የምንጭ በር” ተብሎ የሚጠራ
ውን መልሶ ሠራ፤ መልሶ ከሠራም በኋላ
ከድኖ መዝጊያዎቹን በየቦታቸው አኖረ፤
መወርወሪያዎቹንና መቀርቀሪያዎቹንም
አበጀ። “የንጉሥ አትክልት ቦታ” ተብሎ
በሚጠራው አጠገብ የሚገኘውን የሼላን
መዋኛ ግንብም፣ ከዳዊት ከተማ ጀምሮ
ቍልቍል እስከሚወርደው ደረጃ ድረስ መልሶ
ሠራ። 16ከእርሱም በኋላ የቤት ጹር አውራጃ
እኩሌታ ገዥ የዓዝቡቅ ልጅ ነህምያ እስከ
ዳዊት መቃብር ትይዩ እስከ ሰው ሠራሹ
ኵሬና “የጀግኖች ቤት” ተብሎ እስ ከሚጠ
ራው ድረስ ያለውን መልሶ ሠራ።
17ከእርሱ ቀጥሎ ሌዋውያኑ በባኒ ልጅ
በሬሁ ሥር ሆነው የዕድሳት ሥራ ሠሩ።
ከእርሱ ቀጥሎ የቅዒላ አውራጃ እኩሌታ
ገዥ ሐሸብያ አውራጃውን መልሶ ሠራ።
18ከእርሱ ቀጥሎ ያለውን ክፍል ደግሞ
የሌላው የቅዒላ አውራጃ እኩሌታ ገዥ
የኤንሐዳድ ልጅ በዋይና በእርሱም ሥር
የነበሩት የአገሩ ሰዎች መልሰው ሠሩ።
19ከእርሱም ቀጥሎ ወደ ጦር መሣሪያ ግምጃ
ቤት በሚያወጣውና እስከ ማእዘኑ በሚደ
ርሰው ትይዩ ያለውን ሌላ ክፍል የምጽጳ
ገዥ የኢያሱ ልጅ ኤጽር መልሶ ሠራ።
20ከእርሱም ቀጥሎ የዘባይ ልጅ ባሮክ ከማ
እዘኑ ጀምሮ እስከ ሊቀ ካህኑ እስከ ኤልያ
ሴብ ቤት መግቢያ ያለውን ሌላ ክፍል
በት ጋት መልሶ ሠራ። 21ከእርሱ ቀጥሎ
ከኤል ያሴብ ቤት መግቢያ ጀምሮ እስከ
መጨ ረሻው ያለውን ሌላ ክፍል የአቆስ
ልጅ የኦርዮ ልጅ ሜሪሞት መልሶ ሠራ።
22ከእርሱም ቀጥሎ ያለውን ክፍል ከአካ
ባቢው የመጡት ካህናት መልሰው ሠሩ።
23ከእነርሱ ቀጥሎ ብንያምና አሱብ ከቤታ
ቸው ፊት ለፊት ያለውን መልሰው ሠሩ፤
ከእነርሱም ቀጥሎ የሐናንያ ልጅ የመዕ
ሤያ ልጅ ዓዛርያስ በቤቱ አጠገብ ያለውን
መልሶ ሠራ። 24ከእርሱም ቀጥሎ ከዓ
ዛርያስ ቤት ጀምሮ እስከ ማዕዘኑና እስከ
ማዕዘኑም ጫፍ ያለውን ሌላውን ክፍል
የኤንሐደድ ልጅ ቢንዊ መልሶ ሠራ፤
25የኡዛይ ልጅ ፋላል ከቅጥሩ ማእዘን ትይ
ዩና በዘብ መጠበቂያው አደባባይ አጠገብ
ካለው ከላይኛው ቤተ መንግሥት መጠ
በቂያ ግንብ ጀምሮ ያለውን መልሶ ሠራ።
ከእርሱም ቀጥሎ የፋሮስ ልጅ ፈዳያና
26በዖፌል ኰረብታ ላይ የሚኖሩት የቤተ
መቅደሱ አገልጋዮች “የውሃ በር” ተብሎ
ከሚጠራው ትይዩ ጀምሮ በስተምሥራቅ
እስከሚገኘው ግንብ ድረስ መልሰው ሠሩ።
27ከእነርሱ ቀጥሎ የቴቁሐ ሰዎች ከታላቁ
ግንብ ትይዩ ጀምሮ እስከ ዖፌል ቅጥር
ድረስ ያለውን ሌላ ክፍል መልሰው ሠሩ።
28“የፈረስ በር” ተብሎ ከሚጠራው በላይ
ያለውን ደግሞ ካህናቱ እያንዳንዳቸው በየ
መኖሪያ ቤታቸው ትይዩ ያለውን መል
ሰው ሠሩ። 29ከእነርሱም ቀጥሎ የኢሜር
ልጅ ሳዶቅ በቤቱ ትይዩ ያለውን መልሶ
ሠራ። ከእርሱ ቀጥሎ ያለውን “የምሥ
ራቅ በር” ጠባቂ የሆነው የሴኬንያ ልጅ
ሽማያ መልሶ ሠራ። 30ከእርሱ ቀጥሎ ያለ
ውን ሌላ ክፍል ደግሞ የሰሌምያ ልጅ ሐና
ንያና የሴሌፍ ስድስተኛ ልጅ ሐኖን መል
ሰው ሠሩ። ከእነርሱም ቀጥሎ የበራክያ
ልጅ ሜሱላም ከመኖሪያው ትይዩ ያለ
ውን መልሶ ሠራ። 31ከእርሱ ቀጥሎ ከወርቅ
አንጥረኞች አንዱ መልክያ በመቈጣጠ
ሪያው በር ትይዩ እስከሚገኘው እስከ ቤተ
መቅ ደሱ አገልጋዮችና እስከ ነጋዴዎቹ
ቤት፣ እንዲሁም ከማእዘኑ በላይ እስከ
ሚገኘው ክፍል ያለውን መልሶ ሠራ፤ 32ከ
ማእዘኑ በላይ ከሚገኘው ክፍል ጀምሮ
እስከ በጎች በር ያለውን ደግሞ ወርቅ
አንጥረኞቹና ነጋዴዎቹ መልሰው ሠሩ።

## ቅጥሩ እንዳይሠራ የተደረገ ተቃውሞ

4 ሰንባላጥ ቅጥሩን እንደምንሠራ በሰማ
ጊዜ ተቈጣ፤ እጅግም ተበሳጨ። በአ
ይሁድም ላይ ተሣለቀ፤ 2በተባባሪዎቹና
በሰማርያ ሰራዊት ፊት፣ “እነዚህ ደካማ
አይ ሁድ ምን እያደረጉ ነው? ቅጥራ
ቸውን መልሰው ሊሠሩ ነውን? መሥዋዕ
ት ሊያ ቀርቡ ነውን? በአንዲት ጀንበር
ሠርተው ሊጨርሱ ነውን? እንደዚያ
ተቃጥሎ የፍ ርስራሽ ክምር የሆነውን
ድንጋይ ነፍስ ሊዘ
ሩበት ይችላሉን?” አለ።
3በአጠገቡም ቆሞ የነበረው አሞናዊው
ጦቢያ፣ “ለመሆኑ የሚገነቡት ምንድን ነው?
በድንጋይ የሚሠሩት ቅጥር እኮ ቀበሮ

3፥14 ኤር6፥1
3፥15 ኢሳ8፥6፤ ዮሐ9፥7
3፥16 ኢሱ15፥58፤ ሐሥ2፥29
3፥17 ኢሱ15፥44
3፥21 ዕዝ8፥33
3፥24 ዕዝ8፥33
3፥25 ዕዝ2፥3፤ ኤር32፥2፤37፥21፤ 39፥14
3፥26 2ዜና 33፥14፤ነህ7፥46፤8፥1፡ 3፡16፤11፥21፤12፥37
3፥27 ቍ5፤ መዝ48፥12
3፥28 2ነገ 11፥16
3፥32 ቍ1ዮሐ5፥2
4፥1 ነህ2፥10
4፥2 ዕዝ4፥9-10፤ መዝ79፥1፤ኤር26፥18
4፥3 ነህ2፥10 ኢዮ13፥12፤15፥3

[መ]13 450 ሜትር ያህል ነው።

እንኳ ብትወጣበት ሊፈርስ ይችላል" አለ።
4አምላካችን ሆይ፤ ተንቀናልና ስማን፤
ስድባቸውን በራሳቸው ላይ አውርድባቸው፤
በምርኮ ምድር እንዲበዘበዙ አሳልፈህ
ስጣቸው። 5የፈረሰውን በሚሠሩት ፊት
የስድብ ናዳ አውርደዋልና[ሠ] በደላቸውን
ይቅር አትበል፤ ኀጢአታቸውንም ከፊትህ
አታጥፋው።
6ሕዝቡ ከልቡ ስለሚሠራ፣ ቅጥሩን እኩ
ሌታው ድረስ መልሰን ሠራነው።
7ሰንባላጥ፣ ጦቢያ፣ ዐረቦች፣ የአሞንና
የአሽዶድ ሰዎች፣ የኢየሩሳሌም ቅጥር ሥራ
እየተፋጠነና ክፍት ቦታዎቹም ሁሉ እየ
ተሞሉ መሆናቸውን በሰሙ ጊዜ እጅግ
ተቈጡ። 8መጥተውም ኢየሩሳሌምን ይወጉ
ዘንድ፣ ሽብርንም ይፈጥሩ ዘንድ ሁሉም
በአንድነት አደሙ። 9እኛ ግን ወደ እግ
ዚአብሔር ጸለይን፤ ዛቻቸውንም ለመቋ
ቋም ቀንና ሌሊት የሚጠብቁ ዘቦችን መደ
ብን።
10በዚህ ጊዜ የይሁዳ ሕዝብ፣ "የሠራተ
ኞቹ ጕልበት እየደከመ ነው፤ ከፍርስራ
ሹም ብዛት የተነሣ ቅጥሩን መልሰን ለመ
ሥራት አንችልም" አሉ።
11ጠላቶቻችን ደግሞ፣ "በመካከላቸው ገብ
ተን እስክንገድላቸውና ሥራውን እስክናስ
ቆም ድረስ አያውቁም ወይም አያዩም" አሉ።
12ከዚያም በአጠገባቸው የሚኖሩ አይ
ሁድ መጥተው፣ "እናንተ የትምቦታ ብት
ሆኑ፣ እኛን ማጥቃታቸው አይቀርም!" በማ
ለት ዐሥር ጊዜ ደጋግመው ነገሩን።
13ስለዚህ ከቅጥሩ በስተኋላ በሚገኙ
ግልጽ ቦታዎች ላይ ከሕዝቡ አንዳንዶቹ
ሰይፋቸውን፣ ጦራቸውንና ቀስታቸውን
እንደያዙ በየቤተ ሰባቸው በመመደብ ቦታ
ቸውን እንዲይዙ አደረግሁ። 14ነገሩን በጥ
ሞና ከተመለከትሁ በኋላ መኳንንቱን፣
ሹማምቱንና የቀረውን ሕዝብ፣ "አትፍሯቸው፤
ታላቁንና የተፈራውን እግዚአብሔርን
አስቡ፤ ስለ ወንድሞቻችሁ፣ ስለ ወንዶችና
ሴቶች ልጆቻችሁ፣ ስለ ሚስቶቻችሁና ስለ
ቤት ንብረታችሁ ተዋጉ" አልኋቸው።
15አድማቸውን እንዳወቅንባቸውና እግዚ
አብሔርም ዕቅዳቸውን ከንቱ እንዳደረገባ
ቸው ጠላቶቻችን በሰሙ ጊዜ፣ ሁላችን ወደ
ቅጥሩ፣ እያንዳንዳችንም ወደየሥራችን ተመ
ለስን።
16ከዚያን ቀን ጀምሮ ከሰዎቼ እኩሌቶቹ
ሥራውን ሠሩ፤ የቀሩት ደግሞ ጋሻና
ጦር፣ ቀስትና ጥሩር ይዘው ነበር። የጦር
አለቆች ከመላው የይሁዳ ሕዝብ በስተኋላ
ቆሙ፤ 17እነርሱም ቅጥሩን ይገነቡ ነበር
ዕቃ የሚሸከሙት በአንድ እጃቸው ሥራ
ቸውን ሲሠሩ፣ በሌላው እጃቸው የጦር
መሣሪያቸውን ይዘው ነበር፤ 18እያንዳንዱም
ግንበኛ ቅጥሩን በሚሠራበት ጊዜ ሰይፉን
በወገቡ ላይ ታጥቆ ነበር፤ መለከት የሚ
ነፋው ሰው ግን ከእኔ አይለይም ነበር።
19ከዚያም ለመኳንንቱ፣ ለሹማምቱና
ለቀ ረው ሕዝብ እንዲህ አልሁ፤ "ሥራው
ታላቅ ነው፤ ብዙም ነው፤ እርስ በርሳችን
በቅጥሩ ላይ እጅግ ተራርቀናል፤ 20የመለከት
ድምፅ በምትሰሙበት ጊዜ፣ ወደ እኛ
ተሰብሰቡ። አምላካችን ስለ እኛ ይዋጋል።"
21ስለዚህ ጎሕ ሲቀድ ጀምሮ ከዋክብት
እስኪወጡ ድረስ እኩሌቶቹ ሰዎች ጦራ
ቸውን እንደ ያዙ ሥራውን ቀጠልን። 22በዚ
ያን ጊዜ ለሕዝቡ፣ "ሌሊት ዘብ በመጠበቅና
ቀን ሥራ በመሥራት እንዲያገለግለን እያ
ንዳንዱ ሰው ከነረዳቱ በኢየሩሳሌም
ይቈይ" አልኋቸው። 23እኔም ሆንሁ ወንድ
ሞቼ፣ ሰዎቼም ሆኑ ከእኔ ጋር ያሉት ጠባ
ቂዎች ልብሳችንን አላወለቅንም፤ ለውሃ
እንኳ በምንሄድበት ጊዜ እያንዳንዱ ሰው
የጦር መሣሪያውን እንደያዘ ነበር።[ረ]

### ነህምያ ድኾችን ረዳ

5 በዚህ ጊዜ ወንዶቹና ሚስቶቻቸው አይ
ሁድ ወንድሞቻቸውን በመቃወም
ብርቱ ጩኸት አሰሙ፤ 2አንዳንዶቹ፣
"እኛም ሆን ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችን
በቍጥር ብዙ ነን፤ ታዲያ ለመብላትም
ሆነ በሕይወት ለመቈየት እህል ማግኘት
አለብን" አሉ።
3ሌሎቹ በራቡ ወቅት እህል ለማግኘት
ስንል እርሻችንን፣ የወይን ተክል ቦታችንንና
ቤታችንን እስከ ማስያዝ ደርሰናል አሉ።
4ሌሎቹ ደግሞ እንዲህ አሉ፤ "የእር
ሻችንንና የወይን ተክል ቦታችንን ግብር
ለንጉሡ ለመክፈል ገንዘብ እስከ መበደር
ደርሰናል። 5ምንም እንኳ ከአገራችን
ሰዎች ጋር በሥጋና በደም አንድ ብንሆ
ንም፣ እንደ እነርሱ ልጆች ሁሉ የእኛም
ወንዶች ልጆች ጥሩዎች ቢሆኑም፣ ወንዶ
ችና ሴቶች ልጆቻችንን ባሮች እንዲሆኑ
ሰጥተናል፤ አንዳንድ ሴቶች ልጆቻችን አሁ
ንም በባርነት ላይ ናቸው፤ እርሻችንና የወ
ይን ተክል ቦታችን የሌሎች በመሆናቸው
እኛ ደካሞች ሆነናል።
6እኔም ጩኸታቸውንና እነዚህን አቤቱ
ታዎች በሰማሁ ጊዜ፣ እጅግ ተቈጣሁ፤
7ከዚያም ነገሩን በሐሳቤ ካወጣሁ
ካወረድሁ በኋላ፣ መኳንንቱንና ሹማምቱን

[ሠ]5 ወይም *የፈረሰውን በሚሠሩት ፊት እንድትቈጣ አድር ገውሃልና*

4፥4 መዝ44፥13፤ 123፥3-4፤ኤር33፥24
4፥5 2ነገ14፥27፤ መዝ51፥1፤69፥27-28፤ 109፥14፤ኢሳ2፥9፤ ኤር18፥23፤ሰቆ1፥22
4፥7 ነህ2፥10
4፥8 መዝ2፥2፤ 83፥1-18
4፥10 1ዜና23፥4
4፥14 ዘፍ28፥15፤ ዘዳ1፥29፤2ሳሙ10፥12 ፤ነህ1፥5፡8
4፥15 2ሳሙ 17፥14፤ ኢዮ5፥12
4፥17 መዝ149፥6
4፥18 ዘኍ10፥2
4፥20 ዘፀ14፥14፤ ዘዳ20፥4፤ ኢሱ10፥14፤ሕዝ33፥3
5፥3 ዘፍ47፥23፤ መዝ109፥11
5፥4 ዕዝ4፥13
5፥5 ዘፍ29፥14፤ ዘሌ25፥39-43፤47፤ዘዳ15፥7-11፤ 2ነገ4፥1፤ኢሳ50፥1
5፥7 ዘፀ22፥25-27፤ ዘሌ25፥35-37፤ዘዳ23፥19-20፤ 24፥10-13

ገሠጽኋቸው፤ “ከገዛ አገራችሁ ሰዎች ላይ
እን ዴት ዐራጣ ትበላላችሁ!” አልኳቸውም።
ስለዚህ ከእነርሱ ጋር ለመነጋገር ታላቅ
ስብሰባ ጠራሁ፤ 8ለአሕዛብ ተሸጠው የነበሩ
ትን አይሁድ ወንድሞቻችንን በተቻለን
ሁሉ ተቤዥተናቸዋል፤ አሁንም እናንተ
ወንድሞቻችሁን ትሸጣላችሁ፤ ይህም መል
ሰን እንድንቤዣቸው ለማድረግ ብቻ ነው!”
አልኳቸው፤ እነርሱም የሚመልሱት አልነበ
ራቸውምና ዝም አሉ።
9ስለዚህ በመቀጠል እንዲህ አልሁ፤
“ይህ የምታደርጉት ነገር ትክክል አይደ
ለም፤ የጠላቶቻችንን የአሕዛብን ስድብ ለማ
ስወገድ የአምላካችንን መንገድ በፍርሀት
መከተል አይገባችሁምን? 10እኔ፣ ወንድ
ሞቼና ሰዎቼም እንደዚሁ ለሕዝቡ ገንዘብና
እህል አበድረናል፤ ዐራጣው ግን ያብቃ።
11እርሻቸውን፣ የወይንና የወይራ ዘይት
ተክል ቦታቸውንና ቤታቸውን በቶሎ መል
ሱላቸው፤ እንዲሁም የምታስከፍሏቸውን
የገንዘቡን፣ የእህሉን፣ የአዲሱን ወይንና
ዘይት አንድ መቶኛ ዐራጣ መልሱላቸው”።
12እነርሱም፣ “እንመልሳለን፤ ምንም ዐይነት
ትርፍ አንጠይቃቸውም፤ እንዳልኸን እናደ
ርጋለን” አሉ። ካህናቱን ጠራኋቸው፤
መኳንንቱንና ሹማምቱንም የገቡትን ቃል
እንዲፈጽሙ አማልኋቸው። 13እንዲሁም
የልብሴን ዘርፍ አራግፌ፣ “ይህን የተስፋ
ቃል የማይፈጽመውን ማናቸውንም ሰው
አምላክ ቤቱንና ንብረቱን እንደዚህ ያራ
ግፈው፤ እንደዚህ ያለውም ሰው ይርገፍ፤
ባዶም ይሁን” አልሁ። በዚህም ጉባኤው
ሁሉ፣ “አሜን” በማለት *እግዚአብሔርን*
አመሰገነ፤ ሕዝቡም የገቡትን ቃል ፈጸሙ።
14ከዚህም በላይ በይሁዳ ምድር አገረ
ገዥ ሆኜ ከተሾምሁበት፣ ከአርጤክስስ
ሃያኛ ዓመት ጀምሮ እስከ ሠላሳ ሁለተ
ኛው ዘመነ መንግሥቱ ድረስ፣ ለዐሥራ
ሁለት ዓመት እኔም ሆንሁ ወንድሞቼ
ለአንድ አገረ ገዥ የተመደበውን ምግብ
ተቀብለን አልበላንም። 15ከእኔ በፊት የነ
በሩት የቀድሞዎቹ አገረ ገዦች ግን ከምግ
ቡና ከወይኑ ሌላ፣ በሕዝቡ ላይ ከባድ
ሸክም በመጫን አርባ ሰቅል[ሰ] ብር ይወስዱ
ነበር፤ ረዳቶቻቸውም እንዲሁ ይጭኑባ
ቸው ነበር። እኔ ግን እግዚአብሔርን ከመፍ
ራቴ የተነሣ እንዲህ ያለውን አላደረግ
ሁም። 16ከዚህ ይልቅ ራሴን ለዚህ ቅጥር ሥራ
ሰጠሁ። ሰዎቼም ሁሉ ለሥራው እዚያው
ይሰበሰቡ ነበር፤ ምንም መሬት አልነበረ
ንም[ሸ]።
17ከዚህም በላይ በዙሪያችን ካሉት፣ ወደ
እኛ ከሚመጡት አሕዛብ ሌላ አንድ
መቶ አምሳ አይሁድና ሹማምት ከማእዴ
ይካ ፈሉ ነበር። 18በየዕለቱም አንድ በሬ፣
ስድስት ምርጥ በጎችና የተወሰኑ ዶሮዎች፣
በየዐሥሩም ቀን ብዛት ያለው ልዩ ልዩ የወ
ይን ጠጅ ይዘጋጅልኝ ነበር። ይህም ሁሉ
ሆኖ ለአንድ አገረ ገዥ የተመደበውን
ምግብ ከቶ ጠይቄ አላውቅም፤ በሕዝቡ ላይ
የተጣለው ሸክም ከባድ ነበርና።
19አምላኬ ሆይ፤ ለዚህ ሕዝብ ያደረግሁ
ትን ሁሉ በበጎነት አስብልኝ።

### በቅጥሩ ሥራ ላይ የተነሣ ሌላ ታቃውሞ

6 እስከዚያች ጊዜ ድረስ ለበሮቹ መዝጊያ
ባልገጥምላቸውም እንኳ፣ ቅጥሩን
መሥራቴንና የቀረ ክፍት ቦታ አለመኖሩን
ሰንባላጥ፣ ጦብያ፣ ዓረባዊው ጌሳምና የቀሩ
ትም ጠላቶቻችን በሰሙ ጊዜ፣ 2ሰንባላጥና
ጌሳም “ናና በኦኖ ሜዳ ከሚገኙት መንደ
ሮች[ቀ] በአንዲቱ እንገናኝ” ሲሉ ይህችን
መልእክት ላኩብኝ። እነርሱ ግን እኔን
ለመጒዳት ዐቅደው ነበር። 3እኔም፣ “ታላቅ
ሥራ እየሠራሁ ስለሆነ፣ ወዳላችሁበት
ስፍራ መውረድ አልችልም፤ ትቼው ወደ
እናንተ ወርጄ ሥራው ለምን ይቆማል?”
በማለት ይህን መልስ የሚያደርሱ መልእ
ክተኞችን ወደ እነርሱ ላክሁ።
4አራት ጊዜም ይህንኑ ዐይነት መልእ
ክት ላኩብኝ፤ እኔም በእያንዳንዱ ጊዜ ያንኑ
መልስ ሰጠሁ።
5ከዚያም ሰንባላጥ ለአምስተኛ ጊዜ
ያንኑ መልእክት በረዳቱ ላከብኝ፤ በእጁም
ማኅተም የሌለው ያልታሸገ ደብዳቤ ይዞ
ነበር፤ 6የተጻፈበትም እንዲህ የሚል ነበር፤
“አንተና አይሁዳውያን ለማመፅ እንደ
ምትዶልቱና ቅጥሩንም እንደምትሠሩ
በሕዝቦች መካከል ተወርቶአል፤ ጌሳ
ምም እውነት መሆኑን አረጋግጦአል፤
ከዚህም በተጨማሪ በተወራው መሠረት
አንተ ንጉሣቸው እንደምትሆን፣ 7ስለ
አንተም ‘በአይሁድ ንጉሥ አለ’ ብለው
በኢየሩሳሌም የሚያውጁ ነቢያትን እንኳ
ሳይቀር እንደ ሾምህ ተወርቷል፤ ይህም
ነገር ለንጉሡ መድረሱ አይቀርም፤ ስለዚህ
መጥተህ በአንድነት እንመካከር።”
8እኔም “አንተ የምትለውን የመሰለ
ምንም ነገር አልተደረገም፤ ይህ አንተ ‘23

5፥8 ዘሌ25፥47፤
ኤር34፥8
5፥9ኢሳ52፥5
5፥10 ዘፀ22፥25
5፥11 ኢሳ58፥6
5፥12ዕዝ10፥5
5፥13 ዘዳ27፥15-26፤
ማቴ10፥14
5፥14 ዘፍ42፥6፤
ዕዝ6፥7፤
ነህ2፥6፤ኤር40፥7፤
ሐጌ1፥1
5፥15 ዘፍ20፥11
5፥16 2ተሰ3፥7-10
5፥18 1ነገ4፥23
5፥19 ዘፍ8፥1፤
2ነገ20፥3፤ነህ1፥8
6፥1 ነህ2፥10፡19
6፥2 1ዜና8፥12
6፥5 ነህ2፥10
6፥6 ነህ2፥19

በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትጒርም በትክክል አይታወቅም።
[ሰ]15 0.5 ኪሎ ግራም ያህል ነው።
[ሸ]16 ብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ የሰብዓ ሊቃናት፣ የቩልጌትና የሱረሰት ቅጆች ግን *አልነበረኝም* ይላሉ።
[ቀ]2 የዕብራይስጡ ቅጅ፣ *ኬፍሪም* ይላል።

በአእምሮህ የፈጠርኸው ነው” ብዬ መልስ
ላክሁበት፡፡
9ሁሉም፣ “እጃቸው መሥራት እስኪ
ሳነው ድረስ ይዝላል፤ ሥራውም ሳይጠና
ቀቅ ይቀራል” ብለው በማሰብ ሊያስፈራሩን
ሞከሩ፡፡ እኔ ግን፣ “አሁንም እጄን አበርታ”
ስል ጸለይሁ፡፡
10አንድ ቀን ቤቱ በላዩ ላይ ተዘግቶበት
ወደ ነበረው ወደ መሄጣብኤል ልጅ ወደ
ድላያ ልጅ ወደ ሸማያ ሄድሁ፤ እርሱም፣
“ሰዎች ሊገድሉህ ይመጣሉ፤ በእርግጥም
በሌሊት ሊገድሉህ ይመጣሉ፤ በእግዚአብሔር
ቤት ባለው በቤተ መቅደሱ ውስጥ እንገናኝ፤
የቤተ መቅደሱንም በሮች እንዝ ጋቸው”
አለኝ፡፡
11እኔ ግን፣ “እንደ እኔ ያለ ሰው ሸሽቶ
ይደበቃል? ወይም ደግሞ ሕይወቱን ለማ
ዳን ሲል ወደ ቤተ መቅደስ መግባት
ይገባዋልን? አልሄድም!” አልሁ፡፡ 12በእኔ ላይ
ትንቢት የተናገረው ጦብያና ሰንባላጥ
በገንዘብ ስለ ደለሉት እንጂ እግዚአብሔር
ወደ እኔ እንዳልላከው ተረዳሁ፡፡ 13በገን
ዘብ የተገዛው እኔን ለማስፈራራት ነው፤
ይኸውም ይህን በመፈጸም ኀጢአት እን
ድሠራና በዚህም መጥፎ ስም ሰጥተው
ተቀባይነት እንዳይኖረኝ ለማድረግ ነው፡፡
14 አምላኬ ሆይ፤ ስለ ፈጸሙት ድርጊት
ጦብያንና ሰንባላጥን አስብ፤ ሊያስፈራሩኝ
የሞከሩትን ነቢያቱን ኖዓድያንና ሌሎቹን
ነቢያትም አስብ፡፡

## የቅጥሩ ሥራ መጠናቀቅ

15ቅጥሩም ኤሉል በተባለው ወር ሃያ አም
ስተኛ ቀን፣ በአምሳ ሁለት ቀን ውስጥ
ተጠናቀቀ፡፡ 16ጠላቶቻችን ሁሉ ይህን
ሲሰሙ፣ በዙሪያችን ያሉ አሕዛብ ሁሉ
ፈሩ፤ በራሳቸው መተማመንም አልቻ
ሉም፤ ምክንያቱም ይህ ሥራ የተከናወ
ነው በአምላካችን ርዳታ መሆኑን ተገንዝ
በዋል፡፡
17በዚያን ጊዜ የይሁዳ መኳንንት ለጦብያ
ብዙ ደብዳቤ ይልኩ ነበር፤ ከጦብያም መልስ
ይላክላቸው ነበር፡፡ 18በይሁዳ የሚኖሩ
ሰዎች ምለውለት ነበር፤ ምክንያቱም የኤራ
ልጅ የሴኬንያ አማት ከመሆኑም በላይ ልጁ
የሆሐናን የሌራክያን ሴት ልጅ አግብቶ
ነበር፡፡ 19ከዚህም በተጨማሪ ስለ መልካም
ሥራው በየጊዜው ይነግሩኝና እኔም ያል
ሁትን ይነግሩት ነበር፤ ጦብያም እኔን ለማ
ስፈራራት ደብዳቤ ይልክብኝ ነበር፡፡

7 ቅጥሩ እንደ ገና ከተሠራና መዝጊያ
ዎቹንም በየቦታቸው ከገጠምሁ በኋላ፣

6፥10 ዘኍ18፥7
6፥12 ነህ2፥10፤
ሕዝ13፥22-23
6፥13 ኤር20፥10
6፥14 ዘፀ 15፥20፤
ነህ1፥8፤2፥10፤
ኤር23፥9-40፤
ሕዝ13፥17-23፤
ዘካ13፥2-3፤
ሐሥ21፥9፤ራእ2፥20
7፥1 1ዜና 9፥27፤
26፥12-19፤
ነህ8፥9 መዝ68፥25

7፥2 1ነገ18፥3፤
ነህ1፥2፤2፥8፤10፥23
7፥4 ነህ11፥1
7፥6 2ዜና36፥20፤
ነህ1፥2
7፥7 1ዜና3፥19
7፥20 ዕዝ8፥6

በር ጠባቂዎች፣ መዘምራንና ሌዋውያን
ተመደቡ፡፡ 2በኢየሩሳሌምም ላይ ወንድሜን
አናኒን እንዲሁም ፍጹም ታማኝና ከሌ
ሎች ሰዎች ይልቅ እግዚአብሔርን ይበልጥ
የሚፈራውን የግንቡን አዛዥ ሐናንያን
ኀላፊ አደረግኋቸው፡፡ 3ለእነርሱም፣ “የኢ
የሩሳሌም በሮች ፀሓይ ሞቅ እስክትል
ድረስ አይከፈቱም፤ በር ጠባቂዎቹ ዘብ
በሚቆሙበት ጊዜ ሁሉ፣ በሮቹን
ይዘጓቸው፤ መወርወሪያም ያደርጉባቸው፣
እንዲሁም ከኢየሩሳሌም ነዋሪዎች
አንዳንዶቹን በየጥ በቃ ቦታቸው፣
አንዳንዶቹን ደግሞ በየቤ ታቸው አጠገብ
እንዲቆሙ መድቡ” አል ኋቸው፡፡

## ከምርኮ የተመለሱት ሰዎች ዝርዝር

4ከተማዪቱ ታላቅና ሰፊ ነበረች፤ የሚኖ
ርባት ሕዝብ ግን ጥቂት ሲሆን፣ ቤቶች
ገና አልተሠሩባትም ነበር፡፡ 5ስለዚህ መኳን
ንቱን፣ ሹማምቱንና ተራውን ሕዝብ ሰብ
ስቤ በየቤተ ሰቡ ይመዘገቡ ዘንድ እግዚአ
ብሔር ይህን በልቤ አኖረ፡፡ ወደ ምድራ
ቸው ለመመለስ የመጀመሪያ የሆኑትን
ሰዎች የትውልድ ሐረግ መዝገብ አገኘሁ፤
ተጽፎ ያገኘሁትም ይህ ነው፡፡
6የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ማርኮ
ከወሰዳቸው ምርኮኞች መካከል የተመለ
ሱት የአውራጃው ተወላጆች እነዚህ
ናቸው፤ እያንዳንዳቸውም በኢየሩሳሌምና
በይሁዳ ወደሚገኙት ወደየራሳቸው ከተ
ሞች ተመለሱ፤
7የተመለሱትም ከዘሩባቤል፣ ከኢያሱ፣
ከነህምያ፣ ከአዛርያስ፣ ከረዓምያ፣ ከነሐማኒ፣
ከመርዶክዮስ፣ ከበላሳን፣ ከሚስጴሬት፣
ከበጉዋይ፣ ከነሑምና ከበዓና ጋር ነው፡፡
የእስራኤል ሰዎች ዝርዝር፤

| | |
|---|---|
| 8ከፋሮስ ዘሮች | 2,172 |
| 9ከሰፋጥያስ ዘሮች | 372 |
| 10ከኤራ ዘሮች | 652 |
| 11ከኢያሱና ከኢዮአብ ዘር የሆኑት የፈሐት ሞዓብ ዘሮች | 2,818 |
| 12ከኤላም ዘሮች | 1,254 |
| 13ከዛቱዕ ዘሮች | 845 |
| 14ከዘካይ ዘሮች | 760 |
| 15ከቢንዊ ዘሮች | 648 |
| 16ከቤባይ ዘሮች | 628 |
| 17ከዓዝጋድ ዘሮች | 2,322 |
| 18ከአዶኒቃም ዘሮች | 667 |
| 19ከበጉዋይ ዘሮች | 2,067 |
| 20ከዓዲን ዘሮች | 655 |
| 21በሕዝቅያስ የትውልድ | |

ሐረግ ከአጤር ዘሮች 98
22ከሐሱም ዘሮች 328
23ከቤሳይ ዘሮች 324
24ከሐሪፍ ዘሮች 112
25ከገባዖን ዘሮች 95
26ከቤተ ልሔምና ከነጦፋ
ሰዎች 188
27ከዓናቶት ሰዎች 128
28ከቤት አዝሞት ሰዎች 42
29ከቂርያት ይዓሪም፣
ከከፊራና ከብኤሮት
ሰዎች 743
30ከራማና ከጌባ ሰዎች 621
31ከማክማስ ሰዎች 122
32ከቤቴልና ከጋይ ሰዎች 123
33ከሌላው ናባው ሰዎች 52
34ከሌላው ኤላም ዘሮች 1,254
35ከካሪም ዘሮች 320
36ከኢያሪኮ ዘሮች 345
37ከሎድ፣ ከሐዲድና
ከኦኖም ዘሮች 721
38ከሴናዓ ዘሮች 3,930
39ካህናቱ:-
በኢያሱ ቤተ ሰብ መስመር
ከዮዳኤ ዘሮች 973
40ከኢሜር ዘሮች 1,052
41ከፋስኮር ዘሮች 1,247
42ከካሪም ዘሮች 1,017
43ሌዋውያኑ:-
በቀድምኤል በኩል
በሆዳይዋ የትውልድ
መስመር የኢያሱ
ዘሮች 74
44መዘምራኑ:-
ከአሳፍ ዘሮች 148
45በር ጠባቂዎቹ:-
ከሰሎም፣ ከአጤር ፣
ከጤልሞን፣ ከዓቁብ፣
ከሐጢጣና ከሶባይ ዘሮች 138
46የቤተ መቅደሱ አገልጋዮች:-
ከሲሐ፣ ከሐሡፋ፣ ከጠብዖት ዘሮች፣
47ከኬራስ፣ ከሲዓ ፣ ከፋዶን፣
48ከልባና፣ ከአጋባ፣ ከሰምላይ ዘሮች፣
49ከሐናን፣ ከጌዴል፣ ከጋሐር ዘሮች፣
50ከራያ፣ ከረአሶን፣ ከኔቆዳ ዘሮች፣
51ከጋሴም፣ ከዖዛ፣ ከፋሴሐ ዘሮች
52ከቤሳይ፣ ከምዑኒም፣ ከንፉሰሲም
ዘሮች፣
53ከበቅቡቅ፣ ከሐቀፋ፣ ከሐርሑር
ዘሮች፣
54ከበስሎት፣ ከምሒዳ፣ ከሐርሻ ዘሮች፣
55ከቦርቆስ፣ ከሲሣራ፣ ከቴማ ዘሮች፣

7፥26 2ሳሙ 23፥28
1ዜና 2፥54
7፥27 ኢሱ 21፥18
7፥29 ኢሱ 18፥25፡26
7፥32 ዘፍ 12፥8
7፥36 ነህ 3፥2
7፥37 1ዜና 8፥12
7፥44 ነህ 11፥23
7፥45 1ዜና 9፥17
7፥46 ነህ 3፥26

7፥60 1ዜና 9፥2
7፥65 ዘፀ 28፥30
7፥71 1ዜና 29፥7
7፥72 ዘፀ 25፥2
7፥73 ዕዝ 3፥1 ነህ 1፥10፤
11፥1 መዝ 34፥22፤
103፥21፤
113፥1፥135፥1

56ከንስያ፣ ከሐጢፋ ዘሮች፡፡
57የሰሎሞን አገልጋዮች ዘሮች:-
የሶጣይ፣ የሶፌሬትና፣ የፍሩዳ
ዘሮች፣
58የየዕላ፣ የደርቆን፣ የጊዴል ዘሮች፣
59የሰፋጥያስ፣ የሐጢል፣ የፈከራት
ዘሮች፣ የሐጊቦይምና የአሞን ዘሮች፡፡
60የቤተ መቅደሱ አገልጋዮችና
የሰሎሞን አሽከሮች ዘሮች 392
61ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ደግሞ ከቴልሜላ፣
ከቴላሬሳ፣ ከክሩብ፣ ከአዳንና ከኢሜር
የተመለሱ ናቸው፤ ይሁን እንጂ ዘሮቻ
ቸው ከእስራኤል ወገን መሆናቸውን ማስ
ረዳት አልቻሉም፤
62የዳላያ፣ የጦብያ፣ የኔቆዳ ዘሮች 642
63ከካህናቱ መካከል:-
የኤብያ፣ የአቆስ፣ የቤርዜሊ ዘሮች፤
ይህ ሰው የገለዓዳዊውን የቤርዜሊን ሴት
ልጅ አግብቶ በዚሁ ስም ለመጠራት በቅ
ቶአል፤
64እነዚህ የየቤተ ሰብ ትውልድ ሐረጋቸ
ውን ከመዝገብ ለማግኘት ፈልገው ነበር፤
ነገር ግን ሊያገኙት አልቻሉም፤ ስለዚህ እን
ዳልነጹ ተቈጥረው ከክህነት ተከለከሉ፡፡
65ስለዚህም አገረ ገዡ በኡሪምና በቱሚም
አገልግሎት የሚሰጥ ካህን እስኪነሣ ድረስ
እጅግ ከተቀደሰው ምግብ እንዳይበሉ
አዘዛቸው፡፡
66የማኅበሩ ቍጥር በሙሉ 42,360
ነበር፤ 67ይህ 7,337 የወንድና የሴት አገል
ጋዮቻቸውን አይጨምርም፤ 245 ወንዶችና
ሴቶች መዘምራን ነበሯቸው፡፡ 68736 ፈረ
ሶች፣ 245 በቅሎዎች[ᑎ]፣ 69435 ግመሎችና
6,720 አህዮችም ነበሯቸው፡፡
70አንዳንድ የየቤተ ሰቡ አባቶች ለሥራው
መዋጮ አደረጉ፤ አገረ ገዡም 1,000 የወ
ርቅ ዳሪክ[†]፣ 50 ድስቶቹ 530 አልባሰ
ተክህኖ ለግምጃ ቤቱ ሰጠ፡፡ 71ከየቤተ ሰቡ
አባቶችም አንዳንዶች ለሥራው የሚሆን
20, 000 የወርቅ ዳሪክ[‡] 2,200 የብር
ምናን ለግምጃ ቤቱ ሰጡ፡፡ 72የቀረው ሕዝብ
ባጠቃላይ የሰጠው 20,000 የወርቅ ዳሪክ[ኀ]
2,000 የብር ምናንና 67 አልባሰ ተክህኖ
ነበር፡፡
73ካህናቱ፣ ሌዋውያኑ፣ በር ጠባቂዎቻ
ቸው፣ መዘምራኑና የቤተ መቅደሱ
አገልጋዮች፣ ከሕዝቡም የተወሰነው ክፍልና
የቀሩት እስ ራኤላውያን በየራሳቸው
ከተሞች ሰፈሩ፡፡

[ᑎ]68 አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆች (እንዲሁም ዕዝ 2፥66) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን ይህንን ጥቅስ አይጨምሩም፡፡
[†]70 8.5 ኪሎ ግራም ያህል ነው፡፡
[‡]71 170 ኪሎ ግራም ያህል ነው፡፡
[ኀ]72 1.1 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው፡፡

### ዕዝራ ሕጉን አነበበ

ሰባተኛው ወር በደረሰና እስራኤላውያን
ሁሉ በየከተሞቻቸው በተቀመጡ ጊዜ፣
8 ሕዝቡ ሁሉ ከ“ውሃ በር” ፊት
ለፊት በሚገኘው አደባባይ ላይ
እንደ አንድ ሰው ተሰበሰቡ፤ ከዚያም
እግዚአብሔር ለእስራኤል ያዘዘውን
የሙሴ ሕግ መጽሐፍ እንዲያመጣ
ለጸሓፊው ለዕዝራ ነገሩት።
2ስለዚህ ካህኑ ዕዝራ በሰባተኛው ወር የመ
ጀመሪያ ቀን ወንዶች፣ ሴቶችና ማስተ
ዋል የሚችሉ ሁሉ በተገኙበት ጉባኤ
ፊት የሕጉን መጽሐፍ አመጣ። 3እርሱም
በ“ውሃው በር” ትይዩ ወደሚገኘው አደባ
ባይ ፊቱን አቅንቶ፣ በወንዶች፣ በሴቶችና
በሚያስተውሉ ሰዎች ሁሉ ፊት በመቆም፣
ከማለዳ ጀምሮ እስከ ቀትር ድረስ ድም
ፁን ከፍ አድርጎ አነበበ፤ ሕዝቡም ሁሉ
የሕጉን መጽሐፍ በጥሞና አደመጡ።
4ጸሓፊው ዕዝራ ለዚሁ ተብሎ በተሠራ
ውና ከፍ ብሎ በሚገኘው የዕንጨት መድ
ረክ ላይ ቆሞ ነበር፤ በአጠገቡም በስተ
ቀኙ በኩል መቲትያ፣ ሽማዕ፣ ዓናያ፣
ኦርዮ፣ ኬልቅያስ፣ መዕሤያ፣ በስተ ግራው
በኩል ደግሞ ፈዳያ፣ ሚሳኤል፣ መል
ክያ፣ ሐሱም፣ ሐሽበዳ፣ ዘካርያስና ሜሱላም
ቆመው ነበር።
5ዕዝራም መጽሐፉን ከፈተ፤ ከሕዝቡ
ከፍ ብሎ ቆሞ ስለ ነበረ፣ ሁሉም ያዩት
ነበረ፣ በከፈተውም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ቆሙ።
6ዕዝራም ታላቁን አምላክ *እግዚአብሔርን*
አመሰገነ፤ ሕዝቡም ሁሉ እጆቻቸውን በማ
ንሣት፣ “አሜን! አሜን!” ብለው መለሱ፤
ከዚህ በኋላ በግምባራቸው ወደ መሬት
ተደፍተው *ለእግዚአብሔር* ሰገዱ።
7ሌዋውያኑ ኢያሱ፣ ባኒ፣ ሰራብያ፣
ያሚን፣ ዓቁብ፣ ሳባታይ፣ ሆዲያ፣ መዕ
ሤያ፣ ቆሊጣስ፣ ዓዛርያስ፣ ዮዛባት፣ ሐናን፣
ፌልያ ሕዝቡ በዚያው ቆመው እንዳሉ
ሕጉን አስረዷቸው።
8ሕዝቡ የሚነበበውን መረዳት እንዲ
ችሉ ከእግዚአብሔር ሕግ መጽሐፍ
ካነበቡላቸው በኋላ ይተረጉሙላቸውና
ይተነትኑላቸው ነበር።
9ከዚያም አገረ ገዡ ነህምያ፣ ካህኑና
ጸሓፊው ዕዝራ፣ ሕዝቡንም የሚያስተምሩት
ሌዋውያን፣ “ይህች ቀን *ለአምላካችሁ*
*ለእግ ዚአብሔር* የተቀደሰች ናት፤
አትዘኑ፤ አታ ልቅሱም” አሏቸው፤ ምክንያተ
ም ሕዝቡ ሁሉ የሕጉን ቃል በሚሰሙበት
ጊዜ ያለቅሱ ነበር።
10ነህምያም፣ “ሂዱ፤ ጥሩ ምግብ በመብ
ላት፣ ጣፋጩን በመጠጣት ደስ ይበላ
ችሁ፤ ምንም የተዘጋጀ ነገር ለሌላቸውም
ካላችሁ ላይ ከፍላችሁ ላኩላቸው። ይህች
ቀን ለጌታ ችን የተቀደሰች ናት፤ *የእግዚአ*
*ብሔር* ደስታ ብርታታችሁ ስለሆነ አት
ዘኑ” አላቸው።
11ሌዋውያኑም፣ “ይህች ቀን የተቀደሰች
ስለሆነች ዝም በሉ፤ አትዘኑም” በማ
ለት ሕዝቡን ሁሉ አረጋጉ።
12ስለዚህ ሕዝቡ ሁሉ የተነገራቸውን
ቃል ተረድተው ስለ ነበረ፣ ለመብላት፣
ለመጠጣት፣ ከምግባቸው ከፍለው ለመላ
ክና ሐሤትም ለማድረግ ሄዱ።
13ከወሩም በሁለተኛው ቀን የየቤተ ሰቡ
ሁሉ ኀላፊዎች፣ የሕጉን ቃል ለመማር
ከካህናቱና ከሌዋውያኑ ጋር በጸሓፊው በዕ
ዝራ ዙሪያ ተሰበሰቡ። 14እስራኤላውያን
በሰባተኛው ወር በሚውለው በዓል በዳስ
ውስጥ እንዲቀመጡ *እግዚአብሔር* በሙሴ
አማካይነት የሰጠውን ትእዛዝ በሕጉ
ውስጥ ተጽፎ አገኙ፤ 15ስለዚህ በየከተሞ
ቻቸውና በኢየሩሳሌም ይህን ቃል እንዲ
ያውጁና እንዲያሠራጩ እንዲህ በማ ለት
አዘዟቸው፤ “ወደ ኰረብቶች ውጡ፤
ከዘይትና ከበረሓ ወይራ፣ ከባርስነት፣
ከዘንባባና ከለምለም ዛፎች ቅርንጫፎችን
አምጡ[ነ]፤ በተጻፈው መሠረት ዳሶችን
ሥሩ።”
16ስለዚህ ሕዝቡ ወጥተው ቅርንጫፎች
አመጡ፤ እያንዳንዳቸውም በየቤታቸው ጣራ
ሰገነት፣ በየግቢያቸው፣ በእግዚአብሔር ቤት
አደባባይ፣ በ“ውሃ በር” አደባባይና በኤፍ
ሬም በር አደባባይ ላይ ዳስ ሠሩ። 17ከም
ርኮ የተመለሰውም ማኅበር ሁሉ ዳሱን
ሠርቶ ተቀመጠ። ከነዌ ልጅ ከኢያሱ
ዘመን ጀምሮ እስከዚያን ጊዜ ድረስ እስራ
ኤላውያን እንደዚያ አድርገው በዓሉን አከ
ብረው አያውቁም፤ ደስታቸውም ታላቅ
ነበር።
18ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ እስከ መጨ
ረሻው ድረስ፣ ዕዝራ በየዕለቱ ከእግዚአ
ብሔር ሕግ መጽሐፍ ያነብ ነበር። እነር
ሱም በዓሉን ሰባት ቀን አከበሩ፤ በስም
ንተኛውም ቀን በሕጉ መሠረት የተቀደሰ
ጉባኤ ተደረገ።

### እስራኤላውያን ኀጢአታቸውን ተናዘዙ

9 በዚያኑ ወር ሃያ አራተኛ ቀን እስራ
ኤላውያን ጾመው፣ ማቅ ለብሰው፣ በራ
ሳቸው ላይ ትቢያ ነስንሰው በአንድነት
ተሰበሰቡ። 2የእስራኤላውያን ዘር የሆኑ
ትም ራሳቸውን ከባዕዳን ሁሉ ለዩ።
ቆመውም ኀጢአታቸውንና የአባቶቻቸውን
በደል ተናዘዙ። 3በያሉበትም ቦታ ቆመው

8፥1 ዘጸ28፥61፤ 2ዜና34፥15፤ነህ3፥26
8፥2 ዘሌ23፥23-25፤ ዘኍ29፥1-6፤ ዘዳ31፥11
8፥3 ነህ3፥26
8፥4 2ዜና 6፥13
8፥5 መሳ3፥20
8፥6 ዕዝ9፥5፤ 1ጢሞ2፥8
8፥7 ዘሌ10፥11፤ 2ዜና17፥7፤ዕዝ10፥23
8፥9 ዘዳ12፥7፡12፤ 16፥14-15 ነህ7፥1
8፥10 ዘሌ23፥40፤ ዘዳ12፥18፤16፥11፡ 14-15፤1ሳሙ25፥8፤ 2ሳሙ6፥19፤አስ9፥22፤ ሉቃ14፥12-14
8፥12 አስ9፥22
8፥14 ዘፀ23፥16
8፥16 2ዜና25፥23፤ ነህ3፥26
8፥17 1ነገ8፥2፤ 2ዜና7፥8፤8፥13፤ ሆሴ12፥9
8፥18 ዘሌ 23፥36፤ ዘዳ28፥61፤31፥11፤ 33፥10፤ዕዝ3፥4
9፥1 ዘሌ 26፥40-45 ኢሱ7፥6፤2ዜና7፥14-16
9፥2 ዘሌ 26፥40፤ ዕዝ6፥21፤10፥11፤ ነህ10፥28፤13፥3፤30፤ መዝ106፥6

[ነ]15 ዘሌ23፥37-49 ይመ

ከአምላካቸው *ከእግዚአብሔር ሕግ መጽሐፍ* ሩብ
ቀን አነበቡ፤ የቀረውን ሩብ ቀን ደግሞ
ንስሓ በመግባትና ለአምላካቸው *ለእግዚ
አ
ሔር* በመስገድ አሳለፉ። 4ሌዋውያኑ ኢያሱ፣
ባኒ፣ ቀድምኤል፣ ሰበንያ፣ ቡኒ፣ ሰራብያ፣
ባኒ፣ ከናኒ፣ በመውጫ ደረጃዎች ላይ ቆሙ፤
ወደ አምላካቸው ወደ *እግዚአብሔርም*
በታላቅ ድምፅ ጮኹ። 5ሌዋውያኑ ኢያሱ፣
ቀድም ኤል፣ ባኒ፣ አሰበንያ፣ ሰራብያ፣
ሆዲያ፣ ሰበንያና ፈታያ፣ "ተነሡታችሁ ቀ
-ሙ፤ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም የሚኖረ
ውን አምላካችሁን *እግዚአብሔርን* ወድሱ"
አሉ።
"ክቡር ስምህ የተመሰገነ ይሁን፤ ከም
ስጋና ሁሉና ከውዳሴም በላይ ከፍ ከፍ
ይበል። 6አንተ ብቻ *እግዚአብሔር* ነህ። ሰማ
ያትን፣ ከሰማያት በላይ ያሉትን ሰማያ
ትና የከዋክብታቸውን ሰራዊት ሁሉ፣
ምድር ንና በላይዋ ያለውን ሁሉ፣ ባሕ
ሮችንና በው ስጣቸው ያሉትንም ሁሉ
ፈጥረሃል። ለሁ ሉም ሕይወትን
ትሰጣለህ፤ የሰማይ ሰራዊትም
ይሰግዱልሃል።
7"አብራምን የመረጥኸውና ከከለዳው
ያን ዑር አውጥተህ አብርሃም የሚል ስም
የሰጠኸው አንተ *እግዚአብሔር* አምላክ
ነህ። 8ልቡ ለአንተ የታመነ ሆኖ ስላገኘኸ
ውም፣ የከነዓናውያንን የኬጢያውያንን፣
የአሞራውያንን፣ የፌርዛውያንን፣ የኢያቡ
ሳውያንንና የጌርጌሳውያንን ምድር ለዘሮቹ
ለመስጠት ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን ገባህ፤
ጻድቅ ስለ ሆንህም የሰጠኸውን ተስፋ ጠበ
ቅህ።
9"አንተ በግብፅ የአባቶቻችንን ሥቃይ
አየህ፤ በቀይ ባሕርም[ኘ] ጩኸታቸውን ሰማህ።
10ታምራታዊ ምልክቶችንና ድንቆችን በፈ
ርዖንና፣ በሹማምቱ ሁሉ፣ በምድሩም ሕዝብ
ሁሉ ላይ ላክህ፤ ይህንም ያደረግኸው ግብፃ
ውያን እንዴት በእብሪት እንዳስጨነቋ
ቸው ስላወቅህ ነው። እስከ ዛሬም የሚ
ጠራ ስም ለራስህ እንዲኖርህ አደረግህ።
11በደረቅ ምድር እንዲሻገሩ ባሕሩን በፊ
ታቸው ከፈልህ፤ ያሳደዷቸውን ግን በኀይለኛ
ውሃ ውስጥ እንደሚጣል ድንጋይ ወደ
ጥልቁ ውስጥ ወረወርሃቸው። 12ቀን በደ
መና ዐምድ፣ በሚሄዱበት መንገድ ታበራ
ላቸውም ዘንድ ሌሊት በእሳት ዐምድ መራ
ሃቸው።
13"በሲና ተራራ ላይ ወረድህ፤ ከሰማ
ይም ተናገርሃቸው። ትክክለኛ ደንቦች
ንና እውነተኛ ሕጎችን፣ መልካም ሥርዐ
ቶችንና ትእዛዞችን ሰጠሃቸው። 14የተቀደ
ሰች ሰንበትህን አስታወቅሃቸው፤ ትእዛዞ
ችን፣ ሥርዐቶችንና ሕጎችን በባሪያህ
በሙሴ አማካይነት ሰጠሃቸው። 15በተራቡ
ጊዜ ከሰማይ መና ሰጠሃቸው፤ በተጠሙም
ጊዜ ከዐለት ውሃ አፈለቅህላቸው፤ ልትሰ
ጣቸው በተዘረጋች እጅ ወደ ማልህላቸ
ውም ምድር ገብተው እንዲወርሱ አዘዝ
ሃቸው።
16"እነርሱና አባቶቻችን ግን ትምክሕ
ተኞችና ዐንገተ ደንዳኖች ሆኑ፤ ትእዛዞ
ችህንም አልፈጸሙም። 17ለመስማት አልፈ
ለጉም፤ በመካከላቸውም ያደረግሃቸውን
ታምራት ማስታወስ አልቻሉም። አንገታ
ቸውን አደነደኑ፤ በዐመፃቸውም ወደ
ባርነታቸው ለመመለስ መሪ ሾሙ። አንተ
ግን ይቅር ባይ አምላክ፣ ቸርና ርኅሩኅ፣
ለቍጣም የዘገየህና ምሕረትህ የበዛ ነህ።
ስለዚህ አልተውሃቸውም፤ 18የጥጃ ምስል ለራ
ሳቸው አቅልጠው፣ 'ከግብፅ ያወጣህ አምላክ
ይህ ነው' ባሉና አስጸያፊ የስድብ ቃል በተ
ናገሩ ጊዜ እንኳ አልተለየሃቸውም።
19"ከርኅራኄህ ብዛት የተነሣ በምድረ
በዳ አልተውሃቸውም፤ ቀን የደመናው ዐምድ
በመንገዳቸው ላይ መምራቱን፣ ሌሊትም
የእሳቱ ዐምድ በሚሄዱበት ላይ ማብራቱን
አላቆመም። 20ያስተምራቸው ዘንድ ቸር
መንፈስህን ሰጠሃቸው፤ መናውን ከአፋ
ቸው አልከለከልህም፤ በተጠሙ ጊዜ ውሃ
ሰጠሃቸው። 21በምድረ በዳ አርባ ዓመት
መገብሃቸው፤ ምንም ያጡት አልነበረም፤
ልብሳቸው አላለቀም፤ እግራቸውም አላ
በጠም። 22"በሩቅ የሚገኙትን ድንበሮች
እንኳ ሳይቀር፣ መንግሥታትንና አሕዛብን
ሰጠሃቸው። የሐሴቦን ንጉሥ የሴዎንን
ምድር፣ የባሳን ንጉሥ የዐግን ምድር
ወረሱ። 23ወንዶች ልጆቻቸውን እንደ ሰማይ
ከዋክብት አበዛሃቸው፤ አባቶቻቸው ገብ
ተው እንዲወርሱ ወዳዘዝሃቸውም ምድር
አገባሃቸው። 24በምድሪቱ ወንዶች ልጆቻ
ቸው ገቡባት፤ ወረሷትም። በምድሪቱ ላይ
ይኖሩ የነበሩትን ከነዓናውያን በፊታቸው
አንበረከክህ፤ ያሻቸውን ያደርጉባቸው ዘንድ
ከነዓናውያንን ከንጉሦቻቸውና ከምድሪቱ
ሕዝቦች ጋር በእጃቸው አሳልፈህ ሰጠ
ሃቸው። 25የተመሸጉ ከተሞቻቸውንና የሰ
ባውን ምድር ያዙ፤ በመልካም ነገር ሁሉ
የተሞሉ ቤቶቻቸውን፣ የተቈፈሩ የውሃ
ጕድጓዶቻቸውን፣ የወይን ተክላቸውን፣
የወይራ ዛፎቻቸውንና ስፍር ቍጥር የሌላ
ቸውን የፍሬ ዛፎች ያዙ። እስኪጠግቡ
በሉ፤ ወፈሩም፤ በታላቅ በጎነትህም ደስ
ተሰኙ።

9፥4 አስ10፥23
9፥5 2ሳሙ7፥26፤ መዝ78፥4
9፥6 ዘፍ1፥1፤ ዘፀ8፥19፤ዘዳ6፥4፤ 10፥14፤መዝ95፥5፤ 103፥20፤146፥6፤ 148፥2፤ኢሳ37፥16፤ 40፥26፤45፥12፤ ዮና1፥9፤ሐሥ4፥24፤ ራእ10፥6
9፥7 ዘፍ11፥28፤ 16፥11፤17፥5
9፥8 ዘፍ15፥6፤ 15፥18-21፤ ኢሱ21፥45፤ ዕዝ9፥1፡15
9፥9 ዘፀ2፥23-25፤ 3፥7፤14፥10-30
9፥10 ዘፀ3፥20፤ 6፥6፤10፥1፤ ዘኍ6፥27፤ መዝ74፥9፤ ኤር32፥20፤ዳን9፥15
9፥11 ዘፀ14፥28፤ 15፥4-5፤ 5፤10መዝ78፥13፤ ዕብ11፥29
9፥12 ዘፀ13፥21፤ 15፥13፥ዘዳ1፥33
9፥13 ዘፀ19፥11፡ 19፤20፥1፡22፤ ዘዳ4፥7-8፤ መዝ119፥137
9፥14 ዘፍ2፥3፤ ዘፀ20፥8-11
9፥15 ዘፍ14፥22፤ ዘፀ16፥4፤17፥6፤ ዘኍ20፥7-13፤ ዘዳ1፥8፡21፤ መዝ78፥24-25፤ ዮሐ6፥31
9፥16 ዘፀ32፥9፤ ዘዳ1፥26-33፤ 31፥29፤ኤር7፥26፤ 17፥23፥19፥15
9፥17 ዘፀ22፥27፤ 34፥6፤ዘኍ14፥1-4፡ 17-19፤ ዘዳ4፥31፤ መሳ8፥34፤መዝ77፥11 ፤78፥11፡12፡42፤86፡1 5፤103፥8፤ 105፥5፤ 106፥7፤ 130፥4፤ ኤር7፥26፤19፥15፤ ሕዝ5፥6፤ዳን9፥9፤ ናሆ1፥3
9፥18 ዘፀ20፥23፤ 32፥4
9፥19 ዘፀ13፥21፡22
9፥20 ዘፀ16፥15፤ 17፥6፤ዘኍ9፥17፤ 1፥17፤ መዝ23፥3፤143፥10፤ ኢሳ 63፥11-14፤ ሐጌ2፥5፤ ዘካ4፥6
9፥21 ዘፀ16፥35፤ ዘዳ2፥7፤8፥4
9፥22 ዘኍ21፥21፡ 33፤ዘዳ2፥26፤3፥11፡
9፥23 ዘፍ12፥2፤ ዘሌ26፥9፤ ዘኍ10፥36፤ 9፥24 ኢሱ 11፥23፤ መሳ4፥23፤ 2ዜና14፥13 9፥25 ዘፀ18፥9፤ ዘዳ6፥10-12፤8፥8-11፤ 11፥11፤ 2፥12-15፤መዝ23፥6፤ 25፥7፤69፥16

[ኘ]9 ዕብራይስጡ፣ *ያም ሰፍ*ይላል፤ ይኸውም የደንገል ባሕር ማለት ነው።

26“ነገር ግን እንቢተኞች ሆኑ፤ ዐመፁብ
ህም፤ ሕግህንም አሽቀንጥረው ጣሉ፤ ወደ አንተ
እንዲመለሱ ሲያስጠነቅቋቸው የነበሩት ነቢ
ያትህን ገደሉ፤ አስጸያፊ የስድብ ቃልም
ተናገሩ። 27ስለዚህ ላስጨነቋቸው ጠላቶቻ
ቸው አሳልፈህ ሰጠሃቸው። በተጨነቁ ጊዜ
ግን ወደ አንተ ጮኹ፤ አንተም ከሰማይ ሰማ
ሃቸው፤ ከርኅራኄህም ብዛት የተነሣ ከጠ
ላቶቻቸው እጅ የሚያድኗቸውን ታዳጊ
ዎች ሰጠሃቸው።
28“ነገር ግን ዕረፍት ባገኙ ጊዜ፣ በፊ
ትህ ክፉውን ነገር እንደ ገና ፈጸሙ፤ ከዚ
ያም ይገዟቸው ዘንድ በጠላቶቻቸው እጅ
ጣልሃቸው፤ እንደ ገና ወደ አንተ በጮኹ
ጊዜ፣ ከሰማይ ሰማህ፤ በርኅራኄህም በየጊ
ዜው ታደግሃቸው።
29“ወደ ሕግህ እንዲመለሱ አስጠነቀቅሃ
ቸው፤ እነርሱ ግን እብሪተኞች ሆኑ። ትእ
ዛዞችህንም አልፈጸሙም፤ አንድ ሰው ቢፈ
ጽማቸው በሕይወት የሚኖርባቸውን ሥር
ዐቶችህን ተላለፉ። እምቢተኞች ሆነው
ጀርባቸውን አዞሩብህ፤ ዐንገታቸውን አደነ
ደኑ፤መስማትም አልፈለጉም። 30ብዙ ዘመን
ታገሥሃቸው፤ በነቢያትህ አማካይነት በመ
ንፈስህ አስጠነቀቅሃቸው። ነገር ግን አላ
ደመጡህም፤ ከዚህም የተነሣ ጎረቤቶቻ
ቸው ለሆኑ አሕዛብ አሳልፈህ ሰጠሃቸው።
31አንተ ግን ቸርና መሓሪ አምላክ ነህና
ከምሕረትህ ብዛት የተነሣ፣ ፈጽመህ
አላጠፋሃቸውም፤ አልተውሃቸውምም።
32“አሁንም አምላካችን ሆይ፤ ቃል ኪዳ
ንህንና ዘላለማዊ ፍቅርህን የምትጠብቅ
ታላቅ፣ ኀያልና የተፈራህ አምላክ ሆይ፤
ከአሦር ነገሥታት ዘመን ጀምሮ እስከ
ዛሬ ድረስ በእኛ፣ በነገሥታታችንና በመ
ሪዎቻችን፣ በካህናታችንና በነቢያታችን፣
በአባቶቻችንና በመላው ሕዝብህ ላይ
የደረሰው ይህ ሁሉ መከራ በፊትህ እንደ
ቀላል ነገር አይታይ። 33በደረሰብን ሁሉ
አንተ ጻድቅ ነህ፤ እኛ በደለኞች ነን፤
አንተ ግን ትክክለኛውን አደረግህ። 34ነገ
ሥታታችን፣ መሪዎቻችን፣ ካህናታችንና
አባቶቻችን ሕግህን አልጠበቁም፤ ትእዛ
ዞችህን ወይም የሰጠሃቸውን ማስጠንቀቂ
ያዎች አልሰሙም። 35በገዛ መንግሥታ
ቸው፣ በሰጠሃቸው ታላቅ በጎነትህና በፊ
ታቸውም ባዘጋጀህላቸው ሰፊና ለም ምድር
እንኳ፣ አንተን አላገለገሉም፤ ከክፉ መንገ
ዳቸውም አልተመለሱም።
36“እነሆ፤ ዛሬም ባሮች ነን፤ አባቶቻችን
ፍሬዋንና በረከቷን እንዲበሉ በሰጠሃቸው
ምድር ባሮች ነን። 37ከኀጢአታችን የተ
ነሣ የተትረፈረፈው መከር ሲሳይ የሆነው
በላያችን ላስቀመጥሃቸው ነገሥታት ነው፤
እነርሱም ደስ እንዳሰኛቸው በሰውነታችንና
በቀንድ ከብቶቻችን ላይ ያዛሉ። እኛም
በታላቅ ጭንቀት ውስጥ እንገኛለን።

## የሕዝቡ መስማማት

38“ከዚህ ሁሉ የተነሣም ጽሑፍ ላይ በማ
ስፈር ግዴታ የምንገባበትን የውል ስምም
ነት እናደርጋለን፤ መሪዎቻችን፣ ሌዋውያ
ኖቻችንና ካህናቶቻችንም ማኅተሞቻቸውን
ያኖሩበ ታል።”

10 ያተሙትም እነዚህ ናቸው፤
የሐካልያ ልጅ አገረ ገዡ
ነህምያ፣
ሴዴቅያስ፣ 2ሠራያ፣ ዓዛርያስ፣ ኤርምያስ፣
3 ፋስኮር፣ አማርያ፣ መልክያ፣
4ሐጡስ፣ ሰበንያ፣ መሉክ፣
5 ካሪም፣ ሜሪሞት፣ አብድዩ፣
6 ዳንኤል፣ ጌንቶን፣ ባሮክ፣
7 ሜሱላም፣ አብያ፣ ሚያሚን፣
8መዓዝያ፣ ቤልጋይ፣ ሸማያ፤ እነዚህ
ካህናት ነበሩ።
9ሌዋውያኑ፦
የአዛንያ ልጅ ኢያሱ፣ ከኤንሐዳድ
ወንዶች ልጆች ቢንዊ፣ ቀድምኤል፣
10ወንድሞቻቸው፦
ሰባንያ፣ ሆዲያ፣ ቆሊጣስ፣ ፌልያ፣
ሐናን፣
11ሚካ፣ ረአብ፣ ሐሸብያ፣
12ዘኩር፣ ሰራብያ፣ ሰበንያ፣
13ሆዲያ፣ ባኒ፣ ብኒኑ።
14የሕዝብ መሪዎች፦
ፋሮስ፣ ፈሐት፣ ሞዓብ፣ ኤላም፣
ዛቱዕ፣ ባኒ፣
15ቡኒ፣ ዓዝጋድ፣ ቤባይ፣
16አዶንያስ፣ በጉዋይ፣ ዓዲን፣
17አጤር፣ሕዝቅያስ፣ዓዙር፣
18ሆዲያ፣ ሐሱም፣ ቤሳይ፣
19ሐሪፍ፣ ዓናቶት፣ ኖባይ፣
20መግጲዓስ፣ ሜሱላም፣ ኤዚር፣
21ሜሴዜቤል፣ ሳዶቅ፣ ያዱአ፣
22ፈላጥያ፣ ሐናን፣ ዓናያ፣
23ሆሴዕ፣ ሐናንያ፣አሱብ፣
24አሎኤስ፣ ፈልሃ፣ ሶቤቅ፣
25ሬሁም፣ ሐሰብና፣ መዕሤያ፣
26አኪያ፣ ሐናን፣ ዓናን፣
27መሉክ፣ ካሪምና በዓና።
28የቀሩት ሕዝብ፦ ማለት ካህናቱ፣
ሌዋውያኑ፣ በር ጠባቂዎቹ፣ መዘምራኑ፣
የቤተ መቅደሱ አገልጋዮች፣ ስለ እግዚአብ
ሔር ሕግ ብለው ራሳቸውን ከጎረቤት አሕ

9፥26 ኢሱ7፥25፤ 1ነገ14፥9መሳ2፥12-13፤ ኤር2፥30፤26፥8፤44፥10፤ ማቴ21፥35-36፤ 23፥29-36ሐሥ7፥52
9፥27 ዘኍ25፥17፤ መሳ2፥14፤3፥9፤ መዝ51፥1፤103፥8፤ 106፥45፤ 119፥156፤
9፥29 ቀኍ16-17፤ ዘዳ30፥16፤መሳ6፥8፤ 1ሳሙ8፥3፤መዝ5፥5፤ ኢሳ2፥11፤ ኤር19፥15፤43፥2፤ ዘዳ7፥11-12
9፥28 ዘፀ32፥22፤ መሳ2፥17፤ 2ኛሳሙ24፥14፤ መዝ22፥4፤106፥43፤ 136፥24
9፥30 2ነገ17፥13-18፤ 2ዜና36፥16፤ ኤር16፥11፤ዘካ7፥12
9፥31 ዘዳ4፥31፤ ኢሳ48፥9፤65፥9
9፥32 ዘፀ18፥8፤ ዘዳ7፥9፡21፤1ነገ8፥23፤ ኢዮ9፥19፤ መዝ24፥8፤89፥8፤ 93፥4፤ዳን9፥4
9፥33 ዘፍ18፥25፤ ኤር44፥3ዳን9፥7-8፡14
9፥34 2ነገ23፥11፤ ኤር44፥17
9፥35 ዘዳ28፥45-48፤ ኢሳ63፥7
9፥36 ዕዝ9፥9
9፥37 ዘዳ28፥33፤ ሰቆ5፥5
9፥38 2ዜና23፥16፤ አሳ44፥5
10፥1 ዕዝ2፥2
10፥2 1ዜና9፥12
10፥5 1ዜና24፥8
10፥8 ነህ12፥1
10፥9 ነህ12፥1
10፥16 ዕዝ8፥6
10፥20 1ዜና24፥15
10፥23 ነህ7፥2
10፥28 2ዜና 6፥26፤ ነህ9፥2፤ መዝ135፥1

ዛብ የለዩ ሁሉ፣ ሚስቶቻቸው፣ ወንዶችና
ሴቶች ልጆቻቸው፣ የሚያውቁና የሚያስ
ተውሉ ሁሉ ቃለ መሐላ ፈጸሙ፤ 29እነር
ሱም ከወንድሞቻቸውና ከመኳንንታቸው
ጋር በመሆን በእግዚአብሔር ባሪያ በሙሴ
አማካይነት የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ሕግ
የጌታ ችንን የእግዚአብሔርን ትእዛዞች፣
ደን ቦችና ሥርዐቶች ሁሉ ለመታዘዝ በዚ
ህ ርግማንና መሐላ ቃል ገቡ። 30“ሴት
ልጆ ቻችንን በዙሪያችን ላሉት አሕዛብ
አንሰ ጥም፤ የእነርሱን ሴቶች ልጆች
ለወንዶች ልጆቻችን አንወስድም።
31“አሕዛብ ጎረቤቶቻችን በሰንበት ቀን
ለመሸጥ ሸቀጣ ሸቀጥ ወይም እህል ቢያ
መጡ፣ በሰንበት ወይም በማናቸውም በተ
ቀደሰ ቀን ከእነርሱ አንገዛም። በየሰባት ዓ
መ ቱም ምድሪቱን እናሳርፋለን፤ ዕዳንም
ሁሉ እንሠርዛለን።
32“በየዓመቱ ለእግዚአብሔር ቤት አገልግ
ሎት የሚሆን የሰቅልA አንድ ሦስተኛ
ለመስጠት ቃል እንገባለን፤ 33ይህም በጠ
ረጴዛው ላይ ለሚቀርበው ገጸ ኅብስት፣
ዘወትር ለሚቀርበው የእህል ቍርባን፣ የሚ
ቃጠል መሥዋዕት፣ በሰንበት፣ በወር መባ
ቻና በተደነገጉ በዓላት ለሚቀርበው መሥ
ዋዕት፣ ለተቀደሱ መባዎች፣ ለእስራኤል
ስርየት ለሚቀርበው የኀጢአት መሥዋዕ
ትና ለአምላካችን ቤት ሥራ ሁሉ
የሚውል ነው።
34“እኛ፣ ማለት ካህናቱ፣ ሌዋውያኑና
ሕዝቡ በየዓመቱ በተወሰነው ጊዜ በሕጉ
እንደተጻፈው፣ በአምላካችን በእግዚአብሐ
ር መሠዊያ ላይ የሚነደውን ዕንጨት
የእያን ዳንዳችን ቤተ ሰብ መቼ ወደ
አምላካችን ቤት ማምጣት እንዳለበት
ለመወሰን ዕጣ ተጣ ጣልን።
35“የሰብላችንንና የእያንዳንዱን ዛፍ ፍሬ
በኵራትም ወደ እግዚአብሔር ቤት ለማምጣት
ቃል እንገባለን።
36“እንዲሁም በሕጉ እንደ ተጻፈው የወ
ንድ ልጆቻችንንና፣ የቀንድ ከብቶቻች
ንን፣ የመንጋዎቻችንን፣ የበግና የፍየል
መንጋ ዎቻችንን በኵራት ወደ
አምላካችን ቤት፣ ወደ ሚያገለግሉትም
ካህናት እና መጣለን።
37“ከዚህም በላይ የቡሆአችንን፣ የእህል
ቍርባናችንን፣ የዛፎቻችንን ፍሬ ሁሉ፣ አዲ
ሱን የወይን ጠጃችንንና የዘይታችንን በኵ
ራት ወደ ካህናቱ፣ ወደ አምላካችን
ቤት ዕቃ ቤቶች እናመጣለን። እኛ በምን
ሠራባቸው ከተሞች ሁሉ ያለውን ዐሥራት
የሚሰበስቡት ሌዋውያን ስለሆኑ፣ የሰብላ

10፥29 ዘኍ5፥21፤ መዝ119፥106
10፥30 ዘፀ34፥16፤ ነህ13፥23
10፥31 ዘፀ23፥11፤ ዘሌ25፥1-7፤ዘዳ15፥1፤ ነህ13፥16፡18፤ ኤር17፥27፤ ሕዝ23፥38፤አሞ8፥5
10፥33 ዘሌ 24፥6፤ ዘኍ10፥10፤2ዜና24፥5፤ መዝ81፥3፤ኢሳ1፥14
10፥34 ዘሌ 16፥8፤ ነህ13፥31
10፥35 ዘፀ22፥29፤ ዘኍ18፥12፤ዘዳ26፥1-11
10፥36 ዘፀ13፥2፤ ዘኍ18፥14-16፤ ነህ13፥31
10፥37 ዘሌ27፥30፤ዘኍ18፥12፡21፤ዘዳ14፥22-29፤ ሕዝ44፥30
10፥38 ዘኍ18፥26
10፥39 ነህ13፥11፡12
11፥1 ነህ7፥4፡73፤ ኢሳ48፥2፤52፥1፤ 64፥10፥ዘካ14፥20-21
11፥3 ዕዝ2፥1
11፥4 ዕዝ1፥5፤2፥70

ችንን ዐሥራት ወደ ሌዋውያኑ እናመጣ
ለን። 38ዐሥራቱን በሚቀበሉበት ጊዜም
ከአሮን ዘር የተወለደው ካህን ከሌዋውያኑ
ጋር አብሮ ይገኛል፤ ሌዋውያኑም የዐሥራ
ቱን አንድ ዐሥረኛ ወደ ላይ እስካለው፣
እስከ አምላካችን ቤት ዕቃ ቤቶች ማከ
ማቻ ድረስ ያመጡታል። 39የእስራ
ኤል ሕዝብና ሌዋውያኑ ጭምር፣ ከእህሉ፣
ከአዲሱ ወይን ጠጅና ከዘይቱ ያዋጡትን፣
የመቅ ደሱ ዕቃዎች ወደ ሚቀመጡበት፣
አገልጋይ ካህናት፣ በር ጠባቂዎቹና
መዘምራኑ ወደ ሚያርፉበት ዕቃ ቤቶች
ያምጡ።
“እኛም የአምላካችንን ቤት ቸል
አንልም”

### አዲሶቹ የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች
11፥3-19 ተጓ ምብ 1ዜና 9፥1-17

11 በዚህ ጊዜ የሕዝቡ መሪዎች
መኖሪያቸውን በኢየሩሳሌም አደ
ረጉ፤ ከቀረው ሕዝብ ከዐሥር አንዱ
እጅ በቅድስቲቱ ከተማ በኢየሩሳሌም፣
የቀሩት ዘጠኙ እጅ ደግሞ በየራሳቸው
ከተሞች እንዲኖሩ ዕጣ ተጣጣሉ። 2ሕ
ዝቡም በኢየሩሳሌም ለመኖር በራሳቸው
ፈቃድ የተነሣሡትን ሰዎች ሁሉ
አመሰገኑ።
3እንግዲህ በኢየሩሳሌም የተቀመጡት
የአውራጃዪቱ መሪዎች እነዚህ ናቸው፤
በዚህ ጊዜም በይሁዳ ከተሞች የሚኖሩ
የተወሰኑ እስራኤላውያን፣ ካህናት፣ ሌዋ
ውያን፣ የቤተ መቅደሱ አገልጋዮችና የሰሎ
ሞን አገልጋዮች ዘሮች እያንዳንዳቸው በተ
ለያዩ ከተሞች ባሉት በየራሳቸው ንብረት
ላይ ተቀመጡ፤ 4ከይሁዳና ከብንያም ወገን
የሆኑት የተቀሩት ሰዎች ደግሞ በኢየሩ
ሳሌም ተቀመጡ፤
ከይሁዳ ዘሮች፡-
ከፋሬስ ዘር የመላልኤል ልጅ፣ የሰ
ፋጥያስ ልጅ፣ የአማርያ ልጅ፣ የዘካ
ርያስ ልጅ፣ የዖዝያ ልጅ አታያ፤
5ከሴሎ ዘር የዘካርያስ ልጅ፣ የዮያሪብ
ልጅ፣ የዓዳያ ልጅ፣ የዖዛያ ልጅ፣
የኮልሖዜ ልጅ፣ የባሮክ ልጅ መዕ
ሤያ። 6በኢየሩሳሌም የተቀመጡት
የፋሬስ ዘሮች በጠቅላላ 468 ብርቱ
ሰዎች ናቸው።
7ከብንያም ዘሮች፡-
የየሻያ ልጅ፣ የኢቲኤል ልጅ፣ የመዕሤያ
ልጅ፣ የቆላያ ልጅ፣ የፈዳያ ልጅ፣
የዮእድ ልጅ፣ የሜሱላም ልጅ ሰሉ፤
8ተከታዮቹም ጌቤና ሳላይ 928 ወንዶች፤
9የእነዚህም አለቃ የዝክሪ ልጅ ኢዩኤል
ሲሆን፣ የሐስኑአ ልጅ ይሁዳ የከተማዪቱ

“ሁለተኛ አውራጃ”
የበላይ ነበር፡፡
10ከካህናቱ፡-
የዮያሪብ ልጅ ዮዳኤ፤ ያኪን፤ 11የእግዚ
አብሔር ቤት አለቃ የአኪጦብ ልጅ፣
የመራዮት ልጅ፣ የሳዶቅ ልጅ፣ የሜ
ሱላም ልጅ፣ የኪልቅያስ ልጅ ሡራያ፤
12የቤተ መቅደሱን ሥራ ያከናወኑት ወን
ድሞቻቸው፣ 822 ሰዎች፤ የመልክያ
ልጅ፣ የፋስኮር ልጅ፣ የዘካርያስ
ልጅ፣ የአማሲ ልጅ፣ የፈላልያ ልጅ፣
የይሮሐም ልጅ ዓዳያ፤ 13ወንድሞቹ
የሆኑት የየቤተ ሰቡ አለቆች 242
ወንዶች፤ የኢሜር ልጅ የምሺሌሞት
ልጅ፣ የአሕዛይ ልጅ፣ የኤዝርኤል ልጅ
አማስያ፤ 14እንዲሁም ብርቱ የሆኑት
ወንድሞቹ[ከ] 128 ሰዎች፤ የእነርሱም
ዋና አለቃ የሐግዶሊም ልጅ
ዘብድኤል ነበር፡፡
15ከሌዋውያኑ፡-
የቡኒ ልጅ፣ የአሳብያ ልጅ፣ የዓዝሪ
ቃም ልጅ፣ የአሱብ ልጅ ሻማያ፤
16እንዲሁም የእግዚአብሔር ቤት የውጪ
ሥራ ኀላፊዎች የነበሩት፣ ከሌዋውያን
አለቆች ሁለቱ ሳባ ታይና ዮዛባት፡፡
17በምስጋ ናና በጸሎት ጊዜ ይመራ
የነበረው የዋናው አለቃ የአሳፍ ልጅ፣ የዘ
ብዲ ልጅ፣ የሚካ ልጅ መታንያ፣ ከወን
ድሞቹ ሁለተኛ የሆነው በቅበቃር፣ የኤ
ዶታም ልጅ፣ የጋላል ልጅ፣ የሳሙስ
ልጅ አብድያ፡፡ 18በቅድስቲቱ ከተማ
ውስጥ የነበሩት የሌዋውያኑ ቍጥር
284 ነበረ፡፡
19በር ጠባቂዎች፡-
ዓቁብ፣ ጤልሞንና በሮቹን የሚጠብቁ
ወንድሞቻቸው፣ 172 ሰዎች፡፡
20የቀሩት እስራኤላውያንም ከካህናቱና
ከሌዋውያኑ ጋር በይሁዳ ከተሞች ሁሉ
በየርስታቸው ተቀመጡ፡፡
21የቤተ መቅደሱ አገልጋዮች በዖፌል
ኰረብታ ላይ ተቀመጡ፤ ሲሐና ጊሽጳ በእ
ነርሱ ላይ ያዙ ነበር፡፡
22በኢየሩሳሌም የሌዋውያኑ ዋና አለቃ
የሚካ ልጅ፣ የመታንያ ልጅ፣ የሐሻብያ
ልጅ፣ የባኒ ልጅ ኦዚ ነበረ፤ ኦዚ በእግዚ
አብሔር ቤት አገልግሎት ለሚዘመረው
መዝሙር ኀላፊ ከነበሩት ከአሳፍ ዘሮች
አንዱ ነበረ፡፡ 23መዘምራኑ የየዕለቱን ተግ
ባራቸውን በሚቈጣጠረው በንጉሡ ትእዛዝ
ሥር ነበሩ፡፡
24የይሁዳ ልጅ የዛራ ዘር የሆነው የሜሴዜ
ቤል ልጅ ፈታያ ሕዝቡን በሚመለከት
ጒዳይ ሁሉ የንጉሡ ተወካይ ነበር፡፡

11፥11 2ነገ25፥18፤ ዕዝ2፥2፤7፥2
11፥16 ዕዝ8፥33፤ 10፥15
11፥17 1ዜና9፥15፤ 25፥1፤2ዜና5፥12፤ ነህ12፥8
11፥18 ራእ21፥2
11፥21 ዕዝ2፥43፤ ነህ3፥26
11፥22 1ዜና9፥15
11፥23 ዜና15፥16፤ ነህ7፥44
11፥24 ዘፍ38፥30
11፥25 ዘፍ35፥27፤ ዘኍ21፥30
11፥26 ኢሱ15፥26፡27
11፥27 ዘፍ21፥14፤ ኢሱ15፥28
11፥28 1ሳሙ27፥6
11፥29 ኢሱ10፥3፤ 15፥33፡35
11፥30 ኢሱ10፥3፡ 10፤15፥28፡34፡35፡39
11፥31 ኢሱ 12፥9፤ 21፥17፤1ሳሙ13፥2፤አ
ሳ10፥29
11፥32 ኢሱ21፥18፤ 1ሳሙ21፥1፤ኢሳ10፥30፤ ኤር1፥1
11፥33 ኢሱ 11፥1፤ 18፥25፤2ሳሙ4፥3
11፥34 1ሳሙ 13፥18
11፥35 1ዜና8፥12
12፥1 1ዜና3፥19፤ ዕዝ2፥2፤3፥2፤ ነህ10፥1-8፡9፤ዘካ4፥6-10
12፥4 ቍ16፤ 1ዜና24፥10፤ዘካ1፥1፤ሉ
ቃ1፥5
12፥6 1ዜና24፥7
12፥8 ዕዝ 2፥2፤ ነህ11፥17
12፥10 ዕዝ10፥24፤ ነህ 3፥20

25ከይሁዳ ሕዝብ ጥቂቱ በመንደሮችና
በእርሻ ቦታዎች፣ በቂርያት አርባቅና በዙ
ሪያዋ ባሉ መኖሪያዎቿ፣ በዲቦንና በመኖ
ሪያዎቿ፣ በይቀብጽኤልና በመንደሮቿ ተቀ
መጡ፤ 26በኢያሱ፣ በሞላዳ፣ በቤትጳሌጥ፣
27በሐጸርሹዓል፣ በቤርሳቤህና በመኖሪያ
ዎቿ፣ 28በጺቅላግ፣ በምኮናና በመኖሪያዎቿ፣
29በዓይንሪሞን፣ በጾርዓ፣ በየርሙት፣ 30በዛ
ኖዋ፣ በዓዶላምና በመንደሮቻቸው፣ በለኪ
ሶና በእርሻዎቿ፣ በዓዜቃና በመንደሮቿ፡፡
ስለዚህ ከቤርሳቤህ ጀምሮ እስከ ሄኖም
ሸለቆ ባለው ስፍራ ሁሉ ተቀመጡ፡፡
31ከጌባ የመጡት የብንያም ዘሮች በማክ
ማስ፣ በጋያ፣ በቤቴልና በመኖሪያዎቿ፣
32በዓናቶት፣ በኖብና በሐናንያ፣ 33በሐ
ጾር፣ በራማና በጊቴም፣ 34በሐዲድ፣
በስቦይምና በንበላት፣ 35በሎድና በኦኖ፣
ደግሞም “የእጅ ጥበብ ባለሙያዎች ሸለቆ”
በተባለው ስፍራ ተቀመጡ፡፡
36በይሁዳ ከነበሩት ሌዋውያን ከፊሎቹ
በብንያም ምድር ተቀመጡ፡፡

## ካህናትና ሌዋውያን

12 ከሰላትያል ልጅ ከዘሩባቤልና
ከኢያሱ ጋር የተመለሱት
ካህናትና ሌዋውያን እነዚህ ነበሩ፤
ሡራያ፣ ኤርምያስ፣ ዕዝራ፣
2አማርያ፣ መሉክ፣ ሐጡስ፣
3ሴኬንያ፣ ሬሁም፣ ሜሪሞት፣
4አዶ፣ጌንቶን፣አብያ፣
5ሚያሚን፣ መዓድያ፣ ቢልጋ፣
6ሸማያ፣ ዮያሪብ፣ ዮዳኤ፣
7ሰሉ፣ዓሞቅ፣ ኬልቅያስና ዮዳኤ፡፡
እነዚህ በኢያሱ ዘመን የካህናቱና የወንድ
ሞቻቸው አለቆች ነበሩ፡፡
8ሌዋውያኑ ደግሞ ኢያሱ፣ ቢንዊ፣ ቀድ
ምኤል፣ ሰራብያ፣ ይሁዳ እንዲሁም ከወን
ድሞቹ ጋር የምስጋና መዝሙር ኀላፊ
የሆነው መታንያ ነበሩ፡፡ 9ወንድሞቻቸው
የሆኑት በቅቡቅያና ዑኒም በአገልግሎት ጊዜ
ከእነርሱ ትይዩ ይቆሙ ነበር፡፡
10ኢያሱ ዮአቂምን ወለደ፤ ዮአቂም
ኤልያሴብን ወለደ፤ ኤልያሴብ ዮአዳን
ወለደ፤ 11ዮአዳ ዮናታንን ወለደ፤ ዮናታ
ንም ያዱአን ወለደ፡፡
12በዮአቂም ዘመን የካህናቱ ቤተሰብ
አለቆች እነዚህ ነበሩ፤
ከሡራያ ቤተ ሰብ፣ ምራያ፤
ከኤርምያስ፣ ሐናንያ፤
13ከዕዝራ፣ ሜሱላም፤
ከአማርያ፣ ይሆሐናን፤

[ከ]14 አብዛኞቹ የሰብዓ ሊቃናት ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራ ይስጡ ግን፣ *ወንድሞቻቸው* ይላል፡፡

14ከሙሊኪ፣ ዮናታን፤
ከሰብንያ፣ ዮሴፍ፤
15ከካሪም፣ ዓድና፤
ከመራዮት፣ ሔልቃይ፤
16ከአዶ፣ ዘካርያስ፤
ከጌንቶን፣ ሜሱላም፤
17ከአብያ፣ ዝክሪ፤
ከሚያሚንና ከሞዓድያ፣ ፈልጣይ፤
18ከቢልጋ፣ ሳሙስ፤
ከሸማያ፣ ዮናታን፤
19ከዮያሪብ፣ መትናይ፤
ከዮዳኤ፣ ኦዚ፤
20ከሳላይ፣ ቃላይ፤
ከዓሞቅ፣ ዔቤር፤
21ከኬልቅያስ፣ ሐሸብያ፤
ከዮዳኢ፣ ናትናኤል።

22በኤሊያሴብ፣ በዮአዳ፣ በዮሐናንና በያ
ዱአ ዘመን የሌዋውያኑ ቤተ ሰብ አለቆ
ችና ካህናቱ፣ በፋርሳዊው በዳርዮስ ዘመነ
መንግሥት ተመዝግበው ነበር። 23ከሌዋውያን
ዘሮች መካከል እስከ ኤሊያሴብ ልጅ እስከ
ዮሐናን ድረስ ያሉት የየቤተ ሰቡ ኀላፊ
ዎች በታሪክ መጽሐፍ ተመዝግበው ነበር።
24የሌዋውያኑ መሪዎች ሐሸብያ፣ ሰራብያ፣
የቀድምኤል ልጅ ኢያሱ ነበሩ፤ እነርሱም
ከወንድሞቻቸው ፊት ለፊት ሆነው የእግዚ
አብሔር ሰው ዳዊት በሰጠው መመሪያ
መሠረት እየተቀባበሉ ውዳሴና ምስጋና
ያቀርቡ ነበር።

25በቅጥሩ በሮች አጠገብ ያሉትን ዕቃ ቤቶች
የሚጠብቁት ዘቦች ደግሞ መታንያ፣ በቅ
ቡቅያ፣ አብድዩ፣ ሜሱላም፣ ጤልሞንና
ዓቁብ ነበሩ። 26እነዚህም በኢዮሴዴቅ
ልጅ፣ በኢያሱ ልጅ በዮአቂም፣ በአገረ ገዢ
በነህምያ፣ በካህኑና በጸሓፊው በዕዝራ
ዘመን አገለገሉ።

## የኢየሩሳሌም ቅጥር ምረቃ በዓል

27የኢየሩሳሌም ቅጥር ሲመረቅ ሌዋው
ያኑ በምስጋና መዝሙር፣ በጸናጽል፣ በበገ
ናና በመሰንቆ ድምፅ የምረቃውን በዓል
በደስታ እንዲያከብሩ ከሚኖሩበት ተፈል
ገው ወደ ኢየሩሳሌም መጡ። 28መዘምራ
ኑንም እንደዚሁ በኢየሩሳሌም ዙሪያ
ካለው ከነጦፋውያን መንደሮች በአንድነት
ሰበሰ ቧቸው። 29በኢየሩሳሌም ዙሪያ የራ
ሳቸውን መንደሮች ሠርተው ስለ ነበር፣
መዘምራኑን ያመጧቸው ከቤት ጌልገላ፣
ከጌባና ከዓዝምት አካባቢ ነው። 30ካህናቱና
ሌዋውያኑ በሥርዐቱ መሠረት ራሳቸውን ካነጹ
በኋላ፣ ሕዝቡን፣ ቅጥሩና በሮቹን አነጹ።

31እኔም የይሁዳን መሪዎች በቅጥሩ ግንብ
አናት ላይ እንዲወጡ[ኸ] አደረግሁ፤ ደግሞም
ምስጋና እንዲያቀርቡ ሁለት ታላላቅ የመዘ
ምራን ቡድን መደብሁ። አንዱ በቅጥሩ
ግንብ አናት[ሠ] በስተ ቀኝ በኩል "ቈሻሻ
መጣያ በር" ወደሚባለው ሄደ። 32እነዚ
ህንም ሆሻያና ከይሁዳ አለቆች እኩሌቶቹ
ተከተሏቸው፤ 33የተከተሏቸውም ከዓዛርያስ፣
ከዕዝራ፣ ከሜሱላም፣ 34ከይሁዳ፣ ከብንያም፣
ከሸማያ፣ ከኤርምያስና፣ 35እንዲሁም መለ
ከት ከያዙ ጥቂት ካህናትና ከአሳፍ ልጅ፣
ከዘኩር ልጅ፣ ከሚካያ ልጅ ከመታንያ
ልጅ፣ ከሸማያ ልጅ፣ ከዮናታን ልጅ፣ ከዘ
ካርያስ ጋር ነበር። 36ወንድሞቹ ሸማያ፣
ኤዝርኤል፣ ሚላላይ፣ ጊላላይ፣ መዓይ፣ ናት
ናኤል፣ ይሁዳና አናኒም የእግዚአብሔር ሰው
ዳዊት ባዘዘው መሠረት የዜማ መሣሪ
ያዎቹን ይዘው ሄዱ፤ ሰልፉን የሚመራ
ውም ጸሓፊው ዕዝራ ነበረ። 37"ከምንጭ
በር" ተነሥተው በቀጥታ ወደ "ዳዊት ከተማ"
ደረጃዎች ወጡ፤ ከዚያም በቅጥሩ መውጫ
በኩል አድርገው ከዳዊት ቤት በላይ በስተ
ምሥራቅ ወደ ሚገኘው ወደ "ውሃ በር"
ሄዱ።

38ሁለተኛው የመዘምራን ቡድን በስተግራ
በኩል ሄደ፤ እኔም ከከፊሉ ሕዝብ ጋር
ሆኜ በቅጥሩ ግንብ[ዐ] ላይ፣ የእቶኑን ግንብ
በማለፍ እስከ ሰፊው ቅጥር ተከተልኋ
ቸው፤ 39ከዚያም ከኤፍሬም በር በላይ፣
በአሮጌ በር[ዘ]፣ በዓሣ በር፣ በሐናንኤል
ግንብ፣ በመቶዎቹ ግንብ አልፌ እስከ
"በጎች በር" ድረስ ተከተልኋቸው። እነር
ሱም "በዘበኞች በር" አጠገብ ሲደርሱ
ቆሙ።

40ቀጥሎም ምስጋና ያቀረቡት ሁለቱ
የመዘምራን ቡድኖች፣ በእግዚአብሔር ቤት
ቦታቸውን ያዙ፤ እኔም ከግማሾቹ ሹማምት
ጋር ቦታዬን ያዝሁ፤ 41እንደዚሁም ካህናቱ
ኤልያቄም፣ መዕሤያ፣ ሚንያሚን፣
ሚካያ፣ ኤልዮዔናይ፣ ዘካርያስና ሐናንያ
መለከታቸውን ይዘው፣ 42መዕሤያ፣ ሸማያ፣
አልዓዛር፣ ኦዚ፣ ይሆሐናን፣ መልክያ፣
ኤላምና ኤጽር ቦታቸውን ያዙ፤ መዘም
ራኑ በይዝረሕያ መሪነት ዘመሩ። 43እግዚ
አብሔር ታላቅ ደስታ ስለ ሰጣቸው፣ በዚ
ያች ዕለት ደስ ብሏቸው ብዙ መሥዋዕት
አቀረቡ፤ ሴቶችና ልጆችም እንደዚሁ ደስ
አላቸው፤ ከዚህም የተነሣ በኢየሩሳሌም
የነበረው የደስታ ድምፅ እስከ ሩቅ ድረስ
ይሰማ ነበር፡

12፥16 ቀኍ4
12፥17 1ዜና24፥10
12፥24 2ዜና8፥14፤ዕዝ2፥40
12፥27 ዘዳ20፥5፤ 2ሳሙ6፥5፤ 1ዜና15፥16፤28፤25፥6፤ መዝ92፥3
12፥28 1ዜና 2፥54፤9፥16
12፥30 ዘፀ19፥10፤ ኢዮ1፥5
12፥31 ነህ2፥13
12፥34 ዕዝ1፥5
12፥35 ዕዝ3፥10
12፥36 1ዜና15፥16፤ 2ዜና8፥14፤ዕዝ7፥6
12፥37 ነህ2፥14፤3፥26
12፥38 ነህ3፥8፤11
12፥39 2ነገ14፥13፤ 2ዜና33፥14፤ነህ3፥1፡6

[ኸ]31 ወይም *ከቅጥሩ ጎን እንዲሄዱ*
[ሠ]31 ወይም *ከቅጥሩ ጎን*
[ዐ]38 ወይም *ከቅጥሩ ጎን*
[ዘ]39 ወይም *በጀሻና በር*

44በዚያን ቀን ስጦታው፣ በኵራቱና
ዐሥራቱ የሚቀመጥበት ዕቃ ቤት የሚጠ
ብቁ ሰዎች ተሾሙ፡፡ እነርሱም በየከተሞች
ዙሪያ ከሚገኙት የእርሻ ቦታዎች ሕጉ
በሚያዘው መሠረት የካህናቱንና የሌዋ
ውያኑን ድርሻ ወደ ዕቃ ቤቱ ማምጣት
ነበረባቸው፤ ይሁዳ በሚያገለግሉ ካህናትና
ሌዋውያን ደስ ተሰኝተው ነበርና፡፡ 45እንደ
መዘምራኑና በር ጠባቂዎቹ ሁሉ፣ እነዚ
ህም የአምላካቸውን አገልግሎትና የመንጻተ
-ን ሥርዐት በዳዊትና በልጁ በሰሎሞን
ትእዛዝ መሠረት ፈጸሙ፡፡ 46ቀድሞ
በዳዊትና በአሳፍ ዘመን ለእግዚአብሔር
የሚቀርቡትን የውዳሴ መዝሙሮችና
ምስጋና የሚመሩ የመዘምራን አለቆች
ነበሩ፡፡ 47በዘሩባቤልና በነህምያም ዘመን
እስራኤል ሁሉ ለመዘምራኑና ለበር ጠ
ባቂዎቹ የየዕለቱን ድርሻ ይሰጡ ነበር፤
የሌሎቹን ሌዋውያን ድርሻም ለብቻ
ያስቀምጡ ነበር፤ ሌዋውያኑም ለአሮን ዘሮች
ድርሻቸውን ያስቀምጡላቸው ነበር፡፡

## ነህምያ በመጨረሻ የወሰደው የተሐድሶ እርምጃ

13 በዚያም ቀን የሙሴን መጽሐፍ ከፍ
ባለ ድምፅ ለሕዝቡ አነበቡ፤ አሞ
ናዊም ሆነ ሞዓባዊ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ
ፈጽሞ እንዳይገባ የሚከለክል ተጽፎ
ተገኘ፤ 2ይህ የሆነው እስራኤልን በምግብና
ውሃ መስተንግዶ በመቀበል ፈንታ፣ በለ
ዓም እንዲረግምላቸው በገንዘብ ስለገዙት
ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አምላካችን ርግማኑን
ወደ በረከት ለወጠው፡፡ 3ሕዝቡም ይህን
ሕግ በሰሙ ጊዜ፣ የባዕድ ወገን የሆ ኑትን
ሁሉ ከእስራኤል ለዩ፡፡

4ቀድሞ የአምላካችን ዕቃ ቤቶች ኀላፊ
ሆኖ የተሾመው ካህኑ ኤልያሴብ ነበር፤
እርሱም ከጦብያ ጋር የጠበቀ ወዳጅነት
ነበረው፤ 5ከዚህ በፊት የእህል ቍርባኑ፣
ዕጣኑ፣ የቤተ መቅደሱ ዕቃዎች፣ የእ
ህሉ ዐሥራትና፣ ለሌዋውያን፣ ለመዘምራንና
ለበር ጠባቂዎች የታዘዘው አዲሱ ወይንና
ዘይት፣ ለካህናቱም የሚመጣው ስጦታ
ይቀመጥበት የነበረውን ትልቁን የዕቃ
ቤት እንዲኖርበት ሰጥቶት ነበር፡፡

6ይህ ሁሉ ሲሆን እኔ በኢየሩሳሌም አል
ነበርሁም፤ ምክንያቱም በባቢሎን ንጉሥ
በአርጤክስስ ሠላሳ ሁለተኛ ዓመት ተመልሼ
ወደ ንጉሡ ሄጄ ነበር፡፡ ከጥቂት ጊዜም
በኋላ የንጉሡን ፈቃድ ጠይቄ 7ወደ ኢየሩ
ሳሌም ተመለስሁ፤ በዚያም ኤልያሴብ
በእግዚአብሔር ቤት አደባባይ ለጦብያ አንድ
መኖሪያ ክፍል በመስጠት የፈጸመውን
ክፉ ድርጊት ተረዳሁ፡፡ 8እኔም በጣም ዐዘ
ንሁ፤ የጦብያንም የቤት ዕቃ ሁሉ ከክፍሉ
እያወጣሁ ወደ ውጭ ጣልሁ፡፡ 9ክፍሎቹንም
እንዲያነጹ ትእዛዝ ሰጠሁ፤ ከዚያም
የእግዚአብሔርን ቤት ዕቃዎች፣ የእህሉን
ቍርባንና ዕጣኑን ጭምር መልሼ አስ
ገባሁ፡፡

10እንዲሁም ለሌዋውያን የተመደበው ድርሻ
እንዳልተሰጣቸውና አገልግሎቱን በኀላፊ
ነት የሚመሩ ሌዋውያንና መዘምራን ሁሉ
ወደ የርስታቸው መመለሳቸውን ተረዳሁ፡፡
11ስለዚህ ሹማምቱን ገሥጬ "ቤተ መቅደሱ
እስከዚህ ቸል የተባለው ለምንድን ነው?"
ብዬ ጠየቅኋቸው፡፡ ከዚያም እነርሱን በአን
ድነት ሰብስቤ ወደ ምድብ ሥራቸው እን
ዲመለሱ አደረግሁ፡፡

12ይሁዳም ሁሉ የእህሉን፣ የአዲሱን
ወይንና የዘይቱን ዐሥራት ወደ ዕቃ
ቤቶቹ አስገቡ፡፡ 13ለዕቃ ቤቶቹም ካህኑን
ሰሌምያን፣ ጸሓፊውን ሳዶቅንና ፈዳያ የተ
ባለውን ሌዋዊ ኀላፊ አድርጌ ሾምሁ፤
መደብሁ፤ እንዲሁም የመታንያን ልጅ፣
የዘኩርን ልጅ ሐናን ረዳታቸው አደ
ረግሁ፤ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች ታማኞች
ነበሩ፡፡ ሥራቸውም ለወንድሞቻቸው የተ
መደበውን ቀለብ ማከፋፈል ነበረ፡፡

14አምላኬ ሆይ፤ ስለዚህ ነገር አስበኝ፤
ለአ ምላኬ ቤትና ለአገልግሎቱ ስል በታ
ማ ኝነት ያከናወንሁትን አታጥፋ፡፡

15በእነዚያ ቀናት በይሁዳ በሰንበት ቀን
የወይን መጭመቂያ የሚረግጡ፣ እህል
የሚያስገቡና፣ የወይን ጠጅ፣ የወይን
ዘለላ፣ የበለስና ሌሎችን የጭነት ዐይነቶች
ሁሉ በአህያ ላይ የሚጭኑ ሰዎች አየሁ፤
ይህን ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም ያስገቡ
የነበረው በሰንበት ቀን ነበረ፡፡ ስለዚህ በዚ
ያን ቀን ምግብ እንዳይሸጡ ከለከልኋ
ቸው፡፡ 16በኢየሩሳሌም የሚኖሩ የጢሮስ
ሰዎችም ዓሣና ልዩ ልዩ ሸቀጣ ሸቀጥ
በሰንበት ቀን እያመጡ ለይሁዳ ሕዝብ
በኢየሩሳሌም ይሸጡ ነበር፡፡ 17እኔም የይሁ
ዳን መኳንንት በመገሠጽ እንዲህ አልኋቸው፤
"ሰንበትን በማርከስ ይህ የምትፈጽሙት
ክፉ ድርጊት ምንድን ነው? 18የቀድሞ አባ
ቶቻችሁ ያደረጉት ይህንኑ አልነበረምን?
አምላካችንስ ይህን ሁሉ ጥፋት በእኛና በዚች
ከተማ ላይ ያመጣው በዚሁ በደላችን አይ
ደለምን? አሁንም እናንተ ሰንበትን በማር
ከስ የባሰ መከራ በእስራኤል ላይ ታመጣ
ላችሁ፡፡"

19በሰንበት ዋዜማ በኢየሩሳሌም በሮች
ላይ የምሽቱ ጥላ ማረፍ ሲጀምር በሮቹ
እንዲዘጉና፣ ሰንበት እስኪያልፍ ድረስ

12፥44 ዘሌ27፥30፤ ዘዳ18፥8፤ነህ13፥4
12፥45 1ዜና6፥31፤ 23፥5፤2ዜና8፥14
12፥46 2ዜና35፥15፤ 29፥27፤መዝ137፥4
12፥47 ዘዳ18፥8
13፥1 ቍ 23፥ዘዳ23፥3
13፥2 ዘኍ22፥3-11፤ 23፥7፡11፤ዘዳ23፥3፡4-5
13፥3 ቍ 23፤ነህ9፥2
13፥4 ነህ2፥10፤ 12፥44
13፥5 ዘሌ27፥30፤ ዘኍ18፥21
13፥6 ነህ2፥6
13፥7 ዕዝ10፥24፤ ነህ2፥10
13፥8 ማቴ21፥12-13፤ ማር11፥15-17፤ ሉቃ19፥45-46፤ ዮሐ2፥13-16
13፥9 ዘሌ 2፥1፤ 1ዜና23፥28፤ 2ዜና29፥5
13፥10 ዘዳ12፥19፤ 2ዜና31፥4
13፥11 ነህ10፥37-39፤ ሐጌ1፥1-9ሚል3፥8-9
13፥12 ዘዳ18፥8፤ 1ነገ7፥51፤ 2ዜና31፥5፡6፤ ነህ10፥37-39፤ ሚል3፥10
13፥13 ነህ12፥44፤ ሐሥ6፥1-5
13፥14 ዘፍ8፥12፡ 2ነገ20፥3
13፥15 ዘፀ20፥8-11፤ 34፥21፤ ዘዳ5፥12-15
13፥16 ነህ10፥31
13፥18 ነህ10፥31፤ ኤር44፥23
13፥19 ዘሌ23፥32

እን ዳይከፈቱ አዘዝሁ፤ በሰንበት ቀን
ጭነት እንዳይገባም ከራሴ ሰዎች አንዳ
ንዶቹን በየበሩ ላይ አቆምሁ። 20የልዩ ልዩ
ሸቀጣ ሸቀጥ ነጋዴዎችና ቸርቻሪዎች ከኢ
የሩሳሌም ውጭ አንድ ወይም ሁለት ጊዜ
አድረዋል። 21እኔ ግን፣ “ከቅጥሩ ውጭ
የምታድሩት ለምንድን ነው? እንዲህ
ያለውን ነገር ዳግመኛ ብታደርጉ እጄን
አነሣባችኋለሁ” ስል አስጠነቀቅኋቸው፤
እነርሱም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሰንበት ቀን
አልመጡም። 22ከዚያም ሌዋውያኑ ራ
ሳቸውን እንዲያነጹ፣ ሄደውም የቅጥሩን በር
እንዲጠብቁና የሰንበትንም ቀን እንዲቀድሱ
አዘዝኋቸው።

አምላኬ ሆይ፤ ስለዚህም ደግሞ አስበኝ፤
እንደ ታላቅ ፍቅርህም ብዛት ምሕረት
አድርግልኝ።

23በእነዚያም ቀናት የአሽዶድን፣ የአሞ
ንንና የሞዓብን ሴቶች ያገቡ አይሁድ አገ
ኘሁ። 24ከልጆቻቸውም እኩሌቶቹ የአሽ
ዶድን፣ ወይም ከሌሎቹ ሕዝቦች የአን
ዱን ቋንቋ እንጂ የአይሁድን ቋንቋ መና
ገር አይችሉም ነበር። 25እኔም ገሠጽኋቸው፤
ረግማንም አወረድሁባቸው። አንዳንዶቹን
መታኋቸው፤ ጠጕራቸውንም ነጨሁ። በእግዚ
አብሔር ስም እንዲህ ስል አማልኋቸው፤
“ሴቶች ልጆቻችሁን ለወንዶች ልጆቻቸው

13፥22 ዘፍ8፥1፤ ነህ1፥8
13፥23 ቀኍ1፤ ዘፀ34፥16፤ሩት1፥4፤ ዕዝ9፥1-2፤ ነህ10፥30፤ሚክ2፥11
13፥24 አስ1፥22፤ 3፥12፤8፥9
13፥25 ዘፀ34፥16፤ ዕዝ10፥5
13፥26 ዘፀ34፥16፤ 2ሳሙ12፥25፤ 1ነገ3፥13፤11፥3፤ 2ዜና1፥12
13፥27 ዕዝ9፥14
13፥28 ዕዝ10፥24፤ ነህ2፥10
13፥29 ዘኍ3፥12፤ ነህ1፥8
13፥30 ነህ9፥2
13፥31 ዘፍ8፥1፤ ነህ1፥8፤10፥34፡35-36

አትስጡ፤ ሴቶች ልጆቻቸውንም ለወንዶች
ልጆቻችሁ አትውሰዱ። 26የእስራኤል
ንጉሥ ሰሎሞን ኀጢአት የሠራው እንዲህ
ከመሰለው ጋብቻ የተነሣ አይደለምን?
በብዙ በመንግሥታት መካከል እንደ እርሱ
ያለ ንጉሥ አልነበረም፤ በአምላኩም የተወ
ደደ ነበረ፤ እግዚአብሔርም በእስራኤል ሁሉ
ላይ ንጉሥ አደረገው። ነገር ግን ባዕዳን
ሴቶች ወደ ኀጢአት መሩት። 27እናንተም
ደግሞ ባዕዳን ሴቶችን በማግባት ይህን
የመሰለ ታላቅ በደል እንደምትፈጽሙና
ለአምላካችንም ታማኞች እንዳልሆናችሁ
መስማት ይገባናልን?

28ከሊቀ ካህኑ ከኤልያሴብ ልጅ ከዮ
አዳ ልጆች አንዱ የሖሮናዊው የሰንባላጥ
አማች ነበረ፤ እኔም ከአጠገቤ አባረርሁት።

29አምላኬ ሆይ፤ የክህነትን ማዕረግ፣
የክ ህነትንና የሌዋውያንን ቃል ኪዳን
ስላረ ከሱ አስባቸው።

30ስለዚህ ካህናቱንና ሌዋውያኑን ከማ
ናቸውም ባዕድ ነገር ሁሉ አነጻኋቸው፤
የእያንዳንዱንም ተግባር በመለየት በየሥራ
ቦታቸው መደብኋቸው። 31በተወሰነው ጊዜ
ስለ ሚዋጣውም የማገዶ ዕንጨትና ስለ
በኵራቱ መመሪያ ሰጠሁ። አምላኬ ሆይ፤
በቸርነት አስበኝ።

# መጽሐፈ አስቴር

## ንግሥት አስጢን ከክብሯ ወረደች

1 ከህንድ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ
ያሉትን አንድ መቶ ሃያ ሰባት አገሮች
ይገዛ በነበረው በአርጤክስስ ዘመነ መንግ
ሥት እንዲህ ሆነ፤ 2በዚያን ዘመን ንጉሡ
አርጤክስስ የገዛው በሱሳ ግንብ ባለው ንጉ
ሣዊ ዙፋኑ ሆኖ ነበር። 3እርሱም በነገሡ
በሦስተኛው ዓመት ለመኳንንቱና ለሹማ
ምቱ ሁሉ ታላቅ ግብዣ አደረገ። በግብ
ዣውም የፋርስና የሜዶን የጦር አዛዦች፣
መሳፍንትና የየአውራጃው መኳንንት ተገኝ
ተው ነበር።

4ለእነርሱም የመንግሥቱን ሰፊ ሀብት፣
የግርማውን ታላቅነትና ክብር አንድ መቶ
ሰማንያ ቀን ሙሉ አሳያቸው። 5እነዚህ
ቀናት ካለፉ በኋላ፣ ንጉሡ በሱሳ ግንብ
ለነበሩት፣ ከትንሽ እስከ ትልቅ ላለው
ሕዝብ ሁሉ፣ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ
ዙሪያውን በአትክልት በተከበበው አደባባይ
ሰባት ቀን የፈጀ ግብዣ አደረገ። 6አደባባ
ዩም ከነጭና ከሰማያዊ በፍታ የተሠሩ መጋ
ረጃዎች ነበሩት፤ እነርሱም የብር ቀለበት
በተበጀላቸው፣ ከነጭ በፍታና ከሐምራዊ
ቀለም በተሠሩ ገመዶች በዕብነ በረዱ
ምሰሶዎች ላይ ተንጠልጥለው ነበር። ነጭና
ቀይ ቀለማት ተሰበጣጥረው በተነጠፉበት
ወለል ላይ የወርቅና የብር ድንክ ዐልጋ
ዎች ነበሩ፤ እነርሱም ከዕብነ በረድ፣ ቀስተ
ደመና ከሚመስሉ ቀለሞችና ከሌሎች
የከበሩ ድንጋዮች የተሠሩ ነበሩ። 7የወ
ይን ጠጁም አንዱ ከሌላው ልዩ በሆነ
የወርቅ ዋንጫ ይቀርብ ነበር፤ ከንጉሡም
ልግስና የተነሣ የቤተ መንግሥቱ የወይን
ጠጅ የተትረፈረፈ ነበር። 8ንጉሡ ለእያን
ዳንዱ ሰው የሚፈልገውን ያህል እንዲ
ያቀርቡለት የወይን ጠጅ አሳላፊዎቹን
ሁሉ አዝዞ ስለ ነበረ፣ በንጉሡ ትእዛዝ መሠ
ረት እያንዳንዱ ተስተናጋጅ እንዲጠጣ
ተፈቅዶለት ነበር።

9ንግሥት አስጢንም በንጉሥ አርጤክ
ስስ ቤተ መንግሥት እንደዚሁ ለሴቶች
ግብዣ አድርጋ ነበር።

10በሰባተኛው ቀን ንጉሥ አርጤክስስ
ከወይን ጠጁ የተነሣ ደስ ስለ ተሰኘ፣
አገልጋዮቹ የሆኑትን ሰባቱን ጃንደረቦች
ምሁማንን፣ ባዛንን፣ ሐርቦናን፣ ገበታን፣
ዘቶልያንን፣ ዜታርንና ከርከስን እንዲህ
ብሎ አዘዛቸው፤ 11ይኸውም ንግሥት
አስጢን የደስ ደስ ያላት ነበረችና ውበቷ
ለሕዝቡና ለመኳንንቱ እንዲታይ ዘውዷን
ጭና ንጉሡ ፊት እንዲያመጧት ነበር።
12አገልጋዮቹ የንጉሡን ትእዛዝ በነገሯት
ጊዜ ግን፣ ንግሥት አስጢን መሄድ አልፈ
ለገችም። ከዚያም ንጉሡ በጣም ተቈጣ፤
እጅግም ተናደደ።

13ሕግንና ፍትሕን በተመለከተ የሊቃው
ንቱን ምክር መጠየቅ በንጉሥ ዘንድ የተ
ለመደ ነበርና፣ ስለ ዘመናት ሁኔታ ዕው
ቀት ካላቸው ጠቢባን ጋር ተነጋገረበት፤
14እነዚህ አርቄስዮስ፣ ሼታር፣ አድማታ፣
ተርሺሽ፣ ሜሬስ፣ ማሌሴዓር፣ ምሙካ
የተባሉ ሰባቱ የፋርስና የሜዶን መኳንንት
በንጉሡ ዘንድ የተለየ ስፍራና በመንግሥ
ቱም አመራር ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ያላቸው
ነበሩ።

15ንጉሡም፣ “በጃንደረቦቹ በኩል የተ
ላከባትን የንጉሥ አርጤክስስን ትእዛዝ ስላ
ልፈጸመች፣ በሕጉ መሠረት በንግሥት አስ
ጢን ላይ ምን መደረግ አለበት?” ሲል ጠየ
ቃቸው።

16ከዚያም ምሙካ በንጉሡና በመኳንንቱ
ፊት እንዲህ ሲል መለሰ፤ “ንግሥት አስ
ጢን የበደለችው ንጉሡን ብቻ ሳይሆን፣
መኳንንቱን ሁሉና በመላው የንጉሥ
አርጤክስስ አውራጃዎች የሚኖሩትን ሕዝ
ቦች ጭምር ነው። 17ይህ የንግሥቲቱ አድ
ራጎት በሌሎቹ ሁሉ ዘንድ ስለሚሰማ፣
ባሎቻቸውን ይንቃሉ፤ ‘ንጉሥ አርጤክስስ
ንግሥት አስጢን ወደ እርሱ እንድትመጣ ቢያ
ዛትም፣ እርሷ ግን መሄድ አልፈለገችም’
ይላሉ። 18በዚህች በዛሬዪቱም ዕለት የንግ
ሥቲቱን አድራጎት የሰሙ የፋርስና የሜ
ዶን መኳንንት ሚስቶች፣ ለንጉሡ መኳን
ንት ሁሉ በዚሁ ዐይነት ሊመልሱ ነው፤
እንዲህ ከሆነ ደግሞ ማብቂያ የሌለው
ንቀትና ጠብ ይፈጠራል።

19“ስለዚህ ነገሩ ንጉሡን ደስ የሚያሰኘው
ከሆነ፣ አስጢን ወደ ንጉሡ ወደ አርጤክ
ስስ ዘንድ ከእንግዲህ ወዲህ ፈጽሞ እንዳ
ትገባ ንጉሣዊ ዐዋጅ ይውጣ፤ ይህም የማይ
ሻር ሆኖ በፋርስና በሜዶን ሕጎች ይጻፍ፤
እንዲሁም ንጉሡ የእቴጌነቷን ክብር ከእ
ርሷ ለምትሻል ለሌላዪቱ ይስጥ። 20ከዚ
ያም የንጉሡ ዐዋጅ በሰፊው ግዛቱ ሁሉ
ሲነገር፣ ከትንሽ እስከ ትልቅ ያሉት ሴቶች
ሁሉ ባሎቻቸውን ያከብራሉ።”

1፥1 ዕዝ4፥6፤አስ 8፥9፤9፥30፤ዳን3፥2፤ 6፥1
1፥2 ዕዝ4፥9፤ አስ2፥8
1፥3 1ነገ3፥15
1፥5 መሳ14፥17፤ 2ነገ21፥18
1፥6 አስ7፥8፤ሕዝ 23፥41፤አሞ3፥12፤ 6፥4
1፥7 አስ2፥18፤ ዳን5፥2
1፥9 1ነገ3፥15
1፥10 ዘፍ14፥18፤ መሳ16፥25፤ሩት 3፥7፤አስ3፥15፤5፥6፤7፥ 2፤ምሳ31፥4-7፤ ዳን5፥1-4
1፥11 መዝ45፥11፤ ማሕ2፥4ሕዝ16፥14
1፥12 ዘፍ39፥19፤ አስ2፥21፤7፥7፤ ምሳ19፥12
1፥13 1ዜና12፥32
1፥14 አስ7፥14
1፥18 ምሳ19፥13፤ 27፥15
1፥19 አስ8፥8፤ መክ8፥4፤ዳን6፥8፡12

21ንጉሡና መኳንንቱ ሁሉ በዚህ ምክር
ተደሰቱ፤ ንጉሡም ምሙካ ያቀረበውን ሐሳብ
በሥራ ላይ አዋለው። 22እያንዳንዱ ሰው በራሱ
ቤተ ሰብ ላይ ገዥ እንዲሆን መልእክት
አስተላለፈ፤ መልእክቱም ለየአውራጃዎቹ
በየራሳቸው ጽሑፍና ለእያንዳንዱ ሕዝብ
በየራሱ ቋንቋ ተጽፎ በግዛቱ ሁሉ ተበተነ።

## አስቴር ንግሥት ሆነች

2 ከዚህ በኋላ ንጉሡ አርጤክስስ ቍጣው
ሲበርድለት አስጢንን፣ ያደረገችውን
ነገርና በእርሷም ላይ ያስተላለፈውን ዐዋጅ
ዐሰበ። 2ከዚያም የንጉሡ የቅርብ አገልጋዮች
እንዲህ የሚል ሐሳብ አቀረቡ፤ “ለንጉሡ
ቈንጆ ልጃገረዶች ይፈለጉለት፤ 3እነዚህን
ሁሉ ቈንጆ ልጃገረዶች በሱሳ ግንብ ወደ
ሚገኘው ልዩ የሴቶች መኖሪያ ቦታ እንዲ
ያመጡ፣ ንጉሡ በግዛቱ በሚገኙት አውራ
ጃዎቹ ሁሉ ባለሥልጣኖችን ይሹም፤ እነር
ሱም የሴቶች የበላይ ኀላፊ በሆነው በንጉሡ
ጃንደረባ በሄጌ ኀላፊነት ሥር ይሁኑ፤ የው
በትም እንክብካቤ ይደረግላቸው። 4ከዚ
ያም ንጉሡን ደስ የምታሰኘው ልጃገረድ
በአስጢን ፈንታ ንግሥት ትሁን።” ምክሩ
ንጉሡን ደስ አሰኘው፤ በተባለውም መሠ
ረት አደረገ።

5በዚህ ጊዜ ከብንያም ነገድ የቂስ ልጅ፣
የሰሜኢ ልጅ፣ የኢያዕር ልጅ መርዶክዮስ
የሚባል አንድ አይሁዳዊ በሱሳ ግንብ ይኖር
ነበር፤ 6እርሱም የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር
ከማረካቸው ከይሁዳ ንጉሥ ከኢኮንያን[ሀ]
ጋር ከኢየሩሳሌም በምርኮ ከተወሰዱት አንዱ
ነበር። 7መርዶክዮስ አንዲት ሀደሳ የምትባል
የአጎቱ ልጅ ነበረችው፤ አባትና እናት ስላ
ልነበሯት፣ ያሳደጋት እርሱ ነበር። አስቴር
ተብላ የምትጠራው ይህች ልጃገረድ በተክለ
ሰውነቷም ሆነ በመልኳ እጅግ ውብ ነበረች።
አባቷና እናቷ ከሞቱ በኋላ መርዶክዮስ እንደ
ራሱ ልጅ አድርጎ ወሰዳት።

8የንጉሡ ትእዛዝና ዐዋጅ በወጣ ጊዜ፣
ብዙ ልጃገረዶች ወደ ሱሳ ግንብ ተወስ
ደው ለጠባቂው ለሄጌ ተሰጡ፤ አስቴርም
ወደ ንጉሡ ቤተ መንግሥት ተወስዳ፣ ለሴቶቹ
ጠባቂ ለሄጌ በዐደራ ተሰጠች። 9ልጃገረዲ
ቱም ደስ አሰኘችው፤ በእርሱም ዘንድ
መወደድን አተረፈች፤ እርሱም የውበት
መንከባከቢያዋንና የተለየ ምግብ ወዲያውኑ
ሰጣት። ከቤተ መንግሥቱ የተመረጡ ሰባት
ደንገጡሮችን በመመደብም እርሷንና ደን
ገጡሮቿን ምርጥ ወደ ሆነው የሴቶች
መጠበቂያ አዛወረ።

10መርዶክዮስ እንዳትናገር አዞአት ስለ
ነበር፣ አስቴር የየት አገር ሰውና የእነማን
ወገን እንደ ሆነች አልገለጸችም። 11መር
ዶክዮስም አስቴር እንዴት እንደ ሆነችና
ምንስ እንዳጋጠማት ለማወቅ፣ በየዕለቱ
በሴቶች መጠበቂያ አደባባይ አጠገብ ወዲ
ያና ወዲህ ይመላለስ ነበር።

12አንዲት ልጃገረድ ወደ ንጉሥ አርጤክስስ
ዘንድ ለመግባት ተራዋ ከመድረሱ በፊት
ስድስት ወር በከርቤ ዘይት፣ ስድስት ወር
ደግሞ ልዩ ልዩ ሽቱ በመቀባትና በተለያዩ
የፊት ቀለሞች በመዋብ ባጠቃላይ ዐሥራ
ሁለት ወር መቈየት ነበረባት፤ 13ወደ ንጉሡ
ዘንድ የምትገባውም በዚህ ሁኔታ ሲሆን፣
ሴቶቹ ከሚኖሩበት ስፍራ ወደ ንጉሡ
ቤተ መንግሥት ስትሄድ፣ መውሰድ የምትፈ
ልገው ማናቸውም ነገር ይሰጣት ነበር።
14ሲመሽ ወደዚያው ትሄዳለች፤ ሲነጋም
የቁባቶች ኀላፊ በሆነው በንጉሡ ጃንደረባ
በሻአሽጋዝ ጥበቃ ሥር ወደሚገኘው ወደ
ሌላው የሴቶች መጠበቂያ ቤት ትመለሳ
ለች፤ ደስ የተሰኘባት ካልሆነችና በስሟም
ካልጠራት ዳግመኛ ወደ ንጉሡ ዘንድ
አትገባም።

15መርዶክዮስ እንደ ልጁ አድርጎ ያሳደ
ጋት የአጎቱ የአቢካኢል ልጅ አስቴር ወደ
ንጉሡ ዘንድ የምትሄድበት ተራ በደረሰ ጊዜ
የሴቶች ልዩ ጥበቃ ቤት ኀላፊ የሆነው
ሄጌ የነገራትን እንጂ፣ ሌላ ምንም አልጠ
የቀችም። አስቴር በሚያዩዋት ሁሉ ዘንድ
ሞገስ አገኘች። 16በነገሡ በሰባተኛው ዓመት
ቴቤት በተባለው በዐሥረኛው ወር ወደ
ንጉሥ አርጤክስስ ቤተ መንግሥት ተወ
ሰደች።

17በዚህ ጊዜ ንጉሡ ከሌሎቹ ሴቶች
ሁሉ ይበልጥ አስቴርን ወደዳት፤ ከሌሎቹ
ደናግልም ሁሉ ይልቅ በእርሱ ዘንድ ሞገ
ስንና መወደድን አገኘች። ስለዚህ የእቴጌ
ነት ዘውድ በራሷ ላይ ጫነላት፤ በአስጢ
ንም ፈንታ ንግሥት አደረጋት። 18ንጉሡም
ስለ አስቴር ክብር ለመኳንንቱና ለሹ
ማምቱ ሁሉ ታላቅ ግብዣ አደረገ፤ በዓ
ሉም በየአውራጃዎቹ ሁሉ እንዲከበር ዐወጀ፤
በንጉሣዊ ልግስናውም ስጦታ አደረገ።

## መርዶክዮስ በንጉሡ ላይ የተጠነሰሰውን ሤራ ደረሰበት

19ደናግሉ ለሁለተኛ ጊዜ ተሰብስበው ሳለ፣
መርዶክዮስ በንጉሡ በር ተቀምጦ ነበር።
20አስቴር ግን ልክ መርዶክዮስ እንደ ነገራት
የማን ወገንና የየት አገር ሰው እንደ
ሆነች ደብቃ ነበር፤ ይህ የሆነበት ምክን
ያት መርዶክዮስ በሚያሳድጋት ጊዜ ታደ

1፥22 ነህ13፥24
2፥1 አስ7፥10
2፥5 1ሳሙ9፥1
2፥6 2ነገ24፥15፤ ዳን1፥1-5፤5፥13
2፥7 ዘፍ39፥6፤ 41፥45
2፥8 ነህ1፥1፤ አስ1፥2፤ዳን8፥2
2፥9 ዘፍ37፥3፤ 39፥21፤1ሳሙ9፥22-24፣2ነገ25፥30፤አስ9፥19፤ሕዝ16፥9-13፤ ዳን1፥5
2፥10 ቍ20
2፥12 ምሳ27፥9፤ መሓ1፥3፤ኢሳ3፥24
2፥14 1ነገ11፥3፤ አስ4፥11፤መሓ6፥8፤ ዳን5፥2
2፥15 ዘፍ18፥3፤ 30፥27፤አስ5፥8፤7፥3፤8፥5፤9፥29፤መዝ 45፥14
2፥17 ሕዝ16፥9-13
2፥18 ዘፍ40፥20፤ 1ነገ3፥15፤አስ1፥7
2፥19 አስ4፥2፤5፥13
2፥20 ቍ10

[ሀ]6 በዕብራይስጥ፣ *ኢኮንያን* የሚለው ስም *ኢዮአቂም* ከሚለው ጋር አንድ ዐይነት ነው።

ርግ እንደ ነበረው ሁሉ፣ አሁንም ምክሩን
ትከተል ስለ ነበር ነው።
21መርዶክዮስ በንጉሡ በር ተቀምጦ
ሳለ፣ በሩን ከሚጠብቁት ከንጉሡ የጦር
አለቆች ሁለቱ ገበታና ታራ ተቈጡ፤ ንጉሥ
አርጤክስስንም ለመግደል ዶለቱ። 22መር
ዶክዮስም አድማውን ስለ ደረሰበት፣ ለንግ
ሥት አስቴር ገለጠላት፤ እርሷም ይህን
ከመርዶክዮስ ማግኘቷን ለንጉሡ ገልጣ
ነገረችው። 23ነገሩ ሲጣራም እውነት ሆኖ
ተገኘ፤ ሁለቱም ሹማምት በስቅላት ሞት
ተቀጡ። ይህ ሁሉ በንጉሡ ፊት በታሪክ
መዝገብ ተጻፈ።

## ሐማ አይሁድን ለማጥፋት የሸረበው ሤራ

3 ከዚህም ነገር በኋላ ንጉሥ አርጤክስስ
የአጋጋዊውን የሐመዳቱን ልጅ ሐማን
ከፍ ከፍ አደረገው፤ ከሌሎቹም መኳንንት
ሁሉ ከፍተኛውን ሥልጣን በመስጠት አከበ
ረው። 2ንጉሡ ስለ እርሱ ይህ እንዲደረ
ግለት አዞ ስለ ነበር፣ በንጉሡ በር ያሉት
የመንግሥቱ ሹማምት ሁሉ ለሐማ ተንበ
ርክከው እጅ በመንሣት አክብሮታቸውን
ይገልጡለት ነበር። መርዶክዮስ ግን ወድቆ
አልሰገደለትም፤ አክብሮትም አላሳየውም።
3ታዲያ በንጉሡ በር ያሉት የንጉሡ
አገልጋዮች መርዶክዮስን፣ “የንጉሡን ትእ
ዛዝ ለምን ትተላለፋለህ?” ሲሉ ጠየቁት።
4ይህንንም በየቀኑ ይነግሩት ነበር፤ እርሱ
ግን አልተቀበላቸውም። አይሁዳዊ መሆኑን
ነግሮአቸው ስለ ነበር፣ የመርዶክዮስ ባሕ
ርይ እስከ መቼ ሊቀጥል እንደሚችል ለማ
የት ሲሉ ይህንኑ ለሐማ ነገሩት።
5ሐማም መርዶክዮስ ወድቆ እንዳልሰገደ
ለትና እንዳላከበረው ሲያይ እጅግ ተቈጣ።
6ይልቁንም መርዶክዮስ ከእነማን ወገን መሆ
ኑን በተረዳ ጊዜ፣ መርዶክዮስን ብቻ መግ
ደል እንደ ኢምንት ቈጠረው፤ ስለዚህ ሐማ
በመላው የአርጤክስስ መንግሥት ውስጥ
የሚገኙትንና የመርዶክዮስ ወገን የሆኑትን
አይሁድ ሁሉ ለማጥፋት ዘዴ ፈለገ።
7ንጉሥ አርጤክስስ በነገሠ በዐሥራ ሁለ
ተኛው ዓመት ኒሳን በተባለው በመጀመሪ
ያው ወር፣ ቀኑንና ወሩን ለመለየት ፉር
የተባለ ዕጣ ሐማ ባለበት ጣሉ፤ ዕጣውም
አዳር በተባለው በዐሥራ ሁለተኛው ወር
ላይ ወደቀ።
8ከዚያም ሐማ ንጉሥ አርጤክስስን እንዲህ
አለው፤ “በአሕዛብ መካከል በመንግሥትህ
አውራጃዎች ሁሉ ተሠራጭቶና ተበታትኖ
የሚኖር አንድ ሕዝብ አለ፤ ይህም ሕዝብ
ከሌሎች ሕዝቦች ሁሉ የተለየ ልማድ ያለ
ውና የንጉሡንም ሕግ የማይታዘዝ ነው፤
ታዲያ ይህን ሕዝብ ዝም ማለቱ ለንጉሡ
አይበጅም። 9ነገሩ ንጉሡን ደስ የሚያሰኘው
ከሆነ፣ እነርሱን ለማጥፋት ዐዋጅ ይውጣ፤
እኔም ይህን ተግባር ለሚፈጽሙ ሰዎች
የሚውል ዐሥር ሺህ መክሊት ብር ወደ
መንግሥት ግምጃ ቤት አስገባለሁ።”
10ስለዚህ ንጉሡ የቀለበት ማኅተሙን ከጣቱ
አውልቆ የአይሁድ ጠላት ለሆነው ለአጋ
ጋዊው ለሐማዳቱ ልጅ ለሐማ ሰጠው።
11ንጉሡም ሐማን፣ “ገንዘቡን እዚያው ያዘው፤
ሕዝቡንም እንዳሻህ አድርገው” አለው።
12ከዚያም በመጀመሪያው ወር ዐሥራ
ሦስተኛው ቀን የንጉሡ ጸሓፊዎች ተጠሩ።
እነርሱም የሐማን ትእዛዝ በሙሉ በየአውራ
ጃው ፊደልና በየሕዝቡ ቋንቋ፣ ለንጉሡ
እንደራሴዎች፣ ለልዩ ልዩ አውራጃ ገዦችና
ለልዩ ልዩ ሕዝቦች መኳንንት ጻፉ። ይህም
የተጻፈው በራሱ በንጉሡ አርጤክስስ ስም
ሲሆን፣ የታተመውም በራሱ ማኅተም ነበር።
13አዳር በተባለው በዐሥራ ሁለተኛው ወር፣
በዐሥራ ሦስተኛው ቀን ወጣት፣ ሽማግሌ፣
ሴትና ሕፃን ሳይባል አይሁድ ሁሉ በዚ
ያኑ ዕለት እንዲጠፉ፣ እንዲገደሉና እንዲ
ደመሰሱ፣ ሀብታቸውም እንዲዘረፍ ደብዳቤ
ለንጉሡ አውራጃዎች ሁሉ በመልእክተኞች
እጅ ተላከ። 14ለእያንዳንዱም አውራጃ ሕዝብ
እንዲታወቅ፣ እነርሱም ለዚያ ቀን ዝግጁ
እንዲሆኑ፣ የዋናው ዐዋጅ ቅጅ ሕግ እን
ዲወጣና ወደ እያንዳንዱም አውራጃ እን
ዲላክ ተደረገ።
15መልእክተኞቹ በንጉሡ ትእዛዝ ተቻ
ኰለው ወጡ፤ ዐዋጁም በሱሳ ግንብ ተላ
ለፈ። ንጉሡና ሐማ ለመጠጣት ተቀ
መጡ፤ የሱሳ ከተማ ግን ግራ ተጋብታ
ነበር።

## መርዶክዮስ የአስቴርን ርዳታ ጠየቀ

4 መርዶክዮስ የተደረገውን ሁሉ ባወቀ
ጊዜ፣ ልብሱን ቀደደ፤ ከዚያም ማቅለ
ብሶ፣ በራሱ ላይ ዐመድ ነስንሶ ድምፁን
ከፍ በማድረግ አምርሮ እየጮኸ ወደ ከተ
ማዪቱ መካከል ወጣ። 2ማቅ የለበሰ እንዲ
ገባ ስለማይፈቀድለት፣ የሄደው እስከ ንጉሡ
በር ድረስ ብቻ ነበር። 3የንጉሡ ዐዋጅና
ትእዛዝ በደረሰበት አውራጃ ሁሉ፣ በአይ
ሁድ መካከል ታላቅ ሐዘን ሆነ፤ ጾሙ፤ አለ
ቀሱ፤ ጮኹም። ብዙዎቹም ማቅና ዐመድ
ላይ ተኙ።
4የአስቴር ደንገጡሮችና ጃንደረቦች
መጥተው ስለ መርዶክዮስ በነገሯት ጊዜ፣
እጅግ አዘነች፤ እርሷም በማቁ ፈንታ የሚለ
ብሰውን ልብስ ላከችለት፤ እርሱ ግን አል
ተቀበላቸውም። 5ከዚያም አስቴር ከንጉሡ

2፥21 ዘፍ40፥2፤ አስ1፥12፤3፥5፤5፥9፤ 7፥7
2፥23 ዘፍ40፥19፤ ዘዳ21፥22-23፤አስ 6፥1፤10፥2፤6፥2፤ መዝ7፥14-16፤ምሳ 26፥27፤መክ10፥8
3፥1 ዘፀ17፥8-16፤ ዘኍ24፥7፤ዘዳ25፥17 -19፤1ሳሙ14፥48
3፥3 አስ5፥9፤ ዳን3፥12
3፥4 ዘፍ39፥10
2፥5 አስ2፥21
3፥6 አስ9፥24፤መዝ 74፥8፤83፥4፤ምሳ 16፥25
3፥7 ቀኍ13፤ዘሌ 16፥8፤1ሳሙ10፥21፤ አስ9፥24፡ 26፡፤9፥19
3፥8 ዕዝ4፥15፤ኤር 29፥7፤ዳን6፥13፤ሐሥ 16፥20-21
3፥9 አስ7፥4
3፥10 ዘፍ41፥42
3፥12 ዘፍ38፥18፤ ነህ13፥24
3፥13 ቀኍ7፤1ሳሙ 15፥3፤ዕዝ4፥6፤ አስ8፥11፤9፥10
3፥14 አስ8፥8፤9፥1
3፥15 አስ1፥10፤ 8፥14፡15
4፥1 ዘፀ11፥6፤ ዘኍ14፥6፤2ሳሙ 13፥19፤መዝ30፥11፤ሕ ዝ27፥30-31
4፥2 አስ2፥19

ጃንደረቦች መካከል እርሷን እንዲያገለግል
የተመደበውን ሀታክን ጠርታ፣ መርዶክዮስ
ምን ችግር እንደ ገጠመውና ስለ ምንስ
እንደዚህ እንደ ሆነ እንዲያጣራ ላከችው።
6ስለዚህ ሀታክ በንጉሡ በር ፊት ለፊት
ወደሚገኘው ወደ ከተማዪቱ አደባባይ
ወደ መርዶክዮስ ወጣ። 7መርዶክዮስ የደረ
ሰበትን ነገር ሁሉ፣ እንዲሁም ሐማ የአይ
ሁድን ሕዝብ ለማጥፋት ወደ ንጉሡ
ግምጃ ቤት ለማግባት ቃል የገባውን
የገንዘብ ልክ ጭምር ነገረው። 8አይሁድን ለማ
ጥፋት በሱሳ የወጣውን የዋናውን ዐዋጅ
ቅጅም ለአስቴር እንዲያሳያትና በዝርዝር እን
ዲያስረዳት ሰጠው፤ ወደ ንጉሡም ዘንድ
ገብታ ስለ ሕዝቧ ምሕረት እንድትጠይቅና
እንድትማልድ አጥብቆ ይነግራት ዘንድ
አሳሰበው።
9ሀታክም ተመልሶ መርዶክዮስ የነገረ
ውን ሁሉ ለአስቴር አስታወቃት። 10እር
ሷም ለመርዶክዮስ እንዲህ እንዲለው ነገረ
ችው፤ 11 "የንጉሡ ባሮችና በንጉሡ አውራ
ጃዎች የሚገኙ ሰዎች ሁሉ ወንድም ሆነ
ሴት፣ ማንም ሰው ሳይጠራ ንጉሡ ወዳለ
በት ወደ ውስጠኛው አደባባይ የሚገባ፣
ንጉሡ አንድ ሕግ ብቻ እንዳለው ያውቃል፤
ይኸውም እንዲህ ያደረገው ሰው ይገደላል፤
አንድ ሰው ከእንዲህ ዐይነቱ ሞት
የሚተርፈው፣ ንጉሡ የወርቅ ዘንጉን ሲዘ
ረጋለት ብቻ ነው። እኔ ግን ወደ ንጉሡ
ዘንድ እንድገባ ከተጠራሁ ከሠላሳ ቀን
በላይ ሆነ።"
12የአስቴር ቃል ለመርዶክዮስ በተነገረው
ጊዜ፣ 13ይህን መልስ ላከባት፤ "አንቺ በን
ጉሥ ቤት በመሆንሽ ብቻ ሌላው የአይሁድ
ሕዝብ ሲጠፋ አንቺ የምትተርፊ እንዳይ
መስልሽ፤ 14በዚህ ጊዜ አንቺ ዝም ብትዪ፣
ለአይሁድ ርዳታና ትድግና ከሌላ ስፍራ
ይመጣላቸዋል፤ አንቺና የአባትሽ ቤት
ግን ትጠፋላችሁ፤ ደግሞስ አንቺ ንግሥት
ለመሆን የበቃሽው ለዚህ ጊዜ እንደ ሆነ
ማን ያውቃል?"
15ከዚያም አስቴር ለመርዶክዮስ ይህን
መልስ ላከችበት፤ 16"ሂድና በሱሳ ያሉትን
አይሁድ ሁሉ በአንድነት ሰብስብ፤ ስለ
እኔም ጹሙልኝ፤ ቀንም ይሁን ሌሊት
ለሦስት ቀን አትብሉ፤ አትጠጡም። እኔና
ደንገጡሮቼም እናንተ እንደምታደርጉት
ሁሉ እንጾማለን፤ ይህ ከተፈጸመ በኋላ ግን
ነገሩ ምንም እንኳ ከሕግ ውጭ ቢሆንም፣
ወደ ንጉሡ ዘንድ እሄዳለሁ፤ ከጠፋሁም
ልጥፋ።"
17ስለዚህ መርዶክዮስ ሄደ፤ የአስቴርንም

4፥7 አስ7፥4
4፥11 አስ2፥14፤ 5፥2፤8፥4፤መዝ125፥3፤ ዳን2፥9
4፥14 ዘፍ45፥7፤ 50፥20፤ዘዳ28፥29፤ አስ9፥16፡22፤ኢዮ 34፥29፤መዝ28፥1፤35፥ 22፤መክ3፥7፤ኢሳ 42፥14፤57፥11፤62፥1፤ 64፥12፤አሞ5፥13
4፥16 ዘፍ43፥14፤ 2ዜና20፥3፤አስ9፥31

5፥1 ምሳ21፥1፤ሕዝ 16፥13
5፥2 አስ4፥11
5፥3 አስ7፥2፤ ዳን5፥16፤ማር6፥23
5፥6 አስ1፥10፤9፥ 12፤ዳን5፥16፤ማር 6፥23
5፥8 አስ2፥15፤ 1ነገ3፥15
5፥9 አስ2፥21፤3፥3፤ ምሳ14፥17
5፥10 አስ6፥13
5፥11 አስ9፥10፡13፤ ምሳ13፥16
5፥12 ኢዮ22፥29፤ ምሳ16፥18፤29፥23

ትእዛዝ ሁሉ ፈጸመ።

## አስቴር ለንጉሡ ያቀረበችው ልመና

5 በሦስተኛው ቀን አስቴር የክብር ልብ
ሷን ለብሳ በንጉሡ አዳራሽ ፊት
ለፊት ባለው በቤተ መንግሥቱ ውስጠኛ
አደባባይ ገብታ ቆመች። ንጉሡም አዳራሹ
ውስጥ በመግቢያው ትይዩ በዙፋኑ ላይ
ተቀምጦ ነበር። 2ንግሥት አስቴር በአደባ
ባዩ ላይ ቆማ ሲያያት ደስ አለው፤ በእጁ
የያዘውን የወርቅ ዘንግ ዘረጋላት፤ አስቴ
ርም ቀረብ ብላ የዘንጉን ጫፍ ነካች።
3ከዚያም ንጉሡ፣ "ንግሥት አስቴር ሆይ፤
ለምን መጣሽ? ከእኔ የምትፈልጊውስ
ምንድን ነው? እስከ መንግሥቴ እኩሌታ
እንኳ ቢሆን ይሰጥሻል" አላት።
4አስቴርም መልሳ፣ "ንጉሡን ደስ
የሚያሰኘው ቢሆን፣ ባዘጋጀሁለት ግብዣ
ላይ ንጉሡ ዛሬ ከሐማ ጋር ይገኝልኝ"
አለች።
5ንጉሡም፣ "አስቴር ያለችውን እንድን
ፈጽም፣ ሐማን በፍጥነት ጥሩት" አለ።
ስለዚህ ንጉሡና ሐማ አስቴር ወዳዘጋጀችው
ግብዣ ሄዱ። 6የወይን ጠጅ እየጠጡ ሳለ
ንጉሡ ዳግመኛ አስቴርን፣ "እስቲ የምት
ፈልጊው ምንድን ነው? ይሰጥሻል፤ ደግ
ሞስ የምትጠዪቂው ምንድን ነው? እስከ
መንግሥቴ እኩሌታ እንኳ ቢሆን ይፈቀድ
ልሻል" አላት።
7አስቴርም እንዲህ ስትል መለሰች፤
"ልመናዬም፣ ጥያቄዬም ይህ ነው፤ 8በንጉሡ
ዘንድ ሞገስ ካገኘሁና የምፈልገውን ሊሰጠ
ኝና ልመናዬንም ሊፈጽምልኝ ንጉሡን
ደስ ካሰኘው፣ ንጉሡና ሐማ በማዘጋጅላቸው
ግብዣ ላይ ነገ ይገኙልኝ። ከዚያም እኔ
ለንጉሡ ጥያቄ መልስ እሰጣለሁ።"

## ሐማ በመርዶክዮስ ላይ ያወረደው ቍጣ

9ሐማ በዚያን ቀን ደስ ብሎትና መን
ፈሱ ረክቶ ወጣ፤ ነገር ግን መርዶክዮስን
በንጉሡ በር ላይ ሲያየው ከተቀመጠበት
አለመነሣቱንና በፊቱም አለመንቀጥቀጡን
ሲመለከት፣ ቍጣው በመርዶክዮስ ላይ
ነደደ። 10ሐማ ግን እንደ ምንም ራሱን
ተቈጣጥሮ ወደ ቤቱ ሄደ።
ወዳጆቹንና ሚስቱን ዞሳራን አስጠርቶ
በአንድነት ከሰበሰባቸው በኋላ፣ 11ሐማ ስለ
ሀብቱ ታላቅነት፣ ስለ ልጆቹ ብዛት እንዲ
ሁም ንጉሡ የቱን ያህል እንዳከበረው፣
ከሌሎቹም መኳንንትና ሹማምት ይበልጥ
እንዴት ከፍ ከፍ እንዳደረገው እያጋነነ
ነገራቸው። 12ሐማም፣ "ምን ይኸ ብቻ"
አለ፤ "ንግሥት አስቴር ባዘጋጀችው ግብዣ

ላይ ከንጉሡ ጋር እንድገኝ የጋበዘችው
ሰው አንድ እኔ ብቻ ነኝ፤ ነገም ከንጉሡ
ጋር ጋብዛኛለች። [13]ነገር ግን አይሁዳዊው
መርዶክዮስ በንጉሡ በር ላይ ተቀምጦ
ካየሁት ይህ ሁሉ እኔን ደስ አያሰኘኝም።”
[14]ሚስቱ ዞሳራና ወዳጆቹ በሙሉ፣ “ቁመቱ
አምሳ ክንድ[ሀ] የሆነ መስቀያ አስተክልና
መርዶክዮስ እንዲሰቀልበት በጠዋት ለንጉሡ
ንገረው፤ ከዚያም ደስ ብሎህ ከንጉሡ ጋር
ወደ ግብዣው ግባ” አሉት። ይህም ሐሳብ
ሐማን እጅግ ደስ አሰኘው፤ መስቀያውንም
አስተከለ።

## መርዶክዮስ ከፍ ከፍ አለ

6 በዚያች ሌሊት ንጉሡ እንቅልፍ መተ
ኛት አልቻለም። ስለዚህ በዘመነ መን
ግሥቱ የተመዘገበው የታሪክ መጽሐፍ
ቀርቦ እንዲነበብለት አዘዘ። [2]በዚያም
በሩን ከሚጠብቁት ከንጉሡ የጦር አዛዦች
ሁለቱ፣ ገበታና ታራ ንጉሥ አርጤክስስን
ለመግደል አሢረው እንደ ነበርና ይህንንም
መርዶክዮስ እንደ ተናገረ ተጽፎ ተገኘ።
[3]ንጉሡም፣ “ታዲያ ይህን በማድረጉ
መርዶክዮስ ያገኘው ክብርና ማዕረግ ምን
ድን ነው?” ሲል ጠየቀ።
የቅርብ አገልጋዮቹም፣ “ምንም አልተደ
ረገለትም” ብለው መለሱ።
[4]ንጉሡም፣ “በአደባባዩ ማን አለ?” ሲል
ጠየቀ። በዚህ ጊዜ ሐማ በተከለው ዕን
ጨት ላይ መርዶክዮስ ይሰቀል ዘንድ ለን
ጉሡ ለመናገር በውጭ በኩል ወደሚገኘው
የቤተ መንግሥቱ አደባባይ ገና መድረሱ
ነበር።
[5]የቅርብ አገልጋዮቹም፣ “እነሆ፤ ሐማ
በአደባባዩ ቆሞአል” አሉት።
ንጉሡም፣ “ግባ በሉት” ብሎ አዘዘ።
[6]ሐማ በገባ ጊዜ ንጉሡ፣ “ንጉሥ ሊያ
ከብረው ለወደደው ሰው ምን ሊደረግለት
ይገባል?” ሲል ጠየቀው።
በዚህ ጊዜ ሐማ፣ “ንጉሡ ከእኔ ይልቅ
የሚያከብረው ማን አለ?” ሲል በልቡ ዐሰበ።
[7]ስለዚህ ለንጉሡ እንዲህ ሲል መለሰ፤ “ንጉሡ
ሊያከብረው ለወደደው ሰው፣ [8]ንጉሡ
የሚጐናጸፈው ልብሰ መንግሥት፣ ንጉሡም
የሚቀመጥበትና የንጉሡን ዘውድ በራሱ ላይ
ያደረገ ፈረስ ይምጣለት። [9]ከዚያም ልብ
ሱና ፈረሱ እጅግ ከከበሩት ከንጉሡ ልዑላን
መሳፍንት በአንዱ እጅ ይሰጥለት። ንጉሡ
ሊያከብረው የወደደውን ሰው ያልብሱት፤
በፈረሱም ላይ አስቀመጠውም በከተማ
ዪቱ ዋና ዋና መንገዶች ላይ እየመሩ፣
‘ንጉሡ ሊያከብረው ለሚወደው ሰው ይህ
ተደርጎለታል’ይበሉ።”
[10]ንጉሡም ሐማን፣ “በል ፈጥነህ ሂድ፤
ልብሱንና ፈረሱን ውሰድ፤ በንጉሡ በር
ላይ ለሚቀመጠው ለአይሁዳዊው ለመርዶክ
ዮስም ልክ እንዳልኸው አድርግለት፤ ከተናገ
ርኸውም አንዳች ነገር እንዳይጐድል” ሲል
አዘዘው።
[11]ስለዚህ ሐማ ልብሱንና ፈረሱን ወስዶ
መርዶክዮስን አለበሰው፤ በዋና ዋና መንገ
ዶች ላይ እየመራም፣ “ንጉሥ ሊያከብ
ረው ለሚወደው ሰው ይህ ተደርጎለታል”
እያለ በፊቱ ያውጅ ነበር።
[12]ከዚያም በኋላ መርዶክዮስ ወደ ንጉሡ
በር ተመለሰ፤ ሐማ ግን አዝኖና ራሱን
ተከናንቦ በጥድፊያ ወደ ቤቱ ሄደ።
[13]የደረሰበትንም ሁሉ ለሚስቱ ለዞሳራና
ለወዳጆቹ ሁሉ ነገራቸው።
አማካሪዎቹና ሚስቱ ዞሳራም፣ “በፊቱ
መውደቅ የጀመርህለት መርዶክዮስ ዘሩ
ከአይሁድ ወገን ከሆነ፣ ልትቋቋመው አት
ችልም፤ ያለ ጥርጥር ትጠፋለህ” አሉት።
[14]ከእርሱ ጋር በመነጋገር ላይ ሳሉ፣ የንጉሡ
ጃንደረቦች ደርሰው ሐማን አስቴር ወዳዘጋጀ
ችው ግብዣ አጣደፉት።

## ሐማ ተሰቀለ

7 ስለዚህ ንጉሡና ሐማ ከንግሥት አስ
ቴር ጋር ለመጋበዝ ሄዱ፤ [2]በሁለተ
ኛውም ቀን የወይን ጠጅ እየጠጡ ሳለ፣
ንጉሡ እንደ ገና፣ “ንግሥት አስቴር ሆይ፤
የምትለምኚው ምንድን ነው? ይሰጥሻል፤
የምትጠይቂውስ ምንድን ነው? እስከ መን
ግሥቴ እኩሌታ እንኳ ቢሆን ይደረግል
ሻል” አላት።
[3]ከዚያም ንግሥት አስቴር እንዲህ ስትል
መለሰች፤ “ንጉሥ ሆይ፤ በፊትህ ሞገስ
አግኝቼና ግርማዊነትህን ደስ የሚያሰኝ ከሆነ፣
ሕይወቴን ታደጋት፤ ልመናዬ ይህ ነው፤
ሕዝቤን አትርፍ፤ ጥያቄዬም ይኸው ነው።
[4]እኔና ሕዝቤ ለጥፋት፣ ለዕርድና ለመደ
ምሰስ ተሸጠናልና። ወንዶችና ሴቶች ባሮች
ለመሆን የተሸጥን ቢሆን ኖሮ፣ ዝም ባልሁ
ነበር፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለው ጭንቀት
ንጉሡን ለማስቸገር የሚበቃ አይደለም[ሐ]።”
[5]ንጉሥ አርጤክስስም ንግሥት አስቴ
ርን፣ “ለመሆኑ እርሱ ማን ነው? እንዲህ
ያለውን ነገር ለማድረግ እስከዚህ የደፈረ
ውስ ሰው የታለ?” ሲል ጠየቀ።
[6]አስቴርም፣ “ያ ባላጋራና ጠላት ይህ
ክፉው ሐማ ነው” አለች።

5፥13 አስ2፥19
5፥14 ዕዝ6፥11፤ አስ7፥9
6፥1 አስ2፥23፤ ዳን2፥1፤6፥18
6፥2 አስ2፥21-23
6፥3 መክ9፥13-16
6፥8 ዘፍ41፥42፤ 1ነገ1፥33፤ኢሳ52፥1
6፥9 ዘፍ41፥43
6፥11 ዘፍ41፥42
6፥12 2ሳሙ15፥30፤ አስ7፥8፤ኤር14፥3፡4፤ ሚክ3፥7
6፥13 አስ5፥10፤ 7፥7፤መዝ57፥6፤ምሳ 26፥27፤28፥18
6፥14 1ነገ3፥15
7፥1 ዘፍ40፥20-22፤ ማቴ22፥1-14
7፥2 አስ፥10፤5፥3፤ 9፥12
7፥3 አስ2፥15
7፥4 አስ3፥9፤4፥7

[ሀ]14 23 ሜትር ያህል ነው። [ሐ]4 ወይም፣ *ዝም ባልሁም ነበር፤ ነገር ግን ባላጋራችን የሚሰጠው ካሣ ንጉሡ ከሚያጣው ነገር ጋር ከቶ አይነጻጸርም*

ከዚያም ሐማ በንጉሡና በንግሥቲቱ
ፊት እጅግ ደነገጠ። 7ንጉሡ ከተቀመጠ
በት በቍጣ ተነሣ፤ የወይን ጠጁንም ትቶ
ወደ ቤተ መንግሥቱ የአትክልት ቦታ
ሄደ። ሐማ ግን ንጉሡ ሊያጠፋው ቈርጦ
መነሣቱን ስላወቀ፣ ንግሥት አስቴር ሕይ
ወቱን እንድታተርፍለት ለመማጠን በዚ
ያው ቀረ።

8ንጉሡ ከቤተ መንግሥቱ የአትክልት
ቦታ ወደ ግብዣው አዳራሽ ሲመለስ አስ
ቴር ደገፍ ባለችበት ድንክ ዐልጋ ላይ ሐማ
ተደፍቶ ነበር።

ንጉሡም፣ "ይባስ ብሎ አብራኝ ያለች
ውን ንግሥት በገዛ ቤቴ ሊደፍራት ያስባ
ልን?" ሲል ተናገረ።

ይህ ቃል ከንጉሡ አፍ ገና እንደ ወጣ፣
የሐማን ፊት ሸፈኑት። 9ከዚያም ንጉሡን
በቅርብ ከሚያገለግሉት ጃንደረቦች አንዱ
የሆነው ሐርቦና፣ "እነሆ ቁመቱ አምሳ
ክንድ[መ] የሆነ ግንድ በሐማ ቤት አጠገብ
ተተክሎአል፤ ይህን ያዘጋጀው ንጉሡን ለማ
ዳን በጎ ነገር ለተናገረው ለመርዶክዮስ
ነው" አለ።

ንጉሡም፣ "በዚሁ ላይ ስቀሉት" አለ።
10ስለዚህ ለመርዶክዮስ ባዘጋጀው ግንድ
ላይ ሐማን ሰቀሉት፤ ከዚያም የንጉሡ
ቍጣ በረደ።

## ንጉሡ በአይሁድ ስም የተናገረው ዐዋጅ

8 በዚያኑ ዕለት ንጉሥ አርጤክስስ የአ
ይሁድን ጠላት የሐማን ቤት ንብረት
ለንግሥት አስቴር ሰጣት፤ አስቴርም
መርዶክዮስ እንዴት እንደሚዛመዳት ለንጉሡ
ነግራው ስለ ነበር፣ መርዶክዮስ ወደ ንጉሡ
ዘንድ ቀረበ። 2ንጉሡ ከሐማ መልሶ የወ
ሰደውን ባለ ማኅተም ቀለበት አውልቆ
ለመርዶክዮስ ሰጠው፤ አስቴርም መርዶክ
ዮስን በሐማ ቤት ንብረት ላይ ሾመ
ችው።

3አስቴር በንጉሡ እግር ላይ ወድቃ በማ
ልቀስ ልመናዋን እንደ ገና አቀረበች።
አጋጋዊው ሐማ በአይሁድ ላይ የሸረበው
ክፉ ሤራ እንዲሽር ለመነችው። 4ከዚያም
ንጉሡ የወርቅ ዘንጉን ለአስቴር ዘረጋላት፤
እርሷም ተነሥታ በፊቱ ቆመች።

5እንዲህም አለች፤ "ንጉሡን ደስ የሚያ
ሰኘውና እኔም በፊቱ ሞገስ አግኝቼ ከሆነ፣
ጒዳዩም በንጉሡ ዘንድ ተገቢ ሆኖ ከተገ
ኘና በእኔም ደስ ከተሰኘ፣ የአጋጋዊው የሐ
መዳቱ ልጅ ሐማ በንጉሡ አውራጃዎች
ሁሉ የሚገኙትን አይሁድ ለማጥፋት የሸረ
በውን ሤራና የጻፈውን ደብዳቤ የሚሽር
ትእዛዝ ይጻፍ። 6በሕዝቤ ላይ መዐት ሲወ
ርድ እያየሁ እንዴት ልታገሥ እችላ
ለሁ? የቤተ ሰቤንስ መጥፋት እያየሁ እን
ዴት መቋቋም እችላለሁ?"

7ንጉሥ አርጤክስስም ለንግሥት አስቴ
ርና ለአይሁዳዊው ለመርዶክዮስ እንዲህ
ሲል መለሰላቸው፤ "እነሆ ሐማ አይሁድን
ለማጥፋት ስላቀደ፣ ቤት ንብረቱን ለአስ
ቴር ሰጥቻለሁ፤ እርሱንም በዕንጨት ላይ
ሰቅለውታል። 8በንጉሥ ስም የተጻፈና በቀ
ለበቱ የታተመ ደብዳቤ ሊሻር ስለማይ
ችል፣ እናንተ ደግሞ አይሁድን በተመለ
ከተ መልካም መስሎ የታያችሁን ሌላ ዐዋጅ
በንጉሡ ስም ጽፉችሁ በንጉሡ የቀለበት
ማኅተም አትሙት።"

9ኒሳን በተባለው በሦስተኛው ወር ሃያ
ሦስተኛ ቀን የቤተ መንግሥቱ ጸሓፊዎች
በአስቸኳይ ተጠርተው ነበር፤ እነርሱም
የመርዶክዮስን ትእዛዝ ሁሉ ለአይሁድ፣
እንዲሁም ከህንድ ጀምሮ እስከ ኢትዮ
ጵያ ድረስ፣ በአንድ መቶ ሃያ ሰባት አው
ራጃዎች ለሚገኙ እንደራሴዎች፣ የአውራጃ
ገዦችና መኳንንት ሁሉ ጻፉ። እነዚህም
ትእዛዞች የተጻፉት በእያንዳንዱ አውራጃ
ፊደልና በእያንዳንዱ ሕዝብ ቋንቋ፣ እንደ
ዚሁም ለአይሁድ በገዛ ፊደላቸውና በገዛ
ቋንቋቸው ነበር። 10መርዶክዮስ ትእዛዙን
በንጉሥ አርጤክስስ ስም ጽፎ በንጉሡ
የቀለበት ማኅተም አተመው፤ ከዚያም በተ
ለይ ለንጉሡ በተገሩ ፈጣን ፈረሶች በሚጋ
ልቡ መልእክተኞች እጅ ላከው።

11የንጉሡም ዐዋጅ በየከተማው የሚኖሩ
አይሁድ ሁሉ እንዲሰበሰቡና ራሳቸውን
ከጥቃት እንዲከላከሉ እንዲሁም በራሳቸው፣
በሚስቶቻቸውና በልጆቻቸው ላይ አደጋ የሚ
ያደርስባቸውን የየትኛውንም ዜጋ ወይም
አውራጃ የታጠቀ ኀይል እንዲያጠፉ፣ እን
ዲገድሉ፣ እንዲደመስሱና የጠላቶቻቸውን
ሀብት እንዲዘርፉ ፈቀደላቸው። 12አይሁድ
በመላው የንጉሥ አርጤክስስ አውራጃ
ሁሉ ይህን እንዲፈጽሙ የተወሰነው አዳር
በተባለው በዐሥራ ሁለተኛው ወር ዐሥራ
ሦስተኛ ቀን ነበር። 13አይሁድ በዚያን
ቀን ጠላቶቻቸውን ለመበቀል ዝግጁ እንዲ
ሆኑ፣ የዋናው ዐዋጅ ቅጅ ሕግ ወደየአው
ራጃው እንዲላክና የየአገሩም ሕዝብ እንዲ
ያውቀው ተደረገ።

14በቤተ መንግሥቱ ፈረሶች የተቀመጡ
መልእክተኞችም፣ በንጉሡ አስቸኳይ ትእ
ዛዝ ጋልበው ወጡ፤ ዐዋጁም በሱሳ ግንብ
ተነገረ።

15መርዶክዮስ ሰማያዊና ነጭ የቤተ

[መ]9 23 ሜትር ያህል ነው።

7፥7 ዘፍ34፥7፤ 2ነገ21፥18፤አስ1፥12፤ 6፥13፤ምሳ19፥12፤ 20፥1-2
7፥8 ዘፍ34፥7፤ 39፥14፤አስ1፥6፤6፥12፤ ዮሐ13፥23
7፥9 ዘዳ21፥22-23፤ አስ1፥10፤5፥14፤መዝ7፥14፡16፤9፥16፤ምሳ11፥5-6፤ማቴ7፥2
7፥10 ዘፍ40፥22፤ አስ2፥1፤9፥25፤ምሳ 10፥28፤ዳን6፥24
8፥1 ምሳ22፥22-23
8፥2 ዘፍ24፥22፤ 41፥41፡42፤ምሳ13፥22፤14፥35፤ዳን2፥48
8፥3 ዘፀ17፥8-16
8፥4 አስ4፥11
8፥5 አስ2፥15
8፥6 ዘፍ44፥34
8፥7 ዘዳ21፥22-23
8፥8 ዘፍ38፥18፤ 41፥42፤አስ1፥19፤3፥12-14፤ዳን6፥15
8፥9 ነህ13፥24፤ አስ1፥1
8፥11 ዘፍ14፥23፤ አስ3፥13፤9፥15፡16
8፥12 አስ3፥13፤9፥1
8፥13 አስ3፥14
8፥14 አስ3፥15
8፥15 ዘፍ41፥42፤ አስ3፥15፤9፥4፤10፥2፤2ሳሙ12፥30

መንግሥት ልብስ ለብሶ፣ ትልቅ የወርቅ አክሊል ደፍቶ፣ ከቀጭን በፍታና ከሐምራዊ ግምጃ የተሠራ መጐናጸፊያ ተጐናጽፎ ከንጉሡ ፊት ወጣ፤ የሱሳ ከተማም ደስታ የተሞላበት በዓል አከበረች። 16ጊዜውም ለአይሁድ የደስታና የፈንጠዝያ፣ የተድላና የክብር ወቅት ሆነላቸው። 17የንጉሡ ዐዋጅ በደረሰበት በእያንዳንዱ አውራጃና በእያንዳንዱ ከተማ አይሁድ ደስ አላቸው፤ ሐሤት አደረጉ፤ የፈንጠዝያና የደስታም ቀን ሆነላቸው። አይሁድን ከመፍራታቸው የተነሣ፣ ከሌሎች አገር ዜጎች ብዙ ሕዝብ አይሁድ ሆኑ።

## የአይሁድ ድል ማድረግ

9 አዳር በተባለው በዐሥራ ሁለተኛው ወር ዐሥራ ሦስተኛ ቀን፣ በንጉሡ ትእዛዝ የወጣው ዐዋጅ የሚፈጸምበት ዕለት ነበር። በዚህም ዕለት የአይሁድ ጠላቶች የበላይነቱን እንደሚያገኙ ተማምነው ነበር፤ ሁኔታው ግን ተለወጠና አይሁድ በሚጠሏቸው ላይ የበላይነትን አገኙ። 2የእነርሱን መጥፋት በሚፈልጉ ወገኖች ላይ አደጋ ለመጣል አይሁድ በንጉሥ አርጤክስስ አውራጃዎች ሁሉ ባሉት ከተሞቻቸው ተሰበሰቡ። የሌሎቹ አገር ዜጎች ሕዝብ ሁሉ ፈርተዋቸው ስለ ነበር፣ ማንም ሊደፍራቸው አልቻለም። 3የየአውራጃው መኳንንት ሁሉ፣ እንደራሴዎች፣ የአውራጃ ገዦች እንዲሁም የንጉሡ አስተዳዳሪዎች አይሁድን ረዷቸው፤ ይህን ያደረጉትም መርዶክዮስን ስለ ፈሩ ነበር። 4መርዶክዮስ በቤተ መንግሥቱ ታዋቂ ሆነ፤ ዝናው በየአውራጃው ሁሉ ተሰማ፤ ኀይሉም እየበረታ ሄደ።

5ስለዚህ አይሁድ ጠላቶቻቸውን ሁሉ በሰይፍ እየመቱ ገደሏቸው፤ አጠፏቸውም፤ በሚጠሏቸውም ላይ ደስ ያላቸውን አደረጉ። 6አይሁድ በሱሳ ግንብ አምስት መቶ ሰው ገደሉ፤ አጠፉም። 7ፓርሻንዳታን፣ ደልፎንን፣ አስፓታን፣ 8ፖራታን፣ አዳልያን፣ አሪዳታን፣ 9ፓርማሽታን፣ አሪሳይን፣ አሪዳይንና ዋይዛታንም ገደሉ፤ 10እነዚህም የአይሁድ ጠላት የሆነው የሐመዳቱ ልጅ የሐማ ዐሥር ወንዶች ልጆች ነበሩ። በምርኮው ላይ ግን እጃቸውን አልዘረጉም።

11በሱሳ ግንብ የተገደሉት ሰዎች ብዛት በዚያኑ ዕለት ለንጉሡ ተነገረው። 12ንጉሡም ንግሥት አስቴርን፣ "አይሁድ በሱሳ ግንብ አምስት መቶ ሰውና ዐሥሩን የሐማ ልጆች ገድለዋል፤ አጥፍተዋልም። በተቀሩት በንጉሡ አውራጃዎችስ ምን አድርገው ይሆን? አሁንስ የምትለምኚው ምንድን ነው? ይሰጥሻል፤ የምትጠይቂውስ ምንድን ነው? ይፈቀድልሻል" አላት።

13አስቴርም፣ "ንጉሥን ደስ የሚያሰኘው ከሆነ፣ በሱሳ የሚኖሩ አይሁድ የዛሬውን ዐዋጅ ነገም እንዲደግሙት ፈቃድህ ይሁን፤ ዐሥሩ የሐማ ወንዶች ልጆችም ዕንጨት ላይ ይሰቀሉ" አለች።

14ንጉሡም ይህ እንዲሆን አዘዘ። በሱሳ ዐዋጅ ተነገረ፤ ዐሥሩንም የሐማ ወንዶች ልጆች ሰቀሏቸው። 15በሱሳ የሚኖሩ አይሁድ አዳር በተባለው ወር በዐሥራ አራተኛው ቀን በአንድነት መጡ፤ በሱሳም ሦስት መቶ ሰዎች ገደሉ፤ በምርኮው ላይ ግን እጃቸውን አልዘረጉም።

16በዚህ ጊዜ በሌሎች በንጉሡ አውራጃዎች የሚኖሩ የተቀሩት አይሁድ ራሳቸውን ለመከላከልና ከጠላቶቻቸውም ለመገላገል ተሰበሰቡ፤ ከሚጠሏቸውም ሰባ አምስት ሺህ ገደሉ፤ በምርኮው ላይ ግን እጃቸውን አልዘረጉም። 17ይህ የሆነው አዳር በተባለው ወር ዐሥራ ሦስተኛ ቀን ነበር፤ በዐሥራ አራተኛው ቀን ዐረፉ፤ ዕለቱንም የተድላና የደስታ ቀን አድርገው ዋሉ።

## የፉሪም በዓል መከበር

18በሱሳ የሚኖሩ አይሁድ ግን በዐሥራ ሦስተኛውና በዐሥራ አራተኛው ቀን ተሰብስበው ነበር፤ ከዚያም በዐሥራ አምስተኛው ቀን ዐረፉ፤ ዕለቱንም የተድላና የደስታ ቀን አድርገው ዋሉ።

19በየመንደሩ የሚኖሩ የገጠር አይሁድ፣ የአዳርን ወር ዐሥራ አራተኛ ቀን የተድላና የደስታ፣ እርስ በርሳቸውም ስጦታ የሚለዋወጡበት ቀን አድርገው የሚያከብሩት ከዚሁ የተነሣ ነው።

20መርዶክዮስ የተፈጸሙትን እነዚህን ድርጊቶች ጻፈ፤ ደብዳቤ አዘጋጅቶም በመላው የንጉሥ አርጤክስስ አውራጃ በቅርብና በሩቅ ለሚገኙት አይሁድ ሁሉ ላከ፤ 21የላከውም የአዳርን ወር ዐሥራ አራተኛና ዐሥራ አምስተኛ ቀን በየዐመቱ እንዲያከብሩ ነው፤ 22የሚያከብሩበትም ምክንያት አይሁድ ከጠላቶቻቸው ዕረፍት ያገኙበት፣ ሐዘናቸው ወደ ደስታ፣ ልቅሷቸውም ወደ ክብረ በዓል የተለወጠበት ቀን ስለ ሆነ ነው። ቀኖቹንም የተድላና የደስታ ቀኖች አድርገው፣ እርስ በርሳቸውም የምግብ ስጦታ እየተለዋወጡና ለድኾችም ስጦታ እየሰጡ እንዲያከብሩ ጻፈላቸው።

23ስለዚህ አይሁድ መርዶክዮስ የጻፈላቸውን ለመፈጸምና የጀመሩትን በዓል ለማክበር ተስማሙ፤ 24ምክንያቱም የአይሁድ ሁሉ ጠላት የሆነው የአጋጋዊው የሐመዳቱ ልጅ ሐማ አይሁድን ለማጥፋት

8፥16 አስ4፥1-3፤ መዝ97፥10-12፤ 112፥4፤ኤር29፥4-7
8፥17 ዘፀ15፥14፡16፤ዘዳ11፥15፤አስ9፥3፤መዝ35፥27፤45፥15፤51፥8፤ምሳ11፥10፤ዳን6፥26
9፥1 አስ3፥12-14፤ 8፥12፤ምሳ22፥22-23፤ ኤር29፥4-7
9፥2 ዘፍ22፥17፤ መዝ35፥26፤40፥14፤70፥2፤71፥13፡24
9፥3 ዕዝ8፥36፤አስ 8፥17
9፥4 ዘፀ11፥3፤ 2ሳሙ3፥1፤1ዜና11፥9፤ አስ8፥15
9፥5 ዘዳ25፥17-19፤ 1ሳሙ15፥3፤ዕዝ4፥6
9፥10 ዘፍ14፥23፤ 1ሳሙ14፥32፤15፥33፤ አስ3፥13፤5፥11፤መዝ127፥3-5
9፥12 አስ5፥6፤7፥2
9፥13 ዘዳ21፥22-23፤ አስ5፥11
9፥14 ዕዝ6፥14
9፥15 ዘፍ14፥23፤ አስ8፥11
9፥16 ዘዳ25፥19፤ 1ዜና4፥43፤አስ4፥14፤8፥11
9፥17 1ነገ3፥15
9፥19 አስ2፥9፤3፥7፤ራእ11፥10
9፥22 2ነገ25፥30፤ ነህ8፥10፡12፤አስ4፥14፤ መዝ30፥11-12
9፥24 ዘፀ17፥8-16፤ ዘሌ16፥8፤አስ3፥6፡7
9፥25 ዘዳ21፥22-23፤

አሚሮ ነበር፤ ሊፈጃቸውና ሊያጠፋቸውም
ፉር የተባለ ዕጣ ጥሎ ነበር፡፡ [25]ሤራው
በንጉሡ ዘንድ እንደ ታወቀ[ሠ] ሐማ
በአይሁድ ላይ የሸረበው ሤራ በገዛ ራሱ
ላይ እንዲጠመጠም፣ እርሱና ወንዶች
ልጆቹም በዕንጨት ላይ እንዲሰቀሉ የጽሑፍ
ትእዛዝ አስተላለፈ፡፡ [26]ስለዚህ እነዚህ
ቀኖች ፉር ከሚለው ቃል “ፉሪም” ለመ
ባል በቁ፡፡ በዚህ ደብዳቤ ስለ ተጻፈው
ሁሉ፣ ስላዩትና ስለ ደረሰባቸውም ነገር
ሁሉ፣ [27]አይሁድ በታዘዘውና በተወሰነው
ጊዜ እነርሱና ዘሮቻቸው፣ እነርሱን የተጠ
ጓቸውም ሁሉ እነዚህን ሁለት ቀኖች በየዓ
መቱ ባለማቋረጥ እንዲያከብሩ ሥርዐት
አድርገው ራሳቸው ወሰኑ፡፡ [28]እነዚህም ቀኖች
በእያንዳንዱ ትውልድ፣ በእያንዳንዱ ቤተ
ሰብ፣ በእያንዳንዱ አውራጃና በእያንዳንዱ
ከተማ መታሰብና መከበር ይኖርባቸዋል፤
ይ፥ውም እነዚህ የፉሪም ቀኖች በአይሁድ
ዘንድ ሳይከበሩ እንዳይቀሩ፤ መታሰቢያቸ
ውም ከዘሮቻቸው መካከል እንዳይደመሰስ
ነው፡፡

[29]ስለዚህ የአቢካኢል ልጅ ንግሥት አስ
ቴር ከአይሁዳዊው ከመርዶክዮስ ጋር በመ
ሆን፣ ፉሪምን አስመልክተው ይህችን ሁለ
ተኛዪቱን ደብዳቤ ለማጽናት በሙሉ ሥል
ጣን ጻፉ፡፡ [30]መርዶክዮስም የመልካም
ምኞት መግለጫና ማረጋገጫ የሆነውን

አስ7፥10፤መዝ7፥16
9፥26 አስ3፥7
9፥29 አስ2፥15
9፥30 አስ1፥1

9፥31 አስ4፥1-3፥16
10፥1 መዝ72፥10፤
97፥1
10፥2 ዘፍ41፥44፤
አስ2፥23፤8፥15
10፥3 ዘፍ41፥40፡
43፤ነህ2፥10፤ኤር29፥4
-7፤ዳን5፥7፤6፥3

ደብዳቤ በአርጤክስስ ግዛት ውስጥ በሚገ
ኙት አንድ መቶ ሃያ ሰባት አውራጃዎች
ለሚኖሩት አይሁድ ሁሉ ላከ፤ [31]የላከውም
አይሁዳዊው መርዶክዮስና ንግሥት አስቴር
ባወጁላቸውና እንደዚሁም የጾሙንና
የሰቈቃውን ጊዜ በሚመለከት ለራ
ሳቸውና ለዘራቸው ባጸኑት ውሳኔ መ
ሠረት እነዚህ የፉሪም ቀኖች
በተወሰነላቸው ጊዜ እንዲከበሩ ነው፡፡
[32]የአስቴር ዐዋጅ ስለ ፉሪም የወጣውን
ሥርዐት አጸና፤ ይህም በመዝገብ ተጻፈ፡፡

## የመርዶክዮስ ታላቅነት

10 ንጉሥ አርጤክስስ እስከ ባሕር
ዳርቻ በሚዘልቀው ግዛቱ ሁሉ ላይ
ግብር ጣለ፡፡ [2]የኀይሉና የብርታቱ ሥራ
ሁሉ እንዲሁም ንጉሡ መርዶክዮስን ለዚ
ህ የላቀ ማዕረግ እንዴት እንዳደረሰው
የሚ ናገረው በሜዶንና በፋርስ የታሪክ መ
ጽሐፍ የተጻፈ አይደለምን? [3]አይሁዳዊው
መርዶ ክዮስ በማዕረግ ከንጉሡ ከአርጠ
ክስስ ቀጥሎ ሁለተኛ፣ ከአይሁድ
መካከልም ቀዳሚውን ስፍራ የያዘ ሰው
ነበር፤ ለወገኖቹ መልካም በማድረጉና
ለአይሁድም ሁሉ ደኅንነት የቆመ በመሆኑ፣
በብዙዎቹ አይሁድ ወገኖቹ ዘንድ እጅግ
የተከበረ ነበር፡፡

[ሠ]25 ወይም፣ *አስቴር በንጉሡ ፊት በወጣች ጊዜ*

# መጽሐፈ ኢዮብ

## መግቢያ

1 ዖፅ በሚባል አገር የሚኖር ኢዮብ የተ
ባለ ሰው ነበረ፤ ይህ ሰው ነቀፋ የሌ
ለበት፣ ቅን፣ እግዚአብሔርን የሚፈራና ከክ
ፋት የራቀ ነበር። 2እርሱም ሰባት ወንዶ
ችና ሦስት ሴቶች ልጆች ነበሩት። 3ሀብ
ቱም ሰባት ሺህ በጎች፣ ሦስት ሺህ ግመ
ሎች፣ አምስት መቶ ጥማድ በሬዎችና
አምስት መቶ እንስት አህዮች ነበረ፤
እጅግ ብዙ ባሮችም ነበሩት፤ በምሥራቅ
አገር ከሚኖሩትም ሰዎች ሁሉ ይልቅ
እጅግ ታላቅ ሰው ነበረ።
4ወንዶች ልጆቹም ተራ በተራ በየቤታ
ቸው ግብዣ ያደርጉ ነበር፤ ከእነርሱም
ጋር እንዲበሉና እንዲጠጡ ሦስቱን እኅ
ቶቻቸውን ይጋብዙ ነበር። 5የግብዣው
ጊዜ ካለፈ በኋላ ኢዮብ ልኮ ያስመጣ
ቸውና፣ "ምናልባት ልጆቼ ኀጢአት ሠር
ተው እግዚአብሔርንም በልባቸው ረግመው
ይሆናል" በማለት ጠዋት በማለዳ ስለ እያ
ንዳንዳቸው የሚቃጠል መሥዋዕት በማቅ
ረብ ያነጻቸው ነበር፤ ኢዮብ ይህን ዘወትር
ያደርግ ነበር።

## የመጀመሪያው የኢዮብ ፈተና

6አንድ ቀን መላእክት[ሀ] *በእግዚአብሔር*
*ፊት* ሊቆሙ በመጡ ጊዜ፣ ሰይጣንም[ለ]
መጥቶ በመካከላቸው ቆመ። 7እግዚአብሔ
ርም ሰይጣንን፣ "ከወዴት መጣህ?" አለው።
ሰይጣንም፣ "በምድር ሁሉ ዞርሁ፤ ወዲ
ያና ወዲህም ተመላለስሁባት" ብሎ *ለእግ*
*ዚአብሔር* መለሰ።
8*እግዚአብሔርም* ሰይጣንን፣ "አገልጋዬን
ኢዮብን ተመለከትኸውን? በምድር ላይ
እንደ እርሱ ነቀፋ የሌለበት፣ ቅን፣ እግዚአ
ብሔርን የሚፈራና ከክፋት የራቀ ሰው
የለም" አለው።
9ሰይጣንም፣ ለእግዚአብሔር እንዲህ ሲል
መለሰለት፣ "ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚፈራው
እንዲሁ ነውን? 10በእርሱና በቤተ ሰቦቹ፣
ባለው ንብረትስ ሁሉ ዙሪያ ዐጥር ሠርተህ
ለት የለምን? የበጎቹና የላሞቹ መንጋ
ምድርን ሁሉ እስኪሞሉ ድረስ የእጁን ሥራ
ባርከህለታል። 11እስቲ፣ እጅህን ዘርግተህ
ያለውን ሁሉ ንካበት፤ በእርግጥ ፊት
ለፊት ይረግምሃል።"
12*እግዚአብሔርም* ሰይጣንን፣ "እነሆ፤ እርሱ
ያለው ሁሉ በእጅህ ነው፤ እርሱን ራሱን
ግን እንዳትነካው" አለው።
ከዚህ በኋላ ሰይጣን *ከእግዚአብሔር*
*ፊት* ወጥቶ ሄደ።
13አንድ ቀን የኢዮብ ወንዶችና ሴቶች
ልጆች በታላቅ ወንድማቸው ቤት ተሰብስ
በው ይበሉና የወይን ጠጅ ይጠጡ ነበር፤
14መልእክተኛም ወደ ኢዮብ መጥቶ እንዲህ
አለው፤ "በሬዎች እያረሱ፣ አህዮችም በአጠ
ገባቸው እየጋጡ ሳሉ፣ 15ሳባውያን ጥቃት
አድርሰውባቸው ይዘዋቸው ሄዱ፤ አገልጋዮ
ቹንም በሰይፍ ገደሉ። እኔም ብቻዬን
አመለጥሁ፤ ልነግርህም መጣሁ።"
16እርሱም እየተናገረ ሳለ፣ ሌላ መልእ
ክተኛ መጥቶ፣ "የእግዚአብሔር እሳት ከሰ
ማይ ወረደች፤ በጎችንና አገልጋዮችንም
በላች፤ እኔም ብቻዬን አመለጥሁ፤ ልነግርህም
መጣሁ" አለው።
17እርሱም እየተናገረ ሳለ፣ ሌላ መልእ
ክተኛ መጥቶ፣ "ከለዳውያን በሦስት ቡድን
መጥተው ጥቃት አደረሱ፤ ግመሎችህንም
ይዘው ሄዱ፤ አገልጋዮቹን በሰይፍ ገደሉ፤
እኔም ብቻዬን አመለጥሁ፤ ልነግርህም
መጣሁ" አለው።
18እርሱም እየተናገረ ሳለ፣ ሌላ መልእ
ክተኛ መጥቶ እንዲህ አለው፤ "ወንዶችና
ሴቶች ልጆችህ በታላቅ ወንድማቸው ቤት
ተሰብስበው እየበሉና እየጠጡ ሳሉ፣ 19እነሆ፤
ታላቅ ዐውሎ ነፋስ ከምድረ በዳ መጣ፤
የቤቱንም አራት ማእዘናት መታ፤ እር
ሱም በልጆቹ ላይ ወድቆ ገደላቸው። እኔም
ብቻዬን አመለጥሁ፤ ልነግርህም መጣሁ።"
20ኢዮብም ተነሣ፤ ልብሱን ቀደደ፤ ራሱን
ተላጨ፤ በምድርም ላይ ተደፍቶ ሰገደ፤
21እንዲህም አለ፤

"ዕራቍቴን ከእናቴ ማሕፀን ወጣሁ፤
ዕራቍቴንም እሄዳለሁ።[ሐ]
*እግዚአብሔር* ሰጠ፤ *እግዚአብሔር* ነሣ፤
*የእግዚአብሔር* ስም ቡሩክ ይሁን።"

22በዚህ ሁሉ፣ ኢዮብ አልበደለም፤
በእግዚአብሔርም ላይ ክፉ አልተናገረም።

1፥1 ቍ8፤ዘፍ6፥9፤10፥23፤22፥12፤ዘዳ4፥6፤ኢዮ2፥3፤23፥7፡10፤መዝ11፥7፤107፥42፤ምሳ21፥29፤ሕዝ14፥14፡20፤ሚክ7፥2፤1ተሰ5፥22፤ያዕ5፥11
1፥2 ቍ13፡18፤ሩት4፥15፤ኢዮ42፥13፤መዝ127፥3፤144፥12
1፥3 ቍ8፤ዘፍ12፥16፤13፥2፤25፥6፤ኢዮ29፥25፤42፥10፤መዝ103፥10
1፥4 ቍ13፡18
1፥5 ዘፍ8፥20፤1ነገ21፥10፡13፤ነህ12፥30፤ኢዮ8፥4፤መዝ10፥3፤74፥10
1፥6 ዘፍ6፥2፤2ሳሙ24፥1፤1ነገ22፥19፤2ዜና18፥21፤ኢዮ2፥1፤መዝ109፥6፤ሉቃ22፥31
1፥7 ዘፍ3፥1፤1ጴጥ5፥8
1፥8 ቍ1፤ዘፀ20፥20፤ኢሱ1፥7፤መዝ25፥12፤112፥1፤128፥4
1፥9 1ጢሞ6፥5
1፥10 ቍ3፡12፤1ሳሙ25፥16፤ኢዮ2፥4፤8፥7፤29፥6፤42፥12፡17፤መዝ34፥7
1፥11 ዘሌ24፥11፤ኢዮ2፥5፤19፥21፤ኢሳ3፥8፤65፥3፤ሉቃ22፥31፤ራዕ12፥9-10 1፥12 ቍ10፤ኢዮ2፥6፤1ቆሮ10፥13
1፥13 ቍ2፡4
1፥14 ዘፍ36፥24
1፥15 ዘፍ10፥7፤ኢዮ9፥24
1፥16 ዘፍ18፥17፤ዘሌ10፥2፤ዘኍ11፥1-3፤1ነገ18፥38፤2ነገ1፥12፤ኢዮ20፥26
1፥17 ዘፍ11፥28፤ኢዮ9፥24
1፥18 ቍ2፡4
1፥19 ኢዮ16፥7፤19፥13-15፤መዝ11፥6፤ኢሳ5፥28፤21፥1፤ኤር4፥11፤13፥24፤18፥17፤ሕዝ17፥10፤24፥26፤ሆሴ13፥15፤ማቴ7፥25
1፥20 ዘፍ37፥29፤ኢሳ3፥24፤15፥2፤22፥12፤ኤር7፥29፤16፥6፤ሕዝ27፥31፤29፥18፤ሚክ1፥16፤ማር14፥63፤1ጴጥ5፥6
1፥21 መሳ10፥15፤ሩት1፥ 21፤1ሳሙ2፥7፤ኢዮ2፥10፤መክ7፥14፤5፥15፤ኤር440፥2፤ኤፌ5፥20፤1ተሰ5፥18፤1ጢሞ6፥7፤ያዕ5፥11 1፥22 ኢዮ2፥10፤መዝ39፥1፤ምሳ10፥19፤13፥3፤ኢሳ53፥7፤ሮሜ9፥20

[ሀ]6 በዕብራይስጡ *የእግዚአብሔር ልጆች* ይላል
[ለ]6 *ሰይጣን* ማለት *ከሳሽ* ማለት ነው
[ሐ]21 ወይም *ወደዚያ እመለሳለሁ*

## ሁለተኛው የኢዮብ ፈተና

2 በሌላ ቀን ደግሞ፤ መላእክት[መ] *በእግ
ዚአብሔር* ፊት ለመቆም መጡ፡፡
ሰይጣንም ከእነርሱ ጋር *በእግዚአብሔር*
ፊት ሊቆም መጣ፡፡ 2*እግዚአብሔር* ሰይጣ
ንን፣ “ከወዴት መጣህ?” አለው፡፡
ሰይጣንም፣ “በምድር ሁሉ ዞርሁ፤ ወዲያና
ወዲህም ተመላለስሁባት” ብሎ *ለእግዚአ
ብሔር* መለሰ፡፡
3*እግዚአብሔርም* ሰይጣንን፣
“አገልጋዬን ኢዮብን ተመለከትኸውን?
በምድር ላይ እንደ እርሱ ነቀፋ
የሌለበት፣ ቅን፣ እግዚአ ብሔርን የሚፈራና
ከክፋት የራቀ ሰው የለም፤ ያለ ምክንያት
እንዳጠፋው ብትወተውተኝም፣ ይኸው ፍ
ጹምነቱን እንደ ጠበቀ ነው” አለው፡፡
4ሰይጣንም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “‘ቍር
በት ስለ ቍርበት ነው’ እንዲሉ ሰው ለሕ
ይወቱ ሲል ያለውን ሁሉ ይሰጣል፤ 5እስቲ
እጅህን ዘርግተህ ዐጥንቱንና ሥጋውን
ዳስ፤ በእርግጥ ፊት ለፊት ይሰድብሃል፡፡”
6*እግዚአብሔርም* ሰይጣንን፣ “እነሆ፤ እርሱ
በእጅህ ነው፤ ሕይወቱን ግን እንዳትነካ”
አለው፡፡
7ከዚህ በኋላ ሰይጣን *ከእግዚአብሔር*
ፊት ወጥቶ ሄደ፤ ኢዮብንም ከእግር ጥፍሩ
እስከ ራስ ጠጕሩ በክፉ ቍስል መታው፡፡
8ኢዮብም ገላውን ለማከክ ገል ወሰደ፤ በዐ
መድም ላይ ተቀመጠ፡፡
9ሚስቱም፣ “አሁንም ታማኝነትህን አል
ተውህምን? ይልቁን እግዚአብሔርን ርገምና
ሙት!” አለችው
10እርሱም፣ “አነጋገርሽ እንደማታስተውል
[ሠ] ሴት ነው፤ መልካሙን ነገር ከእግዚአብሐ
ር ዘንድ ተቀበልን፣ ክፉውንስ
አንቀበልምን? አላት፡፡
በዚህ ሁሉ፣ ኢዮብ በንግግሩ አልበደለም፡፡

## ሦስቱ የኢዮብ ወዳጆች

11ሦስቱ የኢዮብ ወዳጆች ቴማናዊው ኤል
ፋዝ፣ ሹሐዊው በልዳዶስ፣ ናዕማታዊውም
ሶፋር በኢዮብ ላይ የደረሰውን መከራ
ሁሉ በሰሙ ጊዜ፣ ሄደው ሊያስተዛዝኑትና
ሊያጽናኑት በመስማማት ከየመኖሪያቸው
በአንድነት መጡ፡፡ 12እነርሱም ከሩቅ ሆነው
ሲመለከቱት እርሱ መሆኑን ሊለዩ አል
ቻሉም፤ በዚህ ጊዜ ድምፃቸውን ከፍ አድ
ርገው አለቀሱ፤ ልብሳቸውንም ቀደው በራ
ሳቸው ላይ ትቢያ ነሰነሱ፡፡ 13ሰባት ቀንና
ሰባት ሌሊት ከእርሱ ጋር መሬት ላይ
ተቀመጡ፤ ሥቃዩ ታላቅ መሆኑንም ስለ
ተረዱ፣ አንዳች ቃል የተናገረው አልነ
በረም፡፡

2፥1 ዘፍ6፥2፤ ኢዮ1፥6
2፥2 ዘፍ3፥1
2፥3 ዘፀ20፥20፤ኢዮ 1፥1፤6፥29፤9፥17፤13፥18፤27፥6፤31፥6፤32፥1፤ 40፥8፤መዝ44፥17
2፥4 ኢዮ1፥10
2፥5 ዘፀ20፥7፤ኢዮ 1፥11፤16፥8፤19፥20፤33፥21፤መዝ102፥5፤ ሰቆ4፥8
2፥6 ኢዮ 1፥12፤ 2ቆሮ12፥7
2፥7 ዘዳ28፥35፤ ኢዮ16፥16
2፥8 ዘፍ18፥27፤አስ 4፥3፤ኢዮ16፥15፤19፥9፤30፥19፤42፥6፤መዝ 7፥5፤ኢሳ58፥5፤61፥3፤ኤር6፥26፤ሰቆ3፥29፤ሕዝ26፥16፤ዮና 3፥5-8፤ማቴ11፥21
2፥9 ዘፀ20፥7፤2ነገ 6፥33፤ኢዮ6፥29፤13፥15፤27፥5፤33፥9፤35፥2፤1ተሰ5፥8
2፥10 ኢዮ1፥21፡ 22፤6፥24፤መክ2፥24፤ ሰቆ3፥38፤ያዕ1፥12፤ 5፥11
2፥11 ዘፍ25፥2፤ 36፥11፤37፥35፤ኢዮ 6፥10፤11፥1፤20፥1፤ ዮሐ11፥19
2፥12 ዘፍ37፥29፤ ኢሱ7፥6፤2ሳሙ1፥2፤ 15፥23፤ኢዮ17፥7፤ኢ ሳ52፥14፤ማር14፥63
2፥13 ዘፍ50፥10፤ ምሳ17፥28፤ኢሳ3፥26፤ 23፥2፤47፥1፡5፤ ኤር48፥18፤ሰቆ2፥10፤ ሕዝ26፥16፤ዮና3፥6፤ሐጌ2፥22
3፥1 ኤር15፥10፤ 20፥14
3፥3 ቍ11፡16፤ኢዮ 10፥18-19፤መክ4፥2፤ 6፥3፤ኤር20፥14-18፤ ማቴ26፥24
3፥5 ኢዮ10፥21፡ 22፤ 34፥22፤38፥17፤ መዝ23፥4፤44፥19፤88፥12፤ኤር2፥6፤13፥16
3፥6 ኢዮ23፥17፤ 30፥26
3፥7 መዝ20፥5፤33፥3፤65፥13፤ኢሳ26፥19፤ ኤር51፥48
3፥8 ዘፍ1፥21፤ኢዮ 10፥18፤41፥1፡8፡10፡ 25፤መዝ74፥14፤104፥26፤ኤር20፥14
3፥9 ኢዮ41፥18፤ዕ ን3፥4
3፥11 ቍ3
3፥12 ዘፍ48፥12፤ ኢሳ66፥12
3፥13 ቍ7፤ኢዮ 7፡8-10፡21፤10፡22፤ 13፡19፤14፡10-12፤

## ኢዮብ ይናገራል

3 ከዚህ በኋላ፣ ኢዮብ አፉን ከፍቶ የተ
ወለደበትን ቀን ረገመ፤ 2እንዲህም አለ፤
3“የተወለድሁበት ቀን ይጥፋ፣
‘ወንድ ልጅ ተፀነሰ’ የተባለበት ሌሊት፡፡
4ያ ቀን ጨለማ ይሁን፤
እግዚአብሔር ከላይ አይመልከተው፤
ብርሃንም አይብራበት፡፡
5ጨለማና የሞት ጥላ[ረ] ይውረሱት፤
ደመናም በላዩ ላይ ይረፍ፤
ብርሃኑን ጽልመት ይዋጠው፡፡
6ያ ሌሊት በድቅድቅ ጨለማ ይያዝ፤
ከዓመቱ ቀናት ጋር አይቈጠር፤
ከወራቱ በአንዱም ውስጥ አይግባ፡፡
7ያ ሌሊት መካን ይሁን፤
እልልታም አይሰማበት፡፡
8ሌዋታንን ለማነሣሣት የተዘጋጁ፤
ቀንንም[ሰ] የሚረግሙ ያን ቀን
ይርገሙት፡፡
9አጥቢያ ኮከቦቹ ይጨልሙ፤
ብርሃንን እየጠበቀ ይጣ፣
የንጋት ጮራ ሲፈነጥቅ አይይ፡፡
10መከራን ከዐይኔ ይሰውር ዘንድ፣
የእናቴን ማሕፀን ደጅ በላዬ
አልዘጋምና፡፡

11“ምነው ገና ስወለድ በጠፋሁ!
ምነው ከማሕፀን ስወጣ በሞትሁ!
12የሚቀበሉኝ ጕልበቶች፤
የሚያጠቡኝ ጡቶች ለምን ተገኙ?
13ይህን ጊዜ በሰላም በተኛሁ፣
አንቀላፍቼም ባረፍሁ ነበር፤
14አሁን ፈርሶ የሚታየውን ስፍራ ለራሳቸው
ካሠሩት፣
ከምድር ነገሥታትና ከአማካሪዎች ጋር፣
15ቤታቸውን በብር ከሞሉ፣
ወርቅም ከነበራቸው ገዦች ጋር
ባረፍሁ ነበር፡፡
16ወይም እንደ ተቀበረ ጭንጋፍ
ብርሃንም እንዳላየ ሕፃን በሆንሁ ነበር፡፡
17በዚያ ክፉዎች ማወካቸውን ይተዋሉ፤
ደካሞችም በዚያ ያርፋሉ፤

17፥13፤19፥27፤21፥13፡23፤27፥19፤30፥23፤መዝ139፥11፤ኢሳ8፥22
3፥14 ኢዮ9፥24፤12፥17፤15፥28፤ኢሳ14፥9፤ኤር51፥37፤ሕዝ 32፥28-32፤ናሆ3፥7 3፥15 ኢዮ12፥21፤15፥29፤20፥10፤27፥17፤ መዝ49፥16-17፤ምሳ13፥22፤28፥8፤መክ2፥26፤ኢሳ2፥7፤45፥1፤ ሶፎ1፥11 3፥16 ቍ3፤መዝ58፥8፤71፥6፤መክ4፥3፤6፥3 3፥17 ቍ13፡26፤ኢዮ30፥26፤መክ4፥2፤ኢሳ14፥3

[መ]1 የዕብራይስጡ ***የእግዚአብሔር ልጆች*** ይላል
[ሠ]10 ***እንደማታስተውል*** ተብሎ የተተረጐመው የዕብራይስጥ ቃል ግብረ ገባዊ ሕጸጽን ያመለክታል
[ረ]5 ወይም *ከባድ ጥላ* [ሰ]8 ወይም *ባሕርን*

18ምርኮኞች እንደ ልባቸው ይቀመጣሉ፤
ከእንግዲህም የአስጨናቂዎቻቸውን
ጩኸት አይሰሙም፡፡
19ትንሹም ትልቁም በዚያ ይገኛል፤
ባሪያው ከጌታው ነጻ ወጥቶአል፡፡

20“በመከራ ላሉት ብርሃን፣
ነፍሳቸው ለተማረረች ሕይወት ለምን
ተሰጠ?
21ሞትን በጕጕት ለሚጠብቁና ለማያገኙት፣
ከተሰወረ ሀብት ይልቅ ለሚሹት፣
22ወደ መቃብር ሲቃረቡ ደስ እያላቸው፣
በሐሤት ለሚሞሉ ሕይወት ለምን
ተሰጠ?
23መንገዱ ለተሰወረበት ሰው፤
እግዚአብሔርም በዐጥር ላጠረው፣
ሕይወት ለምን ተሰጠ?
24ትካዜ ምግብ ሆኖኛልና፤
የሥቃይ ጩኸቴም እንደ ውሃ ይፈሳል፡፡
25የፈራሁት ነገር መጥቶብኛል፤
የደነገጥሁበትም ደርሶብኛል፡፡
26ሰላም የለኝም፤ ርጋታም የለኝም፤
ሁከት እንጂ ዕረፍት የለኝም”

## ኤልፋዝ

4 ቴማናዊው ኤልፋዝም እንዲህ ሲል መለሰ፤
2“አንድ ሰው ከአንተ ጋር ለመናገር
ቢሞክር፣ ቅር ይልሃልን?
ዳሩ ግን ከመናገር ማን ሊቈጠብ
ይችላል?
3እነሆ፤ አንተ ብዙዎችን ታስተምር እንደ
ነበር አስብ፤
የደከሙትንም እጆች ታበረታ ነበር፤
4ቃልህ የተሰናከሉትን ያነሣ ነበር፤
የሚብረከረከውንም ጕልበት ታጸና
ነበር፡፡
5አሁን ግን መከራ አገኘህ፣ አንተም ተስፋ
ቈረጥህ፤
ሸነቈጠህ፤ ደነገጥህም፡፡
6እግዚአብሔርን መፍራት መታመኛህ
ቀና አካሄድህም ተስፋህ አይደለምን?

7“አሁንም አስተውል፤ ንጹሕ ሆኖ የጠፋ፣
ማን ነው?
ቅኖችስ መች ተደምስሰው ያውቃሉ?
8እኔ እንዳየሁ፣ ክፋትን የሚያርሱ፣
መከራንም የሚዘሩ ያንኑ ያጭዳሉ፡፡
9በእግዚአብሔር እስትንፋስ ይጠፋሉ፤
በቍጣውም ወላፈን ይደመሰሳሉ፡፡
10አንበሳ ያገሣል፤ ቍጡውም አንበሳ
ይጮኻል፤
የደቦል አንበሳው ጥርስ ግን
ተሰብሮአል፡፡

3÷18 ዘፍ15÷13፤ ኢዮ39÷7፤ኢሳ51÷14
3÷19 ኢዮ9÷22፤ 17÷16፤21÷33፤24÷24፤30÷23፤መክ12÷5
3÷20 1ሳሙ1÷10፤ሕዝ27÷30-31
3÷21 መዝ119÷127፤ምሳ2÷4፤ራእ9÷6
3÷22 ኢዮ7÷16፤ መክ4÷3፤ኤር8÷3
3÷23 ኢዮ6÷4፤16÷13፤19÷12፤መዝ88÷8፤ምሳ4÷19፤ኢሳ59÷10፤ኤር13÷16፤23÷12፤ሰቆ2÷4፤3÷7፤ ሆሴ2÷6
3÷24 1ሳሙ1÷15፤ ኢዮ6÷7፤30÷16፤33÷20፤መዝ5÷1፤6÷6፤22÷14፤32÷3፤38÷8፡9፤42÷3፡4፤80÷5፤107÷18፤ኢሳ35÷10፤53÷12፤ሰቆ2÷12
3÷25 ዘፍ42÷36፤ ኢዮ7÷9፤9÷28፤30÷15፤ሆሴ13÷3
3÷26 ቍ17፤ኢዮ 7÷4፡14፤10÷18፤19÷8፤ መዝ6÷6፤ኢሳ48÷22፤ዳን4÷5፤ማቴ11÷28፤ዮሐ14÷27
4÷1 ዘፍ36÷11፤ኢዮ 15÷1፤22÷1
4÷2 ኢዮ32÷20፤ ኤር4÷19፤20÷9
4÷3 ዘጻ32÷2፤ኢዮ 26÷2፤29÷23፤መዝ 71÷9፤ኢሳ13÷7፤35÷3፤ሆሴ6÷3፤ሶፎ3÷16፤ ዕብ12÷12
4÷4 ኢዮ16÷5፤29÷11፡15፡16፡25፤፤ኢሳ 1÷17፤35÷3፤ኤር31÷8 ፤ዕብ12÷12
4÷5 ኢሱ1÷9፤ሩት 1÷13፤ኢዮ1÷11፤ 6÷14፤19÷21፤30÷21፤ መዝ38÷2፤ምሳ24÷10፤ኢሳ53÷4
4÷6 ዘፍ6÷9፤2ነገ 18÷19፤ መዝ27÷3፤ 71÷5፤ምሳ3÷26
4÷7 ኢዮ5÷11፤ 8÷20፤3፡6፡7፤መዝ37÷25፤41÷12፤91÷9-10፤ምሳ12÷21፤19÷23፤2ጴጥ2÷9
4÷8 ምሳ14÷18፤ኢ ዮ5÷3፡6፤15÷17፡35፤ መዝ7÷14፡15፤9÷15፤ ምሳ 11÷18፤22÷8፤ኢ ሳ17÷11፤59÷4፤ሆሴ8÷7፤10÷13፤ገላ6÷7-8
4÷9 ዘፀ15÷10፤ዘሌ 26÷38፤ኢዮ41÷21፤ 40÷13፤ኢሳ25÷7፤ 2ተሰ2÷8
4÷10 ኢዮ5÷15፤ 29÷17፤36÷6፤38÷15፤መዝ17÷12፤22÷13፡21፤35÷10፤ 58÷6፤ምሳ28÷15

11ብርቱው አንበሳ አደን በማጣት
ይሞታል፤
የአንበሳዪቱም ግልገሎች ይበተናሉ፡፡

12“ቃል በምስጢር መጣልኝ፤
ጆሮዬም ሹክሹክታውን ሰማች፡፡
13በሚያስጨንቅ የሌሊት ሕልም ውስጥ፣
ከባድ እንቅልፍም በሰዎች ላይ በወደቀ
ጊዜ፣
14ፍርሀትና መንቀጥቀጥ ያዘኝ፤
ዐጥንቶቼም ሁሉ ተናወጡ፡፡
15መንፈስ ሽው ብሎ በፊቴ አለፈ፤
የገላዬም ጠጕር ቆመ፡፡
16እርሱም ቆመ፣
ምን እንደ ሆነ ግን መለየት አልቻልሁም፤
አንድ ቅርጽ በዐይኔ ፊት ነበረ፤
በእርጭታ ውስጥ እንዲህ የሚል ድምፅ
ሰማሁ፤
17‘ሥጋ ለባሽ ከእግዚአብሔር ይልቅ ጻድቅ
ሊሆን ይችላልን?
ሰውስ ከፈጣሪው ይልቅ ንጹሕ ሊሆን
ይችላልን?
18እግዚአብሔር በአገልጋዮቹ ላይ እምነት
ካልጣለ፣
መላእክቱንም በስሕተታቸው ከወቀሰ፤
19ይልቁንስ በጭቃ ቤት የሚኖሩ፣
መሠረታቸው ከዐፈር የሆነ፣
ከብልም ይልቅ በቀላሉ የሚጨፈለቁ
እንዴት ይሆኑ?
20በንጋትና በምሽት መካከል ይደቃሉ፤
ሳይታሰብም ለዘላለም ይጠፋሉ፡፡
21ያለ ጥበብ ይሞቱ ዘንድ፣
የድንኳናቸው ገመድ አልተነቀለምን?[ሸ]

5 “እስቲ ተጣራ፤ የሚመልስልህ አለን?
ከቅዱሳንስ ወደ ማንኛው ዘወር
ትላለህ?
2ሞኙን ሰው ብስጭት ይገድለዋል፤
ቂሉንም ቅናት ያጠፋዋል፡፡

4÷11 ዘጻ28÷41፤ኢዮ5÷4፤27÷14፤29÷17፤መዝ34÷10፤58÷6፤ ምሳ30÷14 4÷12 ቍ17፡21፤ኢዮ26÷14፤32÷13፤33÷14፤ኤር 9÷23 4÷13 ኢዮ33÷15 4÷14 ኢዮ21÷6፤መዝ48÷6፤55÷5፤ 119÷120፡161፤ኤር5÷22፤23÷9፤ዳን10÷8፤ዕን3÷16፤2ቆሮ7÷15 4÷15 ዳን5÷6፤7÷15፡28፤10÷8፤ማቴ14÷26 4÷16 1ነገ19÷12 4÷17 ኢዮ8÷3፤9÷2፤10÷3፤13÷8፤14÷4፤15÷14፤21÷14፤25÷4 ፤31÷15፤32÷22፤35÷10፤36÷3፡13፤37÷23፤40÷19፤መዝ18÷26፤ 51÷5፤119÷73፤143÷2፤ምሳ20÷9፤መክ7÷20፤ኢሳ51÷13፤ሚል 2÷10፤ሐሥ17÷24 4÷18 ኢዮ15÷15፤ 21÷22፤25÷5፤ዕብ1÷14 4÷19 ዘፍ2÷7፤ኢዮ 5÷4፤7÷17፤10÷9፤15÷16፤17÷14፤22÷16፤ 25÷6፤33÷6፤መዝ22÷6፤ኢሳ41÷14፤64÷8፤ሮሜ9÷21፤2ቆሮ4÷7፤ 5÷1 4÷20 ኢዮ14÷2፡20፤15÷33፤20÷7፤24÷24፤መዝ89÷47፤ 90÷5-6፤ያዕ4÷14 4÷21 ኢዮ8÷22፤18÷21፤36÷12፤ምሳ5÷23፤ ኢ ሳ38÷12፤ኤር9÷3፤ዮሐ8÷24 5÷1 ኢዮ15÷15፤ መዝ89÷5፡7፤ ዕን1÷2 5÷2 ኢዮ21÷15፤36÷13፤ምሳ12÷16፤ገላ5÷26

[ሸ]21 አንዳንድ ተርጓሚዎች ቍ 17 ላይ ያቆማሉ

[3]ቂል ሰው ሥር ሰዶ አየሁት፤
ግን ድንገት ቤቱ ተረገመ።
[4]ልጆቹ የኑሮ ዋስትና የራቃቸው፤
በፍርድ አደባባይ ጥቃት የደረሰባቸው፣
ታዳጊ የሌላቸው ናቸው።
[5]ከእሾህ መካከል እንኳ አውጥቶ፤
ራብተኛ ሰብሉን ይበላበታል፤
ጥማተኛም ሀብቱን ይመኝበታል።
[6]ችግር ከምድር አይፈልቅም፤
መከራም ከመሬት አይበቅልም።
[7]ፍንጣሪው ከእሳቱ ላይ ሽቅብ
እንደሚወረወር፣
ሰውም ለመከራ ይወለዳል።

[8]“እኔ ብሆን ኖሮ፣ ወደ እግዚአብሔር
በቀረብሁ፣
ጒዳዬንም በፊቱ በገለጽሁለት ነበር።
[9]እርሱ፣ የማይመረመሩ ድንቅ ነገሮች፣
የማይቈጠሩም ታምራት ያደርጋል።
[10]ምድሪቱን በዝናብ ያረሰርሳል፤
ሜዳውንም ውሃ ያጠጣል።
[11]የተዋረዱትን በከፍታ ቦታ ያስቀምጣል፤
ያዘኑትንም ወደ አስተማማኝ ስፍራ
ያወጣቸዋል።
[12]እጆቻቸው ያሰቡትን እንዳይፈጽም፣
የተንኰለኞችን ዕቅድ ያከሽፋል።
[13]ጠቢባንን በጥበባቸው ይይዛል፤
የተንኰለኞችንም ሤራ ያጠፋል።
[14]ቀኑ ጨለማ ይሆንባቸዋል፤
በቀትርም ጊዜ በሌሊት እንዳለ ሰው
በዳበሳ ይሄዳሉ።
[15]ችግረኛውን ከአፋቸው ሰይፍ፣
ከኀይለኛውም እጅ ያድነዋል።
[16]ስለዚህ ድኻ ተስፋ አለው፤
ዐመፅም አፏን ትዘጋለች።

[17]“እነሆ፤ እግዚአብሔር የሚገሥጸው ሰው
ምስጉን ነው፤
ስለዚህ ሁሉን የሚችለውን[ቀ] አምላክ
ተግሣጽ አትናቅ።
[18]እርሱ ያቈስላል፤ ይፈውሳል፤
እርሱ ይሰብራል፤ በእጁም ይጠግናል፤
[19]እርሱ ከስድስት መቅሠፍት ይታደግሃል፤
በሰባተኛውም ጒዳት አያገኝህም።
[20]በራብ ጊዜ ከሞት፣
በጦርነትም ከሰይፍ ያድንሃል።
[21]ከምላስ ጅራፍ ትሰወራለህ፤
ጥፋት ሲመጣም አትፈራም።
[22]በጥፋትና በራብ ላይ ትሥቃለህ፤
የምድርንም አራዊት አትፈራም።
[23]ከሜዳ ድንጋዮች ጋር ትዋዋላለህና፤
የዱር አራዊትም ከአንተ ጋር
ይስማማሉ።
[24]ድንኳንህ በሚያስተማምን ሁኔታ እንዳለ
ታውቃለህ፤
በረትህን ትቃኛለህ፤ አንዳችም
አይጐድልብህም።
[25]ዘሮችህ አያሌ እንደሚሆኑ፣
የምትወልዳቸውም እንደ ሣር
እንደሚበዙ ታውቃለህ።
[26]የእህል ነዶ ጐምርቶ በወቅቱ
እንደሚሰበሰብ፣
ዕድሜ ጠግበህ ወደ መቃብር ትሄዳለህ።

[27]“እነሆ፤ ይህን ሁሉ መርምረናል፤ እውነት
ሆኖ አግኝተነዋል
ስለዚህ ልብ በል፤ ተቀበለውም።”

## ኢዮብ

6 ኢዮብም እንዲህ ሲል መለሰ፤
[2]“ምነው ሐዘኔ በተመዘነ!
መከራዬም ሚዛን ላይ በተቀመጠ!
[3]ከባሕር አሸዋ ይልቅ በከበደ፣
ኀይለ ቃሌም ባላስገረመ ነበር!
[4]ሁሉን የሚችል አምላክ ፍላጻ በውስጤ
ነው፤
መንፈሴም መርዙን ትጠጣለች፤
የእግዚአብሔር ማስደንገጥ ተሰልፎብኛል።
[5]የሜዳ አህያ ሣር እያለው፣
በሬስ ድርቆሽ እያለው፣ ይጮኻልን?
[6]የማይጣፍጥ ምግብ ያለ ጨው ይበላልን?
ወይስ የዕንቍላል[ሀ] ውሃ ጣዕም አለውን?
[7]እንዲህ ዐይነቱን ምግብ እጸየፋለሁ፤
ለመንካትም አልፈልግም።

[8]“ምነው ልመናዬ በተመለሰልኝ፤
እግዚአብሔር የምመኘውን በሰጠኝ
[9]እግዚአብሔር አድቅቆ ያጠፋኝ ዘንድ፣
ምነው እጁ በተፈታ!

5፥3 ኢዮ4፥8፤ 24፥18፤መዝ37፥22፡ 35-36፤109፥9-10፤ ምሳ3፥33፤6፥15፤ኢሳ 40፥24፤ኤር12፥2፤ ሕዝ17፥6
5፥4 ኢዮ4፥11፡19፤ 20፥10፤27፥14፤መዝ 109፥12፤ኢሳ9፥17፤ አሞ5፥12፤1ዮሐ2፥1
5፥5 ዘሌ26፥16፤ መሳ2፥15፤ኢዮ20፥ 18፤31፥8፤ሚክ6፥15
5፥6 ኢዮ4፥8
5፥7 ዘፍ3፥17፤ኢዮ 10፥17፤15፥35፤ መዝ 51፥5፤58፥3፤90፥10፤ ምሳ22፥8
5፥8 ኢዮ8፥5፤ 11፥13፤13፥3፡15፤ 23፥4፤40፥1፤መዝ35፥2 3፤50፥15፤ኤር12፥1፤1 ቆሮ4፥4
5፥9 ዘዳ29፥29፤ኢዮ 9፥4፡10፤11፥7፤25፥2፤2 6፥14፤33፥12፤36፥ 5፡22፡26፤37፥5፡14፡ 16፡23፤42፥3፤መዝ40፥ 5፤71፥15፡17፤72፥18፤ 78፥4፤111፥2፤131፥1፤ 139፥6፡17፤145፥3፤ኢ ሳ40፥28፤ሮሜ11፥33
5፥10 ዘሌ26፥4፤ኢ ዮ36፥28፤37፥6፡13፤38 ፥28፡34፤መዝ135፥7፤ ኤር14፥22፤ማቴ5፥45
5፥11 1ሳሙ2፥7- 8፤ኢዮ4፥7፤መዝ 75፥7፤113፥7-8፤ኢሳ 61፥2፤ማቴ5፥4፤ 23፥12፤ሮሜ12፥15፤ ያዕ4፥10
5፥12 ነህ4፥15፤ኢዮ 12፥23፤መዝ33፥10፤ 78፥59፤140፥8፤ኢሳ 8፥10፤19፥3፤ ኤር19፥7
5፥13 ኢዮ9፥4፤ 15፥5፤18፥7፤37፥24፤ መዝ36፥3፤ምሳ21፥30 ፤29፥6፤ኢሳ29፥14፤ 44፥25፤ኤር8፥8፡9፤18 ፥18፤51፥57፤ሉቃ20፥ 23፤1ቆሮ3፥19፤2ቆሮ1 1፥3፤ኤፌ4፥14 5፥14 ዘዳ28፥29፤ኢ ዮ15፥22፡30፤18፥5፡ 6፡18፤20፥26፤22፥11፤ 27፥20፤ኢሳ8፥22፤ አሞ8፥9፤ዮሐ12፥35
5፥15 ዘፀ22፥23፤ ኢዮ4፥10፤8፥6፤22፥ 27፤31፥22፤33፥26፤ 36፥15
5፥16 ኢዮ20፥19፤ 31፥16፤መዝ63፥11፤1 07፥42፤ምሳ17፥5፤22፥ 22፤ኢሳ11፥4፤41፥ 17፤61፥1፤ሮሜ3፥19
5፥17 ዘፍ17፥1፤ዘዳ 8፥5፤ኢዮ15፥11፤ 33፥19፤36፥10፤መዝ94፥12፤ምሳ3፥11፤ኤር31፥18፤ሶፎ3፥7፤ዕብ 12፥5-11፤ያዕ1፥12 5፥18 ዘዳ32፥39፤መዝ147፥3፤ኢሳ57፥15፤ 61፥1፤ሆሴ6፥1 5፥19 መዝ34፥19፤91፥10፤ምሳ3፥25-26፤24፥ 15- 16፤ዳን3፥17፤6፥16 5፥20 ቍ22፤መዝ22፥20፤33፥19፤37፥ 19፤91፥7፤140፥7፤144፥10፤ኤር39፥18 5፥21 ቍ15፤መዝ12፥2- 4፤23፥4፤27፥31፤1፥20፤91፥5 5፥22 ቍ20፤ዘሌ25፥18፤ኢዮ 8፥21፤39፥7፡18፡22፤41፥29፤መዝ91፥13፤ሆሴ2፥18፤ማር1፥13
5፥23 2ነገ3፥19፡25፤ኢዮ40፥20፤መዝ91፥12፤ኢሳ11፥6-9፤ 28፥15፤65፥25፤ሕዝ34፥25፤ሆሴ2፥18፤ማቴ13፥8 5፥24 ኢዮ 8፥6፤12፥6፤21፥9፤22፥23 5፥25 ዘዳ28፥4፤መዝ72፥16፥፤112፥ 2፤ኢ ሳ44፥3፡4፤48፥19 5፥26 ዘፍ15፥15፤ዘዳ11፥21፤መክ8፥13፤ ምሳ3፥21-26 5፥27 ኢዮ8፥5፤11፥13፤22፥27፤32፥10፡17 6፥2 ኢ ዮ31፥6፤ምሳ11፥1፤ዳን5፥27 6፥3 ቍ11፡26፤1ነገ4፥29፤ኢዮ 7፥11፤16፥6፤21፥4፤23፥2፤ምሳ27፥3 6፥4 ዘፍ17፥1፤ዘዳ32፥23፡ 32፤ኢዮ3፥23፤7፥20፤9፥34፤13፥21፤16፥12፡13፤18፥11፤19፥12፤ 21፥20፤23፥6፤27፥20፤30፥15፡21፤33፥16፤34፥6፤መዝ38፥2፤88፥ 15-18፤ኤር 15፥18፤30፥12፤ሰቆ3፥12 6፥5 ዘፍ16፥12፤ኢዮ24፥ 6፤30፥7፤ኢሳ30፥24 6፥6 ኢዮ33፥20፤መዝ107፥18 6፥7 ኢዮ 3፥24 6፥8 ኢዮ14፥13 6፥9 ዘኍ11፥15፤ኢዮ19፥2፤መዝ31፥22

[ቀ]17 በዕብራይስጥ ሻዳይ ማለት ሲሆን በዚህ ቍጥርና በኢዮብ መጽሐፍ ውስጥ እንዲሁ ነው
[ሀ]6 በዕብራይስጥ የዚህ ሐረግ ትርጒም አይታወቅም

10ፋታ በማይሰጥ ሕመም ውስጥ
እየተደሰትሁ፣
ይህ መጽናኛ በሆነልኝ ነበር፤
የቅዱሱን ትእዛዝ አልጣስሁምና።

11"አሁንም ተስፋ አደርግ ዘንድ ብርታቴ፣
እታገሥስ ዘንድ አለኝታዬ ምንድን ነው?
12የድንጋይ ጒልበት አለኝን?
ሥጋዬስ ናስ ነውን?
13ያልተሳካልኝ ሰው ነኝና፣
ራሴን ለመርዳት ምን ጒልበት አለኝ?

14"ለወዳጁ በጎነት የማያሳይ ሰው፣
ሁሉን የሚችለውን አምላክ መፍራት
ትቶአል።
15ወንድሞቼ ግን እንደማያዛልቅ ጅረት፣
ለጊዜው ሞልቶ እንደሚፈስ ወንዝ
የማይታመኑ ናቸው፤
16በረዶ በሚሟሟ ጊዜ ወንዙ ይደፈርሳል፤
ዐመዳይም በቀለጠ ጊዜ ይሞላል፤
17በበጋ ወራት ግን ይጠፋል፤
በሙቀትም ጊዜ መፋሰሻው ላይ
አይገኝም።
18ሲራራ ነጋዴዎች ውሃ አጥተው
መንገዳቸውን ይቀይራሉ፤
ወደ በረሓም ገብተው ይጠፋሉ።
19የቴማን ነጋዴዎች ውሃ ይፈልጋሉ
የሳባ መንገደኞችም ተስፋ ያደርጋሉ፤
20እርግጠኞች ሆነው ስለ ነበር ተሰቀቁ፤
እዚያ ደረሱ፣ ግን ዐፈሩ።
21አሁንም እናንተ እንደዚያ ሆናችሁብኝ፣
መከራዬን አይታችሁ ፈራችሁ።
22ለመሆኑ፣ 'ስለ እኔ ሆናችሁ አንድ ነገር
ስጡልኝ፣
በዕዳ የተያዘብኝንም በሀብታችሁ
አስለቅቁልኝ!' ብያለሁን?
23ወይስ፤ 'ከጠላት አስጥሉኝ፤
ከጨካኝም እጅ ተቤዡኝ' አልኋችሁን?

24"አስተምሩኝ፤ እኔም ዝም እላለሁ፤
ምኑ ላይ እንደ ተሳሳትሁ ጠቍሙኝ።
25የቅንነት ቃል ምንኛ ኀያል ነው!
የእናንተ ክርክር ግን ምን ፋይዳ አለው?
26የተናገርሁትን ለማረም፣
ተስፋ የቈረጠውንም ሰው ቃል እንደ
ነፋስ ለመቍጠር ታስባላችሁን?
27በድኻ አደጉ ላይ ዕጣ ትጣጣላላችሁን?
ወይስ ወዳጃችሁን ትሸጣላችሁን?

28"አሁን ግን ፊቃዳችሁ ቢሆን ወደ እኔ
ተመልከቱ፤
ፊት ለፊት እዋሻችኋለሁን?
29መለስ በሉ፤ ፍርደ ገምድል አትሁኑ፤
ጽድቄ ጸንቶ ቆሞአለችና መለስ ብላችሁ
አስተውሉ።
30ከፋት በአንደበቴ አለን?
አፌስ ተንኰልን መለየት አይችልምን?

7 "የሰው ሕይወት በምድር ላይ ብርቱ
ተጋድሎ አይደለምን?
ዘመኑስ እንደ ምንደኛ ዘመን
አይደለምን?
2የምሽትን ጥላ እንደሚመኝ አገልጋይ፣
ደመወዙንም እንደሚናፍቅ ምንደኛ፣
3እንዲሁ ከንቱ ወራት ታደሉኝ፣
የጒስቍልና ሌሊቶችም ተወሰኑልኝ።
4በተኛሁ ጊዜ 'መቼ ነግቶ እነሣለሁ?'
እላለሁ፤
ሌሊቱ ይረዝማል፤ እስኪነጋም
እገላበጣለሁ።
5አካሌ ቈስሎ ትልና ቅርፊት ለብሶአል፤
ቈዳዬ አፈክፍኮአል፤ ቍስሌም
አመርቅዞአል።

6"ዘመኔ ከሸማኔ መወርወሪያ ይልቅ
ይፈጥናል፤
ያለ ተስፋም ያልቃል።
7ሕይወቴ ትንፋሽ ያህል እንደ ሆነች
አስብ፤
ዐይኔም ከእንግዲህ ደስታን አያይም።
8አሁን የሚያየኝ ሰው ዐይን ከእንግዲህ
አያየኝም፤
ትፈልገኛለህ፤ እኔ ግን የለሁም።
9ደመና በኖ እንደሚጠፋ፣
ወደ መቃብር† የሚወርድም
አይመለስም።
10ወደ ቤቱ ዳግመኛ አይመለስም፤
ስፍራውም ከእንግዲህ አያውቀውም።

11"ስለዚህ ከቶ ዝም አልልም፤
በመንፈሴ ጭንቀት እናገራለሁ፤
በነፍሴም ምሬት አጒረመርማለሁ።
12በላዬ ጠባቂ ታደርግ ዘንድ፣
እኔ ባሕር ነኝን ወይስ የባሕር አውሬ?
13አልጋዬ ያጽናናኛል፣
መኝታዬም ማጒረምረሜን ይቀንስልኛል
ባልሁ ጊዜ፣

6፥10 ዘሌ11፥44፤ 2ነገ19፥22፤ኢዮ2፥11፤15፥11፤22፥22፤23፥12፤መዝ38፥17፤94፥19፤119፥102፤ኢሳ31፥1፤ኤር4፥19፤45፥3፤ማር8፥38
6፥11 ቍ3
6፥12 ኢዮ26፥2
6፥13 ኢዮ26፥2
6፥14 ዘፍ17፥1፤ 1ሳሙ20፥42፤ኢዮ4፥5፤12፥4፤15፥4፤17፥2፡6፤19፥19፡21፤21፥3፤30፥1፡10፤መዝ38፥11፤69፥20፤1ዮሐ3፥17
6፥15 ኢዮ13፥4፤16፥2፤21፥34፤መዝ22፥1፤38፥11፤ኤር15፥18
6፥16 መዝ147፥18
6፥17 ኢዮ24፥19
6፥19 ዘፍ10፥7፡28፤25፥15
6፥20 ኤር14፥3፤ኢል1፥11
6፥21 መዝ38፥11
6፥22 ዘኍ35፥31፤ኢዮ33፥24፤መዝ49፥7፤ኤር15፥10
6፥23 2ነገ19፥19
6፥24 ኢዮ2፥10፤19፥ 4፤33፥33፤መዝ39፥1፤141፥3፤ምሳ10፥19፤11፥12፤17፥27፤መክ5፥2
6፥25 ኢሳ22፥23፤መክ12፥11
6፥26 ቍ3፤ዘፍ41፥6፤ኢዮ8፥2፤15፥3፤16፥3፤ኤር5፥13
6፥27 ዘፀ22፥22፡24፤ኢዮ31፥17፡21፤ኢሳ10፥2፤ሕዝ24፥6፤ኢል3፥3፤አብ1፥11፤ናሆ3፥10
6፥28 ኢዮ9፥15፤24፥25፤27፥4፤32፥10፥33፥1፡3፤34፥6፥36፥3፡4
6፥29 ኢዮ2፥3፤9፥21፤10፥7፤11፥2፤12፥4፤19፥6፤23፥7፡10፤27፥2፤33፥9፡32፤34፥5፡36፤35፥2፤40፥8፤42፥6፤መዝ66፥10፤ኢሳ40፥27፤ዘካ13፥9
6፥30 ኢዮ12፥11፤27፥4
7፥1 ዘሌ25፥50፤ኢዮ5፥7፤14፥14፤ኢሳ40፥2
7፥2 ዘሌ19፥13፤ኢዮ14፥1፡6፤መክ2፥23
7፥3 ኢዮ16፥7፤መዝ6፥6፤42፥3፤56፥8፤መክ4፥1፤ኢሳ16፥9፤ኤር9፥1፤ሰቆ1፥2፡16
7፥4 ቍ13-14፤ዘዳ28፥67
7፥5 ዘዳ28፥35፤ኢዮ17፥14፤21፥26፤ 24፥20፤25፥6፤ኢሳ14፥11 7፥6 ኢዮ9፥25፤13፥15፤14፥19፤17፥11፡15፤19፥10፤መዝ37፥4፤39፥5፤52፥9፤ኢሳ38፥12 7፥7 ቍ16፤ዘፍ27፥46፤ኢዮ10፥20፤መዝ39፥4፡5፡11፤62፥9፤78፥39፤89፥47፤144፥4፤መክ7፥15፤ያዕ4፥14 7፥8 ኢዮ3፥13፤8፥18፤15፥29፤20፥7፡9፡21፤27፥17፤መዝ37፥36፤103፥16፤ኢሳ41፥12፤ዮሐ16፥16፤ሐሥ20፥25 7፥9 2ሳሙ12፥23፤ኢዮ3፥13፡25፤11፥8፤14፥13፤17፥16፤26፥6፤38፥17፤አሞ9፥2 7፥10 ቍ8፤ኢዮ18፥21፤21፥18፤27፥21፡23፤መዝ37፥10፤58፥9፤104፥35፤ኤር18፥17፤19፥8 7፥11 ቍ13፤1ሳሙ1፥10፤ኢዮ6፥3፤9፥27፡35፤10፥1፤13፥13፤21፥4፤23፥2፤መዝ6፥3፤22፥2፤40፥9፤ኢሳ38፥15፡17 7፥12 ቍ20፤ዘፍ1፥21፤ኢዮ38፥8-11፤ኢሳ1፥14 7፥13 ቍ11

†9 የዕብራይስጡ ሲኦል ይላል

[14]አንተ በሕልም ታስፈራራኛለህ፤
በራእይም ታስደነግጠኛለህ፤
[15]ስለዚህ እንዲህ ሆኖ ከመኖር፣
መታነቅና መሞትን እመርጣለሁ::
[16]ሕይወቴን እጸየፋለሁ፤ ዘላለም መኖር
አልፈልግም፣
ዘመኔ እንደ እስትንፋስ ነውና ተወኝ::

[17]"ከፍ ከፍ ታደርገው ዘንድ፣
ልብህንም ትጥልበት ዘንድ ሰው ምንድን
ነው?
[18]በየማለዳው ትመረምረዋለህ፤
በየጊዜውም ትፈትነዋለህ::
[19]ዐይንህን ከእኔ ላይ አታነሣምን?
ምራቄን እንኳ እስክውጥ ፋታ
አትሰጠኝምን?
[20]ሰውን የምትከታተል ሆይ፤
ኀጢአት ብሠራ፣ አንተን ምን
አደርግሃለሁ?
ለምን ዒላማህ አደረግኸኝ?
ለምንስ ሸክም ሆንሁብህ?[ቸ]
[21]መተላለፌን ለምን ይቅር አትልም?
ኀጢአቴንስ ለምን አታስወግድልኝም?
ትቢያ ውስጥ የምጋደምበት ጊዜ ደርሶአል፤
ትፈልገኛለህ፤ እኔ ግን የለሁም::"

## በልዳዶስ

# 8
ሹሐዊውም በልዳዶስ እንዲህ ሲል
መለሰ፤

[2]"እንዲህ ያለውን ነገር የምትናገረው፣
ቃልህም እንደ ብርቱ ነፋስ የሚሆነው
እስከ መቼ ነው?
[3]እግዚአብሔር ፍትሕን ያጣምማልን?
ሁሉን ቻይ አምላክስ ጽድቅን
ያጣምማልን?
[4]ልጆችህ በእርሱ ላይ ኀጢአት ሠርተው
ከሆነ፣
ለኀጢአታቸው ቅጣት አሳልፎ
ሰጥቶአቸዋል::
[5]ነገር ግን አንተ ወደ እግዚአብሔር
ብትመለከት፣
ሁሉን ቻይ አምላክን ብትማፀን፣
[6]ንጹሕና ቅን ብትሆን፣እርሱ ስለ አንተ
አሁኑኑ ይነሣል
ወደ ተገቢውም ስፍራህ ይመልስሃል::
[7]ጅማሬህ አነስተኛ ቢመስልም፣
ፍጻሜህ እጅግ ታላቅ ይሆናል::

[8]"የቀደመውን ትውልድ ጠይቅ፤
አባቶቻቸውም የደረሱበትን መርምረህ
አግኝ፤
[9]እኛ ትናንት ስለ ተወለድን አንዳች
አናውቅምና፤
ዘመናችንም በምድር ላይ እንደ ጥላ
ነው::
[10]እነርሱ የሚያስተምሩህና የሚነግሩህ፣
ከልቦናቸውም ቃልን የሚያወጡ
አይደሉምን?
[11]ደንገል ረግረግ በሌለበት ስፍራ
ይበቅላልን?
ቄጠማስ ውሃ በሌለበት ይለመልማልን?
[12]ገና በማደግ ላይ እያለ ሳይታጨድ፣
ከሌሎች ዕፀዋት ፈጥኖ ይደርቃል::
[13]እግዚአብሔርን የሚረሱ መጨረሻቸው
እንዲህ ነው፤
አምላክ የለሽ ኑሮ የሚኖሩም ሁሉ
ተስፋቸው ትጠፋለች::
[14]መተማመኛው ቀጭን ክር፣[ኀ]
ድጋፉም የሸረሪት ድር ነው::
[15]ድሩ ላይ ቢደገፍ፣ ይበጠስበታል፤
አጥብቆም ቢይዘው አይጸናም::
[16]ውሃ እንደ ጠገበ ተክል፣ ፀሓይ
እየሞቀው፣
ቅርንጫፉን ሁሉ በአትክልቱ ስፍራ
ላይ ይዘረጋል::
[17]ሥሩን በድንጋይ ክምር ላይ
ይጠመጥማል፤
በዐለትም መካከል ስፍራ ያበጃል::
[18]ከስፍራው ሲወገድ ግን፣
ያ ቦታ 'አይቼህ አላውቅም' ብሎ
ይክደዋል::
[19]እነሆ፤ ሕይወቱ በዚህ ያከትማል፤[ነ]
ሌሎች አትክልትም ከመሬት ይበቅላሉ::

[20]"እነሆ፤ እግዚአብሔር እንከን የሌለበትን
ሰው አይጥልም፤
የክፉዎችንም እጅ አያበረታም፤
[21]እንደ ገና አፍህን በሣቅ፤
ከንፈሮችህንም በእልልታ ይሞላል::
[22]ጠላቶችህ ኀፍረት ይለብሳሉ፤
የክፉዎችም ድንኳን ይጠፋል::"

## ኢዮብ

# 9
ኢዮብ እንዲህ ሲል መለሰ፤
[2]"በእርግጥ ነገሩ እንዲህ እንደ ሆነ
ዐውቃለሁ፤

**7፥14** ዘፍ41፥8፤ኢዮ3፥26፤9፥34 **7፥15** 1ነገ19፥4፤ኢዮ6፥9፤ዮና4፥3፤ራእ9፥6 **7፥16** ቀኍ7፡19፤1ነገ19፥4፤ኢዮ3፥22፤9፥21፤10፥20፤መዝ39፥13 **7፥17** ኢዮ4፥19፤22፥2፤መዝ8፥4፤144፥3፤ዕብ2፥6 **7፥18** ኢዮ14፥3፤23፥10፤መዝ17፥3፤26፥2፤66፥10፤73፥14፤139፥1-6፡23፤143፥2 **7፥19** ቀኍ16፤ኢዮ9፥18፤13፥26፤14፥6፤27፥2፤መዝ139፥7 **7፥20** ቀኍ12፤ኢዮ6፥4፤35፥6፤ኤር7፥19 **7፥21** ቀኍ8፤ዘፍ3፥19፤ኢዮ3፥13፤9፥28፤10፥9፡14፤16፥6፤34፥15፤መዝ7፥5፤22፥15፤90፥3፤104፥29፤119፥120፤ኢሳ43፥25፤ኤር31፥34፤ዕብ1፥3 **8፥1** ዘፍ25፥2፤ኢዮ18፥1፤25፥1 **8፥2** 2ዜና36፥16፤ኢዮ6፥26፤11፥2፤18፥2 **8፥3** ዘፍ18፥25፤ኢዮ4፥17፤34፥12፤ኢሳ29፥15፤ኤር12፥1፤ሮሜ3፥5 **8፥4** ኢዮ1፥19 **8፥5** ኢዮ5፥8፡27፤9፥15 **8፥6** ኢዮ5፥15፡24፤22፥27፤33፥26፤34፥28፤ኢሳ58፥9፤65፥24 **8፥7** ኢዮ1፥10፤21፥13፤22፥21፤36፥11፤መዝ25፥13፤ኤር29፥11፤31፥17 **8፥8** ዘዳ32፥7፤ መዝ71፥18 **8፥9** ዘፍ47፥9፤1ዜና29፥15፤2ዜና10፥6፤መዝ39፥6 **8፥10** ምሳ1፥8፤2፥1-2፤4፥1 **8፥11** ዘፀ2፥3፤ኢዮ40፥21፤ኢሳ19፥6፤35፥7 **8፥12** ቀኍ19፤2ነገ19፥26፤ኢዮ18፥16፤20፥5፤መዝ90፥5-6፤102፥11፤ኢሳ34፥4፤40፥7፡24 **8፥13** ኢዮ6፥9፤11፥20፤13፥16፤15፥34፤20፥5፤27፥8፤34፥30፤መዝ9፥17፤37፥1-2፡38፤50፥22፤73፥17፤112፥10፤ምሳ10፥28፤11፥7፤ኢሳ51፥13፤ኤር15፥9፤17፥6 **8፥14** ቀኍ15፤ኢዮ27፥18፤ኢሳ59፥5 **8፥15** ቀኍ14፤መዝ49፥11፤ማቴ7፥26-27 **8፥16** መዝ37፥35፤80፥11፤ኢሳ16፥8፤ኤር11፥16 **8፥18** ኢዮ7፥8፤14፥20፤20፥9፤መዝ103፥16 **8፥19** ቀኍ12፤ኢዮ15፥30፤መዝ119፥90፤መክ1፥4 **8፥20** ዘፍ18፥25፤ኢዮ1፥1 **8፥21** ዕዝ3፥13፤ኢዮ5፥22፤35፥10፤መዝ47፥5፤107፥22፤118፥15፤126፥2፤132፥16፤ኢሳ35፥6 **8፥22** 1ሳሙ8፥3፤ኢዮ4፥21፤18፥6፡14፡21፤21፥28፤27፥7፡8፡18፤34፥26፤36፥6፤38፥13፤መዝ6፥10፤35፥26፤44፥7፤52፥5፤53፥5፤71፥13፤86፥17፤109፥29፤132፥18፤ምሳ14፥11፤ሕዝ7፥27፤26፥16 **9፥2** ኢዮ4፥17፤ሮሜ3፥20 **9፥3** ቀኍ12፡14፡

[ቸ]20 ጥቂት የማሶሬቲክ ጽሑፍ ቅጆች፣ የጥንት የዕብራውያን ጸሓፍት ትውፊትና ሰብዓ ሊቃናት እንዲሁ ሲሆኑ አብዛኛው የማሶሬቲክ ጽሑፍ ቅጆች ግን *ለራሴ ሸክም ሆንሁ* ይላሉ::
[ኀ]14 በዕብራይስጥ የዚህ ቃል ትርጒም አይታወቅም
[ነ]19 ወይም *ያለው ደስታ ሁሉ*

ነገር ግን ሥጋ ለባሽ በእግዚአብሔር ፊት
እንዴት ጻድቅ ሊሆን ይችላል?
3ሰው ከእርሱ ጋር ለመከራከር ቢፈልግ፤
ከሺህ ጥያቄ አንዱን እንኳ መመለስ
አይችልም።
4ጥበቡ ጥልቅ፣ ኀይሉም ታላቅ ነውና፤
እርሱን ተቃውሞ ያለ አንዳች ጕዳት
የሄደ ማን ነው?
5ሳያውቁት፣ ተራሮችን ይነቅላቸዋል፤
በቍጣውም ይገለብጣቸዋል።
6ምድርን ከስፍራዋ ያናውጣታል፤
ምሰሶዎቿንም ያንቀጠቅጣል።
7ፀሓይን ያዛታል፤ አትወጣምም፤
ከዋክብትንም በማኅተም ያሽጋል።
8እርሱ ብቻውን ሰማያትን ዘርግቶአል፤
በባሕርም ማዕበል ላይ ይራመዳል።
9እርሱ የድብና የኦሪዮን፣
የፕልያዲስና የደቡብ ከዋክብት ፈጣሪ
ነው፤
10የማይመረመሩ ድንቅ ነገሮችን፣
የማይቈጠሩ ታምራትንም ያደርጋል።
11እነሆ! በአጠገቤ ሲያልፍ አላየውም፤
በጐኔም ሲሄድ፣ ልገነዘበው አልችልም።
12ቢነጥቅ፣ ማን ይከለክለዋል?
"ምን መሥራትህ ነው?" የሚለውስ፣
ማን ነው?
13እግዚአብሔር ቍጣውን አይመልስም፤
ረዓብን የሚረዱ እንኳ ይሰግዱለታል።

14"ታዲያ፣ ከእርሱ ጋር እሟገት ዘንድ፣
ልከራከረውም ቃላት እመርጥ ዘንድ፣
እንዴት እችላለሁ?
15ጻድቅ ብሆንም እንኳ፣ ልመልስለት
አልችልም፤
ዳኛዬን ምሕረት ከመለመን ሌላ ላደርግ
የምችለው የለም።
16ጠርቼው "አቤት!" ቢለኝም፣
ያዳምጠኛል ብዬ አላምንም።
17በዐውሎ ነፋስ ይሰብረኛል፤
ቍስሌንም ያለ ምክንያት ያበዛል፤
18ምሬትን አጠገበኝ እንጂ፣
ለመተንፈስ እንኳ ፋታ አልሰጠኝም።
19የኀይል ነገር ከተነሣ፣ እርሱ ኀያል ነው!
የፍትሕም ነገር ከተነሣ፣ መጥሪያ
ሊሰጠው[ኘ] የሚችል ማን ነው?
20ንጹሕ ብሆን እንኳ፣ አንደበቴ
ይፈርድብኛል፣
እንከን የለሽ እንኳ ብሆን፣ በደለኛ
ያደርገኛል።

21"ያለ ነቀፋ ብሆንም እንኳ፣
ስለ ራሴ ግድ የለኝም፤
የገዛ ሕይወቴንም እንቃታለሁ።
22ሁሉም አንድ ነው፤
'እርሱ ጻድቁንና ኀጥኡን ያጠፋል'
የምለውም ለዚህ ነው።
23መዓት ወርዶ ድንገት ሰው ሲጨርስ፣
በንጹሓን መከራ ይሣለቃል።
24ምድር በክፉዎች እጅ ስትወድቅ፣
እርሱ የፈራጆቿን ዐይን ይሸፍናል፤
ታዲያ፣ ይህን ያደረገው እርሱ ካልሆነ
ማን ሊሆን ይችላል?

25"ዘመኔ ከሚሮጥ ሰው ይልቅ ይፈጥናል፣
አንዳችም ደስታ ሳያይ ያልፋል።
26ከደንገል እንደ ተሠራ ታንኳ፣
ለመንጠቅ ቍልቍል እንደሚበር ንስር
ይፈጥናል።
27'ማጕረምረሜን እረሳለሁ፤
ገጽታዬን ቀይሬ ፈገግ እላለሁ' ብል፣
28ንጹሕ አድርገህ እንደማትቈጥረኝ ስለማውቅ፣
መከራዬን ሁሉ እፈራለሁ።
29በደለኛ መሆኔ ካልቀረ፣
ለምን በከንቱ እለፋለሁ?
30ሰውነቴን በሳሙና[ኣ] ብታጠብ፣
እጄንም በልዩ መታጠቢያ ባነጻ፣
31ልብሴ እንኳ እስኪጸየፈኝ ድረስ፣
በዐዘቅት ውስጥ ታሰጥመኛለህ።

32"መልስ እሰጠው ዘንድ፣ እሟገተውም
ዘንድ፣
እርሱ እንደ እኔ ሰው አይደለም።
33በሁለታችን ላይ እጅ የሚጭን፣
በመካከላችንም የሚዳኝ ቢኖር፣
34ግርማው እንዳያስፈራኝ፣
እግዚአብሔር በትሩን ከእኔ ላይ ቢያነሣ፣
35ሳልፈራው በተናገርሁት ነበር፤
አሁን ባለሁበት ሁኔታ ግን፣ አልችልም።

# 10

"ሕይወቴን እጅግ ጠላሁ፤
ስለዚህም ማጕረምረሜን ያለ
ገደብ እለቃለሁ፤
በነፍሴም ምሬት እናገራለሁ።

29፡32፤ኢዮ10፥2፤12፥14፤13፥9፤14፤22፥4፤23፥7፡13፤37፥19፤40፥2፡5፤መዝ44፥21፤ኢሳ14፥24
9፥4 ቍ19፤2ዜና13፥12፤ኢዮ5፥9፡13፤11፥6፤12፥13፡16፤23፥6፤24፥22፤26፥12፤28፥12፡20፡23፤30፥18፤38፥36፤መዝ51፥6፤ 93፥4፤95፥3፤ምሳ2፥6፤8፥14፤መክ2፥26፤ኢሳ40፥26፤63፥1፤ኤር50፥24፤ዳን2፥20፤4፥35
9፥5 መዝ18፥7፤46፥2-3፤ኢሳ13፥13፤ሚክ1፥4፤ማቴ17፥20
9፥6 ዘፀ19፥18፤2ሳሙ22፥8፤ኢዮ26፥14፤36፥29፤37፥4-5፤መዝ75፥3፤ኢሳ2፥21፤13፥13፤24፥18-20፤አሞ8፥8፤ዕን3፥4፤ዕብ12፥26
9፥7 ኢሳ13፥10፤34፥4፤ኤር4፥23፡28፤ሕዝ32፥8፤ኢል2፥2፡10፡31፤3፥15፤ሶፎ1፥15፤ዘካ14፥6
9፥8 ዘፍ1፥1፡8፤ኢዮ38፥16፤መዝ77፥19፤ምሳ8፥28፤ኢሳ48፥13፤ዕን3፥15፤ማቴ14፥25፤ማር6፥48፤ዮሐ6፥19
9፥9 ዘፍ1፥16፤ኢዮ32፥22፤40፥15፡19
9፥10 ዘዳ6፥22፤ኢዮ5፥9፤መዝ72፥18፤136፥4፤ኤር32፥20
9፥11 ኢዮ23፥8-9፤35፥14
9፥12 ቍ3፤ዘኍ23፥20፤ዘዳ32፥39፤ኢዮ11፥10፤ኢሳ14፥27፤29፥16፤43፥13፤45፥9፤ዳን2፥21፤4፥32፤ሮሜ9፥20
9፥13 ዘኍ14፥18፤ኢዮ10፥15፤26፥12፤መዝ78፥38፤87፥4፤89፥10፤ኢሳ3፥11፤6፥5፤30፥7፤48፥9፤51፥9
9፥14 ቍ3
9፥15 ቍ20፡29፤ዘፍ18፥25፤1ሳሙ24፥12፤ኢዮ8፥5፤10፥15፤13፥19፤15፥6፤23፥4፤34፥5-6፤40፥2፡5፤42፥7፤መዝ50፥6፤96፥13
9፥16 ኢዮ13፥22፤ሮሜ9፥20-21
9፥17 ኢዮ2፥3፤16፥12፡14፤30፥16፡22፤መዝ10፥10፤83፥15፤ኢሳ38፥13፤ዮና1፥4

9፥18 ኢዮ7፥19፤10፥1 9፥19 ቍ4፥33፤ነህ9፥32፤ኤር49፥19
9፥20 ቍ15 9፥21 ቍ14፤ዘፍ6፥9፤ዘኍ11፥15፤ኢዮ6፥29፤7፥16፤10፥1፤13፥13፤34፥6፡7 9፥22 ኢዮ3፥19፤10፥8፤መክ9፥2፡3፤ሕዝ21፥3 9፥23 ኢዮ24፥1፡12፤መዝ64፥4፤ዕን1፥3፤ዕብ11፥36፤1ጴጥ1፥7 9፥24 ኢዮ1፥15፡17፤3፥14፤10፥3፤12፥6፡9፤13፥1፤16፥11፤19፥7፤21፥7፡16፤22፥18፤24፥12፡23፤27፥2፤31፥35፤35፥15፤40፥8፤መዝ73፥3፡12፤መክ8፥11፤ኢሳ41፥20፤ኤር12፥1፤ሰቆ3፥9 9፥25 ኢዮ7፥6፡7፤10፥20 9፥26 ኢዮ24፥18፤39፥29፤መዝ46፥3፤ኢሳ18፥2፤ዕን1፥8
9፥27 ኢዮ7፥11 9፥28 ዘፀ34፥7፤ኢዮ3፥25፤7፥21 9፥29 ቍ3፥15፤መዝ37፥33 9፥30 ኢዮ14፥4፡17፤17፥9፤31፥7፤33፥9፤ኢሳ1፥15፡18፤ኤር2፥22፤ሆሴ13፥12፤ሚል3፥2 9፥31 ኢዮ7፥20፤34፥9፤35፥3፤መዝ35፥7፤40፥2፤51፥9፤73፥13፤ኤር2፥22፤ናሆ3፥6፤ሚል2፥3 9፥32 ቍ3፤ዘኍ23፥19፤መዝ143፥2፤መክ6፥10፤ሮሜ9፥20 9፥33 ቍ19፤1ሳሙ2፥25 9፥34 ኢዮ6፥4፤7፥14፤ 21፥9፤33፥7፤መዝ32፥4፤39፥10፤73፥5 9፥35 ኢዮ7፥11፡15፤13፥21 10፥1 ዘኍ11፥15፤1ሳሙ1፥10፤1ነገ19፥4፤ኢዮ7፥11፤9፥18፡21

[ኘ]19 ሰብዓ ሊቃናት ይመልከቱ፤ የዕብራይስጡ ሊሰጠኝ ይላል
[ኣ]30 ወይም በረዶ

2 እግዚአብሔርን እንዲህ እለዋለሁ፤
በምን ላይ እንዳልተስማማን ንገረኝ
እንጂ አትፍረድብኝ።
3 የክፉዎችን ዕቅድ በደስታ እየተቀበልህ፣
እኔን ግን ስታስጨንቀኝ፣
የእጅህንም ሥራ ስታዋርድ ደስ ይልሃልን?
4 አንተ ዐይንህ የሥጋ ለባሽ ዐይን ነውን?
ሟች የሆነ የሰው ልጅ እንደሚያይ
ታያለህን?
5 ዘመንህ እንደ ሟች ሰው ዘመን ነውን?
ወይስ ዓመታትህ እንደ ሰው ዓመታት
ናቸውን?
6 ታዲያ፣ በደልን የምትፈላልግብኝ፣
ኀጢአቴንም የምትከታተለው ለምንድን
ነው?
7 እኔ በደለኛ እንዳልሆንሁ፣
ከእጅህም ሊያስጥለኝ ማንም
እንደማይችል አንተ ታውቃለህ።

8 "እጅህ አበጀችኝ፤ ሠራችኝም፤
መልሰህ ደግሞ ታጠፋኛለህን?
9 እንደ ሸክላ እንዳበጀኸኝ አስብ፤
አሁን ደግሞ ወደ ትቢያ
ትመልሰኛለህን?
10 እንደ ወተት አላፈሰስኸኝምን?
እንደ እርጎስ አላረጋኸኝምን?
11 ቈዳና ሥጋ አለበስኸኝ፤
በዐጥንትና በጅማትም አገጣጥመህ
ሠራኸኝ።
12 ሕይወትን ሰጠኸኝ፤ በጎነትንም አሳየኸኝ፤
እንክብካቤህም መንፈሴን ጠበቀ።

13 "ይህን ሁሉ ግን በልብህ ሸሸግህ፣
ነገሩ በሐሳብህ እንደ ነበር ዐውቃለሁ፤
14 ኀጢአትን ብሠራ ትመለከተኛለህ፤
መተላለፌንም ሳትቀጣ አታልፍም።
15 በደለኛ ብሆን ወዮልኝ፤
ንጹሕ ብሆንም፣ ራሴን ቀና አላደርግም፤
ውርደትን ተከናንቤአለሁና፤
በመከራም ተዘፍቄአለሁ፤[ከ]
16 ራሴን ከፍ ከፍ ባደርግ፣ እንደ አንበሳ
ታደባብኛለህ፤
አስፈሪ ኀይልህን ደጋግመህ ታሳየኛለህ፤
17 አዳዲስ ምስክሮችን ታመጣብኛለህ፤
ቍጣህንም በላዬ ትጨምራለህ፤
ሰራዊትህም ተከታትሎ ይመጣብኛል።

18 "ታዲያ ለምን ከማሕፀን አወጣኸኝ?
ምነው ዐይን ሳያየኝ በሞትሁ ኖሮ!
19 ምነው ባልተፈጠርሁ!
ወይም ከማሕፀን ቀጥታ ወደ መቃብር
በወረድሁ!
20 ጥቂት የሆነው ዘመኔ እያለቀ አይደለምን?
ከሥቃዬ ፋታ እንዳገኝ ተወት አድርገኝ፤
21 ወደማልመለስበት ስፍራ፣
ወደ ጨለማና ወደ ሞት ጥላ[ኸ] አገር
ከመሄዴ በፊት፣
22 ብርሃኑ እንደ ጨለማ ወደ ሆነበት፣
የሞት ጥላ ወዳረበበበት፣ ሥርዐት የለሽ
ወደ ሆነ ምድር፣
ድቅድቅ ጨለማ ወደ ሰፈነበት አገር
ሳልሄድ ተወኝ።"

## ሶፋር

# 11

1 ነዕማታዊው ሶፋር እንዲህ ሲል
መለሰ፤
2 "ይህ ሁሉ ቃል መልስ ማግኘት
አይገባውምን?
ወይስ ተናጋሪ ሰው እንደ እውነተኛ
ይቈጠርን?
3 በውኑ የአንተ መዘላበድ ሰውን ዝም
ያሰኛልን?
ስታፌዝስ የሚገሥጽህ የለም?
4 እግዚአብሔርንም፣ 'ትምህርቴ የጠራ፤
በዐይንህም ፊት የጸዳሁ ነኝ' ትለዋለህ።
5 ምነው እግዚአብሔር ቢናገርህ!
ከንፈሩንም በአንተ ላይ ቢከፍት!
6 እውነተኛ ጥበብ ባለ ብዙ ፈርጅ ናትና፣
የጥበብንም ምስጢር ምነው በገለጠልህ!
እግዚአብሔር ለኀጢአትህ የሚገባውን
እንዳላስከፈለህ ባወቅህ ነበር።

7 "የእግዚአብሔርን ጥልቅ ምስጢር ልትለካ
ትችላለህን?
ወይስ ሁሉን የሚችለውን አምላክ
መርምረህ ትደርስበታለህን?
8 ከሰማይ ይልቅ ከፍ ይላል፤ ምን ልታደርግ
ትችላለህ?
ከሲኦልም[ሠ] ይጠልቃል፤ ምን ልታውቅ
ትችላለህ?
9 መጠኑ ከምድር ይልቅ ይረዝማል፤
ከባሕርም ይልቅ ይሰፋል።

10 "እርሱ ተከታትሎ መጥቶ በግዞት
ቢያስቀምጥህ፣
የፍርድ ሸንጎም ቢሰበስብ፣ ማን
ሊከለክለው ይችላል?
11 በእውነት እርሱ ሸፍጠኞችን ያውቃል፣
ክፋት ሲሠራም ልብ ይላል።

**10፥2** ኢዮ9፥3፤13፥3፤40፥1፤ኢሳ3፥13፤ሆሴ4፥1፤5፥1፤12፥2፤ሚክ6፥2፤ሮሜ8፥33 **10፥3** ቍ8፤ዘፍ1፥26፤ኢዮ4፥17፤9፥22፡24፤14፥15፤16፥9፡14፤19፥6፡21፤22፥10፤30፥13፡21፤31፥23፤34፥6፡19፤መዝ8፥6፤95፥6፤100፥3፤138፥8፤149፥2፤ኢሳ60፥21፤64፥8 **10፥4** 1ሳሙ16፥7፤ኢዮ11፥11፤14፥16፤24፥23፤28፥24፤31፥4፤34፥21፤41፥11፤መዝ11፥4፤33፥15፤119፥168፤139፥12፤ምሳ5፥21፤15፥3፤ኤር11፥20-23፤16፥17 **10፥5** ኢዮ36፥26፤መዝ39፥5፤90፥2፡4፤102፥24፤2ጴጥ3፥8 **10፥6** ኢዮ14፥16 **10፥7** ቍ15፤ዘዳ32፥39፤ኢዮ6፥29፤11፥4፤16፥17፤27፥5፡6፤31፥6፤32፥1 **10፥8** ቍ3፤ዘፍ2፥7፤2ሳሙ14፥14፤ኢዮ30፥15 **10፥9** ዘፍ2፥7፤ኢዮ4፥19፤7፥21፤ኢሳ29፥16 **10፥11** መዝ139፥13፡15 **10፥12** ዘፍ2፥7፤24፥12፤45፥5፤1ጴጥ2፥25 **10፥13** ኢዮ23፥13፤መዝ115፥3 **10፥14** ዘፀ34፥7፤ኢዮ7፥21፤13፥27 **10፥15** ቍ7፤ኢዮ9፥13፡15፤መዝ25፥16 **10፥16** 1ሳሙ17፥34፤ኢዮ5፥9፤መዝ7፥2፤ኢሳ28፥21፤29፥14፤38፥13፤65፥7፤ኤር5፥6፤25፥38፤ሰቆ3፥10፤ሆሴ5፥14፤13፥7 **10፥17** ሩት1፥21፤1ነገ21፥10፤ኢዮ5፥7፤16፥8 **10፥18** ኢዮ3፥8፡26፤መዝ22፥9፤መክ6፥12 **10፥19** ኢዮ3፥3፤ኤር15፥10 **10፥20** ኢዮ7፥7፡16፤9፥25፤14፥1፤መክ4፥2፤7፥1 **10፥21** 2ሳሙ12፥23፤ኢዮ3፥5፡13፤16፥22፤መዝ39፥13፤መክ12፥5 **10፥22** 1ሳሙ2፥9፤ኢዮ3፥5፡13 **11፥1** ኢዮ2፥11 **11፥2** ዘፍ41፥6፤ኢዮ6፥29፤8፥2፤16፥3 **11፥3** ኢዮ12፥4፤16፥10፤17፥2፤21፥3፤30፥1፤መዝ1፥1፤ኤፌ4፥29፤5፥4 **11፥4** ኢዮ9፥21፤10፥7 **11፥5** ዘፀ20፥19፤ኢዮ23፥5፤32፥13፤38፥1 **11፥6** ዕዝ9፥13፤ኢዮ9፥4፤15፥5፤1ቆሮ2፥10 **11፥7** ኢዮ5፥9፤መክ3፥11 **11፥8** ዘፍ15፥5፤ኢዮ7፥9፤15፥13፡25፤22፥12፤25፥2፤33፥13፤40፥2፤መዝ57፥10፤139፥8፤ኢሳ55፥9፤ኤፌ3፥18 **11፥9** ኢዮ22፥12፤35፥5፤36፥26፤37፥5፡23፤ኢሳ40፥26፤ኤፌ3፥19-20 **11፥10** ኢዮ9፥12፤ራእ3፥7 **11፥11** ኢዮ10፥4፤ 31፥37፤34፥11፡25፤36፥7፤መዝ10፥14

[ከ] 15 ወይም *መከራዬን ዐውቄአለሁ*
[ኸ] 21 ወይም *ከባድ ጥላ* እንዲሁም ቍ 22
[ሠ] 8 ወይም *ከመቃብር*

12 ጅል ሰው ጥበበኛ ከሚሆን ይልቅ፣
የሜዳ አህያ ሰው ሆኖ ቢወለድ
ይቀላል።[0]

13 “ነገር ግን ልብህን ብትሰጠው፣
እጅህንም ወደ እርሱ ብትዘረጋ፣
14 በእጅህ ያለውን ኀጢአት ብታርቅ፣
ክፋትም በድንኳንህ እንዳይኖር
ብታደርግ፣
15 በዚያን ጊዜ ሳታፍር ቀና ትላለህ፤
ያለ ፍርሀት ጸንተህ ትቆማለህ፤
16 መከራህን ትረሳለህ፤
ዐልፎ እንደ ሄደ ጐርፍም ታስበዋለህ።
17 ሕይወትህ ከቀትር ይልቅ ያበራል፤
ጨለማውም እንደ ንጋት ይሆናል።
18 ተስፋ ስላለ ተደላድለህ ትቀመጣለህ፤
ዙሪያህን ትመለከታለህ፤ በሰላምም
ታርፋለህ።
19 ያለ አንዳች ሥጋት ትተኛለህ፤
ብዙ ሰዎችም ደጅ ይጠኑሃል።
20 የክፉዎች ዐይን ግን ትጨልማለች
ማምለጫም አያገኙም፤
ተስፋቸውም ሞት ብቻ ነው።”

## ኢዮብ

# 12 ኢዮብ እንዲህ ሲል መለሰ፤
2 “በእርግጥ ሰው ማለት እናንተ
ናችኋ!
ጥበብም ከእናንተ ጋር ትሞታለቻ!
3 ነገር ግን እኔም እንደ እናንተ አእምሮ
አለኝ፤
ከእናንተ አላንስም፤
እንዲህ ያለውን ነገር የማያውቅ ማን
ነው?
4 እግዚአብሔርን ጠርቼ የመለሰልኝ ሰው
ብሆንም፣
ለባልንጀሮቼ መሣቂያ ሆኛለሁ፤
ጻድቅና ያለ ነቀፋ ሆኜ እያለሁ፣
መሣቂያ
ሆኛለሁ።
5 የደላቸው በመከራ ያፌዛሉ፤
እግሩ የተንሸራተተውንም ይገፈትራሉ።
6 የቀማኞች ድንኳን አይታወክም፤
አምላካቸውን በእጃቸው ይዘው እየዞሩም፣[ʺ]
እግዚአብሔርንም እያስቈጡ በሰላም
ይኖራሉ።

7 “እስቲ እንስሶችን ጠይቁ፤
ያስተምሯችኋል፤
የሰማይ ወፎችንም ጠይቁ፣
ይነግሯችኋል፤
8 ለምድር ተናገሩ፤ ታስተምራችኋለች፤
የባሕርም ዓሣ ይነግራችኋል።
9 የእግዚአብሔር እጅ ይህን እንዳደረገ፣
ከእነዚህ ሁሉ የማያውቅ ማን ነው?
10 የፍጥረት ሁሉ ሕይወት፣
የሰውም ሁሉ መንፈስ በእጁ ናትና፤
11 ምላስ የምግብን ጣዕም እንደሚለይ፣
ጆሮ ቃላትን አይለይምን?
12 ጥበብ ያለው በአረጋውያን ዘንድ
አይደለምን?
ማስተዋልስ ረጅም ዕድሜ ባላቸው ዘንድ
አይገኝምን?

13 “ጥበብና ኀይል የእግዚአብሔር ናቸው፤
ምክርና ማስተዋልም በእርሱ ዘንድ
ይገኛሉ።
14 እርሱ ያፈረሰውን መልሶ የሚገነባ የለም፣
እርሱ ያሰረውን የሚፈታ አይገኝም።
15 እርሱ ውሃን ቢከለክል፣ ድርቅ ይሆናል፤
ቢለቀውም ውሃው ምድሪቱን
ያጥለቀልቃል።
16 ብርታትና ድል ማድረግ በእርሱ ዘንድ
ይገኛል፤
አታላዩም ተታላዩም በእርሱ እጅ
ናቸው።
17 አማካሪዎችን ከጥበባቸው ያራቍታል፤
ፈራጆችንም ማስተዋል ይነሣል።
18 ነገሥታትን ድግ ያስፈታል፤
ገመድም በወገባቸው ያስራል።[ፕ]
19 ካህናትን ከክህነታቸው ያዋርዳል፤
ለዘመናት የተደላደሉትንም ይገለብጣል።
20 ዕውቅ መካሪዎችን ቋንቋ ያሳጣል፤
የሽማግሌዎችንም ማስተዋል ይወስዳል።
21 የተከበሩትን ውርደት ያከናንባል፤
ብርቱዎችንም ትጥቅ ያስፈታል።
22 የጨለማን ጥልቅ ነገሮች ይገልጣል፤
የሞትንም ጥላ ወደ ብርሃን ያወጣል።
23 ሕዝቦችን ታላቅ ያደርጋል፤ መልሶም
ያጠፋቸዋል፤
ሕዝቦችን ያበዛል፤ ያፈልሳቸዋልም።
24 የዓለም መሪዎችን ማስተዋል ይነሣል፤
መንገድ በሌለበት በረሓም
ያቅበዘብዛቸዋል፤
25 ብርሃን በሌለበት ጨለማ በዳበሳ ይሄዳሉ፤
እንደ ሰካራምም ይንገዳገዳሉ።

11፥12 ዘፍ16፥12፤ 2ዜና6፥36
11፥13 ዘፀ9፥29፤ 1ሳሙ7፥3፤ኢዮ5፥8፡ 27፤መዝ78፥8
11፥14 ኢሱ24፥14፤ ኢ22፥23፤መዝ101፥4
11፥15 ዘፍ4፥7፤ 1ሳሙ2፥9፤ኢዮ22፥ 26፤መዝ3፥6፤20፥8፤3 7፥23፤40፥2፤119፥5፤ኤፌ6፥14
11፥16 ኢሱ7፥5፤ ኢዮ22፥11፤መዝ58፥ 7፤112፥10፤ኢሳ26፥ 16፤37፥3፤65፥16፤ ሕዝ21፥7
11፥17 ኢዮ17፥ 12፤18፥6፤22፥28፤29፥ 3፤መዝ18፥28፤37፥6፤ 112፥4፤119፥ 105፤ኢሳ5፥20፤ 58፥8፡10፤62፥ 1፤ዮሐ8፥12
11፥18 ዘሌ 26፥6፤ መዝ3፥5፤4፥8፤127፥2፤ ምሳ3፥24፤መክ5፥12፤ ኢሳ11፥10፤14፥3፤ 28፥12፤30፥15፤32፥ 18፤ዘካ3፥10
11፥19 ዘሌ26፥6፤ ኢሳ45፥14
11፥20 ዘዳ28፥65፤ ኢዮ8፥13፤12፥10፤ 17፥5፤18፥18፤27፥22፤ 34፥22፤36፥6፤መዝ 139፥11-12፤ኤር11፥ 11፤23፥24፤25፥35፤ አሞ2፥14፤9፥2-3
12፥2 ኢዮ15፥8፤ 17፥10
12፥3 ኢዮ13፥2፤ 15፥9
12፥4 ዘፍ6፥9፤38፥ 23፤ኢዮ6፥14፡29፤11፥ 3፤15፥16፤16፥10፤ 19፥14፤መዝ91፥15
12፥5 መዝ17፥5፤ 37፥31፤38፥16፤66፥ 9፤73፥2፤94፥18፤ 123፥4
12፥6 ኢዮ5፥24፤ 9፥24
12፥7 ኢዮ18፥3፤ 35፥11፤ማቴ6፥26፤ ሮሜ1፥20
12፥9 ኢዮ9፥24፤ ኢሳ1፥3
12፥10 ዘፍ2፥7፤ ዘኍ16፥22፤ኢዮ11፥ 20፤ዳን5፥23፤ ሐሥ17፥28
12፥11 ኢዮ34፥3
12፥12 ቍ20፤1ነገ 4፥2፤ኢዮ15፥10፤17፥ 4፤32፥7፡9፤34፥4፡10
12፥13 ዘኍ23፥19፤ 1ነገ3፥12፤ኢዮ9፥4፤ 32፥8፤38፥36፤ምሳ2፥6 ፤21፥30፤ኢሳ40፥13- 14፤45፥9፤ኤር32፥19፤ ዳን1፥17፤1ቆሮ1፥24
13፥1 ኢዮ9፥24

12፥14 ዘዳ13፥16፤ኢዮ9፥3፤16፥9፤19፥10፤መዝ127፥1፤ኢሳ22፥ 22፤24፥20፤25፥2፤ሕዝ26፥14፤ራእ3፥7 12፥15 ዘፍ7፥24፤ዘዳ28፥ 22፤1ነገ17፥1፤ኢዮ28፥25፤ኢሳ40፥12 12፥16 2ዜና18፥22፤ኢዮ 9፥4፤13፥7፡9፤27፥4፤ሮሜ2፥11 12፥17 ቍ19፤ኢዮ3፥14፤19፥9፤ ኢሳ20፥4፤1ቆሮ1፥20 12፥18 ቍ21፤ኢዮ34፥18፤መዝ107፥14፡ 40፤116፥16፤ኢሳ5፥27፤40፥23፤ናሆ1፥13 12፥19 ቍ17፤ዘዳ24፥ 15፤ኢዮ9፥24፤14፥20፤22፥8፤24፥12፡22፤34፥20፡28፤35፥9፤ኢሳ2፥ 22፤31፥8፤40፥17፡23፤ኤር25፥18፤ዳን2፥21፡34፤ሉቃ1፥52 12፥20 ቍ 12፡24፤ዳን4፥33፡34 12፥21 ቍ18፤ኢዮ3፥15፤ኢሳ34፥12 12፥22 ኢዮ3፥5፤መዝ139፥12፤ዳን2፥22፤1ቆሮ4፥5 12፥23 ዘፀ34፥24፤ ኢዮ5፥12፤መዝ2፥1፤46፥6፤107፥38፤ኢሳ9፥3፤13፥4፤26፥15፤54፥ 3፤ኤር25፥9፤ሐሥ17፥26 12፥24 ቍ20፤መዝ 107፥40 12፥25 ዘዳ28፥29፤ኢዮ18፥6፤21፥17፤29፥3፤መዝ107፥ 27፤ኢሳ24፥20

[0] 12 *ወይም የዱር አህያ ለማዳ ሆኖ ሊወለድ ይችላል*
[ʺ] 6 *ወይም የእግዚአብሔር እጅ በምታመጣላቸው ነገር*
[ፕ] 18 *ወይም የነገሥታትን ድግ... ፤ ሠቅ ያስራል*

# 13

"ይህን ሁሉ ዐይኔ አይቶአል፤
ጆሮዬም ሰምቶ አስተውያለሁ፤
2እናንተ የምታውቁትን፣ እኔም
ዐውቃለሁ፤
ከእናንተ የማንስ አይደለሁም።
3ነገር ግን ሁሉን ከሚችል አምላክ ጋር
መነጋገር እፈልጋለሁ፤
ከእግዚአብሔርም ጋር መዋቀስ እሻለሁ።
4እናንተ ግን፣ በሐሰት የምትለብጡ ናችሁ፤
ሁላችሁ የማትረቡ ሐኪሞች ሆናችኋል።
5ምነው ዝም ብትሉ!
ያ ከጥበብ ይቈጠርላችሁ ነበር!
6እንግዲህ ክርክሬን ስሙ፤
የከንፈሬንም አቤቱታ አድምጡ።
7ለእግዚአብሔር ብላችሁ በክፋት
ትናገራላችሁን?
ስለ እርሱስ በማታለል ታወራላችሁን?
8ለእርሱ ታደላላችሁን?
ለእግዚአብሔር ጥብቅና ልትቆሙ ነውን?
9እርሱ ቢመረምራችሁ መልካም ነገር
ይገኝባችኋልን?
ሰውን እንደምታታልሉ፣ ልታታልሉት
ትችላላችሁን?
10በስውር አድልዎ ብታደርጉ፣
በእርግጥ እርሱ ይገሥጻችኋል።
11ግርማው አያስደነግጣችሁምን?
ክብሩስ አያስፈራችሁምን?
12ምሳሌዎቻችሁ የዐመድ ምሳሌዎች
ናቸው፣
መከላከያችሁም የጭቃ ምሽግ ነው።

13"ዝም በሉ፤ እኔ ልናገር፤
የመጣው ይምጣብኝ።
14ሥጋዬን በጥርሴ፣
ሕይወቴንም በእጄ ለምን እይዛለሁ?
15ቢገድለኝም እንኳ በእርሱ ተስፋ
አደርጋለሁ፤
ስለ መንገዴም ፊት ለፊት
እከራከረዋለሁ።[የ]
16ኀጢአተኛ በእርሱ ፊት መቅረብ
ስለማይችል፤
ይህ ድፍረቴ ለመዳኔ ይሆናል።
17ቃሌን በጥንቃቄ አድምጡ፤
እኔ የምለውንም ጆሮአችሁ በሚገባ
ይስማ፤
18እንግዲህ ጉዳዬን ይገቼ ቀርቤአለሁ፤
እንደሚፈርድልኝም ዐውቃለሁ።
19ሊከሰኝ የሚችል አለ?
ካለም፣ ዝም ብዬ ሞቴን እጠብቃለሁ።

20"አምላክ ሆይ፣ እነዚህን ሁለት ነገሮች
ብቻ ስጠኝ፣
ያን ጊዜ ከፊትህ አልሰወርም፤
21እጅህን ከእኔ ላይ አንሣ፤
በግርማህም አታስፈራራኝ፤
22ከዚያ በኋላ ጥራኝ፤ እኔም
እመልስልሃለሁ፤
ወይም እኔ ልናገር፤ አንተ መልስልኝ።
23በደሌና ኀጢአቴ ምን ያህል ነው?
መተላለፌንና ኀጢአቴን አስታውቀኝ።
24ፊትህን ለምን ትሰውራለህ?
እንደ ጠላትህስ ለምን ትቈጥረኛለህ?
25ነፋስ ያረገፈውን ቅጠል ታስጨንቃለህን?
የደረቀውንስ እብቅ ታሳድዳለህን?
26መራራ ነገር ትጽፍብኛለህ፤
የወጣትነቴንም ኀጢአት ታወርሰኛለህ።
27እግሬን በእግር ግንድ ታጣብቃለህ፤
ውስጥ እግሬም ላይ ምልክት አድርገህ፣
ዱካዬን አጥብቀህ ትከታተላለህ።

28"እንደ በሰበሰ ግንድ፣
ብል እንደ በላው ልብስ፣ ሕይወት
እያደር ማለቅ ነው።

# 14

"ከሴት የተወለደ ሰው፣
ዘመኑ አጭርና በመከራ
የተሞላ ነው፤
2እንደ አበባ ይፈካል፤ ይረግፋልም፤
እንደ ጥላ ይፈጥናል፤ አይጸናም።
3እንደዚህ ባለ ሰው ላይ ዐይንህን
ታሳርፋለህን?
ለፍርድስ በፊትህ ታቀርበዋለህን?[ደ]
4ከርኩስ ነገር ውስጥ ንጹሕን ማን ሊያወጣ
ይችላል?
አንድ እንኳ የሚችል የለም!
5የሰው ዕድሜ አስቀድሞ የተወሰነ ነው፣
የወራቱንም ብዛት ወስነህ አስቀምጠሃል፤
ሊያልፈው የማይችለውንም ገደብ
አኖርህለት።
6እንግዲህ ዘመኑን እንደ ምንደኛ
እስኪፈጽም ድረስ፣
ፊትህን ከእርሱ መልስ፤ ተወው።

7"ዛፍ እንኳ ቢቈረጥ፣
እንደ ገና ሊያቈጠቍጥ፣
አዳዲስ ቅርንጫፍም ሊያበቅል ተስፋ
አለው።
8ሥሩ በምድር ውስጥ ቢያረጅ
ጉቶው በመሬት ውስጥ ቢበሰብስም፣

13፥2 ኢዮ12፥3
13፥3 ኢዮ5፥8፡ 17፤9፥14-20፥10፥2፤ 40፥2
13፥4 ኢዮ6፥15፤ መዝ119፥69፤ኢሳ9፥ 15፤ኤር8፥22፤23፥32
13፥5 ቆላ13፤መሳ 18፥19፤ምሳ17፥28
13፥6 ኢዮ33፥1፤ 36፥4
13፥7 ኢዮ12፥16፤ 16፥17
13፥8 ዘሌ19፥15
13፥9 ኢዮ9፥3፤ 12፥16፤ገላ6፥7
13፥10 ዘሌ19፥15፤ 2ዜና19፥7
13፥11 ዘፀ3፥6፤ኢዮ 31፥23
13፥12 ነህ4፥2-3
13፥13 ቆላ5፤ኢዮ 7፥11፤9፥21
13፥14 መሳ9፥17
13፥15 ኢዮ5፥8፤7፥ 6፤27፥5፤መዝ23፥4፤ 27፥1፤ምሳ14፥32፤ ኢሳ12፥2፤ዳን3፥28
13፥16 ዘፍ3፥8፤ ኢዮ8፥13፤መዝ30፥5፤ ኢሳ12፥1፤54፥7- 8፤ሆሴ14፥4፤ፊል1፥19
13፥17 ኢዮ21፥2
13፥18 ቆላ3፤ኢዮ2፥ 3፤9፥21፤23፥4፤ 37፥19
13፥19 ኢዮ3፥13፤ 9፥15፤10፥8፤40፥4፤ ኢሳ50፥8፤ሮሜ8፥33
13፥21 ዘፀ9፥3፤ኢዮ 6፥4፤ዕብ10፥31
13፥22 ኢዮ9፥16፡ 35፤14፥15
13፥23 1ሳሙ26፥ 18፤ኢዮ7፥21፤9፥21፤ 14፥17፤33፥9
13፥24 ዘዳ32፥20፤ ኢዮ16፥9፤19፥11፤ 33፥10መዝ88፥14-15፤ ኤር30፥14፤ሰቆ2፥5
13፥25 ዘሌ26፥36፤ ኢዮ19፥2፥22፥28፤ 21፥18፤መዝ1፥4፤35፥5 ፤83፥13፤ኢሳ17፥ 13፤42፥3፤43፥17፤ ሆሴ13፥3
13፥26 ኢዮ18፥7፤ 20፥11፤21፥23፤መዝ 25፥7
13፥27 ዘፍ40፥15፤ ኢዮ10፥14፤33፥11፤ ኤር20፥2፤ሐሥ16፥24
13፥28 ዘዳ28፥35፤ መዝ39፥11፤102፥26፤ ኢሳ50፥9፤51፥8፤ሆሴ 5፥12፤ማር2፥21፤ ያዕ5፥2
14፥1 ዘፍ3፥17፤ኢዮ 7፥2፤10፥20፤15፥14፤ ማቴ11፥11
14፥2 ኢዮ4፥20፥8፥ 9፤መዝ37፥2፤39፥4፤49፥12፤90፥5-6፤102፥ 11፤103፥15፤109፥23፤144፥4፤መክ6፥12፤ኢሳ40፥6-8፤ያዕ1፥10
14፥3 ኢዮ7፥18፤መዝ8፥4፤144፥3 14፥4 ኢዮ4፥17፤9፥30፤ መዝ51፥10፤ዮሐ3፥6፤ሮሜ5፥12፤7፥14፤ኤፌ2፥1-3 14፥5 ኢዮ 21፥21፤24፥1፤መዝ31፥15፤39፥4፤90፥12፥139፥16፤ሐሥ17፥26
14፥6 ኢዮ7፥1፥2፥19፤መዝ39፥13፤ኢሳ16፥14፤21፥16 14፥7 ኢዮ19፥10፤24፥20፤መዝ52፥5፤ ኢሳ6፥13፤11፥1፤53፥2፤60፥21
14፥8 ኢሳ6፥13፤ 11፥1፤53፥2

[የ]15 ወይም *በእርግጥ እርሱ ይገድለኛል፤ ተስፋ የለኝም፤ ይሁን እንጂ ...* [ደ]3 ሰብዓ ሊቃናት፣ ቩልጌትና ሱርስት እንዲሁ ሲሆን ዕብራስጡ ግን *ታቀርበኛለህን?* ይላል

[9]የውሃ ሽታ ባገኘ ጊዜ ያቈጠቍጣል፤
እንደ ተተከለም ችግኝ ቅርንጫፍ
ያወጣል።
[10]ሰው ግን ይሞታል፤ ክንዱንም
ይንተራሳል፤
ነፍሱም ትወጣለች፤ ከእንግዲህስ የት
ይገኛል?
[11]ውሃ ከባሕር ውስጥ እንደሚያልቅ፣
የወንዝ ውሃም ጠፍቶ እንደሚደርቅ፣
[12]እንደዚሁም ሰው ይተኛል ቀናም
አይልም፤
ሰማይ እስከሚያልፍ ድረስ አይነቃም፤
ከእንቅልፉም አይነሣም።

[13]"ምነው መቃብር[ጀ] ውስጥ በሰወርኸኝ!
ቍጣህም እስከሚያልፍ በሸሸግኸኝ!
ምነው ቀጠሮ ሰጥተህ፣
ከዚያ በኋላ ባስታወስኸኝ!
[14]ሰው ከሞተ በኋላ ተመልሶ በሕይወት
ይኖራል?
እድሳቴ[ገ] እስከሚመጣ ድረስ፣
ተጋድሎ የሞላበትን ዘመኔን ሁሉ
እታገሣለሁ።
[15]ትጠራኛለህ፤ እኔም እመልስልሃለሁ፤
የእጅህንም ሥራ ትናፍቃለህ።
[16]በዚያን ጊዜ በእርግጥ እርምጃዬን
ትከታተላለህ፤
ነገር ግን ኀጢአቴን አትቈጣጠርም።
[17]መተላለፌ በከረጢት ይቋጠራል፤
ኀጢአቴንም ትሸፍናለህ።

[18]"ተራራ እንደሚሸረሸርና
እንደሚወድቅ፣
ዐለትም ከስፍራው እንደሚወገድ፣
[19]ውሃ ድንጋይን እንደሚቦረቡር፣
ጐርፍም ዐፈርን አጥቦ እንደሚወስድ፣
አንተም የሰውን ተስፋ ታጠፋለህ።
[20]አንድ ጊዜ ፈጽመህ ትበረታለህ፤ እርሱም
ያልፋል፤
ገጽታውን ትቀይራለህ፤ ትሸኘዋለህም።
[21]ልጆቹ ቢከበሩ አያውቅም፤
ቢዋረዱም አያይም።
[22]የገዛ አካሉ ሕመም ብቻ ይሰማዋል፤
ለራሱም ብቻ ያለቅሳል።"

## ኤልፋዝ

# 15

ቴማናዊው ኤልፋዝ እንዲህ ሲል
መለሰ፤

[2]"ጠቢብ ሰው በከንቱ ንግግር መልስ
ይሰጣልን?
ወይስ በምሥራቅ ነፋስ ሆዱን ይሞላል?
[3]በማይረባ ቃል፣
ፍሬ ቢስ በሆነም ንግግር ይከራከራልን?
[4]አንተ ግን እግዚአብሔርን መፍራት
ታጣጥላለህ፤
አምልኮተ እግዚአብሔርን ትከለክላለህ።
[5]ኀጢአትህ አፍህን ታስተምረዋለች፤
የተንኰለኞችንም አነጋገር መርጠህ
ትይዛለህ።
[6]የሚፈርድብህ አንደበትህ እንጂ እኔ
አይደለሁም፣
የሚመሰክርብህም እኔ ሳልሆን የገዛ
ከንፈርህ ነው።

[7]"ለመሆኑ ከሰው ሁሉ ቀድመህ የተወለድህ
አንተ ነህን?
ወይስ ከኰረብቶች በፊት ተገኝተሃል?
[8]በእግዚአብሔር የመማክርት ጉባኤ ላይ
ነበርህን?
ጥበብስ የተሰጠው ለአንተ ብቻ ነው?
[9]እኛ የማናውቀው አንተ ግን የምታውቀው
ምን ነገር አለ?
እኛስ የሌለን አንተ ያለህ ማስተዋል የቱ
ነው?
[10]በዕድሜ ከአባትህ የሚበልጡ፣
የሸበቱ ሽማግሌዎች ከእኛ ጋር አሉ።
[11]የእግዚአብሔር ማጽናናት፣
በርጋታ የተነገረህ ቃል አነሰህን?
[12]ልብህ ለምን ይሸፍታል?
ዐይንህንስ ምን ያጕረጠርጠዋል?
[13]በእግዚአብሔር ላይ እንድትቈጣ፣
እንደዚህ ያለ ቃል ከአፍህ እንዲወጣ
ያደረገህ ምንድን ነው?

[14]"ንጹሕ ይሆን ዘንድ ሰው ምንድን ነው?
ጻድቅስ ይሆን ዘንድ፣ ከሴት የተወለደ
ምንድን ነው?
[15]እነሆ፤ እግዚአብሔር በቅዱሳኑ እንኳ
አይታመንም፤
ሰማያትም በእርሱ ፊት ንጹሓን
አይደሉም።
[16]ታዲያ፣ ክፋትን እንደ ውሃ የሚጠጣ!
አስጸያፊና ርኩስ ሰውማ እንዴት ይታመን!

[17]"አድምጠኝ፤ በግልጽ አስረዳሃለሁ፤
ያየሁትንም እነግርሃለሁ፤
[18]ጠቢባን ከአባቶቻቸው የተቀበሉትን፤
ሳይሸሽጉ የተናገሩትን አስረዳሃለሁ፤
[19]ምድሪቱ ለአባቶቻቸው ተሰጠች፤
በመካከላቸውም ባዕድ አልተቀመጠም፤
[20]ክፉ ሰው ዕድሜውን ሙሉ፣
ጨካኙም በተመደበለት ዘመን ሁሉ
ይሠቃያል።

14፥9 ዘሌ26፥4፤ ኢዮ29፥19፤መዝ1፥3፤ ኤር17፥8፤ሕዝ31፥7፤ 34፥27፤ዘካ10፥1
14፥10 ቍ12፤ኢዮ 10፥21፤13፥19
14፥11 2ሳሙ 14፥14
14፥12 ቍ10፤መዝ 102፤26፤ሐሥ3፥21፤ ራእ20፥11፤21፥1
14፥13 ዘፍ8፥1፤ ኢዮ6፥8፤7፥9፤መዝ 30፥5፤ኢሳ26፥20፤ 54፥7
14፥14 2ነገ6፥33፤ ኢዮ7፥1
14፥15 ኢዮ10፥3፤ 13፥22
14፥16 ኢ10፥4፥6፤ መዝ139፥1-3፤ምሳ5፥ 21፤ኤር16፥17፤32፥ 19፤1ቆሮ13፥5
14፥17 ዘዳ32፥34፤ ኢዮ9፥30፤13፥23፤ ኤር32፥10
14፥18 ኢዮ18፥ 4፤ሕዝ38፥20
14፥19 ዘፍ7፥23፤ ኢዮ7፥6፤ሕዝ13፥13
14፥20 ኢዮ4፥20፤ 7፥10፤8፥18፤12፥9፤ 27፥19፤ያዕ1፥10
14፥21 ኢዮ21፥21፤ መክ9፥5፤ኢሳ63፥16
14፥22 ኢዮ21፥21፤ መዝ38፥7፤ኢሳ21፥ 3፤ኤር4፥19
15፥1 ኢዮ4፥1
15፥2 ዘፍ41፥6
15፥3 ነህ4፥2-3፤ ኢዮ6፥26
15፥4 ኢዮ25፥6
15፥5 ኢዮ5፥13፤ 11፥6፤22፥5፤ምሳ 16፥23
15፥6 ኢዮ9፥15፤ 18፥7፤መዝ10፥2፤ማ ቴ12፥37፤ሉቃ19፥22
15፥7 1ሳሙ2፥8፤ ኢዮ38፥21፤መዝ90፥ 2፤ምሳ8፥25
15፥8 ኢዮ12፥2፤ 29፥4፤ኢሳ9፥6፤40፥ 13፤41፥28፤ኤር፥23፥1 8፤ሮሜ11፥34፤ 1ቆሮ2፥11
15፥9 ኢዮ12፥3
15፥10 2ዜና10፥ 6፤ኢዮ12፥12
15፥11 ዘፍ37፥35፤ ዘዳ8፥3፤32፥39፤ኢዮ 5፥17፤6፥10፤22፥22፤2 3፥12፤36፥16፤መዝ 119፥11፥72፤ኤር15፥ 16፤ዘካ1፥13፤2ቆሮ 1፥3-4
15፥12 ኢዮ11፥13፤ 36፥13
15፥13 ኢዮ11፥8፤ 22፥5፤32፥3፤
15፥21 ቍ24፤ 1ሳሙ3፥11፤ኢዮ18፥
መዝ94፥4፤ምሳ29፥11፤ዳን11፥30 15፥14 2ዜና6፥36፤ኢዮ4፥17፤ 14፥1 15፥15 ኢዮ4፥18፤5፥1 15፥16 ዘሌ5፥2፤ኢዮ4፥19፤12፥ 4፤20፥12፤34፥7፤መዝ14፥1፤ምሳ19፥28 15፥17 ኢዮ4፥8 15፥18 ዘዳ32፥7 15፥19 ዘፍ12፥1፤ኢዮ22፥8 15፥20 ቍ24፥ኢዮ24፥ 1፤27፥13-23፤ኢሳ 2፥12፤8፥22፤50፥11፤66፥24፤ኤር46፥10፤አብ 1፥15፤ሰፎ1፥7

[ጀ]13 በዕብራይስጥ ሲኦል ማለት ነው
[ገ]14 ወይም መፈታቴ

21የሚያስደነግጥ ድምፅ በጆሮው ላይ
ይጮኻል፤
በሰላም ጊዜ ቀማኞች አደጋ
ያደርሱበታል።
22ከጨለማ ወጥቶ ማምለጥ
ይፈራል፤
ለሰይፍም የተመደበ ነው።
23የአሞራ እራት[ጠ] ለመሆን ይቅበዘበዛል፤
የጨለማ ቀን መቅረቡን ያውቃል።
24ጭንቀትና ሐዘን ያስፈራሩታል፤
ለማጥቃት እንደ ተዘጋጀ ንጉሥም
ያይሉበታል፤
25እጁን በእግዚአብሔር ላይ አንሥቶአልና፤
ሁሉን የሚችለውን አምላክም ደፍሮአል፤
26ወፍራምና ጠንካራ ጋሻ አንግቦ፣
ሊቋቋመው ወጥቶአል።

27“ፊቱ በስብ ቢሸፈን፣
ሽንጡ በሥጋ ቢደነድንም፣
28መኖሪያው በፈራረሱ ከተሞች፣
የፍርስራሽ ክምር ለመሆን በተቃረቡ፣
ሰው በማይኖርባቸው ወና ቤቶች ውስጥ
ይሆናል።
29ከእንግዲህ ባለ ጠጋ አይሆንም፤ ሀብቱም
አይቈይም፤
ይዞታውም በምድር ላይ አይሰፋም።
30ከጨለማ አያመልጥም፤
ቅርንጫፎቹን ነበልባል ያደርቃቸዋል፤
በእግዚአብሔርም እስትንፋስ ይወሰዳል።
31በአጸፋው አንዳች አያገኝምና፤
ከንቱን ነገር በመታመን ራሱን
አያታልል።
32ጊዜው ሳይደርስ ይጠወልጋል፤
ቅርንጫፉም አይለመልምም።
33ፍሬው በጮርቃነት እንደ ተለቀመበት
የወይን ተክል፤
አበባውም እንደ ረገፈበት የወይራ ዛፍ
ይሆናል።
34የዐመፀኞች ጉባኤ ትመክናለች፤
የጉቦ ሱሰኞችም ድንኳን በእሳት
ትበላለች።
35መከራን ይፀንሳሉ፣ ክፋትንም ይወልዳሉ፤
በሆዳቸውም ተንኰል ይጠነስሳሉ።”

ኢዮብ

16 ኢዮብም እንዲህ ሲል መለሰ፤
2“ይህን የሚመስል ብዙ ነገር
ሰምቻለሁ፤
እናንተ ሁላችሁ የምታስጨንቁ
አጽናኞች ናችሁ።
3ይህ ከንቱ ንግግር አያልቅምን?
ትለፈልፍ ዘንድ የሚገፋፋህ ምንድን
ነው?
4እናንተ በእኔ ስፍራ ብትሆኑ ኖሮ፣
እኔም እንደ እናንተ መናገር እችል
ነበር፤
ቃላት አሳክቼ በመናገር፣
በእናንተ ላይ ራሴን መነቅነቅ በቻልሁ
ነበር።
5ይልቁንም አንደበቴ ባበረታታችሁ፣
የከንፈሬም ማጽናናት ባሳረፋችሁ ነበር።

6“ብናገር ሕመሜ አይሻለኝም፤
ዝም ብልም አይተወኝም።
7እግዚአብሔር ሆይ አሁንስ አድክመኸኛል፤
ወገኖቼንም ሁሉ አጥፍተሃል።
8ጭምትርትር ያደረግኸኝ ምስክር
ሆኖብኛል፣
ዐጥንቴን ያወጣው ክሳቴም ያጋልጠኛል።
9በቍጣው ሰነጠቀኝ፤ በጥላቻው
አስጨነቀኝ፣
ጥርሱን ነከሰብኝ፤
ባላጋራዬ ክፉ ዐይኑን ተከለብኝ።
10ሰዎች በፌዝ አፋቸውን ከፈቱብኝ፤
በንቀት ጕንጬን ጠፈጠፉኝ፤
በአንድነትም በላዬ ተሰበሰቡ።
11እግዚአብሔር ለክፉዎች አሳልፎ ሰጠኝ፤
በጠማሞችም እጅ ጣለኝ።
12በሰላም እኖር ነበር፤ እርሱ ግን ሰባበረኝ፤
ዐንገቴን ይዞ አደቀቀኝ፤
ማነጣጠሪያ ዒላማው አደረገኝ፤
13የእርሱ ቀስተኞች ከበቡኝ፤
ያለ ርኅራኄ ኵላሊቴን ይበጣጥሳል፤
ሐሞቴን መሬት ላይ ያፈሳል።
14ደጋግሞ ይቀጠቅጠኛል፤
እንደ ጦረኛም ተንደርድሮ ይመጣብኛል።

15“በቈዳዬ ላይ ማቅ ሰፍቻለሁ፤
ክብሬን በዐፈር ውስጥ ቀብሬአለሁ።
16ፊቴ ከልቅሶ የተነሣ ቀልቶአል፤
ጨለማም በዐይኖቼ ቆብ ላይ ዐርፎአል፤
17ነገር ግን በእጄ ዐመፅ አይገኝም፤
ጸሎቴም ንጹሕ ነው።

18“ምድር ሆይ፤ ደሜን አትሸፍኚ፤
ጩኸቴም ማረፊያ አያግኝ!

11፤20፥25፤22፥10፤27፥20፤ኢሳ13፥3፤ኤር6፥25፤20፥3፤51፥25፤53፥56፤1ተሰ5፥3
15፥22 ቍ23፤ኢዮ5፥14፤16፥13፤18፥19፤19፥29፤20፥24፤24፥17፤27፥14፤33፥18፤36፥12፤38፥15፤መዝ91፥5፤ምሳ7፥23፤ማሕ3፥8፤ኢሳ1፥20፤ኤር44፥27፤ሆሴ9፥13፤አሞ5፥19
15፥23 ቍ22፤ኢዮ18፥12፤መዝ109፥10፤ምሳ30፥17፤ሕዝ39፥17፤ማቴ24፥28፤ሉቃ17፥37
15፥24 ቍ20፤ኢዮ18፥14፤ኢሳ8፥22፤9፥1
15፥25 ኢዮ11፥8፤35፥12፤36፥9፤40፥8፤መዝ2፥2-3፤44፥16፤73፥9፤75፥5፤ምሳ21፥30፤ኢሳ3፥16፤10፥32፤37፥23፤45፥9
15፥26 ኤር44፥16
15፥27 መሳ3፥17
15፥28 ኢዮ3፥14፤ኢሳ5፥9
15፥29 ኢዮ3፥15፤7፥8፤ኢሳ5፥8 15፥30 ቍ32፡ 34፤ዘፀ15፥10፤ኢዮ5፥14፤8፥19፤16፥7፤18፥16፤20፥26፤22፥20፤29፥19፤31፥12፤ኢሳ40፥23-24፤ሆሴ9፥1-16፤ሚል4፥1
15፥31 ኢዮ20፥7፤22፥13፤27፥9፤31፥5፤35፥13፤ምሳ1፥16፤6፥18፤15፥29፤ኢሳ1፥15፤30፥12፤44፥20፤47፥10፤59፥4፡7፤ኤር7፥4፡8፤11፥11፤ሚክ2፥11፤3፥4፤ማቴ6፥19፤ማር13፥5፤ያዕ1፥16፤
15፥32 ቍ30፤ኢዮ22፥16፤36፥14፤መዝ55፥23፤109፥8፤ምሳ10፥27፤መክ7፥17
15፥33 ኢዮ4፥20፤ዕን3፥17
15፥34 ቍ30፤ዘፀ23፥8፤1ሳሙ8፥3፤ኢዮ8፥13፤ዕብ10፥27
15፥35 ኢዮ4፥8፤5፥7፤ኢሳ29፥20፤ገላ6፥7፤ያዕ1፥15
16፥2 ኢዮ6፥15፤መዝ69፥20
16፥3 ኢዮ6፥26፤11፥2፤18፥2
16፥4 2ነገ19፥21፤መዝ22፥7፤ኢሳ37፥22፤ኤር48፥27፤ሰቆ2፥15፤ሶፎ2፥15፤ማቴ27፥39
16፥5 ዘፍ37፥25፤ኢዮ29፥25 16፥6 ኢዮ6፥3፤7፥21 16፥7 መሳ8፥5፤ኢዮ1፥19፤ 7፥3
16፥8 ኢዮ10፥17፤17፥7፤19፥20፤33፥21፤መዝ6፥7፤22፥17፤88፥9፤102፥5፤109፥24፤ሰቆ5፥17 16፥9 ኢዮ9፥5፤12፥14፤13፥24፤18፥4፤19፥11፤30፥21፤መዝ35፥16፤37፥12፤112፥10፤ሰቆ2፥16፤ሆሴ6፥1፤ሐሥ7፥54 16፥10 ቍ7፤ኢዮ11፥3፤12፥4፤19፥12፡18፤21፥3፤30፥1፡9፡12፤መዝ22፥13፤27፥3፤35፥15፡21፤69፥12፤119፥51፤ኢሳ50፥6፤ሰቆ3፥30፤ሚክ5፥1፤ሐሥ7፥57፤23፥2 16፥11 ኢዮ9፥24
16፥12 ኢዮ6፥4፤ 9፥17፤ሰቆ3፥12 16፥13 ኢዮ3፥23፤20፥24፤ምሳ7፥23፤ሰቆ3፥13 16፥14 ኢዮ9፥17፤10፥3፤ኢል2፥7 16፥15 ዘፍ37፥34፤ ኢዮ2፥8 16፥16 ቍ20፤ኢዮ2፥7፤17፥7፤30፥17፡30፤33፥19፤መዝ6፥6፤ኢሳ52፥14 16፥17 ኢዮ6፥28፤10፥7፤13፥7፤ኢሳ53፥9፤55፥7፤59፥6፤ኤር18፥11፤ዮና3፥8፤ሰፎ3፥13 16፥18 ዘፍ4፥10፤ኢዮ19፥24፤መዝ5፥2፤18፥6፤66፥18-19፤102፥1፤119፥169፤ኢሳ26፥21፤ዕብ11፥4

[ጠ]23 ወይም ለአሞራ እራት ለመፈለግ

19አሁን እንኳ ምስክሬ በሰማይ አለ፤
ጠበቃዬም በላይ በአርያም ይገኛል።
20ወዳጆቼ በንቀት ቢመለከቱኝም፣[ጨ]
ዐይኔ ወደ እግዚአብሔር ያነባል።
21ሰው ለወዳጁ እንደሚማልድ፣
በእግዚአብሔር ፊት የሚማልድ ሰው ምነው
በተገኘ!

22"ከጥቂት ዓመታት በኋላ፣
ወደማልመለስበት መንገድ እሄዳለሁ።

# 17

መንፈሴ ደክሞአል፣
ዘመኔ አጥሮአል፤
መቃብርም ተዘጋጅቶልኛል።
2አላጋጮች ከበውኛል፤
ትኵረቴም ትንኰሳቸው ላይ ነው።

3"እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ተያዥ ሁነኝ፤
ከአንተ ሌላ ዋስ የሚሆነኝ ማን አለ?
4እንዳያስተውሉ ልባቸውን ይዘሃል፤
ስለዚህ ድል አትሰጣቸውም።
5ለጥቅም ሲል ወዳጁን የሚያወግዝ፣
የልጆቹ ዐይን ይታወራል።

6"እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ መተረቻ፣
ፊቱ ላይ የሚተፋበት ሰውም አደረገኝ።
7ዐይኔ ከሐዘን የተነሣ ፈዘዘ፤
መላ አካሌም እንደ ጥላ ሆነ።
8ቅኖች በዚህ ነገር ይደነግጣሉ፤
ንጹሓንም በዐመፀኞች ላይ ይነሣሉ።
9ጻድቃን ግን በያዙት መንገድ ይጸናሉ፤
ንጹሕ እጅ ያላቸውም እየበረቱ ይሄዳሉ።

10"ነገር ግን እናንተ ሁላችሁ፣
እስቲ ተመልሳችሁ እንደ ገና ሞክሩ!
ከመካከላችሁ አንድም ጠቢብ አላገኝም።
11ዕድሜዬ አለቀ፤ ዕቅዴም ከሸፈ፤
የልቤም ሐሳብ ከንቱ ሆነ።
12እነዚህ ሰዎች ሌሊቱን ወደ ቀን
ይለውጣሉ፤
ጨልሞም እያዩ፣ "ብርሃን ቀርቦአል"
ይላሉ።
13ተስፋ የማደርገው ቤት መቃብር[ጸ] ብቻ
ከሆነ፣
መኝታዬንም በጨለማ ካነጠፍሁ፣
14መበስበስን፣ 'አንተ አባቴ ነህ፤
ትልንም፣ 'አንቺ እናቴ' ወይም 'እኅቴ
ነሽ' ካልሁ፣
15ታዲያ፣ የእኔ ተስፋ ወዴት ነው?
ተስፋዬን የሚያይልኝስ ማን ነው?
16ወደ ሞት[ጸ] ደጅ ይወርዳልን?
አብረንስ ወደ ትቢያ እንሄዳለንን?"

## በልዳዶስ

# 18

ሹሐዊው በልዳዶስ እንዲህ ሲል
መለሰ፤
2"ይህን ንግግር የምትጨርሰው መቼ ነው?
እስኪ ልብ ግዛ፤ ከዚያ በኋላ
እንነጋገራለን።
3ለምን እንደ ከብት መንጋ እንቈጠራለን?
እንደ ደንቈሮስ ለምን ታየናለህ?
4አንተ በቍጣ የነደድህ እንደ ሆነ፣
ምድር ባዶዋን ትቀራለች?
ወይስ ዐለት ከሥፍራው ተነቅሎ
ይወሰዳል?

5"የክፉዎች መብራት ይጠፋል፤
የእሳቱም ነበልባል ድርግም ይላል።
6የድንኳኑ ብርሃን ይጨልማል፤
መብራቱም በላዩ ይጠፋል፤
7የርምጃው ብርታት ይደክማል፤
የገዛ ዕቅዱም ይጥለዋል።
8እግሩ በወጥመድ ይያዛል፤
በመረብም ይተበተባል።
9አሽክላ ተረከዙን ይይዘዋል፤
ወስፈንጥርም ያጣብቀዋል።
10በምድር ላይ የሸምበቆ ገመድ፣
በመንገዱም ላይ ወጥመድ በስውር
ይቀመጥለታል።
11ድንጋጤ በዙሪያው ያስፈራራዋል፤
ተከትሎም ያሳድደዋል።
12መቅሠፍት ሊውጠው ቀርቦአል፤
ጥፋትም የእርሱን ውድቀት
ይጠባበቃል።
13ደዌ ቈዳውን ይበላል፤
የሞት በኵርም ቅልጥሙን ይውጣል።
14ተማምኖ ከሚኖርበት ድንኳን ይነቀላል፤
ወደ ድንጋጤም ንጉሥ ይነዳል።
15ድንኳኑ በእሳት ይያያዛል፤[ፀ]
በመኖሪያውም ላይ ዲን ይበተናል።
16ሥሩ ከታች ይደርቃል፤
ቅርንጫፉም ከላይ ይረግፋል።
17መታሰቢያው ከምድር ገጽ ይጠፋል፤
ስሙም በአገር አይነሣም።
18ከብርሃን ወደ ጨለማ ይጣላል፤
ከዓለምም ይወገዳል።

16፥19 ዘፍ31፥50፤ኢዮ19፥27፤21፥17፤22፥12፤25፥2፤27፥13፤31፥2፤42፥2፤መዝ113፥5፤ኢሳ33፥5፤57፥15፤58፥4፤66፥1፤ማር11፥10፤ሮሜ1፥9፤1ተሰ2፥5
16፥20 ቍ16፤ሰቆ2፥19፤ዮሐ15፥15፤ሮሜ8፥34
16፥21 1ነገ8፥45፤መዝ9፥4፤140፥12
16፥22 ኢዮ10፥21
17፥1 መዝ88፥3-4፤143፥4፤መክ12፥1-7፤ኢሳ38፥12
17፥2 ኢዮ6፥14፤11፥3፤መዝ22፥7፤119፥51፥ኤር20፥7፤ሰቆ3፥14
17፥3 መዝ35፥2፡27፤40፥17፤119፥122፤ምሳ6፥1፤ኢሳ38፥14
17፥4 ኢዮ12፥12
17፥5 ዘፀ22፥15፤ኢዮ11፥20
17፥6 ቍ2፤ዘኍ12፥14፤1ነገ9፥7፤ኢዮ30፥9፤ኤር15፥4
17፥7 ኢዮ2፥12፤16፥8፥16
17፥8 ዘፀ4፥14
17፥9 1ሳሙ2፥4፤2ሳሙ22፥21፤ኢዮ9፥30፤መዝ84፥7፤ምሳ4፥18
17፥10 ኢዮ12፥2
17፥11 ቍ15፤ኢዮ7፥6፤ኢሳ38፥10
17፥12 ኢዮ5፥17-26፤11፥17፤ኢሳ50፥11
17፥13 2ሳሙ14፥14፤ኢዮ3፥13፤መዝ88፥18፤139፥8
17፥14 ኢዮ4፥19፤7፥5፤13፥28፤30፥28፡30፤መዝ16፥10፤49፥9
17፥15 ኢዮ7፥6፤መዝ31፥22፤ሰቆ3፥18፤ሕዝ37፥11
17፥16 ዘፍ2፥7፤ኢዮ3፥19፤7፥9፤20፥11፤21፥26፤33፥28፤መዝ9፥13፤30፥3፤107፥18፤ኢሳ38፥10፡17፤ዮና2፥6
18፥1 ኢዮ8፥1
18፥2 ኢዮ8፥2፤16፥3
18፥3 ኢዮ12፥7፤መዝ73፥22
18፥4 ኢዮ13፥14፤14፥18፤16፥9
18፥5 ኢዮ5፥14፤12፥25፤21፥17፤24፥17፤35፥15፤38፥15፤ምሳ13፥9፤20፥20፤24፥20፤ኤር25፥10፤ማቴ25፥8፤ዮሐ8፥12
18፥6 ኢዮ5፥14፤8፥22፤11፥17፤12፥25
18፥7 ኢዮ5፥13፤13፥26፤15፥6 18፥8 ኢዮ19፥6፤መዝ9፥15፤10፥9፤35፥7፤57፥6፤66፥11፤140፥5፤ሰቆ1፥13፤ሚክ7፥2፤ዕን1፥15
18፥9 ኢዮ22፥10፤30፥12፤ምሳ5፥22፤ኢሳ24፥18፤ኤር48፥44፤አሞ5፥19 18፥10 1ሳሙ28፥9፤መዝ140፥5፤ምሳ7፥22፤ኢሳ51፥20 18፥11 ቍ14፡18፤ኢዮ6፥4፤15፥21፤20፥8፡25፤24፥17፤መዝ31፥13፤55፥4፤88፥15፤ኢሳ22፥18፤28፥19፤ኤር15፥8፤ሰቆ2፥22
18፥12 ኢዮ15፥23፤21፥17፤31፥3፤ኢሳ8፥21፤9፥20፤65፥13 18፥13 ዘኍ12፥12፤ዘካ14፥12 18፥14 ቍ11፤ኢዮ8፥22፤15፥ 24
18፥15 ቍ18፤ዘፍ19፥24፤ኢዮ20፥26 18፥16 ዘፍ27፥28፤ ኢዮ8፥12፤15፥30፤ኢሳ5፥24፤ሆሴ5፥12፤አሞ2፥9 18፥17 ዘዳ9፥14፤32፥26፤ኢዮ24፥20፤መዝ9፥5፤34፥16፤69፥28፤ምሳ2፥22፤10፥7፤ኢሳ14፥22፤49፥15 18፥18 ቍ11፤ኢዮ5፥14፤11፥20፤30፥8

[ጨ]20 ወይም ወዳጆቼ አማላጅ ቢሆኑልኝም
[ጸ]13 በዕብራይስጡ፣ ሲኦል ይላል
[ጸ]16 በዕብራይስጡ፣ ሲኦል ይላል
[ፀ]15 ወይም ምንም አይተርፍለትም ማለት ነው

[19]በሕዝቡ መካከል ልጅ ወይም ዘር
አይኖረውም፤
በኖረበትም አገር ተተኪ አያገኝም።
[20]ባጋጠመው ሁኔታ የምዕራብ ሰዎች
ይደነግጣሉ፤
የምሥራቅም ሰዎች በፍርሀት ይዋጣሉ።
[21]በእርግጥ የክፉ ሰው መኖሪያ፣
እግዚአብሔርንም የማያውቅ ሰው መድረሻ
ይህ ነው።"

## ኢዮብ

**19** ኢዮብም እንዲህ ሲል መለሰ፤
[2]"ነፍሴን የምታስጨንቋት፣
በቃልስ የምትደቍሱኝ እስከ መቼ ነው?
[3]እነሆ፤ ዐሥር ጊዜ ዘለፋችሁኝ፤
ያለ ዕፍረትም በደላችሁኝ።
[4]በእውነት ተሳስቼ ከሆነ፣
ስሕተቱ የራሴ ጕዳይ ነው።
[5]ነገር ግን ራሳችሁን በእኔ ላይ ከፍ
ብታደርጉ፣
መዋረዴንም እኔን ለመሞገት
ብትጠቀሙበት፣
[6]እግዚአብሔር እንደ በደለኝ፣
በመረቡም እንደ ከበበኝ ዕወቁ።

[7]" 'ተበደልሁ!' ብዬ ብጮኽ ማንም
አይመልስልኝም፤
ድምፄን ከፍ አድርጌ ባሰማም፣ ፍትሕ
አላገኝም።
[8]እንዳላልፍ መንገዴን ዘግቶአል፤
መሄጃዬንም በጨለማ ጋርዶአል።
[9]ክብሬን ገፍፎኛል፤
ዘውዴንም ከራሴ ላይ ወስዶአል።
[10]እስክወገድ ድረስ በሁሉ አቅጣጫ
አፈራርሶኛል፤
ተስፋዬንም እንደ ዛፍ ነቅሎታል።
[11]ቍጣው በላዬ ነዶአል፤
እንደ ጠላቱም ቈጥሮኛል።
[12]ሰራዊቱ ገፍተው መጡ፤
በዙሪያዬ ምሽግ ሠሩ፤
ድንኳኔንም ከበው ሰፈሩ።

[13]"ወንድሞቼን ከእኔ አርቆአል፤
ከሚያውቁኝም ተገለልሁ።
[14]ዘመዶቼ ትተውኛል፤
ወዳጆቼም ረስተውኛል።
[15]የቤቴ እንግዶችና ሴት አገልጋዮቼ
እንደ
መጻተኛ ቈጠሩኝ፤
እንደ ባዕድም ተመለከቱኝ፤
[16]አገልጋዬን ብጣራ፣
በአንደበቴም ብለምነው፣
አይመልስልኝም።
[17]እስትንፋሴ ለሚስቴ እንኳ የሚያስጠላት
ሆነ፤
የገዛ ወንድሞቼም ተጸየፉኝ።
[18]ሕፃናት እንኳ ይንቁኛል፤
ባዩኝም ቍጥር ያላግጡብኛል።
[19]የቅርብ ወዳጆቼ ሁሉ ተጸየፉኝ፤
የምወዳቸውም በላዬ ተነሡ፤
[20]ቈዳና ዐጥንት ብቻ ሆኜ ቀረሁ፤
ድድ ብቻ ቀርቶልኝ አመለጥሁ።

[21]"ወዳጆቼ ሆይ፤ ራሩልኝ፤
የእግዚአብሔር እጅ መታኛለችና
ዕዘኑልኝ።
[22]እግዚአብሔር እንዳሳደደኝ ለምን
ታሳድዱኛላችሁ?
አሁንም ሥጋዬ አልበቃችሁምን?

[23]"ምነው ቃሌ በተጻፈ ኖሮ!
በመጽሐፍም በታተመ!
[24]ምነው በብረትና በእርሳስ በተጻፈ ኖሮ!
በዐለትም ላይ በተቀረጸ!
[25]የሚቤዠኝ ሕያው እንደ ሆነ፣
በመጨረሻም በምድር ላይ
እንደሚቆም ዐውቃለሁ።
[26]ቈዳዬ ቢጠፋም፣
ከሥጋዬ ብለይም፣ እግዚአብሔርን አየዋለሁ፤
[27]ሌላ ሳይሆን እኔው በገዛ ዐይኔ፣
እኔ ራሴ አየዋለሁ፤
ልቤ በውስጤ ምንኛ ዛለ!

[28]" 'የችግሩ መንሥኤ በውስጡ[ሖ] አለ፤
እኛ እንዴት እናሳድደዋለን?' ብትሉ፣
[29]ቍጣ በሰይፍ መቀጣትን ያስከትላልና፣
ራሳችሁ ሰይፍን ፍሩ፤
በዚያን ጊዜ ፍርድ[ፐ] እንዳለ
ታውቃላችሁ።"

## ሶፋር

**20** ናዕማታዊውም ሶፋር እንዲህ ሲል
መለሰ፤
[2]"እጅግ ታውኬአለሁና፣
ሐሳቤ መልስ እንድሰጥ ይጐተጕተኛል።
[3]የሚያቃልለኝን ንግግር ሰምቼአለሁ፤
መልስም እሰጥ ዘንድ መንፈሴ ገፋፋኝ።

[4]"ሰው[ሀ] በምድር ላይ ከተቀመጠ ጊዜ
ጀምሮ፣

**18፥19** 2ነገ10፥11፤ኢዮ27፥14-15፤መዝ21፥10፤37፥28፤109፥13፤ኢሳ14፥20፤22፤ኤር22፥30፤ሕዝ17፥8 **18፥20** መዝ22፥6-7፤37፥13፤ኢሳ52፥14፤53፥2-3፤ኤር46፥21፤50፥27፤31፤ሕዝ7፥7፤27፥35 **18፥21** ኢዮ4፥21፤7፥10፤21፥28፤ኢሳ57፥20፤1ተሰ4፥5 **19፥2** ኢዮ6፥9፤13፥25 **19፥3** ዘፍ31፥7፤ኢዮ20፥3 **19፥4** ኢዮ6፥24 **19፥5** መዝ35፥26፤38፥16፤55፥12 **19፥6** ኢዮ6፥29፤10፥3፤18፥8 **19፥7** ኢዮ9፥24፤30፥20፤24፤28፤31፥35፤መዝ5፥2፤22፥2፤ዕን1፥2-4 **19፥8** ኢዮ3፥26፤23፥17፤30፥26፤መክ6፥4፤ኢሳ59፥9፤ኤር8፥15፤14፥19፤ሰቆ3፥2፤7፤ሆሴ2፥6 **19፥9** ዘፍ43፥28፤ዘፀ12፥42፤ኢዮ2፥8፤12፥17፤29፥14፤መዝ15፥4፤50፥23፤89፥39፤44፤ምሳ14፥31፤ ሰቆ5፥16 **19፥10** ኢዮ7፥6፤12፥14፤14፥7 **19፥11** ኢዮ13፥24፤ 16፥9 **19፥12** ኢዮ3፥23፤16፥10፤13 **19፥13** ቍ19፤ኢዮ16፥7፤42፥11፤መዝ31፥11፤38፥11፤69፥8፤88፥8 **19፥14** ቍ19፤2ሳሙ15፥12፤ኢዮ12፥4፤16፥20፤መዝ88፥18፤ኤር20፥10፤38፥22 **19፥15** ዘፍ14፥14፤መክ2፥7 **19፥17** መዝ38፥5 **19፥18** 2ነገ2፥23፤ኢዮ16፥10 **19፥19** ቍ13፥14፤ኢዮ6፥14፤30፥10፤መዝ55፥12-13፤ዮሐ13፥18 **19፥20** ኢዮ2፥5 **19፥21** መሳ2፥15፤ኢዮ4፥5፤6፥14፤10፥3፤ሰቆ3፥1 **19፥22** ቍ6፤2ዜና8፥9፤ኢዮ13፥25፤መዝ14፥4፤27፥2፤69፥26፤ምሳ30፥14፤ኢሳ53፥4 **19፥23** ዘፀ17፥14፤መዝ40፥7፤ኢሳ8፥1 **19፥24** ኢዮ16፥18፤ኤር17፥1 **19፥25** ዘፀ6፥6፤ዘሌ25፥25፤1ሳሙ14፥39፤ኢዮ16፥19፤መዝ68፥5፤78፥35፤ምሳ23፥11፤ኢሳ41፥14፤43፥14፤44፥6፤24፤47፥4፤48፥17፤49፥26፤54፥5፤59፥20፤60፥16 **19፥26** ዘኍ12፥8፤ማቴ5፥8፤1ቆሮ13፥12፤1ዮሐ3፥2 **19፥27** መዝ42፥1፤63፥1፤84፥2፤ሉቃ2፥30 **19፥28** ኢዮ13፥25 **19፥29** ኢዮ15፥22፤27፥13-23፤መዝ1፥5፤9፥7፤58፥11፤መክ3፥17፤11፥9፤ 12፥14 **20፥1** ኢዮ2፥11 **20፥2** መዝ42፥5፤ሰቆ1፥20 **20፥3** ኢዮ19፥3 **20፥4** ዘዳ4፥32፤32፥7

[ሖ]28 አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕምና ቩልጌት፣ *በእኔ* ይላሉ
[ፐ]29 ወይም *ሁሉን ቻዩን ታውቃላችሁ* ማለት ነው
[ሀ]4 ወይም *አዳም* ማለት ነው

ከጥንቱ እንዴት እንደ ነበረ
ታውቃለህን?
5የኃጢአተኞች መፈንጨት ለአጭር ጊዜ፣
የክፉዎችም ደስታ ለቅጽበት መሆኑን
አታውቅምን?
6እስከ ሰማይ ከፍ ከፍ ቢልም፣
ዐናቱም ደመናትን ቢነካ፣
7እንደ ኵበት ለዘላለም ይጠፋል፤
ቀድሞ ያዩትም፣ ‘የት ገባ?’ ይላሉ።
8እንደ ሕልም በሮ ይጠፋል፤ አይገኝምም፤
እንደ ሌሊትም ራእይ በቅጽበት
ያልፋል።
9ቀድሞ ያየው ዐይን ዳግመኛ አያየውም፤
የነበረበትም ቦታ ከእንግዲህ
አይመለከተውም።
10ልጆቹ ለድኾች ካሣ መክፈል አለባቸው፤
እጆቹም ሀብቱን መልሰው መስጠት
ይገባቸዋል።
11ዐጥንቱን የሞላው የወጣትነት ብርታት፣
ከእርሱ ጋር በዐፈር ውስጥ ይተኛል።

12“ክፋት በአፉ ውስጥ ቢጣፍጥ፣
ከምላሱም በታች ቢደብቀው፣
13አውጥቶ ለመጣል እየሳሳ፣
በአፉ ውስጥ ቢያቈየው፣
14ምግቡ በሆዱ ውስጥ ይመራል፤
በውስጡም እንደ እባብ መርዝ ይሆናል።
15የዋጠውን ሀብት ይተፋል፤
እግዚአብሔርም መልሶ ከሆዱ ያወጣዋል።
16የእባብ መርዝ ይጠባል፤
የእፉኝትም ምላስ ይገድለዋል።
17ማርና ቅቤ በሚያፈሱ ጅረቶች፣
በወንዞችም አይደሰትም።
18የለፋበትን ሳይበላው ይመልሳል፤
ከንግዱም ባገኘው ትርፍ አይደሰትም፤
19ድኾችን በመጨቈን ባዶ
አስቀርቶአቸዋልና፣
ያልሠራውንም ቤት ነጥቆአል።

20“ክፉ ምኞቱ ዕረፍት አይሰጠውም
ሀብቱም ሊያድነው አይችልም።
21ያለውን አሟጦ ስለሚበላ፣
ዘላቂ ብልጽግና አይኖረውም።
22በተድላ መካከል እያለ ጒስቍልና
ይመጣበታል፤
በከባድ መከራም ይዋጣል።
23ሆዱን በሞላ ጊዜ፣
እግዚአብሔር የሚነድ ቍጣውን
ይሰድበታል፤
መዓቱንም ያወርድበታል።
24ከብረት መሣሪያ ቢሸሽም፣
የናስ ቀስት ይወጋዋል።
25ቀስቱን ከጀርባው፣
የሚያብለጨልጨውንም ጫፍ ከጒበቱ
ይመዛል፤
ፍርሀትም ይይዘዋል፤
26ሀብቱ ለድቅድቅ ጨለማ ተዳርጎአል፤
ሰው ባላራገበው እሳት ይበላል፤
በድንኳኑም ውስጥ የተረፈውን ይልሳል።
27ሰማያት ኀጢአቱን ይገልጡበታል፤
ምድርም ትነሣበታለች፤
28በእግዚአብሔር የቍጣ ቀን ቤቱን ጐርፍ፣
መኖሪያውንም ወራጅ ውሃ^
ይወስድበታል።
29እግዚአብሔር ለኀጢአተኞች የወሰነው ዕድል
ፈንታ፣
ከአምላክም ዘንድ የተመደበላቸው ቋሚ
ቅርስ ይህ ነው።”

## ኢዮብ

21 ኢዮብም እንዲህ ሲል መለሰ፤
2“ቃሌን በጥንቃቄ ስሙ፤
የምታጽናኑኝም በዚህ ይሁን፤
3ንግግሬን በትዕግሥት አድምጡ፤
ከተናገርሁ በኋላ፣ መሣለቅ ትችላላችሁ።

4“በውኑ ቅርታዬ በሰው ላይ ነውን?
ትዕግሥት ማጣትስ አይገባኝምን?
5ተመልከቱኝና ተገረሙ፤
አፋችሁን በእጃችሁ ለጒሙ።
6ስለዚህ ነገር ባሰብሁ ቍጥር
እደነግጣለሁ፤
ሰውነቴም በፍርሀት ይንቀጠቀጣል።
7ኀጢአተኞች ለምን በሕይወት ይኖራሉ?
ለምን ለእርጅና ይበቃሉ? ለምንስ
እያየሉ ይሄዳሉ?
8ዘራቸው በዐይናቸው ፊት፣
ልጆቻቸውም በዙሪያቸው ጸንተው ሲኖሩ
ያያሉ፤
9ቤታቸው ያለ ሥጋት በሰላም ይኖራል፤
የእግዚአብሔርም በትር የለባቸውም።
10ኮርማቸው ዘሩ በከንቱ አይወድቅም፤
ያስረግዛል፤
ላማቸውም ሳትጨነግፍ ትወልዳለች።
11ልጆቻቸውን እንደ በግ መንጋ ያሰማራሉ፤
ሕፃናታቸውም ይቦርቃሉ።
12በከበሮና በክራር ይዘፍናሉ፤
በዋሽንትም ድምፅ ይፈነጫሉ።

20፥5 ኢዮ8፥12፡13፤መዝ37፥35-36፤73፥19፤94፥3
20፥6 ዘፍ11፥4፤ኢዮ33፥17፤ኢሳ14፥13-14፤16፥6፤አብ1፥3-4
20፥7 ኢዮ4፥20፤7፥8፤14፥20
20፥8 ኢዮ18፥11፤27፥20፤34፥20፤መዝ73፥20፤90፥5፡10፤መክ5፥3፤6፥12፤12፥7፤ኢሳ17፥14፤29፥7
20፥9 ኢዮ7፥8
20፥10 ቍ15፡18፡20፤ኢዮ3፥15፤5፥4፤31፥8
20፥11 ኢዮ13፥26፤17፥16፤21፥24
20፥12 ኢዮ15፥16፤መዝ10፥7፤140፥3
20፥13 ዘኍ11፥18-20
20፥14 ዘኍ21፥6፤ምሳ 20፥17፤ኤር2፥19፤4፥18፤ራእ10፥9
20፥15 ቍ10፤ዘሌ18፥25
20፥16 ዘዳ32፥24፡32
20፥17 ዘዳ32፥13፡14፤ኢዮ29፥6፤መዝ36፥8
20፥18 ቍ10፤ኢዮ5፥5፤መዝ109፥11
20፥19 ዘዳ15፥11፤24፥14፤ኢዮ5፥16፤24፥4፡14፤35፥9፤መዝ10፥2፤94፥6፤109፥16፤ምሳ14፥31፤28፥28፤ኢሳ5፥8፤አሞ8፥4
20፥20 ቍ10፤ምሳ11፥4፤መክ5፥12፤ሰፎ1፥18፤ሉቃ12፥15
20፥21 ኢዮ7፥8
20፥22 ቍ29፤መሳ2፥15፤ኢዮ21፥17፡30፤31፥2-3፤ሉቃ12፥16-20
20፥23 ቍ14፤ዘኍ11፥18-20፤መዝ78፥30-31፤ሰቆ4፥11፤ሕዝ5፥13፤6፥12
20፥24 ኢዮ15፥22፤ኢሳ24፥18፤ኤር46፥21፤48፥44
20፥25 ኢዮ15፥21፤18፥11፤መዝ88፥15-16
20፥26 ኢዮ1፥16፤5፥14፤15፥34፤18፥15፤26፥6፤28፥22፤31፥12፤መዝ21፥9
20፥27 ዘዳ31፥28
20፥28 ቍ29፤ዘኍ14፥28-32፤ዘዳ28፥31፤ኢዮ21፥17፡20፡30፤40፥11፤መዝ60፥3፤75፥8፤ምሳ16፥4፤ኢሳ24፥18፤51፥17፤አሞ5፥18፤ማቴ7፥26-27፤ዮሐ3፥36፤ሮሜ1፥18፤ኤፌ5፥6
20፥29 ቍ22፤ኢዮ15፥20፤22፥5፤31፥2፤36፥17፤ኤር13፥25፤ራእ21፥8
21፥2 ቍ34፤ኢዮ13፥17
21፥3 ኢዮ6፥14፤11፥3፤16፥10
21፥4 ኢዮ6፥3፤7፥11
21፥5 መሳ18፥19
21፥6 ዘፍ45፥3፤ኢዮ4፥14
21፥7 ቍ13፤ኢዮ9፥24፤12፥19፤መዝ37፥1፤73፥3፤መክ7፥15፤8፥14፤ዕን1፥13፤ሚል3፥15
21፥8 መዝ17፥14፤ሚል3፥15
21፥9 ኢዮ5፥24፤9፥34
21፥10 ዘፀ23፥26
21፥11 መዝ78፥ 52፤107፥41
21፥12 ዘፍ4፥21፤1ዜና15፥16፤መዝ33፥2፤71፥22፤81፥2፤108፥2፤ኢሳ5፥12፤ማቴ11፥17

^28 ወይም *በቤቱ ውስጥ ያለውን ንብረት ወራጅ ውሃ ይወስድበታል* ማለት ነው

13ዕድሜያቸውን በተድላ ያሳልፋሉ፤
በሰላምም[ሐ] ወደ መቃብር[መ] ይወርዳሉ።
14እግዚአብሔርንም እንዲህ ይሉታል፤
'አትድረስብን!
መንገድህንም ማወቅ አንፈልግም።
15እናገለግለው ዘንድ፣ ሁሉን ቻይ አምላክ
ማን ነው?
ወደ እርሱ ብንጸልይስ ምን እናገኛለን?'
16ይሁንና ብልጽግናቸው በእጃቸው አይደለም፤
ከኀጢአተኞች ምክር እርቃለሁ።

17"የኀጢአተኞች መብራት የጠፋው ስንት
ጊዜ ነው?
የእግዚአብሔር ቍጣ መከራ የመጣባቸው፣
መቅሠፍትም የደረሰባቸው ስንት ጊዜ
ነው?
18በነፋስ ፊት እንዳለ ገለባ፣
በዐውሎ ነፋስም እንደ ተወሰደ ዕብቅ
የሆኑት ስንት ጊዜ ነው?
19እናንተ፣ 'እግዚአብሔር የሰውን ቅጣት
ለልጆቹ ያከማቻል' ትላላችሁ፤
ነገር ግን ያውቀው ዘንድ ለሰውየው
ለራሱ ይክፈለው፤
20ዐይኖቹ የራሱን ውድቀት ይዩ፤
ሁሉን ከሚችል አምላክ[ሠ] ቍጣ ይጠጣ።
21ሰው ወራቱ በተገባደደ ጊዜ፣
ለቀሪ ቤተ ሰቡ ምን ይገደዋል?

22"ከፍ ባሉት ላይ ለሚፈርድ አምላክ፣
ዕውቀትን ሊያስተምረው የሚችል አለን?
23አንድ ሰው በፍጹም ተድላ ደስታ
እየኖረ፣
በሙሉ ብርታቱም እያለ ይሞታል፤
24ሰውነቱ[ረ] በምቾት፣
ዐጥንቱም በስብ ተሞልቶ እያለ በሞት
ይለያል።
25ሌላው ሰው ደግሞ አንዳች መልካም ነገር
ሳያይ፣
በተመረረች ነፍስ ይሞታል፤
26ሁለቱም በዐፈር ውስጥ አንድ ላይ
ይተኛሉ፤
ትልም ይወርሳቸዋል።

27"እነሆ፣ ምክራችሁን፣
በእኔ ላይ ያሤራችሁትንም
ተረድቻለሁ።
28እናንተ፣ 'የትልቁ ሰው ቤት፣
ኀጢአተኛውም የኖረበት ድንኳን የት
አለ?' አላችሁ፤
29መንገደኞችን አልጠየቃችሁምን?
የነገሯችሁንስ ነገር በጥሞና
አላዳመጣችሁምን?
30ክፉ ሰው በመቅሠፍት ቀን
እንደሚጠበቅ፣
በቍጣም ቀን እንደሚተርፍ[ሰ]
አታውቁምን?
31ተግባሩን ፊት ለፊት የሚነግረው ማን
ነው?
የእጁንስ ማን ይሰጠዋል?
32ወደ መቃብር ይወስዱታል፤
ለመቃብሩም ጠባቂ ይደረግለታል።
33የሸለቈው ዐፈር ምቹ ይሆንለታል፤
ሰው ሁሉ ይከተለዋል፤
ስፍር ቍጥር የሌለው ሕዝብ[ሸ] በፊቱ
ይሄዳል።

34"መልሳችሁ ከሐሰት በስተቀር ሌላ
አይገኝበትም፤
ታዲያ፣ በማይረባ ነገር እንዴት
ልታጽናኑኝ ትችላላችሁ!"

## ኤልፋዝ

22 ቴማናዊውም ኤልፋዝ እንዲህ ሲል
መለሰ፤

2"ሰው እግዚአብሔርን ሊጠቅም ይችላልን?
ጠቢብ እንኳ ቢሆን ምን ይጠቅመዋል?
3አንተ ጻድቅ ብትሆን ሁሉን የሚችለውን
አምላክ ምን ደስ ታሰኘዋለህ?
መንገድህ ያለ ነቀፋ ቢሆንስ
የሚተርፈው ምንድን ነው?

4"እርሱ የሚገሥጽህ፣
ፍርድ ቤትም የሚያቀርብህ
ስለምትፈራው ነውን?
5ክፋትህ ታላቅ፣
ኀጢአትህ ፍጻሜ የሌለው አይደለምን?
6ያለ አንዳች ምክንያት ከወንድሞችህ
መያዣ ወስደሃል፤
ሰዎችን ገፈህ፣ ያለ ልብስ
ዕራቍታቸውን አስቀርተሃል።
7የዛሉትን ውሃ አላጠጣህም፤
የተራቡትንም ምግብ ከልክለሃል።
8ባለ ርስትና ኀያል፣
በእርሱም የምትኖር ክቡር ሰው ብትሆንም፣
9መበለቶችን ባዶ እጃቸውን ሰደሃል፤
የድኻ ዐደጎችንም ክንድ ሰብረሃል።
10ድንገተኛ አደጋ ያናወጠህ፤
ወጥመድም ዙሪያህን የከበበህ ለዚህ ነው።

21÷13 ቆላ7፤ኢዮ3÷13፤8÷7፤24÷19፤መዝ10÷1-12፤49÷14፤94÷3፤ኢሳ14÷15
21÷14 ዘጸ32÷15፤1ሳሙ15÷11፤ኢዮ4÷17፤22÷17፤መዝ95÷10፤ምሳ1÷29፤ኢሳ30÷11፤ኤር2÷20፡31
21÷15 ኢዮ5÷2፤34÷9፤35÷3፤መዝ73÷13፤139÷20፤ኢሳ48÷5፤ኤር9÷6፤44÷17
21÷16 ኢዮ22÷18÷መዝ1÷1፤26÷5፤36÷1
21÷17 ኢዮ18÷5፡12፤20÷22፡28
21÷18 ዘፍ7÷23፤19÷15፤ኢዮ7÷10፤13÷25፤ምሳ10÷25
21÷19 ዘፀ20÷5፤ኤር25÷14፤31÷29፤50÷29፤51÷6፡24፡56፤ሕዝ18÷2፤ዮሐ9÷2
21÷20 ዘፀ32÷33፤ዘኍ16÷22፤2ነገ14÷6፤ኢዮ6÷4፤20÷28፤ኤር25÷15፤42÷16፤ራእ14÷10
21÷21 ኢዮ14÷5፡21፡22፤መክ9÷5-6
21÷22 ኢዮ4÷18፤35÷11፤36÷22፤39÷17፤መዝ82÷1፤86÷8፤94÷12፤135÷5፤ኢሳ40÷13-14፤ኤር32÷33፤ሮሜ11÷34
21÷23 ዘፍ15÷15፤ኢዮ3÷13፤13÷26
21÷24 ኢዮ20÷11፤መዝ73÷4፤ምሳ3÷8
21÷25 ኢዮ10÷1
21÷26 ኢዮ7÷5፤17÷16፤24÷20፤መክ9÷2-3፤ኢሳ14÷11
21÷28 ኢዮ1÷3፤8÷22፤12÷21፤29÷25፤31÷37
21÷30 ኢዮ20÷22፡28፤31÷3፤ኢሳ5÷30፤ሮሜ2÷5፤2ጴጥ2÷9
21÷31 ኢዮ34÷11፤መዝ62÷12፤ምሳ24÷11-12÷ኢሳ59÷18
21÷32 ኢሳ14÷18
21÷33 ኢዮ3÷19፡22
21÷34 ቆላ2፤ኢዮ6÷15፤8÷20
22÷1 ኢዮ4÷1
22÷2 ኢዮ7÷17፤ሉቃ17÷10
22÷3 ኢዮ35÷7፤መዝ143÷2፤ምሳ9÷12፤ኢሳ1÷11፤ሐጌ1÷8
22÷4 ኢዮ9÷3፤19÷29፤መዝ143÷2፤ኢሳ3÷14፤ሕዝ20÷35
22÷5 ዕዝ9÷13፤ኢዮ15÷5፡13፤20÷29፤29÷17
22÷6 ዘፀ22÷26፡27፤ዘዳ24÷12-13፤2ነገ4÷1 22÷7 ቆላ9፤ኢዮ29÷12፤31÷17፡21፡31፤ኢሳ58÷7፡10፤ሕዝ18÷7፤ማቴ10÷42፤25÷42 22÷8 ኢዮ12÷19፤15÷19፤ኢሳ3÷3፤5÷13፤9÷15 22÷9 ቆላ7፤ኢዮ6÷27፤24÷3፡21፤29÷13፤31÷16፤መዝ146÷9፤ኢሳ1÷17፤10÷2፤ሉቃ1÷53
22÷10 ኢዮ10÷3፤15÷21፤18÷9
22÷11 ዘፍ7÷23፤

[ሐ]13 በዕብራይስጡ፣ *ሲኦል* ይላል
[መ]13 ወይም *በፍጥነት* ማለት ነው
[ሠ]17-20፤ ቍ 17:18 ቃለ አጋኖዎች ሲሆኑ ቍ 19:20 ደግሞ ብያኔዎች ናቸው።
[ረ]24 የዚህ ቃል የዕብራይስጡ ትርጒም በትክክል አይታወቅም
[ሰ]30 ወይም *ለመቅሠፍት ቀን ተጠብቆ እንደሚቈይ* ማለት ነው
[ሸ]33 ወይም *ስፍር ቍጥር እንደ ሌለው ሕዝብ* ማለት ነው

11እንዳታይ ጨለማ የሆነብህ፣
ጐርፍም ያጥለቀለቀህ ለዚህ ነው።

12“እግዚአብሔር ከፍ ባለው ሰማይ የሚኖር
አይደለምን?
በሩቅ ከፍታ ያሉትን ከዋክብት ያያል!
13ይህም ሆኖ ሳለ እንዲህ አልህ፤ ‘እግዚአብሔር
ምን ያውቃል?
በእንዲህ ያለ ጨለማ ውስጥስ ይፈርዳልን?
14በሰማይ ክበብ ላይ ሲራመድ፣
እንዳያየን ጥቅጥቅ ያለ ደመና ይሸፍነዋል።’
15ኀጢአተኞች በሄዱባት፣
በጥንቷ መንገድ እንደ ተመላለስህ
ትቀራለህን?
16ጊዜያቸው ሳይደርስ ተነጠቁ፤
መሠረታቸውም በጐርፍ ተወሰደ።
17እግዚአብሔርንም ‘አትድረስብን!
ሁሉን የሚችል አምላክም ምን
ያደርግልናል?’ አሉ።
18ቤታቸውን በመልካም ነገር የሞላው ግን
እርሱ ነው፤
ስለዚህ ከኀጢአተኞች ምድር እርቃለሁ።

19“ጻድቃንም የእነዚያን ጥፋት አይተው
ይደሰታሉ፤
ንጹሓንም እንዲህ ብለው ያፌዙባቸዋል፤
20በእርግጥ ጠላቶቻችን ጠፍተዋል፤
ሀብታቸውም በእሳት ተበልቶአል።’

21“ለእግዚአብሔር ተገዛ፤ ከእርሱም ጋር ሰላም
ይኑርህ፤
በረከትም ታገኛለህ።
22ምክርን ከአፉ ተቀበል፤
ቃሉንም በልብህ አኑር።
23ሁሉን ወደሚችል አምላክ ብትመለስ
ትጠገናለህ፤
ክፋትን ከድንኳንህ ብታርቅ፣
24የወርቅህን እንክር ትቢያ ላይ፣
የኦፊር ወርቅህንም ጥልቅ ሸለቆ ውስጥ
ብትጥለው፣

25ሁሉን ቻዩ አምላክ ወርቅ ይሆንልሃል፤
ምርጥ ብር ይሆንልሃል።
26በዚያ ጊዜ ሁሉን በሚችል አምላክ ደስ
ይልሃል፤
ፊትህንም ወደ እግዚአብሔር ታቀናለህ።
27ወደ እርሱ ትጸልያለህ፤ እርሱም
ይሰማሃል፤
አንተም ስእለትህን ትሰጣለህ።
28ያሰብኸው ይከናወንልሃል፤
በመንገድህም ላይ ብርሃን ይበራል።
29ሰዎች ቢዋረዱና አንተ፣ ‘ከፍ
አድርጋቸው’ ብትል፣
እርሱ ዝቅ ያሉትን ያድናል፤
30በጎ ያልሆነውን ሰው እንኳ፣
ከአንተ እጅ ንጽሕና የተነሣ ያድነዋል።”

## ኢዮብ

23 ኢዮብም እንዲህ ሲል መለሰ፤
2“ዛሬም ሐዘኔ መራራ ነው፤
እየቃሰትሁ እንኳ እጁ* በላዩ
ከብዳለች።
3እርሱን የት እንደማገኘው ባወቅሁ፤
ወደ መኖሪያውም መሄድ በቻልሁ!
4ጉዳዬን በፊቱ አቀርብ ነበር፤
አፌንም በሙግት እሞላው ነበር።
5የሚመልስልኝ ቃል ምን እንደ ሆነ
ባወቅሁ ነበር፤
የሚለኝንም ባስተዋልሁ ነበር።
6በታላቅ ኀይሉ ከእኔ ጋር ይሟገት ይሆን?
አይደለም፤ ይልቁን ያደምጠኛል።
7ቅን ሰው ጉዳዩን በእርሱ ፊት ያቀርባል፤
እኔም ከፈራጁ ለዘላለም ነጻ እሆናለሁ።

8“ዳሩ ግን ወደ ምሥራቅ ብሄድ፣ በዚያ
የለም፤
ወደ ምዕራብም ብሄድ፣ እርሱን
አላገኘውም፤
9በሰሜን እየሠራ ሳለ አላየውም፤
ወደ ደቡብ በሚዞርበት ጊዜ ደብዛው
አይገኝም።
10ግን እኔ የምሄድበትን መንገድ ያውቃል፤
ከፈተነኝም በኋላ እንደ ወርቅ
እወጣለሁ።
11እግሮቼ እርምጃውን በጥብቅ
ተከታትለዋል፤
ፈቀቅ ሳልል መንገዱን ጠብቄአለሁ።
12ከአፉ ከወጣው ትእዛዝ አልራቅሁም፣
የአንደበቱን ቃል ከዕለት እንጀራዬ
አብልጬ ይዣለሁ።

13“እርሱ ግን ራሱን ችሎ ብቻውን የሚኖር
ነው፤
የሚቋቋመውስ ማን ነው?
እርሱ የፈቀደውን ያደርጋል።
14በእኔ ላይ የወሰነውን ይፈጽማል፤
ይህን የመሰለ ዕቅድም ገና ብዙ አለው።

ኢዮ5፥14፤36፥28፤ 38፥34፡37፤መዝ69፥1-2፤124፥4-5፤ኢሳ 58፥10-11፤ሰቆ3፥54
22፥12 ኢዮ11፥8፤ 16፥19
22፥13 ቍ14፤መዝ 10፥11፤59፥7፤64፥5፤7 3፥11፤94፥7፤139፥ 11፤ኢሳ29፥15፤ሕዝ 8፥12፤9፥9፤ሰፎ1፥2፤ ኤፌ6፥12
22፥14 ቍ13፤2ነገ 21፥16፤ኢዮ26፥9፤ 37፥18፤መዝ18፥11፤ 97፥2፤105፥39፤ምሳ 8፥27፤ኢሳ40፥22፤ ኤር23፥23-24
22፥15 ኢዮ23፥10፤ 34፥8፡36፤መዝ1፥1፤ 50፥18
22፥16 ዘፍ7፥23፤ ኢዮ4፥19፤15፥32፤ ማቴ7፥26-27
22፥17 ኢዮ21፥15
22፥18 ኢዮ12፥6፤ 21፥16
22፥19 ኢዮ21፥3፤ መዝ5፥11፤9፥2፤32፥ 11፤52፥6፤58፥10፤64፥ 10፤97፥12፤107፥42
22፥20 ኢዮ15፥30፤ መዝ18፥39
22፥21 ዘፍ 17፥1፤ ኢዮ8፥7፤መዝ34፥8-10፤ምሳ3፥10፤ኢሳ 26፥3፡12፤27፥5፤ኤር 9፥24፤ሮሜ5፥1፤ 1ጴጥ5፥6
22፥22 ዘዳ8፥3፤ኢዮ 6፥10፤15፥11፤28፥23፤ መዝ37፥31፤40፥8፤ ምሳ2፥6፤ሕዝ3፥10
22፥23 ኢዮ5፥24፤ 11፥14፤ኢሳ19፥22፤ 31፥6፤44፥22፤55፥7፤5 9፥20፤ኤር3፥14፡22፤ ሕዝ18፥32፤ዘካ1፥3፤ ሚል3፥7፤ሐሥ20፥32
22፥24 ዘፍ10፥29፤ ኢዮ1፥10፤28፥6፤31፥ 25፤መዝ19፥10፤ኢሳ 2፥20፤30፥22፤31፥7፤4 0፥19-20፤ማቴ6፥19
22፥25 2ነገ18፥7፤ ኢዮ31፥24፤መዝ49፥ 6፤52፥7፤ምሳ11፥28፤ኢ ሳ33፥6፤ማቴ6፥ 20-21
22፥26 ኢዮ11፥15፡ 17፤27፥10፤33፥26፤መ ዝ2፥8፤16፥6፤27፥6፤37 ፥4፤100፥1፤ኢሳ 58፥14፤61፥10
22፥27 ዘኍ30፥2፤ ኢዮ5፥15፡27፤መዝ 86፥7፤ኢሳ30፥19
22፥28 ኢዮ11፥17፤ 33፥28፤መዝ97፥11፤ 103፥11፤145፥19፤ ምሳ4፥18

22፥29 አስ5፥12፤መዝ18፥27፤ማቴ23፥12 22፥30 2ሳሙ22፥21፤ኢሳ1፥18፤ሮሜ4፥5 23፥2 1ሳሙ1፥10፤ኢዮ6፥3፤7፥11፤መዝ 6፥6፤32፥4፤ኤር45፥3፤ሕዝ21፥7 23፥3 ዘዳ4፥29 23፥4 ኢዮ9፥15፤13፥18 23፥5 ኢዮ11፥5 23፥6 ኢዮ6፥4፤9፥4 23፥7 ዘፍ 3፥8፤ኢዮ1፥1፤6፥29፤9፥3፤13፥3 23፥9 ኢዮ9፥11 23፥10 ኢዮ 1፥1፤ 6፥29፤7፥18፤22፥15፤27፥6፤31፥6፤36፥7፤መዝ7፥9፤11፥5፤ 12፥6፤34፥15፤37፥18፤94፥11፤119፥168፤139፥1-3፤146፥8፤1ጴጥ 1፥7 23፥11 ኢዮ31፥7፤መዝ17፥5፤40፥4፤44፥18፤119፥51፡59፡ 157፤125፥5፤ኤር11፥20 23፥12 ኢዮ6፥10፤ 15፥11፤ማቴ4፥4፤ ዮሐ4፥32፡34 23፥13 ኢዮ9፥3፤10፥13፤ኢሳ55፥11 23፥14 1ተሰ 3፥3፤1ጴጥ4፥12

*2 በሰብዓ ሊቃናት ትርጒም፣ በሱርስትና በዕብራይስጡ ላይ፣ *እጁ በላዬ* ይላል

15በፊቱ የደነገጥሁትም ለዚህ ነው፤
 ይህን ሁሉ ሳስብ እፈራለሁ።
16እግዚአብሔር ልቤን አባባው፤
 ሁሉንም የሚችል አምላክ አስደነገጠኝ።
17ይህም ሆኖ ሳለ ጨለማው፣
 ፊቴንም የጋረደው ጽልመት ልሳኔን
  አልዘጋውም።

24 “ሁሉን የሚችል አምላክ ለምን የፍርድ ቀን አይወስንም?
 እርሱን የሚያውቁትስ ለምን ያን ቀን
  እንዲያው ይጠባበቃሉ?
2ሰዎች ድንበር ይገፋሉ፤
 የሰረቁትን መንጋ ያሰማራሉ።
3የድኻ ዐደጉን አህያ ቀምተው ይሄዳሉ፤
 የመበለቲቱንም በሬ በመያዣነት
  ይወስዳሉ።
4ችግረኛውን ከመንገድ ያስወግዳሉ፤
 የምድሪቱም ድኾች ይሸሸጋሉ።
5በምድረ በዳ እንዳሉ የሜዳ አህዮች፣
 ድኾች ምግብ ፍለጋ ይራወጣሉ፤
 ከበረሓው ምድር ለልጆቻቸው ምግብ
  ይሻሉ።
6ከሜዳ መኖ ይሰበስባሉ፤
 ከክፉዎች የወይን ቦታም ይቃርማሉ።
7ዕራቍታቸውን ያለ ልብስ ያድራሉ፤
 በብርድም ጊዜ የሚለብሱት የላቸውም።
8ከተራራ በሚወርድ ዝናብ በስብሰዋል፤
 መጠለያ አጥተው ቋጥኝ ዐቅፈዋል።
9አባት የሌለው ልጅ ከዕቅፍ ተነጥቋል፤
 የድኻውም ልጅ በዕዳ ተይዞአል።
10ዕራቍታቸውን ያለ ልብስ ይሄዳሉ፤
 ነዶ ይሸከማሉ፤ ግን ይራባሉ።
11በየተረተሩ[ሀ] የወይራ ዘይት ያወጣሉ፤
 ወይን እየጠመቁ፣ ለራሳቸው ግን ይጠማሉ፤
12የሚኞች ጣር ጩኸት ከከተማዋ ይሰማል፤
 የቈሰሉት ሰዎች ነፍስ ለርዳታ ይጮኻል፤
 እግዚአብሔር ግን ተጠያቂዎቹን ዝም
  ብሎአል።

13“በብርሃን ላይ የሚያምፁ፣
 ጐዳናውን የማያውቁ፣
 በመንገዱም የማይጸኑ አሉ።
14ቀኑ ሲመሽ፣ ነፍሰ ገዳይ ይነሣል፤
 ድኾችንና ችግረኞችን ይገድላል፤
 በሌሊትም እንደ ሌባ ያደባል፤
15አመንዝራ በዐይኑ ድንግዝግዝታን
  ይጠባበቃል፤
 ‘ማንም አያየኝም’ ብሎ ያስባል፤
 ፊቱንም ይሸፍናል።
16በጨለማ፣ ቤት ሰርስረው ይገባሉ፤
 በቀን ግን ይሸሸጋሉ፤
 ብርሃንንም አይፈልጉም።
17ድቅድቅ ጨለማ ለሁላቸው እንደ ንጋት[ለ]
  ነው፤
 አሸባሪውን ጨለማ[ሐ] ይወዳጃሉ።

18“ይሁን እንጂ፣ በውሃ ላይ
  የሚኰረፈረፍ ዐረፋ ናቸው፤
 የወይን ቦታው ሰው የማይደርስበት፣
 ርስታቸው ርጉም ነው።
19ድርቅና ሙቀት የቀለጠውን በረዶ
  ከቦታው እንደሚያስወግድ፣
 ሲኦልም[መ] ኀጢአተኞችን ትነጥቃለች።
20የተሸከመቻቸው ማሕፀን ትረሳቸዋለች፤
 ትል ይቦጠቡጣቸዋል፤
ክፉዎች እንደ ዛፍ ይሰበራሉ፤
 የሚያስታውሳቸውም የለም።
21የማትወልደውን መካኒቱን ይቦጠቡጣሉ፤
 ለመበለቲቱም አይራሩም።
22ነገር ግን እግዚአብሔር ብርቱዎችን
  በኀይሉ ጐትቶ ይጥላል፤
 ቢደላደሉም የሕይወት ዋስትና
  የላቸውም።
23ያለ ሥጋት እንዲኖሩ ትቶአቸው
  ይሆናል፤
 ዐይኖቹ ግን በመንገዳቸው ላይ ናቸው።
24ለጥቂት ጊዜ ከፍ ከፍ ይላሉ፤ ሆኖም
  ይጠፋሉ፤
 ዝቅ ዝቅ ብለው፤ እንደ ሌሎቹ
  ይከማቻሉ።
 እንደ እህል ራስም ይታጨዳሉ።
25“ይህ እንዲህ ካልሆነማ፣ የሚያስተባብለኝ
  ማን ነው?
 ቃሌን ከንቱ የሚያደርገውስ ማን ነው?”

## በልዳዶስ

25 ሹሐዊውም በልዳዶስ እንዲህ ሲል መለሰ፤
2“ገዢነትና ግርማ የእግዚአብሔር ናቸው፤
 በሰማይም ከፍታ ሥርዐትን ያደርጋል።
3ሰራዊቱ ሊቈጠር ይችላልን?
 ብርሃኑስ የማይወጣው በማን ላይ ነው?
4ሰው በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ይሆን
  ዘንድ፣
 ከሴትስ የተወለደ ንጹሕ ይሆን ዘንድ
  ይችላልን?

23፥15 ዘፍ45፥3፤ኢሱ24፥14፤መዝ34፥9፤36፥1፤ 111፥10፤ምሳ1፥7፤መክ3፥14፤12፥13፤2ቆሮ5፥11 23፥16 ዘፀ3፥6፤ዘዳ20፥3፤ኢዮ27፥2፤ራእ6፥16 23፥17 ኢዮ3፥6፤ 19፥8 24፥1 ኢዮ9፥23፤14፥5፤15፥20፤ሐሥ1፥7፤2ጴጥ3፥7 24፥2 ዘፀ20፥15፤ዘዳ19፥14፤28፥31 24፥3 ኢዮ6፥27፤22፥9 24፥4 ኢዮ20፥19፤29፥12፡16፤30፥25፤31፥19፤መዝ12፥5፤41፥1፤82፥3፡4፤ምሳ28፥12፤ኢሳ11፥4 24፥5 ዘፍ16፥12፤ኢዮ30፥3፤መዝ104፤23 24፥6 ቀኍ18፤ሩት2፥22፤1ነገ21፥19፤ኢዮ6፥5 24፥7 ዘፀ22፥27 24፥8 መሳ6፥2፤ሰቆ4፥5፤ዳን4፥25፡33 24፥9 ዘሌ25፥47፤ዘዳ24፥17፤2ነገ4፥1፤እዮ29፥17፤መዝ14፥4፤ምሳ30፥14፤ኢሳ3፥14፤10፥1-2፤ሕዝ18፥12 24፥10 ዘሌ19፥9፤ዘዳ24፥12-13 24፥11 ኢሳ5፥2፤16፥10፤ሚክ6፥15፤ሐጌ2፥16 24፥12 ኢዮ9፥23፤12፥19፤30፥28፤መዝ5፥2፤22፥24፤39፥12፤119፥147፤ኢሳ30፥19፤ኤር50፥46፤51፥52፡54፤ሕዝ26፥15፤ራእ6፥10 24፥13 ቀኍ16፤ኢዮ17፥12፤38፥15፡20፤መዝ18፥28፤ኢሳ5፥20፤ዮሐ3፥19-20፤ኤፌ5፥8-14፤1ተሰ5፥4-5 24፥14 ኢዮ20፥19፤መዝ10፥9፤37፥32፤ኢሳ3፥15፤ሚክ3፥3 24፥15 ኢዮ31፥9፡27፤መዝ10፥11፤ምሳ1፥10፤7፥8-9 24፥16 ቀኍ13፤ዘፀ22፥2፤ማቴ6፥19 24፥17 ኢዮ15፥22፤18፥5፡11 24፥18 ቀኍ6፤ኢዮ5፥3፤9፥26፤22፥16፤ኢሳ57፥20፤ይሁ1፥13 24፥19 ኢዮ6፥17፤21፥13 24፥20 ኢዮ7፥5፤14፥7፤18፥17፤21፥26፤መዝ31፥12፤ዳን4፥14 24፥21 ኢዮ22፥9 24፥22 ዘዳ28፥66፤ማቴ6፥27፤ኢዮ9፥4፤12፥19፤ያዕ4፥14 24፥23 2ዜና16፥9፤ኢዮ9፥24፤10፥4፤አሞ6፥1 24፥24 2ነገ19፥35፤ኢዮ3፥19፤4፥20፤መዝ37፥10፤83፥13፤ኢሳ5፥24፤17፥5፤13፤40፥24፤41፥2፤15 24፥25 ኢዮ6፥28፤16፥17 25፥1 ኢዮ8፥1 25፥2 2ዜና20፥6፤ኢዮ9፥4፤11፥8፤16፥19፤መዝ47፥9፤89፥ 18፤ዘካ9፥7፤ራእ1፥6 25፥3 ማቴ5፥45፤ያዕ1፥17 25፥4 ኢዮ4፥17

[ሀ]11 ወይም *ከወፍጮዎች መካከል የወይራ ዘይት* ማለት ነው፤ ሆኖም የዚህ ቃል የዕብራይስጡ ትርጕም በትክክል አይታወቅም
[ለ]17 ወይም *ለእነርሱ ንጋት እንደ ሞት ጥላ ነው*
[ሐ]17 ወይም *ከሞት ጥላ* ማለት ነው
[መ]19 አንዳንድ ቅጆች፣ *መቃብር* ይሉታል

[5]በፊቱ ጨረቃ እንኳ ብሩህ ካልሆነች፣
ከዋክብትም ንጹሓን ካልሆኑ፣
[6]ይልቁን ከብል የሚቈጠር የሰው ልጅ፣
ትል የሆነውማ ሰው ምንኛ ያንስ!”

## ኢዮብ

# 26

ኢዮብም እንዲህ ሲል መለሰ፤
[2]“ኀይል የሌለውን ምንኛ ረዳኸው!
ደካማውንስ ምንኛ አዳንኸው!
[3]ጥበብ የሌለውን ምንኛ መከርኸው!
ታላቅ ዕውቀትንስ ምንኛ ገለጥህለት!
[4]ይህን ቃል እንድትናገር የረዳህ ማን ነው?
የማንስ መንፈስ በአንደበትህ ተጠቀመ?
[5]“ከውሆችና በውስጣቸው ከሚኖሩ በታች ያሉ፣
የሙታን መንፈስ በጭንቅ ላይ ናቸው፡፡
[6]ሲኦል[a] በእግዚአብሔር ፊት ዕራቍቷን ናት፤
የጥፋትንም[b] ስፍራ የሚጋርድ የለም፡፡
[7]የሰሜንን ሰማይ በሕዋው ላይ ዘረጋው፤
ምድርንም እንዲያው በባዶው ላይ አንጠለጠላት፡፡
[8]ውሆችን በደመናዎቹ ይጠቀልላል፤
ክብደታቸውም ደመናዎቹን አይሸነቍርም፡፡
[9]ደመናዎቹን በላዩ ዘርግቶ፣
የሙሉውን ጨረቃ ፊት ይጋርዳል፡፡
[10]ለብርሃንና ለጨለማ ድንበር ይሆን ዘንድ፣
በውሆች ላይ የአድማስ ክበብ አበጀ፡፡
[11]የሰማይ ምሰሶዎች ይንቀጠቀጣሉ፤
በተግሣጹም ይደነግጣሉ፡፡
[12]በኀይሉ ባሕርን ያናውጣል፤
በጥበቡም ረዓብን ይቈራርጣል፡፡
[13]በእስትንፋሱ ሰማያትን አጠራ፤
እጁም ተወርዋሪውን እባብ ወጋች፡፡
[14]እነዚህ የሥራው ዳር ዳር ናቸው፤
ስለ እርሱ የሰማነው ምንኛ አነስተኛ ነው!
የኀይሉንስ ነጐድጓድ ማን ሊያስተውል ይችላል?”

# 27

ኢዮብም እንዲህ ሲል ንግግሩን ቀጠለ፤
[2]“ፍትሕ የነሣኝ ሕያው እግዚአብሔርን!
ነፍሴንም መራራ ያደረጋት፣ ሁሉን ቻይ አምላክን!
[3]በውስጤ የሕይወት እስትንፋስ፣
በአፍንጫዬም ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ እስካለ ድረስ፣
[4]ከንፈሬ ኀጢአትን አትናገርም፤
አንደበቴም ሽንገላ አይወጣውም፡፡

25፥5 ኢዮ4፥18፤ 31፥26
25፥6 ኢዮ4፥19፤ 7፥5፤መዝ80፥17፤ 144፥3፤ሕዝ2፥1
26፥2 ኢዮ4፥3፤ 6፥12
26፥3 ኢዮ34፥35
26፥4 1ነገ22፥24
26፥5 መዝ88፥10፤ ኢሳ14፥9፤26፥14
26፥6 ኢዮ10፥22፤ 11፥8፤20፥26፤38፥17፤ 41፥11፤መዝ139፥8፡1 1-12፤ምሳ15፥11፤ ዕብ4፥13፤ራእ9፥11
26፥7 ኢዮ9፥8፤38፥ 6፤መዝ104፥5፤ምሳ3፥ 19-20፤8፥27፤ኢሳ 40፥22
26፥8 ዘፍ1፥2፤ኢዮ 36፥27፤37፥11፤መዝ 147፥8፤ምሳ30፥4
26፥9 2ሳሙ22፥ 10፤ኢዮ22፥14
26፥10 ዘፍ1፥4፤ ኢዮ28፥3፤38፥8-11፤ ምሳ8፥27፤ኢሳ40፥22
26፥11 2ሳሙ22፥8
26፥12 ዘፀ14፥21፤ ኢዮ9፥13፤12፥13
26፥13 ኢዮ9፥8፤ ኢሳ27፥1
26፥14 ኢዮ4፥12፤ 9፥6፤42፥5፤ዕን3፥2፤ 1ቆሮ13፥12
27፥1 ኢዮ29፥1
27፥2 1ሳሙ1፥10 ፤ኢዮ6፥29፤7፥19፤9፥ 24፤10፥1፤23፥16፤49፥ 4፥14፤ኢሳ45፥9
27፥3 ዘፍ2፥7፤ኢዮ 32፥8፤33፥4፤34፥14፤ መዝ144፥4
27፥4 ኢዮ6፥28፤ 12፥16፤16፥17
27፥5 ኢዮ2፥9፤ 10፥7፤32፥2
27፥6 ኢዮ2፥3፤10፥ 7፤23፥10፤29፥14፤ 34፥17፤መዝ119፥ 121፥132፥9፤ኢሳ59፥ 17፤61፥10፥ሐሥ23፥ 1፤ሮሜ2፥15
27፥7 ኢዮ8፥22፤ 31፥35
27፥8 ዘኍ16፥22፤ ኢዮ8፥13፡22፤11፥20፤ ሉቃ12፥20
27፥9 ዘዳ1፥45፤ 1ሳሙ8፥18፤ኢዮ 15፥31
27፥10 ኢዮ22፥26
27፥11 ቀ13፤ኢዮ 36፥23
27፥13 ኢዮ16፥19፤ 20፥29
27፥14 ኢዮ4፥11፤ 5፥4፤15፥22፤ሰቆ2፥22
27፥15 መዝ78፥64
27፥16 1ነገ10፥27፤

[5]እናንተን እንደ ቅኖች መቍጠር፣
የማላደርገው ነገር ነው፤
ጨዋነቴንም እስክሞት ድረስ አልጥልም፡፡
[6]ጽድቄን አጥብቄ እይዛለሁ፤ አልለቀውምም፤
በዘመኔም ሁሉ ኅሊናዬ አይወቅሰኝም፡፡
[7]“ጠላቴ እንደ በደለኛ፣
ባላንጣዬም እንደ ክፉ ይሁን፡፡
[8]እግዚአብሔር ሲያስወግደው፣
ነፍሱንም ሲወስድበት ዐመፀኛ ምን ተስፋ አለው?
[9]በውኑ መከራ በገጠመው ጊዜ፣
እግዚአብሔር ጩኸቱን ይሰማልን?
[10]ሁሉን በሚችል አምላክ ደስ ይለዋልን?
ዘወትርስ እግዚአብሔርን ይጠራልን?
[11]“ስለ እግዚአብሔር ክንድ አስተምራችኋለሁ፤
የሁሉን ቻዩንም አምላክ ዕቅድ አልሸሽግም፡፡
[12]ሁላችሁ ይህን አይታችኋል፤
ታዲያ፣ ይህ ከንቱ ንግግር ምንድን ነው?
[13]“እግዚአብሔር ለክፉው የመደበው ዕድል ፈንታ፣
ግፈኛም ሁሉን ከሚችል አምላክ የሚቀበለው ቅርስ ይህ ነው፦
[14]ልጆቹ የቱንም ያህል ቢበዙም ለሰይፍ ይዳረጋሉ፤
ዘሩም ጠግቦ አያድርም፡፡
[15]የተረፉለትም በመቅሠፍት አልቀው ይቀበራሉ፤
መበለቶቻቸውም አያለቅሱላቸውም፡፡
[16]ብርን እንደ ዐፈር ቢከምር፣
ልብስንም እንደ ሸክላ ጭቃ ቢያከማች፣
[17]እርሱ ያከማቸውን ጻድቃን ይለብሱታል፤
ብሩንም ንጹሓን ይከፋፈሉታል፡፡
[18]የሚሠራው ቤት እንደ ሸረሪት ድር፣
እህል ጠባቂም እንደ ቀለሰው መጠለያ ነው፡፡
[19]ሀብታም ሆኖ ይተኛል፤ ዘለቄታ ግን የለውም፤
ዐይኑን በገለጠ ጊዜ ሀብቱ ሁሉ በቦታው የለም፡፡
[20]ድንጋጤ እንደ ጐርፍ ድንገት ያጥለቀልቀዋል፤
ዐውሎ ነፋስም በሌሊት ይዞት ይሄዳል፡፡
[21]የምሥራቅ ነፋስ ይወስደዋል፤ እርሱም አይገኝም፤
ከስፍራውም ይጠርገዋል፡፡

ዘካ9፥3 27፥17 ዘፀ3፥22፤ኢዮ3፥15፤7፥8፤መዝ39፥6፤49፥10፤ ምሳ13፥22፤28፥8፤መክ2፥26 27፥18 ኢዮ8፥14፡22፤ኢሳ1፥8፤ 24፥20 27፥19 ኢዮ3፥13፤7፥8፤14፥20 27፥20 ኢዮ6፥4፤ 15፥21፤20፥8 27፥21 ኢዮ7፥10፤30፥22፤38፥24፤ኤር13፥24፤ 22፥22

[a]6 የዕብራይስጡ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ አንዳንድ ቅጆች ግን፣ ሞት ይላሉ፡፡
[b]6 ዕብራይስጡ፣ አባዶን ይላል፡፡

22ከነፋሱ ብርታት ለማምለጥ ይሮጣል፤
ነገር ግን እየተወረወረ ያለ ርኅራኄ
ይደርስበታል፤
23እጁንም እያጨበጨበ ያሾፍበታል፤
በፉጨትም ከስፍራው ያሽቀነጥረዋል።

28 “የብር ማዕድን የሚወጣበት፣
ወርቅም የሚነጠርበት ስፍራ አለ።
2ብረት ከመሬት ውስጥ ይገኛል፤
መዳብም ከማዕድን ድንጋይ ቀልጦ
ይወጣል።
3ሰው፣ እስከ ጨለማ መጨረሻ ይዘልቃል፤
ከድቅድቅ ጨለማ የማዕድን ድንጋይ
ለማግኘት፣
እስከ ውስጠኛው ዋሻ ገብቶ ይፈልጋል።
4የሰው እግር ረግጦት በማያውቅበት ስፍራ፣
ከሰዎች መኖሪያ ርቆ መውረጃ ጕድጓድ
ይቈፍራል፤
ሰው በሌለበት ቦታ ይንጠላጠላል፤
ይወዛወዛል።
5ከላይዋ ምግብን የምታስገኝ ምድር፣
ከታች በእሳት እንደሚሆን
ትለዋወጣለች።
6ሰንፔር[ኣ] ከዐለቷ ይወጣል፤
ከዐፈሯም የወርቅ አንኳር ይገኛል።
7ያን መንገድ ጭልፊት አያውቀውም፤
የአሞራም ዐይን አላየውም፣
8ኵሩ አራዊት አልረገጡትም፤
አንበሳም በዚያ አላለፈም።
9ሰው እጁን በቡላድ ድንጋይ ላይ ያነሣል፤
ተራሮችንም ከሥር ይገለብጣል።
10በድንጋይ ውስጥ መተላለፊያ ያበጃል፤
ዐይኖቹም የከበሩ ነገሮችን ሁሉ
ያያሉ።
11የወንዞችን ምንጭ ይበረብራል፤[ከ]
የተሰወረውንም ነገር ወደ ብርሃን
ያወጣል።

12“ነገር ግን ጥበብ ከወዴት ትገኛለች?
ማስተዋልስ መኖሪያዋ የት ነው?
13ሰው ዋጋዋን አያውቅም፤
በሕያዋንም ምድር አትገኝም።
14ውቅያኖስ፣ ‘በእኔ ውስጥ የለችም’ ይላል፤
ባሕርም፣ ‘በእኔ ዘንድ አይደለችም’
ይላል።
15ንጹሕ ወርቅ ሊገዛት አይችልም፤
ዋጋዋም በብር አይመዘንም።
16በኦፊር ወርቅ፣
በከበረም መረግድና በሰንፔር
አትገመትም።
17ወርቅም ብርሌም አይወዳደሯትም፤
በወርቅ ጌጥም አትለወጥም።
18ዛጐልና አልማዝ ከቍጥር አይገቡም፤
የጥበብ ዋጋ ከቀይ ዕንቍም ይበልጣል።
19የኢትዮጵያ ቶጳዝዮን ሊስተካከላት
አይችልም፤
ዋጋዋም በንጹሕ ወርቅ አይተመንም።

20“ታዲያ፣ ጥበብ ከወዴት ትመጣለች?
ማስተዋልስ የት ትገኛለች?
21ከሕያዋን ፍጥረታት ዐይን ሁሉ
ተሰውራለች፤
ከሰማይ ወፎችም ተሸሽጋለች።
22ጥፋትና[ኸ] ሞት፣
‘ወሬዋን ብቻ ሰማን’ ይላሉ።
23ወደ እርሷ የሚወስደውን መንገድ
የሚረዳ፣
መኖሪያዋንም የሚያውቅ እግዚአብሔር
ብቻ ነው፤
24እርሱ የምድርን ዳርቻ ይመለከታልና፤
ከሰማይ በታች ያለውንም ሁሉ ያያል።
25ለነፋስ ኀይልን በሰጠ ጊዜ፣
የውሆችን መጠን በለካ ጊዜ፣
26ለዝናብ ሥርዐትን፣
ለነጐድጓድም መንገድን ባበጀ ጊዜ፣
27በዚያን ጊዜ ጥበብን ተመለከታት፤
ገመገማትም፤
አጸናት፤ መረመራትም።
28ከዚያም ሰውን፣
‘እግዚአብሔርን መፍራት ጥበብ ነው፤
ከክፋትም መራቅ ማስተዋል ነው’ አለው።”

29 ኢዮብም እንዲህ ሲል ንግግሩን ቀጠለ፤
2“በእግዚአብሔር የተጠበቅሁበትን ዘመን፣
ያለፈውንም ወራት ምንኛ ተመኘሁ!
3ያን ጊዜ መብራቱ በራሴ ላይ ይበራ ነበር፤
በብርሃኑም በጨለማ ውስጥ ዐልፌ እሄድ
ነበር፤
4እኔም ብርቱ ነበርሁ፤
የእግዚአብሔርም ወዳጅነት ቤቴን ይባርክ
ነበር፤
5ሁሉን የሚችል አምላክ ከእኔ ጋር ነበረ፤
ልጆቼም በዙሪያዬ ነበሩ፤
6መንገዴ በቅቤ የራሰ ነበር፤
ዐለቱም የወይራ ዘይት ያመነጭልኝ
ነበር።

7“ወደ ከተማዪቱ በር ብቅ ባልሁ ጊዜ፣
በአደባባይዋም በወንበር በተቀመጥሁ ጊዜ፣

27፥22 2ነገ7፥15፤ ኢዮ11፥20፤ ኤር 13፥14፤ ሕዝ5፥11፤ 24፥14
27፥23 ዘኍ24፥10፤ ኢዮ7፥10፤ ናሆ3፥19
28፥1 መዝ12፥6፤ 66፥10፤ ኤር9፥7፤ ዳን 11፥35፤ ሚል3፥3
28፥2 ዘዳ8፥9 28፥3 ኢዮ26፥10፤ 38፥19፤ መክ1፥13፤ 7፥25፤ 8፥17
28፥4 ቍ10፤ 2ሳሙ5፥8
28፥5 ዘፍ1፥29፤ መዝ104፥14፤ 145፥15
28፥6 ቍ16፤ ኢዮ 22፥24፤ ማሕ5፥14፤ ኢሳ54፥11
28፥7 ቍ21
28፥8 ኢዮ41፥34፤ ኢሳ35፥9
28፥9 ዘዳ8፥15፤ ዮና2፥6
28፥10 ቍ4፤ ምሳ2፥4
28፥11 ዘፍ7፥11፤ ኢሳ48፥6፤ ኤር33፥3
28፥12 ቍ20፡23፡ 28፤ ምሳ1፥20፤ 3፥13-20፤ 8፥1፤ 9፥1-3፤ መክ7፥24
28፥13 ዘዳ29፥29፤ መዝ27፥13፤ 52፥5፤ 116፥9፤ 142፥5፤ ምሳ3፥15፤ ኢሳ38፥11፤ ኤር 11፥19፤ ሕዝ26፥20፤ 32፥24፤ ማቴ13፥44-46
28፥14 ዘዳ30፥13፤ መዝ42፥7፤ ሮሜ10፥7
28፥15 ቍ17፤ ምሳ 3፥13-14፤ 8፥10-11፤ 16፥16፤ ሐሥ8፥20
28፥16 ቍ6፤ ዘፍ 10፥29፤ ዘፀ24፥10
28፥17 ቍ15፤ መዝ 119፥72፤ ምሳ8፥10
28፥18 ምሳ3፥15፤ 8፥11፤ ሕዝ27፥16፤ ራእ21፥11
28፥19 ዘፀ28፥17፤ ምሳ3፥14-15፤ 8፥10-11፡19፤ ኢሳ11፥11
28፥20 ኢዮ9፥4
28፥21 ቍ7
28፥22 ኢዮ20፥26፤ ምሳ8፥32-36፤ ራእ9፥11
28፥23 ኢዮ9፥4፤ 22፥22፤ ምሳ8፥22-31፤ መክ3፥11፤ 8፥17
28፥24 ኢሱ3፥11፤ ኢዮ10፥4፤ 36፥32፤ 37፥3፤ 38፥18፡24፡35፤ መዝ33፥13-14፤ 66፥7፤ ኢሳ11፥12፤ ዕ4፥13
28፥25 ኢዮ12፥15፤ 38፥8-11
28፥26 ኢዮ36፥28፡ 33፤ 37፥3፡6፡8፡11፤ 38፥27፤ መዝ65፥12፤ 104፥14፤ 147፥8፤ ኢሳ35፥7፤ ኤር51፥16 28፥27 ምሳ3፥19፤ 8፥22-31
28፥28 ዘፀ20፥20፤ ዘዳ4፥6፤ ኢዮ37፥24፤ መዝ11፥5፤ 97፥10፤ ምሳ3፥7፤ 8፥13 29፥1 ኢዮ27፥1 29፥2 ዘፍ31፥30፤ ኤር1፥12፤ 31፥28፤ 44፥27 29፥3 ኢዮ11፥17፤ 12፥25 29፥4 ኢዮ15፥8፤ መዝ25፥14፤ ምሳ3፥32 29፥5 ሩት4፥1፤ መዝ127፥3-5፤ 128፥3 29፥6 ዘፍ49፥20፤ ዘዳ32፥13፤ ኢዮ20፥17፤ መዝ81፥16 29፥7 ቍ21፤ ኢዮ5፥4፤ 31፥21፤ ኤር20፥2፤ 38፥7

[ኣ]6 በዚህና በቍ 16 ላይ፣ *ላፒስ ላዙሊ*
[ከ]11 የሰብዓ ሊቃናት ትርጕምና ቩልጌት ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን *ይገድባል* ይላል
[ኸ]22 ዕብራይስጡ፣ *ዐባይን* ይላል

8ጉበዛዝት አይተውኝ ገለል ይሉ፣
ሽማግሌዎችም ተነሥተው ይቆሙ ነበር።
9የሰፈሩ ታላላቅ ሰዎች ከመናገር ይቈጠቡ፣
እጃቸውንም በአፋቸው ላይ ይጭኑ
ነበር፤
10የመኳንንት ድምፅ ጸጥ ይል፣
ምላሳቸውም ከላንቃቸው ጋር ይጣበቅ
ነበር፤
11የሰሙኝ ሁሉ ያሞጋግሱኝ፣
ያዩኝም ያመሰግኑኝ ነበር፤
12ለርዳታ የሚጮኸውን ችግረኛ፣
ድኻ ዐደጉንም ታድጌአለሁና።
13በሞት አፋፍ ላይ የነበረ መርቆኛል፤
የመበለቲቱንም ልብ አሳርፌአለሁ።
14ጽድቅን እንደ ልብስ ለበስሁ፤
ፍትሕም መጐናጸፊያዬና ጥምጥሜ
ነበር።
15ለዕውራን ዐይን፣
ለአንካሶችም እግር ነበርሁ።
16ለችግረኛው አባት፣
ለባይተዋሩ ተሟጋች ነበርሁ።
17የኀጢአተኛውን ክራንቻ ሰበርሁ፤
የነጠቀውንም ከጥርሶቹ አስጣልሁ።

18"እኔም በልቤ እንዲህ አልሁ፤ 'ዘመኔ
እንደ አሸዋ በዝቶ፣
በቤቴ ተደላድዬ እሞታለሁ፤
19ሥሬ ወደ ውሃ ይዘረጋል፤
ጠልም በቅርንጫፌ ላይ ያድራል፤
20ክብሬ በውስጤ አዲስ እንደ ሆነ፣
ቀስትም በእጄ እንደ በረታ ይኖራል።'

21"ሰዎች ምክሬን በጸጥታ በመጠባበቅ፣
በጒጒት አዳመጡኝ።
22እኔ ከተናገርሁ በኋላ፣ የሚናገር ሰው
አልነበረም፤
ቃሌም እየተንጠባጠበ በጆሯቸው ይገባ
ነበር።
23ዝናብ እንደሚጠብቅ ሰው ጠበቁኝ፤
ቃሌንም እንደ በልግ ዝናብ ጠጡ፤
24በሣቅሁላቸው ጊዜ እውነት
አልመሰላቸውም፤
የፊቴም ብርሃን ብርቃቸው[ω] ነበር።
25መንገድ መርጬላቸው አለቃቸው ሆኜ
ተቀመጥሁ፤
በሰራዊትም መካከል እንዳለ ንጉሥ
ኖርሁ፤
ሐዘንተኞችንም እንደሚያጽናና ነበርሁ።

30 "አሁን ግን በዕድሜ ከእኔ የሚያንሱ፣
ከመንጋዬ ጠባቂ ውሾች ጋር
እንዳይቀመጡ፣
አባቶቻቸውን የናቅኋቸው፣
እነዚህ ይሣለቁብኛል።
2ጒልበት የከዳቸው፤
የክንዳቸው ብርታት ምን ፋይዳ
ይሞላልኝ ነበር?
3ከችጋርና ከራብ የተነሣ ጠወለጉ፤
ሰው በማይኖርበት በረሓ፣
በደረቅም ምድር በሌሊት ተንከራተቱ።[o]
4ከቍጥቋጦ ምድር ጨው ጨው የሚል
አትክልት ለቀሙ፤
ምግባቸውም የክትክታ ሥር ነበር።
5ከኅብረተ ሰቡ ተለይተው ተባረሩ፤
ሰዎች እንደ ሌባ ይጮኹባቸዋል።
6በዐለት መካከል በምድር ጕድጓድ፣
በደረቅ ሸለቆ ዋሻ ውስጥ ለመኖር
ተገደዱ።
7በጫካ ውስጥ ያናፋሉ፤
በእሾሃማ ቍጥቋጦ መካከልም
ይታፈጋሉ።
8ስማቸው የማይታወቅ አልባሌ ናቸው፤
ከምድሪቱም ተባረዋል።

9"አሁን ግን ልጆቻቸው በዘፈን
ይሣለቁብኛል፤
በእነርሱም ዘንድ መተረቻ ሆኛለሁ።
10ይጸየፉኛል ወደ እኔም አይቀርቡም፤
ያለ ምንም ይሉኝታ በፊቴ ይተፋሉ።
11እግዚአብሔር የቀስቴን አውታር ስላላላውና
በመከራም ስለ መታኝ፣
በፊቴ መቈጠብን ትተዋል።
12በቀኜ በኩል ባለጌዎች[ǁ] ሆ! ብለው
ተነሡብኝ፤
ለእግሬም ወጥመድ ዘረጉ፤
የዐፈር ድልድልም አዘጋጁብኝ።
13መንገድ ዘጉብኝ፤
የሚገታቸው[ɯ] ሳይኖር፣
ሊያጠፉኝ ተነሡ።
14በሰፊ ንቃቃት ውስጥ እንደሚመጣ ሰው
መጡብኝ፤
በፍርስራሽም መካከል እየተንከባለሉ
ደረሱብኝ።
15በድንጋጤ ተውጫለሁ፤
ክብሬ በነፋስ እንደሚወሰድ ተወስዶአል፤
በሰላም መኖሬም እንደ ደመና እልም
ብሎ ጠፍቶአል።

16"አሁን ነፍሴ በውስጤ አለቀች፤
የመከራ ዘመንም ይዞኛል።
17ደዌ በሌሊት ዐጥንቴን ይበሳል፤
የሚቈረጥመኝም ፋታ አይሰጠኝም።

29፥8 ዘሌ19፥32፤ 1ጢሞ5፥1
29፥9 ቍ21፤መሳ 18፥19፤ኢዮ31፥21፤ 40፥4፤ምሳ30፥32
29፥10 ቍ22፤መዝ 137፥6
29፥11 ኢዮ4፥4፤ ዕብ11፥4
29፥12 ዘዳ24፥17፤ ኢዮ24፥4፤31፥17፡21፤ መዝ72፥12፤ምሳ21፥13
29፥13 ዘዳ10፥18፤ ኢዮ22፥9፤31፥20
29፥14 2ሳሙ8፥ 15፤ኢዮ19፥9፤27፥6፤ ኤፌ4፥24፤6፥14
29፥15 ዘኍ10፥31፤ ኢዮ4፥4
29፥16 ዘፀ18፥26፤ ኢዮ4፥4፤24፥4፤ምሳ 22፥22-23
29፥17 ኢዮ4፥10፡ 11፤24፥9፤መዝ3፥7
29፥18 መዝ1፥1-3፤ 15፥5፤16፥8፤30፥6፤62፥ 2፤139፥18፤ምሳ3፥1-2
29፥19 ዘፍ27፥28፤ ዘኍ24፥6፤ኢዮ14፥9፤ 15፥30፤መዝ133፥3
29፥20 ዘፍ49፥24፤ ኢዮ30፥11፤መዝ18፥ 34፤92፥14፤ኢሳ 38፥12
29፥21 ቍ7፡9
29፥22 ቍ10፤ ዘዳ32፥2
29፥23 ኢዮ4፥3
29፥24 ዘኍ6፥25፤ ምሳ16፥14፡15
29፥25 ኢዮ1፥3፤ 4፥4፤21፥28
30፥1 ኢዮ6፥14፤ 11፥3፤መዝ119፥21፤ኢሳ56፥10
30፥3 ኢዮ24፥5፤ ኢሳ8፥21፤ኤር17፥6
30፥4 1ነገ19፥4፤ ኢዮ39፥6
30፥6 ኢሳ2፥19፤ ሆሴ10፥8
30፥7 ኢዮ6፥5፤ 39፥5-6 30፥8 መሳ9፥4፤ኢዮ18፥18
30፥9 ኢዮ12፥4፤ 16፥10፥17፥6፤መዝ69፥ 11፤ሰቆ3፥14፡63
30፥10 ዘዳ25፥9፤ኢ. ዮ19፥19፤ማቴ26፥67
30፥11 ዘፍ12፥17 ፤ሩት1፥21፤ኢዮ29፥ 20፤41፥13፤መዝ32፥9
30፥12 ኢዮ16፥10፥ 18፥9፤መዝ109፥6፤ 140፥4-5፤ዘካ3፥1
30፥13 ኢዮ10፥3፤ ኢሳ3፥12
30፥14 2ነገ25፥4
30፥15 ዘፀ3፥6፤ኢዮ 3፥25፤6፥4፤10፥8፤ 31፥2-3፡23፤መዝ55፥4-5 30፥16 ቍ27፤ኢዮ3፥24፤9፥17
30፥17 ዘዳ28፥35፤ኢዮ16፥16

[ω]24 በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጒም በትክክል አይታወቅም
[o]3 ወይም *ተሠቃዩ*
[ǁ]12 በዕብራይስጥ የዚህ ቃል ትርጒም በትክክል አይታወቅም
[ɯ]13 ወይም *'ማንም ሊረዳው አይችልም' አሉ*

18እግዚአብሔር በታላቅ ኀይሉ ልብሴን[የ]
ጨምድዶአል፤
በልብሴም ክሳድ አንቆ ይዞኛል።
19እርሱ ጭቃ ውስጥ ጥሎኛል፤
እኔም ከዐፈርና ከዐመድ አልተሻልሁም።
20“እግዚአብሔር ሆይ፤ ወደ አንተ ጮኽሁ፤
ነገር ግን አልመለስህልኝም፤
በፊትህም ቆምሁ፤ አንተ ግን ዝም
አልኸኝ።
21ተመልሰህ ጨካኝ ሆንህብኝ፤
በክንድህም ብርታት አስጨነቅኸኝ።
22ወደ ላይ ነጥቀህ በነፋስ ፊት አበረርኸኝ፤
በዐውሎ ነፋስም ወዲያ ወዲህ
ወዘወዝኸኝ።
23ለሕያዋን ሁሉ ወደ ተመደበው ስፍራ፣
ወደ ሞት እንደምታወርደኝ ዐውቃለሁ።
24“የተጐዳ ሰው ተጨንቆ ድረሱልኝ ብሎ
ሲጮኽ፣
በእርግጥ ክንዱን የሚያነሣበት ማንም
የለም።
25በመከራ ውስጥ ላሉት አላለቀስሁምን?
ለድኾችስ ነፍሴ አላዘነችምን?
26ነገር ግን መልካም ስጠብቅ፣ ክፉ ነገር
ደረሰብኝ፤
ብርሃንንም ስጠባበቅ፣ ጨለማ መጣብኝ።
27በውስጤ ያለው ነውጥ አላቋረጠም፤
የመከራ ዘመንም መጣብኝ።
28በፀሓይ አይደለም እንጂ፣ ጠቋቍሬ
እዞራለሁ፤
በጉባኤ መካከል ቆሜ ለርዳታ እጮኻለሁ።
29የቀበሮች ወንድም፣
የጕጕቶችም ባልንጀራ ሆኛለሁ።
30ቈዳዬ ጠቍሮ ተቀረፈ፤
ዐጥንቴም በትኵሳት ነደደ።
31በገናዬ ለሐዘን፣
እምቢልታዬም ለልቅሶ ተቃኝቶአል።

31 “ወደ ኰረዳዪቱ ላለመመልከት፣
ከዐይኔ ጋር ቃል ኪዳን ገብቻለሁ።
2ከላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሰው ዕድል
ፈንታው፣
ከአርያም ሁሉን ከሚችል አምላክስ
ዘንድ ቅርሱ ምንድነው?
3ለኀጢአተኞች ጥፋት፣
ክፉ ለሚያደርጉም መቅሠፍት
አይደለምን?
4እርሱ መንገዴን አያይምን?
እርምጃዬንስ ሁሉ አይቈጥርምን?
5“በሐሰት ሂጄ እንደ ሆነ፣
እግሬም ወደ ሽንገላ ቸኵሎ ከሆነ፣
6እግዚአብሔር በእውነተኛ ሚዛን ይመዝነኝ፤
ነውር እንደሌለብኝም ይወቅ።
7እርምጃዬ ከመንገድ ወጣ ብሎ፣
ልቤ ዐይኔን ተከትሎ፣
ወይም እጄ ረክሶ ከሆነ፣
8የዘራሁትን ሌላ ይብላው፤
ሰብሌም ተነቅሎ ይጥፋ።
9“ልቤ ሌላዋን ሴት ከጅሎ፣
በባልንጀራዬ ደጅ አድብቼ ከሆነ፣
10ሚስቴ የሌላ ሰው እህል ትፍጭ፤
ሌሎች ሰዎችም ይተኙት፤
11ይህ አሳፋሪ፣
ፍርድም የሚገባው ኀጢአት ነውና።
12ይህ የሚያቃጥልና የሚያጠፋ[ደ] እሳት
ነው፤
ቡቃያዬንም ሊነቃቅል ነበር።
13“ወንዶችና ሴቶች አገልጋዮቼ አቤቱታ
ባቀረቡ ጊዜ፣
ፍርድ አዛብቼ ከሆነ፣
14እግዚአብሔር ሲነሣ ምን አደርጋለሁ?
ሲጠይቀኝስ ምን መልስ እሰጣለሁ?
15እኔን በማሕፀን ውስጥ የፈጠረኝ እነርሱን
የፈጠረ አይደለምን?
በሆድ ውስጥ የሠራንስ እርሱ ራሱ
አይደለምን?
16“ለድኻ የሚያስፈልገውን ከልክዬ ከሆነ፣
ወይም የመበለቲቱን ዐይን አፍዝዤ
ከሆነ፣
17እንጀራዬን ከድኻ አደጉ ጋር ሳልካፈል፣
ለብቻዬ በልቼ ከሆነ፣
18ይልቁን ድኻ አደጉን ከታናሽነቴ ጀምሮ
እንደ አባት አሳደግሁት፤
መበለቲቱንም ከተወለድሁ ጀምሮ
መንገድ መራኋት፤
19በልብስ ዕጦት ሰው ሲጠፋ፣
ወይም ዕርቃኑን ያልሸፈነ ድኻ አይቼ፣
20በበጎቼ ጠጕር ስላሞቅሁት፣
ልቡ ባርኮኝ ካልሆነ፣
21በአደባባይ ተሰሚነት አለኝ ብዬ፣
በድኻ አደጉ ላይ እጄን አንሥቼ ከሆነ፣
22ትከሻዬ ከመጋጠሚያው ይነቀል፤
ክንዴም ከመታጠፊያው ይሰበር፤

30፥18 ኢዮ9፥4
30፥19 ዘፍ3፥19፤ ኢዮ2፥8፤መዝ40፥2፤ 69፥2፡14፤130፥1፤ኤር 38፥6፡22
30፥20 1ነገ8፥52፤ ኢዮ19፥7፤መዝ34፥ 17፤ምሳ2፥3፤ሰቆ3፥8፤ ሚክ4፥9
30፥21 ኢዮ4፥5፤ 6፥4፤10፥3፤ኢሳ9፥12፤ 14፥26፤31፥3፤ኤር6፥2 3፤30፥14፤50፥42፤ ሕዝ6፥14
30፥22 ኢዮ9፥17፤ 27፥21፤ይሁ1፥12
30፥23 2ሳሙ14፥ 14፤ኢዮ3፥13፡19፤ 10፥3
30፥24 ኢዮ19፥7፤ መዝ145፥14፤ኢሳ 42፥3፤57፥15
30፥25 ኢዮ24፥4፤ መዝ35፥13-14፤ሉቃ 19፥41፤ሮሜ12፥15፤ ፊል3፥18
30፥26 ኢዮ3፥6፡ 17፤19፥8፤መዝ82፥5፤ ኤር4፥23
30፥27 ቍ16፤መዝ 38፥8፤ሰቆ2፥11
30፥28 ኢዮ17፥ 14፤19፥7፤24፥12፤ ሰቆ4፥8
30፥29 መዝ44፥ 19፤102፤6፤ኢሳ34፥ 13፤ኤር 9፥11፤ ሚክ1፥8
30፥30 ዘዳ28፥35፤ ኢዮ16፥16፤17፥14፤ መዝ102፥3፤ሰቆ1፥13፤ 3፥4፤4፥8፤5፥10
30፥31 ዘፍ4፥21፤ 8፥8፤መዝ137፥2፤ኢሳ 16፥11፤24፥8፤ሕዝ 26፥13
31፥1 ዘፀ20፥14፡17፤ ዘዳ5፥18፤ምሳ4፥25፤ 17፥24፤ማቴ5፥28፤ 2ጴጥ2፥14
31፥2 ዘኍ26፥55፤ ኢዮ16፥19፤20፥29፤ መዝ11፥6፤16፥5፤50፥1 8፤መክ3፥22፤5፥19፤9፥ 9
31፥3 ኢዮ18፥12፤ 21፥30፤34፥22፤ሮሜ 2፥9
31፥4 ቍ14፤2ዜና 16፥9፤ኢዮ10፥4፤መዝ 139፥3፤ዳን4፥37፤5፥23
31፥5 ኢዮ15፥31
31፥6 ዘፍ6፥9፤ዘሌ 19፥36፤ኢዮ2፥3፤6፥2፤ 23፥10፤መዝ139፥23
31፥7 ኢዮ9፥30፤ 23፥11፤መዝ7፥3
31፥8 ቍ12፤ኢዮ 5፥5፤20፥10፤ሚክ 6፥15፤ዮሐ4፥37
31፥9 ዘዳ11፥16፤ ኢዮ24፥15፤ምሳ5፥3፤ 7፥5፤ያዕ1፥14 31፥10 ዘዳ28፥30፤መሳ16፥21 31፥11 ዘፍ38፥ 24፤ዘፀ21፥12፤ምሳ6፥32-33፤ዮሐ8፥4-5 31፥12 ቍ8፤ኢዮ15፥ 30፤26፥6 31፥13 ዘፀ21፥2-11፤ዘሌ25፥39-46፤ዘዳ5፥14፤24፥14- 15 31፥14 ቍ4፡37፤ ኢዮ33፥5፤መዝ10፥13፡15፤94፥7፤ኢሳ10፥ 3፤ኤር5፥31፤ሆሴ9፥7፤ሚክ7፥4፤ቈላ4፥1 31፥15 ኢዮ4፥17፤10፥ 3፤ምሳ22፥2፤ኤፌ6፥9 31፥16 ዘሌ25፥17፤ኢዮ5፥16፤22፥7፡9፤ ያዕ1፥27 31፥17 ኢዮ6፥27፤22፥7 31፥18 ኢሳ51፥18 31፥19 ኢዮ22፥6፤24፥4፤ኢሳ58፥7 31፥20 መሳ6፥37፤ኢዮ29፥13 31፥ 21 ኢዮ 22፥7፤29፥7፡9፤ያዕ1፥27 31፥22 ዘኍ15፥30፤ ኢዮ5፥15፤38፥ 15፤መዝ10፥15፤37፥17፤137፥5

[የ]18 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን፣ *እንደ ልብስ ሆኖብኛል* ይላል።
[ደ]12 ዕብራይስጡ *አባዶን* ይላል።

23የእግዚአብሔርን ቍጣ በመፍራቴ፣
እንዲህ ያሉ ነገሮች መፈጸም
አልቻልሁም።

24“ወርቅን ተስፋ አድርጌ፣
ወይም ንጹሑን ወርቅ፣ ‘አንተ
መታመኛዬ ነህ’ ብዬ ከሆነ፣
25እጄ ባገኘችው ሀብት፣
በባለጠግነቴም ብዛት ደስ ብሎኝ ከሆነ፣
26የፀሓይን ድምቀት አይቼ፣
ወይም የጨረቃን አካሄድ ግርማ
ተመልክቼ፣
27ልቤ በስውር ተታልሎ፣
ስለ ክብራቸው አፌ እጄን ስሞ ከሆነ፣
28ለልዑል እግዚአብሔር ታማኝ አለመሆኔ
ነውና፣
ይህም ደግሞ የሚያስቀጣኝ በደል በሆነ
ነበር።

29“በጠላቴ ውድቀት ደስ ብሎኝ፣
በደረሰበትም መከራ ሐሤት አድርጌ
እንደ ሆነ፣
30እኔ ግን በነፍሱ ላይ ክፉ እንዲመጣ
በመራገም፣
አንደበቴን ለኀጢአት ከቶ አሳልፌ
አልሰጠሁም።
31የቤቴ ሰዎች፣ ‘ከኢዮብ ከብት ሥጋ
አስቈርጦ፣
ያልጠገበ ማን ነው’ ብለው ካልሆነ፣
32ነገር ግን ቤቴ ለመንገደኛው ዘወትር
ክፍት ስለ ነበር፣
መጻተኛው በጐዳና ላይ አያድርም ነበር።
33ሰዎች[ጀ] እንደሚያደርጉት በደሌን በልቤ
በመሰወር፤
ኀጢአቴን ሸሽጌ ከሆነ፣
34ሕዝቡን በመፍራት፣
የወገኖቼንም ንቀት በመሸሸ፣
ወደ ደጅ ሳልወጣ፣ ዝም ብዬ ቤት
ውስጥ አልተቀመጥሁም።

35“ምነው የሚሰማኝ ባገኝ!
የመከላከያ ፊርማዬ እነሆ፤ ሁሉን
የሚችል አምላክ ይመልስልኝ፤
ከሳሼም ክሱን በጽሑፍ ያቅርብ።
36በእርግጥ ትከሻዬ ላይ በደረብሁት፣
እንደ አክሊልም ራሴ ላይ በደፋሁት
ነበር።
37እያንዳንዱን ርምጃዬን በገለጽሁለት፣
እንደ ልዑል እየተንጐራደድሁ
በቀረብሁት ነበር።

38“ዕርሻዬ በእኔ ላይ ጮኻ ከሆነ፣
ትልሞቿ ሁሉ በእንባ ርሰው እንደ ሆነ፣
39ፍሬዋን ያለ ዋጋ በልቼ፣
የባለመሬቶቿን ነፍስ አሳዝኜ ከሆነ፣

31፥23 ዘፍ20፥11፤ ኢዮ10፥3፤ 13፥11፤ 30፥15
31፥24 ኢዮ22፥25፤ ማቴ6፥24፤ሉቃ12፥15
31፥25 ዘፍ12፥16፤ ኢዮ22፥24፤መዝ49፥6፤52፥7፤62፥10፤ኢሳ 10፥14፤ሕዝ28፥5፤ ሉቃ12፥20-21
31፥26 ዘፍ1፥16፤ ኢዮ25፥5
31፥27 ዘዳ11፥16፤ ኢዮ24፥15፤ኤር8፥2፤ 16፥11፤ያዕ1፥14
31፥28 ዘፍ38፥24፤ ዘኍ11፥20፤ዘዳ17፥2-7፤ሕዝ8፥16
31፥29 ዘኍ14፥1፤ መዝ35፥15፤ ምሳ 17፥5፤24፥17-18፤አብ 1፥12፤ማቴ5፥44
31፥30 ኢዮ5፥3፤ ሮሜ12፥14
31፥31 ኢዮ22፥7
31፥32 ዘፍ19፥2-3፤ መሳ19፥20፤ማቴ25፥35፤ሮሜ12፥13
31፥33 ዘፍ3፥8፤ መዝ32፥5፤ምሳ 28፥13
31፥34 ዘፀ23፥2፤ መዝ32፥3፤39፥2
31፥35 ኢዮ9፥24፤ 27፥7፤30፥28
31፥36 ዘፀ28፥12፤ ኢዮ29፥14
31፥37 ቍ14፤ኢዮ 11፥11፤21፥28
31፥38 ዘፍ4፥10፤ መዝ65፥10
31፥39 ዘሌ19፥13፤ 1ነገ21፥19፤ያዕ5፥4
31፥40 ዘፍ3፥18፤ መዝ72፥20፤ኤር5 1፥64፤ሰፎ2፥9፤ማቴ 13፥7፡26
32፥1 ቍ15፤ኢዮ 2፥3፤10፥7
32፥2 ቍ1፤ዘፍ 22፥21፤ኢዮ13፥19፤ 27፥5፤30፥21፤35፥2
32፥3 ቍ12-13፤ ኢዮ15፥13፤42፥7
32፥4 ዘሌ19፥32
32፥6 ኢዮ15፥10
32፥7 1ዜና29፥15፤ 2ዜና10፥6
32፥8 ቍ18፤ኢዮ 12፥13፤27፥3፤መዝ 119፥34፤ያዕ1፥5
32፥9 ኢዮ12፥12፡ 20፤መዝ119፥100፤ ሉቃ2፥47፤1ቆሮ1፥26፤ 1ጢሞ4፥12
32፥10 ኢዮ5፥27፤ 33፥1፡31፡33፤34፥2፡ 16፤37፥2፡14፤መዝ 34፥11
32፥12 ቍ3
32፥13 ኢዮ4፥12፤ 11፥5፤መክ9፥11

40በስንዴ ፈንታ እሾህ፣
በገብስም ምትክ ዐረም ይብቀልብኝ።”

የኢዮብ ቃል ተፈጸመ።

## ኤሊሁ

32 ኢዮብ በበኩሉ ራሱን እንደ ጻድቅ
ቈጥሮ ስለ ነበር፣ እነዚህ ሦስት
ሰዎች ለእርሱ መልስ መስጠታቸውን ተዉ።
2ከራም ወገን የሆነው፣ የቡዛዊው የባርክ
ኤል ልጅ ኤሊሁ ግን ኢዮብ ከእግዚአብሔር
ይልቅ ራሱን ጻድቅ ስላደረገ፣ እጅግ ተቈ
ጣው። 3ሦስቱ የኢዮብ ጓደኞች በኢዮብ
ላይ መፍረድ[ገ] እንጂ፣ ነገሩን ሊያሳምኑት
ስላልቻሉ፣ በእነርሱም ላይ ተቈጣ። 4ኤሊ
ሁ፣ ሌሎቹ በዕድሜ ይበልጡት ስለ
ነበር ከእነ ርሱ ቀድሞ ለኢዮብ ሳይናገር
ቈየ። 5ነገር ግን እነዚህ ሦስቱ የሚሉትን
ባጡ ጊዜ ቍጣው ነደደ።
6ስለዚህ የቡዛዊው የባርክኤል ልጅ ኤሊሁ
እንዲህ አለ፤

“እኔ በዕድሜ ታናሽ ነኝ፤
እናንተ ግን አዛውንቶች ናችሁ፤
ከዚህም የተነሣ የማውቀውን ለመናገር
አልደፈርሁም፤
ፈርቼ ዝም አልሁ።
7‘ዕድሜ ይናገራል፤
ረጅም ዘመን ጥበብን ያስተምራል’ ብዬ
ነበር።
8ነገር ግን በሰው ያለው መንፈስ፣
ሁሉን የሚችል አምላክ እስትንፋስ፣
ማስተዋልን ይሰጣል።
9ጠቢባን የሚሆኑት በዕድሜ የገፉ[ጠ] ብቻ
አይደሉም፤
የሚያስተውሉም ሽማግሌዎች ብቻ
አይደሉም።

10“ስለዚህ፣ ‘ስሙኝ፣
እኔም የማውቀውን ልንገራችሁ’
እላለሁ።
11እናንተ በምትነጋገሩበት ጊዜ ታገሥሁ፤
ቃላት እየመረጣችሁ፣
ስትናገሩ በጥሞና ሰማኋችሁ፤
12በሙሉ ልብ አዳመጥኋችሁ፤
ነገር ግን ከእናንተ የኢዮብን ቃል
ያስተባበለ ማንም የለም፤
ለንግግሩም አጻፋ የመለሰ አልተገኘም።
13‘እኛ ጥበብ አግኝተናል፤
ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር ይርታው’
አትበሉ።

[ጀ]33 ወይም *አዳም እንዳደረገው*
[ገ]3 የማሶሬቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ጥንታዊው የዕብራውያን ጸሐፍት ትውፊት ግን *ኢዮብንም ሆነ እግዚአብሔርን ኰነኑ* ይላል።
[ጠ]9 ወይም፣ *ብዙ* ወይም፣ *ታላቅ*

14ኢዮብ ግን ቃሉን በእኔ ላይ አልሰነዘረም፤
እኔም እንደ እናንተ አነጋገር መልስ
አልሰጠውም።

15“እነርሱ ተስፋ ቈርጠው፤ የሚሉት
የላቸውም፤
የሚናገሩትም ጠፍቶአቸዋል።
16እንግዲህ እነርሱ መልስ ስላጡ፣
ጸጥ ብለውም ስለ ቆሙ፣ በትዕግሥት
ልጠብቅን?
17እኔም የምለው ይኖረኛል፤
የማውቀውንም እገልጣለሁ።
18የምናገረው ሞልቶኛልና፤
በውስጤ ያለውም መንፈስ ገፋፍቶኛል።
19ውስጤ እንደ ተከደነና መተንፈሻ እንዳጣ
የወይን ጠጅ፣
ሊፈነዳ እንደ ተቃረበም አዲስ የወይን
ጠጅ አቁማዳ ሆኖአል።
20ተናግሬ መተንፈስ አለብኝ፤
አፌንም ከፍቼ መልስ መስጠት
ይገባኛል።
21ለማንም አላደላም፤
ሰውንም አላቈላምጥም።
22ማቈላመጥን ባውቅበትማ ኖሮ፣
ፈጣሪዬ ፈጥኖ ባጠፋኝ ነበር።

# 33

“አሁን ግን ኢዮብ ሆይ፣ ንግግሬን
ስማ፤
የምለውንም ሁሉ አድምጥ።
2እንግዲህ አፌን እከፍታለሁ፤
አንደበቴም ይናገራል።
3ቃሌ ከቅን ልብ ይወጣል፤
ከንፈሬም የማውቀውን በትክክል ይናገራል።
4የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጥሮኛል፤
ሁሉን የሚችለውም አምላክ
እስትንፋስ ሕይወት ሰጥቶኛል።
5የምትችል ከሆነ መልስልኝ፤
ተዘጋጅተህም በፊቴ ቁም።
6በእግዚአብሔር ፊት እኔም እንዳንተው ነኝ፤
የተፈጠርሁትም ደግሞ ከዐፈር ነው።
7እኔን መፍራት የለብህም፤
እጄም ሊከብድብህ አይገባም።

8“በእርግጥ የተናገርኸውን ሰምቻለሁ፤
እንዲህም ስትል አድምጫለሁ፤
9‘ኀጢአት የሌለብኝ ንጹሕ ነኝ፤
ከበደል ነጻ ነኝ፤ እድፈትም የለብኝም፤
10እግዚአብሔር ግን ሰበብ ፈልጎብኛል፤
እንደ ጠላቱም ቈጥሮኛል፤
11እግሬን በግንድ አጣብቆአል፤
እንቅስቃሴዬንም ሁሉ ይከታተላል።’

12“ነገር ግን እግዚአብሔር ከሰው ስለሚበልጥ፣
ትክክል እንዳልሆንህ እነግርሃለሁ።
13የሰውን አቤቱታ[ጨ] እንደማይሰማ፣
ለምን ታማርርበታለህ?
14ሰው ባያስተውለውም፣
እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ ይናገራ
ል፤
15ሰዎች ዐልጋቸው ላይ ተኝተው ሳሉ፣
ከባድ እንቅልፍ ሲወድቅባቸው፣
በሕልም፣ በሌሊትም ራእይ፣ ይናገራል።
16በጆሯቸው ይናገራል፤
በማስጠንቀቂያም ያስደነግጣቸዋል፤
17ሰውን ከክፉ ሥራው ይመልሳል፤
ከትዕቢት ይጠብቃል፤
18ነፍሱን ከጒድጓድ፤[ጸ]
ሕይወቱንም ከሰይፍ[ጸ] ጥፋት ያድናል።
19ደግሞም ሰው ታሞ በዐልጋው ላይ ሳለ፣
በዐጥንቱ የዘወትር ሥቃይ ይገሥጸዋል፤
20ያኔም ሕይወቱ መብልን ትጠላለች፤
ነፍሱም ምርጥ ምግብን ትጠየፋለች።
21እንዳልነበረ ሆኖ ሥጋው ይመነምናል፤
ተሸፍኖ የነበረው ዐጥንቱም ገጦ ይወጣል።
22ነፍሱ ወደ ጒድጓድ፣[ፀ]
ሕይወቱም ወደ ሞት[ፈ] መልእክተኞች
ትቀርባለች።

23“ሆኖም ትክክለኛውን መንገድ ለሰው
ያመለክት ዘንድ፣
መካከለኛም ይሆንለት ዘንድ፣
ከሺህ አንድ መልአክ ቢገኝ፣
24ለሰውየውም በመራራት፣
‘ቤዛ አግኝቼለታለሁና፣
ወደ ጒድጓድ[ፐ] እንዳይወርድ አድነው’
ቢለው፣
25በዚህ ጊዜ ሥጋው እንደ ሕፃን ልጅ ገላ
ይታደሳል፤
ወደ ወጣትነቱም ዘመን ይመለሳል።
26ወደ እግዚአብሔር ይጸልያል፤ ሞገስም
ያገኛል፤
የእግዚአብሔርን ፊት ያያል፤ ሐሤትም
ያደርጋል፤
እግዚአብሔር ወደ ጽድቅ ቦታው
ይመልሰዋል።
27ከዚያም ወደ ሰዎች መጥቶ እንዲህ ይላል፤
‘ኀጢአትን ሠርቻለሁ፤ ትክክል የሆነውን
አጣምሜአለሁ፤
ነገር ግን የእጄን አላገኘሁም።

32፥14 ኢዮ23፥4
32፥15 ቍ1
32፥17 ኢዮ5፥27፤ 33፥3፤36፥4
32፥18 ቍ8፤ሐሥ 4፥20፤1ቆሮ9፥16፤ 2ቆሮ5፥14
32፥19 ኤር20፥9፤ አሞ3፥8፤ማቴ9፥17
32፥20 ኢዮ4፥2፤ ኤር6፥11
32፥21 ዘሌ19፥15፤ 2ዜና19፥7፤ኢዮ13፥ 10፤ምሳ29፥5፤ማቴ 22፥16፤1ተሰ2፥5
32፥22 ኢዮ4፥17፤ 9፥9፤መዝ12፥2-4
33፥1 ኢዮ6፥28፤ 13፥6፤32፥10
33፥3 1ነገ3፥6፤ኢዮ 6፥28፤መዝ7፥10፤11፥2 ፤64፥10
33፥4 ዘፍ1፥2፤ዘኍ 16፥22፤ኢዮ10፥3፤ 12፥10፤27፥3
33፥5 ቍ32፥ኢዮ 13፥18፤31፥14
33፥6 ኢዮ4፥19፤ ሐሥ14፥15፤ያዕ5፥17
33፥7 ኢዮ9፥34፤ 2ቆሮ2፥4
33፥9 ኢዮ2፥9፤9፥ 30፤10፥7፤13፥23
33፥10 ኢዮ13፥24
33፥11 ኢዮ13፥27፤ 14፥16፤ምሳ3፥6፤ ኢሳ30፥21
33፥12 ኢዮ5፥9፤ መዝ8፥4፤50፥21፤መክ 7፥20፤ኢሳ55፥8-9
33፥13 ኢዮ11፥8፤ 40፥2፤ኢሳ45፥9
33፥14 ቍ29፤ኢ ዮ4፥12፤መዝ62፥11
33፥15 ዘፍ2፥21፤ 15፥1፤20፥3፤ኢዮ4፥ 13፤ዳን2፥19፤ማቴ 27፥19፤ሐሥ16፥9
33፥16 ኢዮ6፥4፤ 36፥10፡15፤መዝ88፥ 15፡16
33፥17 ኢዮ20፥6
33፥18 ቍ22፡24፡ 28፡30፤ኢዮ15፥22፤ መዝ28፥1፤30፥9፤69፥1 5፤88፥6፤103፥4፤ምሳ1 ፥12፤ኢሳ14፥15፤ 38፥17፤ዮና2፥6፤ዘካ9፥ 11፤ማቴ26፥52
33፥19 ዘፍ17፥1፤ ዘዳ8፥5፤ኢዮ5፥17፤ 16፥16፤መዝ6፥2፤38፥3 ፤ኢሳ38፥13፤2ቆሮ 12፥7-10፤ያዕ1፥3
33፥20 ኢዮ3፥24፤ 6፥6፤መዝ102፥4፤ 107፥18
33፥21 ኢዮ2፥5፤ 16፥8
33፥22 ቍ18፤
33፥28 ቍ18፤ዘፀ 15፥13፤ኢዮ17፥16፤ 22፥28፤መዝ34፥22፤
ኢዮ 38፥17፤መዝ9፥13፤88፥3፤107፥18፤116፥3 33፥23 ኢዮ 36፥9-10፤ሚክ6፥8፤ገላ3፥19፤ዕብ8፥6፤9፥15 33፥24 ቍ18፤ኢዮ 6፥22 33፥25 2ነገ5፥14፤መዝ103፥5 33፥26 ዕዝ3፥13፤ኢዮ 5፥15፤22፥26፤መዝ13፥5፤50፥15፤51፥12፤ምሳ8፥35፤12፥2፤18፥22፤ ሉቃ2፥52፤1ዮሐ1፥9 33፥27 ዘኍ22፥34፤ዕዝ9፥13፤መዝ22፥27፤ 51፥13፤ሉቃ15፥21፤ ሮሜ6፥21፤ያዕ2፥13

[ጨ]13 ወይም፣ *ለምግባሩ ምንም እንደማይመልስ*
[ጸ]18 ወይም፣ *ነፍሱን ከመቃብር*
[ጸ]18 ወይም፣ *ወንዝን ከመሻገር*
[ፀ]22 ወይም፣ *ነፍሱ ወደ ሞት*
[ፈ]22 ወይም፣ *ወደ ሙታን*
[ፐ]24 ወይም፣ *ወደ መቃብር*

28ነፍሴ ወደ ጕድጓድ[ሀ] እንዳትወርድ፣
ታድጎአታል፤
በሕይወትም ሆኜ ብርሃን አያለሁ።’

29“እግዚአብሔር ይህን ሁሉ፣
ሁለት ሦስት ጊዜ ለሰው ያደርጋል፤
30ይኸውም የሕይወት ብርሃን ይበራለት ዘንድ፣
ነፍሱን ከጕድጓድ[ለ] ለመመለስ ነው።

31“ኢዮብ ሆይ፤ ልብ ብለህ ስማኝ፤
እኔ ልናገር፤ አንተ ዝም በል።
32የምትለው ካለህ፣ መልስ ስጠኝ፤
ትክክለኛነትህንም ማወቅ እፈልጋለሁና
ተናገር፤
33አለበለዚያ፣ ዝም ብለህ ስማኝ፤
እኔም ጥበብን አስተምርሃለሁ።”

34 ኤሊሁ በመቀጠል እንዲህ አለ፤
2“እናንት ጠቢባን፣ ቃሌን ስሙ፤
ዐዋቂዎችም አድምጡኝ።
3ምላስ ምግብን አጣጥሞ እንደሚለይ፣
ጆሮም የንግግርን ለዛ ለይቶ ያውቃል።
4የሚበጀንን እንምረጥ፣
መልካሙንም አብረን እንወቅ።

5“ኢዮብ እንዲህ ይላል፤ ‘እኔ ንጹሕ ነኝ፤
እግዚአብሔር ግን ፍትሕ ነሣኝ፤
6እውነተኛ ብሆንም፣
እንደ ውሸታም ተቈጥሬአለሁ፤
በደል ባይኖርብኝም፣
በማይፈወስ ቍስል ተመትቻለሁ።’
7ፌዝን እንደ ውሃ የሚጠጣት፣
እንደ ኢዮብ ያለ ሰው ማን ነው?
8ከክፉ አድራጊዎች ጋር ይተባበራል፤
ከኀጢአተኞችም ጋር ግንባር ይፈጥራል።
9‘እግዚአብሔርን ለማስደሰት መሞከር፣
ለሰው አንዳች አይጠቅምም’ ብሎአልና።

10“ስለዚህ፣ እናንተ አስተዋዮች ስሙኝ፤
ክፋትን ማድረግ ከእግዚአብሔር ዘንድ፣
በደልንም መፈጸም ሁሉን ከሚችል
አምላክ ይራቅ።
11ለሰው እንደ ሥራው ይመልስለታል፤
እንደ አካሄዱም ይከፍለዋል።
12በእውነት እግዚአብሔር ክፋትን አይሠራም፤
ሁሉን የሚችል አምላክ ፍትሕን
አያጣምምም።
13ምድርን እንዲገዛ የሾመው አለን?
የዓለምስ ሁሉ ባለቤት ያደረገው ማን ነው?
14እርሱ መንፈሱን መልሶ ቢወስድ፣
እስትንፋሱንም ወደ ራሱ ቢሰበስብ፣
15ሥጋ ለባሽ ሁሉ በአንድነት በጠፋ፣
ሰውም ወደ ዐፈር በተመለሰ ነበር።

16“ማስተዋል ካለህ ይህን ስማ፤
እኔ የምለውንም አድምጥ።
17ፍትሕን የሚጠላ ሊያስተዳድር ይችላልን?
አንተስ ጻድቁንና ኀያል የሆነውን
ትኰንናለህ?
18ነገሥታትን ‘የማትረቡ ናችሁ፣’
መኳንንትንም፣ ‘ክፉዎች ናችሁ’
የሚላቸው እርሱ አይደለምን?
19ሁሉም የእጁ ሥራ ስለ ሆኑ፣
እርሱ ለገዥዎች አያደላም፤
ባለጠጋውንም ከድኻው አብልጦ
አይመለከትም።
20እነርሱም እኩለ ሌሊት ላይ በድንገት
ይሞታሉ፤
ሕዝብ ተንቀጥቅጦ ሕይወቱ ያልፋል፤
ኀያላኑም የሰው እጅ ሳይነካቸው
ይወገዳሉ።

21“ዐይኖቹ የሰውን አካሄድ ይመለከታሉ፤
ርምጃውንም ሁሉ ይከታተላሉ።
22ክፉ አድራጊዎች የሚደበቁበት፣
ጨለማ ስፍራ ወይም የሞት ጥላ የለም።
23ሰው ለፍርድ ፊቱ ይቀርብ ዘንድ፣
እግዚአብሔር ቀጠሮ አይዝለትም።
24ያለ ምንም ጥያቄ ኀያላንን
ያንኰታኵታል፤
ሌሎችንም በቦታቸው ይሾማል።
25እርሱ ሥራቸውን ሁሉ ስለሚያውቅ፣
በሌሊት ይገለብጣቸዋል፤
እነርሱም ይደቃሉ።
26ስለ ክፋታቸውም፣
በሰው ሁሉ ፊት ይቀጣቸዋል፤
27እርሱን ከመከተል ተመልሰዋልና፤
መንገዱንም ችላ ብለዋል።
28የድኾች ልቅሶ ወደ እርሱ እንዲደርስ
ሰበብ ሆኑ፤
የመከረኞችን ጩኸት ሰማ።
29እርሱ ዝም ቢል፣ ማን ሊወቅሰው
ይችላል?
ፊቱንስ ቢሰውር፣ ማን ሊያየው
ይችላል?
እርሱ ከሰውም፣ ከሕዝብም በላይ ነው፤
30ይህም የሆነው ዐመፀኛው ሕዝቡን
እንዳይገዛ፣

107፥20
33፥29 ቍ14፤መዝ 139፥16፤ምሳ16፥9፤ 20፥24፤ኤር10፥23፤ 1ቆሮ12፥6፤ኤፌ1፥11፤ ፊል2፥13
33፥30 ቍ18፤መዝ 49፥19፤56፥13፤116፥9 ፤ኢሳ53፥11፤60፥1፤ ኤፌ5፥14፤ያዕ5፥19
33፥31 ቍ33፤ኢዮ 32፥10፤ኤር23፥18
33፥32 ቍ5፤ ኢዮ 6፥29፤35፥2
33፥33 ቍ31፤ኢዮ 6፥24፤32፥10፤ምሳ10፥ 8፡10፡19
34፥2 ኢዮ32፥10
34፥3 ኢዮ12፥11
34፥4 ኢዮ12፥12፤ 1ተሰ5፥21፤ዕብ5፥14
34፥5 ኢዮ6፥29፤ 10፥7
34፥6 ኢዮ6፥4፡28፤ 9፥21፤10፥3፤ኤር10፥1 9
34፥7 ኢዮ9፥21፤ 15፥16
34፥8 ኢዮ22፥15
34፥9 ኢዮ9፥29- 31፤21፥15
34፥10 ቍ12፡16፤ ዘፍ18፥25፤ዘዳ32፥4፤ኢ ዮ8፥3፤12፥12፤32፥ 10፥36፥23፤መዝ92፥ 15፤ሮሜ3፥5፤9፥14
34፥11 ኢዮ21፥31፤ ኤር17፥10፤32፥19፤ሕ ዝ33፥20፤ማቴ16፥27
34፥12 ቍ10፤ኢዮ 8፥3፤መዝ9፥16፤ቈላ 3፥25፤2ተሰ1፥6፤ቲቶ 1፥2፤ዕብ6፥18
34፥13 ኢዮ36፥23፤ 38፥4፡6፤ኢሳ40፥14፤ ዕብ1፥2
34፥14 ዘፍ6፥3፤ ዘኍ16፥22፤ኢዮ27፥3
34፥15 ዘፍ2፥7፤6፥ 13፤ኢዮ7፥21፤9፥22፤ መዝ90፥10፤ሰቆ3፥22፤ ሚል3፥6፤ዮሐ3፥16
34፥16 ቍ10፤ኢዮ 32፥10
34፥17 ቍ29፡30፤ 2ሳሙ23፥3-4፤ኢዮ 10፥7፤40፥8፤ምሳ20፥8፡ 26፤24፥23-25፤ 28፥28፤ሮሜ3፥5-6
34፥18 ዘፀ22፥28፤ ኢዮ12፥18፤ኢሳ 40፥24
34፥19 ዘሌ19፥15፤ ኢዮ10፥3፤13፥10፤ ሐሥ10፥34፤ያዕ2፥5
34፥20 ቍ25፤ዘፀ 11፥4፤ኢዮ12፥19፤ 20፥8

34፥21 ኢዮ14፥16፤ምሳ15፥3፤ኤር32፥19፤ዕብ4፥13 34፥22 ዘፍ3፥8፤ኢዮ3፥5፤11፥20፤መዝ74፥20 34፥23 ኢዮ11፥11፤ መዝ11፥4 34፥24 ኢዮ12፥19፤ኢሳ8፥9፤9፥4፤ኤር51፥20፤ዳን 2፥21፡34 34፥25 ቍ20፤ኢዮ11፥11፤ምሳ5፥21-23 34፥26 ዘፍ6፥5፤ኢዮ8፥22፤28፥24፤መዝ9፥5፤ኤር44፥5 34፥27 1ሳሙ 15፥11፤መዝ14፥3 34፥28 ዘፀ22፥23፤ኢዮ5፥15፤12፥19 34፥29 ቍ17፤መዝ13፥1፤28፥1፤83፥1፡18፤97፥9፤109፥1፤ሮሜ8፥34 34፥30 ቍ17፤ኢዮ 8፥13፤መዝ25፥15፤31፥4፤ 91፥3፤124፥7፤140፥5፤ምሳ29፥2-12

[ሀ]28 ወይም፣ *ወደ መቃብር እንዳልሄድ ታድጎኛል*
[ለ]30 ወይም፣ *ነፍሱን ከሞት ለመመለስ ነው*

ወጥመድም በፊታቸው እንዳይዘረጋ ነው።
31“ሰው ለእግዚአብሔር እንዲህ ቢል፣ የተሻለ ነበር፤
‘እኔ በደለኛ ነኝ፤ ከእንግዲህ ግን አልበድልም፤
32ማየት ያልቻልሁትን አስተምረኝ፤
ኀጢአት ሠርቼ እንደ ሆነም፣ ደግሜ አልሠራም።’
33ታዲያ አንተ ለመናዘዝ ፈቃደኛ ሳትሆን፤
እግዚአብሔር እንደ ወደድህ ይከፍልሃልን?
መወሰን ያለብህ አንተ ነህ እንጂ፣ እኔ አይደለሁም፤
እንግዲህ የምታውቀውን ንገረኝ።
34“አስተዋዮች ይናገራሉ፤
የሚሰሙኝም ጠቢባን እንዲህ ይሉኛል፤
35‘ኢዮብ ያለ ዕውቀት ይናገራል፤
ቃሉም ማስተዋል ይጐድለዋል።’
36ምነው ኢዮብ እስከ መጨረሻ በተፈተነ ኖሮ!
እንደ ክፉ ሰው መልሶአልና፤
37በኀጢአቱም ላይ ዐመፅን ጨምሮአል፤
በመካከላችን ሆኖ በንቀት አጨብጭቦአል፤
በእግዚአብሔርም ላይ ብዙ ተናግሮአል።

# 35

ኤሊሁ ንግግሩን በመቀጠል እንዲህ አለ፤
2“ ‘በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ ነኝ’[ሐ] ማለትህ፣
ትክክል ይመስልሃልን?
3ደግሞ ‘ያገኘሁት[መ] ጥቅም ምንድን ነው?
ኀጢአት ባለመሥራቴስ ምን አተረፍሁ?’ ብለህ ጠይቀኸዋል።
4“ለአንተና አብረውህ ላሉት ባልንጀሮችህ፣
መልስ መስጠት እፈልጋለሁ።
5ቀና ብለህ ወደ ሰማይ እይ፤
ከአንተ በላይ ከፍ ብለው ያሉትንም ደመናት ተመልከት።
6ኀጢአትህስ ቢበዛ እርሱን ምን ትጐዳዋለህ?
ኀጢአትህስ ቢበዛ ምን ያደርገዋል?
7ጻድቅ ብትሆንም ለእርሱ ምን ትሰጠዋለህ?
ከእጅህስ ምን ይቀበላል?
8ክፋትህ የሚጐዳው እንዳንተ ያለውን ሰው ብቻ ነው፤
ጽድቅህም የሚጠቅመው የሰውን ልጆች ብቻ ነው።
9“ሰው ከጭቈና ብዛት የተነሣ ይጮኻል፤
ከኀያሉም ክንድ ሥር ለመውጣት ለርዳታ ይጣራል።
10ነገር ግን እንዲህ የሚል የለም፤ ‘ፈጣሪዬ እግዚአብሔር ወዴት ነው?
በሌሊት መዝሙርን የሚሰጥ፣
11ከምድር እንስሳት ይልቅ የሚያስተምረን፣
ከሰማይ ወፎችም ይልቅ ጠቢባን የሚያደርገን፣ እርሱ የት አለ?’
12ከዐመፀኞች ትዕቢት የተነሣ፣
ሰዎች ሲጮኹ አይመልስላቸውም፤
13በእርግጥ እግዚአብሔር ከንቱ ጩኸታቸውን አይሰማም፤
ሁሉን የሚችል አምላክ አያዳምጣቸውም።
14ጕዳይህን ፊቱ አቅርበህ፣
ብዙ ጠብቀኸው፣
ግን እንዳላየኸው ስትናገር፣
ታዲያ፣ አንተን እንዴት ይስማህ!
15ደግሞም፣ ቍጣው ቅጣት እንደማያስከትል፣
ኀጢአትንም[ሠ] ከቍጥር እንደማያስገባ ተናግረሃል።
16ስለዚህ ኢዮብ አፉን በከንቱ ይከፍታል፤
ዕውቀት አልባ ቃላትም ያበዛል።

# 36

ኤሊሁ በመቀጠል እንዲህ አለ፤
2“በእግዚአብሔር ፈንታ ሆኜ የምለው አለኝ፤
ጥቂት ታገሠኝና እነግርሃለሁ።
3ዕውቀቴን ከሩቅ አመጣለሁ፤
ፈጣሪዬ ጻድቅ እንደ ሆነ እገልጻለሁ።
4ቃሌ ሐሰት እንዳልሆነ አረጋግጣለሁ፤
በዕውቀቱ ፍጹም የሆነ ሰው ከአንተ ጋር ነው።
5“እግዚአብሔር ኀያል ነው፤ ግን ማንንም አይንቅም፤
ኀያል፣ በዐላማውም ጽኑ ነው።
6ክፉዎችን በሕይወት አያኖርም፤
ለተቸገሩት ግን በቅን ይፈርዳል።
7ዐይኖቹን ከጻድቃን ላይ አያነሣም፤
ከነገሥታት ጋር በዙፋን ላይ ያስቀምጣቸዋል፤
ለዘላለምም ከፍ ከፍ ያደርጋቸዋል።
8ነገር ግን ሰዎች በሰንሰለት ቢታሰሩ፣
በመከራም ገመድ ቢጠፈሩ፣
9በእብሪት የፈጸሙትን በደል፣
ተግባራቸውን ይነግራቸዋል።
10ተግሣጹን እንዲሰሙ ያደርጋቸዋል፤
ከክፋታቸውም እንዲመለሱ ያዛቸዋል።
11ታዘው ቢያገለግሉት፣
ቀሪ ዘመናቸውን በተድላ፣

34፥31 መዝ51፥5፤ ሉቃ15፥21፤ሮሜ7፥24፤1ዮሐ1፥8፥10
34፥32 ዘፀ33፥13፤ ኢዮ33፥27፥35፥11፤ 38፥36፤መዝ15፥2፤25፥4፤27፥11፤51፥6፤86፥11፤139፥23-24፤143፥8፤ሉቃ19፥8
34፥33 2ነገ17፥13፤ ኢዮ33፥23፥36፥10፥15፥18፥21፤41፥11፤42፥6፤ምሳ17፥23፤ዮናን3፥8
34፥35 ኢዮ26፥3፤ 35፥16፤38፥2፤42፥3
34፥36 ኢዮ6፥29፤ 22፥15
34፥37 ኢዮ23፥2፤ 27፥23፥35፥16
35፥2 ኢዮ2፥9፤ 32፥2፤33፥32
35፥3 ኢዮ9፥29-31፤21፥15
35፥5 ዘፍ15፥5፤ዘዳ10፥14፤ኢዮ11፥7-9፤መዝ19፥1-4
35፥6 ኢዮ7፥20
35፥7 ኢዮ22፥2-3፤ሉቃ17፥10፤ሮሜ11፥35፤1ቆሮ4፥7
35፥8 ሕዝ18፥5-9፥24፤ዘካ7፥9-10
35፥9 ዘፀ2፥23፤ኢዮ5፥15፤12፥19፤20፥19
35፥10 ኢዮ4፥17፤ 8፥21፤መዝ42፥8፤77፥6፤119፥62፤149፥5፤ሐሥ16፥25
35፥11 ኢዮ12፥7፤ 21፥22፤ሉቃ12፥24
35፥12 1ሳሙ8፥18፤ኢዮ15፥25፤መዝ66፥ 18
35፥13 ዘዳ1፥45፤ 1ሳሙ8፥18፤ኢዮ15፥31፤ምሳ15፥8
35፥14 ኢዮ9፥11፤ 31፥35፤መዝ37፥6
35፥15 ኢዮ9፥24፤ 18፥5፤መዝ10፥11፤ሆሴ7፥2፤አሞ8፥7
35፥16 ኢዮ34፥35፥37፤1ቆሮ4፥20፤ቲቶ1፥10፤ይሁ1፥10
36፥3 ኢዮ4፥17፤ 6፥28
36፥4 ኢዮ6፥28፤ 13፥6፤32፥17፤37፥5፥16፥23
36፥5 ዘኍ23፥19፤ ኢዮ9፥4፤መዝ5፥2፤22፥24፤31፥22፤69፥33፤102፥17፤103፥10፤ሮሜ11፥29
36፥6 ኢዮ4፥10፤ 34፥26
36፥7 1ሳሙ2፥7-8፤ኢዮ4፥7፤11፥11፤መዝ11፥5፤33፥18፤34፥15፤113፥8፤ኢሳ22፥23፤ማቴ6፥18
36፥8 ቍ10፥15፥21፤2ሳሙ3፥34፤2ነገ23፥33፤መዝ107፥10፥14፤119፥67፥71 36፥9 ኢዮ15፥25 36፥10 ቍ8፤መሳ6፥8፤ኢዮ5፥17፤33፥16፤34፥33፤1ተሰ5፥22

[ሐ]2 ወይም፣ ጽድቄ ከእግዚአብሔር ጽድቅ ይበልጣል
[መ]3 ወይም፣ ያገኘሽው
[ሠ]15 ሲማኮስ፣ ቴዎዶሽንና ቩልጌት ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ነገር ግን በዕብራይስጡ የዚህ ቃል ትርጒም አይታወቅም

ዕድሜያቸውንም በርካታ ይፈጽማሉ።
[12]ባይሰሙ ግን፣
በሰይፍ[ሩ] ይጠፋሉ፤
ያለ ዕውቀትም ይሞታሉ።

[13]"ልባቸው ከእግዚአብሔር የራቀ፣ ቍጣን ያስተናግዳሉ፤
በሰንሰለት ባሰራቸውም ጊዜ እንኳ ወደ እርሱ አይጮኹም።
[14]በቤተ ጣዖት ውስጥ ዝሙት በሚፈጽሙት መካከል፣
ገና በወጣትነታቸው ይቀጫሉ።
[15]ነገር ግን የሚሠቃዩትን ከሥቃያቸው ያድናቸዋል፤
በመከራቸውም ውስጥ ይናገራቸዋል።

[16]"አንተንም ከመከራ መንጋጋ፣
ጭንቀት ወደሌለበት ወደ ሰፊ ስፍራ፣
ምርጥ ምግብ ወደ ሞላበት ማእድ ያወጣሃል።
[17]አሁን ግን ለክፉዎች የሚገባው ፍርድ በላይህ ተጭኖአል፤
ፍርድና ብይን ይዘውሃል።
[18]ባለጠግነት እንዳያታልልህ፣
የእጅ መንሻ ብዛትም እንዳያስትህ ተጠንቀቅ።
[19]ባለጠግነትህም ሆነ ብርቱ ጥረትህ ሁሉ፣
ችግር ውስጥ እንዳትገባ ሊረዳህ ይችላልን?
[20]ሰዎች ከቤታቸው[ሰ] የሚወሰዱበትን፣
ሌሊት አትመኝ።
[21]ከመከራ ይልቅ መርጠኸዋልና፣
ወደ ክፋት እንዳትመለስ ተጠንቀቅ።

[22]"እነሆ፤ እግዚአብሔር በኀይሉ ከፍ ከፍ ብሎአል፤
እንደ እርሱስ ያለ አስተማሪ ማን ነው?
[23]እርሱን መንገድ የሚመራው፣
ወይም 'ይህን አጥፍተሃል' የሚለው ማን ነው?
[24]ሰዎች በመዝሙር ያወደሱትን፣
የእርሱን ሥራ ማወደስ አትዘንጋ።
[25]ሰው ሁሉ አይቶታል፤
ሰዎችም በትኵረት ተመልክተውታል።
[26]እነሆ፤ እግዚአብሔር ከአእምሯችን በላይ ታላቅ ነው!
የዘመኑም ቍጥር ከመታወቅ ያልፋል።

[27]"የውሃን ነጠብጣብ ወደ ላይ ያተናል፤
መልሶም በዝናብ መልክ በጅረቶች ላይ ያወርዳል፤
[28]ደመናት ጠል ያንጠባጥባሉ፤
ዶፍም በሰው ላይ ይወርዳል።
[29]ደመናትን እንዴት እንደሚዘረጋ፣
ከድንኳኑም እንዴት እንደሚያንጐደጕድ
ሊረዳ የሚችል ማን ነው?
[30]መብረቁን በዙሪያው እንዴት እንደሚበትን ተመልከት፤
የባሕሩንም ወለል ይሸፍናል።
[31]እርሱ ሕዝብን የሚያስተዳድረው፣[ሸ]
ምግብንም አትረፍርፎ የሚሰጣቸው በዚህ መንገድ ነው።
[32]እጆቹን በመብረቅ ይሞላቸዋል፤
ዒላማውንም እንዲመታ ያዝዘዋል።
[33]ነጐድጓዱ ውሽንፍር እንደሚከተለው ያመለክታል፤
ከብቶችም እንኳ መምጣቱን ይጠቍማሉ።

# 37

ልቤ በዚህ በኀይል ይመታል፤
ከስፍራውም ዘለል ዘለል ይላል።
[2]ስሙ! የድምፁን ጩኸት ስሙ፤
ከአፉ የሚወጣውን ጕርምርምታ አድምጡ።
[3]መብረቁን ከሰማይ ሁሉ በታች ያባርቃል፤
ወደ ምድርም ዳርቻ ይልካል።
[4]ከዚያም በኋላ የድምፁ ጩኸት ይመጣል፤
በድምፁም ግርማ ያንጐደጕዳል፤
ድምጹ በተሰማ ጊዜ፣
መብረቁን የሚከለክል የለም።
[5]የእግዚአብሔር ድምፅ በሚያስደንቅ ሁኔታ ያንጐደጕዳል፤
እኛ የማናስተውለውንም ታላቅ ነገር ያደርጋል።
[6]በረዶውን፣ 'በምድር ላይ ውደቅ'
ውሽንፍሩንም 'ዶፍህን አውርደው' ይላል።
[7]እርሱ የፈጠራቸው ሰዎች ሁሉ ሥራውን ያውቁ ዘንድ፣
እያንዳንዱ ሰው እንዳይሠራ ይገታዋል።[ቀ]
[8]እንስሳት ይጠለላሉ፤
በየዋሻቸውም ይቈያሉ።
[9]ዐውሎ ነፋስ ከማደሪያው፣
ብርድም ከብርቱ ነፋስ ይወጣል።
[10]የእግዚአብሔር እስትንፋስ በረዶ ያስገኛል፤
ሰፋፊ ውሆች ግግር በረዶ ይሆናሉ።
[11]ደመናትን ርጥበት ያሸክማቸዋል፤
መብረቁንም በውስጣቸው ይበትናል።

36፥11 ዘፀ8፥22፤ ዘሌ26፥33፤ዘዳ8፥1፤ 28፥1፤30፥15፤ኢዮ 8፥7፤ኢሳ1፥19፤ሐጌ 1፥12፤ዮሐ14፥21፤ 1ጢሞ4፥8
36፥12 ዘሌ26፥38፤ ኢዮ4፥21፤15፥22፤ ኤፌ4፥18
36፥13 ኢዮ4፥17፤ 5፥2፤15፥12፤አሞ4፥ 11፤ሮሜ2፥5
36፥14 ዘዳ23፥17፤ ኢዮ15፥32
36፥15 ቍ8፥ኢዮ 5፥15፤33፥16፤34፥33፤ 2ቆሮ12፥10
36፥16 ዘፍ17፥1፤ 2ሳሙ22፥20፤አዮ15 ፥11፤መዝ18፥19፤23፥5 ፤78፥19፤118፥5፤ ሆሴ2፥14
36፥17 ኢዮ20፥29፤ 22፥11
36፥18 ዘፀ23፥8፤ ኢዮ34፥33፤አሞ5፥12
36፥19 መዝ49፥6፤ ኤር9፥23
36፥20 ኢዮ34፥20፡25
36፥21 ቍ8፤ኢዮ 34፥33፤መዝ66፥18፤ ዕብ11፥25
36፥22 ኢዮ 5፥9፤ 9፥4፤21፥22፤ሮሜ 11፥34
36፥23 ዘፍ18፥25፤ ኢዮ27፥11፤34፥10፡ 13፤ሮሜ11፥33
36፥24 ዘፀ15፥1፤ 1ዜና16፥24፤መዝ 35፥27፤92፥5፤111፥2፤ 138፥5፤145፥10፤ ራእ15፥3
36፥25 ሮሜ1፥20
36፥26 ዘፍ21፥33፤ ኢዮ5፥9፤ 10፥5፤ 1ቆሮ13፥12፤ዕብ1፥12
36፥27 2ሳሙ1፥21 ፤ኢዮ26፥8፤28፥26፤ 38፥28፤ኢሳ55፥10
36፥28 ኢዮ5፥10፤ 22፥11፤28፥26፤መዝ 65፥10፤72፥6፤ኢል 2፥23፤ማቴ5፥45
36፥29 ኢዮ9፥6፤ 37፥16፤መዝ18፥7-15 ፤19፥4፡5፤29፥3፤104፥2 ፤ምሳ8፥28፤ኢሳ40፥ 22፤ኤር10፥13
36፥30 ዘፀ19፥16፤ ኢዮ37፥11፡15፤መዝ 18፥12፡14፤68፥22፤ 97፥4፤ኢሳ51፥10፤ ኤር10፥13፤ዕን3፥11
36፥31 ዘዳ28፥23-24፤1ነገ17፥1፤ኢዮ 37፥13፤መዝ104፥14-15፡27-28፤145፥15፤ ኢሳ30፥23፤አሞ4፥7-8፤ሐሥ14፥17
36፥32 ኢዮ28፥24፤ 37፥12፡15፤ መዝ18፥14፤29፥7-9 36፥33 ኢዮ28፥26፤37፥5፤40፥9 37፥1 መዝ38፥10፤ኢሳ15፥5፤ኤር4፥19፤ዕን3፥16 37፥2 ቍ5፤ኢዮ32፥ 10፤መዝ18፥13፤29፥3-9 37፥3 2ሳሙ22፥13፤ኢዮ36፥32፤መዝ 18፥14፤ማቴ24፥27፤ሉቃ17፥24 37፥4 ዘፀ20፥19፤1ሳሙ2፥10
37፥5 1ሳሙ2፥10፤ኢዮ5፥9፤11፥7-9፤36፥4፡33፤ዮሐ12፥29
37፥6 ዘፍ7፥4፤ዘዳ28፥12፤ኢዮ5፥10፤28፥26፤38፥22 37፥7 መዝ104፥19-23፤109፥27፤111፥2 37፥8 ኢዮ28፥26፤38፥40፤ መዝ104፥22 37፥9 መዝ50፥3፤147፥17 37፥10 ኢዮ38፥29-30፤መዝ147፥17 37፥11 ኢዮ26፥8፤28፥26፤36፥30

[ሩ]12 ወይም፣ *ወንዙን ያቋርጣሉ*
[ሰ]20 በዕብራይስጥ ከቍ18-20 ያለው ክፍል ትርጕሙ በትክክል አይታወቅም
[ሸ]30 ወይም፣ *የሚያስተዳድረው*
[ቀ]7 ወይም፣ *ሰዎችን ሁሉ በኀይሉ ያስፈራቸዋል* ማለትም ነው

[12]ያዘዘውን ለመፈጸም፣
እርሱ በሚሰጠው መመሪያ፣
በመላው የምድር ገጽ ላይ ይሽከረከራሉ።
[13]ሰዎችን ለመቅጣት ደመና ያመጣል፤
ወይም በዚሁ ምድሩን አጠጥቶ[∩] ፍቅሩን
ይገልጻል።

[14]"ኢዮብ ሆይ፤ ይህን ስማ፤
ቆም ብለህ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ
ዐስብ።
[15]እግዚአብሔር ደመናትን እንዴት
እንደሚቈጣጠር፣
መብረቁንም እንዴት እንደሚያበርቅ
ታውቃለህን?
[16]ደመናት ሚዛን ጠብቀው እንዴት
እንደሚንሳፈፉ፣
በዕውቀቱ ፍጹም የሆነውን፣ የእርሱን
ድንቅ ሥራ ታውቃለህን?
[17]ምድር በደቡብ ነፋስ ጸጥ ባለች ጊዜ፣
ከሙቀት የተነሣ በልብስህ ውስጥ
የምትዝለፈለፍ ሆይ፤
[18]ከቀለጠ ናስ እንደ ተሠራ መስተዋት
የጠነከረውን ሰማይ ሲዘረጋ፣
አብረኸው መዘርጋት ትችል ነበርን?

[19]"ከጨለማችን የተነሣ እኛ ጒዳያችንን
መግለጽ አንችልም፤
ለእርሱ የምንለውን ንገረን።
[20]እኔ መናገር እንደ ፈለግሁ ሊነገረው
ይገባልን?
ይዋጥ ዘንድ የሚጠይቅ ሰው አለን?
[21]እንግዲህ ነፋስ ሰማያትን ካጠራ በኋላ፣
እጅግ የምታበራዋን ፀሓይ፣
ሊመለከት የሚችል የለም።
[22]እንደ ወርቅ በሚያበራ ክብር ከሰሜን
ይወጣል፤
እግዚአብሔር በሚያስፈራ ግርማ ይመጣል።
[23]ሁሉን የሚችል አምላክ ከአእምሯችን
በላይ ነው፤ በኀይልና በፍርድ ታላቅ
ነው፣
ጽድቁም ብዙ ነው፤ ማንንም
አይጨቍንም።
[24]ስለዚህ፣ ሰዎች ይፈሩታል፤
በልባቸው[†] አስተዋዮች እንደ ሆኑ
የሚያስቡትን አይመለከትም?"

## እግዚአብሔር ተናገረ

**38** እግዚአብሔርም በዐውሎ ነፋስ ውስጥ
ሆኖ ለኢዮብ መለሰለት፤
እንዲህም አለው፤

[2]"ዕውቀት በጐደለው ቃል፣
ዕቅዴን የሚያጨልም ይህ ማን ነው?
[3]እስቲ እንደ ወንድ ወገብህን ታጠቅ፤
እኔ ልጠይቅህ፣
አንተም መልስልኝ።

[4]"ምድርን በመሠረትሁ ጊዜ አንተ የት
ነበርህ?
በእርግጥ የምታስተውል ከሆንህ፣
ንገረኝ።
[5]ካወቅህ፣ መጠኗን ለይቶ ማን ወሰነ?
በላይዋስ መለኪያ ገመድ የዘረጋ ማን ነው?
[6]መሠረቶቿ ምን ላይ ተተከሉ?
የማእዘን ድንጋይዋንስ ማን አቆመ?
[7]ይህም የሆነው የንጋት ከዋክብት
በዘመሩበት ጊዜ፣
መላእክትም[‡] እልል ባሉበት ጊዜ ነበር።

[8]"ባሕር ከማሕፀን በወጣ ጊዜ፣
በር የዘጋበት ማን ነው?
[9]ደመናውን ልብሱ፣
ጨለማንም መጠቅለያው አደረግሁለት፣
[10]ድንበር ወሰንሁለት፤
መዝጊያና መወርወሪያውን አበጀሁለት።
[11]'እስከዚህ ድረስ ትመጣለህ፤ ማለፍ ግን
አትችልም፤
የዕቡይ ማዕበልህም ገደብ ይህ ነው'
አልሁት።

[12]"ከተወለድህ ጀምሮ ንጋትን አዝህ
ታውቃለህን?
ወይስ ወጋገን ስፍራውን እንዲይዝ
አድርገሃል?
[13]በዚህም የምድርን ዳርቻ ይዞ፣
ክፉዎችን ከላይዋ እንዲያራግፍ
አድርገሃልን?
[14]ምድር ከማኅተም በታች እንዳለ የሸክላ
ጭቃ ቅርጿ ይወጣል፤
ቅርጿ እንደ ልብስ ቅርጽ ጐልቶ
ይታያል።
[15]ክፉዎች ብርሃናቸውን ተከልክለዋል፤
ከፍ ያለው ክንዳቸውም ተሰብሮአል።

[16]"ወደ ባሕር ምንጭ ወርደህ ታውቃለህን?
ወይስ ወደ ጥልቀቱ ገብተህ በመሠረቱ
ላይ ተመላልሰሃልን?
[17]የሞት ደጆች ተገልጠውልሃልን?
የሞትንስ ጥላ በሮች አይተሃልን?
[18]የምድርን ስፋት ታውቃለህን?
ይህን ሁሉ ዐውቀህ ከሆነ፣ ንገረኝ።

[19]"ወደ ብርሃን መኖሪያ የሚያደርሰው
መንገድ የትኛው ነው?
የጨለማ መኖሪያስ ወዴት ነው?

**37፥12** ቍ3፤መዝ 147፥16፤148፥8 **37፥13** ዘፍ7፥4፤ዘፀ 9፥22-23፤1ሳሙ12፥ 17፤1ነገ18፥45፤ኢዮ 5፥10፤36፥31፤38፥27 **37፥14** ኢዮ5፥9፤ 32፥10 **37፥15** ኢዮ36፥ 30፡32 **37፥16** ኢዮ5፥9፤ 36፥4፡29 **37፥17** ሐ ሥ27፥13 **37፥18** ዘፍ1፥1፤ዘዳ 28፥23፤ኢዮ22፥14 **37፥19** ኢዮ9፥3፤ 13፥18፤ሮሜ8፥26 **37፥21** መሳ5፥ 31፤ሐሥ22፥11፤ 26፥13 **37፥22** ዘፀ24፥17፤ መዝ19፥5 **37፥23** ኢዮ4፥17፤ 5፥9፤8፥3፤36፥4፤መዝ4 4፥1፤ኢሳ63፥9፤ኤር 25፥5፤ሰቆ3፥33፤ሕዝ 18፥23፡32፤ሮሜ11፥ 33፤1ጢሞ6፥16 **37፥24** ዘፍ22፥12፤ ኢዮ5፥13፤28፥28፤መ ክ12፥13፤ሚክ6፥8፤ማ ቴ10፥28፤ኤፌ5፥15 **38፥1** ዘፀ14፥21፤ 1ሳሙ2፥10፤ኢዮ11፥ 5፤40፥6፤ኢሳ21፥ 1፤ሕዝ1፥4 **38፥2** 1ነገ22፥5፤ ኢዮ34፥35፤ኢሳ40፥ 13፤ማር10፥38፤ 1ጢሞ1፥7 **38፥3** ኢዮ40፥7፤ 42፥4፤ማር11፥29 **38፥4** ቍ5፡18፤ዘፍ 1፥1፤1ሳሙ2፥8፤ኢዮ 34፥13፤ምሳ30፥4 **38፥5** ቍ4፤መዝ 102፥25፤ምሳ8፥29፤ ኢሳ40፥12፤48፥13፤ ኤር31፥37፡39፤ዘካ 1፥16፤4፥9-10 **38፥6** ኢዮ26፥7፤ ምሳ8፥25 **38፥7** ዘፍ1፥16፤ዘዳ 16፥15፤1ነገ22፥19፤መ ዝ19፥1-4፤148፥2-3 **38፥8** ቍ11፤ ዘፍ1፥9-10፤መዝ33፥ 7፤ምሳ8፥29፤ኤር5፥22 **38፥9** ዘፍ1፥2 **38፥10** ነህ3፥3፤ኢዮ 7፥12፤26፥10፤28፥25፤ መዝ33፥7፤104፥9፤ ኢሳ40፥12 **38፥11** ቍ8፤መዝ 65፥7፤89፥9፤104፥6-9 **38፥12** መዝ57፥8፤ 74፥16፤አሞ5፥8 **38፥13** ኢዮ8፥22፤ መዝ104፥35 **38፥14** ዘፀ28፥11 **38፥15** ዘፍ17፥14፤ ዘዳ28፥29፤ኢዮ4፥10፤ኢዮ15፥22፤18፥5፤31፥22 **38፥16** ዘፍ1፥7፤ ኢዮ9፥8 **38፥17** ኢዮ7፥9፤33፥22፤ማቴ16፥18፤ራእ1፥18 **38፥18** ቍ4፤ኢዮ28፥24፤ኢሳ40፥12 **38፥19** ዘፍ1፥4፤ኢዮ28፥ 3፤መዝ139፥11-12

[∩]13 ወይም፣ *ፍቅሩንም ለመግለጽ ደመናን ያመጣል*
[†]24 ወይም፣ *በልባቸው አስተዋዮች ወደ ሆኑ*
[‡]7 ወይም፣ *የእግዚአብሔር ልጆች*

20ወደ ማደሪያቸው ልትወስዳቸው
ትችላለህን?
የመኖሪያቸውን መንገድ ታውቃለህ?
21ያን ጊዜ ተወልደሃል! ዕድሜህ ትልቅ
ነውና፤
አንተስ በእርግጥ ሳታውቅ አትቀርም!

22“ወደ በረዶው መጋዘን ገብተሃልን?
የዐመዳዩንስ ማከማቻ አይተሃልን?
23ይኸውም ለመከራ ጊዜ፣
ለጦርነትና ለውጊያ ቀን ያስቀመጥሁት
ነው።
24መብረቅ ወደሚሰራጭበት ቦታ
የሚያደርሰው መንገድ፣
የምሥራቅም ነፋስ በምድር ላይ
ወደሚበተንበት ስፍራ የሚወስደው
የትኛው ነው?
25ለዝናብ መውረጃን፣
ለመብረቅም መንገድን ያበጀ ማን ነው?
26በዚህም ማንም የማይኖርበትን ምድር፣
ሰውም የሌለበትን ምድረ በዳ የሚያጠ
ጣ፣
27ባድማውንና በረሓውን መሬት
የሚያጠግብ፣
ሣርም እንዲበቅልበት የሚያደርግ ማን
ነው?
28ዝናብ አባት አለውን?
የጤዛን ጠብታ ማን ወለደው?
29በረዶ ከማን ማሕፀን ይወጣል?
የሰማዩንስ ዐመዳይ ማን ይወልዳል?
30ውሆች እንደ ድንጋይ ይጠነክራሉ፤
የጥልቁ ገጽ እንደ በረዶ ይጋገራል።

31“ፕልያዲስ የተባሉትን ውብ ከዋክብት
ልትለጉም፣
ወይም የኦርዮንን ማሰሪያ ልትፈታ
ትችላለህን?
32ማዛሮት የተባለውን የከዋክብት ክምችት
በወቅቱ[ኀ] ልታወጣ፣
ወይም ድብ የተባለውን ኮከብና ልጆቹን
ልትመራ ትችላለህ?
33የሰማያትን ሥርዐት ታውቃለህ?
ይህንስ በምድር ላይ እንዲሠለጥን
ማድረግ ትችላለህ?

34“ድምፅህን ወደ ደመናት አንሥተህ፣
ራስህን በጎርፍ ማጥለቅለቅ ትችላለህን?
35መብረቆችን መስደድ ትችላለህ?
እነርሱስ፣ ‘እነሆ፤ እዚህ አለን’ ይሉሃል?
36ለልብ[ነ] ጥበብን፣
ለአእምሮም ማስተዋልን የሰጠ ማን ነው?
37ትቢያ ሲጠጥር፣
ጓሎችም እርስ በርስ ሲጣበቁ፣
38ደመናትን ለመቍጠር ጥበብ ያለው
ማን ነው?

የሰማያትንስ የውሃ ገንቦ ዘንበል ማድረግ
ማን ይችላል?

39“ለአንበሳዪቱ አድነህ ግዳይ ታመጣለህን?
የተራቡ የአንበሳ ግልገሎችንስ
ታጠግባለህን?
40እነርሱ በዋሻ ውስጥ ያደባሉ፤
በደን ውስጥም ይጋደማሉ።
41ልጆቿ ወደ እግዚአብሔር ሲጮኹ፣
ምግብ አጥተው ሲንከራተቱ፣
ለቍራ መብልን የሚሰጥ ማን ነው?

## 39

“የበረሃ ፍየል የምትወልድበትን ጊዜ
ታውቃለህን?
ዋልያ ስታምጥስ ተከታትለህ
አይተሃል?
2የእርግዝናቸው ወራት ምን ያህል እንደ
ሆነ ትቈጥራለህን?
የሚወልዱበትንስ ጊዜ ታውቃለህን?
3ተንበርክከው ይወልዳሉ፤
ከምጣቸውም ጣር ይገላገላሉ።
4ግልገሎቻቸውም ይጠነክራሉ፤ በሜዳም
ያድጋሉ፤
ተለይተው ይሄዳሉ፤ ወደ እነርሱም
አይመለሱም።

5“ለሜዳ አህያ ነጻነት የሰጠው ማን ነው?
እስራቱንስ ማን ፈታለት?
6ምድረ በዳውን መኖሪያው፣
የጨውንም ምድር ማደሪያው አድርጌ
ሰጠሁት።
7በከተማ ውካታ ይሥቃል፤
የነጂውንም ጩኸት አይሰማም።
8በየተራራው ይሰማራል፤
ሐመልማሉንም ሁሉ ለማግኘት ይወጣል።

9“ጎሽ ያገለግልህ ዘንድ ይታዘዛልን?
በበረትህስ አጠገብ ያድራልን?
10እንዲያርስልህ ልትጠምደው ትችላለህ?
ወይስ እየተከተለህ ዕርሻህን
ይጐለጕልልሃልን?
11ጕልበቱ ብርቱ ስለ ሆነ
ትተማመንበታለህ?
ከባዱን ሥራህንስ ለእርሱ ትተዋለህ?
12እህልህን እንዲሰበስብልህ፣
በዐውድማህም ላይ እንዲያከማችልህ
ታምነዋለህን?

13“ሰጎን ክንፎቿን በደስታ ታራግባለች፤
ነገር ግን እንደ ሽመላ ላባዎች ሊሆኑ
አይችሉም።
14ዕንቍላሏን መሬት ላይ ትጥላለች፤
እንዲሞቅም በአሸዋ ውስጥ ትተወዋለች።

ኀ32 ወይም *በወቅቱ የሚወጣ የንጋት ኮከብ*
ነ36 በዕብራይስጡ የዚህ ቃል ትርጒም በትክክል አይታወቅም

38፥20 ኢዮ24፥13
38፥21 ኢዮ15፥7
38፥22 ዘጸ28፥12፤ ኢዮ37፥6፤መዝ105፥32፤147፥17
38፥23 ዘፀ9፥26፤ ኢሱ10፥11፤መዝ27፥5፤ኢሳ28፥17፤30፥30፤ሕዝ13፥11፥13፤ራእ16፥21
38፥24 ኢዮ27፥21፤28፥24፤ኤር10፥13፤51፥16
38፥25 ኢዮ28፥26
38፥26 ኢዮ36፥27፤መዝ84፥6፤107፥35፤ኢሳ41፥18
38፥27 ኢዮ28፥26፤37፥13፤መዝ104፥14
38፥28 2ሳሙ1፥21፤ኢዮ5፥10
38፥29 መዝ147፥16-17
38፥30 ኢዮ37፥10
38፥31 ኢዮ9፥9፤ አሞ5፥8
38፥32 ዘፍ1፥16፤ 2ነገ23፥5፤ኢሳ13፥10፤40፥26፥45፥12፤ኤር19፥13
38፥33 ዘፍ1፥16፤ መዝ148፥6፤ኤር31፥36
38፥34 ኢዮ5፥10፤22፥11
38፥35 ኢዮ36፥32
38፥36 ኢዮ9፥4፤12፥13፤34፥32፤ያዕ1፥5
38፥37 ኢሱ3፥16፤ ኢዮ22፥11
38፥38 ዘሌ26፥19፤ 1ነገ18፥45
38፥39 ዘፍ49፥9
38፥40 ዘፍ49፥9፤ ኢዮ37፥8
38፥41 ዘፍ1፥30፤ 8፥7፤መዝ147፥9፤ማቴ6፥26፤ሉቃ12፥24
39፥1 ዘፍ49፥21፤ ዘዳ14፥5
39፥2 ዘፍ31፥7-9
39፥5 ዘፍ16፥12
39፥6 ኢዮ24፥5፤ 30፥4፥7፤መዝ107፥34፤ኤር2፥24፤14፥6፤17፥6
39፥7 ኢዮ3፥18፤ 5፥22
39፥8 ኢሳ32፥20
39፥9 ዘፍ42፥27፤ ዘፀ21፥6፤ዘኍ23፥32
39፥10 ኢዮ41፥13፤ መዝ32፥9
39፥11 ቍ19፤ኢዮ40፥16፤41፥12፥22፤መዝ147፥10
39፥13 ዘካ5፥9

15እግር እንደሚሰብረው፣
የዱር አውሬም እንደሚረግጠው
አታስብም።
16የእርሷ እንዳልሆኑ ሁሉ በልጆቿ
ትጨክናለች፣
ድካሟም በከንቱ ቢቀር ደንታ የላትም፣
17እግዚአብሔር ጥበብ ነሥቶአታልና፣
ማስተዋልንም አልሰጣትም።
18ለመሸምጠጥም ክንፎቿን ስትዘረጋ፣
በፈረስና በጋላቢው ትሥቃለች።

19"ለፈረስ ጒልበትን ትሰጠዋለህን?
ዐንገቱንስ ጋማ ታለብሰዋለህን?
20እንደ አንበጣ የምታስዘልለው አንተ
ነህን?
የማንኰራፋቱም ገናናነት አስፈሪ ነው።
21በጒልበቱ እየተመካ በብርቱ
ይጐደፍራል፣
ጦርነት ሊገጥም ይወጣል።
22ያለ አንዳች ሥጋት፣ በፍርሀት ላይ
ይሥቃል፣
ሰይፍ ቢመዘዝበትም ወደ ኋላ አይልም።
23ከሚብረቀረቀው ጦርና አንካሴ ጋር፣
የፍላጻው ኮረጆ ጐኑ ላይ ይንኳኳል።
24በወኔ መሬቱን እየጐደፈረ ወደ ፊት
ይሸመጥጣል፣
የመለከት ድምፅ ሲሰማ ያቅበጠብጠዋል።
25መለከቱ ሲያንባርቅ፣ 'እሰይ' ይላል፣
የአዛዦችን ጩኸትና የሰራዊቱን
ውካታ፣
ጦርነትንም ከሩቅ ያሸታል።

26"ጭልፊት የሚበረው፣
ክንፎቹንም ወደ ደቡብ የሚዘረጋው፣
በአንተ ጥበብ ነውን?
27ንስር ወደ ላይ የሚመጥቀው፣
ጎጆውንም በከፍታ ላይ የሚሠራው፣
በአንተ ትእዛዝ ነውን?
28በገደል ላይ ይኖራል፣ በዚያም ያድራል፣
ምሽጉም የቋጥኝ ጫፍ ነው።
29እዚያ ሆኖ የሚነጥቀውን ይቃኛል፣
ዐይኑም ከሩቅ አጥርቶ ያያል።
30ጫጩቶቹ ደም ይጠጣሉ፣
እርሱም በድን ካለበት አይታጣም።"

# 40

እግዚአብሔርም ኢዮብን እንዲህ
አለው፣

2"ሁሉን ከሚችል አምላክ ጋር ተከራክሮ
የሚረታው አለን?
እግዚአብሔርን የሚወቅስ እርሱ መልስ
ይስጥ!"

3ኢዮብም *ለእግዚአብሔር* እንዲህ ሲል መለሰ፣

4"እኔ ከንቱ ሰው፣ ምን እመልስልሃለሁ?
እጄን በአፌ ላይ እጭናለሁ።
5አንድ ጊዜ ተናገርሁ፣ የምመልሰው የለኝም፣
ሁለተኛም ተናገርሁ፣ ከእንግዲህ አንዳች
አልጨምርም"
6*እግዚአብሔርም* በዐውሎ ነፋስ ውስጥ
ሆኖ፣ ለኢዮብ እንዲህ ሲል ተናገረ፣

7"እንግዲህ እንደ ወንድ ወገብህን ታጠቅ፣
እኔ እጠይቅሃለሁ፣
አንተም መልስልኝ።

8"ፍርዴን ታቃልላለህን?
ወይስ አንተ ጻድቅ ለመሆን እኔን
ትኰንናለህ?
9እንደ እግዚአብሔር ክንድ ያለ ክንድ
አለህን?
ድምፅህስ እንደ እርሱ ድምፅ
ሊያንጐደጒድ ይችላልን?
10እንግዲያስ ክብርንና ልዕልናን ተጐናጸፍ፣
ግርማ ሞገስንም ተላበስ፣
11ቍጣህን አፍስስ፣
ትዕቢተኛውን ሁሉ ተመልክተህ
አዋርደው፣
12ትዕቢተኛውን ሰው ሁሉ ተመልክተህ ዝቅ
አድርገው፣
ክፉዎችንም በቆሙበት ስፍራ
አድቅቃቸው።
13ሁሉንም በአንድ ላይ ከዐፈር
ደባልቃቸው፣
ፊታቸውንም በመቃብር ውስጥ ሸፍን።
14እኔም ቀኝ እጅህ እንደምታድንህ፣
በዚያን ጊዜ አረጋግጬ እቀበላለሁ።

15"አንተን እንደ ፈጠርሁ፣ የፈጠርሁትን፣
'ብሄሞት'[ኘ] ጒማሬን ተመልከት፣
እንደ በሬ ሣር ይበላል፣
16ብርታቱ ወገቡ ውስጥ፣
ኀይሉም በሆዱ ጡንቻ ላይ ነው።
17ጅራቱ[ኦ] እንደ ጥድ ዛፍ ይወዛወዛል፣
የወርቹ ጅማት የተጐነጐነ ነው።
18ዐጥንቱ እንደ ናስ ቱቦ፣
እጅና እግሮቹም እንደ ብረት ዘንግ
ናቸው።
19እርሱ የእግዚአብሔር ሥራ አውራ ነው፣
በሰይፍ ሊቀርበውም የሚችል ፈጣሪው
ብቻ ነው።
20ኰረብቶች ምግቡን ያበቅሉለታል፣
አውሬዎችም ሁሉ በዙሪያው ይፈነጫሉ።

**39፥15** 2ነገ14፥9 **39፥16** ቍ17፤ ሰቆ4፥3 **39፥17** ቍ16፤ኢዮ 21፥22 **39፥18** ኢዮ5፥22 **39፥19** ቍ11 **39፥20** ኢዮ41፥25፤ ኤር8፥16፤ኢል2፥4-5፤ ራእ9፥7 **39፥21** ቍ11፤ ኤር8፥6 **39፥22** ኢዮ5፥22 **39፥23** ኢሳ5፥28፤ ኤር5፥16፤ናሆ3፥3 **39፥24** ዘኍ10፥9፤ ኤር4፥5፡19፤ሕዝ7፥ 14፤አሞ3፥6 **39፥25** ኢሱ6፥5፤ ኤር8፥6፤አሞ1፥14፤ 2፥2 **39፥26** ኤር8፥7 **39፥27** ኤር49፥16፤ አብ1፥4፤ዕን2፥9 **39፥28** ኤር49፥16፤ አብ1፥3 **39፥29** ኢዮ9፥26 **39፥30** ማቴ24፥ 28፤ሉቃ17፥37 **40፥1** ኢዮ5፥8፤ 10፥2 **40፥2** ኢዮ9፥3፡15፤ 11፥8፤13፥3፤33፥13፤ሮ ሜ9፥20 **40፥4** መሳ18፥19፤ 29፥9፤42፥6 **40፥5** ኢዮ9፥3፡15 **40፥6** ዘፀ14፥21፤ ኢዮ38፥1 **40፥7** ኢዮ38፥3 **40፥8** ኢዮ2፥3፤ 15፥25፤27፥2፤34፥17፤ ሮሜ3፥3 **40፥9** ዘፀ20፥19፤ 2ዜና32፥8፤ኢዮ36፥ 33፤መዝ98፥1፤ኢሳ 6፥8፤ሕዝ10፥5 **40፥10** መዝ29፥1- 2፤45፥3፤93፥1፤96፥6፤ 104፥1፤145፥5 **40፥11** ኢዮ20፥28፤ መዝ7፥11፤18፥27፤ ኢሳ2፥11፤5፥25፤9፥ 12፡19፤10፥5፤13፥3 ፡5፤23፥9፤24፥10፤25፥ 12፤26፥5፤30፥27፤32፥ 19፤42፥25፤51፥20፤ኤ ር7፥20፤ናሆ1፥6፤ ሰፎ1፥18 **40፥12** 1ሳሙ2፥7፤ መዝ10፥4፤52፥5፤60፥1 2፤ኢሳ22፥5፤25፥11፤ 28፥3፤63፥2-3፥6፤ኤር 48፥29፤49፥16፤ዳን 5፥20፤ሚክ5፥8፤7፥10፤ ሰፎ2፥10፤ዘካ10፥5፤ሚ ል4፥3፤1ጴጥ5፥5 **40፥13** ዘኍ16፥31- 34፤ኢዮ4፥9 **40፥14** ዘፀ15፥6፡ 12፤መዝ18፥35፤ 20፥6፤48፥10፤60፥5፤108፥6፤ኢሳ41፥10፤63፥5 **40፥15** ኢዮ9፥9፤ ኢሳ11፥7፤65፥25 **40፥16** ኢዮ39፥11፤41፥9 **40፥17** ኢዮ41፥ 15 **40፥18** ኢዮ41፥12፤ኢሳ11፥4፤49፥2 **40፥19** ዘፍ3፥24፤ ኢዮ4፥17፤9፥9፤41፥33፤መዝ40፥5፤139፥14፤ኢሳ27፥1 **40፥20** ኢ ዮ5፥23፤መዝ104፥14፡26

[ኘ]15 ጒማሬ ወይም ዝሆን
[ኦ]17 ምናልባት ግንዱ ማለት ሊሆን ይችላል

21በውሃ ላይ በሚያድጉ ዕፀዋት ጥላ ሥር
ይተኛል፤
በረግረግ ስፍራ ደንገል መካከል
ይደበቃል።
22በውሃ ላይ የሚያድጉ ዕፀዋት በጥላቸው
ይጋርዱታል፤
የወንዝ አኻያ ዛፎች ይሸፍኑታል።
23ወንዙ በኀይል ቢገሠግሥም፣
አይደነግጥም፤
ዮርዳኖስ እስከ አፉ ቢሞላም፣ እርሱ
ተረጋግቶ ይቀመጣል።
24ዐይኑን ሸፍነህ ልትይዘው፣
አጥምደህም አፍንጫውን ልትበሳ
ትችላለህ?

# 41

"ሌዋታንን[ከ] በመንጠቆ ልታወጣው፣
ወይም ምላሱን በገመድ
ልታስረው ትችላለህን?
2መሰንጊያ በአፍንጫው ልታስገባ፣
ወይም ጒንጬን በሜንጦ ልትበሳ
ትችላለህን?
3እርሱ እንድትምረው ይለማመጥሃል?
በለስላሳ ቃላትስ ይናገርሃል?
4ለዘላለም ባሪያ ታደርገው ዘንድ፣
ከአንተ ጋር ይዋዋላልን?
5እንደ ወፍ አልምደኸው ከእርሱ ጋር
ልትጫወት ትችላለህ?
ወይስ ለሴት አገልጋዮችህ መጫወቻነት
ታስረዋለህን?
6ነጋዴዎችስ በእርሱ ላይ ይከራከራሉን?
ለቸርቻሪዎችስ ያከፋፍሉታል?
7ቈዳው ላይ አንካሴ ልትሰካ፣
ጭንቅላቱንም በዓሣ መውጊያ ጦር
ልትበሳ ትችላለህን?
8እርሱን እስቲ ንካው፣
ግብግቡን ታስታውሳለህ፤ ከቶም
አያላምድህም።
9እርሱን በቍጥጥር ሥር አውላለሁ ማለት
ዘበት ነው፤
በዐይን ማየት እንኳ ብርክ ያስይዛል።
10ሊቀሰቅሰው የሚደፍር የለም፤
ማን ፊቱ ሊቆም ይችላል?
11ነክቶት በሰላም የሚሄድ ማን ነው?
ከሰማይ በታች ማንም የለም።

12"ስለ ብርታቱና ስለ አካላቱ ውበት፣
ስለ እጅና እግሩ ከመናገር
አልቈጠብም።
13የደረበውን ልብስ ማን ሊያወልቅ ይችላል?
ማንስ ሊለጒመው ወደ መንጋጋው
ይቀርባል?
14አስፈሪ ጥርሶቹ የተገጠገጡበትን፣
የአፉን ደጅ ማን ደፍሮ ይከፍታል?
15ጀርባው፣ አንድ ላይ የተጣበቁ፣
የጋሻ ረድፎች አሉት፤
16እጅግ የተቀራረቡ ስለ ሆኑ፣
ነፋስ በመካከላቸው አያልፍም፤
17እርስ በርስ የተገጣጠሙ ናቸው፤
አንዱ ከአንዱ ጋር ተጣብቆአልና ማንም
ሊለያያቸው አይችልም።
18እንጥሽታው የብርሃን ብልጭታ ያወጣል፤
ዐይኖቹም እንደ ማለዳ ጮራ ናቸው።
19ከአፉ ፍም ይወጣል፤
የእሳት ትንታግ ይረጫል።
20በሸምበቆ ማገዶ ላይ ከተጣደ ድስት
እንደሚወጣ እንፋሎት፣
ከአፍንጫው ጢስ ይትጐለጐላል።
21እስትንፋሱ ከሰል ያቀጣጥላል፤
የእሳትም ነበልባል ከአፉ ይወጣል።
22ብርታት በዐንገቱ ውስጥ አለ፤
አሸባሪነትም በፊቱ እመር እመር
ይላል።
23የሥጋው ንብርብር እርስ በርስ የተጣበቀ፣
በላዩ የጸናና ከቦታው የማይናጋ ነው።
24ደረቱ እንደ ዐለት የጠጠረ፣
እንደ ወፍጮ ድንጋይም የጠነከረ ነው።
25እርሱ በተነሣ ጊዜ፣ ኀያላን ይርዳሉ፤
በሚንቀሳቀስበትም ጊዜ ወደ ኋላ
ያፈገፍጋሉ።
26ጦር፣ ፍላጻ ወይም አንካሴ፣
ሰይፍም ቢያገኘው አንዳች አይጐዳውም።
27እርሱ ብረትን እንደ አገዳ፣
ናስንም እንደ ነቀዘ ዕንጨት ይቈጥራል።
28ቀስት አያባርረውም፤
የወንጭፍ ድንጋይም ለእርሱ እንደ
ገለባ ነው።
29ቈመጥ በእርሱ ፊት እንደ ገለባ ነው፤
ጦር ሲሰበቅ ይሥቃል።
30የሆዱ ሥር እንደ ሸካራ ገል ነው፤
እንደ መውቂያ መሣሪያም በጭቃ ላይ
ምልክት ጥሎ ያልፋል።
31እንደሚፈላ ምንቸት ጥልቁን
ያናውጠዋል፤
ባሕሩንም እንደ ሽቶ ብልቃጥ
ያደርገዋል።
32ያለፈበትን መንገድ ብሩህ ያደርጋል፤
ቀላዩንም ሽበት ያወጣ ያስመስለዋል።
33ያለ ፍርሀት የተፈጠረ፣
እንደ እርሱ ያለ በምድር ላይ የለም።
34ከፍ ያሉትን ሁሉ በንቀት ይመለከታል፤
በትዕቢተኞችም ሁሉ ላይ ንጉሥ ነው።"

## ኢዮብ

# 42

ኢዮብም እንዲህ ሲል ለእግዚአብሔር
መለሰ፤

[ከ]1 ምናልባት ዐዞ ሊሆን ይችላል
ቍ 11 አንዳንድ ትርጒሞች፣ "በዕዳ የሚጠይቀኝ ማን ነው?
ከሰማይ በታች ያለው ሁሉ ንብረቴ ነው" ይላሉ።

40፥21 ዘፍ41፥2፤ኢዮ8፥11፤መዝ68፥30፤ኢሳ35፥7
40፥22 መዝ1፥3፤ኢሳ44፥4
40፥23 ኢሱ3፥1፤ኢሳ8፥7፤11፥15
40፥24 2ነገ19፥28፤ኢዮ41፥2፥7፥26፤ኢሳ37፥29
41፥1 ኢዮ3፥8፤አሞ4፥2
41፥2 ኢ40፥24፤ሕዝ19፥4
41፥4 1ነገ20፥31
41፥7 ኢዮ40፥24
41፥8 ኢዮ3፥8
41፥9 ኢዮ40፥16
41፥10 2ዜና20፥6፤ኢዮ3፥8፤ኢሳ46፥5፤ኤር50፥44፤ራእ6፥17
41፥11 ኢሱ3፥11፤ኢዮ10፥4፤34፥33፤ሐሥ4፥24፤ሮሜ11፥35፤1ቆሮ10፥26
41፥12 ኢዮ39፥11፤40፥18
41፥13 ኢዮ30፥11፤39፥10
41፥14 መዝ22፥13
41፥15 ኢዮ40፥17
41፥18 ኢዮ3፥9
41፥19 ዳን10፥6
41፥20 መዝ18፥8
41፥21 ኢዮ4፥9፤መዝ18፥8፤ኢሳ10፥17፤11፥4፤30፥27፤33፥14፤40፥7፤66፥14-16፤ኤር4፥4
41፥22 ኢዮ39፥11
41፥24 ማቴ18፥6
41፥25 ኢዮ3፥8፤39፥20
41፥26 ኢሱ8፥18፤ኢዮ40፥24
41፥27 ቍ29
41፥28 መዝ91፥5
41፥29 ቍ27፤ኢዮ5፥22
41፥30 ኢሳ28፥27፤41፥15፤አሞ1፥3
41፥31 1ሳሙ2፥14፤ሕዝ32፥2
41፥33 ኢዮ40፥19
41፥34 ኢዮ28፥8፤መዝ18፥27፤101፥5፤131፥1፤ምሳ6፥17፤21፥4፤30፥13

2“አንተ ሁሉን ማድረግ እንደምትችል፣
ዕቅድህም ከቶ እንደማይሰናከል
ዐወቅሁ።
3አንተ፣ ‘ያለ ዕውቀት ዕቅዴን
የሚያደበዝዝ ይህ ማን ነው’ አልኸኝ፤
በእርግጥ ያልገባኝን ነገር፣
የማላውቀውንና ላስተውለው
የማልችለውን ጉዳይ ተናገርሁ።

4“ ‘ስማኝ፣ ልናገር
እኔ እጠይቃለሁ፤
አንተ ትመልስልኛለህ’ አልኸኝ።

5ጆሮዬ ስለ አንተ ሰምታ ነበር፤
አሁን ግን ዐይኔ አየችህ።
6ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ፤
በትቢያና በዐመድ ላይ ተቀምጬ ንስሓ
እገባለሁ።”

## *መደምደሚያ*

7*እግዚአብሔር* ይህን ለኢዮብ ከተናገረ
በኋላ፣ ቴማናዊውን ኤልፋዝን እንዲህ አለው፤
“እንደ አገልጋዬ እንደ ኢዮብ ስለ እኔ
ቅን ነገር ስላልተናገራችሁ፣ ቍጣዬ በአ
ንተና በሁለቱ ባልንጀሮችህ ላይ ነዶአል።
8አሁን እንግዲህ ሰባት ወይፈኖችና ሰባት
አውራ በጎች ይዛችሁ ወደ አገልጋዬ ወደ
ኢዮብ ሂዱ፤ የሚቃጠል መሥዋዕትም ስለ
ራሳችሁ አቅርቡ። እንደ አሳፋሪ ተግባራ
ችሁ እንዳላደርግባችሁ አገልጋዬ ኢዮብ
ስለ እናንተ ይጸልያል፤ እኔም ጸሎቱን
እቀበላለሁ፤ እንደ አገልጋዬ እንደ ኢዮብ
ስለ እኔ ቅን ነገር አልተናገራችሁምና።”

42፥2 ዘፍ18፥14፤ 2ዜና20፥6፤ኢዮ16፥19፤ማቴ19፥26፤ሐሥ 4፥28፤ኤፌ1፥11
42፥3 ኢዮ5፥9፤ 34፥35
42፥4 ኢዮ38፥3
42፥5 መሳ13፥22፤ ኢዮ26፥14፤ኢሳ6፥5፤ ማቴ5፥8፤ሉቃ2፥30፤ሮ ሜ10፥17፤ ኤፌ1፥17-18
42፥6 ዘፀ10፥3፤ዕዝ 9፥6፤ኢዮ2፥8፤6፥29፤ 34፥33፤40፥4፤ሕዝ 6፥9፤ሮሜ12፥3
42፥7 ቍ8፤ኢሱ 1፥7፤ኢዮ9፥15፤32፥3
42፥8 ቍ7፤ዘፍ 8፥20፤20፥7፤ዘኁ 23፥1፡29፤ኢዮ 1፥8፤22፥30፤ሕዝ 45፥23፤ያዕ5፥15-16፤1ዮሐ5፥16
42፥9 ዘፍ19፥21፤ 20፥17፤ኢዮ2፥11፤ ሕዝ14፥14
42፥10 ዘዳ30፥3፤ ኢዮ1፥3፤መዝ14፥7፤ 85፥1-3፤126፥5-6፤ ፊል2፥8-9፤ያዕ5፥11
42፥11 ዘፍ37፥35፤ ኢዮ19፥13
42፥17 ዘፍ15፥15

9ቴማናዊው ኤልፋዝ፣ ሹሐዊው በልዳዶ
ስና ናዕማታዊው ሶፋር *እግዚአብሔር* እንደ
ተናገራቸው አደረጉ፤ *እግዚአብሔርም* የኢ
ዮብን ጸሎት ተቀበለ።
10ኢዮብ ለወዳጆቹ ከጸለየ በኋላ፣ *እግዚ
አብሔር* እንደ ገና አበለጸገው፤ ቀድሞ
በነ በረው ፈንታ ዕጥፍ አድርጎ ሰጠው።
11ወን ድሞቹና እኅቶቹ፣ ቀድሞም ያውቀ
ት የነበሩ ሁሉ ወደ እርሱ መጡ፤ በቤተ
ም ከእርሱ ጋር ምግብ በሉ።
እነርሱም ሐዘና ቸውን ገለጡለት፤ *እግዚ
አብሔርም* ካመጣ በት መከራ ሁሉ አ
ጽናኑት፤ እያንዳንዳቸ ውም ጥሬ ብርና[ኸ]
የወርቅ ቀለበት ሰጡት።
12*እግዚአብሔርም* ከፊተኛው ይልቅ የኋ
ለኛውን የኢዮብን ሕይወት ባረከ። እር
ሱም ዐሥራ አራት ሺህ በጎች፣ ስድስት ሺህ
ግመሎች፣ አንድ ሺህ ጥማድ በሬዎች፣
አንድ ሺህ እንስት አህዮችም ነበሩት።
13ደግሞም ሰባት ወንዶችና ሦስት ሴቶች
ልጆች ነበሩት፤ 14የመጀመሪያዋን ይሚማ፣
ሁለተኛዋን ቃሥያ፣ ሦስተኛዋንም አማል
ቶያስ ቂራስ ብሎ ሰየማቸው። 15እንደ ኢዮብ
ሴቶች ልጆች የተዋቡ ሴቶች በምድሪቱ
ሁሉ አልተገኙም፤ አባታቸውም ከወንድሞ
ቻቸው ጋር ርስት ሰጣቸው።
16ከዚህ በኋላ ኢዮብ አንድ መቶ አርባ
ዓመት ኖረ፤ ልጆቹንና የልጅ ልጆቹን
እስከ አራት ትውልድ ድረስ አየ። 17በዚህ
ሁኔታ አርጅቶ፣ ዕድሜ ጠግቦ ሞተ።

[ኸ]11 ዕብራይስጡ፣ *ኬሲታ* ይላል፤ ኬሲታ የገንዘብ ዐይነት ነው፤ ግን ክብደቱና መጠኑ በትክክል አይታወቅም

# መጽሐፈ መዝሙር

## አንደኛ መጽሐፍ
## ከመዝሙር 1-41
## መዝሙር 1
### ሁለቱ መንገዶች

1 በክፉዎች ምክር የማይሄድ፣
በኀጢአተኞች መንገድ የማይቆም፣
በፌዘኞችም ወንበር የማይቀመጥ፣
ሰው ብፁዕ ነው።
2 ነገር ግን ደስ የሚሰኘው *በእግዚአብሔር ሕግ* ነው፤
ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያሰላስለዋል።
3 እርሱም በወራጅ ውሃ ዳር እንደ ተተከለች፣
ፍሬዋን በየወቅቱ እንደምትሰጥ፣
ቅጠሏም እንደማይጠወልግ ዛፍ ነው፤
የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል።
4 ክፉዎች ግን እንዲህ አይደሉም፤
ነገር ግን ነፋስ ጠራርጎ
እንደሚወስደው፣
ገለባ ናቸው።
5 ስለዚህ ክፉዎች በፍርድ ፊት፣
ኀጢአተኞችም በጻድቃን ማኅበር
መቆም አይችሉም፤

6 *እግዚአብሔር የጻድቃንን መንገድ ይጠብቃልና፤*
የክፉዎች መንገድ ግን ትጠፋለች።

## መዝሙር 2
### መሢሓዊ ትዕይንት

1 ሕዝቦች ለምን ያሤራሉ?[ሀ]
ሰዎችስ ለምን ከንቱ ነገር ያውጠ
ነጥናሉ?
2 የምድር ነገሥታት ተነሡ፤
ገዦችም *በእግዚአብሔርና* በመሢሑ[ለ]
ላይ፣
ሊመክሩ ተሰበሰቡ፤
3 "ሰንሰለታቸውን እንበጥስ፣
የእግር ብረታቸውንም አውልቀን
እንጣል" አሉ።

4 በሰማይ ዙፋን ላይ የተቀመጠው
ይሥቃል፤
ጌታ ም ይሣለቅባቸዋል።
5 ከዚያም በቍጣው ይናገራቸዋል፤
በመዓቱም ያስደነግጣቸዋል፤
6 ደግሞም፣ "እኔ ግን በተቀደሰው
ተራራዬ፣
በጽዮን ላይ የራሴን ንጉሥ ሾምሁ"
ይላል።

7 *የእግዚአብሔርን* ሕግ ዐውጃለሁ፤
እርሱም እንዲህ አለኝ፤ "አንተ ልጄ ነህ፤
እኔ ዛሬ ወለድሁህ፤[ሐ]
8 ለምነኝ፤
መንግሥታትን ርስት አድርጌ፣
የምድርንም ዳርቻ ግዛት እንዲሆንህ
እሰጥሃለሁ።
9 አንተም በብረት በትር ትቀጠቅጣቸዋለህ፤[መ]
እንደ ሸክላ ዕቃ ታደቃቸዋለህ።"

10 ስለዚህ እናንተ ነገሥታት ልብ በሉ፤
እናንተ የምድር ገዦችም፣
ተጠንቀቁ።
11 *እግዚአብሔርን* በፍርሃት አገልግሉት፤
ለእርሱ መራድም ደስ ያሰኛችሁ።
12 እንዳይቈጣና በመንገድ እንዳትጠፉ፣
ዝቅ ብላችሁ ልጁን ሳሙት፤
ቍጣው ፈጥኖ ይነዳልና።
እርሱን መጠጊያ የሚያደርጉ ሁሉ
የተባረኩ ናቸው።

## መዝሙር 3
### የመከራ ተቀባዩ የጧት ጸሎት

ዳዊት ከልጁ ከአቤሰሎም በሸሸ ጊዜ የዘመረው መዝሙር

1 *እግዚአብሔር ሆይ፤* ጠላቶቼ ምንኛ በዙ!
ስንቱስ በእኔ ላይ ተነሣ!
2 ብዙዎች ነፍሴን፣ "እግዚአብሔር
አይታደግሽም" አሏት። ሴላ[ሠ]

3 *እግዚአብሔር ሆይ፤* አንተ ግን ዙሪያዬን
የምትከልል ጋሻ ነህ፤
ክብሬና፣ ራሴንም ቀና ቀና
የምታደርግ አንተ ነህ።[ረ]
4 ወደ *እግዚአብሔር* ድምፄን ከፍ
አድርጌ እጮኻለሁ፤
እርሱም ከተቀደሰ ተራራው
ይመልስልኛል። ሴላ
5 እተኛለሁ፤ አንቀላፋለሁ፤
*እግዚአብሔር* ደግፎ ይዞኛልና
እነቃለሁ።

1፥1 ዘፍ49፥6፤ዘዳ 33፥29፤ኢዮ11፥3፤ 21፥16፤ መዝ10፥2-11፤26፥4:9፤37፥38፤ 40፥4፤51፥13፤89፥15፤ 104፥35፤128፥4፤ምሳ 1፥22፤ኢሳ 28፥14፤ ሆሴ7፥5
1፥2 ዘፍ24፥63፤ መዝ 19፥7፤112፥1፤ 119፥1:16:35፤ሕዝ 11፥20፤18፥17፤ሮሜ 7፥22
1፥3 ዘፍ39፥3፤ዘኍ 24፥6፤ኢዮ14፥9፤መዝ 46፥4፤52፥8፤65፥9፤92፥12:14፤128፥3፤ኢሳ 1፥30፤33፥21፤64፥6፤ኤር 11፥16፤31፥9፤ ሕዝ17፥5፤47፥12፤ዘካ 4፥3
1፥4 ኢዮ13፥25፤ኢሳ 40፥24፤ኤር13፥24
1፥5 ኢዮ19፥29፤መዝ 5፥5፤26፥12፤35፥18፤ 82፥1፤89፥5፤107፥32፤ 111፥1፤149፥1
1፥6 ዘሌ26፥38፤መዝ 9፥6፤37፥18፤121፥5፤1 45፥20፤ናሆ1፥7
2፥1 መዝ21፥11፤ 83፥5፤ምሳ24፥2
2፥2 1ሳሙ9፥16፤ መዝ48፥4፤ዮሐ1፥41፤ ሐሥ4፥25-26
2፥3 2ሳሙ3፥34፤ ኢዮ36፥8
2፥4 መዝ37፥13፤ ምሳ1፥26፤ኢሳ37፥16፤ 40፥22፤66፥1
2፥5 መዝ6፥1፤21፥9 ፤27፥9፤38፥1፤79፥6፤ 90፥7፤110፥5
2፥6 ዘፀ15፥17፤2ነገ 19፥31፤መዝ9፥11፤10፥16፤24፥10፤48፥2:11፤ 78፥68፤110፥2፤133፥3
2፥7 2ሳሙ7፥14፤ ማቴ3፥17፤4፥3፤ሐሥ 13፥33፤ዕብ1፥5፤5፥5
2፥8 ኢዮ22፥26፤ መዝ22፥27፤67፥7፤ ማቴ21፥38፤ራእ2፥26
2፥9 ዘፍ49፥10፤ዘፀ 15፥6፤ኢሳ30፥14፤ ኤር19፥10፤ራእ2፥27 ፤12፥5፤19፥15
2፥10 መዝ141፥6፤ ምሳ8፥15፤27፥11፤ አሞ2፥3
2፥11 1ዜና16፥30፤ መዝ9፥2፤35፥9፤103፥1 1፤104፥34፤ኢሳ 61፥10
2፥12 ቍ7፤ዘዳ9፥8፤ መዝ5፥11፤34፥8፤64፥10፤84፥12፤ራእ6፥16 3፥1 ርዕስ 2ሳሙ15፥14 3፥2 መዝ22፥8፤ 71፥11፤ኢሳ36፥15፤37፥20 3፥3 ዘፍ15፥1፤መዝ27፥6 3፥4 ኢዮ 30፥20፤መዝ2፥6 3፥5 ዘሌ26፥6፤መዝ17፥15፤139፥18

[ሀ]1 ዕብራይስጡ እንዲሁ ሲሆን ሰብዓ ሊቃናት ግን *ይቈጣሉ* ይላል።
[ለ]2 ወይም *የተቀባው*
[ሐ]7 ወይም ... *አባትህ ሆንሁ*
[መ]9 ወይም *በብረት ዘንግ ትሰባብራቸዋለህ*
[ሠ]2 በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ በተደጋጋሚ የሚገኝ ሲሆን የቃሉ ትርጕም በትክክል አይታወቅም፤ የሙዚቃ ምልክት ሳይሆን አይቀርም

6 በየአቅጣጫው የከበበኝን፣
አእላፍ ሕዝብ አልፈራም።
7 *እግዚአብሔር ሆይ ተነሥ!*
አምላኬ ሆይ፤ ታደገኝ፤
የጠላቶቼን ሁሉ መንጋጋ ትመታለህ፤
የክፉዎችንም ጥርስ ትሰባብራለህ።
8 ማዳን *የእግዚአብሔር* ነው፤
በረከትህ በሕዝብህ ላይ ይሁን።
ሴላ

## መዝሙር 4

### የሠርክ ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች የሚዜም የዳዊት መዝሙር*

1 የጽድቄ አምላክ ሆይ፤
በጠራሁህ ጊዜ መልስልኝ፤
ከጭንቀቴ አሳርፈኝ፤
ማረኝ፤ ጸሎቴንም ስማ።
2 ሰዎች ሆይ፤ እስከ መቼ ድረስ ክብሬን
ዝቅ[ሰ] ታደርጋላችሁ?
እስከ መቼስ ድረስ ከንቱ ነገርን
ትወዳላችሁ?
ሐሰትንስ[ሸ] ትሻላችሁ? ሴላ
3 *እግዚአብሔር* ጻድቁን ለራሱ እንደ ለየ
ዕወቁ፤
*እግዚአብሔር* ወደ እርሱ በተጣራሁ
ጊዜ ይሰማኛል።
4 ስትቈጡ ኀጢአት አትሥሩ፤
በአልጋችሁም ላይ ሳላችሁ፣
ልባችሁን መርምሩ፤ ጸጥም በሉ።
ሴላ
5 የጽድቅን መሥዋዕት አቅርቡ፤
*በእግዚአብሔርም* ታመኑ።
6 ብዙዎች፣ “አንዳች በጎ ነገር ማን
ያሳየናል? ይላሉ፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ የፊትህ ብርሃን
በላያችን ይብራ።
7 ስንዴና አዲስ የወይን ጠጅ በብዛት
ባመረቱ ጊዜ ከሚያገኙት ደስታ
ይልቅ፣
አንተ ልቤን በታላቅ ሐሤት
ሞልተኸዋል።
8 በሰላም እተኛለሁ፤ አንቀላፋለሁም፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ያለ ሥጋት
የምታሳድረኝ አንተ ብቻ ነህና።

## መዝሙር 5

### የጧት ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ በዋሽንት የሚዘመር፣ የዳዊት መዝሙር*

1 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ቃሌን አድምጥ፤
መቃተቴንም ቸል አትበል።
2 ንጉሤና አምላኬ ሆይ፤
ወደ አንተ እጸልያለሁና፣
ድረስልኝ ብዬ ስጮህ ስማኝ።
3 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ በማለዳ ድምፄን
ትሰማለህ፤
በማለዳ ልመናዬን በፊትህ አቀርባለሁ፤
ፊቃድህንም በጥሞና እጠባበቃለሁ፤
4 አንተ በክፉት ደስ የምትሰኝ አምላክ
አይደለህም፤
ክፉም ከአንተ ጋር አያድርም።
5 እብሪተኞች በፊትህ መቆም አይችሉም፤
ክፉ አድራጊዎችንም ሁሉ ጠላህ።
6 ሐሰት የሚናገሩትን ታጠፋቸዋለህ፤
ደም የተጠሙትንና አታላዮችን፣
*እግዚአብሔር* ይጸየፋቸዋል።
7 እኔ ግን በምሕረትህ ብዛት
ወደ ቤትህ እገባለሁ፤
አንተንም በመፍራት፣
ወደ ተቀደሰው መቅደስህ እሰግዳለሁ።
8 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ከጠላቶቼ የተነሣ፣
በጽድቅህ ምራኝ፤
መንገድህንም በፊቴ አቅናልኝ።
9 በንግግራቸው ውስጥ እውነት የለም፤
ልባቸው የጥፋት ጕሬ ነው፤
ጕሮሮአቸው የተከፈተ መቃብር ነው፤
በምላሳቸውም ይሸነግላሉ።
10 አምላክ ሆይ፤ የእጃቸውን ስጣቸው!
ተንኰላቸው መውደቂያቸው ይሁን፤
ከኀጢአታቸው ብዛት የተነሣ
አስወግዳቸው፣
በአንተ ላይ ዐምፀዋልና።
11 አንተን መጠጊያ የሚያደርጉ ሁሉ ግን
ደስ ይበላቸው፤
ዘላለም በደስታ ይዘምሩ፤
ስምህን የሚወዱ በአንተ ደስ እንዲላቸው፣
ተከላካይ ሁንላቸው።
12 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ ጻድቃንን
ትባርካቸዋለህ፤
በሞገስህም እንደ ጋሻ ትከልላቸዋለህ።

## መዝሙር 6

### በጭንቅ ጊዜ የቀረበ ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች የሚዘመር፤ የዳዊት መዝሙር በሸሚኒት[ቀ]*

1 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ በቍጣህ
አትገሥጸኝ፤

**3፥6** ኢዮ11፥15፤ መዝ23፥4፤27፥3፤ 118፥11
**3፥7** 2ዜና6፥41፤ኢዮ16፥10፤29፥17፤መዝ6፥4፤7፥1፤57፥4፤59፥1፤109፥21፤119፥153፤ምሳ30፥14፤ኢሳ25፥9፤33፥22፤35፥4፤36፥15፤37፥20፤ኤር42፥11፤ሰቆ3፥16፤ማቴ6፥13
**3፥8** ዘኍ6፥23፤መዝ27፥1፤29፥11፤37፥39፤62፥1፤129፥8፤ኢሳ43፥3፡11፤44፥6፡8፤45፥21፤ሆሴ13፥4፤ዮና2፥9፤ራእ7፥10
**4፥1** ዘፍ32፥7፤መሳ2፥15፤መዝ13፥3፤17፥6፤30፥10፤54፥2፤69፥16፤84፥8፤86፥7፤88፥2፤102፥2
**4፥2** ዘፀ16፥7፤መሳ2፥17፤1ሳሙ4፥21፤2ነገ19፥26፤ኢዮ8፥22፤መዝ31፥6፤35፥26፤40፥4፤ኤር13፥25፤16፥9፤አሞ2፥4
**4፥3** መዝ6፥8፤12፥1፤30፥4፤31፥23፤79፥2፤ሚክ7፥2፡7፤1ጢሞ4፥7፤2ጴጥ3፥11
**4፥4** መዝ63፥6፤ዳን2፥28፤ኤፌ4፥26
**4፥5** መዝ31፥6፤115፥9፤ምሳ3፥5፤28፥26፤ኢሳ26፥4፤ዮሐ14፥1
**4፥6** ዘኍ6፥25
**4፥7** ዘፍ27፥28፤ዘዳ28፥51፤ኢሳ9፥3፤35፥10፤65፥14፡18፤ሐሥ14፥17
**4፥8** ዘሌ26፥6፤ዘኍ6፥26፤ዘዳ33፥28፤ኢዮ11፥18፤ኤር 32፥37
**5፥1** 1ነገ8፥29፤መዝ17፥1፤38፥9፤40፥1፤116፥2፤ኢሳ35፥10፤51፥11፤ዳን9፥18
**5፥2** ኢዮ19፥7፤24፥12፤36፥5፤መዝ44፥4፤68፥24፤84፥3
**5፥3** መዝ62፥1፤119፥81፤130፥5፤ኢሳ28፥19፤50፥4፤ኤር21፥12፤ሕዝ46፥13፤ዕን 2፥1፤ሶፎ3፥5፤ሮሜ8፥19
**5፥4** መዝ1፥5፤11፥5፤104፥35፤ምሳ2፥22
**5፥5** 2ነገ19፥32፤መዝ1፥5፤45፥7፤73፥3፤75፥4፤101፥3፤119፥104፤ምሳ8፥13፤ኢሳ33፥19፤37፥33
**5፥6** ምሳ19፥22፤ዮሐ8፥44፤ሐሥ5፥3፤ራእ21፥8
**5፥7** ዘዳ13፥4፤2ሳሙ12፥16፤1ነገ8፥48፤መዝ138፥2፤ኤር44፥10፤ዳን6፥26
**5፥8** 1ነገ8፥36፤መዝ23፥3፤31፥1፤71፥2፤85፥13፤89፥16፤ምሳ8፥20፤ዮሐ1፥23 **5፥9** መዝ12፥2፤28፥3፤36፥3፤ምሳ15፥4፤ኤር5፥16፤9፥8፤ሉቃ11፥44፤ሮሜ3፥13 **5፥10** መዝ78፥40፤106፥7፤107፥11፤ሰቆ1፥5፤3፥42 **5፥11** ኢዮ22፥19፤መዝ33፥1፤69፥36፤81፥1፤90፥14፤92፥4፥95፥1፤119፥132፤145፥7 **5፥12** ዘፍ15፥1፤መዝ32፥7፤112፥2 **6፥1** መዝ2፥5

[ረ]3 ወይም *እግዚአብሔር … ወደ ላይ የምታነሣ ክብሬ ሆይ*
[ሰ]2 ወይም *ወደ ራሳችሁ* [ሸ]2 ወይም *የሐሰት አማልክት*
[ቀ]የ6 *መግቢያ* ርእስ ሲሆን በሙዚቃ ውስጥ የሚጠቀሙበት ቃል ሳይሆን አይቀርም።

በመዓትህም አትቅጣኝ።
2እግዚአብሔር ሆይ፤ ዐቅመ ቢስ ነኝና ማረኝ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ ዐጥንቶቼ ተናግጠ ተዋልና ፈውሰኝ።
3ነፍሴ እጅግ ታውካለች፤
እስከ መቼ፤ አንተ እግዚአብሔር ሆይ፤ ይህ እስከ መቼ ድረስ ይሆናል?
4እግዚአብሔር ሆይ፤ ተመለስና ሕይወቴን ታደጋት፤
ስለ ጽኑ ፍቅርህም አድነኝ፤
5በሞት የሚያስታውስህ የለምና፤
በሲኦልስ[∩] ማን ያመሰግንሃል?
6ከመቃተቴ የተነሣ ዝያለሁ፤
ሌሊቱን ሁሉ በልቅሶ ዐልጋዬን አርሳለሁ፤
መኝታዬንም በእንባዬ አሾቃለሁ።
7ዐይኖቼ በሐዘን ብዛት ደክመዋል፤
ከጠላቶቼም ሁሉ የተነሣ ማየት ተስኖአቸዋል።
8እናንተ ክፉ አድራጊዎች ሁሉ፤ ከእኔ ራቁ፤
እግዚአብሔር የልቅሶዬን ድምፅ ሰምቶአልና።
9እግዚአብሔር ልመናዬን አድምጦአል፤
እግዚአብሔር ጸሎቴን ይቀበላል።
10ጠላቶቼ ሁሉ ያፍራሉ፤ እጅግም ይደነግጣሉ፤
በመጡበት ይመለሳሉ፤ ድንገትም ይዋረዳሉ።

## መዝሙር 7

### በስደት ጊዜ የጻድቁ ሰው ጸሎት

*ዳዊት በብንያማዊው በኩዝ ምክንያት ለእግዚአብሔር የዘመረው መዝሙር*

1እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤ አንተ መሸሸጊያዬ ነህ፤
ከሚያሳድዱኝ ሁሉ አድነኝ፤ ታደገኝም፤
2አለበለዚያ እንደ አንበሳ ይዘነጣጥሉኛል፤
የሚያድነኝ በሌለበትም ይቦጫጭቁኛል።
3እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤ ይህን አድርጌ ከሆነ፣
በደልም በእጇ ከተገኘ፣
4በጎ ለዋለልኝ ክፉ መልሼ ብሆን፣
ጠላቴንም በከንቱ ዘርፌ ከሆነ፣
5ጠላቴ አሳዶ ይያዘኝ፤
ሕይወቴን ከምድር ይቀላቅል፤
ክብሬንም ከዐፈር ይደባልቅ። ሴላ
6እግዚአብሔር ሆይ፤ በመዓትህ ተነሥ፤
በቍጣ በተነሡብኝ ላይ ተነሥ፤
አምላኬ ሆይ፤ ንቃ፤ ትእዛዝም አስተላልፍ!
7የሕዝቦች ጉባኤ ይክበብህ፤
አንተም ከላይ ሆነህ ግዛቸው፤
8እግዚአብሔር በሕዝቦች ላይ ይፈርዳል።
እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ ጽድቄ ፍረድልኝ፤
ልዑል ሆይ፤ እንደ ቅን አካሄዴ መልስልኝ።
9ልብንና ኵላሊትን የምትመረምር፣
ጻድቅ አምላክ ሆይ፤
የክፉዎችን ዐመፅ አጥፋ፤
ጻድቁን ግን አጽና።
10ጋሻዬ[+] ልዑል አምላክ ነው፤
እርሱ ልበ ቅኖችን ያድናቸዋል።
11እግዚአብሔር ጻድቅ ዳኛ ነው፤
ቍጣውንም በየዕለቱ የሚገልጥ አምላክ ነው።
12ሰው በንስሓ የማይመለስ ከሆነ ግን፣
ሰይፉን[#] ይስላል፤
ቀስቱን ይገትራል።
13የሚገድሉ ጦር ዕቃዎቹን አሰናድቶአል፤
የሚንበለበሉትን ፍላጻዎቹንም አዘጋጅቶአል።
14ክፋትን እያማጠ ያለ ሰው፣
ቅጥፈትን አርግዞ፣ ሐሰትን ይወልዳል።
15ጕድጓድ ምሶ ዐፈሩን የሚያወጣ፣
ባዘጋጀው ጕድጓድ ራሱ ይገባበታል።
16ተንኰሉ ወደ ራሱ ይመለሳል፤
ዐመፃውም በገዛ አናቱ ላይ ይወርዳል።
17ስለ ጽድቁ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀርባለሁ፤
የልዑል እግዚአብሔርን ስም በመዝሙር አወድሳለሁ።

## መዝሙር 8

### የፈጣሪ ግርማ በፍጥረቱ ላይ

*ለመዘምራን አለቃ፣ በዋሽንት የሚዜም፤ የዳዊት መዝሙር*

1እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ፤
ስምህ በምድር ሁሉ ላይ ምንኛ ግርማዊ ነው!
ክብርህ ከሰማያት በላይ፣
ከፍ ከፍ ብሎአል።
2ከልጆችና ጡት ከሚጠቡ ሕፃናት አፍ፣
ምስጋናን[ኀ] አዘጋጀህ፤
ከጠላትህ የተነሣ፤
ባላንጣንና ቂመኛን ጸጥ ታሰኝ ዘንድ።

[∩]5 ወይም *በመቃብር* [+]10 ወይም *የኔ ልዑል*
[#]12 ወይም *ሰው ንስሓ ካልገባ፣ እግዚአብሔር ሰይፉን ...*
[ኀ]2 ወይም *ብርታትን*

6፥2 ዘኍ12፥13፤መዝ 4፥1፤22፥14፤26፥11፤3 1፥10፤32፥3፤38፥3፤42፥10፤61፥2፤77፥3፤102፥3፤142፥3፤ኢሳ 40፥31፤ኤር3፥12፤8፥18፤12፥15፤31፥20፤ሕዝ21፥7
6፥3 1ሳሙ1፥14፤1ነገ18፥21፤ኢዮ7፥11፤መዝ4፥2፤31፥7፤38፥8፤55፥4፤89፥46፤ኢሳ 6፥11፤ኤር4፥14፤ዕን 1፥2፤ዘካ1፥12፤ዮሐ 12፥27፤ሮሜ9፥2፤2ቆሮ2፥4
6፥4 መዝ13፥5፤25፥16፤31፥2:16፤69፥16፤71፥2፤77፥8፤85፥7፤86፥16፤88፥2፤102፥2፤119፥41:132፤ኢሳ 54፥8:10
6፥5 መዝ30፥9፤88፥10-12፤115፥17፤መክ9፥10፤ኢሳ38፥18
6፥6 መሳ8፥5፤ኢዮ 3፥24፤7፥3፤16፥16፤23፥2፤መዝ12፥5፤77፥3፤102፥5፤ሰቆ1፥8:11:21:22፤ሉቃ7፥38፤ሐሥ 20፥19
6፥7 ኢዮ16፥8፤መዝ 31፥9፤69፥3፤119፥82፤ኢሳ38፥14
6፥8 መዝ5፥5፤119፥115፤139፥19፤ማቴ 7፥23
6፥9 መዝ28፥6፤116፥1
6፥10 2ነገ19፥26፤መዝ40፥14
7 ርዕስ ዕን3፥1
7፥1 መዝ2፥12፤3፥7፤11፥1፤31፥1:15፤119፥86:157:161
7፥2 ዘፍ49፥9፤መዝ 3፥2፤71፥11፤ራእ4፥7
7፥3 ኢሳ59፥3
7፥4 መዝ35፥7:19፤ምሳ24፥28
7፥5 ዘፀ15፥9፤2ሳሙ 22፥43፤2ነገ9፥33፤ኢዮ7፥21፤ኢሳ10፥6፤ሰቆ3፥16
7፥6 2ዜና6፥41፤መዝ35፥23፤44፥23፤138፥7
7፥7 መዝ68፥18
7፥8 ዘፍ3፥5፤20፥5፤ዘኍ24፥16፤1ሳሙ26፥23፤1ዜና16፥33፤መዝ 18፥20፤ማር5፥7
7፥9 1ዜና28፥9፤መዝ 26፥2፤37፥23፤40፥2፤ኤር11፥20፤ራእ2፥23
7፥10 ኢዮ33፥3፤መዝ3፥3
7፥11 ዘፍ18፥25፤ዘዳ 9፥8፤መዝ9፥8፤67፥4፤75፥2፤96፥13፤98፥9፤ኢሳ11፥4፤ኤር 11፥20
7፥12 ዘዳ32፥41፤2ሳሙ22፥35፤መዝ21፥12፤ኢሳ5፥28፤13፥18፤ሕዝ 3፥19 7፥13 መዝ11፥2፤18፥14፤64፥3 7፥14 ኢሳ59፥4፤ያዕ1፥15
7፥15 ኢዮ4፥8፤መዝ 35፥7:8፤40፥2፤94፥13፤ምሳ26፥27
7፥17 ዘፍ14፥18፤ 2ዜና31፥2፤መዝ5፥8፤ሮሜ15፥11፤ዕብ2፥12
8፥1 ዘፀ15፥11፤1ዜና16፥10፤መዝ57፥5፤8፥5፤113፥4፤148፥13፤ዕን3፥3፤ሉቃ2፥9 8፥2 መዝ143፥12፤ማቴ21፥16

3 የጣቶችህን *ሥራ*፣
ሰማያትህን ስመለከት፣
በስፍራቸው ያኖርሃቸውን፣
ጨረቃንና ከዋክብትን ሳይ፣
4 በሐሳብህ ስፍራ ትሰጠው ዘንድ ሰው
ምንድን ነው?
ትጠነቀቅለትም ዘንድ የሰው ልጅ
ምንድን ነው?
5 ከመላእክት በጥቂት አሳነስኸው፤
የክብርንና የሞገስን ዘውድ
አቀዳጀኸው።

6 በእጆችህ *ሥራ* ላይ ሾምኸው፤
ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛህለት፤
7 በጎችንና ላሞችን ሁሉ፣
የዱር አራዊትንም፣
8 የሰማይ ወፎችንና፣
የባሕር ዓሦችን፣
በባሕር ውስጥ የሚርመሰመሱትንም
ሁሉ አስገዛህለት።

9 *እግዚአብሔር* አምላካችን ሆይ፤
ስምህ በምድር ሁሉ ላይ ምንኛ
ግርማዊ ነው!

## *መዝሙር* 9[ነ]

### በክፉ ላይ ፍርድ

*ለመዘምራን አለቃ፤ በሙትላቤን ቅኝት፤ የዳዊት መዝሙር*

1 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ በፍጹም ልቤ
አመሰግንሃለሁ፤
ስለ ድንቅ *ሥራዎችህ*ም ሁሉ እናገራለሁ።
2 በአንተ ደስ ይለኛል፤ ሐሤትም
አደርጋለሁ፤
ልዑል ሆይ፤ ስምህን በመዝሙር
እወድሳለሁ።

3 ጠላቶቼ ወደ ኋላ በተመለሱ ጊዜ፣
ተሰነካክለው ከፊትህ ይጠፋሉ፤
4 ፍርዴም ጉዳዬም በአንተ እጅ ናቸውና፤
ቅን ፍርድ እየሰጠህ በዙፋንህ ላይ
ተቀምጠሃል።
5 ሕዝቦችን ገሥጽህ፤ ክፉዎችንም አጠፋህ፤
ስማቸውንም እስከ ወዲያኛው
ደመሰስህ።
6 ጠላቶች ለዘላለም ጠፉ፤
ከተሞቻቸውንም ገለባበጥሃቸው፤
መታሰቢያቸውም ተደምስሶአል።

7 *እግዚአብሔር* ግን ለዘላለም በዙፋኑ ላይ
ነው፤
መንበሩንም ለፍርድ አጽንቶአል።
8 ዓለምን በጽድቅ ይዳኛል፤
ሕዝቦችንም በፍትሕ ይገዛል።
9 *እግዚአብሔር* ለተጨቈኑት አምባ ነው፤
በመከራም ጊዜ መጠጊያ ይሆናቸዋል።
10 ስምህን የሚያውቁ ይታመኑብሃል፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ የሚሹህን
አትተዋቸውምና።

11 በጽዮን ለሚኖር *ለእግዚአብሔር* ዘምሩ፤
*ሥራውን*ም በሕዝቦች መካከል
በግልጽ አውሩ፤
12 ደም ተበቃዩ አስቦአቸዋልና፤
የጭቍኖችንም ጩኸት አልዘነጋም።
13 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ጠላቶቼ
የሚያደርሱብኝን መከራ
ተመልከት፤
አይተህም ራራልኝ፤ ከሞት ደጆም
አንሥተህ መልሰኝ፤
14 ይህን ስታደርግልኝ፣ በጽዮን ሴት ልጅ
ደጅ፣
ምስጋናህን አውጃለሁ፤
በማዳንህም ሐሤት አደርጋለሁ።
15 አሕዛብ በቈፈሩት ጕድጓድ ገቡ፤
እግራቸውም ራሳቸው በስውር
ባስቀመጡት ወጥመድ ተያዘ።
16 *እግዚአብሔር* በትክክለኛ ፍርዱ የታወቀ
ነው፤
ክፉዎችም በእጃቸው *ሥራ* ተጠመዱ።
ሒጋዮን[ኘ] ሴላ
17 ክፉዎች ተመልሰው ወደ ሲኦል[ኣ]
ይወርዳሉ፤
እግዚአብሔርን የሚዘነጉ ሕዝቦችም ሁሉ
እንደዚሁ።
18 ችግረኞች ግን መቼም ቢሆን
አይረሱም፤
የድኾችም ተስፋ ለዘላለም መና ሆኖ
አይቀርም።

19 *እግዚአብሔር* ሆይ ተነሥ፤ ሰውም
አያይል፤
አሕዛብም በፊትህ ይፈረድባቸው።
20 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ድንጋጤ
አምጣባቸው፤
ሕዝቦች ሰው ከመሆን እንደማያልፉ
ይወቁ። ሴላ

**8፥3** ዘፍ1፥16፤15፥5፤ዘፀ8፥19፤ዘዳ10፥14፤1ዜና16፥26፤ 2ዜና2፥12፤መዝ102፥25፤1ቆሮ15፥41
**8፥4** 1ዜና29፥14
**8፥5** ዘፍ1፥26፤መዝ21፥5፤103፥4
**8፥6** ዘፍ1፥28፤1ነገ5፥3፤ኢዮ10፥3፤መዝ19፥1፤102፥25፤145፥10፤ኢሳ26፥12፤29፥23፤45፥11፤1ቆሮ15፥25:27፤ኤፌ1፥22፤ዕብ1፥10፤2፥6-8
**8፥7** ዘፍ2፥19፤13፥5፤26፥14
**8፥8** ዘፍ1፥26
**8፥9** ቍ1
**9፥1** ዘዳ4፥34፤መዝ86፥12፤111፥1፤119፥2:10:145፤138፥1
**9፥2** 2ዜና31፥2፤ኢዮ22፥19፤መዝ14፥7፤31፥7፤70፥4፤92፥1፤97፥8፤126፥3፤ምሳ23፥15፤ኢሳ25፥9፤ኤር30፥19፤ኢል2፥21፤ሶፎ3፥14፤ማቴ5፥12፤ራእ19፥7
**9፥4** 1ነገ8፥45፤ኢዮ16፥21፤መዝ7፥11፤11፥4፤47፥8፤67፥4፤98፥9፤ኢሳ6፥1፤1ጴጥ2፥23
**9፥5** ዘፍ20፥7፤37፥10፤1ዜና16፥21፤ኢዮ18፥17፤መዝ59፥5፤105፥14፤ኢሳ26፥14፤66፥15
**9፥6** ዘዳ29፥28፤መዝ34፥16፤109፥15፤መክ9፥5፤ኢሳ14፥22፤26፥14፤ኤር2፥3፤46፥1-51:58፤ሶፎ2፥8-10
**9፥7** 1ዜና16፥31፤መዝ11፥4፤47፥8፤93፥2፤ኢሳ6፥1፤66፥1፤ራእ19፥6
**9፥8** ቍ4፤መዝ7፥11፤11፥7፤45፥6፤72፥2
**9፥9** ዘዳ33፥27፤2ሳሙ22፥3፤መዝ10፥18፤32፥7፤74፥21፤121፥7
**9፥10** ዘፍ28፥15፤ዘዳ4፥31፤መዝ22፥1፤37፥25፤70፥4፤71፥11፤91፥14፤ኢሳ49፥14፤ኤር15፥18፤ዕብ13፥5
**9፥11** መዝ2፥6፤7፥17፤18፥49፤44፥11፤57፥9፤105፥1፤106፥27፤ኢሳ24፥13፤ሕዝ20፥23፤1ጢሞ3፥16
**9፥12** ቍ18፤2ሳሙ4፥11፤መዝ10፥17፤22፥24፤72፥4፤ኢሳ 49፥13
**9፥13** ዘኍ10፥9፤ኢዮ17፥16፤መዝ3፥7፤6፥2፤18፥3፤41፥4፤51፥1፤86፥3:16፤119፥132፤ማቴ16፥18

**9፥14** 2ነገ19፥21፤መዝ13፥5፤35፥9፤50፥23፤51፥12:15፤ኢሳ1፥8፤10፥32፤37፥22፤62፥11፤ኤር4፥31፤6፥2፤ሰቆ1፥6፤ሚክ1፥13፤ሶፎ3፥14፤ዘካ2፥10፤ማቴ21፥5፤ዮሐ12፥15፤1ጴጥ2፥9 **9፥15** ኢዮ4፥8፤መዝ35፥7:8፤57፥6 **9፥16** ምሳ5፥22 **9፥17** ዘኍ16፥30፤ኢዮ8፥13፤ምሳ5፥5 **9፥18** ቍ12፤መዝ25፥3፤39፥7፤71፥5፤74፥19፤ምሳ23፥18፤ኤር14፥8 **9፥19** 2ዜና14፥11፤መዝ3፥7፤110፥6፤ኢሳ2፥4፤ኢል3፥12 **9፥20** ዘፍ35፥5፤መዝ31፥13፤ 62፥9፤ኢሳ13፥8፤31፥3፤ሕ28፥2፤ሉቃ21፥26

[ነ]ምዕ9 *መዝ*9 እና 10 በመጀመሪያው የጥንት ቅጅ ላይ አንጓዎቹ ተከታታይ ፊደላት ባሉት የዕብራይስጥ ሆህያት የሚጀምሩ እንዲሁም ጅማሬው ወይም መጨረሻው ትርጒም አዘል የሆነ አንድ ወጥ ግጥም ነበር፤ በሰብዓ ሊቃናት ውስጥ ሁለቱም አንድ መዝሙር ናቸው።
[ኘ]16 ወይም *በተመሥጦ ማሰብ*
[ኣ]17 ወይም *መቃብር*

## መዝሙር 10[ከ]
### ለፍትሕ የቀረበ ልመና

1*እግዚአብሔር ሆይ፤ ለምን እንዲህ ርቀህ ቆምህ?*
በመከራ ጊዜስ ለምን ድምፅህን አጠፋህ?
2ክፉዎች የተጨነቀውን በእብሪት ያሳድዳሉ፤
በወጠኑት ተንኰል ይጠመዱ።
3ክፉ ሰው በልቡ ምኞት ይኵራራል፤
ስግብግቡን ይባርካል፤ *እግዚአብሔርንም* ይዳፈራል።
4ክፉ ሰው ከትዕቢቱ የተነሣ እግዚአብሔርን አይፈልግም፤
በሐሳቡም ሁሉ አምላክ የለም፤
5*መንገዱ* ዘወትር የተሳካ ነው፤
ዕቡይ፣ ከሕግህም የራቀ ነው።
በመሆኑም በጠላቶቹ ላይ ያፌዛል።
6በልቡም፣ "ከስፍራዬ የሚነቀንቀኝ የለም፤
ከትውልድ እስከ ትውልድም መከራ አያገኘኝም" ይላል።
7አፉ መርገምን፣ ቅጥፈትንና ግፍን የተሞላ ነው፤
ሽንገላና ክፋት ከምላሱ ሥር ይገኛሉ።
8በየመንደሩ ሥርቻ ያደፍጣል፤
ንጹሐንን በሰዋራ ስፍራ ይገድላል።
ዐይኖቹንም በምስኪኖች ላይ ያነጣጥራል።
9በደኑ ውስጥ እንዳለ አንበሳ በስውር ያደባል፤
ረዳት የሌለውን ለመያዝ ያሸምቃል፤
ድኻውንም አፈፍ አድርጎ በወጥመዱ ይጐትታል።
10ምስኪኑም ይደቅቃል፤ ዐንገቱን ይደፋል፤
ያልታደለውም በክንዱ ሥር ይወድቃል።
11በልቡም፣ "እግዚአብሔር ረስቶአል፤
ፊቱን ሸፍኖአል፤ ፈጽሞም አያይም" ይላል።

12*እግዚአብሔር ሆይ ተነሥ፤ አምላክ ሆይ፤* ክንድህን አንሣ፤
ረዳት የሌላቸውንም አትርሳ።
13ክፉ ሰው በእግዚአብሔር ላይ ለምን ክፉ ይናገራል?
በልቡስ፣ "ስለ ሥራዬ አይጠይቀኝም" ለምን ይላል?
14አንተ ግን መከራንና ሐዘንን ታያለህ፤
በእጅህም ዋጋ ለመክፈል ትመለከታለህ፤
ምስኪኑም ራሱን በአንተ ላይ ይጥላል፤
ለድኻ አደግም ረዳቱ አንተ ነህ።
15የክፉውንና የበደለኛውን ክንድ ስበር፤
የእጁንም ስጠው፤
ምንም እስከማይገኝ ድረስ።
16*እግዚአብሔር* ከዘላለም እስከ ዘላለም ንጉሥ ነው፤
ሕዝቦችም ከምድሩ ይጠፋሉ።
17*እግዚአብሔር ሆይ፤* የተገፉትን ምኞት ትሰማለህ፤
ልባቸውን ታበረታለህ፤ ጆሮህንም ወደ እነርሱ ጣል ታደርጋለህ፤
18ከዐፈር የተፈጠረ ሰው ከእንግዲህ እንዳያስጨንቃቸው፣
አንተ ለድኻ አደጉና ለተገፋው ትሟገታለህ።

## መዝሙር 11
### የጻድቃን ትምክህት

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር*

1*በእግዚአብሔር ታምኛለሁ፤*
ታዲያ ነፍሴን፣ "እንደ ወፍ ወደ ተራራ ብረሪ"
ለምን ትሏታላችሁ?
2ደግሞም ለምን እንዲህ ትሉኛላችሁ?
"ክፉዎች፣ እነሆ፣ ቀስታቸውን ገትረዋል፤
የቅኑን ሰው ልብ በጨለማ ለመንደፍ፣
ፍላጻቸውን በአውታሩ ላይ ደግነዋል።
3መሠረቱ ከተናደ፣
ጻድቅ ምን ማድረግ ይችላል?"[ኸ]
4*እግዚአብሔር* በተቀደሰ መቅደሱ አለ፤
የ*እግዚአብሔር* ዙፋን በሰማይ ነው።
ዐይኖቹ ሰዎችን ይመለከታሉ፤
ቅንድቦቹም የሰው ልጆችን ይመረምራሉ።
5*እግዚአብሔር* ጻድቁንና ኀጥኡን ይመረምራል፤[ወ]
ዐመፃን የሚወዱትን ግን፣
ነፍሱ ትጠላቸዋለች።
6እርሱ በክፉዎች ላይ የእሳት ፍምና ዲን ያዘንባል፤
የጽዋቸውም ዕጣ ፊንታ፣
የሚለበልብ ዐውሎ ነፋስ ነው።
7*እግዚአብሔር* ጻድቅ ነውና፤
የጽድቅ ሥራም ይወዳል፤
ቅኖችም ፊቱን ያያሉ።

## መዝሙር 12
### ከክፉ ዓለም ለመዳን የቀረበ ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ በስምንተኛው ቅኝት የሚዘመር፤ የዳዊት መዝሙር።*

1*እግዚአብሔር ሆይ፤* ደግ ሰው የለምና

[ከ]ምዕ10 መዝ9 እና 10 በመጀመሪያው የጥንት ቅጅ ላይ አንጓዎች ተከታታይ ፊደላት ባሉት የዕብራይስጥ ሆህያት የሚጀምሩ እንዲሁም ጅማሬው ወይም መጨረሻው ትርጕም አዘል የሆነ አንድ ወጥ ግጥም ነበር በሰብዓ ሊቃናት ውስጥ ሁለቱ አንድ መዝሙር ናቸው።
[ኸ]3 ወይም *ጻደቁ ምን እያደረገ ነው?*
[ወ]5 ወይም *ጻደቁ እግዚአብሔር ኀጥኡን ይመረምራል*

10፥1 መዝ13፥1፤ 22፥1፡11፤35፥22፤ 38፥21፤71፥12
10፥2 ቆላ9፤ኢዮ 20፥19
10፥3 ኢዮ1፥5፤መዝ 49፥6፤94፥4፤ኤር 48፥30
10፥4 መዝ36፥1
10፥5 መዝ18፥27፤ 101፥5፤ምሳ6፥17፤ኢሳ 13፥11፤ኤር48፥29
10፥6 ራእ18፥7
10፥7 ኢዮ20፥12፤ መዝ73፥8፤119፥134፤ መክ4፥1፤ኢሳ30፥12 ፤ሮሜ3፥14
10፥8 መዝ37፥32፤ 59፥3፤71፥10፤ምሳ1፥1 1፤ኤር5፥26፤ሆሴ6፥9፤ ሚክ7፥2
10፥9 ቆላ2፤ኢዮ 18፥8
10፥10 ኢዮ9፥17
10፥11 ኢዮ22፥13፡ 14፤መዝ42፥9፤77፥9
10፥12 መዝ3፥7፤ 9፥12፤17፥7፤20፥6፤ 106፥26፤ኢሳ26፥11 ፤ሚክ5፥9
10፥13 ቆላ3፤ኢዮ 31፥14
10፥14 ቆላ7፤ዘዳ 33፥29፤መዝ22፥11፤3 7፥5
10፥15 ኢዮ31፥22
10፥16 ዘፀ15፥18 ፤ዘዳ8፥20
10፥17 ዘፀ22፥23፤ መዝ9፥12
10፥18 ዘዳ24፥17፤ መዝ9፥9፤146፥9
11፥1 ዘፍ14፥10፤ መዝ7፥1፤50፥11
11፥2 2ሳሙ22፥35 ፤ኢዮ33፥3፤መዝ 7፥10፡13፤10፥8፤58፥7
11፥3 መዝ18፥15፤ 82፥5፤ኢሳ24፥18
11፥4 1ነገ8፥48፤2ዜና 6፥18፤መዝ9፥7፤18፥6፤ 27፥4፤33፥18፤66፥7፤ ምሳ15፥3፤ዮና2፥7፤ሚ ክ1፥2፤ዕን2፥20፤ማቴ 5፥34፤23፥22፤ራእ4፥2
11፥5 ዘዳ7፥13፤ኢዮ 23፥10፤28፥28፤መዝ5፥ 5፤45፥7፤ኢሳ1፥14
11፥6 ዘፍ19፥24፤ 41፥6፤ኢዮ1፥19፤ራእ 9፥17
11፥7 2ዜና12፥6፤ ዕዝ9፥15፤ኢዮ1፥1፤ መዝ9፥8፤17፥15፤33፥5 ፤99፥4፤140፥13፤ኢሳ 28፥17፤30፥18፤56፥1፤ 61፥8፤ኤር 9፥24፤ሉቃ23፥50፤2ጢ ሞ4፥8
12፥1 ኢሳ57፥1፤ ሚክ7፥2

አንተው ድረስልኝ!
ከሰዎችም መካከል አንድ ታማኝ
አይገኝም፡፡
2እርስ በርሳቸው ውሸት ይነጋገራሉ፤
በሸንገላ ከንፈርና በሁለት ልብ
ይናገራሉ፤
3ሸንጋዩን ከንፈር ሁሉ፣
ነገር የምታበዛውንም ምላስ እግዚ
አብሔር ያጥፋ!
4እነዚህም፣ "በአንደበታችን እንረታለን፤
ከንፈራችን የእኛ ነው፤[o] ጌታችንስ
ማነው?"
የሚሉ ናቸው፡፡
5እግዚአብሔር፣ "ስለ ድኾች መከራ፣
ስለ ችግረኞችም ጩኸት፣
አሁን እነሣለሁ፤
በናፈቁትም ሰላም አኖራቸዋለሁ"
ይላል፡፡
6የእግዚአብሔር ቃል የጠራ ቃል ነው፤
ሰባት ጊዜ እንደ ተጣራ፣
በምድር ላይ በከውር እንደ ተፈተነ
ብር ነው፡፡
7እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ትጠብቀናለህ፤
ከዚህም ትውልድ ለዘላለም
ትከልለናለህ፡፡
8በሰዎች ዘንድ ክፋት ከፍ ከፍ ባለ ጊዜ፣
ዐመፀኞች በየአቅጣጫው በዛቻ
ይዞራሉ፡፡

## መዝሙር 13

### በአምላኩ የታመነ ሰው አቤቱታ

ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር፡፡

1እግዚአብሔር ሆይ፤ እስከ መቼ ድረስ
ለዘላለሙ ትረሳኛለህ?
ፊትህንስ ከእኔ የምትሰውረው እስከ
መቼ ድረስ ነው?
2ከሐሳቤ ጋር የምሟገተው፣
ልቤም ቀኑን ሙሉ የሚያዝነው እስከ
መቼ ነው?
ጠላቴስ በእኔ ላይ የሚያይለው እስከ
መቼ ድረስ ነው?
3እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤ ተመልከት፤
ስማኝም፤
የሞት እንቅልፍ እንዳልተኛ ዐይኖቼን
አብራ፤
4በዚህም ጠላቴ፣ "አሸነፍሁት" እንዳይል፣
ባላጋራዎቼም በውድቀቴ ደስ
እንዳይላቸው ርዳኝ፡፡
5እኔ ግን በጸናች ፍቅርህ እታመናለሁ፤
ልቤም በማዳንህ ደስ ይለዋል፡፡
6ቸርነቱ በዝቶልኛልና፣
ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ፡፡

12፥2 መዝ5፥6፥9፤ 34፥13፤141፥3፤ምሳ6፥19፤12፥17፤13፥3፤ ኢሳ32፥7፤ሮሜ16፥18
12፥3 መዝ73፥9፤ ምሳ26፥28፤28፥23፤ ዳን7፥8፤ያዕ3፥5፤ራእ 13፥5
12፥4 ምሳ18፥21፤ ያዕ3፥6
12፥5 መዝ3፥7፤6፥6፤34፥6፤35፥10፤44፥24፤62፥10፤72፥14፤73፥8፤መክ4፥1፤5፥8፤ኢሳ 3፥15፤5፥7፤30፥12፤ 59፥13፤ሐሥ7፥34
12፥6 2ሳሙ22፥31፤ኢዮ23፥10፤28፥1፤መዝ 18፥30፤119፥140፤ ኢሳ48፥10፤ዘካ13፥9
12፥7 መዝ16፥1፤27፥5፤37፥28፤ዮሐ17፥12
12፥8 መዝ55፥10-11
13፥1 ዘዳ31፥17፤ መዝ6፥3፤22፥24፤ 42፥9፤ኢሳ8፥17፤ 54፥9፤ ሰቆ5፥20
13፥2 መዝ42፥4፤ 55፥2፤94፥3፤139፥23፤ ኢሳ33፥18፤ዳን7፥28
13፥3 ዕዝ9፥8፤መዝ 4፥1፤9፥12፤25፥18፤ 31፥7፤35፥23፤59፥4፤ 76፥5፤80፥14፤90፥5፤ 107፥41፤119፥50፥153፤ኤር51፥39
13፥4 1ነገ19፥2፤መዝ 25፥2፤38፥16፤118፥13
13፥5 ኢዮ33፥26፤ መዝ6፥4፤9፥14፤ኢሳ 25፥9፤33፥2
13፥6 ዘፀ15፥1፤መዝ 7፥17
14፥1 መዝ10፥4
14፥2 ዕዝ6፥21፤ኢዮ 41፥34፤መዝ85፥11፤9 2፥6፤102፥19፤ሰቆ3፥50
14፥3 1ሳሙ8፥3፤ 1ነገ8፥46፤መዝ143፥2፤መክ7፥20፤ሮሜ 3፥10-12፤1ጢሞ 5፥15፤2ጴጥ2፥7
14፥4 መዝ27፥2፤ 79፥6፤82፥5፤ኢሳ64፥7፤65፥1፤ኤር4፥22፤10፥ 25፤ሆሴ7፥7፤ሚክ3፥3
14፥6 2ሳሙ22፥3
14፥7 ዘዳ30፥3፤ መዝ 2፥6፤ኤር48፥47
15፥1 ዘፀ15፥17፤ 25፥8፤29፥46፤2ዜና 22፥19፤መዝ20፥2፤23፥ 6፤27፥4፤61፥4፤78፥69፤150፥1
15፥2 ዘፍ6፥9፤መዝ 18፥32፤ምሳ16፥13፤ ኢሳ45፥19፤ኤር7፥28፤9፥5፤ዘካ8፥3፥16፤ሮሜ 9፥1፤ኤፌ1፥4፤4፥25፤ 1ተሰ3፥13፤ቲቶ1፥6
15፥3 ዘሌ19፥16
15፥4 ዘዳ23፥21፤

## መዝሙር 14

### አምላክ የለሽ ሰዎች

14፥1-7 ተጓ ምብ-መዝ53፥1-6

ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር፡፡

1ሞኝ[″] በልቡ፣
"እግዚአብሔር የለም" ይላል፡፡
ብልሹዎች ናቸው፤ ተግባራቸውም
ጸያፍ ነው፤
በጎ ነገር የሚሠራ አንድም የለም፡፡
2የሚያስተውል፣ እግዚአብሔርን የሚፈልግ
መኖሩን ለማየት፣
እግዚአብሔር ከሰማይ
ወደ ሰው ልጆች ተመለከተ፡፡
3ሁሉም ከመንገድ ወጥተዋል፤
በአንድ ላይም ብልሹ ሆነዋል፤
አንድ እንኳ፣
መልካም የሚያደርግ የለም፡፡
4የእግዚአብሔርን ስም የማይጠሩት፣
ሕዝቤን እንደ እንጀራ የሚበሉት፣
ክፉ አድራጊዎች ሁሉ ዕውቀት
የላቸውምን?
5ባሉበት ድንጋጤ ውጦአቸዋል፤
እግዚአብሔር በጻድቃን መካከል
ይገኛልና፡፡
6እናንተ የድኾችን ዕቅድ ለማፋለስ
ትሻላችሁ፤
እግዚአብሔር ግን መጠጊያቸው ነው፡፡
7ምነው እስራኤልን የሚያድን ከጽዮን
በወጣ!
እግዚአብሔር የሕዝቡን ምርኮ
በሚመልስበት ጊዜ፣
ያዕቆብ ደስ ይበለው፤ እስራኤልም
ሐሤት ያድርግ፡፡

## መዝሙር 15

### የእግዚአብሔር ቤተኛ

የዳዊት መዝሙር

1እግዚአብሔር ሆይ፤ በድንኳንህ ውስጥ
ማን ያድራል?
በተቀደሰው ኰረብታህስ ማን መኖር
ይችላል?
2አካሄዱ ንጹሕ የሆነ፣
ጽድቅን የሚያደርግ፤
ከልቡ እውነትን የሚናገር፤
3በምላሱ የማይሸነግል፤
በባልንጀራው ላይ ክፉ የማይሠራ፤
ወዳጁን የማያማ፤
4ነውረኛ በፊቱ የተናቀ፤

[o]4 ወይም *ከንፈራችን ማረሻ ምላጫችን ነው*
[″]1 በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ *ሞኝ* ወይም *ተላላ* ተብለው የተ ተረጐሙት የዕብራይስጥ ቃላት ግብረ ገባዊ ንቅዘ ትን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

እግዚአብሔርን የሚፈሩትን ግን
የሚያከብር፤
ዋጋ የሚያስከፍለውም ቢሆን፣
ቃለ መሐላውን የሚጠብቅ፤
5ገንዘቡን በአራጣ የማያበድር፣
በንጹሐን ላይ ጉቦ የማይቀበል፤

እነዚህን የሚያደርግ፣
ከቶ አይናወጥም።

## መዝሙር 16

### እግዚአብሔር ርስቴ

የዳዊት ቅኔ

1አምላክ ሆይ፤ መጠጊያዬ ነህና፣
በከለላህ ሰውረኝ።

2እግዚአብሔርን፣ "አንተ ጌታዬ ነህ፤
ከአንተ በቀር በጎነት የለኝም"
አልሁት።
3በምድር ያሉ ቅዱሳን፣
ሙሉ ደስታ የማገኝባቸው ክቡራን
ናቸው።[ፕ]
4ሌሎችን አማልክት የሚከተሉ፣
ሐዘናቸው ይበዛል፤
እኔ ግን የደም ቍርባናቸውን አላፈስም፤
ስማቸውንም በአፌ አልጠራም፤

5እግዚአብሔር የርስት ድርሻዬና ጽዋዬ
ነው፤
ዕጣዬም በእጅህ ናት።
6መካለያ ገመድ ባማረ ስፍራ
ተጥሎልኛል፤
በእርግጥም የተዋበች ርስት አግኝቻለሁ።

7የሚመክረኝን እግዚአብሔርን እባርካለሁ፤
በሌሊት እንኳ ልቤ ቀናውን
ያመላክተኛል።
8እግዚአብሔርን ሁልጊዜ በፊቴ
አድርጌአለሁ፤
እርሱ በቀኜ ስላለ አልናወጥም።
9ስለዚህ ልቤ ደስ አለው፤ ነፍሴም
ሐሤት አደረገች፤
ሥጋዬም ያለ ሥጋት ዐርፎ
ይቀመጣል፤
10በሲኦል[የ] ውስጥ አትተወኝምና፤
ቅዱስህም[ዩ] መበስበስን እንዲያይ
አታደርግም።
11የሕይወትን መንገድ ታሳየኛለህ፤[ዩ]
በአንተ ዘንድ የደስታ ሙላት፣
በቀኝህም የዘላለም ፍሥሓ አለ።

## መዝሙር 17

### የንጹሕ ሰው አቤቱታ

የዳዊት ጸሎት

1እግዚአብሔር ሆይ፤ በቅንነት የቀረበውን
አቤቱታዬን ስማ፤
ጩኸቴንም አድምጥ፤
ከአታላይ ከንፈር ያልወጣውን፣
ጸሎቴን አድምጥ።
2ጽድቄ ከአንተ ዘንድ ይምጣ፤
ዐይኖችህም ፍትሕን ይዩ።

3ልቤን መረመርኸው፣ በሌሊት ጠጋ
ብለህ ፈተንኸኝ፣
ፈተሸኸኝ አንዳች አላገኘህብኝም፤
አንደበቴም እላፊ አልሄደም።
4ከሰዎች ተግባር፣
በከንፈርህ ቃል፣
ከዐመፀኞች መንገድ፣
ራሴን ጠብቄአለሁ።
5አረማመዴ በመንገድህ ጸንቶአል፤
እግሮቼም አልተንሸራተቱም።

6አምላክ ሆይ፤ ስለምትመልስልኝ አንተን
እጣራለሁ፤
ጆሮህን ወደ እኔ ጣል አድርገህ፣
ጸሎቴን ስማ።
7ከጠላቶቻቸው መተገኛ ያደረጉህን፣
በቀኝ እጅህ የምትታደግ ሆይ፤
ጽኑ ፍቅርህን ድንቅ አድርገህ ግለጥ።
8እንደ ዐይንህ ብሌን ጠብቀኝ፤
በክንፎችህም ጥላ ሰውረኝ፤
9ከሚያስጨንቁኝ ከክፉዎች፣
ከሚከብቡኝ አደገኛ ባላንጣዎቼ
ጋርደኝ።

10ደንዳና ልባቸውን ደፈኑት፤
በአፋቸውም ትዕቢት ይናገራሉ።
11አሳደው ደረሱብኝ፤ ከበቡኝም፤
መሬት ላይ ሊዘርሩኝም አፈጠጡብኝ።
12እነርሱ ለንጥቂያ እንደሚጓጓ አንበሳ፣
በስውርም እንደሚያደባ ደቦል አንበሳ
ናቸው።

13እግዚአብሔር ሆይ፤ ተነሥተህ
ግጠማቸውና ጣላቸው፤
በሰይፍህም ከክፉዎች ታደገኝ።
14እግዚአብሔር ሆይ፤ እንዲህ ካሉት
ሰዎች በክንድህ አድነኝ፤
ዕድል ፈንታቸው ይህችው ሕይወት
ብቻ ከሆነች፣ ከዚህ ዓለም ሰዎች
ታደገኝ።

[ፕ]3 ወይም *በምድሪቱ ላሉ አረማውያን፣ ካህናትና ደስ ለተሰኙባቸው መኳንንት ሁሉ ይህን እላለሁ*
[የ]10 ወይም *በመቃብር*
[ዩ]10 ወይም *በአንተ የተታመነውን*
[ዩ]11 ወይም *ታሳውቀኛለህ*

ኢሱ9፥18፤ኢዮ19፥9፤ማቴ5፥33፤ሐሥ28፥10
**15፥5** ዘፀ18፥21፤22፥25፤1ሳሙ8፥3፤ኢዮ29፥18፤መዝ21፥7፤112፥6፤ሐሥ2፥25፤24፥26፤ዕብ12፥28፤2ጴጥ1፥10
**16፥1** መዝ2፥12፤12፥7
**16፥2** መዝ31፥14፤73፥25፤118፥28፤140፥6
**16፥3** ዘዳ33፥3፤መዝ30፥4፤85፥8፤101፥6፤ዳን7፥18፤ሐሥ9፥13፤ሮሜ1፥7
**16፥4** ዘፀ18፥11፤20፥3፤23፥13፤ዘዳ8፥19፤31፥20፤መዝ32፥10፤ምሳ23፥29
**16፥5** ዘሌ2፥2፤ኢዮ31፥2፤መዝ23፥5፤75፥8፤116፥13፤ኢሳ51፥17፤ሰቆ4፥21፤ሕዝ23፥32-34፤ዕን2፥16
**16፥6** ዘዳ19፥14፤ኢዮ22፥26፤መዝ104፥9፤ምሳ8፥29፤ኤር5፥22
**16፥7** ኢዮ35፥10፤መዝ42፥8፤73፥24፤77፥6፤ምሳ15፥22፤ኢሳ11፥2
**16፥8** 1ነገ2፥19፤1ዜና6፥39፤መዝ15፥5፤73፥23
**16፥9** ዘዳ33፥28፤መዝ4፥7፤13፥5፤28፥7፤30፥11
**16፥10** ዘኍ16፥30፤2ነገ19፥22፤ኢዮ17፥14፤መዝ30፥3፤31፥17፤86፥13፤ሆሴ13፥14፤ሐሥ2፥31፤13፥35
**16፥11** መዝ21፥6፤80፥17፤139፥24፤ማቴ7፥14፤ሐሥ2፥25-28
**17፥1** መዝ5፥1፡2፤30፥10፤39፥12፤64፥1፤80፥1፤140፥6፤142፥6፤143፥1፤ኢሳ29፥13
**17፥2** መዝ24፥5፤26፥1፤99፥4፤ኢሳ46፥13፤50፥8-9፤54፥17
**17፥3** ኢዮ7፥18፤23፥10፤መዝ39፥1፤139፥1፤ኤር12፥3፤50፥20
**17፥5** ዘዳ32፥35፤ኢዮ23፥11፤መዝ44፥18፤73፥2፤119፥133፤121፥3
**17፥6** መዝ4፥1፤86፥7፤116፥2
**17፥7** መዝ2፥12፤10፥12፤31፥21፤69፥13፤106፥45፤107፥43፤117፥2
**17፥8** ዘኍ6፥24፤ዘዳ32፥10፤ሩት2፥12፤መዝ27፥5፤31፥20፤32፥7፤36፥7፤63፥7፤ምሳ7፥2፤ኢሳ34፥15
**17፥9** መዝ109፥3
**17፥10** 1ሳሙ2፥3፤መዝ73፥7፤119፥70፤ኢሳ6፥10 **17፥11** መዝ88፥17 **17፥12** ዘፍ49፥9፤መዝ7፥2፤ኤር5፥6፤12፥8፤ሰቆ3፥10 **17፥13** ዘኍ10፥35፤መዝ35፥8፤55፥23፤73፥18 **17፥14** መዝ49፥17፤ኢሳ2፥7፤57፥17፤ሉቃ16፥8፡25

ከመዝገብህ ሆዳቸውን ሞላህ፤
ልጆቻቸውም ተትረፍርፎላቸዋል፤
ለልጆቻቸውም ሀብት ያከማቻሉ፡፡
15እኔ ግን በጽድቅ ፊትህን አያለሁ፤
ስነቃም ክብርህን አይቼ እረካለሁ፡፡

## *መዝሙር* 18

### የድል *መዝሙር*

18 ርእስ-50 ተጓ ምብ-2ሳሙ22፥1-51

*ለመዘምራን አለቃ፤ የእግዚአብሔር ባሪያ የዳዊት መዝሙር፤ ይህም እግዚአብሔር ከሳዖልና ከጠላቶቹ ሁሉ እጅ በታደገው ጊዜ፣ ለእግዚአብሔር እንዲህ ሲል የዘመረው ነው፡-*

1ጕልበቴ *እግዚአብሔር* ሆይ፤
እወድሃለሁ፡፡

2*እግዚአብሔር* ዐለቴ፣ መጠጊያዬና
ታዳጊዬ ነው፤
አምላኬ የምሸሸግበት ዐለቴ፤
እርሱ ጋሻዬ፣ የደኅንቴ ቀንድና[ገ]
ዐምባዬ ነው፡፡
3ምስጋና የሚገባውን *እግዚአብሔርን*
እጠራለሁ፤
ከጠላቶቼም እድናለሁ፡፡

4የሞት ገመድ አነቀኝ፤
የጥፋት ጐርፍም አጥለቀለቀኝ፡፡
5የሲኦል[ጠ] ገመድ ተጠመጠመብኝ፤
የሞት ወጥመድም ተጋረጠብኝ፡፡
6በተጨነቅሁ ጊዜ *እግዚአብሔርን*
ጠራሁት፤
እንዲረዳኝም ወደ አምላኬ ጮኽሁ፤
እርሱም ከመቅደሱ ድምፄን ሰማ፤
ጩኸቴም ከፊቱ ደረሰ፤ ወደ ጆሮውም
ገባ፡፡

7ምድር ተንቀጠቀጠች፤ ተናወጠችም፤
የተራሮችም መሠረት ተናጋ፤
ጌታ ተቈጥቶአልና ተንቀጠቀጡ፡፡
8ከአፍንጫው ጢስ ወጣ፤
የሚባላ እሳት ከአፉ፤
የፍም ነበልባል ከእርሱ ፈለቀ፡፡
9ሰማያትን ሰንጥቆ ወረደ፤
ከእግሩም በታች ጥቍር ደመና ነበረ፡፡
10በኪሩቤል ላይ ተቀምጦ በረረ፤
በነፋስም ክንፍ መጠቀ፡፡
11ጨለማን መሰወሪያው፣ በዙሪያውም
አጐበሩ አደረገው፤
በዝናብ አዘል ጥቍር ደመናም ተሸፈነ፡፡
12በፊቱ ካለው ብርሃን የተነሣ፣
ደመናት፣ የበረዶ ድንጋይና መብረቅ
ወጡ፡፡
13*እግዚአብሔር* ከሰማያት አንጐደጐደ፤
ልዑልም ድምፁን አስተጋባ፡፡[ጨ]
14ፍላጻውን አስፈንጥሮ በተናቸው፤
መብረቅ አዥጐድጕዶ አሳደዳቸው፡፡
15*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ከተግሣጽህ የተነሣ፣
ከአፍንጫህም እስትንፋስ የተነሣ፣
የባሕር ወለል ተገለጠ፤
የዓለምም መሠረት ራቍቱን ቀረ፡፡

16ከላይ እጁን ወደ ታች ዘርግቶ ያዘኝ፤
ከብዙ ጥልቅ ውሃም አወጣኝ፤
17ከኀያላን ጠላቶቼ አዳነኝ፤
ከእኔ ከሚበረቱ ባላንጣዎቼም ታደገኝ፡፡
18እነርሱ በመከራዬ ቀን መጡብኝ፤
*እግዚአብሔር* ግን ድጋፍ ሆነኝ፡፡
19ወደ ሰፊ ስፍራ አወጣኝ፤
ደስ ተሰኝቶብኛልና አዳነኝ፡፡

20*እግዚአብሔር* እንደ ጽድቄ መልሶልኛል፤
እንደ እጄ ንጽሕናም ከፍሎኛል፤
21*የእግዚአብሔርን* መንገድ ጠብቄአለሁና፤
አምላኬንም በመተው ክፉ አላደረግሁም፡፡
22ሕጎቹ ሁሉ በፊቴ ናቸው፤
ሥርዐቱን ከፊቴ አላራቅሁም፡፡
23በፊቱ ነቀፋ አልነበረብኝም፤
ራሴንም ከኀጢአት ጠብቄአለሁ፡፡
24*እግዚአብሔር* እንደ ጽድቄ መጠን፣
በፊቱም እንደ እጄም ንጽሕና
ከፍሎኛል፡፡

25ከታማኙ ጋር ታማኝ ትሆናለህ፤
እንከን ከሌለበት ጋር ያለ እንከን
ትሆናለህ፤
26ከንጹሑ ጋር ንጹሕ ሆነህ ትገኛለህ፤
ለጠማማው አንተ ትጠምበታለህ፡፡
27አንተ ትሑታንን ታድናለህ፤
ትዕቢተኛውን ዐይን ግን ታዋርዳለህ፡፡
28*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ መብራቴን
ታበራለህ፤
አምላኬ ሆይ፤ ጨለማዬን ብርሃን
ታደርገዋለህ፡፡
29በአንተ ጕልበት በሰራዊት ላይ እረ
ማመዳለሁ፤[ጸ]
በአምላኬም ኀይል ቅጥር እዘላለሁ፡፡

**17፥15** ዘኍ12፥8፤ መዝ3፥5፤ማቴ5፥8፤ 1ዮሐ3፥2
**18፥1** ዘፀ15፥2፤ዘዳ 33፥29፤1ሳሙ2፥10፤ መዝ22፥19፤28፥7፤ 59፥9፤81፥1፤ኢሳ12፥2፤ 49፥5፤ኤር16፥19
**18፥2** ዘፍ15፥1፤ዘፀ 33፥22፤1ሳሙ2፥1፤ መዝ2፥12፤9፥9፤28፥7፡ 8፤31፥2፡3፤40፥17፤84፥ 9፤94፥22፤119፥ 114፤144፥2፤ኢሳ17፥ 10፤ኤር16፥19፤ሉቃ 1፥69
**18፥3** 1ዜና16፥25 ፤መዝ9፥13
**18፥4** መዝ93፥4፤ 116፥3፤124፥4፤ኢሳ 5፥30፤17፥12፤ኤር 6፥23፤51፥42፡55፤ሕዝ 43፥2
**18፥5** ምሳ13፥14
**18፥6** ዘዳ4፥30፤ኢዮ 16፥18፤መዝ30፥2፤66፥ 19፤99፥6፤102፥2፤116 ፥1፤120፥1
**18፥7** መሳ5፥4፡5፤ ኢዮ9፥5፤መዝ97፥4 ፤ኢሳ5፥25፤64፥3፤ኤር 10፥10
**18፥8** ዘፀ15፥7፤ 19፥18፤ኢዮ41፥20፡ 21፤መዝ50፥3፤97፥3፤ ምሳ25፥22፤ዳን7፥10፤ ሮሜ12፥20
**18፥9** ዘፍ11፥5፤ዘፀ 20፥21፤ዘዳ33፥26፤ መዝ57፥3፤104፥3
**18፥10** ዘፍ3፥24፤ ዘዳ33፥26፤መዝ 104፥3፤ሕዝ10፥18
**18፥11** ዘፀ19፥9፤ዘዳ 4፥11፤ኢዮ22፥14፤ ኢሳ4፥5፤ኤር43፥10
**18፥12** ኢሱ10፥11፤ ኢዮ36፥30፤መዝ 104፥2
**18፥13** ዘፀ9፥23፤ 1ሳሙ2፥10
**18፥14** ዘዳ32፥23፤ መሳ4፥15፤ኢዮ36፥30፤ ራእ4፥5
**18፥15** ዘፀ15፥8፤ መዝ 11፥3፤76፥6፤ 104፥7፤106፥9፤ኢሳ 50፥2
**18፥16** ዘፀ15፥5፤መዝ 69፥2፤ምሳ18፥4፤20፥5
**18፥17** ቈ48፤ምሳ 18፥26፤መዝ38፥19፤5 9፥1፤143፥9
**18፥18** መዝ20፥2፤ ምሳ1፥27፤16፥4፤ኢሳ 3፥1፤ኤር17፥17፤ 40፥2፤አብ1፥13
**18፥19** ዘኍ14፥8፤ መዝ31፥8
**18፥20** ሩት2፥12 ፤1ሳሙ26፥23፤2ዜና 15፥7፤ኢዮ22፥30 ፤መዝ24፥4፤1ቆሮ3፥8 **18፥21** 2ዜና34፥33፤መዝ37፥34፤119፥2፡ 102፤ምሳ8፥32፤23፥26 **18፥22** መዝ119፥30 **18፥23** ዘፍ6፥9 **18፥24** 1ሳሙ26፥23 **18፥25** መዝ25፥10፤31፥23፤37፥28፤ 40፥11፤50፥5፤89፥24፤146፥6፤ምሳ2፥8 **18፥26** ምሳ3፥34፤15፥26፤ ማቴ5፥8፤10፥16፤ሉቃ16፥8፤ፊል1፥10፤1ጢሞ5፥22፤ቲቶ 1፥15፤ 1ዮሐ3፥3 **18፥27** 2ዜና33፥23፤ኢዮ41፥34፤መዝ10፥5፤ምሳ3፥33-34፤ማቴ23፥12 **18፥28** 1ነገ11፥36፤ኢዮ29፥3፤መዝ97፥11፤ 112፥4፤132፥17፤ዮሐ1፥5፤ሐሥ26፥18፤2ቆሮ4፥6፤2ጴጥ1፥19 **18፥29** ቈ32፡39፤ኢሳ45፥5፤ዕብ11፥34

[ገ]2 *ቀንድ* በዚህ ቦታ ብርታትን ያመለክታል
[ጠ]5 ወይም *የመቃብር*
[ጨ]13 አንዳንድ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆችና ሰብዓ ሊቃናት (በተጨማሪ 2ሳሙ22፥14 ይመ) እንዲሁ ሲሆኑ አብዛኛዎቹ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆች ግን ... *አስተጋባ፤ በድንጋይ ዝናብ በድንገተኛ መብረቅ መካከል* የሚለውን ይጨምራሉ፡፡
[ጸ]29 ወይም ... *በመሰናክል ውስጥ መሮጥ እችላለሁ*

30 የአምላክ መንገድ ፍጹም ነው፤
*የእግዚአብሔር* ቃል የነጠረ ነው።
መጠጊያ ለሚያደርጉት ሁሉ፣
እርሱ ጋሻ ነው።
31 *ከእግዚአብሔር* በቀር ማን አምላክ አለ?
ከአምላካችንስ በቀር ዐምባ ማን ነው?
32 ኀይልን የሚያስታጥቀኝ፣
መንገዴንም የሚያቃና እግዚአብሔር
ነው።
33 እርሱ እግሮቼን እንደ ብሖር እግሮች
ያደርጋል፤
በከፍታዎችም ላይ ያቆመኛል።
34 እጆቼን ለጦርነት ያሠለጥናቸዋል፤
ክንዴም የናስ ቀስት መገተር ይችላል።
35 የድል ጋሻ ሰጥተኸኛል፤
ቀኝ እጅህም ደግፋ ይዛኛለች፤
ዝቅ ብለህም ከፍ አደረግኸኝ።
36 ከሥሬ ያለውን ስፍራ ለአረማመዴ
አሰፋህልኝ፤
እግሬም አልተንሸራተተም።
37 ጠላቶቼን አሳድጄ ያዝኋቸው፤
እስኪጠፉም ወደ ኋላዬ
አልተመለስሁም።
38 እንዳያንሰራሩ አድርጌ አደቀቅኋቸው፤
ከእግሬም ሥር ወደቁ።
39 አንተ ለጦርነት ኀይልን አስታጠቅኸኝ፤
ባላንጦቼ እግሬ ላይ እንዲደፉ
አደረግህ።
40 ጠላቶቼ ወደ ኋላቸው እንዲሸሹ አደረግህ፤
እኔም የሚጠሉኝን አጠፋኋቸው።
41 ለርዳታ ጮኹ፤ የሚያስጥላቸው ግን
አላገኙም፤
ወደ *እግዚአብሔር* ጮኹ፤ እርሱም
አልመለሰላቸውም።
42 ነፋስ ጠርጎ እንደሚወስደው ትቢያ
አደቀቅኋቸው፤
እንደ መንገድ ላይ ጭቃም አውጥቼ
ጣልኋቸው።
43 ከሕዝብ ግርግር አወጣኸኝ፤
የሕዝቦች መሪ አድርገህ አስቀመጥኸኝ፤
የማላውቀውም ሕዝብ ተገዛልኝ።
44 ትእዛዜን እንደ ሰሙ ይታዘዙልኛል፤
ባዕዳንም በፊቴ አንገት ደፉ።
45 ባዕዳን በፍርሃት ተዋጡ፤
ከምሽጋቸውም እየተንቀጠቀጡ ወጡ።
46 *እግዚአብሔር* ሕያው ነው! ዐምባዬ
ይባረክ፤
ያዳነኝ አምላክ ከፍ ከፍ ይበል።
47 እርሱ በቀሌን የሚመልስልኝ፣
ሕዝቦችንም የሚያስገዛልኝ አምላክ ነው፤
48 ከጠላቶቼም የሚታደገኝ እርሱ ነው።
አንተ ከባላንጦቼ በላይ ከፍ ከፍ
አደረግኸኝ፤
ከጨካኞች አዳንኸኝ።
49 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ስለዚህ በአሕዛብ
መካከል አመሰግንሃለሁ፤
ስምህንም በመዝሙር እወድሳለሁ።
50 እርሱ ለንጉሡ ታላላቅ ድሎችን
ይሰጣል፤
ጽኑ ፍቅሩንም ለቀባው፣
ለዳዊትና ለዘሩ ለዘላለም ይገልጣል።

## መዝሙር 19

### እግዚአብሔር የጽድቅ ፀሓይ

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር*

1 ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፤
የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ
ያውጃሉ።
2 ቀን ለሌላው ቀን ይናገራል፤
ሌሊትም ለሌሊት ዕውቀትን
ይገልጣል፤
3 ንግግር የለም፤ ቃል የለም፤
ድምፃቸው በጆሮ የሚሰማ አይደለም።[ጸ]
4 ያም ሆኖ ድምፃቸው ወደ ምድር ሁሉ፣
ቃላቸውም[ፀ] እስከ ዓለም ዳርቻ
ይወጣል።
እርሱ በሰማያት ለፀሓይ ድንኳን
ተክሎአል፤
5 ፀሓይም ከእልፍኙ እንደሚወጣ ሙሽራ
ይወጣል፤
ወደ ግቡም እንደሚሮጥ ብርቱ ሰው
ደስ ይለዋል።
6 መውጫው ከሰማያት ዳርቻ ነው፤
ዑደቱም እስከ ሌላኛው ዳርቻ ነው፤
ከትኩሳቱም የሚሰወር የለም።
7 *የእግዚአብሔር* ሕግ ፍጹም ነው፤
ነፍስንም መልሶ ያለመልማል፤
*የእግዚአብሔር* ሥርዐት የታመነ ነው፤
አላዋቂውን ጥበበኛ ያደርጋል።
8 *የእግዚአብሔር* ሕግጋት ትክክል ናቸው፤
ልብን ደስ ያሰኛሉ።
*የእግዚአብሔር* ትእዛዝ ብሩህ ነው፤
ዐይንን ያበራል።
9 *እግዚአብሔርን* መፍራት ንጹሕ ነው፤
ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
*የእግዚአብሔር* ፍርድ የታመነ፣
ሁለንተናውም ጻድቅ ነው፤

**18፥30** ዘዳ32፥4፤ መዝ2፥12፤3፥3፤12፥6፤ምሳ30፥5
**18፥31** ዘፍ49፥24፤ ዘዳ4፥35፤32፥39፤መዝ35፥10፤86፥8፤89፥6፤ኢሳ44፥6፡8፤45፥5፡6፡14፡18፡21፤46፥9
**18፥32** ቆላ29፤መዝ15፥2፤19፥13፤ዕብ10፥14፤1ጴጥ5፥10፤ ያዕ3፥2
**18፥33** ዘዳ32፥13፤ መዝ42፥1፤ምሳ5፥19፤ ኢሳ35፥6፤ዕን3፥19
**18፥34** መዝ144፥1
**18፥35** መዝ3፥5፤ 37፥5፡17፤41፥3፤51፥12፤54፥4፤55፥22፤119፥116፤ኢሳ41፥4፡10፡13፤43፥2፤46፥4
**18፥36** ኢዮ18፥7፤መዝ31፥8፤66፥9
**18፥37** ዘሌ26፥7
**18፥38** መዝ36፥12፤47፥3፤68፥21፤110፥6፤140፥10፤ኢሳ 26፥14
**18፥39** ቆላ32፡47፤ መዝ47፥3፤144፥2፤ ኢሳ 45፥5፡24
**18፥40** ቆላ37፤ኢያሱ7፥12
**18፥41** 1ሳሙ8፥18፤14፥37፤2ነገ14፥26፤ መዝ50፥22፤ኤር11፥11
**18፥42** ዘዳ9፥21፤ ኢሳ2፥22
**18፥43** 2ሳሙ8፥1-14፤ኢሳ55፥5
**18፥44** መዝ54፥3፤144፥7፡11፤ኢሳ25፥5
**18፥45** 1ሳሙ17፥32፤መዝ9፥9፤ኢሳ66፥2፤ ሆሴ3፥5፤11፥10፤ሚክ7፥17፤2ቆሮ4፥1፤ዕብ12፥3
**18፥46** ቆላ31፤ዘፀ33፥22፤ኢያሱ3፥10፤ 1ሳሙ14፥39፤1ዜና16፥35፤መዝ21፥13፤35፥27፤40፥16፤108፥5፤ ሉቃ1፥47፤2ቆሮ13፥4
**18፥47** ቆላ39፤ዘፍ4፥24፤መሳ4፥23
**18፥48** ቆላ17፤መዝ7፥10፤37፥40፤140፥1፤ ዳን3፥17
**18፥49** መዝ7፥17፤ 9፥2፡11፤101፥1፤108፥1፤ 146፥2፤ሮሜ15፥9
**18፥50** 2ሳሙ23፥1፤መዝ89፥4፤144፥10
**19፥1** ዘፍ1፥8፤መዝ4፥2፤8፥1፡6፤50፥6፤ 89፥5፤97፥6፤103፥22፤ 148፥3፤ኢሳ6፥3፤ 40፥22፤ሮሜ1፥19
**19፥2** መዝ74፥16
**19፥4** መሳ5፥31፤ ኢዮ36፥29፤መዝ104፥2፤ሮሜ10፥18

**19፥5** 1ሳሙ17፥4፤ኢዮ36፥29፤ኢል2፥16 **19፥6** ዘዳ30፥4፤ መዝ113፥3፤መክ1፥5 **19፥7** ዘዳ4፥6፤መዝ1፥2፤23፥3፤93፥5፤ 111፥7፤119፥130፡138፡142፡144፤ያዕ1፥25 **19፥8** ዕዝ9፥8፤ መዝ33፥4፤38፥10፤119፥14፡128 **19፥9** መዝ34፥11፤111፥10፤ 119፥138፤ምሳ1፥7፤መክ12፥13፤ኢሳ33፥6

[ጸ]3 ወይም *የሚናገሩት የላቸውም፤ ቃላት የለም፤ ከእርሱ ምንም ድምፅ አይሰማም*
[ፀ]4 ሰብዓ ሊቃናት የሩምና ሱርስት እንዲሁ ሲሆኑ ዕብራይስጡ *ግን ድንበራቸው* ይላል።

10ከወርቅ ይልቅ የከበረ፣
 እጅግ ከጠራ ወርቅም የተሻለ ነው፤
ከማር ይልቅ ይጣፍጣል፤
 ከማር ወለላም ይበልጥ ይጥማል።
11ደግሞም አገልጋይህ በእርሱ ጥንቃቄ
 ያደርጋል፤
 እርሱንም መጠበቅ ወሮታ አለው።

12ስሕተቱን ማን ሊያስተውል ይችላል?
 ከተሰወረ በደል አንጻኝ።
13ባሪያህን ከድፍረት ኀጢአት ጠብቅ፤
 እንዳይሠለጥንብኝም ርዳኝ፤
ያን ጊዜ ያለ እንከን እሆናለሁ፤
 ከታላቅ በደልም እነጻለሁ።

14መጠጊያዬና አዳኜ እግዚአብሔር ሆይ፤
 የአፌ ቃልና የልቤ ሐሳብ፣
 በፊትህ ያማረ ይሁን።

## መዝሙር 20

### ጸሎት ለንጉሡ

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር*

1*እግዚአብሔር* በጭንቅ ቀን ይስማህ፤
 የያዕቆብም አምላክ ስም ይጠብቅህ።
2ከመቅደሱ ረድኤት ይላክልህ፤
 ከጽዮንም ደግፎ ይያዝህ።
3ቍርባንህን ሁሉ ያስብልህ፤
 የሚቃጠል መሥዋዕትህን ይቀበልልህ።
4የልብህን መሻት ይስጥህ፤
 ዕቅድህን ሁሉ ያከናውንልህ።
5በአንተ ድል ደስ ይበለን፤
 በአምላካችን ስም አርማችንን ከፍ
 እናደርጋለን፤
 *እግዚአብሔር* የለመንኸውን ሁሉ
 ይፈጽምልህ።

6*እግዚአብሔር*፣ የቀባውን እንደሚያድን
 አሁን አወቅሁ፤
 የማዳን ኀይል ባለው ቀኝ እጁ፣
 ከተቀደሰው ሰማይ ይመልስለታል።
7እነዚህ በሰረገላ፣ እነዚያ በፈረስ
 ይመካሉ፤
 እኛ ግን ትምክህታችን የአምላካችን
 *የእግዚአብሔር* ስም ነው።
8እነርሱ ተሰነካክለው ወደቁ፤
 እኛ ግን ተነሣን፤ ጸንተንም ቆምን።

9እግዚአብሔር ሆይ፤ ንጉሥን አድን፤
 እኛም በጠራንህ ቀን ስማን።[ፊ]

## መዝሙር 21

### ምስጋና ስለ ንጉሡ

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር*

1*እግዚአብሔር ሆይ*፤ ንጉሥ በኀይልህ
 ደስ ይለዋል፤
 በምትሰጠውም ድል እጅግ ሐሤት
 ያደርጋል።
2የልቡን መሻት ሰጠኸው፤
 የከንፈሮቹንም ልመና አልከለከልኸውም። ሴላ

3መልካም በረከት ይዘህ በመንገዱ ላይ
 ጠብቀኸው፤
 የንጹሕ ወርቅ ዘውድም በራሱ ላይ
 ደፋህለት።
4ሕይወትን ለመነህ፤
 ረዥም ዘመናትንም እስከ ዘላለም
 ሰጠኸው።
5ባቀዳጀኸው ድል ክብሩ ታላቅ ሆነ፤
 ክብርንና ሞገስን አጐናጸፍኸው።

6ዘላለማዊ በረከትን ሰጠኸው፤
 ከአንተ ዘንድ በሚገኝ ፍስሓም ደስ
 አሰኘኸው፤
7ንጉሡ *በእግዚአብሔር* ተማምኖአልና፤
 ከልዑልም ጽኑ ፍቅር የተነሣ፣
 ከቆመበት አይናወጥም።

8እጅህ ጠላቶችህን ሁሉ ታገኛቸዋለች፤
 ቀኝ እጅህም የሚጠሉህን ፈልጋ
 ትይዛለች።
9በምትገለጥበት ጊዜ፣
 እሳት እንደሚንቀለቀልበት ምድጃ
 ታደርጋቸዋለህ፤
*እግዚአብሔር* በመዓቱ እንዳልነበሩ
 ያደርጋቸዋል፤
 እሳቱም ሙጥጥ አድርጋ ትበላቸዋለች።
10ዘራቸውን ከምድር፣
 ዘር ማንዘራቸውንም ከሰው ልጆች
 መካከል ታጠፋለህ።
11ክፋት ቢያስቡብህ፣
 ተንኰል ቢወጥኑብህም አይሳካላቸውም፤
12በመጡበት ትመልሳቸዋለህና፤
 ቀስትህንም በፊታቸው ላይ ታነጣጥራለህ።

13*እግዚአብሔር ሆይ*፤ በብርታትህ ከፍ
 ከፍ በል፤
 ኀይልህን እናወድሳለን፤ እንዘምራለንም።

## መዝሙር 22

### የጻድቅ ሰው መከራና ተስፋ

*ለመዘምራን አለቃ፤ በ"ንጋት አጋዘን" ዜማ የሚዜም፤ የዳዊት መዝሙር*

1አምላኬ፣ አምላኬ ለምን ተውኸኝ?
 እኔን ከማዳን፣
 ከመቃተቴም ቃል ለምን ራቅህ?
2አምላኬ ሆይ፤ በቀን ወደ አንተ
 እጮኻለሁ፤

**19፥10** 2ሳሙ14፥27፤ ኢዮ22፥24፤መዝ 119፥72፥103፤ምሳ 8፥10፤ማሕ4፥11፤ሕዝ 3፥3
**19፥12** መዝ51፥2፤ 90፥8፤መክ12፥14
**19፥13** ዘፍ6፥9፤ ዘኍ15፥30፤መዝ 18፥32፤119፥133
**19፥14** ዘፀ6፥6፤ኢዮ 19፥25፤መዝ18፥31፤ 104፥34
**20፥1** ዘፀ3፥6፤መዝ 4፥1፤46፥7፥11፤59፥1፤6 9፥29፤91፥14
**20፥2** ዘኍ3፥28፤ መዝ2፥6፤18፥18፤30፥1 0፤33፥20፤37፥40፤40፥ 17፤54፥4፤118፥7፤128 ፥5፤134፥3፤ 135፥21
**20፥3** ዘዳ33፥11፤ ሐሥ10፥4
**20፥4** መዝ21፥2 ፤37፥4፤140፥8፤145፥1 6፥19፤ምሳ16፥3፤ኢሳ 26፥8፤ሕዝ24፥25፤ዳን 11፥17፤ሮሜ10፥1
**20፥5** ዘኍ1፥52፤ 1ሳሙ1፥17፤ኢዮ3፥7 ፤መዝ60፥4፤ኢሳ5፥26 ፤ 11፥10፥12፤13፥2፤ 30፥17፤49፥22፤62፥ 10፤ኤር50፥2፤ 51፥12፥27
**20፥6** 2ሳሙ23፥1 ፤ኢዮ40፥14፤መዝ 28፥8፤ዕን3፥13
**20፥7** ዘዳ17፥16፤ 2ነገ19፥23፤2ዜና32፥8 ፤መዝ33፥17፤147፥ 10፤ምሳ21፥31፤ኢሳ 31፥1፤36፥8፥9
**20፥8** ኢዮ11፥15፤ መዝ27፥2፤37፥23፤ ምሳ10፥25፤ኢሳ7፥9፤ 40፥30፤ኤር46፥6፤ 50፥32፤ሚክ7፥8
**20፥9** መዝ17፥6
**21፥1** 1ሳሙ2፥10 ፤2ሳሙ22፥51
**21፥2** መዝ20፥4
**21፥3** 2ሳሙ12፥30 ፤ዘካ6፥11፤ራእ14፥14
**21፥4** መዝ10፥16፤ 45፥17፤48፥14፤133፥3
**21፥5** ቍ1፤መዝ8፥5 ፤18፥50፤44፥4፤45፥3፤ 93፥1፤96፥6፤104፥1
**21፥6** 1ዜና17፥27 ፤መዝ43፥4፤126፥3
**21፥7** ዘፍ14፥18፤ 2ነገ18፥5፤መዝ6፥4፤ 15፥5፤55፥22
**21፥8** ኢሳ10፥10
**21፥9** ዘዳ32፥22፤ መዝ50፥3፤ኤር15፥14
**21፥10** ዘዳ28፥18
**21፥11** ኢዮ10፥3፤ መዝ2፥1፤10፥2፤26፥ 10፤37፥7

**21፥12** ዘፀ23፥27 **21፥13**መዝ18፥1፥46 **22፥1** ኢዮ3፥24፤ 6፥15፤መዝ9፥10፤10፥1፤ማቴ27፥46፤ማር15፥34 **22፥2** ኢዮ19፥7፤ መዝ42፥3፤88፥1

ፊ9 *ወይም አድን! ንጉሥ ሆይ፤ ስማን*

አንተ ግን አልመለስህልኝም፤
በሌሊት እንኳ አላረፍሁም።
3አንተ ግን ቅዱሱ ነጋሢ፤[ፐ]
የእስራኤልም ምስጋና ነህ።
4አባቶቻችን በአንተ ታመኑ፤
ተማመኑብህ፤ አንተም ታደግሃቸው።
5ወደ አንተ ጮኹ፤ ዳኑም፤
በአንተም ታመኑ፤ አላፈሩም።
6እኔ ግን ትል እንጂ ሰው አይደለሁም፤
ሰው ያላገጠብኝ፣ ሕዝብም የናቀኝ ነኝ።
7የሚያዩኝ ሁሉ ይሣለቁብኛል፤
ራሳቸውንም እየነቀነቁ እንዲህ እያሉ ይዘልፉኛል፤
8"*በእግዚአብሔር ተማምኖአል፤*
እንግዲህ እርሱ ያድነው፤
ደስ የተሰኘበትን፣
እስቲ ይታደገው።"
9አንተ ግን ከማሕፀን አወጣኸኝ፤
በእናቴም ጡት ሳለሁ፣
መታመኛ ሆንኸኝ።
10ከማሕፀን ስወጣም በአንተ ላይ ተጣልሁ፤
ከእናቴ ሆድ ጀምሮም አንተ አምላኬ ነህ።
11መከራ እየተቃረበ ነውና፣
የሚረዳኝም የለምና፣
ከእኔ አትራቅ።
12ብዙ ኮርማዎች ከበቡኝ፤
ኀይለኛ የባሳን በሬዎችም ዙሪያዬን ቆሙ።
13እንደሚነጥቅና እንደሚያገሣ አንበሳ፣
አፋቸውን ከፈቱብኝ።
14እንደ ውሃ ፈሰስሁ፤
ዐጥንቶቼም ሁሉ ከመጋጠሚያቸው ወለቁ፤
ልቤ እንደ ሰም ሆነ፤
በውስጤም ቀለጠ።
15ጒልበቴ እንደ ገል ደረቀ፤
ምላሴ ከላንቃዬ ጋር ተጣበቀ፤
ወደ ሞት ዐፈርም አወረድኸኝ።[ሀ]
16ውሾች ከበቡኝ፤
የክፉዎች ሸንጎ በዙሪያዬ ተሰልፎአል፤
እጆቼንና እግሮቼንም ቸነከሩኝ።[ለ]
17ዐጥንቶቼን ሁሉ አንድ በአንድ መቍጠር እችላለሁ፤
እነርሱም አፍጥጠው ይመለከቱኛል።
18ልብሶቼን ተከፋፈሉ፤
በእጀ ጠባቤም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ።
19አንተ ግን፣ እግዚአብሔር ሆይ፤ ከእኔ አትራቅ፤
አጋዤ ሆይ፤ እኔን ለመርዳት ፍጠን።
20ነፍሴን ከሰይፍ ታደጋት፤

22፥3 ዘፀ15፥2፤2ነገ 19፥22፤መዝ71፥22፤148፥14፤ማር1፥24
22፥4 መዝ78፥53፤107፥6
22፥5 1ዜና5፥20፤2ዜና13፥18፤መዝ25፥3፤31፥17፤71፥1፤ኢሳ 8፥17፤25፥9፤26፥3፤30፥18፤49፥23፤ሮሜ9፥33
22፥6 2ሳሙ12፥14፤ኢዮ4፥19፤መዝ31፥11፤64፥8፤69፥19፤109፥25፤119፥141፤ኢሳ 49፥7፤53፥3፤60፥14፤ሚል2፥9፤ማቴ16፥21
22፥7 ኢዮ17፥2፤መዝ 35፥16፤69፥12፤74፥18፤ማቴ27፥39፡41፡44፤ማር15፥29፡31፡32፤ሉቃ23፥36፡39
22፥8 2ሳሙ22፥20፤መዝ3፥2፤ 91፥14፤ማቴ3፥17፤27፥43
22፥9 ኢዮ10፥18፤መዝ71፥6፤78፥7፤ናሆ1፥7
22፥10 መዝ71፥6፤ኢሳ46፥3፤49፥1
22፥11 ቍ19፤2ነገ 14፥26፤መዝ10፥1፡14፤ኢሳ41፥28
22፥12 ዘዳ32፥14፤መዝ17፥9፤27፥6፤49፥5፤68፥30፤109፥3፤140፥9፤ኢሳ2፥13፤ሕዝ 27፥6፤39፥18፤አሞ4፥1
22፥13 ቍ24፤ዘፍ 49፥9፤ሰቆ3፥46፤ሕዝ 22፥25፤ሶፎ3፥3
22፥14 ኢሱ7፥5፤ኢዮ23፥16፤መዝ6፥2፤68፥2፤97፥5፤መዝ107፥26፤ዳን5፥6፤ሚክ1፥4
22፥15 ኢዮ7፥21፤መዝ104፥29፤137፥6፤ኢሳ45፥9፤ሰቆ4፥4፤ሕዝ3፥26፤ዮሐ19፥28
22፥16 ኢሳ51፥9፤53፥5፤ዘካ12፥10፤ዮሐ20፥25፤ፊል3፥2
22፥17 መዝ25፥2፤30፥1፤35፥19፤38፥16፤ሰቆ2፥17፤ሚክ7፥8፤ሉቃ23፥35
22፥18 ዘሌ16፥8፤ማቴ27፥35፤ማር9፥12፤15፥24፤ሉቃ23፥34፤ዮሐ19፥24
22፥19 ቍ11፤መዝ 18፥1፤38፥22፤40፥13፤70፥5፤141፥1
22፥20 ኢዮ5፥20፤መዝ35፥17፤37፥14፤ፊል3፥2
22፥21 ቍ12፡13፤ዘኍ23፥22፤ኢዮ4፥10
22፥22 መዝ26፥12፤35፥18፤40፥9፡10፤68፥26፤ዕብ2፥12

ውድ ሕይወቴንም ከውሾች ጡጫ አድናት።
21ከአንበሶች አፍ አድነኝ፤
ከአውራሪስ ቀንድም ታደገኝ።[ሐ]
22ስምህን ለወንድሞቼ እነግራለሁ፤
በጉባኤም መካከል አመሰግንሃለሁ።
23እናንተ *እግዚአብሔርን* የምትፈሩ፤ አወድሱት፤
እናንተ የያቆብ ዘር ሁላችሁ፤ አክብሩት፤
የእስራኤልም ዘር ሁላችሁ፤ እርሱን ፍሩት።
24እርሱ የተጨነቀውን ሰው ጭንቀት፣
አልናቀም፤ ቸልም አላለምና፤
ፊቱንም ከእርሱ አልሰወረም፤
ነገር ግን ድረስልኝ ብሎ ሲጮኽ ሰማው።
25በታላቅ ጉባኤ የማቀርበው ምስጋናዬ ከአንተ የመጣ ነው፤
እርሱን በሚፈሩት[መ] ፊት ስእለቴን እፈጽማለሁ።
26ምስኪኖች በልተው ይጠግባሉ፤
*እግዚአብሔርን* የሚሹትም ያመሰግኑታል፤
ልባችሁም ለዘላለም ሕያው ይሁን!
27የምድር ዳርቻዎች ሁሉ ያስታውሳሉ፤
ወደ *እግዚአብሔርም* ይመለሳሉ፤
የሕዝቦች ነገዶች ሁሉ፣
በፊቱ ይሰግዳሉ።
28መንግሥት *የእግዚአብሔር* ናትና፤
ሕዝቦችንም የሚገዛ እርሱ ነው።
29የምድር ከበርቴዎች ይበላሉ፤ ይሰግዱለታልም፤
ነፍሱን በሕይወት ማቆየት የማይችለው፣ ወደ ዐፈር፣
ተመላሽ የሆነው ሁሉ በፊቱ ይንበረከካል።
30የኋለኛው ትውልድ ያገለግለዋል፤
ለመጪው ትውልድ ስለ ጌታ ይነገረዋል።

22፥23 ዘዳ14፥23፤መዝ33፥2፡8፤50፥15፤66፥8፤86፥12፤103፥1፤106፥1፤113፥1፤117፥1፤135፥19፤ኢሳ24፥15፤25፥3፤29፥23፤60፥9፤ኤር3፥17 22፥24 ኢዮ24፥12፤36፥5፤መዝ9፥12፤13፥1፤27፥9፤69፥17፤102፥2፡17፤143፥7፤ዕብ5፥7 22፥25 ዘኍ30፥2፤መዝ26፥12፤35፥18፤40፥9፤82፥1 22፥26 መዝ40፥16፤107፥9
22፥27 መዝ2፥8፤86፥9፤102፥22፤ዳን7፥27፤ሚክ4፥1
22፥28 መዝ47፥7፤ዘካ14፥9 22፥29 መዝ45፥12፤89፥48፤95፥6፤96፥9፤99፥5፤ኢሳ26፥19፤27፥13፤49፥7፤66፥23፤ዘካ14፥16
22፥30 መዝ102፥18፤ኢሳ53፥10፤54፥3፤61፥9፤66፥22

[ፐ]3 ወይም *አንተ ግን ቅዱስ ነህ፤ በእስራኤል ምሥጋና ላይ በዙፋን ተቀምጠሃል*
[ሀ]15 ወይም *... ዐፈር ውስጥ ተኛኹኝ*
[ለ]16 አንዳንድ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆች፣ ሰብዓ ሊቃናትና ሱርስት እንዲሁ ሲሆኑ አብዛኞዎቹ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆች *እንደ አንበሳ፣* ይላሉ።
[ሐ]21 ወይም *ሰምተኸኛል*
[መ]25 ዕብራይስጡ *እኔ በሚፈሩኝ* ይላል።

[31]ገና ላልተወለደ ሕዝብ፣
ጽድቁን ይነግራሉ፤
እርሱ ይህን አድርጎአልና።

## *መዝሙር* 23

### *መልካሙ እረኛ*

*የዳዊት መዝሙር*

[1]*እግዚአብሔር* እረኛዬ ነው፤
አንዳች አይጐድልብኝም።
[2]በለመለመ መስክ ያሳርፈኛል፤
በዕረፍት ውሃ ዘንድ ይመራኛል፤
[3]ነፍሴንም ይመልሳታል።
ስለ ስሙም፣
በጽድቅ መንገድ ይመራኛል።
[4]በሞት ጥላ ሸለቆ ውስጥ፤[ሠ]
ብሄድ እንኳ፣
አንተ ከእኔ ጋር ስለ ሆንህ፣
ክፉን አልፈራም፤
በትርህና ምርኩዝህ፣
እነርሱ ያጽናኑኛል።
[5]ጠላቶቼ እያዩ፣
በፊቴ ማዕድ አዘጋጀህልኝ፤
ራሴን በዘይት ቀባህ፤
ጽዋዬም ሞልቶ ይፈስሳል።
[6]በሕይወቴ ዘመን ሁሉ፣
በጎነትና ምሕረት በእርግጥ
ይከተሉኛል፤
እኔም *በእግዚአብሔር* ቤት፣
ለዘላለም እኖራለሁ።

## *መዝሙር* 24

### *ወደ መቅደስ መግቢያ ጸሎት*

*የዳዊት መዝሙር*

[1]ምድርና በእርሷ ያለው ሁሉ፣
ዓለምና በውስጧ የሚኖር ሁሉ *የእግዚ
አብሔር* ነው፤
[2]እርሱ በባሕሮች ላይ መሥርቶአታልና፤
በውሆችም ላይ አጽንቶአታል።
[3]ወደ *እግዚአብሔር* ተራራ ማን ሊወጣ
ይችላል?
በተቀደሰ ስፍራውስ ማን ይቆማል?
[4]ንጹሕ እጅና ቅን ልብ ያለው፤
ነፍሱን ለሐሰት ነገር የማያስገዛ፤
በውሸት የማይምል፤[ረ]
[5]እርሱ በረከትን *ከእግዚአብሔር* ዘንድ፣
ምሕረትንም ከአዳኝ አምላኩ ይቀበላል።
[6]እርሱን የሚፈልግ ትውልድ እንዲህ
ነው፤
የያዕቆብ አምላክ ሆይ፤ ፊትህን[ሰ]
የሚፈልግ እንዲህ ያለ ነው።
ሴላ
[7]እናንተ ደጆች፤ ቀና በሉ፤
እናንተ የዘላለም በሮች፤
የክብር ንጉሥ እንዲገባ ብድግ በሉ!
[8]ይህ የክብር ንጉሥ ማን ነው?
*እግዚአብሔር* ነው ብርቱና ኀያል፤
*እግዚአብሔር* ነው በውጊያ ኀያል።
[9]እናንተ ደጆች፤ ቀና በሉ፤
እናንተ የዘላለም በሮች፤
የክብር ንጉሥ እንዲገባ ብድግ በሉ!
[10]ይህ የክብር ንጉሥ ማን ነው?
የሰራዊት *አምላክ*፣
እርሱ የክብር ንጉሥ ነው። ሴላ

## *መዝሙር* 25[ሸ]

### በአደጋ ጊዜ የቀረበ ጸሎት

*የዳዊት መዝሙር*

[1]*እግዚአብሔር ሆይ*፤ ነፍሴን ወደ አንተ
አነሣለሁ፤
[2]አምላኬ ሆይ፣ በአንተ እታመናለሁ፤
እባክህ አታሳፍረኝ፤
ጠላቶቼም አይዘባነኑብኝ።
[3]አንተን ተስፋ የሚያደርጉ፣
ከቶ አያፍሩም፤
ነገር ግን እንዲያው ያለ ምክንያት፣
ተንኰለኞች የሆኑ ያፍራሉ።
[4]*እግዚአብሔር ሆይ*፤ አካሄድህን
እንዳውቅ አድርገኝ፤
መንገድህንም አስተምረኝ።
[5]አንተ አዳኜ፣ አምላኬም ነህና፣
በእውነትህ ምራኝ፤ አስተምረኝም፤
ቀኑን ሙሉ አንተን ተስፋ
አድርጌአለሁ።
[6]*እግዚአብሔር ሆይ*፤ ምሕረትህንና
ፍቅርህን አስብ፤
እነዚህ ከጥንት የነበሩ ናቸውና።
[7]የልጅነቴን ኀጢአት፣
መተላለፌንም አታስብብኝ፤
*እግዚአብሔር ሆይ*፤ እንደ ቸርነትህ
ብዛት፣
እንደ ምሕረትህም መጠን አስበኝ።
[8]*እግዚአብሔር* መልካምና ቅን ነው፤
ስለዚህ ኀጢአተኞችን በመንገድ
ይመራቸዋል።
[9]ዝቅ ያሉትን በፍትሕ ይመራቸዋል፤
ለትሑታንም መንገዱን
ያስተምራቸዋል።

**22፥31** መዝ5፥8፤ 40፥9፤71፥18፤78፥6፤102፥18፤ሉቃ18፥31፤24፥44
**23፥1** ዘፍ48፥15፤ መዝ28፥9፤34፥9፥10፤84፥11፤107፥9፤ዮሐ10፥11፤ፊል4፥19
**23፥2** መዝ36፥8፤ 46፥4፤ራእ7፥17
**23፥3** መዝ5፥8፤ 19፥7፤25፥9፥11፤31፥3፤73፥24፤79፥9፤106፥8፤109፥21፤143፥11፤ ኢሳ42፥16
**23፥4** ኢዮ3፥5፤መዝ3፥6፤16፥8፤27፥1፤107፥14፤ኢሳ43፥2
**23፥5** ኢዮ36፥16፤ መዝ16፥5፤45፥7፤92፥10፤ሉቃ7፥46
**23፥6** ነህ9፥25
**24፥1** ዘፀ9፥29፤ኢዮ41፥11፤1ቆሮ10፥26
**24፥2** ዘፍ1፥6፤መዝ104፥3፤2ጴጥ3፥5
**24፥3** መዝ2፥6፤ 15፥1፤65፥4
**24፥4** 2ሳሙ22፥21፤መዝ51፥10፤73፥1፤ሕዝ18፥15፤ማቴ5፥8
**24፥5** ዘዳ11፥26፤ መዝ17፥2
**24፥6** መዝ27፥8፤ 105፥4፤119፥58፤ሆሴ5፥15
**24፥7** መዝ29፥3፤ 44፥4፤74፥12፤118፥19፥20፤ኢሳ26፥2፤60፥11፤18፤62፥10፤ ዘካ9፥9፤ማቴ21፥5፤ሐሥ7፥2፤ 1ቆሮ 2፥8
**24፥8** ዘፀ15፥3፥6፤ ዘዳ4፥34፤1ዜና29፥11፤ መዝ89፥13፤ኤር50፥34፤ኤፌ6፥10
**24፥10** 1ሳሙ1፥11
**25፥1** መዝ86፥4፤ 143፥8
**25፥2** መዝ31፥6፤ 143፥8
**25፥3** መዝ22፥5፤ ኢሳ24፥16፤29፥22፤ዕን1፥13፤ሶፎ3፥4፤2ጢሞ3፥4
**25፥4** ኢዮ34፥32
**25፥5** ቍ3፤መዝ24፥5፤31፥3፤33፥20፤39፥7፤42፥5፤43፥3፤71፥5፤130፥7፤131፥3፤ዮሐ16፥13
**25፥6** መዝ5፥7፤ 98፥3፤ኢሳ63፥7፥15፤ኤር31፥20፤ሆሴ11፥8
**25፥7** ዘፀ23፥21፤ 1ዜና16፥34፤ኢዮ13፥26፤መዝ6፥4፤34፥8፤51፥1፤69፥16፤73፥1፤107፥17፤109፥26፤119፥124፤ኢሳ54፥4፤ኤር3፥25፤31፥19፤32፥30፤ሕዝ16፥22፥60
፤23፥3፤2ጢሞ2፥22 **25፥8** መዝ32፥8፤92፥15፤ኢሳ26፥7፤ 28፥26
**25፥9** ቍ4፤መዝ23፥3፤27፥11

[ሠ]4 ወይም *እጅግ ጨለማ በሆነው ሸለቆ ውስጥ*
[ረ]4 ወይም *በሐሰትም ያልማለ*
[ሰ]6 ሁለት የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆችና ሱርስት (እንዲሁም ሰብዓ ሊቃናት ይመ) እንዲሁ ሲሆኑ አብዛኛዎቹ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆች ግን *ያዕቆብ፤ ፊትህን* ..
[ሸ]25 ይህ መዝሙር እያንዳንዱ ጥቅስ ተከታታይ ፊደላት ባሉት የዕብራይስጥ ሆህያት የሚጀምር፣ ጅማሬው ወይም ጅማሬውና መጨረሻው ትርጉም የሚሰጥ ግጥም ነው።

10 ኪዳኑንና ሥርዐቱን ለሚጠብቁ፣
የእግዚአብሔር መንገድ ሁሉ ቸርነትና
እውነት ናቸው።
11 እግዚአብሔር ሆይ፤ ኀጢአቴ ታላቅ
ነውና፣
ስለ ስምህ ይቅር በልልኝ።
12 እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ማን ነው?
በተመረጠለት መንገድ ያስተምረዋል።
13 ዘመኑን በተድላ ደስታ ያሳልፋል፤
ዘሩም ምድርን ይወርሳል።
14 እግዚአብሔር ምስጢሩን ከሚፈሩት
ወዳጆቹ አይሰውርም፤
ኪዳኑንም ይገልጥላቸዋል።
15 ዐይኖቼ ሁልጊዜ ወደ እግዚአብሔር
ናቸው፤
እግሮቼን ከወጥመድ የሚያላቅቃቸው
እርሱ ነውና።
16 እኔ ብቸኛና የተጨነቅሁ እንደ መሆኔ፣
ወደ እኔ ተመለስ፤ ምሕረትም
አድርግልኝ።
17 የልቤ መከራ በዝቶአል፤
ከጭንቀቴ ገላግለኝ።
18 ጭንቀቴንና መከራዬን ተመልከት፤
ኀጢአቴንም ሁሉ ይቅር በለኝ።
19 ጠላቶቼ እንዴት እንደ በዙ ተመልከት፤
እንዴት አምርረው እንደሚጠሉኝ
እይ።
20 ነፍሴን ጠብቃት፤ ታደገኝም፤
መጠጊያዬ ነህና አታሳፍረኝ።
21 አንተን ተስፋ አድርጌአለሁና፣
ታማኝነትና ቅንነት ይጠብቁኝ።
22 አምላክ ሆይ፤ እስራኤልን፣
ከመከራው ሁሉ አድነው።

## መዝሙር 26

### የንጹሕ ሰው ጸሎት

የዳዊት መዝሙር

1 እግዚአብሔር ሆይ፤ ያለ ነቀፋ እንደ
መሆኔ፣
አንተው ፍረድልኝ።
ወዲያ ወዲህ ሳልል ም፣
በእግዚአብሔር ታምኛለሁ።
2 እግዚአብሔር ሆይ፤ ፈትነኝ፤
መርምረኝም፤
ልቤንና ውስጤን መርምር፤
3 ምሕረትህ ከፊቴ አልተለየምና፣
በእውነትህም ተመላለስሁ።
4 ከማይረቡ ጋር አልተቀመጥሁም፤
ከግብዞችም ጋር አልተባበርሁም።
5 የክፉዎችን ማኅበር ተጸየፍሁ፤
ከዐመፀኞችም ጋር አልቀመጥም።
6 እጆቼን በየዋህነት እታጠባለሁ፤

25፥10 መዝ18፥25፤103፥18፤132፥12
25፥11 ዘፀ9፥16፤32፥30፤34፥9፤መዝ31፥3፤78፥38፤79፥9፤ኤር14፥7
25፥12 ቆላ3፥8፤ኢዮ1፥8
25፥13 ዘኍ14፥24፤ዘዳ30፥15፤1ነገ3፥14፤ኢዮ8፥7፤ማቴ5፥5
25፥14 ዘፍ17፥2፤ምሳ3፥32፤ዮሐ7፥17
25፥15 2ዜና20፥12፤ኢዮ34፥30፤መዝ119፥110፤123፥2፤ዕብ12፥2
25፥16 ዘኍ6፥25፤መዝ6፥4፤68፥6
25፥17 1ነገ1፥29፤መዝ6፥3፤34፥6፡17፤39፥2፤40፥12፤54፥7፤116፥3
25፥18 2ሳሙ16፥12፤መዝ13፥3፤103፥3፤ሮሜ12፥12
25፥19 መዝ3፥1፤9፥13፤35፥19፤38፥19፤69፥4
25፥20 ቆላ3፤መዝ2፥12፤17፥13፤22፥21፤43፥1፤71፥2፤86፥2፤116፥4፤140፥1፤142፥6፤144፥11
25፥21 ቆላ3፤ዘፍ20፥5፤1ነገ9፥4፤መዝ85፥10፤111፥8፤ምሳ10፥9፤ኢሳ60፥17፤ሚል2፥6
25፥22 መዝ130፥8፤ሉቃ24፥21
26፥1 1ሳሙ24፥15፤2ነገ20፥3፤መዝ15፥2፤22፥4፤40፥4፤ምሳ20፥7፤ኢሳ12፥2፤25፥9፤ኤር17፥7፤ዳን3፥28፤ዕብ10፥23
26፥2 ዘዳ6፥6፤መዝ7፥9፤66፥10፤ኤር11፥20፤20፥12፤ሕዝ11፥5
26፥3 1ነገ2፥4፤መዝ6፥4፤40፥11፤43፥3፤86፥11፤119፥30
26፥4 መዝ1፥1፤28፥3፤ማቴ6፥2 26፥5 መዝ139፥21 26፥6 መዝ73፥13፤ማቴ27፥24
26፥7 ኢሱ3፥5፤መዝ9፥1፤ኢሳ42፥12፤60፥6
26፥8 ዘፀ29፥43፤2ዜና7፥1፤መዝ96፥6፤122፥6፤ኢሳ66፥10
26፥9 መዝ5፥6፤28፥3፤55፥23፤139፥19፤ምሳ29፥10 26፥10 ኢዮ36፥18፤መዝ21፥11፤ኢሳ1፥23፤ሕዝ22፥12
26፥11 መዝ31፥5፤69፥18፤119፥134፤ቲቶ2፥14

እግዚአብሔር ሆይ፤ መሠዊያህንም
እዞራለሁ፤
7 የምስጋናን ድምፅ አሰማ ዘንድ፣
ታምራትህንም አወራ ዘንድ ነው።
8 እግዚአብሔር ሆይ፤ የምትኖርበትን
ቤት፣
የክብርህን ማደሪያ ቦታ ወደድሁ።
9 ነፍሴን ከኀጢአተኞች ጋር፣
ሕይወቴንም ከደም አፍሳሾች ጋር
አታስወግዳት።
10 በእነርሱ እጅ የተንኰል ዕቅድ አለ፤
ቀኝ እጃቸውም ጉቦን ያጋብሳል።
11 እኔ ግን በተአማኒ ሕይወት እጓዛለሁ፤
አድነኝ፤ ምሕረትንም አድርግልኝ።
12 እግሮቼ በደልዳላ ስፍራ ቆመዋል፤
በታላቅ ጉባኤ መካከልም እግዚአ
ብሔርን እባርከዋለሁ።

## መዝሙር 27

### ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ሰው ድፍረት

የዳዊት መዝሙር

1 እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኀኒ ነው፤
የሚያስፈራኝ ማን ነው?
እግዚአብሔር ለሕይወቴ ዐምባዋ ነው፤
ማንን እፈራለሁ?
2 ሥጋዬን ይበሉ ዘንድ፣[ቀ]
ክፉዎች ገፍተው በመጡ ጊዜ፣
ጠላቶቼና ባላጋራዎቼ በተነሡብኝ ጊዜ፣
እነርሱ ተሰነካክለው ወደቁ።
3 ሰራዊት ቢከበኝ እንኳ፣
ልቤ አይፈራም፤
ጦርነት ቢነሣብኝ እንኳ፣
ልበ ሙሉ ነኝ።
4 እግዚአብሔርን አንዲት ነገር
እለምነዋለሁ፤
እርሷንም እሻለሁ፤
ይኸውም በሕይወቴ ዘመን ሁሉ፣
በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ፣
የእግዚአብሔርን ክብር ውበት አይ
ዘንድ፣
በመቅደሱም ሆኜ አሰላስል ዘንድ ነው።
5 በመከራ ቀን፣
በድንኳኑ ውስጥ ይሰውረኛልና፤
በድንኳኑም ጓዳ ይሸሽገኛል፤
በዐለትም ላይ ያቆመኛል።

26፥12 መዝ22፥25፤27፥11፤40፥2፤143፥10፤ኢሳ26፥7፤40፥3-4፤45፥13፤ዘካ4፥7፤ሉቃ6፥17 27፥1 ዘፀ15፥2፤2ሳሙ22፥29፤ኢዮ13፥15፤መዝ3፥8፤9፥9፤56፥4፡11፤118፥6 27፥2 መዝ9፥3፤20፥8፤37፥24፤ዳን11፥19፤ሮሜ11፥11 27፥3 ዘፍ4፥7፤ኢዮ4፥6፤መዝ 3፥6 27፥4 መዝ23፥6፤61፥4፤ሉቃ10፥42 27፥5 ኢዮ38፥23፤መዝ12፥7፤17፥8፤40፥2

[ቀ]2 ወይም ስሜን ሊያጠፉ

6በዚህ ጊዜ በዙሪያዬ ባሉ ጠላቶቼ ላይ፣
ራሴ ከፍ ከፍ ይላል፤
በድንኳኑም ውስጥ የእልልታ መሥዋዕት
እሠዋለሁ፤
ለእግዚአብሔር እቀኛለሁ፤
እዘምርለታለሁም።
7እግዚአብሔር ሆይ፤ ድምፄን ከፍ
አድርጌ ስጮኽ ስማኝ፤
ራራልኝ፤ ስማኝም።
8"ፊቴን ፈልጉ" ባልህ ጊዜ፤[n]
ልቤ እግዚአብሔር ሆይ፤ ፊትህን
እሻለሁ አለች።
9ፊትህን ከእኔ አትሰውር፤
ተቈጥተህ አገልጋይህን አታርቀው፤
መቼም ረዳቴ ነህና።
አዳኝ አምላኬ ሆይ፤
አትጣለኝ፤ አትተወኝም።
10አባቴና እናቴ ቢተዉኝ እንኳ፣
እግዚአብሔር ይቀበለኛል።
11እግዚአብሔር ሆይ፤ መንገድህን
አስተምረኝ፤
ስለ ጠላቶቼም፣
በቀና መንገድ ምራኝ።
12ለጠላቶቼ ፍላጎት አሳልፈህ አትስጠኝ፤
የሐሰት ምስክሮች ተነሥተውብኛልና፣
ዐመፃ የሚረጩ ናቸው።
13የእግዚአብሔርን ቸርነት፣
በሕያዋን ምድር እንደማይ፣
ሙሉ እምነቴ ነው።
14እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ፤
አይዞህ፣ በርታ፤
እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ።

## መዝሙር 28

### ልመናና ምስጋና

የዳዊት መዝሙር

1እግዚአብሔር ሆይ፤ ወደ አንተ እጣራለሁ፤
ዐለቴ ሆይ፤ ሰምተህ እንዳልሰማ
አትሁንብኝ፤
አንተ ዝም ካልኸኝ፤
ወደ ጒድጓድ እንደሚወርዱ እሆናለሁ።
2ለርዳታ በጮኽሁ ጊዜ፣
ወደ ቅዱስ ማደሪያህ፣
እጆቼን በዘረጋሁ ጊዜ፣
የልመናዬን ቃል ስማ።
3በልባቸው ተንኰል እያለ፣
ከባልንጀሮቻቸው ጋር በሰላም ከሚናገሩ፣
ከክፉ አድራጊዎችና፣
ከዐመፃ ሰዎች ጋር ጐትተህ
አትውሰደኝ።
4እንደ ሥራቸው፣
እንደ ክፉ ተግባራቸው ክፈላቸው፤

27፥6 ዘፀ15፥1፤ 2ሳሙ22፥49፤ዕዝ 3፥13፤ኢዮ22፥26፤ መዝ3፥3፤18፥48፤22፥ 12፤33፥2፤50፥14፤54፥ 6፤92፥1፤107፥22፤ 116፥17፤147፥7፤ ኤፌ5፥19
27፥7 መዝ4፥1፤5፥3 ፤18፥6፤55፥17፤119፥1 49፤130፥2፤ኢሳ 28፥23
27፥8 1ዜና16፥11
27፥9 ዘፍ49፥25፤ ዘዳ4፥31፤31፥17፤33፥2 9፤መዝ2፥5፤18፥46፤2 2፥24፤37፥28፤119፥8፤ ኢሳ41፥17፤62፥12 ፤ኤር14፥9
27፥11 ዘፀ33፥13፤ ዕዝ8፥21፤መዝ5፥8፤ 72፥4፤78፥42፤106፥ 10፤ኤር21፥12
27፥12 ዘዳ19፥16፤ ማቴ26፥60፤ሐሥ6፥13 ፤1ቆሮ15፥15 27፥13 ዘፀ33፥19፤ 2ዜና6፥41፤ኢዮ28፥13 ፤መዝ23፥6፤31፥19፤ 145፥7
27፥14 ዘዳ1፥21፤ መሳ5፥21፤መዝ33፥20 ፤130፥5፥6፤ኢሳ8፥17 ፤30፥18፤ዕን2፥3፤ሶፎ 3፥8፤ሐሥ1፥4፤ኤፌ 6፥10
28፥1 ዘዳ1፥45፤አስ 4፥14፤ኢዮ33፥18
28፥2 ዕዝ9፥5፤መዝ 5፥7፤11፥4፤17፥1፤61፥1 ፤63፥4፤116፥1፤130፥2 ፤141፥2፤142፥1፤143፥ 1፤ሰቆ2፥19፤ 1ጢሞ2፥8
28፥3 መዝ12፥2፤ 26፥4፤55፥21፤ኤር9፥
28፥4 መዝ62፥12፤ ሰቆ3፥64፤2ጢሞ4፥ 14፤ራእ18፥6፤22፥12
28፥5 ኢሳ5፥12
28፥6 ቍ 2፤ዘፍ24፥ 27፤2ቆሮ1፥3፤ኤፌ1፥3 ፤1ጴጥ1፥3
28፥7 ዘዳ16፥15፤ መዝ13፥5፤16፥9፤18፥1 ፤33፥3፤40፥3፤69፥ 30፤112፥7፤144፥9፤14 9፥1፤ኢሳ26፥3
28፥8 ዘፀ15፥2፤መዝ 18፥1፤20፥6፤27፥1፤ ዕን 3፥13
28፥9 ዘፀ34፥9፤ዘዳ 1፥31፤32፥11፤1ዜና 11፥2፤16፥35፤መዝ 23፥1፤78፥52፥71፤ 80፥1፤106፥47፤118፥2 5፤ኢሳ40፥11፤46፥3፤ 63፥9፤ኤር31፥10፤ ሕዝ34፥12-16፥23፥ 31፤ሚክ7፥14
29፥1 ቍ 2፤2ሳሙ 1፥19፤2ዜና16፥28፤መ ዝ8፥1፤103፥20፤

እንደ እጃቸው ሥራ ስጣቸው፤
አጸፋውን መልስላቸው።
5ለእግዚአብሔር ሥራ ግድ ስለሌላቸው፣
ለእጆቹም ተግባራት ስፍራ ስላልሰጡ፣
እርሱ ያፈርሳቸዋል፤
መልሶም አይገነባቸውም።
6የልመናዬን ቃል ሰምቶአልና፣
እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን።
7እግዚአብሔር ብርታቴና ጋሻዬ ነው፤
ልቤ በእርሱ ይታመናል፤ እርሱም
አግዞኛል፤
ልቤ ሐሤት አደረገ፤
በዝማሬም አመሰግነዋለሁ።
8እግዚአብሔር ለሕዝቡ ብርታታቸው
ነው፤
ለቀባውም የመዳን አምባ ነው።
9ሕዝብህን አድን፤ ርስትህንም ባርክ፤
እረኛ ሁናቸው፤ ለዘላለሙም ዐቅፈህ
ያዛቸው።

## መዝሙር 29

### ለማዕበሉ ጌታ የቀረበ ውዳሴ

የዳዊት መዝሙር

1እናንተ ኀያላን፣ ለእግዚአብሔር ስጡ፤
ክብርንና ብርታትን ለእግዚአብሔር
ስጡ።
2ለስሙ የሚገባ ክብር ለእግዚአብሔር
ስጡ፤
በቅድስናው ግርማ ለእግዚአብሔር
ስገዱ።
3የእግዚአብሔር ድምፅ በውሆች ላይ
ነው፤
የክብር አምላክ አንጐደጐደ፤
እግዚአብሔር በታላላቅ ውሆች ላይ
አንጐደጐደ።
4የእግዚአብሔር ድምፅ ኀያል ነው፤
የእግዚአብሔር ድምፅ ግርማዊ ነው።
5የእግዚአብሔር ድምፅ ዝግባን ይሰብራል፤
እግዚአብሔር የሊባኖስን ዝግባ
ይሰባብራል።
6ሊባኖስን እንደ ጥጃ፣
ስርዮንንም[†] እንደ አውራሪስ ግልገል
ያዘልላል።
7የእግዚአብሔር ድምፅ
የእሳት ነበልባል ይረጫል።

ኢሳ10፥13 29፥2 1ዜና16፥29፤መዝ96፥7-9 29፥3 ዘፀ15፥10፤ 1ሳሙ2፥10፤ኢዮ37፥5፤መዝ18፥13፤24፥7፤46፥6፤68፥33፤77፥17፤ ኤር10፥13፤25፥30፤ኤል2፥11፤አሞ1፥2፤ሐሥ7፥2 29፥4 መዝ68፥33 29፥5 መሳ9፥15 29፥6 ዘኍ23፥22፤ዘዳ3፥9፤ኢዮ39፥9፤መዝ 92፥10፤114፥4 29፥7 ሕዝ1፥14፤ራእ8፥5

[n]8 ወይም ልቤ ሆይ፤ ለአንተ "ፊቴን …" አለ
[†]6 አርሞንዔም የተባለው ተራራ ነው።

8 የእግዚአብሔር ድምፅ ምድረ በዳውን
ያናውጣል፤
የእግዚአብሔር ድምፅ የቃዴስን
ምድረ በዳ ያናውጣል።
9 የእግዚአብሔር ድምፅ ወርካዎችን
ይወዘውዛል፤[ቸ]
ጫካዎችንም ይመነጥራል፤
ሁሉም በእርሱ ቤተ መቅደስ ሆኖ
“ይክበር!” ይላል።

10 እግዚአብሔር በጐርፍ ላይ ዙፋኑን
ዘርግቶ ተቀምጦአል፤[ኀ]
እግዚአብሔር በንጉሥነቱ ለዘላለም
በዙፋኑ ላይ ይቀመጣል።
11 እግዚአብሔር ለሕዝቡ ብርታትን
ይሰጣል፤
እግዚአብሔር ሕዝቡን በሰላም ይባርካል።

## መዝሙር 30

### ከክፉ አደጋ የዳነ ሰው ምስጋና

ለቤተ መቅደሱ ምረቃ የተዘመረ፤ የዳዊት መዝሙር

1 እግዚአብሔር ሆይ፤ ከታች
አንሥተኸኛልና፣
ጠላቶቼም በላዬ እንዳይደሰቱ
አድርገሃልና፣
ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ።
2 እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤ ትረዳኝ
ዘንድ ወደ አንተ ጮኽሁ፤
አንተም ፈወስኸኝ።
3 እግዚአብሔር ሆይ ነፍሴን ከሲኦል[ነ]
አወጣሃት፤
ወደ ጒድጓድ ከመውረድም መልሰህ
ሕያው አደረግኸኝ።

4 እናንተ ቅዱሳኑ፤ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤
ቅዱስ ስሙንም አወድሱ።
5 ቍጣው ለአጭር ጊዜ ነው፤
ቸርነቱ ግን እስከ ዕድሜ ልክ ነውና፤
ሌሊቱን በልቅሶ ቢታደርም፣
በማለዳ ደስታ ይመጣል።

6 እኔም በተረጋጋሁ ጊዜ፣
“ከቶ አልናወጥም” አልሁ።
7 እግዚአብሔር ሆይ፤ በአንተ ሞገስ፣
ተራሮቼ[ኘ] ጸኑ፣
ፊትህን በሰወርህ ጊዜ ግን፣
ውስጤ ታወከ።

8 እግዚአብሔር ሆይ፤ ወደ አንተ ተጣራሁ፤
ወደ ጌታ ም እንዲህ ብዬ ጮኽሁ፤
9 “በእኔ ወደ ጒድጓድ መውረድ፣
በመሞቴ ምን ጥቅም ይገኛል?[አ]
ዐፈር ያመሰግንሃልን?
ታማኝነትህንስ ይናገራልን?
10 እግዚአብሔር ሆይ፤ ስማ፤ ማረኝም፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ ረዳት ሁነኝ።”
11 ዋይታዬን ወደ ሽብሸባ ለወጥህልኝ፤
ማቄን አውልቀህ፣ ፍስሓን አለበስኸኝ፤
12 እንግዲህ፣ ነፍሴ ታመስግንህ፤ ዝምም
አትበል፤
እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤ ለዘላለም
አመሰግንሃለሁ።

## መዝሙር 31

### የመከራ ጊዜ ጸሎት

31፥1-4 ተጓ ምብ-መዝ71፥1-3

ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር

1 እግዚአብሔር ሆይ፤ በአንተ ተተግኛለሁ፤
እንግዲህ እፍረት ከቶ አይድረስብኝ፤
በጽድቅህም ታደገኝ።
2 ጆሮህን ወደ እኔ መልሰህ ስማኝ፤
ፈጥነህ አድነኝ፤
መጠጊያ ዐለት ሁነኝ፤
ታድነኝም ዘንድ ምሽግ ሁነኝ።
3 አንተ ዐለቴና መጠጊያዬ ነህና፣
ስለ ስምህ ስትል ምራኝ፤
መንገዱንም ጠቍመኝ።
4 አንተ መጠጊያዬ ነህና፣
በስውር ከተዘረጋብኝ ወጥመድ
አውጣኝ።
5 መንፈሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ፤
እግዚአብሔር የእውነት አምላክ ሆይ፤
አንተ ተቤዠኸኝ።

6 ለከንቱ ጣዖታት ስፍራ የሚሰጡትን
ጠላሁ፤
ነገር ግን በእግዚአብሔር ታመንሁ።
7 በምሕረትህ ደስ እሰኛለሁ፤ ሐሤትም
አደርጋለሁ፤
መከራዬን አይተሃልና፤
የነፍሴንም ጭንቀት ዐውቀሃል።
8 ለጠላት አሳልፈህ አልሰጠኸኝም፤
ነገር ግን እግሮቼን ሰፊ ቦታ ላይ
አቆምሃቸው።

9 እግዚአብሔር ሆይ፤ በመከራ ውስጥ ነኝና
ማረኝ፤
ዐይኖቼ በሐዘን ደክመዋል፤
ነፍስና ሥጋዬም ዝለዋል።
10 ሕይወቴ በመጨነቅ፣
ዕድሜዬም በመቃተት አለቀ፤
ከመከራዬ[ከ] የተነሣ ጒልበት ከዳኝ፤
ዐጥንቴም በውስጤ ሟሟ።
11 ከጠላቶቼ ሁሉ የተነሣ፣
ለጎረቤቶቼ መዘባበቻ፣

29፥8 ዘኍ13፥26፤ 20፥1
29፥9 ዘኍ13፥32፤ መዝ26፥8፤ኢሳ2፥13፤ሕዝ27፥6፤አሞ2፥9
29፥10 ዘፍ6፥17፤ ዘፀ15፥18
29፥11 ዘሌ26፥6፤ ዘኍ6፥26፤መዝ18፥1፤ 28፥8፤68፥35
30፥1 ዘፀ15፥2፤ኢዮ 11፥8፤መዝ22፥17፤63፥9፤107፥26፤ምሳ9፥18፤ ኢሳ14፥15
30፥2 ዘኍ12፥13፤ መዝ5፥2፤88፥13
30፥3 መዝ16፥10፤ 28፥1፤55፥23፤56፥13፤ 69፥15፤86፥13፤143፥7፤ምሳ1፥12፤ኢሳ 38፥17፤ዮና2፥6
30፥4 ዘፀ3፥15፤መዝ 16፥3፤33፥1፥21፤47፥7፤ 68፥4፤103፥1፤145፥21
30፥5 2ሳሙ15፥30፤ዕዝ3፥11፤ኢዮ14፥13፤መዝ6፥6፤103፥9፤12 6፥6፤ኤር31፥16፤2 ቆሮ 4፥17
30፥6 ኢዮ29፥18
30፥7 ዘዳ31፥17
30፥9 ኢዮ33፥18፤ መዝ6፥5፤88፥11፤ኢሳ 38፥18
30፥10 መዝ4፥1፤17፥1፤20፥2
30፥11 ዘፀ15፥20፤ ዘዳ16፥15፤2ሳሙ3፥31፤አስ4፥1፤መዝ16፥9፤3 5፥13
30፥12 መዝ35፥18፤4 4፥8፤52፥9፤75፥1፤118፥21፤ራእ11፥17
31፥1 መዝ5፥8፤7፥1
31፥2 ዘፀ2፥17፤2ሳሙ 22፥3፤መዝ6፥4፤18፥2
31፥3 መዝ18፥2፤ 23፥3
31፥4 1ሳሙ28፥9፤ኢዮ18፥10፤መዝ9፥9
31፥5 ኢሳ45፥19፤ 65፥16፤ሉቃ23፥46፤ሐሥ7፥59
31፥6 ዘዳ32፥21፤ መዝ4፥5
31፥7 መዝ13፥3፤ 25፥17፤ሉቃ22፥44
31፥8 ዘዳ32፥30፤ 2ሳሙ22፥20
31፥9 መዝ4፥1፤ 6፥7፤63፥1
31፥10 ቍ7፤መዝ 6፥2፥6፤22፥15፤25፥18፤ 32፥4፤38፥10፤73፥6
31፥11 ዘዳ30፥7፤ መዝ3፥7፤22፥6፤25፥19፤38፥11፤102፥8

[ቸ]9 ወይም *እግዚአብሔር ኢጋዘን እንድትወልድ ያደርጋል*
[ኀ]10 ወይም *ይቀመጣል* [ነ]3 ወይም *ከመቃብር*
[ኘ]7 ወይም *ኰረብታማ የሆነች አገሬ*
[አ]9 ወይም *ዝም ብል … ይገኛል?*
[ከ]10 ወይም *ከበደሌ*

ለወዳጆቼ መሳለቂያ ሆኛለሁ፤
መንገድ ላይ የሚያገኙኝም ይሸሹኛል።
12እንደ ሞተ ሰው ተረሳሁ፤
እንደ ተሰበረ የሸክላ ዕቃም
ተቈጠርሁ።
13የብዙ ሰዎችን ሹክሹክታ እሰማለሁና፤
ዙሪያው ሁሉ ሽብር አለ፤
በእኔ ላይ ባሤሩ ጊዜ፣
ሕይወቴን ለማጥፋት ዶለቱ።
14እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔ ግን በአንተ
እታመናለሁ፤
"አንተ አምላኬ ነህ" እልሃለሁም።
15ዘመኔ ያለው በእጅህ ነው፤
ከጠላቶቼ እጅ ታደገኝ፤
ከሚያሳድዱኝም አድነኝ።
16ፊትህን በአገልጋይህ ላይ አብራ፤
በምሕረትህም አድነኝ።
17እግዚአብሔር ሆይ፤
ወደ አንተ እጮኻለሁና አልፈር፤
ክፉዎች ግን ይፈሩ፤
ሲኦል[ኸ] ገብተውም ጸጥ ይበሉ።
18በጻድቁ ላይ በእብሪት የሚናገሩ፣
ትዕቢትንና ንቀትን የተሞሉ፣
ዋሾ ከንፈሮች ድዳ ይሁኑ።
19በሰዎች ልጆች ፊት፣
ለሚፈሩህ ያስቀመጥሃት፣
መጠጊያ ላደረጉህም ያዘጋጀሃት፣
በጎነትህ ምንኛ በዛች!
20ከሰዎች ሤራ፣
በማደሪያህ ውስጥ ትሸሽጋቸዋለህ፤
ከአንደበት ጭቅጭቅም፣
በድንኳንህ ውስጥ ትከልላቸዋለህ።
21በተከበበች ከተማ ውስጥ፣
የሚያስደንቅ ምሕረቱን ያሳየኝ፣
እግዚአብሔር ይባረክ።
22እኔ በደነገጥሁ ጊዜ፣
"ከዐይንህ ፊት ተወግጃለሁ" አልሁ፤
አንተ ግን ወደ አንተ ስጮኽ፣
የልመናዬን ቃል ሰማህ።
23እናንተ ቅዱሳኑ ሁሉ፣ እግዚአብሔርን
ውደዱት!
እግዚአብሔር ታማኞችን ይጠብቃል፤
ትዕቢተኞችን ግን ፈጽሞ
ይበቀላቸዋል።
24እግዚአብሔርን ተስፋ የምታደርጉ ሁሉ፤
በርቱ፤ ልባችሁም ይጽና።

## መዝሙር 32

### ግልጥ ኑዛዜ

የዳዊት ትምህርት

1መተላለፉ ይቅር የተባለለት፣
ኀጢአቱም የተሸፈነለት፣
እንዴት ቡሩክ ነው!
2እግዚአብሔር ኀጢአቱን የማይቈጥርበት፣
በመንፈሱም ሽንገላ የሌለበት ሰው፣
እርሱ ቡሩክ ነው።
3ቀኑን ሙሉ ከመቃተቴ የተነሣ፣
ዝም ባልሁ ጊዜ፣
አጥንቶቼ ተበላሹ፤
4በቀንና በሌሊት፣
እጅህ ከብዳብኛለችና፤
ኀይሌም የበጋ ትኵሳት እንደላሰው ነገር፣
ከውስጤ ተሟጠጠ። ሴላ
5ኀጢአቴን ለአንተ አስታወቅሁ፤
በደሌንም አልሸሸግሁም፤
ደግሞም "መተላለፌን
ለእግዚአብሔር እናዘዛለሁ" አልሁ፤
አንተም የኀጢአቴን በደል፣
ይቅር አልህ። ሴላ
6ስለዚህ ጻድቅ ሁሉ፣
በጭንቅ ጊዜ ወደ አንተ ይጸልይ፤
ኀይለኛ ጐርፍ አካባቢውን ቢያጥለ
ቀልቅም፣
እርሱ አጠገብ አይደርስም።
7አንተ መሸሸጊያዬ ነህ፤
ከመከራ ትጠብቀኛለህ፤
በድል ዝማሬም ትከብበኛለህ። ሴላ
8አስተምርሃለሁ፤ በምትሄድበትም
መንገድ እመራሃለሁ፤
እመክርሃለሁ፤ በዐይኔም እከታተልሃለሁ።
9በልባብና በልጓም ካልተገሩ በቀር፣
ወደ አንተ እንደማይቀርቡት፣
ማስተዋል እንደሌላቸው፣
እንደ ፈረስና እንደ በቅሎ አትሁኑ።
10የክፉዎች ወዮታ ብዙ ነው፤
በእግዚአብሔር የሚታመን ግን፣
ምሕረት ይከብበዋል።
11ጻድቃን ሆይ፤ በእግዚአብሔር ደስ
ይበላችሁ፤ ሐሤትም አድርጉ፤
ቅን ልብ ያላችሁም ሁሉ፣ እልል በሉ።

## መዝሙር 33

### ውዳሴ ለቸር አምላክ

1ጻድቃን ሆይ፤ በእግዚአብሔር ደስ
ይበላችሁ፤
ቅኖች ሊወድሱት ይገባቸዋል።
2እግዚአብሔርን በመሰንቆ አመስግኑት፤
ዐሥር አውታር ባለውም በገና ዘምሩለት።
3አዲስ መዝሙር ዘምሩለት፤
በገናውን ባማረ ቅኝት ደርድሩ፤
እልልም በሉ።
4የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነውና፤

[ኸ]17 ወይም መቃብር

31፥12 መዝ28፥1፤88፥4
31፥13 ዘፍ37፥18፤ዘሌ19፥16፤ኢዮ18፥11፤መዝ41፥7፤50፥20፤56፥6፤71፥10፤83፥3፤ኢሳ13፥8፤ኤር6፥25፤20፥3፥10፤46፥5፤49፥5፤ሰቆ2፥22ማቴ12፥14
31፥14 መዝ4፥5
31፥15 ኢዮ14፥5
31፥16 ዘኍ6፥25፤መዝ6፥4
31፥17 1ሳሙ2፥9፤መዝ22፥5፤94፥17፤115፥17
31፥18 1ሳሙ2፥3፤መዝ120፥2፤ምሳ10፥18፤26፥24፤ይሁ1፥15
31፥19 መዝ2፥12፤23፥5፤27፥13፤ሮሜ11፥22
31፥20 ዘፍ37፥18፤መዝ17፥8፤55፥8
31፥21 1ሳሙ23፥7፤መዝ17፥7፤28፥6
31፥22 ኢዮ6፥9፤17፥1፤መዝ6፥9፤37፥9፤66፥19፤88፥5፤116፥1፥11፤145፥19፤ኢሳ38፥12
31፥23 ዘዳ32፥41፤መዝ4፥3፤18፥25፤94፥2፤ራእ2፥10
31፥24 መዝ27፥14
32፥1 መዝ85፥2፤103፥3
32፥2 ዮሐ1፥47፤ሮሜ4፥7-8፤ራእ14፥5
32፥3 ኢዮ3፥24፤31፥34፤መዝ6፥6፤31፥10
32፥4 1ሳሙ5፥6፤ኢዮ9፥34፤መዝ22፥15፤38፥2፤39፥10
32፥5 ዘሌ26፥40፤ኢዮ31፥33፤መዝ103፥12፤ምሳ28፥13፤1ዮሐ1፥9
32፥6 ዘፀ15፥10፤መዝ69፥1፥13፤ኢሳ43፥2፤55፥6
32፥7 መሳ5፥1፤9፥35፤መዝ9፥9
32፥8 መዝ25፥8፤33፥18፤34፥11
32፥9 ኢዮ30፥11፤39፥10፤ያዕ3፥3
32፥10 መዝ4፥5፤ምሳ16፥20፤ሮሜ2፥9
32፥11 መዝ64፥10
33፥1 መዝ5፥11፤11፥7፤101፥1፤147፥1
33፥2 ዘፍ4፥21፤መዝ92፥3፤144፥9፤1ቆሮ14፥7፤ራእ5፥8
33፥3 ኢዮ3፥7፤መዝ35፥27፤40፥3፤47፥1፤ኢሳ42፥10፤ራእ5፥9
33፥4 መዝ18፥25፤

የሚሠራውም ሁሉ የታመነ ነው::
5እርሱ ጽድቅንና ፍትሕን ይወዳል፤
ምድርም በምሕረቱ የተሞላች ናት::
6*በእግዚአብሔር* ቃል ሰማያት ተሠሩ፤
በአፉም እስትንፋስ የከዋክብት
ሰራዊት::
7የባሕርን ውሃ በአንድ ዕቃ ይሰበስባል፤[ወ]
ቀላዩንም በአንድ ስፍራ ያከማቻል::
8ምድር ሁሉ *እግዚአብሔርን* ትፍራው፤
በዓለም የሚኖር ሕዝብ ሁሉ በፊቱ
ይንቀጥቀጥ::
9እርሱ ተናግሮአልና፣ ሆኑ፤
አዞአልና፣ ጸኑም::
10*እግዚአብሔር* የሕዝቦችን ምክክር
ከንቱ ያደርጋል፤
የሕዝብንም ዕቅድ ያጨናግፋል::
11*የእግዚአብሔር* ሐሳብ ግን ለዘላለም
ይጸናል፤
የልቡም ሐሳብ ለትውልድ ሁሉ ነው::
12*እግዚአብሔር* አምላኩ የሆነው ሕዝብ፣
ለርስቱ የመረጠውም ወገን የተባረከ
ነው::
13*እግዚአብሔር* ከሰማይ ይመለከታል፤
የሰውንም ልጆች ሁሉ ያያል፤
14ከማደሪያው ቦታ ሆኖ፣
በምድር ወደሚኖሩት ሁሉ
ይመለከታል፤
15እርሱ የሁሉን ልብ የሠራ፣
የሚያደርጉትን ሁሉ የሚያስተውል
ነው::
16ንጉሥ በሰራዊቱ ታላቅነት አይድንም፤
ጀግናም በኀይሉ ብርታት
አያመልጥም::
17በፈረስ ድል አደርጋለሁ ማለት ከንቱ
ተስፋ ነው፤
በብርቱ ጒልበቱም ማንም አያድንም::
18እነሆ፤ *የእግዚአብሔር* ዐይኖች በሚፈሩት
ላይ ናቸው፤
ምሕረቱንም በሚጠባበቁት ላይ
አትኵረዋል::
19በዚህም ነፍሳቸውን ከሞት ያድናል፤
በራብ ዘመንም በሕይወት
ያኖራቸዋል::
20ነፍሳችን *እግዚአብሔርን* ተስፋ
ታደርጋለች፤
እርሱ ረዳታችንና መጠጊያችን
ነው::
21ልባችን በእርሱ ደስ ይለዋል፤
በቅዱስ ስሙ ታምነናልና::
22*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ተስፋ ባደረግነህ፣
በእኛ ላይ ምሕረትህ ትሁን::

## *መዝሙር* 34[0]

## የእግዚአብሔር ፍትሕ ውዳሴ

*እንደ እብድ ሆኖ አቤሜሌክ ፊት በመቅረቡ ተባርሮ በወጣ ጊዜ የዘመረው፤ የዳዊት መዝሙር*

1*እግዚአብሔርን* ሁልጊዜ እባርከዋለሁ፤
ምስጋናውም ዘወትር ከአፌ አይለይም::
2ነፍሴ *በእግዚአብሔር* ተመካች፤
ትሑታንም ይህን ሰምተው ሐሤት
ያደርጋሉ::
3ኑና ከእኔ ጋር *እግዚአብሔርን* አክብሩት፤
ስሙንም በአንድነት ከፍ ከፍ
እናድርግ::
4*እግዚአብሔርን* ፈለግሁት፤ እርሱም
መለሰልኝ፤
ከፍርሀቴም ሁሉ አዳነኝ::
5ወደ እርሱ የሚመለከቱ ያበራሉ፤
ፊታቸውም ከቶ አያፍርም::
6ይህ ችግረኛ ጮኸ፤ *እግዚአብሔርም*
ሰማው፤
ከመከራውም ሁሉ አዳነው::
7*እግዚአብሔርን* በሚፈሩት ዙሪያ
*የእግዚአብሔር* መልአክ ይሰፍራል፤
ያድናቸዋልም::
8*እግዚአብሔር* ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ
እዩ፤
እርሱን መጠጊያ የሚያደርግ ምንኛ
ቡሩክ ነው!
9እናንተ ቅዱሳኑ፤ *እግዚአብሔርን* ፍሩት፤
እርሱን የሚፈሩት አንዳች አያጡምና::
10አንበሶች ሊያጡ፣ ሊራቡም ይችላሉ፤
*እግዚአብሔርን* የሚሹ ግን መልካም
ነገር አይጐድልባቸውም::
11ልጆቼ ሆይ፣ ኑ፤ ስሙኝ፤
*እግዚአብሔርን* መፍራት
አስተምራችኋለሁ::
12ሕይወትን የሚወድ፣
በጎውንም ያይ ዘንድ ዕድሜን የሚመኝ
ማን ነው?
13አንደበትህን ከክፉ ነገር ከልክል፤
ከንፈርህንም ከሽንገላ ጠብቅ::
14ከክፉ ሽሽ፤ መልካሙንም አድርግ፤
ሰላምን ፈልጋት፤ ተከተላትም::
15*የእግዚአብሔር* ዐይኖች ወደ ጻድቃን
ናቸው፤

19÷8፤25÷10፤119÷142፤ራእ19÷9፤22÷6
**33÷5** መዝ6÷4፤11÷7
**33÷6** ዘፍ1÷3፡16፤ዘፀ8÷19፤2ዜና2÷12፤ዕብ11÷3
**33÷7** ዘፍ1÷10፤አሱ3÷16
**33÷8** ዘዳ6÷13፤4÷23 ፤መዝ2÷11፤49÷1፤ኢሳ18÷3፤ሚክ1÷2
**33÷9** መዝ148÷5
**33÷10** ኢዮ5÷12፤መዝ2÷1፤ኢሳ44÷25
**33÷11** ዘኍ23÷19፤ኤር51÷12፡29
**33÷12** ዘፀ8÷22፤34÷9፤ዘዳ7÷6፤መዝ4÷3፤65÷4፤84÷4፤144÷15
**33÷13** ኢዮ28÷24፤መዝ11÷4፤14÷2፤53÷2፤102÷19፤ዕብ4÷13
**33÷14** ዘሌ15÷31፤1ነገ8÷39
**33÷15** ኢዮ10÷4፡8፤መዝ119÷73፤ኤር32÷19
**33÷16** 1ሳሙ14÷6
**33÷17** መዝ20÷7
**33÷18** ዘፀ3÷16፤መዝ6÷4፤11÷4፤1ጴጥ3÷12
**33÷19** ኢዮ5÷20፤መዝ56÷13፤ሐሥ12÷11
**33÷20** መዝ27÷14
**33÷21** 1ሳሙ2÷1፤መዝ30÷4፤99÷3፤ኢል2÷23
**33÷22** መዝ6÷4
**34** ርዕስ 1ሳሙ21÷13
**34÷1** መዝ71÷6፤ኤፌ5÷20፤1ተሰ5÷18
**34÷2** መዝ44÷8፤69÷32፤107÷42፤119÷74፤ኤር9÷24፤1ቆሮ1÷31
**34÷3** ዘፀ15÷2፤መዝ63÷3፤86÷12፤ዳን4÷37፤ዮሐ17÷1፤ሮሜ15÷6
**34÷4** ቀኍ17፤ዘፀ32÷11፤መዝ18÷43፤22÷4፤56÷13፤77÷2፤86÷13
**34÷5** ዘፀ34÷29፤መዝ25÷3፤44÷15፤69÷7፤83÷16
**34÷6** መዝ25÷17
**34÷7** ዘፍ32÷1፤መዝ22÷4፤37÷40፤41÷1፤97÷10፤ኢሳ31÷5፤ዳን3÷28፤ማቴ18÷10፤ሐሥ12÷11
**34÷8** መዝ2÷12፤ዕብ6÷5፤1ጴጥ2÷3
**34÷9** ዘዳ6÷13፤መዝ23÷1፤ራእ14÷7
**34÷10** መዝ23÷1 **34÷11** መዝ19÷9፤32÷8፤66÷16
**34÷12** መክ3÷13 **34÷13** መዝ12÷2፤39÷1፤141÷3፤ምሳ13÷3፤21÷23፤ያዕ1÷26፤1ጴጥ2÷22 **34÷14** መዝ37÷27፤ኢሳ1÷17፤ሮሜ14÷19፤3ዮሐ1÷11 **34÷15** ኢዮ23÷10፤36÷7፤መዝ33÷18፤ሚል3÷16፤ዮሐ9÷31

[ወ]7 ወይም *የባሕርን ውሃ ይሰበስባል*
[0]34 እያንዳንዱ የዚህ መዝሙር ጥቅስ ተከታታይ ፊደላት ባሉት የዕብራይስጥ ሆህያት የሚጀመር ሲሆን ጅማሬው ወይም ጅማሬውና መጨረሻው ትርጒም የሚሰጥ ግጥም ነው::

ጆሮዎቹም ለጩኸታቸው ክፍት
ናቸው::
16መታሰቢያቸውን ከምድር ለማጥፋት፣
የእግዚአብሔር ፊት በክፉ አድራጊዎች
ላይ ነው::

17ጻድቃን ሲጮኹ፣ እግዚአብሔር
ይሰማቸዋል፤
ከመከራቸውም ሁሉ ያድናቸዋል::
18እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ
ነው፤
መንፈሳቸው የተሰበረውንም ያድናቸዋል::

19የጻድቅ መከራው ብዙ ነው፤
እግዚአብሔር ግን ከሁሉም ያድነዋል::
20ዐጥንቶቹን ሁሉ ይጠብቃል፤
ከእነርሱም አንድ አይሰበርም::

21ኀጢአተኞችን ክፋት ይገድላቸዋል፤
ጻድቃንን የሚጠሉ ይፈረድባቸዋል::
22እግዚአብሔር የባሪያዎቹን ነፍስ
ይቤዣል፤
እርሱንም መጠጊያ ያደረገ
አይፈረድበትም::

## መዝሙር 35

### የተጨቈነ ሰው ጸሎት

የዳዊት መዝሙር

1እግዚአብሔር ሆይ፤ የሚታገሉኝን
ታገላቸው፤
የሚዋጉኝንም ተዋጋቸው::
2ትልቁንና ትንሹን ጋሻ ያዝ፤
እኔንም ለመርዳት ተነሥ::
3በሚያሳድዱኝ ላይ፣
ጦርና ጭሬ ምዘዝ፤ʺ
ነፍሴንም፣ "የማድንሽ እኔ ነኝ" በላት::

4ሕይወቴን የሚፈልጓት፣
ይቅለሉ፣ ይዋረዱ፤
እኔን ለማጥፋት የሚያሤሩ፣
አፍረው ወደ ኋላቸው ይመለሱ::

5በነፋስ ፊት እንዳለ እብቅ ይሁኑ፤
የእግዚአብሔር መልአክ ያሳዳቸው::
6መንገዳቸው ጨለማና ድጥ ይሁን፤
የእግዚአብሔር መልአክ ያባርራቸው::
7ያለ ምክንያት ወጥመዳቸውን በስውር
አስቀምጠውብኛልና፤
ያለ ምክንያት ለነፍሴ ጕድጓድ
ቈፍረውላታል::
8ያልታሰበ ጥፋት ይምጣባቸው፤
የሰወሩት ወጥመድ ይያዛቸው፤
ይጠፉም ዘንድ ወደ ጕድጓዱ
ይውደቁ::
9ነፍሴም በእግዚአብሔር ደስ ይላታል፤
በማዳኑም ሐሤት ታደርጋለች::

34፥16 ዘፀ17፥14፤ ዘሌ17፥10፤መዝ9፥6፤ ኤር23፥30፤1ጴጥ 3፥10-12
34፥17 መዝ145፥19
34፥18 ዘዳ4፥7፤ መዝ51፥17፤109፥16፤ 119፥151፤145፥18፤1 47፥3፤ኢሳ50፥8፤ 61፥1
34፥19 ቍ17፤ኢዮ 5፥19፤መዝ25፥17፤2ጢሞ3፥11
34፥20 ዮሐ19፥36
34፥21 መዝ7፥9፤ 9፥16፤11፥5፤37፥20፤7 3፥27፤94፥23፤106፥43 ፤112፥10፤140፥11፤ምሳ14፥32፤24፥16
34፥22 ዘፀ6፥6፤ 15፥13፤መዝ2፥12፤ ሉቃ1፥68፤ራእ14፥3
35፥1 ዘፀ14፥14፤ 1ሳሙ24፥15
35፥2 ዘፍ50፥24፤ ኢዮ17፥3፤መዝ3፥3:7
35፥3 ዘኍ25፥7፤ ኢሱ8፥18፤መዝ27፥1
35፥4 መዝ25፥3፤ 38፥12፤40፥14፤69፥6: 19፤70፥2፤83፥17፤129 ፥5፤ኢሳ45፥16፤ኤር 4፥30፤ሚል2፥9
35፥5 ኢዮ13፥25፤ መዝ1፥4፤34፥7
35፥7 ኢዮ9፥31፤ 18፥8፤መዝ7፥4፥15፤55 ፥23
35፥8 መዝ7፥15፤ ኢሳ47፥11፤1ተሰ5፥3
35፥9 መዝ2፥11፤ 9፥14፤13፥5፤27፥1፤ ሉቃ1፥47
35፥10 ዘፀ9፥14፤ መዝ12፥5፤18፥17:31፤ 37፥14፤74፥21፤86፥1፤ 109፥16፤113፥5፤ 140፥12፤ኢሳ41፥17
35፥11 ዘፀ23፥1፤ ማቴ26፥60
35፥12 መዝ38፥20 ፤ 109፥5፤ምሳ17፥13 ፤ኤር18፥20
35፥13 2ሳሙ3፥31 ፤1ነገ20፥31፤ኢዮ30፥ 25፤መዝ30፥11፤69፥ 10:11፤109፥24
35፥14 መዝ38፥6፤ 42፥9፤43፥2
35፥15 ኢዮ16፥10፤ 31፥29
35፥16 ኢዮ16፥9፤ መዝ22፥7፤ማር9፥18፤ 10፥34፤ሐሥ7፥54
35፥17 መዝ6፥3፤ 22፥20፤22፥21፤57፥4፤ 58፥6
35፥18 መዝ22፥22 :25፤42፥4፤109፥30
35፥19 ቍ7፤መዝ 9፥13፤38፥19፤69፥4፤ ምሳ6፥13፤10፥10፤
ዮሐ15፥25 35፥20 መዝ38፥12፤55፥21፤ኤር9፥8፤
ሚክ6፥12 35፥21 ኢዮ16፥10፤መዝ40፥15፤70፥3፤
ሕዝ25፥3 35፥22 ዘፀ3፥7፤መዝ10፥1:14

10የሥራ አካላቴ እንዲህ ይልሃል፤
"እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ አንተ
ማን አለ?
ድኻውን ከእርሱ ከሚበረቱ፣
ችግረኛውንና ምስኪኑን ከቀማኞች
ታድናለህ"::

11ጨካኝ ምስክሮች ተነሡ፤
ስለማላውቀውም ነገር ጠየቁኝ::
12በበጎ ፈንታ ክፉ መለሱልኝ፤
ነፍሴንም ብቸኛ አደረጓት::
13እኔ ግን እነርሱ በታመሙ ጊዜ
ማቅ ለበስሁ፤
ነፍሴንም በጾም አደከምኋት፤
ጸሎቴም መልስ አጥቶ ወደ ጕያዬ
ተመለሰ::

14ለወዳጄ ወይም ለወንድሜ እንደ
ማደርግ፣
እየተንቈራጠጥሁ አለቀስሁ፤
ለእናቴም እንደማለቅስ፣
በሐዘን አንገቴን ደፋሁ::
15እነርሱ ግን እኔ ስሰናከል በእልልታ
ተሰበሰቡ፤
ግፈኞች በድንገት ተሰበሰቡብኝ፤
ያለ ዕረፍትም ቦጫጨቁኝ::
16እንደ ምናምንቴዎች አፌዙብኝ፤ʷ
ጥርሳቸውንም አፋጩብኝ::
17ጌታ ሆይ፤ እስከ መቼ ዝም ብለህ
ታያለህ?
ነፍሴን ከክፉ ሥራቸው፣
ብርቅ ሕይወቴን ከአንበሶች ታደጋት::
18በታላቅ ጉባኤ መካከል አመሰግንሃለሁ፤
ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበትም
አወድስሃለሁ::

19ከምድር ተነሥተው ጠላቶቼ የሆኑት፣
በላዬ ደስ አይበላቸው፤
እንዲያው የሚጠሉኝ፣
በዐይናቸው አይጣቀሱብኝ::
20የሰላም ንግግር ከአፋቸው አይወጣም፤
ዳሩ ግን በምድሪቱ በጸጥታ በሚኖሩት
ላይ፣
ነገር ይሸርባሉ::
21አፋቸውን አስፍተው ከፈቱብኝ፤
"እሰይ! እሰይ! በዐይናችን አየነው" አሉ::

22እግዚአብሔር ሆይ፤ ይህን አይተሃልና
ዝም አትበል፤
ጌታ ሆይ፤ ከእኔ አትራቅ::

ʺ3 ወይም ... መንገድ ዝጋ
ʷ16 ሰብዓ ሊቃናት እንዲሁ ሲሆን በዕብራይስጥ ግን ምናምንቴ ፌዘኞች ማለት ሊሆን ይችላል::

23አምላኬ፣ ጌታ ዬ፤ ለእኔ ለመሟገት
ተነሥ!
ልትከራከርልኝም ተንቀሳቀስ።
24እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤ በጽድቅህ
ፍረድልኝ፤
በእኔም ላይ ደስ አይበላቸው።
25በልባቸው፣ “እሰይ! ያሰብነው ተሳካ!
ዋጥ አደረግነውም” አይበሉ።
26በጭንቀቴ ደስ የሚላቸው፣
ይፈሩ፤ ግራም ይጋቡ፤
በእኔ ላይ ራሳቸውን ከፍ ከፍ
የሚያደርጉ፣
እፍረትንና ውርደትን ይከናነቡ።
27ፍትሕ ማግኘቴን የሚወዱ፣
እልል ይበሉ፤ ሐሤትም ያድርጉ፤
ዘወትርም፣ “የባርያው ሰላም ደስ
የሚለው፣
እግዚአብሔር ከፍ ከፍ ይበል!” ይበሉ።
28አንደበቴ ጽድቅህን፣
ምስጋናህንም ቀኑን ሙሉ ይናገራል።

## መዝሙር 36

### የኀጥኡ ክፋት፣ የእግዚአብሔር በጎነት

*ለመዘምራን አለቃ፤ የእግዚአብሔር ባሪያ የዳዊት መዝሙር*

1ክፉውን ሰው፣
በደል በልቡ ታናግረዋለች፤[የ]
እግዚአብሔርን መፍራት፣
በፊቱ የለም፤
2በደሉ ግልጽ ወጥቶ እንዳይጠላ፣
ራሱን በራሱ እጅግ ይሸነግላልና።
3ከአንደበቱ የሚወጣው የክፋትና የተንኰል ቃል ነው፤
ማስተዋልንና በጎ ማድረግን ትቶአል።
4በመኝታው ላይ ክፋትን ያውጠነጥናል፤
ራሱን በጎ ባልሆነ መንገድ ይመራል፤
ክፋትንም አያርቅም።

5እግዚአብሔር ሆይ፤ ምሕረትህ እስከ
ሰማያት ይደርሳል፤
ታማኝነትህም እስከ ጠፈር
ይመጥቃል።
6ጽድቅህ እንደ ታላላቅ ተራሮች፣
ፍርድህም እጅግ ጥልቅ ነው፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ሰውንም
እንስሳንም ታድናለህ።
7አምላክ ሆይ፤ ምሕረትህ እንዴት ክቡር
ነው!
የሰዎች ልጆች ሁሉ፣
በክንፎችህ ጥላ ሥር መጠጊያ ያገኛሉ።
8ከቤትህ ሲሳይ ይመገባሉ፤
ከበረከትህም ወንዝ ይጠጣሉ።
9የሕይወት ምንጭ ከአንተ ዘንድ ነውና፤
በብርሃንህም ብርሃንን እናያለን።
10ለሚያውቁህ ምሕረትህ፣
ልባቸውም ለቀና ጽድቅህ ዘወትር
አይቋረጥባቸው።
11የትዕቢተኛ እግር በላዩ አይምጣ፤
የክፉውም ሰው እጅ አያሳደኝ።
12ክፉ አድራጊዎች እንዴት እንደ ወደቁና
እንደ ተጋደሙ፣
ቀልቀልም እንደ ተወረወሩና
መነሣት እንደማይችሉ ተመልከት!

## መዝሙር 37[ዶ]

### የጻድቁና የክፉው ዕጣ ፈንታ

*የዳዊት መዝሙር*

1ዐመፀኞችን በማየት አትሸበር፤
በክፉ አድራጊዎችም አትቅና፤
2እንደ ሣር ፈጥነው ይደርቃሉና፤
እንደ ለምለም ቅጠልም ይጠወልጋሉ።

3በእግዚአብሔር ታመን፤ መልካምንም
አድርግ፤
በምድሪቱ ተቀመጥ፤ ዘና ብለህ ተሰማራ።
4በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ፤
የልብህንም መሻት ይሰጥሃል።
5መንገድህን ለእግዚአብሔር ዐደራ ስጥ፤
በእርሱ ታመን፤ እርሱም
ያከናውንልሃል፤
6ጽድቅህን እንደ ብርሃን፣
ያንተን ፍትሕ እንደ ቀትር ፀሓይ
ያበራዋል።
7በእግዚአብሔር ፊት ጸጥ በል፤
በትዕግሥትም ተጠባበቀው፤
መንገዱ በተቃናለት፣
ክፋትንም በሚሸርብ ሰው ልብህ
አይሸበር።

8ከንዴት ተቈጠብ፤ ቍጣንም ተወው፤
ወደ እኩይ ተግባር እንዳይመራህ
አትከፋ።
9ክፉ ሰዎች ይጠፋሉና፤
እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉ ግን
ምድርን ይወርሳሉ።

10ለአፍታ እንጂ፣ ክፉ ሰው አይዘልቅም፤
ስፍራውንም ብታስስ አታገኘውም።

35፥23 1ሳሙ24፥15፤ መዝ7፥6፤17፥13፤80፥2
35፥24 መዝ22፥17
35፥25 ቍ21፤ምዘ 124፥3፤ምሳ1፥12፤ሰቆ 2፥16
35፥26 ኢዮ8፥22፤ 19፥5፤መዝ4፥1፤22፥17 ፤38፥16፤109፥29፤ ሚክ7፥10
35፥26 ኢዮ8፥22፤ 19፥5፤መዝ4፥1፤22፥ 17፤38፥16፤109፥29፤ ሚክ7፥10
35፥27 ኢዮ17፥3፤ መዝ9፥4፤20፥5፤33፥3፤ መዝ147፥11፤149፥4
35፥28 መዝ5፥8፤ 51፥14፤71፥15፡24፤72 ፥15
36፥1 ኢዮ21፥6፤ 23፥15፤ኤር2፥19፤36፥ 16፡24፤ሮሜ3፥18
36፥2 ዘዳ29፥19
36፥3 ኢዮ5፥13፤ መዝ5፥6፡9፤10፥7፤43፥ 1፤94፥8፤144፥8፡11፤ኢሳ44፥20፤ኤር4፥22 ፤13፥23፤አሞ3፥10
36፥4 መዝ52፥3፤ ምሳ4፥16፤ኢሳ65፥2፤ ሮሜ12፥9
36፥5 መዝ57፥10፤ 71፥19፤89፥1፡2፤103፥ 11፤108፥4፤119፥90
36፥6 ዘፍ1፥2፤7፥ 11፤ነህ9፥6፤መዝ5፥8፤6 8፥15፤104፥14፤ 145፥16
36፥7 ሩት2፥12፤ መዝ6፥4፤17፥8፤57፥1 ፤91፥4
36፥8 ኢዮ20፥17፤ መዝ23፥2፤63፥5፤65፥4፤ ኢሳ25፥6፤ኤር31፥12፡ 14፤ራእ22፥1
36፥9 መዝ4፥6፤ 27፥1፤76፥4፤87፥7፤ 104፥2፤ምሳ10፥11፤ 16፥22፤ኢሳ2፥5፤9፥2፤ 60፥1፡19፤ኤር2፥13፤ ዮሐ1፥4፤1ጴጥ2፥9
36፥10 መዝ7፥10፤ 11፥2፤94፥15፤125፥4፤ ኤር9፥24፤22፥16፤ 31፥3
36፥11 መዝ71፥4፤ 140፥4
36፥12 መዝ18፥38
37፥1 መዝ73፥3፤ ምሳ3፥31፤23፥17-18፤ 24፥19
37፥2 ቍ38፤2ነገ 19፥26፤ኢዮ14፥2፤ መዝ90፥6፤92፥7፤ 102፥4፤ኢሳ40፥7፤ ያዕ1፥10
37፥3 ዘዳ30፥20፤ ሕዝ34፥14፤ዮሐ10፥9
37፥4 ኢዮ7፥6፤ 27፥10፤መዝ21፥2፤14 5፥19፤ማቴ6፥33

37፥5 መዝ4፥5 37፥6 ኢዮ11፥17፤መዝ18፥24፤103፥17፤ 112፥3
37፥7 ቍ1፤ዘፀ14፥14፤መዝ21፥11፤26፥10፤27፥14፤ 40፥1፤119፥150፤130፥5፤ኢሳ38፥13፤41፥1፤ኤር12፥1፤ዕን3፥16፤ ኤር12፥1፤ዕን3፥16፤ሮሜ8፥25 37፥8 ቍ1፤ኤፌ4፥31፤ቈላ3፥8
37፥9 ቍ22፤መዝ25፥13፤31፥22፤101፥8፤ 118፥10፤ምሳ2፥22፤ ኢሳ25፥9፤26፥8፤40፥31፤49፥8፡23፤51፥5፤57፥13፤ማቴ5፥5
37፥10 ኢዮ7፥10፤ሕዝ27፥36

[የ]1 ወይም ... *ኀጢአት ከኀጥእ ይመነጫል*
[ዶ]ም37 የዚህ መዝሙር እያንዳንዱ ጥቅስ ተከታታይ ፊደላት ባሉት የዕብራይስጥ ሆህያት የሚጀምር ሲሆን ጅማሬው ወይም ጅማሬውና መጨረሻው ትርጒም የሚሰጥ ግጥም ነው።

11 ገሮች ግን ምድርን ይወርሳሉ፤
በታላቅ ሰላምም ሐሤት ያደርጋሉ።

12 ክፉዎች በጻድቃን ላይ ያሤራሉ፤
ጥርሳቸውንም ያፏጩባቸዋል።
13 እግዚአብሔር ግን ይሥቅባቸዋል፤
ቀናቸው እንደ ደረሰ ያውቃልና።

14 ድኾችንና ችግረኞችን ለመጣል፣
አካሄዳቸው ቀና የሆነውንም
ለመግደል፣
ክፉዎች ሰይፋቸውን መዘዙ፤
ቀስታቸውንም ገተሩ።
15 ሰይፋቸው የገዛ ልባቸውን ይወጋል፤
ቀስታቸውም ይሰበራል።

16 የጻድቅ ጥቂት ሀብት፣
ከክፉዎች ብዙ ጥሪት ይበልጣል።
17 የክፉዎች ክንድ ይሰበራልና፤
ጻድቃንን ግን *እግዚአብሔር* ደግፎ
ይይዛቸዋል።

18 *እግዚአብሔር* የንጹሐንን የሕይወት
ዘመን ያውቃል፤
ርስታቸውም ለዘላለም ይኖራል።
19 በክፉ ጊዜ ዕንገት አይደፋም፤
በራብ ዘመንም ይጠግባሉ።
20 ክፉዎች ግን ይጠፋሉ፤
*የእግዚአብሔር* ጠላቶች እንደ መስክ
ውበት ይሆናሉ፤
ይጠፋሉ፤ እንደ ጢስም ተነው ይጠፋሉ።

21 ኀጢአተኛ ይበደራል፤ መልሶም
አይከፍልም፤
ጻድቅ ግን ይቸራል።
22 *እግዚአብሔር* የባረካቸው ምድርን
ይወርሳሉ፤
እርሱ የሚረግማቸው ግን ይጠፋሉ።

23 የሰው አካሄድ *በእግዚአብሔር* ይጸናል፤
በመንገዱ ደስ ይለዋል።
24 ቢሰናከልም አይወድቅም፤
*እግዚአብሔር* በእጁ ደግፎ ይይዘዋልና።

25 ጐልማሳ ነበርሁ፤ አሁን አርጅቻለሁ፤
ነገር ግን ጻድቅ ሲጣል፣
ዘሩም እንጀራ ሲለምን አላየሁም።

26 ሁልጊዜ ቸር ነው፤ ያበድራልም፤
ልጆቹም የተባረኩ ይሆናሉ።

27 ከክፉ ራቅ፤ መልካሙንም አድርግ፤
ለዘላለምም ትኖራለህ።
28 *እግዚአብሔር* ፍትሕን ይወዳልና፤
ታማኞቹንም አይጥልም፤

ለዘላለምም ይጠብቃቸዋል፤
የኀጢአተኛው ዘር ግን ይጠፋል።
29 ጻድቃን ምድርን ይወርሳሉ፤
በእርሷም ለዘላለም ይኖራሉ።

30 የጻድቅ አፍ ጥበብን ይናገራል፤
አንደበቱም ፍትሐዊ ነገር ያወራል።
31 የአምላኩ ሕግ በልቡ አለ፤
አካሄዱም አይወላገድም።

32 ክፉዎች ጻድቁን ይከታተሉታል፤
ሊገድሉትም ይሻሉ።
33 *እግዚአብሔር* ግን በእጃቸው
አይጥለውም፤
ፍርድ ፊት ሲቀርብም አሳልፎ
አይሰጠውም።
34 *እግዚአብሔርን* ደጅ ጥና፤
*መንገዱንም* ጠብቅ፤
ምድሪቱን ትወርስ ዘንድ ከፍ ከፍ
ያደርግሃል፤
ክፉዎችም ሲጠፉ ታያለህ።

35 ክፉና ጨካኙን ሰው፣
እንደ ሊባኖስ ዝግባ ለምልሞ አየሁት፤
36 *ዳግመኛ* በዚያ ሳልፍ፣ እነሆ፣ በቦታው
አልነበረም፤
ብፈልገውም አልተገኘም።

37 ንጹሐንን ልብ በል፤ ቅኑንም አስተውል፤
የሰላም ሰው ተስፋ አለውና።[ጀ]
38 ኀጢአተኞች ግን በአንድነት ይጠፋሉ፤
የክፉዎችም ዘር[ገ] ይወገዳል።

39 የጻድቃን ድነት *ከእግዚአብሔር* ዘንድ
ነው፤
በመከራ ጊዜም መጠጊያቸው እርሱ
ነው።
40 *እግዚአብሔር* ይረዳቸዋል፤
ይታደጋቸዋልም፤
ከክፉዎች እጅ ነጥቆ ያወጣቸዋል፤
እርሱን መጠጊያ አድርገዋልና
ያድናቸዋል።

## መዝሙር 38

### የጭንቅ ሰዓት ጸሎት

የዳዊት መዝሙር፤ ለመታሰቢያ

1 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ በቍጣህ አትገሥጸኝ፤
በመዓትህም አትቅጣኝ።
2 ፍላጻዎችህ ወግተውኛልና፤
እጅህም ተጭናኛለች።
3 ከቍጣህ የተነሣ ሰውነቴ ጤና አጥቶአል፤
ከኀጢአቴም የተነሣ ዐጥንቶቼ ሰላም
የላቸውም።
4 በደሌ ውጦኛል፤
እንደ ከባድ ሸክምም ተጭኖኛል።

37፥11 ዘሌ26፥6፤ ዘኍ6፥26፤14፥24፤ ማቴ5፥5
37፥12 ኢዮ16፥9፤ መዝ2፥1፤31፥12፤ 35፥16፤112፥10
37፥13 1ሳሙ26፥10፤ሕዝ12፥23
37፥14 መዝ11፥2፤ 22፥20፤35፥10
37፥15 1ሳሙ2፥4፤ መዝ9፥16፤46፥9፤ኤር 49፥35
37፥16 ምሳ15፥16፤ 16፥8
37፥17 ኢዮ38፥15፤ መዝ10፥15፤41፥12፤1 40፥12፤145፥14፤ 146፥7
37፥18 ቍ27፥29፤ ኢዮ23፥10፤መዝ 44፥21
37፥20 መዝ34፥21 ፤68፥2፤102፥3፤ኢሳ 51፥6
37፥21 ዘሌ25፥35፤ መዝ112፥5
37፥22 ቍ9፤ኢዮ 5፥3
37፥23 ዘኍ14፥8፤ ኢዮ11፥15፤መዝ 7፥9፤66፥9፤147፥11
37፥24 2ዜና9፥8፤ መዝ 13፥4፤27፥2፤ 38፥17፤41፥12፤55፥22 ፤119፥165፤145፥14፤ ምሳ3፥23፤10፥9
37፥25 ቍ28፤ዘፍ 51፥1፤መዝ111፥5፤14 5፥15፤ማር10፥46፤ዕብ 13፥5
37፥26 ዘሌ25፥35፤ ዘዳ28፥4፤መዝ112፥2
37፥27 ዘኍ24፥21 ፤መዝ34፥14፤3ዮሐ 1፥11
37፥28 ዘፍ17፥14፤ ዘዳ7፥6፤32፥26፤መዝ 18፥25፤97፥10፤ምሳ 2፥22
37፥29 ቍ9፤ምሳ 2፥21፤ኢሳ34፥17
37፥30 መዝ49፥3፤ ምሳ10፥13
37፥31 ዘዳ6፥6፤ 32፥35፤ኢዮ22፥22
37፥32 መዝ10፥8፤ 11፥5
37፥33 ኢዮ32፥3፤ መዝ34፥22፤79፥11፤ 2ጴጥ2፥9
37፥34 ቍ9፤መዝ 18፥21፤27፥14፤52፥6
37፥35 ኢዮ5፥3
37፥36 ቍ10፤ምሳ 12፥7፤ኢሳ41፥12፤ዳን 11፥9
37፥37 ቍ18፤ዘፍ 6፥9፤መዝ11፥7፤18፥25 ፤ኢሳ57፥1-2
37፥38 ቍ2፥9፤መዝ 1፥1፤73፥19 37፥39 መዝ3፥8፤9፥9 37፥40 1ዜና5፥20፤መዝ 2፥12፤18፥48፤20፥2፤34፥7 38፥1 መዝ6፥1 38፥2 ኢዮ6፥4 38፥3 ኢዮ33፥19፤ምሳ3፥8፤ኢሳ4፥22፤66፥14 38፥4 ዘኍ11፥14፤ ዕዝ9፥6፤መዝ40፥12፤65፥3፤ሉቃ11፥46

[ጀ] 37 ወይም *ዘር ይወጣለታል* [ገ] 38 ወይም *ትውልድ*

5 ከንዝህላልነቴ የተነሣ፣
ቍስሌ ሸተተ፤ መገለም፤
6 ዐንገቴን ደፋሁ፤ ጐበጥሁም፤
ቀኑንም ሙሉ በትካዜ ተመላለስሁ።
7 ወገቤ እንደ እሳት ነዶአል፤
ሰውነቴም ጤና የለውም።
8 እጅግ ዝያለሁ፤ ፈጽሞም ደቅቄአለሁ፤
ከልቤም መታወክ የተነሣ እጮኻለሁ።

9 ጌታ ሆይ፤ ምኞቴ ሁሉ በፊትህ
ግልጽ ነው፤
ጭንቀቴም ከአንተ የተሰወረ አይደለም።
10 ልቤ በኀይል ይመታል፤ ጕልበት
ከድቶኛል፤
የዐይኔም ብርሃን ጠፍቶአል።
11 ከቍስሌ የተነሣ ወዳጆቼም
ባልንጀሮቼም ሸሹኝ፤
ጎረቤቶቼም ርቀው ቆሙ።
12 ሕይወቴን ለማጥፋት የሚሹ ወጥመድ
ዘረጉብኝ፤
ሊጐዱኝ የሚፈልጉ ሊያጠፉኝ ዛቱ፤
ቀኑንም ሙሉ ተንኰል ይሸርባሉ።

13 እኔ ግን እንደማይሰማ ደንቈሮ፣
አፉንም መክፈት እንደማይችል ዲዳ
ሆንሁ።
14 በእርግጥም ጆሮው እንደማይሰማ፣
አንደበቱም መልስ መስጠት እንደ
ማይችል ሰው ሆንሁ።
15 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ በተስፋ
እጠብቅሃለሁ፤
ጌታ አምላኬ ሆይ፤ አንተ መልስ
ትሰጠኛለህ።
16 እኔ፣ “ጠላቶቼ በእኔ ላይ ደስ
አይበላቸው፤
እግሬም ሲንሸራተት፣ በላዬ
አይኵራሩብኝ” ብያለሁና።

17 ልወድቅ ተቃርቤአለሁ፤
ከሥቃዬም ከቶ አልተላቀቅሁም።
18 በደሌን እናዘዛለሁ፤
ኀጢአቴም አውካኛለች።
19 ብርቱዎች ጠላቶቼ ብዙ ናቸው፤
ያለ ምክንያት የሚጠሉኝም ስፍር
ቍጥር የላቸውም።
20 መልካሙን ስለ ተከተልሁ፣
በበጎ ፈንታ ክፉ የሚመልሱልኝ
ጠሉኝ።

21 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ አትተወኝ፤
አምላኬ ሆይ፤ ከእኔ አትራቅ።
22 ጌታዬ መድኀኔ ሆይ፤
እኔን ለመርዳት ፍጠን።

**38፥5** ቍ11፤ኢዮ 19፥17፤መዝ69፥5፤147፥3፤ምሳ5፥23፤12፥23፤13፥16፤መክ10፥3
**38፥6** መዝ35፥14፤57፥6፤145፥14፤146፥8
**38፥7** ቍ3፤ኢዮ 14፥22
**38፥8** መዝ6፥3፡6፤22፥1፤34፥18፤ምሳ 5፥11፤17፥22
**38፥9** ኢዮ3፥24፤መዝ119፥20፤143፥7
**38፥10** ኢዮ37፥1፤መዝ6፥7፤19፥8፤31፥10፤88፥9
**38፥11** ቍ5
**38፥12** መዝ31፥4፤35፥4፡20፤41፥5፤140፥5፤141፥9
**38፥13** መዝ115፥6፤135፥17፤ኢሳ43፥8፤ማር7፥37
**38፥15** መዝ17፥6፤27፥14
**38፥16** ዘዳ32፥35፤መዝ22፥17
**38፥17** ቍ7፤ኢዮ 6፥10፤መዝ37፥24
**38፥18** ዘሌ26፥40
**38፥19** መዝ18፥17፤25፥19፤35፥19
**38፥20** ዘፍ44፥4፤መዝ54፥5፤59፥10፤119፥23፤1ዮሐ3፥12
**38፥21** መዝ10፥1፤22፥11፤27፥9፤35፥22፤71፥12፡18፤119፥8
**38፥22** 1ዜና16፥35፤መዝ22፥19፤40፥13
**39፥1** 1ነገ2፥4፤ኢዮ 1፥22፤6፥24፤መዝ34፥13፤119፥9፡59፤ምሳ20፥11፤ያዕ1፥26፤3፥2
**39፥2** ቍ9፤ኢዮ 31፥34፤መዝ6፥3፤25፥17፤31፥10፤77፥4
**39፥3** መዝ1፥2፤48፥9፤77፥12፤119፥15፤ኤር5፥14፤20፥9፤23፥29፤ሉቃ24፥32
**39፥4** ዘፍ47፥9፤ኢዮ7፥7፤14፥2፡5
**39፥5** ኢዮ7፥7፤10፥20፤መዝ62፥9፤89፥45፤102፥23
**39፥6** ኢዮ8፥9፤27፥17፤መዝ102፥11፤127፥2፤መክ6፥12፤ሉቃ12፥20፤ያዕ1፥11፤4፥14
**39፥7** መዝ9፥18፤25፥5
**39፥8** ዘዳ28፥37፤መዝ6፥4፤32፥1፤51፥1፡14፤69፥7፤79፥4፤ኢሳ 43፥28፤53፥5፡8፡10፤ዳን9፥16
**39፥9** ቍ2፤መዝ 38፥13፤ኢሳ38፥15
**39፥10** ዘፀ9፥3፤2ዜና21፥14፤ሕዝ

## መዝሙር 39
### ታላቅ እግዚአብሔር - ታናሽ ሰው

*ለመዘምራን አለቃ፣ ለኤዶታም፤ የዳዊት መዝሙር*

1 እኔ፣ “በአንደበቴ እንዳልበድል፣
መንገዴን እጠብቃለሁ፤
ክፉዎችም በእኔ ዘንድ እስካሉ ድረስ፣
ልጓም በአፌ አስገባለሁ” አልሁ።
2 እንደ ዲዳ ዝም አልሁ፤
ለበጎ ነገር እንኳ አፌን ዘጋሁ፤
ሆኖም ጭንቀቴ ባሰ።
3 ልቤ በውስጤ ጋለ፤
በማሰላሰልበትም ጊዜ እሳቱ ነደደ፤
ከዚያም በአንደበቴ እንዲህ ተናገርሁ፤

4 “*እግዚአብሔር* ሆይ፤ የሕይወቴን ፍጻሜ፣
የዘመኔንም ቍጥር አስታውቀኝ፤
አላፊ ጠፊ መሆኑንም ልረዳ።
5 እነሆ፤ ዘመኔን በስንዝር ለክተህ
አስቀመጥህ፤
ዕድሜዬም በፊትህ እንደ ኢምንት
ነው፤
በእርግጥ የሰው ሁሉ ሕይወት ተን
ነው። ሴላ
6 ሰው የጥላ ውልብታ ነው፤
በከንቱም ይታወካል፤
ለማን እንደሚሆን ሳያውቅ ሀብት
ንብረት ያከማቻል።

7 “ጌታ ሆይ፤ አሁንስ ወደ ማን
ልመልከት?
ተስፋዬ በአንተ ላይ ነው።
8 ከኀጢአቴ ሁሉ አድነኝ፤
የሰነፎች መሣለቂያ አታድርገኝ።
9 ይህን ያደረግህ አንተ ነህና፣
ዝም እላለሁ፤ አፌንም አልከፍትም።
10 ክንድህን አንሣልኝ፤
ከእጅህ ምት የተነሣ ደክሜአለሁና።
11 ሰዎችን ስለ ኀጢአታቸው ለመቅጣት
ትገሥጻቸዋለህ፤
ሀብታቸውንም ብል እንደ በላው
ታደርጋለህ፤
በእርግጥ ሰው ሁሉ ተን ብቻ ነው።
ሴላ

12 “*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ጸሎቴን ስማ፤
ጩኸቴን አድምጥ፤
ልቅሶዬንም ቸል አትበል፤
በአንተ ፊት እኔ መጻተኛ ነኝና፤
እንደ አባቶቼም እንግዳ ነኝ።
13 ሳለመመለስ ከመሰናበቴ በፊት፣
ደግመኛ ደስ ይለኝ ዘንድ ዐይንህን
ከላዬ አንሣ።

7፥9፤24፥16 **39፥11** ዘዳ28፥20፤ኢዮ7፥7፤13፥28፤መዝ90፥7፤94፥10፤ኢሳ26፥16፤51፥8፤66፥15፤ሕዝ5፥15፤ሉቃ12፥33፤ያዕ5፥2፤2ጴጥ2፥16 **39፥12** ዘፍ23፥4፤47፥9፤ዘሌ25፥23፤ዘዳ1፥45፤2ነገ20፥5፤1ዜና29፥15፤መዝ17፥1፤ዕብ11፥13 **39፥13** ኢዮ10፥21

## *መዝሙር* 40
## የምስጋናና የርዳታ ልመና ጸሎት

40፥13-17 *ተጓ ምብ-መዝ*70፥1-5

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር*

[1]*እግዚአብሔርን* ደጅ ጠናሁት፤
እርሱም ዘንበል አለልኝ፤ ጩኸቴንም
ሰማ።
[2]ከሚውጥ ጒድጓድ፣
ከሚያዘቅጥ ማጥ አወጣኝ፤
እግሮቼን በዐለት ላይ አቆመ፤
አካሄዴንም አጸና።
[3]ለአምላካችን የሚሆን ውዳሴ፣
አዲስ ዝማሬን በአፌ ላይ አኖረ፤
ብዙዎች ያያሉ፤ ይፈራሉም፤
*በእግዚአብሔር* ይታመናሉ።

[4]*እግዚአብሔርን* መታመኛው ያደረገ፣
ወደ ትዕቢተኞች የማይመለከት፣
የሐሰት አማልክትን[ጠ] ወደሚከተሉት
የማያይ፣
ሰው ብፁዕ ነው።
[5]*እግዚአብሔር* አምላኬ ሆይ፤
አንተ ያደረግኸው ድንቅ ነገር ብዙ
ነው፤
ለእኛ ያቀድኸውን፣
ሊዘረዝርልህ የሚችል ማንም የለም፤
ላውራው ልናገረው ብል፣
ስፍር ቍጥር አይኖረውም።

[6]መሥዋዕትንና ቍርባንን አልፈለግህም፤
ጆሮቼን ግን ከፈትህ፤[ጨ]
የሚቃጠል መሥዋዕትን፣
የኀጢአትንም መሥዋዕት አልሻህም።
[7]እኔም እንዲህ አልሁ፤ "እነሆ፤
መጥቻለሁ፤
ስለ እኔ በመጽሐፍ ተጽፎአል፤
[8]አምላኬ ሆይ፤ ፈቃድህን ላደርግ እሻለሁ፤
ሕግህም በልቤ ውስጥ አለ።"
[9]በታላቅ ጉባኤ ውስጥ ጽድቅን አበሥርሁ፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ
እንደምታውቀው፣
ከንፈሮቼን አልገጠምሁም።
[10]ጽድቅህን በልቤ አልሸሸግሁም፤
ታማኝነትህንና ማዳንህን እናገራለሁ፤
ምሕረትህንና እውነትህን፣
ከታላቅ ጉባኤ አልደበቅሁም።

[11]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ምሕረትህን
አትንፈገኝ፤
ቸርነትህና እውነትህ ዘወትር
ይጠብቁኝ፤
[12]ስፍር ቍጥር የሌለው ክፋት ከቦኛልና፤
የኀጢአቴ ብዛት ስለ ያዘኝ ማየት
ተስኖኛል፤
ከራሴ ጠጒር ይልቅ በዝቶአል፤
ልቤም ከድቶኛል።

[13]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ታድነኝ ዘንድ
ፈቃድህ ይሁን፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ እኔን ለመርዳት
ፍጠን።
[14]ነፍሴን ለመንጠቅ የሚፈልጉ፣
ይፈሩ፤ ይዋረዱም፤
ጒዳቴንም የሚሹ፣
ተዋርደው በመጡበት ይመለሱ።
[15]በእኔ ላይ፣ "እሰይ! እሰይ!" የሚሉ፣
በራሳቸው እፍረት ይደንግጡ።
[16]አንተን የሚፈልጉ ሁሉ ግን፣
ሐሤት ያድርጉ፤ በአንተም ደስ
ይበላቸው፤
ዘወትር የአንተን ማዳን የሚወዱ፣
"*እግዚአብሔር* ከፍ ከፍ ይበል"
ይበሉ።

[17]እኔ ድኻና ችግረኛ ነኝ፤
ጌታ ግን ያስብልኛል።
አንተ ረዳቴና አዳኜ ነህ፤
አምላኬ ሆይ፤ አትዘግይ።

## *መዝሙር* 41
## የሕመምተኛና የብቸኛ ሰው ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር*

[1]ለድኾች የሚያስብ ሰው ምስጉን ነው፤
እርሱንም *እግዚአብሔር* በክፉ ቀን
ይታደገዋል።
[2]*እግዚአብሔር* ይጠብቀዋል፤ በሕይወትም
ያኖረዋል፤
በምድርም ላይ ይባርከዋል፤
ለጠላቶቹም ምኞትም አሳልፎ
አይሰጠውም።
[3]ታሞ ባለበት ዐልጋ ላይ *እግዚአብሔር*
ይንከባከበዋል፤
በበሽታውም ጊዜ መኝታውን
ያነጥፍለታል።

[4]እኔም፣ "*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ምሕረት
አድርግልኝ፤
አንተን በድያለሁና ነፍሴን ፈውሳት"
አልሁ።
[5]ጠላቶቼ በክፋት በመናገር፣
"የሚሞተው መቼ ነው? ስሙስ
የሚደመሰሰው ምን ቀን ነው?"
ይላሉ።
[6]ሊጠይቀኝ የሚመጣ ቢኖር፣
በልቡ ስድብ እያጠራቀመ፣ ከዐንገት
በላይ ይናገራል፤

**40፥1** *መዝ*6፥9፤ 31፥22፤34፥15፤37፥7፤ 116፥1፤145፥19
**40፥2** *ኢዮ*9፥31፤ 30፥19፤*መዝ*7፥15፤27፥ 5፤31፥8፤69፥14
**40፥3** *ዘፀ*14፥31፤*መዝ* 28፥7፤52፥6፤64፥9፤96፥ 1፤*ራእ*5፥9
**40፥4** *ዘዳ*31፥20፤ *መዝ*4፥2፤26፥1፤34፥8፤ 84፥12፤101፥5፤138፥6 ፤*ምሳ*3፥34፤16፥5፤*ኢሳ* 65፥5፤1*ጴጥ*5፥5
**40፥5** *ዘዳ*4፥34፤ *መዝ* 71፥15፤75፥1፤ 105፥5፤136፥4፤ 139፥17፥18
**40፥6** *ዘፀ*21፥6፤1*ሳሙ* 15፥22፤*መዝ*50፥8፤ 51፥16፤*ኢሳ*1፥11፤ *ኤር* 6፥20፤*ሆሴ*6፥6፤ *አሞ*5፥22
**40፥7** *ኢዮ*19፥23፤ *ኤር*36፥2፤45፥1፤*ሕዝ* 2፥9፤*ዘካ*5፥1
**40፥8** *ዘዳ*6፥6፤*ኢዮ* 22፥22፤*ማቴ*26፥39፤ *ሮሜ*7፥22፤*ዕብ*10፥5-7
**40፥9** *ኢሱ*22፥22፤ *መዝ*22፥25፥31
**40፥10** *መዝ*22፥22 ፤89፥1
**40፥11** *መዝ*26፥3፤ 61፥7፤*ምሳ*20፥28፤*ዘካ*1 ፥12
**40፥12** *መዝ*25፥17 ፤38፥4፤65፥3፤69፥4፤7 3፥26
**40፥13** *መዝ*22፥19 ፤38፥22
**40፥14** 1*ሳሙ*20፥1 ፤*አስ*9፥2፤*መዝ*35፥4፥ 26
**40፥15** *መዝ*35፥21
**40፥16** *ዘዳ*4፥29፤ 1*ዜና*28፥9፤*መዝ*9፥2፥1 0፤35፥27፤119፥2
**40፥17** *መዝ*18፥2፤ 20፥2፤86፥1፤109፥22፤ 119፥60፤144፥3
**41፥1** *ዘዳ*14፥29፤ *ኢዮ*24፥4፤25፥17
**41፥2** *ዘዳ*6፥24፤*ዕዝ* 9፥9፤*መዝ*12፥5፤32፥7፤ 37፥22፤71፥20፤119፥8 8፥159፤138፥7፤143፥1 1
**41፥3** 2*ሳሙ*13፥5 ፤2*ነገ*1፥4፤*መዝ*6፥6
**41፥4** *ዘዳ*32፥39 ፤6፥2፤9፥13፤51፥4
**41፥5** *መዝ*38፥12
**41፥6** *ዘሌ*19፥16፤ *መዝ*12፥2፤101፥7፤ *ምሳ*26፥24፤*ማቴ*5፥11
**41፥7** *መዝ*71፥10
**41፥8** 2*ነገ*1፥4

[ጠ]4 ወይም *ሐሰትን ወደሚከተሉት* ተብሎ መተርጐም ይቻላል።
[ጨ]6 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ግን፣ *አካልን ግን አዘጋጀህልኝ* ይላል።

ወጥቶም ወሬ ይነዛል።
7ጠላቶቼ ሁሉ ግንባር ፈጥረው
ይንሾካሾኩብኛል፤
እንዲህ እያሉም፣
የከፋ ነገር በላዬ ያውጠነጥናሉ፤
8“ክፉ ደዌ ይዞታል፤
ከእንግዲህም ከተኛበት አይነሣም።”
9እንጀራዬን ተካፍሎኝ የበላ፣
የምተማመንበትም የቅርብ ወዳጄ፣
በእኔ ላይ ተረከዙን አነሣ።
10እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ግን ምሕረት
አድርግልኝ፤
የእጃቸውን እንድከፍላቸው አስነሣኝ።
11ጠላቴ በላዬ ድል አላገኘምና፣
እንደ ወደድኸኝ በዚህ አወቅሁ።
12ስለ ጭንቀቴ ደግፈህ ይዘኸኛል፤
በፊትህም ለዘላለም ታኖረኛለህ።
13የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር፣
ከዘላለም እስከ ዘላለም የተባረከ ይሁን፤
አሜን፤ አሜን።

## ሁለተኛ መጽሐፍ
## ከመዝሙር 42-72

### መዝሙር 42[ጸ]
### በስደት ላይ ያለ ሌዋዊ ልቅሶ

ለመዘምራን አለቃ፤ የቆሬ ልጆች ትምህርት።

1ዋላ የምንጭ ውሃ እንደምትናፍቅ፣
አምላክ ሆይ፤ ነፍሴም እንዲሁ አንተን
ትናፍቃለች።
2ነፍሴ አምላክን፣ ሕያው አምላክን
ተጠማች፤
መቼ ደርሼ ነው የአምላክን ፊት
የማየው?
3ሰዎች ቀኑን ሙሉ፣
“አምላክህ የት አለ?” ባሉኝ ቍጥር፣
እንባዬ ቀንና ሌሊት፣
ምግብ ሆነኝ።
4ነፍሴ በውስጤ እየፈሰሰች፣
እነዚህን ነገሮች አስታወስሁኝ፤
ታላቅ ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ቤት እየመራ
ሁ፣
በእልልታና በምስጋና መዝሙር፣
በአእላፍ ሕዝብ መካከል፣
እንዴት ከሕዝቡ ጋር እሄድ እንደ
ነበር ትዝ አለኝ።
5ነፍሴ ሆይ፤ ለምን ትተክዢያለሽ?
ለምንስ በውስጤ ትታወኪያለሽ?
ተስፋሽን በአምላክ ላይ አድርጊ፤
አዳኜና 6አምላኬን፣
ገና አመሰግነዋለሁና።
ነፍሴ በውስጤ ተክዛለች፤
ስለዚህ በዮርዳኖስ ምድር፣
በአርሞንኤም ከፍታ፣
በሚዛር ተራራ አስብሃለሁ።
7በፏፏቴህ ማስገምገም፣
አንዱ ጥልቅ ሌላውን ጥልቅ ይጣራል፤
ማዕበልህና ሞገድህ ሁሉ፣
ሙሉ በሙሉ አጥለቀለቀኝ።
8እግዚአብሔር ምሕረቱን በቀን ያዝዛል፤
ዝማሬውም በሌሊት በእኔ ዘንድ አለ፤
ይህም ለሕይወቴ አምላክ የማቀርበው
ጸሎት ነው።
9እግዚአብሔር ዐለቴን፣
“ለምን ረሳኸኝ?
ጠላትስ እያስጨነቀኝ፣
ለምን በሐዘን እመላለሳለሁ?”
እለዋለሁ።
10ጠላቶቼ ቀኑን ሙሉ፣
“አምላክህ የት አለ?” እያሉ፣
በነገር ጠዘጠዙኝ፣
ዐጥንቴም ደቀቀ።
11ነፍሴ ሆይ፤ ለምን ትተክዢያለሽ?
ለምንስ በውስጤ ትታወኪያለሽ?
ተስፋሽን በአምላክ ላይ አድርጊ፣
አዳኜና አምላኬን፣
ገና አመሰግነዋለሁ።

### መዝሙር 43[ጸ]
### በስደት ላይ ያለ ሌዋዊ ልቅሶ

1አምላክ ሆይ፤ ፍረድልኝ፤
ከጽድቅ ከራቀ ሕዝብ ጋር ተሟገትልኝ፤
ከአታላዮችና ከክፉዎች ሰዎችም አድነኝ።
2አምላክ ሆይ፤ አንተ ብርታቴ ነህና፣
ለምን ተውኸኝ?
ጠላትስ እያስጨነቀኝ፣
ለምን በሐዘን እመላለሳለሁ?
3ብርሃንህንና እውነትህን ላክ፤
እነርሱ ይምሩኝ፤
ወደ ተቀደሰው ተራራህ፣
ወደ ማደሪያህ ያድርሱኝ።
4እኔም ወደ እግዚአብሔር መሠዊያ አቀናለሁ፤
ፍጹም ደስታዬ ወደ ሆነው አምላክ
እሄዳለሁ፤
እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፣
በበገና አመሰግንሃለሁ።
5ነፍሴ ሆይ፤ ለምን ትተክዢያለሽ?
ለምንስ በውስጤ ትታወኪያለሽ?
ተስፋሽን በአምላክ ላይ አድርጊ፤
አዳኜና አምላኬን፣
ገና አመሰግነዋለሁና።

[ጸ]ም42 በብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች መዝሙር42 እና 43 አንድ መዝሙር ነው።
[ጸ]43 በብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች መዝሙር42 እና 43 አንድ መዝሙር ነው።

41፥9 ዘኍ30፥2፤ 2ሳሙ15፥12፤ኢዮ 19፥14፥19፤መዝ55፥20፤89፥34፤ማቴ26፥23፤ሉቃ22፥21፤ዮሐ 13፥18
41፥10 ቍ4፤2ሳሙ 3፥39፤መዝ3፥3፤9፥13
41፥11 ዘኍ14፥8፤ መዝ25፥2
41፥12 ኢዮ4፥7፤መዝ 18፥35፤21፥6፤25፥21፤37፥17፤61፥7፤63፥8
41፥13 ዘፍ24፥27፤ መዝ72፥18፥19፤89፥52፤106፥48
42፥1 ዘዳ10፥7ኢዮ 19፥27፤መዝ18፥33፤ 119፥131፤ኢል1፥20
42፥2 ኢሱ3፥10፤ 1ሳሙ14፥39፤መዝ43፥4፤63፥1፤84፥7፤143፥6፤ ማቴ16፥16፤ሮሜ9፥26
42፥3 ቍ10፤ኢዮ 3፥24፤መዝ79፥10፤115፥2፤ኢል2፥17፤ሚክ 7፥10
42፥4 ኢሱ6፥5፤ 1ሳሙ1፥15፤ዕዝ3፥13፤መዝ35፥18፤55፥14፤95፥2፤100፥4፤109፥30፤122፥1፤147፥7፤ኢሳ 2፥2፤30፥29፤ዮና2፥9
42፥5 ኢዮ20፥2፤መዝ 9፥1፤18፥46፤25፥5፤ 38፥6፤71፥14፤77፥3፤ ሰቆ3፥20፤ማቴ26፥38
42፥6 ቍ11፤ዘፍ 13፥10፤ዘኍ13፥29፤ ዘዳ3፥8፤4፥48፤መዝ 43፥5፤63፥6፤77፥11
42፥7 ዘፍ1፥2፤7፥11፤መዝ69፥2፤ዮና2፥3
42፥8 መዝ16፥7፤ 57፥3፤77፥6፤133፥3፤ መክ5፥18፤8፥15
42፥9 ኢዮ20፥19፤ መዝ9፥13፤10፥11፤18፥31፤35፥14፤43፥2፤ 106፥42
42፥10 ቍ3፤ዘዳ 32፥27፤መዝ6፥2፤44፥16፤89፥51፤102፥8፤ 119፥42
42፥11 ቍ5፤መዝ43፥5
43፥1 መሳ6፥31፤ መዝ25፥20፤36፥3፤ 109፥2
43፥2 መዝ35፥14፤ 42፥9፤44፥9፤74፥1፤88፥14፤89፥38
43፥3 2ሳሙ15፥25፤መዝ2፥6፤25፥5፤26፥3፤27፥1
43፥4 ዘፍ4፥21፤ መዝ16፥3፤21፥6፤26፥6፤42፥2፤84፥3
43፥5 መዝ42፥6

## መዝሙር 44

### ብሔራዊ ሰቆቃ

*ለመዘምራን አለቃ፤ የቆሬ ልጆች ትምህርት።*[θ]

1አምላክ ሆይ፤ በጆሮአችን ሰምተናል፤
አባቶቻችን በቀድሞ ዘመን፣
እነርሱ በነበሩበት ዘመን፣
ያደረግኸውን ነግረውናል።
2ሕዝቦችን በእጅህ አሳደህ አወጣሃቸው፤
አባቶቻችንን ግን ተከልሃቸው፤
ሕዝቦችን አደቀቅህ፤
አባቶቻችንን ግን ነጻ አወጣሃቸው።
3ምድሪቱን የወረሱት በሰይፋቸው
አልነበረም፤
ድልንም የተጐናጸፉት በክንዳቸው
አይደለም፤
አንተ ወደሃቸዋልና ቀኝ እጅህ፣
ክንድህና የፊትህ ብርሃን ይህን
አደረገ።

4እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ንጉሤ ነህ፤[ፊ]
ያዕቆብም ድል እንዲያደርግ የወሰንህ
አንተ ነህ።
5በአንተ ጠላቶቻችን በመጡበት እንዲ
መለሱ እናደርጋለን፤
በስምህም ባላጋራዎቻችንን ከእግራችን
በታች እንረግጣለን።
6በቀስቴ አልተማመንም፤
ሰይፌም አያስጥለኝም።
7አንተ ግን በጠላቶቻችን ላይ ድልን
ትሰጠናለህ፤
ባላንጣዎቻችንንም ታሳፍራለህ።

8ዘወትር በእግዚአብሔር እንመካለን፤
ስምህንም ለዘላለም እንወድሳለን። ሴላ

9አሁን ግን እነሆ ትተኸናል፤
አሳፍረኸናልም፤
ከሰራዊታችንም ጋር አትወጣም።
10ከጠላት ፊት እንድናፈገፍግ አደረግኸን፤
ባላንጣዎቻችንም ዘረፉን።
11እንደሚታረዱ በጎች አደረግኸን፤
በሕዝቦችም መካከል በተንኸን።
12ሕዝብህን በርካሽ ዋጋ ሸጥኸው፤
ከሽያጩም ያገኘኸው ትርፍ የለም።
13ለጎረቤቶቻችን ስድብ፣
በዙሪያችን ላሉትም መሣቂያና መዘበቻ
አደረግኸን።
14በሕዝቦች ዘንድ መተረቻ፣
በሰዎች መካከል በንቀት ራስ
መነቅነቂያ አደረግኸን።
15ውርደቴ ቀኑን ሙሉ በፊቴ ነው፤
ፊቴም ዕፍረትን ተከናንቦአል።
16ይህም ከሚዘልፍና ከሚያላግጥ ሰው
ድምፅ የተነሣ፣
ከጠላትና ከተበቃይ ሁኔታ የተነሣ
ነው።

17አንተን ሳንረሳ፣
ለኪዳንህም ታማኝነታችንን ሳናጓድል፣
ይህ ሁሉ ደረሰብን።
18ልባችን ወደ ኋላ አላለም፤
እግራችንም ከመንገድህ አልወጣም።
19አንተ ግን ተኰላዎች በሚውሉበት ቦታ
ሰባብረህ ጣልኸን፤
በሞት ጥላም ሸፈንኸን።

20የአምላካችንን ስም ረስተን፣
እጃችንንም ወደ ባዕድ አምላክ
ዘርግተን ቢሆን ኖሮ፣
21እግዚአብሔር ይህን ማወቅ ይሳነዋልን?
እርሱ ልብ የሰወረውን የሚረዳ ነውና።
22ይሁን እንጂ ቀኑን ሙሉ ስለ አንተ
ሞትን እንጋፈጣለን፤
እንደሚታረዱ በጎችም ተቈጥረናል።

23ጌታ ሆይ፤ ንቃ! ለምንስ ትተኛለህ?
ተነሥ፤ ለዘላለምም አትጣለን።
24ፊትህን ለምን ትሰውራለህ?
መከራችንንና መጠቃታችንን ለምን
ትረሳለህ?

25ነፍሳችን ዐፈር ውስጥ ሰጥማለች፤
ሆዳችንም ከምድር ጋር ተጣብቆአል።
26ተነሥና እርዳን!
ስለ ምሕረትህ ስትል ተቤዠን።

## መዝሙር 45

### የንጉሣዊ ሰርግ መዝሙር

*ለመዘምራን አለቃ፤ "በጽጌረዳ" ዜማ፤ የቆሬ ልጆች ትምህርት፤ የፍቅር መዝሙር*[T]

1ልቤ መልካም ሐሳብ አፈለቀ፤
የተቀኘሁትን ቅኔ ለንጉሥ አሰማለሁ፤
አንደበቴም እንደ ባለ ሙያ ጸሓፊ
ብርዕ ነው።

2አንተ ከሰዎች ሁሉ ይልቅ ውብ ነህ፤
ከንፈሮችህም የጸጋ ቃል ያፈልቃሉ፤
ስለዚህ እግዚአብሔር ለዘላለም ባርኮሃል።
3ኀያል ሆይ፤ ሰይፍህን በወገብህ ታጠቅ፤
ግርማ ሞገስንም ተላበስ።

44፥1 ዘጸ32፥7፤ መሳ6፥13፤2ሳሙ7፥22፤1ዜና17፥20፤ኢዮ37፥23፤ኤር26፥11
44፥2 ዘፀ15፥17፤ ኢሱ3፥10፤መሳ4፥23፤ 2ዜና14፥13፤መዝ80፥9፤ኢሳ60፥21፤ኤር32፥23፤ሐሥ7፥45
44፥3 ዘፀ15፥16፤ዘዳ4፥37፤ኢሱ24፥12፤ መዝ77፥15፤78፥54፤ 79፥11፤89፥10፡15፤ 98፥1፤ኢሳ40፥10፤ 52፥10፤63፥5
44፥4 መዝ5፥2፤21፥5፤24፥7
44፥5 ኢሱ23፥5፤ መዝ60፥12፤108፥13
44፥6 ዘፍ48፥22፤ ሆሴ1፥7
44፥7 ዘዳ20፥4፤ኢዮ8፥22
44፥8 መዝ30፥12፤ 34፥2፤52፥1፤1ቆሮ1፥31፤2ቆሮ10፥17
44፥9 ዘዳ8፥3፤ 31፥17፤ኢሱ7፥12፤ መዝ43፥2፤107፥39፤ 108፥11፤ኢሳ5፥15
44፥10 ዘሌ26፥17፤መሳ2፥14
44፥11 ቀኍ22፤ዘሌ26፥33፤መዝ9፥11፤ ኤር12፥3፤ሕዝ6፥8፤ ዘካ2፥6
44፥12 ዘዳ32፥30፤ ኢሳ50፥1፤52፥3፤ኤር15፥13
44፥13 ዘዳ28፥37፤ 2ዜና29፥8፤መዝ79፥4፤ 80፥6፤89፥41፤ኢሳ30፥3፤ኤር25፥9፤42፥18፤44፥8፤ሕዝ23፥32፤ሚክ2፥6
44፥14 1ነገ9፥7፤ 2ነገ19፥21
44፥15 ዘፍ30፥23፤ 2ዜና32፥21፤መዝ34፥5፤35፥26
44፥16 1ሳሙ18፥25፤ መዝ10፥13፤42፥10፤ 55፥3፤74፥10፤ኤር11፥19፤ሮሜ12፥19
44፥17 ዘዳ6፥12፤ 32፥18፤መዝ119፥16፡61፡153፡176፤ምሳ3፥1
44፥18 መዝ119፥51፡157
44፥19 2ዜና14፥13፤ኢዮ3፥5፤30፥29፤ መዝ51፥8፤ኢሳ34፥13
44፥20 ዘፀ20፥3፤ዘዳ32፥18፤መሳ3፥7፤ኢሳ43፥12፤ኤር5፥19
44፥21 1ሳሙ16፥7፤1ነገ8፥39፤ምሳ15፥11፤ኤር12፥3፤17፥10
44፥22 ቀኍ11፤ኢሳ53፥7፤ኤር11፥19፤ 12፥3፤ሮሜ8፥36
44፥23 መዝ7፥6፤ 59፥5፤74፥1፤77፥7፤78፥65 44፥24 ዘዳ26፥7፤32፥20፤መዝ13፥1፤ ሰቆ5፥20 44፥25 መዝ119፥25 44፥26 ዘኍ10፥35፤መዝ6፥4፤12፥5፤26፥11፤102፥13 45 ርዕስ ማሕ1፥1 45፥2 መዝ21፥6፤ሉቃ4፥22 45፥3 ዘዳ32፥41፤2ሳሙ1፥19፤ኢዮ40፥10፤ መዝ21፥5፤149፥6፤ራእ1፥16

[θ]44ርእስ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።
[ፊ]4 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም የሱርስቱ ቅጅ *ንጉሤ ነህ፤ አምላኬም ነህ* ይላሉ፤ ዕብራይስጡ ደግሞ፣ *ንጉሤ እግዚአብሔር ሆይ፤* ይላል።
[T]45ርእስ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።

4ስለ እውነት፣ ስለ ትሕትና ስለ ጽድቅ፣
ሞገስን ተጐናጽፈህ በድል አድራጊነት ገሥግሥ፤
ቀኝ እጅህም ድንቅ ተግባር ታሳይ።
5የሾሉ ፍላጻዎችህ በንጉሥ ጠላቶች ልብ ይሰካሉ፤
ሕዝቦችም ከእግርህ በታች ይወድቃሉ።
6አምላክ ሆይ፤ ዙፋንህ ከዘላለም እስከ ዘላለም ይኖራል፤
የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ናት።
7ጽድቅን ወደድህ፤ ዐመፃን ጠላህ፤
ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ፣
ከጓደኞችህ ይልቅ አንተን የደስታ ዘይት ቀባህ።
8ልብስህ ሁሉ በከርቤ፣ በአደስና በጥንጁት መዐዛ ያውዳል፤
በዝሆን ጥርስ ከተዋቡ ቤተ መንግሥቶችም፣
የበገናና የመሰንቆ ድምፅ ደስ ያሰኙሃል።
9ከተከበሩት ሴቶችህ መካከል የነገሥታት ሴቶች ልጆች ይገኛሉ፤
ንግሥቲቱም በኦፊር ወርቅ አጊጣ በቀኝህ ቆማለች።

10ልጄ ሆይ፤ አድምጪ፤ አስተውዪ፤ ጆሮሽንም አዘንብይ፤
ሕዝብሽንና የአባትሽን ቤት እርሺ።
11ንጉሥ በውበትሽ ተማርኮአል፤
ጌታሽ ነውና አክብሪው።
12የጢሮስ ሴት ልጅ እጅ መንሻ ይዛ ትመጣለች፤[ሀ]
ሀብታሞችም ደጅ ይጠኑሻል።

13የንጉሥ ልጅ ከላይ እስከ ታች ተሽልማ እልፍኟ ውስጥ አለች፤
ልብሷም ወርቀ ዘቦ ነው።
14በጥልፍ ሥራ ባጌጠ ልብስ ወደ ንጉሥ ትወሰዳለች፤
ደናግል ጓደኞቿም ተከትለዋት፣
ወደ አንተ ይመጣሉ።
15በደስታና በሐሤት ወደ ውስጥ ይመራቸዋል፤
ወደ ንጉሡም ቤተ መንግሥት ይገባሉ።

16ወንዶች ልጆችህ በአባቶችህ እግር ይተካሉ፤
ገዦችም አድርገሽ በምድር ሁሉ ትሾሚያቸዋለሽ።
17ስምሽን በትውልድ ሁሉ ዘንድ መታሰቢያ አደርጋለሁ፤
ስለዚህ ሕዝቦች ከዘላለም እስከ ዘላለም ያወድሱሃል።

45፥4 ዘጸ4፥34፤ መዝ21፥8፤65፥5፤66፥3፤ሶፎ2፥3፤ራእ6፥2
45፥5 ዘኍ24፥8፤ ዘዳ32፥23፤መዝ9፥13፤ 92፥9
45፥6 ዘፍ21፥33፤ ሰቆ5፥19
45፥7 መዝ2፥2፤ 11፥5፤23፥5፤33፥5፤ ኢሳ45፥1፤61፥1፤ዘካ 4፥14፤ዕብ1፥8-9
45፥8 ዘፍ37፥25፤ዘፀ 30፥24፤ዘኍ24፥6፤ 1ነገ22፥39፤መዝ144፥ 9፤150፥4፤ምሳ27፥9፤ መሓ1፥3፤4፥10፤ኢሳ 38፥20ዮሐ 19፥39
45፥9 ዘፍ10፥29፤ 1ነገ2፥19፤መሓ6፥8፤ኢሳ62፥5
45፥10ሩት1፥11፥ 16፤ኤር5፥1
45፥11 አስ1፥11፤ ሰቆ2፥15፤ኤፌ5፥33፤1 ጴጥ3፥6
45፥12 ኢሱ19፥29፤ 1ነገ9፥16፤2ዜና9፥24
45፥13 ዘፀ39፥3፤ ኢሳ61፥10
45፥14 መሳ5፥30፤ አስ2፥15፤መሓ1፥3
45፥15 አስ8፥17
45፥16 1ሳሙ2፥8፤ መዝ68፥27፤113፥8
45፥17 ዘፀ3፥15፤ መዝ21፥4፤33፥11፤11 9፥90፤135፥13፤ 138፥4፤ራእ22፥5
46፥1 ዘዳ4፥30፤ መዝ9፥9፤18፥1፥6፤25፥ 17፤34፥18፤37፥39፤61 ፥3፤73፥26፤91፥2፥9፤14 2፥5፤ኢሳ33፥16፤ ኤር16፥19፤17፥17፤ ሰቆ 3፥57፤ኢል3፥16 ፤ናሆ1፥7፤ሉቃ1፥54
46፥2 ቀኍ6፤ዘፍ4፥7 ፤ዘፀ15፥8፤መዝ3፥6፤ 18፥7፤82፥5፤97፥5፤ ኢሳ13፥13፤24፥1፥19 ፥20፤54፥10፤ኤር4፥23 ፤ዳን11፥19፤አሞ8፥14 ፤9፥5፤ሚክ1፥4፤ናሆ 1፥5፤ዕን3፥6፤ራእ6፥14
46፥3 መሳ5፥5፤ኢዮ 9፥26፤መዝ93፥3፤ኢሳ 17፥13፤ኤር5፥22፤ ሕዝ1፥24፤ራእ19፥6
46፥4 ዘፍ2፥10፤ 14፥18፤2ሳሙ15፥25፤ መዝ1፥3፤48፥1፥8፤ 87፥3፤101፥8፤ራእ 3፥12፤22፥1
46፥5 ዘዳ23፥14፤ 1ዜና5፥20፤መዝ26፥8፤ 125፥1፤ኢሳ12፥6፤ ዘካ2፥5
46፥6 ቀኍ2፤ኢዮ 12፥23፤መዝ29፥3፤68፥ 32፤74፥23፤102፥22፤ ኢሳ5፥30፤13፥4፥13፤ 17፥12፤23፥11፤33፥34

## መዝሙር 46[ሰ]
## እግዚአብሔር ከእኛ ጋር

*ለመዘምራን አለቃ፤ የቆሬ ልጆች መዝሙር፤ በደናግል የዜማ ስልት የሚዘመር፣ መዝሙር።*

1አምላካችን መጠጊያችንና ኀይላችን፣
በሚደርስብን መከራ ሁሉ የቅርብ ረዳታችን ነው።
2ስለዚህ ምድር ብትነዋወጥ እንኳ፣
ተራሮችም ወደ ባሕር ጥልቅ ቢሰምጡ አንፈራም።
3ውሆች ቢያስገመግሙ፣ ዐረፋ ቢደፍቁም፣
ተራሮችም ከውሆቹ ሙላት የተነሣ ቢንቀጠቀጡም አንደናገጥም።
ሴላ
4የእግዚአብሔርን ከተማ፣
የልዑልን የተቀደሰ ማደሪያ ደስ የሚያሰኝ የወንዝ ፈሳሾች አሉ።
5እግዚአብሔር በመካከሏ ነው፤ አትናወጥም፤
አምላክ በማለዳ ይረዳታል።
6ሕዝቦች በዐመፅ ተነሡ፤ መንግሥታትም ወደቁ፤
ድምፁን ከፍ አድርጎ አሰማ፤ ምድርም ቀለጠች።
7የሰራዊት *አምላክ* ከእኛ ጋር ነው፤
የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው።
ሴላ
8ኑና *የእግዚአብሔርን ሥራ*፣
ምድርንም እንዴት ባድማ እንዳደረጋት እዩ።
9 ከዳር እስከ ዳር ጦርነትን ከምድር ያስወግዳል፤
ቀስትን ይሰብራል፤ ጦርን ያነክታል፤
ጋሻንም[ሐ] በእሳት ያቃጥላል።
10“ዕረፉ፤ እኔም አምላክ እንደ ሆንሁ ዕወቁ፤
በሕዝቦች ዘንድ ከፍ ከፍ እላለሁ፤
በምድርም ላይ ከፍ ከፍ እላለሁ።”
11የሰራዊት *አምላክ* ከእኛ ጋር ነው፤
የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው።
ሴላ

## መዝሙር 47
## እግዚአብሔር፣ የእስራኤል ንጉሥ የዓለም ጌታ

*ለመዘምራን አለቃ፤ የቆሬ ልጆች መዝሙር።*

1ሕዝቦች ሁላችሁ እጆቻችሁን

፤ሕዝ26፥18፤ማቴ4፥8 46፥7 ቀኍ11፤ዘፍ21፥22፤1ሳሙ1፥11፤ መዝ18፥2፤20፥1 46፥8 መዝ66፥5፤ኢሳ17፥9፤64፥10፤ዳን9፥26፤ ሉቃ21፥20 46፥9 መዝ37፥15፤አሳ2፥4፤9፥5፤22፥6፤ሕዝ39፥9፤ ሆሴ2፥18 46፥10 ዘዳ4፥35፤1ነገ18፥36፥39፤መዝ18፥46፤100፥3፤ ኢሳ2፥11፤37፥16፥20፤43፥11፤45፥21፤ሕዝ36፥23 46፥11 ቀኍ7፤ መዝ 20፥1

[ሀ]12 ወይም፣ *የጢሮሳውያን ልብስ ተክህኖ ከስጦታዎቹ መካከል አለ*
[ሰ]ም46 ርእስ ምናልባት የሙዚቃውን ሁኔታ ሊያሳይ ይችላል።
[ሐ]9 ወይም *ሠረገላንም*

አጨብጭቡ፤
ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ለእግዚ
አብሔር እልል በሉ።
2በምድር ሁሉ ላይ ታላቅ የሆነው ንጉሥ፣
ልዑል እግዚአብሔር የሚያስፈራ
ነውና።
3ሕዝቦችን ከእኛ በታች አደረገ፤
መንግሥታትንም ከእግራችን ሥር
አስገዛልን።
4ለሚወደው ለያዕቆብ ክብር የሆነችውን፣
ርስታችንን እርሱ መረጠልን።
5አምላክ በእልልታ፣
እግዚአብሔር በመለከት ድምፅ ዐረገ።
6አምላካችንን አወድሱት፤ አወድሱት፤
ንጉሣችንን አወድሱት፤ አወድሱት፤
7እግዚአብሔር የምድር ሁሉ ንጉሥ
ነውና፤
ምርጥ ዝማሬ[መ] አቅርቡለት።
8እግዚአብሔር በሕዝቦች ላይ ነግሦአል፤
እግዚአብሔር በተቀደሰ ዙፋኑ ላይ
ተቀምጦአል።
9ከአብርሃም አምላክ ሕዝብ ጋር፣
የሕዝቦች መኳንንት ተሰበሰቡ፤
የምድር ነገሥታት[ሠ] የእግዚአብሔር
ናቸውና፤
እርሱም እጅግ ከፍ ከፍ ያለ ነው።

## መዝሙር 48

### የእግዚአብሔር ተራራ ጽዮን

ዝማሬ፤ የቆሬ ልጆች መዝሙር

1እግዚአብሔር ታላቅ ነው፤
በአምላካችን ከተማ በተቀደሰው ተራራ
ከፍ ያለ ምስጋና ይገባዋል።
2የምድር ሁሉ ደስታ የሆነው፣
በሰሜን በኩል[ሪ] በርቀት የሚታየው፣
በከፍታ ላይ አምሮ የደመቀው የጽዮን
ተራራ፣
የታላቁ ንጉሥ ከተማ ነው።
3እግዚአብሔር በአዳራሾቿ ውስጥ ሆኖ፤
ብርቱ ምሽግ እንደ ሆናት
አስመስክሮአል።
4እነሆ፤ ነገሥታት ተባብረው መጡ፤
አንድ ላይ ሆነውም ገሠገሡ።
5አይተውም ተደነቁ፤
ደንግጠውም ፈረጠጡ።
6ምጥ እንደ ያዛት ሴት፣
በዚያ ብርክ ያዛቸው።
7የምሥራቅ ነፋስ የተርሴስን መርከብ
እንደሚሰባብር፣
አንተ አብረከረክሃቸው።
8እንደ ሰማን፣
በሰራዊት አምላክ ከተማ፣
በአምላካችን ከተማ፣
እንዲሁ አየን፤
እግዚአብሔር ለዘላለም ያጸናታል።
ሴላ
9አምላክ ሆይ፤ በቤተ መቅደስህ ውስጥ
ሆነን፣
ምሕረትህን እናስባለን።
10አምላክ ሆይ፤ ምስጋናህ እንደ ስምህ፣
እስከ ምድር ዳርቻ ይዘልቃል፤
ቀኝ እጅህም ጽድቅን የተሞላች ናት።
11ስለ ፍርድህ፣
የጽዮን ተራራ ሐሤት ታድርግ፤
የይሁዳ መንደሮችም ደስ ይበላቸው።
12በጽዮን አካባቢ ተመላለሱ፤ ዙሪያዋንም
ሂዱ፤
የጥበቃ ግንበኞቿንም ቍጠሩ፤
13ለሚቀጥለው ትውልድ ትናገሩ ዘንድ፣
መከላከያ ዕርዶቿን ልብ ብላችሁ
ተመልከቱ፤
መጠበቂያ ማማዎቿን እዩ።
14ይህ አምላክ ከዘላለም እስከ ዘላለም
አምላካችን ነውና፤
እስከ መጨረሻው የሚመራንም እርሱ
ነው።

## መዝሙር 49

### የሀብት ከንቱነት

ለመዘምራን አለቃ፤ የቆሬ ልጆች መዝሙር።

1እናንተ ሕዝቦች ሁላችሁ፤ ይህን ስሙ፤
በዓለም የምትኖሩ ሁሉ፤ ይህን
አድምጡ።
2ዝቅተኞችና ከፍተኞች፤
ባለጠጎችና ድኾች ይህን በአንድነት
ስሙ።
3አፌ የጥበብን ቃል ይናገራል፤
የልቤም ሐሳብ ማስተዋልን ይሰጣል።
4ጆሮዬን ወደ ምሳሌ አዘነብላለሁ፤
እንቆቅልሼንም በበገና እፈታለሁ።
5የአጭበርባሪዎች ክፋት በከበበኝ ጊዜ፣
በክፉ ቀን ለምን እፈራለሁ?
6በሀብታቸው የሚመኩትን፣
በብልጽግናቸውም የሚታመኑትን
ለምን እፈራለሁ?
7የሌላውን ሕይወት መቤዠት የሚችል
ሰው፣
ወይም ለእግዚአብሔር ወጆ የሚከፍልለት
ማንም የለም።
8የነፍስ ቤዛ ውድ ነውና፤
በቂ ዋጋም ከቶ ሊገኝለት አይችልም፤

7፥1 2ነገ11፥12፤መዝ33፥3
47፥2 ዘፍ14፥18፤ ዘዳ7፥21፤መዝ2፥6፤48፥2፤95፥3፤ማቴ5፥35
47፥3 መዝ18፥39፡ 47፤ኢሳ14፥6
47፥4 መዝ2፥8፤ 16፥6፤78፥55፤አሞ6፥8፤8፥7፤1ጴጥ1፥4
47፥5 ዘኍ10፥2፤ 2ሳሙ6፥15፤ኢዮ8፥21፤መዝ68፥18፤ 106፥5፤ኤፌ4፥8
47፥6 2ሳሙ22፥50
47፥7 1ዜና16፥7፤ ዘካ14፥9፤ቈላ3፥16
47፥8 1ነገ22፥19፤ 1ዜና16፥31፤መዝ9፥4፤ ራእ4፥9
47፥9 ኢዮ25፥2፤ መዝ46፥10፤97፥9
48፥1 ዘዳ33፥19፤ 2ሳሙ22፥4፤1ዜና16፥25፤መዝ2፥6፤18፥3፤ 46፥4፤86፥10፤87፥1፤96፥4፤99፥2፤135፥5፤147፥7፤ኢሳ11፥9፤ 32፥16፤ኤር10፥6፤ 31፥23፤ዳን9፥16፤ሚክ4፥1፤ዘካ8፥3
48፥2 ኢሱ13፥27፤ መዝ2፥6፤50፥2፤ሰቆ2፥15፤ሕዝ16፥14፤ ማቴ5፥35
48፥3 ቍ13፤መዝ18፥2፤122፥7
48፥4 2ሳሙ10፥1-19
48፥5 ዘፀ15፥16፤ ኢሳ13፥8፤ኤር46፥5፤ ዳን5፥9
48፥6 ዘፍ3፥16፤ ኢዮ4፥14
48፥7 ዘፍ10፥4፤41፥6፤1ነገ10፥22፤22፥48
48፥8 ኤር23፥6፤ ዘካ8፥13፤14፥11
48፥9 መዝ6፥4፤39፥3
48፥10 ዘፀ6፥3፤ኢሱ7፥9፤1ሳሙ2፥10፤ መዝ22፥27፤65፥5፤ 98፥3፤100፥1፤ኢሳ11፥12፤24፥16፤ 42፥10፤49፥6
48፥11 መዝ97፥8
48፥12 ነህ3፥1
48፥13 ቍ3፤2ሳሙ20፥15፤መዝ71፥18፤ 78፥6፤109፥13፤ኢሳ26፥1፤ሰቆ2፥8፤ዕን2፥1
48፥14 መዝ25፥5፤ 73፥24፤ምሳ6፥22፤ ኢሳ49፥10፤57፥18፤ 58፥11
49፥1 መዝ33፥8፤ 78፥1፤ኢሳ1፥2
49፥2 መዝ62፥9
49፥3 መዝ37፥30፤119፥130
49፥4 ዘኍ12፥8፤ 1ሳሙ16፥16፤መዝ3፥2፤78፥2፤ምሳ1፥6፤ሕዝ12፥22፤16፥44፤18፥2-3፤ሉቃ4፥23
49፥5 መዝ23፥4፤27፥1 49፥6 ኢዮ22፥25፤36፥19፤መዝ10፥3፤ 73፥12፤ኤር48፥7 49፥8 ዘኍ35፥31፤ማቴ16፥26

[መ]7 ዕብራይስጡ ማሽከል ይላል፤ ይኸውም የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የሙዚቃውን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።

[ሠ]9 ወይም *ጋሾች*
[ረ]2 *ዛፎን* የሚለው የዕብራይስጡ ቃል የተቀደሰ ተራራን ወይም የሰሜንን አቅጣጫ ሊያመለክት ይችላል።

9በዚህም ዘላለም ይኖራል፣
መበስበስንም አያይም።

10ጠቢባን ሟች መሆናቸው የሚታይ ነው፤
ቂልና ሞኝም በአንድነት ይጠፋሉ፤
ጥሪታቸውንም ለሌላው ጥለው
ይሄዳሉ።
11መሬቶችን በስማቸው ቢሰይሙም፣
መቃብራቸው የዘላለም ቤታቸው፣
ከትውልድ እስከ ትውልድም
መኖሪያቸው ይሆናል።

12ሰው በሀብቱ እንደ ተከበረ አይዘልቅም፤
ታይተው የሚጠፉ እንስሳትን
ይመስላል።[ሰ]

13ይህ የተላላዎች ዕድል ፈንታ፣
የእነርሱንም አባባል ተቀብለው
ለሚከተሏቸው፣
መጨረሻ ግብ ነው። ሴላ
14እንደ በጎች ለሲኦል[ሸ] የተዳረጉ ናቸው፤
ሞትም እረኛቸው ይሆናል፤
ቅኖች በማለዳ ይገዟቸዋል፤
አካላቸው ከክብር ቤታቸው ርቆ፣
በሲኦል ይፈራርሳል።
15እግዚአብሔር ግን ነፍሴን[ቀ] ከሲኦል እጅ
ይቤዠታል፤
በእርግጥም በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት
አለኝ። ሴላ

16ሰው ባለጠጋ ሲሆን፣
የቤቱም ክብር ሲበዛለት አትፍራ፤
17በሚሞትበትም ጊዜ ይዞት የሚሄደው
አንዳች የለምና፤
ክብሩም አብሮት አይወርድም።
18በሕይወት ሳለ ራሱን እንደ ተባረከ
ቢቈጥርም፣
ሰዎች በበለጸግህ ጊዜ ቢያወድሱህም፣
19ብርሃን ከቶ ወደማያዩት፣
ወደ አባቶች ማኅበር ይቀላቀላል።

20ሰው በሀብቱ እንደ ተከበረ አይዘልቅም፤
ታይተው የሚጠፉ እንስሳትን
ይመስላል።

## መዝሙር 50

## በመንፈስና በእውነት ማምለክ

የአሳፍ መዝሙር

1ኀያሉ አምላክ፣ እግዚአብሔር ተናገረ፤
ከፀሓይ መውጫ እስከ ፀሓይ መግቢያ
ድረስ
ምድርን ጠራት።
2ፍጹም ውብ ከሆነችው ከጽዮን፣
እግዚአብሔር አበራ።
3አምላካችን ይመጣል፤ ዝምም አይልም፤
የሚባላ እሳት በፊቱ፣
የሚያስፈራ ዐውሎ ነፋስም በዙሪያው
አለ።
4በሕዝቡ ይፈርድ ዘንድ፣
በላይ ያለውን ሰማይንና ምድርን
እንዲህ ብሎ ይጠራል፤
5"በመሥዋዕት ከእኔ ጋር ኪዳን የገቡትን፣
ቅዱሳኔን ወደ እኔ ሰብስቧቸው።"
6ሰማያት ጽድቁን ያውጃሉ፤
እግዚአብሔር ራሱ ፈራጅ ነውና። ሴላ
7"ሕዝቤ ሆይ፤ ስማኝ፤ ልንገርህ፤
እስራኤል ሆይ፤ በአንተ ላይ
ልመስክር፤
አምላክህ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።
8ስለ መሥዋዕትህ አልነቅፍሁህም፤
የሚቃጠል መሥዋዕትህማ ሁልጊዜ
በፊቴ ነው።
9እኔ ግን ኮርማህን ከበረት፣
ፍየሎችህንም ከጕረኖ የምፈልግ
አይደለሁም፤
10የዱር አራዊት ሁሉ፣
በሺ ተራራዎች ላይ ያለውም እንስሳ
የእኔ ነውና።
11በየተራራው ያለውን ወፍ ሁሉ
ዐውቃለሁ፤
በሜዳ የሚገኘው ተንቀሳቃሽ ፍጡር
ሁሉ የእኔ ነው።
12ብራብ ለአንተ አልነግርህም፤
ዓለምና በውስጧ ያለውም ሁሉ የእኔ
ነውና።
13ለመሆኑ፣ እኔ የኰርማ ሥጋ እበላለሁን?
የፍየልንስ ደም እጠጣለሁን?
14ለእግዚአብሔር የምስጋና መሥዋዕት
አቅርብ፤
ለልዑልም ስእለትህን ስጥ።
15በመከራ ቀን ጥራኝ፤
አድንሃለሁ፤ አንተም ታከብረኛለህ።"

16ክፉውን ግን እግዚአብሔር እንዲህ ይለዋል፤

"ሕጌን ለማነብነብ፣
ኪዳኔንም በአፍህ ለመናገር ምን
መብት አለህ?
17ተግሣጼን ትጠላለህና፤
ቃሌንም ወደ ኋላህ ትጥላለህ።
18ሌባውን ስታይ አብረኸው ነጐድህ፤
ዕድል ፈንታህንም ከአመንዝሮች ጋር
አደረግህ።
19አፍህን ለክፋት አዋልህ፤

49፥9 መዝ16፥10፤22፥29፤89፥48
49፥10 ኢዮ27፥17፤መዝ92፥6፤94፥8፤መክ2፥16፡18፡21፤ሉቃ12፥20
49፥11 ዘዳ3፥14፤መዝ106፥31፤ማር5፥3፤ሉቃ8፥27
49፥12 ቍ20፤ኢዮ14፥2፤2ጴጥ2፥12
49፥13 ሉቃ12፥20
49፥14 ዘኍ16፥30፤ኢዮ21፥13፤መዝ9፥17፤55፥15፤ኢሳ14፥2፤ኤር43፥11፤ሕዝ31፥14፤ዳን7፥18፤1ቆሮ6፥2
49፥15 ዘፍ5፥24፤መዝ56፥13፤ሆሴ13፥14
49፥17 መዝ17፥14፤1ጢሞ6፥7
49፥18 መዝ10፥6፤ሉቃ12፥19
49፥19 ዘፍ15፥15፤ኢዮ33፥30
49፥20 ቍ12፤ምሳ16፥16
50፥1 ኢሱ22፥22፤መዝ113፥3
50፥2 ዘዳ33፥2፤መዝ2፥6፤48፥2፤ ሰቆ2፥15
50፥3 ቍ21፤ዘሌ10፥2፤ኢዮ37፥9፤መዝ18፥8፤83፥15፤96፥13፤107፥25፤147፥18፤ኢሳ29፥6፤30፥28፤42፥14፤64፥12፤65፥6፤ዮና1፥4፤ናሆ1፥3
50፥4 ዘዳ4፥26፤31፥28፤ኢሳ1፥2፤ዕብ10፥30
50፥5 ዘፀ24፥7፤ዘዳ7፥6፤2ዜና6፥11፤መዝ18፥25
50፥6 ዘፍ16፥5፤ኢዮ9፥15፤መዝ19፥1
50፥7 ዘፀ20፥2፤መዝ48፥14፤ዕብ2፥4
50፥8 2ሳሙ22፥16፤መዝ40፥6
50፥9 ዘሌ1፥5፤16፥5፤ዘኍ32፥16
50፥10 መዝ104፥20፡24፤ኢሳ56፥9፤ሚክ5፥8
50፥11 መዝ8፥7፤80፥13፤ማቴ6፥26
50፥12 ዘፀ19፥5፤ዘዳ10፥14፤ኢሱ3፥11፤መዝ24፥1፤1ቆሮ10፥26
50፥14 ዘኍ30፥2፤ዕዝ1፥4፤መዝ7፥8፤27፥6፤66፥13፤76፥11
50፥15 መዝ3፥7፤4፥1፤22፥23፤69፥17፤81፥7፤86፥7፤107፥6፤142፥2፤ኢሳ55፥6፤58፥9፤ዘካ13፥9፤ያዕ5፥13
50፥16 መዝ25፥10፤ኢሳ29፥13
50፥17 1ነገ14፥9፤ምሳ1፥22
50፥18 ኢዮ22፥15፤ሮሜ1፥32፤1ጢሞ5፥22 50፥19 መዝ10፥7፤36፥3፤52፥2፤101፥7

[ሰ]12 በሰብዓ ሊቃናት ትርጕምና በሱርስቱ ቅጂ ቍ12 ከቍ20 ጋር አንድ ዐይነት ነው፤ ዕብራይስጡ ግን ከዚህ ይለያል።
[ሸ]14 በዚህ እና በቍ15 ላይ ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል አንዳንድ የእንግሊዝኛ ቅጆች ግን *መቃብር* ይላሉ።
[ቀ]15 ወይም *ሕይወቴን*

አንደበትህም ሽንገላን ጐነጐነ።
20ተቀምጠህ ወንድምህን አማኸው፤
የእናትህንም ልጅ ስም አጐደፍህ።
21ይህን አድርገህ ዝም አልሁ፤
እንዳንተም የሆንሁ መሰለህ።
አሁን ግን እገሥጽሃለሁ፣
ፊት ለፊትም እወቅስሃለሁ።

22"እናንተ እግዚአብሔርን የምትረሱ፤ ይህን
ልብ በሉ፤
አለበለዚያ ብትንትናችሁን አወጣለሁ፤
የሚያድናችሁም የለም።
23የምስጋናን መሥዋዕት የሚሠዋ
ያከብረኛል፤
መንገዱንም ቀና ለሚያደርግ፣
የእግዚአብሔርን ማዳን አሳየዋለሁ።"[በ]

## መዝሙር 51

### የኀጢአት ኑዛዜ

*ለመዘምራን አለቃ፤ ዳዊት ወደ ቤርሳቤህ ከገባ በኋላ፣ ነቢዩ ናታን ወደ እርሱ በመጣ ጊዜ፤ የዳዊት መዝሙር።*

1እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ ቸርነትህ መጠ
ን፣
ምሕረት አድርግልኝ፤
እንደ ርኅራኄህም ብዛት፣
መተላለፌን ደምስስ።
2በደሌን ፈጽሞ እጠብልኝ፤
ከኀጢአቴም አንጻኝ።

3እኔ መተላለፌን አውቃለሁና፤
ኀጢአቴም ዘወትር በፊቴ ነው።
4በውሳኔህ ትክክል፣
በምትሰጠው ፍርድም ንጹሕ ትሆን
ዘንድ፣
አንተን፣ በእርግጥ አንተን ብቻ በደልሁ፤
በፊትህም ክፉ ነገር አደረግሁ።
5ስወለድ ጀምሮ በደለኛ፣
ገና እናቴም ስትፀንሰኝ ኀጢአተኛ ነኝ።
6እነሆ፤ እውነትን ከሰው ልብ ትሻለህ፤[ተ]
ስለዚህ ጥልቅ ጥበብን በውስጤ
አስተምረኝ።[ቸ]

7በሂሶጵ እርጨኝ፤ እኔም እነጻለሁ፤
እጠበኝ፤ ከበረዶም ይልቅ ነጭ
እሆናለሁ።
8ሐሤትንና ደስታን አሰማኝ፤
ያደቀቅሃቸው ዐጥንቶቼም ደስ
ይበላቸው።
9ፊትህን ከኀጢአቴ መልስ፤
በደሌንም ሁሉ ደምስስልኝ።

10አምላኬ ሆይ፤ ንጹሕ ልብ ፍጠርልኝ፤
ቀና የሆነውንም መንፈስ በውስጤ
አድስ።
11ከፊትህ አትጣለኝ፤
ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ

**50፥20** ማቴ10፥21
**50፥21** መዝ6፥1፤18፥15፤76፥6፤85፥5፤104፥7፤ኢሳ42፥14፤50፥2፤57፥11፥16፤62፥1፤64፥12፤
**50፥22** ዘዳ32፥39፤ኢዮ8፥13፤ኢሳ17፥10፤ሚክ5፥8
**50፥23** መዝ9፥14፤85፥13፤91፥16፤98፥3፤ኢሳ52፥10
**51** ርዕስ2ሳሙ11፥4፤12፥1
**51፥1** 2ሳሙ12፥13፤24፥14፤2ዜና6፥21፤ነህ4፥5፤9፥27፤መዝ9፥13፤25፥7፤39፥8፤86፥15፤119፥88፤ኢሳ63፥7፤ሐሥ3፥19
**51፥2** ሩት3፥3፤ምሳ20፥30፤ኢሳ4፥4፤ኤር2፥22፤13፥27፤ሕዝ36፥25፤ዘካ13፥1፤ማቴ23፥25-26፤ሐሥ22፥16፤ዕብ9፥14፤1ዮሐ1፥9
**51፥3** ኢሳ59፥12
**51፥4** ዘፍ20፥6፤1ሳሙ15፥24፤ሉቃ15፥21፤ሮሜ3፥4
**51፥5** ዘሌ5፥2፤ኢዮ5፥7
**51፥6** ኢዮ9፥4፤34፥32፤መዝ119፥66፤143፥10
**51፥7** ዘፀ12፥22፤ዘኍ19፥6፤ኢሳ1፥18፤4፥4፤43፥25፤44፥22፤ሕዝ36፥25፤ዘካ13፥1 ፤ዕብ9፥19
**51፥8** ዘፀ12፥46፤ኢሳ35፥10፤ኤር33፥11፤ኢል1፥16
**51፥9** 2ሳሙ12፥13፤ኤር16፥17፤ዘካ4፥10
**51፥10** መዝ24፥4፤78፥37፤ሕዝ18፥31፤36፥26፤ማቴ5፥8፤ሐሥ15፥9
**51፥11** ዘፍ4፥14፤ዘፀ33፥15፤መዝ27፥9፤71፥9፤106፥33፤138፥8፤ኢሳ63፥10፤ኤፌ4፥30
**51፥12** ኢዮ33፥26፤መዝ18፥35፤110፥3
**51፥13** ዘፀ33፥13፤ኢዮ33፥27፤መዝ1፥1፤ሐሥ9፥21-22
**51፥14** 2ሳሙ12፥9፤መዝ5፥8፤25፥5፤35፥28፤39፥8፤68፥20፤71፥15፤88፥1
**51፥15** ዘፀ4፥15
**51፥16** 1ሳሙ15፥22
**51፥17** ምሳ15፥8፤ሐጌ2፥14፤ማቴ11፥29
**51፥18** መዝ69፥35፤102፥16፤147፥2፤ኢሳ14፥32፤44፥26፤51፥3፤ዘካ1፥16-17
**51፥19** ዘዳ33፥19፤

አትውሰድ።
12የማዳንህን ደስታ መልስልኝ፤
በእሽታ መንፈስም ደግፈህ ያዘኝ።
13እኔም ለሕግ ተላላፊዎች መንገድህን
አስተምራለሁ፤
ኀጢአተኞችም ወደ አንተ ይመለሳሉ።
14የድነቴ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤
ደም ከማፍሰስ አድነኝ፤
አንደበቴም ስለ ጽድቅህ በእልልታ
ይዘምራል።
15ጌታ ሆይ ከንፈሮቼን ክፈት፤
አፌም ምስጋናህን ያውጃል።
16መሥዋዕትን ብትወድ ኖሮ ባቀረብሁልህ
ነበር፤
የሚቃጠል መሥዋዕትም ደስ
አያሰኝህም።
17እግዚአብሔር የሚቀበለው መሥዋዕት
የተሰበረ መንፈስ ነው፤[ኀ]
እግዚአብሔር ሆይ፤
አንተ የተሰበረውንና የተዋረደውን
ልብ አትንቅም።

18በበጎ ፈቃድህ ጽዮንን አበልጽጋት፤
የኢየሩሳሌምንም ቅጥሮች ሥራ።
19የጽድቅ መሥዋዕት፣ የሚቃጠል
መሥዋዕትና፣
ሙሉ የሚቃጠል መሥዋዕት ያን
ጊዜ ደስ ያሰኙሃል፤
ኮርማዎች በመሠዊያህ ላይ
የሚሠዉትም ያን ጊዜ ነው።

## መዝሙር 52

### የክፉዎች ዕጣ ፈንታ

*ለመዘምራን አለቃ፤ ኤዶማዊው ዶይቅ ወደ ሳኦል መጥቶ፣ "ዳዊት ወደ አቢሜሌክ ቤት መጥቶአል" ብሎ በነገረው ጊዜ፤ የዳዊት[ነ] ትምህርት*

1ኀያል ሆይ፤ በክፋት ለምን ትኵራራለህ?
አንተ በእግዚአብሔር ዐይን የተናቅህ፣
እንዴትስ ዘወትር ትታበያለህ?
2አንተ ማታለልን ሥራዬ ብለህ የያዝህ፤
አንደበትህ እንደ ሰላ ምላጭ፣
ጥፋትን ያውጠነጥናል።
3ከበጎ ነገር ይልቅ ክፋትን፣
እውነትን ከመናገር ይልቅ ሐሰትን
ወደድህ። ሴላ

መዝ66፥13፥15፤96፥8፤ኤር17፥26 **52** ርዕስ 1ሳሙ21፥7፤22፥9
**52፥1** መዝ10፥3፤44፥8፤94፥4 **52፥2** ዘኍ6፥5፤መዝ5፥9፤ 50፥19
**52፥3** ዘፀ10፥10፤1ሳሙ12፥25፤መዝ58፥3፤ኤር9፥5፤ አሞ5፥14-15፤ዮሐ3፥20፤ራእ21፥8

[በ]23 ወይም *መንገዱን ለሚገዝዘብ* ተብሎ መተርጐም ይችላል።
[ተ]6 በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጒም በትክክል አይታወቅም።
[ቸ]6 *አስተምረህኛል* ወይም *ትፈልጋለህ* ተብሎ መተርጐም ይቻላል።
[ኀ]17 ወይም *አምላክ ሆይ፤ የእኔ መሥዋዕት የተሰበረ*
[ነ]ርእሱ ምናልባት የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።

4አንተ አታላይ አንደበት ሆይ፤
ጐጂ ቃላትን ሁሉ ወደድህ!

5እግዚአብሔር ግን ለዘላለም
ያንኰታኵትሃል፤
ይነጥቅሃል፤ ከድንኳንህም መንጥቆ
ያወጣሃል፤
ከሕያዋንም ምድር ይነቅልሃል፡፡ ሴላ
6ጻድቃን ይህን ዐይተው ይፈራሉ፤
እንዲህ እያሉም ይሥቁበታል፤
7“እግዚአብሔርን መጠጊያ ያላደረገ፣
ነገር ግን በሀብቱ ብዛት የተመካ፣
በክፋቱም የበረታ፣
ያ ሰው እነሆ!”

8እኔ ግን በእግዚአብሔር ቤት፣
እንደ ለመለመ የወይራ ዛፍ ነኝ፤
ከዘላለም እስከ ዘላለም፣
በእግዚአብሔር ምሕረት እታመናለሁ፡፡
9ስላደረግኸው ነገር ለዘላለም አመሰግንሃለሁ፤
ስምህ መልካም ነውና ስምህን ተስፋ
አደርጋለሁ፤
በቅዱሳንም መካከል አመሰግንሃለሁ፡፡

## መዝሙር 53

### አምላክ የለሾች

53፥1-6 ተጓ ምብ-መዝ14፥1-7

ለመዘምራን አለቃ፤ በማኸላት፤ የዳዊት ትምህርት፡፡[ኘ]

1ቂል በልቡ፣
“እግዚአብሔር የለም” ይላል፡፡
ብልሹዎች ናቸው፤ ተግባራቸውም
ጸያፍ ነው፤
በጎ ነገርን የሚያደርግ አንድ እንኳ
የለም፡፡

2በማስተዋል የሚመላለስ፣
እግዚአብሔርን የሚፈልግ እንዳለ ለ
ማየት፣
እግዚአብሔር ከሰማይ፣
ወደ ሰው ልጆች ተመለከተ፡፡
3ሁሉም ወደ ሌላ ዘወር አሉ፤
በአንድነትም ተበላሹ፤
አንድ እንኳ፣
በጎ የሚያደርግ የለም፡፡

4ሰው እንጀራ እንደሚበላ ሕዝቤን
የሚበሉት፣
እግዚአብሔርንም ጠርተው የማያውቁት፣
እነዚያ ክፉ አድራጊዎች ከቶ አይማሩ
ምን?
5የሚያስፈራ ነገር በሌለበት፣
በዚያ፣ በፍርሀት ተዋጡ፤
እግዚአብሔር የዘመቱብህን ሰዎች ዐጥንት
በተነ፤
እርሱ እግዚአብሔር ስለ ናቃቸው፣ አንተ
አሳፈርሃቸው፡፡
6ምነው ለእስራኤል የሚሆን መዳን
ከጽዮን በወጣ!
እግዚአብሔር የሕዝቡን ምርኮ
በሚመልስበት ጊዜ፣
ያዕቆብ ሐሤት ያድርግ፤ እስራኤል
ደስ ይበለው፡፡

## መዝሙር 54

### ለፍትሕ አምላክ የቀረበ አቤቱታ

ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች፤ ዜፋውያን ወደ ሳኦል መጥተው፣ “ዳዊት በእኛ ዘንድ ተደብቆአል” ባሉት ጊዜ፤ የዳዊት ትምህርት፡፡[ኦ]

1እግዚአብሔር ሆይ፤ በስምህ አድነኝ፤
በኀይልህም ፍረድልኝ፡፡
2እግዚአብሔር ሆይ፤ ጸሎቴን ስማልኝ፤
የአፌንም ቃል አድምጥ፡፡

3ባዕዳን ተነሥተውብኛልና፤
ግፈኞች ነፍሴን ሽተዋታል፤
እግዚአብሔርንም ከምንም አልቈጠሩም፡፡
ሴላ
4እነሆ፤ እግዚአብሔር ረዳቴ ነው፤
ጌታ ም ደግፎ ይይዘኛል፡፡

5የገዛ ክፋታቸው በሚያደቡብኝ ላይ
ይመለስባቸው፤
በቃልህ ታማኝ ነህና አጥፋቸው፡፡

6በበጎ ፈቃድ መሥዋዕት እሠዋልሃለሁ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ መልካም ነውና፣
ለስምህ ምስጋና አቀርባለሁ፤
7ከመከራ ሁሉ ታድጎኛልና፤
ዐይኔም የጠላቶቼን ውድቀት ለማየት
በቅቶአል፡፡

## መዝሙር 55

### በስደት ጊዜ የቀረበ ጸሎት

ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች፤ የዳዊት ትምህርት[ከ]

1እግዚአብሔር ሆይ፤ ጸሎቴን ስማ፤
ልመናዬን ቸል አትበል፤
2ወደ እኔ ተመልከት፤ መልስልኝም፡፡
በውስጤ ታውኬአለሁ፤
ተናውጬአለሁም፤
3በጠላት ድምፅ ተሸበርሁ፤
በክፉዎች ድንፋታ ደነገጥሁ፤
መከራ አምጥተውብኛልና፤
በቍጣም ተነሣሥተው ጠላት ሆነውብኛል፡፡

4ልቤ በውስጤ ተጨነቀብኝ፤
የሞት ድንጋጤም በላዬ መጣ፡፡
5ፍርሀትና እንቅጥቃጤ መጣብኝ፤
ሽብርም ዋጠኝ፡፡

[ኘ]ርእሱ ምናልባት የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል፡፡
[ኦ]ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚ ያሳይ ሊሆን ይችላል፡፡
[ከ]ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚ ያሳይ ሊሆን ይችላል፡፡

52፥4 መዝ5፥9፤ 10፥7፤109፥2፤120፥2፥3፤ምሳ10፥31፤12፥19
52፥5 ዘዳ28፥63፤ 29፥28፤ኢዮ28፥13፤ 40፥12፤ኢሳ22፥19፤ ሕዝ17፥24
52፥6 ኢዮ22፥19
52፥7 2ሳሙ22፥3 ፤መዝ49፥6፤ምሳ11፥28፤ማር10፥23
52፥8 መዝ1፥3፤6፥4 ፤13፥5፤ራእ11፥4
52፥9 ዘዳ7፥6፤ኢዮ 7፥6፤መዝ16፥3፤25፥3፤ 30፥12፤54፥6
53፥1 መዝ10፥4፤ 74፥22፤107፥17፤ምሳ10፥23
53፥2 2ዜና15፥2፤ መዝ33፥13፤82፥5፤ ኤር4፥22፤8፥8
53፥3 ሮሜ3፥10-12
53፥5 ዘሌ26፥17 ፤2ነገ17፥20፤23፥14፤ኢዮ8፥22፤መዝ141፥7 ፤ኤር6፥30፤8፥1፤14፥19፤ሰቆ5፥22፤ሕዝ6፥5
54፥ ርዕስ1ሳሙ 23፥19፤26፥1
54፥1 1ሳሙ24፥15፤ 2ዜና20፥6፤መዝ20፥1
54፥2 መዝ4፥1፤5፥1 ፤55፥1
54፥3 1ሳሙ20፥1፤ መዝ18፥48፤36፥1፤ 86፥14፤140፥1፥4፥11
54፥4 1ዜና5፥20፤ መዝ18፥35፤20፥2
54፥5 ዘዳ32፥35፤ መዝ89፥49፤94፥23፤ ምሳ24፥12፤ኢሳ42፥3
54፥6 ዘሌ7፥12፥16፤ ዕዝ1፥4፤መዝ27፥6፤ 44፥8፤52፥9፤69፥30፤ 138፥2፤142፥7፤145፥1
54፥7 መዝ34፥6፤ 59፥10፤92፥11፤ 112፥8፤118፥7
55፥1 መዝ27፥9፤ ሰቆ3፥56
55፥2 1ሳሙ1፥15-16፤መዝ4፥1፤77፥3፤86፥6-7፤142፥2
55፥3 2ሳሙ16፥6-8፤መዝ17፥9፤44፥16፤ 71፥11፤143፥3
55፥4 ኢዮ18፥11፤ መዝ6፥3
55፥5 ዘዳ28፥67፤ ኢዮ4፥14፤ኢሳ21፥4፤ ኤር46፥5፤49፥5፤ሕዝ 7፥18፤2ቆሮ7፥15

6እኔም እንዲህ አልሁ፤ “ምነው የርግብ
ክንፍ በኖረኝ!
በርሬ በሄድሁና ባረፍሁ ነበር፤
7እነሆ፤ ኰብልዬ በራቅሁ፣
በምድረ በዳም በሰነበትሁ ነበር፤ ሴላ
8ከዐውሎ ነፋስና ከውሽንፍር ሽሽቼ፣
ወደ መጠለያዬ ፈጥኜ በደረስሁ
ነበር።”

9ጌታ ሆይ፤ ግፍንና ሁከትን በከተማዪቱ
ውስጥ አይቼአለሁና፣
ግራ አጋባቸው፤ ቋንቋቸውንም
ደበላልቅ።
10ቀንና ሌሊት ቅጥሯ ላይ ወጥተው
ይዞሯታል፤
ተንኰልና መከራ በውስጧ አለ።
11ጥፋት በመካከሏ ይገኛል፤
ግፍና አታላይነትም ከጎዳናዋ
አይጠፋም።

12የሚዘልፈኝ ጠላት አይደለምና፤
ቢሆንማ ኖሮ በታገሥሁት ነበር፤
የሚጠላኝ፣ ራሱንም ቀና ቀና ያደረገብኝ
ባላንጣ አይደለም፤
ቢሆንማ ከእርሱ በተሸሸግሁ ነበር።

13ነገር ግን አድራጊው አንተ ነህ፤
እኩያዬ፣ ባልንጀራዬና ወዳጄ፤
14በእግዚአብሔርም ቤት አብረን በሕዝብ
መካከል ተመላለስን፤
ደስ የሚል ፍቅር በአንድነት ነበረን።
15ሞት ሳይታሰብ ድንገት ይምጣባቸው፤
በሕይወት ሳሉ ወደ ሲኦል[ኸ] ይውረዱ፤
ክፋት በመካከላቸው አድራለችና።

16እኔ ግን ወደ እግዚአብሔር እጣራለሁ፤
*እግዚአብሔርም* ያድነኛል።
17በማታ፣ በጥዋትና በቀትር፣
እጮኻለሁ፤ እቃትታለሁም፤
እርሱም ድምፄን ይሰማል።
18በተቃውሞ የተነሡብኝ ብዙዎች
ናቸውና፣
ከተቃጣብኝ ጦርነት፣
ነፍሴን በሰላም ይቤዥታል።
19አካሄዳቸውን አልቀየሩምና፣
እግዚአብሔርንም አልፈሩትምና፣
ከጥንት ጀምሮ በዙፋኑ ላይ ያለ
አምላክ፣ ሴላ
ሰምቶ ያዋርዳቸዋል።

20ባልንጀራዬ የምለው ሰው እጁን
በወዳጆቹ ላይ ሰነዘረ፤
ቃል ኪዳኑንም አፈረሰ።
21አፉ ከቅቤ ይልቅ የለዘበ ነው፤
በልቡ ግን ጦርነት አለ፤

55፥7 1ሳሙ23፥14
55፥8 መዝ31፥20፤77፥18፤ኢሳ4፥6፤25፥4፤28፥2፤29፥6፤32፥2
55፥9 ዘፍ4፥17፤11፥9፤መዝ11፥5፤ኢሳ59፥6፤ኤር6፥7፤ሕዝ7፥11፤ዕን1፥3፤ሐሥ2፥4
55፥10 1ጴጥ5፥8
55፥11 መዝ5፥9፤10፥7
55፥13 2ሳሙ15፥12
55፥14 መዝ42፥4፤ሐሥ1፥16-17
55፥15 መዝ49፥14፤64፥7፤ምሳ6፥15፤ኢሳ29፥5፤47፥9፡11፤1ተሰ5፥3
55፥17 መዝ5፥3፤88፥13፤92፥2፤141፥2፤ሐሥ3፥1፤10፥3፡ 9፡30
55፥19 ዘፀ15፥18፤ዘዳ33፥27፤መዝ29፥10፤36፥1፤64፥4፤78፥59
55፥20 መዝ7፥4፤41፥9
55፥21 መዝ12፥2፤57፥4፤59፥7፤64፥3፤ምሳ5፥3፤6፥24፤12፥18፤ራእ1፥16
55፥22 መዝ15፥5፤18፥35፤21፥7፤37፥24፤112፥6፤ማቴ6፥25-34፤1ጴጥ5፥7
55፥23 ኢዮ15፥32፤መዝ5፥6፤9፥15፤11፥1፤25፥2፤30፥3፤56፥3፤73፥18፤94፥13፤ኢሳ14፥15፤ሕዝ28፥8፤ሉቃ8፥31
56፥1 መዝ6፥2፤17፥9፤57፥1-3
56፥2 መዝ35፥1፡25፤124፥3
56፥3 መዝ55፥4-5፡23
56፥4 ቍ10፤መዝ27፥1፤118፥6፤ማቴ10፥28፤ዕብ13፥6
56፥5 መዝ41፥7፤2ጴጥ3፥16
56፥6 መዝ17፥11፤59፥3፤71፥10፤94፥21፤ማር3፥6
56፥7 መዝ36፥12፤55፥23፤ምሳ19፥5፤ሕዝ17፥15፤ሮሜ2፥3፤ዕብ12፥25
56፥8 2ነገ20፥5፤ኢሳ4፥3፤ዳን7፥10፤12፥1፤ሚል3፥16
56፥9 ዘኍ14፥8፤ዘዳ31፥6፤መዝ9፥3፤102፥2፤ሮሜ8፥31

ቃሉ ከዘይት ይልቅ የለሰለሰ ነው፤
ይሁን እንጂ የተመዘዘ ሰይፍ ነው።

22የከበደህን ነገር *በእግዚአብሔር* ላይ
ጣል፤
እርሱ ደግፎ ይይዝሃል፤
የጻድቁንም መናወጥ ከቶ አይፈቅድም።
23አንተ ግን፣ እግዚአብሔር ሆይ፤
ክፉዎችን ወደ ጥፋት ጒድጓድ
ታወርዳቸዋለህ፤
ደም የተጠሙ ሰዎችና አታላዮች፣
የዘመናቸውን እኩሌታ አይኖሩም።

እኔ ግን በአንተ እታመናለሁ።

## መዝሙር 56

### በእግዚአብሔር መደገፍ

*ለመዘምራን አለቃ፤ “ርግቢቱ ሩቅ ባለው ወርካ ላይ” በተባለው ቅኝት፤ ፍልስጤማውያን በጌት በያዙት ጊዜ፤ የዳዊት ቅኔ[ሠ]*

1እግዚአብሔር ሆይ፤ የሰዎች መረገጫ
ሆኛለሁና ማረኝ፤
ቀኑንም ሙሉ በውጊያ
አስጨንቀውኛል።
2ጠላቶቼ ቀኑን ሙሉ በላዬ ቆሙ፤
በትዕቢት የሚዋጉኝ ብዙዎች
ናቸውና።

3ፍርሀት በሚይዘኝ ጊዜ፣
እምነቴን በአንተ ላይ አደርጋለሁ።
4ቃሉን በማመሰግነው አምላክ፣
በእግዚአብሔር ታምኛለሁ፤ አልፈራም፤
ሥጋ ለባሽ ምን ሊያደርገኝ ይችላል?

5ቀኑን ሙሉ ቃሌን ያጣምሙታል፤
ዘወትርም ሊጐዱኝ ያሤራሉ።
6ይዶልታሉ፤ ያደባሉ፤
ርምጃዬን ይከታተላሉ፤
ነፍሴንም ለማጥፋት ይሻሉ።

7እግዚአብሔር ሆይ፤ ከቶ እንዳያመልጡ፣
ሕዝቦቹን በቍጣህ ጣላቸው።

8ሰቆቃዬን መዝግብ፤
እንባዬን በዕቃህ አጠራቅም፤[ዐ]
ሁሉስ በመዝገብህ የተያዘ አይደለምን?

9ወደ አንተ በተጣራሁ ቀን፣
ጠላቶቼ ወደ ኋላቸው ይመለሳሉ፤
በዚህም፣ አምላክ ከጐኔ መቆሙን
ዐውቃለሁ።
10ቃሉን በማመሰግነው አምላክ፣
ቃሉን በማመሰግነው *በእግዚአብሔር*፣

[ኸ]15 ዕብራይስጡ *ሲኦል* ይላል፤ አንዳንድ የእንግሊዝኛ ቅጆች ግን *መቃብር* ይላሉ።
[ሠ]ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።
[ዐ]8 *እንባዬን በወይን አቍማዳህ ውስጥ ጨምር* ወይም *እንባዬን በመጽሐፍህ መዝግብ*

11በአምላክ ታምኛለሁ፤ አልፈራም፤
ሥጋ ለባሽ ምን ሊያደርገኝ ይችላል?

12እግዚአብሔር ሆይ፤ የአንተ ስእለት
አለብኝ፤
የማቀርብልህም የምስጋና መሥዋዕት
ነው፤
13በሕያዋን ብርሃን፣[ዘ]
በእግዚአብሔር ፊት እመላለስ ዘንድ፣
ነፍሴን ከሞት፣[ዠ]
እግሬንም ከመሰናክል አድነሃልና።

## መዝሙር 57

### በጨካኝ ጠላቶች ዘንድ

57፥7-11 ተጓ ምብ-መዝ108፥1-5

ለመዘምራን አለቃ፤ "አታጥፋ" በሚለው ቅኝት የሚዘመር፤ ከሳኦል ፊት ሸሽቶ በዋሻ በነበረበት ጊዜ፤ የዳዊት ቅኔ።[የ]

1ማረኝ፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ ማረኝ፤
ነፍሴ አንተን መጠጊያ አድርጋለችና፤
በክንፎችህ ሥር እጠለላለሁ።

2ለእኔ ያሰበውን ወደሚፈጽምልኝ አምላክ፣
ወደ ልዑል እግዚአብሔር እጮኻለሁ።
3ከሰማይ ልኮ ያድነኛል፤
የረገጡኝን ያዋርዳቸዋል፤ ሴላ
እግዚአብሔር ምሕረቱንና ታማኝነቱን
ይልካል።

4ነፍሴ በአንበሶች ተከብባለች፤
በሚዘነጣጥሉ አራዊት መካከል
ወድቄአለሁ፤
እነዚህም፣ ጥርሳቸው ጦርና ፍላጻ፣
ምላሳቸውም የተሳለ ሰይፍ የሆኑ
ሰዎች ናቸው።

5እግዚአብሔር ሆይ፤ ከሰማያት በላይ
ከፍ ከፍ በል፤
ክብርህም በምድር ሁሉ ላይ ትስፋን።
6ለእግሬ ወጥመድን ዘረጉ፤
ነፍሴንም አጐበጧት፤
በመተላለፊያዬ ላይ ጕድጓድ ቈፈሩ፤
ነገር ግን ራሳቸው ገቡበት። ሴላ

7እግዚአብሔር ሆይ፤ ልቤ ጽኑ ነው፤
ልቤ ጽኑ ነው፤
እቀኛለሁ፤ አዜማለሁ።
8ነፍሴ ሆይ፤ ንቂ!
በገናና መሰንቆም ተነሡ!
እኔም በማለዳ እነሣለሁ።

9ጌታ ሆይ፤ በሕዝቦች መካከል
አመሰግንሃለሁ፤
በሰዎችም መካከል እዘምርልሃለሁ፤
10ምሕረትህ እስከ ሰማይ ከፍ ብላለችና፤
ታማኝነትህም እስከ ደመናት
ትደርሳለች።

11እግዚአብሔር ሆይ፤ ከሰማያት በላይ ከፍ
ከፍ በል፤
ክብርህም በምድር ሁሉ ላይ ትስፋን።

## መዝሙር 58

### የምድር ዳኞች ፈራጅ

ለመዘምራን አለቃ፤ "አታጥፋ" በሚለው ቅኝት የሚዘመር፤ የዳዊት ቅኔ[ደ]

1ኀያላን ሆይ፤ በውኑ ጽድቅ ከአፋችሁ
ይወጣል?
የሰው ልጆች ሆይ፤ በቅን
ትፈርዳላችሁን?
2የለም፤ በልባችሁ ክፋትን ታውጠ
ነጥናላችሁ፤
በእጃችሁም ዐመፅን በምድር ላይ
ትጐነጕናላችሁ።
3ክፉዎች በማሕፀን ሳሉ ከመንገድ የወጡ
ናቸው፤
ሲወለዱ ጀምሮ የተሳሳቱና ውሸታሞች
ናቸው።
4መርዛቸው እንደ እባብ መርዝ ነው፤
አልሰማ ብላ ጆሮዋን እንደ ደፈነች
እፉኝት ናቸው፤
5ጆሮዋንም የደፈነችው የመተተኛውን
ወይም የጠቢቡን ደጋሚ ቃል
ላለመስማት ነው።
6አምላክ ሆይ፤ ጥርሳቸውን በአፋቸው
ውስጥ ስበር፤
*እግዚአብሔር ሆይ፤ የአንበሶቹን*
*መንጋጋ አወላልቅ!*
7ፈጥኖ እንደሚያልፍ ወራጅ ውሃ ይጥፉ፤
ቀስታቸውን ሲስቡ ፍላጻቸው ዱልዱም
ይሁን።
8ሲሄድ እንደሚቀልጥ ቀንድ አውጣ
ይሁኑ፤
ፀሓይን እንደማያይ ጭንጋፍ ይሁኑ።
9የእሾኽ እሳት ገና ድስታችሁን
ሳያሰማው፣
እርጥቡንም ደረቁንም እኩል በዐውሎ
ነፋስ ጠራርጎ ይወስዳቸዋል።[ጀ]
10ጻድቃን በቀልን ባዩ ጊዜ ደስ
ይላቸዋል፤
እግራቸውንም በግፈኞች ደም
ይታጠባሉ።
11ሰዎችም፣ "በእርግጥ ለጻድቃን ብድራት
ተቀምጦላቸዋል፤
በእውነትም በምድር ላይ የሚፈርድ
አምላክ አለ" ይላሉ።

**56፥12** መዝ50፥14
**56፥13** ኢዮ33፥30፤ መዝ30፥3፤33፥19፤ 49፥15፤86፥13፤ 107፥20፤116፥8
**57** ርዕስ1ሳሙ22፥1፤24፥3፤መዝ142ርዕስ
**57፥1** ሩት2፥12፤ መዝ2፥12፤9፥9፤34፥22፤ኢሳ26፥20፤ማቴ 23፥37
**57፥2** መዝ138፥8
**57፥3** መዝ18፥9፥16፤25፥10፤40፥11፤56፥1፤69፥14፤115፥1፤142፥6፤144፥5፡7
**57፥4** መዝ35፥17፤ 55፥21፤ምሳ30፥14
**57፥5** ቊ11፤መዝ 108፥5
**57፥6** አስ6፥13፤ መዝ7፥15፤9፥15፤10፥9፤31፥4፤38፥6፤140፥5፤ 145፥14፤ምሳ 28፥10፤መክ10፥8
**57፥7** መዝ112፥7
**57፥8** መዝ33፥2፤ 149፥3፤150፥3
**57፥10** መዝ36፥5
**57፥11** ቊ5፤መዝ 8፥1፤113፥4
**58፥1** መዝ82፥2
**58፥2** መዝ94፥20፤ ኢሳ10፥1፤ማቴ15፥19፤ሉቃ6፥38
**58፥4** ዘኁ21፥6
**58፥5** መዝ81፥11፤ መክ10፥11፤ኤር8፥17
**58፥6** ኢዮ4፥10፤ መዝ3፥7
**58፥7** ዘሌ26፥36፤ ኢዮ11፥16፤መዝ11፥2፤57፥4፤64፥3
**58፥8** ኢዮ3፥16፤ ኢሳ13፥7
**58፥9** ኢዮ7፥10፤ 21፥8፤መዝ118፥12፤ መክ7፥6
**58፥10** ዘዳ32፥35፤ ኢዮ22፥19፤መዝ7፥9፤ 68፥23፤91፥8፤ኤር 11፥20፤ሮሜ12፥17-21
**58፥11** ዘፍ15፥1፤ 18፥25፤መዝ128፥2፤ ሉቃ6፥23

[ዘ]13 ወይም *እኔን ከሞት*
[ዠ]13 ወይም *በሕያዋን ምድር*
[የ]ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።
[ደ]ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።

[ጀ]9 በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጒም በትክክል አይታወቅም።

## መዝሙር 59

### ከፉዎችን በመቃወም የቀረበ ጸሎት

ለመዘምራን አለቃ፤ “አታጥፋ” በሚለው ቅኝት የሚዜም፤ ዳዊትን ለመግደል ሰዎች ቤቱን ከብበው እንዲጠብቁት ሳኦል በላካቸው ጊዜ፤ የዳዊት ቅኔ[ገ]

1አምላክ ሆይ፤ ከጠላቶቼ እጅ አድነኝ፤
ሊያጠቁኝ ከሚነሡብኝም ጠብቀኝ።
2ከክፉ አድራጊዎች ታደገኝ፤
ደም ከተጠሙ ሰዎችም አድነኝ።
3እነሆ በነፍሴ ላይ አድብተዋልና፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ ጨካኞች ያለ
በደሌ፣ ያለ ኀጢአቴ
በላዬ ተሰብስበው ዶለቱብኝ።
4እነርሱ ያለ በደሌ ሊያጠቁኝ
ተዘጋጅተው መጡ፤
አንተ ግን ትረዳኝ ዘንድ ተነሥ፤
ሁኔታዬንም ተመልከት።
5የሰራዊት አምላክ የሆንህ፣ አንተ የእስራኤል
አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤
ሕዝቦችን ሁሉ ለመቅጣት ተነሥ፤
በተንኰላቸው በደል የሚፈጽሙትንም
ሁሉ አትማራቸው። ሴላ

6እንደ ውሻ እያላዘኑ፣
በምሽት ተመልሰው ይመጣሉ፤
በከተማዪቱም ዙሪያ ይራወጣሉ።
7ከአፋቸው የሚወጣውን ተመልከት፤
ሰይፍ በከንፈራቸው ላይ አለ፤
“ማን ሊሰማን ይችላል?” ይላሉና።
8እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ግን
ትሥቅባቸዋለህ፤
ሕዝቦችን ሁሉ በንቀት ታያቸዋለህ።

9ብርታቴ ሆይ፤ አንተን እጠብቃለሁ፤
አምላክ ሆይ፤ አንተ መጠጊያዬ ነህና።

10እግዚአብሔር በምሕረቱ ይገናኘኛል፤
አምላኬ የጠላቶቼን ውድቀት
ያሳየኛል።
11ጋሻችን[ጠ] ጌታ ሆይ፤ አትግደላቸው፤
አለበለዚያ ሕዝቤ ይረሳል፤
በኀይልህ አንከራታቸው፤
ዝቅ ዝቅም አድርጋቸው።
12ከአፋቸው ስለሚወጣው ኀጢአት፣
ከከንፈራቸውም ስለሚሰነዘረው ቃል፣
በትዕቢታቸው ይያዙ።
ስለ ተናገሩት መርገምና ውሸት፣
13በቍጣ አጥፋቸው፤
ፈጽመህም አስወግዳቸው፤
በዚህም እግዚአብሔር የያዕቆብ ገዥ መሆኑ፣
እስከ ምድር ዳርቻ ይታወቃል። ሴላ

14እንደ ውሻ እያላዘኑ፣
በምሽት ተመልሰው ይመጣሉ፤
በከተማዪቱም ዙሪያ ይራወጣሉ።

59 ርዕስ1ሳሙ19፥11
59፥1 መዝ20፥1፤ 143፥9
59፥2 14፥4፤26፥9፤ 36፥12፤53፥4፤92፥7፤94፥16፤139፥19፤ምሳ29፥10
59፥3 መዝ56፥6
59፥4 መዝ13፥3፤ 119፥3፤ማቴ5፥11
59፥5 9፥5፤44፥23፤69፥6፤80፥4፤84፥8፤ኢሳ10፥3፤ኤር18፥23
59፥6 ቍ14፤መዝ 22፥16
59፥7 ኢዮ22፥13፤ መዝ55፥21፤94፥4፤ ምሳ10፥32፤12፥23፤ 15፥2፡28
59፥8 መዝ2፥4፤ 37፥13፤ምሳ1፥26
59፥9 መዝ9፥9፤ 18፥1፡2፤62፥2፤71፥3
59፥11 ዘዳ4፥9፤ 6፥12 ፤መዝ3፥3፤84፥9፤89፥10፤106፥27፤144፥6፤ኢሳ33፥3
59፥12 መዝ10፥7፤ 64፥8፤ምሳ10፥14፤12፥13፤ኢሳ2፥12፤5፥15፤ሶፎ3፥11
59፥13 መዝ83፥18፤104፥35
59፥15 ኢዮ15፥23
59፥16 ዘዳ4፥30፤ 1ሳሙ2፥10፤2ሳሙ22፥3፤መዝ5፥3፤88፥13፤101፥1፤108፥1
59፥17 ቍ10
60 ርዕስ2ሳሙ8፥13
60፥1 2ሳሙ5፥20፤መዝ44፥9፤79፥5፤ 80፥3
60፥2 2ዜና7፥14፤ መዝ18፥7
60፥3 መዝ71፥20፤ 75፥8፤ኢሳ29፥9፤51፥17፤63፥6፤ኤር25፥16፤ ዘካ12፥2፤ራእ14፥10
60፥4 ኢሳ5፥26፤ 11፥10፡12፤18፥3
60፥5 ዘዳ33፥12፤ ኢዮ40፥14
60፥6 ዘፍ12፥6፤ 33፥17
60፥7 ዘፍ41፥52፤ 49፥10፤ዘኍ34፥19፤ ኢሱ13፥31
60፥8 2ሳሙ8፥1
60፥10 ኢሱ7፥12
60፥11 መዝ146፥3

15ምግብ ፍለጋ ይራወጣሉ።
ካልጠገቡም ያላዝናሉ።
16እኔ ግን ስለ ኀይልህ እዘምራለሁ፤
በማለዳም ስለ ምሕረትህ እዘምራለሁ፤
አንተ መጠጊያዬ፣
በመከራም ቀን ዐምባዬ ነህና።
17ብርታቴ ሆይ፤ ውዳሴ አቀርብልሃለሁ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ መጠጊያዬ፣
የምትወደኝም አምላኬ ነህና።

## መዝሙር 60

### ከሽንፈት በኋላ የቀረበ ብሔራዊ ጸሎት

60፥5-12 ተጓ ምብ-መዝ108፥6-13

ለመዘምራን አለቃ፤ “የኪዳን ጽጌረዳ”። በሚለው ቅኝት የሚዘመር፤[ጨ] በሰሜናዊ ምዕራብ መስጴጦምያና[ጰ] በ ማእከላዊ ሶርያ የሚኖሩትን አራማውያን[ጰ] በወጋቸው ጊዜ፣ ኢዮአብም ተመልሶ በጨው ሸለቆ አሥራ ሁለት ሺህ ኤዶማውያንን በፈጀ ጊዜ፣ ለትምህርት፤ የዳዊት ቅኔ

1እግዚአብሔር ሆይ፤ ጣልኸን፤ አንኰታኰትኸን፤
ተቈጣኸንም፤ አሁን ግን መልሰህ
አብጀን።
2ምድሪቱን አናወጥሃት፤ ፍርክስክስ
አደረግሃት፤
ትንገዳገዳለችና ስብራቷን ጠግን።
3ለሕዝብህ አበሳውን አሳየኸው፤
ናላ የሚያዞር የወይን ጠጅ
እንድንጠጣም ሰጠኸን።
4ነገር ግን ከቀስት እንዲያመልጡ፣
ለሚፈሩህ ምልክት አቆምህላቸው።
ሴላ

5ወዳጆችህ ይድኑ ዘንድ፣
በቀኝ እጅህ ርዳን፤ መልስም ስጠን።
6እግዚአብሔር ከመቅደሱ እንዲህ ሲል
ተናገረ፤
“ደስ እያለኝ የሴኬምን ምድር
እሸነሽናለሁ፤
የሱኮትን ሸለቆ አከፋፍላለሁ።
7ገለዓድ የእኔ ነው፤ ምናሴም የእኔ ነው፤
ኤፍሬም የራስ ቍሬ ነው፤
ይሁዳም በትረ መንግሥቴ ነው።
8ሞዓብ የመታጠቢያ ገንዳዬ ነው፤
በኤዶምያስ ላይ ጫማዬን እወረውራለሁ፤
በፍልስጥኤም ላይ በድል እልል
እላለሁ።”

9ወደ ተመሸገው ከተማ ማን ያመጣኛል?
ማንስ ወደ ኤዶምያስ ይመራኛል?
10አምላክ ሆይ፤ የጣልኸን አንተ
አይደለህምን?

[ገ]ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።
[ጠ]11 ወይም ልዑል ተብሎ መተርጐም ይችላል።
[ጨ]ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።
[ጰ]ርእሱ የአራማውያን ወይም የሰሜን ምዕራብ መስጴጦምያ ነው።
[ጰ]ርእሱ በመካከለኛው ሶርያ የሚገኙት አራማውያንን የሚያመለክት ነው።

እግዚአብሔር ሆይ፤ ከሰራዊታችን ጋር
እኮ አልወጣ አልህ!
11 በጠላት ላይ ድልን አቀዳጀን፤
የሰው ርዳታ ከንቱ ነውና፡፡
12 በእግዚአብሔር ክንደ ብርቱ እንሆናለን፤
ጠላቶቻችንን የሚረጋግጥልን እርሱ
ነውና፡፡

## *መዝሙር* 61

### የግዞተኛ ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች የሚዘመር፤ የዳዊት መዝሙር*

1 እግዚአብሔር ሆይ፤ ጩኸቴን ስማ፤
ጸሎቴንም አድምጥ፡፡
2 ልቤ በዛለ ጊዜ፣
ከምድር ዳርቻ ወደ አንተ እጣራለሁ፤
ከእኔ ይልቅ ከፍ ወዳለው ዐለት
ምራኝ፡፡
3 አንተ መጠጊያዬ፣
ከጠላትም የምተገንብህ ጽኑ ግንብ
ሆነኸኛልና፡፡
4 በድንኳንህ ለዘላለም ልኑር፤
በክንፎችህም ጥላ ልከለል፡፡ ሴላ
5 አምላክ ሆይ፤ ስእለቴን ሰምተሃልና፤
ስምህን የሚፈሩትንም ሰዎች ርስት
ለእኔ ሰጠህ፡፡
6 የንጉሡን ዕድሜ አርዝምለት፤
ዘመኑንም እስከ ብዙ ትውልድ
ጨምርለት፤
7 በእግዚአብሔር ፊት ለዘላለም ይንገሥ፤
ይጠብቁት ዘንድ ምሕረትህንና
ታማኝነትህን አዘጋጅለት፡፡
8 ስለዚህ ለስምህ ዘወትር ውዳሴ
አቀርባለሁ፤
ስእለቴንም በየጊዜው እፈጽማለሁ፡፡

## *መዝሙር* 62

### ተስፋ በእግዚአብሔር ላይ ብቻ

*ለመዘምራን አለቃ፤ ለኤዶታም፤ የዳዊት መዝሙር*

1 ነፍሴ ዕረፍት የምታገኘው በእግዚአብሔር
ብቻ ነው፤
ድነቴም የሚመጣልኝ ከእርሱ ዘንድ
ነው፡፡
2 ዐለቴና መድኀኒቴ እርሱ ብቻ ነው፤
መጠጊያዬም እርሱ ነው፤ ከቶም
አልናወጥም፡፡
3 ሰውን የምታጠቁት እስከ መቼ ነው?
ይህን የዘመመ ግድግዳ፣ የተንጋደደ
ዐጥር፣
ሁላችሁ ገፍታችሁ ልትጥሉት
ትሻላችሁ?
4 ከታላቅ ክብሩ ሊያዋርዱት፣
ይህን አንድ ነገር ወጠኑ፤
ሐሰት ባለበት ነገር ደስ ይሰኛሉ፤
በአፋቸው ይመርቃሉ፤
በልባቸው ግን ይራገማሉ፡፡ ሴላ
5 ነፍሴ ሆይ፤ ዐርፈሽ እግዚአብሔርን ብቻ
ጠብቂ፤
ተስፋዬ ከእርሱ ዘንድ ነውና፡፡
6 ዐለቴና መድኀኒቴ እርሱ ብቻ ነው፤
መጠጊያዬም እርሱ ነው፤ እኔም
አልናወጥም፡፡[θ]
7 መዳኔና ክብሬ በእግዚአብሔር ነው፤
ብርቱ ዐለቴና መሸሸጊያዬ በእግዚአብሔር
ነው፡፡
8 ሰዎች ሆይ፤ ሁልጊዜ በእርሱ ታመኑ፤
ልባችሁን በፊቱ አፍስሱ፤
እግዚአብሔር መጠጊያችን ነውና፡፡ ሴላ
9 ከተናቀ ወገን መወለድ ከንቱ፣
ከከበረውም መወለዱ ሐሰት ነው፡፡
በሚዛን ላይ ከፍ ብለው ቢታዩም፣
ሁሉም በአንድነት ከነፋስ የቀለሉ
ናቸው፡፡
10 በዝርፊያ አትታመኑ፤
በቅሚያም ተስፋ አታድርጉ፤
በዚህ ብትበለጽጉም፣
ልባችሁ ይህን አለኝታ አያድርግ፡፡
11 እግዚአብሔር አንድ ነገር ተናገረ፤
እኔም ይህን ሁለት ጊዜ ሰማሁ፤
ኀይል የእግዚአብሔር ነው፡፡
12 ጌታ ሆይ፤ ምሕረትም የአንተ ነው፤
አንተ ለእያንዳንዱ፣
እንደ ሥራው ትከፍለዋለህ፡፡

## *መዝሙር* 63

### እግዚአብሔርን መፈለግ

*በይሁዳ ምድር በዳ በነበረ ጊዜ፤ የዳዊት መዝሙር*

1 እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ አምላኬ ነህ፤
አንተን ከልብ እሻለሁ፤
ውሃ በሌለበት፣
በደረቅና በተራቈተ ምድር፣
ነፍሴ አንተን ተጠማች፤
ሥጋዬም አንተን ናፈቀች፡፡
2 ስለዚህ በመቅደስ ውስጥ አየሁህ፤
ኀይልህንና ክብርህንም ተመለከትሁ፡፡
3 ምሕረትህ ከሕይወት ይበልጣልና፤
ከንፈሮቼ ያመሰግኑሃል፡፡
4 እንግዲህ፣ በሕይወቴ ዘመን አመሰግንሃለሁ፤
በአንተም ስም እጆቼን አነሣለሁ፡፡
5 ነፍሴ በቅቤና በስብ እንደሚረካ ሰው
ትረካለች፤

፤ምሳ3፥5
**60፥12** ኢዮ40፥12፤ መዝ44፥5
**61፥1** መዝ4፥1፤ 64፥1፤86፥6
**61፥2** መዝ6፥2፤ 18፥2፤31፥2፤94፥22
**61፥3** መዝ9፥9፤ 46፥1፤59፥9፤62፥7፤ ምሳ18፥10
**61፥4** ዘጸ32፥11፤ መዝ15፥1፤ማቴ 23፥37
**61፥5** ዘፀ6፥3፤ዘኍ 30፥2፤ዘዳ33፥9፤ነህ 1፥11፤መዝ56፥12፤ 102፥15፤ኢሳ59፥19፤ ማቴ6፥9
**61፥6** 1ነገ3፥14፤ መዝ21፥4
**61፥7** መዝ40፥11፤ 41፥12፤ሉቃ22፥69፤ ኤፌ1፥20፤ቈላ3፥1
**61፥8** ዘፀ15፥1፤ዘኍ 30፥2፤ዘዳ23፥21፤መዝ 7፥17፤30፥4
**62፥1** ቍ5፤መዝ 5፥3
**62፥2** ዘፀ15፥2፤ኢዮ 29፥18፤መዝ18፥31፤5 9፥9፤89፥26
**62፥3** ኢሳ30፥13
**62፥4** መዝ28፥3፤ 55፥21
**62፥5** ቍ1
**62፥7** መዝ61፥3
**62፥8** 1ሳሙ1፥15፤ መዝ37፥5፤42፥4፤ኢሳ 26፥4፤ማቴ26፥36-46
**62፥9** ኢዮ7፥7፤መዝ 49፥2፤ኢሳ40፥15
**62፥10** ኢዮ31፥25፤ መዝ12፥5፤ኢሳ61፥8 ፤ሕዝ22፥29፤ናሆ3፥1፤ ማቴ19፥23-24፤ 1ጢሞ6፥6-10፡17
**62፥11** 1ዜና29፥11 ፤ራእ19፥1
**62፥12** ኢዮ21፥31 ፤መዝ28፥4፤86፥5፤10 3፥8፤130፥7፤ማቴ16፥ 27፤ሮሜ2፥6፤1ቆሮ3፥ 8፤ቈላ3፥25
**63፥1** መዝ42፥2፤84፥ 2፤143፥6
**63፥2** ዘፀ16፥7፤መዝ 15፥1፤27፥4፤68፥24
**63፥3** መዝ36፥7፤ 69፥16፤106፥45፤ 109፥21
**63፥4** መዝ28፥2፤ 104፥33፤146፥2፤ኢሳ 38፥20፤1ጢሞ2፥8
**63፥5** መዝ36፥8፤ ማቴ5፥6

[θ]6 ወይም *ልዑል እግዚአብሔር ድነቴና ክብሬ ነው* ተብሎ
መተርጐም ይችላል፡፡

[6]በመኝታዬ አስብሃለሁ፤
ሌሊቱንም ሁሉ ስለ አንተ
አሰላስላለሁ።
[7]አንተ ረዳቴ ነህና፣
በክንፎችህ ሥር ተጠልዬ በደስታ
እዘምራለሁ።
[8]ነፍሴ አንተን የሙጥኝ ብላለች፤
ቀኝ እጅህም ደግፋ ይዛኛለች።

[9]ነፍሴን ለማጥፋት የሚሹ ግን፣
ወደ ምድር ጥልቅ ይወርዳሉ፤
[10]ለሰይፍ አልፈው ይሰጣሉ፤
የቀበሮዎችም ምግብ ይሆናሉ።

[11]ንጉሥ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለዋል፤
በእግዚአብሔርም ስም ቃል የሚገቡ ሁሉ
ይከብራሉ፤
የሐሰተኞች አንደበትም ትዘጋለች።

## መዝሙር 64

### የተሳዳቢዎች ቅጣት

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር*

[1]አምላክ ሆይ፤ የብሶት ቃሌን ስማ፤
ሕይወቴንም ከሚያስፈራ የጠላት ዛቻ
ከልላት።
[2]ከክፉዎች አድማ ሰውረኝ፤
ከዐመፀኞችም ሸንጎ ጋርደኝ።

[3]እነርሱ ምላሳቸውን እንደ ሰይፍ ይስላሉ፤
መርዘኛ ቃላቸውንም እንደ ፍላጻ
ያነጣጥራሉ።
[4]አሸምቀው ንጹሑን ሰው ይነድፉታል፤
ድንገት ይነድፉታል፤ አይፈሩምም።
[5]ክፉ ተግባር ለማከናወን እርስ በርስ
ይመካከራሉ፤
በሴር ወጥመድ ለመዘርጋት ይነጋገራሉ፤
"ማንስ ሊያየን ይችላል?"[ሬ] ይባባላሉ።
[6]ግፍን ያውጠነጥናሉ፤
ደግሞም፣ "የረቀቀች ሤራ
አዘጋጅተናል" ይላሉ፤
አቤት! ልቡ፣ አእምሮውም እንዴት
ጥልቅ ነው!

[7]እግዚአብሔር ግን በፍላጻው ይነድፋቸዋል፤
እነርሱም ድንገት ይቈስላሉ።
[8]በገዛ ምላሳቸው ያሰናክላቸዋል፤
ጥፋትንም ያመጣባቸዋል፤
የሚያዩአቸውም ሁሉ በትዝብት
ራሳቸውን ይነቀንቃሉ።

[9]የሰው ልጆች ሁሉ ይፈራሉ፤
የእግዚአብሔርን ሥራ በይፋ ያወራሉ፤
ያደረገውንም በጥሞና ያሰላስላሉ።
[10]ጻድቅ *በእግዚአብሔር* ደስ ይበለው፤
እርሱንም መጠጊያ ያድርገው፤
ልበ ቅኖችም ሁሉ ደስ ይበላቸው።

**63፥6** ዘዳ6፥4-9፤ መዝ16፥7፤119፥148፤ ማቴ14፥25
**63፥7** ሩት2፥12፤ መዝ27፥9፤118፥7
**63፥8** ዘኍ32፥12፤ መዝ41፥12፤ሆሴ6፥3
**63፥9** መዝ40፥14፤ 55፥15፤71፥20፤95፥4፤ 139፥15
**63፥10** ኤር18፥21፤ ሰቆ5፥18፤ሕዝ35፥5፤ አሞ1፥11
**63፥11** ኢዮ5፥16፤ ኢሳ19፥18፤45፥23፤ 65፥16፤ሮሜ3፥19
**64፥1** መዝ140፥1፤ 142፥2
**64፥2** ዘፀ1፥10፤መዝ 56፥6፤59፥2
**64፥3** መዝ7፥13፤ 55፥21፤58፥7፤ኢሳ 49፥2
**64፥4** ኢዮ9፥23፤ መዝ10፥8፤11፥2፤ 55፥19
**64፥5** ኢዮ22፥13፤ መዝ91፥3፤119፥110፤ 140፥5፤141፥9
**64፥8** ዘዳ28፥37፤ 2ነገ19፥21፤መዝ59፥ 12፤109፥25፤ምሳ 18፥7
**64፥9** መዝ40፥3፤ ኤር51፥10
**64፥10** ኢዮ22፥19፤ መዝ11፥1፤25፥20፤ 31፥2፤32፥11
**65፥1** ዘዳ23፥21፤ መዝ2፥6፤116፥18
**65፥2** መዝ86፥9፤ ኢሳ66፥23
**65፥3** መዝ40፥12፤ 79፥9፤ሮሜ3፥25፤ዕብ 9፥14
**65፥4** ዘኍ16፥5፤ መዝ33፥12፤36፥8
**65፥5** ዘዳ4፥34፤መዝ 18፥46፤45፥4፤48፥10፤ 68፥19፤85፥4፤106፥22 ፤107፥23፤ኢሳ 64፥3
**65፥6** መዝ18፥1፤ 93፥1፤ኢሳ51፥9፤አሞ 4፥13
**65፥7** ዘዳ32፥41፤ መዝ2፥1፤74፥23፤89፥9 ፤93፥3-4፤107፥29፤ 139፥20፤ኢሳ17፥12- 13፤ማቴ8፥26
**65፥8** መዝ100፥2፤ 107፥22፤126፥2፤ኢሳ 24፥16፤52፥9
**65፥9** ዘፍ27፥28፤ ዘሌ26፥4፤ዘዳ32፥14፤ መዝ68፥9-10፤ 104፥14፥24
**65፥10** ዘዳ32፥2፤ 2ሳሙ1፥21፤ኢዮ 36፥28፤ሐሥ14፥17
**65፥11** ዘዳ28፥12፤ ኢዮ36፥28፤መዝ

## መዝሙር 65

### የምስጋና መዝሙር

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት የምስጋና መዝሙር*

[1]እግዚአብሔር ሆይ፤ በጽዮን ለአንተ ውዳሴ
ይገባል፤[ፐ]
ለአንተ የተሳልነውን እንፈጽማለን።
[2]ጸሎትን የምትሰማ ሆይ፤
የሰው ልጆች ሁሉ ወደ አንተ ይመጣሉ።
[3]ኀጢአት ባጥለቀለቀን ጊዜ፣
አንተ መተላለፋችንን ይቅር አልህ።[ሀ]
[4]አንተ የመረጥኸው፣ ወደ ራስህ
ያቀረብኸው፣
በአደባባይህም ያኖርኸው ምስጉን ነው!
ከተቀደሰው መቅደስህ፣
ከቤትህም በረከት እንረካለን።

[5]እግዚአብሔር አዳኛችን ሆይ፤
በጽድቅ ድንቅ አሠራር መልስልን፤
አንተ ለምድር ዳርቻ ሁሉ፣
በርቀት ላለውም ባሕር ተስፋ ነህ።

[6]ተራሮችን በብርታትህ መሠረትህ፤
ኀይልንም ታጥቀሃል።
[7]አንተ የባሕሮችን ማስገምገም፣
የማዕበላቸውን ፉጨት፣
የሕዝቦችንም ሁከት ጸጥ ታደርጋለህ።
[8]ርቀው በምድር ዳርቻ ያሉት ከድንቅ
ሥራህ የተነሣ ይደነግጣሉ፤
የንጋትንና የምሽትን መምጫዎች፣
በደስታ እልል እንዲሉ
ታደርጋቸዋለህ።

[9]ምድርን ትጐበኛለህ፤ ታጠጣለህም፤
እጅግ ታበለጽጋታለህም።
ለሰዎች እህልን ይለግሱ ዘንድ፣
የእግዚአብሔር ወንዞች ውሃን የተሞሉ
ናቸው፤
አንተ እንዲህ እንዲሆን ወስነሃልና።[ለ]

[10]ትልሞችን በውሃ ታረሰርሳለህ፤
ቦይዋን ታስተካክላለህ፤
በካፊያ ታለሰልሳለህ፤
ቡቃያዋንም ትባርካለህ።
[11]ለዘመኑ በጎነትህን ታጐናጽፋለህ፤
ሠረገላህም በረከትን ተሞልቶ ይፈስሳል።
[12]የምድረ በዳው ሣር እጅግ ለመለመ፤
ኰረብቶችም ደስታን ተጐናጸፉ።
[13]ሜዳዎች መንጋ በመንጋ ሆኑ፤

104፥28፤147፥14፤ ሉቃ6፥38፤ዮሐ10፥10 **65፥12** ኢዮ28፥26፤ መዝ98፥8፤ኢል2፥22 **65፥13** መዝ72፥16፤98፥8፤144፥13፤ኢሳ 14፥8፤30፥23፤44፥23፤49፥13፤55፥12፤ዘካ8፥12

[ሬ]5 ወይም *ማንስ ሊያያቸው ይችላል*
[ፐ]1 በዕብራይስጡ የዚህ ቃል ትርጉም በትክክል አይታወቅም።
[ሀ]3 ወይም *አንተ ተቤዠህን*
[ለ]9 ወይም *"አንተም ለዚህ ነው ምድርን ያዘጋጀሃት"*

ሸለቆችም በእህል ተሸፈኑ፤
እልል ይላሉ፤ ይዘምራሉም።

## መዝሙር 66

### የኅብረት ምስጋና

*ለመዘምራን አለቃ፤ ማኅሌት፤ መዝሙር*

1ምድር ሁሉ ለእግዚአብሔር እልል ይበል!
2ለስሙ ክብር ዘምሩ፤
ውዳሴውንም አድምቁ!
3እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት፤ “ሥራህ
እንዴት ግሩም ነው!
ጠላቶችህ ከኀይልህ ታላቅነት የተነሣ፣
በፊትህ ይርዳሉ።
4ምድር ሁሉ ይሰግድልሃል፤
በዝማሬ ያመሰግኑሃል፤
ለስምህም ይዘምራሉ። ሴላ
5ኑና፣ እግዚአብሔር ያደረገውን እዩ
በሰዎች መካከል ሥራው አስፈሪ ነው!
6ባሕሩን የብስ አደረገው፤
ወንዙን በእግር ተሻገሩ፤
ኑ፣ በእርሱ ደስ ይበለን።
7በኀይሉ ለዘላለም ይገዛል፤
ዐይኖቹ ሕዝቦችን ይመለከታሉ፤
እንግዲህ ዐመፀኞች ቀና ቀና አይበሉ።
ሴላ
8ሕዝቦች ሆይ፤ አምላካችንን ባርኩ፤
የምስጋናውንም ድምፅ አሰሙ።
9እኛን በሕይወት የሚያኖረን፣
እግራችንንም ከመንሸራተት የሚጠብቅ
እርሱ ነው።
10አምላክ ሆይ፤ አንተ ፈተንኸን፤
እንደ ብርም አነጠርኸን።
11ወደ ወጥመድ አገባኸን፤
በጀርባችንም ሸክም ጫንህብን።
12ሰዎች በራሳችን ላይ እንዲፈነጩ
አደረግህ፤
በእሳትና በውሃ መካከል አለፍን፤
የኋላ ኋላ ግን ወደ በረከት አመጣኸን።
13የሚቃጠል መሥዋዕት ይዤ ወደ
መቅደስህ እገባለሁ፤
ስእለቴንም ለአንተ እፈጽማለሁ፤
14በመከራ ጊዜ ከአፌ የወጣ፣
በከንፈሬም የተናገርሁት ስእለት ነው።
15ፍሪዳዎችን የሚቃጠል መሥዋዕት
አድርጌ፣
አውራ በጎችንም የሚጤስ ቍርባን
አድርጌ አቀርብልሃለሁ፤
ኰርማዎችንና ፍየሎችንም እሠዋልሃለሁ።
ሴላ
16እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሁሉ፤ ኑና ስሙ፤
ለነፍሴ ያደረገላትን ልንገራችሁ።
17በአፌ ወደ እርሱ ጮኽሁ፤
በአንደበቴም አመሰገንሁት።
18ኀጢአትን በልቤ አስተናግጄ ቢሆን
ኖሮ፣
ጌታ ባልሰማኝ ነበር።
19አሁን ግን እግዚአብሔር በእርግጥ ሰምቶኛል፤
ጸሎቴንም አድምጦአል።
20ጸሎቴን ያልናቀ፣
ምሕረቱንም ከእኔ ያላራቀ፣
እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው።

## መዝሙር 67

### የመከር ጊዜ መዝሙር

*ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች የሚዘመር፤ የዳዊት መዝሙር፤ ማኅሌት*

1እግዚአብሔር ይማረን፤ ይባርከን፤
ፊቱንም በላያችን ያብራ፤ ሴላ
2መንገድህ በምድር ላይ፣
ማዳንህም በሕዝቦች ሁሉ መካከል
ይታወቅ ዘንድ።
3እግዚአብሔር ሆይ፤ ሰዎች ያመስግኑህ፤
ሰዎች ሁሉ ምስጋና ያቅርቡልህ።
4ለሕዝቦች በቅን ስለምትፈርድላቸው፣
ሰዎችንም በምድር ላይ ስለምትመራ፣
ሕዝቦች ደስ ይበላቸው፤ በእልልታም
ይዘምሩ። ሴላ
5እግዚአብሔር ሆይ፤ ሰዎች ያመስግኑህ፤
ሰዎች ሁሉ ምስጋና ያቅርቡልህ።
6ምድር ፍሬዋን ሰጠች፤
እግዚአብሔር አምላካችንም ይባርከናል።
7እግዚአብሔር ይባርከናል፤
የምድርም ዳርቻዎች ሁሉ እርሱን
ይፈሩታል።

## መዝሙር 68

### ብሔራዊ የድል መዝሙር

*ለመዘምራን አለቃ የዳዊት መዝሙር፤ ማኅሌት*

1እግዚአብሔር ይነሣ፤ ጠላቶቹ ይበተኑ፤
የሚጠሉትም ከፊቱ ይሸሹ።
2ጢስ እንደሚበንን፣
እንዲሁ አብንናቸው።
ሰም በእሳት ፊት እንደሚቀልጥ፣
ክፉዎችም እንዲሁ ከእግዚአብሔር ፊት
ይጥፉ።
3ጻድቃን ግን ደስ ይበላቸው፤
በእግዚአብሔር ፊት ሐሤት ያድርጉ፤
ደስታንና ፍስሓን የተሞሉ ይሁኑ።
4ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤ ለስሙም ተቀኙ፤
በደመናት ላይ የሚሄደውን ከፍ
አድርጉት፤[ሐ]
ስሙ *እግዚአብሔር* በተባለው ፊት፣

66፥1 መዝ81፥1፤84፥8፤95፥1፤98፥4፤100፥1
66፥2 መዝ79፥9፤86፥9፤ኢሳ42፥8፡12፤43፥21
66፥3 ዘዳ7፥21፤10፥21፤2ሳሙ22፥45፤መዝ65፥5፤106፥22፤111፥6፤145፥6
66፥4 መዝ7፥17፤22፥27፤67፥3
66፥5 ቍ3፤መዝ106፥22
66፥6 ዘፍ8፥1፤ዘፀ14፥22፤ዘሌ23፥40፤1ቆሮ10፥1
66፥7 ዘፀ3፥16፤15፥18፤ዘኍ17፥10፤መዝ11፥4፤112፥10፤140፥8፤145፥13
66፥8 መዝ22፥23
66፥9 ዘዳ32፥35፤ኢዮ12፥5፤መዝ30፥3
66፥10 ዘፀ15፥25፤ኢዮ6፥29፤28፥1፤መዝ12፥6
66፥11 ዘፍ3፥17፤ዘፀ1፥14፤መዝ38፥4፤142፥7፤146፥7፤ኢሳ10፥27፤42፥7፡22፤61፥1
66፥12 መዝ18፥19፤ኢሳ51፥23
66፥13 መዝ22፥25፤50፥14፤51፥19፤116፥14፤መክ5፥4፤ዮና2፥9
66፥15 ዘሌ16፥5፤መዝ51፥19
66፥16 መዝ34፥11፤71፥15፡24
66፥18 ዘዳ1፥45፤1ሳሙ8፥18፤ያዕ4፥3
66፥19 መዝ18፥6
66፥20 መዝ22፥24
67፥1 ዘኍ6፥24-26
67፥2 መዝ98፥2፤ኢሳ40፥5፤52፥10፤62፥1፡2፤ሐሥ10፥35፤ቲቶ2፥11
67፥3 ቍ5
67፥4 መዝ9፥4፤68፥32፤96፥10-13፤100፥1-2
67፥6 ዘፍ8፥22፤12፥2፤ዘሌ26፥4፤መዝ85፥12፤ኢሳ55፥10፤ሕዝ34፥27፤ዘካ8፥12
67፥7 መዝ2፥8፤33፥8
68፥1 ዘኍ10፥35፤መዝ12፥5፤18፥14፤89፥10፤92፥9፤132፥8፤144፥6፤ኢሳ17፥13፤21፥15፤33፥3
68፥2 ዘኍ10፥35፤መዝ9፥3፤22፥14፤37፥20፤80፥16
68፥3 መዝ64፥10፤97፥12
68፥4 ቍ33፤ዘፀ

[ሐ]4 ወይም *በምድረ በዳ ለሚሄደው መንገድን አዘጋጁለት* ።

እጅግ ደስ ይበላችሁ።
5እግዚአብሔር በተቀደሰ ማደሪያው፣
ለድኻ አደጉ አባት፣ ለባልቴቲቱም
ተሟጋች ነው።
6እግዚአብሔር ብቸኞችን በቤተ ሰብ
መካከል ያኖራል፤[መ]
እስረኞችን ነጻ አውጥቶ ያስፈነድቃል፤
ዐመፀኞች ግን ምድረ በዳ ይኖራሉ።
7እግዚአብሔር ሆይ፤ በሕዝብህ ፊት በወጣህ
ጊዜ፣
በምድረ በዳም በተጓዝህ ጊዜ፣ ሴላ
8በሲና አምላክ፣ በእግዚአብሔር ፊት፣
በእስራኤል አምላክ፣ በእግዚአብሔር ፊት፣
ምድር ተንቀጠቀጠች፤
ሰማያትም ዶፍ አወረዱ።
9እግዚአብሔር ሆይ፣ በቂ ዝናብ አዘነብህ፤
ክው ያለውን ርስትህን አረሰረስህ።
10መንጋህ መኖሪያው አደረጋት፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ ከበረከትህ ለድኾች
ሰጠህ።
11ጌታ እንዲህ ሲል ቃሉን አስተላለፈ፤
ትእዛዙን የሚያውጁትም ብዙ ሰራዊት
ናቸው፤
12“የሰራዊት ነገሥታት ፈጥነው ይሸሻሉ፤
በሰፈር የዋሉ ሴቶችም ምርኮን
ተካፈሉ።
13በበጎች በረት መካከል[ሠ] ብትገኙ እንኳ፣
ከብር እንደ ተሠሩ የርግብ ክንፎች፣
በቅጠልያ ወርቅ እንደ ተለበጡ ላባዎች
ናችሁ።”
14ሁሉን ቻዩ[ረ] በዚያ የነበሩትን ነገሥታት
በበተነ ጊዜ፣
በሰልሞን እንደሚወርድ በረዶ
አደረጋቸው።
15አንተ ብርቱ ተራራ፣ የባሳን ተራራ
ሆይ፤
አንተ ባለ ብዙ ጫፍ ተራራ፣ የባሳን
ተራራ፤
16እናንተ ባለ ብዙ ጫፍ ተራሮች ሆይ፤
እግዚአብሔር ሊኖርበት የመረጠውን
ተራራ፣
በእርግጥ *እግዚአብሔር* ለዘላለም
የሚኖርበትን ተራራ ለምን በምቀኝነት
ዐይን ታያላችሁ?
17የእግዚአብሔር ሠረገላዎች እልፍ አእላፍ
ናቸው፤
ሺህ ጊዜም ሺህ ናቸው፤
ጌታ ከሲና ወደ መቅደሱ ገባ።
18ወደ ላይ ዓረግህ፤
ምርኮ አጋበስህ፤
*እግዚአብሔር* አምላክ ሆይ፤ አንተ[ሰ] በዚያ
ትኖር ዘንድ፣
ከዐመፀኞችም ሳይቀር፣
ከሰዎች ስጦታን ተቀበልህ።
19ሸክማችንን በየዕለቱ የሚሸከምልን፣
አዳኝ አምላካችን፣ ጌታ ይባረክ።
ሴላ
20አምላካችን የሚያድን አምላክ ነው፤
ከሞት ማምለጥ የሚቻለውም በጌታ
*በእግዚአብሔር* ነው።
21በእርግጥ እግዚአብሔር የጠላቶቹን ራስ፣
በኀጢአታቸውም የሚጸኑትን ሰዎች
ጠጕራም አናት ይፈነካክታል።
22ጌታ እንዲህ ይላል፤ “ከባሳን መልሼ
አመጣቸዋለሁ፤
ከባሕርም ጥልቀት አውጥቼ
አመጣቸዋለሁ፤
23እግርህ በጠላትህ ደም ውስጥ
እንዲጠልቅ፣
የውሻህም ምላስ ከጠላትህ ድርሻውን
እንዲያገኝ ነው።”
24አምላክ ሆይ፤ የክብር አካሄድህ ታየ፤
ይህም አምላኬና ንጉሤ ወደ ቤተ
መቅደሱ የሚያደርገው የክብር
አካሄድ ነው።
25መዘምራን ከፊት፣ መሣሪያ የሚጫወቱ
ከኋላ ሆነው ሲሄዱ፣
ከበሮ የሚመቱ ቈነጃጅትም
በመካከላቸው ነበሩ።
26እግዚአብሔርን በጉባኤ አመስግኑት፤
ከእስራኤል ምንጭ የተገኛችሁ *እግዚ
አብሔርን* አመስግኑ።
27የሚመራቸው ትንሹ ብንያም ነው፤
በዚያ በብዙ የሚቈጠሩ የይሁዳ
መሳፍንት፣
እንዲሁም የዛብሎንና የንፍታሌም
መሳፍንት ይገኛሉ።
28እግዚአብሔር ሆይ፤ ኀይልህን እዘዝ፤[ሸ]
አምላክ ሆይ ቀድሞ እንዳደረግህልን
አሁንም ብርታትህን አሳየን።
29በኢየሩሳሌም ስላለው ቤተ መቅደስህ፣
ነገሥታት እጅ መንሻ ያመጡልሃል።
30በሸምበቆ መካከል ያሉትን አራዊት፣
በሕዝቡ ጥጆች መካከል ያለውንም
የኮርማ መንጋ ገሥጽ፤
ብር ይገብር ዘንድም ይንበርከክ፤

6፥3፤20፥21፤ዘዳ33፥26፤2ሳሙ22፥50፤መዝ7፥17፤30፥4፤66፥2፤83፥18፤96፥2፤100፥4፤135፥3
**68፥5** ዘፀ22፥22ዘዳ10፥18፤26፥15፤መዝ10፥14፤ኤር25፥30
**68፥6** መዝ25፥16፤79፥11፤102፥20፤113፥9፤146፥7፤ኢሳ35፥7፤49፥10፤58፥11፤61፥1፤ሉቃ4፥18
**68፥7** ዘፀ13፥21፤መዝ78፥40፤106፥14
**68፥8** ዘዳ33፥2፤2ሳሙ21፥10፤22፥8፤መሳ5፥4፥5፤መክ11፥3
**68፥9** ዘዳ32፥2፤ኢዮ36፥28፤ሕዝ34፥26
**68፥10** ዘዳ28፥12፤መዝ65፥9
**68፥11** ሉቃ2፥13
**68፥12** ኢሱ10፥16፤መሳ5፥30
**68፥13** ዘፍ49፥14
**68፥14** መሳ9፥48፤2ሳሙ22፥15
**68፥15** ቀኍ22፤ዘኍ21፥33፤መዝ36፥6፤ኤር22፥20
**68፥16** ዘዳ12፥5፤መዝ2፥6፤132፥13፥14
**68፥17** 2ነገ2፥11፤ኢሳ66፥15፤ዳን7፥10፤ዕን3፥8
**68፥18** ዘኍ17፥10 መሳ5፥12፤መዝ7፥7፤47፥5፤ኤፌ4፥8
**68፥19** መዝ65፥5፤81፥6
**68፥20**1ሳሙ10፥19፤መዝ56፥13፤ኤር45፥5፤ሕዝ6፥8
**68፥21** መዝ74፥14፤110፥5፤ዕን3፥13
**68፥22** ኢዮ36፥30፤ማቴ18፥6
**68፥23** 1ነገ21፥19፤2ነገ9፥36፤መዝ58፥10
**68፥24** መዝ63፥2
**68፥25** ዘፍ31፥27፤1ዜና6፥31፤15፥16፤2ዘ˛ና5፥12፤ኢሳ5፥12፤ራዕ18፥22
**68፥26** ዘሌ19፥2፤መዝ22፥22፤ዕብ2፥12
**68፥27** ዘኍ34፥21፤መሳ5፥18፤1ሳሙ9፥21
**68፥28** ዘፀ9፥16፤መዝ29፥11፤ኢሳ26፥12፤29፥23፤45፥11፤60፥21፤64፥8
**68፥29** 2ዜና9፥24፤32፥23
**68፥30** ኢዮ40፥21፤መዝ18፥14፤22፥12፤89፥10፤120፥7፤140፥2፤ኢሳ27፥1፤34፥7፤51፥9፤ኤር50፥27፤ሕዝ29፥3

[መ]6 ወይም *ብቸኞችን በገዛ ምድራቸው*
[ሠ]13 ወይም *በኮርቻ ማስቀመጫዎች*
[ረ]14 ዕብራይስጡ *ሻዳይ* ይላል።
[ሰ]18 ወይም *እናንተ*
[ሸ]28 ብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕምና የሱርስቱ ቅጅ *እግዚአብሔር ሆይ፤ ኀይልህን ጥራ* ይላሉ። አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን *እግዚአብሔር ለአንተ ኀይል ይጠራልሃል* ይላሉ።

ጦርነትን የሚወዱ ሕዝቦችንም
በትናቸው።
31መኳንንት ከግብፅ ይመጣሉ፤
ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር
ትዘረጋለች።
32የምድር መንግሥታት ሆይ፤
ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤
ለጌታ ተቀኙ። ሴላ
33ከጥንት ጀምሮ ከነበሩት ሰማያት በላይ
ለወጣው፣
በኀያል ድምፁ ለሚያስገመግመው
ዘምሩ።
34ግርማው በእስራኤል ላይ፣
ኀይሉም ከደመናት በላይ ነው፣
እግዚአብሔርን ብርታት የአንተ ነው
በሉት።
35እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ በመቅደስህ
ድንቅ ነህ፤
የእስራኤል አምላክ ለሕዝቡ ኀይልና
ብርታትን ይሰጣል።

እግዚአብሔር ይባረክ!

## መዝሙር 69

### እንጕርጕሮ

*ለመዘምራን አለቃ፤ በ"ጽጌረዳ" ዜማ፤ የዳዊት መዝሙር*

1አምላክ ሆይ፤ አድነኝ፤
ውሃ እስከ ዐንገቴ ደርሶብኛልና።
2የእግር መቆሚያ በሌለው፣
በጥልቅ ረግረግ ውስጥ ሰጥሜአለሁ፤
ወደ ጥልቅ ውሃ ገባሁ፤
ሞገዱም አሰጠመኝ።
3በጩኸት ደከምሁ፤
ጕሮሮዬም ደረቀ፤
አምላኬን በመጠባበቅ፣
ዐይኖቼ ፈዘዙ።
4ያለ ምክንያት የሚጠሉኝ፣
ከራሴ ጠጕር በዙ፤
ሕይወቴን ለማጥፋት የሚፈልጉ፣
በከንቱም የሚጠሉኝ ብዙዎች ሆኑ፤
ያልሰረቅሁትን ነገር፣
መልሰህ አምጣ ተባልሁ።
5እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ሞኝነቴን
ታውቃለህ፤
በደሌም ከአንተ የተሰወረ አይደለም።
6ጌታ የሰራዊት አምላክ ሆይ፤
አንተን ተስፋ የሚያደርጉ፣
በእኔ ምክንያት አይፈሩ፤
የእስራኤል አምላክ ሆይ፤
አንተን አጥብቀው የሚሹ፣
ከእኔ የተነሣ አይዋረዱ።
7ስለ አንተ ስድብን ታግሻለሁና፤

68፥31 ኢሳ11፥11፤18፥1፤19፥19፤43፥3፤45፥14፤ሶፎ3፥10
68፥32 መዝ7፥17፤46፥6፤67፥4
68፥33 ዘዐ9፥23፤ዘዳ33፥26፤መዝ29፥3፡4፤ኢሳ30፥30፤33፥3፤66፥6
68፥34 ቍ28፤መዝ45፥3
68፥35 ዘፍ28፥17፤ዘጸ7፥21፤መዝ28፥6፤29፥11፤18፥1፤66፥20፤ኢሳ40፥29፤41፥10፤50፥2፤2ቆሮ1፥3
69፥1 መዝ32፥6፤42፥7፤ዮና2፥5
69፥2 ኢዮ30፥19
69፥3 መዝ6፥6፤119፥82
69፥4 መዝ25፥19፤35፥19፤38፥19፤40፥14፤119፥95፤ኢሳ32፥7፤ዮሐ15፥25
69፥5 መዝ38፥5፤44፥21
69፥7 መዝ39፥8፤44፥15፤ኤር15፥15
69፥8 ኢዮ19፥13-15፤መዝ31፥11፤38፥11፤ኢሳ53፥3፤ዮሐ7፥5
69፥9 መዝ89፥50-51፤ዮሐ2፥17፤ሮሜ15፥3
69፥10 መዝ35፥13
69፥11 2ሳሙ3፥31፤መዝ35፥13
69፥12 ዘፍ18፥1፤23፥10፤ኢዮ30፥9
69፥13 መዝ17፥7፤51፥1፤ኢሳ49፥8፤2ቆሮ6፥2
69፥14 ቍ2፤መዝ144፥7
69፥15 ዘኍ16፥33፤መዝ28፥1፤124፥4-5
69፥16 መዝ63፥3
69፥17 መዝ22፥24፤50፥15፤66፥14፤143፥7
69፥18 መዝ49፥15
69፥19 መዝ22፥6
69፥20 ኢዮ16፥2፤መዝ142፥4፤ኢሳ63፥5
69፥21 ዘኍ6፥3፤ማቴ27፥34፡48፤ማር15፥23፡36፤ሉቃ23፥36፤ዮሐ19፥28-30
69፥22 1ሳሙ28፥9፤ኢዮ18፥10
69፥23 ሮሜ11፥9-10
69፥24 መዝ79፥6፤ኤር10፥25
69፥25 ዘሌ26፥43፤ማቴ23፥38፤ሐሥ1፥20

እናቶችም ፊቴን ሸፍኖአልና።
8ለወንድሞቼ እንደ ባዕድ፣
ለእናቴም ልጆች እንደ እንግዳ
ሆንሁባቸው።
9የቤትህ ቅናት በላችኝ፤
የሚሰድቡህም ስድብ በላዬ ዐርፎአል።
10ነፍሴን በጾም ባስመረርሁ ጊዜ፣
እነርሱ ሰደቡኝ።
11ማቅ በለበስሁ ጊዜ፣
መተረቻ አደረጉኝ።
12በቅጥሩ ደጅ ለሚቀመጡት
የመነጋገሪያ ርእስ፣
ለሰካራሞችም መዝፈኛ ሆንሁ።
13እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔ ግን
በወደድኸው ሰዓት፣
ወደ አንተ እጸልያለሁ፤
አምላክ ሆይ፤ በታላቅ ምሕረትህ፣
በማዳንህም እርግጠኝነት መልስልኝ።
14ከረግረግ አውጣኝ፤
እሰጥም ዘንድ አትተወኝ፤
ከጥልቅ ውሃ፣
ከእነዚያ ከሚጠሉኝ ታደገኝ።
15ጐርፍ አያጥለቅልቀኝ፤
ጥልቅ ውሃም አይዋጠኝ፤
ጕድጓዱም ተደርምሶ አይዘጋብኝ።
16እግዚአብሔር ሆይ፤ ምሕረትህ በጎ
ናትና ስማኝ፤
እንደ ርኅራኄም ብዛት መለስ በልልኝ።
17ፊትህን ከባሪያህ አትሰውር፤
ጭንቅ ውስጥ ነኝና ፈጥነህ መልስልኝ።
18ወደ እኔ ቀርበህ ታደገኝ፤
ስለ ጠላቶቼም ተቤዠኝ።
19የደረሰብኝን ስድብ፣ ዕፍረትና ውርደት
ታውቃለህ፤
ጠላቶቼንም አንድ በአንድ
ታውቃቸዋለህ።
20ስድብ ልቤን ጐድቶታል፤
ተስፋዬም ተሟጦአል፤
አስተዛዛኝ ፈለግሁ፤ አላገኘሁምም፤
አጽናኝም ፈለግሁ፤ አንድም
አልነበረም።
21ምግቤን ከሐሞት ቀላቀሉ፤
ለጥማቴም ሆምጣጤ ሰጡኝ።
22የቀረበላቸው ማእድ ወጥመድ
ይሁንባቸው፤
ለማኅበራቸውም አሽክላ ይሁን።
23ዐይኖቻቸው እንዳያዩ ይጨልሙ፤
ጀርባቸውም ዘወትር ይጕበጥ።
24መዓትህን በላያቸው አፍስስ፤
የቍጣህም መቅሠፍት ድንገት
ይድረስባቸው።
25ሰፈራቸው ባድማ ይሁን፤

በድንኳኖቻቸው የሚኖር አይገኝ፤
26አንተ የመታኻቸውን አሳደዋልና፤
ያቈሰልኻቸውንም ሥቃያቸውን
አባብሰዋል፡፡
27በበደላቸው በደል ጨምርባቸው፤
ወደ ጽድቅህም አይግቡ፡፡
28ከሕይወት መጽሐፍ ይደምሰሱ፤
ከጻድቃንም ጋር አይጻፉ፡፡

29ነገር ግን እኔ በሥቃይና በጭንቅ ላይ
እገኛለሁ፤
አምላክ ሆይ፤ ማዳንህ ደግፎ ይያዘኝ፡፡

30የእግዚአብሔርን ስም በዝማሬ አወድሳለሁ፤
በምስጋናም ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ፡፡
31ከበሬ ይልቅ፣
ቀንድና ጥፍር ካበቀለ እምቦሳም ይልቅ
ይህ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል፡፡
32ድኾች ይህን ያያሉ፤ ደስም ይላቸዋል፤
እናንተ እግዚአብሔርን የምትሹ ልባችሁ
ይለምልም!
33እግዚአብሔር ችግረኞችን ይሰማልና፤
በእስራት ያለውንም ሕዝቡን
አይንቅም፡፡

34ሰማይና ምድር፣ ባሕርም፣
በውስጣቸውም የሚንቀሳቀስ ሁሉ
ያመስግኑት፡፡
35እግዚአብሔር ጽዮንን ያድናታልና፤
የይሁዳንም ከተሞች መልሶ
ይሠራቸዋልና፤
ሕዝቡም በዚያ ይሰፍራል፤
ይወርሳታልም፡፡
36የባሪያዎቹም ዘሮች ይወርሷታል፤
ስሙንም የሚወዱ በዚያ ይኖራሉ፡፡

## መዝሙር 70

### የጭንቀት ጩኸት

70፥1-5 ተጓ ምብ-መዝ40፥13-17

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር፤ ለመታሰቢያ*

1አምላክ ሆይ፤ ታድነኝ ዘንድ ዘንበል በል፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔን ለመርዳት
ፍጠን፡፡
2ሕይወቴን ለማጥፋት የሚሹ፣
ይፈሩ፤ ሁከትም ይምጣባቸው፤
የእኔን መጐዳት የሚመኙ፣
በውርደት ወደ ኋላቸው ይመለሱ፡፡
3በእኔ ላይ፣ "እሰይ! እሰይ!" የሚሉ፣
ተሸማቀው ወደ ኋላ ይመለሱ፡፡
4ነገር ግን የሚሹህ ሁሉ፣
በአንተ ሐሤት ያድርጉ፤ ደስም
ይበላቸው፤
"ማዳንህን የሚወዱ ሁሉ ሁልጊዜ፣
እግዚአብሔር ከፍ ይበል!" ይበሉ፡፡
5እኔ ግን ምስኪንና ችግረኛ ነኝ፤
አምላክ ሆይ፤ ፈጥነህ ድረስልኝ፤
ረዳቴም፣ ታዳጊዬም አንተ ነህና፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ አትዘግይ፡፡

## መዝሙር 71

### የሽማግሌ ጸሎት

71፥1-3 ተጓ ምብ-መዝ31፥1-4

1እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተን መጠጊያ
አደረግሁ፤
ከቶም አልፈር፡፡
2በጽድቅህ ታደገኝ፤ አስጥለኝም፤
ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል፤ አድነኝም፡፡
3ምንጊዜም የምሸሸበት፣
መጠጊያ ዐለት ሁነኝ፤
አንተ ዐለቴ ምሽጌ ነህና፣
ታድነኝ ዘንድ ትእዛዝህ ይውጣ፡፡
4አምላኬ ሆይ፤ ከክፉ እጅ፣
ከግፈኛና ከጨካኝ መዳፍ አውጣኝ፡፡

5ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ተስፋዬ፤
ከልጅነቴም ጀምሮ መታመኛዬ ነህና፡፡
6ከተወለድሁ ጀምሮ በአንተ ተደገፍሁ፤
ከእናቴ ማሕፀን ያወጣኸኝ አንተ ነህ፤
አንተ የዘወትር ምስጋናዬ ነህ፡፡
7ብዙዎች እንደ ጉድ አዩኝ፤
አንተ ግን ጽኑ አምባዬ ነህ፡፡
8ቀኑን ሙሉ ክብርህን ያወራ ዘንድ፣
አፌ በምስጋናህ ተሞልቶአል፡፡

9በእርጅናዬ ዘመን አትጣለኝ፤
ጕልበቴም ባለቀበት ጊዜ አትተወኝ፡፡
10ጠላቶቼ ተነጋግረውብኛልና፤
ሕይወቴን ለማጥፋት የሚሹ በአንድ
ላይ አሢረዋል፤
11እነርሱም፣ "እግዚአብሔር ትቶታል፤
የሚያስጥለው የለምና፣
ተከታትላችሁ ያዙት" አሉ፡፡
12አምላክ ሆይ፤ ከእኔ አትራቅ፤
አምላኬ ሆይ፤ እኔን ለመርዳት ፍጠን፡፡
13ባላንጣ የሆኑብኝ ይፈሩ፤ ይጥፉም፤
ሊጐዱኝ የሚፈልጉ፣
ንቀትንና ውርደትን ይከናነቡ፡፡
14እኔ ግን ሁልጊዜ ተስፋ አደርጋለሁ፤
በምስጋና ላይ ምስጋና አቀርብልሃለሁ፡፡
15አንደበቴ ስለ ጽድቅህ፣
ቀኑን ሙሉ ስለ ማዳንህ ይናገራል፤
ማቆሚያ ልኩንም አላውቅም፡፡
16መጥቼ የጌታ እግዚአብሔርን ብርቱ
ሥራ ዐውጃለሁ፤
የአንተን ጽድቅ ብቻ እናገራለሁ፡፡
17አምላክ ሆይ፤ አንተ ከልጅነቴ ጀምረህ
አስተማርኸኝ፤

69፥26 ኢዮ19፥22፤ ዘካ1፥15
69፥27 ነህ4፥5፤መዝ 109፥14
69፥28 ዘፀ32፥32-33፤ ሕዝ13፥9፤ሉቃ10፥20
69፥29 መዝ20፥1
69፥30 መዝ28፥7፤ 34፥3
69፥31 መዝ50፥9-13፤51፥16
69፥32 መዝ22፥26፤34፥2
69፥33 መዝ12፥5
69፥34 መዝ96፥11፤98፥7፤ኢሳ44፥23
69፥35 ዕዝ9፥9፤ መዝ51፥18፤አብ1፥17
69፥36 መዝ25፥13፤37፥29
70፥1 መዝ22፥19፤71፥12
70፥2 መዝ6፥10፤ 35፥4፡26፤71፥13፤109፥29፤129፥5
70፥3 መዝ35፥21
70፥4 መዝ9፥10፤ 31፥6-7፤32፥11፤ 35፥27፤118፥24
70፥5 መዝ18፥2፤ 30፥10፤33፥20፤86፥1፤ 109፥22፤119፥60፤ 141፥1
71፥1 ዘዳ23፥15፤ ሩት2፥12፤መዝ22፥5
71፥2 2ነገ19፥16
71፥3 መዝ18፥2
71፥4 ዘፍ48፥16፤2 ነገ19፥19፤መዝ140፥4
71፥5 ኢዮ4፥6፤መዝ 9፥18፤25፥5፤ኤር17፥7
71፥6 ኢዮ3፥16፤ መዝ9፥1፤22፥9፡10፤34፥1፤52፥9፤119፥164፤145፥2
71፥7 ዘዳ28፥46፤ 2ሳሙ22፥3፤መዝ61፥3፤ኢሳ8፥18፤1ቆሮ4፥9
71፥8 ቍ15፤መዝ 51፥15፤63፥5፤96፥6፤104፥1
71፥9 ዘዳ4፥31፤ 31፥6፤መዝ51፥11፤ 92፥14፤ኢሳ46፥4
71፥10 ዘፀ1፥10፤ መዝ3፥7፤10፥8፤31፥13፤59፥3፤ምሳ1፥18፤ ማቴ12፥14
71፥11 መዝ7፥2፤9፥10፤ኢሳ40፥27፤54፥7፤ ሰቆ5፥20፤ማቴ27፥46
71፥12 መዝ22፥19፤38፥21፡22
71፥13 ኢዮ8፥22፤ መዝ25፥3፤70፥2፤ኤር 18፥19
71፥14 መዝ25፥3፤ 42፥5፤130፥7፤131፥3
71፥15 ቍ8፤መዝ 51፥14፤66፥16
71፥18 ዘፀ9፥16፤
71፥16 መዝ9፥1፤ 77፥12፤106፥2፤118፥15፤145፥4
71፥17 ዘዳ4፥5፤ኢዮ 5፥9፤መዝ26፥7፤86፥10፤96፥3፤ኤር7፥13

እኔም እስከ ዛሬ ድረስ ድንቅ
ሥራህን ዐውጃለሁ።
18አምላክ ሆይ፤ ሳረጅና ስሸብትም
አትተወኝ፤
ክንድህን ለመጭው ትውልድ፣
ኀይልህን ኋላ ለሚነሣ ሕዝብ ሁሉ፣
እስከምገልጽ ድረስ።
19አምላክ ሆይ፤ ጽድቅህ እስከ ሰማያት
ይደርሳል፤
አንተ ታላላቅ ነገሮችን አድርገሃል፤
አምላክ ሆይ፤ እንደ አንተ ያለ ማን
ነው?
20ብዙ መከራና ጭንቅ ብታሳየኝም፣
ሕይወቴን እንደ ገና ታድሳለህ፤
ከምድር ጥልቅም፣
እንደ ገና ታወጣኛለህ።
21ክብሬን ትጨምራለህ፤
ተመልሰህም ታጽናናኛለህ
22አምላኬ ሆይ፤ ስለ ታማኝነትህ፣
በበገና አመሰግንሃለሁ፤
የእስራኤል ቅዱስ ሆይ፤
በመሰንቆ እዘምርልሃለሁ።
23ዝማሬ በማቀርብልህ ጊዜ ከንፈሮቼ
በደስታ ይሞላሉ፤
አንተ የተቤዠሃትም ነፍሴ እልል
ትላለች።
24አንደበቴ ስለ ጽድቅህ፣
ቀኑን ሙሉ ያወራል፤
የእኔን መጐዳት የሚፈልጉ፣
አፍረዋልና፤ ተዋርደዋልም።

## መዝሙር 72

### በተስፋ የሚጠባበቀው ንጉሥ

ስለ ሰሎሞን

1እግዚአብሔር ሆይ፤ ፍርድህን ለንጉሥ፣
ጽድቅህንም ለንጉሥ ልጅ ዐድል፤
2እርሱም ሕዝብህን በጽድቅ ይዳኛል፤[ቀ]
ለተቸገሩትም በትክክል ይፈርዳል።
3ተራሮች ብልጽግናን፣
ኰረብቶችም የጽድቅን ፍሬ ለሕዝቡ
ያመጣሉ።
4ለተቸገረው ሕዝብ ይሟገታል፤
የድኾችን ልጆች ያድናል፤
ጨቋኙንም ያደቀዋል።
5ፀሓይ እስካለች ድረስ፣
ጨረቃም በምትኖርበት ዘመን ሁሉ፣
ከትውልድ እስከ ትውልድ ይኖራል።[በ]
6እንደ ዝናብ በታጨደ መስክ ላይ
ይወርዳል፤
እንደ ካፊያም ምድርን ያረሰርሳል።
7በዘመኑ ጽድቅ ይሰፍናል፤
ጨረቃ ከስፍራዋ እስከምትታጣ
ድረስም ሰላም ይበዛል።
8ከባሕር እስከ ባሕር ድረስ፣
ከታላቁም ወንዝ[ተ] እስከ ምድር ዳርቻ
ይገዛል።
9የበረሓ ዘላኖች በፊቱ ይሰግዳሉ፤
ጠላቶቹም ዐፈር ይልሳሉ።
10የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት፣
ግብር ያመጡለታል፤
የዐረብና የሳባ ነገሥታት፣
እጅ መንሻ ያቀርባሉ።
11ነገሥታት ሁሉ ይሰግዱለታል፤
ሕዝቦችም ሁሉ ይገዙለታል።
12ችግረኛው በጮኸ ጊዜ፣
ምስኪኑንና ረዳት የሌለውን ይታደገዋል።
13ለድኾችና ለችግረኞች ይራራል፤
ምስኪኖችንም ከሞት ያድናል።
14ሕይወታቸውን ከጭቈናና ከግፍ
ያድናል፤
ደማቸውም በእርሱ ፊት ክቡር ነው።
15ዕድሜው ይርዘም!
ከዐረብ ወርቅ ይምጣለት፤
ዘወትር ይጸልዩለት፤
ቀኑንም ሙሉ ይባርኩት።
16በምድሪቱ ላይ እህል ይትረፍረፍ፤
በተራሮችም ዐናት ላይ ይወዛወዝ።
ፍሬው እንደ ሊባኖስ ይንዠርገግ፤
በከተማ ያለውም እንደ ሜዳ ሣር
እጅብ ብሎ ይውጣ።
17ስሙ ለዘላለም ጸንቶ ይኑር፤
ዝናው ፀሓይ የምትኖረውን ዘመን
ያህል ይዝለቅ፤
ሕዝቦች ሁሉ በእርሱ ይባረኩ፤
ሕዝቡ ሁሉ ቡሩክ ነህ ይበለው።
18ብቻውን ድንቅ ነገር የሚያደርግ፣
የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ።
19ክቡር ስሙ ለዘላለም ይባረክ፤
ምድርም ሁሉ በክብሩ ይሞላ።
አሜን፤ አሜን።
20የእሴይ ልጅ የዳዊት ጸሎት እዚህ ላይ
ተፈጸመ።

## ሦስተኛ መጽሐፍ
## ከመዝሙር 73-89

## መዝሙር 73

### የፍትሕ አሸናፊነት

የአሳፍ መዝሙር

1እግዚአብሔር ልባቸው ንጹሕ ለሆነ፣
ለእስራኤል እንዴት ቸር ነው!

[ቀ]2 ወይም *እርሱ ሕዝቡን በጽድቅ ይዳኝ*
[በ]5 ወይም *የተፈራ ይሆናል*
[ተ]8 የኤፍራጥስ ወንዝ ነው።

ኢዮ8፥8፤መዝ22፥30፥31፤78፥4፤145፥4፤ኢሳ46፥4፤ኢል1፥3
**71፥19** መዝ35፥10፤36፥5፤77፥13፤89፥8፤126፥2፤ሉቃ1፥49
**71፥20** መዝ25፥17፤63፥9፤80፥3፥19፤85፥4፤ሆሴ6፥2
**71፥21** መዝ18፥35፤23፥4፤86፥17፤ኢሳ12፥1፤40፥1-2፤49፥13፤54፥10
**71፥22** 2ነገ19፥22፤ኢዮ21፥12፤መዝ33፥2፤92፥3፤144፥9
**71፥23** ዘፀ15፥13፤መዝ20፥5
**71፥24** ቍ13፤አስ9፥2፤መዝ35፥28
**72፥1** ዘዳ1፥16፤መዝ9፥8
**72፥2** ኢሳ9፥7፤11፥4-5፤16፥5፤32፥1፤59፥17፤63፥1፤ኤር23፥5፤33፥15
**72፥4** ቍ13፤መዝ9፥12፤27፥11፤76፥9፤ኢሳ11፥4፤29፥19፤32፥7፤49፥13
**72፥5** 1ሳሙ13፥13፤መዝ33፥11
**72፥6** ዘዳ32፥2
**72፥7** መዝ92፥12፤ምሳ14፥11
**72፥8** ዘፀ23፥31፤1ነገ4፥21፤ዘካ9፥10
**72፥10** ዘፍ10፥4፥7፤1ነገ9፥16፤2ዜና9፥24፤አስ10፥1
**72፥11** ዘፍ27፥29፤ዕዝ1፥2
**72፥13** ኢሳ60፥10፤ኢል2፥18፤ሉቃ10፥33
**72፥14** 1ሳሙ26፥21፤መዝ69፥18፤ሕዝ13፥23፤34፥10
**72፥15** ዘፍ10፥7፤መዝ35፥28
**72፥16** ዘፍ27፥28፤ዘኍ22፥4፤መዝ4፥7፤92፥12፤104፥16፤ኢሳ4፥2፤27፥6፤44፥4፤58፥11፤66፥14፤ሕዝ34፥27
**72፥17** ዘፍ12፥3፤ዘፀ3፥15፤መዝ89፥36፤ሉቃ1፥48
**72፥18** 1ዜና29፥10፤ኢዮ5፥9፤መዝ41፥13፤106፥48፤ሉቃ1፥68
**72፥19** ዘኍ14፥21፤2ሳሙ7፥26፤መዝ41፥13
**72፥20** ሩት4፥17
**73፥1** መዝ24፥4፤ማቴ5፥8

2እኔ ግን እግሬ ሊሰናከል፣
አዳልጦኝም ልወድቅ ጥቂት ቀረኝ።
3ክፉዎች ሲሳካላቸው አይቼ፣
በዐመፀኞች ቀንቼ ነበርና።

4አንዳች ጣር የለባቸውም፤
ሰውነታቸውም ጤናማና የተደላደለ
ነው።
5በሰዎች የሚደርሰው ጣጣ
አይደርስባቸውም፤
እንደ ማንኛውም ሰው መከራ
አያገኛቸውም።
6ስለዚህ ትዕቢት የዐንገት ጌጣቸው ነው፤
ዐመፅንም እንደ ልብስ ተጐናጽፈዋል።
7የሰባ ዐይናቸው ይጕረጠረጣል፤[ቾ]
ልባቸውም በከንቱ ሐሳብ ተሞልቶ
ይፈስሳል።
8በፌዝና በክፋት ይናገራሉ፤
ቀና ቀና ብለውም በዐመፅ ይዝታሉ።
9አፋቸውን በሰማይ ላይ ያላቅቃሉ፤
አንደበታቸውም ምድርን ያካልላል።
10ስለዚህ ሕዝቡ ወደ እነርሱ ይነጒዳል፤
ውሃቸውንም በገፍ[ኀ] ይጠጣሉ።
11"ለመሆኑ እግዚአብሔር እንዴት ያውቃል?
በልዑልስ ዘንድ ዕውቀት አለ?" ይላሉ።

12እንግዲህ፣ ክፉዎች ይህን ይመስላሉ፤
ሁልጊዜ ግድ የለሽና ሀብት በሀብት
ናቸው።
13ለካ ልቤን ንጹሕ ያደረግሁት በከንቱ
ነው፤
እጄንም በየዋህነት የታጠብሁት
በከንቱ ኖሮአል!
14ቀኑን ሙሉ ተቀሥፍሁ፤
ጠዋት ጠዋትም ተቀጣሁ።

15"እኔ እንደዚህ እናገራለሁ" ብልማ ኖሮ፣
የልጆችህን ትውልድ በከዳሁ ነበር።
16ይህን ነገር ለመረዳት በሞከርሁ ጊዜ፣
አድካሚ ተግባር መስሎ ታየኝ።
17ይኸውም ወደ አምላክ መቅደስ እስክገባ፣
መጨረሻቸውንም እስካይ ድረስ ነበር።
18በእርግጥ በሚያዳልጥ ስፍራ
አስቀመጥኻቸው፤
ወደ ጥፋትም አወረድሃቸው።
19እንዴት ፈጥነው በቅጽበት ጠፉ!
በድንጋጤ ፈጽመው ወደሙ።
20ሰው ከሕልሙ ሲነቃ እንደሚሆነው፣
ጌታ ሆይ፤ አንተም በምትነሣበት ጊዜ፣
እንደ ቅዠት ከንቱ ታደርጋቸዋለህ።

21ነፍሴ በተማረረች ጊዜ፣
ልቤም በተቀሠፈ ጊዜ፣
22ስሜት የሌለውና አላዋቂ ሆንሁ፤
በፊትህም እንደ እንስሳ ሆንሁ።

23ይህም ሆኖ ዘወትር ከአንተ ጋር
ነኝ፤
አንተም ቀኝ እጄን ይዘኸኛል።
24በምክርህ መራኸኝ፤
ኋላም ወደ ክብር ታስገባኛለህ።
25በሰማይ ከአንተ በቀር ማን አለኝ?
በምድርም ከአንተ ሌላ የምሻው
የለኝም።
26ሥጋዬና ልቤ ሊደክሙ ይችላሉ፤
እግዚአብሔር ግን የልቤ ብርታት፣
የዘላለም ዕድል ፈንታዬ ነው።

27እነሆ፤ ከአንተ የሚርቁ ይጠፋሉና፤
አንተ ታማኞች ያልሆኑልህን ሁሉ
ታጠፋቸዋለህ።
28ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ
ይሻለኛል፤
ጌታ እግዚአብሔርን መጠጊያዬ
አድርጌዋለሁ፤
ስለ ሥራህም ሁሉ እናገር ዘንድ።

## መዝሙር 74
## ስለ መቅደሱ መፍረስ የቀረበ ጸሎት

የአሳፍ ትምህርት

1አምላክ ሆይ፤ ለዘላለም የጣልኸን
ለምንድን ነው?
በማሰማሪያህ ባሉ በጎችህስ ላይ ቍጣህ
ለምን ነደደ?
2ጥንት ገንዘብህ ያደረግሃትን ጉባኤ፣
የዋጀሃትን የርስትህን ነገድ፣
መኖሪያህ ያደረግሃትን የጽዮን ተራራ
አስብ።
3እርምጃህን ለዘላለሙ ባድማ ወደ ሆነው
አቅና፤
ጠላት በመቅደስህ ውስጥ ያለውን ሁሉ
አበላሽቶአል።

4ጠላቶችህ በመገናኛ ስፍራህ መካከል
ደነፉ፤
አርማቸውንም ምልክት አድርገው
በዚያ አቆሙ።
5በጫካ መካከል ዛፎችን ለመቍረጥ፣
መጥረቢያ የሚያነሣ ሰው መሰሉ።
6በእደ ጥበብ ያጌጠውን ሥራ ሁሉ፣
በመጥረቢያና በመዶሻ ሰባበሩት።
7መቅደስህን አቃጥለው አወደሙት፤
የስምህንም ማደሪያ አረከሱ።
8በልባቸውም፣ "ፈጽሞ እንጨቍናቸዋለን"
አሉ፤
እግዚአብሔር በምድሪቱ ላይ
የተመለከበትን ስፍራ ሁሉ አቃጠሉ።

[ቾ]7 የዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሱርስቱና የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ግን፣ *ከደነደነው ልባቸው በደል ይወጣል* ይላል።
[ኀ]10 በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጒም በትክክል አይታወቅም።

73፥2 ዘዳ32፥35፤መዝ69፥2፤ኤፌ4፥27
73፥3 ኢዮ9፥24፤21፥7፤ምሳ3፥31፤23፥17፤24፥1-2፤ኤር12፥1፤ሚል3፥15
73፥5 ቍ12፤ሕዝ23፥42
73፥6 ዘፍ6፥11፤41፥42፤ዘሌ26፥19፤ምሳ4፥17፤መሓ4፥9፤ሕዝ16፥11
73፥7 መዝ17፥10
73፥8 መዝ10፥7፤12፥5፤17፥10፤41፥5፤ሕዝ25፥15፤ቈላ3፥8
73፥12 ቍ5፤መዝ49፥6
73፥13 ዘፍ44፥16፤ኢዮ9፥29-31፤21፥15
73፥14 ቍ5
73፥16 መክ8፥17
73፥17 ዘፀ15፥17፤ኢዮ8፥13፤መዝ15፥1፤ፊል3፥19
73፥18 ዘዳ32፥35፤መዝ17፥13፤35፥6
73፥19 ዘፍ19፥15፤ዘዳ28፥20፤ምሳ24፥22፤ኢሳ47፥11
73፥20 ኢዮ20፥8፤መዝ78፥65፤ምሳ12፥11፤28፥19፤ኢሳ29፥8
73፥22 መዝ49፥10፥12፥20፤92፥6፤94፥8፤መክ3፥18፤9፥12
73፥23 ዘፍ48፥13
73፥24 1ነገ22፥5፤መዝ48፥14
73፥25 መዝ16፥2፤ፊል3፥8
73፥26 ዘዳ32፥9፤መዝ18፥1፤31፥10፤40፥12፤84፥2
73፥27 ዘሌ6፥2፤መዝ34፥21፤ኤር5፥11፤ሆሴ4፥12፤9፥1
73፥28 መዝ9፥9፤26፥7፤40፥5፤ሶፎ3፥2፤ዕብ10፥22፤ያዕ4፥8
74፥1 መዝ43፥2፤44፥23፤79፥13፤95፥7፤100፥3
74፥2 ዘፀ15፥13፥16፤34፥9፤ዘዳ32፥7፤መዝ2፥6፤43፥3፤68፥16፤ኢሳ46፥13፤48፥20፤ኢል3፥17፥21፤አብ1፥17፤1ቆሮ 6፥20
74፥3 ኢሳ44፥26፤52፥9
74፥4 ዘኍ2፥2፤ኤር4፥6፤ሰቆ2፥7
74፥5 ኤር46፥22
74፥6 1ነገ6፥18
74፥7 ዘሌ15፥31፤20፥3፤መዝ75፥1፤ሐሥ21፥28
74፥8 2ነገ25፥9፤2ዜና36፥19፤መዝ94፥5፤ኤር21፥10፤34፥22፤

9የምናየው ምልክት የለም፤
ከእንግዲህ የሚነሣ አንድም ነቢይ
የለም፤
ይህ እስከ መቼ እንደሚቀጥል
የሚያውቅ በእኛ ዘንድ የለም።

10አምላክ ሆይ፤ ጠላት የሚያሾፈው እስከ
መቼ ነው?
ባላንጣስ ለዘላለም በስምህ ያላግጣልን?
11እጅህን ለምን ትሰበስባለህ?
ቀኝ እጅህን ለምን በብብትህ ሥር
ታቆያለህ?

12አምላክ ሆይ፤ አንተ ከጥንት ጀምሮ
ንጉሤ ነህ፤
በምድር ላይ ማዳንን አደረግህ።
13ባሕርን በኀይልህ የከፈልህ አንተ ነህ፤
የባሕሩንም አውሬ ራሶች በውሃ ውስጥ
ቀጠቀጥህ።
14የሌዋታንን ራሶች አደቀቅህ፤
ለምድረ በዳ ፍጥረታትም ምግብ
አድርገህ የሰጠሃቸው፣
15ምንጮችንና ፈሳሾችን ያፈለቅህ
አንተ ነህ፤
ሳያቋርጡ የሚፈሱትንም ወንዞች
አደረቅህ።
16ቀኑ የአንተ ነው፤ ሌሊቱም የአንተ
ነው፤
ጨረቃንና ፀሓይን አንተ
አጸናሃቸው።
17የምድርን ዳርቻ ሁሉ የወሰንህ አንተ
ነህ፤
በጋውንም ክረምቱንም አንተ ሠራህ።

18እግዚአብሔር ሆይ፤ ጠላት እንዴት
እንደሚያሾፍ፣
ከንቱ ሕዝብም ስምህን እንዴት
እንዳቃለለ አስብ።
19የርግብህን ነፍስ አሳልፈህ ለዱር
አራዊት አትስጥ፤
የችግረኞች ሕዝብህን ሕይወት
ለዘላለሙ አትርሳ።
20ኪዳንህን አስብ፤
የዐመፅ መናኸሪያ በምድሪቱ ጨለማ
ስፍራዎች ሞልተዋልና።
21የተጨቈኑት አፍረው አይመለሱ፤
ድኾችና ችግረኞች ስምህን ያመስግኑ።

22አምላክ ሆይ፤ ተነሥ፤ ለዐላማህ
ተሟገት፤
ከንቱ ሰው ቀኑን ሙሉ
እንደሚያላግጥብህ አስብ።
23የባላጋራዎችህን ድንፋታ፣
ዘወትር የሚነሣውን የጠላቶችህን
ፉከራ አትርሳ።

52፥13
74፥9 ዘፀ4፥17፤ 10፥1፤1ሳሙ3፥1
74፥10 ቀኍ22፤መዝ 6፥3፤44፥16፤79፥5፤ 80፥4
74፥11 ዘፀ15፥6፤ነህ 5፥13፤ሕዝ5፥3
74፥12 መዝ2፥6፤ 24፥7፤27፥1፤68፥24
74፥13 ዘፀ14፥21፤ ኢሳ27፥1፤51፥9፤ሕዝ 29፥3፤32፥2
74፥14 ኢዮ3፥8፤ ኢሳ13፥21፤23፥13፤ 34፥14፤ኤር50፥39
74፥15 ዘፀ14፥29፤ 17፥6፤ዘኍ20፥11፤ ኢሱ2፥10
74፥16 ዘፍ1፥16፤ መዝ136፥7-9
74፥17 ዘፍ8፥22፤ ዘዳ32፥8፤ሐሥ17፥26
74፥18 ዘዳ32፥6
74፥19 ዘፍ8፥8፤ መዝ9፥18፤ኢሳ59፥11
74፥20 ዘፍ6፥18፤ ኢዮ34፥22
74፥21 መዝ9፥9፤ 10፥18፤35፥10፤103፥6 ፤ኢሳ58፥10
74፥22 መዝ17፥13 ፤53፥1
74፥23 ዘኍ25፥17 ፤መዝ46፥6፤65፥7፤ ኢሳ31፥4
75፥1 ኢሱ3፥5፤ መዝ44፥1፤71፥16፤77፥ 12፤105፥2፤107፥8፡15 ፤145፥5፡12፡18
75፥2 ዘፀ13፥10፤ መዝ7፥11
75፥3 1ሳሙ2፥8፤ 2ሳሙ22፥8፤ኢሳ 24፥19
75፥4 1ሳሙ2፥3፤ መዝ5፥5፤ዘካ1፥21
75፥5 ኢዮ15፥25
75፥7 ዘፍ16፥5፤ 1ሳሙ2፥7፤ኢዮ5፥11 ፤መዝ50፥6፤58፥11፤1 47፥6፤ሕዝ21፥26፤ ዳን2፥21፤ራእ18፥8
75፥8 ምሳ23፥30 ፤ኢሳ51፥17፤ኤር 25፥15፤ዘካ12፥2
75፥9 ዘፍ24፥12፤ መዝ40፥10፤76፥6፤ 108፥1
75፥10 መዝ89፥17 ፤92፥10፤112፥9፤ 148፥14
76፥1 መዝ99፥3
76፥2 ዘፍ14፥18፤ 2ሳሙ5፥7፤መዝ2፥6፤ዕ ብ7፥1
76፥3 መዝ46፥9፤ ሕዝ39፥9
76፥4 መዝ36፥9
76፥5 መሳ20፥44፤ መዝ13፥3፤ማቴ9፥24

## መዝሙር 75

### ለመለኮታዊው ዳኛ የቀረበ ዝማሬ

ለመዘምራን አለቃ፤ "አታጥፋ" በሚለው ቅኝት የሚዜም፤ የአሳፍ መዝሙር ማሕሌት

1አምላክ ሆይ፤ ምስጋና እናቀርብልሃለን፤
ስምህ ቅርብ ነውና ምስጋና
እናቀርብልሃለን፤
ሰዎችም ስለ ድንቅ ሥራህ ይናገራሉ።

2አንተም እንዲህ አልህ፤ "ለይቼ
በወሰንኋት ሰዓት፣
በቅን የምፈርድ እኔ ነኝ።
3ምድርና ሕዝቦቿ ሁሉ በሚናወጡበት
ጊዜ፣
ምሰሶቿን አጽንቼ የምይዝ እኔ ነኝ።
ሴላ
4እብሪተኛውን፣ 'አትደንፋ'፤
ክፉውንም 'ቀንድህን ከፍ
አታድርግ' እለዋለሁ፤
5ቀንድህን ወደ ሰማይ አታንሣ፤
ዐንገትህንም መዝዘህ አትናገር።' "
6ክብር ከምሥራቅ ወይም ከምዕራብ፣
ወይም ከምድረ በዳ አይመጣምና፤
7ነገር ግን የሚፈርድ እግዚአብሔር ነው፤
እርሱ አንዱን ዝቅ፣ ሌላውን ከፍ
ያደርጋል።
8በእግዚአብሔር እጅ ጽዋ አለ፤
በሚገባ የተቀመመና ዐረፋ የሚወጣው
የወይን ጠጅ ሞልቶበታል፤
ይህን ከውስጡ ወደ ውጭ ገለበጠው፤
የምድር ዐመፀኞችም አተላው ሳይቀር
ይጨልጡታል።

9እኔ ግን ይህን ለዘላለም ዐውጃለሁ፤
ለያዕቆብም አምላክ ዝማሬ አቀርባለሁ።
10የክፉዎችን ሁሉ ቀንድ እሰብራለሁ፤
የጻድቃን ቀንድ ግን ከፍ ከፍ ይላል።

## መዝሙር 76

### ግርማው ለሚያስፈራው አምላክ የቀረበ ቅኔ

ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች፤ የአሳፍ መዝሙር ማሕሌት

1እግዚአብሔር በይሁዳ ታወቀ፤
ስሙም በእስራኤል ታላቅ ነው።
2ድንኳኑ በሳሌም፣
ማደሪያውም በጽዮን ነው።
3በዚያም ተወርዋሪውን ፍላጻ፣
ጋሻንና ሰይፍን፣ ጦርንም ሰበረ። ሴላ

4አንተ ብርሃን ተላብሰህ ደምቀሃል፤
ግርማዊነትህም ከዘላለም ተራሮች
ይልቃል።
5ልበ ሙሉ የሆኑት ተዘርፈዋል፤
አንቀላፍተውም ተኝተዋል፤

ከጦረኞቹም መካከል፣
እጁን ማንቀሳቀስ የቻለ የለም።

6 የያዕቆብ አምላክ ሆይ፤ ከተግሣጽህ
የተነሣ፣
ፈረስና ፈረሰኛው ጭልጥ ብለው
ተኝተዋል።
7 መፈራት ያለብህ አንተ ብቻ ነህ፤
በተቈጣህ ጊዜ ማን በፊትህ መቆም
ይችላል?
8 አንተ ፍርድን ከሰማይ አሰማህ፤
ምድርም ፈርታ ጸጥ አለች፤
9 አምላክ ሆይ፤ ይህም የሆነው አንተ
የምድር ጒስቍሎችን ለማዳን፣
ለፍርድ በተነሣህ ጊዜ ነው። ሴላ
10 ሰውን ብትቈጣ እንኳ ለክብርህ
ይሆናል፤
ከቍጣ የተረፉትንም ትገታቸዋለህ።ʼ

11 ለአምላካችሁ *ለእግዚአብሔር* ተሳሉ፤
ስእለቱንም አግቡ፤
በእርሱ ዙሪያ ያሉ ሁሉ፣
አስፈሪ ለሆነው ለእርሱ እጅ መንሻ
ያምጡ።
12 እርሱ የገዦችን መንፈስ ይሰብራል፤
በምድር ነገሥታትም ዘንድ የተፈራ
ነው።

## መዝሙር 77

## የእስራኤል ጥንተ ነገር አሰላስሎ

*ለመዘምራን አለቃ፤ ለኤዶታም፤ የአሳፍ መዝሙር*

1 ድምፄን ከፍ አድርጌ ወደ እግዚአብሔር
ጮኽሁ፤
ይሰማኝም ዘንድ ወደ አምላክ ጮኽሁ።
2 በመከራዬ ቀን እግዚአብሔርን
ፈለግሁት፤
በሌሊትም ያለ ድካም እጆቼን ዘረጋሁ፤
ነፍሴም አልጽናና አለች።

3 አምላክ ሆይ፤ አንተን ባሰብሁ ቍጥር
ቃተትሁ፤
ባወጣሁ ባወረድሁም መጠን
መንፈሴ ዛለች። ሴላ
4 ዐይኖቼ እንዳይከደኑ ያዝሃቸው፤
መናገር እስኪሳነኝ ድረስ ታወክሁ።
5 የድሮውን ዘመን አሰብሁ፤
የጥንቶቹን ዓመታት አውጠነጠንሁ።
6 ዝማሬዬን በሌሊት አስታወስሁ፤
ከልቤም ጋር ተጫወትሁ፤ መንፈሴም
ተነቃቅቶ እንዲህ ሲል ጠየቀ፦

7 "ለመሆኑ፣ ጌታ ለዘላለም ይጥላልን?
ከእንግዲህስ ከቶ በጎነትን አያሳይምን?
8 ምሕረቱስ ለዘላለም ጠፋን?
የገባውስ ቃል እስከ ወዲያኛው ተሻረን?

76፥6 ዘፀ15፥1፤መዝ 50፥21
76፥7 1ዜና16፥25፤ዕዝ9፥15፤መዝ2፥5፤ናሆ1፥6፤ራእ6፥17
76፥8 1ዜና16፥30፤ሕዝ38፥20
76፥9 መዝ9፥8፤58፥11፤72፥4፤74፥22፤82፥8፤96፥13
76፥10 ዘፀ9፥16፤ሮሜ9፥17
76፥11 ዘሌ22፥18፤2ዜና32፥23፤መዝ 50፥14፤መክ5፥4-5
77፥1 1ነገ8፥52
77፥2 ዘፍ32፥7፤37፥35፤ዘፀ9፥29፤2ሳሙ 22፥7፤ኢዮ 11፥13፤መዝ6፥6፤22፥2፤88፥1፤118፥5፤ማቴ2፥18
77፥3 ዘፀ2፥23፤መዝ 6፥2፥6፤78፥35፤ኤር 45፥3
77፥4 መዝ39፥2
77፥5 ዘዳ32፥7፤መዝ44፥1፤143፥5፤መክ7፥10
77፥7 1ዜና28፥9፤መዝ85፥1፤102፥13፤106፥4
77፥8 መዝ6፥4፤90፥14፤2ጴጥ3፥9
77፥9 መዝ25፥6፤40፥11፤51፥1፤ኢሳ 49፥15
77፥10 ዘፀ15፥6
77፥11 ነህ9፥17
77፥12 ዘፍ24፥63፤መዝ143፥5
77፥13 ዘፀ15፥11፤መዝ71፥19፤86፥8
77፥14 ዘፀ3፥20፤34፥10
77፥15 ዘፀ6፥6
77፥16 ዘፀ14፥21፡28፤መዝ114፥4፤ኢሳ 50፥2፤ዕን3፥8፡10
77፥17 ዘፀ9፥23፤ዘዳ32፥23፤መሳ5፥4፤መዝ29፥3
77፥18 መሳ5፥4፤2ሳሙ22፥13፤መዝ 55፥8
77፥19 ዘፀ14፥22፤ኢዮ9፥8
77፥20 ዘፀ4፥16፤13፥21፤ዘኍ33፥1፤መዝ 78፥52፤ኢሳ63፥11
78፥1 ኢሳ51፥4፤55፥3
78፥2 መዝ49፥4፤ማቴ13፥35
78፥3 መሳ6፥13
78፥4 ዘዳ11፥19፤32፥7፤ኢዮ5፥9፤መዝ 26፥7፤71፥17፡18

9 እግዚአብሔር ቸርነቱን ዘነጋ?
ወይስ ከቍጣው የተነሣ ርኅራኄውን
ነፈገ?" ሴላ።

10 እኔም፣ "የልዑል ቀኝ እጅ እንደ
ተለወጠ ማሰቤ፣
ይህ ድካሜ ነው" አልሁ።
11 *የእግዚአብሔርን* ሥራ አስታውሳለሁ፤
የጥንት ታምራትህን በእርግጥ
አስታውሳለሁ፤
12 ሥራህን ሁሉ አሰላስላለሁ፤
ድንቅ ሥራህን ሁሉ አውጠነጥናለሁ።

13 አምላክ ሆይ፤ መንገድህ ቅዱስ ነው፤
እንደ አምላካችን ያለ ታላቅ አምላክ
ማን ነው?
14 ታምራትን የምታደርግ አምላክ አንተ
ነህ፤
በሕዝቦችም መካከል ኀይልህን
ትገልጣለህ።
15 የያዕቆብንና የዮሴፍን ልጆች፣
ሕዝብህን በክንድህ ተቤዠሃቸው። ሴላ

16 አምላክ ሆይ፤ ውሆች አዩህ፤
ውሆች አንተን አይተው ተሸማቀቁ፤
ጥልቆችም ተነዋወጡ።
17 ደመናት ውሃን አንጠባጠቡ፤
ሰማያት አንጐደጐዱ፤
ፍላጾችህም ዙሪያውን አብለጨለጩ።
18 የነጐድጓድህ ድምፅ በዐውሎ ነፋስ
ውስጥ ተሰማ፤
መብረቅህ ዓለምን አበራው፤
ምድርም ራደች፤ ተንቀጠቀጠች።
19 መንገድህ በባሕር ውስጥ ነው፤
መሂጃህም በታላቅ ውሃ ውስጥ ነው፤
ዱካህ ግን አልታወቀም።

20 በሙሴና በአሮን እጅ፣
ሕዝብህን እንደ በግ መንጋ መራኸው።

## መዝሙር 78

## በእስራኤል የተገኘ ታሪክ

የአሳፍ ትምህርት

1 ሕዝቤ ሆይ፤ ትምህርቴን ስማ፤
ጆሮህንም ወደ አንደበቴ ቃል
አዘንብል።
2 አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ፤
ከጥንት በነበረ እንቈቅልሽ እናገራለሁ፤
3 ይህም የሰማነውና ያወቅነው፣
አባቶቻችንም የነገሩን ነው።
4 እኛም ከልጆቻቸው አንደብቀውም፤
*የእግዚአብሔርን* ምስጋና፣
ኀይሉንና ያደረገውን ድንቅ ሥራ፣
ለሚቀጥለው ትውልድ እንናገራለን።

ʼ10 *በሕዝብህ ላይ የምታወርደው ቍጣ ለክብርህ ይሆናል ወይም በቍጣውም መታሰቢያነት ራስህን ታስታጥቃለህ የሚሉ አሉ።*

5 ለያዕቆብ ሥርዐትን መሠረተ፤
በእስራኤልም ሕግን ደነገገ፤
ልጆቻቸውንም እንዲያስተምሩ፣
አባቶቻችንን አዘዘ።
6 ይህም የሚቀጥለው ትውልድ እንዲ
ያውቅ፣
እነርሱም በተራቸው ለልጆቻቸው፣
ገና ለሚወለዱት እንዲነግሩ ነው።
7 እነርሱም በእግዚአብሔር ይታመናሉ፤
የእግዚአብሔርን ሥራ አይረሱም፤
ትእዛዞቹንም ይጠብቃሉ።
8 ነገር ግን እንደ አባቶቻቸው፣
እልከኞችና ዐመፀኞች፣
ልቡን ያላቀና፣
መንፈሱም በእግዚአብሔር የማይታመን
ትውልድ አይሆኑም።

9 የኤፍሬም ልጆች የታጠቁ ቀስተኞች
ቢሆኑም፣
በጦርነት ቀን ወደ ኋላ ተመለሱ።
10 የእግዚአብሔርን ኪዳን አልጠበቁም፤
በሕጉም መሠረት ለመሄድ እንቢ አሉ።
11 እርሱ የሠራውን ሥራ፣
ያሳያቸውንም ድንቅ ነገር ረሱ።
12 አባቶቻቸው በዐይናቸው እያዩ፣
በግብፅ አገር፣ በጣኔዎስ ምድር
ታምራት አደረገ።
13 ባሕሩን ከፍሎ አሻገራቸው፤
ውሃውንም እንደ ክምር አቆመ።
14 ቀን በደመና መራቸው፤
ሌሊቱንም ሁሉ በእሳት ብርሃን።
15 ዐለቱን በምድረ በዳ ሰነጠቀ፤
እንደ ባሕር የበዛ ውሃ
አጠጣቸው፤
16 ምንጭ ከቋጥኝ አፈለቀ፤
ውሃን እንደ ወንዝ አወረደ።

17 እነርሱ ግን በምድረ በዳ በልዑል
ላይ በማመፅ፣
በእርሱ ላይ ኀጢአት መሥራታቸውን
ቀጠሉ።
18 እጅግ የተመኙትን ምግብ በመጠየቅ፣
እግዚአብሔርን በልባቸው ተፈታተኑት።
19 እንዲህም ብለው በእግዚአብሔር ላይ
ተናገሩ፤
"እግዚአብሔር በምድረ በዳ ማዕድ
ማሰናዳት ይችላልን?
20 ዐለቱን ሲመታ፣ ውሃ ተንዶለዶለ፤
ጅረቶችም ጐረፉ፤
ታዲያ፣ እንጀራንም መስጠት ይችላል?
ሥጋንስ ለሕዝቡ ሊያቀርብ ይችላል?"
21 እግዚአብሔር ይህን ሲሰማ፣ እጅግ
ተቈጣ፤
በያዕቆብም ላይ እሳት ነደደ፤
ቍጣውም በእስራኤል ላይ ተነሣ፤
22 በእግዚአብሔር አላመኑምና፤
በእርሱም ማዳን አልታመኑም።
23 እርሱ ግን ከላይ ደመናትን አዘዘ፤
የሰማይንም ደጆች ከፈተ፤
24 ይበሉም ዘንድ መና አዘነበላቸው፤
የሰማይንም መብል ሰጣቸው።
25 ሰዎች የመላእክትን እንጀራ በሉ፤
ጠግበው እስኪተርፍ ድረስ ምግብ
ላከላቸው።
26 የምሥራቁን ነፋስ ከሰማይ አስነሣ፤
የደቡብንም ነፋስ በኀይሉ አመጣ።
27 ሥጋን እንደ ዐፈር፣
የሚበሩትን ወፎች እንደ ባሕር አሸዋ
አዘነበላቸው፤
28 በሰፈራቸውም ውስጥ፣
በድንኳናቸው ዙሪያ አወረደ።
29 እነርሱም እስኪጠግቡ ድረስ በሉ፤
እጅግ የጐመጁትን ሰጥቶአቸዋልና።
30 ነገር ግን ገና ምኞታቸውን ሳያረኩ፣
ምግቡ ገና በአፋቸው ውስጥ እያለ፣
31 የእግዚአብሔር ቍጣ በላያቸው ላይ መጣ፤
ከመካከላቸውም ብርቱ ነን ባዮችን
ገደለ፤
የእስራኤልንም አበባ ወጣቶች ቀጠፈ።

32 ይህም ሁሉ ሆኖ በበደላቸው ገፉበት፤
ድንቅ ሥራዎቹንም አላመኑም።
33 ስለዚህ ዘመናቸውን በከንቱ፣
ዕድሜአቸውንም በድንጋጤ ጨረሰ።
34 እርሱ በገደላቸው ጊዜ ፈለጉት፤
ከልባቸው በመሻትም ወደ እግዚአብሔር
ተመለሱ።
35 እግዚአብሔር ዐለታቸው፣
ልዑል አምላክ ቤዛቸው እንደ ሆነ
አሰቡ።
36 ነገር ግን በአፋቸው ሸነገሉት፤
በአንደበታቸው ዋሹት።
37 ልባቸው በእርሱ የጸና አልነበረም፤
ለኪዳኑም ታማኞች አልነበሩም።
38 እርሱ ግን መሓሪ እንደ መሆኑ፣
በደላቸውን ይቅር አለ፤
አላጠፋቸውም፤
ቍጣውን ብዙ ጊዜ ገታ፤
መዓቱንም ሁሉ አላወረደም።
39 ወጥቶ የማይመለስ ነፋስ፣
ሥጋ ለባሾች መሆናቸውን አሰበ።

40 በምድረ በዳ ስንት ጊዜ ዐመፁበት!
በበረሓስ ምን ያህል አሳዘኑት!
41 ደግመው ደጋግመው እግዚአብሔርን
ተፈታተኑት፤
የእስራኤልንም ቅዱስ አስቈጡት።

78፥5 መዝ19፥7፤ 81፥5፤147፥19
78፥6 መዝ22፥31
78፥7 ዘዳ5፥29፤ 6፥12
78፥8 ዘፀ23፥21፤ 32፥9፤ዘዳ21፥18፤ 2ዜና30፥7፤ኢሳ 30፥9፤65፥2
78፥9 ቍ57፤መሳ 20፥39፤1ዜና12፥2፤ ሆሴ7፥16
78፥10 ዘፀ16፥28፤ ኢሱ7፥11፤2ነገ17፥15 ፤ኤር11፥8
78፥11 መዝ106፥13
78፥12 ዘፀ11፥9፤ ዘኁ13፥22፤ነህ9፥17፤ መዝ106፥22
78፥13 ዘፀ14፥21፡ 22፤15፥8፤መዝ66፥6፤ 136፥13
78፥14 ዘፀ13፥21፤ 105፥39
78፥15 ዘኁ20፥11፤ 1ቆሮ10፥4
78፥17 ቍ32፥40፤ ዘዳ9፥22፤ኢሳ30፥1፤ 63፥10፤ዕብ3፥16
78፥18 ዘፀ15፥24፤ 17፥2፤ዘኁ11፥4፤ 1ቆሮ10፥9
78፥19 ዘኁ21፥5
78፥20 ዘኁ11፥18፤ 20፥11፤ኢሳ35፥6
78፥21 ዘኁ11፥1
78፥22 ዘዳ1፥32፤ ዕብ3፥19
78፥23 ዘፍ7፥11፤ 2ነገ7፥2
78፥24 ዘፀ16፥4፤ ዮሐ6፥31
78፥26 ዘኁ11፥31
78፥27 ዘፀ16፥13፤ ዘኁ11፥31
78፥29 ዘኁ11፥20
78፥30 ዘኁ11፥33
78፥31 ኢሳ10፥16
78፥32 ቍ11፥17፡ 22
78፥33 ዘኁ14፥29፡ 35
78፥34 ዘዳ4፥29፤ ሆሴ5፥15
78፥35 ዘፍ49፥24፤ ዘዳ9፥26
78፥36 ሕዝ33፥31
78፥37 ቍ8፤ሐሥ 8፥21
78፥38 ዘፀ34፥6፤ ኢዮ9፥13፤መዝ25፥11 ፤85፥2፤አሳ1፥25፤27፥9 ፤30፥18፤48፥10፤ ዳን11፥35
78፥39 ዘፍ6፥3፤ ኢዮ7፥7፤ኢሳ29፥5፤ ያዕ4፥14
78፥40 ዘፀ23፥21፤ መዝ95፥8፤106፥14፤ኤ ፌ4፥30
78፥41 ዘፀ17፥2፤ 2ነገ19፥22፤መዝ71፥22፤89፥18

42እነርሱን በዚያን ቀን ከጠላት
የታደገበትን፣
ያን ኀይሉን አላስታወሱም፤
43በግብፅ ያደረገውን ታምራዊ ምልክት፣
በጣኔዎስም በረሓ ያሳየውን ድንቅ ሥ
ራ አላሰቡም::
44ወንዞቻቸውን ወደ ደም ለወጠ፤
ከጅረቶቻቸውም መጠጣት አልቻሉም::
45የዝንብ ሰራዊት ሰደደባቸው፤
ነደፏቸውም፤
ጓጒንቸርም ላከባቸው፤ ሰዎችንም
አጠፉ::
46አዝመራቸውን ለኵብኵባ፣
ሰብላቸውንም ለአንበጣ ሰጠባቸው::
47የወይን ተክላቸውን በበረዶ፣
የበለስ ዛፋቸውንም በውርጭ አጠፋ::
48ከብቶቻቸውን ለበረዶ፣
የከብት መንጋቸውን ለመብረቅ እሳት
ዳረገ::
49ጽኑ ቍጣውን በላያቸው ሰደደ፤
መዓቱን፣ የቅናቱን ቍጣና መቅ
ሠፍቱን ላከባቸው፤
አጥፊ የመላእክት ሰራዊትም
ሰደደባቸው::
50ለቍጣው መንገድ አዘጋጀ፤
ነፍሳቸውንም ከሞት አላተረፈም፤
ነገር ግን ሕይወታቸውን ለመቅሠፍት
አሳልፎ ሰጠ::
51የዐፍላ ጕልበታቸው መጀመሪያ
የሆኑትን በካም ድንኳን፣
በኵሮቻቸውንም ሁሉ በግብፅ ምድር
ፈጀ::
52ሕዝቡን ግን እንደ በግ አወጣቸው፤
በምድረ በዳም እንደ መንጋ መራቸው::
53በሰላም መራቸው፤ እነርሱም አልፈሩም፤
ጠላቶቻቸውን ግን ባሕር ዋጣቸው::
54ቀኝ እጁም ወዳስገኘችው ወደዚህ
ተራራ፣
ወደ ቅድስት ምድር አገባቸው::
55ሕዝቦችን ከፊታቸው አባረረ፤
ምድራቸውን ርስት አድርጎ
አከፋፈላቸው፤
የእስራኤልንም ነገዶች በጠላቶቻቸው
ቤት አኖረ::
56እነርሱ ግን አምላክን ተፈታተኑት፤
በልዑልም ላይ ዐመፁ፤
ሥርዐቱንም አልጠበቁም::
57ተመልሰው እንደ አባቶቻቸው ከዳተኛ
ሆኑ፤
እንደማያስተማምን ጠማማ ቀስት
ተወላገዱ::
58በኰረብታ ማምለኪያዎቻቸው
አስቈጡት፤
ተቀርጸው በተሠሩ ጣዖቶቻቸው
አስቀኑት::
59እግዚአብሔር ይህን በሰማ ጊዜ እጅግ
ተቈጣ፤
እስራኤልንም ፈጽሞ ተወ::
60በሰዎች መካከል ያቆማትን ድንኳን፣
የሴሎን ማደሪያ ተዋት::
61የኀይሉን ምልክት አስማረካት፤
ክብሩንም ለጠላቶቹ እጅ አሳልፎ ሰጠ::
62ሕዝቡን ለሰይፍ ዳረገ፤
በርስቱም ላይ እጅግ ተቈጣ::
63ጐልማሶቻቸውን እሳት በላቸው፤
ልጃገረዶቻቸውም የሰርግ ዘፈን
አልተዘፈነላቸውም::
64ካህናታቸው በሰይፍ ተገደሉ፤
መበለቶቻቸውም ማልቀስ ተሳናቸው::
65ጌታ ም ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ፤
የወይን ጠጅ ስካር እንደ በረደለት
ጀግናም ብድግ አለ::
66ጠላቶቹን መትቶ ወደ ኋላ መለሳቸው፤
የዘላለም ውርደትም አከናነባቸው::
67የዮሴፍን ድንኳን ተዋት፤
የኤፍሬምንም ነገድ አልመረጠም::
68ነገር ግን የይሁዳን ነገድ፣
የወደዳትን የጽዮንን ተራራ መረጠ::
69መቅደሱን እንደ ታላቅ ከፍታ፣
ለዘላለም እንደ መሠረታት ምድር
ሠራት::
70ባሪያውን ዳዊትን መረጠ፤
ከበጎች ጕረኖ ውስጥ ወሰደው፤
71ለሕዝቡ ለያዕቆብ፣
ለርስቱም ለእስራኤል እረኛ ይሆን
ዘንድ፣
የሚያጠቡ በጎችን ከመከተል
አመጣው::
72እርሱም በቅን ልቡ ጠበቃቸው፤
ብልኀት በተሞላ እጁም መራቸው::

## መዝሙር 79

### ብሔራዊ ሰቆቃ

የአሳፍ መዝሙር

1አምላክ ሆይ፤ ሕዝቦች ርስትህን ወረሩ፤
የተቀደሰውን ቤተ መቅደስህን አረከሱ፤
ኢየሩሳሌምንም አፈራርሰው ጣሏት::
2የባሪያዎችህን ሬሳ ለሰማይ ወፎች፣
የቅዱሳንህንም ሥጋ ለምድር አራዊት፣
ምግብ አድርገው ሰጡ::
3ደማቸውንም በኢየሩሳሌም ዙሪያ፣
እንደ ውሃ አፈሰሱ፤
የሚቀብራቸውም አልተገኘም::
4እኛም ለጎረቤቶቻችን መዘባበቻ፣
በዙሪያችንም ላሉት መሣቂያ

78፥42 መሳ3፥7፤ ነህ9፥17፤መዝ27፥11
78፥43 ዘፀ3፥20፤ 10፥1
78፥44 ዘፀ7፥20፡21 ፤መዝ105፥29
78፥45 ዘፀ8፥2፡6፡ 24፤መዝ105፥31
78፥46 ዘፀ10፥13፤ ናሆ3፥15
78፥47ዘፀ9፥23፤መዝ 105፥32፤147፥17
78፥48 ዘፀ9፥25
78፥49 ዘፍ19፥13፤ ዘፀ15፥7፤1ቆሮ10፥10
78፥51 ዘፀ12፥12፤ መዝ105፥23፤ 106፥22፤135፥8
78፥52 ኢዮ21፥11፤ መዝ28፥9
78፥53 ዘፀ14፥28፤ 15፥7፤106፥10
78፥54 መዝ44፥3
78፥55 ዘዳ1፥38፤ ኢሱ13፥7፤መዝ44፥2፤ ሐሥ13፥19
78፥57 ቍ9፤2ዜና 30፥7፤ሕዝ20፥27
78፥58 ዘፀ20፥4፤ ዘሌ26፥30፤ዘዳ5፥8፤32 ፥21፤መሳ2፥12
78፥59 ዘሌ26፥28፤ ዘኍ32፥14፤ዘዳ32፥19 ፤መዝ55፥19
78፥60 ኢሱ18፥1፤ ሕዝ8፥6
78፥61 1ሳሙ4፥17 ፤መዝ132፥8
78፥62 ዘዳ28፥25፤ 1ሳሙ10፥1
78፥63 ዘኍ11፥1፤ 1ነገ4፥32፤ኤር7፥34፤1 6፥9፤25፥10
78፥64 1ሳሙ4፥17
78፥65 መዝ44፥23
78፥66 1ሳሙ5፥6
78፥67 ኤር7፥15፤ ሆሴ9፥13፤12፥1
78፥68 ዘፀ15፥17፤ ዘኍ1፥7፤መዝ68፥16፤ 108፥8
78፥69 መዝ15፥1
78፥70 1ሳሙ16፥1
78፥71 ዘፍ37፥2፤ መዝ28፥9
78፥72 ዘፍ17፥1
79፥1 ዘፀ34፥9፤ዘሌ 20፥3፤2ነገ25፥9፤ነህ 4፥2፤ኢሳ6፥11
79፥2 ዘዳ28፥26፤ኤር 7፥33፤ራእ19፥17-18
79፥3 ኤር16፥4፤ 25፥33፤ራእ11፥9
79፥4 መዝ39፥8፤ 44፥13፤80፥6፤ሕዝ 5፥14

መሣለቂያ ሆንን፡፡

5 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ይህ እስከ መቼ
ነው? የምትቈጣውስ ለዘላለም
ነውን?
ቅናትህስ እንደ እሳት ሲነድ ይኖራልን?
6 በማያውቁህ ሕዝቦች ላይ፣
ስምህን በማይጠሩ፣
መንግሥታት ላይ፣
መዓትህን አፍስስ፤
7 ያዕቆብን በልተውታልና፤
መኖሪያ ቦታውንም ባድማ አድርገዋል፡፡
8 የአባቶቻችንን ኀጢአት በእኛ ላይ
አትቍጠርብን፤
ምሕረትህ ፈጥና ወደ እኛ ትምጣ፤
በጭንቅ ላይ እንገኛለንና፡፡

9 አዳኛችን የሆንህ አምላክ ሆይ፤
ስለ ስምህ ክብር ብለህ እርዳን፤
ስለ ስምህ ስትል፣
ታደገን፤ ኀጢአታችንንም ይቅር በል፡፡
10 ሕዝቦች፣ “አምላካቸው የት አለ?”
ለምን ይበሉ?
የፈሰሰውን የአገልጋዮችህን ደም በቀል፣
ዐይናችን እያየ ሕዝቦች ይወቁት፡፡
11 የእስረኞች ሰቈቃ በፊትህ ይድረስ፤
በክንድህም ብርታት፣
ሞት የተፈረደባቸውን አድን፡፡

12 ጌታ ሆይ፤ ጎረቤቶቻችን በአንተ ላይ
የተዘባበቱትን መዘባበት፣
ሰባት ዕጥፍ አድርገህ አስታቅፋቸው፡፡
13 እኛ ሕዝብህ፣ የማሰማሪያህ በጎችህ፣
ለዘላለም ምስጋና እናቀርብልሃለን፤
ከትውልድ እስከ ትውልድም፣
ውለታህን እንናገራለን፡፡

## መዝሙር 80

### ለእስራኤል ተሐድሶ የቀረበ ጸሎት

ለመዘምራን አለቃ፤ “የኪዳን ጽጌረዳ” በሚለው ቅኝት የሚዜም፤ የአሳፍ መዝሙር

1 ዮሴፍን እንደ በግ መንጋ የምትመራ፣
የእስራኤል እረኛ ሆይ፤ ስማን፤
በኪሩቤል ላይ በዙፋን የምትቀመጥ
ሆይ፤
በብርሃንህ ተገለጥ፤
2 በኤፍሬም፣ በብንያምና በምናሴ ፊት
ደምቀህ ታይ፡፡
ኀይልህን አንቀሳቅስ፤
መጥተህም አድነን፡፡

3 አምላክ ሆይ፤ መልሰን፤
እንድንም ዘንድ፣
ፊትህን አብራልን፡፡

4 የሰራዊት አምላክ *እግዚአብሔር* ሆይ፤
በሕዝብህ ጸሎት ላይ ቍጣህ
የሚነደው፣
እስከ መቼ ድረስ ነው?
5 የእንባ እንጀራ አበላሃቸው፤
ስፍር የሞላ እንባም አጠጣሃቸው፡፡
6 ለጎረቤቶቻችን የጠብ ምክንያት
አደረግኸን፤
ጠላቶቻችንም ተሣሣቁብን፡፡

7 የሰራዊት አምላክ ሆይ፤ መልሰን፤
እንድንም ዘንድ፣
ፊትህን አብራልን፡፡

8 ከግብፅ የወይን ግንድ አመጣህ፤
አሕዛብን አባርረህ እርሷን ተከልሃት፡፡
9 መሬቱን መነጠርህላት፤
እርሷም ሥር ሰዳ አገሩን ሞላች፡፡
10 ተራሮች በጥላዋ ተሸፈኑ፤
ግዙፍ ዝግቦችም በቅርንጫፎቿ
ተጠለሉ፡፡
11 ቅርንጫፎቿን እስከ ባሕሩ፣[ኘ]
ቍጥቋጦዋንም እስከ ወንዙ[ኣ] ዘረጋች፡፡

12 ታዲያ ዐላፊ አግዳሚው ፍሬዋን
እንዲለቅም፣
ለምን ቅጥሯን አፈረስህ?
13 ዕርያ ከዱር ወጥቶ ያበለሻሻታል፤
በሜዳ የሚንጋጋ እንስሳ ሁሉ
ይበላታል፡፡
14 የሰራዊት አምላክ ሆይ፤ እንግዲህ
ወደ እኛ ተመለስ፤
ከሰማይ ተመልከት፤ እይም፤
ይህችን የወይን ተክል ተንከባከባት፤
15 ይህች ቀኝ እጅህ የተከላት ቡቃያ፣
ለራስህ ያጸደቅሃት ተክል[ከ] ናት፡፡

16 እርሷም በእሳት ተቃጥላለች፤
የግንባርህ ተግሣጽ ያጠፋቸዋል፡፡
17 ለራስህ ባበረታኸው የሰው ልጅ ላይ፣
በቀኝ እጅህ ሰው ላይ እጅህ ትሁን፡፡
18 ከእንግዲህ አንተን ትተን ወደ ኋላ
አንመለስም፤
ሕያዋን አድርገን፤ እኛም ስምህን
እንጠራለን፡፡

19 የሰራዊት አምላክ *እግዚአብሔር* ሆይ፤
መልሰን፤
እንድንም ዘንድ፣
ፊትህን አብራልን፡፡

## መዝሙር 81

### ለዳስ በዓል የሚዜም ቅኔ

ለመዘምራን አለቃ፤ በዋሽንት የሚዜም፣ የአሳፍ መዝሙር

1 ብርታታችን ለሆነው አምላክ በደስታ

79፥5 ዘዳ29፥20፤ መዝ74፥1፥10፤85፥5፤89፥46፤ሶፎ3፥8
79፥6 መዝ2፥5፤ 14፥4፤69፥24፤110፥5፤ 147፥20፤ኤር10፥25፤ ራእ16፥1
79፥7 ኢሳ9፥12፤ ኤር10፥25
79፥8 ዘፍ9፥25፤ መዝ116፥6፤142፥6፤ኤር44፥21
79፥9 2ዜና14፥11፤ መዝ25፥11፤31፥3፤ ኤር14፥7
79፥10 ቍ3፤መዝ 42፥3፤94፥1፤ራእ6፥10
79፥12 ዘፍ4፥15፤ ኢሳ65፥6፤ኤር32፥18
79፥13 መዝ44፥8፤ 74፥1
80፥1 ዘፀ25፥22፤ መዝ77፥20
80፥2 ዘኍ2፥18-24 ፤መዝ35፥23፤54፥1፤ 69፥1፤71፥2፤109፥26፤ 116፥4፤119፥94
80፥3 ቍ7፥19፤ዘኍ 6፥25፤መዝ71፥20፤85፥4፤ኤር31፥18፤ሰቆ 5፥21
80፥4 ዘዳ29፥20፤ መዝ74፥10
80፥5 ኢዮ3፥24፤ ኢሳ30፥20
80፥6 መዝ79፥4
80፥7 ቍ3
80፥8 ዘፀ15፥17፤ 23፥28-30፤ኢሱ13፥6 ፤ኢሳ5፥1-2፤ኤር2፥21 ፤ማቴ21፥33-41፤ ሐሥ7፥45
80፥11 መዝ72፥8
80፥12 መዝ89፥40 ኢሳ5፥5፤30፥13፤ኤር 39፥8
80፥13 ኤር5፥6
80፥14 ዘዳ26፥15
80፥16 ዘዳ28፥20፤ መዝ79፥1
80፥17 ኢዮ25፥6
80፥18 መዝ85፥6፤ ኢሳ57፥15፤ሆሴ6፥2
81፥1 መዝ66፥1

[ኘ]11 ሜድትራኒያን ሳይሆን አይቀርም፡፡
[ኣ]11 የኤፍራጥስ ወንዝ ለማለት ነው፡፡
[ከ]15 ወንድ ልጅ የሚሉ ትርጕሞች አሉ፡፡

ዘምሩ፤
ለያዕቆብ አምላክ እልል በሉ።
2ዝማሬውን ጀምሩ፤ ከበሮውን ምቱ፤
በበገናና በመሰንቆ ጥዑም ዜማ አሰሙ።
3በሙሉ ጨረቃ፣ በክብረ በዓላችን ዕለት፣
በወሩ መግቢያ፣ ጨረቃ ስትወለድ
መለከት ንፉ፤
4ይህ ለእስራኤል የተሰጠ ሥርዐት፣
የያዕቆብም አምላክ ድንጋጌ ነውና።
5ሙሉ ለሙሉ ግብፅን ለቆ በወጣ ጊዜ፣
ይህን ለዮሴፍ ደነገገለት፤
በማላውቀውም[ኸ] ቋንቋ እንዲህ ሲል
ሰማሁ፦

6"ትከሻውን ከሸክም ገላገልሁት፤
እጁንም ቅርጫት ከመያዝ አሳረፍሁ።
7በመከራህ ጊዜ ጠራኸኝ፤ እኔም
ታደግሁህ፤
በነጐድጓድ መሰወሪያ ውስጥ መለስሁልህ፤
በመሪባ ውሃ ዘንድ ፈተንሁህ። ሴላ

8"ሕዝቤ ሆይ፤ ሳስጠነቅቅህ ስማኝ፤
እስራኤል ሆይ፤ ምነው ብታደምጠኝ!
9በአንተ ዘንድ ባዕድ አምላክ አይኑር፤
ለሌላም አምላክ አትስገድ።
10ከግብፅ ምድር ያወጣሁህ፣
እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝ፤
አፍህን በሰፊው ክፈተው፤ እኔም
እሞላዋለሁ።

11"ሕዝቤ ግን አላደመጠኝም፤
እስራኤልም እሺ አልሰጥ አለኝ።
12ስለዚህ በገዛ ዕቅዳቸው እንዲሄዱ፣
አሳልፌ ለደንዳናው ልባቸው
ሰጠኋቸው።

13"ምነው ሕዝቤ ቢያደምጠኝ ኖሮ፣
እስራኤል በመንገዴ በሄደ ኖሮ፣
14ጠላቶቻቸውን ፈጥኜ ባንበረከክኋቸው
ነበር፤
እጄን በባላጋራዎቻቸው ላይ ባነሣሁ
ነበር።
15እግዚአብሔርን የሚጠሉ በፊቱ ይርዳሉ፤
ቅጣታቸውም እስከ ዘላለም የሚዘልቅ
ነው።
16እናንተን ግን ምርጡን ስንዴ አበላችኋለሁ፤
ከዐለቱም ማር አጠግባችኋለሁ።"

## መዝሙር 82

### ሙሱናን ዳኞች

የአሳፍ መዝሙር

1እግዚአብሔር በአማልክት ጉባኤ መካከል
ተሰየመ፤
በአማልክትም ላይ ይፈርዳል፤ እንዲህም
ይላል፦

81፥2 ዘፀ15፥20፤ ኢዮ21፥12፤መዝ92፥3
81፥3 ዘፀ19፥13፤ ነህ10፥33
81፥4 ቀኍ1
81፥5 ዘፀ11፥4፤ መዝ114፥1
81፥6 ዘፀ1፥14፤ኢሳ 9፥4፤52፥2
81፥7 ዘፀ2፥23፤ 17፥7፤19፥19፤ዘዳ 33፥8
81፥8 መዝ50፥7፤ 78፥1
81፥9 ዘፀ20፥3
81፥10 ዘፀ6፥6፤ 13፥3፤29፥46፤መዝ 107፥9፤ሕዝ2፥8
81፥11 ዘፀ32፥1-6
81፥12 ሕዝ20፥25፤ ሐሥ7፥42፤ሮሜ1፥24
81፥13 ዘዳ5፥29
81፥14 መዝ47፥3፤ አሞ1፥8
81፥15 2ሳሙ22፥45
81፥16 ዘዳ32፥14
82፥1 ኢዮ21፥22፤ መዝ7፥8፤58፥11፤ኢሳ 3፥13፤66፥16፤ኢል 3፥12
82፥2 ዘዳ1፥17፤መዝ 58፥1-2፤ምሳ18፥5
82፥3 ዘዳ24፥17፤ መዝ140፥12፤ኤር 5፥28፤22፥16
82፥5 መሳ5፥4፤ኢዮ 30፥26፤መዝ11፥3፤ 14፥4፤53፥2፤ኢሳ 5፥30፤8፥21-22፤9፥2፤ 59፥9፤60፥2፤ኤር13፥1 6፤23፥12፤ሰቆ3፥2
82፥6 ዮሐ10፥34
82፥7 መዝ49፥12 ፤ሕዝ31፥14
82፥8 መዝ2፥8፤ 12፥5፤76፥9
83፥1 መዝ28፥1፤ 35፥22፤ኢሳ42፥14፤ 57፥11፤62፥1፤64፥12
83፥2 መሳ8፥28፤ መዝ2፥1፤ኢሳ17፥12
83፥3 ዘፀ1፥10፤መዝ 17፥14፤31፥13
83፥4 አስ3፥6፤ኤር 11፥19፤33፥24
83፥5 መዝ2፥2
83፥6 ዘፍ25፥16፤ 2ዜና20፥1፤መዝ137፥ 7፤ኢሳ34፥5፤ኤር 49፥7፤አሞ1፥11
83፥7 ዘፍ14፥7፤ 19፥38፤ዘፀ15፥14፤ 17፥14፤ኢሱ13፥5፤ ኢሳ23፥3፤ሕዝ27፥3
83፥8 ዘፍ10፥11፤ ዘዳ2፥9

2"ፍትሕን የምታጓድሉት እስከ መቼ
ነው?
ለክፉዎች የምታደሉትስ እስከ መቼ
ነው? ሴላ
3ለዐቅመ ቢሶችና ለድኻ አደጎች
ፍረዱላቸው፤
የችግረኛውንና የምስኪኑን መብት
አስከብሩ።
4ወገን የሌለውንና ችግረኛውን ታደጉ፤
ከግፈኛውም እጅ አስጥሏቸው።

5"ዕውቀትም ማስተዋልም የላቸውም፤
በጨለማ ውስጥ ወዲያ ወዲህ
ይመላለሳሉ፤
የምድርም መሠረቶች ሁሉ ተናወጡ።

6"እኔም፤ 'እናንተ አማልክት ናችሁ፤
ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ'
አልሁ።
7ነገር ግን እንደ ማንኛውም ሰው
ትሞታላችሁ፤
እንደ ማንኛውም ገዥ
ትወድቃላችሁ።"

8አምላክ ሆይ፤ ተነሥ፤ በምድር ላይ
ፍረድ፤
ሕዝቦች ሁሉ ርስትህ ናቸውና።

## መዝሙር 83

### በእስራኤል ጠላቶች ላይ የቀረበ ጸሎት

የአሳፍ መዝሙር፤ ማሕሌት

1አምላክ ሆይ፤ ዝም አትበል፤
አምላክ ሆይ፤ ጸጥ አትበል፤ ጭጭ
አትበል።
2ጠላቶችህ እንዴት እንደ ተነሣሡ፣
ባላንጣዎችህም እንዴት ራሳቸውን ቀና
ቀና እንዳደረጉ ተመልከት።
3በሕዝብህ ላይ በተንኰል አሤሩ፤
በውድ ልጆችህ ላይ በአንድነት
ተመካከሩ።
4"የእስራኤል ስም ከእንግዲህ እንዳይታወስ፣
ኑና ሕዝብ እንዳይሆኑ እንደምስሳቸው"
አሉ።
5በአንድ ሐሳብ ተስማምተው ተማከሩ፤
በአንተም ላይ ተማማሉ፤
6የኤዶምና የእስማኤላውያን ድንኳኖች፣
የሞዓብና የአጋራውያን ድንኳኖች፣
7ጌባል፣[ወ] አሞንና አማሌቅ፣
ፍልስጥኤምም ከጢሮስ ሕዝብ ጋር
ሆነው ዶለቱ፤
8አሦርም ከእነርሱ ጋር ተባበረ፤
የሎጥ ልጆችም ረዳት ሆነ። ሴላ

[ኸ]5 አንዳንዶች *የማናውቀውን ድምፅ ሰማን* ይላሉ።
[ወ]7 *ቢብሎስ* ለማለት ነው።

9በምድያም ላይ እንዳደረግኸው
አድርግባቸው፤
በቂሶንም ወንዝ በሲሣራና በኢያቢስ
ላይ ያደረስኸው ይድረስባቸው።
10እነርሱም በዐይንዶር ጠፉ፤
እንደ ምድርም ጒድፍ ሆኑ።
11መኳንንታቸውን እንደ ሔሬብና እንደ
ዜብ፣
መሳፍንታቸውንም ሁሉ እንደ ዛብሄልና
እንደ ስልማና አድርጋቸው፤
12እነዚህም፣ “የእግዚአብሔርን የግጦሽ ቦታ፣
ወስደን የግላችን እናድርግ” የሚሉ
ናቸው።

13አምላኬ ሆይ፤ በዐውሎ ነፋስ እንደሚነዳ
ትቢያ፣
በነፋስም ፊት እንዳለ ገለባ
አድርጋቸው።
14እሳት ደንን እንደሚያጋይ፣
ነበልባልም ተራራን እንደሚያቃጥል፣
15እንዲሁ በሞገድህ አሳዳቸው፤
በማዕበልህም አስደንግጣቸው።
16እግዚአብሔር ሆይ፤ ስምህን ይሹ ዘንድ፣
ፊታቸውን በዕፍረት ሙላው፤
17ለዘላለም ይፈሩ፤ ይታወኩም፤
በውርደትም ይጥፉ።
18ስምህ እግዚአብሔር የሆነው አንተ
ብቻ፣
በምድር ሁሉ ላይ ልዑል እንደ ሆንህ
ይወቁ።

## መዝሙር 84

### ወደ መቅደሱ ጒዞ መዝሙር

ለመዘምራን አለቃ፤ በዋሽንት የሚዜም የቆሬ ልጆች መዝሙር

1የሰራዊት አምላክ ሆይ፤
ማደሪያህ ምንኛ የተወደደ ነው!
2ነፍሴ የእግዚአብሔርን አደባባዮች
ትናፍቃለች፤
እጅግም ትጓጓለታለች፤
ልቤና ሥጋዬም፣
ለሕያው አምላክ እልል በሉ።
3ንጉሤና አምላኬ የሰራዊት አምላክ ሆይ፤
መሠዊያህ ባለበት ስፍራ፣
ድንቢጥ እንኳ መኖሪያ ቤት፣
ዋኖስም ጫጩቶቿን የምታኖርበት
ጐጆ አገኘች።
4በቤትህ የሚኖሩ የተባረኩ ናቸው፤
እነርሱም ለዘላለም ያመሰግኑሃል። ሴላ

5አንተን ብርታታቸው ያደረጉ፣
በልባቸው የጽዮንን መንገድ የሚያስቡ
ቡሩካን ናቸው።
6በልቅሶ ሸለቆ በሚያልፉበት ጊዜ፣
የምንጭ መፍለቂያ ቦታ ያደርጉታል፤
የበልጉም ዝናብ ያረሰርሰዋል።[o]
7ከኀይል ወደ ኀይል ይሸጋገራሉ፤
እያንዳንዱም በጽዮን ባለው አምላክ ፊት
ይቀርባል።
8የሰራዊት አምላክ ሆይ፤ ጸሎቴን ስማ፤
የያዕቆብ አምላክ ሆይ አድምጠኝ።
ሴላ

9አምላክ ሆይ፤ ጋሻችንን[″] እይልን፤
የቀባኸውንም ተመልከት።

10በሌላ ስፍራ ሺህ ቀን ከመኖር፣
በአደባባይህ አንዲት ቀን መዋል
ይሻላል፤
በክፉዎች ድንኳን ከመቀመጥ ይልቅ፣
በአምላኬ ቤት ደጅ መቆም
እመርጣለሁ።
11እግዚአብሔር አምላክ ፀሓይና ጋሻ
ነውና፤
እግዚአብሔር ሞገስንና ክብርን
ይሰጣል፤
እግዚአብሔር በቅንነት የሚሄዱትን፣
መልካም ነገር አይነፍጋቸውም።

12የሰራዊት አምላክ ሆይ፤
በአንተ የታመነ ሰው ቡሩክ ነው።

## መዝሙር 85

### ለሰላም የቀረበ ጸሎት

ለመዘምራን አለቃ፤ የቆሬ ልጆች፤ መዝሙር

1እግዚአብሔር ሆይ፤ ለምድርህ በጎ
ውለሃል፤
የያዕቆብንም ምርኮ መለስህ።
2የሕዝብህን በደል ይቅር አልህ፤
ኀጢአታቸውንም ሁሉ ሸፈንህ።
3መዓትህን ሁሉ አራቅህ፤
ከብርቱ ቍጣህም ተመለስህ።

4መድኀኒታችን የሆንህ አምላክ ሆይ፤
መልሰን፤
በእኛ ላይ የተቃጣውን ቍጣህን
መልሰው።
5የምትቈጣን ለዘላለም ነውን?
ቍጣህስ ከትውልድ እስከ ትውልድ
ይቀጥላልን?
6ሕዝብህ በአንተ ሐሤት ያደርግ ዘንድ፣
መልሰህ ሕያዋን አታደርገንምን?
7እግዚአብሔር ሆይ፤ ምሕረትህን አሳየን፤
ማዳንህን ለግሰን።
8እግዚአብሔር አምላክ የሚናገረውን
እሰማለሁ፤
ለሕዝቡ፣ ለቅዱሳኑ ሰላምን ይናገራልና፤
ዳሩ ግን ወደ ከንቱ ምግባራቸው
አይመለሱ።

[o]6 ወይም ይባርከዋል [″]9 ወይም ልዑል

83፥9 ዘፍ25፥2፤ ኢሱ11፥1፤መሳ4፥2፡ 23-24፤7፥1-23
83፥10 1ሳሙ28፥7፤2ነገ9፥37፤ኢሳ5፥25፤ኤር8፥2፤9፥22፤16፥4፤25፥33፤ሶፎ1፥17
83፥11 መሳ7፥25፤8፥5
83፥12 2ዜና20፥11፤ሕዝ35፥10
83፥13 ኢዮ13፥25
83፥14 ዘዳ32፥22፤ኢሳ9፥18
83፥15 ኢዮ9፥17፤መዝ50፥3
83፥16 መዝ34፥5፤109፥29፤132፥18
83፥17 2ነገ19፥26፤መዝ35፥4
83፥18 ኢዮ34፥29፤መዝ7፥8፤18፥13፤68፥4
84፥1 ዘዳ33፥27፤መዝ27፥4፤43፥3፤90፥1፤132፥5
84፥2 ኢሱ3፥10፤ኢዮ19፥27
84፥3 መዝ2፥6፤5፥2፤43፥4፤44፥11
84፥5 መዝ81፥1፤ኤር31፥6
84፥6 ኢዮ38፥26፤ኢል2፥23
84፥7 ዘዳ16፥16፤1ነገ8፥1፤ኢዮ17፥9
84፥8 መዝ4፥1
84፥9 1ሳሙ16፥6፤መዝ2፥2፤18፥50፤59፥11፤132፥17
84፥10 1ዜና23፥5
84፥11 ዘፍ15፥1፤መዝ34፥10፤ኢሳ60፥19፤ኤር43፥13፤ራእ21፥23
84፥12 መዝ2፥12
85፥1 ዘዳ30፥3፤መዝ14፥7
85፥2 ዘፀ32፥30፤ዘኍ14፥19፤መዝ78፥38
85፥3 ዘፀ32፥12፤ዘዳ13፥17፤መዝ78፥38፤106፥23፤ዳን9፥16፤ዮና3፥9
85፥4 መዝ65፥5፤71፥20
85፥5 መዝ50፥21
85፥6 መዝ80፥18፤ፊል3፥1
85፥7 መዝ6፥4፤27፥1
85፥8 ዘሌ26፥6፤ምሳ26፥11፤27፥22፤ኢሳ60፥17፤ዮሐ14፥27፤2ተሰ3፥16

9ክብሩ በምድራችን ይኖር ዘንድ፣
ማዳኑ ለሚፈሩት በእርግጥ ቅርብ
ነው።
10ምሕረትና ታማኝነት ተገናኙ፤
ጽድቅና ሰላም ተቃቀፉ።
11ታማኝነት ከምድር በቀለች፤
ጽድቅም ከሰማይ ተመለከተች።
12እግዚአብሔር በጎ ነገር ይለግሳል፤
ምድራችንም ፍሬዋን ትሰጣለች።
13ጽድቅ በፊቱ ይሄዳል፤
ለአረማመዱም መንገድ ያዘጋጃል።

## መዝሙር 86

### የመከራ ጊዜ ጸሎት

የዳዊት ጸሎት

1እግዚአብሔር ሆይ፤ ጆሮህን ወደ እኔ
ጣል፤ ስማኝም፤
እኔ ድኻና ችግረኛ ነኝና።
2ለአንተ የተለየሁ ሰው ነኝና ነፍሴን
ጠብቃት፤
አንተ አምላኬ ሆይ፤
በአንተ የታመነብህን ባሪያህን አድን።
3ጌታ ሆይ፤ ማረኝ፤
ቀኑን ሙሉ ወደ አንተ እጮኻለሁና።
4የባሪያህን ነፍስ ደስ አሰኛት፤
ጌታ ሆይ፤ ነፍሴን ወደ አንተ
አነሣለሁና።
5ጌታ ሆይ፤ አንተ ቸርና ይቅር ባይ ነህ፤
ለሚጠሩህ ሁሉ ምሕረትህ ወሰን
የለውም።
6እግዚአብሔር ሆይ፤ ጸሎቴን አድምጥ፤
የልመናዬን ጩኸት ስማ።
7አንተ ስለምትመልስልኝ፣
በመከራዬ ቀን ወደ አንተ እጣራለሁ።
8ጌታ ሆይ፤ ከአማልክት መካከል እንደ
አንተ ያለ የለም፤
ከአንተም ሥራ ጋር የሚወዳደር
ሥራ የለም።
9ጌታ ሆይ፤ አንተ የሠራሃቸው ሕዝቦች
ሁሉ፣
መጥተው በፊትህ ይሰግዳሉ፤
ለስምህም ክብር ይሰጣሉ፤
10አንተ ታላቅ ነህና፤ ታምራትም ትሠራለህ፤
አንተ ብቻህን አምላክ ነህ።
11እግዚአብሔር ሆይ፤ መንገድህን አስተምረኝ፤
በእውነትህም እሄዳለሁ፤
ስምህን እፈራ ዘንድ፣
ያልተከፋፈለ ልብ ስጠኝ።
12ጌታ አምላኬ ሆይ፤ በፍጹም ልቤ
አመሰግንሃለሁ፤
ስምህንም ለዘላለም አከብራለሁ፤
13ለእኔ ያሳየሃት ምሕረት ታላቅ ናትና፤
ነፍሴንም ከሲኦል[ሠ] ጥልቀት
አውጥተሃል።
14አምላክ ሆይ፤ እብሪተኞች
ተነሥተውብኛል፤
የዐመፀኞችም ጉባኤ ነፍሴን ይሿታል፤
አንተንም ከምንም አልቈጠሩም።
15ጌታ ሆይ፤ አንተ ግን መሓሪና ርኅሩኅ
አምላክ ነህ፤
ለቍጣ የዘገየህ፣ ምሕረትህና
ታማኝነትህ የበዛ።
16ወደ እኔ ተመልከት፤ ማረኝም፤
ለባሪያህ ኀይልህን ስጥ፤
የሴት ባሪያህንም[የ] ልጅ አድን።
17የሚጠሉኝ አይተው ያፍሩ ዘንድ፣
የበጎነትህን ምልክት አሳየኝ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ
ረድተኸኛልና፤ አጽናንተኸኛልም።

## መዝሙር 87

### ጽዮን የሕዝቦች እናት

የቆሬ ልጆች መዝሙር፤ ማሕሌት

1መሠረቱን በተቀደሱ ተራሮች አቆመ፤
2እግዚአብሔር ከያዕቆብ ማደሪያዎች
ሁሉ ይልቅ፣
የጽዮንን ደጆች ይወዳል።
3የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ፤
ስለ አንቺ ክቡር የሆነ ነገር እንዲህ
ተብሎ ይነገራል፤ ሴላ
4"ከሚያውቁኝ መካከል፣
ረዓብንና[ደ] ባቢሎንን እጠቅሳለሁ፤
እነሆ፤ ፍልስጥኤምና ጢሮስ ከኢትዮጵያ
ጋር፣
'ይህ[ጀ] ሰው በዚያ ነው የተወለደው'
ይላሉ።"
5በእርግጥም ስለ ጽዮን፣
"ይህም ያም ሰው በእርሷ ውስጥ ተወለዱ፤
ልዑልም ራሱ ያጸናታል" ይባላል።
6እግዚአብሔር ሕዝቡን ሲመዘግብ፣
"ይህ ሰው የተወለደው በዚያ ነው"
ብሎ ይጽፋል። ሴላ
7የሚያዜሙም መሣሪያ የሚጫወቱም፣
"ምንጩ ሁሉ በአንቺ ውስጥ ይገኛል"
ይላሉ።

## መዝሙር 88

### ሰቆቃ

ማሕሌት፤ የቆሬ ልጆች መዝሙር፤ ለመዘምራን
አለቃ፤ በማኸላት የሚዘመር፤ የይዝራኤላዊው የኤማን
ትምህርት

1አዳኜ የሆንህ አምላክ እግዚአብሔር
ሆይ፤

85፥9 ዘፀ29፥43፤ መዝ27፥1፤ኢሳ43፥3፤45፥8፤46፥13፤51፥5፤56፥1፤60፥19፤62፥11፤ሐጌ2፥9፤ዘካ2፥5
85፥10 መዝ72፥2-3፤89፥14፤115፥1፤ምሳ3፥3፤ኢሳ32፥17
85፥11 ኢሳ45፥8
85፥12 ዘሌ26፥4፤ መዝ67፥6፤84፥11፤ዘካ8፥12፤ያዕ1፥17
86፥1 መዝ17፥6
86፥2 መዝ25፥2፤31፥14
86፥3 መዝ4፥1፤9፥13፤57፥1፤88፥9
86፥4 መዝ46፥5፤143፥8
86፥5 ዘፀ34፥6፤ነህ9፥17፤መዝ103፥8፤145፥8፤ኢል2፥13፤ዮና4፥2
86፥6 መዝ5፥2፤17፥1
86፥7 ኢዮ22፥27፤ መዝ3፥4፤4፥3፤27፥5፤50፥15፤80፥18፤ 91፥15፤94፥13፤ኢሳ30፥19፤58፥9፤65፥24፤ዕን3፥16፤ዘካ13፥19
86፥8 ዘፀ8፥10፤ኢዮ21፥22፤መዝ18፥31
86፥9 መዝ65፥2፤66፥4፤ኢሳ19፥21፤27፥13፤43፥7፤44፥23፤49፥7፤ዘካ8፥20-22፤14፥16፤ራእ15፥4
86፥10 ዘፀ3፥20፤ዘዳ6፥4፤2ሳሙ7፥22፤ መዝ48፥1፤71፥17፤72፥18፤ኢሳ43፥10፤ማር12፥29፤1ቆሮ8፥4
86፥11 ዘፀ33፥13፤ዘዳ6፥24፤1ሳሙ12፥23፤ መዝ25፥5፤26፥3፤ኤር24፥7፤32፥39፤ሕዝ11፥19፤1ቆሮ7፥35
86፥12 መዝ9፥1
86፥13 መዝ16፥10፤34፥4፤49፥15፤56፥13፤116፥8
86፥14 መዝ54፥3
86፥15 ቍ5፤ዘፀ34፥6፤ዘኍ14፥18፤ነህ9፥17፤መዝ51፥1፤103፥8፤111፥4፤116፥5፤145፥8፤ኢል2፥13
86፥16 መዝ6፥4፤9፥13፤18፥1፤116፥16
86፥17 ዘፀ3፥12፤ ማቴ24፥3፤ዮሐ2፥11
87፥1 መዝ48፥1
87፥2 መዝ2፥6
87፥3 መዝ46፥4
87፥4 2ሳሙ8፥1፤ ኢዮ9፥13፤መዝ45፥12፤83፥7፤ኢሳ19፥25፤ ኢል3፥4
87፥6 ዘፀ32፥32፤ መዝ69፥28፤ኢሳ4፥3፤ሚል3፥16
87፥7 መዝ36፥9፤149፥3 88፥1 መዝ3፥4፤22፥2፤51፥14፤ሉቃ18፥7

[ሠ]13 አንዳንዶች *መቃብር* ይላሉ።
[የ]16 *ታማኝ ወንድ ልጅህን* የሚሉ አሉ።
[ደ]4 የግብፅ ቅኔያዊ ስያሜ ነው።
[ጀ]4 ወይም *ረዓብ ባቢሎን፣ ፍልስጥኤምና ኢትዮጵያ*

በቀንና በሌሊት በፊትህ አጮኻለሁ።
[2]ጸሎቴ በፊትህ ትድረስ፤
ጆሮህንም ወደ ጩኸቴ አዘንብል፤

[3]ነፍሴ በመከራ ተሞልታለችና፤
ሕይወቴም ወደ ሲኦል[ገ] ተቃርባለች።
[4]ወደ ጒድጓድ ከሚወርዱት ጋር
ተቈጠርሁ፤
ዐቅምም አጣሁ።
[5]በሙታን መካከል እንደ ተጣሉ፣
ተገድለው በመቃብር ውስጥ እንደ
ተጋደሙ፣
አንተ ከእንግዲህ እንደማታስባቸው፣
ከእጅህም ወጥተው እንደ ተወገዱ
ሆንሁ።

[6]በዐዘቅት ጥልቀት ውስጥ ጣልኸኝ፤
በጨለማ ጒድጓድ ውስጥ ከተትኸኝ።
[7]የቍጣህ ክብደት በላዬ ዐርፎአል፤
በማዕበልህም ሁሉ አጥለቅልቀኸኛል።
ሴላ
[8]የሚቀርቡኝ ባልንጀሮቼን ከእኔ አራቅህ፤
እንዲጸየፉኝም አደረግህ፤
ተከብቤአለሁ፤ ማምለጥም አልችል፤
[9]ዐይኖቼም በሐዘን ፈዘዙ።
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ዘወትር ወደ አንተ
እጣራለሁ፤
እጆቼንም ወደ አንተ ዘረጋሁ።
[10]ድንቅ ሥራህን ለሙታን ታሳያለህን?
የሙታንስ መናፍስት ተነሥተው
ያመሰግኑሃልን?
ሴላ

[11]ምሕረትህ በመቃብር ውስጥ፣
ታማኝነትህስ እንጦርጦስ[ጠ]
ይነገራልን?
[12]ድንቅ ሥራህ በጨለማ ስፍራ፣
ጽድቅህስ በመረሳት ምድር
ትታወቃለችን?

[13]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ እኔ ግን ትረዳኝ
ዘንድ ወደ አንተ እጮኻለሁ፤
በጧትም ጸሎቴን በፊትህ አደርሳለሁ።
[14]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ለምን ታርቀኛለህ?
ፊትህንስ ከእኔ ለምን ትሰውራለህ?

[15]እኔ ከልጅነቴ ጀምሮ ችግረኛና ለሞት
የተቃረብሁ ነበርሁ፤
መዓትህ አሥቃየኝ፤ ግራም ተጋባሁ።
[16]ቍጣህ በላዬ ላይ ተከነበለ፤
መዓትህም አጠፋኝ።
[17]ቀኑን ሙሉ እንደ ጐርፍ ከበቡኝ፤
በአንድነትም ዙሪያዬን አጥረው
ያዙኝ።
[18]ወዳጄንና ባልንጀራዬን ከእኔ አራቅህ፤
ጓደኛዬ ጨለማ ብቻ ሆኖ ቀረ።

88፥3 ኢዮ33፥22፤ መዝ6፥3፤25፥17
88፥4 መዝ18፥1፤ 31፥12
88፥5 መዝ31፥22
88፥6 መዝ30፥1፤ 69፥15፤ሰቆ3፥55፤ዮና2፥3
88፥7 መዝ7፥11፤ 42፥7
88፥8 ኢዮ3፥23፤ 19፥13፤መዝ31፥11፤ኤር32፥2፤33፥1
88፥9 ኢዮ11፥13፤ መዝ5፥2፤38፥10፤ 143፥6
88፥10 መዝ6፥5
88፥11 መዝ30፥9
88፥13 መዝ5፥3፤ 30፥2፤55፥17፤ 119፥147
88፥14 መዝ13፥1፤ 43፥2
88፥15 ኢዮ6፥4፤ 18፥11፤መዝ9፥12፤129፥1፤ኤር22፥21፤ሕዝ16፥22፤ሆሴ2፥15፤2ቆሮ4፥8
88፥16 ኢዮ6፥4፤ መዝ7፥11
88፥17 መዝ124፥4
88፥18 ቍ8፤መዝ 38፥11

89፥1 መዝ36፥5፤ 40፥10፤59፥16
89፥2 መዝ36፥5
89፥4 2ሳሙ7፥12-16፤1ነገ8፥16፤መዝ132፥11-12፤ኢሳ9፥7፤ሕዝ37፥24-25፤ማቴ1፥1፤ሉቃ1፥33
89፥5 መዝ1፥5፤ 19፥1
89፥6 ዘፍ1፥26፤ዘፀ9፥14፤መዝ18፥31፤113፥5
89፥7 ኢዮ5፥1፤መዝ 47፥2፤111፥1
89፥8 መዝ71፥19፤ ኢሳ6፥3
89፥9 መዝ65፥7
89፥10 ኢዮ9፥13፤ መዝ59፥11፤68፥1፤ 92፥9
89፥11 ዘፍ1፥1፤ዘዳ10፥14፤1ዜና29፥11፤መዝ24፥1፤115፥16
89፥12 ዘዳ3፥8፤ 4፥48፤ኢሱ19፥22፤ መዝ98፥8
89፥13 ኢሱ4፥24
89፥14 መዝ85፥10-11፤97፥2

## መዝሙር 89

### መዝሙርና ለእግዚአብሔር ታማኝነት የቀረበ ጸሎት

የይዝራኤላዊው የኤታን ትምህርት

[1]ስለ *እግዚአብሔር* ምሕረት ለዘለላለም
እዘምራለሁ፤
በአፌም ታማኝነትህን ከትውልድ እስከ
ትውልድ እገልጻለሁ።
[2]ምሕረትህን ለዘላለም እንደምትመሠርት፣
ታማኝነትህንም በሰማይ እንደምታጸና
እናገራለሁና።

[3]አንተም እንዲህ ብለሃል፤ "ከመረጥሁት
ጋር ኪዳን ገብቻለሁ፤
ለባሪያዬ ለዳዊት ምያለሁ፤
[4]'ዘርህን ለዘላለም እተክላለሁ፤
ዙፋንህንም ከትውልድ እስከ ትውልድ
አጸናለሁ።' " ሴላ
[5]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ሰማያት ድንቅ
ሥራህን፣
ታማኝነትህንም በቅዱሳን ጉባኤ
መካከል ያወድሳሉ፤
[6]በላይ በሰማያት *ከእግዚአብሔር* ጋር
ማን ሊስተካከል ይችላል?
ከሰማያውያን ፍጥረታትስ መካከል
ማን *እግዚአብሔርን* ይመስለዋል?
[7]እግዚአብሔር በቅዱሳን ጉባኤ መካከል
በጣም የሚፈራ፣
በዙሪያውም ካሉት ሁሉ በላይ እጅግ
የሚከበር ነው።
[8]የሰራዊት አምላክ *እግዚአብሔር* ሆይ፤
እንደ አንተ ያለ ማን ነው?
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ ኀያል ነህ፤
ታማኝነትህም ከብቦሃል።

[9]የባሕርን ቍጣ ትቈጣጠራለህ፤
ሞገዱም ሲነሣ ጸጥ ታደርገዋለህ።
[10]አንተ ረዓብን የተሰየፈ ያህል
አደቀቅኸው፤
በብርቱ ክንድህም ጠላቶችህን
በተንሃቸው።
[11]ሰማያት የአንተ ናቸው፤ ምድርም
የአንተ ናት፤
ዓለምንና በውስጧ ያለውን ሁሉ አንተ
መሠረትህ።
[12]ሰሜንንና ደቡብን የፈጠርህ አንተ ነህ፤
ታቦርና አርሞንኤም በስምህ ሐሤት
ያደርጋሉ።
[13]አንተ ክንደ ብርቱ ነህ፤
እጅህ ኀያል ናት፤ ቀኝ እጅህም ከፍ
ከፍ ያለች ናት።
[14]ጽድቅና ፍትሕ የዙፋንህ መሠረቶች

[ገ]3 *መቃብር* የሚሉ አሉ።
[ጠ]11 በዕብራይስጥ *አባዳን* ማለት ነው፤ *የመውደሚያ ስፍራ* ነው።

ናቸው፤
ምሕረትና ታማኝነት በፊትህ ይሄዳሉ።
15 እግዚአብሔር ሆይ፤ እልልታን
የሚያውቅ፣
በፊትህም ብርሃን የሚሄድ ሕዝብ
ምስጉን ነው።
16 ቀኑን ሙሉ በስምህ ደስ ይላቸዋል፤
በጽድቅህም ሐሤት ያደርጋሉ፤
17 አንተ የብርታታቸው ክብር ነህና፤
በሞገስህም ቀንዳችንን[ጨ] ከፍ ከፍ
አደረግህ።
18 ጋሻችን[ጸ] የእግዚአብሔር ነውና፤
ንጉሣችንም የራሱ የእስራኤል ቅዱስ
ነው።

19 በዚያን ጊዜ በራእይ ተናገርህ፤
ታማኝ ሕዝብህንም እንዲህ አልህ፤
"ኀያሉን ሰው ሥልጣን አጐናጸፍሁት፤
ከሕዝብ መካከል የተመረጠውንም ከፍ
ከፍ አደረግሁት።
20 ባሪያዬን ዳዊትን አገኘሁት፤
በተቀደሰው ዘይቴም ቀባሁት።
21 እጄ ይደግፈዋል፤
ክንዴም ያበረታዋል።
22 በጠላት አይበለጥም፤
ክፉ ሰውም አይበግረውም።
23 ባላንጣዎቹን በፊቱ አደቅቃቸዋለሁ፤
ጠላቶቹንም እቀጠቅጣለሁ።
24 ታማኝነቴና ምሕረቴ ከእርሱ ጋር
ይሆናል፤
በስሜም ቀንዱ ከፍ ከፍ ይላል።
25 እጁን በባሕር ላይ፣
ቀኝ እጁንም በወንዞች ላይ አኖራለሁ።
26 እርሱም፣ 'አንተ አባቴ ነህ፤
አምላኬና መዳኛ ዐለቴም ነህ' ብሎ
ይጠራኛል።
27 እኔም ደግሞ በኵሬ አደርገዋለሁ፤
ከምድር ነገሥታትም በላይ ከፍ ይላል።
28 ምሕረቴንም ለዘላለም ለእርሱ
እጠብቃለሁ፤
ከእርሱ ጋር የገባሁት ኪዳንም ጸንቶ
ይኖራል።
29 የዘር ሐረጉን ለዘላለም፣
ዙፋኑንም በሰማያት ዕድሜ ልክ
አጸናለሁ።

30 "ልጆቹ ሕጌን ቢተዉ፣
ደንቤን ባይጠብቁ፣
31 ሥርዐቴን ቢጥሱ፣
ትእዛዜንም ባያከብሩ፣
32 ኀጢአታቸውን በበትር፣
በደላቸውን በጅራፍ እቀጣለሁ።
33 ምሕረቴን ግን ከእርሱ አላርቅም፤
ታማኝነቴንም አላጓድልበትም።

89፥15 መዝ1፥1፤ 44፥3
89፥16 መዝ30፥4፤ 105፥3
89፥17 ቍ24፤መዝ 18፥1፤75፥10፤92፥10፤ 112፥9፤148፥14
89፥18 መዝ18፥2፤ 47፥9፤ኢሳ16፥5፤ 33፥17፥22
89፥20 ዘፀ29፥7፤ 1ሳሙ2፥35፤2ሳሙ22 ፥51፤1ነገ1፥39፤መዝ 78፥70፤ሐሥ13፥22
89፥21 ቍ13፤መዝ 18፥35
89፥22 መሳ3፥15፤ 2ሳሙ7፥10
89፥23 2ሳሙ7፥9፤ መዝ18፥40
89፥24 2ሳሙ7፥15
89፥25 መዝ72፥8
89፥26 2ሳሙ7፥14 ፤22፥47፤መዝ62፥2፤ ኤር3፥4፤ዕብ1፥5
89፥27 ዘኍ24፥7፤ መዝ2፥6፤ቆላ1፥18፤ራ እ1፥5፤19፥16
89፥28 ቍ33-34፤ ኢሳ55፥3
89፥29 ቍ4፥36
89፥32 2ሳሙ7፥14
89፥33 2ሳሙ7፥15
89፥34 ዘኍ23፥19
89፥36 ቍ4
89፥37 ኤር33፥20- 21
89፥38 1ዜና28፥9፤ መዝ44፥9፤78፥59
89፥39 ሰቆ5፥16
89፥40 መዝ80፥12 ፤ኢሳ22፥5፤ሰቆ2፥2
89፥41 መሳ2፥14፤ መዝ44፥13
89፥42 መዝ13፥2፤ 80፥6
89፥43 መዝ44፥10
89፥45 መዝ39፥5፤ 44፥15፤109፥29
89፥46 መዝ79፥5
89፥47 ዘፍ47፥9፤ ኢዮ7፥7፤መዝ39፥5፤ 1ጴጥ1፥24
89፥48 ዘፍ5፥24፤ መዝ22፥29
89፥50 መዝ69፥19
89፥51 መዝ74፥10

34 ኪዳኔን አላፈርስም፤
ከአፌ የወጣውንም አላጥፍም።
35 በአንድ ጊዜ በቅድስናዬ ምያለሁና፣
ዳዊትን አልዋሽውም።
36 የዘር ሐረጉ ለዘላለም፣
ዙፋኑም በፊቴ እንደ ፀሓይ ጸንቶ
ይኖራል፤
37 በሰማይ ታማኝ ምስክር ሆና
እንደምትኖረው፣
እንደ ጨረቃ እርሱ ለዘላለም
ይመሠረታል።" ሴላ

38 አሁን ግን ናቅኸው፤ ጣልኸውም፤
የቀባኸውንም እጅግ ተቈጣኸው።
39 ከባሪያህ ጋር የገባኸውን ኪዳን አፈረስህ፤
የክብር ዘውዱን ትቢያ ላይ ጥለህ
አቃለልኸው።
40 ቅጥሩን ሁሉ አፈራረስህ፤
ምሽጉንም ደመሰስህ።
41 ዐላፊ አግዳሚው ሁሉ ዘረፈው፤
ለጎረቤቶቹ መዘባበቻ ሆነ።
42 የጠላቶቹን ቀኝ እጅ ከፍ ከፍ አደረግህ፤
ባላንጣዎቹም ሁሉ ደስ አላቸው።
43 የሰይፉን ስለት አጠፍህ፤
በጦርነትም ጊዜ አልረዳኸውም።
44 ግርማዊነቱን አጠፋህበት፤
ዙፋኑንም ከዐፈር ደባለቅኸው።
45 የወጣትነት ዘመኑን አሳጠርኸው፤
ዕፍረትንም አከናነብኸው። ሴላ

46 እግዚአብሔር ሆይ፤ ይህ እስከ መቼ
ይሆናል? ራስህንስ ለዘላለም
ትሰውራለህን?
ቍጣህስ እንደ እሳት የሚነደው እስከ
መቼ ነው?
47 ዘመኔ ምን ያህል አጭር እንደ ሆነች
አስብ፤
የሰውን ልጆች እንዲያው ለከንቱ
ፈጠርሃቸው!
48 ሞትን ሳያይ ሕያው ሆኖ የሚቀር
ሰው አለን?
ራሱን ከሲኦል እጅ ማዳን የሚችል
ማን ነው? ሴላ።
49 ጌታ ሆይ፤ ለዳዊት በታማኝነትህ
የማልህለት፣
የቀድሞው ምሕረትህ የት አለ?
50 ጌታ ሆይ፤ ባሪያህ[ጸ] እንዴት እንደ
ተፌዘበት፣
የብዙ ሰዎችንም ነቀፋ እንደ ታቀፍሁ
አስብ።
51 እግዚአብሔር ሆይ፤ ጠላቶችህ
የተሣለቁበትን፣

[ጨ] 17 የጥንካሬ ምልክት ነው።
[ጸ] 18 ወይም ልዑል ማለት ነው።
[ጸ] 50 ባሮችህ የሚሉ አሉ።

የቀባኸውን ሰው እርምጃ የነቀፉበትን
ሁኔታ አስብ።

52 *እግዚአብሔር* ለዘላለም ይባረክ፤
አሜን፤ አሜን።

**አራተኛ መጽሐፍ**
**ከመዝሙር 90-106**

**መዝሙር** 90
**የሰው ልጅ ሕይወት**

የእግዚአብሔር ሰው የሙሴ ጸሎት

1 *እግዚአብሔር* ሆይ፤
አንተ ከትውልድ እስከ ትውልድ
መጠጊያችን ሆንህልን።
2 ገና ተራሮች ሳይወለዱ፣
ምድርንና ዓለምን ከመፍጠርህ በፊት፣
አንተ ከዘላለም እስከ ዘላለም አምላክ
ነህ።
3 ሰዎችን ወደ ዐፈር ትመልሳለህ፤
"የሰው ልጆች ሆይ፤ ወደ ቦታችሁ
ተመለሱ" ትላለህ፤
4 ሺህ ዓመት በፊትህ፣
እንዳለፈችው እንደ ትናንት ቀን፣
እንደ ሌሊትም እርቦ ነውና።
5 እንደ ጐርፍ ጠርገህ ስትወስዳቸው፣
እንደ ሕልም ይበናሉ፤
እንደ ማለዳ ሣር ታድሰው ይበቅላሉ፤
6 ሣሩም ንጋት ላይ አቈጥቍጦ
ይለመልማል፤
ምሽት ላይ ጠውልጎ ይደርቃል።
7 በቍጣህ አልቀናልና፤
በመዓትህም ደንግጠናል።
8 በደላችንን በፊትህ፣
የተሰወረ ኀጢአታችንንም በገጽህ
ብርሃን ፊት አኖርህ።
9 ዘመናችን ሁሉ በቍጣህ ዐልፎአልና፤
ዕድሜአችንንም በመቃተት እንጨርሳለን።
10 የዕድሜአችን ዘመን ሰባ ዓመት፣
ቢበዛም ሰማንያ ነው፤
ከዚያ በላይ ከሆነም ድካምና መከራ
ብቻ ነው፤
ቶሎ ያልፋልና፤ እኛም ወዲያው
እንነጒዳለን።
11 የቍጣህን ኀይል ማን ያውቃል?
መዓትህም የመፈራትህን ያህል
ታላቅ ነው።
12 ጥበብን የተሞላ ልብ ይኖረን ዘንድ፣
ዕድሜያችንን መቍጠር አስተምረን።
13 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ተመለስ፤ ይህ
እስከ መቼ ይሆናል?
ለአገልጋዮችህም ራራላቸው።
14 በዘመናችን ሁሉ ደስ እንዲለን፣
ሐሤትም እንድናደርግ፣
ምሕረትህን በማለዳ አጥግበን።
15 መከራ ባሳየኸን ዘመን መጠን፣
ክፉም ባየንባቸው ዓመታት ልክ
ደስ አሰኘን።
16 ሥራህ ለአገልጋዮችህ፣
ክብርህም ለልጆቻቸው ይገለጥ።
17 የጌታ የአምላካችን ሞገስ[ፀ] በላያችን
ይሁን፤
የእጆቻችንን ሥራ ፍሬያማ
አድርግልን፤
አዎን፣ ፍሬያማ አድርግልን።

**መዝሙር** 91
**የእግዚአብሔር ጥበቃ**

1 በልዑል መጠጊያ የሚኖር፣
ሁሉን በሚችል አምላክ[ፊ] ጥላ ሥር
ያድራል።
2 *እግዚአብሔርን*፣ "መጠጊያዬ፣ ምሽጌ፣
የምታመንብህ አምላኬ" እለዋለሁ።[ፐ]
3 እርሱ ከአዳኝ ወጥመድ፣
ከአሰቃቂ ቸነፈር ያድንሃልና።
4 በላባዎቹ ይጋርድሃል፤
በክንፎቹ ሥር መሸሸጊያ ታገኛለህ፤
ታማኝነቱ ጋሻና መከታ ይሆንሃል።
5 የሌሊትን አስደንጋጭነት፣
በቀን የሚወረወረውንም ፍላጻ አትፈራም፤
6 በጨለማ የሚያደባ ቸነፈር፣
በቀትር ረፍራፊውም አያሠጋህም።
7 በአጠገብህ ሺህ፣
በቀኝህም አሥር ሺህ ይወድቃል፤
ወደ አንተ ግን አይቀርብም።
8 በዐይንህ ብቻ ትመለከታለህ፤
የክፉዎችንም መቀጣት ታያለህ።
9 *እግዚአብሔርን* መሸሸጊያ፣
ልዑልንም መጠጊያህ አድርገሸዋልና።
10 ክፉ ነገር አያገኝህም፤
መቅሠፍትም ወደ ድንኳንህ አይገባም፤
11 በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ፣
መላእክቱን ስለ አንተ ያዛቸዋልና።
12 እግርህ ከድንጋይ ጋር እንዳይጋጭ፣
በእጆቻቸው ወደ ላይ ያነሡሃል።
13 በአንበሳና በእፉኝት ላይ ትጫማለህ፤
ደቦሉን አንበሳና ዘንዶውን ትረግጣለህ።
14 "ወዶኛልና እታደገዋለሁ፤
ስሜን አውቆአልና እከልለዋለሁ።
15 ይጠራኛል፤ እመልስለታለሁ፤
በመከራው ጊዜ ከእርሱ ጋር እሆናለሁ፤
አድነዋለሁ፤ አከብረዋለሁ።
16 ረጅም ዕድሜን አጠግበዋለሁ፤

**89፥52** መዝ41፥13፤72፥19
**90፥1** ዘዳ33፥27፤ ኤፌ2፥22፤ራእ21፥3
**90፥2** ዘፍ21፥33፤ ኢዮ10፥5፤15፥7፤ መዝ102፥24-27፤ምሳ8፥23-26፤ኢሳ9፥6፤57፥15
**90፥3** ዘፍ2፥7፤ኢዮ7፥21፤34፥15፤ 1ቆሮ15፥47
**90፥4** ኢዮ10፥5፤ 2ጴጥ3፥8
**90፥5** ዘፍ19፥15
**90፥6** ኢሳ40፥6-8፤ ማቴ6፥30፤ያዕ1፥10
**90፥8** መዝ19፥12፤ 2ቆሮ4፥2፤ኤፌ5፥12፤ዕብ4፥13
**90፥9** መዝ78፥33
**90፥10** 2ሳሙ19፥35፤ኢዮ5፥7፤20፥8፤34፥15፤ኢሳ23፥15፡17፤ኤር25፥11
**90፥11** መዝ7፥11፤ 76፥7
**90፥12** ዘዳ32፥29፤ መዝ39፥4፤139፥16፤ ምሳ16፥9፤20፥24
**90፥13** ዘዳ32፥36፤ መዝ6፥3
**90፥14** መዝ5፥11፤ 31፥7፤77፥8፤103፥5፤107፥9፤143፥8፤ 145፥16፡19
**90፥16** መዝ44፥1፤ዕን3፥2
**90፥17** ኢሳ26፥12
**91፥1** ዘፀ33፥22፤ መዝ63፥7፤ኢሳ49፥2፤ሰቆ4፥20
**91፥2** ቍ9፤2ሳሙ22፥2፡3፤መዝ9፥9
**91፥3** 1ነገ8፥37፤ መዝ124፥7፤ምሳ6፥5
**91፥4** ዘዳ32፥10፤ ሩት2፥12፤መዝ17፥8፤35፥2፤ኢሳ27፥3፤ 31፥5፤ዘካ12፥8
**91፥5** ኢዮ5፥21
**91፥8** መዝ37፥34፤ 58፥10
**91፥10** ምሳ12፥21
**91፥11** ዘፍ32፥1፤ መዝ34፥7፤ዕብ1፥14
**91፥12** ማቴ4፥6፤ ሉቃ4፥10-11
**91፥13** ዳን6፥22፤ ሉቃ10፥19
**91፥15** 1ሳሙ2፥30፤ዮሐ12፥26
**91፥16** ዘዳ6፥2፤ መዝ21፥4፤50፥23

[ፀ]17 *ውበት* ለማለት ነው።
[ፊ]1 በዕብራይስጥ *ሻዳይ* ማለት ነው።
[ፐ]2 አንዳንድ ትርጒሞች *ይላል* ይላሉ።

ማዳኔንም አሳየዋለሁ::”

## መዝሙር 92

### ጻድቅ ሰው ሲደሰት

በሰንበት ቀን የሚዘመር መዝሙር፤ ማሕሌት

1እግዚአብሔርን ማመስገን መልካም ነው፤
ልዑል ሆይ፤ ለስምህ መዘመር
ጥሩ ነው፤
2ምሕረትህን በማለዳ፣
ታማኝነትህንም በሌሊት ማወጅ
መልካም ነው፤
3ዐሥር አውታር ባለው በገና፣
በመሰንቆም ቅኝት ታጅቦ ማወጅ
ጥሩ ነው::
4እግዚአብሔር ሆይ፤ በሥራህ ስለ
ተደሰትሁ፣
ስለ እጅህ ሥራ በደስታ እዘምራለሁ::
5እግዚአብሔር ሆይ፤ ሥራህ እንዴት
ታላቅ ነው!
ሐሳብህስ ምን ያህል ጥልቅ ነው!
6ደነዝ ሰው ይህን አያውቅም፤
ነኁላላም አያስተውለውም::
7ክፉዎች እንደ ሣር ቢበቅሉ፣
ክፉ አድራጊዎች ቢለመልሙ፣
ለዘላለሙ ይጠፋሉ፤
8እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ግን
ለዘላለም ልዑል ነህ::
9ጠላቶችህ እግዚአብሔር ሆይ፤
ጠላቶችህ ይጠፋሉና፤
ክፉ አድራጊዎችም ሁሉ ይበተናሉ::
10የእኔን ቀንድ ግን እንደ አውራሪስ
ቀንድ[ሀ] ከፍ ከፍ አደረግኸው፤
በለጋ ዘይትም አረሰረስኸኝ::
11ዐይኖቼ የባላንጦቼን ውድቀት አዩ፤
ጆሮዎቼም የክፉ ጠላቶቼን ድቀት ሰሙ::
12ጻድቃን እንደ ዘንባባ ይንሰራፋሉ፤
እንደ ሊባኖስ ዝግባም ይንዠረገጋሉ::
13በእግዚአብሔር ቤት ተተክለዋል፤
በአምላካችንም አደባባይ ይንሰራፋሉ::
14ባረጁ ጊዜ እንኳ ያፈራሉ፤
እንደ ለመለሙና እንደ ጠነከሩም
ይኖራሉ::
15“እግዚአብሔር ትክክለኛ ነው፤
እርሱ ዐለቴ ነው፤ በእርሱ ዘንድ እንከን
የለም” ይላሉ::

## መዝሙር 93

### የእግዚአብሔር ግርማ

1እግዚአብሔር ነገሠ፤ ግርማንም
ተጐናጸፈ፤
እግዚአብሔር ግርማን ለበሰ፤
ብርታትንም ታጠቀ፤
ዓለም እንዳትናወጥ ጸንታለች፤
ማንም አይነቀንቃትም::
2ዙፋንህ ከጥንት ጀምሮ የጸና ነው፤
አንተም ከዘላለም እስከ ዘላለም አለህ::
3እግዚአብሔር ሆይ፤ ወንዞች ከፍ
አደረጉ፤
ወንዞች ድምፃቸውን ከፍ አደረጉ፤
ወንዞች የሚያስገመግም ማዕበላቸውን
ከፍ አደረጉ::
4ከብዙ ውሆች ድምፅ ይልቅ፣
ከባሕርም ሞገድ ይልቅ፣
ከፍ ብሎ ያለው እግዚአብሔር ኀያል
ነው::
5ሥርዐትህ የጸና ነው፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ እስከ ዘላለሙ፣
ቤትህ በቅድስና ይዋባል::

## መዝሙር 94

### የእግዚአብሔር ፍትሕ

1የበቀል አምላክ፣ አንተ እግዚአብሔር ሆይ፤
የበቀል አምላክ ሆይ፤ ደምቀህ ተገለጥ::
2አንተ የምድር ዳኛ ሆይ፤ ተነሥ፤
ለትዕቢተኞች የእጃቸውን ስጣቸው::
3ክፉዎች እስከ መቼ እግዚአብሔር ሆይ፤
ክፉዎች እስከ መቼ ይፈነጫሉ?
4የእብሪት ቃላት ያዥጐደጕዳሉ፤
ክፉ አድራጊዎች ሁሉ ጕራ ይነዛሉ::
5እግዚአብሔር ሆይ፤ ሕዝብህን አደቀቁ፤
ርስትህንም አስጨነቁ::
6መበለቲቱንና መጻተኛውን ገደሉ፤
የድኻ አደጉንም ነፍስ አጠፉ::
7እነርሱም “እግዚአብሔር አያይም፤
የያዕቆብም አምላክ አያስተውልም”
አሉ::
8እናንት በሕዝቡ መካከል ያላችሁ
ደነዞች፤ ልብ በሉ፤
እናንት ቂሎች፤ ጥበበኞች የምትሆኑት
መቼ ነው?
9ጆሮን የተከለው እርሱ አይሰማምን?
ዐይንንስ የሠራ እርሱ አያይምን?
10ሕዝቦችን በተግሣጽ ወደ መንገድ
የሚመልስ፣
ዕውቀትንስ ለሰው ልጆች የሚያስተምር
አይቀጣምን?
11እግዚአብሔር የሰው ሐሳብ መና፣
ከንቱም እንደ ሆነ ያውቃል::
12እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ
የምትገሥጸው፣
ከሕግህም የምታስተምረው ሰው ምስጉን
ነው::

92÷1 መዝ9÷2፤ 27÷6፤135÷3፤147÷1
92÷2 መዝ55÷17
92÷3 1ሳሙ10÷5፤ ነህ12÷27፤መዝ33÷2፤ 71÷22፤81÷2
92÷4 መዝ5÷11፤ 8÷6፤27÷6፤111÷7፤ 143÷5
92÷5 ኢዮ36÷24፤ መዝ40÷5፤139÷17፤ኢሳ28÷29፤31÷2፤ ሮሜ 11÷33፤ራእ15÷3
92÷6 መዝ73÷22
92÷7 መዝ37÷2
92÷9 መዝ45÷5፤ 68÷1፤89÷10
92÷10 መዝ23÷5፤ 29÷6፤89÷17
92÷11 መዝ54÷7፤ 91÷8
92÷12 መዝ1÷3፤ 52÷8፤72÷7፤ኤር 17÷8፤ሆሴ14÷6
92÷13 መዝ135÷2
92÷14 መዝ1÷3፤ ዮሐ15÷2
92÷15 ኢዮ34÷10
93÷1 1ዜና16÷30: 31፤ኢዮ40÷10፤መዝ 21÷5፤24÷2፤65÷6፤78÷69፤96÷10፤97÷1፤119÷90
93÷2 ዘፍ21÷33፤ 2ሳሙ7÷16
93÷3 ኢዮ9÷8፤መዝ 46÷3፤96÷11፤98÷7፤107÷25:29፤ኢሳ5÷30፤17÷12-13፤51÷15፤ ኤር6÷23፤31÷35፤ ዕን3÷10
93÷4 ነህ9÷32፤ኢዮ 9÷4፤መዝ18÷4፤65÷7፤ ኤር6÷23፤ዮና1÷15
93÷5 መዝ5÷7፤ 23÷6፤29÷2፤96÷9
94÷1 ዘፍ4÷24፤ዘዳ 33÷2፤መዝ80÷1፤ ሮሜ12÷19
94÷2 ዘፍ18÷25፤ ዘኍ10÷35፤መዝ 31÷23፤ዕብ12÷23፤ ያዕ5÷9
94÷3 መዝ13÷2
94÷4 መዝ52÷1፤ ኤር43÷2
94÷5 መዝ28÷9፤ 44÷2፤74÷8፤ኢሳ 3÷15፤ኤር8÷21
94÷6 ዘጸ10÷18፤ 24÷19፤ኢሳ1÷17
94÷7 ዘፍ24÷12፤ ኢዮ22÷14
94÷8 ዘዳ32÷6፤ መዝ73÷22
94÷9 ዘፀ4÷11፤ ምሳ20÷12
94÷10 ዘፀ35÷34፤ ኢዮ35÷11፤መዝ 39÷11፤ኢሳ28÷26
94÷11 መዝ139÷2፤ምሳ15÷26፤ማቴ9÷4፤1ቆሮ3÷20
94÷12 ዘዳ8÷3፤1ሳሙ12÷23፤ ኢዮ5÷17፤1ቆሮ11÷32፤ዕብ12÷5

[ሀ]10 ጥንካሬን የሚያመለክት ነው::

13ለኀጢአተኞች ጒድጓድ እስኪማስላቸው
ድረስ፣
እርሱን ከመከራ ታሳርፈዋለህ።
14እግዚአብሔር ሕዝቡን አይጥልምና፤
ርስቱንም አይተውም።
15ፍርድ ተመልሶ በጽድቅ አሠራር ላይ
ይመሠረታል፤
ልባቸውም ቀና የሆነ ሁሉ
ይከተሉታል።
16ክፉዎችን የሚቋቋምልኝ ማን ነው?
ከክፉ አድራጊዎችስ ጋር የሚሟገትልኝ
ማን ነው?
17እግዚአብሔር ረዳቴ ባይሆን ኖሮ፣
ነፍሴ ወደ ዝምታው ዓለም ፈጥና
በወረደች ነበር።
18እኔ፣ "እግሬ አዳለጠኝ" ባልሁ ጊዜ፣
እግዚአብሔር ሆይ፤ ምሕረትህ ደግፎ
ያዘኝ።
19የውስጤ ጭንቀት በበዛ መጠን፣
ማጽናናትህ ነፍሴን ደስ አሰኛት።
20ዐመፃን ሕጋዊ የሚያደርግ፣
የጥፋት ዙፋን ከአንተ ጋር ሊያብር
ይችላልን?
21በጻድቁ ላይ ተሰልፈው ይወጣሉ፤
በንጹሑም ላይ ሞት ይፈርዳሉ።
22ለእኔ ግን እግዚአብሔር ምሽግ፣
አምላኬም መጠጊያ ዐለት ሆኖኛል።
23በደላቸውን ወደ ራሳቸው ይመልሳል፤
በክፋታቸውም ያጠፋቸዋል፤
እግዚአብሔር አምላካችን ይደመስሳቸዋጠ
ል።

## መዝሙር 95

### የየዕለቱ መዝሙር

1ኑ፤ ደስ እያለን ለእግዚአብሔር
እንዘምር፤
በድነታችንም ዐለት እልል እንበል።
2ምስጋና ይዘን ፊቱ እንቅረብ፤
በዝማሬም እናወድሰው።
3እግዚአብሔር ታላቅ አምላክ ነውና፤
ከአማልክትም ሁሉ በላይ ታላቅ
ንጉሥ ነው።
4የምድር ጥልቆች በእጁ ናቸው፤
የተራራ ጫፎችም የእርሱ ናቸው።
5እርሱ ፈጥሮአታልና፣ ባሕር የእርሱ
ናት፤
እጁም የብስን አበጀ።
6ኑ፤ እናምልከው፤ እንስገድለትም፤
በፈጣሪያችን በእግዚአብሔር ፊት
እንንበርከክ፤
7እርሱ አምላካችን ነውና፤
እኛም በእጁ ጥበቃ ሥር ያለን በጎቹ፣
የመሰማሪያውም ሕዝብ ነን።

94፥13 መዝ7፥15፤55፥23፤86፥7
94፥14 ዘዳ31፥6፤መዝ37፥28፤ሮሜ11፥2
94፥15 መዝ7፥10፤11፥2፤36፥10፤97፥2
94፥16 ዘኍ10፥35፤መዝ17፥13፤59፥2፤ኢሳ14፥22
94፥17 መዝ31፥17፤124፥2
94፥18 ዘዳ32፥35፤ኢዮ12፥5
94፥19 ኢዮ6፥10፤መክ11፥10
94፥20 መዝ58፥2፤ኤር22፥30፤36፥30
94፥21 ዘፍ18፥23፤መዝ56፥6፤106፥38፤ምሳ17፥15፡26፤28፥21፤ኢሳ5፥20፡23፤ማቴ27፥4
94፥22 2ሳሙ22፥3፤መዝ18፥2፤61፥2
94፥23 ዘፀ32፥34፤መዝ9፥5፤37፥35፤54፥5፤145፥20
95፥1 2ሳሙ22፥47፤መዝ5፥11፤34፥11፤80፥2፤81፥1፤ኢሳ44፥23፤ሶፎ3፥14
95፥2 መዝ42፥4፤81፥2፤100፥2፤ሚክ6፥6፤ኤፌ5፥19
95፥3 መዝ47፥2፤48፥1፤86፥10፤96፥4፤97፥9፤145፥3፤147፥5
95፥4 መዝ63፥9
95፥5 ዘፍ1፥9፤መዝ146፥6
95፥6 2ሳሙ12፥16፤2ዜና6፥13፤መዝ22፥29፤100፥3፤149፥2፤ኢሳ17፥7፤54፥5፤ዳን6፥10-11፤ሆሴ8፥14፤ፊል2፥10
95፥7 መዝ74፥1
95፥8 ዘፀ17፥7፤ዘዳ33፥8፤መዝ78፥40፤ማር10፥5፤ዕብ3፥8፡15፤4፥7
95፥9 ዘኍ14፥22፤1ቆሮ10፥9
95፥10 ዘፀ16፥35፤ዘኍ14፥34፤ዘዳ8፥6፤መዝ58፥3፤119፥67፡176፤ምሳ12፥26፤16፥29፤ኢሳ53፥6፤ኤር31፥19፤50፥6፤ሕዝ34፥6፤ ሐሥ7፥36፤ዕብ3፥17
95፥11 ዘኍ14፥23፤ዘዳ1፥35፤ዕብ3፥7-11፤4፥3
96፥1 መዝ30፥4፤33፥3፤40፥3፤98፥1፤144፥9፤149፥1፤ኢሳ42፥10፤ራእ5፥9
96፥2 መዝ27፥1፤68፥4፤71፥15
96፥3 መዝ8፥1፤71፥17፤ራእ15፥3

ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ፣
8በምድረ በዳ በነበራችሁበት ቀን
በማሳህ፣[ሀ]
በመሪባም[ሐ] እንዳደረጋችሁት፣
ልባችሁን አታደንድኑ።
9ሥራዬን ቢያዩም፣
አባቶቻችሁ በዚያ ፈተኑኝ፤
ተፈታተኑኝም።
10የን ትውልድ አርባ ዓመት ሙሉ
ተቈጣሁት፤
እኔም፣ "ልቡ የሸፈተ ሕዝብ ነው፤
መንገዴንም አላወቀም" አልሁ።
11ስለዚህ፣ "ፈጽሞ ወደ ዕረፍቴ
አይገቡም" ብዬ፣
በቍጣዬ ማልሁ።

## መዝሙር 96

### እግዚአብሔር፤ ንጉሥም ዳኛም

96፥1-13 ተጓ ምብ-1ዜና16፥23-33

1ለእግዚአብሔር አዲስ ዝማሬ ዘምሩ፤
ምድር ሁሉ፤ ለእግዚአብሔር ዘምሩ።
2ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤ ስሙንም ባርኩ፤
ማዳኑንም ነጋ ጠባ አውሩ።
3ክብሩን በሕዝቦች መካከል፣
ድንቅ ሥራውንም በሰዎች ሁሉ ፊት
ተናገሩ።
4እግዚአብሔር ታላቅ ነውና፤ ውዳሴም
የሚገባው ነው፤
ከአማልክትም ሁሉ በላይ ሊፈራ
ይገባዋል።
5የሕዝብ አማልክት ሁሉ ጣዖታት ናቸው፤
እግዚአብሔር ግን ሰማያትን ሠራ።
6ክብርና ግርማ በፊቱ ናቸው፤
ብርታትና ውበትም በመቅደሱ ውስጥ
አሉ።
7የሕዝቦች ወገኖች ሆይ፤ ለእግዚአብሔር
ስጡ፤
ክብርንና ብርታትን ለእግዚአብሔር
ስጡ።
8ለስሙ የሚገባ ክብርን ለእግዚአብሔር
ስጡ፤
ቍርባንን ይዛችሁ ወደ አደባባዩ ግቡ።
9በተቀደሰ ውበት ለእግዚአብሔር ስገዱ፤
ምድር ሁሉ፤ በፊቱ ተንቀጥቀጡ።
10በሕዝቦች መካከል፣ "እግዚአብሔር
ነገሠ፤" በሉ

96፥4 ዘዳ28፥58፤1ዜና16፥25፤መዝ48፥1፤89፥7፤95፥3 96፥5 ዘፍ1፥1፤ ዘሌ19፥4፤2ዜና2፥12 96፥6 መዝ21፥5፤29፥1፤89፥17 96፥7 መዝ22፥27፤29፥1 96፥8 መዝ45፥12፤51፥19፤65፥4፤72፥10፤84፥10፤92፥13፤100፥4 96፥9 ዘፀ15፥14፤23፥25፤መዝ33፥8፤93፥5፤114፥7፤ዮና1፥9 96፥10 መዝ24፥2፤58፥11፤67፥4፤78፥69፤93፥1፤97፥1፤98፥9፤119፥90

[ሀ]8 ማሳህ ፈተና ማለት ነው።
[ሐ]8 መሪባ ጠብ ማለት ነው።

ዓለም በጽኑ ተመሥርታለች፤
አትናወጥም፤
እርሱ ለሕዝቦች በእኩልነት ይፈርዳል።
11 ሰማያት ደስ ይበላቸው፤ ምድርም
ሐሤት ታድርግ፤
ባሕርና በውስጧ ያለው ሁሉ ያስተጋባ፤
12 መስኩና በላዩ ያለው ሁሉ ይፈንጥዝ፤
ያን ጊዜ የዱር ዛፎች ሁሉ በደስታ
ይዘምራሉ፤
13 እርሱ ይመጣልና *በእግዚአብሔር* ፊት
ይዘምራሉ፤
በምድር ላይ ሊፈርድ ይመጣል፤
በዓለም ላይ በጽድቅ፣
በሕዝቦችም ላይ በእውነት ይበይናል።

## መዝሙር 97
## የእግዚአብሔር ድል አድራጊነት

1 *እግዚአብሔር ነገሠ*፤ ምድር ደስ ይበላት፤
በሩቅ ያሉ የባሕር ጠረፎች ሐሤት
ያድርጉ።
2 ደመናና ጥቅጥቅ ያለ ጭጋግ በዙሪያው
አለ፤
ጽድቅና ፍትሕ የዙፋኑ መሠረት
ናቸው።
3 እሳት በፊቱ ይሄዳል፤
በዙሪያው ያሉትንም ጠላቶቹን
ይፈጃል።
4 መብረቁ ዓለምን አበራ፤
ምድርም አይታ ተንቀጠቀጠች።
5 ተራሮች *በእግዚአብሔር* ፊት፣
በምድርም ሁሉ ጌታ ፊት እንደ ሰም
ቀለጡ።
6 ሰማያት ጽድቁን ያውጃሉ፤
ሕዝቦችም ሁሉ ክብሩን ያያሉ።
7 ለተቀረጸ ምስል የሚሰግዱ፣
በጣዖታትም የሚመኩ ሁሉ ይፈሩ፤
እናንተ አማልክት ሁሉ፤ ለእርሱ ስገዱ።
8 *እግዚአብሔር ሆይ*፤ ስለ ፍርድህ፣
ጽዮን ሰምታ ደስ አላት፤
የይሁዳም ሴት ልጆች ሐሤት አደረጉ።
9 *እግዚአብሔር ሆይ*፤ አንተ በምድር
ሁሉ ላይ ልዑል ነህና፤
ከአማልክትም ሁሉ በላይ እጅግ ከፍ
ያልህ ነህ።
10 *እግዚአብሔርን* የምትወዱ ክፉትን
ጥሉ፤
እርሱ የታማኞቹን ነፍስ ይጠብቃልና፤
ከዐመፀኞችም እጅ ይታደጋቸዋል።
11 ብርሃን ለጻድቃን፣
ሐሤትም ልባቸው ለቀና ወጣ።
12 እናንተ ጻድቃን *በእግዚአብሔር* ደስ
ይበላችሁ፤
ቅዱስ ስሙንም አመስግኑ።

## መዝሙር 98
## የዓለም ሁሉ ዳኛ

መዝሙር

1 *ለእግዚአብሔር* አዲስ ዝማሬ አቅርቡ፤
እርሱ ድንቅ ነገሮችን አድርጓልና፤
ቀኝ እጁ፣ ቅዱስ ክንዱም፣
ማዳንን አድርገውለታል።
2 *እግዚአብሔር* ማዳኑን አሳወቀ፤
ጽድቁንም በሕዝቦች ፊት ገለጠ።
3 ለእስራኤል ቤት ምሕረቱን፣
ታማኝነቱንም አሰበ፤
የምድር ዳርቻዎችም ሁሉ፣
የአምላካችንን ማዳን አዩ።
4 ምድር ሁሉ *ለእግዚአብሔር* እልል በሉ፤
ውዳሴን አፍልቁ፤ በደስታና በዝማሬ
አመስግኑ፤
5 *ለእግዚአብሔር* በገና ደርድሩለት፤
በበገናና በዝማሬ ድምፅ ዘምሩለት፤
6 በእንቢልታና በመለከት ድምፅ፣
በንጉሡ *በእግዚአብሔር* ፊት እልል
በሉ።
7 ባሕርና በውስጧ ያለው ሁሉ፣
ዓለምና የሚኖሩባትም ሁሉ ያስገምግሙ።
8 ወንዞች በእጃቸው ያጨብጭቡ፤
ተራሮችም በአንድነት ይዘምሩ፤
9 እነዚህ *በእግዚአብሔር* ፊት ይዘምሩ፤
እርሱ በምድር ላይ ሊፈርድ
ይመጣልና፤
በዓለም ላይ በጽድቅ፣
በሕዝቦችም ላይ በእውነት ይበይናል።

## መዝሙር 99
## ጻድቅና ቅዱስ አምላክ

1 *እግዚአብሔር ነገሠ*፤
ሕዝቦች ይንቀጥቀጡ፤
በኪሩቤል ላይ በዙፋን ተቀምጦአል፤
ምድር ትናወጥ።
2 *እግዚአብሔር* በጽዮን ታላቅ ነው፤
ከሕዝቦችም ሁሉ በላይ ከፍ ከፍ
ብሎአል።
3 ታላቁንና አስፈሪውን ስምህን ይወድሱ፤
እርሱ ቅዱስ ነው።
4 ፍትሕን የምትወድ፣ ኀያል ንጉሥ ሆይ፤
አንተ ትክክለኛነትን መሠረትህ፤
ፍትሕንና ቅንነትንም፣
ለያዕቆብ አደረግህ።

**96፥11** መዝ97፥1፤ ኢሳ49፥13፤ራእ12፥12 **96፥12** መዝ65፥13፤ኢሳ44፥23፤55፥12፤ሕዝ17፥24 **96፥13** መዝ7፥11፤86፥11፤ሐሥ17፥31፤ራእ19፥11 **97፥1** ዘፀ15፥18፤ አስ10፥1፤መዝ93፥1፤96፥10፡11፤99፥1፤ኢሳ24፥23፤52፥7 **97፥2** ዘፀ19፥9፤ኢዮ22፥14፤መዝ89፥14 **97፥3** 2ሳሙ22፥9፤ ኢሳ9፥19፤ዳን7፥10፤ ኢል1፥19፤2፡3፤ዕን3፥5 **97፥4** 2ሳሙ22፥8፤ ኢዮ36፥30፤መዝ18፥7፤104፥32፤ራእ6፥12 **97፥5** ኢሱ3፥11፤ መዝ22፥14፤46፥2፡6 **97፥6** መዝ19፥1፤ 50፥6፤98፥2 **97፥7** ዘፀ12፥12፤ዘሌ26፥1፤ዘዳ5፥8፤መዝ16፥4፤ኢሳ42፥17፤ ኤር10፥14፤ዕብ1፥6 **97፥8** መዝ9፥2፤ 48፥11 **97፥9** ኢዮ34፥29፤ መዝ7፥8፤47፥9 **97፥10** ኢዮ28፥28፤ መዝ31፥23፤34፥7፤37፥28፡40፤145፥20፤ምሳ2፥8፤ኤር15፥21፤20፥13፤ዳን3፥28፤6፥16፤ አሞ5፥15፤ሮሜ12፥9 **97፥11** ኢዮ22፥28፤ መዝ7፥10፤11፥5 **97፥12** ኢዮ22፥19፤ ዘፀ3፥15፤መዝ99፥3፤ 104፥34፤ኢሳ41፥16፤ ፊል4፥4 **98፥1** ዘፀ15፥1፡6፤ ኢሱ4፥24፤ኢዮ40፥9፤ መዝ30፥4፤44፥3፤96፥1፡3፤ኢሳ12፥5፤51፥9፤52፥10፤53፥1፤59፥16፤63፥5፤ሉቃ1፥51 **98፥2** መዝ67፥2፤ 97፥6፤ኢሳ52፥10፤ ሉቃ3፥6 **98፥3** ዘፍ49፥10፤ 1ዜና16፥15፤መዝ48፥10፤50፥23 **98፥4** መዝ20፥5፤ ኢሳ12፥6፤44፥23፤ 52፥9፤54፥1፤55፥12 **98፥5** መዝ33፥2፤ 92፥3፤147፥7፤ኢሳ51፥3 **98፥6** ዘፀ19፥13፤ዘኍ10፥2፤2ሳሙ6፥15፤ መዝ2፥6፤20፥5፤47፥7፤100፥1፤ኢሳ12፥6 **98፥7** መዝ24፥1፤ 93፥3 **98፥8** 2ነገ11፥12፤ መዝ148፥9፤ኢሳ44፥23፤55፥12

**98፥9** መዝ96፥10 **99፥1** ዘፀ15፥14፤25፥22፤2ሳሙ6፥2፤1ዜና16፥30፡31፤መዝ97፥1 **99፥2** ዘፀ15፥1፤መዝ2፥6፤46፥10፤48፥1፤97፥9፤113፥4፤148፥13 **99፥3** ዘፀ15፥11፤ዘሌ11፥44፤መዝ30፥4፤33፥21፤76፥1፤97፥12፤103፥1፤106፥47፤111፥10፤145፥21፤148፥5፤ራእ4፥8 **99፥4** ዘፍ18፥19፤1ነገ10፥9፤መዝ2፥6፤98፥9፤ራእ15፥3

5አምላካችንን *እግዚአብሔርን* ከፍ ከፍ
አድርጉት፤
በእግሩ መርገጫ ስገዱ፤
እርሱ ቅዱስ ነውና ።
6ሙሴና አሮን ካህናቱ ከሆኑት መካከል
ነበሩ፤
ሳሙኤልም ስሙን ከጠሩት መካከል
አንዱ ነበረ፤
እነርሱ ወደ *እግዚአብሔር* ተጣሩ፤
እርሱም መለሰላቸው።
7ከደመና ዐምድ ውስጥ ተናገራቸው፤
እነርሱም ሥርዐቱንና የሰጣቸውን
ድንጋጌ ጠበቁ።
8*እግዚአብሔር* አምላካችን ሆይ፤
አንተ መለስህላቸው፤
ጥፋታቸውንም[ሞ] ብትበቀልም እንኳ፣
አንተ ይቅር የምትላቸው አምላክ ነህ።
9አምላካችንን *እግዚአብሔርን* ከፍ ከፍ
አድርጉት፤
በቅዱስ ተራራውም ላይ ስገዱ፤
አምላካችን *እግዚአብሔር* ቅዱስ ነውና።

## መዝሙር 100
## እግዚአብሔርን ለማመስገን የቀረበ ግብዣ

*የምስጋና መዝሙር*

1ምድር ሁሉ ለ*እግዚአብሔር* እልል በሉ፤
2*እግዚአብሔርን* በደስታ አገልግሉት፤
በፍስሓ ዝማሬ ፊቱ ቅረቡ።
3*እግዚአብሔር* አምላክ መሆኑን ዕወቁ፤
እርሱ ፈጠረን፤ እኛም የእርሱ ነን፤
እኛ ሕዝቡ የማሰማሪያው በጎች ነን።
4በምስጋና ወደ ደጆቹ፣
በውዳሴም ወደ አደባባዮቹ ግቡ፤
አመስግኑት፤ ስሙንም ባርኩ፤
5*እግዚአብሔር* ቸር፣ ምሕረቱም ለዘላለም
ነውና፤
ታማኝነቱም ከትውልድ እስከ ትውልድ
ነው።

## መዝሙር 101
## ትክክለኛ አስተዳደር

*የዳዊት መዝሙር*

1ስለ ምሕረትና ስለ ፍትሕ እዘምራለሁ፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ለአንተ በምስጋና
እቀኛለሁ።
2እንከን የማይገኝባትን መንገድ አጥብቄ
እይዛለሁ፤
አንተ ወደ እኔ የምትመጣው መቼ ነው?
በቤቴ ውስጥ፣
በንጹሕ ልብ እመላለሳለሁ።
3በዐይኔ ፊት፣
ክፉ ነገር አላኖርም።
የከሓዲዎችን ሥራ እጠላለሁ፤
ከእኔም ጋር አይጣበቅም።
4ጠማማ ልብ ከእኔ ይርቃል፤
ለክፋትም ዕውቅና አልሰጥም።
5ባልንጀራውን በስውር የሚያማውን፣
አጠፋዋለሁ፤
ትዕቢተኛ ዐይንና ኵራተኛ ልብ ያለውን፣
እርሱን አልታገሠውም።
6ከእኔ ጋር ይኖሩ ዘንድ፣
ዐይኖቼ በምድሪቱ ታማኞች ላይ ናቸው፤
በንጽሕና መንገድ የሚሄድ፣
እርሱ ያገለግለኛል።
7አታላይ የሆነ ማንም ሰው፣
በቤቴ ውስጥ አይኖርም፤
ሐሰትን የሚናገር፣
በፊቴ ቀና ብሎ አይቆምም።
8በምድሪቱ ላይ ያሉትን ክፉዎች ሁሉ፣
በየማለዳው አጠፋቸዋለሁ፤
ክፉ አድራጊዎችንም ሁሉ፣
*ከእግዚአብሔር* ከተማ
እደመስሳቸዋለሁ።

## መዝሙር 102
## በክፉ ጊዜ የቀረበ ጸሎት

*ባዘነና ልመናውን በእግዚአብሔር ፊት ባፈሰሰ ጊዜ፣
የተጨነቀ ሰው ጸሎት*

1*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ጸሎቴን ስማ፤
ጩኸቴም ወደ አንተ ይድረስ።
2በመከራዬ ቀን፣
ፊትህን ከእኔ አትሰውር፤
ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል፤
በጠራሁህ ቀን ፈጥነህ መልስልኝ።
3ዘመኔ እንደ ጢስ ተኖ አልቆአልና፤
ዐጥንቶቼም እንደ ማንደጃ ግለዋል።
4ልቤ ዋግ እንደ መታው ሣር ደርቆአል፤
እህል መብላትም ዘንግቻለሁ።
5ከጩኸቴ ድምፅ የተነሣ፣
ዐጥንቴ ከቈዳዬ ጋር ተጣበቀ።
6የምድረ በዳ እርኩም መሰልሁ፤
በፍርስራሽ መካከል እንዳለ ጒጒት
ሆንሁ።
7ያለ እንቅልፍ አድራለሁ፤
በቤቴ ጒልላት ላይ እንዳለ ብቸኛ ወፍ
ሆንሁ።
8ጠላቶቼ ቀኑን ሙሉ ይዘልፉኛል፤
የሚያክፋፉኝም ስሜን እንደ ርግማን
ቈጥረውታል።
9ዐመድ እንደ እህል ቅሜአለሁና፤
መጠጤንም ከእንባ ጋር ቀላቅያለሁ።

[ሞ]8 ወይም *የተፈጸመባቸውን በደል* ማለት ነው።

99፥5 ዘፀ15፥2 99፥6 ዘፀ24፥6፤28፥1፤ 1ሳሙ7፥5፤መዝ4፥3፤9 1፥15
99፥7 ዘፀ13፥21፤ 19፥9፤ዘኍ11፥25
99፥8 ዘፀ22፥27፤ዘሌ 26፥18፤ዘኍ14፥20
100፥1 መዝ98፥6
100፥2 ዘዳ10፥12፤ መዝ95፥2
100፥3 2ሳሙ24፥17 ፤1ነገ18፥2፤ኢዮ10፥3 ፤መዝ46፥10፤74፥1፤7 9፥13፤ኢሳ19፥25፤ 63፥8፤17-19፤64፥9
100፥4 መዝ42፥4፤ 96፥8፤116፥17
100፥5 1ዜና16፥34 ፤ዕዝ3፥11፤መዝ 106፥1፤108፥4፤ 119፥90
101፥1 መዝ33፥1፤ 51፥14፤89፥1፤145፥7
101፥2 ዘፍ17፥1፤ 1ነገ3፥14፤ፊል1፥10
101፥3 መዝ5፥5፤ ኤር16፥18፤ሕዝ 11፥21፤ሆሴ9፥10
101፥4 ምሳ3፥32፤ 6፥16-19፤11፥20
101፥5 ዘፀ20፥16፤ ዘሌ19፥16፤መዝ10፥5
101፥6 ቈ2፤መዝ 119፥1
101፥8 2ሳሙ3፥39 ፤መዝ5፥3፤46፥4፤ 75፥10፤118፥10-12፤ ኤር21፥12
102፥1 ዘፀ2፥23፤ መዝ4፥1
102፥2 2ነገ19፥16፤ መዝ22፥24፤31፥2፤ 88፥2
102፥3 መዝ37፥20 ፤ሰቆ1፥13፤ያዕ4፥14
102፥4 1ሳሙ1፥7፤ ዕዝ10፥6፤ኢዮ33፥20 ፤መዝ37፥2፤90፥5-6
102፥5 መዝ6፥6
102፥6 ዘዳ14፥15-17፤ኢዮ30፥29፤ኢሳ 34፥11፤ሶፎ2፥14
102፥7 መዝ38፥11 ፤77፥4
102፥8 ዘፀ22፥28፤ መዝ31፥11፤42፥10፤ኢሳ65፥15፤ኤር24፥9 ፤25፥18፤42፥18፤ 44፥12፤ሕዝ14፥8፤ዘካ 8፥13፤ሉቃ22፥63-65 ፤23፥35-37
102፥9 መዝ6፥6፤ 42፥3፤80፥5፤ኢሳ 44፥20

10ከቍጣህና ከመዓትህ የተነሣ፣
ወደ ላይ አንሥተኸኝ የነበርሁትን
መልሰህ ጣልኸኝ።
11ዘመኖቼ እንደ ምሽት ጥላ ናቸው፤
እኔም እንደ ሣር ደርቄአለሁ።

12*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ ግን ለዘላለም
በዙፋንህ ተቀምጠሃል፤
ስምህም ከትውልድ እስከ ትውልድ
ይኖራል።
13ትነሣለህ፤ ጽዮንንም በርኅራኄ ዐይን
ታያለህ፤
ለእርሷ በጎነትህን የምታሳይበት ዘመን
ነውና፤
የተወሰነውም ጊዜ ደርሶአል።
14አገልጋዮችህ በድንጋዮቿ ደስ ይሰኛሉ፤
ለዐፈሯም ይሳሳሉ።
15ሕዝቦች *የእግዚአብሔርን* ስም፣
የምድርም ነገሥታት ሁሉ ክብርህን
ይፈራሉ።
16*እግዚአብሔር* ጽዮንን መልሶ ይሠራታልና፤
በክብሩም ይገለጣል።
17እርሱ ወደ ችግረኞች ጸሎት
ይመለከታል፤
ልመናቸውንም አይንቅም።

18ወደ ፊት የሚፈጠር ሕዝብ *እግዚ
አብሔርን* ያወድስ ዘንድ፣
ይህ ለመጪው ትውልድ እንዲህ
ተብሎ ይጻፍ፤
19"*እግዚአብሔር* በከፍታ ላይ ካለው
መቅደሱ ወደ ታች
ተመልክቶአልና፤
ከሰማይም ሆኖ ምድርን አይቶአል፤
20ይኸውም የእስረኞችን ጩኸት ይሰማ
ዘንድ፣
ሞት የተፈረደባቸውንም ያድን ዘንድ
ነው።"
21ስለዚህ *የእግዚአብሔር* ስም በጽዮን፣
ምስጋናውም በኢየሩሳሌም ይታወጃል፤
22ይህም፣ ሕዝቦችና መንግሥታት፣
*እግዚአብሔርን* ለማምለክ በአንድነት
ሲሰበሰቡ ይሆናል።

23ብርታቴን መንገድ ላይ ቀጨው፤[w]
ዕድሜዬንም ባጭሩ አስቀረው።
24እኔም እንዲህ አልሁ፤
"አምላኬ ሆይ፤ በዘመኔ እኩሌታ
አትውሰደኝ፤
ዘመናትህ ከትውልድ እስከ ትውልድ
ይኖራሉ።
25አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፤
ሰማያትም የእጆችህ ሥራ ናቸው።
26እነርሱ ይጠፋሉ፤ አንተ ግን ጸንተህ
ትኖራለህ፤
ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ፤
እንደ መጐናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፤
እነርሱም ወዲያ ይጣላሉ።
27አንተ ግን ያው አንተ ነህ፤
ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም።
28የአገልጋዮችህ ልጆች ተደላድለው
ይኖራሉ፤
ዘራቸውም በፊትህ ጸንቶ ይኖራል።

## መዝሙር 103

### እግዚአብሔር ፍቅር ነው

የዳዊት መዝሙር

1ነፍሴ ሆይ፤ *እግዚአብሔርን* ባርኪ
የውስጥ ሰውነቴም ሁሉ ቅዱስ ስሙን
ባርኪ።
2ነፍሴ ሆይ፤ እግዚአብሔርን ባርኪ፤
ውለታውንም ሁሉ አትርሺ፤
3ኀጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል፣
ደዌሽንም ሁሉ የሚፈውስ፣
4ሕይወትሽን ከጥፋት ጕድጓድ የሚያድን፣
ምሕረትንና ርኅራኄን የሚያቀዳጅሽ፣
5ጕልማሳነትሽም እንደ ንስር ይታደስ
ዘንድ፣
ምኞትሽን በበጎ ነገር የሚያረካ እርሱ
ነው።

6*እግዚአብሔር* ለተጨቈኑ ሁሉ፣
ቅን ፍርድንና ፍትሕን ይሰጣቸዋል።

7*መንገዱን* ለሙሴ፣
*ሥራውንም* ለእስራኤል ሕዝብ
አሳወቀ።
8*እግዚአብሔር* መሓሪና ይቅር ባይ፣
ለቍጣ የዘገየ፣ ፍቅሩም የበዛ ነው።
9እርሱ ሁልጊዜ በደልን አይከታተልም፤
ለዘላለምም አይቈጣም።
10እንደ ኀጢአታችን አልመለሰልንም፤
እንደ በደላችንም አልከፈለንም።
11ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፣
እንዲሁ ለሚፈሩት ምሕረቱ ታላቅ ናት።
12ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ፣
መተላለፋችንን በዚያው መጠን ከእኛ
አስወገደ።
13አባት ለልጆቹ እንደሚራራ፣
*እግዚአብሔር* ለሚፈሩት እንዲሁ ይራራል።
14እርሱ አፈጣጠራችንን ያውቃልና፤
ትቢያ መሆናችንንም ያስባል።

102፥10 መዝ7፥11፤38፥3
102፥11 1ዜና29፥15፤ኢዮ8፥12፤14፥2፤መዝ39፥6፤ያዕ1፥10
102፥12 ዘፀ3፥15፤15፥18፤መዝ135፥13፤ኢሳ55፥13፤63፥12
102፥13 ዘፀ13፥10፤ዘዳ32፥36፤1ነገ3፥26፤መዝ44፥26፤77፥7፤119፥126፤ኢሳ54፥8፤60፥10፤ዳን8፥19፤ዘካ10፥6፤ሐሥ1፥7
102፥15 1ነገ8፥43፤መዝ67፥7፤76፥12፤138፥4፤148፥11፤ኢሳ2፥2
102፥16 መዝ8፥1፤51፥18፤ኢሳ60፥1-2
102፥17 1ነገ8፥29፤መዝ4፥1፤6፥9
102፥18 መዝ22፥31፤ሮሜ4፥24
102፥19 መዝ53፥2
102፥20 መዝ68፥6፤ሉቃ4፥19
102፥21 መዝ9፥14፤22፥22
102፥22 መዝ22፥27፤ኢሳ49፥22-23፤ዘካ8፥20-23
102፥23 መዝ39፥5
102፥24 ዘፍ21፥33፤ኢዮ36፥26፤መዝ90፥2
102፥25 ዘፍ1፥1፤2ዜና2፥12፤መዝ8፥3፤ዕብ1፥10-12
102፥26 ኢሳ13፥10፤13፤34፥4፤51፥6፤ሕዝ32፥8፤ኢል2፥10፤ማቴ24፥35፤2ጴጥ3፥7-10፤ራእ20፥11
102፥27 ዘኍ23፥19፤መዝ9፥7፤ዕብ13፥8፤ያዕ1፥17
102፥28 መዝ25፥13፤69፥36፤89፥4
103፥1 መዝ28፥6፤30፥4፤104፥1
103፥2 ዘዳ6፥12፤መዝ77፥11፤106፥1፤117፥1
103፥3 ዘፀ15፥26፤34፥7፤ቈላ3፥13፤1ጴጥ2፥24፤1ዮሐ1፥9
103፥4 መዝ8፥5፤23፥6፤34፥22፤56፥13፤ኢሳ43፥1
103፥5 ዘፀ19፥4፤ኢዮ33፥25፤መዝ90፥14፤104፥28፤119፥25፤93፤2ቆሮ4፥16
103፥6 መዝ9፥8፤65፥5፤74፥21፤ኢሳ9፥7፤ሉቃ4፥19
103፥7 ዘፀ33፥13፤መዝ99፥7፤106፥22፤147፥19
103፥8 ዘፀ22፥27፤መዝ86፥15፤ሚክ7፥18-19፤ያዕ5፥11
103፥9 መዝ30፥5፤79፥5፤ኢሳ57፥16፤ኤር3፥5፤12፤ሚክ7፥18
103፥10 ዕዝ9፥13፤ሮሜ6፥23
103፥11 2ዜና6፥31፤መዝ13፥5፤57፥10፤100፥5፤106፥45፤117፥2፤ሰቆ3፥22፤ኤፌ3፥18
103፥12 2ሳሙ12፥13፤ሮሜ4፥7፤ኤፌ2፥5
103፥13 ሚል3፥17፤1ዮሐ3፥1
103፥14 ዘፍ2፥7፤መዝ119፥73፤139፥13-15፤146፥4፤ኢሳ29፥16

[w]23 ወይም *በኀይሉ ብርታቴን ቀጨው*

15 ሰው እኮ ዘመኑ እንደ ሣር ነው፤
እንደ ዱር አበባ ያቈጠቍጣል፤
16 ነፋስ በነፈሰበት ጊዜ ግን ድራሹ ይጠፋል፤
ምልክቱም በቦታው አይገኝም።
17 *የእግዚአብሔር* ምሕረት ግን፣
ከዘላለም እስከ ዘላለም በሚፈሩት ላይ
ነው፤
ጽድቁም እስከ ልጅ ልጅ ድረስ
በላያቸው ይሆናል፤
18 ኪዳኑን በሚጠብቁት ላይ፣
ትእዛዙንም ለመፈጸም በሚተጉት ላይ
ይሆናል።
19 *እግዚአብሔር* ዙፋኑን በሰማይ አጽንቶአል፤
መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች።
20 እናንተ ለቃሉ የምትታዘዙ መላእክቱ፤
ትእዛዙንም የምትፈጽሙ እናንተ
ኀያላን፤
*እግዚአብሔርን* ባርኩ።
21 እናንተ ፈቃዱን የምትፈጽሙ አገልጋዮቹ፤
ሰራዊቱ ሁሉ፣ *እግዚአብሔርን* ባርኩ።
22 እናንተ በግዛቱ ሁሉ የምትኖሩ፣
ፍጥረቱ ሁሉ፣ *እግዚአብሔርን* ባርኩ፤
ነፍሴ ሆይ፤ *እግዚአብሔርን* ባርኪ።

## መዝሙር 104

### የፍጥረት መብት

1 ነፍሴ ሆይ፤ *እግዚአብሔርን* ባርኪ፤
*እግዚአብሔር* አምላኬ ሆይ፤ አንተ እጅግ
ታላቅ ነህ፤
ክብርንና ግርማን ለብሰሃል።
2 ብርሃንን እንደ ሸማ ተጐናጽፈሃል፤
ሰማያትንም እንደ ድንኳን መጋረጃ
ዘረጋህ፤
3 የእልፍኝህን አግዳሚ በውሆች ላይ
አኖርህ፤
ደመናትን ሠረገላህ አደረግህ፤
በነፋስ ክንፍ ትሄዳለህ።
4 መላእክትህን[ሪ] መንፈስ፣
አገልጋዮችህንም የእሳት ነበልባል
ታደርጋለህ።
5 ለዘላለም እንዳትናወጥ፣
ምድርን በመሠረቷ ላይ አጸናሃት።
6 በጥልቁ እንደ ልብስ ሸፈንሃት፤
ውሆችም ከተራሮች በላይ ቆሙ።
7 በገሥጽሃቸው ጊዜ ግን ፈጥነው ሄዱ፤
የነጐድጓድህንም ድምፅ በሰሙ
ጊዜ ሸሹ።
8 በተራሮች ላይ ፈሰሱ፤
ወዳዘጋጀህላቸው ስፍራ፣
ወደ ሸለቆዎች ወረዱ።
9 ተመልሰው ምድርን እንዳይሸፍኑ፣
አልፈውም እንዳይመጡ ድንበር
አበጀህላቸው።
10 ምንጮችን በሸለቆ ውስጥ እንዲሄዱ
አደረግህ፤
በተራሮችም መካከል ይፈሳሉ፤
11 የዱር እንስሳትም ከዚያ ይጠጣሉ፤
የሜዳ አህዮችም ጥማቸውን
ይቈርጣሉ።
12 የሰማይ ወፎች ጎጇቸውን በወንዞቹ ዳር
ይሠራሉ፤
በቅርንጫፎችም መካከል ይዘምራሉ።
13 ከላይ ከእልፍኝህ ተራሮችህን ታጠጣለህ፤
ምድርም በሥራህ ፍሬ ትረካለች።
14 ከምድር ምግብን ታወጣ ዘንድ፣
ለእንስሳት ሣርን፣
ለሰው ልጆች ሥራ ዕፀዋትን
ታበቅላለህ፤
15 የሰውን ልብ ደስ የሚያሰኝ ወይን፣
ፊቱን የሚያወዛ ዘይት፣
ልቡን የሚያበረታ እህል በዚህ
ይገኛል።
16 ደግሞም *የእግዚአብሔር* ዛፎች፣
እርሱ የተከላቸውም የሊባኖስ
ዝግባዎች ጠጥተው ይረካሉ፤
17 ወፎች ጎጆአቸውን በዚያ ይሠራሉ፤
ሽመላ በጥዶቹ ውስጥ ማደሪያ ታገኛለች።
18 ረጃጅሙ ተራራ የዋልያ መኖሪያ፣
የዐለቱም ዋሻዎች የሽኮኮ መሸሸጊያ
ናቸው።
19 ጨረቃን የወቅቶች መለያ አደረግሃት፤
ፀሓይም የምትጠልቅበትን ጊዜ
ታውቃለች።
20 ጨለማን ታመጣለህ፤ ሌሊትም ይሆናል፤
የዱር አራዊትም ሁሉ በዚህ ጊዜ
ወጥተው ይራወጣሉ።
21 የአንበሳ ግልገሎች ምግብ ፍለጋ
ይጮኻሉ፤
የሚበሉትንም ከእግዚአብሔር ይሻሉ።
22 ፀሓይ በወጣች ጊዜም ይመለሳሉ፤
በየጐሬአቸውም ገብተው ይተኛሉ።
23 ሰውም ወደ ሥራው ይሄዳል፤
እስኪመሽም በተግባሩ ላይ ይሰማራል።
24 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ሥራህ እንዴት
ብዙ ነው!
ሁሉን በጥበብ ሠራህ፤
ምድርም በፍጥረትህ ተሞላች።
25 ይህች ባሕር ሰፊና የተንጣለለች ናት፤

**103፥15** ኢዮ14፥2፤ መዝ37፥2፤90፥5፤ 102፥11፤ኢሳ40፥6፤ ያዕ1፥10
**103፥16** ኢዮ7፥8፤ ኢሳ40፥7፤ሐጌ1፥9
**103፥17** ዘፍ48፥11፤ ዕዝ9፥12
**103፥18** ዘኁ15፥40 ፤ዘዳ29፥9፤መዝ119፥52፤ ዮሐ14፥15
**103፥19** መዝ22፥28 ፤47፥8፤66፥7፤80፥1፤ 113፥5፤ዳን4፥17
**103፥20** ነህ9፥6፤ መዝ28፥6፤29፥1፤107፥ 25፤135፥7፤148፥8፤ሉ ቃ2፥13፤ዕብ1፥14
**103፥21** 1ነገ22፥19 ፤ነህ7፥73
**103፥22** ቍ1፤መዝ 19፥1፤67፥3፤104፥1፤1 45፥10፤150፥6
**104፥1** ኢዮ40፥10 ፤መዝ103፥22
**104፥2** ኢዮ9፥8፤ 37፥18፤መዝ18፥12፤ 19፥4፤ኢሳ40፥22፤ 42፥5፤44፥24፤49፥18፤ ኤር43፥12፤51፥15፤ ዘካ12፥1፤1ጢሞ6፥16
**104፥3** ዘዳ33፥26፤ 2ነገ2፥11፤መዝ18፥10 ፤24፥2፤ኢሳ19፥1፤አሞ 9፥6፤ናሆ1፥3
**104፥4** ዘፍ3፥24፤ 2ነገ2፥11፤መዝ148፥8 ፤ዕብ1፥7
**104፥5** ዘፀ31፥17፤ 1ሳሙ2፥8፤ኢዮ26፥7፤ መዝ24፥1-2፤102፥25 ፤121፥2
**104፥6** ዘፍ1፥2፤ 7፥19፤2ጴጥ3፥6
**104፥7** ዘፀ9፥23፤ መዝ18፥15፤29፥3
**104፥8** መዝ33፥7
**104፥9** ዘፍ1፥9፤ መዝ16፥6
**104፥10** መዝ107፥33 ፤ኢሳ41፥18
**104፥11** ቍ13፤ ዘፍ16፥12፤ኢሳ 32፥14፤ኤር14፥6
**104፥13** ቍ17፤ ማቴ8፥20፤13፥32
**104፥13** ዘሌ26፥4፤ መዝ135፥7፤147፥8፤ኤ ር10፥13፤አሞ9፥6፤ዘካ 10፥1
**104፥14** ዘፍ1፥30፤ ኢዮ28፥5፤38፥27፤ መዝ147፥8
**104፥15** ዘፍ14፥18 ፤ዘዳ8፥3፤መሳ9፥13፤ መዝ23፥5፤92፥10፤ ማቴ6፥11፤ሉቃ7፥46
**104፥16** ዘፍ1፥11፤ መዝ72፥16
**104፥17** ቍ12
**104፥18** ዘዳ14፥5፤ ምሳ30፥26 **104፥19** ዘፍ1፥14፤መዝ19፥6 **104፥20** መዝ50፥10 ፤74፥16፤ኢሳ45፥7፤አሞ5፥8 **104፥21** መዝ145፥15፤ኢል1፥20፤ አሞ3፥4፤ማቴ6፥26 **104፥22** ኢዮ37፥8 **104፥23** ዘፍ3፥19፤ መሳ19፥16 **104፥24** ዘፍ1፥31፤መዝ24፥1፤40፥5፤50፥10-11 **104፥25** መዝ69፥34፤ሕዝ47፥10

ሪ4 *መልእክተኞቹን ወይም አገልጋዮቹን*

ታላላቅና ታናናሽ እንስሳት፣
ስፍር ቍጥር የሌላቸውም ነፍሳት
በውስጧ አሉ።
26 መርከቦች በላይዋ ይመላለሳሉ፤
አንተ የፈጠርኸውም ሌዋታን በውስጧ
ይፈነጫል።
27 ምግባቸውን በወቅቱ ትሰጣቸው ዘንድ፣
እነዚህ ሁሉ አንተን ተስፋ ያደርጋሉ።
28 በሰጠሃቸውም ጊዜ፣
አንድ ላይ ያከማቻሉ፤
እጅህንም ስትዘረጋ፣
በመልካም ነገር ይጠግባሉ።
29 ፊትህን ስትሰውር፣
በድንጋጤ ይሞላሉ፤
እስትንፋሳቸውንም ስትወስድባቸው
ይሞታሉ፤
ወደ ዐፈራቸውም ይመለሳሉ።
30 መንፈስህን ስትልክ፣
እነርሱ ይፈጠራሉ፤
የምድርንም ገጽ ታድሳለህ።
31 *የእግዚአብሔር* ክብር ለዘላለም ጸንቶ
ይኑር፤
*እግዚአብሔር* በሥራው ደስ ይበለው፤
32 እርሱ ምድርን ሲመለከት፣ ትንቀጠቀጣለች፤
ተራሮችም እርሱ ሲዳስሳቸው ይጤሳሉ።
33 በሕይወት ሳለሁ *ለእግዚአብሔር*
እዘምራለሁ፤
ቆሜ እስከ ሄድሁ ድረስም አምላኬን
እወድሳለሁ።
34 እኔ *በእግዚአብሔር* ደስ እንደሚለኝ፣
የልቤ ሐሳብ እርሱን
ደስ ያሰኘው።
35 ኀጥአን ከምድር ገጽ ይጥፉ፤
ዐመፀኞች ከእንግዲህ አይገኙ።

ነፍሴ ሆይ፤ *እግዚአብሔርን* ባርኪ፤

ሃሌ ሉያ።[ሰ]

## መዝሙር 105

## የእስራኤል ድንቅ ታሪክ

105÷1-15 ተጓ ምብ-1ዜና 16÷8-22

1 *እግዚአብሔርን* አመስግኑ፤ ስሙንም ጥሩ፤
ሥራውንም በሕዝቦች መካከል ግለጡ።
2 ተቀኙለት፤ ዘምሩለት፤
ድንቅ ሥራዎቹንም ሁሉ ተናገሩ።
3 በቅዱስ ስሙ ተጓደዱ፤
*እግዚአብሔርን* የሚሹት ልባቸው ደስ
ይበለው።
4 *እግዚአብሔርንና* ብርታቱን ፈልጉ፤
ፊቱንም ዘወትር ፈልጉ።
5 የደረጋቸውን ድንቅ ሥራዎች፣
ታምራቱንና ከአፉ የወጣውን ፍርድ
አስቡ፤
6 እናንተ የአገልጋዩ የአብርሃም ዘሮች፣
ለራሱም የመረጣችሁ የያዕቆብ ልጆች
ሆይ፤ አስታውሱ።
7 እርሱ *እግዚአብሔር* አምላካችን ነው፤
ፍርዱም በምድር ሁሉ ላይ ነው።
8 ኪዳኑን ለዘላለም፣
ያዘዘውንም ቃል እስከ ሺህ ትውልድ
ያስታውሳል።
9 ከአብርሃም ጋር ያደረገውን ኪዳን፣
ለይስሐቅም በመሐላ የተሰጠውን ተስፋ
አይረሳም።
10 ይህንም ለያዕቆብ ሥርዐት አድርጎ፣
ለእስራኤልም የዘላለም ኪዳን አድርጎ
አጸናለት፤
11 እንዲህም አለ፤ "የርስትህ ድርሻ
አድርጌ፣
የከነዓንን ምድር እሰጥሃለሁ።"
12 በቍጥር አነስተኞች ሆነው ሳሉ፣
እጅግ ጥቂትና ባይተዋሮች ሳሉ፣
13 ከሕዝብ ወደ ሕዝብ ሲንከራተቱ፣
ከአንዱ መንግሥት ወደ ሌላው
ሲቅበዘበዙ፣
14 ማንም ግፍ እንዲፈጽምባቸው
አልፈቀደም፤
ስለ እነርሱም ነገሥታትን እንዲህ ሲል
ገሠጸ፤
15 "የቀባኋቸውን አትንኩ፤
በነቢያቴም ላይ ክፉ አታድርጉ።"
16 በምድሪቱ ላይ ራብን ጠራ፤
የምግብንም አቅርቦት ሁሉ አቋረጠ፤
17 በባርነት የተሸጠውን ሰው፣
ዮሴፍን ከእነርሱ አስቀድሞ ላከ።
18 እግሮቹ በእግር ብረት ተላላጡ፤
በዐንገቱም የብረት ማነቆ ገባ።
19 የተናገረው ቃል እስኪፈጸምለት፣
*የእግዚአብሔር* ቃል ፈተነው።
20 ንጉሥ ልኮ አስፈታው፤
የሕዝቦችም ገዥ ነጻ አወጣው።
21 የቤቱ ጌታ፣
የንብረቱም ሁሉ አስተዳዳሪ አደረገው፤
22 ይኸውም ሹማምቱን በራሱ መንገድ
ይመራ ዘንድ፣
ታላላቆቹንም ጥበብ ያስተምር ዘንድ
ነበር።
23 እስራኤል ወደ ግብፅ ገባ፤
ያዕቆብ በካም ምድር መጻተኛ ሆነ።
24 *እግዚአብሔር* ሕዝቡን እጅግ አበዛ፤
ከጠላቶቻቸውም ይልቅ አበረታቸው፤

**104÷26** ዘፍ1÷21፤ ኢዮ3÷8፤40÷20፤41÷1፤መዝ107÷23፤ሕዝ 27÷9፤ዮና1÷3
**104÷27** ኢዮ36÷31፤መዝ145÷15፤147÷9
**104÷28** መዝ103÷5፤145÷16፤ኢሳ58÷11
**104÷29** ዘዳ31÷17፤ኢዮ7÷21
**104÷30** ዘፍ1÷2
**104÷31** ዘፍ1÷4፤ዘፀ 40÷35፤መዝ8÷1፤ ሮሜ11÷36
**104÷32** ዘፀ19÷18፤ መዝ97÷4፤144÷5
**104÷33** ዘፀ15÷1፤ መዝ108÷1
**104÷34** መዝ2÷11፤ 9÷2፤32÷11
**104÷35** ኢዮ7÷10፤ መዝ28÷6፤37÷38፤10 5÷45፤106÷48
**105÷1** 1ዜና16÷34፤መዝ80÷18፤99÷6፤1 16÷13፤ኢል2÷32፤ ሐሥ2÷21
**105÷2** መዝ7÷17፤ 18÷49፤27÷6፤30÷4፤3 3÷3፤59÷17፤71÷22፤7 5÷1፤96÷1፤146÷2
**105÷3** መዝ89÷16
**105÷4** መዝ24÷6
**105÷5** ዘዳ7÷18፤ መዝ40÷5
**105÷6** ቍ42፤ዘዳ 10÷15፤መዝ106÷5
**105÷8** ዘፍ9÷15፤ መዝ106÷45፤111÷5፤ ሕዝ16÷60፤ሉቃ1÷72
**105÷9** ዘፍ12÷7፤ 15÷18፤22÷16-18፤ ሉቃ1÷73፤ገላ3÷15-18
**105÷10** ዘፍ28÷ 13-15፤ኢሳ55÷3
**105÷11** ዘፍ12÷7፤ ዘኍ34÷2
**105÷12** ዘፍ23÷4፤ ዘዳ7÷7፤ዕብ11÷19
**105÷13** ዘፍ15÷13- 16፤ዘኍ32÷13፤ 33÷3-49
**105÷14** ዘፍ12÷17- 20፤20÷3፤35÷5፤መዝ 9÷5
**105÷15** ዘፍ20÷7፤ 26÷11፤1ሳሙ12÷3
**105÷16** ዘፍ12÷10፤ዘሌ26÷26፤ኢሳ 3÷1፤ሕዝ4÷16
**105÷17** ዘፍ37÷28፤ሐሥ7÷9
**105÷18** ዘፍ40÷15
**105÷19** ዘፍ12÷10፤40÷20-22፤41÷40
**105÷20** ዘፍ41÷14
**105÷22** ዘፍ41÷40 ፡43-44
**105÷23** ዘፍ46÷6፤ 47÷28፤መዝ78÷51፤ ሐሥ7÷15፤13÷17
**105÷24** ዘፀ1÷7፡9፤ሐሥ7÷17

[ሰ]35 *እግዚአብሔር ይመስገን* የሚሉ ትርጒሞች አሉ፤ በሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ይህ መሥመር በመዝ105 መጀመሪያ ላይ ይገኛል።

25ሕዝቡን እንዲጠሉ፣
በባሪያዎቹም ላይ እንዲያሤሩ
ልባቸውን ለወጠ።
26ባሪያውን ሙሴን፣
የመረጠውንም አሮንን ላከ።
27እነርሱም ታምራታዊ ምልክቶችን
በመካከላቸው፣
ድንቅ ነገሮቹንም በካም ምድር
አደረጉ።
28ጨለማን ልኮ ምድሪቱን ጽልመት
አለበሰ፤
እነርሱም በቃሉ ላይ ማመፅን ተዉ።
29ውሃቸውን ወደ ደም ለወጠ፤
ዓሦቻቸውንም ፈጀ።
30ምድራቸውም፣ የነገሥታታቸው
እልፍኝ ሳይቀር፣
ጓጉንቸር ተርመሰመሰባቸው።
31እርሱ በተናገረ ጊዜ የዝንብ መንጋ
መጣ፤
ትንኞችም ምድራቸውን ወረሩ።
32ዝናባቸውን በረዶ አደረገው፤
ምድራቸውም ሁሉ መብረቅ አወረደ።
33ወይናቸውንና በለሳቸውን መታ፤
የአገራቸውንም ዛፍ ከተከተ።
34እርሱ በተናገረ ጊዜ አንበጣ መጣ፤
ስፍር ቍጥር የሌለውም ኵብኵባ
ከተፍ አለ፤
35የምድሪቱንም ዕፀዋት ሁሉ በላ፤
የመሬታቸውንም ፍሬ ሙጥጥ አደረገ፤
36ደግሞም በአገራቸው ያለውን በኵር
ሁሉ፣
የኀይላቸውንም ሁሉ በኵራት መታ።

37የእስራኤልንም ሕዝብ ብርና ወርቅ
ጭኖ እንዲወጣ አደረገ፤
ከነገዶቻቸውም አንድም አልተደናቀፈም።
38እጅግ ፈርተዋቸው ነበርና፣
ወጥተው ሲሄዱ ግብፅ ደስ አላት።
39ደመናን እንደ መጋረጃ ዘረጋላቸው፤
እሳትም በሌሊት አበራላቸው።
40በለመኑትም ጊዜ፣ ድርጭት አመጣላቸው፤
የሰማይንም እንጀራ አጠገባቸው።
41ዐለቱን ሰነጠቀ፤ ውሃም ተንዶለደለ፤
እንደ ወንዝም በበረሓ ፈሰሰ።

42ለባሪያው ለአብርሃም የሰጠውን፣
ቅዱስ የተስፋ ቃሉን አስቦአልና።
43ሕዝቡን በደስታ፣
ምርጦቹንም በእልልታ አወጣቸው።
44የሌሎችን ሕዝቦች ምድር ሰጣቸው፤
የእነዚህንም የድካም ፍሬ ወረሱ፤
45ይህም ሥርዐቱን ይጠብቁ ዘንድ፣
ሕጉንም ይፈጽሙ ዘንድ ነው።
ሃሌ ሉያ።[ሽ]

**105፥25** ዘፀ1፥6-10፤4፥21፤ሐሥ7፥19
**105፥26** ዘፀ3፥10፤4፥16፤ዘኍ16፥5፤17፥5-8፤33፥1
**105፥27** ቍ28-37፤ዘፀ3፥20፤4፥17፤7፥8-12፡51፤10፥1፤ዳን4፥3
**105፥28** ዘፍ1፥4፤ዘፀ7፥22፤10፥22
**105፥29** ዘፀ7፥21፤78፥44
**105፥30** ዘፀ8፥2፡6
**105፥31** ዘፀ8፥16-18፡21-24፤መዝ78፥45፤107፥25፤148፥8
**105፥32** ዘፀ9፥22-25፤ኢዮ38፥22፤መዝ78፥47
**105፥33** ዘፀ10፥5፡12፤መዝ78፥47
**105፥34** ዘፀ10፥4፡12-15፤1ነገ8፥37፤መዝ107፥25፤ኢል1፥6
**105፥36** ዘፀ4፥23፤12፥12
**105፥37** ዘፀ3፥21፡22
**105፥38** ዘፀ15፥16
**105፥39** ዘፀ13፥21፤መዝ78፥14፤1ቆሮ10፥1
**105፥40** ዘፀ16፥4፡13፤መዝ78፥18፤ዮሐ6፥31
**105፥41** ዘኍ20፥11፤1ቆሮ10፥4
**105፥42** ዘፍ12፥1-3፤13፥14-17፤15፥13-16
**105፥43** ዘፀ15፥1-18፤መዝ106፥12
**105፥44** ዘፀ32፥13፤ዘዳ6፥10-11፤ኢሱ11፥16-23፤12፥8፤13፥6-7፤መዝ78፥55፤111፥6
**105፥45** ዘዳ4፥40፤6፥21-24፤መዝ78፥5-7፤104፥35
**106፥1** ዕዝ3፥11፤መዝ22፥23፤ 103፥2፤119፥68፤136፥1-26፤ኤር33፥11
**106፥2** መዝ71፥16
**106፥3** መዝ15፥2፤112፥5፤ሆሴ12፥6
**106፥4** ዘፍ50፥24፤መዝ25፥6፡7፤77፥7
**106፥5** ዘፀ34፥9፤ዘዳ30፥15፤መዝ1፥3፤20፥5፤27፥6፤47፥5፤105፥6፤118፥15
**106፥6** 1ነገ8፥47፤2ዜና30፥7፤ነህ1፥7፤ሮሜ3፥9
**106፥7** ዘፀ14፥11-12፤መሳ3፥7፤መዝ78፥42
**106፥8** ዘፀ9፥16፤14፥30፡31፤መዝ23፥3

## መዝሙር 106

### ብሔራዊ ኑዛዜ

106፥1፡47-48 ተጓ ምብ-1ዜና 16፥34-36

1ሃሌ ሉያ[ቀ]
ቸር ነውና፣ እግዚአብሔርን አመስግኑ፤
ምሕረቱም ለዘላለም ነውና።
2ስለ እግዚአብሔር ታላቅ ሥራ ማን
ሊናገር ይችላል?
ምስጋናውንስ ሁሉ ማን ተናግሮ
ይጨርሳል?
3ፍትሕ እንዳይዛነፍ የሚጠብቁ፣
ጽድቅን ሁልጊዜ የሚያደርጉ የተባረኩ
ናቸው።
4እግዚአብሔር ሆይ፤ ለሕዝብህ ሞገስ
ስታድል አስበኝ፤
በምታድናቸውም ጊዜ ርዳኝ፤
5ይኸውም የምርጦችህን ብልጽግና አይ
ዘንድ፣
በሕዝብህ ደስታ ደስ ይለኝ ዘንድ፣
ከርስትህም ክብር የተነሣ እጓደድ
ዘንድ ነው።

6እኛም እንደ አባቶቻችን ኀጢአት
ሠራን፤
በደልን፤ ክፉም አደረግን።
7አባቶቻችን በግብፅ ሳሉ፣
ታምራትህን አላስተዋሉም፤
የምሕረትህን ብዛት አላሰቡም፤
በባሕሩ አጠገብ፣ ገና ቀይ ባሕር[በ]
አጠገብ ዐመፁብህ።
8እርሱ ግን የኀይሉን ታላቅነት ለማሳወቅ፣
ስለ ስሙ አዳናቸው።
9ቀይ ባሕርን ገሠጸ፤ እርሱም ደረቀ፤
በምድረ በዳ እንደሚታለፍ በጥልቅ
ውሃ መካከል መራቸው።

10ከባለጋራቸው እጅ አዳናቸው፤
ከጠላትም እጅ ታደጋቸው።
11ባላንጦቻቸውን ውሃ ዋጣቸው፤
ከእነርሱም አንድ አልተረፈም።
12ከዚህ በኋላ የተስፋ ቃሉን አመኑ፤
በዝማሬም አመሰገኑት።

13ነገር ግን ያደረገውን ወዲያውኑ ረሱ፤
በምክሩም ለመሄድ አልታገሡም።
14በምድረ በዳ እጅግ መመኘት አበዙ፤

፤80፥3፤107፥13፤ኢሳ25፥9፤ኢል2፥32 **106፥9** ዘፀ14፥21፤መዝ18፥15፤78፥13፤ኢሳ50፥2፤63፥11-14፤ናሆ1፥4 **106፥10** ዘፀ14፥30፤መዝ78፥42፡53፤107፥2፡13፤ኢሳ35፥9፤62፥12 **106፥11** ዘፀ14፥28 **106፥12** ዘፀ15፥1-21፤105፥43 **106፥13** ዘፀ15፥24፤16፥28፤ዘኍ27፥21 **106፥14** ዘፀ17፥2፤መዝ68፥7፤78፥40፤10፥9

[ሽ]45 *እግዚአብሔር ይመስገን* የሚሉ ትርጉሞች አሉ።
[ቀ]1 *እግዚአብሔር ይመስገን* ማለት ሲሆን በቍ48 ላይም በድጋሚ ተጠቅሶአል።
[በ]7 በዕብራይስጥ *ያም ሱፍ* የሚባል ሲሆን *የደንገል ባሕር* ማለት ነው፤ በቍ9 እና 22 ላይም ይገኛል።

በበረሓም እግዚአብሔርን ተፈታተኑት።
15እርሱም የለመኑትን ሰጣቸው፤
ዳሩ ግን የሚያኰሰምን ሕመም
ሰደደባቸው።

16በሰፈር በሙሴ ላይ፣
ለእግዚአብሔር በተቀደሰውም በአሮን
ላይ ቀኑ።
17ምድር ተከፍታ ዳታንን ዋጠች፤
የአቤሮንን ወገን ሰለቀጠች።
18እሳት በጉባኤያቸው መካከል ነደደ፤
ነበልባሉም ክፉዎችን ፈጅቶ አስወገደ።

19በኮሬብ ጥጃ ሠሩ፤
ቀልጦ ለተሠራ ምስልም ሰገዱ።
20ክብራቸው የሆነውንም ሣር በሚበላ፣
በበሬ ምስል ለወጡ።
21በግብፅ ታላቅ ነገር ያደረገውን፣
ያዳናቸውን አምላክ ረሱ፤
22እርሱ ግን በካም ምድር ድንቅ ሥራ፣
በቀይ ባሕርም አስደናቂ ነገር አደረገ።
23ስለዚህ በመቅሠፍቱ እንዳያጠፋቸው
ይመለስ ዘንድ፣
እርሱ የመረጠው ሙሴ በመካከል ገብቶ፣
በፊቱ ባይቆም ኖሮ፣
እንደሚያጠፋቸው ተናግሮ ነበር።

24ከዚያም በኋላ መልካሚቱን ምድር ናቁ፤
የተስፋ ቃሉንም አላመኑም።
25በድንኳኖቻቸው ውስጥ አጕረመረሙ፤
የእግዚአብሔርንም ድምፅ አላዳመጡም።
26በምድረ በዳ ሊጥላቸው፣
እጁን አንሥቶ ማለ፤
27ዘራቸውንም በሕዝቦች መካከል ሊጥል፣
ወደ ተለያየ ምድርም እንደሚበትናቸው
ማለ።

28ራሳቸውን ከብዔል ፌጎር ጋር አቈራኙ፤
ለሙታን የተሠዋውን መሥዋዕት በሉ፤
29በሥራቸውም እግዚአብሔርን አስቈጡት፤
ቸነፈርም በላያቸው መጣ።
30ፊንሐስም ተነሥቶ ጣልቃ ገባ፤
ቸነፈሩም ተገታ፤
31ይህም ከትውልድ እስከ ትውልድ፣
ለዘላለም ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት።

32ደግሞም በመሪባ ውሃ አጠገብ እግዚ
አብሔርን አስቈጡት፤
ሙሴም ከእነርሱ የተነሣ ተቸገረ፤
33የእግዚአብሔርንም መንፈስ ስላስመረሩት፣
ሙሴ የማይገባ ቃል ከአንደበቱ
አወጣ።†

34እግዚአብሔር ባዘዛቸው መሠረት፣
ሕዝቦችን ከማጥፋት ወደ ኋላ አሉ፤
35እንዲያውም ከሕዝቦቹ ጋር ተደባለቁ፤
ልማዳቸውንም ቀሠሙ፤

106፥15 ዘፀ16፥13፤ ዘኍ11፥33፤መዝ 78፥29
106፥16 ዘኍ16፥1-3
106፥17 ዘፀ15፥12፤ ዘኍ16፥1፤ዘዳ11፥6
106፥18 ዘሌ10፥2
106፥19 ዘፀ32፥4፤ ሐሥ7፥41
106፥20 ኤር2፥11፤ ሮሜ1፥23
106፥21 ዘዳ10፥21 ፤መዝ75፥1፤78፥11
106፥22 ዘፀ3፥20፤ ዘዳ4፥34፤መዝ78፥51
106፥23 ዘፀ32፥10፡ 11-14፤ዘኍ11፥2፤ ዘዳ9፥19
106፥24 ዘኍ14፥11 ፡30-31፤ዘዳ8፥7፤ኤር 3፥19፤ዕብ3፥18-19
106፥25 ዘፀ15፥24፤ ዘዳ1፥27፤1ቆሮ10፥10
106፥26 ዘኍ14፥23 ፤ዘዳ2፥14፤ዕብ3፥17፤4፥3
106፥27 ዘሌ26፥33
106፥28 ዘኍ23፥28
106፥29 ዘኍ16፥46፤ 25፥3፡8፤መዝ64፥2፤14 1፥4
106፥30 ዘፀ6፥25፤ ዘኍ25፥8
106፥31 ዘፍ15፥6፤ ዘኍ25፥11-13፤መዝ 49፥11
106፥32 ዘፀ17፥7፤ ዘኍ20፥2-13
106፥33 ዘፀ17፥4-7፤23፥21፤ዘኍ20፥8-12፤መዝ51፥11፤ 107፥11፤ኢሳ63፥10
106፥34 ዘፀ23፥24፤ ዘዳ2፥34፤7፥16፤ 20፥17፤ኢሱ9፥15፤ መሳ1፥27-36
106፥35 መሳ3፥5-6፤ዕዝ9፥1-2
106፥26 ዘፀ10፥7፤ ዘዳ7፥16
106፥37 ዘፀ22፥20፤ ዘሌ18፥21፤ዘዳ12፥31፤ 32፥17፤ሕዝ16፥20-21፤1ቆሮ10፥20
106፥38 ዘሌ18፥21 ፤ዘዳ18፥10፤2ነገ3፥27
106፥39 ዘፍ3፥17፤ ዘሌ18፥24፤ዘኍ 15፥39፤ሕዝ20፥18
106፥40 ዘፀ34፥9፤ ዘሌ26፥28፤ዘዳ9፥29
106፥41 መሳ2፥14
106፥42 መሳ4፥3
106፥43 ኢሱ10፥14 ፤መሳ2፥16-19፤6፥1-7፤7፥1-25፤ነህ9፥28፤ መዝ81፥13-14
106፥44 መሳ3፥9
106፥45 ዘፍ9፥15፤ ዘፀ32፥14፤መዝ17፥7 ፤103፥11፤105፥8፤

36ጣዖቶቻቸውንም አመለኩ፤
ይህም ወጥመድ ሆነባቸው።
37ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን
ለአጋንንት ሠዉ።
38የወንዶችና የሴቶች ልጆቻቸውን ደም፣
ለከነዓን ጣዖታት የሠዉአቸውን፣
ንጹሕ ደም አፈሰሱ፤
ምድሪቱም በደም ተበከለች።
39በተግባራቸው ረከሱ፤
በድርጊታቸውም አመንዝሮች ሆኑ።

40ስለዚህ የእግዚአብሔር ቍጣ በሕዝቡ
ላይ ነደደ፤
ርስቱንም ተጸየፈ።
41ለአሕዛብ አሳልፎ ሰጣቸው፤
ጠላቶቻቸውም በላያቸው ሠለጠኑ።
42ጠላቶቻቸው ጨቈኗቸው፤
በሥልጣናቸውም ሥር አዋሏቸው።
43እርሱ ብዙ ጊዜ ታደጋቸው፤
እነርሱ ግን ዐመፃን የሙጥኝ አሉ፤
በኀጢአታቸውም ተዋረዱ።

44ሆኖም ጩኸታቸውን በሰማ ጊዜ፣
ጭንቀታቸውን ተመለከተ፤
45ለእነርሱም ሲል ቃል ኪዳኑን አሰበ፤
እንደ ምሕረቱም ብዛት ከቍጣው
ተመለሰ።
46የማረኳቸው ሁሉ፣
እንዲራሩላቸው አደረገ።

47አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ፤ አድነን፤
ለቅዱስ ስምህ ምስጋና እናቀርብ
ዘንድ፣
አንተን በመወደስ እንጓደድ ዘንድ፣
ከሕዝቦች መካከል ሰብስበህ አምጣን።

48የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር፣
ከዘላለም እስከ ዘላለም ይባረክ፤
ሕዝብም ሁሉ፣ “አሜን!” ይበል።
ሃሌ ሉያ።

## አምስተኛ መጽሐፍ
## መዝሙር 107-150

### መዝሙር 107
### ከመከራ ሁሉ የሚታደግ አምላክ

1ቸር ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ፤
ምሕረቱም ለዘላለም ነውና።
2እግዚአብሔር የተቤዣቸው፣
ከጠላት እጅ የታደጋቸው ይህን ይበሉ፤

ሉቃ1፥72 106፥46 ዘፀ3፥21፤1ነገ8፥50 106፥47 መዝ28፥9፤ 30፥4፤99፥3፤105፥1፤107፥3፤147፥2፤ኢሳ11፥12፤27፥13፤56፥8፤ 66፥20፤ኤር31፥8፤ሕዝ20፥34፤ሚክ4፥6 106፥48 መዝ41፥13፤ 72፥19 107፥1 1ዜና16፥8፤2ዜና5፥13፤7፥3 107፥2 መዝ106፥10፤ ኢሳ35፥9

†33 አንዳንዶች ራሱን ባለመቈጣጠርና በችኰላ ተናገረ

3 ከምሥራቅና ከምዕራብ፣ ከሰሜንና
ከደቡብ፣[ቸ]
ከየአገሩ የሰበሰባቸው እንዲህ ይናገሩ፡፡
4 አንዳንዶቹ ጭው ባለ በረሓ ተቅበዘበዙ፤
ወደሚኖሩባት ከተማ የሚያደርስ
መንገድ አጡ፡፡
5 ተራቡ፤ ተጠሙ፤
ነፍሳቸውም በውስጣቸው ዛለች፡፡
6 በተጨነቁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር
ጮኹ፤
እርሱም ከመከራቸው አዳናቸው፡፡
7 ወደሚኖሩባትም ከተማ፣
በቀና መንገድ መራቸው፡፡
8 እግዚአብሔርን ስለ ምሕረቱ፣
ለሰው ልጆችም ስላደረገው ድንቅ
ሥራ ያመስግኑት፤
9 እርሱ የተጠማችውን ነፍስ አርክቶአልና፤
የተራበችውንም ነፍስ በበጎ ነገር
አጥግቦአል፡፡
10 አንዳንዶቹ በብረት ሰንሰለት ታስረው
የተጨነቁ፣
በጨለማ፣ በጥልማሞት ውስጥ
የተቀመጡ ነበሩ፤
11 በእግዚአብሔር ቃል ላይ በማመፅ፣
የልዑልን ምክር አቃለዋልና፡፡
12 ስለዚህ በጕልበት ሥራ ልባቸውን አዛለ፤
ተዝለፈለፉ፤ የሚደግፋቸውም
አልነበረም፡፡
13 በተጨነቁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር
ጮኹ፤
እርሱም ከመከራቸው አዳናቸው፡፡
14 ከጨለማና ከጥልማሞት አወጣቸው፤
እስራታቸውንም በጠሰላቸው፡፡
15 እግዚአብሔርን ስለ ምሕረቱ፣
ለሰው ልጆችም ስላደረገው ድንቅ ሥራ
ያመስግኑት፤
16 እርሱ የናሱን በሮች ሰብሮአልና፤
የብረቱንም መወርወሪያ ቈርጦአል፡፡
17 አንዳንዶቹ ከዐመፃቸው የተነሣ ቂሎች
ሆኑ፤
ከበደላቸው የተነሣ ችግር ውስጥ ገቡ፡፡
18 ሰውነታቸው የምግብ ዐይነት ሁሉ
ተጸየፈች፤
ወደ ሞትም ደጆች ቀረቡ፡፡
19 በተጨነቁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር
ጮኹ፤
እርሱም ከመከራቸው አዳናቸው፡፡
20 ቃሉን ልኮ ፈወሳቸው፤
ከመቃብርም አፋፍ መለሳቸው፡፡
21 እግዚአብሔርን ስለ ምሕረቱ፣
ለሰው ልጆችም ስላደረገው ድንቅ ሥራ
ያመስግኑት፤
22 የምስጋናም መሥዋዕት ያቅርቡለት፤
ሥራውንም ደስ በሚል ዝማሬ
ይግለጹ፡፡
23 አንዳንዶቹ በመርከብ ወደ ባሕር ወረዱ፤
በታላቅም ውሃ ላይ ሥራቸውን
አከናወኑ፤
24 የእግዚአብሔርን ሥራ በዚያ አዩ፤
ድንቅ አድራጎቱንም በጥልቁ ውስጥ
ተመለከቱ፡፡
25 እርሱ ተናግሮ ዐውሎ ነፋስን አስነሣ፤
ነፋሱም ማዕበሉን ከፍ ከፍ አደረገ፡፡
26 ወደ ሰማይ ወጡ፤ ወደ ጥልቅም ወረዱ፤
ከመከራቸውም የተነሣ ሐሞታቸው
ፈሰሰ፡፡
27 እንደ ሰከረ ሰው ዞሮባቸው ወዲያ ወዲህ
ተንገዳገዱ፤
መላው ጠፍቶባቸው የሚያደርጉትን
አጡ፡፡
28 በተጨነቁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር
ጮኹ፤
እርሱም ከመከራቸው አዳናቸው፡፡
29 ዐውሎ ነፋሱን ጸጥ አደረገ፤
የባሕሩም ሞገድ ረጭ አለ፡፡
30 ጸጥ በማለቱም ደስ አላቸው፤
ወዳሰቡትም ወደብ አደረሳቸው፡፡
31 እግዚአብሔርን ስለ ምሕረቱ፣
ለሰው ልጆችም ስላደረገው ድንቅ
ሥራ ያመስግኑት፤
32 በሕዝብ ጉባኤ መካከል ከፍ ከፍ
ያድርጉት፤
በሽማግሌዎችም ሸንጎ ይወድሱት፡፡
33 ወንዞችን ወደ ምድረ በዳ፣
የውሃ ምንጮችንም ወደ ደረቅ ምድር
ለወጠ፡፡
34 ከነዋሪዎቿ ክፋት የተነሣ፣
ፍሬያማዋን ምድር በጨው የተበከለች
አደረጋት፡፡
35 ምድረ በዳውን ወደ ውሃ መከማቻ፣
ደረቁንም ምድር ወደ ውሃ ምንጭ
ቀየረ፡፡
36 የተራቡትን በዚያ አስቀመጠ፤
የሚኖሩባትንም ከተማ ሠሩ፡፡
37 በዕርሻውም ዘሩበት፤ ወይንም ተከሉ፤
ብዙ ፍሬም አመረቱ፡፡
38 ይባርካቸዋል፤ እነርሱም እጅግ ይበዛሉ፤
የከብቶቻቸውም ብዛት እንዲያንስ
አያደርግም፡፡

107፥3 ነህ1፥9
107፥4 ቍ36፤ኢ.ሱ 5፥6
107፥5 ዘፀ15፥22፤16፥3፤17፥2
107፥6 ዘፀ14፥10
107፥7 ቍ36፤ዕዝ 8፥21
107፥8 መዝ6፥4፤75፥1፤105፥1
107፥9 መዝ22፥26፤23፥1፤63፥5፤ኢ.ሳ 58፥11፤ኤር31፥25፤ማቴ5፥6፤ሉ.ቃ1፥53
107፥10 ቍ14፤ኢ.ዮ36፥8፤መዝ88፥6፤102፥20፤143፥3፤ኢ.ሳ 9፥2፤42፥7፥16፤49፥9፤61፥1፤ሚ.ክ7፥9
107፥11 ዘኍ14፥11፤1ነገ22፥5፤2ዜና 36፥16፤መዝ5፥10
107፥12 2ነገ14፥26፤መዝ72፥12
107፥13 መዝ106፥8
107፥14 ቍ10፤ኢ.ዮ36፥8፤መዝ86፥13፤116፥16፤ኢ.ሳ9፥2፤29፥18፤42፥7፤50፥10፤59፥9፤60፥2፤ሉ.ቃ1፥79፤ሐሥ12፥7
107፥15 ቍ8፡21፡31፤መዝ6፥4፤75፥1፤105፥1
107፥17 ዘሌ26፥16፤መዝ25፥7፤53፥1፤ኢ.ሳ 65፥6-7፤ኤር30፥14-15፤ገላ6፥7-8
107፥18 ኢ.ዮ3፥24፤6፥6፤17፥16፤33፥22
107፥19 ቍ13፡28፤መዝ5፥2፤34፥4
107፥20 ዘፀ15፥26፤ዘዳ32፥2፤ኢ.ዮ33፥28፤መዝ16፥10፤30፥3፤56፥13፤147፥15፤ማቴ 8፥8፤ሉ.ቃ7፥7
107፥21 ቍ15፤መዝ 6፥4፤75፥1
107፥22 ዘሌ7፥12፤ኢ.ዮ8፥21፤መዝ9፥11፤65፥8፤73፥28፤118፥17
107፥23 መዝ104፥26፤ኢ.ሳ42፥10
107፥24 መዝ64፥9፤111፥2፤143፥5
107፥25 መዝ50፥3፤93፥3፤105፥31
107፥26 ኢ.ሱ2፥11፤ሉ.ቃ8፥23
107፥27 ኢ.ሳ19፥14፤24፥2፤28፥7
107፥28 ቍ19፤መዝ 4፥1፤ዮና1፥6
107፥29 መዝ65፥7፤93፥3፤ዮና1፥15፤ሉ.ቃ 8፥24
107፥30 ቍ7
107፥31 ቍ15፤መዝ 6፥4፤75፥1፤106፥2
107፥32 መዝ1፥5፤22፥22፤26፥12፤30፥1፤34፥3፤35፥18፤99፥5
107፥33 1ነገ17፥1፤መዝ74፥15፤104፥10፤ኢ.ሳ41፥15፤42፥15፤50፥2 107፥34 ዘፍ13፥10 107፥35 2ነገ3፥17፤ኢ.ዮ38፥26፤መዝ105፥41፤126፥4፤ኢ.ሳ35፥7፤43፥19፤51፥3 107፥37 2ነገ 19፥29፤ኢ.ሳ37፥30 107፥38 ዘፍ12፥2፤49፥25፤ዘዳ7፥13

ቸ3 ዕብራይስጡ ሰሜንና ባሕሩ ይለዋል፡፡

39 በጭንቅ፣ በመከራና በሐዘን፣
ቍጥራቸው አንሶ፣ ተዋርደው ነበር፤
40 በመኳንንቱም ላይ መናቅን አዘነበባቸው፤
መውጫ መግቢያው በማይታወቅ በረሓ
ውስጥም አንከራተታቸው።
41 ችግረኞችን ግን ከጭንቀታቸው መዝዞ
አወጣቸው፤
ቤተ ሰባቸውንም እንደ በግ መንጋ
አበዛ።
42 ልበ ቅኖች ይህን አይተው ሐሤት
ያደርጋሉ፤
ጥመትም ሁሉ አፏን ትዘጋለች።
43 እንግዲህ ማንም ብልህ ቢሆን፣ ይህን
ነገር ልብ ይበል፤
እርሱም *የእግዚአብሔርን* ምሕረት
ያስተውላል።

## መዝሙር 108

## የጧት ውዳሴና ብሔራዊ ጸሎት

108፥1-5 ተጓ ምብ-መዝ57፥7-11
108፥6-13 ተጓ ምብ-መዝ60፥5-12

የዳዊት መዝሙር፤ ማኅሌት

1 አምላክ ሆይ፤ ልቤ ጽኑ ነው፤
እዘምራለሁ፤ በፍጹም ነፍሴም
እዘምራለሁ።
2 በገናም መሰንቆም ተነሡ፤
እኔም ማልጄ እነሣለሁ።
3 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ በሕዝብ መካከል
አመሰግንሃለሁ፤
በሕዝቦችም መካከል እዘምርልሃለሁ።
4 ምሕረትህ ከሰማያት በላይ ታላቅ ናትና፤
ታማኝነትህም እስከ ጠፈር ትደርሳለች።
5 አምላክ ሆይ፤ ከሰማያት በላይ ከፍ ከፍ
በል፤
ክብርህም በምድር ሁሉ ላይ ትንሰራፋ።
6 ወዳጆችህ ይድኑ ዘንድ፣
በቀኝ እጅህ ታደግ፤ መልስልኝም።
7 እግዚአብሔር ከመቅደሱ እንዲህ አለ፤
ደስ እያለኝ ሴኬምን እሸነሽናለሁ፤
“የሱኮትንም ሸለቆ እለካለሁ።
8 ገለዓድ የእኔ ነው፤ ምናሴም የእኔ ነው፤
ኤፍሬም የራስ ቍሬ ነው፤
ይሁዳም በትረ መንግሥቴ።
9 ሞዓብ መታጠቢያ ገንዳዬ ነው፤
በኤዶምያስ ላይ ጫማዬን
እወረውራለሁ፤
በፍልስጥኤም ላይ በድል አድራጊነት
እፎክራለሁ።”
10 ወደ ተመሸገችው ከተማ ማን
ይወስደኛል?
ወደ ኤዶምያስስ ማን ያደርሰኛል?
11 እግዚአብሔር ሆይ፤ የጣልኸን አንተ
አይደለህምን?
አምላክ ሆይ፤ ከሰራዊታችንም ጋር
አልወጣ አልህ!
12 አሁንም የሰው ማዳን ከንቱ ነውና፣
በጠላታችን ላይ ድልን አቀዳጀን።
13 እግዚአብሔር ሲረዳን ብርቱ እንሆናለን፤
ጠላቶቻችንንም ከእግሩ በታች
የሚረግጥ እርሱ ነው።

## መዝሙር 109

## በጠላት ላይ የቀረበ ጸሎት

ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር

1 የምስጋናዬ ምንጭ የሆንህ አምላክ ሆይ፤
ዝም አትበል፤
2 ክፉዎችና አታላዮች፣
አፋቸውን ከፍተውብኛልና፤
በውሸተኛ አንደበት ተናግረውብኛል።
3 በጥላቻ ቃል ከበውኛል፤
ያለ ምክንያትም ጥቃት አድርሰውብኛል።
4 ስወዳቸው ይወነጅሉኛል፤
እኔ ግን እጸልያለሁ።
5 በበጎ ፈንታ ክፉትን፣
በወደድኋቸው ፈንታ ጥላቻን
ይመልሱልኛል።
6 ክፉ ሰውኀ በላዩ ሹም፤
ከሳሽምነ በቀኙ ይቁም።
7 ፍርድ ፊት ሲቆም በደለኛ ሆኖ ይገኝ፤
ጸሎቱም ለፍርድ ትሁንበት።
8 ዕድሜው ይጠር፤
ሹመቱንም ሌላ ይወሰደው።
9 ልጆቹ ድኻ አደጎች ይሁኑ፤
ሚስቱም መበለት ትሁን።
10 ልጆቹ ይንከራተቱ፤ ለማኞችም ይሁኑ፤
ከፈረሰው ቤታቸውም ይሰደዱ።
11 ያለውን ሁሉ ዕዳ ጠያቂ ይውረሰው፤
የድካሙንም ዋጋ ባዕዳን ይቀሙት።
12 ማንም ሰው ምሕረት አያድርግለት፤
ለድኻ አደግ ልጆቹም የሚራራ
አይኑር።
13 ዘሩ ተለይቶ ይጥፋ፤
ስማቸውም በሚቀጥለው ትውልድ
ይደምሰስ።
14 የአባቶቹ በደል *በእግዚአብሔር* ፊት
ይታሰብ፤
የእናቱም ኀጢአት አይደምሰስ።
15 መታሰቢያቸውን ከምድር ያጠፋ ዘንድ፣
ኀጢአታቸው ሁልጊዜ *በእግዚአብሔር*
ፊት ይኑር፤
16 ችግረኛውንና ምስኪኑን፣ ልቡም
የቈሰለውን፣

107፥39 2ነገ10፥32፤
መዝ44፥9፤ሕዝ5፥12
107፥40 ዘዳ32፥10፤
ኢዮ12፥18
107፥41 1ሳሙ2፥8፤
ኢዮ21፥11፤መዝ
113፥7-9
107፥42 ኢዮ5፥16፤
22፥19፤መዝ97፥10-12፤
ሮሜ3፥19
107፥43 መዝ103፥
11፤ኤር9፥12፤ሆሴ
14፥9
108፥1 መዝ18፥49፤
112፥7፤119፥30፥112
108፥2 ኢዮ21፥12
108፥4 ዘፀ34፥6፤
ዘኍ14፥18፤መዝ
36፥5፤106፥45
108፥5 መዝ8፥1፤
57፥5
108፥6 ኢዮ40፥14
108፥7 ዘፍ12፥6፤
33፥17፤መዝ68፥35፤
89፥35፤102፥19
108፥8 መዝ78፥68
108፥9 ዘፍ19፥37፤
2ሳሙ8፥1፥13-14
108፥11 መዝ44፥9
108፥12 መዝ118፥8
፤146፥3፤ኢሳ10፥3፤
30፥5፤31፥3፤ኤር
2፥36፤17፥5
108፥13 መዝ44፥5
፤ኢሳ22፥5፤63፥3፥6
109፥1 ዘፀ15፥2፤ኢዮ
34፥29፤ኤር17፥14
109፥2 መዝ43፥1፤
52፥4
109፥3 መዝ35፥7፤
69፥4፤ዮሐ15፥25
109፥4 መዝ69፥13
፤141፥5
109፥5 ዘፍ44፥4
109፥6 1ዜና21፥1፤
ኢዮ1፥6፤ዘካ3፥1
109፥7 መዝ1፥5፤
ምሳ28፥9፤ኢሳ41፥24
109፥8 ኢዮ15፥32፤
ሐሥ1፥20
109፥9 ዘፀ22፥24፤
ኤር18፥21
109፥10 ዘፍ4፥12
109፥11 ዘኍ14፥3፤
ነህ5፥3፤ኢዮ20፥18፤
ኢሳ1፥7፤6፥11፤36፥1፤
ሰቆ5፥2
109፥12 ኢዮ5፥4
109፥13 ዘኍ14፥12
፤ኢዮ18፥19፤መዝ9፥
፤21፥10፤ምሳ10፥7
109፥14 ዘፀ20፥5፤
ዘኍ14፥18፤ኢሳ
65፥6-7፤ኤር32፥18
109፥15 ዘፀ17፥14፤
ዘዳ32፥26፤መዝ90፥8
109፥16 ኢዮ20፥19
፤መዝ34፥18፤35፥10

ኀ6 ወይም *ክፉው*
ነ6 ወይም *ሰይጣንን*

እስከ ሞት አሳደደ እንጂ፣
ምሕረት ያደርግ ዘንድ አላሰበምና።
17መራገምን ወደደ፤
ወደ እርሱም መጣች፤
በመባረክ ደስ አልተሰኘም፤
በረከትም ከእርሱ ራቀች።
18መርገምን እንደ ልብስ ለበሳት፤
እርሷም እንደ ውሃ ወደ ውስጥ
ሰውነቱ፤
እንደ ዘይትም ወደ ዐጥንቱ ዘለቀች።
19ገላውን እንደሚሸፍንበት ልብስ፣
ዘወትር እንደሚታጠቀውም መቀነት
ትሁነው።
20እግዚአብሔር ለሚወነጅሉኝ ሰዎች፣
በነፍሴም ላይ ክፉ ለሚናገሩ
የሚከፍላቸው ይኸው ይሁን።

21አንተ ግን ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፤
ስለ ስምህ በበጎ ተመልከተኝ፤
ምሕረትህም መልካም ናትና አድነኝ።
22እኔ ድኻና ችግረኛ ነኝና፤
ልቤም በውስጤ ቈስሎአልና።
23እንደ ምሽት ጥላ ከእይታ ተሰውሬአለሁ፤
እንደ አንበጣም ረግፌአለሁ።
24ከጾም የተነሣ ጒልበቴ ዛለ፤
ሰውነቴም ከስቶ ዐመድ ለበሰ።
25ለመሣለቂያ ሆንሁላቸው፤
ሲያዩኝም ራሳቸውን ይነቀንቃሉ።

26እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤ ርዳኝ፤
እንደ ምሕረትህም አድነኝ።
27እግዚአብሔር ሆይ፤ እጅህ ይህን
እንዳደረገች፣
አንተም ይህን እንደ ፈጸምህ ይወቁ።
28እነርሱ ይራገማሉ፤ አንተ ግን
ትባርካለህ፤
በሚነሡበት ጊዜ ይዋረዳሉ፤
ባሪያህ ግን ሐሤት ያደርጋል።
29የሚወነጅሉኝ ውርደትን ይከናነቡ፤
ዕፍረትንም እንደ ሸማ ይልበሱ።

30እግዚአብሔርን በአንደበቴ እጅግ
አመሰግናለሁ፤
በታላቅ ሕዝብም መካከል አወድሰዋለሁ።
31በነፍሱ ላይ ከሚፈርዱት ያድነው
ዘንድ፣
እርሱ በችግረኛው ቀኝ በኩል
ይቆማልና።

## መዝሙር 110

### መሲሑ ንጉሥና ካህን

የዳዊት መዝሙር

1እግዚአብሔር ጌታዬን፣
"ጠላቶችህን ለእግርህ መርገጫ፣
እስከማደርግልህ ድረስ፣
በቀኜ ተቀመጥ" አለው።

2እግዚአብሔር ብርቱ በትርህን ከጽዮን
ወደ ውጭ ይሰዳል፤
አንተም በጠላቶችህ መካከል ሆነህ
ትገዛለህ።
3ለጦርነት በምትወጣበት ቀን፣
ሰራዊትህ በገዛ ፈቃዱ በጐንህ
ይቆማል፤
ከንጋት ማሕፀን፣
በቅዱስ ግርማ ደምቀህ፣
የጐልማሳነትህን ልምላሜ[ኘ] እንደ ጠል
ትቀበላለህ።

4"እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዐት፤
አንተ ለዘላለም ካህን ነህ" ብሎ፣
እግዚአብሔር ምሎአል፤
እርሱ ሐሳቡን አይለውጥም።

5ጌታ በቀኝህ ነው፤
በቍጣውም ቀን ነገሥታትን
ያደቃቸዋል።
6በሕዝቦች መካከል ይፈርዳል፤
በየአገሩ ያሉትንም ራሶች ከስክሶ
ሬሳ በሬሳ ያደርጋቸዋል።
7መንገድ[አ] ዳር ካለች ፈሳሽ ውሃ
ይጠጣል፤
ስለዚህ ራሱን ቀና ያደርጋል።

## መዝሙር 111[ከ]

### ለመለኮቱ ባሕርያት የቀረበ ጸሎት

1ሃሌ ሉያ።

በቅኖች ሸንጎ፣ በጉባኤም መካከል፣
ለእግዚአብሔር በፍጹም ልቤ ምስጋና
አቀርባለሁ።

2የእግዚአሔር ሥራ ታላቅ ናት፤
ደስ የሚሰኙባትም ሁሉ ያውጠነጥኗታል።
3ሥራው ባለ ክብርና ባለ ግርማ ነው፤
ጽድቁም ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
4ድንቅ ሥራው ሲታወስ እንዲኖር
አደረገ፤
እግዚአብሔር ቸር፣ ርኅሩኅም ነው።
5ለሚፈሩት ምግብን ይሰጣል፤
ኪዳኑንም ለዘላለም ያስባል።
6ለሕዝቡ የአሕዛብን ርስት በመስጠት፣
የአሠራሩን ብርታት አሳይቶአል።
7የእጁ ሥራ እውነተኛና ቅን ነው፤
ሥርዐቱም ሁሉ የታመነ ነው፤

109፥17 ምሳ28፥27፤ማቴ7፥2
109፥18 ዘኍ5፥22፤መዝ10፥7
109፥19 ቍ29፤መዝ73፥6፤ሕዝ7፥27
109፥20 ዘፀ32፥34፤መዝ54፥5፤71፥10፤94፥23፤ኢሳ3፥11፤2ጢሞ4፥14
109፥21 ዘፀ9፥16፤መዝ3፥7፤23፥3፤69፥16
109፥23 ኢዮ14፥2
109፥24 ኢዮ16፥8፤መዝ35፥13፤ዕብ12፥12
109፥25 ኢዮ16፥4፤መዝ22፥6፤ማቴ27፥39፤ማር15፥29
109፥26 መዝ12፥1፤119፥86
109፥27 ኢዮ37፥7
109፥28 2ሳሙ16፥12፤መዝ66፥4፤ኢሳ35፥10፤51፥11፤54፥1፤65፥14
109፥29 መዝ35፥26
109፥30 መዝ35፥18
109፥31 መዝ16፥8፤108፥6
110፥1 ኢሱ10፥24፤1ነገ5፥3፤ማቴ22፥44፤ማር12፥36፤16፥19፤ሉቃ20፥42፤ሐሥ2፥34፤1ቆሮ15፥25፤ዕብ1፥13፤12፥2
110፥2 ዘፍ49፥10፤መዝ2፥6፤45፥6፤72፥8፤ኢሳ14፥5፤ኤር48፥17
110፥3 ዘፀ15፥11፤ሚክ5፥7
110፥4 ዘፍ14፥18፤ዘኍ23፥19፤ዘካ6፥13፤ዕብ5፥6፡10፣7፥15-17፡21
110፥5 ዘዳ7፥24፤መዝ2፥5፡12፤16፥8፤68፥21፤76፥12፤ኢሳ60፥12፤ዳን2፥44፤ሮሜ2፥5፤ራእ6፥17፤11፥18
110፥6 መዝ9፥19፤18፥38፤ኢሳ5፥25፤34፥3፤66፥24
110፥7 መዝ3፥3፤27፥6
111፥1 መዝ1፥5፤9፥1፤34፥1፤89፥7፤109፥30፤115፥18፤145፥10
111፥2 ኢዮ36፥24፤መዝ64፥9፤143፥5፤ራእ15፥3
111፥3 መዝ112፥3፡9፤119፥142
111፥4 ዘዳ4፥31፤መዝ86፥15
111፥5 ዘፍ1፥30፤1ዜና16፥15፤መዝ37፥25፤103፥11፤105፥8፤ማቴ6፥31-33
111፥6 መዝ64፥9፤66፥3፡5፤105፥44
111፥7 መዝ19፥7፤ 92፥4፤119፥128

[ኘ]3 ወይም *ጐልማሶችህ እንደ ንጋት ወዳንተ ይመጣሉ* ማለት ነው።
[አ]7 ወይም *ሥልጣን ለመስጠት ኀይል ያለው ሥልጣን ላይ ያስቀምጠዋል*
[ከ]መዝሙር111 የግጥሙ መሥመሮች እያንዳንዳቸው ከላይ እስከ ታች በተከታታይ በዕብራይስጥ ፊደሎች ቅደም ተከተል የተቀመጡ ናቸው።

[8]ከዘላለም እስከ ለዘላለም የጸና ነው፤
በእውነትና በቅንነትም የተሠራ ነው።
[9]ለሕዝቡ መዳንን ሰደደ፤
ኪዳኑንም ለዘላለም አዘዘ፤
ስሙም የተቀደሰና የተፈራ ነው።
[10]*እግዚአብሔርን* መፍራት የጥበብ
መጀምሪያ ነው፤
ትእዛዙንም የሚፈጽሙ ጥሩ ማስተዋል
አላቸው፤
ምስጋናውም ለዘላለም ይኖራል።

**መዝሙር** 112

**የጻድቅ ሰው ባሕርይ**

[1]*ሃሌ ሉያ*።[ኸ]

*እግዚአብሔርን የሚፈራ*፣
በትእዛዙም እጅግ ደስ የሚሰኝ
የተባረከ ነው።

[2]ዘሩ በምድር ላይ ኀያል ይሆናል፤
የቅኖች ትውልድ ትባረካለች።
[3]ሀብትና ብልጽግና በቤቱ ይሞላል፤
ጽድቁም ለዘላለም ይኖራል።
[4]ቸር፣ ርኅሩኅና ጻድቅ እንደ መሆኑ፣
ለቅን ሰው በጨለማ ውስጥ ብርሃን
ይወጣለታል።
[5]ለጋስና ያለ ማንገራገር የሚያበድር፣
ሥራውንም በትክክል የሚያከናውን
ሰው መልካም ይሆንለታል፤
[6]ለዘላለም ከስፍራው አይናወጥምና፤
ጻድቅ ሰው[ወ] ሲታወስ ይኖራል።
[7]ክፉ ወሬ አያሸብረውም፤
ልቡ *እግዚአብሔርን* በመተማመን የጸና
ነው።
[8]ልቡ የጸና ነው፤ አይፈራምም፤
በመጨረሻም የጠላቶቹን ውድቀት ያያል።
[9]በልግስና ለድኾች ሰጠ፤
ጽድቁ ለዘላለም ይኖራል፤
ቀንዱም[ዐ] በክብር ከፍ ከፍ ይላል።

[10]ክፉ ሰው ይህን በማየት ይበሳጫል፤
ጥርሱን ያፋጫል፤ እየመነመነም
ይጠፋል፤
የክፉዎችም ምኞት ትጠፋለች።

**መዝሙር** 113

**ለታላቁና ለመሓሪው ጌታ ምስጋና**

[1]*ሃሌ ሉያ*።[ዘ]

*የእግዚአብሔር* አገልጋዮች ሆይ፤
አመስግኑት፤
*የእግዚአብሔርን* ስም አወድሱ።
[2]ከአሁን እስከ ዘላለም፣
*የእግዚአብሔር* ስም የተመሰገነ ይሁን።
[3]ከፀሓይ መውጫ እስከ መግቢያው
ድረስ፣

111፥8 መዝ119፥89፥152፥160፤ኢሳ40፥8፤ማቴ5፥18
111፥9 መዝ30፥4፤34፥22፤99፥3፤103፥4፤130፥7፤ሉቃ1፥49፥68
111፥10 ዘዳ4፥6፤ኢዮ23፥12፤መዝ19፥9፤28፥6፤89፥52፤119፥98፥104፥130
112፥1 ኢዮ1፥8፤መዝ1፥1-2፤33፥2፤103፥1፥11፤115፥13፤119፥14፥16፥47፥92፤128፥1
112፥2 መዝ25፥13፤37፥26፤128፥2-4
112፥3 ዘዳ8፥18፤መዝ37፥6፤111፥3
112፥4 መዝ5፥12፤18፥28
112፥5 መዝ37፥21፥26፤ሉቃ6፥35
112፥6 መዝ15፥5፤55፥22፤ምሳ10፥7፤መክ2፥16
112፥7 መዝ28፥7፤56፥3-4፤57፥7፤108፥1፤ኢሳ12፥2
112፥8 መዝ3፥6፤27፥1፤54፥7፤56፥11፤ምሳ1፥33፤ኢሳ12፥2
112፥9 መዝ75፥10፤111፥3፤ሉቃ19፥8፤ሐሥ9፥36፤2ቆሮ9፥9
112፥10 ኢዮ8፥13፤መዝ34፥21፤37፥12፤86፥17፤ማቴ8፥12
113፥1 መዝ22፥23፤34፥22፤103፥21፤134፥1
113፥2 መዝ30፥4፤48፥10፤115፥18፤131፥3፤145፥21፤148፥13፤149፥3፤ኢሳ12፥4፤ዳን2፥20
113፥3 ኢሳ24፥15፤45፥6፤59፥19፤ሚል1፥11
113፥4 መዝ8፥1፤57፥11፤99፥2
113፥5 ዘፀ8፥10፤ኢዮ16፥19፤መዝ35፥10፤103፥19
113፥6 መዝ11፥4፤138፥6፤ኢሳ57፥15
113፥7 1ሳሙ2፥8፤መዝ35፥10፤68፥10፤107፥41፤140፥12
113፥8 2ሳሙ9፥11
113፥9 1ሳሙ2፥5
114፥1 ዘፀ13፥3፤29፥46
114፥2 ዘፀ15፥17፤መዝ76፥1፤78፥68-69
114፥3፤ ዘፀ14፥21፤15፥8፤ኢሱ3፥16፤መዝ77፥16
114፥4 መሳ5፥5
114፥5 ዘፀ14፥21
114፥7 ዘፀ15፥14፤1ዜና16፥30
114፥8 ዘፀ17፥6፤ ዘኍ20፥11
115፥1 ዘፀ34፥6፤መዝ29፥2፤66፥2፤96፥8

*የእግዚአብሔር* ስም የተመሰገነ ይሁን።
[4]*እግዚአብሔር* ከሕዝቦች ሁሉ በላይ ከፍ
ያለ ነው፤
ክብሩም ከሰማያት በላይ ነው።
[5]እንደ አምላካችን እንደ *እግዚአብሔር*፣
በላይ በዙፋኑ የተቀመጠ ማን ነው?
[6]በሰማይና በምድር ያሉትንስ ለማየት፣
ራሱን ወደ ታች ዝቅ የሚያደርግ ማን
ነው?
[7]ድኻውን ከትቢያ ያነሣል፤
ችግረኛውን ከዐመድ ከፍ ከፍ ያደርጋል፤
[8]ከመኳንንትም እኩል ስፍራ ይሰጠዋል፤
ከሕዝቡም ሹማምት ጋር
ያስቀምጠዋል።
[9]*መካኒቱን* ሴት በቤት ያኖራታል፤
ደስተኛም የልጆች እናት ያደርጋታል።

*ሃሌ ሉያ*።

**መዝሙር** 114

**ለፋሲካ የቀረበ ውዳሴ**

[1]እስራኤል ከግብፅ ወጥቶ ሲሄድ፣
የያዕቆብም ቤት ቋንቋው ልዩ ከሆነ
ሕዝብ ተለይቶ ሲወጣ፣
[2]ይሁዳ *የእግዚአብሔር* መቅደስ፣
እስራኤልም ግዛቱ ሆነ።

[3]ባሕር አየች፤ ሸሸችም፤
ዮርዳኖስም ወደ ኋላው ተመለሰ።
[4]ተራሮች እንደ አውራ በግ፣
ኰረብቶችም እንደ ጠቦት ዘለሉ።

[5]አንቺ ባሕር፤ የሸሸሽው
አንቺም ዮርዳኖስ ያፈገፈግሽው
ለምንድን ነው?
[6]እናንተ ተራሮች እንደ አውራ በግ፣
ኰረብቶችም እንደ ጠቦት ለምን
ዘለላችሁ?

[7]ምድር ሆይ፤ በጌታ ፊት፣
በያዕቆብ አምላክ ፊት ተንቀጥቀጪ፤
[8]እርሱ ዐለቱን ወደ ኩሬ፤
ቋጥኙንም ወደ ውሃ ምንጭ ለወጠ።

**መዝሙር** 115

**አንዱ እውነተኛው አምላክ**

115፥4-11 ተጓ ምብ-መዝ135፥15-20

[1]ለእኛ ሳይሆን፣ *እግዚአብሔር* ሆይ፤
ለእኛ ሳይሆን፣
ስለ ምሕረትህና ስለ እውነትህ፣

[ኸ]1 *እግዚአብሔር ይመስገን* ማለት ነው።
[ወ]6 ወይም *እግዚአብሔር ቸር ርኅሩኅና ጻድቅ ስለ ሆነ*
[ዐ]9 በዚህ ስፍራ ክብርን ያመለክታል።
[ዘ]1 *እግዚአብሔር ይመስገን* ማለት ሲሆን፣ በቍ9 ላይም ይገኛል።

ለስምህ ክብርን ስጥ።
2አሕዛብ፣ “አምላካቸው የት አለ?”
ለምን ይበሉ?
3አምላካችንስ በሰማይ ነው፤
እርሱ ደስ የሚለውን ያደርጋል።
4የእነርሱ ጣዖታት ግን የሰው እጅ የሠራቸው፣
ብርና ወርቅ ናቸው።
5አፍ አላቸው፤ አይናገሩም፤
ዐይን አላቸው፤ አያዩም፣
6ጆሮ አላቸው፤ አይሰሙም፤
አፍንጫ አላቸው፤ አያሸቱትም፤
7እጅ አላቸው፤ አይዳስሱም፤
እግር አላቸው፤ አይሄዱም፤
በጕሮሮአቸውም ድምፅ አይፈጥሩም።
8እነዚህን የሚያበጁ፣
የሚታመኑባቸውም ሁሉ እንደ እነርሱ ይሁኑ።
9የእስራኤል ቤት ሆይ፤ *በእግዚአብሔር ታመኑ*፤
*ረዳታቸውና ጋሻቸው እርሱ ነው*።
10የአሮን ቤት ሆይ፤ *በእግዚአብሔር ታመኑ*፤
*ረዳታቸውና ጋሻቸው እርሱ ነው*።
11እናንተ *እግዚአብሔርን* የምትፈሩ ሆይ፤
*በእግዚአብሔር ታመኑ*፤
*ረዳታቸውና ጋሻቸው እርሱ ነው*።
12*እግዚአብሔር* ያስበናል፤ ይባርከናልም፤
እርሱ የእስራኤልን ቤት ይባርካል፤
የአሮንንም ቤት ይባርካል።
13*እግዚአብሔርን* የሚፈሩትን ሁሉ፣
ትልቁንም ትንሹንም ይባርካል።
14*እግዚአብሔር* እናንተንና ልጆቻችሁን፣
በባርኮቱ ያብዛችሁ።
15ሰማይንና ምድርን በፈጠረ፣
*በእግዚአብሔር* የተባረካችሁ ሁኑ።
16ሰማየ ሰማያት *የእግዚአብሔር* ናቸው፤
ምድርን ግን ለሰው ልጆች ሰጣት።
17*እግዚአብሔርን* የሚያመሰግኑት
የሞቱት አይደሉም፤
ወደ ዝምታው ዓለም የሚወርዱም
አይደሉም።
18ከአሁን ጀምሮ እስከ ዘላለም፣
*እግዚአብሔርን* የምንባርክ እኛ ነን።
*እግዚአብሔር* ይመስገን።[ሠ]

## መዝሙር 116

### ምስጋና

1የልመናዬን ድምፅ ሰምቶአልና፣
*እግዚአብሔርን* ወደድሁት።
2ጆሮውን ወደ እኔ አዘንብሎአልና፣
በሕይወት ዘመኔ ሁሉ ወደ እርሱ
እጣራለሁ።
3የሞት ወጥመድ ያዘኝ፤
የሲኦልም[የ] ጣር አገኘኝ፤
ጭንቅና ሐዘን አሸነፈኝ።
4እኔም *የእግዚአብሔርን* ስም ጠራሁ፤
“*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ነፍሴን ታድናት
ዘንድ እለምንሃለሁ” አልሁ።
5*እግዚአብሔር* ቸርና ጻድቅ ነው፤
አምላካችን መሓሪ ነው።
6*እግዚአብሔር* ገሮችን ይጠብቃል፤
እጅግ ተቸግሬ ሳለሁ አዳነኝ።
7ነፍሴ ሆይ፤ ወደ ዕረፍትሽ ተመለሺ፤
*እግዚአብሔር* መልካም አድርጎልሻልና፤
8አንተ ነፍሴን ከሞት፣
ዐይኔን ከእንባ፣
እግሮቼን ከመሰናከል አድነሃልና።
9እኔም በሕያዋን ምድር፣
*በእግዚአብሔር* ፊት እመላለሳለሁ።
10“እጅግ ተጨንቄአለሁ” ባልሁበት ጊዜ
እንኳ፣[ደ]
እምነቴን ጠብቄአለሁ።
11ግራ በተጋባሁ ጊዜ፣
“ሰው ሁሉ ሐሰተኛ ነው” አልሁ።
12ስለ ዋለልኝ ውለታ ሁሉ፣
*ለእግዚአብሔር* ምን ልክፈለው?
13የመዳንን ጽዋ አነሣለሁ፤
*የእግዚአብሔርንም* ስም እጠራለሁ።
14በሕዝቡ ሁሉ ፊት፣
ስእለቴን *ለእግዚአብሔር* እፈጽማለሁ።
15የቅዱሳኑ ሞት፣
*በእግዚአብሔር* ፊት የተከበረ ነው።
16*እግዚአብሔር* ሆይ፤ እኔ በእውነት
ባሪያህ ነኝ፤
እኔ የሴት ባሪያህ[ጀ] ልጅ፣ ባሪያህ ነኝ፣
ከእስራቴም ፈታኸኝ።
17ለአንተ የምስጋና መሥዋዕት አቀርባለሁ፤
*የእግዚአብሔርንም* ስም እጠራለሁ።
18በሕዝቡ ሁሉ ፊት፣
ስእለቴን *ለእግዚአብሔር* እፈጽማለሁ፤
19ኢየሩሳሌም ሆይ፤ ይህን በመካከልሽ፣
*በእግዚአብሔር* ቤት አደባባይ አደርጋለሁ።
*ሃሌ ሉያ*።[ገ]

## መዝሙር 117

### የምስጋና ጥሪ

1አሕዛብ ሁላችሁ፤ *እግዚአብሔርን*

115፥2 መዝ42፥3
115፥3 ዕዝ5፥11፤ ነህ1፥4፤መዝ103፥19፤ 135፥6፤136፥26፤ ማቴ6፥9
115፥4 2ነገ19፥18 ፤2ዜና32፥19፤ኤር 10፥3-5፤ሐሥ19፥26፤ ራእ9፥20
115፥5 ኤር10፥5
115፥9 መዝ37፥3፤ 62፥8
115፥10 ዘፀ30፥30፤ መዝ118፥3
115፥11 መዝ22፥23 ፤103፥11፤118፥4
115፥12 ዘፍ12፥2፤ 1ዜና16፥15
115፥13 መዝ112፥1
115፥14 ዘዳ1፥11
115፥15 ዘፍ1፥1፤ ሐሥ14፥15፤ራእ10፥6
115፥16 ዘፍ1፥28፤ መዝ8፥6-8፤89፥11
115፥17 መዝ88፥ 10-12
115፥18 መዝ28፥6 ፤33፥2፤103፥1፤ 111፥1፤113፥2
116፥1 መዝ6፥9፤ 18፥1፤28፥2፤31፥22፤40፥1
116፥2 መዝ5፥1
116፥3 2ሳሙ22፥6 ፤መዝ18፥4-5
116፥4 መዝ80፥2፡ 18፤118፥5
116፥5 ዘፀ9፥27፤ 22፥27፤2ዜና12፥6፤ ዕዝ9፥15፤መዝ86፥15
116፥6 መዝ18፥3፤ 22፥5፤79፥8፤107፥13
116፥7 መዝ13፥6፤ 46፥10፤62፥1፤106፥1፤ 131፥2፤142፥7፤ ማቴ11፥29
116፥8 መዝ86፥13
116፥9 ዘፍ5፥22፤ኢዮ 28፥13፤መዝ27፥13፤56፥13፤89፥15፤ኢሳ 38፥11፤ኤር11፥19
116፥10 መዝ9፥18 ፤72፥2፤107፥17፤119፥ 67፡71፡75፤2ቆሮ4፥13
116፥11 ኤር9፥3-5 ፤ሆሴ7፥13፤ሚክ6፥12፤ ሮሜ3፥4
116፥12 መዝ103፥2 ፤106፥1
116፥13 መዝ105፥1
116፥14 ዘኍ30፥2፤ መዝ66፥13
116፥15 ዘኍ23፥10 ፤መዝ72፥14
116፥16 ኢዮ12፥18 ፤መዝ86፥16፤119፥ 125፤143፥12
116፥17 ዘሌ7፥12 ፤ዕዝ1፥4
116፥18 ቆ14፤ ዘሌ22፥18 116፥19 መዝ92፥13፤96፥8፤100፥4፤102፥21፤ 135፥2 117፥1 መዝ22፥23፤103፥2፤ሮሜ15፥11

[ሠ]18 ዕብራይስጡ *ሃሌ ሉያ* ይላል።
[የ]3 ዕብራይስጡ *ሲኦል* ይላል።
[ደ]10 ወይም *ያኔ እንኳን* [ጀ]16 *ታማኝ አገልጋይህ* ወይም *ታማኝ ልጅህ*
[ገ]19 አንዳንዶች *እግዚአብሔር ይመስገን* ይላሉ።

አመስግኑት፤
ሕዝቦችም ሁሉ፤ በምስጋና ከፍ ከፍ
አድርጉት፤
2 እርሱ ለእኛ ያሳየው ምሕረት ታላቅ
ነውና፤
የእግዚአብሔርም ታማኝነት ጸንቶ
ይኖራል።
ሃሌ ሉያ።[ጠ]

## መዝሙር 118

### ለዳስ በዓል የቀረበ የጕዞ መዝሙር

1 *እግዚአብሔር* ቸር ነውና አመስግኑት፤
ምሕረቱም ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች።
2 የእስራኤል ሕዝብ፣
"ምሕረቱ ለዘላለም ነው" ይበል።
3 የአሮን ቤት፣
"ምሕረቱ ለዘላለም ነው" ይበል።
4 *እግዚአብሔርን* የሚፈሩ ሁሉ፣
"ምሕረቱ ለዘላለም ነው" ይበሉ።
5 በተጨነቅሁ ጊዜ *እግዚአብሔርን* ጠራሁት፤
*እግዚአብሔርም* መለሰልኝ፤ ከመጠ
በብም አወጣኝ።
6 *እግዚአብሔር* ከእኔ ጋር ነው፤ አልፈራም፤
ሰው ምን ሊያደርገኝ ይችላል?
7 ይረዳኝ ዘንድ *እግዚአብሔር* ከእኔ ጋር
ነው፤
የጠላቶቼንም ውድቀት አያለሁ።
8 ሰውን መከታ ከማድረግ ይልቅ፣
በ*እግዚአብሔር* መታመን ይሻላል።
9 በገዦች ተስፋ ከማድረግ ይልቅ፣
በ*እግዚአብሔር* መታመን ይሻላል።
10 ሕዝቦች ሁሉ ከበቡኝ፤
ነገር ግን *በእግዚአብሔር* ስም
አስወግዳቸዋለሁ።
11 መክበቡንስ በየአቅጣጫው ከበቡኝ፤
ነገር ግን *በእግዚአብሔር* ስም
አስወገዳቸዋለሁ።
12 እንደ ንብ መንጋ ከበቡኝ፤
ነገር ግን እንደሚነድ እሾኽ ከሰሙ፤
በእርግጥም *በእግዚአብሔር* ስም
አስወግዳቸዋለሁ።
13 ተገፍትሬ ልወድቅ ተንገደገድሁ፤
*እግዚአብሔር* ግን ረዳኝ።
14 *እግዚአብሔር* ብርታቴና ዝማሬዬ ነው፤
አዳኝ ሆነልኝ።
15 በጻድቃን ድንኳን የእልልታና የሆታ
ድምፅ፣
እንዲህ እያለ ያስተጋባል፤
"*የእግዚአብሔር* ቀኝ እጅ ብርቱ ሥራ
ሠራች፤
16 *የእግዚአብሔር* ቀኝ እጅ ከፍ ከፍ
አለች፤
*የእግዚአብሔር* ቀኝ እጅ ብርቱ ሥራ
ሠራች።
17 ተርፌ በሕይወት እኖራለሁ እንጂ
አልሞትም፤
*የእግዚአብሔርንም* ሥራ ገና እናገራለሁ።
18 *መገሠጹን እግዚአብሔር* እጅግ
ገሥጾኛል፤
ነገር ግን ለሞት አሳልፎ አልሰጠኝም።
19 የጽድቅን ደጆች ክፈቱልኝ፤
በዚያ ገብቼ *እግዚአብሔርን*
አመሰግናለሁ።
20 ይህች *የእግዚአብሔር* ደጅ ናት፤
ጻድቃን በእርሱ በኩል ይገባሉ።
21 ሰምተህ መልሰህልኛልና፣
አዳኝም ሆነህልኛልና አመሰግንሃለሁ።
22 ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣
እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ።
23 *እግዚአብሔር* ይህን አደረገ፤
ለዐይናችንም ድንቅ ናት።
24 *እግዚአብሔር* የሠራት ቀን ይህች ናት፤
በእርሷ ሐሤት እናድርግ፤ ደስም
ይበለን።
25 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ እባክህ አድነን፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ እባክህ አሳካልን።
26 *በእግዚአብሔር* ስም የሚመጣ ቡሩክ
ነው።
*ከእግዚአብሔር* ቤት ባረክናችሁ።
27 *እግዚአብሔር* አምላክ ነው፤
ብርሃኑንም በላያችን አበራ፤
እስከ መሠዊያው[ጨ] ቀንዶች ድረስ
በመውጣት፣
ዝንጣፊ ይዛችሁ በዓሉን ከሚያከብሩት
ጋር ተቀላቀሉ።
28 አንተ አምላኬ ነህ፤ አመሰግንሃለሁ፤
አንተ አምላኬ ነህ፤ ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ።
29 ቸር ነውና፣ *እግዚአብሔርን* አመስግኑ፤
ምሕረቱም ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች።

## መዝሙር 119[ጸ]

### ውዳሴ ለሕገ እግዚአብሔር

*ጰአሌፍ*

1 *መንገዳቸው ነቀፋ የሌለበት፣*

117፥2 መዝ17፥7፤ 103፥11፤119፥90፤14 6፥6
118፥1 1ዜና16፥8፤ 2ዜና5፥13፤7፥3፤ዕዝ 3፥11
118፥2 መዝ106፥1 ፤115፥9፤136፥1-26
118፥3 ዘፀ30፥30፤ መዝ115፥10
118፥4 መዝ115፥11
118፥5 ቍ21፤መዝ 18፥6፤31፥7፤34፥4፤77፥ 2፤86፥7፤116፥1፤ 120፥1፤138፥3
118፥6 ዘዳ31፥6፤ መዝ56፥4፤ዕብ13፥5
118፥7 ዘዳ33፥29፤ መዝ54፥7፤ዕብ13፥6
118፥8 2ዜና32፥7- 8፤መዝ2፥12፤5፥11፤ 9፥9፤37፥3፤40፥4፤ 108፥12፤ኢሳ2፥22፤ 25፥4፤57፥13
118፥9 መዝ146፥3
118፥10 መዝ37፥9
118፥11 መዝ3፥6፤ 88፥17
118፥12 ዘዳ1፥44፤ መዝ37፥9፤58፥9
118፥13 ቍ7፤2ዜና 18፥31፤መዝ86፥17
118፥14 ዘፀ15፥2፤ መዝ62፥2
118፥15 ዘፀ15፥6፤ ኢዮ8፥21፤መዝ 89፥13፤106፥5፤ 108፥6፤ሉቃ1፥51
118፥17 ዘዳ32፥3፤ መዝ64፥9፤71፥16፤ 73፥28፤ዕን1፥12
118፥18 መዝ86፥13 ፤ኤር31፥18፤1ቆሮ11፥ 32፤ዕብ12፥5
118፥19 መዝ24፥7፤ 100፥4
118፥20 መዝ15፥1- 2፤24፥3-4፤122፥1-2፤ ራእ22፥14
118፥21 ቍ5፤መዝ 27፥1
118፥22 ኢሳ8፥14፤ 17፥10፤19፥13፤28፥ 16፤ዘካ4፥7፤10፥4፤ ማቴ21፥42፤ማር 12፥10፤ሉቃ20፥17፤ሐ ሥ4፥11፤1ጴጥ2፥7
118፥23 ማቴ21፥42 ፤ማር12፥11
118፥24 መዝ70፥4
118፥25 መዝ28፥9 ፤116፥4
118፥26 መዝ129፥8 ፤ማቴ11፥3፤21፥9፤ 23፥39፤ማር11፥9፤ ሉቃ 13፥35፤19፥38፤ ዮሐ12፥13
118፥27 ዘፀ27፥2፤ ዘሌ23፥40፤1ነገ18፥ 21፤መዝ27፥1፤ኢሳ 58፥10፤60፥1፤19፥20፤ ሚል4፥2፤1ጴጥ2፥9
118፥28 ዘፍ28፥21 ፤ዘፀ15፥2፤መዝ16፥2 ፤63፥1፤ኢሳ25፥1
119፥1 ዘፍ17፥1፤ ዘዳ18፥13፤መዝ1፥2፤128፥1፤ምሳ11፥20

[ጠ] 2 አንዳንዶች *እግዚአብሔር ይመስገን* ይላሉ።
[ጨ] 27 ወይም *የክብረ በዓልን መሥዋዕት በገመድ ማሰር* ወይም *መውሰድ*
[ጸ] 119 የዚህ መዝሙር የግጥም ስንኞች መነሻ ወይም መነሻና መድረሻ ሆህያት ቀ‍ልቀ‍ል ሲነበቡ ትርጒም አዘል ናቸው። እያንዳንዱ ስንኝ ተመሳሳይ በሆነ በዕብራይስጥ ፊደል ይጀምራል።

*በእግዚአብሔርም ሕግ የሚሄዱ የተባረኩ
ናቸው፡፡*
2ምስክርነቱን የሚጠብቁ፣
በፍጹምም ልብ የሚሹት የተባረኩ
ናቸው፤
3ዐመፅን አያደርጉም፤
ነገር ግን በመንገዱ ይሄዳሉ፡፡
4ጠንቅቀን እንጠብቃት ዘንድ፣
አንተ ሥርዐትን አዘሃል፡፡
5ሥርዐትህን እጠብቅ ዘንድ፣
ምነው መንገዴ ጽኑ በሆነልኝ ኖሮ!
6ወደ ትእዛዛትህ ስመለከት፣
በዚያን ጊዜ አላፍርም፡፡
7የጽድቅ ፍርድህን ስማር፣
በቅን ልብ ምስጋና አቀርብልሃለሁ፡፡
8ሥርዐትህን እጠብቃለሁ፤
ፈጽመህ አትተወኝ፡፡

*ጋ ቤት*

9ጕልማሳ መንገዱን እንዴት ያነጻል?
በቃልህ መሠረት በመኖር ነው፡፡
10በሙሉ ልቤ ፈለግሁህ፤
ከትእዛዛትህ ፈቀቅ እንዳልል አድርገኝ፡፡
11አንተን እንዳልበድል፣
ቃልህን በልቤ ሰወርሁ፡፡
12*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ ቡሩክ ነህ፤
ሥርዐትህን አስተምረኝ፡፡
13ከአንደበትህ የሚወጣውን ደንብ ሁሉ፣
በከንፈሬ እናገራለሁ፡፡
14ሰው በሀብቱ ብዛት ደስ እንደሚለው፣
ምስክርነትህን በመከተል ደስ ይለኛል፡፡
15ድንጋጌህን አሰላስላለሁ፤
ልቤን በመንገድህ ላይ ጥያለሁ፡፡
16በሥርዐትህ ደስ ይለኛል፤
ቃልህንም አልዘነጋም፡፡

*ጋ ጋሜል*

17ሕያው እንድሆን፣ ቃልህንም
እንድጠብቅ፣
ለአገልጋይህ መልካም አድርግ፡፡
18ከሕግህ ድንቅ ነገርን እንዳይ፣
ዐይኖቼን ክፈት፡፡
19እኔ በምድር ላይ መጻተኛ ነኝ፤
ትእዛዛትህን ከእኔ አትሰውር፡፡
20ዘወትር ደንብህን በመናፈቅ፣
ነፍሴ እጅግ ዛለች፡፡
21ከትእዛዛትህ የሳቱትን፣
እብሪተኞችንና ርጉሞችን ትገሥጻለህ፡፡
22ምስክርነትህን ጠብቄአለሁና፣
ስድብንና ንቀትን ከእኔ አርቅ፡፡
23ገዦች ተቀምጠው ቢዶልቱብኝ እንኳ፣
አገልጋይህ ሥርዐትህን ያሰላስላል፡፡
24ምስክርነትህ ለእኔ ደስታዬ ነው፤
መካሪዬም ነው፡፡

*ገዳሌጥ*

25ነፍሴ ከዐፈር ጋር ተጣበቀች፤
እንደ ቃልህ መልሰህ ሕያው አድርገኝ፡፡
26ስለ መንገዴ ገልጬ ነገርሁህ፤ አንተም
መለስህልኝ፤
ሥርዐትህን አስተምረኝ፡፡
27የድንጋጌህን መንገድ እንዳስተውል
አድርገኝ፤
እኔም ድንቅ ሥራህን አሰላስላለሁ፡፡
28ነፍሴ በሐዘን ተዝለፈለፈች፤
እንደ ቃልህ አበርታኝ፡፡
29የሽንገላን መንገድ ከእኔ አርቅ፤
ሕግህን በጸጋህ ስጠኝ፡፡
30የእውነትን መንገድ መርጫለሁ፤
ሕግህንም ፊት ለፊቴ አድርጌአለሁ፡፡
31*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ከምስክርነትህ ጋር
ተጣብቄአለሁ፤
አሳልፈህ ለውርደት አትስጠኝ፡፡
32ልቤን አስፍተህልኛልና፣
በትእዛዛትህ መንገድ እሮጣለሁ፡፡

*ገ ሄ*

33*እግዚአብሔር* ሆይ፤ የሥርዐትህን
መንገድ አስተምረኝ፤
እኔም እስከ መጨረሻው እጠብቀዋለሁ፡፡
34ሕግህን እንድጠብቅ፣ በፍጹም ልቤም
እንድታዘዘው፣
ማስተዋልን ስጠኝ፡፡
35በእርሷ ደስ ይለኛልና፣
በትእዛዝህ መንገድ ምራኝ፡፡
36ከራስ ጥቅም ይልቅ፣
ልቤን ወደ ምስክርነትህ አዘንብል፡፡
37ከንቱ ነገር ከማየት ዐይኖቼን መልስ፤
በራስህ መንገድ* እንደ ገና ሕያው
አድርገኝ፡፡
38ትፈራ ዘንድ፣
ለአገልጋይህ የገባኸውን ቃል ፈጽም፡፡
39የምፈራውን መዋረድ ከእኔ አርቅ፤
ደንብህ መልካም ነውና፡፡
40እነሆ፤ ድንጋጌህን ናፈቅሁ፤
በጽድቅህ ሕያው አድርገኝ፡፡

*ነ ዋው*

41*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ምሕረትህ ወደ እኔ
ይምጣ፤
ማዳንህም እንደ ቃልህ ይላክልኝ፡፡
42በቃልህ ታምኛለሁና፣
ለሚሰድቡኝ መልስ እሰጣለሁ፡፡
43ሕግህን ተስፋ አድርጌአለሁና፣

**119፥2** ቊ146፤ዘዳ 10፥12፤መዝ40፥16፤ 99፥7፤112፥1፤1ዜና 16፥11፤መዝ40፥16፤ 99፥7፤112፥1፤ኢሳ 56፥2
**119፥3** መዝ59፥4፤ 128፥1፤ኤር6፥16፤7፥2 3፤1ዮሐ3፥9፤5፥18
**119፥4** ቊ56፤ዘዳ 6፥17፤መዝ103፥18
**119፥5** ዘሌ19፥37
**119፥6** ቊ46፡80፡ 117
**119፥7** ዘዳ4፥8
**119፥8** መዝ38፥21
**119፥9** ቊ65፡169 ፤መዝ39፥1
**119፥10** ቊ21፡118 ፤መዝ9፥1
**119፥11** ቊ133፡ 165፤ዘዳ6፥6፤ኢዮ 22፥22፤መዝ18፥22-23፤ 19፥13፤ምሳ3፥23፤ ኢሳ 63፥13
**119፥12** ዘፀ18፥20፤ መዝ28፥6፤143፥8፡10
**119፥13** ቊ72
**119፥14** ቊ111
**119፥15** ቊ97፡ 148፤መዝ1፥2
**119፥16** መዝ112፥1
**119፥17** ቊ67፤መዝ 13፥6፤103፥20፤116፥7
**119፥19** ዘፍ23፥4፤ ዕብ11፥13
**119፥20** ቊ131፤ መዝ42፥2፤63፥1፤ 84፥2፤ኢሳ26፥9
**119፥21** ቊ10፡51 ፤ዘዳ27፥26፤ኢዮ30፥1 ፤መዝ5፥5፤ኤር20፥7 ፤50፥32፤ዳን4፥37፤ ሚል3፥15
**119፥22** ቊ2፤መዝ 39፥8
**119፥25** ቊ9፡50፡ 107፤መዝ44፥25፤ 143፥11
**119፥26** መዝ25፥4 ፤27፥11፤86፥11
**119፥27** መዝ105፥2 ፤145፥5
**119፥28** ቊ9፤መዝ 6፥7፤18፥1፤116፥3፤ ኢሳ40፥29፤41፥10፤ 51፥11፤ኤር45፥3
**119፥29** ዘኍ6፥25፤ መዝ26፥4
**119፥30** ኢሱ24፥22 ፤መዝ26፥3፤108፥1
**119፥31** ዘዳ10፥20
**119፥33** ቊ12
**119፥34** ቊ27፡69፡ 73፡144፡169፤ዘዳ6፥25 ፤ኢዮ32፥8፤ምሳ2፥6፤ ዳን2፥21፤ያዕ1፥5
**119፥35** ቊ32፤መዝ 1፥2፤25፥4-5
**119፥36** ኢሱ24፥23 ፤ሕዝ33፥31

**119፥37** ቊ9፡25፤መዝ71፥20 **119፥38** ዘኍ23፥19 **119፥39** ቊ22 መዝ69፥9፤89፥51፤ኢሳ25፥8፤51፥7፤54፥4 **119፥40** ቊ20፡25፡ 149፡154 **119፥41** ቊ76፡116፡154፡170፤መዝ6፥4 **119፥42** መዝ 42፥10፤ምሳ27፥11 **119፥43** ቊ74፡81፡114፡147፤1ነገ17፥24

*37 *አንዳንድ ትርጒሞች እንደ ቃልህ ይላሉ፡፡*

የእውነትን ቃል ከአፌ ፈጽመህ አታርቅ።
44ከዘላለም እስከ ዘላለም፣
ሕግህን ዘወትር እጠብቃለሁ።
45ሥርዐትህን እሻለሁና፣
እንደ ልቤ ወዲያ ወዲህ እመላለሳለሁ።
46ምስክርነትህን በነገሥታት ፊት እናገራለሁ፤
ይህን በማድረግም ዕፍረት አይሰማኝም።
47እኔ እወድዋለሁና፣
በትእዛዝህ ደስ ይለኛል።
48እጆቼን ወደምወዳቸው[θ] ትእዛዛትህ አነሣለሁ፤
ሥርዐትህንም አሰላስላለሁ።

፯ ዛይ

49ለአገልጋይህ የገባኸውን ቃል አስብ፤
በዚያ ተስፋ ሰጥተኸኛልና።
50ቃልህ ሕያው ያደርገኛልና፣
ይህች በመከራዬ መጽናኛዬ ናት።
51እብሪተኞች እጅግ ተሣለቁብኝ፤
እኔ ግን ከሕግህ ንቅንቅ አላልም።
52እግዚአብሔር ሆይ፤ ከጥንት የነበረውን ድንጋጌህን አሰብሁ፤
በዚህም ተጽናናሁ።
53ሕግህን ከተዉ ክፉዎች የተነሣ፣
ቍጣ ወረረኝ።
54በእንግድነቴ አገር፣
ሥርዐትህ መዝሙሬ ናት።
55እግዚአብሔር ሆይ፤ ስምህን በሌሊት አስባለሁ፤
ሕግህንም እጠብቃለሁ።
56ሥርዐትህን እከተላለሁ፤
ይህችም ተግባሬ ሆነች።

፰ ሔት

57እግዚአብሔር ዕድል ፈንታዬ ነው፤
ቃልህን ለመታዘዝ ቈርጫለሁ።
58በፍጹም ልቤ ፊትህን ፈለግሁ፤
እንደ ቃልህ ቸርነትህን አሳየኝ።
59መንገዴን ቃኘሁ፤
አካሄዴንም ወደ ምስክርህ አቀናሁ።
60ትእዛዝህን ለመጠበቅ፣
ቸኰልሁ፤ አልዘገየሁምም።
61የክፉዎች ገመድ ተተበተበብኝ፤
እኔ ግን ሕግህን አልረሳሁም።
62ስለ ጻድቅ ሥርዐትህ፣
በእኩለ ሌሊት ላመሰግንህ እነሣለሁ።
63እኔ ለሚፈሩህ ሁሉ፣
ሥርዐትህንም ለሚጠብቁ ባልንጀራ ነኝ።
64እግዚአብሔር ሆይ፤ ምድር በምሕረትህ ተሞላች፤
ሥርዐትህን አስተምረኝ።

፱ ጤት

65እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ ቃልህ፣
ለአገልጋይህ በጎ ውለሃል።
66በትእዛዛትህ አምናለሁና፣
በጎ ማስተዋልንና ዕውቀትን አስተምረኝ።
67እንዲያው ሳይቸግረኝ መንገድ ስቼ ሄድሁ፤
አሁን ግን ቃልህን እጠብቃለሁ።
68አንተ መልካም ነህ፤ የምታደርገው መልካም ነው፤
እንግዲህ ሥርዐትህን አስተምረኝ።
69እብሪተኞች ስሜን በሐሰት አጠፉ፤
እኔ ግን ትእዛዝህን በፍጹም ልብ እጠብቃለሁ።
70ልባቸው የሰባና የደነደነ ነው፤
እኔ ግን በሕግህ ደስ ይለኛል።
71ሥርዐትህን እማር ዘንድ፣
በመከራ ውስጥ ማለፌ መልካም ሆነልኝ።
72ከአእላፋት ብርና ወርቅ ይልቅ፣
ከአፍህ የሚወጣው ሕግ ይሻለኛል።

፲ ዮድ

73እጆችህ ሠሩኝ፤ አበጃጁኝም፤
ትእዛዛትህን እንድማር ማስተዋልን ስጠኝ።
74ቃልህን ተስፋ አድርጌአለሁና፣
የሚፈሩህ እኔን አይተው ደስ ይበላቸው።
75እግዚአብሔር ሆይ፤ ፍርድህ የጽድቅ ፍርድ፣
ያስጨነቅኸኝም በታማኝነት እንደ ሆነ ዐወቅሁ።
76ለአገልጋይህ በገባኸው ቃል መሠረት፣
ምሕረትህ ለመጽናናት ትሁነኝ።
77ሕግህ ደስታዬ ነውና፣
በሕይወት እኖር ዘንድ ቸርነትህ ትምጣልኝ።
78እብሪተኞች ያለ ምክንያት በደል አድርሰውብኛልና ይፈሩ፤
እኔ ግን ትእዛዛትህን አሰላስላለሁ።
79አንተን የሚፈሩህ፣
ምስክርነትህንም የሚያውቁ ወደ እኔ ይመለሱ።
80እኔ እንዳላፍር፣
ልቤ በሥርዐትህ ፍጹም ይሁን።

፲፩ ካፍ

81ነፍሴ ማዳንህን እጅግ ናፈቀች፤
ቃልህንም ተስፋ አደርጋለሁ።

119÷44 ቍ33፡34፡55፤ዘጸ6÷25
115÷45ቍ94፡155
119÷46 ቍ6፤ማቴ 10÷18፤ሐሥ26÷1-2
119÷47 ቍ77፡97፡127፡143፡159፡163፡165፤መዝ112÷1
119÷48 ዘፍ24÷63
119÷49 ቍ9፡43
119÷50 ቍ25
119÷51 ቍ21፤ ኢዮ 16÷10፤17÷2፤23÷11
119÷52 መዝ103÷18
119÷53 ዘፀ32÷19፤33÷4፤መዝ89÷30
119÷54 ቍ172፤ መዝ101÷1፤138÷5
119÷55 ቍ44፡62፡72፤መዝ1÷2፤42÷8፤63÷6፤77÷2፤ኢሳ 26÷9፤ሐሥ16÷25
119÷56 ቍ4፡100፡134፡168፤ዘኍ15÷40
119÷57 ቍ17፡67፡101፤ዘዳ32÷9፤ኤር 51÷19፤ሰቆ3÷24
119÷58 ቍ41፤ዘፍ 43÷29፤ዘዳ4÷29፤1ዜና 16÷11፤ዕዝ9÷8፤መዝ 34÷4
119÷59ኢሱ24÷14-15፤መዝ39÷1
119÷60 ቍ115
119÷61 ቍ83፡109፡153፡176
119÷62 ቍ7፡55፤ሐሥ16÷25
119÷63 ቍ56፤ መዝ15÷4፤101÷6-7፤103÷11፤111÷10
119÷64 ቍ12፡108፤መዝ33÷5
119÷65 ቍ9፡17፤ መዝ125÷4፤50÷2፤59÷1፤ሚክ2÷7
119÷66 መዝ51÷6
119÷67 ቍ17፤ መዝ95÷10፤116÷10፤ ኤር8÷4
119÷68 ዘፀ18÷20፤ መዝ100÷5፤106÷1፤107÷1፤135÷3
119÷69 ኢዮ13÷4፤ መዝ109÷2
119÷70መዝ17÷10 ኢሳ29÷13፤ሐሥ28÷27
119÷71 ቍ67፡75
119÷72 ኢዮ28÷17፤መዝ19÷10
119÷73 ዘፍ1÷27፤ ኢዮ4÷17፤10÷8፤መዝ 138÷8፤139÷13-16
119÷74 ቍ9፤መዝ 34÷2፤130÷5
119÷75 ቍ7፡138፡172፤ዕብ12÷5-11
119÷76 ቍ41፤ መዝ6÷4 119÷77 ቍ47፤መዝ90÷13፤103÷13
119÷78 ቍ51፡ 86፡161፤መዝ35÷19፤ኤር50÷32
119÷79 ቍ27፡125 119÷80 ቍ1፡6፤ዘፍ26÷5፤ 1ነገ8÷61 119÷81 ቍ20፡43፡ 123፤መዝ84÷2

[θ]48 *ወይም ለምወዳቸው*

82“መቼ ታጽናናኛለህ?” እያልሁ፣
ዐይኖቼ ቃልህን በመጠባበቅ ደከሙ።
83ጢስ የጠጣ የወይን አቍማዳ
ብመስልም፣
ሥርዐትህን አልረሳሁም።
84የባሪያህ ዕድሜ ስንት ቢሆን ነው?
ታዲያ፣ በሚያሳድዱኝ ላይ
የምትፈርደው መቼ ይሆን?
85በሕግህ መሠረት የማይሄዱ፣
እብሪተኞች ጒድጓድ ቈፈሩልኝ።
86ትእዛዛትህ ሁሉ አስተማማኝ ናቸው፤
ሰዎች ያለ ምክንያት አሳደውኛልና
ርዳኝ።
87ከምድር ላይ ሊያስወግዱኝ ጥቂት
ቀራቸው፤
እኔ ግን ትእዛዛትህን አልተውሁም።
88እንደ ምሕረትህ መልሰህ ሕያው
አድርገኝ፤
እኔም የአፍህን ምስክርነት
እጠብቃለሁ።

ל ላሜድ

89እግዚአብሔር ሆይ፤ ቃልህ በሰማይ፣
ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
90ታማኝነትህ ከትውልድ እስከ ትውልድ
ሁሉ ይኖራል፤
ምድርን መሠረትሃት፤ እርሷም ጸንታ
ትኖራለች።
91ሁሉም አገልጋይህ ነውና፣
በሕግህ መሠረት እስከ ዛሬ ድረስ
ጸንተው ይኖራሉ።
92ሕግህ ደስታዬ ባይሆን ኖሮ፣
በመከራዬ ወቅት በጠፋሁ ነበር።
93በእርሱ ሕያው አድርገኸኛልና፣
ትእዛዝህን ከቶ አልረሳም።
94እኔ የአንተ ነኝ፤ እባክህ አድነኝ፤
ሕግህንም ፈልጌአለሁና።
95ክፉዎች ሊያጠፉኝ አድብተዋል፤
እኔ ግን ምስክርነትህን አሰላስላለሁ።
96ለፍጹምነት ሁሉ ዳርቻ እንዳለው አየሁ፤
ትእዛዝህ ግን እጅግ ሰፊ ነው።

מ ሜም

97አቤቱ፤ ሕግህን ምንኛ ወደድሁ!
ቀኑን ሙሉ አሰላስለዋለሁ።
98ትእዛዛትህ ምን ጊዜም ስለማይለዩኝ፣
ከጠላቶቼ ይልቅ አስተዋይ አደረጉኝ።
99ምስክርነትህን አሰላስላለሁና፣
ከአስተማሪዎቼ ሁሉ የላቀ አስተዋይ
ልብ አገኘሁ።
100መመሪያህን ተከትዬ እሄዳለሁና፣
ከሽማግሌዎች ይልቅ አስተዋይ ሆንሁ።
101ቃልህን እጠብቅ ዘንድ፣
እግሬን ከክፉ መንገድ ሁሉ ከለከልሁ።
102አንተው ራስህ አስተምረኸኛልና፣
ከድንጋጌህ ዘወር አላልሁም።
103ቃልህ ለምላሴ ምንኛ ጣፋጭ ነው!
ለአፌም ከማር ወለላ ይልቅ ጣዕም አለው።
104ከመመሪያህ ማስተዋልን አገኘሁ፤
ስለዚህ የሐሰትን መንገድ ሁሉ ጠላሁ።

נ ኖን

105ሕግህ ለእግሬ መብራት፣
ለመንገዴም ብርሃን ነው።
106የጽድቅ ሕግህን ለመጠበቅ፤
ምያለሁ፤ ይህንኑ አጸናለሁ።
107እጅግ ተቸግሬአለሁ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ ቃልህ
መልሰህ ሕያው አድርገኝ።
108እግዚአብሔር ሆይ፤ ፈቅጄ
ያቀረብሁትን የአፌን የምስጋና
መሥዋዕት ተቀበል፤
ሕግህንም አስተምረኝ።
109ነፍሴ ዘወትር አደጋ ላይ ናት፤
ሕግህን ግን አልረሳሁም።
110ክፉዎች ወጥመድ ዘረጉብኝ፤
እኔ ግን መመሪያህን አልተላለፍሁም።
111ምስክርነትህ የዘላለም ውርሴ ናት፤
ልቤ በዚህ ሐሤት ያደርጋልና።
112ትእዛዝህን ለዘላለም፣ እስከ ወዲያኛው
ለመፈጸም፣
ልቤን ወደዚያው አዘነበልሁ።

ס ሳምኬት

113መንታ ልብ ያላቸውን ጠላሁ፤
ሕግህን ግን ወደድሁ።
114አንተ መጠጊያዬና ጋሻዬ ነህ፤
ቃልህን በተስፋ እጠብቃለሁ።
115የአምላኬን ትእዛዛት እጠብቅ ዘንድ፣
እናንት ክፉ አድራጊዎች፣ ከእኔ ራቁ።
116እንደ ቃልህ ደግፈኝ፤ እኔም ሕያው
እሆናለሁ፤
ተስፋዬም መና ቀርቶ አልፈር።
117ያለ ሥጋት እቀመጥ ዘንድ ደግፈህ
ያዘኝ፤
ሥርዐትህንም ዘወትር እመለከታለሁ።
118መሰሪነታቸው በከንቱ ነውና፣
ከሥርዐትህ ውጭ የሚሄዱትን ሁሉ
ወዲያ አስወገድሃቸው።
119የምድርን ክፉዎች ሁሉ እንደ ጥራጊ
አስወገድሃቸው፤
ስለዚህ ምስክርህን ወደድሁ።

119፥82 ቍ41፡123፤ መዝ6፥7፤69፥3፤ ሰቆ2፥11
119፥83 ቍ61
119፥84 ቍ51፤መዝ 6፥3፤ኤር12፥3፤15፥15 ፤20፥11፤ራእ6፥10
119፥85 ቍ51፤ መዝ35፥7፤57፥6፤ኤር 18፥20፡22
119፥86 ቍ78፡138 ፤መዝ7፥1፤109፥26
119፥87 ቍ150፤ ኢሳ1፥4፡28፤58፥2፤ 59፥13
119፥88 ቍ2፡100፡ 124፡129፡134፡168፤ መዝ41፥2፤51፥1፤ 109፥26
119፥89 ቍ111፡ 144፤መዝ111፥8፤ኢሳ 51፥6፤ማቴ5፥18፤ 1ጴጥ1፥25
119፥90 ኢዮ8፥19፤ መዝ36፥5፤45፥17፤ 148፥6
119፥91 መዝ104፥ 2-4፤ኤር31፥35፤ 33፥25
119፥92 ቍ50፡67፤ መዝ37፥4፤112፥1
119፥93 ቍ83፤ መዝ103፥5
119፥94 ቍ45፡ 146፤መዝ54፥1፤116፥ 4፤ኤር17፥14፤31፥18፤ 42፥11
119፥95 ቍ99፤ መዝ69፥4
119፥96 መዝ19፥7
119፥97 ቍ15፡47
119፥98 ቍ130፤ ዘዳ4፥6፤መዝ19፥7፤ 2ጢሞ3፥15
119፥99 ቍ15
119፥100 ቍ56፤ ዘዳ6፥17
119፥101 ቍ57፤ ምሳ1፥15
119፥102 ዘዳ4፥5፤ 17፥20
119፥103 መዝ19፥ 10፤ምሳ24፥13-14
119፥104 ቍ128፤ መዝ111፥10
119፥105 ቍ130፤ ምሳ6፥23፤20፥27፤ 2ጴጥ1፥19
119፥106 ቍ7፤ ነህ10፥29
119፥107 ቍ25
119፥108 ቍ64፤ መዝ51፥15፤63፥5፤ 71፥8፤109፥30
119፥109 ቍ61፤ መሳ12፥3
119፥110 ቍ10፤ መዝ25፥15፤64፥5፤ ኢሳ8፥14፤አሞ3፥5
119፥111 ቍ14፡162
119፥112 ቍ33፤ መዝ108፥1
119፥113 ቍ47፤1ነገ18፥21፤ያዕ1፥8፤4፥8
119፥114 ቍ43፤ዘፍ15፥1፤መዝ18፥2
119፥115 መዝ6፥8
119፥116 ቍ41፤መዝ18፥35፤41፥3፤55፥22፤ኢሳ46፥4፤ሮሜ5፥5
119፥117 ቍ6፤መዝ34፥4፤ኢሳ41፥10፤46፥4
119፥118 ቍ10
119፥119 ቍ47፤ኢሳ1፥22፡25፤ሕዝ2፥18፡19

120 ሥጋዬ አንተን በመፍራት
ይንቀጠቀጣል፤
ፍርድህንም እፈራለሁ።

ע ዔ

121 ፍትሕና ጽድቅ ያለበትን ሠርቻለሁ፤
ለሚጨቍኑኝ አሳልፈህ አትስጠኝ።
122 ለባሪያህ በጎነት ዋስትና ሁን፤
እብሪተኛ እንዲጨቍነኝ
አትፍቀድላቸው።
123 ዐይኖቼ ማዳንህን፣
የጽድቅ ቃልህን በመጠባበቅ ደከሙ።
124 ለባሪያህ እንደ ምሕረትህ መጠን
አድርግ፤
ሥርዐትህንም አስተምረኝ።
125 እኔ ባሪያህ ነኝ፤
ምስክርነትህን ዐውቅ ዘንድ ማስተዋልን
ስጠኝ።
126 እግዚአብሔር ሆይ፤
ሕግህ እየተጣሰ ነውና፣
ጊዜው አንተ የምትሠራበት ነው።
127 ስለዚህ ከወርቅ፣ ከንጹሕ ወርቅ ይልቅ፣
ትእዛዛትህን ወደድሁ።
128 መመሪያህ ሙሉ በሙሉ ልክ ነው
አልሁ፤
ስለዚህ የሐሰትን መንገድ ሁሉ ጠላሁ።

פ ፌ

129 ምስክርነትህ ሁሉ ድንቅ ነው፤
ስለዚህ ነፍሴ ትጠብቀዋለች።
130 የቃልህ ትርጓሜ ያበራል፤
አላዋቂዎችንም አስተዋዮች ያደርጋል።
131 ትእዛዝህን ናፍቄአለሁና፣
አፌን ከፈትሁ አለከለክሁም።
132 ስምህን ለሚወዱ ማድረግ ልማድህ
እንደ ሆነ ሁሉ፣
ወደ እኔ ተመልሰህ፣ ምሕረት
አድርግልኝ።
133 አካሄዴን እንደ ቃልህ ቀና አድርግልኝ፤
ኀጢአትም በላዬ እንዲሠለጥን
አትፍቀድ።
134 ትእዛዝህን መጠበቅ እንድችል፣
ከሰዎች ጥቃት ታደገኝ።
135 በባሪያህ ላይ ፊትህን አብራ፤
ሥርዐትህንም አስተምረኝ።
136 ሕግህ ባለመከበሩ፤
እንባዬ እንደ ውሃ ይፈሳል።

צ ጻዴ

137 እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ጻድቅ ነህ፤
ፍርድህም ትክክል ነው።
138 ምስክርነትህን በጽድቅ አዘዝህ፤
እጅግ አስተማማኝም ነው።
139 ጠላቶቼ ቃልህን ዘንግተዋልና፣
ቅናት አሳረረኝ።
140 ቃልህ እጅግ የነጠረ ነው፤
ባሪያህም ወደደው።
141 እኔ ታናሽና የተናቅሁ ነኝ፤
ነገር ግን መመሪያህን አልዘነጋሁም።
142 ጽድቅህ ዘላለማዊ ጽድቅ ነው፤
ሕግህም እውነት ነው።
143 መከራና ሥቃይ ደርሶብኛል፤
ነገር ግን ትእዛዝህ ደስታዬ ነው።
144 ምስክርነትህ ለዘላለም የጽድቅ
ምስክርነት ነው፤
በሕይወት እኖር ዘንድ ማስተዋልን
ስጠኝ።

ק ቆፍ

145 እግዚአብሔር ሆይ፤ በፍጹም ልቤ
እጮኻለሁና መልስልኝ፤
ሥርዐትህንም እጠብቃለሁ።
146 ወደ አንተ እጣራለሁና አድነኝ፤
ምስክርነትህንም እጠብቃለሁ።
147 ትረዳኝ ዘንድ ጎሕ ሳይቀድ ተንሥቼ
እጮኻለሁ፤
ቃልህንም ተስፋ አደርጋለሁ።
148 ቃልህን አሰላስል ዘንድ፣
ዐይኔ ሌሊቱን ሙሉ ሳይከደን
ያድራል።
149 እንደ ቸርነትህ መጠን ድምፄን ስማ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ ሕግህ
መልሰህ ሕያው አድርገኝ።
150 ደባ የሚያውጠነጥኑ ወደ እኔ ቀርበዋል፤
ከሕግህ ግን የራቁ ናቸው።
151 እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ግን ቅርብ
ነህ፤
ትእዛዛትህም ሁሉ እውነት ናቸው።
152 ለዘላለም እንደ መሠረትሃቸው፣
ከጥንት ምስክርነትህ ተረድቻለሁ።

ר ሬስ

153 ሕግህን አልረሳሁምና፣
ሥቃዬን ተመልከት፤ ታደገኝም።
154 ተሟገትልኝ፤ አድነኝም፤
እንደ ቃልህም ሕያው አድርገኝ።
155 ሥርዐትህን ስለማይሹ፣
ድነት ከክፉዎች የራቀ ነው።
156 እግዚአብሔር ሆይ፤ ርኅራኄህ ታላቅ
ነው፤
እንደ ሕግህ ሕያው አድርገኝ።
157 የሚያሳድዱኝ ጠላቶቼ ብዙዎች ናቸው፤
እኔ ግን ከምስክርህ ዘወር አላልሁም።

119፥120 ኢሱ 24፥14፤ኢዮ4፥14፤ ኢሳ64፥2፤ኤር10፥7 ፤ዕን3፥2
119፥121 2ሳሙ 8፥15፤ኢዮ27፥6
119፥122 ቍ 21፡121፡134፤ኢዮ17፥3፤ መዝ106፥42
119፥123 ቍ81፡82 ፤ኢሳ38፥14
119፥124 ቍ12፡88 ፤መዝ25፥7
119፥125 ቍ79፤ መዝ116፥16
119፥126 ዘኍ15፥ 31
119፥127 ቍ47፤ ኢዮ3፥21፤መዝ19፥10
119፥128 ቍ104፡ 163፤መዝ19፥8፤31፥6 ፤ምሳ13፥5
119፥129 ቍ18፡ 22፡88
119፥130 ቍ105፤ መዝ19፥7
119፥131 ቍ20፤ መዝ42፥1 119፥132 2ሳሙ 24፥14፤መዝ5፥11፤6፥4፤ 9፥13፤2ሳሙ24፥14
119፥133 ቍ9፡11፤ ሮሜ6፥16
119፥134 ቍ56፡ 88፡122
119፥135 ቍ12፤ ዘኍ6፥25፤መዝ4፥6፤ 67፥1፤80፥3
119፥136 ቍ158፤ መዝ6፥6፤106፥25፤ ኤሳ22፥4፤42፥24፤ ኤር9፥1፡18፤13፥17፤ 14፥17፤ሰቆ1፥16፤ 34፥8፤ሕዝ9፥4
119፥137 ዘፀ9፥27 ፤ዕዝ9፥15፤ነህ9፥13
119፥138 ቍ75፡86 ፤መዝ19፥7
119፥139 መዝ69፥9 ፤ዮሐ2፥17
119፥140 ቍ47፤ ኢሱ23፥14፤ መዝ12፥6
119፥141 ቍ61፡ 134፤መዝ22፥6
119፥142 ቍ151፡ 160፤መዝ19፥7
119፥143 ቍ24፡47
119፥144 ቍ34
119፥145 ቍ10፡ 22፡55
119፥146 ቍ94
119፥147 መዝ5፥3 ፤57፥8፤108፥2
119፥148 መዝ63፥6
119፥149 ቍ40፡ 124፤መዝ27፥7
119፥150 መዝ37፥7
119፥151 ቍ142፤ መዝ34፥18፤ፊል4፥5
119፥152 ቍ7፡73፡89፤መዝ111፥8፤ሉቃ21፥33
119፥153 መዝ3፥7፤13፥3፤44፥17 119፥154 ቍ25፡41፤ 1ሳሙ24፥15፤መዝ35፥1፤ኤር50፥34፤ሚክ7፥9 119፥155 ቍ94 ፡118 119፥156 ቍ25፡149፤ነህ9፥27፤ያዕ5፥11
119፥157 መዝ7፥1፤44፥18

158 ቃልህን አይጠብቁምና፣
ከዳተኞችን አይቼ አርቃቸዋለሁ።
159 መመሪያህን እንዴት እንደምወድ
ተመልከት፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ ምሕረትህ
ሕያው አድርገኝ።
160 ቃልህ በሙሉ እውነት ነው፤
ጻድቅ የሆነው ሕግህም ዘላለማዊ ነው።

*ש ሳን*

161 ገዦች ያለ ምክንያት አሳደዱኝ፤
ልቤ ግን ከቃልህ የተነሣ እጅግ ፈራ።
162 ትልቅ ምርኮ እንዳገኘ ሰው፤
በቃልህ ደስ አለኝ።
163 ሐሰትን እጠላለሁ፤ እጸየፋለሁ፤
ሕግህን ግን ወደድሁ።
164 ጻድቅ ስለ ሆነው ሕግህ፤
በቀን ሰባት ጊዜ አመሰግንሃለሁ።
165 ሕግህን የሚወዱ ብዙ ሰላም አላቸው፤
ዕንቅፋትም የለባቸውም።
166 እግዚአብሔር ሆይ፤ ማዳንህን ተስፋ
አደርጋለሁ፤
ትእዛዝህንም እፈጽማለሁ።
167 ነፍሴ ምስክርነትህን ትጠብቃለች፤
እጅግ እወደዋለሁና።
168 መንገዴ ሁሉ በፊትህ ግልጽ ነውና፣
ሕግህንና ምስክርነትህን እጠብቃለሁ።

*ת ታው*

169 እግዚአብሔር ሆይ፤ ጩኸቴ ከፊትህ
ይድረስ፤
እንደ ቃልህም ማስተዋልን ስጠኝ።
170 ልመናዬ ከፊትህ ይድረስ፤
እንደ ቃልህም ታደገኝ።
171 ሥርዐትህን አስተምረኸኛልና፣
ከንፈሮቼ ምስጋናን አፈለቁ።
172 ትእዛዛትህ ሁሉ የጽድቅ ትእዛዛት
ናቸውና፣
አንደበቴ ስለ ቃልህ ይዘምር።
173 ትእዛዝህን መርጫለሁና፣
እጅህ እኔን ለመርዳት ዝግጁ ይሁን።
174 እግዚአብሔር ሆይ፤ ማዳንህን ናፈቅሁ፤
ሕግህም ደስታዬ ነው።
175 አመሰግንህ ዘንድ በሕይወት ልኑር፤
ሕግህም ይርዳኝ።
176 እንደ ጠፋ በግ ተቅበዘበዝሁ፤
ትእዛዛትህን አልረሳሁምና፣
ባሪያህን ፈልገው።

## መዝሙር 120

### የሰላም ፀሮች

*መዝሙረ መዓርግ*

1 በተጨነቅሁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር
ተጣራሁ፤
እርሱም መለሰልኝ።
2 እግዚአብሔር ሆይ፤ ከሐሰተኛ ከንፈር፣
ከአታላይ ምላስም አድነኝ።

3 ሐሰተኛ አንደበት ሆይ፤ ምን ይከፈልህ?
ከዚህስ የባሰ ምን ይደረግብህ?
4 በተሳለ የጦረኛ ቀስት፣
በግራር ከሰል ፍም ይቀጣሃል።

5 በሜሼክ እኖራለሁና፣
በቄዳር ድንኳኖች መካከል
እቀመጣለሁና ወዮልኝ!
6 ሰላምን በሚጠሉ መካከል፣
ነፍሴ እጅግ ብዙ ጊዜ ኖረች።
7 እኔ ሰላም ፈላጊ ነኝ፤
እነርሱ ግን በተናገርሁ ጊዜ ጠብ ይሻሉ።

## መዝሙር 121

### የእስራኤል ጠባቂ

*መዝሙረ መዓርግ*

1 ዐይኖቼን ወደ ተራሮች አነሣሁ፤
ረድኤቴ ከወዴት ይመጣል?
2 ረድኤቴ ሰማይንና ምድርን ከፈጠረ፣
ከእግዚአብሔር ዘንድ ይመጣል።

3 እግርህ እንዲሸራተት አይፈቅድም፤
የሚጠብቅህም አይተኛም።
4 እነሆ፤ እስራኤልን የሚጠብቅ፣
አይተኛም፤ አያንቀላፋምም።

5 እግዚአብሔር ይጠብቅሃል፤
እግዚአብሔር በቀኝህ በኩል
ይከልልሃል።
6 ፀሓይ በቀን አያቃጥልህም፤
ጨረቃም በሌሊት ጉዳት አታመጣብህም።

7 እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ ይጠብቅሃል፤
ነፍስህንም ይንከባከባታል።
8 እግዚአብሔር ከአሁን ጀምሮ እስከ ዘላለም፣
መውጣትህንና መግባትህን ይጠብቃል።

## መዝሙር 122

### ኢየሩሳሌም እልል በዪ!

*የዳዊት መዝሙረ መዓርግ*

1 "ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ"
ባሉኝ ጊዜ፣
ደስ አለኝ።
2 ኢየሩሳሌም ሆይ፤
እግሮቻችን ከደጅሽ ውስጥ ቆመዋል።
3 ኢየሩሳሌም እጅግ እንደ ተጠጋጋች፣
ከተማ ሆና ተሠርታለች።
4 ለእስራኤል በተሰጠው ሥርዐት
መሠረት፣
የእግዚአብሔርን ስም ለማመስገን፣
የእግዚአብሔር ነገዶች፣
ወደዚያ ይመጣሉ።

119፥158 ቊ104፡136፤ዘፀ32፥19
119፥159 ቊ25፤መዝ41፥2 119፥160 ቊ89፤ መዝ111፥8
119፥161 ቊ23፡120፡122፡157፤1ሳሙ24፥14-15
119፥162 ቊ111፤1ሳሙ30፥16፤ኢሳ9፥3፤53፥12
119፥163 ቊ47፡128
119፥164 ቊ7፡160
119፥165 ቊ11፤መዝ37፥11፡24፤ኢሳ26፥3፡12፤27፥5፤32፥17፤57፥19፤66፥12፤1ዮሐ2፥10
119፥166 ቊ81
119፥167 ቊ47
119፥168 ቊ2፡22፡56፡88፤ኢዮ10፥4፤23፥10፤መዝ139፥3፤ምሳ5፥21
119፥169 ቊ9፡34፤ኢዮ16፥18
119፥170 ቊ41፤1ነገ8፥30፤2ዜና6፥24፤መዝ3፥7፤22፥20፤28፥2፤59፥1፤140፥6፤143፥1
119፥171 መዝ51፥15፤63፥3፤94፥12፤ኢሳ2፥3፤ሚክ4፥2
119፥172 ቊ7፡75፤መዝ51፥14
119፥173 ኢሱ24፥22፤መዝ37፥24፤73፥23፤ኢሳ41፥10
119፥174 ቊ16፡24፡166
119፥175 ቊ116፡159፤ኢሳ55፥3
119፥176 ቊ10፤መዝ44፥17፤95፥10፤ኤር50፥17፤ሕዝ34፥11፤ሉቃ15፥4
120፥1 2ሳሙ22፥7፤መዝ18፥6፤118፥5
120፥2 መዝ31፥18፤52፥4
120፥4 ዘዳ32፥23
120፥5 ዘፍ25፥13፤ኤር2፥10
121፥2 ዘፍ1፥1፤መዝ104፥5
121፥4 መዝ127፥1
121፥5 መዝ1፥6
121፥6 ኢሳ49፥10
121፥7 መዝ9፥9
121፥8 ዘዳ28፥6

5በዚያም የፍርድ ዙፋኖች የሆኑት፣
የዳዊት ቤት ዙፋኖች ተዘርግተዋል።
6እንዲህ ብላችሁ ለኢየሩሳሌም ሰላም ጸልዩ፤
"የሚወዱሽ ይለምልሙ፤
7በቅጥርሽ ውስጥ ሰላም ይሁን፤
በምሽግሽም ውስጥ መረጋጋት ይስፈን"።
8ስለ ወንድሞቼና ስለ ባልንጀሮቼ፣
"በውስጥሽ ሰላም ይስፈን" እላለሁ።
9ስለ አምላካችን ስለ *እግዚአብሔር* ቤት፣
በጎነትሽን እሻለሁ።

## መዝሙር 123
### የተጨነቀ ሰው ጸሎት

*መዝሙረ መዓርግ*

1በሰማይ ዙፋን ላይ የተቀመጥህ ሆይ፤
ዐይኖቼን ወደ አንተ አነሣለሁ።
2የባሪያዎች ዐይን ወደ ጌታቸው እጅ፣
የባሪያዪቱም ዐይን ወደ እመቤቷ እጅ እንደሚመለከት፣
ምሕረት እስከሚያደርግልን ድረስ፣
የእኛም ዐይኖች ወደ አምላካችን ወደ *እግዚአብሔር* ይመለከታሉ።
3*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ንቀት በዝቶብናልና፣
ማረን፣ እባክህ ማረን።
4ነፍሳችን የቅንጡዎች ስድብ፣
የትዕቢተኞችም ንቀት እጅግ በዝቶባታል።

## መዝሙር 124
### የእስራኤል አዳኝ

*የዳዊት መዝሙረ መዓርግ*

1እስራኤል እንዲህ ይበል፦
"*እግዚአብሔር* ከእኛ ጋር ባይሆን ኖሮ፣
2ሰዎች በእኛ ላይ በተነሡ ጊዜ፣
*እግዚአብሔር* ከእኛ ጋር ባይሆን ኖሮ፣
3ቍጣቸው በላያችን በነደደ ጊዜ፣
በቁመናችን በዋጡን ነበር፤
4ጐርፍ ባጥለቀለቀን፣
ፈረሰኛው ውሃ ባሰጠመን፣
5ደራሽ ውሃም
ጠራርጎ በወሰደን ነበር።
6በጥርሳቸው ከመዘንጠል የጠበቀን፣
*እግዚአብሔር* ይባረክ።
7ነፍሳችን እንደ ወፍ፣
ከአዳኝ ወጥመድ አመለጠች፤
ወጥመዱ ተሰበረ፤
እኛም አመለጥን።
8የሰማይና የምድር ፈጣሪ፣
የ*እግዚአብሔር* ስም ረዳታችን ነው።

122፥6 መዝ26፥8
122፥7 1ሳሙ25፥6፤መዝ48፥3
122፥9 መዝ128፥5
123፥1 መዝ68፥5፤ኢሳ6፥1፤63፥15
123፥2 መዝ25፥15
124፥1 መዝ129፥1
124፥4 መዝ81፥4፤88፥17
124፥7 መዝ25፥15፤91፥3
124፥8 ዘፍ1፥1፤1ሳሙ17፥45፤መዝ115፥15፤121፥2፤134፥3
125፥1 መዝ46፥5፤48፥2-5፡12፤ኢሳ33፥20
125፥2 1ዜና21፥15፤መዝ32፥10፤ዘካ2፥4-5
125፥3 1ሳሙ24፥10፤አስ4፥11፤መዝ89፥22፤ምሳ22፥8፤ኢሳ13፥11፤14፥5
125፥4 መዝ36፥10፤119፥65
125፥5 ኢዮ23፥11፤መዝ92፥7፤128፥6፤ምሳ2፥15፤17፥6፤ኢሳ59፥8፤ገላ6፥16
126፥1 ዕዝ1፥1-3፤መዝ85፥1፤ሆሴ6፥11
126፥2 ዘፍ21፥6፤ዘዳ10፥21፤ኢዮ8፥21፤መዝ65፥8፤71፥19፤ሉቃ1፥49
126፥3 መዝ9፥2፤16፥11፤106፥21፤ኢል2፥21፡26
126፥4 ዘዳ30፥3፤መዝ107፥35፤ኢሳ43፥19፤51፥3
126፥5 መዝ6፥6፤16፥11፤20፥5፤23፥6፤80፥5፤ኢሳ35፥10፤51፥11፤60፥15፤61፥7፤ኤር31፥6-7፡12፤50፥4፤ገላ6፥9
126፥6 ዘኍ25፥6፤መዝ30፥5
127፥1 መዝ78፥69፤121፥4

## መዝሙር 125
### እግዚአብሔር የሚታመኑበትን ይጠብቃል

*መዝሙረ መዓርግ*

1*በእግዚአብሔር የሚታመኑ*፣
ሳትናወጥ ለዘላለም እንደምትኖር እንደ ጽዮን ተራራ ናቸው።
2ተራሮች ኢየሩሳሌምን እንደ ከበቧት፣
ከአሁን ጀምሮ ለዘላለም፣
*እግዚአብሔር* በሕዝቡ ዙሪያ ነው።
3ጻድቃን እጃቸውን፣
ለክፋት እንዳያነሡ፣
የክፉዎች በትር፣
ለጻድቃን በተመደበች ምድር ላይ አያርፍም።
4*እግዚአብሔር* ሆይ፤ መልካም ለሆኑ፣
ልባቸውም ለቀና መልካም አድርግ።
5ወደ ጠማማ መንገዳቸው የሚመለሱትን ግን፣
*እግዚአብሔር* ከክፉ አድራጊዎች ጋር ያስወግዳቸዋል።
በእስራኤል ላይ ሰላም ይውረድ።

## መዝሙር 126
### የስደት ተመላሾች መዝሙር

*መዝሙረ መዓርግ*

1*እግዚአብሔር* የጽዮንን ምርኮ[ፊ] በመለሰ[ፐ] ጊዜ፣
ሕልም እንጂ እውን አልመሰለንም።
2በዚያን ጊዜ አፋችን በሣቅ፣
እንደበታችንም በእልልታ ተሞላ፤
በዚያን ጊዜም በሕዝቦች መካከል፣
"*እግዚአብሔር* ታላቅ ነገር አደረገላቸው" ተባለ።
3*እግዚአብሔር* ታላቅ ነገር አደረገልን፤
እኛም ደስ አለን።
4*እግዚአብሔር* ሆይ፤ በኔጌብ እንዳሉ ጅረቶች፣
ምርኳችንን መልስ።[ሀ]
5በእንባ የሚዘሩ፣
በእልልታ ያጭዳሉ።
6ዘር ቋጥረው፣
እያለቀሱ የተሰማሩ፣
ነዶአቸውን ተሸክመው፣
እልል እያሉ ይመለሳሉ።

## መዝሙር 127
### በእግዚአብሔር መታመን

*የሰሎሞን መዝሙረ መዓርግ*

1*እግዚአብሔር* ቤትን ካልሠራ፣

[ፊ]1 ወይም *እግዚአብሔር ሀብቷን ይመልሳል።*
[ፐ]1 ወይም *የሰዎቿ ጤንነት ይታደሳል።*
[ሀ]4 ወይም *ሀብታችንን መልስ*

ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ፤
እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ፣
ጠባቂ በከንቱ ይተጋል።
2የዕለት ጒርስ ለማግኘት በመጣር፣
ማልዳችሁ መነሣታችሁ፣
አምሽታችሁም መተኛታችሁ ከንቱ ነው፤
እርሱ ለሚወዳቸው እንቅልፍን ያድላልና።^
3እነሆ፤ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ
ናቸው፤
የማሕፀንም ፍሬ ከቸርነቱ የሚገኝ ነው።
4በወጣትነት የተገኙ ወንዶች ልጆች፣
በጦረኛ እጅ እንዳሉ ፍላጾች ናቸው።
5ኰረጆዎቹ በእነዚህ የተሞሉ፣
የተባረከ ሰው ነው፤
ከጠላቶቻቸው ጋር በአደባባይ በሚሟ
ገቱበት ጊዜ፣
አይዋረዱም።

## መዝሙር 128
### የጻድቃን በረከት

መዝሙረ መዓርግ

1እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሁሉ፣
በመንገዱም የሚሄዱ የተባረኩ ናቸው።
2የድካምህን ፍሬ ትበላለህ፤
ትባረካለህ፤ ይሳካልሃልም።
3ሚስትህ በቤትህ፣
እንደሚያፈራ ወይን ናት፤
ወንዶች ልጆችህ በማእድህ ዙሪያ፣
እንደ ወይራ ተክል ናቸው።
4እነሆ፤ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው፣
እንዲህ ይባረካል።

5እግዚአብሔር ከጽዮን ይባርክህ፤
በሕይወትህ ዘመን ሁሉ፣
የኢየሩሳሌምን ብልጽግና ያሳይህ፤
6የልጅ ልጅ ለማየትም ያብቃህ።

በእስራኤል ላይ ሰላም ይውረድ።

## መዝሙር 129
### በጽዮን ጠላቶች ላይ የቀረበ ጸሎት

መዝሙረ መዓርግ

1እስራኤል እንዲህ ይበል፦
"ከልጅነቴ ጀምሮ ብዙ ጊዜ
አስጨነቁኝ፤
2በእርግጥ ከልጅነቴ ጀምሮ ብዙ ጊዜ
አስጨነቁኝ፤
ዳሩ ግን ድል አላደረጉኝም።
3ዐራሾች ጀርባዬን ዐረሱት፤
ትልማቸውንም አስረዘሙት።"
4እግዚአብሔር ግን ጻድቅ ነው፤
የክፉዎችን ገመድ በጣጥሶ ጣለው።

5ጽዮንን የሚጠሉ ሁሉ፣
ዐፍረው ወደ ኋላቸው ይመለሱ።
6ገና ከመብቀሉ እንደሚደርቅ፣
በጣራ ላይ እንደ በቀለ ሣር ይሁኑ፤
7ደግሞም ለዐጫጅ እጁን፣
ለነዶ ሰብሳቢ ዕቅፉን እንደማይሞላ
ይሁኑ።
8መንገድ ዐላፊዎችም፣
"የእግዚአብሔር በረከት በእናንተ ላይ
ይሁን፤
በእግዚአብሔር ስም እንባርካችኋለን"
አይበሉ።

## መዝሙር 130
### ለርዳታ የቀረበ ጥሪ

መዝሙረ መዓርግ

1እግዚአብሔር ሆይ፤
ከጥልቅ ወደ አንተ እጮኻለሁ።
2ጌታ ሆይ፤ ድምፄን ስማ፤
ጆሮዎችህ የልመናዬን ቃል፣
የሚያዳምጡ ይሁኑ።
3እግዚአብሔር ሆይ፤ ኀጢአትን
ብትቈጣጠር፣
ጌታ ሆይ፤ ማን ሊቆም ይችላል?
4ነገር ግን በአንተ ዘንድ ይቅርታ አለ፤
ስለዚህም ልትፈራ ይገባሃል።

5እግዚአብሔርን ደጅ እጠናለሁ፤ ነፍሴም
በትዕግሥት ትጠብቀዋለች፤
በቃሉም ተስፋ አደርጋለሁ።
6ዘብ ዐዳሪ ንጋትን ከሚጠባበቅ ይልቅ፣
አዎን፤ ዘብ ዐዳሪ ንጋትን ከሚጠባበቅ
ይልቅ፣
ነፍሴ ጌታን ትጠባበቃለች።
7በእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረት፣
በእርሱም ዘንድ ማዳን አለና፣
እስራኤል ሆይ፤ በእግዚአብሔር
ተስፋ አድርግ።
8እርሱም እስራኤልን፣
ከኀጢአቱ ሁሉ ያድነዋል።

## መዝሙር 131
### በእግዚአብሔር መታመን

የዳዊት መዝሙረ መዓርግ

1እግዚአብሔር ሆይ፤ ልቤ አልታበየም፤
ዐይኔ ከፍ ከፍ አላለም፤
ሐሳቤ ለዐጒል ትልቅነት አልተነሣሣም፤
ከዐቅሜም በላይ አልተንጠራራሁም።
2ነገር ግን ነፍሴን ጸጥ፣ ዝም አሰኘኋት፤
ጡት የጣለ ልጅ ዐርፎ እናቱ ላይ
እንደሚቀመጥ፣
ነፍሴ ጡት እንዳስተዉት ሕፃን
በውስጤ ጸጥ አለች።
3እስራኤል ሆይ፤ ከአሁን ጀምሮ
ለዘላለም፣

^2 ወይም ተኝተው ሳሉ ምግብ ያዘጋጅላቸዋል።

127፥2 ዘፍ3፥17፤ ዘኊ6፥26፤ዘዳ33፥12፤ ኢዮ11፥18፤መክ2፥25
127፥3 ዘፍ1፥28
127፥4 መዝ112፥2 ፤127፥5ዘፍ23፥10፤ 24፥60፤መዝ128፥2-3
127፥5 ዘፍ23፥10፤ 24፥60፤መዝ128፥2-3
128፥1 መዝ103፥11 ፤112፥1፤119፥1-3
128፥2 ዘፍ39፥3፤ መዝ58፥11፤109፥11፤ ምሳ10፥22፤ኢሳ3፥10
128፥3 ዘፍ49፥22 ፤ኢዮ29፥5፤መዝ 52፥8፤144፥12
128፥4 መዝ1፥1፤ 112፥1
128፥5 መዝ20፥2፤ 122፥9
128፥6 ዘፍ48፥11፤ መዝ125፥5
129፥1 ዘፀ1፥13፤ መዝ88፥15፤124፥1
129፥2 ኤር1፥19፤ 15፥20፤20፥11፤ማቴ 16፥18
129፥4 ዘፀ9፥27፤ መዝ37፥9፤140፥5
129፥5 መዝ70፥2፤ ሚክ4፥11
129፥6 2ነገ19፥26፤ መዝ102፥11፤ኢሳ 37፥27
129፥7 ዘዳ28፥38፤ መዝ79፥12
129፥8 መዝ118፥26
130፥1 ኢዮ30፥19፤ መዝ22፥2፤42፥7፤55፥1 7፤142፥5፤ሰቆ3፥55
130፥2 2ዜና6፥40 ፤መዝ27፥7፤28፥2፥6፤3 1፥22፤86፥6፤140፥6
130፥3 1ሳሙ6፥20 ፤ዕዝ9፥15፤መዝ143፥2 ፤ናሆ1፥6፤ራእ6፥17
130፥4 ዘፀ34፥7፤ 2ሳሙ24፥14፤1ነገ 8፥40፤ኤር31፥34
130፥5 መዝ5፥3፤ 27፥14፤119፥74፤ኢሳ 8፥17፤26፥8፤30፥18፤4 9፥23
130፥6 2ሳሙ23፥4 ፤መዝ63፥6
130፥7 1ዜና21፥13 ፤መዝ25፥5፤71፥14፤ 111፥9፤ሮሜ3፥24
130፥8 ዘፀ34፥7፤ ሉቃ1፥68፤ማቴ1፥21
131፥1 2ሳሙ22፥ 28፤ኢዮ5፥9፤41፥34፤ መዝ101፥5፤139፥6፤ኢ ሳ2፥12፤ኤር45፥5፤ ሮሜ12፥16
131፥2 መዝ116፥7 ፤ማቴ18፥3፤1ቆሮ 13፥11፤14፥20
131፥3 መዝ25፥5፤ 113፥2፤119፥43፤130፥7

*በእግዚአብሔር* ተስፋ አድርግ።

## **መዝሙር** 132

### የክብረ በዓል መዝሙር

132፥8-10 ተጓ ምብ-2ዜና 6፥41-42

*መዝሙረ መዓርግ*

[1]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ዳዊትን፣
የታገሠውንም መከራ ሁሉ ዐስብ፤
[2]እርሱ *ለእግዚአብሔር* ማለ፤
ለያዕቆብም ኀያል አምላክ እንዲህ ሲል
ተሳለ፤
[3]“ወደ ቤቴ አልገባም፤
ዐልጋዬም ላይ አልወጣም፤
[4]ለዐይኖቼ እንቅልፍን፣
ለሽፋሽፍቶቼም ሽለብታ አልሰጥም፤
[5]*ለእግዚአብሔር* ስፍራን፣
ለያዕቆብም ኀያል አምላክ ማደሪያን
እስካገኝ ድረስ።”

[6]እነሆ፤ በኤፍራታ ሰማነው፤
በቂርያት ይዓሪም[ሐ] አገኘነው።
[7]“ወደ ማደሪያው እንግባ፤
እግሮቹ በሚቆሙበት ቦታ እንስገድ።
[8]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ተነሥ፤
አንተና የኀይልህ ታቦት ወደ ማረፊያህ
ስፍራ ሂዱ።
[9]ካህናትህ ጽድቅን ይልበሱ፤
ቅዱሳንህም እልል ይበሉ።”

[10]ስለ አገልጋይህ ስለ ዳዊት ስትል፣
የቀባኸውን ሰው አትተወው።

[11]*እግዚአብሔር* ለዳዊት በእውነት ማለ፤
በማይታጠፍም ቃሉ እንዲህ አለ፤
“ከገዛ ራስህ ፍሬ፣
በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ።
[12]ወንዶች ልጆችህ ኪዳኔን፣
የማስተምራቸውንም ምስክርነቴን
ቢጠብቁ፣
ልጆቻቸው በዙፋንህ ላይ፣
ለዘላለም ይቀመጣሉ።

[13]*እግዚአብሔር* ጽዮንን መርጦአታልና፣
ማደሪያውም ትሆን ዘንድ ወዶአልና
እንዲህ አለ፤
[14]“ይህች ለዘላለም ማረፊያዬ ናት፤
ፈልጌአታለሁና በእርሷ እኖራለሁ።
[15]እጅግ አትረፍርፌ እባርካታለሁ፤
ድኾቿን እንጀራ አጠግባለሁ።
[16]ለካህናቷ ድነትን አለብሳለሁ፤
ቅዱሳኗም በደስታ ይዘምራሉ።

[17]“በዚህም ለዳዊት ቀንድ[መ] አበቅላለሁ፤
ለቀባሁትም ሰው መብራት አዘጋጃለሁ።
[18]ጠላቶቹን ኀፍረት አከናንባቸዋለሁ፤
እርሱ ግን በራሱ ላይ የደፋው ዘውድ

132፥1 1ሳሙ 18፥11፤2ሳሙ 15፥14
132፥2 ዘፍ49፥24፤ኢሳ49፥26፤60፥16
132፥3 2ሳሙ7፥2፡27
132፥5 1ነገ8፥17፤ሐሥ7፥46
132፥6 ኢሱ9፥17፤1ሳሙ7፥2፤17፥12
132፥7 2ሳሙ15፥25፤1ዜና28፥2፤መዝ5፥7፤122፥1
132፥8 ዘኍ10፥35
132፥9 ኢዮ27፥6፤መዝ16፡3፤30፡4፤149፡5፤ኢሳ61፥3፥10፤ዘካ3፥4፤ሚል3፥3፤ኤፌ6፥14
132፥11 1ዜና17፥11-14፤መዝ89፥3-4፡35፤ማቴ1፥1፤ሉቃ3፥31
132፥12 2ዜና6፥16፤መዝ25፥10፤ሉቃ1፥32፤ሐሥ2፥30
132፥13 ዘፀ15፥17፤1ነገ8፥13፤መዝ48፥1-2፤68፥16
132፥14 ቍ8፤2ሳሙ6፥2፤መዝ68፥6፤80፥1
132፥15 መዝ107፥9፤147፥14
132፥16 2ዜና6፥41፤ኢዮ8፥21፤መዝ149፥5
132፥17 1ሳሙ2፥10፤1ነገ11፥36፤2ነገ8፥19፤2ዜና21፥7፤መዝ18፥28፤84፥9፤92፥10፤ሕዝ29፥21፤ሉቃ1፥69
132፥18 2ሳሙ12፥30፤ኢዮ8፥22
133፥1 ዘፍ13፥8፤ዮሐ17፥11፤ሮሜ12፥10
133፥2 ዘፀ29፥7
133፥3 ዘፀ15፥17፤ዘሌ25፥21፤ዘዳ3፥8፤4፥48፤ኢዮ29፥19፤መዝ2፥6፤21፥4፤74፥2፤ምሳ19፥12፤ኢሳ18፥4፤26፥19፤45፥8፤ሆሴ14፥5፤ሚክ5፥7
134፥1 ዘኍ16፥9፤1ዜና15፥2፤23፥30፤መዝ113፥1፤135፥1-2፤ራእ19፥5
134፥2 መዝ15፥1፤28፥2፤33፥2፤103፥1፤1ጢሞ2፥8
134፥3 ዘሌ25፥21፤መዝ20፥2፤መዝ124፥8
135፥1 ነህ7፥73
135፥2 1ዜና15፥2፤መዝ116፥19፤ሉቃ2፥37
135፥3 1ዜና16፥34፤መዝ68፥4፤92፥1፤119፥68፤147፥1
135፥4 ዘፀ19፥5፤ዘዳ7፥6፤10፥15፤ሚል3፥17፤ቲቶ2፥14
135፥5 ዘፀ12፥12፤

ያበራል።

## **መዝሙር** 133

### የወንድማማች ፍቅር

*የዳዊት መዝሙረ መዓርግ*

[1]ወንድሞች ተስማምተው በአንድነት
ሲኖሩ፣
እንዴት መልካም ነው! ምንኛስ ደስ
ያሰኛል!
[2]በራስ ላይ ፈሶ፣
እስከ ጢም እንደሚዘልቅ፣
እስከ አሮን ጢም እንደሚወርድ፣
እስከ ልብሱም ዐንገትጌ እንደሚደርስ
ውድ ሽቱ ነው።
[3]ደግሞም በጽዮን ተራራ ላይ
እንደሚወርድ፣
እንደ አርሞንዔም ጠል ነው፤
በዚያ *እግዚአብሔር* በረከቱን፣
ሕይወትንም እስከ ዘላለም አዞአልና።

## **መዝሙር** 134

### የሠርክ መዝሙር

*መዝሙረ መዓርግ*

[1]እናንት በሌሊት ቆማችሁ *በእግዚአብሔር*
ቤት የምታገለግሉ፣
*የእግዚአብሔር* ባሪያዎች ሁላችሁ፤
*እግዚአብሔርን* ባርኩ።
[2]በመቅደሱ ውስጥ እጆቻችሁን አንሡ፤
*እግዚአብሔርንም* ባርኩ።
[3]ሰማይንና ምድርን የሠራ *እግዚአብሔር*፣
ከጽዮን ይባርክህ።

## **መዝሙር** 135

### የምስጋና መዝሙር

135፥15-20 ተጓ ምብ-መዝ 115፥4-11

[1]ሃሌ ሉያ።[ሠ]

*የእግዚአብሔርን* ስም ወድሱ፤
እናንት *የእግዚአብሔር* አገልጋዮች
ሆይ፤ አመስግኑት፤
[2]*በእግዚአብሔር* ቤት፣
በአምላካችን ቤት አደባባይ የምትቆሙ
አመስግኑት።
[3]*እግዚአብሔር* ቸር ነውና *እግዚአብሔርን*
አመስግኑ፤
መልካም ነውና፣ ለስሙ ዘምሩ፤
[4]*እግዚአብሔር* ያዕቆብን ለራሱ፣
እስራኤልንም ውድ ንብረቱ አድርጎ
መርጦአልና።

[5]*እግዚአብሔር* ታላቅ እንደ ሆነ፣

[ሐ]6 አንዳንዶቹ *ያዓር* ይላሉ።
[መ]17 እዚህ ላይ ቀንድ የጥንካሬ ትእምርት ሲሆን ንጉሥን ያመለታል።
[ሠ]1 ቍ3 እና 21 ጭምር በአንዳንድ ትርጕሞች *እግዚአብሔር ይመስገን* ይላሉ።

ጌታ ችንም ከአማልክት ሁሉ
እንደሚበልጥ
ዐውቃለሁና።
6በሰማይና በምድር፣
በባሕርና በጥልቅ ሁሉ ውስጥ፣
እግዚአብሔር ደስ ያሰኘውን ሁሉ
ያደርጋል።
7እርሱ ደመናትን ከምድር ዳርቻ
ያስነሣል፤
መብረቅ ከዝናብ ጋር እንዲወርድ
ያደርጋል፤
ነፋሳትንም ከማከማቻው ያወጣል።
8በኵር ሆኖ በግብፅ የተወለደውን፣
ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳ ቀሠፈ።
9ግብፅ ሆይ፤ በፈርዖንና በአገልጋዮቹ ሁሉ
ላይ፣
በመካከልሽ ታምራትንና ድንቅን
ሰደደ።
10ብዙ ሕዝቦችን መታ፤
ኀያላን ነገሥታትንም ገደለ።
11የአሞራውያንን ንጉሥ ሴዎንን፣
የባሳንን ንጉሥ ዐግን፣
የከነዓንን ነገሥታት ሁሉ ገደለ፤
12ምድራቸውንም ርስት አድርጎ፣
ለሕዝቡ ርስት እንዲሆን ለእስራኤል
ሰጠ።
13እግዚአብሔር ሆይ፤ ስምህ ዘላለማዊ
ነው፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ መታሰቢያህም
ከትውልድ እስከ ትውልድ ይኖራል።
14እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይፈርዳልና፣
ለአገልጋዮቹም ይራራላቸዋል።
15የአሕዛብ ጣዖታት ከብርና ከወርቅ
የተሠሩ፣
የሰው እጅ ያበጃቸው ናቸው።
16አፍ አላቸው፤ አይናገሩም፤
ዐይን አላቸው፤ አያዩም፤
17ጆሮ አላቸው፤ አይሰሙም፤
በአፋቸውም እስትንፋስ የለም።
18እነዚህን የሚያበጁ፣
የሚታመኑባቸውም ሁሉ እንደ እነርሱ
ይሆኑ።
19የእስራኤል ቤት ሆይ፤ እግዚአብሔርን
ባርኩ፤
የአሮን ቤት ሆይ፤ እግዚአብሔርን
ባርኩ፤
20የሌዊ ቤት ሆይ፤ እግዚአብሔርን ባርኩ፤
እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሆይ፤ እግዚ
አብሔርን ባርኩ።
21በኢየሩሳሌም የሚኖር እግዚአብሔር፣
ከጽዮን ይባረክ።

1ዜና16፥25፤ኢዮ
21፥22፤መዝ48፥1፤
145፥3
135፥6 መዝ115፥3
፤ዳን4፥35፤ማቴ6፥10
135፥7 ዘዳ28፥12፤
ኢዮ5፥10፤መዝ68፥9፤
ኢሳ30፥23፤ኤር10፥
13፤51፥16፤ኢል2፥23
፤አሞ4፥13፤ዘካ10፥1
135፥8 ዘፀ4፥23፤
12፥12
135፥9 ዘፀ7፥9፤
መዝ136፥10-15
135፥10ዘኍ21፥21-
25፤ኢሱ24፥8-11፤
መዝ44፥2፤78፥55፤
136፥17-21
135፥11ዘኍ21፥21
፡26፡33፤ኢሱ12፥7-24
፤24፥12
135፥12 ዘዳ29፥8
135፥13 ዘፀ3፥15፤
መዝ102፥12
135፥14 ዘዳ32፥36
፤1ሳሙ24፥15፤ዕብ
10፥30
135፥15 መዝ96፥5
፤ኢሳ2፥8፤31፥7፤37፥
19፤40፥19፤ኤር1፥16፤
10፥5፤ራእ9፥20
135፥16 1ነገ18፥26
135፥17 ኤር10፥14
፤ዕን2፥19
135፥19 መዝ22፥23
135፥21 1ነገ8፥13፤
2ዜና6፥2፤መዝ128፥5፤
134፥3
136፥1 ቍ2-26፤
2ዜና5፥13፤ዕዝ3፥11፤
መዝ100፥5፤105፥1፤1
06፥1፤118፥1-4፤145፥9፤
ኤር33፥11፤ናሆ1፥7
136፥2 ዘዳ10፥17፤
መዝ105፥1
136፥3 ዘዳ10፥17፤
መዝ105፥1፤1ጢሞ
6፥15
136፥4 ዘፀ3፥20፤
ኢዮ9፥10
136፥5 ዘፍ1፥1፤
ምሳ3፥19፤ኤር51፥15
136፥6 ዘፍ1፥1፡6፤
ኢሳ42፥5፤ኤር10፥12
፤33፥2
136፥7 ዘፍ1፥14፡16፤
መዝ74፥16፤ያዕ1፥17
136፥8 ዘፍ1፥16
136፥10 ዘፀ4፥23፤
12፥12
136፥11 ዘፀ6፥6፤
13፥3፤105፥43
136፥12 ዘፀ3፥20፤
ዘዳ5፥15፤9፥29
136፥13 መዝ78፥13
136፥14 ዘፀ14፥22፤
መዝ106፥9
136፥15 ዘፀ14፥27
136፥16 ዘፀ13፥18፤
መዝ78፥52
136፥17 ዘኍ21፥23

ሃሌ ሉያ።

## መዝሙር 136

### ምስጋና በቅብብሎሽ መዝሙር

1እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ቸር ነውና፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።
2የአማልክትን አምላክ አመስግኑ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።
3የጌቶችን ጌታ አመስግኑ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።
4እርሱ ብቻውን ታላላቅ ታምራትን
የሚያደርግ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
5ሰማያትን በብልሃት የሠራ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
6ምድርን በውሃ ላይ የዘረጋ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።
7ታላላቅ ብርሃናትን የሠራ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
8ፀሓይ በቀን እንዲሠለጥን ያደረገ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
9ጨረቃና ከዋክብት በሌሊት
እንዲሠለጥኑ ያደረገ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
10የግብፅን በኵር የመታ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
11እስራኤልን ከመካከላቸው ያወጣ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
12በኀያል እጅና በተዘረጋች ክንድ
ይህን ያደረገ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
13የኤርትራን ባሕር ለሁለት የከፈለ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
14እስራኤልን በመካከሉ ያሳለፈ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
15ፈርዖንንና ሰራዊቱን በኤርትራ ባሕር
ያሰጠመ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
16ሕዝቡን በምድረ በዳ የመራ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
17ታላላቅ ነገሥታትን የመታ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
18ኀያላን ነገሥታትን የገደለ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
19የአሞራውያንን ንጉሥ ሴዎንን የገደለ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
20የባሳንን ንጉሥ ዐግን የገደለ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
21ምድራቸውን ርስት አድርጎ የሰጠ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤

-25፤ኢሱ24፥8-11፤መዝ78፥55፤135፥9-12 136፥18 ዘዳ29፥7፤
ኢሱ12፥7-24 136፥19 ዘኍ21፥21-25 136፥20 ዘኍ21፥33
-35 136፥21 ዘዳ1፥38፤ኢሱ12፥1፤14፥1

22ለባሪያው ለእስራኤል ርስት አድርጎ የሰጠ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
23በውርደታችን ጊዜ ያሰበን፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
24ከጠላቶቻችን እጅ ያዳነን፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
25ለፍጡር ሁሉ ምግብን የሚሰጥ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
26የሰማይን አምላክ አመስግኑ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።

## *መዝሙር* 137

### የግዞተኞች ቅኔ

1በባቢሎን ወንዞች አጠገብ፣ በዚያ
ተቀምጠን ሳለን፣
ጽዮን ትዝ ባለችን ጊዜ አለቀስን።
2እዚያም በአኻያ ዛፎች ላይ፣
በገናዎቻችንን ሰቀልን።
3የማረኩን በዚያ እንድንዘምርላቸው ጠየቁን፤
የሚያሠቃዩን የደስታ ዜማ ፈለጉብን፤
ደግሞም፣ “ከጽዮን መዝሙሮች አንዱን
ዘምሩልን” አሉን።
4*የእግዚአብሔርን* ዝማሬ፣
እንዴት በባዕድ ምድር እንዘምር!
5ኢየሩሳሌም ሆይ፤ ብረሳሽ፣
ቀኝ እጄ ትክዳኝ።
6ሳላስታውስሽ ብቀር፣
ኢየሩሳሌምን የደስታዬ ቍንጮ
ባላደርግ፣
ምላሴ ከትናጋዬ ጋር ትጣበቅ።
7*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ኢየሩሳሌም
በወደቀችበት ቀን፣
ኤዶማውያን እንዴት እንደ ዛቱ ዐስብ፤
ደግሞም፣ “አፍርሷት፤
ፈጽማችሁ አፈራርሷት!” አሉ።
8አንቺ አጥፊ የሆንሽ የባቢሎን ልጅ ሆይ፤
በእኛ ላይ ስለ ፈጸምሺው ድርጊት፣
የእጅሽን የሚሰጥሽ የተመሰገነ ነው፤
9ሕፃናትሽንም ይዞ፣
በዐለት ላይ የሚፈጠፍጥ የተመሰገነ
ነው።

## *መዝሙር* 138

### የምስጋና መዝሙር

*የዳዊት መዝሙር*

1እግዚአብሔር ሆይ፤ በፍጹም ልቤ
አመሰግንሃለሁ፤
በአማልክት ፊት በመዝሙር
እወድስሃለሁ።
2ወደ ቅዱስ መቅደስህ እሰግዳለሁ፤
ስለ ምሕረትህና ስለ ታማኝነትህ፣
ለስምህ ምስጋና አቀርባለሁ፤
ስምህንና ቃልህን፣
ከሁሉ በላይ ከፍ ከፍ አድርገሃልና።
3በጠራሁህ ቀን መልስ ሰጠኸኝ፤
ነፍሴን በማደፋፈርም ብርቱ
አደረግኸኝ።
4*እግዚአብሔር* ሆይ፤ የአፍህን ቃል
በሰሙ ጊዜ፣
የምድር ነገሥታት ሁሉ ያመስግኑህ።
5*የእግዚአብሔር* ክብር ታላቅ ነውና፣
ስለ *እግዚአብሔር* መንገድ ይዘምሩ።
6*እግዚአብሔር* በከፍታ ስፍራ ቢሆንም፣
ዝቅ ያለውን ይመለከተዋል፤
ትዕቢተኛውን ከሩቅ ያውቀዋል።
7በመከራ መካከል ብሄድም፣
አንተ ሕይወቴን ትጠብቃታለህ፤
በጠላቶቼ ቍጣ ላይ እጅህን ትዘረጋለህ፤
በቀኝ እጅህም ታድነኛለህ።
8*እግዚአብሔር* በእኔ ላይ ያለውን ዐላማ
ይፈጽማል፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ምሕረትህ
ለዘላለም ነው።
የእጅህንም ሥራ ቸል አትበል።

## *መዝሙር* 139

### ሁሉን ዐዋቂ አምላክ

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር*

1*እግዚአብሔር* ሆይ፤ መረመርኸኝ፤
ደግሞም ዐወቅኸኝ።
2አንተ መቀመጤንና መነሣቴን ታውቃለህ፤
የልቤንም ሐሳብ ገና ከሩቁ
ታስተውላለህ።
3መሄድ መተኛቴን አጥርተህ ታውቃለህ፤
መንገዶቼንም ሁሉ ተረድተሃቸዋል።
4*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ገና ቃል ከአንደበቴ
ሳይወጣ፣
እነሆ፤ አንተ ሁሉንም ታውቃለህ።
5አንተ ከኋላም ከፊትም ዙሪያዬን
ከለልኸኝ፤
እጅህንም በላዬ አደረግህ።
6እንዲህ ያለው ዕውቀት ለኔ ድንቅ ነው፤
ልደርስበትም የማልችል ከፍ ያለ ነው።
7ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ?
ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ?
8ወደ ሰማይ ብወጣ፣ አንተ በዚያ አለህ፤
መኝታዬንም በሲኦል[ሰ] ባደርግ በዚያ
ትገኛለህ።

**136፥22** ዘዳ29፥8፤ መዝ78፥55፤ኢሳ 20፥3፤41፥8፤42፥19፤43፥10፤44፥1፡21፤ 45፥4፤49፥5-7 **136፥23** መዝ78፥39 ፤103፥14፤115፥12 **136፥24** ዘዳ6፥19፤ ኢሱ10፥14፤ነህ9፥28 **136፥25** ዘፍ1፥30፤ ማቴ6፥26 **136፥26** ዕዝ3፥11፤ መዝ105፥1፤115፥3 **137፥1** ነህ1፥4፤ ኢሳ3፥26፤ሰቆ1፥4፤ ሕዝ 1፥1፡3፤3፥15፤ 10፥15 **137፥2** ዘሌ23፥40፤ ኢዮ30፥31፤ኢሳ24፥8፤ ሕዝ26፥13፤አሞ6፥5 **137፥3** ኢዮ30፥9፤ መዝ79፥1-4፤80፥6፤ ሰቆ1፥5፤ሕዝ16፥57፤ 22፥4፤34፥29 **137፥4** ነህ12፥46 **137፥5** ኢሳ2፥3፤ 56፥7፤65፥11፤66፥20 **137፥6** ዘዳ4፥29፤ ነህ2፥3፤መዝ22፥15፤ ኤር51፥50፤ሕዝ6፥9 **137፥7** ዘፍ25፥30፤ 2ነገ25፥1-10፤2ዜና 28፥17፤መዝ74፥8፤ 83፥6፤ሰቆ4፥21-22፤ አብ1፥11 **137፥8** ኢሳ13፥1፡ 19፤47፥1-15፤ኤር25፥ 12፡26፤50፥1፡2-51፡58 **137፥9** 2ነገ8፥12፤ ኢሳ13፥16፤ሉቃ 19፥44 **138፥1** መዝ27፥6፤ 95፥3፤96፥4፤108፥1 **138፥2** 1ነገ8፥29፤ መዝ5፥7፤74፥21፤ 97፥12፤108፥4፤115፥1 ፤119፥9፤140፥13 **138፥3** መዝ18፥6፤ 28፥7፤30፥2፤99፥6፤ 116፥4፤118፥5፤ምሳ 28፥1፤ሐሥ4፥29 **138፥4** መዝ72፥11 ፤102፥15 **138፥5** መዝ21፥5፤ 51፥14፤71፥16፤ 145፥7 **138፥6** መዝ40፥4፤ 113፥6፤ማቴ23፥12 **138፥7** ዘፀ7፥5፤ መዝ7፥6፤17፥7፡14፤ 20፥6፤23፥4፤41፥2፤ 60፥5፤108፥6 **138፥8** ዕዝ3፥11፤ኢዮ 10፥3፡8፤መዝ51፥11፤ 100፥5፤ፊል1፥6 **139፥1** መዝ17፥3፤ 44፥21፤ሮሜ8፥27 **139፥2** 2ነገ19፥27፤ መዝ94፥11፤ምሳ24፥ 12፤ኤር12፥3 **139፥3** 2ነገ19፥27፤ ኢዮ31፥4 **139፥4** ዕብ4፥13 **139፥5** 1ሳሙ25፥16፤መዝ32፥10፤ 34፥7፤125፥2 **139፥6** መዝ131፥1፤ሮሜ11፥33 **139፥7** ኤር 23፥24፤ዮና1፥3 **139፥8** ዘዳ30፥12-15፤ኢዮ17፥13፤አሞ9፥2-3

[ሰ]13 ዕብራይስጡ *ያመሱፍ* የሚለው በቍ15 ከሚገኘው ጭምር የሸምበቆ ባሕር ይለዋል።

ሰ8 አንዳንድ ትርጒሞች *በጥልቁ ውስጥ* ይላሉ።
[9]በንጋት ክንፍ ተነሥቼ ብበር፣
እስከ ባሕሩ ዳርቻ መጨረሻ ብሄድ፣
[10]በዚያም ቢሆን እጅህ ትመራኛለች፤
ቀኝ እጅህም አጥብቃ ትይዘኛለች።

[11]እኔም፣ "ጨለማው በእርግጥ ይሰውረኛል፤
በዙሪያዬ ያለውም ብርሃን ሌሊት
ይሆናል" ብል፣
[12]ጨለማ የአንተን ዐይን አይዝም፤
ሌሊቱም እንደ ቀን ያበራል፤
ጨለማም ብርሃንም ለአንተ አንድ
ናቸውና።

[13]አንተ ውስጣዊ ሰውነቴን ፈጥረሃልና፤
በእናቴም ማሕፀን ውስጥ አበጃጅተህ
ሠራኸኝ።
[14]ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና
አመሰግንሃለሁ፤
ሥራህ ድንቅ ነው፤
ነፍሴም ይህን በውል ተረድታለች።
[15]እኔ በስውር በተሠራሁ ጊዜ፣
ዐጥንቶቼ ከአንተ አልተደበቁም፤
በምድር ጥልቀት ውስጥ በጥበብ
በተሠራሁ ጊዜ፣
[16]ዐይኖችህ ገና ያልተበጀውን አካሌን
አዩ፤
ለእኔ የተወሰኑልኝም ዘመናት፣
ገና አንዳቸው ወደ መኖር ሳይመጡ፣
በመጽሐፍ ተመዘገቡ።

[17]አምላክ ሆይ፤ ለእኔ ያለህ ሐሳብ
እንዴት ክቡር ነው!
ቍጥሩስ ምንኛ ብዙ ነው!
[18]ልቍጠራቸው ብል፣
ከአሸዋ ይልቅ ይበዙ ነበር።
ተኛሁም ነቃሁም፣
ገና ከአንተው ጋር ነኝ።

[19]አምላክ ሆይ፣ ክፉዎችን ብትገድላቸው
ምናለበት!
ደም የተጠማችሁ ሰዎች ሆይ፤ ከእኔ ራቀ
ሁ!
[20]ስለ አንተ በክፋት ይናገራሉና፤
ጠላቶችህም ስምህን በከንቱ ያነሣሉ።
[21]እግዚአብሔር ሆይ፤ የሚጠሉህን
አልጠላምን?
በአንተ ላይ የሚነሡትንስ
አልጸየፍምን?
[22]በፍጹም ጥላቻ ጠልቻቸዋለሁ፤
ባላጋራዎቼም ሆነዋል።

[23]እግዚአብሔር ሆይ፤ መርምረኝ፤ ልቤንም
ዕወቅ፤
ፈትነኝ፤ ሐሳቤንም ዕወቅ፤
[24]የክፋት መንገድ በውስጤ ቢኖር እይ፤
በዘላለምም መንገድ ምራኝ።

139፥10 መዝ23፥3፤108፥6፤ኢሳ41፥10
139፥12 ኢዮ34፥22፤ዳን2፥22
139፥13 ኢዮ10፥11፤መዝ119፥73፤ኢሳ44፥2፡24፤46፥3፤49፥5፤ኤር1፥5
139፥14 ኢዮ40፥19፤መዝ119፥164፤145፥10
139፥15 ኢዮ10፥11፤መዝ63፥9፤መክ11፥5
139፥16 ኢዮ33፥29፤መዝ90፥12
139፥17 ኢዮ5፥9፤መዝ92፥5
139፥18 ኢዮ29፥18፤መዝ3፥5፤40፥5
139፥19 መዝ5፥6፤6፥8፤59፥2፤ኢሳ11፥4
139፥20 ዘዳ5፥11፤መዝ65፥7
139፥21 2ዜና19፥2፤መዝ26፥5፤31፥6፤119፥113
139፥22 ማቴ5፥43
139፥23 1ሳሙ16፥7፤1ዜና29፥17፤ኢዮ31፥6፤መዝ7፥9፤ምሳ17፥3፤ኤር11፥20፤ራእ2፥23
139፥24 መዝ5፥8፤23፥2፤143፥10፤ኤር25፥5፤36፥3
140፥1 ቍ11፤መዝ17፥13፤25፥20፤59፥2፤71፥4፤86፥14፤142፥6፤143፥9
140፥2 መዝ36፥4፤52፥2፤68፥30፤ምሳ6፥14፤16፥27፤ኢሳ59፥4፤ሆሴ7፥15
140፥3 መዝ57፥4፤58፥4፤ሮሜ3፥13፤ያዕ3፥8
140፥4 መዝ36፥11፤141፥9
140፥5 ኢዮ18፥8፡9፤34፥30፤መዝ31፥4፤38፥12፤119፥110
140፥6 መዝ16፥2፤28፥2፡6
140፥7 መዝ68፥20
140፥8 መዝ10፥2-3፤66፥7
140፥9 ምሳ18፥7
140፥10 መዝ11፥6፤21፥9፤ማቴ3፥10፤ሉቃ12፥49፤ራእ20፥15
140፥11 መዝ34፥21
140፥12 1ነገ8፥45፤መዝ35፥10፤82፥3
140፥13 መዝ11፥7፤16፥11፤138፥2
141፥1 መዝ4፥1፤5፥1-2፤22፥19፤27፥7፤143፥1
141፥2 ዘፀ29፥39፡41፤30፥8፤መዝ28፥2፤

## መዝሙር 140
## በክፉዎች ላይ የቀረበ ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር*

[1]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ከክፉ ሰዎች
አድነኝ፤
ከዐመፀኞችም ሰዎች ጠብቀኝ፤
[2]እነርሱ በልባቸው ክፉ ነገር
ያውጠነጥናሉ፤
በየዕለቱም ጦርነት ይጭራሉ።
[3]ምላሳቸውን እንደ እባብ ያሾላሉ፤
ከከንፈራቸውም በታች የእፉኝት
መርዝ አለ። ሴላ

[4]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ከክፉዎች እጅ
ጠብቀኝ፤
እግሮቼንም ለመጥለፍ ከሚያደቡ
ዐመፀኞች ሰውረኝ።
[5]ትዕቢተኞች ወጥመድ በስውር አስቀመጡብኝ፤
የመረባቸውን ገመድ ዘረጉብኝ፤
በመንገዴም ላይ አሽክላ አኖሩ። ሴላ

[6]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ "አንተ አምላኬ ነህ"
እልሃለሁ፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ የልመና ጩኸቴን
ስማ።
[7]ብርቱ አዳኝ የሆንህ፣ ጌታ *እግዚአብሔር*
ሆይ፤
በጦርነት ዕለት የራስ ቍር ሆንኸኝ።
[8]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ የክፉዎች ምኞት
አይፈጸም፤
በትዕቢትም እንዳይኵራሩ፣
ዕቅዳቸው አይሳካ። ሴላ

[9]ዙሪያዬን የከበቡኝ ሰዎች ራስ፣
የከንፈራቸው መዘዝ ይጠምጠምበት።
[10]የእሳት ፍም በላያቸው ይውረድ፤
ዳግመኛም እንዳይነሡ ወደ እሳት ይጣሉ፤
ማጥ ወዳለበት ጒድጓድ ይውደቁ።
[11]ምላሰኛ በምድሪቱ ጸንቶ አይኑር፤
ዐመፀኛውን ሰው ክፋት አሳዶ
ያጥፋው።

[12]*እግዚአብሔር* ለድኻ ፍትሕን
እንደሚያስከብር፣
ለችግረኛውም ትክክለኛ ፍርድን
እንደሚሰጥ ዐውቃለሁ።
[13]ጻድቃን በእውነት ስምህን ያመሰግናሉ፤
ቅኖችም በፊትህ ይኖራሉ።

## መዝሙር 141
## የክፉዎችን ድሎት ለመመኘት የቀረበ ጸሎት

[1]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ወደ አንተ እጣራ
ለሁ፤ ፈጥነህ ድረስልኝ፤
ወደ አንተ ስጣራም ድምፄን ስማ።
[2]ጸሎቴ በፊትህ እንደ ዕጣን ትቈጠርልኝ፤

እጄን ማንሣቴም እንደ ሠርክ
መሥዋዕት ትሁን።

3እግዚአብሔር ሆይ፤ ለአፌ ጠባቂ
አድርግ፤
የከንፈሮቼንም መዝጊያ ጠብቅ።
4ከዐመፀኞች ጋር፣
በክፉ ሥራ እንዳልተባበር፣
ልቤን ወደ ክፉ አታዘንብል፤
ከድግሳቸውም አልቋደስ።

5ጻድቅ[ሸ] ሰው ይቅጣኝ፤ ይህ በጎነት ነው፤
ይገሥጸኝም፤ በራሴ ላይ እንደሚፈስ
ዘይት ነው፤
ራሴም ይህን እንቢ አይልም።

ጸሎቴ ግን በክፉዎች ተግባር ላይ ነው፤
6ሹማምታቸው ከገደል አፋፍ ቍልቍል
ይወረወራሉ፣
ቃሌ የምታረካ ናትና፣ ይሰሚታል።
7ደግሞም፣ "ሰው ምድርን እንደሚያርስና
ዐፈሩን እንደሚፈረካክስ፣
እንዲሁ ዐጥንታችን በሲኦል[ቀ] አፋፍ
ላይ ተበታተነ" ይላሉ።

8ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፤ ዐይኖቼ ግን
ወደ አንተ ይመለከታሉ፤
መጠጊያዬም አንተ ነህ፤ እንግዲህ
ነፍሴን አትተዋት።
9ከዘረጉብኝ ወጥመድ፣
ከክፉ አድራጊዎችም አሽክላ ጠብቀኝ።
10እኔ ብቻ በደህና ሳመልጥ፣
ክፉዎቹ በገዛ ወጥመዳቸው ይውደቁ።

## መዝሙር 142

### የሚታደን ሰው ጸሎት

ዋሻ ውስጥ በነበረ ጊዜ፤ የዳዊት ትምህርት፤[በ] ጸሎት

1ድምፄን ከፍ አድርጌ ወደ እግዚአብሔር
እጮኻለሁ፤
ድምፄን ከፍ አድርጌ ወደ እግዚ
አብሔር ልመና አቀርባለሁ።
2ብሶቴን በፊቱ አፈስሳለሁ፤
ችግሬንም በፊቱ እናገራለሁ።

3መንፈሴ በውስጤ ሲዝል፣
መንገዴን የምታውቅ አንተ ነህ፤
በመተላለፊያ መንገዴ ላይ፤
ወጥመድ በስውር ዘርግተውብኛል።
4ወደ ቀኜ ተመልከት፤ እይም፤
ስለ እኔ የሚገደው የለም፤
ማምለጫም የለኝም፤
ስለ ነፍሴም ደንታ ያለው የለም።

5እግዚአብሔር ሆይ፤ ወደ አንተ እጮኻለሁ፤
ደግሞም፣ "አንተ መጠጊያዬ ነህ፤
በሕያዋንም ምድር ዕድል ፈንታዬ ነህ"
እላለሁ።
6እጅግ ተስፋ ቈርጫለሁና፣
ጩኸቴን ስማ፤
ከዐቅም በላይ ሆነውብኛልና፣
ከሚያሳድዱኝ አድነኝ።
7ስምህን አመሰግን ዘንድ፣
ነፍሴን ከወህኒ አውጣት፤
ከምታደርግልኝም በጎ ነገር የተነሣ፣
ጻድቃን በዙሪያዬ ይሰበሰባሉ።

## መዝሙር 143

### ትሑት ልመና

የዳዊት መዝሙር

1እግዚአብሔር ሆይ፤ ጸሎቴን ስማ፤
ልመናዬን አድምጥ፤
በታማኝነትህና በጽድቅህም፣
ሰምተህ መልስልኝ።
2ሰው ሆኖ በፊትህ ጻድቅ የለምና፣
ባሪያህን ወደ ፍርድ አታቅርበው።

3ጠላት እስከ ሞት አሳዶኛል፤
ሕይወቴንም አድቅቆ ከዐፈር
ቀላቅሎአል፤
ቀደም ብለው እንደ ሞቱትም፣
በጨለማ ውስጥ አኑሮኛል።
4ስለዚህ መንፈሴ በውስጤ ዝላለች፤
ልቤም በውስጤ ደንግጦአል።

5የቀድሞውን ዘመን አስታወስሁ፤
ሥራህንም ሁሉ አሰላሰልሁ፤
የእጅህንም ሥራ አውጠነጠንሁ።
6እጆቼን ወደ አንተ ዘረጋሁ፤
ነፍሴም እንደ ምድረ በዳ አንተን
ተጠማች። ሴላ

7እግዚአብሔር ሆይ፤ ፈጥነህ መልስልኝ፤
መንፈሴ ደከመች፤
ወደ ጕድጓድ እንደሚወርዱት
እንዳልሆን፣
ፊትህን ከእኔ አትሰውር።
8በአንተ ታምኛለሁና፣
በማለዳ ምሕረትህን አሰማኝ፤
ነፍሴን ወደ አንተ አንሥቻለሁና፣
የምሄድበትን መንገድ አሳየኝ።
9እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተን መሰወሪያ
አድርጌአለሁና፣
ከጠላቶቼ አድነኝ።
10አንተ አምላኬ ነህና፣
ፈቃድህን እንድፈጽም አስተምረኝ፤
መልካሙ መንፈስህም፣
በቀናችው መንገድ ይምራኝ።
11እግዚአብሔር ሆይ፤ ስለ ስምህ ሕያው

63፥4፤ሉቃ1፥9፤1ጢሞ 2፥8፤ራእ5፥8፤8፥3
141፥3 መዝ12፥2፤34፥13 ፤ያዕ1፥26፤3፥8
141፥4 ኢሱ24፥23፤ መዝ106፥29፤ምሳ 23፥1-3
141፥5 ዘፀ29፥7፤መዝ 23፥5፤ምሳ9፥8፤19፥25፤ 25፥12፤መክ7፥5
141፥6 2ዜና25፥12
141፥7 ዘኍ16፥30፡ 32-33፤መዝ129፥3
141፥8 መዝ2፥12 ፤11፥1፤123፥2
141፥9 መዝ38፥12 ፤64፥5፤140፥4
141፥10 መዝ7፥15 ፤35፥8፤57፥6፤124፥7
142 ርዕስ 1ሳሙ 22፥1፤24፥3፤መዝ57 ርዕስ
142፥1 1ነገ8፥52፤ መዝ3፥4፤30፥8
142፥2 መዝ50፥15 ፤64፥1
142፥3 መዝ6፥2፤ 77፥3፤84፥2፤88፥4፤ 143፥4፡7፤ኤር8፥18፤ ሰቆ1፥22
142፥4 ኤር25፥35፤ 30፥17
142፥5 ዘዳ32፥9፤ ኢዮ28፥13፤መዝ 16፥5፤27፥13፤46፥1
142፥6 መዝ17፥1፤ 25፥20፤79፥8፤ኤር 31፥11
142፥7 2ዜና6፥41፤ መዝ7፥17፤9፥2፤ 66፥11
143፥1 ዘፀ34፥6፤ መዝ28፥2፤71፥2፤ 89፥1-2፤130፥2፤ 141፥1
143፥2 መዝ14፥3፤ ሮሜ3፥10
143፥3 መዝ107፥ 10፤ሰቆ3፥6
143፥4 መዝ30፥7
143፥5 ዘፍ24፥63፤ መዝ77፥6
143፥6 ዘፀ9፥29፤ ኢዮ11፥13
143፥7 መዝ22፥24 ፤27፥9፤30፥7፤69፥17፤ 142፥3
143፥8 ዘፀ33፥13፤ ኢዮ34፥32፤መዝ6፥4 ፤25፥1-2፤27፥11፤ 32፥8፤86፥4፤90፥14
143፥9 መዝ18፥17 ፤31፥15፤140፥1
143፥10 ነህ9፥20፤ መዝ25፥4-5፤26፥12፤ 31፥14፤119፥12
143፥11 መዝ25፥11 ፤31፥1፤41፥2፤71፥2

[ሸ]5 ወይም *ጻደቀ*
[ቀ]7 አንዳንድ ትርጕሞች *መቃብር* ይላሉ።
[በ]ርእሱ ላይ ሥነ ጽሑፋዊ ወይም የዜማ ቃል ሊሆን ይችላል።

አድርገኝ፤
በጽድቅህም ነፍሴን ከመከራ አውጣት፡፡
12ጠላቶቼንም ለእኔ ስላለህ ምሕረት
ደምስሳቸው፤
እኔ ባሪያህ ነኝና፣
ነፍሴን የሚያስጨንቋትን ሁሉ
አጥፋቸው፡፡

## መዝሙር 144

### የጦርነት መዝሙር

*የዳዊት መዝሙር*

1እጆቼን ለጦርነት፣
ጣቶቼን ለውጊያ የሚያሠለጥን፣
*እግዚአብሔር* ዐለቴ ይባረክ፡፡
2እርሱ አፍቃሪ አምላኬና ጽኑ ዐምባዬ
ነው፤
ምሽጌና ታዳጊዬ፣
የምከለልበትም ጋሻዬ ነው፤
ሕዝቤን የሚያስገዛልኝም[†] እርሱ ነው፡፡
3*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ይህን ያህል በልብህ
ስፍራ ትሰጠው ዘንድ ሰው ምንድን
ነው?
ታስበውስ ዘንድ የሰው ልጅ እስከዚህ
ምንድን ነው?
4ሰው እንደ እስትንፋስ ነው፤
ዘመኑም ፈጥኖ እንደሚያልፍ ጥላ
ነው፡፡
5*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ሰማያትህን
ሰንጥቀህ ውረድ፤
ይጤሱም ዘንድ ተራሮችን ዳስስ፡፡
6የመብረቅ ብልጭታ ልከህ በትናቸው፤
ፍላጻህን ሰደህ ግራ አጋባቸው፡፡
7እጅህን ከላይ ዘርጋ፤
ከኀይለኛ ውሃ፣
ከባዕዳንም እጅ፣
ታደገኝ፤ አድነኝም፤
8አንደበታቸው ሐሰትን ይናገራል፤
ቀኝ እጃቸውም የቅጥፈት ቀኝ እጅ
ናት፡፡
9አምላክ ሆይ፤ አዲስ ቅኔ እቀኝልሃለሁ፤
ዐሥር አውታር ባለው በገና
እዘምርልሃለሁ፡፡
10ነገሥታትን ድል የሚያጐናጽፍ፣
ባሪያውን ዳዊትን ከሚጐዳ ሰይፍ
የሚያድነው እርሱ ነው፡፡
11አንደበታቸው ሐሰትን ከሚናገር፣
ቀኝ እጃቸው የቅጥፈት ቀኝ እጅ
ከሆነችው፣
ከባዕዳን እጅ፣
ታደገኝ፤ አድነኝም፡፡
12ወንዶች ልጆቻችን በወጣትነታቸው፣
የተሟላ ዕድገት እንዳገኘ ተክል፣
ሴቶች ልጆቻችንም ቤተ መንግሥት
ለማስጌጥ፣
እንደ ተቀረጹ የማእዘን ዐምዶች
ይሁኑ፡፡
13ጐተራዎቻችን በተለያየ የእህል ዐይነት፣
የተሞሉ ይሁኑ፤
በጎቻችን እስከ ሺህ ይውለዱ፤
በመስኮቻችንም እስከ ዐሥር ሺህ
ይባዙ፡፡
14ከብቶቻችን ይክበዱ፤[‡]
አይጨንግፉ፤ አይጥፉም፡፡
እኛም በምርኮ አንወሰድ፤
በአደባባዮቻችንም ዋይታ አይሰማ፡፡
15ይህ ባርኮት ገንዘቡ የሆነ ሕዝብ ምስጉን
ነው፤
*እግዚአብሔር* አምላኩ የሆነ ሕዝብ
ምስጉን ነው፡፡

## መዝሙር 145[ኀ]

### ምስጋና ለንጉሡ ለእግዚአብሔር

*የዳዊት የምስጋና መዝሙር*

1አምላኬና ንጉሤ ሆይ፤ ከፍ ከፍ
አደርግሃለሁ፤
ስምህን ከዘላለም እስከ ዘላለም
እባርካለሁ፡፡
2በየቀኑ እባርክሃለሁ፤
ስምህንም ከዘላለም እስከ ዘላለም
አመሰግናለሁ፡፡
3*እግዚአብሔር* ታላቅ ነው፤ እጅግ
ሊመሰገንም ይገባዋል፤
ታላቅነቱም አይመረመርም፡፡
4ሥራህን አንዱ ትውልድ ለሌላው
ትውልድ ያስተጋባል፤
ብርቱ ሥራህን ያውጃል፡፡
5ስለ ግርማህ ውበትና ክብር ይናገራሉ፤
ስለ ድንቅ ሥራህም[ነ] ያወራሉ፡፡
6ስለ ድንቅ ሥራህ ብርታት ይነጋገራሉ፤
እኔም ስለ ታላቅነትህ አውጃለሁ፡፡
7የበጎነትህን ብዛት በደስታ ያወሳሉ፤
ስለ ጽድቅህም በእልልታ ይዘምራሉ፡፡
8*እግዚአብሔር* ቸር ነው፤ ርኅሩኅም ነው፤
ለቍጣ የዘገየ፣ ምሕረቱ የበዛ፡፡
9*እግዚአብሔር* ለሁሉ ቸር ነው፤
ምሕረቱም በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ነው፡፡
10*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ፍጥረትህ ሁሉ
ያመሰግንሃል፤

[†]2 አንዳንዶች ሕዝቦችን የሚያስገዛልኝ ይላሉ፡፡
[‡]14 ወይም *መሪዎቻችን ይጠነክራሉ*፡፡
[ኀ]ም145 ይህ መዝሙር ተከታታይ በሆኑ የዕብራይስጥ ፊደላት የሚጀምር ሲሆን (ከቍ13 ጭምር) መነሻዎቹ ወይም መነሻዎቹና መድረሻዎቹ ሆህያት ቀልቀል ሲነበቡ ትርጉም ያላቸውን ቃላት የሚፈጥሩ ናቸው፡፡

143፥12 መዝ8፥2፤ 54፥5፤116፥16
144፥1 ዘፍ49፥24
144፥2 ዘፍ15፥1፤ መሳ4፥23፤መዝ18፥2፡ 39፤27፥1፤37፥39፤ 43፥2፤59፥9፤91፥2
144፥3 ዕብ2፥6
144፥4 1ዜና29፥15 ፤ኢዮ7፥7፤14፥2፤27፥3 ፤ኢሳ2፥22፤ያዕ4፥14
144፥5 ዘፍ11፥5፤ መዝ18፥9፤57፥3፤ 104፥32፤ኢሳ64፥1
144፥6 መዝ7፥12-13፤18፥14፤59፥11፤ 68፥1፤ዕን3፥11፤ ዘካ9፥14
144፥7 2ሳሙ22፥17 ፤መዝ3፥7፤18፥44፤ 57፥3፤69፥2
144፥8 ዘፍ14፥22፤ ዘዳ32፥40፤መዝ12፥2፤ 36፥3፤41፥6
144፥9 መዝ28፥7፤ 33፥2-3፤71፥22፤96፥1
144፥10 2ሳሙ8፥14 ፤ኢዮ5፥20፤መዝ 18፥50
144፥11 መዝ3፥7፤ 12፥2፤18፥44፤25፥20፤ 36፥3፤41፥6-7፤ 106፥26፤ኢሳ44፥20
144፥12 መዝ92፥12-14፤128፥3፤መሓ4፥4 ፤7፥4
144፥13 ምሳ3፥10
144፥14 2ነገ25፥11 ፤ምሳ14፥4፤ኢሳ24፥ 11፤ ኤር14፥2-3
144፥15 ዘዳ28፥3
145፥1 መዝ2፥6፤ 5፥2፤30፥1፤34፥1፤ 54፥6
145፥2 መዝ34፥1፤ 71፥6፤ኢሳ25፥1፤ 26፥8
145፥3 2ሳሙ22፥4 ፤ኢዮ5፥9፤መዝ95፥3 ፤96፥41
145፥4 ዘዳ11፥19፤ መዝ22፥30፤71፥16
145፥5 መዝ75፥1፤ 96፥6፤148፥13
145፥6 ዘዳ32፥3፤ መዝ66፥3፤75፥1፤78፥4 ፤106፥22
145፥7 ዘፀ18፥9፤ መዝ5፥11፤27፥13፤10 1፥1፤138፥5
145፥8 መዝ86፥5፡ 15፤103፥8
145፥9 1ዜና16፥34 ፤መዝ103፥13-14፤ 136፥1፤ማቴ19፥17፤ ማር10፥18
145፥10 መዝ8፥6፤ 30፥4፤103፥22፤115፥1 7-18፤139፥14፤

ቅዱሳንህም ይባርኩሃል፡፡
11ስለ መንግሥትህ ክብር ይናገራሉ፤
ስለ ኀይልህም ይነጋገራሉ፤
12በዚህም ብርቱ ሥራህን፣
የመንግሥትህንም ግርማ ክብር
ያስታውቃሉ፡፡
13መንግሥትህ የዘላለም መንግሥት ናት፤
ግዛትህም ለትውልድ ሁሉ ጸንቶ
ይኖራል፡፡

እግዚአብሔር ቃሉን ሁሉ ይጠብቃል፤
በሥራውም[ኘ] ሁሉ ቸር ነው፡፡
14እግዚአብሔር የሚንገዳገዱትን ሁሉ
ይደግፋል፤
የወደቁትንም ሁሉ ያነሣል፡፡
15የሁሉ ዐይን አንተን በተስፋ ይጠብቃል፤
አንተም ምግባቸውን በወቅቱ
ትሰጣቸዋለህ፡፡
16አንተ እጅህን ትዘረጋለህ፤
የሕያዋን ፍጥረታትንም ሁሉ ፍላጎት
ታረካለህ፡፡

17እግዚአብሔር በመንገዱ ሁሉ ጻድቅ፣
በሥራውም ሁሉ ቸር ነው፡፡
18እግዚአብሔር ለሚጠሩት ሁሉ፣
በእውነት ለሚጠሩት ሁሉ ቅርብ ነው፡፡
19ለሚፈሩት ፍላጎታቸውን ይፈጽማል፤
ጩኸታቸውን ይሰማል፤ ያድናቸዋልም፡፡
20እግዚአብሔር የሚወዱትን ሁሉ
ይጠብቃል፤
ክፉዎችን ሁሉ ግን ያጠፋል፡፡

21አፌ የእግዚአብሔርን ምስጋና ይናገራል፤
ፍጡር ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም፣
ቅዱስ ስሙን ይባርክ፡፡

## መዝሙር 146

### ለረድኤት አምላክ ምስጋና

1ሃሌ ሉያ፡፡[አ]
ነፍሴ ሆይ፤ እግዚአብሔርን ባርኪ፡፡
2በምኖርበት ዘመን ሁሉ እግዚአብሔርን
አመሰግናለሁ፤
በሕይወትም እስካለሁ ለአምላኬ
እዘምራለሁ፡፡
3በገዦች አትታመኑ፤
ማዳን በማይችሉ ሥጋ ለባሾችም
አትመኩ፡፡
4መንፈሳቸው ትወጣለች፤ ወደ
መሬታቸውም ይመለሳሉ፤
ያን ጊዜም ዕቅዳቸው እንዳልነበር
ይሆናል፡፡

5ረዳቱ የያዕቆብ አምላክ የሆነ፣
ተስፋውንም በአምላኩ በእግዚአብሔር
ላይ የጣለ ሰው ምስጉን ነው፤
6እርሱ ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንም፣

148፥14፤149፥9
145፥11 ቍ12-13፤ ዘፀ15፥2፤መዝ21፥13፤ ማቴ6፥33
145፥12 ቍ11፤መዝ 75፥1፤103፥19፤105፥1 ፤ኢሳ2፥10፥19፥21
145፥13 ዘፀ15፥18፤ ዘዳ7፥9፤ኢሱ23፥14፤ 1ቆሮ1፥9፤1ጢሞ 1፥17፤2ጴጥ1፥11፤ ራእ11፥15
145፥14 1ሳሙ2፥8 ፤መዝ37፥17፤38፥6፤ 146፥8
145፥15 ዘፍ1፥30፤ ኢዮ28፥5፤መዝ 37፥25፤ማቴ6፥26
145፥16 መዝ90፥14 ፤104፥28
145፥17 ቍ13፤ዘፀ 9፥27፤ዕዝ9፥15
145፥18 ዘኍ23፥21 ፤መዝ18፥6፤46፥1፤ 80፥18፤ፊል4፥5
145፥19 1ሳሙ10፥ 19፤ኢዮ22፥28፤መዝ 7፥10፤20፥4፤31፥22፤3 4፥18፤40፥1
145፥20 መዝ1፥6፤ 31፥23፤91፥14፤94፥23 ፤97፥10
145፥21 ዘፀ3፥15፤ መዝ30፥4፤65፥2፤71፥8፤ 99፥3፤150፥6
146፥1 መዝ103፥1፤ 104፥1
146፥2 መዝ63፥4፤ 104፥33፤105፥2
146፥3 መዝ60፥11፤ 108፥12፤118፥9፤ኢሳ 2፥22
146፥4 ዘፍ3፥19፤ኢዮ 7፥21፤መዝ33፥10፤ 103፥14፤መክ12፥7፤ 1ቆሮ2፥6
146፥5 መዝ33፥18፤ 37፥9፤70፥5፤71፥5፤ 119፥43፤121፥2፤ 144፥15፤ኤር17፥7
146፥6 ዘዳ7፥9፤2ዜና 2፥12፤መዝ18፥25፤ 108፥4፤115፥15፤117፥2፤ ሐሥ14፥15፤ራእ10፥6
146፥7 መዝ37፥17፤ 66፥11፤68፥6፤103፥6፤ 107፥9፤145፥15
146፥8 ዘፀ4፥11፤ዘዳ 7፥13፤ኢዮ23፥10፤ መዝ38፥6፤ምሳ20፥12፤ ኢሳ29፥18፤32፥3፤ 35፥5፤42፥7፥18-19፤ 43፥8፤ማቴ11፥5
146፥9 ዘፀ22፥22፤ ዘሌ19፥34፤መዝ10፥18 ፤ያዕ1፥27
146፥10 ዘፍ21፥33፤ 1ዜና16፥31፤መዝ93፥1 ፤99፥1፤ራእ11፥15
147፥1 መዝ33፥1፤ 135፥3
147፥2 መዝ51፥18

በእነዚህም ውስጥ ያለውን ሁሉ የፈጠረ፣
ታማኝነቱንም ለዘላለም የሚጠብቅ ነው፤
7ለተበደሉት የሚፈርድ፣
ለተራቡት ምግብን የሚሰጥ እርሱ ነው፤
እግዚአብሔር እስረኞችን ከእስራት
ያወጣል፤
8እግዚአብሔር የዕውራንን ዐይን ያበራል፤
እግዚአብሔር የተዋረዱትን ከፍ
ያደርጋል፤
እግዚአብሔር ጻድቃንን ይወዳል፤
9እግዚአብሔር ስደተኞችን ይጠብቃል፤
ድኻ አደጎችንና መበለቶችን ይደግፋል፤
የክፉዎችን መንገድ ግን ያጠፋል፡፡

10እግዚአብሔር ለዘላለም ይነግሣል፤
ጽዮን ሆይ፤ አምላክሽ ለትውልድ ሁሉ
ንጉሥ ነው፡፡

ሃሌ ሉያ፡፡

## መዝሙር 147

### መዝሙር ለሁሉን ቻይ አምላክ

1ሃሌ ሉያ፡፡[ከ]

አምላካችንን በመዝሙር ማወደስ እንዴት
መልካም ነው፤
እርሱን ማመስገን ደስ ያሰኛል፤ ይህ
ተገቢም ነው፡፡

2እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን መልሶ
ይሠራታል፤
ከእስራኤል የተበተኑትን ይሰበስባል፡፡
3ልባቸው የተሰበረውን ይፈውሳል፤
ቍስላቸውንም ይጠግናል፡፡
4የከዋክብትን ብዛት ያውቃል፤
እያንዳንዱንም በስሙ ይጠራዋል፡፡
5ጌታ ችን ታላቅ ነው፤ እጅግ ኀያልም
ነው፤
ለጥበቡም ወሰን የለውም፡፡
6እግዚአብሔር የተናቁትን ከፍ ያደርጋል፤
ክፉዎችን ግን ወደ ምድር ይጥላል፡፡

7ለእግዚአብሔር በምስጋና ዘምሩ፤
ለአምላካችንም በመሰንቆ ምስጋና
አቅርቡ፡፡
8ሰማይን በደመናት የሚሸፍን እርሱ ነው፤

፤106፥47 147፥3 ዘኍ12፥13፤ኢዮ5፥18፤መዝ34፥18፤ኢሳ1፥6፤ ሕዝ34፥16 147፥4 ዘፍ15፥5 147፥5 ዘፀ14፥31፤መዝ48፥1፤ 145፥3፤ኢሳ40፥28 147፥6 2ዜና33፥23፤መዝ37፥9-10፤ 145፥20፤146፥8-9 147፥7 መዝ27፥6፤30፥4፤33፥3፤42፥4፤ 98፥5 147፥8 ዘዳ11፥14፤32፥2፤2ሳሙ1፥21፤ኢዮ5፥10፤ 26፥8፤28፥26፤መዝ104፥14

[ኀ]5 የሙት ባሕር ጥቅልሎች እና ሱርስት (የሰብዓ ሊቃናትን ትርጒም ይመ) ስለግርማህ ታላቅነትና ክብር፣ ዕፁብ ድንቅ ሥራህን አሰላስላለሁ ይላሉ፡፡
[ኘ]13 አንድ የማስሬቲክ ቅጅ፣ የሙት ባሕር ጥቅልሎች እና ሱርስት (የሰብዓ ሊቃናትን ትርጒም ይመ) እንዲሁም አብ ዛኛው የማስሬቲክ ቅጆች የቍ13 ሁለት ስንኞች የሏቸውም፡፡
[አ]1 አንዳንዶች ከ10 ጭምር እግዚአብሔር ይመስገን ይላሉ፡፡
[ከ]1 አንዳንዶች ከቍ20 ጭምር እግዚአብሔር ይመስገን ይላሉ፡፡

ለምድርም ዝናብን ይሰጣል፤
በተራሮችም ላይ ሣር ያበቅላል።
9ለእንስሳት ምግባቸውን፣
የቍራ ጫጩቶችም ሲንጫጩ
የሚበሉትን ይሰጣቸዋል።

10እርሱ በፈረስ ኀይል አይደሰትም፤
በሯጭም ብርታት ላይ ደስታውን
አያደርግም።
11ነገር ግን *እግዚአብሔር* በሚፈሩት፣
በምሕረቱ በሚታመኑትም ይደሰታል።

12ኢየሩሳሌም ሆይ፤ *እግዚአብሔርን*
አመስግኚ፤
ጽዮን ሆይ፤ አምላክሽን አወድሺ፤
13እርሱ የደጆችሽን መወርወሪያ
አጽንቶአልና፤
ልጆችሽንም በውስጥሽ ባርኮአል።
14በድንበርሽ ውስጥ ሰላም ያሰፍናል፤
ማለፊያ ስንዴም ያጠግብሻል።

15ትእዛዙን ወደ ምድር ይልካል፤
ቃሉም እጅግ በፍጥነት ይሮጣል።
16ዐመዳዩን እንደ በርኖስ ይዘረጋል፤
ውርጩን እንደ ዐመድ ይነሰንሳል።
17የበረዶውን ድንጋይ ቍልቍል ይለቃል
ይወረውረዋል፤
በውሽንፍሩስ ቅዝቃዜ ፊት ማን ሊቆም
ይችላል?
18ቃሉን ልኮ፤ ያቀልጣቸዋል፤
ነፋሱን ያነፍሳል፤ ውሆችንም ያፈሳል።

19ቃሉን ለያዕቆብ፣
ሥርዐቱንና ፍርዱን ለእስራኤል
ይገልጣል።
20ይህን ለማንኛውም ሌላ ሕዝብ
አላደረገም፤
እነርሱም ፍርዱን አላወቁም።

ሃሌ ሉያ።

## *መዝሙር* 148

### ፍጥረተ ዓለም ሁሉ ያመስግን

1ሃሌ ሉያ።[ኸ]

*እግዚአብሔርን* ከሰማያት አመስግኑት፤
በላይ በአርያም አመስግኑት።
2መላእክቱ ሁሉ አመስግኑት፤
ሰራዊቱ ሁሉ አመስግኑት፤
3ፀሓይና ጨረቃ አመስግኑት፤
የምታበሩ ከዋክብት ሁሉ አመስግኑት።
4ሰማየ ሰማያት አመስግኑት፤
ከሰማያትም በላይ ያላችሁ ውሆች
አወድሱት።
5እርሱ ስላዘዘ ተፈጥረዋልና፣
*የእግዚአብሔርን* ስም ያመስግኑት።
6ከዘላለም እስከ ዘላለም አጸናቸው፤
የማይሻርም ሕግ ደነገገላቸው።

7የባሕር ውስጥ ግዙፍ ፍጥረትና ጥልቅ
ውሆች ሁሉ፣
*እግዚአብሔርን* ከምድር አመስግኑት።
8እሳትና በረዶ፣ ዐመዳይና ጭጋግ፣
ትእዛዙንም የሚፈጽም ዐውሎ ነፋስ፣
9ተራሮችና ኰረብቶች ሁሉ፣
የፍሬ ዛፎችና ዝግቦች ሁሉ፣
10የዱር አራዊትና የቤት እንስሳት ሁሉ፣
በምድር የሚሳቡ ፍጥረታትና የሚበሩ
ወፎችም፣
11የምድር ነገሥታትና ሕዝቦች ሁሉ፣
መሳፍንትና የምድር ገዦች ሁሉ፣
12ወጣት ወንዶችና ደናግል፣
አረጋውያንና ልጆች ያመስግኑት።

13ስሙ ብቻውን ከፍ ያለ ነውና፣
ክብሩም ከምድርና ከሰማይ በላይ ነውና፣
እነዚህ ሁሉ *የእግዚአብሔርን* ስም
ያመስግኑ።
14እርሱ ለሕዝቡ ቀንድን[ሠ] አስነሥቶአል፤
ለቅዱሳኑ ሁሉ ምስጋና፣
እጅግ ቅርቡ ለሆነው ሕዝቡ፣ ለእስራኤል
ልጆች።

ሃሌ ሉያ።

## *መዝሙር* 149

### የድል *መዝሙር*

1ሃሌ ሉያ።[ዐ]

*ለእግዚአብሔር* አዲስ ቅኔ ተቀኙ፤
ምስጋናውንም በቅዱሳን ጉባኤ ዘምሩ።

2እስራኤል በፈጣሪው ደስ ይበለው፤
የጽዮንም ልጆች በንጉሣቸው ሐሤት
ያድርጉ።
3ስሙን በሽብሰባ ያመስግኑ፤
በከበሮና በመሰንቆ ይዘምሩለት።
4*እግዚአብሔር* በሕዝቡ ደስ ይለዋልና፤
የዋሃንንም በማዳኑ ውበት ያጐናጽፋል።
5ቅዱሳን በዚህ ክብር ይኵራሩ፤
በመኝታቸውም ላይ እልል እያሉ ይዘምሩ።

6የአምላክ ውዳሴ በአንደበታቸው፣
ባለ ሁለት ልሳን ሰይፍም በእጃቸው
ይሁን፤
7በዚህ ሕዝቦችን ይበቀላሉ፤
ሰዎችንም ይቀጣሉ፤

**147፥9** ዘፍ1፥30፤ 8፥7፤መዝ104፥27-28፤ማቴ6፥26
**147፥10**1ሳሙ16፥7፤ኢዮ39፥11፤መዝ33፥16-17
**147፥11** መዝ6፥4፤ 33፥18፤35፥27፤103፥11፤119፥43
**147፥12** መዝ48፥1
**147፥13** ዘዳ33፥25፤ዘሌ25፥21፤መዝ128፥5፤134፥3
**147፥14** ዘሌ26፥6፤ ዘዳ32፥14፤2ሳሙ7፥10፤መዝ132፥15፤ኢሳ 48፥18
**147፥15** ኢዮ37፥12፤መዝ33፥9፤148፥5፤ ኢሳ55፥1
**147፥16**መዝ148፥8፤ ኢዮ37፥12፤38፥29
**147፥17** ዘፀ9፥22-23፤ ኢዮ38፥22፤መዝ78፥47
**147፥18** ቍ15፤መዝ 33፥9፤50፥3፤107፥20
**147፥19** ዘፀ20፥1፤ ዘዳ33፥4፤ኢሱ1፥8፤ 2ነገ22፥8፤መዝ78፥5፤ ሚል4፥4፤ሮሜ3፥2፤ 9፥4
**147፥20** ዘዳ4፥7-8 ፡32-34፤መዝ33፥2፤ 79፥6፤103፥1
**148፥1** መዝ19፥1፤ 33፥2፤69፥34፤103፥1፤ 150፥1
**148፥2** 1ነገ22፥19፤ መዝ103፥20
**148፥3** መዝ19፥1
**148፥4** ዘፍ1፥7፤ ዘዳ10፥14
**148፥5** መዝ145፥21፤147፥15
**148፥6** ኤር31፥35-36፤33፥25
**148፥7** ዘፍ1፥21፤ ዘዳ33፥13፤መዝ33፥2፤ 74፥13-14
**148፥8** ዘፀ9፥18፤ ኢሱ10፥11፤ኢዮ37፥ 11-12፤መዝ103፥20፤ 147፥15-18
**148፥9** ኢሳ44፥23፤ 49፥13፤55፥12
**148፥10** ኢሳ43፥20፤ሆሴ2፥18
**148፥11** መዝ102፥15
**148፥13** መዝ8፥1፤ 113፥2፤138፥4፤145፥5
**148፥14** ዘፀ15፥2፤ ዘዳ26፥19፤1ሳሙ2፥1፤ መዝ22፥3፤145፥10
**149፥1** መዝ1፥5፤ 28፥7፤33፥2፤96፥1፤ 103፥1፤ራእ5፥9
**149፥2** ኢዮ10፥3፤ መዝ10፥16፤47፥6፤ 95፥6፤ኢሳ13፥3፤32፥1፤ 44፥2፤45፥11፤54፥5፤ኤር51፥48፤ዘካ9፥9

**149፥3** ዘፀ15፥20፤57፥8 **149፥4** መዝ35፥27፤132፥16፤ 147፥11 **149፥5** ኢዮ35፥10፤ 42፥8፤132፥16 **149፥6** ነህ4፥17፤መዝ66፥17፤ዕብ4፥12፤ራእ1፥16
**149፥7** ዘኍ31፥3፤ ዘዳ32፥41፤መዝ81፥15

[ኸ]1 አንዳንዶች ከቍ14 ጭምር *እግዚአብሔር ይመስገን* ይላሉ።
[ሠ]14 ቀንድ የጥንካሬ ትእምርት ሲሆን *ንጉሥን* ያመለክታል።
[ዐ]1 አንዳንዶች ከቍ9 ጭምር *እግዚአብሔር ይመስገን* ይላሉ።

8ነገሥታታቸውን በሰንሰለት፣
መኳንንታቸውንም በእግር ብረት
ያስራሉ፤
9ይህም በእነርሱ ላይ የተጻፈውን ፍርድ
ለመፈጸም ነው።
ለቅዱሳኑም ሁሉ ይህች ክብር ናት።

ሃሌ ሉያ።

## መዝሙር 150

### የምስጋና መዝሙር

1ሃሌ ሉያ።"

እግዚአብሔርን በመቅደሱ አመስግኑት፤
በታላቅ ጠፈሩ አወድሱት።
2ስለ ብርቱ ሥራው አመስግኑት፤
እጅግ ታላቅ ነውና ወድሱት።
3በመለከት ድምፅ አመስግኑት፤
በበገናና በመሰንቆ ወድሱት።
4በከበሮና በሽብሸባ አመስግኑት፤
በባለ አውታር መሣሪያና በእምቢልታ
አወድሱት።
5ተርገብጋቢ ድምፅ ባለው ጸናጽል
አመስግኑት፤
ድምፀ መልካም በሆነ ጸናጽል
ወድሱት።

6እስትንፋስ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን
ያመስግን።

ሃሌ ሉያ።

"1 አንዳንዶች ከቍ6 ጭምር እግዚአብሔር ይመስገን ይላሉ።

149፥8 2ሳሙ3፥34፤2ዜና33፥11፤ኢሳ14፥1-2
149፥9 ዘዳ7፥1፤መዝ145፥10፤ሕዝ28፥26
150፥1 መዝ68፥24-26፤73፥17፤102፥19፤112፥1፤148፥1
150፥2 ዘፀ15፥7፤ዘዳ3፥24
150፥3 ዘኍ10፥2፤መዝ57፥8
150፥4 ዘፍ4፥21፤ዘፀ15፥20፤መዝ45፥8
150፥5 2ሳሙ6፥5
150፥6 መዝ103፥22

# መጽሐፈ ምሳሌ

## መግቢያ የምሳሌዎቹ ዐላማና ጭብጥ

1 የእስራኤል ንጉሥ፣ የዳዊት ልጅ
የሰሎሞን ምሳሌዎች፤

2ጥበብንና ተግሣጽን ለመቀበል፤
ጥልቅ ሐሳብ የሚገልጡ ቃላትን
ለማስተዋል፤
3ጽድቅን፣ ፍትሕንና ሚዛናዊ ብያኔን
በማድረግ፣
የተገራ ጠቢብ ልቦናን ለማግኘት፤
4ብስለት ለሌላቸው አስተዋይነትን፣
በዕድሜ ለጋ ለሆኑት ዕውቀትንና
ልባምነትን ለመስጠት፤
5ጥበበኞች ያድምጡ፤ ትምህርታቸውንም
ያዳብሩ፤
አስተዋዮችም መመሪያ ያግኙበት፤
6ይህም የጠቢባንን ምሳሌዎችንና
ተምሳሌቶችን፣
አባባሎችንና ዕንቆቅልሾችን ይረዱ
ዘንድ ነው።

7*እግዚአብሔርን መፍራት የዕውቀት
መጀመሪያ ነው፤
ተላሎች*[ሀ] *ግን ጥበብንና ተግሣጽን
ይንቃሉ።*

## ጥበብን ገንዘብ ለማድረግ የተሰጠ ምክር

8ልጄ ሆይ፤ የአባትህን ምክር አድምጥ፤
የእናትህንም ትምህርት አትተው።
9ለራስህ ሞገስን የሚያጐናጽፍ አክሊል፣
አንገትህን የሚያስውብ ድሪ
ይሆንልሃል።

10ልጄ ሆይ፤ ኀጢአተኞች ቢያባብሉህ፣
እሺ አትበላቸው፤
11"ከእኛ ጋር ናና፣
ደም ለማፍሰስ እናድባ፤
በደል በሌለበት ሰው ላይ እንሸምቅ፤
12እንደ መቃብር፣ ወደ ጕድጓድ[ለ]
እንደሚወርዱ፣
ከነሕይወታቸው እንዳሉ እንዋጣቸው፤
13ውድ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ በያይነቱ
እናገኛለን፤
ቤቶቻችንንም በዝርፊያ እንሞላለን፤
14ከእኛ ጋር ዕጣህን ጣል፤
የጋራ ቦርሳ ይኖረናል" ቢሉህ፣
15ልጄ ሆይ፤ አብረሃቸው አትሂድ፤
በሚሄዱበትም መንገድ እግርህን
አታንሣ፤
16እግራቸው ወደ ኀጢአት ይቸኵላል፤
ደም ለማፍሰስም ፈጣኖች ናቸው።
17ወፎች ፊት እያዩ ወጥመድ መዘርጋት፣
ምንኛ ከንቱ ነው!
18እነዚህ ሰዎች የሚያደቡት በገዛ
ደማቸው ላይ ነው፤
የሚሸምቁትም በራሳቸው ላይ ብቻ
ነው።
19ያላግባብ ለጥቅም የሚሯሯጡ ሁሉ
መጨረሻቸው እንዲህ ነው፤
የሕይወታቸው መጥፊያም ይኸው
ነው።

## ጥበብን ለሚያናንቁ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

20ጥበብ በጐዳና ላይ ጮኻ ትጣራለች፤
በየአደባባዩ ድምፅዋን ከፍ ታደርጋለች፤
21ዉካታ በበዛባቸው ጐዳናዎች ላይ[ሐ]
ትጮኻለች፤
በከተማዪቱም መግቢያ በር ላይ
እንዲህ ትላለች፤

22"እናንት ብስለት የሌላችሁ[መ] ማስተዋል
የሌለበት መንገዳችሁን እስከ መቼ
ትወዱታላችሁ?
ፌዘኞች በፌዝ ደስ የሚሰኙት፣
ሞኞችስ ዕውቀትን የሚጠሉት እስከ
መቼ ነው?
23ዘለፋዬን ብትሰሙኝ ኖሮ፣
ልቤን ባፈሰስሁላችሁ፣
ሐሳቤንም ባሳወቅኋችሁ ነበር።
24ነገር ግን በተጣራሁ ጊዜ እምቢ
ስላላችሁኝ፣
እጄንም ስዘረጋ ማንም ግድ
ስላልነበረው፣
25ምክሬን ሁሉ ስለ ናቃችሁ፣
ዘለፋዬንም ስላልተቀበላችሁ፣
26እኔ ደግሞ በመከራችሁ እሥቅባችኋለሁ፤
መዓት በሚወርድባችሁም ጊዜ
አፌዝባችኋለሁ፤
27መዓት እንደ ማዕበል ሲያናውጣችሁ፣
መከራም እንደ ዐውሎ ነፋስ
ሲጠራርጋችሁ፣
ሥቃይና ችግር ሲያጥለቀልቃችሁ
አፌዝባችኋለሁ።

1፥1 1ነገ4፥29-34፤ ምሳ10፥1፤25፥1፤መክ 1፥1፤ማቴ13፥3
1፥4 ምሳ8፥5፡12
1፥5 ምሳ9፥9
1፥6 ዘኍ12፥8፤መሳ 14፥12፤መዝ49፥4፤ ምሳ22፥17፤24፥23፤ ማቴ13፥10-17
1፥7 ዘፀ20፥20፤ዘዳ 4፥6፤ኢዮ23፥15፤መዝ 34፥4-22፤112፥1 ፤ምሳ8፥33-36፤9፥7-9 ፡10፤12፥1፤13፥18፡19፤ 15፥32፡33፤ኢሳ33፥6 ፤50፥10፤59፥19፤ኤር8 ፥9
1፥8 ቀኍ8-9፤ዘዳ 21፥18፤ምሳ2፥1፤3፥1፤ 4፥1፤5፥1፤6፥1፡20፤7፥1 ፤19፥27፤22፥17፤23፥2 6-28፤ኤር35፥8
1፥9 ምሳ3፥21-22፤ 4፥1-9
1፥10ቀኍ15፤ዘዳ13፥8 ፤ኢዮ24፥15፤መዝ1፥1 ፤ምሳ16፥29
1፥11 መዝ10፥8
1፥12 ቀኍ16-18፤ ኢዮ33፥18፤መዝ30፥3 ፤35፥25
1፥14 ቀኍ19
1፥15ዘፍ49፥6፤መዝ 119፥101፤ምሳ4፥14
1፥16 ኢዮ15፥31፤ ምሳ 6፥18፤ኢሳ59፥7
1፥18 ቀኍ11-12 ፤መዝ71፥10
1፥19 ቀኍ13-14፤ ምሳ4፥14-17፤11፥19
1፥20 ኢዮ28፥12፤ ምሳ7፥10-13፤9፥1-3 ፡13-15
1፥22 መዝ50፥17፤ ምሳ 6፥32፤7፥7፤8፥5 ፤9፥4፡16
1፥24 1ሳሙ8፥19፤ ኢሳ65፥12፤66፥4፤ ኤር7፥13፤26፥5፤35፥1 7፤36፥31
1፥26 ቀኍ33ዘዳ28፥ 63 ፤2ነገ19፥21፤መዝ 2፥4፤59፥8
1፥27 መዝ18፥18፤ ምሳ5፥12-14

[ሀ]7 በመጽሐፈ ምሳሌና በብሉይ ኪዳን ሌሎች መጻሕፍት ውስጥ *ተላላ* የሚለው በተደጋጋሚ ተጽፏል፤ ይህም የሞራል ጕድለትን ያመለክታል።
[ለ]12 በዕብራይስጡ *ሲኦል* ይላል።
[ሐ]21 በዕብራይስጡና በሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች *በቅጥሮች ጫፍ ላይ* ይላሉ።
[መ]22 በዕብራይስጡ *ብስለት የሌለው* የሚለው ቃል በዚህ መጽሐፍ በአጠቃላይ መልካም ምግባር የሌለውንና ክፋትን ለማ ድረግ ልቡ ያዘነበለ ሰውን ያመለክታል።

28“በዚያን ጊዜ ይጠሩኛል፤ እኔ ግን
አልመልስላቸውም፤
አጥብቀው ይፈልጉኛል፤ ነገር ግን
አያገኙኝም።
29ዕውቀትን ስለ ጠሉ፣
እግዚአብሔርንም መፍራት
ስላልመረጡ፣
30ምክሬን ለመቀበል ስላልፈለጉ፣
ዘለፋዬን ስለ ናቁ፣
31የመንገዳቸውን ፍሬ ይበላሉ፤
የዕቅዳቸውንም ውጤት ይጠግባሉ።
32ብስለት የሌላቸውን ስድነታቸው
ይገድላቸዋል፤
ተላሎችንም ቸልተኝነታቸው
ያጠፋቸዋል፤
33የሚያዳምጠኝ ሁሉ ግን በሰላም ይኖራል፤
ክፉን ሳይፈራ ያለ ሥጋት
ይቀመጣል።”

## ከጥበብ የሚገኝ በረከት

2 ልጄ ሆይ፤ ቃሌን ብትቀበል፣
ትእዛዜንም በልብህ ብታኖር፣
2ጆሮህን ወደ ጥበብ ብታቀና፣
ልብህንም ወደ ማስተዋል ብትመልስ፣
3እንዲሁም የመለየት ጥበብን ብትማጠን፣
ድምፅህን ከፍ አድርገህ ማስተዋልን
ብትጣራ፣
4እርሷንም እንደ ብር ብትፈልጋት፣
እንደ ተሸሸገ ሀብት አጥብቀህ
ብትሻት፣
5በዚያን ጊዜ ፈሪሃ እግዚአብሔርን
ትረዳለህ፤
አምላክንም ማወቅ ታገኛለህ።
6እግዚአብሔር ጥበብን ይሰጣልና፤
ከአንደበቱም ዕውቀትና ማስተዋል
ይወጣል።
7እርሱ ለቅኖች ድልን ያከማቻል፤
ያለ ነቀፋ ለሚሄዱትም ጋሻ
ይሆናቸዋል፤
8የፍትሕን መንገድ ይጠብቃል፤
የታማኞቹንም አካሄድ ያጸናል።
9በዚያን ጊዜ ጽድቅን፣ ፍትሕን፣
ሚዛናዊነትን፣
መልካሙንም መንገድ ሁሉ
ትገነዘባለህ፤
10ጥበብ ልብህ ውስጥ ትገባለችና፤
ዕውቀትም ነፍስህን ደስ ታሰኛለች፤
11የመለየት ችሎታ ይጋርድሃል፤
ማስተዋልም ይጠብቅሃል።
12ጥበብ ንግግራቸው ጠማማ ከሆነ ሰዎች፣
ከክፉዎችም መንገድ ታድንሃለች፤
13እነዚህም በጨለማ መንገድ ለመሄድ፣
ቀናውን ጐዳና የሚተዉ ናቸው፤
14ክፉ በመሥራት ደስ የሚላቸው፣
በክፉት ጐዳና ሐሤት የሚያደርጉ፣
15መንገዳቸው ጠማማ፣
በአካሄዳቸው ጠመዝማዞች ናቸው።
16ከአመንዝራ ሴትም ትጠብቅሃለች፤
በአንደበቷም ከምታታልል ዘልዛላ
ታድንሃለች፤
17ይህችም የልጅነት ባሏን የተወች፣
በአምላኳ ፊት የገባችውን ኪዳንᵂ
ያቃለለች ናት።
18ቤቷ ወደ ሞት ያደርሳል፤
መንገዷም ወደ መናፍስተ ሙታን
ያመራል።
19ወደ እርሷ የሚገባ ማንም አይመለስም፤
የሕይወትንም መንገድ አያገኝም።
20አንተም በደጋግ ሰዎች ጐዳና ትሄዳለህ፤
የጻድቃንንም መንገድ ይዘህ ትጓዛለህ።
21ቅኖች በምድሪቱ ይቀመጣሉና፤
ነቀፋ የሌለባቸውም በእርሷ ላይ
ጸንተው ይኖራሉ።
22ክፉዎች ግን ከምድሪቱ ይወገዳሉ፤
ታማኝነት የጐደላቸውም ከእርሷ
ይነቀላሉ።

## ከጥበብ የሚገኝ ተጨማሪ በረከት

3 ልጄ ሆይ፤ ትምህርቴን አትርሳ፤
ትእዛዛቴን በልብህ ጠብቅ፤
2ቀኖችን ይጨምሩልሃል ዓመቶችንም
ያረዝሙልሃል፤
ሕይወት፣ ሀብትንና ሰላምን ያበዙልሃል።
3ፍቅርና ታማኝነት ከቶ አይለዩህ፤
በዐንገትህ ዙሪያ እሰራቸው፤
በልብህም ጽላት ላይ ጻፋቸው።
4በዚያን ጊዜ ሞገስንና መልካም ስምን፣
በእግዚአብሔርና በሰው ዘንድ ታገኛለህ።
5በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፤
በራስህ ማስተዋል አትደገፍ፤
6በመንገድህ ሁሉ እርሱን ዕወቅ፤
እርሱም ጐዳናህን ቀና ያደርገዋል።ᶜ
7በራስህ አስተያየት ጠቢብ ነኝ አትበል፤
እግዚአብሔርን ፍራ፤ ከክፉም ራቅ።
8ይህም ለሰውነትህ ጤንነትን፣
ለዐጥንትህም ልምላሜን ያመጣልሃል።
9እግዚአብሔርን በሀብትህ፣
ከምርትህ ሁሉ በኵራት አክብረው፤
10ይህን ብታደርግ፣ ጎተራህ ሞልቶ
ይትረፈረፋል፤
መጥመቂያህም በአዲስ የወይን ጠጅ
ቲፍ ብሎ ይሞላል።

1፥28 ዘዳ1፥45፤ 1ሳሙ8፥18፤ኢዮ27፥9፤ ምሳ8፥17፤ኤር 11፥11፤ሕዝ8፥18፤ ሆሴ5፥6፤ዘካ7፥13
1፥29 ኢዮ21፥14
1፥30 ቊ25
1፥31 2ዜና36፥16፤ መዝ14፥14፤ኤር6፥19 ፤14፥16፤21፥14፤30፥15
1፥32ምሳ5፥22፤15፥ 10፤ኢሳ66፥4
1፥33 ቊ21-26ዘኁ 24፥21፤ዘዳ33፥28፤ ምሳ3፥23፤መዝ112፥8
2፥1 ምሳ 1፥8
2፥2 መዝ22፥17፤ 23፥12
2፥3 ያዕ1፥5
2፥4 ኢዮ3፥21፤ ማቴ13፥44
2፥5 ዘዳ4፥6
2፥6 ኢዮ9፥4፤12፥13፤ 22፥22፤መዝ119፥34
2፥7 ዘፍ6፥9፤15፥1 ፤መዝ84፥11፤ምሳ30፥ 5-6
2፥8 1ሳሙ2፥9፤ መዝ18፥25፤97፥10
2፥9 ዘዳ1፥16
2፥10 ምሳ14፥33
2፥11 ምሳ4፥6
2፥12 ቊ16፤ምሳ 3፥13-18፤4፥5
2፥13 ምሳ4፥19
2፥14 ምሳ10፥23፤ 15፥21
2፥15 መዝ125፥5፤ ምሳ21፥8
2፥16 ምሳ5፥1-6፥ 20- 29፤7፥5-27
2፥17 ሚል2፥14
2፥18 ምሳ5፥5፤ 7፥27፤9፥18
2፥19 ምሳ3፥16-18፤ 5፥8፤መክ7፥26
2፥21 መዝ37፥29
2፥22 ዘዳ 28፥63፤ 29፥28፤ኢዮ18፥17፤ መዝ5፥4፤37፥9፥28- 29፤ምሳ10፥30
3፥1 መዝ44፥17፤ ምሳ1፥8
3፥2 ዘዳ5፥16፤11፥ 21፤30፥15፥16፤1ነገ 3፥13፥14፤ምሳ9፥6፥10-11
3፥3 ዘፀ13፥9፤ዘዳ 6፥6፤መዝ85፥10፤ምሳ 6፥21፤7፥3፤2ቆሮ3፥3
3፥4 1ሳሙ2፥26፤ ሉቃ2፥52
3፥5 መዝ4፥5
3፥6 ኢዮ33፥11፤ መዝ5፥8፤ምሳ16፥3፤ ኢሳ30፥11፤40፥3፤ ኤር42፥3
3፥7 ዘፀ20፥20፤ዘዳ 4፥6፤ኢዮ1፥1፤መዝ11 1፥10፤ምሳ26፥5፥12
3፥8 ኢዮ21፥24፤ መዝ38፥3ምሳ4፥22 3፥9 ዘፀ22፥29፤ዘዳ26፥1-15
3፥10 ኢዮ22፥21፤መዝ144፥13፤ኢል2፥24፤ሚል3፥10-12

ᵂ17 ወይም የአምላኳን ኪዳን

11 ልጄ ሆይ፤ የእግዚአብሔርን
ተግሣጽ አትናቅ፤
በዘለፋውም አትመረር፤
12 አባት ደስ የሚሰኝበትን ልጁን
እንደሚቀጣ[ለ] ሁሉ፣
እግዚአብሔርም የሚወደውን
ይገሥጻልና።

13 ጥበብን የሚያገኛት፣
ማስተዋልንም ገንዘቡ የሚያደርጋት
ሰው ቡሩክ ነው፤
14 እርሷ ከብር ይልቅ ትርፍ የምታመጣ፣
ከወርቅም ይልቅ ጥቅም የምታስገኝ
ናትና።
15 ከቀይ ዕንቍ ይበልጥ ውድ ናት፤
አንተ ከምትመኘውም ሁሉ
የሚስተካከላት የለም።
16 በቀኝ እጇ ረጅም ዕድሜ አለ፤
በግራ እጇም ሀብትና ክብር ይዛለች።
17 መንገዷ ደስ የሚያሰኝ ነው፤
ጐዳናዋም ሁሉ ሰላም ነው።
18 ለሚያቅፏት የሕይወት ዛፍ ናት፤
የሚይዟትም ይባረካሉ።
19 እግዚአብሔር በጥበብ ምድርን
መሠረተ፤
በማስተዋል ሰማያትን በየስፍራቸው
አጸና፤
20 በዕውቀቱ ቀላያት ተከፈሉ፤
ደመናትም ጠልን አንጠበጠቡ።

21 ልጄ ሆይ፤ ትክክለኛ ፍርድንና
አስተውሎ መለየትን ጠብቅ፤
እነዚህ ከእይታህ አይራቁ፤
22 ለነፍስህ ሕይወት፣
ለዐንገትህም ጌጥ ይሆናሉ።
23 ከዚያም መንገድህን በሰላም ትሄዳለህ፤
እግርህም አይሰናከልም፤
24 ስትተኛ አትፈራም፤
ትተኛለህ እንቅልፍህም ጣፋጭ
ይሆናል።
25 ድንገተኛን መከራ፣
በክፉዎች ላይ የሚደርሰውንም ጥፋት
አትፍራ፤
26 እግዚአብሔር መታመኛህ ይሆናልና፤
እግርህንም በወጥመድ ከመያዝ
ይጠብቃል።
27 ማድረግ እየቻልህ
ለሚገባቸው መልካም ነገር ከማድረግ
አትከልክል።
28 አሁን በእጅህ እያለ፣
ጐረቤትህን፣ "ቈይተህ ተመለስ፤ ነገ
እሰጥሃለሁ" አትበለው።
29 አንተን ተማምኖ በአጠገብህ በተቀመጠ፣
በጐረቤትህ ላይ ክፉ አትምከርበት።

30 ምንም ጕዳት ሳያደርስብህ፣
ያለ ምክንያት ሰውን አትክሰስ።
31 በክፉ ሰው አትቅና፤
የትኛውንም መንገዱን አትምረጥ፤
32 እግዚአብሔር ጠማማን ሁሉ ይጸየፋልና፤
ለቅን ሰው ግን ምስጢሩን
ይገልጥለታል።
33 የእግዚአብሔር ርግማን በክፉዎች ቤት
ላይ ነው፤
የጻድቃንን ቤት ግን ይባርካል።
34 እርሱ በዕቡያን ፌዘኞች ላይ ያፌዛል፤
ለትሑታን ግን ሞገስን ይሰጣል።
35 ጠቢባን ክብርን ይወርሳሉ፤
ሞኞችን ግን ለውርደት ያጋልጣቸዋል።

## ጥበብ ከሁሉ በላይ መሆኗ

4 ልጆቼ ሆይ፤ የአባትን ምክር
አድምጡ፤
ልብ ብላችሁ ስሙ፤ ማስተዋልንም
ገንዘብ አድርጉ።
2 በጎ ትምህርት እሰጣችኋለሁ፤
ስለዚህ ትምህርቴን አትተዉ።
3 በአባቴ ቤት ገና ለግላጋ ወጣት፣
ለእናቴም አንድ ልጇ ብቻ በነበርሁ
ጊዜ፣
4 አባቴ እንዲህ ሲል አስተማረኝ፤
"ቃሌን በሙሉ በልብህ ያዝ፤
ትእዛዜንም ጠብቅ፤ በሕይወት
ትኖራለህ።
5 ጥበብን አግኛት፤ ማስተዋልን ያዛት፤
ቃሌን አትርሳ፤ ከእርሷም ዘወር
አትበል።
6 ጥበብን አትተዋት፤ እርሷም ከለላ
ትሆንሃለች፤
አፍቅራት፤ እርሷም ትጠብቅሃለች።
7 ጥበብ ታላቅ ነገር ናት፤ ስለዚህ ጥበብን
አግኛት፤
ያለህን ሁሉ[ሐ] ብታስከፍልህም
ማስተዋልን ገንዘብህ አድርጋት።
8 ክብርን ስጣት፤ ከፍ ከፍ ታደርግሃለች፤
እቀፋት ታከብርሃለች፤
9 በራስህ ላይ ሞገሳም አክሊል
ትደፋልሃለች፤
የክብር ዘውድም ታበረክትልሃለች።

10 ልጄ ሆይ፤ አድምጠኝ፤ ቃሌንም
ልብ በል፤
የሕይወት ዘመንህም ትበዛለች።
11 በጥበብ ጐዳና አስተምርሃለሁ፤
ቀጥተኛውንም መንገድ አሳይሃለሁ።
12 ስትሄድ እርምጃህ አይሰናከልም፤

3፥11 ኢዮ5፥17፤ ምሳ1፥8-9
3፥12 ዘዳ8፥5፤ኢዮ 5፥17፤ምሳ13፥24፤ዕብ 12፥5-6፤ራእ3፥19
3፥14 ኢዮ28፥15፤ ምሳ8፥19፤16፥16
3፥15 ኢዮ28፥17-19
3፥16 ዘፍ15፥15፤ 1ነገ3፥13፡14
3፥17 ማቴ11፥28-30
3፥18 ዘፍ2፥9፤2፥12፤ 4፥3-9፥8፤8፥17-21፤ ምሳ10፥11፤ራእ2፥7
3፥19 ዘፍ1፥31፤ኢዮ 28፥25-27፤መዝ136 ፥5-9፤ምሳ8፥27-29
3፥21 ምሳ1፥8-9፤ 4፥20-22፤6፥20
3፥22 ዘዳ30፥20፤ ምሳ1፥8-9፤4፥13
3፥23 መዝ37፥24፤ 119፥11፤ምሳ1፥33፤4፥ 12
3፥24 ዘሌ26፥6፤ኢ ዮ11፥18፤መዝ91፥5፤1 12፥8፤ኤር31፥26
3፥26 1ሳሙ2፥9፤ 2ነገ18፥5፤ኢዮ4፥6 ፤5፥19
3፥28 ዘሌ19፥13፤ ዘዳ24፥15፤ሉቃ10፥25 -37
3፥29 ዘካ8፥17
3፥31 መዝ37፥1፤ ምሳ24፥1-2
3፥32 ኢዮ29፥4፤ መዝ101፥4
3፥33 ኢዮ5፥3፤መዝ 37፥22፤ምሳ14፥11፤ ዘካ5፥4
3፥34 2ነገ19፥21፤ መዝ18፥25-27፤ 40፥4፤ማቴ23፥12 ፤ያዕ4፥6፤1ጴጥ5፥5
4፥1 ኢዮ8፥10፤ምሳ 1፥8፤19፥20
4፥4 1ነገ9፥4፤ምሳ 7፥2
4፥5 ምሳ2፥12፤3፥ 13-18
4፥6 ምሳ2፥11፤ 2ተሰ2፥10
4፥7 ምሳ23፥23፤ ማቴ13፥44-46
4፥8 ምሳ3፥18
4፥9 ምሳ1፥8-9
4፥10 ዘዳ11፥21፤ መዝ34፥11-16፤ምሳ 1፥8-9
4፥11 1ሳሙ12፥23፤2 ሳሙ22፥37፤መዝ5፥8
4፥12 ኢዮ18፥7፤ ምሳ3፥23

[ሀ]6 ወይም ጐዳናህን ያቀናልሃል
[ለ]12 ወይም እንደሚገሥጽ
[ሐ]7 ወይም ያገኘኸውን ሁሉ

ስትሮጥም አትደናቀፍም፡፡
13 ምክርን አጥብቀህ ያዛት፤ አትልቀቃት፤
ጠብቃት፤ ሕይወትህ ናትና፡፡
14 ወደ ኀጥኣን ጐዳና እግርህን አታንሣ፤
በክፉ ሰዎች መንገድ አትሂድ፤
15 ከዚያ አትድረስ አትጓዝበት፤
ሽሸው፤ መንገድህን ይዘህ ሂድ፡፡
16 ክፉ ካላደረጉ አይተኙምና፤
ሰውን ካላሰናከሉ እንቅልፍ ባይናቸው
አይዞርም፡፡
17 የክፋት እንጀራ ይበላሉ፤
የዐመፅ ወይን ጠጅ ይጠጣሉ፡፡
18 የጻድቃን መንገድ ሙሉ ቀን እስኪሆን
ድረስ፣
ብርሃኑ እየጐላ እንደሚሄድ የማለዳ
ውጋጋን ነው፡፡
19 የክፉዎች መንገድ ግን እንደ ድቅድቅ
ጨለማ ነው፤
ምን እንደሚያሰናክላቸውም
አያውቁም፡፡

20 ልጄ ሆይ፤ የምነግርህን አስተውል፤
ቃሌንም በጥንቃቄ አድምጥ፡፡
21 ከእይታህ አታርቀው፤
በልብህም ጠብቀው፤
22 ለሚያገኘው ሕይወት፤
ለመላው የሰው አካልም ጤንነት
ነውና፡፡
23 ከሁሉም በላይ ልብህን ጠብቅ፤
የሕይወት ምንጭ ነውና፡፡
24 ጥመትን ከአፍህ አስወግድ፤
ብልሹ ንግግርም ከከንፈሮችህ ይራቅ፡፡
25 ዐይኖችህ በቀጥታ ይመልከቱ፤
ትክ ብለህም ፊት ለፊት እይ፡፡
26 የእግርህን ጐዳና አስተካክል፤[ቀ]
የጸናውን መንገድ ብቻ ያዝ፡፡
27 ወደ ቀኝ ወደ ግራ አትበል፤
እግርህን ከክፉ ጠብቅ፡፡

## ከአመንዝራነት መጠንቀቅ

5 ልጄ ሆይ፤ ጥበቤን ልብ በል፤
የማስተዋል ቃሌንም በጥሞና
አድምጥ፤
2 ይህም ልባምነትን ገንዘብ እንድታደርግ፣
ከንፈሮችህም ዕውቀትን እንዲጠብቁ
ነው፡፡
3 የአመንዝራ ሴት ከንፈር ማር
ያንጠባጥባልና፤
አንደበቷም ከቅቤ ይለሰልሳል፤
4 በመጨረሻ ግን እንደ እሬት ትመራለች፤
ሁለት አፍ እንዳለውም ስል ሰይፍ
ትሆናለች፡፡
5 እግሮቿ ወደ ሞት ይወርዳሉ፤
እርምጃዎቿም በቀጥታ ወደ ሲኦል[በ]
ያመራሉ፡፡
6 ስለ ሕይወት መንገድ ደንታ የላትም፤
መንገዶቿ ዘወርዋራ ናቸው፤ ለእርሷ
ግን አይታወቃትም፡፡

7 እንግዲህ፣ ልጆቼ ሆይ፤ አድምጡኝ፤
ከምነግራችሁ ቃል ፈቀቅ አትበሉ፡፡
8 መንገድህን ከእርሷ አርቅ፤
በደጃፏም አትለፍ፤
9 ይኸውም ጉብዝናህን ለሌሎች፣
ዕድሜህንም ለጨካኞች እንዳትሰጥ
ነው፤
10 ባዕዳን በሀብትህ እንዳይፈነጥዙ፣
ልፋትህም የሌላውን ሰው ቤት
እንዳያበለጽግ ነው፡፡
11 በዕድሜህ መጨረሻ ታቃሥታለህ፤
ሥጋህና ሰውነትህ ሲከዳህ፡፡
12 እንዲህም ትላለህ፤ “ምነው! ተግሣጽን
ጠላሁ፤
ልቤስ ምነው! መታረምን ናቀ፤
13 የመምህሮቼን ቃል አልሰማሁም፤
አሰልጣኞቼንም አላደመጥኋቸውም፤
14 በመላው ጉባኤ ፊት፣
ወደ ፍጹም ጥፋት ተቃርቤአለሁ፡፡”

15 ከገዛ ማጠራቀሚያህ ውሃ፣
ከገዛ ጕድጓድህም የሚፈልቀውን
ውሃ ጠጣ፡፡
16 ምንጮችህ ተርፈው ወደ ሜዳ፣
ወንዞችህስ ወደ አደባባይ ሊፈሱ
ይገባልን?
17 ለአንተ ብቻ ይሁኑ፤
ባዕዳን አይጋሩህ፡፡
18 ምንጭህ ቡሩክ ይሁን፤
በልጅነት ሚስትህም ደስ ይበልህ፡፡
19 እርሷ እንደ ተወደደች ዋላ፣ እንደ
ተዋበች ሚዳቋ ናት፤
ጡቶቿ ዘወትር ያርኩህ፤
ፍቅሯም ሁልጊዜ ይማርክህ፡፡
20 ልጄ ሆይ፤ በአመንዝራ ሴት ፍቅር
ለምን ትሰክራለህ?
የሌላይቱንስ ሴት ብብት ስለምን
ታቅፋለህ?
21 የሰው መንገድ *በእግዚአብሔር* ፊት
ግልጥ ነውና፤
እርሱ መሂጃውን ሁሉ ይመረምራል፡፡
22 ክፉውን ሰው የገዛ መጥፎ ሥራው
ያጠምደዋል፤
የኀጢአቱም ገመድ ጠፍሮ ይይዘዋል፡፡
23 ከተግሣጽ ጕድለት የተነሣ ይሞታል፤
ከተላላነቱም ብዛት መንገድ ይስታል፡፡

4፥13 ምሳ3፥22
4፥14 መዝ1፥1፤ምሳ 1፥15
4፥16 መዝ36፥4፤ ሚክ7፥3
4፥17 ዘፍ49፥5፤ መዝ73፥6፤መዝ73፥6፤ ምሳ1፥10-19፤14፥22 ፤ኢሳ59፥6፤ኤር22፥3፤ ዕን1፥2፤ሚል12፥16
4፥18 2ሳሙ23፥4፤ ኢዮ17፥9፤22፥28፤ ዳን12፥3፤ማቴ5፥14፤ ዮሐ8፥12፤ፊል2፥15
4፥19 ዘዳ32፥35፤ ኢዮ3፥23፤ምሳ2፥13፤ 13፥9፤ኢሳ8፥15
4፥20 መዝ34፥11-16፤ምሳ1፥8-9፤5፥1
4፥21 ምሳ3፥21
4፥22 ምሳ3፥8
4፥23 2ነገ10፥31፤ ምሳ10፥11፤ሉቃ6፥45
4፥25 ኢዮ31፥1
4፥26 ዕብ12፥13
4፥27 ዘሌ10፥11፤ ዘዳ5፥32
5፥1 ምሳ1፥8፤4፥20
5፥3 መዝ55፥21፤ ምሳ7፥5
5፥4 መክ7፥26
5፥5 መዝ9፥17፤ምሳ 2፥18፤7፥26-27
5፥6 ምሳ9፥13፤ 30፥20
5፥7 ምሳ1፥8-9
5፥8 ምሳ2፥16-19፤ 6፥20-29፤7፥1-27
5፥10 ምሳ29፥3
5፥12 ምሳ12፥1
5፥14 ምሳ1፥24-27፤ 6፥33፤31፥3
5፥18 ዘዳ20፥7፤ምሳ 2፥17፤መክ9፥9፤ማሕ 4፥12-15፤ሚል2፥14
5፥19 ማሕ4፥5፤ 8፥14
5፥21 ኢዮ10፥4፤ 14፥6፤ምሳ15፥3፤መዝ 119፥168፤ኤር29፥23፤ 32፥19፤ዕብ4፥13
5፥22 ዘኍ32፥23፤ ኢዮ18፥9፤መዝ7፥15-16፤መዝ9፥16፤ምሳ1፥ 31-32
5፥23 ኢዮ4፥21፤ 34፥21-25፤ምሳ10፥

[ቀ] 26 ወይም *ተመልከት*
[በ] 5 ወይም *መቃብር*

## ከተላላነት መራቅ

6 ልጄ ሆይ፤ ለጐረቤትህ ዋስ ብትሆን፣
ስለ ሌላውም ሰው እጅ መትተህ
ቃል ብትገባ፣
2በተናገርኸው ነገር ብትጠመድ፣
ከአፍህ በወጣውም ቃል ብትያዝ፣
3ልጄ ሆይ፤ ራስህን ለማዳን ይህን
አድርግ፤
በጎረቤትህ እጅ ስለወደቅህ፣
ሂደህ ራስህን አዋርድ፤
ጎረቤትህን አጥብቀህ ነዝንዘው፡፡
4ዐይኖችህ እንቅልፍ አይያዛቸው፣
ሽፋሽፍቶችህም አያንጐላጁ፡፡
5ከአዳኝ እጅ እንዳመለጠች ሚዳቋ፣
ከአጥማጅ ወጥመድ እንዳፈተለከች
ወፍ ራስህን አድን፡፡
6አንተ ታካች፤ ወደ ጕንዳን ሂድ፤
ዘዴውን አስተውለህ ጠቢብ ሁን፤
7አዛዥ የለውም፤
አለቃም ሆነ ገዥ የለውም፤
8ሆኖም ግን በበጋ ምግቡን ያከማቻል፤
በመከርም ወቅት ቀለቡን ይሰበስባል፡፡
9አንተ ታካች፤ እስከ መቼ ትተኛለህ?
ከእንቅልፍህስ መቼ ትነሣለህ?
10ጥቂት ማንቀላፋት፤ ጥቂት ማንጐላቸት፤
እጅን አጣጥፎ "እስቲ ጥቂት ልረፍ"
ማለት፤
11ድኽነት እንደ ወንበዴ፣
ዕጦትም መሣሪያ እንደ ታጠቀ ሰው[+]
ከተፍ ይልብሃል፡፡
12ወሮበላና ጨካኝ፣
ነውረኛ አንደበቱን ይዞ የሚዞር፣
13በዐይኑ የሚጠቅስ፣
በእግሩ ምልክት የሚሰጥ፣
በጣቶቹ የሚጠቍም፣
14በልቡ ተንኰል ክፋትን የሚያውጠነጥን፣
ምንጊዜም ጠብ ይጭራል፡፡
15ስለዚህ በቅጽበት መዓት ይወርድበታል፤
በድንገት ይጠፋል፤ መዳኛም የለውም፡፡
16እግዚአብሔር የሚጠላቸው ስድስት
ነገሮች አሉ፤
የሚጸየፋቸውም ሰባት ናቸው፤
እነርሱም፡-
17ትዕቢተኛ ዐይን፣
ሐሰተኛ ምላስ፣
ንጹሕ ደም የሚያፈሱ እጆች፣
18ክፋትን የሚያውጠነጥን ልብ፣
ወደ ክፋት የሚቻኰሉ እግሮች፣
19በውሸት ላይ ውሸት የሚጨምር
ሐሰተኛ ምስክር፣
በወንድማማቾች መካከል ጠብን
የሚጭር ሰው፡፡

## ከዝሙት መራቅ

20ልጄ ሆይ፤ የአባትህን ትእዛዝ አክብር፤
የእናትህንም ትምህርት አትተው፡፡
21ምንጊዜም በልብህ አኑራቸው፤
በአንገትህም ዙሪያ እሰራቸው፡፡
22በምትሄድበት ሁሉ ይመሩሃል፤
በምትተኛበት ጊዜ ይጠብቁሃል፤
በምትነቃበት ጊዜም ያነጋግሩሃል፡፡
23እነዚህ ትእዛዞች መብራት ናቸውና፤
ይህችም ትምህርት ብርሃን፣
የተግሣጽ እርምትም የሕይወት
መንገድ ናት፤
24እርሷም ከምግባረ ብልሹ ሴት፣
ልዝብ አንደበት ካላት ዘልዛላ ሴት
ትጠብቅሃለች፡፡
25ውበቷን በልብህ አትመኝ፤
በዓይኗም አትጠመድ፤
26ጋለሞታ ሴት ቍራሽ እንጀራ
ታሳጣሃለችና፤
አመንዝራዪቱም በሕይወትህ በራሱ
ላይ ትሸምቃለች፡፡
27ለመሆኑ ልብሱ ሳይቃጠል፣
በጕያው እሳት መያዝ የሚችል ሰው
አለን?
28አንድ ሰው እግሮቹ ሳይቃጠሉ፣
በፍም ላይ መሄድ ይችላልን?
29ከሰው ሚስት ጋር የሚተኛም እንደዚሁ
ነው፤
የሚደርስባትም ከቅጣት አያመልጥም፡፡
30ሌባ በተራበ ጊዜ ራቡን ለማስታገሥ
ቢሰርቅ፣
ሰዎች አይንቁትም፡፡
31በቤቱ ያለውን ሀብት ሁሉ የሚጠይቀው
ቢሆንም፣
ከተያዘ ሰባት እጥፍ መክፈል አለበት፡፡
32የሚያመነዝር ሰው ግን ማመዛዘን
ይጐድለዋል፤
እንዲህ የሚያደርግ ሁሉ ራሱን
ያጠፋል፡፡
33መደብደብና ውርደት ዕጣው ነው፤
ኀፍረቱም ከቶ አይወገድም፤
34ቅናት የባልን ቍጣ ይቀሰቅሳልና፤
በሚበቀልበትም ጊዜ ምሕረት
አያደርግም፡፡
35 ምንም ዐይነት ካሣ አይቀበልም፤
የቱንም ያህል ብዙ ቢሆን መማለጃን
እሺ አይልም፡፡

## ከአመንዝራ ሴት መራቅ

7 ልጄ ሆይ፤ ቃሌን ጠብቅ፤
ትእዛዜንም በውስጥህ አኑር፡፡

21፤11፥5
6፥1 ኢዮ17፥3፤ምሳ 1፥8፤11፥15፤17፥18፤22፥26-27
6፥4 መዝ132፥4
6፥5 2ሳሙ2፥18፤ መዝ91፥3፤ኢሳ13፥14
6፥6 ቍ6-11፤ምሳ 20፥4
6፥8 ምሳ10፥4፤ 30፥24-25
6፥9 ምሳ24፥30-34 ፤26፥13-16
6፥10 ምሳ24፥33፤ መክ4፥5
6፥11 ቍ10-11፤ ምሳ20፥13፤24፥30-34
6፥13 መዝ35፥19፤ ምሳ16፥30፤ኢሳ58፥9
6፥14 ቍ16-19፤ መዝ140፥2
6፥15 ኢዮ5፥3፤መዝ 55፥15፤ምሳ14፥32፤29 ፥1
6፥16 ቍ16-19፤ ምሳ 3፥32፤8፥13፤ 15፥8፡9፡26፤16፥5
6፥17 ዘጸ19፥10፤ ኢዮ41፥34፤መዝ10፥5 ፤ምሳ1፥16፤12፥22፤ ኢሳ1፥21፤59፥7፤ ኤር2፥34፤ሚክ7፥2
6፥18 ኢዮ15፥31
6፥19 ቍ12-15፤ዘጸ 19፥16፤መዝ12፥2፤ ምሳ15፥18፤ዘካ8፥17
6፥20 ምሳ1፥8፤ 3፥21
6፥21 ዘዳ6፥8፤ምሳ 3፥3፤7፥1-3
6፥23 መዝ119፥105 ፤ምሳ10፥17
6፥24 ዘፍ39፥8፤ መዝ 55፥21፤ምሳ 2፥16፤7፥5
6፥26 ምሳ7፥22-23
6፥29 ዘፀ20፥14፤ ምሳ2፥16-19፤5፥8
6፥31 ዘፀ22፥14
6፥32 ዘፀ20፥14፤ ምሳ 7፥7፤9፥4፡16
6፥33 ምሳ5፥9-14
6፥34 ዘፍ34፥7፤ ዘኍ5፥14
6፥35 ኢዮ31፥9-11 ፤ማሕ 8፥7
7፥1 ምሳ1፥8

[+]11 ወይም እንደ ቦዘኔ/ እጦት እንደ ለማኝ

[2]ትእዛዜን ጠብቅ፤ በሕይወት ትኖራለህ፤
ትምህርቴንም እንደ ዐይንህ ብሌን
ተንከባከበው።
[3]በጣትህ ላይ እሰረው፤
በልብህ ጽላት ላይ ጻፈው።
[4]ጥበብን፣ "እኅቴ ነሽ" በላት፤
ማስተዋልንም፣ "ዘመዴ ነህ" በለው፤
[5]ከአመንዝራ ሴት፣
በአንደበቷም ከምታታልል ዘልዛላ ሴት
ይጠብቁሃል።

[6]በቤቴ መስኮት፣
በዐይነ ርግቡ ወደ ውጭ ተመለከትሁ።
[7]ማስተዋል የጐደለውን ወጣት፣
ብስለት ከሌላቸው መካከል አየሁት፤
ከጎልማሶችም መካከል ለየሁት።
[8]የቤቷን አቅጣጫ ይዞ፣
በቤቷ ማእዘን አጠገብ ባለው መንገድ
ያልፍ ነበር፤
[9]ቀኑ መሸትሸት ብሎ ጀንበሯ ልትጠልቅ
ነው፣
የሌሊቱ ጨለማ በመግባት ላይ ነበር።
[10] ከዚያም አንዲት ሴት ልታገኘው
ወጣች፤
እንደ ዝሙት አዳሪ ለብሳ፣ ለማሳሳት
ታጥቃ።
[11]ጯኺና ማን አለብኝ ባይ ናት፤
እግሮቿ አርፈው ቤት አይቀመጡም፤
[12]አንዴ በመንገድ፣ አንዴ በአደባባይ፤
በየማእዘኑም ታደባለች።
[13]አፈፍ አድርጋ ይዛ ሳመችው፤
ኀፍረቷንም ጥላ እንዲህ አለችው፤

[14]"በቤቴ የኅብረት መሥዋዕት[ቶ] ማቅረብ
ነበረብኝ፤
ዛሬ ስእለቴን ፈጸምሁ፤
[15]ስለዚህ አንተን ለማግኘት ወጣሁ፤
ፈልጌህ ነበር፤ ይኸው አገኘሁህ።
[16]ዐልጋዬን ከግብፅ የመጣ፣
ጌጠኛ በፍታ አልብሼዋለሁ።
[17]ዐልጋዬን፣
የከርቤ፣ የዓልሙንና የቀረፋ ሽቱ
አርከፍክፌበታለሁ።
[18]ና፤ እስኪነጋ በጥልቅ ፍቅር እንርካ፤
በፍቅር ራሳችንን እናስደስት።
[19]ባሌ እቤት የለም፤
ሩቅ አገር ሄዷል።
[20]በገንዘብ የተሞላ ቦርሳ ወስዷል፤
ጨረቃዋ ሙሉ እስክትሆን
አይመለስም።"
[21]በሚያግባቡ ቃላት አሳተችው፤
በለሰለሰ አንደበቷ አታለለችው።
[22]ለዕርድ እንደሚነዳ በሬ፣
ፍላጻ ጉበቱን እስኪወጋው ድረስ፣
ወደ ወጥመድ[ኀ] እንደሚገባ አጋዘን፣[ነ]
[23]ወደ ወጥመድ በራ እንደምትገባ ወፍ፣
ሳያንገራግር ተከተላት፤
ነገሩ ሕይወቱን እንደሚያሳጣው
አላወቀም።

[24]ልጆቼ ሆይ፤ አሁንም አድምጡኝ፤
የምለውንም ልብ ብላችሁ ስሙኝ።
[25]ልባችሁን ወደ መንገዷ አታዘንብሉ፤
ወደ ስሕተት ጐዳናዋም አትግቡ።
[26]አዋርዳ የጣለቻቸው ብዙ ናቸው፤
የገደለቻቸውም ስፍር ቍጥር
የላቸውም።
[27]ቤቷ ወደ ሲኦል[ኘ] የሚወስድ፣
ወደ ሞት ማደሪያም የሚያወርድ
ጐዳና ነው።

## የጥበብ ጥሪ

**8** ጥበብ ጮኻ አትጣራምን?
ማስተዋልስ ድምፅዋን ከፍ አድርጋ
አታሰማምን?
[2]በመንገድ አጠገብ ባሉ ኰረብቶች፣
መንገዶቹ በሚገናኙበትም ላይ
ትቆማለች፤
[3]ወደ ከተማዪቱ በሚያስገቡት በሮች
አጠገብ፣
በመግቢያዎቹ ላይ፣ ድምጿን ከፍ
አድርጋ እንዲህ ስትል ትጮኻለች፤
[4]"ሰዎች ሆይ፤ የምጠራውኮ እናንተን
ነው፤
ለሰው ልጆች ሁሉ ድምፄን ከፍ
አደርጋለሁ።
[5]እናንተ ብስለት የጐደላችሁ ጠንቃቃ
ነትን ገንዘብ አድርጉ፤
እናንተ ተላሎች፤ ማስተዋልን አትርፉ።
[6]የምናገረው ጠቃሚ ነገር ስላለኝ
አድምጡኝ፤
ቀና ነገር ለመናገር ከንፈሮቼን
እከፍታለሁ።
[7]አንደበቴ እውነትን ይናገራል፤
ከንፈሮቼ ክፋትን ይጸየፋሉና።
[8]ከአንደበቴ የሚወጡት ቃሎች ሁሉ
ጽድቅ ናቸው፤
አንዳቸውም ጠማማና ግራ የሚያጋቡ
አይደሉም።
[9]በጥልቅ ለሚያስተውሉ ሁሉም ቀና
ናቸው፤
ዕውቀት ላላቸውም ስሕተት

7፥2 ምሳ4፥4
7፥3 ምሳ3፥3
7፥5 ቀኍ21፤ኢዮ31፥9፤ምሳ2፥16፤6፥24
7፥7 ምሳ1፥22፤6፥32
7፥9 ኢዮ24፥15
7፥11 ምሳ9፥13
7፥12 ምሳ8፥1-36፤23፥26-28
7፥13 ዘፍ39፥12፤ምሳ1፥20
7፥14 ዘሌ7፥11-18
7፥17 ዘፍ37፥25፤አስ1፥6፤ኢሳ57፥7፤ሕዝ23፥41፤አሞ6፥4
7፥18 ዘፍ39፥7
7፥21 ቀኍ5
7፥22 ኢዮ18፥10
7፥23 ኢዮ15፥22፤16፥13፤ምሳ6፥26፤መክ7፥26
7፥24 ምሳ1፥8-9፤8፥32
7፥25 ምሳ5፥7-8
7፥27 መሳ16፥19፤ምሳ2፥18፤ራእ22፥15
8፥1 ኢዮ28፥12
8፥3 ምሳ7፥6-13
8፥4 ኢሳ42፥2
8፥5 ምሳ1፥4፡22፣
8፥7 ዮሐ8፥14

[ቶ]14 በተለምዶ ***የሰላም መሥዋዕት*** ይባላል።
[ኀ]22 የሱርሰት (የሰብዓ ሊቃናትም) ትርጕም እና ዕብራይስጡ ***ተላላ*** ይላሉ።
[ነ]22 የዚህ ስንኝ የዕብራይስጡ ትርጓሜ በእርግጠኝነት አይ ታወቅም።
[ኘ]27 ወይም ***መቃብር***

የለባቸውም።
10 ከብር ይልቅ ምክሬን፣
ከንጹሕ ወርቅ ይልቅ ዕውቀትን
ምረጡ፤
11 ጥበብ ከቀይ ዕንቍ ይበልጥ ውድ
ናትና፤
ከምትመኙት ነገር ሁሉ አንዳች
የሚስተካከላት የለም።
12 “እኔ ጥበብ ከማስተዋል ጋር አብሬ
እኖራለሁ፤
ዕውቀትና ልባምነት ገንዘቦቼ ናቸው።
13 *እግዚአብሔርን* መፍራት ክፉትን
መጥላት ነው፤
እኔም ትዕቢትንና እብሪትን፣
ክፉ ጠባይንና ጠማማ ንግግርን
እጠላለሁ።
14 ምክርና ትክክለኛ ፍርድ የእኔ ናቸው፤
ማስተዋል አለኝ፤ ብርታት አለኝ።
15 ነገሥታት በእኔ ይነግሣሉ፤
ገዦችም ትክክል የሆነውን ሕግ
ይደነግጋሉ፤
16 መሳፍንት በእኔ ይገዛሉ፤
በምድር ላይ የሚገዙ መኳንንትም ሁሉ
በእኔ ያስተዳድራሉ።[ኦ]
17 የሚወዱኝን እወዳቸዋለሁ፤
ተግተው የሚሹኝም ያገኙኛል።
18 ሀብትና ክብር፣
ዘላቂ ብልጽግናና ስኬት በእኔ
ዘንድ አሉ።
19 ፍሬዬ ከንጹሕ ወርቅ ይበልጣል፤
ስጦታዬም ከነጠረ ብር።
20 እኔ በጽድቅ መንገድ፣ እሄዳለሁ፤
በፍትሕም ጐዳና እጓዛለሁ፤
21 ለሚወዱኝ ብልጽግና እሰጣለሁ፤
ግምጃ ቤታቸውንም እሞላለሁ።
22 *እግዚአብሔር* ከቀድሞ ሥራዎቹ በፊት፣
የተግባሮቹ መጀመሪያ[ከ] አድርጎ
አመጣኝ፤[ኸ]
23 ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ፣
ከጥንት ከዘላለም ተሾምሁ።[ወ]
24 ከውቅያኖሶች በፊት፣
የውሃ ምንጮች ከመፍለቃቸው በፊት
ተወለድሁ፤
25 ተራሮች ገና ሳይመሠረቱ፣
ከኰረብቶችም በፊት ተወለድሁ፤
26 ምድርን ወይም ሜዳዎቿን፣
ወይም ምንም ዐይነት የዓለም ትቢያን
ከመፍጠሩ በፊት እኔ ተወለድሁ።
27 ሰማያትን በዘረጋ ጊዜ፣
በውቅያኖስ ላይ የአድማስ ምልክት
ባደረገ ጊዜ እኔ እዚያ ነበርሁ፤
28 ደመናትን በላይ ባጸና ጊዜ፣
የውቅያኖስን ምንጮች በመሠረተ
ጊዜ፣
29 ለባሕር ድንበርን በከለለ ጊዜ፣
ውሆችም የእርሱን ትእዛዝ እንዳያልፉ፣
የምድርንም መሠረቶች ወሰን ባበጀ
ጊዜ፣
30 በዚያን ጊዜ ከጐኑ ዋና ባለሙያ
ነበርሁ።
ሁልጊዜ በፊቱ ሐሤት እያደረግሁ፣
ዕለት ተዕለት በደስታ እሞላ ነበር፤
31 የእርሱ በሆነው መላው ዓለም ሐሤት
እያደረግሁ፣
በሰው ልጆች ደስ እሰኝ ነበር።
32 “እንግዲህ፣ ልጆቼ ሆይ፤ አድምጡኝ፤
መንገዴን የሚጠብቁ ቡሩካን ናቸው።
33 ምክሬን አድምጡ፤ ጥበበኞች ሁኑ፤
ቸልም አትበሉት።
34 በየለቱ ደጃፌ ላይ የሚጠብቅ፣
በበራፌ ላይ የሚጠባበቅ፣
የሚያዳምጠኝ ሰው ቡሩክ ነው።
35 የሚያገኘኝ ሁሉ ሕይወትን ያገኛልና፤
ከእግዚአብሔርም ዘንድ ሞገስን
ይቀበላል።
36 የሚያጣኝ ሁሉ ግን ራሱ ይጐዳል፤
የሚጠሉኝም ሁሉ ሞትን ይወዳሉ።

## ጠቢብነትና ተላላነት

9 ጥበብ ቤቷን ሠራች፤
ሰባቱን ምሰሶዎቿንም ጠርባ
አቆመች፤
2 ፍሪዳዋን አረደች፤ የወይን ጠጇን
ጠመቀች፤
ማእዷንም አዘጋጀች።
3 ሴት አገልጋዮቿንም ላከች፤
ከከተማዪቱም ከፍተኛ ቦታ ተጣራች።
4 እርሷም ማመዛዘን ለጐደላቸው፣
“ማስተዋል የሌላችሁ ሁሉ ወደዚህ ኑ!”
አለች።
5 “ኑ፤ ምግቤን ተመገቡ፤
የጠመቅሁትንም የወይን ጠጅ ጠጡ።
6 የሞኝነት መንገዳችሁን ተዉ፤ በሕይወት
ትኖራላችሁ፤
በማስተዋልም መንገድ ተመላለሱ።
7 “ፌዘኛን የሚገሥጽ ሁሉ ስድብን በራሱ
ላይ ያመጣል፤
ክፉውን ሰው የሚዘልፍ ሁሉ ውርደት
ያገኘዋል።

**8፥10** ኢዮ28፥17፤መዝ19፥10
**8፥11** ቍ19፤ኢዮ28፥17-19፤ምሳ3፥13-15
**8፥12** ምሳ1፥4
**8፥13** ዘፍ22፥12፤ዘፀ20፥20፤ኢዮ28፥28፤ኤር44፥4
**8፥14** ኢዮ9፥4፤ምሳ21፥22፤መክ7፥19
**8፥15** መዝ2፥10
**8፥16** 2ዜና1፥10፤ምሳ29፥4
**8፥17** 1ሳሙ2፥30፤1ዜና16፥11፤ምሳ1፥28፤3፥13-18፤ማቴ7፥7-11፤ዮሐ14፥21-24
**8፥18** ዘዳ8፥18፤1ነገ3፥13
**8፥19** ኢዮ28፥17-19፤ምሳ3፥13-14
**8፥20** መዝ5፥8
**8፥21** ምሳ15፥6፤24፥4
**8፥24** ዘፍ7፥11
**8፥25** ኢዮ15፥7፤38፥6
**8፥26** መዝ90፥2
**8፥27** ኢዮ22፥14፤26፥7
**8፥28** ዘፍ1፥7፤ኢዮ9፥8፤26፥10፤36፥29
**8፥29** ዘፍ1፥9፤1ሳሙ2፥8፤ኢዮ38፥5፡8፤መዝ16፥6
**8፥30** ምሳ3፥19-20፤ራእ3፥14
**8፥31** ኢዮ28፥25-27፤38፥4-38፤መዝ104፥1-30፤ምሳ30፥4፤ዮሐ1፥1-4፤ቆላ1፥15-20
**8፥32** 2ሳሙ22፥22፤መዝ18፥21፤ሉቃ11፥28
**8፥34** 1ነገ10፥8
**8፥35** ኢዮ33፥26፤ምሳ9፥6፤3፥13-18፤ዮሐ5፥39-40
**8፥36** ኢዮ28፥22፤ምሳ15፥32፤ኢሳ3፥9፤ኤር40፥2
**9፥1** ኤፌ2፥20-22፤1ጴጥ2፥5
**9፥2** ኢሳ25፥6፤62፥8፤ሉቃ14፥16-23
**9፥3** ቁ14፤ምሳ1፥20፤8፥1-3
**9፥4** ቁ16፤ምሳ1፥22፤6፥32
**9፥5** መዝ42፥2፤63፥1፤143፥6፤ኢሳ44፥3፤55፥1፤ዮሐ7፥37-38
**9፥6** ምሳ3፥1-2፤8፥35
**9፥7** ምሳ23፥9፤ማቴ7፥6

[ኦ]16 አያሌ የዕብራይስጥ ቅጆችና የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም፣ ብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች *በምድር ላይ በጽድቅ የሚገዙ* ይላሉ።
[ከ]22 ወይም *የመንገዱ፣ የግዛቱ*
[ኸ]22 ወይም *እግዚአብሔር በሥራው መጀመሪያ ያዘኝ* ወይም *እግዚአብሔር በሥራው መጀመሪያ አመጣኝ*
[ወ]23 ወይም *ተሠራው*

8ፌዘኛን አትዝለፈው፤ ይጠላሃል፤
ጠቢብን ገሥጸው፤ ይወድሃል።
9ጠቢብን አስተምረው፣ ይበልጥ ጥበበኛ
ይሆናል፤
ጻድቁን ሰው አስተምረው፤ ዕውቀቱን
ይጨምራል።
10"የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን
መፍራት ነው፤
ቅዱሱንም ማወቅ ማስተዋል ነው፤
11ዘመንህ በእኔ ምክንያት ይረዝማልና፤
ዕድሜም በሕይወትህ ላይ
ይጨመርልሃል።
12ጠቢብ ብትሆን ጥበበኛነትህ ለራስህ
ነው፤
ፌዘኛ ብትሆን የምትጐዳው ያው
አንተው ነህ።"
13ጥበብ የለሽ ሴት ለፍላፊ ናት፤
እርሷም ስድና ዕውቀት የለሽ ናት።
14በቤቷ ደጃፍ ላይ ትጐለታለች፤
በከተማዪቱ ከፍተኛ ቦታ በመቀመጫ
ላይ ትቀመጣለች።
15በዚያ የሚያልፉትን፣
መንገዳቸውን ይዘው የሚሄዱትን
ትጣራለች።
16እርሷም ማመዛዘን ለጐደላቸው፣
"ማስተዋል የሌላችሁ ሁሉ ወደዚህ ኑ!"
ትላለች።
17"የስርቆት ውሃ ይጣፍጣል፤
ተሸሽገው የበሉት ምግብ ይጥማል።"
18እነርሱ ግን ሙታን በዚያ እንዳሉ፣
ተጋባዦቿም በሲኦል[0] ጥልቀት ውስጥ
እንደ ሆኑ አያውቁም።

## የሰሎሞን ምሳሌዎች

10 የሰሎሞን ምሳሌዎች፤
ጠቢብ ልጅ አባቱን ደስ
ያሰኛል፤
ተላላ ልጅ ግን ለእናቱ ሐዘንን
ያተርፋል።

2ያላግባብ የተገኘ ሀብት አይጠቅምም፤
ጽድቅ ግን ከሞት ይታደጋል።

3እግዚአብሔር፣ ጻድቁ እንዲራብ
አያደርግም፤
የክፉዎችን ምኞት ግን ያጨናግፋል።

4ሰነፍ እጆች ሰውን ያደኸያሉ፤
ትጉ እጆች ግን ብልጽግናን ያመጣሉ።

5ሰብሉን በበጋ የሚሰበስብ ጠቢብ ልጅ
ነው፤
በመከር ጊዜ የሚተኛ ግን ውርደት
ይከተለዋል።

6በረከት በጻድቃን ራስ ላይ ነው፤
መዓት ግን የክፉዎችን አፍ ይዘጋል።[H]

7የጻድቃን መታሰቢያቸው በረከት ነው፤
የክፉዎች ስም ግን እንደጠፋ ይቀራል።

8በልቡ ጠቢብ የሆነ ትእዛዝ ይቀበላል፤
ለፍላፊ ተላላ ግን ወደ ጥፋት ያመራል።

9ሐቀኛ ሰው ያለ ሥጋት ይራመዳል፤
በጠማማ ጐዳና የሚሄድ ግን
ይጋለጣል።
10በተንኰለኛ ዐይን የሚጠቅስ ሐዘን
ያስከትላል፤
ለፍላፊ ተላላም ወደ ጥፋት ያመራል።

11የጻድቅ አንደበት የሕይወት ምንጭ
ናት፤
መዓት ግን የክፉዎችን አፍ ይዘጋል።

12ጥላቻ ጠብን ያነሣሣል፤
ፍቅር ግን ስሕተትን ሁሉ ይሸፍናል።

13ጥበብ በአስተዋይ ሰው ከንፈር
ትገኛለች፤
በትር ግን ማመዛዘን ለጐደለው ሰው
ጀርባ ነው።

14ጠቢባን ዕውቀት ያከማቻሉ፤
የተላላ አንደበት ግን ጥፋትን
ይጋብዛል።

15የባለጠጎች ሀብት የተመሸገ ከተማቸው
ነው፤
ድኽነት ግን የድኾች መጥፊያ ናት።

16የጻድቃን ደመወዝ ሕይወት
ታስገኝላቸዋለች፤
የክፉዎች ትርፍ ግን ቅጣትን
ታመጣባቸዋለች።

17ተግሣጽን ነቅቶ የሚጠብቅ የሕይወትን
መንገድ ያሳያል፤
እርምትን የማይቀበል ግን ሌሎችን
ወደ ስሕተት ይመራል።

18ጥላቻውን የሚሸሽግ ሐሰተኛ አንደበት
ያለው ነው፤
ሐሜትን የሚዘራ ሁሉ ተላላ ነው።

19 ከቃላት ብዛት ኀጢአት አይታጣም፤
አንደበቱን የሚገታ ግን ጠቢብ ነው።

20የጻድቅ አንደበት የነጠረ ብር ነው፤
የክፉ ሰው ልብ ግን ርባና የለውም።

21የጻድቃን ከንፈሮች ብዙዎችን ያንጻሉ፤
ተላሎች ግን ከማመዛዘን ጒድለት
ይሞታሉ።

22የእግዚአብሔር በረከት ብልጽግናን

[0]18 ወይም መቃብር
[H]6 ወይም የክፉዎች አፍ ግን መዓትን ይሰውራል፤ እንዲሁም ቊ 11 ይመ።

9፥8 መዝ141፥5፤ ምሳ15፥12
9፥9 ምሳ1፥5፡7፤ 12፥15፤13፥10፤14፥6፤ 15፥31፤19፥25
9፥10 ዘጸ4፥6፤መዝ 22፥3፤ምሳ1፥7፤30፥3
9፥11 ዘፍ15፥15፤ዘጸ 11፥21፤ምሳ3፥1-2፤ 10፥27
9፥13 ምሳ5፥6፤7፥11
9፥14 ቊ3፤ሕዝ፤16፥25
9፥15 ምሳ1፥20
9፥16 ምሳ1፥22
9፥17 ምሳ20፥17
9፥18 ምሳ2፥18፤ 7፥26-27
10፥1 1ነገ4፥32፤ ምሳ 1፥1፤15፥20፤ 17፥21፤19፥13፤23፥22 -25፤27፥11፤29፥3
10፥2 ቊ16፤ምሳ 11፥4፤11፥19፤12፥28፤ 13፥11፤21፥6
10፥3 ምሳ13፥25፤ ማቴ6፥25-34
10፥4 ምሳ6፥6-8፤ 12፥24፤19፥15፤21፥5፤ 24፥30-34
10፥5 ምሳ24፥30-34
10፥6 ቊ8፡11፡14፤ ምሳ12፥13፤13፥3፤ መክ10፥12
10፥7 ኢዮ18፥17፤ መዝ 9፥6፤112፥6፤ መዝ109፥13
10፥8 ቊ14፤ኢዮ 33፥33፤ማቴ7፥24-27
10፥9 መዝ25፥21፤ 37፥24፤ምሳ28፥18፤
10፥10 መዝ35፥19
10፥11 ቊ6፡27፤ ምሳ 3፥18፤4፥23፤11 30፤13፥12፡14፥19፤14 ፥27፤15፥4፤16፥22
10፥12 ምሳ17፥9፤ 1ቆሮ13፥4-7፤1ጴጥ4፥8
10፥13 ቊ31፤ዘጸ 25፥2፤መዝ37፥30፤ም ሳ14፥3፤15፥7፤26፥3
10፥14 ቊ6፤መዝ 59፥12፤ምሳ11፥13፤12 ፥23፤14፥3፤18፥6፡7 ማቴ12፥37
10፥15 ምሳ18፥11፤ ምሳ19፥7
10፥16 ዘጸ30፥15፤ ምሳ11፥18-19፤15፥6፤ ሮሜ6፥23
10፥17 ምሳ6፥23፤ 15፥5
10፥18 መዝ31፥18
10፥19 ኢዮ1፥22፤ 6፥24፤ምሳ17፥28፤20፥ 25፤21፥33፤ያዕ1፥19፤ 3፥2-12
10፥21 ምሳ5፥22- 23፤ኢሳ5፥13፤ኤር 5፥4፤ሆሴ4፥1፡6፥14
10፥22 ዘፍ13፥2፤ 49፥25፤ዘጸ8፥18፤2

ታመጣለች፤
መከራንም አያክልባትም።
23 ተላላ ሰው በክፉ ተግባር ይደሰታል፤
አስተዋይ ሰው ግን በጥበብ ደስ
ይለዋል።
24 ክፉ ሰው የፈራው ይደርስበታል፤
ጻድቅ የሚመኘው ይፈጸምለታል።
25 ዐውሎ ነፋስ ሲነሣ ክፉዎች ተጠራርገው
ይወሰዳሉ፤
ጻድቃን ግን ለዘላለም ጸንተው
ይኖራሉ።
26 ሆምጣጤ ጥርስን፣ ጢስ ዐይንን
እንደሚጐዳ፣
ሰነፍም ለሚልኩት እንዲሁ ነው።
27 እግዚአብሔርን መፍራት ዕድሜን
ያረዝማል፤
የክፉዎች ዕድሜ ግን በአጭር
ይቀጫል።
28 የጻድቃን አለኝታ ደስታ ነው፤
የክፉዎች ተስፋ ግን ከንቱ ሆኖ
ይቀራል።
29 የእግዚአብሔር መንገድ ለጻድቃን
መጠጊያ፣
ክፉ ለሚያደርጉ ግን መጥፊያቸው
ነው።
30 ጻድቃን ፈጽሞ አይነቀሉም፤
ክፉዎች ግን በምድር አይኖሩም።
31 የጻድቃን አንደበት ጥበብን ያፈልቃል፤
ጠማማ ምላስ ግን ትቈረጣለች።
32 የጻድቃን ከንፈሮች ተገቢውን ነገር
ያውቃሉ፤
የክፉዎች አንደበት ግን የሚያውቀው
ጠማማውን ብቻ ነው።

11 እግዚአብሔር፣ የተጭበረበረ
ሚዛንን ይጸየፋል፤
ትክክለኛ መለኪያ ግን ደስ ያሰኘዋል።
2 ትዕቢት ስትመጣ ውርደትም
ትከተላለች፤
በትሑት ዘንድ ግን ጥበብ ትገኛለች።
3 ቅኖችን ትክክለኛነታቸው ትመራ
ቸዋለች፤
ወስላቶች ግን በገዛ አታላይነታቸው
ይጠፋሉ።
4 በቍጣ ቀን ሀብት ፋይዳ የለውም፤
ጽድቅ ግን ከሞት ትታደጋለች።
5 ለፍጹማን ሰዎች ጽድቃቸው
መንገዳቸውን ታቃናላቸዋለች፤
ክፉዎች ግን በገዛ ክፋታቸው

ዜና25፥9፤መዝ128፥2
**10፥23** ምሳ2፥14
**10፥24** ዘፍ42፥36፤
መዝ37፥4፤145፥17-
19፤ኢሳ65፥7፤ሕዝ
11፥8
**10፥25** መዝ20፥8፤
ምሳ12፥3፡7፤ማቴ
7፥24-27
**10፥26** ምሳ13፥17፤
25፥13፤26፥6፤ኢሳ65፥5
**10፥27** ቀኑ11፤ዘዳ
11፥9፤ኢዮ15፥32፤
ምሳ9፥10-11፤19፥23
፤22፥4
**10፥28** አስ7፥10፤
ኢዮ8፥13፤መዝ
112፥10፤ምሳ11፥7
**10፥29** ምሳ21፥15፤
ሆሴ14፥9
**10፥30** መዝ37፥9፡
28-29፤ምሳ2፥20-22
**10፥31** ቀኑ13፤መዝ
52፥4፤ምሳ15፥2፤31፥26
**10፥32** መዝ59፥7፤
መክ10፥12
**11፥1** ዘሌ19፥36፤
ዘዳ25፥13-16፤ኢዮ
6፥2፤ምሳ20፥10፡23፤1
6፥11፤ሕዝ45፥10
**11፥2** ምሳ16፥18፤
18፥12፤29፥23
**11፥3** ቀኑ5፤ምሳ13፥6
**11፥4** ኢዮ20፥20፤
ምሳ10፥2፤ሕዝ7፥19
፤27፥27
**11፥5** ቀኑ3፤1ነገ
8፥36፤ምሳ21-23፤
13፥6፤21፥7
**11፥6** አስ7፥9
**11፥7** ኢዮ8፥13፤
ምሳ10፥28
**11፥8** ምሳ21፥18
**11፥9** ምሳ12፥6፤
ኤር45፥5
**11፥10** 2ነገ11፥20፤
አስ8፥17
**11፥11** ምሳ14፥34፤
29፥8
**11፥12** ኢዮ6፥24፤
ምሳ14፥21
**11፥13** ምሳ10፥14፤
20፥19
**11፥14** 2ሳሙ15፥34፤
ምሳ15፥22፤20፥18
፤24፥6
**11፥15** ምሳ6፥1፤
17፥18፤22፥26-27
**11፥16** ምሳ31፥31
**11፥18** ዘፀ1፥20፤
ኢዮ4፥8፤ሆሴ10፥12-13
**11፥19** ዘዳ30፥15፤
1ሳሙ2፥6፤መዝ89፥
48፤ምሳ1፥18-19፤
10፥2፤መክ7፥2፤ኤር
43፥11
**11፥20** ዘኍ14፥8፤
1ዜና29፥17፤መዝ15፥
2፤101፥1-4፤119፥1፤
ምሳ3፥32፤12፥2፡22
፤15፥9

ይወድቃሉ።
6 ቅኖችን ጽድቃቸው ትታደጋቸዋለች፤
ወስላቶች ግን በክፉ ምኞታቸው
ይጠመዳሉ።
7 ክፉ ሰው ሲሞት ተስፋው ከንቱ
ትሆናለች፤
በኀይሉ የተመካበትም ሁሉ እንዳልነበረ
ይሆናል።
8 ጻድቅ ከመከራ ይድናል፤
ይልቁን መከራው በክፉው ላይ
ይደርሳል።
9 ክፉ ሰው ባልንጀራውን በአፉ ያጠፋል፤
ጻድቃን ግን በዕውቀት ያመልጣሉ።
10 ጻድቃን ሲሳካላቸው ከተማ ደስ
ይላታል፤
ክፉዎች ሲጠፉ እልልታ ይሆናል።
11 በቅኖች በረከት ከተማ ከፍ ከፍ
ትላለች፤
በክፉዎች አንደበት ግን ትጠፋለች።
12 ማመዛዘን የጐደለው ሰው ባልንጀራውን
ያንኳስሳል፤
አስተዋይ ግን አንደበቱን ይገዛል።
13 ሐሜተኛ ምስጢር አይጠብቅም፤
ታማኝ ሰው ግን ምስጢር ይጠብቃል።
14 በአመራር ጒድለት መንግሥት
ይወድቃል፤
የመካሮች ብዛት ግን ድልን እርግጠኛ
ያደርጋል።
15 ለማይታወቅ ሰው ዋስ የሚሆን መከራ
ያገኘዋል፤
ዋስትና ለመስጠት እጅ የማይመታ
ግን ምንም አይደርስበትም።
16 ርኅሩኅ ሴት ክብር ታገኛለች፤
ጒልበተኛ ሰዎች ግን ብልጽግናን ብቻ
ያገኛሉ።
17 ደግ ሰው ራሱን ይጠቅማል፤
ጨካኝ ግን በራሱ ላይ መከራ
ያመጣል።
18 ክፉ ሰው የሚያገኘው ትርፍ መቅኖ
የለውም፤
ጽድቅን የሚዘራ ግን አስተማማኝ ዋጋ
ያገኛል።
19 እውነተኛ ጻድቅ ሕይወትን ያገኛል፤
ክፋትን የሚከተል ግን ወደ ሞቱ
ይጓዛል።
20 እግዚአብሔር ልበ ጠማሞችን ይጸየፋል፤
በመንገዳቸው ነቀፋ በሌለባቸው ሰዎች
ግን ደስ ይሰኛል።

[21]ክፉ ሳይቀጣ እንደማይቀር ዕወቅ፣
ጻድቃን ግን በነጻ ይሄዳሉ።

[22]በእርያ አፍንጫ ላይ እንደተሰካ የወርቅ
ቀለበት፣
ማስተዋል የጐደላት ቆንጆ ሴት እንዲሁ
ናት።

[23]የጻድቃን ምኞት ምንጊዜም ፍጻሜው
ያማረ ነው፤
የክፉዎች ተስፋ ግን በቍጣ
ያከትማል።

[24]አንዱ በለጋስነት ይሰጣል፤ ሆኖም
ይበልጥ ያገኛል፤
ሌላው ያለመጠን ይሰስታል፤ ግን
ይደኸያል።

[25]ለጋስ ይበለጽጋል፤
ሌሎችን የሚያረካም ራሱ ይረካል።

[26]በድብቅ እህል የሚያከማቸውን ሕዝብ
ይረግመዋል፤
አውጥቶ የሚሸጥ ግን በረከት ይጐና
ጸፋል።

[27]በጎ ነገርን ተግቶ የሚሻ በጎ ነገር
ይጠብቀዋል፤
ክፉ ነገር የሚፈልገውን ግን ክፉ
ያገኘዋል።

[28]በሀብቱ የሚታመን ሁሉ ይወድቃል፤
ጻድቃን ግን እንደ አረንጓዴ ቅጠል
ይለመልማሉ።

[29]ቤተ ሰቡን የሚያውክ ሰው ነፋስን
ይወርሳል፤
ተላላም ሰው የጠቢብ ሎሌ ይሆናል።

[30]የጻድቅ ፍሬ የሕይወት ዛፍ ናት፤
ነፍሳትን የሚማርክም ጠቢብ ነው።

[31]ጻድቃን ለሠሩት ሥራ በምድር
የእጃቸውን የሚያገኙ ከሆነ፣
የክፉዎችና የኀጢአተኞችማ የቱን
ያህል የባሰ ይሆን?

12 ተግሣጽን የሚወድ ዕውቀትን
ይወዳል፤
መታረምን የሚጠላ ግን ደነዝ ነው።

[2]መልካም ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ
ሞገስ ያገኛል፤
ተንኰለኛውን ግን እግዚአብሔር
ይፈርድበታል።

[3]ሰው በክፋት ላይ ተመሥርቶ ሊጸና
አይችልም፤
ጻድቃን ግን ከቦታቸው አይነቃነቁም።

[4]መልካም ሴት ለባሏ ዘውድ ናት፤
አሳፋሪ ሚስት ግን አጥንቱ ውስጥ
እንዳለ ንቅዘት ናት።

11፥21 ምሳ16፥5
11፥25 1ዜና29፥17፤ምሳ22፥9፤ኢሳ32፥8፤2ቆሮ9፥6-9
11፥27 መዝ7፥15-16
11፥28 ኢዮ31፥24-28፤መዝ49፥6፤52፥7፡8፤62፥10፤92፥12-14፤ኤር9፥23
11፥29 ምሳ14፥19
11፥30 ዘፍ2፥9፤ምሳ10፥11
11፥31 ኤር25፥29፤49፥12፤1ጴጥ4፥18
12፥1 ምሳ5፥11-14፤9፥7-9፤13፥1፡18፤15፥5፡10፡12፡32
12፥2 2ሳሙ15፥3፤ኢዮ33፥26፤ መዝ84፥11፤ምሳ11፥20
12፥3 ምሳ10፥25
12፥4ሩት3፥11፤ምሳ18፥22፤31፥10-11
12፥6 ምሳ11፥9፤14፥3
12፥7 መዝ37፥36፤ምሳ10፥25፤14፥11፤15፥25
12፥8 ኢሳ19፥14፤29፥24
12፥10 ዘኍ22፥29
12፥11 ምሳ28፥19
12፥13መዝ59፥12፤ምሳ10፥6፤18፥7፤21፥23
12፥14 ምሳ13፥2፤14፥14፤15፥23፤18፥20
12፥15 ምሳ9፥7-9፤14፥12፤16፥2፡25፤19፥20
12፥161ሳሙ25፥25፤ኢዮ5፥2፤ምሳ29፥11
12፥17 መዝ12፥2፤ምሳ14፥5፡25
12፥18 መዝ55፥21፤ምሳ15፥4፤25፥18
12፥20 ሮሜ14፥19

[5]የጻድቃን ሐሳብ ቀና ነው፤
የክፉዎች ምክር ግን ሸር አለበት።

[6]የክፉዎች ቃል ደም ለማፍሰስ ታደባለች፤
የቅኖች ንግግር ግን ይታደጋቸዋል።

[7]ክፉ ሰዎች ይገለበጣሉ፤ ድራሻቸውም
ይጠፋል፤
የጻድቃን ቤት ግን ጸንቶ ይኖራል።

[8]ሰው በጥበቡ ይመሰገናል፤
ጠማማ ልብ ያላቸው ግን የተናቁ
ናቸው።

[9]የሚበላው ሳይኖረው ከሚኰራራ ይልቅ፣
ራሱን ዝቅ አድርጎ ሠራተኛ የሚያሳድር
ይሻላል።

[10]ጻድቅ ሰው ለእንስሳቱ ይራራል፤
ክፉዎች ራሩ ቢባል እንኳ ዞሮ ዞሮ
ሥራቸው ጭካኔ ነው።

[11]መሬቱን የሚያርስ የተትረፈረፈ ምግብ
ያገኛል፤
ከንቱ ተስፋን የሚያሳድድ ግን
ማመዛዘን ይጐድለዋል።

[12]ኀጥኣን የክፉዎችን ምርኮ ይመኛሉ፤
የጻድቅ ሥር ግን ይንሰራፋል።

[13]ክፉ ሰው በእኩይ ንግግሩ ይጠመዳል፤
ጻድቅ ሰው ግን ከመከራ ያመልጣል።

[14]ሰው ከከንፈሩ ፍሬ የተነሣ በበጎ ነገር
ይሞላል፤
እንደ እጁ ሥራም ተገቢውን ዋጋ
ያገኛል።

[15]ተላላ ሰው መንገዱ ትክክል መስሎ
ይታየዋል፤
ጠቢብ ሰው ግን ምክር ይሰማል።

[16]ተላላ ሰው ቍጣው ወዲያውኑ
ይታወቅበታል፤
አስተዋይ ሰው ግን ስድብን ንቆ
ይተዋል።

[17]ሐቀኛ ምስክር በእውነት ይመሰክራል፤
ሐሰተኛ ምስክር ግን ውሸት ይናገራል።

[18]ግድ የለሽ ቃል እንደ ሰይፍ ይወጋል፤
የጠቢብ አንደበት ግን ፈውስን
ያመጣል።

[19]እውነት የሚናገሩ ከንፈሮች ለዘላለም
ጸንተው ይኖራሉ፤
ሐሰተኛ አንደበት ግን ለቅጽበት ያህል
ብቻ ነው።

[20]ክፋትን በሚያውጠነጥኑ ሰዎች ልብ
አታላይነት አለ፤
ሰላምን የሚያራምዱ ግን ደስታ
አላቸው።

21 ጻድቃን ጕዳት አያገኛቸውም፤
ክፉዎች ግን በመከራ የተሞሉ ናቸው።
22 እግዚአብሔር ሐሰተኛ ከንፈርን
ይጸየፋል፤
በእውነተኞች ሰዎች ግን ደስ ይለዋል።
23 አስተዋይ ሰው ዕውቀቱን ይሰውራል፤
የተላሎች ልብ ግን ድንቍርናን
ይነዛል።
24 ትጉ እጆች ለገዥነት ሲያበቁ፣
የስንፍና ፍጻሜ ግን የባርነት ሥራ
ነው።
25 ሥጉ ልብ ሰውን በሐዘን ይወጥራል፤
መልካም ቃል ግን ደስ ያሰኘዋል።
26 ጻድቅ ሰው ለወዳጁ መልካም ምክር
ይሰጣል፤[ፕ]
የክፉዎች መንገድ ግን ወደ ስሕተት
ይመራቸዋል።
27 ሰነፍ አድኖ ያመጣውን እንኳ
አይጠብስም፤[የ]
ትጉ ሰው ግን ለንብረቱ ዋጋ ይሰጣል።
28 በጽድቅ መንገድ ላይ ሕይወት አለ፤
በዚያ ጐዳና ላይ ሞት የለም።

13 ጠቢብ ልጅ የአባቱን ምክር
በማስተዋል ይሰማል፤
ፌዘኛ ግን ተግሣጽን አያዳምጥም።
2 ሰው ከከንፈሩ ፍሬ መልካም ነገር
ያገኛል፤
ወስላቶች ግን ዐመፅን ይናፍቃሉ።
3 አንደበቱን የሚጠብቅ ሕይወቱን
ይጠብቃል፤
አፉ እንዳመጣለት የሚናገር ግን
ይጠፋል።
4 ሰነፍ አጥብቆ ይመኛል፤ አንዳችም
አያገኝም፤
የትጉዎች ምኞት ግን ይረካል።
5 ጻድቅ ሐሰትን ይጠላል፤
ክፉ ሰው ግን ኀፍረትንና ውርደትን
ያመጣል።
6 ጽድቅ ቅን የሆነውን ሰው ትጠብቀዋለች፤
ክፋት ግን ኀጢአተኛውን ትጥለዋለች።
7 ምንም ሳይኖረው ባለጠጋ መስሎ
የሚታይ ሰው አለ፤
ሌላው ድኻ መስሎ ይታያል፤ ግን ብዙ
ሀብት አለው።
8 የሰው ሀብቱ ለሕይወቱ ቤዛ ሊሆነው
ይችላል፤
ድኻው ግን ሥጋት የለበትም።
9 የጻድቃን ብርሃን ደምቆ ይበራል፤
የክፉዎች መብራት ግን ይጠፋል።
10 ትዕቢት ጠብን ብቻ ያስፋፋል፤
ጥበብ ግን ምክርን በሚቀበሉ ዘንድ
ትገኛለች።
11 ያላግባብ የተገኘ ገንዘብ እየተመናመነ
ያልቃል፤
ገንዘቡን ጥቂት በጥቂት የሚያከማች
ግን ይጠራቀምለታል።
12 ለነገ የሚባል ተስፋ ልብን ያሳምማል፤
የተሳካ ምኞት ግን የሕይወት ዛፍ ነው።
13 ምክርን የሚያቃልል በራሱ ላይ ጥፋት
ያመጣል፤
ትእዛዝን የሚያከብር ግን ወሮታን
ይቀበላል።
14 የጠቢብ ትምህርት የሕይወት ምንጭ
ናት፤
ሰውን በሞት ወጥመድ እንዳይያዝ
ታደርገዋለች።
15 መልካም ማስተዋል ሞገስን ታስገኛለች፤
የከዳተኞች መንገድ ግን አስቸጋሪ
ነው።[ዶ]
16 አስተዋይ ሰው ሥራውን በዕውቀት
ያከናውናል፤
ተላላ ግን ሞኝነቱን ይገልጣል።
17 ክፉ መልእክተኛ መከራ ውስጥ ይገባል፤
ታማኝ መልእክተኛ ግን ፈውስን
ያመጣል።
18 ተግሣጽን የሚንቅ ወደ ድኽነትና
ኀፍረት ይሄዳል፤
እርምትን የሚቀበል ሁሉ ግን ይከበራል።
19 ምኞት ስትፈጸም ነፍስን ደስ ታሰኛለች፤
ተላሎች ግን ከክፋት መራቅን
ይጸየፋሉ።
20 ከጠቢብ ጋር የሚሄድ ጠቢብ ይሆናል፤
የተላሎች ባልንጀራ ግን ጕዳት
ያገኘዋል።
21 መጥፎ ዕድል ኀጢአተኛን ይከታተላል፤
ብልጽግና ግን የጻድቃን ዋጋ ነው።
22 ደግ ሰው ለልጅ ልጆቹ ውርስ ትቶ
ያልፋል፤
የኀጢአተኞች ሀብት ግን ለጻድቃን
ይከማቻል።
23 የድኾች ዕርሻ የተትረፈረፈ ምርት
ያስገኛል፤
የፍትሕ መጓደል ግን ጠራርጎ
ይወስደዋል።

12፥21 ኢዮ4፥7
12፥22 1ነገ13፥18፤መዝ18፥19፤ምሳ6፥17፤11፥20
12፥23 መዝ38፥5፤59፥7፤ምሳ10፥14፤18፥2
12፥24 ምሳ10፥4
12፥25 ምሳ15፥13
12፥26 መዝ95፥10
12፥28 ዘዳ30፥15፤ምሳ10፥2
13፥1 ምሳ12፥1፤15፥5
13፥2 ምሳ12፥14
13፥3 ኢዮ1፥22፤መዝ12፥2፤34፥13፤ምሳ10፥6፤18፥7፡20-21፤21፥23
13፥4 ምሳ21፥25-26
13፥5 መዝ119፥128
13፥6 ምሳ11፥3፡5፤ኤር44፥5
13፥7 2ቆሮ6፥10፤ራእ3፥17
13፥8 ምሳ15፥16
13፥9 ኢዮ18፥5፤ምሳ4፥18-19
13፥10 መሳ19፥30፤ምሳ9፥9
13፥11 ምሳ10፥2
13፥12 ምሳ10፥11
13፥13 ዘፀ9፥20፤ዘኍ15፥31፤ምሳ16፥20
13፥14 ምሳ10፥11፤14፥27
13፥16 አስ5፥11፤መዝ38፥5፤መክ10፥3
13፥17 ምሳ10፥26፤25፥13
13፥18 መዝ141፥5፤ ምሳ1፥7፤12፥1፤25፥12፤መክ7፥5
13፥19 ምሳ10፥11
13፥20 2ዜና10፥8
13፥21 2ሳሙ3፥39፤መዝ25፥13፤32፥10፤ኤር40፥3፤50፥7፤ሕዝ14፥13፤18፥4
13፥22 አስ8፥2፤ኢዮ27፥17፤መክ2፥26

[ፕ]26 ወይም *ለወዳጁ መሪ ነው።* ሆኖም የዕብራይስጡ ፍቺ በውል አይታወቅም።
[የ]27 ለዚህ ቃል የዕብራይስጡ ትርጓሜ በእርግጠኝነት አይታወቅም
[ዶ]15 ወይም *የከዳተኞች መንገድ ግን አይጸናም*

[24]በአርጩሜ ከመቅጣት የሚሳሳለት
ልጁን ይጠላል፤
የሚወደው ግን በጥንቃቄ ይቀጣዋል።

[25]ጻድቅ እስኪጠግብ ድረስ ይበላል፤
የክፉዎች ሆድ ግን እንደ ተራበ
ይኖራል።

14 ጠቢብ ሴት ቤቷን ትሠራለች፤
ተላላ ሴት ግን በገዛ እጇ
ታፈርሰዋለች።

[2]አካሄዱ ቅን የሆነ ሰው እግዚአብሔርን
ይፈራል፤
መንገዱ ጠማማ የሆነ ግን ይንቀዋል።

[3]የተላላ ሰው ንግግር ለጀርባው በትር
ታስከትልበታለች፤
የጥበበኛ ከንፈር ግን ትጠብቃቸዋለች።

[4]በሬዎች በሌሉበት ገንዳው ባዶ ይሆናል፤
በበሬ ጉልበት ግን ብዙ ምርት
ይገኛል።

[5]ታማኝ ምስክር አይዋሽም፤
ሐሰተኛ ምስክር ግን ውሸትን
ይዘከዝካል።

[6]ፌዘኛ ጥበብን ይሻል፤ ሆኖም
አያገኛትም፤
ዕውቀት ግን ለአስተዋዮች በቀላሉ
ትገኛለች።

[7]ከተላላ ሰው ራቅ፤
ከከንፈሮቹ ዕውቀት አታገኝምና።

[8]የአስተዋዮች ጥበብ መንገዳቸውን ልብ
ማለት ነው፤
የተላሎች ሞኝነት ግን መታለል ነው።

[9]ተላሎች በሚያቀርቡት የበደል ካሳ
ያፌዛሉ፤
በቅኖች መካከል ግን በጎ ፈቃድ
ትገኛለች።

[10]እያንዳንዱ ልብ የራሱን መራራ ሐዘን
ያውቃል፤
ደስታውንም ማንም ሊጋራው አይጠ
ችልም።

[11]የክፉዎች ቤት ይፈርሳል፤
የቅኖች ድንኳን ግን ይስፋፋል።

[12]ለሰው ቀና መስሎ የሚታይ መንገድ
አለ፤
በመጨረሻ ግን ወደ ሞት ያደርሳል።

[13]በሣቅ ጊዜ እንኳ ልብ ይተክዛል፤
ደስታም በሐዘን ሊፈጸም ይችላል።

[14]ልባቸውን ከጽድቅ የሚመልሱ
የእጃቸውን ሙሉ ዋጋ ይቀበላሉ፤
ደግ ሰውም ወሮታውን ያገኛል።

13፥24 2ሳሙ7፥14፤ምሳ3፥12፤19፥18፤22፥15፤23፥13-14፤29፥15፡17፤ኤፌ6፥4፤ዕብ12፥7
13፥25 ምሳ10፥3
14፥1 ሩት3፥11፤ምሳ24፥3
14፥3 ምሳ10፥13፡14፤12፥6፤መክ10፥12
14፥4 መዝ144፥14
14፥5 መዝ12፥2፤ምሳ12፥17
14፥6 ምሳ9፥9
14፥8 ቆላ15፡24፤ምሳ15፥28፤21፥29
14፥11 ኢዮ8፥22፤መዝ72፥71፤ምሳ3፥33፤12፥7፤21፥12
14፥12 ምሳ12፥15፤16፥25
14፥13 መክ2፥2፤7፥3፡6
14፥14 2ዜና15፥7፤ምሳ1፥31፤12፥14
14፥15 ቆላ8
14፥16 ዘፀ20፥20፤1ሳሙ25፥25፤ምሳ22፥3
14፥17 ቆላ29፤2ነገ5፥12፤አስ5፥9፤ምሳ15፥18፤16፥28፤26፥21፤28፥25፤29፥22
14፥19 ምሳ11፥29
14፥20 ምሳ19፥4፡7
14፥21 ምሳ11፥12፤19፥17
14፥22 ምሳ4፥16-17
14፥24 ቆላ8
14፥25 ምሳ12፥17
14፥26 መዝ9፥9፤ምሳ18፥10
14፥27 መዝ18፥5፤ምሳ10፥11፤13፥14
14፥28 2ሳሙ19፥7
14፥29 ቆላ17፤2ነገ5፥12፤ምሳ17፥27፤መክ7፥8-9
14፥30 ምሳ17፥22
14፥31 ዘዳ24፥14፤ኢዮ20፥19፤ምሳ17፥5፤ማቴ10፥42

[15]ተላላ ሰው ሁሉን ያምናል፤
አስተዋይ ግን እርምጃውን ያስተውላል።

[16]ጠቢብ ሰው ጥንቁቅ ነው፤ ከክፉም
ይርቃል፤
ተላላ ግን ችኩልና ደንታ ቢስ ነው።

[17]ግልፍተኛ ሰው የቂል ተግባር
ይፈጽማል፤
መሠሪም ሰው አይወደድም።

[18]ብስለት የሌላቸው ተላላነትን ይወርሳሉ፤
አስተዋዮች ግን ዕውቀትን እንደ ዘውድ
ይጭናሉ።

[19]ክፉዎች በደጎች ፊት፣
ኀጥኣንም በጻድቃን ደጅ ያጐነብሳሉ።

[20]ድኾችን ወዳጆቻቸው እንኳ
ይጠሏቸዋል፤
ባለጠጎች ግን ብዙ ወዳጆች አሏቸው።

[21]ጎረቤቱን የሚንቅ ኀጢአት ይሠራል፤
ለተቸገሩት የሚራራ ግን ቡሩክ ነው።

[22]ክፉ ነገር የሚያቅዱ ከትክክለኛው
መንገድ ይወጡ የለምን?
በጎ ነገር የሚያቅዱ ግን ፍቅርንና
ታማኝነትን ያተርፋሉ።[፳]

[23]ለፍተው የሠሩት ሁሉ ትርፍ ያስገኛል፤
ከንቱ ወሬ ግን ወደ ድኽነት ያመራል።

[24]ጠቢባን ብልጥግና ዘውዳቸው ነው፤
የተላሎች ተላላነት ግን ፍሬው ከንቱነት
ነው።

[25]እውነተኛ ምስክር ሕይወት ያድናል፤
ሐሰተኛ ምስክር ግን አባይ ነው።

[26]እግዚአብሔርን የሚፈራ ጽኑ አምባ
አለው፤
ልጆቹም መጠጊያ ይኖራቸዋል።

[27]እግዚአብሔርን መፍራት የሕይወት
ምንጭ ነው፤
ሰውን ከሞት ወጥመድ ያድነዋል።

[28]የሕዝብ ብዛት የንጉሥ ክብር ሲሆን፣
የዜጎች ማነስ ግን ለገዥ መጥፊያው
ነው።

[29]ታጋሽ ሰው ትልቅ ማስተዋል አለው፤
ግልፍተኛ ሰው ግን ቂልነትን
ይገልጣል።

[30]ሰላም ያለው ልብ ለሰውነት ሕይወት
ይሰጣል፤
ቅናት ግን ዐጥንትን ያነቅዛል።
[31]ድኾችን የሚያስጨንቅ ፈጣሪያቸውን
ይንቃል፤

[፳]22 ወይም *ታማኝነትን ያሳያሉ*

ለተቸገሩ የሚራራ ሁሉ ግን አምላክን
ያከብራል።
32ክፉዎች በክፋታቸው ይወድቃሉ፤
ጻድቃን ግን በሞት ጊዜ እንኳ መጠጊያ
አላቸው።
33ጥበብ በአስተዋዮች ልብ ታድራለች፤
በተላሎች መካከል ራሷን ትገልጣለች።[ገ]
34ጽድቅ ሕዝብን ከፍ ከፍ ታደርጋለች፤
ኀጢአት ግን ለየትኛውም ሕዝብ
ውርደት ነው።
35ጠቢብ አገልጋይ ንጉሥን ደስ ያሰኛል፤
አሳፋሪ አገልጋይ ግን ቍጣውን በራሱ
ላይ ያመጣል።

15 የለዘበ መልስ ቍጣን ያበርዳል፤
ክፉ ቃል ግን ቍጣን ይጭራል።
2የጠቢብ አንደበት ዕውቀትን
ታወድሳለች፤
የተላሎች አንደበት ግን ቂልነትን
ያፈልቃል።
3*የእግዚአብሔር* ዐይኖች በሁሉም ስፍራ
ናቸው፤
ክፉዎችንም ደጎችንም ነቅተው
ይመለከታሉ።
4ፈውስ የምታመጣ ምላስ የሕይወት ዛፍ
ናት፤
አታላይ ምላስ ግን መንፈስን
ትሰብራለች።
5ተላላ የአባቱን ምክር ይንቃል፤
መታረምን የሚቀበል ግን
አስተዋይነቱን ያሳያል።
6የጻድቃን ቤት በብዙ ሀብት የተሞላ
ነው፤
የክፉዎች ገቢ ግን መከራን
ታመጣባቸዋለች።
7የጠቢባን ከንፈር ዕውቀትን ታስፋፋለች፤
የተላሎች ልብ ግን እንዲህ አይደለም።
8*እግዚአብሔር* የክፉዎችን መሥዋዕት
ይጸየፋል፤
የቅኖች ጸሎት ግን ደስ ያሰኘዋል።
9*እግዚአብሔር* የክፉዎችን መንገድ
ይጸየፋል፤
ጽድቅን የሚከታተሉትን ግን
ይወዳቸዋል።
10 ከመንገድ የሚወጣ ሰው ጥብቅ ቅጣት
ይጠብቀዋል፤
እርምትን የሚጠላ ይሞታል።
11ሲኦልና የሙታን ዓለም[ጠ] *በእግዚአብሔር*
ፊት የተገለጡ ናቸው፤
የሰዎች ልብማ የቱን ያህል የታወቀ
ነው!
12ፌዘኛ መታረምን ይጠላል፤
ጠቢባንንም አያማክርም።
13ደስተኛ ልብ ፊትን ያፈካል፤
የልብ ሐዘን ግን መንፈስን ይሰብራል።
14አስተዋይ ልብ ዕውቀትን ይሻል፤
የተላላ አፍ ግን ቂልነትን ያመነዥካል።
15የተጨቈኑ ሰዎች ዘመናቸው ሁሉ የከፋ
ነው፤
በደስታ የተሞላ ልብ ግን የማይቋረጥ
ፈንጠዝያ አለው።
16*እግዚአብሔርን* ከመፍራት ጋር ያለ
ጥቂት ነገር፣
ሁከት ካለበት ትልቅ ሀብት
ይበልጣል።
17ፍቅር ባለበት ጐመን መብላት፣
ጥላቻ ባለበት የሰባ ፍሪዳ ከመብላት
ይሻላል።
18ግልፍተኛ ሰው ጠብ ያነሣሣል፤
ታጋሽ ሰው ግን ጠብን ያበርዳል።
19የሀኬተኛ መንገድ በእሾህ የታጠረች
ናት፤
የቅኖች መንገድ ግን የተጠረገ አውራ
ጐዳና ነው።
20ጠቢብ ልጅ አባቱን ደስ ያሰኛል፤
ተላላ ሰው ግን እናቱን ይንቃል።
21ማመዛዘን የጐደለው ሰው ቂልነት
ያስደስተዋል፤
አስተዋይ ሰው ግን ቀጥተኛውን መንገድ
ይከተላል።
22ምክር ሲጓደል ዕቅድ ይፋለሳል፤
በብዙ አማካሪዎች ግን ይሳካል።
23ሰው ተገቢ መልስ በመስጠት ደስታን
ያገኛል፤
በወቅቱም የተሰጠ ቃል ምንኛ መልካም
ነው!
24ወደ ሲኦል[ጨ] ከመውረድ እንዲድን፣
የሕይወት መንገድ ጠቢቡን ሰው ወደ
ላይ ትመራዋለች።
25*እግዚአብሔር* የትዕቢተኛውን ቤት
ያፈርሰዋል፤
የመበለቲቱን ዳር ድንበር ግን
እንዳይደፈር ይጠብቃል።
26*እግዚአብሔር* የክፉውን ሰው ሐሳብ

**14፥32** ኢዮ13፥15፤ መዝ34፥21፤ምሳ6፥15
**14፥33** ምሳ2፥6-10
**14፥34** ምሳ11፥11
**14፥35** አስ8፥2፤ ማቴ24፥45-51፤ 25፥14-30
**15፥1** 1ነገ12፥7፤ 2 ዜና10፥7፤ምሳ25፥15
**15፥2** ቍ7፤መዝ 59፥7፤ምሳ10፥31፤ መክ10፥12
**15፥3** 2ዜና16፥9፤ ኢዮ10፥4፤31፥4፤ 34፥21፤ምሳ5፥21፤ ኤር16፥17፤ዕብ4፥13
**15፥4** መዝ5፥9፤ምሳ 10፥11፤12፥18
**15፥5** ምሳ10፥17፤ 12፥1፤13፥1
**15፥6** ምሳ8፥21፤ 10፥16
**15፥7** ቍ2፤ምሳ 10፥13
**15፥8** ቍ29፤ኢዮ 35፥13፤መዝ51፥17፤ ምሳ6፥16፤21፥27፤28፥ 9፤ኢሳ1፥13፤ዮሐ 9፥31
**15፥9** ዘዳ7፥13፤ ምሳ6፥16፤11፥20፤
**15፥10** ምሳ1፥31- 32፤12፥1
**15፥11** 1ሳሙ2፥3፤ 2ዜና6፥30፤ኢዮ26፥6 ፤መዝ44፥21፤ራእ 2፥23
**15፥12** ምሳ9፥8፤ 12፥1
**15፥13** ቍ15፤ምሳ 12፥25፤17፥22፤18፥14
**15፥14** ምሳ18፥15
**15፥15** ቍ13
**15፥16** ቍ17፤መዝ 37፥16-17፤ምሳ13፥8፤ 16፥8፤17፥1
**15፥17** ቍ16፤ምሳ 17፥1፤መክ4፥6
**15፥18** ዘፍ13፥8፤ ምሳ6፥16-19፤14፥17
**15፥19** ምሳ22፥25
**15፥20** ምሳ10፥1
**15፥21** ምሳ2፥14
**15፥22** 1ነገ1፥12፤ መዝ16፥7፤ምሳ11፥14 ፤24፥6
**15፥23** ምሳ12፥14፤ 25፥11
**15፥25** ዘዳ19፥14፤ ምሳ12፥7፤23፥10-11
**15፥26** መዝ94፥11፤ 18፥26፤ምሳ6፥16

[ገ]33 ዕብራይስጡ፣ የሰብዓ ሊቃናትና የሱርሰት ትርጕሞች *በተላሎች ልብ ግን አትታወቅም* ይላሉ።
[ጠ]11 በዕብራይስጡ *ሲኦልና አባዶን* ይላል።
[ጨ]24 ወይም *መቃብር*

ይጸየፋል፤
የንጹሓን ሐሳብ ግን ደስ ያሰኘዋል።
27 ስስታም ሰው በቤተ ሰቡ ላይ ችግር
ያመጣል፤
ጉቦን የሚጠላ ግን በሕይወት ይኖራል።
28የጻድቅ ሰው ልብ የሚሰጠውን መልስ
ያመዛዝናል፤
የክፉ ሰው አፍ ግን ክፋትን ያጕርፋል።
29እግዚአብሔር ከክፉዎች ሩቅ ነው፤
የጻድቃንን ጸሎት ግን ይሰማል።
30ብሩህ ገጽታ ልብን ደስ ያሰኛል፤
መልካም ዜናም ዐጥንትን ያለመልማል።
31ሕይወት ሰጪ የሆነውን ተግሣጽ
የሚሰማ፣
በጠቢባን መካከል ይኖራል።
32ተግሣጽን የሚንቅ ራሱን ይንቃል፤
እርምትን የሚቀበል ግን ማስተዋልን
ያገኛል።
33እግዚአብሔርን መፍራት ጥበብን
መማር ነው፤*
ትሕትናም ክብርን ትቀድማለች።

# 16

የልብ ዕቅድ የሰው ነው፤
የአንደበት መልስ ግን
ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።
2ለሰው መንገዱ ሁሉ ንጹሕ መስሎ
ይታየዋል፤
መነሻ ሐሳቡ ግን በእግዚአብሔር
ይመዘናል።
3የምታደርገውን ሁሉ ለእግዚአብሔር
ዐደራ ስጥ፤
ዕቅድህም ሁሉ ይሳካልሃል።
4እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ለራሱ
ዐላማ ሠርቶአል፤
ክፉዎችንም እንኳ ለጥፋት ቀን
አዘጋጅቶአል።
5እግዚአብሔር በልብ የሚታበዩትን ሁሉ
ይጸየፋል፤
እነርሱም ከቅጣት እንደማያመልጡ
በእርግጥ ዕወቅ።
6በፍቅርና በታማኝነት ኀጢአት ይሰረያል፤
እግዚአብሔርን በመፍራት ሰው ከክፋት
ይርቃል።
7የሰው መንገድ እግዚአብሔርን ደስ
ሲያሰኘው፣
ጠላቶቹ እንኳ አብረውት በሰላም
እንዲኖሩ ያደርጋል።
8ከጽድቅ ጋር ጥቂቱ ነገር፣
በግፍ ከሚገኝ ብዙ ትርፍ ይሻላል።

15፥27 ዘፀ23፥8፤ መዝ15፥5፤ኢሳ 1፥23፤33፥15
15፥28 መዝ59፥7፤ ምሳ14፥8
15፥29 ቊ8፤ኢዮ 15፥31፤መዝ145፥18-19፤ኢሳ59፥2፤ዮሐ 9፥31
15፥30 ምሳ25፥25
15፥31 ምሳ9፥7-9፤ 12፥1
15፥32 ምሳ1፥7፤ 9፥7-9፤12፥1፤መክ 7፥5
15፥33 ምሳ1፥7፤ 16፥18፤18፥12፤ 22፥4፤29፥23፤ኢሳ 66፥2
16፥1 ቊ9፤ምሳ 19፥21
16፥2 1ሳሙ2፥3፤ 2ዜና6፥30፤ምሳ12፥15 ፤20፥27፤21፥2፤30፥12 ፤ሉቃ16፥15
16፥3 2ዜና20፥20፤ መዝ20፥4፤37፥5-6፤ ምሳ3፥5-6
16፥4 ዘፀ9፥16፤ 2ዜና 34፥24፤መዝ 18፥18፤ሮሜ9፥22
16፥5 መዝ40፥4፤ ምሳ6፥16፤11፥20-21
16፥6 ዘፍ20፥11፤ዘፀ 1፥17፤20፥20
16፥7 ዘፍ39፥21፤ መዝ105፥15፤ኤር39፥ 12፤40፥1፤42፥12፤ዳን 1፥9
16፥8 መዝ37፥16፤ ምሳ15፥16፤መክ4፥6
16፥9 ቊ1፤ኢዮ 33፥29፤መዝ90፥12
16፥10 ምሳ17፥7
16፥11 ምሳ11፥1 ፤ሕዝ45፥10
16፥12 ምሳ25፥5፤ 26፥28፤29፥14፤31፥5
16፥13 ምሳ22፥11
16፥14 ዘፍ40፥2፤ኢ ዮ29፥24፤ምሳ20፥2፤2 5፥15፤29፥8መክ10፥4
16፥15 ዘፍ40፥2፤ ኢዮ29፥24፤ምሳ 19፥12፤25፥2-7
16፥16 ኢዮ28፥15፤ መዝ49፥20፤ምሳ3፥13 -14
16፥17 ምሳ19፥16
16፥18 1ሳሙ17፥42፤ አስ5፥12፤መዝ 18፥27፤ምሳ11፥2፤ 15፥33፤18፥12፤29፥ 23፤ኢሳ13፥11፤ኤር 48፥29
16፥20 መዝ32፥10 ፤40፥4፤ምሳ13፥13 ፤19፥18፤29፥25፤ኤር1 7፥7
16፥21 ቊ23
16፥22 ምሳ10፥11
16፥23 ቊ21፤ኢዮ

9ሰው በልቡ መንገዱን ያቅዳል፤
እግዚአብሔር ግን ርምጃውን
ይወስንለታል።
10የንጉሥ ከንፈሮች እንደ አምላክ ቃል
ይናገራሉ፤
አንደበቱ ፍትሕን ያዛባ ዘንድ
አይገባም።
11ሐቀኛ መስፈሪያና ሚዛን ከእግዚአብሔር
ናቸው፤
በከረጢት ውስጥ ያሉት መመዘኛዎችም
ሁሉ ሥራዎቹ ናቸው።
12 ክፋትን ማድረግ ለነገሥታት አጸያፊ
ነው፤
ዙፋን የሚጸናው በጽድቅ ነውና።
13ነገሥታት በታማኝ ከንፈሮች ደስ
ይላቸዋል፤
እውነት የሚናገረውን ሰው ይወዱታል።
14የንጉሥ ቍጣ የሞት መልእክተኛ ነው፤
ጠቢብ ሰው ግን ቍጣውን ያበርዳል።
15የንጉሥ ፊት ሲፈካ ሕይወት አለ፤
በጎነቱም ዝናብ እንዳዘለ የበልግ ደመና
ነው።
16ከወርቅ ይልቅ ጥበብን ማግኘት፣
ከብርም ማስተዋልን መምረጥ ምንኛ
ይበልጣል!
17የቅኖች ጐዳና ከክፋት የራቀ ነው፤
መንገዱንም የሚጠብቅ ሕይወቱን
ይጠብቃል።
18ትዕቢት ጥፋትን፣
የእብሪት መንፈስም ውድቀትን ትቀድ
ማለች።
19በተዋረደ መንፈስ ከተጨቈኑት ጋር
መሆን፣
ከትዕቢተኞች ጋር ብዝበዛን ከመካፈል
ይሻላል።
20ምክርን የሚሰማ ይለመልማል፤
በእግዚአብሔርም የሚታመን ቡሩክ
ነው።
21ልባቸው ጠቢብ የሆነ አስተዋዮች
ይባላሉ፤
ደስ የሚያሰኙ ቃላትም ዕውቀትን
ያዳብራሉ።*
22ማስተዋልን ገንዘብ ላደረጋት የሕይወት
ምንጭ ናት፤
ቂልነት ግን በተላሎች ላይ ቅጣት
ታመጣባቸዋለች።

*33 ወይም ጥበብ እግዚአብሔርን መፍራት ታስተምራለች።
*21 ወይም ቃላትም ተደማጭነት ያስገኛሉ

[23]የጠቢብ ሰው ልብ አንደበቱን ይመራል፤
ከንፈሮቹም ዕውቀትን ያዳብራሉ።[θ]
[24]ደስ የሚያሰኝ ቃል የማር ወለላ ነው፤
ለነፍስ ጣፋጭ፣ ለዐጥንትም ፈውስ
ነው።
[25]ለሰው ቀና መስሎ የሚታይ መንገድ
አለ፤
በመጨረሻ ግን ወደ ሞት ይመራል፤
[26]ሠራተኛን የዕለት ጕርስ ፍላጎቱ ታታሪ
ያደርገዋል፤
ራቡም ይገፋፋዋል።
[27]ወራዳ ሰው ክፋትን ያውጠነጥናል፤
ንግግሩም እንደሚለበልብ እሳት ነው።
[28]ጠማማ ሰው ጠብን ይዘራል፤
ሐሜተኛም የቅርብ ወዳጆችን
ይለያያል።
[29]ክፉ ሰው ባልንጀራውን ያባብለዋል፤
መልካም ወዳልሆነውም መንገድ
ይመራዋል።
[30]በዐይኑ የሚጠቅስ ሰው ጠማማነትን
ያውጠነጥናል፤
በከንፈሩ የሚያሽሟጥጥም ወደ ክፋት
ያዘነብላል።
[31]ሽበት የክብር ዘውድ ነው፤
የሚገኘውም በጽድቅ ሕይወት ነው።
[32]ታጋሽ ሰው ከጦረኛ፣
ስሜቱን የሚገዛም ከተማን በጕልበቱ
ከሚይዝ ይበልጣል።
[33]ዕጣ በጕያ ውስጥ ይጣላል፤
ውሳኔው በሙሉ ግን *ከእግዚአብሔር*
ዘንድ ነው።

# 17

ጠብ እያለ ግብዣ[ፊ] ከሞላበት
ቤት ይልቅ፣
በሰላምና በጸጥታ የእንጀራ ድርቆሽ
ይሻላል።
[2]ጠቢብ አገልጋይ በወራዳ ልጅ ላይ
ሥልጣን ይኖረዋል፤
ከወንድማማቾቹም እንደ አንዱ ውርስ
ይካፈላል።
[3]ማቅለጫ ለብር፣ ከውር ለወርቅ ነው፤
*እግዚአብሔር* ግን ልብን ይመረምራል።
[4]እኩይ ሰው ክፉ ንግግር ያዳምጣል፤
ሐሰተኛም የተንኰለኛን አንደበት
በጥንቃቄ ይሰማል።
[5]በድኾች የሚያፌዝ ፈጣሪያቸውን
ይንቃል፤
በሌላው ሰው መከራ ደስ የሚለው
ከቅጣት አያመልጥም።

[6]የልጅ ልጆች ለአረጋውያን ዘውድ
ናቸው፤
ወላጆችም ለልጆቻቸው አለኝታ
ናቸው።
[7]መልካም አነጋገር[T] ለተላላ
አይሰምርለትም፤
ለገዥማ ሐሰተኛ አንደበት የቱን ያህል
የከፋ ይሆን!
[8]እጅ መንሻ ለሰጭው እንደ ድግምት ዕቃ
ነው፤
በሄደበትም ቦታ ሁሉ ይሳካለታል።
[9]በደልን የሚሸፍን ፍቅርን ያዳብራል፤
ነገርን የሚደጋግም ግን የልብ ወዳጆችን
ይለያያል።
[10]መቶ ግርፋት ተላላን ከሚሰማው
ይልቅ፣
ዘለፋ ለአስተዋይ ጠልቆ ይሰማል።
[11]ክፉ ሰው ዐመፅን ብቻ ይፈልጋል፤
በእርሱም ላይ ጨካኝ መልእክተኛ
ይላክበታል።
[12]ተላላን በቂልነቱ ከመገናኘት፣
ግልገሎቿን የተነጠቀችን ድብ መጋፈጥ
ይሻላል።
[13]በበጎ ፈንታ ክፉ የሚመልስ ሰው፣
ክፉ ነገር ከቤቱ አይርቅም።
[14]ጠብ መጫር ግድብን እንደ መሸንቈር
ነው፤
ስለዚህ ጠብ ከመጫሩ በፊት ነገርን
ራቅ።
[15]በደለኛውን ንጹሕ ማድረግ ሆነ፣
ንጹሑን በደለኛ ማድረግ፣
ሁለቱም *በእግዚአብሔር* ዘንድ አጸያፊ
ናቸው።
[16]ጥበብን ለማግኘት ፍላጎት ስለሌለው፣
ተላላ እጅ የገባ ገንዘብ ጥቅሙ ምንድን
ነው?
[17]ወዳጅ ምንጊዜም ወዳጅ ነው፤
ወንድምም ለክፉ ቀን ይወለዳል።
[18]ማስተዋል የጎደለው ሰው ቃል
በመግባት እጅ ይመታል፤
ለወዳጁም ዋስ ይሆናል።
[19]ጠብ የሚወድ ኀጢአትን ይወዳል፤
በሩን ከፍ አድርጎ የሚሠራም ጥፋትን
ይጋብዛል።
[20]ጠማማ ልብ ያለው ሰው አይሳካለትም፤
በአንደበቱ የሚቀላምድም መከራ ላይ

15፥5
**16፥24** 1ሳሙ14፥27፤ምሳ24፥13-14
**16፥25** አስ3፥6፤ምሳ12፥15፤14፥12
**16፥27** መዝ140፥2፤ያዕ3፥6
**16፥28** ምሳ14፥17፤17፥9
**16፥29** ምሳ1፥10፤12፥26
**16፥30** ምሳ6፥13
**16፥31** ምሳ20፥29
**16፥33** ዘሌ16፥18፤ኢሱ7፥14፤1ሳሙ10፥21፤14፥41፤ምሳ18፥18፤29፥26፤ሕዝ21፥21፤ዮና1፥7
**17፥1** ምሳ15፥16፡17፤16፥8
**17፥3** 1ዜና29፥17፤መዝ26፥2፤139፥23፤ምሳ27፥21፤1ጴጥ1፥7
**17፥5** ኢዮ5፥16፥ኢዮ5፥16፤31፥29፤ምሳ14፥31፤ሕዝ25፥3፤አብ1፥12
**17፥6** መዝ125፥5
**17፥7** ምሳ16፥10
**17፥8** ዘፀ23፥8፤ምሳ19፥6
**17፥9** ምሳ10፥12፤16፥28
**17፥12** 1ሳሙ25፥25
**17፥13** ዘፍ44፥4፤1ሳሙ19፥4፤መዝ35፥12
**17፥14** ማቴ5፥25-26
**17፥15** ዘፀ23፥6-7፤መዝ94፥21፤ምሳ18፥5፤ኢሳ5፥23፤ሰቆ3፥34-36
**17፥16** ምሳ23፥23
**17፥17** 2ሳሙ15፥21፤ምሳ27፥10
**17፥18** ምሳ6፥1-5፤11፥15፤22፥26-27

[θ]23 ወይም *አንደበቱን አሳማኝ ያደርጋሉ*
[ፊ]1 በዕብራይስጡ *መሥዋዕት*
[T]7 ወይም *የኵራት አነጋገር*

ይወድቃል።
21 ተላላ ልጅ መውለድ ሐዘን ያስከትላል፤
የተላላም አባት ደስታ የለውም።
22 ደስተኛ ልብ ጥሩ መድኀኒት ነው፤
የተሰበረ መንፈስ ግን ዐጥንትን
ያደርቃል።
23 ክፉ ሰው ፍትሕ ለማዛባት፣
በስውር ጕቦ ይቀበላል።
24 አስተዋይ ሰው ጥበብን ከፊቱ
አይለያትም፤
የተላሎች ዐይኖች ግን እስከ ምድር
ዳርቻ ይንከራተታሉ።
25 ተላላ ልጅ በአባቱ ላይ ሐዘን
ያስከትላል፤
ለወለደችውም ምሬት ይሆንባታል።
26 ንጹሑን ሰው መቅጣት ተገቢ
አይደለም፤
ሹሞችን ስለ ቅንነታቸው መግረፍ
መልካም አይደለም።
27 ዐዋቂ ሰው ንግግሩ ቊጥብ ነው፤
አስተዋይም መንፈሱ የረጋ ነው።
28 አላዋቂ እንኳ ዝም ቢል ጠቢብ፣
አንደበቱንም ቢገዛ አስተዋይ
ይመስላል።

# 18

ወዳጅነትን የማይፈልግ ሰው የራ
ሱን ፍላጎት ብቻ ይከተላል፤
ቅን የሆነውን ፍርድ ሁሉ ይቃወማል።
2 ተላላ ከማስተዋል ርካታን አያገኝም፤
የራሱን ሐሳብ በመግለጥ ግን ደስ
ይለዋል።
3 ክፋት ስትመጣ ንቀት ትከተላለች፤
ከዕፍረትም ጋር ውርደት ትመጣለች።
4 ከሰው አፍ የሚወጡ ቃላት ጥልቅ
ውሆች ናቸው፤
የጥበብም ምንጭ እንደሚንዶለዶል
ፏፏቴ ነው።
5 ለክፉ ሰው ማድላት፣
ንጹሑንም ፍትሕ መንሣት ተገቢ
አይደለም።
6 የተላላ ከንፈር ጠብ ያመጣበታል፤
አፉም በትር ይጋብዛል።
7 ተላላ ሰው አፉ መጥፊያው ነው፤
ከንፈሮቹም ለነፍሱ ወጥመድ ናቸው።
8 የሐሜተኛ ቃል እንደ ጣፋጭ ጕርሻ
ነው፤
ወደ ሰው ውስጣዊ ክፍል ዘልቆ
ይገባል።
9 ለሥራው ደንታ የሌለው ሰው፣
የአጥፊ ወንድም ነው።
10 *የእግዚአብሔር* ስም ጽኑ ግንብ ነው፤
ጻድቅ ወደ እርሱ በመሮጥ ተገን
ያገኝበታል።
11 የባለጠጎች ሀብት የተመሸገ ከተማቸው
ነው፤
እንደማይወጣ ረጅም ግንብም
ይቈጥሩታል።
12 ከውድቀቱ በፊት ሰው ልቡ ይታበያል፤
ትሕትና ግን ክብርን ትቀድማለች።
13 ከማዳመጡ አስቀድሞ የሚመልስ፣
ቂልነትና ዕፍረት ይሆንበታል።
14 በሕመም ጊዜ፣ ሰውን መንፈሱ
ትደግፈዋለች፤
የተሰበረውን መንፈስ ግን ማን ሊሸከም
ይችላል?
15 የአስተዋይ ልብ ዕውቀትን ይገበያል፤
የጠቢብም ጆሮ አጥብቆ ይሻታል።
16 እጅ መንሻ ለሰጪው መንገድ
ትከፍትለታለች፤
ታላላቅ ሰዎች ፊትም ታቀርበዋለች።
17 አስቀድሞ ጕዳዩን የሚያሰማ ትክክለኛ
ይመስላል፤
ይኸውም ባላንጣው መጥቶ
እስከሚመረመር ድረስ ነው።
18 ዕጣ መጣጣል ሙግትን ያስቆማል፤
ኀይለኛ ባላንጣዎችንም ይገላግላል።
19 የተበደለ ወንድም ከተመሸገ ከተማ
ይበልጥ የማይበገር ነው፤
ጠቡም እንደ ጠንካራ የግንብ መዝጊያ
ነው።
20 ሰው በአንደበቱ ፍሬ ሆዱ ይጠግባል፤
በከንፈሩም ምርት ይረካል።
21 አንደበት የሞትና የሕይወት ኀይል
አላት፤
የሚወዷትም ፍሬዋን ይበላሉ።
22 ሚስት የሚያገኝ መልካም ነገርን
ያገኛል፤
*ከእግዚአብሔርም* ዘንድ ሞገስን
ይቀበላል።
23 ድኻ በመለማመጥ ምሕረት ይለምናል፤
ሀብታም ግን በማናለብኝነት ይመልሳል።
24 ወዳጅ የሚያበዛ ሰው ራሱን ለጥፋት
ይዳርጋል፤
ነገር ግን ከወንድም አብልጦ የሚቀርብ
ጓደኛም አለ።

17፥21 ምሳ10፥1
17፥22 ዘፀ12፥46፤ መዝ38፥8፤ምሳ14፥30፤15፥13፤18፥14
17፥23 ዘፀ18፥21፤ 23፥8፤1ሳሙ8፥3፤ ኢዮ34፥33
17፥24 ኢዮ31፥1
17፥25 ምሳ10፥1
17፥26 መዝ94፥21
17፥27 ኢዮ6፥24፤ ምሳ14፥29
17፥28 ኢዮ2፥13፤ 13፥5፤ምሳ10፥19
18፥2 ምሳ12፥23
18፥4 መዝ18፥16
18፥5 መዝ82፥2፤ ምሳ17፥15፤24፥23-25፤28፥21
18፥6 ምሳ10፥14
18፥7 መዝ64፥8፤ 140፥9፤ምሳ10፥14፤12፥13፤13፥3፤መክ10፥12
18፥8 ምሳ26፥22
18፥9 ምሳ28፥24
18፥10 መዝ20፥1፤ 61፥3፤ምሳ14፥26
18፥11 ምሳ10፥15
18፥12 ምሳ11፥2፤ 15፥33፤16፥18
18፥13 ምሳ20፥25
18፥14 ምሳ15፥13፤ 17፥22
18፥15 ምሳ15፥14
18፥16 ዘፍ32፥13፤ 1ሳሙ10፥4፤ምሳ19፥6
18፥18 ምሳ16፥33
18፥19 1ሳሙ17፥28
18፥20 ምሳ12፥14
18፥21 መዝ12፥4፤ 13፥2-3፤ማቴ12፥37
18፥22 ኢዮ33፥26፤ ምሳ12፥4፤19፥14፤31፥10
18፥24 1ሳሙ20፥42፤ ዮሐ15፥13-15

19 ንግግሩ ጠማማ ከሆነ አጕል ሰው
ይልቅ፣
ያለ ነውር የሚሄድ ድኻ ሰው ይሻላል።
2ዕውቀት አልባ የሆነ ቀናዒነት መልካም
አይደለም፤
ጥድፊያም መንገድን ያስታል።
3ሰው በራሱ ተላላነት ሕይወቱን ያበላሻል፤
በልቡ ግን እግዚአብሔርን ያማርራል።
4ሀብት ብዙ ወዳጅ ታፈራለች፤
ድኻን ግን ወዳጁ ገሸሽ ያደርገዋል።
5ሐሰተኛ ምስክር ከቅጣት አያመልጥም፤
ውሸት የሚነዛም ሳይቀጣ አይቀርም።
6ብዙ ሰዎች በገዥ ዘንድ ሞገስ ለማግኘት
ያሸረግዳሉ፤
ስጦታን ከሚሰጥ ሰው ጋር ሁሉም
ወዳጅ ነው።
7ድኻ በሥጋ ዘመዶቹ ሁሉ የተጠላ ነው፤
ታዲያ ወዳጆቹማ የቱን ያህል ይሸሹት!
እየተከታተለ ቢለማመጣቸውም፣
ከቶ አያገኛቸውም።[ሀ]
8ጥበብን ገንዘቡ የሚያደርጋት ነፍሱን
ይወዳል፤
ማስተዋልን የሚወዳት ይሳካለታል።
9ሐሰተኛ ምስክር ከቅጣት አያመልጥም፤
ውሸት የሚነዛም ይጠፋል።
10ተላላ ተንደላቆ መኖር አይገባውም፤
ባሪያ የመሳፍንት ገዥ ከሆነማ የቱን
ያህል ይከፋ!
11ጥበብ ሰውን ታጋሽ ታደርገዋለች፤
በደልን ንቆ መተውም መከበሪያው
ነው።
12የንጉሥ ቍጣ እንደ አንበሳ ግሣት ነው፤
በፊቱ ሞገስ ማግኘትም በሣር ላይ
እንዳለ ጠል ነው።
13ተላላ ልጅ ለአባቱ መጥፊያ ነው፤
ጨቅጫቃ ሚስትም እንደማያቋርጥ
ጠፈጠፍ ናት።
14ቤትና ሀብት ከወላጆች ይወረሳሉ፤
አስተዋይ ሚስት ግን ከእግዚአብሔር
ዘንድ ናት።
15ስንፍና ከባድ እንቅልፍ ላይ ይጥላል፤
ዋልጌም ሰው ይራባል።
16ትእዛዛትን የሚያከብር ሕይወቱን
ይጠብቃል፤
መንገዱን የሚንቅ ግን ይሞታል።
17ለድኻ የሚራራ ለእግዚአብሔር
ያበድራል፤
ስላደረገውም ተግባር ዋጋ ይከፍለዋል።
18ገና ተስፋ ሳለ፣ ልጅህን ሥርዐት
አስይዘው፤
ሲሞት ዝም ብለህ አትየው።
19ግልፍተኛ ሰው ቅጣትን መቀበል
ይገባዋል፤
በምሕረት ካለፍከው ሌላም ጊዜ
አይቀርልህም።
20ምክርን ስማ፤ ተግሣጽን ተቀበል፤
በመጨረሻም ጠቢብ ትሆናለህ።
21በሰው ልብ ብዙ ሐሳብ አለ፤
የሚፈጸመው ግን የእግዚአብሔር ሐሳብ
ነው።
22ሰው የሚመኘው ጽኑ ፍቅር ነው፤
ውሸታም ከመሆንም ድኻ መሆን
ይሻላል።[ለ]
23እግዚአብሔርን መፍራት ወደ ሕይወት
ይመራል፤
እንዲህ ያለውም ሰው እፎይ ብሎ
ያርፋል፤ መከራም አያገኘውም።
24ሰነፍ እጁን ከወጭቱ ያጠልቃል፤
ወደ አፉ ግን መመለስ እንኳ ይሳነዋል።
25ፌዘኛን ግረፈው፤ ብስለት የሌለውም
ማስተዋልን ይማራል፤
አስተዋይን ገሥጸው፤ ዕውቀትን
ይገበያል።
26አባቱን የሚዘርፍ፣ እናቱንም
የሚያሳድድ፣
ዕፍረትና ውርደት የሚያመጣ ልጅ
ነው።
27ልጄ ሆይ፤ እስቲ፣ ምክርን ማዳመጥ
ተው፤
ከዕውቀትም ቃል ትስታለህ።
28ዐባይ ምስክር በፍትሕ ላይ ያፌዛል፤
የክፉዎችም አፍ በደልን ይሰለቅጣል።
29ለፌዘኞች ቅጣት፣
ለተላሎችም ጀርባ ጅራፍ
ተዘጋጅቶአል።

20 የወይን ጠጅ ፌዘኛ፣ ብርቱ
መጠጥም ጠበኛ ያደርጋል፤
በእነዚህ የሳተ ሁሉ ጠቢብ አይደለም።
2የንጉሥ ቍጣ እንደ አንበሳ ግሣት ነው፤
የሚያስቈጣውም ሰው ሕይወቱን
ለመከራ ይዳርጋል።
3ከጠብ መራቅ ለሰው ክብሩ ነው፤
ተላላ ሁሉ ግን ለጥል ይቸኵላል።
4ሰነፍ ሰው በወቅቱ አያርስም፤
ስለዚህ በመከር ወራት ይፈልጋል፤

19፥1 ምሳ28፥6
19፥2 ምሳ29፥20
19፥3 መዝ14፥1፤ ምሳ9፥13፤24፥9፤ኢሳ 32፥6፤ያዕ1፥13-15
19፥4 ቊ7፤ምሳ 14፥20
19፥5 ቊ9፤ዘፀ23፥1 ፤ዘዳ19፥19፤መዝ56፥7 ፤ምሳ21፥28
19፥6 ምሳ17፥8፤ 18፥16፤29፥26
19፥7 ቊ4፤ምሳ 10፥15
19፥8 ምሳ16፥20
19፥9 ቊ5፤ዘዳ 19፥19
19፥10 ምሳ26፥1፤ 30፥21-23፤መክ 10፥5-7
19፥11 2ነገ5፥12
19፥12 አስ1፥12፤ 7፥7፤መዝ72፥5-6፤ 133፥3፤ምሳ16፥14- 15፤20፥2
19፥13 አስ1፥18፤ ምሳ10፥1፤21፥9
19፥14 ምሳ18፥22፤ 2ቆሮ12፥14
19፥15 ምሳ10፥4፤ 20፥13
19፥16 ምሳ16፥17፤ ሮሜ10፥5
19፥17 ዘዳ24፥14፡ 19፤ምሳ14፥21፤22፥9፤ ማቴ10፥42
19፥18 ምሳ13፥24፤ 23፥13-14
19፥20 ምሳ4፥1፤ 12፥15
19፥21 መዝ33፥11 ፤ ምሳ16፥9፤20፥24 ፤ኢሳ8፥10፤14፥24 ፡27፤31፥2፤40፥8፤46፥1 0፤48፥14፤55፥11፤ ኤር44፥29፤ሰቆ3፥37
19፥23 ኢዮ4፥7፤ ምሳ10፥27
19፥24 ምሳ26፥15
19፥25 መዝ141፥5 ፤ምሳ9፥9፤21፥11
19፥26 ምሳ28፥24
19፥27 ምሳ1፥8
19፥28 ኢዮ15፥16
19፥29 ዘዳ25፥2
20፥1 ዘሌ10፥9፤ 1ሳሙ25፥36፤1ነገ 20፥16፤ምሳ31፥4፤ ዕን2፥5
20፥2 አስ7፥7፤ምሳ 16፥14፤19፥12
20፥3 ዘፍ13፥8፤ 1ሳሙ25፥25
20፥4 ምሳ6፥6፤ መክ10፥18

[ሀ]7 ለዚህ ዐረፍተ ነገር የገባው የዕብራይስጡ ትርጓሜ በትክ ክል አይታወቅም።
[ለ]22 ወይም *የሰው ስስት ውርደት/ ኀፍረት ያመጣበታል።*

አንዳችም አያገኝም።

[5]የሰው ልብ ሐሳብ እንደ ጥልቅ ውሃ
ነው፤
አስተዋይ ሰው ግን ከዚያ ቀድቶ
ያወጣዋል።
[6]ብዙ ሰው ጽኑ ፍቅር እንዳለው ይናገራል፤
ታማኝን ሰው ግን ማን ሊያገኘው
ይችላል?
[7]ጻድቅ ነቀፋ የሌለበት ሕይወት
ይመራል፤
ከእርሱም በኋላ የሚከተሉት ልጆቹ
ቡሩካን ናቸው።
[8]ንጉሥ ለፍርድ ዙፋኑ ላይ በሚቀመጥበት
ጊዜ፣
ክፉውን ሁሉ በዐይኖቹ አበጥሮ
ይለያል።

[9]ለመሆኑ፣ “ልቤን በንጽሕና ጠብቄአለሁ፤
ንጹሕ ነኝ፤ ኀጢአት የለብኝም” የሚል
ማን ነው?

[10]ሁለት ዐይነት ሚዛን፣ ሁለት ዐይነት
መስፈሪያ፣
ሁለቱንም እግዚአብሔር ይጸየፋቸዋል።

[11]ሕፃን እንኳ ጠባዩ ንጹሕና ቅን መሆኑ፣
ከአድራጎቱ ይታወቃል።

[12]የሚሰሙ ጆሮዎች፣ የሚያዩ ዐይኖች፣
ሁለቱንም እግዚአብሔር ሠርቷቸዋል።

[13]እንቅልፍ አትውደድ፤ አለዚያ ድኻ
ትሆናለህ፤
ዐይንህን ክፈት፤ የተትረፈረፈ ምግብ
ይኖርሃል።
[14]ዕቃ የሚገዛ፣ “የማይረባ ነው፤ የማይረባ
ነው” ብሎ ያራክሳል፤
ሲመለስ ግን በግዢው ይኵራራል።

[15]ወርቁም አለ፤ ቀዩም ዕንቍ
ተትረፍርፎአል፤
ዕውቀት የሚናገሩ ከንፈሮች ግን ብርቅ
ጌጦች ናቸው።
[16]ለማይታወቅ ሰው ዋስ የሆነውን ልብሱን
ግፈፈው፤
ለዘልዛላ ሴት የተዋሰውን በቃሉ ያዘው።

[17]ሰው በማጭበርበር ያገኘው ምግብ
ይጣፍጠዋል፤
በመጨረሻ ግን አፉን ኰረት ሞልቶት
ያገኘዋል።
[18]ምክር ጠይቀህ ዕቅድ አውጣ፤
ጦርነት የምትገጥም ከሆነ መመሪያ
ተቀበል።

[19]ሐሜተኛ ምስጢር ያባክናል፤
ስለዚህ ለፍላፊን ሰው አርቀው።

20፥5 መዝ18፥16
20፥6 መዝ12፥1
20፥7 መዝ26፥1፤37፥25-26፤112፥2
20፥8 ቍ26፤1ነገ 7፥7፤ምሳ25፥4-5
20፥9 1ነገ8፥46፤ ኢዮ15፥14፤መክ 7፥20፤1ዮሐ1፥8
20፥10 ቍ23፤ምሳ 11፥1
20፥11 መዝ39፥1
20፥12 መዝ94፥9
20፥13 ምሳ6፥11፤ 19፥15
20፥16 ዘፀ22፥26፤ ምሳ27፥13
20፥17 ኢዮ20፥14፤ ምሳ9፥17፤ሰቆ3፥16
20፥18 ምሳ11፥14፤ 24፥6
20፥19 ምሳ11፥13
20፥20 ዘፀ21፥17፤ ኢዮ18፥5፤ምሳ30፥11
20፥22 ምሳ24፥29፤ ኢሳ37፥20፤ኤር 1፥19፤42፥11፤ሮሜ 12፥19
20፥23 ቍ10፤ዘዳ 25፥13
20፥24 ኢዮ33፥29፤ መዝ 90፥12፤ምሳ 19፥21፤ኤር10፥23
20፥25 ምሳ10፥19፤ 18፥13፤መክ5፥2፡4-5 ፤ኤር44፥25
20፥26 ቍ8
20፥27 መዝ119፥ 105፤ምሳ16፥2
20፥28 መዝ40፥11 ፤ምሳ16፥12፤ኢሳ 16፥5
20፥29 ምሳ16፥31
20፥30 መዝ51፥2፤ ምሳ22፥15፤ኢሳ1፥5
21፥1 አስ5፥1፤ኤር 39፥11-12
21፥2 ምሳ16፥2
21፥3 1ሳሙ15፥22፤ ኢሳ1፥11፤ሚክ6፥6-8
21፥4 ኢዮ41፥34
21፥5 ምሳ10፥4

[20]አባቱን ወይም እናቱን የሚሰድብ፣
መብራቱ በድቅድቅ ጨለማ ይጠፋል።

[21]ከጅምሩ ወዲያው የተገኘ ርስት፣
በመጨረሻ በረከት አይኖረውም።

[22]“ለደረሰብኝ በደል ብድሬን ባልመልስ!”
አትበል፤
እግዚአብሔርን ጠብቅ፤ እርሱ
ይታደግሃል።
[23]ሁለት ዐይነት ሚዛን *በእግዚአብሔር*
ዘንድ አጸያፊ ነው፤
አባይ ሚዛን አይወደድም።

[24]የሰው አካሄዱ *በእግዚአብሔር* ይመራል፤
ሰውስ የገዛ መንገዱን እንዴት
ማስተዋል ይችላል?

[25]በችኰላ ስእለት መሳል፣
ከተሳሉም በኋላ ማቅማማት ለሰው
ወጥመድ ነው።

[26]ጠቢብ ንጉሥ ክፉዎችን አበጥሮ
ይለያል፤
የመውቂያ መንኰራኵርንም በላያቸው
ላይ ይነዳል።
[27]የሰው መንፈስ *ለእግዚአብሔር* መብራት
ነው፤[ሐ]
ውስጣዊ ማንነቱንም ይፈትሻል።

[28]ፍቅርና ታማኝነት ንጉሥን
ይጠብቁታል፤
በፍቅርም ዙፋኑ ይጸናል።

[29]የጎልማሶች ክብር ብርታታቸው፣
የሽማግሌዎችም ሞገስ ሽበታቸው ነው።

[30]የሚያቈስል በትር ክፋትን ያስወግዳል፤
ግርፋትም የውስጥ ሰውነትን ያጠራል።

21 የንጉሥ ልብ *በእግዚአብሔር* እጅ
ነው፤
እርሱም እንደ ቦይ ውሃ ደስ ወዳሰኘው
ይመራዋል።

[2]ለሰው መንገዱ ሁሉ ቀና ይመስለዋል፤
እግዚአብሔር ግን ልብን ይመዝናል።

[3]ከመሥዋዕት ይልቅ ጽድቅንና ፍትሕን
ማድረግ፣
*በእግዚአብሔር* ዘንድ ተቀባይነት
አለው።

[4]ትዕቢተኛ ዐይን፣ እብሪተኛ ልብ፣
የክፉዎችም መብራት ኀጢአት ናቸው።

[5]የትጕህ ሰው ዕቅድ ወደ ትርፍ
ያመራል፤
ችኰላም ወደ ድኽነት ያደርሳል።

[ሐ]27 ወይም *የእግዚአብሔር መብራት የሰውን መንፈስ ይመረምራል*

6 በሐሰተኛ አንደበት የተገኘ ሀብት፣
በኖ የሚጠፋ ተን፣ ለሞትም የሚያበቃ
ወጥመድ ነው።[መ]

7 ክፉዎችን ዐመፃቸው ይጠራርጋቸዋል፤
ቅን ነገር ማድረግ አይወዱምና።

8 የበደለኛ መንገድ ጠማማ ነው፤
የንጹሕ ሰው ጠባይ ግን ቀና ነው።
9 ከጨቅጫቃ ሚስት ጋር በአንድ ቤት
ከመኖር፣
በጣራ ላይ ጥግ ይዞ መኖር ይሻላል።
10 ክፉ ሰው ክፉትን አጥብቆ ይመኛል፤
ባልንጀራውም ከእርሱ ዘንድ ርኅራኄን
አያገኝም።

11 ፌዘኛ ሲቀጣ፣ አላዋቂ ጥበብን
ያተርፋል፤
ጠቢብ ሰው ቢማር ዕውቀትን ያገኛል።

12 ጻድቁ[ሠ] የክፉዎችን ቤት ልብ ብሎ
ይመለከታል፤
ክፉዎችንም ያጠፋቸዋል።

13 ሰው የድኾችን ጩኸት ላለመስማት
ጆሮውን ቢዘጋ፣
እርሱም ይጮሃል፤ መልስም አያገኝም።

14 በስውር የተደረገ ስጦታ ቍጣን
ያበርዳል፤
በጕያ የተሸሸገ እጅ መንሻም ታላቅ
ቍጣን ጸጥ ያደርጋል።
15 ፍትሕ ሲሰፍን ጻድቁን ደስ ያሰኘዋል፤
ክፉ አድራጊዎችን ግን ያሸብራል።

16 የማስተዋልን መንገድ የሚስት ሰው፣
በሙታን ጉባኤ ያርፋል።

17 ቅንጦትን የሚወድ ይደኸያል፤
የወይን ጠጅና ዘይት የሚወድም ባለጠጋ
አይሆንም።

18 ክፉ ሰው ለጻድቅ፣
ወስላታም ለቅን ሰው ወጆ ይሆናል።

19 ከጨቅጫቃና ከቍጡ ሚስት ጋር
ከመኖር፣
በምድር በዳ መኖር ይሻላል።

20 በጠቢብ ቤት ምርጥ ምግብና ዘይት
ተከማችቶ ይገኛል፤
ተላላ ሰው ግን ያለ የሌለውን
ያሚጥጣል።

21 ጽድቅንና ፍቅርን የሚከተል፤
ሕይወትን ብልጽግናንና[ረ] ክብርን
ያገኛል።

22 ጠቢብ የኀያላንን ከተማ ቅጥር ጥሶ
ይገባል፤
መታመኛ ምሽጋቸውንም ያፈርሳል።

23 አንደበቱንና ምላሱን የሚቈጣጠር፣
ራሱን ከመቅሠፍት ይጠብቃል።

24 ትዕቢተኛና ኵሩ ሰው፣ "ፌዘኛ"
ይባላል፤
በጠባዩም እብሪተኛ ነው።

25 ታካችን የሚገድለው ምኞቱ ነው፤
እጆቹ መሥራት አይፈልጉምና።

26 ክፉ ሰው ቀኑን ሙሉ ይመኛል፤
ጻድቅ ግን አንዳች ሳያስቀር ይሰጣል።

27 የክፉ ሰው መሥዋዕት አጸያፊ ነው፤
በክፉ ዐላማ ሲያቀርብማ የቱን ያህል
አስከፊ ይሆን!

28 ሐሰተኛ ምስክር ይጠፋል፤[ሰ]
እውነቱን የሚናገር ግን ጸንቶ ይኖራል።
29 ክፉ ሰው በአጕል ድፍረት ይቀርባል፤
ቅን ሰው ግን አደራረጉን ያስተውላል።

30 እግዚአብሔርን ለመቋቋም የሚያስችል፣
አንዳችም ጥበብ ማስተዋልና ዕቅድ
የለም።

31 ፈረስ ለጦርነት ቀን ይዘጋጃል፤
ድል ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።

22 መልካም ስም ከብዙ ብልጽግና
ይመረጣል፤
መከበርም ከብርና ከወርቅ ይበልጣል።

2 ባለጠጋና ድኻ የሚጋሩት ነገር፣
እግዚአብሔር የሁላቸውም ፈጣሪ
መሆኑ ነው።

3 አስተዋይ ሰው አደጋ ሲያይ መጠጊያ
ይሻል፤
ብስለት የጐደለው ግን በዚያው
ይቀጥላል፤ መከራም ያገኘዋል።

4 ትሕትናና እግዚአብሔርን መፍራት፣
ሀብትን፣ ክብርንና ሕይወትን
ያስገኛል።

5 በክፉዎች መንገድ ላይ እሾህና ወጥመድ
አለ፤
ነፍሱን የሚጠብቅ ግን ከእነዚህ
ይርቃል።

6 ልጅን የሚሄድበትን መንገድ
አስተምረው፤[ሸ]
በሚሸመግልበት ጊዜ ከዚያ ፈቀቅ
አይልም።

21፥6 ምሳ10፥2
21፥7 ምሳ11፥5
21፥8 ምሳ2፥15
21፥9 ቍ19፤ምሳ 19፥13፤25፥24
21፥11 ምሳ19፥25
21፥12 ምሳ14፥11
21፥13 ዘፀ11፥6፤ ኢዮ29፥12
21፥14 ዘፍ32፥20
21፥15 ምሳ10፥29
21፥16 ሕዝ18፥24
21፥17 ምሳ23፥20-21፡29-35
21፥18 ምሳ11፥8፤ ኢሳ43፥3
21፥19 ቍ9
21፥21 መዝ25፥13፤ ማቴ5፥6
21፥22 ምሳ8፥14
21፥23 መዝ34፥13 ፤ምሳ10፥19፤12፥13፤ 13፥13
21፥24 ኤር43፥2
21፥25 ምሳ13፥4
21፥26 ዘሌ25፥35፤ 2ሳሙ17፥27
21፥27 1ነገ14፥24 ፤ምሳ15፥8
21፥28 ምሳ19፥5፤ ኢሳ29፥21
21፥29 ምሳ14፥8
21፥30 2ዜና13፥12 ፤ኢዮ5፥13፤12፥13 ፤15፥25፤ኢሳ8፥10
21፥31 መዝ33፥12-19፤ኢሳ31፥1
22፥1 መክ7፥1
22፥2 ኢዮ31፥15፤ ምሳ29፥13፤ማቴ5፥45
22፥3 ምሳ14፥16፤ 27፥12
22፥4 ምሳ10፥27፤ 15፥33፤ዳን4፥36
22፥5 ምሳ15፥19
22፥6 ዘፍ14፥14፤ ዘዳ6፥7፤ኤፌ6፥4

[መ]6 አንዳንድ የዕብራይስጥ ጽሑፎች፣ የሰብዓ ሊቃናትና የቩልጌት ትርጕሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አያሌ የዕብራይስጥ ጽሑፎች ግን *ሞትን ለሚሹ በኖ እንደሚጠፉ ተን ነው* ይላሉ።
[ሠ]12 ወይም *ጻድቁ ሰው*
[ረ]21 ወይም *ጽድቅን*
[ሰ]28 ወይም *እርሱን የሚሰማውም ሁሉ ለዘላለም ይጠፋል*
[ሸ]6 ወይም *አስጀምረው*

7ባለጠጋ ድኻን ይገዛል፤
ተበዳሪም የአበዳሪ ባሪያ ነው።

8ክፋትን የሚዘራ መከራን ያጭዳል፤
የቍጣውም በትር ይጠፋል።
9ቸር ሰው ራሱ ይባረካል፤
ምግቡን ከድኾች ጋር ይካፈላልና።

10ፌዘኛን አስወጣው፤ ጠብ ይወገዳል፤
ጥልና ስድብም ያከትማል።

11የልብ ንጽሕናን ለሚወድና ንግግሩም
ሞገስ ላለው ሰው፣
ንጉሥ ወዳጁ ይሆናል።

12*የእግዚአብሔር* ዐይኖች ዕውቀትን
ይጠብቃሉ፤
የማይታመኑትን ሰዎች ቃል ግን እርሱ
ከንቱ ያደርጋል።
13ሰነፍ፣ “አንበሳ ውጪ አለ፤
መንገድ ላይ እገደላለሁ” ይላል።

14የአመንዝራ ሴት አፍ ጥልቅ ጕድጓድ
ነው፤
*እግዚአብሔር* የተቈጣውም ይገባበታል።

15ሞኝነት በሕፃን ልብ ታስሮአል፤
የተግሣጽ በትር ግን ከእርሱ
ያርቅለታል።

16ሀብቱን ለማካበት ድኻን የሚበድል፣
ለባለጠጋም ስጦታ የሚያቀርብ፣
ሁለቱም ይደኸያሉ።

## የጠቢባን ምክር

17የጠቢባንን ቃል ልብ ብለህ ስማ፤
ልብህም ወደ ትምህርቴ ያዘንብል፤
18በልብህ ስትጠብቃቸው፣
ሁሉም በከንፈሮችህ ላይ የተዘጋጁ
ሲሆኑ ደስ ይላልና።
19ስለዚህ እምነትህ *በእግዚአብሔር* ላይ
እንዲሆን፣
ዛሬ አንተን ራስህን አስተምርሃለሁ።
20የምክርና የዕውቀት ቃል የሆኑ፣
መልካም ትምህርቶችን[ቀ]
አልጻፍሁልህምን?
21ለላከህ ተገቢውን መልስ ትሰጥ ዘንድ፣
እውነተኛውና የታመኑ ቃሎችን
እንዳስተምርህ አይደለምን?
22ድኾች በመሆናቸው ብቻ ድኾችን
አትበዝብዛቸው፤
ችግረኛውንም በአደባባይ አታንገላታው፤
23*እግዚአብሔር* ይፋረድላቸዋልና፤
የሚቀሟቸውንም ይቀማቸዋል።

24ከግልፍተኛ ጋር ወዳጅ አትሁን፤
በቀላሉ ቱግ ከሚልም ሰው ጋር
አትወዳጅ፤

25አለበለዚያ መንገዱን ትማራለህ፤
ራስህም ትጠመድበታለህ።

26በዋስትና ቃል እጅ አትምታ፤
ለብድር ተያዥ አትሁን፤
27የምትከፍለው ካጣህ፣
የምትተኛበት ዐልጋ ከሥርህ
ይወሰድብሃል።
28የቀድሞ አባቶችህ ያስቀመጡትን፣
የጥንቱን የወሰን ምልክት አታፋልስ።
29በሙያው ሥልጡን የሆነውን ሰው
አይተሃልን?
በነገሥታት ዘንድ ባለሟል ይሆናል፤
አልባሌ ሰዎችን አያገለግልም።

23 ከገዥ ጋር ለመብላት
በምትቀመጥበት ጊዜ፣
በፊትህ ያለውን በሚገባ[በ] አስተውል፤
2ስግብግብም ብትሆን እንኳ፣
በጕሮሮህ ላይ ካራ አጋድምበት፤
3የእርሱ ጣፋጭ መብል አያስጐምጅህ፤
ምግቡ አታላይ ነውና።

4ሀብት ለማግኘት ስትል ራስህን አታድክም፤
ሐሳብህን የመግታት ጥበብ ይኑርህ።
5በሀብት ላይ ዐይንህን ብትጥል፤
ወዲያው ይጠፋል፤
ወደ ሰማይ እንደሚበርር ንስር፣
በእርግጥ ክንፍ አውጥቶ ይበራል፤

6የስስታምን ምግብ አትብላ፤
ጣፋጭ መብሉም አያስጐምጅህ፤
7ሁልጊዜ ስለ ዋጋ የሚያሰላ ሰው ነውና፤[ተ]
“ብላ፣ ጠጣ” ይልሃል፤
ልቡ ግን ከአንተ ጋር አይደለም።
8የበላሃት ትንሿ እንኳ ታስመልስሃለች፤
የምስጋና ቃልህንም ከንቱ ታደርጋለህ።

9ከጅል ጋር አትነጋገር፤
የቃልህን ጥበብ ያንኳስሳልና።

10የጥንቱን የወሰን ምልክት አታፋልስ፤
አባት የሌላቸውንም ልጆች መሬት
አትግፋ፤
11ታዳጊያቸው ብርቱ ነውና፤
እርሱ ይፋረድላቸዋል።

12ልብህን ለምክር፣
ጆሮህንም ለዕውቀት ቃል ስጥ።
13ልጅን ከመቅጣት ወደ ኋላ አትበል፤
በአርጩሜ ብትገርፈው አይሞትም።
14በአርጩሜ ቅጣው፤
ነፍሱንም ከሞት[ቸ] አድናት።

[ቀ]20 ወይም *አስቀድሜ አልጻፍሁልህምን?፣* ወይም *ሠላሳ ትምህርቶችን*
[በ]1 ወይም *ማን መሆኑን*
[ተ]7 ወይም *በልቡ እንዳሰበ እንዲሁ ነውና* ወይም *ግብዣ አዘጋጅቶ*
[ቸ]14 ዕብራይስጡ *ሲኦል* ይላል

22፥8 ዘፀ1፥20፤ኢዮ 4፥8፤ሆሴ8፥7፤ገላ6፥7-8
22፥9 ዘዳ14፥29፤ ምሳ11፥25፤19፥17፤28፥27
22፥10 ምሳ26፥20
22፥11 ምሳ16፥13፤ ማቴ5፥8
22፥13 ምሳ26፥13
22፥14 ምሳ5፥3-5፤ 23፥27፤መክ7፥26
22፥15 ምሳ13፥24፤ 20፥30
22፥17 ምሳ1፥6፥8፤ ምሳ2፥2፤30፥1፤31፥1
22፥21 መክ12፥10
22፥22 ዘፀ23፥6፤ ዘሌ25፥17፤ኢዮ5፥16
22፥23 አስ8፥1፤9፥1፤ኢዮ29፥16፤መዝ 140፥12፤ምሳ 23፥10-11
22፥25 1ቆሮ15፥33
22፥26 ምሳ6፥1-5
22፥27 ምሳ11፥15፤ 17፥18
22፥28 ዘዳ19፥14
22፥29 ዘፍ39፥4፤ 41፥46፤1ነገ11፥28
23፥1 ቈላ6-8፤መዝ 141፥4
23፥5 ምሳ27፥24፤ ማቴ6፥19
23፥6 ቈላ1-3፤ መዝ141፥4
23፥9 ምሳ9፥7
23፥10 ዘዳ19፥14
23፥12 ምሳ2፥2
23፥11 ዘፀ22፥22-24፤ኢዮ19፥25፤መዝ 24፥8፤ምሳ15፥25፤22፥22-23
23፥14 ምሳ13፥24፤19፥18

15ልጄ ሆይ፤ ልብህ ጠቢብ ቢሆን፣
የእኔም ልብ ሐሤት ያደርጋል፤
16ከንፈሮችህ ትክክሉን ቢናገሩ፣
ውስጣዊ ሁለንተናዬ ሐሤት ያደርጋል።

17ልብህ በኀጢአተኞች አይቅና፤
ነገር ግን ዘወትር እግዚአብሔርን
ለመፍራት ትጋ።
18ለነገ እርግጠኛ አለኝታ ይኖርሃል፤
ተስፋህም ከንቱ አይሆንም።

19ልጄ ሆይ አድምጥ፤ ጠቢብም ሁን፤
ልብህም ከትክክለኛው መንገድ
አይውጣ።
20ብዙ የወይን ጠጅ ከሚጠጡ፣
ሥጋ ከሚሰለቅጡ ጋር አትወዳጅ፤
21ሰካራሞችና ሆዳሞች ድኾች ይሆናሉና፤
እንቅልፋምነትም ቡትቶ ያለብሳቸዋል።

22የወለደህን አባትህን አድምጥ፤
እናትህንም ባረጀች ጊዜ አትናቃት።
23እውነትን ግዛት እንጂ አትሽጣት፤
ጥበብን፣ ተግሣጽንና ማስተዋልን
ገንዘብህ አድርግ።
24የጻድቅ ሰው አባት እጅግ ደስ ይለዋል፤
ጠቢብ ልጅ ያለውም በእርሱ ሐሤት
ያደርጋል።
25አባት እናትህ ደስ ይበላቸው፤
ወላጅ እናትህም ሐሤት ታድርግ።

26ልጄ ሆይ፤ ልብህን ስጠኝ፤
ዐይኖችህም ከመንገዴ አይውጡ፤
27ዘልዛላ ሚስት ጠባብ ጕድጓድ፣
አመንዝራም ሴት ዐዘቅት ናትና፤
28እንደ ወንበዴ ታደባለች፤
በሰዎችም መካከል ወስላቶችን
ታበዛለች።
29ዋይታ የማን ነው? ሐዘንስ የማን ነው?
ጠብ የማን ነው? ብሶትስ የማን ነው?
በከንቱ መቍሰል የማን ነው? የዐይን
ቅላትስ የማን ነው?
30የወይን ጠጅ በመጠጣት ጊዜያቸውን
ለሚያባክኑ ነው፤
እየዞሩ ድብልቅ የወይን ጠጅ
ለሚቀማምሱ ሰዎች ነው።
31መልኩ ቀይ ሆኖ፣
በብርጭቆ ውስጥ ሲያንጸባርቅ፣
ሰተት ብሎ በሚወርድበትም ጊዜ፣
ወደ ወይን ጠጅ ትክ ብለህ
አትመልከት።
32በመጨረሻው እንደ እባብ ይነድፋል፤
እንደ እፉኝትም መርዙን ይረጫል።
33ዐይኖችህ እንግዳ ነገር ያያሉ፤
አእምሮህም ይቀባዠራል።
34በባሕር ላይ የተኛህ፣
በመርከብ ምሰሶ ጫፍ ላይ የተጋደምህ
ትመስላለህ።
35አንተም፣ "መቱኝ፤ አልተጐዳሁም፤
ደበደቡኝ፤ አልተሰማኝም፤
ታዲያ፣ ሌላ መጠጥ እንዳገኝ፣
መቼ ነው የምነቃው?" ትላለህ።

24 በክፉ ሰዎች አትቅና፤
ጓደኝነታቸውም አይመርህ፤
2ልባቸው ዐመፅን ያውጠነጥናልና፤
ከንፈራቸውም ሸፍጥ ያወራል።

3ቤት በጥበብ ይሠራል፤
በማስተዋልም ይጸናል፤
4በዕውቀትም ውድና ውብ በሆነ ንብረት፣
ክፍሎቹ ይሞላሉ።
5ጠቢብ ሰው ታላቅ ኀይል አለው፤
ዕውቀት ያለውም ሰው ብርታትን
ይጨምራል፤
6ጦርነት ለመግጠም መልካም ምክር፣
ድል ለማድረግም ብዙ አማካሪዎች
ያስፈልጋሉ።

7ጥበብ ለተላላ በጣም ሩቅ ናት፤
በከተማዪቱ በር ሸንጎ ላይም መናገር
አይችልም።

8ክፋት የሚያውጠነጥን፣
‘ተንኰለኛ’ በመባል ይታወቃል።
9የተላላ ዕቅድ ኀጢአት ነው፤
ሰዎችም ፌዘኛን ይጸየፋሉ።

10በመከራ ጊዜ ፈራ ተባ ካልህ፣
ዐቅምህ ምንኛ ደካማ ነው!
11ወደ ሞት የሚነዱትን ታደጋቸው፤
እየተጐተቱ ለእርድ የሚሄዱትን
አድናቸው።
12አንተም፣ "ስለዚህ ነገር ምንም
አላውቅም" ብትል፣
ልብን የሚመረምር እርሱ
አያስተውልምን?
ሕይወትህን የሚጠብቃት እርሱ
አያውቅምን?
ለእያንዳንዱስ እንደ ሥራው መጠን
አይከፍለውምን?
13ልጄ ሆይ፤ መልካም ነውና ማር ብላ፤
የማር ወለላም ጣዕም ይጣፍጥሃል።
14ጥበብም ለነፍስህ እንደዚሁ ጣፋጭ
እንደ ሆነች ዕወቅ፤
ብታገኛት ለነገ አለኝታ ይኖርሃል፤
ተስፋህም ከንቱ አይሆንም።

15በጻድቅ ሰው ቤት ላይ እንደ ወንበዴ
አታድፍጥ፤
መኖሪያውንም በድንገት አታጥቃ፤
16ጻድቅ ሰባት ጊዜ እንኳ ቢወድቅ

23፥16 ቍ24፤ምሳ 27፥11፤29፥3
23፥17 መዝ37፥1፤ 73፥3
23፥18 መዝ9፥18፤ 37፥1-4፤ምሳ24፥14፡ 19-20
23፥19 ዘዳ4፥9፤ምሳ 28፥7
23፥20 ኢሳ5፥11፡ 22፤56፥12፤ዕን2፥15
23፥21 ምሳ21፥17
23፥22 ዘሌ19፥32
23፥23 ምሳ4፥7፤ 17፥16
23፥24 ቍ15-16
23፥25 ምሳ10፥1
23፥26 መዝ18፥21 ፤ምሳ5፥1-6
23፥27 ምሳ22፥14
23፥28 ምሳ7፥11-12
23፥30 ቍ20-21፤ ኢሳ5፥11
23፥35 ምሳ20፥1
24፥1 ምሳ3፥31-32 ፤23፥17-18
24፥2 መዝ2፥1፤10፥ 7፤ኢሳ32፥6፤55፥7-8 ፤59፥7፤65፥2፤66፥18፤ ሆሴ4፥1
24፥3 ምሳ14፥1
24፥4 ምሳ8፥21
24፥6 ምሳ11፥14፤ 20፥18፤ሉቃ14፥31
24፥10 ኢዮ4፥5
24፥11 መዝ82፥4
24፥12 1ሳሙ2፥3፤ ኢዮ34፥11፤መዝ54፥5 ፤62፥12፤139፥2፤ማቴ 16፥27፤ሮሜ2፥6
24፥14 መዝ119፥ 103፤ ምሳ16፥24፤ 23፥18
24፥16 ኢዮ5፥19፤ መዝ 34፥21

ይነሣልና፤
ክፉዎች ግን በጥፋት ይወድቃሉ።

17ጠላትህ ሲወድቅ ደስ አይበልህ፤
ሲሰናከልም ልብህ ሐሤት አያድርግ፤
18አለዚያ እግዚአብሔር ይህን አይቶ
ደስ አይለውም፤
ቍጣውንም ከእርሱ ይመልሳል።

19በጨካኞች ድርጊት አትጨነቅ፤
በክፉዎችም አትቅና፤
20ግፈኛ ተስፋ የለውምና፤
የክፉዎችም መብራት ድርግም ብላ
ትጠፋለች።

21ልጄ ሆይ፤ እግዚአብሔርንና ንጉሥን
ፍራ፤
ከዐመፀኞችም ጋር አትተባበር፤
22ሁለቱም የሚያመጡት መዓት፤
ምን እንደሚሆን ማን ያውቃል?

## ተጨማሪ የጠቢባን ምሳሌዎች

23እነዚህም ደግሞ የጠቢባን ምሳሌዎች
ናቸው፦

በዳኝነት አድልዎ ማድረግ ተገቢ
አይደለም፤
24በደለኛውን፣ "አንተ ንጹሕ ነህ"
የሚለውን፣
ሕዝቦች ይረግሙታል፤ መንግሥታትም
ያወግዙታል።
25በደለኛውን፣ "አንተ ጥፋተኛ ነህ"
የሚሉት ግን መልካም ነገር
ይገጥማቸዋል፤
የተትረፈረፈ በረከትም ይወርድላቸዋል።
26እውነተኛ መልስ መስጠት፣
ከንፈርን እንደ መሳም ነው።

27በደጅ ያለውን ሥራህን ፈጽም፤
ዕርሻህን አዘጋጅ፤
ከዚያም በኋላ ቤትህን ሥራ።
28በባልንጀራህ ላይ ያለ ምክንያት
አትመስክር፤
በከንፈርህም አትሸንግል።
29"በእኔ ላይ እንደሠራብኝ እሠራለታለሁ፤
ስለ አድራጎቱም የጁን እመልስለታለሁ"
አትበል።

30በሰነፍ ሰው ዕርሻ በኩል አለፍሁ፤
ማስተዋል የጐደለውን ሰው የወይን ቦታ
አልፌ ሄድሁ፤
31በያለበት እሾህ በቅሎበታል፤
መሬቱም ዐረም ለብሶአል፤
ቅጥሩም ፈራርሷል።
32ያየሁትን ነገር አወጣሁ አወረድሁ፤
ካስተዋልሁትም ትምህርት አገኘሁ፤
33"ጥቂት ሳንቀላፋ፣ ጥቂት ሳሸልብ፣

24፥17 2ሳሙ 3፥32፤አብ1፥12፤ሚክ7፥8
24፥18 ኢዮ31፥29
24፥19 መዝ37፥1
24፥20 ኢዮ18፥5፤ምሳ23፥17-18
24፥21 ሮሜ13፥1-5
24፥22 መዝ73፥19
24፥23 ዘፀ18፥16፤ዘሌ19፥15፤መዝ72፥2፤ምሳ1፥6፤28፥21፤31፥8-9፤ኤር22፥16
24፥24 ምሳ17፥15
24፥28 መዝ7፥4
24፥29 ምሳ20፥22፤ማቴ5፥38-41
24፥30 ምሳ6፥6-11፤26፥13-16
24፥33 ምሳ6፥10
24፥34 ምሳ10፥4፤መክ10፥18
25፥1 1ነገ4፥32፤ምሳ1፥1
25፥2 ምሳ16፥10-15
25፥5 2ሳሙ7፥13፤ምሳ16፥12፤20፥8፤29፥14
25፥7 ሉቃ14፥7-10
25፥8 ማቴ5፥25-26
25፥11 ቊ12፤ምሳ15፥23
25፥12 ቊ11፤መዝ141፥5፤13፥18
25፥13 ምሳ10፥26፤13፥17

እጄን አጣጥፌ ጥቂት ልረፍ" ብትል፣
34ድኽነት እንደ ወንበዴ፣
እጦትም እንደ ታጠቀ ሰው
ይመጣብሃል።ጎ

## የሰሎሞን ተጨማሪ ምሳሌዎች

25 እነዚህ የይሁዳ ንጉሥ የሕዝቅያስ
ሰዎች የቀዷቸው ሌሎች የሰሎ
ሞን ምሳሌዎች ናቸው፦

2ነገርን መሰወር ለእግዚአብሔር ክብሩ ነው፤
ነገርን ፈልፍሎ ማውጣት ግን
ለነገሥታት ክብራቸው ነው።

3ሰማያት ከፍ ያሉ እንደ ሆኑ፣ ምድርም
ጥልቅ እንደ ሆነች ሁሉ፣
የነገሥታትም ልብ እንደዚሁ
አይመረመርም።

4ከብር ዝገትን አስወግድ፤
አንጥረኛውም ንጹህ ነገርነ ያገኛል፤
5ክፉን ከንጉሥ ፊት አርቅ፤
ዙፋኑም በጽድቅ ትጸናለች።
6በንጉሥ ፊት ራስህን ከፍ ከፍ
አታድርግ፤
በታላላቆች መካከል መገኘትም
አይመርህ፤
7በትልቅ ሰው ፊት ከሚያዋርድህ፣
ራሱ፣ "ወደዚህ ከፍ በል" ቢልህ
ይሻላልና።

በዐይንህ ያየኸውን ሁሉ፣
8ወደ ፍርድ አደባባይ በችኰላ አታውጣው፤ኘ
ባልንጀራህ ካሳፈረህ፣
ኋላ ምን ይውጥሃል?

9ስለ ራስህ ጕዳይ ከባልንጀራህ ጋር
በምትከራከርበት ጊዜ፣
የሌላውን ሰው ምስጢር አታውጣ፤
10ያለዚያ ይህን የሚሰማ ያሳፍርሃል፤
አንዴ የጠፋውን ስምህንም ፈጽሞ
መመለስ አትችልም።

11ባግባቡ የተነገረ ቃል፣
በብር መደብ ላይ እንደ ተቀረጸ
የወርቅ እንኮይ ነው።
12የጠቢብ ሰው ዘለፋ ለሚሰማ ጆሮ፣
እንደ ወርቅ ጕትቻ ወይም እንደ ጥሩ
የወርቅ ጌጥ ነው።

13በመከር ጊዜ የበረዶ ቅዝቃዜ ለሰስ
እንደሚያደርግ ሁሉ፣
ታማኝ መልእክተኛም ለላኩት እንደዚሁ
ነው፤

ጎ34 ወይም *እንደ ቦዘኔ/ እጦትም እንደ ለማኝ*
ነ4 ወይም *ጽዋ*
ኘ7፥8 ወይም *ዐይንህን የጣልህበት ሰው፣* 8… *አትውጣ*

የጌቶቹን መንፈስ ያሳርፋልና።
14የማይለግሰውን ስጦታ እቸራለሁ ብሎ
ጕራ የሚነዛ ሰው፣
ዝናብ እንደ ሌለው ደመናና ነፋስ ነው።
15በትዕግሥት ገዥን ማግባባት ይቻላል፤
ለስላሳ አንደበትም ዐጥንት ይሰብራል።
16ማር ስታገኝ በልክ ብላ፤
ከበዛ ያስመልስሃል።
17ወደ ባልንጀራህ ቤት እግር አታብዛ፤
ታሰለቸውና ይጠላሃል።
18በባልንጀራው ላይ በሐሰት የሚመሰክር፣
እንደ ቈመጥ፣ እንደ ሰይፍና እንደ
ተሳለ ፍላጻ ነው።
19በመከራ ጊዜ በወስላታ ሰው
መተማመን፣
በተበላሸ ጥርስና በሰለለ እግር እንደ
መታመን ነው።
20ላዘነ ልብ የሚዘምር፣
በብርድ ቀን ልብሱን እንደሚያወልቅ፣
ወይም በሶዳ ላይ እንደ ተጨመረ
ሆምጣጤ ነው።
21ጠላትህ ቢራብ አብላው፤
ቢጠማም ውሃ አጠጣው።
22ይህን በማድረግህም፣ በራሱ ላይ ፍም
ትከምራለህ፤
እግዚአብሔርም ዋጋህን ይከፍልሃል።
23የሰሜን ነፋስ ዝናብ እንደሚያመጣ
ሁሉ፣
ሐሜተኛ ምላስም ቍጡ ፊት
ታስከትላለች።
24ከጨቅጫቃ ሚስት ጋር በአንድ ቤት
ከመኖር፣
በጣራ ማዕዘን ላይ መኖር ይሻላል።
25ከሩቅ የሚመጣ መልካም ዜና፣
የተጠማችን ነፍስ እንደሚያረካ ቀዝቃዛ
ውሃ ነው።
26ለክፉ ሰው የሚንበረከክ ጻድቅ፣
እንደ ደፈረሰ ምንጭ ወይም እንደ
ተበከለ የጕድጓድ ውሃ ነው።
27ከመጠን በላይ ማር መብላት ጥሩ
አይደለም፤
የራስንም ክብር መሻት አያስከብርም።
28ራሱን የማይቈጣጠር ሰው፣
ቅጥሯ እንደ ፈረሰ ከተማ ነው።

26 በረዶ በበጋ፣ ዝናብ በመከር
እንደማያስፈልግ ሁሉ፣
ክብርም ለተላላ አይገባውም።

25፥15 ምሳ15፥1፤ መክ10፥4
25፥16 ቍ27
25፥18 ምሳ12፥18
25፥22 2ዜና28፥15፤መዝ18፥8፤ማቴ5፥44፤ሮሜ12፥20
25፥24 ምሳ21፥9
25፥25 ምሳ15፥30
25፥27 ቍ16፤ምሳ27፥2፤ማቴ23፥12
26፥1 ቍ8፤1ሳሙ12፥17፤ምሳ19፥10
26፥2 ዘዳ23፥5
26፥3 መዝ32፥9፤ ምሳ10፥13
26፥4 ቍ5፤ኢሳ36፥21
26፥5 ቍ4፤ምሳ3፥7
26፥6 ምሳ10፥26
26፥7 ቍ9
26፥8 ቍ1
26፥9 ቍ7
26፥11 መዝ85፥8፤ 2ጴጥ2፥22
26፥12 ምሳ3፥7፤ 29፥20
26፥13 ምሳ6፥6-11፤22፥13፤24፥30-34
26፥14 ምሳ6፥9
26፥15 ምሳ19፥24

2ከንፎቿን እንደምታርገበግብ ድንቢጥ
ወይም ቱር እንደምትል ጨረባ፣
ከንቱ ርግማንም በማንም ላይ
አይደርስም።
3ለፈረስ አለንጋ፣ ለአህያ መሸበቢያ፣
ለተላላ ጀርባም በትር ይገባዋል።
4ቂልን እንደ ቂልነቱ አትመልስለት፤
አለዚያ አንተም ራስህ እንደ እርሱ
ትሆናለህ።
5ቂልን እንደ ቂልነቱ መልስለት፤
አለዚያ ጠቢብ የሆነ ይመስለዋል።
6በተላላ እጅ መልእክትን መላክ፣
የገዛ እግርን እንደ መቍረጥ ወይም
ዐመፃን እንደ መጋት ነው።
7በቂል አንደበት የሚነገር ምሳሌ፣
ሰላላ የሽባ ሰው እግር ነው።
8ለተላላ ክብር መስጠት፣
በወንጭፍ ላይ ድንጋይ እንደ ማሰር
ነው።
9በአላዋቂ አንደበት የሚነገር ምሳሌ፣
በሰካራም እጅ እንዳለ እሾኽ ነው።
10ቂልን ወይም የትኛውንም ዐላፊ
አግዳሚ የሚቀጥር፣
ፍላጻውን በነሲብ እየወረወረ ወገኖቹን
እንደሚያቈስል ቀስተኛ ነው።
11ውሻ ወደ ትፋቱ እንደሚመለስ ሁሉ፣
ተላላም ቂልነቱን ይደጋግማል።
12ራሱን እንደ ጠቢብ የሚቈጥረውን ሰው
አይተሃልን?
ከእርሱ ይልቅ ለተላላ ተስፋ አለው።
13ሰነፍ፣ “በመንገድ ላይ አንበሳ አለ፤
አስፈሪ አንበሳ በአውራ ጐዳና ላይ
ይጐማለላል” ይላል።
14መዝጊያ በማጠፊያው ላይ እንደሚዞር፣
ሰነፍም በዐልጋው ላይ ይገላበጣል።
15ሰነፍ እጁን ወጭት ውስጥ ያጠልቃል፤
ወደ አፉ ለመመለስ ግን እጅግ
ይታክታል።
16በማስተዋል መልስ ከሚሰጡ ከሰባት
ሰዎች ይልቅ፣
ሰነፍ ራሱን ጠቢብ አድርጎ ይቈጥራል።
17በሌሎች ጠብ ጥልቅ የሚል መንገደኛ፣
የውሻ ጆሮ እንደሚይዝ ሰው ነው።
18ትንታግ ወይም የሚገድል ፍላጻ
እንደሚወረውር ዕብድ፣
19“ቀልዴን እኮ ነው” እያለ
ባልንጀራውን የሚያታልል ሰውም

እንደዚሁ ነው።

20ዕንጨት ከሌለ እሳት ይጠፋል፤
አሾክሻኪ ከሌለም ጠብ ይበርዳል።
21ከሰል ፍምን፣ ዕንጨትም እሳትን
እንደሚያቀጣጥል፣
አዋኪ ሰውም ጠብን ያባብሳል።
22የሐሜተኛ ቃል እንደ ጣፋጭ ጕርሻ
ነው፤
ወደ ሰው ውስጠኛው ክፍል ዘልቆ
ይገባል።
23ክፋትን በልብ ቋጥሮ ለስላሳ ቃል
የሚናገር ከንፈር፣
በብር ፈሳሽ[ኣ] እንደ ተለበጠ የሸክላ ዕቃ
ነው።
24ተንኰለኛ በከንፈሩ ይሸነግላል፤
በልቡ ግን ክፋትን ይቋጥራል።
25ንግግሩ ማራኪ ቢሆንም አትመነው፤
ሰባት ርኵሰት ልቡንሞልቶታልና።
26ተንኰሉ በሽንገላው ይሸፈን ይሆናል፤
ነገር ግን ክፋቱ በጉባኤ ይገለጣል።
27ጕድጓድ የሚምስ ራሱ ይገባበታል፤
ድንጋይ የሚያንከባልልም ተመልሶ
በላዩ ላይ ይገለበጥበታል።
28ሐሰተኛ ምላስ የጐዳቻቸውን ትጠላለች፤
ሸንጋይ አንደበትም ጥፋትን
ታመጣለች።

27 ነገ በሚሆነው አትመካ፤
ቀን የሚያመጣውን
አታውቅምና።
2ሌላው ያመስግንህ እንጂ የገዛ አፍህ
አይደለም፤
ሌላ ሰው ያወድስህ እንጂ የገዛ ከንፈርህ
አይሁን።
3ድንጋይ ይከብዳል፤ አሸዋም ሸክም ነው፤
የተላላ ሰው ጕነጣ ግን ከሁለቱም
ይከብዳል።
4ንዴት ጨካኝ፣ ቍጣም ጎርፍ ነው፤
በቅናት ፊት ግን ማን መቆም ይችላል?
5 የተገለጠ ዘለፋ፣
ከተደበቀ ፍቅር ይሻላል።
6ከጠላት ደጋግሞ መሳም ይልቅ፣
የወዳጅ ማቍሰል ይታመናል።
7ለጠገበ ማር አይጥመውም፤
ለተራበ ግን እሬት እንኳ ይጣፍጠዋል።
8ከቤቱ ወጥቶ የሚባዝን ሰው፣
ጎጆዋን ለቃ እንደ ምትባዝን ወፍ
ነው።
9ሽቱና ዕጣን ልብን ደስ ያሰኛሉ፤
የወዳጅ ማስደሰትም ከቅን ምክሩ
ይመነጫል።
10የራስህንም ሆነ የአባትህን ወዳጅ
አትተው፤
መከራ በሚያጋጥምህ ጊዜ ወደ
ወንድምህ ቤት አትሂድ፤
ሩቅ ካለ ወንድም ቅርብ ያለ ጎረቤት
ይሻላል።
11ልጄ ሆይ፤ ጠቢብ ሁን፤ ልቤን ደስ
አሰኘው፤
ለሚንቁኝ ሁሉ መልስ መስጠት እችል
ዘንድ።
12ጥንቁቅ አደጋን አይቶ ይሸሸጋል፤
ማስተዋል የጐደለው ግን ወደዚያው
ይሄዳል፤ ይጐዳልም።
13ለማይታወቅ ሰው የተዋሰን ልብሱን
ግፈፈው፤
ለዘልዛላ ሴት ከተዋሰማ አግተው።
14ሰው ድምፁን ከፍ አድርጎ ባልንጀራውን
በማለዳ ቢመርቅ፣
እንደ ርግማን ይቈጠራል።
15ጨቅጫቃ ሚስት፣
በዝናብ ቀን እንደሚወርድ የማያቋርጥ
ጠፈጠፍ ናት፤
16እርሷን ለመግታት መሞከር፣
ነፋስን እንደ መግታት ወይም ዘይትን
በእጅ እንደ መጨበጥ ነው።
17ብረት ብረትን እንደሚስል፣
ሰውም ሌላውን ሰው እንደዚሁ
ይስለዋል።
18በለስን የሚንከባከብ ፍሬዋን ይበላል፤
ጌታውን የሚያገለግልም ክብርን
ይጐናጸፋል።
19ውሃ ፊትን እንደሚያሳይ፣
የሰውም ልብ ማንነቱን ገልጦ ያሳያል።
20ሲኦልና የሙታን ዓለም[ከ] እንደማይጠግቡ
ሁሉ፣
የሰውም ዐይን አይረካም።
21ብር በማቅለጫ፣ ወርቅ በከውር
እንደሚፈተን፣
ሰውም በሚቀበለው ምስጋና ይፈተናል።
22ጅልን በሙቀጫ ብትወቅጠው፣
እንደ እህልም በዘነዘና ብታደቀው፣
ጅልነቱን ልታስወግድለት አትችልም።
23በጎችህ በምን ሁኔታ እንዳሉ ደህና
አድርገህ ዕወቅ፤

[ኣ]23 ወይም *በሚያብለጨልጭ ነገር*
[ከ]20 ወይም *ሞትና ጥፋት*

26፥20 ምሳ22፥10
26፥21 ምሳ14፥17
26፥22 ምሳ18፥18
26፥24 መዝ31፥18፤41፥6
26፥25 መዝ28፥3፤ኤር9፥4
26፥27 አስ2፥23፤6፥13፤7፥9፤መዝ7፥15፤35፥8፤141፥10፤ምሳ28፥10፤29፥6፤ኢሳ50፥11
26፥28 መዝ12፥3፤ምሳ29፥5
27፥1 1ነገ20፥11፤ማቴ6፥34፤ያዕ4፥13-16
27፥2 ምሳ25፥27
27፥3 ኢዮ 6፥3
27፥4 ዘኍ 5፥14
27፥6 መዝ141፥5፤ምሳ28፥23
27፥8 ኢሳ16፥2
27፥9 አስ2፥12፤መዝ45፥8
27፥10 ምሳ17፥17
27፥11 ዘፍ24፥60፤ምሳ10፥1፤23፥15-16
27፥12 ምሳ 22፥3
27፥13 ምሳ20፥16
27፥15 አስ 1፥18
27፥18 ሉቃ19፥12-27፤1ቆሮ9፥7
27፥20 ምሳ30፥15-16፤መክ1፥8፤6፥7፤ዕን 2፥5
27፥21 ምሳ17፥3
27፥23 ምሳ12፥10

*መንጋህንም* ተንከባከብ፤
24 ሀብት ለዘላለም አይኖርምና፤
ዘውድም ከትውልድ ወደ ትውልድ
ጸንቶ አይኖርም።
25 ደረቁ ሣር ተወግዶ፣ አዲሱ ብቅ ሲል፣
በየኰረብታው ላይ ያለው ሣር
ተሰብስቦ ሲገባ፣
26 ከበግ ጠቦቶች ልብስ ታገኛለህ፤
ፍየሎችም የዕርሻ መሬት መግዣ
ይሆኑሃል።
27 አንተንና ቤተ ሰብህን፣
ገረዶችህንም ጭምር ለመመገብ፣
የተትረፈረፈ የፍየል ወተት ይኖርሃል።

28 ክፉ ሰው ማንም ሳያሳድደው
ይሸሻል፤
ጻድቅ ግን እንደ አንበሳ ልበ ሙሉ
ነው።

2 አገር ስታምፅ፣ ገዦቿ ይበዛሉ፤
አስተዋይና ዐዋቂ ሰው ግን ሥርዐትን
ያሰፍናል።

3 ድኾችን የሚያስጨንቅ ሰው፣[ኸ]
ሰብል እንደሚያጠፋ ኀይለኛ ዝናብ
ነው።

4 ሕግን የሚተዉ ክፉዎችን ያወድሳሉ፤
ሕግን የሚጠብቁ ግን ይቋቋሟቸዋል።

5 ክፉዎች ፍትሕን አያስተውሉም፤
*እግዚአብሔርን* የሚሹ ግን ሙሉ
በሙሉ ያውቁታል።

6 በአካሄዱ ነውር የሌለበት ድኻ፣
*መንገዱ* ጠማማ ከሆነ ባለጠጋ ይሻላል።

7 ሕግን የሚጠብቅ አስተዋይ ልጅ ነው፤
ከሆዳሞች ጋር ጓደኛ የሚሆን ግን
አባቱን ያዋርዳል።

8 በከፍተኛ ወለድ ሀብቱን የሚያካብት፣
ለድኻ ለሚራራ፣ ለሌላው ሰው
ያከማችለታል።

9 ሕግን ላለመስማት ጆሮውን የሚደፍን፣
ጸሎቱ እንኳ አስጸያፊ ነው።

10 ቅኖችን በክፉ *መንገድ* የሚመራ፣
በቈፈረው ጕድጓድ ይገባል፤
ንጹሓን ግን መልካም ነገርን ይወርሳሉ።
11 ባለጠጋ ራሱን ጠቢብ አድርጎ ይቈጥር
ይሆናል፤
አስተዋይ የሆነ ድኻ ግን መርምሮ
ያውቀዋል።

12 ጻድቃን ድል ሲነሡ ታላቅ ደስታ
ይሆናል፤
ክፉዎች ሥልጣን ሲይዙ ግን ሕዝብ
ይሸሸጋል።

13 ኀጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤
የሚናዘዝና የሚተወው ግን ምሕረትን
ያገኛል።

14 *እግዚአብሔርን* ዘወትር የሚፈራ ሰው
ቡሩክ ነው፤
ልቡን የሚያደነድን ግን መከራ ላይ
ይወድቃል።
15 ታዳጊ በሌለው ሕዝብ ላይ የተሾመ
ጨካኝ ገዥ፣
እንደሚያገሣ አንበሳ ወይም ተንደንድሮ
እንደሚይዝ ድብ ነው።

16 ጨካኝ ገዥ ማመዛዘን ይጎድለዋል፤
ያላግባብ የሚገኝን ጥቅም የሚጸየፍ
ግን ዕድሜው ይረዝማል።

17 የሰው ደም ያለበት ሰው፣
ዕድሜ ልኩን ሲቅበዘበዝ ይኖራል፤
ማንም ሰው አይርዳው።

18 አካሄዱ ነቀፋ የሌለበት ሰው ክፉ
አያገኘውም፤
*መንገዱ* ጠማማ የሆነ ግን ድንገት
ይወድቃል።
19 *መሬቱን* የሚያርስ የተትረፈረፈ ምግብ
ያገኛል፤
ከንቱ ተስፋን ይዞ የሚጓዝ ግን
ድኽነትን ይወርሳል።

20 ታማኝ ሰው እጅግ ይባረካል፤
ሀብት ለማግኘት የሚጣደፍ ግን ከቅጣት
አያመልጥም።

21 አድልዎ ማድረግ መልካም አይደለም፤
ሰው ግን ለቍራሽ እንጀራ ሲል በደል
ይፈጽማል።

22 ስስታም፣ ሀብት ለማከማቸት
ይስገበገባል፤
ድኽነት እንደሚጠብቀውም አያውቅም።
23 ሸንጋይ አንደበት ካለው ይልቅ፣
ሰውን የሚገሥጽ ውሎ ዐድሮ
ይወደዳል።

24 ከአባት ከእናቱ ሰርቆ፣
"ይህ ጥፋት አይደለም" የሚል
የአጥፊ ተባባሪ ነው።

25 ስስታም ሰው ጠብን ያነሣሣል፤
*በእግዚአብሔር* የሚታመን ግን
ይባረካል።

26 በራሱ የሚታመን ተላላ ነው፤
በጥበብ የሚመላለስ ግን ክፉ
አያገኘውም።

27 ለድኾች የሚሰጥ አይቸገርም፤

27፥24 ምሳ23፥5
28፥1 ዘሌ 26፥17፤ 2ነገ7፥7፤መዝ138፥3
28፥6 ምሳ 19፥1
28፥7 ምሳ 23፥19-21
28፥8 ዘፀ18፥21፤ ኢዮ3፥15፤27፥17፤ መዝ112፥9፤ሉቃ14፥12-14፤ሉቃ14፥12-14
28፥9 መዝ109፥7፤ ምሳ15፥8፤ኢሳ1፥13
28፥10 መዝ57፥6፤ ምሳ26፥27
28፥12 ቍ28፤2ነገ 11፥20፤ኢዮ24፥4፤ ምሳ29፥2
28፥13 ዘሌ5፥5፤ 2ሳሙ12፥13፤ኢዮ 31፥33፤መዝ32፥1-5 ፤ዳን4፥27፤1ዮሐ1፥9
28፥17 1ሳሙ30፥17 ፤ 1ነገ20፥20፤ኤር 41፥15፤44፥14
28፥18 አስ6፥13፤ ምሳ10፥9፤ኤር39፥18
28፥19 ምሳ12፥11
28፥20 ቍ22
28፥21 ዘሌ19፥15፤ መዝ94፥21፤ምሳ18፥5 ፤ሕዝ13፥19
28፥22 ቍ20
28፥23 ምሳ27፥5-6
28፥24 ምሳ18፥9፤ 19፥26
28፥25 ምሳ14፥17 ፤29፥25
28፥26 መዝ4፥5፤ 1ቆሮ3፥18
28፥27 ዘዳ24፥19፤ መዝ109፥17፤ምሳ22፥9

[ኸ]3 ወይም *ድኻ*

አይቶአቸው እንዳላየ የሚሆን ግን ብዙ
ርግማን ይደርስበታል።
28ክፉዎች ሥልጣን በሚይዙ ጊዜ ሕዝብ
ይሸሸጋል፤
ክፉዎች በሚጠፉበት ጊዜ ግን ጻድቃን
ይበዛሉ።

29 ከብዙ ተግሣጽ በኋላ ዐንገቱን
የሚያደነድን ሰው፣
በድንገት ይጠፋል፤ መዳኛም የለውም።
2ጻድቃን ሥልጣን ሲይዙ ሕዝብ ሐሤት
ያደርጋል፤
ክፉዎች ሲገዙ ግን ሕዝብ ያቃስታል።
3ጥበብን የሚወድ ሰው አባቱን ደስ
ያሰኛል፤
የአመንዝራዎች ወዳጅ ግን ሀብቱን
ያባክናል።
4ፍትሕን በማስፈን ንጉሥ አገርን
ያረጋጋል፤
ጉቦ ለማግኘት የሚጎመጅ ግን
ያፈራርሳታል።
5ባልንጀራውን የሚሸነግል፣
ለገዛ እግሩ መረብ ይዘረጋል።
6ክፉ ሰው በራሱ ኀጢአት ይጠመዳል፤
ጻድቅ ግን ይዘምራል፤ ደስም ይለዋል።
7ጻድቅ ለድኾች ፍትሕ ይጨነቃል፤
ክፉ ሰው ግን ደንታ የለውም።
8ተሳዳቢዎች ከተማን ያውካሉ፤
ጠቢባን ግን ቍጣን ያበርዳሉ።
9ጠቢብ ሰው ከተላላ ጋር ወደ ሸንጎ
ቢሄድ፣
ተላላ ይቈጣል፤ ያፌዛል፤ ሰላምም
አይኖርም።
10ደም የተጠሙ ሰዎች ሐቀኛን ሰው
ይጠላሉ፤
ቅን የሆነውንም ለመግደል ይሻሉ።
11ተላላ ሰው ቍጣውን ያለ ገደብ
ይለቀዋል፤
ጠቢብ ሰው ግን ራሱን ይቈጣጠራል።
12ገዥ የሐሰት ወሬ የሚሰማ ከሆነ፣
ሹማምንቱ ሁሉ ክፉዎች ይሆናሉ።
13ድኻውና ጨቋኙ የጋራ ነገር አላቸው፤
*እግዚአብሔር* ለሁለቱም የዐይን
ብርሃንን ሰጥቶአቸዋል።
14 ንጉሥ ለድኻ ትክክለኛ ፍርድ ቢሰጥ፣
ዙፋኑ ዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
15የተግሣጽ በትር ጥበብን ታጐናጽፋለች፤
መረን የተለቀቀ ልጅ ግን እናቱን
ያሳፍራል።
16ክፉዎች ሥልጣን ሲይዙ ኀጢአት
ይበዛል፤
ጻድቃን ግን የእነርሱን ውድቀት
ያያሉ።
17ልጅህን ቅጣው፤ ሰላም ይሰጥሃል፤
ነፍስህንም ደስ ያሰኛታል።
18ራእይ በሌለበት ሕዝብ መረን ይሆናል፤
ሕግን የሚጠብቅ ግን የተባረከ ነው።
19አገልጋይ በቃል ብቻ ሊታረም
አይችልም፤
ቢያስተውለውም እንኳ በጀ አይልም።
20በችኰላ የሚናገርን ሰው ታያለህን?
ከእርሱ ይልቅ ተላላ ተስፋ አለው።
21ሰው አገልጋዩን ከልጅነቱ ጀምሮ
ቢያቀማጥል፣
የኋላ ኋላ ሐዘን[ሠ] ያገኘዋል።
22ቍጡ ሰው ጠብን ይጭራል፤
ግልፍተኛም ብዙ ኀጢአት ይሠራል።
23ሰውን ትዕቢቱ ያዋርደዋል፤
ትሑት መንፈስ ያለው ግን ክብርን
ይጐናጸፋል።
24የሌባ ግብረ አበር የገዛ ራሱ ጠላት
ነው፤
የመሐላውን ርግማን እየሰማ ጭጭ
ይላል።
25ሰውን መፍራት ወጥመድ ነው፤
*በእግዚአብሔር* የሚታመን ግን በሰላም
ይኖራል።
26ብዙዎች በገዥ ፊት ተደማጭነት
ማግኘት ይሻሉ፤
ሰው ፍትሕ የሚያገኘው ግን *ከእግዚ
አብሔር* ዘንድ ነው።
27ጻድቃን አታላዮችን ይጸየፋሉ፤
ክፉዎችም ቅኖችን ይጠላሉ።

## አጉር የተናገራቸው ምሳሌዎች

30 የያቄ ልጅ የአጉር ቃል ይህ
ነው፤[ዐ]
ይህ ሰው ለኢቲኤል፣
ለኢቲኤልና ለኡካል ተናገረ፤[ዘ]
2"እኔ ከሰው ሁሉ ይልቅ ጅል ነኝ፤
ሰው ያለው ማስተዋል የለኝም።
3ጥበብን አልተማርሁም፤
ስለ ቅዱሱም ዕውቀት የለኝም።

28፥28 ቍ12፤ኢዮ 20፥19
29፥1 ዘፀ32፥9፤ዘዳ 9፥27፤2ዜና36፥16፤ምሳ6፥15፤ኤር19፥15፤36፥31፤ዕን2፥7
29፥2 2ነገ11፥20፤ ምሳ28፥12፤30፥22፤መክ10፥6
29፥3 ምሳ5፥8-10፤ 10፥1፤23፥15-16፤ ሉቃ5፥11-32
29፥4 ቍ14፤ምሳ 8፥15-16
29፥5 ኢዮ32፥21፤ ምሳ26፥28
29፥6 ኢዮ5፥13፤ ምሳ26፥27፤መክ9፥12
29፥7 ምሳ31፥8-9
29፥8 ምሳ11፥11 ፤16፥14
29፥10 ቍ27፤ 1ዮሐ3፥12
29፥11 ኢዮ15፥13 ፤ምሳ12፥16
29፥12 2ነገ21፥9 ፤ኢዮ34፥30
29፥13 ምሳ22፥2፤ ማቴ5፥45
29፥14 ቍ4፤መዝ 72፥1-5፤ምሳ16፥12
29፥15 ቍ17፤ምሳ 13፥24
29፥16 መዝ91፥8፤ 92፥11
29፥17 ቍ15
29፥18 መዝ1፥1-2 ፤19፥11፤119፥1-2
29፥20 ምሳ19፥2፤ 26፥12
29፥22 ምሳ14፥17
29፥23 አስ5፥12፤ ምሳ11፥2፤15፥33፤ 16፥18
29፥24 ዘሌ5፥1
29፥25 1ሳሙ15፥24 ፤ምሳ16፥20፤28፥25
29፥26 ምሳ16፥33 ፤19፥6
29፥27 ቍ10
30፥1 ምሳ22፥17
30፥3 ምሳ9፥10

[ሠ]21 በዕብራይስጡ የዚህ ቃል ትርጓሜ በእርግጠኝነት አይታወቅም
[ዐ]1 ወይም *የማሳው ያቄ*
[ዘ]1 የማስሬቲክ ጽሑፍ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የዕብራይስጡ ግን *ተናገረ*፤ "አቤቱ እግዚአብሔር፤ እኔ ደክሜአለሁ/ አቤቱ እግዚአብሔር፤ እኔ ደክሜአለሁ፤ እንደ ሞተ ሰውም ሆኛለሁ" ይላል።

4ወደ ሰማይ የወጣ፣ የወረደስ ማነው?
ነፋስን በእጁ ሰብስቦ የያዘ ማነው?
ውሆችንስ በመጐናጸፊያው የጠቀለለ
ማነው?
የምድርን ዳርቻዎች ሁሉ የወሰነ ማነው?
ስሙ ማን ነው? የልጁስ ስም ማን
ይባላል?
የምታውቅ ከሆነ እስቲ ንገረኝ!

5"የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ እንከን
የለበትም፤
እርሱ ለሚታመኑበት ሁሉ ጋሻቸው
ነው።
6በእርሱ ቃል ላይ አንዳች አትጨምር፤
አለዚያ ይዘልፍሃል፤ ሐሰተኛም
ያደርግሃል።

7"እግዚአብሔር ሆይ፤ ሁለት ነገር
እለምንሃለሁ፤
እነዚህንም ከመሞቴ በፊት
አትከልክለኝ፤
8ሐሰትንና ሐሰት መናገርን ከእኔ
አርቅልኝ፤
ድኽነትንም ሆነ ብልጽግናን አትስጠኝ፤
ብቻ የዕለት እንጀራዬን ስጠኝ።
9ያለዚያ ግን ያለ ልክ እጠግብና
እክድሃለሁ፤
'እግዚአብሔር ማን ነው?' እላለሁ፤
ወይም ድኻ እሆንና እሰርቃለሁ፤
የአምላኬንም ስም አሰድባለሁ።
10"አገልጋይን በጌታው ፊት በክፉ
አታንሣው፤
አለዚያ ይረግምህና ጕዳት ያገኝሃል።

11"አባቱን የሚረግም፣
እናቱን የማይባርክ ትውልድ አለ፤
12ራሳቸውን ንጹሓን አድርገው የሚቈጥሩ፣
ሆኖም ከርኵሰታቸው ያልነጹ አሉ፤
13ዐይናቸው ትዕቢተኛ የሆነ፣
አስተያያቸው ንቀት የሞላበት፣
14ድኾችን ከምድር፣
ችግረኞችንም ከሰው ዘር መካከል
ለማጥፋት፣
ጥርሳቸው ሰይፍ የሆነ፣
መንጋጋቸውም ካራ የሆነ አሉ።

15"አልቅት ሁለት ሴት ልጆች አሉት፤
'ስጡን! ስጡን!' እያሉ ይጮኻሉ፤
"ፈጽሞ የማይጠግቡ ሦስት ነገሮች አሉ፤
'በቃኝን' ከቶ የማያውቁ አራት
ናቸው፤
16እነርሱም መቃብር፣[ፕ] መካን ማኅፀን፣
ውሃ ጠጥታ የማትረካ ምድር፣
'በቃኝ' የማይል እሳት ናቸው።

17"በአባት ላይ የምታፌዝ ዐይን፣
የእናትንም ትእዛዝ የምትንቅ፣
የሸለቆ ቍራዎች ይጐጠጕጧታል፤
ጆፌ አሞሮችም ይበሏታል።

18"እጅግ የሚያስደንቁኝ ሦስት ነገሮች
አሉ፤
የማላስተውላቸውም አራት ናቸው፤
19የንስር መንገድ በሰማይ፣
የእባብ መንገድ በቋጥኝ፣
የመርከብ መንገድ በባሕር፣
የሰውም መንገድ ከሴት ልጅ ጋር
ናቸው።

20"የአመንዝራዪቱ መንገድ ይህ ነው፤
በልታ አፏን በማበስ፣
'ምንም የሠራሁት ጥፋት የለም'
ትላለች።
21"ምድር በሦስት ነገር ትናወጣለች፤
እንዲያውም መሸከም የማትችላቸው
አራት ነገሮች ናቸው፤
22ባሪያ ሲነግሥ፣
ሰነፍ እንጀራ ሲጠግብ፣
23የተጠላች ሴት ባል ስታገባ፣
ሴት ባሪያ በእመቤቷ እግር ስትተካ።

24"በምድር ላይ አራት ነገሮች ትንንሽ
ናቸው፤
ሆኖም እጅግ ጠቢባን ናቸው፤
25ጕንዳኖች ደካማ ፍጡራን ናቸው፤
ሆኖም ምግባቸውን በበጋ ያከማቻሉ።
26ሽኮኮዎች ዐቅመ ደካማ ናቸው፤
ሆኖም መኖሪያቸውን በቋጥኞች
መካከል ይሠራሉ፤
27አንበጦች ንጉሥ የላቸውም፤
ሆኖም ቅደም ተከተል ይዘው ይጓዛሉ፤
28እንሽላሊት በእጅ ትያዛለች፤
ሆኖም በቤተ መንግሥት ትገኛለች።

29"አረማመዳቸው ግርማዊ የሆነ ሦስት
ነገሮች አሉ፤
እንዲያውም በሞገስ የሚጐማለሉ አራት
ናቸው፤
30ከአራዊት መካከል ኀይለኛ የሆነው፣
ከምንም ነገር ፊት ግንባሩን የማያጥፈው
አንበሳ፤
31ጐርደድ ጐርደድ የሚል አውራ ዶሮ፣
አውራ ፍየል፣
እንዲሁም በሰራዊቱ የታጀበ ንጉሥ
ናቸው።[የ]

32ተላላ ሆነህ ራስህን ከፍ ከፍ ካደረግህ፣
ወይም ክፉ ነገር ካቀድህ፣
እጅህን በአፍህ ላይ አድርግ።

30፥4 ዘፍ1፥2፤ዘዳ 30፥12፤ኢዮ26፥8፤ መዝ24፥1-2፤ምሳ8፥ 22-31፤ኢሳ40፥12፤ ዮሐ3፥13፤ኤፌ4፥7- 10፤ራእ19፥12
30፥5 ዘፍ15፥1፤ መዝ12፥6፤18፥30
30፥6 ዘዳ4፥2
30፥8 ማቴ6፥11
30፥9 ዘዳ6፥12፤ 8፥10-14፤ኢሱ24፥27 ፤ኢሳ1፥4፤59፥13፤ ሆሴ13፥6
30፥11 ምሳ20፥20
30፥12 ምሳ16፥2፤ ኤር2፥23፡25
30፥13 2ሳሙ22፥28 ፤ኢዮ41፥34
30፥14 ኢዮ4፥11፤ 19፥22፤24፥9፤መዝ3፥7 ፤57፥4፤አሞ8፥4፤ ሚክ2፥2
30፥15 ምሳ27፥20
30፥16 ኢሳ5፥14፤ 14፥9፡11፤ዕን2፥5
30፥17 ዘዳ21፥18- 21፤ኢዮ15፥23
30፥20 ምሳ5፥6
30፥22 ምሳ19፥10 ፤29፥2
30፥25 ምሳ6፥6-8
30፥26 መዝ104፥ 18
30፥27 ዘፀ10፥4
30፥32 ኢዮ29፥9

[ፕ]16 ዕብራይስጡ *ሲኦል* ይላል
[የ]31 ወይም *ከተቃውሞ የተጠበቀ ንጉሥ*

[33]ወተት ሲናጥ ቅቤ እንደሚወጣው፣
አፍንጫን ሲያሹት እንደሚደማ፣
ቍጣን ማነሣሣትም ጥልን ይፈጥራል።

## ንጉሥ ልሙኤል የተናገራቸው ምሳሌዎች

31 ንጉሥ ልሙኤልን እናቱ
ያስተማረችው ቃል ይህ ነው፤

[2]“ልጄ ሆይ፤ የማሕፀኔ ልጅ ሆይ፤
የስእለቴ ልጅ ሆይ፤[ዶ]
[3]ጒልበትህን በሴት አትጨርስ፤
ብርታትህንም ነገሥታትን ለሚያጠፉ
አታውል።

[4]“ልሙኤል ሆይ፤ ነገሥታት ይህን
ማድረግ የለባቸውም፤
ነገሥታት የወይን ጠጅ ሊጠጡ፣
ገዦችም የሚያሰክር መጠጥ
ሊያስጐመጃቸው አይገባም፤
[5]አለዚያ ጠጥተው የሕጉን ድንጋጌ
ይረሳሉ፤
የተጨቈኑትን ሁሉ መብት ይገፋሉ።
[6]ለሚጠፉት የሚያሰክር መጠጥ፣
በሥቃይ ላሉትም የወይን ጠጅ
ስጧቸው፤
[7]ጠጥተው ድኽነታቸውን ይርሱ፤
ችግራቸውንም ከእንግዲህ አያስቡ።

[8]“ስለ ራሳቸው መናገር ለማይችሉት፣
ለችግረኞችም ሁሉ መብት ተሟገት።
[9]ተናገር፤ በቅንነትም ፍረድ፤
የምስኪኖችንና የድኾችን መብት
አስከብር።”

## መዝጊያ ክፍል፤ ጠባየ መልካም ሚስት

[10]ጠባየ መልካምን ሚስት ማን ያገኛታል?[ጀ]
ከቀይ ዕንቍ እጅግ ትበልጣለች።
[11]ባሏ ሙሉ በሙሉ ይተማመንባታል፤
የሚጐድልበትም ነገር የለም።
[12]በሕይወት ዘመኗ ሁሉ፣
መልካም ታደርግለታለች እንጂ
አትጐዳውም።
[13]የበግ ጠጒርና የተልባ እግር መርጣ፣
ሥራ በሚወዱ እጆቿ ትፈትላቸዋለች።
[14]እንደ ንግድ መርከብ፣
ምግቧን ከሩቅ ትሰበስባለች።
[15]ገና ሳይነጋ ትነሣለች፤
ለቤተሰቧ ምግብ፣
ለሴት አገልጋዮቿም ድርሻቸውን
ትሰጣለች።

31፥1 ምሳ22፥17
31፥2 መሳ11፥30
31፥3 ዘዳ17፥17፤ 1ነገ11፥3፤ምሳ5፥1-14
31፥4 ምሳ20፥1፤ መክ10፥16-17፤ ኢሳ5፥22
31፥5 1ነገ16፥9፤ ምሳ16፥12
31፥6 ዘፍ14፥18
31፥7 አስ1፥10
31፥8 1ሳሙ19፥4
31፥9 ምሳ24፥23 ፤29፥7
31፥10 ሩት3፥11፤ ምሳ8፥35፤18፥22
31፥11 ዘፍ2፥18 ፤ምሳ12፥4
31፥13 1ጢሞ2፥9-10
31፥20 ዘዳ15፥11
31፥23 ዘፀ3፥16
31፥26 ምሳ10፥31
31፥31 ምሳ11፥16

[16]ራሷ አስባ የዕርሻ መሬት ትገዛለች፤
በምታገኘውም ገንዘብ ወይን
ትተክላለች።
[17]ብርታትን ታጥቃ ሥራዋን
ታከናውናለች፤
ክንዶቿም ለሥራ ብርቱ ናቸው።
[18]ሥራዋ ትርፋማ መሆኑን ታስተውላለች፤
በሌሊትም መብራቷ አይጠፋም።
[19]በእጇ እንዝርት ትይዛለች፤
በጣቶቿም ዘንጒን ታሾራለች።
[20]ክንዶቿን ለድኾች ትዘረጋለች፣
እጆቿንም ለችግረኞች ፊታ
ታደርጋለች።
[21]በረዶ ቢጥል ለቤተ ሰዎቿ አትሠጋም፤
ሁሉም ቀይ ልብስ ለብሰዋልና።
[22]ለመኝታዋ የዐልጋ ልብስ ትሠራለች፤
ቀጭን በፍታና ሐምራዊ ልብስ
ለብሳለች።
[23]ባሏ በአገር ሽማግሌዎች መካከል
በአደባባይ በተቀመጠ ጊዜ የተከበረ
ነው።
[24]የበፍታ መጐናጸፊያዎችን ሠርታ
ትሸጣለች፤
ለነጋዴዎችም ድግ ታቀርባለች።
[25]ብርታትንና ሞገስን ተጐናጽፋለች፤
መጭውን ጊዜ በደስታ ትቀበላለች።
[26]በጥበብ ትናገራለች፤
በአንደበቷም ቀና ምክር አለ።
[27]የቤተ ሰዎቿን ጒዳይ በትጋት
ትከታተላለች፤
የስንፍና እንጀራ አትበላም።
[28]ልጆቿ ተነሥተው፤ ቡርክት ይሏታል፤
ባሏም እንዲሁ፤ ሲያመሰግናትም
እንዲህ ይላል፤
[29]“ብዙ ሴቶች መልካም አድርገዋል፤
አንቺ ግን ሁሉንም ትበልጫለሽ።”
[30]ቍንጅና አታላይ ነው፤ ውበትም
ይረግፋል፤
እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን
የተመሰገነች ናት።
[31]የሚገባትን ሽልማት ስጧት፤
ሥራዋም በየአደባባዩ ያስመስግናት።

[ዶ]2 ወይም *የጸሎቴ መልስ ሆይ*
[ጀ]10 ከ10-31 ያለው እያንዳንዱ ቍጥር የሚጀምረው በዕብራይስጡ ሆህያት ቅደም ተከተል መሠረት ነው።

# መጽሐፈ መክብብ

## ሁሉም ነገር ከንቱ ነው

1 በኢየሩሳሌም የነገሠው፣ የዳዊት
ልጅ፣ የሰባኪው ቃል[ሀ]፤

2ሰባኪው፣
“ከንቱ፣ ከንቱ፣
የከንቱ ከንቱ፤
ሁሉም ነገር ከንቱ ነው” ይላል።

3ከፀሓይ በታች ከሚለፋበት ተግባር ሁሉ፣
ሰው ምን ትርፍ ያገኛል?
4ትውልድ ይሄዳል፤ ትውልድ ይመጣል፤
ምድር ግን ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች።
5ፀሓይ ትወጣለች፤ ትጠልቃለችም፤
ወደምትወጣበትም ለመመለስ
ትጣደፋለች።
6ነፋስ ወደ ደቡብ ይነፍሳል፤
ወደ ሰሜንም ይመለሳል፤
ዞሮ ዞሮ ይሄዳል፤
ዘወትርም ወደ ዑደቱ ይመለሳል።
7ወንዞች ሁሉ ወደ ባሕር ይፈሳሉ፤
ባሕሩ ግን ፈጽሞ አይሞላም፤
ወንዞች ወደ መጡበት ስፍራ፣
ወደዚያ እንደ ገና ይመለሳሉ።
8ሰው መናገር ከሚችለው በላይ፣
ነገሮች ሁሉ አድካሚ ናቸው፤
ዐይን ከማየት አይጠግብም፤
ጆሮም በመስማት አይሞላም።
9የነበረው ነገር እንደ ገና ይሆናል፤
የተደረገውም ተመልሶ ይደረጋል፤
ከፀሓይ በታች ምንም አዲስ ነገር የለም።
10ማንም፣ “እነሆ፤ ይህ አዲስ ነገር ነው!”
ሊል የሚችለው አንዳች ነገር አለን?
ቀድሞውኑ በዚሁ የነበረ ነው፤
ከእኛ በፊት የሆነ ነው።
11የቀድሞ ነገሮች መታሰቢያ የላቸውም፤
ወደ ፊት የሚመጡትም ቢሆኑ፣
ከእነርሱ በኋላ በሚተኩት፣
አይታወሱም።

## ጥበብ ከንቱ ነው

12እኔ ሰባኪው፣ በኢየሩሳሌም የእስራ
ኤል ንጉሥ ነበርሁ። 13ከሰማይ በታች
የተደ ረገውን ሁሉ በጥበብ ለማጥናትና
ለመመር መር ራሴን አተጋሁ፤ አምላክ
በሰዎች ላይ የጫነው እንዴት ያለ ከባድ
ሸክም ነው! 14ከፀሓይ በታች የተደረገውን
ነገር ሁሉ አየሁ፤ ሁሉም ከንቱ፣ ነፋስንም
እንደ መከ ተል ነው።

15የተጣመመው ሊቃና አይችልም፤
የሌለም ነገር ሊቈጠር አይችልም።

16እኔም በልቤ፣ “እነሆ፤ ከእኔ በፊት
በኢየሩሳሌም ከገዙት ከማንኛቸውም ይልቅ
ታላቅ ሆኛለሁ፤ ጥበብም በዝቶልኛል፤ በብዙ
ጥበብና ዕውቀት ተመክሮም ዐልፌአለሁ”
አልሁ። 17ከዚያም የጥበብንና የእብደትን፣
የሞኝነትንም ነገር ለመገንዘብ ራሴን አተ
ጋሁ፤ ይህም ነፋስን እንደ መከተል መሆኑን
ተረዳሁ።

18ጥበብ ሲበዛ፣ ትካዜ ይበዛልና፤
ዕውቀት ሲጨምርም ሐዘን ይበዛል።

## ምድራዊ ደስታ ከንቱ ነው

2 እኔም በልቤ፣ “መልካም የሆነውን ለ
ማ ወቅ፣ በተድላ ደስታ
እፈትንሃለሁ” አልሁ፤ ነገር ግን ያም
ከንቱ ነበረ። 2ደግ ሞም፣ “ሣቅ ሞኝነት
ነው፤ ተድላ ደስታስ ምን ይጠቅማል?”
አልሁ። 3አሁንም አእም ሮዬ በጥበብ እየመ
ራኝ ራሴን በወይን ጠጅ ደስ ለማሰኘት፣
ሞኝነትንም ለመያዝ ሞከ ርሁ፤ ሰዎች
በአጭር የሕይወት ዘመናቸው ከሰማይ
በታች ባለው ላይ ቢሠሩት ሊጠቅማቸው
የሚችል ምን እንደ ሆነ ለማየት ፈለግሁ።
4ታላላቅ ነገሮችን አከናወንሁ፤ ለራሴ
ቤቶችን ሠራሁ፤ ወይንንም ተከልሁ፤ 5አት
ክልትን ተከልሁ፤ የመዝናኛ ስፍራዎችን
አዘጋጀሁ፤ በእነዚህም ላይ ፍሬ የሚያፈሩ
የዛፍ ዐይነቶችን ሁሉ ተከልሁባቸው፤ 6የሚ
ለመልሙ ዛፎችን ለቦይ የሚሆኑ የውሃ
ማጠራቀሚያዎችን ሠራሁ። 7ወንድና ሴት
ባሪያ ዎችን ገዛሁ፤ በቤቴም የተወለዱ
ሌሎች ባሪያዎች ነበሩኝ። ከእኔ በፊት በኢ
የሩሳሌም ከነበሩት ይልቅ ብዙ የከብት፣
የበግና የፍየል መንጋዎች ነበሩኝ። 8ለራ
ሴም ብርንና ወር ቅን፣ የነገሥታትና
የአውራጃዎችን ሀብት አካበትሁ፤ ወንድና
ሴት አዝማሪዎች፣ የሰው መደሰቻ የሆኑ
ቅምጦች[ለ] ነበሩኝ። 9ከእኔ በፊት በኢየሩ
ሳሌም ከነበሩት ሁሉ ይልቅ እጅግ ታላቅ
ሆንሁ፤ በዚህ ሁሉ ጥበቤ ከእኔ ጋር
ነበረች።

10ዐይኔ የፈለገውን ሁሉ
አልከለከልሁትም፤
ለልቤም ምድራዊ ደስታን አልነፈግሁትም፤

1፥1 ቆ 12፤ምሳ1፥1፤መክ7፥27፤12፥10
1፥2 መዝ39፥5-6፤62፥9፤መክ12፥8፤ሮሜ 8፥20-21
1፥3 መክ2፥11፡22፤3፥9፤5፥15-16
1፥4 ኢዮ 8፥19
1፥5 መዝ19፥5-6
1፥7 ኢዮ 36፥28
1፥8 ምሳ 27፥20
1፥9 መክ 2፥12፤3፥15
1፥11 ዘፍ40፥23፤መዝ88፥12፤መክ2፥16፤8፥10፤9፥5፡15
1፥12 ቆ 1መክ2፥9
1፥13 ዘፍ3፥17፤ኢዮ 28፥3፤መክ3፥10
1፥14 መክ2፥11፡17፤4፥4፤6፥9
1፥15 መክ7፥13
1፥16 1ነገ3፥12
1፥17 መክ7፥23፤8፥16፤መክ2፥3፡12፤7፥25
1፥18 መክ2፥23፤12፥12፤ኤር45፥3
2፥1 ቆ 24፤መክ7፥4፤8፥15
2፥2 ምሳ14፥13
2፥3 ቆ 24-25፤መሳ 9፥13፤ሩት3፥3፤መክ 1፥17፤3፥12-13፤5፥18፤8፥15
2፥4 2ዜና 2፥1፤8፥1-6፤ማሕ8፥11
2፥7 2ዜና 8፥7-8
2፥8 መሳ3፥15፤2ሳሙ19፥35፤1ነገ9፥28
2፥9 1ዜና29፥25፤መክ1፥12

[ሀ]1 ወይም *የጉባኤ መሪ*፤ እንዲሁም በቆ 2 እና 12

ልቤ በሠራሁት ሁሉ ደስ አለው፤
ይህም የድካሜ ሁሉ ዋጋ ነበረ።
[11]ሆኖም እጆቼ የሠሩትን ሁሉ፣
ለማግኘትም የደከምሁትን ድካም ሁሉ
ሳስብ፣
ሁሉም ከንቱ፣ ነፋስንም እንደ መከተል
ነበር፤
ከፀሓይ በታች ምንም ትርፍ አልነበረም።

## ጥበብና ሞኝነት ከንቱ ናቸው

[12]ከዚያም ጥበብን፣
እብደትንና ሞኝነትን ለመመርመር
ሐሳቤን መለስሁ፤
አስቀድሞ ከተደረገው በቀር፣
ከንጉሥ በኋላ የሚመጣው ሰው ምን
ሊያደርግ ይችላል?
[13]ብርሃን ከጨለማ እንደሚበልጥ ሁሉ፣
ጥበብም ከሞኝነት እንደሚበልጥ
ተመለከትሁ።
[14]የጠቢብ ሰው ዐይኖች ያሉት በራሱ
ውስጥ ነው፤
ሞኝ ግን በጨለማ ውስጥ ይራመዳል፤
ሆኖም የሁለቱም ዕድል ፈንታ፣
አንድ መሆኑን ተገነዘብሁ።

[15]ከዚያም በልቤ፣
“የሞኙ ዕድል ፈንታ በእኔም ላይ
ይደርሳል፤
ታዲያ ጠቢብ በመሆኔ ትርፌ ምንድን ነው?”
አልሁ።
በልቤም፣ “ይህም ደግሞ ከንቱ
ነው” አልሁ።
[16]ጠቢቡም ሰው እንደ ሞኙ ለዘላለም
አይታወስምና፤
በሚመጡት ዘመናት ሁለቱም ይረሳሉ።
ለካ፣ ጠቢቡም እንደ ሞኙ መሞቱ
አይቀርም!

## ጥረት ከንቱ ነው

[17]ስለዚህ ከፀሓይ በታች የሚሠራው ሥራ
አሳዛኝ ስለ ሆነብኝ ሕይወትን ጠላሁ፤
ይህም ሁሉ ከንቱ፣ ነፋስንም እንደ መከተል
ነው። [18]ከፀሓይ በታች የደከምሁበትን
ነገር ሁሉ ጠላሁት፣ ከኋላዬ ለሚመጣው
የግድ እተውለታለሁና። [19]እርሱ ጠቢብ
ወይም ሞኝ ይሆን እንደ ሆነ ማን ያውቃል?
ሆኖም ከፀሓይ በታች ድካሜንና
ችሎታዬን ባፈሰስሁበት ሥራ ሁሉ ላይ
ባለቤት ይሆንበ ታል፤ ይህም ደግሞ ከንቱ
ነው። [20]ስለዚህ ከፀሓይ በታች በደከምሁበት
ነገር ሁሉ ላይ ልቤ ተስፋ መቍረጥ ጀመረ፤
[21]ምክንያቱም ሰው ሥራውን በጥበብ፣ በዕ
ውቀትና በብል ኀት ሠርቶ፣ ከዚያ ያለውን
ሁሉ ለሌላ ላልለፋበት ሰው

2፥11 መክ1፥3፥14
2፥12 መክ1፥9፥17
2፥13 መክ7፥11-12፥19፤9፥18
2፥14 መዝ49፥10፤ መክ3፥19፤6፥6፤7፥2፤9፥3፤11-12
2፥15 ቍ19፤ መክ6፥8
2፥16 መዝ49፥10፤ 112፥6፤መክ1፥11
2፥17 መክ1፥14
2፥18 መዝ39፥6፤ 49፥10
2፥19 ቍ15

2፥22 መክ 1፥3
2፥23 ዘፍ3፥17፤ ኢዮ7፥2፤ መክ1፥18
2፥24 ቍ1፥3፤ኢዮ 2፥10፤መክ3፥12-13፤22፤5፥17-19፤ 7፥14፤9፥7-10፤ 11፥7-10
2፥25 መዝ127፥2
2፥26 ኢዮ 9፥4፤ 27፥17፤ምሳ13፥22
3፥1 ቍ11፥17፤ መክ8፥6
3፥2 ኢሳ28፥24
3፥3 ዘዳ5፥17
3፥7 አስ4፥14
3፥9 መክ1፥3
3፥10 መክ1፥13

ይተውለታል። ይህም ደግሞ ከንቱና
ትልቅ ጕዳት ነው። [22]ሰው ከፀሓይ በታች
በሚደክምበት ጥረትና ልፋት ሁሉ ትርፉ
ምንድን ነው? [23]በዘመኑ ሁሉ ሥራው
ሥቃይና ሐዘን ነው፤ በሌሊትም እንኳ ቢ
ሆን አእምሮው አያርፍም። ይህም ደግሞ
ከንቱ ነው።
[24]ለሰው ከመብላትና ከመጠጣት፣ በሥራ
ውም ከመርካት ሌላ የሚሻለው ነገር የለ
ውም፤ ይህም ደግሞ ከእግዚአብሔር እጅ
እንደ ሚሰጥ አየሁ፤ [25]ከእርሱ ዘንድ ካልሆነ
ማን መብላትና መደሰት ይችላል? [26]እግዚ
አብሔር፣ ደስ ለሚያሰኘው ሰው ጥበብን፣ ዕ
ውቀትንና ደስታን ይሰጠዋል። ለኀጢአተኛ
ግን፣ እግዚአብሔርን ደስ ለሚያሰኘው
ይተውለት ዘንድ፣ ሀብትን የመሰብሰብና የ
ማከናወን ተግባር ይሰጠዋል። ይህም ከንተ
.፣ ነፋስንም እንደ መከተል ነው።

## ለሁሉም ጊዜ አለው

3 ለሁሉም ነገር ጊዜ አለው፤
ከሰማይ በታች ለሚከናወነው
ለማንኛውም ነገር ወቅት አለው፤
[2]ለመወለድ ጊዜ አለው፤ ለመሞትም
ጊዜ አለው፤
ለመትከል ጊዜ አለው፤ ለመንቀልም
ጊዜ አለው፤
[3]ለመግደል ጊዜ አለው፤ ለማዳንም
ጊዜ አለው፤
ለማፍረስ ጊዜ አለው፤ ለመገንባትም
ጊዜ አለው፤
[4]ለማልቀስ ጊዜ አለው፤ ለመሣቅም
ጊዜ አለው፤
ለሐዘን ጊዜ አለው፤ ለጭፈራም
ጊዜ አለው፤
[5]ድንጋይ ለመጣል ጊዜ አለው፤ ድንጋይ
ለመሰብሰብም ጊዜ አለው፤
ለመተቃቀፍ ጊዜ አለው፤
ለመለያየትም ጊዜ አለው፤
[6]ለመፈለግ ጊዜ አለው፤ ለመተው
ጊዜ አለው፤
ለማስቀመጥ ጊዜ አለው፤ አውጥቶ
ለመጣልም ጊዜ አለው፤
[7]ለመቅደድ ጊዜ አለው፤ ለመስፋትም
ጊዜ አለው፤
ለዝምታ ጊዜ አለው፤ ለመናገርም ጊዜ
አለው፤
[8]ለመውደድ ጊዜ አለው፤ ለመጥላትም
ጊዜ አለው፤
ለጦርነት ጊዜ አለው፤ ለሰላምም ጊዜ
አለው።
[9]ሠራተኛ ከጥረቱ የሚያገኘው ትርፍ
ምንድን

^8 በዕብራይስጥ የዚህ ሐረግ ትርጕም አይታወቅም

ነው? [10]ሰዎች ይደክሙበት ዘንድ እግዚአብሔር
የሰጣቸውን ከባድ የሥራ ጫና አየሁ።
[11]ሁሉ ንም ነገር በጊዜው ውብ አድርጎ ሠ
ራው፤ በሰዎችም ልብ ዘላለማዊነትን
አኖረ፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር
ከመጀመሪያ እስከ መጨ ረሻ ያደረገውን
ማወቅ አይችሉም። [12]ለሰ ዎች፣ በሕይወት
እያሉ ደስ ከመሰኘትና መልካምን ነገር ከ
ማድረግ የተሻለ ነገር እንደሌለ ዐወቅሁ።
[13]ሰው ሁሉ ይበላና ይጠጣ ዘንድ፣
በሚደክምበትም ሁሉ ርካታን ያገኝ ዘንድ
ይህ የእግዚአብሔር ችሮታ ነው። [14]እግዚአብሔር
ያደረገው ሁሉ ለዘላለም እንደሚኖር ዐ
ውቃለሁ፤ በእርሱ ላይ ምንም
አይጨመርም፤ ከእርሱም ምንም
አይቀነስም፤ ሰዎች ያከብሩት ዘንድ ይህን
አደረገ።

[15]አሁን ያለው ከዚህ በፊት የነበረው ነው፤
ወደፊት የሚሆነውም ቀድሞ የነበረ ነው፤
እግዚአብሔርም ያለፈውን መልሶ ይሻዋል[ሐ]።

[16]ከፀሓይ በታችም ሌላ ነገር አየሁ፤

በፍርድ ቦታ ዐመፅ ነበር፤
በፍትሕ ቦታ ግፍ ነበር።

[17]እኔም በልቤ “ለማንኛውም ድርጊት፣
ለማንኛውም ተግባር ጊዜ ስላለው፣
እግዚአብሔር ጻድቁንና ኀጢአተኛውን
ወደ ፍርድ ያመጣቸዋል” ብዬ
አሰብሁ።

[18]እንዲህም ብዬ አሰብሁ፤ “ሰዎች፣
እንደ እንስሳት መሆናቸውን ያዩ ዘንድ እግዚ
አብሔር ይፈትናቸዋል። [19]የሰው ዕድል ፈንታ
እንደ እንስሳት ነው፤ ሁለቱም ዕጣ ፈንታ
ቸው አንድ ነው፤ አንዱ እንደሚሞት፣
ሌላውም እንዲሁ ይሞታል። ሁሉ አንድ
ዐይነት እስትንፋስ[መ] አላቸው፤ ሰውም ከእ
ንስሳ ብልጫ የለውም፤ ሁሉም ከንቱ ነው።
[20]ሁሉም ወደ አንድ ቦታ ይሄዳሉ፤ ሁሉም
ከዐፈር እንደ ሆኑ፣ ተመልሰው ወደ ዐፈር
ይሄዳሉ። [21]የሰው መንፈስ ወደ ላይ መው
ጣቱን፣ የእንስሳ እስትንፋስ[ሠ] ደግሞ ወደ
ታች ወደ ምድር መውረዱን ማን ያው
ቃል?”

[22]ስለዚህ ለሰው ዕጣ ፈንታው ስለ ሆነ፣
በሥራው ከመደሰት የተሻለ ነገር እንደ
ሌለው አየሁ፤ ከእርሱ በኋላ የሚሆነውንስ
ተመልሶ እንዲያይ የሚያደርገው ማን ነው?

## ግፍ፣ጥረት፣ብቸኝነት

4 እንደ ገና ከፀሓይ በታች የሚደረገ
ውን ግፍ ሁሉ አየሁ፤ አስተዋልሁም፤

የተገፉትን ሰዎች እንባ ተመለከትሁ፤
የሚያጽናናቸውም አልነበረም፤
ኀይል በሚገፏቸው ሰዎች እጅ ነበረ፤
የሚያጽናናቸውም አልነበረም።
[2]እኔም የቀድሞ ሙታን፣
ዛሬ በሕይወት ካሉት ሕያዋን ይልቅ፣
ደስተኞች እንደ ሆኑ ተናገርሁ።
[3]ነገር ግን ከሁለቱም ይልቅ፣
ገና ያልተወለደው፣
ከፀሓይ በታች የሚደረገውንም፣
ክፋት ያላየው ይሻላል።

[4]እንዲሁም ጥረትና የሥራ መከናወን
ሁሉ ሰው በባልንጀራው ላይ ካለው ቅናት
እንደሚመነጭ ተመለከትሁ፤ ይህም ደግሞ
ከንቱ፣ ነፋስንም እንደ መከተል ነው።

[5]ሰነፍ እጁን አጣጥፎ ይቀመጣል፤
የገዛ ራሱንም ሥጋ ይበላል።
[6]በድካምና ነፋስን በመከተል
ከሚገኝ ሁለት ዕፍኝ ይልቅ፣
በርጋታ የሚገኝ አንድ ዕፍኝ ይሻላል።

[7]ደግሞም ከፀሓይ በታች ከንቱ የሆነን
ነገር
አየሁ፤

[8]ልጅም ሆነ ወንድም የሌለው፣
ብቸኛ ሰው አለ፤
ጥረቱ ማለቂያ የለውም፤
ዐይኑም ባለው ሀብት ገና አልረካም፤
እርሱም፣ “ለማን ብዬ ነው የምደክመው?
ራሴን ከማስደሰትስ የምቈጠበው
ለምንድን ነው?” ብሎ ጠየቀ፤
ይህም ደግሞ ከንቱ፣
የጭንቅ ኑሮ ነው።

[9]ለሥራቸው መልካም ውጤት
ስለሚያገኙ፣
ከአንድ፣ ሁለት መሆን ይሻላል፤
[10]አንዱ ቢወድቅ፣
ባልንጀራው ደግፎ ያነሣዋል።
ቢወድቅ የሚያነሣው ረዳት የሌለው ግን፣
እንዴት አሳዛኝ ነው!
[11]ደግሞም ሁለቱ አብረው ቢተኙ
ይሞቃቸዋል፤
ነገር ግን አንዱ ብቻውን እንዴት
ሊሞቀው ይችላል?
[12]አንድ ሰው ብቸኛውን ቢያጠቃውም፣
ሁለት ከሆኑ ይመክቱታል፤
በሦስት የተገመደ ገመድም ቶሎ
አይበጠስም።

## በልጦ መገኘት ከንቱ ነው

[13]ምክርን መቀበል ከማያውቅ
ሞኝና ሸማግሌ ንጉሥ ይልቅ ጠቢብ
የሆነ ድኻ ወጣት ይሻላል። [14]ወጣቱ
ከእስር ቤት ወደ

3፥11 ቆላ1፤ ኢዮ11፥7፤ 28፥23፤ሮሜ11፥33
3፥13 ዘዳ12፥7፡18፤ መዝ34፥12፤ መክ2፥3፡24
3፥14 ኢዮ23፥15፤ መክ5፥7፤7፥18፤ 8፥12-13
3፥15 መክ1፥9፤ 6፥10
3፥17 ቆላ1፤ ኢዮ19፥29፤ መክ11፥9፤12፥14
3፥18 መዝ73፥22
3፥19 መክ2፥14
3፥20 ዘፍ2፥7፤ ኢዮ34፥15
3፥21 መክ12፥7
3፥22 ኢዮ31፥2፤ መክ2፥24
4፥1 መዝ12፥5፤ ሰቆ1፥16
4፥2 ኢዮ3፥17፤ 10፥18፤ኤር20፥17-18፤22፥10
4፥3 ኢዮ3፥16፡22
4፥4 መክ1፥14
4፥5 ምሳ6፥10
4፥6 ምሳ15፥16-17፤ 16፥8
4፥8 ምሳ27፥20

[ሐ]15 ወይም እግዚአብሔር ያለፈውን መልሶ ይጠራዋል
[መ]19 ወይም መንፈስ
[ሠ]21 ወይም የሰው መንፈስ ወደ ላይ እንደሚሄድ ወይም የእንስሳት መንፈስ

ንጉሥነት የመጣ ወይም በግዛቱ ውስጥ
በድኽነት የተወለደ ሊሆን ይችላል። 15ከፀ
ሓይ በታች የሚኖሩና የሚመላለሱ ሁሉ፣
ንጉሡን የሚተካውን ወጣት ተከትለውት
አየሁ። 16በፊቱ የነበረው ሕዝብ ሁሉ
ቍጥር ስፍር አልነበረውም፤ ከእርሱ በኋላ
የመጡት ግን በተተኪው አልተደሰቱም።
ይህም ደግሞ ከንቱ፣ ነፋስንም እንደ መከ
ተል ነው።

### እግዚአብሔርን ፍራ

5 ወደ እግዚአብሔር ቤት ስትሄድ እግር
ህን ጠብቅ። ለመስማት መቅረብ የሰ
ነፎችን መሥዋዕት ከማቅረብ ይበልጣል፤
እነርሱ ክፉ እንደሚሠሩ አያውቁምና።

2በአፍህ አትፍጠን፤
በእግዚአብሔርም ፊት ማንኛውንም ነገር
ለመናገር፣
በልብህ አትቸኵል፤
እግዚአብሔር በሰማይ፣
አንተ ደግሞ በምድር ነህ፤
ስለዚህ ቃልህ ጥቂት ይሁን።
3በሥራ ብዛት ሕልም እንደሚታይ፣
ብዙ ቃል ባለበትም የሞኝ ንግግር
ይገለጣል።

4ለእግዚአብሔር ስእለትን በተሳልህ ጊዜ ለመ
ፈጸም አትዘግይ፤ በሰነፎች ደስ አይለው
ምና፤ ስእለትህን ፈጽም። 5ስእለት ተስሎ
ካለመፈጸም፣ አለመሳል ይሻላል። 6አንደበ
ትህ ወደ ኀጢአት እንዲመራህ አትፍቀድ፤
ለቤተ መቅደስ መልእክተኛም፣ "የተሳል
ሁት በስሕተት ነበር" አትበል። እግዚአብሔር
በተናገርኸው ተቈጥቶ የእጅህን ሥራ ለምን
ያጥፋ? 7ብዙ ሕልምና ብዙ ቃል ከንቱ
ነው፤ ስለዚህ እግዚአብሔርን ፍራ።

### ባለጠግነት ከንቱ ነው

8በአገር ውስጥ ድኻ ተጨቍኖ፣ ፍትሕ
ተጓድሎ፣ መብትም ተረግጦ ብታይ፣ እንደ
ነዚህ ባሉ ነገሮች አትደነቅ፤ ምክንያቱም
አንዱን አለቃ የበላዩ ይመለከተዋል፤ በእነ
ዚህ በሁለቱም ላይ ሌሎች ከፍ ያሉ አሉ።
9ከምድሩ የሚገኘው ትርፍ ለሁሉም ነው፤
ንጉሡም ራሱ የሚጠቀመው ከዕርሻ ነው።

10ገንዘብን የሚወድ፣ ገንዘብ አይበቃውም፤
ብልጽግናም የሚወድ፣ በትርፉ
አይረካም፤
ይህም ከንቱ ነው።

11ሀብት በበዛ ቍጥር፣
ተጠቃሚውም ይበዛል፤
በዐይኑ ብቻ ከማየት በቀር
ታዲያ፣ ለባለቤቱ ምን ይጠቅመዋል?

5፥2 መሳ11፥35፤ ኢዮ6፥24፤ ምሳ20፥25
5፥3 ኢዮ20፥8፤ መክ10፥14
5፥4 ዘኍ30፥2-4፤ ዘዳ23፥21፤መሳ 11፥35፤መዝ66፥13-14፤119፥60
5፥5 ዘኍ30፥24፤ ዮና2፥9
5፥7 መክ3፥14
5፥8 መዝ12፥5
5፥12 ኢዮ20፥20
5፥13 መክ6፥1-2
5፥15 ኢዮ1፥21፤ መዝ49፥17፤ መክ1፥3፤1ጢሞ6፥7
5፥16 መክ1፥3
5፥18 መክ2፥3፥24
5፥19 1ዜና29፥12፤ ኢዮ31፥2፤ መክ2፥24፤6፥2
5፥20 ዘዳ12፥7፥18
6፥2 መክ5፥13፥19
6፥3 ኢዮ 3፥3፥6

12ጥቂትም ይሁን ብዙ ቢበላ፣
የሠራተኛ እንቅልፍ ጣፋጭ ነው፤
የሀብታም ሰው ብልጽግና ግን
እንቅልፍ ይነሣዋል።

13ከፀሓይ በታች የሚያሳዝን ክፉ ነገር
አየሁ፦

ይህም ለባለቤቱ ጕዳት የተከማቸ
ሀብት፣
14ወይም በአንድ መጥፎ አጋጣሚ የጠፋ
ብልጽግና ነው፤
ልጅ ሲወልድም፣
ለእርሱ የሚያስቀርለት ምንም ነገር
አይኖርም።
15ሰው ከእናቱ ማሕፀን
ዕራቍቱን ይወለዳል፤
እንደ መጣው እንዲሁ ይመለሳል።
ከለፋበትም ነገር፣
አንድም እንኳ በእጁ ይዞ ሊሄድ
አይችልም።

16ይህ ደግሞ እጅግ ክፉ ነገር ነው፤

ሰው እንደ መጣ እንዲሁ ይሄዳል፤
የሚደክመው ለነፋስ ስለ ሆነ፣
ትርፉ ምንድ ነው?
17በብዙ ጭንቀት፣ መከራና ብስጭት፣
ዘመኑን ሁሉ በጨለማ ውስጥ ይበላል።

18የሰው ዕጣው ይህ ስለ ሆነ፣ እግዚአብሔር
በሰጠው በጥቂት ዘመኑ ከፀሓይ በታች
በሚደክምበት ነገር ርካታን ያገኝ ዘንድ፣
መብላቱና መጠጣቱም መልካምና ተገቢ
መሆኑን ተገነዘብሁ። 19እግዚአብሔር ለሰው
ባለጠግነትና ሀብት መስጠቱ፣ እንዲደሰ
ትበትም ማስቻሉ፣ ዕጣውን እንዲቀበልና
በሥራውም እንዲደሰት ማድረጉ፣ ይህ የእ
ግዚአብሔር ስጦታ ነው። 20እግዚአብሔር
የልብ ደስታ ስለሚሰጠውም በሕይወቱ
ዘመን ያሉትን ቀናት እምብዛም
አያስባቸውም።

6 ከፀሓይ በታች ሌላ ክፉ ነገር አየሁ፤
እርሱም ለሰዎች እጅግ የሚከብድ ነው፤
2ሰው ልቡ የሚሻውን እንዳያጣ፣ እግዚአብሔር
ባለጠግነትን፣ ሀብትንና ክብርን ይሰጠ
ዋል፤ እግዚአብሔር ግን እንዲደሰትበት ሥል
ጣን አልሰጠውም፤ ይልቁን ባዕድ ይደሰት
በታል። ይህም ከንቱ፣ እጅግም ክፉ ነገር
ነው።
3አንድ ሰው መቶ ልጅ ሊኖረውና ብዙ
ዓመት ሊኖር ይችላል፤ ምንም ያህል ይኑር፣
በሀብቱ ደስ ካልተሰኘበትና በአግባብ ካል
ተቀበረ፣ ከእርሱ ይልቅ ጭንጋፍ ይሻላል
እላለሁ፤ 4ምክንያቱም በከንቱ ይመጣል፤
በጨለማም ይሄዳል፤ ስሙም በጨለማ
ተሸፍኖአል። 5ፀሓይን ባያይና ምንም ነገር

ባያውቅ እንኳ፣ እርሱ ከዚያ ሰው ይልቅ
ዕረፍት አለው፤ [6]ሁለት ጊዜ ሺህ ዓመት
ቢኖር ነገር ግን በሀብቱ ደስ ባይሰኝበት
ሁሉ ወደዚያ ስፍራ የሚሄድ አይደለምን?

[7]የሰው ጥረት ሁሉ ለአፉ ነው፤
ፍላጎቱ ግን ፈጽሞ አይረካም።
[8]ጠቢብ ከሞኝ ይልቅ ምን ብልጫ አለው?
ድኻስ በሌሎች ፊት እንዴት እንደሚኖር
በማወቁ፣
ትርፉ ምንድን ነው?
[9]በምኞት ከመቅበዝበዝ፣
በዐይን ማየት ይሻላል፤
ይህም ደግሞ ከንቱ፣
ነፋስንም እንደ መከተል ነው።

[10]አሁን ያለው ሁሉ አስቀድሞ ስም
የተሰጠው ነው፤
ሰው የሚሆነውም አስቀድሞ የታወቀ
ነው፤
ከራሱ ይልቅ ከሚበረታ ጋር፣
ማንም አይታገልም።
[11]ቃል በበዛ ቍጥር፤
ከንቱነት ይበዛል፤
ይህ ታዲያ ለሰው ምን ይጠቅማል?

[12]ሰው በሕይወት ሳለ፣ እንደ ጥላ በሚያ
ልፉት ጥቂትና ከንቱ በሆኑት ቀኖቹ፣
ለሰው መልካም የሆነውን የሚያውቅ ማን
ነው? እርሱ ከሄደ በኋላስ ከፀሓይ በታች
የሚሆነውን ማን ሊነግረው ይችላል?

## ጥበብ

7 መልካም ስም ከመልካም ሽቱ
ይበልጣል፤
ከልደትም ቀን የሞት ቀን ይሻላል።
[2]ወደ ግብዣ ቤት ከመሄድ፣
ወደ ሐዘን ቤት መሄድ ይሻላል፤
ሞት የሰው ሁሉ ፍጻሜ ነውና፤
ሕያው የሆነም ይህን ልብ ማለት
ይገባዋል።
[3]ሐዘን ከሣቅ ይሻላል፤
ያዘነ ፊት ለልብ መልካም ነውና።
[4]የጠቢባን ልብ በሐዘን ቤት ነው፤
የሞኞች ልብ ግን በደስታ ቤት ነው።
[5]የሞኞችን መዝሙር ከመስማት፣
የጠቢባንን ሰዎች ተግሣጽ መስማት
ይሻላል።
[6]የሰነፎች ሣቅ፣
ከድስት ሥር እንደሚንጣጣ የእሾኽ ማገዶ
ነው፤
ይህም ደግሞ ከንቱ ነው።

[7]ግፍ ጠቢብን ሞኝ ያደርጋል፤
ጒቦም ልብን ያበላሻል።

6፥6 መክ2፥14
6፥7 ምሳ27፥20
6፥8 መክ2፥15
6፥9 መክ1፥14
6፥10 መክ3፥15
6፥12 1ዜና29፥15፤ ኢዮ10፥20፤14፥2፤ 20፥8፤መዝ39፥6
7፥1 ኢዮ10፥18፤ ምሳ22፥1፤ማሕ1፥3
7፥2 ምሳ11፥19፤ መክ2፥14
7፥3 ምሳ 14፥13
7፥4 መክ2፥1፤ ኤር16፥8
7፥5 ምሳ13፥18፤ 15፥31-32
7፥6 መዝ58፥9፤ ምሳ14፥13
7፥7 ዘፀ18፥21፤ 23፥8
7፥8 ምሳ14፥29
7፥9 ምሳ14፥29፤ ማቴ5፥22
7፥10 መዝ77፥5
7፥11 መክ2፥13፤ 11፥7
7፥13 መክ1፥5፤ 2፥24
7፥14 ኢዮ1፥21፤ መክ2፥24
7፥15 ኢዮ7፥7፤ 21፥7፤መክ8፥12-14፤ኤር12፥1
7፥17 ኢዮ15፥32
7፥18 መክ 3፥14
7፥19 ምሳ8፥14፤ መክ2፥13
7፥20 2ዜና6፥36፤ ኢዮ4፥17፤መዝ14፥3፤ ምሳ20፥9፤ሮሜ3፥12
7፥21 ምሳ30፥10

[8]የአንድ ነገር ፍጻሜ ከጅማሬው ይሻላል፤
ትዕግሥተኛም ከትዕቢተኛ ይሻላል፤
[9]የሞኞች ቍጣ በዕቅፋቸው ውስጥ ስለ ሆነ፣
በመንፈስህ ለቍጣ አትቸኰል።

[10]አንተም፣ "ከእነዚህ ቀናት የቀድሞዎቹ
ለምን ተሻሉ?" አትበል፤
እንዲህ ያሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ
ጠቢብነት አይደለምና።

[11]ጥበብ እንደ ርስት መልካም ነገር ነው፤
ጠቃሚነቱም ፀሓይን ለሚያዩ ሰዎች
ነው።
[12]ገንዘብ ጥላ ከለላ እንደ ሆነ ሁሉ፣
ጥበብም ጥላ ከለላ ነው፤
የዕውቀት ብልጫዋ ግን፣
ጥበብ የባለቤቷን ሕይወት መጠበቋ
ነው።

[13]እግዚአብሔር ያደረገውን ተመልከት፤

እርሱ ያጣመመውን፣
ማን ሊያቃናው ይችላል?
[14]ጊዜው መልካም ሲሆን፣ ደስ ይበልህ፤
ጊዜው ክፉ ሲሆን ግን ይህን አስብ፤
እግዚአብሔር አንዱን እንዳደረገ፣
ሌላውንም አድርጎአል፤
ስለዚህ ሰው ስለ ወደ ፊት ሁኔታው፣
ምንም ሊያውቅ አይችልም።

[15]በዚህ ከንቱ በሆነው ሕይወቴ እነዚህን
ሁለቱን ነገሮች አይቻለሁ፤

ጻድቅ በጽድቁ ሲጠፋ፣
ኀጥእም በክፋቱ ዕድሜው ሲረዝም።
[16]እጅግ ጻድቅ፣
እጅግም ጠቢብ አትሁን፤
ራስህን ለምን ታጠፋለህ?
[17]እጅግ ክፉ አትሁን፤
ሞኝም አትሁን፤
ለምንስ ያለ ቀንህ ትሞታለህ?
[18]አንዱን ይዞ ሌላውንም አለመልቀቅ
መልካም ነው፤
እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው
ጽንፈኝነትን ያስወግዳል[ሀ]።

[19]በአንድ ከተማ ካሉ ዐሥር ገዦች ይልቅ፣
ጥበብ ጠቢቡን ሰው ኀያል
ታደርገዋለች።

[20]ትክክለኛውን ነገር የሚያደርግና ፈጽሞ
ኀጢአት የማይሠራ፣
ጻድቅ ሰው በምድር ላይ የለም።

[21]የሚነገረውን ቃል ሁሉ ለማዳመጥ
አትሞክር፤
አለበለዚያ አገልጋይህ ሲረግምህ ትሰማ

[ሀ]18 ወይም *ሁለቱንም ይከተላቸዋል*

ይሆናል፤
22ብዙ ጊዜ አንተ ራስህ፣
ሌሎችን እንደረገምህ ልብህ ያውቃልና
23እኔም ይህን ሁሉ በጥበብ ፈትኜ፣
“ጠቢብ ለመሆን ቈርጫለሁ” አልሁ፤
ይህ ግን ከእኔ የራቀ ነበር።
24ጥበብ ምንም ይሁን ምን፣
እጅግ ጥልቅና ሩቅ ነው፤
ማንስ ሊደርስበት ይችላል?
25ስለዚህ ጥበብንና የነገሮችን አሠራር
ለመመርመርና ለማጥናት፣
የክፋትን መጥፎነት፣
የሞኝነትንም እብደት ለማስተዋል፣
አእምሮዬን መለስሁ።
26ልቧ ወጥመድ፣
እጆቿም እግር ብረት የሆኑ፣
አሽክላ የሆነች፣
ከሞት የከፋችዋን ሴት አገኘሁ፤
እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ከእጇ ያመጠ
ልጣል፤
ኀጢአተኛውን ግን አጥምዳ ትይዘዋለች።
27ሰባኪው[ሰ] እንዲህ ይላል፤ “እነሆ፤ መርምሬ
ያገኘሁት ነገር ይህ ነው፤
“የነገሮችን ብልኀት መርምሮ ለማግኘት፣
አንዱን በአንዱ ላይ በመጨመር፣
28ገና በመመርመር ላይ ሳለሁ፣
ግን ያላገኘሁት፣
ከሺህ ወንዶች መካከል አንድ ቅን ሰው
አገኘሁ፣
በእነዚያ ሁሉ መካከል ግን አንዲት
ቅን ሴት አላገኘሁም።
29ይህን አንድ ነገር ብቻ አገኘሁ፤
እግዚአብሔር ሰውን ቅን አድርጎ
መሥራቱን፣
ሰዎች ግን ውስብስብ ዘዴ ቀየሱ።”

8 ነገሮችን መግለጽ የሚችል፣
እንደ ጠቢብ ያለ ሰው ማን ነው?
ጥበብ የሰውን ፊት ታበራለች፤
የከበደ ገጽታውንም ትለውጣለች።

## ንጉሥን ታዘዝ

2በእግዚአብሔር ፊት መሐላ ስለ ፈጸምህ፣
የንጉሥን ትእዛዝ አክብር እልሃለሁ። 3ከን
ጉሥ ፊት ተጣድፈህ አትውጣ፤ የወደደ
ውንም ማድረግ ስለሚችል ለጥፋት አትሰ
ለፍ። 4የንጉሥ ቃል በላይ ስለ ሆነ እርሱን፣
“ምን ታደርጋለህ?” ማን ሊለው ይችላል?
5እርሱን የሚታዘዝ ሁሉ አይጐዳም፤
ጥበበኛም ልብ ትክክለኛውን ጊዜና
ተገቢውን አሠራር ያውቃል።
6የሰው መከራ እጅግ ቢጫነውም፣

7፥23 መክ1፥17
7፥24 ኢዮ28፥12
7፥25 ኢዮ28፥3፤ መክ1፥17
7፥26 ዘፀ10፥7፤መሳ 14፥15፤ምሳ2፥16-19፤ 5፥3-5፤7፥23፤22፥14
7፥27 መክ1፥1
7፥28 1ነገ11፥3
8፥3 መክ10፥4
8፥4 አስ1፥19
8፥6 መክ3፥1
8፥10 መክ1፥11
8፥12 ዘፀ1፥20፤ ዘዳ12፥28፤መክ3፥14
8፥13 ዘዳ4፥40፤ ኢዮ5፥26፤መዝ 34፥12፤መክ3፥14፤ ኢሳ65፥20 ኢዮ21፥7፤መክ7፥15
8፥15 ዘፀ32፥6፤መዝ 42፥8፤መክ2፥1፥3
8፥16 መክ1፥13፥17
8፥17 ኢዮ28፥3 ፥23፤ሮሜ11፥33
9፥1 መክ10፥14

ለሁሉም ነገር ትክክለኛ ጊዜና ተገቢ
አሠራር አለው።
7ሰው የወደፊቱን ስለማያውቅ፣
ሊመጣ ያለውን ማን ሊነግረው ይችላል?
8ሰው ነፋስን መቈጣጠር አይችልም[ሸ]፤
በዕለተ ሞቱም ላይ ሥልጣን ያለው ማንም
የለም፤
በጦርነት ጊዜ ማንም ከግዴታ ነጻ
እንደማይሆን፣
ክፋትም የሚለማመዷትን
አትለቃቸውም።

9ከፀሓይ በታች የተሠራውን ሁሉ በአእ
ምሮዬ መርምሬ፣ ይህን ሁሉ አየሁ። ሰው
ሰውን ለመጕዳት ገዥ የሚሆንበት ጊዜ
አለ። 10እንዲሁም ወደ ቅዱሱ ስፍራ ይመ
ጡና ይሄዱ የነበሩት ክፉዎች ተቀብረው
አየሁ፤ ይህን ባደረጉበት ከተማም ይመሰ
ገኑ ነበር[ቀ]፤ ይህም ደግሞ ከንቱ ነው።
11በወንጀል ላይ ባፋጣኝ ፍርድ ካልተሰጠ፣
የሰዎች ልብ ክፉን በማድረግ ዕቅድ ይሞ
ላል። 12ኀጥእ መቶ ወንጀል ሠርቶ ዕድሜው
ቢረዝምም፣ እግዚአብሔርን የሚያከብሩ፣ ፈሪሃ
እግዚአብሔር ያላቸው ሰዎች መልካም
እንደሚ ሆንላቸው ዐውቃለሁ። 13ነገር ግን
ክፉዎች እግዚአብሔርን ስለማይፈሩ መልካም
አይሆን ላቸውም፤ ዕድሜያቸው እንደ
ጥላ አይረ ዝምም።
14በምድር ላይ የሚከሠት ሌላም ከንቱ
ነገር አለ፤ ጻድቃን ለክፉዎች የሚገባውን፣
ክፉ ሰዎችም ለጻድቃን የሚገባውን ይቀበ
ላሉ፤ ይህም ደግሞ ከንቱ ነገር ነው አልሁ።
15ለሰው፣ ከፀሓይ በታች ከመብላት፣ ከመጠ
ጣትና ከመደሰት ሌላ የተሻለ ነገር ስለ
ሌለ፣ በሕይወት ደስ መሰኘት መልካም ነው
አልሁ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ከፀሓይ በታች
በሰጠው የሕይወት ዘመኑ ሁሉ በሥራው
ደስታ ይኖረዋል።
16ጥበብን ለማወቅና ሌት ተቀን እንቅ
ልፍ የማያውቀውን በምድር ያለውን የሰውን
ድካም ለመገንዘብ በአእምሮዬ ስመረምር፣
17እግዚአብሔር ያደረገውን ሁሉ አየሁ። ከፀ
ሓይ በታች የሚደረገውን ማንም ሊያውቅ
አይችልም፤ ሰው ለመመርመር ብዙ ቢጥ
ርም፣ ትርጕሙን ማግኘት አይችልም፤ ጠቢ
ብም እንኳ ዐውቀዋለሁ ቢል፣ ፈጽሞ ሊገ
ነዘበው አይችልም።

## የሁሉም የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ

9 ስለዚህ ይህን ሁሉ በልቤ አስቤ እን
ዲህ አልሁ፤ ጻድቃንና ጠቢባን፣ የሚ

[ሰ]27 ወይም የጉባኤ መሪ
[ሸ]8 ወይም መንፈሱን ለማቆየት አይችልም

ሡሩትም ሥራ በእግዚአብሔር እጅ ነው፤
ነገር ግን ፍቅር ይሁን ወይም ጥላቻ የሚጠ
ብቀውን ማንም አያውቅም። 2ጻድቃንና
ኀጥአን፣ ደጎችና ክፉዎች[በ]፣ ንጹሓንና
ርኩሳን፣ መሥዋዕት የሚያቀርቡና የማያ
ቀርቡ የሁሉም የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ አንድ
ነው።

ለደጉ ሰው እንደ ሆነው ሁሉ፣
  ለኀጢአተኛውም እንዲሁ ነው፤
ለሚምሉት እንደ ሆነው ሁሉ፣
  መሐላን ለሚፈሩትም እንዲሁ ነው።

3ከፀሓይ በታች በሁሉም ላይ የሚሆነው
ክፉት ይህ ነው፤ የሁሉም የመጨረሻ ዕጣ
ፈንታ አንድ ነው። በዚህም ላይ የሰዎች
ልብ በክፉት የተሞላ ነው፤ በሕይወት እያ
ሉም በልባቸው ውስጥ እብደት አለ፤ በመ
ጨረሻም ወደ ሙታን ይወርዳሉ። 4በሕያዋን
መካከል ያለ ማንኛውም ሰው ተስፋ
አለው[ተ]፤ በሕይወት ያለ ውሻ ከሞተ አንበሳ
ይሻላልና!

5ሕያዋን እንደሚሞቱ ያውቃሉና፤
  ሙታን ግን ምንም አያውቁምና፤
መታሰቢያቸው ይረሳል፤
  ምንም ዋጋ የላቸውም።
6ፍቅራቸው፣ ጥላቻቸው፣
  ቅናታቸውም ከጠፋ ቈይቶአል፤
ከፀሓይ በታች በሚሆነው ነገር ሁሉ፣
  ፈጽሞ ዕጣ ፈንታ አይኖራቸውም።

7ሂድ፤ ምግብህን በደስታ ብላ፤ ወይንህንም
ልብህ ደስ ብሎት ጠጣ፤ ባደረግኸው ነገር
እግዚአብሔር ደስ ብሎታልና። 8ዘወትር ልብ
ስህ ነጭ ይሁን፤ ራስህንም ዘወትር በዘይት
ቅባ። 9እግዚአብሔር ከፀሓይ በታች በሰጠህ
በዚህ ትርጕም የለሽ የሕይወት ዘመን
ሁሉ፣ ከንቱ በሆኑትም ቀኖችህ ሁሉ ከም
ትወዳት ሚስትህ ጋር ደስ ይበልህ፤ በሕ
ይወትህና ከፀሓይ በታች በምትደክምበት
ነገር ሁሉ ይህ ዕድል ፈንታህ ነውና።
10እጅህ የሚያገኘውን ሥራ ሁሉ በሙሉ
ኀይልህ ሥራው፤ ልትሄድበት ባለው መቃ
ብር[ቸ] ውስጥ መሥራትም ሆነ ማቀድ፣ ዕው
ቀትም ሆነ ጥበብ የለምና።

11ሌላም ነገር ከፀሐይ በታች አየሁ፡

ሩጫ ለፈጣኖች፣
  ውጊያም ለኀያላን አይደለም፤
እንጀራ ለጥበበኞች፣
  ወይም ባለጠግነት ለብልሆች፣
ወይም ሞገስ ለዐዋቂዎች አይሆንም፤
  ጊዜና ዕድል ግን ሁሉን ይገናኛቸዋል።

12ደግሞም የራሱን ጊዜ የሚያውቅ ሰው
    የለም፤
ዓሦች በክፉ መረብ እንደሚያዙ፣
  ወይም ወፎች በወጥመድ
    እንደሚጠመዱ፣
ሰዎችም ሳያስቡት በሚመጣባቸው፣
  በክፉ ጊዜ ይጠመዳሉ።

## ጥበብ ከሞኝነት ይበልጣል

13እንዲሁም እጅግ ያስገረመኝን ይህን
የጥበብ ምሳሌ ከፀሓይ በታች አየሁ፡-
14ጥቂት ሰዎች የሚኖሩባት አንዲት ትንሽ
ከተማ ነበረች፤ አንድ ኀያል ንጉሥም መጣ
ባት፤ ከበባት፤ በላይዋም ትልቅ ምሽግ ሠራ
ባት። 15በዚያችም ከተማ ጥበበኛ የሆነ አንድ
ድኻ ሰው ይኖር ነበር፤ በጥበቡም ከተማ
ዋን አዳናት፤ ነገር ግን ያን ድኻ ማንም
አላስታወሰውም። 16ስለዚህ፣ “ጥበብ ከኀ
ይል ይበልጣል” አልሁ፤ ሆኖም የድኻው
ጥበብ ተንቆአል፤ ቃሉም አልተሰማም።

17ሞኞችን ከሚያስተዳድር ገዥ ጩኸት
    ይልቅ፣
  ጠቢብ በዝግታ የሚናገረው ቃል
    ይደመጣል።
18ጥበብ ከጦር መሣሪያ ይበልጣል፤
  ነገር ግን አንድ ኀጢአተኛ ብዙ መልካም
    ነገርን ያጠፋል።

10 የሞቱ ዝንቦች ሽቶን
    እንደሚያገሙ፣
  ትንሽ ሞኝነትም ጥበብንና ክብርን
    ያቃልላል።
2የጠቢብ ልብ ወደ ቀኝ፣
  የሞኝ ልብ ግን ወደ ግራ ያዘነብላል።
3ሞኝ በጐዳና ሲሄድ ማስተዋል
    ይጐድለዋል፤
  ጅል መሆኑንም ለማንም ይገልጻል።
4የገዥ ቍጣ በተነሣብህ ጊዜ፣
  ስፍራህን አትልቀቅ፤
  ትዕግሥት ታላቁን ጥፋት ጸጥ
    ያደርጋልና።

5ከፀሓይ በታች ያየሁት ክፉ ነገር አለ፤
  ይህም ከገዥ የሚወጣ ስሕተት ነው፤
6ሞኞች በብዙ የክብር ስፍራዎች ሲቀመጡ፣
  ሀብታሞች ግን በዝቅተኛ ስፍራ ሆነዋል።
7መሳፍንት እንደ ባሮች በእግራቸው ሲሄዱ፣
  ባሮች ፈረስ ላይ ተቀምጠው አይቻለሁ።

8ጕድጓድን የሚምስ ራሱ ይገባበታል፤

9፥2 ኢዮ9፥22፤ መክ2፥14
9፥3 ኢዮ9፥22፤ 21፥26፤መክ2፥14፤ ኤር11፥8፤13፥10፤ 16፥12፤17፥9
9፥5 ኢዮ14፥21፤ መዝ9፥6፤መክ1፥11
9፥6 ኢዮ21፥21
9፥7 ዘኍ6፥20፥መክ2፥24
9፥8 ራእ 3፥4
9፥9 ኢዮ31፥2፤ ምሳ5፥18
9፥10 ዘኍ16፥33፤ 1ሳሙ10፥7፤መዝ 6፥5፤መክ2፥24፤11፥6፤ ኢሳ38፥18
9፥11 ዘዳ8፥18፤ኢዮ 32፥13፤መክ2፥14፤ ኢሳ47፥10፤ኤር 9፥23፤አሞ2፥14-15
9፥12 መዝ73፥22፤ መሳ29፥6፤መክ2፥14
9፥13 2ሳሙ20፥22
9፥15 ዘፍ40፥14፤ መክ1፥11
9፥16 አስ6፥3
9፥18 መክ2፥13
10፥1 ምሳ13፥16፤ 18፥2
10፥3 ምሳ13፥16
10፥4 መክ8፥3፤ ምሳ16፥14
10፥6 ምሳ29፥2
10፥7 ምሳ19፥10
10፥8 አስ2፥23፤ መዝ9፥16፤57፥6፤አሞ 5፥19

[ቀ]10 አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆችና ሰብዓ ሊቃናት (አቍዊላ) እን ዲሁ ሲሆኑ አብዛኛዎቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን *ተረስተዋል* ይላሉ።
[በ]2 ሰብዓ ሊቃናት (አቍዊላ) ቨልጌትና ሱርስት እንዲሁ ሲሆኑ ዕብራይስጡ ግን ክፉዎች የሚለው የለም
[ተ]4 ወይም *ታዲያ የሚመረጠው ምንድነው? ለሕያዋን ሁሉ ተስፋ አለ*
[ቸ]10 በዕብራይስጥ *ሲኦል* ማለት ነው

ቅጥርንም የሚያፈርስ እባብ ይነድፈዋል።
9 ድንጋይ የሚፈነቅል ይጐዳበታል፤
ግንድንም የሚፈልጥ አደጋ ላይ መውደቁ
አይቀርም።

10 መጥረቢያ ቢደንዝ፣
ጫፉም ባይሳል፣
ብዙ ጕልበት ይጨርሳል፤
ብልኀት ግን ለውጤት ያበቃል።

11 እባብ በድግምት ከመፍዘዙ በፊት ቢ
ነድፍ፣
ለደጋሚው ምንም አይጠቅመውም።

12 ከጠቢብ አፍ የሚወጣ ቃል ባለ ሞገስ
ነው፤
ሞኝ ግን በገዛ ከንፈሩ ይጠፋል፤
13 ቃሉ በመጀመሪያ ሞኝነት ነው፤
በመጨረሻም ደግሞ ክፉ እብደት ነው፤
14 ሞኙም ቃልን ያበዛል።

የሚመጣውን የሚያውቅ የለም፤
ከእርሱ በኋላ የሚሆነውንስ ማን ሊነግረው
ይችላል?

15 የሞኝ ሥራ ራሱን ያደክመዋል፤
ወደ ከተማ የሚወስደውንም መንገድ
አያውቅም።

16 አንቺ፣ ንጉሥሽ ልጅ[ጎ] የሆነ፣
መሳፍንትሽም በጠዋት ግብዣ
የሚያደርጉ ምድር ሆይ፤ ወዮልሽ!
17 አንቺ ንጉሥሽ ከተከበረው ዘር የሆነ፣
ለመስከር ሳይሆን ለብርታት፣
በተገቢው ጊዜ የሚበሉ መሳፍንት
ያሉሽ
ምድር ሆይ፤ የተባረክሽ ነሽ፤

18 ሰው ሰነፍ ከሆነ ጣራው ይዘብጣል፤
እጆቹም ካልሠሩ ቤቱ ያፈሳል።
19 ግብዣ ለሣቅ ያዘጋጃል፤
ወይንም ሕይወትን ያስደስታል፤
ገንዘብም ካለ ሁሉ ነገር አለ።

20 በሐሳብህም እንኳ ንጉሥን አትንቀፍ፤
በመኝታ ክፍልህም ባለጠጋን
አትርገም፤
የሰማይ ወፍ ቃልህን ልትወስድ፣
የምትበረዋም ወፍ የምትለውን
ልታደርስ ትችላለችና።

## እንጀራ በውሃ ላይ

11 እንጀራህን በውሃ ላይ ጣል፤
ከብዙ ቀን በኋላ መልሰህ
ታገኘዋለህና።
2 ሀብትህን ሰባት ቦታ፣ እንዲያውም
ስምንት ቦታ ከፍለህ አስቀምጥ፤
በምድሪቱ ላይ የሚመጣውን ጥፋት
አታውቅምና።

10፥9 ምሳ26፥27
10፥11 መዝ58፥5፤ ኢሳ3፥3
10፥12 ምሳ10፥6፡32፤14፥3፤15፥2፤18፥7
10፥14 መክ5፥3፤ 9፥1
10፥16 ኢሳ3፥4-5፡12
10፥17 ዘዳ14፥26፤ 1ሳሙ25፥36፤ ምሳ31፥4
10፥18 ምሳ20፥4፤ 24፥30-34
10፥19 ዘፍ14፥18፤ መሳ9፥13
10፥20 ዘፀ22፥28
11፥1 ቈ6፤ዘዳ 24፥19፤ኢሳ32፥20 ፤ሆሴ10፥12
11፥5 ዮሐ3፥8-10፤ መዝ139፥14-16፤
11፥6 መክ9፥10
11፥7 መክ7፥11
11፥8 መክ12፥1
11፥9 ኢዮ19፥29፤ መክ2፥24፤3፥17
11፥10 መዝ94፥19፤ መክ2፥24
12፥1 2ሳሙ19፥35፤ መክ11፥8
12፥4 ኤር25፥10

3 ደመናት ውሃ ካዘሉ፣
በምድር ላይ ዝናብን ያዘንባሉ፤
ዛፍ ወደ ደቡብም ሆነ ወደ ሰሜን ቢወድቅ፣
በወደቀበት ቦታ በዚያ ይጋደማል።
4 ነፋስን የሚጠባበቅ አይዘራም፤
ደመናትንም የሚያይ አያጭድም።

5 የነፋስን መንገድ እንደማታውቅ፣
ሕይወት ወይም መንፈስ በእናት ማሕፀን
ውስጥ ወደሚገኘው አካል እንዴት
እንደሚገባም[1] እንደማታውቅ ሁሉ፣
ሁሉን ሠሪ የሆነውን፣ የእግዚአብሔርን ሥራ
ማስተዋል አትችልም።

6 ጠዋት ላይ ዘርህን ዝራ፤
ማታም ላይ እጅህ ሥራ አይፍታ፤
ይህ ወይም ያ፣
ወይም ሁለቱ መልካም ይሁኑ፣
የቱ እንደሚያፈራ አታውቅምና።

## ወጣት ሳለህ ፈጣሪህን አስብ

7 ብርሃን መልካም ነው፤
ፀሓይንም ማየት ለዐይን ደስ ያሰኛል።
8 ሰው ምንም ያህል ብዙ ዓመት ቢኖር፣
በእነዚህ ሁሉ ይደሰት፤
ነገር ግን ጨለማዎቹንም ቀናት ያስብ፤
እነርሱ ይበዛሉና፤
የሚመጣውም ነገር ሁሉ ከንቱ ነው።

9 አንተ ወጣት በወጣትነትህ ጊዜ ደስ ይበልህ፤
በወጣትነትህም ዘመን ልብህ ደስ ያሰኝህ፤
የልብህን መንገድ፣
ዐይንህ የሚያየውንም ሁሉ ተከተል።
ነገር ግን ስለ እነዚህ ነገሮች ሁሉ፣
እግዚአብሔር ወደ ፍርድ እንደሚያመጣህ
ዕወቅ።
10 ስለዚህ ጭንቀትን ከልብህ አርቅ፤
ክፉ ነገርንም ከሰውነትህ አስወግድ፤
ወጣትነትና ጕብዝና ከንቱ ናቸውና።

12 የጭንቀት ጊዜ ሳይመጣ፣
"ደስ አያሰኙኝም"
የምትላቸው ዓመታት ሳይደርሱ፣
በወጣትነትህ ጊዜ፣
ፈጣሪህን አስብ።
2 ፀሓይና ብርሃን፣
ጨረቃና ከዋክብት ሳይጨልሙ፣
ደመናትም ከዝናብ በኋላ ሳይመለሱ፣
3 ቤት ጠባቂዎች ሲርዱ፣
ብርቱዎች ሲጕብጡ፣
ጥቂት በመሆናቸው ፈጪታዎች ሲያቆሙ፣
በመስኮት የሚያዩትም ሲፈዙ፣
4 ወደ አደባባይ የሚያወጡ በሮች ሲዘጉ፣
ወፍጮ ሚልጦ ድምፁ ሲላሽ፣

[ጎ]16 ወይም አሽከር

ሰው በወፍ ድምፅ ሲነሣ፣
  ዝማሬው ሁሉ ሲዳከም፤
5ዳገት መውጣት ሲያርድ፣
  መንገድም ሲያስፈራ፣
የለውዝ ዛፍ ሲያብብ፣
  አንበጣም ራሱን ሲጐትት፣
ፍላጎት ሲጠፋ፤
  በዚያም ጊዜ ሰው ወደ ዘላለማዊ ቤቱ
    ይሄዳል፤
  አልቃሾችም በአደባባዮች ይዞራሉ።

6የብር ሰንሰለት ሳይበጠስ፣
  የወርቅ ሳሕንም ሳይሰበር፣
የውሃ መቅጃው በምንጩ አጠገብ
    ሳይከሰከስ፣
  ወይም መንኰራኵሩ በውሃ ጒድጓድ
    ላይ ሳይሰበር፣
7ዐፈር ወደ መጣበት መሬት ሳይመለስ፣
  መንፈስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር
    ሳይመለስ፣
  ፈጣሪህን አስብ።

8ሰባኪው[ኘ] "ከንቱ! ከንቱ!
  ሁሉም ነገር ከንቱ ነው!" ይላል።

## የነገሩ ፍጻሜ

9ሰባኪው ጥበበኛ ብቻ አልነበረም፤ ነገር
ግን ለሕዝቡ ዕውቀትንም ያስተምር ነበር።
እርሱም በጥልቅ አሰበ፤ ተመራመረም፤
ብዙ ምሳሌዎችንም በሥርዐት አዘጋጀ።
10ሰባኪው ትክክለኛውን ቃል ለማግኘት ተመ
ራመረ፤ የጻፈውም ቅንና እውነት ነበር።
11የጠቢባን ቃላት እንደ ሹል የከብት
መንጃ ናቸው፤ የተሰበሰቡ አባባሎቹም እጅግ
ተቀብቅበው እንደ ገቡ ችንካሮች ሲሆኑ፣
ከአንድ እረኛ የተሰጡ ናቸው። 12ልጄ
ሆይ፤ ከዚህ ሁሉ በላይ በማንኛውም
ነገር ተጠንቀቅ፤ አንዳችም አትጨምር።
ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ማብቂያ የለ
ውም፤ ብዙ ማጥናትም ሰውነትን ያደክማል።

13እነሆ፤ ሁሉ ነገር ከተሰማ ዘንድ፤
  የነገሩ ሁሉ ድምዳሜ ይህ ነው፤
እግዚአብሔርን ፍራ፤ ትእዛዛቱንም ጠብቅ፤
  ይህ የሰው ሁለንተናዊ ተግባሩ ነውና።
14መልካምም ይሁን ክፉ፣
  ስውር የሆነውን ነገር ሁሉ አንድ
    ሳይቀር፣
  ማንኛውንም ሥራ እግዚአብሔር ወደ
    ፍርድ ያመጣዋልና።

12፥5 ኢዮ10፥21፤ ኤር9፥17፤አሞ5፥16
12፥7 ዘፍ2፥7፤ ኢዮ20፥8፤መዝ 146፥4፤መክ3፥21፤
12፥8 መክ1፥1፡2
12፥9 1ነገ4፥32
12፥10 ምሳ22፥20-21
12፥11 ዕዝ9፥8፤ኢዮ 6፥25
12፥12 መክ1፥18
12፥13 ዘዐ20፥20፤ ዘዳ4፥2፡6፤1ሳሙ12፥24 ፤ኢዮ23፥15፤37፥24
12፥14 ኢዮ19፥29፤ 34፥21፤መዝ19፥12፤ መክ3፥17፤ኤር16፥17 ፤23፥24

[ነ]5 *ወይም አካል በእናት ማሕፀን ውስጥ እንዴት እንደሚሠራ እንደማታውቅ ሁሉ*
[ኘ]8 *ወይም የጉባኤ መሪ* እንዲሁም በቍ9 እና 10

# ማሕልየ መሓልይ

1 ከመዝሙር ሁሉ የሚበልጥ የሰሎሞን
መዝሙር።

### ሙሽራዪቱ

2 በከንፈሩ መሳም ይሳመኝ
ፍቅርህ ከወይን ጠጅ ይልቅ ደስ
ያሰኛልና።
3 የሽቱህ መዐዛ ደስ ያሰኛል፤
ስምህ እንደሚፈስ ሽቱ ነው፤
ታዲያ ቈነጃጅት ቢወዱህ ምን
ያስደንቃል
4 ይዘኸኝ ሂድ፤ እንፍጠን፤
ንጉሡ ወደ ዕልፍኞቹ አምጥቶኛል።

### ባልንጀሮቿ

በአንተ[ሀ] ደስ ይለኛል፤ ሐሤትም
እናደርጋለን፤
ከወይን ጠጅ ይልቅ ፍቅርህን
እንወድሳለን።

### ሙሽራዪቱ

አንተን እንደዚህ ማፍቀራቸው
ትክክል ነው።
5 እናንት የኢየሩሳሌም ቈነጃጅት ሆይ፤
እኔ ጥቍር ነኝ፤ ይሁን እንጂ
ውብ ነኝ፤
ጥቍሬቴ እንደ ቄዳር ድንኳኖች፣
እንደ ሰሎሞን[ለ] ቤተ መንግሥት
መጋረጃዎችም ነው።

6 ጥቍር ስለ ሆንሁ ትኵር
ብላችሁ አትዩኝ፤
መልኬን ያጠቈረው ፀሓይ ነውና፤
የእናቴ ልጆች ወንድሞቼ ተቈጡኝ፤
የወይን ተክል ቦታዎችም
ጠባቂ አደረጉኝ፤
የራሴን የወይን ተክል ቦታ ተውሁት።
7 ውዴ ሆይ፤ መንጋህን የት
እንደምታሰማራ፣
በቀትርም የት እንደምትመስጋቸው
እባክህ ንገረኝ፤
በወዳጆችህ መንጎች ኋላ፣
ፊቷን ሸፍና እንደምትቅበዘበዝ
ሴት ለምን ልሁን?

### ባልንጀሮቿ

8 አንቺ ከሴቶች ሁሉ ይበልጥ የተዋብሽ
ሆይ፤ የማታውቂ ከሆነ፣
የበጎቹን ዱካ ተከተዪ፤
የፍየል ግልገሎችሽንም፣
በእረኞቹ ድንኳን አጠገብ አሳማሪ።

### ሙሽራው

9 ውዴ ሆይ፤ የፈርዖንን ሠረገሎች ከሚስቡ
ፈረሶች መካከል፣
በአንዲቱ ባዝራ መሰልሁሽ።
10 ጒንጮችሽ በጒትቻ፣
ዐንገትሽም በዕንቍ ሐብል አጊጠዋል።
11 እኛም ባለ ብር ፈርጥ፣
የወርቅ ጒትቻ እናሠራልሻለን።

### ሙሽራዪቱ

12 ንጉሡ ማእዱ ላይ ሳለ፣
ሽቱዬ መዐዛውን ናኘው።
13 ውዴ ለእኔ በጡቶቼ መካከል እንዳረፈ፣
በምቋጠሪያ እንዳለ ከርቤ ነው።
14 ውዴ ለእኔ ከዓይንጋዲ የወይን ተክል
ቦታ፣
እንደ መጣ የሂና አበባ ዕቅፍ ነው።

### ሙሽራው

15 ውዴ ሆይ፤ እንዴት ውብ ነሽ
እንዴትስ ያለሽ ቈንጆ ነሽ
ዐይኖችሽም እንደ ርግብ
ዐይኖች ናቸው።

### ሙሽራዪቱ

16 አንተ ውዴ ሆይ፤ እንዴት ውብ ነህ
እንዴትስ ታምራለህ
ዐልጋችንም እንደ ለምለም ሣር ነው።

### ሙሽራው

17 የቤታችን ተሻካሚዎች ዝግባዎች፣
የጣራችን ማዋቀሪያዎችም ጥዶች
ናቸው።

### ሙሽራይቱ

2 እኔ የሳሮን ጽጌረዳ፣
የሸለቆም አበባ[ሐ] ነኝ።

### ሙሽራው

2 በእሾኽ መካከል እንዳለ ውብ አበባ፣
ውዴም በቈነጃጅት መካከል እንዲሁ
ናት።

### ሙሽራዪቱ

3 በዱር ዛፎች መካከል እንዳለ እንኰይ፣
ውዴም በጐልማሶች መካከል እንዲሁ

[ሀ]4 በዕብራይስጥ ነጠላ ተባዕታይ ነው።
[ለ]5 ወይም ሳልማ
[ሐ]1 ጸደይ ከመሆኑ ቀደም ብሎ የሚቀበል ቢጫ፣ሐምራዊና ነጭ ቀለም ያሉት የአበባ ተክል ዝርያ ሊሆን ይችላል፡

1፥1 1ነገ4፣32፤ መዝ45 ርዕስ
1፥2 ቍ4፤ ዘፍ 14፥18፤ መሳ9፥13፤ማሕ 4፥10፤8፥6
1፥3 አስ2፥12፤ መዝ45፥8፥14፤ መክ7፥1
1፥4 ቍ2፤ መዝ45፥15፤ ማሕ2፥3
1፥5 ዘፍ25፥13፤ ማሕ2፥14፤4፥3፤ 5፥16
1፥6 ማሕ2፥15፤ 7፥12፤8፥12
1፥7 ዘፍ24፥65፤ ኢሳ13፥20
1፥8 ማሕ5፥9፤6፥1
1፥9 2ዜና1፥17
1፥10 ማሕ5፥13፤ ኢሳ61፥10
1፥12 ማሕ4፥11-14
1፥13ዘፍ37፥25
1፥14 ቍ16፤ 1ሳሙ23፥29፤ 2ዜና20፥2፤ማሕ 2፥3፥17፤4፥13፤5፥8
1፥15 መዝ74፥19፤ ማሕ2፥14፤ 4፥1፥7፤5፥2፥12፤6፥9፤7፥6፤ ኤር48፥28
1፥16 ቍ14
1፥17 1ነገ 6፥9
2፥1 1ዜና27፥29፤ ማሕ5፥13፤ ኢሳ35፥1፤ሆሴ14፥5
2፥3 ማሕ1፥4፡ 14፤4፥16

ነው፤
በጥላው ሥር መቀመጥ ደስ ያሰኛል፤
የፍሬውም ጣፋጭነት ያረካኛል።
4ወደ ግብዣው አዳራሽ ወሰደኝ፤
በእኔ ላይ ያለው ዐላማው
ፍቅር ነው።
5በዘቢብ አበረታቱኝ፤
በእንኰይም አስደስቱኝ፤
በፍቅሩ ተይዤ ታምሜአለሁና።
6ግራ እጁን ተንተርሻለሁ፤
ቀኝ እጁም ዐቅፎኛል።
7እናንት የኢየሩሳሌም ቈነጃጅት፣
ራሱ እስኪፈልግ ድረስ፣
ፍቅርን እንዳታስነሡት ወይም
እንዳትቀሰቅሱት፣
በሚዳቋና በሜዳ ዋልያ
አማጥናችኋለሁ።
8እነሆ፤ የውዴ ድምፅ
በተራሮች ላይ እየዘለለ፣
በኰረብቶችም ላይ እየተወረወረ፣
ሲመጣ ይሰማኛል።
9ውዴ ሚዳቋ ወይም የዋልያ ግልገል
ይመስላል፤
እነሆ፤ ከቤታችን ግድግዳ ኋላ ቆሞአል፤
በመስኮት ትክ ብሎ ወደ ውስጥ ያያል፤
በፍርግርጉም እያሾለከ ይመለከታል።
10ውዴም እንዲህ አለኝ፤
"ፍቅሬ ሆይ፤ ተነሺ፤
አንቺ የእኔ ቈንጆ፤ ከእኔ ጋር ነዪ።
11እነሆ! ክረምቱ ዐለፈ፤
ዝናሙም አባርቶ አበቃ፤
12አበቦች በምድር ላይ ታዩ፤
የዝማሬ ወቅት ወጥቶአል፤
የርግቦች ድምፅም፣
በምድራችን ተሰማ።
13በለስ ፍሬዋን አፈራች፤
ያበቡ ወይኖችም መዐዛቸውን ሰጡ፤
ፍቅሬ ሆይ፤ ተነሺና ነዪ፤
አንቺ የእኔ ቈንጆ፤ ከእኔ ጋር ነዪ።"

**ሙሽራው**

14አንቺ በገደል ዐለት ንቃቃት፣
በተራሮችም ባሉ መደበቂያ ስፍራዎች
ውስጥ ያለሽ ርግቤ ሆይ!
ፊትሽን አሳይኝ፤
ድምፅሽንም አሰሚኝ፤
ድምፅሽ ጣፋጭ፣
መልክሽም ውብ ነውና።
15የወይን ተክሉን ቦታ፣
በማበብ ላይ ያለውን የወይን ተክል
ቦታችንን፣
የሚያጠፉትን ቀበሮዎች፣
እነዚያን ትንንሽ ቀበሮዎች አጥምዳችሁ

2፥4 ዘኍ1፥52፤ አስ1፥11
2፥5 ማሕ5፥8፤7፥8
2፥6 ምሕ8፥3
2፥7 ማሕ3፥5፤ 5፥8፤8፥4
2፥8 ቍ17፤ማሕ 8፥14
2፥9 ቍ17፤ 2ሳሙ2፥18፤ማሕ8፥14
2፥13 ማሕ7፥12፤ ኢሳ28፥4፤ኤር24፥2፤ ሆሴ9፥10፤ሚክ7፥1፤ ናሆ3፥12
2፥14 ዘፍ8፥8፤ ማሕ1፥5፥15
2፥15 መሳ15፥4፤ ማሕ1፥6፤7፥12
2፥16 ማሕ4፥5፤ 6፥3፤7፥10
2፥17 ቍ8፥9፤ ማሕ1፥4፤4፥6
3፥1 ማሕ5፥6
3፥3 ማሕ5፥7
3፥4 ማሕ6፥9፤ 8፥2፥5
3፥5 ማሕ2፥7፤8፥4
3፥6 ዘፀ30፥34፤ ማሕ 4፥6፥14፤8፥5
3፥7 1ሳሙ8፥11
3፥8 ኢዩ15፥22፤ መዝ91፥5

ያዙልን።

**ሙሽራዪቱ**

16ውዴ የእኔ ነው፤ እኔም የእርሱ ነኝ፣
እርሱ መንጋውን በውብ አበቦች
መካከል ያሰማራል።
17ጎሕ ከመቅደዱ በፊት፣
ጥላውም ሳይሸሽ፣
ውዴ ሆይ፤ ተመለስ፣
ሚዳቋን ምሰል፤
ወይም በወጣ ገባ ኰረብቶች[መ]
እንዳለው የዋልያ ግልገል ሁን።

3 ሌሊቱን ሙሉ በአልጋዬ ላይ ሆኜ፣
ውዴን ተመኘሁ፤
ተመኘሁት፤ ነገር ግን አላገኘሁትም።
2ተነሥቼ ወደ ከተማዪቱ እወጣለሁ፤
በዋና ዋና መንገዶችና በአደባባዮች
እዘዋወራለሁ፤
ውዴንም እፈልገዋለሁ፤
ስለዚህም ፈለግሁት፤ ነገር ግን
አላገኘሁትም።
3በከተማዪቱ ውስጥ ሲዘዋወሩ፣
የከተማዪቱ ጠባቂዎች አገኙኝ፤
እኔም፣ "ውዴን አይታችኋል?"
አልኋቸው።
4ከእነርሱ ጥቂት ዕልፍ እንዳልሁ፣
ውዴን አገኘሁት፤
ያዝሁት፤
ወደ እናቴ ቤት እስካመጣው፣
በማሕፀን ወደ ተሸከመችኝም ዕልፍኝ
እስካገባው ድረስ አልለቀውም።
5እናንት የኢየሩሳሌም ቈነጃጅት፤
ራሱ እስኪፈልግ ድረስ፣
ፍቅርን እንዳታስነሡት ወይም
እንዳትቀሰቅሱት፣
በሚዳቋና በሜዳ ዋልያ
አማጥናችኋለሁ።
6ከከርቤና ከዕጣን፣
ከነጋዴም ቅመማ ቅመም ሁሉ
በተዘጋጀ ሽቱ፣
መዐዛዋ የሚያውድ፣
እንደ ጢስ ዐምድ ከምድረ በዳ የም
ትዋጣው ይህች ማን ናት?
7እነሆ፤ የሰሎሞን ሠረገላ
በታዋቂዎቹ የእስራኤል መኳንንት፣
ሥልሳ ጦረኞች ታጅባለች፤
8ሁሉም ሰይፍ የታጠቁ፣
ሁሉም በጦርነት የተፈተኑ ናቸው፤
የሌሊት አደጋን ለመከላከልም፣
እያንዳንዳቸው ሰይፋቸውን በወገባቸው
ታጥቀዋል።
9ንጉሥ ሰሎሞን የራሱን ሠረገላ ሠራ፤

[መ]17 ወይም *የቤጠር ኰረብቶች*

የሠራውም ከሊባኖስ በመጣ ዕንጨት
ነው።
[10]ምሰሶዎቹን ከብር፣
መደገፊያውንም ከወርቅ ሠራ፤
መቀመጫውም በሐምራዊ ሐር የተሸፈነ
ነው፤
ውስጡም በኢየሩሳሌም ቈነጃጅት፣
አምሮ የተለበጠ ነው።[ሠ]
[11]እናንት የጽዮን ቈነጃጅት ውጡ፤
ንጉሥ ሰሎሞን አክሊሉን ደፍቶ እዩት፤
ዘውዱም ልቡ ሐሤት ባደረገባት፣
በዚያች በሰርጉ ዕለት፣
እናቱ የደፋችለት ነው።

**ሙሽራው**

4 ውዴ ሆይ፤ እንዴት ውብ ነሽ!
እንዴትስ ያለሽ ቈንጆ ነሽ
ከመሸፈኛሽ ውስጥ ያሉት ዐይኖችሽ
እንደ ርግብ ዐይኖች ናቸው፤
ጠጕርሽም ከገለዓድ ተራራ
እንደሚወርድ፣
የፍየል መንጋ ነው።
[2]ጥርሶችሽ ወዲያው ተሸልተው፣
ከመታጠቢያ እንደ ወጡ የበግ መንጋ
ናቸው፤
ሁሉም መንታ መንታ የወለዱ፣
ከመካከላቸውም መካን የሌለባቸው
ናቸው።
[3]ከንፈሮችሽ ቀይ የሐር ፈትል ይመስላሉ፤
አፍሽም ውብ ነው፤
ከመሸፈኛሽ ውስጥ ያሉት ጕንጮችሽ፣
ለሁለት የተከፈለ ሮማን ይመስላሉ።
[4]ዐንገትሽ አምሮ የተሠራውን፣[ረ]
በላዩም የጦረኞች ጋሻዎች ሁሉ
ያሉበትን፣
ሺህ ጋሻዎች የተንጠለጠሉበትን፣
የዳዊትን የመጠበቂያ ማማ ይመስላል።
[5]ሁለቱ ጡቶችሽ መንታ ሆነው
የተወለዱ፣
በውብ አበቦች መካከልም የተሰማሩ፣
ሁለት የሚዳቋ ግልገሎችን ይመስላሉ።
[6]ጎሕ ከመቀደዱ በፊት፣
ጥላውም ሳይሸሽ፣
ወደ ከርቤ ተራራ፣
ወደ ዕጣኑም ኰረብታ እወጣለሁ።
[7]ውዴ ሆይ፤ ሁለንተናሽ ውብ ነው፤
እንከንም አይወጣልሽም።
[8]ሙሽራዬ ሆይ፤ ከሊባኖስ አብረሽኝ ነዪ፤
አዎን ከሊባኖስ አብረሽኝ ነዪ፤
ከአንበሶች ዋሻ፣
ከነብሮች ተራራ፣
ከኤርሞን ራስ፣ ከሳኔር ጫፍ፣
ከአማና ዐናት ውረጂ።

3፥11 ኢሳ3፥16፤ 4፥4፤32፥9-13፤ 54፥5፤62፥5፤ ኤር3፥14
4፥1 ዘፍ24፥65፤ 37፥24፤ዘኍ32፥1፤ ማሕ1፥15፤6፥5፤ ኤር22፥6፤ሚክ7፥14
4፥2 ማሕ6፥6
4፥3 ማሕ1፥5፤ 5፥16፤6፥7
4፥4 መዝ144፥12፤ ሕዝ27፥10
4፥5 ምሳ5፥19፤ ማሕ2፥16፤7፥3
4፥6 ማሕ2፥17፤3፥6
4፥7 ማሕ1፥15፤5፥2
4፥8 ቀኍ9፡12፤ ዘዳ3፥9፤1ዜና5፥23፤ ማሕ5፥1
4፥9 ቀኍ8፤ ዘፍ41፥42፤መዝ73፥6
4፥10 ቀኍ16፤ መሳ9፥13፤መዝ45፥8፤ ማሕ1፥2፤7፥6፤ ኢሳ57፥9
4፥11 መዝ19፥10፤ ማሕ5፥1፤ ሆሴ14፥6 144፥12 ቀኍ8፡16፤ ምሳ5፥15-18፤ ማሕ5፥1፤6፥2፤ ኢሳ5፥7
4፥13 ማሕ1፥14፤ 7፥12
4፥14 ዘፀ30፥23፤ ዘኍ24፥6፤ ማሕ1፥12፤3፥6
4፥15 ምሳ5፥18፤ አሳ27፥2፤58፥11፤ ኤር31፥12
4፥16 ቀኍ10፡12፤ ማሕ2፥3፤7፥13
5፥1 ማሕ4፥8፡11፡ 12፤ኢሳ55፥1፤ ኢል3፥18

[9]እኅቴ ሙሽራዬ፣ ልቤን ሰርቀሽዋል፤
በአንድ አፍታ እይታሽ፣
ከሐብልሽም በአንዱ ዕንቍ፣
ልቤን ሰርቀሽዋል።
[10]እኅቴ ሙሽራዬ፣ ፍቅርሽ እንዴት ደስ
ያሰኛል!
ፍቅርሽ ከወይን ጠጅ ይልቅ ምንኛ
የሚያረካ ነው፤
የሽቱሽም መዐዛ ከቅመም ሁሉ
ይልቅ የቱን ያህል ይበልጥ!
[11]ሙሽራዬ ሆይ፤ ከንፈሮችሽ የማር ወለላ
ያንጠባጥባሉ፤
ከአንደበትሽም ወተትና ማር
ይፈልቃል፤
የልብስሽም መዐዛ እንደ ሊባኖስ ሽታ
ነው።
[12]እኅቴ ሙሽራዬ፤ የታጠረ የአትክልት
ቦታ፣
ዙሪያውን የተከበበ ምንጭ፣ የታተመም
ፏፏቴ ነሽ።

[13]ተክልሽ ሮማን፣
ምርጥ ፍሬዎች፣
ሄናና ናርዶስ ያሉበት ነው።
[14]እንዲሁም ናርዶስና ቀጋ፣
ጠጅ ሣርና ቀረፋ፣
የተለያዩ የዕጣን ዛፎች፣
ከርቤና እሬት፣
ምርጥ ቅመሞች ሁሉ አሉበት።
[15]አንቺ[ሰ] የአትክልት ቦታ ፏፏቴ፣
ከሊባኖስ የሚወርድ፣
የፈሳሽ ውሃ ጕድጓድ ነሽ።

**ሙሽራዪቱ**

[16]የሰሜን ነፋስ ሆይ፤ ንቃ፤
የደቡብም ነፋስ ሆይ፤ ና!
መዐዛው ያውድ ዘንድ፣
በአትክልት ቦታዬ ላይ ንፈስ፤
ውዴ ወደ አትክልት ቦታው ይግባ፤
ምርጥ ፍሬዎቹንም ይብላ።

**ሙሽራው**

5 እኅቴ ሙሽራዬ፣ ወደ አትክልት
ቦታዬ መጥቻለሁ፤
ከርቤዬን ከቅመሜ ጋር ሰብስቤአለሁ፤
የማር እንጀራዬን ከነወለላው በልቻለሁ፤
ወይኔንና ወተቴንም ጠጥቻለሁ።

**ባልንጀሮቿ**

ወዳጆች ሆይ፤ ብሉ፤ ጠጡ፤
እናንት ፍቅረኞች ሆይ፤ እስክትረኩ

[ሠ]10 ወይም *የተለበጠውም ውስጥ፣ ከኢየሩሳሌም ቈነጃጅት የሆነ የፍቅር ስጦታ*
[ረ]4 በዕብራይስጥ የዚህ ቃል ትርጕም አይታወቅም
[ሰ]15 ወይም እኔ *ሙሽራዪቱ የተናገረችው*

ጠጡ።

### ሙሽራዪቱ

[2]እኔ ተኝቻለሁ፤ ልቤ ግን ነቅቶአል፤
ስሙ! ውዴ በር ያንኳኳል፤ እንዲህ
ይላል፤
“እኅቴ ወዳጄ፣ ርግቤ፣
አንቺ እንከን የሌለብሽ፤ ክፈቺልኝ፤
ራሴ በጤዛ፣
ጠጕሬም በሌሊቱ ርጥበት
ረስርሶአል።”
[3]ቀሚሴን አውልቄአለሁ፤
ታዲያ እንዴት እንደ ገና ልልበስ?
እግሬን ታጥቤአልሁ፤
እንዴት እንደ ገና ላቈሽሸው?
[4]ውዴ እጁን በበሩ ቀዳዳ አሾለከ፤
ልቤም ስለ እርሱ ይታወክ ጀመር።
[5]ለውዴ ልከፍትለት ተነሣሁ፤
በከርቤ ነጠብጣብ የራሱት እጆቼ፣
በከርቤም ፈሳሽ የተነከሩት ጣቶቼ፣
የመወርወሪያውን እጀታ ያዙ።
[6]ለውዴ ከፈትሁለት፤
ውዴ ግን አልነበረም፤ ሄዶአል፤
በመሄዱም ልቤ ደነገጠ፤[ሽ]
ፈለግሁት፤ ነገር ግን አላገኘሁትም፤
ጠራሁት፤ ነገር ግን አልመለሰልኝም።
[7]የከተማዪቱም ጠባቂዎች፣
በከተማዪቱ ውስጥ ሲዘዋወሩ
አገኙኝ፤
እነዚህ የቅጥሩ ጠባቂዎች፣
ደበደቡኝ፤ አቈሰሉኝ፤
ልብሴንም ገፈፉኝ።
[8]እናንት የኢየሩሳሌም ቈነጃጅት ሆይ፤
አማጥናችኋለሁ፤
ውዴን ካገኛችሁት፣
ምን ትሉት መሰላችሁ?
በፍቅሩ መታመሜን ንገሩት።

### ባልንጀሮቿ

[9]አንቺ ከሴቶች ሁሉ የተዋብሽ ሆይ፤
ውድሽ ከሌሎች እንዴት ቢበልጥ ነው?
እስከዚህ የምትማጠኚንስ፣
ውድሽ ከሌሎች እንዴት ቢበልጥ ነው?

### ሙሽራዪቱ

[10]ውዴ ፍልቅልቅና ደመ ግቡ ነው፤
ከዐሥር ሺሆችም የሚልቅ ነው።
[11]ራሱ የጠራ ወርቅ፣
ጠጕሩ ዞማ፣
እንደ ቍራም የጠቈረ ነው።
[12]ዐይኖቹ፣
በጅረት አጠገብ እንዳሉ ርግቦች፣
በወተት የታጠቡ፣
እንደ ዕንቍም ጕብ ጕብ ያሉ
ናቸው።
[13]ጕንጮቹ የሽቱ መዐዛ የሚያመጡ፣
የቅመማ ቅመም መደቦችን ይመስላሉ፤
ከንፈሮቹም ከርቤ እንደሚያንጠባጥቡ፣
ውብ አበቦች ናቸው።
[14]ክንዶቹ በዕንቍ ፈርጥ ያጌጠ፣
የወርቅ ዘንግን ይመስላሉ፤
ሰውነቱም በሰንፔር ፈርጥ[ቀ] ያጌጠ፣
አምሮ የተሠራ የዝሆን ጥርስን
ይመስላል።
[15]እግሮቹ በንጹሕ ወርቅ መቆሚያ ላይ
የተተከሉ፣
የዕብነ በረድ ምሰሶዎችን ይመስላሉ፤
መልኩ እንደ ሊባኖስ ነው፤
እንደ ዝግባ ዛፎቹም ምርጥ ነው።
[16]አፉ ራሱ ጣፋጭ ነው፤
ሁለንተናውም ያማረ ነው፤
እናንተ የኢየሩሳሌም ቈነጃጅት ሆይ፤
ውዴ ይህ ነው፤ ባልንጀራዬም እርሱ
ነው።

### ባልንጀሮቿ

6 አንቺ ከሴቶች ሁሉ የተዋብሽ ሆይ፤
ውድሽ ወዴት ሄደ?
አብረንሽም እንድንፈልገው፣
ውድሽ የሄደው በየት በኩል ነው?

### ሙሽራዪቱ

[2]ውዴ መንጋውን ለማሰማራት፣
ውብ አበቦችንም ለመሰብሰብ፣
የቅመማ ቅመም መደቦቹ ወዳሉበት፣
ወደ አትክልት ቦታው ወርዶአል።
[3]እኔ የውዴ ነኝ፤ ውዴም የእኔ ነው፤
መንጋውንም በውብ አበቦች መካከል
ያሰማራል።

### ሙሽራው

[4]ውዴ ሆይ፤ አንቺ እንደ ቴርሳ
የተዋብሽ፣
እንደ ኢየሩሳሌም ያማርሽ፣
ዐርማቸውን እንደ ያዙ ወታደሮችም
ግርማን የተጐናጸፍሽ ነሽ።
[5]አስጨንቀውኛልና፣
እባክሽ ዐይኖችሽን ከእኔ ላይ አንሺ፤
ጠጕርሽ ከገለዓድ ተራራ የሚወርድ፣
የፍየል መንጋ ይመስላል።
[6]ጥርሶችሽ
ከመታጠቢያ እንደ ወጡ የበግ መንጋ
ናቸው፤
ሁሉም መንታ መንታ የወለዱ፣

5፥2 ማሕ1፥15፤ 4፥7፤6፥9
5፥5 ቍ13
5፥6 ማሕ3፥1፤ 6፥1፡2
5፥7 ማሕ3፥3
5፥8 ማሕ1፥14፤ 2፥5፡7
5፥9 ማሕ1፥8
5፥10 መዝ45፥2
5፥12 ዘፍ49፥12፤ ማሕ1፥15
5፥13 ቍ5፤ ማሕ1፥10፤2፥1፤6፥2
5፥14 ኢዮ28፥6
5፥15 1ነገ4፥33፤ ማሕ7፥4
5፥16 ማሕ1፥5፤ 4፥3፤7፥9
6፥1 ማሕ1፥8፤5፥6
6፥2 ማሕ4፥12፤ 5፥6፡13
6፥3 ማሕ2፥16፤ 7፥10
6፥4 ዘኍ1፥52፤ አሱ12፥24፤1ነገ 15፥33፤መዝ48፥2፤ 50፥2
6፥5 ማሕ4፥1
6፥6 ማሕ4፥2

[ሽ]6 ወይም *በተናገረ ጊዜ ልቤ ወደ እርሱ ሄደ*
[ቀ]14 ወይም *ላፒስ ላዙሊ*

ከመካከላቸውም መካን የሌለባቸው
ናቸው።
7ከመሸፈኛሽ ውስጥ ያሉት ጉንጮችሽ፣
ለሁለት የተከፈለ ሮማን ይመስላሉ።
8ሥልሳ ንግሥቶች፣
ሰማንያ ቁባቶች፣
ቍጥራቸውም የበዛ ደናግል ሊኖሩ
ይችላሉ፤
9እንከን የሌለባት ርግቤ ግን ልዩ ናት፤
እርሷ ለወለደቻት የተመረጠች፤
ለእናቷም አንዲት ናት፤
ቈነጃጅት አይተው "የተባረክሽ ነሽ"
አሏት፤
ንግሥቶችና ቁባቶችም አመሰገኗት።

## ባልንጀሮቿ

10እንደ ንጋት ብርሃን ብቅ የምትል፣
እንደ ጨረቃ የደመቀች፣ እንደ ፀሓይ
ያበራች፣
ዐርማ ይዞ በሰልፍ እንደ ወጣ ሰራዊት
ግርማዋ የሚያስፈራ ይህች ማን ናት?

## ሙሽራው

11በሸለቆው ውስጥ አዲስ የበቀሉትን
አትክልቶች ለማየት፣
ወይኑ ማቈጥቈጡን፣
ሮማኑ ማበቡን ለመመልከት፣
ወደ ለውዙ ተክል ቦታ ወረድሁ።
12ይህን ከማወቁ በፊት፣
ምኞቴ በሕዝቤ ንጉሣዊ ሠረገሎች
መካከል[ሀ] አስቀመጠኝ።

## ባልንጀሮቿ

13አንቺ ሱላማጢስ ሆይ፤ ተመለሺ፤
ኧረ ተመለሺ፤
እንድናይሽ ተመለሽ፤ እባክሺ
ተመለሺ።

## ሙሽራው

የመሃናይምን ዘፈን እንደሚመለከት
ሰው፣
ሱላማጢስን የምትመለከቷት ለምንድን
ነው?

7 አንቺ የልዑል ልጅ ሆይ፤
ነጠላ ጫማ የተጫሙ እግሮችሽ
እንዴት ያምራሉ!
ሞገሰን የተጐናጸፉ ዳሌዎችሽ ፣
ብልኀ አንጥረኛ የተጠበባቸውን
የዕንቍ ሐብል ይመስላሉ።
2ዕንብርትሽ ጥሩ የወይን ጠጅ እንደ
ማይጐድልበት፣
እንደ ክብ ጽዋ ነው፤
ወገብሽ ዙሪያውን በውብ አበባ የታሰረ

6፥7 ዘፍ24፥65፤ ማሕ4፥3
6፥8 ዘፍ22፥24፤ አስ2፥14፤መዝ45፥9
6፥9 ማሕ1፥15፤ 3፥4፤5፥2
6፥11 ማሕ7፥12
6፥13 ዘፀ15፥20
7፥1 መዝ45፥13
7፥3 ማሕ4፥5
7፥4 ዘኍ21፥26፤ መዝ144፥12፤ ማሕ5፥15
7፥5 ኢሳ35፥2
7፥6 ማሕ 4፥10
7፥7 ማሕ4፥5
7፥8 ማሕ2፥5
7፥9 ማሕ5፥16
7፥10 መዝ45፥11፤ ማሕ2፥16፤6፥3
7፥12 ማሕ1፥6፤ 2፥13፥15፤ 4፥13፤6፥11
7፥13 ዘፍ30፥14፤ ማሕ4፥16

የስንዴ ክምር ይመስላል።
3ሁለት ጡቶችሽ፣
መንታ የዋልያ ግልገሎችን ይመስላሉ።
4ዐንገትሽ በዝሆን ጥርስ እንዳጌጠ
መጠበቂያ ማማ ነው፤
ዐይኖችሽ በባትረቢ በር አጠገብ
እንዳሉት፣
እንደ ሐሴቦን ኵሬዎች ናቸው፤
አፍንጫሽ ወደ ደማስቆ አቅጣጫ
እንደሚመለከት፣
እንደ ሊባኖስ መጠበቂያ ማማ ነው።
5የራስሽ ቅርጽ እንደ ቀርሜሎስ ተራራ
አክሊል ሆኖልሻል፤
ጠጕርሽ የሐር ጕንጕን የመሰለ ነው፤
ንጉሡም በሹሩባሽ ታስሮ ተይዞአል።
6እንዴት ውብ ነሽ! እንዴትስ ደስ
የምትይ ነሽ!
ፍቅሬ ሆይ፤ የምታስደስቺ ነሽ።
7ቁመናሽ እንደ ዘንባባ ዛፍ መለል ያለ
ነው፤
ጡቶችሽም የፍሬውን ዘለላ ይመስላሉ።
8እኔም፣ "የዘንባባውን ዛፍ እወጣለሁ፤
ዘለላዎቹንም እይዛለሁ" አልሁ።
ጡቶችሽ የወይን ዘለላ፣
የእስትንፋስሽም መዐዛ እንደ እንኰይ
ፍሬ ይሁኑ፤
9ከናፍሮችሽም እንደ ማለፊያ የወይን
ጠጅ ይጣፍጡ።

## ሙሽራዪቱ

የወይን ጠጁ በቀስታ እየተንቈረቈረ፣
ወደ ውዴ ከንፈሮችና ጥርሶች
ይውረድ።[+]
10እኔ የውዴ ነኝ፤
የእርሱም ምኞት እኔው ነኝ።
11ውዴ ሆይ፤ ና ወደ ገጠር እንሂድ፤
ወደ መንደርም[ቶ] ገብተን እንደር፤
12ማልደን ወደ ወይኑ ተክል ቦታ እንሂድ፣
ወይኑ እንቡጥ አውጥቶ፣
አበባው ፈክቶ፣
ሮማኑ አፍርቶ እንደ ሆነ እንይ፤
በዚያም ራሴን በፍቅር እሰጥሃለሁ።
13ትርንጐዎች መዐዛቸውን ሰጡ፤
አዲስ የተቀጠፈውም ሆነ የበሰለው፣
ጣፋጩ ፍሬ ሁሉ በደጃፋችን አለ፤
ውዴ ሆይ፤ ለአንተ አስቀም
ጬልሃለሁ።

8 ምነው አንተ የእናቴን ጡት እንደ ጠባ፣
እንደ ወንድሜ በሆንህ!

[ሀ]12 ወይም *ከአሚናዳብ ሠረገሎች መካከል*፤ወይም *ከልዑል ሕዝቦች ሠረገሎች መካከል*
[+]9 ሰብዓ ሊቃናት፣ አቀኵሚላ፣ ቨልጌትና ሱርስት እንዲሁ ሲሆኑ ዕብራይስጡ ግን *ወደ ተኙ ሰዎች ከንፈሮች* ይላል
[ቶ]11 ወይም *ወደ ሄና ቍጥቋጦች*

ከዚያም ውጭ ባገኝህ፣
እስምህ ነበር፤
ታዲያ ማንም ባልናቀኝ!
2እኔም ወደ አስተማረችኝ፣
ወደ እናቴም ቤት፣
እጅህን ይዤ በወሰድሁህ ነበር፤
የምትጠጣውን ጣፋጭ የወይን ጠጅ፣
የሮማኔን ጭማቂም በሰጠሁህ።
3ግራ እጁን ተንተርሻለሁ፤
ቀኝ እጁም ዐቅፎኛል።
4እናንት የኢየሩሳሌም ቈነጃጅት፤
ራሱ እስኪፈልግ ድረስ፣
ፍቅርን እንዳታስነሡት ወይም
እንዳትቀሰቅሱት አማጥናችኋለሁ።

## ባልንጀሮቿ

5ውዷን ተደግፋ፣
ከምድረ በዳ የምትወጣ ይህች ማን
ናት?

## ሙሽራዪቱ

ከእንኰይ ዛፍ ሥር አስነሣሁህ፤
በዚያ እናትህ ፀነሰችህ፤
በዚያም ታምጥ የነበረችው አንተን
ወለደችህ።
6በልብህ እንዳለ፣
በክንድህም እንደምትይዘው ማኅተም
አስቀምጠኝ፤
ፍቅር እንደ ሞት የበረታች፣
ቅናቷም[ኀ] እንደ መቃብር[ኁ] ጨካኝ
ናትና፤
እንደሚንቦገቦግ እሳት፣
እንደ ኀይለኛም ነበልባል ትነዳለች።[ኂ]
7የውሃ ብዛት ፍቅርን ሊያጠፋ
አይችልም፣
ፈሳሾችም አያስጥሟትም፤
ሰው የቤቱን ሀብት ሁሉ
ስለ ፍቅር ቢሰጥ
ፈጽሞ ይናቃል።

## ባልንጀሮቿ

8ትንሽ እኅት አለችን፤

8፥2 ማሕ3፥4
8፥3 ማሕ2፥6
8፥4 ማሕ2፥7፤3፥5
8፥5 ማሕ3፥4፥6
8፥6 ዘኍ5፥14፤ ማሕ1፥ 2
8፥7 ምሳ6፥35
8፥11 መክ2፥4፤ ኢሳ7፥23
8፥12 ማሕ1፥6
8፥14 ምሳ5፥19፤ ማሕ2፥8፥9

ጡትም ገና አላወጣችም፤
ስለ እርሷ በምንጠየቅበት ቀን
ምን ማድረግ እንችል ይሆን?
9እርሷ ቅጥር ብትሆን፣
በላይዋ የብር መጠበቂያ ማማ
እንሠራባታለን፤
በር ብትሆን፣
በዝግባ ዕንጨት እንከልላታለን።

## ሙሽራዪቱ

10እነሆ እኔ ቅጥር ነኝ፤
ጡቶቼም እንደ ማማ ግንቦች
ናቸው፤
እኔም በዐይኖቹ ፊት፣
ሰላምን እንደሚያመጣ ሰው ሆንሁ።
11ሰሎሞን በብኤላሞን የወይን ተክል ቦታ
ነበረው፤
የወይኑን ተክል ቦታም ለአትክልተኞች
አከራየው፤
እያንዳንዳቸውም የፍሬውን ዋጋ፣
አንድ አንድ ሺህ ሰቅል ብር
ያመጡለት ነበር።
12የወይኔ ተክል ቦታ የራሴ፣ የግሌ ነው፤
ሰሎሞን ሆይ፤ አንድ ሺሁ ሰቅል
ለአንተ፤
ፍሬውን ለሚጠብቁ ደግም ሁለት መቶ
ይሁን።

## ሙሽራው

13አንቺ በአትክልቱ ቦታ የምትኖሪ ሆይ፤
ባልንጀሮቼ ድምፅሽን ይሰማሉ፤
እስቲ እኔም ልስማው።

## ሙሽራዪቱ

14ውዴ ሆይ፤ ቶሎ ናልኝ፤
ሚዳቋን፣
ወይም በቅመም ተራራ ላይ የሚዘል፣
የዋልያን ግልገል ምሰል።

[ኀ]6 ወይም *ኀልቅ ስሜት*
[ኁ]6 ዕብራይስጡ *ሲኦል* ይለዋል
[ኂ]6 ወይም *እንደ እግዚአብሔም ነበልባል*

# ትንቢተ ኢሳይያስ

1 በይሁዳ ነገሥታት በዖዝያን፣ በኢዮአ
ታም፣ በአካዝና በሕዝቅያስ ዘመን፣
የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ ስለ ይሁዳና ስለ
ኢየሩሳሌም ያየው ራእይ፤

## እምቢተኛ ሕዝብ

2ሰማያት ሆይ፤ ስሙ! ምድር ሆይ፤ አድምጪ!
*እግዚአብሔር* እንዲህ ሲል ተናግሮአልና፤
“ልጆች ወለድሁ፣ አሳደግኋቸውም፤
እነርሱ ግን ዐመፁብኝ።
3በሬ ጌታውን፣
አህያ የባለቤቱን ጋጥ ያውቃል፤
እስራኤል ግን አላወቀም፤
ሕዝቤም አላስተዋለም።”

4እናንተ ኀጢአተኛ ሕዝብ፣
በደል የሞላበት ወገን፣
የክፉ አድራጊ ዘር፣
ምግባረ ብልሹ ልጆች ወዮላችሁ!
*እግዚአብሔርን* ትተዋል፤
የእስራኤልን ቅዱስ አቃለዋል፤
ጀርባቸውንም በእርሱ ላይ አዙረዋል።

5ለምን ዳግመኛ ትመታላችሁ?
ለምንስ በዐመፅ ትጸናላችሁ?
ራሳችሁ በሙሉ ታሞአል፤
ልባችሁ ሁሉ ታውኮአል።
6ከእግር ጥፍራችሁ እስከ ራስ ጠጕራችሁ
ጤና የላችሁም፤
ቍስልና ዕባጭ እንዲሁም እዥ ብቻ ነው፤
አልታጠበም፤ አልታሰረም፤
በዘይትም አልለዘበም።

7አገራችሁ ባድማ፣
ከተሞቻችሁ በእሳት የተቃጠሉ ይሆናሉ፤
ዐይናችሁ እያየ፣
መሬታችሁ በባዕድ ይነጠቃል፤
ጠፍም ይሆናል።
8የጽዮን ሴት ልጅ
በወይን አትክልት ውስጥ እንዳለ ዳስ፣
በዱባ ተክል ወስጥ እንደሚገኝ ጐጆ፣
እንደ ተከበበም ከተማ ተተወች።
9የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*
ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ፣
እንደ ሰዶም በሆንን
ገሞራንም በመሰልን ነበር።

10እናንተ የሰዶም ገዦች፤
*የእግዚአብሔርን* ቃል ስሙ፤
እናንተ የገሞራ ሰዎች፤
*የእግዚአብሔርን* ሕግ አድምጡ።

1÷1 1ሳሙ3÷1፤ 2ነገ14÷21፤16÷1፤ 1ዜና3÷12፡13፤ 2ዜና26÷22፤ነህ1÷1፤ኢሳ2÷1፤13÷1፤22÷1፡5፤40÷9፤44÷26፤ አብ1÷1፤ናሆ1÷1
1÷2 ቀኍ4፡23፤ ዘዳ4÷26፤መሳ11÷10፤ ኢሳ23÷4፤24÷5፡20፤ 30÷1፡9፤46÷8፤ 48÷8፤57÷4፤63÷16፤ 65÷2፤66÷24፤ ኤር42÷5፤ሕዝ24÷3፤ ሚክ1÷2፤ሐጌ1÷12፤ ሚል1÷6፤3÷5
1÷3 ዘፍ42÷27፤ ዘዳ32÷28፤ኢዮ12÷9፤ ኢሳ42÷25፤48÷8፤ ኤር4÷22፤5÷4፤9÷3፡6፤ ሆሴ2÷8፤4÷1፡6፤ 7÷9
1÷4 ቀኍ2፤ዘዳ32÷15፤ 2ነገ19÷22፤ መዝ14÷3፤119÷87፤ ምሳ30÷9፤ኢሳ5÷18፡19፡24፤9÷17፤14÷20፤ 31÷1፡2፤37÷23፤ 41÷14፤43÷14፤45÷11፤ 47÷4፤59÷13፤ ኤር23÷14፤ሕዝ39÷7
1÷5 ቀኍ2፤ ምሳ20÷30፤ ኢሳ30÷26፤ 31÷6፤33÷6፡24፤ 58÷8፤ኤር2÷30፤ 5÷3፤8÷5፤30÷17፤ 44÷16-17፤ሰቆ2÷11፤ 5÷17፤ዕብ3÷16
1÷6 ዘዳ28÷35፤ 2ሳሙ14÷2፤መዝ23÷5፤38÷3፤45÷7፤104÷15፤147÷3፤ኢሳ30÷26፤ 53÷5፤61÷3፤ኤር8÷22፤ 14÷19፤30÷17፤ ሰቆ2÷13፤ሕዝ34÷4፤ ሉቃ10÷34
1÷7 ዘሌ26÷16፡31፡34፤ ዘዳ29÷23፤ መሳ6÷3-6፤ 2ነገ18÷13፤ መዝ109÷11፤ ኢሳ62÷8፤ኤር5÷17
1÷8 ኢዮ27÷18፤ መዝ9÷14፤ ኢሳ10÷32፤30÷17፤ 49÷21
1÷9 ዘፍ19÷24፤ 45÷7፤2ነገ21÷14፤ ኢሳ4÷2፤6÷13፤ 27÷12፤28÷5፤ 37÷4፡31-32፤45÷25፤ 56÷8፤ኤር23÷3፤ ኢል2÷32፤ሮሜ9÷29
1÷10 ዘፍ13÷13፤ 18÷20፤ኢሳ5÷24፤ 8÷20፤13÷19፤28÷14፤ 30÷9፤

11“*የመሥዋዕታችሁ* ብዛት
ለእኔ ምኔ ነው?” ይላል *እግዚአብሔር*።
“የሚቃጠለውን የአውራ በግና
የሰቡ እንስሳትን ስብ ጠግቤአለሁ፤
በበሬ፣ በበግ ጠቦትና በፍየል ደም ደስ
አልሰኘም።
12በፊቴ ለመቅረብ ስትመጡ፣
ይህን ሁሉ እንድታመጡ፣
የመቅደሴን ደጅ እንድትረግጡ ማን
ጠየቃችሁ?
13ከንቱውን መባ አታቅርቡ፤
ዕጣናችሁን እጸየፋለሁ፤
የወር መባቻ በዓላችሁን፣
ሰንበቶቻችሁን፣ ጉባኤያችሁንና
በክፋት የተሞላውን ስብሰባችሁን መታገሥ
አልቻልሁም።
14የወር መባቻችሁንና የተደነገጉ በዓሎቻችሁን
ነፍሴ ጠልታለች፤
ሸክም ሆነውብኛል፤
መታገሥም አልቻልሁም።
15እጆቻችሁን ለጸሎት ወደ እኔ ስትዘረጉ፣
ዐይኖቼን ከእናንተ እሰውራለሁ፤
አብዝታችሁ ብትጸልዩም እንኳ አልሰማችሁም፤
እጆቻችሁ በደም ተበክለዋል፤
16ታጠቡ፤ ራሳችሁንም አንጹ፤
ክፉ ሥራችሁን
ከፊቴ አርቁ፤
ክፉ ማድረጋችሁን ተዉ፤
17መልካም ማድረግን ተማሩ፤
ፍትሕን እሹ፣
የተገፉትን አጽናኑ[ሀ]፤
አባት ለሌላቸው ቁሙላቸው፤
ለመበለቶችም ተሟገቱ።

ሕዝ16÷49፤ሮሜ9÷29፤ራእ11÷8 1÷11 1ሳሙ15÷22፤ኢዮ22÷3፤ መዝ40÷6፤50÷8፤ኢሳ66÷3፤ኤር6÷20፤አሞ6÷4፤ሚል1÷10፤ዕብ10÷4
1÷12 ዘፀ23÷17፤ ዘዳ31÷11 1÷13 ዘኍ10÷10፤1ነገ14÷24፤ 1ዜና23÷31፤መዝ115÷8፤ ምሳ15÷8፤28÷9፤ኢሳ41÷24፤66÷3፤ ኤር7÷9፤18÷15፤44÷8፤ሐጌ2÷14፤ሚል2÷11 1÷14 ዘፀ12÷16፤ ዘሌ23÷1-44፤ ዘኍ28÷11-29፡39፤ዘዳ16÷1-17፤ ነህ10÷33፤ ኢዮ7÷12፤ መዝ11÷5፤69÷3፤ኢሳ5÷12፤7÷13፤29÷1፤43÷22፡24፤ ኤር44÷22፤ሆሴ2÷11፤ ሚል2÷17፤3÷14 1÷15 ዘፀ9÷29፤ ዘዳ1÷45፤31÷17፤ 1ሳሙ8÷18፤ኢዮ9÷30፤15÷31፤ኢሳ4÷4፤ 57÷17፤59÷2፡3፤ኤር2÷34፤ሕዝ7÷23፤ሆሴ4÷2፤ኢል3÷21፤ዮሐ9÷31
1÷16 ዘኍ19÷11፡ 16፤ሩት3÷3፤ኢሳ52÷11፤55÷7፤ኤር25÷5፤ ማቴ27÷24፤ያዕ4÷8 1÷17 ቀኍ23፤ ዘፀ22÷22፤ዘዳ14÷29፤ ኢዮ22÷9፤መዝ34÷14፤72÷1፤82÷3፤94÷6፤ ኢሳ10÷2፤11÷4፤ 33÷5፤56÷1፤61÷8፤ ሕዝ18÷31፤22÷7፤ አሞ5÷14-15፤ ሚክ6÷8፤ሰፎ2÷3፤ ሉቃ18÷3፤ያዕ1÷27

[ሀ] 17 ወይም፣ *ጨቋኙን ገሥጹ* ማለት ነው።

[18]“ኑና፤ እንዋቀስ”
ይላል እግዚአብሔር፤
“ኀጢአታችሁ እንደ ዐለላ ቢቀላ
እንደ በረዶ ይነጣል፤
እንደ ደም ቢቀላም
እንደ ባዘቶ ነጭ ይሆናል።
[19]እሺ ብትሉ፣ ብትታዘዙም
የምድርን በረከት ትበላላችሁ፤
[20]እምቢ ብላችሁ ብታምፁ ግን
ሰይፍ ይበላችኋል።”
የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና።

[21]ታማኝ የነበረችው ከተማ
እንዴት አመንዝራ እንደ ሆነች ተመልከቱ!
ቀድሞ ፍትሕ የሞላባት፣
ጽድቅ የሰፈነባት ነበረች፤
አሁን ግን የነፍሰ ገዳዮች ማደሪያ ሆነች!
[22]ብርሽ ዝጎአል፣
ምርጥ የወይን ጠጅሽ ውሃ ገባው፤
[23]ገዦዎችሽ ዐመፀኞችና
የሌባ ግብረ ዐበሮች ናቸው፤
ሁሉም ጉቦን ይወዳሉ፤
እጅ መንሻንም በብርቱ ይፈልጋሉ፤
አባት ለሌላቸው አይቆሙም፤
የመበለቶችንም አቤቱታ አይሰሙም።
[24]ስለዚህ ጌታ፣ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሐ
ር፣
የእስራኤል ኀያል እንዲህ ይላል፤
“በባላንጣዎቼ ላይ ቍጣዬን እገልጣለሁ፤
ጠላቶቼንም እበቀላለሁ።
[25]እጄን በአንቺ ላይ አነሣለሁ፣
ዝገትሽን ፈጽሜ አጠራለሁ፤
ጕድፍሽንም ሁሉ አስወግዳለሁ።
[26]ፈራጆችሽን እንደ ጥንቱ፣
አማካሪዎችሽንም እንደ ቀድሞው እመልሳለሁ፤
ከዚያም የጽድቅ መዲና፣
የታመነች ከተማ
ተብለሽ ትጠሪያለሽ።

[27]ጽዮን በፍትሕ፣
በንስሓ የሚመለሱ ነዋሪዎቿም
በጽድቅ ይዋጃሉ።
[28]ዐመፀኞችና ኀጢአተኞች ግን
በአንድነት ይደቃሉ፤
እግዚአብሔርንም የሚተዉ ይጠፋሉ።
[29]“ደስ በተሰኛችሁባቸው የአድባር ዛፎች
ታፍራላችሁ፤
በመረጣችኋቸውም የአትክልት ቦታዎች
ትዋረዳላችሁ።
[30]ቅጠሉ እንደ ጠወለገ ወርካ፣
ውሃም እንደሌለው የአትክልት ቦታ ትሆና
ላችሁ።
[31]ብርቱ ሰው እንደ ገለባ፣
ሥራውም እንደ ብልጭታ ይሆናል፤

1፥18 1ሳሙ2፥25፤ መዝ51፥7፤ኢሳ41፥1፤ 43፥9፡26፤55፥7፤ ራእ7፥14
1፥19 ዘዳ30፥15-16፤ ዕዝ9፥12፤ኢዮ36፥11፤ መዝ34፥10፤ ኢሳ30፥23፤50፥10፤ 55፥2፤58፥14፤62፥9፤6 5፥13፡21-22
1፥20 ዘኍ23፥19፤ 1ሳሙ12፥15፤ ኢዮ15፥22፤ኢሳ3፥25፤ 21፥17፤27፥1፤34፥16፤40 ፥5፤58፥14፤65፥12፤66፥1 6፤ ኤር17፥27፤49፥13፤ ሚክ4፥4፤ዘካ1፥6፤ ራ እ1፥16
1፥21 ምሳ6፥17፤ ኢሳ5፥7፤46፥13፤ 57፥3-9፤59፥14፤ ኤር2፥20፤3፥2፡9፤ 13፥27፤ሕዝ23፥3፤ ሆሴ2፥1-13፤ አሞ6፥12
1፥22 መዝ119፥119
1፥23 ቆላ2፤ ዘፀ3፥8፤ዘዳ19፥14፤ ኢ ሳ10፥2፤ኤር5፥28፤ ሕዝ22፥6-7፤አሞ 5፥12፤ሚክ2፥1-2፤ 3፥9፤ 6፥12፤ዕን1፥4
1፥24 ዘፍ49፥24፤ ዘዳ32፥43፤ ኢሳ10፥3፤34፥2፡8፤ 35፥4፤47፥3፤59፥17፤6 1፥2፤63፥4፤ ኤር51፥6፤ሕዝ5፥13
1፥25 ዘዳ28፥63፤ 2ዜና29፥15፤ መዝ78፥38፤ 119፥119፤ኢሳ48፥10፤ ኤር6፥29፤9፥7፤ ሕዝ22፥22፤ሚል3፥3
1፥26 ዘፍ32፥28፤ ኢሳ4፥3፤32፥16፤ 33፥5፤46፥13፤48፥2፡ 18፤52፥1፤60፥14፤ 61፥11፤62፥1፡2፤ 64፥10፤ኤር31፥23፤ 33፥7፡11፤ዳን9፥24፤ሚ ክ4፥8፤ዘካ8፥3
1፥27 ኢሳ30፥15፤ 31፥6፤35፥10፤41፥14፤ 43፥1፤52፥3፤59፥20፤ 62፥12፤63፥4፤ ሕዝ18፥30፤ሆሴ2፥19
1፥28 ዘዳ32፥15፤ መዝ9፥5፤ኢሳ24፥20፤ 33፥14፤43፥27፤48፥8፤ 50፥1፤59፥2፤66፥24፤ኤ ር4፥18፤16፥4፤ 42፥22፤44፥12፤ 2ተሰ1፥8-9
1፥29 መዝ97፥7፤ ኢ ሳ42፥17፤ 44፥9፡11፤ 45፥16፤57፥5፤65፥3፤ 66፥17፤ኤር10፥14፤ ሕዝ6፥13፤ሆሴ4፥13
1፥30 መዝ1፥3
1፥31 ኢሳ4፥4፤5፥24፤

ሁለቱም አብረው ይቃጠላሉ፤
እሳቱንም የሚያጠፋው የለም።

## የእግዚአብሔር ተራራ

2 የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ ስለ ይሁዳና ስለ
ኢየሩሳሌም ያየው ይህ ነው፤
[2]በዘመኑም ፍጻሜ፣

የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ተራራ
ከተራሮች ከፍ ብሎ ይመሠረታል፤
ኰረብቶችም በላይ ከፍ ከፍ ይላሉ፤
ሕዝቦችም ሁሉ ወደዚያ ይጐርፋሉ።

[3]ብዙ ሕዝቦችም መጥተው እንዲህ ይላሉ፤

“ኑ፤ ወደ እግዚአብሔር ተራራ፣
ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንውጣ፤
እርሱ መንገዱን ያስተምረናል፤
በጐዳናውም እንሄዳለን።”
ሕግ ከጽዮን፣
የእግዚአብሔር ቃል ከኢየሩሳሌም
ይወጣልና።
[4]እርሱ በሕዝቦች መካከል ይፈርዳል፤
የብዙ ሰዎችን አለመግባባት ያስወግዳል።
እነርሱም ሰይፋቸውን ቀጥቅጠው ማረሻ
ጦራቸውንም ማጭድ ያደርጋሉ።
ሕዝብ በሕዝብ ላይ ሰይፍ አያነሣም፤
ጦርነትንም ከእንግዲህ አይማሩም።

[5]እናንተ የያዕቆብ ቤት ሆይ፤ ኑ፤
በእግዚአብሔር ብርሃን እንመላለስ።

## የእግዚአብሔር ቀን

[6]የያዕቆብ ቤት የሆነውን፣
ሕዝብህን ትተሃል፤
እነርሱ በምሥራቅ ሰዎች ከንቱ አምልኮ
ተሞልተዋልና፤
እንደ ፍልስጥኤማውያን ያሟርታሉ፤
ከባዕዳን ጋር አገና ይማታሉ።
[7]ምድራቸው በብርና በወርቅ
ተሞልታለች፤
ሀብታቸውም ልክ የለውም።
ምድራቸው በፈረሶች ተሞልታለች፤
የሠረገሎቻቸውም ብዛት ልክ የለውም።
[8]ምድራቸው በጣዖታት ተሞልታለች፤
ጣቶቻቸው ላበጇቸው፣

9፥18-19፤10፥17፤ 24፥6፤26፥11፤30፥27፡33፤33፥14፤34፥10፤ 66፥15-16፡24፤ ኤር5፥14፤7፥20፤ 21፥12፤አብ1፥18፤ሚል3፥2፤ 4፥1፤ ማቴ25፥41 2፥1 ኢሳ1፥1 2፥2 መዝ102፥15፤ኢሳ11፥9፤ 24፥23፤ 25፥6፡10፤27፥13፤ 56፥7፤57፥13፤65፥9፡25፤66፥20፤ ኤር16፥19፤31፥23፤ዳን11፥45፤ኢል3፥17፤ሚክ4፥7፤ዘካ14፥10፤ ሐሥ2፥17፤ዕብ1፥2 2፥3 ዘዳ33፥19፤ መዝ137፥5፤ኢሳ1፥10፤ 33፥22፤45፥14፡23፤ 49፥1፡12፡23፤51፥4፡7፤55፥5፤60፥3-6፡14፤ 66፥18፤ኤር3፥17፤ ኢል3፥2፤ሶፎ3፥8፤ዘካ14፥2፤ሉቃ24፥47፤ ዮሐ4፥22 2፥4 ዘፍ49፥10፤ መዝ7፥6፤9፥19፤46፥9፤96፥13፤ 98፥9፤ኢ ሳ1፥27፤3፥13፤ 9፥5፡7፤11፥6-9፤ 32፥18፤42፥4፤51፥4፤ 57፥19፤65፥25፤ ኤር30፥10፤ዳን11፥45፤ሆሴ2፥18፤ኢል3፥10፡14፤ ሚክ4፥3፤ዘካ9፥10 2፥5 ኢሳ58፥1፤ 60፥1፡19-20፤ዮሐ1፥5፡7 2፥6 ዘዳ18፥10፤31፥17፤2ነገ1፥2፤ 16፥7፤2ዜና26፥6፤ ምሳ6፥1፤ኢ ሳ44፥25፤ኤር12፥7፤ሚክ5፥12 2፥7 ዘፍ41፥43፤ ዘዳ17፥16፡17፤ መዝ17፥14፤ ኢሳ31፥1፤ሚክ5፥10

ለእጆቻቸው ሥራ ይሰግዳሉ።
9ሰው ዝቅ ብሎአል፤
የሰው ልጅም ተዋርዶአል፤
ስለዚህ በደላቸውን ይቅር አትበል[ለ]።
10ከእግዚአብሔር አስፈሪነት
ከግርማው ሽሽ፤
ወደ ዐለቶች ሂድ፤
በመሬትም ውስጥ ተሸሸግ።
11የእብሪተኛ ሰው ዐይን ይሰበራል፤
የሰዎችም ትዕቢት ይዋረዳል፤
በዚያን ቀን እግዚአብሔር ብቻውን ከፍ ከፍ ይላል።

12የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር
እብሪተኛውንና ትዕቢተኛውን ሁሉ፣
የተከ ራራውን በሙሉ
የሚያዋርድበት ቀን አለው።
13ረዥምና ከፍ ከፍ ያሉትን የሊባኖስ ዝግባዎች ሁሉ፣
የባሳንን የወርካ ዛፎች ሁሉ፣
14ታላላቁን ተራራ ሁሉ፣
ከፍ ያለው ኰረብታ ሁሉ፣
15ረጃጅሙን ግንብ ሁሉ፣
የተመሸገውን ቅጥር ሁሉ፣
16የተርሴስን መርከቦች[ሐ] ሁሉ፣
የክብር ጀልባዎችን ሁሉ የሚያዋርድበት ቀን አለው።
17የሰው እብሪት ይዋረዳል፤
የሰውም ኩራት ይወድቃል፤
በዚያን ቀን እግዚአብሔር ብቻ ከፍ ከፍ ይላል፤
18 ጣዖቶች ሁሉ ፈጽሞ ይወድማሉ።

19እግዚአብሔር ምድርን ለማናወጥ በሚነሣበት ጊዜ፣
ሰዎች ከአስፈሪነቱ
ከግርማውም የተነሣ፣
ወደ ዐለት ዋሻ
ወደ መሬትም ጕድጓድ ለመሸሸግ
ይሮጣሉ።
20በዚያን ቀን ሰዎች
ሊያመልኳቸው ያበጇቸውን፣
የብርና የወርቅ ጣዖቶቻቸውን
ለፍልፈልና ለሌሊት ወፍ ይወረውራሉ።
21እግዚአብሔር ምድርን ለማናወጥ በሚነ ሣበት ጊዜ፣
ሰዎች ከአስፈሪነቱ
እንዲሁም ከግርማው የተነሣ፣
ወደ ድንጋይ ዋሻ፣
ወደ ዐለት ስንጣቂ ሮጠው ይገባሉ።
22እስትንፋስ አፍንጫው ላይ ባለች
በሰው አትታመኑ፤
ከቶ ምን የሚበጅ ነገር አለው!

2፥8 2ዜና32፥19፤ መዝ135፥15፤ ኢሳ10፥9-11፤17፥8፤ 44፥17፤ ሚክ5፥13፤ ራእ9፥20
2፥9 ቍ11፡17፤ ነህ4፥5፤መዝ62፥9፤ ኢሳ5፥15፤13፥11
2፥10 ቍ19፤ ዘኍ3፥11፤ መዝ145፥12፤ ናሆ3፥11፤2ተሰ1፥9፤ራእ6፥15-16
2፥11 ቍ9፡17፡20፤ ነህ9፥29፤ኢዮ40፥11፤ መዝ46፥10፤ኢሳ3፥7፡18፤4፥1፡2፤5፥15፡30፤7፥18፤10፥12፤17፥4፡7፤24፥21፤25፥9፤ 26፥1፤27፥1፤37፥23፤ ሕዝ31፥10፤ዕን2፥5
2፥12 2ሳሙ22፥28፤ ኢዮ40፥11፤ መዝ59፥12፤76፥12፤ኢሳ13፥6፡9፤ 22፥5፡8፡12፤24፥4፡21፤34፥8፤ 60፥11፤61፥2፤ ኤር30፥7፤ሰቆ1፥12፤ ሕዝ7፥7፤30፥3፤ ኢል1፥15፤2፥11፤ አሞ5፥18፤ሶፎ1፥14፤ ሚል4፥1
2፥13 መሳ9፥15፤ መዝ22፥12፤ ኢሳ10፥33፡34፤ 29፥17፤ሕዝ27፥5፤ ዘካ11፥2
2፥14 ኢሳ30፥25፤ 40፥4
2፥15 ኢሳ25፥2፡12፤ 30፥25፤32፥14፤33፥18፤ ሶፎ1፥16
2፥16 ዘፍ10፥4፤ 1ነገ9፥26
2፥17 ቍ9፡11፤ 2ሳሙ22፥28፤ ኢዮ40፥11
2፥18 ዘዳ9፥21፤ 1ሳሙ5፥2፤ኢሳ21፥9፤ ኤር10፥11፤ ሕዝ36፥25፤ሚክ5፥13
2፥19 ቍ21፤ ዘዳ2፥25፤መሳ6፥2፤ ኢዮ9፥6፤30፥6፤ መዝ145፥12፤ ኢሳ7፥19፤14፥16፤ ሉቃ23፥30፤ ዕብ12፥26፤ራእ6፥15
2፥20 ቍ11፤ ዘሌ11፥19፤ ኢዮ22፥24፤ ሕዝ7፥19-20፤14፥6፤ 36፥25፤ራእ9፥20
2፥21 ቍ19፤ ዘፀ33፥22፤መዝ145፥12፤ ኢሳ33፥10
2፥22 ዘፍ2፥7፤ ኢዮ12፥19፤መዝ8፥4፤ 18፥42፤118፥6፡8፤ 144፥3፡4፤146፥3፤ ኢሳ17፥13፤29፥5፤ 40፥15፤51፥12፤

## በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ላይ የሚመጣ ፍርድ

3 እነሆ፤ ጌታ ፣
የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር
ከኢየሩሳሌምና ከይሁዳ
ድጋፉንና ርዳታውን፣
የምግብና የውሃ ርዳታውን ሁሉ ይነሣል፤
2ጀግናውንና ተዋጊውን፣
ፈራጁንና ነቢዩን፣
አስማተኛውንና ሽማግሌውን፣
3የአምሳ አለቃውንና ባለ ማዕረጉን፣
አማካሪውንና ጠቢቡን የእጅ ባለሙያ፣
ብልኁንም ምትሀተኛ ይነሣል።

4ልጆችን መሪዎቻቸው አደርጋለሁ፤
ያልበሰሉ ሕፃናትም ይገዟቸዋል።
5ሕዝብ እርስ በርሱ ይጨቋቈናል፤
ሰው በሰው ላይ፤ ባልንጀራ በባልንጀራው ላይ፣
ወጣቱ በሽማግሌው ላይ፣
ተራው ሰው በተከበረው ላይ ይነሣል።

6ሰውም በአባቱ ቤት
ከወንድሞቹ አንዱን ይዞ፣
"አንተ ልብስ ስላለህ መሪ ሁነን፤
ይህንንም የፍርስራሽ ክምር ግዛ" ይለዋል።
7እርሱ ግን በዚያ ቀን ድምፁን ከፍ
አድርጎ፣
"እኔ መፍትሔ አልሆንም፤
በቤቴም ልብስና ምግብ የለኝም፤
የሕዝብ መሪ አታድርጉኝ" ይላል።

8ኢየሩሳሌም ተንገዳገዳለች፤
ይሁዳም ለመውደቅ ተቃርባለች፤
ንግግራቸውም ሆነ ድርጊታቸው እግዚአብሔርን የሚቃወም፣
የክብሩንም መገኘት የሚያቃልል ነውና።
9የፊታቸው ገጽታ ይመሰክርባቸዋል፤
ኀጢአታቸውን እንደ ሰዶም በይፋ ይናገራሉ፤
አይደብቁትምም፤
ጥፋትን በራሳቸው ላይ ስላመጡ።
ወዮላቸው!

10ጻድቃን መልካም ነገር እንደሚያገኙ ንገሯቸው፤
የሥራቸውን ፍሬ ያበላሉና።

ኤር17፥5፤ያዕ4፥14 3፥1 ዘሌ26፥26፤መዝ18፥18፤ኢሳ5፥13፤ 65፥13፤ሕዝ4፥16፤አሞ4፥6 3፥2 ዘዳ18፥10፤ኢሳ9፥14-15፤ ሕዝ17፥13 3፥3 2ነገ1፥9፤24፥14፤ኢዮ22፥8፤መክ10፥11፤ ኤር8፥17
3፥4 ቍ12፤ መክ10፥16 3፥5 መዝ28፥3፤ኢሳ9፥19፤ ኤር9፥8፤ሚክ7፥2፡6 3፥7 ኢሳ2፥11፤24፥2፤ኤር30፥12፤ሕዝ34፥4፤ ሆሴ5፥13፤ኢል1፥16 3፥8 2ዜና33፥6፤ኢዮ1፥11፤መዝ73፥9፡11፤ ኢሳ1፥7፤ 9፥15፡17፤28፥15፤30፥9፤59፥3፡13፤65፥7
3፥9 ዘፍ13፥13፤ ዘኍ32፥23፤ 2ዜና34፥24፤ምሳ8፥36፤ ኢሳ59፥12፤ ኤር14፥7፤ ሆሴ5፥5፤ሮሜ6፥23 3፥10 ዘፍ15፥1፤ ዘዳ5፥33፤12፥28፤ 28፥1-14፤መዝ37፥17፤ 128፥2፤ኤር22፥15

[ለ]9 ወይም፣ *ከፍ አታድርጋቸው* ማለት ነው።
[ሐ]16 ወይም *የንግድ መርከቦች* ማለት ነው

11በደለኞች ወዮላቸው፤ ጥፋት ይመጣባቸዋል፤
የእጃቸውን ያገኛሉና።
12ወጣቶች ሕዝቤን ያስጨንቃሉ፤
ሴቶችም ይገዟቸዋል።
ሕዝቤ ሆይ፤ መሪዎችህ አሳስተውሃል፤
ከመንገድህም መልሰውሃል።

13*እግዚአብሔር* በፍርድ ወንበር ላይ
ተቀምጦአል፤
በሕዝቡም ላይ ለመፍረድ ተነሥቶአል።
14*እግዚአብሔር*፣
ከአለቆችና ከሕዝቡ ሽማግሌዎች ጋር
እንዲህ ሲል ይፋረዳል፤
"የወይኔን ቦታ ያጠፋችሁ እናንተ ናችሁ፤
ከድኾች የዘረፋችሁትም በቤታችሁ
ይገኛል፤
15ሕዝቤን በችግር ስታደቁት፣
የድኾችንም ፊት በሐዘን ስታገረጡት
ምን ማለታችሁ ነው?"
ይላል ጌታ ፣
የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*።
16*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
የጽዮን ሴቶች ኰርተዋል፤
ዐንገታቸውን እያሰገጉ፣
በዐይናቸውም እየጠቀሱ ይሄዳሉ፤
እየተቄነኑ በመራመድ፣
የእግራቸውን ዐልቦ ያቃጭላሉ።
17ስለዚህ፣ ጌታ በጽዮን ሴቶች ዐናት ላይ
ቈረቈር ያመጣል፤
*እግዚአብሔርም* ራሳቸውን በሀ ያደርጋል።

18በዚያም ቀን ጌታ የክብር ጌጣቸውን ይነ
ጥቃቸዋል፤ የእግር አንባሩን፣ የጠጕር ጌጡን፣
የጨረቃ ቅርጽ ያለውን የዐንገት ጌጥ፣
19የጆሮ ጕትቻውን፣ የእጅ አንባሩን፣ የፊት
መሸፈኛውን፣ 20የራስ መሸፈኛውን፣ ዐል
ቦውን፣ ሻሹን፣ የሽቶ ብልቃጡን፣ አሸን
ክታቡን፣ 21የጣት ቀለበቶችንና የአፍንጫ
ቀለበቶችን፣ 22ያማረውን ቀሚስ፣ የውስጥ
ልብሱን፣ ካባውን፣ የእጅ ቦርሳውን፣ 23መስ
ታወቱን፣ ከጥሩ በፍታ የተሠራውን ልብስ፣
የራስ ጌጡን፣ ዐይነ ርግቡን ሁሉ ይነጥቃ
ቸዋል።

24በሽቶ ፈንታ ግማት፣
በሻሽ ፈንታ ገመድ፣
አምሮ በተሠራ ጠጕር ፈንታ ቡሀነት፣
ባማረ ልብስ ፈንታ ማቅ፣
በውበትም ፈንታ ጠባሳ ይሆናል።
25ወንዶቻችሁ በሰይፍ ስለት፣
ተዋጊዎቻችሁ በጦርነት ይወድቃሉ።
26የጽዮን ደጆች ያዝናሉ፣ ያለቅሳሉም፤
እርሷም ተረስታ በመሬት ላይ ትቀ
መጣለች።

3፥11 ዘዳ28፥15-68፤
2ዜና6፥23፤ኢዮ9፥13፤
ኢሳ57፥20፤ኤር21፥14፤
ሰቆ5፥16፤ሕዝ24፥14
3፥12 ቊ 4፤
ኢሳ9፥16፤19፥14፤
28፥7፤29፥9፤
ኤር23፥13፤25፥16፤ሚ
ክ3፥5
3፥13 ኢዮ10፥2፤
መዝ82፥1፤ኢሳ2፥4
3፥14 1ሳሙ12፥7፤
ኢዮ22፥4፤24፥9፤
ኢሳ11፥4፤25፥4፤
ያዕ2፥6
3፥15 ኢዮ24፥14፤
መዝ94፥5፤ኢሳ5፥7፤
10፥6፤11፥4፤26፥6፤
29፥19፤32፥6፤51፥23
3፥16 ኢዮ15፥25፤
መሓ3፥11
3፥17 ቊ 24፤
ሕዝ27፥31፤አሞ8፥10
3፥18 ዘፍ41፥42፤
መሳ8፥21፤ኢሳ2፥11
3፥19 ዘፍ24፥47፤
ሕዝ16፥11-12
3፥20 ዘፀ39፥28፤
ሕዝ24፥17፡23፤
44፥18
3፥21 ዘፍ24፥22
3፥22 ሩት3፥15
3፥23 ዘፀ29፥6፤
መሓ3፥11፤
ኢሳ61፥3፤62፥3፤
ሕዝ16፥10፤23፥26
3፥24 ቊ 17፤
ዘፍ37፥34፤ዘሌ13፥40፤
2ሳሙ10፥4፤አስ2፥12፤
ኢዮ1፥20፤16፥15፤
ምሳ31፥24፤
ኢሳ4፥4፤20፥2፡4፤
ኤር4፥8፤ ሰቆ2፥10፤
ሕዝ27፥30-31፤
ዮና3፥5-8፤1ጴጥ3፥3
3፥25 ኢሳ1፥20፤
ኤር15፥8
3፥26 ዘሌ26፥31፤
ኢዮ2፥13፤መዝ137፥1፤
ኢሳ14፥31፤24፥4፡
7፡12፤29፥2፤33፥9፤
45፥2፤ኤር4፥28፤
14፥2፤ሰቆ4፥5
4፥1 ዘፍ30፥23፤
ኢሳ2፥11፤13፥12፤
32፥9፤2ተሰ3፥12
4፥2 መዝ72፥16፤ ኢ
ሳ1፥9፤2፥11፤ 11፥1-
5፤33፥17፤
52፥13፤53፥2፤
60፥15፤ኤር23፥5-6፤
33፥15-16፤
ሕዝ17፥22፤34፥29፤
36፥8፤ዘካ3፥8፤6፥12
4፥3 ዘፀ19፥6፤
መዝ56፥8፤87፥6፤
ኢሳ1፥9፡26፤26፥2፤
45፥25፤52፥1፤60፥21፤
ኢል3፥17፤አብ1፥17፤
ሰፎ3፥13፤ሉቃ10፥20፤
ሮሜ11፥5
4፥4 መዝ51፥2፤

4 በዚያን ቀን ሰባት ሴቶች
አንዱን ወንድ ይዘው፣
"የራሳችንን ምግብ እንበላለን፤
የራሳችንንም ልብስ እንለብሳለን፤
በአንተ ስም ብቻ እንጠራና፣
ውርደታችንን አስቀርልን" ይሉታል።

## የእግዚአብሔር ዛፍ ቅርንጫፍ

2በዚያን ቀን *የእግዚአብሔር* ዛፍ ቅርንጫፍ
ያማረና የከበረ ይሆናል፤ የምድሪቱም
ፍሬ ከጥፋት ለተረፈው የእስራኤል ወገን
ኵራትና ክብር ይሆናል። 3በጽዮን የቀ
ሩት፣ በኢየሩሳሌምም የተረፉት፣ በኢየሩ
ሳሌም በሕይወት ከተመዘገቡት ሁሉ ጋር
ቅዱሳን ተብለው ይጠራሉ። 4ጌታ የጽዮንን
ሴቶች እድፍ ያጥባል፤ ኢየሩሳሌምንም
ከተነከረችበት ደም በፍርድና በሚያቃጥል
መንፈስ[ሙ] ያነጻታል። 5ከዚያም *እግዚአብሐ
ር* በጽዮን ተራራ ላይና በዚያ
በሚሰበሰቡትም ሁሉ ላይ በቀን ደመናኝ ጢ
ስን፣ በሌሊትም የሚንበለበለውን የእሳት
ብርሃን ይፈጥራል፤ በክብሩ ሁሉ ላይ
መጋረጃ ይሆናል፤ 6ከቀኑ ሙቀት ጥላና
መከለያ፣ ከውሽንፍርና ከዝና ብም መጠጊ
ያና መሸሸጊያ ስፍራ ይሆናል።

## ስለ ወይን ቦታ የተነገረ ቅኔ

5 ስለ ወዳጄ፣
ደግሞም ስለ ወይን ቦታው ልዘምር፤
ወዳጄ በለምለም ኰረብታ ላይ
የወይን ቦታ ነበረው።
2መሬቱን ቈፈረ፤ ድንጋይንም ለቅሞ
አወጣ፤
ምርጥ የሆነውንም ወይን ተከለበት።
በመካከሉ መጠበቂያ ማማ ሠራ፤
የወይን መጭመቂያ ጕድጓድም አበጀ፤
ከዚያ መልካም ፍሬ ያፈራል ብሎ አሰበ፤
ነገር ግን ኮምጣጣ ፍሬ አፈራ።
3"እናንት በኢየሩሳሌም የምትኖሩና የይሁዳ
ሰዎች ሆይ፤
በእኔና በወይኔ ቦታ መካከል እስቲ ፍረዱ።
4ከዚህ ካደረግሁለት በላይ ለወይኔ ቦታ ምን
ሊደረግለት ይገባ ነበር?
መልካም የወይን ፍሬ ያፈራል ብዬ ስጠብቅ
ለምን ኮምጣጣ ፍሬ አፈራ?

ማሕ3፥11፤ኢሳ1፥15፡ 31፤3፥24፤ 28፥6፤ 30፥30፤ዘካ13፥9፤
ማቴ3፥11፤ ሉቃ3፥17 4፥5 ዘፀ13፥21፤ መዝ18፥11፤ኢሳ35፥2፤
41፥20፤58፥8፤60፥1፤65፥18፤ራእ7፥15፤ 14፥1 4፥6 ዘሌ23፥34-43፤
መዝ27፥5፤55፥8፤ ኢሳ8፥14፤14፥32፤ 25፥4፤30፥2፤57፥13፤
ሕዝ11፥16 5፥1 መዝ80፥8-9፤ ኢሳ27፥2፤ዮሐ15፥1
5፥2 ዘፀ15፥17፤ 1ሳሙ2፡9፤ኢዮ24፥11፤ኢሳ16፥8፤27፥3፤
31፥5፤49፥8፤ማቴ21፥19፡33፤ማር11፥13፤ሉቃ13፥6
5፥3 ማቴ21፥40 5፥4 2ዜና36፥15፤ ኤር2፥5-7፡21፤24፥2፤
29፥17፤ሚክ6፥3-4፤ማቴ23፥37

ሙ4 ወይም *በእግዚአብሔር መንፈስ* ማለት ነው።

[5]እንግዲህ በወይኔ ቦታ
ምን እንደማደርግ ልንገራችሁ፤
ዐጥሩን እነቅላለሁ፤
ለጥፋት ይጋለጣል፤
ግንቡንም አፈርሳለሁ፣
መረጋገጫም ይሆናል።
[6]የማይኰተኰትና የማይታረም
ጠፍ መሬት አደርገዋለሁ፤
ኵርንችትና እሾኽም ይበቅልበታል፤
ዝናብም እንዳይዘንብበት
ደመናዎችን አዝዛለሁ።”

[7]የሰራዊት ጌታ *የእግዚአብሔር*
የወይን ቦታው የእስራኤል ቤት ነው፤
የይሁዳ ሰዎችም
የደስታው አትክልት ናቸው።
ፍትሕን ፈለገ፤ ነገር ግን ደም ማፍሰስን አየ፤
ጽድቅን ፈለገ፤ ነገር ግን የጭንቅን ጩኸት ሰማ።

## ወዮታና ፍርድ

[8]ስፍራ ለሌሎች እስከማይተርፍ፣
ቤትን በቤት ላይ በመጨመር፣
መሬትን ከመሬት ጋር በማያያዝ፣
ለብቻችሁ በምድር ተስፋፍታችሁ
ለምትኖሩ ወዮላችሁ!

[9]የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* ጆሮዬ እየሰማ
እንዲህ ሲል ተናገረ፤

“ታላላቅ ቤቶች ወና ይቀራሉ፣
የሚያማምሩም ቤቶች ኗሪ ያጣሉ።
[10]ከሩብ ጋሻ[ሠ] የወይን ቦታ አንድ የባዶስ
መስፈሪያ ያህል የወይን ጭማቂ ብቻ ይገ
ኛል፤ አንድ የቆሮስ መስፈሪያ ዘር ተዘርቶ
አንድ የኢፍ መስፈሪያ እህል ብቻ
ይሰጣል።[ረ]

[11]የሚያሰክር መጠጥ ፍለጋ
ማልደው ለሚነሡ፣
እስኪያነዳቸውም ወይን በመጠጣት
ሌሊቱን ለሚያነጉ ወዮላቸው!
[12]በግብዣቸው ላይ በገናና መሰንቆ፣
ከበሮና ዋሽንት እንዲሁም የወይን ጠጅ አለ፤
ነገር ግን ለእግዚአብሔር ሥራ ቦታ አልሰጡም፤
ለእጆቹም ሥራ ክብር አላሳዩም።
[13]ስለዚህ ሕዝቤ
ዕውቀት በማጣቱ ይማረካል፤
መኳንንቱም በራብ ይሞታሉ፤
ሕዝቡም በውሃ ጥም ይቃጠላል።
[14]ስለዚህ ሲኦል[ሰ] ሆዷን አሰፋች፣
አፏንም ያለ ልክ ከፈተች፤
መኳንንቱና ሕዝቡ
ከረብሸኞቻቸውና ከጨፋሪዎቻቸው ጋር
ወደዚያ ይወርዳሉ።

[15]ሰው ይዋረዳል፤
የሰው ልጅም ዝቅ ዝቅ ይላል፤
የእብሪተኛውም ዐይን ይሰበራል።
[16]የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* ግን በፍትሕ
ከፍ ከፍ ይላል፤
ቅዱሱም አምላክ ቅድስናውን በጽድቅ
ይገልጻል።
[17]በጎችም በገዛ መሰማሪያቸው እንደሚሰማሩ
ሆነው ይግጣሉ፤
የበግ ጠቦቶችም በባለጠጎች ፍርስራሽ ላይ
ሣር ይበላሉ[ሸ]።

[18]ኀጢአትን በማታለል ገመድ ለሚስቡ፣
በደልንም በሠረገላ ማሰሪያ ለሚጐትቱ
ወዮላቸው!
[19]በዐይናችን እንድናይ
*እግዚአብሔር* ይቸኵል፤
ሥራውንም ያፋጥን፤
የእስራኤልን ቅዱስ፣ የእርሱን ዕቅድ
እንድናውቃት ትቅረብ፤
ትምጣም ለሚሉ ወዮላቸው!”

[20]ክፉውን መልካም፣
መልካሙን ክፉ ለሚሉ
ብርሃኑን ጨለማ፣
ጨለማውን ብርሃን ለሚያደርጉ፣
ጣፋጩን መራራ፣
መራራውንም ጣፋጭ ለሚያደርጉ
ወዮላቸው!

[21]ራሳቸውን እንደ ብልኅ ለሚቈጥሩ፣
በራሳቸውም አመለካከት ጥበበኛ ለሆኑ
ወዮላቸው!

[22]የወይን ጠጅ ለመጠጣት ጀግኖች፣
የሚያሰክር መጠጥ ለመደባለቅ ብርቱ
ለሆኑ ወዮላቸው!
[23]ጉቦን በመቀበል በደለኛን ንጹሕ ለሚያደርጉ፣
ለበደል አልባ ሰው ፍትሕን ለሚነፍጉ
ወዮላቸው!
[24]ስለዚህ የእሳት ነበልባል ገለባን እንደሚበላ፣
ድርቆሽም በእሳት ጋይቶ እንደሚጠፋ፣
የእነርሱም ሥር እንዲሁ ይበሰብሳል፤
አበባቸውም እንደ ትቢያ ይበናል፤

**5፥5** 2ዜና36፥21፤ መዝ80፥12፤ ኢሳ6፥12፤10፥6፤ 22፥5፤26፥6፤27፥10፤28፥3፡18፤41፥25፤ 63፥3፤ኤር12፥10፤ 34፥22፤ሰቆ1፥15፤ ሆሴ2፥12፤ሚክ7፥10፤ ሚል4፥3፤ሉቃ21፥24
**5፥6** ቍ10፡17፤ ዘፍ6፥13፤ዘሌ26፥32፤ዘዳ28፥24፤2ሳሙ1፥21፤ 23፥6፤ኢሳ6፥13፤ 7፥23፡24፤32፥13፤ 34፥13፤49፥17፡19፤ 51፥3፤55፥13፤ ሕዝ28፥24፤ሆሴ2፥12፤ ኢል1፥10፤አሞ4፥7፤ ዕብ6፥8
**5፥7** መዝ12፥5፤ 80፥8፤ኢሳ1፥21፤ 10፥2፤17፥10፤ 18፥5፤29፥21፤32፥7፤37፥30፤59፥15፤ 61፥8፤ሕዝ9፥9፤ 22፥29
**5፥8** ቍ11፡18፡20፤ ኢዮ20፥19፤ኢሳ6፥5፤ 10፥1፤24፥16፤ ኤር22፥13፤ሚክ2፥2፤ ዕን2፥9-12
**5፥9** ኢሳ6፥11-12፤ 22፥14፤ኤር44፥11፤ ማቴ23፥38
**5፥10** ቍ6፤ ዘሌ26፥26፤ዘዳ28፥38፤ ዘካ8፥10
**5፥11** ቍ8፤ 1ሳሙ25፥36፤ ምሳ23፥29-30
**5፥12** 1ሳሙ12፥24፤ ኢዮ21፥12፤ መዝ28፥5፤68፥25፤ ኢሳ24፥8፤ሕዝ26፥13
**5፥13** ኢዮ22፥8፤ ምሳ10፥21፤ኢሳ1፥3፤ 3፥1፤49፥21
**5፥14** ዘኍ16፥30፤ ምሳ30፥16፤ኢሳ22፥2፡13፤23፥7፤24፥8
**5፥15** ኢሳ2፥9፡11፤10፥33
**5፥16** ዘሌ10፥3፤ መዝ97፥9፤ኢሳ28፥17፤ 29፥23፤30፥18፤33፥5፡10፤61፥8፤ሕዝ36፥23
**5፥17** ኢሳ7፥25፤ 17፥2፤32፥14፤ ሶፎ2፥6፡14
**5፥18** ቍ8፤ ኢሳ59፥4-8፤ ኤር23፥14፤ሆሴ11፥4
**5፥19** ኢሳ1፥4፤ 29፥23፤30፥11፡12፤ 60፥22፤ኤር17፥15፤ ሕዝ12፥22፤2ጴጥ3፥4
**5፥20** ቍ8፤ ዘፍ18፥25፤1ነገ22፥8፤ ኢዮ24፥13፤ መዝ94፥21፤አሞ5፥7፤ ማቴ6፥22-23፤ ሉቃ11፥34-35
**5፥21** ምሳ3፥7፤ ኢሳ47፥10፤ሮሜ12፥16፤ 1ቆሮ3፥18-20 **5፥22** 1ሳሙ25፥36፤ ምሳ23፥20፤31፥4፤ኢሳ22፥13፤65፥11፤ኤር7፥18 **5፥23** ቍ7፤ ዘፀ23፥8፤መዝ94፥21፤ ኢሳ1፥17፤10፥2፤ 29፥21፤59፥4፡13-15፤ ሕዝ22፥12፤አሞ5፥12፤ያዕ5፥6 **5፥24** 2ነገ19፥30፤ኢዮ6፥10፤ 18፥16፤ 24፥24፤መዝ107፥11፤ኢሳ1፥4፡31፤8፥6፤10፥20፤12፥6፤ 30፥9፡12፤40፥8፤47፥14፤ ናሆ1፥10

[ሠ]10 በዕብራይስጥ፣ *ሩብ ጋሻ* መሬት በዐሥር ጥማድ በሬ በአንድ ቀን የሚታረስ ነው።
[ረ]10 ምናልባት አንድ ባዶስ ሀያ ሁለት ሊትር ያህል ነው።
አንድ የቆሮስ መስፈሪያ ሰማኒያ ኪሎ ግራም ያህል ነው።
አንድ የኢፍ መስፈሪያ ዐሥራ ስምንት ኪሎ ግራም ያህል ነው።
[ሰ]14 በዕብራይስጡ፣ *መቃብር* ማለት ነው።
[ሸ]17 በዕብራይስጡ፣ *እንግዶች ይበሉታል* ይለዋል

የሰራዊት ጌታ *የእግዚአብሔርን ሕግ*
ንቀዋልና፤
የእስራኤል ቅዱስ የተናገረውንም ቃል
አቃለዋል።
25*የእግዚአብሔር* ቍጣ በሕዝቡ ላይ ነዶአል፤
እጁን አንሥቶ መቶአቸዋል፤

ተራሮች ራዱ፤
ሬሳዎችም በመንገድ ላይ እንደ ተጣለ
ጥራጊ ሆኑ፤
ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ቍጣው ገና አልተመለሰም፤
እጁም እንደ ተነሣ ነው።

26ከሩቅ ያሉትን ሕዝቦች የሚጠራበትን
ምልክት ያቆማል፤
ከምድር ዳርቻም በፉጨት ይጠራቸዋል፤
እነርሱም እየተጣደፉ
በፍጥነት ይመጣሉ።
27በመካከላቸው ደካማና ስንኩል አይገኝም፤
የሚያንቀላፋና የሚተኛ አይኖርም፤
የወገባቸው መቀነት አይላላም፤
የጫማቸውም ማሰሪያ አይበጠስም።
28ፍላጻቸው የተሳለ፣
ቀስታቸውም የተደገነ ነው፤
የሠረገሎቻቸውም መንኰራኵሮች እንደ
ዐውሎ ነፋስ ናቸው።
29ጩኸታቸው እንደ አንበሳ ነው፤
እንደ አንበሳ ደቦል ያገሣሉ፤
ያደኑትንም ይዘው ይጮኻሉ፤
ተሸክመውት ይሄዳሉ፤ የሚያስጥልም
የለም።
30በዚያን ቀን
እንደ ባሕር ሞገድ ይጮኹበታል፤
ማንም ወደ ምድር ቢመለከት፣
ጨለማንና መከራን ያያል፤
ብርሃን እንኳ በደመናዎች ይጋረዳል።

## የኢሳይያስ ተልእኮ

6 ንጉሥ ዖዝያን በሞተበት ዓመት
እግዚአብሔርን ከፍ ባለና በከበረ
ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት፤ የልብሱም
ዘርፍ ቤተ መቅደሱን ሞልቶት ነበር። 2ሱራ
ፌልም ከእርሱ በላይ ቆመው ነበር፤
እያንዳንዳ ቸውም ስድስት ክንፍ ነበራ
ቸው። በሁለት ክንፍ ፊታቸውን ይሸፍኑ
ነበር፤ በሁለት ክንፍ እግራቸውን ይሸፍኑ
ነበር፤ በሁለቱም ክንፍ ይበሩ ነበር፤ 3እርስ
በርሳቸው በመ ቀባበልም

"ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ የሰራዊት ጌታ
*እግዚአብሔር፤*
ምድር ሁሉ በክብሩ ተሞልታለች" ይሉ
ነበር።

4ከድምፃቸው ጩኸት የተነሣ የመድረኩ
መሠረት ተናወጠ፤ ቤተ መቅደሱም በጢስ
ተሞላ። 5እኔም፣ "ከንፈሮቼ የረከሱብኝ
ሰው ነኝ፤ የምኖረውም ከንፈሮቹ
በረከሱበት ሕዝብ መካከል ነው፤ ዐይኖቼም
ንጉሡን፣ የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔርን*
አይተዋልና ጠፍ ቻለሁ፣ ወዮልኝ!"
አልሁ።
6ከዚያም ከሱራፌል አንዱ፣ ከመ
ሠዊያው ላይ የእሳት ፍም በጕጠት ወስዶ፣
ወደ እኔ እየበረረ መጣ። 7አፌንም በእሳቱ
ነክቶ፣ "እነሆ፤ ይህ ከንፈሮችህን ነክቶአል፤
በደልህ ተወግዶልሃል፤ ኀጢአትህም ተሰር
ዮልሃል" አለኝ።

8ከዚያም የጌታ ድምፅ፣ "ማንን እልካለሁ?
ማንስ ይሄድልናል?" ሲል ሰማሁት።
እኔም፣ "እነሆኝ፤ እኔን ላከኝ" አልሁ።
9እርሱም እንዲህ አለኝ፤ "ወደዚህ ሕዝብ ሂድ፤

" 'መስማትን ትሰማላችሁ፤ ነገር ግን
አታስተውሉም፤
ማየትንም ታያላችሁ፤ ነገር ግን ልብ
አትሉም' ብለህ ንገራቸው።
10የዚህን ሕዝብ ልብ አደንድን፤
ጆሮአቸውን ድፈን፤
ዐይኖቻቸውንም ክደን፤
ይህ ካልሆነማ፣
በዐይናቸው አይተው፣ በጆሮአቸው ሰምተው፣
በልባቸውም አስተውለው
በመመለስ ይፈወሳሉ።"

11እኔም፣ "ጌታ ሆይ፤ ይህ የሚሆነው እስከ
መቼ ነው?" አልሁት፤
እርሱም መልሶ እንዲህ አለኝ፤
"ከተሞች እስኪፈራርሱና፣
የሚኖሩባቸው እስኪያጡ፣

ቤቶችም ወና እስኪሆኑና፣
ምድርም ፈጽሞ ባድማ እስክትሆን ድረስ፤
12*እግዚአብሔርም* ሰዎችን እስከሚያርቅ፣
ምድሪቱም ጨርሶ ባዶ እስክትሆን፣
13ከዐሥር አንድ ሰው እንኳ በምድሪቱ ቢቀር፣
እርሱም ደግሞ ይጠፋል፤
ነገር ግን የኮምበልና የባሉጥ ዛፍ በተቈረጠ
ጊዜ ጕቶ እንደሚቀር፣
ቅዱሱም ዘር
እንዲሁ በምድሪቱ ጕቶ ሆኖ ይቀራል።"

**5፥25** ዘፀ19፥18፤ 2ሳሙ22፥43፤ 2ነገ9፥37፤22፥13፤ ኢዮ40፥11፤ መዝ110፥6፤ኢሳ9፥12፡17፡21፤10፥4፡17፤ 26፥11፤31፥9፤ 66፥15፤ኤር4፥8፤ 6፥12፤ዳን9፥16
**5፥26** ዘዳ28፥49፤ መዝ20፥5፤ኢሳ7፥18፤ 13፥5፤18፥3፤ዘካ10፥8
**5፥27** ኢዮ12፥18፤ ኢሳ14፥31፤22፥21፤ 40፥29-31፤ ሕዝ23፥15፤ ኢል2፥7-8
**5፥28** 2ነገ2፥1፤ ኢዮ1፥19፤39፥23፤ መዝ7፥12፤45፥5፤ ሕዝ26፥11
**5፥29** 2ነገ17፥25፤ ኢሳ10፥6፤42፥22፤ 49፥24-25፤ ኤር51፥38፤ ሚክ5፥8፤ሶፎ3፥3፤ ዘካ11፥3
**5፥30** መሳ6፥2፤ 1ሳሙ2፥9፤ኢዮ21፥30፤ መዝ18፥28፤44፥19፤ 82፥5፤93፥3፤ ኢሳ2፥11፤13፥10፤ 22፥5፤33፥2፤50፥3፤ ኤር4፥23-28፤50፥42፤ ኢል2፥10፤ሉቃ21፥25
**6፥1** ዘፀ24፥10፤ ዘኍ12፥8፤1ነገ22፥19፤ 2ነገ15፥7፤2ዜና26፥22፡23፤መዝ9፥4፤123፥1፤ ኢሳ52፥13፤53፥12፤ ዮሐ12፥41፤ራእ1፥13፤ 4፥2፤
**6፥2** ሕዝ1፥5፡11፤ 10፥15፤ራእ4፥8
**6፥3** ዘፀ15፥11፤ 16፥7፤ዘኍ14፥21፤ መዝ72፥19፤89፥8፤ ኢሳ11፥9፤54፥5፤ ሚል1፥11፤ራእ4፥8
**6፥4** ዘፀ19፥18፤ 40፥34፤ሕዝ43፥5፤ 44፥4፤ራእ15፥8
**6፥5** ዘፀ6፥12፤ 24፥10፤ዘኍ17፥12፤ ዘዳ5፥26፤ኢዮ42፥5፤ መዝ45፥3፤ኢሳ5፥8፤ 24፥23፤32፥1፤33፥17፤ 59፥3፤ኤር9፥3-8፤ 51፥57፤ሉቃ5፥8
**6፥6** ዘሌ10፥1፤ ሕዝ10፥2
**6፥7** ዘሌ26፥41፤ ኢሳ45፥25፤ኤር1፥9፤ ዳን10፥16፤12፥3፤ 1ዮሐ1፥7
**6፥8** ዘፍ1፥26፤ 22፥1፤ዘፀ3፥4፤ ኢዮ40፥9፤ኤር26፥12፡15፤ሐሥ9፥4
**6፥9** ኤር5፥21፤ ሕዝ3፥11፤አሞ7፥15፤ ማቴ13፥15፤28፥19፤ ሉቃ8፥10
**6፥10** ዘፀ4፥21፤ ዘዳ29፥4፤32፥15፡39፤ መዝ119፥70፤ኢሳ29፥9፤42፥18-20፤ 43፥8፤44፥18፤ሕዝ12፥2፤ማቴ13፥13-15፤ማር4፥12፤8፥18፤ ዮሐ12፥40፤ሐሥ28፥26-27
**6፥11** ዘሌ26፥31፡43፤ መዝ79፥1፡5፤ 109፥11፤ኢሳ24፥10፤ኤር4፥13፤35፥17
**6፥12** ዘዳ28፥64፤ ኢሳ5፥5፡9፤60፥15፤ 62፥4፤ኤር4፥29፤30፥17
**6፥13** ዘሌ27፥30፤ ዘዳ14፥2፤ኢዮ14፥7፡8፤ኢሳ1፥9፤5፥6፤ 10፥22

## የአማኑኤል ምልክትነት

7 የዖዝያን የልጅ ልጅ፣ የኢዮአታም ልጅ
አካዝ የይሁዳ ንጉሥ በነበረበት ዘመን፣
የሶርያ ንጉሥ ረአሶንና የእስራኤል ንጉሥ
የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ ኢየሩሳሌምን ሊወጉ
ወጡ፤ ነገር ግን ድል ሊያደርጓት አልቻሉም።
2ለዳዊት ቤት፣ “ሶርያና ኤፍሬም ተባ
ብረዋል” የሚል ወሬ በደረሰ ጊዜ፣ የዱር
ዛፍ በነፋስ እንደሚናወጥ የአካዝና የሕዝቡ
ልብ እንዲሁ ተናወጠ።
3እግዚአብሔርም ኢሳይያስን እንዲህ
አለው፤ “አንተና ልጅህ ሸአር ያሹብ[ቀ]
አካዝን ለመገናኘት ወደ ልብስ አጣቢ
ው ዕርሻ በሚወስደው መንገድ ወዳለው ወደ
ላይኛው የኵሬ መስኖ ጫፍ ውጡ፤ 4እንዲ
ህም በለው፤ ‘ተጠንቀቅ፤ ተረጋጋ፤ አትፍ
ራ በእነዚህ ከእሳት ተርፈው በሚጤሱት
በሁለቱ የዕንጨት ጒማጆች፣ በሶርያና
በንጉሥዋ በረአሶን እንዲሁም በሮሜልዩ
ልጅ ቍጣ አትሸበር። 5ሶርያ
ኤፍሬምና፣ የሮሜልዩ ልጅ ሊያጠፉህ
እንዲህ ብለው ተማከሩ፤ 6“ይሁዳን
እንውረር፤ እንበታትነው ተከፋ ፍለንም
እንግዛው፤ የጣብኤልንም ልጅ
እናንግሥባት።” 7ልዑል እግዚአብሔር ግን
እንዲህ ይላል፦

“ ‘ይህ ምክራቸው አይፈጸምም፤
ከቶም አይደረግም፤
8የሶርያ ራስ ደማስቆ፣
የደማስቆ ራስ ረአሶን ነውና፤
በሥልሳ አምስት ዓመት ውስጥ፣
የኤፍሬም ሕዝብ ይበታተናል፤ ሕዝብ
መሆኑም ይቀራል።
9የኤፍሬም ራስ ሰማርያ፣
የሰማርያም ራስ የሮሜልዩ ልጅ ነው።
እንግዲህ በእምነታችሁ ካልጸናችሁ፣
ፈጽሞ መቆም አትችሉም።’ ”

10እንደ ገናም እግዚአብሔር አካዝን እንዲህ
አለው፤ 11“ከጥልቁ ጥልቅ ወይም ከከፍ
ታው ከፍታ ምልክት እንዲሰጥህ ከእግዚ
አብሔር ከአምላክህ ለምን።”
12አካዝ ግን፣ “አልለምንም፣ እግዚአብሔርንም
አልፈታተንም” አለ። 13ኢሳይያስም እንዲህ
አለ፤ “እናንተ የዳዊት ቤት ሆይ፤ ስሙ፤
የሰውን ትዕግሥት መፈታተናችሁ አንሶ
የአምላኬን ትዕግሥት ትፈታተናላችሁን?
14ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤
እነሆ፤ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም
ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል[በ] ብላ ትጠ
ራዋለች። 15ክፉውን መተውና መልካሙን
መምረጥ ሲችል ቅቤና ማር ይበላል።
16ነገር ግን ሕፃኑ ክፉውን መተውና

7፥1 ቍ5፡8፡9፤ 2ነገ15፥25፡37፤ 1ዜና3፥13፤2ዜና28፥5፤ ኢሳ8፥6
7፥2 ቍ13፤ 2ሳሙ7፥11፤ኢሳ6፥4፤ 9፥9፤16፥5፤22፥22፤ ኤር21፥12፤ዳን5፥6፤ሆሴ5፥3፤አሞ9፥11
7፥3 2ነገ18፥17፤ ኢሳ10፥21-22፤36፥2
7፥4 ዘፍ15፥1፤ ዘዳ3፥2፤20፥3፤ 2ነገ15፥27፤ኢሳ8፥12፤ 10፥24፤12፥2፤21፥4፤30፥15፤35፥4፤37፥6፤51፥13፤54፥14፤ ሰቆ3፥26፤አሞ4፥11፤ ዘካ3፥2፤ማቴ24፥6
7፥5 ቍ1፡2
7፥7 መዝ2፥1፤ ኢሳ8፥10፤14፥24፤ 24፥3፤25፥8፤ 28፥16፡18፤40፥8፤ 46፥10፤ሐሥ4፥25
7፥8 ቍ1፤ ዘፍ14፥15፤2ነገ17፥24፤ኢሳ8፥4፤9፥11፤ 17፥1-3
7፥9 2ነገ15፥29፤ 2ዜና20፥20፤ መዝ20፥8፤ኢሳ8፥6-8፡10፤9፥9፤28፥1፡3፤ 30፥12-14፤40፥8
7፥11 ዘፀ7፥9፤ ዘዳ13፥2፤መዝ139፥8
7፥12 ዘዳ4፥34
7፥13 ቍ2፤ዘፍ30፥15፤ መዝ63፥1፤118፥28፤ኢሳ1፥14፤25፥1፤ 49፥4፤61፥10
7፥14 ዘፍ3፥15፤ 21፥22፤24፥43፤ ዘፀ3፥12፤ኢሳ8፥8፡10፤ ማቴ1፥23፤ሉቃ1፥31፤ 2፥12
7፥15 ቍ22፤ ዘፍ18፥8
7፥16 ዘዳ1፥39፤ 13፥16፤ኢሳ8፥4፤ 17፥3፤ኤር7፥15፤ ሆሴ5፥9፡13፤አሞ1፥3-5
7፥17 ቍ20፤ 1ነገ12፥16፤2ዜና28፥20
7፥18 ቍ20፡21፤ ኢሳ2፥11፤5፥26፤ 13፥5
7፥19 ቍ25፤ ኢሳ2፥19፤17፥9፤ 34፥13፤55፥13
7፥20 ቍ17፡18፤ ዘዳ28፥49፤ 2ሳሙ10፥4፤ 2ነገ18፥16፤ኢሳ8፥7፤ 10፥5፡15፤11፥15፤ 29፥16፤ኤር2፥18
7፥21 ቍ23፤ ኢሳ2፥17፤ኤር39፥10
7፥22 ቍ15፤ ዘፍ18፥8፤14፥30
7፥23 ቍ21፤

መልካሙን መምረጥ ከመቻሉ በፊት የፈራ
ሃቸው የሁለቱ ነገሥታት ምድር ባድማ
ይሆናል። 17ኤፍሬም ከይሁዳ ከተለየበት
ቀን ጀምሮ እግዚአብሔር ከዚህ በፊት
ታይቶ የማይታወቅ ዘመን በአንተ፣ በሕዝብህና
በአባትህ ቤት ላይ ያመጣል፤ የሚያመጣውም
የአሦርን ንጉሥ ነው።”
18በዚያን ቀን እግዚአብሔር ራቅ ካሉት
ከግብፅ ወንዞች ዝንቦችን፣ ከአሦርም ምድር
ንቦችን በፉጨት ይጠራል። 19እነርሱም
በሙሉ መጥተው፣ በየበረሓው ሸለቆ፣ በየዐ
ለቱ ንቃቃት፣ በየእሾኹ ቍጥቋጦና በየው
ሃው ጒድጓድ ሁሉ ይሰፍራሉ። 20በዚያን
ቀን፣ እግዚአብሔር ከወንዝ[ተ] ማዶ በተከራ
የው ምላጭ፣ ማለትም በአሦር ንጉሥ፣ የ
ራስና የእግር ጠጒራችሁን እንዲሁም ጢ
ማችሁን ይላጫል። 21በዚያን ቀን፣ አንድ
ሰው አንዲት ጊደርና ሁለት በግ ብቻ
ይተርፈዋል። 22ከሚ ሰጡትም የተትረፈረፈ
ወተት ቅቤ ይበላል፤ በምድሪቱም የቀሩ
ሁሉ ቅቤና ማር ይበ ላሉ። 23በዚያን ቀን
ሺህ ሰቅል[ቶ] ብር የሚ ያወጣ አንድ ሺህ
የወይን ተክል የነበረበት ቦታ ሁሉ፣
ኵርንችትና እሾኽ ብቻ ይሆናል። 24ምድሪቱ
በኵርንችትና በእሾኽ ስለምት ሸፈን፣
ሰዎች ወደዚያ የሚገቡት ቀስትና ፍላጻ
ይዘው ነው፤ 25ኵርንችትና እሾኹን በመፍ
ራት ከዚህ በፊት በመቈፈሪያ ተቈፍረው ወደ
ነበሩት ወደ እነዚያ ኰረብታዎች ሁሉ
ከእንግዲህ አትሄድም፤ ነገር ግን የከብቶች
መሰማሪያና የበጎች መፈንጫ ቦታ ይሆናሉ።

## አሦር የእግዚአብሔር መሣሪያ

8 እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፤ “ትልቅ
ሰሌዳ ወስደህ፣ ‘ማኸር-ሻላል-ሃሽ-ባዝ’[ኀ]
ብለህ በተለመደው በሰው ፊደል ጻፍበት።
2እኔም፣ ካህኑን ኡሪያንንና የበራክዩን ልጅ
ዘካርያስን ታማኝ ምስክሮቼ እንዲሆኑ
እጠራቸዋለሁ።”
3እኔም ወደ ነቢዪቱ ሄድሁ፤ እርሷም
ፀነሰች፤ ወንድ ልጅም ወለደች። እግዚ
አብሔርም፣ እንዲህ አለኝ፤ “ስሙን ማኸር-
ሻላል-ሃሽ-ባዝ ብለህ ጥራው። 4ሕፃኑም፣

ማሕ8፥11፤ኢሳ5፥6፤ ሆሴ2፥12 7፥24 ኢሳ5፥6 7፥25 ቍ19፤ ኢሳ5፥17፤ሐጌ1፥11 8፥1 ቍ3፤ ዘዳ27፥8፤ኢዮ19፥23፤ ኢሳ30፥8፤ኤር20፥3፤51፥60፤ሆሴ1፥4 8፥2 ቍ16፤ ኢሱ24፥22፤ሩት4፥9፤ 2ነገ16፥10፤ኤር32፥10፡12፡25፡44 8፥3 ቍ1፤ዘፍ3፥15፤ ዘፀ15፥20

[ቀ]3 ሸአር ያሹብ ማለት፣ ቅሬታዎች ይመለሳሉ ማለት ነው
[በ]14 አማኑኤል ማለት፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ማለት ነው።
[ተ]20 የኤፍራጥስ ወንዝ ነው።
[ቶ]23 11.5 ኪሎ ግራም ያህል ነው።
[ኀ]1 በዚህና በቍጥር 3 ላይ፣ ማኸር-ሻላል-ሃሽ-ባዝ ማለት፣ ምርኮ ፈጠነ፤ ብዝበዛ ቸኰለ ማለት ነው።

‘አባባ’ ወይም ‘እማማ’ ብሎ መጥራት ከመ
ቻሉ በፊት፣ የደማስቆ ሀብትና የሰማርያ
ምርኮ በአሦር ንጉሥ ይወሰዳል::”

5*እግዚአብሔርም* እንደ ገና እንዲህ ሲል
ተናገረኝ፤
6“ይህ ሕዝብ በጸጥታ የሚፈሰውን
የሰሊሆምን ውሆች ትቶ፣
በረአሶንና
በሮሜልዩ ልጅ ተደስቶአልና::
7ስለዚህ ጌታ ታላቁንና ብርቱውን
የጐርፍ ውሃ[ነ]፣
የአሦርን ንጉሥ ከነግርማ ሞገሱ ሁሉ
ያመጣባቸዋል::
ውሃውም ከቦዩ ዐልፎ ተርፎ
በወንዙ ዳር ያለውን ምድር ሁሉ ያጥለ
ቀልቃል፤
8እየጠራረገ ወደ ይሁዳ ይወርዳል፤
እያጥለቀለቀ ያልፋል፤
እስከ ዐንገትም ይደርሳል፤
አማኑኤል[ኘ] ሆይ፤
የተዘረጉ ክንፎቹ ምድርህን ከዳር እስከ
ዳር ይሸፍናሉ::”

9እናንተ አሕዛብ፣ ፎክሩ[ኦ]፤
ግን ደንግጡ::
በሩቅ አገር ያላችሁ አድምጡ፤
ለጦርነትም ተዘጋጁ፤ ነገር ግን ደንግጡ፤
ለጦርነትም ተዘጋጁ፤ ነገር ግን ደንግጡ፤
10ተመካከሩ፤ ግን አይሳካም፤
ዕቅድ አውጡ፤ ሆኖም አይጸናም፤
እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነውና::[ከ]

### *እግዚአብሔርን ፍሩ*

11*እግዚአብሔር* ብርቱ እጁን በላዬ አድርጎ
የእነዚህን ሰዎች መንገድ እንዳልከተል
አስጠነቀቀኝ፤ እንዲህም አለኝ፤

12“እነዚህ ሰዎች፣ ‘አድማ’ ብለው የሚጠሩትን፣
ማንኛውንም ነገር፣ ‘አድማ’ አትበሉ፤[ኸ]
እነርሱ የሚፈሩትን አትፍሩ፤
አትሸበሩለትም::
13ልትቀድሱ የሚገባው የሰራዊት ጌታ *እግዚ
አብሔርን* ብቻ ነው፤
ልትፈሩት የሚገባው እርሱን ነው፤
ልትንቀጠቀጡለት የሚገባውም እርሱ
ነው::
14እርሱም መቅደስ ይሆናል፤
ለሁለቱ የእስራኤል ቤት ግን
የሚያደናቅፍ ድንጋይ
የሚያሰናክልም ዐለት ይሆንባቸዋል፤
ለኢየሩሳሌም ሕዝብም
ወጥመድና አሽክላ ይሆናል::
15ከእነርሱ ብዙዎች ይሰናከላሉ፤
ይወድቃሉ፤ ይሰበራሉ፤

8፥4 ዘፍ1415፤
ኢሳ7፥8፥16
8፥6 ነህ3፥15፤
ኢሳ5፥24፤7፥1፤ዮሐ9፥7
8፥7 ኢሱ3፥15፤
2ዜና28፥20፤ኢሳ7፥20፤
10፥16፤17፥12-13፤
28፥2፥17፤30፥28፤
43፥2፤ዳን11፥40፤
ናሆ1፥8
8፥8 ኢሳ7፥14፤
18፥6፤28፥15፤46፥11፤ኤ
ር4፥13፤48፥40
8፥9 ኢሱ6፥5፤
ኢዮ34፥24፤
ኢሳ17፥12-13፤
ኤር6፥4፤46፥3፤
51፥12፥27-28፤
ሕዝ38፥7፤ኢል3፥9፤
ዘካ14፥2-3
8፥10 ኢዮ5፥12፤
ምሳ19፥21፤21፥30፤
ኢሳ7፥7፥14፤
ማቴ1፥23፤ሮሜ8፥31
8፥11 ሕዝ1፥3፤
2፥8፤3፥14
8፥12 ኢሳ7፥2፥4፤
20፥5፤30፥1፤36፥6፤
ማቴ10፥28፤
1ጴጥ3፥14
8፥13 ዘፀ20፥20፤
ዘኍ20፥12፤ኢሳ29፥23
8፥14 መዝ118፥22፤
119፥110፤ኢሳ4፥6፤
24፥17-18፤ኤር6፥21፤
ሕዝ3፥20፤14፥3፥7፤
ሉቃ2፥34፤20፥18፤
ሮሜ9፥33፤1ጴጥ2፥8
8፥15 ምሳ4፥19፤ ኢ
ሳ28፥13፤59፥10፤
ሮሜ9፥32
8፥16 ሩት4፥7፤
ኢሳ29፥11-12፤
ኤር32፥14፤ዳን8፥26፤
12፥4
8፥17 ዘዳ31፥17፤
መዝ22፥5፤27፥14፤
ዕብ2፥13
8፥18 ዘፍ33፥5፤
ዘፀ3፥12፤ዘዳ28፥46፤
መዝ9፥11፤ሕዝ4፥3፤
12፥6፥11፤24፥24፤
ሉቃ2፥34፤ዕብ2፥13
8፥19 ዘሌ19፥31፤
ዘኍ27፥21፤1ሳሙ28፥8፤
ኢሳ29፥4 8፥20
ቆ22፤ሩት4፥7፤ኢ
ሳ1፥10፤
9፥2፤59፥9፤60፥2፤
ሚክ3፥6፤ሉቃ16፥29
8፥21 ዘፀ22፥28፤ኢ
ዮ18፥12፤ 30፥3፤ራ
እ16፥11
8፥22 ቆ20፤
ኢዮ3፥13፤15፥24፤
ኢሳ5፥30፤ኢል2፥2፤
ማቴ25፥30፤
ራእ16፥10
9፥1 2ነገ15፥29፤
ኢዮ15፥24
9፥2 መዝ36፥9፤
82፥5፤107፥10፥14፤

ወጥመድ ይገባሉ፤ ይያዛሉም::”

16ምስክርነቱን አሽገው፤
ሕጉንም በደቀ መዛሙርቴ መካከል
አትመው::
17ፊቱን ከያዕቆብ ቤት የሸሸገውን
*እግዚአብሔርን* እጠብቃለሁ፤
እርሱንም ተስፋ አደርጋለሁ::

18እነሆ፤ እኔና *እግዚአብሔር* የሰጠኝ ልጆች
በጽዮን ተራራ ከሚኖረው ከሰራዊት ጌታ
*ከእግዚአብሔር* ለእስራኤል ምልክትና ድንቅ
ነን::
19ሰዎች፣ “የሚያነበንቡትንና የሚያሾካ
ሹኩትን ሟርተኞችንና መናፍስት ጠሪዎችን
ጠይቁ ቢሏችሁ፣ ሕዝቡ አምላኩን መጠ
የቅ አይገባውምን? በሕያዋን ምትክ ሙታ
ንን መጠየቅ ለምን አስፈለገ? 20ወደ ሕጉና
ወደ ምስክር ቃሉ ሂዱ! እነርሱም እንዲህ
ያለውን ቃል ባይናገሩ የንጋት ብርሃን አይበራ
ላቸውም:: 21ተጨንቀውና ተርበው በምድሪቱ
ላይ ይንከራተታሉ፤ ክፉኛ ሲራቡም ይቈ
ጣሉ፤ ወደ ላይ እየተመለከቱ ንጉሣቸው
ንና አምላካቸውን ይራገማሉ:: 22ከዚያም
ወደ ምድር ይመለከታሉ፣ የሚያዩትም
ጭንቀት፣ ጨለማና የሚያስፈራም
ጭጋግ ብቻ ነው፤ ወደ ድቅድቅ ጨለማም
ይጣላሉ::

### ሕፃን ተወለደልን

9 ነገር ግን ተጨንቀው የነበሩ ከእንግዲህ
ተስፋ ቢስ አይሆኑም:: በቀደመው
ዘመን የዛብሎንንና የንፍታሌምን ምድር
አዋረደ፤ በሚመጣው ዘመን ግን ከዮርዳ
ኖስ ማዶ፣ በባሕር መንገድ አጠገብ ያለውን
የአሕዛብን ገሊላ ያከብራል፤

2በጨለማ የሚኖር ሕዝብ
ታላቅ ብርሃን አየ፤
በሞት ጥላ[ወ] ምድር ለኖሩትም
ብርሃን ወጣላቸው::
3ሕዝብን አበዛህ፤
ደስታቸውንም ጨመርህ፤
ሰዎች ምርትን ሲሰበስቡ፣
ምርኮንም ሲከፋፈሉ
ደስ እንደሚላቸው ሁሉ፣

ኢሳ8፥20፤42፥6፤ 49፥6፤58፥8፤60፥19፤ሚል4፥2፤ ማቴ4፥15-16፤
ሉቃ1፥79፤ኤፌ5፥8 9፥3 ዘፀ15፥9፤ኢሱ22፥8፤ኢዮ12፥23፤
መዝ4፥7፤119፥162፤ኢሳ25፥9

[ነ]7 የኤፍራጥስ ወንዝ ነው::
[ኘ]8 *አማኑኤል* ማለት፣ *እግዚአብሔር ከእኛ ጋር* ማለት ነው፡
[ኦ]9 ወይም፣ *የከፋውን ነገር አድርጉ*
[ከ]10 ዕብራይስጡ፣ *አማኑኤል* ይላል::
[ኸ]12 ወይም *ለስምምነት አትጥሩ እነዚህ ሰዎች ሁል ጊዜ ለስምምነት ይጠራሉ*
[ወ]2 ወይም፣ *በጨለማ ምድር*::

እነርሱም በፊትህ ደስ ይላቸዋል።
4ምድያም ድል በተመታ ጊዜ እንደ ሆነው፣
የከበዳቸውን ቀንበር፣
በትከሻቸው ላይ የነበረውን በትር፣
የተጨቈኑበትንም ዘንግ ሰብረህላቸዋል።
5የጦረኞች ጫማ ሁሉ፣
በደም የተለወሰ ልብስም ሁሉ፣
ለእሳት ይዳረጋል፤
ይማገዳልም።
6ሕፃን ተወልዶልናልና፤
ወንድ ልጅ ተሰጥቶናል፤
አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል።
ስሙም፣
ድንቅ መካር፣[o] ኀያል አምላክ፣
የዘላለም አባት፣ የሰላም ልዑል ይባላል።
7ለመንግሥቱ ስፋት፣
ለሰላሙም ብዛት ፍጻሜ የለውም፤
ከአሁን ጀምሮ እስከ ዘላለም፣
መንግሥቱን በፍትሕና በጽድቅ
ይመሠርታል፤
ደግፎ በመያዝም ያጸናዋል።
በዳዊት ዙፋን ይቀመጣል፤
አገሩንም ሁሉ ይገዛል፤
የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ቅናት
ይህን ያደርጋል።

### *የእግዚአብሔር ቍጣ በእስራኤል ላይ*

8ጌታ በያዕቆብ ላይ ቃል ላከ፤
በእስራኤልም ላይ ይወድቃል።
9ሕዝቡ በሙሉ፣
ኤፍሬምና የሰማርያ ነዋሪዎች
ይህን ያውቃሉ፤
በትዕቢትና በልብ እብሪትም እንዲህ
ይላሉ፤
10"ጡቦቹ ወድቀዋል፤
እኛ ግን በጥርብ ድንጋይ መልሰን
እንገነባለን፤
የሾላ ዛፎቹ ተቈርጠዋል፤
እኛ ግን በዝግባ እንተካለን።"
11ነገር ግን እግዚአብሔር የረአሶንን ጠላቶች
ያጠናክራል፤
በእነርሱም ላይ ያመጣባቸዋል፤
ባለጋራዎቻቸውንም ያነሣሣባቸዋል።
12ሶርያውያን ከምሥራቅ፣ ፍልስጥኤማውያን
ከምዕራብ፤
አፋቸውን ከፍተው እስራኤልን ይቦጫጭ
ቋታል።

ይህም ሁሉ ሆኖ፣ ቍጣው ገና አልበረደም፤
እጁ እንደተዘረጋ ነው።
13ሕዝቡ ግን ወደ ቀጣቸው ፊታቸውን
አልመለሱም፤
የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔርንም
አልፈለጉም።
14ስለዚህ እግዚአብሔር ራስንና ጅራትን፣
የዘንባባውን ቅርንጫፍና ሸምበቆውን
ከእስራኤል በአንድ ቀን ይቈርጣል።
15ሽማግሌዎችና የተከበሩ ሰዎች ራስ፣
ሐሰትን የሚያስተምሩ ነቢያት ደግሞ
ጅራት ናቸው።
16ይህን ሕዝብ የሚመሩት ያስቱታል፤
የሚመራውም ሕዝብ ከመንገድ ወጥቶ
ይባዝናል።
17ስለዚህ ጌታ በጐበዛዝት ደስ አይሰኝም፤
አባት ለሌላቸውና ለመበለቶች አይራ
ራም፤ ሁሉም ፈሪሀ እግዚአብሔር ያላደ
ረበትና ክፉ አድራጊ ነው፤
የሁሉ አፍ አስጸያፊ ቃል ይናገራልና።

ይህም ሁሉ ሆኖ፣ ቍጣው ገና አልበረደም፤
እጁም እንደተዘረጋ ነው።

18እንግዲህ ርኵሰት እንደ እሳት ይቀጣጠላል፤
እሾህንና ኵርንችትን ይበላል፤
ጥቅጥቅ ያለውን ደን ያነዳል፤
ጢሱም ተትጐልጕሎ እንደ ዐምድ
ይቆማል።
19በሰራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ቍጣ
ምድር ትጋያለች፤
ሕዝቡም እሳት ውስጥ እንደሚጨመር
ማገዶ ይሆናል፤
ወንድሙንም ማዳን የሚችል ማንም
የለም።
20በቀኝ በኩል ይጐርሳሉ፤
ነገር ግን ራባቸው አይታገሥም፤
በግራም በኩል ይበላሉ፤
ነገር ግን አይጠግቡም፤
እያንዳንዱም የገዛ ወገኑን″ ሥጋ ይበላል።
21ምናሴ ኤፍሬምን፣ ኤፍሬም ምናሴን
ይበላል፤
በይሁዳም ላይ በአንድነት ይነሣሉ፤

ይህም ሁሉ ሆኖ፣ ቍጣው ገና አልበረደም፤
እጁም እንደ ተዘረጋ ነው።

10 ፍትሕ የጐደለውን ሕግ ለሚያወጡ፣
ጭቈና የሞላበትን ሥርዐት ለሚ
ደነግጉ ወዮላቸው!
2የድኾችን መብት ለሚገፉ፣
የተጨቈነውን ሕዝቤን ፍትሕ ለሚያዛቡ፣

9፥4 መሳ7፥25፤ ኢዮ34፥24፤መዝ81፥6፤ ኢሳ10፥27፤14፥4፥25፤ 16፥4፤29፥5፥20፤ 37፥36-38፤49፥26፤ 51፥13፤54፥14፤ 58፥6፥9፤60፥18፤ ኤር2፥20፤30፥8፤ ሕዝ30፥18፤ናሆ1፥13፤ ማቴ11፥30
9፥5 ኢሳ2፥4
9፥6 ዘፍ3፥15፤ ዘፀ4፥22፤ዘዳ7፥21፤ ኢዮ15፥8፤መዝ24፥8፤ 90፥2፤ኢሳ10፥21፤ 11፥2፤22፥22፤ 26፥3፥12፤28፥29፤ 42፥13፤53፥2፥5፤ 64፥8፤66፥12፤ ኤር33፥6፤ሚክ5፥5፤ ማቴ28፥18፤ሉቃ2፥11 ፥14፤ዮሐ3፥16፤ 14፥9-10
9፥7 2ሳሙ7፥13፤ 2ነገ19፥31፤ መዝ72፥2፤85፥8፤ 119፥165፤ኢሳ1፥26፤ 2፥4፤ 11፥4፥9፤16፥5፤ 26፥3፥11፥12፤32፥1፥ 16፥17፤33፥5፤37፥32፤ 42፥1፥13፤48፥18፤ 59፥17፤60፥17፤ 63፥15፤ኤር23፥5፤ 33፥14፤ዳን2፥44፤ 4፥3፤ሉቃ1፥33፤ ዮሐ12፥34፤ 1ቆሮ15፥25
9፥8 ዘዳ32፥2
9፥9 ኢሳ7፥2፥9፤ 46፥12፤48፥4፤ ሕዝ2፥4፤ዘካ7፥11
9፥10 ዘፍ11፥3፤ 1ነገ7፥2-3፤አሞ7፥14፤ ሉቃ19፥4
9፥11 ኢሳ7፥8
9፥12 2ነገ16፥6፤ 2ዜና28፥18፤ ኢዮ40፥11፤መዝ79፥7፤ ኢሳ5፥25
9፥13 2ዜና28፥22፤ ኢሳ2፥3፤17፥7፤31፥1፤ 55፥6፤ኤር5፥3፤50፥4፤ ሕዝ7፥9፤ዳን9፥13፤ ሆሴ3፥5፤7፥7፥10፤ አሞ4፥6፥10፤ ሶፎ1፥6፤3፥7፤ ሐጌ2፥17
9፥14 ቍ14፥15፤ ኢሳ19፥15፤ራእ18፥8
9፥15 ኢዮ13፥4፤ ኢሳ3፥2-3፥8፤5፥13፤ 28፥7፤44፥20፤ ሕዝ13፥2፥22፤ ማቴ24፥24
9፥16 ኢሳ3፥12፤ ማቴ15፥14፤23፥16፥24
9፥17 ኢዮ5፥4፤ ኢሳ1፥4፤3፥8፤5፥25፤ 10፥6፤27፥11፤32፥6፤ኤር9፥21፤11፥22፤ 13፥14፤18፥21፤ 48፥15፤49፥26፤ አሞ4፥10፤8፥13፤ ሚክ7፥2፤ማቴ12፥34፤ሮሜ3፥13-14
9፥18 ዘዳ29፥23፤ መዝ83፥14፤ኢሳ1፥31፤5፥6
9፥19 ኢዮ40፥11፤ መዝ97፥3፤ ኢሳ1፥31፤ 3፥5፤13፥9፥13፤ ኤር17፥27
9፥20 ዘሌ26፥26፤ ኢዮ18፥12፤ ኢሳ49፥26፤ዘካ11፥9
9፥21 መሳ7፥22፤ 12፥4፤2ዜና28፥6፤ኢሳ5፥25
10፥1 መዝ58፥2፤ ኢሳ5፥8
10፥2 ዘዳ10፥18፤ ኢዮ6፥27፤ኢሳ1፥17፤ 3፥14፤5፥23

[o]6 ወይም፣ *ድንቅ፣ መካር*።
″20 ወይም፣ *ክንዱን*

መበለቶችን ለሚበዘብዙ፣
ወላጅ የሌላቸውን ልጆች ለሚመዘብሩ
ወዮላቸው!
3በምትጐበኙበት ቀን ምን ይውጣችኋል?
ጥፋት ከሩቅ ሲመጣስ ምን ትሆናላችሁ?
ርዳታን ለማግኘትስ ወደ ማን ትሸሻላችሁ?
ሀብታችሁንስ የት ታገኙታላችሁ?
4ከእስረኞች ጋር ከመርበትበት፣
ከታረዱትም ጋር ከመጣል በቀር ምንም
አይተርፋችሁም።

ይህም ሁሉ ሆኖ፣ ቍጣው ገና አልበረደም፤
እጁም እንደ ተዘረጋ ነው።

## *የእግዚአብሔር ፍርድ በአሦር ላይ*

5“የቍጣዬ በትር ለሆነ፣
የመቅሠፍቴም ዱላ በእጁ ላለው ለአሦራ
ዊው ወዮለት!
6ሀብታቸውን እንዲዘርፍ፣ ምርኮን እንዲ
ያግበሰብስ፣
እንደ መንገድ ላይ ጭቃም እንዲረግጣቸው፣
አምላክ በሌለው ሕዝብ ላይ እልከዋለሁ፣
በሚያስቈጣኝም ሕዝብ ላይ እሰደዋለሁ።
7እርሱ ግን እንዲህ አላሰበም፤
በልቡም ይህ አልነበረም፤
ነገር ግን ዕቅዱ ለማጥፋት፣
ብዙ ሕዝቦችንም ለመደምሰስ ነበር።
8እንዲህም ይል ነበር፤
‘የጦር አዛዦቼ በሙሉ ነገሥታት
አይደሉምን?
9ካልኖ እንደ ከርከሚሽ፣
ሐማት እንደ አርፋድ፣
ሰማርያስ እንደ ደማስቆ አይደሉምን?

10የጣዖታትን መንግሥታት፣
ምስሎቻቸው ከኢየሩሳሌምና ከሰማርያ
መንግሥታት የሚበልጡትን
እጄ እንደ ያዘች ሁሉ፣

11በሰማርያና በጣዖቶቿ ያደረግሁትን፣
በኢየሩሳሌምና በተቀረጹ ምስሎቿስ
እንዲሁ አላደርግምን?።”

12ጌታ በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም
ላይ የሚያደርገውን ሁሉ ከፈጸመ በኋላ፣
እንዲህ ይላል የአሦርን ንጉሥ ስለ ልቡ
ትዕቢትና ስለ ንቀት አመለካከቱ
እቀጣዋለሁ፤ 13የአሦር ንጉሥ እንዲህ
ይላልና፤

“‘ይህን ሁሉ ያደረግሁት በክንዴ ብርታት
ነው፤
ደግሞም በጥበቤ አስተዋይ ነኝና።
የመንግሥታትን ድንበር አፈረስሁ፤
ሀብታቸውን ዘረፍሁ፤
ነገሥታታቸውን እንደ አንድ ኀያል ሆኜ
አዋረድሁ።[ሠ]

14ሰው እጁን ወደ ወፍ ጎጆ እንደሚሰድ፣
እኔም እንዲሁ እጄን ወደ መንግሥታት
ሀብት ሰደድሁ፤
ሰዎች የተተወ ዕንቍላል እንደሚሰበስቡ፣
እኔም እንዲሁ ምድርን ሁሉ ሰበሰብሁ፤
ክንፉን ያራገበ የለም፤
አፉንም ከፍቶ የጮኸ አልነበረም።’ ”

15መጥረቢያ በሚቈርጥበት ሰው ላይ ይኵራ
ራልን?
መጋዝስ በሚስበው ላይ ይታበያልን?
በትር በሚያነሣው ሰው ላይ ራሱን
እንደሚነቀንቅ፣
ዘንግም ራሱን ዕንጨት እንዳልሆነ አድርጎ
እንደሚኵራራ ነው።
16ስለዚህ ጌታ፣ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሐ
ር፣
በፈረጠሙ ጦረኞቹ ላይ የሚያከሳ በሽታ
ይልካል፤
ከክብሩም በታች
እንደ ነበልባል የሚንቦገቦግ እሳት
ይለኰሳል።
17የእስራኤል ብርሃን እሳት፣
ቅዱሱም ነበልባል ይሆናል፤
በአንድ ቀንም
እሾኹንና ኵርንችቱን እሳት ይበላዋል፤
18ሕመምተኛ እየመነመነ እንደሚሞት፣
የደኑን ክብርና የለማውን ዕርሻ፣
ነፍስና ሥጋንም ፈጽሞ ያጠፋል።
19በደኑ ውስጥ የሚተርፉት ዛፎች በጣም
ጥቂት ናቸው፤
ሕፃን ልጅ እንኳ ቈጥሮ ሊመዘግባቸው
ይችላል።

## የተረፉት የእስራኤል ዘሮች

20በዚያን ቀን ከእስራኤል ዘር የተረፉት፣
ከያዕቆብም ቤት የዳኑት፣
ከእንግዲህ ወዲህ
በመታቸው ላይ አይታመኑም፤
ነገር ግን በእስራኤል ቅዱስ *በእግዚአብሔር*
ላይ፣
በእውነት ይታመናሉ።
21የተረፉት ይመለሳሉ፣[የ]
ከያዕቆብ ቤት የተረፉት ወደ ኀያሉ
አምላክ ይመለሳሉ።

10፥3 ቍ25፤ ኢዮ31፥14፤መዝ59፥5፤ 108፥12፤ኢሳ1፥24፤ 13፥6፤14፥23፤20፥6፤2 4፥6፤26፥14፤30፥7፤31፥ 3፤47፥11፤ኤር5፥9፤ 9፥9፤50፥15፤ ሉቃ19፥44
10፥4 ኢሳ5፥25፤ 12፥1፤22፥2፤24፥22፤ 34፥3፤63፥10፤64፥5፤6 6፥16፤ኤር4፥8፤ 30፥24፤39፥6፤ ሰቆ1፥12፤ናሆ3፥3፤ ዘካ9፥11
10፥5 ቍ12፥15፡ 18፥24፤2ነገ19፥21፤ ኢሳ7፥20፤9፥4፤13፥3፡ 5፡13፤14፥5፡25፤ 26፥20፤28፥1፤ 30፥30፡31፤31፥8፤ 34፥2፤ 37፥7፤41፥15፤ 45፥1፤54፥16፤63፥6፤ 66፥14፤ኤር50፥23፤ 51፥20፤ ሕዝ30፥24-25፤ ሶፎ2፥13
10፥6 መሳ6፥4፤ 2ሳሙ22፥43፤ 2ዜና28፥9፤መዝ7፥5፤ ኢሳ5፥5፡29፤8፥1፤ 9፥17፡19፤37፥26-27፤ ዕን1፥12
10፥7 ዘፍ50፥20፤ ሐሥ4፥23-28
10፥8 2ነገ18፥24
10፥9 ዘፍ10፥10፤ 14፥15፤ ዘኍ34፥8፤ 2ነገ16፥9፤17፥6፤ 18፥34፤2ዜና8፥4፤ 35፥20፤ኢሳ11፥11፤ ኤር49፥24
10፥10 2ነገ19፥18
10፥11 2ነገ19፥13፤ ኢሳ2፥8፤36፥18-20፤ 37፥10-13
10፥12 ቍ5፤ 2ነገ19፥7፡31፤ መዝ18፥27፤ ኢሳ2፥11፤28፥21-22፤ 30፥31-33፤37፥36-38፤ 65፥7፤66፥4፤ ኤር5፥29፤50፥18፤ ሕዝ28፥17
10፥13 ዘዳ8፥17፤ 32፥26-27፤ ኢሳ14፥13-14፤47፥7፤ ሕዝ28፥4፤ዳን4፥30
10፥14 2ነገ19፥22-24፤ ኢዮ31፥25፤ ኢሳ14፥6፤37፥24-25፤ ኤር49፥16፤አብ1፥4፤ዕ ን2፥6-11
10፥15 ቍ5፤ ኢሳ7፥20፤45፥9፤ ሮሜ9፥20-21
10፥16 ቍ18፤ ዘኍ11፥33፤ መዝ78፥31፤ኢሳ8፥7፤ 17፥4፤ኤር21፥14
10፥17 ዘኍ11፥1-3፤ 2ሳሙ23፥6፤ ኢዮ41፥21፤ኢሳ1፥31፤ 9፥18፤31፥9፤37፥23፤ዘካ2፥5 10፥18 ቍ5፤ 2ነገ19፥23
10፥19 ቍ33-34፤ ኢሳ17፥6፤21፥17፤ 27፥13፤32፥19፤ ኤር44፥28 10፥20 ቍ27፤ 2ነገ16፥7፤ 2ዜና14፥11፤28፥20፤ ኢሳ1፥9፤5፥24፤ 11፥10፡11፤12፥1፡4፤17፥7፤19፥18፡19፤ 24፥21፤28፥5፤48፥2፤ 50፥10፤52፥6፤ ኤር21፥2፤ሕዝ7፥16፤ ሆሴ3፥5፤6፥1፤ ሚክ3፥11፤7፥7፤ ዘካ9፥16 10፥21 ዘፍ45፥7፤ ኢሳ6፥13፤7፥3፤9፥6፤ ሶፎ3፥13

[ሠ]13 ወይም፣ *ኀይላቸውን አዋረድሁ*።
[የ]21 በዚህና በቍ22 ላይ ዕብራይስጡ፣ *ሼር - ያሹብ* ይላል።

22እስራኤል ሆይ፤
ሕዝብህ እንደ ባሕር አሸዋ ቢሆንም፣
የተረፉት ብቻ ይመለሳሉ።
ታላቅና ጻድቅ የሆነ ጥፋት ታውጇል።
23ጌታ ፣ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣
የወሰነውን ጥፋት በምድር ሁሉ ላይ
ያመጣል።

24ስለዚህ ጌታ ፣ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤
"በጽዮን የምትኖሩ ሕዝቤ ሆይ፤
ግብፅ እንዳደረገብህ ሁሉ በትር ያነሡብህን፣
በሽመል የደበደቡህን
አሦራውያንን አትፍራቸው።
25በአንተ ላይ ያመጣሁትን ቅጣት በጥቂት
ጊዜ ውስጥ አቆማለሁ፤
በእነርሱም ላይ መቅሠፍቴን አመጣለሁ።"

26የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድያምን
በሔሬብ ዐለት አካባቢ እንደ መታ፣
በጅራፍ ይገርፋቸዋል፤
በግብፅ እንዳደረገውም ሁሉ፣
በትሩን በውሆች ላይ ያነሣል።
27በዚያን ቀን ሸክማቸው ከትከሻህ፣
ቀንበራቸውም ከዐንገትህ ላይ ይነሣል፤
ከውፍረትህም የተነሣ
ቀንበሩ ይሰበራል።ዶ

28ወደ ዐያት ይገባሉ፣
በሚግሮን ያልፋሉ፤
ጓዛቸውንም በማክማስ ያከማቻሉ።
29መተላለፊያውን ዐልፈው እንዲህ ይላሉ፤
"በጌባዕ ሰፍረን እናድራለን።"
ራማ ደነገጠች፤
የሳኦል ከተማ ጊብዓ ሸሸች።
30የጋሊም ሴት ልጅ ሆይ፤ ጩኺ!
ላይሻ ሆይ፤ አድምጪ!
ምስኪን ዓናቶት ሆይ፤ መልሺላት!
31ማድሜናህ በሽሽት ላይ ነች፤
የጌቢም ሕዝብ ሊደበቅ ይሮጣል።
32በዚህ ቀን ኖብ ይደርሳሉ፤
እጃቸውን በኢየሩሳሌም ኰረብታ፣
በጽዮን ሴት ልጅ ተራራ ላይ በዛቻ
ነቀነቁ።
33እነሆ፤ ጌታ ፣ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣
በታላቅ ኀይል ቅርንጫፎችን ይቈራ
ርጣል፤
ረጃጅም ዛፎች ይገነደሳሉ፤
ከፍ ከፍ ያሉትም ይወድቃሉ።
34ጥቅጥቅ ያለውን ደን በመጥረቢያ ይቈራርጣል፤
ሊባኖስም በኀያሉ ፊት ይወድቃል።

10፥22 ቍ23፤ ዘፍ12፥2፤ዕዝ1፥4፤ ኢሳ11፥11፤28፥22፤ 46፥3፤ 48፥19፤ ኤር33፥22፤40፥2፤ ዳን9፥27
10፥23 ቍ22፤ ኢሳ6፥12፤28፥22፤ ሮሜ9፥27-28 10፥24 ቍ5፤ ዘፀ5፥14፤መዝ87፥5-6፤ ኢሳ7፥4
10፥25 ቍ3፥5፤ መዝ30፥5፤ኢሳ13፥5፤ 17፥14፤24፥21፤ 26፥20፤29፥17፤ 30፥30፤34፥2፤66፥14፤ ዳን8፥19፤11፥36፤ ሚክ5፥6፤ሐጌ2፥6
10፥26 ዘፀ14፥16፤ ኢሳ9፥4፤30፥32፤ 37፥36-38
10፥27 ቍ20፤ ዘሌ26፥13፤ መዝ66፥11፤ኢሳ9፥4፤ 14፥25፤47፥6፤52፥2፤ኤር30፥8
10፥28 ኢሱ1፥11፤ 1ሳሙ13፥2፤14፥2
10፥29 ኢሱ18፥24፥ 25፤መሳ19፥14፤ ነህ11፥31፤ኢሳ15፥5
10፥30 1ሳሙ25፥44፤ ነህ11፥32
10፥32 1ሳሙ21፥1፤ ኢዮ15፥25፤መዝ9፥14፤ ኢሳ16፥1፤ኤር6፥23
10፥33 ዘፀ12፥12፤ ኢሳ2፥13፤5፥15፤ 18፥5፤27፥11፤ ሕዝ17፥4፤አሞ2፥9
10፥34 ዘፍ49፥24፤ 2ነገ19፥23፤ መዝ93፥4፤ኢሳ33፥21፤ ናሆ1፥12፤ዘካ11፥2
11፥1 ቍ10፤ 2ነገ19፥26፥30፤ ኢዮ14፥7፥8፤ ኢሳ4፥2፤9፥7፤27፥6፤ ማቴ1፥1፤ራእ4፥2፤ 9፥7፤27፥6፤ማቴ1፥1፤ ራእ5፥5
11፥2 ዘፀ28፥3፤ መሳ3፥10፤ኢሳ9፥6፤ 32፥15፤42፥1፤44፥3፤ 48፥16፤59፥21፤61፥1፤ ሕዝ37፥14፤39፥29፤ ኢል2፥28፤ማቴ3፥16፤ ዮሐ1፥32-33፤16፥13፤ ኤፌ1፥17፤ቈላ2፥3፤ 2ጢሞ1፥7
11፥3 ኢሳ33፥6፤ ዮሐ2፥25፤7፥24
11፥4 ኢዮ4፥9፤ 5፥16፤40፥18፤ መዝ2፥9፤18፥8፤ 72፥2፥ 4፤139፥19፤ ኢሳ3፥14፤9፥7፤ 14፥30፤27፥7፤30፥28፥ 31፥33፤ 40፥24፤ 59፥19፤ሕዝ21፥31፤ ዘካ14፥12፤ሚል4፥6፤ 2ተሰ2፥8፤

## ከእሴይ ግንድ የወጣ ቍጥቋጥ

11 ከእሴይ ግንድ ቍጥቋጥ ይወጣል፤
ከሥሮቹም አንዱ ቅርንጫፍ ፍሬ
ያፈራል።
2የእግዚአብሔር መንፈስ፣
የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፣
የምክርና የኀይል መንፈስ፣
የዕውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት
መንፈስ ያርፍበታል።
3እግዚአብሔርን በመፍራት ደስ ይለዋል፤
ዐይኑ እንዳየ አይፈርድም፤
ጆሮውም እንደ ሰማ አይበይንም።
4ነገር ግን ለድኾች በጽድቅ ይፈርዳል፤
ለምድር ምስኪኖችም ፍትሕን ይበይናል፤
በአፉ በትር ምድርን ይመታል፤
በከንፈሩም እስትንፋስ ክፉዎችን
ይገድላል።
5ጽድቅ የወገቡ መታጠቂያ፣
ታማኝነትም የጐኑ መቀነት ይሆናል።

6ተኵላ ከበግ ጠቦት ጋር ይኖራል፤
ነብርም ከፍየል ግልገል ጋር ይተኛል፤
ጥጃ፣ የአንበሳ ደቦልና የሰባ ከብት፮ በአን
ድነት ይሰማራሉ፤
ትንሽ ልጅም ይመራቸዋል።
7ላምና ድብ በአንድነት ይሰማራሉ፤
ልጆቻቸውም አብረው ይተኛሉ፤
አንበሳም እንደ በሬ ገለባ ይበላል።
8ጡት የሚጠባ ሕፃን በአደገኛ እባብ ጕድጓድ
ላይ ይጫወታል፤
ጡት የጣለም ሕፃን እጁን በእፉኝት
ጕድጓድ ይከትታል።
9በተቀደሰው ተራራዬ ሁሉ ላይ
ጕዳት ወይም ጥፋት አያደርሱም፤
ውሃ ባሕርን እንደሚሸፍን፣
ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን በማወቅ
ትሞላለችና።

10በዚያን ቀን፣ የእሴይ ሥር ለሕዝቦች
ምልክት ሆኖ ይቆማል፤ መንግሥታት ወደ
እርሱ ይመጣሉ፤ ማረፊያውም የከበረ ይሆ

ራእ19፥11፥15 11፥5 ዘፀ12፥11፤1ነገ18፥46፤ ኢሳ25፥1፤ ኤፌ6፥14 11፥6 ኢሳ65፥25 11፥7 ኢዮ40፥15
11፥8 ኢሳ14፥29፤ 30፥6፤59፥5፤65፥20 11፥9 ዘፀ7፥5፤ ዘኍ25፥12፤ 1ሳሙ17፥46፤ መዝ48፥1፤98፥2-3፤ ኢሳ2፥2፥4፤9፥7፤ 19፥21፤45፥6፥14፥ 22፤48፥20፤49፥26፤ 52፥10፤ኤር24፥7፤ 31፥34፤ዕን2፥14 11፥10 ቍ1፤ መዝ20፥5፤116፥7፤ኢሳ2፥4፤ 10፥20፤ 14፥1፥3፤18፥3፤ 28፥12፤32፥17-18፤ 40፥2፤49፥23፤ 56፥3፥6፤ 60፥5፥10፤ኤር4፥6፤6፥16፤30፥10፤46፥27፤ሐጌ2፥9፤ ዘካ2፥5፤ ሉቃ2፥32፤ዮሐ12፥32፤ሐሥ11፥18፤ሮሜ15፥12

ዶ27 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ግን፣ *ቀንበሩ ከትከሻህ ላይ ይሰበራል* ይላል።
፮6 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ግን፣ *የሰባ አንበሳ ይበላል* ይላል።

ናል። 11በዚያን ቀን፣[ገ] ጌታ እጁን ዘርግቶ
እንደ ገና የተረፈውን የሕዝቡን ቅሬታ
ከአሦር፣ ከታችኛው ግብፅ፣ ከላይኛው
ግብፅ፣ ከኢትዮጵያ፣ ከኤላም፣ ከባቢሎን፣
ከሐማትና ከባሕር ጠረፍ ምድር ይሰበ
ስባል።

12ለመንግሥታት ምልክትን ያቆማል፤
ከእስራኤልም የተሰደዱትን መልሶ ያመ
ጣቸዋል፤
የተበተኑትን የይሁዳ ሕዝብ፣
ከአራቱ የምድር ማእዘን ይሰበስባል።
13የኤፍሬም ምቀኝነት ያከትማል፤
የይሁዳ ጠላቶችም[ጠ] ይቈረጣሉ፤
ኤፍሬም በይሁዳ አይቀናም፤
ይሁዳም ኤፍሬምን አይጠላም።
14በምዕራብ በኩል በፍልስጥኤም ተረተር
ላይ
ይወርዳሉ፤
ሁለቱም ተባብረው በምሥራቅ ያለውን
ሕዝብ ይዘርፋሉ፤
በኤዶምና በሞዓብ ላይ እጃቸውን ያነሣሉ፤
አሞናውያንም ይገዙላቸዋል።
15*እግዚአብሔር*
በሚጋረፍም ነፋስ
የግብፅን ባሕረ ሰላጤ ያደርቃል፤
እጁን በኤፍራጥስ ወንዝ[ጨ] ላይ ይዘረጋል፤
ሰባት ታናናሽ ጅረትም አድርጎ ይለያየዋል፤
ስለዚህ ሰዎች ከነጫማቸው መሻገር ይችላሉ።
16እስራኤል ከግብፅ በወጣ ጊዜ
እንደ ሆነው ሁሉ፣
ከአሦር ለተረፈው ቅሬታ ሕዝብ፣
እንዲሁ ጐዳና ይዘጋጅለታል።

## የውዳሴ መዝሙር

12 በዚያን ቀን እንዲህ ትላለህ፤
"*እግዚአብሔር* ሆይ፤
ቀድሞ ተቈጥተኸኝ ነበር፤
አሁን ግን ከቍጣህ ተመለስህ፤
ደግሞም አጽናንተኸኛልና እወድስሃለሁ።
2እነሆ፣ እግዚአብሔር ድነቴ ነው፤
እታመናለሁ፣ ደግሞም አልፈራም፤
*ጌታ *እግዚአብሔር* ብርታቴና ዝማሬዬ ነው፤
ድነቴም ሆኖአል።"
3ከድነቴ ምንጮች
ውሃ በደስታ ትቀዳላችሁ።

4በዚያን ቀን እንዲህ ትላላችሁ፤
"*እግዚአብሔርን* አመስግኑ፤ ስሙንም ጥሩ፤
ያደረገውንም በአሕዛብ መካከል አስታውቁ፤
ስሙ ከፍ ከፍ ማለቱንም ዐውጁ።
5ለ*እግዚአብሔር* ዘምሩ፤ ታላቅ ሥራ
ሠርቶአልና፤
ይህም ለዓለም ሁሉ ይታወቅ።

11፥11 ዘፍ10፥6፡22፤ ዘዳ30፥4፤ኢሳ1፥9፤ 10፥9፡20፤19፥24፤ 24፥15፤41፥1፡5፤ 42፥4፡10፡12፤49፥1፡ 12፤51፥5፤59፥18፤ 60፥9፤66፥19፤ ኤር16፥15፤44፥1፡15፤4 6፥27፤ሕዝ29፥14፤ 30፥14፤38፥8፤ ሆሴ11፥11፤ ሚክ7፥12፤ዘካ8፥7፤ 10፥10፤ሐሥ8፥27
11፥12 ነህ1፥9፤ መዝ20፥5፤48፥10፤ 67፥7፤106፥47፤ ኢሳ14፥1፡2፤41፥5፡14፤ 43፥5፤49፥5፡22፤ 54፥7፤ኤር16፥15፤ 31፥10፤32፥37፤ ሕዝ28፥25፤ሶፎ3፥10፤ ራእ7፥1
11፥13 2ዜና28፥6፤ ኤር3፥18፤ሕዝ37፥16-17፡22፤ሆሴ1፥11
11፥14 ዘኍ24፥18፤ መሳ6፥3፤ 11፥14-18፤2ዜና26፥6፤28፥18፤ መዝ137፥7፤ ኢሳ15፥1፤16፥14፤ 25፥3፡10፤34፥5-6፤ 60፥12፤63፥1፤ ኤር48፥40፤49፥22፤ ሕዝ25፥12፤ዳን11፥41፤ ኢል3፥19፤አብ1፥1፤ ሶፎ2፥8፡11፤ሚል1፥4
11፥15 ዘፍ41፥6፤ ዘፀ14፥22፡29፤ ዘዳ11፥10፤ኢሳ7፥20፤ 19፥16፤30፥32፤ 37፥25፤42፥15፤ ኤር50፥38፤51፥36
11፥16 ቍ11፤ ዘፍ45፥7፤ ዘፀ14፥26-31፤ ኢሳ19፥23፤35፥8፤ 40፥3፤49፥11፤51፥10፤ 57፥14፤62፥10፤ ኤር50፥5
12፥1 ኢዮ13፥16፤ መዝ9፥1፤71፥21፤ ኢሳ10፥20፤25፥1
12፥2 ዘፀ15፥2፤ ኢዮ13፥15፤ መዝ18፥1፤ 26፥1፤112፥7፤ ኢሳ17፥10፤25፥9፤ 26፥3፡4፤33፥6፤ 38፥11፤45፥17፤ 51፥5፡6፤54፥8፤ 59፥16፤61፥10፤ 62፥11፤ዳን6፥23
12፥3 ዘፀ15፥25፤ 2ነገ3፥17፤መዝ36፥9፤ ኤር2፥13፤17፥13፤ ዮሐ4፥10፡14
12፥4 ዘፀ3፥15፤ መዝ80፥18፤105፥1፤1 13፥2፤ኢሳ10፥20፤ 24፥15፤25፥1፤26፥8፡1 3፤54፥5፤60፥3፤ ኤር10፥7፤ሶፎ2፥11፤ ሚል1፥11
12፥5 ዘፀ15፥1፤ መዝ98፥1

6የጽዮን ሕዝብ ሆይ፤ እልል በሉ፤ በደስታም
ዘምሩ፤
በመካከላችሁ ያለው የእስራኤል ቅዱስ
ታላቅ ነውና።

## በባቢሎን ላይ የተነገረ ትንቢት

13 የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ ስለ ባቢ
ሎን ያየው ንግር፤
2በተራቈተ ኰረብታ ዐናት ላይ ምልክት
ስቀሉ፤
ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ጩኹ፤
በመሳፍንቱም በር እንዲገቡ፣
በእጅ ምልክት ስጡ።
3በድል አድራጊነቴ ደስ የሚላቸውን
ቅዱሳኔን አዛለሁ፤
ቍጣዬንም እንዲፈጽሙ፣
ተዋጊዎቼን ጠርቻለሁ።

4በተራሮች ላይ እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ፣
የሚሰማውን ጩኸት አድምጡ!
በመንግሥታትም መካከል፣
እንደ ተጨናነቀ ሕዝብ ድምፅ የሆነውን
ውካታ ስሙ!
የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*
ሰራዊቱን ለጦርነት አሰልፎአል።
5*እግዚአብሔርና* የቍጣው ጦር መሣሪያ፣
ምድሪቱን በሙሉ ለማጥፋት፣
ከሩቅ አገር፣
ከሰማያትም ዳርቻ መጥተዋል።

6*የእግዚአብሔር* ቀን ቀርቦአልና አልቅሱ፤
ሁሉን ቻይ[ጸ] ከሆነ አምላክ ዘንድ ጥፋት
ይመጣልና።
7ስለዚህ እጆች ሁሉ ሽባ ይሆናሉ፤
የሰውም ሁሉ ልብ ይቀልጣል።
8ሽብር ይይዛቸዋል፤
ሥቃይና ጭንቀት ይደርስባቸዋል፤
ምጥ እንደ ያዛት ሴት ያምጣሉ፤

12፥6 ዘፍ21፥6፤ መዝ46፥5፤48፥1፤ 78፥41፤98፥4፤99፥2፤ ኢሳ1፥24፤10፥20፤ 17፥7፤24፥14፤29፥19፤37፥23፤43፥3፡14፤45፥11፤ 48፥20፤ 49፥26፤52፥8፤55፥5፤ኤር20፥13፤31፥7፤ሕዝ39፥7፤ ሶፎ3፥14-17፤ዘካ2፥10 13፥1 ቍ19፤ ዘፍ10፥10፤ኢሳ1፥1፤ 14፥4፡28፤15፥1፤ 20፥2፤21፥1፡9፤ 37፥2፤46፥1-2፤48፥14፤ ኤር24፥1፤25፥12፤ናሆ1፥1፤ዕን1፥1፤ዘካ9፥1፤12፥1፤ ሚል1፥1፤ ራእ14፥8 13፥2 መዝ20፥5፤ ኢሳ24፥12፤45፥2፤ ኤር50፥2፤ 51፥27፡58 13፥3 ቍ17፤ኢዮ40፥11፤መዝ149፥2፤ኢሳ10፥5፤21፥2፤ ኤር51፥11፤ዳን5፥28፡31፤ኢል3፥11 13፥4 መዝ46፥6፤ ኢሳ42፥13፤ 46፥6፤ 47፥4፤51፥15፤ኤር50፥41፤ኢል3፥14 13፥5 ኢሱ6፥17፤ኢሳ5፥26፤10፥25፤24፥1፤30፥25፤34፥2፤45፥1፤ 54፥16፤ ኤር50፥25 13፥6 ዘፍ17፥1፤ኢሳ2፥12፤10፥3፤ 14፥15፡31፤15፥2፤ 16፥7፤23፥1፤ሕዝ30፥2፤ያዕ5፥1 13፥7 ኢሱ2፥11፤ 2ነገ19፥26፤ኢዮ4፥3፤ኤር47፥3፤ሕዝ21፥7 13፥8 ዘፍ3፥16፤ዘፀ15፥14፤መዝ31፥13፤ 48፥5፤ ኢሳ21፥4፤ ኢል2፥6፤ ናሆ2፥10፤ ዮሐ16፥21

[ገ]11 ዕብራይስጡ፣ *ከጳትሮስ* ይላል።
[ጠ]13 ወይም፣ *ባላንጣዎቹ*። [ጨ]15 ዕብራይስጡ *ወንዙ* ይላል።
[ጸ]6 ዕብራይስጡ *ሻዳይ* ይላል።
* እግዚአብሔር በሚለው ስም ፈንታ ተተክቶ የገባ ነው።

እርስ በርሳቸው በድንጋጤ ይተያያሉ፤
ፊታቸውም በፍርሀት ቀይ ይሆናል።
9እነሆ፤ የእግዚአብሔር ቀን ጨካኝ ነው፤
ምድርን ባድማ ሊያደርጋት፣
በውስጧም ያሉትን ኀጢአተኞች ሊያጠፋ፣
ከመዓትና ከብርቱ ቍጣ ጋር ይመጣል።
10የሰማይ ከዋክብትና ሰራዊታቸው፣
ብርሃን አይሰጡም፤
ፀሓይ ገና ከመውጣቷ ትጨልማለች፤
ጨረቃም ብርሃኗን አትሰጥም።
11ዓለምን ስለ ክፋቷ፣
ክፉዎችንም ስለ ኀጢአታቸው እቀጣለሁ፤
የትዕቢተኞችን እብሪት እሽራለሁ፤
የጨካኞችንም ጕራ አዋርዳለሁ።
12ሰውን ከነጠረ ወርቅ ይልቅ ውድ፣
ከኦፊርም ወርቅ ይበልጥ ብርቅ አደርጋለሁ።
13ስለዚህ በሰራዊት ጌታ በእግዚአብሔር መዓት፣
ቍጣው በሚነድበት ቀን፣
ሰማያትን እነቀንቃለሁ፤
ምድርንም ከስፍራዋ አናውጣለሁ።
14እንደሚታደን ሚዳቋ፣
እረኛም እንደሌለው የበግ መንጋ፣
እያንዳንዱ ወደ ወገኑ ይመለሳል፣
እያንዳንዱም ወደ አገሩ ይሸሻል።
15የተማረከ ሁሉ ይወጋል፤
የተያዘም ሁሉ በሰይፍ ይወድቃል።
16ዐይናቸው እያየ ሕፃናታቸው ይጨፈጨፋሉ፤
ቤታቸው ይዘረፋል፤ ሚስቶቻቸው ይደፈራሉ።
17እነሆ፤ ለብር ደንታ የሌላቸውን፣
በወርቅም ደስ የማይሰኙትን፣
ሜዶናውያንን አስነሣባቸዋለሁ።
18ቀስታቸው ጐበዞችን ይፈጃል፤
ሕፃናትን አይምሩም፤
ዐይናቸውም ለልጆች አይራራም።
19የመንግሥታት ዕንቍ፣
የከለዳውያን[ጸ] ትምክሕት፣
የሆነችውን ባቢሎንን፣
እግዚአብሔር እንደ ሰዶምና እንደ ገሞራ ይገለብጣታል።
20በዘመናት ሁሉ የሚቀመጥባት አይኖርም፤
የሚቀመጥባትም የለም
ዐረብ በዚያ ድንኳኑን አይተክልም፤
እረኛም መንጋውን በዚያ አያሳርፍም።
21ነገር ግን የምድረ በዳ አራዊት በዚያ ይተኛሉ፤
ቀበሮዎች ቤቶቿን ይሞላሉ፤
ጕጕቶች በዚያ ይኖራሉ፤
በበረሓ ፍየል የሚመስሉ አጋንንትም ይዘላለሉባታል።

13፥9 ኢሳ2፥12፤ 9፥19፤26፥21፤66፥16፤ ኤር6፥23፤25፥31፤ 51፥2፤ኢል3፥2
13፥10 ዘፀ10፥22፤ ኢዮ9፥7፤ኢሳ5፥30፤ 24፥23፤ሕዝ32፥7፤ አሞ5፥20፤8፥9፤ ዘካ14፥7፤ማቴ24፥29፤ ማር13፥24፤ራእ8፥12
13፥11 መዝ10፥5፤ 125፥3፤ምሳ16፥18፤ ኢሳ2፥9፤3፥11፤11፥4፤ 23፥9፤25፥3፡5፤ 26፥21፤29፥5፡20፤ 49፥25፡26፤65፥6-7፤ 66፥16፤ሕዝ28፥2፤ ዳን4፥37፤5፥23
13፥12 ዘፍ10፥29፤ ኢሳ4፥1
13፥13 ኢዮ9፥5፡6፤ መዝ102፥26፤ ኢሳ9፥19፤14፥16፤ 34፥4፤51፥6፤ ማቴ24፥7፤ማር13፥8
13፥14 ዘፍ11፥9፤ 1ነገ22፥17፤ምሳ6፥5፤ኢሳ17፥13፤21፥15፤ 22፥3፤33፥3፤ኤር4፥9፤46፥16፤50፥16፤51፥9፤ናሆ3፥7፤ማቴ9፥36፤ ዮሐ10፥11
13፥15 ኢሳ14፥19፤ ኤር50፥25፤51፥4
13፥16 ቍ18፤ ዘፍ34፥29፤ዘኍ16፥27፤ 2ነገ8፥12፤ሆሴ13፥16
13፥17 ቍ3፤ 2ነገ18፥14-16፤ ምሳ6፥34-35፤ ኤር50፥9፡41፤51፥1
13፥18 ቍ16፤ ዘዳ32፥25፤መዝ7፥12፤ኢሳ14፥22፤41፥2፤ 47፥6፡9፤ኤር6፥23፤49፥26፤50፥9፡14፡29፡ 30፡42፤51፥4
13፥19 ቍ1፤ ዘፍ19፥25፤ መዝ137፥8፤ ኢሳ1፥9-10፤47፥5፤ ዳን2፥37፡38፤4፥30፤ ሮሜ9፥29፤ራእ14፥8
13፥20 2ዜና17፥11፤ ኢሳ14፥23፤34፥10-15፤ ኤር51፥29፡37-43፡62
13፥21 ዘሌ11፥16-18፤ 17፥7፤ዘዳ14፥15-17፤ 2ዜና11፥15፤ መዝ74፥14፤ኤር14፥6፤ ራእ18፥2
13፥22 ዘዳ32፥35፤ ኢሳ25፥2፤32፥14፤ 34፥13፡14፤35፥7፤ 43፥20፤ኤር9፥11፤ 48፥16፤49፥33፤ 50፥39፤51፥33፡37፤ሚል1፥3
14፥1 ዘፍ18፥19፤ ዘፀ12፥43፤2ዜና6፥6፤ መዝ102፥13፤ ኢሳ11፥10፤41፥8፤ 42፥1፤44፥1፤45፥4፤

22ጅቦች በምሽጎቿ፣
ቀበሮዎችም በተዋቡ ቤተ መንግሥቶቿ ይጮኻሉ፤
ጊዜዋ ቀርቦአል፤
ቀኗም አይራዘምም።

14 እግዚአብሔር ለያዕቆብ ይራራለታል፤
እስራኤልን እንደ ገና ይመርጠዋል፤
በራሳቸውም አገር ያኖራቸዋል።
መጻተኞች አብረዋቸው ይኖራሉ፤
ከያዕቆብም ቤት ጋር ይተባበራሉ።
2አሕዛብም ይወስዷቸዋል፤
ወደ ገዛ ስፍራቸውም ይመልሷቸዋል።
የእስራኤል ቤት አሕዛብን ርስት ያደርጓቸዋል፤
በእግዚአብሔርም ምድር ወንዶችና ሴቶች
ባሪያዎች አድርገው ይገዟቸዋል፤
የማረኳቸውን ይማርኳቸዋል፤
የጨቈኗቸውንም ይገዟቸዋል።
3እግዚአብሔር ከሥቃይህ፣ ከመከራህና
ከጽኑ ባርነትህ ባሳረፈህ ቀን፣ 4በባቢሎን
ንጉሥ ላይ ትሣለቃለህ፤ እንዲህም ትላለህ፤
ጨቋኙ እንዴት አበቃለት!
አስገባሪነቱስ[ፊ] እንዴት አከተመ!
5እግዚአብሔር የክፉዎችን ዘንግ፣
የገዦችንም በትረ መንግሥት ሰብሮአል፤
6ሕዝቦችን በማያቋርጥ ቍጣ የመታውን፣
ያለ ርኅራኄ እያሳደደ
የቀጠቀጠውን ሰብሮአል።
7ምድር ሁሉ ሰላምና ዕረፍት አግኝታለች፤
የደስታም ዝማሬ ታስተጋባለች።
8ጥድና የሊባኖስ ዝግባ እንኳ ደስ ብሎአቸው፣
"አንተም ወደቅህ፤
ዕንጨት ቈራጭም
መጥረቢያ አላነሣብንም" አሉ።
9በመጣህ ጊዜ
ሲኦል[ፐ] ልትቀበልህ ተነሣሥታለች፤

49፥7፡10፡13፤54፥7-8፡10፤65፥9፡22፤ኤር3፥18፤16፥15፤ 23፥8፤33፥26፤ሕዝ47፥22፤ዘካ1፥17፤ 2፥12፤3፥2፤8፥22-23፤ 10፥6፤ኤፌ2፥12-19 14፥2 መዝ49፥14፤ 149፥8፤ኢሳ11፥12፤ 26፥15፤43፥14፤ 45፥14፤49፥7፡23፡25፤ 54፥3፤60፥9፡12፡14፤ 61፥5፤ኤር30፥16፤ 40፥1፤49፥2፤ሕዝ39፥10፤ሶፎ3፥19፤ዘካ2፡9 14፥3 ዘፀ1፥14፤ኢዮ3፥17፤ኢሳ11፥10 14፥4 ኢሳ9፥4፤ 13፥1፤ሚክ2፥4፤ዕን2፥6 14፥5 መዝ110፥2፤125፥3፤ኢሳ10፥15 14፥6 2ነገ15፥29፤ መዝ47፥3፤ኢሳ10፥14፤47፥6፤ ዕን1፥17 14፥7 ዘኍ6፥26፤ መዝ98፥1፤126፥1-3፤ኢሳ12፥6፤ ኤር50፥34፤ ዘካ1፥11 14፥8 2ነገ19፥23፤ 1ዜና16፥33፤ መዝ65፥13፤ኢሳ37፥24፤ሕዝ31፥16 14፥9 ኢዮ3፥14፤26፥5፤ ምሳ30፥16፤ሕዝ32፥21፤ዘካ10፥3

[ጸ]19 ወይም፣ *ባቢሎናውያን* ማለት ነው።
[ፊ]4 የሙት ባሕር ጥልቅ፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒምና የሱርስቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ነገር ግን በማሶሬቱ ቅጅ የቃሉ ትርጒም በትክክል አይታወቅም።
[ፐ]9 በዚህና በቍጥር 11 እንዲሁም 15 ላይ አንዳንድ ቅጆች፣ *መቃብር* ይላሉ።

ይቀበሉህም ዘንድ የሙታንን መናፍስት፣
በዓለም ገዥ የነበሩትን ሁሉ ቀሰቀሳለች፤
በአሕዛብ ላይ የነገሡትን ነገሥታት
ከዙፋናቸው አውርዳለች፡፡
10እነርሱ ሁሉ ይመልሱልሃል፤
እንዲህም ይሉሃል፤
“አንተም እንደ እኛ ደከምህ፤
እንደ እኛም ሆንህ፡፡”
11ክብርህ፣ ከነበገና ድምፁ
ወደ ሲኦል ወረደ፤
ብሎች ከበታችህ ተነጥፈዋል፤
ትሎችም መደረቢያህ ይሆናሉ፡፡

12አንተ የንጋት ልጅ፣ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፤
እንዴት ከሰማይ ወደቅህ!
አንተ ቀድሞ መንግሥታትን ያዋረድህ፤
እንዴት ወደ ምድር ተጣልህ!
13በልብህም እንዲህ አልህ፤
“ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፤
ዙፋኔንም
ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ አደ ርጋለሁ፤
በተራራው መሰብሰቢያ፣
በተቀደሰውም ተራራ[ሀ] ከፍታ ላይ በዙፋኔ እቀመጣለሁ፤
14ከደመናዎችም ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፤
ራሴንም እንደ ልዑል አደርጋለሁ፡፡”
15ነገር ግን ወደ ሲኦል፣
ወደ ጥልቁም ጕድጓድ ወርደሃል፡፡

16የሚያዩህም አትኵረው እየተመለከቱህ፣
በመገረም ስለ አንተ እንዲህ ይላሉ፤
“ያ ምድርን ያናወጠ፣
መንግሥታትን ያንቀጠቀጠ፣ ይህ ሰው ነውን?
17ዓለምን ምድረ በዳ ያደረገ፤
ከተሞችን ያፈራረሰ፣
ምርኮኞቹንም ወደ አገራቸው እንዳይሄዱ የከለከለ ይህ ነውን?”

18የአሕዛብ ነገሥታት ሁሉ በክብር
አንቀላፍተዋል፤
በየመቃብራቸው ዐርፈዋል፡፡
19አንተ ግን እንደማይፈለግ ቅርንጫፍ፣
ከመቃብር ወጥተህ ተጥለሃል፤
በሰይፍ በተወጉት፣
ወደ ጥልቁ ድንጋዮች በወረዱት፣
በተገደሉትም ተሸፍነሃል፡፡
እንደ ተረገጠም ሬሳ ሆነሃል፡፡
20ከእነርሱ ጋር በመቃብር አትሆንም፤
ምድርህን አጥፍተሃልና፤
ሕዝብህንም ፈጅተሃልና፡፡

የክፉ አድራጊዎች ዘር
ፈጽሞ አይታወስም፡፡
21ተነሥተው ምድርን እንዳይወርሱ፣
ዓለምንም በከተሞቻቸው እንዳይሞሉ፣
ስለ አባቶቻቸው ኀጢአት፣
ወንድ ልጆቹ የሚታረዱበትን ስፍራ አዘጋጁ፡፡
22“በእነርሱ ላይ እነሣለሁ”
ይላል የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*፡፡
“ስሟንና ትሩፋኖቿን፣
ዘሯንና ትውልዷን ከባቢሎን እቈርጣለሁ”
ይላል *እግዚአብሔር*፡፡
23“የጃርት መኖሪያ፣
ረግረጋማ ቦታ አደርጋታለሁ፤
በጥፋትም መጥረጊያ እጠርጋታለሁ”
ይላል የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*፡፡

## በአሦር ላይ የተነገረ ትንቢት

24የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ብሎ ምሎአል፤
“እንደ ዐቀድሁት በእርግጥ ይከናወናል፤
እንደ አሰብሁትም ይሆናል፡፡
25አሦርን በምድሬ ላይ አደቃለሁ፤
በተራራዬም ላይ እረግጠዋለሁ፤
ቀንበሩ ከሕዝቤ ላይ ይነሣል፤
ሸክሙም ከትከሻቸው ላይ ይወርዳል፡፡”

26ለምድር ሁሉ የታሰበው ዕቅድ ይህ ነው፤
በአሕዛብም ሁሉ ላይ የተዘረጋው እጅ ይኸው ነው፡፡
27የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ አስቦአል፤
ማንስ ያግደዋል?
እጁም ተዘርግቶአል?
ማንስ ይመልሰዋል?

## በፍልስጥኤማውያን ላይ የተነገረ ትንቢት

28ንጉሡ አካዝ በሞተበት ዓመት እንዲህ የሚል ንግር መጣ፤
29“እናንት ፍልስጥኤማውያን ሆይ፤
የመታችሁ በትር ስለ ተሰበረ ሁላችሁ ደስ
አይበላችሁ፤
ከእባቡ ሥር እፉኝት ይወጣልና፤
ፍሬውም ተወርዋሪ መርዘኛ እባብ ይሆናል፡፡
30ከድኻም ድኻ የሆኑት መሰማሪያ ያገኛሉ፤
ችግረኞችም ተዝናንተው ይተኛሉ፤
ሥርህን ግን በራብ እገድላለሁ፤
ትሩፋንህንም እፈጃለሁ፡፡
31በር ሆይ፣ ዋይ በል፤ ከተማ ሆይ ጩኽ፣

**14፥10** ሕዝ26፥20፤ 32፥21 **14፥11** ዘኍ16፥30፤ ኢዮ7፥5፤21፥26፤ 24፥20፤ምሳ30፥16፤ ኢሳ5፥12፤51፥8፤ 66፥24፤ሕዝ26፥13፤ አሞ6፥5 **14፥12** ሕዝ26፥17፤ ሉቃ10፥18፤ 2ጴጥ1፥19፤ራእ2፥28፤ 8፥10፤9፥1 **14፥13** መዝ82፥1፤ ኢሳ37፥24፤ሕዝ28፥2፤ ዳን5፥23፤8፥10፤ አብ1፥4፤ማቴ11፥23፤ 2ተሰ2፥4 **14፥14** ዘፍ3፥5፤ ዘኍ24፥16፤ኢዮ20፥6፤ ኢሳ10፥13፤47፥8፤ ኤር50፥29፤51፥53፤ ዳን11፥36፤2ተሰ2፥4 **14፥15** ኢዮ21፥13፤ መዝ55፥23፤ኢሳ13፥6፤ 45፥7፤47፥11፤ ኤር51፥8፥43፤ ሕዝ31፥16፤32፥23፤ ማቴ11፥23፤ ሉቃ10፥15 **14፥16** ኢሳ2፥19፤ 13፥13፤ኤር50፥23፤ ኢል3፥16፤ ሐጌ2፥6፥21፤ ራእ18፥9 **14፥17** ዘፀ7፥14፤ 2ነገ15፥29፤መዝ52፥7፤ ኢሳ15፥6፤ኤር50፥33፤ ኢል2፥3፤ራእ18፥18 **14፥18** ኢዩ21፥32 **14፥19** ኢሳ13፥15፤ 22፥16-18፤34፥3፤ ኤር8፥1፤36፥30፤ 41፥7-9 **14፥20** ዘዳ32፥26፤ 1ነገ21፥19፤ኢዮ18፥19፤ ኢሳ1፥4 **14፥21** ዘፍ9፥25፤ ዘሌ26፥39፤ ዘኍ16፥27 **14፥22** 2ሳሙ18፥18፤ 1ነገ14፥10፤ኢዮ18፥17፥ 19፤መዝ9፥6፤94፥16፤ 109፥13፤ኢሳ13፥18፤ ናሆ1፥14 **14፥23** ዘሌ11፥16-18፤ኢሳ10፥3፤34፥11-15፤ኤር25፥12፤50፥3፤ 51፥62፤ሶፎ2፥14 **14፥24** ኢዮ9፥3፤ ኢሳ7፥7፤19፥12፥17፤ 23፥8-9፤25፥1፤ 45፥23፤46፥10-11፤ 49፥18፤54፥9፤62፥8፤ሕዝ12፥25፤ዳን4፥35፤ ሐሥ4፥28 **14፥25** ኢሳ9፥4፤ 10፥5፥12፥27፤ 37፥36-38 **14፥26** ዘፀ15፥12፤ ኢዮ30፥21፤ኢሳ23፥9 **14፥27** ዘፀ14፥21፤ 2ዜና20፥6፤ኢሳ43፥13፤ ኤር49፥20፤ዳን4፥35

**14፥28** 2ነገ15፥7፤ 16፥1፤ኢሳ13፥1 **14፥29** ዘዳ8፥15፤ ኢሱ13፥3፤2ነገ1፥2፤ 2ዜና26፥6፤ኢሳ11፥8 **14፥30** ኢሳ3፥15፤ 7፥21-22፤8፥21፤ 9፥20፤25፥4፤51፥19፤ኤር25፥16፤ ሕዝ25፥15-17፤ ሶፎ2፥5፤ዘካ9፥5-6 **14፥31** ዘፍ10፥14፤ኢሳ3፥26፤ 5፥27፤13፥6፤41፥25፤ኤር1፥14፤4፥6፤6፥1፥22፤ 10፥22፤13፥20፤ 25፥9፤46፥20፥24፤ 47፥2፤50፥41፤

[ሀ] 13 ወይም *ሰሜን*፤ በዕብራይስጡ፣ *ዛፎን* ተብሎ መተርጐም ይችላል፡፡

ፍልስጥኤማውያን ሆይ፤ ሁላችሁም
በፍርሀት ቅለጡ!
ጢስ ከሰሜን መጥቶብሃል፤
ከሰልፉ ተነጥሎ የሚቀር የለምና።
[32]ከዚያ ሕዝብ ለሚመጡ መልእክተኞች
ምን መልስ ይሰጣል?
መልሱ፣ “እግዚአብሔር ጽዮንን መሥርቶአል፤
መከራን የተቀበለው ሕዝብም፣
በእርሷ ውስጥ መጠጊያን አግኝቶአል”
የሚል ነው።

## በሞዓብ ላይ የተነገረ ትንቢት

**15** ስለ ሞዓብ የተነገረው ንግር ይህ
ነው፤
የሞዓብ ዔር ፈራረሰች፤
በአንድ ሌሊትም ተደመሰሰች።
የሞዓብ ቂር ፈራረሰች፣
በአንድ ሌሊት ተደመሰሰች።
[2]ዲቦን ወደ መቅደሱ ወጣ፤
ሊያለቅስም ወደ ኰረብታው ሄደ፤
ሞዓብ ስለ ናባው፣ ስለ ሜድባም ዋይታ
ያሰማል፤
ራስ ሁሉ ተመድምዶአል፤
ጢምም ሁሉ ተላጭቶአል።
[3]በየመንገዱም ማቅ ይለብሳሉ፤
በየሰገነቱና በየአደባባዩ
ሁሉም ያለቅሳሉ፤
እንባም ይራጫሉ።
[4]ሐሴቦንና ኤልያሊ ጮኹ፤
ድምፃቸው እስከ ያሀድ ድረስ ተሰማ፤
ስለዚህ የሞዓብ ጦረኞች ጮኹ፤
ልባቸውም ራደ።

[5]ልቤ ስለ ሞዓብ አለቀሰ፤
ስደተኞቿም እስከ ዞዓር፣
እስከ ዔግላት ሺሊሺያ ሸሹ፤
እንባቸውን እያፈሰሱ
ወደ ሉሒት ወጡ፤
በሖሮናይም መንገድም፣
ስለ ጥፋታቸው ዋይ እያሉ ነጐዱ።
[6]የኔምሬ ውሆች ደርቀዋል፤
ሣሩ ጠውልጎአል፤
ቡቃያውም ጠፍቶአል፤
ለምለም ነገር አይታይም።
[7]ስለዚህ ያገኙትን ሀብት፣
ያከማቹትን ንብረት ከአኻያ ወንዝ ማዶ
ተሸክመው ያሻግሩታል።
[8]ጩኸታቸው እስከ ሞዓብ ዳርቻ ድረስ
ያስተጋባል፤
ዋይታቸው እስከ ኤግላይም፣
ሰቈቃቸውም እስከ ብኤርኢሊም
ደረሰ።
[9]የዲሞን[ሰ] ወንዞች በደም ተሞልተዋል፤

ሕዝ32፥30
14፥32 መዝ51፥18፤ 87፥2፡5፤ኢሳ2፥2፤ 4፥6፤26፥1፤ 28፥16፤ 31፥5፤33፥5፡20፤37፥9፤ 44፥28፤51፥21፤ 54፥11፤ያዕ2፥5
15፥1 ዘኍ17፥12፤ 21፥15፤22፥3-6፤ ዘዳ23፥6፤2ነገ3፥25፤ ኢሳ11፥14፤13፥1፤ 25፥12፤26፥5፤ ኤር48፥24፡41፤51፥58
15፥2 ዘሌ13፥40፤ ዘኍ21፥30፤32፥38፤ 2ሳሙ10፥4፤ 1ነገ11፥7፤ኢዮ1፥20፤ ኢሳ13፥6፤16፥12፤ 65፥14፤ኤር48፥35
15፥3 ቀኍ5፤ ኢሱ2፥8፤ኢሳ3፥24፤ 14፥31፤16፥9፤22፥4፤ኤር47፥2፤48፥38፤ ሰቆ2፥11፤ሕዝ7፥18፤ ሚክ1፥8
15፥4 ዘኍ21፥23፡ 25፤32፥3፤ኢሱ13፥26
15፥5 ቀኍ3፤ ዘፍ13፥10፤ ዘኍ21፥29፤ኢሳ16፥11፤ ኤር4፥20፤48፥31፡34
15፥6 መዝ37፥2፤ ኢሳ14፥17፤16፥8፤ 19፥5-7፤24፥4፡7፡11፤ 33፥9፤34፥4፤37፥27፤40፥7፤51፥6፡12፤ ኤር14፥5፤48፥34፤ ሆሴ4፥3፤ኢል1፥12
15፥7 ኢሳ30፥6፤ ኤር48፥36
15፥8 ዘኍ21፥16
15፥9 2ነገ17፥25፤ ሕዝ25፥8-11
16፥1 መሳ1፥36፤ 2ነገ3፥4፤2ዜና32፥23፤ ኢሳ10፥32፤አብ3
16፥2 ዘኍ21፥13-14፡ 29፤መሳ12፥5፤ ምሳ27፥8፤ኤር48፥20
16፥3 1ነገ18፥4
16፥4 ኢሳ2፥2-4፤ 9፥4፤58፥7
16፥5 1ሳሙ13፥14፤ ምሳ20፥28፤ኢሳ7፥2፤ 9፥7፤ዳን7፥14፤ ሚክ4፥7፤ሉቃ1፥32
16፥6 ዘሌ26፥19፤ ኢዮ20፥6፤ኤር25፥21፤ 49፥16፤ሕዝ25፥8፤ አሞ2፥1፤አብ1፥3፤ ሶፎ2፥8፡10
16፥7 2ነገ3፥25፤ 1ዜና16፥3፤ኢሳ13፥6፤ ኤር48፥20፤49፥3
16፥8 ዘኍ21፥25፡ 32፤32፥3፤ኢዮ8፥16፤ መዝ80፥11፤ኢሳ5፥2፤ 15፥6

በዲሞን ላይ ግን ከዚያ ነገር የበለጠ
አመጣለሁ፤
ከሞዓብ በሚሸሹት፣
በምድሪቱም ላይ በሚቀሩት አንበሳ
እሰድዳለሁ።

**16** ከምድረ በዳው ማዶ ካለችው ከሴላ፣
ለምድሪቱ ገዥ፣
ወደ ጽዮን ሴት ልጅ ተራራ
የበግ ጠቦት ግብር ላኩ።
[2]ከጐጆአቸው ተባርረው
ግራ እንደ ተጋቡ ወፎች፣
የሞዓብ ሴቶችም
በአርኖን ወንዝ መሻገሪያ እንዲሁ
ይሆናሉ።
[3]“ምክር ለግሱን፤
ውሳኔ ስጡን፤
በቀትር ጥላችሁን
እንደ ሌሊት አጥሉብን፤
የሸሹትን ደብቁ፤
ስደተኞችን አሳልፋችሁ አትስጡ።
[4]የሞዓባውያን ስደተኞች ከእናንተ ጋር
ይቈዩ፤
እናንተም ከአጥፊው መጠጊያ ሁኗቸው።”

የጨቋኙ ፍጻሜ ይመጣል፤
ጥፋቱ ያከትማል፤
አብሪተኛም ከምድር ገጽ ይጠፋል።
[5]ዙፋን በፍቅር ይመሠረታል፤
ከዳዊት ቤት[ሐ] የሆነ፣
በፍርድ ፍትሕን የሚሻ፣
ጽድቅንም የሚያፋጥን፣
አንድ ሰው በታማኝነት በላዩ
ይቀመጣል።
[6]የሞዓብን መዘባነን፣
እጅግ መታበዩንና ኵራቱን፣
እብሪቱንና ስድነቱን ሰምተናል፤
ትምክህቱ ግን ከንቱ ነው።
[7]ስለዚህ ሞዓባውያን ዋይ ይላሉ፤
በአንድነትም ስለ ሞዓብ ዋይታ ያሰማሉ፤
ስለ ቂርሐራሴት ከተማ ሰዎች ትዝታ፣
በሐዘን ያለቅሳሉ።
[8]የሐሴቦን ዕርሻ፣
የሴባማም የወይን ተክል ጠውልጎአል፤
የአሕዛብ ገዦች፣
ኢያዜርን ዐልፈው፣
ምድረ በዳውን ዘልቀው፣
ሥሮቻቸውን
እስከ ባሕር ሰድደው የነበሩትን
የተመረጡ የወይን ተክሎችን ረጋግጠዋል።

[ሰ]9 የማሶሪቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሙት ባሕር ጥቅል፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒምና የቩልጌት ቅጅ ግን፣ *ዲቦን* ይላሉ።
[ሐ]5 ዕብራይስጡ *ድንኳን* ይላል።

9ስለዚህ ስለ ሴባማ የወይን ተክል፣
ኢያዜር እንዳለቀሰች፣ እኔም አለቅሳለሁ፤
ሐሴቦን ሆይ፤ ኤልያሊ ሆይ፤
በእንባዬ አርስሻለሁ፤
ፍሬ ባፈራሽበት ወቅት የነበረው ሆታ፣
መከርሽም ሲደርስ የነበረው ደስታ
ተቋርጦአልና።
10ደስታና ሐሤትም ከአትክልቱ ቦታ
ተወግዷል፤
በወይን ተክልም ቦታ ዝማሬ የለም፤
እልልታም ቀርቶአል።
በወይን መጭመቂያ ቦታ የሚረግጥ የለም፤
የረጋጮችን ሆታ አጥፍቻለሁና።
11ስለዚህ ልቤ ስለ ሞዓብ እንደ በገና
የሐዘን እንጕርጕሮ ታሰማለች፤
አንጀቴም ስለ ቄርሔሬስ ታለቅሳለች፤
12ሞዓብ ወደ ኰረብታዋ ብትወጣ፣
ትርፏ ድካም ብቻ ነው፤
ለጸሎት ወደ መቅደሷ ብትገባም፣
ዋጋ የለውም።

13እግዚአብሔር አስቀድሞ ስለ ሞዓብ
የተናገረው ቃል ይህ ነው። 14አሁን ግን እግዚ
አብሔር እንዲህ ይላል፤ “የተቀጠረ ሠራተኛ
ቀን እንደ ሚቈጥር፣ የሞዓብ ክብርና የሕዝቧ
ብዛት በሦስት ዓመት ውስጥ ይዋረዳል፤
የሚቀረውም ሕዝብ ጥቂትና ደካማ ይሆናል።”

## በደማስቆ ላይ የተነገረ ንግር

17 ስለ ደማስቆ የተነገረ ንግር፤
“እነሆ፤ ደማስቆ ከእንግዲህ ከተ
ማነቷ ይቀራል፤
የፍርስራሽ ክምር ትሆናለች።
2የአሮኤር ከተሞች ባድማ ይሆናሉ፤
የመንጎች መሰማሪያ ይሆናሉ፤
የሚያስፈራቸውም የለም።
3የተመሸገ ከተማ ከኤፍሬም፣
የመንግሥት ሥልጣን ከደማስቆ ይወርዳል፤
የሶርያም ቅሬታ
እንደ እስራኤላውያን ክብር ይሆናል”
ይላል የሰራዊት ጌታ እግዚአብሐ
ር።

4“በዚያን ቀን የያዕቆብ ክብር ይደበዝዛል፤
የሰውነቱም ውፍረት ይሟሽሻል።
5አጫጅ የቆመውን ሰብል ሰብስቦ፣
ዛላውንም በክንዱ እንደሚያጭድ፣
ይህም በራፋይም ሸለቆ
እንደሚለቀም ቃርሚያ ይሆናል።
6ሆኖም የወይራ ዛፍ ሲመታ፣
ሁለት ወይም ሦስት ፍሬ በቅርንጫፍ ራ
ስ
ላይ እንደሚቀር፣
አራት ወይም አምስት ፍሬም ችፍግ
ባለው ቅርንጫፍ ላይ እንደሚቀር፣
እንዲሁ ጥቂት ቃርሚያ ይተርፋል”
ይላል የእስራኤል አምላክ
እግዚአብሔር።
7በዚያ ቀን ሰዎች ወደ ፈጣሪያቸው
ይመለከታሉ፤
ዐይኖቻቸውም ወደ እስራኤል ቅዱስ
ያያሉ።
8በእጃቸውም ወደ ሠሯቸው መሠዊያዎች
አይመለከቱም፤
በጣቶቻቸው ላበጇቸው የዕጣን
መሠዊያዎች፣
ለአሼራም የአምልኮ ዐምዶች
ክብር አይሰጡም።

9በዚያን ቀን በእስራኤል ልጆች ምክንያት
የተተውት ጠንካራ ከተሞች ጥሻና
ውድማ እንደ ሆኑ ሁሉ፣ እነዚህ ሁሉ ባድ
ማ ይሆናሉ።

10አዳኝ አምላክህን ረስተሃል፤
መሸሸጊያ ዐለትህንም አላስታወስህም፤
ስለዚህ ምርጥ ተክል ብትተክልም፣
እንግዳ ዘርንም ብትዘራ፣
11በተከልህበት ቀን እንዲበቅል፣
በዘራህበትም ማግሥት እንዲያብብ
ብታደርግ እንኳ፣
መከሩ በደዌና በማይሽር ሕመም ቀን፣
እንዳልነበረ ይሆናል።

12አቤት፤ የብዙ ሕዝቦች የቍጣ ድምፅ
እንደ ባሕር ሞገድ ይጮኻል፤
አቤት፤ የሰዎች ከፍተኛ ጩኸት!
እንደ ኀይለኛ ውሃ ያስገመግማል።
13ሰዎቹ እንደ ኀይለኛ ውሃ ጩኸት
ቢያስገመግሙም፣
እርሱ ሲገሥጻቸው፣
በኰረብታ ላይ በነፋስ እንደሚበን ትቢያ፣
በዐውሎ ነፋስ ፊት እንደሚበተን ገለባ
ይበተናሉ።
14እነሆ፤ ሲመሽ ድንገተኛ ሽብር ሆነ!
ከመንጋቱ በፊት ግን አንዳቸውም
አልተገኙም።
የዘረፉን ዕድል ፈንታ፣
የበዘበዙን ዕጣ ይህ ሆነ።

## በኢትዮጵያ ላይ የተነገረ ትንቢት

18 በኢትዮጵያ ወንዞች ዳር ለምትገኝ፣
ፉር ፉር የሚሉ ክንፎች
ላሉባት[መ] ምድር ወዮላት!
2ይህችውም መልእክተኞችን በባሕር፣

16፥9 ዘኍ32፥3፤ ኢዮ7፥3፤ዕዝ3፥13፤ ኢሳ15፥3፤ኤር40፥12፤ ሕዝ27፥31
16፥10 መሳ9፥27፤ ኢዮ24፥11፤ኢሳ5፥2፤ 24፥7-8፤ኤር25፥30
16፥11 ኢዮ30፥31፤ ኢሳ15፥5፤63፥15፤ ሆሴ11፥8፤ፊል2፥1
16፥12 1ነገ11፥7፤ 18፥29፤መዝ11፥54-7፤ ኢሳ15፥2፤44፥17-18፤ 1ቆሮ8፥4
16፥14 ዘሌ19፥13፤ 25፥50፤ኢሳ203፤ 21፥17፤25፥10፤ 37፥30፤ኤር48፥42
17፥1 ዘፍ14፥15፤ ዘዳ13፥16፤ኢሳ13፥1፤ 25፥2፤ሐሥ9፥2
17፥2 ዘሌ26፥6፤ 2ነገ10፥33፤ኢሳ5፥17፤ 7፥21፤27፥10፤ ኤር7፥33፤ሕዝ25፥5፤ ሚክ4፥4
17፥3 ቍ4፤ ኢሳ7፥8፡16፤8፥4፤ 21፥16፤25፥2፡12፤ ሆሴ9፥11፤10፥14
17፥4 ቍ3፤ ኢሳ2፥11፤10፥16
17፥5 ቍ11፤ ኢሱ17፥15፤ 1ዜና11፥15፤ ኢዮ24፥24፤ኢሳ33፥4፤ ኤር51፥33፤ኢል3፥13፤ ማቴ13፥30
17፥6 ቍ11፤ ዘዳ4፥27፤ኢሳ10፥19፤ 24፥13፤27፥12
17፥7 መዝ95፥6፤ ኢሳ2፥11፤9፥13፤ 10፥20፤12፥6
17፥8 ዘሌ26፥30፤ መሳ3፥7፤2ነገ17፥10፤2 ዜና32፥19፤ኢሳ2፥8፡ 18፡20፤30፥22፤46፥6፤ ራእ9፥20
17፥9 ኢሳ7፥19
17፥10 ዘፍ49፥24፤ ዘዳ6፥12፤8፥11፤ መዝ18፥2፤50፥22፤ 106፥21፤ኢሳ5፥7፤ 12፥2፤51፥13፤57፥11፤ ኤር2፥32፤3፥21፤ 13፥25፤18፥15፤ ሕዝ22፥12፤23፥35፤ ሆሴ8፥14፤13፥6፤ ሉቃ1፥47
17፥11 ቍ5፤ ዘሌ26፥20፤ዘዳ28፥39፤ ኢዮ4፥8፤መዝ90፥6፤ ኤር10፥19፤30፥12፤ ሆሴ8፥7፤ኢል1፥11፤ ሐጌ1፥6
17፥12 ቍ13፤ መዝ18፥4፤46፥6፤ ኢሳ8፥7፡9፤41፥11፤ ሉቃ21፥25
17፥13 ዘዳ28፥20፤ ኢዮ13፥25፤21፥18፤ መዝ9፥5፤46፥3፤ 65፥7፤68፥1፤ኢሳ2፥22፤13፥14፤ 41፥2፡15-16፤ ዳን2፥35
17፥14 2ነገ19፥35፤ኢሳ29፥5፤30፥13፤33፥18፤47፥11፤ 48፥3፤54፥14
18፥1 ዘፍ10፥6፤ መዝ68፥31፤ኢሳ5፥8፤ሕዝ29፥10 18፥2 ቍ7፤ ዘፍ10፥8-9፤41፥14፤ዘፀ2፥3፤2ዜና12፥3፤ኢዮ9፥26፤ አብ1፥1

[መ]1 ወይም፣ *አንበጣ* ማለት ነው።

ከወንዞች ማዶ በደንገል ጀልባ
የምትልክ ናት።
እናንት ፈጣን መልእክተኞች፤
ረጃጅምና ቈዳው ወደ ለሰለሰ፣
ከቅርብም ከሩቅም ወደሚፈራ ሕዝብ፣
ኀያልና ቋንቋው ወደማይገባ፣
ወንዞች ምድሩን ወደሚከፍሉት
መንግሥት፣ ሂዱ!

3እናንት የዓለም ሕዝቦች፣
በምድርም የምትኖሩ ሁሉ፣
በተራሮች ላይ ምልክት ሲሰቀል
ታዩታላችሁ፤
መለከትም ሲነፋ ትሰሙታላችሁ።
4እግዚአብሔር እንዲህ ብሎኛል፤
"ጸጥ ብዬ እቀመጣለሁ፤
ከማደሪያዬም በፀሓይ ሐሩር እንደሚያ
ብረቀርቅ ትኵሳት፣
በመከርም ሙቀት እንደ ደመና ጠል ሆኜ
እመለከታለሁ።"
5ከመከር በፊት የአበባው ወቅት ሲያልፍ፣
አበባው የጐመራ የወይን ፍሬ ሲሆን፣
የወይን ሐረጉን ተቀጥላ በመግረዣ ይገርዘዋል፤
የተንሰራፋውንም ቅርንጫፍ ቈራርጦ
ያስወግደዋልና።
6ሁሉም በተራራ ላይ ለሚኖሩ ነጣቂ አሞሮች
ለዱርም አራዊት ይተዋሉ፤
አሞሮች በጋውን ሁሉ ሲበሉት ይበጃሉ፤
የዱር አራዊትም ክረምቱን ሁሉ ሲበሉት
ይከርማሉ።
7በዚያን ጊዜ ለሰራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር፣
ረጃጅምና ቈዳው ከለሰለሰ፣
ከቅርብም ከሩቅም ከሚፈራ ሕዝብ፣
ኀያልና ቋንቋው ከማይገባ፣
ወንዞችም ምድሩን ከሚከፍሉት
መንግሥት፣
ገጸ በረከት ይመጣለታል፤ ገጸ በረከቱም
የሚመጣለት የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር
ስም ወዳለበት ወደ ጽዮን ተራራ ነው።

## ስለ ግብፅ የተነገረ ትንቢት

19 ስለ ግብፅ የተነገረ ንግር፤
እነሆ፤ እግዚአብሔር በፈጣን
ደመና ላይ ተቀምጦ
ወደ ግብፅ ይመጣል፤
የግብፅ ጣዖቶች በፊቱ ይርዳሉ፤
የግብፃውያንም ልብ በውስጣቸው ይቀ
ልጣል።
2"ግብፃዊውን በግብፃዊው ላይ አስነሣለሁ፤
ወንድም ወንድሙን፣
ባልንጀራ ባልንጀራውን፣
ከተማም ከተማን፣
መንግሥትም መንግሥትን ይወጋል።
3የግብፃውያን ልብ ይሰለባል፤

18፥3 ኢሱ6፥20፤ መሳ3፥27፤መዝ33፥8፤ 60፥4፤ኢሳ5፥26፤ 11፥10፤13፥2፤31፥9፤ኤር4፥21
18፥4 መሳ5፥31፤ 2ሳሙ1፥21፤ መዝ18፥12፤133፥3፤ ኢሳ26፥19፡21፤62፥1፤ 64፥12፤ሆሴ5፥15፤ 14፥5፤ሚክ1፥3፤ ዕን3፥4
18፥5 ኢሳ10፥33፤ 17፥10-11፤ሕዝ17፥6
18፥6 ኢሳ8፥8፤ 37፥36፤56፥9፤ ኤር7፥33፤ሕዝ32፥4፤ 39፥17
18፥7 ቍ2፤ ዘፍ41፥14፤2ዜና9፥24፤ መዝ68፥31፤ኢሳ60፥7፤ ዕን1፥7
19፥1 ዘፀ12፥12፤ ዘዳ10፥14፤ኢሱ2፥11፤ 2ሳሙ22፥10፤ ኢሳ13፥1፤20፥3፤ ኤር44፥3፤ኢል3፥19፤ ራእ1፥7
19፥2 መሳ7፥22፤ 12፥4፤2ዜና15፥6፤ 20፥23፤ማቴ10፥21፡ 36፤24፥7፤ማር13፥8፤ ሉቃ21፥10
19፥3 ቍ11፤ ዘሌ9፥31፤2ዜና10፥13፤ ኢዮ5፥12፤መዝ18፥45፤ ኢሳ47፥13፤ዳን2፥2፡10፤ 3፥8፤5፥7
19፥4 ኢሳ20፥4፤ ኤር46፥26፤ ሕዝ29፥19፤32፥11
19፥5 2ሳሙ14፥14፤ ኢሳ44፥27፤50፥2፤ ኤር50፥38፤51፥36
19፥6 ዘፍ41፥2፤ ዘፀ7፥18፤ኢዮ8፥11፤ ኢሳ15፥6፤37፥25፤ ሕዝ30፥12
19፥7 ዘኍ11፥5፤ ዘዳ29፥23፤ኢሳ23፥3፤ ዘካ10፥11
19፥8 ዘኍ11፥5፤ ሕዝ47፥10፤አሞ4፥2፤ ዕን1፥15
19፥9 ኢሱ2፥6፤ ምሳ7፥16፤ሕዝ16፥10፤ 27፥7
19፥11 ቍ3፤ ዘፍ41፥37፤ዘኍ13፥22፤ 1ነገ4፥30፤ሐሥ7፥22
19፥12 ኢሳ14፥24፤ ሮሜ9፥17፤1ቆሮ1፥20
19፥13 ዘኍ13፥22፤ መዝ118፥22፤ ኤር2፥16፤44፥1፤ 46፥14፡19፤ሕዝ30፥13፡ 16፤ሆሴ9፥6
19፥14 መዝ107፥27፤ ምሳ12፥8፤ማቴ17፥17
19፥15 ኢሳ9፥14

ዕቅዳቸውንም መና አስቀራለሁ፤
እነርሱም ጣዖታትንና የሙታንን
መናፍስት፤
መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችን ምክር
ይጠይቃሉ።
4ግብፃውያንን አሳልፌ፣
ለጨካኝ ጌታ ክንድ እሰጣቸዋለሁ፤
አስፈሪ ንጉሥም ይገዛቸዋል"
ይላል የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር።
5የዐባይ ወንዝ ይቀንሳል፤
ውሃውም እየጐደለ ይሄዳል።
6መስኖዎቹ ይከረፋሉ፤
የግብፅ ጅረቶች ይጐድላሉ፤ ይጠፋሉም።
ደንገሉና ቄጠማውም ይጠወልጋል፤
7እንዲሁም በዐባይ ዳር፣
በወንዙ መፋሰሻ ላይ ያሉት ተክሎች
ይጠወልጋሉ።
በዐባይ ዳር የተዘራው ዕርሻ ሁሉ፣
በነፋስ ይወሰዳል፤ ምንም አይቀርም።
8ዓሣ አጥማጆች ያዝናሉ፤
በዐባይ ወንዝ ላይ መንጠቆአቸውን
የሚወረውሩ ሁሉ ያለቅሳሉ፤
በውሃ ላይ መረባቸውን የሚጥሉ ሁሉ፣
ጕልበታቸው ይዝላል።
9የተነደፈ የተልባ እግር የሚፈትሉ፣
የተባዘተ ጥጥ የሚሠሩ ሸማኔዎችም
ተስፋ ይቈርጣሉ።
10ልብስ ሠሪዎች ያዝናሉ፤
ደመወዝተኞችም ልባቸው ይሰበራል።

11የጣኔዎስ አለቆች በጣም ሞኞች ናቸው፤
የፈርዖን ጠቢባን ምክራቸው የማይረባ
ነው፤
ፈርዖንን፣ "እኔ ከጥበበኞች አንዱ ነኝ፤
የጥንት ነገሥታትም ደቀ መዝሙር ነኝ"
እንዴት ትሉታላችሁ?
12የእናንተ ጠቢባን አሁን የት አሉ?
የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር
በግብፅ ላይ ያሰበውን ነገር፣
እስቲ ያሳዩአችሁ፤ ያሳውቋችሁም።
13የጣኔዎስ አለቆች ተሞኝተዋል፤
የሜምፊስ ሹማምንት ተታለዋል፤
የሕዝቧ ዋና ዋናዎች፣
ግብፅን አስተዋታል።
14እግዚአብሔር የድንዛዜን መንፈስ
አፍሶባቸዋል፤
ሰካራም በትፋቱ ዙሪያ እንደሚንገዳገድ፣
ግብፅንም በምታደርገው ነገር ሁሉ
እንድትንገዳገድ አደረጓት።
15ራስም ይሁን ጅራት፣ የዘንባባ ዝንጣፊም
ይሁን ደንገል፣
ለግብፅ የሚያደርጉላት አንዳች ነገር
የለም።

[16]በዚያን ቀን ግብፃውያን እንደ ሴት
ይሆናሉ፤ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር
በእነርሱ ላይ ካነሣው ክንዱ የተነሣ
በፍርሀት ይንቀጠቀጣሉ:: [17]የይሁዳ ምድር
በግብፅ ላይ ሽብር ትነዛለች፤ የሰራዊት
ጌታ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ
ካቀደው የተነሣ፣ ስለ ይሁዳ፣ ወሬ የሰማ
ሁሉ ይሸ በራል::
[18]በዚያ ቀን አምስት የግብፅ ከተሞች
በከነዓን ቋንቋ ይናገራሉ፤ የሰራዊት ጌታ
የእግዚአብሔርም ወገን ለመሆን ቃል ኪዳን
ይገባሉ፤ ከእነዚህም ከተሞች አንዷቱ
የጥፋት ከተማ ተብላ ትጠራለች::
[19]በዚያ ቀን በግብፅ ምድር መካከል ለእ
ግዚአብሔር መሠዊያ ይሠራል፤ በድንበሯም
ላይ ለእግዚአብሔር ዐምድ ይቆማል:: [20]ይህም
በግብፅ ምድር ለሰራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር
ምልክትና ምስክር ይሆናል፤ ከሚያስጨን
ቋቸውም የተነሣ ወደ እግዚአብሔር ሲጮኹ፣
አዳኝና ታዳጊ ይልክላቸዋል፤ እርሱም ያድና
ቸዋል:: [21]እግዚአብሔር ራሱን ለግብፃውያን
ይገልጣል፤ እነርሱም በዚያ ቀን እግዚአ
ብሔርን ያውቁታል፤ በመሥዋዕትና በእህል
ቍርባንም ያመልኩታል:: ለእግዚአብሔር
ስለት ይሳላሉ፤ የተሳሉትንም ይፈ
ጽሙታል:: [22]እግዚአብሔር ግብፅን በመቅ
ሠፍት ይመታ ታል፤ መትቶም፤ ይፈጠ
ውሳቸዋል:: እነርሱም ወደ እግዚአብሔር
ይመለሳሉ፤ እርሱም ልመናቸውን ሰምቶ
ይፈውሳቸዋል::
[23]በዚያ ቀን ከግብፅ ወደ አሦር አውራ
መንገድ ይዘረጋል፤ አሦራውያን ወደ ግብፅ፣
ግብፃውያንም ወደ አሦር ይሄዳሉ፤ ግብፃው
ያንና አሦራውያን በአንድነት ያመልካሉ::
[24]በዚያ ቀን እስራኤል፣ ከግብፅና ከአሦር
ጋር የምድር በረከት ለመሆን በሦስተኛነት
ትቈጠራለች:: [25]የሰራዊት ጌታ እግዚአ
ብሔርም፣ "ሕዝቤ ግብፅ፣ የእጄ ሥራ
አሦር፣ ርስቴም እስራኤል የተባረኩ ይሁኑ"
ብሎ ይባርካቸዋል::

## በግብፅና በኢትዮጵያ ላይ የተነገረ ትንቢት

**20** ዋናው የጦር አዛዥ[ሠ] በአሦር
ንጉሥ በሳርጎን ተልኮ፣ የአዛጦንን
ከተማ ወሮ በያዘበት ዓመት፣ [2]በዚያ
ጊዜ እግዚአብሔር የአሞጽን ልጅ ኢሳይ
ያስን፣ "ማቁን ከሰውነትህ፣ ጫማህን ከእግርህ
አውልቅ" ሲል ተናገረው:: እርሱም እንዲሁ
አደረገ፤ ዕርቃኑንና ባዶ እግሩን ተመላለሰ::
[3]ከዚያም እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤
"ባሪያዬ ኢሳይያስ ሦስት ዓመት በግብፅና
በኢትዮጵያ ለምልክትና ለማስጠንቀቂያ ዕር
ቃኑንና ባዶ እግሩን እንደ ሄደ፣ [4]እንዲሁ
የአሦር ንጉሥ ወጣትና ሽማግሌ የሆኑትን
የተማረኩ ግብፃውያንንና የተሰደዱ ኢትዮጵ
ያውያንን ዕርቃናቸውንና ባዶ እግራቸውን
ይወስዳቸዋል፤ መቀመጫቸውን ገልቦ በመስ
ደድም ግብፅን ያዋርዳል:: [5]በኢትዮጵያ
ተስፋ ያደረጉ፣ በግብፅ የተመኩ ይፈራሉ፤
ይዋረዳሉም:: [6]በዚያ ቀን በዚህ ባሕር ጻርቻ
የሚኖረው ሕዝብ፣ 'የተመካንባቸው፣ ከአሦር
ንጉሥ ለማምለጥና ነጻ ለመውጣት የተሸሸግ
ንባቸው ምን እንደ ደረሰባቸው ተመልከቱ!
እንግዲህ እኛስ እንዴት እናመልጣለን?'
ይላል::"

## በባቢሎን ላይ የተነገረ ትንቢት

**21** በባሕሩ ዳር ባለው ምድረ በዳ ላይ
የተነገረ ንግር፤

ዐውሎ ነፋስ ከደቡብ እየጠራረገ
እንደሚመጣ፣
ወራሪ ከአሸባሪ ምድር፣
ከምድረ በዳ ይመጣል::
[2]የሚያስጨንቅ ራእይ አየሁ፤
ከሓዲ አሳልፎ ይሰጣል፤ ዘራፊ ይዘር
ፋል::
ኤላም ሆይ፤ ተነሺ! ሜዶን ሆይ፤ ክበቢ!
እርሷ ያደረሰችውን ሥቃይ ሁሉ አስቀ
ራለሁ::

[3]ወገቤ በዚህ ሥቃይ ተሞላ፤
በምጥ ላይ እንዳለች ሴት ጭንቅ ያዘኝ፤
በሰማሁት ነገር ተንገዳገድሁ፤
ባየሁትም ነገር ተሸበርሁ::
[4]ልቤ ተናወጠ፤
ፍርሀት አንቀጠቀጠኝ፤
የጓጓሁለት ውጋጋን፣
ታላቅ ፍርሀት አሳደረብኝ::

[5]ማእዱን አሰናዱ፤
ምንጣፉን አነጠፉ፤
በሉ፤ ጠጡም!
እናንት ሹማምንት ተነሡ፤
ጋሻውን በዘይት ወልውሉ!

[6]ጌታ እንዲህ አለኝ፤
"ሂድ፤ ጠባቂ አቁም፤
ያየውንም ይናገር፤

19፥16 ዘጻ2፥25፤ ኢሳ2፥17፤11፥10፡15፤ ኤር50፥37፤51፥30፤ ናሆ3፥13፤ዕብ10፥31
19፥17 ዘፍ35፥5፤ ኢሳ14፥24
19፥18 መዝ22፥27፤ 63፥11፤ኢሳ10፥20፤ 17፥1፤24፥12፤32፥19፤ 48፥1፤ኤር4፥2፤ 43፥13፤44፥1
19፥19 ዘፍ28፥18፤ ኢሱ22፥10፤ መዝ68፥31፤ ኢሳ10፥20
19፥20 ዘፍ21፥30፤ ዘጻ28፥29፤መሳ2፥18፤ ኢሳ25፥9፤49፥24-26
19፥21 ቍ19፤ ዘፍ27፥29፤ዘኍ30፥2፤ ዘጻ23፥21፤መዝ86፥9፤ ኢሳ11፥9፤43፥10፤ 56፥7፤60፥7፤ ሚል1፥11
19፥22 ዘዐ11፥10፤ 12፥23፤ዘጻ32፥39፤ ኢሳ45፥14፤ሕዝ33፥11፤ ሆሴ6፥1፤10፥12፤ 12፥6፤14፥1፤ ኢል2፥13፤ዕብ12፥11
19፥23 ቍ16፥24፤ ዘፍ27፥29፤ኢሳ2፥3፤ 11፥16፤20፥6፤27፥13፤ 66፥23፤ሚክ7፥12
19፥24 ቍ23፤ ዘፍ12፥2፤ኢሳ11፥11
19፥25 ዘፍ12፥3፤ ዘዐ34፥9፤መዝ87፥4፤ 100፥3፤ኢሳ29፥23፤ 43፥7፤45፥11፤60፥21፤ 64፥8፤ኤር30፥22፤ ሆሴ2፥23፤ኤፌ2፥10፡ 11-14
20፥1 ኢሱ11፥22፤ 13፥3፤2ነገ18፥17
20፥2 1ሳሙ19፥24፤ 2ነገ1፥8፤ኢሳ3፥24፤ 13፥1፤ሕዝ4፥1-12፤ 24፥17፡23፤ሚክ1፥8፤ ዘካ13፥4፤ማቴ3፥4
20፥3 ቍ5፤ ዘፍ10፥6፤ዘዐ3፥12፤ ዘጻ28፥46፤ ኢሳ8፥18፤16፥14፤ 19፥1፤22፥20፤37፥9፡ 30፤38፥7፤41፥8-9፤ 42፥1፤43፥3፡10፤ 49፥3፡5-7፤50፥10፤ 52፥13፤53፥11፤ ኤር7፥25፤ሐጌ2፥23፤ ዘካ4፥14
20፥4 ኢዮ12፥17፤ ኢሳ3፥24፤18፥1፤ 19፥4፤47፥3፤ ኤር13፥22፡26፤ 46፥19፤ናሆ3፥5፡10፤ ሶፎ2፥12
20፥5 ቍ3፤ 2ነገ18፥21፤ኢሳ8፥12፤ 30፥5፤ሕዝ29፥16
20፥6 2ነገ18፥21፤ ኢሳ2፥11፤10፥3፤ 19፥23፤ኤር30፥15-17፤ 31፥2፤46፥25፤ማቴ23፥33፤1ተሰ5፥3፤ዕብ2፥3
21፥1 ኢዮ1፥19፤ ኢሳ13፥1፡21፤ ኤር50፥12፤51፥43፤ ዳን11፥40፤ዘካ9፥14
21፥2 ዘፍ10፥22፤መዝ60፥3፤ኢሳ13፥3፤22፥6፤24፥16፤33፥1፤ ኤር25፥25፤51፥28
21፥3 ዘፍ3፥16፤ኢዮ14፥22፤መዝ48፥6፤ ኢሳ26፥17፤37፥3፤ ኤር30፥6፤48፥41፤ 49፥22፤ዳን7፥28፤ 8፥27፤10፥16፤ ዮሐ16፥21
21፥4 መዝ55፥5፤ኢሳ7፥4፤13፥8፤ 35፥4፤ዘጻ5፥9
21፥5 2ሳሙ1፥21፤ 1ነገ10፥16-17፤ኢሳ5፥12፤ 22፥2፡13፤ 23፥7፤24፥8፤32፥13፤ኤር25፥16፡27፤46፥3፤51፥11፡ 39፡57፤ ዳን5፥2
21፥6 2ነገ9፥17

[ሠ]1 ዋናው የጦር አዛዥ የሚለውን ዕብራይስጡ ተርታን ይለዋል

7በፈረሶች የሚሳብ፣
ሠረገሎችን ሲያይ፣
በአህያ ላይ የሚቀመጡትን፣
በግመል የሚጋልቡትን ሲመለከት፣
ያስተውል፣
በጥንቃቄም ያስተውል።”
8ጠባቂው ጮኸ፤[መ] እንዲህም አለ፤
“ጌታ ሆይ፤ በየቀኑ ማማ ላይ ቆሜአለሁ፤
በየሌሊቱም በቦታዬ አለሁ።
9እነሆ፤ አንድ ሰው በፈረሶች በሚሳብ
በሠረገላ መጥቶአል፤
እንዲህም ሲል መለሰ፣
‘ባቢሎን ወደቀች፣ ወደቀች!
የአማልክቷም ምስሎች ሁሉ፣
ተሰባብረው ምድር ላይ ወደቁ።’ ”
10በዐውድማ ላይ የተወቃህ ሕዝቤ ሆይ፤
ከሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣
ከእስራኤል አምላክ፣
የሰማሁትን እነግርሃለሁ።

## በኤዶም ላይ የተነገረ ትንቢት

11ስለ ኤዶም የተነገረ ንግር፤
አንዱ ከሴይር ጠርቶኝ፣
“ጠባቂ ሆይ፤ ሊነጋ ምን ያህል ቀረው?
ጠባቂ ሆይ፤ ሊነጋ ምን ያህል ቀረው?”
አለኝ።
12ጠባቂውም መለሰ፤
“ይነጋል፤ ግን ተመልሶ ይመሻል፤
መጠየቅ ከፈለጋችሁ፣ ጠይቁ፤
ነገር ግን ተመልሳችሁ ኑ” አለ።

## በዐረብ ላይ የተነገረ ትንቢት

13ስለ ዐረብ አገር የተነገረ ንግር፤
እናንተ በዐረብ ዱር የምትሰፍሩ፣
የድዳን ሲራራ ነጋዴዎች፣
14ለተጠሙ ውሃ አምጡ።
በቴማን የምትኖሩ፣
ለስደተኞች ምግብ አምጡ።
15ከሰይፍ፣
ከተመዘዘ ሰይፍ፣
ከተደገነ ቀስት፣
ከተፋፋመ ጦርነት ሸሽተዋልና።

16ጌታ ም እንዲህ አለኝ፤ “በውል የተቀጠ
ረ ሠራተኛ ቀን እንደሚቈጥር፣ የቄዳር
ክብር በአንድ ዓመት ውስጥ ያበቃለታል።
17የተረ ፈው ቀስተኛ፣ የቄዳር ጦረኛ
ጥቂት ይሆ ናል፤ የእስራኤል አምላክ እግዚ
አብሔር ተናግ ሮአልና።”

## ስለ ኢየሩሳሌም የተነገረ ትንቢት

22 ስለ ራእይ ሸለቆ የተነገረ ንግር፤
እስቲ ምን ቢጨንቃችሁ ነው፤
ሁላችሁም ሰገነት ላይ የወጣችሁት?
2አንቺ ጫጫታ የሞላብሽ ከተማ፤
የውካታና የፈንጠዝያ ከተማ ሆይ፤
የተገደሉብሽ በሰይፍ የተሠዉ አይደሉም፤
በጦርነትም አልሞቱም።
3መሪዎችሽ በሙሉ በአንድ ላይ ሸሽተዋል፤
ቀስት እንኳ ሳያነሡ ተማርከዋል፤
ጠላት ገና በሩቅ ሳለ የሸሻችሁ ሁሉ፣
ተይዛችሁ በአንድነት ታስራችኋል።
4ስለዚህ፣ “ከእኔ ራቁ፤
አምርሬ ላልቅስበት፣
ስለ ሕዝቤ ጥፋት፣
ልታጽናኑኝ አትሞክሩ” አልሁ።

5እግዚአብሔር የሰራዊት ጌታ እግዚአብሐ
ር
በራእይ ሸለቆ፣
የመጯጯኺያ የመረገጥና የሽብር፣
ቅጥሮችን የማፈራረስ፣
ወደ ተራሮችም የሚጮኽበት ቀን አለው።
6ኤላም የፍላጻ ሰገባ፣
ፈረሷንና ሠረገላዋን አዘጋጀች፤
ቂርም ጋሻዋን አነገበች
7መልካሞቹ ሸለቆዎችሽ በሠረገሎች
ተሞልተዋል፤
ፈረሰኞችም በከተማዪቱ በሮች ላይ
ቆመዋል፤
8የይሁዳን መከላከያዎች ገልጧል።
በዚያን ቀን በዱር ግምጃ ቤት
የነበረውን፣
የጦር መሣሪያ ተመለከትህ፤
9የዳዊት ከተማ፣
ብዙ ፍርስራሾች እንዳሉበት አያችሁ፤
በታችኛውም ኵሬ፣
ውሃ አጠራቀማችሁ።
10በኢየሩሳሌም ያሉትን ቤቶች ቈጠራችሁ፤
ቅጥሩን ለመጠገንም ቤቶቹን
አፈረሳችሁ።
11ለጥንቱ ኵሬ ውሃ የሚሆን፣
በሁለቱ ቅጥሮች መካከል ውሃ ማጠራ
ቀሚያ ሠራችሁ፤
ነገር ግን ይህን ያደረገውን አልተመለከ
ታችሁም፤
ቀድሞ ዐቅዶ የሠራውንም አላስታወ
ሳችሁም።
12በዚያን ቀን ጌታ የሰራዊት ጌታ እግዚ
አብሔር፣
እንድታለቅሱና በዋይታ እንድትጮኹ፣
ጠጕራችሁን እንድትነጩ
ማቅም እንድትለብሱ ጠራችሁ።
13ነገር ግን እነሆ፤ ተድላና ደስታ፣
ፍሪዳ መጣልና ሙክት ማረድ፣

21፥7 ቍ9፤ መሳ6፥5
21፥8 ሚክ7፥7፤ዕን2፥1
21፥9 ቍ7፤ ዘሌ26፥30፤ኢሳ2፥18፤ 13፥1፤46፥1፤ 47፥1፡5፡11፤ ኤር50፥2፤51፥8፡ 44፤ራእ14፥8
21፥10 ኢሳ27፥12፤ 28፥27፡28፤41፥15፤ ኤር51፥33፤ሚክ4፥13፤ ዕን3፥12፤ማቴ3፥12
21፥11 ዘፍ25፥14፤ 32፥3፤ኢሳ34፥11
21፥13 ዘፍ10፥7፤ 25፥3፤2ዜና9፥14፤ ኢሳ13፥1
21፥14 ዘፍ25፥15
21፥15 ኢሳ13፥14፤ 31፥8
21፥16 ዘፍ25፥13፤ ዘሌ25፥50፤ኢሳ17፥3
21፥17 ዘጸ4፥27፤ ኢሳ1፥20፤10፥19፤ 16፥14
22፥1 ኢሱ2፥8፤ መዝ125፥2፤ኢሳ1፥1፤ 13፥1፤ኤር21፥13፤ 48፥38፤ኢል3፥2፡12፡14
22፥2 2ነገ25፥3፤ ኢሳ5፥14፤10፥4፤ 21፥5፤ሕዝ22፥5
22፥3 2ነገ25፥6፤ ኢሳ13፥14
22፥4 ኢሳ15፥3፤ ኤር9፥1፤ሰቆ1፥16፤ ሕዝ21፥6፤ሉቃ19፥41
22፥5 2ሳሙ22፥43፤ ነህ6፥15፤ኢዮ40፥12፤ መዝ89፥40፤108፥13፤ ኢሳ1፥1፤2፥12፤5፥5፤ 13፥3፤ኤር30፥7፤ 39፥8፤ሰቆ1፥5፤ ሕዝ8፥17-18፤9፥9-10፤ 13፥14፤ኢል2፥31፤ አሞ5፥18-20፤ሶፎ1፥15
22፥6 2ነገ16፥9፤ መዝ46፥9፤ኢሳ21፥2፤ ኤር49፥35፤51፥56
22፥7 ኢሱ15፥8፤ 2ዜና32፥1-2
22፥8 1ነገ7፥2፤ 2ዜና32፥5፤ኢሳ2፥12
22፥9 2ነገ18፥17፤ 2ዜና32፥4፤ነህ1፥3
22፥10 2ዜና32፥5፤ ኤር33፥4
22፥11 1ሳሙ12፥24፤ 2ነገ19፥25፤25፥4፤ 2ዜና32፥4፡5፤ ኤር39፥4
22፥12 ዘሌ13፥40፤ ኢሳ2፥12፤3፥24፤ ኢል1፥9፤2፥17፤ ሚክ1፥16
22፥13 1ሳሙ25፥36፤ መክ8፥15፤ኢሳ5፥22፤ 21፥5፤28፥7-8፤ 56፥12፤ሉቃ17፥26-29፤ 1ቆሮ15፥32

[መ]8 የሙት ባሕር ጥቅልና የሱርስቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማ ማል፤ የማሶሬቱ ቅጅ ግን፣ አንበሳ ጮኸ ይላል።

*ሥጋ መብላትና የወይን ጠጅ መጠጣት አለ፤*
“እንብላ እንጠጣ
*ነገ እንሞታለንና” አላችሁ።*

[14]የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* ይህን
ገለጠልኝ፤ እንዲህም ሲል በጆሮዬ ሰማሁ፤
“ይህ ኀጢአት እስከምትሞቱበት ቀን
ድረስ አይ ሰረይላችሁም” ይላል ጌታ የሰ
ራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*።

[15]ጌታ የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤

“ሂድና ይህን መጋቢ፣
የቤቱንም ኀላፊ ሳምናስን እንዲህ በለው፤
[16]‘እዚህ ምን ታደርጋለህ?
በዚህ ስፍራ ለራስህ መቃብርን እንድ
ታዘጋጅ፣
በከፍታውም ላይ መቀበሪያህን እንድትወቅር፣
ሬሳህ የሚያርፍበትንም ዐለት እንድ
ትጠርብ ማን ፈቀደልህ?’

[17]አንተ ኀያል ሰው ሆይ፤ ተጠንቀቅ፤
*እግዚአብሔር* አጥብቆ ሊይዝህ፣ በእጆቹም
ጨብጦ ሊወረውርህ ነው።
[18]አዙሮ አዙሮ እንደ ኩር አጡዞ፣
ወደ ሰፊ አገር ይወነጭፍሃል፤
አንተ የጌታህ ቤት ዕፍረት!
በዚያ ትሞታለህ፤
የክብር ሠረገሎችህም እዚያ ይቀራሉ።
[19]ከማዕረግህ አወርድሃለሁ፤
ከኀላፊነትህም ትባረራለህ።

[20]“በዚያን ቀን አገልጋዬን፣ የኬልቅያስን
ልጅ ኤልያቄምን እጠራለሁ፤ [21]መጐናጸፊያህን
አለብሰዋለሁ፤ መታጠቂያህን አስታጥቀ
ዋለሁ፤ ሥልጣንህንም አስረክበዋለሁ። እር
ሱም በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ፣ ለይሁዳም
ቤት አባት ይሆናል። [22]የዳዊትን ቤት
መክፈቻ በጫንቃው ላይ አደርጋለሁ፤ እርሱ
የሚከፍተውን ማንም አይዘጋም፤ የሚዘጋ
ውንም ማንም አይከፍትም። [23]በአስተማ
ማኝ ስፍራ እንደ ካስማ እተክለዋለሁ፤ ለአ
ባቱም ቤት የክብር ዙፋን[ሠ] ይሆናል።
[24]የቤተ ሰቡ ክብር፣ ልጅና የልጅ ልጅ፣
እንዲሁም ከማሰሮ ጀምሮ እስከ ጋን ድረስ
ያለ የቤት ዕቃ ሁሉ በርሱ ላይ ይንጠ
ለጠላል።

[25]“በዚያ ቀን” ይላል የሰራዊት ጌታ *እግ
ዚአብሔር*፣ “በአስተማማኝ ስፍራ የተተከለ
ካስማ ይነቀላል፤ ተሰብሮም ይወድቃል፤
በእርሱም ላይ የተንጠለጠለው ሸክም ወድቆ
ይከሰከሳል፤” *እግዚአብሔር* ይህን ተናግ
ሮአልና።

22፥14 1ሳሙ2፥25፤ ኢሳ5፥9፤13፥11፤ 26፥21፤30፥13-14፤ ሕዝ24፥13
22፥15 ቍ21፤ ዘፍ41፥40፤2ነገ16፥30፤ 18፥18
22፥16 ዘፍ50፥5፤ ዘኍ32፥42፤ማቴ27፥60
22፥17 ኤር10፥18፤ 13፥18፤22፥26
22፥18 ዘፍ41፥43፤ ኢዮ18፥11፤ ኢሳ14፥19፤17፥13
22፥19 1ሳሙ2፥7፤ መዝ52፥5፤ሉቃ16፥3
22፥20 ቍ25፤ 2ነገ18፥18፤ኢሳ20፥3፤ 36፥3
22፥21 ቍ15፤ ኢሳ5፥27
22፥22 1ዜና9፥27፤ ኢዮ12፥14፤ ኢሳ7፥2፤9፥6፤ ማቴ16፥19፤ራእ3፥7
22፥23 ቍ25፤ 1ሳሙ2፥7-8፤ዕዝ9፥8፤ ኢዮ6፥25፤36፥7፤ ሕዝ15፥3፤ዘካ10፥4
22፥25 ቍ20፥23፤ ኢሳ46፥11፤ሚክ4፥4

23፥1 ዘፍ1፥2፤ 10፥4፤ኢሱ19፥29፤ 1ነገ5፥1፤10፥22፤ ኢሳ2፥16፤13፥6፤ ኤር47፥4፤ ሕዝ26፥4፤ ኢል3፥4-8፤ አሞ1፥9-10፤ዘካ9፥2-4
23፥2 መሳ1፥31፤ ኢዮ2፥13፤ሕዝ27፥5-24
23፥3 ዘፍ41፥5፤ መዝ83፥7፤ኢሳ19፥7
23፥4 ዘፍ10፥15፡ 19፤ኢሳ54፥1
23፥5 ሕዝ26፥17-18፤ 30፥9
23፥6 ዘፍ10፥4
23፥7 ቍ12፤ ኢሳ5፥14፤21፥5፤ 32፥13፤ሕዝ26፥13
23፥8 ሕዝ28፥5፤ ናሆ3፥16፤ራእ18፥23
23፥9 ኢዮ40፥11፤ ኢሳ5፥13፤9፥15፤ 13፥11፤14፥24፤ ሕዝ27፥3
23፥11 ቍ14፤ ዘፀ14፥21፤መዝ46፥6፤ ኢሳ25፥2፤ሕዝ26፥4፤ ዘካ9፥3-4

## ስለ ጢሮስ የተነገረ ትንቢት

**23** ስለ ጢሮስ የተነገረ ንግር፤
የተርሴስ መርከቦች ሆይ፤ ዋይ
በሉ፤
ጢሮስ ተደምስሳለችና፤
ያለ ቤትና ያለ ወደብ ቀርታለች።
ከቆጵሮስ ምድር፣
ዜናው ወጥቶላቸዋል።

[2]እናንት የባሕር ተጓዦች ያበለጠጓችሁ፣
በደሴቲቱ የምትኖሩ፣
የሲዶና ነጋዴዎችም ጸጥ በሉ።
[3]በታላላቅ ውሆች ላይ፣
ለጢሮስ የሺሖር እህል ይመጣላት ነበር፤
የዐባይ መከር[ረ] ገቢዋ ነበር፤
እርሷም የመንግሥታቱ የንግድ መናኸሪያ
ሆነች።
[4]አንቺ ሲዶና ሆይ፣
አንቺ የባሕር ምሽግ ሆይ፣ ዕፈሪ፤
ባሕሩ፣ “አላማጥሁም፤ አልወለድሁም፤
ወንዶችና ሴቶች ልጆችን አላሳደግሁም”
ብሎአልና።
[5]ከጢሮስ የሚመጣው ዜና፣
በግብፅ በሚሰማበት ጊዜ ጭንቅ
ይይዛቸዋል።

[6]እናንት በደሴቲቱ የምትኖሩ፣ በዋይታ
አልቅሱ፤
ወደ ተርሴስም ተሻገሩ፤
[7]እግሮቿ ሩቅ አገር የወሰዷት፣
በዚያም እንድትሰፍር ያደረጓት፣
ጥንታዊቷ የድሮ ከተማ፣
የተድላ የደስታ ከተማችሁ ይህች ናትን?
[8]አክሊል በምታቀዳጀዋ፣
ነጋዴዎቿ መሳፍንት በሆኑ፣
በምድር የከበሩ ሻጮችና ለዋጮች
በነበሯት፣
በጢሮስ ላይ ይህን ያሰበ ማን ነበር?
[9]የክብርን ሁሉ ትዕቢት ሊያዋርድ፣
በምድር ከፍ ከፍ ያለውንም ሁሉ ዝቅ
ሊያደርግ፣
የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* ወስኖአል።
[10]የተርሴስ ልጅ ሆይ፤
ከእንግዲህ የሚከለክልሽ የለምና
እንደ ዐባይ ወንዝ ምድርሽን
አጥለቅልቂ።
[11]*እግዚአብሔር* እጁን በባሕር ላይ ዘረጋ፤
*መንግሥታቷንም አስደነገጠ፤*
የከነዓንም[ሰ] ምሽጎች እንዲፈርሱ፣
ትእዛዝ ሰጠ፤

[ሠ]23 ወይም፣ *መቀመጫ* ተብሎ መተርጐም ይችላል።
[ረ]2፥3 የማሶሬቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ አንድ የሙት ባሕር ቅጅ ግን፣ *ሲዶን /በባሕሩ ላይ የምትሻገሪ/ ተጓዦችሽ [3]በትልቁ ባሕር ላይ የሆኑ/ የሺሖር እህል/ የዐባይ መከር* ይላል።
[ሰ]11 አንዳንድ ቅጆች፣ *ፊንቄ* ይላሉ።

12እንዲህም አለ፤ “አንቺ የተቀጠቀጥሽ የሲዶን
ድንግል ሆይ!
ከእንግዲህ ደስ አይበልሽ፤
“ተነሺ ወደ ቆጵሮስ ተሻገሪ፤
በዚያም እንኳ ሰላም አታገኚም።”
13እነሆ፤ የባቢሎናውያንን[ሸ] ምድር ተመልከተ
ሁ፤
ሕዝቡ ከንቱ ሆኖአል።
አሦራውያን የምድረ በዳ አራዊት
መፈንጫያ አደረጓት፤
የግንብ ማማቸውን ሠሩባት፤
ምሽጎቿን አወደሙ፤
የፍርስራሽ ክምር አደረጓት።
14እናንት የተርሴስ መርከቦች፣ ዋይ በሉ፤
ምሽጋችሁ ፈርሶአል።
15በዚያ ጊዜ ጢሮስ፣ የአንድ ንጉሥ የሕ
ይወት ዘመን ያህል፣ ለሰባ ዓመታት ትረሳለጠ
ች። ከሰባ ዓመት በኋላ ግን፣ ስለ
ጋለሞታዪቱ የተዘፈነው በጢሮስ ላይ
ይሆናል፤
16“አንች የተረሳሽ ጋለሞታ፤
በገና አንሺ፤ በከተማዪቱ ውስጥ ዙሪ፤
እንድትታወሽም፣
በገናሽን አሳምረሽ ምቺ፤ ብዙ ዘፈን
ዝፈኚ።”
17ሰባው ዓመት ካለፈ በኋላ እግዚአብሔር
ጢሮስን ይጐበኛታል፤ ወደ ቀድሞው የግል
ሙትና ሥራዋ ተመልሳ፣ በምድር ላይ
ካሉት የዓለም መንግሥታት ሁሉ ጋር
በንግዷ ትገለሙታለች። 18ያም ሆኖ ትርፏና
ያገኘችው ሁሉ ለእግዚአብሔር የተለየ
ይሆናል፤ አይከማችም፤ አይጠራቀምም።
ትርፏም በእግዚአብሔር ፊት ለሚኖሩት
የተትረፈረፈ ምግብና ጥሩ ልብስ ይሆናል።

## *እግዚአብሔር ምድርን ፈጽሞ ያጠፋታል*

24 እነሆ፤ *እግዚአብሔር ምድርን* ባድማ
ያደርጋታል፤
ፈጽሞ ያጠፋታል፤
የፍርስራሽ ክምር ያደርጋታል፤
ነዋሪዎቿንም ይበትናል።
2ነገሩ ሁሉም አንድ ዐይነት ይሆናል፤
በሕዝቡ ላይ የሚሆነው በካህኑ፣
በአገልጋዩ ላይ የሚሆነው በጌታው፣
በአገልጋይዋ ላይ የሚሆነው በእመቤቷ፣
በገዢው ላይ የሚሆነው በሻጩ፣
በተበዳሪው ላይ የሚሆነው በአበዳሪው፣
በብድር ከፋይ ላይ የሚሆነው በብድር
ሰጪው ይሆናል።
3ምድር ፈጽሞ ባድማ ትሆናለች፤
ጨርሶም ትበዘበዛለች፤
እግዚአብሔር ይህን ቃል ተናግሮአልና።
4ምድር ትደርቃለች፤ ትረግፋለች፤
ዓለም ትዝላለች፤ ትረግፋለች፤
የምድርም መሳፍንት ይዝላሉ።
5ምድር በሕዝቧ ትረክሳለች፤
ሕግን ጥሰዋል፤
ሥርዐትን ተላልፈዋል፤
ዘላለማዊውንም ኪዳን አፍርሰዋል።
6ስለዚህ ርግማን ምድርን ትበላለች፤
ሕዝቦቿም ስለ በደላቸው ይቀጣሉ፤
ስለዚህ የምድር ነዋሪዎች ተቃጥለዋል፤
በጣም ጥቂት የሆኑት ቀርተዋል።
7አዲሱ የወይን ጠጅ አለቀ፤ የወይኑም
ተክል
ደረቀ፤
ደስተኞችም ሁሉ አቃሰቱ።
8የከበሮ ደስታ ጸጥ አለ፤
የጨፋሪዎች ጩኸት አበቃ፤
ደስ የሚያሰኘውም በገና እረጭ አለ።
9ከእንግዲህ እየዘፈኑ የወይን ጠጅ
አይጠጡም፤
መጠጡም ለሚጠጡት ይመራል።
10የፈራረሰችው ከተማ ባድማ ሆነች፤
የየቤቱም መግቢያ ተዘጋ።
11በየአደባባዩ የወይን ጠጅ ያለህ እያሉ
ይጮኻሉ፤
ደስታው ሁሉ ወደ ሐዘን ይለወጣል፤
ሐሤቱም ሁሉ ከምድር ገጽ
ጠፍቶአል።
12ከተማዪቱ ፈጽማ ፈርሳለች፤
በሮቿም ደቀው ወድቀዋል።
13የወይራ ዛፍ ሲመታ፣
የወይንም ዘለላ ሲቈረጥ ቃርሚያ
እንደሚቀር
ሁሉ፣
በምድሪቱ ላይ፣
በሕዝቦችም ላይ እንዲሁ ይሆናል።
14ድምፃቸውን ከፍ ያደርጋሉ፤ በደስታም
ይጮኻሉ፤
ከምዕራብም የእግዚአብሔርን ክብር
ያስተጋባሉ።
15ስለዚህ በምሥራቅ ለእግዚአብሔር ክብር
ስጡ፤
ከባሕር ደሴቶችም፣
የእስራኤልን አምላክ፣ የእግዚአብሔርን ስም
ከፍ ከፍ አድርጉ።
16“ለጻድቁ ክብር ይሁን” የሚል ዝማሬ፣
ከምድር ዳርቻ ሰማን፤
እኔ ግን፣ “ከሳሁ፤ መነመንሁ፤
ወዮልኝ!

23፥12 ቊ7፤ ዘፍ10፥4፤ኢሳ37፥22፤ 47፥1፤ኤር14፥17፤ 46፥11፤ሰቆ2፥13፤ ሶፎ3፥14፤ዘካ2፥10፤ ራእ18፥22
23፥13 2ነገ25፥1፤ መዝ74፥14፤ኢሳ10፥5፡ 7፤18፥6፤43፥14፤ ኤር51፥12
23፥14 ቊ11፤ ዘፍ10፥4፤1ነገ10፥22፤ ኢሳ2፥16
23፥15 መዝ90፥10፤ ኤር25፥22
23፥16 ምሳ7፥10
23፥17 ዘዳ23፥17-18፤ መዝ90፥10፤ ኤር25፥26፤ ሕዝ16፥26፤ናሆ3፥4፤ ራዕ17፥1፤18፥3፡9
23፥18 ዘፀ28፥36፤ 39፥30፤ኢሱ6፥17-19፤ መዝ72፥10፤ ኢሳ18፥7፤60፥5-9፤61፥6፤አሞ1፥9-10፤ሚክ4፥13፤ ዘካ14፥1፡14
24፥1 ቊ20፤ ዘፍ11፥9፤ኢሱ6፥17፤ ኢሳ2፥19-21፤13፥5፤ 33፥9፤ኤር25፥29
24፥2 ዘሌ25፥35-37፤ ዘዳ23፥19-20፤ ኢሳ3፥1-7፤ ሕዝ7፥12፤ሆሴ4፥9፤ 1ቆሮ7፥29-31
24፥3 ዘፍ6፥13፤ ኢሳ6፥11-12፤7፥7፤10፥6
24፥4 ኢሳ2፥12፤ 3፥26፤15፥6፤ ኤር12፥11፤14፥4፤ ኢል1፥10
24፥5 ዘፍ3፥17፤ 9፥11፤ኢሳ1፥2፤ 9፥17፤10፥6፤59፥12፤ኤር7፥28፤11፥10
24፥6 ኢሱ23፥15፤ ኢሳ1፥31
24፥7 ኢሳ3፥26፤ 7፥23፤15፥6፤16፥8-10፤ 32፥10፤ኤር48፥33፤ ኢል1፥5
24፥8 ዘፍ31፥27፤ መዝ137፥2፤ኢሳ5፥12፡ 14፤21፥5፤ኤር7፥34፤16፥9፤25፥10፤33፥11፤ ሰቆ5፥14፤ሕዝ26፥13፤ ሆሴ2፥11፤ራእ18፥22
24፥9 ኢሳ5፥11፡ 20፡22
24፥10 ዘፍ1፥2፤ ኢሳ6፥11፤25፥2፤26፥5
24፥11 መዝ144፥14፤ ኢሳ15፥6፤16፥10፤ 32፥13፤ኤር14፥3፤ ሰቆ2፥12
24፥12 ኢሳ3፥26፤ 13፥2፤19፥18
24፥13 ዘዳ30፥4፤ ኢሳ17፥6፤አብ1፥5፤ ሚክ7፥1
24፥14 ኢሳ12፥6፤ 43፥5፤49፥12 24፥15 ዘፀ5፥2፤ መዝ113፥3፤ኢሳ11፥11፤12፥4፤25፥3፤42፥12፤ 59፥19፤66፥19፤ ሚል1፥11፤ 2ተሰ1፥12 24፥16 ዘሌ26፥39፤ 1ሳሙ4፥8፤ ዕዝ9፥15፤ መዝ25፥3፤48፥10፤ 65፥8፤ኢሳ5፥8፤ 21፥2፤28፥5 33፥1፤60፥1፡19፤ኤር3፥6፡20፤5፥11፤9፥2፤10፥19፤45፥3፤ሆሴ5፥7፤ 9፥1፤

[ሸ]13 ወይም፣ *ከለዳውያን*

ከጻተኞች አሳልፈው ሰጡ፤
ከጻተኞች በክሕደታቸው አሳልፈው ሰጡ”
አልሁ።
17በምድር የምትኖር ሕዝብ ሆይ፤
ሽብር፣ ጕድጓድና ወጥመድ ይጠብቁሃል።
18ከሽብር ድምፅ የሚሸሽ፣
ወደ ጕድጓድ ይገባል፤
ከጕድጓድ የወጣም፣
በወጥመድ ይያዛል።

የሰማይ መስኮቶች ተከፍተዋልና፤
የምድርም መሠረት ተናወጠ።
19ምድር ተከፈለች፤
ምድር ተሰነጠቀች፤
ምድር ፈጽማ ተናወጠች።
20ምድር እንደ ሰካራም ዞረባት፤
ነፋስ እንደሚወዘውዘውም ጐጆ ሆነች፣
የዐመጿ ሸክም ከባድ ስለ ሆነ ትወድቃለች፤
እንደ ገናም አትነሣም

21በዚያ ቀን እግዚአብሔር፣
በላይ በሰማያት ያሉትን ኀይሎች፣
በታችም በምድር ያሉትን ነገሥታት
ይቀጣቸዋል።
22በጕድጓድ ውስጥ እንዳሉ እስረኞች፣
በአንድ ላይ ይታጐራሉ፤
በእስር ቤት ይዘጋባቸዋል[ᵠ]፣
ከብዙ ቀንም በኋላ ለፍርድ ይቀርባሉ።
23የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣
በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም፣
በሽማግሌዎቹም ፊት በክብሩ ይነግሣል፤
ጨረቃ ትሸማቀቃለች፤ ፀሓይም ታፍ
ራለች።

## ምስጋና ለእግዚአብሔር

25 እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ አምላኬ
ነህ፤
ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ፤ ስምህንም
አወድሳለሁ፤
አስቀድሞ የታሰበውን፣
ድንቅ ነገር፣
በፍጹም ታማኝነት አድርገሃልና።
2ከተማዪቱን የድንጋይ ክምር አድርገሃታል፤
የተመሸገችውንም ከተማ አፈራርሰሃታል፤
የተመሸገችው የባዕድ ከተማ ከእንግዲህ
አትኖርም፤
ተመልሳም አትሠራም።
3ስለዚህ ብርቱ ሕዝቦች ያከብሩሃል፤
የጨካኝ አሕዛብ ከተሞችም ይፈሩሃል።
4ለድኻ መጠጊያ፣
በጭንቅ ጊዜ ለችግረኛ መጠለያ፣
ከማዕበል መሸሸጊያ፣
ከፀሓይ ትኵሳትም ጥላ ሆነሃል።
የጨካኞች እስትንፋስ፣
ከግድግዳ ጋር እንደሚላጋ ማዕበል ነውና፤
5እንደ ምድረ በዳም ትኵሳት ነው።
የባዕድን ጩኸት እረጭ ታደርጋለህ፤
ትኵሳት በደመና ጥላ እንደሚበርድ፣
የጨካኞችም ዝማሬም እንዲሁ ጸጥ ይላል።

6የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር በዚህ ተራራ
ላይ፣
ለሕዝብ ሁሉ ታላቅ የምግብ ግብዣ፣
የበሰለ የወይን ጠጅ ድግስ፣
ማለፊያ ጮማና ምርጥ የወይን ጠጅ
ያዘጋጃል።
7በዚህም ተራራ ላይ፣
በሕዝብ ሁሉ ላይ የተጣለውን መጋረጃ፣
በመንግሥታት ላይ የተዘረጋውን
መሸፈኛ
ያጠፋል፤
8ሞትንም ለዘላለም ይውጣል።
ጌታ እግዚአብሔር
ከፊት ሁሉ እንባን ያብሳል፤
የሕዝቡንም ውርደት
ከምድር ሁሉ ያስወግዳል፤
እግዚአብሔር ተናግሮአልና።

9በዚያን ቀን እንዲህ ይባላል፤
“እነሆ፤ አምላካችን ይህ ነው፤

በእርሱ ታመንን፤ እርሱም አዳነን፤
እግዚአብሔር ይህ ነው፤ በእርሱ
ታመንን፤
በማዳኑም ደስ ይበለን፤ ሐሤትም እናድርግ።”

10የእግዚአብሔር እጅ በዚህ ተራራ ላይ
ያርፋል፤
ነገር ግን ጭድ ከጭቃ ጋር እንደሚረገጥ፣
ሞዓብም እንዲሁ ይረገጣል።
11ዋናተኛ ሲዋኝ እጁን እንደሚዘረጋ፣
በውስጡ ሆነው እጃቸውን ይዘረጋሉ፤
ጌታ በእጃቸው ተንኰል ሳይታለል፣
ትዕቢታቸውን ያዋርዳል።
12ከፍ ብሎ የተመሸገውን ቅጥርህን ዝቅ
ያደርገዋል፤
ወደ ታች ያወርደዋል፤
ወደ ምድር አውርዶም
ትቢያ ላይ ይጥለዋል።

## የምስጋና መዝሙር

26 በዚያ ቀን ይህ መዝሙር በይሁዳ
ምድር ይዘመራል፤
ብርቱ ከተማ አለችን፣

24፥17 ዘዳ32፥23-25፤ ኢሳ8፥14፤ኤር48፥43፤ ሉቃ21፥35
24፥18 ዘፍ7፥11፤ መሳ5፥4፤ኢዮ9፥6፤18፥9፤20፥24፤ መዝ11፥3፤ኢሳ8፥14፤ 42፥22፤ሰቆ3፥47፤ ሕዝ12፥13፤38፥19
24፥19 ዘዳ11፥6፤ መዝ46፥2
24፥20 ኢዮ12፥14፡ 25፤27፥18፤መዝ46፥2፤ኢሳ1፥2፡28፤43፥27፤ 58፥1
24፥21 ኢሳ2፥11፡12፤ 10፥12፡20፤13፥11፤ ኤር25፥29፤1ቆሮ6፥3፤ኤፌ6፥11-12፤ ራእ16፥14
24፥22 ኢሳ10፥4፤ 42፥7፡22፤ሕዝ38፥8፤ ሉቃ8፥31፤ራእ20፥7-10
24፥23 መዝ97፥1፤ ኢሳ2፥2፤13፥10፤ 28፥5፤41፥16፤45፥25፤60፥19፤ሕዝ48፥35፤ ዘካ2፥5፤ዕብ12፥22፤ ራእ21፥23፤22፥5
25፥1 ዘኍ23፥19፤ መዝ40፥5፤98፥1፤ 145፥2፤ኢሳ7፥13፤ 11፥5፤12፥1፡4፤ 14፥24፤37፥26፤ 46፥11፤ኢል2፥21፡ 26፤ኤፌ1፥11
25፥2 ዘዳ13፥16፤ ኢዮ12፥14፤ኢሳ13፥22፤ 17፥1፡3፤26፥5፤37፥26
25፥3 ዘፀ6፥2፤ መዝ22፥23፤ኢሳ11፥14፤ 13፥11
25፥4 2ሳሙ22፥3፤ መዝ55፥8፤118፥8፤ ኢሳ3፥14፤4፥6፤ 14፥30፤17፥10፤27፥5፤29፥5፡19፤33፥16፤ 49፥25፤ኢል3፥16
25፥5 መዝ18፥44፤ ኢሳ13፥11፤ ኤር51፥55
25፥6 ዘፍ29፥22፤ 1ነገ1፥25፤መዝ36፥8፤ ምሳ9፥2፤ኢሳ1፥19፤ 2፥2፤55፥1-2፤66፥11፤ ኢል3፥18፤ማቴ8፥11፤ 22፥4፤ራእ19፥9
25፥7 ኢዮ4፥9፤ 2ቆሮ3፥15-16፤ ኤፌ4፥18
25፥8 ዘፍ30፥23፤ መዝ119፥39፤ ኢሳ7፥7፤15፥3፤26፥19፤ 30፥19፤35፥10፤ 51፥11፤65፥19፤ ኤር31፥16፤ሆሴ13፥14፤ ማቴ5፥11፤ 1ቆሮ15፥54-55፤ 1ጴጥ4፥14፤ራእ7፥14፡ 17፤21፥4
25፥9 ዘዳ32፥43፤ መዝ9፥2፤13፥5፤22፥5፤ 145፥19፤ኢሳ2፥11፤ 9፥3፤10፥20፤12፥2፤ 19፥20፤33፥22፤ 35፥2፡4፡10፤40፥9፤ 41፥16፤43፥3፡11፤ 45፥15፡21፤49፥25-26፤ 51፥3፤60፥16፤ 61፥7፡10፤63፥8፤ 66፥14፤ኤር14፥8
25፥10 ዘፍ19፥37፤ ዘኍ21፥29፤ዘዳ23፥6፤ኢሳ2፥2፤11፥14፤አሞ2፥1-3
25፥11 ዘሌ26፥19፤ኢዮ40፥12፤ኢሳ5፥25፤ 14፥26፤16፥14
25፥12 ኢዮ40፥11፤ኢሳ2፥15፤15፥1፤ ኤር51፥44
26፥1 መዝ48፥13፤ ኢሳ10፥20፤14፥32፤ 30፥29፤32፥18፤ 60፥18፤ዘካ2፥5፤9፥8

ᵠ22 ወይም፣ ይላቀቃሉ።

አምላካችን ቅጥሮቿንና ምሽጎቿን፣
ለድነት አድርጎአል።
2በእምነቱ የጸና
ጻድቅ የሆነ ሕዝብ ይገባ ዘንድ፣
በሮቿን ክፈቱ።
3በአንተ ላይ ታምናለችና፣
በአንተ የምትደገፈውን ነፍስ
ፈጽመህ በሰላም ትጠብቃታለህ።
4በእግዚአብሔር ለዘላለም ታመኑ፤
ጌታ እግዚአብሔር የዘላለም ዐምባ ነውና።
5በከፍታ የሚኖሩትን ዝቅ ዝቅ ያደርጋል፤
ከፍ ከፍ ያለችውን ከተማ ያዋርዳል፤
ወደ ምድር ይጥላታል፤
ከትቢያም ጋር ይደባልቃታል።
6እግር
የተጨቋኞች እግር፣
የድኾችም ኮቴ ይረግጣታል።
7የጻድቃን መንገድ ቅን ናት፤
አንተ ቅን የሆንህ ሆይ፤
የጻድቃንን መንገድ ታቃናለህ።
8እግዚአብሔር ሆይ፤ በሕግህ[በ] ጐዳና በመሄድ፣
አንተን ተስፋ አድርገናል፤
ስምህና ዝናህ፣
የልባችን ምኞት ነው።
9ነፍሴ በሌሊት ትናፍቅሃለች፤
መንፈሴም በውስጤ ትፈልግሃለች።
ፍርድህ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ፣
የዓለም ሕዝቦች ጽድቅን ይማራሉ።
10ክፉዎች ርኅራኄ ቢደረግላቸው እንኳ፣
ጽድቅን አይማሩም፤
በቅንነት ምድር እንኳ ክፋትን ያደርጋሉ፤
የእግዚአብሔርንም ግርማ አያስተውሉም።
11እግዚአብሔር ሆይ፤ ክንድህ ከፍ ከፍ ብሎአል፤
እነርሱ ግን አላስተዋሉም፤
ለሕዝብህ ያለህን ቅናት ይዩ፤ ይፈሩም፤
ለጠላቶችህም የተዘጋጀው እሳት ይብላቸው።
12እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ሰላምን መሠረትህልን፤
የሠራነውንም ሁሉ አንተ አከናወንህልን።
13እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ፤
ከአንተ ሌላ ሌሎች ጌቶች ገዝተውናል፤
እኛ ግን የአንተን ስም ብቻ እናከብራለን።
14እነርሱ ሞተዋል፤ ከእንግዲህ በሕይወት አይኖሩም፤
መንፈሳቸው ተነሥቶ አይመጣም።
አንተ ቀጣሃቸው፤ አጠፋሃቸው፤
መታሰቢያቸውንም ሁሉ ደመሰስህ።
15እግዚአብሔር ሆይ፤ ሕዝብን አበዛህ፤
ሕዝብን አበዛህ።
ክብሩን ለራስህ አደረግህ፤
የምድሪቱንም ወሰን ሁሉ አሰፋህ።
16እግዚአብሔር ሆይ፤ በተጨነቁ ጊዜ ወደ አንተ መጡ፤
በገሠጽሃቸውም ጊዜ፣
በለሆሳስ ድምፅ ይጸልያሉ[+]።
17እግዚአብሔር ሆይ፤ የፀነሰች ሴት ልትወልድ ስትል፣
በምጥ እንደምትጨነቅና እንደምትጮኽ፣
እኛም በፊትህ እንዲሁ ሆነናል።
18አረገዝን በምጥም ተጨነቅን፤
ነገር ግን ነፋስን ወለድን፤
ለምድርም ድነትን አላመጣንም፤
የዓለምን ሕዝብ አልወለድንም
19ነገር ግን ሙታንህ ሕያዋን ይሆናሉ፤
በድናቸውም ይነሣል።
እናንት በዐፈር ውስጥ የምትኖሩ፣
ተነሡ፤ በደስታም ዘምሩ።
ጠልህ እንደ ንጋት ጠል ነው፤
ምድር ሙታንን ትወልዳለች።
20ሕዝቤ ሆይ፤ ሂድ ወደ ቤትህ ግባ፤
በርህን ከኋላህ ዝጋ፤
ቍጣው እስኪያልፍ ድረስ፣
ለጥቂት ቀን ተሸሸግ።
21በምድር ላይ የሚኖረውን ሕዝብ ስለ ኀጢአቱ ለመቅጣት፣
እነሆ፤ እግዚአብሔር ከመኖሪያው ወጥቶ ይመጣል፤
ምድር በላይዋ የፈሰሰውን ደም ትገልጣለች፤
የተገደሉትንም ከእንግዲህ አትሸሽግም።

## የእስራኤል ዐርነት መውጣት

27 በዚያ ቀን እግዚአብሔር፣
ተወርዋሪውን እባብ ሌዋታንን፣
የሚጠቀለለውን ዘንዶ ሌዋታንን
በብርቱ፣ በታላቁና በኀይለኛ ሰይፍ ይቀጣዋል፤
የባሕሩንም ግዙፍ አውሬ ይቈራርጠዋል።
2በዚያን ቀን እንዲህ ይባላል፤
"ለመልካሙ የወይን ቦታ ዘምሩለት፤
3እኔ እግዚአብሔር ጠባቂው ነኝ፤
ዘወትር ውሃ አጠጣዋለሁ፤
ስለዚህ ማንም አይጐዳውም፣
ቀንና ሌሊት እጠብቀዋለሁ፤
4እኔ አልቈጣም።
እሾኽና ኵርንችት ምነው በተነሡብኝ!
ለውጊያ በወጣሁባቸው፣

26፥2 መዝ24፥3-4፡7፤85፥13፤ኢሳ1፥26፤4፥3፤9፥7፤50፥8፤53፥11፤54፥14፤58፥8፤62፥2
26፥3 1ዜና5፥20፤ ኢዮ22፥21፤መዝ22፥5፤28፥7፤ኢሳ9፥6፥7፤12፥2፤ፊል4፥7
26፥4 ዘፍ49፥24፤ መዝ62፥8፤ኢሳ12፥2፤50፥10
26፥5 ኢሳ25፥2፡12፤ሕዝ26፥11
26፥6 ኢሳ5፥5፤3፥15፤14፥30፤49፥26
26፥7 ዘፀ14፥19፤ መዝ25፥8፤26፥12፤ ኢሳ40፥4፤42፥16
26፥8 ዘዳ18፥18፤ መዝ1፥2፤37፥9፤130፥5፤145፥2፤ ኢሳ12፥4፤56፥1፤64፥5
26፥9 1ዜና16፥14፤ መዝ42፥1-3፤63፥1፤78፥34፤119፥55፤ ኢሳ55፥6፤ማቴ6፥33
26፥10 1ሳሙ12፥24፤ ኢሳ22፥12-13፤32፥6፤59፥7፡13፤ኤር2፥19፤ ሆሴ11፥7፤ማቴ5፥45፤ ዮሐ5፥37-38፤ ሮሜ2፥4
26፥11 መዝ10፥12፤ ኢሳ1፥31፤9፥7፤18፥3፤44፥9፡18፤ኢል2፥18፤ ሚክ7፥16፤ዘካ1፥14፤ ዕብ10፥27
26፥12 መዝ68፥28፤119፥165፤ኢሳ9፥6
26፥13 ኢሳ2፥8፤10፥5፡11፤12፥4፤42፥8፤63፥7
26፥14 ዘዳ4፥28፤ ኢዮ26፥5፤መዝ9፥5፡6፤ ኢሳ10፥3
26፥15 ኢዮ12፥23፤ ኢሳ14፥2፤33፥17
26፥16 መሳ6፥2፤ መዝ39፥11፤ኢሳ5፥30፤29፥4
26፥17 ኢሳ21፥3፤ ዮሐ16፥21፤ራእ12፥2
26፥18 ዘፍ49፥10፤ መዝ17፥14፤ ኢሳ33፥11፤42፥6፤49፥6፤51፥4፤59፥4፤ ኤር12፥16
26፥19 ዘፍ27፥28፤ መዝ22፥29፤ኢሳ18፥4፤25፥8፤66፥24፤ ሕዝ37፥1-14፤ ዳን12፥2፤ኤፌ5፥14
26፥20 ዘፀ12፥23፤ ኢዮ14፥13፤መዝ91፥1፡4፤ኢሳ10፥25፤30፥27
26፥21 ኢዮ16፥18፤ ኢሳ13፥9፡11፤18፥4፤29፥6፤30፥12-14፤ ሉቃ11፥50-51፤ ይሁ1፥14
27፥1 ቀኑ13፤ ዘፍ3፥24፤ዘዳ32፥41፤ ኢዮ3፥8፤26፥13፤ መዝ68፥30፤74፥13፤ኢሳ2፥11፤28፥5፤31፥8፤34፥6፤65፥12፤ 66፥16፤ሕዝ21፥3፤ ናሆ3፥15፤ራእ12፥9
27፥2 ኢሳ5፥1፤ 24፥21፤ኤር2፥21 27፥3 መዝ91፥4፤ ኢሳ5፥2፤58፥11፤ ዮሐ6፥39 27፥4 ቀኑ11፤ኢሳ10፥17፤ማቴ3፥12፤ ዕብ6፥8

[በ]8 ወይም፣ *በፍርድህ* ተብሎ መተርጐም ይችላል
[+]16 በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጕም በትክክል አይታወቅም።

አንድ ላይ ባቃጠልኋቸው!
5አለዚያ ይምጡና መሸሸጊያቸው ያድርጉኝ፤
ከእኔ ጋር ሰላም ይፍጠሩ፤
አዎን፤ ከእኔ ጋር ሰላም ያድርጉ::”

6በሚመጡት ቀናት ያዕቆብ ሥር ይሰዳል፤
እስራኤልም ያቈጠቍጣል፤ ያብባልም፤
በፍሬያቸውም ምድርን ሁሉ ይሞላሉ::

7የመቷትን እንደ መታቸው፣
እግዚአብሔር እርሷንስ መታትን?
የገደሏትን እንደ ገደላቸው፣
እርሷስ ተገደለችን?
8በጦርነትና በስደት ተፋለምሃት[ቸ]፤
የምሥራቅ ነፋስ እንደሚነፍስበት ቀን፣
በብርቱ ዐውሎ ነፋስ አሳደድሃት::
9ያዕቆብ የመሠዊያ ድንጋዮችን፣
እንደ ኖራ ድንጋይ ፈጭቶ ሲ
ያደቃቸው፣
የአሼራን ዐምድና የዕጣን መሠዊያዎችን፣
ከቦታቸው ነቅሎ ሲጥል፣
በዚያን ጊዜ በደሉ ይሰረይለታል፤
ይህም ኀጢአቱን የማስወገዱ ሙሉ ፍሬ
ይሆናል::
10የተመሸገባት ከተማ ባዶዋን ቀርታለች፤
እንደ ምድረ በዳም የተተወች ስፍራ
ሆናለች፤
ጥጆች በዚያ ይሰማራሉ፤
እዚያም ይተኛሉ፤
ቅርንጫፎቿንም ልጠው ይበላሉ::
11ጫፎቿ ሲደርቁ ይሰበራሉ፤
ሴቶችም መጥተው ይማግዷቸዋል::
ማስተዋል የሌለው ሕዝብ ስለ ሆነ፣
ፈጣሪው አይራራለትም፤
ያበጀውም አይምረውም::

12በዚያ ቀን ከኤፍራጥስ ወንዝ አንሥቶ
እስከ ግብፅ ደረቅ ወንዝ፤ እግዚአብሔር እህ
ሉን ይወቃል፤ እናንተም የእስራኤል ልጆች
ሆይ፤ አንድ በአንድ ትሰበሰባላችሁ::
13በዚያ ቀን ታላቅ መለከት ይነፋል፤ በአ
ሦር የጠፉትና በግብፅ የተሰደዱትም
መጥተው፣ በተቀደሰው ተራራ በኢየሩ
ሳሌም እግዚአብሔርን ያመልካሉ::

**ወዮ ለኤፍሬም**

**28** ለኤፍሬም ሰካራሞች የመታበያ አክ
ሊል ለሆነች፣
በለመለመ ሸለቆ ዐናት ላይ ጒብ ብላ፣
የክብሩ ውበት ለሆነች ጠውላጋ አበባ፣
የወይን ጠጅ ለዘራቸው መኰ…ራሪያ ለሆነች፣
ለዚያች ከተማ ወዮላት!
2እነሆ፤ ጌታ ኀያልና ብርቱ የሆነ ነገር
አለው፤
ይህም እንደ በረዶ ወጀብ፣ እንደሚያጠፋ
ዐውሎ ነፋስ፣

27÷5 ኢዮ22÷21፤ መዝ119÷165፤ ኢሳ25÷4፤ሮሜ5÷1፤ 2ቆሮ5÷20
27÷6 ዘፍ40÷10፤ 2ነገ19÷30፤ መዝ72÷16፤ ኢሳ11÷1፡10፤ 37÷31፤ሕዝ17÷23፤ 36÷8፤ሆሴ14÷8
27÷7 ኢሳ10÷26፤ 11÷4፤37÷36-38
27÷8 ዘፍ41÷6፤ ኢሳ49÷14፤50÷1፤54÷7
27÷9 ዘፀ23÷24፤ 34÷13፤ዘሌ26÷30፤ 2ዜና14÷5፤ መዝ78÷38፤ ሮሜ11÷27
27÷10 ዘፍ1÷2፤ ዘዳ13÷16፤ኢሳ5÷5፡ 6፡17፤17÷2፤32÷14፤ኤር10÷22፤26÷6፤ ሰቆ1÷4፤5÷18
27÷11 ቍ4፤ ዘዳ32÷18፡28፤ ኢሳ1÷3፤9÷17፤10÷33፤ 33÷12፤41÷8፤43÷1፡7፡ 15፤44÷1-2፡21፡24፤ ኤር11÷16
27÷12 ዘፍ15÷18፤ ዘዳ30÷4፤ኢሳ1÷9፤ 11÷12፤17÷6፤21÷10፤ ማቴ3÷12
27÷13 ቍ1፤ ዘፍ27÷29፤ዘሌ25÷9፤ መሳ3÷27፤መዝ22÷29፤8 6÷9፤106÷47፤ ኢሳ2÷2፤10÷19፤ 19÷21፡25፤ ማቴ24÷31
28÷1 ቍ3፡4፤ ዘሌ10÷9፤ኢሳ5÷11፤ 7÷2፤9÷9፤10÷5፤ 29÷1፤30÷1፤31÷1፤ 33÷1፤ሆሴ7÷5፤ አሞ6÷6
28÷2 ኢሱ10÷11፤ ኢሳ8÷7፤29÷6፤ 40÷10፤ዳን9÷26
28÷3 ቍ1፤ ኢዮ40÷12፤ኢሳ5÷5
28÷4 ቍ1፤ መሓ2÷13፤ሆሴ9÷10፤ ናሆ3÷12
28÷5 ኢሳ1÷9፤ 10÷20፤24÷16፡23፤ 27÷1፤29÷18፤30÷23፤ 62÷3፤ኤር13÷18፤ ሕዝ16÷12፤21÷26፤ ዘካ9÷16
28÷6 መሳ9÷44-45፤ 2ሳሙ14÷20፤ 2ዜና32÷8፤ኢሳ4÷4፤ 11÷2-4፤32÷1፡16፤ 33÷5፤ዮሐ5÷30
28÷7 ዘሌ10÷9፤ መዝ107÷27፤ኢሳ1÷1፤ 3÷12፤9÷15፤22÷13፤ 24÷2፤29÷11፤ ኤፌ5÷18
28÷8 ኤር48÷26
28÷9 ቍ26፤

እንደ ኀይለኛ ማዕበል፣ እንደ ከባድ ዝናብ፣
በኀይል ወደ ምድር ይጥላታል::
3የኤፍሬም ሰካራሞች የመታበያ አክሊል፣
በእግር ይረገጣል::
4በለምለሙ ሸለቆ ዐናት ላይ ጒብ ብላ፣
የክብሩ ውበት የሆነች ጠውላጋ አበባ፣
ከመከር በፊት እንደ ደረሰች፣
ሰውም ድንገት አይቶ እንደሚቀጥፋት
ወዲያውኑም እንደሚውጣት በለስ
ትሆናለች::

5በዚያን ቀን የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣
ለተረፈው ሕዝቡ፣
የክብር ዘውድ፣
የውበትም አክሊል ይሆናል::
6እርሱም በፍርድ ወንበር ላይ ለሚቀመጠው፣
የፍትሕ መንፈስ፣
ጦርን ከከተማዪቱ በር ላይ ለሚመልሱም፣
የኀይል ምንጭ ይሆናል::

7እነዚህም በወይን ጠጅ ይንገዳገዳሉ፤
በሚያሰክርም መጠጥ ይወላገዳሉ፤
ካህናቱና ነቢያቱ በሚያሰክር መጠጥ
ተንገደገዱ፤
በወይን ጠጅ ነገር ተምታታባቸው፤
በሚያሰክር መጠጥ ተወላገዱ፤
ራእይ ሲያዩ ይስታሉ፤
ፍርድ ሲሰጡም ይሰናከላሉ::
8የማዕድ ገበታቸው ሁሉ በትፋት
ተሞልቶአል፤
ከትውኪያም የጸዳ ቦታ የለም::
9እነርሱም እንዲህ ይላሉ፤ “የሚያስተምረው
ማንን ነው?
መልእክቱን የሚያብራራውስ ለማን ነው?
ወተት ለተወዉት ሕፃናት?
ወይስ ጡት ለጣሉት?
10በትእዛዝ ላይ ትእዛዝ፣ በትእዛዝ ላይ
ትእዛዝ፤
በደንብ ላይ ደንብ፣ በደንብ ላይ ደንብ፤[ቸ]
እዚህ ጥቂት፣ እዚያ ጥቂት ነውና::
11እንግዲያማ እግዚአብሔር፣
በባዕድ ልሳን በእንግዳ ቋንቋ ለዚህ ሕዝብ
ይናገራል::
12እርሱ፣ “ይህቺ የዕረፍት ቦታ ናት፤
የደከመው
ይረፍ፤
ይህቺ የእፎይታ ቦታ ናት” ያለው ለማን

መዝ32÷8፤131÷2፤ኢሳ2÷3፤30÷20፤48÷17፤50÷4፤52÷7፤53÷1፤ 54÷13፤ኤር31÷34፤32÷33፤ ዕብ5÷12-13፤1ጴጥ2÷2
28÷10 ቍ13 28÷11 ዘፍ11÷7፤ኢሳ33÷19፤ኤር5÷15፤ሕዝ3÷5፤ 1ቆሮ14÷21 28÷12 ዘፀ14÷14፤ ኢሱ1÷13፤ኢዮ11÷18፤ ኢሳ11÷10፤ማቴ11÷28-29

[ቸ]8 በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጒም በትክክል አይታወቅም::
[ቸ]10 በዚህና በቍጥር 13 ላይ ይብራይስጡ፣ *ላቭ ላሳቭ ሳቭ ላሳቭ፣ ካቭ ላካቭ ካቭ ለካቭ* ይላል፤ ምናልባት ትርጒም የለሽ ንግግርን ለማሳየት ይሆናል፤ ይኸውም የነቢያትን ቃል አስመስሎ መናገርን ሊሆን ይችላል::

ነበር?
እነርሱ ግን መስማት አልፈለጉም።
13ስለዚህ *የእግዚአብሔር ቃል*፣
በትእዛዝ ላይ ትእዛዝ፣ በትእዛዝ ላይ ትእዛዝ፤
በደንብ ላይ ደንብ፣ በደንብ ላይ ደንብ፤
እዚህ ጥቂት እዚያ ጥቂት ይሆንባቸዋል።
ይህ የሚሆንባቸው ሄደው ወደ ኋላ እንዲወድቁ፣
እንዲቈስሉና በወጥመድ እንዲያዙ፣
እንዲማረኩም ነው።
14ስለዚህ በኢየሩሳሌም ያለውን ሕዝብ የምትገዙ፣
እናንት ፌዘኞች *የእግዚአብሔርን ቃል* ስሙ።
15እናንት፣ “ከሞት ጋር ቃል ኪዳን ገብተናል፤
ከሲኦልም ጋር ስምምነት አድርገናል፤
ውሸትን መጠጊያችን፣
ሐሰትን[ጎ] መደበቂያችን አድርገናል፤
ታላቅ መቅሠፍት እየጠራረገ ሲያልፍ፣
ሊነካን አይችልም” በማለት ታብያችኋል።
16ስለዚህ ልዑል *እግዚእብሔር* እንዲህ ይላል፤
‘እነሆ፤ የተፈተነ ድንጋይ፣ የመሠረት ድንጋይ፣
ለጽኑ መሠረት የሚሆን የከበረ የማእዘን ድንጋይ፣
በጽዮን አስቀምጣለሁ፤
በእርሱም የሚያምን አያፍርም።
17ፍትሕን የመለኪያ ገመድ፣
ጽድቅንም ቱንቢ አደርጋለሁ፤
ውሸት መጠጊያችሁን የበረዶ ዝናብ ይጠራርገዋል
መደበቂያችሁንም ውሃ ያጥለቀልቀዋል።
18ከሞት ጋር የገባችሁት ቃል ኪዳን ይሻራል፤
ከሲኦልም ጋር ያደረጋችሁት ስምምነት ይፈርሳል፤
ታላቁ መቅሠፍት እየጠራረገ ሲያልፍ፣
እናንተም ትጠራረጋላችሁ።
19በመጣ ቍጥር ይዞአችሁ ይሄዳል፤
ማለዳ ማለዳ፣ በቀንና በሌሊትም ይጠራርጋል።”
ይህን ቃል ብታስተውሉ፣
ሽብር በሽብር በሆነ ነበር።
20እግር ዘርግቶ እንዳይተኛ ዐልጋው አጭር ነው፤
ሰውነትንም ለመሸፋፈን ብርድ ልብሱ ጠባብ ነው።
21*እግዚአብሔር ሥራውን*፣ አዎን ድንቅ ሥራውን ሊሠራ፣
ተግባሩን፣ እንግዳ የሆነ ተግባሩን ሊያከናውን፣
በፐራሲም ተራራ እንዳደረገው ይነሣል፣

28፥13 ቍ10፤ ኢሳ8፥15፤ማቴ21፥44
28፥14 2ዜና36፥16፤ ኢሳ1፥10
28፥15 ቍ2፡18፤ መሳ9፥35፤ኢዮ5፥23፤ ኢሳ8፥7-8፡19፤9፥15፤ 10፥26፤29፥6፡15፤ 30፥28፤ኤር23፥24፤ ዳን11፥22
28፥16 መዝ118፥22፤ ኢሳ8፥14-15፤14፥32፤ 29፥22፤45፥17፤50፥7፤54፥4፤ኤር51፥26፤ ዳን2፥34-35፡45፤ ዘካ12፥3፤ሐሥ4፥11፤ ሮሜ9፥33፤10፥11፤ 1ቆሮ3፥11፤ 2ጢሞ2፥19፤1ጴጥ2፥6
28፥17 ኢሱ10፥11፤ 2ነገ21፥13፤መዝ11፥7፤ኢሳ5፥16፤8፥7
28፥18 ቍ15፤ ኢሳ5፥5፤7፥7፤63፥18፤ ዳን8፥13
28፥19 2ነገ24፥2፤ ኢዮ18፥11፤መዝ5፥3
28፥20 ኢሳ59፥6
28፥21 ዘፍ38፥29፤ ኢሱ9፥3፤1ዜና14፥11፤ ኢሳ10፥12፤65፥7፤ ሉቃ19፥41-44
28፥22 2ዜና36፥16፤ ኢሳ10፥22፡23፤ ኤር29፥18፤ሰቆ2፥15፤ሶፎ2፥15
28፥23 ኢሳ32፥9
28፥24 መክ3፥2
28፥25 ዘፀ9፥31፡32፤ ሕዝ4፥9፤ማቴ23፥23
28፥26 መዝ94፥10
28፥27 ኢዮ41፥30፤ ኢሳ10፥5፤21፥10
28፥28 ኢሳ21፥10
28፥29 መዝ92፥5፤ ኢሳ9፥6፤ሮሜ11፥33
29፥1 ቍ2፡7፤ 2ሳሙ5፥7፤ኢሳ1፥14፤ 22፥12-13፤28፥1
29፥2 ቍ1፤ ኢሳ3፥26፤ሰቆ2፥5፤ ሕዝ43፥15
29፥3 2ነገ25፥1፤ ሉቃ19፥43-44
29፥4 ዘሌ19፥31፤ ኢሳ8፥19፤26፥16፤ 47፥1፤52፥2

በገባዖን ሸለቆ እንዳደረገው ይነሣሣል።
22እንግዲህ ፌዛችሁን አቁሙ፤
አለዚያ እስራታችሁ ይጸናባችኋል፤
ጌታ የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*፣
መላውን ምድር ለማጥፋት ያወጀውን ዐዋጅ ሰምቻለሁ።
23አድምጡ ድምፄን ስሙ፤
አስተውሉ ቃሌንም ስሙ።
24ገበሬ ሊዘራ መሬቱን ሲያዘጋጅ ያለማቋረጥ ያርሳልን?
ጓሉን ሲከሰክስ፣ ዐፈሩን ሲያለሰልስ ይከርማልን?
25ዕርሻውን አስተካክሎ፣
ጥቍር አዝሙድና ከሙን አይዘራምን?
ስንዴውንስ በትልሙ[ነ]፣
ገብሱን በተገቢ ቦታው፣
አጃውንም በተመደበው ስፍራ አይዘራምን?
26አምላኩ ያስተምረዋል፤
ትክክለኛውንም መንገድ ያሳየዋል።
27ጥቍር አዝሙድ በመውቂያ መሣሪያ አይወቃም፤
ከሙን የሠረገላ መንኰራኵር አይሄድበትም፤
ጥቍር አዝሙድ በበትር፣
ከሙንም በዘንግ ይወቃል።
28እንጀራን ለመጋገር እህል ይፈጫል፤
ስለዚህ አንድ ሰው ለዘላለም እህል ሲወቃ አይኖርም።
የመውቂያውን መንኰራኵር ቢያኼድበትም፣
ፈረሶቹ አይደፈጥጡትም።
29ይህ ሁሉ የሚሆነው በምክሩ ድንቅ በጥበቡ ታላቅ ከሆነው፣
ከሰራዊት ጌታ *ከእግዚአብሔር* ዘንድ ነው።

## ወዮ ለዳዊት ከተማ

29 ዳዊት የሰፈረብሽ ከተማ፣
አርኤል፣ አርኤል ወዮልሽ!
ዓመት በዓመት ላይ ጨምሪ፣
ዐውደ ዓመትሽም ይቀጥል።
2ነገር ግን አርኤልን[ኘ] እከባለሁ፤
ታለቅሳለች፤ ዋይ ዋይ ትላለች፤
ለእኔም እንደ መሠዊያ ስፍራ ትሆንልኛለች።
3በዙሪያሽ እሰፍራለሁ፤
በቅጥር እከብሻለሁ፤
የከበባ ዐምባም ሠርቼ አስጨንቅሻለሁ።
4ወደ ታች ትወርጃለሽ፤ ከምድርም በታች ትናገሪያለሽ፤
ንግግርሽ ከትቢያ እየተጕተመተመ ይወጣል፤
ድምፅሽ እንደ መናፍስት ድምፅ ከመሬት

[ጎ]15 ወይም፣ *ሐሰተኛ ጣዖታትን*
[ነ]25 በዕብራይስጡ የዚህ ቃል ትርጒም በትክክል አይታወቅም።
[ኘ]2 በዕብራይስጡ፣ ***የመሠዊያ መሬት*** የሚለው ቃል ድምፀት፣ ***አርኤል*** ከሚለው ቃል ጋር አንድ ዐይነት ነው።

ወደ ላይ ይመጣል፤
ንግግርሽ ከትቢያ ያንሾካሹካል።
5ነገር ግን ብዙ ጠላቶችሽ እንደ ትቢያ ብናኝ፣
መንጋ ጨካኞችም በነፋስ እንደሚነጻ ገለባ ይሆናሉ።
ድንገት ሳይታሰብም፣
6የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*፣
በነጐድጓድ፣ በምድር መናወጥና በታላቅ ድምፅ፣
በዐውሎ ነፋስና በኀይለኛ ሞገድ ፈጽሞ በሚባላም የእሳት ነበልባል ይመጣል።
7አርኤልን የሚወጋ የአሕዛብ ሁሉ መንጋ፣
በእርሷና በምሽጓ ላይ አደጋ የሚጥልና የሚከባት፣
እንደ ሕልም
በሌሊትም እንደሚታይ ራእይ ይሆናል።
8የተራበ ሰው በሕልሙ ሲበላ ዐድሮ፣
ነገር ግን ሲነቃ ራቡ እንዳልለቀቀው፣
የጠማውም ሰው በሕልሙ ሲጠጣ ዐድሮ፣
ነገር ግን ሲነቃ እንደ ዛለና ጥማቱም እንዳልተወው፣
የጽዮንን ተራራ የሚወጋ፣
የአሕዛብ መንጋ ሁሉ እንዲሁ ይሆናል።

9ነሁሉሉ፤ ተደነቁም፤
ተጨፈኑ፤ እስከ ወዲያኛውም ታውራችሁ ቅሩ፤
በወይን ጠጅ አይሁን እንጂ ስከሩ፤
በሚያሰክር መጠጥ አይሁን እንጂ ተንገዳገዱ።
10*እግዚአብሔር* ከባድ እንቅልፍ ጥሎባችኋል፤
ዐይኖቻችሁን፣ ነቢያትን ጨፍኖባችኋል፤
ራሶቻችሁን፣ ባለ ራእዮችን ሸፍኖባችኋል።

11ይህ ሁሉ ራእይ በጥቅልል መጽሐፍ ውስጥ እንደ ታሸገ ቃል ሆኖባችኋል። ጥቅልሉንም መጽሐፍ ማንበብ ለሚችል ሰው፣ “እባክህ አንብልን” ብላችሁ ብትሰጡት፣ “ታሽጓልና አልችልም” ይላችኋል።
12ደግሞም ጥቅልሉን መጽሐፍ ማንበብ ለማይችል ሰው፣ “እባክህን አንብልን” ብላችሁ ብትሰጡ፣ “ማንበብ አልችልም” ይላችኋል።

13እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“ይህ ሕዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባል፤
በከንፈሩም ያከብረኛል፤
ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው፤
የሚያመልከኝም፣
ሰው ባስተማረው ሰው ሠራሽ ሥርዐት ብቻ ነው[a]።
14ስለዚህ ይህን ሕዝብ በድንቅ ላይ ድንቅ ነገር እያደረግሁ፣
ዳግመኛ አስገርመዋለሁ፤
የጥበበኞች ጥበብ ይጠፋል፤
የአስተዋዮችም ማስተዋል ይበናል።”
15ሐሳባቸውን *ከእግዚአብሔር* ለመደበቅ፣
ወደ ጥልቅ ጒድጓድ ለሚወርዱ
ሥራቸውንም በጨለማ ለሚያከናውኑ፣
“ማን ያየናል? ማንስ ያውቅብናል” ለሚሉ ወዮላቸው!
16እናንተ ነገሮችን ትገለብጣላችሁ!
ሸክላ ሠሪውን እንደ ሸክላ ትመለከታላችሁ፤
ለመሆኑ፣ ተሠሪ ሠሪውን፣
“እርሱ አልሠራኝም” ይለዋልን?
ሸክላ የሠራውን፣
“እርሱ ምንም አያውቅም” ይለዋልን?

17ሊባኖስ ወደ ለም ዕርሻነት ለመለወጥ፣
ለም የሆነውም መሬት ወደ ዱርነት ለመለወጥ ጥቂት ጊዜ አልቀረውምን?
18በዚያን ጊዜ ደንቈሮ የጥቅልሉን መጽሐፍ ቃል ይሰማል፤
የዐይነ ስውሩም ዐይኖች
ከጭጋግና ከጨለማ ተላቀው ያያሉ።
19ትሑታን *በእግዚአብሔር*፣
ምስኪኖችም በእስራኤል ቅዱስ እንደ ገና ሐሤት ያደርጋሉ።
20ጨካኞች እንዳልነበሩ ይሆናሉ፤
ፌዘኞችም በነው ይጠፋሉ፤
ለክፋት ያደፈጡ ሁሉ ይወገዳሉ።
21ሰውን በነገር በደለኛ የሚያደርጉ፣
በተከሳሽ ላይ ወጥመድ የሚዘረጉ፣
በሐሰት ምስክር ፍትሕን ከንጹሓን የሚቀሙ ይቈረጣሉ።

22ስለዚህ አብርሃምን የተቤዠው *እግዚአብሔር* ለያዕቆብ ቤት እንዲህ ይላል፤

“ያዕቆብ ከእንግዲህ ወዲያ አያፍርም፤
ፊቱም ከእንግዲህ አይለዋወጥም።
23በመካከላቸው የእጄ ሥራ የሆኑ፣
ልጆቻቸውን ሲያዩ፣
ስሜን ይቀድሳሉ፤
የያዕቆብን ቅዱስ ቅድስና ያውቃሉ፤
በእስራኤልም አምላክ ፊት በፍርሀት ይቆማሉ።

29፥5 ዘዳ9፥21፤ መዝ55፥15፤78፥39፤ 103፥15፤ኢሳ2፥22፤ 13፥11፤17፥13፡14፤ 37፥27፤40፥6፤51፥12፤ 1ተሰ5፥3
29፥6 ዘፀ19፥16፤ ዘሌ10፥2፤መዝ50፥3፤55፥8፤83፥13-15፤ ኢሳ26፥21፤28፥15፤ ዘካ14፥1-5፤ማቴ24፥7፤ ማር13፥8፤ሉቃ21፥11፤ ራእ6፥12፤11፥19
29፥7 ቍ1፤ ኢዮ20፥8፤ሚክ4፥11-12፤ ዘካ12፥9
29፥8 ቍ5፡7፤ መዝ73፥20፤ኢሳ17፥12-14፤41፥11፡15፤ 54፥17፤ኤር30፥16፤ ዘካ12፥3
29፥9 ቍ14፤ ዘሌ10፥9፤መዝ60፥3፤ ኢሳ3፥12፤6፥10፤ 28፥1፤51፥17፡21-22፤ 63፥6፤ኤር4፥9፤ 13፥13፤25፥27፤ዕን1፥5
29፥10 መሳ4፥21፤ 1ሳሙ9፥9፤ መዝ69፥23፤ ኢሳ6፥9-10፤44፥18፤ ዮና1፥5፤ሚክ3፥6፤ ሮሜ11፥8፤2ተሰ2፥9-11
29፥11 ኢሳ8፥16፤ 28፥7፤ዳን8፥26፤ 12፥9፤ማቴ13፥11፤ ራእ5፥1-2
29፥13 መዝ50፥16፤ 119፥70፤ኢሳ58፥2፤ ኤር12፥2፤14፥11፤ ሕዝ33፥31፤ሐጌ1፥2፤ 2፥14፤ማቴ15፥8-9፤ ማር7፥6-7፤ቈላ2፥22
29፥14 ኢዮ5፥13፤ 10፥16፤ኢሳ6፥9-10፤ ኤር8፥9፤49፥7፤ 1ቆሮ1፥19
29፥15 ዘፍ3፥8፤ 2ነገ21፥16፤ኢዮ8፥3፤ 22፥13፤መዝ10፥11-13፤ 94፥7፤ኢሳ28፥15፤ 47፥10፤57፥12፤ ሕዝ8፥12፤9፥9
29፥16 ዘፍ2፥7፤ ኢዮ9፥12፤10፥9፤ ኢሳ10፥15፤45፥9፤ 64፥8፤ኤር18፥6፤ ሮሜ9፥20-21
29፥17 መዝ84፥6፤ 107፥33፤ኢሳ2፥13፤ 10፥25፤32፥15
29፥18 መዝ107፥14፤ 146፥8፤ኢሳ28፥5፤ 32፥3፤ማቴ11፥5፤ ማር7፥37፤ሉቃ7፥22
29፥19 ቍ23፤ መዝ25፥9፤37፥11፤ 72፥4፤ኢሳ1፥4፤3፥15፤ 5፥19፤12፥6፤14፥30፤30፥11፤61፥1፤ ማቴ5፥5፤11፥5፡29፤ ሉቃ7፥22፤ያዕ1፥9፤ 2፥5
29፥20 2ዜና36፥16፤ኢዮ15፥35፤መዝ7፥14፤ ኢሳ9፥4፤13፥11፤ 28፥22፤32፥7፤33፥11፤34፥12፤59፥4፤ሕዝ11፥2፤ሚክ2፥1፤ ናሆ1፥11
29፥21 ምሳ21፥28፤ኢሳ5፥23፤32፥7፤አሞ5፥10፡15፤ዕን1፥4
29፥22 ዘፍ17፥16፤ ዘፀ6፥6፤መዝ22፥5፤ 25፥3፤ኢሳ28፥16፤ 41፥8፤49፥23፤51፥2፤61፥7፤63፥16፤ ኤር30፥6፡10፤ ኢል2፥6፡21፡26፤ ናሆ2፥10፤ሶፎ3፥11
29፥23 ቍ19፤መዝ8፥6፤ ኢሳ5፥19፤ 19፥25፤49፥20-26፤53፥10፤54፥1-3፤ማቴ6፥9

[a] 13 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ግን፣ *በከንቱ ያመልኩኛል፤ ትምህርታቸው ሰው ያስተማረው ሰው ሠራሽ ሥርዐት ብቻ ነው* ይላል።

24በመንፈስ የሳቱ ያስተውላሉ፤
የሚያጒረመርሙም ምክር ይቀበላሉ።”

## ወዮ ለእምቢተኛ ሕዝብ

# 30

“ለዐመፀኞች ልጆች ወዮላቸው”
ይላል እግዚአብሔር፤
“የእኔ ያልሆነውን ሐሳብ ይከተላሉ፤
ከመንፈሴ ያልሆነውን ቃል ኪዳን
ያደርጋሉ፤
በኀጢአት ላይ ኀጢአት ይጨምራሉ።
2እኔን ሳይጠይቁ፣
ወደ ግብፅ ይወርዳሉ፤
የፈርዖንን ከለላ፣
የግብፅንም ጥላ ለመጠጊያነት
ይፈልጋሉ።
3ነገር ግን የፈርዖን ከለላ ውርደት
ይሆንባችኋል፤
የግብፅም ጥላ ኀፍረት ያመጣባችኋል።
4ምንም እንኳ ሹሞች በጣኔዎስ ቢኖሯ
ቸውም፣
መልእክተኞቻቸው ሓኔስ ቢደርሱም፣
5ውርደትና ኀፍረት ብቻ እንጂ
ርዳታም ሆነ ረብ በማያስገኙላቸው
ምንም ጥቅም በማይሰጧቸው ሰዎች ምክንያት
ሁሉም ለኀፍረት ይዳረጋሉ።”
6በኔጌብ ስላሉት እንስሳት የተነገረ ንግር፤
መልእክተኞች ሀብታቸውን በአህያ፣
ውድ ዕቃዎቻቸውን በግመል ጭነው፣
ተባዕትና እንስት አንበሶች፣
መርዘኛና ተወርዋሪ እባቦች በሚኖሩበት፣
መከራና ጭንቅ ባለበት ምድር ዐልፈው፣
ወደማይጠቅማቸው ወደዚያ ሕዝብ፣
7ርዳታዋም ፈጽሞ ዋጋ ቢስ ወደ ሆነው ወደ
ግብፅ ይሄዳሉ።
ስለዚህ ስሟን፣
ረዓብ፣ ምንም የማትጠቅም ብዬ እጠራ
ታለሁ።

8አሁንም ሂድ፤ በሰሌዳ ላይ ጻፍላቸው፤
በጥቅልል መጽሐፍ ላይ ክተብላቸው፤
ለሚመጡትም ዘመናት፣
ለዘላለም ምስክር ይሆናል፤
9እነዚህም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመስማት
የማይፈልጉ፣
ዐመፀኛ ሕዝቦችና አታላይ ልጆች ናቸው።
10ባለ ራእዮችን፣
“ከእንግዲህ ራእይን አትዩ” ይላሉ፤
ነቢያትንም እንዲህ ይላሉ፤
“እውነተኛውን ትንቢት ከእንግዲህ
አትንገሩን፤
ደስ የሚያሰኘውን ንገሩን፤
የሚያማልለውን ተንብዩልን።
11ከዚህ መንገድ ፈቀቅ በሉ፤
ከጐዳናውም ራቁ፤
ከእስራኤል ቅዱስ ጋር
ፊት ለፊት አታጋጥሙን።”

12ስለዚህ፣ የእስራኤል ቅዱስ እንዲህ ይላል፤

“ይህን ቃል ስላቃለላችሁ፣
ግፍን ስለታመናችሁ፣
ማታለልን ስለ ተደገፋችሁ፣
13ስለዚህ ይህ ኀጢአት፣
ተሰነጣጥቆ ሊወድቅ እንደ ደረሰ፣
ሳይታሰብ ድንገት እንደሚወድቅ ረጅም
ቅጥር ይሆንባችኋል።
14ከሸክላ ሠሪ እንደ ወደቀ ገንቦ ሆኖ
ይከሰከሳል፤
ከምድጃ ፍም ለመጫር፣
ከጕድጓድም ውሃ ለመጨለፍ የሚሆን
ገል እስከማይገኝ ድረስ፣
ምንም ሳይቀር ክፉኛ እንደሚንኰታኰት፣
የሸክላ ዕቃ ይደቃል።”

15የእስራኤል ቅዱስ ጌታ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤

“በመመለስና በማረፍ ትድናላችሁ፤
በጸጥታና በመታመን ትበረታላችሁ፤
እናንተ ግን ይህን አላደረጋችሁም፤
16ደግሞም ‘አይሆንም፣ በፈረስ እንሸሻለን’
አላችሁ፤
ስለዚህ ትሸሻላችሁ።
ደግሞም፣ ‘በፈጣን ፈረስ እናመልጣለን’
አላችሁ፤
ስለዚህ አሳዳጆቻችሁም ፈጣን ይሆናሉ።
17በተራራ ዐናት ላይ እንደ ተተከለ ሰንደቅ
ዐላማ፣
በኰረብታም ላይ እንደ ቆመ ምልክት፣
ሆናችሁ እስክትቀሩ ድረስ
በአንድ ሰው ዛቻ፣
ሺህ ሰው ይሸሻል፤
በአምስት ሰው፣
ሁላችሁ ትሸሻላችሁ።”
18እግዚአብሔር ግን ምሕረት ሊያደርግላችሁ
ይታገሣል፤
ርኅራኄም ሊያሳያችሁ ይነሣል።
እግዚአብሔር የፍትሕ አምላክ ነውና፣
እርሱን በመተማመን የሚጠባበቁት
የተባረኩ ናቸው።

19በኢየሩሳሌም የምትኖሩ የጽዮን ሕዝብ
ሆይ፤ ከእንግዲህ ወዲህ አታለቅሱም።
ለርዳታ ወደ እርሱ ስትጮኹ እንዴት
ምሕረት አያደርግላችሁም! ጩኸትህን እንደ
ሰማም ፈጥኖ ይመልስልሃል። 20ጌታ
የጭንቀት

29፥24 መዝ95፥10፤ ምሳ12፥8፤ኢሳ1፥3፤ 28፥7፤30፥21፤32፥4፤ 41፥20፤42፥16፤ 60፥16፤ዕብ5፥2 30፥1 ዘዳ21፥18፤ 2ነገ17፥4፤ኢሳ1፥2፤ 8፥12፤28፥1 30፥2 ዘፍ25፥22፤ ዘኍ27፥21፤ 2ነገ25፥26፤ ኢሳ4፥6፤31፥1፤ 36፥6፡9፤ኤር2፥18፡36፤ 42፥14፤ሕዝ17፥15፤ 29፥16 30፥3 ቍ5፤ መሳ9፥8-15፤ መዝ44፥13፤ ኢሳ20፥4-5፤36፥6 30፥4 ዘኍ13፥22 30፥5 ቍ3፡7፤ 2ነገ18፥21፤ መዝ108፥12፤ ኢሳ20፥5፤31፥1፤ 36፥6፤ኤር37፥3-5፤ ሕዝ17፥15 30፥6 ዘፍ42፥26፤ ዘፀ1፥13፤5፥10፡21፤ ዘዳ8፥15፤መሳ1፥9፤ 1ሳሙ25፥18፤ ኢሳ5፥29፡30፤8፥22፤ 13፥1፤15፥7፤35፥9፤ ኤር11፥4 30፥7 2ነገ18፥21፤ ኢዮ9፥13፤ኤር2፥36 30፥8 ዘፀ17፥14፤ ዘዳ27፥8፤ኢሱ24፥26-27፤ኢሳ8፥1፤ ኤር25፥13፤30፥2፤ 36፥28፤ዕን2፥2 30፥9 መዝ78፥8፤ ኢሳ1፥2፡10፤28፥15፤ 59፥3-4፤ሕዝ2፥6 30፥10 1ሳሙ9፥9፤ 1ነገ22፥8፤ኤር4፥10፤11፥21፤23፥26፤25፥9፤ 26፥9፤32፥3፤36፥29፤ሕዝ13፥7፤አሞ7፥13፤ ሮሜ16፥18፤ 2ጢሞ4፥3-4 30፥11 ቍ21፤ ኢዮ21፥14፤ምሳ3፥6፤ ኢሳ29፥19፤35፥8-9፤ 48፥17 30፥12 ቍ15፤ መዝ10፥7፤12፥5፤ ኢሳ5፥7፡19፡24፤31፥1 30፥13 1ነገ20፥30፤ ነህ2፥17፤መዝ62፥3፤ 80፥12፤ኢሳ17፥14 30፥14 መዝ2፥9 30፥15 ቍ12፤ ዘፀ14፥14፤ኢሱ1፥13፤ 2ዜና20፥12፤ኢሳ8፥6፤ 32፥17፤42፥24፤ 57፥17፤ኤር7፥20፤ ሕዝ3፥11 30፥16 ዘዳ17፥16፤ 1ነገ10፥28-29፤ መዝ20፥7፤ ኢሳ31፥1፡3፤ 36፥8፤ኤር46፥6 30፥17 ዘሌ26፥8፡36፤ዘዳ28፥25፤ 2ነገ7፥7፤መዝ20፥5፤ኢሳ1፥8 30፥18 ዘፍ43፥31፤ መዝ11፥7፤ 27፥14፤ 78፥38፤ኢሳ5፥16፤25፥9፤33፥2፤40፥31፤ 42፥14፤48፥9፤64፥4፤ ሰቆ3፥25፤ዳን12፥12፤ዮና3፥10፤2ጴጥ3፥9፡ 15 30፥19 ኢዮ22፥27፤ 24፥12፤መዝ50፥15፤ 86፥7፤ኢሳ25፥8፤ 41፥17፤58፥9፤60፥20፤ 61፥3፤65፥24፤ ዘካ13፥9፤ማቴ7፥7-11 30፥20 1ነገ22፥27፤ መዝ74፥9፤ኢሳ28፥9፤ አሞ8፥11

እንጀራና የመከራ ውሃ ቢሰጥህም፣ አስተ
ማሪህ ከእንግዲህ አይሰወርብህም፤ ዐይ
ኖችህም አስተማሪህን ያያሉ:: 21ወደ ቀኝም
ሆነ ወደ ግራ ዘወር ብትል ጆሮህ ከኋላህ፣
“መንገዱ ይህ ነው፤ በእርሱ ሂድ” የሚል
ድምፅ ይሰማል:: 22ከዚያም በብር የተለበጡ
ትን ጣዖቶችህንና በወርቅ የተለበዱ ምስ
ሎችህን ታዋርዳለህ፤ “ከዚህ ወግዱ!” ብለህም
እንደ መርገም ጨርቅ ትጥላቸዋለህ::
23በምድርም ለዘራኸው ዘር ዝናብን ይሰጥሃል፤
ከመሬትም የሚገኘው ፍሬ ምርጥና የተትረፈ
ረፈ ይሆናል:: በዚያን ቀን ከብቶችህ በትልቅ
ሜዳ ላይ ይሰማራሉ:: 24የዕርሻ በሬዎችና
አህ ዮች በመንሽና በላይዳ የተለየውን ገፈራ
ና ድርቆሽ ይበላሉ:: 25በታላቁ የዕልቂት
ቀን ምሽጎች ሲፈርሱ፣ በረጅም ተራራ
ሁሉና ከፍ ባለውም ኰረብታ ሁሉ ላይ
ወራጅ ወንዝ ይፈስሳል:: 26እግዚአብሔር
የሕዝቡን ስብራት ሲጠግን፣ ያቈሰለውንም
ሲፈውስ፣ ጨረቃ እንደ ፀሓይ ታበራለች፤
የፀሓይም ብርሃን እንደ ሰባት ቀን
ብርሃን ሰባት
ዕጥፍ ይደምቃል::

27እነሆ፤ *የእግዚአብሔር* ስም፣
ከሚነድ ቍጣ፣ ጥቅጥቅ ካለና
ከሚትጐለጐል
የጢስ ደመና ጋር ከሩቅ ይመጣል፤
ከንፈሮቹ ቍጣን የተሞሉ ናቸው፤
ምላሱም የሚባላ እሳት ነው::
28እስትንፋሱ እንደሚጠራርግ፣
እስከ ዐንገት እንደሚደርስም የውሃ
ሙላት ነው፤
መንግሥታትን በጥፋት ወንፊት ያበጥራ
ቸዋል፤
በሕዝቦችም መንጋጋ፣
መንገድ የሚያስት ልጓም ያስገባል::
29በሌሊት የተቀደሰ በዓል ስታከብሩ
እንደምትዘምሩ፣
ትዘምራላችሁ፤
ወደ *እግዚአብሔር* ተራራ፣
ወደ እስራኤል ዐለት፣
ሰዎች ዋሽንት እየነፉ በደስታ እንደሚወጡ፣
የእናንተም ልብ እንዲሁ ሐሤት ያደርጋል::
30*እግዚአብሔር* በሚነድ ቍጣና በሚባላ
እሳት፣
በወጀብና በነጐድጓድ፣ በበረዶም
ድንጋይ፣
ግርማ የተሞላበትን ድምፁን ሰዎች እንዲ
ሰሙ አድርጎ ያሰማል፤
ክንዱም ስትወርድ ያሳያቸዋል::
31*የእግዚአብሔር* ድምፅ አሦርን ያስደነግጣል፤
በትሩም ይመታቸዋል::

32*እግዚአብሔር* የሚያወርድባቸው የቅጣት
በትር ሁሉ፣
በከበሮና በበገና ድምፅ የታጀበ ነው፤
በጦርነትም ክንዱን አሳይቶ መታቸው::
33ከቀድሞ ጀምሮ ቶፌት የተባለ የማቃጠያ
ስፍራ ተዘጋጅቶአል፤
ለንጉሡም ተበጅቶአል፤
ማንደጃ ጕድጓዱም ሰፊና ጥልቅ ነው፤
በውስጡም ብዙ እሳትና ማገዶ አለ፤
*የእግዚአብሔርም* እስትንፋስ
እንደ ፈሳሽ ድኝ ያቀጣጥለዋል::

## በግብጽ ለሚደገፉ ወዮውላቸው

31 ወደ እስራኤል ቅዱስ ለማይመለከቱ፣
*ከእግዚአብሔርም* ርዳታን ለማ
ይሹ፣
ነገር ግን፤ ለርዳታ ብለው ወደ ግብፅ
ለሚወርዱ፣
በፈረሶች ለሚታመኑ፣
በሠረገሎቻቸው ብዛት፣
በፈረሶቻቸውም ታላቅ ብርታት
ለሚመኩ
ወዮላቸው!
2እርሱም ግን ጠቢብ ነው፤ ጥፋትን ያመጣል፤
ቃሉን አያጥፍም::
በክፉ አድራጊዎች ቤት ላይ፣
በደለኞችንም በሚረዱ ላይ ይነሣል::
3ግብፃውያን ሰዎች እንጂ አምላክ
አይደሉም፤
ፈረሶቻቸውም ሥጋ እንጂ መንፈስ
አይደሉም፤

*እግዚአብሔር* እጁን ሲዘረጋ፣
ርዳታ ሰጪው ይሰናከላል፤
ተረጂውም ይወድቃል፤
ሁለቱም በአንድ ላይ ይጠፋሉ::

4*እግዚአብሔር* እንዲህ ብሎኛል፤

“አንበሳ ወይም የአንበሳ ደቦል
የሰበረውን ይዞ ሲያገሣ፣
ብዙ እረኞች
ተጠራርተው ሲመጡበት፣
ጩኸታቸው እንደማያስፈራው፣
በድምፃቸውም እንደማይታወክ፣
የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*፣
በጽዮን ተራራና በከፍታዎቿ ላይ ለውጊያ
እንዲሁ ይወርዳል::
5በዐናት ላይ እንደሚያንዣብቡ ወፎች፣
የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* ኢየሩሳሌምን
እንዲሁ ይጋርዳታል፤
ይከልላታል፤ ይታደጋታል፤
በላይዋ ያልፋል፤ ያድናታልም::”

**30፥21** ቍ11፤ ኢዮ33፥11፤ኢሳ29፥24
**30፥22** ዘፀ32፥4፤ ዘሌ15፥19-23፤ ኢዮ22፥24፤ ኢሳ17፥8፤31፥7፤ ሕዝ7፥19-20
**30፥23** ዘዳ28፥12፤ ኢዮ36፥31፤ መዝ65፥13፤ኢሳ25፥6፤ 28፥5፤55፥2፤62፥8፤ 65፥21-22፤ኤር31፥14
**30፥24** ኢዮ6፥5፤ ኢሳ32፥14፥20፤ ማቴ3፥12፤ሉቃ3፥17
**30፥25** ዘፀ17፥6፤ ኢሳ2፥15፤13፥5፤32፥2፤ 34፥6፤41፥18፤65፥12፤ ኤር25፥32፤50፥27፤ ኢል3፥18፤ዘካ14፥8
**30፥26** ዘዳ32፥39፤ 2ዜና7፥14፤ መዝ107፥20፤ ኢሳ1፥5፤24፥23፤ 60፥19-20፤ኤር3፥22፤ 17፥14፤ሆሴ14፥4፤ ዘካ14፥7፤ራእ21፥23፤ 22፥5
**30፥27** ቍ30፤ 1ነገ18፥24፤ኢዮ41፥21፤ መዝ20፥1፤ኢሳ10፥5፤ 13፥5፤26፥20፤59፥19፤ 64፥2፤66፥14፤ ሕዝ22፥31
**30፥28** 2ነገ19፥28፤ መዝ50፥3፤ኢሳ8፥8፤ 11፥4፤28፥15፤ አሞ9፥9
**30፥29** ዘፍ49፥24፤ 1ሳሙ10፥5፤ መዝ42፥4፤ኢሳ12፥1፤ 25፥6፤ማቴ26፥30
**30፥30** ቍ27፤ ዘፀ9፥18፤20፥18፤ መዝ29፥3፤68፥33፤ ኢሳ4፥4፤9፥12፤10፥25፤ 40፥10፤47፥14፤ 51፥9፤52፥10፤53፥1፤ 59፥16፤62፥8፤63፥12
**30፥31** ኢሳ10፥5፡ 12፤ 11፥4
**30፥32** ዘፀ15፥20፤ ኢሳ10፥26፤11፥15፤ ሕዝ32፥10
**30፥33** ዘፍ19፥24፤ ዘፀ15፥10፤ 2ሳሙ22፥16፤ 2ነገ23፥10፤ኢሳ1፥31፤ ራእ9፥17
**31፥1** ዘዳ17፥16፤ 20፥1፤ኢዮ6፥10፤ ምሳ21፥31፤ኢሳ1፥4፤ 2፥7፤9፥13፤28፥1፤ 30፥2፥5፥12፥16፤ ኤር37፥5፤46፥9፤ ሕዝ29፥16
**31፥2** ዘኍ23፥19፤ መዝ92፥5፤ምሳ19፥21፤ኢሳ1፥4፤29፥15፤32፥6፤ 45፥7፤47፥11፤ አሞ3፥6፤ሮሜ16፥27
**31፥3** ነህ1፥10፤ ኢዮ30፥21፤መዝ9፥20፤ ኢሳ9፥17፥21፤10፥3፤ 20፥5፥6፤30፥5-7፥16፤ 36፥9፤ኤር17፥5፤ 51፥25፤ሕዝ20፥34፤ 28፥9፤2ተሰ2፥4
**31፥4** ዘኍ24፥9፤ 1ሳሙ17፥34፤ መዝ74፥23፤ኢሳ42፥13፤ ኤር3፥15፤23፥4፤ ሕዝ34፥23፤ ሆሴ11፥10፤አሞ3፥8፤ናሆ3፥18
**31፥5** ዘፍ1፥2፤ ዘፀ12፥23፤መዝ34፥7፤ 91፥4፤ኢሳ5፥2፤37፥35፤ 38፥6፤ዘካ9፥15፤ ማቴ23፥37

6እናንተ እስራኤላውያን ሆይ፤ እጅግ
ወዳመፃችሁበት ወደ እርሱ ተመለሱ። 7በዚ
ያን ቀን በኀጢአት የተሞላ እጃችሁ የሠራ
ቸውን የወርቅና የብር ጣዖቶች ሁላችሁም
ትጥላላችሁና።

8"አሦር የሰው ባልሆነ ሰይፍ ይወድቃል፤
*የሥጋ* ለባሽ ያልሆነም ሰይፍ ይበላዋል።
ከሰይፍ ፊት ይሸሻል፤
ጕልማሶቹም የግዳጅ ሥራ ይሠራሉ።
9ጠንካራ ምሽጉ በሽብር ምክንያት ይወድቃል፤
*መሪዎቹም* የጦር ዐርማ ሲያዩ በድንጋጤ
ይዋጣሉ"
ይላል እሳቱ በጽዮን፣
ማንደጃውም በኢየሩሳሌም የሆነ *እግዚ
አብሔር*።

## የጽድቅ መንግሥት

**32** እነሆ፤ ንጉሥ በጽድቅ ይነግሣል፤
ገዦችም በፍትሕ ይገዛሉ።
2እያንዳንዱ ሰው ከነፋስ መከለያ፣
ከወጀብም መጠጊያ ይሆናል።
በበረሓም እንደ ውሃ ምንጭ፣
በተጠማም ምድር እንደ ትልቅ ቋጥኝ ጥላ
ይሆናል።

3የሚያዩ ሰዎች ዐይን ከእንግዲህ አይጨፈንም፤
የሚሰሙም ጆሮዎች ነቅተው ያዳምጣሉ።
4የችኵል አእምሮ ያውቃል፤ ያስተውላልም፤
የተብታባም ምላስ የተፈታ ይሆናል፤
አጥርቶም ይናገራል።
5ከእንግዲህ ሰነፍ ጨዋ አይባልም፤
ጋጠወጥም አይከበርም።
6ሰነፍ ስንፍናን ይናገራል፤
አእምሮው ክፋትን ያውጠነጥናል፤
ፈሪሀ *እግዚአብሔር* የሌለበትን አድራጐት
ይፈጽማል፤
በ*እግዚአብሔርም* ላይ የስሕተት ቃል
ይናገራል፤
ለተራበ ምግብ ይከለክላል፤
ለተጠማ ውሃ አይሰጥም።
7የጋጠወጥ ዘዴ ክፉ ነው፤
የችግረኛም አቤቱታ ትክክል ቢሆን፣
ድኻን በሐሰት ለማጥፋት፣
ክፋት ያውጠነጥናል።
8ጨዋ ግን ሐሳቡም ጨዋ ነው፤
በጨዋነት ምግባርም ጸንቶ ይገኛል።

## የኢየሩሳሌም ሴቶች

9እናንት ትዕቢት የወጠራችሁ ሴቶች፣
ተነሡ፤ ድምፄን ስሙ፤
እናንት ተደላድላችሁ የምትኖሩ፣ ሴቶች
ልጆች ሆይ፤
የምነግራችሁን አድምጡ።
10ዓመቱ ገና እንዳለፈ፣
ተደላድላችሁ የነበራችሁ ትንቀጠ
ቀጣላችሁ፤
የወይን ተክል ፍሬ አይሰጥም፤
የፍራፍሬም ወቅት አይመጣም።
11እናንት ትዕቢት የወጠራችሁ ሴቶች
ተንቀጥቀጡ፤
እናንት ተደላድላችሁ የምትኖሩ ሴቶች
ልጆች፤ በፍርሀት ተርበትበቱ፤
ልብሳችሁን አውልቁ፣
ወገባችሁን በማቅ ታጠቁ።
12ስለ ለሙ መሬት ደረታችሁን ምቱ፤
ስለ ፍሬያማው የወይን ተክል ዕዘኑ፤
13ስለ ሕዝቤ ምድር፣
እሾኽና አሜከላ ስለ በቀለበት ምድር፣
ስለ ፈንጠዝያ ቤቶች ሁሉ፣
ስለዚህችም መፈንጫ ከተማ አልቅሱ።
14ዐምባ ምሽጉ ወና ይሆናል፤
ውካታ የበዛበት ከተማ ጭር ይላል፤
ምሽጉና ማማው ለዘላለሙ ዋሻ፣
የዱር አህያ መፈንጫ፣ የመንጋም መሰማሪያ
ይሆናል፤
15ይህም የሚሆነው መንፈስ ከላይ እስኪ
ፈስልን፣
ምድረ በዳው ለም መሬት፣
ለሙ መሬትም ጫካ እስኪመስል ድረስ
ነው።
16በምድረ በዳ ፍትሕ ይሰፍናል፤
በለሙም መሬት ጽድቅ ይኖራል፤
17የጽድቅ ፍሬ ሰላም፣
የጽድቅ ውጤትም ጸጥታና ለዘላለም
መታመን ይሆናል።
18ሕዝቤ ሰላማዊ በሆነ መኖሪያ፣
በሚያስተማምን ቤት፣
ጸጥ ባለም ስፍራ ዐርፎ ይኖራል።
19ደኑ በበረዶ ቢመታ፣
ከተማውም ፈጽሞ ቢወድም፣
20በየወንዙ ዳር ዘር የምትዘሩ፣
በሬዎቻችሁንና አህዮቻችሁን በነጻነት
የምታሰማሩ፣
ምንኛ የተባረካችሁ ናችሁ።

## የጭንቅ ጊዜና ርዳታ

**33** አንተ ሳትጠፋ የምታጠፋ፣
አንት አጥፊ፣ ወዮልህ!
አንተ ሳትካድ የምትክድ፣
አንት ከዳተኛ፣ ወዮልህ!
ማጥፋትን በተውህ ጊዜ፣
ትጠፋለህ፤

31፥6 ኢዮ22፥23፤ ኢሳ1፥5፡27
31፥7 መዝ135፥15፤ ኢሳ29፥18፤30፥22
31፥8 ዘፍ49፥15፤ ዘፀ12፥12፤ዘዳ20፥11፤ ኢሳ10፥12፤14፥25፤ 27፥1፤33፥1፤37፥7፤ ኤር25፥12፤ዕን2፥8
31፥9 ዘዳ32፥31፡ 37፤መዝ21፥9፤ ኢሳ10፥17፤18፥3፤ ኤር4፥6፤51፥9፤ ናሆ3፥7፤ሚል4፥1
32፥1 መዝ72፥1-4፤ 149፥2፤ኢሳ6፥5፤ 9፥7፤ 28፥6፤55፥4፤ ሕዝ37፥24
32፥2 1ነገ18፥4፤ መዝ23፥2፤55፥8፤ 107፥35፤ኢሳ30፥25፤ 44፥3፤49፥10፤ ኤር31፥9
32፥3 ዘዳ29፥4፤ ኢሳ29፥18፤35፥5፤ 42፥7፡16
32፥4 ኢሳ6፥10፤ 29፥24፤35፥6
32፥5 1ሳሙ25፥25
32፥6 ምሳ19፥3፤ 24፥2፤ኢሳ3፥12፡15፤ 9፥16፡17፤26፥10
32፥7 መዝ72፥4፤ ኢሳ29፥19፡20፡21፤ 61፥1፤ኤር5፥26-28፤ ዳን12፥10፤ሚክ7፥3
32፥8 1ዜና29፥9፤ ምሳ11፥25፤ ኢሳ14፥24
32፥9 ቍ11፤ ኢሳ4፥1፤28፥23፤ 47፥8፤ዳን4፥4፤ አሞ6፥1፤ሶፎ2፥15
32፥10 ኢሳ5፥5-6፤ 24፥7፤37፥30
32፥11 ቍ9፤ ኢሳ3፥24፤ኢሳ33፥14፤ 47፥2፤ሚክ1፥8፤ ናሆ3፥5
32፥12 ኢሳ16፥9፤ ናሆ2፥7
32፥13 ኢሳ5፥6፤ 23፥7፤24፥11፤ ሆሴ10፥8
32፥14 መዝ104፥11፤ ኢሳ2፥15፤5፥17፤ 6፥11፤13፥22፤27፥10፤ 34፥13
32፥15 መዝ107፥35፤ ኢሳ11፥2፤29፥17፤ 35፥1-2፤ሕዝ37፥9
32፥16 መዝ48፥1፤ ኢሳ1፥26፤9፥7፤28፥6፤ 35፥1፡6፤42፥11
32፥17 መዝ85፥10፤ 119፥165፤ኢሳ9፥7፤ 30፥15፤ሮሜ14፥17፤ ዕብ12፥11፤ያዕ3፥18
32፥18 ኢሱ1፥13፤ ኢዮ11፥18፤ኢሳ2፥4፤ 26፥1፤33፥20፤37፥33፤ ሆሴ2፥18-23፤ አሞ9፥14
32፥19 ኢዮ40፥11፤ኢሳ10፥19፤ 19፥18፤ 24፥10፤27፥10፤ 28፥17፤ዘካ11፥2
32፥20 ዘዳ28፥12፤ ኢዮ39፥8፤መክ11፥1፤ኢሳ30፥24
33፥1 2ነገ19፥21፤ ኢሳ21፥2፤28፥1፤31፥8፤ኤር30፥16፤ሕዝ39፥10፤ማቴ7፥2

ክሕደትህንም በተውህ ጊዜ
ትከዳለህ።

2 እግዚአብሔር ሆይ፤ ማረን፤
አንተን ተስፋ አድርገናል።
በየማለዳው ብርታት፣
በጭንቅ ጊዜም ድነት ሁነን።
3 ሕዝቦች በድምፅህ ነጐድጓድ ይሸሻሉ፣
መንግሥታት ስትነሣ ይበተናሉ።
4 ሕዝቦች ሆይ፤ አንበጣ እንደሚሰበስብ
ብዝበዛችሁም ይሰበሰባል፤
ሰዎችም እንደ ኩብኩባ ይጨፍሩበታል።

5 እግዚአብሔር በአርያም ተቀምጦአልና ከፍ
ከፍ አለ፤
ጽዮንን በጽድቅና በፍትሕ ይሞላታል።
6 እርሱ ለዘመንህ የሚያስተማምን መሠረት፣
የድነት፣ የዕውቀትና የጥበብ መዝገብ
ይሆናል፤
እግዚአብሔርንም መፍራት የዚህ ሀብት
ቍልፍ ነው[ከ]።

7 እነሆ፤ ጐበዞቻቸው በየመንገዱ
ይጮኻሉ፤
የሰላም መልእክተኞችም አምርረው
ያለቅሳሉ።
8 አውራ ጐዳናዎች ባዶ ናቸው፤
በመንገድ ላይ ሰው የለም፤
ስምምነቱ ፈርሶአል፤
መካሪዎቹ[ኸ] ተንቀዋል፤
የሚከበርም የለም።
9 ምድሪቱ አለቀሰች[ወ]፤ መነመነች፤
ሊባኖስ ዐፈረች፤ ጠወለገች፤
ሳሮን እንደ ዐረባ ምድረ በዳ ሆነች፤
ባሳንና ቀርሜሎስ ቅጠላቸውን አረገፉ።

10 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ "አሁን
እነሣለሁ፤
አሁን ከፍ ከፍ እላለሁ፤
አሁን እከብራለሁ።
11 ገለባን ፀነሳችሁ፤
እብቅንም ወለዳችሁ፤
እስትንፋሳችሁም የሚበላችሁ እሳት
ነው።
12 ሕዝቦች ኖራ እንደሚወጣው ድንጋይ
ይቃጠላሉ፤
እንደ እሾኽ ቍጥቋጦ በእሳት ይጋያሉ።"

13 እናንት በሩቅ ያላችሁ ያደረግሁትን ስሙ፤
እናንት በቅርብ ያላችሁ ኀይሌን ዕወቁ!
14 በጽዮን ያሉ ኀጢአተኞች ደነገጡ፤
አምላክ የሌላቸውም ፍርሀት ይዞአቸው፣
"ከእኛ መካከል ከሚባላ እሳት ጋር ማን
መኖር ይችላል፣
ከዘላለም እሳትስ ጋር ማን መኖር ይች
ላል?" አሉ።
15 በጽድቅ የሚራመድ፣
ቅን ነገር የሚናገር፣
በሸንገላ የሚገኝ ትርፍ የሚንቅ፣
መማለጃን ላለመቀበል እጁን የሚሰ
በስብ፣
የግድያን ሤራ ላለመስማት ጆሮውን
የሚደፍን፣
ክፋትን ላለማየት ዐይኑን የሚጨፍን፣
16 ይህ ሰው በከፍታ ላይ ይኖራል፤
የተራራም ምሽግ መጠጊያው ይሆናል፤
እንጀራ ይሰጠዋል፣
ውሃውም አይቋረጥበትም።

17 ዐይኖችህ ንጉሡን በውበቱ ያዩታል፤
በሩቅ የተዘረጋችውንም ምድር ይመለ
ከታሉ።
18 የቀደመው መከራ ትዝ እያለህ፣
"ያ ዋና አለቃ የት አለ?
ግብር ተቀባዩስ ወዴት ሄደ?
የመጠበቂያ ማማ ኀላፊውስ የት አለ?"
ትላለህ።
19 እነዚያ ንግግራቸው የማይገባ፣
የሚሉትም የማይታወቅ፣
ሊረዱት የማይቻል ቋንቋ የሚናገሩትን
ጋጠወጥ ሕዝብ ከእንግዲህ አታያ
ቸውም።

20 በዓላታችንን የምናከብርባትን ከተማ
ጽዮንን
ተመልከት፤
ሰላማዊ መኖሪያ፣ የማትነቃነቅ ድንኳን
የሆነችውን፣
ካስማዋ የማይነቀል፣
ከገመዷ አንዱ እንኳ የማይበጠሰውን፣
ኢየሩሳሌምን ዐይኖችህ ያያሉ።
21 እግዚአብሔር በዚያ ኀይላችን ይሆናል፤
ባለ መቅዘፊያ ጀልባዎች እንደማያል
ፉባቸው፣
ታላላቅ መርከቦችም እንደማይሻገሯቸው፣
ሰፋፊ ወንዞችና ጅረቶች ይሆንልናል።
22 እግዚአብሔር ዳኛችን ነው፤
እግዚአብሔር ሕግ ሰጪያችን ነው፤
እግዚአብሔር ንጉሣችን ነው፤
የሚያድነንም እርሱ ነውና።
23 መወጠሪያ ገመድህ ላልቶአል፤
ምሰሶው ጠብቆ አልተተከለም፤
ሸራው አልተወጠረም፤
በዚያ ጊዜ ታላቅ ምርኮ ይከፋፈላል፤
አንካሳ እንኳ ሳይቀር ምርኮ ይወስዳል።
24 በጽዮን ተቀምጦ፣ "ታምሜአለሁ" የሚል

65፥21፤66፥14፤
33፥2 ዘፍ43፥29፤ ዕዝ9፥8፤መዝ13፥5፤ ኢሳ5፥30፤12፥2፤ 40፥10፤51፥9፤59፥16፤ 63፥5
33፥3 ቍ10፤ ዘኍ10፥35፤ መዝ12፥5፤46፥6፤ 68፥1፡33፤ኢሳ13፥14፤ 59፥16-18
33፥4 ዘኍ14፥3፤ 2ነገ7፥16፤ኢሳ17፥5፤ ኢል1፥4፤3፥13
33፥5 ኢዮ16፥19፤ ኢሳ1፥26፤5፥16፤ 9፥7፤28፥6
33፥6 ዘፍ39፥3፤ ኢዮ22፥25፤ምሳ1፥7፤ ኢሳ11፥2-3፤12፥2፤ 26፥1፤ 51፥6፤ 60፥18፤ማቴ6፥33
33፥7 2ነገ18፥37፤ ኢሳ10፥34
33፥8 መሳ5፥6፤ 2ነገ18፥14፤ ኢሳ30፥21፤35፥8፤ 60፥15፤ዘካ7፥14
33፥9 1ነገ18፥19፤ 2ነገ19፥23፤ 1ዜና27፥29፤ኢሳ2፥13፤ 3፥26፤15፥6፤35፥2፤ 37፥14፤ኤር22፥6፤ ሚክ7፥14፤ናሆ1፥4
33፥10 ቍ3፤ ኢሳ2፥21፤5፥16
33፥11 መዝ7፥14፤ ኢሳ1፥31፤26፥18፤ 59፥4፤ያዕ1፥15
33፥12 ኢሳ5፥6፤ 10፥17፤27፥11፤ አሞ2፥1
33፥13 መዝ48፥10፤ 49፥1፤ኢሳ34፥1፤ 48፥16፤49፥1
33፥14 ኢሳ1፥28፡ 31፤30፥30፤32፥11፤ ዘካ13፥9፤ዕብ12፥29
33፥15 መዝ15፥2፤ 24፥4፤119፥37፤ ምሳ15፥27፤ኢሳ58፥8፤ ሕዝ22፥13፤33፥31
33፥16 ዘዳ32፥13፤ መዝ18፥1-2፤46፥1፤ ኢሳ25፥4፤26፥1፤ 48፥21፤49፥10፤ 65፥13
33፥17 ኢሳ4፥2፤ 6፥5፤26፥15
33፥18 ኢሳ2፥15፤ 17፥14
33፥19 ዘፍ11፥7፤ መዝ5፥5፤ኢሳ28፥11
33፥20 ቍ6፤ ዘፍ26፥22፤መዝ46፥5፤ 125፥1፤ኢሳ32፥18
33፥21 ዘፀ17፥6፤ መዝ1፥3፤ኢሳ10፥34፤ 23፥1፤32፥2፤41፥18፤48፥18፤49፥10፤ 66፥12፤ናሆ3፥8
33፥22 መዝ89፥18፤ ኢሳ2፥3፤11፥4፤25፥9፤ ያዕ4፥12
33፥23 2ነገ7፥8፥16
33፥24 ዘኍ23፥21፤ 2ዜና6፥21፤ ኢሳ30፥26፤43፥1፤ 48፥20፤ ኤር31፥34፤33፥8፤ 1ዮሐ1፥7-9

[ከ]6 ወይም *እግዚአብሔርን መፍራት ከእግዚአብሔር የሆነ ሀብት ነው*
[ኸ]8 የሙት ባሕር ጥቅሎች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ የማሶሬቱ ቅጅ ግን፣ *ከተሞች* ይላል።
[ወ]9 ወይም *ደረቀች (ጠወለገች)*

አይኖርም፤
በዚያ የሚኖሩ ሰዎች ኀጢአትም ይቅር
ይባላል።

## ፍርድ በአሕዛብ ላይ

**34** እናንተ አሕዛብ ሆይ፤ ኑ አድምጡም፤
እናንተ ሰዎች ሆይ፤ አስተውሉ።
ምድርና በውስጧ ያለ ሁሉ፣
ዓለምና ከእርሷ የሚበቅል ሁሉ ይስማ።
2*እግዚአብሔር* አሕዛብን ሁሉ ተቈጥቶአል፤
ቍጣውም በሰራዊታቸው ሁሉ ላይ ነው፤
ፈጽሞ ያጠፋቸዋል[ዐ]፤
ለዕርድም አሳልፎ ይሰጣቸዋል።
3ከእነርሱም የተገደሉት ወደ ውጭ ይጣላሉ፤
ሬሳቸው ይከረፋል፤
ተራሮችም ደም በደም ይሆናሉ።
4የሰማይ ከዋክብት ሁሉ ይሟሸሻሉ፤
ሰማይ እንደ ብራና ይጠቀለላል፤
የከዋክብት ሰራዊት ሁሉ፣
ጠውልጎ እንደ ረገፈ የወይን ቅጠል፣
ደርቆም እንደ ወደቀ የበለስ ቅጠል
ይሆናሉ።
5ሰይፌ በሰማያት እስኪበቃት ጠጥታለች፤
እነሆ፤ ወደ ኤዶም፣
ፈጽሞ ወዳጠፋሁት ሕዝብ ለፍርድ
ወርዳለች።
6*የእግዚአብሔር* ሰይፍ በደም ተነክራለች፤
ሥብ ጠግባለች፤
በበግ ጠቦትና በፍየል ደም፣
በአውራም በግ ኵላሊት ሥብ
ተሸፍናለች።
*እግዚአብሔር* በባሶራ ከተማ መሥዋዕት፣
በኤዶምም ታላቅ ዕርድ አዘጋጅቶአልና።
7ጐሽ አብሮአቸው፣
ኮርማም ከወይፈን ጋር ይወድቃል፤
ምድራቸው በደም ትርሳለች፤
ዐፈራቸውም ሥብ በሥብ ይሆናል።

8*እግዚአብሔር* የበቀል ቀን፣
ስለ ጽዮንም የሚሟገትበት ዓመት
አለውና።
9የኤዶም ምንጮች ሬንጅ፣
ዐፈሯ የሚቃጠል ድኝ፣
ምድሯም የሚንበለበል ዝፍት ይሆናል።
10እሳቷ ሌሊትና ቀን አይጠፋም፤
ጢሷም ለዘላለም ይትጐለጐላል፤
ከትውልድ እስከ ትውልድ ባድማ ትሆናለች፤
ማንም በዚያ ዳግም አያልፍም።
11ጭልፊትና[ʺ] ጃርት ይወርሷታል፤
ጕጕትና ቍራም ጎጆ ይሠሩባታል።
እግዚአብሔር በኤዶም ላይ፣
የመፈራረሷን ገመድ፣
የመጥፊያዋንም ቱንቢ ይዘረጋል።
12መሳፍንቷም መንግሥት ተብለው ለመጠራት
የሚያስችላቸው ነገር አይኖራቸውም፤
አለቆቿም በሙሉ ጥርግ ብለው ይጠ
ፋሉ።
13በቅጥር የተመሸጉ ከተሞቿን እሾኽ፣
ምሽጎቿንም ሳማና አሜከላ ይወርሷቸዋል፤
የቀበሮዎች ጕድጓድ፣
የጕጕቶችም መኖሪያ ትሆናለች።
14የምድረ በዳ አራዊት ከጅቦች ጋር
አብረው
ይሆናሉ፤
በበረሓ ፍየል የሚመሰሉ አጋንንትም እርስ
በእርስ ይጠራራሉ፤
የሌሊት ፍጥረታት ማረፊያቸውን በዚያ
ያደርጋሉ፤
ለራሳቸውም የማረፊያ ቦታ ያገኛሉ።
15ጕጕት በዚያ ጎጆ ሠርታ ዕንቍላል
ትጥላለች፤
ትቀፈቅፋለች፤ ጫጩቶቿን በክንፎቿ
ትታቀፋቸዋለች፤
ጭላቶችም ጥንድ ጥንድ ሆነው፣
ለርቢ በዚያ ይሰበሰባሉ።

16*በእግዚአብሔር* መጽሐፍ እንዲህ
የሚለውን
ተመልከቱ፤ አንብቡም፤
ከእነዚህ አንዱ አይጐድልም፤
እያንዳንዷም አጣማጇን አታጣም፤
ይህ ትእዛዝ ከአፉ ወጥቶአል፤
መንፈሱ በአንድ ላይ ይሰበስባቸዋልና።
17ድርሻ ድርሻቸውን ይመድብላቸዋል፤
እጁም ለክታ ታካፍላቸዋለች።
ለዘላለም የእነርሱ ትሆናለች፤
ከትውልድ እስከ ትውልድም ይኖሩባታል።

## የተቤዠ ሕዝብ ደስታ

**35** ምድረ በዳውና ደረቁ ምድር ደስ
ይላቸዋል፤
በረሓው ሐሤት ያደርጋል፤ ይፈካል፤
እንደ አደይም ያብባል።
2በደስታና በዝማሬ ሐሤት ያደርጋል፤
የሊባኖስ ክብር ይሰጠዋል፤
የቀርሜሎስንና የሳሮንን ግርማ ይለብሳል።
የአምላካችንን ታላቅ ግርማ፣
*የእግዚአብሔርን* ክብር ያያሉ።

3የደከሙትን እጆች አበርቱ፤
የላሉትንም ጕልበቶች አጽኑ፤
4የሚፈራ ልብ ላላቸው እንዲህ በሉ፤

**34፥1** ዘዳ4፥26፤ መዝ24፥1፤49፥1፤ ኢሳ33፥13፤41፥1፤ 43፥9 **34፥2** ኢሳ10፥25፤ 13፥5፤30፥25፤ዘካ5፥3 **34፥3** ቍ7፤ 2ሳሙ1፥22፤ መዝ110፥6፤ ኢሳ5፥25፤10፥4፤ 63፥6፤ሕዝ5፥17፤ 14፥19፤32፥6፤35፥6፤3 8፥22፤39፥11፤ ኢል2፥20፤አሞ4፥10 **34፥4** ኢዮ8፥12፤ 9፥7፤ኢሳ13፥13፤15፥6፤ 38፥12፤ማቴ21፥19፤ 24፥29፤ማር13፥25፤ ዕብ1፥12፤2ጴጥ3፥10 **34፥5** ዘዳ13፥15፤ 32፥41-42፤ኢሱ6፥17፤ 2ሳሙ8፥13-14፤ 2ዜና28፥17፤ ኢሳ24፥6፤ኤር47፥6፤ ሕዝ21፥5፤አሞ1፥11-12፤ 3፥14-15፤6፥11፤ ዘካ13፥7፤ሚል1፥4 **34፥6** ዘፍ36፥33፤ ዘሌ3፥9፤ዘዳ32፥41፤ ኢሳ27፥1፤30፥25፤ ኤር25፥34፤ራእ19፥17 **34፥7** ዘኍ23፥22፤ 2ሳሙ1፥22፤መዝ68፥30 **34፥8** ኢሳ1፥24፤ 2፥12፤35፥4፤47፥3፤ 59፥18፤63፥4፤ ሕዝ25፥12-17፤ ኢል3፥4፤አሞ1፥6-8፡ 9-10 **34፥9** ዘፍ19፥24 **34፥10** ቍ17፤ ኢሳ1፥31፤13፥20፤ 24፥1፤ኤር49፥18፤ ሕዝ29፥12፤35፥3፤ ሚል1፥3፤ ራእ14፥10-11፤19፥3 **34፥11** ዘፍ1፥2፤ 8፥7፤ዘሌ11፥16-18፤ ዘዳ14፥15-17፤ 2ነገ21፥13፤ ኢሳ21፥11፤ ሕዝ35፥15፤ኢል3፥19፤ አሞ7፥8፤አብ1፥1፤ ሚል1፥4፤ ራእ18፥2 **34፥12** ኢዮ12፥21፤ መዝ107፥40፤ ኢሳ29፥20፤ 40፥23፤41፥11-12፤ ኤር21፥7፤27፥20፤ 39፥6፤ሕዝ24፥5 **34፥13** ዘሌ11፥16-18፤መዝ44፥19፤ ኢሳ5፥6፤7፥19፤13፥22፤ ኤር9፥11፤10፥22 **34፥14** መዝ74፥14፤ ኢሳ13፥22፤ራእ18፥2 **34፥15** ዘዳ14፥13፤ መዝ17፥8 **34፥16** ኢሳ1፥20፤ 30፥8፤40፥26፤48፥13፤ 58፥14 **34፥17** ቍ10፤ **35፥5** መዝ146፥8፤ ኢሳ17፥14፤ኤር13፥25 **35፥1** ማሕ2፥1፤ኢሳ27፥6፡10፤32፥15፡ 16፤41፥18-19፤51፥3 **35፥2** ዘፍ21፥6፤ ዘፀ16፥7፤1ዜና27፥29፤ ዕዝ3፥7፤መዝ105፥43፤ማሕ7፥5፤ኢሳ4፥5፤ 12፥6፤25፥9፤33፥9፤ 44፥23፤ 51፥11፤ 52፥9፤55፥12፤59፥19፤65፥10 **35፥3** ኢዮ4፥4፤ ዕብ12፥12 **35፥4** ዘዳ20፥3፤ኢሱ1፥9፤2ዜና32፥6፤ኢሳ1፥24፤ 7፥4፤21፥4፤25፥9፤34፥8፤40፥2፡9፡10-11፤51፥5፤62፥11፤ ዳን10፥19፤ዘካ1፥13፤ ራእ22፥12

ዐ2 በዚህና በቍጥር 5 ላይ የዕብራይስጡ ቃል አንድን ሰው ወይም ነገር ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠትን የሚያመለክት ነው።
ʺ11 የእነዚህ አዕዋፍ ትክክለኛ ማንነታቸው በትክክል አይታወቅም።

“በርቱ፤ አትፍሩ፤
አምላካችሁ ይመጣል፤
ሊበቀል ይመጣል፤
እርሱም ብድራቱን ይዞ፣
ሊያድናችሁ ይመጣል።”

5በዚያን ጊዜም የዕውር ዐይኖች ይገለጣሉ፤
የደንቈሮም ጆሮዎች ይከፈታሉ።
6አንካሳ እንደ ሚዳቋ ይዘላል፤
የድዳውም አንደበት በደስታ ይዘምራል፤
ውሃ ከበረሓ ይወጣል፤
ምንጮችም ከምድረ በዳ ይፈልቃሉ።
7ንዳዳማው ምድር ኵሬ ይሆናል፤
የተጠማው መሬት ውሃ ያመነጫል።
ቀበሮዎች በተኙባቸው ጕድጓዶች፣
ሣር፣ ሸምበቆና ደንገል ይበቅልበታል።

8በዚያ አውራ ጐዳና ይሆናል፤
“የተቀደሰ መንገድ” ተብሎ ይጠራል።
የረከሱ አይሄዱበትም፤
በመንገዱ ላይ ላሉት ብቻ ይሆናል።
ገራገሮችም ከመንገዱ አይስቱም።
9አንበሳ አይኖርበትም፤
ነጣቂ አውሬም አይወጣበትም፤
እነዚህማ በዚያ ስፍራ አይገኙም፤
የዳኑት ብቻ በዚያ ይሄዳሉ፤
10እግዚአብሔር የዋጃቸው ይመለሳሉ።
እየዘመሩ ወደ ጽዮን ይገባሉ፤
ዘላለማዊ ደስታን እንደ አክሊል ይቀዳጃታል፤
ፍሥሓና ሐሤት ያገኛሉ፤
ሐዘንና ትካዜ ከዚያ ይሸሻሉ።

## የሰናክሬም ዛቻ በኢየሩሳሌም ላይ

36 ንጉሥ ሕዝቅያስ በነገሠ በዐሥራ
አራተኛው ዓመት፣ የአሦር ንጉሥ
ሰናክሬም የተመሸጉትን የይሁዳ ከተሞች
ሁሉ አጥቅቶ ያዛቸው። 2የአሦርም ንጉሥ
የጦር አዛዡን ከብዙ ሰራዊት ጋር ከለኪሶ፣
ንጉሡ ሕዝቅያስ ወዳለበት፣ ወደ ኢየሩ
ሳሌም ላከው። የጦር አዛዡም ወደ ልብስ
አጣቢው ዕርሻ በሚወስደው መንገድ፣ በላ
ይኛው ኵሬ ቦይ አጠገብ ደርሶ ቆመ፤
3የቤተ መንግሥቱ አስተዳዳሪ፣ የኬልቅያስ
ልጅ ኤልያቄም፣ ጸሓፊው ሳምናስ፣ ታሪክ
መዝጋቢውም የአሳፍ ልጅ ዮአስ ወደ
እርሱ ወጡ።

4የጦር አዛዡም እንዲህ አላቸው፤
“ለሕዝቅያስ እንዲህ ብላችሁ ንገሩት፤

“ ‘ታላቁ ንጉሥ የአሦር ንጉሥ እንዲህ ይላል፤
እስከዚህ የተማመንህበት ነገር ምንድን ነው?
5የጦር ስልትና ጠንካራ ሰራዊት አለኝ
ትላለህ፤ ነገር ግን ፍሬ ቢስ ቃል ብቻ
ትናገራለህ። ለመሆኑ፣ በእኔ ላይ ያመፅኸ
ው በማን ተማምነህ ነው? 6እነሆ፤ ሰው ሲ
መረ ኰዘው እጅ ወግቶ በሚያቈስለው፣
በተሰ ነጠቀ ሸምበቆ በግብፅ ተማምነሃል፤
የግብፅ ንጉሥ፣ ፈርዖንም ለሚታመኑበት
ሁሉ እን
ዲሁ ነው። 7ደግሞም፣ “በአምላካችን በእግዚ
አብሔር እንታመናለን” የምትለኝ ከሆነ፣
የእርሱንማ ማምለኪያ ኰረብቶችና መሠዊ
ያዎች ሕዝቅያስ አፍርሶበት ለይሁዳና ለኢ
የሩሳሌም፣ “እናንተ መስገድ ያለባችሁ እን
ዲህ በለው በአንዱ መሠዊያ ፊት ብቻ
ነው” ብሎ የለምን?

8“ ‘አሁን፣ ናና፣ ከጌታዬ ከአሦር ንጉሥ
ጋር ተደራደር፤ የሚቀመጡባቸው ሰዎች
ካሉህ፣ ሁለት ሺህ ፈረሶች እሰጥሃለሁ።
9እንግዲህ በግብፅ ሠረገሎችና ፈረሰኞች
የምትተማመን ከሆነ፣ ከጌታዬ መኰንንኖች
አንዱን ዝቅተኛ መኰንን እንዴት መመለስ
ይቻልሃል? 10ደግሞስ ይህን ምድር ለማጥቃትና
ለማጥፋት የመጣሁት ያለ እግዚአብሔር
ትእዛዝ ይመስልሃልን? እግዚአብሔር ራሱ
በዚህ አገር ላይ ዘምቼ እንዳጠፋው ነግሮ
ኛል።’ ”

11ኤልያቄምና ሳምናስ እንዲሁም ዮአስ
የጦር አዛዡን፣ “እባክህ በምናውቀው በሶ
ርያ ቋንቋ ለባሪያዎችህ ተናገረን፤ በቅጥሩ
ላይ ያለው ሕዝብ በሚያውቀው በዕብራይስጥ
ቋንቋ አትናገረን” አሉት።

12ነገር ግን የጦር አዛዡ መልሶ፣ “ጌታዬ
እነዚህን ነገሮች እንድናገር የላከኝ ለጌታህና
ለአንተ ብቻ ነበርን? እንደ እናንተ የራ
ሳቸውን ኩስ ለመብላትና ሽንታቸውንም
ለመጠጣት በቅጥሩ ላይ ለተቀመጡት
ሰዎችም አይደለምን?” አላቸው።

13የጦር አዛዡም ቆሞ በዕብራይስጥ ቋንቋ
በታላቅ ድምፅ እንዲህ አለ፤ “የታላቁን
ንጉሥ፣ የአሦርን ንጉሥ ቃል ስሙ። 14ንጉሡ
እንዲህ ይላል፤ ‘ሕዝቅያስ አያታልላችሁ፤
እርሱ ሊያድናችሁም አይችልም። 15“እግዚ
አብሔር በእርግጥ ያድነናል፤ ይህች ከተማ
ለአሦር አትሰጥም’ እያለ ሕዝቅያስ በእግዚ
አብሔር እንድትታመኑ አያድርጋችሁ።’

16“ሕዝቅያስን አትስሙ። የአሦር ንጉሥ
እንዲህ ይላችኋል፤ ‘ከእኔ ጋር ተስማሙ፤
ወደ እኔም ውጡ። ከዚያም እያንዳንዳችሁ
ከወይናችሁና ከበለሳችሁ ትበላላችሁ፤
ከጕድ ጓዳችሁም ውሃ ትጠጣላችሁ፤ 17ይኸ
ውም መጥቼ የእህልና የአዲስ ወይን ጠጅ
ምድር ወደ ሆነችው፣ የእንጀራና የወይን
ምድር ወደ ሆነችው፣ ምድራችሁን ወደ
ምትመስል አገር እስካፈልሳችሁ ድረስ

ኢሳ29፥18፤42፥18፤
50፥4፤ሐሥ26፥18፤
ዮሐ9፥6-7
35፥6 ዘፀ17፥6፤
2ሳሙ22፥34፤
መዝ20፥5፤ኢሳ32፥4፤
ማቴ9፥32-33፤
12፥22፤15፥30፤
ማር7፥35፤ሉቃ7፥22፤
11፥14፤ዮሐ5፥8-9፤
7፥38፤ሐሥ3፥8 35፥7
ኢዮ8፥11፤
40፥21፤መዝ68፥6፤
107፥35፤ኢሳ13፥22፤
41፥17፤44፥3፤49፥10፤
55፥1፤58፥11
35፥8 ኢሳ4፥3፤
11፥16፤33፥8፤52፥1፤
ኤር31፥21፤
ማቴ7፥13-14፤
1ጴጥ1፥15
35፥9 ዘፀ6፥6፤
ዘሌ25፥47-55፤
ኢሳ11፥6፤13፥22፤
30፥6፤34፥14፤51፥11፤
62፥12፤63፥4
35፥10 ኢዮ19፥25፤
መዝ4፥7፤51፥8፤
126፥5፤ኢሳ1፥27፤
25፥9፤30፥19፡29፤
51፥3፤ራእ7፥17፤
21፥4
36፥1 2ነገ18፥9፤
2ዜና32፥1፤
መዝ109፥11
36፥2 ኢሱ10፥3፤ ኢ
ሳ7፥3
36፥3 ቀኍ11፤
ዘፍ41፥40፤2ሳሙ8፥16፡
17፤2ነገ18፥18፤
ኢሳ22፥20፡20-21፤
37፥2
36፥5 2ነገ18፥7
36፥6 2ነገ17፥4፤ ኢ
ሳ8፥12፤30፥2፡5፤
42፥3፤58፥5፤
ሕዝ17፥17፤29፥6-7
36፥7 ዘዳ12፥2-5፤
2ነገ18፥4፤2ዜና31፥1፤
መዝ22፥8፤ማቴ27፥43
36፥8 መዝ20፥7፤ ኢ
ሳ30፥16
36፥9 መዝ20፥7፤ ኢ
ሳ30፥2-5፤31፥3፤
37፥24
36፥10 1ነገ13፥18፤
ኢሳ10፥5-7
36፥11 ቀኍ3፤ዕዝ4፥7
36፥12 ነገ6፥25፤
ሕዝ4፥12
36፥13 2ዜና32፥18፤
ኢሳ37፥4
36፥14 2ዜና32፥15
36፥15 መዝ3፥2፡7፤
ኢሳ37፥10
36፥16 1ነገ4፥25፤
ምሳ5፥15
36፥17 ዘፍ27፥28፤
ዘዳ28፥51፤2ነገ15፥29
36፥19 2ነገ15፥29፤

ነው::’
[18]“ሕዝቅያስ፣ ‘እግዚአብሔር ያድነናል’
በማለት አያታልላችሁ”፤ ለመሆኑ፣ እስካ
ሁን ምድሩን ከአሦር ንጉሥ እጅ ያዳነ
የየትኛው ሕዝብ አምላክ ነው:: [19]የሐማትና
የአርፋድ አማልክት የት አሉ? የሴፈርዋይም
አማልክትስ የት አሉ? እነዚህ ሰማርያን
ከእጄ አድነዋታልን? [20]ከእነዚህ አገሮች
አማልክት ሁሉ፣ ምድሩን ከእጄ ለማዳን የቻለ
የትኛው ነው? ታዲያ፣ እግዚአብሔር እንዴት
ኢየሩሳሌምን ከእጄ ሊያድን ይችላል?”
[21]ሕዝቡ ግን ንጉሡ፣ “መልስ አትስጡት”
ብሎ አዞ ስለ ነበር፣ ዝም አሉ፤ አንዳችም
አልመለሱለትም::
[22]የቤተ መንግሥት አስተዳዳሪ የነበረው
የኬልቅያስ ልጅ ኤልያቄም፣ ጸሓፊው
ሳምናስ፣ ታሪክ መዝጋቢው የአሳፍ ልጅ
ዮአስ ልብሳቸውን ቀደው ወደ ሕዝቅያስ
መጡ፤ የጦር አዛዡ የተናገረውንም ሁሉ
ነገሩት::

## የኢየሩሳሌም ዐርነት ታወጀ

37 ንጉሡ ሕዝቅያስ ይህን ሲሰማ፣
ልብሱን ቀደደ፤ ማቅ ለበሰ፤ ወደ
እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ገባ:: [2]የቤተ
መንግሥቱን አስተዳዳሪ ኤልያቄምንና ጸሓፊ
ውን ሳምናስን እንዲሁም ከካህናቱ ዋና ዋና
ዎቹን ማቅ ለብሰው ሁሉም ወደ አሞጽ ልጅ
ወደ ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲሄዱ ላካቸው::
[3]እነርሱም እንዲህ አሉት፤ “ሕዝቅያስ እንዲህ
ይላል፤ ይህ ቀን የጭንቀት፣ የተግሣጽና
የውርደት ቀን ነው፤ ሕፃናት ሊወለዱ ሲሉ
ብርታት እንደሚታጣበት ቀን ሆኖአል::
[4]ሕያው አምላክን ይገዳደር ዘንድ ጌታው
የአሦር ንጉሥ የላከውን የጦር አዛዡን ቃል
እግዚአብሔር አምላክህ ይሰማ ይሆናል፤
እግዚአብሔር አምላክህም ሰምቶ ይገሥ
ጸው ይሆናል፤ ስለዚህ አንተም በሕይወት
ለተ ረፉት ቅሬታዎች ጸልይ::”
[5]የንጉሡ የሕዝቅያስ መልእክተኞች ወደ
ኢሳይያስ መጡ፤ [6]ኢሳይያስም እንዲህ አላቸው፤
“ጌታችሁን እንዲህ በሉት፤ ‘እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤ የአሦር ንጉሥ ባሪያዎች እኔን
ስለ ሰደቡኝ፣ በሰማኸው ቃል አትሸበር::
[7]እነሆ፤ በላዩ መንፈስን እሰዳለሁ፤ ወሬም
ሰምቶ ወደ አገሩ ይመለሳል፤ በገዛ አገሩም
በሰይፍ እንዲወድቅ አደርጋለሁ::’ ”
[8]የጦር አዛዡም፣ የአሦር ንጉሥ ለኪሶን
ለቆ መሄዱን ሲሰማ፣ ከነበረበት ተመለሰ፤
ንጉሡም የልብናን ከተማ ሲወጋ አገኘው::
[9]ደግሞም ሰናክሬም፣ የኢትዮጵያ
ንጉሥ ቲርሐቅ ሊወጋው መምጣቱን ሰማ፤
ይህን ንም እንደ ሰማ ወደ ሕዝቅያስ
መልእክ ተኞች ላከ፤ እንዲህም አለ፤
[10]“ለይሁዳ ንጉሥ ለሕዝቅያስ እንዲህ
በሉት፤ ‘ኢየሩሳሌም በአሦር ንጉሥ
አትያዝም’ ብሎ የተማመ ንህበት አምላክ
አያታልህ:: [11]እነሆ፤ የአሦር ነገሥታት
በአገሮች ሁሉ ላይ ያደረጉትን፣ ፈጽሞም
እንዳጠፏቸው ሰምተሃል፤ አንተስ
የምታመልጥ ይመስልሃልን? [12]የቀደሙት አባ
ቶቼ ያጠፏቸውን፣ የጎዛንን፣ የካራንን፣ የራ
ፊስን እንዲሁም በተላሳር የሚኖሩ የዔ
ድንን ሰዎች የአሕዛብ አማልክት አድነዋቸ
ዋልን? [13]የሐማት ንጉሥ፣ የአርፋድ ንጉሥ፣
የሴፈርዋይም ከተማ ንጉሥ፣ የሄና ንጉሥ
ወይም የዒዋ ንጉሥ የት አሉ?”

## የሕዝቅያስ ጸሎት

[14]ሕዝቅያስ ደብዳቤውን ከመልእክተኞቹ
ተቀብሎ አነበበው፤ ወደ እግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ ወጥቶም ደብዳቤውን በእግዚአብሔር
ፊት ዘረጋው:: [15]ሕዝቅያስም እንዲህ ሲል ወደ
እግዚአብሔር ጸለየ፤ [16]“በኪሩቤል ላይ
የምት ቀመጥ፣ የእስራኤል አምላክ፣ የሰራ
ዊት ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፤ በምድር
ባሉ መንግ ሥታት ሁሉ ላይ አንተ ብቻ
አምላክ ነህ፤ ሰማይንና ምድርንም ፈጥረሃል::
[17]አቤቱ፣ እግዚአብሔር ሆይ፤ ጆሮህን
አዘንብል፤ አድምጥም:: እግዚአብሔር
ሆይ፤ ዐይኖችህን ክፈት፤ ተመልከትም::
ሰናክሬም ሕያው አምላክን ለመሳደብ
የላከውን ቃል ስማ::
[18]“እግዚአብሔር ሆይ፤ በእርግጥ የአሦር
ነገሥታት እነዚህን ሕዝቦች፣ ምድራ
ቸውንም ሁሉ ባድማ አድርገዋል:: [19]አ
ማልክታ ቸውን ወደ እሳት ጥለዋል፤
በሰው እጅ የተቀረጹ የድንጋይና የዕ
ንጨት ምስሎች እንጂ አማልክት
አልነበሩምና:: [20]አሁንም፣ እግዚአብሔር
አምላካችን ሆይ፤ የምድር መን ግሥታት
ሁሉ አንተ እግዚአብሔር ብቻ አምላክ
እንደ ሆንህ ያውቁ ዘንድ፣ አቤቱ ከእጁ
አድነን::”

## የሰናክሬም ውድቀት

[21]ከዚህ በኋላ የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ እን
ዲህ የሚል መልእክት ወደ ሕዝቅያስ ላከ፤
“የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤ ‘ስለ አሦር ንጉሥ፣ ስለ ሰናክሬም
ወደ እኔ ጸልየሃልና፣ [22]እግዚአብሔር በእርሱ
ላይ የተናገረው ቃል ይህ ነው፤

“ ‘ድንግሊቱ የጽዮን ልጅ፣
ንቃሃለች፣ አፊዛብሃለች፤
የኢየሩሳሌም ልጅ፣
አንተ ስትሸሽ ራሷን ነቅንቃብሃለች::

17፥24፤18፥34
36፥20 ዘፀ5፥2፤ 1ነገ20፥23፤ 2ዜና25፥15፤ ኢሳ10፥8-11፤ 37፥10-13፤18-20፤ 40፥18፤ዳን3፥15
36፥21 ምሳ9፥7-8፤ 26፥4
36፥22 ዘፍ37፥29፤ 2ሳሙ8፥16፤ 2ነገ18፥18፤2ዜና34፥19
37፥1 ቍ14፤ ዘፍ37፥29፤34፤ 1ነገ8፥33፤2ዜና34፥19፤ ማቴ21፥13
37፥2 ቍ21፤ 2ነገ18፥18፤ኢሳ1፥1፤ 13፥1፤36፥3፤38፥1
37፥3 መሳ6፥2፤ ኢሳ5፥30፤26፥18፤ 66፥9፤ሆሴ13፥13
37፥4 ቍ23-24፤ ኢሱ3፥10፤1ሳሙ7፥8፤ 2ዜና32፥17፤ኢሳ1፥9፤ 36፥13፤18-20፤አሞ7፥2
37፥6 ዘኍ15፥30፤ ኢሱ1፥9፤ኢሳ7፥4
37፥7 ቍ9፤ 1ዜና5፥26፤ኢሳ31፥8
37፥8 ዘኍ33፥20፤ ኢሱ10፥3
37፥9 ቍ7፤ 2ዜና32፥1፤ኢሳ20፥3
37፥10 2ዜና32፥11፡ 15፤ኢሳ36፥15
37፥11 ኢሳ36፥18-20
37፥12 ዘፍ11፥31፤ 12፥1-4፤2ነገ18፥11፤ ሕዝ27፥23፤አሞ1፥5፤ ሐሥ7፥2
37፥13 2ነገ17፥24፤ ኢሳ10፥9፤36፥20
37፥14 ቍ1፡38፤ 1ነገ8፥33፤ 2ዜና32፥17
37፥15 2ዜና32፥20
37፥16 ዘፍ1፥1፤ 3፥24፤ዘጸ10፥17፤ መዝ2፥4፤46፥10፤ 86፥10፤136፥2-3፤ ኢሳ11፥12፤41፥9፤ 43፥6፤ዳን4፥34፤ ሐሥ4፥24
37፥17 ኢሱ3፥10፤ 1ነገ8፥29፤2ዜና6፥40፤ 32፥1፡17፤ኤር25፥29፤ ዳን9፥18
37፥18 2ነገ15፥29፤ ናሆ2፥11-12
37፥19 ኢሱ7፥15፤ 2ዜና13፥9፤ 2ዜና32፥19፤ መዝ135፥15፤ ኢሳ26፥14፤36፥20፤ 40፥17፡18-20፤41፥24፡ 29፤44፥9-11፤ ኤር2፥11፤5፥7፤ 16፥20፤ገላ4፥8
37፥20 ኢሱ4፥24፤ መዝ3፥2፡7፤46፥10፤ምሳ20፥22 37፥21 ቍ2 37፥22 ኢዮ16፥4፤ ኢሳ10፥32፤23፥12

23የሰደብኸውና ያቃለልኸው ማንን ነው?
ድምፅህንስ ከፍ ከፍ ያደረግኸው፣
ዐይንህን በትዕቢት ያነሣኸው በማን ላይ ነው?
በእስራኤል ቅዱስ ላይ ነው እኮ!
24በመልእክተኞችህ በኩል፣
በጌታ ላይ ብዙ የስድብ ቃል ተናገርህ፤
እንዲህም አልህ፤
"በሰረገሎቼ ብዛት፣
የተራሮችንም ከፍታ፣
የሊባኖስንም ጫፍ ወጥቻለሁ፤
ረጃጅም ዝግባዎችን፣
የተመረጡ ጥዶችን ቈርጫለሁ፤
እጅግ ወደራቀት ከፍታዎች፣
እጅግ ውብ ወደ ሆኑትም ደኖች
ደርሻለሁ፤
25በባዕድ ምድር[ሠ] ጒድጓዶችን ቈፈርሁ፤
ከዚያም ውሃ ጠጣሁ፡፡
የግብፅን ምንጮች ሁሉ፣
በእግሬ ረግጬ አደረቅሁ፡፡"
26" 'ይህን ቀድሞ እንደ ወሰንሁት፣
ጥንትም እንዳቀድሁት፣
አልሰማህምን?
አሁን ደግሞ እንዲፈጸም አደረግሁት፤
አንተም የተመሸጉትን ከተሞች የድንጋይ
ክምር አደረግሃቸው፡፡
27የሕዝቦቻቸው ኀይል ተሟጦአል፤
ደንግጠዋል፤ ተዋርደዋልም፤
በሜዳ እንዳሉ ዕፀዋት፣
እንደ ለጋ ቡቃያ፣
በሰገነት ላይ እንደ በቀለ ሣር፣
በእንጭጩ ዋግ እንደ መታው ሆነዋል፡፡
28" 'እኔ ግን የት እንዳለህ፣
መምጣት መሄድህ ምን ጊዜ እንደ ሆነ፣
በእኔም ላይ እንዴት በቍጣ እንደም
ትነሣሣ ዐውቃለሁ፡፡
29በእኔ ላይ በቍጣ ስለ ተነሣሣህ፣
እብሪትህም ወደ ጆሮዬ ስለ ደረሰ፣
በአፍንጫህ ስናጌን፣
በአፍህ ልጓሜን አገባለሁ፤
በመጣህበትም መንገድ እንድትመለስ
አደርግሃለሁ፡፡'
30"ሕዝቅያስ ሆይ፤ ይህ ምልክት ይሆንልሃል፤
"በዚህ ዓመት የገቦውን፣
በሚቀጥለው ዓመት ከገቦው የበቀለውን
ትበላላችሁ፤
በሦስተኛው ዓመት ግን ትዘራላችሁ፤
ታጭዳላችሁ፤
ወይን ትተክላላችሁ፤ ፍሬውንም ትበላ ላችሁ፡፡
31እንደ ገናም የይሁዳ ቤት ቅሬታ፣
ሥሩን ወደ ታች ይሰዳል፤ ከላይም ፍሬ
ያፈራል፤
32ቅሬታ የሆኑት ከኢየሩሳሌም፣
የተረፉትም ከጽዮን ተራራ ይመጣሉና፤
የሰራዊት ጌታ የእግዚአብሔር ቅናት
ይህን ያደርጋል፡፡
33"ስለዚህ እግዚአብሔር ስለ አሦር ንጉሥ
እንዲህ ይላል፤
"ወደዚች ከተማ አይገባም፤
ፍላጻ አይወረውርባትም፤
ጋሻ አንግቦ አይመጣባትም፤
በዐፈር ቍልልም አይከባትም፡፡
34በመጣበት መንገድ ይመለሳል፤
ወደዚች ከተማም አይገባም"
ይላል እግዚአብሔር፡፡
35"ስለ ራሴና፣ ስለ አገልጋዬም ስለ ዳዊት፣
ይህችን ከተማ እጋርዳታለሁ፤ አድናታ
ለሁም፡፡"

36ከዚያም የእግዚአብሔር መልአክ ወጣ፤
ከአሦራውያን ሰፈር አንድ መቶ ሰማንያ
አምስት ሺህ ሰው ገደለ፤ በሰፈር ያሉት
ማለዳ ሲነሡ፤ ቦታው ሬሳ በሬሳ ነበር፡፡
37ስለዚህ የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም አመለጠ፤
ወደ ነነዌም ተመልሶ በዚያ ተቀመጠ፡፡
38ሰናክሬም በአምላኩ በናሳራክ ቤተ
ጣዖት በሚሰግድበት ጊዜ፣ ልጆቹ አድ
ራሜሌክና ሳራሳር በሰይፍ ገደሉት፤ ከዚ
ያም ወደ አራራት ምድር ኰበለሉ፤ ልጁ
ም አስራዶን በምትኩ ነገሠ፡፡

## የሕዝቅያስ መታመም

38 በዚያ ጊዜ ሕዝቅያስ ታመመ፤
ሞት አፋፍ ደረሰ፤ የአሞጽ ልጅ
ነቢዩ ኢሳይያስም ወደ እርሱ መጥቶ፣
"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ 'ከሕመምህ
አትድንም፤ ትሞታለህና ቤትህን አሰናዳ' "
አለው፡፡
2ሕዝቅያስም ፊቱን ወደ ግድግዳ አዞሮ፣
እንዲህ ሲል ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ 3"እግዚ
አብሔር ሆይ፤ በፊትህ በታማኝነትና በፍ
ጹም ልብ ደስ የሚያሰኝህንም በማድረግ
እንዴት እንደ ኖርሁ አቤቱ አስብ፡፡" ሕዝቅ
ያስም አምርሮ አለቀሰ፡፡
4የእግዚአብሔርም ቃል ወደ ኢሳይያስ
እንዲህ ሲል መጣ፤ 5"ሂድና ለሕዝቅያስ
እንዲህ ብለህ ንገረው፤ 'የአባትህ የዳዊት
አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
"ጸሎትህን ሰምቻለሁ፤ እንባህንም
አይቻለሁ፤ በዕድሜህም ላይ ዐሥራ
አምስት ዓመት

1ሳሙ17፥46፤
37፥23 ቀኍ4፤
ዘኊ15፥30፤ኢዮ15፥25፤
ኢሳ1፥4፤2፥11፤12፥6፤
52፥5፤ሕዝ36፥20፡23፤
ዳን7፥25
37፥24 1ነገ5፥8-10፤
7፥2፤ኢሳ14፥8፡13፤
33፥9፤36፥9፤41፥19፤5
5፥13፤60፥13፤
ሆሴ14፥8
37፥25 ዘዳ11፥10፤
ኢሳ10፥14፤19፥6፤
44፥27፤ዳን4፥30
37፥26 ዘዳ13፥16፤
ኢሳ10፥6፤25፥1፡2፤
ሐሥ2፥23፤4፥27-28፤
1ጴጥ2፥8
37፥27 መዝ129፥6፤
ኢሳ15፥6
37፥28 መዝ2፥1፤
139፥1-3
37፥29 ቀኍ34፤
2ዜና33፥11፤
ኢዮ40፥24፤ኢሳ10፥12
37፥30 ዘሌ25፥4፤
መዝ107፥37፤
ኢሳ16፥14፤20፥3፤
30፥23፤32፥10፤
65፥21፤ኤር31፥5
37፥31 ኢሳ11፥10፤
27፥6
37፥32 ኢሳ1፥9፤
9፥7፤11፥11
37፥33 2ሳሙ20፥15፤
ኢሳ32፥18
37፥34 ቀኍ29
37፥35 1ዜና17፥19፤
ኢሳ31፥5፤43፥25፤
48፥9፡11፤
ሕዝ36፥21-22
37፥36 ዘፀ12፥12፡23፤
ኢሳ10፥12
37፥37 ዘፍ10፥11፤
2ዜና32፥1፤ናሆ1፥1
37፥38 ቀኍ14፤
ዘፍ8፥4፤2ነገ17፥24፤
ኢሳ9፥4፤10፥26፤
14፥25፤ኤር51፥27
38፥1 2ሳሙ17፥23፤
2ነገ8፥10፤ኢሳ37፥2
38፥3 ዘዳ6፥18፤
10፥20፤1ነገ8፥61፤
1ዜና29፥19፤
መዝ6፥8፤26፥3
38፥4 1ሳሙ13፥13፤
ኢሳ39፥5
38፥5 2ነገ18፥2፡3፤
መዝ6፥6

[ሠ]25 የሙት ባሕር ቅጆች (እንዲሁም 2 ነገ 19፥24 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ የማሶሬቱ ቅጅ ግን፣ *በባዕድ ምድር* የሚለውን ሐረግ አይጨምርም፡፡

እጨምርልሃለሁ፡፡ 6አንተንና ይህቺን ከተማ
ከአሦር ንጉሥ እጅ እታደጋለሁ፤ ለከተ
ማዋም እከላከልላታለሁ፡፡
7“ ‘*እግዚአብሔር* የገባልህን ቃል እንደሚ
ፈጽምልህ፣ የ*እግዚአብሔር* ምልክት ይህ ነው፤
8በአካዝ የሰዓት መቍጠሪያ ደረጃ ላይ፣
የወረደውን የፀሓይ ጥላ በዐሥር ደረጃ ወደ
ኋላ እንዲመለስ አደርጋለሁ፡፡’ ” ስለዚህ ወርዶ
የነበረው የፀሓይ ጥላ ያንኑ ያህል ወደ
ኋላ ተመለሰ፡፡

9የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ ከሕመሙ
ከተፈወሰ በኋላ የጻፈው ጽሕፈት፤

10እኔ፣ “በዕድሜዬ እኩሌታ፣
በሲኦል ደጆች ማለፍ አለብኝን?
የቀረውንስ ዘመኔን ልነጠቅ ይገባልን?”
አልሁ፡፡
11እንዲህም አልሁ፤ “ዳግም *እግዚአብሔርን*፣
*እግዚአብሔርን* በሕያዋን ምድር አላይም፤
ከእንግዲህም የሰውን ዘር አላይም፤
በዚህ ዓለም ከሚኖሩትም ጋር
አልሆንም፡፡
12ቤቴ እንደ እረኛ ድንኳን ተነቀለ፤
ከእኔም ተወሰደ፤
ሕይወቴን እንደ ሸማኔ ጠቀለልሁ፤
ከመጠቅለያ ቈርጦኛል፤
ከጠዋት እስከ ማታ ልትጨርሰኝ ፈጠንህ፡፡
13እስከ ማለዳ በትዕግሥት ጠበቅሁ፤
እርሱ ግን እንደ አንበሳ ዐጥንቶቼን ሁሉ
ሰባበረ፤
ከጠዋት እስከ ማታም ልትጨርሰኝ
ፈጠንህ፡፡
14እንደ ጨረባ፣ እንደ ሽመላም ተንጫጫሁ፤
እንደ ርግብ አልጐመጐምሁ፤
ዐይኖቼ ወደ ሰማይ በመመልከት ደከሙ፤
ጌታ ሆይ፤ ተጨንቄአለሁና ታደገኝ፡፡”

15እንግዲህ ምን እላለሁ?
እርሱ ተናግሮኛል፤ ራሱ ደግሞ ይህን
አድርጓል፤
ስለ ነፍሴ ጭንቀት፣
ዕድሜዬን ሁሉ በትሕትና እሄዳለሁ፡፡
16ጌታ ሆይ፤ ሰዎች በእነዚህ ነገሮች ይኖራ
ሉ፤
መንፈሴም እንዲሁ በእነዚህ ሕይወትን
ያገኛል፤
ፈወስኸኝ፤
በሕይወትም አኖርኸኝ፡፡
17እነሆ፤ በሥቃይ የተጨነቅሁት፣
ለጥቅሜ ሆነ፤
ከጥፋት ጒድጓድ፣
በፍቅርህ ጠበቅኸኝ፤
ኀጢአቴንም ሁሉ፣
ወደ ኋላህ ጣልኸ፡፡
18ሲኦል አያመሰግንህም፤
ሞት አያወድስህም፤
ወደ ጒድጓድ የሚወርዱ፣
የአንተን ታማኝነት ተስፋ አያደርጉም፡፡
19እኔ ዛሬ እንደማደርገው፣
ሕያዋን እነርሱ ያመሰግኑሃል፡፡
ስለ አንተ ታማኝነትም፣
አባቶች ለልጆቻቸው ይነግራሉ፡፡
20*እግዚአብሔር* ያድነኛል፤
ስለዚህ በዕድሜ ዘመናችን ሁሉ፣
በ*እግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ፣
አውታር ባለው መሣሪያ እንዘምራለን፡፡

21ኢሳይያስም፣ “የበለስ ጥፍጥፍ ወስዳችሁ
በዕባጩ ላይ አድርጉለት እርሱም ይፈወሳል”
ብሎ ነበር፡፡

22ሕዝቅያስም፣ “ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስ እወጣ ዘንድ ምልክቱ ምንድን
ነው?” ብሎ ነበር፡፡

## ከባቢሎን የመጡ መልእክተኞች

39 በዚያን ጊዜ የባቢሎን ንጉሥ፣
የባልዳን ልጅ፣ መሮዳክ ባልዳን
የሕዝቅያስን መታመምና መፈወስ ሰምቶ
ስለ ነበር፣ ደብዳቤና ስጦታ ላከለት፡፡
2ሕዝቅያስም መልእክተኞቹን በደስታ ተቀ
በለ፤ ለእነርሱም በግምጃ ቤቱ ውስጥ
ያለውን ብሩን፣ ወርቁን፣ ቅመማ ቅመሙን፣
ምርጡን ዘይት እንዲሁም የጦር መሣሪያ
ውን በሙሉ፣ ያለውንም ንብረት አንዳች
ሳያስቀር አሳያቸው፡፡ በቤተ መንግሥቱም
ሆነ በግዛቱ ሁሉ ሕዝቅያስ ያላሳያቸው
ነገር አልነበረም፡፡
3ከዚያም ነቢዩ ኢሳይያስ ወደ ንጉሡ ሕ
ዝ ቅያስ መጥቶ፣ “እነዚያ ሰዎች ምን
አሉህ? ወደ አንተ ዘንድ የመጡትስ ከየት
ነው?” አለው፡፡
ሕዝቅያስም፣ “ወደ እኔ የመጡት ከሩቅ
አገር፣ ከባቢሎን ነው” አለው፡፡
4ነቢዩም፣ “በቤተ መንግሥትህ ያዩት
ምንድን ነው?” አለው፡፡
ሕዝቅያስም፣ “በቤተ መንግሥቴ ያለውን
ሁሉ አይተዋል፤ ከንብረቴ ያላሳየኋቸው
ምንም ነገር የለም” አለ፡፡
5ኢሳይያስም ሕዝቅያስን እንዲህ አለው፤
“የሰራዊት ጌታ የ*እግዚአብሔርን* ቃል ስማ፤
6‘እነሆ፤ በቤተ መንግሥትህ ያለው ሁሉ፣
አባቶችህ እስከዚህች ቀን ድረስ ያከማቹትም
ሁሉ ወደ ባቢሎን ተማርኮ የሚወሰድበት
ቀን ይመጣል፤ አንዳች የሚተርፍ ነገር
የለም፤ ይላል *እግዚአብሔር*፡፡ 7ከአብራክህ
ከሚከፈሉት፣ ከዘርህ፣ ከአንተ ከሚወለዱት
ልጆች ተወስደው፣ በባቢሎን ንጉሥ ቤተ
መንግሥት ጃንደረባዎች ይሆናሉ፡፡’ ”

38፥6 ኢሳ31፥5
38፥7 ዘፍ24፥14፤ 2ዜና32፥31፤ ኢሳ7፥11፡14፤20፥3
38፥8 ኢሱ10፥13
38፥10 ኢዮ17፥11፡16፤መዝ102፥24፤ 107፥18፤2ቆሮ1፥9
38፥11 ኢዮ28፥13፤ መዝ116፥9፤ኢሳ12፥2
38፥12 ቀኑ13፤ ዘኍ11፥15፤ኢዮ4፥21፤ 7፥6፤መዝ31፥22፤ 32፥4፤73፥14፤ ኢሳ33፥20፤34፥4፤ 2ቆሮ5፥1፡4፤ ዕብ1፥12፤ 2ጴጥ1፥13-14
38፥13 ቀኑ12፤ ኢዮ9፥17፤10፥16፤ መዝ37፥7፤51፥8፤ ኤር34፥17፤ሰቆ3፥4፤ዳ ን6፥24
38፥14 ዘፍ8፥8፤ 50፥24፤ኢዮ17፥3፤ መዝ6፥7፤ኢሳ59፥11
38፥15 2ሳሙ7፥20፤ 1ነገ21፥27፤ኢዮ7፥11፤ መዝ39፥9
38፥16 መዝ119፥25፤ ዕብ12፥9
38፥17 ኢዮ7፥11፤ 17፥16፤መዝ30፥3፤ 103፥3፡12፤119፥71፡7 5፤ኢሳ43፥25፤ ኤር31፥34፤ ሚክ7፥19፤ ሮሜ8፥28፤ዕብ12፥11
38፥18 ዘኍ16፥30፤ መዝ6፥5፤30፥9፤ 88፥10-11፤115፥17፤ መክ9፥10
38፥19 ዘዳ11፥19፤ መዝ118፥17፤119፥75
38፥20 መዝ23፥6፤ 33፥2፤45፥8፤63፥4፤ 68፥25፤116፥3፡17-19
38፥22 2ዜና32፥31
39፥1 2ዜና32፥31
39፥2 2ነገ18፥15፤ 2ዜና32፥27-29፡31
39፥3 ዘዳ28፥49
39፥5 ኢሳ38፥4
39፥6 መሳ6፥4፤ 2ነገ24፥13
39፥7 2ነገ24፥15፤ ዳን1፥1-7

[8]ሕዝቅያስም፣ "የተናገርኸው የእግዚ
አብሔር ቃል መልካም ነው" አለው፤ "በዘ
መኔ ሰላምና ጸጥታ ከኖረ ዘንድ" ብሎ ዐስቦ
ነበርና።

## የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያጽናና ቃል

40 አጽናኑ፤ ሕዝቤን አጽናኑ፤
ይላል አምላካችሁ።
[2]ለኢየሩሳሌም አለዝባችሁ ንገሯት፤
ዐውጁላትም፤
በባርነት ያገለገለችበት ዘመን አብቅቶአል፤
የኀጢአቷም ዋጋ ተከፍሎአል፤
ስለ ኀጢአቷ ሁሉ ከእግዚአብሔር እጅ
ሁለት ዕጥፍ ተቀብላለች።

[3]የዐዋጅ ነጋሪ ድምፅ እንዲህ ይላል፤
"የእግዚአብሔርን መንገድ፣
በምድረ በዳ አዘጋጁ፤
ለአምላካችን አውራ ጐዳና፣
በበረሓ አስተካክሉ።
[4]ሸለቆው ሁሉ ከፍ ይላል፤
ተራራውና ኰረብታው ሁሉ ዝቅ ይላል፤
ወጣ ገባው ምድር ይስተካከላል፤
ሰርጓጕጡም ሜዳ ይሆናል።
[5]የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጣል፤
ሰው ሁሉ በአንድነት ያየዋል፤
የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና።"

[6]ድምፅም፣ "ጩኽ" አለኝ፤
እኔም፣ "ምን ብዬ ልጩኽ?" አልሁ።

"ሰው ሁሉ እንደ ሣር ነው፤
ክብሩም ሁሉ እንደ ሜዳ አበባ ነው።
[7]ሣሩ ይደርቃል፤ አበባውም ይረግፋል፤
የእግዚአብሔር እስትንፋስ ነፍሶበታልና፤
ሕዝቡ በእርግጥ ሣር ነው።
[8]ሣሩ ይደርቃል፤ አበባውም ይረግፋል፤
የአምላካችን ቃል ግን ለዘላለም ጸንቶ
ይኖራል።"

[9]አንተ ለጽዮን የምሥራችን የምትነግር፤
ከፍ ወዳለው ተራራ ውጣ፤
አንተ ለኢየሩሳሌም ብሥራት የምትነግር፣[የ]
ድምፅህን ከፍ አድርገህ ጩኽ።
ከፍ አድርገው፤ አትፍራ፤
ለይሁዳም ከተሞች፣
"እነሆ፤ አምላካችሁ!" በል።
[10]እነሆ፤ ልዑል እግዚአብሔር በኀይል
ይመጣል፤
ክንዱ ስለ እርሱ ይገዛል።
እነሆ፤ ዋጋው ከእርሱ ጋር ነው፤
የሚከፍለውም ብድራት አብሮት አለ።
[11]መንጋውን እንደ እረኛ ያሰማራል፤
ጠቦቶቹን በክንዱ ይሰበስባል፤
በዕቅፉም ይይዛቸዋል፤
የሚያጠቡትንም በጥንቃቄ ይመራል።
[12]ውሆችን በዕፍኙ የሰፈረ፣
ሰማያትን በስንዝሩ የለካ፣
የምድርን ዐፈር በመስፈሪያ ሰብስቦ የያዘ፣
ተራሮችን በሚዛን፣
ኰረብቶችንም በመድሎት የመዘነ ማነው?
[13]የእግዚአብሔርን መንፈስ የተረዳ፣
አማካሪውስ ሆኖ ያስተማረው ማነው?
[14]ዕውቀት ለማግኘት እግዚአብሔር ማንን
አማከረ?
ትክክለኛውንስ መንገድ ማን አስተ
ማረው?
ዕውቀትን ያስተማረው፣
የማስተዋልንም መንገድ ያሳየው ማን
ነበር?

[15]እነሆ፤ አሕዛብ በገንቦ ውስጥ እንዳለች ጠብታ
ናቸው፤
በሚዛን ላይ እንዳለ ትቢያ ይቈጠራሉ፤
ደሴቶችንም እንደ ደቃቅ ዐፈር
ይመዝናቸዋል።
[16]ሊባኖስ ለመሥዋዕት እሳት አትበቃም፤
የእንስሶቿም ቍጥር ለሚቃጠል መሥ
ዋዕት ያንሳል።
[17]አሕዛብ ሁሉ በፊቱ እንደ ኢምንት
ናቸው፤
ከምንም የማይቈጠሩ መና ናቸው።

[18]እንግዲህ፣ እግዚአብሔርን ከማን ጋር
ታወዳድሩታላችሁ?
ከየትኛውስ ምስል ጋር ታነጻጽሩታላችሁ?
[19]የተቀረጸውንማ ምስል ባለጅ ይቀር
ጸዋል፤
ወርቅ አንጥረኛም በወርቅ ይለብጠዋል፤
የብር ሰንሰለትም ያበጅለታል።
[20]እንዲህ ያለውን መባ ማቅረብ የማይችል
ምስኪን ድኻ፣
የማይነቅዝ ዕንጨት ይመርጣል፤
የማይወድቅ ምስልን ለማቆምም፣
ታዋቂ ባለሙያ ይፈልጋል።
[21]አላወቃችሁምን?
አልሰማችሁምን?
ከጥንት አልተነገራችሁምን?
ምድር ከተመሠረተች ጀምሮ አላስተዋ
ላችሁምን?

39፥8 መሳ10፥15፤ 2ዜና32፥36፤ ኢዮ1፥21፤መዝ39፥9
40፥1 ኢሳ12፥1፤ 49፥13፤51፥3፡12፤ 52፥9፤57፥18፤61፥2፤6 6፥13፤ኤር31፥13፤ ሶፎ3፥14-17፤ ዘካ1፥17፤2ቆሮ1፥3
40፥2 ዘፍ34፥3፤ ዘሌ26፥41፤ኢዮ7፥1፤ ኢሳ35፥4፤41፥11-13፤ 49፥25፤51፥19፤61፥7፤ኤ ር16፥18፤17፥18፤ ዘካ9፥12፤ ራእ18፥6
40፥3 ምሳ3፥5-6፤ ኢሳ11፥16፤43፥19፤ ሚል3፥1፤ማቴ3፥3፤ ማር1፥3፤ዮሐ1፥23
40፥4 መዝ26፥12፤ ኢሳ2፥14፤26፥7፤ 45፥2፡13፤49፥11፤ ኤር31፥9
40፥5 ዘፀ16፥7፤ ዘኍ14፥21፤ኢሳ1፥20፤ 52፥10፤58፥14፤ 59፥19፤62፥2፤ ሉቃ2፥30፤3፥4-6
40፥6 ዘፍ6፥3፤ ኢሳ29፥5
40፥7 ዘፀ15፥10፤ ኢ ዮ8፥12፤41፥21፤ መዝ103፥16፤ ኢሳ15፥6፤ሕዝ22፥21
40፥8 መዝ119፥89፤ ምሳ19፥21፤ኢሳ5፥24፤ 7፥7፡9፤55፥11፤59፥21፤ ኤር39፥16፤ማቴ5፥18፤ ያዕ1፥10፤ 1ጴጥ1፥24-25
40፥9 ኢሳ1፥1፤ 25፥9፤41፥27፤44፥28፤ 52፥7-10፤61፥1፤ ናሆ1፥15፤ ሐሥ13፥32፤ ሮሜ10፥15፤ 1ቆሮ15፥1-4
40፥10 መዝ44፥3፤ ኢሳ9፥6-7፤28፥2፤ 30፥30፤33፥2፤35፥4፤5 9፥20፤ማቴ21፥5፤ ራ እ22፥7፡12
40፥11 ዘፍ33፥13፤ 48፥15፤ዘኍ11፥12፤ ዘዳ26፥19፤30፥4፤ መዝ28፥9፤ኢሳ49፥10፤ ሚክ5፥4፤ዮሐ10፥11
40፥12 ኢዮ12፥15፤ 38፥5፡10፡18፤ ምሳ16፥11፤30፥4፤ ዕብ1፥10-12
40፥13 ኢዮ15፥8፤ ኢሳ11፥2፤42፥1፤ ሮሜ 11፥34፤1ቆሮ2፥16
40፥14 ኢዮ12፥13፤ 21፥22፤34፥13፤ ኢሳ55፥9፤ቈላ2፥3
40፥15 ዘዳ9፥21፤ መዝ62፥9፤ኢሳ2፥22
40፥16 መዝ50፥9-11፤ኢሳ33፥9፤37፥24፤ ሚክ6፥7፤ዕብ10፥5-9
40፥17 ኢዮ12፥19፤ ኢሳ29፥7፤30፥28፤ 37፥19፤ዳን4፥35
40፥18 ዘፀ8፥10፤ ዘዳ4፥15፤1ሳሙ2፥2፤ሐሥ17፥29
40፥19 ዘፀ20፥4፤ መዝ115፥4፤ኢሳ2፥20፤ 31፥7፤37፥19፤41፥7፤ 42፥17፤46፥6፤ ኤር2፥8፡28፤10፥3፡8፤16፥19፤ዕን2፥18፤ ዘካ10፥2
40፥20 1ሳሙ5፥3፤ 12፥21፤ኢሳ44፥19
40፥21 ቀኍ28፤ ዘፍ1፥1፤2ነገ19፥25፤መዝ19፥1፤50፥6፤ኢሳ41፥22፤42፥9፤ 44፥8፤48፥3፡5፡13፤ 51፥13፤ሐሥ14፥17፤ ሮሜ1፥19

[የ]9 ወይም፣ *ጽዮን ሆይ፤ የምሥራቹን የምታበስሪ፤ ወደ ረጅም ተራራ ላይ ውጪ። የምሥራቹን የምታበስሪ ኢየሩሳሌም ሆይ*

22እርሱ ከምድር ክበብ በላይ በዙፋን ላይ
ይቀመጣል፤
ሕዝቦቿም እንደ አንበጣ ናቸው፡፡
ሰማያትን እንደ ድባብ ይዘረጋቸዋል፤
እንደ መኖሪያ ድንኳንም ይተክላቸዋል፡፡
23አለቆችን ኢምንት፣
የዚህን ዓለም ገዦች እንዳልነበሩ
ያደርጋቸዋል፡፡
24ተተክለው ምንም ያህል ሳይቈዩ፣
ተዘርተው ምንም ያህል ሳይሰነብቱ፣
ገና ሥር መስደድ ሳይጀምሩ
አነፈሰባቸው፤ እነርሱም ደረቁ፤
ዐውሎ ነፋስም እንደ ገለባ ጠራርጎ
ወሰዳቸው፡፡
25ቅዱሱ፣ “ከማን ጋር ታወዳድሩኛላችሁ?
የሚስተካከለኝስ ማን አለ?” ይላል፡፡
26ዐይናችሁን አንሡ፤ ወደ ሰማይ ተመልከተ
፡፤
እነዚህን ሁሉ የፈጠረ ማን ነው?
የከዋክብትን ሰራዊት አንድ በአንድ
የሚያወጣቸው፣
በየስማቸው የሚጠራቸው እርሱ ነው፡፡
ከኀይሉ ታላቅነትና ከችሎታው ብርታት
የተነሣ፣
አንዳቸውም አይጠፉም፡፡

27ያዕቆብ ሆይ፤ ለምን እንዲህ ትላለህ?
እስራኤል ሆይ፤ ለምን እንዲህ ትናገራለህ?
“መንገዴ ከእግዚአብሔር ተሰውራለች፤
ፍርዴም በአምላኬ ቸል ተብላለች”
ለምን ትላለህ?
28አታውቅምን?
አልሰማህምን?
እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ፣
የምድር ዳርቻ ፈጣሪ ነው፡፡
አይደክምም፤ አይታክትም፤
ማስተዋሉም በማንም አይመረመርም፡፡
29ለደከመው ብርታት ይሰጣል፤
ለዛለው ጕልበት ይጨምራል፡፡
30ወጣቶች እንኳ ይደክማሉ፤ ይታክታሉም፤
ጕበዛዝትም ተሰናክለው ይወድቃሉ፡፡
31እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉ ግን፣
ኀይላቸውን ያድሳሉ፤
እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፤
ይሮጣሉ፤ አይታክቱም፤
ይሄዳሉ፤ አይደክሙም፡፡

## የእስራኤል ረዳት

41 “ደሴቶች ሆይ፤ በፊቴ ዝም በሉ፤
አሕዛብ ኀይላቸውን ያድሱ፤
ቀርበው ይናገሩ፤
በፍርድም ፊት እንገናኝ፡፡

2“ከምሥራቅ አንዱን ያነሣው፣
በጽድቅም ወደ አገልግሎቱ የጠራው
ማን ነው?[ዩ]
አሕዛብን አሳልፎ ሰጠው፤
ነገሥታትን በፊቱ አስገዛለት
በሰይፉም እንደ ትቢያ አቦነናቸው፤
በቀስቱም በነፋስ እንደ ተበተነ ገለባ
አደረጋቸው፡፡
3አሳደዳቸው ያለ ችግር ዐልፎ ሄደ፤
እግሩም ቀድሞ ባልረገጠው መንገድ ተጓዘ፡፡
4ይህን የሠራና ያደረገ፣
ትውልድን ከጥንት የጠራ ማን ነው?
እኔ እግዚአብሔር ከፊተኛው፣
ከኋለኛውም ጋር፤ እኔው ነኝ፡፡”
5ደሴቶች አይተው ፈሩ፤
የምድር ዳርቻች ደነገጡ፤
ቀረቡ፤ ወደ ፊትም መጡ፡፡
6እያንዳንዱ ይረዳዳል፤
ወንድሙንም፣ “አይዞህ” ይለዋል፡፡
7ባለጅ የወርቅ አንጥረኛውን ያበረታታዋል፤
በመዶሻ የሚያሳሳውም፣
በመስፍ ላይ የሚቀጠቅጠውን ያነቃቃዋል፤
ስለ ብየዳም ሥራው፣ “መልካም ነው”
ይለዋል፤
የጣዖቱ ምስል እንዳይወድቅም በምስ
ማር ያጣብቀዋል፡፡

8“አንተ ግን፣ ባሪያዬ እስራኤል፣
የመረጥሁ ያዕቆብ፣
የወዳጄ የአብርሃም ዘር ሆይ፤
9ከምድር ዳርቻ ያመጣሁህ፣
ከአጥናፍም የጠራሁህ፣
‘አንተ ባሪያዬ ነህ’ ያልሁህ፤
መረጥሁህ እንጂ፤ አልጣልሁህም፡፡
10እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፤
አምላክህ ነኝና አትደንግጥ፡፡
አበረታሃለሁ፤ እረዳሃለሁ፤
በጽድቄም ቀኝ እጄ ደግፌ እይዝሃለሁ፡፡
11“እነሆ፤ የተቈጡህ ሁሉ፣
እጅግ ያፍራሉ፤ ይዋረዳሉም፤
የሚቋቋሙህ፣
እንዳልነበሩ ይሆናሉ፤ ይጠፋሉም፡፡
12ጠላቶችህን ብትፈልጋቸው እንኳ፣
አታገኛቸውም፤
የሚዋጉህም፣
እንዳልነበሩ ይሆናሉ፡፡
13እኔ እግዚአብሔር አምላክህ
‘አትፍራ፤

40፥22 ዘፍ1፥1፤ 1፥8፤ዘኍ13፥33፤ 2ዜና6፥18፤ ኢዮ22፥14፤26፥7፤ 36፥29፤መዝ2፥4፤ ኢሳ48፥13
40፥23 ኢዮ12፥18፡ 19፤ኢሳ34፥12፤ አሞ2፥3
40፥24 2ሳሙ22፥16፤ ኢዮ5፥3፤8፥12፤18፥16፤ 24፥24፤ኢሳ11፥4፤ 41፥16፤41፥2
40፥25 1ሳሙ2፥2፤ 1ዜና16፥25፤ኢሳ1፥4፤ 37፥23
40፥26 ቍ28፤ 2ነገ17፥16፤ነህ9፥6፤ ኢዮ9፥4፤38፥32፤ መዝ89፥11-13፤ ኢሳ34፥16፤42፥5፤ 45፥24፤51፥6፤66፥2፤ ኤፌ1፥19
40፥27 ኢዮ6፥29፤ 27፥2፤ሉቃ18፥7-8
40፥28 ቍ21፥26፤ ዘዳ33፥27፤መዝ90፥2፤1 47፥5፤ኢሳ37፥16፤ 44፥12፤ሮሜ11፥33
40፥29 ዘፍ18፥14፤ መዝ68፥35፤119፥28፤ኢ ሳ50፥4፤57፥19፤ ኤር31፥25
40፥30 መዝ20፥8፤ ኢሳ5፥27፤9፥17፤ ኤር6፥11፤9፥21፤
40፥31 ዘፀ19፥4፤ 1ሳሙ2፥4፤2ነገ6፥33፤መ ዝ37፥9፤40፥1፤ ኢሳ30፥18፤ሉቃ18፥1፤ 2ቆሮ4፥1፡16፤ ዕብ12፥1-3
41፥1 1ሳሙ2፥4፤ መዝ37፥7፤ኢሳ1፥18፤ 11፥11፤34፥1፤48፥16፤50 ፥8፤57፥3፤ዕን2፥20፤ ሶፎ1፥7፤ዘካ2፥13
41፥2 ቍ25፤ 2ሳሙ22፥43፤ ዕዝ1፥2፤መዝ1፥4፤ ኢሳ13፥4፡17፡18፤ 40፥24፤44፥28፤45፥1፡8፡ 13፤48፥14፤ ኤር25፥9፤50፥3፤ 51፥11
41፥3 ዳን8፥4
41፥4 ቍ9፥26፤ ዘፍ1፥1፤ዘዳ32፥39፤ ኢሳ43፥7፤44፥6፤ 46፥10፤48፥12፤ ራእ1፥8፡17
41፥5 ዘዳ30፥4፤ ኢሳ11፥11፡12፤ ሕዝ26፥17-18
41፥6 ኢሱ1፥6
41፥7 1ሳሙ5፥3፤ ኢሳ40፥19፤44፥13፤ 46፥7፤ኤር10፥3-5
41፥8 2ዜና20፥7፤ መዝ136፥22፤ ኢሳ14፥1፤27፥11፤ 29፥22፤51፥2፤63፥16፤ ያዕ2፥23

41፥9 ቍ4፤ ዘዳ7፥6፤ኢሳ11፥12፤ 20፥3፤37፥16
41፥10 ቍ13-14፤ ዘፍ15፥1፤ዘፀ3፥20፤ ዘዳ3፥22፤ኢሱ1፥9፤ ኢዮ40፥14፤ መዝ18፥35፤68፥35፤119፥28፡117፤ኢሳ43፥2፡ 5፤44፥2፤ 49፥8፤50፥7፡9፤ኤር30፥10፤46፥27-28፤ሮሜ8፥31
41፥11 ዘፀ23፥22፤ኢሳ17፥12፤29፥8፡22፤45፥24፤54፥17፤ ኤር2፥3
41፥12 ኢዮ7፥8፤ መዝ37፥35-36፤ኢሳ17፥14፤29፥20፤ 34፥12
41፥13 ቍ10፤ መዝ73፥23፤ኢሳ42፥6፤ 45፥1፤51፥18

[ዩ]2 ወይም በእያንዳንዱ እርምጃ ድል የሚያጋጥመው

እረዳሃለሁ’
ብዬ ቀኝ እጅህን እይዛለሁና።
14አንት ትል ያዕቆብ፣
ታናሽ እስራኤል ሆይ፤
‘አትፍራ እኔ እረዳሃለሁ’ ”
ይላል *እግዚአብሔር*፤
የሚቤዥህ
የእስራኤል ቅዱስ ነው።
15“እነሆ፣ አዲስ
የተሳለና ብዙ ጥርስ ያለው ማሄጃ
አደርግሃለሁ፤
ተራሮችን ታሄዳለህ፤ ታደቃቸዋለህ፤
ኰረብቶችንም ገለባ ታደርጋቸዋለህ።
16ታበጥራቸዋለህ፤ ነፋስ ጠርጎ ይወስዳቸዋል፤
ዐውሎ ነፋስም ይበትናቸዋል።
አንተ ግን *በእግዚአብሔር* ደስ ይልሃል፤
በእስራኤል ቅዱስ ሞገስ ታገኛለህ።
17“ድኾችና ችግረኞች ውሃ ይፈልጋሉ፤
ዳሩ ግን ምንም አያገኙም፤
ጕሮሮአቸው በውሃ ጥም ደርቆአል።
ነገር ግን እኔ *እግዚአብሔር* እመልስላቸዋለሁ፤
እኔ የእስራኤል አምላክ አልተዋቸውም።
18በተራቈቱ ኰረብቶች ላይ ወንዞችን፣
በሸለቆዎች ውስጥ ምንጮች አፈልቃለሁ።
ምድረ በዳውን የውሃ ኵሬ፣
የተጠማውን ምድር የውሃ ምንጭ አደርጋለሁ።
19በምድረ በዳ፣
ዝግባን፣ ግራርን፣ ባርሰነትንና ወይራን
አበቅላለሁ፤
በበረሃ፣
ጥድን፣ አስታንና ሸውሸዌን በአንድነት
እተክላለሁ።
20ስለዚህ ሰዎች ያያሉ፤ ያውቃሉ፤
*የእግዚአብሔር* እጅ ይህን እንዳደረገ፣
የእስራኤል ቅዱስ እንደ ፈጠረው፣
በአንድነት ይገነዘባሉ፤ ያስተውላሉም።
21“ሙግታችሁን ይዛችሁ ቅረቡ” ይላል
*እግዚአብሔር*፤
“ማስረጃችሁን አምጡ” ይላል የያዕቆብ
ንጉሥ።
22“የሚሆነውን እንዲነግሩን፣
ጣዖቶቻችሁን አምጡ፤
እንድንገነዘብ፣
ፍጻሜአቸውን እንድናውቅ፣
የቀደሙት ነገሮች ምን እንደ ነበሩ ንገሩን፤
ስለሚመጡትም ነገሮች ግለጹልን።
23እናንት አማልክት መሆናችሁን እናውቅ
ዘንድ፣
ወደ ፊት ስለሚሆነው ንገሩን፤
እንድንደነግጥ፣ በፍርሀት እንድንዋጥ፣
መልካምም ሆነ ክፉ፣ አንድ ነገር
አድርጉ።
24እነሆ፤ እናንት ከምንም የማትቈጠሩ ናችሁ፤
ሥራችሁ ፈጽሞ ዋጋ ቢስ ነው፤
የመረጣችሁም አስጸያፊ ነው።
25“አንዱን ከሰሜን አስነሣሁት፤ እርሱም
ይመጣል፤
ከፀሓይ መውጫ የሚመጣው፣ ስሜን
የሚጠራ ነው፤
ሸክላ ሠሪ ዐፈር እንደሚረግጥ፣
አለቆችን እንዲሁ እንደ ጭቃ ይረግጣል።
26እኛ እናውቅ ዘንድ ይህን ከመጀመሪያው
የተናገረ፣
‘እርሱ ትክክል ነው’ እንልም ዘንድ ቀድሞ
የተናገረ ማነው?
ማንም አልተናገረም፤
ቀደም ብሎ የተናገረ የለም፤
ቃላችሁንም የሰማ የለም።
27በመጀመሪያ፣ ‘እነሆ፤ ተመልከቷቸው!’
ብዬ ለጽዮን የተናገርሁ እኔ ነበርሁ፤
ለኢየሩሳሌምም
የምሥራች ነጋሪን ሰጥቻለሁ።
28ተመለከትሁ ማንም አልነበረም፤
ከመካከላቸው አማካሪ የለም፤
ስጠይቅም መልስ የሚሰጥ የለም።
29እነሆ፤ ሁሉም ከንቱ ናቸው፤
ሥራቸውም መና ነው፤
ምስሎቻቸውም ባዶ ነፋስ ናቸው።

## *የእግዚአብሔር አገልጋይ*

42 “ደግፌ የያዝሁት አገልጋዬ፣
በእርሱም ደስ የሚለኝ ምርጤ
ይህ ነው፤
መንፈሴን በእርሱ ላይ አደርጋለሁ፤
ለአሕዛብም ፍትሕን ያመጣል።
2አይጮኽም፣ ቃሉን ከፍ አያደርግም፤
ድምፁን በመንገድ ላይ በኀይል አያሰማም።
3የተቀጠቀጠ ሸምበቆ አይሰብርም፤
የሚጤስም የጧፍ ክር አያጠፋም፤
ፍትሕን በታማኝነት ያመጣል።
4ፍትሕን በምድር እስኪያመጣ ድረስ፣
አይደክምም፤ ተስፋም አይቈርጥም፤
ደሴቶች በሕጉ ይታመናሉ።”
5ሰማያትን የፈጠረ፣ የዘረጋቸውም፣
ምድርንና በውስጧ ያሉትን ሁሉ ያበጀ፣
ለሕዝቧ እስትንፋስን፣
ለሚኖሩባትም ሕይወትን የሚሰጥ፣
ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

41፥14 ቍ10፡16፡20፤ዘፍ15፡1፤ዘፀ15፡13፤ኢዮ4፡19፤19፡25፤መዝ22፡6፤ ኢሳ1፡4፡27
41፥15 ቍ2፤ዘፀ19፡18፤ኢዮ41፡30፤መዝ107፡33፤ኢሳ10፡5፤21፡10፤ኤር9፡10፤ሕዝ33፡28
41፥16 ቍ14፤ኢሳ25፡9፤40፡24፤45፡25፤ 60፡19፤ኤር15፡7፤51፡2፤ዳን2፡35፤ማር1፡24
41፥17 ዘዳ31፡6፤መዝ27፡9፤ኢሳ30፡19፤35፡7፤43፡20
41፥18 2ነገ3፡17፤ኢዮ38፡26፤ኢሳ30፡25፤35፡7፤43፡19
41፥19 ዘፀ25፡5፡10፤ኢሳ35፡1፤37፡24፤44፡14፤51፡3፤60፡13
41፥20 ቍ14፤ዘፀ6፡7፤ዕዝ7፡6፤8፡31፤ኢሳ4፡5፤29፡24፤43፡3፡14፤50፡2፤51፡1፡9፤59፡1፤66፡14፤ኤር32፡17
41፥21 ቍ1፤ኢሳ43፡15፤44፡6
41፥22 ቍ26፤ኢሳ42፡9፤43፡9፡18፡19፡26፤44፡7፤45፡21፤46፡9፡10፤48፡3፡6፡14፤65፡17፤ዮሐ13፡19
41፥23 2ነገ19፡26፤ኢሳ45፡3፤ኤር10፡5
41፥24 1ሳሙ12፡21፤መዝ109፡7፤ኢሳ1፡13፤37፡19፤48፡8፤ኤር8፡19፤10፡5፡8፡15፤1ቆሮ8፡4
41፥25 ቍ2፤2ሳሙ22፡43፤ዕዝ1፡2፤ኢሳ5፡5፤ኤር50፡9፡41፤51፡48፤ናሆ3፡14
41፥26 ቍ4፡22፤1ነገ18፡26፤ኢሳ52፡6፤ዕን2፡18-19
41፥27 ኢሳ40፡9፤48፡3፡16
41፥28 1ነገ18፡26፤መዝ22፡11፤ኢሳ40፡13-14፤50፡2፤59፡16፤63፡5፤64፡7፤65፡12፤66፡4፤ኤር25፡4፤ሕዝ22፡30
41፥29 1ሳሙ12፡21፤ኢሳ37፡19፤ኤር5፡13
42፥1 ዘፍ49፡10፤ኢሳ9፡7፤11፡2፤14፡1፤20፡3፤44፡3፤ማቴ3፡16-17፤20፡28፤ሉቃ9፡35፤23፡35፤ዮሐ3፡34፤1ጴጥ2፡4፡6
42፥2 ምሳ8፡1-2
42፥3 ኢዮ13፡25፤30፡24፤መዝ72፡2፤96፡13፤ኢሳ36፡6
42፥4 ቍ21፤ዘፍ49፡10፤ዘፀ34፡29፤ኢሳ2፡4፤11፡11፤51፡4፤ማቴ12፡18-21
42፥5 ዘፍ1፡1፡6፤2፡7፤መዝ24፡2፤102፡25፤ኢሳ48፡13፤ሐሥ17፡24፡25

[6]“እኔ *እግዚአብሔር* በጽድቅ ጠርቼሃለሁ፤
እጅህንም እይዛለሁ፤
እጠብቅሃለሁ፤
ለሕዝቡ ቃል ኪዳን፣
ለአሕዛብም ብርሃን አደርግሃለሁ፡፡
[7]የዕውሮችን ዐይን ትከፍታለህ፤
ምርኮኞችን ከእስር ቤት፣
በጨለማ የተቀመጡትንም ከወህኒ
ታወጣለህ፡፡

[8]“እኔ *እግዚአብሔር* ነኝ፤ ስሜም ይህ ነው፤
ክብሬን ለሌላ፣
ምስጋናዬንም ለጣዖት አልሰጥም፡፡
[9]እነሆ፤ የቀድሞው ነገር ተፈጽሞአል፤
እኔም አዲስ ነገር እናገራለሁ፤
ከመብቀሉም በፊት፣
ለእናንተ አስታውቃለሁ፡፡

### *ለእግዚአብሔር* የውዳሴ መዝሙር

[10]እናንት ወደ ባሕር የምትወርዱ፣ በዚያም
ያላችሁ ሁሉ፣
ደሴቶችና በዚያ የምትኖሩ በሙሉ፣
*ለእግዚአብሔር* አዲስ መዝሙር፣
ከምድር ዳርቻም ምስጋናውን ዘምሩ፡፡
[11]ምድረ በዳውና ከተሞቹ ድምፃቸውን ከፍ
ያድርጉ፤
ቄዳር ያለችበት መንደር ደስ ይበለው፤
የሴላ ሕዝቦች በደስታ ይዘምሩ፤
ከተራሮችም ራስ ላይ ይጮኹ፡፡
[12]ክብር *ለእግዚአብሔር* ይስጡ፤
ምስጋናውንም በደሴቶች ያውጁ፡፡
[13]*እግዚአብሔር* እንደ ኀያል ሰው
ይዘምታል፤
እንደ ተዋጊ በወኔ ይነሣል፤
የቀረርቶ ጩኸት ያሰማል፤
ጠላቶቹንም ድል ያደርጋል፡፡
[14]“ለረጅም ጊዜ ዝም አልሁ፤
ጸጥ አልሁ፤ ራሴንም ገታሁ፤
አሁን ግን ምጥ እንደ ያዛት ሴት፣
እጮኻለሁ፤ ቁና ቁና እቃትታለሁ፤
እተነፍሳለሁ፡፡
[15]ተራራውንና ኰረብታውን አፈርሳለሁ፤
ዕፀዋቱን ሁሉ አደርቃለሁ፤
ወንዙንም ደሴት አደርጋለሁ፤
ኵሬውን አደርቃለሁ፡፡
[16]ዕውሮችን በማያውቁት መንገድ እመራቸዋለሁ፤
ባልተለመደ ጐዳና እወስዳቸዋለሁ፡፡
ጨለማውን በፊታቸው ብርሃን አደርጋለሁ፤
ጐርባጣውን ስፍራ አስተካክላለሁ፡፡
ይህን አደርጋለሁ፤
አልተዋቸውም፡፡
[17]በጣዖት የሚታመኑ ግን፣
ምስሎችን፣ ‘አምላኮቻችን ናችሁ’
የሚሉ፣
ወደ ኋላቸው ይመለሳሉ፤ ፈጽመው ይዋ
ረዳሉም፡፡

### ዕውሯና ደንቆሮዋ እስራኤል

[18]“እናንት ደንቈሮዎች ስሙ፤
እናንት ዕውሮች እዩ፤ ተመልከቱም፡፡
[19]አገልጋዬ እንጂ፣ ሌላ ዕውር ማን አለ?
ከምልከው መልእክተኛዬስ በቀር ማን
ደንቈሮ አለ?
ለእኔ ታማኝ እንደ ሆነ ሰው የታወረ፣
እንደ *እግዚአብሔርስ* አገልጋይ ዕውር
ማነው?
[20]ብዙ ነገርን አያችሁ፤ ነገር ግን
አላስተዋላችሁም፤
ጆሮአችሁ ክፍት ነው፤ ነገር ግን ምንም
አትሰሙም፡፡”
[21]*እግዚአብሔር* ስለ ጽድቁ ሲል፣
ሕጉን ታላቅና የተከበረ በማድረግ ደስ
አለው፡፡
[22]ይህ ሕዝብ ግን የተበዘበዘና የተዘረፈ፣
በጕድጓድ ውስጥ የተጠመደበት፣

በወህኒ ቤት የተዘጋበት ነው፤
ተበዝብዘዋል፣
የሚያድናቸውም የለም፤
ተማርከዋል፣
“መልሷቸው” የሚልም የለም፡፡

[23]ከእናንተ ይህን የሚሰማ፣
ለሚመጣውም ጊዜ አስተውሎ የሚያ
ደምጥ ማነው?
[24]ያዕቆብን ለዝርፊያ፣
እስራኤልን ለምርኮ የዳረገ ማነው?
በኀጢአት የበደልነው፣
*እግዚአብሔር* አይደለምን?
መንገዱን ለመከተል፣
ለሕጉም መታዘዝ አልፈለጉምና፡፡
[25]ስለዚህ የሚነድ ቍጣውን፣
የጦርነትንም መዓት አፈሰሰባቸው፤
በእሳት ነበልባል ከበባቸው፤ እነርሱ ግን
አላስተዋሉም፤
አቃጠላቸው፤ እነርሱ ግን ልብ አላሉም፡፡

### የእስራኤል ብቸኛ አዳኝ

43 አሁን ግን፣ ያዕቆብ ሆይ! የፈጠረህ፤
እስራኤል ሆይ! የሠራህ፣
*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“ተቤዥቼሃለሁና አትፍራ፤

**42፥6** ዘፀ31፥2፤ መሳ4፥10፤ኢሳ9፥2፤ 26፥3፡18፤27፥3፤ 41፥9-10፡13፤43፥1፤ 45፥1፡24፤49፥8፤ 54፥10፤59፥21፤61፥8፤ ኤር23፥6፤31፥31፤ 32፥40፤ዳን9፥7፤ ሚል3፥1፤ሉቃ2፥32፤2 2፥20
**42፥7** መዝ66፥11፤ 107፥10፡14፤146፥8፤ኢሳ24፥22፤32፥3፤ 48፥20፤49፥9፤51፥14፤52፥2፤ዘካ2፥7፤9፥11፤ ማቴ11፥5፤ሉቃ4፥19፤ ሐሥ26፥18፤ ዕብ2፥14-15፤ 2ጢሞ2፥26
**42፥8** ዘፀ3፥15፤ 6፥3፤8፥10፤20፥4፤ መዝ81፥10፤ ኢሳ43፥3፡11፡15፤ 46፥9፤48፥11፤49፥23
**42፥9** ኢሳ40፥21፤ 41፥22፤ሕዝ2፥4
**42፥10** ዘፀ15፥1፤ ዘዳ30፥4፤1ነገ10፥9፤ 1ዜና16፥32፤ መዝ48፥10፤65፥5፤ 96፥1፡11፤ኢሳ11፥11፤ 49፥6፤60፥6
**42፥11** ዘፍ25፥13፤ መሳ1፥36፤ኢሳ32፥16፤ 52፥7፤60፥7፤ናሆ1፥15
**42፥12** 1ዜና16፥24፤ መዝ26፥7፤66፥2፤ ኢሳ11፥11፤24፥15፤ 1ጴጥ2፥9
**42፥13** ዘፀ14፥14፤ ኢሱ6፥5፤ኢሳ9፥6፤ 26፥11፤66፥14፤ ኤር25፥30፤ሆሴ11፥10፤ ኢል3፥16፤አሞ1፥2፤ 3፥4፥8
**42፥14** ዘፍ43፥31፤ አስ4፥14፤መዝ50፥21፤ ኤር4፥31፤ ሉቃ18፥7፤2ጴጥ3፥9
**42፥15** መዝ107፥33፤ ኢሳ11፥15፤50፥2፤ ሕዝ38፥20፤ናሆ1፥4-6
**42፥16** ዘዳ4፥31፤ መዝ18፥28፤ኢሳ26፥7፤ 29፥24፤32፥3፤40፥11፤ 57፥18፤58፥8፡10፡11፤ ኤር31፥8-9፤ ሉቃ1፥78-79፤ 3፥5፤ሐሥ26፥18፤ ዕብ13፥5
**42፥17** ዘፀ32፥4፤ መዝ97፥7፤ኢሳ1፥29
**42፥18** ኢሳ35፥5
**42፥19** ኢሳ26፥3፤ 41፥8-9፤43፥8፤ 44፥26፤ሕዝ12፥2፤ ሐጌ1፥13
**42፥20** ኢሳ6፥9-10፤ 43፥8፤ኤር5፥21፤ 6፥10
**42፥21** ቍ4፤ ኢሳ43፥25፤2ቆሮ3፥7
**42፥22** መሳ6፥4፤ 2ነገ24፥13፤ መዝ66፥11፤ኢሳ5፥29፤ 24፥18፥22
**42፥23** ዘዳ32፥29፤ መዝ81፥13፤ኢሳ47፥7፤ 48፥18፤57፥11
**42፥24** ኢሱ1፥7፤ 2ነገ17፥6፤ መዝ119፥136፤ኢሳ5፥24፤10፥5-6፤30፥15፤43፥28፤ 47፥6፤ኤር44፥10
**42፥25** 2ነገ22፥13፤ 25፥9፤ኢዮ40፥11፤ ኢሳ1፥3፤29፥13፤47፥7፤ 51፥17፤57፥1፡11፤66፥15፤ኤር4፥4፤ 21፥12፤ሰቆ2፥3፤ሕዝ7፥19፤ሆሴ7፥9፤ ናሆ1፥6
**43፥1** ቍ7፤ ዘፍ2፥7፤32፥28፤ዘፀ6፥6፤ዘዳ7፥6፤ኢዮ19፥25፤ኢሳ27፥11፤42፥6፤ 44፥21፤45፥3-4፤ 49፥1፤ሚል3፥17

በስምህ ጠርቼሃለሁ፤ አንተ የእኔ ነህ፤
2በውሃ ውስጥ በምታልፍበት ጊዜ፣
ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤
ወንዙን ስትሻገረው፣
አያሰጥምህም፤
በእሳት ውስጥ ስትሄድ፣
አያቃጥልህም፤
ነበልባሉም አይፈጅህም።
3እኔ *እግዚአብሔር* አምላክህ፣
የእስራኤልም ቅዱስ መድኀኒትህ ነኝና፤
ግብፅን ለአንተ ቤዛ እንድትሆን፣
ኢትዮጵያንና ሳባን በአንተ ፈንታ
እሰጣለሁ።
4ለዐይኔ ብርቅና ክቡርም ስለ ሆንህ፣
እኔም ስለምወድህ፣
ሰዎችን በአንተ ምትክ፣
ሕዝቦችንም በሕይወትህ ፈንታ
እሰጣለሁ።
5ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፤
ልጆችህን ከምሥራቅ አመጣለሁ፤
ከምዕራብም እሰበስብሃለሁ።
6ሰሜንን፣ ‘አምጣ’፣
ደቡብንም፣ ‘ልቀቅ’ እላለሁ፤
ወንዶች ልጆቼን ከሩቅ፣
ሴቶች ልጆቼንም ከምድር ዳርቻ፣
7በስሜ የተጠራውን ሁሉ፣
ለክብሬ የፈጠርሁትን፣
ያበጀሁትንና የሠራሁትን አምጡ።”

8ዐይን እያላቸው የታወሩትን፣
ጆሮ እያላቸው የደነቈሩትን አውጣ።
9ሕዝብ ሁሉ በአንድነት ይሰብሰብ፤
ሰውም ይከማች፤
ከእነርሱ አስቀድሞ ይህን የነገረን፣
የቀድሞውን ነገር ያወጀልን ማን ነው?
ሌሎችን ሰምተው፣ “እውነት ነው” እንዲ
ሉ፣
ትክክለኝነታቸውም እንዲረጋገጥ
ምስክሮቻቸውን ያቅርቡ።
10“ታውቁና ታምኑብኝ ዘንድ፣
እርሱ እኔ እንደ ሆንሁ ትረዱ ዘንድ፣
እናንተ ምስክሮቼ፣
የመረጥሁትም ባሪያዬ ናችሁ” ይላል
*እግዚአብሔር*።
“ከእኔ በፊት አምላክ አልተሠራም፤
ከእኔም በኋላ አይኖርም።
11እኔ፣ እኔ *እግዚአብሔር* ነኝ፤
ከእኔም ሌላ የሚያድን የለም።
12ገልጫለሁ፤ አድኛለሁ፤ ተናግሬአለሁ፤
በመካከላችሁ እኔ እንጂ ባዕድ አምላክ
አልነበረም።
እኔ አምላክ እንደ ሆንሁ፣
እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ” ይላል *እግዚ
አብሔር*፤

43፥2 ዘፍ26፥3፤ ዘፀ14፥22፤ መዝ66፥12፤ ኢሳ8፥7፤29፥6፤30፥27፤ ዳን3፥25-27
43፥3 ዘፍ10፥7፤ ዘፀ14፥30፤20፥2፤ መሳ2፥18፤መዝ3፥8፤ 68፥31፤ምሳ21፥18፤ ኢሳ19፥1፤20፥3፤25፥9፤ 41፥20፤ሕዝ29፥20
43፥4 ዘፀ19፥5፤ ኢሳ49፥5፤63፥9፤ ራእ3፥9
43፥5 ዘፍ15፥1፤ 21፥22፤ዘፀ14፥22፤ ኢሳ11፥12፤24፥14፤ 41፥8፤44፥2፤49፥18፤ 54፥3፤61፥9፤66፥22፤ኤር30፥10-11፤ ዘካ8፥7፤ ማቴ8፥11
43፥6 ዘዳ30፥4፤ መዝ107፥3፤ ኢሳ11፥12፤60፥4፤ ኤር23፥8፤ሕዝ16፥61፤36፥24፤ 2ቆሮ6፥18
43፥7 ቍ1፡21፤ መዝ86፥9፤100፥3፤ ኢሳ19፥25፤27፥11፤ 48፥1፤56፥5፤62፥2፤ 63፥19፤65፥1፤ ኤር15፥16፤ያዕ2፥7
43፥8 ኢሳ6፥9-10፤ 42፥20፤ሕዝ12፥2
43፥9 ኢሳ41፥1፡ 26፤45፥20፤48፥14
43፥10 ቍ11፡12፤ ዘፀ6፥7፤ ዘዳ4፥35፤ 32፥39፤ኢሱ24፥22፤ መዝ86፥10፤ ኢሳ19፥21፤20፥3፤ 41፥8-9፤44፥6፡8፤ 45፥5-6፡14፤ ኤር14፥22
43፥11 ቍ10፤ ዘፀ6፥2፤መዝ3፥8፤ 18፥31፤ኢሳ25፥9፤ 42፥8፤64፥4
43፥12 ቍ10፤ ዘዳ32፥12
43፥13 ዘኍ23፥8፤ ዘዳ32፥39፤ኢዮ9፥12፤ መዝ90፥2፤ኢሳ46፥4፤ 48፥12
43፥14 ዘፀ15፥13፤ ኢዮ19፥25፤ኢሳ1፥4፤ 13፥14-15፤23፥13፤ 41፥20
43፥15 ኢሳ27፥11፤ 41፥21፤42፥8፤45፥11
43፥16 ዘፀ14፥29፤ 15፥8፤ኢሳ11፥15
43፥17 ዘፀ14፥9፡22፤ ኢዮ13፥25፤ መዝ76፥5-6፤118፥12፤ ኢሳ1፥31፤ኤር51፥21፤ ሕዝ38፥4
43፥18 ኢሳ41፥22
43፥19 መዝ126፥4፤ ኢሳ33፥21፤35፥7፤ 40፥3፤41፥22፤ ኤር16፥14-15፤

13“ከጥንት ጀምሮ እኔው ነኝ፤
ከእጄም ማውጣት የሚችል የለም፤
እኔ የምሠራውን ማን ማገድ ይችላል?”

## *የእግዚአብሔር ምሕረትና የእስራኤል አለመታመን*

14የእስራኤል ቅዱስ፣
የሚቤዣችሁ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤
“ስለ እናንተ በባቢሎን[ጀ] ላይ ሰራዊት
እሰዳለሁ፤
በሚመኩባቸውም መርከቦች፣
ባቢሎናውያንን ሁሉ እንደ ኰብላይ
አመጣለሁ።
15እኔ *እግዚአብሔር*፣ የእናንተ ቅዱስ፣
የእስራኤል ፈጣሪ፣ ንጉሣችሁ ነኝ።”

16በባሕር ውስጥ መንገድ፣
በማዕበል ውስጥ መተላለፊያ ያበጀ፣
*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
17እንደ ገና ላይነሡ እዚያው እንዲተኙ፣
እንደ ጧፍ ኵስታሪ ረግፈው እንዲጠፉ፣
ሠረገሎችንና ፈረሶችን፣
ሰራዊቱንና ደጀኑን በአንድነት ያወጣ
እንዲህ ይላል፤
18“የቀደመውን ነገር አታስቡ፤
ያለፈውን እርሱ።
19እነሆ፤ አዲስ ነገር አደርጋለሁ፤
እርሱም አሁን ይበቅላል፤ አታስተውሉ
ትምን?
በምድረ በዳም መንገድ አዘጋጃለሁ፤
በበረሓም ምንጭ አፈልቃለሁ፤
20የምድረ በዳ አራዊት፣
ቀበሮና ጕጕት ያከብሩኛል፤
በምድረ በዳ ውሃ፣
በበረሓም ምንጭ እሰጣለሁና።
ለመረጥሁት ሕዝቤ ውሃ እሰጣለሁ፤
21ለራሴ ያበጀሁት ሕዝብ
ምስጋናዬን ያውጅ ዘንድ ይህን
አደርጋለሁ።

22“ያዕቆብ ሆይ፤ አንተ ግን አልጠራኸኝም፤
እስራኤል ሆይ፤ የእኔ ነገር ታክቶሃል።
23ለሚቃጠል መሥዋዕት በጎች አላመጣህ
ልኝም፤
በመሥዋዕትህም አላከበርኸኝም።
በእህል ቍርባን አላስቸገርሁህም፤
በዕጣን መሥዋዕትም አላሰለቸሁህም።

23፥7-8፤2ቆሮ5፥17፤ራእ21፥5
43፥20 ዘኍ20፥8፤ መዝ148፥10፤ኢሳ13፥22
43፥21 ቍ7፤ ዘፍ2፥7፤መዝ66፥2፤ 102፥18፤ሚል3፥17፤1ጴጥ2፥9
43፥22 ኢሱ22፥5፤ ኢሳ1፥14፤30፥11
43፥23 ዘፀ29፥41፤ 30፥35፤ዘሌ2፥1፤ ኤር7፥22፤አሞ5፥25፤ ሚክ6፥3፤ዘካ7፥5-6፤ ሚል1፥6-8፤12-13

[ጀ]14 ወይም፣ *ከለዳውያን* ማለት ነው።

24መልካም መዐዛ ያለው ዕጣን አልገዛህልኝም፤
በመሥዋዕትህ ሥብ አላጠገብኸኝም፤
ነገር ግን የኀጢአት ሸክምህን ጫንህብኝ፤
በበደልህም አደከምኸኝ።

25“ስለ ራሴ ስል መተላለፍህን የምደመስ
ስልህ፣
እኔ፣ እኔው ነኝ፤
ኀጢአትህን አላስባትም።
26እስቲ ያለፈውን አስታውሰኝ፤
ተቀራርበን እንከራከርበት፤
ትክክለኛ ስለ መሆንህም አስረዳ።
27የመጀመሪያው አባትህ ኀጢአት ሠርቶአል፤
መምህሮችህም ዐመፀውብኛል።
28ስለዚህ የመቅደስህን አለቆች አዋርዳለሁ፤
ያዕቆብን ለጥፋት፣[ገ]
እስራኤልን ለስድብ እዳርጋለሁ።

## የተመረጠው እስራኤል

44 “ነገር ግን አሁንም ባሪያዬ ያዕቆብ፣
የመረጥሁህ እስራኤል ሆይ፣
ስማ፤

2የፈጠረህ፣ በማሕፀን የሠራህ፣
የሚረዳህ፣
*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
ባሪያዬ ያዕቆብ፣
የመረጥሁህ ይሹሩን ሆይ፣ አትፍራ።
3በተጠማ ምድር ላይ ውሃ፤
በደረቅ መሬት ላይ ወንዞችን አፈሳለሁና፤
መንፈሴን በዘርህ፣
በረከቴንም በልጅ ልጅህ ላይ
አወርዳለሁ።
4እነርሱም በለመለመ መስክ ላይ እንደ
ሣር፣
በወንዝ ዳር እንደ አኻያ ዛፍ ይበቅላሉ።
5አንዱ፣ ‘እኔ *የእግዚአብሔር* ነኝ’ ይላል፤
ሌላው ራሱን በያዕቆብ ስም ይጠራል
ሌላው ደግሞ በእጁ ላይ ‘*የእግዚአብሔር* ነኝ’
ብሎ ይጽፋል፤
ራሱን በእስራኤል ስም ይጠራል።

## አምላክ *እግዚአብሔር* ብቻ ነው

6“የእስራኤል ንጉሥና ቤዛ *እግዚአብሔር*፣
የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
የፊተኛውም እኔ ነኝ፤ የኋለኛውም እኔ ነኝ፤
ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም።
7እስቲ እንደ እኔ ማን አለ? ይናገር፤
ሕዝቤን ከጥንት ስመሠርት ምን እንደ
ነበረ፣
ገና ወደ ፊት ምን እንደሚሆን፣
ይናገር፤ በፊቴ ያስረዳ፤
ስለሚመጣውም ነገር አስቀድሞ ይናገር።
8አትፍሩ፤ አትደንግጡ፤
ይህን አልነገርኋችሁምን? ቀድሞስ አላሳወ
ቅኋችሁምን?

43፥24 ዘፀ30፥23፤ ዘሌ3፥9፤ኢሳ1፥14፤ 7፥13፤ኤር8፥21፤ 44፥22፤ሚል2፥17
43፥25 2ሳሙ12፥13፤ 2ዜና6፥21፤ኢዮ7፥21፤ ኢሳ37፥35፤38፥17፤ 64፥9፤ሕዝ20፥44፤ ሚክ7፥18፤ማር2፥7፤ ሉቃ5፥21፤ሐሥ3፥19
43፥26 ኢሳ1፥18፤ 41፥1፤49፥25፤50፥8
43፥27 ዘፍ12፥18፤ ኢሳ9፥15፤24፥20፤ 28፥7፤48፥8፤ኤር5፥31
43፥28 ዘኍ5፥27፤ ዘዳ13፥15፤መዝ39፥8፤ ኢሳ42፥24፤ኤር24፥9፤ ዘካ5፥3፤ሕዝ5፥15
44፥1 ቍ21፤ ዘፍ16፥11፤ኢሳ14፥1
44፥2 ቍ21፤ ዘፍ2፥7፤ዘኍ23፥21፤ ዘዳ32፥15፤መዝ139፥ 13፤149፥2፤ኢሳ27፥11፤ 41፥10፤43፥5፤ ኤር30፥10፤46፥27
44፥3 ምሳ9፥5፤ ኢሳ11፥2፤32፥2፤35፥7፤ 61፥9፤65፥23፤ ሕዝ36፥27፤ ኢል3፥18፤ሚል3፥10፤ ማር1፥8፤ዮሐ4፥10፤ ሐሥ2፥17
44፥4 ዘሌ23፥40፤ ኢዮ5፥25፤40፥22፤ መዝ72፥16፤
44፥5 ዘፀ13፥9፤ መዝ116፥16፤ ኢሳ19፥21፤60፥3፤ 66፥23፤ኤር50፥5፤ ዘካ8፥20-22፤13፥9፤ 14፥16
44፥6 ዘዳ6፥4፤ 1ዜና17፥20፤ ኢዮ19፥25፤ መዝ18፥31፤ኢሳ41፥4፤ 41፥21፤43፥1፡10፤ ራእ1፥8፡17
44፥7 ዘዳ32፥39፤ ኢሳ41፥22፡26
44፥8 ዘፍ49፥24፤ ኢሳ40፥21፤42፥9፤ 43፥10
44፥9 ዘፀ20፥4፤ ዘሌ19፥4፤ኢሳ1፥29፤ 26፥11፤40፥19፤ 41፥24፤65፥13፤ 66፥5፤ኤር22፥22
44፥10 ኢሳ40፥19፤ 41፥29፤ኤር10፥5፤ ሐሥ19፥26
44፥11 ቍ9፤ 2ነገ19፥18፤ ኢሳ1፥29፤ 37፥19
44፥12 ኢሳ40፥19፡ 28፤41፥6-7፤ 54፥16፤ሐሥ17፥29
44፥13 መሳ17፥4-5፤ መዝ115፥4-7፤ ኢሳ41፥7
44፥14 ኢሳ41፥19

ለዚህ እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ። ከእኔ በቀር
ሌላ አምላክ አለን? ፈጽሞ!
ወይም ሌላ ዐለት አለ? የለም! ማንንም
አላውቅም።”

9ጣዖት የሚሠሩ ሁሉ ከንቱዎች፣
የሚሰሩባቸውም ነገሮች ዋጋ ቢስ
ናቸው፤
የሚናገሩላቸው ዕውሮች ናቸው፤
ዕውቀት የላቸውም ያፍራሉም።
10ለምንም የማይጠቅመውን አምላክ
የሚቀርጽ፣
ጣዖትን የሚያበጅስ ማነው?
11ጣዖት የሚሠራ ሰው እንጂ ሌላ
አይደለም፤
እርሱና መሰሎቹም ያፍራሉ፤
ሁሉም ተሰብስበው በአንድ ላይ ይቁሙ፤
ይደነግጣሉ፤ ይዋረዳሉም።
12ብረት ቀጥቃጭ መሥሪያን ይይዛል፤
በከሰል ፍም ላይ ይሠራዋል፤
ጣዖትን በመዶሻ ቅርጽ ይሰጠዋል፤
በክንዱም ኀይል ያበጀዋል።
ከዚያም ይራባል፤ ጕልበት ያጣል፤
ውሃ ይጠማል፤ ይደክማል።
13ጠራቢ በገመድ ይለካል፤
በጠመኔ ንድፍ ያወጣል፤
በመሮ ይቀርጸዋል፤
በድርከል ምልክት ያደርግበታል።
በሰው አምሳል ይቀርጸዋል፤
የሰውንም ውበት ያለብሰዋል፤
በማምለኪያም ስፍራ ያስቀምጠዋል።
14ዝግባ ይቈርጣል፤
ሾላ ወይም ዋንዛ ይመርጣል፤
በደን ውስጥ ካሉት ዛፎች ጋር እንዲያድግ
ይተወዋል፤
ወይም ጥድን ይተክላል፤ ያንንም ዝናም
ያሳድገዋል።
15ሰው ለማገዶ ይጠቀምበታል፤
ከዚያም ጥቂት ወስዶ በማንደድ ይሞ
ቀዋል፤
እንጀራም ይጋግርበታል።
ከዚሁ ጠርቦ አምላክ ያበጃል፤
ያመልከዋል፤
ጣዖትን ይሠራል፤ ወድቆም ይሰግድ
ለታል።
16ግማሹን ዕንጨት ያነደዋል፤
በላዩ ምግቡን ያበስልበታል፤
ሥጋ ጠብሶበት እስኪጠግብ ይበላል፤
እሳቱን እየሞቀ እንዲህ ይላል፤
“እሰይ ሞቀኝ፤ እሳቱም ይታየኛል።”

44፥15 ቍ19፤ ዘፀ20፥5፤2ዜና25፥14፤ ራእ9፥20
44፥16 ኢሳ47፥14

[ገ]28 የዕብራይስጡ ቃል አንድን ሰው ወይም ነገር ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠትን ያመለክታል።

17በቀረው ዕንጨት የጣዖት አምላኩን ይሠ
ራበታል፤
ወድቆ ይሰግድለታል፤ ያመልከዋል፤
ወደ እርሱም እየጸለየ፣
“አንተ አምላኬ ነህ፤ አድነኝ” ይላል።
18ምንም አያውቁም፤ አያስተውሉም፤
እንዳያዩ ዐይናቸው ተሸፍኖአል፤
እንዳያስተውሉ ልባቸው ተዘግቶአል።
19ማንም ቆም ብሎ አላሰበም፤
ዕውቀት ወይም ማስተዋል ስለሌለው
እንዲህ ማለት አልቻለም፤
“ግማሹን በእሳት አቃጥዬዋለሁ፤
በፍሙ እንጀራ ጋግሬበታለሁ፤
ሥጋ ጠብሼበት በልቻለሁ፤
ታዲያ፣ በቀረው እንዴት ጸያፍ ነገር
እሠራለሁ?
ለግንድስ መስገድ ይገባኛልን?”
20ዐመድ ይቅማል፤ ተታላይ ልብ አስቶታል፤
ራሱን ለማዳን አይችልም፤
“ይህ በቀኝ እጄ ያለው ነገር ሐሰት
አይደለምን?”
ለማለት አልቻለም።

21“እስራኤል ሆይ፤ ባሪያዬ ነህና፣
ያዕቆብ ሆይ፤ ይህን አስብ።
እኔ ሠርቼሃለሁ፤ አንተም ባሪያዬ ነህ፤
እስራኤል ሆይ፤ አልረሳህም።
22መተላለፍህን እንደ ደመና፣
ኀጢአትህን እንደ ማለዳ ጭጋግ ጠርጌ
አስወግጃለሁ፤
ተቤዥቼሃለሁና
ወደ እኔ ተመለስ።”

23ሰማያት ሆይ፤ እግዚአብሔር ይህን
አድርጎአልና ዘምሩ፤
የምድር ጥልቆች ሆይ፤ በደስታ ጩኹ።
እናንት ተራሮች፣
እናንት ደኖችና ዛፎቻችሁ ሁሉ እልል
በሉ፤
እግዚአብሔር ያዕቆብን ተቤዥቶአል፣
በእስራኤልም ክብሩን ገልጦአልና።

## ኢየሩሳሌም የሰው መኖሪያ ትሆናለች

24“ከማሕፀን የሠራህ፣ የተቤዠህም፣
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤

ሁሉን ነገር የፈጠርሁ፣
ብቻዬን ሰማያትን የዘረጋሁ፣
ምድርን ያንጣለልሁ፣
እኔ እግዚአብሔር ነኝ።
25የሐሰተኞችን ነቢያት ምልክቶች አከሽ
ፋለሁ፤
ሟርተኞችን አነሆልላለሁ፤
የጥበበኞችን ጥበብ እገለባብጣለሁ፤
ዕውቀታቸውንም ከንቱ አደርጋለሁ።
26የባሪያዎቼን ቃል እፈጽማለሁ፤
የመልእክተኞቼን ምክር አጸናለሁ።

ኢየሩሳሌምን ‘የሰው መኖሪያ ትሆኛለሽ’፣
የይሁዳ ከተሞችንም፣ ‘ይታነጻሉ’፣
ፍርስራሻቸውን፣ ‘አድሳለሁ’ እላለሁ።
27ጥልቁን ውሃ፣ ‘ደረቅ ሁን፤
ወንዞችህን አደርቃለሁ’ እላለሁ።
28ቂሮስንም፣ ‘እርሱ እረኛዬ ነው፤
ፈቃዴን ሁሉ ይፈጽማል፤
ኢየሩሳሌምም፣ “እንደ ገና ትሠራ”፣
ቤተ መቅደሱም፣ “መሠረቱ ይጣል” ይላል’
እላለሁ።

# 45

“ለቀባሁት፣ ቀኝ እጁን ለያዝሁት፣
ነገሥታትን ትጥቅ አስፈታ ዘንድ፣
ሕዝብን ሁሉ ላስገዛለት፣
ደጆች እንዳይዘጉ፣
በሮቹን በፊቱ ለምከፍትለት፣
ለቂሮስ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
2‘በፊትህ እሄዳለሁ፤
ተራሮችንᵐ እደለድላለሁ፤
የናስ በሮችን እሰብራለሁ፤
የብረት መወርወሪያዎችንም እቈርጣለሁ።
3በስምህ የምጠራህ የእስራኤል አምላክ፣
እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቅ ዘንድ፣
በተሰወረ ስፍራ የተከማቸውን ሀብት፣
በጨለማም ያለውን ንብረት እሰጥሃለሁ።
4ስለ ባሪያዬ ስለ ያዕቆብ፣
ስለ መረጥሁት ስለ እስራኤል፣
አንተ ባታውቀኝ እንኳ፣
በስምህ ጠርቼሃለሁ፤
የክብርም ስም ሰጥቼሃለሁ።
5እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ከእኔ ሌላ ማንም የለም፤
ከእኔ በቀር አምላክ የለም።
አንታ ባታውቀኝም እንኳ፣
እኔ አበረታሃለሁ።
6ይኸውም ሰዎች ከፀሓይ መውጫ፣
እስከ መጥለቂያው፣
ከእኔ በቀር ሌላ እንደሌለ እንዲያውቁ ነው፤
እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ከእኔ ሌላ ማንም
የለም።
7እኔ ብርሃንን ሠራሁ፤ ጨለማንም ፈጠርሁ፤
አበለጽጋለሁ፤ አደኸያለሁ፤

44፥17 ዘፀ20፥5፤ መሳ10፥14፤ 1ነገ18፥26፤ኢሳ2፥8፤ 45፥20፤46፥7፤47፥15፤ ኤር1፥16
44፥18 ኢሳ1፥3፤ 6፥9-10፤16፥12፤ 29፥10፤ኤር4፥22፤ 10፥8፡14-15
44፥19 ቍ15፡18-19፤ ዘዳ27፥15፤ኢሳ5፥13፤ 27፥11፤40፥20፤45፥20
44፥20 ዘዳ4፥28፤ ኢዮ15፥31፤መዝ102፥9፤ ኢሳ59፥3፡4፥13፤ ኤር9፥3፤10፥14፤ 51፥17፤ሆሴ10፥5፤ 13፥2፤ሮሜ1፥21-23፡ 25፡28፤2ተሰ2፥11፤ 2ጢሞ3፥13
44፥21 መዝ27፥10፤ 136፥22፤ኢሳ27፥11፤ 43፥1፤46፥8፤49፥15፤ኤ ር31፥20፤ዘካ10፥9
44፥22 2ሳሙ12፥13፤ 2ዜና6፥21፤ኢዮ22፥23፤ ኢሳ33፥24፤45፥22፤ 55፥7፤ኤር36፥3፤ ሚል3፥7፤ማቴ20፥28፤ ሐሥ3፥19፤1ቆሮ6፥20
44፥23 ዘፀ6፥6፤ 16፥7፤ዘሌ10፥3፤ 1ዜና16፥31፤ መዝ65፥13፤98፥4፡8፤1 48፥7፤ኢሳ4፥2፤ 12፥6፤43፥7፤46፥13፤4 9፥3፤51፥11፤ 52፥1፤55፥5፤60፥9፡21፤ 61፥3፤62፥12፤ ኤር30፥19
44፥24 ዘፍ1፥1፤ 2፥1፤ኢዮ19፥25፤ መዝ139፥13፤ ኢሳ27፥11፤42፥5፤ 43፥14
44፥25 ዘሌ19፥26፤ 1ሳሙ6፥2፤ 2ሳሙ15፥31፤ ኢዮ5፥13፤መዝ33፥10፤ ኢሳ2፥6፤8፥19፤47፥13፤ ኤር27፥9፤ዳን2፥2፡ 10፤4፥7፤ሚክ3፥7፤ ዘካ10፥2፤1ቆሮ1፥19- 20፡27
44፥26 ዕዝ9፥9፤ መዝ51፥18፤74፥3፤ ኢ ሳ1፥1፤46፥10፤ 49፥8- 21፤51፥3፤ 55፥11፤59፥21፤61፥4፤ ኤር23፥20፤39፥16፤ ሰቆ2፥17፤ዳን9፥12፤ ዘካ1፥6፤ማቴ5፥18
44፥27 ኢሳ11፥15፤ 19፥5፤ራእ16፥12
44፥28 2ዜና36፥22፤ ዕዝ1፥2-4፤ኢሳ14፥32፤ 28፥16፤41፥2፤58፥12
45፥1 2ዜና36፥22፤ መዝ45፥7፤73፥23፤ ኢ ሳ41፥2፡13፤42፥6፤ 48፥14፤ኤር50፥35፤ 51፥20፡24፤ሚክ4፥13
45፥2 ዘፀ23፥20፤ መዝ107፥16፤147፥13፤ኢሳ13፥2፤40፥4፤ኤር51፥30፤ሰቆ2፥9፤ናሆ3፥13
45፥3 ዘፀ33፥12፤ 2ነገ24፥13፤ኢሳ41፥23፤ 43፥1፤ኤር41፥8፤ 50፥37፤51፥13 45፥4 ኢሳ14፥1፤ 41፥8-9፤ሐሥ17፥23
45፥5 ዘዳ32፥12፤ መዝ18፥31፡39፤ኢሳ43፥10፤44፥8፤ ሕዝ30፥24-25 45፥6 ቍ5፡18፤ መዝ113፥3፤ኢሳ11፥9፤ 14፥13-14፤ 43፥5፤47፥8፡10፤ ሶፎ2፥15 45፥7 ዘፍ1፥4፤ ዘፀ10፥22፤ኢሳ14፥15፤31፥2፤ሰቆ3፥38

ᵐ2 የሙት ባሕር ጥቅሎችና የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ በማሶሬቱ ቅጅ ግን የቃሉ ትርጒም አይታወቅም።

ይህን ሁሉ የማደርግ እኔ *እግዚአብሔር*
ነኝ።’
8“እናንት ሰማያት፣ ጽድቅን ከላይ አዝንቡ፤
ደመናትም ወደ ታች አንጠብጥቡ፤
ምድር ትከፈት፤
ድነት ይብቀል፤
ጽድቅም አብሮት ይደግ፤
እኔ *እግዚአብሔር* ፈጥሬዋለሁ።

9“ከዐፈር ሸክላዎች መካከል፣
ከሠሪው ጋር ክርክር ለሚገጥም ወዮለት፤
ጭቃ፣ ሸክላ ሠሪውን፣
‘ምን እየሠራህ ነው?’ ይለዋልን?
የምትሠራውስ ሥራ፣
‘እጅ የለህም’ ይልሃልን?
10አባቱን፣
‘የወለድኸው ምንድን ነው?’ ለሚል፣
እናቱንም፣
‘ምን ወለድሽ’? ለሚል ወዮለት።

11“የእስራኤል ቅዱስ፣ ሠሪውም የሆነ *እግዚ
አብሔር*፣
ስለሚመጡ ነገሮች እንዲህ ይላል፤
‘ስለ ልጆቼ ትጠይቁኛላችሁን?
ስለ እጆቼስ ሥራ ታዙኛላችሁን?
12ምድርን የሠራሁ እኔ ነኝ፤
ሰውንም በላይዋ ፈጥሬአለሁ፤
እጆቼ ሰማያትን ዘርግተዋል፤
የሰማይንም ሰራዊት አሰማርቻለሁ።
13ቂሮስን[ጫ] በጽድቅ አስነሣቸለሁ፤
መንገዱን ሁሉ አስተካክዬለታለሁ፤
ከተማዬን እንደ ገና ይሠራታል፤
ምርኮኞቼን ያለ ክፍያ ወይም ያለ ዋጋ፣
ነጻ ያወጣል፤’
ይላል የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*።”

14*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

“የግብፅ ሀብትና የኢትዮጵያ ንግድ፣
ቁመተ ረጃጅሞቹ የሳባ ሰዎች፣
ወደ አንተ ይመጣሉ፤
የአንተ ይሆናሉ፤
ከኋላ ይከተሉሃል፤
በሰንሰለትም ታስረው ወደ አንተ በመምጣት፣
በፊትህ እየሰገዱ፣
‘በእውነት *እግዚአብሔር* ከአንተ ጋር ነው፤
ከእርሱም በቀር ሌላ አምላክ የለም’
ብለው ይለምኑሃል።”

15አዳኙ የእስራኤል አምላክ ሆይ፤
አንተ በእውነት ራስህን የምትሰውር
አምላክ ነህ።
16ጣዖት ሠሪዎች ሁሉ ያፍራሉ፤ ይቀላሉ፤
በአንድነት ይዋረዳሉ።
17እስራኤል ግን *በእግዚአብሔር*፣
በዘላለም ድነት ይድናል፤
እናንተም ለዘላለም፣
አታፍሩም፤ አትዋረዱም።

18ሰማያትን የፈጠረ፣
እርሱ *እግዚአብሔር* ነው፤
ምድርን ያበጃት፣ የሠራት፣
የመሠረታት፣
የሰው መኖሪያ እንጂ፣
ባዶ እንድትሆን ያልፈጠራት፣
*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላልና፤
‘እኔ *እግዚአብሔር* ነኝ፤
ከእኔም በቀር ሌላ የለም።
19በጨለማ ምድር፣
በምስጢር አልተናገርሁም፤
ለያዕቆብም ዘር፣
“በከንቱ ፈልጉኝ” አላልሁም።
እኔ *እግዚአብሔር* እውነትን እናገራለሁ፤
ትክክለኛውንም ነገር ዐውጃለው።’

20“በአንድነት ተሰብሰቡ፤ ቅረቡም፤
እናንት ከአሕዛብ የኰበለላችሁ፣ ኑ።
የዕንጨት ጣዖት የሚሸከሙ፣
ማዳን ወደማይችል አምላክ የሚጸልዩ፣
ዕውቀት የላቸውም።
21ጉዳያችሁን ተናገሩ፤ አቅርቡ፤
ተሰብስበውም ይማከሩ።
ይህን አስቀድሞ ማን ዐወጀ?
ከጥንትስ ማን ተናገረ?
እኔ *እግዚአብሔር* አይደለሁምን?
ጻድቅና አዳኝ የሆነ አምላክ፣
ከእኔ በቀር ማንም የለም፤
ከእኔ ሌላ *አምላክ* የለም።

22“እናንት የምድር ዳርቻ ሁሉ፣
እኔ አምላክ ነኝ፤ ከእኔም በቀር ሌላ የለምና፤
ትድኑ ዘንድ ወደ እኔ ተመለሱ።
23ጉልበት ሁሉ በእኔ ፊት ይንበረከካል፤
አንደበትም ሁሉ በእኔ ይምላል፤
ብዬ በራሴ ምያለሁ፤
የማይታጠፍ ቃል፣
ከአፌ በጽድቅ ወጥቶአል።
24ስለ እኔም ሲናገሩ፣ ‘ጽድቅና ኀይል፣
*በእግዚአብሔር* ብቻ ነው’ ይላሉ።”
በእርሱ ላይ በቍጣ የተነሡ ሁሉ፣
ወደ እርሱ መጥተው ያፍራሉ።
25ነገር ግን የእስራኤል ዘር ሁሉ፣
*በእግዚአብሔር* ይጸድቃሉ፤ ሞገስንም
ያገኛሉ።

**45፥8** ቍ24፤ መዝ72፥6፤85፥9፥11፤133፥3፤ኢሳ12፥3፤41፥2፤46፥13፤48፥18፤60፥21፤61፥10፥11፤62፥1፤ሆሴ10፥12፤ ኢ.ል2፥23፤3፥18፤ አሞ5፥24፤ሚል4፥2
**45፥9** ኢዮ9፥12፤12፥13፤15፥25፤27፥2፤33፥13፤መዝ22፥15፤ኢሳ10፥15፤29፥16፤ዳን4፥35፤ሮሜ9፥20-21፤1ቆሮ10፥22
**45፥11** መዝ8፥6፤149፥2፤ኢሳ1፥4፤19፥25፤51፥13
**45፥12** ዘፍ1፥1፤2፥1፤ነህ9፥6፤ኢዮ38፥32፤ኢሳ48፥13
**45፥13** 1ነገ8፥36፤2ዜና36፥22፤ዕዝ1፥2፤መዝ26፥12፤ኢሳ40፥4፤41፥2፤52፥3
**45፥14** ዘፍ27፥29፤2ሳሙ3፥34፤8፥2፤መዝ18፥31፤ኢሳ2፥3፤11፥9፤14፥1-2፤18፥7፤43፥10፤60፥5፥11፤62፥2፤ኤር16፥19፤ዘካ8፥20-23፤1ቆሮ14፥25
**45፥15** ዘዳ31፥17፤መዝ44፥24፤ኢሳ1፥15፤25፥9
**45፥16** መዝ35፥4፤ኢሳ1፥29
**45፥17** ዘፍ30፥23፤ኢሳ12፥2፤29፥22፤41፥11፤ኤር23፥6፤33፥16፤ሮሜ11፥26
**45፥18** ቍ5፤ዘፍ1፥1፥2፥26፤ዘዳ4፥35
**45፥19** ቍ25፤ዘዳ4፥29፤30፥11፤2ዜና15፥2፤ኢሳ41፥8፤48፥16፤65፥4፥9፤ኤር2፥31፤31፥36
**45፥20** ዘዳ32፥37፤መዝ115፥7፤ኢሳ43፥9፤44፥17፥19፤46፥1፤ኤር1፥16፤2፥28፤10፥5
**45፥21** ቍ5፤መዝ3፥8፤11፥7፤46፥10፤ኢሳ25፥9፤41፥22፤46፥9፥10፤ማር12፥32
**45፥22** ዘፍ49፥10፤ዘኍ21፥8-9፤2ዜና20፥12፤ኢሳ11፥9፥12፤44፥22፤49፥6፥12፤ሆሴ13፥4፤ዘካ12፥10
**45፥23** ቍ14፤ዘፍ22፥16፤ዘዳ30፥11፤መዝ63፥11፤ኢሳ14፥24፤19፥18፤55፥11፤ሮሜ14፥11፤ፊል2፥10-11፤ዕብ6፥13
**45፥24** ቍ8፤ዘዳ33፥29፤መዝ18፥39፤ኢሳ40፥26፤41፥11፤63፥1፤ኤር33፥16
**45፥25** ቍ19፤ኢሳ4፥3፤24፥23፤ 41፥16፤49፥4

ጫ13 ዕብራይስጡ፣ *እርሱን* ይላል።

## የባቢሎን አማልክት

46 ቤል ተዋረደ፤ ናባው እጅግ ዝቅ
አለ፤
ጣዖቶቻቸው በአጋሰስ ተጭነዋል[ጸ]፤
ይዘዋቸው የሚዞሩት ምስሎች ሸክም
ናቸው፤
ለደከሙ እንስሳት ከባድ ጭነት ናቸው::
2እነርሱም በአንድ ላይ ዝቅ ይላሉ፤
ያጐነብሳሉ፤
ጭነቱን ለማዳን አይችሉም፤
ራሳቸውም በምርኮ ይወሰዳሉ::

3“እናንት የያዕቆብ ቤት ሆይ፤
የእስራኤል ቤት ቅሬታ ሁሉ፣
ከተፀነሳችሁበት ጊዜ ጀምሮ የያዝኋችሁ፣
ከተወለዳችሁበት ጊዜ ጀምሮ የተሸከ
ምኋችሁ ስሙኝ::
4እስከ ሽምግልናችሁ፣ እስከ ሽበትም፣
የምሸከማችሁ እኔ ነኝ፤ እኔው ነኝ::
ሠርቻችኋለሁ፤ እሸከማችኋለሁ፤
እደግፋችኋለሁ፤ አድናችኋለሁ::

5“ከማን ጋር ታወዳድሩኛላችሁ? ከማንስ ጋር
እኩል ታደርጉኛላችሁ?
እንመሳሰልስ ዘንድ ከማን ጋር ታነጻጽሩ
ኛላችሁ?
6ሰዎች ወርቅ ከከረጢታቸው ይዘረግፋሉ፤
ብርንም በሚዛን ይመዝናሉ፤
አንጥረኛን ይቀጥራሉ፤ እርሱም አምላክ
አድርጎ ያበጅላቸዋል::
እነርሱም ይሰግዱለታል፤
ያመልኩታልም::
7አንሥተው በትከሻቸው ይሸከሙታል፤
እቦታው ያደርጉታል፤ በዚያም ይቆማል፤
ከዚያም ቦታ አይንቀሳቀስም፤
ማንም ወደ እርሱ ቢጮኽ አይመልስም፤
ከጭንቀቱም አያድነውም::

8“እናንት በደለኞች፣ ይህን አስታውሱ፤
አስቡበትም፤
በልባችሁም ያዙት::
9የጥንቱን፣ የቀደመውን ነገር አስታውሱ፤
እኔ አምላክ ነኝ፤ ከእኔም በቀር ሌላ የለም፤
እኔ አምላክ ነኝ፤ እንደ እኔ ያለ የለም::
10የመጨረሻውን ከመጀመሪያው፣
ገና የሚመጣውንም ከጥንቱ ተናግሬአለሁ፤
‘ዐላማዬ የጸና ነው፤
ደስ የሚያሰኘኝንም ሁሉ አደርጋለሁ’
እላለሁ::
11ከምሥራቅ ነጣቂ አሞራ፣
ከሩቅ ምድር ዐላማዬን የሚፈጽም ሰው
እጠራለሁ::
የተናገርሁትን አደርጋለሁ፤
ያቀድሁትን እፈጽማለሁ::
12እናንት እልኸኞች፣
ከጽድቅም የራቃችሁ ስሙኝ::
13ጽድቄን እያመጣሁ ነው፤
ሩቅም አይደለም፤
ማዳኔም አይዘገይም::
ለጽዮን ድነትን፣
ለእስራኤል ክብሬን አጐናጽፋለሁ::

## የባቢሎን ውድቀት

47 “አንቺ የባቢሎን[ጸ] ድንግል ልጅ
ሆይ፤
ውረጂ፤ በትቢያ ላይ ተቀመጪ፤
አንቺ የባቢሎናውያን ልጅ ሆይ፤
ከዙፋንሽ ውረጂ፤ መሬት ላይ ተቀመጪ፤
ከእንግዲህ ውብ ወይም ለግላጋ፣
ተብለሽ አትጠሪም::
2ወፍጮ ወስደሽ እህል ፍጪ፤
መሸፋፈኛሽን አውልቂ፤
ቀሚስሽንም ከፍ ከፍ አድርጊ፤ ባትሽን
ግለጪ፤
እየተንገዳገድሽ ወንዙን ተሻገሪ::
3ዕርቃንሽ ይገለጥ፤
ኀፍረትሽ ይታይ፤
እበቀላለሁ፤
እኔ ማንንም አልተውም::

4የሚቤዠን የእስራኤል ቅዱስ፣
ስሙ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው::
5“አንቺ የባቢሎናውያን ልጅ ሆይ፤
ወደ ጨለማ ግቢ፤ ዝም ብለሽም ተቀመጪ፤
ከእንግዲህ የመንግሥታት እመቤት፣
ተብለሽ አትጠሪም::
6ሕዝቤን ተቈጥቼ ነበር፤
ርስቴን አርክሼው ነበር፤
አሳልፌ በእጅሽ ሰጠኋቸው፤
አንቺ ግን አልራራሽላቸውም፤
በዕድሜ በገፉት ላይ እንኳ፣
እጅግ ከባድ ቀንበር ጫንሽባቸው::
7አንቺም፣ ‘እስከ መጨረሻው፣
ለዘላለም ንግሥት እሆናለሁ!’ አልሽ፤
ሆኖም እነዚህን ነገሮች አላስተዋልሽም፤
ፍጻሜያቸው ምን እንደሚሆንም አላ
ሰብሽም::

8“አሁንም አንቺ ቅምጥል ፍጡር፣
በራስሽ ተማምነሽ የምትቀመጪ፣
በልብሽም፣
‘እኔ ነኝ፣ ከእኔ በቀር ሌላ የለም፤
ከእንግዲህ መበለት አልሆንም፤
የወላድ መካንም አልሆንም’ የምትይ ስሚ!

46፥1 ቆላ7፤ 1ሳሙ5፥2፤ኢሳ21፥9፤ 45፥20፤ኤር50፥2፤ 51፥44
46፥2 መሳ18፥17-18፤ ሳሙ5፥21፤ ኤር51፥47
46፥3 ቆላ12፤ ዘዳ1፥31፤መዝ22፥10፤ 28፥9፤139፥13፤ ኢሳ1፥9፤44፥2፤ 48፥12፤51፥1
46፥4 ዘዳ32፥39፤ መዝ18፥35፤71፥18፤1 19፥117፤ኢሳ43፥13
46፥5 ዘፀ15፥11፤ ኢዮ41፥10፤ኢሳ40፥18፡ 25፤ኤር49፥19
46፥6 ዘፀ20፥5፤ ኢሳ40፥19፤44፥17፤ ሆሴ13፥2
46፥7 ቆላ1፤ 1ሳሙ5፥3፤1ነገ18፥26፤ ኢሳ41፥7፤44፥17፤ 47፥13
46፥8 ኢሳ1፥2፤ 44፥21፤
46፥9 ዘፀ8፥10፤ ዘዳ32፥7፤ኢሳ41፥22፤ 45፥21፤ማር12፥32
46፥10 ምሳ19፥21፤ ኢሳ7፥7፡9፤41፥4፡22፤ 44፥26፤45፥21፤ ሐሥ5፥39፤ኤፌ1፥11
46፥11 ዘፍ41፥25፤ መሳ4፥10፤ዕዝ1፥2፤ ኢሳ8፥8፤25፥1፤ ኤር44፥28
46፥12 ቆላ3፤ ዘፀ32፥9፤ መዝ119፥150፤ ኢሳ9፥9፤48፥1፤ ኤር2፥5
46፥13 መዝ74፥2፤ 85፥9፤ኢሳ1፥26፤ 44፥23፤45፥8፤ ኢል2፥32፤ሮሜ3፥21
47፥1 ዘዳ28፥56፤ ኢዮ2፥13፤መዝ137፥8፤ ኢሳ21፥9፤23፥12፤ 29፥4፤ኤር50፥42፤ 51፥33፤ዘካ2፥7
47፥2 ዘፍ24፥65፤ ዘፀ11፥5፤መሳ16፥21፤ ኢሳ32፥11፤ማቴ24፥41
47፥3 ዘፍ2፥25፤ ኢሳ1፥24፤13፥18-19፤ 20፥4፤34፥8፤ ሕዝ16፥37፤ናሆ3፥5
47፥4 ኢዮ19፥25፤ ኢሳ1፥4፤13፥4፤48፥2፤ ኤር50፥34፤አሞ4፥13
47፥5 ቆላ7፤ ኢዮ2፥13፤ኢሳ9፥2፤ 13፥10፡19፤21፥9፤ ሰቆ1፥1፤ራእ17፥18፤ 18፥7
47፥6 ዘዳ13፥15፤ 2ዜና28፥9፤ኢሳ10፥13፤ 14፥6፤42፥24፤ ኤር2፥7፤50፥11
47፥7 ቆላ5፤ ዘዳ32፥29፤ኢሳ10፥13፤ 42፥23፡25፤ዳን4፥30፤ራእ18፥7
47፥8 ኢሳ32፥9፤45፥6፤ 49፥21፤54፥4፤ሰቆ1፥1፤ራእ18፥7

[ጸ]1 ወይም *አውሬና አጋሰስ ብቻ ናቸው*
[ጸ]1 ወይም በዚህና በቍ5 ላይ *ከለዳውያን*

9እነዚህ ሁለት ነገሮች፣
መበለትነትና የወላድ መካንነት፣
አንድ ቀን ድንገት ይመጡብሻል፤
የቱን ያህል አስማት፣
የቱንም ያህል መተት ቢኖርሽ፣
በሙሉ ኀይላቸው ይመጡብሻል።
10በክፋትሽ ተማምነሽ፣
‘ማንም አያየኝም’ አልሽ፤
ደግሞም፣ ‘እኔ ነኝ፣ ከእኔ በቀር ሌላ የለም’
ባልሽ ጊዜ፣
ጥበብሽና ዕውቀትሽ አሳሳቱሽ።
11ጥፋት ይመጣብሻል፤
ነገር ግን በአስማትሽ እንዴት እንደም
ታርቂው አታውቂም፤
ወጀ ከፍለሽ ለማስወገድ የማትችዪው፣
ጒዳት ይወድቅብሻል፤
ያላሰብሽው አደጋ፣
ድንገት ይደርስብሻል።

12በይ እንግዲህ፣ “ከልጅነትሽ ጀምሮ
የደከምሽባቸውን፣
አስማቶችሽን፣
ብዙ መተቶችን ቀጥዪባቸው፤
ምናልባት ይሳካልሽ፤
ምናልባትም ጠላቶችሽን ታሸብሪባቸው
ይሆናል።
13የተቀበልሽው ምክር ሁሉ ድካም ብቻ
ሆኖ አስቀርቶሻል፤
እነዚያ ከወር እስከ ወር ከዋክብትን
አንጋጦ በማየት የሚተነብዩ፣
ኮከብ ቈጣሪዎች እስቲ ይምጡ፤
ከሚደርስብሽም ነገር እስቲ ያድኑሽ።
14እነሆ፣ እነርሱ ገለባ ናቸው፤
እሳት ይበላቸዋል፤ ከነበልባሉ ወላፈን
የተነሣ፣
ራሳቸውን ማዳን አይችሉም።
ሰው የሚሞቀው ፍም አይኖርም፤
ተቀምጠው የሚሞቁትም እሳት የለም።
15ከልጅነት ጀምሮ አብረሻቸው
የደከምሽው፣
አብረሽ የተገበያየሻቸው፣
ሊያደርጉ የሚችሉት ይህንኑ ብቻ ነው።
እያንዳንዱ በስሕተቱ ይገፋበታል፤
አንቺን ግን የሚያድን የለም።

## እልከኛዪቱ እስራኤል

# 48

“የያዕቆብ ቤት ሆይ፤
እናንት በእስራኤል ስም የተጠ
ራችሁ፣
ከይሁዳ ዘር የተገኛችሁ፣
እናንት *በእግዚአብሔር* ስም የምትምሉ፣
በእውነት ወይም በጽድቅ ሳይሆን፣
የእስራኤልን አምላክ የምትጠሩ ይህን
ስሙ!
2እናንት የቅድስቲቱ ከተማ ነዋሪዎች ነን
ብላችሁ ራሳችሁን የምትጠሩ፣
በእስራኤል አምላክ የምትታመኑ፣
ስሙ የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*
የሆነው የሚለውን አድምጡ፤
3የቀደሙትን ነገሮች ከብዙ ዘመን በፊት
ተናግሬአለሁ፤
ከአፌ ወጥተዋል፤ እንዲታወቁም
አድርጌአለሁ፤
እኔም ድንገት ሠራሁ እነርሱም፤
ተፈጸሙ።
4የቱን ያህል እልኸኛ እንደ ነበርህ
ዐውቃለሁና፤
የዐንገትህ ጅማት ብረት፣
ግንባርህም ናስ ነበር።
5ስለዚህ እነዚህን ነገሮች ገና ድሮ ነገርሁህ፤
ከመፈጸማቸው በፊት አስታወቅሁህ፤
ይህም፣
‘ጣዖቶቼ ይህን አደረጉ፤
ከዕንጨት የተቀረጸው ምስልና ከብረት
የተሠራው አምላኬ ይህን ወስኖአል’
እንዳትል ነው።
6እነዚህን ነገሮች ሰምተሃል፤ ሁሉንም
ተመልከታቸው፤
ራስህ ትክክለኛነታቸውን አትመሰክ
ርምን?

“ከአሁን ጀምሮ አዳዲስ ነገሮችን፣
የተሰወሩብህን ያላወቅሃቸውን ነገሮች
እነግርሃለሁ።
7እነርሱም የተፈጠሩት አሁን እንጂ
ጥንት
አይደለም፤
ስለ እነርሱም ከዛሬ በፊት አልሰማህም።
ስለዚህ፣
‘አዎን፤ ስለ እነርሱ ዐውቃለሁ’ ማለት
አትችልም።
8አልሰማህም ወይም አላወቅህም፤
ጆሮህ ከጥንት የተከፈተ አልነበረም፤
አንተ አታላይ እንደ ነበርህ፣
ከልጅነትህ ጀምሮ ዐመፀኛ
መባልህን ዐውቄአለሁና።
9ስለ ስሜ ስል ቍጣዬን አዘገያለሁ፤
ስለ ምስጋናዬም ስል ከአንተ እገታዋለሁ፤
ይኸውም እንዳልቈርጥህ ነው።
10እነሆ፤ እንደ ብር ባይሆንም አንጥሬሃለሁ፤
በመከራ እቶን ፈትኜሃለሁ።
11ስለ ራሴ፣ ስለ ራሴ ስል አደርጋለሁ፤
ራሴን ለውርደት እንዴት አሳልፌ
እሰጣለሁ?
ክብሬን ለማንም አልሰጥም።

## እስራኤል ነጻ ሆነች

12“ያዕቆብ ሆይ፤
የጠራሁህ እስራኤል ሆይ፤ ስማኝ፤

47፥9 ቍ12፤ ዘጸ18፥10-11፤ መዝ55፥15፤73፥19፤ኢሳ4፥1፤13፥18፤ ኤር15፥8፤18፥21፤ ናሆ3፥4፤ሚል3፥5፤ 1ተሰ5፥3፤ራእ9፥21፤ 18፥8-10፥23
47፥10 2ነገ21፥16፤ ኢዮ15፥31፤መዝ52፥7፤ 62፥10፤ኢሳ5፥21፤ 29፥15፤44፥20
47፥11 መዝ55፥15፤ ኢሳ10፥3፤14፥15፤ 17፥14፤21፥9፤31፥2፤ሉቃ17፥27፤1ተሰ5፥3
47፥12 ቍ9፤ ዘፀ7፥11
47፥13 ቍ15፤ ኢሳ5፥29፤19፥3፤ 43፥13፤44፥25፤46፥7፤ 57፥10፤ኤር51፥58፤ ዕን2፥13
47፥14 ኢሳ5፥24፤ 10፥17፤30፥30፤ኤር51፥30፥32፥58
47፥15 ቍ13፤ ኢሳ44፥17፤ራእ18፥11
48፥1 ዘፍ17፥5፤ 29፥35፤ዘፀ23፥13፤ 1ሳሙ20፥42፤ 2ሳሙ14፥11፤ መዝ50፥16፤ ኢሳ19፥18፤43፥7፤ 58፥2፤59፥14፤ ኤር4፥2፤5፥2፤7፥9-10፤44፥26፤ዳን8፥12፤ ዘካ8፥3
48፥2 ነህ11፥1፤ ኢሳ1፥26፤10፥20፤ 47፥4፤ማቴ4፥5፤ ሮሜ2፥17
48፥3 ኢሳ17፥14፤ 30፥13፤40፥21፤ 41፥22፤45፥21
48፥4 ዘፀ32፥9፤ ዘዳ9፥27፤ኢሳ9፥9፤ ሕዝ3፥9፤ሐሥ7፥51
48፥5 ኢሳ40፥21፤ 42፥9፤ኤር44፥15-18
48፥6 ኢሳ41፥22፤ ሮሜ16፥25
48፥7 ዘፀ6፥7፤ ኢሳ45፥21፤65፥18
48፥8 ዘዳ9፥7፥24፤ 29፥4፤መዝ58፥3፤ ኢሳ1፥2፥3፤41፥24፤ 43፥27፤58፥1፤ ሚል2፥11፥14
48፥9 1ሳሙ12፥22፤ ነህ9፥31፤ኢዮ9፥13፤ ኢሳ30፥18፤37፥35
48፥10 ዘፀ1፥13፤ 15፥25፤1ነገ8፥51፤ ኢሳ1፥25፤ዘካ13፥9፤ ሚል3፥3፤1ጴጥ1፥7
48፥11 ዘሌ18፥21፤ ዘዳ32፥27፤1ሳሙ12፥22፤ኢሳ37፥35፤ 42፥8፤ኤር14፥7፥21፤ ሕዝ20፥9፥14፥22፥44
48፥12 ኢሳ41፥4፥8፤42፥6፤43፥1፥13፤

እኔ እኔው ነኝ፤
ፊተኛው እኔ ነኝ፤ ኋለኛውም እኔ ነኝ፡፡
13ምድርን የመሠረተች የእኔው እጅ ናት፤
ሰማያትን የዘረጋችም ቀኝ እጄ ናት፤
በምጠራቸው ጊዜ፣
ሁሉም በአንድነት ይቆማሉ፡፡

14“ሁላችሁም በአንድነት ተሰብሰቡ፤
አድምጡም፤
ከጣዖቶች አስቀድሞ እነዚህን የተናገረ
ማን ነው?
*የእግዚአብሔር* ምርጥ ወዳጅ የሆነ፣
እርሱ በባቢሎን[θ] ላይ ያቀደውን እንዲ
ፈጽም ያደርገዋል፤
ክንዱም በባቢሎናውያን ላይ ይሆናል፡፡
15እኔ፣ እኔው ራሴ ተናግሬአለሁ፤
በእርግጥ እኔ ጠርቼዋለሁ፤
አመጣዋለሁ፤
ሥራውም ይከናወንለታል፡፡

16“ወደ እኔ ቅረቡ፤ ይህን ስሙ፤

“ከመጀመሪያ ጀምሮ በስውር
አልተናገርሁም፤
ሲፈጸምም እኔ እዚያው ነበርሁ፡፡”
አሁንም ጌታ *እግዚአብሔርና* መንፈሱ
ልከውኛል፡፡
17የተቤዠህ፣ የእስራኤል ቅዱስ፣
*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“እኔ *እግዚአብሔር* አምላክህ፣
የሚበጅህ ምን እንደ ሆነ የማስተምርህ፣
መሄድ በሚገባህ መንገድ የምመራህ ነኝ፡፡
18ትእዛዜን ሰምተህ ብቻ ቢሆን ኖሮ፣
ሰላምህ እንደ ወንዝ፣
ጽድቅህም እንደ ባሕር ሞገድ በሆነ
ነበር፡፡
19ዘርህ እንደ አሸዋ፣
ልጆችህ ስፍር እንደሌለው ትቢያ በሆኑ
ነበር፤
ስማቸው አይወገድም፤
ከፊቴም አይጠፋም፡፡

20ከባቢሎን ውጡ፣
ከባቢሎናውያንም ሽሹ!
ይህን በእልልታ አስታውቁ፤ ዐውጁት፤
እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ተናገሩ፤
“*እግዚአብሔር* ባሪያውን ያዕቆብን
ተቤዥቶታል” በሉ፡፡
21በምድረ በዳ ሲመራቸው አልተጠሙም
ነበር፤
ውሃ ከዐለት አፈለቀላቸው፤
ዐለቱን ሰነጠቀ፤
ውሃውም በኀይል ፈልቆ ወጣ፡፡

22“ለክፉዎች ሰላም የላቸውም” ይላል *እግዚ
አብሔር*፡፡

46፥3፤ራእ1፥17
**48፥13** ዘፍ2፥1፤ ዘፀ
20፥11፤ኢዮ9፥8፤ ኢ
ሳ34፥16፤40፥22፤
42፥5፤45፥18፤51፥16፤65
፥17፤ዕብ1፥10-12
**48፥14** ኢሳ21፥9፤
41፥2፡22፤43፥9፤
45፥1፤46፥10-11፤
ኤር50፥45
**48፥15** መሳ4፥10፤
ኢሳ44፥4፡28-45
**48፥16** ኢሳ11፥2፤
33፥13፤41፥1፤45፥19፤
50፥5፡7፡9፤ዘካ2፥9፡11
**48፥17** ኢዮ19፥25፤
ኢሳ28፥9፤30፥11፤
47፥4፤49፥7፡10፤
54፥8፤57፥18፤58፥11፤ኤ
ር7፥13
**48፥18** መዝ147፥14፤
ኢሳ1፥26፤9፥7፤33፥21፤
42፥23፤45፥8፤54፥13፤66
፥12
**48፥19** ዘፍ12፥2፤
ኢዮ5፥25፤ኢሳ43፥5፤
44፥3፤56፥5፤61፥9፤
65፥23፤66፥22፤
ኤር35፥19
**48፥20** ዘፍ49፥10፤
ዘፀ6፥6፤ዘዳ30፥4፤
ኢሳ12፥6፤33፥24፤
49፥13፤51፥11፤
52፥9፡11፤63፥9፤
ኤር25፥22፤48፥6፤
50፥8፤ 51፥6፡45፤
ሚክ4፥10፤ዘካ2፥6-7፤
ራእ18፥4
**48፥21** ዘኍ20፥11፤
ኢሳ30፥25፤33፥16፤
35፥6
**48፥22** ኢዮ3፥26፤
ኢሳ3፥11፤57፥21
**49፥1** ዘፀ33፥12፤
ኢሳ7፥14፤9፥6፤11፥11፤
33፥13፤43፥1፤44፥2፡2
4፤46፥3፤ኤር1፥5፤
ማቴ1፥20፤ገላ1፥15
**49፥2** ዘፀ33፥22፤
ዘዳ32፥23፤ኢዮ40፥18፤
መዝ64፥3፤91፥1፤
ዘካ9፥13፤ኤፌ6፥17፤ራ
እ1፥16
**49፥3** ዘሌ10፥3፤
ኢሳ20፥3፤44፥23፤
ዘካ3፥8
**49፥4** ዘሌ26፥20፤
ኢዮ27፥2፤ኢሳ35፥4፤
45፥25፤50፥8፤53፥10፤
54፥17፤ 55፥2፤65፥23
**49፥5** ዘዳ30፥4፤
መዝ18፥1፤39፥13፤
ኢሳ11፥12፤43፥4፤
ገላ1፥15
**49፥6** ቀኍ3፤
ዘዳ30፥4፤መዝ48፥10፤
ኢሳ1፥9፤9፥2፤26፥18፤
55፥5፤ዘካ8፥22፤
ማቴ28፥19፤ሉቃ2፥32፤
ዮሐ1፥9፤11፥52፤
ሐሥ13፥47
**49፥7** ዘፍ27፥29፤
ዘዳ7፥9፤ዕዝ1፥2፤

## *የእግዚአብሔር* ባሪያ

**49** እናንት ደሴቶች ስሙኝ፤
እናንት በሩቅ ያላችሁ ሕዝቦች
ይህን አድምጡ፤
በእናቴ ማሕፀን ሳለሁ *እግዚአብሔር*
ጠራኝ፤
ከመወለዴ በፊት በስም ጠራኝ፡፡
2አፌን እንደ ተሳለ ሰይፍ አደረገው፤
በእጁ ጥላ ሰወረኝ፤
የተወለወለ ፍላጻ አደረገኝ፤
በሰገባውም ውስጥ ሸሸገኝ፡፡
3እርሱም፣ “እስራኤል፤ አንተ ባሪያዬ ነህ፤
በአንተ ክብሬን እገልጣለሁ” አለኝ፡፡
4እኔ ግን፣ “ዐላማ ሳይኖረኝ እንዲሁ ደከምሁ፤
ምንም ጥቅም ለሌለውና ለከንቱ ነገር
ጕልበቴን ጨረስሁ፤
ሆኖም ግን ብድራቴ *በእግዚአብሔር* እጅ፣
ዋጋዬም በአምላኬ ዘንድ ነው” አልሁ፡፡

5*በእግዚአብሔር* ዐይን ፊት ከብሬአለሁ፤

አምላኬ ጕልበት ሆኖልኛል፤
ባሪያው እንድሆን ከማሕፀን የሠራኝ፣
ያዕቆብን ወደ እርሱ እንድመልስ፣
እስራኤልን ወደ እርሱ እንድሰበስብ
ያደረገኝ፣
*እግዚአብሔር* አሁንም እንዲህ ይላል፤

6እርሱም፣
“ባሪያዬ መሆንህ፣
የያዕቆብን ነገዶች እንደ ገና መመለስህ፣
የጠበቅኋቸውን እስራኤል መልሰህ
ማምጣት
ለአንተ ቀላል ነገር ነው፤
ድነቴን እስከ ምድር ዳርቻ እንድታመጣ፣
ለአሕዛብ ብርሃን አደርግሃለሁ” አለኝ፡፡

7*እግዚአብሔር*፣
ታዳጊ የሆነው የእስራኤል ቅዱስ፣
ለተናቀውና በሕዝብ ለተጠላው፣
የገዦች አገልጋይ እንዲህ ይላል፤
“ነገሥታት አይተውህ ይነሣሉ፤
ልዑላንም አይተው፤ ይሰግዳሉ፤
ምክንያቱም የመረጠህ የእስራኤል ቅዱስ፣
*እግዚአብሔር* ታማኝ ነው፡፡”

## የእስራኤል እንደ ገና መቋቋም

8*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

“በወደድሁ ጊዜ እመልስልሃለሁ፤
በድነትም ቀን እረዳሃለሁ፡፡

መዝ22፥6፡29፤ 69፥7-9፤86፥9፤ኢሳ14፥1፤48፥17፤ 52፥15፤1ቆሮ1፥9
**49፥8** ዘሌ25፥10፤ ዘኍ34፥13፤መዝ37፥9፤ 69፥13፤ ኢ
ሳ5፥2፤26፥3፤ 41፥10፤42፥6፤44፥26፤58፥12፤60፥10፡21፤ 61፥2፡4፤ሕ
ዝ36፥10፡33፤አሞ9፥11፡14፤2ቆሮ6፥2

θ14 በዚህና በቍ 14 ላይ ወይም፣ *ከለዳውያን*

ለሕዝቡ ቃል ኪዳን እንድትሆን፣
ምድሪቱን እንደ ገና እንድትሠራት፣
ጠፍ የሆኑትን ርስቶች ለየባለቤታቸው
እንድትመልስ፣
እጠብቅሃለሁ፤ እሠራሃለሁም፤
[9]የተማረኩትን፣ ‘ኑ ውጡ’
በጨለማ ያሉትን፣ ‘ነጻ ሁኑ’ እንድትል
አድርጌሃለሁ።

“በየመንገዱ ዳር ይመገባሉ፤
በተራቈተውም ኰረብታ ሁሉ ላይ
መሰማሪያ ያገኛሉ።
[10]አይራቡም፤ አይጠሙም፤
የምድረ በዳ ትኵሳት ወይም የፀሓይ ቃጠሎ
አይጐዳቸውም።
የሚራራላቸው ይመራቸዋል፤
በውሃ ምንጭ ዳርም ያሰማራቸዋል።
[11]ተራሮቼን ሁሉ መንገድ አደርጋለሁ፤
ጐዳናዎቼም ከፍ ይላሉ።
[12]እነሆ፤ ከሩቅ አገር ይመጣሉ፤
አንዳንዶች ከሰሜን ሌሎች ከምዕራብ፣
የቀሩት ደግሞ ከሲኒም[ፊ] ይመጣሉ።

[13]ሰማያት ሆይ፤ እልል በሉ፤
ምድር ሆይ፤ ደስ ይበልሽ፤
ተራሮች ሆይ፤ በደስታ ዘምሩ፤
እግዚአብሔር ሕዝቡን ያጽናናል፤
ለተቸገሩትም ይራራልና።

[14]ጽዮን ግን፣ “እግዚአብሔር ትቶኛል፤
ጌታም ረስቶኛል” አለች።

[15]“እናት የምታጠባውን ልጇን ልትረሳ
ትችላለችን?
ለወለደችውስ ልጅ አትራራለትምን?
ምናልባት እርሷ ትረሳ ይሆናል፣
እኔ ግን እልረሳሽም።
[16]እነሆ፤ በእጄ መዳፍ ላይ ቀርጬሻለሁ፤
ቅጥሮችሽ ምንጊዜም በፊቴ ናቸው።
[17]ወንዶች ልጆችሽ ፈጥነው ይመለሳሉ፤
ያፈራረሱሽም ከአንቺ ይሸሻሉ።
[18]ዐይንሽን ቀና አድርጊ፤ ዙሪያውንም ተመ
ልከቺ፤
ወንዶች ልጆችሽ ሁሉ ተሰብስበው ወደ
አንቺ ይመጣሉ።
“በሕያውነቴ እምላለሁ፤
እነዚህን ሁሉ እንደ ጌጥ ትለብሻቸዋለሽ፤
እንደ ሙሽራም ትጐናጸፊያቸዋለሽ”
ይላል እግዚአብሔር።
[19]“ፈራርሰሽ ባድማ ብትሆኚ፣
ምድርሽ ፈጽሞ ቢጠፋ፣
ዛሬ ለሕዝብሽ ጠባብ ብትሆኚም እንኳ፣
የዋጡሽ ከአንቺ ይርቃሉ።
[20]በሐዘንሽ ዘመን የወለድሻቸው ልጆች፣
ጆሮሽ እየሰማ፣
‘ይህ ቦታ በጣም ጠቦናል፤
የምንኖርበት በቂ ስፍራ ስጪን’
ይሉሻል።
[21]በልብሽም እንዲህ ትያለሽ፣
‘እነዚህን የወለደልኝ ማን ነው?
እኔ ሐዘንተኛና መካን፣
የተሰደድሁና የተጠላሁ ነበርሁ፤
እነዚህን ማን አሳደጋቸው?
ብቻዬን ቀርቼ ነበር፤
ታዲያ፣ እነዚህ ከየት መጡ?’

[22]ልዑል እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤

“እነሆ፤ አሕዛብን በጥቅሻ እጣራለሁ፤
ዐርማዬንም ለሕዝቦች ከፍ አደርጋለሁ፤
ወንዶች ልጆችሽን በዕቅፋቸው
ያመጡልሻል፤
ሴቶች ልጆችሽንም በትከሻቸው
ይሸከሙልሻል።
[23]ነገሥታት አሳዳጊ አባቶችሽ፣
እቴጌዎቻቸው ሞግዚቶችሽ ይሆናሉ፤
በግንባራቸው ተደፍተው ይሰግዱልሻል፤
የእግርሽን ትቢያ ይልሳሉ፤
አንቺም እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ
ታውቂያለሽ፤
እኔን ተስፋ የሚያደርጉም አያፍሩም።”

[24]ከተዋጊ ብዝበዛ ማስጣል፣
ከጨካኝስ[T] ምርኮኞችን ማዳን ይቻላልን?

[25]እግዚአብሔር ግን እንዲህ ይላል፤
“ከተዋጊዎች ላይ ምርኮኞች በእርግጥ
ይወሰዳሉ፤
ከጨካኞችም ላይ ምርኮ ይበዘበዛል፤
ከአንቺ ጋር የሚጣሉትን እጣላቸዋለሁ፤
ልጆችሽንም እታደጋለሁ።
[26]አስጨናቂዎችሽ የራሳቸውን ሥጋ እንዲ
በሉ
አደርጋቸዋለሁ፤
በወይን ጠጅ እንደሚሰከር ሁሉ፣ በገዛ
ደማቸው ይሰክራሉ።
ከዚያም የሰው ዘር ሁሉ፣
እኔ እግዚአብሔር አዳኝሽ፣
ታዳጊሽም የያዕቆብ ኀያል እንደ ሆንሁ
ያውቃል።”

## የእስራኤል ኀጢአትና የእግዚአብሔር ባሪያ ታዛዥነት

**50** እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“እናታችሁን የፈታሁበት

49፥9 መዝ107፥10፤ ኢሳ41፥18፤42፥7፤ 61፥1፤ሉቃ4፥19
49፥10 መዝ48፥14፤ 121፥6፤ኢሳ14፥1፤ 33፥16፡21፤35፥7፤ 42፥16፤48፥17፤ ራእ7፥16
49፥11 ኢሳ11፥16፤ 40፥4፤ኤር31፥9
49፥12 ኢሳ2፥3፤ 11፥11፤43፥5-6፤ 59፥19፤ማቴ8፥11
49፥13 መዝ9፥12፤ 65፥12-13፤71፥21፤ 96፥11፤98፥4፤ ኢሳ14፥1፤40፥1፤ 44፥23፤48፥20፤ 2ቆሮ1፥4
49፥14 መዝ9፥10፤ 71፥11፤ኢሳ27፥8፤ 40፥9
49፥15 1ነገ3፥26፤ ኢሳ44፥21፤66፥13
49፥16 ዘፍ38፥18፤ ዘፀ28፥9፤መዝ48፥12-13፤ኢሳ62፥6
49፥17 ኢሳ5፥6፤ 10፥6፤37፥18
49፥18 ዘኍ14፥21፤ ኢሳ11፥12፤14፥1፤ 43፥5፤45፥23፤51፥3፤ 52፥1፤54፥7፡9፤61፥10፤ 62፥8፤ኤር2፥32፤ ሮሜ14፥11
49፥19 ዘሌ26፥33፤ ኢሳ1፥20፤5፥6፤54፥1፡ 3፤60፥18፤62፥4፤ ሕዝ36፥10-11፤ ዘካ10፥10
49፥20 ኢሳ54፥1-3፤ ዘካ2፥4፤10፥10
49፥21 መዝ142፥4፤ ኢሳ1፥8፤5፥13፤ 29፥23፤47፥8፤51፥18፤ 54፥1፡6፤60፥8፤ 66፥7-8፤ኤር10፥20
49፥22 ዘፍ15፥2፤ ኢሳ11፥10፡12፤14፥2፤ ሉቃ15፥5
49፥23 ዘፍ3፥14፤ 27፥29፤ዘፀ6፥2፤ ዘኍ11፥12፤ መዝ22፥5፡23፤37፥9፤72፥9፤130፥5፤ ኢሳ29፥22፤41፥11፤ 42፥8፤60፥3፡10-11፡ 16፤ራእ3፥9
49፥24 ማቴ12፥29፤ ማር3፥27፤ሉቃ11፥21
49፥25 1ሳሙ24፥15፤ ኢሳ13፥11፤14፥2፤ 25፥4፡5፡9፤33፥22፤ 35፥4፤43፥26፤51፥22፤ ኤር50፥33-34፤ ማር3፥27
49፥26 ዘፍ49፥24፤ ዘፀ6፥7፤ዘኍ23፥24፤ ኢዮ19፥25፤መዝ132፥2፤ ኢሳ9፥4፡20፤11፥9፤ 13፥11፤25፥9፤48፥17፤ ኤር25፥27፤ሕዝ39፥7፤ ናሆ1፥10፤3፥11፤
ራእ16፥6 50፥1 ዘዳ24፥1፤ 32፥30፤መሳ3፥8፤ ነህ5፥5፤ኢሳ1፥28፤ ሆሴ2፥2፤ማቴ18፥25፤ 19፥7፤ማር10፥4

[ፊ]12 የማሶሬቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማል፣ የሙት ባሕር ጥቅሎች ግን፣ *አስዋን* ይላሉ።
[T]24 የሙት ባሕር ጥቅሎች፣ ቩልጌትና የሱርስቱ ቅጅ (እንዲሁም የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ቍ 25 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ የማሶሬቱ ቅጅ ግን፣ *ከጻድቅስ* ይላል።

የፍቺ ወረቀት የት አለ?
ወይስ እናንተን የሸጥኋችሁ
ለየትኛው አበዳሪዬ ነው?
እነሆ፤ ስለ ኀጢአታችሁ ተሸጣችኋል፤
ስለ መተላለፋችሁም እናታችሁ
ተፈታለች፡፡
2በመጣሁ ጊዜ ለምን በዚያ ሰው
አልነበረም?
በተጣራሁስ ጊዜ የሚመልስ ሰው እንዴት
በዚያ ታጣ?
ስለ እናንተ ወጀ ለመክፈል ክንዴ አጥራ
ነበርን?
እናንተንስ ለማዳን ኀይል አነሰኝን?
እነሆ፤ በተግሣጼ ባሕሩን አደርቃለሁ፤
ወንዞችን ምድረ በዳ አደርጋለሁ፤
ዓሦቻቸው ውሃ በማጣት ይሸታሉ፤
በጥማትም ይሞታሉ፡፡
3ሰማይን ጨለማ አለብሰዋለሁ፤
ማቅን መሸፈኛው አደርጋለሁ፡፡
4ልዑል *እግዚአብሔር* የተባ አንደበት
ሰጥቶኛል፤
ስለዚህ ደካሞችን ብርቱ ለማድረግ ምን
ማለት እንዳለብኝ ዐውቃለሁ፤
በየማለዳው ያነቃኛል፤
በመማር ላይ እንዳለ ተማሪ ለመስማት
ጆሮዬን ያነቃዋል፡፡
5ልዑል *እግዚአብሔር* ጆሮዬን ከፍቶታል፤
እኔም ዐመፀኛ አይደለሁም፤
ወደ ኋላም አላፈገፈግሁም፡፡
6ለሚገርፉኝ ጀርባዬን፣
ጢሜን ለሚነጩ ጕንጬን ሰጠሁ፤
ፊቴን ከውርደት፣
ከጥፋትም አልሰወርሁም፡፡
7ልዑል *እግዚአብሔር* ስለሚረዳኝ
አልዋረድም፤
ስለዚህ ፊቴን እንደ ባልጩት ድንጋይ
አድርጌአለሁ፤
እንደማላፍርም ዐውቃለሁ፡፡
8ንጹሕ መሆኔን የሚያረጋግጥልኝ በአጠ
ገቤ አለ፤
ታዲያ ማን ሊከሰኝ ይችላል?
እስቲ ፊት ለፊት እንጋጠም!
ተቃዋሚዬስ ማን ነው?
እስቲ ይምጣ!
9የሚረዳኝ እርሱ ጌታ *እግዚአብሔር* ነው፤
የሚፈርድብኝስ ማን ነው?
እነሆ፤ ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ፤
ብልም ይበላቸዋል፡፡

10ከእናንተ *እግዚአብሔርን* የሚፈራ፣
የባሪያውንም ቃል የሚሰማ ማን ነው?
ያ ሰው በጨለማ የሚሄድ ከሆነና፣
ብርሃንም ከሌለው፣
*በእግዚአብሔር* ይታመን፤
በአምላኩም ይደገፍ፡፡
11አሁን ግን እናንት እሳት አንድዳችሁ፣
የራሳችሁን የሚንቦገቦግ ችቦ የያዛችሁ
ሁሉ፣
በሉ የእሳት ብርሃን ሂዱ፤
ባንቦገቦጋችሁትም የችቦ ብርሃን
ተመላለሱ፡፡
እንግዲህ ከእጄ የምትቀበሉት ይህ ነው፤
በሥቃይም ትጋደማላችሁ፡፡

**የዘላለም ድነት ለጽዮን**

# 51

“እናንት ጽድቅን የምትከታተሉ፣
*እግዚአብሔርን* የምትፈልጉ
ስሙኝ፤
ተቈርጣችሁ የወጣችሁበትን ዐለት፣
ተቈፍራችሁ የወጣችሁባትንም ጕድጓድ
ተመልከቱ፡፡
2ወደ አባታችሁ ወደ አብርሃም፣
ወደ ወለደቻችሁም ወደ ሣራ ተመልከቱ፤
በጠራሁት ጊዜ አንድ ራሱን ብቻ ነበር፤
ባረክሁት፤ አበዛሁትም፡፡
3*እግዚአብሔር* ጽዮንን በእርግጥ ያ
ጽናናታል፤
ፍርስራሾቿንም በርኅራኄ ይመለከታል፤
ምድረ በዳዋን እንደ ዔድን፣
በረሓዋንም እንደ *እግዚአብሔር* ተክል
ቦታ ያደርጋል፤
ተድላና ደስታ፣
ምስጋናና የዝማሬ ድምፅ በእርሷ ይገኛሉ፡፡
4“ወገኔ ሆይ፤ አድምጠኝ፤
ሕዝቤ ሆይ፤ ስማኝ፤
ሕግ ከእኔ ይወጣል፤
ፍርዴም ለሕዝቦች ብርሃን ይሆናል፡፡
5ጽድቄ በፍጥነት እየቀረበ፣
ማዳኔም እየደረሰ ነው፤
ክንዴም ለመንግሥታት ፍትሕን ያመጣል፤
ደሴቶች ወደ እኔ ይመለከታሉ፤
ክንዴንም በተስፋ ይጠብቃሉ፡፡
6ዐይኖቻችሁን ወደ ሰማያት አንሡ፤
ወደ ታች ወደ ምድርም ተመልከቱ፤
ሰማያት እንደ ጢስ በነው ይጠፋሉ፤
ምድር እንደ ልብስ ታረጃለች፤
ነዋሪዎቿም እንደ አሸን ፈጥነው ይረግፋሉ፤
ማዳኔ ግን ለዘላለም ይኖራል፤
ጽድቄም መጨረሻ የለውም፡፡

7“እናንት ጽድቅን የምታውቁ፣
ሕጌንም በልባችሁ ያኖራችሁ ሰዎች
ስሙኝ፤
ሰዎች ሲዘብቱባችሁ አትፍሩ፤
ሲሰድቧችሁ አትደንግጡ፡፡

50፥2 ዘፍ18፥14፤ ዘፀ14፥22፤ ዘኍ11፥23፤ 1ሳሙ8፥19፤ መዝ18፥15፤ 68፥35፤ 107፥33፤ ኢሳ41፥28፤ 59፥1፤ ኤር14፥9
50፥3 ዘፀ10፥22፤ ኢሳ5፥30፤ ራእ6፥12
50፥4 ቆላ5፤ ዘፀ4፥12፤ መዝ5፥3፤ 88፥13፤ 119፥147፤ 143፥8፤ ኢሳ28፥9፤ 40፥29፤ 61፥1፤ ማቴ11፥28
50፥5 ኢሳ35፥5፤ 48፥16፤ ሕዝ2፥8፤ 24፥3፤ ማቴ26፥39፤ ዮሐ8፥29፤ 14፥31፤ 15፥10፤ ሐሥ26፥19፤ ዕብ5፥8
50፥6 ዘኍ12፥14፤ 2ሳሙ10፥14፤ ኢሳ53፥5፤ ሰቆ3፥30፤ ማቴ26፥67፤ 27፥30፤ ማር10፥34፤ 14፥65፤ 15፥19፤ ሉቃ22፥63፤ ዮሐ19፥1
50፥7 ኢሳ28፥16፤ 29፥22፤ 41፥10፤ 42፥1፤ 48፥16፤ ኤር1፥18፤ 15፥20፤ ሕዝ3፥8-9
50፥8 ኢዮ13፥19፤ መዝ34፥18፤ ኢሳ26፥2፤ 41፥1፤ 43፥26፤ 49፥4፤ ሮሜ8፥32-34
50፥9 ኢዩ13፥28፤ ኢሳ41፥10፤ 48፥16፤ 51፥8፤ ሮሜ8፥1፡34
50፥10 መዝ107፥14፤ ምሳ1፥7፤ ኢሳ1፥19፤ 10፥20፤ 26፥4፤ 49፥3፤ ሐጌ1፥12፤ ሐሥ26፥18
50፥11 ዘዳ21፥22-23፤ ኢዮ15፥20፤ ምሳ26፥18፡27፤ ኢሳ1፥31፤ 65፥13-15፤ ያዕ3፥6
51፥1 ቆላ7፤ ዘዳ7፥13፤ 16፥20፤ መዝ94፥15፤ ኢሳ17፥10፤ 46፥3፤ 55፥6፤ 63፥8፤ 65፥10፤ ሮሜ9፥30-31
51፥2 ዘፍ12፥2፤ 17፥6፤ ኢሳ29፥22፤ ሮሜ4፥16፤ ዕብ11፥11
51፥3 ዘፍ2፥8፤ መዝ51፥18፤ ኢሳ5፥6፤ 25፥9፤ 35፥10፤ 40፥1፤ 41፥19፤ 44፥26፤ 52፥9፤ 61፥4፤ 65፥18፤ 66፥10፤ ኤር16፥9፤ 17፥26፤ 30፥19፤ 33፥11
51፥4 ዘፀ6፥7፤ ዘዳ18፥18፤ መዝ50፥7፤ 78፥1፤ ኢሳ2፥4፤ 3፥15፤ 26፥18፤ 49፥6፤ 63፥8፤ 64፥9
51፥5 ዘፍ49፥10፤ መዝ37፥9፤ 85፥9፤ 98፥1፤ ኢሳ11፥11፤ 12፥2፤ 35፥4፤ 40፥10፤ 50፥2፤ 52፥10፤ 59፥16፤ 63፥1፡5
51፥6 ቆላ8፤ መዝ37፥20፤ 89፥33፤ 102፥25-26፤ 119፥89፤ ኢሳ12፥2፤ 54፥10፤ ማቴ24፥35፤ ሉቃ21፥33፤ ዕብ1፥10-12፤ 2ጴጥ3፥10
51፥7 ቆላ1፤ ዘዳ6፥6፤ መዝ119፥11፡39፤ ኢሳ50፥7፤ 54፥4፤ ማቴ5፥11፤ ሉቃ6፥22፤ ሐሥ5፥41

8ብል እንደ ልብስ ይበላቸዋል፤
ትል እንደ በግ ጠጕር ይውጣቸዋል፤
ጽድቄ ግን ለዘላለም፣
ማዳኔም ከትውልድ እስከ ትውልድ ጸንታ
ትኖራለች።”

9የእግዚአብሔር ክንድ ሆይ፤
ተነሥ፤ ተነሥ! ኀይልን ልበስ፤
እንዳለፉት ዘመናት፣
በጥንት ትውልዶችም እንደ ሆነው ሁሉ
ተነሥ።
ረዓብን የቈራረጥህ፣
ታላቁን ዘንዶ የወጋህ አንተ አይደለህምን?
10የዳኑት እንዲሻገሩ ባሕሩን፣
የታላቁን ጥልቅ ውሆች ያደረቅህ፣
በጥልቁም ውስጥ መንገድ ያበጀህ፣
አንተ አይደለህምን?
11እግዚአብሔር የተቤዣቸው ይመለሳሉ፤
በዝማሬ ወደ ጽዮን ይገባሉ፤
የዘላለማዊ ደስታን አክሊል ይቀዳጃሉ፤
ተድላና ደስታ ያገኛሉ፤
ሐዘንና ልቅሶም ከእነርሱ ይሸሻል።

12“የማጽናናችሁ እኔ፣ እኔው ብቻ ነኝ፤
ሟች የሆኑትን ሰዎች፣
እንደ ሣር የሚጠወልጉትን የሰው ልጆች
ለምን ትፈራለህ?
13የፈጠረህን፣
ሰማያትን የዘረጋውን፣
ምድርን የመሠረተውን እግዚአብሔርን
ረስተሃል፤
ሊያጠፋህ ከተዘጋጀው፣
ከጨቋኙ ቍጣ የተነሣ፣
በየቀኑ በሽብር ትኖራለህ፤
ታዲያ የጨቋኙ ቍጣ የት አለ?
14 ዐንገታቸውን የደፉ እስረኞች በፍጥነት
ነጻ ይወጣሉ፤
በታሰሩበትም ጕድጓድ ውስጥ አይሞቱም፤
እንጀራ አያጡም።
15ሞገዱ እንዲተም ባሕሩን የማናውጥ፣
እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝና፤
ስሙም የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው።
16ቃሌን በአፍህ አኖርሁ፤
በእጄ ጥላ ጋረድሁህ፤
ሰማያትን በስፍራቸው ያስቀመጥሁ፣
ምድርን የመሠረትሁ፣
ጽዮንንም፣ ‘አንቺ ሕዝቤ ነሽ’ ያልሁ እኔ
ነኝ።

## የእግዚአብሔር የቍጣ ጽዋ

17ከእግዚአብሔር እጅ፣
የቍጣውን ጽዋ የጠጣሽ፣
ዝቃጩ እንኳ ሳይቀር፣
ሰዎችን የሚያንገደግደውን ዋንጫ የጨ

51፥8 ቍ6፤ ኢዮ13፥28፤ ኢሳ14፥11፤ያዕ5፥2
51፥9 ዘፍ18፥14፤ ዘፀ6፥6፤ዘዳ4፥34፤ 32፥7፤መሳ5፥12፤ ኢዮ9፥13፤መዝ65፥6፤ 68፥30፤74፥13፤98፥1፤ኢሳ30፥30፤33፥2፤ 40፥31፤52፥1
51፥10 ዘፀ14፥22፤ 15፥5፡8፡13፤ኢዮ36፥30፤ ዘካ10፥11፤ራእ16፥12
51፥11 መዝ109፥28፤ ኢሳ30፥19፤35፥9፤ 44፥23፤48፥20፤ 65፥14፤ኤር30፥19፤ 31፥13፤33፥11፤ ሶፎ3፥14፤ራእ7፥17
51፥12 2ነገ1፥15፤ ኢሳ2፥22፤15፥6፤ 40፥1፡6-7፤2ቆሮ1፥4፤ 1ጴጥ1፥24
51፥13 ዘፍ1፥1፤ ኢዮ4፥17፤8፥13፤ ኢሳ7፥4፤9፥4፤17፥7፡ 10፤45፥11፤48፥13፤ 54፥5
51፥14 ኢሳ42፥7፤ 49፥10
51፥15 ዘፀ14፥21፤ መዝ93፥3፤ ኢሳ13፥4
51፥16 ዘፀ4፥12፡15፤ 33፥22፤ኢሳ48፥13፤ ኤር7፥23፤ 11፥4፤ 24፥7፤ሕዝ14፥11፤ ዘካ8፥8
51፥17 ቍ20፡22፡ 23፤መሳ5፥12፤ ኢዮ21፥20፤መዝ16፥5፤ 60፥3፤75፥8፤ ኢሳ42፥25፤52፥1፤ 66፥15፤ማቴ20፥22፤ ራእ14፥10፤16፥19
51፥18 ኢዮ31፥18፤ መዝ88፥18፤ ኢሳ41፥13፤49፥21
51፥19 ኢሳ14፥30፤ 40፥2፤47፥9፤49፥13፤ 54፥11፤60፥18፤62፥4፤ ኤር14፥12፤15፥5፤ 24፥10፤48፥3፤ ሰቆ3፥47፤ናሆ3፥7
51፥20 ቍ17፤ ዘዳ28፥20፤ ኢዮ18፥10፤40፥11፤ ኢሳ5፥25፤ኤር14፥16፤ 44፥6፤ሰቆ2፥19
51፥21 ቍ17፤ ኢሳ14፥32፤29፥9
51፥22 ቍ17፤ ኢሳ49፥25፤ኤር25፥15፤ 51፥7፤ዕን2፥16፤ ማቴ20፥22
51፥23 ቍ17፤ ኢሱ10፥24፤ መዝ66፥12፤ኢሳ14፥4፤ 49፥26፤ኤር25፥15-17፡ 26፡28፤49፥12፤ ሚክ7፥10፤ዘካ12፥2
52፥1 ዘፍ34፥14፤ ዘፀ28፥2፡40፤

ለጥሽ፣
ኢየሩሳሌም ሆይ፤ ተነሺ፤
ተነሺ፤ ተነሺ።
18ከወለደቻቸው ወንዶች ልጆች ሁሉ፣
የመራት አንድም አልነበረም፤
ካሳደገቻቸው ወንዶች ልጆች ሁሉ፣
እጇን ይዞ የወሰዳት ማንም አልነበረም።
19እነሆ፤ በጥፋት ላይ ጥፋት መጥተውብሻል፤
ታዲያ ማን ያጽናናሻል?
እነርሱም መፈራረስና ጥፋት፣ ራብና ሰይፍ
ናቸው፤
ታዲያ ማን ያስተዛዝንሽ?[ሀ]
20ወንዶች ልጆችሽ ዝለዋል፤
በወጥመድ እንደ ተያዘ ሚዳቋ፣
በየጐዳናው አደባባይ ላይ ተኝተዋል።
የእግዚአብሔር ቍጣ፣
የአምላክሽም ተግሣጽ ሞልቶባቸዋል።

21ስለዚህ አንቺ የተጐዳሽ፣
ያለ ወይን ጠጅ የሰከርሽ ይህን ስሚ።
22ሕዝቡን የሚታደግ አምላክሽ፣
ልዑል እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“እነሆ፤ ከእጅሽ፣
ያንገደገደሽን ጽዋ ወስጃለሁ፤
ያንን ጽዋ፣ የቍጣዬን ዋንጫ፣
ዳግም አትጠጪውም፤
23ባስጨነቁሽ፣
‘በላይሽ ላይ እንድንሄድ ተነጠፊልን’
ባሉሽ እጅ ላይ አደርገዋለሁ፤
ጀርባሽን እንደ መሬት፣
እንደ መሸጋገሪያም መንገድ አደረግሽ
ላቸው።”

# 52

ጽዮን ሆይ፤ ተነሺ፤ ተነሺ፤
ኀይልን ልበሺ፤
ቅድስቲቱ ከተማ፤ ኢየሩሳሌም ሆይ!
የክብር ልብስሽን ልበሺ፤
ያልተገረዘ የረከሰም
ከእንግዲህ ወደ አንቺ አይገባም።
2ትቢያሽን አራግፊ፤
ኢየሩሳሌም ሆይ፤ ተነሺ በዙፋንሽ ላይ
ተቀመጪ፤
ምርኮኛዪቱ የጽዮን ልጅ ሆይ፤
የዐንገትሽን የእስራት ሰንሰለት አውልቀሽ
ጣዪ።

3እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“ያለ ዋጋ ተሸጣችሁ ነበር፤

1ሳሙ2፥4፤ነህ11፥1፤አስ6፥8፤መዝ110፥3፤ኢሳ1፥26፤35፥8፤ 49፥18፤51፥9፡17፤ 61፥10፤ኢል3፥17፤ ናሆ1፥15፤ዘካ3፥4፤ 9፥8፤ ማቴ4፥5፤ ራእ21፥2፡27 52፥2 መዝ9፥14፤ 81፥6፤ኢሳ10፥27፤ 29፥4፤60፥1 52፥3 መዝ44፥12፤ኢሳ1፥27፤45፥13፤ 1ጴጥ1፥18

[ሀ]19 የሙት ባሕር ጥቅሎች፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም፣ የቩልጌትና የሱርስቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ የማሶሬቱ ቅጅ ግን፣ ታዲያ እንዴት አስተዛዝንሻለሁ ይላል።

ያለ ገንዘብ ትቤዣላችሁ።”

4ልዑል እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“በመጀመሪያ ሕዝቤ ይኖር ዘንድ ወደ ግብፅ ወረደ፤
በኋላም አሦር ያለ ምክንያት አስጨንቆ ገዛው።

5“አሁን እዚህ ምን አለኝ?” ይላል እግዚአብሔር፤

“ሕዝቤ ያለ ምክንያት ተወስዶአል፤
የገዧቸው ተሣልቀውባቸዋል”[ለ]
ይላል እግዚአብሔር።

“ቀኑን ሙሉ፣
ስሜ ያለ ማቋረጥ ይሰደባል።
6ስለዚህ ሕዝቤ ስሜን ያውቃል፤
በዚያ ቀንም፣
አስቀድሜ የተናገርሁ እኔ መሆኔን ይረዳል፤
እነሆ፤ እኔው ነኝ።”

7በተራሮች ላይ የቆሙ፣
የምሥራች ይዘው የሚመጡ እግሮች፣
ሰላምን የሚናገሩ፣
መልካም ዜና የሚያበስሩ፣
ድነትን የሚያውጁ፣
ጽዮንንም፣
“አምላክሽ ነግሦአል” የሚሉ እንዴት ያማሩ ናቸው።
8ስሚ፤ ጠባቂዎችሽ ድምፃቸውን ከፍ አድርገዋል፤
በአንድነት በእልልታ ይዘምራሉ።
እግዚአብሔር ወደ ጽዮን ሲመለስ፣
በዐይኖቻቸው ያያሉ።
9እናንት የኢየሩሳሌም ፍርስራሾች፣
በአንድነት በእልልታ ዘምሩ፤
እግዚአብሔር ሕዝቡን አጽናንቶአል፤
ኢየሩሳሌምንም ተቤዥቶአልና።
10እግዚአብሔር በመንግሥታት ሁሉ ፊት፣
የተቀደሰ ክንዱን ይገልጣል፤
በምድር ዳርቻዎች ያሉ ሁሉ፣
የአምላካችንን ማዳን ያያሉ።

11እናንት የእግዚአብሔርን ዕቃ የምትሸከሙ፣
ተለዩ፤ ተለዩ፤ ከዚያ ውጡ፤
ርኩስ ነገር አትንኩ፤
ከዚያ ውጡ ንጹሓንም ሁኑ።
12ሆኖም በችኰላ አትወጡም፤
ሸሽታችሁም አትሄዱም፤
እግዚአብሔር ፊት ፊታችሁ ይሄዳል፤
የእስራኤል አምላክ ደጀን ይሆናችኋል።

## የባሪያው ሥቃይና ክብር

13እነሆ፤ ባሪያዬ የሚያከናውነው
በማስተዋል ነው፤[ሐ]
ገናና ይሆናል፤ ከፍ ከፍ ይላል፤ እጅግ ይከብራልም።
14ብዙዎች በእርሱ[መ] እስኪደነግጡ ድረስ፣
መልኩ ከማንም ከሰው የተለየ፤
ከሰው ልጆችም ሁሉ ይልቅ ተጐሳቍሎ።
15ስለዚህ ብዙ መንግሥታትን ያስደንቃል፤
በእርሱ ምክንያት ነገሥታት አፋቸውን ይይዛሉ፤
ያልተነገራቸውን ያያሉ፤
ያልሰሙትን ያስተውላሉ።

# 53

የሰማነውን ነገር ማን አመነ?
የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገለጠ?
2በፊቱ እንደ ቡቃያ፣
ከደረቅም መሬት እንደ ወጣ ሥር በቀለ፤
የሚስብ ውበት ወይም ግርማ የለውም፤
እንድንወደውም የሚያደርግ መልክ አልነበረውም።
3በሰዎች የተናቀና የተጠላ፣
የሕማም ሰውና ሥቃይ ያልተለየው ነበር።
ሰዎች ፊታቸውን እንደሚያዞሩበት ዐይነት፣
የተናቀ ነበር፤ እኛም አላከበርነውም።
4በእርግጥ እርሱ ደዌያችንን ወሰደ፤
ሕመማችንንም ተሸከመ፤
እኛ ግን በእግዚአብሔር እንደ ተመታ፣
እንደ ተቀሠፈ፣ እንደ ተሠቃየም ቈጠርነው።
5ነገር ግን እርሱ ስለ መተላለፋችን ተወጋ፤
ስለ በደላችንም ደቀቀ፤
በእርሱ ላይ የወደቀው ቅጣት ለእኛ ሰላም አመጣልን፤
በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።
6እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤
እያንዳንዳችንም በየመንገዳችን ነጐድን፤
እግዚአብሔርም፣
የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ ጫነው።
7ተጨነቀ፤ ተሠቃየም፤
ነገር ግን አፉን አልከፈተም፤
እንደ ጠቦትም ለዕርድ ተነዳ፤

52፥4 ዘፍ46፥6፤ ኢሳ10፥24
52፥5 ኢሳ37፥23፤ ሮሜ2፥24
52፥6 ዘፀ6፥3፤ ኢሳ10፥20፤41፥26፤ 49፥23
52፥7 2ሳሙ18፥26፤ 1ዜና16፥31፤መዝ97፥1፤ ኢሳ40፥9፤ 42፥11፤ ናሆ1፥15፤ሉቃ2፥14፤ ሮሜ10፥15፤ 1ቆሮ15፥24-25፤ ኤፌ6፥15
52፥8 ዘኍ10፥36፤ 1ሳሙ14፥16፤ ኢሳ12፥6፤40፥9፤ 56፥10፤59፥20፤62፥6፤ ኤር6፥17፤31፥6፤ ሕዝ3፥17፤33፥7፤ ዘካ8፥3
52፥9 ዕዝ9፥9፤ መዝ74፥3፤98፥4፤ ኢሳ35፥2፤40፥1፤ 48፥20፤51፥3፤ ሉቃ2፥25
52፥10 ኢሱ4፥24፤ 2ዜና32፥8፤ መዝ44፥3፤67፥2፤ ኢሳ11፥9፤30፥30፤ 66፥18፤ሉቃ2፥30፤ 3፥6
52፥11 ዘኍ8፥6፤ 2ዜና36፥10፤ ኢሳ1፥16፤48፥20፤ 2ቆሮ6፥7፤ 2ጢሞ2፥19
52፥12 ዘፀ12፥11፤ 14፥19፤ሚክ2፥13፤ ዮሐ10፥4
52፥13 ኢሱ1፥8፤ ኢሳ4፥2፤6፥1፤20፥3፤ 57፥15፤ሐሥ3፥13፤ ፊል2፥9
52፥14 ዘሌ26፥32፤ 2ሳሙ10፥4፤ኢዮ2፥12፤ 16፥16፤18፥20
52፥15 ዘሌ14፥7፤ 16፥14-15፤ መሳ18፥19፤ መዝ107፥42፤ ኢሳ49፥7፤ሮሜ15፥21፤ ኤፌ3፥4-5
53፥1 መዝ98፥1፤ ኢሳ28፥9፤30፥30፤ ዮሐ12፥38፤ ሮሜ10፥16
53፥2 2ነገ19፥26፤ ኢዮ14፥7፤ኢሳ4፥2፤ 11፥10፤52፥14
53፥3 ቍ4፥10፤ ዘፀ1፥10፤ዘዳ31፥17፤ 1ሳሙ2፥30፤መዝ22፥6፤ 69፥29፤ኢሳ1፥15፤ ማቴ16፥21፤27፥29፤ ሉቃ18፥31-33፤ ዮሐ1፥10-11፤ዕብ5፥8
53፥4 ቍ3፤ ዘፍ12፥17፤ዘዳ5፥24፤ሩት1፥21፤ ኢዮ4፥5፤ኤር23፥5-6፤ 25፥34፤ሕዝ34፥23-24፤ ሚክ5፥2-4፤ዘካ13፥7፤ ማቴ8፥17፤ዮሐ19፥7
53፥5 ዘፀ28፥38፤ዘዳ32፥39፤2ዜና7፥14፤ መዝ22፥16፤34፥18፤39፥8፤ኢሳ1፥6፤9፥6፤50፥6፤ ማቴ27፥26፤ዮሐ3፥17፤ 19፥1፤ሮሜ4፥25፤5፥1፤1ቆሮ15፥3፤ዕብ9፥28፤ 1ጴጥ2፥24-25
53፥6 ቍ12፤ዘፀ28፥38፤1ሳሙ8፥3፤መዝ95፥10፤ ኢሳ56፥11፤57፥17፤ ሚክ3፥5፤ሮሜ4፥25፤ 1ጴጥ2፥24-25
53፥7 መዝ44፥22፤ ኢሳ49፥26፤ማቴ27፥31፤ማር14፥61፤ ዮሐ1፥29፤1ጴጥ2፥23

[ለ]5 የሙት ባሕር ጥቅሎችና ቩልጌት ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ የማሶሬቱ ቅጅ ግን፣ *ሙሾ* ይላል።
[ሐ]13 ወይም *ይበለጽጋል*
[መ]14 ዕብራይስጡ፣ *በአንተ* ይላል።

በሸላቾች ፊት ዝም እንደሚል በግ፣
አፉን አልከፈተም።
8 በማስጨነቅና[መ] በፍርድ ተወሰደ፤
ስለ ሕዝቤ ኀጢአት ተመቶ፣
ከሕያዋን ምድር እንደ ተወገደ፣
ከትውልዱ ማን አስተዋለ?
9 በአፉ ተንኰል ሳይገኝበት፣
ምንም ወንጀል ሳይሠራ፣
አሟሟቱ ከክፉዎች፣
መቃብሩም ከባለጠጎች ጋር ሆነ።

10 *መድቀቁና መሠቃየቱ ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበር፤*
*እግዚአብሔር* ነፍሱን የኀጢአት *መሥዋዕት* ቢያደርገውም እንኳ፣
ዘሩን ያያል፤ ዕድሜውም ይረዝማል፤
*የእግዚአብሔርም ፈቃድ* በእጁ ይከናወናል።
11 ከነፍሱ *ሥቃይ* በኋላ፣
የሕይወት ብርሃን[ሠ] ያያል፤ ደስም ይለዋል፤
ጻድቅ ባሪያዬ በዕውቀቱ ብዙዎቹን ያጸድቃል፤
መተላለፋቸውንም ይሸከማል።
12 ስለዚህ ድርሻውን ከታላላቆች[ረ] ጋር እሰጠዋለሁ፤
ምርኮውን ከኀያላን[ሰ] ጋር ይካፈላል፤
እስከ ሞት ድረስ ሕይወቱን አሳልፎ በመስጠቱ፣
ከክፉ አድራጊዎችም ጋር በመቈጠሩ፣
የብዙዎችን ኀጢአት ተሸከመ፤
ስለ ዐመፀኞችም ማለደ።

## የወደፊቱ የጽዮን ክብር

54 "አንቺ መካን ሴት፤
አንቺ ልጅ ወልደሽ የማታውቂ፤ ዘምሪ፤
እልል በዪ፤ በደስታ ጩኺ፤
አንቺ አምጠሽ የማታውቂ፣
ባል ካላት ሴት ይልቅ፣
የፈቷ ልጆች ይበዛሉና" ይላል እግዚአብሔር።
2 "የድንኳንሽን ቦታ አስፊ፤
የድንኳንሽን መጋረጃዎች በትልቁ ዘርጊ፤
ፈጽሞ አትቈጥቢ፤
ገመዶችሽን አርዝሚአቸው፤
ካስማዎችሽንም ቀብቅቢ።
3 ወደ ቀኝም ወደ ግራም ትስፋፊያለሽ፤
ዘሮችሽ መንግሥታትን ይወርሳሉ፤
በባድማ ከተሞቻቸውም ይኖራሉና።

4 "አይዞሽ አትፍሪ፤ ኀፍረት አይገጥምሽም፤
ውርደት ስለማይደርስብሽ አትሸማቀቂ፤
የወጣትነት ኀፍረትሽን ትረሺዋለሽ፤
የመበለትነት ስድብሽንም ከእንግዲህ አታስታውሺውም።
5 ባልሽ ፈጣሪሽ ነውና፤
ስሙም የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* ነው፤
ታዳጊሽ የእስራኤል ቅዱስ ነው፤
እርሱም የምድር ሁሉ *አምላክ* ይባላል።
6 እንደ ተናቀች የልጅነት ሚስት፣
ከልብ እንዳዘነችና እንደ ተጠላች ሚስት፣
*እግዚአብሔር* እንደ ገና ይጠራሻል"
ይላል *አምላክሽ*።
7 "ለጥቂት ጊዜ ተውሁሽ፤
ነገር ግን በታላቅ ርኅራኄ መልሼ እሰበስብሻለሁ።
8 ለጥቂት ጊዜ እጅግ ስለ ተቈጣሁ፣
ፊቴን ከአንቺ ሰወርሁ፤
ነገር ግን በዘላለማዊ ቸርነቴ፣
እራራልሻለሁ"
ይላል ታዳጊሽ *እግዚአብሔር*።

9 "ይህ ለእኔ የኖኅ ውሃ ምድርን ዳግመኛ
እንዳያጥለቀልቃት እንደማልሁበት፣
እንደ ኖኅ ዘመን ነው፤
አሁንም አንቺን ዳግም እንዳልቈጣ፣
እንዳልገሥጽሽም ምያለሁ።
10 ተራሮች ቢናወጡ፣
ኰረብቶች ከስፍራቸው ቢወገዱ እንኳ፣
ለአንቺ ያለኝ ጽኑ ፍቅር አይናወጥም፤
የገባሁትም የሰላም ቃል ኪዳን አይፈርስም"
ይላል መሓሪሽ *እግዚአብሔር*።

11 "አንቺ የተጨነቅሽ ከተማ ሆይ፤ በዐውሎ ነፋስ የተናወጥሽ፣ ያልተጽናናሽም፤
እነሆ፤ በከበሩ ድንጋዮች[ሸ] አስጊጬ እገነባሻለሁ፤
በሰንፔር ድንጋይም እመሠርትሻለሁ።
12 ጒልላትሽን በቀይ ዕንቊ፣
በሮችሽን በሚያብረቀርቁ ዕንቊዎች፣
ቅጥሮችሽንም በከበሩ ድንጋዮች እሠራለሁ።
13 ወንዶች ልጆችሽ ሁሉ *ከእግዚአብሔር* የተማሩ ይሆናሉ፤
የልጆችሽም ሰላም ታላቅ ይሆናል።

**53÷8** ቀ^12፤ መዝ39÷8፤88÷5፤ ዳን9÷26፤ማር14÷49፤ ሐሥ8÷32-33
**53÷9** ኢዮ16÷17፤ ኢሳ42÷1-3፤ ማቴ27÷38፡57-60፤ ማር15÷27፡43-46፤ ሉቃ23÷32፡50-53፤ ዮሐ19÷18፡38-41፤ 1ጴጥ2÷22፤ 1ዮሐ3÷5፤ ራእ14÷5
**53÷10** ቀ^3፡5፤ ዘፍ12÷17፤ ዘሌ5÷15፤ ኢሱ1÷8፤መዝ22÷30፤ ኢሳ46÷10፤49÷4፤ 55÷11፤ዮሐ3÷17፤ ሐሥ2÷23
**53÷11** ዘፀ28÷38፤ ኢዮ33÷30፤ኢሳ6÷7፤ 20÷3፤ዮሐ1÷29፤ 10÷14-18፤ሐሥ7÷52፤ 10÷43፤ሮሜ4÷25
**53÷12** ቀ^6፤ ዘፀ15÷9፤ መዝ119÷162፤ ኢሳ6÷1፤59÷16፤ ማቴ26÷28፡38፡39፡ 42፤27÷38፤ ማር15÷27፤ ሉቃ11÷22፤22÷37፤ 23÷32፤ሮሜ8÷34፤ ፊል2÷9፤ዕብ9÷28፤ 1ጴጥ2÷24
**54÷1** ዘፍ21÷6፤ 30÷1፤1ሳሙ2÷5፤ መዝ98÷4፤ ኢሳ49÷19፡20፤ 66÷7፤ገላ4÷27
**54÷2** ዘፍ26÷22፤ ዘፀ35÷18፤39÷40፤ ኢሳ26÷15፤49÷19-20
**54÷3** ዘፍ13÷14፤ ኢዮ12÷23፤ኢሳ14÷2፤ 48÷19፤49÷19፤ 60÷4-11
**54÷4** ዘፍ30÷23፤ መዝ25÷7፤119÷39፤ኢሳ28÷16፤29÷22፤ 41÷11፤ 47÷8፤51÷7፤ ኤር2÷2፤22÷21፤ 30÷10፤ኢል2÷21
**54÷5** መዝ95÷6፤ 149÷2፤መሓ3÷11፤ ኢሳ1÷4፤6÷3፤12÷4፤ 48÷17፤49÷7፤51÷13፤55÷5፤60÷9፤ኤር3÷14፤ 31÷32፤ሆሴ2÷7፡16
**54÷6** ቀ^6-7፤ ዘፀ20÷14፤ኢሳ1÷4፤ 49÷14-21፤50÷1-2፤ 60÷15፤62÷4፡12፤ ኤር44÷2፤ሆሴ1÷10፤ ሚል2÷15
**54÷7** ኢዮ14÷13፤ መዝ51÷1፤71÷11፤ኢሳ26÷20፤27÷8፤ 49÷18
**54÷8** ቀ^10፤ መዝ25÷6፤92÷2፤ 102÷13፤ኢሳ1÷15፤ 9÷12፤14÷1፤26÷20፤48÷17፤55÷3፤60÷10፤
**54÷14** 2ሳሙ7÷10፤

63÷7፤ሆሴ2÷19 **54÷9** ዘፍ8÷21፤ዘዳ28÷20፤መዝ13÷1፤103÷9፤ ኢሳ12÷1፤ 14÷24፤49÷18፤57÷16፤ኤር3÷5፡12፤ሕዝ39÷29፤ ሚክ7÷18 **54÷10** ቀ^8፤ዘፍ9÷16፤ ዘፀ34÷10፤ ዘኍ25÷12፤ መዝ6÷4፤46÷2፤89÷34፤ኢሳ14÷1፤ 42÷6፤51÷6፤ 55÷7፤ ዕብ12÷27፤ ራእ6÷14 **54÷11** ዘፀ24÷10፤ 1ዜና29÷2፤ኢዮ28÷6፤ ኢሳ14÷32፤28÷2፡16፤ 29÷6፤51÷19፤ራእ21÷18፡19-20 **54÷12** ራእ21÷21 **54÷13** ዘሌ26÷6፤ኢሳ28÷9፤ 48÷18፤ ሚክ4÷2፤ዮሐ6÷45፤ ዕብ8÷11

[መ] 8 ወይም፣ *በእስር*
[ሠ] 11 የሙት ባሕር ጥቅሎች (እንዲሁም የሰብዓ ሊቃናት ትርጒምን ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ የማሶሬቱ ቅጅ ግን፣ *የሕይወት ብርሃን* የሚለውን ሐረግ አይጨምርም።
[ረ] 12 ወይም፣ *ከብዙዎች ጋር*
[ሰ] 12 ወይም፣ *እጅግ ብዙ ከሆኑ ጋር*
[ሸ] 11 በዕራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጒም በትክክል አይታወቅም።

14በጽድቅ ትመሠረቻለሽ፤
የግፍ አገዛዝ ከአንቺ ይርቃል፤
የሚያስፈራሽ አይኖርም፤
ሽብር ከአንቺ ይርቃል፤
አጠገብሽም አይደርስም።
15ማንም ጥቃት ቢያደርስብሽ፣ ከእኔ አይደለም፤
ጥቃት ያደረሰብሽ ሁሉ ለአንቺ እጁን ይሰጣል።

16"እነሆ የከሰሉ ፍም እንዲቀጣጠል የሚያራግበውን፣
የጦር መሣሪያ የሚያበጀውን፣ አንጥረኛውን የፈጠርሁ እኔ ነኝ፤
ጥፋት እንዲያደርስም የፈጠርሁ እኔ ነኝ አጥፊውንም የፈጠርሁ እኔ ነኝ፤
17 በአንቺ ላይ እንዲደገን የተበጀ መሣሪያ ይከሽፋል፤
የሚከስሽንም አንደበት ሁሉ ትረቺያለሽ፤
እንግዲህ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ርስት ይህ ነው፤
ከእኔ የሚያገኙትም ጽድቃቸው ይኸው ነው፤"
ይላል እግዚአብሔር።

## ጥሪ ለተጠሙ

55 እናንት የተጠማችሁ ሁሉ ኑ፤
እናንት ገንዘብ የሌላችሁ፣
ወደ ውሆች ኑ፤
ኑና ግዙ፤ ብሉም፤
ኑና ያለ ገንዘብ፣ ያለ ዋጋ፣
የወይን ጠጅና ወተት ግዙ።
2ገንዘባችሁን እንጀራ ባልሆነ ነገር ላይ ለምን ታጠፋላችሁ?
በማያጠግብስ ነገር ላይ ለምን ጒልበታችሁን ትጨርሳላችሁ?
ስሙ፤ እኔን ስሙኝ፤ መልካም የሆነውንም ብሉ፤
ነፍሳችሁም በጥሩ ምግብ ትደሰታለች።
3ጆሮአችሁን ከፍታችሁ ወደ እኔ ቅረቡ፤
ነፍሳችሁም እንድትኖር አድምጡኝ።
ለዳዊት በገባሁት በጽኑ ፍቅሬ፣
ከእናንተም ጋር የዘላለም ኪዳን አደርጋለሁ።
4እነሆ፤ እርሱን ለሕዝቦች ምስክር፣
መሪ፣ የጦር አዝማችም አድርጌዋለሁ።
5እነሆ፤ የማታውቃቸውን መንግሥታት ትጠራለህ፤
የማያወቁህ መንግሥታት በፍጥነት ወደ አንተ ይመጣሉ፤
ምክንያቱም እግዚአብሔር አምላክህ፣
የእስራኤል ቅዱስ፣
በክብሩ ከፍ ከፍ አድርጎሃል።
6እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት፤
ቀርቦም ሳለ ጥሩት።

7ክፉ ሰው መንገዱን፣
በደለኛም ሐሳቡን ይተው።
ወደ እግዚአብሔር ይመለስ፤ እርሱም ምሕረት ያደርግለታል፤
ወደ አምላካችን ይመለስ፤ ይቅርታው ብዙ ነውና።

8"ሐሳቤ እንደ ሐሳባችሁ፣
መንገዴ እንደ መንገዳችሁ አይደለምና"
ይላል እግዚአብሔር።
9"ሰማያት ከምድር ከፍ እንደሚሉ፣
መንገዴ ከመንገዳችሁ፣
ሐሳቤም ከሐሳባችሁ እንዲሁ ከፍ ያለ ነው።
10ዝናምና በረዶ
ከሰማይ ወርዶ፣
ምድርን በማራስ፣
እንድታበቅልና እንድታፈራ
ለዘሪው ዘር፣ ለበላተኛም እንጀራ እንድትሰጥ ሳያደርግ፣
ወደ ላይ እንደማይመለስ ሁሉ፣
11ከአፌ የሚወጣውም ቃሌ፣
በከንቱ ወደ እኔ አይመለስም፤
ነገር ግን የምሻውን ያከናውናል፤
የተላከበትንም ዐላማ ይፈጽማል።
12በደስታ ትወጣላችሁ፤
በሰላምም ትሸኛላችሁ፤
ተራሮችና ኰረብቶች፣
በፊታችሁ በእልልታ ይዘምራሉ፤
የሜዳ ዛፎች ሁሉ፣
ያጨበጭባሉ።
13በእሾኽ ፈንታ የጥድ ዛፍ፣
በኵርንችት ፈንታ ባርሰነት ይበቅላል።
ይህም የእግዚአብሔር መታሰቢያ፣
ሊጠፋ የማይችል፣
የዘላለም ምልክት ይሆናል።"

## ለሌሎች የተሰጠ ድነት

56 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
"ፍትሕን ጠብቁ፤
መልካሙን አድርጉ፤
ማዳኔ በቅርብ ነው፤
ጽድቄም ፈጥኖ ይገለጣልና።
2ሰንበትን ሳያረክስ የሚያከብር፣
ክፉን ከማድረግ እጁን የሚሰበስብ፣ የሚገታ፣
እነዚህን የሚፈጽም ሰው የተባረከ ነው።"
3ወደ እግዚአብሔር የተጠጋ መጻተኛ፣

ኢሳ9፥4፤17፥14፤ 26፥2፤ኤር30፥20፤ ሶፎ3፥15፤ዘካ9፥8
**54፥15** ኢሳ41፥11-16
**54፥16** ኢሳ10፥5፤ 13፥5፤44፥12
**54፥17** መዝ17፥2፤ ኢሳ29፥8፤41፥11፤ 56፥6-8፤63፥17፤65፥8፡ 9፥13-15፤66፥14፤ ዘካ1፥20-21
**55፥1** ምሳ9፥5፤ መሓ5፥1፤ኢሳ35፥7፤ ኤር2፥13፤ሰቆ5፥4፤ ሕዝ47፥1፡12፤ ሆሴ14፥4፤ዘካ14፥8፤ ማቴ5፥6፤10፥8፤ 13፥44፤ ሉቃ6፥21፤ ዮሐ4፥14፤7፥37፤ 1ጴጥ2፥2፤ራእ3፥18፤ 21፥6፤22፥17
**55፥2** መዝ22፥26፤ መክ6፥2፤ኢሳ1፥19፤ 30፥23፤49፥4፤ ኤር12፥13፤ሆሴ4፥10፤ 8፥7፤ሚክ6፥14፤ ሐጌ1፥6
**55፥3** ዘፍ9፥16፤ ዘሌ18፥5፤መዝ78፥1፤ ኢሳ54፥8፡10፤ ዮሐ6፥27፤ ሐሥ13፥34፤ ሮሜ10፥5፤ዕብ13፥20
**55፥4** 1ሳሙ13፥14፤ 2ዜና7፥18፤ኢሳ32፥1፤ ራእ1፥5
**55፥5** ኢሳ2፥3፤ 12፥6፤44፥23፤49፥6፤5 4፥5
**55፥6** ዘዳ4፥29፤ 2ዜና15፥2፤መዝ32፥6፤ 50፥15፤ኢሳ9፥13፤ 49፥8፤65፥24፤ ኤር29፥12፤33፥3፤ ሐሥ17፥27፤ 2ቆሮ6፥1-2
**55፥7** 2ዜና6፥21፤ 7፥14፤30፥9፤ኢሳ1፥18፤ 32፥7፤40፥2፤44፥22፤ 54፥10፤59፥7፤ኤር26፥3፤ ሕዝ18፥27-28፡32
**55፥8** ኢሳ53፥6፤ ሚክ4፥12፤ፊል2፥5፤ 4፥8
**55፥9** ዘኍ23፥19፤ ኢዮ11፥8፤ መዝ103፥11፤ ኢሳ40፥13-14
**55፥10** ዘፍ47፥23፤ ዘሌ25፥19፤ኢዮ14፥9፤ መዝ67፥6፤ኢሳ30፥23፤ 2ቆሮ9፥10
**55፥11** ዘዳ32፥2፤ ምሳ19፥21፤ኢሳ40፥8፤ 44፥26፤45፥23፤ ሕዝ12፥25፤ ማቴ5፥18፤ዮሐ1፥1፤ ዕብ4፥12
**55፥12** 1ዜና16፥33፤ መዝ65፥12-13፤ 96፥12-13፤98፥4፡8፤ ኢሳ35፥2፤54፥10፡13
**56፥4** ዘፀ31፥13፤

**55፥13** ዘኍ33፥55፤ መዝ102፥12፤ኢሳ5፥6፤ 41፥19፤63፥12፤ ኤር32፥20፤33፥9 **56፥1** መዝ11፥7፤ 85፥9፤ኢሳ1፥17፤ 26፥8፤ኤር22፥3፤ 23፥6፤ዳን9፥24 **56፥2** ዘፀ20፥8፡10፤ መዝ119፥2
**56፥3** ዘፀ12፥43፤ ዘሌ21፥20፤ዘዳ23፥3፤1ነገ8፥41፤ ኢሳ11፥10፤ ኤር38፥7፤ዘካ8፥20-23፤ሐሥ8፥27

“*እግዚአብሔር በእርግጥ* ከሕዝቡ
ይለየኛል” አይበል፤
ጃንደረባም፣
“እኔ ደረቅ ዛፍ ነኝ” አይበል።

4*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“ሰንበቶቼን ለሚያከብሩ ጃንደረቦች፣

ደስ የሚያሰኘኝን ለሚመርጡ፣
ቃል ኪዳኔን፣ ለሚጠብቁ
5በቤተ መቅደሴና በቅጥሮቼ ውስጥ፣
ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች የበለጠ፣
መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ፤
ለዘላለም፣
የማይጠፋ ስም እሰጣቸዋለሁ።
6እርሱን ለማገልገል፣
ራሳቸውን *ከእግዚአብሔር* ጋር ያቈራኙ
መጻተኞች፣
*የእግዚአብሔርን* ስም በመውደድ፣
እርሱንም በማምለክ፣
ሰንበትን ሳያረክሱ የሚያከብሩትን ሁሉ፣
ቃል ኪዳኔንም የሚጠብቁትን፣
7ወደ ተቀደሰው ተራራዬ አመጣቸዋለሁ፤
በጸሎት ቤቴም ውስጥ ደስ
አሰኛቸዋለሁ።
የሚቃጠል መሥዋዕታቸውንና ሌሎች
መሥዋዕቶቻቸውን፣
በመሠዊያዬ ቢሠዉ እቀበላቸዋለሁ፤
ቤቴ፣ ለሕዝቦች ሁሉ
የጸሎት ቤት ተብሎ ይጠራልና።”
8የተበተኑትን እስራኤል የሚሰበስብ፣
ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“ከተሰበሰቡት በተጨማሪ፣

ሌሎችን እንደ ገና እሰበስባለሁ።”

**በክፉዎች ላይ የእግዚአብሔር ወቀሳ**

9እናንት የምድር አራዊት ሁሉ ኑ፤
እናንት የዱር አራዊት ሁሉ ኑና በጥርሳችሁ
ቦጫጭቁ።
10የእስራኤል ጠባቂዎች ዕውሮች ናቸው፤
ዕውቀት የላቸውም፤
ሁሉም ድምፅ የለሽ ውሾች ናቸው፤
መጮኽ አይችሉም፤
ተጋድመው ያልማሉ፤
እንቅልፋሞች ናቸው።
11እጅግ ሲበዛ ሆዳም ውሾች ናቸው፤
ጠገብሁን አያውቁም፤
የማያስተውሉ እረኞች ናቸው፤
ሁሉም በየራሳቸው መንገድ ሄዱ፤
እያንዳንዳቸውም የግል ጥቅማቸውን ፈለጉ።
12እርስ በርሳቸውም፣ “ኑና የወይን ጠጅ
እንገባበዝ፤
እስክንሰክር እንጠጣ፤
ነገም ያው እንደ ዛሬ፣

ኤር38፥7
**56፥5** ዘኍ32፥42፤
1ሳሙ15፥12፤
ኢሳ26፥1፤43፥7፤
48፥19፤55፥13፤
60፥18
**56፥6** ቀኍ2፥4፤
ዘፀ12፥43፤1ነገ8፥41፤
1ዜና22፥2፤ኢሳ60፥7፡
10፤61፥5፤ሚል1፥11
**56፥7** ኢሳ2፥2፤
19፥21፤ሕዝ20፥40፤
ማቴ21፥13፤
ማር11፥17፤
ሉቃ19፥46፤
ሮሜ12፥1፤
ፊል4፥18፤ዕብ13፥15
**56፥8** ዘዳ30፥4፤
ኢሳ1፥9፤11፥12፤
60፥3-11፤ሕዝ34፥12፤
ዮሐ10፥16
**56፥9** ኢሳ18፥6፤
ኤር12፥9፤ሕዝ34፥5፡
8፤39፥17-20
**56፥10** ኢሳ52፥8፤
62፥6፤ኤር2፥8፤6፥17፤10
፥21፤14፥13-14፤
31፥6፤ሕዝ3፥17፤
33፥7፤ናሆ3፥18
**56፥11** ኢሳ1፥3፤
53፥6፤57፥17፤
ኤር6፥13፤8፥10፤
22፥17፤23፥1፤
ሕዝ13፥19፤34፥2፤
ሆሴ4፥7-8፤ሚክ3፥11
**56፥12** ዘሌ10፥9፤
መዝ10፥6፤ምሳ23፥20፤
ኢሳ22፥13፤
ሉቃ12፥18-19
**57፥1** 2ነገ22፥20፤
መዝ12፥1፤
ኢሳ42፥25፤ሕዝ21፥3
**57፥2** ኢሳ26፥7፤
ዳን12፥13
**57፥3** ቀኍ7-8፤
ዘፀ22፥18፤ኢሳ1፥21፤
ኤር2፥20፤ሚል3፥5፤
ማቴ16፥4፤ያዕ4፥4
**57፥4** ኢሳ1፥2
**57፥5** ዘዳ12፥2፤
18፥10፤ዘሌ18፥21፤
2ነገ16፥4፤
መዝ106፥37-38፤
ኢሳ1፥29፤ሕዝ16፥20
**57፥6** 2ነገ17፥10፤
ኤር3፥9፤5፥9፡29፤
7፥18፤9፥9፤19፥13፤
44፥18፤ዕን2፥19
**57፥7** ኢሳ65፥7፤
ኤር3፥6፤13፥27፤
ሕዝ6፥3፡13፤16፥16፤
20፥27-28፡29
**57፥8** ሕዝ16፥15፡
26፡36፤23፥7፡18
**57፥9** ዘሌ18፥21፤
1ነገ11፥5፤ማሕ4፥10፤
ኢሳ8፥19፤
ሕዝ23፥16፡40
**57፥10** 1ሳሙ2፥4፤
ኢሳ47፥13፤ኤር2፥25፤
18፥12፤ሚል3፥14

ምናልባትም የተሻለ ቀን ይሆንልናል”
ይባባላሉ።

**57** ጻድቅ ይሞታል፤
ይህን ግን ማንም ልብ አይልም፤
ለእግዚአብሔር ያደሩ ሰዎች ይወሰዳሉ፤
ጻድቃን ከክፉ ይድኑ ዘንድ፣
መወሰዳቸውን፣
ማንም አያስተውልም።
2በቅንነት የሚሄዱ፣
ሰላም ይሆንላቸዋል፤
መኝታቸው ላይ ያርፋሉ።

3“እናንት የአስማተኛዪቱ ልጆች ግን፣
እናንት የአመንዝራውና የጋለሞታዪቱ
ዘር፤ እናንት፣ ወዲህ ኑ፤
4የምትሣለቁት በማን ላይ ነው?
የምታሽሟጥጡት ማንን ነው?
ምላሳችሁንስ አውጥታችሁ የምታሾፉት በማን
ላይ ነው?
እናንት የዐመፀኞች ልጆች፣
የሐሰተኞች ዘር አይደላችሁምን?
5በባሉጥ ዛፎች መካከል፣
ቅጠሉ በተንዠረገገ ዛፍ ሥር በዝሙት
የምትቃጠሉ፣
በሸለቆዎች፣
በዐለት ስንጣቂዎችም ውስጥ ልጆቻችሁን
የምትሠዉ አይደላችሁምን?
6በሸለቆው በሚገኙት ለስላሳ ድንጋዮች
ውስጥ ያሉት ጣዖቶች የአንቺ
ናቸው፤
እነርሱም ዕጣ ፈንታዎችሽ ናቸው፤
እርግጥ ነው፣ በእነርሱ ላይ የመጠጥ ቍርባን
አፍስሰሻል፤
የእህል ቍርባንም አቅርበሻል፤
ታዲያ፣ ስለ እነዚህ ነገሮች ዝም እላለሁን?
7ዐልጋሽን ከፍ ባለውና በረጅሙ ኰረብታ
ላይ አነጠፍሽ፤
በዚያም መሥዋዕትሽን ልታቀርቢ ወጣሽ።
8ከመዝጊያሽና ከመቃንሽ ጀርባ፣
የጣዖት ምስሎችሽን ሰቀልሽ፤
እኔን ትተሽ መኝታሽን ገላለጥሽ፤
በላይም ወጥተሽ በጣም ገለጥሽው፤
መኝታቸውን ከወደድሽላቸው ጋር
ስምምነት
አደረግሽ፤
ዕርቃናቸውንም አየሽ።
9የወይራ ዘይት ይዘሽ፣
ሽቶ በላዩ ጨምረሽ ወደ ሞሌክ[ቀ] ሄድሽ፤
መልእክተኞችሽን[ሀ] ወደ ሩቅ አገር ላክሽ፤
እስከ ራሱ እስከ ሲኦልም ዘለቅሽ።
10በመንገድ ብዛት ደከምሽ፤

[ቀ]9 ወይም *ወደ ንጉሡ* ተብሎ
[ሀ]9 ወይም፣ *ጣዖቶቻችሽን* ተብሎ

ነገር ግን ‘ተስፋ የለውም’ አላልሽም፤
የጒልበት መታደስ አገኘሽ፤
ስለዚህም አልዛልሽም።
11“እኔን የዋሸሽኝ፤
ማንን ፈርተሽ፣ ማንንስ ሠግተሽ ነው?
እኔን ያላስታወስሽው፣
ይህንንም በልብሽ ያላኖርሽው፣
እኔን ያልፈራሽው፣
ዝም ስላልሁ አይደለምን?
12ጽድቅሽንና ሥራሽን አጋልጣለሁ፤
እነርሱም አይጠቅሙሽም።
13ለርዳታ በምትጮኺበት ጊዜ፣
የሰበሰብሻቸው ጣዖቶች እስቲ ያድኑሽ!
ነፋስ ጠራርጎ ይወስዳቸዋል፤
ሽውሽውታም ይበትናቸዋል።
እኔን መጠጊያው ያደረገ ሰው ግን፣
ምድሪቱን ይወርሳል፤
የተቀደሰ ተራራዬንም ገንዘቡ ያደርገዋል።”

### ልባቸው ለተሰበረ መጽናናት

14እንዲህ ይባላል፤
“አብጁ፤ አብጁ፤ መንገድ አዘጋጁ፤
ከሕዝቤ መንገድ ዕንቅፋት አስወግዱ።”
15ከፍ ከፍ ያለውና ልዕልና ያለው እርሱ፣
ስሙም ቅዱስ የሆነው፣ ለዘላለም የሚኖረው
እንዲህ ይላል፤
“የተዋረዱትን መንፈሳቸውን ለማነሣሣት፣
የተሰበረ ልብ ያላቸውን ለማነቃቃት፣
ከፍ ባለውና በቅዱሱ ስፍራ እኖራለሁ፤
የተሰበረ ልብ ካለውና በመንፈሱ
ከተዋረደው ጋር እሆናለሁ።
16የሰው መንፈስ በፊቴ እንዳይዝል፣
የፈጠርሁትም ሰው እስትንፋስ እንዳይቆም፣
ለዘላለም አልወቅስም፤
ሁልጊዜም አልቈጣም።
17ኀጢአት ስለ ሞላበት ስግብግብነቱ
ተቈጣሁት፤
ቀጣሁት፤ ፊቴንም በቍጣ ከእርሱ
ሸሸግሁ፤
ያም ሆኖ በገዛ መንገዱ ገፋበት።
18መንገዶቹን አይቻለሁ፤ ቢሆንም እፈው
ሰዋለሁ፤
እመራዋለሁ፤ ለእርሱና ስለ እርሱ ለሚያለ
ቅሱትም መጽናናትን እመልሳለሁ፤
19 በእስራኤል አልቃሾች ከንፈር ላይ ምስጋና
እፈጥራለሁ።
በቅርብና በሩቅ ላሉት ሰላም፣ ሰላም
ይሁን፤
እኔ እፈውሳቸዋለሁ” ይላል እግዚአብሔር።
20ክፉዎች ግን ማዕበሉ ጭቃና ጒድፍ
እንደሚያወጣ፣
ጸጥ ማለት እንደማይችል፣
እንደሚናወጥ ባሕር ናቸው።
21አምላኬ፣ “ለክፉዎች ሰላም የላቸውም”
ይላል።

### እውነተኛ ጾም

58 “በኀይል ጩኸ፤ ምንም አታስቀር፤
ድምፅህን እንደ መለከት አሰማ፤
ለሕዝቤ ዐመፃቸውን፣
ለያዕቆብም ቤት ኀጢአታቸውን ተናገር።
2ዕለት በዕለት ይፈልጉኛል፤
መንገዴን ለማወቅ የሚጓጉ ይመስላሉ፤
ትክክለኛውን ነገር እንደሚያደርግ፣
የአምላኩንም ትእዛዝ እንዳልተወ ሕዝብ
ሁሉ፣
ተገቢ የሆነ ፍትሕ ይለምኑኛል፤
እግዚአብሔር ወደ እነርሱ እንዲቀርብ
የሚወዱም ይመስላሉ።
3‘አንተ ካልተቀበልኸው፣
ስለ ምን ብለን ጾምን?
አንተ ከጒዳይ ካልቈጠርኸው፣
ስለምን ራሳችንን አዋረድን?’ ይላሉ።

“ሆኖም በጾማችሁ ቀን የልባችሁን
ታደርጋላችሁ፤
ሠራተኞቻችሁንም ትበዘብዛላችሁ።
4ጾማችሁ በጥልና በክርክር፣
በግፍ ጡጫና በመደባደብ ይፈጸማል፤
ከእንግዲህ ዛሬ እንደምትጾሙት ጾማችሁ፣
ድምፃችሁ ወደ ላይ እንደሚሰማም ተስፋ
አታድርጉ።
5እኔ የመረጥሁት ጾም እንዲህ ዐይነቱን ነውን?
ሰውስ ራሱን የሚያዋርደው በእንዲህ ያለው
ቀን ብቻ ነውን?
እንደ ደንገል ራስን ዝቅ ማድረግ ነውን?
ወይስ ማቅ ለብሶ በዐመድ ላይ መንከ
ባለል ነውን?
ታዲያ ጾም ብለህ የምትጠራው ይህን
ነውን?
እግዚአብሔርስ የሚቀበለው እንዲህ
ያለውን ቀን ነውን?

6“እንግዲህ እኔ የመረጥሁት ጾም፣
የጭቈናን ሰንሰለት እንድትበጥሱ፣
የቀንበርን ገመድ እንድትፈቱ፣
የተጨቈኑትን ነጻ እንድታወጡ፣
ቀንበርን ሁሉ እንድትሰብሩ አይደለምን?
7ምግብህን ለተራብ እንድታካፍለው፣
ተንከራታቹን ድኻ ወደ ቤትህ
እንድታስገባው፣
የተራቈተውን ስታይ እንድታለብሰው፣
የሥጋ ዘመድህንም ፊት እንዳትነሣው

57፥11 2ነገ1፥15፤ አስ4፥14፤ምሳ29፥25፤ መዝ50፥21፤83፥1፤ ኢሳ7፥2፤ 17፥10፤ 42፥23፤ ኤር2፥32፤ 3፥21፤13፥25፤18፥15፤ ሕዝ22፥12
57፥12 ኢሳ29፥15፤ 58፥1፤59፥6፥12፤ 65፥7፤66፥18፤ ሕዝ16፥2፤ ሚክ3፥2-4፥8
57፥13 መሳ10፥14፤ መዝ37፥9፤118፥8፤ ኢሳ2፥2-3፤40፥7፥ 24፤56፥7፤65፥9-11፤ ኤር22፥20፤30፥15
57፥14 ኢሳ11፥16፤ 62፥10፤18፥15
57፥15 ዘዳ33፥27፤ 2ነገ22፥19፤ኢዮ5፥18፤ 16፥19፤መዝ34፥18፤51፥17፤90፥2፤147፥3፤ኢሳ52፥13፤66፥2፤ ሚክ6፥8፤ማቴ5፥3፤ 23፥12
57፥16 ዘፍ2፥7፤ መዝ50፥21፤103፥9፤ኢሳ3፥13-14፤54፥9፤ ዘካ12፥1
57፥17 ኢሳ1፥4፥15፤ 30፥15፤53፥6፤56፥11፤66፥3፤ኤር8፥10
57፥18 ዘዳ32፥39፤ 2ዜና7፥14፤መዝ48፥14፤ ኢሳ30፥26፤42፥16፤ 48፥17፤49፥13፤ 61፥1-3
57፥19 ኢሳ2፥4፤ 6፥7፤26፥3፥12፤ 32፥17፤51፥16፤ 59፥21፤ሉቃ2፥14፤ ሐሥ2፥39፤ ዕብ13፥15
57፥20 ዘፍ49፥4፤ ኢዮ18፥5-21፤ መዝ69፥14፤ ኤፌ4፥14፤ይሁ1፥13
57፥21 ኢሳ26፥3፤ 48፥22፤59፥8፤ ሕዝ13፥16
58፥1 ዘፀ20፥18፤ ኢሳ24፥20፤40፥6፤ 48፥8፤57፥12፤ ሕዝ3፥17
58፥2 ዘዳ32፥15፤ መዝ119፥87፤ ኢሳ29፥13፤48፥1፤ ቲቶ1፥16፤ ያዕ4፥8
58፥3 ዘፀ10፥3፤ ዘሌ16፥29፤2ዜና6፥37፤ ኢሳ22፥13፤ ኤር44፥10፤ዘካ7፥5-6፤ ሚል3፥14
58፥4 1ሳሙ8፥18፤ 1ነገ21፥9-13፤ ኢሳ59፥2፥6፤ኤር6፥7፤ ሰቆ3፥44፤ሕዝ7፥11፤ 8፥18፤ሚክ3፥4፤ ሚል2፥16
58፥5 1ነገ21፥27፤ ኢዮ2፥8፤ኢሳ36፥6፤ ማቴ6፥16፤ዘካ7፥5
58፥6 ዘዳ14፥29፤ ነህ5፥10-11፤ኢሳ9፥4፤ 61፥1፤ኤር34፥9፤ ኢል2፥12-14፤ አሞ4፥1፤ሉቃ4፥19
58፥7 ዘፍ29፥14፤ ኢዮ22፥7፤31፥19-20፤ኢሳ16፥4፤ሕዝ18፥16፤ማቴ25፥36፤ ሉቃ3፥11፤10፥31-32፤ ዕብ13፥2

አይደለምን?
8ይህ ከሆነ ብርሃንህ እንደ ንጋት ጮራ
ይፈነጥቃል፤
ፈውስህ ፈጥኖ ይደርሳል፤
ጽድቅህ† ቀድሞህ ይሄዳል፤
*የእግዚአብሔር* ክብር ደጀን ይሆንልሃል።
9የዚያን ጊዜ ትጣራለህ፤
*እግዚአብሔርም* ይመልስልሃል፤
ለርዳታ ትጮኻለህ፤ እርሱም፣ ‘አለሁልህ’
ይልሃል።

“የጭቈና ቀንበር፣
የክፉትን ንግግርና ጣት መቀሰርን ከአንተ
ብታርቅ፣
10ለተራበው ብትራራለት፣
የተገፉት እንዲጠግቡ ብታደርግ፣
ብርሃንህ በጨለማ ያበራል፤
ሌሊትህም እንደ ቀትር ፀሓይ ይሆናል።
11*እግዚአብሔር* ሁልጊዜ ይመራሃል፤
ፀሓይ ባቃጠለው ምድር ፍላጎትህን ያሚላል፤
ዐጥንትህን ያበረታል፤
በውሃ እንደ ረካ የአትክልት ቦታ፣
እንደማይቋርጥም ምንጭ ትሆናለህ።
12ወገኖችህ የቀድሞ ፍርስራሾችን መልሰው
ይሠራሉ፤
የጥንቱንም መሠረት ያቆማሉ፤
አንተም፣ የተናዱ ቅጥሮችን አዳሽ፣
ባለ አውራ መንገድ ከተሞችን ጠጋኝ
ትባላለህ።

13“እግሮችህ ሰንበትን እንዳይሽሩ ብታሳርፍ፣
በተቀደሰው ቀኔ የልብህን ባታደርግ፣
ሰንበትን ደስታ፣
*የእግዚአብሔርን* ቅዱስ ቀን የተከበረ
ብለህ ብትጠራው፣
በገዛ መንገድህ ከመሄድ፣
እንደ ፈቃድህ ከማድረግና ከከንቱ ንግግር
ብትቈጠብ፣
14በዚያን ጊዜ *በእግዚአብሔር* ደስ ይልሃል፤
በምድር ከፍታዎች ላይ እንድትጋልብ፣
የአባትህን የያዕቆብን ርስት ጠግበህ እንድ
ትበላ አደርግሃለሁ”
*የእግዚአብሔር* አፍ ይህን ተናግሮአልና።

## ኀጢአት፣ ንስሓና መበዠት

59 እነሆ፤ *የእግዚአብሔር* እጅ ከማዳን
አላጠረችም፤
ጆሮውም መስማት አልተሳናትም
2ነገር ግን በደላችሁ ከአምላካችሁ ለይቶአ
ችኋል፤
ኀጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል፤
በዚህም ምክንያት አይሰማም።
3እጆቻችሁ በደም፣
ጣቶቻችሁ በበደል ተነክረዋል፤
ከንፈሮቻችሁ ሐሰትን ተናገሩ፤
ምላሶቻችሁ ክፉ ነገርን አሰሙ።
4ፍትሕን የሚጠራ ማንም የለም፤
ጉዳዩን በቅንነት የሚያቀርብ የለም፤
በከንቱ ነገር ታመኑ፤ ሐሰትን ተናገሩ፤
ሁከትን ፀነሱ፤ ክፋትንም ወለዱ።
5የእባብ ዕንቍላል ታቀፉ፤
የሸረሪት ድር አደሩ፤
ዕንቍላሎቻቸውን የሚበላ ሁሉ ይሞታል፤
አንዱ በተሰበረ ጊዜም እፉኝት ይወጣል።
6ድሮቻቸው ልብስ አይሆኑም፤
በሚሠሩትም ሰውነታቸውን መሸፈን
አይችሉም፤
ሥራቸው ክፉ ነው፤
እጆቻቸውም በዐመፅ ሥራ የተሞላ ነው።
7እግሮቻቸው ወደ ኀጢአት ይሮጣሉ፤
ንጹሕ ደም ለማፍሰስ ይፈጥናሉ፤
የሚያስቡት ክፉ ሐሳብ ነው፤
ማጥፋትና ማፈራረስም የመንገዳቸው
ምልክት ነው።
8የሰላምን መንገድ አያውቁም፤
በጐዳናቸውም ፍትሕ የለም፤
መንገዳቸውን ጠማማ አድርገውታል፤
በዚያም የሚሄድ ሰላም አያገኝም።

9ስለዚህ ፍትሕ ከእኛ ርቆአል፤
ጽድቅም ወደ እኛ አይመጣም፤
ብርሃንን ፈለግን፤ ነገር ግን ሁሉ ጨለማ ነው፤
የብርሃንን ጸዳል ፈለግን፤ የምንሄደው ግን
በድንግዝግዝታ ነው።
10በቅጥሩ ላይ እንደ ዕውር ተደናበርን፤
አካሄዳችንም ዐይን እንደሌላቸው በዳበሳ
ሆነ፤
ጀምበር በምትጠልቅበት ጊዜ እንደሚሆነው
በእኩለ ቀን ተደናበርን፤
በብርቱዎች መካከልም እንደ ሙታን
ሆንን።
11ሁላችን እንደ ድቦች እንቦርቃለን፤
እንደ ርግቦችም በመቃተት እንጮኻለን፤
ፍትሕን ፈለግን፤ ግን አላገኘንም፤
ትድግናን ፈለግን፤ ነገር ግን ከእኛ ርቆአል።

12በደላችን በፊትህ በዝቶአል፤
ኀጢአታችን መስክሮብናል፤
በደላችን ከእኛ አልተለየም፤
ዐመፀኝነታችንንም እናውቃለን።
13*በእግዚአብሔር* ላይ ዐምፀናል፤ ሐሰት
ተናግረናል፤
አምላካችንን ከመከተል ዘወር ብለናል፤
ዐመፃንና ግፍን አውርተናል፤
ልባችን የፀነሰውን ውሸት ተናግረናል።

**58፥8** ዘፀ14፥19፤ ኢዮ11፥17፤ኢሳ1፥5፤ 9፥2፤26፥2፤30፥26
**58፥9** ኢዮ8፥6፤ መዝ12፥2፤50፥15፤ ምሳ6፥13፤ኢሳ30፥19፤ 59፥13፤ዳን9፥20፤ ዘካ10፥6
**58፥10** ዘዳ15፥7-8፤ ኢዮ11፥17፤ኢሳ42፥16
**58፥11** መዝ48፥14፤ 68፥6፤72፥16፤ 104፥28፤107፥9፤ ኢሳ35፥7፤42፥16፤ 48፥17፤ማሕ4፥15፤ ዮሐ4፥14
**58፥12** ነህ2፥17፤ ኢሳ44፥28፤49፥8
**58፥13** ዘፀ20፥8፤ መዝ37፥4፤42፥4፤ 84፥2፤10፤ኢሳ59፥3
**58፥14** ዘዳ32፥13፤ ኢዮ22፥26፤ መዝ105፥10-11፤ ኢሳ1፥20
**59፥1** ኢሳ30፥19፤ 41፥20፤50፥2፤58፥9፤65፥24
**59፥2** መዝ18፥41፤ ኢሳ58፥4፤ኤር5፥25፤ 11፥11፤ሕዝ39፥23፤ ዮሐ9፥31
**59፥3** 2ነገ21፥16፤ መዝ7፥3፤ኢሳ1፥15፤ 3፥8፤ሕዝ22፥9
**59፥4** ኢዮ4፥8፤ 15፥31፤ኢሳ5፥23፤ 29፥20፤44፥20፤ ያዕ1፥15
**59፥5** ኢዮ8፥14፤ ኢሳ11፥8፤ማቴ3፥7
**59፥6** መዝ55፥9፤ ምሳ4፥17፤ኢሳ28፥20፤ 58፥4
**59፥7** 2ነገ21፥16፤ ምሳ6፥17፤24፥2፤ ኢሳ26፥10፤ሚክ3፥10፤ ማር7፥21-22፤ ሮሜ3፥15-17
**59፥8** መሳ5፥6፤ ኢሳ57፥21፤ሉቃ1፥79፤ ሮሜ3፥15-17
**59፥9** ኢዮ19፥8፤ መዝ107፥14፤ ኢሳ5፥30፤8፥20፤ ሉቃ1፥79
**59፥10** ዘዳ28፥29፤ ኢዮ3፥23፤ ኢሳ6፥9-10፤8፥15፤ 56፥10፤ሰቆ3፥6፤ 4፥14፤ሶፎ1፥17፤ ዮሐ11፥9-10
**59፥11** ዘፍ8፥8፤ መዝ74፥19፤ኢሳ38፥14፤ ኤር48፥28፤ሕዝ7፥16፤ ናሆ2፥7
**59፥12** ዘፍ4፥7፤ ዕዝ9፥6፤መዝ51፥3፤ ኢሳ3፥9፤57፥12፤ ኤር2፥19
**59፥13** ዘኁ11፥20፤ መዝ12፥5፤ምሳ30፥9፤ ኢሳ3፥8፤5፥7፤44፥20፤ 46፥8፤48፥8፤ማቴ10፥33፤ማር7፥21-22፤ ቲቶ1፥16

†8 ወይም *የአንተ ጻድቅ*

14ስለዚህ ፍትሕ ከእኛ ርቆአል፤
ጽድቅም በሩቁ ቆሞአል፤
እውነት በመንገድ ላይ ተሰናክሎአል፤
ቅንነትም መግባት አልቻለም።
15እውነት የትም ቦታ አይገኝም፤
ከክፋት የሚርቅ ለጥቃት የተጋለጠ ነው።
እግዚአብሔር ተመለከተ፤
ፍትሕ በመታጣቱም ዐዘነ።
16ማንም እንደሌለ አየ፤
ወደ እርሱ የሚማልድ ባለመኖሩ ተገረመ፤
ስለዚህ የገዛ ክንዱ ድነት አመጣለት፤
የራሱም ጽድቅ ደግፎ ያዘው።
17ጽድቅን እንደ ጥሩር አጠለቀ፤
የድነትን ቍር በራሱ ላይ ደፋ፤
የበቀልንም ልብስ ለበሰ፤
መጐናጸፊያ እንደሚደረብም ቅናትን ደረበ።
18እንደ ሥራቸው መጠን፣
ቍጣን ለባላጋራዎቹ፣
ፍዳን ለጠላቶቹ፣
እንደዚሁ ይከፍላቸዋል፤
ለደሴቶችም የእጃቸውን ይሰጣቸዋል።
19በምዕራብ ያሉት የእግዚአብሔርን ስም ይፈራሉ፤
በፀሓይ መውጫ ያሉት ለክብሩ ይገዛሉ፤
የእግዚአብሔር እስትንፋስ እንደ ተቋተ፣
እንደ ተከማቸም ጐርፍ ይመጣልና።ቸ

20"አዳኝ ወደ ጽዮን፣
ኀጢአታቸውንም ወደ ተናዘዙት ወደ ያዕቆብ ቤት ይመጣል"
ይላል እግዚአብሔር።

21"በእኔ በኩል፣ ከእነርሱ ጋር ያለኝ ቃል
ኪዳን ይህ ነው" ይላል እግዚአብሔር፤
"በአንተም ላይ ያለው መንፈሴ፣ በአፍህ
ያስቀመጥሁት ቃሌ ከአፍህ፣ ከልጆችህ
አፍ፣ ከዘር ዘሮቻቸውም አፍ ከዛሬ ጀምሮ
እስከ ዘላለም አይለይም" ይላል እግዚአ
ብሔር።

**የጽዮን ክብር**

60 "ብርሃንሽ መጥቶአልና ተነሺ አብሪ፤
የእግዚአብሔርም ክብር ወጥቶ ልሻል።
2እነሆ፤ ጨለማ ምድርን፣
ድቅድቅ ጨለማም ሕዝቦችን ይሸፍናል፤
ነገር ግን እግዚአብሔር ወጥቶልሻል፤
ክብሩንም ይገልጥልሻል።
3ሕዝቦች ወደ ብርሃንሽ፣
ነገሥታትም ወደ ንጋትሽ ጸዳል ይመጣሉ።
4"ቀና በዪ፤ ዙሪያሽን ተመልከቺ፤
ሁሉም ተሰብስበው ወደ አንቺ ይመጣሉ፤
ወንዶች ልጆችሽ ከሩቅ፣
ሴቶች ልጆችሽም በዕቅፍ ወደ አንቺ ይመጣሉ።
5ከዚያም ታያለሽ፤ ታብረቀርቂያለሽ፤
ልብሽ ይዝላል፤ በደስታም ይሞላል።
በባሕሮች ያለው ሀብት ወደ አንቺ ይመጣል፤
የነገሥታትም ብልጥግና የአንቺ ይሆናል።
6የግመል መንጋ፣
የምድያምና የጌፌር ግልገል ግመሎች ምድርሽን ይሞላሉ፤
ወርቅና ዕጣን ይዘው፣
የእግዚአብሔርን ምስጋና እያወጁ፣
ሁሉም ከሳባ ይመጣሉ።
7የቄዳር የበግ መንጋ ሁሉ ወደ አንቺ ይሰበሰባል፤
የነባዮት አውራ በጎች ያገለግሉሻል።
እነዚህም በመሠዊያዬ ላይ ተቀባይነት የሚኖራቸው መሥዋዕቶች ይሆናሉ፤
እኔም የክብር መቅደሴን ግርማ አጐና ጽፋዋለሁ።

8"ርግቦች ወደ ጐጆአቸው እንደሚበሩ፣
እንደ ደመና የሚጓዙ እነዚህ እነማን ናቸው?
9በእርግጥ ደሴቶች እኔን ተስፋ ያደርጋሉ፤
እርሱ ክብሩን ስላጐናጸፈሽ፣
ለእስራኤል ቅዱስ፣
ለእግዚአብሔር አምላክሽ ክብር፣
ከሩቅ ወንዶች ልጆችሽን፣
ከነብራቸውና ከነወርቃቸው ለማምጣት፣
የተርሴስ መርከቦችነ ቀድመው ይወጣሉ።

10"ባዕዳን ቅጥሮችሽን ይሠራሉ፤
ነገሥታቶቻቸው ያገለግሉሻል፤
በቍጣዬ ብመታሽም፣
ርኅራኄዬን በፍቅር አሳይሻለሁ።
11በሮችሽ ምንጊዜም የተከፈቱ ይሆናሉ፤
ቀንም ሆነ ሌሊት ከቶ አይዘጉም፤
ይህም ሰዎች የመንግሥታትን ብልጥግና ወደ አንቺ እንዲያመጡ፤
ነገሥታታቸውም በድል ወደ አንቺ እንዲገቡ ነው።
12ለአንቺ የማይገዛ ሕዝብና መንግሥት ይጠ
ፋል፤
ፈጽሞም ይደመሰሳል።

13የመቅደሴን ቦታ ለማስጌጥ፣
የሊባኖስ ክብር፣
ጥዱ፣ አስታውና ባርሰነቱ በአንድነት ወደ

59፥14 ኢሳ1፥21፤ 29፥21፤ 48፥1፤ ኤር33፥16
59፥15 ኢሳ5፥7፤ ኤር7፥28፤9፥5፤ ዳን8፥12
59፥16 ኢሳ41፥28፤ 45፥8፥13፤46፥13፤ 51፥5፤53፥12
59፥17 ኢዮ27፥6፤ ኢሳ1፥24፤9፥7፤ 63፥3፤ሕዝ5፥13፤ ኤፌ6፥14፥17፤ 1ተሰ5፥8
59፥18 ዘሌ26፥28፤ ዘኍ10፥35፤ኢሳ11፥11፤ 34፥8፤41፥5፤ ማቴ16፥27
59፥19 መዝ97፥6፤ 113፥3፤ኢሳ11፥4፤ 24፥15፤35፥2፤40፥5፤49፥12፤52፥10፤ 66፥18፤ማቴ8፥11
59፥20 ኢዮ19፥25፤ 22፥23፤ኢሳ1፥27፤ 52፥8፤60፥16፤63፥16፤ኤር35፥15፤ኢል3፥21፤ ሮሜ11፥26-27፤ ሐሥ2፥38-39
59፥21 ዘፍ9፥16፤ ዘፀ4፥15፤ዘዳ29፥14፤ ኢሱ1፥8፤ኢሳ11፥2፤ 42፥6፤44፥3
60፥1 ዘፀ16፥7፤ መዝ36፥9፤118፥27፤ኢሳ4፥5፤9፥2፤52፥2፤ ዮሐ8፥12፤ኤፌ5፥14፤ ራእ21፥11
60፥2 1ሳሙ2፥9፤ መዝ82፥5፤107፥14፤ ኢሳ8፥20፤ኤር13፥16፤ ቈላ1፥13
60፥3 ኢሳ9፥2፤ 42፥6፤44፥5፤45፥14፤49፥23፤ማቴ2፥1-11፤ራእ21፥24
60፥4 ኢሳ2፥3፤ 11፥12፤43፥6፤ 49፥20-22፤ኤር30፥10
60፥5 ዘፀ34፥29፤ ዘዳ33፥19፤መሳ3፥15፤ ኢሳ35፥2፤65፥13፤ 66፥14፤ዘካ10፥7፤ ራእ21፥26
60፥6 ዘፍ10፥7፥28፤ 25፥2፥4፤መሳ6፥5፤ 1ነገ5፥7፤ኢሳ42፥10፤ 43፥23፤ኤር6፥20፤ ማቴ2፥11
60፥7 ቍ13፤ ዘፍ25፥13፤ኢሳ18፥7፤ 19፥21፤ሕዝ20፥40፤ 43፥27፤ሶፎ3፥10፤ ሐጌ2፥3፥7፥9
60፥8 ኢሳ19፥1፤ 49፥21
60፥9 ቍ14፤ ዘፍ10፥4፤1ነገ10፥22፤ መዝ22፥23፤ኢሳ1፥4፤ 2፥16፤11፥11፤14፥2፤43፥6፤44፥23፤54፥5፤55፥5፤ኤር30፥19
60፥10 ዘፀ1፥11፤ ዕዝ1፥2፤መዝ102፥13፤ ኢሳ14፥1-2፤49፥8፤ 56፥6፤ራእ21፥24
60፥11 ቍ5፥18፤ መዝ24፥7፤149፥8፤ ኢሳ2፥12፤61፥6፤ 62፥10፤ሚክ2፥13፤ ራእ21፥25፥26
60፥12 ዘፍ27፥29፤ መዝ110፥5፤ኢሳ11፥14፤14፥2፤ ዳን2፥34
60፥13 ቍ7፤ 1ዜና28፥2፤ዕዝ3፥7፤ ኢሳ41፥19

[ቾ]19 ወይም፣ *ጠላት እንደ ጐርፍ በሚመጣበት ጊዜ/ የእግዚአብሔር መንፈስ በውጊያ ያዋርደዋል*
[ኀ]9 ወይም፣ *የንግድ መርከቦች*

አንቺ ይመጣሉ፤
እግሬ የሚያርፍበትንም ስፍራ አከብራለሁ፡፡
14 የአስጨናቂዎችሽ ወንዶች ልጆች እየሰገዱ
ወደ አንቺ ይመጣሉ፤
የናቁሽም ሁሉ እግርሽ ላይ ይደፋሉ፣
የእግዚአብሔር ከተማ፣
የእስራኤል ቅዱስ ገንዘብ የሆንሽው ጽዮን
ብለው ይጠሩሻል፡፡

15 “የተተውሽና የተጠላሽ፣
ማንም ሰው የማያልፍብሽ ብትሆኝም እንኳ፣
እኔ የዘላለም ትምክሕት፣
የትውልድም ሁሉ ደስታ አደርግሻለሁ፡፡
16 የመንግሥታትን ወተት ትጠጫለሽ፤
የነገሥታትንም ጡት ትጠቢያለሽ፤
ከዚያም እኔ *እግዚአብሔር* አዳኝሽ፣
ቤዛሽም እኔ የያዕቆብ ኀያል እንደ ሆንሁ
ታውቂያለሽ፡፡
17 በናስ ፈንታ ወርቅ፣
በብረትም ፈንታ ብር አመጣልሻለሁ፡፡
ሰላምን ገዥሽ፣
ጽድቅንም አለቃሽ አደርጋለሁ፡፡
18 ከእንግዲህ በምድርሽ ሁከት፣
በጠረፎችሽም ጥፋትና መፈራረስ
አይሰማም፤
ነገር ግን ቅጥሮችሽን ድነት፣
በሮችሽንም ምስጋና ብለሽ ትጠሪያቸ
ዋለሽ፡፡
19 ከእንግዲህ በቀን የፀሓይ ብርሃን
አያስፈልግሽም፤
በሌሊትም የጨረቃ ብርሃን አያበራልሽም፤
*እግዚአብሔር* የዘላለም ብርሃን፣
አምላክሽም ክብርሽ ይሆናልና፡፡
20 ፀሓይሽ ከእንግዲህ አትጠልቅም፤
ጨረቃሽም ብርሃን መስጠቷን
አታቋርጥም?
*እግዚአብሔር* የዘላለም ብርሃንሽ ይሆናል፤
የሐዘንሽም ቀን ያከትማል፡፡
21 ሕዝብሽም ሁሉ ጻድቃን ይሆናሉ፤
ምድሪቱንም ለዘላለም ይወርሳሉ፤
ለክብሬ መግለጫ ይሆኑ ዘንድ፣
የእጆቼ ሥራ፣
እኔ የተከልኋቸው ቍጥቋጦች ናቸው፡፡
22 ከአንቺ ታናሽ የሆነው ሺህ፣
ከሁሉም የመጨረሻው ታናሽ ኀያል
መንግሥት ይሆናል፤
እኔ *እግዚአብሔር* ነኝ፤
ጊዜውም ሲደርስ ይህን በፍጥነት
አደርጋለሁ፡፡”

## የተወደደው *የእግዚአብሔር* ዓመት

# 61

የጌታ *የእግዚአብሔር* መንፈስ በእኔ
ላይ ነው፤
ለድኾች የምሥራች እንድሰብክ፣
*እግዚአብሔር* ቀብቶኛል፡፡
ልባቸው የተሰበረውን እንድጠግን፣
ለምርኮኞች ነጻነትን፣
ለእስረኞች መፈታትን እንዳውጅ[ነ]
ልኮኛል፤
2 የተወደደውን *የእግዚአብሔርን* ዓመት፣
የአምላካችንንም የበቀል ቀን እንዳውጅ፣
የሚያለቅሱትን ሁሉ እንዳጽናና ልኮኛል፤
3 በጽዮን ያዘኑትን እንዳረጋጋ፣
በዐመድ ፈንታ፣
የውበት አክሊል እንድደፋላቸው፣
በልቅሶ ፈንታ፣
የደስታ ዘይት በራሳቸው ላይ እንዳፈስላቸው፣
በትካዜ መንፈስ ፈንታ፣
የምስጋና መጐናጸፊያ እንድደርብላቸው
ልኮኛል፤
እነርሱም የክብሩ መግለጫ እንዲሆኑ፣
*እግዚአብሔር* የተከላቸው፣
የጽድቅ ዛፎች ተብለው ይጠራሉ፡፡

4 የጥንት ፍርስራሾችን መልሰው ይሠራሉ፤
በቀድሞ ጊዜ የወደሙትን መልሰው
ያቆማሉ፤
ከብዙ ትውልድ በፊት የወደሙትን
ፍርስራሽ ከተሞች እንደ ገና ይሠራሉ፡፡
5 መጻተኞች የበግ መንጎቻችሁን ያግዳሉ፤
ባዕዳን በዕርሻችሁና በወይን ተክል
ቦታችሁ ላይ ይሠሩላችኋል፡፡
6 እናንተም *የእግዚአብሔር* ካህናት ተብላችሁ
ትጠራላችሁ፤
የአምላካችን ባሮች ትባላላችሁ፤
የመንግሥታትን ሀብት ትመገባላችሁ፤
በብልጽግናቸውም ትኵራላችሁ፡፡

7 ሕዝቤ በኀፍረታቸው ፈንታ፣
ዕጥፍ ይቀበላሉ፤
በውርደታቸው ፈንታ፣
በርስታቸው ደስ ይላቸዋል፤
የምድራቸውንም ዕጥፍ ርስት ይወርሳሉ፤
ዘላለማዊ ደስታም የእነርሱ ይሆናል፡፡

8 “እኔ *እግዚአብሔር* ፍትሕን ስለምወድ፣
ዝርፊያንና በደልን እጠላለሁ፤
በታማኝነቴም የሚገባቸውን እሰጣቸዋለሁ፤
ከእነርሱም ጋር የዘላለም ኪዳን
አደርጋለሁ፡፡
9 ዘሮቻቸው በመንግሥታት፣
ልጆቻቸውም በሕዝቦች ዘንድ የታወቁ
ይሆናሉ፤

**60÷14** ቍ9፤ ዘፍ27÷29፤32÷28፤ ኢሳ1÷26፤2÷3፤14÷2፤ ዕብ12÷22፤ራእ3÷9
**60÷15** መዝ126÷5፤ ኢሳ1÷7-9፤4÷2፤ 6÷12፤33÷8፤54÷6፤ 65÷18
**60÷16** ዘፍ49÷24፤ ዘፀ6÷2፡7፤14÷30፤ ኢዮ19÷25፤ መዝ132÷2፤ ኢሳ25÷9፤49÷23፤ 59÷20፤66÷11፡12
**60÷17** 1ነገ10÷21፤ መዝ85÷8፤ኢሳ9÷7፤ 66÷12፤ሐጌ2÷9
**60÷18** ዘሌ26÷6፤ 2ሳሙ7÷10፤ኢሳ9÷4፤ 33÷6፤49÷19፤51÷19፤ 61÷11፤62÷7፤ ኤር33÷9፤ሶፎ3÷20
**60÷19** መዝ36÷9፤ 85÷9፤118÷27፤ ኢሳ24÷16፡23፤ ራእ21÷23፤22÷5
**60÷20** ኢሳ30÷19፡ 26፤35÷10፤ራእ7÷17
**60÷21** ዘፀ15÷17፤ ዘሌ10÷3፤ኢዮ10÷3፤ መዝ8÷6፤37÷11፡22፤44÷2፤80÷8-11፤ ኢሳ4÷3፤19÷25፤ 26÷2፤44÷23፤ 49÷8፤57÷13፤ 61÷7፤65÷9፤ ኤር32÷41፤ አሞ9÷15፤ዘካ8÷12፤ ማቴ15÷13፤ ኤፌ2÷10፤ራእ21÷27
**60÷22** ዘፍ12÷2፤ ዘዳ1÷10፤ኢሳ5÷19
**61÷1** ዘሌ25÷10፤ 2ሳሙ18÷26፤ 2ነገ22÷19፤ ኢዮ5÷16፡18፤ መዝ45÷7፤68÷6፤ ኢሳ11÷2፤40÷9፤ 49÷9፤50÷4፤ ዳን9÷24-26፤ ማቴ11÷5፤ሉቃ7÷22፤ ሐሥ4÷26፤2ቆሮ3÷17
**61÷2** ኢዮ5÷11፤ ኢሳ1÷24፤40÷1፤49÷8፤ ማቴ5÷4፤ ሉቃ4÷18-19፤6÷21
**61÷3** ሩት3÷3፤ ኢዮ2÷8፤መዝ1÷3፤ 92÷12-13፤ኢሳ1÷6፤ 3÷23፤44÷23፤ ኤር31÷13፤ማቴ5÷4፤ 15÷13፤1ቆሮ3÷9፤ ዕብ1÷9
**61÷4** ኢሳ44÷26፤ 51÷3፤65÷21፤ ሕዝ36÷33፤አሞ9÷14፤ ዘካ1÷16-17
**61÷5** ኢሳ14÷1-2፤ 56÷6
**61÷6** ዘፀ19÷6፤ ዘዳ33÷19፤ኢሳ60÷11፤ 1ጴጥ2÷5
**61÷7** ዘዳ21÷17፤ መዝ126÷5፤ኢሳ25÷9፤29÷22፤ 40÷2፤41÷11፤60÷21
**61÷8** ዘፍ9÷16፤ መዝ11÷7፤ኢሳ1÷17፤ 5÷16፤42÷6፤ ዕብ13÷20
**61÷9** ዘፍ12÷2፤ ዘዳ28÷3-12፤ኢሳ43÷5፤48÷19

[ነ]1 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ግን፣ *ዕውራንን ከጨለማ አወጣቸው ዘንድ* ይላል፡፡

የሚያዩአቸውም ሁሉ፣
እግዚአብሔር የባረካቸው ሕዝብ እንደ ሆኑ
ያውቃሉ።

[10]*በእግዚአብሔር እጅግ ደስ ይለኛል፤*
ነፍሴ በአምላኬ ሐሤት ታደርጋለች፤
ሙሽራ ራሱን እንደሚያሳምር፣
ሙሽራዪቱም በዕንቍቿ እንደምታጌጥ፣
የድነትን ልብስ አልብሶኛል፤
የጽድቅንም መጐናጸፊያ ደርቦልኛል።
[11]ምድር ቡቃያ እንደምታበቅል፣
የተክል ቦታ ችግኝ እንደሚያፈላ፣
ጌታ እግዚአብሔርም በመንግሥታት ሁሉ
ፊት፣
ጽድቅንና ምስጋናን ያበቅላል።

## አዲሱ የጽዮን ስም

62 ጽድቋ እንደ ማለዳ ወጋገን
እስኪፈነጥቅ፣
ድነቷ እንደሚያንጸባርቅ ፋና እስኪታይ፣
ስለ ጽዮን ዝም አልልም፤
ስለ ኢየሩሳሌምም ጸጥ አልልም።
[2]መንግሥታት ጽድቅሽን፣
ነገሥታት ክብርሽን ያያሉ፤
የእግዚአብሔር አፍ በሚያወጣልሽ፣
በአዲስ ስም ትጠሪያለሽ።
[3]*በእግዚአብሔር እጅ የክብር አክሊል፣*
በአምላክሽም እጅ የመንግሥት ዘውድ
ትሆኛለሽ።
[4]ከእንግዲህ፣ “የተተወች” ብለው አይጠሩሽም፤
ምድርሽም፣ “የተፈታች” አትባልም፤
ነገር ግን፣ “ደስታዬ በእርሷ” ትባያለሽ፤
ምድርሽም፣ “ባለ ባል” ትባላለች፤
እግዚአብሔር በአንቺ ደስ ይለዋል፤
ምድርሽም ባለ ባል ትሆናለች።
[5]ጐልማሳ ድንግሊቱን እንደሚያገባ፣
ልጆችሽ[ኘ] እንዲሁ ያገቡሻል፤
ሙሽራ በሙሽራዪቱ ደስ እንደሚለው፣
አምላክሽም በአንቺ ደስ ይለዋል።

[6]ኢየሩሳሌም ሆይ፤ ዘብ ጠባቂዎችን በቅጥ
ሮችሽ ላይ አቁሜአለሁ፤
ቀንም ሆነ ሌሊት ፈጽሞ አይታክቱም።
እናንት ወደ እግዚአብሔር አቤት፣ አቤት
የምትሉ፣
ፈጽሞ አትረፉ፤
[7]ኢየሩሳሌምን እስኪያጸናት፣
የምድርም ምስጋና እስኪያደርጋት ዕ
ረፍት
አትስጡት።

[8]እግዚአብሔር በቀኝ እጁ፣
በኀያል ክንዱም እንዲህ ሲል ምሎአል፤
“ከእንግዲህ እህልሽን፣
ለጠላቶችሽ መብል እንዲሆን አልሰጥም፤
ከእንግዲህ የደከምሽበትን፣
አዲስ የወይን ጠጅ ባዕዳን አይጠጡ
ትም።
[9]ነገር ግን መከሩን የሰበሰቡ ይበሉታል፤
እግዚአብሔርንም ያመሰግናሉ፤
የወይኑን ፍሬ የለቀሙም በመቅደሴ
አደባባዮች ይጠጡታል።”

[10]ዕለፉ፤ በበሮቹ በኩል ዕለፉ፤
ለሕዝቡ መንገድ አዘጋጁ፤
አስተካክሉ፤ ጐዳናውን አስተካክሉ፤
ድንጋዩን አስወግዱ፤
ለመንግሥታትም ምልክት አሳዩ።

[11]እግዚአብሔር እስከ ምድር ዳርቻ፣
እንዲህ ሲል ዐውጆአል፤
“ለጽዮን ሴት ልጅ፣
‘እነሆ፤ አዳኝሽ መጥቶአል፤
ዋጋሽ በእጁ አለ፤
ዕድል ፈንታሽም ከእርሱ ጋር ነው’ በሏት።”
[12]እነርሱም ቅዱስ ሕዝብ፣
እግዚአብሔር የተቤዣቸው ተብለው
ይጠራሉ፤
አንቺም የምትፈለግ፣
ከእንግዲህም የማትተው ከተማ ትባያለሽ።

## እግዚአብሔር የሚቤዥበትና የሚበቀልበት ቀን

63 ይህ ከኤዶም፣
ቀይ የተነከረ መጐናጸፊያ ለብሶ
ከባሶራ የሚመጣ ማን ነው?
ይህ ክብርን የተጐናጸፈ፣
በኀይሉ ታላቅነት እየተራመደ የሚመጣውስ
ማን ነው?

“በጽድቅ የምናገር፣
ለማዳንም ኀይል ያለኝ፣ እኔው ነኝ።”

[2]መጐናጸፊያህ፣ ለምን
በወይን መጭመቂያ ወይን እንደሚረግጠ
ሰዎች ልብስ ቀላ?

[3]“እኔ በመጭመቂያው ወይኑን ብቻዬን
ረገጥሁ፤
ከመንግሥታት ማንም ከእኔ ጋር
አልነበረም፤
በቍጣዬ ረገጥኋቸው፤
በመዓቴም ጨፈለቅኋቸው፤
ደማቸው በመጐናጸፊያዬ ላይ ተረጭቶአል፤
ልብሴንም በክዬዋለሁ።
[4]የበቀል ቀን በልቤ አለ፤
የምቤዥበትም ዓመት ደርሶአል።
[5]ተመለከትሁ፤ የሚረዳ ግን አልነበረም፤
የሚያግዝ ባለመኖሩም ተገረምሁ፤
ስለዚህ የገዛ ክንዴ ድነትን አመጣልኝ፤
የገዛ ቍጣዬም አጸናኝ፤

**61፥10** ዘፀ39፥28፤ ኢዮ27፥6፤መዝ2፥11፤ 132፥9፤ኢሳ7፥13፤ 25፥9፤49፥18፤52፥1፤ዕን3፥18፤ሉቃ1፥47፤ራእ19፥8፤21፥2
**61፥11** ዘፍ47፥23፤ ኢሳ45፥8፤58፥11
**62፥1** አስ4፥14፤ ኢዮ11፥17፤ መዝ50፥21፤67፥2፤ 83፥1፤ኢሳ1፥26፤ 45፥8
**62፥2** ዘፍ32፥28፤ መዝ67፥2፤ኢሳ1፥26፤ 40፥5፤45፥14፤52፥10፤ ራእ2፥17፤3፥12
**62፥3** ኢሳ28፥5፤ 1ተሰ2፥19
**62፥4** ዘሌ26፥43፤ 2ነገ21፥1፤ኢሳ6፥12፤ 49፥19፤51፥19፤54፥5፡6፤ 65፥19፤ኤር3፥14፤ 32፥41፤ሆሴ2፥19፤ ሶፎ3፥17፤ሚል3፥12
**62፥5** ዘዳ28፥63፤ መሓ3፥11፤ኢሳ65፥19፤ ኤር31፥12፤ሶፎ3፥17
**62፥6** መዝ132፥4፤ ኢሳ52፥8፤ዕብ13፥17
**62፥7** ዘዳ26፥19፤ ኢሳ60፥18፤ማቴ15፥21-28፤ ሉቃ18፥1-8
**62፥8** ዘፍ22፥16፤ ዘዳ28፥30-33፤ ኢሳ1፥7፤14፥24፤ 49፥18
**62፥9** ዘሌ23፥39፤ ዘዳ12፥7፤ኢሳ1፥19፤ ኢል2፥26፤አሞ9፥14
**62፥10** መዝ24፥7፤ ኢሳ11፥10፡16፤ 57፥14፤60፥11
**62፥11** ዘዳ30፥4፤ መዝ9፥14፤ኢሳ35፥4፤ 40፥10፤ዘካ9፥9፤ ማቴ21፥5፤ራእ22፥12
**62፥12** ዘፍ32፥28፤ ዘፀ19፥6፤መዝ27፥9፤ 106፥10፤ኢሳ35፥9፤ 42፥16፤44፥23፤ 54፥6፤1ጴጥ2፥9
**63፥1** ቍ5፤ ዘፍ36፥33፤ 2ዜና28፥17፤ ኢዮ9፥4፤ኢሳ11፥14፤ 45፥24፤46፥13፤51፥5፤ ኤር42፥11፤አሞ1፥12፤ ሶፎ3፥17፤ራእ19፥13
**63፥2** ዘፍ49፥11
**63፥3** መሳ6፥11፤ ኢዮ40፥12፤ መዝ108፥13፤ኢሳ5፥5፤ 22፥5፤ራእ14፥20፤ 19፥13
**63፥4** ኢሳ1፥24፤ ኤር50፥15
**63፥5** 2ነገ14፥26፤ መዝ44፥3፤98፥1፤ ኢሳ33፥2፤41፥28፤ 59፥16

[ኘ]5 ወይም፣ *ግንበኞችሽ*

6 መንግሥታትን በቍጣዬ ረጋገጥሁ፤
በመዓቴም አሰከርኋቸው፤
ደማቸውንም በምድር ላይ አፈሰስሁ።”

**ውዳሴና ጸሎት**

7 የእግዚአብሔርን ቸርነት፣
እግዚአብሔር ስላደረገልን ሁሉ፣
ስለሚመሰገንበት ሥራው፣
እንደ ፍቅሩና እንደ ቸርነቱ መጠን፣
ለእስራኤል ቤት ያደረገውን፣
አዎን፣ ስላደረገው መልካም ነገር
እናገራለሁ።
8 እርሱም፣ “እርግጥ ነው፤ እነርሱ ሕዝቤ
ናቸው፤
የማይዋሹኝ ወንዶች ልጆቼ ናቸው” አለ።
ስለዚህም አዳኝ ሆነላቸው።
9 በጭንቃቸው ሁሉ ተጨነቀ፤
የፊቱም መልአክ አዳናቸው፤
በፍቅሩና በምሕረቱ ዋጃቸው፤
በቀደመው ዘመን ሁሉ አነሣቸው፤
ተሸከማቸውም።
10 እነርሱ ግን ዐመፁ፤
ቅዱስ መንፈሱንም አሳዘኑ፤
ስለዚህ ተመልሶ ጠላት ሆናቸው፤
እርሱ ራሱ ተዋጋቸው።

11 ከዚያም ሕዝቡ የጥንቱን ዘመን፣
የሙሴንና የሕዝቡን ጊዜ እንዲህ በማለት
አስታወሱ፤
የበጎቹን እረኛ፣
ከባሕሩ ያወጣቸው እርሱ የት አለ?
ቅዱስ መንፈሱንም፣
በመካከላቸው ያኖረ እርሱ የት አለ?
12 የከበረው ኀያል ክንድ፣
በሙሴ ቀኝ እጅ ላይ እንዲያርፍ አደረገ፤
ለራሱ የዘላለም ዝና እንዲሆንለት፣
ውሆችን በፊታቸው ከፈለ።
13 ፈረስ በምድረ በዳ እንደሚያልፍ ሁሉ፣
እነርሱንም በጥልቁ ውስጥ አሳልፎ
መራቸው፤
ስለዚህም አልተሰናከሉም፤
14 ወደ ሸለቆ እንደሚወርድ የከብት መንጋ፣
በእግዚአብሔር መንፈስ ዕረፍት
ተሰጣቸው።
ሕዝብህን በዚህ ሁኔታ የመራሃቸው፣
ስምህን የከበረ ለማድረግ ነው።

15 ከተቀደሰው፣ ከተከበረውና ከፍ ካለው
ዙፋንህ፣
ከሰማይ ወደ ታች ተመልከት፤
ኀይልህና ቅናትህ የት አለ?
ገርነትህና ርኅራኄህ ከእኛ ርቀዋል።
16 አብርሃም ባያውቀን፣
እስራኤልም ባያስታውሰን እንኳ፣
አንተ እኮ አባታችን ነህ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ አባታችን ነህ፤
ከጥንትም ቢሆን ስምህ “ቤዛችን” ነው።
17 እግዚአብሔር ሆይ፤ ከመንገድህ እንድንወጣ፣
ልባችንን በማደንደን ለምን እንዳንፈራህ
አደረግኸን?
ስለ ባሮችህ ስትል፣
ስለ ርስትህ ነገዶች ስትል እባክህ
ተመለስ።
18 ለጥቂት ጊዜ ሕዝብህ የተቀደሰውን ስፍራ
ወርሶ ነበር፤
አሁን ግን ጠላቶቻችን መቅደስህን
ረገጡት።
19 እኛ እኮ ጥንትም የአንተው ነን፤
እነርሱን ግን አንተ አላገዝሃቸውም፤
በስምህም አልተጠሩም።[a]

# 64

አቤቱ፤ ሰማያትን ቀድደህ
ምነው በወረድህ፤
ምነዋ ተራሮች በፊትህ በተናወጡ፤
2 እሳት ሲለኵስ ጭራሮን እንደሚያቀጣጥል፣
ውሃንም እንደሚያፈላ፣
ስምህ በጠላቶችህ ዘንድ እንዲታወቅ
ውረድ፤
መንግሥታትም በፊትህ እንዲንቀጠቀጡ
አድርግ።
3 እኛ ያልጠበቅነውን አስፈሪ ነገር ባደረግህ
ጊዜ፣
አንተ ወረድህ፤ ተራሮችም በፊትህ
ተንቀጠቀጡ።
4 ከጥንት ጀምሮ፣
በተስፋ ለሚጠባበቁት የሚደርስላቸው፣
እንደ አንተ ያለውን አምላክ ያየ ዐይን፣
ያደመጠ ጆሮ ፈጽሞ አልነበረም።
5 በደስታ ቅን ነገር የሚያደርጉትን፣
መንገድህን የሚያስቡትንም ትረዳለህ፤
እኛ ግን በእነርሱ ላይ ሳናቋርጥ ኀጢአት
በመሥራታችን፣
እነሆ፣ ተቈጣህ፤
ታዲያ እንዴት መዳን እንችላለን?
6 ሁላችን እንደ ረከሰ ሰው ሆነናል፤
የጽድቅ ሥራችን እንደ መርገም ጨርቅ
ነው፤
ሁላችን እንደ ቅጠል ረግፈናል፤
ኀጢአታችንም እንደ ነፋስ ጠራርጎናል።
7 ማንም በጸሎት ስምህን አይጠራም፤
አንተንም ለመያዝ የሚሞክር የለም፤
ፊትህን ከእኛ ሰውረሃል፤
ስለ ኀጢአታችንም ትተኸናል።
8 ይህም ሆኖ፣ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ

63፥6 ኢዮ40፥12፤ መዝ108፥13፤ ኢሳ29፥9፤4፥3፤ ሰቆ4፥21
63፥7 ዘፀ18፥9፤ መዝ51፥1፤ኢሳ54፥8፤ ኤፌ2፥4
63፥8 ዘፀ14፥30፤ መዝ100፥3፤ኢሳ25፥9፤ 51፥4
63፥9 ዘፀ14፥19፤ 33፥14፤ዘዳ1፥31፤ 7፥7-8፤32፥7፤ዕዝ9፥9፤ ኢዮ37፥23፤መዝ28፥9፤ ኢሳ48፥20
63፥10 ኢሱ10፥14፤ መዝ51፥11፤78፥17፤106፥40፤ኢሳ10፥4፤ ሕዝ20፥8፤ ሐሥ7፥39-42፥51፤ ኤፌ4፥30
63፥11 ዘፀ14፥22፡ 30፤ዘኍ11፥17፤ መዝ77፥20
63፥12 ዘፍ49፥24፤ ዘፀ3፥20፤14፥21-22፤ መዝ102፥12፤ ኢሳ11፥15፤55፥13፤ ኤር13፥11
63፥13 ዘፀ14፥22፤ ዘዳ32፥12፤መዝ119፥11፤ ኤር31፥9
63፥14 ዘፀ33፥14፤ ዘዳ12፥9
63፥15 ዘፍ43፥31፤ ዘዳ26፥15፤1ነገ3፥26፤22፥19፤መዝ25፥6፤132፥1፤ኢሳ9፥7፤26፥11፤ 64፥12፤ሰቆ3፥50
63፥16 ዘፀ4፥22፤ ኢዮ14፥21፤ኢሳ41፥14፤ 44፥6፤59፥20፤ ኤር3፥4፤ዮሐ8፥41
63፥17 ዘፍ20፥13፤ ዘፀ4፥21፤34፥9፤ ዘኍ10፥36፤ኢሳ29፥13፤ ሰቆ3፥9
63፥18 ዘሌ26፥31፤ ዘዳ4፥26፤11፥17፤ 2ነገ25፥9፤ ኢሳ28፥18፤ዳን8፥13፤ ሉቃ21፥24
63፥19 ኢሳ43፥7፤ ኤር14፥9
64፥1 ቀኍ3፤ ዘፀ19፥18፤መዝ18፥9፤ 144፥5፤ሚክ1፥3
64፥2 መዝ99፥1፤ 119፥120፤ኢሳ30፥27፤ ኤር5፥22፤33፥9
64፥3 መዝ18፥7፤ 65፥5፤
64፥4 ኢሳ30፥18፤ 43፥10-11፤1ቆሮ2፥9
64፥5 ኢሳ10፥4፤ 26፥8
64፥6 ዘሌ5፥2፤ 12፥2፤መዝ1፥3፥4፤ 90፥5-6፤ኢሳ46፥12፤ 48፥1፤ኤር4፥12
64፥7 ዘዳ31፥18፤ መዝ14፥4፤ኢሳ1፥15፤ 9፥18፤41፥28፤54፥8፤59፥4፤63፥5፤ኤር8፥6፤ሕዝ22፥18-22፥30
64፥8 ዘፀ4፥22፤ኢዮ10፥3፤ኢሳ19፥25፤29፥16፤ኤር3፥4፤ሮሜ9፥20-21

[a] 19 ወይም፣ *አንተ እንዳልገዛሃቸው እንመስላለን፣ ልክ በአንተ ስም እንዳልተጠሩት*

አባታችን ነህ፤
እኛ ሸክላዎች፣ አንተም ሸክላ ሠሪ ነህ፤
ሁላችንም የእጅህ ሥራ ነን፤
9እግዚአብሔር ሆይ፤ ከልክ በላይ አትቈጣን፤
ኀጢአታችንንም ለዘላለም አታስብ፤
እባክህ ተለመነን፤ ፊትህን ወደ እኛ መልስ፤
ሁላችንም የአንተ ሕዝብ ነንና።
10የተቀደሱ ከተሞችህ ምድረ በዳ ሆኑ፤
ጽዮን ራሷ እንኳ ምድረ በዳ፣ ኢየሩ
ሳሌምም የተፈታች ሆናለች።
11አባቶቻችን አንተን ያመሰገኑበት የተቀደሰውና
የተከበረው ቤተ መቅደሳችን፣
በእሳት ተቃጥሎአል፤
ያማሩ ቦታዎቻችንም ሁሉ እንዳልነበር
ሆነዋል።
12እግዚአብሔር ሆይ፤ ይህ ሁሉ ሆኖ
አትመለስምን?
ዝም ብለህ ከልክ በላይ ትቀጣናለህን?

## ፍርድና ድነት

65 "ላልለመኑኝ ራሴን ገለጥሁላቸው፤
ላልፈለጉኝ ተገኘሁላቸው።
ስሜን ላልጠራ ሕዝብ፣
'አለሁልህ፤ አለሁልህ' አልሁት።
2ለዐመፀኛ ሕዝብ፣
መልካም ባልሆኑ መንገዶች ለሚሄዱ፣
የልባቸውን ምኞት ለሚከተሉ፣
ቀኑን ሙሉ እጆቼን ዘረጋሁ።
ዘወትር በፊቴ የሚያስቈጡኝ ሕዝቦች፣
3በአትክልት ቦታዎች መሥዋዕት የሚያቀርቡ፣
በሸክላ መሠዊያዎች ላይ ዕጣን የሚያጥኑ፣
ዘወትር በፊቴ የሚያስቈጡኝ ሕዝብ ናቸው፤
4በመቃብር መካከል የሚቀመጡ፣
በስውር ቦታዎች የሚያድሩ፣
የዕሪያ ሥጋ የሚበሉ፣
ማሰሮዎቻቸውን በረከሰ ሥጋ መረቅ
የሚሞሉ ናቸው፤
5'ዘወር በል፤ አትቅረበኝ፤
አትጠጋኝ፤ እኔ ከአንተ ይልቅ ቅዱስ ነኝ'
የሚሉ ናቸው።
እንዲህ ያለው ሕዝብ በአፍንጫዬ ዘንድ እንደ
ጢስ፣
ቀኑን ሙሉ እንደሚነድድ እሳት ነው።
6"እነሆ፤ እንዲህ የሚል ተጽፎ በፊቴ
ተቀምጦአል፤
ዝም አልልም፤ ነገር ግን እንደ ሥራው
እሰጠዋለሁ፤
የእጃቸውንም እከፍላቸዋለሁ፤
7የእናንተን ኀጢአት የአባቶቻችሁንም ኀጢአት
እበቀላለሁ"
ይላል እግዚአብሔር።
"በተራሮች ላይ የሚቃጠል መሥዋዕት ስላቀረቡ፣
በኰረብቶች ላይ ስለ ሰደቡኝ፣
በሰፈሩት ቍና ይሰፈርባቸዋል፤
ስለ ቀደሙት ሥራዎቻቸውም የእጃቸውን
ያገኛሉ።"

8እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤

"በወይኑ ዘለላ ውስጥ ጭማቂው ገና
እንዳለ ሁሉ፣
ሰዎችም፣ 'በውስጡ ጥሩ ነገር ስላለ
አትቍረጡት' እንደሚሉ፣
እኔም ስለ ባሮች ስል እንዲሁ አደርጋለሁ፤
ሙሉ በሙሉ አላጠፋቸውም።
9ከያዕቆብ ዘር የሆኑትን፣
ከይሁዳም ተራሮቼን የሚወርሱትን
አመጣለሁ።
የተመረጠው ሕዝቤ ይወርሳቸዋል፤
ባሪያዎቼም በዚያ ይኖራሉ።
10አጥብቀው ለሚፈልጉኝ ሕዝቤ፣
ሳሮን የበጎች መሰማሪያ፣
የአኮር ሸለቆም የከብቶች ማረፊያ ይሆናል።
11"ነገር ግን እግዚአብሔርን ለተዋችሁት
ለእናንተ፣
የተቀደሰ ተራራዬን ለረሳችሁት፣
'ዕጣ ፈንታ' ለተባለ ጣዖት ቦታ ላዘጋጃ
ችሁት፣

'ዕድል' ለተባለም ጣዖት ድብልቅ የወይን
ጠጅ በዋንጫ ለሞላችሁት፣
12ተጣርቼ ስላልመለሳችሁ፣
ተናግሬ ስላልሰማችሁ፣
በፊቴ ክፉ ነገር ስላደረጋችሁ፣
የሚያስከፋኝን ነገር ስለ መረጣችሁ፣
ለሰይፍ እዳርጋችኋለሁ፤
ሁላችሁም ለመታረድ ትጐነበሳላችሁ።"
13ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
"ባሮቼ ይበላሉ፤
እናንተ ግን ትራባላችሁ፤
ባሮቼ ይጠጣሉ፤
እናንተ ግን ትጠማላችሁ፤
ባሮቼ ደስ ይላቸዋል፤
እናንተ ግን ታፍራላችሁ።
14ባሮቼ፣
ከልብ በመነጨ ደስታ ይዘምራሉ፤
እናንተ ግን፣
ልባችሁ በማዘኑ ትጮኻላችሁ፤
መንፈሳችሁ በመሰበሩም ወዮ ትላላችሁ።
15ስማችሁንም፣
የተመረጠው ሕዝቤ ርግማን እንዲ
ያደርገው ትተዋላችሁ፤
ጌታእግዚአብሔር ይገድላችኋል፤
ለአገልጋዮቹ ግን ሌላ ስም ይሰጣቸዋል።
16ስለዚህ በምድሪቱ ላይ በረከትን የሚጠራ፣
በእውነት አምላክ ስም ይባረካል፤

64፥9 መዝ100፥3፤ ኢሳ43፥25፤51፥4፤54፥8፤ 57፥17፤60፥10፤ሰቆ5፥22
64፥10 ዘዳ29፥23፤ መዝ78፥54፤ኢሳ1፥26
64፥11 ቀኍ10-11፤ ዘሌ26፥31፤2ነገ25፥9፤መ ዝ74፥3-7፤ ሰቆ1፥7፥10፤2፥7
64፥12 ዘፍ43፥31፤ አስ4፥14፤መዝ50፥21፤7 4፥10-11፤83፥1
65፥1 መዝ14፥4፤ ኢ ሳ43፥7፤ሆሴ1፥10፤ ሮሜ9፥24-26፥30፤ 10፥20፤ኤፌ2፥12
65፥2 መዝ78፥8፤ 81፥11-12፤ምሳ24፥2፤ ኢሳ1፥2፥23፤66፥18፤ ሮሜ10፥21
65፥3 ዘሌ2፥2፤ ኢዮ1፥11፤ኢሳ1፥29፤ ኤር41፥5፤44፥17፤ ሕዝ23፥41
65፥4 ዘሌ11፥7፤ 19፥31፤ኢሳ8፥19
65፥5 መዝ40፥4፤ ምሳ10፥26፤ ማቴ9፥11፤ሉቃ7፥39፤ 18፥9-12
65፥6 2ዜና6፥23፤ መዝ50፥3፤79፥12፤ ኢ ሳ59፥18፤ ኤር16፥18፤ሕ ዝ9፥10፤ ሉቃ6፥38
65፥7 ዘፀ20፥5፤ ምሳ10፥24፤ ኢሳ10፥12፤22፥14፤ 57፥7፤ኤር32፥18
65፥8 ኢሳ5፥2፤ 54፥17
65፥9 ዘኍ34፥13፤ ኢሳ14፥1፤32፥18፤ 45፥19፤60፥21፤ ኤር50፥19፤ አሞ9፥11-15
65፥10 ኢሱ7፥26፤ 1ዜና27፥29፤ ኢሳ35፥2፤51፥1፤ ኤር31፥12፤33፥12፤ ሕዝ34፥13-14፤ ሐሥ9፥35
65፥11 ዘዳ28፥20፤ 29፥24-25፤32፥15፤ 33፥19፤መዝ137፥5፤ ኢሳ1፥28፤5፥22፤ ኤር2፥13፤19፥4
65፥12 ዜና36፥15-16፤ መዝ149፥7፤ ምሳ1፥24-25፤ ኢሳ1፥20፥24፤27፥1፤ 30፥25፤41፥28፤66፥4፤ ኤር7፥13፥27፤13፥11፤ 25፥3፤26፥5፤ሚክ5፥15
65፥13 ኢዮ18፥12፤ ኢሳ1፥19፤3፥1፤33፥16፤ 41፥17፤44፥9፤60፥5፤6 1፥7፤ሉቃ6፥25
65፥14 መዝ109፥28፤ ኢሳ15፥2፤ ሶፎ3፥14-20፤ ማቴ8፥12፤ ሉቃ13፥28፤ያዕ5፥13

በምድሪቱ መሐላን የሚምል፣
በእውነት አምላክ ስም ይምላል፤
ያለፉት ችግሮች ተረስተዋል፤
ከዐይኖቼም ተሰውረዋል።

## አዲስ ሰማያትና አዲስ ምድር

17“እነሆ፤ እኔ፣
አዲስ ሰማያትንና አዲስ ምድርን እፈጥራለሁ፤
ያለፉት ነገሮች አይታሰቡም፤
አይታወሱም።
18ነገር ግን በምፈጥረው፣
ደስ ይበላችሁ፤ ለዘላለም ሐሤት አድርጉ።
ኢየሩሳሌምን ለደስታ፣
ሕዝቧን ለሐሤት እፈጥራለሁና።
19በኢየሩሳሌም እደሰታለሁ፤
በሕዝቤ ሐሤት አደርጋለሁ፤
የልቅሶና የጩኸት ድምፅ፣
ከእንግዲህ በዚያ አይሰማም።
20“ከእንግዲህም በዚያ፣
ለጥቂት ጊዜ ብቻ በሕይወት የሚኖር ሕ
ፃን፣
ወይም ዕድሜ ያልጠገበ አረጋዊ አይኖርም፤
አንድ መቶ ዓመት የሞላው ሰው ቢሞት፣
በአጭር እንደ ተቀጨ ይቈጠራል፤
አንድ ሰው መቶ ዓመት ሳይሞላው ቢሞት፣
እንደ ተቀሠፈ ይገመታል።
21ሰዎች ቤት ይሠራሉ፤ በውስጡም ይኖራ
ሉ፤
ወይንን ይተክላሉ፤ ፍሬውንም ይበላሉ።
22ከእንግዲህ ለሌሎች መኖሪያ ቤት አይሠሩም፤
ወይም ሌላው እንዲበላው አይተክሉም፤
የሕዝቤ ዕድሜ፣
እንደ ዛፍ ዕድሜ ይረዝማል፤
እኔ የመረጥኋቸው፣
በእጃቸው ሥራ ለረጅም ዘመን ደስ
ይላቸዋል።
23ድካማቸው በከንቱ አይቀርም፤
ዕድለ ቢስ ልጆችም አይወልዱም፤
እነርሱና ዘራቸው፣
*እግዚአብሔር* የባረከው ሕዝብ ይሆናሉ።
24ገና ሳይጣሩ እመልስላቸዋለሁ፤
ተናግረው ሳይጨርሱ እሰማለሁ።
25ተኵላና የበግ ጠቦት በአንድነት ይበላሉ፤
አንበሳ እንደ በሬ ሣር ይበላል፤
እባብ ትቢያ ይልሳል፤
በተቀደሰው ተራራዬም፣
ጕዳት አያደርሱም፤ ጥፋት አያመጡም፤”
ይላል *እግዚአብሔር*።

## ፍርድና ተስፋ

66 *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“ሰማይ ዙፋኔ ነው፤
ምድርም የእግሬ ማረፊያ ናት፤
ታዲያ የምትሠሩልኝ ቤት፣
የማርፍበትስ ስፍራ የቱ ነው?

**65፥15** ዘፍ32፥28፤ ዘኍ5፥27፤ መዝ102፥8፤ራእ2፥17
**65፥16** ዘዳ29፥19፤ ኢዮ11፥16፤መዝ31፥5፤ 63፥11፤ኢሳ19፥18፤ ራእ3፥14
**65፥17** ኢሳ41፥22፤ 43፥18፤66፥22፤ ኤር3፥16፤2ቆሮ5፥17፤ 2ጴጥ3፥13፤ራእ7፥17
**65፥18** ዘዳ32፥43፤ መዝ98፥1-9፤ ኢሳ25፥9፤ራእ21፥2
**65፥19** ዘዳ30፥9፤ ኢሳ25፥8፤35፥10፤ 62፥5፤ራእ7፥17
**65፥20** ዘፍ5፥1-32፤ 15፥15፤መክ8፥13፤ ኢሳ11፥8፤ዘካ8፥4
**65፥21** 2ነገ19፥29፤ ኢሳ32፥18፤37፥30፤ 61፥4፤ሕዝ28፥26፤ አሞ9፥14
**65፥22** ዘዳ28፥30፤ መዝ1፥3፤21፥4፤ 91፥16፤92፥12-14፤ ኢሳ14፥1
**65፥23** ዘፍ12፥2፤ ዘዳ28፥3-12፥32፥41፤ ኢሳ44፥3፤49፥4፤ ኤር16፥3-4፤ሐሥ2፥39፤ 1ቆሮ15፥58
**65፥24** ኢዮ8፥6፤ ኢሳ30፥19፤55፥6፤ ዳን9፥20-23፤10፥12፤ ዘካ10፥6፤ማቴ6፥8
**65፥25** ዘፍ3፥14፤ ኢዮ5፥23፤40፥15፤ ኢሳ2፥4፤11፥6፤ ሚክ7፥17
**66፥1** 2ሳሙ7፥7፤ 1ነገ8፥27፤2ዜና6፥18፤መዝ2፥4፤9፥7፤ማቴ5፥34-35፤23፥22፤ ዮሐ4፥20-21፤ ሐሥ7፥49፤17፥24
**66፥2** ዕዝ9፥4፤ ኢሳ40፥26፤57፥15፤ ማቴ5፥3-4፤ ሉቃ18፥13-14፤ ሐሥ7፥50፤17፥24
**66፥3** ቍ17፤ ዘሌ2፥2፤11፥7፤ ዘዳ27፥15፤ ኢሳ1፥11፤57፥17፤ ሕዝ8፥9-13
**66፥4** 1ሳሙ8፥19፤ 2ነገ21፥2፥4፥6፤ ምሳ10፥24፤ ኢሳ10፥12፤ 41፥28፤59፥12፤ 65፥12
**66፥5** ዕዝ9፥4፤ መዝ38፥20፤ኢሳ44፥9፤ 60፥15፤ ሉቃ13፥17፤ ዮሐ15፥21
**66፥6** ዘሌ26፥28፤ 1ሳሙ2፥10፤ መዝ68፥33፤ኢሳ65፥6፤ ኢል3፥7
**66፥7** ኢሳ54፥1፤ ራእ12፥5

2እነዚህን ነገሮች ሁሉ እጄ አልሠራችምን?
እንዲገኙስ ያደረግሁ እኔ አይደለሁምን?”
ይላል *እግዚአብሔር*።

“ነገር ግን እኔ ወደዚህ፣
ትሑት ወደ ሆነና መንፈሱ ወደ ተሰበረ፣
በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው
እመለከታለሁ።
3ነገር ግን ወይፈን የሚሰዋልኝ፣
ሰው እንደሚገድል ነው፤
የበግ ጠቦት የሚያቀርብልኝ፣
የውሻ ዐንገት እንደሚሰብር ሰው ነው፤
የእህል ቍርባን የሚያዘጋጅልኝ፣
የዕሪያ ደም እንደሚያቀርብልኝ ሰው ነው፤
የመታሰቢያን ዕጣን የሚያጥንልኝም፣
ጣዖትን እንደሚያመልክ ሰው ነው፤
የገዛ መንገዳቸውን መርጠዋል፤
ነፍሳቸውም በርኵሰታቸው ደስ ይላታል።
4ስለዚህ ችግር እንዲደርስባቸው አደርጋለሁ፤
የፈሩትንም አመጣባቸዋለሁ፤
በተጣራሁ ጊዜ የመለሰ፣
በተናገርሁ ጊዜ ያደመጠ ሰው
የለምና።
በፊቴ ክፉ ነገር አደረጉ፤
የሚያስከፋኝንም መረጡ።”

5እናንት በቃሉ የምትንቀጠቀጡ፣
ይህን የ*እግዚአብሔር* ቃል ስሙ፤
“እናንት ወንድሞቻችሁ የጠሏችሁ፣
ስለ ስሜም አውጥተው የጣሏችሁ፣
‘እስቲ *እግዚአብሔር* ይክበርና፣
የእናንተን ደስታ እንይ’ አሏችሁ፤
ይሁን እንጂ ማፈራቸው አይቀርም።
6ያን የጩኸት ድምፅ ከከተማው ስሙ!
ያን ጫጫታ ከቤተ መቅደሱ ስሙ!
ይኸውም የ*እግዚአብሔር* ድምፅ ነው፤
ለጠላቶቹም የሚገባቸውን ሁሉ
ይከፍላቸዋል።

7“ከማማጧ በፊት፣
ትወልዳለች፤
በምጥ ጣር ከመያዟ በፊት፣
ወንድ ልጅ ትገላገላለች።
8እንዲህ ያለ ነገር ማን ሰምቶ ያውቃል?
እንዲህ ያለ ነገርስ ማን አይቶ ያውቃል?
አገር በአንድ ጀምበር ይፈጠራልን?
ወይስ ሕዝብ በቅጽበት ይገኛል?
ጽዮንን ምጥ ገና ሲጀምራት፣
ልጆቿን ወዲያውኑ ትወልዳለች።
9ሊወለድ የተቃረበውን፣
እንዳይወለድ አደርጋለሁን?” ይላል
*እግዚአብሔር*።
“በሚገላገሉበት ጊዜስ፣

**66፥8** ኢሳ49፥20፥21፤64፥4፤ኤር18፥13 **66፥9** ኢሳ37፥3

ማሕፀን እዘጋለሁን?” ይላል አምላክሽ።
10“ወዳጆቿ የሆናችሁ ሁሉ፣
ከኢየሩሳሌም ጋር ደስ ይበላችሁ፤
ስለ እርሷም ሐሤት አድርጉ፤
ለእርሷ ያለቀሳችሁ ሁሉ፣
ከእርሷ ጋር እጅግ ደስ ይበላችሁ።
11ከሚያጽናኑ ጡቶቿ፣
ትጠባላችሁ፤ ትረካላችሁም፤
እስክትረኩም ትጠጣላችሁ፤
በተትረፈረፈ ሀብቷም ትደሰታላችሁ።

12እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤

“እነሆ ሰላምን እንደ ወንዝ ውሃ
አፈስላታለሁ፤
የመንግሥታትንም ብልጥግና እንደ ጅረት ውሃ
አጐርፍላታለሁ፤
ትጠባላችሁ፤ በዕቅፏም ትያዛላችሁ፤
በጭኖቿም ላይ ትፈነድቃላችሁ።
13እናት ልጇን እሹሩሩ እንደምትል፣
እኔም እናንተን እሹሩሩ እላችኋለሁ፤
በኢየሩሳሌምም ትጽናናላችሁ።

14ይህን ስታዩ፣ ልባችሁ ሐሤት ያደርጋል፤
ዐጥንቶቻችሁም እንደ ሣር ይለመልማሉ፤
የእግዚአብሔር እጅ ከባሮቹ ጋር መሆኑ
ይታወቃል፤
ቍጣው ግን በጠላቶቹ ላይ ይገለጣል።
15እነሆ፤ እግዚአብሔር በእሳት ነበልባል
ይመጣል፤
ሠረገሎቹም እንደ ዐውሎ ነፋስ ናቸው፤
ንዴቱን በቍጣ፣
ተግሣጹንም በእሳት ነበልባል ይገልጣል።
16በእሳትና በሰይፍ፣
እግዚአብሔር ፍርዱን በሰው ሁሉ ላይ
ያመጣል፤
በእግዚአብሔር ሰይፍ የሚታረዱት ብዙ
ይሆናሉ።
17“ወደ አትክልት ቦታዎች ለመሄድና
ከተክሎቹ አንዱን ለማምለክ ራሳቸውን
የሚቀድሱና የሚያነጹ፣ የዕሪያዎችንና የዐ
ይጦችን ሥጋ፣ የረከሱ ነገሮችንም የሚበሉ
ሁሉ የመጨረሻ ፍርዳቸውን በአንድነት
ይቀበላሉ” ይላል እግዚአብሔር።
18“እኔም ሥራቸውንና ሐሳባቸውን ስለ
ማውቅ፣ መንግሥታትንና ልሳናትን ሁሉ
ልሰበስብ እመጣለሁ፤[ከ] እነርሱም መጥተው
ክብሬንም ያያሉ።
19“በመካከላቸው ምልክት አደርጋለሁ፤ ከእነ
ርሱም የተረፉትን አንዳንዶቹን ወደ አሕ
ዛብ ወደ ተርሴስ፣ ወደ ፉጥ፣ ወደ ታወቁት
ቀስተኞች ወደ ሉድ፣ ወደ ቶባልና ያዋን
እንዲሁም ዝናዬን ወዳልሰሙትና ክብሬን
ወዳላዩት ራቅ ወዳሉት ደሴቶች እልካቸዋ
ለሁ፤ በሕዝቦችም መካከል ክብሬን ይናገራሉ።
20ለእግዚአብሔር ቍርባን እንዲሆኑ ወንድሞ
ቻችሁን ሁሉ ከየመንግሥታቱ ወደ ተቀደሰው
ተራራዬ ወደ ኢየሩሳሌም በፈረስ፣ በሠረገ
ላና በጋሪ፣ በበቅሎና በግመል ያመጧቸዋል”
ይላል እግዚአብሔር። “እስራኤላውያን
የእህል ቍርባናቸውን በሥርዐቱ መ
ሠረት በነጹ
ዕቃዎች ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
እንደሚያቀርቡ እነዚህንም ያቀርቧቸዋል።
21እኔም ካህናትና ሌዋውያን ይሆኑ ዘንድ
አንዳንዶቹን እመርጣቸዋለሁ” ይላል እግዚ
አብሔር።
22“እኔ የምሠራቸው አዲስ ሰማያትና አዲስ
ምድር በፊቴ ጸንተው እንደሚኖሩ፣ የእናንተና
የዘራችሁ ስም እንደዚሁ ጸንቶ ይኖራል”
ይላል እግዚአብሔር፤ 23“ከአንዱ ወር መባቻ
እስከ ሌላው፣ እንዲሁም ከአንዱ ሰንበት
እስከ ሌላው፣ የሰው ልጅ ሁሉ በፊቴ ሊሰግድ
ይመጣል” ይላል እግዚአብሔር፤ 24“ወጥተ
ውም በእኔ ላይ ያመፁትን ሰዎች ሬሳ
ያያሉ፤ ትላቸው አይሞትም፤ እሳታቸው
አይጠፋም፤ ለሰውም ዘር ሁሉ አስጸያፊ
ይሆናሉ።”

**66፥10** ዘዳ32፥43፤ መዝ26፥8፤ኢሳ25፥9፤ 57፥19፤61፥2፤ ሮሜ15፥10
**66፥11** ዘፍ49፥25፤ ዘኍ11፥12፤25፥1፤ ኢሳ25፥6፤60፥16
**66፥12** ዘኍ11፥12፤ መዝ72፥3፤119፥165፤ኢሳ9፥6፤33፥21፤ 60፥4፡5፤61፥6
**66፥13** ኢሳ40፥1፤ 49፥15፤2ቆሮ1፥4፤ 1ተሰ2፥7
**66፥14** ዕዝ5፥5፤ መዝ72፥16፤ኢሳ10፥5፤ 25፥9፤30፥27፤41፥20፤54፥17፤60፥5፤ኢል2፥23
**66፥15** ዘዳ28፥20፤ 2ነገ2፥1፡11፤መዝ9፥5፤ 39፥11፤68፥17፤ ኢሳ1፥31፤42፥25
**66፥16** ኢሳ1፥20፤ 10፥4፤13፥9፡11፤ 27፥1፤30፥30፤ ኤር2፥35፤ሕዝ14፥21፤ 36፥5፤አሞ7፥4፤ ሚል4፥1
**66፥17** ዘሌ11፥7፡29፤ መዝ37፥20፤ ኢሳ1፥28፡ 29
**66፥18** ዘፀ16፥7፤ ምሳ24፥2፤ ኢሳ2፥3፤ 59፥19፤65፥2፤ዘካ12፥3
**66፥19** ዘፍ10፥2፤ 2ነገ19፥31፤ 1ዜና16፥24፤ኢሳ2፥16፤ 11፥10፡11፤24፥15፤ 49፥22፤ኤር31፥10፤ 46፥9፤ሕዝ27፥10፤ ዳን11፥18፤ማቴ24፥30
**66፥20** ዘዳ33፥19፤ ዕዝ2፥66፤ኢሳ2፥2፤ 11፥12፤52፥11፤ ኤር25፥22፤31፥23፤ ሕዝ34፥13
**66፥21** ዘፀ19፥6፤ 1ጴጥ2፥5፡9
**66፥22** ኢሳ48፥19፤ 65፥17፤ዮሐ10፥27-29፤ ዕብ12፥26-27፤ 1ጴጥ1፥4-5፤ 2ጴጥ3፥13
**66፥23** መዝ22፥29፤ ኢሳ19፥21፤44፥5፤ ሕዝ46፥1-3፤ራእ15፥4 **66፥24** መዝ110፥6፤ ኢሳ1፥2፤ 14፥11፤ማቴ25፥41፤ማር9፥48

[ከ]18 በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጕም በትክክል አይታወቅም።

# ትንቢተ ኤርምያስ

1 የኬልቅያስ ልጅ፣ ኤርምያስ የተናገ
ረው ቃል ይህ ነው፤ አባቱ በብንያም
አገር በዓናቶት ከሚገኙት ካህናት አንዱ
ነበረ። [2]*የእግዚአብሔር* ቃል የይሁዳ ንጉሥ፣
የአሞን ልጅ ኢዮስያስ በነገሠ በዐሥራ
ሦስተኛው ዓመት ወደ ኤርምያስ መጣ፤
[3]ደግሞም በይሁዳ ንጉሥ፣ በኢዮስያስ
ልጅ በኢዮአቄም ንግሥ ዘመን፤ እንዲሁም
በይሁዳ ንጉሥ፣ በኢዮስያስ ልጅ በሴዴ
ቅያስ ንግሥ ዘመን፤ እስከ ዐሥራ አንደ
ኛው ዓመት መጨረሻ ድረስ የኢየሩሳ
ሌም ሕዝብ ተማርኮ እስከ ሄደበት እስከ
አምስተኛው ወር ድረስ ወደ እርሱ ይመጣ
ነበር።

## የኤርምያስ መጠራት

[4]*የእግዚአብሔር* ቃል ወደ እኔ መጣ፤
እንዲህም አለኝ፤

[5]"በማሕፀን ሳልሠራህ ዐወቅሁህ፤
ከመወለድህ በፊት ለየሁህ፤[ሀ]
ለሕዝቦችም ነቢይ እንድትሆን
ሾምሁህ።"

[6]እኔም፣ "ጌታ *እግዚአብሔር* ሆይ፤ እን
ዴት እንደምናገር አላውቅም፤ ገና ሕፃን
ልጅ ነኝና" አልሁ።
[7]*እግዚአብሔር* ግን እንዲህ አለኝ፤ "'ገና
ሕፃን ልጅ ነኝ' አትበል፤ ወደምልክህ ሁሉ
ሄደህ፣ ያዘዝሁን ሁሉ ትናገራለህ፤ [8]እኔ
አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ
ቸው" ይላል *እግዚአብሔር*።
[9]*እግዚአብሔርም* እጁን ዘርግቶ አፌን
ዳሰሰና እንዲህ አለኝ፤ "እነሆ፤ ቃሌን
በአፍህ
አኑሬአለሁ፤ [10]እንግዲህ፣ እንድትነቅልና
እንድታፈርስ፣ እንድታጠፋና እንድትገለ
ብጥ፣ እንድታንጽና እንድትተክል በአሕዛ
ብና በመንግሥታት ላይ ዛሬ ሾምሁህ።"
[11]*የእግዚአብሔር* ቃል፣ "ኤርምያስ ሆይ፣
ምን ታያለህ'" ሲል ወደ እኔ መጣ።
እኔም፣ "የለውዝ በትር አያለሁ" አልሁ።
[12]*እግዚአብሔርም*፣ "ትክክል አይተሃል፤
ቃሌን እፈጽመው ዘንድ እተጋለሁና"[ለ] አለኝ።
[13]ዳግመኛም *የእግዚአብሔር* ቃል፣ "ምን
ታያለህ?" ሲል ወደ እኔ መጣ።
እኔም፣ "አንድ የሚፈላ ማሰሮ አያለሁ፤
አፉም ከሰሜን ወደዚህ ያዘነበለ ነው"
አልሁ።
[14]*እግዚአብሔርም* እንዲህ አለኝ፤ "ከሰሜን

1፥1 ኢሱ21፥18
1፥2 2ነገ22፥1፤ሕዝ 1፥3፤ሆሴ1፥1፤ኢል 1፥1
1፥3 2ነገ23፥34፤ 24፥17፤ዕዝ5፥12፤ኤር 52፥15
1፥5 ቀኊ10፤መዝ 139፥13፡16፤ኢሳ 49፥1፤ኤር25፥15-26 ፤ዮሐ10፥36
1፥6 ዘፀ3፥11፤6፥12 ፤1ነገ3፥7
1፥8 ቀኊ19፤ዘፍ 15፥1፤26፥3፤ኢሱ1፥5 ፤8፥1፤ኤር15፥20፡21፤ 26፥24፤36፥26፤42፥ 11፤20፥11
1፥9 ዘፀ4፥12፤ኢሳ 6፥7
1፥10 ኤር 25፥17፤ 46፥1፤ 12፥17፤ 18፥7-10፤24፥6፤ 31፥4፡28
1፥11 ኤር24፥3፤ አሞ7፥8
1፥12 ኢዮ29፥2፤ ኤር44፥27
1፥13 ኤር24፥3፤ዘካ 4፥2፤5፥2
1፥14 ኢሳ14፥31
1፥15 ኤር4፥16፤ 9፥11፤10፥22
1፥16 ዘፍ6፥5፤ዘፀ 20፥3፤ዘኍ25፥3፤መዝ 115፥4-8፤135፥15፤ ኤር2፥13፤4፥12፤7፥9፤ 17፥13፤19፥4፤44፥3፡5
1፥17 ቀኊ7፤ዘዳ31፥6፤ 2ነገ1፥15ኤር7፥27 ፤26፥2፡15፤42፥4
1፥18 ኢሳ50፥7
1፥19 ቀኊ8፤ዘፍ26፥3፤ መዝ129፥2፤ምሳ20፥2 2፤ኢሳ43፥2፤ኤር 20፥11፤ሐሥ26፥17
2፥1 ኢሳ38፥4፤ሕዝ 1፥3፤ሚክ1፥1
2፥2 ዘፀ13፥21፤ዘዳ 1፥19፤መዝ71፥17፤ ኢ. ሳ54፥4፤ኤር3፥4 ፤ሕ ዝ16፥8-14፡60፤ ሆሴ2፥15፤11፥1፤ ራእ 2፥4፤
2፥3 ዘፀ19፥6፤ዘሌ 23፥9-14፤ዘዳ7፥6፤ኢሳ 41፥11፤ኤር10፥25 ፤30፥16፤50፥7፤ያዕ 1፥18፤ራእ14፥4፤

በምድሪቱ በሚኖሩ ሁሉ ላይ ድንገት መዓ
ት ይወርድባቸዋል። [15]እነሆ፤ የሰሜን
መንግ ሥታትን ሕዝቦች ሁሉ እጠራለሁ"
ይላል *እግዚአብሔር*፤

"ንጉሦቻቸው ይመጣሉ፤
ዙፋናቸውን በኢየሩሳሌም መግቢያ
በሮች፣
በቅጥሮቿ ዙሪያ ሁሉ፣
በይሁዳም ከተሞች ሁሉ ይዘረጋሉ።
[16]እኔን በመተው ክፋት ስለ ሠሩ፣
ለሌሎች አማልክት ዕጣን ስላጠኑ፣
እጆቻቸው የሠሯቸውን ስላመለኩ፣
በሕዝቤ ላይ ፍርድን ዐውጃለሁ።

[17]"አንተ ግን ወገብህን ታጠቅ፤ ተነሥ
ተህም ያዘዝሁን ሁሉ ንገራቸው፤ አትፍራ
ቸውም፤ አለዚያ በፊታቸው አስፈራሃለሁ።
[18]እነሆ፤ ዛሬ በመላዪቱ ምድር ላይ አስነ
ሣሃለሁ ይኸውም የይሁዳን ነገሥታት፣
አለቆቿን፣ ካህናቷንና የምድሪቱን ሕዝብ
ሁሉ መቋቋም እንድትችል የተመሸገ
ከተማ፣ የብረት ምሰሶና የናስ ቅጥር አድ
ርጌሃለሁ። [19]ይዋጉሃል፤ ዳሩ ግን አድንህ
ዘንድ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አያሸንፉህም"
ይላል *እግዚአብሔር*።

## የእስራኤል ሕዝብ አምላኩን መተው

2 *የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤

[2]"ሂድና ጮኸህ ይህን ለኢየሩሳሌም ጆሮ
አሰማ፤
"*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
'በወጣትነትሽ ጊዜ የነበረሽን ታማኝነት፣
በሙሽርነትሽም ወራት እንዴት እንደ
ወደድሽኝ፣
በምድረ በዳ ዘር በማይዘራበት ምድር፣
እንዴት እንደተከተልሽኝ
አስታውሳለሁ።
[3]እስራኤል *ለእግዚአብሔር* ቅዱስ ነበረች፤
የመከሩም በኵር ነበረች፤
የዋጧት ሁሉ በደለኞች ሆኑ፤
መዓትም ደረሰባቸው'"
ይላል *እግዚአብሔር*።

[4]የያዕቆብ ቤት ሆይ፤
የእስራኤል ቤት ወገን ሁላችሁ፣

[ሀ]5 ወይም *መረጥሁህ*
[ለ]12 *እተጋለሁ* ለሚለው የዕብራይስጡ አነባብ *የለውዝ በትር* ከሚለው ጋር ይመሳሰላል።

የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ።

5እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“አባቶቻችሁ ከእኔ የራቁት፣
ከንቱ ነገርን የተከተሉት፣
ራሳቸውም ከንቱ የሆኑት፣
ምን ጥፋት አግኝተውብኝ ነው?
6እነርሱም፣ ‘ከግብፅ ምድር ያወጣን፣
በወና ምድረ በዳ፣
በጕድጓዳና በበረሓ መሬት፣
በደረቅና በጨለማ[ሐ] ቦታ፣
ሰው በማያልፍበትና በማይኖርበት ስፍራ፣
የመራን እግዚአብሔር ወዴት ነው?’
ብለው አልጠየቁም።
7እኔ፣ ፍሬዋንና በረከቷን እንድትበሉ፣
ለም ወደ ሆነ መሬት አመጣኋችሁ፤
እናንተ ግን መጥታችሁ ምድሬን
አረከሳችሁ፤
ርስቴንም ጸያፍ አደረጋችሁ።
8‘እግዚአብሔር ወዴት ነው?’ ብለው፣
ካህናቱ አልጠየቁም፤
ከሕጉ ጋር የሚውሉት አላወቁኝም፤
መሪዎቹ ዐመፁብኝ፤
ነቢያቱም በበኣል ስም ተነበዩ፤
ከንቱ ነገሮችን ተከተሉ።
9“ስለዚህ እንደገና ከእናንተ ጋር
እፋረዳለሁ፤”
“ከልጅ ልጆቻችሁም ጋር እከራከራለሁ።
ይላል እግዚአብሔር።
10ወደ ኪቲም[መ] ጠረፍ ተሻገሩና እዩ፤
ወደ ቄዳርም[መ] ልካችሁ በጥንቃቄ
መርምሩ፣
እንዲህ ዐይነት ነገር ተደርጎ ያውቅ
እንደሆነ ተመልከቱ፤
11የእውነት አማልክት ባይሆኑም እንኳ፣
አማልክቱን የለወጠ ሕዝብ አለን?
ሕዝቤ ግን ክብራቸው[ሠ] የሆነውን፣
በከንቱ ነገር ለወጡ።
12ሰማያት ሆይ፤ በዚህ ተገረሙ፤
በታላቅ ድንጋጤም ተንቀጥቀጡ፤”
ይላል እግዚአብሔር።
13“ሕዝቤ ሁለት ኀጢአት ፈጽመዋል፣
ሕያው የውሃ ምንጭ የሆንሁትን፣
እኔን ትተዋል፤
ውሃ መያዝ የማይችሉትን ቀዳዳ የውሃ
ማጠራቀሚያ ጕድጓዶች፣
ለራሳቸው ቈፍረዋል።
14እስራኤል ባሪያ ነውን? ወይስ የቤት
ውልድ ባሪያ?
ታዲያ፣ ስለምን ለብዝበዛ ተዳረገ?
15አንበሶች በእርሱ ላይ አገሡ፤
በኀይለኛ ድምፅም ጮኹበት።
ምድሩን ባድማ አድርገውበታል፤
ከተሞቹ ተቃጥለዋል፤ ወናም ሆነዋል።

16ደግሞም የሜምፎስና[ረ] የጣፍናስ ሰዎች፣
መኻል ዐናትሽን ላጩሽ።[ሰ]
17በመንገድ የሚመራሽን፣
እግዚአብሔር አምላክሽን በመተውሽ፣
ይህን በራስሽ ላይ አላመጣሽምን?
18ከሺሖር[ሸ] ወንዝ ውሃ ለመጠጣት፣
አሁንስ ለምን ወደ ግብፅ ወረድሽ?
ከኤፍራጥስ ወንዝስ ውሃ ለመጠጣት፣
ወደ አሦር መውረድ ለምን አስፈለገሽ?
19ክፋትሽ ቅጣት ያስከትልብሻል፤
ክህደትሽም ተግሣጽ ያመጣብሻል፤
እግዚአብሔር አምላክሽን ስትተዪ፣
እኔንም መፍራት ችላ ስትዪ፣
ምን ያህል ክፉና መራራ
እንደሚሆንብሽ፣
አስቢ፤ እስቲ አስተውዪ፤”
ይላል የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር።
20“ከጥንት ጀምሮ ቀንበርሽን ሰበርሁ፤
እስራትሽን በጣጠስሁ፤
አንቺም፣ ‘አላገለግልህም!’ አልሽ፤
ከፍ ባለውም ኰረብታ ሁሉ ሥር፣
በያንዳንዱም ለምለም ዛፍ ሥር፣
ለማመንዘር ተጋደምሽ።
21እኔ፣ እንደ ምርጥ የወይን ተክል፣
ጤናማና አስተማማኝ ዘር አድርጌ
ተክዬሽ ነበር፤
ታዲያ ብልሹ የዱር ወይን ተክል ሆነሽ፣
እንዴት ተለወጥሽብኝ?
22በልዩ ቅጠል ብትታጠቢ፣
ብዙ ሳሙና ብትጠቀሚም፣
የበደልሽ ዕድፍ አሁንም በፊቴ ነው፤”
ይላል ጌታ እግዚአብሔር።
23“ ‘አልረከስሁም፣
በኣሊምን አልተከተልሁም’ እንዴት
ትያለሽ?
በሸለቆ ውስጥ ምን እንዳደረግሽ እስቲ
አስቢ፣
ምንስ እንደ ፈጸምሽ ተገንዘቢ፤
እንደምትፋንን ፈጣን ግመል ሆነሻል፤
24በምድረ በዳ እንደ ለመደች፣
በፍትወቷ ነፋስን እንደምታነፈንፍ፣
የሜዳ አህያ ነሽ፤
ከመጎምጀቷ ማን ሊገታት ይችላል?
ለሚፈልጓት ሁሉ ያለ ምንም ድካም፤
በፍትወቷ ወራት በቀላሉ
ትገኝላቸዋለች።

2፥5 ዘዳ 32፥21፤ 1ሳሙ 12፥21፤ 2ነገ 17፥15፤ መዝ31፥6
2፥6 ዘፀ6፥6፤ ዘዳ 1፥19፤ 32፥10፤ ኤር 51፥43፤ ሆሴ13፥4
2፥7 ዘኍ13፥27፤ ዘዳ8፥7-9፤ 11፥10-12፤ መዝ106፥34-39፤ ኤር 3፥9፤ 7፥30፤ 16፥18፤ ሕዝ11፥21፤ 36፥17
2፥8 ቀኍ25፥1 ሳሙ 2፥12፤ 1ነገ18፥22፤ ኢሳ40፥19፤ 56፥10፤ ኤር3፥15፤ 4፥22፤ 5፥19፤ 9፥14፤ 16፥19፤ 22፥9፤ 23፥1፤ 25፥34፤ 50፥6፤
2፥9 ኤር25፥31፤ ሆሴ4፥1፤ ሚክ 6፥2
2፥10 ዘፍ10፥4፤ 25፥13
2፥11 ኢሳ37፥19፤ ኤር16፥20፤ 1ሳሙ4፥21፤ ሮሜ1፥23፤ ገላ 4፥8
2፥13 ዘዳ31፥16፤ ኢሳ12፥3፤ 65፥11፤ ዮሐ4፥14
2፥14 ዘፀ4፥22፤ ኤር 31፥9
2፥15 ዘሌ26፥43፤ ኢሳ1፥7፤ 2ነገ25፥9፤ ኤር4፥7፤ 50፥17
2፥16 ኢሳ19፥13፤ ኤር43፥7-9
2፥17 ኢሳ1፥28፤ ኤር4፥18፤ 17፥13፤ 19፥4
2፥18 ኢሱ13፥3፤ 2ነገ16፥7፤ ኢሳ7፥20፤ 30፥2፤ ሆሴ5፥13፤ 7፥11፤ 8፥9
2፥19 ኢዮ20፥14፤ መዝ36፥1፤ ኢሳ3፥9፤ 59፥12፤ ኤር3፥11፤ 22፤ 7፥24፤ 11፥10፤ 14፥7፤ 19፥4፤ ሆሴ5፥5፤ 14፥4፤ አሞ 8፥10፤
2፥20 ዘሌ26፥13፤ ዘዳ12፥2፤ ኢዮ21፥14፤ መዝ2፥3፤ ኢሳ1፥21፤ 57፥7፤ ኤር3፥23፤ 5፥5፤ 17፥2፤ ሕዝ16፥15
2፥21 ዘፀ15፥17፤ መዝ80፥8፤ ኢሳ5፥4
2፥22 ኢዮ9፥30፤ መዝ51፥2፤ ኤር17፥1፤ ሰቆ1፥8፥17
2፥23 ቀኍ 25፥33፤ ምሳ30፥12፤ 2ነገ23፥10፤ ኤር7፥31፤ 9፥14፤ 19፥2፤ 23፥27፤ 31፥22፥ 40
2፥24 ዘፍ16፥12፤ ኢ ዮ39፥6፤ ኤር14፥6

[ሐ]6 ወይም *በሞት ጥላ*
[መ]10 *ኪቲም* ቆጵሮስና የምዕራባዊ የባህር ዳርቻ ማለት ነው
[መ]10 *ቄዳር* በሶርያዊ ዐረቢያ ምድረ በዳ የሚገኙ የበዶይን ነገዶች መኖሪያ
[ሠ]11 የዕብራውያን የጥንት ጸሐፍት ትውፊት የሆነው የማሶሬቲክ ጽሑፍ *ክብሬን* ይላል
[ረ]16 ሜምፎስ በዕብራይስጡ *ኖፍ* ይላል ወይም *ጭንቅላትሽን ፈጠፈጡ* /ሰነጠቀ [ሰ]
[ሸ]18 የዐባይ ወንዝ አንዱ ተነጣይ ጅረት ነው

25እግርሽ እስኪነቃ አትሩጪ፤
ጕሮሮሽም በውሃ ጥም እስኪደርቅ
አትቅበዝበዢ።
አንቺ ግን፣ ‘በከንቱ አትድከም፤
ባዕዳን አማልክትን ወድጃለሁ፤
እነርሱን እከተላለሁ’ አልሽ።

26“ሌባ በተያዘ ጊዜ እንደሚያፍር፣
የእስራኤልም ቤት አፍሮአል፤
እነርሱ፣ ንጉሦቻቸውና ሹሞቻቸው፣
ካህናታቸውና ነቢያታቸው እንዲሁ
ያፍራሉ።
27ዛፉን፣ ‘አንተ አባቴ ነህ’
ድንጋዩንም፣ ‘አንተ ወለድኸኝ’ አሉ፤
ፊታቸውን ሳይሆን፣
ጀርባቸውን ሰጥተውኛልና፤
በመከራቸው ጊዜ ግን፣
‘መጥተህ አድነን!’ ይላሉ።
28ታዲያ፣ ለታመልካቸው ያበጀሃቸው
አማልክት ወዴት ናቸው?
በመከራህ ጊዜ ሊያድኑህ የሚችሉ
ከሆነ፣
ይሁዳ ሆይ፤ እስቲ ይምጡና ያድኑህ፤
የከተሞችህን ቍጥር ያህል፣
የአማልክትህም ብዛት እንዲሁ ነውና።

29“ለምን በእኔ ታማርራላችሁ?
ያመፃችሁብኝ እናንተ ሁላችሁ ናችሁ፤”
ይላል *እግዚአብሔር*።
30“ልጆቻችሁን በከንቱ ቀጣኋቸው፤
እነርሱም አልታረሙም።
ሰይፋችሁ እንደ ተራበ አንበሳ፣
ነቢያታችሁን በልቶአል።

31“የዚህ ትውልድ ሰዎች ሆይ፤ የ*እግዚ
አብሔር*ን ቃል አስተውሉ፤
“እኔ ለእስራኤል ሕዝብ ምድረ በዳ፣
ወይስ ድቅድቅ ጨለማ ያለበት ምድር
ሆንሁበትን?
ሕዝቤ፣ ‘እንደ ልባችን ልንሆን
እንፈልጋለን፤
ተመልሰንም ወደ አንተ አንመጣም’
ለምን ይላል?
32ለመሆኑ ቆንጆ ጌጣጌጧን፣
ሙሽራ የሰርግ ልብሷን ትረሳለችን?
ሕዝቤ ግን፣
እጅግ ብዙ ቀን ረስቶኛል።
33በፍትወት ለማጥመድ እንዴት ስልጡን
ነሽ?
ልክስክስ ክፉ ሴቶች እንኳ ከመንገድሽ
ብዙ ክፉት ይማራሉ።
34በስርቆት ያልያዝሻቸው፣
የንጹሓን ድኾች ደም፣
በልብስሽ ላይ ተገኝቶአል።
ይህን ሁሉ አድርገሽም፣
35‘እኔ ንጹሕ ነኝ፤
በእርግጥ ቍጣው ከእኔ ርቆአል’
ትያለሽ።
እኔ ግን እፈርድብሻለሁ፤
‘ኀጢአት አልሠራሁም’ ብለሻልና።
36መንገድሽን እየለዋወጥሽ፣
ለምን ትሮጫለሽ?
አሦር እንዳዋረደሽ፣
ግብፅም እንዲሁ ያዋርድሻል።
37የታመንሽባቸውን *እግዚአብሔር*
ስላዋረደ፣
በእነርሱም ስለማይከናወንልሽ፣
እጆችሽን በራስሽ ላይ አድርገሽ፣
ከዚያም ትወጫለሽ።

3 “ሰው ሚስቱን ቢፈታ፣
እርሷም ሄዳ ሌላ ሰው ብታገባ፣
ወደ እርሷ ይመለሳልን?
ምድሪቱስ ፈጽማ አትረክስምን?
አንቺ ግን ከብዙ ወዳጆችሽ ጋር
አመንዝረሻል፤
ታዲያ አሁን ወደ እኔ መመለስ
ትፈልጊያለሽን?”
ይላል *እግዚአብሔር*።
2“እስቲ ቀና ብለሽ ጭር ያሉትን
ኰረብቶች ተመልከቺ፣
በርኵሰት ያልተጋደምሽበት ቦታ
ይገኛልን?
በበረሓ፣ እንደ ተቀመጠ ዘላን ዐረብ፣
በየመንገዱ ዳር ተቀምጠሽ
ወዳጆችሽን ጠበቅሽ።
በዝሙትሽና በክፉትሽ፣
ምድሪቱን አረከስሽ።
3ስለዚህ ካፊያ ተከለከለ፤
ኋለኛው ዝናብም ጠፋ።
አንቺ ግን አሁንም የጋለሞታ ገጽታ
አለብሽ፤
ዐይንሽን በዕፍረት አልሰብር ብለሻል።
4አሁንም ወደ እኔ ተጣርተሽ፣
‘አባቴ፣ የልጅነት ወዳጄ፣
5ሁልጊዜ ትቈጣለህን?
ቍጣህስ ለዘላለም ነውን?’ አላልሽኝም?
የምትናገሪው እንዲህ ነው፤
ይሁን እንጂ የቻልሽውን ክፉት ሁሉ
ታደርጊያለሽ።”

## ከዳተኛዋ እስራኤል

6*እግዚአብሔር* በንጉሥ ኢዮስያስ ዘመን
እንዲህ አለኝ፤ “ከዳተኛዪቱ እስራኤል ያደ
ረገችውን አየህን? ከፍ ወዳለው ኰረብታ
ሁሉ ወጥታ፣ ወደ ለመለመው ዛፍ ሥር
ሁሉ ሄዳ በዚያ አመንዝራለች። 7ይህን ሁሉ

2፥25 ቍ8፥23፤ዘዳ 32፥16፤ኢሳ57፥10፤ ኤር3፥13፤14፥10
2፥26 ኤር32፥32፤ 44፥17፡21፤48፥27፤ ሰቆ1፥7፤ሕዝ16፥54፤ 22፥26፤36፥4
2፥27 መሳ10፥10፤ 1ነገ14፥9፤2ዜና29፥6፤ መዝ14፥3፤ኢሳ26፥16 ፤37፥20፤ኤር3፥9፤10፥ 8፤18፥17፤32፥33፤ሕዝ 7፥22፤8፥16፤ሆሴ 5፥15
2፥28 ዘዳ32፥37፤ 2ነገ17፥29፤ኢሳ 40፥19፤45፥20፤
2፥29 ኤር5፥1፤ 6፥13፤ዳን9፥11፤ሚክ 3፥11፤7፥2
2፥30 ዘሌ26፥23፤ ነህ9፥26፤ኤር11፥21፤ ሐሥ7፥52፤1ተሰ2፥15
2፥31 ኢዮ21፥14፤ ኢሳ 45፥19
2፥32 ዘዳ32፥18፤ ኢ ሳ 57፥11
2፥33 ቍ 23
2፥34 ዘፀ 22፥2፤ 2ነገ21፥16፤ምሳ6፥17
2፥35 2ሳሙ12፥13፤ ምሳ30፥12፤ኢሳ66፥ 16፤ኤር25፥31፤39፥7፤ 45፥5፤ሕዝ17፥20፤ 20፥35፡ኢል3፥2፤ 1ዮሐ1፥8፡10
2፥36 መዝ108፥12፤ ኢሳ30፥2፡ 3፡7፤ኤር31፥22፤37፥7
2፥37 2ሳሙ13፥19፤ ኤር37፥7
3፥1 ዘፍ3፥17፤ዘዳ 24፥1-4፤2ነገ16፥7፤ ኢሳ1፥21፤ኤር2፥20፡ 25፤4፥30፤ሰቆ1፥2፤ ሕ ዝ16፥26፡29፤ሆሴ 2፥5፡7፡12፤3፥1
3፥2 ቍ9፥21፤ዘፍ 38፥14፤ዘኍ15፥39፤ ኢሳ1፥21፤ሕዝ16፥25
3፥3 ዘሌ26፥19፤ ዘዳ11፥14፤ኤር5፥25፤ 6፥15፤14፥4፤ሕዝ3፥7፤ 16፥30፤8፥12፤ኢል 1፥10፤አሞ4፥7፤ሶፎ 2፥1፤3፥5
3፥4 ቍ19፤ዘዳ32፥ 6፤መዝ89፥26፤ኢሳ 63፥16፤64፥8፤ኤር 31፥9፤2፥2
3፥5 መዝ103፥9፤ ኢ ሳ54፥9
3፥6 ቍ12፡22፤ ዘሌ17፥7፤ ዘዳ12፥2፤ 1ዜና3፥14፤ኢሳ 24፥16፤ኤር2፥20፤ 17፥2፤31፥22፤49፥4፤ሕ ዝ20፥28፤ሆሴ4፥13
3፥7 ሕዝ16፥46፤

ካደረገች በኋላ፣ ወደ እኔ ትመለሳለች ብዬ
ነበር፤ ሆኖም አልተመለሰችም፤ ከሓዲዋ
እኅቷ ይሁዳም ይህን አየች። 8ለከዳተኛ
ዪቱ እስራኤል ስለ ምንዝርናዋ ሁሉ
የፍች ወረቀቷን ሰጥቼ አባረርኋት። ከሓዲዋ
እኅቷ ይሁዳም ይህን አይታ እንዳልፈራች
አየሁ፤ ወጥታም አመነዘረች። 9በቅሌቷም
ምድሪቱን አረከሰች፤ ከድንጋይና ከግንድ
ጋር አመነዘረች፤ 10ይህም ሁሉ ሆኖ ከሓዲዋ
እኅቷ ይሁዳ ወደ እኔ የተመለሰችው በማ
ስመሰል እንጂ በሙሉ ልቧ አልነበረም”
ይላል *እግዚአብሔር*።
11*እግዚአብሔር* እንዲህ አለኝ፤ “ከከሓዲዋ
ይሁዳ ይልቅ ከዳተኛዪቱ እስራኤል ጻድቅ
ሆና ተገኘች። 12ሂድና ይህን መልእክት
ወደ ሰሜን እንዲህ ብለህ ተናገር፤

“ ‘ከዳተኛዪቱ እስራኤል ሆይ፤ ተመለሽ’
ይላል *እግዚአብሔር*፤
‘እኔ መሓሪ ስለ ሆንሁ፣
ከእንግዲህ በቍጣ ዐይን አላይሽም’
ይላል *እግዚአብሔር*።
‘ለዘላለም አልቈጣም።
13በአምላክሽ *በእግዚአብሔር* ላይ
በማመፅሽ፣
ክብርሽንም ለእንግዶች አማልክት፣
በየለምለሙ ዛፍ ሥር አሳልፈሽ
በመስጠት፣
ለእኔ ባለመታዘዝሽ፣
በደለኛ መሆንሽን ይህን አንድ ነገር
ብቻ እመኚ’ ”
ይላል *እግዚአብሔር*።

14“ከዳተኛ ልጆች ሆይ፤ እኔ ባለቤታ
ችሁ ነኝና ተመለሱ” ይላል *እግዚአብሔር*፤
“ከአንድ ከተማ አንድ፣ ከአንድ ነገድ ሁለት
መርጫችሁ ወደ ጽዮን አመጣችኋለሁ።
15እንደ ልቤም የሆኑ፣ በዕውቀትና በማስ
ተዋል የሚመሯችሁን እረኞች እሰጣችኋ
ለሁ። 16ቍጥራችሁ በምድሪቱ እጅግ በሚ
በዛበት ጊዜም ይላል *እግዚአብሔር*፤ “በዚያ
ዘመን፣ ‘*የእግዚአብሔር* የኪዳኑ ታቦት’
ብለው ከእንግዲህ አይጠሩም፤ ትዝ አይላ
ቸውም፤ አያስታውሱትምም፤ አይጠፋም፤
ሌላም አይሠራም። 17በዚያ ጊዜ ኢየሩሳ
ሌምን፣ ‘*የእግዚአብሔር* ዙፋን’ ብለው
ይጠሯታል፤ መንግሥታትም ሁሉ *የእግዚአ
ብሔርን* ስም ለማክበር በኢየሩሳሌም ይሰበ
ሰባሉ፤ የክፉ ልባቸውንም እልኸኝነት ከእ
ንግዲህ አይከተሉም። 18በዚያን ዘመን የይ
ሁዳ ቤትና የእስራኤል ቤት በአንድነት
ሆነው ከሰሜን ምድር ለአባቶቻቸው
ርስት አድርጌ ወደ ሰጠኋቸው ምድር
ይመጣሉ።

19“እኔም፣
“ ‘የተመረጠችውን ምድር፣
የትኛውም ሕዝብ ያላገኘውን የተዋበች
ርስት ልሰጥሽ፣
እንደ ወንዶች ልጆቼ ምንኛ በደስታ
ልቈጥርሽ” አልሁ፤
‘አባቴ’ ብለሽ የምትጠሪኝ፣
እኔንም ከመከተል ዘወር የማትይ
መስሎኝ ነበር።
20የእስራኤል ቤት ሆይ፤ ለባሏ ታማኝ
እንዳልሆነች ሚስት፣
ስታታልሉኝ ኖራችኋል፤”
ይላል *እግዚአብሔር*።

21*እግዚአብሔር* አምላካቸውን በመርሳት፣
መንገዳቸውን አጣመዋልና፣
የእስራኤል ሕዝብ ጩኸት፣
አሳዛኝ ልቅሶ ባድማ ከሆኑት
ኰረብታዎች ተሰማ።

22“እናንት ከዳተኞች ልጆች ተመለሱ፤
ከዳተኝነታችሁን እፈውሳለሁ።”
“አንተ *እግዚአብሔር* አምላካችን ነህና፤
አዎን፤ ወደ አንተ እንመጣለን።
23በእርግጥ በኰረብቶች ላይ፣
እንዲሁም በተራሮች ላይ፣ ሆ! ብለን
መውጣታችን መታለል ነው፤
በእርግጥ የእስራኤል መዳን፣
በአምላካችን *በእግዚአብሔር* ነው።
24ከለጋ ዕድሜአችን ጀምሮ፣
የአባቶቻችንን የድካም ፍሬዎች፣
በጎቻቸውንና ከብቶቻቸውን፣
ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን፣
ነውረኛ ጣዖቶች በሏቸው።
25እንግዲህ ዕፍረታችንን ተከናንበን እንተኛ፤
ውርደታችንም ይሸፍነን፤
እኛም አባቶቻችንም፣
*እግዚአብሔር* አምላካችንን በድለናልና፤
ከልጅነታችን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ፣
አምላካችንን *እግዚአብሔርን*
አልታዘዝንም።”

4 “እስራኤል ሆይ፤ ብትመለስ፣
ወደ እኔ ብትመለስ፤”
ይላል *እግዚአብሔር*፤
“አስጸያፊ ነገሮችህን ከፊቴ ብታስወግድ፣
ባትናወጥ ብትቆምም፣
2በእውነት፣ በቅንነትና በጽድቅ፣
‘ሕያው *እግዚአብሔርን*!’ ብለህ
ብትምል፣
አሕዛብ በእርሱ ይባረካሉ፤
በእርሱም ይከበራሉ።”

23÷2፡11፤አሞ4÷8
3÷8 ዘዳ4÷27፤ኤር 11÷10፤24÷1፤ሕዝ 16÷47፤23÷11
3÷9 ቍ2፤ዘሌ17÷7 ፤ኢሳ1÷21፤57÷6፤ ኤር2÷27
3÷10 2ነገ17÷19፤ ኢሳ31÷6፤ኤር12÷2 ፤ሕዝ33÷31፤አሞ4÷9 ፤ሐጌ2÷17
3÷11 ቍ7፤ኤር 2÷19፤ሕዝ16÷52፤ 23÷11
3÷12 ቍ6፡14 ዘዳ4÷30፤ 1ነገ3÷26፤ 2ነገ17÷3-6፤መዝ6÷2 ፤103÷9፤ኢሳ54÷9፤ ኤር31÷21፡22፤ሕዝ 14÷6፤33÷11፤ሆሴ 14÷1
3÷13 ቍ25፤ ዘዳ12÷2፤30÷1-3፤ ኤር2÷25፤14÷20፤ 22÷21፤1ዮሐ1÷9
3÷14 ቍ12፤ኢዮ 22÷23፤ኢሳ54÷5፤ ኤር 4÷1
3÷15 ኢሳ31÷4፤ ሐሥ13÷22
3÷16 ዘኍ3÷31፤ 1ዜና 15÷25፤ኢሳ 65÷17
3÷17 መዝ22÷23፤ 47÷8፤ 81÷12፤ኢሳ 2÷3፤ኤር7÷24፤9÷14፤ 11÷8፤13÷10፡11፤16÷ 12፤17÷12፤18÷12፤ 33÷9፡16፤ሕዝ1÷26፤ 43÷7፤48÷35፤ሚክ 4÷1
3÷18 ዘዳ31÷7፤ኢሳ 11÷13፤14÷1፤ኤር 16÷15፤30÷3፤31÷8፤ 50÷4፤ሕዝ11÷17፤ 37÷19፡22፤አሞ9÷15
3÷19 ቍ4፤ዘፀ4÷ 22፤ዘዳ8÷7፤2ሳሙ 7÷14፤መዝ106÷24፤ ሕዝ 20÷6
3÷20 ኢሳ 24÷16
3÷21 ቍ2፤ኢሳ 57÷11፤ኤር31÷18
3÷22 ቍ12፤ኢዮ 22÷23፤ኢሳ30÷26፤ 57÷18፤ኤር2÷19፤ 33÷6፤ ሆሴ 6÷1
3÷23 መዝ3÷8፤ኤር 2÷20፤ 17÷14
3÷24 ኤር11÷13፤ ሆሴ9÷10
3÷25 ቍ13፤ መሳ10÷10፤1ነገ 8÷47፤ዕዝ9÷6፤መዝ 25÷7፤ኤር14÷20፤ 22÷21፤31÷19፤ሕዝ 2÷3፤ ዳን 9÷7
4÷1 ዘዳ4÷30፤ 2ነገ 17÷13፤21÷4፤ኤር 16÷18፤35÷15፤ሕዝ 8÷5 ሆሴ 12÷6
4÷2 ዘፍ12÷2፤ዘኍ 14÷21፤ዘዳ10÷20፤ ኢ

3እግዚአብሔር ለይሁዳና ለኢየሩሳሌም ሰዎች
እንዲህ ያላል፤

“ዕዳሪውን መሬት ዕረሱ፤
በእሾህም መካከል አትዝሩ፡፡
4እናንተ የይሁዳ ሰዎች፣ የኢየሩሳሌምም
ነዋሪዎች፤
ለእግዚአብሔር ተገረዙ፤
የልባችሁንም ሸለፈት አስወግዱ፤
አለዚያ ስለ ሠራችሁት ክፋት፣
ቍጣዬ እንደ እሳት ይንበለበላል፤
ሊገታውም የሚችል የለም፡፡

## ጥፋት ከሰሜን መምጣቱ

5“ ‘በምድሪቱ ሁሉ መለከትን ንፉ’
ብላችሁ፤
በይሁዳ ተናገሩ፣ በኢየሩሳሌም ዐውጁ፤
ጮኹ፤ እንዲህም በሉ፤
‘በአንድነት ተሰብሰቡ፤
ወደ ተመሸጉት ከተሞች እንሽሽ!’
6ወደ ጽዮን ለመግባት ሰንደቅ ዐላማ
አንሡ፤
ቶሎ ሸሽታችሁ አምልጡ፤
ከሰሜን መቅሠፍትን፣
ታላቅ ጥፋትን አመጣለሁና፡፡”

7አንበሳ ከደኑ ወጥቶአል፤
ሕዝብንም የሚያጠፋ ተሰማርቶአል፤
ምድርሽን ባዶ ሊያደርግ፣
ከስፍራው ወጥቶአል፡፡
ከተሞችሽ ፈራርሰው ይወድቃሉ፤
ያለ ነዋሪም ይቀራሉ፡፡
8ስለዚህ ማቅ ልበሱ፤
እዘኑ፤ ዋይ በሉ፤
የእግዚአብሔር አስፈሪ ቍጣ፣
ከእኛ አልተመለሰምና፡፡

9“ “በዚያ ቀን” ይላል እግዚአብሔር፤
“ንጉሡና ሹማምንቱ ወኔ ይከዳቸዋል፤
ካህናቱ ድንጋጤ ይውጣቸዋል፤
ነቢያቱም ብርክ ይይዛቸዋል፡፡”

10እኔም፣ “ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፤ ሰይፍ
አንገታቸው ላይ ተቃጥቶ ሳለ፣ ‘ሰላም ይሆ
ንላችኋል’ ብለህ ይህን ሕዝብና ኢየሩሳ
ሌምን ለምን እጅግ አታለልህ?” አልሁ፡፡
11በዚያን ጊዜ፣ ለእዚህ ሕዝብና ለኢ
የሩሳሌም እንዲህ ተብሎ ይነገራል፤ “ለማ
በጠር ወይም ለማጥራት ሳይሆን፣ ከዚያ
የበረታ የሚጠብስ ደረቅ ነፋስ በምድረ
በዳ ካሉት ባድማ ኰረብቶች ወደ ወገኔ
ሴት ልጅ 12በእኔ ትእዛዝ ይነፍሳል፤[ቀ]
እንግዲህ ፍርዴን በእነርሱ ላይ እናገራ
ለሁ፡፡”

13እነሆ፤ እንደ ደመና ይንሰራፋል፤
ሠረገሎቹ እንደ ዐውሎ ነፋስ
ይመጣሉ፤
ፈረሶቹም ከንስር ይፈጥናሉ፤
መጥፋታችን ነውና ወዮልን!
14ኢየሩሳሌም ሆይ፤ እንድትድኚ ከልብሽ
ክፋት ታጠቢ፤
እስከ መቼ ክፉ ሐሳብ በውስጥሽ
ይኖራል?
15ድምፅ ከዳን ይሰማልና፤
ከኤፍሬም ተራሮችም ጥፋትን
ያውጃል፡፡
16“ይህን ለሕዝቦች አሳውቁ፤
ለኢየሩሳሌምም እንዲህ ብላችሁ በይፋ
ንገሩ፤
‘ከበው የሚያስጨንቁ ከሩቅ አገር
ይመጣሉ፤
በይሁዳ ከተሞችም ላይ ይደነፋሉ፤
17ሰብል እንደሚጠብቁ ሰዎች ይከቧታል፤
በእኔ ላይ ዐምፃለችና፤’ ”
ይላል እግዚአብሔር፡፡
18“የገዛ መንገድሽና ተግባርሽ፣
ይህን አምጥቶብሻል፤
ይህም ቅጣትሽ ነው፤
ምንኛ ይመራል!
እንዴትስ ልብ ይሰብራል!”
19ወይ አበሳዬ! ወይ አበሳዬ!
ሥቃይ በሥቃይ ላይ ሆነብኝ፤
አወይ፣ የልቤ ጭንቀት!
ልቤ ክፉኛ ይመታል፤
ዝም ማለት አልችልም፤
የመለከትን ድምፅ፣
የጦርነትንም ውካታ ሰምቻለሁና፡፡
20ጥፋት በጥፋት ላይ ይመጣል፤
ምድሪቱም በሞላ ባድማ ትሆናለች፤
ድንኳኔ በድንገት፣
መጠለያዬም በቅጽበት ጠፋ፡፡
21እስከ መቼ የጦርነት ዐርማ
እመለከታለሁ?
እስከ መቼስ የመለከት ድምፅ
እሰማለሁ?
22“ሕዝቤ ተላሎች ናቸው፤
እኔን አያውቁኝም፡፡
ማስተዋል የጐደላቸው፣
መረዳትም የማይችሉ ልጆች ናቸው፡፡
ክፋትን ለማድረግ ጥበበኞች፤
መልካም መሥራት ግን የማያውቁ፡፡”

ሳ19፥18፤ 65፥16፤ ኤር5፥2፤9፥24፤12፥16፤44፥26፤ሆሴ4፥15፤ ገላ3፥8
4፥3 ሆሴ10፥12፤ ማር4፥18
4፥4 ዘፀ 32፥22፤ ዘሌ26፥41፤ኢዮ41፥21፤ኢሳ1፥31፤አሞ 5፥6፤ሶፎ1፥18፤2፥2
4፥5 ቀኍ21፤ዘኍ10፥2፡7፤ኢሱ10፥20፤ኢዮ 39፥24፤ኤር5፥20፤ 11፥2፡6
4፥6 ቀኍ21፤መዝ 74፥4፤ኢሳ11፥10፤ 14፥31፤31፥9፤ኤር 11፥11፤18፥11፤ 50፥2፡3
4፥7 ቀኍ29፤ ዘሌ26፥31፤2ነገ24፥1፤ኢሳ1፥7፤6፥11፤22፥7፤48፥8፤51፥1፡53፤ ኤር2፥15፤6፥26፤ 15፥8፤25፥38፤ሕዝ 12፥20፤1፥31፤25፥7 ሆሴ5፥14፤13፥7፤ናሆ 2፥12፤
4፥8 1ነገ21፥27፤ ኢሳ3፥24፤10፥4፤ኤር 6፥26፤7፥29፤9፥20፤ 30፥24፤ሕዝ7፥18፤ ኢል1፥8፤ አሞ 5፥1
4፥9 1ሳሙ17፥32፤ ኢሳ 29፥9
4፥10 ዘፀ5፥23፤ኢሳ 30፥10፤ኤር6፥14፤8፥11፤14፥13፤23፥17፤ ሕዝ13፥10፤ሚክ3፥5፤ 1ተሰ5፥3፤2ተሰ2፥11
4፥11 ዘፍ41፥6፤ዘሌ 26፥33፤ኢዮ1፥19
4፥12 ኢሳ 64፥6፤ ኤር 1፥16
4፥13 ቀኍ 20፡27፤ ዘዳ28፥49፤2ሳሙ22፥10፤2ነገ2፥1፤ኢሳ 6፥11፤19፥1፤24፥3፤ 66፥15፤ኤር7፥34፤ 9፥11፡19፤12፥11፤ 25፥11፤44፥6፤ሕዝ 26፥10፤ሚክ2፥4፤ናሆ 2፥4፤ዕን1፥8፤3፥8
4፥14 ሩት3፥3፤መዝ 51፥2፤ 6፥3፤ ኢሳ 45፥22፤ያዕ 4፥8
4፥15 ዘፍ 30፥6፤ ኤር31፥6
4፥16 ቀኍ19፤ዘዳ28፥49፤ ኤር1፥15፤ ሕዝ 21፥22
4፥17 1ሳሙ12፥15፤ 2ነገ25፥1፡4፤ኤር5፥23
4፥18 መዝ107፥17፤ ኢሳ1፥28፤ኤር5፥25፤ 2፥17፡19
4፥19 ቀኍ16፡21፤ዘኍ10፥2፡9፤ኢዮ4፥2፤ 6፥10፤14፥22፤37፥1፤ 39፥24፤ኢሳ22፥4፤ኤር 6፥24፤9፥10፤10፥19፤ 20፥9፤23፥9፤49፥2፤ ሰቆ1፥20፤ሶፎ1፥16፤
4፥20 ቀኍ13፤ዘኍ24፥5፤ዘዳ31፥17፤ኤር 10፥20፤ሰቆ2፥4
4፥21 ቀኍ5፡6፡19፤ዘኍ2፥2፤ኢሱ6፥20፤ኢሳ18፥3፤ ኤር6፥1፤ሆሴ5፥8፤አሞ3፥6፤ሶፎ1፥16
4፥22 መዝ14፥4፤ 36፥3፤ 53፥2፤10፥8፤ኢሳ1፥3፤27፥11፤ኤር2፥8፤5፥21፤6፥6፤8፥7፤13፥23፤ ሆሴ5፥4፤1ቆሮ14፥20

[ቀ]12 ወይም በእኔ ትእዛዝ የሚመጣው

23ምድርን ተመለከትሁ፤
እነሆ ቅርጽ የለሽና ባዶ ነበረች፤
ሰማያትንም አየሁ፣
ብርሃናቸው ጠፍቶአል።
24ተራሮችን ተመለከትሁ፣
እነሆ ይንቀጠቀጡ ነበር፤
ኰረብቶችም ሁሉ ተናጡ።
25አየሁ፤ ሰው አልነበረም፤
የሰማይ ወፎች ሁሉ በረው ጠፍተዋል።
26ተመለከትሁ፤ እነሆም፣ ፍሬያማው
ምድር በረሓ ሆነ፤
ከተሞቹ ሁሉ *በእግዚአብሔር* ፊት፣
ከብርቱ ቍጣው የተነሣ ፈራረሱ።

27*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
"ምድር ሁሉ ባድማ ትሆናለች፤
ነገር ግን ፈጽሜ አላጠፋትም።
28ስለዚህ ምድር ታለቅሳለች፤
ሰማያትም በላይ ይጨልማሉ፤
ተናግሬአለሁ፤ ሐሳቤን አልለውጥም፤
ወስኛለሁ፤ ወደ ኋላም አልልም።

29ከፈረሰኞችና ከቀስተኞች ጩኸት
የተነሣ፣
ከተማ ሁሉ ይሸሻል፤
አንዳንዶች ደን ውስጥ ይገባሉ፤
ሌሎችም ቋጥኝ ላይ ይወጣሉ፤
ከተሞች ሁሉ ባዶ ቀርተዋል፤
የሚኖርባቸውም የለም።

30አንቺ ለጥፋት የተዳረግሽ ሆይ፤ ምን
መሆንሽ ነው?
ቀይ ቀሚስ የለበስሽው ለምንድ ነው?
ለምን በወርቅ አጌጥሽ?
ዐይኖችሽንስ ለምን ተኳልሽ?
እንዲያው በከንቱ ተሽሞንሙነሻል፤
የተወዳጀሻቸው ንቀውሻልና፤
ነፍስሽንም ሊያጠፉ ይፈልጋሉ።

31የበኵር ልጇን ለመውለድ
እንደምታምጥ፣
በወሊድ እንደምትጨነቅ ሴት ድምፅ
ሰማሁ፤
የጽዮን ሴት ልጅ ትንፋሽ አጥሮአት
ስትጮኽ፣
እጇን ዘርግታ፣
"ወዮልኝ! ተዝለፈለፍሁ፣
በነፍሰ ገዳዮች እጅ ወደቅሁ!" ስትል
ሰማሁ።

## ቅን ሰው አለመገኘቱ

5 "በኢየሩሳሌም መንገዶች እስቲ ውጡ፤
ወደ ላይ ወደታችም ውረዱ፤
ዙሪያውን ተመልከቱ ቃኙ፤
በአደባባይዋም ፈልጉ፤
እውነትን የሚሻና በቅንነት የሚሄድ፣
አንድ ሰው እንኳ ብታገኙ፣
እኔ ይህቺን ከተማ እምራታለሁ።
2'ሕያው *እግዚአብሔርን!*' ቢሉም፣
የሚምሉት በሐሰት ነው።"

3*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ዐይኖችህ እውነትን
አይመለከቱምን?
አንተ መታሃቸው፤ እነርሱ ግን
አልተሰማቸውም፤
አደቀቅሃቸው፤ እነርሱ ግን አልታረሙም፤
ፊታቸውን ከድንጋይ ይልቅ አጠነከሩ
በንስሓ ለመመለስም አልፈለጉም።
4እኔም በልቤ እንዲህ አልሁ፤ "እነዚህ
ድኾች ናቸው፤
ሞኞች ናቸው፤
*የእግዚአብሔርን* መንገድ፣
የአምላካቸውን ሕግ አላወቁምና።
5ስለዚህ ወደ ታላላቆቹ እሄዳለሁ፤
ለእነርሱም እናገራለሁ፤
በእርግጥ እነርሱ *የእግዚአብሔርን*
መንገድ፣
የአምላካቸውንም ሕግ ያውቃሉና።"
ነገር ግን እነርሱም ቢሆኑ ያው እንደዚ
ያው ቀንበሩን ሰብረዋል፤
እስራቱንም በጥሰዋል።
6ስለዚህ አንበሳ ከዱር ወጥቶ
ይሰባብራቸዋል፣
የበረሓ ተኵላም ይቦጫጭቃቸዋል፤
ብቅ የሚለውን ሰው ሁሉ ለመገነጣጠል፣
ነብር በከተሞቻቸው ዙሪያ ያደባል፤
ዐመፃቸው ታላቅ፣
ክሕደታቸው ብዙ ነውና።

7"ታዲያ፣ እንዴት ይቅር ልልሽ
እችላለሁ?
ልጆችሽ ትተውኛል፤
እውነተኛውን አምላክ ትተው አማልክት
ባልሆኑት ምለዋል፤
እስኪጠግቡ ድረስ መገብኋቸው፤
እነርሱ ግን አመነዘሩ፤
ወደ ጋለሞቶችም ቤት ተንጋጉ።
8እንደ ተቀለበ ብርቱ ድንጒላ ፈረስ ሆኑ፤
እያንዳንዱም የሌላውን ሚስት ተከትሎ
አሽካካ።
9ስለ እነዚህ ነገሮች አልቀጣቸውምን?"
ይላል *እግዚአብሔር*።
"እኔ ራሴ እንደዚህ ዐይነቱን ሕዝብ፣
አልበቀልምን?
10"ወደ ወይን አትክልቷ ስፍራ ገብታችሁ
አበላሹት፤
ነገር ግን ፈጽማችሁ አታጥፉት፤
ቅርንጫፎቿን ገነጣጥሉ፤

4፥23 ቈላ28፤ ዘፍ 1፥2፤ኢዮ9፥7፤30፥26፤ ኢሳ5፥30፤59፥9፤ሰቆ 3፥2
4፥24 ዘፀ19፥18፤ ኢዮ9፥6
4፥25 ኤር7፥20፤ 9፥10፤12፥4፤ሆሴ4፥3፤ ሶፎ1፥3
4፥26 ዘፍ13፥10፤ ኢሳ6፥11፤ኤር12፥4፡ 13፤23፥10፤25፥38
4፥27 ቈላ13፤ዘሌ26 ፥44፤ኤር5፥10፡18፤12 ፥12፤30፥11፤46፥28፤ሕዝ20፥17፤አሞ 9፥8
4፥28 ቈላ8፡23፤ዘኍ 23፥19፤ኤር12፥4፡11፤ 14፥2፤23፥20፤30፥24፤ ሆሴ4፥3
4፥29 ቈላ7፡13፤ዘፀ 33፥22፤1ሳሙ26፥20፤ 2ነገ25፥4፤ኢሳ6፥12፤ ኤር6፥23፤8፥16
4፥30 2ነገ9፥30፤ኢዮ19፥14፤መዝ35፥4፤ ኢሳ10፥3-4፤ሰቆ1፥2 ፤ሕዝ16፥11፤23፥9፡ 22፤23፥40
4፥31 ዘፍ3፥16፤ ዘዳ32፥25፤መዝ9፥14፤ ኢሳ42፥14፤1፥15፤ ኤር6፥24፤13፥21፤22፥ 23፤30፥6፤ሰቆ1፥17፤ 2፥21፤ሚክ4፥10
5፥1 ቈላ31፤ዘፍ 18፥24፡32፤2ዜና16፥9 ፤መዝ45፥10፤ኤር2፥ 29፤14፥14፤ሕዝ 13፥6፤22፥30
5፥2 ዘሌ19፥12፤ ኤር4፥2
5፥3 ዘሌ26፥23፤ 2ዜና28፥22፤16፥9፤ ኢሳ1፥5፤9፥13፤ኤር7፥ 26፤19፥15፤ሕዝ2፥4- 5፤3፥8-9፤36፥26፤አሞ 4፥16፤ዘካ7፥11፡12
5፥4 ቈላ21፤ምሳ10፥ 21፤ኢሳ1፥3፤ኤር 4፥22
5፥5 ኤር2፥20፤ ሚክ3፥1፡9፤
5፥6 ዘሌ26፥22፤ መዝ17፥12፤ኤር14፥7 ፤30፥14፤ሆሴ13፥7
5፥7 ዘኍ25፥1፤ዘዳ 32፥21፤ኢሱ23፥7፤ ኤር2፥11፤13፥27፤ 16፥20፤ገላ 4፥8
5፥8 ኤር29፥23፤ ሕዝ22፥11፤33፥26
5፥9 ቈላ29፤ኢሳ 57፥6፤ ኤር9፥9
5፥10 ኤር 4፥27፤ አሞ 9፥8

*የእግዚአብሔር* አይደሉምና፤
11የእስራኤል ቤትና የይሁዳ ቤት፣
ፈጽመው ከድተውኛል፤”
ይላል *እግዚአብሔር*።
12*በእግዚአብሔር* ላይ ሐሰትን ተናገሩ፤
እንዲህም አሉ፤ “እሱ ምንም
አያደርግም!
ክፉ ነገር አይደርስብንም፤
ሰይፍም ራብም አናይም፤
13ነቢያቱ ነፋስ እንጂ ሌላ ነገር
አይደሉም፤
ቃሉም በውስጣቸው የለም፤
ያሉት ሁሉ በእነርሱ ላይ ይመለስ።”

14ስለዚህ የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*
እን ዲህ ይላል፤

“ሕዝቡ ይህን ቃል ስለ ተናገረ፣
ቃሌን በአፍህ ውስጥ የሚፋጅ እሳት፣
ይህንም ሕዝብ ማገዶ አደርጋለሁ፤
እሳቱም ይበላቸዋል።
15የእስራኤል ቤት ሆይ፣” ይላል
*እግዚአብሔር*፤
“ከሩቅ ሕዝብን አመጣባችኋለሁ፤
ጥንታዊና ብርቱ፣
ቋንቋውን የማታውቁት፣ ንግግሩንም
የማትረዱት ሕዝብ ነው።
16የፍላጻቸው ሰገባ እንደ ተከፈተ
መቃብር ነው፤
ሁሉም ብርቱ ተዋጊዎች ናቸው።
17ሰብልህንና ምግብህን ጠራርገው
ይበሉብሃል፤
ወንዶችና ሴቶች ልጆችህን ይውጣሉ፣
በጎችህንና ከብቶችህን ይፈጇሉ፤
የወይን ተክሎችህንና የበለስ ዛፎችህን
ያወድማሉ፤
የታመንህባቸውንም የተመሸጉ ከተሞች፣
በሰይፍ ያጠፉአቸዋል።

18“ይሁን እንጂ፣ በዚያን ዘመን እንኳ”
ይላል *እግዚአብሔር*፤ “ፈጽሜ አላጠፋች
ሁም። 19ሕዝቡ፣ ‘*እግዚአብሔር* አምላካችን
ይህን ሁሉ ነገር ለምን አደረገብን?’ ብለው
ቢጠይቁ ‘እኔን፣ እንደ ተዋችሁኝና በራ
ሳችሁ ምድር ባዕዳን አማልክትን እንዳገ
ለገላችሁ፣ እንደዚሁ የእናንተ ባልሆነ ምድር
ባዕዳንን ታገለግላላችሁ’ ትላቸዋለህ።

20“በያዕቆብ ቤት ይህን አሰሙ፣
በይሁዳም እንዲህ ብላችሁ ዐውጁ፤
21እናንት ዐይን እያላችሁ የማታዩ፣
ጆሮ እያላችሁ የማትሰሙ፣
ሞኞችና የማታስተውሉ ሰዎች
ይህን ስሙ፤

5፥11 1ነገ19፥10፤ መዝ73፥27፤ኢሳ 24፥16
5፥12 ኢሳ28፥15፤ ኤር14፥13፤23፥17፤ 27፥8
5፥13 2ዜና36፥16፤ ኢዮ6፥26፤ኤር14፥15
5፥14 መዝ39፥3፤ ኢሳ1፥31፤ኤር23፥29 ፤ሆሴ6፥5
5፥15 ዘፍ11፥7፤ዘዳ 28፥49፤2ነገ24፥2፤ ኢሳ28፥11
5፥16 ኢዮ 39፥23
5፥17 ዘሌ26፥16፡25 ፤ዘኍ16፥14፤ዘዳ28፥ 31፡32፡33፤ኢሱ10፥ 20፤ኢሳ1፥7፤ኤር8፥ 13፡16፤30፥16፤50፥7፡ 17፤ሆሴ2፥12
5፥18 ኤር 4፥27
5፥19 ዘዳ 4፥28፤ 28፥48፤1ነገ9፥9፤ኤር 2፥8፤15፥14፤16፥13፤ 17፥4
5፥20 ኤር 4፥5
5፥21 ቀኁ4፤ዘዳ29፥ 4፤32፥6፤ኢሳ6፥10፤ 42፥20፤ኤር4፥22፤ ሕዝ12፥2፤ዕን2፥18፤ ማቴ13፥15፤ማር8፥18
5፥22 ዘፍ1፥9፤ ዘዳ 28፥58፤ኢዮ4፥14፤ መዝ46፥3፤ኢሳ64፥2
5፥23 ዘዳ 21፥18፤ መዝ14፥3
5፥24 ዘፍ8፥22፤ ዘሌ26፥4፤ዘዳ 6፥24፤ 2ሳሙ1፥21፤ሐሥ 14፥17፤ያዕ5፥7
5፥25 መዝ 84፥11
5፥26 መዝ 10፥8፤ መክ9፥12፤ኤር9፥8፤ ሆሴ5፥1፤ሚክ7፥2፤ ማቴ7፥15
5፥27 ኤር 8፥5፤ 9፥6፤12፥1
5፥28 ዘፀ22፥21-24 ፤ዘዳ32፥15፤መዝ82፥3 ፤ኢሳ1፥23፤ኤር7፥6 ፤ሕዝ16፥49፥አሞ 5፥12 ዘካ 7፥10፤
5፥29 ኢሳ57፥6
5፥30 ቀኁ30-31፤ ኤር18፥13፤23፥14፤ ሆሴ6፥10
5፥31 ቀኁ1፤ሰቆ4፥ 13፤ሆሴ9፥5፤ሚክ 2፥11
6፥1 ዘኁ10፥7፤ 2ዜና11፥6፤ነህ3፥14፤ ኤር4፥6፡21፤አሞ1፥1

22ልትፈሩኝ አይገባችሁምን?” ይላል
*እግዚአብሔር*፤
“በእኔ ፊት ልትንቀጠቀጡስ አይጠ
ገባምን?
ለዘላለም ዐልፎት መሄድ እንዳይችል፣
አሸዋን ለባሕር ድንበር አደረግሁ፤
ማዕበሉ እየጋለበ ቢመጣ ከዚያ
አያልፍም፤
ሞገዱ ቢጮኽም ሊያቋርጠው አይጠ
ችልም።
23ይህ ሕዝብ ግን የሸፈተና እልከኛ
ልብ አለው፤
መንገድ ለቆ ሄዶአል፤
24በልባቸውም፣
‘የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ
በጊዜው የሚያዘንበውን፣
መከርን በወቅቱ የሚያመጣልንን፣
አምላካችንን *እግዚአብሔርን* እንፍራ’
አላሉም።
25በደላችሁ እነዚህን አስቀርቶባችኋል።
ኀጢአታችሁ መልካሙን ነገር
ከልክሎአችኋል።

26“በሕዝቤ መካከል ክፉ ሰዎች አሉና፤
ወፍ እንደሚያጠምዱ ሰዎች፣
ወጥመድ ዘርግተው ሰው እንደሚይዙ
ሰዎችም ያደባሉ።
27ወፎች እንደሞሉት ጐጆ፣
ቤታቸው በማጭበርበር የተሞላ ነው፤
ባለጠጎችና ኀያላን ሆነዋል፤
28ወፍረዋል፤ ሰብተዋልም።
ክፋታቸው ገደብ የለውም፤
ወላጅ የሌላቸው ፍትሕ እንዲያገኙ
አልቆሙላቸውም፤
ለድኾችም መብት አልተከራከሩም።
29ስለ እነዚህ ነገሮች ልቀጣቸው
አይገባኝምን?”
ይላል *እግዚአብሔር*።
እንዲህ ዐይነቶቹን ሕዝብ፣
እኔ ራሴ ልበቀላቸው አይገባኝምን?

30“የሚያስፈራና የሚያስደነግጥ ነገር፣
በምድሪቱ ላይ ሆኖአል፤
31ነቢያት በሐሰት ትንቢት ይናገራሉ፤
ካህናት በነቢያቱ ምክር ያስተዳድራሉ፤
ሕዝቤም እንዲህ ያለውን ይወዳሉ፤
ፍጻሜው ሲደርስ ግን ምን ታደርጉ
ይሆን?

**የኢየሩሳሌም መከበብ**

6 “እናንት የብንያም ልጆች፤ ክፉ
ነገር፣
ታላቅም ጥፋት ከሰሜን ድንገት
ይመጣልና፣
ከኢየሩሳሌም ሸሽታችሁ አምልጡ፤

በቴቁሔ መለከትን ንፉ፤
በቤትሐካሪም ላይ ምልክት ከፍ
አድርጋችሁ አሳዩ።
2ውብና ሽሙንሙን የሆነችዋን፣
የጽዮንን ሴት ልጅ አጠፋታለሁ።
3እረኞች መንጎቻቸውን ይዘው
ይመጡባታል፤
ድንኳናቸውን በዙሪያዋ ይተክላሉ፤
እያንዳንዳቸውም በየአቅጣጫቸው
መንጋቸውን ያሰማራሉ።"
4"በእርሷ ላይ ጦርነት ዐውጁ፤
ተነሡ! በቀትር አደጋ እንጣልባት፤
ወይ ጉድ! ቀኑ እኮ መሸብን!
ጥላው ረዘመ።
5እንግዲህ ተነሡ በሌሊት እናጥቃት፤
ምሽጎቿንም እንደምስስ!"

6የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

"ዛፎቹን ቍረጡ፤
በኢየሩሳሌም ዙሪያ የዐፈር ድልድል
ሥሩ።
ይህቺ ከተማ ቅጣት ይገባታል፤
ግፍን ተሞልታለችና።
7የውሃ ጕድጓድ ውሃ እንደሚያመነጭ፣
እርሷም እንዲሁ ክፋቷን ታፈልቃለች።
ዐመፅና ጥፋት በውስጧ ይስተጋባል፤
ሕመሟና ቍስሏ ዘወትር ይታየኛል።
8ኢየሩሳሌም ሆይ፤ ተጠንቀቂ፤
አለበለዚያ ከአንቺ ዘወር እላለሁ፤
ማንም ሊኖርባት እስከማይችል ድረስ፣
ምድርሽን ባዶ አደርጋለሁ።"

9የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

"የወይን ፍሬ ተሚጦ እንደሚቃረም፣
ከእስራኤል የተረፉትን እንዲሁ
ይቃርሚቸው።
ወይን ለቃሚ እንደሚለቅም፣
እጅህን ወደ ቅርንጫፎቹ ደጋግመህ
ዘርጋ።"

10ለማን ልናገር? ማንን ላስጠንቅቅ?
ማንስ ይሰማኛል?
እነሆ፣ ጆሮዎቻቸው አልተገረዙምና፣[ሀ]
መስማት አይችሉም።
*በእግዚአብሔር* ቃል ይሣለቃሉ፤
ደስም አይሰኙበትም።
11በእነርሱ ላይ *በእግዚአብሔር* ቍጣ
ተሞልቻለሁ፤
በውስጤም ልይዘው አልቻልሁም።
"*መንገድ* ላይ በሚገኙ ሕፃናት፣
በተሰበሰቡ ወጣቶችም ላይ አፍስሰው፤
ባልም ሚስትም፣
ያረጁና የጃጁም አያመልጡም።

12በምድሪቱ በሚኖሩት ላይ፣
እጄን በምዘረጋበት ጊዜ፣
ዕርሻቸውና ሚስቶቻቸው ሳይቀሩ፣
ቤቶቻቸው ለሌሎች ይሆናሉ፤"
ይላል *እግዚአብሔር*።
13"ከትንሹ እስከ ትልቁ ሰው፣
ሁሉም ለጥቅም የሚስገበገቡ ናቸው፤
ነቢያቱም ካህናቱም ሳይቀሩ፣
ሁሉም ያጭበረብራሉ።
14የሕዝቤን ቍስል እንደ ቀላል ቈጠሩ፣
እንዲፈወስም ተገቢውን እንክብካቤ
አላደረጉለትም፤
ሰላምም ሳይኖር፣
'ሰላም፣ ሰላም' ይላሉ።
15ስለ ጸያፉ ተግባራቸው ዐፍረዋል እንዴ?
ኧረ ጨርሶ ዕፍረት የላቸውም!
ዕፍረት ምን እንደ ሆነ እንኳ አያውቁም፤
ስለዚህ ከሚወድቁት ጋር ይወድቃሉ፤
በምቀጣቸውም ጊዜ ይዋረዳሉ፤"
ይላል *እግዚአብሔር*።

16*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

"*መንታ መንገድ* ላይ ቁሙ፣ ተመልከቱም፤
*መልካሚን*፣ የጥንቷን *መንገድ* ጠይቁ፤
በእርሷም ላይ ሂዱ።
ለነፍሳችሁ ዕረፍት ታገኛላችሁ፤
እናንተ ግን፣ 'በእርሷ አንሄድም'
አላችሁ።
17ጠባቂዎችን አቆምሁላችሁ፤
'*የመለከትን*ም ድምፅ ስሙ' አልኋችሁ፤
እናንተ ግን፣ 'አንሰማም' አላችሁ።
18እንግዲህ ሕዝቦች ሆይ ስሙ፤
እናንተም ምስክሮች ምን
እንደሚገጥማቸው አስተውሉ።
19ምድር ሆይ፤ ስሚ፤
ቃሌን ስላላደመጡ፣
ሕጌንም ስለናቁ፣
በዚህ ሕዝብ ላይ የሐሳባቸውን ውጤት፣
ጥፋትን አመጣባቸዋለሁ።
20ዕጣን ከሳባ ምድር፣
ጣፋጩ ቅመም ከሩቅ አገር ቢመጣ
ምን ይጠቅመኛል?
የሚቃጠል መሥዋዕታችሁን አልቀበልም፤
ሌላውም መሥዋዕታችሁ ደስ
አያሰኘኝም፤

21ስለዚህ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

"በዚህ ሕዝብ ፊት መሰናክልን
አስቀምጣለሁ፤
አባቶችና ወንዶች ልጆች በአንድነት
ይደናቀፉበታል፤
ጎረቤቶችና ባልንጀሮችም ይጠፋሉ።"

[ሀ]10 ወይም *ጆሮዎቻቸው ተደፍነዋል*

**6፥2** መዝ9፥14፤ ሰቆ4፥5
**6፥3** 2ነገ25፥4፤ኤር 12፥10፤ሉቃ19፥43
**6፥4** ኤር15፥8፤ 22፥7
**6፥6** ዘዳ20፥19-20፤ 28፥33፤2ሳሙ20፥15፤ ኤር25፥38፤32፥24፤ 52፥4፤ሕዝ26፥8፤ሶፎ 3፥1
**6፥7** መዝ55፥9፤ኢሳ 58፥4፤ኤር20፥8
**6፥8** ሕዝ23፥18
**6፥9** ዘፍ45፥7
**6፥10** ኢሳ 42፥20፤ ኤር4፥4፤7፥13፡24፤ 15፥10፡15፤20፥8፤ 35፥15፤ሐሥ7፥51
**6፥11** 2ዜና36፥17፤ ኢዮ32፥20፤ኢሳ40፥ 30፤ኤር7፥20፤15፥17፤ 20፥9፤ ሰቆ2፥21
**6፥12** ዘዳ28፥30፤ 1ነገ11፥4፤ኢሳ5፥25፤ ኤር8፥10፤21፥5፤ 29፥23፤32፥21፤38፥ 22፤43፥6፤44፥9፡15፤ ሕዝ6፥14፤35፥3፤ሚክ 2፥4፤ሶፎ1፥4
**6፥13** ኢሳ56፥11፤ ኤር2፥29፤ሰቆ4፥13
**6፥14** ኢሳ30፥10፤ ኤር4፥10
**6፥15** 2ዜና25፥16፤ ኤር3፥3፤8፥10-12፤ 27፥15፤ሚክ3፥7፤ዘካ 13፥4
**6፥16** ኢሱ1፥13፤ 1ነገ8፥36፤መዝ119፥ 3፤ኢሳ11፥10፤ኤር 18፥15፤ማቴ11፥29
**6፥17** ዘፀ20፥18፤ ኢ ሳ52፥8፤ኤር11፥7-8 ፤ሕዝ33፥4፤ዘካ1፥4
**6፥19** ዘዳ4፥26፤ኢሱ 23፥15፤ምሳ1፥31፤ ኤር8፥9፤11፥11፤19፥3 ፤22፥29፤29፥19፤ ሕዝ20፥13፤አሞ 2፥4፤ሚክ1፥2
**6፥20** ዘፍ10፥7፤ ዘፀ 30፥23፤መዝ50፥8-10 ፤ኢሳ1፥11፤ኤር7፥21፤ 14፥12፤ሆሴ8፥13፤ 9፥4፤አሞ5፥22፤ሚክ 6፥7-8፤ሚል1፥9
**6፥21** ዘሌ 26፥37፤ ኢሳ8፥14

22እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“እነሆ፤ ሰራዊት፣
ከሰሜን ምድር እየመጣ ነው፤
ከምድር ዳርቻም፣
ታላቅ ሕዝብ እየተነሣሣ ነው።
23ቀስትና ጦር ይዘዋል፤
ጨካኞችና ምሕረት የለሽ ናቸው፤
ፈረሶቻቸውን ሲጋልቡ፤
ድምፃቸው እንደተናወጠ ባሕር ነው፤
የጽዮን ልጅ ሆይ፤ ለሰልፍ የታጠቁ
ሆነው፣
ሊወጉሽ ይመጣሉ።”

24ስለ እነርሱ ወሬ ደርሶናል፤
ክንዶቻችንም ዝለዋል፤
ጭንቀት ይዞናል፤ እንደምታምጥም
ሴት ሆነናል።
25ጠላት ሰይፍ ታጥቆአል፤
በየቦታውም ሽብር ሞልቶአል፤
ስለዚህ ወደ ውጭ አትውጡ፤
በየመንገዱ አትዘዋወሩ።
26የሕዝቤ ልጅ ሆይ፤ ማቅ ልበሺ፤
በዐመድም ላይ ተንከባለዪ፤
አንድያ ልጁን እንዳጣ ሰው፣
ምርር ብለሽ አልቅሺ፤
አጥፊው በድንገት፣
በላያችን ይመጣልና።

27“ብረት እንደሚፈተን፣ የሕዝቤን
መንገድ፣
አካሄዳቸውንም እንድትፈትን፣
አንተን ፈታኝ አድርጌሃለሁ።
28ሁሉም ለማማት የሚዞሩ፣
ድድር ዐመፀኞች፣
ናስና ብረት የሆኑ፣
ምግባረ ብልሹዎች ናቸው።
29ርሳሱን ለማቅለጥ፣
ወናፉ በብርቱ አናፋ፤
ግን ምን ይሆናል፣ ከንቱ ልፋት ነው፤
ክፉዎች ጠርገው አልወጡምና።
30እግዚአብሔር ንቆአቸዋልና፣
የተናቀ ብር ተብለው ይጠራሉ።

## ዋጋ ቢስ አምልኮ

7 ከእግዚአብሔር ወደ ኤርምያስ የመ
ጣው ቃል ይህ ነው፤ 2“በእግዚአብሔር
ቤት በር ቁም፤ በዚያም ይህን መልእ
ክት ዐውጅ፤
“ ‘እግዚአብሔርን ለማምለክ፣ በእነዚህ
በሮች የምትገቡ የይሁዳ ሕዝብ ሁላችሁ፣
የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ። 3የእስራኤል
አምላክ፣ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር
እን ዲህ ይላል፤ “መንገዳችሁንና ሥራችሁን
አስ ተካክሉ፤ እኔም በዚህ ስፍራ
እንድትኖሩ አደርጋችኋለሁ። 4ይህ ‘የእግዚ
አብሔር ቤተ መቅደስ፣ የእግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ፣ የእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ’ ነው እያ ላችሁ በሐሰት ቃል
አትታመኑ። 5መንገ ዳችሁንና ሥራ
ችሁን በእርግጥ ብታሳ ምሩ፣
በመካከላችሁ ቅንነት ቢኖር፣ 6መጻ
ተኛውንና ድኻ አደጉን፣ መበለቲቱንም
ባትጨቍኑ፣ በዚህም ስፍራ ንጹሕ ደም
ባታ ፈሱ፣ የሚጐዷችሁን ሌሎች አ
ማልክት ባትከተሉ፣ 7ለአባቶቻችሁ
ለዘላለም ርስት አድርጌ በሰጠኋቸው
ምድር፣ በዚህ ስፍራ አኖራችኋለሁ።
8እናንተ ግን፣ ከንቱ በሆኑ የሐሰት ቃላት
ታምናችኋል።”
9“ ‘ትሰርቃላችሁ፤ ሰው ትገድላላችሁ፤
ታመነዝራላችሁ፤ በሐሰት ትምላላችሁ፤†
ለበኣል ታጥናላችሁ፤ የማታውቋቸውንም
ሌሎች አማልክት ትከተላላችሁ፤ 10ስሜ ወደ
ሚጠራበት ወደዚህ ቤት መጥታችሁ
በፊቴ ትቆሙና “ደህና ነን”። እያላችሁ
እነዚህን አስጸያፊ ነገሮች ታደርጋላችሁ።
11ስሜ የሚጠራበት፣ ይህ ቤት በእናንተ
ዘንድ የወንበዴዎች ዋሻ ሆኖአልን? እነሆ፤
የምታደርጉትን ነገር አይቻለሁ! ይላል እግዚ
አብሔር።
12“ ‘እንግዲህ ቀድሞ የስሜ ማደሪያ
አድርጌው ወደ ነበረው ስፍራ ወደ ሴሎ
ሂዱ፤ ከሕዝቤ ከእስራኤል ክፋት የተነሣ
ያደረግሁበትንም እዩ። 13እነዚህን ሁሉ ስታ
ደርጉ፣ ይላል እግዚአብሔር፤ ደጋግሜ
ተናገርኋችሁ፤ እናንተ ግን አላደመጣች
ሁኝም፤ ጠራኋችሁ፤ እናንተ ግን አልመለ
ሳችሁም። 14ስለዚህ በሴሎ እንዳደረግሁ
አሁንም ስሜ በተጠራበት ቦታ፣ በታመ
ናችሁበት ቤተ መቅደስ፣ ለአባቶቻችሁና
ለእናንተ በሰጠሁት በዚህ ስፍራ እንዲሁ
አደርጋለሁ፤ 15ወንድሞቻችሁ የሆኑትን፣
የኤፍሬምን ሁሉ ሕዝብ እንዳስወገድሁ፣
እናንተንም ከፊቴ እጥላችኋለሁ።’
16“እንግዲህ ስለማልሰማህ፣ ለዚህ ሕዝብ
አትጸልይ፤ ልመና አታቅርብ፤ አትማጠን፤
አትማልድላቸውም። 17እነርሱ በይሁዳ
ከተ ሞችና በኢየሩሳሌም መንገዶች ላይ
የሚ ያደርጉትን አታይምን? 18ለሰማይዋ
ንግ ሥት ቂጣ ሊጋግሩ፣ ልጆች እንጨት
ይለ ቅማሉ፤ አባቶች እሳት ያቀጣጥላሉ፤
ሴቶ ችም ሊጥ ያቦካሉ፤ ሊያስቈጡኝም
ለሌ ሎች አማልክት የመጠጥ ቍርባን
ያቀር ባሉ። 19ለመሆኑ ይህን
የሚያደርጉት እኔን

6፥22 ዘዳ 28፥49፤ ኤር 4፥6
6፥23 መዝ 18፥4፤ 93፥3፤ኢሳ10፥32፤ 13፥18፤ኤር4፥29
6፥24 ኢሳ13፥7፤ኤር 4፥19፡31፤50፥43
6፥25 ኢዮ15፥21፤ መዝ31፥13፤ኤር49፥29
6፥26 ዘፍ 21፥16፤ ዘፀ12፥23፤ኢዮ 2፥8፤ ኤር4፥7፡8፤9፥1፤18፥ 22፤20፥16፤25፥34፡ 36፤ሕዝ27፥30፤ዮና 3፥6
6፥27 ኤር 9፥7፤ ዘካ 13፥9
6፥28 ዘሌ19፥16፤ ኤር5፥23፤ሕዝ22፥18
6፥29 ሚል 3፥3
6፥30 መዝ 53፥5፤ 119፥119፤ምሳ17፥3፤ ኤር7፥29፤ሰቆ5፥22፤ ሕዝ22፥18፤ሆሴ9፥17
7፥2 ኤር 17፥19
7፥3 ቁ-7፤ኤር18፥ 11፤26፥13፤35፥15
7፥4 ቁ-8፤ኢዮ15፥ 31፤ኤር28፥15፤ሚክ 3፥11
7፥5 ቁ- 3፤ ዘፀ 22፥22፤ዘሌ25፥17፤ ኢሳ1፥17፤ኤር18፥11 ፤26፥13፤35፥15
7፥6 ዘፀ20፥3፤ዘዳ 8፥19፤2ነገ21፥16፤ኤር 2፥34፤5፥28፤19፥4፤ 22፥3፤ሕዝ22፥7
7፥7 ዘዳ4፥40፤ኢሱ 1፥6
7፥8 ቁ-4፤ኢዮ 15፥31
7፥9 ዘፀ20፥3፡6፡ 13፡14፡15፤ዘሌ19፥12 ፤ዘኁ25፥1፤ኢሳ1፥13፤ ኤር11፥13፡17፤32፥ 29፤ ሆሴ2፥13፤ዘካ 8፥17፤ሚል3፥5
7፥10 ቁ- 30፤2ነገ 21፥4-5፤ኢሳ48፥1፤ ኤር23፥11፤32፥34፤ ሕዝ 23፥38-39፤ 33፥25
7፥11 ዘፍ 31፥50፤ መሳ11፥10፤ኢሳ56፥7 ፤ኤር29፥23፤42፥5፤ ማቴ 21፥13፤ማር 11፥17፤ ሉቃ19፥46
7፥12 ዘፀ 40፥2፤ ኢ ሱ18፥1፡10፤1ሳሙ 2፥32፤4፥10-11፡22፤ መዝ78፥60-64፤ዳን 9፥18
7፥13 ቁ-26፤2ዜና 36፥15፤መዝ71፥17፤ ምሳ1፥24፤ኢሳ48፥ 17፤65፥12፤ኤር 32፥33፤ 35፥17
7፥14 ቁ-4፤መሳ 18፥31፤1ሳሙ2፥32፤ 1ነገ9፥7፤ሕዝ24፥21
7፥15 ዘፍ 4፥14፤ ዘፀ33፥15፤2ነገ17፥20፤መዝ78፥67፤ኤር23፥39 7፥16 ዘፀ32፥10፤ ዘኁ23፥19፤ዘዳ9፥14፤ኤር15፥1 7፥18 ዘዳ31፥17፤1ነገ14፥9፤ኢሳ 57፥6፤ኤር44፥17-19 7፥19 ዘዳ32፥21፤ኢዮ7፥20፤ኤር9፥19፤ 20፥11፤22፥22፤44፥3

†9 ወይም በሐሰተኛ አማልክት ትምላላችሁ

ለማስቈጣት ነውን? ይላል እግዚአብሔር፤
“ይልቁን ይህን በማድረጋቸው በሚደርስባ
ቸው ዕፍረት የሚጐዱት ራሳቸውን አይደ
ለምን?
20“ ‘ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤ “ቍጣዬና መዓቴ በዚህ ስፍራ በሰ
ውና በእንስሳ ላይ፣ በዱር ዛፍና በምድር
ፍሬ ላይ ይፈሳል፤ ይነዳል፤ አይጠፋ
ምም::”
21“ ‘የእስራኤል አምላክ የሰራዊት
ጌታ
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ “የሚቃጠል
መሥዋዕታችሁን በሌሎች መሥዋዕታችሁ
ላይ ጨምሩ፤ ሥጋውንም ራሳችሁ ብሉ::
22የቀድሞ አባቶቻችሁን ከግብፅ ባወጣኋ
ቸው ጊዜ፣ ስለ መሥዋዕቶችና ስለሚቃጠል
መሥዋዕት አልተናገርኋቸውም፤ ትእዛዝም
አልሰጠኋቸውም:: 23ነገር ግን ድምፄን
ስሙ፤ እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ፤
እናንተም
ሕዝቤ ትሆናላችሁ፤ መልካም እንዲሆንላ
ችሁም፣ ባዘዝኋችሁ መንገድ ሁሉ ሂዱ
ብዬ አዘዝኋቸው:: 24እነርሱ ግን አልሰ
ሙም፤ ልብ ብለው ለማድመጥም አልፈለ
ጉም፤ ይልቁን የክፉ ልባቸውን ሐሳብ
በእልኸኝነት ተከተሉ፤ ወደ ፊት በመሄድ
ፈንታም ወደ ኋላቸው ተመለሱ:: 25አባቶ
ቻችሁ ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ
ጀምሮ እስካሁን ድረስ፣ በየቀኑ ሳላሰልስ
አገልጋዮቼን ነቢያትን ላክሁባቸው:: 26ሕ
ዝቡ ግን አልሰማኝም፤ ልብ ብሎ ለማድመ
ጥም አልፈለገም፤ ዐንገታቸውን አደነደኑ
አባ ቶቻቸው ከሠሩት የባሰም ክፉ
አደረጉ::” ’
27“ይህን ሁሉ ትነግራቸዋለህ፤ እነርሱ
ግን አይሰሙህም፤ ትጠራቸውማለህ፤ አይ
መልሱልህም:: 28ስለዚህ እንዲህ በላቸው፤
‘ይህ ሕዝብ አምላኩን እግዚአብሔርን ያል
ታዘዘ፣ ምክሩን ያልተቀበለ ወገን ነው፤
እውነት ጠፍቶአል፤ ከአንደበታቸውም ሸሽቶ
አል:: 29እግዚአብሔር ቍጣው የወረደበ
ትን ይህን ትውልድ ስለ ናቀውና ስለ
ተወው፣ ጠጕርሽን ቈርጠሽ ጣይ፤ በባድ
ሞቹ ኰረብቶች ላይ ሆነሽም ሙሾ
አውጪ::

### የዕርድ ሸለቆ

30“ ‘የይሁዳ ሕዝብ በፊቴ ክፉ ነገር
አድርጓል፤ ይላል እግዚአብሔር፤ አስጸያፊ
ነገራቸውን ስሜ በተጠራበት ቤት በማስቀ
መጥ አርክሰውታል:: 31እኔ ያላዘዝኋቸ
ውን፣ ከቶም ያላሰብሁትን ወንዶችና
ሴቶች ልጆቻቸውን በእሳት አቃጥለው
ለመሠዋት በሄኖም ልጅ ሸለቆ የቶፌትን
መስገጃ ኰረብቶች ሠሩ:: 32ስለዚህ አስተ
ውሉ፤ ይላል እግዚአብሔር፤ ስፍራ እስከ
ማይገኝ ድረስ ሙታንን በቶፌት ስለሚቀ
ብሩ፣ የዕርድ ሸለቆ እንጂ ከእንግዲህ
ቶፌት ወይም የሄኖም ልጅ ሸለቆ ተብሎ
የማይጠራበት ጊዜ ይመጣል::
33የዚህም ሕዝብ ሬሳ ለሰማይ ወፎችና
ለምድር አራዊት ሲሳይ ይሆናል፤ የሚያባር
ራቸውም አይኖርም:: 34የደስታና የተድላን
ድምፅ፣ የሙሽራና የሙሽራዪቱን ድምፅ
ከይሁዳ ከተሞችና ከኢየሩሳሌም መንገ
ዶች አጠፋለሁ፤ ምድሪቱ ባድማ ትሆናለ
ችና::

8 “ ‘በዚያን ጊዜ፣ ይላል እግዚአብሔር፤
የይሁዳን ነገሥታትና መኳንንት ዐፅም፣
የካህናትና የነቢያት ዐፅም፣ የኢየሩሳሌም
ሕዝብ ዐፅም ከየመቃብራቸው ይወጣል::
2በወደዷቸውና በአገለገሏቸው እንዲሁም በተ
ከተሏቸው፣ ባማከሯቸውና ባመለኳቸው
በፀሓይ፣ በጨረቃና በሰማያት ከዋክብት
ሁሉ ፊት ይሰጣል፤ አይሰበሰብም ወይም
አይቀበርም፤ ነገር ግን እንደ ተጣለ ጕድፍ
በምድር ላይ ይበተናል:: 3ከዚህ ክፉ ሕዝብ
የተረፉት ሁሉ፣ ባሳደድኋቸው ስፍራ ሁሉ
ከሕይወት ይልቅ ሞትን ይመርጣሉ፤ ይላል
የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር::’

### ኀጢአትና ያስከተለው ቅጣት

4“እንዲህ በላቸው፤ ‘እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤

“ ‘ሰዎች ቢወድቁ፣ እንደ ገና ከወደቁበት
አይነሡምን?
ሰው ተሳስቶ ወደ ኋላ ቢሄድ፣
ከስሕተቱ አይመለስምን?
5ታዲያ፣ ይህ ሕዝብ ለምን ፊቱን አዙሮ
ወደ ኋላ ይሄዳል?
ለምንስ ኢየሩሳሌም ዘወትር ወደ ኋላ
ትመለሳለች?
ተንኰልን የሙጥኝ ብለው ይዘዋል፤
ሊመለሱም ፈቃደኛ አይደሉም::
6እኔ በጥንቃቄ አደመጥኋቸው፤
ትክክለኛ የሆነውን ግን አይናገሩም::
ማንም ስለ ክፋቱ ንስሓ የገባ የለም፤
“ምን አድርጌአለሁ?” ይላል::
ለጦርነት እንደ ተዘጋጀ ፈረስ፣
እያንዳንዱ በራሱ መንገድ ይሄዳል::
7ሽመላ እንኳ በሰማይ፣
የተወሰነ ጊዜዋን ታውቃለች፣
ዋኖስ፣ ጨረባና ዋርዳም፣
የሚሰደዱበትን ጊዜ ያውቃሉ፤

7፥20 አዮ40፥11፤ ኢሳ1፥31፤30፥15፤ኤር 6፥11-12፤11፥16፤ 13፥14፤15፥6፡14፤ 17፥4፡27፤42፥18፤ ሰቆ4፥11፤2፥3-5፤ሕዝ 20፥47-48
7፥21 1ሳሙ2፥12-17፤ ኤር6፥20፤ሆሴ8፥13፤ አሞ5፥21-22
7፥22 1ሳሙ15፥22፤ ኢሳ43፥23፤
7፥23 1ዮሐ 3፥23፤ ዘፀ19፥5፤ዘሌ26፥12፤ ዘዳ5፥33፤1ነገ8፥36፤መዝ119፥3፤ኢሳ 51፥16፤
7፥24 ኤር6፥10፤ 11፥8፤17፥23፤34፥14፤ 3፥17፤2፥19፤ሕዝ 37፥23
7፥25 ዘኍ11፥29፤ 2ዜና36፥15፤ኢሳ20፥3 ፤ኤር25፥4፤35፥15
7፥26 ቍ 13፡24፤ ዘፀ32፥9፤2ዜና36፥16፤ መዝ81፥11፤ኤር13፥11፤ 16፥12፤22፥21፤25፥3፤ 35፥15፤ሕዝ20፥8፡21፤ ሚል3፥7፤ሉቃ11፥47፤ ሐሥ7፥51
7፥27 ቍ 13፤ኢሳ 65፥12፤ሕዝ2፥7፤ 3፥7፤ዘካ7፥13
7፥28 ዘሌ 26፥23፤ መዝ15፥2፤ኢሳ59፥ 15፤ሶፎ3፥7
7፥29 ዘሌ 21፥5፤ ኢዮ1፥20፤ኤር4፥8፤ 6፥30፤12፥7፤ሕዝ19፥ 1፤ሆሴ11፥8፤ሚክ5፥3
7፥30 ቍ10፤ ዘሌ 18፥21፤20፥3፤ኤር 2፥7፤4፥1፤32፥34፤ሕዝ 7፥20-22፤
7፥31 ዘሌ18፥21፤ ኢሱ15፥8፤2ነገ23፥10 ፤2ዜና33፥6፤ኤር19፥5 32፥35፤ሕዝ16፥20፤ 20፥31፤ሚክ6፥7
7፥32 ኤር19፥6፡11
7፥33 ዘፍ15፥11፤ዘዳ 28፥26፤ኤር6፥11፤ 14፥16፤ሕዝ29፥5
7፥34 ዘሌ26፥34፤ ኢሳ24፥7-12፡8፤ኤር 33፥10፤ዘካ7፥14፤ማቴ 23፥38፤ራእ18፥23
8፥1 መዝ53፥5፤ኢሳ 14፥19
8፥2 2ነገ 9፥37፤ 23፥5፤ኢዮ31፥27፤ ኤር14፥16፤19፥13፤ 31፥40፤36፥30፤ሕዝ 29፥5፤37፥1፤ሶፎ1፥5፤ ሐሥ7፥42
8፥3 ዘዳ 29፥28፤ ኢ ዮ3፥22፤ራእ 9፥6
8፥4 መዝ119፥67፤ ምሳ24፥16፤ኤር31፥ 19፤ሚክ7፥8
8፥5 ኤር5፥27፤ዘካ 7፥11 8፥6 መዝ14፥1-3፤ሚል3፥16፤ራእ9፥20
8፥7 ዘዳ32፥28፤ኤር4፥22

ሕዝቤ ግን፣
*የእግዚአብሔርን ሥርዐት አላወቀም፡፡*
8“ ‘የጸሓፊዎቻችሁ ሐሰተኛ ብርዕ ሐሰት
እያስተናገደ እንዴት፣ “ዐዋቂዎች ነን፣
*የእግዚአብሔር* ሕግ አለን” ትላላችሁ?
9ጥበበኞች ያፍራሉ፤
ይዋረዳሉ፤ በወጥመድም ይያዛሉ፡፡
*የእግዚአብሔርን* ቃል ተቃውመው፣
ምን ዐይነት ጥበብ ይኖራቸዋል?
10ስለዚህ ሚስቶቻቸውንም ለሌሎች
ወንዶች እሰጣለሁ፤
ዕርሻዎቻቸውንም ለባዕዳን እሰጣለሁ፤
ከታናሹ እስከ ታላቁ ድረስ፣
ሁሉም ተገቢ ላልሆነ ጥቅም
ይስገበገባሉ፤
ነቢያትና ካህናትም እንዲሁ፤
ሁሉም ያጭበረብራሉ፡፡
11የሕዝቤን ቍስል ብርቱ እንዳይደለ
በመቍጠር፣
የተሚላ ፈውስ ሳይኖር እንዲሁ
ያክማሉ፤
ሰላም ሳይኖር፣
“ሰላም፣ ሰላም” ይላሉ፡፡
12ርኵሰት ሲፈጽሙ ዐፍረው ነበርን?
የለም! በጭራሽ አላፈሩም፤
ኀፍረት ምን እንደሆነም አያውቁም፡፡
ስለዚህ ከወደቁት ጋር ይወድቃሉ፤
በምቀጣቸው ጊዜ ይዋረዳሉ፤”
ይላል *እግዚአብሔር፡፡*

13“ ‘ያመረቱትን ሁሉ እወስድባቸዋለሁ፤
ይላል *እግዚአብሔር፤*
በወይን ተክል ላይ የወይን ፍሬ
አይኖርም፤
በበለስ ዛፍ ላይ የበለስ ፍሬ አይገኝም፤
ቅጠሎቻቸውም ይረግፋሉ፡፡
የሰጠኋቸው በሙሉ፣
ከእነርሱ ይወሰድባቸዋል፡፡[ቾ]’ ”

14“ለምን እዚህ እንቀመጣለን?
በአንድነት ተሰብሰቡ!
ወደ ተመሸጉት ከተሞች እንሽሽ፤
በዚያም እንጥፋ!
በእርሱ ላይ ኀጢአትን ስላደረግን፣
*እግዚአብሔር* አምላካችን እንድንጠፋ
አድርጎናል፤
የተመረዘ ውሃ እንድንጠጣ ሰጥቶናል፡፡
15ሰላምን ተስፋ አደረግን፤
መልካም ነገር ግን አልመጣም፤
የፈውስ ጊዜን ተመኘን፤
ነገር ግን ሽብር ብቻ ሆነብን፡፡
16የጠላት ፈረሶች ፋርፋርታ፣
ከዳን ይሰማል፤
በድንጉላ ፈረሶቻቸው ማሽካካት፣
መላዋ ምድር ተንቀጠቀጠች፡፡
ምድሪቱንና በውስጧ ያለውን ሁሉ፣
ከተማዪቱንና በውስጧ የሚኖሩትን
ሁሉ፣
ሊውጡ መጡ፡፡”

17“እነሆ፤ በመካከላችሁ መርዘኛ እባቦችን፣
የአስማተኛ ብልኀት የማይገታቸው
እፉኝቶችን እሰዳለሁ፤
እነርሱም ይነድፉአችኋል፤”
ይላል *እግዚአብሔር፡፡*
18በሐዘኔ የምታጽናናኝ[ጎ] ሆይ፤
ልቤ በውስጤ ዝላለች፡፡
19እንዲህ የሚለውን የሕዝቤን ጩኸት፣
ከሩቅ ምድር ስማ፡-
*እግዚአብሔር* በጽዮን የለምን?
ንጉሥዋስ በዚያ አይኖርምን?”
“በተቀረጹ ምስሎቻቸው፣
እንዲሁም ከንቱ በሆኑ ባዕዳን ለምን
አስቈጡኝ?”

20“መከሩ ዐለፈ፤
በጋው አበቃ፤
እኛም አልዳንም፡፡”

21ሕዝቤ ሲቈስል፣
እኔም ቈሰልሁ፤
አለቀስሁ፤ ድንጋጤ ያዘኝ፡፡
22በገለዓድ የሚቀባ መድኀኒት የለምን?
ወይስ በዚያ ሐኪም አልነበረምን?
ለሕዝቤ ቍስል፣
ለምን ፈውስ አልተገኘም?

9 ስለ ታረዱት ወገኖቼ፣
ቀንና ሌሊት አለቅስ ዘንድ፣
ምነው፣ ራሴ የውሃ ምንጭ በሆነ!
ምነው ዐይኖቼ የእንባ መጕረፊያ
በሆኑልኝ!
2ሕዝቤን ትቼ፣ ርቄ እንድሄድ፣
በምድረ በዳ የእንግዶች ማደሪያ ማን
በሰጠኝ!
ሁሉም አመንዝሮች፣
የአታላዮች መንጋ ሆነዋላ!

3“ሐሰትን ለመናገር፣
ምላሳቸውን እንደ ቀስት ገተሩ፤
በእውነት ሳይሆን፣
በሐሰት በምድሪቱ ገነኑ፤
ከክፋት ወደ ክፋት ሄዱ፤
እኔንም አላወቁኝም፤”
ይላል *እግዚአብሔር፡፡*

[ቾ]13 በዕብራይስጡ የዚህ ስንኝ/ ዐ/ነገር ትርጕም በግልጽ አይ ታወቅም
[ጎ]18 ***የምታጽናናኝ*** በዕብራይስጡ የዚህ ቃል ትርጕም በግልጽ አይ ታወቅም

**8፥8** ሮሜ 2፥17
**8፥9** 2ነገ 19፥26፤ ኢዮ5፥13፤ምሳ1፥7፤ ኢሳ29፥14፤ኤር6፥19 ፤1ቆሮ1፥20
**8፥10** ኢሳ 56፥11፤ ኤር6፥12፤14፥14፤ ኤር23፥11፡15፤ ሰቆ 2፥14
**8፥11** ቍ 15፤ ኤር 4፥10፤ሕዝ7፥25
**8፥12** መዝ52፥5-7፤ ኢሳ3፥9፤ኤር 3፥3፤ 6፥15
**8፥13** ኤር 5፥17፤ ሆሴ2፥12፤ኢል1፥7፤ ማቴ21፥19፤ሉቃ 13፥6
**8፥14** ዘዳ 29፥18፤ ኢሱ10፥20፤ኤር9፥ 15፤14፥7፡20፤23፥15፤ 35፥11፤ዳን9፥5
**8፥15** ቍ11፤ኢዮ 19፥8፤ኤር14፥19
**8፥16** ዘፍ30፥6፤ኤር 4፥29፤5፥17፤51፥29
**8፥17** ዘኍ21፥6፤ ዘዳ32፥24፤መዝ58፥5፤ ኢሳ3፥3
**8፥18** ሰቆ 5፥17
**8፥19** ዘዳ 28፥64፤ 32፥21፤ኢሳ41፥24፤ ኤር9፥16፤44፥3፤ሚክ 4፥9
**8፥21** መዝ94፥5፤ 78፥40፤ኢሳ43፥24፤ ኤር4፥19፤10፥19፤ 14፥17፤30፥14፤ሰቆ 2፥13፤ሕዝ6፥9
**8፥22** ዘፍ37፥25፤ ኢዮ13፥4፤ኢሳ1፥6፤ ኤር30፥12
**9፥1** መዝ119፥136፤ ኢሳ22፥4፤ኤር13፥17 ፤14፥17፤ሰቆ2፥11፡ 18፤3፥48
**9፥2** ዘኍ 25፥1፤ 1ነገ19፥10፤መዝ55፥7 ፤ኢሳ24፥16፤ኤር23፥ 10፤ሆሴ4፥2፤7፥4
**9፥3** ቍ 8፤ ዘፀ 20፥16፤መዝ 64፥3፤ ኢሳ1፥3፤44፥20፤ኤር 18፥18፤ሚክ6፥12

4“እያንዳንዱ ወንድም አታላይ፣[ʾ]
ባልንጀራም ሁሉ ሐሜተኛ ስለ ሆነ፣
ወንድም ከወንድሙ፣ ይጠንቀቅ፣
ባልንጀራም በጓደኛው አይታመን።
5ባልንጀራ ባልንጀራውን ያታልላል፤
እውነትን የሚናገር የለም፤
ሐሰትን ይናገር ዘንድ ምላሳቸውን
አሠልጥነዋል፤
ኀጢአትንም በማድረግ ራሳቸውን
አድክመዋል።
6መኖሪያህ[ʾʾ] በሽንገላ መካከል ነው፤
ከሽንገላቸውም የተነሣ ሊያውቁኝ
አልፈቀዱም፤”
ይላል *እግዚአብሔር*።

7ስለዚህ የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እን
ዲህ ይላል፤

“እነሆ፤ እንደ ብረት አነጥራቸዋለሁ፤
እፈትናቸዋለሁም፤
ስለ ሕዝቤ ኀጢአት፣
ከዚህ የተለየ ምን ማድረግ እችላለሁ?
8ምላሳቸው የሚገድል ቀስት ነው፤
በሽንገላ ይናገራል፤
ሁሉም ከባልንጀራው ጋር በፍቅር
ይናገራል፤
በልቡ ግን ያደባበታል።
9ታዲያ ስለ እነዚህ ነገሮች ልቀጣቸው
አይገባኝምን?”
ይላል *እግዚአብሔር*፤
“እንደዚህ ዐይነቱንስ ሕዝብ፣
አልበቀልምን?

10ስለ ተራሮች አለቅሳለሁ፤ ዋይ ዋይ
እላለሁ፤
በምድረ በዳ ስላሉትም መሰማሪያዎች
አዝናለሁ፤
ሰው የማያልፍባቸው ባድማ ሆነዋል፤
የከብቶች ጩኸት አይሰማም፤
የሰማይ ወፎች ሸሽተዋል፤
የዱር አራዊትም ጠፍተዋል።

11“ኢየሩሳሌምን የፍርስራሽ ክምር፣
የቀበሮም ጐሬ አደርጋታለሁ፤
የይሁዳንም ከተሞች፣
ሰው የማይኖርባቸው ባድማ
አደርጋቸዋለሁ።”

12ይህን መረዳት የሚችል ጥበበኛ ሰው
ማን ነው? *እግዚአብሔር* ገልጾለት ይህንስ
ማስረዳት የሚችል ማን ነው? ምድሪቱስ
ሰው እንደማያልፍበት በረሓ ለምን ጠፋች?
ለምን ወና ሆነች?
13*እግዚአብሔርም* እንዲህ አለ፤ “ይህ
የሆነው የሰጠኋቸውን ሕጌን ትተው ስላል
ታዘዙኝና ሥርዐቴን ስላልተከተሉ ነው።
14በዚህ ፈንታ፣ በልባቸው እልኸኝነት በመ
ሄድ አባቶቻቸው ያስተማሯቸውን በአሊ
ምን ተከተሉ።” 15ስለዚህ የእስራኤል አም
ላክ የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*፣ እንዲ
ህ ይላል፤ “እነሆ፤ ይህን ሕዝብ መራራ
ምግብ አበላዋለሁ፤ የተመረዘንም ውሃ
አጠጣዋ ለሁ። 16እነርሱንም ሆነ
አባቶቻቸውን በማ ያውቋቸው ሕዝቦች
መካከል እበትናቸዋ ለሁ፤ እስካጠፋቸውም
ድረስ በሰይፍ አሳዳ ድቸዋለሁ።”

17የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

“እንግዲህ አስቡበት፤ አልቃሽ ሴቶች
ጥሩ፤
ሥልጡን ሙሾ አውራጆች አስመጡ፤
18እነርሱ ፈጥነው ይምጡ፤
ዐይኖቻችን እንባ እስኪያጐርፉ፣
ሽፋሽፍቶቻችንም ውሃ እስኪያመነጩ፣
ስለ እኛ ሙሾ ያውርዱልን።
19እነሆ የዋይታ ድምፅ ከጽዮን
ተሰምቶአል፤ እንዲህም ይላል፤
. . ‘ምንኛ ወደቅን!
ውርደታችንስ እንዴት ታላቅ ነው!
ቤቶቻችን ፈራርሰዋልና፤
አገራችንን ጥለን እንሂድ።’ ”

20እናንት ሴቶች ሆይ፤ *የእግዚአብሔርን*
ቃል ስሙ፤
ጆሮቻችሁን ከአንደበቱ ለሚወጡት
ቃላት ክፈቱ፤
ሴቶች ልጆቻችሁን ዋይታ፣
አንዳችሁም ሌላውን ሙሾ አስተምሩ።
21ሞት በመስኮቶቻችን ገብቶአል፤
ወደ ምሽጎቻችንም ዘልቆአል፤
ሕፃናትን ከየመንገዱ፣
ወጣቶችን ከየአደባባዩ ጠራርጎ
ወስዶአል።

22እንዲህ በሉ፤ “*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“ ‘የሰዎች ሬሳ፣
በሜዳ እንደተጣለ ጕድፍ፣
ማንም እንደማይሰበስበው፣
ከዐጫጅ ኋላ እንደተተወ ቃርሚያ
ይወድቃል።’ ”

23*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“ጥበበኛ በጥበቡ አይታበይ፤
ኀያልም በኀይሉ አይመካ፤
ሀብታምም በሀብቱ አይኵራራ፤
24የሚመካ ግን፣
እኔ *እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ

9፥4 ዘፍ 27፥35፤ ዘፀ20፥16፤ዘሌ19፥16፤ 2ሳሙ15፥12፤ሚክ 7፥5-6
9፥5 ዘሌ 6፥2፤ መዝ15፥2፤52፥3፤ኢሳ 59፥15
9፥6 ኤር 5፥27
9፥7 ኢዮ 28፥1፤ ኢሳ1፥25፤ኤር6፥27
9፥8 ቀኑ 3፥4፤መዝ 35፥20፤ኢሳ3፥5፤ኤር 5፥26
9፥9 ዘዳ 32፥43፥ ኢሳ 10፥3
9፥10 ኤር 23፥10፤ ኢል1፥19፤ኤር4፥25፤ 12፥4፤ሆሴ4፥3፤ኢል 1፥18
9፥11 ዘሌ 26፥31፤ ኢዮ30፥29፤ኢሳ25፥ 2፤34፥13፤ኤር1፥15፤ 4፥13፤26፥9፥18፤33፥ 10፤50፥3፥13፤51፥62፤ ሰቆ1፥4
9፥12 መዝ 107፥43
9፥13 2ዜና 7፥19፤ መዝ89፥30-32
9፥14 ኤር 2፥8፥23፤ 3፥17፤7፥24፤አሞ2፥4
9፥15 ኤር 8፥14፤ ሰቆ3፥15
9፥16 ዘሌ26፥33፤ ዘዳ4፥32፤ኤር8፥19፤ 14፥12፤24፥10፤44፥ 27፤ሕዝ5፥2፥12
9፥17 መክ 12፥5
9፥18 መዝ 119፥ 136፤ሰቆ3፥48
9፥19 ኤር 4፥13
9፥20 ኢሳ32፥9-13፤ ኤር23፥16
9፥21 2ዜና36፥17፤ ኢሳ40፥30፤ኤር 16፥6፤ኢል 2፥9
9፥22 2ነገ 9፥37
9፥23 1ነገ 20፥11፤ ኢዮ4፥12፤መዝ62፥ 10፤ ምሳ11፥28፤ መክ9፥11፤ኤር48፥7፤ 49፥4፤ ሕዝ 28፥4-5
9፥24 መዝ 34፥2፤ መዝ36፥6፥10፤51፥1፤ 1ቆሮ1፥31፤2ቆሮ

[ʾ]4 ወይም *አታላይ ያዕቆብ*
[ʾʾ]6 ኤርምያስን ያመለክታል (በዕብራይስጡ በነጠላ ቍጥር ተጽፏል)

በማወቁና፣
በምድር ላይ ምሕረትን፣ ፍትሕንና
ጽድቅን የማደርግበት መሆኔን
በመረዳቱ፣
በዚህ ይመካ፤ እኔ በእነዚህ ነገሮች፣
እደሰታለሁና።”
ይላል እግዚአብሔር።

[25]እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ “ሥጋቸ
ውን ብቻ የተገረዙትን ሁሉ የምቀጣበት ጊ
ዜ ይመጣል፤ [26]እነርሱም ግብፅ፣
ይሁዳ፣ ኤዶም፣ አሞን፣ ሞዓብና ጠጕራ
ቸው ዙሪ ያውን የሚከረከም የበረሓ[ሀ]
ነዋሪዎች ሁሉ ናቸው፤ እነዚህ ሕዝቦች
ሁሉ በእርግጥ የተገረዙ አይደሉምና፤
የእስራኤልም ቤት ሁሉ ልባቸው
አልተገረዘም።

## ባዕድ አምልኮና እውነተኛው አምልኮ

10፥12-16 ተጓ ምብ-ኤር51፥15-19

**10** የእስራኤል ቤት ሆይ፤ እግዚአ
ብሔር የሚላችሁን ስሙ። [2]እግዚ
አብሔር እንዲህ ይላል፤

“የአሕዛብን መንገድ አትከተሉ፤
እነርሱ በሰማይ ምልክቶች ይታወካሉ፣
እናንተ ግን በእነዚህ አትረበሹ።
[3]የአሕዛብ ልማድ ከንቱ ነውና፤
ዛፍ ከጫካ ይቈርጣሉ፤
አናጺም በመሣሪያው ቅርጽ
ያበጅለታል፤
[4]በብርና በወርቅ ይለብጡታል፤
እንዳይወድቅም፣
በመዶሻ መትተው በምስማር
ያጣብቁታል።
[5]ጣዖቶቻቸው በዱባ ዕርሻ መካከል እንደ
ቆመ ማስፈራርቾ ናቸው፤
የመናገር ችሎታ የላቸውም፤
መራመድም ስለማይችሉ፣
ተሸካሚ ያስፈልጋቸዋል፤
ጕዳት ማድረስም ሆነ፣
መልካምን ነገር ማድረግ ስለማይችሉ፣
አትፍሯቸው።”
[6]እግዚአብሔር ሆይ፤ እንዳንተ ያለ ማንም
የለም፤
አንተ ታላቅ ነህ፤
የስምህም ሥልጣን ታላቅ ነው።
[7]የሕዝቦች ሁሉ ንጉሥ ሆይ፤
አንተን የማይፈራ ማነው?
ክብር ይገባሃልና።
ከምድር ጠቢባን ሁሉ፣
ከመንግሥቶቻቸውም ሁሉ መካከል፣
እንዳንተ ያለ የለም።
[8]ከከንቱ የዕንጨት ጣዖት ትምህርት
የሚቀስሙ ሁሉ፣
ጅሎችና ሞኞች ናቸው።
[9]የተጠፈጠፈ ብር ከተርሴስ፣
ወርቅም ከአፌዝ ይመጣል።
ባለሙያውና አንጥረኛው የሠሯቸው፣
ብልኀተኞችም ያበጇቸው ሁሉ፣
ሰማያዊና ሐምራዊ ልብስ ተጐናጽፈዋል።
[10]እግዚአብሔር ግን እውነተኛ አምላክ
ነው፤
እርሱ ሕያው አምላክ፣ ዘላለማዊም
ንጉሥ ነው፤
በሚቈጣበት ጊዜ ምድር ትንቀጠቀጣለች፤
መንግሥታትም ቍጣውን ሊቋቋሙ
አይችሉም።

[11]“እናንተም፣ ‘እነዚህ ሰማያትንና ምድ
ርን ያልፈጠሩ አማልክት ከምድር ላይ፣ ከሰ
ማያትም በታች ይጠፋሉ’ ትሏቸዋላችሁ።”[ለ]

[12]እግዚአብሔር ግን ምድርን በኀይሉ ፈጠረ፤
ዓለምን በጥበቡ መሠረተ፤
ሰማያትንም በማስተዋሉ ዘረጋ።
[13]ድምፁን ሲያንጐደጕድ፣ በሰማያት ያሉ
ውሆች ይናወጣሉ፤
ጉሙን ከምድር ዳር ወደ ላይ እንዲ
ወጣ ያደርገዋል፤
መብረቅን ከዝናብ ጋር ይልካል፤
ነፋስንም ከግምጃ ቤቱ ያወጣል።
[14]እያንዳንዳቸው ጅሎችና ዕውቀት
የለሾች ናቸው።
ወርቅ አንጥረኛውም ሁሉ በሠራው
ጣዖት ዐፍሮአል፤
የቀረጻቸው ምስሎቹ የሐሰት ናቸው፤
እስትንፋስም የላቸውም።
[15]እነርሱ ከንቱ የፌዝ ዕቃዎች ናቸው፤
ፍርድ ሲመጣባቸው ይጠፋሉ።
[16]የያዕቆብ ዕድል ፈንታ የሆነው ግን
እንደነዚህ አይደለም፤
እርሱ የሁሉ ነገር ፈጣሪ ነውና፤
እስራኤልም የርስቱ ነገድ ነው።
ስሙ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር
ነው።

## ሊመጣ ያለው ግዞት

[17]አንቺ የተከበብሽ፤
ከያለበት ንብረትሽን ሰብስቢ፤
[18]እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፤
“በዚህች ምድር የሚኖሩትን፣
አሁን ወደ ውጪ እወነጭፋቸዋለሁ፤
ጕዳቱ እንዲሰማቸው፣
መከራ አመጣባቸዋለሁ፤”

[19]ስለ ስብራቴ ወዮልኝ፤
ቍስሌም የማይድን ነው፤

[ሀ]26 ወይም *በበረሓ በተራራቁ ስፍራዎች የሚኖሩ*
[ለ]11 ይህ ጥቅስ የተጻፈው በአራማይክ ቋንቋ ነው

10፥17፤ገላ6፥14
**9፥25** ዘሌ 26፥41፤ ሮሜ2፥25
**9፥26** 1ሳሙ 14፥6፤ ኤር25፥23፤49፥32፤ ሕዝ 31፥18፤ ሐሥ 7፥51
**10፥2** ዘፍ 1፥14፤ ዘፀ23፥24፤ዘሌ20፥23
**10፥3** ዘዳ9፥21፤1ነገ 8፥36፤ኢሳ 40፥19፤ ኤር44፥8፤ሕዝ7፥20
**10፥4** 1ሳሙ 5፥3፤ መዝ135፤ 15፤ኢሳ 41፥7፤ሆሴ13፥2፤ዕን 2፥19
**10፥5** 1ነገ 18፥26፤ ኢሳ45፥20፤ 41፥23፡ 24፤44፥9-20፤ 46፥7 ፤ሐሥ19፥26፤ 1ቆሮ 12፥2
**10፥6** ዘፀ 8፥10፤ 2ሳሙ7፥22፤መዝ 48፥1
**10፥7** መዝ 22፥28፤ ኢሳ12፥4፤ኤር5፥22፤ ራእ15፥4
**10፥8** ዘዳ 32፥21፤ ኢሳ44፥18፤40፥19፤ ኤር 4፥22
**10፥9** ዘፍ 10፥4፤ መዝ115፥4፤ ኢሳ 40፥19
**10፥10** ዘፍ21፥33፤ ኢሱ3፥10፤ መሳ5፥4፤ ኢዮ9፥6፤መዝ18፥7፤ 29፥8፤76፥7፤ኤር 21፥12፤ዳን 6፥26፤ ናሆ1፥6፤ማቴ16፥16
**10፥11** ኢሳ 2፥18
**10፥12** ቍ16፤ ዘፍ 1፥1፡8፡31፤1ሳሙ2፥8
**10፥13** ዘዳ 28፥12፤ ኢዮ36፥29፡30፤መዝ 104፥13፤135፥7
**10፥14** መዝ97፥7፤ ኢሳ1፥29፤44፥20
**10፥15** ኢሳ41፥24፤ ኤር14፥22
**10፥16** ቍ12፤ዘፀ 34፥9፤ዘዳ32፥9፤መዝ 74፥2፤119፥57፤ኤር 31፥35፤32፥17፡18፤ 33፥2
**10፥17** ሕዝ12፥3-12
**10፥18** ዘዳ 28፥52፤ 1ሳሙ25፥29፤ኢሳ 22፥17፤
**10፥19** ኢዮ34፥6፤ ኤር14፥17፤15፥18፤ 30፥12፡15፤ሰቆ2፥13፤ ሚክ1፥9፤7፥9፤ናሆ 3፥19

ግን ለራሴ እንዲህ አልሁት፤
“ይህ የኔው ሕመም ነው
ልሸከመውም ይገባኛል።”
20ድንኳኔ ፈርሶአል፤
ገመዶቹም ሁሉ ተበጣጥሰዋል፤
ልጆቼ ጥለውኝ ሄደዋል፤ ከእንግዲህም
አይመለሱም፤
ድንኳኔን ለመትከል፣
መጋረጃዬንም ለመዘርጋት ማንም የቀረ
የለም።
21እረኞቹ አእምሮ የላቸውም፤
እግዚአብሔርን አይጠይቁም፤
ስለዚህ አልተከናወነላቸውም፤
መንጎቻቸውም ሁሉ ተበታትነዋል።
22መርዶ ስሙ! እነሆ፤ ከሰሜን ምድር፣
ታላቅ ሽብር እየመጣ ነው፤
የይሁዳን ከተሞች ባድማ፣
የቀበሮዎችም መናኸሪያ ያደርጋል።

## የኤርምያስ ጸሎት

23እግዚአብሔር ሆይ፤ የሰው ሕይወት
በራሱ እጅ እንዳልሆነች፣
አካሄዱንም በራሱ አቃንቶ ሊመራ
እንደማይችል ዐውቃለሁ።
24እግዚአብሔር ሆይ፤ ቅጣኝ፤ ብቻ
በመጠኑ ይሁንልኝ፤
ፈጽሞ እንዳልጠፋ፣
በቍጣህ አትምጣብኝ።
25ያዕቆብን አሚጠው ስለበሉት፣
ፈጽመው ስለዋጡት፣
መኖሪያውንም ወና ስላደረጉ፣
በማያውቁህ ሕዝቦች፣
ስምህንም በማይጠሩ ወገኖች ላይ፣
ቍጣህን አፍስስ።

## ያልተከበረው ኪዳን

11 ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ኤርም
ያስ የመጣው ቃል ይህ ነው፤
2“የዚህን ኪዳን ቃል ስማ፤ ለይ
ሁዳ ሕዝብና በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ሰዎች
ንገራቸው፤ 3የእስራኤል አምላክ እግዚ
አ ብሔር እንዲህ ይላል በላቸው፤ ‘ለዚህ ኪ
ዳን ቃል የማይታዘዝ ሰው የተረገመ ይሁን፤
4ይህም ትእዛዝ የቀድሞ አባቶቻችሁን ከግ
ብፅ ምድር፣ ከብረት ማቅለጫው ምድጃ
ባወጣኋቸው ጊዜ ድምፄን ቢሰሙ፣ ትእዛ
ዜንም ሁሉ ቢጠብቁ፣ እነርሱ ሕዝቤ፣
እኔም አምላካቸው እንድሆን የሰጠኋቸው
ቃል ነው፤ 5ዛሬም እንደ ሆነው ሁሉ
ወተትና ማር የምታፈሰውን ምድር
ለአባቶቻችሁ ለመስጠት የገባሁትን
መሐላ እፈጽማ ለሁ።’ ”
እኔም፣ “እግዚአብሔር ሆይ፤ አሜን”
ብዬ መለስሁ።

10፥20 ኤር4፥20፤ 31፥15፤ሰቆ1፥5
10፥21 ቍ8፤ኢሳ 56፥10፤ኤር22፥22፡ 30፤23፥1፡2፤25፥34፤ 50፥6፤ሕዝ34፥6
10፥22 ኢሳ34፥13፤ ኤር6፥22፤27፥6፤49፥ 28፡30፤ሕዝ12፥19
10፥23 ኢዮ33፥29፤ ምሳ3፥5-6፤20፥24
10፥24 መዝ6፥1፤ 38፥1፤ኤር7፥20፤18፥2 3፤46፥28፤30፥11
10፥25 መዝ14፥4፤ 69፥24፤79፥6-7፤ኤር 2፥3፤ሶፎ2፥2፤3፥8
11፥2 ዘጸ 5፥2
11፥3 ዘዳ11፥26-28 ፤27፥26፤28፥15-68፤ ገላ3፥10
11፥4 ቍ7፤ዘፀ24፥8 ፤1ነገ8፥51፤ኤር7፥23 ፤31፥33፤ሕዝ11፥20
11፥5 ዘፀ3፥8፤6፥8 ፤13፥5፤ዘዳ7፥12፤27 ፥26፤መዝ105፥8-11
11፥6 ዘፀ 15፥26፤ ዘዳ15፥5፤ኤር 4፥5፤ ያዕ1፥22
11፥7 2ዜና 36፥15
11፥8 ዘሌ26፥14-43 ፤ዘዳ28፥15-68፤ኢሱ 23፥15፤ 2ዜና7፥19፤ መዝ78፥10፤መክ9፥3፤ ኤር3፥17፤7፥26፤26፥ 4፤32፥23፤44፥10
11፥9 ሕዝ 22፥25
11፥10 ዘዳ 9፥7፤ መሳ2፥12-13፤10፥13 ፤2ዜና30፥7፤ኢሳ24፥5 ፤ኤር16፥11፤34፥18፤ ሕዝ20፥8፤ሆሴ 6፥7፤ 8፥1፤ ዘካ 7፥11
11፥11 ቍ14፤ 2ነገ 22፥16፤ኢዮ 11፥20፤ 27፥9፤መዝ66፥18፤ ምሳ1፥28፤ኢሳ1፥15 ፤59፥2፤ኤር 14፥12፤ 4፥6፤ሰቆ2፥22፤ሕዝ 8፥8፡18፤ ዘካ7፥13፤ ሚል2፥13
11፥12 ዘዳ 32፥37፡ 38፤መሳ10፥14፤ ኤር 44፥17
11፥13 ዘፀ 20፥3፤ 2ነገ17፥29፤ኤር3፥24 ፤7፥9፤19፥4፤ 44፥21
11፥14 ቍ11፤ ዘፀ 32፥10
11፥15 ኤር7፥9-10 ፤ሐጌ2፥12
11፥16 መዝ1፥3፤ ኢ ሳ27፥11፤ኤር7፥20 ፤21፥14፤ሆሴ 14፥6፤ ሮሜ11፥17-24
11፥17 ቍ11፤ዘፀ 15፥17፤ኢሳ5፥2፤45፥4 ፤ኤር7፥18፤7፥9፤12፥2

6እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፤ “ይህን
ቃል ሁሉ በይሁዳ ከተሞችና በኢየሩሳ
ሌም አደባባዮች ተናገር፤ እንዲህም በል፤
‘የዚህን ኪዳን ቃል ስሙ፤ አድርጉትም፤
7የቀድሞ አባቶቻችሁን ከግብፅ ምድር ካወ
ጣሁበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ፣
“ታዘዙኝ“ በማለት ደጋግሜ አስጠነቀቅኋ
ቸው። 8እነርሱ ግን የክፉ ልባቸውን እልከ
ኝነት ተከተሉ እንጂ አልታዘዙኝም፤ ጆሮ
አቸውንም ወደ እኔ አላዘነበሉም፤ ስለዚህ
እንዲከተሉት አዝዤአቸው ያላደረጉትን
የዚህን ኪዳን ርግማን ሁሉ አመጣሁባ
ቸው።’ ”
9እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፤ “በይ
ሁዳ ሕዝብና በኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ዘንድ
አድማ ተገኝቶአል። 10ቃሌን መስማት ወዳ
ልፈለጉት ወደ ቀድሞ አባቶቻቸው ኀጢ
አት ተመለሱ፤ ሊያገለግሏቸውም ሌሎችን
አማልክት ተከተሉ። የእስራኤልና የይሁዳ
ቤት ከቀድሞ አባቶቻቸው ጋር የገባሁትን
ኪዳን አፈረሱ። 11ስለዚህ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤ ‘ሊያመልጡት የማይችሉ
ትን ጥፋት አመጣባቸዋለሁ፤ ወደ እኔ
ቢጮኹም አልሰማቸውም። 12የይሁዳ ከተ
ሞችና የኢየሩሳሌም ሕዝቦች ወደሚያጥኑ
ላቸው አማልክት ሄደው ይጮኻሉ፤
እነርሱ ግን በመከራቸው ጊዜ ከቶ ሊ
ረዷቸው አይችሉም። 13ይሁዳ ሆይ፤ የአ
ማልክትህ ቍጥር የከተሞችህን ብዛት
ያህል ነው፤ አሳፋሪ ለሆነው ጣዖት፣
ለበኣል ማጠኛ የሠራችኋቸው መ
ሠዊያዎቻችሁ ብዛት የኢየሩሳሌምን
መንገዶች ያህል ነው።’ ”
14“በተጨነቁ ጊዜ ወደ እኔ ሲጮኹ
አልሰማቸውምና አንተም ስለዚህ ሕዝብ
አትጸልይ፤ ልመና አታቅርብ፤ አትማጠ
ን።
15“ወዳጄ፣ ከብዙዎች ጋር ተንኰሏን
እየሸረበች፣
በቤቴ ውስጥ ምን ጕዳይ አላት?
ስእለት ወይም የመሥዋዕት ሥጋ
ቅጣትሽን ሊያስቀርልሽ ይችላልን?
እነዚህንስ በመፈጸም፣ ደስተኛ መሆን
ትችያለሽን?”[ኸ]
16እግዚአብሔር፣ ‘የተዋበ ፍሬ ያላት፣
የለመለመች የወይራ ዛፍ’ ብሎሽ ነበር፤
አሁን ግን በታላቅ ዐውሎ ነፋስ ድምፅ፣
እሳት ያነድባታል፤
ቅርንጫፎቿ ይሰባበራሉ።
17የእስራኤልና የያዕቆብ ቤት ለበኣል በማ
ጠን ባደረጉት ክፋት ስላስቈጡኝ፣ አን
ቺን የተከለሽ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር

ክፉ ነገር ዐውጆብሻል::

## በኤርምያስ ላይ የተደረገ ሤራ

18እግዚአብሔር ስውር ዕቅዳቸውን
ገለጠልኝ፤ እኔም ዐወቅሁ፤ በዚያን ጊዜ
ሥራቸውን አሳይቶኝ ነበርና:: 19እኔም
ለመታ ረድ እንደሚነዳ ጠቦት ነበርሁ፤
እነር ሱም፣

"ዛፉን ከፍሬው ጋር እንቍረጥ፤
ከሕያዋን ምድር እናጥፋው፤
ከእንግዲህም ወዲያ ስሙ አይታሰብ::"
ብለው እንዳደሙብኝ ዐላወቅሁም ነበር::
20ልብንና ኵላሊትን የምትመረምር፣
በጽድቅም የምትፈርድ የሰራዊት ጌታ
እግዚአብሔር ሆይ፤
ጒዳዬን ላንተ ትቻለሁና፤
በእነርሱ ላይ የምትፈጽመውን
በቀል ልይ::

21"እንግዲህ ሕይወትህን ለማጥፋት ለሚ
ሹና፣ 'በእግዚአብሔር ስም ትንቢት አት
ናገር፤ አለዚያ በእጃችን ትሞታለህ' ለሚ
ሉህ ለዓናቶት ሰዎች እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤ 22ስለዚህ የሰራዊት ጌታ እግዚአ
ብሔር እንዲህ ይላል፤ 'እነሆ እኔ እቀጣቸ
ዋለሁ፤ ጐልማሶቻቸው በሰይፍ፣ ወንዶችና
ሴቶች ልጆቻቸውም በራብ ይሞታሉ::
23በሚቀጡበት ዓመት በዓናቶት ሰዎች
ላይ መዓት ስለማመጣ፣ ከእነርሱ የሚተ
ርፍ አንድም አይኖርም::' "

## የኤርምያስ ማጒረምረም

12 እግዚአብሔር ሆይ፤ ጒዳዬን በፊ
ትህ ሳቀርብ፣
አንተ ጻድቅ መሆንህን እያወቅሁ ነው::
የክፉዎች መንገድ ለምን ይሰምራል?
የከዳተኞችስ ኑሮ ለምን ይሳካል?
2አንተ ተክለሃቸዋል፤ ሥርም ሰደዋል፤
አድገዋል፤ ፍሬም አፍርተዋል::
ሁልጊዜ አንተ በአፋቸው ላይ አለህ፤
ከልባቸው ግን ሩቅ ነህ::
3ነገር ግን እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ
እኔን ታውቀኛለህ፤ ታየኛለህ፤
ስለ አንተም ያለኝን ሐሳብ
ትመረምራለህ::
እንደሚታረዱ በጎች ንዳቸው፤
ለዕርድም ቀን ለይተህ አቈያቸው፤
4ምድሪቱ በዝናብ እጦት የምትጐዳው፣[ሠ]
የሜዳውም ሣር ሁሉ በድርቅ
የሚመታው እስከ መቼ ነው?
ከነዋሪዎቿ ክፋት የተነሣ፣
እንስሳትና አዕዋፍ ጠፍተዋል፤
ደግሞም ሕዝቡ፣

11÷19 ቀኍ21፤ኢዮ 28÷13፤መዝ44÷16 :22፤54÷3፤71÷10፤ 83÷4፤116÷9፤20÷10፤ ኢሳ53÷8፤ኤር 18÷18
11÷20 1ሳሙ2÷3፤ 1ዜና29÷17፤መዝ 7÷11፤26÷2፤58÷10፤ ሰቆ3÷60
11÷21 ቀኍ19፤ኢሱ 21÷18፤ኢሳ30÷10፤ ኤር2÷30፤12÷6፤ 18÷23፤21÷7፤26÷8: 11፤34÷20፤38÷4
11÷22 ኢሳ9÷17፤ ኤር18÷21
11÷23 ኤር6÷9፤ 23÷12
12÷1 ዕዝ9÷15፤ኢዮ 5÷8፤8÷3፤ 21÷7፡13፤ መዝ37÷7፤ኤር5÷27- 28፤ሕዝ18÷25፤ዳን 9÷14
12÷2 ኢዮ5÷3፤ኢሳ 29÷13፤ኤር3÷10፤ 11÷17፤ሕዝ22÷27፤ ማቴ15÷8፤ማር7÷6፤ ቲቶ 1÷16
12÷3 መዝ7÷9፤ 11÷5፤44÷11፤139÷1- 4፤ ኤር16÷18፤ 17÷18፤ 20÷11
12÷4 ቀኍ11፤ ዘዳ 28÷15-18፤ኤር4÷25: 26፡28፤52÷10፤ኢል 1÷10-12፤አሞ1÷2
12÷5 ኤር49÷19፤ 50÷44
12÷6 መዝ12÷2፤ ምሳ26÷24-25፤ኤር 9÷4
12÷7 2ነገ21÷14፤ ኢሳ5÷1፤ኤር7÷29፤ 17÷4
12÷8 መዝ17÷12፤ 5÷5፤ሆሴ9÷15፤አሞ 6÷8
12÷9 ዘዳ28÷26፤ ኢ ሳ56÷9፤ኤር15÷3 ፤ሕ ዝ23÷25፤ 39÷17-20
12÷10 ኢሳ5÷1-7፤ ኤር9÷10፤23÷1፤25÷ 11፡34፤ሕዝ34÷2-10
12÷11 ቀኍ4፤ኢሳ 5÷6፤24÷4፤ኤር9÷12፤ 14÷4፤23÷10
12÷12 ዘዳ32÷41: 42፤ኢሳ31÷8፤ ኤር 3÷2፤7÷10፤46÷10፤ 47÷6፤ሕዝ 4÷17፤ 21÷3-4፡28፤33÷2
12÷13 ዘፀ15÷7፤ ዘሌ26÷20፤ዘዳ28÷ 38፤ኤር4÷26

"በእኛ ላይ የሚሆነውን አያይም"
ብለዋል::

## የእግዚአብሔር ምላሽ

5"ከእግረኞች ጋር ሮጠህ፣
እነርሱ ካደከሙህ፣
ከፈረሰኞች ጋር እንዴት ልትወዳደር
ትችላለህ?
በሰላም አገር ከተሰናከልህ፣[ዐ]
በዮርዳኖስ ደን ውስጥ እንዴት ልትሆን
ነው?
6ወንድሞችህና የገዛ ቤተ ሰብህ፣
እነርሱ እንኳ አሚረውብሃል፣
በአንተም ላይ ይጮኻሉ፤
በመልካም ቢናገሩህም እንኳ
አትመናቸው::

7"ቤቴን እተዋለሁ፤
ርስቴን እጥላለሁ፤
የምወዳትን እርሷን፣
አሳልፌ በጠላቶቿ እጅ እሰጣታለሁ::
8ርስቴ፣ በዱር እንዳለ አንበሳ
ተነሥታብኛለች
በእኔም ላይ ጮኻብኛለች፤
ስለዚህ ጠላኋት::
9ርስቴ ሌሎች አሞሮች፣
ሊበሏት እንደ ከበቧት፣
እንደ ዝንጒርጒር አሞራ አልሆነችምን?
ሂዱ፤ የዱር አራዊትን ሁሉ ሰብስቡ፤
እንዲቀራመቷትም አምጧቸው::
10ብዙ እረኞች የወይን ቦታዬን ያጠፋሉ፤
ይዞታዬንም ይረግጣሉ፤
ደስ የምሰኝበትንም ማሳ፣
ጭር ያለ በረሓ ያደርጉታል::
11በፊቴ ባድማ፣
ደረቅና ወና ይሆናል፤
መላዪቱም ምድር ጠፍ ትሆናለች፤
ስለ እርሷ የሚገደው የለምና::
12በምድረ በዳ ባሉት ወና ኰረብቶች
ላይ፣
አጥፊዎች ይሰማራሉ፤
የእግዚአብሔር ሰይፍ ከምድር ጫፍ እስከ
ምድር ጫፍ፣
አንዳች ሳያስቀር ይበላል፤
የሚተርፍም የለም::
13ስንዴን ይዘራሉ፤ እሾኽን ያጭዳሉ፤
ይደክማሉ፤ የሚያገኙት ግን የለም፤
ከእግዚአብሔርም ጽኑ ቍጣ የተነሣ፣
በመከራችሁ ውጤት ታፍራላችሁ::"

[ኸ]15 *ወይም ስእለት ወይም የመሥዋዕት ሥጋ ቅጣትሽን ያስቀርልሽ ይችል ይሆን?/ የዚያን ጊዜ ትደሰቻለሽ*
[ሠ]4 *ወይም ምድሪቱ የምታዝነው*
[ዐ]5 *ወይም በሰላም ምድር ከታመንህ*

[14]*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ “ለሕ
ዝቤ ለእስራኤል የሰጠሁትን ርስት የሚ
ይዙትን ክፉ ጎረቤቶቼን ሁሉ፣ ከምድራ
ቸው እነቅላቸዋለሁ፤ የይሁዳንም ቤት
ከመካከላቸው እነቅላለሁ፤ [15]ከነቀልኋቸው
በኋላ ግን መልሼ እምራቸዋለሁ፤ እያንዳን
ዳቸውንም ወደ ገዛ አገራቸውና ወደ ገዛ
ርስታቸው መልሼ አመጣቸዋለሁ፤ [16]የሕ
ዝቤን መንገድ በትጋት ቢማሩና ሕዝቤን
በበኣል እንዲምል እንዳስተማሩት ሁሉ፣
‘ሕያው *እግዚአብሔርን*’ ብለው በስሜ
ቢምሉ፣ በዚያን ጊዜ በሕዝቤ መካከል
ይመሠረታሉ፤ [17]የማይሰማኝን ሕዝብ ግን
ፈጽሜ እነቅለዋለሁ፤ አጠፋዋለሁም” ይላል
*እግዚአብሔር*።

## ከተልባ እግር የተሠራ መቀነት

**13** *እግዚአብሔር*፣ “ሄደህ ከተልባ
እግር የተሠራ መቀነት ግዛ፤ ወገ
ብህንም ታጠቅበት፤ ነገር ግን ውሃ አታስ
ነካው” አለኝ። [2]ስለዚህ *እግዚአብሔር* እን
ዳዘዘኝ መቀነቱን ገዛሁ፤ ወገቤንም ታጠቅ
ሁበት።

[3]ለሁለተኛም ጊዜ *የእግዚአብሔር* ቃል
ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፤ [4]“ገዝተህ
የታጠቅህበትን መቀነት ይዘህ፣ ወደ ኤፍ
ራጥስ″ ሂድ፤ በዚያም በዐለት ንቃቃት
ውስጥ ሸሽገው።” [5]ስለዚህ *እግዚአብሔር*
በነገረኝ መሠረት ወደ ኤፍራጥስ″ ሄጄ
ሸሸግሁት።

[6]ከብዙ ቀን በኋላም *እግዚአብሔር*፣
“ተነሥተህ ወደ ኤፍራጥስ ሂድ፤ በዚያ
እንድትሸሽገው የነገርሁህን መቀነት አምጣ”
አለኝ። [7]እኔም ወደ ኤፍራጥስ ሄጄ፤ መታጠ
ቂያውን ከሸሸግሁበት ቦታ ቈፍሬ አወ
ጣሁ፤ መታጠቂያውም ተበላሽቶ፣ ከጥቅም
ውጭም ሆኖ ነበር።

[8]*የእግዚአብሔርም* ቃል ወደ እኔ እንዲ
ህ ሲል መጣ፤ [9]“*እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤ ‘የይሁዳን ትዕቢትና የኢየሩሳሌምን
እብሪት እንደዚሁ አጠፋለሁ። [10]ቃሌን
መስማት እምቢ ብለው በልባቸው
እልኸኝነት በመ ሄድ ሊያመልኳቸውና ሊ
ሰግዱላቸው ሌሎ ችን ጣዖቶች የሚከተሉ
እነዚህ ክፉ ሕዝ ቦች ከጥቅም ውጭ
እንደ ሆነው እንደዚህ መቀነት
ይበላሻሉ። [11]መቀነት በሰው ወገብ ላይ
እንደሚታሰር፣ መላው የእስራኤልና
የይሁዳ ቤት ከእኔ ጋር ተጣብቆ ለስሜ
ምስጋናና ክብር፣ የኔ ሕዝብ እንዲሆንልኝ
አድርጌው ነበር፤ ሕዝቤ ግን አልሰማም’
ይላል *እግዚአብሔር*።

12፥14 ዘዳ29፥28፤ 28፥63፤2ዜና7፥20፤ መዝ 9፥6፤ዘካ 2፥7-9
12፥15 ዘዳ30፥3፤ መዝ6፥2፤አሞ9፥14-15
12፥16 ኢሱ23፥7፤ ኢሳ26፥18፤49፥6፤ኤር 3፥17፤4፥2፤18፥8
12፥17 ዘፍ27፥29
13፥3 ኤር 33፥1
13፥4 ዘፍ 2፥14
13፥5 ዘፀ 40፥16
13፥9 ዘሌ26፥19፤ ማቴ23፥12፤ሉቃ 1፥51
13፥10 መሳ10፥13፤ ዘዳ8፥19፤መክ9፥3፤ ኤር3፥17፤9፥14፤ 22፥21፤ሕዝ 5፥3
13፥11 ዘፀ19፥5-6፤ ኢሳ43፥21፤63፥12፤ 65፥12፤ኤር3፥17፤ 7፥26፤32፥20
13፥13 መዝ60፥3፤ 75፥8፤ኢሳ 9፥9፤ ኤር25፥18፤51፥57
13፥14 ዘዳ29፥20፤ ኢሳ9፥19-21፤ኤር 7፥20፤16፥5፤49፥32፡ 36፤ሰቆ2፥21፤ሕዝ5፥ 10፤7፥4፤8፥18፤9፥5፡ 10፤24፥14፤ዘካ11፥6
13፥15 ዘፀ 23፥21፤ መዝ95፥7-8
13፥16 ዘሌ26፥37፤ ኢሱ7፥19፤ኢዮ3፥5፡ 23፤ ሳሙ2፥9፤መዝ 82፥5፤ኢሳ51፥17፤ ኤር23፥12
13፥17 መዝ80፥1፤ ኤር9፥1፤3፥1፤14፥18 ፤29፥1፤ሚል 2፥2
13፥18 ሳሙ12፥30 ፤1ነገ2፥19፤2ነገ24፥8፤ ኢሳ22፥17፤ኤር21፥ 11፤22፥1፤ሰቆ5፥16፤ ሕዝ16፥12፤21፥26
13፥19 ኤር20፥4፤ 52፥30፤ሰቆ1፥3
13፥20 ኤር6፥22፤ 23፥2፤ዕን1፥6
13፥21 መዝ41፥9፤ ኤር4፥30፡31፤20፥10 ፤38፥22፤አብ1፥7

## የወይን ጠጅ ማድጋ

[12]“እንዲህ በላቸው፤ ‘የእስራኤል አምላክ
*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ “ማድጋ ሁሉ
በወይን ጠጅ ይሞላል” ይላል። እነርሱም፣
“ማድጋ ሁሉ በወይን ጠጅ እንደሚሞላ
እኛ አናውቅምን?” ቢሉህ፣ [13]እንዲህ በላ
ቸው፤ “*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ ‘በዳ
ዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጡትን ነገሥ
ታት፣ ካህናትን፣ ነቢያትን እንዲሁም
በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን ሁሉ ጨምሮ
በዚህች ምድር የሚኖሩትን ሁሉ በስካር
እሞላቸዋለሁ።’ ” [14]አንዱን ሰው ከሌላው
ጋር፣ አባትንና ወንድ ልጅን እርስ በእርስ
አጋጫለሁ፤ ይላል *እግዚአብሔር*፤ ያለ ሐዘ
ኔታ፣ ያለ ምሕረትና ያለ ርኅራኄ አጠፋ
ቸዋለሁ።’ ”

## የትዕቢት ውጤት

[15]*እግዚአብሔር* ተናግሮአልና፣
ስሙ፤ ልብ በሉ፤
ትዕቢተኛም አትሁኑ።
[16]ጨለማን ሳያመጣ፣
በሚጨልሙትም ተራሮች ላይ፣
እግሮቻችሁ ሳይሰናከሉ፣
ለአምላካችሁ *ለእግዚአብሔር* ክብርን
ስጡ።
ብርሃንን ተስፋ ታደርጋላችሁ፤
እርሱ ወደ ጨለማ ይለውጠዋል፤
ድቅድቅ ጨለማም ያደርገዋል።
[17]ባትሰሙ ግን፣
ነፍሴ ስለ ትዕቢታችሁ፣
በስውር ታለቅሳለች፤
*የእግዚአብሔር* መንጋ ተማርኮአልና፣
ዐይኔ አምርሮ ያለቅሳል፤
እንባዬም እንደ ጐርፍ ይወርዳል።
[18]ለንጉሡና ለእናቱ ለእቴጌዪቱ፣
የክብር ዘውዳችሁ፣
ከራሳችሁ ይወድቃልና፣
ከዙፋናችሁ ውረዱ” በላቸው።
[19]በኔጌቭ ያሉ ከተሞች ይዘጋሉ፤
የሚከፍታቸውም አይኖርም፤
ይሁዳ ሁሉ ተማርኮ ይሄዳል፤
ሙሉ በሙሉም ይዘጋል።
[20]ዐይኖቻችሁን ከፍታችሁ፣
ከሰሜን የሚመጡትን እዩ።
ለአንቺ የተሰጠው መንጋ፣
የተመካሽባቸው በጎች የት አሉ?
[21]ልዩ ወዳጆች እንዲሆኑሽ
ያስተማርሻቸው፣
ባለ ሥልጣን ሲሆኑብሽ ምን ትያለሽ?

″4 ወይም *ፌሬጥ*

እንደምትወልድ ሴት፣
ምጥ አይዝሽምን?
22“ይህ ለምን ደረሰብኝ’ ” ብለሽ
ራስሽን ብትጠይቂ፣
ልብስሽን ተገልበሽ የተገፈተርሽው፣
በሰውም እጅ የተንገላታሽው፣
ከኀጢአትሽ ብዛት የተነሣ ነው።
23ኢትዮጵያዊ[ሠ] መልኩን፣
ነብርስ ዝንጕርጕርነቱን መለወጥ
ይችላልን?
እናንት ክፉ ማድረግ የለመዳችሁትም፣
መልካም ማድረግ አትችሉም።

24“የበረሓ ነፋስ ብትንትኑን
እንደሚያወጣው ገለባ፣
እንዲሁ እበታትናችኋለሁ።
25እኔን ረስተሽ፣
በከንቱ አማልክት ስለታመንሽ፣
ያወጅሁልሽ ድርሻሽ፣
ዕጣ ፈንታሽ ይህ ነው፤”
ይላል *እግዚአብሔር*፤
26“ኀፍረትሽ እንዲገለጥ፣
ልብስሽን ፊትሽ ድረስ እገልባለሁ፤
27በኰረብቶችና በሜዳዎች ላይ፣
አስጸያፊ፣ ተግባርሽን፣
ምንዝርናሽንና ማሽካካትሽን፣
ኀፍረተቢስ ግልሙትናሽን አይቻለሁ።
ኢየሩሳሌም ሆይ፤ ወዮልሽ፤
ከርኵሰትሽ የማትጸጂው እስከ መቼ
ነው’ ”

## ድርቅ፣ ራብ፣ ሰይፍ

14 ስለ ድርቅ ወደ ኤርምያስ የመጣው *የእግዚአብሔር* ቃል ይህ ነው፤

2“ይሁዳ ታለቅሳለች፤
ከተሞቿም ይማቅቃሉ፤
በምድር ላይ ተቀምጠው ይቈዝማሉ፤
ጩኸትም ከኢየሩሳሌም ወጥቶ ይሰማል።
3መሳፍንት አገልጋዮቻቸውን ውሃ ፍለጋ
ይሰዳሉ፤
እነርሱ ወደ ውሃ ጕድጓዶች ይወርዳሉ፤
ነገር ግን ውሃ አያገኙም፤
ዐፍረውና ተስፋ ቈርጠው፣
ራሳቸውን ተከናንበው፣
ባዶ እንስራ ይዘው ይመለሳሉ።
4በምድሪቱ ዝናብ ስለ ሌለ፣
መሬቱ ተሰነጣጥቆአል፤
ገበሬዎችም ዐፍረው፣
ራሳቸውን ተከናንበዋል።
5አንዳች ሣር ባለመኖሩ፣
የሜዳ አጋዘን እንኳ፣
እንደ ወለደች ግልገሏን ጥላ ትሄዳለች።

13፥22 1ነገ9፥9፤ ኢሳ20፥1፤ኤር9፥2-6፡ 16፥10-12፤ሰቆ1፥8 ፤ሕዝ16፥37፤23፥26፤ ናሆ3፥5-6
13፥23 2ዜና6፥36
13፥24 ዘሌ26፥33፤ ኢዮ1፥19፤27፥21፤ መዝ1፥4
13፥25 ዘዳ31፥20፤ ኢዮ20፥29፤መዝ4፥2 ፤106፥19-21፤ኢሳ 17፥10፤ማቴ 24፥51
13፥26 ሰቆ1፥8፤ ሕዝ16፥37፤ናሆ3፥5
13፥27 ኢሳ57፥7 ፤ሕዝ6፥13፤23፥29፤ ሆሴ8፥5
14፥1 ዘዳ28፥22፤ ኢሳ5፥6
14፥2 ኢሳ3፥26
14፥3 ዘዳ28፥48፤ 2ነገ 18፥31፤ አስ 6፥12፤ኢዮ6፥19-20
14፥4 ኤር3፥3፤ 12፥11፤አሞ 4፥8፤ ዘካ14፥7
14፥5 ኢሳ15፥6
14፥6 ዘፍ47፥4፤ኢዮ 39፥5-6፤መዝ104፥11 ፤ ኤር2፥24
14፥7 1ሳሙ12፥22 ፤መዝ79፥9፤ኢሳ3፥9 ፤ኤር2፥19፤5፥6፤ 8፥14፤ሆሴ5፥5
14፥8 መዝ9፥18፤ 18፥46፤46፥1ኢሳ 25፥9፤ ኤር 17፥13፤ 50፥7
14፥9 ዘፍ17፥7፤ መዝ27፥9፤ኢሳ50፥2 ፤63፥19፤ኤር8፥19፤ 15፥16
14፥10 መዝ119፥ 101፤ኤር2፥25፤6፥20 ፤44፥21-23፤ሆሴ7፥2 ፤8፥13፤9፥9አሞ3፥2፤ 5፥22፤8፥7
14፥11 ዘፀ32፥10፤ 1ሳሙ2፥25
14፥12 ዘሌ1፥1-17፤ 2፥1-16፤ዘዳ1፥45፤ 1ሳሙ8፥18፤ኢሳ 51፥ 19፤ኤር7፥21፤9፥16፤ 11፥11፤15፥2፤16፥4፤ 21፥6፤27፥8፥13፤ 32፥24፤34፥17፤ሕዝ 14፥21፤አሞ5፥22
14፥13 ዘዳ 18፥22፤ ኢሳ30፥10፤ኤር4፥10 ፤5፥12፤27፥14፤ 37፥19
14፥14 ኤር5፥1፤ 23፥16፡21፡25፡32፤ 27፥14፤29፥31፤ሰቆ 2፥9፤ሕዝ12፥24፤ 13፥2፡6
14፥15 ኤር5፥12-13፤16፥4፤20፥6፤ሰቆ 1፥19፤ሕዝ14፥9

6የሜዳ አህዮች ባድማ ኰረብቶች ላይ
ቆሙ፤
እንደ ቀበሮም አየር ፍለጋ አለከለኩ፤
ግጦሽ ባለመገኘቱ፣
ዐይኖቻቸው ፈዘዙ።”

7*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ከአንተ መኰብለል
አብዝተናል፤
በአንተም ላይ ዐምፀናል፤
ኀጢአታችን ቢመሰክርብንም እንኳ፣
ስለ ስምህ ብለህ አንድ ነገር
አድርግልን።
8አንተ የእስራኤል ተስፋ፤
በጭንቀት ጊዜ አዳኙ፣
ለምን በምድሪቱ እንደ ባዕድ፣
እንደ ሌት አዳሪ መንገደኛ ትሆናለህ?
9ግራ እንደ ተጋባ ሰው፣
ለመታደግም ኀይል እንዳጣ ተዋጊ
ትሆናለህ?
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ በመካከላችን
አለህ፤
በስምህም ተጠርተናል፤
እባክህ አትተወን።

10*እግዚአብሔር* ስለዚህ ሕዝብ እንዲህ ይላል፤

“መቅበዝበዝ እጅግ ይወዳሉ፤
እግሮቻቸው አይገቱም፤
ስለዚህ *እግዚአብሔር* በእነርሱ ደስ
አይለውም፤
አሁን በደላቸውን ያስባል፤
በኀጢአታቸውም ይቀጣቸዋል።”

11*እግዚአብሔርም* እንዲህ አለኝ፤ “ለዚህ
ሕዝብ በጎነት አትጸልይ፤ 12ቢጾሙም ጩኸ
ታቸውን አልሰማም፤ የሚቃጠል መሥዋዕ
ትና የእህል ቍርባን ቢያቀርቡም አልቀበ
ላቸውም፤ ነገር ግን በሰይፍ፣ በራብና በቸ
ነፈር አጠፋቸዋለሁ።”
13እኔም፣ “ጌታ *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ወዮ!፣
ነቢያቱ ‘ሰይፍ አታዩም፤ ራብም አያገኛ
ችሁም፤ ነገር ግን በዚህ ስፍራ ዘለቄታ
ያለው ሰላም እሰጣችኋለሁ’ ይላል ይሏቸ
ዋል” አልሁ።
14*እግዚአብሔርም* እንዲህ አለኝ፤ “ነቢ
ያቱ በስሜ የሐሰት ትንቢት[የ] ይናገራሉ፤
እኔ አልላክኋቸውም፤ አላዘዝኋቸውም፤
አልተናገርኋቸውምም። የሐሰት ራእይ፣
ሟርት፣ ከንቱ ነገርንና የልባቸውን ሽንገላ
ይተነብዩላችኋል። 15ስለዚህ በስሜ የሐሰት
ትንቢት ስለሚናገሩ ነቢያት *እግዚአብሔር*
እንዲህ ይላል፤ እኔ ሳልልካቸው፣

[ሠ]23 ዕብራይስጡ *ኩሻዊ* ይላል (ምናልባት በላይኛው ዐባይ አካባቢ የሚኖር ሰው ሊሆን ይችላል)።
[የ]14 ወይም *ራእይ፣ (ከንቱ) ሟርት*

‘ሰይፍና ራብ በዚች ምድር ላይ አይመ
ጣም’ የሚሉ እነዚህ ነቢያት በሰይፍና
በራብ ይጠፋሉ፤ 16ትንቢቱ የተነገረለ
ትም ሕዝብ ከሰይፍና ከራብ የተነሣ በኢ
የሩሳሌም አደባባዮች ይወድቃል፤ እነርሱ
ንም ሆነ ሚስቶቻቸውን ወይም ወንዶችና
ሴቶች ልጆቻቸውን የሚቀብራቸው አይገ
ኝም፡፡ ለበደላቸው የሚገባውንም ቅጣት
በላያቸው አወርዳለሁ፡፡

17“ይህን ቃል እንዲህ ብለህ ንገራቸው፤
“ ‘ድንግሊቱ ልጄ፣ ሕዝቤ፣
በታላቅ ስብራት፣
በብርቱ ቍስል ተመትታለችና
ዐይኖቼ ቀንና ሌሊት፣ ሳያቋርጡ
እንባ ያፈስሳሉ
18ወደ ገጠር ብወጣ፣
በሰይፍ የተገደሉትን አያለሁ፤
ወደ ከተማ ብገባ፣ በራብ የወደቁትን
አያለሁ
ነቢዩም ካህኑም፣
ወደማያውቁት አገር ሸሽተዋል፡፡’ ”

19ይሁዳን ፈጽመህ ጥለኸዋልን?
ነፍስህስ ጽዮንን ተጸየፈቻትን?
ፈውስ እስከማይገኝልን ድረስ፣
ለምን ክፉኛ መታኸን?
ሰላምን ተስፋ አደረግን፤
ሆኖም በጎ ነገር አላገኘንም፤
የፈውስን ጊዜ ተጠባበቅን፤
ነገር ግን ሽብር ብቻ ሆነ፡፡
20*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ክፋታችንን
ዐውቀናልና፤
የአባቶቻችንን በደል ተረድተናልና፤
በእርግጥም በአንተ ላይ ኀጢአት
ሠርተናል፡፡
21ስለ ስምህ ብለህ አትናቀን፤
የክብርህንም ዙፋን አታዋርድ፡፡
ከእኛ ጋር የገባኸውን ኪዳን አስብ፤
አታፍርሰውም፡፡
22ከአሕዛብ ከንቱ ጣዖቶች መካከል ዝናብ
ሊያዘንብ የሚችል አለን?
ሰማያትስ በራሳቸው ማካፋት
ይችላሉን?
አይ! አይችሉም፣ *እግዚአብሔር*
አምላካችን ሆይ፤
ይህን ሁሉ የምታደርግ አንተ ነህ፣
ስለዚህም ተስፋችን በአንተ ላይ ነው፡፡

15 *እግዚአብሔርም* እንዲህ አለኝ፤
“ሙሴና ሳሙኤል እንኳ በፊቴ
ቢቆሙ፣ ልቤ ለዚህ ሕዝብ አይራራምና፤
ከፊቴ አስወጣቸው፤ ይሂዱ፡፡ 2እነርሱም፣
‘ወዴት እንሂድ?’ ቢሉህ፣ እንዲህ ብለህ
ንገራቸው፤ ‘*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

“ ‘ለሞት የተመደበ ወደ ሞት፣
ለሰይፍ የተመደበ ወደ ሰይፍ፣
ለራብ የተመደበ ወደ ራብ፣
ለምርኮ የተመደበ ወደ ምርኮ
ይሄዳል፡፡’

3“*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ ‘አራት
ዐይነት አጥፊዎችን እሰድባቸዋለሁ፤ እነዚ
ህም፦ ለመግደል ሰይፍ፣ ለመጐተት ውሾች፣
እንዲሁም ጠራርጎ ለመብላትና ለማጥፋት
የሰማይ ወፎችና የምድር አራዊት ናቸው፡፡
4የይሁዳ ንጉሥ የሕዝቅያስ ልጅ ምናሴ
በኢየሩሳሌም ካደረገው በደል የተነሣ፣
ለምድር ነገሥታት ሁሉ መሰቀቂያ አደ
ርጋቸዋለሁ፡፡

5“ኢየሩሳሌም ሆይ፤ የሚራራልሽ ማን
ነው?
ማንስ ያለቅስልሻል?
ደኅንነትሽንስ ማን ጎራ ብሎ
ይጠይቃል?
6እኔን ጥለሽኛል” ይላል *እግዚአብሔር*፤
“ወደ ኋላም እያፈገፈግሽ ነው፤
ስለዚህ እጄን በአንቺ ላይ አነሣለሁ፤
አጠፋሻለሁም፤
ከእንግዲህም አልራራልሽም፡፡
7በአገሪቱ የከተማ ደጆች፣
በመንሽ እበትናቸዋለሁ፤
ከመንገዳቸው አልተመለሱምና፣
ሕዝቤን በሐዘን እመታለሁ፤
ጥፋትም አመጣባቸዋለሁ፤
8የመበለቶቻቸውን ቍጥር፣
ከባሕር አሸዋ ይልቅ አበዛለሁ፤
ይጐበዛዝት እናቶች በሆኑትም ላይ፣
አጥፊውን በቀትር አመጣባቸዋለሁ፡፡
ሽብርንና ድንጋጤን፣
በድንገት አወርድባቸዋለሁ፡፡
9የሰባቶቹ እናት ትዝለፈለፋለች፤
ትንፋሿም ይጠፋል፤
ገና ቀን ሳለ ፀሓይዋ ትጠልቃለች፤
እርሷም ታፍራለች፤ ትዋረዳለችም፤
የተረፉትንም በጠላቶቻቸው ፊት፣
ለሰይፍ እዳርጋቸዋለሁ፤”
ይላል *እግዚአብሔር*፡፡

10ወይኔ እናቴ! ለምድር ሁሉ፣
የጭቅጭቅና የክርክር ሰው የሆንሁትን
ምነው ወለድሽኝ!
ለማንም አላበደርሁም፤ ከማንም
አልተበደርሁም፤
ነገር ግን ሰው ሁሉ ይረግመኛል፡፡
11*እግዚአብሔር* እንዲህ አለ፤

14፥16 መዝ79፥3፤ ምሳ1፥31፤ኤር7፥33፤ 17፥10
14፥17 2ነገ19፥21 ፤መዝ119፥136፤ኢሳ 23፥12፤ኤር8፥21
14፥18 2ዜና36፥10 ፤ኤር 13፥17፤ ሕዝ 7፥15
14፥19 ኢዮ19፥8፤ ኢሳ1፥6፤ኤር7፥29፤ 8፥15፤ 30፥12-13
14፥20 ዘሌ 26፥40 ፤መሳ10፥10፤1ነገ 8፥ 47፤ዕዝ9፥6፤ኤር3፥13 ፤ዳን9፥7-8
14፥21 ቀኑ7፤ዘፀ 2፥24፤ኢሱ7፥9፤ኢሳ 62፥7፤ኤር3፥17
14፥22 1ነገ8፥36፤ መዝ135፥7፤ኢሳ41፥ 24፤43፥10፤44፥10፤ ኤር10፥15፤16፥19፤ ዕን2፥18
15፥1 ዘፀ32፥11፤ ዘኍ14፥13-20፤1ሳሙ 1፥20፤7፥8፤1ሳሙ 2፥25፤2ነገ17፥20፤ ኤር7፥1616፥13
15፥2 ዘዳ28፥26፤ ኤር14፥12፤42፥22፤ 43፥11፤44፥13፤ሰቆ 4፥9፤ሕዝ12፥11፤ራእ 13፥10
15፥3 ዘሌ26፥22፡ 25፤ዘኍ33፥4፤ዘዳ28፥ 26፤1ነገ21፥19፤2ነገ 9፥36፤ሕዝ14፥21፤ 33፥27
15፥4 ዘዳ 28፥25፤ 2ነገ21፥2፤23፥26-27፤ ኢዮ17፥6፤ኤር24፥9፤ 29፥18፤34፥17
15፥5 ኢሳ27፥11፤ 51፥19፤ኤር13፥14፤ 16፥13፤21፥7፤ናሆ 3፥7
15፥6 ዘዳ32፥15፤ኢ ሳ31፥3፤ኤር6፥19፤7፥ 20፤አሞ7፥8፤ሶፎ1፥4
15፥7 2ዜና28፥22፤ ኢሳ41፥16፤3፥26፤ ኤር18፥21
15፥8 ኢዮ18፥11፤ ኢሳ47፥9፤ኤር4፥7፤ 6፥4
15፥9 1ሳሙ2፥5፤ 2ነገ25፥7፤ኢዮ8፥13፤ ኤር7፥19፤19፥7፤21፥7 ፤25፥31
15፥10 ዘሌ25፥36፤ ነህ5፥1-12፤ኢዮ3፥1፤ 10፥18-19፤ኤር1፥19፤ 6፥10
15፥11 ቀኑ21፤ኤር

“በእርግጥ ለበጎ ዐላማ እታደግሃለሁ፤
በመከራና በጭንቅ ጊዜም፣
ጠላቶችህ ደጅ እንዲጠኑህ በእውነት
አደርጋለሁ።

12“ሰው ብረትን፣ ከሰሜን የመጣን
ብረት፣
ነሐስንስ መስበር ይችላልን?
13በመላ አገርህ፣
ስላለው ኀጢአትህ ሁሉ፣
ሀብትና ንብረትህን፣
ያለ ዋጋ አሳልፌ ለምርኮ እሰጣለሁ።
14ቍጣዬ በላያችሁ፣
የሚነድ እሳት ትጭራለችና፣
በማታውቀው አገር፣
ለጠላቶችህ[ሀ] ባሪያ አደርግሃለሁ።”

15*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ
ታውቃለህ፤
እንግዲህ አስበኝ፤ ጐብኘኝም፤
አሳዳጆቼን ተበቀልልኝ።
ታጋሽ እንደ መሆንህ አታጥፋኝ፤
ባንተ ምክንያት የሚደርስብኝን ነቀፋ
አስብ።
16ቃልህ በተገኘ ጊዜ በላሁት፤
የሠራዊት አምላክ *እግዚአብሔር* ሆይ፤
በስምህ ተጠርቻለሁና፣
ቃልህ ሐሤትና የልብ ደስታ
ሆነልኝ።
17ፈንጠዝያ ከሚያደርጉት ጋር
አልተቀመጥሁም፤
ከእነርሱም ጋር አልፈነጨሁም፤
እጅህ በላዬ ስለ ነበር፣ በቍጣህ ስለ
ሞላኸኝ፣
ለብቻዬ ተቀመጥሁ።
18ሕመሜ ለምን ጸናብኝ?
ቍስሌስ ለምን በረታብኝ? ለምንስ
የማይፈወስ ሆነ?
እንደሚያታልል ወንዝ፣
እንደሚያሳስት ምንጭ ትሆንብኛለህን?

19ስለዚህ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

“ብትመለስ፣ መልሼ አቆምሃለሁ፤
ታገለግለኛለህም፤
የከበረውን ከማይረባው ለይተህ ብትናገር፣
አፍ ትሆነኛለህ፤
እነርሱ ወደ አንተ ይመለሳሉ እንጂ፣
አንተ ወደ እነርሱ አትመለስም፤
20ለዚህ ሕዝብ የናስ ቅጥር፣ የተመሸገ
የናስ ቅጥር አደርግሃለሁ፤
ሊታደግህና፣ ላድንህም፣
እኔ ከአንተ ጋር ነኝና፤
ቢዋጉህም እንኳ፣
ሊያሸንፉህ አይችሉም፤”

21፥1-2፤37፥3፤40፥4፤
42፥1-3
**15፥12** ዘጸ28፥48፤
ኤር28፥14፤ሰቆ1፥14፤
ሆሴ10፥11
**15፥13** 2ነገ25፥15፤
24፥13፤መዝ44፥12፤
ኤር17፥3፤ሕዝ
38፥12-13
**15፥14** ዘዳ28፥36፤
መዝ21፥9፤ኤር5፥19
**15፥15** ዘፀ34፥6፤
መሳ16፥28፤መዝ
44፥22፤69፥7-9፤
119፥84፤ኤር6፥10
**15፥16** ኢዮ15፥11፤
መዝ119፥72፡103፤
ኢሳ43፥7፤ኤር14፥9
፤ሕዝ2፥8፤3፥3፤ራእ
10፥10
**15፥17** ሩት3፥3፤
2ነገ3፥15፤መዝ1፥1፤
26፥4-5፤ኤር16፥8
**15፥18** ኢዮ6፥4፡15
፤መዝ9፥10፤ኤር10፥
19፤30፥12፤ሚክ1፥9
**15፥19** ዘፀ4፥16፤
ዘካ3፥7
**15፥20** መዝ129፥2
፤ኢሳ50፥7፤ኤር1፥8፤
20፥11፤42፥11፤ሕዝ
3፥8
**15፥21** ዘፍ48፥16፤
መዝ97፥10፤ኤር1፥8
፤50፥34
**16፥2** ማቴ19፥12፤
1ቆሮ7፥26-27
**16፥3** ኤር6፥21
**16፥4** ቀኁ6፤ዘዳ28፥
26፤መዝ79፥1-3፤ኤር
9፥22፤14፥12፡15፤
19፥7፤25፥33
**16፥5** ኤር15፥5
**16፥6** ቀኁ4፤ዘሌ
19፥28፤21፥5፤ኢዮ
1፥20፤ኤር9፥21፤ሕዝ
9፥5-6
**16፥7** 2ሳሙ3፥35፤
ኤር22፥10፤ሰቆ1፥9፡
11፤ሕዝ24፥17፤ሆሴ
9፥4
**16፥8** ዘፀ32፥6፤መክ
7፥2-4፤ኤር15፥17
**16፥9** መዝ78፥63
፤ኢሳ22፥12-14፤24፥8
፤51፥3፤ሕዝ 26፥13፤
አሞ 6፥4-7፤ራእ
18፥23
**16፥10** ዘዳ29፥24፤
ኤር5፥19
**16፥11** ዘዳ29፥25-
26፤1ነገ9፥9፤ኢዮ31፥
27፤መዝ106፥35-43
**16፥12** ዘፀ32፥8፤
መክ9፥3፤ኤር3፥17፤
7፥26፤ሕዝ20፥30፤
አሞ2፥4፤

ይላል *እግዚአብሔር*፤
21“ከክፉዎች እጅ እቤዥሃለሁ፤
ከጨካኞችም ጭምደዳ እታደግሃለሁ።”

**የጥፋት ቀን**

16 *የእግዚአብሔር* ቃል ወደ እኔ እን
ዲህ ሲል መጣ፤ 2“በዚህ ስፍራ
ሚስት አታግባ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆ
ችም አይኑሩህ፤” 3በዚህች ምድር ስለሚወ
ለዱ ወንዶችና ሴቶች ልጆች፣ እንዲሁም
ስለ እናቶቻቸው ስለ አባቶቻቸው *እግዚአ
ብሔር* እንዲህ ይላልና፤ 4“በአደገኛ በሽታ
ይሞታሉ፤ አይለቀስላቸውም፤ አይቀበሩም፤
በምድርም ላይ እንደ ጕድፍ ይጣላሉ።
በሰይፍና በራብ ይጠፋሉ፤ ሬሳቸውም ለሰ
ማይ ወፎችና ለምድር አራዊት መብል
ይሆናል።”
5*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላልና፤ “በረከቴን፣
ፍቅሬንና ምሕረቴን ከዚህ ሕዝብ አርቄ
አለሁና፤ ልቅሶ ወዳለበት ቤት አትግባ፤
ታለቅስና ታዝንም ዘንድ አትሂድ” ይላል
*እግዚአብሔር*። 6“ታላላቆችና ታናናሾች በዚ
ህች ምድር ይሞታሉ፤ አይቀበሩም፤ አይ
ለቀስላቸውም፤ ሰውነቱን የሚቧጥጥላቸው፣
ጠጕሩንም የሚላጭላቸው አይገኝም፤ 7ሐዘን
ተኞችን ለማጽናናት የእዝን እንጀራ የሚ
ያመጣ አይኖርም፤ አባትም ሆነ እናት
የሞተባቸውንም ለማጽናናት መጠጥ የሚያ
ቀርብ አይገኝም።
8“ከእነርሱ ጋር ተቀምጠህ ለመብላትና
ለመጠጣት ድግስ ወዳለበት ቤት አትግባ፤
9የእስራኤል አምላክ የሰራዊት ጌታ *እግዚ
አብሔር* እንዲህ ይላልና፤ ‘እነሆ፤ በዐይ
ናችሁ ፊት፣ በዘመናችሁም የደስታና የሐ
ሤት ድምፅ፣ የሙሽራውንና የሙሽራዪቱን
ድምፅ ከዚህ ስፍራ አስወግዳለሁ።’
10“ይህን ሁሉ ለዚህ ሕዝብ በምትነግር
በት ጊዜ ሰዎቹ፣ ‘*እግዚአብሔር* ይህን ሁሉ
ታላቅ ጥፋት በእኛ ላይ ለምን ዐወጀ?
በደላችንስ ምንድን ነው? በአምላካችንስ
*በእ ግዚአብሔር* ላይ የሠራነው ኀጢአት
ምን ድን ነው?’ ብለው ቢጠይቁህ፣
11እንዲህ ትላቸዋለህ፤ ‘አባቶቻችሁ እኔን
ስለተውኝ ነው’ ይላል *እግዚአብሔር*፤
‘ሌሎችን አማ ልክት በመከተል፣
ስላገለገሏቸውና ስላመለ ኳቸው ነው፤
ትተውኝ ኰበለሉ፤ ሕጌንም አልጠበቁም።
12እናንተም ደግሞ ከአባቶ ቻችሁ የባሰ
ክፉ ነገር አድርጋችኋል፤ እያ ንዳንዳችሁ
እኔን በመታዘዝ ፈንታ የልባ

[ሀ]14 አንዳንድ የዕብራይስጥ ጽሑፎች፣ ሰብዓ ሊቃናትና ሱር
ሰት ጽሑፎች *ጠላቶችህ እንዲወስዱህ አደርጋለሁ*
ይላሉ

ችሁን ክፋት ምን ያህል በእልኸኝነት እን
ደምትከተሉ ተመልከቱ። 13ስለዚህ
ከዚህች ምድር አውጥቼ፣ እናንተም ሆነ
አባ ቶቻችሁ ወደማታውቁት ምድር
እጥላችኋ ለሁ፤ ምሕረትንም
አላደርግላችሁምና በዚያ ሌሎችን አ
ማልክት ቀንና ሌሊት ታገለግ ላላችሁ።'
14"ስለዚህ ሰዎች፦ 'እስራኤላውያንን ከግ
ብፅ ምድር ያወጣ ሕያው እግዚአብሔርን'
ብለው ከእንግዲህ የማይምሉበት ዘመን
ይመ ጣል" ይላል እግዚአብሔር፤ 15"ነገር
ግን፣ እስራኤላውያንን ከሰሜን ምድርና
እነርሱን ከበተነባቸው ከሌሎች አገሮች
ሁሉ ያወጣ
ሕያው እግዚአብሔርን!' ይላሉ፤ ለአባቶቻ
ቸው ወደ ሰጠኋቸው ምድር እመልሳቸዋ
ለሁና።
16"አሁን ግን ብዙ ዓሣ አጥማጆችን እል
ካለሁ" ይላል እግዚአብሔር፤ "እነርሱም
ያጠምዷቸዋል። ከዚያም በኋላ ብዙ አዳኞ
ችን እሰዳለሁ፤ እነርሱም ከየተራራው፣ ከየ
ኮረብታው ሁሉ ከየዐለቱም ስንጣቂ አድ
ነው ይይዟቸዋል። 17ዐይኔ በመንገዳቸው
ሁሉ ላይ ነው፤ በፊቴ የተገለጡ ናቸው፤
ኀጢአታቸውም ከዐይኔ የተሰወረ አይደ
ለም። 18ምድሬን በድን በሆኑ አስጸያፊ
ጣዖቶቻቸው ስላረከሱ፣ ርስቴንም በአሳፋሪ
ነገሮች ስለሞሉ፣ ሳደረጉት በደልና ኀጢ
አት ዕጥፍ እከፍላቸዋለሁ።"

19ብርታቴና ምሽጌ፣
በመከራ ቀን መጠጊያዬ የሆንህ
እግዚአብሔር ሆይ፤
አሕዛብ ከምድር ዳርቻ፣
ወደ አንተ መጥተው እንዲህ ይላሉ፤
"አባቶቻችን ለአንዳች ነገር ያልረቧቸውን
ከንቱ ጣዖቶች፣
የሐሰት አማልክትን ወረሱ።
20ሰዎች ለራሳቸው አማልክትን ያበጃሉን?
ያደርጉ ይሆናል፤ እንዲህ ዐይነቶቹ ግን
አማልክት አይደሉም።"
21"ስለዚህ አስተምራቸዋለሁ፤
ኀይሌንና ታላቅነቴን፣
አሁን አስተምራቸዋለሁ፤
እነርሱም ስሜ እግዚአብሔር፣
እንደ ሆነ ያውቃሉ።

## 17

"የይሁዳ ኀጢአት በብረት ብርዕ፣
በሾለ የአልማዝ ጫፍ፣ ተጽፎ
አል፤
በልባቸው ጽላት፣
በመሠዊያቸውም ቀንዶች ላይ
ተቀርጾአል።
2ልጆቻቸው እንኳ ሳይቀሩ፣

16፥13 ዘዳ4፥28፤ 28፥36፤1ነገ9፥9፤2ዜና 7፥20፤ኤር5፥19፤ 15፥5
16፥14 ዘዳ15፥15፤ ኤር29፥10፤30፥3፤31፥ 27፡38
16፥15 ዘዳ30፥3፤ መዝ53፥6፤ኢሳ11፥11 ፡12፤14፥1፤ኤር3፥18፤ 23፥8፤30፥3፤32፥44፤ሕ ዝ38፥14፤ኢል3፥1
16፥16 1ሳሙ26፥ 20፤አሞ4፥2፤9፥3፤ ሚክ7፥2፤ዕን1፥14-15
16፥17 ዘፍ3፥8፤ ምሳ15፥3፤መክ12፥14 ፤መዝ51፥9፤ሶፎ1፥12፤ ማር4፥22፤1ቆሮ4፥5 ፤ዕብ4፥13
16፥18 ዘኍ35፥34 ፤1ነገ14፥24፤መዝ 101፥3፤ኢሳ65፥6፤ 40፥2፤2፥7፤4፥1፤12፥3 ፤ሕዝ5፥11፤8፥10፤ ራእ18፥6
16፥19 ዘዳ32፥21፤ 1ሳሙ12፥21፤2ሳሙ 22፥3፤መዝ4፥2፤46፥1፤ ኢሳ2፥2፤40፥19፤ ኤር3፥17፤14፥22
16፥20 መዝ115፥ 4-7፤ኤር2፥11፤ሮሜ 1፥23
16፥21 ዘፀ 3፥15
17፥1 ዘፀ 27፥2፤ ዘዳ6፥6፤ኢዮ19፥24፤ 2ቆሮ3፥3
17፥2 2ዜና 24፥18፤ኤር2፥20
17፥3 2ነገ24፥13፤ ኤር26፥18፤15፥13፤ ሚክ3፥12
17፥4 ዘዳ28፥48፤ ኤር7፥20፤12፥7፤16፥ 13፤22፥28፤ሰቆ5፥2
17፥5 መዝ108፥12 ፤ኢሳ2፥22፤2ቆሮ1፥9
17፥6 ዘዳ29፥23፤ ኢ ዮ30፥3፤39፥6፤መዝ 107፥34፤ኤር48፥9
17፥7 መዝ146፥5፤ 26፥1፤34፥8፤40፥4፤ም ሳ16፥20፤ኤር39፥18
17፥8 ኢዮ14፥9፤ መዝ1፥3፤92፥12-14፤ ኤር14፥1-6፤ሕዝ 19፥10፤47፥12
17፥9 መክ9፥3፤ ማቴ13፥15፤ማር 7፥21-22
17፥10 ዘሌ26፥28፤ ኢሱ22፥22፤2ዜና 6፥30፤መዝ17፥3፤ 62፥12፤139፥23፤ኤር 11፥20፤12፥13፤14፥16 ፤20፥12፤21፥14፤ 32፥19፤ሕዝ11፥5፤ 38፥10፤ማቴ16፥27፤ ራእ2፥23
17፥11 ሉቃ12፥20

በለመለሙ ዛፎች ሥር፣
ከፍ ባሉ ኮረብቶችም ላይ ያሉትን፣
መሠዊያቸውንና አሼራ የተባለችውን
ጣዖት ምስል[ጀ] ያስባሉ።
3በአገርህ ሁሉ ከተፈጸመው ኀጢአት
የተነሣ፣
በምድሪቱ ያለህ ተራራዬ፣[ገ]
ሀብትህንና ንብረትህን ሁሉ፣
መስገጃ ኮረብቶችህንም ጭምር፣
ለብዝበዛ አደርገዋለሁ።
4በገዛ ጥፋትህ፣
የሰጠሁህን ርስት ታጣለህ፤
በማታውቀውም ምድር፣
ለጠላቶችህ ባሪያ አደርግሃለሁ፤
ለዘላለም የሚነደውን፣
የቍጣዬን እሳት ጭረሃልና።"
5እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
"በሰው የሚታመን፣
በሥጋ ለባሽ የሚመካ፣
ልቡንም ከእግዚአብሔር የሚያርቅ
የተረገመ ነው።
6በምድረ በዳ እንዳለ ቍጥቋጦ ይሆናል፤
መልካም ነገር ሲመጣ አያይም፤
ሰው በሌለበት በጨው ምድር፣
በምድረ በዳ በደረቅ ስፍራ
ይቀመጣል።
7"ነገር ግን በእግዚአብሔር የሚታመን፣
መታመኛውም እግዚአብሔር የሆነ
ሰው ቡሩክ ነው።
8በውሃ ዳር እንደ ተተከለ፣
ሥሩንም ወደ ወንዝ እንደ ሰደደ
ዛፍ ነው፣
ሙቀት ሲመጣ አይፈራም፤
ቅጠሉም ዘወትር እንደለመለመ ነው፤
በድርቅ ዘመን አይሠጋም፤
ፍሬ ማፍራቱንም አያቋርጥም።"
9የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነው፤
ፈውስም የለውም፤
ማንስ ሊረዳው ይችላል?
10"እኔ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ እንደ
መንገዱ፣
እንደ ሥራው ፍሬ ለመስጠት፣
ልብን እመረምራለሁ፤
የአእምሮንም ሐሳብ እፈትናለሁ።"
11ሀብትን በግፍ የሚያከማች ሰው፣
ያልፈለፈለችውን ጫጩት እንደ
ምትታቀፍ ቆቅ ነው፤
በዕድሜው አጋማሽ ትቶት ይሄዳል፤

[ጀ]2 ወይም የአሼራ ዐጸድ
[ገ]3 ወይም በምድሪቱ ያሉ ተራራዎችን

በመጨረሻም ሞኝነቱ ይረጋገጣል።

12የመቅደሳችን ስፍራ፣
ከጥንት ጀምሮ ከፍ ያለ የክብር
ዙፋን ነው።
13የእስራኤል ተስፋ *እግዚአብሔር* ሆይ፤
ጥለውህ የሚሄዱ ሁሉ ያፍራሉ፤
ፊታቸውን ከአንተ የሚመልሱ በዐፈር
ላይ ይደፋሉ፤
የሕይወትን ውሃ ምንጭ፣
*እግዚአብሔርን* ትተዋልና።

14*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ፈውሰኝ፤
እፈወሳለሁ፤
አድነኝ እኔም እድናለሁ፤
አንተ ምስጋናዬ ነህና።
15እነርሱ ደጋግመው፣
"*የእግዚአብሔር* ቃል የት አለ?
እስቲ አሁን ይፈጸም!" ይሉኛል።
16እረኛ ሆኜ አንተን ከማገልገል ወደ
ኋላ አላልሁም፤
ክፉ ቀን እንዳልተመኘሁ ታውቃለህ፤
ከአንደበቴ የሚወጣውም በፊትህ
ግልጽ ነው።
17አስደንጋጭ አትሁንብኝ፤
በመከራ ቀን መሸሸጊያዬ አንተ ነህ።
18አሳዳጆቼ ይፈሩ፤
እኔን ግን ከዕፍረት ጠብቀኝ፤
እነርሱ ይደንግጡ፤
እኔን ግን ከድንጋጤ ሰውረኝ፤
ክፉ ቀን አምጣባቸው፤
በዕጥፍ ድርብ ጥፋት አጥፋቸው።

## ሰንበትን ማክበር

19*እግዚአብሔር* እንዲህ አለኝ፤ "ሄደህ የይ
ሁዳ ነገሥታት በሚገቡበትና በሚወጡበት
በሕዝቡ በር በሌሎቹም የኢየሩሳሌም በሮች
ሁሉ ቁም፤ 20እንዲህም በላቸው፤ 'በእነዚህ
በሮች የምትገቡ የይሁዳ ነገሥታት ሆይ፤
የይሁዳ ሕዝብና በኢየሩሳሌም የምትኖሩ
ሁሉ፤ *የእግዚአብሔርን* ቃል ስሙ። 21*እግ
ዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ "በሰንበት ቀን
ሸክም ተሸክማችሁ በኢየሩሳሌም በሮች
እንዳታስገቡ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። 22አባ
ቶቻችሁን እንዳዘዝኋቸው ሰንበትን አክ
ብሩ እንጂ በሰንበት ቀን ከየቤታችሁ ሸክም
ይዛችሁ አትውጡ፤ ምንም ሥራ አትሥሩ።"
23እነርሱ ግን አልሰሙም፤ ልብም አላ
ሉም፤ እንዳይሰሙና እንዳይገሠጹም ዐንገ
ታቸውን አደነደኑ። 24ነገር ግን በጥንቃቄ
ብትታዘዙኝ ይላል *እግዚአብሔር*፤ በሰንበ
ትም ቀን በዚህች ከተማ በሮች ሸክም
ይዛችሁ ባትገቡ፣ የሰንበትንም ቀን ምንም
ሳትሠሩ ብትቀድሱት፣ 25በዳዊት ዙፋን

17፥12 ኤር 3፥17
17፥13 መዝ69፥28፤71፥5፤87፥6፤ኢሳ 12፥3፤ኤር2፥17፤14፥8፤ሕዝ13፥9፤ዳን 12፥1፤ዮሐ4፥10
17፥14 ዘፀ15፥2፤ ኢሳ30፥26፤መዝ 109፥1፤ 119፥94፤ ኤር15፥18
17፥15 ኢሳ5፥19፤ 2ጴጥ3፥4
17፥16 መዝ139፥4
17፥17 መዝ18፥18፤46፥1፤88፥15-16፤ ኤር16፥19፤ናሆ1፥7
17፥18 መዝ35፥1-8፤ኢሳ40፥2፤ኤር12፥3
17፥19 ኤር7፥2፤ 26፥2
17፥20 ኤር19፥3፤ 22፥2
17፥21 ዘኍ15፥32-36፤ዘዳ5፥14፤ነህ13፥15-21፤ዮሐ5፥10
17፥22 ዘፍ2፥3፤ ዘፀ 20፥8፤ኢሳ56፥2-6
17፥23 2ዜና28፥22፤ኤር7፥26፤28፤19፥15፤ዘካ7፥11
17፥24 ቍ 22
17፥25 2ሳሙ7፥13፤ኢሳ9፥7፤ኤር22፥2፡4፤30፥10፤33፥16፤ሕዝ 28፥26ሉቃ1፥32
17፥26 ኤር32፥44፤ 33፥13፤ዘካ7፥7
17፥27 1ነገ9፥6፤ 2ነገ25፥9፤ነህ10፥31፤ኤር7፥20፤22፥5፤ ሆሴ8፥14፤አሞ2፥5
18፥6 ዘፍ2፥7፤ ኢሳ 29፥16፤45፥9፤ሮሜ 9፥20-21፤
18፥7 ኤር1፥10
18፥8 ዘፀ32፥14፤ መዝ25፥11፤ኤር 26፥13፤31፥28፤ 36፥3፤42፥10፤ዳን 9፥14፤ሆሴ11፥8-9፤ ኢል2፥13፤ዮና3፥8-10፤4፥2
18፥9 ኤር1፥10፤ 31፥28
18፥10 1ሳሙ2፥29-30፤13፥13፤ኢ1፥10፤ሕዝ33፥18
18፥11 ቍ18፤ዘዳ4 4፥30፤2ነገ17፥13፤22፥16፤ኢዮ16፥17፤ኢሳ 1፥16-19፤ኤር4፥6፤ 7፥3
18፥12 ኢሳ57፥10፤ ኤር3፥17

ላይ የሚቀመጡ ነገሥታትና መኳንንታ
ቸው በዚህች ከተማ በሮች ይገባሉ፤ በፈረ
ሶችና በሠረገሎች ተቀምጠው በይሁዳ
ሰዎችና በኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ታጅበው
ይመጣሉ፤ ይህቺም ከተማ ለዘላለም የሰው
መኖሪያ ትሆናለች። 26ሰዎች ከይሁዳ ከተ
ሞች፣ ከኢየሩሳሌም ዙሪያ፣ ከብንያምም
አገር፣ ከቈላውና ከደጋው አገር እንዲሁም
ከኔጌቭ የሚቃጠል መሥዋዕትና ሌላ መሥ
ዋዕት፣ የእህል ቍርባን፣ ዕጣንና የምስጋና
መሥዋዕት ይዘው ወደ *እግዚአብሔር*
ቤት ይመጣሉ። 27ነገር ግን የሰንበትን ቀን
ሳትቀድሱ፣ በሰንበት ቀን ሸክም ተሸክ
ማችሁ በኢየሩሳሌም በሮች በመግባት ትእ
ዛዜን ብትጥሱ፣ በኢየሩሳሌም በሮች ላይ
ምሽጎቿን የሚበላ፣ የማይጠፋ እሳት እጭ
ራለሁ።"

## በሸክላ ሠሪው ቤት

18 *ከእግዚአብሔር* ወደ ኤርምያስ እን
ዲህ የሚል ቃል መጣ፦ 2"ተነ
ሥተህ ወደ ሸክላ ሠሪው ቤት ውረድ፤ በዚያ
መልእክቴን እሰጥሃለሁ።" 3እኔም ወደ
ሸክላ ሠሪው ቤት ወረድሁ፤ ሸክላውንም
በመንኰራኵር ላይ ይሠራ ነበር። 4ከጭቃ
ይሠራው የነበረውም ሸክላ በእጁ ላይ
ተበላሸ፤ ሸክላ ሠሪውም በሚፈልገው ሌላ
ቅርጽ መልሶ አበጀው።
5*የእግዚአብሔርም* ቃል ወደ እኔ እን
ዲህ ሲል መጣ፤ 6"የእስራኤል ቤት ሆይ፤
ሸክላ ሠሪው እንደሚሠራው፣ እኔ በእና
ንተ ላይ መሥራት አይቻለኝምን?" ይላል
*እግዚአብሔር*፤ "የእስራኤል ቤት ሆይ፤
ጭቃው በሸክላ ሠሪው እጅ እንዳለ፣ እና
ንተም እንዲሁ በእጄ ውስጥ ናችሁ።
7አንድ ሕዝብ ወይም መንግሥት እንዲ
ነቀል፣ እንዲፈርስና እንዲጠፋ በተናገርሁ
ጊዜ፣ 8ያስጠነቀቅሁት ሕዝብ ከክፋቱ
ቢመለስ፣ እኔ ላደርስበት ያሰብሁትን ክፉ
ነገር እተዋለሁ። 9በሌላም ጊዜ
አንድን
ሕዝብ ወይም መንግሥት አንጸውና እተክ
ለው ዘንድ ተናግሬ፣ 10በፊቴ ክፉ ነገር
ቢያደርግና ባይታዘዘኝ፣ አደርግለታለሁ ብዬ
ያሰብሁትን መልካም ነገር እስቀርበታለሁ።
11"አሁንም እንግዲህ ለይሁዳ ሕዝብና በኢ
የሩሳሌም ለሚኖሩ እንዲህ በላቸው፤ '*እግ
ዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ "እነሆ፤ ጥፋ
ትን እያዘጋጀሁላችሁ ነው፤ ክፋትንም እየጠ
ነ ሰስሁላችሁ ነው። ስለዚህ ሁላችሁ ከክፉ
መንገዳችሁ ተመለሱ፤ መንገዳችሁንና ተግ
ባራችሁን አቅኑ።"' 12እነርሱ ግን፣ 'በከ
ንቱ አትድከም፤ ባቀድነው እንገፋበታለን፤

እያንዳንዳችንም የክፉ ልባችንን እልኸኝ
ነት እንከተላለን’ ይላሉ።”

13ስለዚህ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

“እስቲ አሕዛብን፣
‘እንዲህ ዐይነት ነገር በመካከላችሁ
ተሰምቶ ያውቃል?’ ብላችሁ ጠይቁ።
ድንግሊቱ እስራኤል፣
እጅግ ክፉ ነገር አድርጋለች።
14የሊባኖስ ተራራ ድንጋያማ ተረተር፣
በረዶ ተለይቶት ያውቃልን?
ከጋራው የሚወርደውስ ቀዝቃዛ ውሃ፤
መፍሰሱን ያቋርጣልን?[ጠ]
15ሕዝቤ ግን ረስቶኛል፤
ለማይረቡ ነገሮች ዐጥኖአል፣ በራሱ
መንገድ፣
በቀደሞው ጐዳና ተሰናክሎአል፤
በሻካራው መሂጃ፣
ባልቀናውም ጥርጊያ መንገድ ሄዶአል።
16ምድራቸው ባድማ፣
ለዘላለም መሣለቂያ ይሆናል፤
በዚያ የሚያልፍ ሁሉ ይደነቃል፤
በመገረምም ራሱን ይነቀንቃል።
17ከምሥራቅ እንደሚወጣ ነፋስ፣
በጠላቶቻቸው ፊት እበትናቸዋለሁ፤
በመጥፊያቸው ቀን፣
ጀርባዬን እንጂ ፊቴን አላሳያቸውም።”

18እነርሱም፣ “ሕግ ከካህናት፣ ምክር ከጠ
ቢባን፣ ቃልም ከነቢያት ስለማይታጣ ኑና
በኤርምያስ ላይ እንማከር፤ ኑ፤ በአንደበ
ታችን እናጥቃው፣ እርሱ የሚናገረውንም
ሁሉ አንስማ” አሉ።

19*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ስማኝ፤
ባላንጣዎቼ የሚሉትን አድምጥ።
20የመልካም ተግባር ወሮታው ክፉ ነውን?
እነርሱ ግን ጕድጓድ ቈፈሩልኝ፤
ቍጣህን ከእነርሱ እንድትመልስ፣
በፊትህ ቆሜ ፣
ስለ እነርሱ እንደ ተናገርሁ አስብ።
21ስለዚህ ልጆቻቸውን ለራብ፣
ለሰይፍም ስለት አሳልፈህ ስጥ፤
ሚስቶቻቸው የወላድ መካን፣ መበለትም
ይሁኑ፤
ወንዶቻቸው በሞት ይቀሠፉ፤
ጐልማሶቻቸው በጦር ሜዳ ለሰይፍ
ይዳረጉ።
22ሊይዙኝ ጕድጓድ ስለ ቈፈሩ፣
ለእግሮቼም በስውር ወጥመድ ስለ ዘረጉ፣
በድንገት ወራሪ ስታመጣባቸው፣
ከቤታቸው ጩኸት ይሰማ።
23አንተ ግን *እግዚአብሔር* ሆይ፤
ሊገድሉኝ ያሴሩብኝን ሴራ ሁሉ
ታውቃለህ፤
በደላቸውን ይቅር አትበል፤
ኀጢአታቸውንም ከፊትህ አትደምስስ፤
በፊትህ ወድቀው የተጣሉ ይሁኑ፤
በቍጣህም ጊዜ አትማራቸው።

19 *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“ሂደህ፣ ከሸክላ ሠሪ ገምቦ ግዛ፤
ከሕዝቡና ከካህናቱ መካከል ታላላቅ የሆኑ
ትን አንዳንዶቹን ይዘህ፣ 2በገል በር መግቢ
ያ አጠገብ ወዳለው ወደ ሄኖም ልጅ
ሸለቆ ውጣ። በዚያም የምነግርህን ቃል
ተናገር፤ 3እንዲህም በል፤ ‘የይሁዳ
ነገሥታትና በኢየሩሳሌም የምትኖሩ ሆይ፤
የ*እግዚአብሔ ር*ን ቃል ስሙ፤ የእስራኤል
አምላክ የሠራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲ
ህ ይላል፤ “ለሰሚው ሁሉ ጆሮ የሚዘገንን
ክፉ ነገር እነሆ በዚህ ስፍራ አመጣለሁ፤
4እኔን ትተውኝ፣ ይህን ስፍራ የባዕድ አ
ማልክት ቦታ አድርገውታልና። እነርሱም
ሆኑ አባ ቶቻቸው፣ የይሁዳ ነገሥታትም
ለማያው ቋቸው አማልክት ሠውተዋል፤
ይህንም ስፍራ በንጹሓን ደም
ሞልተውታል፤ 5እኔም ያላዘዝኋቸውን፣
ያልተናገርኋቸውን፣ ፈጽሞም
ያላሰብሁትን፣ ወንዶች ልጆቻቸ ውን
በእሳት ሊሠውለት ለበኣል መስገጃ
ኰረብታዎች ሠርተዋል። 6ስለዚህ ሰዎች
ይህን ስፍራ የዕርድ ሸለቆ እንጂ ከእንግ
ዲህ ቶፌት ወይም የሄኖም ልጅ ሸለቆ
ብለው የማይጠሩበት ዘመን ይመጣል፤
ይላል *እግዚአብሔር*።
7“ ‘በዚህ ስፍራ የይሁዳንና የኢየሩሳሌ
ምን ዕቅድ አፈርሳለሁ፤[ጬ] በጠላቶቻቸው
ፊት ሕይወታቸውን በሚሹት እጅ በሰ
ይፍ እንዲወድቁ አደርጋለሁ፤ ሬሳቸው
ንም ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት
ምግብ አድርጌ እሰጣለሁ። 8ይህችን ከተማ
ድምጥማጧን አጠፋለሁ፤ ለመሣለቂያም
አደርጋታለሁ፤ በዚያም የሚያልፉ ሁሉ
ከደረሰባት ጕዳት የተነሣ ወይ ጕድ!
ይላሉ ያሾፉሉም። 9የወንዶችና የሴቶች
ልጆቻቸውን ሥጋ እንዲበሉ
አደርጋለሁ፤
ሕይወታቸውን ለማጥፋት የሚሹ ጠላቶቻ
ቸው ከበው ሲያስጨንቋቸው፣ አንዱ የሌ
ላውን ሥጋ ይበላል።’
10“ገምቦውንም ከአንተ ጋር በሄዱ ሰዎች
ፊት ትሰብራለህ፤ 11እንዲህም ትላቸዋለህ፤
‘የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤ “የሸክላ ሠሪው ገንቦ እንደ ተሰበረና
ሊጠገን እንደማይቻል፣ ይህን ሕዝብና

18፥13 2ነገ19፥21፤ኢሳ66፥8፤ኤር5፥30
18፥15 ኢሳ1፥13፤17፥10፤57፥14፤62፥10፤ኤር6፥16፤10፥15፤44፥15፡19፤51፥18፤ሕዝ44፥12፤ሆሴ11፥2፤ሚል2፥8
18፥16 ዘሌ26፥32፤ዘዳ28፥37፤2ነገ19፥21፤ኢዮ16፥4፤መዝ22፥7፤ኤር19፥8፤25፥9፤42፥18፤ሰቆ1፥12፤ሕዝ33፥28-29
18፥17 2ዜና29፥6፤ኢዮ7፥10፤ኤር2፥27፤13፥24
18፥18 ቍ11፤ኢዮ5፥13፤መዝ52፥2፤64፥2-8፤ኤር2፥8፤5፥13፤9፥3፤11፥19፤ ሕዝ7፥26፤ሐጌ2፥11፤ሚል2፥7
18፥19 መዝ71፥13
18፥20 ዘፍ20፥7፤44፥4፤ዘዳ9፥19፤መዝ35፥7፤57፥6፤106፥23፤119፥85፤ኤር14፥7-9፤15፥1
18፥21 1ሳሙ15፥33፤መዝ63፥10፤109፥9፤ኢሳ9፥17፤47፥9፤ኤር11፥22፤14፥16፤ሰቆ 5፥3
18፥22 መዝ35፥15፤119፥85፤140፥5፤ኤር5፥26፤6፥26፤20፥10
18፥23 ነህ4፥5፤መዝ59፥5፤ኤር10፥24፤11፥21፤37፥15
19፥1 ዘኍ11፥17፤1ነገ8፥1፤ኤር18፥2
19፥2 ኢሱ 15፥8
19፥3 1ሳሙ3፥11፤ኤር17፥20፤ 6፥19
19፥4 ዘፀ20፥3፤ዘሌ18፥21፤ዘዳ31፥16፤2ነገ21፥16፤ኢሳ65፥11፤ ኤር1፥16
19፥5 ዘሌ18፥21፤2ነገ3፥27፤መዝ106፥37-38፤ኤር7፥31፤ሕዝ16፥36
19፥6 ኢሱ15፥8፤2ነገ23፥10፤ኤር7፥32
19፥7 ቍ9፤ዘሌ26፥17፤ዘዳ28፥25፡26፤መዝ33፥10-11፤ኤር16፥4፤34፥20
19፥8 ዘሌ26፥32፤ዘዳ28፥37፤29፥22፤ኤር18፥16፤25፥9፤ሰቆ2፥15-16
19፥9 ቍ7፤ዘሌ26፥ 29፤ዘዳ28፥49-57፤ኤር21፥7፤34፥20፤ሰቆ4፥10
19፥10 ቍ1፤መዝ2፥9፤ኤር13፥14
19፥11 መዝ2፥9፤ ኢሳ30፥14፤ኤር7፥32

[ጠ]14 በዕብራይስጡ የዚህ ዐ/ነገር ትርጕም በግልጽ አይታወቅም
[ጬ]7 *አፈርሳለሁ* የሚለው የዕብራይስጡ ቃል አነባበብ *ገንቦ* ከሚለው ጋር ይመሳሰላል (ቍ1 እና 10 ይመ)።

ይህቺን ከተማ እንዲሁ እሰብራለሁ፤ የቀ
ብር ቦታ ከመታጣቱ የተነሣ ሙታናቸ
ውን በቶፌት ይቀብራሉ። 12በዚህ ስፍራና
በውስጡም በሚኖሩት ላይ ይህን አደርጋ
ለሁ፤ ይላል እግዚአብሔር። ይህቺን ከተማ
እንደ ቶፌት አደርጋታለሁ። 13በጣራዎቻ
ቸው ላይ ለሰማይ ሰራዊት ዕጣን የታጠ
ነባቸውና ለባዕዳን አማልክት የመጠጥ
ቍርባን የቀረበባቸው፣ የኢየሩሳሌም ቤቶ
ችና የይሁዳ ነገሥታት ቤቶች እንደ ቶፌት
የረከሱ ይሆናሉ።

14ኤርምያስም እግዚአብሔር ትንቢት እን
ዲናገር ልኮት ከነበረበት ከቶፌት ተመ
ልሶ፣ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አደባ
ባይ በመቆም፣ ለሕዝቡ ሁሉ እንዲህ አለ፤
15"የእስራኤል አምላክ የሰራዊት ጌታ
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ 'እነሆ ዐ
ንገታቸ ውን በማደንደን ቃሌን ስላልሰሙ
በዚህች ከተማና በዙሪያዋ ባሉ መንደሮች
ሁሉ ላይ ሳደርስ ያሰብሁትን ጥፋት ሁሉ
አመ ጣለሁ።" '

## ኤርምያስና ጳስኮር

20 በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
ውስጥ አለቃ የነበረው፣ የኢሜር
ልጅ ካህኑ ጳስኮር እነዚህን ነገሮች ኤር
ምያስ እንደ ተነበየ በሰማ ጊዜ፣ 2ነቢዩ
ኤርምያስን መታው፣ በእግዚአብሔርም
ቤተ መቅደስ በላይኛው የብንያም በር
በእ ግር ግንድ ጠረቀው። 3በማግስቱም
ጳስ ኮር ኤርምያስን ከተጠረቀበት ግንድ
አወ ጣው፤ ኤርምያስም እንዲህ አለው፤
"እግዚአብሔር ከእንግዲህ ማጎርሚሳቢብ[*]
ብሎ ይጠራሃል እንጂ ጳስኮር አይልህም፤
4እግ ዚአብሔር እንዲህ ይላልና፤
'አንተንና ባል ንጀሮችህን ሁሉ ለሽብር
እዳርጋለሁ፤ የገዛ ዐይንህ እያየ በጠ
ላቶቻቸው ሰይፍ ይወድቃሉ። ይሁዳን ሁሉ
ለባቢሎን ንጉሥ አሳልፌ እሰጣለሁ፤
እርሱም ወደ ባቢሎን
ያፈልሳቸዋል፤ በሰይፍም ይገድላቸዋል። 5የዚ
ህችን ከተማ ሀብት ሁሉ፣ ጥሪቷን፣ የይ
ሁዳን ነገሥታት ውድ ዕቃና ንብረት ሁሉ
ለጠላቶቻቸው አሳልፌ እሰጣለሁ፤ እነር
ሱም ዘርፈው ወደ ባቢሎን ይዘውት ይሄ
ዳሉ። 6ጳስኮር ሆይ፤ አንተና በቤትህ የሚ
ኖሩት ሁሉ ወደ ባቢሎን ትጋዛላችሁ።
አንተና በሐሰት ትንቢት የተነበይህላቸው
ባልንጀሮችህ በዚያ ትሞታላችሁ፤ በዚያም
ትቀበራላችሁ።' "

## የኤርምያስ ማጒረምረም

7እግዚአብሔር ሆይ፤ አታለልኸኝ፤[*] እኔም
ተታለልሁ፤
አንተ ከእኔ እጅግ በረታህ፤ አሸነፍህም፤
ቀኑን ሙሉ ማላገጫ ሆንሁ፤
ሁሉም ተዘባበቱብኝ።
8በተናገርሁ ቍጥር እጮኻለሁ፤
"ሁከትና ጥፋት!" ብዬ ዐውጃለሁ፤
ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል፣
ቀኑን ሙሉ ስድብና ነቀፋ
አስከተለብኝ።
9ነገር ግን፣ "ከእንግዲህ የእርሱን ስም
አላነሣም፤
በስሙም አልናገርም" ብል፣
ቃሉ በልቤ እንደ እሳት፣
በዐጥንቴም ውስጥ እንደ ረመጥ
ሆነብኝ፤
ዐፍኜ መያዝ አቃተኝ፤
ጨርሶ መቋቋም አልቻልሁም።
10"በየቦታው ሽብር አለ፤
አውግዙት፤ እናውግዘው፤"
ብለው ብዙ ሲያንሾካሽኩ ሰማሁ፤
መውደቄን በመጠባበቅ፣
ባልንጀሮቼ የነበሩ ሁሉ፣
"ይታለል ይሆናል፣
ከዚያም እናሸንፈዋለን፤
እንበቀለዋለንም" ይላሉ።
11ነገር ግን እግዚአብሔር እንደ ኀያል
ተዋጊ ከእኔ ጋር ነው፤
ስለዚህ አሳዳጆቼ ይሰናከላሉ እንጂ
አያሸንፉም፤
ክፉኛ ይዋረዳሉ እንጂ አይሳካላቸውም፤
ውርደታቸውም ከቶ አይረሳም።
12ጻድቁን የምትፈትን ልብንና አእምሮን
የምትመረምር፣
የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፤
ጒዳዬን ለአንተ አሳልፌ ሰጥቻለሁና
ስትበቀላቸው ለማየት አብቃኝ።
13ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤
ለእግዚአብሔር ምስጋናን አቅርቡ፤
የችግረኛውን ነፍስ፣
ከክፉዎች እጅ ታድጎአልና።
14የተወለድሁባት ዕለት የተረገመች
ትሁን፤
እናቴ እኔን የወለደችባት ቀን
አትባረክ።
15"ወንድ ልጅ ተወልዶልሃል" ብሎ፣
ለአባቴ የምሥራች የነገረ፣
ደስ ያሰኘውም ሰው የተረገመ ይሁን።
16ያ ሰው እግዚአብሔር ሳይራራ፣
እንደ ገለበጣቸው ከተሞች ይሁን፤
በማለዳ ዋይታን፣
በቀትርም የጦርነትን ውካታ ይስማ፤

[*]3 ማጎርሚሳቢብ ማለት ዙሪያ-ገባው ሽብር ማለት ነው
[*]7 ወይም ሐሳቤን አስለወጥኸኝ

19፥13 ዘዳ4፥19፤ 2ነገ17፥16፤23፥12፤ ኢዮ38፥32፤መዝ 74፥7፤ኢሳ57፥6፤ ኤር8፥2፤32፥29፤ 52፥13፤ሕዝ16፥41፤ 20፥28፤ሐሥ7፥42
19፥14 2ዜና20፥5፤ ኤር7፥2፤26፥2
19፥15 ቍ3፤ነህ 9፥16፤ኤር11፥11፤ 22፥21፤ሐሥ7፥51
20፥1 2ነገ25፥18፤ 1ዜና24፥14፤ሉቃ 22፥52
20፥2 ዘዳ25፥2-3፤ ኢዮ29፥7፤13፥27፤ ኤር 1፥19፤15፥15፤ 9፥26፤37፥13፥15፤ 38፥7፤ዘካ14፥10፤ሐሥ 16፥24፤2ቆሮ11፥24፤ዕ ብ11፥36
20፥3 ቍ10፤መዝ 31፥13፤ሆሴ1፥4
20፥4 ኤር13፥19፤ 21፥10፤25፥9፤29፥21፤ 39፥9፤52፥27
20፥5 2ነገ20፥17፤ 25፥15፤ኤር17፥3
20፥6 ኤር14፥15፤ ሰቆ2፥14
20፥7 ዘፀ5፥23፤ 22፥16፤ኢዮ12፥4፤ 17፥2፤መዝ119፥21 ኢሳ8፥11፤አሞ3፥8፤ 1ቆሮ 9፥16
20፥8 2ዜና36፥16 ፤ኤር6፥7፥10፤28፥8
20፥9 ኢዮ4፥2፤ መዝ39፥3፤ኤር4፥19 ፤6፥11፤44፥16፤አሞ 3፥8፤ሐሥ4፥20
20፥10 1ሳሙ18፥ 25፤1ነገ19፥2፤ነህ6፥6- 13፤ኢዮ19፥14፤መዝ 57፥4፤ኢሳ29፥21፤ ኤር6፥25፤11፥19፤ 13፥21፤18፥22፤ሉቃ 11፥53-54
20፥11 መዝ129፥2 ፤ኤር1፥8፤7፥19፤15፥ 15፤17፥18፤23፥40፤ ሮሜ8፥31
20፥12 ዘዳ32፥35፤ መዝ7፥9፤62፥8፤ኤር 11፥20፤17፥10፤ሮሜ 12፥19
20፥13 መዝ34፥6፤ 35፥10፤97፥10፤ኢሳ 12፥6
20፥14 ኢዮ3፥8፥16 ፤ኤር15፥10
20፥16 ዘፍ19፥25፤ ኤር 6፥26

[17]እናቴ መቃብር ትሆነኝ ዘንድ፣
ማሕፀንም ሰፊ የዘላለም ማደሪያዬ
እንዲሆን፣
ከማሕፀንም ሳልወጣ አልገደለኝምና።
[18]ችግርና ሐዘንን ለማየት፣
ዘመኔንም በውርደት ለመፈጸም፣
ለምን ከማሕፀን ወጣሁ?

## ለንጉሥ ሴዴቅያስ የተሰጠ ምላሽ

21 የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ፣ የመጠ
ልክያን ልጅ ጳስኮርን እንዲሁም
የመዕሤያን ልጅ ካህኑን ሶፎንያስን ወደ
እርሱ በላከ ጊዜ፣ ቃል *ከእግዚአብሔር*
ወደ ኤርምያስ መጣ፤ የተላኩትም እንዲህ
ብለውት ነበር፤ [2]“የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደ
ነፆር[θ] ሊወጋን ስለ ሆነ፣ እባክህን ፈጥነህ፣
*እግዚአብሔርን* ጠይቅልን፤ ምናልባት
ንጉሡ ከእኛ ይመለስ ዘንድ *እግዚአብሔር*
እንደ ቀድሞው ታምራት ያደርግልን ይሆ
ናል” ብለው ነበር።
[3]ኤርምያስ ግን እንዲህ አላቸው፤ “ለሴ
ዴቅያስ እንዲህ ብላችሁ ንገሩት፤ [4]‘የእስ
ራኤል አምላክ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤ ከቅጥሩ ውጭ የከበቧችሁን የባቢ
ሎንን ንጉሥና ባቢሎናውያንን[ፊ] ለመው
ጋት በእጃችሁ የያዛችሁትን የጦር መሣ
ሪያ በእናንተው ላይ አዞራለሁ፤ ወደዚህ
ችም ከተማ ሰብስቤ አስገባቸዋለሁ። [5]እኔ
ራሴ ለቅጣት በተዘረጋ እጅና በብርቱ
ክንድ፣ በቍጣና በመዓት፣ በታላቅም
መቅሠፍት እወጋችኋለሁ። [6]በዚህች ከተማ
የሚኖሩትን፣ ሰዎችንም ሆኑ እንስሳትን
እመታለሁ፤ እነርሱም በታላቅ መቅሠፍት
ይሞታሉ። [7]ከዚያ በኋላ፣ ይላል *እግዚአብሔር*፤
የይሁዳን ንጉሥ ሴዴቅያስንና መኳንን
ቱን፣ ከመቅሠፍት፣ ከሰይፍና ከራብ የተ
ረፈውንም ሕዝብ ለባቢሎን ንጉሥ ለናቡ
ከደነፆርና ሕይወታቸውን ለማጥፋት ለሚሹ
ጠላቶቻቸው አሳልፌ እሰጣለሁ፤ እርሱም
በሰይፍ ይመታቸዋል፤ አያዝንላቸውም፤
አይራራላቸውም፤ አይምራቸውምም።’
[8]“በተጨማሪም ለዚህ ሕዝብ እንዲህ
በል፤ ‘*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
እነሆ፤ የሕይወትን መንገድና የሞትን
መንገድ በፊታችሁ አድርጌአለሁ፤ [9]በዚህች
ከተማ የሚቈይ ሁሉ በሰይፍ፣ በራብና
በመቅሠፍት ይሞታል፤ ወጥቶ
ለከበቧችሁ ባቢሎናውያን እጁን የሚሰጥ
ግን ነፍሱን ያተርፋል፤ በሕይወትም
ይኖራል። [10]በዚህች ከተማ ላይ በጎ
ሳይሆን ክፉ ለማድረግ ወስኛለሁ፤ ይላል
*እግዚአብሔር*፤ ለባቢሎን ንጉሥ
ትሰጣለች፤ እርሱም በእሳት ያጠፉታል።’
[11]“ለይሁዳ ንጉሥ ቤትም እንዲህ በል፤
‘*የእግዚአብሔርን* ቃል ስሙ፤ [12]የዳዊት
ቤት ሆይ፤ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

“ ‘ካደረጋችሁት ክፋት የተነሣ፣
ቍጣዬ እንዳይቀጣጠል፣
ማንም ሊያጠፋው እስከማይችል
እንዳይነድ፣
በየማለዳው ፍትሕን አድርጉ፤
የተበዘበዘውን ሰው፣
ከጨቋኙ እጅ አድኑት።
[13]ከሸለቆው በላይ፣
በድንጋያማው ዐምባ ላይ የምትኖሪ
ሆይ፤
እኔ በአንቺ ላይ ወጥቻለሁ፤
ይላል *እግዚአብሔር*።
“ማን በእኛ ላይ ይወጣል?
ማንስ ወደ መኖሪያችን ደፍሮ
ይገባል?” የምትሉ ሆይ፤
[14]እንደ ሥራችሁ መጠን እቀጣችኋለሁ፤
ይላል *እግዚአብሔር*፤
በዱሯም እሳት እለኩሳለሁ፤
በዙሪያዋ ያለውንም ሁሉ ይበላል።

## በክፉዎች ነገሥታት ላይ የተሰጠ ፍርድ

22 *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ “ወደ
ይሁዳ ንጉሥ ቤተ መንግሥት
ውረድ፤ ይህንም መልእክት በዚያ እንዲህ
ብለህ ተናገር፤ [2]‘በዳዊት ዙፋን የተቀመ
ጥህ፣ የይሁዳ ንጉሥ ሆይ፤ አንተና መኳን
ንትህ፣ በእነዚህም በሮች የሚገባ ሕዝ
ብህ፣ *የእግዚአብሔርን* ቃል ስሙ። [3]*እግዚ
አብሔር* እንዲህ ይላል፤ “ፍትሕንና ጽድ
ቅን አድርጉ፤ የተበዘበዘውን ከጨቋኙ እጅ
አድኑት፤ መጻተኛውን፣ ወላጅ የሌለውንና
መበለቲቱን አትበድሉ፤ አትግፏቸውም፤
በዚህም ስፍራ ንጹሕ ደም አታፍስሱ።
[4]እነዚህን ትእዛዛት በሚገባ ብትጠብቁ፣
በዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጡ ነገሥ
ታት፣ ከመኳንንታቸውና ከሕዝባቸው ጋር
በሠረገሎችና በፈረሶች ተቀምጠው በዚህ
ቤተ መንግሥት በሮች ይገባሉ፤ ይወጣ
ሉም። [5]ነገር ግን እነዚህን ትእዛዛት ባትጠ
ብቁ፣ ይህ ቤተ መንግሥት እንዲወድም
በራሴ ምያለሁ፤ ይላል *እግዚአብሔር*። ’ ”

[6]ስለዚህ *እግዚአብሔር* ስለ ይሁዳ ንጉሥ
ቤተ መንግሥት እንዲህ ይላል፤

“አንተ ለእኔ እንደ ገለዓድ፣

**20፥17** ኢዮ 3፥16፤ 10፥18-19
**20፥18** ዘፍ3፥17፤ 1ነገ19፥4፤ኢዮ3፥10-11፤5፥7፤መዝ90፥9፤ 102፥3፤መክ4፥2
**21፥1** 2ነገ24፥18፤ 25፥18፤1ዜና9፥12፤ ኤር52፥1
**21፥2** ዘፍ10፥10፤ 25፥22፤2ነገ22፥18፤ 25፥1፤መዝ44፥1-4፤ ኤር32፥17
**21፥4** ኤር32፥5፤ 37፥8-10
**21፥5** ዘፀ3፥20፤ኢሱ 10፥14፤2ነገ22፥13፤ ኤር6፥12፤ሕዝ 5፥8
**21፥6** ኤር7፥20፤ 14፥12
**21፥7** ዘሌ26፥17፤ 2ነገ25፥7፤2ዜና29፥19፤36፥17፤ኤር11፥21፤14፥12፤15፥5፡9፤ 19፥9፤27፥6፡8፤32፥4፤ 34፥3፤36፥10፤37፥17፤ 38፥18፤39፥5፤52፥9፤ሕዝ7፥9፤12፥14፤ዕን 1፥6
**21፥8** ዘዳ 30፥15
**21፥9** ኤር14፥12፤ 27፥11፡12፤38፥2፡17፤ 39፥18፤40፥9፤45፥5፤ሕዝ 5፥12
**21፥10** 2ነገ25፥9፤ 1ዜና36፥19፤ኤር20፥4፤32፥28፤38፥2-3፤ 44፥11፡27፤አሞ9፥4
**21፥11** ኤር13፥18
**21፥12** ዘፀ22፥22፤ ዘሌ25፥17፤መዝ27፥11፤ኢሳ1፥31፤42፥25፤ ኤር10፥10፤23፥2
**21፥13** 2ሳሙ5፥6-7፤መዝ125፥2፤ኤር 23፥30፤49፥4፤50፥31 51፥25፤ሰቆ4፥12፤ሕዝ 5፥8፤13፥8፤21፥3፤ 29፥10፤34፥10፤አብ 1፥3-4፤ናሆ2፥13፤3፥5
**21፥14** 2ነገ19፥23፤ 2ዜና36፥19፤ምሳ1፥31፤ኢሳ3፥10-11፤ኤር 17፥10፤ሰቆ2፥3፤ሕዝ 20፥47
**22፥1** ኤር13፥18፤ 34፥2
**22፥2** ኤር17፥20፡ 25፤አሞ7፥16፤ሉቃ 1፥32
**22፥3** ዘፀ22፥22፤ ዘሌ25፥17፤መዝ72፥4፤ኢሳ1፥17፤56፥1፤ኤር 5፥1፡28፤7፥6፤21፥12፤ ሕዝ33፥14፤45፥9፤ ሆሴ12፥6፤አሞ5፥24፤ ሚክ6፥8፤ዘካ7፥9
**22፥4** ኤር17፥25
**22፥5** ዘፍ22፥16፤ ኤር17፥27፤ዕብ6፥13
**22፥6** ዘፍ31፥21፤ 1ነገ7፥2፤ማሕ4፥1፤ ኢሳ33፥9፤ሚክ3፥12

θ2 *ናቡከደነፆር* አቻ የሆነው የዕብራይስጡ *ናቡከደነፆር* በዚህ ክፍልና ብዙ ጊዜ በኤርምያስና ሕዝቅኤል መጽሐፍ ይገኛል
ፊ4 ወይም *ከለዳውያን*፤ ቍ9 ላይ ይመ።

እንደ ሊባኖስ ተራራ ጫፍ ውብ
ብትሆንም፣
በእርግጥ እንደ ምድረ በዳ፣
ሰው እንደማይኖርባቸው ከተሞች
አደርግሃለሁ።
7በነፍስ ወከፍ መሣሪያ የሚይዙትን፣
አጥፊዎችን በአንተ ላይ አዘጋጃለሁ።
ምርጥ የዝግባ ዛፎችን ይቈርጣሉ፤
ወደ እሳትም ይጥሏቸዋል።

8“ከተለያየ አገር የመጡ ሕዝቦች በዚ
ህች ከተማ በኩል ሲያልፉ፣ ‘*እግዚአብሔር*
በዚህች ታላቅ ከተማ ላይ ለምን እንዲህ
አደረገ?’ እያሉ እርስ በርስ ይነጋገራሉ፤
9ከዚያም፣ ‘የአምላካቸውን *የእግዚአብሔ*
*ርን* ኪዳን ትተው ሌሎችን አማልክት
ስላመለ ኩና ስላገለገሉ ነው’ ይላሉ።”

10ከእንግዲህ ስለማይመለስ፣
የተወለደባትንም ምድር ዳግመኛ
ስለማያይ፣
ለተማረከው ንጉሥ አምርራችሁ አልቅሱ
እንጂ፣
ቀድሞ ለሞተው አታልቅሱ፤ አትዘኑም።

11በአባቱ ምትክ በይሁዳ ላይ ስለ ነገ
ሠው፣ ከዚህ ስፍራ በምርኮ ስለ ተወሰደው፣
ስለ ኢዮስያስ ልጅ ስለ ሰሎ[ፐ] *እግዚአብሔር*
እንዲህ ይላልና፤ “ከእንግዲህ አይመለስም፤
12ተማርኮ በሄደበት አገር ይሞታል እንጂ
ይህቺን ምድር ዳግመኛ አያይም።”

13“ቤተ መንግሥቱን በግፍ ለሚሠራ፣
ሰገነቱንም ፍትሕ በማዛባት ለሚገነባ፣
ወገኑን በነጻ ለሚያሠራ፣
የድካሙንም ዋጋ ለማይከፍለው፣
14‘ባለ ትልልቅ ሰገነት፣
ሰፊ ቤተ መንግሥት ለራሴ እሠራለሁ’
ለሚል ወዮለት!
ሰፋፊ መስኮቶችን ያበጅለታል፤
በዝግባ እንጨት ያስጌጠዋል፤
ቀይ ቀለምም ይቀባዋል።

15“በዝግባ ዕንጨት ብዛት፣
የነገሥህ ይመስልሃልን?
አባትህስ ፍትሕንና ጽድቅን በማድረጉ፣
የሚበላውና የሚጠጣው ጐድሎት ነበርን?
እነሆ፣ ሁሉም መልካም ሆነለት።
16የድኾችንና የችግረኞችን ፍትሕ
አላጓደለም፤
ስለዚህም ሁሉ መልካም ሆነለት።
እኔን ማወቅ ማለት ይህ አይደለምን?”
ይላል *እግዚአብሔር*።
17“የአንተ ዐይንና ልብ ያረፉት ግን፣
አጭበርብሮ ጥቅምን በማግኘት፣
የንጹሑን ደም በማፍሰስ፣
ጭቈናንና ግፍን በመሥራት ላይ ብቻ
ነው።

18ስለዚህ *እግዚአብሔር* ስለ ይሁዳ
ንጉሥ ስለ ኢዮስያስ ልጅ ስለ ኢዮአቄም
እንዲህ ይላል፤

“ ‘ዋይ ወንድሜ! ዋይ፣ እኅቴን!’
ብለው አያለቅሱለትም።
‘ዋይ፣ ጌታዬን! ዋይ፣ ለግርማዊነቱ!’
ብለውም አያለቅሱለትም።
19አህያ እንደሚቀበር ይቀበራል፤
ከኢየሩሳሌም በሮች ውጪ፤
ተጐትቶ ይጣላል።

20“ሊባኖስ ላይ ወጥተሽ ጩኺ፤
ድምፅሽን በባሳን አሰሚ፤
በዓባሪም ሆነሽ ጩኺ፤
ወዳጆችሽ ሁሉ ወድመዋልና።
21ተመችቶሽ በነበረ ጊዜ አስጠነቀቅሁሽ፤
አንቺ ግን፣ ‘አልሰማም’ አልሽ፤
ከትንሽነትሽ ጀምሮ መንገድሽ ይኸው
ነበር፤
ቃሌንም አልሰማሽም።
22እረኞችሽ ሁሉ በነፋስ ይወሰዳሉ፤
ወዳጆችሽም ተማርከው ይሄዳሉ፤
ከክፋትሽም ሁሉ የተነሣ፣
ታፍሪያለሽ፤ ትዋረጂያለሽም።
23አንቺ፣ ‘በሊባኖስ’[ሀ] ውስጥ የምትኖሪ፣
መኖሪያሽን በዝግባ ዛፍ የሠራሽ ሆይ፤
ምጥ እንደ ያዛት ሴት፣
መከራ በላይሽ ሲመጣ ጩኸትሽ
እንዴት ይሆን!

24“በሕያውነቴ እምላለሁ”፤ ይላል *እግዚ*
*አብሔር* “የይሁዳ ንጉሥ የኢዮአቄም ልጅ
ኢኮንያን[ለ] የቀኝ እጄ የቀለበት ማኅተም
ብትሆን እንኳ ኖሮ፣ አውልቄ እጥልሃለሁ”፤
25“ሕይወትህን ለሚሿት፣ ለምትፈራቸው
ለባ ቢሎናውያንና[ሐ] ለባቢሎን ንጉሥ
ለናቡከደ ናፆር አሳልፌ እሰጥሃለሁ።
26አንተንና የወ ለደችህን እናትህን
ወዳልተወለዳችሁበት ወደ ሌላ አገር
ወርውሬ እጥላችኋለሁ፤ በዚያም
ትሞታላችሁ። 27ልትመለሱባት ወደ
ምትናፍቋት ምድር ከቶ አትመለሱም።”

28ይህ ኢኮንያን የተባለ ሰው፣ የተናቀና
የተሰበረ ገምቦ፣
ማንም የማይፈልገው ዕቃ ነውን?

[ፐ]11 *ኢዮአካዝ* ተብሎም ይጠራል

[ሀ]23 *ሊባኖስ* የተባለው በኢየሩሳሌም ያለው ቤተመንግሥት ነው (1ነገ7፥23 ይመ).

[ለ]24 በዕብራይስጥ *ኮንያ* ሲሆን *የኢዮአኪን* አቻ ስም ቃል ነው፤ ቁ 28 ይመ።

[ሐ]25 ወይም *ከለዳውያን*

22፥7 2ዜና36፥19፤ መዝ74፥5፤ኢሳ10፥34 ፤ኤር4፥7፤6፥4፤ዘካ 11፥1
22፥8 ዘዳ29፥25-26 ፤1ነገ9፥8-9፤ኤር 16፥10-11
22፥9 1ነገ9፥9፤ኤር 16፥11፤ሕዝ39፥23
22፥10 ቍ18፡27፤ መክ4፥2፤ኤር24፥9፤ 29፥18፤42፥18፤ሕዝ 24፥16
22፥11 2ነገ23፥31
22፥12 2ነገ23፥34
22፥13 ዘሌ19፥13፤ ኢሳ5፥8፤ሚክ3፥10፤ ፤ዕን2፥9፤ያዕ5፥4
22፥14 2ሳሙ 7፥2፤ኢሳ5፥8-9፤ሕዝ 23፥14
22፥15 2ነገ23፥25፤ መዝ128፥2፤ኢሳ3፥10
22፥16 መዝ36፥10 ፤72፥1-4፡12-13፤ 82፥3፤ምሳ24፥23
22፥17 ዘዳ28፥33፤ 2ነገ24፥4፤ኢሳ56፥11 ፤ሕዝ18፥12፤ሚክ2፥2
22፥18 2ሳሙ1፥26
22፥19 2ነገ24፥6፤ ኤር8፥2፤36፥30
22፥20 ቍ22፤ዘኍ 27፥12፤መዝ68፥15፤ ኢሳ57፥13፤ኤር30፥ 14፤ሰቆ1፥19፤ሕዝ 16፥33-34፤ሆሴ8፥9
22፥21 ዘዳ9፥7፤ መዝ25፥7፤ኢሳ54፥4፤ ኤር3፥13፡25፤7፥23- 28፤31፥19፤32፥30፤ ሶፎ3፥2፤ዘካ 7፥7
22፥22 ቍ20፤ዘዳ 28፥64፤ኢዮ27፥21፤ ኤር7፥19፤10፥21
22፥23 1ነገ 7፥2፤ ኤር4፥31፤ሕዝ17፥3
22፥24 ዘፍ38፥18፤ 2ነገ24፥6፡8
22፥25 2ነገ24፥16፤ 2ዜና36፥10
22፥26 1ሳሙ25፥ 29፤ 1ነገ2፥19፤ 2ነገ24፥8፤2ዜና 36፥10፤ኢሳ22፥17፤ ሕዝ19፥9-14
22፥27 ቍ 10
22፥28 2ነገ24፥6፤ መዝ31፥12፤ኤር15፥1 ፤17፥4፤19፥10፤ 25፥34፤48፥38

እርሱና ልጆቹ ለምን ወደ ውጪ ተጣሉ?
ወደማያውቁትስ ምድር ለምን
ተወረወሩ?
29ምድር ሆይ፤ አንቺ ምድር፣ አንቺ
ምድር፤
*የእግዚአብሔርን ቃል ስሚ!*
30*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
"አንድ እንኳ የረባ ዘር የማይወጣለት፣
አንድ እንኳ በዳዊት ዙፋን የሚቀመጥ፣
ወይም በይሁዳ የሚገዛ የማይኖረው
ነውና፤
በሕይወት ዘመኑ የማይከናወንለት፣
መካን ሰው ብላችሁ መዝግቡት።"

**ጻድቁ ቅርንጫፍ**

23 "በማሰማሪያ ቦታዬ ያሉትን በጎ
ቼን ለሚያጠፉና ለሚበትኑ እረ
ኞች ወዮላቸው!" ይላል *እግዚአብሔር።*
2ስለዚህ የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር*
ሕዝቤን ስለሚጠብቁ እረኞች እንዲህ
ይላል፤ "መንጋዬን ስለ በተናችሁ፣ ስላባረ
ራችሁና ተገቢውን ጥንቃቄ ስላላደረጋችሁ
ላቸው፣ ለክፉታችሁ ተገቢውን ቅጣት
አመጣባችኋለሁ" ይላል *እግዚአብሔር፤* 3"የመ
ንጋዬንም ቅሬታ ካባረርሁባቸው አገሮች
ሁሉ እኔ ራሴ ሰብስቤ፣ ወደ መሰማሪያ
ቸው እመልሳቸዋለሁ፤ በዚያም ፍሬያማ
ይሆ ናሉ፤ ይበዛሉም። 4የሚጠብቋቸውን
እረ ኞች አስነሣላቸዋለሁ፤ ከእንግዲህም
አይ ፈሩም፤ አይደነግጡም ከእነርሱም
አንድ እንኳ አይጐድልም" ይላል *እግዚ
አብሔር።*

5"እነሆ፤ ለዳዊት፣[መ]
ጻድቅ ቅርንጫፍ የማስነሣበት ጊዜ
ይመጣል፤
እርሱም ፍትሕንና ጽድቅን የሚያደርግ፣
በጥበብ የሚገዛ ንጉሥ ይሆናል" ይላል
*እግዚአብሔር።*
6በእርሱም ዘመን ይሁዳ ይድናል፤
እስራኤልም በሰላም ይኖራል፤
የሚጠራበትም ስም፣
. . '*እግዚአብሔር ጽድቃችን*' የሚል
ነው።

7"ስለዚህ ሰዎች፣ 'እስራኤላውያንን ከግ
ብፅ ምድር ያወጣ ሕያው *እግዚአብሔ
ር*ን!' ብለው ከእንግዲህ የማይምሉበት
ዘመን ይመጣል" ይላል *እግዚአብሔር፤*
8ነገር ግን፣ 'እስራኤልን ከሰሜን ምድርና
እነር ሱን ከበተነባቸው ከሌሎች አገሮች
ያወጣ ሕያው *እግዚአብሔር*ን!' ይላሉ፤
ከዚያ በኋላ በገዛ ምድራቸው ይኖራሉ።

**ሐሰተኛ ነቢያት**

9ስለ ነቢያት፣
ልቤ በውስጤ ተሰብሮአል፤
ዐጥንቶቼም ተብረክርከዋል፤
*ከእግዚአብሔር* የተነሣ፣
ከቅዱስ ቃሉም የተነሣ፣
የወይን ጠጅ እንዳሸነፈው፣
እንደ ሰካራም ሰው ሆኛለሁ።
10ምድሪቱ በአመንዝሮች ተሞልታለች፤
ከርግማን የተነሣ[ሠ] ምድሪቱ ታለቅሳለች፤
በምድረ በዳ ያሉት መሰማሪያዎች
ደርቀዋል።[ረ]
ነቢያቱም ጠማማ መንገድ ተከትለዋል፤
ሥልጣናቸውን ያለ አግባብ
ተጠቅመዋል።

11"ነቢዩም፣ ካህኑም በጽድቅ መንገድ
የማይሄዱ ናቸው፤
በቤተ መቅደሴ እንኳ ሳይቀር
ክፋታቸውን አይቻለሁ።"
ይላል *እግዚአብሔር።*
12"ስለዚህ መንገዳቸው ድጥ ይሆናል፤
ወደ ጨለማ ይጣላሉ፤
ተፍገምግመውም ይወድቃሉ፤
በሚቀጡበትም ዓመት፣
መዓት አመጣባቸዋለሁ፤"
ይላል *እግዚአብሔር።*
13"በሰማርያ ባሉ ነቢያት ላይ፣
ደስ የማያሰኝ ነገር አይቻለሁ፤
በበኣል ስም ትንቢት ተናገሩ፤
ሕዝቤን እስራኤልን አሳቱ።
14በኢየሩሳሌም ባሉ ነቢያትም ላይ፣
የሚዘገንን ነገር አይቻለሁ፤
ያመነዝራሉ፤ በመዋሸትም ይኖራሉ፤
ማንም ከክፋቱ እንዳይመለስ፣
የክፉዎችን እጅ ያበረታሉ፤
በእኔ ዘንድ ሁሉም እንደ ሰዶም፣
ነዋሪዎቿም እንደ ገሞራ ናቸው።"

15ስለዚህ የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*
ስለ እነዚህ ነቢያት እንዲህ ይላል፤
"ከኢየሩሳሌም ነቢያት፣
በምድሪቱ ሁሉ ርኵሰት ተሠራ
ጭቶአልና፤
መራራ ምግብ አበላቸዋለሁ፤
የተመረዘም ውሃ አጠጣቸዋለሁ።"

16የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
"እነዚህ ነቢያት የሚተነብዩላችሁን
አትስሙ፤
በባዶ ተስፋ ይሞሏችኋል፤

[መ]5 ወይም *ከዳዊት የዘር ግንድ*
[ሠ]10 ወይም *ከእነዚህ ነገሮች የተነሣ*
[ረ]10 ወይም *ምድሪቱ ደርቃለች*

**22፥29** ኤር6፥19
**22፥30** 1ዜና3፥18፤ ኢዮ18፥19፤መዝ 94፥20፤ኤር10፥21፤ 38፥23፤52፥10፤ማቴ 1፥12
**23፥1** መዝ100፥3፤ ኢሳ56፥11፤ኤር10፥ 21፤12፥10፤13፥17፤ 25፥36፤ሕዝ34፥1-10፥ 31፤ዘካ10፥2፤11፥15- 17፤
**23፥2** ኤር10፥21፤ 13፥20፤21፥12፤ሕዝ 34፥8-10፤ዮሐ10፥8
**23፥3** 1ነገ8፥48፤ኢ ሳ11፥10-12፤ኤር32፥ 37፤ሕዝ34፥11-16
**23፥4** ዘፍ48፥15፤ ኢሳ31፥4፤ኤር31፥10 ፤30፥10፤46፥27-28፤ ዮሐ6፥39
**23፥5** ዘፍ18፥19፤ 2ነገ19፥26፤ኢሳ4፥2፤ 9፥7፤ሕዝ17፥22፤ማቴ 1፥1፤2፥2
**23፥6** ዘፀ23፥21፤ ዘሌ25፥18፤ዘዳ32፥8፤ዕ ዝ9፥15፤ኢሳ42፥6፤ ኤር33፥16፤ሆሴ2፥18፤ ማቴ1፥21-23፤ሮሜ 3፥21-22፤1ቆሮ1፥30
**23፥7** ዘዳ15፥15፤ ኤር30፥3
**23፥8** ኢሳ14፥1፤ 43፥5-6፤ኤር30፥10 ፤ሕዝ20፥42፤34፥13፤ አሞ9፥14-15
**23፥9** ኢዮ4፥14፤ ኤር4፥19፤20፥8-9
**23፥10** ዘዳ28፥23- 24፤መዝ107፥34፤ኤር 4፥26፤9፥2፥10፤12፥11
**23፥11** 2ነገ21፥4፤ ኤር6፥13፤7፥10፤ 8፥10፤ሶፎ3፥4
**23፥12** ዘዳ32፥35፤ ኢዮ3፥23፤ኤር11፥23 ፤13፥16
**23፥13** ቊ32፤1ነገ 18፥22፤ኢሳ3፥12፤ ሕዝ13፥10
**23፥14** ቊ22፤ ዘፍ18፥20፤ኢሳ5፥18፤ ኤር5፥30፤ 0፥16፤ 29፥23፤ሆሴ6፥10፤ አሞ4፥11፤ማቴ11፥24
**23፥15** ኤር8፥10፥ 14፤9፥15
**23፥16** ኤር9፥20፤ 14፥14፤27፥9-10፥14 ፤ሕዝ13፥3፤ማቴ7፥15

ከእግዚአብሔር አፍ የወጣ ሳይሆን፣
ከገዛ ልባቸው የሆነውን ራእይ ይናገራሉ።
17እኔን ለሚንቁኝ፣
. . ‘እግዚአብሔር ሰላም ይሆንላችኋል
ብሏል’ ይላሉ፤
የልባቸውን እልኸኝነት ለሚከተሉም ሁሉ፣
. . ‘ክፉ ነገር አይነካችሁም’ ይሏቸዋል።
18ቃሉን ለማየትና ለመስማት፣
እነማን የእግዚአብሔር ምክር ባለበት
ቆመዋል?
ቃሉን ያደመጠ፣ የሰማስ ማን ነው?
19እነሆ፤ የእግዚአብሔር ዐውሎ ነፋስ፣
በቍጣ ይነሣል፤
ብርቱም ማዕበል፣
የክፉዎችን ራስ ይመታል።
20እግዚአብሔር የልቡን ሐሳብ፣
ሙሉ በሙሉ ሳይፈጽም፣
ቍጣው እንዲሁ አይመለስም፤
በኋለኛው ዘመን፣
ይህን በግልጽ ትረዳላችሁ።
21እኔ እነዚህን ነቢያት አልላክኋቸውም፤
እነርሱ ግን ለራሳቸው መልእክታቸውን
ይዘው ሮጡ፣
ሳልናገራቸውም፣
ትንቢት ተናገሩ።
22ምክሬ ባለበት ቢቆሙ ኖሮ፣
ቃሌን ለሕዝቤ ባሰሙ ነበር፤
ከክፉ መንገዳቸው፣
ከክፉ ሥራቸውም በመለሷቸው ነበር።

23“እኔ የቅርብ አምላክ ብቻ ነኝን?
ይላል እግዚአብሔር፤
“የሩቅስ አምላክ አይደለሁምን?
24እኔ እንዳላየው፣
በስውር ቦታ ሊሸሸግ የሚችል አለን?”
ይላል እግዚአብሔር።
“ሰማይንና ምድርንስ የሞላሁ እኔ
አይደለሁምን”
ይላል እግዚአብሔር።

25“ ‘ሕልም አለምሁ! ሕልም አለምሁ!’
እያሉ በስሜ የሐሰት ትንቢት የሚናገሩ
ትን የነቢያትን ቃል ሰምቻለሁ፤ 26ይህ
ነገር፣ የገዛ ልባቸውን ሽንገላ በሚተነብዩ
በሐሰተኞች ነቢያት ልብ ውስጥ የሚቈ
የው እስከ መቼ ነው? 27አባቶቻቸው በኣልን
በማምለክ ስሜን እንደ ረሱ፣ እነርሱ በሚ
ነጋገሩት ሕልም፣ ሕዝቤ ስሜን እንዲረሳ
ያደረጉ ይመስላቸዋል። 28ሕልመኛ ነቢይ ሕል
ሙን ያውራ፤ ቃሌ ያለው ግን በታማኝ
ነት ይናገር፤ ገለባና እህል ምን አንድ
አድርጎአቸው!” ይላል እግዚአብሔር።
29“ቃሌ እንደ እሳት፣ ድንጋይንም እንደ

23፥17 ቀኊ31፤1ነገ 22፥8፤ኤር4፥10፤5፥12፤13፥10፤አሞ9፥10፤ሚክ3፥11
23፥18 1ነገ22፥19፤ሮሜ11፥34
23፥19 ኢሳ30፥30፤ኤር25፥32፤30፥23፤ዘካ7፥14
23፥20 2ነገ23፥36፤ኤር4፥28
23፥21 ኤር14፥14፤27፥15
23፥22 ቀኊ14፤ዘዳ 33፥10፤1ነገ22፥19፤2ነገ17፥13፤ኤር25፥5፤አሞ3፥7፤ዘካ1፥4
23፥23 መዝ139፥1-10
23፥24 ዘፍ3፥8፤1ነገ 8፥27፤ኢዮ11፥20፤22፥12-14፤መክ12፥14፤ኢሳ28፥15፤1ቆሮ4፥5
23፥25 ቀኊ16፡28፡32፤ዘዳ13፥1፤ኤር14፥14፤27፥9፡10፤29፥8
23፥26 ኢሳ30፥10፤ኤር14፥14፤ሕዝ13፥2፤1ጢሞ4፥1-2
23፥27 ዘዳ13፥1-3፤መሳ3፥7፤8፥33-34፤ኤር29፥8፤2፥23
23፥28 ቀኊ25፤1ሳሙ3፥17
23፥29 መዝ39፥3፤ኤር5፥14፤1ቆሮ3፥13፤ዕብ4፥12
23፥30 ቀኊ2፤ዘዳ 18፥20፤መዝ34፥16፤ኤር14፥15፤21፥13
23፥31 ቀኊ 17
23፥32 ቀኊ25፡13፤ኢዮ13፥4፤ኤር7፥8፤14፥14፤50፥6፤ሰቆ2፥14፤ሕዝ13፥3፤22፥28
23፥33 2ነገ21፥14፤ሚል1፥1
23፥34 ሰቆ2፥14፤ዘካ13፥3
23፥35 ኤር33፥3፤42፥4
23፥36 ኢሱ3፥10፤ገላ1፥7-8፤2ጴጥ3፥16
23፥39 ኤር7፥15
23፥40 ኤር20፥11፤ሕዝ5፥14-15
24፥1 ዘፀ23፥19፤ዘዳ26፥2፤2ነገ24፥16፤2ዜና36፥9፤አሞ8፥1-2

ሚያደቅ መዶሻ አይደለምን?” ይላል እግ
ዚአብሔር።
30“ስለዚህ ቃሌን እርስ በእርስ በመሰራ
ረቅ ከእኔ እንደ ተቀበሉ አድርገው የሚና
ገሩትን ነቢያት እቃወማለሁ” ይላል
እግዚአብሔር። 31“አፈጮሌነታቸውን
በመጠቀም፣ ‘እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል’ የሚ ሉትን ነቢያት እቃወማለሁ”
ይላል እግዚአብሔር፤ 32“እነሆ፤ ሐ
ሰተኛ ሕልም ተመ ርኰዘው ትንቢት
የሚናገሩትን ነቢያት እቃወማለሁ” ይላል
እግዚአብሔር፤ እኔ ሳልልካቸው ወይም
ሳልሾማቸው ደፍረው ውሸት ይናገራሉ፤ ሕ
ዝቤንም ያስታሉ፤ ለዚህም ሕዝብ አንዳች
አይረቡትም” ይላል እግዚአብሔር።

## የእግዚአብሔር ሸክም ምንድ ነው?

33“ይህ ሕዝብ ወይም ነቢይ ወይም
ካህን፣ ‘የእግዚአብሔር ሸክም ምንድን
ነው?’ ብለው ቢጠይቁ፣ ‘ሸክሙ እናንተ
ናችሁ፤[ሀ] እወረውራችኋለሁ ይላል እግዚአብሐ
ር’ ብለህ መልስላቸው። 34ነቢይ ወይም
ካህን ወይም ማንኛውም ሰው፣ ‘የእግዚ
አብሔር ሸክም’ እያለ ቢናገር፣ ያን
ሰውና ቤቱን እቀጣ ለሁ። 35እያንዳንዱ
ለባልንጀራው ወይም ለዘመዱ፣ ‘እግዚ
አብሔር ምን መልስ ሰጠ?’ ወይም፣
‘እግዚአብሔር ምን ተናገረ?’ ማለት
ይገባዋል። 36ከእንግዲህ ግን፣ ‘የእግዚአብሐ
ር ሸክም’ ብላችሁ መናገር አይገባ
ችሁም፤ ምክንያቱም ለሰው ሁሉ የገዛ
ራሱ ቃል ሸክሙ ስለሚሆን፣
የአምላካችንን የሰራዊት ጌታ የእግዚአብሐ
ርን፣ የሕያው አምላክን ቃል ታጣም
ማላችሁ። 37ስለዚህ ለነቢዩ፣ ‘እግዚአብሔር
ምን መልስ ሰጠህ’ ወይም፣ ‘እግዚአብሔር
ምን ተናገረህ?’ ትለዋለህ፤ 38‘የእግዚአብሐ
ር ሸክም’ ብትሉ እንኳ፣ እግዚአብሔር
ግን እንዲህ ይላል፤ ‘እኔ፣ “የእግዚአብሔር
ሸክም” አትበሉ ብዬ ብነግራችሁም፣ እናንተ፣
“የእግዚአብሔር ሸክም” ብላችኋል፤ 39ስለዚህ
እናንተን፣ እንዲሁም ለእናንተና
ለአባቶቻችሁ የሰጠኋትን ከተማ
ጭምር ፈጽሜ እተዋችኋለሁ፤ ከፊቴ
እጥላችኋለሁ፤ 40ለዘላለም የማይ ረሳ ዕ
ፍረት፣ የዘላለምም ውርደት አመ
ጣባችኋለሁ።

## መልካሙና መጥፎው በለስ

24 የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር፣
የኢዮአቄምን ልጅ የይሁዳን ንጉሥ

[ሀ]33 ወይም ንግር። (ለንግር እና ለሸክም የሚተካው የዕብራ
ይስጥ ቃል አንድ ዐይነት ነው)

ኢኮንያንንና[ሽ] ባለሥልጣኖቹን እንዲሁም
የይሁዳን አናጺዎችና ብረት ቀጥቃጮች
ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢሎን ማርኮ ከወሰዳ
ቸው በኋላ፣ *እግዚአብሔር* ሁለት ቅር
ጫት በለስ *በእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ
ፊት ለፊት ተቀምጦ አሳየኝ። 2አንዱ
ቅርጫት፣ ቶሎ የደረሰ ፍሬ የሚመስል
እጅግ መልካም በለስ ነበረበት፣
በሌላው ቅርጫት ግን ከመበላሸቱ የተነሣ
ሊበላ የማ ይቻል እጅግ መጥፎ በለስ
ነበረበት።

3*እግዚአብሔርም*፣ "ኤርምያስ ሆይ፤ የም
ታየው ምንድን ነው?" አለኝ።

እኔም፣ "በለስን አያለሁ፤ ጥሩ የሆነው
እጅግ መልካም ነው፤ የተበላሸው ግን እጅግ
መጥፎ በመሆኑ ሊበላ የማይችል ነው"
አልሁ።

4እንደ ገናም *የእግዚአብሔር* ቃል ወደ
እኔ እንዲህ ሲል *መጣ*፤ 5"የእስራኤል አም
ላክ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ 'እንደ
ዚህ እንደ መልካሙ በለስ፣ ከዚህ ስፍራ
ወደ ባቢሎናውያን[ቀ] ምድር የሰደድሁትን
የይሁዳ ምርኮ በመልካም አስበዋለሁ። 6ዐይ
ኔን ለበጎነት በእነርሱ ላይ አደርጋለሁ፤
ወደዚህችም ምድር እመልሳቸዋለሁ፤ እሠ
ራቸዋለሁ እንጂ አላፈርሳቸውም፤ እተክላ
ቸዋለሁ እንጂ አልነቅላቸውም። 7እኔ *እግ
ዚአብሔር* እንደ ሆንሁ የሚያውቅ ልብ
እሰጣቸዋለሁ፤ በፍጹም ልባቸውም ወደ እኔ
ስለሚመለሱ፣ እነርሱ ሕዝብ ይሆኑኛል፤
እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ።

8" 'ነገር ግን ከመበላሸቱ የተነሣ ሊበላ
እንደማይቻለው እንደ መጥፎ በለስ' ይላል
*እግዚአብሔር*፤ 'የይሁዳን ንጉሥ ሴዴቅያ
ስንና ባለሥልጣኖቹን እንዲሁም በኢየሩሳ
ሌም የቀሩትንም ሆነ በግብፅ የሚኖሩ
ትን፣ እንዲሁ አደርግባቸዋለሁ። 9በምድር
*መንግሥታት* ሁሉ ፊት የሚያስጸይፉና
የሚሰደቡ ይሆናሉ፤ በምበትናቸውም ስፍራ
ሁሉ ለማላገጫና ለመተረቻ፣ ለመሣለቂ
ያና ለርግማን አደርጋቸዋለሁ። 10ለእነር
ሱና ለአባቶቻቸው ከሰጠኋቸው ምድር እስ
ኪጠፉ ድረስ ሰይፍ፣ ራብና መቅሠፍት
እሰድባቸዋለሁ።

## ሰባ የምርኮ ዓመታት

25 የይሁዳ ንጉሥ የኢዮስያስ ልጅ ኢ
ዮ አቄም በነገሠ በአራተኛው ዓ
መት፣ ይህም ማለት በባቢሎን ንጉሥ
በናቡከደነ ፆር ዘመነ መንግሥት
በመጀመሪያው ዓመት፣ ስለ ይሁዳ ሕ
ዝብ ሁሉ ለኤርም ያስ ቃል መጣለት፤
2ስለዚህ ነቢዩ ኤርም ያስ ለይሁዳ ሕዝብ
ሁሉ፣ በኢየሩሳሌም ለሚኖሩትም ሁሉ
እንዲህ ሲል ተናገረ፡- 3የይሁዳ ንጉሥ
የአሞን ልጅ ኢዮስያስ ከነገሠበት ከዐሥራ
ሦስተኛው ዓመት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ
ሃያ ሦስት ዓመት ሙሉ *የእግዚአብሔር*
ቃል ወደ እኔ *መጣ*፤ ደጋግሜም
ነገርኋችሁ፤ እናንተ ግን አልሰማችሁም።

4*እግዚአብሔር* አገልጋዮቹን ነቢያትን ሁሉ
ደጋግሞ ወደ እናንተ ላከ፤ ሆኖም አልሰ
ማችሁም፤ ትኵረትም አልሰጣችሁትም።
5እነርሱም እንዲህ አሉ፤ "እንግዲህ ሁላ
ችሁ ከክፉ መንገዳችሁና ከክፉ *ሥራችሁ*
ተመለሱ፤ *እግዚአብሔር* ለእናንተና ለአባቶ
ቻችሁ በሰጣት ምድር ለዘላለም ትቀመጣላ
ችሁ። 6*ታገለግሏቸውና ታመልኳቸው* ዘንድ
ሌሎቹን አማልክት አትከተሉ፤ እጃችሁ
በሠራው ነገር አታስቈጡኝ፤ እኔም ክፉ አላ
ደርግባችሁም።"

7"ነገር ግን አልሰማችሁኝም" ይላል *እግ
ዚአብሔር*፤ "እጃችሁ በሠራው ነገር አስቈ
ጣችሁኝ፤ በራሳችሁም ላይ ክፉ ነገር አመ
ጣችሁ።"

8ስለዚህ የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*
እንዲህ ይላል፤ "ቃሌን ስላልሰማችሁ፣
9የሰሜንን ሕዝብ ሁሉ፣ አገልጋዬንም የባ
ቢሎንን ንጉሥ ናቡከደነፆርን እጠራለሁ"
ይላል *እግዚአብሔር*፤ "በዚህች ምድርና
በነዋሪዎቿም ላይ፣ በአካባቢዋም ባሉ ሕዝ
ቦች ሁሉ ላይ አመጣባቸዋለሁ፤ ፈጽሜም
አጠፋቸዋለሁ፤[በ] ሰዎች የሚጸየፉአቸውና
የሚሣለቁባቸው፣ የዘላለምም ባድማ አደር
ጋቸዋለሁ፤ 10የደስታንና የእልልታን ድምፅ፣
የሙሽራውንና የሙሽራዪቱን ድምፅ፣ የወ
ፍጮን ድምፅና የመብራትን ብርሃን አስቀ
ራለሁ። 11አገሪቱ በሞላ ባድማና ጠፍ
ትሆናለች፤ እነዚህም ሕዝቦች ለባቢሎን
ንጉሥ ሰባ ዓመት ይገዛሉ።

12"ነገር ግን ሰባው ዓመት ከተፈጸመ
በኋላ፣ የባቢሎንን ንጉሥና ሕዝቡን፣ የባ
ቢሎናውያንንም[ተ] ምድር ስለ በደላቸው
እቀጣቸዋለሁ" ይላል *እግዚአብሔር*፤ "ለዘ
ላለምም ባድማ አደርጋታለሁ፤ 13በምድሪቱ
ላይ የተናገርሁትን ሁሉ ይኸውም በዚህ
መጽሐፍ የተጻፈውንና ኤርምያስ በሕዝ
ቦች ሁሉ ላይ የተናገረውን ትንቢት አመ
ጣባታለሁ። 14ሕዝቧም ለብዙ ሕዝቦችና
ለታላላቅ ነገሥታት ባሮች ይሆናሉ፤ እንደ
አድራጎታቸውና እንደ እጃቸውም ሥራ
እከፍላቸዋለሁ።"

24፥2 ማሕ2፥13፤ ኢ
ሳ5፥4
24፥3 ኤር1፥11፤
አሞ8፥2
24፥5 ኤር29፥4፡20
24፥6 ዘዳ30፥3፡9፤
ኤር1፥10፤27፥22፤
29፥10፤30፥3፤33፥7፤
42፥10፤ሕዝ11፥17፤
አሞ9፥14-15
24፥7 ዘሌ26፥12፤
2ዜና6፥37፤ኢሳ11፥9፤
51፥16፤ኤር32፥40፤
ሕዝ11፥19፤ዘካ2፥11
፤ዕብ8፥10
24፥8 ኤር29፥17፤
32፥4-5፤38፥18፡23፤
39፥5፡6፡9፤44፥1፡26፡3
0፤46፥14
24፥9 ዘዳ28፥25፡37
፤1ነገ9፥7፤2ነገ22፥19፤
ኤር15፥4፤25፥18፤
29፥18፤ዳን 9፥7
24፥10 ዘዳ28፥21፤
ኢሳ51፥19፤ኤር9፥16
፤15፥2፤27፥8፤ራእ6፥8
25፥1 2ነገ24፥1፡2
25፥2 ኤር18፥11
25፥3 1ዜና3፥14፤
ኢሳ65፥12፤ኤር
7፥26፤11፥7፤26፥5
25፥4 ኤር6፥17፤
7፥25፡26፤29፥19፤
34፥14፤44፥5
25፥5 ዘፍ12፥7፤ዘዳ
4፥40፤መሳ6፥8፤2ዜና
7፥14፤30፥9፤ኤር
23፥22
25፥6 ዘፀ20፥3፤ዘዳ
8፥19
25፥7 ዘዳ32፥21፤
2ነገ17፥20፤21፥15፤
ኤር30፥14፤32፥35
44፥5
25፥9 ዘኍ21፥2፤
2ዜና29፥8፤36፥6፤ኢሳ
13፥3-5፤14፥31፤41፥2
፤ኤር19፥8፤20፥4፤
27፥6፤ሕዝ12፥20
25፥10 ኢዮ18፥5፤
መክ12፥3-4፤ኢሳ
24፥8፤ኤር7፥34፤33፥1
1፤ሰቆ5፥15፤ሕዝ26፥
13፤ራእ18፥22-23
25፥11 ዘሌ26፥31-
32፤2ዜና36፥21፤ኤር
4፥26-27፤12፥11-12፤
28፥14
25፥12 ዘፍ10፥10፤
መዝ137፥8፤ኢሳ13፥
19-22፤14፥22-23፤
ኤር27፥7፤29፥10
25፥13 ኢሳ30፥8
25፥14 ዘዳ32፥41፤
ኢዮ21፥19፤ኢሳ14፥6
፤ኤር27፥7፤50፥9፤
51፥6፡27-28

[ሽ]1 በዕብራይስጡ *ኢኮንያን*፣ *የኢዮአኪን* አቻ ስም ነው።
[ቀ]5 ወይም *ከለዳውያን*

## የቍጣው ጽዋ

[15]የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር* እን
ዲህ አለኝ፤ “በቍጣዬ የወይን ጠጅ የተሞ
ላውን ይህን ጽዋ ከእጄ ውሰድ፤ እኔ ወደ
ምልክህም ሕዝቦች ሁሉ ሄደህ አጠጣቸው።
[16]በጠጡም ጊዜ ይንገዳገዳሉ፤
በመካከላቸው ከምሰደው ሰይፍ የተነሣ
ያብዳሉ።”

[17]ስለዚህ ጽዋውን *ከእግዚአብሔር* እጅ
ተቀብዬ እርሱ ወደ ላከኝ ሕዝቦች ሁሉ
ሄድሁ፤ እንዲጠጡትም አደረግሁ፤ [18]ዛሬ
እንደ ሆነው ሁሉ ባድማና ሰዎች የሚጸየ
ፉአቸው መዘባበቻና ርግማን እንዲሆኑ፦
ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች፣ ነገሥ
ታቷንና ባለሥልጣኖቿን፣ [19]የግብፅን ንጉሥ
ፈርዖንን፣ አገልጋዮቹን፣ ባለሥልጣኖቹ
ንና ሕዝቡን ሁሉ፣ [20]በዚያ የሚኖሩትን
ድብልቅ ሕዝብ ሁሉ፣ የዖፅ ምድር ነገሥ
ታትን ሁሉ፣ በአስቀሎና፣ በጋዛ፣ በአቃሮ
ንና በአዛጦንም ሕዝብ ቅሬታ ያሉትን
የፍልስጥኤም ነገሥታት፣ [21]ኤዶምን፣ ሞዓ
ብን፣ አሞንን፣ [22]የጢሮስንና የሲዶናን ነገ
ሥታት ሁሉ፣ ከባሕሩ ማዶ ያሉ የጠረፍ
ምድር ነገሥታትን፣ [23]ድዳንን፣ ቴማንን፣
ቡዝን፣ ጠጕራቸውን ዙሪያውን የሚከረከ
ሙትን ሕዝብ ሁሉ፣[ቸ] [24]የዐረብ ነገሥታ
ትን ሁሉ፣ በምድረ በዳ የሚኖሩትን የድ
ብልቅ ሕዝብ ነገሥታት ሁሉ፣ [25]የዘምሪ፣
የኤላምና የሜዶን ነገሥታትን ሁሉ፣
[26]በቅርብና በሩቅ ያሉትን የሰሜን ነገሥታ
ትንም ሁሉ በማከታተል፣ በምድር ላይ
ያሉትን መንግሥታት ሁሉ አጠጣኋቸው፤
ከእነዚህም ሁሉ በኋላ የሺሻክ[ኀ] ንጉሥ
ደግሞ ይጠጣል።

[27]“አንተም እንዲህ ብለህ ንገራቸው፤ ‘የእ
ስራኤል አምላክ የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሐ
ር* እንዲህ ይላል፦ ጠጡ፤ ስከሩ፤
አስታውኩም፤ ዳግመኛም ላትነሡ
በመካከላችሁ በምሰ ደው ሰይፍ ፊት
ውደቁ።’ [28]ነገር ግን ጽዋውን ከእጅህ
ለመውሰድና ለመጠጣት እንቢ ካሉ፣ እንዲ
ህ በላቸው፦ ‘የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሐ
ር* እንዲህ ይላል፤ በግድ ትጠጣላችሁ።
[29]እነሆ፤ ስሜ የተጠራበትን ከተማ
ማጥፋት እጀምራለሁ፤ ታዲያ ያለ ቅጣት
ታመልጣላችሁን? ሳትቀጡ አትለ ቀቁም፤
በምድር በሚኖሩት ሁሉ ላይ ሰይፍን እጠ
ራለሁና ሳትቀጡ አታመልጡም፤ ይላል የሰ
ራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*።’

[30]“እንግዲህ ይህን ቃል ሁሉ ትንቢት ተና
ገርባቸው፤ እንዲህም በላቸው፣

“‘*እግዚአብሔር* ከላይ ይጮኻል፤
ከቅዱስ ማደሪያው ነጐድጓዳማ ድምፁን
ያሰማል፤
በራሱ ምድር ላይ እጅግ ይጮኻል፤
እንደ ወይን ጨማቂዎች፣
በምድር በሚኖሩት ሁሉ ላይም
ያስገመግማል፤
[31]*እግዚአብሔር* ከሕዝቦች ጋር
ይፋረዳልና፣
ታላቅ ጩኸት እስከ ምድር ዳርቻ
ያስተጋባል፤
በሰው ሁሉ ላይ ፍርድን ያመጣል፤
ክፉዎችንም ለሰይፍ ይዳርጋል”
ይላል *እግዚአብሔር*።

[32]የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

“እነሆ፤ ጥፋት፣
ከአገር ወደ አገር እየተዛመተ
መጥቶአል፤
ብርቱ ዐውሎ ነፋስ፣
ከምድር ዳርቻ ተነሥቶአል።

[33]በዚያን ጊዜ *በእግዚአብሔር* የተገደ
ሉት ከምድር ዳር እስከ ምድር ዳር
በሁሉ ስፍራ ተረፍርፈው ይታያሉ፤ እንደ
ጕድፍ በምድር ላይ ይጣላሉ እንጂ፣
አይለቀስላቸ ውም፤ ሬሳቸውም
አይሰበሰብም፤ አይቀበር ምም።

[34]እናንት እረኞች፤ አልቅሱ፤ ዋይ በሉ፤
እናንት የመንጋው ጌቶች፤ በዐመድ
ላይ ተንከባለሉ፤
የምትታረዱበት ቀን ደርሶአልና፤
እንደ ውብ የሸክላ ዕቃ ወድቃችሁ
ትከሰክሳላችሁ።
[35]እረኞች የሚሸሹበት፣
የመንጋ ጠባቂዎችም የሚያመልጡበት
የለም።
[36]*እግዚአብሔር* ማሰማሪያቸውን
አጥፍቶአልና፣
የእረኞችን ጩኸት፣
የመንጋ ጠባቂዎችን ዋይታ ስሙ።
[37]*ከእግዚአብሔር* ጽኑ ቍጣ የተነሣ፣
ሰላማዊው ምድር ባድማ ይሆናል።
[38]እንደ አንበሳ ከጕሬው ይወጣል፤
ከአስጨናቂው ሰይፍ፣[ነ]
ከቍጣውም የተነሣ፣
ምድራቸው ባድማ ትሆናለች።

**25፥15** ኢሳ51፥17፤ ኤር1፥5፤49፥12፤ሰቆ 4፥21፤ሕዝ23፥31፤ ራእ14፥10
**25፥16** ቍ26-29፤ መዝ60፥3፤ኤር51፥7
**25፥17** ኤር1፥10፤ 27፥3
**25፥18** ዘፍ19፥13፤ ኢዮ12፥19፤2ዜና 29፥8፤ኤር13፥13፤ 24፥9፤44፥22
**25፥19** 2ነገ18፥21፤ ኢሳ19፥1፤20፥3፤ኤር 44፥30፤ሕዝ29፥2
**25፥20** ዘፍ10፥19፡ 23፤ኢሱ13፥3፤2ዜና 26፥6፤28፥18፤ኤር 47፥5፤አሞ1፥7-8፤ ሶፎ2፥4-7
**25፥21** ዘፍ25፥30 ፤19፥37፡38፤ዘዳ23፥6 ፤ኤር27፥3፤49፥1
**25፥22** ዘፍ10፥15፤ ኢሱ19፥29፤ኢሳ 11፥11፤48፥20፤66፥ 20፤ኤር31፥10፤ሕዝ 27፥15፤39፥6፤ዳን 11፥18
**25፥23** ዘፍ22፥21፤ 25፥3፡15፤ኤር9፥26፤ 49፥32
**25፥24** ቍ20፤2ዜና 9፥14
**25፥25** ዘፍ10፥22፤ 25፥2፤ኢሳ21፥2
**25፥26** ቍ9፤ኢሳ 23፥17፤ኤር50፥3፡9፤ 51፥11፡41፡48
**25፥27** ቍ16፡28፤ ኢሳ29፥9፤49፥26፤ ኤር12፥12፤51፥57፤ ሕዝ14፥17፤21፥4፤ 23፥32-34፤ናሆ3፥18 ፤ዕን2፥16
**25፥28** ኢሳ51፥23
**25፥29** ቍ27፡30-31 ፤ዘዳ28፥10፤2ሳሙ5፥7 ፤ምሳ11፥31፤ኢሳ 10፥12፤24፥1፤34፥2፤3 7፥17፤ኤር13፥12-14፤ 39፥1
**25፥30** ኢሳ16፥10፤ 42፥13፤63፥3፤መዝ 46፥6፤68፥5፤ኢል 3፥13፤ራእ14፥19-20
**25፥31** ቍ29፤1ሳሙ 12፥7፤ኤር2፥9፡35፤ 15፥9፤23፥19፤ሕዝ 36፥5
**25፥32** ዘዳ28፥49፤ ኢሳ30፥25፤34፥2፤ ኤር23፥19
**25፥33** መዝ79፥3፤ ኢሳ66፥16፤ኤር8፥2 ፤ሕዝ39፥17-20
**25፥34** መዝ44፥22 ፤ኢሳ34፥6፤ኤር2፥8፤ 6፥26፤22፥28፤50፥27፤ 51፥40፥ዘካ10፥3፤ 11፥4፡7
**25፥35** ኢዮ11፥20

**25፥36** ኤር6፥26፤23፥1፤ዘካ11፥3 **25፥38** ዘፀ15፥7፤ኢዮ 10፥16፤ኤር4፥7፡26፤44፥22፤46፥16፤50፥16

[በ]9 *አጠፋቸዋለሁ* ለሚለው የሚተካው የዕብራይስጥ ቃል የሚያመለክተው ነገሮች ወይም ሰዎች (ደግሞ ላይመለሱ) ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ መሰጠታቸውን ነው።
[ተ]12 ወይም *ከለዳውያን*
[ቸ]23 ወይም *በሩቅ ስፍራዎች ያሉትን*
[ኀ]26 *ሺሻክ* የባቢሎን ምስጢራዊ ቃል ነው።
[ነ]38 አንዳንድ የዕብራይስጥና የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች (ኤር46፥16 እና 50፥16 ይመ) *ቍጣ* ይላሉ

## በኤርምያስ ላይ የግድያ ዛቻ

26 በይሁዳ ንጉሥ፣ በኢዮስያስ ልጅ፣
በኢዮአቄም ዘመነ መንግሥት መጀ
መሪያ ላይ ይህ ቃል ከእግዚአብሔር
ዘንድ መጣ፤ 2“እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
በእግዚአብሔር ቤት አደባባይ ቆመህ፣
ለማምለክ ወደ እግዚአብሔር ቤት ከይ
ሁዳ ከተሞች ለሚመጣው ሕዝብ ሁሉ
ተናገር፤ አንዲትም ቃል ሳታስቀር የማዝ
ህን ሁሉ ንገራቸው:: 3ምናልባትም ሰም
ተው እያንዳንዳቸው ከክፉ መንገዳቸው
ይመለሱ ይሆናል፤ እኔም ስላደረጉት ክፋት
ላመጣባቸው ያሰብሁትን ቅጣት እተዋ
ለሁ:: 4እንዲህም በላቸው፤ ‘እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤ ባትሰሙኝና የሰጠኋች
ሁን ሕጌን ባትጠብቁ፣ 5ልትሰሚቸው
ይገባ የነበረውን ወደ እናንተ ደጋግሜ
የላክኋቸውን የአገልጋዮቼን የነቢያትን
ቃል ባትሰሙ፣ 6ይህን ቤት እንደ ሴሎ
አደርጋለሁ፤ ይህችንም ከተማ በምድር
ሕዝብ ሁሉ ፊት የተረገመች አደርጋታ
ለሁ::’ ”

7ኤርምያስ ይህን ቃል በእግዚአብሔር
ቤት ሲናገር፣ ካህናቱና ነቢያቱ፣ ሕዝቡም
ሁሉ ሰሙ:: 8ነገር ግን ኤርምያስ እግዚአ
ብሔር ለሕዝቡ ሁሉ እንዲናገር ያዘዘውን
ሁሉ ተናግሮ በጨረሰ ጊዜ፣ ካህናቱ፣ ነቢ
ያቱና ሕዝቡም ሁሉ ይዘውት እንዲህ አሉ፤
“አንተ መገደል አለብህ! 9ይህ ቤት እንደ
ሴሎ ይሆናል፤ ይህቺም ከተማ ባድማና
ወና ትሆናለች ብለህ በእግዚአብሔር ስም
ለምን ትንቢት ትናገራለህ?” ’ ሕዝቡም
ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ተሰብስ
በው ኤርምያስን ከበቡት::

10የይሁዳም ባለሥልጣኖች ስለ እነዚህ
ነገሮች በሰሙ ጊዜ፣ ከቤተ መንግሥት
ወደ እግዚአብሔር ቤት ወጡ፤ በእግዚ
አብሔር ቤት፣ ‘አዲሱ በር በተባለው
መግቢያ ተቀመጡ:: 11ካህናቱና ነቢያቱም
ለባለሥልጣኖቹና ለሕዝቡ ሁሉ፣ “በጆሮአ
ችሁ እንደ ሰማችሁት ይህ ሰው በዚህች
ከተማ ላይ ትንቢት ስለ ተናገረ ሞት
ይገባዋል” አሉ::

12ኤርምያስም፣ ለባለሥልጣኖቹና ለሕ
ዝቡ ሁሉ እንዲህ አለ፤ “የሰማችሁትን
ሁሉ በዚህ ቤትና በዚህች ከተማ ላይ
ትንቢት እንድናገር እግዚአብሔር ልኮ
ኛል:: 13አሁንም መንገዳችሁንና ሥራ
ችሁን አስተካክሉ፣ አምላካችሁን እግዚ
አብሔርን ታዘዙ:: እግዚአብሔርም
በእናንተ ላይ ለማ ምጣት የተናገረውን
ክፉ ነገር ይተዋል:: 14ስለ እኔ ከሆነ ግን
እነሆ፤ በእጃችሁ ነኝ፤ መልካምና ተገቢ
መስሎ የሚታያችሁን ሁሉ አድርጉብኝ::
15ነገር ግን የሰማችሁ ትን ይህን ሁሉ
ቃል በጆሮአችሁ እንድ ናገር እግዚአብሐ
ር በእርግጥ ስለ ላከኝ ብትገድሉኝ፣ የን
ጹሕ ሰው ደም በማፍሰ ሳችሁ እናንተ ራ
ሳችሁንና ይህቺን ከተማ፣ በውስጧም
የሚኖረውን በደለኛ እንዳታ ደርጉ ተጠ
ንቀቁ::”

16ባለሥልጣኖቹና ሕዝቡም ሁሉ ለካህና
ትና ለነቢያት፣ “ይህ ሰው በአምላካችን
በእ ግዚአብሔር ስም ተናግሮአልና ሊገደል
አይ ገባውም” አሉ::

17ከአገሩ ሽማግሌዎችም አንዳንዶቹ
ተነሥተው ለተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ እን
ዲህ አሉ፤ 18“ሞሬታዊው ሚክያስ በይሁዳ
ንጉሥ በሕዝቅያስ ዘመን፣ ለይሁዳም
ሕዝብ ሁሉ እንዲህ ሲል ትንቢት ተናግሮ
ነበር፤ ‘የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እን
ዲህ ይላል፤

“ ‘ጽዮን እንደ ዕርሻ ትታረሳለች፤
ኢየሩሳሌም የፍርስራሽ ክምር
ትሆናለች፤
የቤተ መቅደሱም ተራራ፣ ዳዋ
የወረሰው ኰረብታ ይሆናል::’ⁿ

19“ታዲያ፣ የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስም
ሆነ የይሁዳ ሕዝብ ሁሉ ገደሉትን? ሕዝ
ቅያስ እግዚአብሔርን ፈርቶ ምሕረት አል
ለመነምን?’ እግዚአብሔርስ በእነርሱ ላይ
ለማምጣት ያሰበውን ቅጣት አልተወምን?
በራሳችን ላይ እኮ ታላቅ ጥፋት እያመ
ጣን ነው::”

20ደግሞም የቂርያትይዓሪም ሰው፣ የሸ
ማያ ልጅ ኦርዮ፣ በእግዚአብሔር ስም
ትንቢት የተናገረ ሌላው ሰው ነበር፤ እርሱም
እንደ ኤርምያስ በዚህች ከተማና በዚህ
ምድር ላይ ትንቢት ተናግሮ ነበር:: 21ንጉሥ
ኢዮአቄም፣ የጦር አለቆቹና ባለሥልጣኖቹ
ሁሉ ይህን በሰሙ ጊዜ፣ ንጉሡ ሊገድለው
ፈለገ፤ ኦርዮም ይህን ሰምቶ በፍርሀት
ወደ ግብፅ ሸሸ:: 22ይሁን እንጂ ንጉሥ
ኢዮአቄም የዓክቦርን ልጅ ኤልናታንንና
ከእርሱም ጋር ሌሎችን ሰዎች ወደ ግብፅ
ላካቸው፤ 23እነርሱም ኦርዮን ከግብፅ አም
ጥተው፣ ወደ ንጉሥ ኢዮአቄም ወሰዱት፤
እርሱም በሰይፍ ገደለው፤ ሬሳውንም ተራ
ሰዎች በሚቀበሩበት ስፍራ ጣለው::
24ነገር ግን የሳፋን ልጅ አኪቃም
ከኤር
ምያስ ጐን ስለ ቆመ፣ ኤርምያስ ይገደል
ዘንድ ለሕዝቡ ዐልፎ አልተሰጠም::

26፥1 2ነገ23፥36
26፥2 ቀኍ12፤ዘዳ 4፥2፤ኤር1፥17፤17፥19፤19፥14፤ማቴ 28፥20፤ሐሥ20፥27
26፥3 ዘዳ30፥2፤ 2ዜና33፥12-13፤ኢሳ 55፥7፤ኤር18፥8፤35፥15፤36፥7
26፥4 ዘፀ20፥1-23፥33፤ዘሌ26፥14፤1ነገ 9፥6፤ኤር11፥8፤25፥3
26፥5 ምሳ1፥24፤ ኢሳ65፥12፤ኤር25፥4፤44፥5
26፥6 ዘዳ28፥25፤ ኢሱ18፥1፤መሳ18፥31፤2ነገ22፥19
26፥8 ዘሌ24፥15-16፤ነህ9፥26፤ኤር11፥21፤43፥1፤ሐሥ6፥12፤21፥27
26፥9 ዘሌ26፥32፤ኤር9፥11፤ሐሥ21፥32
26፥10 ቀኍ16፤ዘፍ 23፥10፤ኤር34፥19፤ሕዝ22፥27
26፥11 ዘዳ18፥20፤ መዝ44፥1፤ኤር11፥21፤18፥23፤ማቴ26፥66፤ ሐሥ6፥11
26፥12 ቀኍ2፥15፤ ኢሳ6፥8፤ኤር1፥18፤ አሞ7፥15፤ሐሥ4፥18-20፤5፥29
26፥13 ኤር7፥5፤ 11፥4፤18፥8፤ኢል 2፥12-14
26፥14 ኢሱ 9፥25፤ ኤር 38፥5
26፥15 ቀኍ12፤ዘዳ 19፥10፤ኤር1፥17
26፥16 ቀኍ10፤ሐሥ 23፥9፥29
26፥18 2ነገ25፥9፤ ነህ4፥2፤ኢሳ2፥3፤ኤር 9፥11፤17፥3፤ሚክ1፥1፤4፥1፤ዘካ 8፥3
26፥19 ዘፀ32፥14፤ 1ሳሙ13፥12፤1ዜና 3፥13፤2ዜና32፥24-26፤ኢሳ37፥14-20፤ ኤር18፥8፤44፥7፤ዕን 2፥10
26፥20 ኢሱ9፥17
26፥21 ቀኍ10፤ዘፍ 31፥21፤1ነገ19፥2፤ ኤር2፥30፤ማቴ 10፥23፤23፥37
26፥22 ኤር36፥12፥25
26፥23 2ነገ23፥6፤ ዕብ11፥37
26፥24 2ነገ22፥12

ⁿ18 ሚክያስ 3፥12

## የይሁዳ በናቡከደነፆር ሥር መውደቅ

27 በይሁዳ ንጉሥ፣ በኢዮስያስ ልጅ
በሴዴቅያስ[ኣ] ዘመነ መንግሥት መጀ
*መሪያ ላይ ይህ የእግዚአብሔር ቃል* ወደ
ኤርምያስ መጣ፤ 2*እግዚአብሔርም* እንዲህ
አለኝ፤ "የዕንጨት ቀንበር ሠርተህ በጠ
ፍር ማነቆ አያይዘውና በዐንገትህ አስገ
ባው፤ 3ወደ ይሁዳ ንጉሥ ወደ ሴዴቅያስ ወደ
ኢየሩሳሌም በመጡት ሰዎች በኩል ለኤ
ዶም፣ ለሞዓብ፣ ለአሞን፣ ለጢሮስና ለሲ
ዶና ነገሥታት መልእክት ላክ፡፡ 4ለጌቶቻ
ቸውም እንዲያሳውቁ እንዲህ ብለህ ንገራ
ቸው፤ 'የእስራኤል አምላክ የሰራዊት ጌታ
*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ "ለጌቶቻ
ችሁ ይህን ንገሯቸው፤ 5በታላቁ ኀይሌና
በተዘረጋው ክንዴ ምድርን፣ በላይዋ የሚ
ኖሩትን ሰዎችና እንስሳት ፈጥሬአለሁ፤
ለምወደውም እሰጣለሁ፡፡ 6አሁንም እነዚህን
አገሮች ሁሉ ለአገልጋዬ ለባቢሎን ንጉሥ
ለናቡከደነፆር አሳልፌ እሰጣለሁ፤ የዱር አራ
ዊት እንኳ እንዲገዙለት አደርጋለሁ፡፡ 7የእ
ርሱ አገር በተራው ለሌሎች እስከሚገዛ
በት ጊዜ ድረስ፣ ሕዝቦች ሁሉ ለእርሱ፣
ለልጁና ለልጅ ልጁ ይገዛሉ፤ በዚያን ጊዜ
ብዙ ሕዝቦችና ታላላቅ ነገሥታት እርሱን
ይገዙታል፡፡
8" ' "ነገር ግን ለባቢሎን ንጉሥ
ለናቡከ ደናፆር የማይገዛ፣ ዐንገቱንም
ከቀንበሩ በታች ዝቅ የማያደርግ
ማንኛውንም ሕዝብ ወይም መንግሥት
በእጁ እስከማጠፋው ድረስ በሰይፍና በራ
ብ፣ በመቅሠፍትም እቀ ጣዋለሁ፤ ይላል
*እግዚአብሔር*፤ 9ስለዚህ፣ 'የባቢሎንን
ንጉሥ አታገለግሉም' የሚሏች ሁን ነቢ
ያታችሁን፣ ሟርተኞቻችሁን፣ ሕል
መኞቻችሁን፤ መናፍስት ጠሪዎቻችሁንና
መተተኞቻቸሁን አትስሙ፤ 10ከምድራችሁ
እንድትፈናቀሉ፣ እኔም እንዳሳድዳችሁና
እንዳጠፋችሁ የሐሰት ትንቢት ይነግሯች
ኋልና፡፡ 11ነገር ግን ከባቢሎን ንጉሥ ቀን
በር በታች ዐንገቱን ዝቅ የሚያደርገውንና
የሚያገለግለውን ማንኛውንም ሕዝብ በገዛ
ምድሩ እንዲቀርና እያረሰም በዚያ እንዲ
ኖር አደርገዋለሁ፤ ይላል *እግዚአብሔር*፡፡" ' "
12ለይሁዳ ንጉሥ ለሴዴቅያስም ይህንኑ
መልእክት እንዲህ ብዬ ነገርሁት፤ "አንገ
ታችሁን ከባቢሎን ንጉሥ ቀንበር በታች
ዝቅ አድርጉ፤ እርሱንና ሕዝቡን አገልግሉ፤
በሕይወትም ትኖራላችሁ፡፡ 13አንተና ሕዝ
ብህ፣ *እግዚአብሔር* ለባቢሎን ንጉሥ አል
ገዛም ያለውን ሕዝብ ባስጠነቀቀበት በሰ
ይፍ፣ በራብና በመቅሠፍት ለምን ታል
ቃላችሁ? 14ሐሰተኛ ትንቢት ስለሚነግሯ
ችሁ፣ 'የባቢሎንን ንጉሥ አታገለግሉም'
የሚሏችሁን ነቢያት አትስሙ፤ 15'እኔ አል
ላክኋቸውም' ይላል *እግዚአብሔር* 'የሐሰት
ትንቢት በስሜ ይናገራሉ፤ ስለዚህ እናን
ተንና ትንቢት የሚናገሩላችሁን ነቢያት
አሳዳለሁ፤ እናንተም ትጠፋላችሁ፡፡' "
16እኔም ለካህናቱና ለዚህ ሕዝብ ሁሉ
እንዲህ አልሁ፤ "*እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤ '*የእግዚአብሔር* ቤት ዕቃ ከባቢ
ሎን ቶሎ ይመለሳል' የሚሏችሁን ነቢያት
አትስሟቸው፤ የሚነግሯችሁ የሐሰት ትን
ቢት ነውና፡፡ 17ስለዚህ እነርሱን መስማት
ትታችሁ ለባቢሎን ንጉሥ ተገዙ፤ በሕይ
ወትም ትኖራላችሁ፤ ባለመታዘዛችሁስ ይህቺ
ከተማ ለምን ትፈራርስ? 18እውነተኞች
ነቢያት ከሆኑና በእርግጥ *የእግዚአብሔር*
ቃል ካላቸው፣ *በእግዚአብሔር* ቤትና በይ
ሁዳ ንጉሥ ቤተ መንግሥት በኢየሩሳሌ
ምም የቀሩት ዕቃዎች ወደ ባቢሎን እን
ዳይወሰዱ ወደ ሰራዊት ጌታ ወደ *እግዚ
አብሔር* እስቲ ይማልዱ! 19የሰራዊት ጌታ
*እግዚአብሔር* በዚህች ከተማ ስለ ቀሩት፡-
ዐምዶች፣ ከናስ ስለ ተሠራው ትልቁ
ገንዳ፣ ስለ ተንቀሳቃሽ ማስቀመጫዎችና
ስለ ሌሎቹም ዕቃዎች እንዲህ ይላልና፤
20የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር የይሁዳን
ንጉሥ የኢዮአቄምን ልጅ ኢኮንያንን፣[ከ]
ከኢየሩሳሌምና ከይሁዳ መኳንንት ጋር
ማርኮ ወደ ባቢሎን በወሰደ ጊዜ እነዚህ
በከተማዪቱ የቀሩ ዕቃዎች ስለ ሆኑ፣
21*በእግዚአብሔር* ቤትና በይሁዳ ንጉሥ
ቤተ መንግሥት በኢየሩሳሌምም ስለ ቀሩት
ዕቃዎች፣ የእስራኤል አምላክ የሰራዊት
ጌታ *እግዚአብሔር* የሚለው እንዲህ
ነው፡- 22'ወደ ባቢሎን ይወሰዳሉ፤ እኔ
እርሱን እስከምጐበኝበት ቀን ድረስ በዚያ
ይቀመጣሉ' ይላል *እግዚአብሔር*፤ 'በዚያ
ጊዜም እመልሳቸዋለሁ፤ ወደዚህም ስፍራ
አመጣቸዋለሁ፡፡' "

## ሐሰተኛው ነቢይ ሐናንያ

28 በዚያው ዓመት የይሁዳ ንጉሥ
ሴዴቅያስ እንደ ነገሠ በዐራተ
ኛው ዓመት፣ አምስተኛ ወር፣ የገባዖኑ
ሰው የዓዙር ልጅ ነቢዩ ሐናንያ *በእግዚ
አብሔር* ቤት በካህናቱና በሕዝቡ ሁሉ
ፊት እንዲህ አለኝ፤ 2"የእስራኤል አምላክ
የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

27፥1 2ዜና36፥11
27፥2 ዘሌ26፥13፤ 1ነገ22፥11
27፥3 ዘፍ10፥15፤ ኤር25፥17፡21፡22
27፥5 ዘፍ1፥1፡25፤ ዘዳ9፥29፤መዝ115፥16፤ ዳን4፥17
27፥6 ኤር21፥7፤ 25፥9፤28፥14፤ዳን 2፥37-38
27፥7 2ዜና36፥20፤ ኤር25፥12፡14፤ 51፥47፤ዳን5፥18፡28
27፥8 ኤር5፥12፤ 9፥16፤14፥12፤21፥9
27፥9 ዘፍ30፥27፤ ዘፀ7፥11፤ዘዳ13፥1፤ 18፥11፤ኢሳ44፥25፤ ኤር6፥14፤23፥25፤ ሕዝ13፥1-23
27፥10 2ነገ23፥27፤ ኤር23፥25፤ማር13፥5
27፥11 ዘዳ6፥2፤ኤር 21፥9
27፥12 ኤር17፥4፤ 21፥9
27፥13 ኤር14፥12፤ ሕዝ18፥31
27፥14 ኤር14፥13፡ 14፤23፥16፤ማቴ7፥15
27፥15 ኤር6፥15፤ 23፥21፤29፥9፤44፥16፤ ማቴ15፥12-14
27፥16 1ነገ7፥48-50፤2ነገ24፥13
27፥17 ኤር23፥16፤ 42፥11
27፥18 ዘኍ21፥7፤ 1ሳሙ 7፥8
27፥19 1ነገ7፥23-26፡51፤ኤር52፥17-23
27፥20 ዘዳ28፥36፤ 2ዜና36፥10፤ኤር22፥24፤ማቴ1፥11
27፥22 2ነገ20፥17፤ 25፥13፤2ዜና36፥21፤ ኤር24፥6፤ዕዝ 7፥19
28፥1 ኢሱ9፥3፤ 2ዜና36፥11
28፥2 ኤር27፥12

[ኣ]1 ጥቂት የዕብራይስጥ ጽሑፎችና የሱርሰት ትርጒም (ኤር 27፥3፡12 እና 28፥1 ይመ)፣ አዳንድ የዕብራይስጥ ጽሑፎች ***ኢዮአቄም*** ይላሉ (አብዛኛዎቹ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች ይህ ጥቅስ/ ቍጥር የላቸውም)፡፡
[ከ]20 ***ኢኮንያን የኢዮአኪን*** ሌላው አቻ ስም ነው

‘የባቢሎን ንጉሥ የጫነባችሁን ቀንበር እሰ
ብራለሁ፤ 3የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር
*ከእግዚአብሔር* ቤት ወደ ባቢሎን የወሰዳ
ቸውን ዕቃዎች ሁሉ በሁለት ዓመት ጊዜ
ውስጥ መልሼ አመጣለሁ። 4የይሁዳንም
ንጉሥ የኢዮአቄምን ልጅ ኢኮንያንን፣ከ
ሌሎች ከይሁዳ ወደ ባቢሎን ተማርከው
የተወሰዱትንም ሁሉ ወደዚህ ስፍራ እመ
ልሳለሁ’ ይላል *እግዚአብሔር*፤ የባቢሎን
ንጉሥ የጫነባቸውን ቀንበር እሰብራለ
ሁና።’ ”

5ነቢዩ ኤርምያስም በካህናቱና *በእግዚ
አብሔር* ቤት ቆመው በነበሩት ሕዝብ
ሁሉ ፊት፣ ለነቢዩ ለሐናንያ እንዲህ ብሎ
መለሰለት፡- 6“አሜን፤ *እግዚአብሔር* ያድ
ርገው፤ *የእግዚአብሔርን* ቤት ዕቃ ሁሉ፣
ተማርከው የተወሰዱትንም ምርኮኞች ሁሉ
ከባቢሎን በመመለስ፣ *እግዚአብሔር* የተና
ገርኸውን ቃል ይፈጽም። 7ነገር ግን ለአን
ተም ለዚህም ሕዝብ የምናገረውን ቃል ስ
ማ፤

8ከአንተና ከእኔ በፊት ጥንት የተነሡ
ነቢያት፣ በብዙ አገሮችና በታላላቅ መንግ
ሥታት ላይ ስለ ጦርነት፣ ስለ ጥፋትና
ስለ መቅሠፍት ትንቢት ተናግረዋል።
9ነገር ግን ስለ ሰላም ትንቢት የተናገረ
ነቢይ *እግዚአብሔር* በእውነት እንደ ላከው
የሚታወቀው የተናገረው ትንቢት ሲፈጸም
ነው።

10ነቢዩም ሐናንያ ቀንበሩን ከነቢዩ ኤር
ምያስ ዐንገት ወስዶ ሰበረው፤ 11በሕዝ
ቡም ፊት፣ “*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
‘በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የባቢሎንን
ንጉሥ የናቡከደናፆርን ቀንበር ከሕዝቡ
ሁሉ ጫንቃ ላይ ልክ እንደዚህ እሰብራ
ለሁ’ አለ። በዚህ ጊዜ፣ ነቢዩ ኤርምያስ
ትቶት መንገዱን ቀጠለ።

12ነቢዩም ሐናንያ ቀንበሩን ከነቢዩ
ከኤርምያስ አንገት ወስዶ ከሰበረ ከጥቂት
ጊዜ በኋላ፣ *የእግዚአብሔር* ቃል ወደ
ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፤ 13“ሄደህ
ለሐናንያ እንዲህ ብለህ ንገረው፤ ‘*እግዚአ
ብሔር* እንዲህ ይላል፤ አንተ የዕንጨት
ቀንበር ሰብረሃል፤ እኔ ግን በምትኩ የብ
ረት ቀንበር እሠራለሁ። 14የእስራኤል አም
ላክ የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤ የባቢሎንን ንጉሥ ናቡከደነፆርን
እንዲያገለግሉ፣ በእነዚህ ሕዝቦች ላይ የብ
ረት ቀንበር አደርጋለሁ፤ እነርሱም
ይገዙለ ታል፤ በዱር አራዊት ላይ እንኳ
ሥልጣን እሰጠዋለሁ።’ ”

15ነቢዩ ኤርምያስም ለነቢዩ ሐናንያ
እንዲህ አለው፤ “ሐናንያ ሆይ፤ ስማ! *እግ*

28፥3 2ነገ24፥13
28፥4 2ነገ25፥30፤ ኤር22፥24-27፤ሆሴ 7፥3
28፥6 ዘካ6፥10
28፥8 ዘሌ26፥14-17፤ኢሳ5፥5-7፤ናሆ 1፥14
28፥9 ዘዳ18፥22፤ ሕዝ33፥33
28፥10 ዘሌ26፥13፤ 1ነገ22፥11
28፥11 ኤር14፥14፤ 27፥10
28፥14 ዘዳ28፥48፤ ኤር15፥12፤25፥11፤ 27፥6፤39፥1፤ዳን1፥1፤ 5፥18
28፥15 ኤር7፥4፤ 20፥6፤29፥21፡31፤ ሰቆ2፥14፤ሕዝ 13፥6
28፥16 ዘፍ7፥4፤ ዘዳ13፥5፤18፥20፤ ኤር29፥32፤ዘካ13፥3
28፥17 2ነገ1፥17
29፥1 ቍ28፤2ዜና 36፥10፤ኤር13፥17
29፥2 2ነገ24፥8፡12
29፥4 ኤር24፥5
29፥5 ቍ28
29፥6 ኤር30፥19
29፥7 አስ3፥8፤ 1ጢሞ2፥1-2
29፥8 ዘዳ13፥1፤ ኤር23፥25፡27፤ 37፥9፤1ዮሐ4፥1
29፥9 ኤር23፥21፤ 27፥15፤ሰቆ2፥14፤ሕዝ 13፥6
29፥10 ሩት1፥6፤ 1ነገ8፥56፤2ዜና36፥ 21፤ኤር16፥14፤24፥6፤ 32፥42፤33፥14፤ዳን 9፥2
29፥11 ኢዮ8፥7፤ መዝ40፥5፤ኢሳ55፥12 ፤ዘካ8፥15

*ዚአብሔር* ሳይልክህ ይህ ሕዝብ በሐሰት
እንዲታመን አድርገሃል፤ 16ስለዚህ *እግዚ
አብሔር* እንዲህ ይላል፡- ‘ከምድር ገጽ አስ
ወግድሃለሁ፤ *በእግዚአብሔርም* ላይ ዐመፅ
ተናግረሃልና፣ በዚህ ዓመት ትሞታለህ።’ ”

17ነቢዩም ሐናንያ በዚያው ዓመት በሰ
ባተኛው ወር ሞተ።

## በምርኮ ላሉት የተላከ ደብዳቤ

29 ነቢዩ ኤርምያስ በምርኮ ተወስ
ደው በሕይወት ለቀሩት ሽማግሌ
ዎች፣ ለካህናቱ፣ ለነቢያቱና ናቡከደነፆር
ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢሎን ማርኮ ለወሰዳ
ቸው ሕዝብ ሁሉ የላከው የደብዳቤ ቃል
ይህ ነው፤ 2ይህም የሆነው ንጉሡ ኢኮን
ያንሠ እቴጌዪቱ እናቱ፣ የቤተ መንግሥቱ
ባለሟሎች፣ የይሁዳና የኢየሩሳሌም መሪ
ዎች፣ አናጺዎችና ብረት ቀጥቃጮች ተማ
ርከው ከኢየሩሳሌም ከተወሰዱ በኋላ
ነበር። 3ደብዳቤውንም ከይሁዳ ንጉሥ ከሴ
ዴቅያስ ወደ ባቢሎን ንጉሥ ወደ ናቡከ
ደነፆር በተላኩት መልእክተኞች በሳፋን
ልጅ በኤልዓሣና በኬልቅያስ ልጅ በገማ
ርያ እጅ ላከው፤ ደብዳቤውም እንዲህ
የሚል ነበር፤

4የእስራኤል አምላክ የሰራዊት ጌታ
*እግዚአብሔር*፣ ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢ
ሎን ላስማረካቸው ሁሉ እንዲህ ይላል፤
5“ቤት ሠርታችሁ ተቀመጡ፤ አትክልት
ተክላችሁ ፍሬውን ብሉ፤ 6አግብታችሁ
ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ውለዱ፤ ወን
ዶች ልጆቻችሁንና ሴቶች ልጆቻችሁን
አጋቡ፤ እነርሱም ወንዶችና ሴቶች ልጆችን
ይውለዱ፤ ቍጥራችሁም በዚያ ምድር
ይብዛ እንጂ አይነስ። 7ተማርካችሁ ለሄዳ
ችሁባት ከተማ ሰላምና ብልጽግናን እሹ፤
ወደ *እግዚአብሔርም* ጸልዩላት፤ ምክንያ
ቱም እርሷ ብትበለጽግ እናንተም ትበለ
ጽጋላችሁ።” 8የእስራኤል አምላክ የሰራዊት
ጌታ *እግዚአብሔር* በእርግጥ እንዲህ ይላ
ልና፤ “በመካከላችሁ ያሉት ነቢያትና ጠን
ቋዮች አያታልሏችሁ፤ የሚያልሙላችሁ
ንም ሕልም አትስሙ፤ 9በስሜ ሐሰተኛ
ትንቢት ይነግሯችኋል እንጂ እኔ
አልላክኋ ቸውም” ይላል *እግዚአብሔር*።

10*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ ‘ሰባው
ዓመት የባቢሎን ቈይታችሁ በተፈጸመ ጊዜ
እጐበኛችኋለሁ፤ ወደዚህም ሥፍራ ልመል
ሳችሁ የገባሁላችሁን መልካሚቱን ቃሌን
እፈጽምላችኋለሁ። 11ለእናንተ ያለኝን
ዕቅድ እኔ ዐውቃለሁ” ይላል *እግዚአብሔር*፤

ከ4 ወይም *ኢዮአኪን* ይላል።
ሠ2 *ኢኮንያን የኢዮአኪን* ሌላው አቻ ስም ነው

“ዕቅዱም ፍጻሜው ያማረና ተስፋ የሚ
ሰጥ፣ እናንተንም የሚጠቅም እንጂ የሚ
ጐዳ አይደለም። 12እናንተም ትጠሩኛላ
ችሁ፤ ቀርባችሁ ወደ እኔ ትጸልያላችሁ፤
እኔም እሰማችኋለሁ። 13እናንተ ትፈልጉኛ
ላችሁ፣ በፍጹም ልባችሁም ከፈለጋችሁኝ
ታገኙኛላችሁ፤ 14እኔም እገኝላችኋለሁ”
ይላል *እግዚአብሔር*፤ “ከምርኮም° እመልሳ
ችኋለሁ፤ እናንተንም ከበተንሁበት አገርና
ስፍራ ሁሉ እመልሳችኋለሁ” ይላል *እግዚአ*
*ብሔር*፤ “በምርኮ ምክንያት ወዳስለቀቅኋ
ችሁም ምድር እመልሳችኋለሁ።”

15እናንተም፣ “*እግዚአብሔር* በባቢሎን
ነቢያት አስነሥቶልናል” ትላላችሁ፤ 16*እግ*
*ዚአብሔር* ግን በዳዊት ዙፋን ላይ ስለሚ
ቀመጠው ንጉሥና ከእናንተ ጋር ተማርኮ
ስላልሄደው ወገንህ በዚህ ከተማ ስለ
ቀረው ሕዝብ ሁሉ እንዲህ ይላል፤ 17የሰራ
ዊት ጌታ *እግዚአብሔር* በእርግጥ እንዲህ
ይላል፤ “ሰይፍን፣ ራብንና መቅሠፍትን እሰ
ድባቸዋለሁ፤ ከመበላሸቱ የተነሣም ሊበላ
እንደማይቻል እንደ መጥፎ የበለስ ፍሬ
አደርጋቸዋለሁ። 18በሰይፍ፣ በራብና በመቅ
ሠፍት አሳድዳቸዋለሁ፤ በምድር መንግሥ
ታት ሁሉ ፊት የሚያስጸይፉ አደርጋቸዋ
ለሁ፤ በማሳዳቸውም ሕዝቦች ዘንድ የርግ
ማንና የድንጋጤ፣ የመሣቂያና የመዘባበቻ
ምልክት ይሆናሉ፤ 19በአገልጋዮቼ በነቢ
ያት በኩል ደጋግሜ የላክሁላቸውን ቃሌን
አል ሰሙምና” ይላል *እግዚአብሔር*፤
“እናንተ ምርኮኞችም አልሰማችሁም”
ይላል *እግዚአብሔር*።

20“ስለዚህ ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢሎን
የሰደድኋችሁ ምርኮኞች ሁሉ፣ *የእግዚአ*
*ብሔርን* ቃል ስሙ። 21የእስራኤል አምላክ
የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* በስሜ የሐ
ሰት ትንቢት ስለሚነግሯችሁ ስለ ቆላያ
ልጅ ስለ አክዓብና ስለ መዕሤያ ልጅ ስለ
ሴዴቅያስ እንዲህ ይላል፤ ‘እነዚህን ለባቢ
ሎን ንጉሥ ለናቡከደናፆር አሳልፌ እሰጣ
ቸዋለሁ፤ እርሱም ዐይናችሁ እያየ ይገድ
ላቸዋል። 22በእነርሱ ላይ ከደረሰው የተነሣ
በባቢሎን ያሉ የይሁዳ ምርኮኞች ሁሉ፣
“*እግዚአብሔር*፣ የባቢሎን ንጉሥ በእሳት
እንደ ጠበሳቸው እንደ ሴዴቅያስና እንደ
አክዓብ ያድርግብህ” ብለው ይራገማሉ፤
23ከባልንጀሮቻቸው ሚስቶች ጋር በማመን
ዘርና ያልነገርኋቸውን ቃል በስሜ በሐሰት
በመናገር በእስራኤል ዘንድ በደል ፈጽመ
ዋልና። ይህንም እኔ ዐውቃለሁ፤ ምስክር
ነኝ’ ” ይላል *እግዚአብሔር*።

29፥12 1ነገ8፥30፤ መዝ145፥19፤ኢሳ 55፥6፤ሆሴ2፥23፤ሶፎ 3፥12፤ዘካ13፥9
29፥13 ዘዳ4፥29፤ 2ዜና6፥37፤ማቴ7፥7
29፥14 ዘዳ30፥3፤ ኤር23፥3-4፤30፥3፥10 ፤46፥27፤ሕዝ37፥21፤ 39፥25፤አሞ9፥14፤ ሶፎ3፥20
29፥17 ኢሳ5፥4፤ ኤር27፥8
29፥18 ዘኍ5፥27፤ ዘዳ28፥25፥37፤ኢሳ 28፥22፤ኤር15፥4፤ 18፥16፤22፥10፤ 44፥12፤ሚክ 2፥6
29፥19 ኤር6፥19፤ 7፥25፤25፥4
29፥20 ኤር24፥5
29፥21 ቍ9፤ኤር 14፥14
29፥22 ዳን3፥6
29፥23 ዘፍ31፥48፤ ኤር7፥1123፥14፤ዕብ 4፥13
29፥25 2ነገ25፥18
29፥26 1ሳሙ10፥ 11፤ኤር20፥2፤ሆሴ 9፥7፤ዮሐ10፥20
29፥28 ቍ1፥5፥10
29፥29 ኤር21፥1
29፥31 ቍ24፤ ኤር14፥14
29፥32 ቍ10፤ 1ሳሙ2፥30-33፤ኤር 28፥16
30፥2 ኢሳ30፥8፤ ኤር36፥2
30፥3 ኤር16፥14፥ 15፤24፥6፤29፥14
30፥5 ኤር6፥25

## ለሸማያ የተላከ መልእክት

24“ለኔሔላማዊው ለሸማያ እንዲህ ብለህ
ንገረው፤ 25‘የእስራኤል አምላክ የሰራዊት
ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ በኢ
የሩሳሌም ላለው ሕዝብ ሁሉ፣ ለካህኑ
ለመዕሤያ ልጅ ለሶፎንያስና ለሌሎችም
ካህናት ሁሉ በገዛ ስምህ ደብዳቤዎችን
ልከሃል፤ ለሶፎንያስም እንዲህ ብለሃል፤
26“*በእግዚአብሔር* ቤት ኀላፊ ትሆን
ዘንድ *እግዚአብሔር* በካህኑ በዮዳሄ ምትክ
ካህን አድርጎ ሾሞሃል፤ ነቢይ ነኝ እያለ
ትንቢት የሚናገር ማንኛውም ያበደ ሰው
እግሩን በግንድ፣ ዐንገቱን በሰንሰለት መቀ
ፍደድ ይገባሃል። 27ታዲያ፣ ነቢይ ነኝ
ባዩን የዓናቶቱን ኤርምያስን ለምን አልገ
ሠጽኸውም? 28ይህ ሰው፣ ‘የምርኮው ጊዜ
ረዥም ስለ ሆነ፣ ቤት ሥርታችሁ ተቀ
መጡ፤ አትክልትም ተክላችሁ ፍሬውን
ብሉ’ በማለት ወደ ባቢሎን መልእክት
ልኮብናል።” ’ ”

29ካህኑ ሶፎንያስም ደብዳቤውን ለነቢዩ
ኤርምያስ አነበበለት። 30*የእግዚአብሔርም*
ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፤
31“ይህን መልእክት በምርኮ ላሉት ሁሉ
እንዲህ ብለህ ላክ፤ ‘ስለ ኔሔላማዊው ስለ
ሸማያ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ “እኔ
ሳልልከው ሸማያ ትንቢት ተናግሮላችሁ፣
በሐሰት እንድትታመኑ አድርጎአችኋልና፣
32*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ “እነሆ፤
ኔሔላማዊውን ሸማያንና ዘሩን እቀጣለሁ፤
በእኔ ላይ ዐመፅን ተናግሮአልና፣ በዚህ ሕዝብ
መካከል የሚተርፍ ዘር አይኖረውም” ’
ይላል *እግዚአብሔር*፤ ‘ለሕዝቤ የማደርገ
ውንም መልካም ነገር አያይም።’ ”

## የእስራኤል ሕዝብ መመለስ

30 *ከእግዚአብሔር* ዘንድ ወደ ኤር
ምያስ የመጣው ቃል ይህ ነው፤
2“የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር*
እንዲህ ይላል፤ ‘የነገርሁህን ቃል ሁሉ በመ
ጽሐፍ ጻፈው። 3እነሆ፣ ሕዝቤን እስራኤል
ንና ይሁዳን’ ይላል *እግዚአብሔር*፤ ‘ለአባ
ቶቻቸው ወደ ሰጠኋት ምድር የምመልስ
በት ጊዜ ተቃርቦአል፤″ እነርሱም ይወርሷ
ታል’ ይላል *እግዚአብሔር*።”

4*እግዚአብሔር* ስለ እስራኤልና ስለ ይሁዳ
የተናገረው ቃል ይህ ነው፤ 5“*እግዚአብሔር*
እንዲህ ይላል፤

“ ‘የፍርሀትና የሽብር ጩኸት ተሰምቶአል፤

°14 ወይም *ዕድል ፈንታችሁን እመልስላችኋለሁ*
″3 ወይም *የሕዝቤን የእስራኤልንና የይሁዳን ዕድል ፈንታ እመልሳለሁ*

ሰላምም የለም።
6 እስቲ ጠይቁ፤ ተመልከቱም፤
ወንድ መውለድ ይችላል?
ታዲያ ወንድ ሁሉ ምጥ እንደ ያዛት
ሴት፣
እጁን በሆዱ ላይ አድርጎ፣
የሰውስ ሁሉ ፊት ጠቍሮ የማየው
ለምንድን ነው?
7 ያ ቀን ምንኛ አስጨናቂ ይሆናል!
እንደዚያም ያለ አይኖርም፤
ለያዕቆብ የመከራ ጊዜ ነው፤
ነገር ግን ይተርፋል።
8 " 'በዚያን ቀን' ይላል የሰራዊት ጌታ
*እግዚአብሔር፤*
'በጫንቃቸው ላይ ያለውን ቀንበር
እሰብራለሁ፤
እስራታቸውንም እበጥሳለሁ፤
ከእንግዲህ ባዕዳን አይገዙአቸውም።
9 ነገር ግን ለአምላካቸው *ለእግዚአብሔር፣*
ለማስነሣላቸውም ለንጉሣቸው፣
ለዳዊት ይገዛሉ።
10 " 'ስለዚህ፤ አገልጋዬ ያዕቆብ ሆይ፤
አትፍራ፤
እስራኤል ሆይ፤ አትደንግጥ፤'
ይላል *እግዚአብሔር፤*
'አንተን ከሩቅ አገር፣
ዘርህንም ከተማረኩበት ምድር
እታደጋለሁ፤
ያዕቆብ ተመልሶ በሰላምና በርጋታ
ይቀመጣል፣
የሚያስፈራውም አይኖርም።
11 እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፤ አድንሃለሁም፣
ይላል *እግዚአብሔር፤*
'በአሕዛብ መካከል በትኜሃለሁ፤
እነዚህን አሕዛብ ሁሉ ፈጽሜ
አጠፋለሁ፤
አንተን ግን ሙሉ በሙሉ አላጠፋህም፤
በመጠኑ እቀጣሃለሁ እንጂ፣
ያለ ቅጣት አልተውህም።
12 "*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
" 'ስብራትህ የማይጠገን፣
ቍስልህም የማይድን ነው።
13 የሚሟገትልህ ሰው የለም፤
ለቍስልህ መድኃኒት አይኖርም፤
ፈውስም አታገኝም።
14 ወዳጆችህ ሁሉ ረስተውሃል፤
ስለ አንተም ግድ የላቸውም።
ጠላት እንደሚመታ መታሁህ፤
እንደ ጨካኝም ቀጣሁህ፤
በደልህ ታላቅ፣
ኀጢአትህም ብዙ ነውና።
15 ፈውስ ለማይገኝለት ሕመምህ፣
ስለቍስልህ ለምን ትጮኻለህ?
በደልህ ታላቅ፣ ኀጢአትህም ብዙ ስለሆነ፣
እነዚህን ሁሉ አድርጌብሃለሁና።
16 " 'ነገር ግን አሚጠው የበሉህ ሁሉ
እንደዚያው ይበላሉ፤
ጠላቶችህ ሁሉ ለምርኮ ዐልፈው
ይሰጣሉ፤
የሚዘርፉህ ይዘረፋሉ፤
የሚበዘብዙህም ሁሉ ይበዘበዛሉ።
17 አንተን ግን መልሼ ጤነኛ አደርግሃለሁ፤
ቍስልህንም እፈውሳለሁ፤'
ይላል *እግዚአብሔር።*
" 'የተናቀች፣
ማንም የማይፈልጋት ጽዮን"
ብለውሃልና።'
18 "*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
" 'እነሆ የያዕቆብን ድንኳን ምርኮ
እመልሳለሁ፤
ለማደሪያውም እራራለሁ፤
ከተማዪቱ በፍርስራሿ ጉብታ ላይ
ትሠራለች፤
ቤተ መንግሥቱም በቀድሞ ቦታው
ይቆማል።
19 ከእነርሱም የምስጋና መዝሙር፣
የእልልታ ድምፅ ይሰማል።
እኔ አበዛቸዋለሁ፤
ቍጥራቸውም አይቀንስም፣
አከብራቸዋለሁ፤
የተናቁም አይሆኑም።
20 ልጆቻቸው እንደ ቀድሞው ይሆናሉ፤
ማኅበረ ሰቡም በፊቴ የጸና ይሆናል፤
የሚጨቍኗቸውን ሁሉ እቀጣለሁ።
21 መሪያቸው ከራሳቸው ወገን ይሆናል፤
ገዥቸውም ከመካከላቸው ይነሣል፤
ወደ እኔ አቀርበዋለሁ፤ እርሱም ይቀርበኛል፤
አለዚያማ ደፍሮ፣
ወደ እኔ የሚቀርብ ማን ነው?
ይላል *እግዚአብሔር።*
22 " 'ስለዚህ እናንተ ሕዝብ ትሆኑኛላችሁ፤
እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ።' "
23 እነሆ፣ *የእግዚአብሔር* ማዕበል፣
በቍጣ ይነሣል፤
የሚገለባብጥም ዐውሎ ነፋስ፣
በክፉዎች ዐናት ላይ ይወርዳል።
24 የልቡን ሐሳብ ሳይፈጽም፣
*የእግዚአብሔር* ቍጣ፣
እንዲሁ አይመለስም፤
በሚመጡትም ዘመናት፣
ይህን ታስተውላላችሁ።

# 31
"በዚያ ዘመን" ይላል *እግዚአብሔር፤*
"ለእስራኤል ነገድ ሁሉ

30፥6 ኢሳ29፥22፤ ኤር4፥31
30፥7 ቀኑ10፤ኢሳ 2፥12፤22፥5፤ኤር 23፥3፤ሶፎ1፥15
30፥8 መዝ107፥14 ፤ኢሳ9፥4፤ኤር25፥14፤ 27፥7፤ሕዝ34፥27
30፥9 ቀኑ21፤1ሳሙ 13፥14፤ኤር33፥15፤ ሕዝ34፥23-24፤ 37፥24፤ሆሴ1፥11፤ 3፥5፤ማቴ1፥1
30፥10 ቀኑ7፤ኢሳ 35፥9፤41፥10፤44፥2፤ ኤር17፥25፤23፥4፤ 29፥14፡22፤54፥4፤ሕዝ 34፥25-28
30፥11 ዘሌ26፥44፤ ኢሱ1፥5፤ኤር5፥18፤ 10፥24፤46፥28፤ሆሴ 11፥9፤አሞ9፥8
30፥12 ኢዮ6፥4፤ ኤር8፥22፤10፥19
30፥13 መሳ6፥31፤ ኤር8፥22፤14፥19፤ 46፥11፤ናሆ3፥19
30፥14 ኢዮ13፥24፤ 30፥21፤ኤር22፥20፤ 25፥7፤ሰቆ1፥2
30፥15 ምሳ1፥31፤ ኤር10፥19፤ሰቆ 1፥5
30፥16 ኢሳ14፥2፤ 29፥8፤33፥1፤ኤር2፥3፤ 49፥2፤50፥10፤ኢል 3፥4-8
30፥17 መዝ142፥4 ፤ኢሳ1፥5፤6፥12፤ኤር 33፥24፤ሆሴ6፥1
30፥18 ቀኑ3፤ዘኍ 24፥5፤ዘዳ30፥3፤መዝ 102፥13፤ኤር31፥4፡ 23፡24፡38፤32፥44፤ 33፥7፡26፤ሕዝ36፥10፡ 33፤39፥25፤አሞ9፥14
30፥19 ዘፍ15፥5፤ 22፥17፤መዝ9፥2፤ 126፥1-2፤ኢሳ35፥10፤ 44፥23፤51፥11፤60፥9፤ ኤር31፥4፤33፥22፤ ሕ ዝ37፥26፤ዘካ2፥4
30፥20 ዘፀ23፥22፤ ኢሳ54፥13፡14፤ኤር 31፥17፤ዘካ8፥5
30፥21 ቀኑ9፤ዘኍ 16፥5፤ዘዳ17፥15፤ኤር 23፥5-6
30፥22 ዘሌ26፥12፤ ኢሳ19፥25፤ሆሴ2፥23
30፥23 ኤር23፥19
30፥24 ኤር4፥8፡28 ፤23፥19-20፤ሰቆ1፥12
31፥1 ዘሌ26፥12

አምላካቸው እሆናለሁ፤ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ።”

2 *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“ከሰይፍ የተረፈው ሕዝብ፣
በምድረ በዳ ሞገስን ያገኛል፤
እኔም ለእስራኤል ዕረፍት ለመስጠት
እመጣለሁ።”

3 *እግዚአብሔር* ከሩቅ[ዡ] ተገለጠልን፤ እንዲህም አለን፤

“በዘላለማዊ ፍቅር ወድጄሻለሁ፤
ስለዚህም በርኅራኄ ሳብሁሽ።
4 የእስራኤል ድንግል ሆይ፤ እንደ ገና
አንጽሻለሁ፤
አንቺም ትታነጪያለሽ፤
ከበሮችሽንም እንደ ገና አንሥተሽ፣
ከሚፈነጥዙት ጋር ትፈነድቂያለሽ።
5 እንደገናም በሰማርያ ኰረብቶች ላይ፣
ወይን ትተክያለሽ፤
አትክልተኞች ይተክሏቸዋል፤
በፍሬውም ደስ ይላቸዋል።
6 ጠባቂዎች፣ በኤፍሬም ኰረብቶች ላይ፣
‘ኑ፤ ወደ ጽዮን፣
ወደ አምላካችን ወደ *እግዚአብሔር*
እንውጣ!’
ብለው የሚጮኹበት ቀን ይመጣል።

7 *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

“ስለ ያዕቆብ በደስታ ዘምሩ፤
ስለ ሕዝቦች አለቃ እልል በሉ፤
ምስጋናችሁን አሰሙ፤
‘*እግዚአብሔር* ሆይ፤ የእስራኤልን
ቅሬታ፣
ሕዝብህን አድን’ በሉ።
8 እነሆ፤ ከሰሜን ምድር አመጣቸዋለሁ፤
ከምድርም ዳርቻ እሰበስባቸዋለሁ፤
በመካከላቸውም ዕውሮችና አንካሶች፣
ነፍሰ ጡርና በምጥ ላይ ያሉ ሴቶች
ይገኛሉ፤
ታላቅም ሕዝብ ሆነው ይመለሳሉ።
9 እያለቀሱ ይመጣሉ፤
እያጽናናሁ አመጣቸዋለሁ፤
እኔ ለእስራኤል አባት ነኝና፣
ኤፍሬም በኵር ልጄ ነውና፣
በውሃ ምንጭ ዳር፣
በማይሰናከሉበት ቀና መንገድ
እመራቸዋለሁ።

10 “ሕዝቦች ሆይ፤ *የእግዚአብሔርን*
ቃል ስሙ፤
ሩቅ ባሉ የባሕር ጠረፎችም፣
‘እስራኤልን የበተነ እርሱ ይሰበስበዋል፤
መንጋውንም እንደ እረኛ ይጠብቃል’
ብላችሁ ዐውጁ።

31፥2 ዘፀ33፥14፤ ዘኍ14፥20፤ ዘዳ12፥9
31፥3 ዘዳ4፥37፤ ሆሴ 11፥4፤ ዮሐ6፥44
31፥4 ዘፍ31፥27፤ ዘፀ15፥20፤ 2ነገ19፥21፤ ኤር1፥10፤ 30፥18፡19
31፥5 ዘዳ20፥6፤ ኢሳ 37፥30፤ ኤር33፥13፤ 50፥19፤ አሞ9፥14፤ አብ1፥19
31፥6 ቍ12፤ ዘዳ 33፥19፤ ኢሳ52፥8፤ 56፥10፤ ኤር50፥4-5፤ ሚክ 4፥2
31፥7 ዘዳ28፥13፤ መዝ14፥7፤ 28፥9፤ ኢሳ 12፥6፤ 37፥31፤ 61፥9
31፥8 ዘፍ33፥13፤ ዘዳ30፥4፤ መዝ106፥ 47፤ ኢሳ42፥16፤ ኤር 3፥18፤ ሕዝ34፥12-14፡ 16፤ ሚክ4፥6
31፥9 ዘፀ4፥22፤ ዘኍ20፥8፤ ዕዝ3፥12፤ መዝ1፥3፤ 126፥5፤ ኢሳ 32፥2፤ 40፥4፤ 49፥11፤ 63፥13፤ ኤር3፥4
31፥10 ዘሌ26፥33፤ ዘዳ30፥4፤ ኢሳ11፥12፤ 40፥11፤ 49፥1፤ 66፥19፤ ኤር25፥22፤ 50፥19፤ ሕ ዝ34፥12
31፥11 ዘፀ6፥6፤ መዝ142፥6፤ ዘካ9፥16
31፥12 ቍ24፤ ዘኍ 18፥12፤ መዝ36፥8፤ 12 6፥5፤ መሓ4፥15፤ ኢሳ 30፥19፤ 62፥5፤ 65፥10፤ ሕዝ17፥23፤ 20፥40፤ 40፥2፤ ሆሴ2፥21-22፤ ኢል2፥19፤ 3፥18፤ ሚክ 4፥1፤ ዮሐ16፥22፤ ራእ 7፥17
31፥13 መዝ30፥11 ፤ ኢሳ40፥1፤ 51፥11፤ 61፥3
31፥14 ቍ25፤ ዘሌ 7፥35-36፤ መዝ36፥8፤ ኢሳ30፥23
31፥15 ዘፍ37፥35፤ ኢሱ18፥25፤ ኤር10፥ 20፤ ማቴ2፥17-18
31፥16 ሩት2፥12፤ 2ዜና15፥7፤ መዝ30፥5 ፤ ኢሳ25፥8፤ 30፥19፤ ኤር30፥3፤ ሕዝ11፥17
31፥17 ኢዮ8፥7፤ ኤር30፥20፤ ሰቆ3፥29
31፥18 ኢዮ5፥17፤ መዝ80፥3፤ ኤር50፥11 ፤ ሆሴ4፥16፤ 10፥11
31፥19 ዕዝ9፥6፤ መዝ25፥7፤ 95፥10፤ ኤር8፥4፤ 22፥21፤ ሕዝ 36፥31፤ 21፥12፤ ሉቃ 18፥13
31፥20 1ነገ3፥26፤ መዝ6፥2፤ ኢሳ44፥21፤ 55፥7፤ ሰቆ3፥33፤ ሚክ 7፥18

11 *እግዚአብሔር* ያዕቆብን ይዋጀዋልና፤
ከእርሱም ከሚበረቱት እጅ
ይታደገዋልና።
12 መጥተውም በጽዮን ተራራ ላይ በደስታ
ይዘምራሉ፤
*በእግዚአብሔርም* ልግስና፣
በእህሉ፣ በወይን ጭማቂውና በዘይቱ፣
በፍየልና በበግ ጠቦት፣ በወይፈንና
በጊደር ደስ ይሰኛሉ፤
ውሃ እንደማይቋረጥባት የአትክልት ስፍራ
ይሆናሉ፤
ከእንግዲህም አያዝኑም።
13 ኰረዶች ይዘፍናሉ፤ ደስም ይላቸዋል፤
ጐረምሶችና ሽማግሌዎችም ይፈነጥዛሉ፤
ልቅሶአቸውን ወደ ደስታ እለውጣለሁ፤
ከሐዘናቸውም አጽናናቸዋለሁ፤
ደስታንም እሰጣቸዋለሁ።
14 ካህናቱን አትረፍርፌ እባርካለሁ፤
ሕዝቤም በልግስናዬ ይጠግባል፤”
ይላል *እግዚአብሔር*።

15 *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

“ዋይታና መራራ ልቅሶ፣
ከራማ ተሰማ፤
ልጆቿ የሉምና፣
ራሔል አለቀሰች፤
መጽናናትም እንቢ አለች።”

16 *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

“ድምፅሽን ከልቅሶ፣
ዐይኖችሽንም ከእንባ ከልክይ፤
ድካምሽ ያለ ዋጋ አይቀርምና፤”
ይላል *እግዚአብሔር*።
“ከጠላት ምድር ይመለሳሉ፤
17 ስለዚህ ወደ ፊት ተስፋ አለሽ”
ይላል *እግዚአብሔር*።
“ልጆችሽ ወደ ገዛ ምድራቸው
ይመለሳሉ።

18 “የኤፍሬምን የሲቃ እንጕርጕሮ
በእርግጥ ሰምቻለሁ፤
‘እንዳልተገራ ወይፈን ቀጣኸኝ፤
እኔም ተቀጣሁ።
አንተ *እግዚአብሔር* አምላኬ ነህና፣
መልሰኝ፤ እኔም እመለሳለሁ።
19 ከአንተ ከራቅሁ በኋላ፣
ተመልሼ ተጸጸትሁ፤
ባስተዋልሁም ጊዜ፣
ጭኔን መታሁ፣
የወጣትነት ውርደቴን ተሸክሜአለሁና፣
ዐፈርሁ፤ ቀለልሁም።’
20 ኤፍሬም የምወደው፣

ዡ3 *ወይም እግዚአብሔር ከጥንት/ ከቀድሞ ተገለጠልን*

ደስም የምሰኝበት ልጄ አይደለምን?
ብዙ ጊዜ ተቃውሜው ብናገርም፣
መልሼ ስለ እርሱ አስባለሁ፤
አንጀቴ ይላወሳል፤
በታላቅ ርኅራኄም እራራለታለሁ፤”
ይላል እግዚአብሔር።

21“የጐዳና ምልክት አቁሚ፤
መንገድ አመልካች ትከዪ፤
የምትሄጂበትን መንገድ፣
አውራ ጐዳናውን አስተውዪ፤
ድንግሊቱ እስራኤል ሆይ፤ ተመለሺ፤
ወደ ከተሞችሽም ግቢ።
22አንቺ ከዳተኛ ልጅ ሆይ፤
እስከ መቼ ትቅበዘበዣለሽ?
እግዚአብሔር በምድር ላይ አዲስ ነገር
ይፈጥራል፤
ሴት በወንድ ላይ ከበባ ታደርጋለች።[የ]

23የእስራኤል አምላክ የሰራዊት ጌታ
እግ ዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“ምርኮአቸውን በመለስሁላቸው ጊዜ፣[ደ]
እነርሱ በይሁዳ ምድርና በከተሞቿ፣
‘አንተ የጽድቅ ማደ ሪያ ቅዱስ ተራራ
ሆይ፤ እግዚአብሔር ይባ ርክህ!’ የሚል
አነጋገር እንደ ገና ይጠቀማሉ።
24ገበሬዎችና ዘላን ከብት አርቢዎች
በይሁዳና በከተሞቿ በአንድነት ይኖራሉ።
25የዛለችውን ነፍስ ዐድሳለሁ፤ የደከ
መችውንም አበረታለሁ።”

26በዚህ ጊዜ ከእንቅልፌ ነቅቼ ዙሪያዬን
ተመለከትሁ፤ እንቅልፌም ጣፋጭ ሆኖልኝ
ነበር።

27“እነሆ፤ የእስራኤልን ቤትና የይሁዳን
ቤት” ይላል እግዚአብሔር፤ “በሰውና በእ
ንስሳት ዘር የምሞላበት ጊዜ ይመጣል፤
28ልነቅላቸውና ላፈርሳቸው፣
ልገለብጣቸ ውና ላጠፋቸው፣ መከራም
ላመጣባቸው እንደ ተጋሁ ሁሉ፣
ላንጻቸውና ልተክላቸው ደግሞ እተጋለሁ”
ይላል እግዚአብሔር።

29“በዚያ ዘመን ሰዎች ዳግመኛ፣
‘አባቶች በበሉት ጐምዛዛ የወይን ፍሬ፣
የልጆች ጥርስ ጠረሰ’ የሚለውን ምሳሌ
አይናገሩም።

30ነገር ግን፣ እያንዳንዱ በገዛ ኀጢአቱ
ይሞታል፤ ጐምዛዛ የወይን ፍሬ የሚበላ
ሁሉ የራሱን ጥርስ ይጠርሳል።

31“ከእስራኤል ቤትና፣
ከይሁዳ ቤት ጋር” ይላል እግዚአብሔር፤
“አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት፣
ጊዜ ይመጣል።
32ከግብፅ አወጣቸው ዘንድ፣

31፥21 ቍ4፤ኢሳ 35፥8፤52፥11፤ኤር3፥12፤50፥5፤ሕዝ21፥19
31፥22 ዘዳ32፥10፤ ኢሳ43፥19፤ኤር2፥23፤3፥6
31፥23 ዘፍ28፥3፤ ዘኍ6፥24፤መዝ 48፥1፤ኢሳ1፥26፤2፥2፤ ኤር30፥18
31፥24 ቍ12፤ኤር 30፥18፤ዘካ8፥4-8
31፥25 ኢሳ40፥29፤ ዮሐ4፥14
31፥26 ዘካ4፥1
31፥27 ኤር16፥14፤ ሆሴ2፥23
31፥28 ኢዮ29፥2፤ ዘዳ28፥63፤29፥28፤ 30፥9፤ኤር1፥10፤18፥8፤ሕዝ36፥10-11፤ አሞ9፥14
31፥29 ዘፍ9፥25፤ ዘዳ24፥16፤ሰቆ5፥7፤ ሕዝ18፥2
31፥30 2ነገ14፥6፤ ኢሳ3፥11፤ገላ 6፥7
31፥31 ዘዳ29፥14፤ ኢሳ42፥6፤54፥10፤ ሉቃ22፥20፤ዕብ 8፥8-12፤10፥16-17
31፥32 ዘፀ24፥8፤ ዘዳ5፥3፤ኤር11፥4
31፥33 ዘፀ4፥15፤ ዘዳ6፥6፤ኤር 11፥4፤ 2ቆሮ3፥3፤ዕብ10፥16
31፥34 ኢዮ7፥21፤ ኢሳ11፥9፤38፥17፤ መዝ85፥2፤130፥4፤ ኤር33፥8፤50፥20፤ሚክ7፥19፤ዮሐ6፥45፤ዕብ10፥17፤1ዮሐ2፥27
31፥35 ዘፍ1፥16፤ ዘፀ14፥21፤መዝ93፥3፤ 136፥7-9፤ኤር10፥16
31፥36 ኢዮ38፥33፤ መዝ89፥36-37፤ኤር 33፥20-26
31፥37 ኢዮ38፥5፤ ኤር33፥22፡24-26፤ ሮሜ11፥1-5
31፥38 2ነገ14፥13፤ 2ዜና25፥23፤ነህ3፥1፤ ኤር30፥18
31፥39 1ነገ7፥23
31፥40 2ሳሙ15፥23፤2ነገ11፥16፤ኢሳ 4፥3፤ኤር2፥23፤7፥31-32፤8፥2፤ኢል3፥17፤ ዘካ14፥21፤ዮሐ18፥1

እጃቸውን ይዤ በመራኋቸው ጊዜ፣
ከአባቶቻቸው ጋር እንደገባሁት ኪዳን
አይደለም፤[ጀ]
የእነርሱ ባል[ገ] ሆኜ ሳለሁ፣
ቃል ኪዳኔን አፍርሰዋልና።”
ይላል እግዚአብሔር።
33“ነገር ግን ከዚያ ጊዜ በኋላ፣
ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ኪዳን
ይህ ነው” ይላል እግዚአብሔር፤
“ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፤
በልባቸውም እጽፈዋለሁ።
እኔ አምላክ እሆናቸዋለሁ፤
እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ።
34ከእንግዲህ ማንም ሰው ባልንጀራውን፣
ወይም ወንድሙን፣ ‘እግዚአብሔርን
ዕወቅ’ ብሎ አያስተምርም፤
ከትንሹ ጀምሮ እስከ ትልቁ፣
ሁሉም እኔን ያውቁኛልና፤”
ይላል እግዚአብሔር።
“በደላቸውን ይቅር እላለሁ፤
ኀጢአታቸውንም መልሼ አላስብም።”

35በቀን እንድታበራ፣
ፀሓይን የመደበ፣
በሌሊት እንዲያበሩ፣
ጨረቃንና ከዋክብትን ያዘዛቸው፣
የሞገዱ ድምፅ እንዲተምም፣
ባሕሩን የሚያናውጥ፣
ስሙ የሰራዊት ጌታ የሆነ፣
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
36“ይህ ሥርዐት በፊቴ ከተሻረ፣”
ይላል እግዚአብሔር፤
“በዚያ ጊዜ የእስራኤልም ዘር በፊቴ፣
መንግሥት መሆኑ ለዘላለም ይቀራል።”
37እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“በላይ ያሉትን ሰማያትን መለካት፣
በታችም ያሉትን የምድር መሠረቶች
መመርመር ከተቻለ፣
በዚያ ጊዜ የእስራኤልን ዘር ሁሉ፣
ስላደረጉት ነገር ሁሉ እጥላቸዋለሁ፤”
ይላል እግዚአብሔር።

38“እነሆ ከሐናንኤል ግንብ ጀምሮ እስከ
ማእዘኑ በር ድረስ” ይላል እግዚአብሔር፤
“ይህች ከተማ ለእግዚአብሔር የምትሠራ
በት ጊዜ ይመጣል፤ 39መለኪያ ገመዱም
ከዚያ ጀምሮ በቀጥታ ወደ ጋሬብ ኰረብታ፣
አልፎም ወደ ጎዓ ይዞረጋል። 40ሬሳና ዐመድ
የሚጣልበት ሸለቆ በሙሉ፣ በምሥራቅ በኩል
የቄድሮንን ሸለቆ ይዞ እስከ ፈረስ በር

[የ]22 ወይም መፈለግ ትጀምራለች ወይም መጠበቅ ትጀምራለች
[ደ]23 ወይም ዕድል ፈንታቸውን በመለስኩላቸው
[ጀ]32 የዕብራይስጡ፣ የሰብዓ ሊቃናትና የሱርስት ትርጕሞች እኔም ዘወር አልሁባቸው ይላሉ።
[ገ]32 ወይም የእነርሱ ጌታ

የሚደርሰው ደልዳላ ቦታ ሁሉ *ለእግዚ
አብሔር* የተቀደሰ ይሆናል፤ ከእንግዲህም
ከተማይቱ አትነቀልም፤ አትፈርስምም::"

## ኤርምያስ የዕርሻ ቦታ መግዛቱ

32 የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ በነገሠ
በዐሥረኛው ዓመት፣ ይኸውም
በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነፆር ዐሥራ ስም
ንተኛ ዘመነ መንግሥት፣ *ከእግዚአብሔር*
ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣው ቃል ይህ
ነው፤ 2በዚያን ጊዜም የባቢሎን ንጉሥ
ሰራዊት ኢየሩሳሌምን ከቦ ነበር፤ ነቢዩ
ኤርምያስም በይሁዳ ንጉሥ ቤተ መንግሥት
በዘብ ጠባቂዎች አደባባይ ተዘግቶበት
ነበር::

3የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስም እንዲህ
በማለት አሳስሮት ነበር፤ "እንዴት እንደ
ዚህ ያለ ትንቢት ትናገራለህ? '*እግዚአ
ብሔር፤* "ይህችን ከተማ ለባቢሎን ንጉሥ
አሳልፌ እሰጣታለሁ፤ እርሱም ይይዛታል::
4የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስም ለባቢሎን
ንጉሥ ዐልፎ ይሰጣል፤ ፊት ለፊትም
ያነጋግረዋል፤ በዐይኖቹም ያየዋል እንጂ
ከባቢሎናውያን[ጠ] እጅ አያመልጥም:: 5ሴዴ
ቅያስንም ወደ ባቢሎን ይወስደዋል፤ በፍ
ርዴ እስከምጐበኘውም ድረስ በዚያ ይቈ
ያል፤ ይላል *እግዚአብሔር፤* ከባቢሎናውያን
ጋር ብትዋጉ አይሳካላችሁም" ይላል' ትላ
ለህ::"

6ኤርምያስም *የእግዚአብሔር* ቃል ወደ
እኔ እንዲህ ሲል መጣ አለ:- 7"የአጎትህ
የሰሎም ልጅ አናምኤል ወደ አንተ መጥቶ፣
'የመቤዠት መብት የአንተ ስለሆነ፣ በዓ
ናቶት ያለውን መሬቴን ግዛኝ' ይልሃል::"

8*እግዚአብሔርም* እንደ ተናገረኝ፣ የአጎቴ
ልጅ አናምኤል ወደ ዘብ ጠባቂዎቹ አደ
ባባይ መጥቶ፣ "የመቤዠቱን ርስት የማ
ድረጉ መብት የአንተ ስለ ሆነ፣ በብንያም
አገር በዓናቶት ያለውን መሬቴን ለራስህ
እንዲሆን ግዛው" አለኝ:: ይህም *የእግዚ
አብሔር* ቃል እንደ ሆነ ዐወቅሁ፤ 9ስለዚህ
በዓናቶት ያለውን መሬት ከአጎቴ ልጅ
ከአናምኤል ገዛሁ፤ ዐሥራ ሰባት ሰቅል[ጪ]
ብር መዝኜ ሰጠሁት:: 10በውሉም ሰነድ
ላይ ፈረምሁ፤ አሸግሁትም:: ብሩንም
በምስክሮች ፊት በሚዛን መዘንሁለት::
11የስምምነቱ ዝርዝር ያለበትን፣ የታሸገው
ንና ያልታሸገውን የግዢውን የውል ሰነድ
ወሰድሁ፤ 12በአጎቴም ልጅ በአናምኤልና
በውሉ ላይ በፈረሙት ምስክሮች ፊት እን
ዲሁም በዘብ ጠባቂዎች አደባባይ ተቀ
ምጠው በነበሩ አይሁድ ሁሉ ፊት ለመሕ

32÷1 2ነገ25÷1፤ ኤር25÷1
32÷2 2ነገ25÷1፤ ነህ3÷25፤መዝ 88÷8
32÷3 ቀኍ28፤ኤር 21÷4፤26÷8-9፤ 34÷2-3
32÷4 ቀኍ24፤ኤር 21÷7፤34÷21፤38÷18፡23፤39÷5-7፤44÷30፤ 52÷9
32÷5 2ነገ25÷7፤ ኤር21÷4፤39÷7፤ሰቆ 1÷14፤ሕዝ12÷13
32÷7 ዘሌ25÷24-25፤ሩት4÷3-4፤ኢሱ 21÷18፤ማቴ27÷10
32÷8 ቀኍ25
32÷9 ዘፍ23÷16፤ ኤር37÷12
32÷10 ዘፍ23÷20፤ሩት4÷9፤ኢሳ8÷2
32÷12 ቀኍ16፤ኤር 36÷4፤43÷3፡6፤ 45÷1፤51÷59
32÷14 ኢሳ8÷16
32÷15 ቀኍ43-44፤ ኢሳ44÷26፤ኤር30÷18፤ሕዝ28÷26፤አሞ 9÷14-15
32÷16 ቀኍ12
32÷17 ዘፍ1÷1፤ዘዳ 9÷29፤2ነገ3÷18፤ 19÷15፤መዝ102÷25፤ኤር1÷6፤10÷16፤ 51÷15፤ማቴ19÷26
32÷18 ዘፀ20÷5፤ዘዳ 5÷10፤መዝ79÷12፤10 9÷14፤ኤር10÷6፡16
32÷19 ኢዮ12÷13፤ 14÷16፤34÷11፤ምሳ 5÷21፤ኤር16÷17፤ ዳን2÷20፤ማቴ16÷27
32÷20 ዘፀ3÷20፤ 9÷16፤ኢዮ9÷10፤ኢሳ 55÷13፤ኤር13÷11
32÷21 ዘፀ6÷6፤ዘዳ 5÷15፤26÷8፤ኤር 6÷12፤ዳን9÷15
32÷22 ዘፀ3÷8፤ሕዝ 20÷6
32÷23 ዘፀ16÷28፤ ዘዳ28÷64፤31÷29፤ ኢሱ1÷7፤1ነገ9÷6፤ መዝ44÷2፤78÷54-55፤ኤር11÷8፤ዳን9÷14
32÷24 ዘዳ4÷25-26፤28÷2፤ኢሱ23÷15-16፤ 2ሳሙ20÷15፤ ኤር6÷6፤14÷12
32÷25 ቀኍ8፤ኢሳ 8÷2

ሢያ ልጅ ለኔርያ ልጅ ለባሮክ ሰጠሁት::
13በእነርሱ ፊት ለባሮክ እንዲህ የሚል
ትእዛዝ ሰጠሁት፤ 14"የእስራኤል አምላክ
የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
'የታሸገውንና ያልታሸገውን፣ ሁለቱን የግዢ
ውል ሰነዶች ለብዙ ጊዜ ሳይበላሹ እንዲ
ቈዩ ወስደህ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አኑራ
ቸው:: 15የእስራኤል አምላክ የሰራዊት
ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላልና፤
ሰዎች በዚህ ምድር ቤት፣ የዕርሻ ቦታና
የወይን አትክልት ስፍራ እንደገና
ይገዛሉ::' "

16"ለኔርያ ልጅ ለባሮክ የግዢ ውሉን
ከሰጠሁ በኋላ፣ ወደ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ብዬ ጸለይሁ፤

17"አቤት፣ ጌታ *እግዚአብሔር* ሆይ፤
አንተ ሰማያትንና ምድርን በታላቅ ኀይ
ልህና በተዘረጋች ክንድህ ፈጥረሃል፤ የሚሳ
ንህም አንዳች ነገር የለም:: 18ፍቅርና
ቸርነትን ለእልፍ አእላፍ ታሳያለህ፤ ይሁን
እንጂ የአባቶችን በደል ከእነርሱ በኋላ
በሚነሡ ልጆቻቸው ጒያ ትመልሳለህ፤
ስምህ የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* የሆነ፣
ታላቅና ኀያል አምላክ ሆይ፤ 19ዕቅድህ
ታላቅ፣ በሥራም ብርቱ ነህ፤ ዐይኖችህ
የሰው ልጆችን መንገዶች ሁሉ ያያሉ፤
ለእያንዳንዱም እንደ መንገዱና እንደ
ሥራው ትከፍለዋለህ:: 20በግብፅ ታምራ
ትንና ድንቆችን አደረግህ፤ እስከ ዛሬም
ድረስ በእስራኤልና በሰው ልጆች ሁሉ
መካከል እንደዚያው እያደረግህ ዛሬም
ስምህ ገናና ነው:: 21በታምራትና በድንቅ፣
በብርቱ እጅና በተዘረጋች ክንድ፣ እጅግ
በሚያስፈራም ግርማ ሕዝብህን እስራኤ
ልን ከግብፅ አወጣህ:: 22ለአባቶቻችን ልት
ሰጣቸው የማልህላቸውን፣ ማርና ወተት
የምታፈሰውን ይህችን ምድር ሰጠሃቸው፤
23ወደዚያም ገብተው ወረሷት፤ ነገር ግን
አልታዘዙህም፤ ሕግህንም አልጠበቁም፤
እንዲያደርጉት ያዘዝሃቸውን ከቶ አላደረ
ጉም፤ ስለዚህ ይህን ሁሉ ጥፋት በላያ
ቸው አመጣህ::

24"እነሆ፤ ከተማዪቱን ለመያዝ የዐፈር
ድልድል በዙሪያዋ ተሠርቶአል፤ ከሰይፍ፣
ከራብና ከቸነፈር የተነሣ ከተማዪቱን
ለሚወጓት ለባቢሎናውያን ዐልፋ ልትሰጥ
ነው፤ እንደምታየውም የተናገርኸው እየተ
ፈጸመ ነው:: 25አንተ ግን ጌታ *እግዚአ
ብሔር* ሆይ፤ ከተማዪቱ ለባቢሎናውያን
አልፋ እየተሰጠች፣ 'መሬቱን በብር ግዛ፤
ግዢውንም በምስክሮች ፊት ፈጽም' ትለ
ኛለህ::"

[ጠ]4 ወይም *ከለዳውያን፤* በቍ5፡24፡25፡28፡29፡እና 43 ይመ::
[ጪ]9 200 ግራም ያህል ነው::

[26]ከዚያም በኋላ *የእግዚአብሔር* ቃል
ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፤ [27]"እነሆ፤
እኔ የሰው ልጆች ሁሉ አምላክ *እግዚአብሔር*
ነኝ፤ በውኑ የሚያቅተኝ ነገር አለን? [28]ስለዚህ
*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ እነሆ፤ ይህቺን
ከተማ ለባቢሎናውያንና ለባቢሎን ንጉሥ
ለናቡከደናፆር አሳልፌ እሰጣታለሁ፤ እር
ሱም ይይዛታል። [29]ከተማዪቱን የሚወጓት
ባቢሎናውያን ወደ ውስጥ ይገባሉ፤ በእሳ
ትም ያቃጥሏታል፤ ያስቈጡኝ ዘንድ ሕዝቡ
በየሰገነቱ ላይ ለበኣል ያጠኑባቸውንና ለሌ
ሎችም አማልክት የመጠጥ ቍርባን ያቀ
ረቡባቸውን ቤቶች ጭምር ያነዳሉ።
[30]"የእስራኤል ሕዝብና የይሁዳ ሕዝብ
ከታናሽነታቸው ጀምሮ ከክፉ ነገር በቀር
በፊቴ አንዳች በጎ ነገር አልሠሩም፤ በእ
ርግጥም የእስራኤል ሕዝብ በእጃቸው
ሥራ አስቈጡኝ፤ ይላል *እግዚአብሔር*።
[31]ይህች ከተማ፣ ከተመሠረተችበት ጊዜ
አንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ ከፊቴ እንዳስወግ
ዳት ቍጣዬንና መዓቴን አነሣሥታለች፤
[32]የእስራኤልና የይሁዳ ሕዝብ፦ እነርሱ፣
ነገሥታታቸው፣ ባለሥልጣኖቻቸው፣ ካህና
ታቸው፣ ነቢያታቸው፣ የይሁዳ ሰዎችና
የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ባደረጉት ክፉት
ሁሉ አስቈጡኝ። [33]ፊታቸውን ሳይሆን ጀር
ባቸውን ሰጡኝ፤ ደጋግሜ ባስተምራቸውም
አይሰሙም፤ ተግሣጽም አይቀበሉም። [34]ስሜ
በተጠራበት ቤት አስጸያፊ ጣዖታቸውን
አቆሙ፤ አረከሱትም። [35]ወንዶችና ሴቶች[ጸ]
ልጆቻቸውን ለሞሌክ ይሠው ዘንድ በሄ
ኖም ሸለቆ ለበኣል መስገጃ ኰረብቶችን
ሠሩ፤ ነገር ግን ይሁዳን ኀጢአት ለማሠ
ራት እንደዚህ ያለውን አስጸያፊ ተግባር
እንዲፈጽሙ እኔ አላዘዝሁም፤ ከቶም አላሰ
ብሁም።
[36]" 'በሰይፍ፣ በራብና በቸነፈር ለባቢ
ሎን ንጉሥ ዐልፋ ትሰጣለች' ስላልሃት
ስለዚህች ከተማ፣ የእስራኤል አምላክ
*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ [37]"በጽኑ
ቍጣዬና በታላቅ መቅሠፍቴ እነርሱን
ካሳደድሁበት ምድር ሁሉ በእውነት
እሰበስባቸዋለሁ፤ ወደዚህም ስፍራ
እመልሳቸዋለሁ፤ በሰላ ምም እንዲቀመጡ
አደርጋቸዋለሁ። [38]እነ ርሱ ሕዝብ
ይሆኑኛል፤ እኔም አምላክ እሆ ናቸዋለሁ።
[39]ለእነርሱና ከእነርሱም በኋላ ለልጆቻቸው
መልካም እንዲሆንላቸው ዘወ ትር
ይፈሩኝ ዘንድ፣ አንድ ልብ አን ድም ሐ
ሳብ እሰጣቸዋለሁ። [40]መልካምን ነገር
ለእነርሱ ከማድረግ እንዳልቈጠብና
ከእኔም ፈቀቅ እንዳይሉ መፈራቴን በውስ
ጣቸው ላኖር ከእነርሱ ጋር የዘላለም ቃል
ኪዳን እገባለሁ። [41]ለእነርሱ መልካም በማ
ድረግ ደስ ይለኛል፤ በፍጹም ልቤና በፍ
ጹም ነፍሴ በእውነት በዚህች ምድር እተ
ክላቸዋለሁ።' "
[42]"*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ 'በዚህ
ሕዝብ ላይ ይህን ሁሉ ታላቅ ጥፋት እን
ዳመጣሁ እንደዚሁ ቃል የገባሁላቸውን
መልካም ነገር ሁሉ እሰጣቸዋለሁ። [43]እናን
ተም፣ "ለባቢሎናውያን ዐልፋ ስለ ተሰጠች፣
ሰውና እንስሳ የማይኖሩባት ባድማ ናት"
ባላችኋት በዚህች ምድር እንደ ገና መሬት
ይገዛል። [44]ምርኮአቸውን ስለምመልስላቸው
[ጸ]
በብንያም አገር፣ በኢየሩሳሌም ዙሪያ ባሉ
መንደሮች፣ በይሁዳ ከተሞችና በተራራ
ማው አገር ከተሞች፣ በምዕራብ ተራሮች
ግርጌና በኔጌብ ባሉ ከተሞች መሬት በጥሬ
ብር ይገዛል፤ ውሉም ተፈርሞ፤ በምስክሮች
ፊት ይታሸጋል፤ ይላል *እግዚአብሔር*።' "

## የመመለስ ተስፋ

33 ኤርምያስ በዘብ ጠባቂዎች አደ
ባባይ በግዞት ሳለ *የእግዚአብሔር*
ቃል እንዲህ ሲል ዳግመኛ ወደ እርሱ
መጣ፦ [2]"ምድርን የፈጠራት፣ ያበጃትና
የመሠረታት *እግዚአብሔር*፣ ስሙ *እግዚ
አብሔር* የሆነ፣ እርሱ እንዲህ ይላል፤
[3]'ወደ እኔ ጩኽ፤ እኔም እመልስልሃለሁ፤
አንተም የማታውቀውን ታላቅና የማይመረ
መር ነገር እገልጥልሃለሁ፤' [4]የእስራኤል
አምላክ *እግዚአብሔር* ከባቢሎናውያን[ፀ] ጋር
ባለው ውጊያ፣ ዐፈር በመደልደልና
በሰይፍ የሚደረገውን ጥቃት ለመከላከል
ስለ ፈረ ሱት ስለዚህች ከተማ ቤቶችና
ስለ ይሁዳ ነገሥታት ቤተ መንግሥት
እንዲህ ይላል፤ [5]'እነዚህ በቍጣዬና በመዓ
ቴ በምገድ ላቸው ሰዎች ሬሳ ይሞላሉ፤
ስለ ክፉቷ ሁሉ ከዚህች ከተማ ፊቴን
እሰውራለሁ።
[6]" 'ይሁን እንጂ፣ ፈውስንና ጤንነትን
እንደገና እሰጣታለሁ፤ ሕዝቤንም እፈውሳ
ለሁ፤ በብዙ ሰላምና በርጋታ እንዲኖሩ
አደርጋለሁ። [7]የይሁዳን ምርኮና የእስራ
ኤልን ምርኮ እመልሳለሁ፤[ፊ] ቀድሞ እንደ
ነበሩት ሁኔታ አድርጌ አበጃቸዋለሁ፤ [8]እኔን
ከበደሉበት ኀጢአት ሁሉ አነጻቸዋለሁ፤
በእኔ ላይ ያመፁበትንም ኀጢአታቸውን
ሁሉ ይቅር እላለሁ። [9]ይህች ከተማ፣ ለእርሷ
ያደረግሁትን በጎ ነገር ሁሉ በሚሰሙት
የምድር ሕዝቦች ሁሉ ፊት ለዝና፣ ለደስታ፣
ለምስጋናና ለክብር ትሆናለች፤ ከምሰጣትም

32፥27 ዘፍ18፥14፤ ዘኍ16፥22፤2ነገ3፥18
32፥28 ቍ3፤2ዜና 36፥17፤ ኤር21፥10
32፥29 2ዜና36፥19 ፤ኤር7፥9፤19፥13፤44፥18
32፥30 መዝ25፥7፤ ኤር8፥19፤22፥21፤25፥7
32፥31 1ነገ11፥7-8 ፤2ነገ21፥4-5፤23፥27፤ ማቴ23፥37
32፥32 1ነገ14፥9፤ ኤር2፥26፤ 44፥9፤ ዳን9፥8
32፥33 ዘዳ4፥5፤ 1ነገ14፥9፤መዝ14፥3 ፤ኢሳ28፥9፤ኤር2፥27፤ 7፥13፥28፤ሕዝ8፥16፤ ዘካ7፥11
32፥34 2ነገ21፥4፤ ኤር7፥10፤7፥30፤ 34፥15፤ሕዝ 8፥3-16
32፥35 ዘሌ18፥21፤ 1ነገ14፥24፤ኤር19፥5፤ 25፥7
32፥36 ቍ24
32፥37 ዘሌ25፥18፤ ኢሳ11፥12፤21፥5፤ ሕዝ34፥28፤39፥26
32፥38 ኤር24፥7፤ 2ቆሮ6፥16
32፥39 ዘዳ6፥24፤ 10፥16፤2ዜና30፥12፤ መዝ86፥11፤ዮሐ 17፥21፤ሐሥ4፥32
32፥40 ዘፍ9፥16፤ ዘዳ4፥10፤ኢሳ42፥6፤ ኤር24፥7
32፥41 ዘዳ28፥3-12 ፥63፤ኢሳ62፥4፤ኤር 24፥6፤31፥28፤ሚክ 7፥18
32፥42 ኤር29፥10፤ ሰቆ3፥38
32፥43 ቍ15፤ኤር 33፥12
32፥44 ቍ10፤ሩት 4፥9፤ዕዝ9፥9፤መዝ 14፥7፤ኢሳ8፥2፤ኤር 17፥26
33፥1 መዝ88፥8፤ኤር 13፥3፤37፥21፤38፥28
33፥2 ዘፀ3፥15፤መዝ 136፥6፤ኤር10፥16
33፥3 ኢዮ28፥11፤ ኢሳ55፥6
33፥4 2ነገ25፥1፤ ኤር32፥24፤ሕዝ4፥2፤ 26፥8፤ዕን1፥10
33፥5 ዘዳ31፥17፤ ኢ ሳ8፥17፤ኤር21፥4-7
33፥6 ዘዳ32፥39፤ ኢ ሳ9፥6፤30፥26
33፥7 ኢሳ1፥26፤ ኤር24፥6፤30፥3፤ 32፥44፤ሕዝ39፥25፤ አሞ 9፥14
33፥8 ዘሌ16፥30፤ 2ሳሙ24፥14፤ኤር 31፥34፤ዕብ 9፥13-14
33፥9 ኢሳ55፥13፤

[ጸ]35 ወይም *ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን በእሳት ያሳልፉ ዘንድ*
[ጸ]44 ወይም *ከምርኮ ስለምመልሳቸው*
[ፀ]4 ወይም *ከለዳውያን*
[ፊ]7 ወይም *ይሁዳንና እስራኤልን ከምርኮ እመልሳለሁ*

የተትረፈረፈ ብልጽግናና ሰላም የተነሣ ይፈ
ራሉ፤ ይንቀጠቀጣሉም፡፡’
10“እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ይህ
ችን ስፍራ፣ ‘ሰውና እንስሳት የማይኖሩባት
ባድማ ናት’ ትላላችሁ፤ ነገር ግን ሰውም
ሆነ እንስሳ ባልነበሩባቸውና ባድማ በሆ
ኑት በይሁዳ ከተሞችና በኢየሩሳሌም መን
ገዶች፣ እንደ ገና ድምፅ ይሰማል፤ 11የሐ
ሤትና የደስታ ድምፅ፣ የሙሽራውና የሙ
ሽራዪቱ ድምፅ፣ እንዲሁም፦

“እግዚአብሔር ቸር ነውና፤
ምሕረቱም ለዘላለም ነውና፤
የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔርን
አመስግኑ፤”

የሚል የምስጋናን መሥዋዕት ይዘው
ወደ እግዚአብሔር ቤት የሚመጡ ሰዎች
ድምፅ ይሰማል፤ የምድሪቱን ምርኮ ቀድሞ
እንደ ነበረ እመልሳለሁና፤ ይላል እግዚ
አብሔር፡፡
12“የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤ ‘ሰውም ሆነ እንስሳት በማይኖሩ
በት በዚህ ባዶ ስፍራ፣ በከተማዎቹም
ሁሉ እረኞች መንጎቻቸውን የሚያሳርፉበት
እንደ ገና ያገኛሉ፡፡ 13በተራራማው አገር፣
በምዕራብ ተራሮች ግርጌና በኔጌብ ባሉ
ከተሞች በብንያም አገር፣ በይሁዳ ከተ
ሞች እንዲሁም በኢየሩሳሌም ዙሪያ ባሉ
መንደሮች መንጎች እንደ ገና በሚቈጥራ
ቸው ሰው እጅ ሥር ያልፋሉ’ ይላል እግ
ዚአብሔር፡፡
14“ ‘ለእስራኤል ቤትና ለይሁዳ ቤት
የገባሁትን የተስፋ ቃል የምፈጽምበት
ጊዜ ይመጣል’ ይላል እግዚአብሔር፡፡

15“ ‘በዚያ ዘመንና በዚያ ጊዜ፣
ከዳዊት ቤት ጽድቅ ቅርንጫፍ
አበቅላለሁ፤
በምድሪቱም ፍትሕንና ጽድቅን
ያደርጋል፡፡
16በዚያ ዘመን ይሁዳ ይድናል፤
ኢየሩሳሌም በሰላም ትኖራለች፤
የምትጠራበትም ስም፣
“እግዚአብሔር ጽድቃችን” የሚል
ይሆናል፡፡’

17እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፤ ‘ከዳ
ዊት ዘር በእስራኤል ቤት ዙፋን ላይ የሚ
ቀመጥ ሰው ፈጽሞ አይታጣም፤ 18ሌዋው
ያን ከሆኑት ካህናትም የሚቃጠል መሥ
ዋዕት ለማቅረብ፣ የእህል ቍርባን ለማ
ቃጠልና ሌላውንም መሥዋዕት ለመሠ
ዋት ሁል ጊዜ በፊቴ የሚቆም ሰው አይ
ታጣም፡፡’ ”
19የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤርምያስ
እንዲህ ሲል መጣ፤ 20“እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤ ‘ለቀንና ለሌሊት የወሰንሁትን
ሥርዐት በማፍለስ ቀንና ሌሊት በተወሰ
ነላቸው ጊዜ እንዳይፈራረቁ ኪዳኔን ማፍ
ረስ ብትችሉ፣ 21በዚያ ጊዜ ከአገልጋዬ
ከዳዊት ጋር የገባሁትን ኪዳን፣ እንዲሁም
በፊቴ በክህነት ከሚያገለግሉት ሌዋውያን
ጋር የገባሁትን ኪዳን ማፍረስ ይቻላል፤
ዳዊትም ከእንግዲህ በዙፋኑ ላይ የሚነ
ግሥ ዘር አይኖረውም፡፡ 22የአገልጋዬን የዳ
ዊትን ዘር እንዲሁም በፊቴ የሚቆሙትን
ሌዋውያን እንደማይቈጠሩ እንደ ሰማይ
ከዋክብትና እንደማይሰፈር የባሕር አሸዋ
አበዛቸዋለሁ፡፡’ ”
23የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤርምያስ
እንዲህ ሲል መጣ፤ 24“ይህ ሕዝብ፣ ‘እግ
ዚአብሔር፣ የመረጣቸውን ሁለቱን መንግ
ሥታት[ፐ] ጥሎአል’ እንደሚሉ አላስተዋል
ህምን? ሕዝቤን ንቀዋል፤ እንደ ሕዝብም
አልቈጠሯቸውም፡፡ 25እግዚአብሔር እን
ዲህ ይላል፤ ‘የቀንና የሌሊት ኪዳኔን፣ የሰ
ማይንና የምድርንም ሥርዐት ያጸናሁ እኔ
ካልሆንሁ፣ 26የያዕቆብንና የአገልጋዬን የዳ
ዊትን ዘር እጥላለሁ፤ ከልጆቹም በአብር
ሃም፣ በይስሐቅና በያዕቆብ ዘር ላይ ገዥ
እንዲሆኑ አልመርጥም፤ ይህንም የምለው
ምርኮአቸውን ስለምመልስና[ሀ] ስለምራራ
ላቸው ነው፡፡’ ”

## ለሴዴቅያስ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

34 የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደናፆርና
ሰራዊቱ ሁሉ፣ በግዛቱም ሥር
ያሉ መንግሥታትና ሕዝቦች ሁሉ ኢየሩ
ሳሌምንና በአካባቢዋ የሚገኙትን ከተሞች
ይወጉ በነበረ ጊዜ፣ እንዲህ የሚል ቃል
ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ኤርምያስ
መጣ፤ 2“የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤ ወደ ይሁዳ ንጉሥ ወደ
ሴዴቅያስ ሂደህ እንዲህ ብለህ ንገረው፤
‘እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ይህችን ከተማ
ለባቢሎን ንጉሥ አሳልፌ ልሰጣት ነው፤
እርሱም በእሳት ያቃጥላታል፤ 3አንተም
በእርግጥ ትያዛለህ ዐልፈህም ለእርሱ ትሰ
ጣለህ እንጂ ከእጁ አታመልጥም፡፡ የባቢ
ሎንን ንጉሥ በዐይኖችህ ታየዋለህ፤ ፊት
ለፊትም ያነጋግርሃል፤ ወደ ባቢሎንም
ትሄዳለህ፡፡
4“ ‘ነገር ግን፣ የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ
ሆይ፤ የእግዚአብሔርን ቃል ስማ፤ እግዚ

[ፐ]24 ወይም ወገን [ሀ]26 ወይም ከምርኮ እመልሳቸዋለሁ

60፥18፤64፥2፤ኤር 3፥17
33፥10 ዘሌ26፥32፤ ኤር9፥11፤32፥43
33፥11 ዘሌ7፥12፤ 1ዜና16፥34፤2ዜና5፥13፤7፥3፤መዝ25፥8፤51፥8፤100፥4-5፤136፥1፤ኢሳ1፥26፤24፥8፤51፥3፤ናሆ1፥7፤14፥7
33፥12 ቊ10፤ኢሳ 65፥10፤ኤር32፥43፤ ሕዝ34፥11-15
33፥13 ዘሌ27፥32፤ ኤር17፥26፤31፥5፤ አብ1፥20
33፥14 ዘዳ28፥1-14፤ኢሱ23፥15፤ኤር 29፥10
33፥15 2ሳሙ7፥12፤መዝ72፥2፤ኢሳ4፥2
33፥16 ኢሳ45፥17፤ 59፥14፤ኤር3፥17፤ 17፥25፤32፥37፤ሕዝ 48፥35፤ሶፎ3፥13፤ዘካ 8፥3፥16፤1ቆሮ1፥30
33፥17 2ሳሙ7፥13፤2ዜና7፥18፤መዝ 89፥29-37፤ ሉቃ 1፥33
33፥18 ዘኍ25፥11-13፤ዘዳ18፥1፤ዕን 13፥15፤ዕብ7፥17-22
33፥20 ዘፍ1፥14፤ መዝ89፥36
33፥21 ዘዳ18፥1፤ 2ሳሙ7፥13፤2ዜና 7፥18፤መዝ 9፥34
33፥22 ዘፍ12፥2፤ ኤር30፥19፤ሆሴ1፥10
33፥24 ነህ4፥4፤ኤር 30፥17፤ሕዝ36፥20፤ 37፥22
33፥25 ዘፍ1፥8፤ መዝ74፥16-17፤ 148፥6
33፥26 ቊ7፤ዘሌ 26፥44፤መዝ14፥7፤ ኢሳ14፥1፤ኤር30፥18
34፥1 2ነገ25፥1፤ ኤር27፥7፤39፥1
34፥2 ቊ22፤2ዜና 36፥11፤ኤር32፥29፤ 37፥8
34፥3 2ነገ25፥7፤ ኤር21፥7
34፥4 ኤር52፥11

*አብሔር* ስለ አንተ እንዲህ ይላል፤ በሰ
ይፍ አትሞትም፤ [5]በሰላም ትሞታለህ።
ሕዝቡ ከአንተ በፊት ለነበሩት ነገሥታት
አባቶችህ ክብር በቀብራቸው ጊዜ እሳት
እንዳነደዱ፣ በቀብርህም ጊዜ ስለ ክብርህ
እሳት ያነዳሉ፤ “ዋይ ዋይ ጌታችን!” እያ
ሉም ያለቅሱልሃል፤ እኔ ራሴ ይህን ቃል
ተናግሬአለሁና፤ ይላል *እግዚአብሔር*።’ ”
[6]ነቢዩ ኤርምያስ ይህን ሁሉ ለይሁዳ
ንጉሥ ለሴዴቅያስ በኢየሩሳሌም ነገረው፤
[7]በዚህም ጊዜ የባቢሎን ንጉሥ ሰራዊት ኢ
የሩሳሌምንና የቀሩትን የይሁዳ ከተሞች
ለኪሶንና ዓዜቃን እየወጋ ነበር፤ ከተመ
ሸጉት የይሁዳ ከተሞችም የቀሩት እነዚሁ
ብቻ ነበሩና።

## የባሪያዎች ነጻ አለመውጣት

[8]ንጉሡ ሴዴቅያስ ባሪያዎችን ነጻ ለማ
ውጣት ከኢየሩሳሌም ሕዝብ ሁሉ ጋር
ቃል ኪዳን ካደረገ በኋላ፣ *የእግዚአብሔር*
ቃል ወደ ኤርምያስ መጣ። [9]እያንዳንዱ
ሰው፣ ዕብራዊ የሆነውን ወንድ ባሪያውንና
ዕብራዊት የሆነችውን ሴት ባሪያውን ነጻ
ማውጣት ነበረበት፤ ማንም ሰው አይሁዳዊ
ወንድሙን በባርነት መግዛት አልነበረበ
ትም። [10]በዚህ ቃል ኪዳን የተስማሙት
ባለሥልጣኖችና ሕዝቡ ሁሉ ወንድ ወይም
ሴት ባሪያዎቻቸውን ነጻ ለመልቀቅና ከእ
ንግዲህ ባሪያ አድርገው ላይገዟቸው ተስ
ማሙ። [11]በኋላ ግን ሐሳባቸውን ቀይረው
ነጻ የለቀቋቸው ባሪያዎቻቸውን እንዲመለሱ
አደረጓቸው፤ እንደገናም ባሪያ አድርገው
ገዟቸው።
[12]ስለዚህ *የእግዚአብሔር* ቃል ወደ ኤር
ምያስ እንዲህ ሲል መጣ፤ [13]“የእስራኤል
አምላክ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ በባርነት
ከተገዙበት ከግብፅ ምድር ባወጣኋቸው ጊ
ዜ፣ ከአባቶቻችሁ ጋር እንዲህ ብዬ
ቃል ኪዳን አደረግሁ፤ [14]‘ራሱን
በባርነት ለእና ንተ የሸጠውን ዕብራዊ
ወንድማችሁን እያ ንዳንዳችሁ በየሰባት ዓ
መቱ ነጻ ትለቃላ ችሁ፤ ስድስት ዓመት
ከተገዛላችሁ በኋላ ነጻ ታወጡታላችሁ።’[ለ]
አባቶቻችሁ ግን አልሰሙኝም
ጆሮአቸውንም ወደ እኔ አላ ዘነበሉም።
[15]እናንተም አሁን ንስሓ በመግ ባት
በፊቴ ትክክለኛ ነገር አደረጋችሁ፤
እያንዳንዳችሁም ለወገኖቻችሁ ነጻነት ዐወ
ጃችሁ፤ ስሜ በሚጠራበት ቤትም በፊቴ
ቃል ኪዳን ገባችሁ። [16]ነገር ግን ተመልሳ
ችሁ ስሜን አረከሳችሁ፤ ወደ ፈለጉበት
እንዲሄዱ ነጻ የለቀቃችኋቸውንም ወንዶ
ችና ሴቶች ባሪያዎቻችሁን መለሳችሁ፤
እንደ ገናም ባሪያዎቻችሁ አደረጋችኋ
ቸው።
[17]“ስለዚህ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
ለወንድሞቻችሁና ለወገኖቻችሁ ነጻነት አላ
ወጃችሁምና አልታዘዛችሁኝም። እንግዲህ
እኔ ‘ነጻነት’ ዐውጅላችኋለሁ፤ ይላል *እግዚ
አብሔር*። ይኸውም በሰይፍ፣ በቸነፈርና
በራብ የምትወድቁበት ‘ነጻነት’ ነው። ለም
ድር መንግሥታት ሁሉ መሠቀቂያ አደር
ጋችኋለሁ። [18]ኪዳኔን ያፈረሱትንና በፊቴ
የገቡትን የኪዳኑን ቃል ያልፈጸሙትን
ሰዎች ሥጋውን ሁለት ቦታ ከፍለው በመ
ካከሉ እንዳለፉት፣ እንደ እንቦሳው አደር
ጋቸዋለሁ። [19]የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን መሪ
ዎች፣ የቤተ መንግሥቱን ባለሟሎች፣ ካህ
ናቱንና በእንቦሳው ሥጋ መካከል ያለፉ
ትን ሕዝብ ሁሉ፣ [20]ነፍሳቸውን ለሚሹ ጠላ
ቶቻቸው አሳልፌ እሰጣለሁ፤ ሬሳቸውም
ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት መብል
ይሆናል።
[21]“የይሁዳን ንጉሥ ሴዴቅያስንና መኳ
ንንቱን፣ ነፍሳቸውን ለሚሹ ጠላቶቻቸው
ይኸውም ለጊዜው እናንተን ከመውጋት
ለተመለሱ ለባቢሎን ንጉሥ ሰራዊት አሳልፌ
እሰጣለሁ። [22]እነሆ፤ አዛቸዋለሁ፤ ይላል
*እግዚአብሔር*፤ ወደዚህችም ከተማ እንደ
ገና እመልሳቸዋለሁ። እነርሱም ይወጓ
ታል፤ ይይዟታል፤ በእሳትም ያቃጥሏታል።
የይሁዳንም ከተሞች ሰው የማይኖርባቸው፣
ባድማ አደርጋቸዋለሁ።

## የሬካባውያን ታማኝነት

35 በይሁዳ ንጉሥ በኢዮስያስ ልጅ፣
በኢዮአቄም ዘመነ መንግሥት፣
*ከእግዚአብሔር* ዘንድ እንዲህ የሚል ቃል
ወደ ኤርምያስ መጣ፤ [2]“ወደ ሬካባውያን
ሄደህ ወደ *እግዚአብሔር* ቤት አምጣ
ቸው፤ ወደ አንዱም ክፍል አስገብተህ
የሚጠጡትን ወይን ጠጅ ስጣቸው።”
[3]ስለዚህ የካባስን ልጅ የኤርምያስን
ልጅ ያእዛንያን፣ ወንድሞቹንና ወንዶች
ልጆቹን ሁሉ፣ የሬካባውያንን ወገን በአጠ
ቃላይ ሂጄ ጠራኋቸው፤ [4]ወደ *እግዚአ
ብሔር* ቤት አመጣኋቸው፤ ወደ ሐናን
ልጆች ክፍልም አስገባኋቸው፤ የሐናን
አባት ጌዴልያም *የእግዚአብሔር* ሰው
ነበረ። ክፍሉም በመኳንንቱ ክፍል አጠ
ገብ፣ ከመዕሤያ ክፍል በላይ ነበር፤ መዕ
ሤያም የበር ጠባቂው የሰሎም ልጅ ነበረ፤
[5]በሬካባውያንም ሰዎች ፊት በወይን ጠጅ
የተሞሉ ማድጋዎችን አቀረብሁ፤ ዋንጫዎች
ንም ሰጥቻቸው፣ “በሉ፤ የወይን ጠጅ ጠጡ”

34፥5 2ዜና16፥14፤ ኤር22፥18
34፥7 ኢሱ10፥3፡10፤2ዜና11፥9
34፥8 ዘፀ21፥2፤ዘሌ 25፥10፡39-41፤2ነገ 11፥17፤ነህ5፥5-8
34፥9 ዘዳ15፥12-18
34፥11 መዝ78፥37
34፥13 ዘፀ24፥8፤ ዘዳ15፥15
34፥14 ዘፀ21፥2፤ 2ነገ17፥14፤ኤር 7፥26
34፥15 ቀ-8፤ኤር 32፥24
34፥16 ዘሌ19፥12 ፤ሕዝ3፥20፤18፥24
34፥17 ኤር14፥12፤ 15፥4፤21፥7፤24፥9፤ 29፥18፤ማቴ7፥2፤ገላ 6፥7
34፥18 ዘፍ15፥10፤ ኤር11፥10
34፥19 ኤር26፥10፤ ሶፎ 3፥3-4
34፥20 ዘዳ28፥26፤ ኤር11፥21፤21፥7፤ ሕዝ16፥27፤23፥28
34፥21 2ነገ25፥21፤ 2ዜና36፥10፤ኤር 21፥7፤32፥4፤ 37፥5፤ 39፥6፤52፥24-27
34፥22 ዘሌ26፥32፤ ነህ2፥17፤ኢሳ 1፥7፤ ኤር38፥18፤39፥1-2፡ 8፤ሕዝ23፥47
35፥1 2ዜና36፥5
35፥2 1ነገ 6፥5፤ 2ነገ10፥15
35፥4 ዘዳ33፥1፤ 2ነገ12፥9፤23፥4፤ 1ዜና9፥19

[ለ]14 ዘዳ 15፥12

አልኋቸው፡፡
6እነርሱ ግን እንዲህ አሉ፤ “የወይን
ጠጅ አንጠጣም፤ አባታችን የሬካብ ልጅ
ኢዮናዳብ እንዲህ ብሎ አዝዞናል፤ ‘እናንተና
ዘራችሁ ከቶ የወይን ጠጅ አትጠጡ፤
7ቤት አትሥሩ፤ ዘር አትዝሩ፤ ወይን አት
ትከሉ፤ ሁልጊዜ በድንኳን ኑሩ እንጂ
ከእነዚህ ነገሮች አንዱም አይኑራችሁ፤
ይህም ሲሆን እንደ መጻተኛ በሆናችሁበት
ምድር ረዥም ዘመን ትኖራላችሁ፡፡’ 8እኛም
አባታችን የሬካብ ልጅ ኢዮናዳብ ያዘዘንን
ሁሉ ፈጽመናል፤ እኛና ሚስቶቻችን፣ ወን
ዶችና ሴቶች ልጆቻችንም የወይን ጠጅ
ጠጥተን አናውቅም፤ 9የምንቀመጥበትም
ቤት አልሠራንም፤ የወይን ቦታ፣ የዕርሻ
ስፍራ ወይም የእህል ዘር የለንም፡፡ 10በድን
ኳን ኖረናል፤ አባታችን ኢዮናዳብ ያዘዘን
ንም ሁሉ ጠብቀናል፡፡ 11ነገር ግን የባቢ
ሎን ንጉሥ ናቡከደናፆር ይህችን ምድር
በወረረ ጊዜ፣ ኑ፤ ከባቢሎን[ሐ] ሰራዊትና
ከሶርያ ሰራዊት ሸሽተን ወደ ኢየሩሳሌም
እንሂድ’ ተባባልን፤ ስለዚህም በኢየሩሳሌም
ተቀመጥን፡፡” 12*የእግዚአብሔር* ቃል ወደ
ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፤ 13“የእስራ
ኤል አምላክ የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*
እንዲህ ይላል፤ ሂድ፤ ለይሁዳ ሰዎችና ለኢ
የሩሳሌም ሕዝብ እንዲህ ብለህ ተናገር፤
‘ቃሌን ትጠብቁ ዘንድ ከዚህ አትማሩ
ምን?’ ይላል *እግዚአብሔር*፤ 14‘የሬካብ
ልጅ ኢዮ ናዳብ ልጆቹ የወይን ጠጅ
እንዳይጠጡ አዘዛቸው፤ ይህም ትእዛዝ
ተጠብቆአል፤ የአባታቸውን ትእዛዝ
ስለ ጠበቁ እስከ ዛሬ ድረስ የወይን ጠጅ
አይጠጡም፤ እና ንተ ግን እኔ ደጋግሜ
ብናገራችሁም፤ አልታዘዛችሁኝም፡፡
15አገልጋዮቼን ነቢያ ትን ሁሉ ደጋግሜ
ወደ እናንተ ላክሁ፤ እነርሱም፣
“እያንዳንዳችሁ ከክፉ መንገዳ ችሁ
ተመለሱ፤ ምግባራችሁን አስተካክሉ፤
ለእናንተና ለአባቶቻችሁ በሰጠኋቸው ምድር
ትኖሩ ዘንድ ሌሎቹን አማልክት ለ
ማገልገል
አትከተሉ” አልኋችሁ፡፡ እናንተ ግን ጆሮአ
ችሁን ወደ እኔ አላዘነበላችሁም፤ አልሰ
ማችሁኝምም፡፡ 16የሬካብ ልጅ የኢዮናዳብ
ዘሮች አባታቸው የሰጣቸውን ትእዛዝ ጠብ
ቀዋል፤ ይህ ሕዝብ ግን አልታዘዘኝም፡፡’
17“ስለዚህ የእስራኤል አምላክ፤ የሰራ
ዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
‘እነሆ፤ በይሁዳና በኢየሩሳሌም በሚኖሩት
ሁሉ ላይ አደርሳለሁ ያልሁትን ጥፋት ሁሉ
አመ ጣባቸዋለሁ፤ በተናገርኋቸው ጊዜ፣
አልሰ ሙኝምና በጠራኋቸውም ጊዜ

35፥6 ዘሌ10፥9፤ ዘኍ6፥2-4፤2ነገ 10፥15፤ሉቃ1፥15
35፥7 ዘፀ20፥12፤ ኤፌ6፥2-3፤ዕብ11፥9
35፥8 ምሳ1፥8፤ቆላ 3፥20
35፥9 1ጢሞ6፥6
35፥11 ኢሱ10፥20፤ 2ነገ24፥1፤ኤር8፥14
35፥13 ኤር6፥10፤ 11፥6፤23፥33
35፥14 ቀኍ6-10፡16 ፤ኢሳ30፥9፤ኤር7፥13
35፥15 ዘፀ20፥3፤ ዘዳ4፥40፤2ነገ17፥13፤ ኢሳ1፥16-17፤59፥20፤ ኤር4፥1፤6፥10፤7፥25፡ 26፤18፥11፤25፥5፤ 26፥3፤ 44፥4-5፤ሕዝ 14፥6፤18፥30
35፥16 ዘሌ20፥9፤ ሚል1፥6
35፥17 ኢሱ23፥15፤ 1ነገ13፥34፤ምሳ1፥24፤ ኤር7፥13፤21፥4-7፤ ሮሜ10፥21
35፥18 ዘፍ31፥35
35፥19 ኢሳ48፥19፤ ኤር15፥19፤33፥17
36፥1 2ዜና36፥5
36፥2 ቀኍ4፤ዘፀ 17፥14፤መዝ40፥7፤ ኤር1፥2፤25፥3፤30፥2፤ ሕዝ2፥7፤ዕን2፥2
36፥3 ቀኍ7፤2ነገ 17፥13፤ኢሳ6፥9፤ 44፥22፤ኤር18፥8፤ 26፥3፤ሕዝ 2፥3፤ አሞ5፥15፤ማር4፥12፤ ሐሥ3፥19
36፥4 ቀኁ2፡18፤ኤር 32፥12፤51፥59፤ሕዝ 2፥9፤ዳን7፥1፤ዘካ5፥1
36፥6 ቀኍ9፤ዘፀ 4፥16፤2ዜና20፥4
36፥7 ኤር26፥3፤ 37፥20፤42፥2፤ዘዳ 31፥17
36፥9 ቀኍ22፤2ዜና 20፥3
36፥10 ቀኁ12፡25፤ ዘፍ23፥10፤ኤር26፥24 ፤29፥3፤52፥25

አልመለሱል ኝም፡፡’ ”
18ኤርምያስም ሬካባውያንን እንዲህ አላ
ቸው፤ “የእስራኤል አምላክ የሰራዊት ጌታ
*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ ‘የአባታች
ሁን የኢዮናዳብን ትእዛዝ ስለ ጠበቃችሁ፤
መመሪያውን ስለ ተከተላችሁ፤ ያዘዛችሁንም
ሁሉ ስለ ፈጸማችሁ’ 19የእስራኤል አምላክ
የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
‘ከሬካብ ልጅ ከኢዮናዳብ ወገን የሚያገ
ለግለኝ ሰው ለዘላለም አይታጣም፡፡’ ”

## ኢዮአቄም የኤርምያስን ብራና አቃጠለ

36 የይሁዳ ንጉሥ የኢዮስያስ ልጅ
የነበረው ኢዮአቄም በነገሠ በአራ
ተኛው ዓመት እንዲህ የሚል ቃል *ከእግ
ዚአብሔር* ዘንድ ወደ ኤርምያስ መጣ፤
2“የብራና ጥቅልል ውሰድ፤ ለአንተም
መናገር ከጀመርሁበት ከኢዮስያስ ዘመነ
መንግሥት አንሥቶ እስካሁን ድረስ ስለ
እስራኤል፣ ስለ ይሁዳና ስለ ሌሎች ሕዝ
ቦች ሁሉ የነገርሁህን ቃል ሁሉ ጻፍበት፤
3ምናልባትም የይሁዳ ሕዝብ ላመጣባቸው
ያሰብሁትን ጥፋት ሁሉ ሲሰሙ፣ እያንዳን
ዳቸው ከክፉ መንገዳቸው ይመለሱ ይሆ
ናል፤ እኔም ክፋታቸውንና ኀጢአታቸ
ውን ይቅር እላለሁ፡፡”
4ኤርምያስም የኔርያን ልጅ
ባሮክን
ጠራው፤ ባሮክም *እግዚአብሔር* የተናገረ
ውን ቃል ሁሉ ከኤርምያስ አፍ ተቀብሎ
በብራናው ላይ ጻፈ፡፡ 5ኤርምያስም ባሮክን
እንዲህ አለው፤ “እኔ ተከልክያለሁና ወደ
*እግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ መግባት አልች
ልም፤ 6ስለዚህ ወደ *እግዚአብሔር* ቤት
ሂደህ፣ በቃል እየነገርሁህ በብራናው ላይ
የጻፍኸውን *የእግዚአብሔርን* ቃል በጾም
ቀን ለተሰበሰበው ሕዝብ አንብብ፤ ከየከተ
ሞቻቸው ለመጡት ለይሁዳ ሕዝብ ሁሉ
አንብብ፡፡ 7*እግዚአብሔር* በዚህ ሕዝብ ላይ
የተናገረው ቍጣና መቅሠፍት ታላቅ ስለ
ሆነ፣ ምናልባት ልመናቸውን *በእግዚአብሔር*
ፊት በማቅረብ እያንዳንዳቸው ከክፉ መን
ገዳቸው ይመለሱ ይሆናል፡፡”
8የኔርያ ልጅ ባሮክ ነቢዩ ኤርምያስ
የነገረውን ሁሉ አደረገ፤ *በእግዚአብሔርም*
ቤተ መቅደስ *የእግዚአብሔርን* ቃል ከብ
ራናው አነበበ፡፡ 9የይሁዳ ንጉሥ የኢዮስያስ
ልጅ የሆነው ኢዮአቄም በነገሠ በአምስተ
ኛው ዓመት በዘጠነኛው ወር በኢየሩ
ሳሌም የሚኖረው ሕዝብ ሁሉና ከይሁዳ
ከተሞች የመጡት ሰዎች *በእግዚአብሔር*
ፊት ጾም ዐወጁ፡፡ 10ባሮክም በብራና ላይ
የተጻፈውን የኤርምያስን ቃል *በእግዚአ*

[ሐ]11 ወይም *ከለዳውያን*

*ብሔር* ቤት በላይኛው አደባባይ፣ ‘አዲሱ
በር’ በሚባለው በቤተ መቅደሱ መግቢያ
ላይ በሚገኘው በጸሓፊው በሳፋን ልጅ በገ
ማርያ ክፍል ውስጥ ሆኖ ለሕዝቡ ሁሉ
አነበበው።

11የሳፋን ልጅ የገማርያ ልጅ ሚክያስ
ከብራናው የተነበበውን *የእግዚአብሔርን*
ቃል ሁሉ በሰማ ጊዜ፣ 12በቤተ መንግ
ሥቱ ውስጥ ወዳለው ወደ ጸሓፊው ክፍል
ወረደ፤ በዚያም መኳንንቱ ሁሉ፦ ጸሓፊው
ኤሊሳማ፣ የሸማያ ልጅ ድላያ፣ የዓክቦር
ልጅ ኤልናታን፣ የሳፋን ልጅ ገማርያ፣
የሐናንያ ልጅ ሴዴቅያስ እንዲሁም ሌሎች
መኳንንት ሁሉ ተቀምጠው ነበር። 13ባሮክ
ለሕዝቡ ከብራናው ሲያነብ ሚክያስ የሰ
ማውን ሁሉ ከነገራቸው በኋላ፣ 14መኳን
ንቱ ሁሉ የኩሲን ልጅ የሴሌምያን ልጅ
የናታንያን ልጅ ይሁዲን፣ “ለሕዝቡ ያነበ
ብኸውን ብራና ይዘህ እንድትመጣ” ብለው
ወደ ባሮክ ላኩ። የኔርያም ልጅ ባሮክ
ብራናውን ይዞ ወደ እነርሱ መጣ፤ 15እነር
ሱም፣ “እስቲ ተቀምጠህ አንብብልን”
አሉት። ባሮክም አነበበላቸው፤ 16እነርሱም
ቃሉን ሁሉ በሰሙ ጊዜ እርስ በርሳቸው
በፍርሀት በመተያየት ባሮክን፣ ይህን ሁሉ
ቃል ለንጉሡ መንገር ይገባናል።” አሉት፤
17ደግሞም፣ “ይህን ሁሉ እንዴት ልትጽፍ
እንደ ቻልህ ንገረን፤ ኤርምያስ በቃል እየ
ነገረህ ነውን?” ብለው ባሮክን ጠየቁት።

18ባሮክም፣ “አዎን ይህን ሁሉ በቃሉ
ነገረኝ፤ እኔም በብራናው ላይ በቀለም
ጻፍሁ” ብሎ መለሰላቸው።

19መኳንንቱም ባሮክን፣ “እንግዲያውስ
አንተና ኤርምያስ ሂዳችሁ ተሸሸጉ፤ የት
እንዳላችሁም ማንም አይወቅ” አሉት።

20የብራናውን ጥቅልል በጸሓፊው በኤ
ሊሳማ ክፍል ካስቀመጡት በኋላ፣ ንጉሡ
ወዳለበት አደባባይ ሄደው የሆነውን ሁሉ
ነገሩት። 21ንጉሡም ብራናውን ያመጣ ዘንድ
ይሁዲን ላከው፤ ይሁዲም ከጸሓፊው ከኤ
ሊሳማ ክፍል ብራናውን አምጥቶ፣ ለንጉ
ሡና በንጉሡ አጠገብ ቆመው ለነበሩት
መኳንንት ሁሉ አነበበላቸው። 22ዘጠነኛው
ወር እንደ መሆኑ፣ ንጉሡ የክረምትን
ወራት በሚያሳልፍበት ቤት ተቀምጦ ነበር፤
በምድጃ የሚነድ እሳትም ፊት ለፊቱ
ነበር። 23ይሁዲ ከብራናው ሦስት ወይም
አራት ዐምድ ባነበበ ቍጥር ንጉሡ ብራ
ናው ሁሉ እስከሚያልቅ ድረስ በጸሓፊ
ቢላዋ እየቈረጠ እንዲቃጠል ወደ እሳቱ
ምድጃ ይጥል ነበር። 24ንጉሡም ሆነ ይህን
ሁሉ ቃል የሰሙት መኳንንት ሁሉ አንዳች
አልፈሩም፤ ልብሳቸውንም አልቀደዱም።
25ኤልናታን፣ ድላያ፣ ገማርያም ንጉሡ ብራ
ናውን እንዳያቃጥል ቢለምኑትም እንኳ
አልሰማቸውም፣ 26ይልቁንም ጸሓፊውን
ባሮክንና ነቢዩን ኤርምያስን ይዘው ያስሩ
ዘንድ የንጉሡን ልጅ ይረምሕኤልን፣ የዓ
ዝርኤልን ልጅ ሠራያንና የአብድኤልን
ልጅ ሰሌምያን አዘዘ፤ *እግዚአብሔር*
ግን ሰውሮአቸው ነበር።

27ንጉሡ፣ ባሮክ ከኤርምያስ አፍ ተቀ
ብሎ የጻፈው ቃል ያለበትን ብራና ካቃጠለ
በኋላ፤ *የእግዚአብሔር* ቃል ወደ ኤርም
ያስ እንዲህ ሲል መጣ፤ 28“ሌላ ብራና ወስ
ደህ፣ የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም ባቃጠ
ለው በመጀመሪያው ብራና ላይ የነበረ
ውን ቃል ሁሉ ጻፍበት፤ 29ለይሁዳ ንጉሥ
ለኢዮአቄም እንዲህ ብለህ ንገረው፤
‘*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ “የባቢሎን
ንጉሥ በእርግጥ ይመጣል፤ ይህቺን ምድር፣
በእርሷም ላይ የሚኖሩትን ሰዎችንና እን
ስሳትን ያጠፋል በማለት የጻፍህበት ለምን
ድን ነው?” ብለህ ብራናውን አቃጥለሃል።
30ስለዚህ *እግዚአብሔር* ስለ ይሁዳ ንጉሥ
ስለ ኢዮአቄም እንዲህ ይላል፤ በዳዊት
ዙፋን ላይ የሚቀመጥ ከዘሩ አይገኝም፤
ሬሳውም ወደ ውጭ ተጥሎ ለቀን ሐሩ
ርና ለሌት ቍር ይጋለጣል። 31እርሱንና
ልጆቹን መኳንንቱንም ስለ ክፋታቸው
እቀጣለሁ፤ አልሰሙኝምና አመጣባቸዋለሁ
ያልሁትን ጥፋት ሁሉ በእነርሱና በኢየሩ
ሳሌም በሚኖሩት፣ በይሁዳም ሕዝብ ላይ
አመጣለሁ።’ ”

32ኤርምያስም ሌላ ብራና ወስዶ ለኔ
ርያ ልጅ ለጸሓፊው ለባሮክ ሰጠው፤ ባሮ
ክም የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም በእሳት
ባቃጠለው ብራና ላይ የነበረውን ቃል
ሁሉ ከኤርምያስ አፍ ተቀብሎ ጻፈበት፤
ብዙ ተመሳሳይ ቃልም ተጨመረበት።

## የኤርምያስ መታሰር

37 የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር የኢ
ዮስያስን ልጅ ሴዴቅያስን በይሁዳ
ላይ አነገሠው፤ እርሱም በኢዮአቄም ልጅ
በኢኮንያን[መ] ፈንታ ነገሠ። 2ነገር ግን እር
ሱም ሆነ መኳንንቱ የምድሪቱም ሕዝብ
በነቢዩ በኤርምያስ አማካይነት የተነገረ
ውን *የእግዚአብሔርን* ቃል አልሰሙም።

3ንጉሡ ሴዴቅያስም፣ “ወደ አምላካችን
ወደ *እግዚአብሔር* ስለ እኛ ጸልይ” በማ
ለት የሰሌምያን ልጅ ዮካልንና ካህኑን
የመዕሤያን ልጅ ሶፎንያስን ወደ ነቢዩ
ወደ ኤርምያስ ላከ።

36፥12 2ሳሙ8፥17፤ኤር26፥22፤38፥4
36፥14 ቀኍ4፡21
36፥16 መዝ36፥1
36፥17 ኤር30፥2
36፥18 ቀኍ4
36፥19 1ነገ17፥3፤ኤር26፥16
36፥21 ቀኍ14፤2ነገ22፥10
36፥22 አሞ3፥15
36፥23 ቀኍ2፤1ነገ22፥8
36፥24 ዘፍ37፥29፤ዘኍ14፥6፤መዝ36፥1
36፥25 ቀኍ10፡12
36፥26 1ነገ17፥3፤መዝ11፥1፤ኤር1፥8፤15፥21፤ማቴ23፥34
36፥27 ቀኍ 4
36፥28 ቀኍ 2
36፥29 ኢሳ30፥10፤ኤር33፥12
36፥30 2ነገ24፥6፤ኢሳ14፥19፤ኤር8፥2፤ኤር52፥2
36፥31 ዘፀ20፥5፤ምሳ29፥1፤1፥24
36፥32 ቀኍ4፡23፤ዘፀ34፥1፤ኤር30፥2
37፥1 1ሳሙ11፥1፤2ነገ24፥8፡12፡17፤ኤር22፥24፤ሕዝ17፥13
37፥2 2ነገ24፥19
37፥3 ቀኍ17፤ዘፀ8፥28፤ዘኍ21፥7፤1ሳሙ12፥19፤1ነገ13፥6፤2ነገ19፥4፤25፥18፤ኤር29፥25፤38፥1፡14፤42፥2፤52፥24

[መ]1 የዕብራይስጡ *ኢኮንያን የኢዮአቄም* አቻ ስም ነው።

4ኤርምያስ ገና እስር ቤት ስላልገባ፣
በሕዝቡ መካከል እንደ ልቡ ይወጣና ይገባ
ነበር። 5የፈርዖንም ሰራዊት ከግብፅ ወጥቶ
ነበርና ኢየሩሳሌምን ከበው የነበሩት
ባቢሎናውያን[ሠ] ይህን ሲሰሙ ኢየሩሳሌ
ምን ለቀው ሄዱ።
6*የእግዚአብሔርም* ቃል ወደ ነቢዩ ወደ
ኤርምያስ እንዲህ ሲል *መጣ*፤ 7“የእስራ
ኤል አምላክ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
ትጠይቁኝ ዘንድ ወደ እኔ የላካችሁን የይ
ሁዳን ንጉሥ እንዲህ በሉት፤ ‘ሊረዳችሁ
የወጣው የፈርዖን ሰራዊት ወደ ገዛ አገሩ
ወደ ግብፅ ይመለሳል፤ 8ባቢሎናውያንም
ተመልሰው ይህችን ከተማ ይወጓታል፤
ይዘውም *ያቃጥሏታል*።’
9“*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ ‘ባቢሎ
ናውያን በእርግጥ ትተውን ይሄዳሉ’ ብላ
ችሁ አታስቡ፤ አይሄዱምና ራሳችሁን አታ
ታሉ። 10የሚዋጋችሁን የባቢሎናውያንን[ረ] ሰ
ራ ዊት ሁሉ አሸንፋችሁ፣ ቍስለኞች
ብቻ በድንኳኖቻቸው ውስጥ ቢቀሩ እንኳ፤
እነዚህ ሰዎች መጥተው ይህችን ከተማ
*ያቃጥሏ ታል*።”
11የባቢሎን ሰራዊት ከፈርዖን ጭፍራ
የተነሣ ከኢየሩሳሌም ከወጣ በኋላ፣ 12ኤር
ምያስ በሕዝቡ መካከል የርስቱን ድርሻ
ለመካፈል፣ ከኢየሩሳሌም ወደ ብንያም
አገር ሊሄድ ተነሣ፤ 13ነገር ግን ወደ ብን
ያም በር ሲደርስ፣ የዘበኞች አለቃ የነበረው
የሐናንያ ልጅ የሴሌምያ ልጅ የሪያ የተ
ባለው፣ “ከድተህ ወደ ባቢሎናውያን ልት
ሄድ ነው!” በማለት ያዘው።
14ኤርምያስም፣ “ሐሰት ነው! ከድቼ ወደ
ባቢሎናውያን መሄዴ አይደለም” አለ፤
የሪያ ግን አልሰማውም፤ እንዲያውም ኤር
ምያስን አስሮ ወደ መኳንንቱ አመጣው።
15*መኳንንቱም* እጅግ ተቈጥተው ኤርምያ
ስን ደበደቡት፤ የግዞት ቤትም አድርገ
ውት በነበረው፤ በጸሐፊው በዮናታን ቤት
አሰሩት።
16ኤርምያስም በምድር ቤት በሚገኝ
ክፍል ውስጥ እንዲቀመጥ ተደረገ፤ በዚ
ያም ረጅም ጊዜ ቈየ። 17ከዚያም በኋላ
ንጉሡ ሴዴቅያስ ላከበትና ወደ ቤተ መን
ግሥት አስመጣው፤ ለብቻውም ወስዶ፣
“*ከእግዚአብሔር* የመጣ ቃል አለህ?” በማ
ለት ጠየቀው።
ኤርምያስም፣ “አዎን አለ፤ ለባቢሎን
*ንጉሥ* ዐልፈህ ትሰጣለህ” አለው።
18ኤርምያስም ንጉሡ ሴዴቅያስን እን
ዲህ አለው፤ “*ያሰራችሁኝ* በአንተና በመኳ
ንንትህ ወይም በዚህ ሕዝብ ላይ ምን ወን
ጀል ፈጽሜ ነው? 19*ለመሆኑ*፣ ‘የባቢሎን
ንጉሥ እናንተንም ይህችንም ምድር አይ
ወጋም’ ብለው ትንቢት ይናገሩ የነበሩት
ነቢያታችሁ ወዴት ናቸው? 20አሁንም
ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፤ እባክህ አድምጠኝ፤
ልመናዬን በፊትህ ላቅርብ፤ በዚያ እንዳል
ሞት ወደ ጸሓፊው ወደ ዮናታን ቤት
አትመልሰኝ።”
21ንጉሡም ሴዴቅያስ፣ ኤርምያስ በዘብ
ጠባቂዎች አደባባይ እንዲቀመጥና በከተ
ማዪቱ ያለው እንጀራ እስኪያልቅ ድረስ
ከእንጀራ ጋጋሪዎች ሰፈር በየቀኑ አንድ
አንድ እንጀራ እንዲሰጠው አዘዘ፤ ስለዚህ
ኤርምያስ በዘብ ጠባቂዎች አደባባይ ተቀ
መጠ።

## ኤርምያስ በውሃ ጕድጓድ ውስጥ ተጣለ

38 ኤርምያስ ለሕዝቡ የተናገረውን
ቃል የማታን ልጅ ሰፋጥያስ፣
የጳስኮር ልጅ ጎዶልያስ፣ የሰሌምያ ልጅ
ዮካል[ሰ] እንዲሁም የመልክያ ልጅ ጳስኮር
ሰሙ፤ ቃሉም እንዲህ የሚል ነበር፦
2“*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ ‘በዚህች
ከተማ የሚቀር ሁሉ በሰይፍ፣ በራብ
ወይም በቸነፈር ይሞታል፤ ይህን ስፍራ ለቆ
ወደ ባቢሎናውያን[ሸ] የሚሄድ ሁሉ ይተ
ርፋል፤ ያመልጣል፤ በሕይወትም ይኖራል።’
3*እግዚአብሔርም* እንዲህ ይላል፤ ‘ይህች
ከተማ በእርግጥ ለባቢሎን ንጉሥ ሰራዊት
ዐልፋ ትሰጣለች፤ እርሱም ይይዛታል።’ ”
4*መኳንንቱም* ንጉሡን እንዲህ አሉት፤
“ይህ ሰው በሚናገረው ነገር በዚህች ከተማ
የቀሩትን ወታደሮችና ሕዝቡንም ሁሉ
ተስፋ የሚያስቈርጥ ስለ ሆነ መሞት አለ
በት፤ ይህ ሰው የሕዝቡን መጥፋት እንጂ
*መልካም* ነገር አይሻም።”
5ንጉሡ ሴዴቅያስም፤ “እርሱ በእጃችሁ
ነው፤ ንጉሡ እናንተን ተቃውሞ ምንም
ማድረግ አይችልም” አለ።
6ስለዚህ ኤርምያስን ወስደው፣ በዘበኞች
አደባባይ በነበረው በንጉሡ ልጅ በመል
ክያ የውሃ ማጠራቀሚያ ጕድጓድ ውስጥ
ጣሉት፤ በገመድም ኤርምያስን ወደ ጕድ
ጓዱ አወረዱት። ጕድጓዱም ጭቃ እንጂ
ውሃ አልነበረበትም፤ ኤርምያስም ወደ
ጭቃው ዘልቆ ገባ።
7በቤተ መንግሥት ባለ ሥልጣን የነበረው
ኢትዮጵያዊ[ቀ] ጃንደረባ[በ] አቤሜሌክ፣ ኤር

37፥4 ቍ15፤ኤር 32፥2
37፥5 ዘፍ 15፥18፤ ኢሳ30፥5፤31፥1፤ ኤር34፥11፡21፤ሕዝ 17፥15
37፥7 ቍ5፤ዘፍ 25፥22፤2ነገ18፥21፤ 22፥18፤ኤር2፥36፤ ሰቆ1፥7፤4፥17
37፥8 ኤር21፥10፤ 38፥3፡18፤39፥8
37፥9 ኤር29፥8፤ ማር13፥5
37፥10 ኤር21፥10
37፥11 ቍ 5
37፥12 ኤር32፥9
37፥13 ኤር20፥2፤ 21፥9
37፥14 ኢሳ58፥6፤ ኤር 40፥4
37፥15 ቍ20፤1ነገ 22፥27፤ኤር20፥2፤ 38፥26፤ዕብ11፥36
37፥17 ቍ3፤ዘፍ 25፥22፤ኤር15፥11፤ 21፥7፤38፥16
37፥18 1ሳሙ 26፥18፤ዮሐ10፥32፤ ሐሥ25፥8
37፥19 ኤር14፥13 ፤ሕዝ13፥2
37፥20 ቍ 15
37፥21 ዘሌ26፥26 ፤2ነገ25፥3፤ኢሳ 33፥16፤ኤር32፥2፤ 38፥6፡9፡13፡28፤ 39፥13-14፤ሰቆ1፥11
38፥1 ኤር37፥3፤ 1ቆሮ9፥12
38፥2 ቍ17፤ኤር 21፥9፤34፥17፤ 39፥18፤45፥5
38፥3 ኤር21፥4፤10
38፥4 1ሳሙ17፥32 ፤ኤር11፥21፤36፥12
38፥5 1ሳሙ15፥24 ፤ኤር26፥14
38፥6 ዘፍ37፥24፤ ኢሱ2፥15፤ኢዮ 30፥19፤ኤር37፥21፤ ሰቆ3፥53
38፥7 ኢዮ29፥7፤ ኢ ሳ56፥3-5፤ኤር 39፥16፤ሐሥ8፥27

[ሠ]5 ወይም *ከለዳውያን*፤ ቍ8፡9፡13እና 14 ይመ።
[ረ]10 ወይም *ከለዳውያን*፤ ቍ11 ይመ።
[ሰ]1 የዕብራይስጡ *ዮካል የሁካል* አቻ ስም ነው።
[ሸ]2 ወይም *ከለዳውያን*፤ ቍ18፡19 እና23 ይመ።
[ቀ]7 ከላይኛው ዐባይ አካባቢ የሚኖር ሊሆን ይችላል፤
[በ]7 ወይም *ሹም*

ምያስን በውሃ ማጠራቀሚያ ጕድጓድ
ውስጥ እንደ ጣሉት ሰማ:: ንጉሡም በብ
ንያም በር ተቀምጦ ሳለ፣ [8]አቤሜሌክ
ከቤተ መንግሥት ወጥቶ ንጉሡን እንዲህ
አለው፤ [9]"ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፤ እነዚህ
ሰዎች በነቢዩ በኤርምያስ ላይ ባደረጉት
ነገር ሁሉ ክፉትን አድርገዋል፤ ከከተማ
ዪቱም እንጀራ በጠፋ ጊዜ በራብ እንዲሞት
ጕድጓድ ውስጥ ጥለውታል::"

[10]ንጉሡም ኢትዮጵያዊውን አቤሜሌ
ክን፣ "ሠላሳ ሰዎች ከዚህ ይዘህ ሂድ፤
ነቢዩ ኤርምያስንም ሳይሞት ከጕድጓድ አው
ጣው" ብሎ አዘዘው::

[11]አቤሜሌክም ሰዎቹን ይዞ በቤተ መን
ግሥቱ ግምጃ ቤት ሥር ወዳለው ክፍል
ሄደ፤ ያረጀ ጨርቅና ያለቀ ልብስ ከዚያ
ወስዶ ወደ ኤርምያስ ወደ ጕድጓዱ
ውስጥ በገመድ አወረደለት። [12]ኢትዮጵያዊው
አቤሜሌክ ኤርምያስን፣ "ይህን ያረጀ ጨር
ቅና ያረጀ ልብስ ገመዱ እንዳይከረክርህ
በብብትህ ሥር አድርገው አለው፤ ኤር
ምያስም እንዲሁ አደረገ፤ [13]እነርሱም በገ
መዱ ጐትተው ከጕድጓዱ አወጡት::
ኤርምያስም በዘበኞች አደባባይ ሰነበተ::

### ሴዴቅያስ ኤርምያስን እንደ ገና አነጋገረው

[14]ንጉሡ ሴዴቅያስ ወደ ነቢዩ ወደ
ኤርምያስ ልኮ ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስ ሦስተኛው በር አስመጣውና፤ "አንድ
ነገር እጠይቅሃለሁ፤ ምንም አትሸሽገኝ"
አለው::

[15]ኤርምያስም ሴዴቅያስን፣ "መልስ ብሰ
ጥህ አትገድለኝምን? ምክር ብሰጥህ አትሰ
ማኝም" አለው::

[16]ንጉሥ ሴዴቅያስ፣ "ለኤርምያስ፣ እስ
ትንፋስ የሰጠ ሕያው *እግዚአብሔርን!* በእ
ርግጥ አልገድልህም፤ ሕይወትህንም ለሚሿት
አሳልፌ አልሰጥም" ብሎ በምስጢር ማለ
ለት::

[17]ኤርምያስም ሴዴቅያስን እንዲህ አለው፤
"የእስራኤል አምላክ የሰራዊት ጌታ *እግዚ
አብሔር* እንዲህ ይላል፤ 'ለባቢሎን ንጉሥ
የጦር መኰንኖች እጅህን ብትሰጥ፣ ሕይ
ወትህ ትተርፋለች፤ ይህችም ከተማ አት
ቃጠልም፤ አንተና ቤተ ሰብህም በሕይ
ወት ትኖራላችሁ:: [18]ለባቢሎን ንጉሥ
የጦር መኰንኖች እጅህን ባትሰጥ ግን
ይህች ከተማ ለባቢሎናውያን ዐልፋ
ትሰጣለች፤ እነርሱም ያቃጥሏታል፤ አንተም
ራስህ ከእጃ ቸው አታመልጥም::' "

[19]ንጉሡም ሴዴቅያስ ኤርምያስን፣ "ወደ
ባቢሎን የኰበለሉት አይሁድ እንዲያሳግጡ
ብኝ፣ ባቢሎናውያን ለእነርሱ ዐሳልፈው
ይሰጡኛል ብዬ እፈራለሁ" አለው::

[20]ኤርምያስም እንዲህ አለው፤ "ዐሳል
ፈው አይሰጡህም፣ ብቻ የምነግርህን *የእግዚ
አብሔር* ቃል ታዘዝ፤ መልካም ይሆንል
ሃል፤ ሕይወትህም ትተርፋለች:: [21]እጅህን
ለመስጠት እንቢ ብትል ግን፣ *እግዚአብሔር*
የገለጠልኝ ነገር ይህ ነው፤ [22]በይሁዳ ቤተ
መንግሥት የቀሩ ሴቶች ሁሉ ወደ ባቢሎ
ናውያን ባለ ሥልጣኖች ይወሰዳሉ፤ ሴቶቹም
እንዲህ ይላሉ፤

" 'እነዚያ የተማመንህባቸው ወዳጆችህ፣
  አሳሳቱህ፤ አሸነፉህ::
 እግርህ ጭቃ ውስጥ ተሰንቅሮአል፣
  ወዳጆችህ ጥለውህ ሄደዋል::'

[23]"ሚስቶችህና ልጆችህ ሁሉ ተወስደው
ለባቢሎናውያን ይሰጣሉ፤ አንተም ራስህ
በባቢሎን ንጉሥ ትያዛለህ እንጂ ከእጃ
ቸው አታመልጥም፤ ይህችም ከተማ በእሳት
ትቃጠላለች::"[†]

[24]ሴዴቅያስም ኤርምያስን እንዲህ አለው፤
"ስለዚህ ስለ ተነጋገርነው ነገር ማንም
አይወቅ፤ አለዚያ ትሞታለህ:: [25]መኳንንቱ
ከአንተ ጋር እንደ ተነጋገርሁ ሰምተው
ወደ አንተ ቢመጡና፣ 'ንጉሡን ምን እንዳ
ልኸው፣ ንጉሡም ምን እንዳለህ ንገረን፤
ሳትደብቅ ንገረን፤ አለዚያ እንገድልሃለን'
ቢሉህ፣ [26]'በዚያ እንዳልሞት ወደ ዮናታን
ቤት አትመልሰኝ ብዬ ንጉሡን ስለምን
ነበር' በላቸው::"

[27]መኳንንቱ ሁሉ ወደ ኤርምያስ መጥ
ተው ጠየቁት፤ እርሱም ንጉሡ ያዘዘውን
ቃል ሁሉ ነገራቸው፤ ከንጉሡ ጋር የተነጋ
ገሩትን ነገር የሰማ አንድም ሰው ስላልነበረ፣
ከዚህ በላይ አላነጋገሩትም::

[28]ኢየሩሳሌም እስከ ተያዘችበት ቀን
ድረስ ኤርምያስ በዘበኞች አደባባይ ተቀ
መጠ::

### የኢየሩሳሌም መውደቅ

39፥1-10 ተጓ ምብ-2ነገ25፥1-12፤ኤር52፥4-16

**39** ኢየሩሳሌም የተያዘችው እንዲህ
ነበር፤ በይሁዳ ንጉሥ በሴዴቅያስ
ዘመነ መንግሥት በዘጠነኛው ዓመት በዐ
ሥረኛው ወር፣ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነ
ፆር ሰራዊቱን ሁሉ አሰልፎ በመምጣት
ኢየሩሳሌምን ከበባት:: [2]በሴዴቅያስ ዘመነ
መንግሥት በዐሥራ አንደኛው ዓመት በአ
ራተኛው ወር፣ በወሩም በዘጠነኛው ቀን
የከተማዪቱ ቅጥር ተሰበረ:: [3]የባቢሎን

[†]23 ወይም *ይህችም ከተማ በእሳት እንድትቃጠል ምክንያት ትሆናላችሁ*

38፥9 ዘፍ37፥20፤ ኤር37፥21
38፥11 ኢሱ2፥15
38፥13 ኤር37፥21
38፥14 1ሳሙ3፥17፤ኤር37፥3
38፥16 ቀኑ4፤ኢሳ 42፥5፤57፥16፤ኤር 37፥17
38፥17 ኤር 21፥9፤ 27፥8
38፥18 ቀኑ3፤ኤር 24፥8፤32፥4፤37፥8
38፥19 ኢሳ 51፥12፤ኤር39፥9፤52፥15፤ ዮሐ12፥42
38፥20 ዘዳ5፥33፤ ኢ ሳ55፥3፤ኤር11፥4፤ 40፥9
38፥22 ኢዮ19፥14፤ 30፥19፤መዝ69፥14፤ ኤር 6፥12፤13፥21
38፥23 2ነገ25፥6፤ ኤር24፥8፤21፥10፤ 32፥4፤37፥8፤ሕዝ 17፥15
38፥24 ኤር37፥17
38፥26 1ሳሙ16፥2፤ኤር37፥15
38፥28 ኤር37፥21
39፥1 2ነገ24፥1፤ 25፥1፤2ዜና36፥11፤ ኤር25፥29፤28፥14፤ 52፥4፤ሕዝ4፥3፤ 24፥2
39፥2 2ነገ14፥13፤ሕዝ33፥21፤ዘካ 8፥19
39፥3 ቀኑ13፥ኤር 21፥4

ንጉሥ መኳንንት ሁሉ:- የሳምጋሩ ኤርጌል
ሳራስር፣ ዋና አዛዡ ናቦሠርሰኪም[ቸ]፣ ከፍተ
ኛው ሹም ኤርጌል ሳራሳር እንዲሁም
ሌሎቹ የባቢሎን ንጉሥ መኳንንት ሁሉ
ገብተው በመካከለኛው በር ተቀመጡ። 4የይ
ሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስና ወታደሮቹ ሁሉ
እነርሱን ባዩ ጊዜ ሸሹ፤ በሌሊት በንጉሡ
አትክልት ስፍራ በኩል አድርገው በሁለቱ
ቅጥር መካከል ከከተማዪቱ ወጡ፤ ወደ ዓረ
ባም[ኀ] አመሩ።

5የባቢሎን[ነ] ሰራዊት ግን ተከትሎ አሳደ
ዳቸው፣ በኢያሪኮም ሜዳ ደርሶባቸው ሴዴ
ቅያስን ያዘ፤ ማርከውም በሐማት ምድር
ወዳለችው ወደ ሪብላ ወደ ባቢሎን ንጉሥ
ወደ ናቡከደነፆር አመጡት፤ በዚያም ፍርድ
ወሰነበት። 6የባቢሎንም ንጉሥ በሪብላ የሴ
ዴቅያስን ወንዶች ልጆች፣ አባታቸው
እያየ ዐረዳቸው፤ የይሁዳን መሳፍንት ሁሉ
ገደላቸው፤ 7የሴዴቅያስንም ዐይኖች አወጣ፤
ወደ ባቢሎን ሊወስደውም በናስ ሰንሰለት
አሰረው።

8ባቢሎናውያን[ኘ] ቤተ መንግሥቱንና የሕ
ዝቡን ቤት በእሳት አቃጠሉ፤ የኢየሩሳሌ
ምንም ቅጥር አፈረሱ። 9የባቢሎን መንግ
ሥት የክብር ዘበኞች አዛዥ ናቡዘረዳን፤
በከተማዪቱ የቀረውን ሕዝብ ሁሉ ማርኮ
ወደ ባቢሎን ወሰዳቸው። 10ንብረት ያልነበ
ራቸውን ድኾች ግን የክብር ዘበኞች
አዛዥ ናቡዘረዳን፣ በይሁዳ ምድር ተዋ
ቸው፤ በዚያ ጊዜም የወይን አትክልት
ቦታና የዕርሻ መሬት ሰጣቸው።

11የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር በክብር
ዘበኞቹ አዛዥ በናቡዘረዳን በኩል ስለ ኤር
ምያስ እንዲህ የሚል ትእዛዝ ሰጠ፤
12“ውሰደውና እንክብካቤ አድርግለት፤ የሚ
ፈልገውን ነገር ፈጽምለት እንጂ አትጕ
ዳው። 13የክብር ዘበኞች አዛዥ ናቡዘረ
ዳን፣ ዋና አዛዡ ናቡሽዝባን፣ ከፍተኛ ሹሙ
ኤርጌል ሳራስር እንዲሁም ሌሎች የባቢ
ሎን ንጉሥ መኳንንት ሁሉ፣ 14ልከው ኤር
ምያስን ከዘበኞች አደባባይ አስወጡት፤
የሳፋን ልጅ የአኪቃም ልጅ ጎዶልያስ
ወደ ቤቱ እንዲወስደው በዐደራ ሰጡት፤
ኤርምያስም በራሱ ሕዝብ መካከል ተቀ
መጠ። 15ኤርምያስ በዘበኞች አደባባይ
ታስሮ በነበረበት ጊዜ *የእግዚአብሔር* ቃል
ወደ እርሱ እንዲህ ሲል መጣ፤ 16“ሂድና
ለኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ እንዲህ በለው፤
‘የእስራኤል አምላክ የሰራዊት ጌታ *እግዚ
አብሔር* እንዲህ ይላል፤ እድገት ሳይሆን
ጥፋት በማምጣት በዚህች ከተማ ላይ ቃሌን
እፈጽማለሁ፤ በዚያ ጊዜ በዐይንህ እያየህ

39፥4 ኢሳ22፥11፤ሕዝ12፥12
39፥5 ዘኍ34፥11፤ ኤር21፥7፤24፥8፤ 32፥4
39፥6 ኢሳ34፥12
39፥7 ዘኍ16፥14፤ ኤር2፥35፤ሕዝ12፥13
39፥8 ነህ1፥3፤መዝ 80፥12፤ኢሳ22፥5፤ ኤር34፥22፤ሰቆ2፥8
39፥9 ኤር21፥9፤ 40፥1፤ሰቆ1፥5
39፥12 ምሳ16፥7፤ ኤር15፥20-21፤ 1ጴጥ 3፥13
39፥13 ቍ 3
39፥14 2ነገ25፥22፤22፥3፡12፤ነህ3፥25፤ ኤር37፥21፤40፥5
39፥16 ኢሱ23፥15፤ መዝ33፥11፤ኢሳ 14፥27፤40፥8፤ኤር 21፥10፤38፥7፤44፥28፤ ሰቆ2፥17፤ማቴ1፥22
39፥17 መዝ34፥22፤41፥1-2
39፥18 1ሳሙ 17፥47፤ኢዮ5፥20፤ ኤር17፥7፤21፥9፤ 38፥2፤ሐሥ16፥31፤ ሮሜ10፥11
40፥1 ዘዳ21፥10፤ ኢ ሱ18፥25፤1ሳሙ 8፥4፤2ነገ24፥1፤2ዜና 36፥10፤ናሆ3፥10፤ ማቴ2፥18
40፥2 ኢሱ23፥15፤ 2ዜና34፥24፤መዝ 18፥18፤ምሳ8፥36፤ ኢሳ10፥22፤ሮሜ 13፥4፤ገላ6፥7-8
40፥3 ዘሌ26፥33፤ ዘዳ28፥45-52፤29፥ 24-28፤31፥17-18፤ 1ነገ9፥9፤ምሳ13፥21፤ ኤር22፥8-9፤ዳን 9፥14፤ሐሥ7፥39፤ ሮሜ2፥5-9፤6፥23፤ ያዕ1፥15
40፥4 ዘፍ13፥9፤ መዝ105፥18-20፤ ኤር37፥14፤ሰቆ3፥7
40፥5 ዘፍ32፥20፤ 1ሳሙ9፥7፤2ነገ 22፥12-14፤25፥22፤ ነህ5፥14፤ኤር39፥14፤ 41፥2፤44፥2፤ዘካ1፥12
40፥6 ቍ10፤መሳ 20፥1፤1ሳሙ7፥5-17
40፥7 ዘፍ41፥41፤ 2ነገ24፥14፤ነህ5፥14፤ ሐሥ24፥17፤ያዕ2፥5
40፥8 ቍ13፡14፡15 ፤ዘዳ3፥14፤2ሳሙ23፥ 28፤ኤር41፥1፡2፡11

ይህ ይፈጸማል። 17አንተን ግን በዚያ ቀን
አድንሃለሁ፤ ይላል *እግዚአብሔር*፤ ለምትፈ
ራቸው ሰዎች ዐልፈህ አትሰጥም። 18እታ
ደግሃለሁ፤ በእኔ ታምነሃልና በሕይወት
ታመልጣለህ እንጂ በሰይፍ አትወድቅም፤
ይላል *እግዚአብሔር*።’ ”

## ኤርምያስ በነጻነት መኖሩ

40 የክብር ዘበኞች አዛዥ ናቡዘረዳን
ኤርምያስን ከኢየሩሳሌምና ከይ
ሁዳ ወደ ባቢሎን በሚወስዱት ምርኮኞች
ሁሉ መካከል በራማ በሰንሰለት ታስሮ ባገ
ኘው ጊዜ አስፈታው፤ ከዚህ በኋላ *የእግዚ
አብሔር* ቃል ወደ ኤርምያስ መጣ። 2የዘ
በኞቹ አዛዥ ኤርምያስን ለብቻው ወስዶ፣
እንዲህ አለው፤ “አምላክህ *እግዚአብሔር*
በዚህች ምድር ላይ ይህን ጥፋት ተናገረ፤
3አሁንም *እግዚአብሔር* አመጣው፤ እንደ
ተናገረውም አደረገ። ይህ ሁሉ የሆነው
እናንተ *በእግዚአብሔር* ላይ ኀጢአት ስለ
ሠራችሁና እርሱን ስላልታዘዛችሁ ነው።
4እነሆ፤ ዛሬ የእጅህን ሰንሰለት ፈታሁ
ልህ። ከፈለግህ ከእኔ ጋር ወደ ባቢሎንና፤
እኔም እንከባከብሃለሁ፤ ካልፈለግህ ግን
አትምጣ። እነሆ፤ አገሪቱ ሁሉ በፊትህ
ናት፤ ደስ ወዳሰኘህ ሂድ።” 5ኤርምያስ ገና
መልስ ሳይሰጥ[ኣ] ናቡዘረዳን በመቀጠል፣
“የባቢሎን ንጉሥ በይሁዳ ከተሞች ላይ
ወደ ሾመው ወደ ሳፋን ልጅ ወደ አኪ
ቃም ልጅ ወደ ጎዶልያስ ተመለስ፤ ከእር
ሱም ጋር በሕዝቡ መካከል ተቀመጥ፤
ወይም ደስ ወዳሰኘህ ስፍራ ሂድ” አለው።
የዘበኞቹ አዛዥ ስንቅና ስጦታ ሰጥቶ
አሰናበተው፤ 6ኤርምያስም የአኪቃም ልጅ
ጎዶልያስ ወዳለበት ወደ ምጽጳ ሄደ፤ ከእር
ሱም ጋር በምድሪቱ በቀረው ሕዝብ መካከል
ኖረ።

## የጎዶልያስ መገደል

40፥7-9፤ 41፥1-3 ተጓ ምብ-2ነገ25፥22-26

7በየሜዳው የነበሩት የጦር መኰንኖችና
ሰዎቻቸው ሁሉ የባቢሎን ንጉሥ የአኪቃ
ምን ልጅ ጎዶልያስን በምድሪቱ ላይ ገዥ
አድርጎ እንደ ሾመውና ወደ ባቢሎን በም
ርኮ ባልተወሰዱት በምድሪቱ ድኾች ወን
ዶች፣ ሴቶችና ልጆች ላይ ሥልጣን እንደ
ሰጠው በሰሙ ጊዜ፣ 8ወደ ምጽጳ፣ ጎዶል
ያስ ዘንድ መጡ፤ የናታንያ ልጅ እስማ
ኤል፣ የቃሬያ ልጆች ዮሐናንና ዮናታን፣

[ቸ]3 ወይም *ኤርጌል ሳርሰር፣ ሳምጋር ናባ፣ ሠርሰኪም*
[ኀ]4 ወይም *በዮርዳኖስ ሸለቆ*
[ነ]5 ወይም *ከለዳውዲዎን*
[ኘ]8 ወይም *ከለዳውያን*
[ኣ]5 ወይም *ኤርምያስ ሳይመልስ*

የተንሖት ልጅ ሡራያ፤ የነጦፋዊው የዮፌ
ልጆች፣ የማዕካታዊ ልጅ ያእዛንያን[ከ] ሰዎ
ቻቸውም ነበሩ:: 9የሳፋን ልጅ የአኪቃም
ልጅ ጎዶልያስ ለእነርሱና ለሰዎቻቸው
እንዲህ ሲል ቃል ገባላቸው፤ “ለባቢሎናው
ያን[ኸ] መገዛት አትፍሩ፤ በምድሪቱ ተቀም
ጣችሁ የባቢሎንን ንጉሥ አገልግሉ፤ መል
ካም ይሆንላችኋል:: 10እኔም ራሴ ወደ እኛ
በሚመጡት በባቢሎናውያን ፊት ልቆምላ
ችሁ፣ በምጽጳ እቀመጣለሁ፤ እናንተ ግን
ወይን፣ የበጋ ፍሬና ዘይት አምርቱ፤ በማከ
ማቻ ዕቃዎቻችሁ ውስጥ ክተቱ፤ በያዛችኋቸ
ውም ከተሞች ተቀመጡ::”

11በሞዓብ፣ በአሞን፣ በኤዶምና በሌ
ሎች አገሮች ሁሉ የነበሩ አይሁድ በሙሉ
የባቢሎን ንጉሥ፣ ሰዎችን በይሁዳ እንዳስ
ቀረና የሳፋን ልጅ የአኪቃምን ልጅ ጎዶ
ልያስን በላያቸው እንደ ሾመ በሰሙ ጊዜ፣
12ሁላቸውም ከተበታተኑበት አገር ሁሉ ወደ
ይሁዳ ምድር ተመለሱ፤ በምጽጳ ወደሚኖ
ረውም ወደ ጎዶልያስ መጡ፤ ወይንና
የበጋ ፍሬም በብዛት አከማቹ:: 13የቃሬያ
ልጅ ዮሐናንና ገና በየሜዳው የነበሩት
የጦር መኰንኖች ሁሉ ወደ ጎዶልያስ ወደ
ምጽጳ መጥተው፣ 14“የአሞናውያን ንጉሥ
በአሊስ አንተን ለመግደል የናታንያን ልጅ
እስማኤልን እንደ ላከው አታውቅምን?”
አሉት:: የአኪቃም ልጅ ጎዶልያስ ግን አላመ
ናቸውም::

15የቃሬያ ልጅ ዮሐናን፣ “ማንም ሳያውቅ
የናታንያን ልጅ እስማኤልን ሄጄ ልግደ
ለው፤ ሸሽተው ወደ አንተ የመጡት አይ
ሁድ እንዲበተኑ፣ በይሁዳም የቀሩት እን
ዲጠፉ ለምን ይገድልሃል?” ብሎ በምጽጳ
ለጎዶልያስ በምስጢር ነገረው::

16የአኪቃም ልጅ ጎዶልያስ ግን የቃሬያን
ልጅ ዮሐናንን፣ “ስለ እስማኤል የምትነ
ግረኝ ሁሉ እውነት አይደለምና ይህን
ነገር አታድርግ” አለው::

41 ከንጉሣዊ ቤተ ሰብ የሆነው ከንጉሡ
የጦር መኰንንኖች አንዱ የነበ
ረው የኤሊሳማ ልጅ የናታንያ ልጅ እስ
ማኤል፣ በሰባተኛው ወር ከዐሥር ሰዎች
ጋር ወደ ምጽጳ ወደ አኪቃም ልጅ ወደ
ጎዶልያስ መጣ፣ በዚያም በአንድነት ሊበሉ
በማእድ ተቀምጠው ሳለ፣ 2የናታንያ ልጅ
እስማኤልና አብረውት የነበሩ ዐሥሩ ሰዎች
ተነሥተው፣ የባቢሎን ንጉሥ በምድሪቱ
ላይ ገዥ አድርጎ የሾመውን የሳፋንን ልጅ
የአኪቃምን ልጅ ጎዶልያስን በሰይፍ
መቱት፤ ገደሉትም:: 3ደግሞም እስማኤል
በምጽጳ ከጎዶልያስ ጋር የነበሩትን አይ
ሁድ ሁሉ፣ በዚያም የተገኙትን የባቢሎን[ወ]
ወታደሮች ገደላቸው::

4ጎዶልያስ በተገደለ ማግስት፣ ማንም
ስለ ሁኔታው ከማወቁ በፊት፣ 5ሰማንያ
ሰዎች ጢማቸውን ተላጭተው፣ ልብሳቸውን
ቀደው፣ ገላቸውን ነጭተው የእህል ቍር
ባንና ዕጣን በመያዝ ከሴኬም፣ ከሴሎና
ከሰማርያ ወደ እግዚአብሔር ቤት ለማቅ
ረብ መጡ:: 6የናታንያ ልጅ እስማኤል
ሊገናኛቸው እያለቀሰ ከምጽጳ ወጣ፣ ሲያገ
ኛቸውም፣ “ወደ አኪቃም ልጅ ወደ ጎዶ
ልያስ ኑ” አላቸው:: 7ወደ ከተማዪቱ በገቡ
ጊዜ፣ የናታንያ ልጅ እስማኤልና አብረ
ውት የነበሩ ሰዎች ዐረዷቸው፤ በውሃ
ማጠራቀሚያ ጕድጓድ ውስጥም ጣሏ
ቸው:: 8ከተገደሉት ጋር የነበሩ ዐሥር
ሰዎች ግን እስማኤልን፣ “እባክህ አትግደ
ለን! በዕርሻችን ውስጥ የሸሸግነው ስንዴና
ገብስ፣ የወይራ ዘይትና ማር ስላለን እባክ
ህን አትግደለን” አሉት:: እርሱም ተዋ
ቸው፤ ከሌሎቹም ጋር አልገደላቸውም::
9እስማኤል ከጎዶልያስ በተጨማሪ የገደላ
ቸው ሰዎች ሁሉ ሬሳ የተጣለበት የውሃ
ማጠራቀሚያ ጕድጓድ ንጉሡ አሳ የእስራ
ኤልን ንጉሥ ባኦስን ስለ ፈራ ለመከላከል
ያሠራው ነበር፤ ይህን ጕድጓድ፤ የናታንያ
ልጅ እስማኤል በሬሳ ሞላው::

10እስማኤል በምጽጳ የቀረውን ሕዝብ
ሁሉ ምርኮኛ አደረገ፤ እነርሱም የባቢሎን
የክብር ዘበኞች አዛዥ ናቡሪዘረዳን የአ
ኪቃ ምን ልጅ ጎዶልያስን በላያቸው ገዥ
አድርጎ የሾመባቸው የንጉሡ ሴቶች ልጆ
ችና በዚያ የቀሩት ሌሎች ሰዎች ሁሉ
ነበሩ:: የናታንያ ልጅ እስማኤል እነዚህን
ማርኮ ወደ አሞናውያን ለመሻገር ተነሣ::

11የቃሬያ ልጅ ዮሐናና ከእርሱ ጋር
የነበሩት የጦር መኰንኖች ሁሉ የናታንያ
ልጅ እስማኤል የፈጸመውን ግፍ ሁሉ
በሰሙ ጊዜ፣ 12የናታንያን ልጅ እስማኤ
ልን ሊወጉ ሰዎቻቸውን ሁሉ ይዘው ሄዱ፤
በገባዖንም ባለው በታላቁ ኵሬ አጠገብ
ደረሱበት:: 13እስማኤል የያዛቸው ሰዎች
ሁሉ የቃሬያን ልጅ ዮሐናንንና አብረ
ውት የነበሩትን የጦር መኰንኖች ባዩ ጊዜ
ደስ አላቸው:: 14እስማኤል ከምጽጳ ማርኮ
የወሰዳቸው ሰዎች ሁሉ አምልጠው ወደ
ቃሬያ ልጅ ወደ ዮሐናን ገቡ:: 15የናታ
ንያ ልጅ እስማኤል ግን አብረውት ከነ
በሩት ስምንት ሰዎች ጋር ከዮሐናን አመ
ለጠ፤ ሸሽቶም ወደ አሞናውያን ገባ::

[ከ]8 የዕብራይስጡ *ያእዛንያን የያዛንያ* አቻ ስም ነው
[ኸ]9 ወይም *ከለዳያን*፤ ቍ10 ይመ
[ወ]3 ወይም *የከለዳውያን*

40፥9 ኤር5፥19፤ 27፥11፤38፥20፤ሰቆ 1፥1፤ሕዝ23፥23፤ሮሜ 13፥1-2፤ኤፌ6፥5-8
40፥10 ቍ6፤ዘፍ 27፥28፤ዘፀ7፥19፤ 23፥16፤ ዘዳ1፥39፤ 2ቆሮ4፥7
40፥11 ዘፍ25፥30፤ ዘኍ21፥11፤25፥1፤ ኤር12፥14
40፥12 ኤር43፥5
40፥13 ቍ8፤ኤር 42፥1
40፥14 ቍ8፤ዘፍ 19፥38፤2ሳሙ10፥1-19፤ኤር25፥21፤ 41፥10፤49፥1
40፥15 ቍ8፤ዘፍ 11፥4፤ዘሌ26፥33፤ ዘዳ5፥17፤2ነገ21፥14 ፤ኢሳ1፥9፤ማቴ5፥21-22፤26፥31፤ዮሐ11፥52 ፤ሮሜ11፥5፤ያዕ1፥1
40፥16 ኤር 43፥2
41፥1 ኤር 40፥8
41፥2 ኢሱ11፥10፤ 2ሳሙ3፥27፤20፥9-10 ፤መዝ41፥9፤109፥5፤ ኤር40፥5፡8፡15፤ዕብ 11፥37
41፥5 ዘፍ12፥6፤ 33፥18፤37፥29፤ዘሌ 10፥6፤19፥27፡28፤ ዘኍ16፥40፤ኢሱ 18፥1፤መሳ9፥1-57፤ 1ነገ3፥2፤6፥38፤ 12፥1፤16፥24፤2ነገ 25፥9፤ኤር47፥5፤ 48፥37፤ማር14፥63፤ ሉቃ1፥9
41፥6 2ሳሙ3፥16፤ መዝ5፥9፤ሆሴ7፥11፤ ራእ20፥10
41፥7 ዘፍ37፥24፤ 2ነገ10፥14
41፥8 ኢሳ45፥3
41፥9 መሳ6፥2፤ 1ነገ15፥22፤2ዜና 16፥1፡6
41፥10 ኤር38፥23፤ 40፥7፡12፡14
41፥11 ኤር40፥8
41፥12 ዘፀ14፥14፤ ኢሱ9፥3፤ዮሐ9፥7፤ 18፥36
41፥13 ቍ10
41፥14 ኤር40፥6
41፥15 ኢዮ21፥30፤ ምሳ28፥17

### ሽሽት ወደ ግብፅ

16የቃሬያ ልጅ ዮሐናንና ከእርሱ ጋር
የነበሩት የጦር መኰንንኖች ሁሉ የናታ
ንያ ልጅ እስማኤል የአኪቃምን ልጅ
ጎዶልያስን ከገደለ በኋላ፣ በምጽጳ ከማረካ
ቸው የተረፉትን ሰዎች በማስመለስ ይዘው
ሄዱ፤ እነዚህም፦ ወታደሮች፣ ሴቶች ሕፃ
ናትና ከገባዖን ያመጧቸው የቤተ መንግ
ሥት ባለ ሥልጣኖች ነበሩ። 17ከዚያም
ተነሥተው ሄዱ፤ ወደ ግብፅም በማምራት
በቤተልሔም አጠገብ ባለችው በጌሮት
ከመዓም ዐረፉ፤ 18ወደ ግብፅም የሄዱት ከባ
ቢሎናውያን[0] ለማምለጥ ነበር፤ ባቢሎናውያ
ንንም የፈሩት የናታንያ ልጅ እስማኤል
የባቢሎን ንጉሥ የምድሪቱ ገዥ አድርጎ
የሾመውን የአኪቃምን ልጅ ጎዶልያስን
በመግደሉ ነው።

42 የቃሬያን ልጅ ዮሐናንና የሆሻ
ያን ልጅ ያእዛንያን[ዘ] ጨምሮ፣
የጦር መኰንኖች ሁሉ እንዲሁም ሕዝቡ
ሁሉ ከትንሹ እስከ ትልቁ ቀርበው፣ 2ነቢዩ
ኤርምያስን እንዲህ አሉት፤ “ቀድሞ ብዙ
ዎች ነበርን አሁን እንደምታየን ግን የቀረ
ነው ጥቂት ነን፤ ስለዚህ እባክህ ልመናችንን
ስማ፤ ለዚህ ለተረፈው ሕዝብ ሁሉ ወደ
አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይ።
3አምላ ክህ እግዚአብሔር ወዴት መሄድ
እንዳለብ ንና ምን ማድረግ እንደሚገባን
እንዲነግ ረን ጸልይልን።”

4ነቢዩ ኤርምያስም፣ “ሰምቻችኋለሁ፤
እን ዳላችሁት ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚ
አብሔር በእርግጥ እጸልያለሁ፤ እግዚአብሐ
ር ያለ ኝን ሁሉ አንዳች ሳላስቀር እነግ
ራችኋ ለሁ” አላቸው።

5እነርሱም ኤርምያስን እንዲህ አሉት፤
“እግዚአብሔር አምላክህ በአንተ በኩል
የሚለውን ነገር ሁሉ ባናደርግ፣ እግዚአ
ብሔር ራሱ በእኛ ላይ እውነተኛና ታማኝ
ምስክር ይሁን። 6አምላካችንን እግዚአብሔ
ርን በመታዘዝ መልካም ይሆንልን ዘንድ
ነገሩ ቢስማማንም ባይስማማንም፣ አንተን
ወደ እርሱ የምንልክህን አምላካችንን እግዚ
አብሔርን እንታዘዛለን።”

7ከዐሥር ቀን በኋላ የእግዚአብሔር ቃል
ወደ ኤርምያስ መጣ። 8ስለዚህ የቃሬያን
ልጅ ዮሐናንንና፣ ከእርሱም ጋር የነበሩ
ትን የጦር መኰንኖች ሁሉ እንዲሁም ሕዝ
ቡን ሁሉ ከትንሽ እስከ ትልቅ ጠርቶ፤
9እንዲህ አላቸው፤ “ልመናችሁን በፊቱ
እንዳቀርብ ወደ እርሱ የላካችሁኝ የእስራ
ኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
10 ‘ባመጣሁባችሁ ጥፋት አዝኛለሁና በዚ
ህች ምድር ብትቀመጡ እሠራችኋለሁ
እንጂ አላፈርሳችሁም፤ እተክላችኋለሁ
እንጂ አልነቅላችሁም። 11አሁን የሚያስፈ
ራችሁን የባቢሎንን ንጉሥ አትፍሩ፤ አድ
ናችሁ ዘንድ ከእጁም አስጥላችሁ ዘንድ፤
እኔ ከእናንተ ጋር ነኝና አትፍሩ ይላል
እግዚአብሔር፤ 12እርሱ እንዲምራችሁና
ወደ አገራችሁ እንዲመልሳችሁ እኔ እም
ራችኋለሁ።’

13“እናንተ ግን፤ ‘በዚህች ምድር አንቀ
መጥም’ ብትሉና አምላካችሁን እግዚአብሐ
ር ን ባትታዘዙ፣ 14ደግሞም፣ ‘ጦርነት
ወደማናይበት፣ የመለከት ድምፅ ወደ
ማንሰማ በትና ወደማንራብበት ወደ ግብፅ
ምድር ሄደን በዚያ እንኖራለን’ ብትሉ፣
15እንግ ዲህ የይሁዳ ቅሬታ ሆይ፤ የእግዚ
አብሔ ርን ቃል ስሙ፤ የእስራኤል
አምላክ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤ ‘ወደ ግብፅ ለመሄድ
ወስናችሁ እዚያ ለመቀመጥ ብትሄዱ፣
16የፈራችሁት ሰይፍ በዚያ ያገኛችኋል፤ የ
ሠጋችሁበት ራብ እስከ ግብፅ ድረስ
ተከትሎአችሁ ይመ ጣል፤ በዚያም
ትሞታላችሁ። 17በዚያም ለመ ኖር ወደ ግብፅ
ለመሄድ የወሰኑ ሁሉ በሰ ይፍ፣ በራብና
በቸነፈር በእርግጥ ይሞ ታሉ፤ ከ
ማመጣባቸውም ጥፋት አንድ እንኳ
የሚተርፍ ወይም የሚያመልጥ አይ
ገኝም።’ 18የእስራኤል አምላክ የሰራዊት
ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦
‘ቍጣዬና መዓቴ በኢየሩሳሌም በሚኖሩት
ሁሉ ላይ እንደ ፈሰሰ፣ እንዲሁ ወደ
ግብፅ በገባችሁ ጊዜ መዓቴ በእናንተ ላይ
ይፈሳል፤ እናን ተም የመነቀፊያና የድንጋጠ
፣ የመረገሚ ያና የመዘባበቻ ምልክት
ትሆናላችሁ፤ ይህንም ስፍራ ዳግመኛ
አታዩም።’

19“እናንተ የይሁዳ ቅሬታ ሆይ፤ እግዚ
አብሔር፤ ‘ወደ ግብፅ አትሂዱ’ ብሎአች
ኋል፤ እኔም ዛሬ እንዳስጠነቀቅኋችሁ በእ
ርግጥ ዕወቁ፤ 20‘ወደ አምላካችን ወደ
እግዚአብሔር ጸልይልን፤ እርሱ ያለህን
ሁሉ ንገረን፤ እኛም እንታዘዛለን’ ብላችሁ
ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር
በላካችሁኝ ጊዜ
ሕይወታችሁን የሚያጠፋ ስሕተት[ፐ] ፈጽማ
ችሁ። 21እነሆ፤ ዛሬ በግልጥ ነገርኋችሁ፤
እናንተ ግን እግዚአብሔር አምላካችሁ
ልኮኝ

41፥16 ኢሳ1፥9፤ ኤር42፥1፤43፥2፥4፤ ሕዝ7፥16፤14፥22፤ ሶፎ2፥9
41፥17 ዘፍ35፥19፤ 2ሳሙ19፥37፤ኤር 42፥14፤ሚክ 5፥2
41፥18 ዘኍ14፥9፤ 2ነገ25፥22፤ኢሳ 51፥12፤ኤር42፥16፤ ሉቃ12፥4-5
42፥1 ኤር6፥13፤ 40፥13፤41፥16፤ 44፥12
42፥2 ዘፍ20፥7፤ ዘሌ26፥22፤ኢሳ1፥9፤ ኤር36፥7፤ሰቆ1፥1፤ ሐሥ8፥24፤ያዕ5፥16
42፥3 ቀኍ20፤መዝ 86፥11ምሳ3፥6፤ኤር 15፥11
42፥4 ዘፀ8፥29፤ዘኍ 22፥18፤1ሳሙ3፥17 ፤12፥23፤ኤር1፥17
42፥5 ዘፍ31፥48፤ ዘዳ4፥26፤7፥9፤1ነገ 22፥16፤መዝ119፥ 160፤ኢሳ1፥2፤ዮሐ 8፥26፤ሮሜ1፥9፤3፥4፤ 1ቆሮ1፥9፤ራእ 1፥5
42፥6 ቀኍ19፤ዘፀ 24፥7፤ዘዳ5፥29፤ 6፥3፤ኢሱ24፥24፤ ኤር7፥23፤ 2፥15
42፥8 ቀኍ1፤ኤር 41፥16፤ማር9፥35፤ ሉቃ7፥28፤ዕብ8፥11
42፥9 ቀኍ2፤2ነገ 22፥15
42፥10 ዘዳ29፥28፤ 30፥9፤2ዜና34፥24፤ መክ3፥2፤ኢሳ30፥26፤ ኤር18፥8፤24፥6፤ 43፥4፤ 45፥4፤ሕዝ 36፥36፤ዳን 1፥4
42፥11 ዘኍ14፥9፤ 1ሳሙ15፥24፤መዝ 3፥7፤18፥27፤23፥4፤ 69፥35፤119፥94፤ምሳ 20፥22፤ኢሳ63፥1፤ ኤር1፥8፤27፥11፤ማቴ 10፥28፤ሮሜ8፥31፤ 2ጢሞ1፥7፤ዕብ7፥25
42፥12 ዘፍ31፥3፤ ዘፀ3፥21፤2ሳሙ24፥ 14፤ነህ1፥9፤መዝ106፥ 44-46፤2ቆሮ1፥3
42፥13 ዘዳ11፥28
42፥14 ዘኍ11፥4-5 ፤ዘዳ8፥3፤17፥16፤ኢሱ 6፥20፤1ሳሙ2፥5፤ምሳ 10፥3፤ኢሳ30፥2፤65፥ 13፤ማቴ4፥2-4፤ 24፥31
42፥15 ኤር44፥24
42፥16 ዘፍ41፥55፤ 2፥17፤ዘሌ26፥33፤2ዜና25፥4፤ኢዮ21፥20፤ ኤር41፥18፤ሕዝ3፥19 ፤11፥8፤14፥17፤18፥4
42፥17 ቀኍ22፤ኤር 21፥7፤44፥13
42፥22 ቀኍ17፤ኢሳ 1፥28፤ኤር15፥2፤

42፥18 ዘኍ5፥27፤ዘዳ28፥25፤37፤29፥18-20፤2ዜና12፥7፤36፥19፤ መዝ44፥13፤ኤር22፥10፤25፥18፤39፥1-9 42፥19 ቀኍ6፤ዘዳ 17፥16፤ኢሳ30፥7፤ኤር40፥15፤43፥2፤44፥16 42፥20 ቀኍ2፤ሕዝ 14፥7-8 42፥21 ዘፀ24፥7፤ኤር40፥3፤ሕዝ2፥7፤12፥2፤ዘካ7፥11-12

[0]18 ወይም ከለዳውያን
[ዘ]1 የዕብራይስጡና የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች (43፥2 ይመ) አዛርያ ይላሉ [ፐ]20 ወይም በልባችሁ ስሕተት ሠራችሁ

የነገርኋችሁን ሁሉ አሁንም አልታዘዛች
ሁም፤ 22እንግዲህ ሄዳችሁ ልትኖሩበት በፈ
ለጋችሁት ስፍራ በሰይፍ፣ በራብና በቸነ
ፈር እንደምትሞቱ በእርግጥ ዕወቁ።”

43 ኤርምያስ፣ እግዚአብሔር ለእነ
ርሱ እንዲነግራቸው የላከውን የአ
ምላካቸውን *የእግዚአብሔርን* ቃል ሁሉ
ለሕዝቡ ተናግሮ በጨረሰ ጊዜ፣ 2የሆሽያ
ልጅ ዓዛርያስ፣ የቃሬያ ልጅ ዮሐናንና
ትዕቢተኞች የሆኑ ሰዎች ሁሉ ኤርምያስን
እንዲህ አሉት፤ “ትዋሻለህ! አምላካችን *እግዚ
አብሔር* ‘እዚያ ለመኖር ወደ ግብፅ አት
ሂዱ ብለህ ንገራቸው’ ብሎ አልላከህም፤
3ነገር ግን ባቢሎናውያን እንዲገድሉን
ወይም ማርከው ወደ ባቢሎን እንዲወስ
ዱን ለእነርሱ[የ] አሳልፈህ ትሰጠን ዘንድ
የኔርያ ልጅ ባሮክ በእኛ ላይ አነሣሥቶ
ሃል።”

4ስለዚህ የቃሬያ ልጅ ዮሐናንና፣
የጦር መኰንኖቹ ሁሉ እንዲሁም ሕዝቡ
በሙሉ *እግዚአብሔር* በይሁዳ ምድር እን
ዲቀመጡ ያዘዛቸውን ቃል አልሰሙም።
5ነገር ግን፣ የቃሪያ ልጅ ዮሐናንና የጦር
መኮንኖቹ ሁሉ፣ በይሁዳ ምድር ለመቀ
መጥ ከተበተኑበት ከአሕዛብ ሁሉ መካከል
የተመለሱትን የይሁዳን ቅሬታዎች ሁሉ
ይዘው ሄዱ፤ 6በተጨማሪም ወንዶችን፣
ሴቶችንና ሕፃናትን እንዲሁም የክብር ዘበ
ኞች አዛዥ ናቡዘረዳን በአኪቃም ልጅ
በጎዶልያስ እጅ የተዋቸውን የንጉሡን ሴቶች
ልጆች፣ ነቢዩ ኤርምያስንና የኔርያን ልጅ
ባሮክን ወሰዷቸው፤ 7*የእግዚአብሔርንም*
ቃል ባለመታዘዝ ወደ ግብፅ ገቡ፤ ዘልቀ
ውም እስከ ጣፍናስ ድረስ ሄዱ።

8በጣፍናስም *የእግዚአሔር* ቃል ወደ
ኤርምያስ እንዲህ ሲል *መጣ*፤ 9“ትልልቅ
ድንጋዮች ውሰድና በጣፍናስ ባለው የፈር
ዖን ቤተ መንግሥት በር ላይ የይሁዳ
ሰዎች
እያዩ በሸክላ ጡብ ወለል ውስጥ ቅበራ
ቸው፤ 10እንዲህም በላቸው፤ ‘የእስራኤል
አምላክ የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤ አገልጋዬን የባቢሎንን ንጉሥ ናቡ
ከደነፆርን እንዲመጣ አደርጋለሁ፤ ዙፋኑ
ንም እዚህ በቀበርኋቸው ድንጋዮች ላይ
እዘረጋለሁ፤ የንጉሥ ድንኳኑንም በላያቸው
ይተክላል። 11እርሱም መጥቶ ግብፅን ይወ
ጋል፤ ሞት የሚገባቸውን ለሞት፣ ለምርኮ
የተመደቡትን ወደ ምርኮ፣ ለሰይፍ የተዳ
ረጉትን ለሰይፍ አሳልፎ ይሰጣል። 12እርሱ
የግብፅ አማልክት ቤተ ጣዖቶች ላይ
እሳት ይለኵሳል፤ ያቃጥላቸዋልም፣ አማል
ክታቸውንም ማርኮ ይወስዳል። እረኛ

24፥10፤ሕዝ6፥11፤
ሆሴ9፥6
43፥1 ኤር26፥8፤
42፥9-22
43፥2 ዘፍ19፥14፤
ዘፀ24፥7፤ዘዳ 13፥3፤
2ነገ25፥24፤ነህ9፥29፤
ኤር18፥19፤40፥16፤
41፥16፤42፥19፤ሕዝ
37፥14፤ሮሜ9፥1፤
1ቆሮ4፥18-21፤2ቆሮ
11፥31፤1ጢሞ2፥7
43፥3 ኤር32፥12፤
38፥4፤41፥18፤52፥30
43፥4 2ዜና25፥16፤
ኤር41፥16፤42፥5-6፥10
43፥5 ኤር40፥12
43፥6 ኤር6፥12፤
32፥12
43፥7 2ነገ25፥26፤
ኤር2፥16፤44፥1፤
46፥14፤ሕዝ30፥18
43፥8 መዝ139፥7፤
ኤር2፥16
43፥9 ዘፍ11፥3፤
31፥45-53፤47፥14
፤ኢሱ4፥1-7፤1ነገ
18፥31-32
43፥10 መዝ18፥11
፤ኢሳ44፥28፤45፥1፤
ኤር25፥9፤27፥6፤
46፥13፤49፥38
43፥11 ዘዳ28፥64፤
ምሳ11፥19፤መዝ
49፥14፤ኤር15፥2፤
46፥13-26፤ሕዝ
29፥19-20፤32፥11፤
ዘካ11፥9፤ሮሜ6፥23፤
ዕብ 9፥27፤ራእ13፥10
43፥12 ቀኍ13፤ ዘፀ
12፥12፤ኢሱ7፥15፤
1ነገ16፥32፤መዝ104፥
2፤109፥18-19፤ኢሳ
2፥18፤ኤር46፥25፤
ሕዝ30፥13፤ዳን11፥8
፤ዘካ13፥2
43፥13 ዘፍ1፥16፤
ዘዳ4፥19፤ኢሳ19፥18፤
ኤር52፥17፤ሕዝ26፥11
44፥1 ዘፀ14፥2፤
ዘዳ32፥42፤ኢሳ11፥11፤
19፥13፤ኤር43፥7
፥8፤24፥8
44፥2 ዘሌ26፥31፤
ዘዳ29፥23፤2ዜና34፥24፤
ኢሳ6፥11፤ኤር40፥5
44፥3 ቀኍ8፤ዘፀ32፥
22፤ዘኍ11፥33፤16፥
40፤25፥3፤ዘዳ13፥6-
11፤29፥26፤መሳ2፥19፤
ኢሳ19፥1
44፥4 ዘኍ11፥29፤
ዘዳ18፥9፤1ነገ14፥24፤
ኤር7፥13፤1ጴጥ4፥3
44፥5 ቀኍ21፤ዘፍ
6፥5፤ ኤር1፥16፤11፥
8-10፤25፥4፥7፤ሕዝ
8፥11፤16፥18፤23፥41፤
ዳን9፥6፤ሮሜ1፥18፤
2ጢሞ2፥19

ልብሱን እንደሚጐናጸፍ የግብፅን ምድር
ተጐናጽፎ ከዚያ በሰላም ይሄዳል።[ደ] 13በግ
ብፅ ምድር የሚገኙትን የፀሓይ[ጀ] አምላክ
ቤተ ጣዖት ሐውልቶች ይሰባብራል፤ የግ
ብፅንም አማልክት ቤተ ጣዖቶች በእሳት
ያቃጥላል።

## ጣዖትን ማምለክ ያስከተለው ጥፋት

44 በግብፅ ሰሜናዊ ክፍል በሚግ
ዶል፣ በጣፍናስና በሜምፎስ[ገ] እን
ዲሁም በግብፅ ደቡባዊ ክፍል[ጠ] ስለሚኖ
ሩት የአይሁድ ሕዝብ እንዲህ የሚል ቃል
*ከእግዚአብሔር* ዘንድ ወደ ኤርምያስ
*መጣ*፤ 2“የእስራኤል አምላክ የሰራዊት
ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ በኢ
የሩሳሌ ምና በይሁዳ ከተሞች ሁሉ ላይ
ያመጣሁ ትን ታላቅ ጥፋት
አይታችኋል፤ ዛሬ ማንም የ
ማይኖርባቸው ባድማ ሆነው ይታ ያሉ፤
3ይህም የሆነው ስላደረጉት ክፋት ነው።
እነርሱም ሆኑ እናንተ ወይም አባቶቻ ችሁ
ላላወቋቸው ለሌሎች አማልክት በማጠንና
በማምለክ አስቈጥተውኛል። 4እኔም፣
‘ይህን የምጠላውን አስጸያፊ ነገር አታድ
ርጉ’ በማለት አገልጋዮቼን ነቢያትን ደጋ
ግሜ ላክሁባቸው። 5እነርሱ ግን አልሰ
ሙም፤ ልብም አላሉም፤ ከክፋታቸው አል
ተመለሱም፤ ለሌሎችም አማልክት ማጠን
አልተውም። 6ስለዚህ መዓቴና ቍጣዬ
ፈሰሰ በይሁዳ ከተሞችና በኢየሩሳሌም
መንገዶች ላይ ነደደ፤ ዛሬ እንደሚታዩትም
ማንም የማይኖርባቸው ፍርስራሾች አደረ
ጋቸው።

7“አሁንም የእስራኤል አምላክ የሰራዊት
ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ ‘ዘር
እንዳይቀርላችሁ ወንዶችና ሴቶች፣ ልጆ
ችና ሕፃናት በይሁዳ እንዳይገኙ ለምን
እንዲህ ዐይነት ታላቅ ጥፋት በራሳችሁ
ላይ ታመጣላችሁ? 8ልትኖሩባት በመጣች
ሁባት በግብፅ ምድር ለሌሎች አማልክት
በማጠን፣ እጆቻችሁ ባበጇቸው ነገሮች
ለምን ታስቈጡኛላችሁ? በምድር ባሉት
ሕዝቦች ሁሉ ዘንድ የርግማንና የመዘባ
በቻ ምልክት ለመሆን ራሳችሁን ታጠፋ
ላችሁን? 9በይሁዳ ምድርና በኢየሩሳሌም

44፥6 ዘሌ26፥31፥34፤ዘዳ29፥23፤ሰቆ1፥13፤ሕዝ8፥18፤20፥34፤
ዘካ7፥14 44፥7 2ነገ21፥14፤ኤር26፥19፤51፥22 44፥8 ቀኍ3፥17-25፤
ዘፀ12፥12፤መዝ44፥13፤ኢሳ40፥18-20፤ኤር10፥3፤41፥5፤ሮሜ1፥23፤
1ቆሮ10፥22 44፥9 ቀኍ17፥21፤መሳ2፥19፤1ነገ21፥25፤2ነገ23፥11፤
ምሳ31፥10፤ኤር6፥12፤11፥12፤32፥32

[የ]3 ወይም *ከለዳውያን*
[ደ]12 ወይም እኔ *እለኵሳለሁ፤ … አቃጥላለሁ፤ … እወስዳለሁ፤*
[ጀ]13 ወይም *በሔሎፖሊስ/ በፀሓይ ከተማ*
[ገ]1 ዕብራይስጡ *ኖፍ*
[ጠ]1 ዕብራይስጡ *ከጳትሮስ*

መንገዶች አባቶቻችሁ የይሁዳ ነገሥታትና
ሚስቶቻቸው፣ እንዲሁም እናንተና ሚስቶ
ቻችሁ ያደረጋችሁትን ክፋት ረስታችሁታ
ልን? 10እስከ ዛሬ ድረስ ራሳቸውን ዝቅ
በማድረግ ክብርን አልሰጡኝም፤ በእናን
ተና በአባቶቻችሁ ፊት ያኖርሁትንም
ሕጌንና ሥርዐቴን አልተከተሉም።’
11“ስለዚህ የእስራኤል አምላክ የሰራዊት
ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ ‘በእና
ንተ ላይ ጥፋት ለማምጣትና ይሁዳን ሁሉ
ለመደምሰስ ቈርጬ ተነሥቻለሁ። 12ሄደው
በግብፅ ለመቀመጥ የወሰኑትን የይሁዳ
ቅሬታዎች ሁሉ እነጥቃለሁ፤ ሁሉም ይጠ
ፋሉ፤ በግብፅ ምድር በሰይፍ ይወድቃሉ፤
በራብ ያልቃሉ፤ ከትንሽ እስከ ትልቅ
በሰይፍና በራብ ይሞታሉ፤ የመነቀፊያና
የድንጋጤ፣ የመረገሚያና የመዘባበቻ ምል
ክት ይሆናሉ። 13ኢየሩሳሌምን
እንደቀጣሁ፣ በግብፅ የሚኖሩትን በሰይፍ፣
በራብና በቸ ነፈር እቀጣለሁ፤ 14ወደ ግብፅ
የመጡት የይሁዳ ቅሬታዎች ወደ ይሁዳ
ለመመለስ ቢመኙም ከጥቂት ስደተኞች
በስተቀር አምልጦ ወይም ተርፎ ወደ
ይሁዳ የሚ መለስ አንድም ሰው
አይኖርም።’ ”
15ሚስቶቻቸው ለሌሎች አማልክት ማጠ
ናቸውን ያወቁ ወንዶች ሁሉና በዚያ የነ
በሩት ሴቶች ሁሉ ይህም ማለት በሰሜ
ንና በደቡብ ግብፅ^ጪ^ የሚኖረው ሕዝብ ሁሉ
ታላቅ ጉባኤ ሆነው ለኤርምያስ እንዲህ
አሉት፤ 16“አንተ *በእግዚአብሔር* ስም የነ
ገርኸንን መልእክት አንሰማም፤ 17እናደርጋ
ለን ያልነውን ሁሉ እናደርጋለን፤ አባቶቻ
ችን፣ ነገሥታታችንና ባለ ሥልጣኖቻችን
በይሁዳ ከተሞችና በኢየሩሳሌም መንገ
ዶች እንዳደረጉት ሁሉ እኛም ለሰማይዋ
ንግሥት እናጥናለን፤ የመጠጥ ቍርባን
እናፈስላታለን። በዚያን ጊዜ የተትረፈረፈ
ምግብ ነበረን፤ በመልካም ሁኔታ እንገኝ
ነበር እንጂ ምንም ክፉ ነገር አልገጠመ
ንም። 18ነገር ግን ለሰማይዋ ንግሥት ማጠ
ንና የመጠጥ ቍርባን ማፍሰስ ከተውን
ወዲህ፣ ሁሉን ነገር አጥተናል፤ በሰይፍና
በራብም እያለቅን ነው።
19ሴቶቹም፣ “ለሰማይዋ ንግሥት በም
ናጥንበት ጊዜና የመጠጥ ቍርባን በምናፈስ
በት ጊዜ የጋገርነውንና እንደ ምስሏ ያለ ዕን
ጐቻ ያፈሰስነውንም የመጠጥ ቍርባን ባሎ
ቻችን ሳያውቁት ኖሮአልን?” አሉ።
20ኤርምያስ ይህን መልስ ለሰጠው
ሕዝብ፣ ለወንዶችና ለሴቶች ሁሉ እንዲህ
አለ፤ 21“እናንተና አባቶቻችሁ፣ ነገሥታታ
ችሁና ባለሥልጣኖቻችሁ እንዲሁም የምድ
ሪቱ ሕዝብ በይሁዳ ከተሞችና በኢየሩ
ሳሌም መንገዶች ያጠናችሁትን *እግዚአ
ብሔር* የማያስታውሰውና የዘነጋው ይመስ
ላችኋልን? 22*እግዚአብሔር* ክፉ አድራጎታ
ችሁንና አስጸያፊ ተግባራችሁን ሊታገሥ
ባለመቻሉ፣ ዛሬ እንደ ሆነው ምድራችሁ
የርግማን ምልክት፣ ሰው የማይኖርበት
ባዶ ምድረ በዳ ሆኖአል። 23ዕጣን በማጠን
*በእግዚአብሔር* ላይ ኀጢአት ስለ ሠራች
ሁና ቃሉን ስላልጠበቃችሁ ሕጉን፣ ሥር
ዐቱንና ትእዛዙን ስላላከበራችሁ ዛሬ እንደ
ምታዩት ጥፋት መጥቶባችኋል።”
24ኤርምያስም ለሕዝቡና ለሴቶቹ ሁሉ
እንዲህ አለ፤ “በግብፅ የምትኖሩ የይሁዳ
ሕዝብ ሁሉ፤ *የእግዚአብሔርን* ቃል ስሙ።
25የእስራኤል አምላክ የሰራዊት ጌታ *እግዚ
አብሔር* እንዲህ ይላል፤ እናንተና ሚስቶ
ቻችሁ፣ ‘ለሰማይዋ ንግሥት ለማጠንና
የመጠጥ ቍርባን ለማፍሰስ የተሳልነውን
ስእለታችንን በእርግጥ እንፈጽማለን’ ብላ
ችሁ የገባችሁትን ቃል በተግባር አሳይታ
ችኋል።’
“እንግዲያውስ ወደ ኋላ አትበሉ፤ ቃል
የገባችሁትን፤ ስእለታችሁንም ፈጽሙ።
26በግብፅ የምትኖሩ አይሁድ ሁሉ *የእግዚ
አብሔርን* ቃል ስሙ፤ ‘*እግዚአብሔር* እን
ዲህ ይላል “ከእንግዲህ ወዲህ በየትኛውም
የግብፅ ክፍል የሚኖር ማንኛውም አይሁ
ዳዊ፣ ‘ሕያው *እግዚአብሔርን*!’ ብሎ ስሜ
ን እንዳይጠራ፣ እንዳይምልም በታላቁ
ስሜ ምያለሁ፤ 27ለመልካም ሳይሆን ለክፉ
እተ ጋባቸዋለሁና፤ በግብፅ የሚኖሩ
አይሁድ ፈጽሞ እስኪጠፉ ድረስ
በሰይፍና በራብ ይደመሰሳሉ። 28ከሰይፍ
አምልጠው፣ ከግ ብፅ ወደ ይሁዳ ምድር
የሚመለሱት በጣም ጥቂት ሰዎች
ይሆናሉ። በግብፅ ምድር ለመኖር የመጠ
ት የይሁዳ ቅሬታ ሁሉ፣ ከእኔ ወይም
ከእነርሱ የማንኛችን ቃል እንደሚጸና
ያውቃሉ።
29“ ‘በእናንተ ላይ አመጣለሁ ያልሁትን
ክፉ ነገር እንደሚፈጸም ታውቁ ዘንድ በዚህ
ስፍራ እንደምቀጣችሁ ይህ ምልክት ይሁ
ናችሁ’ ይላል *እግዚአብሔር*። 30*እግዚአብሐ
ር* እንዲህ ይላል፦ ‘የይሁዳን ንጉሥ
ሴዴቅያ ስን ሊገድለው ለፈለገው ጠላቱ
ለባቢሎን
ንጉሥ ለናቡከደናፆር አሳልፌ እንደ ሰጠሁ፣
እንዲሁ የግብፅን ንጉሥ ፈርዖን ሖፍራን ሊገ

44፥10 ዘሌ18፥4፤ ዘዳ6፥13፤8፥3፤1ነገ 9፥6-9፤2ነገ17፥17፤ ኢሱ1፥7፤ መዝ5፥7፤ ኤር11፥8፤ማቴ5፥17-20፤23፥12፤ገላ3፥19፤ ፊል2፥8፤1ዮሐ3፥4
44፥11 2ዜና34፥24፤ አሞ9፥4፤ራእ4፥8
44፥12 ቍ7፤ዘዳ28፥25፤ኢሳ1፥28፤ኤር29፥18፤40፥15፤42፥1
44፥13 ዘፀ32፥24፤ ዘሌ26፥14-17፤ኤር 15፥2፤42፥17
44፥14 ኤር22፥24-27፤49፥5፤ሰቆ4፥15፤ ሕዝ6፥8፤ሮሜ9፥27
44፥15 ዘፍ3፥6፤ ምሳ31፥10፤ኢሳ11፥11፤ኤር6፥12፤18፥15፤ 1ጢሞ2፥14
44፥16 1ሳሙ8፥19፤ኢዮ15፥25-26፤ኤር 11፥8-10፤42፥19
44፥17 ቍ9፥25፥28፤ዘፀ16፥3፤ዘኍ11፥4-6፤ዘዳ23፥23፤ነህ9፥34፤ ኢዮ21፥15፤ኢሳ3፥9፤ 65፥3፤ኤር2፥26፤11፥12፤ሆሴ2፥5-13፤9፥1፤ ዘካ 1፥6
44፥18 ዘሌ23፥18፤ ኤር42፥16፤ሚል 3፥13-15
44፥19 ዘፍ3፥6፤ዘሌ 7፥12፤26፥1፤ኤር18፥15፤7፥18፤ሐሥ17፥29፤ኤፌ5፥22
44፥21 ቍ9፤መዝ 79፥8፤ኢሳ64፥9፤ኤር 2፥26፤11፥13፤14፥10፤ ሆሴ8፥13
44፥22 ዘፍ19፥13፤ ዘሌ26፥31፥32፤መዝ 107፥33-34፤ኢሳ1፥14፤ኤር25፥18፤ሕዝ 33፥28-29
44፥23 ዘሌ18፥4፤ 26፥33፤1ነገ9፥6፥9፤ ኤር7፥13-15፤40፥2፤ሕዝ39፥23፤ዳን 9፥11-12
44፥24 ዘፍ3፥6፤ ኤር43፥7
44፥25 ቍ17፤ዘዳ 32፥38፤ምሳ20፥25፤ 31፥10፤ሕዝ20፥39፤ ያዕ 1፥13-15
44፥26 ዘፍ15፥2፤ 22፥16፤ዘዳ32፥40፤ መዝ50፥16፤ኢሳ48፥1፤ኤር24፥8፤4፥2፤ሐሥ 19፥13፤ዕብ6፥13-17
44፥27 ዘፍ41፥15፤ ዘሌ26፥38፤ኢዮ15፥22፤ኤር1፥12፤9፥16፤ 21፥10፤ዳን9፥14፤አሞ 9፥8፤2ጴጥ3፥9
44፥28 ቍ13-4፥17፥25-26፤2ነገ21፥14፤ ኢሳ7፥9፤10፥19፤ኤር39፥16፤42፥15-18፤45፥5፤ሕዝ6፥8 44፥29 ዘፍ24፥14፤ዘፀ3፥12፤ 32፥34፤ዘኍ16፥38፤ምሳ19፥21፤ማቴ12፥38፤24፥3 44፥30 2ነገ 25፥1-7፤ኤር24፥8፤25፥19፤43፥9-13፤46፥26፤ሕዝ30፥21፤32፥32

ጪ15 ዕብራይስጡ በግብፅና በጳጥሮስ ይላል።

ድሉት ለሚፈልጉ ጠላቶቹ አሳልፌ እሰጠ
ዋለሁ።’ ”

## ለባሮክ የተነገረ መልእክት

45 በይሁዳ ንጉሥ በኢዮስያስ ልጅ
በኢዮአቄም ዘመነ መንግሥት በአ
ራተኛው ዓመት፣ ኤርምያስ በቃል የነገረ
ውን ባሮክ በብራና ላይ ከጻፈ በኋላ፣ ነቢዩ
ኤርምያስ ለኔርያ ልጅ ለባሮክ የተናገረው
ይህ ነው፤ 2“ባሮክ ሆይ፤ የእስራኤል አም
ላክ የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይልሃል፤ 3አንተ፣ ‘*እግዚአብሔር* በሕመሜ
ላይ ሐዘን ጨምሮብኛልና ወዮልኝ፤ ከልቅ
ሶዬ ብዛት የተነሣ ደክሜያለሁ፤ ዕረፍትም
የለኝም’ ብለሃል።”

4*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ “እንዲህ
በለው፤ ‘*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
በምድር ሁሉ የገነባሁትን አፈርሳለሁ፤ የተ
ከልሁትን እነቅላለሁ። 5ታዲያ፣ ለራስህ
ታላቅ ነገር ትሻለህን? በሰው ልጆች ሁሉ
ላይ ጥፋት አመጣለሁና አትፈልገው፤
ይላል *እግዚአብሔር*፤ ነገር ግን በሄድህበት
ሁሉ ሕይወትህ እንዲተርፍልህ አደርጋ
ለሁ።’ ”

## ስለ ግብፅ የተነገረ መልእክት

46 ስለ ሕዝቦች ወደ ነቢዩ ወደ ኤር
ምያስ የመጣው *የእግዚአብሔር*
ቃል ይህ ነው፤

2ስለ ግብፅ ፤

በይሁዳ ንጉሥ በኢዮስያስ ልጅ በኢዮአ
ቄም ዘመነ መንግሥት በአራተኛው ዓመት
በኤፍራጥስ ወንዝ በከርከሚሽ የባቢሎን
ንጉሥ ናቡከደነፆር ባሸነፈው በግብፅ ንጉሥ
በፈርዖን ኒካዑ ሰራዊት ላይ የተነገረ መል
እክት ይህ ነው፤

3“ትልቁንና ትንሹን ጋሻ አዘጋጁ፤
ለውጊያም ውጡ!
4ፈረሶችን ጫኑ፤
በላያቸውም ተቀመጡ፤
የራስ ቍር ደፍታችሁ፣
በየቦታችሁ ቁሙ፤
ጦራችሁን ወልውሉ፤
ጥሩራችሁን ልበሱ!
5ነገር ግን ይህ የማየው ምንድነው?
እጅግ ፈርተዋል፤
ወደ ኋላ እያፈገፈጉ ነው፤
ብርቱ ጦረኞቻቸው ተሸንፈዋል፤
ዘወር ብለውም ሳያዩ፣
በፍጥነት እየሸሹ ነው፤
በየቦታውም ሽብር አለ፣”
ይላል *እግዚአብሔር*።

6“ፈጣኑ መሸሽ አይችልም፤
ብርቱውም አያመልጥም፤
በሰሜን በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ፣
ተሰናክለው ወደቁ።

7“ይህ እንደ ዐባይ ወንዝ ሙላት
የሚዘለው፣
እንደ ደራሽ ወንዝ የሚፈሰው ማነው?
8ግብፅ እንደ ዐባይ ወንዝ ሙላት ይዘላል፤
እንደ ደራሽ ወንዝ ይወረወራል፤
‘እወጣለሁ፤ ምድርንም እሸፍናለሁ፤
ከተሞችንና ነዋሪዎቻቸውን
አጠፋለሁ’ ይላል።
9ፈረሶች ሆይ ዘላችሁ ውጡ!
ሠረገሎችም ሽምጥጡ፤
ጋሻ ያነገባችሁ የኢትዮጵያና*
የፉጥ ሰዎች፣
ቀስት የገተራችሁ የሉድ ጀግኖች፣
እናንተ ብርቱ ጦረኞች ተነሥታችሁ
ዝመቱ።
10ያ ቀን ግን የሰራዊት ጌታ *የእግዚአ
ብሔር* ቀን ነው፤
ጠላቶቹን የሚበቀልበት የበቀል ቀን።
ሰይፍ እስኪጠግብ ድረስ ይበላል፤
ጥማቱም እስኪረካ ድረስ ደም
ይጠጣል።
በሰሜን ምድር በኤፍራጥስ ወንዝ
አጠገብ፣
የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* መሥዋዕት
አዘጋጅቶአልና።

11“ድንግሊቱ የግብፅ ሴት ልጅ ሆይ፤
ወደ ገለዓድ ውጪ፤ የሚቀባ
መድኀኒትም አምጪ፤
ነገር ግን መድኀኒት የምታበዢው በከንቱ
ነው፤
ፈውስ አታገኚም።

12ሕዝቦች ኀፍረትሽን ይሰማሉ፤
ልቅሶሽም ምድርን ይሞላል።
ጦረኛ በጦረኛው ይደናቀፋል፤
ሁለቱም ተያይዘው ይወድቃሉ።”

13የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደናፆር መጥቶ
ግብፅን እንደሚወጋ፣ *እግዚአብሔር* ለነ
ቢዩ ለኤርምያስ የተናገረው መልእክት ይህ
ነው፤

14“ይህን በግብፅ ተናገር፤ በሚግዶልም
አሰማ፤
በሜምፎስና* በጣፍናስም እንዲህ ብለህ
ዐውጅ፤
በቦታችሁ ቁሙ፤ ተዘጋጁም፤
በዙሪያችሁ ያሉትን ሰይፍ

45፥1 ዘፀ17፥14፤ 2ዜና36፥5፤መዝ40፥7፤ ኤር32፥12፤51፥59
45፥3 ኢሱ1፥13፤ ኢዮ6፥10፤23፥2፤መዝ 69፥3፤119፥28፤ኢሳ 24፥16፤ማቴ11፥28፤ ማር14፥34፤ሮሜ9፥2፤ 1ቆሮ9፥16፤ዕብ4፥3
45፥4 ዘዳ28፥63፤ 30፥9፤ኢሳ5፥5-7፤ ኤር11፥17፤18፥7-10 ፤42፥10
45፥5 መዝ68፥20፤ 131፥1፤ኤር2፥35፤ 11፥11፤21፥9፤40፥2፤ 44፥28፤ማቴ6፥25-27 ፥33
46፥1 ኤር1፥10
46፥2 ዘፍ2፥14፤ዘፀ 1፥8፤2ነገ23፥29፤2ዜና 35፥20፤ኤር1፥3፤25፥1 ፤35፥1፤36፥1፤45፥1፤ ዳን 1፥1
46፥3 ኢሳ21፥5
46፥4 1ሳሙ17፥5፥ 38፤2ዜና26፥14፤ነህ 4፥16፤ሕዝ21፥9-11
46፥5 ቀኑ21፤መዝ 31፥13፤48፥5፤ኤር 48፥44
46፥6 ቀኑ12፥16፤ ዘፍ2፥14፤15፥18፤ መዝ20፥8፤ኢሳ30፥16
46፥7 ኤር47፥2
46፥8 ሕዝ29፥3፥9፤ 30፥12፤አሞ8፥8፤ዳን 11፥10
46፥9 ዘፍ10፥6፤ኢሳ 66፥19፤ኤር47፥3፤ ሕዝ26፥10፤ናሆ3፥2
46፥10 ዘፍ2፥14፤ 15፥18፤ዘሌ3፥9፤ዘኍ 31፥3፤ዘዳ32፥41፤ 2ሳሙ2፥26፤2ነገ23፥ 29-30፤ሕዝ32፥10፥ 42፤ኢል1፥15፤ አብ 1፥15፤ሶፎ1፥7፤2፥12፤
46፥11 ዘፍ37፥25፤ 2ነገ19፥21፤ኤር 30፥13፤ሚክ1፥9
46፥12 ቀኑ6፤ኢሳ 19፥4፤ናሆ3፥8-10
46፥13 ቀኑ26፤ኢሳ 19፥1፤ኤር27፥7፤ሕዝ 32፥11
46፥14 ዘዳ32፥42፤ 2ሳሙ2፥26፤ኢሳ19፥ 13፤ኤር24፥8፤43፥8

*9 የላይኛው ዐባይ አካባቢ ነው
*14 ዕብራይስጡ ኖፍ ይላል፤ ቍ 19 ይመ።

ይበላቸዋልና፡፡
15ጦረኞችህ ለምን ተዘረሩ?
*እግዚአብሔር* ገፍትሮ ስለሚጥላቸው
መቆም አይችሉም፡፡
16ደጋግመው ይሰናከላሉ፤
አንዱም በሌላው ላይ ይወድቃል፤
‘ተነሡ እንሂድ፤
ወደ ሕዛባችንና ወደ ትውልድ
አገራችን እንመለስ፤
ከጠላትም ሰይፍ እናምልጥ’ ይላሉ፡፡
17በዚያም የግብፅን ንጉሥ ፈርዖንን፣
በተሰጠው ዕድል ያልተጠቀመ፣
አለሁ አለሁ ባይ ደንፊ!’ ብለው
ይጠሩታል፡፡
18ስሙ የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*
የሆነው ንጉሡ እንዲህ ይላል፤
በሕያውነቴ እምላለሁ፡፡
በተራሮች መካከል ያለውን የታቦር ተራራ
የሚመስል፣
ባሕርም አጠገብ ያለውን የቀርሜሎስ
ተራራ የሚመስል አንድ የሚመጣ
አለ፡፡
19እናንተ በግብፅ የምትኖሩ ሆይ፤
በምርኮ ለመወሰድ ጓዛችሁን አሰናዱ፤
ሜምፎስ ፈራርሳ፣
ሰው የማይኖርባት ባድማ ትሆናለችና፡፡
20“ግብፅ ያማረች ጊደር ናት፣
ነገር ግን ተናዳፊ ዝንብ፣
ከሰሜን ይመጣባታል፡፡
21ቅጥረኞች ወታደሮቿም፣
እንደ ሰቡ ወይፈኖች ናቸው፤
የሚቀጡበት ጊዜ ስለ ደረሰ፣
ጥፋታቸው ስለ ተቃረበ፣
እነርሱም ወደ ኋላ ተመልሰው በአንድነት
ይሸሻሉ፣
በቦታቸውም ጸንተው ሊቋቋሙ
አይችሉም፡፡
22ጠላት ገፍቶ ሲመጣባት፣
ግብፅ እንደሚሸሽ እባብ ታፏጫለች፤
ዛፍ እንደሚቈርጡ ሰዎች፣
መጥረቢያ ይዘው ይመጡባታል፡፡
23ጥቅጥቅ ጫካ ቢሆንም፣ ደን
ይመነጥራሉ፤”
ይላል *እግዚአብሔር*፤
“ብዛታቸው እንደ አንበጣ ነው፤
ሊቈጠሩም አይችሉም፡፡
24የግብፅ ሴት ልጅ ለኀፍረት
ትጋለጣለች፤
ለሰሜን ሕዝብም ዐልፋ ትሰጣለች፡፡”
25የእስራኤል አምላክ፣ የሰራዊት ጌታ *እግ
ዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ “በቴብስ[ሀ] አም

46፥15 ኢሱ23፥5፤ ኢሳ66፥15-16
46፥16 ቀኁ6፤ዘሌ 26፥37፤ኢሳ13፥14፤ ኤር 25፥38
46፥17 1ነገ20፥10-11፤ኢሳ19፥11-16
46፥18 ኢሱ19፥22፤ 1ነገ18፥42፤ኤር 48፥15
46፥19 ኢሳ20፥4፤ 19፥13፤ሕዝ29፥10፡ 12፤35፥7
46፥20 ቀኁ24፤ኢሳ 14፥31፤ኤር47፥2
46፥21 ቀኁ5፤2ነገ 7፥6፤ኢዮ18፥20፤ 20፥24፤መዝ18፥18፤ 37፥13፤ኤር18፥17፤ ሉቃ15፥27
46፥22 መዝ74፥5
46፥23 ዘዳ28፥42፤ መሳ7፥12
46፥24 2ነገ24፥7
46፥25 2ነገ24፥7፤ ኢሳ20፥6፤ኤር43፥12 ፤ሕዝ30፥14፡22፤ናሆ 3፥8
46፥26 ቀኁ13፤ኢሳ 19፥4፤ኤር44፥30፤ ሕዝ29፥11-16
46፥27 ኢሳ11፥11፤ 41፥8፤43፥5፤44፥1፡2፤ ኤር29፥14፤50፥19፤ 51፥46፤ሚል1፥2
46፥28 ዘፀ14፥22፤ ዘኁ14፥9፤ኢሳ8፥9-10፤ኤር4፥27
47፥1 ዘፍ10፥14፡ 19፤መሳ3፥31፤ዘካ 9፥5-7
47፥2 ኢሳ14፥31፤ 15፥3
47፥3 ኢሳ13፥7፤ ኤር46፥9፤50፥43፤ ሕዝ7፥17፤21፥7፤ 23፥24
47፥4 ዘፍ10፥14፡ 15፤ዘዳ2፥23፤ኢሳ 23፥1፤ኤር25፥22፤ ኢል3፥4፤አሞ1፥9-10፤ዘካ9፥2-4

ላክ በአሞን ላይ፣ በፈርዖን ላይ፣ በግብፅና
በአማልክቷ ላይ፣ በነገሥታቷም ላይ፤ እን
ዲሁም በፈርዖን በሚታመኑት ላይ ቅጣት
አመጣለሁ፤ 26ነፍሳቸውን ለሚሹት ለባቢ
ሎን ንጉሥ ለናቡከደነፆርና ለጦር መኰን
ኖቹ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ፤ ከጥቂት ጊዜ
በኋላ ግን ግብፅ እንደ ቀድሞው ዘመን
የሰው መኖሪያ ትሆናለች” ይላል *እግዚአ
ብሔር*፡፡

27“አገልጋዬ ያዕቆብ ሆይ፤ አትፍራ፤
እስራኤል ሆይ፤ አትሸበር፤
አንተን ከሩቅ ስፍራ፣
ዘርህንም ተማርኮ ከሄደበት ምድር
አድናለሁ፡፡
ያዕቆብም ተመልሶ በሰላምና በርጋታ
ይቀመጣል፤
የሚያስፈራውም አይኖርም፡፡
28አገልጋዬ ያዕቆብ ሆይ፤ አትፍራ፤
እኔ ከአንተ ጋር ነኝና” ይላል
*እግዚአብሔር*፤
“አንተን የበተንሁበትን ሕዝብ ሁሉ፣
ፈጽሜ ባጠፋም እንኳ፣
አንተን ግን ፈጽሜ አላጠፋህም፡፡
ተገቢውን ቅጣት እሰጥሃለሁ እንጂ፣
ያለ ቅጣት አልተውህም፡፡

## ስለ ፍልስጥኤማውያን የተነገረ መልእክት

47 *ፈርዖን ጋዛን ድል ከማድረጉ በፊት፣
ስለ ፍልስጥኤማውያን ወደ ነቢዩ
ወደ ኤርምያስ የመጣው የእግዚአብሔር
ቃል ይህ ነው፤*

2*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

“እነሆ፤ በሰሜን በኩል ውሃ እየሞላ ነው፣
ኀይለኛ ጐርፍ ይሆናል፤
አገሪቷንና በውስጧ ያሉትንም ሁሉ፣
ከተሞቿንና ነዋሪዎቻቸውን ያጥለቀ
ልቃል፡፡
ሕዝቡም ድምፁን ከፍ አድርጎ ይጮኻል፤
የምድሪቱ ነዋሪ ሁሉ ዋይ ዋይ ይላል፤
3ከፈረስ ኰቴ ድምፅ፣
ከጠላት ሠረገላ ጩኸትና፣
ከሠረገላው ሽክርክሪት ፍትጊያ ድምፅ
የተነሣ፣
አባቶች ልጆቻቸውን ለመርዳት ወደ
ኋላ መለስ አይሉም፤
እጃቸውም ስንኩል ይሆናል፡፡
4ፍልስጥኤማውያንን ሁሉ ለማጥፋት፣
ተርፈውም የሚረዷቸውን ሁሉ፣
ከጢሮስና ከሲዶና ለመቍረጥ፣
ቀኑ ደርሶአልና፡፡
*እግዚአብሔር* በከፍቶር[ለ] ዳርቻ የቀሩትን፣

[ሀ]25 ወይም ኖእ [ለ]4 ቀርጤስ ነው

ፍልስጥኤማውያንን ሊያጠፋ
ተነሥቶአል።
5 ጋዛ በማዘን ራሷን ትላጫለች፣
አስቀሎና አፏን ትይዛለች።
በሜዳማ ስፍራ የምትገኙ ትሩፋን ሆይ፤
እስከ መቼ ሰውነታችሁን
ትቧጥጣላችሁ?
6 “ ‘*የእግዚአብሔር* ሰይፍ ሆይ፤
የማታርፈው እስከ መቼ ነው?
ወደ ሰገባህ ተመልሰህ ግባ፤
ጸጥ ብለህ ተቀመጥ’ ትላላችሁ።
7 ነገር ግን *እግዚአብሔር* አስቀሎናንና
የባሕሩን ዳርቻ፣
እንዲወጋ ሲያዝዘው፣
እንዲፈጽመውም ትእዛዝ ሲሰጠው፣
እንዴት ማረፍ ይችላል?”

## ስለ ሞዓብ የተነገረ መልክት

48፥29-36 ተጓ ምብ-ኢሳ16፥6-12

# 48

ስለ ሞዓብ፤
የእስራኤል አምላክ የሰራዊት ጌታ
*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“ናባው ትጠፋለችና ወዮላት፤
ቂርያታይም ትዋረዳለች፤ ትያዛለችም፤
ምሽጎች[ፐ] ይደፈራሉ፤ ይፈራርሳሉም።
2 ከእንግዲህ ሞዓብ አትከበርም፤
ሰዎች በሐሴቦን[ሀ] ተቀምጠው፣
‘ኑ ያቺን አገር እናጥፋት’ ብለው
ይዶልቱባታል።
መድሜን[ለ] ሆይ፤ አንቺም ደግሞ ጸጥ
ትደረጊያለሽ፤
ሰይፍም ያሳድድሻል።
3 ከሖሮናይም የሚወጣውን ጩኸት፣
የመውደምና የታላቅ ጥፋት ድምፅ
ስሙ!
4 ሞዓብ ትሰበራለች፤
ልጆቿም ጩኸት ያሰማሉ።[ሐ]
5 ክፉኛ እያለቀሱ፣
ወደ ሉሒት ሽቅብ ይወጣሉ፤
ስለ ደረሰባቸውም ጥፋት መራራ ጩኸት
እያሰሙ፣
ወደ ሖርናይም ቍልቍል ይወርዳሉ።
6 ሽሹ፤ ሕይወታችሁንም አትርፉ!
በምድረ በዳ እንዳለ ቍጥቋጦ[መ] ሁኑ።
7 በድርጊታችሁና በብልጽግናችሁ
ስለምትታመኑ፣
እናንተም ትማረካላችሁ፣
ካሞሽም ከካህናቱና ከመኳንንቱ ጋር፣
በምርኮ ይወሰዳል።
8 በእያንዳንዱ ከተማ ላይ አጥፊ ይመጣል፤
አንድም ከተማ አያመልጥም።
*እግዚአብሔር* ተናግሮአልና፣

47፥5 ዘሌ19፥28፤ ኤር25፥20፤41፥5
47፥6 ኢሳ34፥5፤ ኤር12፥12፤48፥10፤ 50፥35፤ሕዝ21፥30
47፥7 ሕዝ25፥15-17
48፥1 ዘፍ19፥37፤ ዘኍ32፥37፡38፤ዘዳ 23፥6፤ኢሱ 3፥19
48፥2 ቍ42፤ዘኍ 21፥25፤ኢሱ13፥26፤ ኢሳ16፥14
48፥3 ኢሳ15፥5
48፥5 ቍ3፤ኢሳ 15፥5
48፥6 ዘፍ19፥17፤ ኤር 17፥6
48፥7 ዘኍ21፥29፤ መዝ49፥6፤ምሳ11፥28 ፤ኢሳ46፥1-2፤ኤር 49፥3፤አሞ 2፥3
48፥8 ዘፀ12፥23፤ ኢ. ሱ13፥9፤ኤር 4፥7
48፥9 መሳ9፥45፤ ኤር51፥29
48፥10 ሳሙ15፥11 ፤1ነገ20፥42፤2ነገ 13፥15-19፤ኤር47፥6
48፥11 ዘካ1፥15፤ ሶፎ1፥12
48፥13 ቍ7፤ኢሱ 7፥2፤ሆሴ10፥6
48፥14 መዝ33፥16
48፥15 ኢሳ9፥17፤ ኤር46፥18፤51፥40፡57
48፥16 ኢሳ13፥22
48፥17 2ነገ3፥4-5፤ መዝ110፥2
48፥18 ቍ8፤ዘኍ 21፥30፤ኢሱ13፥9፤ ኢ. ሳ47፥1

ሸለቆው ይጠፋል፤
ዐምባውም ይፈርሳል።
9 በራ እንድታመልጥ፣
ለሞዓብ ክንፍ ስጧት፤
ከተሞቿም ምንም እስከማይኖርባቸው
ድረስ፣
ባድማ[ሠ] ይሆናሉ።
10 “*የእግዚአብሔርን ሥራ በቸልታ*
የሚያከናውን ርጉም ይሁን፤
ሰይፉን ደም ከማፍሰስ የሚከላከል
የተረገመ ይሁን፤
11 “ሞዓብ በአምቡላው ላይ እንዳረፈ
የወይን ጠጅ፣
ከልጅነት ጀምሮ የተረጋጋ ነበረ፤
ከዕቃ ወደ ዕቃ አልተገላበጠም፤
በምርኮም አልተወሰደም፤
ቃናው እንዳለ ነው፤
መዐዛውም አልተለወጠም።
12 ስለዚህ ዕቃውን የሚገለብጡ ሰዎችን፤
የምልክበት ጊዜ ይመጣል፤”
ይላል *እግዚአብሔር*።
“እነርሱም ይደፉታል፤
ዕቃውን ባዶ ያስቀራሉ፤
ማንቆርቆሪያዎቹንም ይሰባብራሉ።
13 የእስራኤል ቤት፤
በቤቴል ታምኖ እንዳፈረ ሁሉ፣
ሞዓብም በካሞሽ ያፍራል።
14 “እናንተ፣ ‘እኛ ተዋጊዎች ነን፤
በጦርነትም ብርቱ ነን’ ልትሉ እንዴት
ቻላችሁ?
15 ሞዓብ ትጠፋለች፤ ከተሞቿም ይወረራሉ፤
ምርጥ ወጣቶቿም ወደ መታረድ
ይወርዳሉ፤”
ይላል ስሙ የሰራዊት ጌታ
*እግዚአብሔር* የሆነው ንጉሥ፤
16 “የሞዓብ ውድቀት ተቃርቦአል፤
ጥፋቱም ፈጥኖ ይመጣበታል።
17 በዙሪያው የምትኖሩ ሁሉ፤
ዝናውን የምታውቁ ሁሉ አልቅሱለት፤
‘ብርቱው ከዘራ፣
የከበረው በትር እንዴት ሊሰበር ቻለ’
በሉ።
18 “ሞዓብን የሚያጠፋ፣
በአንቺ ላይ ይመጣልና፤

[ፐ]1 ወይም *ሚሥጋብ*
[ሀ]2 *ሐሴቦን* የሚለው የዕብራይስጡ ቃል አነባበብ *መዶለት* ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው።
[ለ]2 *መድሜን* የሚለው የሞአባውያን ከተማ ስም አነባበብ *ጸጥ* ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው።
[ሐ]4 የዕብራይስጡና የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች *ለዞአር ያውጃሉ* ይላሉ
[መ]6 ወይም *እንደ አሮኤር*
[ሠ]9 ወይም *የተተወች ምድር እንድትሆን/ በሞዓብ ላይ ጨው ነስንሱባት*

የተመሸጉ ከተሞችሽንም ያጠፋልና፤
አንቺ የዲቦን ሴት ልጅ ሆይ፣
ከክብርሽ ውረጂ፣
በደረቅም መሬት ተቀመጪ።
19አንቺ በአሮዔር የምትኖሪ ሆይ፤
በመንገድ አጠገብ ቆመሽ ተመልከቺ፤
የሚሸሸውን ወንድ፣ የምታመልጠውንም
ሴት፣
ምን ተፈጠረ?' ብለሽ ጠይቂ።
20ሞዓብ በመፍረሱ ተዋርዷል፤
ዋይ በሉ፤ ጩኹ፤
የሞዓብን መደምሰስ፣
በአርኖን አጠገብ አስታውቁ።
21ፍርድ በዐምባው ምድር፦
በሖሎን፣ በያሳና በሜፍዓት ላይ፣
22በዲቦን፣ በናባውና በቤት ዲብላታይም
ላይ፣
23በቂርያታይም፣ በቤት ጋሙልና
በቤትምዖን ላይ፣
24በቂርዮትና በባሶራ ላይ፤
በሩቅና በቅርብ፣
ባሉት በሞዓብ ከተሞች ሁሉ ላይ
መጥቶአል።
25የሞዓብ ቀንድ[ሬ] ተቈርጦአል፤
እጁም ተሰባብሮአል፤"
ይላል እግዚአብሔር።

26"እግዚአብሔርን ንቆአልና፣
ሞዓብን በመጠጥ አስክሩት።
ሞዓብ በትፋቱ ላይ ይንከባለል፤
ለመዘባበቻም ይሁን።
27በእስራኤል ላይ ስታላግጥ አልነበረምን?
ስለ እርሷ በተናገርህ ቍጥር፣
እያቃለልሃት ራስህን የምትነቀንቀውስ፣
ከሌቦች ጋር ስትሰርቅ ተይዛለችን?
28እናንተ በሞዓብ የምትኖሩ ሆይ፤
ከከተማ ወጥታችሁ በዐለት መካከል
ኑሩ፤
በገደል አፋፍ ላይ ጐጆዋን
እንደምትሠራ፣
እንደ ርግብ ሁኑ።

29"ስለ ሞዓብ ትዕቢት፣
ስለ እብሪቱና ስለ ኵራቱ፣
ስለ ትምክሕቱና ስለ መጓደዱ፣
ስለ ልቡም ማበጥ ሰምተናል።
30መዳፉን ዐውቃለሁ፤ ነገር ግን ከንቱ
ነው፤"
ይላል እግዚአብሔር።
"ጉራውም ፋይዳ አይኖረውም።
31ስለዚህ ለሞዓብ አለቅሳለሁ፤
ለሞዓብ ምድር ሁሉ ዋይ እላለሁ፤
ለቂርሔሬስ ሰዎችም የልቅሶ ድምፅ
አሰማለሁ።
32የሴባማ ወይን ሆይ፤
ለኢያዜር ካለቀስሁት እንኳ ይልቅ
አለቅስልሻለሁ፤
ቅርንጫፎችሽ እስከ ባሕሩ ተዘርግተዋል፤
እስከ ኢያዜርም ደርሰዋል፤
ለመከር በደረሰው ፍሬሽና በወይንሽ ላይ፣
አጥፊው መጥቶአል።
33ከሞዓብ የአትክልት ቦታና እርሻ፣
ሐሤትና ደስታ ርቆአል፤
የወይን ጠጅ ከመጭመቂያው
እንዳይወርድ አድርቄዋለሁ፤
በእልልታ የሚጨምቀውም አይገኝም፤
በዚያ ድምፅ ቢሰማም፣
የእልልታ ድምፅ አይደለም።

34"ከሐሴቦን እስከ ኤልያሊና እስከ ያሀጽ፣
ከዞዓር እስከ ሖሮናይም፣ እስከ ዔግላት
ሺሊሺያ ድረስ፣
ጩኸታቸው ከፍ ብሎ ይሰማል፤
የኔሞሬም ውሃ እንኳ ደርቆአልና።
35በመስገጃ ኰረብቶች ላይ የሚሠዉትን፣
ለአማልክታቸው የሚያጥኑትን፣
ከሞዓብ አጠፋለሁ፤"
ይላል እግዚአብሔር፤
36"ስለዚህ ልቤ ለሞዓብ እንደ ዋሽንት
ያንጐራጒራል፤
ለቂርሔሬስ ሰዎችም እንደ ዋሽንት
ያንጐራጒራል።
ያከማቹት ንብረት ጠፍቶአልና።
37የእያንዳንዱ ሰው ራስ፣
ጢምም ሁሉ ተላጭቶአል፤
እጅ ሁሉ ተቸፍችፎአል፤
ወገብም ሁሉ ማቅ ታጥቆአል።
38በሞዓብ ቤቶች ጣራ ሁሉ ላይ፤፣
በሕዝብም አደባባዮች፣
ሐዘን እንጂ ሌላ የለም፤
እንደማይፈለግ እንስራ፣
ሞዓብን ሰብሬአለሁና፤"
ይላል እግዚአብሔር።
39"እንዴት ተንኰታኰተ! ምንኛስ
አለቀሱ!
ሞዓብ እንዴት ዐፍሮ ጀርባውን አዞረ!
ሞዓብ የመሰደቢያ፣
በዙሪያው ላሉትም ሁሉ የሽብር
ምልክት ሆነ።"
40እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
"እነሆ፤ እንደ ንስር ተወርውሮ
ይወርድበታል፤
ክንፎቹንም በሞዓብ ላይ ይዘረጋል።
41ከተሞቹ[ሰ] ይወረራሉ፤

[ሬ]25 **ቀንድ** እዚህ ቦታ ኀይልን በትእምርትነት ይመለከታል
[ሰ]41 ወይም ቂርያት

48፥19 ዘኍ32፥34
48፥20 ዘኍ21፥13፤ ኢሳ16፥7
48፥21 ዘኍ21፥23፤ ኢሱ13፥9፡18፡21፤ 15፥51፤ኢሳ15፥4
48፥22 ዘኍ21፥30፤ 32፥38፤ኢሱ 3፥9፡17
48፥23 ዘኍ32፥37፤ ኢሱ13፥17፡19
48፥24 ኢሳ15፥1፤ ኤር49፥13፤አሞ2፥2
48፥25 መዝ10፥15፤ 37፥17፤75፥10፤ሕዝ 30፥21
48፥26 ቍ39፡42፤ 1ሳሙ17፥26፤ኢሳ 28፥8፤ኤር25፥16፡27፤ 51፥39
48፥27 ዘዳ28፥37፤ 2ነገ17፥3-6፤ ኢዮ 16፥4፤መዝ44፥14፤ ኤር2፥26፤18፥16፤ ሚክ7፥8-10፤ሶፎ 2፥8፡10
48፥28 ዘፍ8፥8፤ መሳ6፥2፤ማሕ 1፥15
48፥29 ዘሌ26፥19፤ ኢዮ40፥12፤መዝ 10፥5፤ምሳ16፥18
48፥30 መዝ10፥3
48፥31 ቍ36፤2ነገ 3፥25፤ኢሳ15፥5-8
48፥32 ዘኍ32፥3፤ ኢሱ13፥25
48፥33 ኢሳ24፥7፤ ኢል1፥12፤አሞ5፥17
48፥34 ዘፍ13፥10፤ ዘኍ21፥23፡25፤ 32፥3፤ኢሱ13፥26፤ ኢሳ15፥4-6
48፥35 ኢሳ15፥2፤ ኤር11፥13
48፥36 ቍ31፤2ነገ 3፥25፤ኢሳ15፥7
48፥37 ዘፍ37፥34፤ ዘሌ19፥27፤2ሳሙ 10፥4፤ኢሳ3፥24፤ 15፥2፤ኤር41፥5፤ 16፥6፤ሕዝ27፥31፤ 29፥18፤አሞ8፥10
48፥38 ኢሳ15፥3፤ ኤር 22፥28
48፥39 ቍ26፤ኤር 50፥23፤
48፥40 ዘዳ28፥49፤ ኢሳ8፥8፤ዕን1፥8
48፥41 ኢሳ15፥1፤

ምሽጎቹም ይያዛሉ፤
በዚያን ቀን የሞዓብ ጦረኞች ልብ፣
በምጥ እንደ ተያዘች ሴት ልብ ይሆናል።
42ሞዓብ *እግዚአብሔርን* አቃልሎአልና
ይጠፋል፤
*መንግሥትነቱም* ይቀራል።
43የሞዓብ ሕዝብ ሆይ፤
ሽብርና ጒድጓድ፣ ወጥመድም
ይጠብቅሃል፤"
ይላል *እግዚአብሔር*።
44"ከሽብር የሚሸሽ ሁሉ፣
ጒድጓድ ውስጥ ይገባል፤
ከጒድጓዱም የሚወጣ፣
በወጥመድ ይያዛል፤
በሞዓብ ላይ፣
የቅጣቱን ዓመት አመጣለሁና፣"
ይላል *እግዚአብሔር*፤

45"የሞዓብን ግንባር፣
የደንፊዎችን ዐናት የሚያቃጥል፣
እሳት ከሐሴቦን፣
ነበልባል ከሴዎን ቤት ወጥቶአልና፤
ኰብላዮች በሐሴቦን ጥላ ሥር፣
ተስፋ ቈርጠው ቆመዋል።
46ሞዓብ ሆይ፤ ወዮልህ!
የካሞሽ ሕዝብ ተደምስሶአል፤
ወንዶች ልጆችህ በምርኮ ተወስደዋል፣
ሴቶች ልጆችህም ተግዘዋል።
47"ነገር ግን የኋላ ኋላ፣
የሞዓብን ምርኮ እመልሳለሁ፤"
ይላል *እግዚአብሔር*።
በሞዓብ ላይ የተወሰነው ፍርድ
ይኸው ነው።

## ስለ አሞን የተነገረ መልእክት

49 ስለ አሞናውያን፤
*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
"እስራኤል ወንዶች ልጆች አልወለደምን?
ወራሾችስ የሉትምን?
ታዲያ፣ ሚልኮም[ሸ] ጋድን ለምን ወረሰ?
የእርሱ ሰዎች ለምን በከተሞቿ
ይኖራሉ?
2ስለዚህ፣ በአሞናውያን ከተማ በረባት
ላይ፣
የጦርነት ውካታ ድምፅ፣
የሚሰማበት ጊዜ ይመጣል፤"
ይላል *እግዚአብሔር*፤
"እርሷም የፍርስራሽ ክምር ትሆናለች፤
በዙሪያዋ ያሉት መንደሮችም
ይቃጠላሉ፤
እስራኤልም ከአገሯ ያስወጧትን፣
ከአገሯ ታስወጣለች፤"
ይላል *እግዚአብሔር*፤

3ሐሴቦን ሆይ፤ ጋይ ጠፍታለችና
ዋይ በይ፤
የራባት ሴቶች ልጆች ሆይ ጩኹ፤
ማቅ ለብሳችሁ አልቅሱ፤
ሚልኮም ከካህናቱና ከመኳንንቱ ጋር፣
ተማርኮ ይወሰዳልና፣
በቅጥር ውስጥ ወዲያ ወዲህ ተሯሯጡ።
4አንቺ ከዳተኛ ልጅ ሆይ፣
በሸለቆችሽ ለምን ትመኪያለሽ?
ለምንስ በፍሬያማ ሸለቆሽ ትኵራሪያለሽ?
በብልጽግናሽ ተማምነሽ፣
'ማን ሊነካኝ ይችላል?' ትያለሽ።
5በዙሪያሽ ካሉት ሁሉ ዘንድ፣
ሽብር አመጣብሻለሁ፤"
ይላል የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*፤
"እያንዳንዳችሁ ትሰደዳላችሁ፤
በሽሽት ላይ ያሉትንም የሚሰበስብ
አይገኝም።
6"ከዚያ በኋላ ግን፣
የአሞናውያንን ምርኮ እመልሳለሁ፣"
ይላል *እግዚአብሔር*።

## ስለ ኤዶም የተነገረ መልእክት

49፥9-10 ተጓ ምብ-አብ5-6
49፥14-16 ተጓ ምብ-አብ1-4

7ስለ ኤዶም፤
የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*
እንዲህ ይላል፤
"ጥበብ ከቴማን ጠፍቶአልን?
ምክር ከአስተዋዮች ርቆአልን?
ጥበባቸውስ ተሟጧልን?
8ዔሳውን በምቀጣ ጊዜ፣
ጥፋት ስለማመጣበት፣
እናንተ በድዳን የምትኖሩ ሆይ፤
ወደ ኋላ ተመልሳችሁ ሽሹ፤ ጥልቅ
ጒድጓድ ውስጥ ተደበቁ።
9ወይን ለቃሚዎች ወዳንተ ቢመጡ፣
ጥቂት ወይን አያስቀሩምን?
ሌቦችስ በሌሊት ቢመጡ፣
የሚሰርቁት የሚፈልጉትን ብቻ
አይደለምን?
10እኔ ግን ዔሳውን አራቍተዋለሁ፤
መደበቅም እንዳይችል፣
መሸሸጊያ ስፍራዎቹን እገልጣለሁ፤
ልጆቹ፣ ዘመዶቹና ጎረቤቶቹ ይጠፋሉ፤
እርሱም ራሱ አይኖርም።

11ወላጆች የሌላቸውን ልጆችህን ተዋቸው፤
እኔ ለሕይወታቸው እጠነቀቃለሁ፤ መበለ
ቶቻችሁም በእኔ ይታመኑ።"

12*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ "ከጽዋው
መጠጣት የማይገባቸው ሊጠጡ ግድ ከሆነ፣

21፥3፤አሞ2፥16
48፥42 ቀኍ2፥26፤ ኢሳ16፥14
48፥43 ኢሳ24፥17፤ ኤር49፥5
48፥44 1ነገ19፥7፤ ኢዮ20፥24፤ኢሳ24፥18፤ኤር11፥23፤23፥12፤46፥5
48፥45 ዘኍ21፥21፡26-28፤24፥17፤ኢሱ12፥2
48፥46 ዘኍ21፥29
48፥47 መዝ14፥7፤ ኢሳ11፥11፤ኤር12፥15፤49፥6፡39፤ሕዝ16፥53፤ዳን11፥41
49፥1 ዘፍ19፥38፤ 30፥11፤ዘሌ18፥21፤ 1ሳሙ11፥1-11፤ 2ሳሙ10፥1-19
49፥2 ዘዳ3፥11፤ 13፥16፤ኢሳ14፥2፤ ኤር4፥19፤30፥16፤ ሕዝ21፥28-32፤ 25፥2-11
49፥3 ዘፍ12፥8፤ 37፥34፤ኢሱ8፥28፤ 13፥26፤ኤር48፥7፤ ሶፎ 1፥5
49፥4 ኤር3፥6፤ 9፥23፤21፥13፤1ጢሞ6፥17
49፥5 ኤር44፥14
49፥6 ኤር12፥14-17፤48፥47
49፥7 ዘፍ25፥30፤ 36፥11፡15፡34፤መዝ83፥6
49፥8 ዘፍ10፥7፤ 25፥3፤መሳ6፥2
49፥10 ዘፍ3፥8፤ኢሳ34፥10-12፤ኤር11፥23፤ሕዝ35፥4፤አብ1፥18፤ሚል1፥2-5
49፥11 ዘዳ10፥18፤ ሆሴ14፥3፤ያዕ 1፥27
49፥12 ምሳ11፥31፤ ኢሳ51፥23፤ ኤር25፥15፤ማቴ20፥22

[ሸ]1 ወይም *ንጉሣቸው*፤ ዕብራይስጡ *መልካም* ይላል፤ ቍ3 ይመ።

አንተ እንዴት ሳትቀጣ ትቀራለህ? መቀ
ጣትህ አይቀርም፤ መጠጣት ይገባሃል።
13ባሶራ ፈራርሳ የድንጋጤ፣ የመዘባበቻና
የርግማን ምልክት እንደምትሆን በራሴ
ምያለሁ” ይላል *እግዚአብሔር*፤ “ከተሞ
ቿም ሁሉ ለዘላለም ባድማ ይሆናሉ።”

14*ከእግዚአብሔር* ዘንድ መልእክት
ሰምቻለሁ፤
“እርሷን ለመውጋት ተሰብሰቡ፤
ለጦርነትም ውጡ!”
የሚል መልእክተኛ ወደ ሕዝቦች
ተልኮአል።
15“እነሆ፤ በሕዝቦች መካከል ታናሽ፣
በሰዎችም ዘንድ የተናቅህ አደርግሃለሁ።
16አንተ በዐለት ንቃቃት ውስጥ
የምትኖር፣
የተራራውንም ከፍታ የያዝህ ሆይ፤
የምትነዛው ሽብር፣
የልብህም ኵራት አታሎሃል፤
መኖሪያህን እንደ ንስር በከፍታ ቦታ
ብትሠራም፣
ከዚያ ወደ ታች እጥልሃለሁ፤”
ይላል *እግዚአብሔር*።
17“ኤዶም የድንጋጤ ምልክት ትሆናለች፤
ከቍስሎቿም ሁሉ የተነሣ፣
በዚያ የሚያልፍ ሁሉ በመደነቅ
ያላግጥባታል።”
18በዙሪያቸው ካሉት ከተሞች ጋር፣
ሰዶምና ገሞራ እንደ ተገለበጡ፣”
ይላል *እግዚአብሔር*።
እንዲሁ ማንም በዚያ አይኖርም፤
አንድም ሰው አይቀመጥባትም።

19“አንበሳ ከዮርዳኖስ ደኖች፣
ወደ ግጦሽ ሜዳ ብቅ እንደሚል፣
እኔም በኤዶም ላይ ድንገት እወጣለሁ፤
ከምድሩም አባርረዋለሁ።
የመረጥሁትን በእርሱ ላይ እሾማለሁ፤
እንደ እኔ ያለ ማን ነው? ማንስ
ሊገዳደረኝ ይችላል?
የትኛውስ እረኛ ሊቋቋመኝ ይችላል?
20ስለዚህ *እግዚአብሔር* በኤዶም ላይ
ያለውን ዕቅድ፣
በቴማን በሚኖሩትም ላይ ያሰበውን
አሳብ ስሙ፤
ታናናሹ መንጋ ተጐትቶ ይወሰዳል፤
በእነርሱም ምክንያት መሰማሪያቸውን
ፈጽሞ ያጠፋል።
21በውድቀታቸው ድምፅ ምድር
ትናወጣለች፤
ጩኸታቸውም እስከ ቀይ ባሕር[*]
ያስተጋባል።

49፥13 ቊ17፤ዘፍ 22፥16፤36፥33፤ኤር 19፥8፤42፥18፤ሕዝ 35፥9
49፥16 ኢዮ39፥27፡28፤ሕዝ35፥13፤አብ 1፥12
49፥17 ቊ13፤ዘዳ 29፥22፤ሕዝ35፥7
49፥18 ቊ33፤ዘፍ 19፥24፤ኢሳ34፥10፤ ኤር23፥14
49፥19 ዘፀ 8፥10፤ 1ሳሙ17፥34፡35፤ 2ዜና20፥6፤ኢዮ 9፥19፤ኢሳ46፥5፤ ኤር12፥5፤50፥44
49፥20 ቊ7፡10፤ ዘፍ36፥11፤ኢሳ34፥5 ፤14፥27፤ኤር50፥45፤ አብ1፥10፤ሚል1፥3-4
49፥21 መዝ114፥7 ፤ኤር50፥46፤51፥29፤ ሕዝ26፥15፡18፤ 27፥28፤31፥16
49፥22 ዘፍ36፥33፤ ዘዳ28፥49፤ኢሳ13፥8 ፤ኤር50፥36፤ሆሴ 8፥1፤ናሆ3፥13፤ዕን 1፥8
49፥23 ዘፍ14፥15፤ 49፥4፤1ነገ8፥65፤ 2ነገ14፥28፤18፥34፤ 19፥13፤2ዜና16፥2፤ ኢሳ10፥9፤ሕዝ47፥16 ፤አሞ6፥2፤ዘካ9፥2፤ ሐሥ 9፥2
49፥24 ኤር13፥21
49፥26 ኢሳ9፥17፤ 13፥18፤17፥12-14
49፥27 ዘፍ14፥15፤ 1ነገ15፥18ኤር21፥14 ፤43፥12፤50፥32፤ሕዝ 30፥8፤39፥6፤አሞ 1፥4፤ ኢሳ 17፥1፤
49፥28 ዘፍ25፥13፤ ኢሱ11፥1፤ኤር 10፥22፤መሳ 6፥3
49፥29 ቊ32፤ኤር 6፥25
49፥30 መሳ6፥2፤ ኢ. ሱ11፥1፤ኤር10፥22
49፥31 ሕዝ38፥11

22እነሆ፤ እንደ ንስር ተወርውሮ
ይወርድባታል፤
ክንፎቹንም በባሶራ ላይ ይዘረጋል፤
በዚያን ቀን የኤዶም ጦረኞች ልብ፣
በምጥ እንደ ተያዘች ሴት ልብ
ይሆናል።

## ስለ ደማስቆ የተነገረ መልእክት

23ስለ ደማስቆ፤

“ክፉ ወሬ ሰምተዋልና፣
ሐማትና አርፋድ ደንግጠዋል፣
እንደ[በ] ተናወጠ ባሕርም ታውከዋል፤
ልባቸውም ቀልጦአል።
24ደማስቆ ተዳከመች፤
ትሸሽም ዘንድ ወደ ኋላ ተመለሰች፤
ብርክ ያዛት፣
ምጥ እንደ ያዛት ሴት፣
ጭንቅና መከራ ዋጣት።
25ደስ የምሰኝባት፣
የታወቀችው ከተማ እንዴት ተተወች?
26በእርግጥ ወንዶች ወጣቶቿ በየአደባባዩ
ይረግፋሉ፤
በዚያ ቀን ወታደሮቿ ሁሉ
ይወድቃሉ፤”
ይላል የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*፤
27“በደማስቆ ቅጥር ላይ እሳት
እለኵሳለሁ፤
የወልደ አዴርንም ዐምባ ይበላል።”

## ስለ ቄዳርና ስለ ሐጾር የተነገረ መልእክት

28የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ስለወጋ
ቸው ስለ ቄዳርና ስለ ሐጾር መንግሥታት
የተነገረ፤ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

“ተነሡ፣ ቄዳርን ውጉ፤
የምሥራቅንም ሕዝብ ደምስሱ።
29ድንኳኖቻቸውና መንጎቻቸው ይወሰዳሉ፤
መጠለያቸውና ግመሎቻቸው ሳይቀሩ፣
ከነዕቃዎቻቸው ይነጠቃሉ፤
ሰዎች፣ ‘ሽብር በሽብር ላይ
መጥቶባቸዋል፤’
እያሉ ይጮኹባቸዋል።
30በሐጾር የምትኖሩ ሆይ፣
በጥድፊያ ሽሹ! በጥልቅ ጒድጓድ
ተሸሸጉ፤”
ይላል *እግዚአብሔር*፤
የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር በእናንተ
ላይ መክሮአልና፣
ወረራም ዶልቶባችኋል።
31“ተነሡ፣ ተዘልሎ የተቀመጠውን፣
በራሱ ተማምኖ የሚኖረውን ሕዝብ

[*]21 ዕብራይስጡ *ያም ሱፍ* ይላል፤ ትርጒሙ የሸንበቆ ባሕር ማለት ነው

ውጉ፤”
*ይላል እግዚአብሔር፤*
መዝጊያና መቀርቀሪያ በሌለው፣
ለብቻው በሚኖረው ሕዝብ ላይ
ዝመቱ።”
32ግመሎቻቸው ይዘረፋሉ፤
ከብቶቻቸውንም አንጋግተው
ይነዱባቸዋል፤
ጠጕሩን የሚቀነብበውን ወገን[†]
እበትናለሁ ከየአቅጣጫው መዓት
አመጣባቸዋለሁ፤
*ይላል እግዚአብሔር፤*
33“ሐጾር የቀበሮዎች መፈንጫ፣
ለዘላለም ባድማ ትሆናለች፤
ማንም በዚያ አይኖርም፤
የሚቀመጥባትም አይገኝም።”

## ስለ ኤላም የተነገረ መልእክት

34በይሁዳ ንጉሥ በሴዴቅያስ ዘመነ መን
ግሥት መጀመሪያ ላይ ወደ ነቢዩ ወደ
ኤርምያስ የመጣው *የእግዚአብሔር* ቃል
ይህ ነው፤

35የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

“እነሆ፤ የኀያልነቷን መሠረት፣
የኤላምን ቀስት እሰብራለሁ።
36ከአራቱ የሰማይ ማእዘናት፣
በኤላም ላይ አራቱን ነፋሳት
አመጣለሁ፤
ወደ አራቱም ነፋሳት እበትናቸዋለሁ፤
ከኤላም የሚማረኩት የማይደርሱበት፣
አገር አይገኝም።
37ነፍሳቸውን በሚሹ ጠላቶቻቸው ፊት፣
ኤላምን አርበደብዳለሁ፤
በላያቸው ላይ መዓትን፣
ይኸውም ቍጣዬን አመጣባቸዋለሁ፤”
*ይላል እግዚአብሔር፤*
“ፈጽሜ እስካጠፋቸውም ድረስ፣
በሰይፍ አሳድዳቸዋለሁ።
38ዙፋኔን በኤላም እዘረጋለሁ፤
ነገሥታቷንና መኳንንቷን
አጠፋለሁ፤”
*ይላል እግዚአብሔር፤*
39“ነገር ግን የኋላ ኋላ፣
የኤላምን ምርኮ እመልሳለሁ፤”
*ይላል እግዚአብሔር።*

## ስለ ባቢሎን የተነገረ መልእክት

51፥15-19 ተጓ ምብ-ኤር10፥12-16

50 *እግዚአብሔር* ስለ ባቢሎንና ስለ
ባቢሎናውያን[‡] ምድር፣ በነቢዩ
ኤር ምያስ በኩል የተናገረው ቃል ይህ
ነው፤

2“በሕዝቦች መካከል ተናገሩ፤
አስታውቁም፤
ሰንደቅ ዐላማ አንሡ፣ ዐውጁ፣
አንዳች ሳታስቀሩ፣ እንዲህ በሉ፤
‘ባቢሎን ትያዛለች፤
ቤል ይዋረዳል፤
ሜሮዳክ በሽብር ይሞላል፤
ጣዖቶቿ ይዋረዳሉ፤
አማልክቷም ይሸበራሉ።’
3ከሰሜን አንድ መንግሥት መጥቶ
ይወጋታል፤
ምድሯንም ባድማ ያደርጋል፤
የሚኖርባትም አይገኝም፤
ሰዎችና እንስሳትም ሸሽተው ይሄዳሉ።

4“በዚያ ዘመን፣ በዚያ ጊዜም፤”
*ይላል እግዚአብሔር፤*
“የእስራኤል ሕዝብና የይሁዳ ሕዝብ
በአንድነት ይመጣሉ፤
አምላካቸውንም *እግዚአብሔርን*
በመፈለግ እያለቀሱ ይመጣሉ።
5ወደ ጽዮን የሚወስደውን መንገድ
ይጠይቃሉ፤
ፊታቸውንም ወደዚያ ያቀናሉ።
መጥተውም ከቶ በማይረሳ፣
በዘላለም ቃል ኪዳን፣
*ከእግዚአብሔር* ጋር ይጣበቃሉ።

6“ሕዝቤ የጠፉ በጎች ሆነዋል፤
እረኞቻቸው አሳቷቸው፤
በተራሮችም ላይ እንዲቅበዘበዙ
አደረጓቸው፤
በተራራና በኰረብታ ላይ ተንከራተቱ፤
ማደሪያቸውንም ረሱ።
7ያገኟቸው ሁሉ ይውጣቸዋል፤
ጠላቶቻቸውም፣ ‘እኛ በደለኞች
አይደለንም፤
እነርሱ የአባቶቻቸውን ተስፋ
እግዚአብሔርን፣
እውነተኛ ማደሪያቸው የሆነውን *እግዚ
አብሔርን* በድለዋል’ አሉ።
8“ከባቢሎን ሽሹ፤
የባቢሎናውያንን ምድር ልቀቁ፤
መንጋ እንደሚመራ የፍየል አውራ
ሁኑ።
9የታላላቅ መንግሥታትን ማኅበር፣
ከሰሜን በባቢሎን ላይ አስነሣለሁ፤
እነርሱም በእርሷ ላይ ይሰለፋሉ፤
መጥተውም ይይዟታል።
ቀስቶቻቸው ባዶ እጃቸውን እንደ
ማይመለሱ፣

[n]23 ዕብራይስጡ *በተናወጠ* ይላል
[†]32 ወይም *በሩቅ ስፍራ ያለውን*
[‡]1 ወይም *ከለዳውያን*፤ በቍ8፡25፡35 እና 45 ይመ።

49፥32 ቍ29፡36፤ መሳ6፥5፤ኤር9፥26፤ 13፥24
49፥33 ቍ18፤ኢሱ 11፥1፤ኢሳ13፥22፤ ኤር48፥9፤ 51፥37
49፥34 ዘፍ10፥22፤ 2ነገ 24፥18
49፥35 መዝ37፥15፤ኢሳ22፥6
49፥36 ቍ32፤ዳን 11፥4
49፥37 ኤር30፥24፤ 9፥16፤ሕዝ32፥24
49፥39 ኤር48፥47
50፥1 ዘፍ10፥10፤ መዝ137፥8
50፥2 ቍ9፡38፤ ዘሌ26፥30፤ዘዳ30፥4፤ መዝ20፥5፤97፥7፤ኢሳ 13፥2፤21፥9፤46፥1፡6፤ ኤር4፥16፤51፥31፡47፡ 52፤
50፥3 ቍ13፡26፤ ኢሳ14፥22-23፤ 25፥26፤ 41፥25፤ ኤር9፥11፤ሶፎ1፥3
50፥4 ዕዝ3፥12፤ኢሳ 9፥13፤ኤር3፥18፤ሕዝ 37፥17፡22፤ሆሴ3፥5
50፥5 ዘዳ29፥14፤ 1ሳሙ29፥1፤ኢሳ 11፥16፤55፥3፤ኤር 31፥21፤32፥40፤33፥7፤ ዕብ8፥6-10
50፥6 ቍ19፤መዝ 95፥10፤119፥176፤ ኤር2፥8፤3፥6፤10፥21፤ 23፥32፤ሕዝ13፥10፤ 34፥6፤ማቴ9፥36፤ 10፥6
50፥7 ኤር2፥3፤ 5፥17፤10፥25፤14፥8፤ሕዝ35፥12
50፥8 ቍ28፤ኢሳ 48፥20
50፥9 ቍ2፤ኢሳ 13፥17፡18፤ኢሳ41፥ 25፤ኤር25፥14፡26፤

እንደ ሥልጡን ተዋጊዎች ናቸው።
10የባቢሎን ምድርጎ ትዘረፋለች፤
የሚዘርፏትም ሁሉ እስኪበቃቸው
ይመዘብሩአታል፤”
*ይላል እግዚአብሔር።*

11“እናንተ ርስቴን የበዘበዛችሁ ሆይ፤
ደስ ስላላችሁና ሐሤትም ስላደረጋችሁ፣
በመስክ እንዳለች ጊደር ስለ ፈነጫችሁ፣
እንደ ድንጉላ ፈረስ ስለ አሽካካችሁ፣
12እናታችሁ እጅግ ታፍራለች፤
የወለደቻችሁም ትዋረዳለች።
እርሷም ምድረ በዳ፣ ደረቅ ምድርና
በረሓ፣
ከመንግሥታትም ሁሉ ያነሰች
ትሆናለች።
13ከእግዚአብሔር ቍጣ የተነሣ ባድማ
ትሆናለች እንጂ፣
የሚኖርባት አይገኝም፤
በቍስሎችዋም ሁሉ ምክንያት፣
በባቢሎን የሚያልፍ ሁሉ ይገረማል፤
ያፌዝባታልም።
14“እናንተ ቀስት የምትገትሩ ሁሉ፣
በባቢሎን ዙሪያ ተሰለፉ፤
አንዳች ሳታስቀሩ ፍላጻችን ስደዱባት፤
በእግዚአብሔር ላይ ኀጢአት
ሠርታለችና።
15ከየአቅጣጫው ጩኹባት፤
እጇን ትሰጣለች፤ ምሽጓም ይወድቃል፤
ቅጥሮቿ ይፈርሳሉ።
ይህ የእግዚአብሔር በቀል ነውና፣
እርሷን ተበቀሏት፤
በሌሎቹ ላይ እንዳደረገችውም
አድርጉባት።
16ከባቢሎን፣ ዘር የሚዘራውን፣
በመከር ጊዜ ማጭድ የጨበጠውንም
ዐጭድ አጥፉት፤
ከአጥፊው ሰይፍ የተነሣ፣
እያንዳንዱ ወደ ገዛ ሕዝቡ ይመለስ፤
ወደ ገዛ ምድሩም ይሽሽ።

17“እስራኤል አንበሶች ያሳደዱት፣
የተበተነ መንጋ ነው፤
መጀመሪያ የአሦር ንጉሥ፣
ቦጫጭቆ በላው፤
በኋላም የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር፣
አጥንቱን ቈረጣጠመው።”

18ስለዚህ የእስራኤል አምላክ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤

“የአሦርን ንጉሥ እንደ ቀጣሁት ሁሉ፣
የባቢሎንን ንጉሥና ምድሩን
እቀጣለሁ።
19እስራኤልንም ወደ መሰማሪያው
እመልሰዋለሁ፤
በቀርሜሎስና በባሳን ላይ ይሰማራል፤
በኤፍሬም ተራሮችና በገለዓድም ላይ፣
እስኪጠግብ ይመገባል።
20በዚያ ጊዜያት፣ በዚያ ዘመን፣”
*ይላል እግዚአብሔር፤*
“የእስራኤል በደል ይፈለጋል፤
አንዳችም አይገኝም፤
የይሁዳም ኀጢአት ይፈለጋል፤
ከቶም የለም፤
እንዲተርፉ ያደረግኋቸውን ትሩፋን
እምራለሁና።

21“የምራታይምን ምድር፣
የፋቁድ ነዋሪዎችንም፣
አሳዷቸው፤ ግደሏቸው፤ ፈጽማችሁም
አጥፏቸው፤”ነ
*ይላል እግዚአብሔር፤*
“ያዘዝኋችሁንም ሁሉ አድርጉ።
22በምድሪቱ የጦርነት ውካታ፣
የታላቅ ጥፋት ድምፅ ተሰማ።
23የምድር ሁሉ መዶሻ፣
እንዴት ተሰበረ! እንዴትስ ደቀቀ!
በሕዝቦች መካከል፣
ባቢሎን እንዴት ባድማ ሆነች!
24ባቢሎን ሆይ፤ ወጥመድ ዘርግቼልሻለሁ፤
አንቺም ሳታውቂ ተይዘሻል፤
እግዚአብሔርን ተገዳድረሻልና፣
ተገኘሽ፤ ተያዝሽም።
25እግዚአብሔር የመሣሪያ ግምጃ ቤቱን
ከፍቶአል፤
የቍጣውን የጦር ዕቃ አውጥቶአል፤
የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣
በባቢሎናውያን ምድር ሥራ አለውና።
26ከሩቅ መጥታችሁ በእርሷ ላይ ውጡ፤
ጐተራዎቿን አፈራርሱ፤
እንደ እህል ክምር ከምሯት፤
ፈጽማችሁ አጥፏት፤
ምንም አይቅር።
27ወይፈኖቿን ሁሉ ዕረዱ፤
ወደ መታረጃም ይውረዱ!
የሚቀጡበት ጊዜ፣
ቀናቸው ደርሶአልና ወዮላቸው!
28እግዚአብሔር አምላካችን የተበቀለውን፣
ስለ ቤተ መቅደሱ የተበቀለውን በቀል፣
ከባቢሎን የመጡ ኰብላዮችና ስደተኞች፣
በጽዮን የሚናገሩትን ስሟቸው።

29“ቀስት የሚገትሩትን፣

50፥10 ኢሳ47፥11፤ ኤር 30፥16
50፥11 ኢሳ47፥6፤ ኤር31፥18
50፥12 ቍ13፤ኢሳ 21፥1፤ኤር25፥12፤ 51፥26፡47
50፥13 ቍ3፡12፤ ዘዳ29፥22፤ኤር9፥11 ፤18፥16፤48፥9፤ 51፥37፡41፡62፤ሕዝ 27፥36፤ዕን2፥6
50፥14 ቍ29፡42፤ ኢሳ13፥18
50፥15 ቍ28፡29፤ 2ነገ25፥4፤መዝ 137፥8፤ኢሳ10፥3፤ 63፥4፤ኤር51፥6፡14፡ 24፡44፡58፤ዕን2፥7-8፤ ራእ18፥6
50፥16 ኢሳ13፥14፤ ኤር25፥38፤51፥9
50፥17 ዘሌ26፥33፤ ዘኍ24፥8፤ዘዳ4፥27፤ 2ነገ15፥29፤24፥1፡17፤ 25፥7፤መዝ119፥176፤ ኤር2፥15፤5፥17፤ 51፥34፤ሰቆ3፥4
50፥18 ኢሳ10፥12 ፤ሕዝ31፥3፤ሶፎ2፥13
50፥19 ኤር31፥5፡ 10፡14፤ሕዝ34፥13፤ ሚክ7፥14፤ዘካ10፥10
50፥20 ዘፍ45፥7፤ መዝ17፥3፤103፥12፤ ኢሳ1፥9፤10፥20-22፤ 33፥24፤38፥17፤ሕዝ 33፥16፤ሚክ7፥18፡19፤ ዘካ3፥4፡9፤ሮሜ9፥27
50፥21 ሕዝ23፥23
50፥22 ኤር4፥19- 21፤51፥54
50፥23 ኢሳ10፥5፤ 14፥16፤ኤር51፥25
50፥24 ኢዮ9፥4፤ ኤር51፥12፡31
50፥25 ኢሳ13፥5፤ ኤር51፥25፡55
50፥26 ቍ3፡41፤ ሩት3፥7፤ኢሳ14፥22- 23፤ኤር51፥11
50፥27 ኢዮ18፥20፤ መዝ68፥30፤ኢሳ 30፥25፤ኤር25፥34፤ 48፥15፤51፥6
50፥28 ቍ8፡15፤ 2ነገ24፥13፤ኢሳ 48፥20፤ኤር51፥10፡ 11፤52፥13
50፥29 ቍ14፤ዘዳ 32፥41፤ኢዮ21፥19፤ መዝ78፥41፤ ኢሳ 13፥18፤14፥13-14፤ 41፥20፤47፥10፤ኤር 51፥3፡5፡6፤ሕዝ 35፥11፤ዳን5፥23፤ አብ1፥15፤ራእ18፥6

ጎ10 ወይም *ከላውዴዎን*
ነ21 *አጥፏቸው* ለሚለው የሚተካው የዕብራይስጡ ቃል የሚ ያመለክተው ነገሮችን ወይም ሰዎችን ዳግም ላይመለሱ ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ መስጠትን ነው፤ ቍ26 ይመ።

ቀስተኞችን ሁሉ በባቢሎን ላይ ጥሩ፤
አንድም ሰው እንዳያመልጥ፣
ዙሪያውን ሁሉ መሽጉ፤
የእስራኤልን ቅዱስ፣
*እግዚአብሔርን* አቃለለችና፣
እንደ ሥራዋ መጠን መልሱላት፤
በሌሎች ላይ እንዳደረገችውም
አድርጉባት፡፡
30ስለዚህ ወንዶች ወጣቶቿ በየአደባባዩ
ይረግፋሉ፤
በዚያ ቀን ወታደሮቿ ሁሉ
ይወድቃሉ፤”
ይላል *እግዚአብሔር*፤
31“አንተ ትዕቢተኛ፤ እነሆ፣ በአንተ ላይ
ተነሥቻለሁ፤”
ይላል የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*፤
“የምትቀጣበት ጊዜ፣
ቀንህ ደርሶአልና፡፡
32ትዕቢተኛው ይሰናከላል፤ ይወድቃልም፤
የሚያነሣውም የለም፤
በዙሪያው ያሉትን ሁሉ የሚበላ እሳት፣
በከተሞቹ ውስጥ አስነሣለሁ፡፡

33የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

“የእስራኤል ሕዝብና የይሁዳ ሕዝብ፣
በአንድነት ተጨቍነዋል፤
የማረኳቸውም ሁሉ አጥብቀው
ይዘዋቸዋል፤
ይለቅቋቸውም ዘንድ እንቢ ብለዋል፡፡
34ነገር ግን ቤዛቸው ብርቱ ነው፤
ስሙም የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*
ነው፤
ለምድራቸው ዕረፍትን ለመስጠት፤
ተግቶ ይሟገትላቸዋል፤
በባቢሎን የሚኖሩትን ግን ዕረፍት
ይነሣቸዋል፡፡

35“ሰይፍ በባቢሎናውያን ላይ መጣ!”
ይላል *እግዚአብሔር*፤
“በባቢሎን ነዋሪዎች ላይ፤
በባለሥልጣኖቿና በጥበበኞቿም ላይ
ተመዘዘ!
36ሰይፍ በሐሰተኞች ነቢያቷ ላይ መጣ!
እነርሱም ሞኞች ይሆናሉ፤
ሰይፍ በጦረኞቿ ላይ ተመዘዘ፤
እነርሱም ይሸበራሉ፡፡
37ሰይፍ በፈረሰኞቿና በሠረገሎቿ ላይ፣
በመካከሏ ባሉት ባዕዳን ወታደሮች ሁሉ
ላይ መጣ!
እነርሱም እንደ ሴቶች ይሆናሉ፤
ሰይፍ በሀብት ንብረቷ ላይ መጣ!
ለዝርፊያም ይሆናሉ፡፡
38ድርቅ[ኘ] በውሆቿ ላይ መጣ!
እነሆ፤ ይደርቃሉ፤
ምድሪቱ በፍርሀት በሚሸበሩ አማልክት፣
በጣዖትም ብዛት ተሞልታለችና፡፡

39“ስለዚህ የምድረ በዳ አራዊትና የጅብ
መኖሪያ፣
የጕጕትም ማደሪያ ትሆናለች፤
ከእንግዲህ ወዲህ ማንም አይኖርባትም፤
ከትውልድ እስከ ትውልድም
የሚቀመጥባት አይገኝም፡፡
40*እግዚአብሔር* ሰዶምንና ገሞራን፤
በዙሪያቸውም የነበሩትን ከተሞች ያለ
ነዋሪ እንዳስቀራቸው፤”
ይላል *እግዚአብሔር*፡፡
“እንዲሁ ማንም በዚያ አይኖርም፣
የሚቀመጥባትም አይገኝም፡፡
41“እነሆ፤ ሰራዊት ከሰሜን ይመጣል፤
አንድ ኀያል መንግሥትና ብዙ
ነገሥታት፣
ከምድር ዳርቻ ተነሣሥተዋል፡፡
42ቀስትና ጦር ይዘዋል፤
ጨካኞች ናቸው፤ ምሕረትም
አያደርጉም፤
በፈረሳቸው እየጋለቡ ሲመጡ፣
ድምፃቸው እንደ ባሕር ሞገድ ይተማል
ያስገመግማል፡፡
አንቺ የባቢሎን ሴት ልጅ ሆይ፤
ለጦርነት እንደ ተዘጋጁ ተዋጊዎች
ይመጡብሻል፡፡
43የባቢሎን ንጉሥ ስለ እነርሱ ሰማ፤
እጆቹም በድን ሆኑ፤
ጭንቀት ይዞታል፤
ምጥ እንደ ያዛት ሴት ታሟል፡፡
44አንበሳ ከዮርዳኖስ ደኖች ድንገት
ወጥቶ፣
ወደ ግጦሽ ሜዳ ብቅ እንደሚል፣
እኔም ባቢሎንን ሳይታሰብ ከምድሯ
አባርራታለሁ፤
የመረጥሁትንም በእርሷ ላይ እሾማለሁ፤
እንደ እኔ ያለ ማን ነው? ማንስ
ሊገዳደረኝ ይችላል?
የትኛውስ እረኛ ሊቋቋመኝ ይችላል?
45ስለዚህ *እግዚአብሔር* በባቢሎን ላይ
ያቀደውን፣
በባቢሎናውያንም ምድር ላይ ያሰበውን
ስሙ፤
ከመንጋው ታናናሹ ተጐትቶ ይወሰዳል፤
በእነርሱም ምክንያት መሰማሪያቸውን
ፈጽሞ ያጠፋል፡፡
46በባቢሎን ውድቀት ድምፅ ምድር
ትናወጣለች፤
ጩኸቷም በሕዝቦች መካከል ያስተጋባል፡፡

[ኘ]38 *ወይም ሰይፍ*

50፥30 ኢሳ13፥18
50፥31 ኢዮ18፥20፤ ኤር21፥13፤ራእ18፥7-8
50፥32 መዝ20፥8፤ 119፥21፤ኤር49፥27፤ አሞ 5፥2
50፥33 ኢሳ14፥17፤ 58፥6
50፥34 ዘፀ6፥6፤ኢዮ 19፥25፤መዝ119፥154 ፤ኢሳ14፥7፤49፥25፤ ኤር15፥21፤31፥35፤ 51፥19፡36፤ሰቆ3፥58
50፥35 ኢሳ45፥1፤ ኤር47፥6፤ዳን 5፥7
50፥36 ኤር49፥22፤ 51፥30፡32
50፥37 2ነገ19፥23፤ ኢሳ19፥16፤45፥3፤ ኤር51፥21
50፥38 ቊ2፤መዝ 137፥1፤ኢሳ11፥15፤ ኤር51፥13፡36
50፥39 መዝ74፥14 ፤ኢሳ13፥19-22፤ 34፥13-15፤ኤር 51፥37፤ራእ 18፥2
50፥40 ዘፍ19፥24፤ ኤር51፥62፤ማቴ 10፥15
50፥41 ቊ26፤ኢሳ 13፥4፡17፤41፥25፤ ኤር51፥22-28
50፥42 ቊ14፤ኢዮ 30፥21፤ኢሳ5፥30፤ 13፥18፤ 47፥1
50፥43 ኤር6፥22-24፤47፥3
50፥44 ዘኍ16፥5፤ ኢዮ41፥10፤ኢሳ 46፥9፤ኤር12፥5፤ 49፥19
50፥45 መዝ33፥11 ፤ኢሳ48፥14፤ኤር 51፥11
50፥46 መሳ5፥4፤ ኢ. ዮ24፥12፤ኤር49፥ 21፤ ራእ 18፥9-10

51 *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“እነሆ፤ በባቢሎንና[ሀ] በምድሯ ላይ፣
የሚያጠፋ ነፋስ አስነሣለሁ።
2እንዲያበጥሯትና እንዲያወድሟት፣
ባዕዳንን በባቢሎን ላይ እልካለሁ፤
በመከራዋም ቀን፣
ከበው ያስጨንቋታል።
3ቀስተኛው ቀስቱን እስኪገትር፣
የጦር ልብሱንም እስኪለብስ ፋታ
አትስጡት፤
ለወጣቶቿ አትዘኑ፤
ሰራዊቷንም ፈጽማችሁ አጥፉ።[ለ]
4በባቢሎን[ሐ] ምድር ታርደው፣
በአደባባዮቿም እስከ ሞት ቈስለው
ይወድቃሉ።
5ምድራቸው[መ] በእስራኤል ቅዱስ ፊት፣
በበደል የተሞላች ብትሆንም፣
እስራኤልንና ይሁዳን አምላካቸው፣
የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*
አልጣላቸውም።

6“ከባቢሎን ሽሽታችሁ ውጡ!
ፈጥናችሁም ሕይወታችሁን አትርፉ!
በኀጢአቷ ምክንያት አትጥፉ።
*የእግዚአብሔር* የበቀል ጊዜ ነው፤
እርሱም የሥራዋን ይከፍላታል።
7ባቢሎን *በእግዚአብሔር* እጅ የወርቅ
ጽዋ ነበረች፤
ምድርንም ሁሉ አሰከረች።
ሕዝቦች ከወይን ጠጇ ጠጡ፤
ስለዚህ አሁን አብደዋል።
8ባቢሎን በድንገት ወድቃ ትሰበራለች፤
ዋይ በሉላት!
ምናልባት ልትፈወስ ስለምትችል፣
ለቍስሏ የሚቀባ መድኀኒት
ፈልጉላት።

9“ ‘ባቢሎንን ለመፈወስ ሞክረን ነበር፤
እርሷ ግን ልትፈወስ አትችልም፤
ፍርዷ እስከ ሰማይ ስለ ደረሰ፣
እስከ ደመናም ድረስ ከፍ ስላለ፣
ትተናት ወደየአገራችን እንሂድ።’

10“ ‘*እግዚአብሔር* ቅንነታችንን መሰከረ፤
ኑ፤ አምላካችን *እግዚአብሔር*
ያደረገውን፣
በጽዮን እንናገር።’
11“ፍላጾችን ሳሉ፤
ጋሻዎችን አዘጋጁ፤
*የእግዚአብሔር* ሐሳብ ባቢሎንን
ለማጥፋት ስለ ሆነ፣
የሜዶንን ነገሥታት አነሣሥቶአል፤
*እግዚአብሔር* ይበቀላል፤
ስለ ቤተ መቅደሱ ይበቀላል።

51፥1 ኢሳ13፥17፤ ኤር25፥12
51፥2 ኢሳ13፥5፡9፤ 41፥16፤ማቴ3፥12
51፥3 ኤር46፥4፤ 50፥29
51፥4 ኢሳ13፥15፡ 18
51፥5 ዘሌ26፥44፤ ኢሳ54፥6-8፤ሆሴ4፥1
51፥6 ቀኍ24፡56፤ ዘኍ16፥26፤ዘዳ32፥35፤ኢዮ21፥19፤ኢሳ1፥24፤48፥20፤ኤር25፥14፤50፥15፡27፡29፤ ሰቆ3፥64፤ራእ18፥4
51፥7 ኢሳ51፥22፤ ኤር25፥15-16፤49፥12፤ራእ14፥8-10
51፥8 ኢሳ14፥15፤ 21፥9፤ኤር8፥22፤ 46፥11፤ራእ14፥8
51፥9 ኢሳ13፥14፤ 31፥9፤ኤር50፥16፤ ራእ 18፥4-5
51፥10 መዝ64፥9፤ ኤር50፥28፤ሚክ7፥9
51፥11 ቀኍ28፤ዘሌ 26፥25፤ኢሳ13፥3፤ 21፥5፤41፥2፡25፤ኤር 50፥9፡28፡45
51፥12 ቀኍ27፤ 2ሳሙ18፥24፤መዝ 20፥5፤ 33፥11፤ኤር 50፥24፤ሕዝ33፥2
51፥13 ኢሳ45፥3፤ ኤር50፥3፡38፤ሕዝ 22፥27፤ዕን2፥9
51፥14 ቀኍ27፤ዘፍ 22፥16፤ኤር50፥15፤ አሞ6፥8፤7፥1፤ ናሆ 3፥15
51፥15 ዘፍ1፥1፤ መዝ104፥2፡24፤ 136፥15
51፥16 ዘዳ28፥12፤ ኢዮ28፥26፤መዝ 135፥7፤18፥11-13፤ ዮና1፥4
51፥17 ኢሳ44፥20፤ ዕን2፥18-19
51፥18 ኤር18፥15
51፥19 ዘፀ34፥9፤ መዝ119፥57
51፥20 ኢዮ 34፥24፤ኢሳ10፥5፤ 45፥1፤ ሚክ 4፥13፤ ዘካ 9፥13
51፥21 ዘፀ 15፥1፤ ኢሳ 43፥17፤ ኤር 50፥37

12በባቢሎን ቅጥር ላይ ዐላማ አንሡ!
ጥበቃውን አጠናክሩ፤
ዘብ ጠባቂዎችን አቁሙ፤
ደፈጣ ተዋጊዎችን አዘጋጁ!
*እግዚአብሔር* በባቢሎን ሕዝብ ላይ
የወሰነውን፣
ዐላማውን ያከናውናል።
13አንቺ በብዙ ውሃ አጠገብ የምትኖሪ፣
በሀብትም የበለጸግሽ ሆይ፤
የምትወገጂበት ጊዜ ወጥቶአል፤
ፍጻሜሽ ደርሶአል።
14የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ሲል በራሱ ምሎአል፤
ብዛቱ እንደ አንበጣ መንጋ የሆነ
ሰራዊት ያጥለቀልቅሻል፤
እነርሱም በድል አድራጊነት በላይሽ
ያቅራራሉ።

15“ምድርን በኀይሉ የሠራ፣
ዓለምን በጥበቡ የመሠረተ፣
ሰማያትንም በማስተዋሉ የዘረጋ እርሱ
ነው።
16ድምፁን ባንጐደጐደ ጊዜ በሰማይ
ውሆች ይናወጣሉ፤
ጉሙን ከምድር ዳርቻ ወደ ላይ
እንዲወጣ ያደርገዋል፤
መብረቅን ከዝናብ ጋር ይልካል፤
ነፋስንም ከግምጃ ቤቱ ያወጣል።

17“እያንዳንዱ ሰው ጅልና ዕውቀት
የለሽ ነው፤
የወርቅ አንጥረኛው ሁሉ በሠራው
በጣዖቱ ዐፍሮአል፤
የቀረጻቸው ምስሎቹ የሐሰት ናቸው፤
እስትንፋስ የላቸውም።
18እነርሱ ከንቱ የፌዝ ዕቃዎች ናቸው፣
ፍርድ ሲመጣባቸው ይጠፋሉ።
19የያዕቆብ ዕድል ፈንታ የሆነው ግን
እንደ እነዚህ አይደለም፤
እርሱ የሁሉ ነገር ፈጣሪ ነውና፤
እስራኤልም የርስቱ ነገድ ነው።
ስሙ የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር*
ነው።

20“አንቺ የእኔ ቈመጥ፣
የጦር መሣሪያዬ ነሽ፤
በአንቺ ሕዝቦችን እሰባብራለሁ፤
በአንቺ መንግሥታትን አጠፋለሁ፤
21በአንቺ ፈረሱንና ፈረሰኛውን
እሰባብራለሁ፤

[ሀ]1 *ሌብ ካማይ* የከላውዴዎን ማለትም የባቢሎን ስም ነው።
[ለ]3 *አጥፉ* ለሚለው የዕብራይስጡ ቃል የሚያመለክተው ነገሮችን ወይም ሰዎችን ዳግም ላይመለሱ ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ መስጠት ነው።
[ሐ]4 ወይም *ከላውዴዎን*
[መ]5 ወይም *የባቢሎናውያን ምድር*

በአንቺ ሠረገላውንና ሠረገላ ነጂውን
እሰባብራለሁ፤
22 በአንቺ ወንዱንና ሴቱን እሰባብራለሁ፤
በአንቺ ሽማግሌውንና ወጣቱን
እሰባብራለሁ።
በአንቺ ጐረምሳውንና ኰረዳዪቱን
እሰባብራለሁ።
23 በአንቺ እረኛውንና መንጋውን
እሰባብራለሁ፣
በአንቺ ገበሬውንና በሬውን
እሰባብራለሁ፤
በአንቺ ገዦችንና ባለ ሥልጣኖችን
እሰባብራለሁ።

24 “በጽዮን ላይ ስላደረሱት ጥፋት ሁሉ
ለባቢሎንና በባቢሎን[o] ለሚኖሩት ሁሉ ዐይ
ናችሁ እያየ ዋጋቸውን እከፍላቸዋለሁ”
ይላል *እግዚአብሔር።*

25 “አንቺ ምድርን ሁሉ ያጠፋሽ፣
አጥፊ ተራራ ሆይ፤ እኔ በአንቺ ላይ
ነኝ፣”
ይላል *እግዚአብሔር፤*
“እጄን በአንቺ ላይ አነሣለሁ፤
ከገመገም ቍልቍል አንከባልልሻለሁ፤
የተቃጠለም ተራራ አደርግሻለሁ።
26 ከአንቺ ለማእዘን የሚሆን ድንጋይ፣
ለመሠረትም የሚሆን ዐለት
አይወሰድም፤
ለዘላለም ባድማ ትሆኛለሽ፤”
ይላል *እግዚአብሔር።*
27 “በምድር ሁሉ ላይ ሰንደቅ ዐላማ አን
ሡ!
በሕዝቦች መካከል መለከት ንፉ!
ሕዝቦችን ለጦርነት በእርሷ ላይ አዘጋጁ፤
የአራራትን፣ የሚኒንና የአስከናዝን
መንግሥታት፣
ጠርታችሁ በእርሷ ሰብስቡአቸው፤
የጦር አዝማች ሹሙባት፤
ፈረሶችንም እንደ አንበጣ መንጋ
ስደዱባት።
28 የሜዶንን ነገሥታት፣
ገዦቿንና ባለሥልጣኖቿን ሁሉ፣
በግዛታቸው ሥር ያሉትን አገሮች ሁሉ፣
እነዚህን ሕዝቦች ለጦርነት
አዘጋጁባት።
29 ሰው በዚያ መኖር እስከማይችል ድረስ፣
የባቢሎንን ምድር ባድማ ለማድረግ፣
*እግዚአብሔር* በባቢሎን ላይ ያቀደው
ስለሚጸና፣
ምድር ትናወጣለች፤ በሥቃይም
ትወራጫለች።
30 የባቢሎን ጦረኞች መዋጋት ትተዋል፤
በምሽጎቻቸው ውስጥ ተቀምጠዋል፤

51፥22 2ዜና 36፥17፤ ኢሳ 13፥17-18
51፥23 ቍ57
51፥24 ቍ6፥35፤ ዘዳ 32፥41፤ ኤር 50፥15፤ ሰቆ 3፥64፤ ኢሳ 45፥1
51፥25 ዘፀ 3፥20፤ ኤር 21፥13፤ 50፥23፤ ዘካ 4፥7
51፥26 ቍ29፤ ኢሳ 13፥19-22፤ ኤር 50፥12
51፥27 ቍ14፤ ዘፍ 8፥43፤ 10፥3፤ መዝ 20፥5፤ ኢሳ 13፥2፤ ኤር 25፥14
51፥28 ቍ 11፥48
51፥29 ቍ43፤ መሳ 5፥4፤ መዝ 33፥11፤ ኢሳ 13፥20፤ ኤር 48፥9፤ 49፥21
51፥30 ኢሳ 19፥16፤ 45፥2፤ 47፥14፤ ኤር 50፥36
51፥31 2ሳሙ 18፥19-31፤ኤር 50፥2፤ዳን5፥30
51፥32 ኢሳ47፥14፤ ኤር50፥36
51፥33 ኢሳ13፥22፤ 17፥5፤21፥10፤47፥1
51፥34 ቍ44፤ ዘሌ 18፥25፤ኤር50፥17፤ ሆሴ8፥8፤ናሆ2፥12
51፥35 ቍ24፤መዝ 137፥8፤ኢል3፥19፤ ዕን 2፥17
51፥36 ቍ6፤መዝ 140፥12፤ኢሳ11፥15፤ 19፥5፤ኤር20፥12፤ 50፥34፤ሰቆ3፥58፤ ሆሴ13፥15፤ሮሜ 12፥19
51፥37 ኢሳ13፥22፤ ኤር50፥13፥39፤ናሆ 3፥6፤ሚል2፥9፤ራእ 18፥2፤
51፥38 ኢሳ5፥29

ኀይላቸው ተሟጦአል፤
እንደ ሴት ሆነዋል፤
በማደሪያዎቿም እሳት ተለኵሶአል፤
የደጇም መወርወሪያ ተሰብሮአል።
31 ከተማዪቱ ሙሉ በሙሉ መያዟን፣
ለባቢሎን ንጉሥ ለመንገር፣
አንዱ ወሬኛ ሌላውን ወሬኛ፣
አንዱ መልእክተኛ ሌላውን
መልእክተኛ ወዲያው ወዲያው
ይከተላል፤
32 መልካዎቿ እንደተያዙ፣
የወንዝ ዳር ምሽጎቿ እንደ ተቃጠሉ፣
ወታደሮቿም እንደ ተደናገጡ ሊነግሩት
ይሯሯጣሉ።”

33 የእስራኤል አምላክ የሰራዊት ጌታ *እግዚ
አብሔር* እንዲህ ይላል፤

“የባቢሎን ሴት ልጅ በመረገጥ ላይ
እንዳለ፣
የእህል መውቂያ አውድማ ናት፤
የመከር ወራቷም ፈጥኖ ይደርስባታል።

34 “የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር በላን፣
አድቅቆ ፈጨን፤
እንደ ባዶ ማድጋ አደረገን፤
እንደ ዘንዶ ዋጠን፣
እንደ ጣፋጭ በልቶን ሆዱን ሞላ፤
በኋላም አንቅሮ ተፋን፤
35 የጽዮን ነዋሪዎች፣ እንዲህ ይላሉ፤
“በሥጋችን[ǁ] ላይ የተፈጸመው ግፍ
በባቢሎን ላይ ይሁን፤”
ኢየሩሳሌም እንዲህ ትላለች፤
“ደማችን በባቢሎን ምድር በሚኖሩት
ላይ ይሁን።”

36 ስለዚህ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

“እነሆ፤ እሟገትልሻለሁ፣
በቀልሽንም እኔ እበቀልልሻለሁ፤
ባሕሯን አደርቃለሁ፣
የምንጮቿንም ውሃ።
37 ባቢሎን የፍርስራሽ ክምር፣
የቀበሮዎች መፈንጫ፣
የድንጋጤና የመሣለቂያ ምልክት
ትሆናለች፤
የሚኖርባትም አይገኝም።
38 ሕዝቦቿ ሁሉ እንደ ደቦል አንበሳ
ያገሣሉ፤
እንደ አንበሳ ግልገልም ያጕረመርማሉ።
ጕሮሮአቸው በደረቀ ጊዜ
ድግስ አዘጋጅላቸዋለሁ፤
እንዲሰክሩም አደርጋቸውና፤”

[o]24 ወይም *ከላውዴዎን፤* ቍ35 ይመ።
[ǁ]35 ወይም *በእኛና በልጃችን ላይ የተፈጸመው*

39በሣቅ እየፈነደቁ፣
ለዘላለም ሳይነቁ ይተኛሉ፡፡”
ይላል *እግዚአብሔር፡፡*
40“እንደ ጠቦት፣
እንደ አውራ በግና እንደ ፍየል፣
ወደ መታረድ አወርዳቸዋለሁ፡፡
41“ሼሻክ[ሠ] እንዴት ተማረከች!
የምድር ሁሉ ትምክህትስ እንዴት
ተያዘች!
ባቢሎን በሕዝብ ሁሉ ዘንድ፣
ምንኛ አስደንጋጭ ሆነች፡፡
42ባሕር በባቢሎን ላይ ይወጣል፤
ሞገዱም እየተመመ ይሸፍናታል፡፡
43ከተሞቿ ሰው የማይኖርባቸው፣
ዝርም የማይልባቸው፣
ደረቅና በረሓማ ቦታ፣
ባድማ ምድርም ይሆናሉ፡፡
44ቤልን በባቢሎን ውስጥ እቀጣለሁ፤
የዋጠውን አስተፋዋለሁ፤
ሕዝቦች ከእንግዲህ ወደ እርሱ አይጠ
ጐርፉም፤
የባቢሎንም ቅጥር ይወድቃል፡፡

45“ሕዝቤ ሆይ፤ ከመካከሏ ውጡ!
ሕይወታችሁን አትርፉ!
ከአስፈሪው *የእግዚአብሔር* ቍጣ
አምልጡ፡፡

46ወሬ በምድሪቱ ሲሰማ፣
ተስፋ አትቍረጡ ፤ አትፍሩም፤
ገዥ በገዥ ላይ ስለ መነሣቱ፣
ዐመፅም በምድሪቱ ስለ መኖሩ፣
አንድ ወሬ ዘንድሮ፣ ሌላውም ለከርሞ
ይመጣል፤
47የባቢሎንን ጣዖታት የምቀጣበት ጊዜ፣
በእርግጥ ይመጣልና፡፡
ምድሯ በሙሉ ትዋረዳለች፤
የታረዱትም በሙሉ በውስጧ
ይወድቃሉ፡፡
48ሰማይና ምድር በውስጣቸውም ያለው
ሁሉ፣
በባቢሎን ላይ እልል ይላሉ፤
አጥፊዎች ከሰሜን ወጥተው፣
እርሷን ይወጓታልና፤”
ይላል *እግዚአብሔር፡፡*

49“በምድር ሁሉ የታረዱት፣
በባቢሎን ምክንያት እንደ ወደቁ፣
ባቢሎንም በእስራኤል በታረዱት
ምክንያት መውደቅ ይገባታል፡፡
50ከሰይፍ ያመለጣችሁ ሆይ፤
ሂዱ! ጊዜ አትፍጁ፤
በሩቅ ምድር ያላችሁ *እግዚአብሔርን*
አስታውሱ፤

51፥39 ቍ57፤መዝ 13፥3፤ኢሳ 21፥5፤ ኤር50፥24
51፥40 ሕዝ39፥18
51፥41 ኢሳ13፥19፤ ኤር 25፥26፤ 50፥13
51፥42 መዝ18፥4፤ ኢሳ 8፥7
51፥43 ቍ29፡62፤ ኢሳ 13፥20፤ 21፥1፤ ኤር 2፥6
51፥44 ቍ34፡58፤ 2ነገ25፥4፤ኢሳ21፥9፤ 25፥12፤46፥1፤ኤር 50፥15
51፥45 ቍ50፤ መዝ76፥10፤ 79፥6፤ ኢሳ 48፥20
51፥46 2ነገ19፥7፤ መዝ18፥45፤ኤር 46፥27
51፥47 ኢሳ46፥1-2 ፤ኤር27፥7፤50፥2፡12
51፥48 ቍ11፡53፡ 56፤ኢዮ 3፥7፤መዝ 149፥2፤ኢሳ41፥25፤ ኤር25፥26፤ ራእ 18፥20
51፥49 መዝ137፥8 ፤ ኤር 50፥29
51፥50 ቍ45፤ መዝ137፥6፤ኤር 23፥23
51፥51 መዝ44፥13-16፤79፥4፤ሰቆ 1፥10
51፥52 ቍ47፤ኢዮ 24፥12
51፥53 ቍ48፤ዘፍ 11፥4፤ኢዮ15፥21፤ ኢሳ14፥13-14
51፥54 ኢዮ24፥12፤ ኤር50፥22
51፥55 መዝ18፥4፤ ኢሳ25፥5
51፥56 ቍ6፡48፤ ዘፍ4፥24፤ዘዳ32፥41፤ ኢዮ15፥21፤መዝ 46፥9፤94፥1-2፤ዕብ 2፥8
51፥57 ቍ23፡39፤ ኢዮ5፥13፤መዝ76፥5 ፤ኢሳ6፥5፤21፥5፤ኤር 25፥27
51፥58 ቍ44፡64፤ 2ነገ25፥4፤ኢሳ15፥1 ፤13፥2፤47፥13፡14
51፥59 ኤር28፥1፤ 36፥4፤52፥1
51፥60 ዘፀ 17፥14፤ ኤር30፥2፤ 36፥2

ኢየሩሳሌምንም አስቧት፡፡”
51“ባዕዳን ሰዎች ወደ ተቀደሰው፣
ወደ *እግዚአብሔር* ቤት ስለ ገቡ፣
እኛ ተሰድበናል፤
ዕፍረትም ፊታችንን ሸፍኖአል፤
ውርደትም ተከናንበናል፡፡”
52“እንግዲህ ጣዖቶቿን የምቀጣበት ዘመን
ይመጣል፤”
ይላል *እግዚአብሔር፤*
“በምድሯም ሁሉ፤
ቍስለኞች ያቃስታሉ፡፡
53ባቢሎን ወደ ሰማይ ብትወጣም፣
ከፍ ያለ ምሽጓን ብታጠናክርም፣
አጥፊዎች እሰድባታለሁ፤”
ይላል *እግዚአብሔር፡፡*
54“ከባቢሎን ጩኸት፣
ከባቢሎናውያንም[የ] ምድር፣
የታላቅ ጥፋት ድምፅ ይሰማል፡፡
55*እግዚአብሔር* ባቢሎንን ያጠፉታል፤
ታላቅ ጩኸቷንም ጸጥ ያደርጋል፡፡
ሞገዳቸው እንደ ታላቅ ውሃ ይተማል፤
ጩኸታቸውም ያስተጋባል፡፡
56በባቢሎን ላይ አጥፊ ይመጣል፤
ጦረኞቿ ይማረካሉ፤
ቀስታቸውም ይሰበራል፤
*እግዚአብሔር* ግፍን የሚበቀል፣
ተገቢውንም ሁሉ የሚከፍል አምላክ
ነውና፡፡
57ባለ ሥልጣኖቿንና ጥበበኞቿን፣
ገዦቿንና መኳንንቷን፣ ጦረኞቿንም
አሰክራለሁ፤
ለዘላለም ይተኛሉ፤ አይነቁምም፤”
ይላል ስሙ የሰራዊት ጌታ
*እግዚአብሔር* የሆነው ንጉሥ፡፡
58የሰራዊት ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“ወፍራሙ የባቢሎን ቅጥር ፈጽሞ
ይፈርሳል፤
ከፍ ያሉት ደጆቿም በእሳት
ይቃጠላሉ፤
ሰዎቹ በከንቱ ይደክማሉ፤
የሕዝቡም ልፋት ለእሳት ይሆናል፡፡”

59የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ በነገሠ በአራ
ተኛው ዓመት፣ የንጉሡ የግቢ አስከልካይ
የነበረው የመሕሤያ ልጅ የኔርያ ልጅ
ሡራያ ከንጉሡ ጋር ወደ ባቢሎን በሄደ
ጊዜ፣ ነቢዩ ኤርምያስ የሰጠው መልእክት
ይህ ነው፡፡ 60ኤርምያስ ስለ ባቢሎን ጽፎ
ያስቀመጠውን ሁሉ፣ በባቢሎን ላይ የሚ

[ሠ]41 *ሼሻክ* የባቢሎን ስውር ስም ነው፡፡

*መጣውን* ጥፋት ሁሉ በብራና ጥቅልል
ላይ ጻፈው፤ [61]ለሠራያም እንዲህ አለው፤
“ባቢሎን በደረስህ ጊዜ፣ ይህን ቃል ሁሉ
ድምፅህን ከፍ አድርገህ ማንበብ አትዘንጋ
[62]እንዲህም በል፤ ‘*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ይህ
ችን ስፍራ ሰውም ሆነ እንስሳ እስከማይ
ኖርባት ድረስ ለዘላለም ባድማ አደርጋታ
ለሁ ብለሃል።’ [63]ይህን ብራና አንብበህ
ከጨ ረስህ በኋላ፣ ድንጋይ አስረህበት
ኤፍራጥስ ወንዝ ውስጥ ጣለው፤ [64]እንዲ
ህም በል፤ ‘ባቢሎንም እኔ ከማመጣባት
ጥፋት የተነሣ፣ እንደዚሁ ትሰጥማለች፤
ከእንግዲህም አትነሣም፤ ሕዝቧም
ይወድቃል።’ ”

የኤርምያስ ቃል እዚህ ላይ ይፈጸማል።

## የኢየሩሳሌም መውደቅ

52፥1-3 ተጓ ምብ-2ነገ24፥18-20፤2ዜና36፥11-16
52፥4-16 ተጓ ምብ-ኤር39፥1-10
52፥4-21 ተጓ ምብ-2ነገ25፥1-21፤2ዜና36፥17-20

52 ሴዴቅያስ ሲነግሥ ዕድሜው ሃያ
አንድ ዓመት ነበረ፤ በኢየሩሳ
ሌም ዐሥራ አንድ ዓመት ነገሠ፤ የእና
ቱም ስም አሚጣል ሲሆን፣ እርሷም የሊ
ብና ሰው የኤርምያስ ልጅ ነበረች። [2]ሴዴ
ቅያስም ኢዮአቄም እንዳደረገው ሁሉ፣ *በእ
ግዚአብሔር* ፊት ክፉ ነገር አደረገ። [3]*እግ
ዚአብሔር* በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ላይ
ይህን ሁሉ ያደረሰውንና በመጨረሻም
ከፊቱ ያስወገዳቸው ከቍጣው የተነሣ ነበር።
ሴዴቅያስም በባቢሎን ንጉሥ ላይ ዐመፀ።
[4]ስለዚህ ሴዴቅያስ በነገሠ በዘጠነኛው
ዓመት በዐሥረኛው ወር፣ ከወሩም በዐ
ሥረኛው ቀን፣ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነ
ፆር ሰራዊቱን ሁሉ አስከትቶ በኢየሩሳ
ሌም ላይ ዘመተ፤ ከተማዪቱንም ከበባት፤
በዙሪያውም የዐፈር ድልድል ሠሩ። [5]ከተ
ማዪቱም እስከ ንጉሡ እስከ ሴዴቅያስ
ዐሥራ አንደኛ ዘመነ መንግሥት ተከባ
ነበር።
[6]በአራተኛው ወር በዘጠነኛው ቀን
በከተማዪቱ ራብ ጸንቶ ስለ ነበር ሕዝቡ
የሚበላውን አጣ፤ [7]የከተማዪቱም ቅጥር
ተነደለ፤ ሰራዊቱም ሁሉ ኰብልሎ ሄደ።
ባቢሎናውያን[ደ] በከተማዪቱ ዙሪያ ቢኖሩም፣
በንጉሡ የአትክልት ስፍራ አጠገብ በሁ
ለት ቅጥሮች መካከል ባለው በር በሌሊት
ከተማዪቱን ጥለው ሸሹ፤ ወደ ዓረባም[ጀ]
አመሩ። [8]የባቢሎናውያንም[ገ] ሰራዊት ንጉሥ
ሴዴቅያስን ተከታትሎ በማሳደድ በኢያ
ሪኮ ሜዳ ደረሰበት፤ ወታደሮቹም ሁሉ
ከእርሱ ተለይተው ተበታትነው ሳለ፣ ንጉ
ሡን ያዙት።
[9]እርሱም በሐማት ምድር በሪብላ ወደ
ነበረው ወደ ባቢሎንም ንጉሥ ተወሰደ፤
የባቢሎን ንጉሥ በዚያ ፈረደበት። [10]በሪብ
ላም የባቢሎን ንጉሥ፣ የሴዴቅያስን ወንዶች
ልጆች በአባታቸው ፊት ዐረዳቸው፤ የይሁ
ዳንም ባለሥልጣኖች ሁሉ ገደላቸው፤
[11]የሴዴቅያስንም ዐይኖች አወጣ፤ በናስ
ሰንሰለትም አስሮ ወደ ባቢሎን ወሰደው፤
በዚያም እስከ ዕለተ ሞቱ በእስር ቤት
አቈየው።
[12]የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር በነገሠ
በዐሥራ ዘጠነኛው ዓመት በአምስተኛው
ወር፤ ከወሩም በዐሥረኛው ቀን፣ የባቢሎን
ንጉሥ ባለሟል የክብር ዘበኞች አዛዥ የነ
በረው ናቡዘረዳን ወደ ኢየሩሳሌም መጣ።
[13]*የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስና የንጉ
ሡን ቤተ መንግሥት እንዲሁም በኢየሩ
ሳሌም የነበሩትን ቤቶች ሁሉ በእሳት
አቃጠለ፤ ሌሎች ትልልቅ ሕንጻዎችንም
በእሳት አወደመ። [14]በክብር ዘበኞቹ አዛዥ
ሥር የነበሩት የባቢሎናውያን ሰራዊት
ሁሉ በኢየሩሳሌም ዙሪያ ያለውን ቅጥር
በሙሉ አፈረሱ። [15]የዘቦቹ አዛዥ
ናቡዘረዳን አንዳንድ ድኾችንና በከተ
ማዪቱ የቀረ ውን ሕዝብ፣ የእጅ ጥበብ
ያላቸውንና[ጠ] ሸሽተው ወደ ባቢሎን ንጉሥ
የተጠጉትን አፈለሳቸው። [16]ነገር ግን
የክብር ዘበኞቹ አዛዥ ናቡዘረዳን ሌሎች
የምድሪቱን ድኾች ወይን ተካዮችና ዐራ
ሾች እንዲሆኑ አስቀራቸው።
[17]ባቢሎናውያን *በእግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስ የነበሩትን የናስ ዐምዶች፣ ተን
ቀሳቃሽ ማስቀመጫዎችንና ከናስ የተሠራ
ውን የውሃ ገንዳ ሰባበሩ፤ ናሱንም ሁሉ
ወደ ባቢሎን ይዘው ሄዱ። [18]ከእነዚህም
ሌላ ምንቸቶቹን፣ መጫሪያዎቹን፣ መኰስተ
ሪያዎቹን፣ ወጭቶችን፣ ጭልፋዎቹንና
ለቤተ መቅደስ አገልግሎት የሚውሉትን
የናስ ዕቃዎች በሙሉ ወሰዱ። [19]የክብር
ዘበኞቹ አዛዥ ከንጹሕ ወርቅና ከንጹሕ ብር
የተሠሩትን ዕቃዎች ሁሉ ጐድጓዳ ሳሕኖ
ችን ጥናዎችን፣ ወጭቶችን፣ ምንቸቶችን፣
መቅረዞችን፣ ጭልፋዎችንና ለመጠጥ ቍር
ባን ማቅረቢያ የሚሆኑ ወጭቶችን ይዞ
ሄደ።
[20]ንጉሥ ሰሎሞን *ለእግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስ ከናስ ያሠራቸው፦ ሁለቱ ዐምዶች፣
ትልቁ የውሃ ገንዳ፣ ከሥሩ ያሉት ዐሥራ
ሁለት ወይፈኖችና ተንቀሳቃሽ ማስቀመ
ጫዎች ክብደታቸው ሚዛን ከሚችለው

51፥62 ኢሳ13፥20፤ ኤር9፥11፤50፥13
51፥63 ዘፍ2፥14
51፥64 ቍ58፤ኢዮ 31፥40፤ሕዝ26፥21፤ 28፥19፤ ራእ 18፥21
52፥1 ዘኍ 33፥20፤ ኢሱ 10፥29፤ 2ነገ 8፥22፤ 24፥17
52፥2 ኤር 36፥30
52፥3 ዘፍ 4፥14፤ ዘፀ 33፥15፤ ኢሳ 3፥1፤ሕዝ17፥12-16
52፥4 ኤር 6፥6፤ 34፥1፤ሕዝ24፥1-2፤ ዘካ 8፥19
52፥6 ዘሌ26፥26፤ ኢሳ3፥1፤ ሰቆ1፥11
52፥7 ሰቆ4፥19
52፥9 ዘኍ13፥21፤ 34፥11፤ኤር21፥7፤ 32፥4
52፥10 ኤር22፥30
52፥11 ኤር34፥4 ፤ሕዝ12፥13፤17፥16
52፥12 ቍ26፤ዘካ 7፥5፤8፥19
52፥13 ዘዳ13፥16፤ 29፥24፤2ዜና36፥19 ፤መዝ74፥8፤79፥1፤ ኤር19፥13፤ሰቆ2፥6 ሚክ3፥12፤
52፥14 ነህ1፥3፤ ሰቆ 2፥8
52፥15 2ነገ24፥1፤ ኤር1፥3፤38፥19
52፥16 ኤር40፥6
52፥17 1ነገ7፥15፡ 27-37፤27፥19-22
52፥18 ዘፀ27፥3፤ ዘኍ4፥14፤1ነገ7፥45
52፥19 ዘፀ25፥29፤ ዘሌ10፥1፤ዘኍ3፥31 ፤4፥7፤1ነገ7፥50፤ዕዝ 1፥7፤ዳን5፥2
52፥20 1ነገ7፥25፡47

[የ]54 ወይም *ከለዳውያን*
[ደ]7 ወይም *ከለዳውያን*፤ ቍ 17 ይመ።
[ጀ]7 ወይም *የርዳኖስ ሸለቆ*
[ገ]8 ወይም *ከለዳውያን*፤ ቍ 14 ይመ።
[ጠ]15 ወይም *ተራው ሕዝብ*

በላይ ነበር። 21እያንዳንዱም ዐምድ ከፍ
ታው ዐሥራ ስምንት ክንድ ዙሪያ ክቡም[ጨ]
ዐሥራ ሁለት ክንድ ነበረ፤ ውስጡ ክፍት
ስለ ሆነ የእያንዳንዱ ከንፈር ውፍረት አራት
ጣት ነበረ። 22በአንዱ ዐምድ ዐናት ላይ
ያለው የናስ ጕልላት ቁመት አምስት ክንድ[ጸ]
ሲሆን፣ ዙሪያውንም ሁሉ የሮማን ቅርጽ
ባላቸው የናስ ጌጣ ጌጦች የተዋበ ነበር፤
ሌላውም ዐምድ የሮማኑን ጌጣጌጥ ጨምሮ
ከዚሁ ጋር አንድ ዐይነት ነበር። 23ዘጠና
ስድስቱ ሮማኖች ከጐን በቀላሉ የሚታዩ
ሲሆኑ፣ በአጠቃላይ በዙሪያው ካለው ጌጥ
በላይ ያለው የሮማኖች ቍጥር አንድ
መቶ ነበር።

24የክብር ዘበኞቹ አዛዥ የካህናት አለቃ
የነበረውን ሠራያን፣ ምክትሉንም ካህን
ሶፎንያስንና ሦስቱን በር ጠባቂዎች
አስሮ ወሰዳቸው፤ 25በከተማው ውስጥ ከቀሩ
ትም ሕዝብ፣ የተዋጊዎቹ ኀላፊ የነበረውን
መኰንን፣ ሰባቱን የንጉሡን አማካሪዎች ከአ
ገሬው ሕዝብ ወታደር የሚመለምለውን
መኰንን ጸሓፊና በከተማው ውስጥ የተገ
ኙትን ሌሎች ስድሳ ሰዎች ወሰደ። 26የክ
ብር ዘበኞቹ አዛዥ ናቡዘረዳን እነዚህን
ሁሉ ይዞ የባቢሎን ንጉሥ ወደ ነበረበት
ወደ ሪብላ አመጣቸው። 27ንጉሡም በሐ
ማት ምድር በነበረችው በሪብላ ፈጃቸው።

ይሁዳም በዚህ ሁኔታ ከምድሯ በምርኮ
ተወሰደች። 28ናቡከደነፆር ማርኮ የወሰ
ደው ሕዝብ ቍጥር እንደሚከተለው ነው፦

በነገሠ በሰባተኛው ዓመት፣ ሦስት ሺህ
ሃያ ሦስት አይሁድ፤ 29ናቡከደነፆር በነገሠ
በዐሥራ ስምንተኛው ዓመት፣ ስምንት መቶ
ሠላሳ ሁለት ሰዎች ከኢየሩሳሌም፤

30ናቡከደነፆር በነገሠ በሃያ ሦስተኛው
ዓመት፣ የክብር ዘበኞች አዛዥ ናቡዘረዳን
ሰባት መቶ አርባ አምስት አይሁድ ማርኮ
ወስዶአል፤ በአጠቃላይ አራት ሺህ ስድ
ስት መቶ ሰዎች ነበሩ።

## የዮአኪን መፈታት

31የይሁዳ ንጉሥ ዮአኪን በተማረከ በሠ
ላሳ ሰባተኛው ዓመት፣ ዮርማሮዴክ[ኸ] በባቢ
ሎን ነገሠ፤ በዚሁ ዓመት፣ በዐሥራ ሁለ
ተኛው ወር ከወሩም በሃያ አምስተኛው
ቀን የይሁዳን ንጉሥ ዮአኪንን አሰበው፤
ከእስር ቤትም አወጣው፤ 32በመልካምም
ቃል አናገረው፤ ከእርሱም ጋር በባቢሎን በም
ርኮ ከነበሩት ነገሥታት ይልቅ ከፍ ባለ
የክብር ቦታ አስቀመጠው። 33ዮአኪንም እስር
ቤት ለብሶት የነበረውን ልብሱን አውልቆ
ጣለ፤ በቀረውም የሕይወቱ ዘመን ሁሉ
ከንጉሡ ማእድ ይበላ ነበር። 34የባቢሎንም
ንጉሥ፣ ዮአኪን እስኪሞት ድረስ፣ በሕይ
ወት ዘመኑ ሁሉ ሳያቋርጥ በየዕለቱ ቀለ
ቡን ይሰጠው ነበር።

52፥21 1ነገ7፥15
52፥22 ዘፀ28፥33፤ 1ነገ7፥16
52፥23 ቍ17፤1ነገ 7፥20፤ ኤር 27፥19
52፥24 2ነገ 12፥9፤ 25፥18፤ ኤር 37፥3
52፥25 ኤር 36፥10
52፥26 ቍ12
52፥27 ዘኍ 34፥11፤ ኤር 20፥4
52፥28 ዘዳ 28፥36፤ 2ዜና 36፥20፤ ነህ 1፥2
52፥30 ኤር 13፥19፤ 43፥3
52፥31 2ዜና 36፥9
52፥33 2ዜና 9፥7
52፥34 2ሳሙ 9፥10

[ጨ]21 ከፍታው 27 ጫማ (8.1 ሜትር) እና ዙሪያ ክቡ 18 ጫ
ማ (5.4 ሜትር) ገደማ ነው።
[ጸ]22 7½ ጫማ (2.3 ሜትር) ገደማ ነው።
[ኸ]31 እንዲሁም *አሜልማርዱክ* ተብሎ ይጠራል።

# ሰቆቃወ ኤርምያስ

1 [ሀ]አሌፍ፤ በሕዝብ ተሞልታ የነበረችው
ከተማ፣
እንዴት የተተወች ሆና ቀረች!
በሕዝቦች መካከል ታላቅ የነበረችው፣
እርሷ እንዴት እንደ መበለት ሆነች!
በአውራጃዎች መካከል ልዕልት
የነበረችው፣
አሁን ባሪያ ሆናለች።

2ቤት፤ በሌሊት አምርራ ታለቅሳለች፤
እንባዋ በጉንጮቿ ላይ ይወርዳል፤
ከወዳጆቿ ሁሉ መካከል ፣
የሚያጽናናት ማንም የለም፤
ባልንጀሮቿ ሁሉ ከድተዋታል፤
ጠላቶቿም ሆነዋል።

3ጋሜል፤ በመከራና በመረገጥ ብዛት
ይሁዳ ተማርካ ሄደች፤
በሕዝቦችም መካከል ተቀመጠች፤
የምታርፍበትንም ስፍራ አጣች፤
በጭንቀቷ መካከል ሳለች፣
አሳዳጆቿ ሁሉ አገኟት።

4ዳሌጥ፤ የጽዮን መንገዶች ያለቅሳሉ፤
በዓላቷን ለማክበር
የሚመጣ የለምና፤
በበሮቿ ሁሉ የሚገባና የሚወጣ የለም፤
ካህናቷ ይቃትታሉ፤
ደናግሏ ክፉኛ አዝነዋል፤
እርሷም በምሬት ትሠቃያለች።

5ሄ፤ ባላጋሮቿ ገዦቿ ሆኑ፤
ጠላቶቿ ተመችቶአቸዋል፤
ከኀጢአቷ ብዛት የተነሣ፣
*እግዚአብሔር* ከባድ ሐዘን
አምጥቶባታል።
ልጆቿ በጠላት ፊት ተማርከው፣
ወደ ግዞት ሄደዋል።

6ዋው፤ የጽዮን ሴት ልጅ፣
ግርማ ሞገሷ ሁሉ ተለይቶአታል፤
መሳፍንቶቿ፣
መሰማሪያ እንዳጣ ዋልያ ናቸው፤
በአሳዳጆቻቸው ፊት፣
በድካም ሸሹ።

7ዛይ፤ በተጨነቀችባቸውና በተንከራ
ተተችባቸው ቀናት፣
ኢየሩሳሌም በጥንት ዘመን የነበራትን፣
ሀብት ሁሉ ታስባለች፤
ሕዝቦቿ በጠላት እጅ በወደቁ ጊዜ፣
የረዳት ማንም አልነበረም፤
ጠላቶቿ ተመለከቷት፤
በመፈራረሷም ሣቁ።

8ሔት፤ ኢየሩሳሌም ከባድ ኀጢአት
ሠርታለች፤
ስለዚህም የረከሰች ሆናለች፤
ያከበሯት ሁሉ ናቋት፤
ዕራቍቷን ሆና አይተዋታልና፤
እርሷ ራሷ ታጕረመርማለች፤
ወደ ኋላዋም ዞወር ብላለች።

9ጤት፤ ርኵሰቷ በቀሚሷ ላይ ታየ፤
ወደፊት የሚሆንባትን አላሰበችም፤
አወዳደቋ አስደንጋጭ ሆነ፤
የሚያጽናናትም አልነበረም፤
"*እግዚአብሔር* ሆይ፤ መከራዬን
ተመልከት፤
ጠላት ድል አድርጎአልና!"
10ዮድ፤ በሀብቷ ሁሉ ላይ፣
ጠላት እጁን ዘረጋ፤
ወደ ጉባኤህ እንዳይገቡ፣
የከለከልሀቸው፣
ጣዖት የሚያመልኩ አሕዛብ፣
ወደ መቅደሷ ሲገቡ አየች።

11ካፍ፤ እንጀራ በመፈለግ፣
ሕዝቧ ሁሉ በሥቃይ ይጮኻል፤
በሕይወት ለመኖር፣
የከበረ ሀብታቸውን በምግብ
ይለውጣሉ፤
"አቤቱ *እግዚአብሔር* ሆይ፤ አስበኝ፤
ተመልከተኝም፤
እኔ ተዋርጃለሁና"

12ላሜድ፤ "እናንት መንገድ ዐላፊዎች
ሁሉ፤ ይህ ለእናንተ ምንም
አይደለምን?
ተመልከቱ፤ እዩም፤
በጽኑ ቍጣው ቀን፣
*እግዚአብሔር* ያመጣብኝን፣
በእኔ ላይ የደረሰውን፣
የእኔን መከራ የመሰለ መከራ አለን?

13ሜም፤ "ከከፍታ ስፍራ እሳትን ላከ፤
ወደታች ወደ ዐጥንቶቼም ሰደደው፤
በእግሮቼ ላይ መረብ ዘረጋ፤
ወደ ኋላም ጣለኝ፤
ቀኑን ሙሉ በማድከም፣

1፥1 ዘሌ26፥43፤1ነገ 4፥21፤ኢሳ3፥26፤ 47፥8፤ ኤር40፥9፤ 42፥2፤ሕዝ5፥5
1፥2 ቍ16፤መዝ 6፥6፤ ኤር3፥1፤ 4፥30፤30፥14፤ ሚክ 7፥5
1፥3 ዘፀ15፥9፤ዘዳ 28፥65፤ኤር13፥19
1፥4 ቍ21፤መዝ 137፥1፤ኢሳ27፥10፤ ኤር9፥11፤ኢል 1፥8-13
1፥5 መዝ5፥10፤ 137፥3፤ኢሳ22፥5፤ ኤር10፥20፤30፥15፤39 ፥9፤52፥28-30፤ ሰቆ2፥17
1፥6 ዘሌ26፥36፤ መዝ9፥14፤ኤር13፥18
1፥7 2ነገ14፥16፤ ኤር2፥26፤37፥7፤ሰቆ 4፥17
1፥8 ቍ20፡21፡22፤ መዝ6፥6፤38፥8፤ኤር 2፥22፤13፥22፡26
1፥9 ዘዳ32፥28-29፤ መዝ25፥18፤ኤር13፥1 8፤16፥7፤መክ4፥1፤ ሕዝ24፥13
1፥10 ዘዳ23፥3፤ መዝ 74፥7-8፤ 79፥1፤ኢሳ 64፥11፤ ኤር51፥51
1፥11 መዝ6፥6፤ 38፥8፤ኤር37፥21፤52፥6
1፥12 ቍ18፤ኢሳ 10፥4፤13፥13፤ኤር 18፥16፤30፥24
1፥13 ኢዮ18፥8፤ 30፥30፤መዝ102፥3፤ኤ ር44፥6፤ዕን3፥16

[ሀ]1 ይህ ምዕራፍ ጥቅሶቹ ተከታታይ ፊደላት ባሉት የዕብራይስጥ ሆህያት የሚጀምር፣ የመጀመሪያው ወይም የመጨረሻው መሥመር ትርጕም የሚሰጥ ቃል ወይም ዐረፍተ ነገር ያለው ግጥም ነው።

ባዶ አድርጎ አስቀመጠኝ።

14ኖን፤ “ኀጢአቶቼ ቀንበር ሆኑ፤[ለ]
በእጆቹ አንድ ላይ ተገመዱ፤
በዐንገቴም ላይ ተጭነዋል፤
ኀይሌንም አዳከመ፤
ልቋቋማቸው ለማልችላቸው፣
እርሱ አሳልፎ ሰጠኝ።

15ሳምኬት፤ “በውስጤ ያሉትን ተዋጊዎች ሁሉ፣
እግዚአብሔር ተቃወመ፤
ጕልማሶቼን ለማድቀቅ፣
ሰራዊት በላዬ ላይ ጠራ[ሐ]፤
ድንግሊቱን የይሁዳ ሴት ልጅ፣
እግዚአብሔር በወይን መጭመቂያ ውስጥ
ረገጣት።

16“የማለቅሰው ስለ እነዚህ ነገሮች ነው፤
ዐይኖቼ በእንባ ተሞልተዋል፣
ሊያጽናናኝ የቀረበ፣
መንፈሴንም ሊያረጋጋ የሞከረ ማንም የለም፤
ጠላት በርትቶአልና
ልጆቼ ተጨንቀዋል።”

17ፌ፤ ጽዮን እጆቿን ዘረጋች፤
የሚያጽናናትም የለም፤
ጎረቤቶቹ ጠላቶቹ እንዲሆኑ፣
እግዚአብሔር በያዕቆብ ላይ ትእዛዝ አውጥቶአል፤
ኢየሩሳሌምም በመካከላቸው፣
እንደ ርኩስ ነገር ተሐጠረች።

18ጻዴ፤ “እግዚአብሔር ጻድቅ ነው፤
እኔ ግን በትእዛዙ ላይ ዐመፅ አድርጌ ነበር፤
እናንተ ሕዝቦች ሁሉ ስሙ፤
መከራዬንም ተመልከቱ፤
ወይዛዝርቶቼና ጐበዛዝቶቼ፣
ተማርከው ሄደዋል።

19ቆፍ፤ “ወዳጆቼን ጠራኋቸው፤
እነርሱ ግን ከዱኝ፤
ካህናቶቼና ሽማግሌዎቼ፣
ሕይወታቸውን ለማትረፍ፣
ምግብ ሲፈልጉ፣
በከተማዪቱ ውስጥ አለቁ።

20ሬስ፤ “አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፤ እንዴት ተጨንቄአለሁ!
በውስጤ ተሠቃይቼአለሁ፤
በልቤ ታውኬአለሁ፤
እጅግ ዐመፀኛ ሆኛለሁና፤
በውጭ ሰይፍ ይፈጃል፤
በቤትም ውስጥ ሞት አለ።

21ሳን፤ “ሰዎች የሥቃይ ልቅሶዬን ሰሙ፤
የሚያጽናናኝ ግን ማንም የለም፤
ጠላቶቼ ሁሉ ጭንቀቴን ሰሙ፤
አንተ ባደረግኸውም ደስ አላቸው፤
አቤቱ የተናገርኻት ቀን ትምጣ፤
እነርሱም እንደ እኔ ይሁኑ።

22ታው፤ “ክፋታቸው ሁሉ በፊትህ ይቅረብ፤
ከኀጢአቴ ሁሉ የተነሣ፣
በእኔ ላይ እንዳደረግኸብኝ፣
በእነርሱም ላይ አድርግባቸው፤
የሥቃይ ልቅሶዬ በዝቶአል፤
ልቤም ደክሞአል።”

# 2

አሌፍ፤[መ] እግዚአብሔር የጽዮንን ሴት ልጅ፣
በቍጣው ደመና እንዴት ጋረዳት![ሠ]
ከሰማይ ወደ ምድር፣
የእስራኤልን ክብር ወርውሮ ጣለው፤
በቍጣው ቀን፣
የእግሩን መቀመጫ አላስታወሰም።

2ቤት፤ የያዕቆብን መኖሪያ ሁሉ፣
እግዚአብሔር ያለ ርኅራኄ ዋጣቸው፤
የይሁዳን ሴት ልጅ ምሽጎች፣
በቍጣው አፈረሳቸው፤
መንግሥቷንና መሳፍንቷን፣
በማዋረድ ወደ ምድር ጣላቸው።

3ጋሜል፤ በጽኑ ቍጣው፣
የእስራኤልን ቀንድ ሁሉ[ረ] ሰበረ፤
ጠላት በተቃረበ ጊዜ፣
ቀኝ እጁን ወደ ኋላ መለሰ፤
በዙሪያው ያለውን ሁሉ እንደሚበላ እሳት፣
በያዕቆብ ላይ የእሳት ነበልባል ነደደ።

4ዳሌጥ፤ እንደ ጠላት ቀስቱን ገተረ፤
ቀኝ እጁ ተዘጋጅታለች፤
ለዐይን ደስ የሚያሰኙትን ሁሉ፤
እንደ ጠላት ዐረዳቸው፤
በጽዮን ሴት ልጅ ድንኳን ላይ፣
ቍጣውን እንደ እሳት አፈሰሰ።

5ሄ፤ እግዚአብሔር እንደ ጠላት ሆነ፤
እስራኤልንም ዋጠ፤
ቤተ መንግሥቶቿን ሁሉ ዋጠ፤
ምሽጎቿን አፈራረሰ፤
በይሁዳ ሴት ልጅ፣
ለቅሶንና ሰቈቃን አበዛ።

1፥14 ዘዳ28፥48፤ ኢሳ 47፥6፤ ኤር 15፥12፤32፥5
1፥15 መሳ6፥11፤ኢሳ 5፥5፤28፥18፤41፥2፤ኤር 14፥17፤18፥21፤37፥10
1፥16 ቍ2፤ኢዮ 7፥3፤መዝ69፥20፤119፥136፤መክ4፥1፤ኢሳ 22፥4፤ኤር13፥17፤14፥17፤16፥7፤ ሰቆ 2፥11፥18፤3፥48-49
1፥17 ዘፀ23፥21፤ ዘሌ18፥25-28፤ኤር 2፥22፤4፥31
1፥18 ቍ12፤ዘፀ9፥27፤ ዘዳ28፥32፥41፤1ሳሙ12፥14፤ዕዝ9፥15
1፥19 ኤር14፥15፤ 22፥20፤ሰቆ2፥20
1፥20 ቍ8፤ዘዳ 32፥25፤ ኤር4፥19፤ሰቆ2፥11፤ሕዝ7፥15
1፥21 ቍ4፥8፤ መዝ 6፥6፤38፥8፤ኢሳ47፥11፤ ኤር30፥16፤ሰቆ2፥15
1፥22 ቍ8፤ነህ4፥5፤መዝ6፥6
2፥1 መዝ99፥5፤ 132፥7፤ኤር12፥7፤ሰቆ3፥44
2፥2 ቍ17፤መዝ 21፥9፤89፥39-40፤ኢሳ 25፥12፤ሰቆ3፥43
2፥3 መዝ74፥11፤ 75፥5፥10፤ኢሳ42፥25፤ ኤር21፥4-5፥14
2፥4 2ዜና34፥21፤ኢዮ 3፥23፤16፥13፤መዝ48፥2፤ኢሳ 42፥25፤ኤር 4፥20፤7፥20፤ሰቆ3፥12-13፤ሕዝ20፥34፤ 24፥16፥25
2፥5 ቍ2፤ኢዮ13፥24 ፤ኢሳ29፥2፤ኤር7፥20፤ 9፥17-20

[ለ]14 አብዛኛዎቹ የዕብራይስጥ ቅጆች እንዲሁ ሲሆኑ ሰብዓ ሊቃናት ግን *ኀጢአቶቼን ያለማቋረጥ ይከታተላል* ይላል።

[ሐ]15 ወይም *…በሚያደቅበት ጊዜ፣ ለኔ ጊዜን ወሰነልኝ።*

[መ]1 ይህ ምዕራፍ ጥቅሶቹ ተከታታይ ፊደላት ባሉት የዕብራይስጥ ሆሄያት የሚጀምር፣ የመጀመሪያው ወይም የመጨረሻው መስመር ትርጒም የሚሰጥ ቃል ወይም ዐረፍተ ነገር ያለው ግጥም ነው።

[ሠ]1 ወይም *እግዚአብሔር በቍጣው የጽዮንን ሴት ልጅ እንዴት አዋረዳት!*

[ረ]3 ወይም *ብርታትን ሁሉ፤* ወይም *ንጉሥ ሁሉ፤ ቀንድ* በዚህ ቦታ ብርታትን ያመለክታል።

6ዋው፤ ማደሪያውን እንደ አትክልት ስፍራ
ባዶ አደረገ፤
መሰብሰቢያ ስፍራውን አፈረሰ፤
እግዚአብሔር ጽዮንን፣
ዓመት በዓላቶቿንና ሰንበታቷን
እንድትረሳ አደረጋት፤
በጽኑ ቍጣው፣
ንጉሡንና ካህኑን እጅግ ናቀ፡፡

7ዛይ፤ እግዚአብሔር መሠዊያውን ናቀ፤
መቅደሱንም ተወ፤
የቤተ መንግሥቶቿን ቅጥሮች፣
ለጠላት አሳልፎ ሰጠ፤
በዓመት በዓል ቀን እንደሚደረገው
በእግዚአብሔር ቤት በኀይል ጮኹ፡፡

8ሔት፤ በጽዮን ሴት ልጅ ዙሪያ ያለውን
ቅጥር፣
እግዚአብሔር ለማፍረስ ወሰነ፤
የመለኪያ ገመድ ዘረጋ፤
ከማጥፋትም እጆቹን አልሰበሰበም፤
ምሽጎችና ቅጥሮች እንዲያለቅሱ አደረገ፤
በአንድነትም ጠፉ፡፡

9ጤት፤ በሮቿ ወደ ምድር ሰመጡ፤
የብረት መወርወሪያዎቻቸውን ሰባበረ፤
አጠፋቸውም፤
ንጉሥዋና መሳፍንቶቿ በአሕዛብ መካከል
ተማርከው ተሰደዋል፤
ሕጉ ከእንግዲህ አይኖርም፤
ነቢያቶቿም ከእንግዲህ፣
ከእግዚአብሔር ራእይ አያገኙም፡፡

10ዮድ፤ የጽዮን ሴት ልጅ ሽማግሌዎች፣
በምድር ላይ በዝምታ ተቀምጠዋል፤
በራሳቸው ላይ ትቢያ ነሰነሱ፤
ማቅም ለበሱ፤
የኢየሩሳሌም ወጣት ሴቶች፣
ራሳቸውን ወደ ምድር ዝቅ አደረጉ፡፡

11ካፍ፤ ዐይኔ በለቅሶ ደከመ፤
ነፍሴ በውስጤ ተሠቃየች፤
ልቤም በሐዘን ፈሰሰች፣
በከተማዪቱ መንገዶች ላይ፣
ሕዝቤ ተደምስሰዋልና፤
ልጆችና ሕፃናት ደክመዋልና፡፡

12ላሜድ፤ በከተማዪቱ መንገዶች ላይ፣
እንደ ቈሰሉ ሰዎች ሲደክሙ፣
በእናታቸው ክንድ ላይ፣
ነፍሳቸው በመውጣት ላይ ሳለች፣
"እንጀራና የወይን ጠጅ የት አለ?"
እያሉ እናቶቻቸውን ይጠይቃሉ፡፡

13የኢየሩሳሌም ሴት ልጅ ሆይ፤ ስላንቺ
ምን ማለት እችላለሁ?
ከምንስ ጋር አወዳድርሻለሁ? ድንግሊቱ
የጽዮን ልጅ ሆይ፤
አጽናናሽ ዘንድ፣
በምን ልመስልሽ እችላለሁ?
ቍስልሽ እንደ ባሕር ጥልቅ ነው፤
ማንስ ሊፈውስሽ ይችላል?

14ኖን፤ የነቢያቶችሽ ራእይ፣
ሐሰትና ከንቱ ነው፤
ምርኮኛነትሽን ለማስቀረት፣
ኀጢአትሽን አይገልጡም፡፡
የሚሰጡሽም የትንቢት ቃል፣
የሚያሳስትና ከመንገድ የሚያወጣ
ነው፡፡

15ሳምኬት፤ በአጠገብሽ የሚያልፉ ሁሉ፣
እጃቸውን ያጨበጭቡብሻል፤
"የውበት መደምደሚያ፣ የምድር ሁሉ
ደስታ፣
የተባለች ከተማ ይህች ናትን?"
እያሉ ራሳቸውን በመነቅነቅ፣
በኢየሩሳሌም ሴት ልጅ ላይ ያሾፋሉ፡፡

16ዔ፤ ጠላቶችሽ ሁሉ በአንድ ላይ፣
አፋቸውን በኀይል ከፈቱ፤
ጥርሳቸውን እያፏጩ አሾፉ፤
እንዲህም አሉ፤ "ውጠናታል፤
የናፈቅነው ጊዜ ይህ ነበር፤
ኖረንም ልናየው በቃን፡፡"

17ፌ፤ እግዚአብሔር ያሰበውን አደረገ፤
ከረዥም ጊዜ በፊት የተናገረውን፣
ቃሉን ፈጸመ፤
ያለ ርኅራኄ አፈረሰሽ፤
ጠላት በሥቃይሽ ላይ እንዲደሰት፣
የጠላትሽንም ቀንድ[ሰ] ከፍ ከፍ አደረገ፡፡

18ጻዴ፤ የሕዝቡ ልብ፣ ወደ እግዚአብሔር
ጮኸ፡፡
የጽዮን ሴት ልጅ ቅጥር ሆይ፤
ቀንና ሌሊት፣
እንባሽ እንደ ወንዝ ይፍሰስ፤
ለራስሽ ዕረፍትን አትስጪ፣
ዐይኖችሽ ከማንባት አያቋርጡ፡፡

19ቆፍ፤ የሌሊቱ ሰዓት ሲጀምር፣
ተነሺ በሌሊት ጩኺ፤
በእግዚአብሔር ፊት፣
ልብሽን እንደ ውሃ አፍስሺ፤
በየመንገዱ ዳር ላይ፣ በራብ ስለወደቁት፣
ስለ ልጆችሽ ሕይወት፣ እጆችሽን ወደ
እርሱ አንሺ፡፡

20ሬስ፤ አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ እይ፤
ተመልከትም፤
በማን ላይ እንዲህ አድርገህ
ታውቃለህ?

**2፥6** 2ዜና36፥19፤ኢሳ 43፥28፤ኤር7፥14፤52፥13፤ሰቆ4፥16፤5፥12፤ሰፎ3፥18
**2፥7** ዘሌ26፥31፤ መዝ 74፥7-8፤ኢሳ 64፥11፤ኤር21፥4፤ 33፥4-5፤52፥13፤ሕዝ 7፥21-22፡24
**2፥9** ዘዳ28፥36፤ 1ሳሙ 3፥1፤2ነገ24፥15፤2ዜና 15፥3፤ነህ1፥3፤ኢሳ 45፥2፤ኤር14፥14፤ 16፥13፤ሆሴ3፥4፤11፥6
**2፥10** ኢሱ7፥6፤ኢዮ 2፥12፡13፤ኢሳ3፥24፡ 26፤ሰቆ3፥28፤ሕዝ27፥30-31
**2፥11** ቀኁ19፤ኢዮ 30፥27፤መዝ22፥14፤1 19፥82፤ኢሳ1፥5፤ 15፥3፤ኤር9፥1፤ሰቆ1፥16፤1፥20፤3፥48-51፤ 4፥4
**2፥12** ኢዮ3፥24፤ኢሳ 24፥11፤ሰቆ4፥4
**2፥13** 2ነገ19፥21፤ኢሳ 1፥6፤37፥22፤ኤር14፥17፤30፥12-15፤ሰቆ 1፥12
**2፥14** ኤር2፥8፤ 8፥11፤ 20፥6፤23፥25-32፡33-40፤28፥15፤29፥9፤ሕዝ 13፥3፤22፥28
**2፥15** ዘኁ24፥10፤ ዘዳ 28፥37፤ኢዮ16፥4፤መዝ45፥11፤48፥2፤ 50፥2፤ኢሳ28፥22፤ ኤር19፥8፤ሰቆ1፥21፤ሕዝ16፥14፤25፥6፤ ናሆ3፥19
**2፥16** ኢዮ16፥9፤ መዝ 22፥13፤35፥25፤ ሰቆ3፥46፤ሕዝ36፥3፤ ሚክ4፥11
**2፥17** ቀኁ2፤ዘዳ 28፥15-45፤ መዝ 22፥17፤ 89፥42፤ኢሳ 44፥26፤ኤር39፥16፤ሰቆ 1፥5፤ ሕዝ5፥11፤7፥9፤8፥ 18፤ዘካ1፥6
**2፥18** ቀኁ8፤መዝ 119፥145፤ኤር9፥1፤ ሰቆ1፥16፤3፥49
**2፥19** ቀኁ11፤1ሳሙ 1፥15፤መዝ28፥2፤ኢሳ 26፥9፤51፥20
**2፥20** ዘዳ28፥53፤ መዝ78፥64፤ኤር14፥15፤23፥11-12፤19፥9፤ ሰቆ1፥19፤4፥10፤ሕዝ 5፥10

[ሰ]17 ***ቀንድ*** በዚህ ቦታ ብርታትን ያመለክታል

በውኑ እናቶች ሕፃኖቻቸውን፣
ተንከባክበው ያሳደጓቸውን ልጆች
ይብሉን?
ካህኑና ነቢዩስ፣
በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ
ይገደሉን?

21ሳን፤ በየመንገዱ ዐቧራ ላይ፣
ወጣትና ሽማግሌ በአንድነት ወደቁ፤
ወይዛዝርቴና ጐበዛዝቴ፣
በሰይፍ ተገደሉ፤
በቍጣህ ቀን ገደልሃቸው፤
ያለ ርኅራኄም ዐረድሃቸው።

22ታው፤ "በበዓል ቀን ለግብዣ እንደምትጠራ፣
ሽብርን ከየአቅጣጫው በእኔ ላይ ጠራህ፤
*በእግዚአብሔር* የቍጣ ቀን፣
ማንም አላመለጠም ወይም
አልተረፈም፤
የተንከባከብኋቸውንና ያሳደግኋቸውን፣
ጠላቴ አጠፋብኝ።"

# 3

አሌፍ፤ሽ በቀጣው በትር፣
መከራ ያየ ሰው እኔ ነኝ።
2ከፊቱ አስወጣኝ፤
በብርሃን ሳይሆን በጨለማ እንድሄድ
አደረገኝ።
3በእርግጥ ቀኑን ሁሉ በመደጋገም፣
እጁን በላዬ ላይ መለሰ።

4ቤት፤ እርሱ ሥጋዬንና ቈዳዬን አስረጀ፤
ዐጥንቶቼንም ሰባበረ።
5በምሬትና በድካም፣
ቅጥር ሠራብኝ፤ ዙሪያዬንም ከበበኝ።
6ከሞቱ ብዙ ጊዜ እንደሆናቸው፣
በጨለማ እንድኖር አደረገኝ።

7ጋሜል፤ በቅጥር ውስጥ ዘጋብኝ፤ ስለዚህ
ማምለጥ አልቻልሁም፤
የእስር ሰንሰለቴንም አከበደብኝ።
8ርዳታ ፈልጌ ብጣራና ብጮኽ እንኳ፣
ጸሎቴን መስማት አልፈለገም።
9መንገዴን በተጠረቡ ድንጋዮች ዘጋ፤
ጐዳናዬንም አጣመመ።

10ዳሌጥ፤ አሸምቆ እንደ ተኛ ድብ፣
እንደ አደባም አንበሳ፣
11ከመንገድ ጐትቶ አስወጣኝ፤
ሖራረጠኝም፤
ያለ ረዳትም ተወኝ።
12ቀስቱን ገተረ፤
ለፍላጻዎቹም ዒላማ አደረገኝ።

13ሄ፤ ፍላጻዎችን ከሰገባው አውጥቶ፣
ልቤን ወጋው።
14ለሕዝቤ ሁሉ ማላገጫ ሆንሁኝ፤
ቀኑን ሙሉ በመሣለቅ ያዜሙብኛል።

15መራራ ሥር አበላኝ፤
ሐሞትም አጠገበኝ።

16ዋው፤ ጥርሴን በድንጋይ ሰበረ፤
በትቢያ ውስጥ ረጋገጠኝ።
17ነፍሴ ሰላምን አጣች፤
ደስታ ምን እንደ ሆነ ረሳሁ።
18ስለዚህ፣ "ክብሬ፣
ከእግዚአብሔርም ተስፋ ያደረግሁት
ሁሉ ሄዶአል" አልሁ።

19ዛይ፤ የጭንቀቴንና የመንከራተቴን፣
ምሬትንና ሐሞትን አስባለሁ።
20 ዘወትር አስበዋለሁ፤
ነፍሴም በውስጤ ተዋርዳለች።
21ሆኖም ይህን አስባለሁ
እንግዲያስ ተስፋ አለኝ፤

22ሔት፤ ያልጠፋነው *ከእግዚአብሔር* ታላቅ
ፍቅር የተነሣ ነው፤
ርኅራኄው አያልቅምና።
23ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው፤
ታማኝነትህም ብዙ ነው።

24ራሴን እንዲህ አልሁት፤ "*እግዚአብሔር*
ዕድል ፈንታዬ ነው፤
ስለዚህ ተስፋ አደርገዋለሁ።

25ጤት፤ እርሱን ተስፋ ለሚያደርጉት፣
ለሚፈልገውም ሰው *እግዚአብሔር*
መልካም ነው።
26ሰው *የእግዚአብሔርን* ማዳን፣
ዝም ብሎ ተስፋ ቢያደርግ መልካም
ነው።
27ሰው በወጣትነቱ፣
ቀንበር ቢሸከም መልካም ነው።

28ዮድ፤ ብቻውን ዝም ብሎ ይቀመጥ፤
እግዚአብሔር አሸክሞታልና።
29ፊቱን በዐቧራ ውስጥ ይቅበር፤
ተስፋ ሊኖር ይችላልና።
30ጒንጩን ለሚመታው ሰው ይስጥ፤
ውርደትንም ይጥገብ።

31ካፍ፤ እግዚአብሔር ሰውን፣
ለዘላለም አይጥልምና፤
32መከራን ቢያመጣ እንኳ ይራራል፤
ታላቅ ፍቅሩ አይለወጥምና
33ሆን ብሎ ችግርን፣
ወይም መከራን በሰው ልጆች ላይ
አያመጣምና።

34ላሜድ፤ የምድሪቱ እስረኞች ሁሉ፣
በእግር ሲረገጡ፣
35በልዑል ፊት፣

ሽ1 የዚህ ምዕራፍ እያንዳንዱ አንጓ ተከታታይ ፊደላት ባሉት የዕብራይስጥ ሆሄያት የሚጀምር ሲሆን በእያንዳንዱ አንጓ ውስጥ ያሉት ጥቅሶች በአንድ ዐይነት ፊደል ይጀምራሉ።

2፥21 ዘዳ32፥25፤ 2ዜና36፥17፤መዝ78፥62-63፤ኤር6፥11፥13፥14፤ሰቆ3፥43፤ዘካ11፥6
2፥22 ኢዮ27፥14፤መዝ31፥13፤ኤር11፥11፥20፥10፤ሆሴ9፥13
3፥1 ኢዮ19፥21፤ መዝ88፥7፤ኤር15፥17-18
3፥2 ኢዮ19፥8፤መዝ82፥5፤ኤር4፥23
3፥3 መዝ38፥2፤ኢሳ5፥25
3፥4 ኢዮ30፥30፤ መዝ51፥8፤ኢሳ38፥13፤ኤር50፥17፤ሰቆ4፥8
3፥5 ቊ19፤ኤር23፥15
3፥6 መዝ88፥5-6፤143፥3፤ኢሳ59፥10
3፥7 ኢዮ3፥23፤ኤር40፥4
3፥8 ቊ44፤ዘዳ1፥45፤ኢዮ30፥20፤መዝ 5፥2፤22፥2
3፥9 ኢዮ9፥24፤ 19፥8፤ኢሳ63፥17፤ሆሴ2፥6
3፥10 ኢዮ10፥16፤ ሆሴ13፥8፤አሞ5፥18-19
3፥11 ሆሴ6፥1
3፥12 ኢዮ7፥20፤16፥12፤መዝ7፥12-13፤38፥2፤ሰቆ2፥4
3፥13 ኢዮ6፥4፤ 16፥13
3፥14 ዘፍ38፥23፤ ኢዮ17፥2፤30፥9፤መዝ22፥6-7፤ኤር 20፥7
3፥15 ቊ19፤ኤር9፥15
3፥16 መዝ7፥5፤ምሳ20፥17
3፥18 ቊ54፤ኢዮ17፥15
3፥19 ቊ5፥15
3፥20 መዝ42፥5፤11፤43፥5
3፥22 ዘፀ78፥38፤130፥7፤103፥11፤ኢዮ34፥15፤ሆሴ11፥9
3፥23 ዘፀ34፥6፤ሶፎ3፥5
3፥24 መዝ119፥57
3፥25 መዝ33፥18፤ኢሳ 25፥9፤30፥18
3፥26 መዝ37፥7፤40፥1፤ኢሳ7፥4
3፥28 ኤር15፥17፤ሰቆ2፥10
3፥29 ኢዮ2፥8፤ኤር31፥17
3፥30 ኢዮ16፥10፤ኢሳ50፥6፤ሚክ5፥1
3፥31 መዝ94፥14፤ኢሳ54፥7
3፥32 መዝ78፥38፤106፥43-45፤ሆሴ11፥8፤ ናሆ1፥12
3፥33 ኢዮ37፥23፤ኤር31፥20፤ሕዝ18፥23፤ 33፥11
3፥35 ዘፍ14፥18፤19፥20፥22

ሰው መብቱ ሲነፈገው፣
36ሰው ፍትሕ ሲጓደልበት፣
ጌታ እንዲህ ዐይነቱን ነገር አያይምን?

37ሜም፤ እግዚአብሔር ካላዘዘ በቀር፤
ተናግሮ መፈጸም የሚችል ማን ነው?
38ክፉም ሆነ መልካም ነገር፣
ከልዑል አፍ የሚወጣ አይደለምን?
39ታዲያ ሕያው ሰው በኀጢአቱ ሲቀጣ፣
ስለምን ያጕረመርማል?

40ኖን፤ መንገዳችንን እንመርምር፤
እንፈትን፤
ወደ እግዚአብሔርም እንመለስ።
41ልባችንን ከእጃችን ጋር
በሰማይ ወዳለው ወደ አምላካችን
እናንሣ፤ እንዲህም እንበል፤
42“ዐምፀናል፤ ኀጢአትም ሠርተናል፤
አንተም ይቅር አላልኸንም።

43ሳምኬት፤ “ራስህን በቍጣ ከደንህ፤
አሳደድኸንም፤
ያለ ርኅራኄም ገደልኸን።
44ጸሎት እንዳያልፍ፣ ራስህን በደመና
ሸፈንህ።
45በአሕዛብ መካከል፣
አተላና ጥራጊ አደረግኸን።

46ዔ፤ “ጠላቶቻችን ሁሉ፣
አፋቸውን በእኛ ላይ ከፈቱ።
47በጥፋትና በመፈራረስ፣
በችግርና በሽብር ተሠቃየን።
48የእንባ ጐርፍ ከዐይኔ ፈሰሰ፤
ሕዝቤ አልቋልና።

49ፌ፤ ያለ ዕረፍት፣
ያለ ማቋረጥ ዐይኖቼ እንባ ያፈሳሉ፤
50እግዚአብሔር ከላይ፣
ከሰማይ እስኪያይ ድረስ።
51በከተማዬ ባሉት ሴቶች ሁሉ ላይ
የደረሰውን ማየቴ፣
ነፍሴን አስጨነቃት።

52ጻዴ፤ ያለ ምክንያት ጠላቶቼ የሆኑ፣
እንደ ወፍ አደኑኝ።
53ሕይወቴን በጕድጓድ ውስጥ ሊያጠፉ
ሞከሩ፣
ድንጋይም በላዬ አደረጉ።
54ውሃ ሞልቶ በዐናቴ ላይ ፈሰሰ፤
ጠፍቻለሁ ብዬ አሰብሁ።

55ቆፍ፤ በጥልቁ ጕድጓድ ውስጥ ሳለሁ፣
እግዚአብሔር ሆይ፤ የአንተን ስም
ጠራሁ።
56ልመናዬን ሰምተሃል፤ “ርዳታም ፈልጌ
ስጮኽ፣
ከመስማት ጆሮህን አትከልክል።”

57በጠራሁህ ጊዜ ቀረብኸኝ፣
እንዲሁም፣ “አትፍራ” አልኸኝ።

58ሬስ፤ ጌታ ሆይ፤ ለእኔ ተሟገትኽልኝ፤
ሕይወቴንም ተቤዠህ።
59እግዚአብሔር ሆይ፤ በእኔ ላይ
የተደረገውን ግፍ አየህ፤
ፍርዴን ፍረድልኝ!
60በቀላቸውን ሁሉ፣
በእኔም ላይ ያሰቡትን ዐድማ አየህ።

61ሳን፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ ስድባቸውን
ሁሉ፣
በእኔ ላይ ያሰቡትን ዐድማ ሁሉ ሰማህ፤
62ይህም ቀኑን ሙሉ በእኔ ላይ፣
ጠላቶቼ የሚያውጠነጥኑትና
የሚያንሾካሹኩት ነው።
63ተመልከታቸው! ቆመውም ሆነ
ተቀምጠው፣
በዘፈናቸው ይሣለቁብኛል።

64ታው፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ እጆቻቸው
ላደረጉት፣
የሚገባውን መልሰህ ክፈላቸው።
65በልባቸው ላይ መጋረጃን ዘርጋ፤
ርግማንህም በላያቸው ይሁን!
66ከእግዚአብሔር ሰማያት በታች፣
በቍጣህ አሳድዳቸው፤ አጥፋቸውም።

4 አሌፍ፤[ቀ] ወርቁ እንዴት ደበሰ!
ንጹሑስ ወርቅ እንዴት ተለወጠ!
የከበሩ ድንጋዮች፣
በየመንገዱ ዳር ተበታትነዋል።

2ቤት፤ እንደ ወርቅ ይሐጠሩ የነበሩ፣
የከበሩ የጽዮን ወንዶች ልጆች፣
የሸክላ ሠሪ እጅ እንደ ሠራው፣
እንዴት አሁን እንደ ሸክላ ዕቃ ሆኑ!

3ጋሜል፤ ቀበሮዎች እንኳን ግልገሎቻቸውን
ለማጥባት፣
ጡታቸውን ይሰጣሉ፤
ሕዝቤ ግን በምድረ በዳ እንዳሉ ሰጎኖች፣
ጨካኞች ሆኑ።

4ዳሌጥ፤ ከውሃ ጥም የተነሣ፣
የሕፃናት ምላስ ከላንቃቸው ጋር ተጣበቀ፤
ልጆቹ ምግብ ለመኑ፤
ነገር ግን ማንም አልሰጣቸውም።

5ሂ፤ ምርጥ ምግብ ይበሉ የነበሩ፣
ተቸግረው በየመንገዱ ላይ ተንከራተቱ፤
ሐምራዊ ግምጃ ለብሰው ያደጉ፣
አሁን በዐመድ ክምር ላይ ተኙ።

6ዋው፤ በሕዝቤ ላይ የደረሰው ቅጣት፣

[ቀ]1 ይህ ምዕራፍ፣ ጥቅሶቹ ተከታታይ ፊደላት ባሉት የዕብራይስጥ ሆህያት የሚጀምር ቃል ወይም ዐረፍተ ነገር ያለው ግጥም ነው።

3፥36 መዝ140፥12፤ ምሳ17፥15፤ኤር22፥3፤ ዕን1፥13
3፥37 መዝ33፥9-11፤ ምሳ19፥21፤21፥30
3፥38 ኢዮ2፥10፤ ኢሳ45፥7፤ኤር32፥42
3፥39 ኤር30፥15፤ ሚክ7፥9
3፥40 መዝ119፥59፤ 139፥23-24፤2ቆሮ 13፥5
3፥41 መዝ25፥1፤ 28፥2
3፥42 2ነገ24፥4፤ ኤር5፥7-9፤14፥20፤ ዳን9፥5
3፥43 ቍ66፤መዝ 35፥6፤ሰቆ2፥2፤17፥21
3፥44 ቍ8፤መዝ 97፥2፤ኢሳ58፥4፤ሰቆ 2፥1፤ዘካ7፥13
3፥45 1ቆሮ4፥13
3፥46 መዝ22፥13፤ ሰቆ2፥16
3፥47 ኢሳ24፥17-18፤ 51፥19፤ኤር48፥43
3፥48 መዝ119፥136፤ ኤር9፥1፥18፤ሰቆ1፥16፤ 2፥11
3፥49 ኤር14፥17፤ ሰቆ2፥18
3፥50 መዝ14፥2፤ 80፥14፤ኢሳ63፥15
3፥52 መዝ35፥7
3፥53 ኤር37፥16፤ 38፥6
3፥54 ቍ18፤መዝ 69፥2፤88፥5፤ሕዝ37፥ 11፤ዮና2፥3-5
3፥55 መዝ88፥6፤ 130፥1፤ዮና2፥2
3፥56 መዝ55፥1፤ 116፥1-2
3፥57 መዝ46፥1፤ ኢሳ41፥10
3፥58 መዝ34፥22፤ ኤር50፥34፤51፥36
3፥59 መዝ35፥23፤ 43፥1፤ኤር18፥19-20
3፥60 ኤር11፥20፤ 18፥18
3፥61 መዝ89፥50፤ ሰፎ2፥8
3፥62 መዝ36፥3
3፥63 ኢዮ30፥9
3፥64 መዝ28፥4፤ ኤር51፥6
3፥65 ዘፀ14፥8፤ ዘዳ2፥30፤ኢሳ6፥10
3፥66 ቍ43
4፥1 ሕዝ7፥19
4፥2 ኢሳ51፥18
4፥3 ኢዮ39፥16
4፥4 ዘዳ28፥48፤ 2ነገ18፥31፤መዝ22፥ 15፤ሰቆ2፥11፥12
4፥5 ኢሳ3፥26፤ኤር 6፥2፤አሞ6፥3-7
4፥6 ዘፍ19፥25

የማንም እጅ ሳይረዳት፣
በድንገት ከተገለበጠችው፣
ሰዶም ላይ ከደረሰው ቅጣት ይልቅ
ታላቅ ነው።
7ዛይ፤ መሳፍንቶቻቸው ከበረዶ ይልቅ
ብሩህ፣
ከወተትም ይልቅ ነጭ ነበሩ፤
ሰውነታቸው ከቀይ ዕንቊ የቀላ፣
መልካቸውም እንደ ሰንፔር[ሀ] ነበር።
8ሔት፤ አሁን ግን ከጥላሸት ይልቅ
ጠቊረዋል፤
በመንገድም የሚያውቃቸው የለም፤
ፏዳቸው ከዐጥንታቸው ጋር ተጣብቆአል፤
እንደ ዕንጨትም ደርቀዋል።
9ጤት፤ በራብ ከሚሞቱት ይልቅ፣
በሰይፍ የተገደሉት ይሻላሉ፤
ምግብ በሜዳ ላይ ካለማግኘታቸው
የተነሣ፣
በራብ ደርቀው ያልቃሉ።
10ዮድ፤ ሕዝቤ ባለቀበት ጊዜ፣
ምግብ እንዲሆኑአቸው፣
ርኅሩኆቹ ሴቶች በገዛ እጆቻቸው፣
ልጆቻቸውን ቀቀሉ።
11ካፍ፤ እግዚአብሔር ለመቅሠፍቱ መውጫ
በር ከፈተ፤
ጽኑ ቍጣውን አፈሰሰ፤
መሠረትዋን እንዲበላ፣
በጽዮን እሳት ለኰሰ።
12ላሜድ፤ ጠላቶችም ሆኑ ወራሪዎች፣
የኢየሩሳሌምን በሮች ጥሰው
ይገባሉ ብለው፣
የምድር ነገሥታት፣
ወይም ከዓለም ሕዝብ አንዳቸውም
አላመኑም።
13ሜም፤ ይህ ግን ከነቢያት ኀጢአት፣
ከካህናቷም መተላለፍ የተነሣ
ሆኖአል፤
በውስጧ፣
የጻድቃንን ደም አፍስሰዋልና።
14ኖን፤ እንደ ታወሩ ሰዎች፣
በየመንገዱ ላይ ይደናበራሉ፤
ማንም ሰው ደፍሮ ልብሳቸውን መንካት
እስከማይችል ድረስ፣
በደም እጅግ ረክሰዋል።
15ሳምኬት፤ ሰዎች "ሂዱ! እናንት ርኩሳን!"
ብለው ይጮኹባቸዋል፤
"ወግዱ! ወግዱ! አትንኩን!"
ይሏቸዋል፤
ሸሽተው በሚቅበዘበዙበትም ጊዜ፣
በአሕዛብ መካከል ያሉ ሰዎች፣

4፥8 ኢዮ30፥28፤ መዝ 102፥3-5፤ ሰቆ3፥4
4፥9 2ነገ25፥3፤ኤር 15፥2፤16፥4፤ሰቆ5፥10
4፥10 ዘሌ26፥29፤ ዘዳ 28፥53-57፤ኤር 19፥9፤ ሰቆ2፥20፤ሕዝ 5፥10
4፥11 ዘዳ32፥22፤ 2ዜና 34፥21፤ኢዮ 20፥23፤ኤር7፥20፤17፥ 27፤ሕዝ22፥31፤ናሆ 1፥6፤ሶፎ2፥2፤3፥8
4፥12 1ነገ9፥9፤ኤር 21፥13
4፥13 2ነገ21፥16፤ ኤር5፥31፤6፥13፤ሕ ዝ22፥28፤ሚክ3፥11
4፥14 ኢሳ59፥10፤ ኤር19፥4
4፥15 ዘሌ13፥46፤ ኤር44፥14፤ሚክ2፥10
4፥16 ኢሳ9፥14-16፤ ሰቆ2፥6፤5፥12
4፥17 ዘፍ15፥18፤ኢሳ 20፥5፤ኤር37፥7፤ሰቆ 1፥7፤ሕዝ29፥16
4፥18 ሕዝ7፥2-12፤ አሞ8፥2
4፥19 ዘዳ28፥49፤ ዘሌ 26፥36፤ኢሳ5፥ 26-28፤ኤር52፥7
4፥20 1ሳሙ26፥9፤ 2ሳሙ19፥21፤መዝ91፥ 1፤ኤር39፥5፤ሕዝ 12፥12-13፤19፥4፡8
4፥21 ዘፍ10፥23፤ መዝ16፥5፤ኢሳ34፥6- 10፤63፥6፤ኤር25፥15፤ ሕዝ35፥15፤ አሞ1፥ 11-12፤አብ1፥16፤ዕን 2፥16
4፥22 መዝ137፥7፤ ኢሳ40፥2፤ኤር33፥ 8፤ሕዝ25፥12-14፤ ሚል1፥4
5፥1 መዝ44፥13- 16፤89፥50
5፥2 መዝ79፥1፤ 109፥11፤ኤር17፥4፤ ሶፎ1፥13
5፥3 ዘፀ22፥24፤ ኤር15፥8፤18፥21

"ከእንግዲህ በዚህ መቀመጥ አይ
ገባቸውም!" ይላሉ።
16ፌ፤ እግዚአብሔር ራሱ በትኖአቸዋል፤
ከእንግዲህ ወዲያ አይጠብቃቸውም፤
ካህናቱ አልተከበሩም፤
ሽማግሌዎቹም ከበሬታ አላገኙም።
17ፌ፤ ከሁሉም በላይ በከንቱ ርዳታን
ስንጠባበቅ፣
ዐይኖቻችን ደከሙ፤
ከግንብ ማማችን ላይ ሆነን፣
ሊያድን ከማይችል ሕዝብ ርዳታ
ጠበቅን።
18ጻዴ፤ ሰዎች እግር እግራችንን
ተከታተሉን፤
ስለዚህ በመንገዳችን መሄድ
አልቻልንም፤
መጨረሻችን ቀርቦአል፤ ቀኖቻችንም
ተሐጥረዋል፤
ፍጻሜያችን መጥቶአልና።
19ቆፍ፤ ከሰማይ ንስሮች ይልቅ፣
ጠላቶቻችን ፈጣኖች ናቸው፤
በተራሮች ላይ አሳደዱን፤
በምድረ በዳም ሸመቁብን።
20ሬስ፤ በእግዚአብሔር የተቀባው፣
የሕይወታችን እስትንፋስ፣
በወጥመዳቸው ተያዘ፤
በጥላው ሥር፣
በአሕዛብ መካከል እንኖራለን ብለን
አስበን ነበር።
21ሳን፤ አንቺ በዖፅ ምድር የምትኖሪ፣
የኤዶምያስ ሴት ልጅ ሆይ፤ ደስ
ይበልሽ፤ ሐሴትም አድርጊ!
ነገር ግን ለአንቺም ደግሞ ጽዋው
ይደርስሻል፤
ትሰክሪያለሽ፤ ዕርቃንሽንም
ትጋለጫለሽ።
22ታው፤ የጽዮን ልጅ ሆይ፤ ቅጣትሽ
ያበቃል፤
እርሱም የስደትሽን ዘመን አያራ
ዝምም፤
ነገር ግን አንቺ የኤዶምያስ ልጅ ሆይ፤
ኀጢአትሽን ይቀጣል፤
ክፋትሽንም ይፋ ያወጣል።

5 እግዚአብሔር ሆይ፤ በእኛ ላይ
የደረሰውን አስብ፤
ውርደታችንን እይ፤ ተመልከትም።
2ርስታችን ለመጻተኞች፣
ቤቶቻችን ለባዕዳን ዐልፈው ተሰጡ።
3ወላጅ አልባና አባት የሌላቸው ሆንን፤

[ሀ]7 ወይም ላፒስ ላዙሊ

እናቶቻችን እንደ መበለቶች ሆኑ።
4 ለምንጠጣው ውሃ መክፈል ነበረብን፤
ዕንጨታችንንም የምናገኘው በግዢ
ነበር።
5 የሚያሳድዱን ከተረከዞቻችን ሥር
ናቸው፤
ተጨንቀናል ዕረፍትም አጥተናል።
6 እንጀራ እንጠግብ ዘንድ፣
ለአሦርና ለግብፅ እጃችንን ሰጠን።
7 አባቶቻችን ኀጢአት ሠርተው አለፉ፤
እኛም የእነርሱን ቅጣት ተሸከምን።
8 ባሮች ሠልጥነውብናል፤
ከእጃቸው ነጻ የሚያወጣን ማንም
የለም።
9 በምድረ በዳ ካለው ሰይፍ የተነሣ፣
በሕይወታችን ተወራርደን እንጀራ
አገኘን።
10 ቈዳችን እንደ ምድጃ ጠቍሮአል፤
በራብም ተቃጥሎአል።
11 ሴቶች በጽዮን፣
ደናግል በይሁዳ ከተሞች ተደፈሩ።
12 መሳፍንት በእነርሱ እጅ ተሰቀሉ፤
ሽማግሌዎችም አልተከበሩም።

13 ጕልማሶች ወፍጮ እንዲፈጩ ተገደዱ፤
ወንዶች ልጆች በዕንጨት ሸክም
ተንገዳገዱ።
14 ሽማግሌዎች ከከተማዪቱ በር ሄደዋል፤
ጕልማሶች ዝማሬያቸውን አቁመዋል።
15 ደስታ ከልባችን ጠፍቶአል፤
ጭፈራችን ወደ ልቅሶ ተለውጦአል።
16 አክሊላችን ከራሳችን ላይ ወድቆአል፤
ወዮልን፤ ኀጢአት ሠርተናልና!
17 ከዚህ የተነሣ ልባችን ደከመ፤
ከእነዚህ የተነሣም ዐይናችን ፈዘዘ፤
18 ባዶዋን የቀረችው የጽዮን ተራራ፣
የቀበሮዎች መፈንጫ ሆናለችና።

19 አቤቱ *እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ
ለዘላለም ትገዛለህ፤
ዙፋንህ ከትውልድ እስከ ትውልድ
ይኖራል።
20 ስለምን ፈጽመህ ትረሳናለህ?
ስለምንስ ለረዥም ጊዜ ትተወናለህ?
21 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ወደ አንተ
መልሰን፤ እኛም እንመለሳለን፤
ዘመናችንን እንደ ቀድሞው አድስ፤
22 ፈጽመህ ካልጣልኸን፣
ከመጠን በላይ ካልተቈጣኸን።

5፥4 ኢሳ3፥1፤ኢሳ 55፥1፤ሕዝ4፥16-17
5፥5 ኢሱ1፥13፤ነህ 9፥37፤ኢሳ47፥6
5፥6 ኤር2፥36፤ሆሴ 5፥13፤7፥11፤9፥3
5፥7 ኤር14፥20፤ 16፥12፤31፥29
5፥8 ነህ5፥15፤ዘካ 11፥6
5፥10 ኢዮ30፥ 30፤ሰቆ4፥8-9
5፥11 ዘፍ34፥29፤ ዘካ14፥2
5፥12 ዘሌ19፥32፤ ሰቆ2፥6፤4፥16
5፥14 ኢሳ24፥8፤ ኤር7፥34
5፥15 ኤር25፥10፤ አሞ8፥10
5፥16 ኢዮ19፥9፤ መዝ89፥39፤ኢሳ3፥ 11፤ኤር13፥18፤14፥20
5፥17 ኢዮ16፥8፤ መዝ 6፥7፤ኢሳ1፥5፤ ኤር8፥18
5፥18 መዝ74፥2-3፤ ኢሳ27፥10፤ሚክ3፥12
5፥19 1ዜና16፥31፤ መዝ45፥6፤102፥12፡ 24-27
5፥20 መዝ13፥1፤ 44፥24፤71፥11
5፥21 መዝ80፥3፤ኢሳ60፥20-22
5፥22 መዝ53፥5፤ 60፥1-2፤ ኢሳ64፥9፤ ኤር6፥30

# ትንቢተ ሕዝቅኤል

## ሕያዋኑ ፍጡራንና የእግዚአብሔር ክብር

1 በሠላሳኛው ዓመት፣[ሀ] በአራተኛው ወር፣
በአምስተኛው ቀን፣ በኮቦር ወንዝ
አጠገብ በምርኮኞች መካከል ሳለሁ፣ ሰማ
ያት ተከፈቱ፤ እኔም የእግዚአብሔርን ራእይ
አየሁ::
2ንጉሡ ዮአኪን በተማረከ በአምስተ
ኛው ዓመት፣ በአምስተኛው ቀን፣ 3በባቢ
ሎናውያን[ለ] ምድር በኮቦር ወንዝ አጠገብ፣
*የእግዚአብሔር* ቃል ወደ ቡዝ ልጅ፣[ሐ]
ወደ ካህኑ ወደ ሕዝቅኤል መጣ፤ በዚያ
*የእግዚአብሔር* እጅ በእርሱ ላይ ነበረች::
4እኔም አየሁ፤ ስመለከትም፣ እነሆ ዐውሎ
ነፋስ ከሰሜን በኩል መጣ፤ ይኸውም
በታላቅ ብርሃን የተከበበ፣ መብረቅን የሚ
ረጭ ታላቅ ደመና ነበረ፤ የእሳቱም መኻል
የጋለ ብረት ይመስል ነበር:: 5በእሳቱም
ውስጥ የአራት ሕያዋን ፍጡራን አምሳያ
ነበረ፤ መልካቸውም የሰው ቅርጽ ይመስል
ነበር:: 6እያንዳንዳቸውም አራት አራት
ፊትና አራት አራት ክንፍ ነበራቸው:: 7እግ
ራቸው ቀጥ ያለ ነበር፤ ኮቴያቸውም እንደ
ጥጃ ኮቴ ያለ ሲሆን፣ እንደ ተወለወለ
ናስም ያብለጨልጭ ነበር:: 8በአራቱ ጐኖ
ቻቸው ባሉት ክንፎቻቸው ሥር የሰው
እጅ ነበራቸው:: አራቱም ፊቶችና ክንፎች
ነበሯቸው፤ 9ክንፎቻቸውም እርስ በርስ ይነካኩ
ነበር:: እያንዳንዱም ቀጥ ብሎ ይሄድ
ነበር፤ ወደ ኋላቸውም ዞር ብለው አይመ
ለከቱም ነበር::
10ፊታቸውም እንዲህ ነበር፤ አራቱም
እያንዳንዳቸው የሰው ፊት ነበራቸው፤
በቀኝ በኩል የአንበሳ ፊት፣ በግራ
በኩልም የበሬ ፊት ነበራቸው፤
እያንዳንዳቸውም ደግሞ የንስር ፊት ነበራ
ቸው:: 11እንግዲህ ፊታቸው ይህን
ይመስል ነበር፤ ክንፋቸ ውም ወደ ላይ
ተዘርግቶ ነበር፤ እያንዳ ንዳቸው ሁለት
ሁለት ክንፍ ነበራቸው፤ የእያንዳንዱም
ክንፍ የሌላውን ክንፍ ይነካ ነበር፤ ሁለቱ
ክንፎቻቸው ሰውነታ ቸውን ይሸፍኑ
ነበር:: 12እያንዳንዱ ቀጥ ብሎ ወደ ፊት
ይሄድ ነበር፤ ወደ ኋላም ሳይዞር መንፈስ
ወደሚሄድበት ሁሉ ይሄድ ነበር:: 13የሕ
ያዋን ፍጡራኑ መልክም እንደሚነድ
የከሰል ፍምና የተቀጣጠለ ችቦ ይመስል
ነበር፤ በፍጡራኑ መካከል እሳት ወዲያ
ወዲህ ይንቀሳቀስ ነበር፤ ብርሃኑም ደማቅ
ነበር፤ ከእሳቱም ውስጥ መብረቅ ይወጣ
ነበር:: 14ፍጡራኑም እንደ መብረቅ ብል
ጭታ ፍጥነት ወዲያ ወዲህ ይወረወሩ ነበር::
15ሕያዋን ፍጡራኑን ስመለከታቸው፣ አራት
ፊቶች ባሉት በእያንዳንዱ ፍጡር አጠገብ
አንዳንድ መንኰራኵር በምድር ላይ አየሁ::
16የመንኰራኵሮቹ መልክና አሠራር እንዲህ
ነበር፤ እንደ ቢረሌ ያንጸባርቁ ነበር፤ የአ
ራቱም ቅርጽ ተመሳሳይ ሆኖ፤ እያንዳንዱ
መንኰራኵር በመንኰራኵር ውስጥ ተሰ
ክቶ የተሠራ ይመስል ነበር:: 17በሚሄዱበት
ጊዜም፣ ፍጡራኑ ወደሚዞሩበት ወደ አራቱ
አቅጣጫ ሁሉ መንቀሳቀስ ይችሉ ነበር፤
ፍጡራኑ በሚሄዱበትም ጊዜ መንኰራኵ
ሮቹ ወዲያና ወዲህ[መ] አይሉም ነበር::
18የመንኰራኵሮቹ ክብ ጠርዝ ረጅምና አስ
ፈሪ ነበር፤ የአራቱም መንኰራኵሮች ክብ
ጠርዝ ዙሪያውን በዐይኖች የተሞላ ነበር::
19ሕያዋኑ ፍጡራን ሲንቀሳቀሱ፣ በአጠገ
ባቸው ያሉ መንኰራኵሮችም ይንቀሳቀሱ
ነበር፤ ሕያዋኑ ፍጡራን ከምድር ከፍ ከፍ
ሲሉ፣ መንኰራኵሮቹም አብረዋቸው ከፍ
ከፍ ይሉ ነበር:: 20መንፈስ ወደሚሄድበት
ሁሉ ይሄዳሉ፤ የሕያዋኑ ፍጡራን መንፈስ
በውስጣቸው ስላለ መንኰራኵሮቹ አብረዋ
ቸው ይነሣሉ፤ 21ፍጡራኑ ሲንቀሳቀሱ ይን
ቀሳቀሳሉ፤ ፍጡራኑ ቀጥ ብለው ሲቆሙ እነ
ርሱም ይቆማሉ፤ ፍጡራኑ ከምድር ከፍ
ከፍ ሲሉ፣ የሕያዋኑ ፍጡራን መንፈስ
በውስጣቸው ስላለ መንኰራኵሮቹ አብረ
ዋቸው ይነሣሉ::
22ከሕያዋኑ ፍጡራን ራስ በላይ የሚያስ
ፈራና፤ እንደ በረዶ የሚያንጸባርቅ ጠፈር
የሚመስል ነገር ነበር:: 23ከጠፈሩም በታች
የአንዱ ክንፍ ወደ ሌላው ተዘርግቶ ነበር፤
እያንዳንዱም ሰውነቱን የሚሸፍንበት ሁለት
ክንፍ ነበረው:: 24ፍጡራኑ በሚንቀሳቀሱበት
ጊዜ የክንፎቻቸውን ድምፅ ሰማሁ፤ ድምፁም
እንደሚጐርፍ ውሃ ጨኸት፣ ሁሉን እንደ
ሚችል[ሠ] አምላክ ድምፅና እንደ ሰራዊት
ውካታ ነበር:: መንቀሳቀሳቸውን ሲያቆሙም
ክንፎቻቸውን ዝቅ ያደርጉ ነበር::
25መንቀሳቀሳቸውን አቁመው ክንፎቻቸ
ውን ዝቅ እንዳደረጉ፣ ከራሳቸው በላይ
ካለው

1፥1 ዘፀ24፥10፤ዘዳ 21፥10፤መዝ137፥1፤ ሕዝ11፥24-25፤ ማቴ3፥16
1፥2 2ነገ24፥15
1፥3 2ነገ3፥15፤ኢሳ 8፥11፤ሕዝ3፥14፡22፤ 8፥1፤24፥24፤33፥22 ፤37፥1፤40፥1
1፥4 ኢዮ38፥1፤ኤር 1፥14፤ሕዝ8፥2
1፥5 ቍ26፤ኢሳ6፥ 2፤ዳን7፥13፤ራእ4፥6
1፥6 ሕዝ10፥14
1፥7 ሕዝ40፥3፤ ዳን10፥6፤ራእ1፥15
1፥8 ሕዝ10፥8
1፥9 ሕዝ10፥22
1፥10 ሕዝ10፥14፤ ራዕ 4፥7
1፥11 ኢሳ6፥2
1፥12ሕዝ10፥16-19
1፥13 2ሳሙ22፥9፤ ራእ4፥5
1፥14 መዝ29፥7
1፥15 ሕዝ3፥13፤ 10፥2፤ዳን7፥9
1፥16 ዘፀ28፥20
1፥17 ቍ9
1፥18 ራእ4፥6
1፥20 ቍ12
1፥21 ሕዝ10፥9-12
1፥22 ሕዝ10፥1
1፥24 2ነገ7፥6፤ መዝ46፥3፤ሕዝ3፥13፤ 10፥5፤43፥2፤ ዳን 10፥6፤ራዕ1፥15፤ 14፥2፤19፥6

[ሀ]1 ወይም *ዓመቴ*
[ለ]3 ወይም *በከለዳውያን*
[ሐ]3 ወይም *ወደ ካህኑ ቡዝ ልጅ ወደ ሕዝቅኤል*
[መ]17 ወይም *ወደ ሌላ*
[ሠ]24 በዕብራይስጡ *ሻዳይ* ይላል

ጠፈር ድምፅ ተሰማ። 26ከራሳቸው በላይ
ካለው ጠፈር ከፍ ብሎ የሰንፔር‹ ዙፋን
የሚመስል ነገር ነበር፤ በዙፋኑም ላይ
የሰው መልክ የሚመስል ነበር። 27ወገቡ
ከሚመስለው ጀምሮ ወደ ላይ በእሳት
መካከል እንዳለ የጋለ ብረት፣ ከወገቡም
በታች እሳት ይመስል እንደነበር አየሁ፤
ደማቅ ብርሃንም በዙሪያው ነበር። 28በዝ
ናብ ቀን በደመና ውስጥ እንደሚታየው
ቀስተ ደመና በዙሪያው ያለው ጸዳል እን
ዲሁ ነበር።

ይህም *የእግዚአብሔር* ክብር መልክ አም
ሳያ ነበረ። ባየሁትም ጊዜ በግንባሬ
ተደፋሁ፤ የአንድ ተናጋሪን ድምፅ ሰማሁ።

## የሕዝቅኤል መጠራት

2 እርሱም፣ "የሰው ልጅ ሆይ፤ ተነሥተህ
በእግርህ ቁም፤ እኔም እናገርሃለሁ"
አለኝ። 2እርሱም ሲናገር፣ መንፈስ ወደ
ውስጤ ገብቶ በእግሬ አቆመኝ፤ ሲናገ
ረኝም ሰማሁት።

3እርሱም እንዲህ አለኝ፤ "የሰው ልጅ
ሆይ፤ በእኔ ላይ ወደ ዐመፀው ወደ ዐ
መፀኛው የእስራኤል ሕዝብ እልክሃለሁ፤
እነርሱና አባቶቻቸው እስከ ዛሬ ድረስ ዐ
ምፀውብኛል። 4ሕዝቡም እልኸኛና ዐንገተ
ደንዳና ነው፤ እኔ ወደ እነርሱ እልክሃለሁ፤
አንተም 'ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል'
በላቸው። 5እነርሱ ዐመፀኛ ቤት ስለ ሆኑ፤
ቢሰሙም ባይሰሙም በመካከላቸው ነቢይ
እንደነበር ያውቃሉ። 6አንተ የሰው ልጅ
ሆይ፤ እነርሱን ወይም ቃላቸውን አትፍራ፤
ኵርንችትና እሾኽ በዙሪያህ ቢኖሩም፣ በጊ
ንጦች መካከል ብትቀመጥም አትፍራ።
እነርሱ ዐመፀኛ ቤት ቢሆኑም፣ አንተ
በሚሉህ ነገር አትፍራ፤ እነርሱም
አያስደንግጡህ። 7እነርሱ ዐመፀኛ ቤት
ስለሆኑ፣ ቢሰሙም ባይሰሙም አንተ
ቃሌን ንገራቸው። 8አንተ ግን የሰው ልጅ
ሆይ፤ እኔ የምልህን ስማ፤ እንደዚያ ዐመፀኛ
ቤት ዐታምፅ፤ አፍህን ክፈት፤ የምሰጥህንም
ብላ።"

9ከዚህም በኋላ፣ እነሆ አንድ እጅ ወደ
እኔ ተዘርግቶ አየሁ፤ ጥቅልል መጽሐፍም
ነበረበት፤ 10እርሱም በፊቴ ዘረጋው፤ መጽሐ
ፉም ከፊትና ከኋላው የሰቈቃ፣ የልቅሶና
የዋይታ ቃላት ተጽፎበት ነበር።

3 እርሱም፣ "የሰው ልጅ ሆይ፤ በፊትህ
ያለውን ብላ፤ ይህን ጥቅልል መጽሐፍ
ብላና ሄደህ ለእስራኤል ቤት ተናገር"
አለኝ። 2ስለዚህ አፌን ከፈትሁ፤ እርሱም
መጽሐፉን አጐረሰኝ።

3እርሱም፣ "የሰው ልጅ ሆይ፤ እኔ
የምሰ ጥህን ይህን ጥቅል መጽሐፍ ብላ፤
ሆድህ ንም ሙላ" አለኝ። እኔም በላሁት፤
በአ ፌም ውስጥ እንደ ማር ጣፈጠኝ።

4እርሱም እንዲህ አለኝ፤ "የሰው ልጅ
ሆይ፤ ተነሥተህ ወደ እስራኤል ቤት
ሂድ፤ ቃሌንም ንገራቸው። 5ወደ እስራ
ኤል ቤት እንጂ፣ ንግግሩ ወደማይገባና
ቋንቋው ወደማይታወቅ ሕዝብ አልተላ
ክህም፤ 6ንግግራቸው ወደማይገባና ቋንቋቸው
ወደማይታወቅ፣ ቃላቸውንም መረዳት
ወደማይቻልህ ብዙ ሕዝብ አልላክሁህም።
ወደ እነርሱ ልኬህ ቢሆን ኖሮ፣ በእርግጥ
ይሰሙህ ነበር። 7ነገር ግን የእስራኤል ቤት
ሁሉ ልበ ደንዳኖችና እልኸኞች ስለሆኑ
ሊሰሙኝ አልፈለጉም፤ ስለዚህ የእስራኤል
ቤት አንተንም አይሰሙህም። 8እነሆ እኔ
በእነርሱ ፊት የማትበገር ጠንካራ አደር
ግሃለሁ። 9ግንባርህን ከባልጩት ይልቅ
እንደሚጠነክር ድንጋይ አደርገዋለሁ። ዐመ
ፀኛ ቤት ቢሆኑም እንኳ አትፍራቸው፤ በፊታ
ቸውም አትሸበር።"

10እርሱም እንዲህ አለኝ፤ "የሰው ልጅ
ሆይ፤ የምነግርህን ቃል ሁሉ በጥንቃቄ አድ
ምጥ፤ በልብህም ያዝ። 11ተነሥተህም
በምርኮ ወዳሉት ወገኖችህ ሄደህ ተናገ
ራቸው፤ ቢሰሙህም ባይሰሙህም፣
'ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል'
በላቸው።"

12መንፈስም ወደ ላይ ከፍ አድርጎ አነ
ሣኝ፤ ከኋላዬም '*የእግዚአብሔር* ክብር
በማደሪያ ስፍራው ይባረክ!' የሚል ታላቅ
ህምህምታ ሰማሁ፤ 13ይህም የሕያዋኑ ፍጡ
ራን ክንፎች እርስ በርስ ሲጋጩና በአጠ
ገባቸው ያሉት መንኰራኵሮች የሚያሰሙት
ታላቅ ህምህምታ ነበር። 14መንፈስ ወደ ላይ
ከፍ አድርጎ ወሰደኝ፤ እኔም በምሬትና
በመንፈሴ ቍጣ ሄድሁ፤ *የእግዚአብሔርም*
ጽኑ እጅ በላዬ ነበረች። 15ከዚያም በኮቦር
ወንዝ አጠገብ በቴልአቢብ ወደሚኖሩት ምር
ኮኞች መጣሁ፣ በድንጋጤ ፈዝዤም ከእነ
ርሱ ጋር ሰባት ቀን በመካከላቸው
ተቀመጥሁ።

## ለእስራኤል የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

16ከሰባቱም ቀን በኋላ *የእግዚአብሔር* ቃል
ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፤ 17"የሰው ልጅ
ሆይ፤ ለእስራኤል ቤት ጠባቂ አድርጌሃለሁ፤
ስለዚህ ቃሌን ስማ፤ የምነግርህንም ማስጠ
ንቀቂያ አስተላልፍላቸው። 18እኔ ኀጢአተ
ኛውን ሰው፣ 'በእርግጥ ትሞታለህ'
ባልሁት ጊዜ አንተ ባታስጠነቅቀው፣
ነፍሱንም ያድን ዘንድ ከክፉ ሥራው እንዲ
መለስ ባትነግረው፣

1፥26 ቀኍ5፤ ዘፀ24፥10፤1ነገ22፥19፤ ኢሳ6፥1፤ኤር3፥17፤ ሕዝ2፥1፤ራእ1፥3
1፥27 ሕዝ8፥2
1፥28 ዘፍ9፥13፤ 17፥3፤ዘፀ16፥7፤24፥16፤ዘኍ14፥5፤ሉቃ 2፥9፤ራእ4፥2፤10፥1
2፥1 ኢዮ25፥6፤ መዝ8፥4፤ሕዝ1፥26፤ ዳን7፥13፤8፥15፤ 10፥11፤ሐሥ9፥6፤ 14፥10፤26፥16
2፥2 ሕዝ3፥24፤ ዳን8፥18
2፥3 ኤር3፥25፤ ሕዝ 5፥6፤ 20፥8-24፤24፥3
2፥4 ዘፀ32፥9፤ ኢሳ9፥9፤ሕዝ3፥7፤ አሞ7፥15
2፥5 ኤር5፥3፤ ሕዝ3፥11፡27፤ 33፥33፤ ዮሐ15፥22
2፥6 ዘኍ33፥55፤ ዘዳ31፥6፤2ነገ1፥15፤ ኢሳ1፥2፤9፥18፤ 30፥9፤ሕዝ24፥3፤ 44፥6፤ሚክ7፥4
2፥7 ኤር1፥7፤ 7፥27፤42፥21፤ ሕዝ 3፥10-11
2፥8 ዘኍ20፥10-13፤ መዝ81፥10፤ኢሳ 8፥11፤50፥5፤ኤር 15፥16፤ራእ10፥9
2፥9 መዝ40፥7፤ ሕዝ 8፥3
3፥3 መዝ19፥10፤ ኤር15፥16፤ ራእ10፥9-10
3፥4 ሕዝ11፥4፡25
3፥5 ኢሳ28፥11፤ ዮና1፥2
3፥6 ዮና3፥5-10፤ ማቴ11፥21-23፤ ሐሥ 13፥46-48
3፥7 ኢሳ48፥4፤ ኤር3፥3፤7፥27፤ሕዝ 2፥4፤ዮሐ15፥20-23
3፥8 ኤር1፥18፤ 15፥20
3፥9 ኢሳ48፥4፤ 50፥7፤ኤር5፥3፤ሕዝ 2፥6፤44፥6፤ሚክ3፥8
3፥10 ኢዮ22፥22
3፥11 ቀኍ27፤ ኢሳ6፥9፤ሕዝ2፥4-5፡ 7፤11፥24-25
3፥12 ቀኍ14፤ሕዝ 8፥3፤43፥5
3፥13 ሕዝ1፥15፡24፤ 10፥5፡16-17
3፥14 ቀኍ12፡22፤ 1ነገ18፥12፤ኢሳ8፥11፤ ሕዝ 37፥1
3፥15 ዘፍ50፥10፤ መዝ137፥1
3፥16 ኤር42፥7
3፥17 ኢሳ52፥8፤ 58፥1፤ኤር1፥17፤ ሕዝ11፥4፤ዕን2፥1
3፥18 ቀኍ20፤ዘፍ 2፥17፤ ዮሐ8፥21፡24

‹26 ወይም *ላፒስ ላዙሊ*

ያ ኀጢአተኛ በኀጢአቱ[ሰ] ይሞታል፤ አንተንም
ስለ ደሙ በኀላፊነት እጠይቅሃለሁ።
19ነገር ግን ኀጢአተኛውን ሰው አስጠ
ንቅቀኸው፣ ከኀጢአቱና ከክፉ መንገዱ
ባይመለስ፣ እርሱ በኀጢአቱ ይሞታል፤
አንተ ግን ነፍስህን ታድናለህ።
20"ጻድቁ ሰው ደግሞ ከጽድቁ ተመልሶ
ኀጢአት ቢሠራ፣ እኔም መሰናክል በፊቱ
ባስቀምጥ እርሱ ይሞታል፤ አንተ ሳላስጠነ
ቀቅኸውምና በኀጢአቱ ይሞታል፤ ያደረገ
ውም ጽድቅ አይታሰብለትም፤ አንተንም ስለ
ደሙ በኀላፊነት እጠይቅሃለሁ። 21ነገር ግን
ጻድቁን ሰው ኀጢአት እንዳይሠራ ብታስጠ
ነቅቀውና እርሱም ኀጢአትን ባይሠራ፣
ተጠንቅቆአልና በእርግጥ በሕይወት ይኖ
ራል፤ አንተም ነፍስህን ታድናለህ።"
22*የእግዚአብሔር* እጅ በላዬ ነበረ፤ እር
ሱም፣ "ተነሥተህ ወደ ረባዳው ስፍራ ሂድ፤
በዚያ እናገርሃለሁ" አለኝ። 23እኔም ተነሥቼ
ወደ ረባዳው ስፍራ ሄድሁ። በኮቦር ወንዝ
አጠገብ ያየሁት ዐይነት ክብር፣ *የእግዚ
አብሔር* ክብር በዚያ ቆሞ ነበር፤ እኔም በግ
ንባሬ ተደፋሁ።
24መንፈስ በውስጤ ገብቶ በእግሬ አቆመኝ፤
እንዲህም ሲል ተናገረኝ፤ "ሂድ፤ ቤትህ ገብ
ተህ በርህን ዝጋ። 25አንተ፣ የሰው ልጅ
ሆይ፤ በገመድ ይጠፍሩሃል፤ ወጥተህም
በሕዝብ መካከል እንዳትመላለስ ያስሩሃል።
26ዐመፀኛ ቤት ቢሆኑም ልትገሥጻቸው
እንዳ ትችል ምላስህን ከላንቃህ ጋር
አጣብቃለሁ፤ ድዳም ትሆናለህ። 27ነገር
ግን በምናገርህ ጊዜ አፍህን እከፍታለሁ፤
አንተም፣ 'ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል' ትላቸዋለህ። የሚሰማ ይስማ፤ የ
ማይሰማም አይስማ፤ ዐመ
ፀኛ ቤት ናቸውና።

## የኢየሩሳሌም መከበብ ምሳሌ

4 "አንተ፣ የሰው ልጅ ሆይ፤ አንድ የሸ
ክላ ጡብ ወስደህ ከፊት ለፊትህ አስቀ
ምጥ፤ የኢየሩሳሌምን ከተማ ካርታ ሥራ
በት። 2ከዚያም በወታደር እንደሚከበብ
ክበባት፤ ምሽግ ሥራባት፤ ዐፈር ደልድልባት፤
ጦር ሰፈሮችን ቀብቅብባት፤ ቅጥር መደር
መሻ ግንዶችንም በዙሪያዋ አስቀምጥባት።
3የብረት ምጣድ ወስደህ በአንተና በከተማ
ዪቱ መካከል እንደ ብረት ቅጥር አቁመው፤
ፊትህንም ወደ እርሷ አዙር፤ የተከበበች
ትሆናለች፤ አንተም ትከባታለህ። ይህም
ለእስራኤል ቤት ምልክት ይሆናል።
4"አንተ በግራ ጐንህ ተኛ፤ የእስራኤልም
ቤት ኀጢአት በአንተ ላይ[ሸ] ይሁን፤ በዚህ
ጐንህ በተኛህበት ቀን ቍጥር ኀጢአታቸ
ውን ትሸከማለህ። 5እነርሱ ኀጢአት ባደረ
ጉባቸው ዓመታት መጠን የቀን ቍጥር
መድቤብሃለሁ። ስለዚህ ሦስት መቶ ዘጠና
ቀን የእስራኤልን ቤት ኀጢአት ትሸከ
ማለህ።
6"ይህን ከፈጸምህ በኋላ ደግሞ በቀኝ
ጐንህ ተኝተህ የይሁዳን ቤት ኀጢአት ትሸ
ከማለህ፤ ለእያንዳንዱ ዓመት አንድ አንድ
ቀን በማድረግ አርባ ቀን መድቤብሃለሁ።
7ፊትህን ወደ ኢየሩሳሌም ከበባ ታዞራለህ፣
በራቍት ክንድህ ትንቢት ተናገርባት።
8የከ በባህን ወራት እስክትፈጽም ድረስ
ከአንዱ ጐን ወደ ሌላው መገላበጥ እንዳ
ትችል በገመድ አስርሃለሁ።
9"ስንዴና ገብስ፣ ባቄላና ምስር እንዲሁም
ዘንጋዳና ጠመዥ ወስደህ በአንድ ሸክላ ውስጥ
አስቀምጥ፤ ከዚያም ለራስህ እንጀራ ጋግር፤
ሦስት መቶ ዘጠና ቀን በጐንህ በምትተኛበት
ጊዜ ትመገበዋለህ። 10በየቀኑ የምትበላውን
እህል ሃያ ሃያ ሰቅል መዝነህ አስቀምጥ፤
በተወሰነ ጊዜ ትበላዋለህ፤ 11የምትጠጣውንም
ውሃ *አንድ ስድስተኛ ኢን ለክተህ አስቀ
ምጥ፤ በተወሰነ ጊዜ ትጠጣዋለህ። 12የገብስ
ዕንጎቻ እንደምትበላ አድርገህ ትበላለህ፤
የሰውንም ዐይነ ምድር አንድደህ በሕዝብ
ፊት ጋግረው። 13*እግዚአብሔርም*፣ "በዚህ
ሁኔታ የእስራኤል ሕዝብ እነርሱን በምበት
ንበት በአሕዛብ መካከል ርኩስ ምግብ
ይበላሉ" አለ።
14እኔም፣ "ጌታ *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ወይኔ!
ከቶ ረክሼ አላውቅም፤ ከልጅነቴ ጀምሮ
እስከ ዛሬ ጥምብ ወይም አውሬ የጣለውን
በልቼ አላውቅም፤ ርኩስ ሥጋም በአፌ
አልገባም" አልሁ።
15እርሱም፣ "መልካም ነው፤ በሰው ዐይነ
ምድር ሳይሆን፤ እንጀራህን በኩበት እንድት
ጋግር ፈቅጄልሃለሁ" አለኝ።
16ደግሞም እንዲህ አለኝ፤ "የሰው ልጅ
ሆይ፤ የኢየሩሳሌምን የምግብ ምንጭ አደር
ቃለሁ፤ ሕዝቡም የተወሰነ ምግብ በጭንቀት
ይበላል፤ የተመጠነ ውሃም በሥጋት ይጠ
ጣል።
17የምግብና የውሃ ዕጥረት ስለሚኖር፣
እርስ በርስ ሲተያዩ ይደነግጣሉ፤ ከኀጢ
አታቸውም የተነሣ[ቀ] መንምነው ይጠፋሉ።

5 "አንተም፤ የሰው ልጅ ሆይ፤ የተሳለ
ሰይፍ ወስደህ እንደ ጢም መላጫ ጠጕ
ርህንና ጢምህን ተላጭበት፤ ጠጕሩ
ንም

[ሰ]18 ወይም *ስለ ኀጢአቱ፤* እንዲሁም ቍ19 እና 20 ይመ
[ሸ]4 ወይም *በአንተ በኩል ይሁን*
*አንድ ስድስተኛ (1/6ኛ) ኢን ግማሽ ሊትር ያህል ነው።
[ቀ]17 ወይም *በኀጢአታቸው መንምነው ይጠፋሉ*

3፥19 ዘፍ6፥5፤ 2ነገ17፥13፤ መዝ7፥12፤ ኤር42፥16፤ ሕዝ14፥14፡20፤ ሐሥ18፥6፤20፥26፤ 1ጢሞ4፥14-16
3፥20 ቍ18፤ ዘሌ26፥37፤ መዝ125፥5፤ኢሳ8፥14፤ ኤር34፥16፤ሕዝ7፥19፤ 18፥24፤ 33፥12፡18
3፥21 ሐሥ20፥31
3፥22 ቍ4፤ ሕዝ1፥3፤8፥4፤ ሐሥ9፥6
3፥23 ዘፍ17፥3፤ ሕዝ1፥1
3፥24 ኤር15፥17፤ ሕዝ2፥2
3፥25 ሕዝ4፥8
3፥26 መዝ22፥15፤ ሕዝ2፥5፤24፥27፤ 33፥22፤ሆሴ4፥4
3፥27 ቍ11፤ ሕዝ 2፥5፤12፥3፤ 24፥27፤29፥21፤ 33፥22፤ራእ22፥11
4፥2 ኤር6፥6፤ 33፥4፤ሕዝ17፥17፤ 21፥22፤ዳን11፥15
4፥3 ቍ7፤ዘሌ2፥5፤ ኢሳ8፥18፤20፥3፤ ኤር13፥1-7፤18፥1-4፤ 19፥1-2፤39፥1፤ ሕዝ5፥1-4፤12፥3-6፤ 20፥46፤21፥2
4፥6 ዘፀ28፥38፤ ዘኍ14፥34፤ዳን9፥24 -26፤12፥11-12
4፥7 ቍ3፤ ሕዝ6፥2፤13፥17
4፥8 ሕዝ3፥25
4፥9 ኢሳ28፥25
4፥10 ዘፀ30፥13
4፥11 ቍ16
4፥12 ኢሳ36፥12
4፥13 ሆሴ9፥3፤ አሞ7፥17
4፥14 ዘፀ22፥31፤ ዘሌ11፥39፤ዘዳ14፥3፤ 32፥37-38፤ኤር1፥6፤ ሕዝ9፥8፤20፥49፤ ዳን1፥8፤ሆሴ9፥3-4
4፥16 ቍ10-11፤ ዘሌ26፥26፤ መዝ105፥16፤ኢሳ3፥1፤ ሕዝ12፥19
4፥17 ዘሌ26፥39፤ ሰቆ5፥4፤ሕዝ5፥16፤ 12፥18-19፤24፥23፤ 33፥10፤አሞ4፥8
5፥1 ዘሌ21፥5፤ ዘኍ6፥5፤2ሳሙ10፥4፤ ሕዝ44፥20

በሚዛን ከፋፍል። 2የከበባው ጊዜ ሲፈጸም
የጠጕሩን ሢሶ በከተማው ውስጥ አቃጥ
ለው፤ ሌላውን ሢሶ ጠጕር በከተማዪቱ
ዙሪያ ሁሉ በሰይፍ ቈራርጠው፤ የቀረው
ንም ሢሶ ደግሞ ለነፋስ በትነው፤ እኔም
በተመዘዘ ሰይፍ አሳድዳቸዋለሁና። 3ደግ
ሞም ከጠጕሮቹ ጥቂት ወስደህ በመጐና
ጸፊያህ ጫፍ ቋጥር፤ 4እንደ ገናም ከእነዚህ
ጥቂት ወስደህ እሳት ውስጥ ጨምራቸው፤
አቃጥላቸውም። እሳትም ከዚያ ወጥቶ ወደ
እስራኤል ቤት ሁሉ ይሰራጫል።

5“ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ ‘አገ
ሮችን በዙሪያዋ ሁሉ አድርጌ፣ በአሕ
ዛብም መካከል ያስቀመጥኋት ኢየሩሳሌም
ይህች ናት። 6እርስዋም በዙሪያዋ ካሉት
አገሮችና አሕዛብ ይልቅ በሕጌና በሥርዐቴ
ላይ በክፋቷ ዐመፀች፤ ሕጌን ጥላለች፤ ሥርዐ
ቴንም አልተከተለችም።’

7“ስለዚህ ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
‘በዙሪያችሁ ካሉት አሕዛብ ይልቅ ሞገደ
ኞች ሆናችኋል፤ ሥርዐቴን አልተከተላ
ችሁም፤ ለሕጌም አልታዘዛችሁም። በዙሪያ
ችሁ የሚገኙ አሕዛብ የሚጠብቁትን ሕግ
እንኳ አልጠበቃችሁም።[በ]

8“ስለዚህ ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤ ‘እነሆ፤ እኔ ራሴ በአንቺ ላይ ተነ
ሥቻለሁ፤ በአሕዛብም ፊት ፍርድ አመጣ
ብሻለሁ። 9በጸያፍ ተግባርሽ ሁሉ ምክን
ያት ካሁን ቀደም ያላደረግሁትን፣ ወደ
ፊትም የማላደርገውን በአንቺ ላይ አደርጋ
ለሁ። 10ስለዚህ በመካከልሽ አባቶች ልጆቻ
ቸውን፣ ልጆችም አባቶቻቸውን ይበላሉ፤
ፍርድንም አመጣብሻለሁ፤ ከአንቺ የተረፉ
ትንም ለነፋስ እበትናለሁ። 11ስለዚህ በሕ
ያ ውነቴ እምላለሁ ይላል ጌታ *እግዚአብሔ
ር*፤ መቅደሴን በረከሱ ምስሎችሽና በ
ጸያፍ ተግባርሽ ሁሉ ስላጐደፍሽ፣ ፊቴን
ከአንቺ እመልሳለሁ፤ በርኅራኄ
አልመለከትሽም፤ አልምርሽም። 12ከሕ
ዝብሽ ሢሶው በቸነፈር ይሞታል፤
በመካከልሽም በራብ ያልቃል፤ ሌላው ሢሶ
ከቅጥርሽ ውጪ በሰይፍ ይወ ድቃል፤
የቀረውን ሢሶ ደግሞ ለነፋስ እበ ትናለሁ፤
በተመዘዘም ሰይፍ አሳድደዋለሁ።

13“ከዚያም ቍጣዬ ይበርዳል፤ በእነርሱ
ላይ የመጣው መቅሠፍቴ ይመለሳል፤
ስበቀላቸው እረካለሁ፤ በእነርሱም ላይ መዓ
ቴን ካወረድሁ በኋላ፣ እኔ *እግዚአብሔር*
በቅናት እንደ ተናገርሁ ያውቃሉ።

14“በዙሪያሽ ባሉ አሕዛብ መካከል፤ በአጠ
ገብሽም በሚያልፉ ሁሉ ፊት ባድማና
መሳለቂያ አደርግሻለሁ። 15በቍጣና
በመ ዓት፣ እንዲሁም በጭካኔ ፍርድ በ
ማመጣብሽ ጊዜ፣ በዙሪያሽ ባሉ አሕዛብ
ዘንድ የመሣ ቂያና የመሣለቂያ፣ የተግሣጽና
የማስደንገጫ ምልክት ትሆኛለሽ። እኔ *እግዚ
አብሔር* ተናግ ሬአለሁ። 16የሚገድለውንና
አጥፊ የሆነውን የራብ ፍላጻ በእናንተ
ላይ በምወረውርበት ጊዜ በእርግጥ ላጠ
ፋችሁ እሰድዳለሁ። በራብ ላይ ራብ
አመጣባችኋለሁ፤ የምግብ ምንጫ ችሁንም
አደርቃለሁ። 17ራብንና የዱር አራ ዊትን
እሰድባችኋለሁ፤ እነርሱም ልጅ አልባ
ያደርጓችኋል። ቸነፈርና ደም መፋሰስ ያጥ
ለቀልቃችኋል፤ ሰይፍንም አመጣባችኋለሁ፤
እኔ *እግዚአብሔር* ተናግሬአለሁ።”

## ስለ እስራኤል ተራሮች የተነገረ ትንቢት

6 *የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል ወደ
እኔ መጣ፤ 2“የሰው ልጅ ሆይ፤ ፊትህን
ወደ እስራኤል ተራሮች አዙር፤ ትንቢትም
ተናገርባቸው፤ 3እንዲህም በል፤ ‘የእስራኤል
ተራሮች ሆይ፤ የጌታ *የእግዚአብሔርን* ቃል
ስሙ፤ ጌታ *እግዚአብሔር* ለተራሮችና
ለኰረብ ቶች፤ ለገደላገደሎችና ለሸለቆች
እንዲህ ይላል፤ “ሰይፍን አመጣባችኋለሁ፤
የማምለ ኪያ ኰረብቶቻችሁን አጠፋለሁ።
4መሠዋ ̣ያዎቻችሁ ይፈርሳሉ፤ የዕጣን መ
ሠዊያዎቻ ችሁም ይሰባበራሉ፤ የታረዱ
ሰዎቻችሁን በጣዖቶቻችሁ ፊት እጥላለሁ።
5የእስራኤላ ውያንን ሬሳ በጣዖቶቻችሁ ፊት
አጋድማለሁ፤
ዐጥንቶቻችሁንም በመሠዊያዎቻችሁ ዙሪያ
እበትናለሁ። 6መሠዊያዎቻችሁ እንዲፈራ
ርሱና እንዲወድሙ፣ ጣዖቶቻችሁ እንዲ
ሰባበሩና እንዲደቁ፣ የዕጣን መ
ሠዊያዎቻችሁ እንዲንኰታኰቱ፣
የእጆቻችሁም ሥራ እንዲ ደመሰስ፣
የምትኖሩባቸው ከተሞች ሁሉ ባድማ
ይሆናሉ፤ ማምለኪያ ኰረብቶችም
እንዳልነበሩ ይሆናሉ። 7የታረዱ ሰዎቻችሁ
በመካከላችሁ ይወድቃሉ፤ እኔም *እግዚአ
ብሔር* እንደሆንሁ ታውቃላችሁ።”

8“በአሕዛብ መካከል ስትበተኑ፣ አንዳንዶ
ቻችሁ ከሰይፍ ታመልጣላችሁና፣ ጥቂት
ሰዎችን አስቀራለሁ። 9እነዚህ ከሰይፍ የተ
ረፉት፣ ከእኔ ዘወር ባለ አመንዝራ ልባቸ
ውና ጣዖትን በተከተለ አመንዝራ ዐይና
ቸው የቱን ያህል እንዳሳዘኑኝ፤ በአሕዛብ

**5፥2** ቍ10፡12፤ ዘሌ26፥33፤ኤር9፥16፤ 13፥24፤21፥10፤ 39፥1-2፤ሕዝ15፥7፤ ዘካ13፥8
**5፥3** 2ነገ25፥12፤ መዝ74፥11፤ ኤር39፥10
**5፥4** ሕዝ10፥7፤ 15፥7
**5፥5** ዘዳ4፥6፤ ሰቆ1፥1፤ሕዝ16፥14
**5፥6** 2ነገ17፥15፤ ነህ9፥17፤ኤር11፥10፤ ሕዝ2፥3፤16፥47-51፤ ዘካ7፥11
**5፥7** 2ነገ21፥9፤ 2ዜና33፥9፤ ኤር2፥10-11፤ ሕዝ16፥47
**5፥8** ኤር21፥5፡13፤ 24፥9፤ሕዝ11፥9፤ 15፥7፤ዘካ14፥2
**5፥9** ዳን9፥12፤ ማቴ24፥21
**5፥10** ዘሌ26፥29፡ 33፤መዝ44፥11፤ ኤር13፥14፤ሰቆ2፥20፤ ሕዝ12፥14
**5፥11** ዘፍ15፥2፤ ዘሌ15፥31፤ዘኍ14፥ 21፤2ዜና36፥14፤ ኢዮ27፥22፤ኤር16፥18፤ ሰቆ2፥17፤ሕዝ7፥4፡ 9፡20፤8፥18፤9፥5፤ 11፥18
**5፥12** ቍ2፡10፡17፤ መዝ107፥39፤ኤር13፥ 24፤15፥2፤21፥9፤ ሕዝ6፥11-12፤7፥15፤ 12፥14፤አሞ9፥4፤ ዘካ3፥8፤ራእ6፥8
**5፥13** 2ዜና12፥7፤ ኢዮ20፥23፤ኢሳ1፥24፤ 59፥17፤ሕዝ16፥42፤ 21፥17፤24፥13፤ 38፥19፤ሆሴ10፥10፤ ዘካ6፥8
**5፥14** ዘሌ26፥32፤ ነህ2፥17፤መዝ74፥3 -10፤ 79፥1-4፤ ኢሳ64፥11፤ሕዝ6፥6፤ 22፥4፤ዳን9፥16፤ ሚክ3፥12
**5፥15** ዘዳ28፥20፡ 46፤1ነገ9፥7፤ ኢሳ43፥28፤ ኤር22፥8-9፤24፥9፤ 23፥40፤ሕዝ14፥8
**5፥16** ዘሌ26፥26፤ ዘዳ32፥24
**5፥17** ቍ12፤ዘሌ 26፥25፤ሕዝ14፥15፡ 21፤28፥23፤38፥22
**6፥2** ቍ13፤ሕዝ 4፥7፤18፥6፤ ሚክ6፥1
**6፥3** ዘሌ26፥30፤ ሕዝ36፥4
**6፥4** 2ዜና14፥5፤ ሕዝ9፥6፤14፥13፤ 20፥16

**6፥5** ቍ13፤ዘሌ26፥ 30፤ዘኍ19፥16፤መዝ53፥5፤ኤር8፥1-2
**6፥6** ዘፀ12፥20፤ዘሌ 26፥30፤1ሳሙ5፥4፤ ኢሳ6፥11፤ሕዝ5፥14፤ ሕዝ30፥13፤ሆሴ10፥8፤ሚክ1፥7፤ ዘካ13፥2 **6፥7** ቍ10፡13፡14፤ ሕዝ9፥7፤11፥10-12 **6፥8** ዘፍ11፥4፤መዝ44፥11፤68፥20፤ ኢሳ6፥13፤ኤር44፥14፡28፤ሕዝ7፥16፤12፥16፤ 14፥22 **6፥9** ዘፀ 22፥20፤ 32፥22፤ኢዮ42፥6፤ መዝ137፥6፤ኢሳ7፥13፤ኤር8፥21፤ ሕዝ20፥7፡24፡43፤ 23፥14-16፤36፥31፤ ሚክ5፥13፤ዘካ10፥9

[በ]7 አብዛኛዎቹ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆችና አንዳንድ የዕብራይስጥና የሱርስት የጥንት ቅጆች ***የሚጠብቁትን ሕግ ጠብቃችኋል*** ይላሉ።

ምድር ሆነው ያስታውሱኛል፤ ካደረጉት ክፉ
ትና ከፈጸሙት ርኩስ ተግባር ሁሉ የተነ
ሣም ራሳቸውን ይጸየፋሉ። 10እነርሱም እኔ
እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ፤
ይህንም ክፉ ነገር አመጣባቸዋለሁ ብዬ
የተናገርሁት በከንቱ አይደለም።
11“ ‘ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“የእስራኤል ቤት ካደረጉት ክፉትና ከፈ
ጸሙት ጸያፍ ተግባራቸው ሁሉ የተነሣ በሰ
ይፍ በራብና በቸነፈር ይወድቃሉና፤ በእጅህ
እያ ጨበጨብህ በእግርህም መሬት እየረ
ገጥህ፣ ‘ወየው!’ ብለህ ጩኽ። 12በሩቅ ያለው
በቸነፈር ይሞታል፤ በቅርብ ያለው በሰይፍ
ይወድቃል፤ በሕይወት የተረፈውና የዳነው
በራብ ያልቃል። መዓቴንም በዚህ ዐይነት
ሁኔታ በእነርሱ ላይ እፈጽማለሁ። 13የታረዱት
ሰዎቻቸው በመሠዊያው ዙሪያ በጣዖቶቻ
ቸው መካከል፣ ከፍ ባሉ ኰረብቶች ሁሉና
በተራሮች ዐናት ሁሉ ላይ፣ በለመለመ
ዛፍ ሁሉና ቅጠሉ በበዛ ወርካ ሁሉ ሥር፣
በአጠቃላይ ለጣዖቶቻቸው ጣፋጭ ሽታ
ያለውን ዕጣን ባቀረቡበት ስፍራ ሁሉ ተጥ
ለው ሲታዩ፣ ያን ጊዜ እኔ እንደ ሆንሁ
ታውቃላችሁ። 14እጄን በእነርሱ ላይ አነሣ
ለሁ፤ የሚኖሩበትንም ስፍራ ከምድረ በዳው
እስከ ዴብላታ[†] ድረስ ምድሪቱን ባድማ
አደርጋታለሁ፤ ያን ጊዜም እኔ እግዚአብሔር
እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።”

### ፍጻሜው ደረሰ

7 የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ
እኔ መጣ፤ 2“አንተ የሰው ልጅ ሆይ፤ ጌታ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ምድር እንዲህ
ይላል፤ ‘ፍጻሜ! በአራቱም የምድሪቱ ማእ
ዘን ፍጻሜ መጥቶአል። 3አሁንም መጨ
ረሻሽ ደርሶአል፤ ቍጣዬን በአንቺ ላይ
አፈሳለሁ፤ እንደ አካሄድሽ እፈርድብሻለሁ፤
ስለ ጸያፍ ተግባርሽ ሁሉ ተገቢውን ቅጣት
እከፍልሻለሁ። 4በርኅራኄ ዐይን አልመለከት
ሽም፤ ምሕረትም አላደርግልሽም፤ ስለ አካ
ሄድሽና በመካከልሽ ስላለው ጸያፍ ተግባር
ተገቢውን ቅጣት እከፍልሻለሁ፤ በዚያ ጊዜ
እኔ እግዚአብሔር እንደሆንሁ ታውቃላችሁ።’
5“ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ‘መዓት!
ተሰምቶ የማይታወቅ መዓት[‡] ይመጣል።
6ፍጻሜ መጥቶአል! ፍጻሜ መጥቶአል! በአ
ንቺ ላይ ተነሣሥቶአል፤ እነሆ፤ ደርሶአል!
7እናንት በምድሪቱ የምትኖሩ ሆይ፤ የጥፋት
ፍርድ መጥቶባችኋል፤ ጊዜው ደርሶአል፤
በተ ራሮች ላይ እልልታ ሳይሆን ሽብር
የሚሰማበት ቀን ቀርቦአል። 8እነሆ፤ መዓ
ቴን በቅርብ ቀን አፈስብሻለሁ፤ በአንቺ
ላይ ቍጣዬን እፈጽምብሻለሁ፤ እንደ
አካሄድሽ እፈርድብሻለሁ፤ ስለ ጸያፍ
ተግባርሽም ሁሉ
ተገቢውን ቅጣት እከፍልሻለሁ። 9በርኅራኄ
ዐይን አልመለከትሽም፤ ምሕረት አላደርግ
ልሽም፤ ስለ አካሄድሽና በመካከልሽ ስላለው
ጸያፍ ተግባር ተገቢውን ቅጣት እከፍል
ሻለሁ፤ በዚያ ጊዜ፣ የምቀሥፍ እኔ እግዚ
አብሔር መሆኔን ታውቃላችሁ።
10“ ‘እነሆ ቀኑ! ይኸው ደረሰ! የጥፋት
ፍርድ ተገልጦአል፤ በትሩ አቈጥቍጦአል፤
ትዕቢት አብቦአል። 11ዐመፅ አድጎ[ጎ] የክፉት
በትር ሆነች፤ ከሕዝቡ አንድም አይተርፍም፤
ከሰዎቹ፣ ከሀብታቸውና እርባና ካለው ነገር
አንዳች አይቀርም። 12ጊዜው ደርሶአል፤ ቀኑም
ይኸው! መዓት በሕዝቡ ሁሉ ላይ ስለ
መጣ፣ የሚገዛ አይደሰት፤ የሚሸጥም አይዘን።
13ሁለቱ በሕይወት እስካሉ ድረስ ሻጩ
የሸጠውን መሬት አያስመልስም፤ ስለ
መላው ሕዝብ የተነገረው ራእይ
አይለወጥምና። ከኀጢአ ታቸው የተነሣ ሕ
ይወቱን ማትረፍ የሚችል አንድም
አይገኝም። 14መለከት ቢነፉም፣ ሁሉንም
ነገር ቢያዘጋጁም፣ ወደ ጦርነት የሚሄድ
አንድ እንኳ አይኖርም፤ መዓቴ በሕዝብ
ሁሉ ላይ መጥቶአልና።
15“በውጭ ሰይፍ፣ በውስጥ ደግሞ ቸነፈ
ርና ራብ አለ፤ በገጠር ያሉት በሰይፍ ይወድ
ቃሉ፤ በከተማ ያሉትም በራብና በቸነፈር
ያልቃሉ። 16ተርፈው ያመለጡት ሁሉ በሸ
ለቆ እንደሚኖሩ ርግቦች ስለ ኀጢአታቸው
እያለቀሱ በተራራ ላይ ይሆናሉ። 17እጅ ሁሉ
ይዝላል፤ ጕልበት ሁሉ ውሃ ይሆናል።
18ማቅ ይለብሳሉ፤ ሽብርም ይውጣቸዋል።
ፊታቸው ኀፍረት ይለብሳል፤ ራሳቸውም
ይላጫል። 19ብራቸውን በየጐዳናው ይጥላሉ፤
ወርቃቸውም እንደ ርኵስ ነገር ይቈጠራል።
በእግዚአብሔር የቍጣ ቀን ብራቸውና
ወርቃቸው ሊያድናቸው አይችልም፤ በኀጢ
አት እንዲወድቁ ዕንቅፋት ሆኖባቸዋልና
በልተው አይጠግቡበትም፤ ሆዳቸውንም አይሞ
ሉበትም። 20በውብ ዕንቋቸው ታብየዋል፤
ይህንም አስጸያፊ የጣዖት ምስሎቻቸውንና
ርኵስ ቅርጻ ቅርጾችን ለመሥራት ተጠቅ
መውበታል። ስለዚህ እነዚህን ነገሮች ወደ
ርኵሰት እለውጥባቸዋለሁ። 21ለባዕዳን ዝር
ፊያ፣ ለምድር ክፉዎችም ብዝበዛ አድርጌ
አሳልፌ እሰጣለሁ፤ እነርሱም ያረክሱታል።

6፥10 ቍ7፤ ዘዳ28፥52፤ ኤር40፥2
6፥11 ኤር42፥22፤ ሕዝ21፥14፡17፤ 22፥13፤25፥6
6፥12 ኢዮ20፥23፤ ሕዝ5፥12፤7፥15
6፥13 ዘሌ26፥30፤ 1ነገ14፥23፤ ኢሳ 1፥29፤ ኤር2፥20፤ ሕዝ18፥6፤20፥28፤ ሆሴ4፥13
6፥14 ዘፀ7፥5፤ ኢዮ 30፥21፤ ኤር6፥12፤ 51፥25፤ ሕዝ12፥19፤ 14፥13፤20፥34
7፥2 አሞ8፥2፡10፤ ራእ7፥1፤20፥8
7፥3 ዘፍ6፥13፤ ሕዝ18፥30
7፥4 ኤር13፥14፤ ሕዝ5፥11፤23፥49
7፥5 2ነገ21፥12
7፥6 ሕዝ39፥8
7፥7 ኢዮ18፥20፤ ኢሳ2፥12፤ ሕዝ12፥23፤ 30፥3፤ አሞ5፥18-20፤ ሶፎ1፥14፤ ሚል3፥2
7፥8 ኢሳ42፥25፤ ሕዝ9፥8፤14፥19፤ 20፥8፡21፤22፥22፤ 36፥19፤ ሆሴ5፥10፤ ናሆ1፥6
7፥9 ዘዳ32፥35፤ መዝ39፥10፤ ኢሳ 9፥13፤ ኤር21፥7፤ ሕዝ5፥11፤22፥31
7፥10 መዝ89፥32፤ ኢሳ10፥5
7፥11 መዝ55፥9፤ ኢሳ58፥4፤ ኤር16፥6 ፤ሶፎ1፥18
7፥12 ቍ7፤ ኢሳ 5፥13-14፤24፥2፤ ሕዝ30፥3
7፥13 ዘሌ25፥24-28
7፥14 ኢዮ39፥24፤ ኤር25፥38
7፥15 ዘዳ32፥25፤ ኤር14፥18፤ ሰቆ1፥20 ፤ሕዝ5፥12፤33፥27
7፥16 ዘፍ8፥8፤ ዕዝ 9፥15፤ ኢሳ10፥20፤ 59፥11፤ ኤር9፥19፤4 1፥16፤42፥17፤ ሕዝ6፥8
7፥17 2ነገ19፥26፤ ኤር47፥3፤ ሕዝ21፥7፤ 22፥14፤ ዳን5፥6
7፥18 መዝ55፥5፤ ኢሳ15፥2-3፤ ኤር4፥8 ፤8፥37፤49፥3፤ ሕዝ 27፥31፤ አሞ8፥11
7፥19 ምሳ11፥4፤ ኢሳ 42፥25፤55፥2፤ ሰቆ4፥ 1፤ ሕዝ3፥20፤13፥5፤ 14፥3፤30፥3፤ ሆሴ4፥ 5፤ ኢል1፥15፤2፥1፤ ሶፎ1፥7፡18፤2፥2
7፥20 ኢሳ2፥20፤ 30፥22፤ ኤር10፥3፤ ሕዝ5፥11፤16፥17
7፥21 ዘኍ14፥3፤ 2ነገ24፥13

[†]14 አብዛኞዎቹ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆች እንዲሁ ናቸው፤ ጥቂት የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆች ግን *ሪብላህ* ይላሉ
[‡]5 አብዛኞዎቹ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆች እንዲሁ ናቸው፤ አንዳንድ የዕብራይስጥና የሱርስት የጥንት ቅጆች ግን *በጥፋት ላይ ጥፋት* ይላሉ
[ጎ]11 ወይም *ዐመፀኛው የክፉት በትር*

22ፊቴን ከእነርሱ እመልሳለሁ፤ እነርሱም
የከበረውን ቦታዬን ያረክሳሉ፤ ወንበዴዎች
ይገቡበታል፤ ያረክሱታልም።
23“ ‘ምድር በደም መፋሰስ፣ ከተማዪ
ቱም በዐመፅ ተሞልታለችና ሰንሰለት አዘ
ጋጅ። 24እጅግ የከፉትን ከአሕዛብ አምጥቼ
ቤቶቻቸውን እንዲነጥቁ አደርጋለሁ፣ የኀ
ያላኑንም ትዕቢት አጠፋለሁ፤ መቅደሳቸውም
ይረክሳል። 25ሽብር በመጣ ጊዜ ሰላምን
ይሻሉ፤ ነገር ግን አያገኙትም። 26ጥፋት
በጥፋት ላይ፣ ወሬም በወሬ ላይ ይመጣል።
ራእይን ከነቢይ ለማግኘት ይጥራሉ፤ የሕግ
ትምህርት ከካህኑ፣ ምክርም ከሽማግሌው
ዘንድ ይጠፋል። 27ንጉሡ ያለቅሳል፤ መስፍኑ
ተስፋ መቍረጥን ይከናነባል፤ የምድሪቱም
ሕዝብ እጅ ትንቀጠቀጣለች። የእጃቸውን
እከፍላቸዋለሁ፤ ራሳቸው ባወጡት
መስፈርት መሠረት እፈርድባቸዋለሁ።
በዚያ ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ
ያውቃሉ።’ ”

## ባዕድ አምልኮ በቤተ መቅደስ

8 በስድስተኛው ዓመት፣ በስድስተኛው ወር፣
በአምስተኛው ቀን በቤቴ ተቀምጬ
ሳለሁ፣ የይሁዳም ሽማግሌዎች በፊቴ ተቀ
ምጠው ሳሉ፣ በዚያ የጌታ እግዚአብሔር
እጅ በላዬ መጣች። 2እኔም አየሁ፤ እነሆ፤
የሰውን ልጅ የሚመስል' ነበረ፤ ወገቡ ከሚ
መስለው በታች እንደ እሳት ያለ ነበር፤
ወገቡንም ከሚመስለው ጀምሮ ወደ ላይ
እንደ ጋለ ብረት ያበራ ነበር። 3እርሱም
እጅ መሳይ ዘርግቶ የራስ ጠጕሬን ያዘ፤
መንፈስም በምድርና በሰማይ መካከል
አነሣኝ፤ እርሱም ቅናት የሚያነሣው
ጣዖት ወደ ቆመበት፣ ወደ ውስጠኛው
አደባባይ መግቢያ ወደ ሰሜን በር ወደ ኢ
የሩሳሌም በእግዚአብሔር ራእይ ወሰደኝ።
4እነሆ፤ በረ ባዳው ስፍራ በራእይ ያየሁት
የእስራኤል አምላክ ክብር በዚያ ነበረ።
5እርሱም፣ “የሰው ልጅ ሆይ፤ ወደ ሰሜን
ተመልከት” አለኝ። እኔም ተመለከትሁ፤ እነሆ
ከመሠዊያው በር በሰሜን በኩል መግቢ
ያው ላይ ይህ የቅናት ጣዖት ነበረ።
6ደግሞም፣ “የሰው ልጅ ሆይ፤ የእስራኤል
ቤት ከመቅደሴ ያርቀኝ ዘንድ በዚህ የሚያ
ደርገውን እጅግ አስጸያፊ ነገር ታያለህን?
ከዚህም የባሰ አስጸያፊ ነገር ታያለህ” አለኝ።
7ከዚያም በኋላ ወደ አደባባዩ መግቢያ
አመጣኝ፤ እኔም ግንቡን ተመለከትሁ፤ ቀዳ
ዳም ነበረበት። 8እርሱም፣ “የሰው ልጅ
ሆይ፤ ግንቡን ንደለው” አለኝ፤ እኔም
ግንቡን ነደልሁት፤ አንድ በርም አገኘሁ።
9እርሱም፣ “ግባና በዚህ የሚፈጽሙትን
እጅግ የከፋ ርኵሰት ተመልከት አለኝ።
10እኔም ገብቼ አየሁ፤ እነሆ በደረታቸው
የሚሳቡ ፍጡራንና የርኩሳን አራዊት ዐይ
ነት ሁሉ፣ የእስራኤልም ቤት ጣዖታት
ሁሉ ዙሪያውን በግንቡ ላይ ተቀርጸው
ነበር። 11በእነዚህም ፊት ከእስራኤል ቤት
ሰባ ሽማግሌዎች ቆመው ነበር፤ በመካከላ
ቸውም የሳፋን ልጅ ያእዛንያ ቆሞ ነበር፤
እያንዳንዳቸውም በእጃቸው ጥና ይዘዋል፤
መልካም መዐዛ ያለው የዕጣን ጢስም እየተ
ትጐለጐለ ይወጣ ነበር።
12እርሱም፣ “የሰው ልጅ ሆይ፤ የእስራኤል
ቤት ሽማግሌዎች እያንዳንዳቸው በጣዖታቸው
ምስል ጓዳ ውስጥ በጨለማ የሚያደርጉትን
አይተሃልን? እነርሱ፣ ‘እግዚአብሔር አያየንም፤
እግዚአብሔር ምድሪቱን ትቶአል’ ይላሉ”
አለኝ። 13ደግሞም፣ “ከእነዚህ የባሰ አስጸያፊ
ነገር ሲሠሩ ታያለህ” አለኝ።
14ከዚህም በኋላ በሰሜን በኩል ወዳለው
ወደ እግዚአብሔር ቤት በር መግቢያ አመ
ጣኝ፤ በዚያም ሴቶች ተቀምጠው ተሙዝ
ለተባለው ጣዖት ሲያለቅሱ አየሁ። 15እር
ሱም፣ “የሰው ልጅ ሆይ፤ ይህን አይተሃልን?
ከዚህም የባሰ አስጸያፊ ነገር ታያለህ” አለኝ።
16ደግሞም ወደ እግዚአብሔር ቤት ወደ
ውስጠኛው አደባባይ አመጣኝ፤ እነሆም በመተ
ላለፊያውና በመሠዊያው መካከል በቤተ
መቅደሱ መግቢያ ላይ ሃያ አምስት ሰዎች
ያህል ነበሩ፤ ጀርባቸውን ወደ እግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ፣ ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ
አድርገው ለምትወጣዋ ፀሓይ ይሰግዱ
ነበር።
17እርሱም እንዲህ አለኝ፤ “የሰው ልጅ
ሆይ፤ ይህን አይተሃልን? የይሁዳ ቤት በዚህ
ቦታ የሚፈጽሙት ጸያፍ ተግባር ቀላል
ነገር ነውን? ምድሪቱንስ በዐመፅ
በመሙላት ዘወትር ያስቈጡኝ ዘንድ
ይገባልን? እነሆ፤ ቅርንጫፉን ወደ
አፍንጫቸው አቅርበዋል! 18ስለዚህ በቍጣ
እመጣባቸዋለሁ፤ በርኅራኄ
ዐይን አላያቸውም፤ ከሚመጣባቸው ነገር
አላድናቸውም፤ ወደ ጆሮዬም ቢጮኹ አል
ሰማቸውም።”

## የጣዖት አምላኪዎች መገደል

9 ከዚያም እኔ እየሰማሁ ከፍ ባለ ድምፅ፣
“እያንዳንዳቸው በእጃቸው የጦር መሣሪያ
የያዙ፣ ከተማዪቱን የሚቀጡ ወደዚህ ይምጡ”
ብሎ ከፍ ባለ ድምፅ ጮኸ። 2እነሆም፤
አጥፊ የሆነ የጦር መሣሪያ በእጃቸው
የያዙ ስድስት ሰዎች በሰሜን አቅጣጫ
ካለው ከላይኛው በር መጡ፤ ከእነርሱም
ጋር ቀጭን በፍታ የለበሰ፣ በጐኑም የ
ጽሕፈት

7፥22 መዝ74፥7-8፤ ኤር2፥27፤19፥13፤ ሰቆ2፥7፤ሕዝ39፥23-24
7፥23 ዘፍ6፥11፤ 2ነገ21፥16፤ኢሳ1፥15፤ ሕዝ11፥6፤22፥9
7፥24 2ዜና7፥20፤ ሰቆ2፥7፤ሕዝ24፥21፤ 28፥7
7፥25 ኤር6፥14፤ 8፥11፤ሕዝ13፥10፡16
7፥26 ዘዳ29፥21፤ 31፥17፤1ሳሙ3፥1፤ ኢሳ47፥11፤ ኤር18፥18፤ ሕዝ20፥1-3፤ አሞ8፥11፤ሚክ3፥6
7፥27 ቍ4፤ መዝ109፥19፤ኢሳ 3፥11፤ሕዝ18፥20፤ 26፥16
8፥1 2ነገ6፥32፤ ሕዝ1፥1-3፤14፥1፤ 24፥1፤33፥31፤40፥1
8፥2 ሕዝ1፥4፡26-27
8፥3 ቍ5፡16፤ ዘፀ20፥5፤24፥10፤ ዘዳ32፥16፤ሕዝ2፥9፤ 3፥12፤11፥1
8፥4 ዘፀ24፥16፤ ሕዝ3፥22
8፥5 መዝ78፥58፤ ኤር4፥1፤32፥34
8፥6 መዝ78፥60፤ ሕዝ5፥11፤ሆሴ 5፥6
8፥10 ዘፀ20፥4፤ዘዳ 4፥15-18፤መሳ 17፥4-5፤ኤር16፥18፤ 44፥4፤ሕዝ11፥12፤ 23፥14
8፥11 ዘፀ3፥16፤ ዘሌ10፥1፤ዘኍ16፥17፡ 35፤ኤር44፥5፤ ሕዝ11፥1-2
8፥12 2ነገ21፥16፤ ኢዮ22፥13፤መዝ 10፥11፤ኢሳ29፥15 ፤ሕዝ9፥9፤ሶፎ1፥12
8፥14 ሕዝ11፥12
8፥16 ቍ3፤ ዘፍ1፥16፤ዘዳ4፥19፤ 17፥3፤ኢዮ31፥28፤ ኤር2፥27፤ሕዝ9፥6፤ 11፥1፡12፤40፥6፤ 43፥1
8፥17 ዘፍ6፥11፤ ዘኍ11፥33፤1ነገ14፥9፤ ሕዝ16፥2፡26
8፥18 1ሳሙ8፥18፤ ኢሳ58፥4፤ ኤር11፥11፤13፥14፤ 44፥6፤ሕዝ5፥11፤ 9፥10፤ 24፥14
9፥2 ዘሌ16፥4፤ ሕዝ10፥2፤ዳን10፥5፤ 12፥6፤ራእ15፥6

'2 *ወይም እሳት የሚመስል አየሁ*

ዕቃ ማኅደር ያነገበ ሰው ነበር። እነርሱም
ገብተው በናሱ መሠዊያ አጠገብ ቆሙ።
3በዚህ ጊዜ የእስራኤል አምላክ ክብር
ከነ በረበት ከኪሩብ በላይ ተነሥቶ ወደ
ቤተ መቅደሱ መድረክ ሄደ። እግዚአብሔርም
በፍታ የለበሰውን በጐኑም የጽሕፈት ዕቃ
ማኅደር ያነገበውን ሰው ጠራ፤ 4እግዚ
አብሔርም፣ “በኢየሩሳሌም ከተማ ሁሉ
ሂድና በውስጧ ስለ ተሠራው ጸያፍ ተግባር
ሲያዝኑና ሲያ ለቅሱ በነበሩ ሰዎች ግምባር
ላይ ምልክት አድርግ” አለው።
5እኔም እየሰማሁ፣ ለሌሎቹ እንዲህ አለ፤
“በከተማዋ ሁሉ እርሱን ተከትላችሁ ግደሉ፤
አዘኔታና ርኅራኄ አታሳዩ፤ ግደሉ፤ 6ሽማ
ግሌውን፣ ጕልማሳውንና ልጃገረዲቱን፣ ሴቶች
ንና ሕፃናትን ፈጽማችሁ አጥፉ፤ ነገር ግን
ምልክቱ ያለበትን ሰው አትንኩ፤ ከቤተ
መቅደሴም ጀምሩ።” ስለዚህ በቤተ መቅ
ደሱ ፊት ለፊት ከነበሩት ሽማግሌዎች
ጀመሩ።
7እርሱም፣ “ቤተ መቅደሴን አርክሱ፤ አደ
ባባዩንም ሬሳ በሬሳ አድርጉ፤ ሂዱ!” አላ
ቸው። እነርሱም ወጥተው በከተማዪቱ ሁሉ
እየተዘዋወሩ መግደል ጀመሩ። 8እነርሱ
እየገደሉ እኔም ብቻዬን ሳለሁ፣ በግንባሬ
ተደፍቼ፣ “ወዮ! ልዑል *እግዚአብሔር* ሆይ፤
በኢየሩሳሌም ላይ መዓትህን አውርደህ የእ
ስራኤልን ትሩፋን ሁሉ ልታጠፋ ነውን?”
በማለት ጮኽሁ።
9እርሱም እንዲህ ሲል መለሰልኝ፤ “የእስ
ራኤልና የይሁዳ ቤት ኀጢአት እጅግ በዝቶ
አል፤ ምድሪቱ በደም ተጥለቅልቃለች፤
ከተማዪቱም ግፍን ተሞልታለች። እነርሱ፣
‘*እግዚአብሔር* ምድሪቱን ትቶአታል፤ *እግ
ዚአብሔር* አያይም’ ይላሉ፤ 10እኔም የሠሩ
ትን ሥራ በራሳቸው ላይ እመልስባቸዋለሁ
እንጂ በርኅራኄ ዐይን አላያቸውም፤ ከሚ
መጣባቸውም ነገር አላድናቸውም።”
11እነሆ በፍታ የለበሰውና በጐኑም የጽሕ
ፈት ዕቃ ማኅደር ያነገበው ሰው ተመልሶ፣
“እንዳዘዝኸው ፈጽሜአለሁ” አለ።

## የእግዚአብሔር ክብር ከቤተ መቅደሱ ተለየ

10 እኔም አየሁ፤ እነሆ ከኪሩቤል ራስ
በላይ ካለው ጠፈር ከፍ ብሎ፣
የሰንፔር ዙፋን[ኘ] የሚመስል ነገር ነበረ።
2*እግዚአብሔርም* በፍታ የለበሰውን ሰው፣
“በኪሩቤል ሥር ወዳሉት መንኰራኵሮች
መካከል ግባ፤ በኪሩቤል መካከል ካለውም
የእሳት ፍም እጅህን ሞልተህ ዝገን፤ በከተ
ማዪቱም ላይ በትነው” አለው። ሰውዬውም
እያየሁት ገባ።

3ሰውዬው ወደ ውስጥ በገባ ጊዜ፣ ኪሩ
ቤል በቤተ መቅደሱ ውስጥ በደቡብ በኩል
ቆመው ነበር፤ ደመናም ውስጠኛውን አደባ
ባይ ሞላ። 4*የእግዚአብሔርም* ክብር ከነበ
ረበት ከኪሩቤል በላይ ተነሥቶ ወደ ቤተ
መቅደሱ መድረክ ሄደ፤ ደመናው ቤተ
መቅደሱን ሞላ፤ አደባባዩም *በእግዚአብሔር*
ክብር ብርሃን ተሞላ። 5ሁሉን የሚገዛ[ኣ]
አምላክ ሲናገር እንደሚሰማው ድምፅ ዐይነት፣
የኪሩቤል ክንፎች ድምፅ እስከ ውጪው
አደባባይ ድረስ ይሰማ ነበር።
6*እግዚአብሔር* በፍታ የለበሰውን ሰው፣
“ከኪሩቤል ዘንድ ከመንኰራኵሮቹ መካከል
እሳት ውሰድ” ብሎ ባዘዘው ጊዜ፣ ሰውዬው
ወደ ውስጥ ገብቶ በአንዱ መንኰራኵር
አጠገብ ቆመ። 7ከኪሩቤልም አንዱ በመካ
ከላቸው ወዳለው እሳት እጁን ዘርግቶ
ጥቂት ወሰደ፤ በፍታ በለበሰው ሰው እጅ
ላይ አኖረው፤ እርሱም ይዞ ወጣ። 8ከኪሩ
ቤል ክንፎች ሥር የሰው እጅ የሚመስል
ይታይ ነበር።
9እኔም አየሁ፤ እነሆ፤ በኪሩቤል አጠገብ
አራት መንኰራኵሮች ነበሩ፤ በእያንዳንዱ
ኪሩብ አጠገብ አንድ መንኰራኵር ነበር፤
የመንኰራኵሮቹም መልክ እንደ ቢረሌ
ያንጸባርቅ ነበር። 10የአራቱም መልክ
ይመ ሳሰል ነበር፤ እያንዳንዱም መንኰራ
ኵር በመንኰራኵር ውስጥ ተሰክቶ የተሠ
ራ ይመስል ነበር። 11መንኰራኵሮቹ
በሚንቀ ሳቀሱበት ጊዜም ኪሩቤል ወደ
ዞሩበት ወደ አራቱ አቅጣጫ ሁሉ መሄድ
ይችሉ ነበር፤ ኪሩቤል በሚሄዱበት ጊዜ
መንኰራኵሮቹ ወዲያ ወዲህ[ከ] አይሉም
ነበር፤ ኪሩቤል በሚሄዱበት ጊዜ ወዲያ
ወዲህ ሳይሉ፣ ራስ ወደ ዞረበት ወደ
ማንኛውም አቅጣጫ ይጓዙ ነበር።
12ጀርባቸውን፣ እጃቸውን፣ ክንፋቸውን
ጨምሮ መላ ሰውነታቸው እን ዲሁም አራ
ቱ መንኰራኵሮቻቸው በጠቅ ላላ በዐይን
የተሞሉ ነበሩ። 13መንኰራኵ ሮቹም፣
“ተሽከርካሪ መንኰራኵሮች” ተብ ለው
ሲጠሩ ሰማሁ። 14እያንዳንዱም ኪሩብ አራ
ት አራት ፊት ነበሩት፤ ይኸውም አንደ
ኛው ፊት የኪሩብ፣ ሁለተኛው የሰው ፊት፣
ሦስተኛው የአንበሳ ፊት፣ አራተኛውም
የንስር ፊት ነበር።
15ኪሩቤልም ወደ ላይ ተነሡ፤ እነዚህም
በኮቦር ወንዝ አጠገብ ያየኋቸው ሕያዋን
ፍጡራን ነበሩ። 16ኪሩቤል ሲንቀሳቀሱ፣
መንኰራኵሮቹም ከጐናቸው ይንጠ
ቀሳቀሱ

9፥3 1ሳሙ4፥21፤ ሕዝ10፥4፤ሕዝ 11፥22
9፥4 ዘፍ4፥15፤ ዘፀ12፥7፤ መዝ119፥53፡136፤ ኤር7፥29፤13፥17፤ 25፥29፤ሕዝ21፥6፤ አሞ6፥6፤2ቆሮ1፥22፤ ራእ7፥3
9፥5 ዘፀ32፥27፤ ኢሳ13፥18፤ኤር13፥14፤ ሕዝ5፥11
9፥6 ዘፍ4፥15፤ ዘፀ12፥7፤ 2ዜና36፥17፤ ኤር7፥32፤16፥6፤ 25፥29፤ሕዝ6፥4፤ 8፥11-13፡16፤ 1ጴጥ4፥17
9፥7 ሕዝ6፥7
9፥8 ኢሱ7፥6፤ ሕዝ4፥14፤7፥8፤ 11፥13፤አሞ7፥1-6
9፥9 ኢዮ22፥13፤ መዝ58፥2፤ኤር12፥1፤ ሕዝ8፥12፤14፥23፤ 22፥29፤ዕን1፥4
9፥10 ኢሳ22፥5፤ 65፥6፤ኤር13፥14፤ ሕዝ8፥18፤11፥21፤ 23፥49
10፥1 ዘፍ3፥24፤ ዘፀ24፥10፤ሕዝ1፥22፤ ራእ4፥2
10፥2 2ሳሙ22፥9፤ ሕዝ1፥15፤9፥2፤ ራእ8፥5
10፥4 ዘፀ24፥16፤ ሕዝ9፥3፤44፥4
10፥5 ኢዮ40፥9፤ ሕዝ3፥13
10፥6 ዳን7፥9
10፥7 ሕዝ5፥4
10፥8 ሕዝ1፥8
10፥9 ዘፀ28፥20፤ ራእ21፥20
10፥12 ሕዝ1፥15 -21፤ራእ4፥6-8
10፥14 1ነገ7፥29፡ 36፤ሕዝ1፥6፡10፤ 41፥19፤ራእ4፥7
10፥15 መዝ137፥1፤ ኢሳ6፥2

[ኘ]1 ወይም *ላፒስላዙሉ*
[ኣ]5 ዕብራይስጡ *ኤል-ሻዳይ ይለዋል*
[ከ]11 ወይም *ወደ አንድ ወገን አይሉም ነበር*

ነበር፤ ኪሩቤልም ከምድር ለመነሣት ክንፋ
ቸውን ሲዘረጉ፣ መንኰራኵሮቹ ከአጠገባቸው
አይለዩም ነበር። [17]ኪሩቤል ቀጥ ብለው
በሚቆሙበት ጊዜ እነርሱም ደግሞ ይቆ
ማሉ፤ ኪሩቤል ከምድር ከፍ ከፍ በሚሉበት
ጊዜ፣ የሕያዋኑ ፍጡራን መንፈስ በውስጣ
ቸው ስላለ፣ መንኰራኵሮችም አብረዋቸው
ይነሡ ነበር።

[18]ከዚህ በኋላ፣ *የእግዚአብሔር* ክብር
ከቤተ መቅደሱ ደጃፍ ላይ ተነሥቶ ከኪሩ
ቤል በላይ ቆመ። [19]ኪሩቤልም እኔ
እያየኋቸው ክንፎ ቻቸውን ዘርግተው
ከምድር ተነሥተው ሄዱ፤ መንኰራኵሮቹም
አብረዋቸው ሄዱ፤ *በእግ ዚአብሔርም* ቤት
በምሥራቁ በር መግቢያ ላይ ቆሙ፤ የእስራ
ኤልም አምላክ ክብር በላያ ቸው ላይ
ነበር።

[20]እነዚህ በኮቦር ወንዝ አጠገብ ከእስራኤል
አምላክ በታች ያየኋቸው ሕያዋን ፍጡራን
ነበሩ፤ ኪሩቤልም እንደሆኑ አስተዋልሁ።
[21]እያንዳንዳቸው አራት አራት ፊት፣ አራት
አራት ክንፍ፣ ከክንፎቻቸውም ሥር የሰውን
እጅ የሚመስል ነበራቸው። [22]ፊታቸውም
በኮቦር ወንዝ አጠገብ ካየኋቸው ጋር ይመ
ሳሰል ነበር፤ እያንዳንዱም ቀጥ ብሎ ወደ
ፊት ይሄድ ነበር።

## በእስራኤል መሪዎች ላይ የተላለፈ ፍርድ

**11** መንፈስም ወደ ላይ አነሣኝ፤ ከዚ
ያም በምሥራቅ በኩል ወዳለው
ወደ *እግዚአብሔር* ቤት በር አመጣኝ።
በበሩም መግቢያ ላይ ሃያ አምስት ሰዎች
ነበሩ፤ በእነርሱም መካከል የሕዝቡን መሪዎች
የዓዙርን ልጅ ያእዛንያንና የበናያስን ልጅ
ፈላጥያንን አየሁ። [2]*እግዚአብሔርም* እንዲህ
አለኝ፤ "የሰው ልጅ ሆይ፤ እነዚህ ሰዎች
ክፋትን የሚያቅዱና በዚህችም ከተማ ላይ
ተንኰልን የሚመክሩ ናቸው። [3]እነርሱም፣
'ቤቶች የሚሠሩበት ጊዜ ቅርብ አይደለ
ምን?[ኸ] ይህች ከተማ ድስት ናት፤ እኛም
ሥጋ ነን' ብለዋል። [4]ስለዚህ ትንቢት
ተናገርባቸው፤ የሰው ልጅ ሆይ፤ ትንቢት
ተናገር።"

[5]*የእግዚአብሔርም* መንፈስ በላዬ ወረደ
እንዲህም አለኝ፤ "*እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤ 'የእስራኤል ቤት ሆይ፤ እናንተ እን
ዲህ ብላችኋል፤ እኔ ግን የልባችሁን ሐሳብ
ዐውቃለሁ። [6]በዚህች ከተማ ብዙ ሰው
ገድላችኋል፤ መንገዶቿንም ሬሳ በሬሳ አድ
ርጋችኋል።'

[7]"ስለዚህ ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤ 'በዚያ የጣላችኋቸው ሬሳዎች እነርሱ
ሥጋ ናቸው፤ ይህችም ከተማ ድስት ናት፤
እናንተን ግን ከውስጧ አወጣችኋለሁ።
[8]ሰይፍን ፈርታችኋል፤ እኔም ሰይፍ እልክ
ባችኋለሁ፤ ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*።
[9]ከከተማዪቱ አውጥቼ ለባዕዳን አሳልፌ
እሰጣችኋለሁ፤ ፍርድንም አመጣባችኋለሁ።
[10]በሰይፍ ትወድቃላችሁ፤ በእስራኤል ድንበር
ላይ እፈርድባችኋለሁ፤ በዚያ ጊዜም እኔ
*እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ።
[11]ይህች ከተማ ድስት አትሆንላችሁም፤
እናንተም በውስጧ ሥጋ አትሆኑም፤ በእስ
ራኤልም ድንበር ላይ እፈርድባችኋለሁ፤
[12]በዚያ ጊዜ እኔ *እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ
ታውቃላችሁ፤ እናንተ በዙሪያችሁ ያሉትን
አሕዛብ ሥርዐት ተከተላችሁ እንጂ ትእዛዜን
አልፈጸማችሁም ሕጌንም አልጠበቃችሁ
ምና።"

[13]ትንቢት እየተናገርሁ ሳለ፣ የበናያስ
ልጅ ፈላጥያ ሞተ፤ እኔም በግንባሬ ተደ
ፍቼ፣ "ጌታ *እግዚአብሔር* ሆይ፣ ወዮ!
የእስራኤልን ቅሬታ ፈጽመህ ታጠፋለህን?"
በማለት በታላቅ ድምፅ ጮኽሁ።

[14]*የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል ወደ
እኔ መጣ፤ [15]"የሰው ልጅ ሆይ፤ ወንድሞችህ፣
የራስህ ዘመዶችና[ሠ] የእስራኤል ቤት ሁሉ፤
'*ከእግዚአብሔር* ርቀዋል፤ ይህች ምድር
ርስት ሆና ለኛ ተሰጥታናለች' ብለው የኢ
የሩሳሌም ነዋሪዎች የተናገሩባቸው ናቸው።[ዐ]

## የእስራኤል የመመለስ ተስፋ

[16]"ስለዚህ እንዲህ በል፤ 'ጌታ *እግዚአብሔር*
እንዲህ ይላል፤ "በአሕዛብ መካከል ብሰድ
ዳቸውም፤ በአገሮች መካከል ብበታት
ናቸውም፣ በሄዱባቸው አገሮች ሁሉ ለጥቂት
ጊዜ መቅደስ ሆኜአቸዋለሁ' "።

[17]"ስለዚህ እንዲህ በል፤ 'ጌታ *እግዚአ
ብሔር* እንዲህ ይላል፤ "ከአሕዛብ መካከል
እሰበስባችኋለሁ፤ ከተበተናችሁባቸው አገሮች
እመልሳችኋለሁ፤ የእስራኤልንም ምድር እንደ
ገና እሰጣችኋለሁ።"

[18]"ወደዚያ በተመለሱ ጊዜ የረከሱ ምስሎቿ
ንና ጸያፍ ተግባሯን ያስወግዳሉ። [19]የማያ
ወላውል ልብ እሰጣቸዋለሁ፤ አዲስ መንፈስ
በውስጣቸው አኖራለሁ፤ ድንጋዩን ልብ ከውስ
ጣቸው አወጣለሁ፤ ሥጋ ልብም እሰጣቸዋ
ለሁ። [20]ስለዚህ ትእዛዜን ይፈጽማሉ፤ ሕጌን
ይጠብቃሉ። እነርሱ ሕዝቤ ይሆናሉ፤ እኔም
*አምላካቸው* እሆናለሁ። [21]ነገር ግን ልባቸው
ወደ ረከሱ ምስሎቻቸውና ወደ ጸያፍ ተግ

10፥17 ሕዝ3፥13
10፥18 1ሳሙ4፥21፤ መዝ18፥10
10፥19 ሕዝ11፥1፡ 22፤43፥4
10፥20 ሕዝ1፥1
10፥21 ሕዝ1፥6፤ 41፥18
10፥22 ሕዝ1፥1
11፥1 ቍ13፤ ኤር5፥5፤ሕዝ8፥16፤ 10፥19፤43፥4-5
11፥2 ኢሳ29፥20 ፤ሕዝ8፥11፤ናሆ1፥11
11፥3 ቍ7፤ ኤር1፥13፤ሕዝ12፥22፡ 27፤24፥3፤ሚክ3፥3
11፥4 ሕዝ3፥4፡17
11፥5 መዝ26፥2፤ ኤር17፥10
11፥6 ሕዝ7፥23፤ 22፥6
11፥7 ቍ3፤ ኤር1፥13፤ ሕዝ24፥3-13፤ ሚክ3፥2-3
11፥8 ዘሌ26፥25፤ ምሳ10፥24፤ ኢ. ሳ66፥4፤ኤር42፥16
11፥9 ዘዳ28፥36፤ መዝ106፥41፤ ሕዝ 5፥8
11፥10 2ነገ14፥25
11፥11 ቍ3፤ ሕዝ24፥6
11፥12 ዘሌ18፥4፤ ሕዝ6፥7፤8፥10፤ 18፥9
11፥13 ቍ1፤ ሕዝ9፥8፤አሞ7፥2
11፥15 ሕዝ33፥24
11፥16 መዝ31፥20፤ 90፥1፤91፥9፤ ኢሳ 4፥6
11፥17 ነህ1፥9፤ ኤር3፥18፤24፥5-6፤ 31፥16፤ሕዝ20፥41፤ 28፥25፤34፥13፤ 36፥28
11፥18 ሕዝ5፥11፤ 37፥23
11፥19 2ዜና30፥12፤ መዝ86፥11፤ ሕዝ18፥31፤ ዘካ7፥12፤ሮሜ2፥5፤ 2ቆሮ3፥3
11፥20 ዘፀ6፥7፤ መዝ1፥2፤ኤር11፥4፤ 32፥38፤ሕዝ14፥11፤ 34፥30፤36፥26-28፤ ሆሴ1፥9፤ዘካ8፥8፤ ዕብ8፥10
11፥21 ኤር16፥11፤ 16፥18፤ሕዝ9፥10፤ 16፥43

[ኸ]3 ወይም *ቤቶችን ለመሥራት ጊዜው አሁን አይደለም*
[ሠ]15 ወይም *በምርኮ ከአንተ ጋር የነበሩና* (ሰብዐ ሊቃናትና ሱርስትን ይመ)
[ዐ]15 ወይም *የኢየሩሳሌም ሰዎች የተናገሩባቸው፣ 'ከእግዚአ ብሔር ራቁ'*

ባራቸው ያዘነበለውን እንደ ሥራቸው እከፍ
ላቸዋለሁ፤ ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*።”
22ኪሩቤልም ክንፎቻቸውን ዘረጉ፤ መንኰ
ራኵሮቹም በአጠገባቸው ነበሩ፤ የእስራ
ኤልም አምላክ ክብር በላያቸው ላይ
ነበር። 23*የእግዚአብሔርም* ክብር ከከተ
ማዪቱ ውስጥ ተነሥቶ ወጣ፤ ከከተማዪቱም
በስተ ምሥ ራቅ ካለው ተራራ በላይ ቆም
አለ። 24መን ፈስም ወደ ላይ አነሣኝ፤
በእግዚአብሔርም መንፈስ በተሰጠው ራ
እይም በባቢሎን‴ ምድር ወደ ነበሩት
ምርኮኞች አመጣኝ።
ከዚያም ያየሁት ራእይ ከእኔ ወጥቶ ሄደ፤
25እኔም *እግዚአብሔር* ያሳየኝን ነገር ሁሉ
ለምርኮኞቹ ተናገርሁ።

### ምርኮው በትእምርት መቅረቡ

**12** *የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤ 2“የሰው ልጅ ሆይ፤
በዐመፀኛ ሕዝብ መካከል ተቀምጠሃል፤ የሚ
ያዩበት ዐይን አላቸው፤ ነገር ግን አያዩም፤
የሚሰሙበትም ጆሮ አላቸው፤ ነገር ግን
አይሰሙም፤ ዐመፀኛ ሕዝብ ናቸውና።
3“ስለዚህ የሰው ልጅ ሆይ፤ እነርሱ እያዩህ
በቀን ጓዝህን ጠቅልለህ ለመሰደድ ተዘጋጅ፤
ካለህበትም ስፍራ ተነሥተህ ወደ ሌላ ቦታ
ሂድ፤ ዐመፀኛ ቤት ቢሆኑም ምናልባት
ይህን ያስተውሉታል። 4በቀን እያዩ ጓዝህን
እንደ ስደተኛ ጓዝ አውጣው፤ በምሽትም
እያዩህ ስደተኛ እንደሚወጣ ውጣ። 5እነ
ርሱ እያዩ ግንቡን ነድለህ ጓዝህን በዚያ
አሹልክ። 6በፊታቸው ጓዝህን በትከሻህ
ላይ አስቀምጥ፣ በምሽትም ተሸክመህ
ውጣ። ለእስራኤል ቤት ምልክት አድር
ጌሃለሁና ምድሪቱን እንዳታይ ፊትህን
ሸፍን።”
7እኔም በታዘዝሁት መሠረት አደረግሁ፤
በቀን ጓዜን ጠቅልዬ እንደ ስደተኛ ጓዝ
አወጣሁ፤ በምሽትም ግንቡን በእጄ ነደል
ሁት፤ እያዩኝም በምሽት ጓዜን በትከሻዬ
ላይ ተሸክሜ አወጣሁ።
8በማግስቱም ጠዋት *የእግዚአብሔር* ቃል
እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፤ 9“የሰው ልጅ
ሆይ፤ ዐመፀኛው የእስራኤል ቤት፣ ‘ይህ
የም ታደርገው ምንድን ነው?’ ብለው ጠ
ይቀውህ አልነበረምን?”
10“እንዲህ በላቸው፤ ‘ጌታ *እግዚአብሔር*
እንዲህ ይላል፤ “ይህ የትንቢት ቃል በኢ
የሩሳሌም ለሚኖረው መስፍንና በዚያ ለሚገ
ኙት ለእስራኤል ቤት ሁሉ ነው’ ”።
11‘እኔ ምልክታችሁ ነኝ’ በላቸው።
“እኔ እንዳደረግሁት፤ እንዲሁ በእነርሱ
ይደረግባቸዋል፤ በምርኮኛነትም ተሰደው
ይሄዳሉ።
12“በመካከላቸው ያለው መስፍን በምሽት
ጓዙን በትከሻው ተሸክሞ ይወጣል፤ ሾልኮ
እንዲሄድ ግንቡ ይነደልለታል፤ ምድሪቱንም
እንዳያይ ፊቱን ይሸፍናል። 13መረቤን በእርሱ
ላይ እዘረጋለሁ፤ በወጥመዴም ይያዛል፤ ወደ
ከለዳውያን ምድር ወደ ባቢሎን አመጣ
ዋለሁ፤ ነገር ግን እርሷን ሳያያት በዚያ
ይሞታል። 14በዙሪያው ያሉትን ረዳቶቹንና
ወታደሮቹን ሁሉ ወደ ነፋስ እበትናቸዋለሁ፤
በተመዘዘም ሰይፍ አሳድዳቸዋለሁ።
15“በአሕዛብ መካከል ስበትናቸውና በአገ
ሮችም መካከል ስዘራቸው፤ በዚያን ጊዜ እኔ
*እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።
16ነገር ግን በሄዱባቸው አሕዛብ መካከል
ስለ ጸያፍ ተግባራቸው ይናገሩ ዘንድ
ከእነርሱ ጥቂቶቹን ከሰይፍ ከራብና
ከቸነፈር አተርፋለሁ። በዚያን ጊዜ እኔ
*እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።”
17*የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል ወደ
እኔ መጣ፤ 18“የሰው ልጅ ሆይ፤ ምግብህን
በድንጋጤ ብላ፤ ውሃህንም በፍርሀትና በመ
ንቀጥቀጥ ጠጣ። 19ለምድሪቱ ሕዝብ እንዲህ
በል፤ ‘ጌታ *እግዚአብሔር* በኢየሩሳሌምና
በእስራኤል ምድር ስለሚኖሩት እንዲህ
ይላል፤ “በዚያ ከሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ዐመፅ
የተነሣ ምድራቸው ስለምትራቈት፣ ምግባ
ቸውን በጭንቀት ይመገባሉ፤ ውሃቸውንም
በፍርሀት ይጠጣሉ። 20ሰው ይኖርባቸው
የነበሩ ከተሞች ባድማ ይሆናሉ፤ ምድሪቱም
ወና ትሆናለች። በዚያ ጊዜ እኔ *እግዚ
አብሔር* እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ።’ ”
21*የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል ወደ
እኔ መጣ፤ 22“የሰው ልጅ ሆይ፤ በእስራኤል
ምድር፣ ‘ዘመኑ ረዝሞአል፤ ራእዩ ሁሉ ከንቱ
ሆኖአል’ የምትሉት ይህ አባባል ምንድነው?
23እንዲህ በላቸው፤ ‘ጌታ *እግዚአብሔር* እን
ዲህ ይላል፤ “ይህን አባባል እሽራለሁ፤ በእ
ስራኤልም ምድር ዳግመኛ በንግግራቸው
አይጠቀሙበትም”። እንዲህም በላቸው፤
“ራእዩ ሁሉ የሚፈጸምበት ጊዜ ቀርቦአል፤
24በእስራኤል ሕዝብ መካከል ከእንግዲህ ሐሰ
ተኛ ራእይና አሳሳች ሟርት አይገኝምና።
25ነገር ግን እኔ *እግዚአብሔር* እናገራለሁ፤
የምናገረውም ቃል ሳይዘገይ ይፈጸማል፤
እናንተ ዐመፀኛ ቤት ሆይ፤ የተናገርሁትን
ሁሉ በዘመናችሁ እፈጽማለሁ” ይላል ጌታ
*እግዚአብሔር*።’ ”
26*የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል ወደ
እኔ መጣ፤ 27“የሰው ልጅ ሆይ፤ የእስራኤል

11፥22 ዘፀ24፥16፤ ሕዝ9፥3፤10፥19
11፥23 ሕዝ1፥28፤ 10፥4፤ዘካ14፥4
11፥24 ሕዝ37፥1፤ 43፥5፤2ቆሮ12፥2-4
11፥25 ሕዝ3፥4:11
12፥2 መዝ78፥40፤ ኢሳ6፥10፤ኤር42፥21፤ማቴ13፥15፤ ማር4፥12፤8፥18
12፥3 ቀኍ11፤ኤር 26፥3፤36፥3፤ሕዝ3፥27፤2ጢሞ2፥25-26
12፥4 ቀኍ12፤2ነገ 25፥4፤ኤር39፥4
12፥5 ኤር52፥7፤ አሞ4፥3
12፥6 ቀኍ12፤ኢሳ 8፥18፤20፥3
12፥7 ሕዝ24፥18፤ 37፥10
12፥9 ሕዝ17፥12፤ 20፥49፤24፥19
12፥11 2ነገ25፥7፤ ኢሳ8፥18፤ኤር15፥2፤ 52፥15፤ዘካ3፥8
12፥12 ኤር39፥4፤ 52፥7
12፥13 ኢሳ24፥17-18፤ኤር24፥8፤ 39፥7፤52፥11፤ ሰቆ4፥20፤ሕዝ1፥3፤ 17፥16:20፤19፥8፤ 32፥3፤ሆሴ7፥12
12፥14 2ነገ25፥5፤ ኤር21፥7፤ሕዝ5፥10: 12፤17፥21
12፥15 ዘሌ26፥33
12፥16 ኤር22፥8-9፤ ሕዝ6፥8-10፤14፥22፤ 36፥20
12፥18 ሰቆ5፥9
12፥19 ኤር10፥22፤ ሕዝ4፥16፤6፥6-14፤ 23፥33፤ሚክ7፥13፤ ዘካ7፥14
12፥20 ኢሳ7፥23-24፤ኤር4፥7፤25፥9
12፥22 መዝ49፥4፤ ኢሳ5፥19፤ሕዝ11፥3፤ አሞ6፥3፤2ጴጥ3፥4
12፥23 መዝ37፥13፤ ሕዝ7፥7፤18፥3፤ ኢል2፥1፤ሶፎ1፥14
12፥24 ኤር14፥14፤ ሕዝ13፥23፤ሚክ3፥6፤ ዘካ13፥2-4
12፥25 ዘኍ11፥23፤ 14፥28-34፤ ኢሳ14፥24፤55፥11፤ ኤር16፥9፤ሕዝ13፥6፤ ዕን1፥5፤2፥3

‴24 ወይም *ከለዳውያን*

ቤት፣ ‘ይህ ሰው የሚያየው ራእይ ገና
ለሩቅ ዘመን የሚሆን ነው፤ የሚናገረውም
ትንቢት የረጅም ጊዜ ትንቢት ነው’ ይላሉ።
28“ስለዚህ እንዲህ በላቸው፣ ‘ጌታ *እግዚ
አብሔር* እንዲህ ይላል፤ “ከተናገርሁት ቃል
ከእንግዲህ የሚዘገይ የለም፤ የምለው ሁሉ
ይፈጸማል” ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*።’ ”

## የሐሰተኛ ነቢያት መወገዝ

13 *የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤ 2“የሰው ልጅ ሆይ፤
ትንቢት በሚናገሩት በእስራኤል ነቢያት
ላይ ትንቢት ተናገር፤ ከገዛ ራሳቸው ትንቢት
የሚናገሩትን እንዲህ በላቸው፤ ‘*የእግዚአ
ብሔርን* ቃል ስሙ፤ 3ጌታ *እግዚአብሔር*
እንዲህ ይላል፤ “አንዳች ነገር ሳያዩ የራሳ
ቸውን መንፈስ ለሚከተሉ ሞኞች[ሠ] ነቢያት
ወዮላቸው! 4እስራኤል ሆይ፤ ነቢያትሽ
በፍ ርስራሽ መካከል እንደሚኖሩ
ቀበሮዎች ናቸው። 5*በእግዚአብሔር* ቀን
በሚሆነው ጦርነት ጸንቶ መቆም እንዲችል፣
የተሰነጠቀ ውን ቅጥር ለእስራኤል ቤት
ለመጠገን ወደዚያ አልወጣችሁም። 6ራ
እያቸው ሐሰት፣ ትንቢታቸው ውሸት ነው፤
*እግዚአብሔር* ሳይልካቸው፣ ‘*እግዚአብሔር*
እንዲህ ይላል’ ይላሉ፤ ይህም ሆኖ የተናገሩ
ት ይፈጸማል ብለው ይጠብቃሉ። 7እኔ
ሳልናገር፣ ‘*እግዚ አብሔር* እንዲህ ይላል’
ስትሉ ሐሰተኛ ራእይ ማየታችሁ፣
ውሸተኛስ ትንቢት መናገራችሁ
አይደለምን?”
8“ ‘ስለዚህ ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤ “ቃላችሁ ሐሰት፣ ራእያችሁም ውሸት
ስለ ሆነ እኔ በእናንተ ላይ ተነሥቻለሁ፤
ይላል ልዑል *እግዚአብሔር*። 9እጄ የሐ
ሰት ራእይ በሚያዩና በሚያሟርቱ ነቢያት
ላይ ተነሥቶአል። የሕዝቤ ጉባኤ ተካፋይ
አይሆኑም፤ በእስራኤል ቤት መዝገብ አይጻ
ፉም፤ ወደ እስራኤልም ምድር አይገቡም።
በዚያ ጊዜ እኔ ጌታ *እግዚአብሔር* እንደ
ሆንሁ ታውቃላችሁ።
10“ሰላም ሳይኖር፣ ‘ሰላም አለ’
እያሉ
ሕዝቤን ያስታሉ፤ ሕዝቡ ካብ ሲሰራ እነርሱ
በኖራ ይለስናሉ፤ 11ስለዚህ በኖራ ለሚለስኑት
ካቡ እንደሚወድቅ ንገራቸው። ዶፍ ይወ
ርዳል፤ ታላቅ የበረዶ ድንጋይ እሰዳለሁ፤
ዐውሎ ነፋስም ይነሣል። 12እነሆ ካቡ ሲፈ
ርስ ሕዝቡ ‘የለሰናችሁበት ኖራው ወዴት
ሄደ?’ ብለው አይጠይቋችሁምን?”
13“ ‘ስለዚህ ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤ “በመዓቴ ዐውሎ ነፋስ እሰዳለሁ፣
በቍጣዬ የበረዶ ድንጋይ እልካለሁ፤ ዶፍም
ከታላቅ ጥፋት ጋር ይወርዳል። 14በኖራ

12፥27 ሕዝ11፥3፤ ዳን10፥14፤ ማቴ24፥48-50፤ 2ጴጥ3፥4
13፥2 ቍ17፤ ኢሳ9፥15፤ኤር23፥16፤ 28፥15፤37፥19፤ ሕዝ22፥28
13፥3 ኤር23፥25 -32፤ሰቆ2፥14፤ ሆሴ9፥7
13፥5 ኢሳ58፥12፤ ሕዝ7፥19፤22፥30፤ 30፥3
13፥6 ኤር5፥1፤ 14፥14፤23፥16፤ 28፥15፤29፥9፤ ሕዝ12፥24-25፤22፥28
13፥7 ኢሳ30፥10
13፥8 ኤር21፥13
13፥9 ዘፀ6፥2፤ 32፥32፤ዘዳ13፥3፤ ኤር17፥13፤20፥3-6፤ ሕዝ 20፥38
13፥10 ኤር4፥10፤ 23፥13፤50፥6፤ ሕዝ7፥25፤22፥28
13፥11 ኢሱ10፥11፤ ኢዮ38፥23፤ መዝ11፥6፤ሕዝ38፥22
13፥13 ዘፀ9፥25፤ ኢሱ10፥11፤ ኢዮ 14፥19፤38፥23፤ ኢ ሳ30፥30፤ ራእ11፥19፤16፥21
13፥14 ኢሳ22፥5፤ ኤር6፥15፤ሚክ1፥6
13፥16 ኢሳ57፥21፤ ኤር6፥14፤ሕዝ7፥25
13፥17 ቍ2፤ ዘፀ15፥20፤ሕዝ4፥7፤ 25፥2፤28፥21፤ ራእ2፥20
13፥19 ምሳ28፥21፤ ኢሳ56፥11፤ ኤር44፥26፤ ሕዝ20፥39፤22፥26፤ 36፥20፤ 39፥7፤ሚክ3፥11
13፥20 መዝ124፥7
3፥21 መዝ91፥3
13፥22 ኢሳ9፥15፤ ኤር23፥14፤ ሕዝ18፥21፤33፥14-16
13፥23 ነህ6፥12፤ መዝ72፥14፤ ሕዝ12፥24፤ሚክ3፥6
14፥1 ሕዝ8፥1፤ 20፥1
14፥3 ቍ7፤ ኢሳ1፥15፤ሕዝ6፥4፤ 7፥19፤20፥31

የለሰናችሁትን ካብ አፈርሳለሁ፤ መሠረቱም
ተገልጦ እስኪታይ ድረስ ከምድር ጋር
አደባልቀዋለሁ። ቅጥሩ[የ] በሚወድቅበት ጊዜ፣
እናንተም በውስጡ ታልቃላችሁ። በዚያን
ጊዜ እኔ *እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ ታው
ቃላችሁ። 15*መዓቴንም* በቅጥሩና ኖራ
በለሰኑት ሰዎች ላይ እሰዳለሁ፤ እናንተንም
እንዲህ እላችኋለሁ፤ ‘ቅጥሩና ቅጥሩን
በኖራ የለሰኑት የሉም፤ 16ኢየሩሳሌም ትን
ቢት የተናገሩላትና ሰላም ሳይኖር የሰላም
ራእይ ያዩላት የእስራኤል ነቢያት ጠፍ
ተዋል፤ ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*።’ ”
17“አሁንም የሰው ልጅ ሆይ፤ ከራሳቸው
አመንጭተው ትንቢት ወደሚናገሩ ወደ ሕዝ
ብህ ሴቶች ልጆች ፊትህን መልስ፤ ትንቢ
ትም ተናገርባቸው፤ 18እንዲህም በል፤ ‘ጌታ
*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ “የሕዝብን
ነፍስ ለማጥመድ፣ ለአስማታቸው ለእጃቸው
አንጓ ሁሉ አሸንክታብ ለሚያሰፉና፣
የተለያየ መጠን ያለውን የራስ መሸፈኛ
ለሚያበጁ ሴቶች ወዮላቸው! በውኑ የሕ
ዝቤን ነፍስ እያጠመዳችሁ የራሳችሁን
ነፍስ ታድናላ ችሁን? 19ዕፍኝ ለማይሞላ
ገብስና ለቍራሽ እንጀራ ስትሉ ሐሰትን
የሚያደምጥ ሕዝቤን እየዋሻችሁ መሞት የ
ማይገባውን በመግደል፣ መኖር የ
ማይገባውንም በማትረፍ በሕዝቤ መካከል
አርክሳችሁኛል።
20“ ‘ስለዚህ ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤ “እነሆ የሕዝብን ነፍስ እንደ ወፍ
በምታጠምዱበት አሸንክታብ ላይ ተነሥቻ
ለሁ፤ ከክንዳችሁ ላይ እቀዳድደዋለሁ፤ እንደ
ወፍ የምታጠምዱትንም ሕዝብ ነጻ አወጣ
ዋለሁ። 21መሸፈኛችሁን ቀድጄ ሕዝቤን
ከእጃችሁ አድናለሁ፤ ከእንግዲህም ወዲህ
በቍጥጥራችሁ ሥር አይሆኑም፤ በዚያ ጊዜ
እኔ *እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ ታውቃላ
ችሁ። 22እኔ ያላሳዘንሁትን ጻድቅ በውሸት
ስላሳዘናችሁ፣ ኀጢአተኛም ከክፉ መንገዱ
ተመልሶ ሕይወቱን እንዳያድን በኀጢአቱ
ስላበረታታችሁት፣ 23ከእንግዲህ የሐሰት
ራእይ አታዩም፣ ሟርትም አታሟርቱም፤ ሕዝ
ቤን ከእጃችሁ አድናለሁ፤ በዚያ ጊዜ እኔ
*እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ።’
”

## ባዕድ አምልኮ ተከታዮች መወገዛቸው

14 ከእስራኤል ሽማግሌዎች አንዳንዶቹ
ወደ እኔ መጥተው በፊቴ ተቀመጡ።
2*የእግዚአብሔርም* ቃል እንዲህ ሲል ወደ
እኔ መጣ፤ 3“የሰው ልጅ ሆይ፤ እነዚህ ሰዎች
ጣዖቶቻቸውን በልባቸው አኑረዋል፤ ክፉታ
ቸውን እንደ ማሰናከያ ድንጋይ በፊታቸው

[ሠ]3 ወይም *ክፉዎች*
[የ]14 ወይም *ከተማው*

አስቀምጠዋል፤ ታዲያ ከእኔ አንዳች ነገር
እንዲጠይቁ ልፍቀድላቸውን? [4]ስለዚህ እንዲህ
ብለህ ንገራቸው፤ ‘ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤ “ማንኛውም እስራኤላዊ ጣዖትን በልቡ
አኑሮ፣ ክፋቱንም የማሰናከያ ድንጋይ
አድርጎ በፊቱ በማስቀመጥ ወደ ነቢይ ቢ
መጣ፣ እኔ እግዚአብሔር እንደ ጣዖቱ
ብዛት እመልስለታለሁ። [5]በጣዖቶቻቸው
ምክንያት ከእኔ የተለዩትን የእስራኤልን
ቤት ሁሉ ልብ ወደ ራሴ ለመመለስ ይህን
አደርጋለሁ።’

[6]“ስለዚህ ለእስራኤል ቤት እንዲህ በል፤
‘ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ “ንስሓ
ግቡ! ከጣዖቶቻችሁ ተመለሱ፤ ጸያፍ ተግባ
ራችሁንም ሁሉ ተዉ።”

[7]“ ‘ማንኛውም እስራኤላዊ ወይም በእስ
ራኤል የሚኖር ማንኛውም መጻተኛ ራሱን
ከእኔ በመለየት ጣዖቶችን በልቡ አኑሮ፣
ክፋቱንም የማሰናከያ ድንጋይ በማድረግ
በፊቱ አስቀምጦ ከእኔ ለመጠየቅ ወደ ነቢይ
ቢመጣ፣ እኔ ራሴ እግዚአብሔር እመልስለ
ታለሁ። [8]ፊቴን በክፉት ወደዚያ ሰው እመልሳ
ለሁ፤ መቀጣጫና መተረቻ
አደርገዋለሁ፤ ከሕዝቤም መካከል
አስወግደዋለሁ፤ በዚያን ጊዜ እኔ እግዚ
አብሔር እንደ ሆንሁ ታው ቃላችሁ።

[9]“ ‘ነቢዩ ትንቢት ይናገር ዘንድ ቢታለል፣
ያንን ነቢይ ያታለልሁ እኔ እግዚአብሔር
ነኝ፤ ክንዴን በእርሱ ላይ አነሣለሁ፤ ከሕ
ዝቤ ከእስራኤል መካከልም አጠፋዋለሁ።
[10]በደላቸው በራሳቸው ላይ ይሆናል፤ ነቢዩም
እርሱን ሊጠይቀው ከመጣው ሰው ጋር እኩል
በደለኛ ይሆናል። [11]ከእንግዲህ የእስራኤል
ሕዝብ መንገድ ስቶ ከእኔ አይለይም፤ ተመ
ልሶም በኀጢአቱ ሁሉ ራሱን አያረክስም።
እነርሱ ሕዝቤ ይሆናሉ፤ እኔም አምላካቸው
እሆናለሁ፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።”

## የማያመልጡት ፍርድ

[12]የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤ [13]“የሰው ልጅ ሆይ፤ አንድ
አገር በእኔ ባለመታመን ቢበድለኝና እኔም
እጄን በላዩ ዘርግቼ የምግብ ምንጬን
ባደርቅ፣ ራብንም አምጥቼበት ሰውንና
እንስሳቱን ብገድል፣ [14]ኖኅ፣ ዳንኤልና[ዶ] ኢ
ዮብ እነዚህ ሦስቱ በዚያ ቢኖሩ እንኳ፣ በ
ጽድቃቸው የሚያድኑት ራሳቸውን ብቻ
ነው፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።

[15]“የዱር አራዊትንም በአገሪቱ ላይ ሰድጄ
አገሪቱን ሕፃናት አልባ ቢያደርጓትና ከአ
ራዊቱም የተነሣ ምድሪቱ ሰው እስከማያል
ፍባት ባድማ ብትሆን፣ [16]‘እኔ ሕያው እግዚ
አብሔርን!’ በራሴ እምላለሁ ይላል ጌታ እግ

14፥5 ዘጸ32፥15፤ ኤር2፥11፤ሕዝ16፥45፤ ሆሴ5፥7፤ ዘካ11፥8
14፥6 ነህ1፥9፤ ኢሳ2፥20፤30፥22፤ ኤር3፥12፤35፥15
14፥7 ቍ3፤ ዘፍ 25፥22፤ ዘፀ12፥48፤20፥10፤ ኢሳ8፥14፤ ሆሴ4፥5፤5፥5
14፥8 ዘኍ16፥38፤ መዝ102፥8፤ ኤር42፥20፤ ሕዝ5፥15፤15፥7
14፥9 1ነገ22፥23፤ 2ዜና18፥22፤ ኢሳ63፥17፤ኤር4፥10፤ 14፥15፤ዘካ13፥3
14፥11 ኢሳ51፥16፤ ሕዝ11፥19-20፤ 37፥23፤48፥11
14፥13 ዘሌ26፥26፤ ምሳ13፥21፤ ሕዝ5፥16፤6፥14፤15፥8
14፥14 ቍ20፤ ዘፍ6፥8፡9፤ኢዮ1፥1፤ 42፥9፤ኤር15፥1፤ ሕዝ3፥19፤18፥20፤ 28፥3፤ዳን1፥6፤6፥13
14፥15 ዘሌ26፥22፤ ሕዝ5፥17
14፥16 ዘፍ19፥29፤ ሕዝ 18፥20
14፥17 ዘሌ26፥25፤ ኤር25፥27፤42፥16፤ ሕዝ25፥13፤ሶፎ1፥3
14፥19 ኢሳ34፥3፤ ኤር14፥12፤ሕዝ7፥8፤ 38፥22
14፥20 ቍ14
14፥21 ዘኍ33፥4፤ 2ሳሙ24፥13፤ኢሳ 31፥8፤34፥6፤66፥16 ፤ኤር14፥12፤15፥3፤ 27፥8፤ሕዝ5፥17፤ 21፥13፡19፤33፥27፤ አሞ4፥6-10፤ራእ6፥8
14፥22 ኤር41፥16፤ ሕዝ12፥16፤20፥43፤ 31፥16፤32፥31
14፥23 ኤር22፥8-9፤ ሕዝ8፥6-18፤9፥9
15፥2 መዝ80፥8-16፤ ኢሳ5፥1-7፤27፥2-6፤ ኤር2፥21፤ሆሴ10፥1 ፤ዮሐ15፥2
15፥3 ኢሳ22፥23፤ ኤር13፥10
15፥4 ሕዝ17፥3-10፤ 19፥14፤ዮሐ15፥6

ዚአብሔር፤ እነዚህ ሦስቱ ሰዎች ቢኖሩባት
እንኳ፣ ወንዶች ወይም ሴቶች ልጆቻቸውን
ማዳን አይችሉም፤ እነርሱ ብቻ ይድናሉ፤
ምድሪቱ ግን ባድማ ትሆናለች።’

[17]“ሰይፍን በአገሪቱ ላይ አምጥቼ፣ ‘ሰይፍ
በዚህ ምድር ይለፍ’ ብል፣ ሰውንና
እንስሳን ባጠፋ፣ [18]በሕያውነቴ እምላለሁ
ይላል እግዚአብሔር፤ እነዚህ ሦስት ሰዎች
ቢኖሩባትም እንኳ ራሳቸው ብቻ ይድናሉ
እንጂ ወንዶች ወይም ሴቶች ልጆቻቸውን
ማዳን አይች ሉም።

[19]“ቸነፈርንም በምድሪቱ ላይ ብሰድና ደም
በማፍሰስ መዓቴን አውርጄ ሰውንና እንስሳን
ባጠፋ፣ [20]በሕያወነቴ በራሴ እምላለሁ
ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ኖኅ፣ ዳንኤልና
ኢዮብ ቢኖሩባትም እንኳ በጽድቃቸው ራ
ሳቸውን ብቻ ያድናሉ እንጂ ወንዶችን ወይም
ሴቶች ልጆቻቸውን አያድኑም።

[21]“ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፤
‘ሰውንና እንስሳቱን ለማጥፋት አራቱን አስ
ፈሪ ፍርዶቼን፦ ሰይፍን፣ ራብን፣ የዱር
አራዊትንና ቸነፈርን በኢየሩሳሌም ላይ
በማመጣበት ጊዜ ምንኛ የከፋ ይሆን! [22]ነገር
ግን ከዚያ ወጥተው የሚተርፉ ወንዶችና
ሴቶች ልጆች አሉ፤ እነርሱም ወደ እናንተ
ይመጣሉ፤ እናንተም አካሄዳቸውንና ተግባ
ራቸውን በምታዩበት ጊዜ በኢየሩሳሌም
ላይ ስላመጣሁት መከራ፣ ስላደረስሁባትም
አስከፊ ነገር ሁሉ ትጽናናላችሁ። [23]አካሄዳ
ቸውንና ተግባራቸውን በምታዩበት ጊዜ፣
ትጽናናላችሁ፤ አንዳች ነገር በከንቱ እንዳላ
ደረገሁ ትረዳላችሁና፤ ይላል ጌታ እግዚአ
ብሔር።’ ”

## የማይረባው የወይን ግንድ

**15** የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤ [2]“የሰው ልጅ ሆይ፤
የወይን ግንድ በዱር ካሉት ዛፎች ሁሉ
ቅርንጫፍ የሚሻለው በምንድን ነው? [3]የሚጠ
ቅም ነገር ለመሥራት ከግንዱ አንዳች
ተወስዶ ያውቃልን? ዕቃ የሚንጠለጠ
ልበትስ ኵላብ ከእርሱ ይበጃልን? [4]እንዲነድ
እሳት ላይ ከተጣለ በኋላ፣ እሳቱ ጫፍና
ጫፉን አቃጥሎ፣ መኻሉን ከለበለበው፣
ለአንዳች ነገር ይጠቅማልን? [5]እንግዲህ ደኅና
ሆኖ ሳለ ለምንም ነገር ካልጠቀመ፣ እሳት
ካቃጠለውና ከለበለበው በኋላ የቱን ያህል
የሚረባ ይሆን!

[6]“ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤ ከዱር ዛፎች መካከል የወይን ግንድ

[ዶ]14 ወይም ዳኔል፤ የዕብራይስጡን ቃል አጻጻፍ ስንመለከት ነቢዩ ዳንኤልን ሳይሆን ሌላን ሰው የሚያመለክት ነው፤ እንዲሁም ቍ20

እንዲነድ ለእሳት አሳልፌ እንደ ሰጠሁ፣
እንዲሁ የኢየሩሳሌምን ነዋሪዎች አሳልፌ
እሰጣለሁ። 7ፊቴን በክፋት ወደ እነርሱ
እመልሳለሁ፤ ከእሳት ቢያመልጡም፣ ገና
እሳት ይበላቸዋል። ፊቴን በክፋት ወደ
እነርሱ በመለስሁ ጊዜ፣ እኔ *እግዚአብሔር*
እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ። 8*ታማኝ ካለመ
ሆናችሁ የተነሣ ምድሪቱን ባድማ አደርጋ
ታለሁ፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።*"

## ኢየሩሳሌም ታማኝ ስላለመሆኗ የተሰጠ ተራዛሚ ተለዋጭ ዘይቤ

16 *የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ *መጣ*፤ 2"የሰው ልጅ ሆይ፤
ለኢየሩሳሌም አስጸያፊ ተግባሯን ፊት ለፊት
ንገራት፤ 3እንዲህም በል፤ 'ልዑል *እግዚ
አብሔር* ኢየሩሳሌምን እንዲህ ይላታል፤
"ዘርሽና ትውልድሽ ከከነዓን ምድር ነው፤
አባትሽ አሞራዊ፣ እናትሽም ኬጢያዊት
ነበሩ። 4በተወለድሽበት ቀን እትብትሽ አልተ
ቈረጠም፤ ንጹሕ እንድትሆኚ በውሃ
አልታጠብሽም፤ በጨው አልታሸሽም፤ በጨ
ርቅም አልተጠቀለልሽም። 5በርኅራኄ ዐይን
ተመልክቶሽ ወይም አዝኖልሽ ከእነዚህ አን
ዱን እንኳ ያደረገልሽ ሰው አልነበረም፤
ይል ቁንም በተወለድሽበት ቀን ተንቀሽ
ስለ ነበር ሜዳ ላይ ተጣልሽ።

6" 'እኔም በዚያ ሳልፍ፣ በደምሽ ውስጥ
ወዲያ ወዲህ ስትንፈራገጪ አየሁሽ፤ በደም
ሽም ውስጥ ተኝተሽ ሳለሽ፣ "በሕይወት
ኑሪ!"[ጀ] አልሁሽ። 7ሜዳ ላይ እንዳለ
ቡቃያ አሳደግሁሽ፤ አንቺም አደግሽ፤
ብርቅ ዕንቍ ሆንሽ[ገ]። ጡቶችሽ አጐጠ
ጐጡ፤ ጠጕርሽም
አደገ፤ ነገር ግን ከእናትሽ ማሕፀን እንደ
ወጣሽ ዕርቃንሽን ነበርሽ።

8"*ዳግመኛም* በአጠገብሽ በማልፍበት ጊዜ
ወደ አንቺ ተመለከትሁ፤ ለመፈቀርም እንደ
ደረስሽ ባየሁ ጊዜ፣ የመጐናጸፊያዬን ዘርፍ
በላይሽ ዘርግቼ ዕርቃንሽን ሸፈንሁ። ማልሁ
ልሽ፤ ከአንቺም ጋር ቃል ኪዳን ተጋባሁ፤
ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*፤ አንቺም የእኔ
ሆንሽ።

9"በውሃ አጥቤ[ጠ] ከደም አጠራሁሽ፤ ዘይትም
ቀባሁሽ። 10ወርቀ ዘቦ አለበስሁሽ፤ ምርጥ
ቈዳ ጫማም አደረግሁልሽ፤ ያማረ በፍታ
አለበ ስሁሽ ውድ መደረቢያም አጐና
ጸፍሁሽ።
11በጌጣጌጥ አንቈጠቈጥሁሽ፤ በእጅሽ አን
ባር፣ በዐንገትሽም ድሪ አጠለቅሁልሽ፤
12በአፍንጫሽ ቀለበት፣ በጆሮሽ ጉትቻ፣ በራ
ስሽም ላይ ውብ አክሊል አደረግሁልሽ፤
13በወርቅና በብር አጌጥሽ፤ ልብስሽም ያማረ
በፍታ፣ ሐርና ወርቀ ዘቦ ነበር፤ ምግብሽም
የላመ ዱቄት፣ ማርና የወይራ ዘይት ነበር።
እጅግ ውብ ሆንሽ፤ ንግሥት ለመሆንም
በቃሽ። 14እኔ ከሰጠሁሽ ሞገስ የተነሣ ውበ
ትሽ ፍጹም በመሆኑ ዝናሽ በአሕዛብ
መካከል ገነነ፤ ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*።

15" '*ነገር ግን በውበትሽ ተመካሽ*፤ ዝናሽ
ንም ለአመንዝራነት ተጠቀምሽበት፤ ከዐላፊ
አግዳሚው ጋር ያለገደብ አመነዘርሽ ውበት
ሽም ለማንም ሆነ።[ጨ] 16ከልብስሽ አንዳንዱን
ወስደሽ የምታመነዝሪበትን መስገጃ ስፍራ
አስጌጥሽበት፤ እንዲህ ዐይነት ነገር ከዚህ
ቀደም አልታየም፤ ወደፊትም አይኖርም።
17ከሰጠሁሽ ወርቄና ብሬ የተሠራውን ምርጥ
ጌጣጌጥ ወስደሽ የወንድ ምስሎች ለራስሽ
አበጀሽ፤ ከእነርሱም ጋር ዝሙት ፈጸምሽ።
18ወርቀዘቦ ልብስሽን ወስደሽ ደረብሽላቸው፤
ዘይቴንና ዕጣኔንም በፊታቸው አቀረብሽ።
19እንድትበዪ የሰጠሁሽን ምግብ ይኸውም
ምርጡን ዱቄት፣ ማሩንና የወይራ ዘይቱን
መልካም መዐዛ ያለው ዕጣን አድርገሽ አቀረ
ብሽላቸው፤ እንዲህ ያለ ነገር ተፈጽሞአል፤
ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*።

20" 'ለእኔ የወለድሻቸውን ወንዶችና
ሴቶች ልጆችሽን እንዲበሏቸው ለምስሎቹ
ሠዋሽላ ቸው፤ አመንዝራነትሽ አንሶ ነውን?
21ልጆ ቼን ዐርደሽ ለጣዖት መሥዋዕት
አድርገሽ አቀረ ብሻቸው።[ጸ] 22በእነዚህ አስ
ጸያፊ ተግባ ሮችሽና አመንዝራነትሽ ሁሉ፣
ከእናትሽ ማሕፀን እንደ ወጣሽ ዕርቃንሽን
ሆነሽ በደ ምሽ ውስጥ ስትንፈራገጪ
የነበርሽበት የሕፃንነትሽ ወራት ትዝም
አላለሽ!።

23" 'ወዮ! ወዮልሽ! ይላል ጌታ *እግዚአ
ብሔር*፤ ከሌላው ክፋትሽ ሁሉ በተጨ
ማሪ፣ 24ለራስሽ ጕብታን አበጀሽ፤ በየአደ
ባባዩም የማምለኪያ ኰረብታ ሠራሽ።
25በየመንገዱ መጠምዘዣ ላይም የመስገጃ
ኰረብታ አበጀሽ፤ ገላሽን ለዐላፊ አግዳሚው
በማቅረብና አመንዝራነትሽን በማበራከት
ውበትሽንም አረከስሽ። 26ዘማውያን ከሆኑ
ግብፃውያን ጎረቤቶችሽ ጋር አመነዘርሽ፤
ገደብ በሌለው የዝሙት ተግባርሽም ለቍጣ
አነሣሣሽኝ። 27ስለዚህ ክንዴን በአንቺ ላይ

**15፥7** ዘሌ26፥17፤ መዝ34፥16፤ ኢሳ24፥18፤ ሕዝ5፥2፡4፤14፥8፤ አሞ9፥1-4
**15፥8** ሕዝ14፥13፤ 17፥20፤18፥24
**16፥2** ኢሳ57፥12፤ ሕዝ8፥17፤20፥4፤ 22፥2፤23፥36
**16፥3** ቍ45፤ ዘፍ10፥15፤ 11፥25-29፤12፥18፤ 15፥16፤ዘዳ7፥1፤ ኢሱ24፥14-15፤ ሕዝ21፥30
**16፥4** ሆሴ2፥3
**16፥6** ቍ22፤ ዘፀ19፥4፤ ሕዝ18፥23፡32
**16፥7** ዘፀ1፥7፤ ዘዳ1፥10
**16፥8** ቍ59፤ ሩት3፥9፤ኤር2፥2፤ 11፥10፤ሆሴ2፥7፡ 19-20፤ሚል2፥14
**16፥9** ሩት3፥3
**16፥10** ቍ18፤ ዘፀ26፥36፤ኢሳ3፥23፤ 19፥9፤ሕዝ27፥16
**16፥11** ዘፍ41፥42፤ መዝ73፥6፤ኢሳ3፥19፤ ኤር4፥30፤ ሕዝ23፥40፡42
**16፥12** ዘፍ35፥4፤ ምሳ1፥9፤ኢሳ3፥19፡ 21፤28፥5፤ ኤር13፥18
**16፥13** ዘዳ32፥13 -14፤1ሳሙ10፥1፤ 1ነገ4፥21፤አስ2፥9፡ 17፤5፥1
**16፥14** 1ነገ10፥24፤ አስ1፥11፤መዝ48፥2፤ ሰቆ2፥15፤ሕዝ5፥5
**16፥15** ቍ25፤ ኢሳ57፥8፤ኤር2፥20፤ ሕዝ 23፥3፤27፥3
**16፥16** 2ነገ23፥7፤ ኢሳ57፥7
**16፥17** ሕዝ7፥20፤ ሆሴ2፥13
**16፥18** ኤር44፥5
**16፥19** ሆሴ2፥8
**16፥20** ዘፀ13፥2፤ መዝ106፥37-38፤ ኢሳ57፥5፤ኤር7፥31፤ ሕዝ23፥37
**16፥21** 2ነገ17፥17፤ ኤር19፥5፤
**16፥22** ቍ6፤ መዝ25፥7፤88፥15፤ ኤር2፥2፤ሆሴ2፥3፡15፤ 11፥1
**16፥23** ሕዝ24፥6
**16፥24** ቍ31፤ መዝ78፥58፤ ኢሳ57፥7፤ኤር2፥20፤ 3፥2፤44፥21፤ ሕዝ20፥28
**16፥25** ቍ15፤ ምሳ9፥14፤ኤር3፥2
**16፥26** 1ነገ14፥9፤ ኢሳ23፥17፤57፥8፤ ኤር3፥1፤11፥15፤ ሕዝ8፥17፤20፥8፤ 23፥19-21 **16፥27** 2ዜና28፥18፤ ኤር34፥20፤ ሕዝ20፥33፤25፥13

[ጀ]6 ጥቂት የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆች ሰብዓ ሊቃናትና ሱርስቱ እንዲሁ ሲሆኑ አብዛኞዎቹ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆች ግን *"በሕይወት ኑሪ!" በደምሽ ውስጥ ተኝተሽ ሳለሽ "በሕይወት ኑሪ!" አልሁሽ* ይላል
[ገ]7 ወይም *የበሰልሽ ሆንሽ*
[ጠ]9 ወይም *በውሃ አጠብሁሽ*
[ጨ]15 ከአብዛኞዎቹ የጥንት የዕብራይስጥ ቅጆች ጋር ተመሳሳይ ሲሆን አንድ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጅ ግን (አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት የጥንት ቅጆችን ይመ) *ከዐላፊ አግዳሚ ...አመነዘርሽ፤ እንዲህ ያለው ነገር መሆን የለበትም* ይላል
[ጸ]21 ወይም *በእሳት ውስጥ አሳለፉችኋቸው*

አንሥቼ ድርጎሽን ቀነስሁ፤ ከክፉ መንገድ
ሽም የተነሣ በብልግናሽ ለሚያፍሩ ጠላቶ
ችሽ ለፍልስጥኤማውያን ሴቶች ልጆች
አሳልፌ ሰጠሁሽ፡፡ [28]ገና ስላልረካሽም ከአሦ
ራውያን ጋር ደግሞ አመነዘርሽ፤ ከዚያም
በኋላ እንኳ አልረካሽም፡፡ [29]ርኵሰትሽንም
እስከ ነጋዴዎች ምድር እስከ ባቢሎን[ጸ] ድረስ
አበዛሽ፤ ያም ሆኖ አልረካሽም፡፡

[30]“ ‘እንደ ዐይን አውጣ አመንዝራ ይህን
ሁሉ መፈጸምሽ ምን ዐይነት ደካማ ልብ
ቢኖርሽ ነው! ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*፡፡
[31]በየመንገዱ መጠምዘዣ ላይ ጕብታሽን
ባበጀሽና በየአደባባዩም መስገጃ ኰረብታ
በሠራሽ ጊዜ እንደማንኛውም ዝሙት አዳሪ
አልነበርሽም፤ ምክንያቱም ዋጋ አላስከፈ
ልሽም፡፡

[32]“ ‘አንቺ ከገዛ ባሏ ይልቅ ሌሎችን የም
ታስተናግድ አመንዝራ ነሽ! [33]ማንኛዋም አመ
ንዝራ ሴት ዋጋ ይከፈላታል፤ አንቺ ግን
ለወዳጆችሽ ሁሉ ስጦታ ታበረክቻለሽ፤ ከየ
አቅጣጫው መጥተው ከአንቺ ጋር ያመነ
ዝሩ ዘንድ እጅ መንሻ ታቀርቢላቸዋለሽ፡፡
[34]ስለዚህ ያንቺ ግልሙትና ከሌሎቹ የተለየ
ነው፤ ማመንዘር የሚሻ ማንም ሰው፣
አንቺን አሳዶ ማግባባት አያስፈልገውም፡፡
ዋጋ ትከፍያለሽ እንጂ አይከፈልሽም፤ አንቺ
የሌሎች ፍጹም ተቃራኒ ነሽ፡፡

[35]“ ‘አንቺ አመንዝራ ሆይ፤ እንግዲህ የእ
ግዚአብሔርን ቃል ስሚ! [36]ጌታ *እግዚ
አብሔር* እንዲህ ይላል፤ ሀብትሽን[ፀ] ስላፈሰ
ስሽ፣ ከወዳጆችሽ ጋር ያለ ገደብ ስላመነዘ
ርሽና ዕርቃንሽን ስለ ገለጥሽ፣ ስለ አስጸያ
ፊዎቹ ጣዖቶችሽ ሁሉና ለእነርሱም የልጆች
ሽን ደም ስላቀረብሽ፣ [37]በዚህ ምክንያት
ደስ የተሰኘሽባቸውን ወዳጆችሽን፣ የወደድ
ሻቸውንና የጠላሻቸውን ሁሉ እሰበስባለሁ፤
ከየአቅጣጫው ሁሉ በዙሪያሽ እሰበስባቸዋ
ለሁ፤ በፊታቸው ዕርቃንሽን እገልጣለሁ፤
እነርሱም ኀፍረተ ሥጋሽን ሁሉ ያያሉ፡፡
[38]ለአመንዝራና ለነፍሰ ገዳይ ሴቶች የሚገባ
ውን ፍርድ እፈርድብሻለሁ፤ በመዓቴና በቅ
ናቴ እስከ ደም እበቀልሻለሁ፡፡ [39]ለወዳጆችሽ
አሳልፌ እሰጥሻለሁ፤ እነርሱም ጕብታሽንና
የማምለኪያ ኰረብታሽን ያፈርሳሉ፤ ልብስሽን
ይገፉሻል፤ ምርጥ ጌጣጌጥሽን ይቀሙሻል፤
ዕርቃንሽንና ባዶ እጅሽን ያስቀሩሻል፡፡
[40]ሕዝብ ያነሣሡብሻል፤ በድንጋይ ይወግሩሻል፤
በሰይፍ ይቈራርጡሻል፤ [41]ቤቶችሽን ያቃጥ
ላሉ፤ በብዙ ሴቶችም ፊት ቅጣት ያመጡ
ብሻል፡፡ ግልሙትናሽን አስተውሻለሁ፤ ከእንግ
ዲህም ለወዳጆችሽ ዋጋ አትከፍዪም፡፡ [42]በዚ
ህም በአንቺ ላይ የነበረው ቍጣዬ ይበርዳል፤
የቅናቴ ቍጣም ከአንቺ ይርቃል፡፡ እኔም
ዝም እላለሁ፤ ከእንግዲህም አልቈጣም፡፡

[43]“ ‘በእነዚህ ነገሮች አስቈጣሽኝ እንጂ
የልጅነትሽን ወራት አላሰብሽም፤ ስለዚህ የሥ
ራሽን እከፍልሻለሁ፤ ይላል ጌታ *እግዚአ
ብሔር*፡፡ በሌላው አስጸያፊ ተግባርሽ ሁሉ
ላይ ዘማዊነትን አልጨመርሽምን?

[44]“ ‘በምሳሌ የሚናገር ሁሉ፣ “ሴት ልጅ
በእናቷ ትወጣለች” እያለ ይመስልብሻል፡፡
[45]አንቺ ባሏንና ልጆቿን የምትጸየፍ የእ
ናትሽ ልጅ ነሽ፤ ባሎቻቸውንና ልጆቻቸውን
የሚጸየፉ የእኅቶችሽ እኅት ነሽ፡፡ እናታችሁ
ኬጢያዊት፣ አባታችሁም አሞራዊ ነበሩ፡፡
[46]ታላቂቱ እኅትሽ ከአንቺ በስተ ሰሜን
ከሴት ልጆቿ ጋር የምትኖረው ሰማርያ ናት፤
ታናሺቱ እኅትሽም ከአንቺ በስተ ደቡብ
ከሴት ልጆቿ ጋር የምትኖረው ሰዶም ናት፡፡
[47]አንቺም በእነርሱ መንገድ መሄድና አስ
ጸያፊ ተግባራቸውን መከተል ብቻ ሳይሆን፣
ከእነርሱ ይልቅ ፈጥነሽ ምግባረ ብልሹ
ሆንሽ፡፡ [48]እኔ ሕያው እግዚአብሔርን! በራሴ
እምላለሁ ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*፤ አን
ቺና ሴት ልጆችሽ ያደረጋችሁትን እኅትሽ
ሰዶምና ልጆቿ እንኳ አላደረጉትም፡፡

[49]“ ‘እነሆ የእኅትሽ የሰዶም ኀጢአት ይህ
ነበር፤ እርሷና ሴት ልጆቿ እብሪተኞች፣
ጥጋበኞችና ደንታ ቢሶች ነበሩ፤ ድኾችንና
ችግረኞችንም አይረዱም ነበር፡፡ [50]ኵራተ
ኞች ነበሩ፤ በፊቴ አስጸያፊ ተግባር መፈ
ጸማቸውን ባየሁ ጊዜም አስወገድኋቸው፡፡
[51]ሰማርያ አንቺ ያደረግሽውን ኀጢአት ግማ
ሹን እንኳ አልሠራችም፡፡ አንቺ ግን
ከእነርሱ የባሰ አስጸያፊ ተግባር በመፈ
ጸምሽ፣ በዚህ ሁሉ እኅቶችሽን ጻድቃን
አስመሰልሻቸው፡፡ [52]እኅቶችሽን እንደ
ጻድቃን በማስቈጠርሽ፣
ዕፍረትሽን ተከናነቢ፤ ኀጢአትሽ ከኀጢአ
ታቸው የከፋ ስለ ሆነ፣ እነርሱ ከአንቺ ይልቅ
ጻድቃን ሆኑ፡፡ እንግዲህ እኅቶችሽን ጻድቃን
ስላስመሰልሻቸው፣ አንቺ ተዋረጂ፤ ዕፍረት
ሽንም ተከናነቢ፡፡

[53]“ ‘ነገር ግን የሰዶምንና የሴት ልጆቿን፣
እንዲሁም የሰማርያንና የሴት ልጆቿን ምርኮ
እመልሳለሁ፤ የአንቺንም ምርኮ የእነርሱን
በምመልስበት ጊዜ እመልሳለሁ፡፡ [54]ይህም
የሚሆነው ለእነርሱ መጽናኛ በመሆንሽ እንድ
ትዋረጂና ባደረግሽው ሁሉ እንድታፍሪ ነው፡፡
[55]እኅቶችሽ ሰዶምና ሴት ልጆቿ እንዲሁም
ሰማርያና ሴት ልጆቿ ቀድሞ ወደ ነበሩበት
ሁኔታ ይመለሳሉ፤ አንቺና ሴት ልጆችሽም
ቀድሞ ወደ ነበራችሁበት ሁኔታ ትመለሳላ

16፥28 2ነገ16፥7፤
ኢሳ57፥8
16፥29 ኤር3፥1፤
ሕዝ23፥14-17፤
ናሆ3፥4
16፥30 ኤር3፥3
16፥31 ቍ24
16፥33 ዘፍ30፥15፤
ኢሳ30፥6፤57፥9፤
ሆሴ8፥9-10
16፥36 ኤር19፥5፤
ሕዝ23፥10
16፥37 ኢሳ47፥3፤
ኤር13፥22፤
ሕዝ23፥22፤ሆሴ2፥3፡
10፤8፥10፤ራእ17፥16
16፥38 ዘፍ38፥24፤
ዘሌ20፥10
16፥39 2ነገ18፥11፤
ሕዝ21፥31፤ሆሴ2፥3
16፥40 ዮሐ8፥5፡7
16፥41 ዘዳ13፥16፤
ኤር19፥13፤
ሕዝ22፥15፤23፥10፤
23፥27፡48
16፥42 2ሳሙ24፥25፤
ኢሳ40፥1-2፤54፥9፤
ሕዝ5፥13፤39፥29
16፥43 ዘፀ15፥24፤
መዝ78፥42፤
ሕዝ11፥21፤22፥31
16፥44 መዝ49፥4
16፥45 ቍ3፤
ኤር44፥19፤ሕዝ14፥5፤
23፥2
16፥46 ዘፍ13፥10
-13፤ኤር3፥7፡8-11፤
ሕዝ23፥4፤ራእ11፥8
16፥47 ሕዝ5፥7
16፥48 ዘፍ15፥2፤
19፥25፤ማቴ10፥15፤
11፥23፡24
16፥49 ዘፍ13፥13፤
19፥9፤መዝ138፥6፤
ኢሳ1፥10፤22፥13፤
ኤር5፥28፤ሕዝ18፥7፡
12፡16፤28፥2፤
አሞ6፥4-6፤
ሉቃ12፥16-20፤
16፥19፤ያዕ5፥5
16፥50 ዘፍ18፥20
-21፤19፥5፤
መዝ18፥27
16፥51 ኤር3፥8-11፤
ሕዝ5፥6-7፤23፥11
16፥52 ኤር3፥11፤
ሕዝ23፥35
16፥53 ዘዳ30፥3፤
ኢሳ19፥24-25፤
ኤር 48፥47፤
ሕዝ39፥25
16፥54 ኤር2፥26
16፥55 ሕዝ36፥11፤
ሚል3፥4

[ጸ]29 ወይም *ካላዲያ*
[ፀ]36 ወይም *ምኞትሽን*

ችሁ:: 56በታበይሽበት ወቅት የእኅትሽን
የሰዶምን ስም ለመጥራት እንኳ ፈቃደኛ
አልነበርሽም፤ 57ይህም ኀጢአትሽ ከመገለጡ
በፊት ነበር:: አሁን ግን በዙሪያሽ ሆነው
ለሚንቁሽ ለኤዶም[ፊ] ሴት ልጆችና ለጎረቤ
ቶቿ ሁሉ፣ እንዲሁም ለፍልስጥኤም ሴት
ልጆች መሣለቂያ ሆነሻል:: 58ለብልግናሽና
ለአስጸያፊ ተግባርሽ የሚገባውን ቅጣት ትሸ
ከሚያለሽ፤ ይላል እግዚአብሔር::
59“ ‘ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
ቃል ኪዳኔን በማፍረስ መሐላዬን ንቀሻልና
ተገቢውን ቅጣት ከእኔ ዘንድ ትቀበ
ያለሽ:: 60ነገር ግን በልጅነትሽ ጊዜ ከአንቺ
ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳን አስባለሁ፤ ለዘላ
ለምም የሚኖር ቃል ኪዳን ከአንቺ ጋር
እመሠርታለሁ:: 61ከአንቺ ታላላቅ የሆኑትንና
ታናናሽ የሆኑትን እኅቶችሽን ስትቀበዪ፣
አካሄ ድሽን ታስቢአለሽ፤ ታፍሪአለሽም::
ሴት ልጆች እንዲሆኑሽም እነርሱን ለአንቺ
እሰጣለሁ፤ ከአንቺ ጋር በገባሁት ቃል ኪዳን
መሠረት ግን አይደለም:: 62ስለዚህ ከአንቺ
ጋር ቃል ኪዳኔን ዐድሳለሁ፤ በዚያ ጊዜ
እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቂአ
ለሽ:: 63ያደረግሽውን ሁሉ ይቅር ባልሁሽ
ጊዜ፣ በደልሽ ትዝ ሲልሽ ታፍሪያለሽ፤
ከውርደትሽም የተነሣ አፍሽን ከቶ አትከ
ፍቺም፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር::’ ”

### የንስሮቹና የወይኑ ምሳሌ

17 የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤ 2“የሰው ልጅ ሆይ፤
እንቆቅልሽ አቅርብ፤ ለእስራኤልም ቤት በተም
ሳሌት ተናገር፤ 3እንዲህም በል፤ ‘ጌታ እግዚ
አብሔር እንዲህ ይላል፤ ትልቅ ክንፍና
ረጅም ማርገብገቢያ ያለው እንዲሁም አካሉ
በላባ የተሸፈነ መልኩ ዥጕርጕር የሆነ
ታላቅ ንስር ወደ ሊባኖስ መጥቶ የዝግባ
ዛፍ ጫፍ ያዘ፤ 4ከጫፉም የላይኛውን ቀንበጥ
ቀንጥቦ ወደ ነጋዴዎች ምድር ወሰደ፤
በሸቀጥ ነጋዴዎችም ከተማ ተከለው::
5“ ‘ከዚህ በኋላ ከምድሪቱ ዘር ወስዶ
በመልካም ዐፈር አኖረው፤ ውሃ እንደ
ልብ ባለበት ቦታ አጠገብ እንደ አኻያ
ዛፍ ተከለው፤ 6በበቀለም ጊዜ አጭርና ወደ
ጐን የተንሰራፋ የወይን ተክል ሆነ፤ ቅርን
ጫፎቹም ወደ እርሱ አቅጣጫ ዐደጉ፤
ሥሮቹ ግን እዚያው ከበታቹ ቀሩ:: ስለዚህ
የወይን ተክል ሆነ፤ ቅርንጫፎችን አወጣ፤
ለምለም ቅጠሎችንም አበቀለ::
7“ ‘ደግሞም ትልቅ ክንፍ ያለውና አካሉ
በላባ የተሸፈነ ሌላ ታላቅ ንስር ነበር:: ያ
የወይን ተክልም ውሃ ለማግኘት ከተተከለ
በት ቦታ ሥሩን ወደ እርሱ ሰደደ፤ ቅርን
ጫፉንም ወደ እርሱ ዘረጋ:: 8ቅርንጫፍ
እንዲያወጣ፣ ፍሬ እንዲያፈራና ያማረ
የወይን ተክል እንዲሆን በአጠገቡ ብዙ ውሃ
ባለበት በመልካም መሬት ተተክሎ ነበር::”
9“እንዲህም በላቸው፣ ‘ጌታ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤ ያድግ ይሆን? ይጠወልግ
ዘንድ ሥሩ ተነቅሎ ፍሬው አይረግፍምን?
ቀንበጡም ሁሉ ይደርቃል:: ከሥሩ ለመን
ቀል ብርቱ ክንድና የብዙ ሰው ጕልበት
አያስፈልገውም:: 10በሌላ ስፍራ ቢተከልስ
ይጸድቅ ይሆን? የምሥራቅ ነፋስ ሲመታውስ
ባደገበት ስፍራ ፈጽሞ አይደርቅምን?’ ”
11የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ
እኔ መጣ፤ 12“ለዚህ ዐመፀኛ ቤት እንዲህ
በል፤ ‘የእነዚህ ነገሮች ትርጕም ምን እንደ
ሆነ አታውቁምን?’ እንዲህ በላቸው፤ ‘የባቢ
ሎን ንጉሥ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ፤ ንጉሥዋ
ንና መሳፍንቷን ማረከ፤ ወደ ባቢሎንም
ይዞአቸው ተመለሰ:: 13ከንጉሣውያን ቤተ
ሰብ አንዱን ወስዶ ከእርሱ ጋር ውል
አደረገ፤ በመሐላም ቃል አስገባው፤ የምድሪ
ቱንም ታላ ላቅ ሰዎች ማርኮ ወሰደ፤ 14ይኸ
ውም የምድሪቱ መንግሥት ተዋርዳ የእር
ሱን ውል በመጠበቅ ብቻ እንድትኖር እንጂ
፣ ዳግመኛ እንዳታንሰራራ ለማድረግ
ነበር:: 15ንጉሡ ግን በእርሱ ላይ ዐመፀ፤
ፈረሶችና ብዙ ሰራዊት ለማግኘት
መልእክተኞችን ወደ ግብፅ ላከ፤ ይሳካለት
ይሆን? እንዲህ
ዐይነቱን ነገር የፈጸመ ያመልጣልን? ውል
ያፈረሰስ ሳይቀጣ ይቀራልን?
16“ ‘በሕያውነቴ እምላለሁ! ይላል ልዑል
እግዚአብሔር፤ መሐላውን ባቀለለበት፣ ውሉን
ባፈረሰበት፣ በዙፋኑም ላይ ባስቀመጠው
ንጉሥ ምድር በባቢሎን ይሞታል:: 17በባቢ
ሎናውያን ብዙ ሕይወት ለማጥፋት በከተ
ማዋ ዙሪያ ዐፈር በሚደለድሉበትና
ምሽግ በሚሠሩበት ጊዜ፣ ፈርዖን ከኀያል
ሰራዊቱና ከብዙ ጭፍሮቹ ጋር በጦርነት
ሊረዳው አይችልም:: 18ያደረገውን መሐላ
በማቃለልና እጁን ያስገባበትን ውል በማፍ
ረስ ይህን ሁሉ ስለ ፈጸመ ከቅጣት አያ
መልጥም::
19“ ‘ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤ በሕያወነቴ እምላለሁ! ያቃለለውን
መሐላዬንና ያፈረሰ ውን ኪዳኔን በራሱ ላይ
አመጣለሁ:: 20መረቤን በላዩ እዘረጋለሁ፤
በወጥመዴም ይያዛል:: ወደ ባቢሎን
እወስደዋለሁ፤ በእኔ ላይ ስላመፀም በዚያ
እፈርድበታለሁ:: 21የሚሸሸው ወታደሩ

16፥57 2ነገ16፥6፤ መዝ137፥3
16፥58 ሕዝ23፥49
16፥59 ቍ8፤ ሕዝ17፥19
16፥60 ዘፍ6፥18፤ 9፥15፡16፤መዝ25፥7 ፤ኤር2፥2፤ሕዝ37፥36
16፥62 ዘዳ29፥14፤ ኤር24፥7፤ሕዝ20፥ 37፡43-44፤34፥25፤ 37፥26፤ሆሴ2፥19 -20
16፥63 መዝ39፥9፤ 65፥3፤78፥38፤79፥9 ፤ሕዝ36፥31-32፤ ዳን 9፥7-8፤ ሮሜ3፥19
17፥2 መሳ14፥2፤ ሕዝ20፥49
17፥3 ዘዳ28፥49፤ ኤር22፥23፤49፥22፤ ዳን7፥4፤ሆሴ8፥1
17፥4 ኢሳ10፥33
17፥5 ዘዳ8፥7-9፤ መዝ1፥3፤ኢሳ44፥4፤ ሕዝ31፥5
17፥6 ኢዮ5፥3፤ ኢሳ18፥5
17፥7 ሕዝ31፥4
17፥8 ኢዮ18፥19፤ ሚል4፥1
17፥9 ኤር42፥10፤ አሞ2፥9
17፥10 ኢዮ1፥19፤ ሕ ዝ15፥4፤ሆሴ12፥1፤ 13፥15
17፥12 ዘዳ21፥10፤ 2ነገ24፥15፤ 2ዜና36፥10፤ ሕዝ12፥9፤24፥19
17፥13 ዘፀ23፥32፤ 2ዜና36፥13፤ ኢሳ3፥2፤ኤር37፥1
17፥14 ሕዝ29፥14
17፥15 ዘዳ17፥16፤ መዝ56፥7፤ ኢሳ30፥2፡5፤ኤር34፥3፤ 37፥5፤38፥18፤52፥3 ፤ሕዝ29፥16
17፥16 2ነገ24፥17፤ ኤር52፥11፤ ሕዝ12፥13
17፥17 ኢሳ36፥6፤ ኤር37፥5፡7፤ ሕዝ4፥2፤29፥6-7
17፥18 2ነገ10፥15፤ 1ዜና29፥24
17፥19 ኤር7፥9፤ ሕዝ16፥59፤21፥23፤ ሆሴ10፥4
17፥20 ኤር2፥35፤ ሕዝ12፥13፤15፥8
17፥21 ዘሌ26፥33፤ 2ነገ25፥5፡11፤ ኤር27፥8፤ ሕዝ12፥14፤ዘካ2፥6

[ፊ]57 ከብዙዎቹ የዕብራይስጥና የሱርስት የጥንት ቅጆች ጋር ተመሳሳይ ሲሆን አብዛኛ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ ሰብዓ ሊቃናትና ቩልጌት ግን አራም ይላሉ

ሁሉ በሰይፍ ይወድቃል፤ የተረፉ ትም
ወደ ነፋስ ይበተናሉ፤ እኔ እግዚአ ብሔር
እንደ ተናገርሁ ታውቃላችሁ።
22“ ‘ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“ከረጅሙ ዝግባ ጫፍ እኔው ራሴ ቀን
በጡን ወስጄ እተክለዋለሁ፤ ከቀንበጦቹ
ጫፍ አንዱን ቀንጥሼ ከሁሉ ከፍ ባለው
ተራራ ላይ እተክለዋለሁ። 23ከፍ ባለው
የእስራኤል ተራራ ላይ እተክለዋለሁ፤ ቅርን
ጫፎች ያወጣል፤ ፍሬ ያፈራል፤ ያማረም
ዝግባ ይሆናል። የወፍ ዐይነት ሁሉ መኖ
ሪያውን በዚያ ያደርጋል፤ በቅርንጫፎቹም
ጥላ ሥር ያርፋል። 24የዱር ዛፎች ሁሉ
ረጅሙን ዛፍ፣ ዝቅ ዝቅ ያለውንም ዛፍ
ከፍ የማደርግ እኔ እግዚአብሔር እንደ
ሆንሁ ያውቃሉ፤ የለመለመውን ዛፍ አደ
ርቃለሁ፤ ደረቁንም አለመልማለሁ።”
“ ‘እኔ እግዚአብሔር ተናግሬአለሁ፤ እኔው
አደርገዋለሁ።’ ”

## ኀጢአት የምትሠራ ነፍስ ትሞታለች

**18** የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤ 2“ስለ እስራኤል
ምድር፣
“ ‘አባቶች ጐምዛዛ የወይን ፍሬ በሉ፤
የልጆችንም ጥርስ አጠረሰ’ እያላችሁ የም
ትመስሉት ተምሳሌት ምን ለማለት ነው?
3“በሕያውነቴ እምላለሁ! ይላል ልዑል እግዚ
አብሔር፤ ከእንግዲህ ይህን ምሳሌ በእስራ
ኤል ምድር አትመስሉም። 4እነሆ ነፍስ
ሁሉ የእኔ ናት፤ የአባት ነፍስ የእኔ እንደ
ሆነች ሁሉ የልጁም ነፍስ የእኔ ናት፤ ኀጢ
አት የምትሠራ ነፍስ እርሷ ትሞታለች።
5“በቅንነትና በትክክል የሚሠራ፣
ጻድቅ ሰው ቢገኝ፣
6በኰረብታ ባሉ አብያተ ጣዖት የቀረበውን
አይበላም፤
በእስራኤል ቤት ወዳሉት ጣዖታት
አይመለከትም
የባልንጀራውን ሚስት አያባልግም፤
ከሴት ጋር በወር አበባዋ ጊዜ
አይተኛም።
7ማንንም አይጨቍንም፤
ነገር ግን በመያዣ የወሰደውን እንኳ
ለተበዳሪው ይመልሳል፤
ለተራብ የራሱን እንጀራ፣
ለተራቈተም ልብስ ይሰጣል እንጂ፣
በጕልበት አይቀማም።
8በዐራጣ አያበድርም፣
ከፍተኛ ወለድም አይቀበልም[T]።
እጁን ከበደል ይሰበስባል፤
በሰውና በሰው መካከል በትክክል
ይፈርዳል።
9ሥርዐቴን ይከተላል፤
ሕጌንም በቅንነት ይጠብቃል።
ይህ ሰው ጻድቅ ነው፤
ፈጽሞ በሕይወት ይኖራል፤
ይላል ጌታ እግዚአብሔር።
10“ነገር ግን ይህ ሰው ደም የሚያፈስ
ወይም ከሚከተሉት ኀጢአቶች ማንኛው
ንም[υ] የሚፈጽም ዐመፀኛ ልጅ ቢኖረው፣
11አባትየው አንዱንም ባያደርግ፣
“ልጁ ግን በኰረብታ መስገጃ የቀረበውን
ቢበላ፣
የባልንጀራውን ሚስት ቢያባልግ፣
12ድኻውንና ችግረኛውን ቢጨቍን፣
በጕልበት ቢቀማ፣
በመያዣነት የወሰደውን ባይመልስ፣
ወደ ጣዖታት ቢመለከት፣
አስጸያፊ ተግባራትን ቢፈጽም፣
13በዐራጣ ቢያበድር፤
ከፍተኛ ወለድም ቢቀበል፣
እንዲህ ዐይነቱ ሰው በሕይወት ይኖራልን?
ከቶ አይኖርም! እነዚህን አስጸያፊ ነገሮች
አድርጓልና በእርግጥ ይሞታል፤ ደሙም
በገዛ ራሱ ላይ ይሆናል።
14“ይህም ልጅ ደግሞ በተራው ልጅ ቢወ
ልድና ልጁም አባቱ ያደረገውን ኀጢአት
ሁሉ አይቶ ባይፈጽም፣ ይኸውም፦
15በኰረብታ መስገጃ የቀረበውን ባይበላ፣
በእስራኤል ቤት ወዳሉት ጣዖታት
ባይመለከት፣
የባልንጀራውን ሚስት ባያባልግ፣
16ሰውን ባይጨቍን፣
ብድር ለመስጠት መያዣ ባይጠይቅ፣
በጕልበቱ ባይቀማ፣
ነገር ግን ምግቡን ለተራብ፣
ልብሱን ለተራቈተ ቢሰጥ፣
17እጁን ደኻን ከመበደል ቢሰበስብ፣
ዐራጣ ወይም ከፍተኛ ወለድ ባይቀበል፣
ሕጌን ቢጠብቅ፣ ሥርዐቴንም ቢከተል፣
በሕይወት ይኖራል እንጂ በአባቱ ኀጢአት
አይሞትም። 18አባቱ ግን የሰውን መብት
ስለ ደፈረ፣ ወንድሙን በጕልበት ስለ ቀማና
በሕዝቡ መካከል የማይገባውን ስላደረገ በገዛ
ኀጢአቱ ይሞታል።
19“እናንተ ግን፣ ‘ልጅ ስለ አባቱ ኀጢአት
ለምን አይቀጣም?’ ትላላችሁ። ልጁ
ቀናና ትክክለኛውን ነገር ስላደረገ፣ ሥርዐ
ቴንም ሁሉ በጥንቃቄ ስለ ጠበቀ በሕ
ይወት ይኖ

17፥22 ቍ23፤ 2ነገ19፥30፤ኢሳ2፥2፤ 4፥2፤ኤር23፥5፤ ሕዝ 20፥40፤36፥1፤ 37፥22፤40፥2፤ 43፥12
17፥23 ቍ22፤ መዝ92፥12፤ኢሳ 2፥2፤27፥6፤ኤር 31፥12፤ሕዝ31፥6፤ ዳን4፥12፤ሆሴ14፥5-7፤ ማቴ13፥32
17፥24 ዘኍ17፥8፤ 1ሳሙ2፥7-8፤ መዝ52፥5፤96፥12፤ ኢሳ2፥13፤27፥6፤ ዳን5፥21፤ሕዝ19፥12፤ 21፥26፤22፥14፤ 37፥13፤አሞ9፥11
18፥2 ኢዮ21፥19፤ ኢሳ3፥15፤ኤር31፥29
18፥3 መዝ49፥4
18፥4 ቍ20፤ ዘፍ18፥23፤ዘፀ17፥14፤ 2ነገ14፥6፤ኢዮ21፥20፤ ምሳ13፥21፤ ኢሳ42፥5፤ሕዝ33፥8፤ ሮሜ6፥23
18፥6 ዘሌ12፥2፤ 15፥24፤ዘዳ4፥19፤ ሕዝ6፥2፡13፤20፥24፤ አሞ5፥26
18፥7 ዘፀ20፥15፤ 22፥21፡26፤ ዘዳ15፥11፤ኢዮ22፥7፤ ሕዝ16፥49፤ሚል3፥5፤ ማቴ25፥36፤ ሉቃ3፥11፤ያዕ5፥4
18፥8 ዘፀ18፥21፤ 22፥25፤ዘሌ25፥35 -37፤ዘዳ23፥19-20፤ ኤር22፥3፤ዘካ8፥16
18፥9 ዘሌ18፥5፤ 19፥37፤ሕዝ11፥12፤ 20፥11፤አሞ5፥4፤ ዕን2፥4
18፥10 ዘፀ21፥12፤ ሕዝ22፥6
18፥11 ሕዝ22፥9
18፥12 ዘፀ22፥22፡ 27፤2ነገ21፥11፤ ኢዮ24፥9፤ኢሳ 59፥6-7፤ኤር22፥17፤ ሕዝ16፥49፤አሞ4፥1፤ ዕን2፥6
18፥13 ዘፀ22፥25፤ ዘሌ20፥9፤ሕዝ33፥4 -5፤ሆሴ12፥14
18፥14 2ዜና34፥21፤ ምሳ23፥24
18፥15 መዝ24፥4፤ ሕዝ22፥9
18፥16 ዘፀ22፥27፤ መዝ41፥1፤ኢ ሳ58፥7፡ 10፤ሕ ዝ16፥49
18፥17 መዝ1፥2
18፥19 ዘፀ20፥5፤ ዘዳ5፥9፤ኤር15፥4፤ ዘካ1፥3-6

[T]8 ወይም *ወለድ አይወስድም፤* እንዲሁም በቍ13 እና 17
[υ]10 ወይም *ማናቸውንም በወንድሙ ላይ*

ራል:: 20መሞት የሚገባት ኀጢአት የሠራ
ችው ነፍስ ናት:: ልጅ በአባቱ ኀጢአት
አይቀጣም፤ አባትም በልጁ ኀጢአት አይቀ
ጣም:: ጻድቁ የጽድቁን ፍሬ ያገኛል፤ ኀጢ
አተኛውም የኀጢአቱን ዋጋ ይቀበላል::
21"ኀጢአተኛ ከሠራው ኀጢአት ሁሉ ተመ
ልሶ ሥርዐቴን ሁሉ ቢጠብቅ፣ ቀናና ትክክ
ለኛውን ነገር ቢያደርግ ፈጽሞ በሕይወት
ይኖራል እንጂ አይሞትም:: 22በደሉ ሁሉ
አይታሰብበትም፤ በጽድቅ መንገድ ሄዶአልና
በሕይወት ይኖራል:: 23በውኑ ኀጢአተኛ
ሲሞት ደስ ይለኛልን? ይላል ጌታ እግዚ
አብሔር፡ ይልቁን ከመንገዱ ተመልሶ በሕ
ይወት ሲኖር ደስ አይለኝምን?
24"ጻድቅ ሰው ግን ከጽድቁ ተመልሶ
ኀጢአት ቢሠራ፣ ኀጢአተኛው የሚያደርገ
ውንም አስጸያፊ ነገር ቢፈጽም፤ ይህ ሰው
በውኑ በሕይወት ይኖራልን? ከሠራው
ጽድቅ አንዱም አይታሰብለትም፤ ታማኝ
ባለመሆኑና ከፈጸመው ኀጢአት የተነሣ
ይሞታል::
25"እናንተ ግን፣ 'የጌታ መንገድ ቀና
አይደለችም' ትላላችሁ:: የእስራኤል ቤት
ሆይ፤ ስማ፤ መንገዴ ቀና አይደለችምን? ቀና
ያልሆነውስ የእናንተ መንገድ አይደለምን?
26ጻድቅ ከጽድቁ ተመልሶ ኀጢአት ቢሠራ
በኀጢአቱ ይሞታል፤ ከፈጸመውም በደል
የተነሣ በሕይወት አይኖርም:: 27ኀጢአተኛው
ግን ከክፉ ሥራው ተመልሶ በታማኝነትና
በቅንነት ቢኖር ሕይወቱን ያድናል:: 28የፈ
ጸመውን በደል ሁሉ ተገንዝቦ ካደረገው
ክፋት ሁሉ ስለ ተመለሰ፣ ፈጽሞ በሕይወት
ይኖራል እንጂ አይሞትም:: 29የእስራኤል
ቤት ግን፣ 'የጌታ መንገድ ቀና
አይደለችም' ይላል:: የእስራኤል ቤት ሆይ!
መንገዴ ቀና አይደለችምን? ቀና
ያልሆነችውስ የእናንተ መንገድ
አይደለችምን?
30"የእስራኤል ቤት ሆይ፤ ስለዚህ እንደየ
ሥራችሁ በእያንዳንዳችሁ ላይ እፈርዳለሁ፤
ይላል ጌታ እግዚአብሔር፡ እንግዲህ ንስሓ
ግቡ! በኀጢአት እንዳትጠፉ፣ ከኀጢአታችሁ
ሁሉ ተመለሱ:: 31በእኔ ላይ የፈጸማችሁትን
በደል ሁሉ ወደ ኋላ ጣሉት፤ አዲስ ልብና
አዲስ መንፈስ ይኑራችሁ:: የእስራኤል ቤት
ሆይ፤ ለምን ትሞታላችሁ? 32ማንም እንዲሞት
አልሻምና፣ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ወደ
እኔ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ!

### ስለ እስራኤል መሳፍንት የወጣ ሙሾ

19 "ስለ እስራኤል መሳፍንት ሙሾ
አውጣ፤ 2እንዲህም በል፤

18፥20 ዘኍ15፥31፤
ዘዳ24፥16፤1ነገ8፥32፤
2ነገ14፥6፤ኢሳ3፥11፤
ሕዝ7፥27፤14፥14፤
ማቴ16፥27፤ዮሐ9፥2
18፥21 ዘፍ26፥5፤
ኤር18፥8፤
ሕዝ13፥22፤36፥27
18፥22 መዝ18፥20
-24፤ኢሳ43፥25፤
ዳን4፥27፤ሚክ7፥19
18፥23 ኢዮ37፥23፤
መዝ147፥11፤
ሰቆ3፥33፤ሕዝ16፥6፤
ሚክ7፥18፤1ጢሞ2፥4
18፥24 1ሳሙ15፥11፤
2ዜና24፥17-20፤
ኢዮ35፥8፤ምሳ21፥16፤
ኤር34፥16፤ሕዝ3፥20፤
20፥27፤2ጴጥ2፥20-22
18፥25 ዘፍ18፥25፤
ኤር2፥29፤12፥1፤
ሕዝ33፥17፤ሶፎ3፥5፤
ሚል2፥17፤3፥13-15
18፥27 ኢሳ1፥18፤
ሕዝ13፥22
18፥28 ኢሳ55፥7
18፥30 ኢሳ1፥27፤
ኤር35፥15፤ሕዝ7፥3፤
24፥14፤33፥20፤
ሆሴ12፥6፤ማቴ3፥2፤
1ጴጥ1፥17
18፥31 መሳ6፥8፤
መዝ51፥10፤
ኢሳ1፥16-17፤
ኤር27፥13፤
ሕዝ11፥19፤36፥26
18፥32 2ዜና7፥14፤
ኢዮ22፥23፤37፥23፤
ኢሳ55፥7፤ሕዝ16፥6፤
ሚል3፥7
19፥1 ቍ14፤2ነገ
24፥6፤ኤር7፥29፤9፥10
፡20፤ሕዝ26፥17፤
27፥2፡32፤28፥12፤
32፥2፡16፤አሞ5፥1
19፥2 ዘፍ49፥9፤
ዘኍ23፥24
19፥4 2ነገ23፥33
-34፤2ዜና36፥4፤
ኢዮ41፥2፤ሰቆ4፥20
19፥5 ዘፍ49፥9፤
2ነገ23፥34
19፥6 2ነገ24፥9፤
2ዜና36፥9
19፥7 ሕዝ29፥10፤
30፥12
19፥8 2ነገ24፥2፡
11፤ሰቆ4፥20፤
ሕዝ12፥13
19፥9 2ነገ19፥28፤
24፥15፤25፥7፤
2ዜና36፥6፤ዘካ11፥3
19፥10 ዘፍ49፥22፤
መዝ80፥8-11፤
ኤር17፥8
19፥11 ሕዝ31፥3፤
ዳን4፥11
19፥12 ዘፍ41፥6፤
ዘዳ29፥28፤ኢሳ27፥11፤
ሕዝ17፥24፤
28፥17፤ሆሴ13፥15

" 'እናትህ በአንበሶች መካከል እንዴት
  ያለች አንበሳ ነበረች!
በደቦል አንበሶች መካከል ተጋደመች፤
  ግልገሎቿንም በዚያ አሳደገች::
3ከግልገሎቿ መካከል አንዱን አሳደገችው፤
  እርሱም ብርቱ አንበሳ ሆነ::
ግዳይ መንጠቅን ተማረ፤
  ሰዎችንም በላ::
4አሕዛብም ስለ እርሱ ሰሙ፤
  በጒድጓዳቸውም ገብቶ ተያዘ፤
እነርሱም በስናግ ጐትተው፣
  ወደ ግብፅ ምድር ወሰዱት::

5" 'ተስፋዋ መጨናገፉን፣
  የጠበቀችውም አለመሳካቱን ባየች ጊዜ፣
ከግልገሎቿ ሌላውን ወስዳ፣
  ብርቱ አንበሳ አድርጋ አሳደገችው::
6እርሱም በአንበሶች መካከል ተጐማለለ፤
  እየበረታም ሄደ፤
ግዳይ መንጠቅን ተማረ
  ሰዎችንም በላ::
7ምሽጎቻቸውን አወደመ፤[ሰ]
  ከተሞቻቸውንም ባድማ አደረገ፤
ምድሪቷና በውስጧ ያሉት ሁሉ፣
  ከግሣቱ የተነሣ ተንቀጠቀጡ::
8በዙሪያው ያሉ አሕዛብ ተነሡበት፤
  ከየአገሩም ሁሉ ተሰበሰቡበት፤
መረባቸውን ዘረጉበት፤
  በጒድጓዳቸውም ገብቶ ተያዘ::
9በስናግም በመጐተት ቀፎ ውስጥ ከተው፣
  ወደ ባቢሎን ንጉሥ አመጡት፤
ድምፁ በእስራኤል ተራሮች ላይ፣
    ዳግመኛ እንዳይሰማ፣
  በእስር ቤት አኖሩት::

10" 'እናትህ በውሃ አጠገብ የተተከለ፣
  በዕርሻ ውስጥ ያለ፣[ሐ]
ከውሃም ብዛት የተነሣ፣
  ያፈራና የተንሰራፋ የወይን ተክል
    መሰለች::
11ቅርንጫፎቿ ለበትረ መንግሥት
    የሚሆኑ፣ ጠንካሮች ነበሩ፤
ጥቅጥቅ ባሉ ቅጠሎች መካከል፣
  በቁመቷና በብዙ ቅርንጫፎቿ፣
  ዘለግ ብላ፣ ጐልታ ትታይ ነበር::
12ነገር ግን በቍጣ ተነቀለች፤
  ወደ ምድርም ተጣለች::
የምሥራቅ ነፋስ አደረቃት፤
  ፍሬዎቿንም አረገፈባት::
ብርቱዎቹ ቅርንጫፎቿ ክው አሉ፤

[ሰ]7 ከታርጒም (ሰብዐ ሊቃናት ይመ) ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፣ ዕብራይስጡ ግን *ምሽጎቻቸውን ያውቃል* ይላል
[ሐ]10 ከሁለት የጥንት የዕብራይስጥ ቅጆች ጋር ተመሳሳይ ሲሆን አብዛኞዎቹ የጥንት ቅጆች ግን *ያንተ ደም* ይላሉ

እሳትም በላቸው።
[13]አሁን ውሃ በተጠማ ደረቅ ምድር፣
በበረሓ ውስጥ ተተክላለች።
[14]ከዋና ቅርንጫፎቿ[መ] ከአንዱ እሳት ወጣ፤
ፍሬዋንም በላ።
በትረ መንግሥት የሚሆን፣
አንድም ጠንካራ ቅርንጫፍ አልተረፈም።’

ይህ ሙሾ ነው፤ ለሐዘን እንጕርጕሮም ይሆ
ናል።”

## ዐመፀኛዪቱ እስራኤል

20 በሰባተኛው ዓመት፣ በአምስተኛው
ወር፣ ከወሩም በዐሥረኛው ቀን
ከእስራኤል ሽማግሌዎች አንዳንዶቹ የእግዚ
አብሔርን ሐሳብ ሊጠይቁ መጡ፤ በፊቴም
ተቀመጡ።
[2]የእግዚአብሔርም ቃል እንዲህ ሲል ወደ
እኔ መጣ፤ [3]“የሰው ልጅ ሆይ፤ ለእስራኤል
ሽማግሌዎች እንዲህ ብለህ ንገራቸው፤ ‘ጌታ
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ “ሐሳቤን ልትጠ
ይቁ መጣችሁን? በሕያውነቴ እምላለሁ! ከእኔ
ጠይቃችሁ እንድትረዱ አልፈቅድም”፤ ይላል
ጌታ እግዚአብሔር።’
[4]“የሰው ልጅ ሆይ፤ እነዚህን ለፍርድ
ታቀርባቸዋለህን? በውኑ ለፍርድ ታቀርባቸ
ዋለህን? የቀድሞ አባቶቻቸውን አስጸያፊ
ተግባር ግለጽላቸው፤ [5]እንዲህም በላቸው፤
‘ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ “እስ
ራኤልን በመረጥሁበት ቀን፣ ለያዕቆብ ቤት
ዘር እጄን አንሥቼ ማልሁላቸው፤ በግብፅም
ራሴን ገለጥሁላቸው። እጄንም አንሥቼ፣
‘እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ’
አልኋቸው። [6]በዚያን ቀን፣ ከግብፅ
አውጥቻቸው ከምድር ሁሉ ይልቅ ውብ ወደ
ሆነችው፣ ማርና ወተት ወደምታፈስሰው፣
ወዳዘጋጀሁላቸውም ምድር እንደማስገባቸው
ማልሁላቸው።” [7]እኔም፣ “እያንዳንዳችሁ ዐ
ይኖቻችሁን ያሳረፋችሁባቸውን ርኩስ
ምስሎች አስወግዱ፤ በግብፅ ጣዖታትም ራ
ሳችሁን አታርክሱ፤ እኔ እግዚአብሔር
አምላካችሁ ነኝ” አልኋቸው።
[8]“ ‘እነርሱ ግን በእኔ ላይ ዐመፁ፤ ሊሰ
ሙኝም አልፈለጉም፤ ዐይኖቻቸውን ያሳረፉ
ባቸውን ርኩስ ምስሎች አላስወገዱም፤ የግ
ብፅንም ጣዖታት አልተዉም። እኔም በዚ
ያው በግብፅ ምድር መዓቴን በላያቸው
ላፈስ፣ ቍጣዬንም ላወርድባቸው ወስኜ
ነበር። [9]ነገር ግን በመካከላቸው በኖሩባቸ
ውና እስራኤልን ከግብፅ ምድር ለመታደግ
ቃል ስገባ፣ በእነርሱ ዘንድ በተገለጥሁት
በአሕዛብ ፊት ስሜ እንዳይረክስ ስለ
ስሜ ክብር ተቈጠብሁ። [10]ስለዚህ ከግብፅ
አውጥቼ ወደ ምድረ በዳ አመጣኋቸው።
[11]ሰው ቢጠብቀው ኖሮ በሕይወት የሚኖር
በትን ሥርዐቴን ሰጠኋቸው፤ ሕጌንም አስ
ታወቅኋቸው። [12]ደግሞም እኔ እግዚአብሔር
እንደ ቀደስኋቸው ያውቁ ዘንድ፣ በእኔና
በእነርሱ መካከልም ምልክት እንዲሆን ሰን
በቴን ሰጠኋቸው።
[13]“ ‘ነገር ግን የእስራኤል ሕዝብ በምድረ
በዳ ዐመፀብኝ፤ ሰው ቢጠብቀው በሕይወት
የሚኖርበትን ሥርዐቴን አልጠበቁም፤ ሕጌ
ንም ተላለፉ፤ ሰንበቴንም ፈጽሞ አረከሱ።
እኔም መዓቴን ላፈስባቸው፣ በምድረ በዳም
ላጠፋቸው ወስኜ ነበር። [14]ነገር ግን ከመ
ካከላቸው ሳወጣቸው ባዩ አሕዛብ ፊት
ስሜ እንዳይረክስ ስለ ስሜ ተቈጠብሁ።
[15]ደግሞም ከምድር ሁሉ ይልቅ ውብ ወደ
ሆነችው፣ ማርና ወተት ወደምታፈሰው፣
ወደ ሰጠኋቸውም ምድር እንደማላስገባቸው
እጆቼን አንሥቼ በምድረ በዳ በፊታቸው
ማልሁ፤ [16]ምክንያቱም ሕጎቼን ተላልፈዋል፤
ሥርዐቴን አልጠበቁም፤ ሰንበቴንም አርክሰ
ዋል፤ ልባቸው ከጣዖቶቻቸው ጋር ተጣብቆ
አልና። [17]እኔ ግን በርኅራኄ ተመለከትኋቸው
እንጂ አላጠፋኋቸውም፤ በምድረ በዳም አል
ፈጀኋቸውም። [18]ለልጆቻቸው በምድረ በዳ
እንዲህ አልኋቸው፤ “የአባቶቻችሁን ሥርዐት
አትከተሉ፤ ወጋቸውን አትጠብቁ፤ ራሳችሁ
ንም በጣዖቶቻቸው አታርክሱ። [19]እኔ እግዚ
አብሔር አምላካችሁ ነኝ፤ ሥርዐቴን
ተከተሉ፤
ሕጌንም ለመጠበቅ ትጉ። [20]በእኔና በእናንተ
መካከል ምልክት ይሆን ዘንድ ሰንበቴን
የተቀደሰ ቀን አድርጉት፤ እኔ እግዚአ
ብሔር አምላካችሁ እንደ ሆንሁም ታውቃ
ላችሁ።”
[21]“ ‘ልጆቻቸው ግን በእኔ ላይ ዐመፁ፤ ሰው
ቢጠብቀው በሕይወት የሚኖርበትን ሥርዐ
ቴን አልተከተሉም፤ ሕጌን ለመጠበቅ አል
ተጉም፤ ሰንበቴንም አረከሱ። እኔም በምድረ
በዳ መዓቴን አፈስባቸዋለሁ፤ ቍጣዬንም
አወርድባቸዋለሁ ብዬ ነበር። [22]ነገር ግን
ከግብፅ ሳወጣቸው ባዩ አሕዛብ ፊት ስሜ
እንዳይረክስ እጄን ሰበሰብሁ። [23]ደግሞም
በአሕዛብ መካከል እንደምበትናቸውና ወደ
ተለያዩ አገሮች እንደማፈልሳቸው በምድረ
በዳ እጄን አንሥቼ በፊታቸው ማልሁ፤
[24]ምክንያቱም ሥርዐቴን አቃለሉ፤ ሰንበቴን
አረከሱ እንጂ ሕጌን አልጠበቁም፤ ዐይናቸ
ውም ከአባቶቻቸው ጣዖታት ጋር ተጣብቆ
አል። [25]እኔም መልካም ላልሆነ ሥርዐትና
በሕይወት ለማይኖሩበት ሕግ አሳልፌ ሰጠ

19፥13 ሕዝ20፥35፤ ሆሴ2፥3፡14
19፥14 ቍ1፤ ሕዝ 15፥4፤20፥47
20፥1 ዘፍ25፥22፤ ሕዝ1፥1-2፤8፥1፤ 21፥1
20፥3 ዘፍ25፥22፤ 1ሳሙ28፥6፤ ኢሳ1፥15፤ ሕዝ7፥26፤14፥3፤ አሞ8፥12፤ሚክ3፥7
20፥4 ሕዝ16፥2፤ 22፥2፤ማቴ23፥32
20፥5 ዘፍ14፥22፤ ዘሌ11፥44፤ ዘኍ14፥30፤ዘዳ7፥6
20፥6 ዘፀ3፥8፤6፥8፤ ዘዳ8፥7፤ዳን8፥9፤ 11፥41፤ሚል3፥12
20፥7 ዘፀ20፥2፡4፤ ዘሌ18፥3፤ዘዳ29፥18፤ ሕዝ6፥9
20፥8 ዘፀ32፥7፤ ዘዳ 9፥7፤ ኢሳ63፥10፤ኤር7፥26፤ 11፥10፤ሕዝ7፥8፤ 16፥26
20፥9 ኢሳ48፥11፤ ሕዝ36፥22፤39፥7
20፥10 ዘፀ13፥18፤ 19፥1
20፥11 ዘፀ20፥1-23፤ ዘሌ18፥5፤ ዘዳ4፥7-8፤ሕዝ18፥9፤ ሮሜ10፥5
20፥12 ዘፀ20፥10፤ 31፥13፤ዘሌ20፥8፤ ኤር17፥22
20፥13 ቍ24፤ ዘፀ32፥10፤ዘሌ26፥15፡ 43፤ዘኍ14፥29፤ ዘዳ9፥8፤መዝ78፥40፤ 95፥8-10፤ኢሳ56፥6፤ ኤር6፥19፤11፥8
20፥14 ኢሳ48፥11፤ ሕዝ36፥23
20፥15 ዘኍ14፥22 -23፤ዘዳ1፥34፤ መዝ95፥11፤106፥26፤ ዕን3፥11
20፥16 ቍ24፤ ዘኍ15፥39፤ ኤር11፥8፤ሕዝ6፥4፤ አሞ2፥4፤5፥26
20፥17 ኤር4፥27
20፥18 2ዜና30፥7፤ መዝ106፥39፤ ዘካ 1፥4
20፥19 ዘፀ20፥2፤ ዘዳ5፥32-33፤6፥1-2፤ 8፥1፤11፥1፤12፥1
20፥20 ዘፀ20፥10፤ 31፥13፤ኤር17፥22
20፥21 ዘኍ25፥3፤ ኤር7፥26፤ሕዝ7፥8
20፥22 መዝ78፥38፤ ኢሳ48፥11
20፥23 ዘሌ26፥33፤ መዝ9፥11
20፥24 ቍ13፡16፤ ሕዝ2፥3፤6፥9፤18፥6፤ አሞ2፥4 20፥25 መዝ81፥12፤ ኢሳ66፥4፤ሮሜ1፥28፤ 2ተሰ2፥11

[መ]14 ወይም *ከዋና ቅርንጫፎቿ ሥር*

ኋቸው፤ 26እኔ *እግዚአብሔር* እንደሆንሁ
እንዲያውቁ፣ አስደነግጣቸውም ዘንድ በእ
ሳት በሚያቀርቡት የበኵር ልጅ *መሥዋዕት*
እንዲረክሱ አደረግኋቸው፡፡’[ሠ]
27“ስለዚህ የሰው ልጅ ሆይ፤ ለእስራ
ኤል
ሕዝብ እንዲህ ብለህ ተናገር፤ ‘ጌታ *እግዚ
አብሔር* እንዲህ ይላል፤ “አባቶቻችሁ እኔን
በመተው በዚህ ደግሞ አቃለሉኝ፤ 28ልሰጣ
ቸው ወደ ማልሁላቸው ምድር ባስገባኋቸው
ጊዜ፣ ከፍ ያለውን ኰረብታ ሁሉና የለመለ
መውን ዛፍ ሁሉ ተመለከቱ፤ በዚያም *መሥ
ዋዕታቸውን* ሠዉ፤ ቍርባናቸውን በማ
ቅረብ ቍጣዬን አነሣሡ፤ *መልካም መዐዛ*
ያለውን ዕጣናቸውን ዐጠኑ፤ የመጠጥ ቍር
ባናቸውንም አፈሰሱ፡፡” 29እኔም፣ “የምትሄ
ዱበት ይህ ከፍታ ቦታ ምንድን ነው?”
አልኋቸው፡፡’ እስከ ዛሬም ድረስ ስሙ ባማ[ረ]
ተብሎ ይጠራል፡፡

## ቅጣትና ምሕረት

30“ስለዚህ ለእስራኤል ቤት እንዲህ በል፤
‘ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ “አባ
ቶቻችሁ እንዳደረጉት ራሳችሁን ታረክሳላ
ችሁን? በረከሱ ምስሎቻቸው ምኞት
ትቃጠላላችሁን? 31ቍርባናችሁን በምታቀር
ቡበት ጊዜ ልጆቻችሁን ለእሳት በመዳረግ[ሰ]
እስከ ዛሬ ድረስ በጣዖቶቻችሁ ሁሉ እየረ
ከሳችሁ ናችሁ፡፡ የእስራኤል ቤት ሆይ፤
ታዲያ የእኔን ሐሳብ እንድትጠይቁ ልፍቀ
ድላችሁን? በሕያውነቴ እምላለሁ! እንድትጠ
ይቁኝ አልፈቅድም፤ ይላል ጌታ *እግዚአ
ብሔር*፡፡”
32“‘እናንተም፣ “ለዕንጨትና ለድንጋይ
እንደሚሰግዱ እንደ አሕዛብ፣ በዓለምም
እንደሚኖረው ሕዝብ ሁሉ እንሁን” አላችሁ፤
ነገር ግን በልባችሁ ያሰባችሁት ከቶ አይሆ
ንላችሁም፡፡ 33በሕያውነቴ እምላለሁ ይላል
ጌታ *እግዚአብሔር*፤ በብርቱ ክንድና በተዘ
ረጋች እጅ መዓትንም በማፍሰስ በላያችሁ
እነግሣለሁ፡፡ 34ከአሕዛብ መካከል አወጣች
ኋለሁ፤ በብርቱ ክንድና በተዘረጋች እጅ፣
መዓትንም በማፍሰስ ከተበተናችሁባቸውም
አገሮች ሁሉ እሰበስባችኋለሁ፡፡ 35ወደ አሕ
ዛብ ምድረ በዳ አመጣችኋለሁ፤ በዚያም
ፊት ለፊት ከእናንተ ጋር እፋረዳለሁ፡፡
36በግብፅ ምድረ በዳ ከአባቶቻችሁ ጋር
እንደ ተፋረድሁ፣ ከእናንተም ጋር እፋረ
ዳለሁ ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*፡ 37ከበትሬ
በታች አሳልፋችኋለሁ፤ ከቃል ኪዳኔም
ጋር አጣብቃችኋለሁ፡፡ 38በእኔ ላይ ያመፁ
ትንና የበደሉኝን ከመካከላችሁ አስወግዳለሁ፤
ከሚኖሩበት አገር አወጣቸዋለሁ፤ ወደ እስ
ራኤል ምድር ግን አይገቡም፤ በዚያን ጊዜ
እኔ *እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ፡፡
39“‘የእስራኤል ቤት ሆይ፤ ስለ እናንተ
ግን ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ “የ
ማ ትሰሙኝ ከሆነ፣ እያንዳንዳችሁ ሂዱና
ለጣዖታቶቻችሁ ስገዱ! ነገር ግን በቍርባና
ችሁና በጣዖቶቻችሁ ቅዱሱን ስሜን ከእንግ
ዲህ አታረክሱም፡፡ 40በቅዱሱ ተራራዬ፣
ከፍ ባለው የእስራኤል ተራራ ላይ በዚያ
ምድር የእስራኤል ቤት ሁሉ ያመልከኛልና፤
ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*፤ እኔም በዚያ
እቀበላቸዋለሁ፡፡ ቍርባናችሁንና በኵራታ
ችሁን ከተቀደሱ መሥዋዕቶቻችሁ ሁሉ ጋር
በዚያ እሻለሁ፡፡ 41ከሕዝቦች መካከል ባወጣ
ኋችሁ ጊዜ፣ ከተበተናችሁባቸውም አገሮች
በሰበሰብኋችሁ ጊዜ፣ መልካም መዐዛ እንዳ
ለው ዕጣን እቀበላችኋለሁ፤ በእናንተም
መካከል ቅዱስ መሆኔን በአሕዛብ ፊት
እገልጣለሁ፡፡ 42ለአባቶቻችሁ ልሰጥ እጄን
አንሥቼ ወደማልሁላቸው ምድር ወደ እስ
ራኤል አገር በማስገባችሁ ጊዜ፣ እኔ *እግዚ
አብሔር* እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ፡፡ 43በዚ
ያም መንገዳችሁንና ራሳችሁን ያረከሳችሁበ
ትን ተግባር ሁሉ ታስታውሳላችሁ፤ በፈ
ጸማችሁትም ክፋት ሁሉ ራሳችሁን ትጸ
የፋላችሁ፡፡ 44የእስራኤል ቤት ሆይ፤
እንደ ክፉ መንገዳችሁና እንደ ብልሹ ተግባ
ራችሁ ሳይሆን፣ ስለ ስሜ ስል በምጐበ
ኛችሁ ጊዜ እኔ *እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ
ታውቃላችሁ፤ ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*፡፡’ ”

## በደቡቡ አገር ላይ የተነገረ ትንቢት

45*የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል ወደ
እኔ መጣ፤ 46“የሰው ልጅ ሆይ፤ ፊትህን ወደ
ደቡብ አዙር፤ በደቡብ ላይ ቃል ተናገር፤
በደቡብ አገር ደን ላይም ትንቢት ተን
ብይ፡፡ 47ለደቡቡ ደን እንዲህ በል፤ ‘*የእግዚ
አብሔርን* ቃል ስማ፤ ጌታ *እግዚአብሔር*
እንዲህ ይላል፤ “በአንተ ላይ እሳት ልለኵስ
ነው፤ እሳቱ የለመለመውንና የደረቀውን
ዛፍህን ሁሉ ይበላል፤ የሚንቦገቦገው ነበልባ
ሉም አይጠፋም፤ ከደቡብ እስከ ሰሜን
ያለውን ፊት ሁሉ ይለበልባል፡፡ 48ሰው
ሁሉ እኔ *እግዚአብሔር* እንዳነደድሁት ያያል፤
የሚያጠፋውም የለም፡፡’ ”
49እኔም፤ “ጌታ *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ወዮ!
እነርሱ ስለ እኔ፣ ‘ተምሳሌት ብቻ ይመስላል’
ይሉኛል” አልሁ፡፡

20፥26 ዘሌ18፥21፤ 20፥2-5፤2ነገ17፥17
20፥27 ዘኍ15፥30፤ መዝ78፥57፤ ሕዝ 18፥24፤ሮሜ2፥24
20፥28 ነህ9፥23፤ መዝ78፥55፡58፤ ኤር2፥7፤3፥6፤ 19፥13፤ሕዝ6፥13
20፥29 ሕዝ16፥16፤ 43፥7
20፥30 ቍ43፤ መሳ2፥16-19፤ ኤር16፥12
20፥31 መዝ106፥37-39፤ ኤር7፥31፤ ሕዝ14፥3፤16፥20፤ አሞ8፥12፤ዘካ7፥13
20፥33 ኤር21፥5፤ ሕዝ16፥27፤25፥16
20፥34 ዘዳ30፥4፤ መዝ106፥47፤ ኢሳ 27፥12-13፤ 31፥3፤ኤር44፥6፤ ሰቆ2፥4፤ሕዝ6፥14፤ 2ቆሮ6፥17
20፥35 1ሳሙ12፥7፤ ኢዮ22፥4፤ኤር2፥35፤ ሕዝ19፥13
20፥36 ዘኍ11፥1 -35፤14፥28-30፤ 1ቆሮ10፥5-10
20፥37 ዘሌ27፥32፤ ሕዝ16፥62
20፥38 መዝ95፥11፤ ኤር44፥14፤ ሕዝ13፥9፤23፥49፤ 34፥17-22፤ሆሴ2፥14፤ አሞ9፥9-10፤ ዘካ13፥8-9፤ ሚል3፥3፤4፥1-3፤ ዕብ4፥3
20፥39 ዘፀ20፥7፤ ኤር44፥25፤ሕዝ13፥19፤ ሕዝ43፥7፤አሞ4፥4
20፥40 ኢሳ56፥7፤ 60፥7፤ሕዝ17፥22፤ 34፥14፤ሚል3፥4
20፥41 ዘዳ30፥4፤ ኢሳ5፥16፤ሕዝ11፥7፤ 28፥25፤36፥23፤ 2ቆሮ2፥14፤6፥17
20፥42 ኤር23፥8፤ 30፥3፤ሕዝ34፥13፡27፤ 36፥24፤37፥21፤ 38፥23
20፥43 ዘሌ26፥41፤ ሕዝ6፥9፤14፥22፤ 16፥61፤ሆሴ5፥15
20፥44 መዝ109፥21፤ ኢሳ43፥25፤ሕዝ 16፥62፤36፥22፡32
20፥46 ኢሳ30፥6፤ ኤር13፥19፤ሕዝ4፥3፤ 13፥17፤21፥2፤ አሞ7፥16
20፥47 2ነገ19፥23፤ ኢሳ9፥18-19፤13፥8፤ ሕዝ19፥14፤21፥4
20፥48 ኤር7፥20፤ ሕዝ21፥5፡32፤23፥25

20፥49 መሳ14፥12፤ መዝ78፥2፤ሕዝ4፥14፤12፥9፤ማቴ13፥13፤ ዮሐ16፥25

[ሠ]26 ወይም *የበኵር ልጅን ሁሉ በእሳት ውስጥ በማሳለፍ*
[ረ]29 *ባማ ማለት ከፍታ ቦታ ማለት ነው*
[ሰ]31 ወይም *ልጆቻችሁን በእሳት ውስጥ በማሳለፍ*

## የቅጣት በትር የሆነችው ባቢሎን

21 *የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል*
ወደ እኔ *መጣ*፤ 2“የሰው ልጅ ሆይ፤
ፊትህን ወደ ኢየሩሳሌም አዙር፤ በመቅደሱ
ላይ ቃል ተናገር፤ በእስራኤል ምድር ላይ
ትንቢት ተንብይ፤ 3እንዲህም በል፤ ‘*እግዚ
አብሔር* እንዲህ ይላል፤ እኔ በአንቺ ላይ
ተነሥቻለሁ፤ ሰይፌን ከሰገባው እመዛለሁ፤
ጻድቁንም፣ ክፉውንም ከአንተ ዘንድ አስወ
ግዳለሁ። 4ጻድቁንም ክፉውንም ስለማስወ
ግድ ሰይፌ ከደቡብ ጀምሮ እስከ ሰሜን
ባለው ሕዝብ ሁሉ ላይ ከሰገባው ይመዘዛል።
5ሰይፌን ከሰገባው የመዘዝሁት እኔ *እግዚ
አብሔር* እንደ ሆንሁ ሕዝቡ ሁሉ ያውቃል፤
እርሱም ወደ ሰገባው አይመለስም።’
6“ስለዚህ የሰው ልጅ ሆይ፤ አቃስት፤ በተ
ሰበረ ልብና በመረረ ሐዘን አቃስት፤ 7እነርሱም፣
‘ለምን ታቃስታለህ?’ ቢሉህ፣ “ስለሚመጣው
ክፉ ወሬ ነው፤ ልብ ሁሉ ይቀልጣል፤
እጅም ሁሉ ይዝላል፤ ነፍስ ሁሉ ይደክ
ማል፤ ጕልበ ትም ሁሉ ውሃ ይሆናል’
በላቸው። እነሆ ይመጣል፤ ይፈጸማልም፤
ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*።”
8*የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ
እኔ መጣ*፤ 9“የሰው ልጅ ሆይ፤ ትንቢት
ተናገር፤ እንዲህም በል፤ ‘*እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤

“ሰይፍ! ሰይፍ!
የተሳለ የተወለወለም፤
10የተሳለው ሊገድል፣
የተወለወለውም እንደ መብረቅ
ሊብረቀረቅ ነው!

“ ‘ታዲያ፣ እንዴት ደስ ሊለን ይችላል?
ሰይፉ የልጄን በትረ መንግሥት እንደ ማንኛ
ውም በትር ንቆአል።

11“ ‘በእጁ እንዲያዝ፣
ሰይፉ ሊወለወል ተሰጥቶአል፤
ገዳዩ በእጁ እንዲጨብጠው፣
ተስሎአል፤ ተወልውሎአል።
12የሰው ልጅ ሆይ፤ ይህ በሕዝቤ ላይ፣
በእስራኤልም መሳፍንት ሁሉ ላይ
መጥቶአልና፤
ጨኽት፣ ዋይታም አሰማ።
እነርሱ ከሕዝቤ ጋር በአንድ ላይ፣
ለሰይፍ ተጥለዋል፤
ስለዚህ ደረትህን ምታ።

13“ ‘ፈተና በእርግጥ ይመጣል፤ ሰይፉ የና
ቀው በትረ መንግሥት ዘላቂነት ባይኖረ
ውስ? ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*።’
14“እንግዲህ፣ የሰው ልጅ ሆይ፤ ትንቢት
ተናገር፤
በእጅህም አጨብጭብ፤
ሰይፉ ሁለት ጊዜ፣
ሦስት ጊዜም ይምታ፤
በእጅጉ የሚገድል፣
ለግድያ የሚሆን፣
በየአቅጣጫውም የሚከባቸው ሰይፍ ነው።
15ልብ ሁሉ ይቀልጥ ዘንድ፣
የሚወድቁትም እንዲበዙ፣
በበሮቻቸው ሁሉ፣
የግድያውን ሰይፍ[ሽ] አኑሬአለሁ።
ወዮ! እንዲያብረቀርቅ ተወልውሎአል፤
ለመግደልም ተመዞአል።
16ሰይፍ ሆይ፤ በስለትህ አቅጣጫ ሁሉ፣
ወደ ቀኝም፣
ወደ ግራም ቍረጥ።
17እኔም በእጄ አጨበጭባለሁ፤
ቍጣዬም ይበርዳል፤
እኔ *እግዚአብሔር* ተናግሬአለሁ።”

18*የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ
እኔ መጣ*፤ 19“የሰው ልጅ ሆይ፤ የባቢሎን
ንጉሥ ሰይፍ የሚመጣባቸውን የሁለት
መንገ ዶች ካርታ ንደፍ፤ መንገዶቹም
ከአንድ አገር የሚነሡ ናቸው፤ መንገዱ
ወደ ከተማው በሚገነጠልበት ቦታ ላይ
ምልክት አቁም። 20በአሞናውያን ከተማ
በረባት ላይ ለሚመ ጣው ሰይፍ
አንደኛውን መንገድ ምልክት አድርግ፤
በይሁዳና በተመሸገችው ከተማ በኢየሩሳሌም
ላይ ለሚመጣውም ሰይፍ ሁለተ ኛውን
መንገድ ምልክት አድርግ። 21የባቢሎን
ንጉሥ በጥንቈላ ምሪት ለማግኘት በመንታ
መንገድ ላይ በሁለቱ ጐዳናዎች መጋጠ
ሚያ ላይ ይቆማል፤ ቀስቶቹን በመወ
ዝወዝ ዕጣ ይጥላል፤ አማልክቱን ያማክራል፤
ጕበትንም ይመረምራል። 22የቅጥር መደርመሻ
አምጥቶ እንዲያቆም፣ ለመግደል ትእዛዝ
እንዲሰጥ፣ ፉከራ እንዲያሰማ፣ ቅጥር መደ
ርመሻውን በከተሞች በር ላይ እንዲ
ያደርግ፣ የዐፈር ድልድል እንዲያበጅና
ምሽግ እን ዲሠራ የኢየሩሳሌም ዕጣ በቀኝ
እጁ ወጣ። 23ይህም ከእርሱ ጋር ቃል ኪ
ዳን ለገቡት የተሳሳተ ምሪት ይመስላል፤
እርሱ ግን በደላቸውን ያሳስባቸዋል፤ ማርኮም
ይዞአቸው ይሄዳል።
24“ስለዚህ ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤ ‘እናንተ በምታደርጉት ሁሉ ኀጢአ
ታችሁን በመግለጽ፣ በግልጽም በማመፅ በደ
ላችሁን ስላሳሰባችሁ፣ እንዲህም ስላደረጋ
ችሁ በምርኮ ትወሰዳላችሁ።
25“ ‘አንተ የግፍ ጽዋህ የሞላ፣ የምትቀ

21፥1 ሕዝ20፥1
21፥2 ኤር26፥11-12፤ሕዝ9፥6፤13፥7፤20፥46
21፥3 ቍ9-11፤ ኢዮ9፥22፤ኢሳ27፥1፤57፥1፤ኤር21፥13፤47፥6-7፤ሕዝ14፥21
21፥4 ዘሌ26፥25፤ ኤር25፥27፤ ሕዝ20፥47
21፥5 ቍ30፤ ኢሳ34፥5፤ ሕዝ20፥47-48፤ ናሆ1፥9
21፥6 ቍ12፤ ኢሳ22፥4፤ኤር30፥6፤ ሕዝ9፥4
21፥7 ዘሌ26፥36፤ ኢሱ7፥5፤ኢዮ11፥16፤23፥2፤መዝ6፥2፤ኤር47፥3፤ሕዝ22፥14
21፥10 ዘዳ32፥41፤ መዝ110፥5-6፤ ኢሳ34፥5-6
21፥11 ኤር46፥4
21፥12 ኤር31፥19
21፥14 ቍ17፤ ዘኍ24፥10፤ ሕዝ6፥11፤30፥24
21፥15 2ሳሙ17፥10፤መዝ22፥14
21፥17 ቍ14፤ ሕዝ5፥13፤6፥11፤16፥42፤22፥13
21፥19 ኤር31፥21፤ ሕዝ14፥21፤32፥11
21፥20 ዘዳ3፥11
21፥21 ዘኍ22፥7፤23፥23፤ምሳ16፥33፤ዘካ10፥2
21፥22 2ነገ25፥1፤ ኤር4፥16፤32፥24፤ ሕዝ4፥2፤26፥9
21፥23 ዘኍ5፥15፤ ሕዝ17፥19
21፥25 ሕዝ22፥4፤35፥5

[ሽ]15 ከሰብዓ ሊቃናት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን በዕብራይስጡ ግን
የዚህ ቃል ትርጒም አይታወቅም

ጣበት ቀን የደረሰ፣ ርኩስና ክፉ የእስራኤል
መስፍን ሆይ፤ 26ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤ “ጥምጥምህን አውልቅ፤ ዘውድህን
ጣል፤ እንደ ከዚህ በፊቱ አይሆንም፤ ዝቅ
ያለው ከፍ ይላል፤ ከፍ ያለውም ዝቅ
ይላል፡፡ 27ባድማ! ባድማ! ባድማ አደርጋታ
ለሁ፤ የሚገባው ባለ መብት እስከሚመጣ
ድረስ እንደ ቀድሞው አትሆንም፤ ለእር
ሱም ደግሞ እሰጣታለሁ፡፡” ’
28“አንተ የሰው ልጅ ሆይ! እንዲህ ብለህ
ተናገር፤ ‘ስለ አሞናውያንና ስለ ስድባቸው
ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

“ ‘ሰይፍ! ሰይፍ!
ሊገድል የተመዘዘ፣
ሊያጠፋ የተጠረገ፣
እንደ መብረቅ ሊያብረቀርቅ የተወለወለ፤
29የታለመልህ የሐሰት ራእይ፣
የተነገረልህ የውሸት ሟርት ቢኖርም፣
የግፍ ጽዋቸው በሞላ፣
ቀናቸው በደረሰ፣
መታረድ በሚገባቸው ክፉዎች፣
አንገት ላይ ይሆናል፡፡
30ሰይፉን ወደ ሰገባው መልሰው፤
በተፈጠርህበት ምድር፣
በተወለድህበትም አገር፣
በዚያ እፈርድብሃለሁ፡፡
31መዓቴን በላይህ አፈሳለሁ፤
የቍጣዬንም እሳት አነድብሃለሁ፣
በጥፋት ለተካኑ፣
ለጨካኞች ሰዎች አሳልፌ እሰጥሃለሁ፡፡
32ለእሳት ማገዶ ትሆናለህ፣
ደምህ በምድርህ ይፈሳል፣
ከእንግዲህ መታሰቢያ አይኖርህም፤
እኔ *እግዚአብሔር* ተናግሬአለሁና፡፡’ ”

## የኢየሩሳሌም ኀጢአት

22 *የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤* 2“የሰው ልጅ
ሆይ፤ አትፈርድባትምን? ደም
በምታፈሰው በዚህች ከተማ ላይ
አትፈርድባትምን? ጸያፍ ተግባሯን ፊት
ለፊት ንገራት፤ 3እንዲህም በላት፤ ‘ጌታ
*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ “በመካከልሽ
ደምን በማፍሰስና ጣዖታትን በመሥራት
ራስሽን የምታረክሺ፣ ፍርድንም በራስሽ ላይ
የምታፈጥኚ ከተማ ሆይ፤ 4ባፈ ሰስሽው
ደም በድለሻል፤ በሠራሽውም ጣዖት
ረክሰሻል፤ ከዚህም የተነሣ ቀንሽን አቅር
በሻል፤ ዕድሜሽንም አሳጥረሻል፡፡ ስለዚህ
ለአሕዛብ መዘባበቻ፣ ለአገሩም ሁሉ መሣለ
ቂያ አደርግሻለሁ፡፡ 5አንቺ የተዋረድሽና ሽብር
የሞላብሽ ሆይ፤ በቅርብም በሩቅም ያሉ
ይሣለቁብሻል፡፡

6“ ‘እነሆ በመካከልሽ ያለ እያንዳንዱ የእ
ስራኤል መስፍን ደም ለማፍሰስ ሥልጣኑን
ይጠቀማል፡፡ 7አባቶችና እናቶች በውስጥሽ
ተዋረዱ፤ መጻተኞች ተጨቈኑ፤ ድኻ አደጎ
ችና መበለቶች ተንገላቱ፡፡ 8ንዋያተ ቅድሳ
ቴን አቃለልሽ፤ ሰንበታቴንም አረከስሽ፡፡
9ደምን ለማፍሰስ ወሬ የሚያቀብሉ በውስ
ጥሽ አሉ፤ በኰረብታ ቤተ ጣዖት የተሠዋ
ውን የሚበሉና ዝሙትን የሚፈጽሙ ሰዎች
በመካከልሽ ይገኛሉ፡፡ 10የአባታቸውን መኝታ
የሚደፍሩ ሰዎች በውስጥሽ አሉ፤ በሥርዐቱ
መሠረት ንጹሕ ባልሆኑበት በወር አበባቸው
ጊዜ ሴቶችን በማስገደድ የሚደፍሩ በመካከ
ልሽ ይገኛሉ፡፡ 11በውስጥሽ አንዱ የባልንጀ
ራውን ሚስት ያባልጋል፤ ሌላውም የልጁን
ሚስት ያስነውራል፤ ሌላው ደግሞ የገዛ
እኅቱ የሆነችውን የአባቱን ልጅ ይደፍራል፡፡
12በመካከልሽ ያሉ ሰዎች ደም ለማፍሰስ
ጉቦ ይቀበላሉ፤ አንቺም ዐራጣና ከፍተኛ
ወለድ[ቀ] በመውሰድ ከባልንጀራሽ የማይገባ
ትርፍ ዘረፍሽ፤ እኔንም ረስተሻል፤ ይላል ጌታ
*እግዚአብሔር*፡፡
13“ ‘ያለ አግባብ ባገኘሽው ጥቅምና በመ
ካከልሽ ባፈሰስሽው ደም ላይ እጄን አጨበ
ጭባለሁ፡፡ 14እኔ ልቀጣሽ በምነሣበት ጊዜ
በልበ ሙሉነት መቆም ትችያለሽን? ወይስ
እጅሽ ሊበረታ ይችላልን? እኔ *እግዚአብሐ
ር* ተናግሬአለሁ፤ አደርገዋለሁም፡፡ 15በሕ
ዝቦች መካከል እበትንሻለሁ፤ በየአገሩም እዘ
ራሻለሁ፤ ከርኵሰትሽም አጠራሻለሁ፡፡ 16በሕ
ዝቦች ዘንድ በምትረክሺበት ጊዜ፣[በ] እኔ
*እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ ታውቂያለሽ፡፡’
”

17*የእግዚአብሔርም ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤* 18“የሰው ልጅ ሆይ፤ የእስራ
ኤል ቤት የብረት ጕድፍ ሆነብኝ፤ ሁሉም
በከውር ውስጥ ቀልጦ እንደሚቀር መዳብ፣
ቈርቈሮ፣ ብረትና እርሳስ ናቸው፤ እነዚ
ህ ከብር የሚወጡ ጕድፍ ናቸው፡፡ 19ስለዚህ
ልዑል *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፣
‘ሁላችሁም የብረት ጕድፍ ስለ ሆናችሁ
ወደ ኢየሩሳሌም እሰበስባችኋለሁ፡፡
20ሰው ብርንና መዳብን፣ ብረትንና
እርሳስን እንዲሁም ቈርቈሮን ለማቅለጥ
በከውር ውስጥ አስገ ብቶ እሳት
እንደሚያነድበት፣ እኔም እን ደዚሁ
በቍጣዬና በመዓቴ ወደ ከተማዪቱ
እሰበስባችኋለሁ፤ በዚያም አቀልጣችኋለሁ፡፡
21ሰብስቤአችሁ የቍጣዬን እሳት በእስትን
ፋሴ አነድባችኋለሁ፤ እናንተም በዚያ ውስጥ
ቀልጣችሁ ትቀራላችሁ፤ እኔ *እግዚአብሔር*

21፥26 መዝ75፥7፤ ኢሳ28፥5፤40፥4፤ ኤር13፥18፤ ሕዝ17፥24፤ ማቴ23፥12
21፥27 ዘፍ49፥10፤ መዝ2፥6፤ኤር23፥5-6፤ሕዝ 37፥24፤ ሐጌ2፥21-22
21፥28 ዘፍ19፥38፤ ኤር12፥12፤ሶፎ2፥8
21፥29 ቍ25፤ ኤር27፥9፤ ሕዝ22፥28፤35፥5
21፥30 ቍ5፤ ኤር47፥6፤ሕዝ16፥3
21፥31 መዝ18፥15፤ 79፥6፤ኢሳ11፥4፤ ኤር4፥7፤51፥20-23፤ ሕዝ16፥39፤ 22፥20-21
21፥32 ሕዝ20፥47-48፤25፥10፤ ሚል4፥1
22፥2 ሕዝ16፥2፤ 23፥36፤24፥6፤ ሆሴ4፥2፤ናሆ3፥1፤ ዕን2፥12
22፥3 ቍ6፡13፡27፤ ሕዝ23፥37፡45፤24፥6
22፥4 2ነገ21፥16፤ መዝ44፥13-14፤ 137፥3፤ሕዝ5፥14፤ 21፥25
22፥5 ኢሳ22፥2
22፥6 ሕዝ11፥6፤ 18፥10፤33፥25
22፥7 ዘፀ22፥21-22፤23፥9፤ዘዳ5፥16፤ ሚክ7፥6
22፥8 ዘፀ20፥8፤ ሕዝ23፥38-39
22፥9 ዘሌ19፥16፤ ኢሳ59፥3፤ሕዝ11፥6፤ 18፥11፤23፥29፤ ሆሴ4፥2፡10፡14፤6፥9
22፥10 ዘሌ12፥2፤ 18፥7፡8፡9
22፥11 ዘፍ11፥31፤ ዘሌ18፥9፡15፤ 2ሳሙ13፥14፤ ኤር5፥8፤ሕዝ18፥6
22፥12 ዘፀ18፥21፤ ዘሌ19፥13፤ዘዳ27፥25፤ መዝ26፥10፤ 106፥21፤ኢሳ5፥23፤ 17፥10፤57፥11፤ ሕዝ11፥6፤18፥8፤ አሞ5፥12፤ሚክ7፥3
22፥13 ቍ3፡27፤ ዘኍ24፥10፤ኢሳ33፥15፤ ሕዝ6፥11፤21፥17
22፥14 መዝ76፥7፤ ሕዝ7፥17፤17፥24፤ 24፥14፤ኢል2፥11፤ ናሆ1፥6፤ሚል3፥2
22፥15 ዘሌ26፥33፤ ዘዳ4፥27፤ሕዝ16፥41፤ 24፥11፤ዘካ7፥14
22፥18 መዝ119፥119፤ኢሳ48፥10፤ኤር6፥28-30 22፥19 መዝ119፥119 22፥20 ሆሴ8፥10፤ ሚል3፥2 22፥21 መዝ68፥2፤ ኢሳ40፥7፤ሕዝ21፥31፤ሐጌ1፥9

[ቀ]12 ወይም *ዐራጣና ወለድ*
[በ]16 ወይም *ርስትሽን ለአንቺ በሰጠሁሽ ጊዜ*

ቍጣዬን በላያችሁ እንዳ ፈሰስሁ ታውቃ
ላችሁ። 22ብር በከውር ውስጥ እንደሚቀልጥ፣
እናንተም በከተማዋ ውስጥ ትቀልጣላችሁ፤
በዚያን ጊዜ እኔ እግዚአብሔር ቍጣዬን
በላያችሁ እንዳፈሰስሁ ታውቃላችሁ።’ ”
23የእግዚአብሔርም ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤ 24“የሰው ልጅ ሆይ፤ ምድ
ሪቱን፣ ‘አንቺ ያልነጻሽ በቍጣም ቀን ዝናብ
ያላገኘሽ[+] ምድር ነሽ’ በላት። 25መሳፍንቷ[ቸ]
እያገሣ ግዳዩን እንደሚቦጫጭቅ አንበሳ
በውስጧ ያሤራሉ፤ ሕዝቡን ይበላሉ፤ ንብረ
ትንና የከበሩ ነገሮችን ይነጥቃሉ፤ ብዙዎ
ችንም ሴቶች መበለት ያደርጋሉ። 26ካህናቷ
በሕጌ ላይ ያምፃሉ፤ ንዋያተ ቅድሳቴን
ያረክሳሉ፤ የተቀደሰውን ከረከሰው አይለ
ዩም፤ በጐደፈውና በንጹሑ መካከል ልዩነት
እንደሌለ ያስተምራሉ፤ ሰንበታቴን ከማክ
በር ዘወር ብለዋል፤ በዚህም በመካከላቸው
ተንቄአለሁ። 27በውስጧ የሚገኙ መኳንንቷ
ግዳይ እንደሚቦጫጭቁ ተኵላዎች ናቸው፤
በግፍ ትርፍ ለመሰብሰብ ደም ያፈሳሉ፤
ሕይወትም ያጠፋሉ። 28ነቢያቷም በሐሰት
ራእይና በውሸት ሟርት ይህን ሁሉ ድርጊት
ያድበሰብሱላቸዋል፤ እግዚአብሔርም ሳይና
ገር፣ ‘ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል’
ይላሉ። 29በምድሪቱ የሚኖረው ሕዝብ ይቀ
ማል፤ ይዘርፋል፤ ፍትሕ በማጕደልም ድኻው
ንና ችግረኛውን ይጨቍናል፤ መጻተኛውንም
ይበድላል።
30“ምድሪቱን እንዳላጠፋት ቅጥሩን የሚጠ
ግን፣ በፈረሰውም በኩል በፊቴ የሚቆምላት
ሰው ከመካከላቸው ፈለግሁ፤ ነገር ግን አን
ድም አላገኘሁም። 31ስለዚህ መዓቴን አፈስ
ባቸዋለሁ፤ በጽኑ ቍጣዬም አነዳቸዋለሁ፤
ያደረጉትንም በራሳቸው ላይ እመልሳለሁ፤
ይላል ጌታ እግዚአብሔር”።

## ሁለቱ ዘማውያት እኅትማማቾች

23 የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤ 2“የሰው ልጅ ሆይ፤
ከአንድ እናት የተወለዱ ሁለት ሴቶች
ልጆች ነበሩ፤ 3ገና በወጣትነታቸው ዘማው
ያት በመሆን በግብፅ ሳሉ አመነዘሩ፤ በዚ
ያችም ምድር አጐጠጐጤአቸው ተዳበሰ፤
የድንግልናቸውም ጕያ በእጅ ተሻሸ። 4የታ
ላቂቱ ስም ኦሖላ፣ የእኅቷም ኦሖሊባ
ነበር፤ ሁለቱም የእኔ ሆኑ፤ ወንዶችና
ሴቶች ልጆችም ወለዱ። ስማቸውም፣ ኦሖላ
ሰማርያ ናት፤ ኦሖሊባም ኢየሩሳሌም።
5“ኦሖላ የእኔ ሆና ሳለ በእኔ ላይ አመነ
ዘረች፤ ጦረኞች ከሆኑት ጎረቤቶቿ ከአሦራ
ውያን ውሽሞቿ ጋር ሴሰነች፤ 6እነርሱም ሐም
ራዊ የለበሱ፣ ገዦችና አዛዦች፣ ሁሉም መልከ
ቀና ጐበዛዝትና ፈጣን ፈረሰኞች ነበሩ።
7እርሷ በዝሙት ራሷን ምርጥ ለሆኑት አሦራ
ውያን ሁሉ አሳልፋ ሰጠች፤ አብረዋት
ባመነዘሩት ሰዎች ጣዖት ሁሉ ረከሰች።
8በግብፅ የጀመረችውን አመንዝራነቷን አል
ተወችም፤ በዚያ ወንዶች በወጣትነቷ
ከእርሷ ጋር ተኙ፤ የድንግልናዋን ጡት አሻሹ፤
ፍትወታቸውን አፈሰሱባት።
9“ስለዚህ አብራቸው ላመነዘረች ለአሦራ
ውያን ውሽሞቿ አሳልፌ ሰጠኋት። 10እነር
ሱም ዕርቃን አስቀሯት፤ ወንዶችና ሴቶች
ልጆቿን ነጠቋት፤ እርሷንም በሰይፍ ገደ
ሏት፤ በሴቶችም ዘንድ መተረቻ ሆና ቀረች፤
ፍርድም ተፈጸመባት።
11“እኅቷ ኦሖሊባ ይህን አይታ ነበር፤
ሆኖም በፍትወቷና በዘማዊነቷ ከእኅቷ
የባሰች ብልሹ ሆነች። 12ደግሞም ገዦችና
አዛዦች፣ ጌጠኛ ልብስ የለበሱ ጦረኞች፣
ፈጣን ፈረሰኞችና፣ ሁሉም መልከ ቀና
ከሆኑት አሦራውያን ጐበዛዝት ጋር
አመነዘረች። 13ይህችም እንደ ረከሰች
አየሁ፤ ሁለቱም በአንድ መንገድ ሄዱ።
14“በአመንዝራነቷ እየባሰች ሄደች፤ በደ
ማቅ ቀይ ቀለም በግድግዳ ላይ የተቀረጹ
የከለዳውያንን[ኀ] ወንዶች ምስል አየች፤ 15እነ
ርሱም ወገባቸውን በቀበቶ የታጠቁና በራ
ሳቸው ላይ ተንጠልጣይ ያለው ጥምጥም
የጠመጠሙ ነበሩ፤ ሁሉም የከለዳውያን[ነ]
ተወላጆችና የባቢሎን ሠረገላ አዛዦች ይመ
ስሉ ነበር። 16ባየቻቸውም ጊዜ በፍትወት
ተቃጠለች፤ ወደ ከላውዴዎን መልእክተኞች
ላከችባቸው። 17ባቢሎናውያንም መጥተው
ወደ ፍቅር መኝታዋ ገቡ፤ በፍትወታቸውም
አረከሷት፤ እርሷም በእነርሱ ከረከሰች በኋላ
ጠልታቸው ከእነርሱ ዘወር አለች። 18ግልሙ
ትናዋን በአደባባይ በፈጸመችና ዕርቃን
በገለጠች ጊዜ ከእኅቷ ዘወር እንዳልሁ፣
ጠልቼአት ከእርሷም ዘወር አልሁ። 19እርሷ
ግን በግብፅ ያመነዘረችበት የወጣትነት
ዘመኗ ትዝ እያላት የባሰ ዘማዊት ሆነች።
20በዚያም አባለዘራቸው እንደ አህያ፣ የዘር
ፍሰታቸውም እንደ ድንጐላ ፈረስ ዘር
ፍሰት ከሆነ ውሽሞቿ ጋር አመነዘረች፤
21በግብፅ ምድር ጕያሽን የታሸሸበትንና
የወጣትነት
ጡቶችሽን የተዳበስሽበትን[ኘ] የኰረዳነትሽን

[+]24 ከሰብዓ ሊቃናት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን *ያልነጻሽ ወይም ያልዘነበብሽ* ይለዋል
[ቸ]25 ከሰብዓ ሊቃናት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን *ነቢያት* ይለዋል
[ኀ]14 ወይም *የባቢሎናውያን*
[ነ]15 ወይም *የባቢሎናውያን*፤ እንዲሁም በቍ16
[ኘ]21 ከሱርስቱ ጋር (በተጨማሪ ቍ3 ይመ) ተመሳሳይ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን *በወጣትነት ጡቶችሽ ምክንያት የተዳበስ ሽበትን* ይላል

22፥22 ኢሳ1፥25፤ 64፥7፤ሕዝ7፥8
22፥24 ሕዝ24፥13
22፥25 መዝ22፥13፤ ኤር11፥9፤15፥8፤ 18፥21፤ሆሴ6፥9
22፥26 ቍ8፤ ዘሌ18፥21፤20፥25፤ 1ሳሙ2፥12-17፤ ኤር 2፥8፡26፤ ሕዝ13፥19፤42፥20፤ 44፥23፤ሆሴ 9፥7-8፤ ሶፎ3፥4፤ሐጌ2፥11 -14፤ ሚል2፥7-8
22፥27 ቍ3፡13፤ ዘፍ37፥24፤ኢሳ1፥23፤ ኤር12፥2፤26፥10፤ 51፥13፤ሕዝ11፥6፤ 33፥25፡31፤34፥2-3፤ ሚክ3፥2፡10፤ሶፎ3፥3፤ ማቴ7፥15
22፥28 ሰቆ2፥14፤ 4፥13፤ሕዝ13፥2፡6 -7፡ 10፤21፥29
22፥29 ዘፀ22፥21፤ መዝ62፥10፤ኢሳ5፥7
22፥30 መዝ106፥23፤ ኢሳ64፥7፤ኤር5፥1፤ ሕዝ13፥5
22፥31 ዘፀ32፥10፤ ኢ. ሳ30፥27፤ሰቆ4፥11፤ ሕዝ7፥8-9፤16፥43፤ ሮሜ2፥8
23፥2 ኤር3፥7፤ ሕዝ16፥45
23፥3 ዘሌ17፥7፤ ኢሱ24፥14፤ መዝ25፥7፤ኢሳ1፥21፤ ሕዝ16፥15
23፥4 ሕዝ16፥46
23፥5 2ነገ16፥7፤ ሆሴ5፥13፤8፥9
23፥7 ኢሳ57፥8፤ ሆሴ5፥3፤6፥10
23፥8 ዘፀ32፥4፤ ሕዝ16፥15
23፥9 2ነገ18፥11፤ ኤር4፥30፤ሆሴ11፥5
23፥10 ኤር42፥10፤ ሕዝ16፥36፡41፤ ሆሴ2፥10
23፥11 ኤር3፥7፡8 -11፤ሕዝ16፥51
23፥12 2ነገ16፥7 -15፤2ዜና28፥16፤ ሕዝ16፥15፡28
23፥13 2ነገ17፥19፤ ሆሴ12፥2
23፥14 ኤር22፥14፤ ሕዝ8፥10፤ናሆ2፥3
23፥15 ኢሳ5፥27
23፥16 ኢሳ57፥9፤ ሕዝ6፥9
23፥17 ኤር40፥9፤ ሕዝ16፥29
23፥18 መዝ78፥59፤ 106፥40፤ኢሳ57፥8፤ ኤር6፥8፤12፥8፤ አሞ5፥21
23፥21 ሕዝ16፥26

ብልግና ተመኘሽ፡፡
22“ስለዚህ፣ ኦሖሊባ ሆይ፤ ጌታ እግዚአ
ብሔር እንዲህ ይላል፤ ‘ጠልተሻቸው ከእነ
ርሱ ዘወር ያልሽውን ውሽሞችሽን በአንቺ
ላይ አስነሣለሁ፤ እነርሱንም ከየአቅጣጫው
አመጣብሻለሁ፤ 23እነርሱም ባቢሎናውያንና
ከለዳውያን ሁሉ፣ የፋቁድ፣ የሱሔና የቆዓ
ሰዎች፣ ከእነርሱም ጋር አሦራውያን ሁሉ
ናቸው፡፡ እነዚህም መልከ ቀና ጐበዛዝት
ሲሆኑ፣ ሁላቸውም በፈረስ ላይ የተቀመጡ
ገዦችና አዛዦች፣ የሠረገላ አዛዦችና ከፍተኛ
ባለ ሥልጣኖች ነበሩ፡፡ 24እነርሱም የጦር
መሣሪያ[ሀ]፣ ሠረገላና ጋሪ በመያዝ ብዙ ሕዝብ
ሆነው ይመጡብሻል፤ ትላልቅና መለስተኛ
ጋሻ በማንገብና የራስ ቍር በመድፋት
በየአቅጣጫው ይሰለፉብሻል፤ እኔም ለፍርድ
በእጃቸው አሳልፌ እሰጥሻለሁ፤ በሕጋቸ
ውም መሠረት ይቀጡሻል፡፡ 25የቅናት
ቍጣዬን በአንቺ ላይ አመጣለሁ፤ እነርሱም
በአንቺ ላይ በቍጣ ይወጣሉ፤ አፍንጫሽንና
ጆሮሽን ይቈርጣሉ፤ ከአንቺ ወገን የተ
ረፉትም በሰይፍ ይወድቃሉ፡፡ ወንዶችና
ሴቶች ልጆችሽን ይወስዱብሻል፤ የተረፉ
ትንም እሳት ይበላቸዋል፡፡ 26ልብስሽን
ይገፉሻል፤ ምርጥ ጌጣ ጌጥሽንም ይወስዱ
ብሻል፡፡ 27በግብፅ የጀመርሽውን ብልግናና
ሴሰኝነት ከአንቺ አስወግዳለሁ፤ አንቺም ዐይ
ንሽን ወደ እነዚህ አታነሺም፤ ከእንግዲህ
ግብፅን አታስቢም፡፡
28“ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፤
‘እነሆ ተጸይፈሻቸው ከእነርሱ ዘወር ላልሽው
ለጠላሻቸው አሳልፌ እሰጥሻለሁ፡፡ 29እነርሱም
በጥላቻ ይቀርቡሻል፤ የለፋሽበትንም ሁሉ
ይቀሙሻል፤ ከማሕፀን እንደ ወጣሽ ዕር
ቃንሽን ያስቀሩሻል፤ የሴሰኝነትሽ ኀፍረት
ይገለጣል፡፡ ብልግናሽና ገደብ የለሽ ርኵሰ
ትሽ፣ 30ይህን አምጥተውብሻል፤ ከአሕዛብ
ጋር በማመንዘር በጣዖቶቻቸው ረክሰሻልና፡፡
31በእኅትሽ መንገድ ስለ ሄድሽ የእርሷን
ጽዋ በእጅሽ አስጨብጥሻለሁ፡፡’

32“ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“ሰፊና ጥልቅ የሆነውን ጽዋ፣
የእኅትሽን ጽዋ ትጠጪአለሽ፤
ብዙም ስለሚይዝ ስድብና ነቀፌታ
ትጠግቢአለሽ፡፡
33በእኅትሽ በሰማርያ ጽዋ፣
በመፍረስና በጥፋት ጽዋ፣
በስካርና በሐዘን ትሞዪአለሽ፡፡
34ትጠጪዋለሽ፤ ትጨልጪዋለሽም፤
ከዚያም ጽዋውን ትሰባብሪዋለሽ፤
ጡትሽንም ትቈራርጪአለሽ፤
እኔ ተናግሬአለሁ፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፡፡

23፥22 ኤር4፥30፤ ሕዝ16፥37
23፥23 ዘፍ11፥28፤ 2ነገ20፥14-18፤24፥2፤ኤር40፥9፤50፥21
23፥24 ኤር39፥5-6፤47፥3፤ሕዝ26፥7፡10፤ናሆ2፥4
23፥25 ቍ47፤ ዘጻ29፥20፤ኤር12፥9፤ ሕዝ16፥38፤ 20፥47-48፤24፥21
23፥26 ኢሳ3፥18-23፤ኤር13፥22፤ ሕዝ16፥39
23፥27 ሕዝ16፥41
23፥28 ኤር34፥20
23፥29 ዘዳ28፥48፤ ኤር13፥27፤ ሕዝ16፥36፤22፥9፤ ሚክ1፥11
23፥30 መዝ106፥37-38፤ ሶፎ3፥1
23፥31 2ነገ21፥13፤ ኤር25፥15
23፥32 መዝ44፥13፤ 60፥3፤ኢሳ51፥17፤ ኤር25፥15፤ሆሴ7፥16
23፥33 ኤር25፥15-16፤ሕዝ12፥19
23፥34 መዝ16፥5፤ ኤር25፥27
23፥35 ዘዳ32፥18፤ 1ነገ14፥9፤2ዜና29፥6፤ኢሳ17፥10፤ሕዝ 16፥52
23፥36 ኢሳ58፥1፤ ሕዝ16፥2፤22፥2፤ ሚክ3፥8
23፥37 ሕዝ16፥36
23፥38 ዘሌ15፥31፤ ነህ10፥31
23፥39 2ነገ21፥4፤ ኤር7፥10፤ሕዝ22፥8
23፥40 2ነገ9፥30፤ ኢሳ57፥9፤ኤር4፥30፤ ሕዝ16፥13-19፤ ሆሴ2፥13
23፥41ዘኍ18፥12፤ አስ1፥6፤ምሳ7፥17፤ ኢሳ57፥9፤65፥3፡11፤ ኤር44፥5፤ ሕዝ41፥22፤44፥16፤ ሚል 1፥7፡12
23፥42 ዘፍ24፥30፤ 2ዜና9፥1፤መዝ73፥5፤ሕዝ16፥11-12
23፥43 ቍ3
23፥45 ዘሌ20፥10፤ ሕዝ16፥38፤22፥3፤ ሆሴ2፥2፤6፥5
23፥46 ዘዳ28፥25፤ ኤር25፥9፤ሕዝ16፥40
23፥47 ቍ25፤ 2ዜና 36፥17፡19፤ ኤር34፥22
23፥48 ሕዝ16፥41፤ 2ጴጥ2፥6
23 49 ሕዝ7፥4፤ 9፥10፤16፥58፤

35“ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤ ‘ረስተሽኛል፤ ወደ ኋላም ገሸሽ አድ
ርገሽኛልና የብልግናሽንና የሴሰኝነትሽን
ውጤት ትሸከሚአለሽ፡፡’
36እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፤ “የሰው ልጅ
ሆይ፤ በኦሖላና በኦሖሊባ ትፈርዳለህን? እን
ግዲያውስ ጸያፍ ተግባራቸውን ንገራቸው፡፡
37አመንዝረዋል እጃቸውም በደም ተበክሎአ
ልና፡፡ ከጣዖቶቻቸው ጋር አመነዘሩ፤ የወለ
ዱልኝን ልጆቻቸውን እንኳ ለእነርሱ መብል
ይሆኑ ዘንድ በእሳት ሠውተውላቸዋል፡፡[ለ]
38ደግሞም ይህን አደረጉብኝ፤ በዚያኑ ቀን
ቤተ መቅደሴን አረከሱ፤ ሰንበታቴንም አቃ
ለሉ፡፡ 39ልጆቻቸውን ለጣዖቶቻቸው በሠዉባት
ዕለት ወደ መቅደሴ ገብተው አረከሷት፤
እንግዲህ በቤቴ ውስጥ ያደረጉት እንዲህ
ያለውን ነው፡፡
40“ከዚህም በላይ ወንዶች ከሩቅ እንዲ
መጡላቸው መልእክተኛ ላኩ፤ እነርሱም
መጡ፡፡ አንቺም ገላሽን ታጥበሽ፣ ዐይንሽን
ተኵለሽና በጌጣጌጥ ተውበሽ ጠበቅሻቸው፡፡
41በተዋበ ዐልጋ ላይ ተቀመጥሽ፤ ዕጣኔንና
ዘይቴን ያኖርሽበትንም ጠረጴዛ ከዐልጋው
ፊት ለፊት አደረግሽ፡፡
42“የሚፈነጥዙ ሰዎች ድምፅ በዙሪያዋ
ነበር፤ ከሚያውኩ ሰዎች ጋር ከበረሓ የመጡ
ሰካራሞች ነበሩ፤ በሴትየዋና በእኅትዋም
ላይ አንባር፣ በራሳቸውም ላይ የተዋበ አክ
ሊል አደረጉላቸው፡፡ 43እኔም በአመንዝራነት
ሰውነቷ ስላለቀው፣ ‘እርሷ ሕይወቷ ይኸው
ስለ ሆነ እንደ ዝሙት ዐዳሪ ይጠቀሙ
ባት’ አልሁ፡፡ 44እነርሱም ከእርሷ ጋር ተኙ፤
ሰው ከአመንዝራ ሴት ጋር እንደሚ ተኛ
ከእነዚያ ባለጌ ሴቶች፣ ከኦሖላና ከኦሖሊባ
ጋር ተኙ፡፡ 45ጻድቃን ግን ለአመንዝራና
ለነፍሰ ገዳይ ሴቶች የሚገባቸውን ፍርድ
ይፈርዱባቸዋል፡፡ አመንዝሮች ናቸውና፤ እጃ
ቸውም በደም ተበክሎአል፡፡
46“ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ‘ሕዝ
ብን ቀስቅሰህ አምጣባቸው፤ ለሽብርና ለዝር
ፊያም አሳልፈህ ስጣቸው፡፡ 47ሕዝቡ በድንጋይ
ይወግራቸዋል፤ በገዛ ሰይፋቸው ይቈራርጣ
ቸዋል፤ ወንድና ሴት ልጆቻቸውን ይገድ
ላል፤ ቤቶቻቸውንም ያቃጥላል፡፡
48“ ‘ስለዚህ ሴቶች ሁሉ እንዲጠነቀቁና
መጥፎ ፈለጋችሁን እንዳይከተሉ፣ ሴሰኝነትን
ከምድሪቱ አጠፋለሁ፡፡ 49የሴሰኝነታችሁን
ዋጋ ታገኛላችሁ፤ ጣዖት በማምለክ ለፈ
ጸማችሁት ኀጢአት ቅጣት ትሸከማላችሁ፤

[ሀ]24 በዕብራይስጥ የዚህ ቃል ትርጒም አይታወቅም
[ለ]37 ወይም *የወለዱልኝን ልጆች እንኳ በእሳት ውስጥ አሳለፏቸው*

በዚያን ጊዜ እኔ ጌታ *እግዚአብሔር* እንደ
ሆንሁ ታውቃላችሁ።’ ”

**የድስቱ ምሳሌ**

24 በዘጠነኛው ዓመት፣ በዐሥረኛው
ወር፣ በዐሥረኛው ቀን *የእግዚአ
ብሔር* ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፤
2“የሰው ልጅ ሆይ፤ ይህን ቀን፣ የዛሬውን
ዕለት ለይተህ መዝግብ፤ የባቢሎን ንጉሥ
ኢየሩሳሌምን በዚህ ቀን ከቦአታልና። 3ለዚህ
ዐመፀኛ ቤት እንዲህ ብለህ ተምሳሌት
ተናገር፤ ‘ልዑል *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

“ ‘ብረት ድስት በእሳት ላይ ጣድ፤
ከጣድህም በኋላ ውሃ ጨምርበት።
4ሙዳ፣ ሙዳ ሥጋ፣
ምርጥ ምርጡን ቍርጥ ሁሉ፣ ጭንና
ወርቹን ጨምርበት፤
የተመረጡ ዐጥንቶችንም ሙላበት።
5ከመንጋው ሙክቱን ውሰድ፤
ዐጥንቱን ለማብሰል ብዙ ማገዶ ከሥሩ
ጨምር፤
ሙክክ እስከሚል ቀቅለው፤
ዐጥንቱም ይብሰል።

6“ ‘ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላልና፤

“ ‘ለዛገችው ብረት ድስት
ዝገቷም ለማይለቅ፣
ደም ላፈሰሰችው ከተማ ወዮላት!
መለያ ዕጣ ሳትጥል
አንድ በአንድ አውጥተህ ባዶ
አድርገው።

7“ ‘የሰው ደም በመካከሏ አለ፤
በገላጣ ዐለት ላይ አደረገችው እንጂ፣
ዐፈር ሊሸፍነው በሚችል፣
በመሬት ላይ አላፈሰሰችውም።
8ቍጣዬ እንዲነድና ለመበቀል እንዲያመቸኝ፣
ይሸፈንም ዘንድ እንዳይችል፣
ደሟን በገላጣ ዐለት ላይ አፈሰስሁ።

9“ ‘ስለዚህ ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤

“ ‘ደም ላፈሰሰችው ከተማ ወዮላት!
እኔም ደግሞ የምትቃጠልበትን ማገዶ
እቈልላለሁ።
10ማገዶውን ከምርበት፤
እሳቱን አንድድ፤
ቅመም ጨምረህበት፣
ሥጋውን በሚገባ ቀቅል፤
ዐጥንቱም ይረር።
11ጕድፉ እንዲቀልጥ፣
ዝገቱም በእሳት እንዲበላ፣
ባዶው ድስት እስኪሞቅ፣
መደቡም እስኪግል ከሰል ላይ ጣደው።
12ብዙ ጕልበት ቢፈስበትም፣
የዝገቱ ክምር፣
በእሳት እንኳ፣ ሊለቅ አልቻለም።

13“ ‘የረከስሽው በብልግናሽ ነው፤ ቍጣዬ
በአንቺ ላይ እስኪፈጸም ድረስ ከእንግዲህ
ንጹሕ አትሆኚም፤ ከርኵሰትሽ ላነጻሽ ፈልጌ፣
መንጻት አልወደድሽምና።
14“ ‘እኔ *እግዚአብሔር* ተናግሬአለሁ፤ የም
ሠራበትም ጊዜ ደርሶአል፤ ወደ ኋላ
አልልም፤ አልራራም፤ አላመነታምም። እንደ
መንገድሽና እንደ ተግባርሽ ይፈረድብሻል፤
ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*።’ ”

**የሕዝቅኤል ሚስት መሞት**

15*የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል ወደ
እኔ መጣ፤ 16“የሰው ልጅ ሆይ፤ የዐይንህ
ማረፊያ የሆነውን ነገር በመቅሠፍት እወስ
ድብሃለሁ፤ አንተ ግን ዋይታ አታሰማ፤
አታልቅስ፤ እንባህንም አታፍስስ፤ 17ድምፅ
ህን ዝቅ አድርገህ በሐዘን አንጐራጕር
እንጂ ለሞተው አታልቅስ። ጥምጥምህን
ከራስህ አታውርድ፤ ጫማህንም አታውልቅ፤
አፍህ ድረስ አትሸፋፈን፤ የዕዝን እንጀራም
አትብላ።”
18እኔም በማለዳ ለሕዝቡ ተናገርሁ፤ ሚስ
ቴም ማታውኑ ሞተች፤ በማግሥቱም ጠዋት
እንደ ታዘዝሁ አደረግሁ።
19ሕዝቡም፣ “ይህን ስታደርግ ለእኛ
የም ታስተላልፈው መልእክት ምን እንደ
ሆነ አትነግረንምን?” አሉኝ።
20እኔም እንዲህ አልኋቸው፤ “*የእግዚአብሔር*
ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፤ 21ለእስ
ራኤል ቤት እንዲህ በል፤ ‘ጌታ *እግዚአ
ብሔር* እንዲህ ይላል፤ “የኀይላችሁን ትም
ክሕት፣ የዐይናችሁ ማረፊያና የልባችሁ
ደስታ የሆነውን መቅደሴን አረክሳለሁ።
ትታችኋቸው የሄዳችሁ ወንድና ሴት ልጆ
ቻችሁ በሰይፍ ይወድቃሉ። 22እኔ እንዳደ
ረግሁም ታደርጋላችሁ፤ አፋችሁ ድረስ
አትሸፋፈኑም፤ የዕዝን እንጀራም አትበሉም፤
23ጥምጥማችሁን ከራሳችሁ አታወርዱም፤
ጫማችሁንም አታወልቁም። በኀጢአታችሁ
ትመነምናላችሁ፤ እርስ በርስ ታቃስታላችሁ
እንጂ ሐዘን አትቀመጡም፤ አታለቅሱምም።
24ሕዝቅኤል ምልክት ይሆናችኋል፤ እርሱ
እንዳደረገው ታደርጋላችሁ፤ ይህ
በሚሆንበት ጊዜ እኔ ጌታ *እግዚአብሔር*
እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ።’ ”
25“አንተም የሰው ልጅ ሆይ፤
ኀይላቸውን፣ ደስታቸውንና፣ ክብራቸውን፣
የዐይናቸው ማረፊያና የልባቸው ደስታ

20፥38፤24፥13
24፥1 ሕዝ8፥1፤
26፥1፤29፥17
24፥2 2ነገ25፥1፤
ኢሳ30፥8፤ኤር39፥1፤
ዕን2፥2
24፥3 ኢሳ1፥2፤
ሕዝ 2፥3፡6፤11፥3፤
20፥49
24፥4 ሕዝ11፥7
24፥5 ኢሳ34፥12፤
ኤር52፥10፡24-27፤
ሚክ3፥2-3
24፥6 ኢዮ6፥27፤
ሕዝ11፥11፤16፥23፤
22፥2፤ኢል3፥3፤
አብ1፥11፤ናሆ3፥10
24፥7 ዘሌ17፥13
24፥11 ኤር21፥10
24፥13 ኢሳ22፥14፤
ኤር6፥28-30፤
ሰቆ1፥9፤ሕዝ16፥42፤
22፥24፤23፥36-49፤
ሆሴ7፥1፤ዘካ6፥8
24፥14 ዘኍ11፥23፤
ኢዮ27፥22፤ኢሳ3፥11፤
ሕዝ8፥18፤18፥30፤
22፥14፤36፥19፤
ዘካ8፥14
24፥16 ቍ21፤
መዝ39፥10፤84፥1፤
ኤር13፥17፤16፥5፤
22፥10፤ሰቆ2፥4
24፥17 ቍ22፤
ዘፀ28፥39፤
ዘሌ13፥45፤
መዝ39፥9፤ኢሳ3፥20፤
20፥2፤ኤር16፥7
24፥18 ሕዝ12፥7
24፥19 ሕዝ12፥9፤
37፥18
24፥21 ቍ16፤
ዘሌ26፥19፤26፥31፤
መዝ27፥4፤ኤር7፥14፡
15፤ሕዝ7፥24፤23፥25፤
ሆሴ9፥12፡16፤
ሚል2፥12
24፥22 ዘሌ13፥45፤
ኤር16፥7
24፥23 ዘፀ28፥39፤
33፥4፤ዘሌ26፥16፤
መዝ78፥64፤
ኢሳ3፥20፤20፥2
24፥24 ኢሳ20፥3፤
ሕዝ1፥3፤12፥11
24፥25 ዘዳ28፥32፤
መዝ20፥4፤
ኤር11፥22፤ሰቆ2፥4

የሆኑትን ወን ድና ሴት ልጆቻቸውን
ጭምር በምወስድ ባቸው ቀን፣ 26በዚያን
ቀን፣ ያመለጠ ሰው ይህን ወሬ ሊነግርህ
ወደ አንተ ይመጣል፤ 27በዚያን ቀን አፍህ
ተከፍቶ ከእርሱ ጋር ትነጋገራለህ፤ ከዚያም
በኋላ እንደ ድዳ አት ሆንም፤ ምልክትም
ትሆናቸዋለህ፤ እኔም *እግዚአብሔር*
እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።”

## በአሞን ላይ የተነገረ ትንቢት

25 *የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤ 2“የሰው ልጅ ሆይ፤
ፊትህን ወደ አሞናውያን አድርገህ፣ ትንቢት
ተናገርባቸው፤ 3እንዲህም በላቸው፤ ‘የጌታ፣
*እግዚአብሔርን* ቃል ስሙ፤ ጌታ *እግዚ
አብሔር* እንዲህ ይላል፤ “መቅደሴ በረከሰ
ጊዜ፣ የእስራኤልም ምድር ባድማ በሆነች
ጊዜ፣ የይሁዳም ቤት ተማርኮ በተወሰደ
ጊዜ፣ ‘እሰይ’ ብላችኋልና፣ 4ለምሥራቅ ሕዝብ
ትገዙ ዘንድ አሳልፌ እሰጣችኋለሁ፤ እነር
ሱም በመካከላችሁ ይሰፍራሉ፤ ድንኳኖቻቸ
ውንም በዚያ ይተክላሉ፤ ፍሬያችሁን ይበ
ላሉ፤ ወተታችሁንም ይጠጣሉ። 5የራባን
ከተማ የግመሎች መሰማሪያ፣ አሞንንም
የበጎች መመሰጊያ አደርጋለሁ፤ በዚያን ጊዜ
እኔ *እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ ታውቃላ
ችሁ።” 6ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላ
ልና፤ “በልባችሁ ክፋት ሁሉ፣ በእስራኤል
ውድቀት ላይ በመደሰት በእጃችሁ አጨብ
ጭባችኋልና፤ በመዝለልም ጨፍራችኋልና
7ክንዴን በእናንተ ላይ አነሣለሁ፤ በአሕዛብ
እንድትበዘበዙ አደርጋለሁ፤ ከሕዝቦች መካ
ከል አውጥቼ፣ ከአገሮችም ለይቼ አጠፋች
ኋለሁ፤ እደመስሳችኋለሁም። በዚያን ጊዜ
እኔ *እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ ታውቃ
ላችሁ።’ ”

## በሞዓብ ላይ የተነገረ ትንቢት

8“ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
‘ሞዓብና ሴይር፣ “እነሆ የይሁዳ ቤት እንደ
ሌሎቹ አሕዛብ ሁሉ ሆነ” ብለዋልና፤ 9በም
ድሪቱ ድንበር ላይ ካሉትና ክብሯ ከሆ
ኑት ከተሞች ከቤትየሺሞት፣ ከበአልሜዎ
ንና ከቂርያታይም ጀምሬ የሞዓብን ዐምባ
እገልጣለሁ። 10ሞዓባውያንንም ከአሞናውያን
ጋር ይገዙላቸው ዘንድ ለምሥራቅ ሕዝብ
አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ፤ አሞናውያን በአሕ
ዛብ ዘንድ ከእንግዲህ መታሰቢያ አይኖራ
ቸውም። 11ሞዓብንም እቀጣለሁ፤ በዚያን ጊዜ
እኔ *እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።’ ”

## በኤዶም ላይ የተነገረ ትንቢት

12“ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
‘ኤዶም የይሁዳን ቤት ተበቅሎአልና፤ በዚ

24÷26 1ሳሙ4÷12፤ ኢዮ1÷15-19
24÷27 ሕዝ3÷26፤ 33÷22፤ዳን10÷15
25÷2 ኤር49÷1-6፤ ሕዝ13÷17፤21÷28፤ 29÷2
25÷3 መዝ35÷21፤ ምሳ17÷5፤ሕዝ26÷2፤ 36÷2፤ሶፎ2÷8
25÷4 ዘፍ25÷6፤ ዘኍ31÷10፤ ዘዳ28÷33:51፤ መሳ6÷3:33
25÷5 ዘዳ3÷11፤ ኢሳ17÷2
25÷6 ዘኍ24÷10፤ ሕዝ6÷11፤አብ1÷12፤ ሶፎ2÷8
25÷7 ቍ13-14:17፤ ዘኍ14÷3፤ ሕዝ21÷31፤ አሞ1÷14-15፤ሶፎ1÷4
25÷8 ዘፍ14÷6፤ 19÷37፤ዘዳ23÷6፤ ኢሳ16÷6
25÷9 ዘኍ32÷3: 37፤33÷49፤ ኢሱ13÷17:19
25÷10 ሕዝ21÷32
25÷11 ኢሳ15÷9፤ 16÷1-14፤ኤር48÷1፤ አሞ2÷1-3
25÷12 2ሳሙ8÷ 13-14፤2ዜና28÷17፤ ኢሳ11÷14
25÷13 ዘፍ36÷11: 15:34፤ዘፀ7÷5፤ ኤር 25÷23፤49÷10፤ ሕዝ14÷17፤16÷27፤ 29÷8
25÷14 መዝ137÷7፤ ሕዝ32÷29፤35÷2 -3:11፤36÷5፤አሞ1÷ 11፤አብ1÷1:10-16፤ ሚል1÷4
25÷15 ኢሱ13÷3፤ 2ዜና28÷18፤መዝ 73÷8
25÷16 1ሳሙ30÷ 14፤2ዜና26÷6፤ሕዝ 20÷33፤አሞ1÷8
25÷17 ዘፀ6÷2፤ 8÷22፤ዘኍ31÷3፤ ኢሳ11÷14፤14÷30፤ ኤር44÷13፤47÷7፤ ኢል3÷4
26÷1 ሕዝ24÷1፤ 29÷1፤30÷20
26÷2 ኢሱ19÷29፤ 2ሳሙ5÷11፤ሕዝ 25÷3
26÷3 ቍ19፤ኢሳ 5÷30፤ኤር50÷42፤ 51÷42
26÷4 ኢሳ23÷1:11፤ አሞ1÷10
26÷5 ዘኍ14÷3፤ ሕዝ27÷32፤29÷19፤ 47÷10፤ዘካ9÷2-4
26÷7 ዕዝ7÷12፤ ኤር27÷6፤39÷1፤ሕዝ

ህም በደለኛ ሆኖአልና፤ 13ጌታ *እግዚአብሔር*
እንዲህ ይላል፤ “ክንዴን በኤዶም ላይ አነ
ሣለሁ፤ ሰዎቹንና እንስሶቻቸውን እገድላ
ለሁ፤ ባድማ አደርጋታለሁ፤ ከቴማንም
ጀምሮ እስከ ድዳን ድረስ በሰይፍ ይወድ
ቃሉ። 14በሕዝቤ በእስራኤል አማካይነት
ኤዶምን እበቀላለሁ፤ እነርሱም እንደ ቍጣ
ዬና እንደ መዓቴ መጠን በኤዶም ሕዝብ
ላይ ያደርጋሉ፤ ኤዶማውያንም በቀሌን
ያውቃሉ፤ ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*።’ ”

## በፍልስጥኤም ላይ የተነገረ ትንቢት

15“ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ ‘ፍል
ስጥኤማውያን በቂም ተነሣሥተው በክፉ
ልብ ተበቅለዋልና፣ ይሁዳንም በቈየ ጠ
ላትነት ለማጥፋት ፈልገዋልና፤ 16ስለዚህ
ጌታ *እግዚ አብሔር* እንዲህ ይላል፤
“ክንዴን በፍልስ ጥኤማውያን ላይ
አነሣለሁ፤ ከሊታውያንንም እቈርጣለሁ፤
በባሕሩ ጠረፍ ላይ የቀሩትንም አጠፋለሁ።
17በታላቅ በቀል እበቀላቸዋለሁ፤ በመዓቴም
እቀጣቸዋለሁ፤” በምበቀላቸውም ጊዜ፣ እኔ
*እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ ያው ቃሉ።’ ”

## በጢሮስ ላይ የተነገረ ትንቢት

26 በዐሥራ አንደኛው ዓመት፣ በመጀ
መሪያው ቀን፣ *የእግዚአብሔር* ቃል
እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፤ 2“የሰው ልጅ
ሆይ! ጢሮስ ስለ ኢየሩሳሌም፣ ‘እሰይ! የሕ
ዝቦች በር ተሰበረች፤ ደጆቿም ወለል ብለው
ተከፈቱልኝ፤ እንግዲህ እርሷ ስለ ፈራረሰች
እኔ እከብራለሁ’ ብላለችና፤ 3ስለዚህ ጌታ
*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ ‘ጢሮስ ሆይ፤
እነሆ በአንቺ ላይ ተነሥቻለሁ፤ ባሕር ሞገዷን
እንደምታስነሣ፣ ብዙ ሕዝብ አስነሣብሻለሁ።
4የጢሮስን ቅጥሮች ያወድማሉ፤ ምሽጎቿ
ንም ያፈርሳሉ። ዐፈሯን ከላይዋ ጠርጌ
የተራቈተ ዐለት አደርጋታለሁ። 5እኔ ልዑል
*እግዚአብሔር* ተናግሬአለሁና፤ በባሕር
ውስጥ የመረብ ማስጫ ቦታ ትሆናለች፤
አሕዛብም ይበዘብዟታል፤ 6መኻል አገር
ያሉ ሰፈሮቿም በሰይፍ ይወድማሉ፤ በዚያን
ጊዜ እኔ *እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ
ያውቃሉ።
7“ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላልና፤
‘የነገሥታት ንጉሥ የሆነውን የባቢሎንን
ንጉሥ ናቡከደነፆርን[ኸ] ከፈረሶችና ከሠረገ
ሎች ጋር፣ ከፈረሰኞችና ከታላቅ ሰራዊትም
ጋር ከሰሜን በጢሮስ ላይ አመጣለሁ።
8እርሱ መኻል አገር ያሉ ሰፈሮችሽን በሰ

23÷24፤ናሆ2÷3-4 26÷8 ኤር6÷6፤ 33÷4

[ኸ]7 በዕብራይስጥ *ናቡከደነፆር* የሚለው ቃል አማራጭ ትርጒም *ናቡከነፆር* ነው፤ በዚህ ክፍልና በአብዛኛው በሕዝቅኤልና በኤርምያስ መጽሐፍ ውስጥ እንደዚሁ ነው

ይፍ ያወድማቸዋል፤ በዙሪያሽ ካብ ይክባል፤
እስከ ቅጥሮችሽ ጫፍ ድረስ ዐፈር ይደለድ
ልብሻል፤ ጋሻውንም በአንቺ ላይ ያነሣል።
9ግንብ መደርመሻውን በቅጥሮቿ ላይ ያነጣ
ጥራል፤ በመሣሪያም ምሽጎችሽን ያፈርሳል።
10ከፈረሶቹ ብዛት የተነሣ ዐቧራ ይሸፍንሻል፤
ሰዎች ቅጥሮችዋ ወደ ፈረሱ ከተማ እንደ
ሚገቡ እርሱ በበሮችሽ በሚገባበት ጊዜ፣
ከፈረሶቹና ከጋሪዎቹ፣ ከሠረገሎቹም ድምፅ
የተነሣ ቅጥሮችሽ ይናወጣሉ። 11መንገዶችሽ
ሁሉ በፈረሶቹ ኰቴ ይረጋገጣሉ፤ ሕዝብሽን
በሰይፍ ይገድላል፤ ታላላቅ ምሰሶዎችሽ ወደ
ምድር ይወድቃሉ። 12ሀብትሽን ይዘርፋሉ፤
ሸቀጥሽን ይበዘብዛሉ፤ ቅጥሮችሽን ያፈርሳሉ፤
የተዋቡ ቤቶችሽን ያወድማሉ፤ ድንጋይሽን፣
ዕንጨትሽንና የግንቦች ፍርስራሽ ወደ ባሕር
ይጥላሉ። 13ዘፈንሽን ጸጥ አደርጋለሁ፤ ከእንግ
ዲህም የበገናሽ ድምፅ አይሰማም። 14የተራ
ቈተ ዐለት አደርግሻለሁ፤ የመረብ ማስጫ
ቦታ ትሆኛለሽ፤ እንደ ገናም ተመልሰሽ
አትሠሪም እኔ እግዚአብሔር
ተናግሬአለሁና፤ ይላል ጌታ እግዚአብሐ
ር።"

15"ጌታ እግዚአብሔር ጢሮስን እንዲህ
ይላል፤ 'የቈሰሉት ሲያቃስቱ፣ በውስጥሽም
ጭፍጨፋ ሲካሄድ፣ ከውድቀትሽ ድምፅ
የተነሣ ደሴቶች አይነዋወጡምን? 16የባሕር
ጠረፍ መሳፍንት ሁሉ ከዙፋኖቻቸው ይወ
ርዳሉ፤ መጐናጸፊያቸውን ይጥላሉ፤ ወርቀ ዘቦ
ልብሳቸውን ያወልቃሉ። ፍርሀት ተከናንበው
በመሬት ላይ በመቀመጥ ባለማቋረጥ፣ እየተ
ንቀጠቀጡ በአንቺ ላይ በደረሰው ነገር
ይሸበራሉ፤' 17ስለ አንቺም እንዲህ ብለው
ሙሾ ያወርዳሉ፤

"በባሕር ሰዎች የሚኖሩብሽ፣
ባለዝናዋ ከተማ ሆይ፤ እንዴት ጠፋሽ!
ከነዋሪዎችሽ ጋር፣
የባሕር ላይ ኀያል ነበርሽ፤
በዚያ በሚኖሩትም ሁሉ ዘንድ
የተፈራሽ ነበርሽ።
18አሁን በመውደቂያሽ ቀን፣
በጠረፍ ያሉ አገሮች ተናወጡ፤
ከመፍረስሽም የተነሣ፤
በባሕር ውስጥ ያሉ ደሴቶች ተደናገጡ።'
19"ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
'ሰው እንደማይኖርባቸው ከተሞች ባድማ
ሳደርግሽ፣ የውቅያኖስንም ውሃ በላይሽ
አድርጌ በቀላይ ስሸፍንሽ፣ 20የጥንት ዘመን
ሰዎች ወደ ገቡበት ጕድጓድ ከሚወርዱት
ጋር አወርድሻለሁ፤ ወደ ጕድጓድ ከሚወር
ዱት ጋር በጥንቱ ፍርስራሽ ከምድር በታች
አኖርሻለሁ፤ ከዚህም በኋላ በሕያዋን ምድር

26፥9 ሕዝ21፥12
26፥10 ኤር4፥13፤ 46፥9፤23፥24
26፥11 ኢሳ5፥28፤ 26፥5፤ኤር43፥13
26፥12 ኢሳ23፥8፤ ኤር4፥7፤ሕዝ27፥3 -27፤28፥8፤ዕን1፥8
26፥13 ኢዮ30፥31፤ መዝ137፥2፤ኢሳ 14፥11፤23፥7፤ኤር7 ፥34፤16፥9፤25፥10፤ ራእ18፥22
26፥14 ኢዮ12፥14፤ ሚል1፥4
26፥15 ኢዮ24፥12፤ ኢሳ41፥5፤ኤር49፥21፤ ሕዝ27፥35
26፥16 ዘፀ26፥36፤ ዘሌ26፥32፤ኢዮ2፥8፡ 13፤8፥22፤ሕ ዝ32፥10
26፥17 ኢሳ14፥12፤ ሕዝ19፥1
26፥18 መዝ46፥6፤ ኢሳ23፥5፤41፥5፤ ኤር49፥21፤ሕዝ27፥35
26፥19 ቍ3፤ ዘፍ7፥11፤ኢሳ8፥7-8
26፥20 ዘኍ16፥30፤ ኢዮ28፥13፤ መዝ 28፥1፤88፥6፤ ኢሳ14፥9-10፤ ሕዝ31፥14፤32፥18፤ አሞ9፥2፤ዮና2፥2፡6
26፥21 ኤር20፥4፤ 51፥64፤ሕዝ27፥36፤ 28፥19፤ዳን11፥19፤ ራእ18፥21
27፥2 ሕዝ19፥1
27፥3 ቍ33፤ መዝ 83፥7፤ኢሳ23፥9፤ ሕዝ16፥15፤ሆሴ9፥13
27፥4 ሕዝ28፥12
27፥5 ዘዳ3፥9፤ ኢሳ2፥13
27፥6 ዘፍ10፥4፤ ዘኍ21፥33፤ መዝ29፥9፤ ኢሳ23፥12፤ ኤር22፥20፤ ዘካ11፥2
27፥7 ዘፍ10፥4፤ ዘፀ25፥4፤26፥36፤ ኢሳ19፥9፤ኤር10፥9
27፥8 ዘፍ10፥18፤ 1ነገ9፥27
27፥9 ኢሱ13፥5፤ መዝ104፥26
27፥10 ዘፍ10፥6፤ 2ዜና36፥20፤ዕ ዝ1፥1፤ ኢሳ66፥19፤ ሕዝ30፥5፤38፥5፤ ዳን8፥20፤ናሆ3፥9፤ ማሕ4፥4
27፥11 ቍ27

ተመልሰሽ ቦታ አታገኚም፤[ሠ] 21መጨረሻሽን
አሳዛኝ አደርጋለሁ፤ ከእንግዲህም አትኖሪም፤
ትፈለጊያለሽ፤ ከቶም አትገኚም፤ ይላል ጌታ
እግዚአብሔር።'"

### ለጢሮስ የወጣ ሙሾ

27 የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤ 2"የሰው ልጅ ሆይ፤
ስለ ጢሮስ ሙሾ አውርድ፤ 3በባሕር መግቢያ
ላይ ለምትገኘውና በብዙ ጠረፎች ከሚ
ኖሩ ሕዝቦች ጋር ለምትነግደው ለጢሮስ
እንዲህ በላት፤ 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤
" 'ጢሮስ ሆይ!፤
"ፍጹም ውብ ነኝ" ብለሻል፤
4ዳርቻሽ በባሕር መካከል ነው፤
ሠሪዎችሽም ፍጹም ውብ አድርገውሻል።
5ሳንቃዎችሽን ሁሉ፣
ከሳኔር[ሀ] በመጣ ጥድ ሠሩ፤
ደቀልንም ይሠሩልሽ ዘንድ፤
ከሊባኖስ ዝግባ አመጡ።
6ከባሳን በመጣ ወርካ፣
መቅዘፊያሽን ሠሩ፤
ከቆጵሮስ[ለ] ጠረፍ በመጣ ዝግባ፣[ሐ]
በዝሆን ጥርስ ለብጠው ወለልሽን ሠሩ።
7የመርከቦችሽ ሸራ ጥልፍ ሥራ ያለበት
የግብፅ በፍታ ነበረ፤
ይህም እንደ ዐርማ አገለገለሽ።
መጋረጃዎችሽ ከኤሊሳ ጠረፍ የመጡ፣
ባለ ሰማያዊና ሐምራዊ ቀለም ነበሩ።
8ቀዛፊዎችሽ ከሲዶናና ከአራድ የመጡ
ነበሩ፤
ጢሮስ ሆይ፤ የራስሽ ጠቢባን የመር
ከቦችሽ መሪዎች ነበሩ።
9ልምድ ያካበቱ የጌባል[መ] ባለሙያዎች፣
መርከብሽን ለመገጣጠም በመካከልሽ
ነበሩ፤
የባሕር መርከቦችና መርከበኞቻቸው ሁሉ፣
ከአንቺ ጋር ሊገበያዩ ይመጡ ነበር።
10" 'የፋርስ፣ የሉድና የፉጥ ሰዎች፣
ወታደር ሆነው በሰራዊትሽ ውስጥ
አገለገሉ፤
ሞገስም ይሆኑሽ ዘንድ፣
ጋሻቸውንና የራስ ቍራቸውን
በግድግዳሽ ላይ ሰቀሉ።
11የአራድና የሔሌክ ሰዎች፣
ቅጥርሽን በየአቅጣጫው ጠበቁ፤
የገማድ ሰዎችም፣ በምሽግሽ ውስጥ ነበሩ።

[ሠ]20 ከሰብዓ ሊቃናት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን በዕብራይስጡ ግን *ተመላሽ፤ ክብርን እሰጣለሁ* ይላል
[ሀ]5 ሄርሞንን ማለት ነው
[ለ]6 ዕብራይስጡ *ኪቲም* ይለዋል
[ሐ]6 በታርጕምም እንዲሁ ሲሆን የማሶሬቱ መጽሐፍ የድምፅ ተቀባዮች ፊደል አከፋፈል ግን የተለየ ነው
[መ]6 ባይብሎስ ማለት ነው

ጋሻቸውንም በቅጥርሽ ዙሪያ ሰቀሉ፤
ውበትሽንም ፍጹም አደረጉ።

12“ ‘ከሀብትሽ ብዛት የተነሣ፣ ተርሴስ
ከአንቺ ጋር የንግድ ልውውጥ ታደርግ ነበር፤
ብርና ብረት፣ ቈርቈሮና እርሳስ አምጥታ
ሸቀጥሽን ትለውጥ ነበር።
13“ ‘ያዋን፣ ቶቤልና ሞሳሕ ከአንቺ ጋር
ይነግዱ ነበር፤ ባሪያዎችንና የናስ ዕቃዎችን
በሸቀጥሽ ይለውጡ ነበር።
14“ ‘የቤት ቴርጋማ ሰዎችም መጋዣዎችን፣
የጦር ፈረሶችንና በቅሎዎችን በሸቀጥሽ
ለወጡ።
15“ “የድዳን[ዶ] ሰዎች ከአንቺ ጋር ተገበያዩ፤
ብዙ የጠረፍ አገሮችም የንግድ ደንበኞችሽ
ነበሩ፤ በዝኆን ጥርስና በዞጲ ሸቀጥሽን ይገዙ
ነበር።
16“ ‘ምርትሽ ብዙ እንደ መሆኑ፣ ሶርያ[ጀ]
ከአንቺ ጋር ትገበያይ ነበር፤ ሸቀጥሽንም
በበሉር፣ በሐምራዊ ጨርቅ፣ በወርቀ ዘቦ፣
በጥሩ በፍታ፣ በዛጐልና በቀይ ዕንቍ
ይለውጡ ነበር።
17“ ‘ይሁዳና እስራኤል እንኳ ከአንቺ
ጋር ተገበያይተዋል፤ የሚኒትን ስንዴ፣
ጣፋጭ ቂጣ፣[ገ] ማር፣ ዘይትና በለሳን በ
ማምጣት በሸቀጥሽ ይለውጡ ነበር።
18“ ‘ከሀብት ከንብረትሽ ብዛት የተነሣ፣
ደማስቆ የኬልቦንን የወይን ጠጅና፣ የዛሐ
ርን የበግ ጠጕር በማቅረብ ከአንቺ ጋር
ተገበያይታለች።
19“ ‘ዌንዳንና ያዋን ከኦሴል መጥተው
ከአንቺ ጋር የንግድ ልውውጥ ያደርጉ ነበር፤
ቀልጦ የተሠራ ብረትን፣ ብርጕድንና ቀረፋን
በሸቀጥሽ ይለውጡ ነበር።
20“ ‘ድዳን ግላስ በማቅረብ ከአንቺ ጋር
ትነግድ ነበር።
21“ ‘የዐረብና የቄዳር መሳፍንት ሁሉ ደምበ
ኞችሽ ነበሩ፤ ጠቦትና አውራ በግ፣ ፍየልም
አምጥተው ከአንቺ ጋር ይገበያዩ ነበር።
22“ “የሳባና የራዕማ ነጋዴዎች ከአንቺ ጋር
ይገበያዩ ነበር፤ ምርጥ የሆነውን የሽቱ
ቅመም ዐይነት ሁሉ፣ የከበረ ድንጋይና
ወርቅ በማቅረብ በሸቀጥሽ ይለውጡ ነበር።
23“ ‘ካራን፣ ካኔ፣ ዔደን፣ የሳባ ነጋዴዎች፣
አሦርና ኪልማድ ከአንቺ ጋር የንግድ ልው
ውጥ ያደርጉ ነበር። 24እነዚህም በገበያሽ
ውስጥ ያማረ ልብስ፣ ሰማያዊ ካባ፣ ወርቀ
ዘቦ እንዲሁም በኅብረ ቀለም ያሸበረቀና
በጥብቅ የተታታ ስጋጃ በማቅረብ ከአንቺ
ጋር ይነግዱ ነበር።

25“ ‘የተርሴስ መርከቦች፣
ሸቀጥሽን አጓጓዡልሽ፤
በባሕር መካከልም፣
በከባድ ጭነት ተሞልተሽ ነበር።
26ቀዛፊዎችሽ፣
ወደ ጥልቁ ባሕር ይወስዱሻል፤
የምሥራቁ ነፋስ ግን፣
በባሕሩ መካከል ይሰባብርሻል።
27የመርከብ አደጋ በሚደርስበሽ ቀን፣
ሀብትሽ፣ ሸቀጥሽና የንግድ ዕቃሽ፣
መርከብ ነጂዎችሽ፣ መርከበኞችሽና
መርከብ ሠሪዎችሽ፣
ነጋዴዎችሽና ወታደሮችሽ ሁሉ፣
በመርከብ ላይ ያሉትም ሁሉ፣
ወደ ባሕሩ ወለል ይዘቅጣሉ።
28መርከበኞችሽ ሲጮኹ፣
የባሕሩ ጠረፍ ይናወጣል።
29ቀዛፊዎች ሁሉ፣
መርከባቸውን ጥለው ይሄዳሉ፤
መርከብ ነጂዎችና መርከበኞችም ሁሉ፣
ወርደው ባሕሩ ዳር ይቆማሉ፤
30ድምፃቸውን ከፍ አድርገው፣
በምሬት ያለቅሱልሻል፤
በራሳቸውም ላይ ዐቧራ ነስንሰው፣
በዐመድ ላይ ይንከባለላሉ።
31ስለ አንቺ ጠጕራቸውን ይላጫሉ፤
ማቅም ይለብሳሉ፤
በነፍስ ምሬት፣
በመራራም ሐዘን ያለቅሱልሻል።
32ስለ አንቺ በዋይታ ያለቅሳሉ፤
እንዲህም እያሉ ሙሾ ያወርዳሉ፤
“ባሕር ውጦት የቀረ፣
እንደ ጢሮስ ማን አለ?”
33ሸቀጥሽ ከባሕር በወጣ ጊዜ፤
ብዙ ሕዝቦችን ታጠግቢ ነበር፣
በታላቅ ሀብትሽና ሸቀጥሽ፣
የምድርን ነገሥታት ታበለጽጊ ነበር።
34አሁን ግን በጥልቅ ውሃ ውስጥ፣
በባሕር ተንኰታኵተሻል፤
ጭነትሽና ተሳፋሪዎችሽ ሁሉ፣
ከአንቺ ጋር ሰጥመዋል።
35በጠረፍ አገር የሚኖሩ ሁሉ፣
በአንቺ ሁኔታ ተደናገጡ፤
ንጉሦቻቸው በፍርሀት ራዱ፤
ፊታቸውም ተለዋወጠ።
36በሌሎች ሕዝቦች መካከል ያሉ ነጋዴዎች
ምንኛ አፏጩብሽ!

27፥12 ቈ18፡33፤ ዘፍ10፥4
27፥13 ዘፍ10፥2፤ ኢሳ66፥19፤ ሕዝ32፥26፤38፥2፤ 39፥1፤ኢል3፥6፤ ራእ18፥13
27፥14 ዘፍ10፥3
27፥15 ዘፍ10፥7፤ 1ነገ10፥22፤ ኤር25፥22፤ራእ18፥12
27፥16 ዘፀ28፥18፤ 39፥11፤መሳ10፥6፤ ኢዮ28፥18፤ ኢሳ7፥1-8፤ሕዝ16፥10፤ 28፥13
27፥17 ዘፍ43፥11፤ መሳ11፥33፤1ነገ5፥9 ፤ሐሥ12፥20
27፥18 ቈ12፤ ዘፍ14፥15፤ ሕዝ47፥16-18
27፥19 ዘፍ10፥2፡ 27፤ዘፀ30፥24
27፥20 ዘፍ10፥7
27፥21 ዘፍ25፥13፤ 2ዜና9፥14፤ ኢሳ21፥17
27፥22 ዘፍ10፥7፡ 28፤43፥11፤ ራእ18፥22
27፥23 ዘፍ10፥22፤ 11፥26፤ዘኍ24፥24፤ ኢሳ37፥12
27፥25 ዘፍ10፥4፤ ኢሳ2፥16፤ራእ18፥3
27፥26 ዘፍ41፥6፤ ኤር18፥17
27፥27 ምሳ11፥4፤ ሕዝ28፥8
27፥28 ኤር49፥21
27፥30 ኢሱ7፥6፤ 2ሳሙ1፥2፤ኤር6፥26፤ ራእ18፥18-19
27፥31 ዘሌ13፥40፤ አስ4፥1፤ኢዮ1፥20፤ 3፥20፤ኢሳ3፥17፤ 16፥9፤22፥12፤ ኤር6፥26፤48፥37፤ ሰቆ2፥10፤ሕዝ7፥18፤ ራእ18፥15
27፥32 ኢሳ23፥1 -6፤ሕዝ19፥1፤26፥5
27፥33 ቈ3፡12፤ ሕዝ28፥4-5
27፥34 ዘካ9፥4
27፥35 ዘሌ26፥32፤ ኢዮ18፥20፤ ሕዝ26፥15፡17-18፤ 32፥10
27፥36 መዝ37፥10፡ 36፤ኤር19፥8፤49፥17፤ 50፥13፤ሕዝ26፥21፤ ሶፎ2፥15

[ዶ]15 ከሰብዓ ሊቃናት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን ***ዴዳን*** ይለዋል
[ጀ]16 በአብዛኞዎቹ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆችም እንዲሁ ሲሆን አንዳንድ የጥንት የዕብራይስጥ ቅጆችና ሱርስቱ ግን ***ኤዶም*** ይላሉ
[ገ]17 በዕብራይስጥ የዚህ ቃል ትርጉም አይታወቅም

መጨረሻሽ አስደንጋጭ ሆነ፤
ለዘላለምም አትገኚም፡፡’ ”

## በጢሮስ ንጉሥ ላይ የተነገረ ትንቢት

28 *የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤ 2“የሰው ልጅ ሆይ፤
ለጢሮስ ገዥ እንዲህ በለው፤ ‘ጌታ *እግዚ
አብሔር* እንዲህ ይላል፤

“ ‘ልብህ በትዕቢት ተወጥሮ፣
“እኔ አምላክ ነኝ፤
በአምላክ ዙፋን ላይ፣
በባሕሮችም ልብ ተቀምጫለሁ” አልህ፡፡
ምንም እንኳ እንደ አምላክ ጠቢብ ነኝ
ብለህ ብታስብም፣
አንተ ሰው እንጂ አምላክ አይደለህም፡፡
3ከዳንኤል[ጣ] ይልቅ ጠቢብ ነህን?
ከአንተስ የተሰወረ ምስጢር የለምን?
4በጥበብህና በማስተዋልህ፣
የራስህን ሀብት አከማቸህ፤
ወርቅም ብርም፣
በግምጃ ቤትህ አጠራቀምህ፡፡
5በንግድ ሥራ እጅግ ከመራቀቅህ የተነሣ፣
በሀብት ላይ ሀብት አካበትህ፤
ከሀብትህ ብዛት የተነሣም፤
ልብህ በትዕቢት ተወጠረ፡፡

6“ ‘ስለዚህ ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“ ‘እንደ አምላክ ጥበበኛ ነኝ፤ ብለህ
ስለምታስብ፣
7ከአሕዛብ መካከል እጅግ ጨካኞች
የሆኑትን ባዕዳን፣
በአንተ ላይ አመጣለሁ፤
በጥበብህ ውበት ላይ ሰይፋቸውን ይመዝሉ፤
ታላቅ ክብርህንም ያረክሳሉ፡፡
8ወደ ጕድጓድ ያወርዱሃል፤
በጥልቁም ባሕር ውስጥ፣
በባሕሮችም ልብ ውስጥ አስከፊ ሞት
ትሞታለህ፡፡
9ታዲያ በገዳዮችህ ፊት፣
“አምላክ ነኝ” ትላለህን?
በገዳዮችህ እጅ ስትገባ፣
አንተ ሰው እንጂ አምላክ አይደለህም፡፡
10በባዕዳን እጅ፣
ያልተገረዙትን ሰዎች አሟሟት
ትሞታለህ፤

እኔ ተናግሬአለሁ፤ ይላል ጌታ *እግዚ
አብሔር*፡፡’ ”

11*የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤ 12“የሰው ልጅ ሆይ፤
ስለ ጢሮስ ንጉሥ ሙሾ አውርድ፤ እንዲ
ህም በለው፤ ‘ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤

“ ‘ጥበብን የተሞላህ፣ ፍጹም ውበትን
የተላበስህ፣
የፍጹምነት ምሳሌ ነበርህ፡፡
13በእግዚአብሔር የአትክልት ቦታ፣
በዔድን[ጨ] ነበርህ፤
እያንዳንዱ የከበረ ድንጋይ አስጊጦህ ነበር፤
ሰርድዮን፣ ቶጳዝዮን፣ አልማዝ፣
መረግድ፣ ኢያሰጲድ፣ ሰንፔር፣
በሉር፣ ቢረሌና የከበረ ዕንቍ፡፡[ጸ]
ልብስህም የሚያብረቀርቅ ዕንቍ ወርቅ
ነበር፤
የተዘጋጁትም አንተ በተፈጠርህበት ዕለት
ነበር፡፡
14ጠባቂ ኪሩብ ሆነህ ተቀብተህ ነበር፤
ለዚሁም ሾምሁህ፤
በእግዚአብሔር ቅዱስ ተራራ ላይ ነበርህ፤
በእሳት ድንጋዮች መካከል ተመላለስህ፡፡
15ከተፈጠርህበት ቀን ጀምሮ፣
ክፋት እስከ ተገኘብህ ድረስ፣
በመንገድህ ነቀፌታ አልነበረብህም፡፡
16ንግድህ ስለ ደረጀ፣
በዐመፅ ተሞላህ፣
ኀጢአትም ሠራህ፤
ስለዚህ ከእግዚአብሔር ተራራ በውርደት
አሳደድሁህ፤
ጠባቂ ኪሩብ ሆይ፤ ከእሳት ድንጋዮች
መካከል አስወጣሁህ፡፡
17በውበትህ ምክንያት፣
ልብህ ታበየ፤
ከክብርህ ታላቅነት የተነሣም፣
ጥበብህን አረከስህ፡፡
ስለዚህ ወደ ምድር ወረወርሁህ፤
ለነገሥታት ትዕይንት አደረግሁህ፡፡
18በኀጢአትህና በተጭበረበረው ንግድህ
ብዛት፣
መቅደስህን አረከስህ፡፡
ስለዚህ እሳት ከአንተ እንዲወጣ አደረግሁ፤
እርሱም በላህ፤
በሚመለከቱህ ሁሉ ፊት፣
በምድር ላይ ዐመድ አደረግሁህ፡፡
19የሚያውቁህን አሕዛብ ሁሉ፣
ሁኔታህ አስደንግጦአቸዋል፤
መጨረሻህ የሚያሳዝን ሆነ፤
ከእንግዲህ ሕልውና የለህም፡፡

## በሲዶን ላይ የተነገረ ትንቢት

20*የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤ 21“የሰው ልጅ ሆይ፤
ፊትህን ወደ ሲዶና አዙር፤ ትንቢትም
ተናገርባት፤

[ጣ]3 ወይም *ዳኔል፤* የዕብራይስጡን ቃል አጻጻፍ ስንመለከት ነቢዩ ዳንኤልን ሳይሆን ሌላን ሰው የሚያመለክት ነው
[ጨ]13 ወይም *ላፒስ ላዙሊ*
[ጸ]13 ከእነዚህ የከበሩ ድንጋዮች መካከል አንዳንዶቹ ትክክለኛ ማንነታቸው ተለይቶ አይታወቅም

28፥2 ዘፍ3፥5፤ መዝ9፥20፤82፥6-7፤ ኢሳ13፥11፤14፥13፤ ሕዝ16፥49፤ሶፎ2፥15፤ 2ተሰ2፥4
28፥3 ሕዝ14፥14፤ ዳን1፥20፤2፥20-23፡ 28፤5፥11-12
28፥4 ኢሳ10፥13፤ ዘካ9፥3
28፥5 ኢዮ31፥25፤ መዝ52፥7፤62፥10፤ ኢሳ23፥8፤ኤር9፥23፤ ሕዝ27፥33፤ ሆሴ12፥8፤13፥6
28፥7 ኤር9፥23፤ ሕዝ7፥24፤30፥11፤ ዕን1፥6
28፥8 መዝ55፥23፤ ሕዝ26፥12፤27፥27፤ 32፥30፤ራእ18፥7
28፥9 ኢሳ31፥3፤ ሕዝ16፥49
28፥10 1ሳሙ14፥6፤ ኤር9፥26፤ ሕዝ32፥19፡24
28፥12 ሕዝ19፥1፤ 27፥2-4
28፥13 ዘፍ2፥8፤ ኢሳ14፥11፤ ሕዝ27፥16፤31፥8-9፤ ራእ17፥4፤21፥20
28፥14 ዘፀ25፥17 -20፤30፥26፤40፥9
28፥16 ዘፍ3፥24፤ 6፥11፤ዕን2፥17
28፥17 ኢሳ10፥12፤ ሕዝ16፥49፤19፥12፤ 31፥10
28፥18 አብ1፥18፤ ዘካ9፥2-4፤ሚል4፥3
28፥19 ዘሌ26፥32፤ ኤር51፥64፤ሕዝ 26፥21
28፥21 ዘፍ10፥15፤ ኤር25፥22፤ሕዝ 13፥17

[22]እንዲህም በል፤ ‘ጌታ እግዚአብሔር እን
ዲህ ይላል፤

“ ‘ሲዶን ሆይ፤ በአንቺ ላይ ተነሥቻለሁ፤
በውስጥሽ እከብራለሁ፤
ቅጣትን ሳመጣባት፣
ቅድስናዬንም በውስጧ ስገልጥ፣
እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።
[23]በእርሷ ላይ መቅሠፍት አመጣለሁ፤
በመንገዶቿ ላይ ደም እንዲፈስ
አደርጋለሁ፤
ከየአቅጣጫው በሚመጣ ሰይፍ፣
የታረዱት በውስጧ ይወድቃሉ፤
ከዚያም እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንኩ
ያውቃሉ።

[24]“ ‘ከእንግዲህ ወዲያ የእስራኤል ሕዝብ
የሚያሠቃይ አሜከላና የሚወጋ እሾኽ የሆኑ
ጎረቤቶች አይኖሯቸውም፤ ከዚያም እኔ ጌታ
እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።
[25]“ ‘ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
የእስራኤልን ሕዝብ ከተበተኑባቸው አገሮች
መካከል በምሰበስብበት ጊዜ፣ አሕዛብ እያዩ
ቅድስናዬን በመካከላቸው እገልጣለሁ፤ ከዚ
ያም በገዛ ምድራቸው ይኖራሉ፤ ይህም ለባ
ሪያዬ ለያዕቆብ የሰጠሁት ነው። [26]በዚያም
በሰላም ይኖራሉ፤ ቤቶች ይሠራሉ፤ የወይን
ተክል ቦታም ያበጃሉ። ያጣጣሏቸው ጎረ
ቤቶቻቸውን ሁሉ በምቀጣበት ጊዜ እነ
ርሱ በሰላም ይኖራሉ፤ ከዚያም እኔ እግዚአ
ብሔር አምላካቸው እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።’
”

## በግብፅ ላይ የተነገረ ትንቢት

29 በዐሥረኛው ዓመት፣ በዐሥረኛው
ወር፣ በዐሥራ ሁለተኛው ቀን የእግ
ዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ
መጣ፤ [2]“የሰው ልጅ ሆይ፤ ፊትህን ወደ
ግብፅ ንጉሥ ወደ ፈርዖን አዙር፤ በእርሱና
በግብፅ ሁሉ ላይ ትንቢት ተናገር፤ [3]እንዲ
ህም ብለህ ተናገረው፤ ‘ጌታ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል።

“ ‘በወንዞችህ መካከል የምትተኛ አንተ
ታላቅ አውሬ፣
የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን፤ በአንተ ላይ
ተነሥቻለሁ።
“የዐባይ ወንዝ የእኔ ነው፤
ለራሴም ሠርቼዋለሁ” ትላለህ።
[4]ነገር ግን በመንጋጋህ መንጠቆ አስገባለሁ፤
የወንዞችህን ዓሦች ከቅርፊትህ ጋር
አጣብቃለሁ፤
ቅርፊትህ ላይ ከተጣበቁት ዓሦች ሁሉ ጋር፣
ከወንዞችህ ጐትቼ አወጣሃለሁ።

28፥22 ዘሌ10፥3፤ ሕዝ30፥19፤39፥13
28፥23 ሕዝ5፥17፤ 38፥22
28፥24 ኢሳ5፥6፤ ሕዝ2፥6
28፥25 መዝ106፥47፤ ኢሳ11፥12፤ ኤር12፥15፤23፥8፤ ሕዝ11፥47፤20፥41፤ 34፥27፤37፥25
28፥26 ዘሌ25፥18፤ ዘዳ20፥6፤1ነገ4፥25፤ መዝ149፥9፤ኢሳ 65፥21፤ኤር17፥25፤ 32፥15፤ሕዝ38፥8፤ 39፥26-27፤ሆሴ2፥15፤ 11፥11፤አሞ9፥14 -15
29፥1 ቍ17፤ሕዝ 26፥1
29፥2 ኢሳ19፥1-17፤ ኤር25፥19፤46፥2፤ ሕዝ25፥2፤30፥1-26፤ 31፥1-18፤32፥1-32
29፥3 መዝ68፥30፤ 74፥13፤ኤር44፥30፤ 46፥8፤ሕዝ32፥2
29፥4 2ነገ19፥28፤ ኢዮ41፥2፤ሕዝ38፥4
29፥5 ኤር7፥33፤ 8፥2፤34፥20፤ ሕዝ31 ፥13፤ 32፥4-6፤39፥4
29፥6 2ነገ18፥21
29፥7 2ነገ18፥21፤ ኢሳ36፥6፤ኤር17፥5፤ ሕዝ17፥15-17
29፥8 ሕዝ25፥13፤ 32፥11-13
29፥9 ኤር46፥8፤ ሕዝ30፥7-8፡13-19
29፥10 ዘፀ3፥22፤ 14፥2፤ኢሳ18፥1፤ ኤር 21፥13፤46፥19፤ ሕዝ 30፥4፡6
29፥11 ሕዝ32፥13
29፥12 ኢሳ34፥10፤ ኤር46፥19፤30፥7፡ 23፡26
29፥14 ኢሳ11፥11፤ 19፥22፤ኤር46፥26፤ ሕዝ17፥14፤30፥14
29፥15 ዘካ10፥11
29፥16 ዘኍ5፥15፤ 2ዜና32፥10፤ ኢሳ 20፥5፤30፥2፤ ሰቆ 4፥17፤ሆሴ8፥13
29፥17 ቍ1፤ሕዝ 24፥1፤30፥20፤40፥1
29፥18 ዘፍ49፥15፤ ዘሌ13፥40፤ኢዮ1፥ 20፤ኤር27፥6፤39፥1፤ 48፥37

[5]አንተንና በወንዞችህ ያለውን ዓሣ ሁሉ፣
በምድረ በዳ እጥላለሁ።
በገላጣ መሬት ላይ ትወድቃለህ፤
የሚሰበስብህ፣ የሚያነሣህም አይኖርም።
ለምድር አራዊትና ለሰማይ ወፎች፣
ምግብ እንድትሆን አሳልፌ እሰጥሃለሁ።

[6]ከዚያም በግብፅ የሚኖሩ ሁሉ እኔ
እግዚ አብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።
“ ‘ለእስራኤል ቤት የሸምበቆ በትር ነበ
ርህ፤ [7]በእጃቸው ሲይዙህ ተሰንጥረህ ትከ
ሻቸውን ወጋህ፤ ሲደገፉህም ተሰብረህ ጀርባ
ቸውን አጐበጥ።[*]
[8]“ ‘ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤ ሰይፍ አመጣብሃለሁ፤ ሰዎችህንና
እንስሶቻቸውን እገድላለሁ። [9]ግብፅ ባድ
ማና ምድረ በዳ ትሆናለች፤ ከዚያም እኔ
እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።
“ ‘የዐባይ ወንዝ የእኔ ነው፤ እኔም ሠር
ቼዋለሁ” ብለሃልና፤ [10]ስለዚህ በአንተ ላይ
ተነሥቻለሁ፤ በወንዞችህ ላይ ተነሥቻለሁ፤
የግብፅንም ምድር ከሚግዶል እስከ አስዋን
ከዚያም እስከ ኢትዮጵያ ወሰን ድረስ ፍር
ስራሽና ባድማ አደርጋታለሁ። [11]የሰው እግርም
ሆነ የእንስሳ ኰቴ በውስጧ አያልፍም፤ እስከ
አርባ ዓመት ማንም አይኖርባትም። [12]የግብፅን
ምድር ከጠፉት ምድሮች መካከል እንደ
አንዱ ባድማ አደርጋታለሁ፤ ከተሞቿም
በፈራረሱት ከተሞች መካከል አርባ ዓመት
ባድማ ይሆናሉ፤ ግብፃውያንንም በአሕዛብ
መካከል እበትናቸዋለሁ፤ በአገሮችም
መካከል እዘራቸዋለሁ።
[13]“ ‘ያም ሆኖ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤ ከአርባ ዓመት በኋላ ግብፃውያንን
ከተበተኑበት አገሮች መካከል እሰበስባ
ቸዋለሁ። [14]ከተማረኩበት አመጣቸዋለሁ፤ ወደ
አባቶቻቸው ምድር ወደ ጳትሮስ እመልሳ
ቸዋለሁ። [15]ከመንግሥታት ሁሉ አነስተኛ
ትሆናለች፤ ከሌሎችም አሕዛብ በላይ ራሷን
ከፍ ማድረግ አትችልም። እጅግ ደካማ
አደርጋታለሁ፤ ስለዚህ ሌሎችን አሕዛብ
እንደ ገና መግዛት አትችልም። [16]ግብፅ ከእን
ግዲህ ለእስራኤል ሕዝብ መታመኛ አትሆ
ንም፤ ለርዳታ ወደ እርሷ ዘወር ባሉ ጊዜ
ላደረጉት ኀጢአት ግን መታሰቢያ ትሆናለች።
ከዚያም እኔ ጌታ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ
ያውቃሉ።’ ”
[17]በሃያ ሰባተኛው ዓመት፣ በመጀመሪያው
ወር፣ በመጀመሪያው ቀን የእግዚአብሔር
ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፤ [18]“የሰው
ልጅ ሆይ፤ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር
አስቸጋሪ በሆነ ዘመቻ ሰራዊቱን በጢሮስ

[*]7 በሱርስቱም (በተጨማሪ ሰብዓ ሊቃናትና ቩልጌትን ይመ)
እንዲሁ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን ጀርባቸውን ቀጥ አደረግህ ይላል

ላይ አንቀሳቀሰ፤ የሁሉም ራስ
ተመልጦአል፤ የሁሉም ትከሻ ተልጧል፤
ይሁን እንጂ እር ሱና ሰራዊቱ በጢሮስ ላይ
ካደረጉት ዘመቻ ያተረፉት ነገር የለም።
19ስለዚህ ልዑል እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤ ግብፅን ለባቢሎን ንጉሥ
ለናቡከደነፆር እሰጣለሁ፤ ሀብቷን ሁሉ
ያግዛል፤ ለሰራዊቱም ደመወዝ ይሆን
ዘንድ ምድሪቱን ይበዘብዛል፤ ይመዘብራ
ልም። 20እርሱና ሰራዊቱ ለእኔ
በመልፋታቸው፣ ግብፅን ለድካሙ ዋጋ
ሰጥቼዋለሁ፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።
21"በዚያ ቀን ለእስራኤል ቤት ቀንድ[ፀ]
አበቅላለሁ፤ በመካከላቸውም አፍህን እከፍ
ታለሁ፤ ከዚያም እኔ እግዚአብሔር እንደ
ሆንሁ ያውቃሉ።

## ስለ ግብፅ የወጣ ሙሾ

30 የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤ 2"የሰው ልጅ
ሆይ፤ ትንቢት ተናገር፤ እንዲህም በል፤
'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤

" 'ዋይ! በል፤ እንዲህም በል፤
"ወዮ ለዚያ ቀን!"
3ቀኑ ቅርብ ነው፤
የእግዚአብሔር ቀን ቅርብ ነው፤
የደመና ቀን፣
ለአሕዛብም የጥፋት ቀን ነው።
4በግብፅ ላይ ሰይፍ ይሆናል፤
በኢትዮጵያም ላይ ጭንቀት ይመጣል።
የታረዱት በግብፅ ሲወድቁ፣
ሀብቷ ይወሰዳል፤
መሠረቶቿም ይፈርሳሉ።

5ኢትዮጵያና ፉጥ፣ ልድያና መላው ዐረብ፣
ሊብያና[ፈ] የቃል ኪዳኑ ምድር ሕዝብ ከግ
ብፅ ጋር በአንድነት በሰይፍ ይወድቃሉ።

6" 'እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
" 'የግብፅ ተባባሪዎች ይወድቃሉ፤
የምትኩራራበት ብርታቷ ይወድቃል።
ከሚግዶል እስከ አስዋን፣
በውስጧ በሰይፍ ይወድቃሉ፤
ይላል ጌታ እግዚአብሔር።
7" 'በባድማ መሬቶች መካከል፣
ባድማ ይሆናሉ፤
ከተሞቻቸውም፣
ከፈራረሱ ከተሞች መካከል ይሆናሉ።
8በግብፅ ላይ እሳት ስጭር፣
ረዳቶቿ ሁሉ ሲደቁ፣
በዚያን ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እንደ
ሆንሁ ያውቃሉ፤

9" 'በዚያ ቀን ከእኔ ዘንድ መልእክተኞች
በመርከብ ወጥተው ተዘልላ ከተቀመጠችበት
ሁኔታ ለማውጣት ኢትዮጵያን ያስፈራሯ
ታል፤ ግብፅ በጨለማ በምትዋጥበት ቀን
ጭንቅ ይይዛቸዋል፤ ቀኑ በእርግጥ ይመጣልና።

10" 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
" 'በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነፆር እጅ፣
ስፍር ቍጥር የሌለውን የግብፅን ሕዝብ
እደመስሳለሁ።
11ከአሕዛብ ሁሉ እጅግ ጨካኝ የሆኑት፣
እርሱና ሰራዊቱ፣
ምድሪቱን ለማጥፋት እንዲመጡ ይደረጋል፤
ሰይፋቸውን በግብፅ ላይ ይመዛሉ፤
ምድሪቱንም ሬሳ በሬሳ ያደርጋሉ፤
12የዐባይን ወንዝ ውሃ አደርቃለሁ፤
ምድሪቱን ለክፉ ሰዎች እሸጣለሁ፤
በባዕዳን እጅ፣ ምድሪቷንና በውስጧ
ያለውን ሁሉ ባድማ አደርጋለሁ፤

እኔ እግዚአብሔር ተናግሬአለሁ።

13" 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤

" 'ጣዖታትን አጠፋለሁ፤
በሜምፊስ[ፐ] ያሉትን ምስሎች
እደመስሳለሁ።
ከእንግዲህ በግብፅ ገዥ አይኖርም፣
በምድሪቱም ላይ ፍርሀት እሰዳለሁ።
14ጳጥሮስን ባድማ አደርጋለሁ፤
በጣኔዎስ ላይ እሳት እለኩሳለሁ፤
በቴብስ[ሀ] ላይ ቅጣት አመጣለሁ።
15የግብፅ ምሽግ በሆነችው፣
በሲን ላይ መዓቴን አፈሳለሁ፤
ስፍር ቍጥር የሌለውን የቴብስን ሕዝብ
አጠፋለሁ።
16በግብፅ ላይ እሳት አነዳለሁ፤
ሲን በጭንቅ ትናጣለች፤
ቴብስ በማዕበል ትወሰዳለች፤
ሜምፊስ በማያቋርጥ ጭንቀት ውስጥ
ትገባለች።
17የሄልዮቱና[ለ] የቡባስቱ[ሐ] ጕልማሶች፣
በሰይፍ ይወድቃሉ፤
ከተሞቹ ራሳቸውም ይማረካሉ።
18የግብፅን ቀንበር በምሰብርበት ጊዜ፣
በጣፍናስ ቀኑ ይጨልማል፤
ከዚያም የተኩራራችበት ብርታት
ይንኰታኰታል።
በደመና ትሸፈናለች፤
መንደሮቿም ይማረካሉ።
19ስለዚህ በግብፅ ላይ ቅጣቴን አመጣለሁ፤

[ፀ]21 *ቀንድ* በዚህ ቦታ ጥንካሬን ያመለክታል
[ፈ]5 ዕብራይስጡ *ኩብ* ይላል
[ፐ]13 ዕብራይስጡ *ኖፍ* ይለዋል፤ እንዲሁም በቍ16
[ሀ]14 ዕብራይስጡ *ኖ* ይለዋል፤ እንዲሁም በቍ15 እና 16
[ለ]17 ዕብራይስጡ *አዌን* (*ወይም ኦን*) ይለዋል
[ሐ]17 ዕብራይስጡ *ፊ-ቢሴት* ይላል

**29፥19** ኢሳ19፥4፤ ኤር43፥10-13፤ሕዝ 26፥5፤30፥4፡10፡24 -25፤32፥11
**29፥20** ኢሳ10፥6 -7፤43፥3፤45፥1፤ኤር 25፥9
**29፥21** መዝ132፥17 ፤ሕዝ3፥27፤33፥22፤ ሉቃ1፥69
**30፥2** ኢሳ13፥6፤ ያዕ5፥1
**30፥3** ቍ18፤ ሕዝ7፥7፡12፡19፤32፥7፤ 34፥12፤ኢል1፥15፤ 2፥1፡11፤አብ1፥15
**30፥4** ዘፍ10፥6፤ ኤር25፥19፤ ሕዝ29፥10፡19፤ ዳን11፥43
**30፥5** 2ዜና9፥14፤ ኤር25፥20፤ ሕዝ27፥10፤ናሆ3፥9
**30፥6** ሕዝ29፥10
**30፥7** ሕዝ29፥12
**30፥8** ኤር49፥27፤ ሕዝ29፥9፤39፥6፤ አሞ1፥4፡7፡10፤ ናሆ1፥6
**30፥9** ዘፍ10፥6፤ ኢሳ23፥5፤ ሕዝ32፥9-10፤ ሶፎ2፥12
**30፥10** ኤር39፥1፤ ሕዝ29፥19
**30፥11** ቍ24-25፤ ሕዝ28፥7
**30፥12** ኢሳ19፥6፤ ኤር46፥8፤ሕዝ19፥7፤ 29፥9
**30፥13** ኢሳ19፥13፤ ኤር43፥12፤ሕዝ6፥6፤ ዘካ10፥11
**30፥14** ዘኍ13፥22፤ ኤር46፥25፤ ሕዝ 29፥14
**30፥16** ኢሱ7፥15፤ ኢሳ19፥13
**30፥17** ዘፍ41፥45
**30፥18** ቍ3፤ ዘሌ26፥13፤ኢሳ9፥4፤ ኤር43፥7
**30፥19** ሕዝ28፥22

እነርሱም እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ
ያውቃሉ::’ ”
[20]በዐሥራ አንደኛው ዓመት፣ በመጀመሪ
ያው ወር በሰባተኛው ቀን፣ የእግዚአብሔር
ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፤ [21]“የሰው
ልጅ ሆይ፤ የግብፅን ንጉሥ የፈርዖንን ክንድ
ሰብሬአለሁ፤ ይፈወስ ዘንድ ክንዱ አልተጠ
ገነም፤ ወይም ሰይፍ መያዝ ይችል ዘንድ
እጁ በመቃ አልታሰረም:: [22]ስለዚህ ጌታ
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ በግብፅ ንጉሥ
በፈርዖን ላይ ተነሥቻለሁ፤ ደኅናውንና የተሰ
በረውን፣ ሁለቱንም ክንዶቹን እሰብራለሁ፤
ሰይፉም ከእጁ እንዲወድቅ አደርጋለሁ::
[23]ግብፃውያንን በሕዝቦች መካከል እበትና
ቸዋለሁ፤ በአገሮችም መካከል እዘራቸዋለሁ::
[24]የባቢሎንን ንጉሥ ክንድ አበረታለሁ፤ ሰይ
ፌንም አስይዘዋለሁ፤ የፈርዖንን ክንድ ግን
እሰብራለሁ፤ እርሱም በፊቱ ክፉኛ እንደ
ቈሰለ ሰው ያቃስታል:: [25]የባቢሎንን
ንጉሥ ክንድ አበረታለሁ፤ የፈርዖን ክንድ
ግን ይዝላል፤ ሰይፌን በባቢሎን ንጉሥ
እጅ ሳስይዝ፣ እርሱም ሲነቀንቀው፣ ያኔ
እግዚአብሔር መሆኔን ያውቃሉ:: [26]በሕዝቦች
መካከል እበትናቸዋለሁ፤ በአገሮችም መካ
ከል እዘራቸዋለሁ፤ ከዚያም እኔ እግዚአብሔር
መሆኔን ያውቃሉ::”

## የሊባኖስ ዝግባ

31 በዐሥራ አንደኛው ዓመት፣ በሦስተ
ኛው ወር፣ በመጀመሪያው ቀን
የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ
መጣ፤ [2]“የሰው ልጅ ሆይ፤ ለግብፅ ንጉሥ
ለፈርዖንና ስፍር ቍጥር ለሌለው ሕዝቡ
እንዲህ በል፤

“ ‘በክብር ከአንተ ጋር ማን ሊወዳደር
ይችላል፤
[3]ለጫካው ጥላ የሆኑ የሚያማምሩ
ቅርንጫፎች የነበሩትን፣
እጅግ መለሎ ሆኖ፣
ጫፉ ሰማይ የደረሰውን፣
የሊባኖስን ዝግባ አሦርን ተመልከት::
[4]ውሆች አበቀሉት፤
ጥልቅ ምንጮች አሳደጉት፤
ጅረቶቻቸው ፈሰሱ፤
የሥሮቹንም ዙሪያ ሁሉ አረሰረሱ፤
በመስኩ ላይ ወዳሉት ዛፎች ሁሉ፣
መስኖዎቻቸውን ለቀቁት::
[5]ስለዚህ በደን ካሉት ዛፎች ሁሉ፣
እጅግ ከፍ አለ፤
ቅርንጫፎቹ በዙ፤
ቀንበጦቹ ረዘሙ፤
ከውሃውም ብዛት የተነሣ ተስፋፉ::

30፥20 ሕዝ26፥1፤ 29፥17፤31፥1፤32፥1
30፥21 ኤር30፥13፤ 44፥30፤46፥11፤ 48፥25
30፥22 ዘፍ15፥18፤ መዝ37፥17፤ ኤር46፥25፤ ዘካ11፥17
30፥23 ሕዝ29፥12
30፥24 ኤር51፥52፤ ሕዝ 21፥14፤ ሶፎ 2፥12፤ ዘካ10፥6፡12፤12፥5
30፥25 1ዜና21፥12፤ ኢሳ10፥5፤45፥1፤ ሕዝ29፥19
30፥26 ሕዝ29፥12
31፥1 ኤር52፥5፤ ሕዝ30፥20፤32፥17
31፥3 2ነገ19፥23፤ ኢሳ10፥34፤ ኤር 50፥18፤ ሕዝ19፥11፤ ዕን2፥17፤ዘካ11፥1
31፥4 ሕዝ17፥7፤ ዳን4፥10
31፥5 ቍ10፤ዘኍ 24፥6፤ሕዝ17፥5
31፥6 ዘፍ31፥7-9፤ ሕዝ17፥23፤ማቴ 13፥32
31፥7 ኢዮ14፥9
31፥8 ዘፍ2፥8-9፤ 30፥37፤መዝ80፥10
31፥9 ዘፍ2፥8፤ 13፥10፤ሕዝ28፥13
31፥10 ኢሳ2፥11፤ 14፥13-14፤ሕዝ 28፥17
31፥11 ዳን5፥20
31፥12 ሕዝ28፥7፤ 32፥5፡11-12፤35፥8፤ ዳን4፥14
31፥13 ኢሳ18፥6፤ ሕዝ29፥5፤32፥4
31፥14 ዘኍ14፥11፤ መዝ49፥14፤63፥9፤8 2፥7፤ሕዝ26፥20፤ 32፥24
31፥15 2ሳሙ1፥21

[6]የሰማይ ወፎች ሁሉ፣
በቅርንጫፎቹ ላይ ጐጆአቸውን ሠሩ፤
የምድር አራዊት ሁሉ፣
ከቅርንጫፎቹ ሥር ግልገሎቻቸውን
ወለዱ::
ታላላቅ መንግሥታትም ሁሉ፣
ከጥላው ሥር ኖሩ::
[7]ከተንሰራፉት ቅርንጫፎቹ ጋር፣
ውበቱ ግሩም ነበር፤
ብዙ ውሃ ወዳለበት፣
ሥሮቹ ጠልቀው ነበርና::
[8]በእግዚአብሔር ገነት ያሉ ዝግባዎች፣
ሊወዳደሩት አልቻሉም፤
የጥድ ዛፎች፣
የእርሱን ቅርንጫፎች አይተካከሉትም፤
የአስታ ዛፎችም፣
ከእርሱ ቅርንጫፎች ጋር አይወዳደሩም፤
በእግዚአብሔር ገነት ያለ ማናቸውም ዛፍ፣
በውበት አይደርስበትም::
[9]በብዙ ቅርንጫፎች፣
ውብ አድርጌ ሠራሁት፤
በእግዚአብሔርም የአትክልት ቦታ፣
በገነት ያሉትን ዛፎች የሚያስቀና
አደረግሁት::

[10]“ ‘ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤ “ጥቅጥቅ ባለው ቅጠል ላይ ጫፉን
ከፍ በማድረግ ራሱን በማንጠራራቱ፣ በር
ዝማኔውም በመኵራራቱ፣ [11]እንደ ክፋቱ
መጠን የሥራውን ይከፍለው ዘንድ፣ ለአሕ
ዛብ ገዥ አሳልፌ ሰጠሁት:: አውጥቼ
ጥየዋለሁ፤ [12]ከአሕዛብ ወገን እጅግ ጨካኝ
የሆኑትም ባዕዳን ሰዎች ቈራርጠው ጣሉት::
ቀንበጦቹ በተራራዎቹና በሸለቆዎቹ ሁሉ
ላይ ወድቀዋል፤ ቅርንጫፎቹም በውሃ
መውረጃዎቹ ሁሉ ላይ ተሰባብረው ወድቀ
ዋል፤ የምድሪቱ ሰዎች ሁሉ ከጥላው ሥር
በመውጣት ትተውት ሄደዋል:: [13]የሰማይ
ወፎች ሁሉ በወደቀው ዛፍ ላይ ሰፈሩ፤
የምድር አራዊት ሁሉ በወደቀው ዛፍ ቅር
ንጫፎች ላይ ሰፈሩ:: [14]ስለዚህ በውሃ አጠ
ገብ ያለ ማንኛውም ዛፍ፣ ጫፎቹን ችምችም
ካለው ቅጠል በላይ ከፍ በማድረግ፣ ከእን
ግዲህ ራሱን በትዕቢት አያንጠራራም::
ከእንግዲህ ውሃ በሚገባ ያገኘ ማንኛውም
ዛፍ ወደዚህ ዐይነቱ ከፍታ አይደርስም::
ሁሉም ከምድር በታች ወደ ጒድጓድ
ከሚወርድ ሟች ጋር አብሮ እንዲሞት
ተወስኖበታልና::”
[15]“ ‘ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“ወደ መቃብር[መ] በወረደበት ቀን ጥልቅ

[መ]15 ዕብራይስጡ ሲኦል ይላል፤ እንዲሁም በቍ16 እና 17

ምንጮችን ስለ እርሱ በሐዘን ሸፈንኋቸው፤
ወንዞቹን ገታሁ፤ ታላላቅ ፈሳሾችም ተቋ
ረጡ። በእርሱም ምክንያት ሊባኖስን ጨለማ
አለበስሁ፤ የደን ዛፎችም ሁሉ ደረቁ። 16ወደ
ጕድጓድ ከሚሄዱት ጋር ወደ መቃብር
ባወረድሁት ጊዜ ሲወድቅ በተሰማው ድምፅ
አሕዛብ ደነገጡ። ከዚያም የዔድን ዛፎች
ሁሉ፣ ምርጥና ልዩ የሆኑት የሊባኖስ ዛፎች፣
ውሃ የጠገቡትም ዛፎች ሁሉ ከምድር
በታች ሆነው ተጽናኑ። 17ከአሕዛብ መካከል
ከእርሱ ጋር ያበሩ፣ በጥላው ሥር የኖሩ፣
በሰይፍ ከሞቱት ጋር ለመቀላቀል ወደ
መቃብር ወርደዋል።”

18“ ‘በዔድን ካሉት ዛፎች በውበትና በት
ልቅነት የሚወዳደርህ የትኛው ነው? ይሁን
እንጂ አንተም እንደዚሁ ከዔድን ዛፎች ጋር
ከመሬት በታች ትወርዳለህ፤ በሰይፍ ከተገ
ደሉት፣ ካልተገረዙትም መካከል ትጋደማ
ለህ።

“ ‘እንግዲህ ፈርዖንና ስፍር ቍጥር የሌ
ለው ሕዝቡ የሚደርስባቸው ይህ ነው፤ ይላል
ጌታ እግዚአብሔር።’ ”

## ስለ ፈርዖን የወጣ ሙሾ

32 በዐሥራ ሁለተኛው ዓመት፣ በዐ
ሥራ ሁለተኛው ወር፣ በመጀመ
ሪያው ቀን የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ
ሲል ወደ እኔ መጣ፤ 2“የሰው ልጅ ሆይ፤
ለግብፅ ንጉሥ ለፈርዖን ሙሾ አውርድ፤
እንዲህም በለው፤

“ ‘አንተ በሕዝቦች መካከል እንደ አንበሳ፣
በባሕሮችም ውስጥ እንደ አስፈሪ
አውሬ ነህ፤
በወንዞችህ የምትንቦጫረቅ፣
ውሃውን በእግርህ የምትመታ፣
ምንጮችን የምታደፈርስ ነህ።

3“ ‘ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤

“ ‘ብዙ ሕዝብ ይዤ፣
መረቤን በላይህ ላይ እጥላለሁ፤
በመረቤም ጐትተው ያወጡሃል።
4በምድር ላይ እጥልሃለሁ፤
ሜዳም ላይ እዘረጋሃለሁ፤
የሰማይ ወፎች ሁሉ እንዲሰፍሩብህ
አደርጋለሁ፤
የምድር አራዊት ሁሉ በመስገብገብ
ይበሉሃል።
5ሥጋህን በተራሮች ላይ እበታትነዋለሁ፤
የተረፈውንም በየሸለቆው እሞላዋለሁ።
6እስከ ተራሮች ባለው መንገድ ሁሉ፣
በሚፈሰው ደምህ ምድሪቱን አርሳታለሁ፤
ሸለቆዎችም በሥጋህ ይሞላሉ።

7አንተን በማጠፋ ጊዜ ሰማያትን
እሸፍናለሁ፤
ከዋክብታቸውንም አጨልማለሁ፤
ፀሓይን በደመና እሸፍናለሁ፤
ጨረቃም ብርሃኗን አትሰጥም።
8በሰማይ የሚያበሩትን ብርሃናት ሁሉ፣
በአንተ ላይ አጨልማለሁ፤
በምድርህ ላይ ጨለማን አመጣለሁ፤
ይላል ጌታ እግዚአብሔር።
9በማታውቀው ምድር፣
በሕዝቦች መካከል ያንተን ጥፋት
ሳመጣ፣ሠ
የብዙ ሕዝብን ልብ አስጨንቃለሁ።
10ሕዝቦች በአንተ ላይ ከደረሰው የተነሣ
እንዲደነግጡ አደርጋለሁ፤
ሰይፌን በፊታቸው ስነቀንቅ፣
በአንተ ላይ ከደረሰው ሁኔታ የተነሣ
ንጉሦቻቸው ይንቀጠቀጣሉ።
አንተ በምትወድቅበት ቀን፣
እያንዳንዳቸው ስለ ራሳቸው ሕይወት
በመፍራት፣
በየቅጽበቱ ይርበደበዳሉ።
11“ ‘ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፤

“ ‘የባቢሎን ንጉሥ ሰይፍ፣
በአንተ ላይ ይመጣል።
12ከሕዝቦች ሁሉ እጅግ ጨካኝ በሆኑት፣
በኀያላን ሰዎች ሰይፍ፣
ያከማቸኸው ሰራዊት እንዲወድቅ
አደርጋለሁ፤
የግብፅን ኵራት ያንኰታኵታሉ፤
የሰራዊቷም ብዛት ይጠፋል፤
13ብዙ ውሃ ባለበት አጠገብ ያለውን፣
የከብት መንጋዋን አጠፋለሁ፤
ከእንግዲህ የሰው እግር አይረጋግጠውም፤
የከብትም ኮቴ አያደፈርሰውም።
14ከዚያም ውሆቿን አጠራለሁ፤
ወንዞቿም እንደ ዘይት እንዲፈሱ
አደርጋለሁ፤
ይላል ጌታ እግዚአብሔር።
15ግብፅን ባድማ ሳደርጋት፣
ምድሪቱም ያላትን ሁሉ ያጣች ስትሆን፣
በዚያም የሚኖሩትን ሁሉ ስመታ፣
ያን ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ
ያውቃሉ።”

16“ስለ እርሷ የሚያወርዱት ሙሾ ይህ ነው፤
የሕዝቦች ሴት ልጆች ያዜሙታል፤
ስለ ግብፅና ስለ ብዙ ሰራዊቷ ሁሉ ሙሾ
ያወርዳሉ፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።”

17በዐሥራ ሁለተኛው ዓመት፣ ከወሩም በዐ
ሥራ አምስተኛው ቀን የእግዚአብሔር
ቃል

ሠ9 በዕብራይስጡም እንዲሁ ሲሆን ሰብዓ ሊቃናት ግን በአሕ
ዛብ መካከል ወደ ምርኮ ሳመጣው ይላል

31፥16 ዘፍ2፥8፤ ኢሳ14፥8፡15፤ኤር 49፥21፤ሕዝ14፥22፤ 32፥18
31፥17 መዝ9፥17
31፥18 ኤር9፥26
32፥1 ሕዝ31፥1፤ 33፥21
32፥2 ቈ13፤ ዘፍ1፥21፤ 2ሳሙ1፥17፤ 2ነገ24፥1፤ 2ዜና35፥25፤ ኢዮ3፥8፤41፥31፤ መዝ74፥13፤ሕዝ19፥1፤ 29፥3፤34፥18፤ ናሆ2፥11-13
32፥3 ሕዝ12፥13፤ ዕን1፥15
32፥4 ኢሳ18፥6፤ ሕዝ31፥12-13፤ 39፥4-5፡17
32፥5 ሕዝ31፥12
32፥6 ኢሳ34፥3፤ ሕዝ29፥5
32፥7 ኢሳ13፥10፤ 34፥4፤ሕዝ30፥3፤ ኢል2፥2፡31፤3፥15፤ ማቴ24፥29፤ ራእ8፥12
32፥8 ኢዮ9፥7፤ መዝ 102፥26፤ ኤር4፥23፤ኢል2፥10
32፥10 ኢሳ30፥32፤ ኤር46፥10፤ ሕዝ26፥16፤27፥35፤ 30፥9፤ራእ18፥9-10
32፥11 ኢሳ19፥4፤ ኤር46፥13፤ ሕዝ21፥19፤29፥19
32፥12 ሕዝ28፥7፤ 31፥11-12
32፥13 ቈ2፤ ሕዝ29፥8፡11
32፥15 ዘፀ7፥5፤ 14፥4፡18፤ መዝ107፥33-34
32፥16 ዘፍ50፥10፤ ሕዝ19፥1
32፥17 ቈ1

እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፤ 18“የሰው ልጅ
ሆይ፤ ስለ ብዙው የግብፅ ሰራዊት አልቅስ፤
እርሷንና የኀያላንን ሕዝቦች ሴት ልጆች
ወደ ጒድጓድ ከሚወርዱት ጋር ከምድር
በታች አውርዳቸው:: 19እንዲህም በላቸው፤
‘እናንተ ከሌሎች የተለያችሁ ናችሁን?
ውረዱ፤ ባልተገረዙትም መካከል ተጋደሙ::’
20እነርሱም በሰይፍ በተገደሉት መካከል
ይወድቃሉ፤ ሰይፉ ተመዟል፤ ከብዙ ሰራ
ዊቷ ሁሉ ጋር ትጐተት:: 21በመቃብርም[ሬ]
ውስጥ ኀያላኑ መሪዎች ስለ ግብፅና ስለ
ተባባሪዎቿ፣ ‘ወደ ታች ወርደዋል፤ በሰይፍ
ከተገደሉትና ካልተገረዙትም ጋር በአንድ ላይ
ተጋድመዋል’ ይላሉ::

22“አሦር ከመላው ሰራዊቷ ጋር በዚያ
ትገኛለች፤ በሰይፍ በወደቁባትና በታረዱባት
ሰዎች ሁሉ መቃብር ተከባለች:: 23መቃብ
ራቸው በጥልቁ ጒድጓድ ውስጥ ነው፤ ሰራ
ዊቷም በመቃብሯ ዙሪያ ተረፍርፏል:: በሕ
ያዋን ምድር ሽብርን የነዙ ሁሉ ታርደዋል፤
በሰይፍም ወድቀዋል::

24“ኤላም በዚያ አለች፤ ሰራዊቷም ሁሉ
በመቃብሯ ዙሪያ አለ፤ ሁሉም ታርደዋል፤
በሰይፍ ወድቀዋል:: በሕያዋን ምድር ሽብር
የነዙ ሁሉ ሳይገረዙ ከምድር በታች ወርደ
ዋል፤ ወደ ጒድጓድ ከወረዱት ጋር ዕፍ
ረታቸውን ተሸክመዋል፤ 25በመቃብሯ ዙሪያ
ካለው መላው ሰራዊቷ ጋር፣ በታረዱት
መካከል መኝታ ተዘጋጅቶላታል:: ሁሉም
ያልተገረዙና በሰይፍ የተገደሉ ናቸው፤
ሽብራቸው በሕያዋን ምድር ስለ ተነዛ፣
ወደ ጒድጓድ ከሚወርዱት ጋር ዕፍረታ
ቸውን ይሸከማሉ፤ በታረዱትም መካከል
ይጋደማሉ::

26“ሞሳህና ቶቤል መቃብሮቻቸው በብዙ
ሰራዊታቸው መቃብር ተከበው ይገኛሉ፤ ሁሉም
ያልተገረዙ ሲሆኑ፣ በሕያዋን ምድር ሽብ
ራቸውን ስለነዙ በሰይፍ ተገድለዋል:: 27ከዘ
መናት በፊት ከወደቁት ከኀያላን ሰዎች፣
ከእነዚያ ሰይፉቸውን ተንተርሰው፣ ጋሻቸው
ንም ደረታቸው ላይ ይዘው ከነሙሉ ትጥ
ቃቸው ወደ መቃብር ከወረዱት ጋር አይ
ጋደሙምን? የእነዚህ ተዋጊዎች ሽብር
በሕያዋን ምድር ባሉት ኀያላን ላይ ቢደ
ርስም የኀጢአታቸው ቅጣት በዐጥንታቸው
ላይ ይሆናል::

28“ፈርዖን ሆይ፤ አንተም እንደዚሁ ትሰ
በራለህ፤ በሰይፍ ከተገደሉት ከእነዚያ ካልተገ
ረዙት ጋር ትጋደማለህ::

29“ኤዶምም በዚያ አለች፤ ንጉሦቿና ገዥ
ቿም ሁሉ በዚያ አሉ፤ ኀይል የነበራቸው
ቢሆኑም፣ በሰይፍ ከተገደሉት ጋር ተጋድ
መዋል፤ ወደ ጒድጓድ ከወረዱት ከእነዚያ
ካልተገረዙትም ጋር ተኝተዋል::

30“የሰሜን ገዦች በሙሉ፣ ሲዶናውያንም
ሁሉ በዚያ ይገኛሉ፤ ከዚህ በፊት በኀይላ
ቸው ምክንያት ሽብር የፈጠሩ ቢሆኑም፣
ከታረዱት ጋር በኀፍረት ወረዱ፤ ሳይገረዙም
በሰይፍ ከተገደሉት ጋር ይጋደማሉ፤ ወደ
ጒድጓድ ከወረዱትም ጋር ኀፍረታቸውን
ይሸከማሉ::

31“ፈርዖንና ሰራዊቱ ሁሉ ያዩአቸዋል፤
በሰይፍ ከተገደለበት ሰራዊትም ሁሉ ሐዘን
ይጽናናል፤ ይላል ጌታ *እግዚአብሔር::*
32በሕያዋን ምድር ሽብር እንዲያስፋፋ
ብፈቅድም እንኳ፣ ፈርዖንና ሰራዊቱ ሁሉ
በሰይፍ ከተገደሉት ጋር ባልተገረዙት መካ
ከል ይጋደማሉ፤ ይላል ጌታ *እግዚአብሔር::*

## ሕዝቅኤል ጒበኛው

33 *የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤ 2“የሰው ልጅ ሆይ፤
ለአገርህ ሰዎች ተናገር፤ እንዲህም በላቸው፤
‘በምድር ላይ ሰይፍን ሳመጣ፣ የምድሪቱ
ሕዝብ ከሰዎቻቸው አንዱን መርጠው ጒበኛ
ቢያደርጉት፣ 3እርሱም በምድሪቷ ላይ ሰይፍ
ሲመጣ አይቶ፣ ሕዝቡን ለማስጠንቀቅ
መለከት ቢነፋ፣ 4ከዚያም ማንም መለከቱን
ሰምቶ ባይጠነቀቅ፣ ሰይፍም መጥቶ ሕይወቱን
ቢያጠፋ፣ ደሙ በገዛ ራሱ ላይ ይሆናል::
5የመለከቱን ድምፅ ሰምቶ ባለመጠንቀቁ፣
ደሙ በገዛ ራሱ ላይ ይሆናል፤ ቢጠነቀቅ ኖሮ
ግን ራሱን ባዳነ ነበር:: 6ነገር ግን ጒበኛ
ሰይፍ ሲመጣ አይቶ፣ ሕዝቡን ለማስጠንቀቅ
መለከት ሳይነፋ ቢቀርና ከመካከላቸው
የአንዱን ሰው ሕይወት ሰይፍ ቢያጠፋ፣ ያ
ሰው ስለ ኀጢአቱ ይወሰዳል፤ ጒበኛውን ግን
ስለ ሰውዬው ደም ተጠያቂ አደርገዋለሁ::’

7“የሰው ልጅ ሆይ፤ አንተን ለእስራኤል
ቤት ጒበኛ አድርጌሃለሁ፤ ስለዚህ የምናገ
ረውን ቃል ስማ፤ ማስጠንቀቂያዬንም ስጣ
ቸው:: 8ክፉውን፣ ‘አንተ ክፉ ሰው፤ በእርግጥ
ትሞታለህ’ ባልሁት ጊዜ፣ እርሱን ከመንገዱ
እንዲመለስ ባታደርገው፣ ያ ክፉ ሰው
በኀጢአቱ ይሞታል፤ አንተ ግን ስለ ደሙ
ተጠያቂ ትሆናለህ:: 9ነገር ግን ክፉውን
ሰው ከመንገዱ እንዲመለስ ነግረኸው እሺ
ባይል፣ እርሱ ስለ ኀጢአቱ ይሞታል፤ አንተ
ግን ራስህን አድነሃል::

10“የሰው ልጅ ሆይ፤ ለእስራኤል ቤት
እንዲህ በል፤ ‘እንዲህ ትላላችሁ፤ “በደላች
ንና ኀጢአታችን ከብዶናል፤ ከዚህም[ሰ] የተነሣ

32፥18 ኤር1፥10፤ ሕዝ26፥20፤31፥14፡ 16፤ሚክ1፥8
32፥19 ቀኍ29-30፤ ሕዝ28፥10
32፥20 መዝ28፥3፤ ሕዝ31፥17-18
32፥21 ኢሳ14፥9፤ ሕዝ28፥10
32፥23 ኢሳ14፥15፤ ናሆ1፥14
32፥24 ዘፍ10፥22፤ ኢዮ28፥13፤ኤር 49፥37፤ሕዝ26፥20
32፥25 ሕዝ28፥10
32፥26 ሕዝ27፥13
32፥27 ሕዝ28፥10
32፥29 መዝ137፥7፤ ኢሳ34፥5-15፤ኤር 49፥7፤ሕዝ25፥12 -14፤35፥15፤አብ1፥1
32፥30 ዘፍ10፥15፤ ኢሳ14፥31፤ ኤር25፥22፡26፤ ሕዝ26፥20፤28፥8፡ 10፤38፥6፤ 39፥2
32፥31 ሕዝ14፥22
32፥32 ኢዮ3፥14፤ ኤር44፥30
33፥3 ዘፀ20፥18፤ ዘኍ10፥7፤ሆሴ5፥8፤ 8፥1
33፥4 ዘሌ20፥9፤ 2ዜና25፥16፤ኤር6፥1 7፤ዘካ1፥4፤ሐሥ18፥6
33፥5 ዘፀ9፥21፤ ዘሌ20፥9
33፥6 ኢሳ56፥10 -11፤ሕዝ3፥18
33፥7 ኢሳ52፥8፤ ኤር1፥17፤26፥2
33፥8 ቀኍ14፤ ኢሳ3፥11፤ሕዝ18፥4
33፥9 መዝ7፥12፤ ሕዝ3፥17-19
33፥10 ዘሌ26፥16፡ 39፤ሕዝ4፥17

ሬ21 ዕብራይስጡ *ሲኦል* ይላል፤ በቍ 27ትም እንዲሁ
ሰ10 ወይም *በእርሱ*

ልንጠፋ ነው፤ ታዲያ እንዴት መኖር እን
ችላለን?" 11እንዲህ በላቸው፤ 'በሕያውነቴ
እምላለሁ፤ ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*፤ ከመን
ገዳቸው ተመልሰው በሕይወት እንዲኖሩ
እንጂ በክፉዎች ሞት ደስ አልሰኝም።
ተመለሱ! ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ!
የእስራኤል ቤት ሆይ፤ ለምን ትሞታ
ላችሁ?'
12"አሁንም የሰው ልጅ ሆይ፤ ለአገርህ
ሰዎች እንዲህ በላቸው፤ 'ጻድቅ ሰው ትእ
ዛዝን በተላለፈ ጊዜ የቀድሞ ጽድቁ አያድነ
ውም፤ ኀጢአተኛ ሰው ከኀጢአቱ ከተመ
ለሰ፣ ከቀድሞ ክፋቱ የተነሣ አይጠፋም።
ጻድቅ ሰው ኀጢአት ቢሠራ፣ በቀድሞ
ጽድቁ ምክንያት በሕይወት እንዲኖር አይደረ
ግም።' 13ጻድቁን ሰው በእርግጥ በሕይወት
ትኖራለህ ብለው፣ እርሱም ጽድቁን ተማ
ምኖ ክፋት ቢሠራ፣ ከጽድቅ ሥራው አን
ዱም አይታሰብለትም፤ በኀጢአቱም ምክን
ያት ይሞታል። 14እንዲሁም ክፉውን ሰው፣
'በእርግጥ ትሞታለህ' ብለው፣ እርሱም
ከኀጢአቱ ተመልሶ ቀና የሆነውንና ትክክለ
ኛውንም ነገር ቢያደርግ፣ 15ለሰጠው ብድር
የተቀበለውን መያዣ ቢመልስ፣ የሰረቀው
ንም መልሶ ቢሰጥ፣ ሕይወት የሚሰጡትን
ትእዛዛት ቢከተል፣ ክፉ ነገርንም ባያደርግ፣
በእርግጥ እርሱ በሕይወት ይኖራል፤ አይሞ
ትምም። 16ከሠራው ኀጢአት አንዱም አይ
ታሰብበትም፤ ቀናውንና ትክክለኛውን አድ
ርጓልና፤ በእርግጥ በሕይወት ይኖራል።
17"ይህም ሆኖ የአገርህ ሰዎች፣ 'የጌታ
መንገድ ቀና አይደለችም' ይላሉ፤ ቀና ያል
ሆነው ግን የእነርሱ መንገድ ነው። 18ጻድቅ
ሰው የጽድቁን ሥራ ትቶ ክፉ ነገር ቢያ
ደርግ፣ ስለ ኀጢአቱ ይሞታል። 19ክፉም
ሰው ከክፉ ሥራው ተመልሶ ቀናውንና
ትክክለኛውን ነገር ቢያደርግ፣ ይህን በማድ
ረጉ በሕይወት ይኖራል። 20ይሁን እንጂ
የእስራኤል ቤት ሆይ፤ 'የጌታ መንገድ
ቀና አይደለችም' ትላላችሁ፤ ነገር ግን
በእያንዳንዳችሁ ላይ እንደ መንገዳችሁ
እፈርድባ ችኋለሁ።"

## የኢየሩሳሌም መውደቅ

21በተማረክን በዐሥራ ሁለተኛው ዓመት፣
በዐሥረኛው ወር፣ በአምስተኛው ቀን፣
ከኢየሩሳሌም ያመለጠ አንድ ሰው ወደ
እኔ መጥቶ፣ "ከተማዪቱ ወደቀች!" አለኝ።
22ሰውየው ከመድረሱ በፊት በነበረው ምሽት፣
*የእግዚአብሔር* እጅ በላዬ ላይ ነበረች፤
በማለዳም ሰውየው ወደ እኔ ከመምጣቱ
በፊት እግዚአብሔር አፌን ከፈተ፤ አፌም
ተከፈተ፤ ከዚያ በኋላ ዝም አላልሁም።
23ከዚያም *የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ
ሲል ወደ እኔ መጣ፤ 24"የሰው ልጅ ሆይ፤
በእስራኤል ምድር በፍርስራሾች ውስጥ
የሚኖሩት ሕዝቦች፣ 'አብርሃም አንድ ራሱን
ብቻ ነበር፤ ያም ሆኖ ምድሪቱን ወረሰ፤ እኛ
ግን ብዙዎች ነን፤ በእርግጥ ምድሪቱ ርስት
ሆና ተሰጥታናለች' ይላሉ። 25ስለዚህ እንዲህ
በላቸው፣ 'ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
ሥጋውን ከነደሙ ትበላላችሁ፤ ዐይኖቻችሁን
ሁንም ወደ ጣዖቶቻችሁ ታነሣላችሁ፤ ደምም
ታፈሳላችሁ፤ ታዲያ በዚህ ሁኔታ ምድሪቱን
ልትወርሱ ታስባላችሁ? 26በሰይፋችሁ ትመ
ካላችሁ፤ አስጸያፊ ነገሮችን ትፈ
ጽማላችሁ፤ እያንዳንዳችሁም የባልንጀራ
ችሁን ሚስት ታረክሳላችሁ፤ ታዲያ በዚህ
ሁኔታ ምድሪቱን ልትወርሱ ይገባችኋል?'
27"እንዲህ በላቸው፤ 'ጌታ *እግዚአብሔር*
እንዲህ ይላል፤ በሕያውነቴ እምላለሁ፤ በፍር
ስራሾች ውስጥ የተረፉት በሰይፍ ይወድቃሉ፤
በገጠር ያሉትን በጫጭቀው እንዲበሏቸው
ለዱር አራዊት እሰጣቸዋለሁ፤ በምሽግና
በዋሻ ያሉትም በቸነፈር ይሞታሉ። 28ምድ
ሪቱን ጠፍና ባድማ አደርጋታለሁ፤ የምት
መካበት ጕልበቷ እንዳልነበረ ይሆናል፤
የእስ ራኤልም ተራሮች ማንም
እንዳያልፍባቸው ባድማ ይሆናሉ።
29ካደረጓቸው አስጸያፊ ነገሮች ሁሉ
የተነሣ፤ ምድሪቱን ባድማ በማ ደርግበት
ጊዜ፣ እኔ *እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ
ያውቃሉ።'
30"አንተን በሚመለከት፣ የሰው ልጅ ሆይ፤
የአገርህ ሰዎች በየቤቱ በርና ግድግዳ
ሥር ሆነው ስለ አንተ ይነጋገራሉ፤ እርስ
በራሳቸውም እንዲህ ይባባላሉ፤ 'ኑና
*ከእግዚአብሔር* የመጣውን መልእክት
እንስማ።' 31ሁልጊዜ
እንደሚያደርጉት ሕዝቤ ወደ አንተ
ይመጣሉ፤ ቃልህንም ለመስማት ከፊትህ
ይቀመጣሉ፤ ነገር ግን አይፈጽሙትም።
በከንፈራቸው ብዙ ፍቅርን ይገልጣሉ፤ ልባ
ቸው ያረፈው ግን ተገቢ ባልሆነ ጥቅም
ላይ ነው። 32ቃልህን ሰምተው ሥራ ላይ
የማያውሉት በመሆናቸው፣ አንተ ለእነርሱ
በአማረ ድምፅ የፍቅር ዘፈን የሚዘፍን፣
በዜማ መሣሪያም አሳምሮ የሚጫወት ሙዚ
ቀኛ ሆነህላቸዋል።
33"ይህ ሁሉ ሲሆን፣ በእርግጥም ይሆናል፤
በመካከላቸው ነቢይ እንደ ነበረ፣ እንዳለ
ያውቃሉ።"

## እረኞችና በጎች

34 *የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤ 2"የሰው ልጅ ሆይ፤

33፥11 2ዜና30፥9፤ ኢሳ19፥22፤ኤር3፥12፤44፥7-8፤ሰቆ3፥33፤ሕዝ18፥23፤ሆሴ11፥8፤ኢል2፥12፤1ጢሞ 2፥4
33፥12 ቍ2፤2ዜና7፥14፤ሕዝ3፥20፤18፥21
33፥13 ዕን10፥38፤2ጴጥ2፥20-21
33፥14 ኤር22፥3
33፥15 ዘፀ22፥1-4፡26፤ዘሌ6፥2-5፤ኢሳ55፥7፤ኤር18፥7-8፤ሉቃ19፥8
33፥16 ኢሳ43፥25፤ኤር50፥20
33፥18 ኤር18፥10፤ሕዝ3፥20
33፥19 ቍ14-15
33፥20 ኢዮ34፥11
33፥21 2ነገ25፥4፡10፤ኤር39፥1-2፤52፥4-7፤ሕዝ24፥26፤32፥1
33፥22 ሕዝ1፥3፤3፥26-27፤24፥27፤29፥21፤ሉቃ1፥64
33፥24 ዘዳ1፥10፤ኢሳ51፥2፤ኤር40፥7፤ሕዝ11፥15፤36፥4፤ሉቃ3፥8፤ሐሥ7፥5
33፥25 ዘፍ9፥4፤ኤር7፥9-10፡21፤ሕዝ22፥6፡27
33፥26 ኤር41፥7፤ሕዝ22፥11
33፥27 1ሳሙ13፥6፤ኢሳ2፥19፤ኤር42፥22፤ሕዝ7፥15፤14፥21፤39፥4
33፥28 ዘፍ6፥7፤ኢሳ41፥15፤ኤር9፥10
33፥29 ዘሌ26፥34፤ኤር18፥16፤44፥22፤ሕዝ36፥4፤ሚክ7፥13
33፥31 መዝ78፥36-37፤119፥36፤ኢሳ29፥13፤33፥15፤ኤር3፥10፤6፥17፤ሕዝ8፥1፤22፥27፤ማቴ13፥22፤1ዮሐ3፥18
33፥32 1ነገ4፥32፤ማር6፥20
33፥33 1ሳሙ3፥20፤ኤር28፥9፤ሕዝ2፥5
34፥2 መዝ78፥70-72፤ኢሳ40፥11፤ኤር3፥15፤23፥1፤ሚክ3፥11፤ዮሐ10፥11፤21፥15-17፤ይሁ1፥12

በእስራኤል እረኞች ላይ ትንቢት ተናገር፤
ትንቢት ተናገር፤ እንዲህም በላቸው፤ ‘ጌታ
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ራሳቸውን
ብቻ ለሚንከባከቡ ለእስራኤል እረኞች
ወዮላቸው! እረኞች መንጋውን ማሰማራት
አልነበረባቸውምን? 3ጮማውን ትበላላችሁ፤
ከጠጕሩ የተሠራውን ሱፍ ትለብሳላችሁ፤
የሰባውን ዐረዳችሁ፤ ነገር ግን መንጋውን
አትንከባከቡትም። 4ደካማውን አላበረታችሁ
ትም፤ በሽተኛውን አልፈወሳችሁትም፤ የተ
ጐዳውንም አልጠገናችሁትም። የባዘኑትን
አልመለሳችሁም፤ የጠፉትንም አልፈለጋች
ሁም፤ በግፍና በጭካኔ ገዛችኋቸው። 5ስለዚህ
እረኛ የለምና ተበተኑ፤ በመበተናቸውም
ለአራዊቱ ሁሉ መብል ሆኑ። 6በጎቼ በየተ
ራራው ሁሉና በየኰረብታው ላይ ተንከራ
ተቱ። በምድር ሁሉ ተበተኑ፤ የፈለጋቸውም፤
የፈቀዳቸውም የለም።
7“ “ስለዚህ እናንት እረኞች፣ የእግዚአ
ብሔርን ቃል ስሙ፤ 8በሕያውነቴ
እምላለሁ፣ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤
እረኞቼ መንጋዬን ስላልፈለጉ፣ ከመንጋዬም
ይልቅ ራሳቸውን ስለተንከባከቡ፣ መንጋዬ
እረኛ አጥቶ ለንጥ ቂያ ተዳርጎአል፤ ለአራ
ዊትም ሁሉ መብል ሆኖአል። 9ስለዚህ
እረኞች ሆይ፤ የእግዚአብሔርን ቃል
ስሙ፤ 10ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ እኔ
በእረኞች ላይ ተነሥቻለሁ፤ ስለ መንጋዬ እጠ
ይቃቸዋለሁ፤ ከእንግዲህ እረኞች ራ
ሳቸውን መመገብ እንዳይችሉ፣ መንጋዬን
እንዳያሰማሩ አደርጋለሁ። መንጋ ዬን
ከአፋቸው አስጥላለሁ፤ ከእንግዲህም
ምግብ አይሆናቸውም።
11“ ‘ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፤
እኔ ራሴ በጎቼን እፈልጋቸዋለሁ፤ እጠ
ብቃቸዋለሁም። 12እረኛ ከመንጋው ጋር
ሳለ፣ የተበተኑበትን በጎች እንደሚፈልግ
ሁሉ፣ እኔም በጎቼን እፈልጋለሁ። በደመ
ናና በጨለማ ቀን ከተበተኑበት ስፍራ ሁሉ
አድናቸዋለሁ። 13ከአሕዛብ መካከል አወጣቸ
ዋለሁ፤ ከየአገሮቹ እሰበስባቸዋለሁ፤ ወደ
ገዛ ምድራቸውም አመጣቸዋለሁ። በእስራ
ኤል ተራሮች፣ በየወንዙ ዳርና፣ በምድሪቱ
መኖሪያዎች ሁሉ እንዲሰማሩ አደርጋለሁ።
14በመልካሙ ስፍራ አሰማራቸዋለሁ፤ የእስ
ራኤል ተራሮች ከፍታም የግጦሽ መሬት
ይሆናቸዋል። በመልካሙ ግጦሽ መሬት
ላይ ይተኛሉ፤ እዚያም በእስራኤል ተራሮች
ለምለም መስክ ላይ ይመገባሉ። 15እኔ ራሴ
በጎቼን አሰማራለሁ፤ አስመስጋቸዋለሁም።
ይላል ጌታ እግዚአብሔር። 16የጠፉትን እፈል
ጋለሁ፤ የባዘኑትንም እመልሳለሁ። የተጐ
ዱትን እጠግናለሁ፤ የደከሙትንም አበረታ
ለሁ፤ የወፈ ረውንና የበረታውን ግን አጠ
ፋለሁ። መንጋውን በፍትሕ እጠብቃለሁ።
17“ ‘መንጋዬ ስለ ሆናችሁት ስለ እናንተ
ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ በበግና
በበግ መካከል፣ በአውራ በግና በአውራ
ፍየል መካከል እፈርዳለሁ። 18በለምለሙ
መስክ ላይ መመገቡ አይበቃችሁምን?
የተረፈውን መሰማሪያችሁን ደግሞ በእግ
ራችሁ መረጋ ገጥ ይገባችኋልን? ንጹሕ
ውሃ መጠጣቱ አይበቃችሁምን? የተረፈውንስ
በእግራችሁ ማደፍረስ ይገባችኋልን? 19መን
ጋዬ የረጋገጣችሁትን መመገብና በእግራ
ችሁ ያደፈረሳችሁትን መጠጣት ይገባዋ
ልን?
20“ ‘ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላቸዋል፤ “እነሆ እኔ ራሴ በሰባው በግና
በከሳው በግ መካከል እፈርዳለሁ። 21ደካሞ
ቹን በጎች በጐናችሁና በትከሻችሁ ስለምት
ገፈትሩ፣ እስኪባረሩም ድረስ በቀንዳችሁ
ስለምትወጓቸው፣ 22እኔ መንጋዬን አድናለሁ፤
ከእንግዲህ ለንጥቂያ አይዳረጉም፤ በአንዱ
በግና በሌላውም በግ መካከል እፈርዳለሁ።
23በእነርሱ ላይ አንድ እረኛ፣ ባሪያዬን
ዳዊትን አቆማለሁ፤ እርሱም ያሰማራ
ቸዋል፤ እረኛቸውም ይሆናል። 24እኔ
እግዚአብሔር አምላካቸው እሆናለሁ፤
ባሪያዬ ዳዊትም በመካከላቸው ገዥ
ይሆናል፤ እኔ እግዚአብሔር ተናግሬአለሁ።”
25“ ‘ከእነርሱ ጋር የሰላም ቃል ኪዳን
እገባለሁ፤ ከዚያም ምድሪቱን ከዱር አራ
ዊት ነጻ አደርጋለሁ፤ እነርሱም በምድረ በዳ
ይኖራሉ፤ በደንም ውስጥ በሰላም ይተኛሉ።
26እነርሱንና በኰረብታዬ ዙሪያ ያሉትን
ስፍራዎች እባርካለሁ።[ሸ] በወቅቱም ዝናብ
አወርድላቸዋለሁ፤ ዝናቡም የበረከት ዝናብ
ይሆናል። 27የየሜዳው ዛፍ ፍሬ ይሰጣል፤
መሬቱም እህል ያበቅላል። ሕዝቡም በምድ
ሪቱ ላይ በሰላም ይኖራሉ። የቀንበሮቻቸ
ውን ማነቆ ሰብሬ በባርነት ከገዟቸው እጅ
ሳድናቸው፣ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ
ያውቃሉ። 28ከእንግዲህ ለሌሎች ሕዝቦች
ንጥቂያ አይዳረጉም፤ የዱር አራዊት አይበ
ጫጭቋቸውም፤ በሰላም ይኖራሉ፤ የሚያስ
ፈራቸውም አይኖርም። 29ከእንግዲህ በምድሪቱ
ላይ የራብ ተጠቂ እንዳይሆኑ፣ የአሕዛብንም
ስድብ እንዳይሸከሙ ፍሬ በመስጠት የታ
ወቀውን መሬት እሰጣቸዋለሁ። 30ከዚያም
እኔ እግዚአብሔር አምላካቸው ከእነርሱ ጋር
እንደ ሆንሁ፤ የእስራኤል ቤት የሆኑት
እነርሱም ሕዝቤ እንደ ሆኑ ያውቃሉ፣
ይላል

34፥3 ኢሳ56፥11፤ ሕዝ22፥27፤አሞ6፥4፤ ዘካ11፥5
34፥4 ቀኍ16፤ ዘሌ25፥43፤ኢሳ1፥6፤ 3፥7፤ሚክ3፥3፤ ዘካ11፥15-17
34፥5 ቀኍ28፤ዘኍ 27፥17፤ኢሳ56፥9፤ ሐሥ20፥29
34፥6 ዘሌ26፥33፤ 2ዜና18፥16፤ መዝ95፥10፤142፥4፤ ኤር 10፥21፤50፥6፤ ሆሴ7፥13፤ማቴ9፥36፤ 18፥12-13፤ ሉቃ15፥5፤1ጴጥ2፥25
34፥8 መሳ2፥14፤ ኢሳ56፥9፤ይሁ1፥12
34፥10 1ሳሙ2፥ 29-30፤መዝ72፥14፤ ኤር21፥13፤23፥2፤ ዘካ10፥3
34፥11 መዝ119፥ 176
34፥12 ኢሳ40፥11፤ ኤር31፥10፤ሕዝ32፥7፤ ዘካ10፥3፤ሉቃ19፥10
34፥13 ዘፍ48፥21፤ ዘዳ30፥4፤ኢ ሳ66፥20፤ ኤር23፥3፤8፤50፥19፤ ሕዝ11፥17፤28፥25፤ 36፥24፤ሚክ4፥6
34፥14 መዝ23፥2፤ 37፥3፤ኢሳ65፥10፤ ሕዝ20፥40፤36፥29 -30፤37፥22፤አሞ 9፥14፤ሚክ7፥14
34፥15 መዝ23፥1 -2፤ኤር33፥12፤ሚክ 5፥4፤ሶፎ3፥13
34፥16 መዝ147፥3፤ ኢ ሳ10፥16፤ኤር31፥8 ፤ሚክ4፥6፤ሶፎ3፥19፤ ሉቃ5፥32፤19፥10
34፥17 ማቴ25፥32 -33
34፥18 ዘፍ30፥15፤ ሕዝ32፥2
34፥20 ማቴ25፥32
34፥21 ዘዳ33፥17
34፥22 መዝ72፥12-14፤ ኤር23፥2-3፤ሕዝ 20፥37-38
34፥23 ኢሳ31፥4፤ 40፥11፤ሚክ5፥4
34፥24 መዝ89፥49፤ ኢሳ53፥4፤ኤር23፥ 4-5፤30፥9፤33፥14፤ ሕ ዝ36፥28፤ዘካ13፥7፤ ዮሐ10፥16፤ራ እ7፥17
34፥25 ዘሌ25፥18፤ 26፥6፤ዘኍ25፥12፤ ኢሳ11፥6-9፤ሕዝ 16፥62፤ሆሴ2፥18
34፥26 ዘፍ12፥2፤ ዘዳ11፥13-15፤ 28፥12፤መዝ68፥9፤ ኢሳ44፥3፤ኢል2፥23
34፥27 ዘሌ26፥13፤ ዘኍ24፥21፤ኢዮ14፥9፤ መዝ67፥6፤72፥16፤

[ሸ]26 ወይም እነርሱንና በኰረብታዬ ዙሪያ ያሉትን ስፍራዎች በረከት አደርጋቸዋለሁ

ጌታ እግዚአብሔር። 31እናንተ በጎቼ የማሰማሪ
ያዬ በጎች ያልኋችሁ፣ ሕዝብ ናችሁ፤ እኔም
አምላካችሁ ነኝ፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።

## በኤዶም ላይ የተነገረ ትንቢት

35 የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤ 2“የሰው ልጅ ሆይ፤
ፊትህን ወደ ሴይር ተራራ አዙር፤ ትንቢ
ትም ተናገርበት፤ 3እንዲህም በል፤ ‘ጌታ
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ የሴይር ተራራ
ሆይ፤ በአንተ ላይ ተነሥቻለሁ፤ እጄን በአ
ንተ ላይ እዘረጋለሁ፤ ባድማና ጠፍ አደርግ
ሃለሁ። 4ከተሞችህን ፍርስራሽ አደርጋቸዋ
ለሁ፤ ባድማ ትሆናለህ፤ ከዚያም እኔ እግዚ
አብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃለህ።
5“ ‘እስራኤላውያን ቀጣታቸው እጅግ
መራራ ከሆነ ደረጃ ላይ ደርሶ ፍዳቸውን
በሚቀበሉበት ጊዜ፣ የጥንቱን ቂም ቋጥ
ረህ ለሰይፍ ስለ ዳረግሃቸው፤ 6በሕያውነቴ
እምላለሁ፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ለደም
ማፍሰስ አሳልፌ እሰጥሃለሁ፤ እርሱም ያሳድ
ድሃል። ደም ማፍሰስን ስላልጠላህ፣ ደም
ማፍሰስ ያሳድድሃል። 7የሴይርን ተራራ ባድ
ማና ጠፍ አደርጋለሁ፤ በእርሱም ላይ የሚ
ወጡትንና የሚወርዱትን አስቀራለሁ።
8ተራሮችህን በሬሳ እሞላለሁ፤ በሰይፍ የተገ
ደሉት ሁሉ በተራሮችህ፣ በሸለቆዎችህና
በውሃ መውረጃዎችህ ሁሉ ላይ ይወድቃሉ።
9ለዘላለም ባድማ አደርግሃለሁ፤ ከተሞችህ
መኖሪያ አይሆኑም። ከዚያም እኔ እግዚ
አብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ።
10“ ‘እኔ እግዚአብሔር በዚያ እያለሁ፣
“እነዚህ ሁለት ሕዝቦችና ሁለት አገሮች
የእኛ ይሆናሉ፤ እኛም እንወርሳቸዋለን።”
ብለሃልና፤ 11ስለዚህ በሕያውነቴ እምላለሁ፤
ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ከጥላቻችሁ
የተነሣ በእነርሱ ላይ በገለጣችሁት ቍጣና
ቅናት ልክ እፈርድባችኋለሁ፤ በእናንተም
ላይ በም ፈርድበት ጊዜ፣ ማንነቴ በእነርሱ
መካከል እንዲታወቅ አደርጋለሁ። 12ከዚ
ያም ስለ እስራኤል ተራሮች፣ “ጠፍ
ሆነዋል፤ ቦጫጭቀን እንድንበላቸው ለእኛ
ተሰጥተዋል” ብለህ በንቀት የተናገርኸውን
እኔ እግዚአብሔር እንደ ሰማሁ በዚያን ጊዜ
ታውቃለህ። 13በእኔ ላይ ታብየሃል፤
በድፍረትም በእኔ ላይ ተና ግረሃል፤ እኔም
ሰምቼዋለሁ። 14ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤ መላዪቱ ምድር በምትደሰትበት ጊ
ዜ አንተን ባድማ አደርግ ሃለሁ። 15የእስራ
ኤል ቤት ርስት ባድማ በሆነች ጊዜ ስለ
ተደሰትህ፣ እኔም እንዲሁ አደርግብሃለሁ።
የሴይር ተራራ ሆይ፤ አንተና መላዋ ኤዶም
ባድማ ትሆናላችሁ፤ ከዚያም እኔ እግዚ
አብሔር እንደ ሆንሁ ያው ቃሉ።

## ለእስራኤል ተራሮች የተነገረ ትንቢት

36 “የሰው ልጅ ሆይ፤ ለእስራኤል ተራ
ሮች ትንቢት ተናገር፤ እንዲ
ህም በል፤ ‘የእስራኤል ተራሮች ሆይ፤
የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ። 2ጌታ እግዚአ
ብሔር እንዲህ ይላል፤ “ጠላት ስለ አንቺ፣
‘እሰይ! እነዚያ የጥንት ተራሮች የእኛ ርስት
ሆነዋል’ ብሎአል።”’ 3ስለዚህ ትንቢት ተና
ገር፤ እንዲህም በል፤ ‘ጌታ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤ “ከየአቅጣጫው ከበው በመ
ውጋት ስላጠቋችሁ፣ ለቀሩት ሕዝቦች ሁሉ
ርስት ሆናችሁ፤ ለሕዝብም መሣቂያና መሣ
ለቂያ ሆናችሁ።” 4ስለዚህ የእስራኤል ተራ
ሮች ሆይ፤ የጌታ እግዚአብሔርን ቃል ስሙ፤
ጌታ እግዚአብሔር ለተራሮችና ለኰረብ
ቶች፣ ለሸለቆዎችና ለውሃ መውረጃዎች፣
ለፈራረሱ ባድማዎችና፣ በሌሎቹ በዙሪያ
ችሁ ባሉት ሕዝቦች ተዘርፈውና መዘባበቻ
ሆነው መና ለቀሩት ከተሞች እንዲህ ይላል፤
5ልዑል እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“በሚቃ
ጠል ቅናቴ በቀሩት ሕዝቦች ሁሉና በኤዶም
ሁሉ ላይ ተናግሬአለሁ፤ ከልብ በመነጨ
ደስታና በንቀት ተሞልተው የግጦሽ መሬቷን
ይዘው ይበዝ ብዙት ዘንድ የራሳቸው ርስት
አድርገውታልና።” 6ስለዚህ የእስራኤልን
ምድር የሚመለከት ትንቢት ተናገር፤ ለተ
ራሮች፣ ለኰረብቶች፣ ለሸለቆዎችና ለውሃ
መውረጃዎች እንዲህ በል፤ ‘ጌታ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤ “በሕዝቦች ዘለፋ ስለ ተሠቃ
ያችሁ ቍጣ በተሞላ ቅናቴ እናገራለሁ።”
7ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“እጄን አንሥቼ እምላለሁ፤ በዙሪያችሁ ያሉ
ሕዝቦች ዘለፋ ይወርድባቸዋል።”
8“ ‘የእስራኤል ተራሮች ሆይ፣ እናንተ ግን፤
ለሕዝቤ ለእስራኤል ቅርንጫፍ ታወጣላችሁ፤
ፍሬም ታፈራላችሁ፤ በቅርቡ ወደ አገራ
ቸው ይመለሳሉና። 9ስለ እናንተ ይገደኛል፤
በበጎነትም እመለከታችኋለሁ፤ ትታረሳላችሁ፤
ዘርም ይዘራባችኋል። 10መላው የእስራኤል
ቤት እንኳ ሳትቀሩ፣ የሰዎችን ቍጥር በእ
ናንተ ላይ አበዛለሁ። ከተሞች የሰው
መኖሪያ ይሆናሉ፤ የፈረሱት እንደ ገና ይሠ
ራሉ። 11በእናንተ ላይ የሰዎችንና የእንስሳትን
ቍጥር እጨምራለሁ፤ ፍሬያማ ይሆናሉ፤
ቍጥራቸውም ይበዛል። እንዳለፈው ጊዜ ሁሉ
ሰዎች በውስጣችሁ እንዲኖሩ አደርጋለሁ፤

ኤር30፥8፤ሕዝ20፥42፤28፥25
34፥28 ኤር30፥10፤32፥37፤ሕዝ28፥26፤39፥26፤ሆሴ11፥11፤አሞ9፥15፤ሶፎ3፥13፤ዘካ14፥11
34፥29 መዝ137፥3፤ኢሳ4፥2፤ሕዝ36፥6፡15፡29፤ኢል2፥19
34፥30 ሕዝ14፥11፤37፥27
34፥31 መዝ28፥9፤ኤር23፥1
35፥2 ዘፍ14፥6
35፥3 ኢሳ34፥10፤ኤር6፥12፤ሕዝ25፥12-14
35፥4 ቍ9፤ኤር44፥2፤49፥10
35፥5 መዝ63፥10፤137፥7፤ሕዝ21፥29፤አብ1፥13
35፥6 ኢሳ34፥3፤63፥2-6
35፥7 ኤር46፥19፤49፥17
35፥8 ሕዝ31፥12
35፥9 ኢሳ34፥5-6፤ኤር49፥13፤አብ1፥10
35፥10 መዝ83፥12፤ሕዝ36፥2፡5
35፥11 መዝ9፥16፤ሕዝ25፥14፤አብ1፥15፤ማቴ7፥2
35፥12 ኤር50፥7
35፥13 ኤር49፥16፤ዳን11፥36
35፥14 ኤር51፥48
35፥15 ቍ3፤ኢሳ 34፥5-6፡11፤ኤር50፥11-13፤ሰቆ4፥21፤ሕዝ32፥29፤36፥5፤አብ 1፥12
36፥1 ሕዝ17፥22
36፥2 ዘዳ32፥13፤ሕዝ6፥2-3፤25፥3፤35፥10
36፥3 መዝ44፥13-14፤ሰቆ2፥16፤3፥62፤አብ1፥13
36፥4 ዘሌ26፥43፤ዘዳ11፥11፤መዝ79፥4፤ኤር2፥26፤ሕዝ6፥3፤33፥24፡28-29
36፥5 ዘዳ29፥20፤ኢሳ66፥16፤ኤር25፥31፤50፥11፤ሕዝ25፥12-14፤35፥10፡15፤38፥22፤ኢል3፥2፡14
36፥6 መዝ123፥3-4፤ሕዝ34፥29
36፥7 ዘኍ14፥30፤ኤር25፥9
36፥8 ኢሳ4፥2፤27፥6፤ሕዝ47፥12
36፥9 ቍ34-36፤ኤር31፥27
36፥10 ኢሳ49፥8፡17-23፤ኤር30፥18
36፥11 ዘፍ1፥22፤ ዘሌ26፥9፤ኢዮ42፥13፤ ኢሳ49፥19፤ኤር31፥28፤ሕዝ16፥55፤ ሚክ7፥14፤ዘካ10፥8

ካለፈው የበለጠ አበለጽጋችኋለሁ፤ ከዚ
ያም እኔ *እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ ታውቃ
ላችሁ። 12ሰዎችን፣ ሕዝቤን እስራኤልን
በእናንተ ላይ እንዲመላለሱ አደርጋለሁ፤
ይወርሷችኋል፤ እናንተም ርስታቸው ትሆና
ላችሁ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ አልባ
አታደ ርጓቸውም።

13“ ‘ልዑል *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“ሕዝቡ እናንተን፣ ‘ሰዎችን ቦጫጭቀው
ይበላሉ፤ ሕዝብንም ልጅ አልባ ያደርጋሉ’
ስላሏችሁ፣ 14ከእንግዲህ ሰው አትበሉም፤
ሕዝቡንም ልጅ አልባ አታደርጉትም፤ ይላል
ጌታ *እግዚአብሔር።* 15ከእንግዲህ የሕዝቦ
ችን ዘለፋ እንድትሰሙ አላደርግም፤
በሰዎ ችም ስድብ አትሠቃዩም፤ ከእንግዲ
ህ ለሕዝባችሁ መሰናከል አትሆኑም፤
ይላል ጌታ *እግዚአብሔር።*”

16እንደ ገና *የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ
ሲል ወደ እኔ መጣ፤ 17የሰው ልጅ ሆይ፤
የእስራኤል ሕዝብ በገዛ ምድራቸው ይኖሩ
በነበረበት ጊዜ በሥራቸውና በአኗኗራቸው
አረከሷት፤ ጠባያቸውም በፊቴ፣ ሴት በወር
አበባዋ ወቅት እንደምትረክሰው ዐይነት
ነበር። 18ስለዚህ በምድሪቱ ላይ ደም ስላፈ
ሰሱና በጣዖታቶቻቸው ስላረከሷት፣ መዓ
ቴን አፈሰስሁባቸው። 19በአሕዛብ መካከል
በተንኳቸው፤ እነርሱም በየአገሩ ተበታተኑ፤
እንደ ጠባያቸውና እንደ ሥራቸው መጠን
ፈረድሁባቸው። 20በአሕዛብ መካከል በሄዱ
በት ሁሉ ቅዱስ ስሜን አረከሱ፤ ስለ
እነርሱ፣ ‘እነዚህ *የእግዚአብሔር* ሕዝብ
ናቸው፤ ዳሩ ግን የእርሱን ምድር ትተው
እንዲሄዱ ተገደዱ’ ተብሎአልና። 21የእስራ
ኤል ቤት በሄዱበት በአሕዛብ መካከል
ሁሉ፣ ስላረከሱት ቅዱስ ስሜ ገዶኛል።

22“ስለዚህ ለእስራኤል ቤት እንዲህ በል፤
‘ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ “የእስ
ራኤል ቤት ሆይ፤ ይህን ሁሉ የማደርገው
ስለ እናንተ ብዬ ሳይሆን፣ በየሄዳችሁባቸው
አሕዛብ መካከል ስላረከሳችሁት ስለ ቅዱስ
ስሜ ስል ነው። 23በአሕዛብ መካከል የረከሰ
ውን፣ እናንተ በእነርሱ ዘንድ ያረከሳችሁ
ትን ፣ የታላቁን ስሜን ቅድስና አሳያለሁ፤
ከዚያም ዐይኖቻቸው እያዩ፣ በእናንተ አማ
ካይነት ራሴን ቅዱስ አድርጌ ስገልጥ፣
አሕዛብ እኔ *እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ
ያውቃሉ፤ ይላል ጌታ *እግዚአብሔር።*”

24“ ‘ከአሕዛብ መካከል አስወጣችኋለሁ፤
ከየአገሩ ሁሉ እሰበስባችኋለሁ፤ ወደ ገዛ ምድ
ራችሁም መልሼ አመጣችኋለሁ። 25ንጹሕ
ውሃ እረጫችኋለሁ፤ እናንተም ንጹሕ ትሆ
ናላችሁ፤ ከርኵሰታችሁ ሁሉና
ከጣዖታቶቻ ችሁ ሁሉ አነጻችኋለሁ።
26አዲስ ልብ እሰ ጣችኋለሁ፤ አዲስ
መንፈስም በውስጣችሁ አሳድራለሁ፤
የድንጋይ ልባችሁን ከእናንተ አስወግዳለሁ፤
የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ። 27መንፈሴን
በውስጣችሁ አሳድራለሁ፤ ሥርዐ ቴን
እንድትከተሉና ሕጌን በጥንቃቄ እንድ
ትጠብቁ አደርጋለሁ። 28ለቀድሞ
አባቶቻችሁ በሰጠኋቸው ምድር ትኖራ
ላችሁ፤ ሕዝቤም ትሆናላችሁ፤ እኔም
አምላክ እሆናችኋሁ። 29ከርኵሰታችሁ ሁሉ
አነጻችኋለሁ፤ እህሉን አጠራለሁ፤
አበዛዋለሁም፤ ራብንም አላመ ጣባችሁም።
30ከራብ የተነሣ በአሕዛብ መካ ከል
በውርደት እንዳትሳቀቁ፣ የዛፉን ፍሬና የዕ
ርሻውን ሰብል አበዛለሁ። 31ከዚያም ክፉ
መንገዳችሁንና የረከሰ ሥራችሁን ታስታው
ሳላችሁ፤ ስለ ኀጢአታችሁና ስለ አስጸያፊ
ድርጊታችሁ ራሳችሁን ትጠላላችሁ። 32ለእናንተ
ስል ይህን እንደማላደርግ እንድታውቁ፤
ይላል ጌታ *እግዚአብሔር።* የእስራኤል
ቤት ሆይ፤ በአድራጎታችሁ ዕፈሩ፤ ተሸማቀ
ቁም!

33“ ‘ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“ከኀጢአታችሁ ሁሉ በማነጻችሁ ቀን፣ ከተ
ሞቻችሁ እንደ ገና መኖሪያ ይሆናሉ።
የፈረሷትም እንደ ገና ይታደሳሉ። 34በዕ
ላፊ አግዳሚው ዐይን ጠፍ ሆኖ ይታይ የነበ
ረው፣ ባድማ መሬት ይታረሳል። 35እነር
ሱም፣ “ጠፍ የነበረው ይህ ምድር እንደ ዔድን
ገነት መሰለ፤ የተደመሰሱ፣ የፈራረሱና ባድማ
የሆኑት ከተሞች አሁን መኖሪያና ምሽግ
ሆነዋል” ይላሉ። 36ከዚያም በዙሪያችሁ የነ
በሩ የቀሩት አሕዛብ ፈርሶ የነበረውን መልሼ
የሠራሁ፣ ጠፍ የነበረውን ያለመለምሁ እኔ
*እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ ያውቃሉ። እኔ
*እግዚአብሔር* ተናግሬአለሁ፤ እኔም አደርገ
ዋለሁ።”

37“ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
‘እንደ ገና ለእስራኤል ቤት ልመና እሺ
እላለሁ፤ ይህንም አደርግላቸዋለሁ፤ ሕዝባ
ቸውን እንደ በግ መንጋ አበዛዋለሁ፤
38በኢየሩሳሌም በዓላት ላይ እንደሚገኘው
የመሥዋዕት በግ መንጋ አበዛዋለሁ። እነሆ!
ፈራርሰው የነበሩት ከተሞች የብዙ ሕዝብ
መኖሪያ ይሆናሉ፤ ከዚያም እኔ *እግዚ
አብሔር* እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።’ ”

### የደረቅ ዐጥንቶች ሸለቆ

**37** *የእግዚአብሔር* እጅ በላዬ ነበረ፤
እርሱም *በእግዚአብሔር* መንፈስ
አወጣኝ፤ በሸለቆ መካከልም አኖረኝ፤ ሸለቆ
ውም በዐጥንቶች ተሞልቶ ነበር። 2በእነር
ሱም መካከል ወደ ፊትና ወደ ኋላ

36፥12 ሕዝ47፥14፡22
36፥13 ዘኍ13፥32
36፥15 መዝ89፥50-51፤ኢሳ54፥4፤ሕዝ34፥29
36፥17 ዘሌ5፥2፤12፥2፤መዝ106፥37-38፤ኤር2፥7
36፥18 2ዜና34፥21
36፥19 ዘሌ18፥24-28፤ዘዳ28፥64፤ሕዝ7፥8፤24፥14፤39፥24
36፥20 ዘሌ18፥21፤ኢሳ52፥5፤ኤር33፥24፤ሕዝ12፥16፤13፥19፤ሮሜ2፥24
36፥21 መዝ74፥18፤ኢሳ48፥9
36፥22 ዘዳ9፥5-6፤መዝ106፥8፤ኢሳ37፥35፤ሕዝ20፥9፡44፤ሮሜ2፥24
36፥23 ዘኍ6፥27፤መዝ46፥10፤126፥2፤ኢሳ5፥16፤37፥23፤ሕዝ20፥14፡41፤38፥23፤39፥7፡27-28
36፥24 ኢሳ43፥5-6፤ሕዝ34፥13፤37፥21
36፥25 ዘሌ14፥7፤16፥14-15፤ዕዝ6፥21፤መዝ51፥2፡7፤ኢሳ2፥18፤ኢል3፥21፤ዘካ3፥4፤13፥2፤ሐሥ22፥16፤ዕብ9፥13
36፥26 መዝ51፥10፤ኤር5፥3፤24፥7፤ሕዝ18፥31፤2ቆሮ3፥3
36፥27 ኢሳ44፥3፤ኤር 50፥20፤ሕዝ18፥21፤ኢል2፥29፤ዮሐ3፥5፤1ተሰ4፥8
36፥28 ኤር30፥22፤31፥33፤ሕዝ11፥17፤14፥11፤34፥24፤37፥14፡27፤ዘካ8፥8
36፥29 ሕዝ34፥29
36፥30 ዘሌ26፥4-5፤ሕዝ34፥13-14፤ሆሴ 2፥21-22
36፥31 ኢሳ6፥5፤ኤር31፥19፤ሕዝ6፥9
36፥32 ዘዳ9፥5፤ሕዝ16፥63
36፥33 ዘሌ16፥30፤26፥31፤ኢሳ49፥8
36፥35 ዘፍ2፥8፤አሞ9፥14
36፥36 ኤር42፥10፤ሕዝ17፥22፤37፥14፤39፥27-28
36፥37 መዝ102፥17፤ኤር29፥12-14፤ዘካ 10፥6፤13፥9
36፥38 ዘፀ6፥2፤1ነገ8፥63፤ 2ዜና35፥7-9
37፥1 ኤር7፥32፤8፥2፤ሕዝ1፥3፤11፥24፤40፥1፤ሉቃ4፥1፤ሐሥ8፥39

አመላለሰኝ፤ በሸለቆውም ወለል ላይ በጣም
የደረቁ እጅግ ብዙ ዐጥንቶች አየሁ። 3እር
ሱም፣ “የሰው ልጅ ሆይ፤ እነዚህ ዐጥን
ቶች በሕይወት ሊኖሩ ይችላሉን?” ሲል ጠየ
ቀኝ።

እኔም፣ “ጌታ *እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ
ብቻ ታውቃለህ” አልሁ።

4ከዚያም እንዲህ አለኝ፤ “ለእነዚህ ዐጥን
ቶች ትንቢት ተናገር፤ እንዲህም በላቸው፤
‘እናንት ደረቅ ዐጥንቶች፤ *የእግዚአብሔርን*
ቃል ስሙ! 5ጌታ *እግዚአብሔር* ለእነዚህ፤
ዐጥንቶች እንዲህ ይላል፤ “እስትንፋስ[ቀ] አገ
ባባችኋለሁ፤ እናንተም በሕይወት ትኖራላ
ችሁ። 6ጅማት አደርግላችኋለሁ፤ ሥጋ አለ
ብሳችኋለሁ፤ በቆዳ እሸፍናችኋለሁ፤ በውስጣ
ችሁም እስትንፋስ አገባባችኋለሁ፤ በሕይወት
ትኖራላችሁ፤ እኔም *እግዚአብሔር* እንደ
ሆንሁ ታውቃላችሁ።” ’

7ስለዚህ እንደ ታዘዝሁት ትንቢት ተናገ
ርሁ፤ ትንቢቱን በምናገርበትም ጊዜ የኰሽ
ኰሽታ ድምፅ ተሰማ፤ ዐጥንቶቹም አንድ
ላይ ሆኑ፤ ዐጥንት ከዐጥንት ጋር ተጋጠመ።
8እኔም ተመለከትሁ፤ ጅማት ነበረባቸው፤
ሥጋም በላያቸው ታየ፤ ቆዳም ሸፍኖአቸዋል፤
እስትንፋስ ግን በውስጣቸው አልነበረም።

9ከዚያም እንዲህ አለኝ፤ “የሰው ልጅ
ሆይ፤ ለነፋሱ ትንቢት ተናገር፤ ትንቢት
ተናገር፤ እንዲህም በለው፤ ‘ጌታ *እግዚ
አብሔር* እንዲህ ይላል፤ “ነፋስ ሆይ፤ ከአ
ራቱ ነፋሳት ዘንድ ና፤ በሕይወት እንዲ
ኖሩም በእነዚህ በተገደሉት ላይ እፍ በልባ
ቸው።” ’ 10ስለዚህም እንዳዘዘኝ ትንቢት
ተናገርሁ፤ እስትንፋስም ገባባቸው፤ ሕያዋ
ንም ሆኑ፤ እጅግ ታላቅ ሰራዊት ሆነው በእ
ግራቸው ቆሙ።

11ከዚያም እንዲህ አለኝ፤ “የሰው ልጅ
ሆይ፤ እነዚህ ዐጥንቶች መላው የእስራኤል
ቤት ናቸው፤ እንዲህም ይላሉ፤ ‘ዐጥንቶቻችን
ደርቀዋል፤ ተስፋ የለንም፤ ተቈርጠናል።”
12ስለዚህ ትንቢት ተናገር እንዲህም
በላቸው፤ ‘ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“ሕዝቤ ሆይ፤ መቃብሮቻችሁን
እከፍታለሁ፤ ከውስ ጣቸው አወጣችኋለሁ፤
ወደ እስራኤል ምድር መልሼ
አመጣችኋለሁ። 13ከዚያም እናንተ
ሕዝቤ ሆይ፤ መቃብሮቻችሁን ከፍቼ ሳወጣ
ችሁ፣ እኔ *እግዚአብሔር* እንደ ሆንሁ ታው
ቃላችሁ። 14*መንፈሴን* በውስጣችሁ አስቀም
ጣለሁ፤ እናንተም በሕይወት ትኖራላችሁ፤
በገዛ ምድራችሁ አስቀምጣችኋለሁ፤ ከዚ
ያም እኔ *እግዚአብሔር* እንደ ተናገርሁ፣
እንዳደረግሁትም ታውቃላችሁ፤ ይላል *እግዚ
አብሔር*።” ’

## አንድ ሕዝብ በአንድ ንጉሥ

15*የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤ 16“የሰው ልጅ ሆይ፤ አንድ
በትር ወስደህ፣ ‘የይሁዳና የተባባሪዎቹ
የእስራኤላውያን’ ብለህ ጻፍበት። ከዚያም
ሌላ በትር ወስደህ፣ ‘የኤፍሬም፣ የዮሴፍና
የተባ ባሪዎቹ የእስራኤል ቤት ሁሉ’
ብለህ ጻፍበት። 17እንደ አንድ በትር ይሆኑ
ዘንድ በእጅህ ላይ አጋጥመህ ያዛቸው።

18“የአገርህ ልጆች፣ ‘ይህስ ምን ማለትህ
እንደ ሆነ አትነግረንምን?’ ብለው ሲጠይ
ቁህ፣ 19እንዲህ በላቸው፤ ‘ጌታ *እግዚአብሔር*
እንዲህ ይላል፤ “በኤፍሬም እጅ ያለውን
የዮሴፍን በትርና የተባባሪዎቹን የእስራ
ኤላውያንን ነገድ በትር እወስዳለሁ፤ ከይሁዳ
በትር ጋር አጋጥሜ አንድ ወጥ በትር አደ
ርጋቸዋለሁ፤ እነርሱም በእጄ አንድ በትር
ይሆናሉ።’ ” 20የጻፍህባቸውን በትሮች ከፊት
ለፊታቸው ያዝ፤ 21እንዲህም በላቸው፤ ‘ጌታ
*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ “እስራኤላው
ያንን ከሄዱባቸው አሕዛብ መካከል አወጣቸ
ዋለሁ፤ ከየስፍራው ሰብስቤ ወደ ገዛ ምድ
ራቸው እመልሳቸዋለሁ። 22በምድሪቱ በእስ
ራኤል ተራሮች ላይ አንድ ሕዝብ አደርጋቸ
ዋለሁ፤ በሁሉም ላይ አንድ ንጉሥ ይነግሣል፤
ከእንግዲህም ሁለት ሕዝብ አይሆኑም፤
መንግሥታቸውም ከሁለት አይከፈልም።
23በጣዖታቶቻቸው፣ በአስጸያፊ ምስሎቻቸው
ወይም በማንኛውም ኀጢአት ራሳቸውን
አያረክሱም፤ ነገር ግን እኔን በመተው ከሠ
ሩት ኀጢአት ሁሉ አድናቸዋለሁ፤[በ] አነጻ
ቸዋለሁም። እነርሱ ሕዝቤ ይሆናሉ፤ እኔም
አምላካቸው እሆናለሁ።”

24“ ‘ባሪያዬ ዳዊት በላያቸው ይነግሣል፤
ሁሉም አንድ እረኛ ይኖራቸዋል፤ ሕጌን
ይከተላሉ፤ ሥርዐቴንም በጥንቃቄ ይጠብ
ቃሉ። 25አባቶቻችሁ በኖሩበት፣ ለባሪያዬ
ለያዕቆብ በሰጠሁት ምድር ይኖራሉ። በዚ
ያም እነርሱ፣ ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻ
ቸው ለዘላለም ይኖራሉ፤ ባሪያዬ ዳዊትም
ለዘላለም ንጉሣቸው ይሆናል። 26ከእነርሱም
ጋር የሰላም ቃል ኪዳን አደርጋለሁ፤ ቃል ኪዳ
ኑም የዘላለም ይሆናል። አጸናቸዋለሁ፤
አበዛቸዋለሁ፤ መቅደሴንም በመካከላቸው
ለዘላለም አኖራለሁ። 27ማደሪያዬ ከእነርሱ

[ቀ]5 በዕብራይስጥ *ነፋስ* ወይም *መንፈስ* ማለትም ነው (ከቍ6-14 ይመ)
[በ]23 በብዙ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆችም እንዲሁ (በተጨማሪ ሰብዓ ሊቃናት ይመ) ሲሆን፣ አብዛኛዎቹ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆች ግን *ኀጢአት የሠሩባቸውን የመኖሪያ ስፍራዎቻቸውን ሁሉ* ይላሉ

37፥3 ዘዳ32፥39፤ 1ሳሙ2፥6፤ ኢሳ26፥19፤ 1ቆሮ15፥35
37፥4 ኤር22፥29
37፥5 ዘፍ2፥7፤ መዝ104፥29-30፤ ራእ11፥11
37፥6 ዘፀ6፥2፤ ሕዝ38፥23
37፥9 ቍ14፤ መዝ 104፥30፤ ኢሳ32፥15፤ ኤር49፥36፤ ሕዝ39፥29፤ዳን7፥2፤ 8፥8፤11፥4፤ዘካ2፥6፤ 6፥5፤12፥10፤ራእ7፥1
37፥10 ሕዝ12፥7፤ ራእ11፥11
37፥11 ኢዮ17፥15፤ ሰቆ3፥54
37፥12 ቍ21፤ ዘዳ32፥39፤1ሳሙ2፥6፤ ኢሳ26፥19፤ኤር29፥14፤ሆሴ13፥14፤ አሞ9፥14-15፤ ሶፎ3፥20፤ዘካ8፥8
37፥13 ዘፀ6፥2፤ ሕዝ17፥24፤ሆሴ13፥14
37፥14 ቍ9፤ ኢሳ11፥2፤ኤር43፥2፤ ሕዝ36፥27-28፡36፤ ኢል2፥28-29፤ ራእ11፥11
37፥16 ዘኍ17፥2-3፤1ነገ12፥20፤ 2ዜና10፥17-19፤ 15፥9
37፥17 ቍ24፤ ኢሳ11፥13፤ ኤር50፥4፤ሆሴ1፥11
37፥18 ሕዝ24፥19
37፥19 ዘካ10፥6
37፥21 ቍ12፤ኢሳ43፥5-6፤ሕዝ20፥42፤ 39፥27፤ሚክ 4፥6
37፥22 ኢሳ11፥13፤ ኤር33፥24፤50፥4፤ ሕዝ17፥22፤34፥13-14፤ሆሴ1፥11
37፥23 ኤር7፥24፤ ሕዝ11፥18፤36፥28፤ 43፥7፤ናሆ2፥2
37፥24 1ሳሙ13፥14፤መዝ78፥70-71፤ ኢሳ32፥1፤55፥4፤ኤር30፥21፤ሕዝ21፥27፤ ሆሴ3፥5፤ዘካ 13፥7
37፥25 ዕዝ9፥12፤ መዝ89፥3-4፤ኢሳ11፥1፤ሕዝ28፥25፤ 34፥23-24፤አሞ9፥15
37፥26 ዘፍ9፥16፤ ዘሌ26፥11፤ዘኍ25፥12፤ዘዳ29፥14፤ኤር30፥19፤ሕዝ16፥62፤ ዕብ13፥20
37፥27 ዘሌ26፥11፤ ሕዝ34፥30፤36፥28፤ 2ቆሮ6፥16

ጋር ይሆናል፤ አምላካቸው እሆናለሁ፤ እነር
ሱም ሕዝቤ ይሆናሉ። 28መቅደሴም ለዘላ
ለም በመካከላቸው በሚሆንበት ጊዜ፣ አሕ
ዛብ እኔ *እግዚአብሔር* እስራኤልን እንደ
ቀደስሁ ያውቃሉ።’ ”

## በጎግ ላይ የተነገረ ትንቢት

38 *የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤ 2“የሰው ልጅ ሆይ፤
ፊትህን በማጎግ ምድር በሚገኘው፣ በሞሳሕና
በቶቤል ዋና አለቃ⁺ በጎግ ላይ አድርግ፤
በእርሱ ላይ ትንቢት ተናገር፤ 3እንዲህም
በል፤ ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“የሞሳሕና የቶቤል ዋና አለቃ⁺⁺ ጎግ ሆይ፤
ተነሥቼብሃለሁ። 4ወደ ኋላ እመልስሃለሁ፤
መንጋጋህ ውስጥ መንጠቆ አስገብቼ ከመ
ላው ሰራዊትህ ጋር፣ ፈረሶችህን፣ ፈረሰኞ
ችህን ከነሙሉ ትጥቃቸው፣ ትልቅና ትንሽ
ሰይፍ የያዙትን ሁሉ፣ ሰይፋቸውንም የወለ
ወሉትን ሁሉ አስወጣለሁ። 5ጋሻ የያዙና
የራስ ቍር የደፉት ሁሉ፣ ፋርስ፣ ኢትዮ
ጵያና ፉጥ ከእነርሱ ጋር ይሆናሉ። 6ደግ
ሞም ጎሜርን ከወታደሮቹ ጋር፣ ራቅ
ካለው ሰሜንም የቴርጋማን ቤት ከወታደሮቹ
ሁሉ ጋር ብዙ ሕዝቦችን ከአንተ ጋር አስ
ወጣለሁ።”

7“ ‘አንተና በዙሪያህ የተሰበሰቡት ሁሉ
ተነሡ፤ ተዘጋጁ፤ አንተም መሪያቸው ሁን።
8ከብዙ ቀን በኋላ ለጦርነት ትጠራለህ።
በኋለኛው ዘመንም ከጦርነት ያገገመችውን፣
ሕዝቧ ከአያሌ አሕዛብ መካከል ወጥቶ የተ
ሰበሰበውን፣ ለብዙ ጊዜ ባድማ በነበረው
በእስራኤል ተራሮች ላይ የሰፈረውን ወገን
ትወራለህ። ከሕዝቦች መካከል ወጥተው፣
አሁን ሁሉም በሰላም ይኖራሉ። 9አንተና
ወታደሮችህ ሁሉ፣ ከአንተም ጋር ያሉት
ብዙ ሕዝቦች እንደ ማዕበል ትወጣላችሁ፤
ምድርን እንደሚሸፍን ደመናም ትሆና
ላችሁ።

10“ ‘ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“በዚያ ቀን ሐሳብ ወደ አእምሮህ ይመጣል፤
ክፉትንም ታውጠነጥናለህ።” 11እንዲህም ትላ
ለህ፤ “ቅጥር የሌላቸውን መንደሮች ምድር
እወራለሁ፤ ሁሉም ያለ ቅጥር፣ ያለ በርና
ያለ ብረት መወርወሪያ የሚኖረውን፣ ሰላ
ማዊና ያለ ሥጋት የተቀመጠውን ሕዝብ
እወጋለሁ፤ 12እዘርፋለሁ፤ እነጥቃለሁ፤ እን
ዲሁም ከአሕዛብ ተሰባስቦ እንደ ገና በሰፈ
ረው፣ በከብትና በሸቀጥ በከበረው፣ በምድ
ሪቱም መካከል በሚኖረው ሕዝብ ላይ
እጄን አነሣለሁ።” 13ሳባና ድዳን፣ የተርሴስ
ነጋዴዎችና መንደሮቿም ሁሉ⁺⁺⁺ እንዲህ
ይሉሃል፤ “ልትዘርፍ መጣህን? ሰራዊትህን
ያሰባሰብኸው ለመበዝበዝ፣ ወርቅና ብሩን
አጋብሶ ለመሄድ፣ ከብቱንና ሸቀጡን
ለመውሰድ፣ ብዙ ምርኮ ይዞ ለመመለስ
ነውን?” ’

14“ስለዚህ የሰው ልጅ ሆይ፤ ትንቢት
ተናገር፤ ጎግንም እንዲህ በለው፤ ‘ጌታ *እግ
ዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ “በዚያ ቀን ሕዝቤ
እስራኤል በሰላም መቀመጡን ዐውቀህ
አትንቀሳቀስምን? 15በስተ ሰሜን ርቆ ከሚ
ገኘው ቦታ ትመጣለህ፤ አንተና ከአንተም
ጋር ብዙ ሕዝቦች፣ እጅግ ታላቅ ኀያል ሰራ
ዊትም በፈረሶች ላይ ሆናችሁ ትመጣላ
ችሁ። 16ምድርን እንደሚሸፍን ደመና
ሆነህ በሕዝቤ በእስራኤል ላይ ትወጣለህ።
ጎግ ሆይ፤ በፊታቸው ቅድስናዬን ስገልጥ
ሕዝቦች እኔን ያውቁ ዘንድ በኋለኛው ዘመን
በምድሬ ላይ አመጣሃለሁ።”

17“ ‘ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“በቀደመው ዘመን በባሪያዎቼ በእስራኤል
ነቢያት ስለ እርሱ የተናገርሁለት ያ ሰው
አንተ አይደለህምን? በዚያን ወቅት አንተን
በእነርሱ ላይ እንደማመጣባቸው ለብዙ ዓመ
ታት ትንቢት ተናገሩ።” 18በዚያን ጊዜ እን
ዲህ ይሆናል፤ “ጎግ የእስራኤልን ምድር
ሲወጋ፣ ብርቱ ቍጣዬ ይነሣሣል፤ ይላል
ጌታ *እግዚአብሔር*። 19በዚያን ጊዜ በቅናቴና
በሚያስፈራው ቍጣዬ በእስራኤል ታላቅ
የምድር መንቀጥቀጥ ይሆናል ብዬ ተናግ
ሬአለሁ። 20የባሕር ዓሦች፣ የሰማይ ወፎች፣
የምድር አራዊት፣ በምድር ላይ የሚሳብ
ማንኛውም ፍጡር፣ እንዲሁም በምድር
ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ፣ በፊቴ ይንቀጠ
ቀጣሉ፤ ተራሮች ይገለባበጣሉ፤ ገደሎች
ይናዳሉ፤ 21በተራሮቼም ሁሉ በጎግ ላይ ሰይፍ
እጠራለሁ፤ ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*፤ የእያ
ንዳንዱም ሰው ሰይፍ በወንድሙ ላይ
ያርፋል። 22በቸነፈርና በደም መፋሰስ እፈ
ርድበታለሁ፤ የዝናብ ዶፍ፣ የበረዶ ድንጋይ፣
የሚያቃጥል ድኝ፣ በእርሱና በወታደሮቹ፣
ከእርሱም ጋር ባሉት ሕዝቦች ላይ አወር
ዳለሁ። 23በዚህም ታላቅነቴንና ቅድስናዬን
አሳያለሁ፤ በብዙ ሕዝቦች ፊት ራሴን
አሳውቃለሁ፤ ከዚያም እኔ *እግዚአብሔር*
እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።” ’

39 “አንተ የሰው ልጅ ሆይ፤ በጎግ ላይ
ትንቢት ተናገር፤ እንዲህም በል፤
‘ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“የሞሳሕና የቶቤል ዋና አለቃ⁺⁺⁺⁺ ጎግ ሆይ፤

37፥28 ዘፀ31፥13፤ ሕዝ43፥9፤ሆሴ1፥10-11፤ሶፎ3፥15
38፥2 ቍ14፤ ዘፍ10፥2፤ሕዝ27፥13፤ 39፥11
38፥3 ሕዝ39፥1
38፥4 2ነገ19፥28፤ ኢሳ43፥17፤ሕዝ29፥4፤39፥2፤ዳን11፥40
38፥5 ዘፍ10፥6፤ ሕዝ27፥10
38፥6 ዘፍ10፥2፡3፤ ሕዝ32፥30
38፥7 ኢሳ8፥9
38፥8 ቍ14፤ኢሳ 11፥11፤24፥22፤ኤር 23፥6፤ሕዝ28፥26፤ ኢል3፥1
38፥9 ቍ16፤ኢሳ 25፥4፤28፥2፤ኤር 4፥13፤ኢል2፥2፤ ራእ20፥8
38፥10 መዝ36፥4፤ ኤር17፥10፤ሚክ2፥1
38፥11 ዘፍ34፥25፤ ኤር49፥31፤ዘካ2፥4
38፥13 ዘፍ10፥4፡7፤ 25፥3፤ኢሳ10፥6፤ 33፥23፤ኤር15፥13
38፥14 ቍ8፤ዘሌ 25፥18፤ኤር16፥15፤ ዘካ 2፥5
38፥15 ሕዝ32፥30፤ 39፥2፤ራእ20፥8
38፥16 ቍ9፤ ዘሌ10፥3፤ኢሳ29፥23፤ ሕዝ39፥21፤ ኢል3፥11
38፥19 መዝ18፥7፤ ኢሳ24፥18፤ሕዝ 5፥13፤ኢል2፥10፤ 3፥16፤ሐጌ2፥6፡21፤ ራእ6፥12
38፥20 ዘፀ15፥14፤ ኢዮ14፥18፤መዝ 76፥8፤ኢሳ42፥15፤ ሆሴ4፥3፤ናሆ1፥5
38፥21 1ሳሙ14፥ 20፤2ዜና20፥23፤ኢሳ 66፥16፤ኤር25፥29፤ ሐጌ2፥22
38፥22 ዘፍ19፥24፤ ዘፀ9፥18፤መዝ18፥12፤ኢሳ66፥16፤ኤር25፥31፤ሕዝ13፥11፤ 14፥19፤28፥23፤36፥5፤ራእ9፥17፤16፥21
38፥23 ሕዝ20፥42፤ 36፥23፤37፥6
39፥1 ዘፍ10፥2፤ ሕዝ27፥13፤38፥2፡3

⁺2 ወይም *የሮሽ አለቃ* ⁺⁺3 ወይም *የሮሽ አለቃ ጎግ*
⁺⁺⁺13 ወይም *ጠንካራ መንደሮችዋ*
⁺⁺⁺⁺1 ወይም *የሮሽ አለቃ ጎግ*

ተነሥቼብሃለሁ፤ 2ወደ ኋላ እመልስሃለሁ፤
እንዲሁም እጐትትሃለሁ፤ ከሩቅ ሰሜን
አምጥቼ በእስራኤል ተራሮች ላይ እሰድሃ
ለሁ። 3በግራ እጅህ ያለውን ቀስትህን እመ
ታለሁ፤ በቀኝ እጅህ የያዝሃቸውንም ፍላጾች
አስረግፍሃለሁ። 4አንተና ወታደሮችህ ሁሉ፣
ከአንተም ጋር ያሉ ሕዝቦች በእስራኤል ተራ
ሮች ላይ ትወድቃላችሁ። ነጣቂ አሞሮችና
የዱር አራዊት ይበሏችሁ ዘንድ አሳልፌ
እሰጣችኋለሁ። 5አውላላ ሜዳ ላይ ትወድ
ቃለህ፤ እኔ ተናግሬአለሁና፤ ይላል ጌታ
*እግዚአብሔር*። 6በማጎግና ያለ ሥጋት
በባሕር ዳርቻ በሚኖሩት ላይ እሳት እሰ
ዳለሁ፤ እነርሱም እኔ *እግዚአብሔር* እንደ
ሆንሁ ያውቃሉ።”
7“ ‘ቅዱሱ ስሜ በሕዝቤ በእስራኤል ዘንድ
እንዲታወቅ አደርጋለሁ፤ ከእንግዲህ ወዲያ
ቅዱስ ስሜ እንዲናቅ፣ እንዲቃለል አልፈል
ግም፤ አሕዛብም እኔ *እግዚአብሔር* የእስ
ራኤል ቅዱስ እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።
8እነሆ ይመጣል፤ በእርግጥም ይሆናል፤ ይላል
ጌታ *እግዚአብሔር*፤ ያ ያልሁት ቀን ይህ
ነው።
9“ ‘ከዚያም በእስራኤል ከተሞች የሚኖሩ
ሁሉ ወጥተው የጦር መሣሪያውን፣ ትልል
ቁንና ትንንሹን ጋሻ፣ ቀስቱን፣ ፍላጻውን፣
የጦር ዱላውንና ጦሩን ሰብስበው ማገዶ
በማድረግ ያነዱታል፤ ሰባት ዓመት ይማግ
ዱታል። 10ከሜዳ ላይ ዕንጨት መልቀም፣
ከዱርም ዛፍ መቍረጥ አያስፈልጋቸውም፤
የጦር መሣሪያቸውን በመማገድ ይጠቀማ
ሉና። የዘረፏቸውን ይዘርፋሉ፤ የበዘበዟቸውን
ይበዘብዛሉ፤ ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*።
11“ ‘በዚያ ቀን ሰዎች በምሥራቅ በኩል
ወደ ባሕሩ[ኘ] በሚጓዙበት ሸለቆ፣ ለጎግ
የመ ቃብር ስፍራ በእስራኤል እሰጠዋለሁ።
ጎግና ሰራዊቱ ሁሉ በዚያ ስለሚቀበሩ፣
የተጓዥ ችን መንገድ ይዘጋሉ፤ ስለዚህም
የሐሞን ጎግ[አ] ሸለቆ ይባላል።
12“ ‘ምድሪቱን ለማጽዳት፣ የእስራኤል ቤት
ሰዎች ሰባት ወር ሙሉ ይቀብሯቸዋል።
13የምድሪቱ ሰዎች ሁሉ ይቀብሯቸዋል፤ እኔ
የምከብርበትም ዕለት የመታሰቢያ ቀን ይሆ
ናቸዋል፤ ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*።
14“ ‘ሰዎች ምድሪቱን ለማጽዳት በየጊ
ዜው ይቀጠራሉ። አንዳንዶቹ ምድሪቱን
ያስሳሉ፤ ከእነርሱም በተጨማሪ ሌሎች
ሳይቀበሩ የቀሩትን ይቀብራሉ። ከሰባት ወር
በኋላም ፍለጋ ይጀምራሉ። 15እነርሱም
በምድሪቱ መካከል ሲሄዱ፣ ከእነርሱ አንዱ
የሰው ዐፅም ባየ ቍጥር ምልክት ያደርግ
በታል፤ ይህም መቃብር ቈፋሪዎች በሐ
ሞን ጎግ ሸለቆ እስኪቀብሩት ድረስ ነው።
16በዚያም ሐሞና[ከ] የምትባል ከተማ
አለች፤ ስለዚህ ምድሯን ያጸዳሉ።’
17“ ‘የሰው ልጅ ሆይ፤ ጌታ *እግዚአብሔር*
እንዲህ ይላል፤ ‘ማንኛውንም ዐይነት ወፍና
የዱር አራዊት ሁሉ ጥራ፤ እንዲህም በላቸው፤
“ከየአቅጣጫው ተሰብስባችሁ እኔ ወደማዘጋ
ጅላችሁ መሥዋዕት ኑ፤ ይህም በእስራ
ኤል ተራሮች ላይ የሚሆን ታላቁ መሥ
ዋዕት ነው። በዚያ ሥጋ ትበላላችሁ፤ ደምም
ትጠጣላችሁ። 18እንደ አውራ በግና እንደ
ጠቦት፣ እንደ ፍየልና እንደ ወይፈን፣
የኀያላን ሰዎችን ሥጋ ትበላላችሁ፤ የምድር
ንም መሳፍንት ደም ትጠጣላችሁ፤ እነዚህ
ሁሉ የሰቡ የባሳን ከብቶች ናቸው። 19እኔ
በማዘጋጅላችሁም መሥዋዕት እስክትጠ
ግቡ ስብ ትበላላችሁ፤ እስክትሰክሩም ደም
ትጠጣላችሁ። 20በገበታዬም ፈረሶችንና ፈረሰ
ኞችን፣ ኀያላን ሰዎችንና ከየወገኑ የሆኑትን
ወታደሮች እስክትጠግቡ ትበላላችሁ፤” ይላል
ጌታ *እግዚአብሔር*።’
21“ክብሬን በአሕዛብ መካከል እገልጣለሁ፤
አሕዛብም ሁሉ በእነርሱ ላይ ያመጣሁትን
ቅጣትና በላያቸው ላይ የጫንሁትን እጅ
ያያሉ። 22ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእስራኤል
ቤት እኔ *እግዚአብሔር*፣ አምላካቸው
እንደ ሆንሁ ያውቃሉ። 23አሕዛብም የእስ
ራኤል
ሕዝብ ለእኔ ታማኞች ባለመሆን ከሠሩት
ኀጢአት የተነሣ እንደ ተሰደዱ ያውቃሉ፤
ስለዚህ ፊቴን ከእነርሱ ሰወርሁ፤ ለጠላቶቻ
ቸው አሳልፌ ሰጠኋቸው፤ ሁሉም በሰይፍ
ወደቁ። 24እንደ ርኵሰታቸውና እንደ በደላ
ቸው መጠን ፈረድሁባቸው፤ ፊቴንም ከእነ
ርሱ ሰወርሁ።
25“ስለዚህ ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤ ያዕቆብን አሁን ከስደት እመልሰዋ
ለሁ፤[ኸ] ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ እራራለሁ፤
ስለ ቅዱስ ስሜም እቀናለሁ። 26የሚያስፈ
ራቸው ማንም ሳይኖር በምድራቸው
በሰላም በሚኖሩበት ጊዜ፣ ውርደታቸውንና
ለእኔ ታማኝ ሆነው ያልኖሩበትን ዘመን
ይረሳሉ። 27ከአሕዛብ ምድር መልሼ ሳመ
ጣቸው፣ ከጠላቶቻቸው አገር ስሰበስባቸው
የራሴን ቅድስና በእነርሱ በኩል በብዙ ሕዝ
ቦች ፊት አሳያለሁ። 28በአሕዛብ መካከል
እንዲሰደዱ ባደርግም፣ አንድም ሳላስቀር
ወደ ገዛ ምድራቸው እመልሳቸዋለሁ፤ ከዚ
ያም እኔ *እግዚአብሔር* አምላካቸው
እንደ ሆንሁ ያውቃሉ። 29ከእንግዲህ ፊቴን
ከእነርሱ

39፥2 ሕዝ32፥30፤ 38፥4፡15
39፥3 መዝ76፥3፤ ሆሴ1፥5፤አሞ2፥15
39፥4 ቍ17-20፤ ዘፍ40፥19፤ኤር25፥33፤ሕዝ29፥5፤33፥27
39፥5 ሕዝ32፥4
39፥6 ዘፍ10፥2፤ዘዐ6፥7፤ኤር25፥22፤ሕዝ30፥8፤ራእ20፥9
39፥7 ዘፀ20፥7፤ኢሳ12፥6፤49፥26፤54፥5፤ሕዝ13፥19፤20፥9፤36፥23
39፥8 ሕዝ7፥6
39፥9 መዝ46፥9፤ 76፥3
39፥10 ዘፀ3፥22፤ ኢሳ14፥2፤33፥1፤ ዕን2፥8
39፥11 ኢሳ34፥3፤ ሕዝ38፥2
39፥12 ዘዳ21፥23
39፥13 ሕዝ28፥22
39፥17 ኢዮ15፥23፤ ሕዝ32፥4
39፥18 መዝ22፥12፤ ኤር51፥40
39፥19 ዘሌ3፥9
39፥20 ኢሳ59፥9፤ ኤር12፥9፤ራእ19፥17-18
39፥21 ዘፀ9፥16፤ ኢሳ37፥20፤ሕዝ38፥16
39፥23 ኢሳ1፥15፤ 59፥2፤ኤር22፥8-9፤ 44፥23
39፥24 2ነገ17፥23፤ ኤር2፥17፡19፤4፥18፤ ሕዝ7፥22፤ዳን9፥7
39፥25 ኢሳ27፥12-13፤ኤር30፥18፤ 33፥7፤ሕዝ16፥53
39፥26 1ነገ4፥25፤ ኢሳ17፥2፤ኤር32፥37፤ ሕዝ34፥28፤38፥8፤ ሚክ4፥4
39፥27 ሕዝ37፥21
39፥28 መዝ147፥2፤ ሕዝ36፥23፡36
39፥29 ዘዳ31፥17፤ ኢሳ11፥2፤ሕዝ16፥42 ፤37፥9፤ሐሥ2፥17

[ኘ]11 የሙት ባሕርን ያመለክታል
[አ]11 *ሐሞንጎግ ማለት የጎግ መንጋ ማለት ነው*
[ከ]16 *ሐሞና ማለት መንጋ ማለት ነው*
[ኸ]25 ወይም *አሁን የያዕቆብን ዕድል ዐድሳለሁ*

አልሰውርም፤ መንፈሴን በእስራኤል ቤት
ላይ አፈሳለሁና፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።”

## አዲሱ ቤተ መቅደስ

40 በተሰደድን በሃያ አምስተኛው ዓመት፣
በዓመቱ መጀመሪያ፣ በዐሥረኛው
ቀን፣ ከተማዪቱ በወደቀች በዐሥራ አራተ
ኛው ዓመት፣ በዚያው ዕለት የእግዚአብሔር
እጅ በላዬ ነበር፤ እርሱም ወደዚያ ወሰደኝ።
2በእግዚአብሔር ራእይ ወደ እስራኤል ምድር
አመጣኝ፤ ከፍ ባለ ተራራ ላይ አኖረኝ፤
ከተራራውም በስተ ደቡብ፣ ከተማ የሚመ
ስሉ ሕንጻዎች ነበሩ። 3ወደዚያ ወሰደኝ፤
እነሆ መልኩ ናስ የሚመስል ሰው አየሁ፤
እርሱም የሐር ገመድና መለኪያ ዘንግ በእጁ
ይዞ በመግቢያው በር ላይ ቆሞ ነበር።
4ሰውየውም እንዲህ አለኝ፤ “የሰው ልጅ
ሆይ፤ በዐይንህ እይ፤ በጆሮህ ስማ፤ የማሳ
ይህንም ሁሉ ልብ ብለህ አስተውል፤ ወደዚህ
የመጣኸው ለዚህ ነውና ያየኸውንም ሁሉ
ለእስራኤል ቤት ንገር።”

## ወደ ውጩ አደባባይ የሚያወጣው የምሥራቅ በር

5የቤተ መቅደሱን ዙሪያ ሙሉ በሙሉ
የከበበ ቅጥር አየሁ፤ በሰውየውም እጅ ርዝ
መቱ ስድስት ክንድ የሆነ መለኪያ ዘንግ
አየሁ፤ እያንዳንዱ ክንድ፣ አንድ ክንድ
ከስንዝር ነበር፤ እርሱም ቅጥሩን ለካው፤
ስፋቱ አንድ መለኪያ ዘንግ ሲሆን፣ ቁመ
ቱም እንዲሁ አንድ መለኪያ ዘንግ ነበር።
6ከዚያም በምሥራቅ ትይዩ ወዳለው በር
መጣ፤ ደረጃዎቹን ወጥቶ የበሩን መግቢያ
መድረክ ለካ፤ ቍመቱም አንድ ዘንግ
ነበር።[ሠ] 7የዘብ ጠባቂ ቤቶች፣ ቁመታቸው
አንድ መለኪያ ዘንግ፣ ወርዳቸውም አንድ
መለኪያ ዘንግ ነበር፤ በቤቶቹም መካከል
ያሉት ግንቦች ውፍረት አምስት ክንድ
ነበር። ከቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት ባለው
መተላለፊያ በረንዳ አጠገብ በውስጥ በኩል
ያለው የበሩ መድረክ ወለል አንድ ዘንግ
ነበር።
8ከዚያም የመግቢያውን በር መተላለፊያ
ውን በረንዳ ለካ፤ 9ቍመቱ[ዐ] ስምንት ክንድ፣
የዐምዶቹም ውፍረት ሁለት ክንድ ነበር።
የመግቢያው በር መተላለፊያ በረንዳ፣ ከቤተ
መቅደሱ ትይዩ ነው።
10በምሥራቁ በር ግራና ቀኝ መጠናቸው
እኩል የሆነ ሦስት ሦስት የዘብ ቤቶች ነበሩ
፤ በመካከላቸው ወጣ ወጣ ብለው
የሚታዩትም ግንቦች ተመሳሳይና እኩል
ነበሩ። 11ከዚያም የበሩን ስፋት ለካ፤
ወርዱ ዐሥር ክንድ፣ ርዝመቱም ዐሥራ
ሦስት ክንድ ነበር። 12በእያንዳንዱ ዘብ
ቤት ፊት ለፊት ከፍታው አንድ ክንድ
የሆነ መከለያ የግንብ ዐጥር አለ፤ የዘብ
ቤቶቹም ስፋት እኩል በኩል ስድስት
ክንድ ነበር። 13ከዚያም ከዘብ ቤቱ የኋላ
ግድግዳ ጀምሮ እስከ ሌላው ጫፍ ድረስ
ያለውን የመግቢያ በር ለካ፤ ከአንዱ
መከለያ ግድግዳ እስከ ሌላው መከለያ ግድ
ግዳ ያለው ርቀት ሃያ አምስት ክንድ
ነበር። 14በመግቢያው በር ዙሪያ ባሉት ወጣ
ወጣ ባሉት ግንቦች ሁሉ ፊት ለፊት ያለውን
ቦታ ለካ፤ ሥልሳ ክንድም ነበር። የተለካውም
ከአደባባዩ[ዘ] ፊት ለፊት እስካለው መተላለ
ፊያ በረንዳ[ዠ] ድረስ ነበር። 15ከበሩ መግቢያ
እስከ መተላለፊያ በረንዳው መጨረሻ ድረስ
ያለው ርቀት አምሳ ክንድ ነበር። 16ክፍ
ሎቹ እንደ መተላለፊያ በረንዳዎቹ ከግራና
ከቀኝ በኩል ትንንሽ መስኮቶች አሏቸው።
በዙሪያው ያሉ መስኮቶች በመግቢያው
በር ፊት ለፊት የነበሩ ሲሆን፣ በእያንዳንዱ
ክፍል ግራና ቀኝ ግድግዳ ላይ ደግሞ
የዘንባባ ዛፍ ተቀርጾበታል።

## የውጩ አደባባይ

17ከዚያም ወደ ውጩ አደባባይ አመ
ጣኝ፤ እዚያም በአደባባዩ ዙሪያ የተሠሩ
ክፍሎችና ድንጋይ የተነጠፈበት መመላለሻ
አየሁ፤ በመመላለሻውም ዙሪያ ሠላሳ ክፍ
ሎች ነበሩ። 18የታችኛው ንጣፍ ወለል ከመ
ግቢያው በር ጋር ተያይዞ የተሠራ ሲሆን፣
ስፋቱ እንደ በሮቹ ርዝመት መጠን ነበር።
19ከዚያም ከታችኛው መግቢያ በር ፊት
ጀምሮ እስከ ውስጠኛው አደባባይ ፊት ድረስ
ያለውን ርቀት ለካ፤ በምሥራቅም ሆነ
በሰሜን በኩል ያለው ርቀት አንድ መቶ
ክንድ ነበር።

## የሰሜኑ በር

20ከዚያም በሰሜን ትይዩ ያለውን፣
ወደ ውጩ አደባባይ የሚያመራውን በር
ርዝመትና ወርድ ለካ። 21እንደ መጀመሪ
ያው በር ሁሉ ይኸኛውም በየጐኑ ያሉት
ሦስት ሦስት የዘብ ቤቶች፣ በየመካከሉ
ወጣ ወጣ ያሉ ግንቦችና መተላለፊያ በረ
ንዳዎቹ መጠናቸው እኩል ነበር። ርዝመቱ
አምሳ ክንድ፣ ወርዱም ሃያ አምስት ክንድ
ነበር። 22መስኮቶቹ፣ መተላለፊያ በረንዳዎቹና

40፥1 2ነገ25፥7፤ ኤር39፥1-10፤52፥4-11፤ሕዝ1፥3፤29፥17
40፥2 ዘፀ24፥10፤ ኤር31፥12፤ሕዝ17፥22፤ዳን7፥1፡7፤ ራእ21፥10
40፥3 ሕዝ1፥7፤ 47፥3፤ዘካ2፥1-2፤ራእ 1፥15፤11፥1፤21፥15
40፥4 ዘዳ6፥6፤ኤር 26፥2፤ሕዝ44፥5
40፥5 ሕዝ42፥20
40፥6 ሕዝ8፥16
40፥7 ቍ36
40፥14 ዘፀ27፥9
40፥16 ቍ21-22፤ 2ዜና3፥5፤ሕዝ41፥26
40፥17 ራእ11፥2፤ ሕዝ41፥6፤42፥1
40፥19 ቍ23፡27፤ ሕዝ46፥1
40፥21 ቍ7፡30
40፥22 ቍ16፡26፡49

[ሠ]6 ከሰብዓ ሊቃናት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን *የመጀመሪያው ጕበን ርዝመቱ አንድ ዘንግ ነበር* ይላል
[ዐ]8-9 በብዙ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆች በሰብዓ ሊቃናት፣ በቩልጌትና በሱርስቱም እንዲሁ ሲሆን አብዛኛዎቹ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆች ግን *በቤተ መቅደሱ ትይዩ ያለ የመግቢያ በር ነው፤ አንድ ክንድ ነበር 9. ከዚያም የመግቢያ በሩን መተላለፊያ በረንዳ፣ ለካው፤* ... ይላሉ
[ዘ]14 ሰበዓ ሊቃናቱም እንዲሁ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን *ወጣ ያለ ግንብ* ይለዋል
[ዠ]14 በዕብራይስጥ የዚህ ቃል ትርጒም አይታወቅም

የዘንባባ ዛፍ ቅርጾቹ ልካቸው በምሥራቁ
በር ካሉት ጋር ተመሳሳይ ነበር። ወደዚያ
የሚ ያመሩ ሰባት ደረጃዎች አሉ፤
መተላለፊያ በረንዳዎቹም ከእነርሱ ጋር
ትይዩ ነበር። 23ልክ በምሥራቅ በኩል
እንዳለው ሁሉ፣ ከሰሜኑ በር ጋር ትይዩ የሆነ
ወደ ውስጠኛው አደባባይ የሚያመራ በር
አለ። ከአንዱ በር እስከ ሌላኛው በር
ያለውን ለካው፤ ይህም አንድ መቶ ክንድ
ነበር።

## የደቡቡ በር

24ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ መራኝ፤
እዚያም ፊቱን ወደ ደቡብ ያደረገ በር አየሁ፤
እርሱም የውስጠኛውን ግድግዳና
መተላለፊያ በረንዳውን ለካ፤ የእነዚህም
መጠን እንደ ሌሎቹ በሮች ነበር።
25የመግቢያው በርና መተላለፊያ በረንዳው
እንደ ሌሎቹ ሁሉ በዙሪያው ጠባብ
መስኮቶች ነበሩት፤ ርዝመቱ አምሳ ክንድ፤
ወርዱም ሃያ አምስት ክንድ ነበር።
26ከመተላለፊያ በረንዳው ትይዩ የሆኑ ሰባት
ደረጃዎች ወደ መግቢያው በር ያመ ራሉ፤
ወጣ ወጣ ብለው በሚታዩ ግድግዳ ዎችም
ላይ የዘንባባ ቅርጽ አለ። 27ውስጠኛው
አደባባይ ደግሞ ከደቡብ ጋር ትይዩ የሆነ
በር አለው፤ እርሱም ከዚህ በር አንሥቶ
በደቡብ አቅጣጫ እስካለው እስከ ውጭው
በር ድረስ ለካው፤ ይህም አንድ መቶ ክንድ
ሆነ።

## ወደ ውስጠኛው አደባባይ የሚያስገቡ በሮች

28ከዚያም በደቡብ በር በኩል ወደ ውስጠ
ኛው አደባባይ አመጣኝ፤ የደቡብንም በር
ለካው፤ መጠኑም እንደ ሌሎቹ በሮች
ነበር። 29የዘብ ቤቶቹ፣ በየመካከሉ ወጣ ወጣ
ያሉት ግንቦችና መተላለፊያ በረንዳዎቹ
መጠናቸው ከሌሎቹ ጋር ተመሳሳይ ነበር።
መግቢያው በርና መተላለፊያ በረንዳዎቹ
በዙሪያቸው መስኮቶች ነበሯቸው። ርዝመቱ
አምሳ ክንድ ወርዱም ሃያ አምስት ክንድ
ነበር። 30በውስጠኛው አደባባይ ዙሪያ ያሉት
የመግቢያው በር መተላለፊያ በረንዳዎቹ
ርዝመት ሃያ አምስት ክንድ ሲሆን፣ ወር
ዳቸው ደግሞ አምስት ክንድ ነበር። 31መተላ
ለፊያ በረንዳው ከውጭው አደባባይ ጋር
ትይዩ ነው፤ የዘምባባ ዛፎች በዐምዶቹ ላይ
ተቀርጸዋል፤ እስከ መግቢያው ድረስም ስም
ንት ደረጃዎች ነበሩት።
32ከዚያም በምሥራቅ በኩል ወደ ውስጠ
ኛው አደባባይ አመጣኝ፤ መግቢያ በሩንም
ለካው፤ መጠኑም ከሌሎቹ ጋር ተመሳሳይ
ነበር። 33የዘብ ቤቶቹ፣ ወጣ ወጣ ያሉት
ግንቦችና መተላለፊያ በረንዳዎቹ መጠና
ቸው ከሌሎቹ ጋር ተመሳሳይ ነበር፤ መግ
ቢያው በርና መተላለፊያ በረንዳው ዙሪያ
ውን መስኮቶች ነበሩት፤ የዚህም ርዝመቱ
አምሳ ክንድ፣ ወርዱ ሃያ አምስት ክንድ
ነበር። 34መተላለፊያ በረንዳው ከውጩ አደ
ባባይ ትይዩ ነው፤ በዐምዶቹ ላይ የዘንባባ
ዛፍ ተቀርጾአል፤ እስከ መግቢያ ድረስም
ስምንት ደረጃዎች ነበሩት።
35ከዚያም ወደ ሰሜን በር አመጣኝ፤ ለካ
ውም፤ መጠኑም ከሌሎቹ ጋር ተመሳሳይ
ነበር። 36የዘብ ቤቶቹ፣ ወጣ ወጣ ያሉት
ግንቦቹና መተላለፊያ በረንዳው መጠናቸው
ከሌሎቹ ጋር ተመሳሳይ ነበር፤ በዙሪያውም
መስኮቶች ነበሩት። የዚህም ርዝመቱ አምሳ
ክንድ ወርዱም ሃያ አምስት ክንድ ነበር።
37መተላለፊያ በረንዳው[የ] ከውጩ አደባባይ
ትይዩ ነው፤ በዐምዶቹም ላይ የዘንባባ ዛፍ
ተቀርጾአል፤ እስከ መግቢያው ድረስም ስም
ንት ደረጃዎች ነበሩት።

## መሥዋዕት የሚዘጋጅባቸው ክፍሎች

38በእያንዳንዱ የውስጥ መግቢያ በር
መተላለፊያ በረንዳ አጠገብ የሚቃጠል
መሥዋዕት የሚታጠብበት በር ያለው ክፍል
አለ። 39በመግቢያው በር ላይ ባለው መተ
ላለፊያ በረንዳው ሥር በግራና በቀኝ
የሚቃጠል መሥዋዕት፣ የኀጢአትና የበደል
መሥዋዕት የሚታረዱበት ሁለት ሁለት ጠረ
ጴዛዎች አሉ። 40ከመግቢያው በር ላይ ባለው
መተላለፊያ በረንዳ በስተ ውጭው ግንብ
ወደ ሰሜን በር መግቢያ ላይ ባሉት
ደረጃዎች አጠገብ ከግራና ከቀኝ ሁለት
ሁለት ጠረጴዛዎች ይገኛሉ። 41ስለዚህ በአንዱ
በር በኩል አራት፣ በሌላውም በኩል አራት
ጠረጴዛዎች፤ መሥዋዕቱ የሚታረድባቸው
በድምሩ ስምንት ጠረጴዛዎች አሉ ማለት
ነው። 42ለሚቃጠለው መሥዋዕት መገልገያ
የሆኑ፣ ከተጠረበ ድንጋይ የተሠሩ አራት
ጠረጴዛዎች ነበሩ፤ የእያንዳንዳቸው ርዝመት፣
ወርድና ቁመት አንድ ክንድ ተኩል ነበር፤
በእነዚህም ላይ ለሚቃጠለው መሥዋዕትና
ለሌላውም መሥዋዕት ማረጃ የሚሆኑ መሣ
ሪያዎች ይቀመጡባቸው ነበር። 43እንዲሁም
አንዳንድ ስንዝር የሚሆኑ ሁለት ጣት
ያላቸው ሜንጦዎች በግንቡ ዙሪያ ተንጠል
ጥለው ነበር፤ ጠረጴዛዎቹም የመሥዋዕቱ
ሥጋ ማስቀመጫ ነበሩ።

## ለካህናት የተመደቡ ክፍሎች

44በውስጠኛው አደባባይ፣ ከውስጠኛው
በር ውጭ፣ ሁለት ክፍሎች ነበሩ፤ አንዱ[ዶ]
በደ

40፥23 ቍ 19
40፥24 ቍ 32፡35
40፥25 ቍ 33
40፥26 ቍ 22
40፥27 ቍ 19፡32
40፥28 ቍ 35
40፥29 ቍ 7፡25
40፥30 ቍ 21
40፥31 ቍ 22፡34፡37
40፥32 ቍ 24
40፥33 ቍ 7
40፥34 ቍ 22
40፥35 ቍ 24፤ ሕዝ 44፥4፤47፥2
40፥36 ቍ 7
40፥37 ቍ 22፡34
40፥38 2ዜና4፥6፤ ሕዝ42፥13
40፥39 ቍ 42፤ ዘሌ 4፥3፡28፤7፥1፤ ሕዝ 46፥2
40፥42 ቍ 39፤ ዘፀ20፥25

[የ]37 ሰብዓ ሊቃናቱም (በተጨማሪ ቍ31 እና 34 ይመ) እንዲሁ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን *መቃኖች* ይላል

[ዶ]44 ሰብዓ ሊቃናቱም እንዲሁ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን *የመዘመራን ክፍሎች ነበሩ፤* ይላል

ቡብ[ጀ] ትይዩ በሰሜን በር በኩል ሲሆን፣
ሌላው በሰሜን ትይዩ በደቡብ በር በኩል
ነበር፡፡ 45እርሱም እንዲህ አለኝ፤ “በደቡብ
ትይዩ ያለው ክፍል በቤተ መቅደስ ውስጥ
ለሚያገለግሉ ካህናት ሲሆን፣ 46በሰሜን
ትይዩ ያለው ክፍል ደግሞ በመሠዊያው
ላይ ለሚያገለግሉ ካህናት ነው፡፡ እነዚህም
የሳዶቅ ልጆች ሲሆኑ፣ *በእግዚአብሔር ፊት*
ቀርበው ማገልገል የሚችሉ ሌዋውያን እነርሱ
ብቻ ናቸው፡፡”
47ከዚያም አደባባዩን ለካው፤ ርዝመቱ አንድ
መቶ ክንድ፣ ወርዱ መቶ ክንድ እኩል
በእኩል ባለ አራት ማእዘን ነበር፡፡ መሠዊ
ያውም በቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት ነበር፡፡

**ቤተ መቅደሱ**

48ወደ ቤተ መቅደሱም መተላለፊያ በረ
ንዳ አመጣኝ፤ የመተላለፊያ በረንዳዎቹን
ዐምዶች ለካ፤ በአንዱ በኩል አምስት ክንድ
በሌላውም እንዲሁ አምስት ክንድ
ነበር፡፡
የመግቢያው በር ርዝመት ዐሥራ አራት
ክንድ ሲሆን፣ ወጣ ወጣ ያሉት ግንቦች
ስፋት በአንዱ በኩል ሦስት ክንድ፣ በሌ
ላውም እንዲሁ ሦስት ክንድ ነበሩ፡፡[ገ] 49የመ
ተላለፊያው በረንዳ ርዝመት ሃያ ክንድ፣
ከፊት እስከ ኋላ ያለውም ወርድ ዐሥራ
ሁለት[ጠ] ክንድ ነበር፡፡ ወደ ቤተ መቅደሱም
የሚያደርሱ ዐሥር ደረጃዎች የነበሩ ሲሆን፣
በየዐምዱም ጐንና ጐን ምሰሶዎች ነበሩ፡፡

41 ከዚያም ወደ መቅደሱ አገባኝ፤ ዐም
ዶቹንም ለካ፤ የዐምዶቹም ወርድ[ጨ]
በአንዱ በኩል ስድስት ክንድ፣ በሌላውም
በኩል ስድስት ክንድ ነበር፡፡ 2የመግቢ
ያውም በር ወርድ ዐሥር ክንድ ሲሆን፣
በግራና በቀኝ በኩል ወጣ ወጣ ያሉት
ግንቦች ወርድ አምስት ክንድ ነበር፡፡
ደግሞም የውስጡን መቅደስ ለካ፤ ርዝመቱ
አርባ ክንድ፣ ወርዱም ሃያ ክንድ ነበር፡፡
3ከዚያም ወደ ውስጥ ገባ፤ የመግቢ
ያውን
ዐምዶች ለካ፤ የእያንዳንዱም ወርድ ሁለት
ክንድ ነበር፡፡ የመግቢያውም ወርድ ስድስት
ክንድ ሲሆን፣ ግራና ቀኝ ወጣ ወጣ ያሉት
ግንቦች ወርድ ደግሞ ሰባት ክንድ ነበር፡፡
4እርሱም የውስጠኛውን መቅደስ ርዝመት
ለካ፤ ሃያ ክንድ ነበር፤ ወርዱም የውጪውን
ግድግዳ ጨምሮ ሃያ ክንድ ነበር፤ እርሱም፣
“ይህ ቅድስተ ቅዱሳን ነው” አለኝ፡፡
5ከዚያም የቤተ መቅደሱን ግንብ ለካ፤
ውፍረቱ ስድስት ክንድ ነው፤ በቤተ መቅ
ደሱ ግንብ ዙሪያ ግራና ቀኝ ያለው የእያ
ንዳንዱ ክፍል ወርድ አራት ክንድ ነበር፡፡
6ግራና ቀኝ ያሉት ክፍሎች፣ ባለሦስት
ደርብ ናቸው፤ በእያንዳንዱም ደርብ ላይ
ሠላሳ ክፍሎች ነበሩ፤ በግንቡም ዙሪያ ግራና
ቀኝ ያሉትን እነዚህን ክፍሎች ደግፈው
የሚይዙ ተሸካሚዎች ነበሩ፤ ሆኖም ተሸካሚ
ዎቹ ወደ ቤተ መቅደሱ ግንብ ዘልቀው
አልገቡም ነበር፡፡ 7በቤተ መቅደሱ ዙሪያ
ያሉት ክፍሎች ስፋት በየደርቡ እየጨ
መረ የሚሄድ ነው፡፡ በቤተ መቅደሱ ዙሪያ
ያለው ሕንጻ አሠራሩ ከታች ወደ ላይ እየሰፋ
የሚሄድ በመሆኑ፣ ወደ ላይ በተሄደ ቍጥር
የክፍሎቹ ስፋት እየጨመረ የሚሄድ ነው፡፡
በመካከለኛው ደርብ በኩል አድርጎ ከታች
ወደ ላይ የተዘረጋም ደረጃ አለ፡፡
8ቤተ መቅደሱ ዙሪያውን ከፍ ብሎ የተ
ሠራ መሠረት ያለው መሆኑን አየሁ፤ ይህ
ግራና ቀኝ ላሉት ክፍሎች መሠረት ሲሆን፣
ርዝመቱ ስድስት ክንድ ነው፤ ይህም የዘንጉ
ቁመት ነበር፡፡ 9በውጭ በኩል ያለው የግራና
የቀኙ ክፍሎች ግንብ ውፍረት አምስት
ክንድ ነበር፤ ክፍቱ ቦታ በቤተ መቅደሱና
10በካህናቱ ክፍሎች መካከል ያለ ሲሆን፣
ስፋቱ በቤተ መቅደሱ ዙሪያ ሃያ ክንድ
ነበር፡፡ 11ከክፍቱ ቦታ ግራና ቀኝ ወዳሉ ክፍ
ሎች የሚያስገቡ በሮች ነበሩ፡፡ አንዱ በሰሜን
በኩል ሲሆን፣ ሌላው በር ደግሞ በደቡብ
በኩል ነው፡፡ ክፍቱን ቦታ ዙሪያውን የሚያ
ገናኘው መሠረት ስፋቱ አምስት ክንድ ነው፡፡
12በምዕራብ በኩል ከቤተ መቅደሱ ግቢ
ትይዩ የሆነው ሕንጻ ወርድ ሰባ ክንድ ነበር፡፡
የሕንጻው ግንብ ውፍረት ዙሪያውን አምስት
ክንድ ሲሆን፣ ርዝመቱ ዘጠና ክንድ ነበር፡፡
13ከዚያም ቤተ መቅደሱን ለካ፤ ርዝመቱ
አንድ መቶ ክንድ ሲሆን፣ የቤተ መቅደሱ
ግቢና ሕንጻ ከነግንቡ ደግሞ አንድ መቶ
ክንድ ሆነ፡፡ 14በምሥራቅ በኩል የቤተ መቅ
ደሱ ግቢ ስፋት፣ ከቤተ መቅደሱ ፊት
ለፊት ያለውን ስፍራ ጨምሮ አንድ መቶ
ክንድ ነበር፡፡
15ከዚያም ከቤተ መቅደሱ በስተ ጀርባ
ከግቢው ትይዩ ያለውን ሕንጻ ለካ፤ ይህም
በግራና በቀኝ ያሉትን መተላለፊያዎች የሚ
ጨምር ሲሆን፣ ርዝመቱ አንድ መቶ ክንድ
ነበር፡፡
የውጩ መቅደስና የውስጡ መቅደስ
ከአደባባዩ ትይዩ ያለው መተላለፊያ በረ
ንዳ፣ 16እንዲሁም መድረኮቹና ጠበብ
ያሉት

40፥45 1ዜና9፥23
40፥46 ዘኍ16፥5፤ 18፥5፤2ሳሙ8፥17፤ ዕዝ7፥2፤ሕዝ42፥13፤ 43፥19፤44፥15፤45፥ 4፤48፥11
40፥47 ሕዝ41፥13 -14
40፥48 1ነገ6፥2
40፥49 ቍ22፤1ነገ 6፥3፤7፥15
41፥1 ቍ23
41፥2 2ዜና3፥3
41፥4 ዘፀ26፥33፤ 1ነገ6፥20፤ዕብ9፥3-8
41፥6 1ነገ6፥5፤ ሕዝ40፥17
41፥7 1ነገ6፥8
41፥14 ሕዝ40፥47
41፥15 ሕዝ42፥3
41፥16 ቍ25-26፤ 1ነገ6፥4፡15፤ሕዝ 42፥3

[ጀ]44 ሰብዓ ሊቃናቱም እንዲሁ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን *በምሥራቅ* ይላሉ
[ገ]48 ሰብዓ ሊቃናቱም እንዲሁ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን *ወጣ ወጣ ያሉት ግንቦች መግቢያ ... ነበሩ* ይላል
[ጠ]49 ሰብዓ ሊቃናቱም እንዲሁ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን *ዐሥራ አንድ* ይላል
[ጨ]1 አንድ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጅና ሰብዐ ሊቃናት እንዲሁ ሲሆኑ አብዛኛዎቹ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆች ግን ... *የድንኳኑ ወርድ* ይላሉ

መስኮቶች፣ በሦስቱም ዙሪያ ያሉት መተላ
ለፊያዎች፣ ከመድረኩ በላይና ራሱ መድረ
ኩም ጭምር ሁሉም በዕንጨት ተለብዶ
ነበር። ወለሉ፣ እስከ መስኮቶቹ ያለው ግን
ብና መስኮቶቹ ተለብደዋል። [17]ከውስጡ
መቅደስ መግቢያ በላይ ያለው ውስጡና
ውጪ እንዲሁም በውስጡ መቅደስና በውጪ
መቅደስ መካከል ያለው ሁሉ ዙሪያውን
[18]ኪሩቤልና የዘንባባ ዛፍ ተቀርጾውበት
ነበር፤ የዘንባባ ዛፎቹ የተቀረጹት በኪሩ
ብና በኪሩብ መካከል ነበር። እያንዳንዱም
ኪሩብ ሁለት ፊት ነበረው፤ [19]የሰው ፊት
ያለው ኪሩብ በአንድ በኩል ወዳለው ዘን
ባባ የዞረ ሲሆን፣ የአንበሳ ፊት ያለውም
በሌላ በኩል ወዳለው ዘንባባ ዞሮ ነበር።
ሁሉም በቤተ መቅደሱ ዙሪያ ላይ ተቀር
ጾው ነበር። [20]ከወለሉ አንሥቶ ከመግቢያው
በላይ እስካለው ስፍራ ድረስ፣ የውስጡ
መቅደስ የውጭ ግድግዳ ላይ ኪሩቤልና
የዘንባባ ዛፍ ተቀርጾአል።

[21]የውስጡ መቅደስ በር መቃን ባለ አራት
ማእዘን ነበር፤ ከቅድስተ ቅዱሳኑም ፊት
ለፊት ያለው በር እንዲሁ ባለ አራት
ማእዘን ነበር። [22]ሦስት ክንድ ቁመት፣
ሁለት ክንድ[ጸ] ወርድ፣ ሁለት ክንድ
ርዝመት ያለው የዕንጨት መሠዊያ ነበር፤
ማእዘኖቹ፣ መሠረቱና[ጸ] ጐኖቹ ሁሉ ከዕን
ጨት የተሠሩ ነበሩ። ሰውዬውም፣ "ይህች
*በእግዚአብሔር* ፊት ያለች ገበታ ናት" አለኝ።
[23]የውስጡ መቅደስና ቅድስተ ቅዱሳኑ እያ
ንዳንዳቸው ሁለት ሁለት በር አላቸው፤
[24]እያንዳንዱ በር መካከሉ ላይ በመታጠ
ፊያ የተያያዙ መዝጊያዎች አሉት። [25]በግ
ንቦቹ ላይ እንዳለው ሁሉ በውስጡ መቅደስ
በሮችም ላይ ኪሩቤልና የዘንባባ ዛፎች
ተቀርጸዋል፤ በመተላለፊያ በረንዳውም ፊት
ለፊት የዕንጨት መዝጊያ ተንጠልጥሎአል።
[26]በመተላለፊያ በረንዳውም ግራና ቀኝ ግንብ
ላይ የዘንባባ ዛፍ ቅርጽ ያለባቸው ጠባብ
መስኮቶች ነበሩ። ግራና ቀኝ ያሉት ክፍ
ሎችም በደረጃው በኩል የሚሸፍን ጣሪያ
ነበራቸው።

## ለካህናት የተመደቡ ክፍሎች

42 ከዚያም ያ ሰው በሰሜን በኩል
ወዳለው ወደ ውጪ አደባባይ በማ
ምጣት፣ በቤተ መቅደሱ አደባባይ ትይዩና
በሰሜን በኩል ባለው ግንብ ትይዩ ወደ
አሉት ክፍሎች አመጣኝ። [2]በሩ በሰሜን
ትይዩ የሆነው ሕንጻ ርዝመቱ አንድ መቶ
ክንድ ወርዱም አምሳ ክንድ ነበር። [3]ከው
ስጠኛው አደባባይ ሃያ ክንድ ርቀት ላይና
በአንጻሩም ከውጪ አደባባይ የንጣፍ ድን
ጋይ ፊት ለፊት ርቀት ላይ በሦስት ደር
ቦች ትይዩ የሆኑ ሰገነቶች ነበሩ። [4]ከክፍሎቹ
ፊት ለፊት ወርዱ ዐሥር ክንድ፣ ርዝመቱ
አንድ መቶ ክንድ[ፀ] የሆነ መተላለፊያ በው
ስጥ በኩል ነበር። የክፍሎቹም በሮች
በሰሜን በኩል ነበሩ። [5]የላይኞቹ ክፍሎች
ጠበብ ያሉ ናቸው፤ ምክንያቱም ሰገነቶቹ
ታችና መካከል ላይ ካሉት ከሕንጻው ክፍ
ሎች ይልቅ ሰፋ ያሉ ቦታዎች ይዘውባ
ቸዋልና። [6]አደባባዮቹ ዐምዶች ሲኖሯቸው፣
በሦስተኛው ደርብ ላይ ያሉት ክፍሎች ግን
ዐምድ የላቸውም። ስለዚህ የወለላቸው
ስፋት በታችኛውና በመካከለኛው ደርብ
ካሉት ክፍሎች ይልቅ ጠበብ ያለ ነው።
[7]ከክፍሎቹና፣ ከውጪ አደባባይ ትይዩ
የሆነ የውጪ ግንብ አለ፤ ይህም በክፍሎቹ
ፊት ለፊት ሆኖ አምሳ ክንድ ይረዝማል።
[8]ከውጪ አደባባይ ቀጥሎ ያሉት መደዳ
ክፍሎች ርዝመት አምሳ ክንድ ሲሆን፣ ከቤተ
መቅደሱ አጠገብ ያሉት መደዳ
ክፍሎች ርዝመት ደግሞ አንድ መቶ
ክንድ ነበር። [9]ከውጪ አደባባይ ወደ ውስጥ
ሲገባ፣ በስተ ምሥራቅ የታችኞቹ
ክፍሎች መግቢያ ይገኛል።

[10]በደቡብ በኩል[ፈ] የውጪን
አደባባይ ግንብ ተከትሎ፣ ከቤተ
መቅደሱ አደባባይ ጋር የተያያዙና ከውጪ
ግንብ ጋር ትይዩ የሆኑ ክፍሎች አሉ፤
[11]ከፊት ለፊታቸውም መተላለፊያ መንገድ
አለ። እነዚህ በሰሜን በኩል ካሉት ክፍሎች
ጋር ተመሳሳይ ሲሆኑ፣ ርዝመትና
ወርዳቸው፣ መውጫና መጠና ቸው
አንድ ዐይነት ነበር፤ በሰሜን በኩል
እንዳሉት በሮች፣ [12]በደቡብ በኩል ያሉት
ክፍሎች በሮች መጠናቸው ተመሳሳይ ነበር።
ከመመላለሻው መነሻ ላይ መግቢያ በር አለ፤
መመለሻውም ፊት ለፊት ካለው ወደ ምሥ
ራቅ ከሚያመራው ግንብ ጋር ተጓዳኝ ነው።

[13]ከዚያም እንዲህ አለኝ፤ "ከቤተ መቅደሱ
አደባባይ ፊት ለፊት ያሉት የሰሜኑና የደ
ቡቡ ክፍሎች የካህናቱ ሲሆኑ፣ እነዚህም
*በእግዚአብሔር* ፊት የሚቀርቡት ካህናት
እጅግ የተቀደሱትን ቍርባኖች የሚበሉባ
ቸው ናቸው። በዚያም እጅግ የተቀደሱትን
ቍርባኖች ማለት የእህሉን ቍርባን፣ የኀጢ
አቱን ቍርባን፣ የበደሉን ቍርባን ያስቀም
ጣሉ፤ ቦታው ቅዱስ ነውና። [14]ካህናቱ
አንድ ጊዜ ወደ ተቀደሰው ቦታ ከገቡ በኋላ፣

41፥18 ዘፀ37፥7፤ 1ነገ6፥18፡29፤7፥36፤ 2ዜና3፥7፤ሕዝ10፥21
41፥19 ሕዝ10፥14
41፥21 ቍ1
41፥22 ዘፀ25፥23፤ 30፥1፤ሕዝ23፥41
41፥23 ቍ1፤1ነገ 6፥32
41፥24 1ነገ6፥34
41፥26 ቍ15-16፤ ሕዝ40፥16
42፥1 ቍ13፤ዘፀ 27፥9፤ሕዝ40፥17፤ 41፥12-14
42፥3 ሕዝ41፥15፡16
42፥4 ሕዝ46፥19
42፥9 ሕዝ44፥5፤ 46፥19
42፥10 ቍ1፤ሕዝ 41፥12-14
42፥13 ቍ1፤ዘፀ 29፥31፤ዘሌ6፥29፤7፥ 6፤10፥12-13፡17፤ 14፥13፤ዘኍ18፥9 -10 ፤ኤር41፥5፤ሕ ዝ40፥ 46፤41፥12 -14
42፥14 ዘፀ29፥9፤ ዘሌ8፥7-9፤16፥23፤ ሕዝ44፥19

[ጸ]22 ሰብዓ ሊቃናቱ እንዲሁ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን ***ርዝመቱ ሁለት ወርድ*** ይላል
[ጸ]22 ሰብዓ ሊቃናቱ እንዲሁ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን ***ርዝመቱ*** ይላል
[ፀ]4 ሰብዓ ሊቃናቱና ሱርስቱ እንዲሁ ሲሆኑ ዕብራይስጡ ግን ... ***አንድ ክንድ*** ይላል
[ፈ]10 ሰብዓ ሊቃናቱም እንዲሁ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን ***በስተ ምሥራቅ*** ይላል

ያገለገሉበትን ልብስ ሳያወልቁ ወደ ውጪ
አደባባይ መውጣት አይችሉም፤ የተቀደሰ
ነውና፤ ወደ ሕዝቡ ቦታ ከመምጣታቸው
በፊት ሌላውን ልብሳቸውን መልበስ አለባ
ቸው::”
15በቤተ መቅደሱ ውስጥ ያለውን ስፍራ
ለክቶ ከጨረሰ በኋላ፣ በምሥራቅ በር
በኩል ወደ ውጪ አወጣኝ፤ በዙሪያው
ያለውንም ስፍራ ሁሉ ለካ፤ 16በምሥራቅ
ያለውንም በመለኪያው ዘንግ ለካ፤ አምስት
መቶ ክንድ[ፐ] ሆነ:: 17ሰሜኑንም ለካ፤ በመ
ለኪያው ዘንግ አምስት መቶ ክንድ[ሀ] ሆነ::
18ደቡቡንም ለካ፤ በመለኪያው ዘንግ አምስት
መቶ ክንድ ሆነ:: 19ከዚያም ወደ ምዕራብ
ጐን ዞሮ ለካ፤ በመለኪያው ዘንግ አምስት
መቶ ክንድ ሆነ:: 20ስለዚህ በአራቱም ማእ
ዘን ለካው፤ የተቀደሰውን ስፍራ ከሌላው
የሚለይ በዙሪያው ግንብ ነበረ፤ የግንቡም
ርዝመት አምስት መቶ ክንድ ሲሆን፣ ወርዱ
አምስት መቶ ክንድ ነበር::

### የእግዚአብሔር ክብር ወደ ቤተ መቅደሱ መመለስ

43 ከዚያም ያ ሰው ለምሥራቅ ትይዩ
ወደ ሆነው በር አመጣኝ፤ 2እኔም
የእስራኤል አምላክ ክብር ከምሥራቅ ሲመጣ
አየሁ፤ ድምፁ እንደ ባሕር ሞገድ ድምፅ
ነበር፤ ምድሪቱም ከክብሩ የተነሣ ታበራ
ነበር:: 3ያየሁትም ራእይ ከተማዪቱን ለማ
ጥፋት በመጣ ጊዜ ያየሁትን ራእይ የሚመ
ስልና እንዲሁም በኮቦር ወንዝ ካየሁት ራእይ
ጋር የሚመሳሰል ነበር፤ እኔም በግንባሬ
ተደፋሁ:: 4*የእግዚአብሔር* ክብር ለምሥራቅ
ትይዩ በሆነው በር ወደ ቤተ መቅደሱ ገባ::
5ከዚያም መንፈስ አነሣኝ፤ ወደ ውስጠኛው
አደባባይ አመጣኝ፤ *የእግዚአብሔርም* ክብር
ቤተ መቅደሱን ሞላው::
6ያ ሰው በአጠገቤ ቆሞ ሳለ፣ ከቤተ መቅ
ደሱ ውስጥ ሲናገረኝ ሰማሁ፤ 7እርሱም እን
ዲህ አለኝ፤ “የሰው ልጅ ሆይ፤ ይህ የዙፋኔ
መቀመጫ የእግሬም ጫማ ማሳረፊያ ነው፤
በእስራኤላውያን መካከል ለዘላለም የምኖር
በትም ስፍራ ነው:: የእስራኤል ቤትም
ሆኑ ነገሥታታቸው በአመንዝራነታቸውና[ለ]
በማምለኪያ ኰረብታቸው ላይ በሚያመልኳ
ቸው፣ ሕይወት በሌላቸው በነገሥታታቸው
ጣዖታት[ሐ] ከእንግዲህ ቅዱስ ስሜን አያረክ
ሱም:: 8በእኔና በጣዖታቱ መካከል ግንብ
ብቻ ሲቀር፣ መድረኮቻቸውን ከመድረኬ
አጠገብ፣ መቃኖቻቸውን ከመቃኖቼ አጠ
ገብ በማድረግ፣ በአስጸያፊ ድርጊታቸው
ቅዱስ ስሜን አረከሱ፤ ስለዚህ በቍጣዬ
አጠፋኋቸው:: 9ከእንግዲህ አመንዝራነታቸ
ውንና ሕይወት የሌላቸውን የንጉሦቻቸውን
ጣዖታት ከእኔ ዘንድ ያርቁ፤ እኔም በመካ
ከላቸው ለዘላለም እኖራለሁ::
10“የሰው ልጅ ሆይ፤ ስለ ኀጢአታቸው
ያፍሩ ዘንድ፣ ለእስራኤል ሕዝብ ቤተ መቅ
ደሱን አሳያቸው፤ ንድፉንም ያስተውሉ፤
11ስላደረጉት ነገር ሁሉ ኀፍረት የሚሰ
ማቸው ከሆነ፣ የቤተ መቅደሱን ንድፍ
እንዲያውቁት አድርግ፤ ይኸውም አሠራሩን፣
መውጫና መግቢያውን፣ አጠቃላይ ንድፉን፣
ሥርዐቱንና ሕጉን ሁሉ[መ] ነው:: ንድፉንና
ሥርዐቱን እንዲጠብቁና እንዲከተሉ እነዚ
ህን ሁሉ እነርሱ ባሉበት ጻፋቸው::
12“የቤተ መቅደሱ ሕግ ይህ ነው፤ በተ
ራራው ጫፍ አካባቢ ያለው ስፍራ ሁሉ
እጅግ የተቀደሰ ይሆናል:: የቤተ
መቅደሱም ሕግ ይኸው ነው::

### የቤተ መቅደሱ መሠዊያ

13“የመሠዊያው ልክ በረጅም ክንድ
ይህ ነው፤ ይኸውም ክንድ ከስንዝር ማለት
ነው፤ ቦዩ አንድ ክንድ ጥልቀት፣ አንድ ክንድ
ወርድ ያለው ሲሆን፣ ዙሪያው አንድ
ስንዝር ጠርዝ አለው፤ የመሠዊያውም
ከፍታ ይህ ነው፤ 14ከቦዩ መሠረት
አንሥቶ እስከ ታችኛው
ዕርከን ድረስ ሁለት ክንድ ቁመት፣ ሁለት
ክንድ ወርድ ያለው ሲሆን፣ ከትንሹ ዕርከን
አንሥቶ እስከ ትልቁ ዕርከን ድረስ ደግሞ
አራት ክንድ ቁመት፣ አንድ ክንድ ወርድ
አለው:: 15የመሠዊያው ምድጃ ከፍታው
አራት ክንድ ሲሆን፣ ከምድጃው ወጣ ወጣ
ያሉ አራት ቀንዶች አሉ:: 16የመሠዊያው
ምድጃ እኩል በእኩል ሲሆን፣ ርዝመቱ ዐሥ
ራ ሁለት ክንድ፣ ወርዱም ዐሥራ ሁለት
ክንድ ነው:: 17ላይኛው ዕርከንም እንዲሁ
እኩል በእኩል ሆኖ ዐሥራ አራት ክንድ
ርዝመትና
ዐሥራ አራት ክንድ ወርድ አለው፤ ግማሽ
ክንድ ጠርዝና ዙሪያውን በሙሉ አንድ
ክንድ የሆነ ቦይ ነበረው:: የመሠዊያው
ደረጃዎችም በምሥራቅ ትይዩ ናቸው::”
18ከዚያም እንዲህ አለኝ፤ “የሰው ልጅ
ሆይ፤ ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
መሠዊያው ተሠርቶ፣ የሚቃጠል መሥ
ዋዕት በሚሠዋበትና በመሠዊያው ላይ ደም
በሚረጭበት ጊዜ ሥርዐቶቹ እነዚህ ናቸው፤
“19በፊቴ ቀርበው ለሚያገለግሉኝ ካህናት፣

[ፐ]16 ከሰብዓ ሊቃናት ቍ17ን ይመ፤ ዕብራይስጡ ግን *ዘንጎች* ይለዋል፤ እንዲሁም ቍ18 እና 19
[ሀ]17 ሰብዓ ሊቃናቱም እንዲሁ ሲሆን፣ ዕብራይስጡ ግን *ዘንጎች* ይላል
[ለ]7 ወይም *መንፈሳዊ ግልሙትናቸውን*፤ እንዲሁም ቍ9
[ሐ]7 ወይም *ሬሳ*፤ እንዲሁም ቍ 9
[መ]11 አንዳንድ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆችና ሰብዐ ሊቃናት እንዲሁ ሲሆኑ አብዛኛዎቹ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆች ግን *ሥርዓቶቹንና የራሱን ንድፎች ሁሉ* ይላሉ

42፥15 ሕዝ43፥1
42፥20 ሕዝ22፥26፤40፥5፤43፥12፤45፥2፤ዘካ2፥5፤ራእ21፥16
43፥1 1ዜና9፥18፤ሕዝ8፥16፤42፥15፤44፥1
43፥2 መዝ18፥4፤ኢሳ6፥3፤ራእ1፥15፤18፥1፤21፥11
43፥4 ሕዝ1፥28፤ሕዝ10፥19፤44፥2
43፥5 ዘፀ16፥7፤ኢሳ6፥4፤ሕዝ3፥12፤11፥24
43፥7 ዘሌ26፥30፤ኤር3፥17፤ሕዝ20፥29፡39፤37፥23
43፥9 ሕዝ37፥26-28
43፥10 ሕዝ16፥61
43፥11 ሕዝ44፥5
43፥12 ሕዝ17፥22፤42፥20
43፥13 ዘፀ20፥24፤2ዜና4፥1
43፥15 ዘፀ27፥2፤ኢሳ29፥2
43፥16 ራእ21፥16
43፥17 ቍ20፤ዘፀ20፥26፤27፥1፤ሕዝ 45፥19
43፥18 ዘፀ40፥29፤ዘሌ1፥5፡11፤ዕብ 9፥21-22
43፥19 ዘሌ4፥3፤ዘኍ16፥40፤2ሳሙ8፥17፤ዕዝ7፥2፤ሕዝ40፥46

ለሌዋውያኑ ለሳዶቅ ቤተ ሰብ የኀጢአት
መሥዋዕት የሚሆን አንድ ወይፈን ስጥ፤
ይላል ጌታ እግዚአብሔር። 20ከደሙም ጥቂት
ወስደህ፣ በመሠዊያው አራት ቀንዶች፣ በላ
ይኛው ዕርከን አራት ጐኖች ላይ እንዲ
ሁም በጠርዙ ዙሪያ ሁሉ ታደርጋለህ፤ በዚህ
ሁኔታ መሠዊያውን ታነጻለህ፤ ታስተሰር
ይለታለህም። 21ወይፈኑን ስለ ኀጢአት መሥ
ዋዕት ወስደህ፣ በቤተ መቅደሱ አካባቢ
ከመቅደሱ ውጪ ለዚሁ ተብሎ በተመደ
በው ስፍራ ታቃጥለዋለህ።
22"በሁለተኛው ቀን እንከን የሌለበት
ተባት ፍየል ወስደህ ለኀጢአት መሥዋዕት
ታቀርባለህ፤ መሠዊያው በወይፈኑ እንደ ነጻ
ሁሉ፣ በዚህም መንጻት አለበት። 23ማንጻቱን
ከፈጸምህ በኋላ፣ ከመንጋው እንከን የሌለባ
ቸውን አንድ ወይፈንና አንድ አውራ በግ
ታቀርባለህ። 24*በእግዚአብሔር ፊት* ታቀርባ
ቸዋለህ፤ ካህናቱ ጨው ይነሰንሱባቸዋል፤
*ለእግዚአብሔርም* የሚቃጠል መሥዋዕት
አድርገው ያቀርቧቸዋል።
25"በየዕለቱ ለሰባት ቀን ተባት ፍየል
ለኀጢአት መሥዋዕት ታቀርባለህ፤
26ሰባት ቀን ለመሠዊያው
ያስተሰርዩለታል፤ ያነጹ ታልም፤ እንዲህም
አድርገው ይቀድሱታል። 27እነዚህ ቀኖች
ካለፉ በኋላም፣ ከስምንተኛው ቀን ጀምሮ
ካህናቱ የሚቃጠለውን መሥ ዋዕ
ታችሁንና የኅብረት መሥዋዕታችሁንሠ
በመሠዊያው ላይ ያቀርባሉ። ከዚያም እኔ
እቀበላችኋለሁ፤ ይላል ጌታ *እግዚአብሔር።*"

## ገዢው፣ ሌዋውያኑ፣ ካህናቱ

44 ከዚያም ያ ሰው ለምሥራቅ ትይዩ
ወደ ሆነው በስተ ውጪ ወዳለው
ወደ መቅደሱ በር መልሶ አመጣኝ፤ ተዘግ
ቶም ነበር። 2*እግዚአብሔር* እንዲህ አለኝ፤
"ይህ በር እንደ ተዘጋ ይኖራል፤ መከፈት
የለበትም፤ ማንም አይገባበትም፤ የእስራኤል
አምላክ *እግዚአብሔር* ገብቶበታልና፤
ተዘግቶ ይኖራል። 3*በእግዚአብሔር* ፊት
ይበላ ዘንድ በመግቢያው በር ገብቶ ውስጥ
ሊቀመጥ የሚችለው ገዡ ራሱ ብቻ ነው፤
በመግቢያው መተላለፊያ በረንዳ እንደ ገባ
መውጣ ትም የሚችለው በዚያው ነው።"
4ከዚያም ያ ሰው በሰሜኑ በር በኩል
ወደ ቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት አመጣኝ፤
እኔም ተመለከትሁ፤ *የእግዚአብሔርም*
ክብር *የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስ ሞል
ቶት አየሁ፤ በግንባሬም ተደፋሁ።
5*እግዚአብሔር* እንዲህ አለኝ፤ "የሰው
ልጅ ሆይ፤ ስለ *እግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ
ሥርዐት የምነግርህን ሁሉ በጥንቃቄ አስተ
ውል፤ በሚገባ አድምጥ፤ ልብም በለው።

43፥20 ቍ17፤ ዘሌ4፥7፤16፥19
43፥21 ዘፀ29፥14፤ ዕብ13፥11
43፥23 ዘፀ29፥1፤ ዘሌ22፥20
43፥24 ዘሌ2፥13፤ ማር9፥49-50
43፥25 ዘፀ29፥37፤ ዘሌ8፥33
43፥27 ዘፀ32፥6፤ ዘሌ9፥1፤17፥5፤ኢሳ 60፥7
44፥1 ሕዝ43፥1
44፥2 ሕዝ43፥4-5
44፥3 ዘፀ24፥9-11፤ ሕዝ46፥2፡8
44፥4 ኢሳ6፥4፤ ሕዝ 10፥4፤40፥35፤ ዳን 8፥17፤ራእ15፥8
44፥5 ሕዝ40፥4፤ 42፥9፤43፥10-11
44፥6 ሕዝ3፥9
44፥7 ዘፍ17፥14፤ ዘፀ12፥48፤ዘሌ22፥25፤ 26፥41
44፥8 ዘኍ18፥7፤ ዘሌ22፥2
44፥9 ኢል3፥17፤ ዘካ14፥21
44፥10 ዘኍ18፥23፤ መዝ95፥10
44፥11 ዘኍ3፥5-37፤ 16፥9፤1ዜና26፥12 -19፤2ዜና29፥34
44፥12 2ነገ16፥10 -16፤መዝ106፥26፤ ኤር14፥10፤18፥15
44፥13 ዘኍ18፥3፤ ሕዝ16፥61፤ሆሴ5፥1
44፥14 1ሳሙ2፥36፤ 2ነገ23፥9፤1ዜና23፥ 28-32
44፥15 ዘፀ29፥13፤ 2ሳሙ8፥17፤ዕዝ7፥2፤ ኤር33፥18፤ሕዝ 40፥46፤ዘካ3፥7
44፥16 ዘሌ3፥16 -17፤17፥5-6፤ ዘኍ18፥5፤ 1ሳሙ2፥35፤ ሕዝ41፥22፤ዘካ3፥7
44፥17 ራእ19፥8
44፥18 ዘፀ28፥39፡ 42፤ዘሌ16፥4፤ ኢሳ3፥20

የቤተ መቅደሱን መግቢያና የመቅደሱን
መውጫዎች ሁሉ አስተውል፤ 6ለዐመፀ
ኛው የእስራኤል ቤት እንዲህ በል፤ 'ጌታ
*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ "የእስራኤል
ቤት ሆይ፤ አስጸያፊ ሥራችሁ ከእንግዲህ
ያብቃ! 7ከአስጸያፊ ሥራችሁም ሌላ ምግብ፣
ስብና ደም ስታቀርቡ ልባቸውንና ሥጋቸ
ውን ያልተገረዙትን እንግዶች ወደ መቅደሴ
በማ ስገባት ቤተ መቅደሴን አረከሳችሁ፤
ቃል ኪዳኔንም አፈረሳችሁ። 8እናንተ ራሳችሁ
ማድረግ የሚገባችሁን ቅዱሳት ሥርዐቶቼን
በመፈጸም ፈንታ ባዕዳንን በኀላፊነት በመ
ቅደሴ አስቀመጣችሁ። 9ጌታ *እግዚአብሔር*
እንዲህ ይላል፤ በልቡና በሥጋው ያልተገረዘ
ባዕድ በእስራኤላውያን መካከል የሚኖር
ቢሆንም እንኳ ወደ መቅደሴ አይግባ።
10' "እስራኤል እኔን ከመከተል በራቁ
ጊዜ፣ ከእኔ የራቁትና ጣዖቶቻቸውን በመከ
ተል የተቅበዘበዙት ሌዋውያን የኀጢአታ
ቸውን ዕዳ ይሸከማሉ። 11የቤተ መቅደሱ
በር ኀላፊ በመሆንና በእርሱም ውስጥ በማገል
ገል፣ መቅደሴን ሊያገለግሉ ይችላሉ፤ የሚ
ቃጠለውን መሥዋዕት ዐርደው ስለ ሕዝቡ
ሊሠዉ፣ በፊታቸው ሊቆሙና ሊያገለግሏቸው
ይችላሉ። 12ነገር ግን ሕዝቡን በጣዖቶቻቸው
ፊት ስላገለገሏቸውና የእስራኤል ቤት
በኀጢአት እንዲወድቅ ስላደረጉ፣ ስለዚህ
የኀጢአታቸውን ዋጋ መቀበል እንዳለባቸው
እጄን አንሥቼ ምያለሁ፤ ይላል ጌታ *እግዚ
አብሔር።* 13እንደ ካህናት ያገለግሉኝ ዘንድ
ወደ እኔ አይቀርቡም፤ ወይም ቅዱስ ወደ
ሆነው ነገሬ ሁሉ፣ ወይም እጅግ ወደ
ተቀደሱ መሥዋዕቶቼ አይቀርቡም፤ የአስ
ጸያፊ ድርጊታቸውን ኀፍረት ይሸከማሉ።
14ያም ሆኖ የቤተ መቅደሱን ሥራ በኀላ
ፊነት እንዲሠሩ፣ በውስጡ የሚከናወኑትንም
ሥራዎች ሁሉ እንዲቈጣጠሩ አደርጋቸዋለሁ።
15' "ነገር ግን እስራኤላውያን ከመንገዴ
ስተው በወጡ ጊዜ፣ የመቅደሴን ሥራ በታ
ማኝነት ያከናወኑት የሳዶቅ ዘርና ሌዋውያን
የሆኑት፣ በፊቴ ቀርበው ያገለግሉኛል፤
በፊቴ ቆመው የስብና የደም መሥዋዕት
ያቀርቡ ልኛል፤ ይላል ጌታ *እግዚአብሔር።*
16እነርሱ ብቻ ወደ መቅደሴ ይገባሉ፤
እነርሱ ብቻ በፊቴ ሊያገለግሉ፣ ሥርዐ
ቴንም ሊፈጽሙና ወደ ገበታዬ ሊቀርቡ
ይችላሉ።
17' "ወደ ውስጠኛው አደባባይ
በሮች ሲገቡ፣ የበፍታ ፈትል ይልበሱ፤
በውስጠኛው አደባባይ በሮችም ሆነ በቤተ
መቅደሱ ውስጥ ሲያገለግሉ፣ ከበግ ጠጕር
የተሠራ ልብስ አይልበሱ። 18በራሳቸው
ላይ ከበፍታ

ሠ27 በትውፊት *የድነት መሥዋዕት* ይባላል

ፈትል የተሠራ ጥምጥም ያድርጉ፤ እንዲ
ሁም ከበፍታ ፈትል የተሠራ ሱሪ በወገባ
ቸው ላይ ይታጠቁ፤ እንዲያልባቸው የሚያ
ደርግ ማንኛውንም ልብስ አይልበሱ።
19ሕዝቡ ወዳለበት ወደ ውጪ አደባባይ
ሲወጡ፣ ሲያገለግሉበት የነበረውን ልብስ
አውልቀው በተቀደሱት ክፍሎች በመተው
ሌሎች ልብሶችን ይልበሱ፤ ይኸውም ሕዝ
ቡን በልብሳቸው እንዳይቀድሱ ነው።
20' "የራሳቸውን ጠጕር አይላጩት፤ ወይም
አያርዝሙት፤ ነገር ግን ይከርክሙት። 21ማን
ኛውም ካህን ወደ ውስጠኛው አደባባይ
በሚገባበት ጊዜ የወይን ጠጅ አይጠጣ።
22መበለቶችን ወይም ፈት ሴቶችን አያ
ግቡ፤ ነገር ግን ከእስራኤል ዘር የሆኑ ድን
ግሎችን ወይም የካህናት ሚስቶች የነበሩ
ትን መበለቶች ማግባት ይችላሉ። 23በተቀደ
ሰውና ባልተቀደሰው መካከል ያለውን ልዩነት
ለሕዝቤ ያስተምሩ፤ የረከሰውንና ያልረከሰ
ውን እንዴት እንደሚለዩም ያሳዩአቸው።
24' "በማንኛውም ክርክር ካህናት ዳኞች
ሆነው ያገልግሉ፤ በሥርዐቴም መሠረት
ይወስኑ። የተለዩ በዓላቴን የሚመለከቱ ሕጎ
ቼንና ሥርዐቶቼን ሁሉ ይጠብቁ፤ ሰንበታ
ቴንም ቅዱስ አድርገው ይጠብቁ።
25' "ካህን ወደ ሞተ ሰው ሬሳ በመጠ
ጋት ራሱን አያርክስ፤ ይሁን እንጂ ሟች
አባቱ ወይም እናቱ፣ ወንድ ልጁ ወይም ሴት
ልጁ፣ ወንድሙ ወይም ያላገባች እኅቱ
ብትሆን፣ ራሱን ማርከስ ይችላል። 26ከነጻም
በኋላ፣ ሰባት ቀን መቈየት አለበት። 27በመ
ቅደሱ ለማገልገል፣ ወደ መቅደሱ ውስጠ
ኛው አደባባይ በሚገባበት ቀን፣ ስለ ራሱ
የኀጢአት መሥዋዕት ያቅርብ፤ ይላል
ጌታ *እግዚአብሔር*።
28' "ለካህናቱ ርስታቸው እኔ ብቻ ነኝ፤
በእስራኤል ምንም ዐይነት ርስት አትስጧ
ቸው፤ እኔ ርስታቸው እሆናለሁ። 29የእህሉን
ቍርባን፣ የኀጢአቱንና የበደሉን መሥዋዕት
ይበላሉ፤ በእስራኤል *ለእግዚአብሔር* የተ
ሰጠው[ረ] ሁሉ የእነርሱ ይሆናል። 30ከፍሬ
በኵራት ምርጥ የሆነው ሁሉ እንዲሁም
ከልዩ ስጦታዎቻችሁ የመጀመሪያው ሁሉ
ለካህናት ይሆናል፤ ለቤተ ሰዎቻችሁ ሁሉ
በረከት እንዲሆን ከምድር የምታገኙትን መብል
በኵራት ለእነርሱ ስጧቸው። 31ካህናት ሞቶ
የተገኘውን ወይም በዱር አራዊት የተዘነጠ
ለውን ወፍም ይሁን ሌላ እንስሳ፣ ማንኛ
ውንም ነገር መብላት የለባቸውም።

44፥19 ዘፀ39፥27-29፤ዘሌ6፥10-11፡27፤ሕዝ42፥14
44፥20 ዘሌ21፥5፤ዘኍ6፥5፤ሕዝ5፥1
44፥21 ዘሌ10፥9
44፥22 ዘሌ21፥7
44፥23 ዘፍ7፥2፤ዘሌ13፥50፤15፥31፤ኤር15፥19፤ሕዝ22፥26፤ሐጌ2፥11-13
44፥24 ዘሌ23፥2፤ዘዳ17፥8-9፤19፥17፤21፥5፤1ዜና23፥4፤2ዜና19፥8
44፥25 ዘሌ21፥1-4
44፥26 ዘኍ19፥14
44፥27 ዘሌ4፥28፤ዘኍ3፥28፤6፥11
44፥28 ዘኍ18፥20፤ዘዳ18፥1-2፤ኢሱ13፥33
44፥29 ዘሌ6፥16፤27፥21፤ዘኍ18፥9፡14፤ኢሱ13፥14
44፥30 ዘሌ25፥21፤ዘኍ15፥18-21፤18፥12-13፤2ዜና31፥5፡10፤ነህ10፥35-37
44፥31 ዘፀ22፥31፤ዘሌ11፥39፡40

## የምድሪቱ አከፋፈል

45 1' "ምድሪቱን ርስት አድርጋችሁ
በዕጣ በምትከፋፈሉበት ጊዜ፣
ርዝመቱ ሃያ አምስት ሺህ[ሰ] ክንድ፣ ወርዱ
ሃያ ሺህ ክንድ የሆነውን አንዱን ክፍል፣
*ለእግዚአብሔር* የተቀደሰ ስፍራ አድርጋችሁ
ስጡ፤ ስፍራውም በሙሉ ቅዱስ ይሆናል፤
2ከዚሁም አምስት መቶ ክንድ በአምስት
መቶ ክንድ፣ ዙሪያው አምሳ ክንድ ባዶ
ቦታ ቀርቶ፣ ለመቅደሱ ይሁን። 3ከተቀደ
ሰውም ስፍራ ላይ ርዝመቱ ሃያ አምስት
ሺህ ክንድ፣ ወርዱም ዐሥር ሺህ ክንድ
ለካ፤ በዚህም ውስጥ መቅደሱ፣ ይኸውም
ቅድስተ ቅዱሳኑ ይሆናል። 4ይህም በቤተ
መቅደሱ ውስጥ ለሚያገለግሉና፣ *በእግዚ
አብሔር* ፊት ለአገልግሎት ለሚቀርቡ
ካህናት፣ ቅዱስ የሆነ የምድሪቱ ክፍል
ይሆናል። 5ርዝመቱ ሃያ አምስት ሺህ
ክንድ፣ ወርዱ ዐሥር ሺህ ክንድ ስፋት
ያለው ስፍራ መኖሪያ ከተሞ ቻቸውን እን
ዲከትሙ[ሸ] በቤተ መቅደስ ለሚያገለግሉ
ሌዋውያን ርስት ይሆናል።
6' "ከተቀደሰው ስፍራ ጋር የተያያዘ
ወርዱ አምስት ሺህ ክንድ፣ ርዝመቱ ሃያ
አምስት ሺህ ክንድ የሆነ ቦታ ለከተማዪቱ
ርስት አድርገህ ስጥ፤ ይህም ለመላው
የእስራኤል ቤት ይሆናል።
7' "ገዢ ከቅዱሱ ስፍራና ከከተማው
ወሰን ግራና ቀኝ ርስት ይኖረዋል፤ ይህም
ከምዕራብ በኩል ወደ ምዕራብ
አቅጣጫ ምሥራቅ በመዝለቅ፣ ከምዕራ
ብ እስከ ምሥ ራቅ ያለውን ወሰን ርዝመት
ተከትሎ ለአንዱ ነገድ ከተሰጠው ርስት
ጋር ጐን ለጐን ይሄዳል። 8ይህም መሬት
በእስራኤል ምድር የገዢ ርስት ይሆናል።
ከእንግዲህ ገዞቼ
ሕዝቤን አይጨቍኑም፤ ነገር ግን የእስራ
ኤል ቤት በየነገዳቸው ርስት እንዲይዙ
ይፈቅዱላቸዋል።
9' "ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
'የእስራኤል ገዞች ሆይ! ከልክ ዐልፋችኋል፤
ይብቃችሁ፤ ዐመፅንና ጭቈናን ተዉ፤ ቀናና
ትክክል የሆነውን ነገር አድርጉ። የሕዝ
ቤን ርስት መቀማት ይቅርባችሁ፤ ይላል
ጌታ *እግዚአብሔር*። 10ትክክለኛ ሚዛን
ትክክለኛ ኢፍና[ቀ] ትክክለኛ ባዶስ[በ] ይኑራ
ችሁ። 11የኢፍና የባዶሱ መመዘኛ ተመሳሳይ

45፥1 ዘኍ34፥13፤ሕዝ48፥8-9፡29
45፥2 ሕዝ42፥20
45፥4 ሕዝ40፥46፤48፥10-11
45፥5 ሕዝ48፥13
45፥6 ሕዝ48፥15-18
45፥7 ሕዝ48፥21
45፥8 ዘኍ26፥53፤ሕዝ46፥18
45፥9 መዝ12፥5፤ኤር22፥3፤ዘካ7፥9-10፤8፥16
45፥10 ዘሌ19፥36፤ዘዳ25፥15፤ምሳ11፥1፤አሞ8፥4-6፤ሚክ6፥10-11
45፥11 ኢሳ5፥10

[ረ]29 የዕብራይስጡ ቃል ዕቃዎችን ወይም ሰዎችን ለእግዚአብሔር ከመስጠት አኳያ የማይለወጥ መደበኛ መስጠትን ያመለክታል
[ሰ]1 ሰብዓ ሊቃናትም (በተጨማሪ ቍ3፣ 5እና 48፥9 ይመ) እን ዲሁ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን *ዐሥር ሺህ* ይላል
[ሸ]5 ሰብዓ ሊቃናትም እንዲሁ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን *በቤተ መቅደስ ... ሃያ ክፍሎች በንብረትነት ይኖራቸዋል*
[ቀ]10 ኢፍ የደረቅ ነገር መስፈሪያ ነው
[በ]10 ባዶስ የፈሳሽ ነገር መለኪያ ነው

ይሁን፤ አንድ ባዶስ የሆመር[†] አንድ ዐሥረኛ
እንዲሁም አንድ ኢፍ የሆመር አንድ ዐሥረኛ
ይሆናል፤ ሆመር ለሁለቱም ሚዛኖች መደ
በኛ መለኪያ ነው። [12]አንድ ሰቅል ሃያ ጌራህ
የሚይዝ ይሆናል፤ በሃያ ሰቅል ላይ ሃያ
አምስት ሰቅልና ዐሥራ አምስት ሰቅል ሲጨ
መር አንድ ምናን ይሆናል።’

## ልዩ ልዩ መሥዋዕትና በዓላት

[13]‘ “የምታቀርቡት ልዩ መባ ይህ ነው፤
ከአንድ ሆመር መስፈሪያ ስንዴ አንድ ስድ
ስተኛ ኢፍ እንዲሁም ከእያንዳንዱ ሆመር
ገብስ አንድ ስድስተኛ ኢፍ ነው። [14]ዘይቱ
በባዶስ ሲለካ የተወሰነው መስፈሪያ ከእያን
ዳንዱ ሆመር አንድ ዐሥረኛ ባዶስ ይሆ
ናል፤ ይኸውም ዐሥር ባዶስ ወይም አንድ
ሆመር ነው፤ ዐሥር ባዶስ ከአንድ ሆመር
ጋር እኩል ነውና። [15]እንዲሁም ውሃ ከጠገ
በው ከእስራኤል መሰማሪያ፣ ሁለት መቶ
በግ ካለው ከእያንዳንዱ መንጋ አንድ በግ
ይውሰድ። ይህ ሁሉ ለሕዝቡ ማስተስረያ
ለሚሆነው ለእህል ቍርባን፣ ለሚቃጠል
መሥዋዕትና ለኅብረት መሥዋዕት[‡] ይው
ላል፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። [16]የምድ
ሪቱ ሕዝብ ሁሉ ይህን ልዩ መባ ለእስራ
ኤል ገዥ ይሰጣሉ። [17]በበዓላት፣ በወር መባ
ቻና በሰንበታት፣ ለእስራኤል ቤት በተወሰኑት
በዓላት ሁሉ የሚቃጠል መሥዋዕት፣ የእ
ህል ቍርባንና የመጠጥ ቍርባን ማቅረብ የገዡ
ኀላፊነት ነው፤ ለእስራኤል ቤት ማስተስረያ
እንዲሆንም የኀጢአት መሥዋዕት፣ የእህል
ቍርባን፣ የሚቃጠል መሥዋዕትና የኅብረት
መሥዋዕት ያቀርባል።’

[18]“ ‘ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
‘በመጀመሪያው ወር፣ በመጀመሪያው ቀን
ነውር የሌለበትን ወይፈን ውሰድ፤ መቅደሱ
ንም አንጻው። [19]ካህኑም ከኀጢአቱ መሥ
ዋዕት ደም በመውሰድ በቤተ መቅደሱ በር
መቃኖች፣ በመሠዊያው ላይኛ ዕርከን አራት
ማእዘንና በውስጠኛው አደባባይ በር መቃ
ኖች ላይ ይርጨው። [20]አንድ ሰው ሳያስብ
ወይም ባለማወቅ ኀጢአት ቢሠራ፤ ወር
በገባ በሰባተኛው ቀን ይህን ታደርጋለህ፤ በዚህ
ዐይነት ለቤተ መቅደሱ ታስተሰርያላችሁ።’

[21]“ ‘በመጀመሪያው ወር በዐሥራ አራ
ተኛው ቀን የፋሲካን በዓል ታከብራላችሁ፤
ይህም እርሾ የሌለበትን እንጀራ
የምትበሉበት ሰባት ቀን የሚከበር በዓል
ነው። [22]በዚያም ቀን ገዢው ስለ ራሱና
ስለ ምድሪቱ ሕዝብ ሁሉ አንድ ወይፈን
የኀጢአት መሥዋዕት አድርጎ ያቀርባል።
[23]በዓሉ በሚከበርበት በሰባቱ ቀን ገዡ በየዕ
ለቱ እንከን የሌለባቸውን ሰባት ወይጠ
ፈኖችና ሰባት አውራ በጎች የሚቃጠል
መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ያቅርብ፤
በየዕለቱም ለኀጢአት መሥዋዕት አውራ
ፍየል ያቅርብ። [24]ለአንዱ ወይፈን አንድ
የኢፍ መስፈሪያ፣ ለአንድ አውራ በግ አንድ
የኢፍ መስፈሪያ የእህል ቍርባን አድርጎ፣
ለእያንዳንዱም ኢፍ አንድ የኢን መስፈሪያ
ዘይት አብሮ ያቅርብ።

[25]“ ‘በሰባተኛው ወር በዐሥራ አምስተኛው
ቀን በሚጀመረው በሰባቱ ቀን በዓል፣ ለኀጢ
አት መሥዋዕት፣ ለሚቃጠል መሥዋዕት፣ ለእ
ህል ቍርባንና ለዘይቱም እንዲሁ ያቅርብ።

46 “ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
ለምሥራቅ ትይዩ የሆነው የውስጠ
ኛው አደባባይ በር በስድስቱ የሥራ ቀኖች
ይዘጋ፤ ነገር ግን በሰንበት ቀንና በወር
መባቻ ቀን ይከፈት። [2]ገዡ ከውጭ በኩል
በመግቢያው መተላለፊያ በረንዳ በመግባት
በበሩ መቃን አጠገብ ይቁም፤ ካህናቱም
የእርሱን የሚቃጠል መሥዋዕትና የኅብረት
መሥዋዕት[ጎ] ያቅርቡለት፤ በበሩ መግቢያ
ደፍ ላይ ሆኖ ይስገድ፤ ከዚያም ይውጣ፤
በሩ ግን እስከ ምሽት ድረስ አይዘጋ። [3]የም
ድሪቱም ሕዝብ በሰንበታትና በወር መባቻ
በዓላት በእግዚአብሔር ፊት በበሩ መግቢያ
ላይ ይስገዱ። [4]ገዡ በሰንበት ቀን በእግዚ
አብሔር ፊት የሚያቀርበው የሚቃጠል
መሥዋዕት ስድስት የበግ ጠቦትና አንድ
አውራ በግ ነው፤ ሁሉም እንከን የሌላቸው
ይሁኑ። [5]ከአውራ በጉ ጋር የሚቀርበው
የእህል ቍርባን አንድ የኢፍ መስፈሪያ
ይሁን፤ ከበግ ጠቦቶቹ ጋር የሚቀርበውም
የእህል ቍርባን ሰውየው የወደደውን ያህል
ይሁን፤ እያንዳንዱም የኢፍ መስፈሪያ አንድ
የኢን መስፈሪያ ዘይት ይኑረው። [6]በወር
መባቻ በዓል አንድ ወይፈን፣ ስድስት የበግ
ጠቦትና አንድ አውራ በግ ያቅርብ፤ ሁሉም
እንከን የሌለባቸው ይሁኑ። [7]ከወይፈኑ ጋር
አንድ የኢፍ መስፈሪያ፣ ከአውራው በግም
ጋር አንድ የኢፍ መስፈሪያ የእህል ቍርባን
ያቅርብ፤ ከበግ ጠቦቶቹ ጋር የሚቀርበው
የእህል ቍርባን ደግሞ ሰውየው የወደደውን
ያህል ይሁን፤ እያንዳንዱም የኢፍ መስፈሪያ
የኢን መስፈሪያ ዘይት ይኑረው። [8]ገዡ
ሲገባ፣ በመግቢያው በር መተላለፊያ በረንዳ
ይግባ፤ ሲወጣም በዚያው ይውጣ።

[9]“ ‘በተወሰኑት በዓላት የምድሪቱ ሕዝብ
በእግዚአብሔር ፊት በሚቀርብበት ጊዜ፣
ይሰግድ ዘንድ በሰሜን በር የገባ ሁሉ
በደቡብ በር ይውጣ፤ በደቡብ በር የገባም

45፥12 ዘፀ30፥13፤ ዘሌ27፥25፤ዘኍ3፥47
45፥15 ዘሌ1፥4፤ 6፥30
45፥17 ዘሌ23፥38፤ ዘኍ10፥10፤1ነገ8፥62፤2ዜና31፥3፤ኢሳ66፥23፤ሕዝ46፥4-12
45፥18 ዘፀ12፥2፤ ዘሌ 16፥33፤22፥20፤ ዕብ9፥14
45፥19 ዘሌ16፥18-19፤ሕዝ43፥17
45፥20 ዘሌ4፥27
45፥21 ዘፀ12፥11
45፥22 ዘሌ4፥14
45፥23 ዘኍ22፥40፤ 28፥16-25፤ኢዮ42፥8
45፥24 ዘኍ28፥12-13፤ሕዝ46፥5-7
45፥25 ዘሌ23፥34-43፤ዘኍ29፥12-38፤ ዘዳ16፥13
46፥1 ቍ6፤1ዜና 9፥18፤ኢሳ66፥23፤ ሕዝ40፥19
46፥2 ቍ8፡12፤ ሕዝ40፥39፤44፥3
46፥3 ኢሳ66፥23፤ ሉቃ1፥10
46፥5 ቍ11
46፥6 ቍ1፤ዘሌ 22፥20፤ዘኍ10፥10
46፥7 ሕዝ45፥24
46፥8 ቍ2፤ ሕዝ44፥3
46፥9 ዘፀ23፥14፤ 34፥20

[†]11 ሆመር የደረቅ ነገር መስፈሪያ ነው
[‡]15 በትውፊት *የድኅነት መሥዋዕት* ይባላል
[ጎ]2 በትውፊት *የድኅነት መሥዋዕት* ይባላል፤ እንዲሁም በቍ17

በሰሜኑ በር ይውጣ፤ በፊት ለፊቱ ባለው
በር ይመለስ እንጂ ማንም በገባበት በር
አይውጣ። 10ገዡ በመካከላቸው በመሆን፣
ሲገቡ ይገባል፤ ሲወጡም ይወጣል።
11“ ‘በበዓላትና በተወሰኑት በዓላት፣ ከወ
ይፈኑ ጋር አንድ የኢፍ መስፈሪያ፣ ከአውራ
በጉም ጋር አንድ የኢፍ መስፈሪያ የእህል
ቍርባን ያቅርብ፤ ከበግ ጠቦቶቹ ጋር የሚ
ያቀርበው የእህል ቍርባን ግን ሰውየው
የወደደውን ያህል ይሁን፤ እያንዳንዱም የኢፍ
መስፈሪያ አንድ የኢን መስፈሪያ ዘይት
ይኑረው። 12ገዡ በፈቃዱ ለእግዚአብሔር
የሚቃጠል መሥዋዕትም ሆነ የኅብረት
መሥዋዕት በሚያቀርብበት ጊዜ፣ በምሥራ
ቅ ትይዩ የሆነው በር ይከፈትለት፤
በሰንበት ቀን እንደሚያደርገው ሁሉ
የሚቃጠል መሥዋዕቱንም ሆነ የኅብረት
መሥዋዕቱን ያቅርብ፤ ከዚያ በኋላ ይወጣል፤
በሩም ይዘጋል።
13“ ‘በየቀኑ እንከን የሌለበትን የአንድ ዓመት
ጠቦት የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገህ
ለእግዚአብሔር አቅርብ፤ ይህንንም በየማ
ለዳው ታቀርበዋለህ። 14ከዚህም ጋር አንድ
ስድስተኛ የኢፍ መስፈሪያ ዱቄት መለወሻም
የሚሆን የኢን መስፈሪያ ሢሶ ዘይት አድ
ርገህ በየማለዳው የእህል ቍርባን አቅርብ፤
ይህን የእህል ቍርባን ለእግዚአብሔር ማቅ
ረብም የዘላለም ሥርዐት ነው። 15ስለዚህ
ዘወትር ለሚቀርበው የሚቃጠል መሥዋዕት
በየማለዳው የበግ ጠቦት፣ የእህል ቍርባንና
ዘይት ይቅረብ።
16“ ‘ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ገዡ
ከርስቱ ላይ ከወንድ ልጆቹ ለአንዱ ስጦታ
ቢያደርግ፣ ያ ስጦታ ለዘሩ የሚተላለፍ ነው፤
በውርስም ንብረታቸው ይሆናል። 17ይሁን
እንጂ ገዡ ከርስቱ ላይ ከባሪያዎቹ ለአንዱ
ቢሰጥ፣ ባሪያው ነጻ እስከሚወጣበት ዓመት
ድረስ የራሱ ሊያደርገው ይችላል፤ ከዚ
ያም ርስቱ ለገዡ ይመለስለታል፤ ርስቱም
ለወንድ ልጆቹ ብቻ የሚተላለፍ ይሆናል፤
የእነርሱም ነው። 18ገዡ ከንብረታቸው በማ
ፈናቀል፤ የትኛውንም የሕዝቡን ርስት መው
ሰድ አይገባውም፤ ለወንድ ልጆቹ ርስት
መስ ጠት ያለበት ከራሱ ንብረት ነው፤ ይኸ
ውም ከሕዝቤ ማንም ከርስቱ እንዳይነቀል
ነው።’ ”
19ከዚያም ያ ሰው በበሩ አጠገብ ባለው
መግቢያ አድርጎ፣ ለሰሜን ትይዩ ወደ ሆኑት
ወደ ካህናቱ የተቀደሱ ክፍሎች አመጣኝ፤
በምዕራብም መዳረሻ ያለውን ቦታ አሳየኝ።
20እርሱም፣ “ይህ ስፍራ ሕዝቡን ለመቀደስ
መሥዋዕቱን ወደ ውጪ አደባባይ እንዳያ
ወጡ፣ ካህናቱ የበደሉን መሥዋዕትና የኀጢ
አቱን መሥዋዕት የሚቀቅሉበት፣ የእህሉንም
ቍርባን የሚጋግሩበት ቦታ ነው” አለኝ።
21ከዚያም ወደ ውጪ አደባባይ አመ
ጣኝ፤ በአራቱም ማእዘን ዙሪያ መራኝ፤ በእ
ያንዳንዱም ማእዘን ሌላ አደባባይ አየሁ።
22በውጪ አደባባይ ባለው በአራቱ ማእዘን
የታጠሩ[ነ] አደባባዮች አሉ፤ ርዝመታቸው አርባ
ክንድ፣ ወርዳቸውም ሠላሳ ክንድ
ነበር፤ በአራቱም ማእዘን ያሉት አደባባዮች
እኩል ናቸው። 23ከሥሩ ዙሪያውን ምድጃ
የነበረበት፣ በአራቱም አደባባዮች ውስጥ
ዙሪያ የድን ጋይ ዕርከን ነበር። 24እርሱም
እንዲህ አለኝ፤ “እነዚህ፣ በቤተ መቅደሱ
የሚያገለ ግሉቱ፣ የሕዝቡን መሥዋዕት
የሚቀቅሉ ባቸው ስፍራዎች ናቸው።”

### ከቤተ መቅደሱ ተነሥቶ የሚፈውስ ወንዝ

47 ከዚያም ያ ሰው ወደ ቤተ መቅደሱ
መግቢያ መልሶ አመጣኝ፤ ከቤተ
መቅደሱ መድረክ ሥር ውሃ እየወጣ፣
ወደ ምሥራቅ ይፈስ ነበር፤ ቤተ መቅደሱ
ለምሥራቅ ትይዩ ነበርና። ውሃው ከቤተ
መቅደሱ በስተ ደቡብ በኩል፣ በመሠዊያው
ደቡብ በኩል፣ ሥር ሥሩን ይወርዳል።
2ከዚያም በሰሜኑ በር በማውጣት በውጭ
አዞሮ በምሥራቅ አቅጣጫ ወዳለው የውጭ
በር መራኝ፤ ውሃውም በደቡብ በኩል ይፈስ
ነበር።
3ያም ሰው የመለኪያውን ገመድ በእጁ
ይዞ ወደ ምሥራቅ በመሄድ፣ አንድ ሺህ
ክንድ ለካ፤ ከዚያም እስከ ቁርጭምጭሚት
በሚደርሰው ውሃ ውስጥ መራኝ፤ 4ቀጥሎም
አንድ ሺህ ክንድ ለካ፤ እስከ ጕልበት ወደ
ሚደርስም ውሃ መራኝ፤ ከዚያም ሌላ አንድ
ሺህ ክንድ ለካ፤ እስከ ወገብ ወደሚደርስም
ውሃ መራኝ። 5እንደ ገናም አንድ ሺህ
ክንድ ለካ፤ አሁን ግን ልሻገረው የማልችል
ወንዝ ሆነ፤ ምክንያቱም ውሃው ስለ ሞላና
ጥልቅ ስለ ነበረ፣ በዋና ካልሆነ በስተቀር
በእ ግር ሊሻገሩት የማይቻል ነበረ። 6እር
ሱም፣ “የሰው ልጅ ሆይ፤ ይህን ታየዋለ
ህን?” ሲል ጠየቀኝ።
ከዚያም መልሶ ወደ ወንዙ ዳር መራኝ፤
7እዚያም በደረስሁ ጊዜ፣ በወንዙ ግራና
ቀኝ ብዙ ዛፍ አየሁ። 8እርሱም እንዲህ
አለኝ፤ “ይህ ውሃ ወደ ምሥራቅ ምድር
ይፈሳል፤ ወደ ባሕሩ ወደሚገባበት ወደ ዓረባ[ኘ]
ይወርዳል፤ ወደ ባሕሩም[አ] ሲፈስ፣ በዚያ
የነበረው ውሃ ንጹሕ ይሆናል። 9ወንዙ በሚ
ፈስበት ስፍራ ሁሉ ብዙ ሕያዋን ፍጡራን
ይኖራሉ። ይህ ውሃ በዚያ ስለሚፈስና ጨውማ

46፥10 2ሳሙ6፥14-15፤መዝ42፥4
46፥11 ቍ5
46፥12 ቍ2፤ ዘሌ 7፥16፤ ሕዝ45፥17
46፥13 ዘፀ29፥38፤ ዘኍ28፥3፤መዝ5፥3
46፥14 ዘኍ15፥6፤ ዳን8፥11
46፥15 ዘፀ29፥38፡42፤ዘኍ28፥5-6
46፥16 2ዜና21፥3
46፥17 ዘሌ25፥10
46፥18 ዘሌ25፥23፤ 1ሳሙ8፥14፤ ሕዝ45፥8፤ሚክ2፥1-2
46፥19 ሕዝ42፥4፡9
46፥20 ቍ24፤ ዘሌ 6፥27፤ዘካ14፥20
47፥1 መዝ46፥4፤ ኢሳ55፥1፤ኢ ል3፥18፤ራእ22፥1
47፥2 ሕዝ40፥35
47፥3 ሕዝ40፥3
47፥5 ዘፍ2፥10፤ ኢሳ11፥9፤ዕን2፥14
47፥7 ቍ2፤ ራእ 22፥2
47፥8 ዘዳ1፥1፤ 3፥17፤ኢሳ41፥18
47፥9 ኢሳ12፥3፤ 55፥1፤ዮሐ4፥14፤ 7፥37-38

[ነ]22 በዕብራይስጥ የዚህ ቃል ትርጕም አይታወቅም
[ኘ]8 ወይም *ወደ ዮርዳኖስ ሸለቆ*
[አ]8 ሙት ባሕርን ያመለክታል

የሆነውን ውሃ ንጹሕ ስለሚያደርገው፣ ዓሣ
በብዛት ይኖራል፤ ስለዚህ ወንዙ በሚፈስበት
ስፍራ ሁሉ ማንኛውም ነገር በሕይወት
ይኖራል። 10ዓሣ አጥማጆች በወንዙ ዳር
ይቆማሉ፤ ከዓይ ንጋዲ እስከ ዓ
ይንኤግላይም ድረስ ያለው ቦታ መረብ
መዘርጊያ ይሆ ናል፤ ዓሣውም እንደ
ታላቁ ባሕር[ከ] ዓሣ፣ የተለያየ ዐይነት
ይሆናል። 11ነገር ግን ረግ ረጉና ዕቋሪው
ውሃ ንጹሕ አይሆንም፤ ጨው እንደ ሆነ
ይቀራል። 12በወንዙም ዳርና ዳር፣ ፍሬ
የሚያፈሩ የዛፍ ዐይነቶች ሁሉ ይበቅላሉ፤
ቅጠላቸው አይደርቅም፤ ፍሬ አል ባም
አይሆኑም። ከመቅደሱ የሚወጣው ውሃ
ስለሚፈስላቸው በየወሩ ያፈራሉ፤ ፍሬያቸው
ለምግብ፣ ቅጠላቸውም ለፈውስ ይሆናል።

### የምድሪቱ ወሰን

13ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ "ምድ
ሪቱን ርስት አድርገህ ለዐሥራ ሁለቱ የእስራ
ኤል ነገድ የምታከፋፍሉባቸው፣ ወሰኖች
እነዚህ ናቸው፤ ዮሴፍ ሁለት ዕጣ ይኑረው።
14እኩል አድርጋችሁ ከፋፍሉት፤ ለቀድሞ
አባቶቻችሁ እሰጣቸው ዘንድ በተዘረጋች
እጅ ስለ ማልሁ፣ ምድሪቱ ርስታችሁ ትሆ
ናለች።
15"የምድሪቱ ወሰን ይህ ነው፤

"በሰሜን በኩል ከታላቁ ባሕር አንሥቶ
በሔትሎን መንገድ በሐማት መተላለፊያ
አድርጎ እስከ ጽዳድ ይደርሳል፤ 16ከዚ
ያም ቤሮታን፣[ኸ] በደማስቆና በሐማት
ወሰን መካከል ያለውን ሲብራይምን ዐልፎ፣
በሐውራን ወሰን ላይ እስካለው እስከ
ሐጸርሃ ቲኮን ይዘልቃል። 17ወሰኑ ከባሕሩ
በመነሣት፣ በሰሜኑ የደማስቆ ድንበር
አድርጎ፣ የሐማትንም ዳርቻ ወደ ሰሜን
ትቶ እስከ ሐጸርዔናን[ወ] ይዘልቃል።
18"በምሥራቅ በኩል ወሰኑ በሐውራንና
በደማስቆ መካከል፣ በገለዓድና በእስራ
ኤል ምድር መካከል ዮርዳኖስ ይሆናል፤
የምሥራቁ ድንበር እስከ ምሥራቁ ባሕር
ይወርድና እስከ ታማር[ዐ] ይዘልቃል፤
ይህም የምሥራቁ ወሰን ይሆናል።
19"በደቡብ በኩል ወሰኑ ከታማር ይነሣና
እስከ ሜሪባ ቃዴስ ውሃ ይደርሳል፤ ከዚ
ያም የግብፅን ደረቅ ወንዝ ተከትሎ
እስከ ታላቁ ባሕር ይዘልቃል፤ ይህ የደ
ቡብ ወሰን ነው።
20"በምዕራብ በኩል ወሰኑ ከሐማት መግቢያ
ፊት ለፊት እስካለው ቦታ ድረስ ታላቁ
ባሕር ይሆናል፤ ይህም የምዕራብ ወሰን
ይሆናል። 21"እነሆ፤ ይህችን ምድር በእስ
ራኤል ነገድ ቍጥር ልክ
ትከፋፈላላችሁ፤ 22ለራሳችሁ፣
በመካከላችሁ ለሚኖሩት ልጆች
ላሏቸው መጻተኞች ርስት አድር ጋችሁ
መድቡ፤ እነርሱንም እንደ እስራኤል
ተወላጆች ቍጠሯቸው፤ እንደ እናንተ
ከእስራኤል ነገዶች ርስት ይመደብ
ላቸው። 23መጻተኛ በማንኛውም ነገድ
መካከል ቢቀመጥ፣ በዚያ ርስቱን ስጡት"
ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*።

47፥10 ዘኍ34፥6፤ ኢሱ15፥62፤ መዝ 104፥25፤ ኢሳ19፥8፤ ሕዝ26፥5፤ማቴ4፥19፤13፥47
47፥11 ዘዳ29፥23
47፥12 ቍ7፤ ዘፍ2፥9፤መዝ1፥3፤ ኢሳ55፥1፤ኤር17፥8፤ ሕዝ 36፥8፤ ራእ22፥2
47፥13 ዘፍ48፥16፤ 49፥26፤ዘኍ34፥2-12
47፥14 ዘፍ12፥7፤ ዘዳ1፥8፤ሕዝ36፥12
47፥15 ቍ19፤ ዘኍ34፥2፡6፤ ሕዝ48፥1
47፥16 ዘኍ13፥21፤ 2ሳሙ8፥8፤ ኤር49፥23፤ሕዝ48፥1
47፥17 ሕዝ48፥1
47፥18 ሕዝ27፥18
47፥19 ቍ15፤ ዘፍ 15፥18፤ ዘዳ32፥51፤ ኢሳ27፥12፤ ሕዝ 48፥28
47፥20 ዘኍ13፥21፤ 34፥6፤ሕዝ48፥1
47፥22 ዘሌ24፥22፤ ዘኍ15፥29፤26፥55-56፤ዘዳ24፥19፤ ኢሳ14፥1፤56፥6-7፤ ሕዝ36፥12፤ ሚል3፥5፤ ሮሜ10፥12፤ ኤፌ 2፥12-16፤3፥6፤ ቈላ 3፥11
47፥23 ዘዳ10፥19
48፥1 ዘፍ30፥6፤ ሕዝ47፥15-17፡20
48፥2 ኢሱ19፥24-31
48፥3 ኢሱ19፥32-39
48፥4 ኢሱ17፥1-11
48፥5 ኢሱ16፥5-9፤ 17፥7-10፡17
48፥6 ኢሱ13፥15-21
48፥7 ኢሱ15፥1-63
48፥8 ቍ21
48፥9 ሕዝ45፥1
48፥10 ቍ21፤ ሕዝ 45፥3-4

### የምድሪቱ አከፋፈል

48 "ስማቸው የተዘረዘረው ነገዶች እነ
ዚህ ናቸው፤ በሰሜኑ ድንበር የዳን
ነገድ አንድ ድርሻ ይኖረዋል፤ ይህም የሔ
ትሎንን መንገድ ተከትሎ እስከ ሐማት መተ
ላለፊያ ይደርሳል። ሐጸርዔናንንና ከሐማት
ቀጥሎ ያለው የደማስቆ ሰሜናዊ ድንበር
ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ላለው ወሰኑ አንድ
ክፍል ይሆናል።
2"የአሴር ነገድ አንድ ድርሻ ይኖረዋል፤
ይህም የዳንን ምድር ከምሥራቅ እስከ ምዕ
ራብ ያዋስናል።
3"የንፍታሌም ነገድ አንድ ድርሻ ይኖረ
ዋል፤ ይህም የአሴርን ምድር ከምሥራቅ
እስከ ምዕራብ ያዋስናል።
4"የምናሴ ነገድ አንድ ድርሻ ይኖረዋል፤
ይህም የንፍታሌምን ምድር ከምሥራቅ
እስከ ምዕራብ ያዋስናል።
5"የኤፍሬም ነገድ አንድ ድርሻ ይኖረ
ዋል፤ ይህም የምናሴን ምድር ከምሥራቅ
እስከ ምዕራብ ያዋስናል።
6"የሮቤል ነገድ አንድ ድርሻ ይኖረዋል፤
ይህም የኤፍሬምን ምድር ከምሥራቅ እስከ
ምዕራብ ያዋስናል።
7"የይሁዳ ነገድ አንድ ድርሻ ይኖረዋል፤
ይህም የሮቤልን ምድር ከምሥራቅ እስከ
ምዕራብ ያዋስናል።
8"ይሁዳን ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ የሚ
ያዋስነው ምድር ለመባ የሚቀርብ ድርሻ
ይሆናል፤ ስፋቱም ሃያ አምስት ሺህ ክንድ
ነው፤ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ያለውም
ርዝመቱ፣ ከነገዶቹ ድርሻ እንደ አንዱ
ሆኖ፣ መቅደሱ በመካከሉ ይሆናል።
9"*ለእግዚአብሔር* የምታቀርቡት የዚህ
መባ ርዝመት ሃያ አምስት ሺህ ክንድ
ሲሆን፣ ስፋቱ ዐሥር ሺህ ክንድ ይሆናል።
10ይህ ለካህናቱ የተቀደሰ ድርሻ ይሆናል፤
በሰሜን በኩል ርዝመቱ ሃያ አምስት ሺህ

[ከ]10 *ሜድትራኒያንን ያመለክታል፤ እንዲሁም* ቍ19 እና 20
[ኸ]15-16 ሰብዓ ሊቃናትንና ሕዝ48፥1 ይመ፤ ዕብራይስጡ ግን ... *ወደ ድደድ የሚወስደው መንገድ፣ 16. ሐማት ቤሮታን ... ይላል*
[ወ]17 በዕብራይስጥ *ዔኖን የዔናን* አማራጭ ትርጒም ነው
[ዐ]18 ሰብዓ ሊቃናትና ሱርስት እንዲሁ ሲሆኑ ዕብራይስጡ ግን *እስራኤል ባሕሩን በምሥራቅ በኩል ትለካለህ፤ ይላል*

ክንድ፣ በምዕራብ በኩል ወርዱ ዐሥር ሺህ
ክንድ በምሥራቅ በኩል ወርዱ ዐሥር ሺህ
ክንድ ሲሆን በደቡብ በኩል ርዝመቱ ሃያ
አምስት ሺህ ክንድ ይሆናል፤ *የእግዚአ*
*ብሔርም* መቅደስ በመካከሉ ይቆማል።
11ይህም እስራኤላውያን በሳቱ ጊዜ፣ እንደ
ሳቱት ሌዋውያን ሳይስቱ ለቀሩት፣ በታ
ማኝነት ላገለገሉኝ ለተቀደሱት ካህናት
ለሳዶቃውያን ይሆናል። 12የሌዋውያንን ምድር
ከሚያዋስነው፣ ከምድሪቱ ቅዱስ ድርሻ እጅግ
የተቀደሰው ድርሻ ለእነርሱ ልዩ ስጦታ
ይሆናል።

13“ከካህናቱም ምድር ጐን ለጐን ሌዋው
ያኑ ሃያ አምስት ሺህ ክንድ ርዝመትና ዐሥር
ሺህ ክንድ ወርድ ያለው ይዞታ ይኖራ
ቸዋል፤ ጠቅላላ ርዝመቱ ሃያ አምስት ሺህ
ክንድ፣ ወርዱም ዐሥር ሺህ ክንድ ይሆናል።
14ከዚህ ላይ መሸጥ ወይም መለወጥ የለባቸ
ውም። ይህ ከምድሪቱ ሁሉ ምርጥ ስለ ሆነ፣
ወደ ሌላ እጅ አይተላለፍም፤ *ለእግዚአብሔር*
የተቀደሰ ነውና።

15“አምስት ሺህ ክንድ ወርድና ሃያ
አም ስት ሺህ ክንድ ርዝመት ያለው
የቀረው ቦታ ለከተማዪቱ የጋራ ጥቅም፣
ለቤት ሥራና ለከብት ማሰማሪያ
ይውላል፤ ከተማዪቱም በመካከሉ
ትሆናለች፤ 16የከተማዪቱም መጠን
በሰሜን አራት ሺህ አምስት መቶ ክንድ፣
በደቡብ አራት ሺህ አምስት መቶ ክንድ፣
በምሥራቅ አራት ሺህ አምስት መቶ
ክንድ፣ የምዕራቡም እንዲሁ አራት ሺህ
አምስት መቶ ክንድ ይሆናል። 17የከተ
ማዪቱ ከብት ማሰማሪያ ቦታ፣ በሰሜን
ሁለት መቶ አምሳ ክንድ፣ በደቡብ ሁለት
መቶ አምሳ ክንድ፣ በምሥራቅ ሁለት መቶ
አምሳ ክንድ፣ በምዕራብም ሁለት መቶ አምሳ
ክንድ ይሆናል። 18ከዚህ የሚቀረው፣
የተቀደሰውን ክፍል የሚያዋስነውና በተጓዳኝ
ያለው ቦታ በምሥራቅ ዐሥር ሺህ ክንድ፣
በምዕራብ ዐሥር ሺህ ክንድ ይሆናል።
ምርቱም ለከተማዪቱ ሠራተኞች ምግብ
ይሆናል። 19ምድሪቱን የሚያርሱ የከተማ
ዪቱ ሠራተኞች ከሁሉም ነገዶች ይመጣሉ።
20አጠቃላይ ይዞታው በአራቱም ማእዘን
እኩል ሲሆን፣ እያንዳንዱ ማእዘን ሃያ
አምስት ሺህ ክንድ ነው፤ ከከተማዪቱ ድርሻ
ጋር የተቀደሰውን ክፍል ልዩ መባ በማ
ድረግ ታስቀምጣላችሁ።

21“በተቀደሰው ድርሻና በከተማዪቱ ቦታ
ግራና ቀኝ ያለው ቀሪ ቦታ፣ ለገዡ ይሆናል፤
ይህም ሃያ አምስት ሺህ ክንድ ከሆነው
ከተቀደሰው ቦታ አንሥቶ በምሥራቅ በኩል
እስከ ምሥራቁ ወሰን ይዘልቃል፤ በምዕራ
ቡም በኩል እንዲሁ ሃያ አምስት ሺህ
ክንድ ከሆነው ይዞታ አንሥቶ እስከ ምዕራቡ
ወሰን ይዘልቃል። የየነገዱ ድርሻ ከሆነውም
መሬት ጐን ለጐን የሚሄዱት ቦታዎች የገዡ
ይሆናሉ። የተቀደሰው ቦታና መቅደሱ በመ
ካከላቸው ይሆናሉ። 22ስለዚህ የሌዋውያኑ
ይዞታና የከተማዪቱ ይዞታ ለገዡ በተሰጠው
ቦታ መካከል ይሆናል፤ የገዡ ቦታም በይሁዳ
ድንበርና በብንያም ድንበር መካከል ይሆ
ናል።

23“የቀሩት ነገዶች ድርሻ እንደሚከተለው
ይሆናል፤ ‘የብንያም ነገድ አንድ ድርሻ
ይኖረዋል፤ ይህም ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ
ይዘልቃል።

24“ ‘የስምዖን ነገድ አንድ ድርሻ ይኖረዋል፤
ይህም የስምዖንን ምድር ከምሥራቅ እስከ
ምዕራብ ያዋስናል።

25“ ‘የይሳኮር ነገድ አንድ ድርሻ ይኖረዋል፤
ይህም የስምዖንን ምድር ከምሥራቅ እስከ
ምዕራብ ያዋስናል።

26“ ‘የዛብሎን ነገድ አንድ ድርሻ ይኖረዋል፤
ይህም የይሳኮርን ምድር ከምሥራቅ እስከ
ምዕራብ ያዋስናል።

27“ ‘የጋድ ነገድ አንድ ድርሻ ይኖረዋል፤
ይህም የዛብሎንን ግዛት ከምሥራቅ እስከ
ምዕራብ ያዋስናል።

28“ ‘የጋድ ደቡባዊ ወሰን ከታማር ደቡብ
እስከ ሜሪባ ቃዴስ ውሆች ይደርሳል፤ የግ
ብፅን ደረቅ ወንዝ ይዞ እስከ ታላቁ ባሕር[//]
ይዘልቃል።

29“ ‘ለእስራኤል ነገዶች ርስት አድርጋ
ችሁ የምታከፋፍሏት ምድር ይህች ናት፤
ድርሻዎቻቸውም እነዚህ ናቸው” ይላል ጌታ
*እግዚአብሔር*።

## የከተማዪቱ በሮች

30“ ‘የከተማዪቱ መውጫ በሮች እነዚህ
ናቸው፤ ከሰሜን በኩል አራት ሺህ
አምስት መቶ ክንድ ርዝመት ካለው በር
አንሥቶ፣ 31የከተማዪቱ በሮች በእስራኤል
ነገዶች ስም ይጠራሉ፤ በሰሜን በኩል ያሉት
ሦስቱ በሮች የሮቤል ነገድ በር፣ የይሁዳ
ነገድ በርና የሌዊ ነገድ በር ይሆናሉ።

32“ ‘በምሥራቅ በኩል አራት ሺህ አምስት
መቶ ክንድ ርዝመት ባለው በር ሦስት
በሮች ይኖራሉ፤ እነዚህም የዮሴፍ በር፣
የብንያም በርና የዳን በር ናቸው።

33“ ‘በደቡብ በኩል አራት ሺህ አምስት
መቶ ክንድ ርዝመት ባለው በር ሦስት
በሮች አሉ፤ እነዚህም የስምዖን በር፣ የይሳ
ኮር በርና የዛብሎን በር ናቸው።

48፥11 ዘሌ8፥35፤ 2ሳሙ8፥17፤ ሕዝ14፥11፤44፥15
48፥13 ሕዝ45፥5
48፥14 ዘሌ25፥34፤ 27፥10፡28
48፥16 ራእ21፥16
48፥18 ሕዝ45፥6
48፥21 ቍ8፡10፤ ሕዝ45፥7
48፥23 ኢሱ18፥11-28
48፥24 ዘፍ29፥33፤ ኢሱ19፥1-9
48፥25 ኢሱ19፥17-23
48፥26 ኢሱ19፥10-16
48፥27 ኢሱ13፥24-28
48፥28 ዘፍ14፥7፤ ዘኍ34፥6፤ ሕዝ 47፥19
48፥29 ሕዝ45፥1

[//]28 ሜድትራኒያንን ያመለክታል

34“ ‘በምዕራብ በኩል አራት ሺህ አም
ስት መቶ ክንድ ርዝመት ባለው በር ሦስት
በሮች ይኖራሉ፤ እነዚህም የጋድ በር፣ የአ
ሴር በርና የንፍታሌም በር ናቸው።

48፥34 2ዜና4፥4፤ ራእ21፥12-13
48፥35 ኢሳ12፥6፤ 24፥23፤ኤር3፥17፤ 14፥9፤ኢል3፥21፤ ራእ 3፥12፤21፥3

35“ ‘የከተማዪቱም ዙሪያ ዐሥራ ስምንት
ሺህ ክንድ ይሆናል፤
“ ‘የከተማዪቱ ስም፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ
“*እግዚአብሔር በዚያ አለ*” ይሆናል።’ ”

# ትንቢተ ዳንኤል

## ዳንኤል በባቢሎን እንዲሠለጥን ተደረገ

1 የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም በነገሠ በሦስተ
ኛው ዓመት የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደ
ነፆር ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ከበባት።
2 ጌታ ም የይሁዳን ንጉሥ ኢዮአቄምን በእግዚ
አብሔር ቤተ መቅደስ ካሉት ዕቃዎች
ከጥቂቶቹ ጋር በእጁ አሳልፎ ሰጠው፤ ወደ
አምላኩ ቤት ወደ ባቢሎን[ሀ] ወሰዳቸው፤
በአምላኩም ግምጃ ቤት ውስጥ አኖራ
ቸው።

3 ከዚያ በኋላ ንጉሡ የቤተ መንግሥቱን
ጃንደረቦች አለቃ አስፋኔዝን፣ ከንጉሣዊው
ቤተ ሰብና ከመሳፍንቱ ዘር የሆኑትን እስ
ራኤላውያንን እንዲያመጣ አዘዘው፤ 4 እነርሱም
የአካል ጉዳት የሌለባቸው መልከ መልካሞች፣
ማንኛውንም ትምህርት የመማር ችሎታ
ያላቸው፣ ዕውቀት የሞላባቸው፣ ሁሉን ነገር
በፍጥነት መረዳት የሚችሉትንና በንጉ
ሡም ቤት ለማገልገል ብቃት ያላቸው
ወጣት ወንዶች ናቸው፤ የባቢሎናውያንን[ለ]
ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ እንዲያስተምራቸውም
አዘዘው። 5 ንጉሡም በየዕለቱ የሚበሉትን
ምግብና የሚጠጡትን የወይን ጠጅ ከንጉሡ
ማዕድ ድርሻ እንዲሰጣቸው አደረገ፤ ለሦ
ስት ዓመት ከሠለጠኑ በኋላ በንጉሡ አገል
ግሎት ላይ የሚሰማሩ ናቸው።

6 ከነዚህም መካከል ከይሁዳ የመጡት ዳን
ኤል፣ አናንያ፣ ሚሳኤልና አዛርያ ነበሩ፤
7 የጃንደረቦቹ አለቃም አዲስ ስም አወጣላ
ቸው፤ ዳንኤልን ብልጣሶር፣ አናንያን ሲድራቅ፤
ሚሳኤልን ሚሳቅ፣ አዛርያን አብድናጎ ብሎ ጠራ
ቸው።

8 ዳንኤል ግን በንጉሡ ምግብና የወ
ይን ጠጅ እንዳይረክስ ወሰነ፤ በዚህ መንገድ
ራሱን እንዳያረክስም የጃንደረቦቹን አለቃ
ፈቃድ ጠየቀው። 9 እግዚአብሔርም ለዳንኤል
በጃንደ ረቦቹ አለቃ ፊት ሞገስንና
መወደድን ሰጠው። 10 ሆኖም የጃንደረቦቹ
አለቃ ለዳን ኤል፣ "መብሉንና መጠጡን
የመደበላችሁን ጌታዬን ንጉሡን እፈራለሁ፤
በዕድሜ እንደ እናንተ ካሉ ወጣቶች ይልቅ
ከስታችሁ ብትታዩ፣ በንጉሡ ዘንድ በራሴ
ላይ አደጋ ታስከትሉብኛላችሁ።" ብሎ
ነገረው።

11 ዳንኤልም የጃንደረቦቹን አለቃ በዳን
ኤል፣ በአናንያ፣ በሚሳኤልና በአዛርያስ ላይ
የሾመውን መጋቢ እንዲህ አለው፤ 12 "እባ
ክህ አገልጋዮችህን ለዐሥር ቀን ያህል
ፈትነን፤ ለመብል ከአትክልት፣ ለመጠጥም
ከውሃ በስተቀር ምንም አይሰጠን፣ 13 ከዚ
ያም የእኛን መልክና የንጉሡን መብል
የሚበሉትን ወጣቶች መልክ አስተያይ፤
በአገልጋዮችህ ላይ የወደድኸውን አድርግብን።"
14 እርሱም በዚህ ነገር ተስማማ፤ ለዐሥር ቀንም
ፈተናቸው።

15 ከዐሥር ቀን በኋላም የንጉሡን መብል
ከበሉት ከሌሎች ወጣቶች ይልቅ ጤናማ
ዎችና ሰውነታቸው የወፈረ ሆነው ተገኙ።
16 ስለዚህ መጋቢው ምርጥ የሆነውን ምግባ
ቸውንና ሊጠጡት የሚገባውን የወይን ጠጅ
አስቀርቶ በምትኩ አትክልት ሰጣቸው።

17 እግዚአብሔር ለእነዚህ አራት ወጣቶች
በማንኛውም ሥነ ጽሑፍና ትምህርት ዕውቀ
ትንና ማስተዋልን ሰጣቸው፣ ዳንኤልም ማንኛ
ውንም ራእይና ሕልም የመረዳት ችሎታ ነበ
ረው።

18 ወደ እርሱ እንዲመጡ ንጉሡ የወሰ
ነው ጊዜ ሲደርስ፣ የጃንደረቦቹ አለቃ
ወደ ናቡከደነፆር አቀረባቸው፤ 19 ንጉሡም
ባነጋገራቸው ጊዜ ከመካከላቸው እንደ ዳን
ኤል፣ አናንያ፣ ሚሳኤልና አዛርያ ያለ ከቶ
አልተገኘም፤ ስለዚህ በንጉሡ አገልግሎት
ላይ ተሰማሩ። 20 ንጉሡ በጠየቃቸው በማ
ንኛውም የጥበብና የማስተዋል ጉዳይ
በመላ ግዛቱ ካሉት አስማተኞችና ድግም
ተኞች ሁሉ ዐሥር እጅ በልጠው አገኛ
ቸው።

21 ዳንኤልም፣ ንጉሥ ቂሮስ እስከ ነገሠ
በት እስከ መጀመሪያው ዓመት ድረስ እዚ
ያው ቈየ።

## ናቡከደነፆር ያለመው ሕልም

2 ናቡከደነፆር በነገሠ በሁለተኛው ዓመት
ሕልም አለመ፤ መንፈሱ ታወከ፤ እንቅ
ልፍም ከእርሱ ራቀ። 2 ያለመውንም ሕልም
እንዲነግሩት ንጉሡ ጠንቋዮችን፣ አስማተ
ኞችን፣ መተተኞችንና ኮከብ ቈጣሪዎችን[ሐ]
እንዲጠሩ አዘዘ፤ እነርሱም ገብተው በፊቱ
ቆሙ፤ 3 እርሱም፣ "አንድ ሕልም አለምሁ፤
ሕልሙም ምን እንደሆነ[መ] ለማወቅ መንፈሴ
ተጨንቆአል" አላቸው።

4 ከዚያም ኮከብ ቈጣሪዎቹ ለንጉሡ
በአረማይክ[ሠ] ቋንቋ "ንጉሥ ሆይ፤ ለዘላለም
ንገሥ! ሕልምህን ለአገልጋዮችህ ንገረን፤
እኛም እንፈታልሃለን" አሉት።

[ሀ]2 ዕብራይስጡ *ሺናር* ይላል [ለ]4 ወይም *ከለዳውያን*
[ሐ]2 ወይም *ከለዳውያንን* እንዲሁም 4፡5 እና 10
[መ]3 ወይም *ምን እንደ ነበር*
[ሠ]4 ይህ ምዕራፍ ከዚህ ጀምሮ እስከ ም 7 ድረስ የተጻፈው
በአረማይስጥ ነው።

1፥1 2ነገ24፥1፤2ዜና 36፥6፤ኤር28፥14፤ 35፥11፤46፥2፤50፥1
1፥2 2ነገ24፥13፤2ዜና 36፥7፤ኤር27፥19-20፤ ዘካ5፥5-11
1፥3 2ነገ20፥18፤ 24፥15፤ኢሳ39፥7
1፥4 ቀ-17፤ዘፍ3 9፥6፤ ዕዝ4፥7
1፥5 ቀ-8፡10፡ 18፡19፤ አስ2፥5-6፡9
1፥6 ሕዝ14፥14፤ ዳን 2፥17፡25
1፥7 ኢሳ39፥7፤ ዳን 2፥26፡49፤3፥12፤ 4፥8፤5፥12፤10፥1
1፥8 ሕዝ4፥13-14
1፥9 ዘፍ39፥21፤ 1ነገ8፥50፤ ምሳ16፥7
1፥10 ቀ-5
1፥12 ራእ2፥10
1፥13 ቀ-16
1፥14 ራእ2፥10
1፥15 ዘፀ23፥25
1፥16 ቀ-12-13
1፥17 ኢዮ12፥13፤ ዳን2፥19፡23፡30፤5፥11፤ 7፥1፤8፥1፤ቈላ1፥9፤ያዕ 1፥5
1፥18 ቀ-5
1፥19 ዘፍ41፥46
1፥20 ዘፍ41፥8፤1ነገ 4፥30፤አስ2፥15፤ሕዝ 28፥3፤ዳን2፥13፡28፤ 4፥18፤6፥3
1፥21 2ዜና36፥22፤ ዳን6፥28፤10፥1
2፥1 ቀ-3፤ዘፍ20፥3፤ 41፥8፤አስ6፥1፤ኢዮ 33፥15፡18፤ዳን4፥5
2፥2 ቀ-10፤ዘፍ 41፥8፤ዘፀ7፥11፤ ኢሳ19፥3፤44፥25፤ኤር 27፥9፤ዳን4፥6
2፥3 ዳን4፥5
2፥4 ዕዝ4፥7፤ነህ2፥3

5ንጉሡም ለኮከብ ቈጣሪዎቹ እንዲህ ሲል
መለሰ፤ “ሕልሙንና ትርጕሙን ባትነግሩኝ
አካላችሁ እንዲቈራረጥና ቤቶቻችሁም የፍ
ርስራሽ ክምር እንዲሆኑ ወስኛለሁ 6ነገር
ግን ሕልሙንና ትርጕሙን ብትነግሩኝ፣ ስጦ
ታና ሽልማት፣ ታላቅ ክብርም ከእኔ ትቀበላላ
ችሁ፤ ሕልሙን ንገሩኝ፤ ትርጕሙንም አሳ
ውቁኝ።”
7እነርሱም እንደ ገና፣ “ንጉሥ ሕልሙን
ለአገልጋዮቹ ይንገረን፤ እኛም እንተረጕመዋ
ለን” ብለው መለሱ።
8ንጉሡም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፤
“እኔ ምን ብዬ እንደወሰንሁ ስለምታውቁ፣
ጊዜ ለማራዘም እንደምትሞክሩ ተረድቼአ
ለሁ፤ 9ሕልሙን ባትነግሩኝ፣ አንድ ቅጣት
ይጠብቃችኋል፤ ሁኔታው ይለወጣል ብላ
ችሁ በማሰብ የሚያሳስቱ ነገሮችንና ክፉ ሐሳ
ቦችን ልትነግሩኝ አሲራችኋል፤ ስለዚህ ሕል
ሙን ንገሩኝ፤ ትርጕሙንም ልትነግሩኝ
እንደምትችሉ በዚህ ዐውቃለሁ።”
10ኮከብ ቈጣሪዎቹም ለንጉሡ እንዲህ
ብለው መለሱ፤ “ንጉሡ የጠየቀውን ጥያቄ
ሊመልስ የሚችል ሰው በምድር ላይ አይ
ገኝም! ማንም ንጉሥ ምንም ያህል ታላቅና
ኀያል ቢሆን፣ እንዲህ ዐይነት ነገር ማንኛ
ውንም ጠንቋይ፣ አስማተኛ ወይም ኮከብ
ቈጣሪን ጠይቆ ዐያውቅም። 11ንጉሡ የሚ
ጠይቀው እጅግ አስቸጋሪ ነገር ነው፤ በሰዎች
መካከል ከማይኖሩት ከአማልክት በቀር
ለንጉሡ የሚገልጽለት የለም።”
12ይህም ንጉሡን እጅግ አበሳጨው፤ አስ
ቈጣውም፤ በባቢሎን ያሉ ጠቢባን ሁሉ
እንዲገደሉም አዘዘ፤ 13ጠቢባን ሁሉ እንዲ
ገደሉም ዐዋጅ ወጣ፤ ዳንኤልንና ጓደኞቹን
ፈልገው እንዲገድሉ ሰዎች ተላኩ።
14የንጉሡ ዘበኞች አለቃ አርዮክ፣ የባቢ
ሎንን ጠቢባን ለመግደል በመጣ ጊዜ፣
ዳንኤል በጥበብና በዘዴ አነጋገረው። 15የን
ጉሡን መኰንን፣ “ንጉሡ እንዲህ ዐይነት
ከባድ ዐዋጅ ያወጣው ስለ ምንድነው?” ሲል
ጠየቀው፤ አርዮክም ነገሩን ለዳንኤል ገለ
ጠለት። 16በዚህን ጊዜ፣ ዳንኤልም ገብቶ
ሕልሙን ይተረጕምለት ዘንድ ጊዜ እን
ዲሰጠው ንጉሡን ጠየቀው።
17ከዚህ በኋላ ዳንኤል ወደ ቤቱ ተመልሶ
ለጓደኞቹ ለአናንያ፣ ለሚሳኤልና ለአዛርያ
ነገሩን ገለጠላቸው። 18እርሱና ጓደኞቹ
ከቀሩት የባቢሎን ጠቢባን ጋር እንዳይገ
ደሉ፣ የሰማይ አምላክ ምሕረት ያደርግላ
ቸውና ምስጢሩንም ይገልጥላቸው ዘንድ
እንዲጸልዩ አሳሰባቸው። 19ለዳንኤልም
ምስጢሩ በሌሊት በራእይ ተገለጠለት፤
ዳንኤልም የሰማይን አምላክ አመሰገነ፤
20እንዲህም አለ፤

“ጥበብና ኀይል የእርሱ ነውና፣
የእግዚአብሔር ስም ከዘላለም እስከ
ዘላለም ይባረክ።
21ጊዜንና ወቅትን ይለውጣል፤
ነገሥታትን በዙፋን ያስቀምጣል፣
ደግሞም ያወርዳቸዋል፤
ጥበብን ለጠቢባን፣
ዕውቀትንም ለሚያስተውሉ ይሰጣል።
22የጠለቀውንና የተሰወረውን ነገር
ይገልጣል፤
በጨለማ ያለውን ያውቃል፤
ብርሃንም ከእርሱ ጋር ይኖራል።
23የአባቶቼ አምላክ ሆይ፤ አመሰግንሃለሁ፤
አከብርሃለሁም፤
ጥበብንና ኀይልን ሰጥተኸኛልና፤
ከአንተ የጠየቅነውን ነገር አሳውቀኸ
ኛል፤
የንጉሡን ሕልም አሳውቀኸናል።”

## ዳንኤል ሕልሙን ተረጐመ

24ዳንኤልም የባቢሎንን ጠቢባን እንዲ
ገድል ንጉሡ ወዳዘዘው ወደ አርዮክ ሄዶ፣
“የባቢሎንን ጠቢባን አትግደል፤ ወደ ንጉሡ
ውሰደኝ፤ እኔም ሕልሙን እተረጕምለታለሁ”
አለው።
25አርዮክም ዳንኤልን ወዲያውኑ ወደ
ንጉሡ በመውሰድ፣ “ሕልሙንና ትርጕሙን
ለንጉሡ መግለጥ የሚችል ሰው ከይሁዳ ምር
ኮኞች መካከል አግኝቻለሁ” አለው።
26ንጉሡም ብልጣሶር የተባለውን ዳንኤ
ልን፣ “ያየሁትን ሕልምና ትርጕሙን ልት
ነግረኝ ትችላለህን?” አለው።
27ዳንኤልም እንዲህ አለ፤ “አንድም ጠቢብ፣
አስማተኛ፣ ጠንቋይም ሆነ ቃላተኛ ንጉሡ
የጠየቀውን ምስጢር መግለጥ የሚችል
የለም፤ 28ነገር ግን ምስጢርን የሚገልጥ
አምላክ በሰማይ አለ፤ እርሱም በሚመጡት
ዘመናት የሚሆነውን ነገር ለንጉሥ ናቡከ
ደነፆር ገልጦአል፤ በዐልጋህ ላይ ተኝተህ ሳለ
በአእምሮህ የነበረው ሕልምና ራእይ ይህ
ነው፦
29“ንጉሥ ሆይ፤ ተኝተህ ሳለ፣ አእምሮህ
ወደፊት ሊሆን ስላለው ነገር ያሰላስል
ነበር፤ ምስጢርን ገላጭ የሆነውም ወደ ፊት
የሚሆነውን ነገር አሳየህ። 30ይህ ምስጢር
ለእኔ የተገለጠው፣ ከሰው ሁሉ ይልቅ ታላቅ
ጥበብ ስላለኝ አይደለም፤ ነገር ግን ንጉሥ
ሆይ፤ አንተ ትርጕሙን እንድታውቅና
በአእምሮህ ታሰላስለው የነበረው ነገር ምን
እንደ ሆነ ትረዳ ዘንድ ነው።

2፥5 ቍ12፤ዘፍ 41፥32፤ዕዝ6፥11፤ ዳን3፥29
2፥6 ቍ48፤ዳን 5፥7፡16
2፥9 አስ4፥11፤ኢሳ 41፥22-24
2፥10 ቍ2፡27፤ዳን 3፥8፤4፥7፤5፥8
2፥11 ዘፍ41፥38
2፥12 ቍ5፤ዳን 3፥13፡19
2፥13 ዳን1፥20፤ 5፥19
2፥17 ዳን1፥6
2፥18 ቍ23፤ዕዝ 1፥2፤ነህ1፥4፤ኢሳ 37፥4፤ኤር33፥3፤ዮና 1፥9፤ራእ11፥13
2፥19 ቍ28፤ኢሱ 22፥33፤ኢዮ 33፥15፤ ዳን1፥17
2፥20 ኢዮ9፥4፤ መዝ113፥2፤145፥ 1-2፤ኤር32፥19
2፥21 2ሳሙ14፥17፤ ኢዮ12፥19፤ መዝ 75፥6-7፤119፥34፤ ዳን4፥17፤7፥25፤ሮሜ 13፥1፤ያዕ1፥5
2፥22 ዘፍ40፥8፤ ኢዮ 12፥22፤ መዝ139፥11-12፤ ኢሳ45፥7፤ኤር 23፥24፤ዳን5፥11፤ 1ቆሮ2፥10፤ዕብ4፥13፤ ያዕ1፥17
2፥23 ዘፍ31፥5፤ ዘፀ3፥15፤ሕዝ28፥3፤ ዳን1፥17
2፥24 ቍ14
2፥25 ዘዳ21፥10፤ ዳን1፥6፤5፥13፤6፥13
2፥26 ዳን1፥7
2፥27 ቍ10፤ዘፍ 41፥8
2፥28 ዘፍ40፥8፤ 49፥1፤መዝ4፥4፤ ኤር 10፥7፤ ሕዝ28፥3፤ ዳን1፥20፤4፥5፤ 10፥14፤አሞ 4፥13፤ ማቴ24፥6፤ራእ1፥1፤ 22፥6
2፥29 ዘፍ41፥25
2፥30 ኢሳ45፥3፤ዳን 1፥17፤አሞ 4፥13

31“ንጉሥ ሆይ፤ በፊት ለፊትህ ግዙፍ
የሆነ፣ የሚያብረቀርቅና የሚያስፈራ ታላቅ
ምስል ቆሞ አየህ፤ 32የምስሉ ራስ ከንጹሕ
ወርቅ፣ ደረቱና ክንዶቹ ከብር፣ ሆዱና
ጭኖቹ ከናስ የተሠሩ ነበሩ፤ 33ቅልጥሞቹም
ከብረት፣ እግሮቹም ከፊሉ ከብረት፣ ከፊ
ሉም ከሸክላ የተሠሩ ነበሩ። 34ይህን በመ
መልከት ላይ ሳለህ፣ አንድ ድንጋይ የሰው
እጅ ሳይነካው ተፈንቅሎ ወረደ፤ ከብረ
ትና ከሸክላ የተሠሩትን የምስሉን እግሮች
መታቸው፤ አደቀቃቸውም። 35ወዲያውኑም
ብረቱ፣ ሸክላው፣ ናሱ፣ ብሩና ወርቁ ተሰባ
በሩ፤ በበጋ ወራት በዐውድማ ላይ እንደሚ
ገኝ እብቅም ሆኑ፤ ነፋስም አንዳች ሳያስ
ቀር ጠራረጋቸው፤ ምስሉን የመታው ድን
ጋይ ግን ታላቅ ተራራ ሆነ፤ ምድርንም ሞላ።
36“ሕልሙ ይህ ነበር፤ አሁን ትርጒሙን
ለንጉሥ እንናገራለን። 37ንጉሥ ሆይ፤ አንተ
የነገሥታት ንጉሥ ነህ፤ የሰማይ አምላክ መን
ግሥትንና ሥልጣንን፣ ኀይልንና ክብርን
ሰጥቶሃል፤ 38የሰው ልጆችን፣ የምድር አራ
ዊትንና የሰማይ ወፎችን በእጅህ አሳልፎ
ሰጥቶሃል፤ በየትም ቦታ ቢሆኑ፣ በሁሉም ላይ
ገዥ አድርጎሃል፤ እንግዲህ የወርቁ ራስ
አንተ ነህ።
39“ከአንተም በኋላ ከአንተ የሚያንስ ሌላ
መንግሥት ይነሣል፤ ቀጥሎም በናስ የተመሰ
ለው ሦስተኛ መንግሥት ይነሣል፤ መላውን
ምድርም ይገዛል። 40በመጨረሻም ሁሉን ነገር
እንደሚቀጠቅጥና እንደሚሰብር ብረት ብርቱ
የሆነ አራተኛ መንግሥት ይነሣል፤ ብረት
ሁሉን ሰባብሮ እንደሚያደቅ ከእርሱ በፊት
የነበሩትን መንግሥታት ሁሉ ሰባብሮ ያደ
ቃቸዋል። 41እግሮቹና ጣቶቹ ከፊል ብረትና
ከፊል ሸክላ ሆነው እንዳየህ፣ እንዲሁ የተከ
ፋፈለ መንግሥት ይሆናል፤ ነገር ግን ብረ
ትና ሸክላ ተደባልቀው እንዳየህ በከፊል
የብረት ጥንካሬ ይኖረዋል። 42የእግሮቹ ጣቶች
ከፊሉ ብረት ከፊሉ ሸክላ እንደ ሆኑ ሁሉ
ይህም መንግሥት በከፊሉ ብርቱ በከፊሉ
ደካማ ይሆናል። 43ብረትና ሸክላ ተደባልቀው
እንዳየህ ሁሉ ሕዝቡም ድብልቅ ይሆናል፤
ብረትና ሸክላ እንደማይዋሃድ ሁሉ ሕዝቡም
በአንድነት አይኖሩም።
44“በነዚያ ነገሥታት ዘመን፣ የሰማይ
አምላክ ፈጽሞ የማይፈርስና ለሌላም ሕዝብ
የማይሰጥ መንግሥት ይመሠርታል፤ እነዚ
ያን መንግሥታት ሁሉ ያደቃል፤ እስከ
መጨረሻውም ያጠፋቸዋል፤ ይህ መንግሥት
ራሱ ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል። 45የሰው
እጅ ሳይነካው ከተራራ ተፈንቅሎ የወረደውና
ብረቱን፣ ናሱን፣ ሸክላውን፣ ብሩንና ወርቁን
ያደቀቀው ድንጋይ ራእይ ትርጓሜ ይህ ነው፦
“ታላቁ አምላክ ወደ ፊት የሚሆነውን
ለንጉሡ አሳይቶታል፤ ሕልሙ እውነት ነው፤
ትርጓሜውም የታመነ ነው።”
46ከዚያም ንጉሥ ናቡከደነፆር በግንባሩ
ተደፍቶ ለዳንኤል ሰገደለት፤ አከበረውም፤
መሥዋዕትና ዕጣንም እንዲያቀርቡለት አዘዘ።
47ንጉሡም ዳንኤልን፣ “ይህን ምስጢር
ልትገልጥ ችለሃልና፣ በእውነት አምላካችሁ
የአማልክት አምላክና የነገሥታት ጌታ፣
ምስጢርንም ገላጭ ነው” አለው።
48ንጉሡም ዳንኤልን በከፍተኛ ሥልጣን
ላይ አስቀመጠው፤ እጅግ ብዙ ስጦታዎች
ንም ሰጠው፤ የመላው ባቢሎን አውራጃ ገዥ
አደረገው፤ በባቢሎን ጠቢባን ሁሉ ላይም
አለቃ አድርጎ ሾመው። 49ከዚህም በላይ
በዳንኤል አሳሳቢነት ንጉሡ ሲድራቅን፣
ሚሳቅንና አብደናጎን የባቢሎን አውራጃ
አስተዳዳሪዎች አድርጎ ሾማቸው፤ ዳንኤል
ግን በቤተ መንግሥት ተቀመጠ።

## የወርቁ ምስልና የእቶን እሳት

3 ንጉሡ ናቡከደነፆር ከፍታው ሥልሳ
ክንድ፣ ወርዱ ስድስት ክንድ የሆነ
የወርቅ ምስል አሠራ፤ በባቢሎንም አውራጃ
በዱራ ሜዳ አቆመው። 2ከዚያም መኳንንትን፣
ሹማምንትን፣ አገረገዦችን፣ አማካሪዎችን፣
የግምጃ ቤት ኀላፊዎችን፣ ዳኞችን፣ ሌሎች
የሕግ ዐዋቂዎችንና በየአውራጃው ያሉትን
ሹማምንት ሁሉ ላቆመው ምስል ምረቃ በዓል
እንዲመጡ ጠራ። 3መኳንንቱ፣ ሹማምንቱ፣
አገረገዦችን፣ አማካሪዎችን፣ የግምጃ ቤት
ኀላፊዎቹ፣ ዳኞቹ፣ ሌሎች የሕግ ዐዋቂዎ
ችና በየአውራጃው ያሉ ሹማምንት ሁሉ
ንጉሥ ናቡከደነፆር ላቆመው ምስል ምረቃ
በዓል ተሰበሰቡ፤ በምስሉም ፊት ቆሙ።
4ከዚያም ከፍ ባለ ድምፅ እንዲህ የሚል
ዐዋጅ ታወጀ፤ “ሕዝቦች ሆይ፤ መንግሥታ
ትና ልዩ ልዩ ቋንቋ የምትናገሩ ሰዎች ሁሉ፤
እንድታደርጉ የታዘዛችሁት ይህ ነው፦
5የመለከትና የእንቢልታ፣ የመሰንቆና የክራር፣
የበገናና የዋሽንት እንዲሁም የዘፈን ሁሉ
ድምፅ ስትሰሙ፣ ንጉሥ ናቡከደነፆር ላቆ
መው የወርቅ ምስል ተደፍታችሁ መስገድ
አለባችሁ፤ 6ተደፍቶ የማይሰግድ ማንም
ሰው ቢኖር፣ ወዲያውኑ በሚንበለበለው
የእሳት እቶን ውስጥ ይጣላል።”
7ስለዚህ የመለከትና የእንቢልታ፣ የመሰን
ቆና የክራር፣ የበገናና የዋሽንት፣ የዘፈንም ሁሉ
ድምፅ በሰሙ ጊዜ ወዲያውኑ ሕዝቡ ሁሉ፣
መንግሥታትና ልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ
ሰዎች፣ ንጉሥ ናቡከደነፆር ላቆመው የወርቅ
ምስል ተደፍተው ሰገዱ።

2፥31 ኢሳ25፥3-5፤ ዕን1፥7
2፥34 ቀኍ44-45፤ ኢዮ12፥19፤ 34፥24፤ መዝ2፥9፤ ኢሳ 60፥12፤ ዳን8፥25፤ዘካ4፥6
2፥35 መዝ1፥4፤ 37፥10፤ ኢሳ2፥3፤ 17፥13፤41፥15-16፤ ሚክ 4፥1፤ዘካ12፥3
2፥36 ዘፍ40፥12
2፥37 ዕዝ7፥12፤ኤር 27፥7፤ዳን 4፥26
2፥38 ኤር27፥6፤ዳን 4፥21-22፤5፥18
2፥39 ዳን7፥5
2፥40 ዳን7፥7
2፥44 ዘፍ27፥29፤ 1ሳሙ9፥20፤መዝ2፥9፤ 110፥5፤145፥13፤ ኢሳ9፥7፤ዳን 4፥34፤ 6፥26፤7፥14፥27፤ አብ 1፥21፤ ሚክ4፥7፥13፤ ሐጌ2፥22፤ ማቴ 21፥43-44፤ ሉቃ1፥ 33፤ 1ቆሮ15፥24፤ ራእ11፥15
2፥45 ዘፍ41፥25፤ ኢሳ28፥16፤ዳን8፥25፤ ራእ22፥6
2፥46 ዳን8፥17፤ ሐሥ10፥25፤14፥13
2፥47 ቀኍ22፥28፤ ዘዳ10፥17፤ዳን4፥9፥25፤ 11፥36፤1ቆሮ14፥25፤1 ጢሞ6፥15
2፥48 ቀኍ6፤2ነገ25፥ 28፤አስ8፥2፤ዳን1፥20፤ 4፥9፤5፥11፤8፥27
2፥49 ዳን1፥7፤3፥30፤ 6፥2
3፥1 ቀኍ14፤ኢሳ 46፥6፤ኤር16፥20፤ ዕን2፥19
3፥2 ቀኍ27፤ አስ 1፥1፤ዳን6፥7
3፥4 ዳን4፥1፤6፥25፤ራ እ10፥11
3፥5 ቀኍ10፥15፤ ዘፍ4፥21፤ራእ13፥12
3፥6 ቀኍ11፥15፥21፤ ኤር29፥22፤ዳን5፥19፤ 6፥7፤ማቴ13፥42፥50፤ ራእ13፥15
3፥7 ቀኍ5

8በዚህ ጊዜ አንዳንድ ኮከብ ቈጣሪዎች‹
ወደ ፊት ቀርበው አይሁድን ከሰሱ፤ 9ንጉሥ
ናቡከደነፆርንም እንዲህ አሉት፤ “ንጉሥ
ሆይ፤ ለዘላለም ንገሥ! 10ንጉሥ ሆይ፤
አንተ እንዲህ ብለህ ዐዋጅ አውጥተህ
ነበር፤ የመለከትና የእንቢልታ፣ የመሰንቆና
የክራር፣ የበገናና የዋሽንት፣ የዘፈንም
ድምፅ የሰማ ሁሉ ለወርቁ ምስል ተደፍቶ
መስገድ አለበት፤ 11ማንም ተደፍቶ ለወርቁ
ምስል ባይሰግድ በሚንበለበለው የእሳት
እቶን ውስጥ ይጣላል። 12ነገር ግን ንጉሥ
ሆይ፤ በባቢሎን አውራጃ አስተዳዳሪዎች
አድርገህ የሾምሃቸው ሲድራቅ፣ ሚሳቅና
አብደናጎ የሚባሉት አንዳንድ አይሁድ ትእዛ
ዝህን አይቀበሉም፤ አማልክትህን አያገለግሉም፤
አንተም ላቆምኸው የወርቅ ምስል አይሰግ
ዱም።”
13ንጉሥ ናቡከደነፆር በታላቅ ቍጣ ሲድ
ራቅን፣ ሚሳቅንና አብደናጎን አስጠራቸው፤
እነዚህንም ሰዎች በንጉሡ ፊት አቀረቧቸው፤
14ናቡከደነፆርም እንዲህ አላቸው፤ “ሲድራቅ፣
ሚሳቅና አብደናጎ ሆይ፤ እኔ ላቆምሁት ምስል
አለመስገዳችሁ፣ አማልክቴንም አለማገልገ
ላችሁ እውነት ነው? 15አሁንም ቢሆን የመ
ለከቱንና የእምቢልታውን፣ የመሰንቆውንና
የክራሩን፣ የበገናውንና የዋሽንቱን፣ የዘፈ
ኑንም ሁሉ ድምፅ ስትሰሙ፣ እኔ ላቆምሁት
የወርቅ ምስል ተደፍታችሁ ለመስገድ ዝግጁ
ከሆናችሁ መልካም! ባትሰግዱለት ግን ወዲያ
ውኑ ወደሚንበለበለው የእቶን እሳት ውስጥ
ትጣላላችሁ፤ ታዲያ ከእጄ ሊያድናችሁ የሚችል
አምላክ ማን ነው?”
16ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብደናጎ ለንጉሡ
እንዲህ ብለው መለሱ፤ “ናቡከደነፆር ሆይ፤
በዚህ ጕዳይ ላይ ስለ ራሳችን መልስ መስጠት
አያስፈልገንም። 17ንጉሥ ሆይ፤ በሚንበለበ
ለው የእቶን እሳት ውስጥ ብንጣል፣ የምናመ
ልከው አምላክ ሊያድነን ይችላል፤ ከእጅህም
ያድነናል። 18ነገር ግን ንጉሥ ሆይ፤ ባያድነንም
እንኳ፤ አማልክትህን እንደማናገለግል፣ ላቆምኸ
ውም የወርቅ ምስል እንደማንሰግድ ዕወቅ።”
19ከዚያም ናቡከደነፆር በሲድራቅ፣ በሚ
ሳቅና በአብደናጎ እጅግ ተቈጣ፣ ፊቱም
ተለወጠባቸው፤ የእቶኑ እሳትም ቀደም ሲል
ከነበረው ሰባት ዕጥፍ ተደርጎ እንዲነድ
አዘዘ፤ 20ከሰራዊቱም ብርቱ የሆኑትን
ጥቂት ወታደሮች፣ ሲድራቅን፣ ሚሳቅንና አብ
ደናጎን አስረው ወደሚንበለበለው የእቶን እሳት
ውስጥ እንዲጥሏቸው አዘዘ። 21እነርሱም
መጐናጸፊያቸውን፣ ሱሪያቸውን፣ የራስ ጥምጥ
ማቸውንና ሌሎች ልብሶቻቸውን እንደ
ለበሱ ታስረው በሚንበለበለው የእቶን እሳት
ውስጥ ተጣሉ። 22የንጉሡ ትእዛዝ አስቸ
ኳይ ስለነበረና የእቶኑም እሳት እጅግ ስለ
ነደደ፤ የእሳቱ ወላፈን ሲድራቅን፣ ሚሳቅ
ንና አብደናጎን ወስደው የጣሏቸውን ወታ
ደሮች ገደላቸው። 23ሦስቱ ሰዎች ግን ተጠ
ፍረው እንደ ታሰሩ በሚንበለበለው የእቶን
እሳት ውስጥ ወደቁ።
24ከዚህ በኋላ ንጉሥ ናቡከደነፆር በአድና
ቆት ከተቀመጠበት ዘሎ በመነሣት አማካሪዎ
ቹን “አስረን በእሳት ውስጥ የጣልናቸው ሰዎች
ሦስት አልነበሩምን?” ሲል ጠየቀ።
እነርሱም፣ “ንጉሥ ሆይ፤ እውነት ነው”
አሉ።
25እርሱም፣ “እነሆ፤ ያልታሰሩና ያልተጎዱ
አራት ሰዎች በእሳቱ ውስጥ ሲመላለሱ
አያለሁ፤ አራተኛውም የአማልክትን ልጅ
ይመስላል” አላቸው።
26ናቡከደነፆርም ወደሚነደው የእቶን
እሳት በር ቀረብ ብሎ ከፍ ባለ ድምፅ፣
“እናንተ የልዑል አምላክ አገልጋዮች ሲድራቅ፣
ሚሳቅና አብድናጎ፤ ኑ ውጡ! ወደዚህ ኑ!”
አላቸው።
ስለዚህ ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጎ
ከእሳቱ ወጡ፤ 27መኳንንቱ፣ ሹማምንቱ፣
አገረገዦቹና የቤተ መንግሥት አማካሪዎ
ችም በዙሪያቸው ተሰበሰቡ፤ እነርሱም እሳቱ
ሰውነታቸውን እንዳልጎዳ፣ ከራሳቸውም ጠጕር
አንዲቷ እንኳ እንዳልተቃጠለች አዩ፤ የመጐ
ናጸፊያቸው መልክ አልተለወጠም፤ የእሳትም
ሽታ በላያቸው አልነበረም።
28ከዚያም ናቡከደነፆር እንዲህ አለ፤
“መልአኩን ልኮ አገልጋዮቹን ያዳነ፣ የሲ
ድራቅ፣ የሚሳቅና የአብደናጎ አምላክ ይባ
ረክ፤ በእርሱ በመታመን የንጉሡን ትእዛዝ
ጥሰው፣ ከአምላካቸው በቀር ሌላ አምላክ ለማ
ገልገልም ሆነ ለእርሱ ለመስገድ ፈቃደኛ
ባለ መሆን ሕይወታቸውን አሳልፈው ሰጥ
ተዋልና። 29ስለዚህ እንደዚህ የሚያድን
ሌላ አምላክ የለምና በሲድራቅ፣ በሚሳቅና
በአብደናጎ አምላክ ላይ ማናቸውንም ቃል
የሚናገሩ ሕዝቦችም ሆኑ ልዩ ልዩ ቋንቋ
የሚናገሩ ሁሉ ይቈራረጣሉ፤ ቤቶቻ
ቸውም የፍርስራሽ ክምር ይሆናሉ ብዬ
አዝዣለሁ።”
30ከዚያም ንጉሡ ሲድራቅን፣ ሚሳቅንና
አብደናጎን በባቢሎን አውራጃ ላይ ሾማቸው።

## ናቡከደነፆር በሕልሙ ዛፍ አየ

4 ከንጉሥ ናቡከደነፆር፣ በምድር ሁሉ
ለሚኖሩ ሕዝቦች፣ መንግሥታትና
ልዩ ልዩ ቋንቋዎችን ለሚናገሩ ሰዎች ሁሉ፤

3፥8 ኢሳ19፥3፤ ዳን2፥10
3፥9 ነህ2፥3፤ዳን 5፥10፤6፥6
3፥10 ቍ4-6፤ ዳን6፥12
3፥12 አስ3፥3፤ ዳን2፥49፤6፥13
3፥13 ዳን2፥12
3፥14 ቍ1፤ኢሳ 46፥1፤ኤር50፥2
3፥15 2ዜና32፥15፤ ኢሳ36፥18-20
3፥16 ዳን1፥7
3፥17 ዘፍ48፥16፤ ኢ ዮ5፥19፤መዝ 18፥48፤27፥1-2፤ኤር 1፥8፤ዳን6፥20
3፥18 ቍ28፤ዘፀ 1፥17፤ኢሱ24፥15
3፥19 ዘሌ26፥18-28
3፥20 ዳን1፥7
3፥22 ዳን1፥7
3፥26 ዳን4፥2፡34
3፥27 ቍ2፤መዝ 91፥3-11፤ኢሳ43፥2፤ ዳን6፥7፡23፤ዕብ 11፥ 32-34
3፥28 ቍ18፤ዘዳ 31፥20፤ኢዮ13፥15፤ መዝ26፥1፤34፥7፤84፥1 2፤97፥10፤ ዳን 6፥22፤ሐሥ5፥19፤ 12፥11
3፥29 ዕዝ6፥11፤ ዳን6፥26፡ዕ27
3፥30 ዳን2፥49
4፥1 ዳን3፥4፤6፥25

‹8 ወይም *ከላዳውያን*

ሰላም ይብዛላችሁ!
2ልዑል አምላክ ያደረገልኝን ታምራዊ ምል
ክቶችንና ድንቅ ሥራዎች ስነግራችሁ እጅግ
ደስ እያለኝ ነው።

3ምልክቱ እንዴት ታላቅ ነው!
ድንቁስ እንዴት ብርቱ ነው!
መንግሥቱ የዘላለም መንግሥት ነው፤
ግዛቱም ከትውልድ እስከ ትውልድ
ይኖራል።

4እኔ ናቡከደነፆር በቤቴ ደልቶኝ በቤተ
መንግሥቴም ተመችቶኝ እኖር ነበር፤ 5አንድ
ያስፈራኝ ሕልም አየሁ፤ በዐልጋዬ ላይ ተኝቼ
ሳለሁ፣ ወደ አእምሮዬ የመጡት ምስሎችና
ራእዮች አስደነገጡኝ። 6ስለዚህ የባቢሎን
ጠቢባን ሁሉ ወደ እኔ መጥተው ሕልሜን
እንዲተረጒሙልኝ አዘዝሁ። 7ጠንቋዮቹ፣
አስማተኞቹ፣ ኮከብ ቈጣሪዎቹና[ሰ] መተተ
ኞቹ በመጡ ጊዜ ሕልሙን ነገርኋቸው፤
ነገር ግን ሊተረጒሙልኝ አልቻሉም። 8በመ
ጨረሻም በአምላኬ ስም ብልጣሶር ተብሎ
የተጠራውና የቅዱሳን አማልክት መንፈስ
ያለበት ዳንኤል ገብቶ በፊቴ ቆመ፤ ሕልሜ
ንም ነገርሁት።
9እኔም እንዲህ አልሁት፤ "የጠቢባን አለቃ
ብልጣሶር ሆይ፤ የቅዱሳን አማልክት መን
ፈስ በአንተ ውስጥ እንዳለ ዐውቃለሁ፤
ምንም ዐይነት ምስጢር አያስቸግርህም፤
ያየሁት ሕልም እነሆ፤ ተርጒምልኝ። 10በዐ
ልጋዬ ላይ ተኝቼ ሳለሁ ያየሁት ራእይ ይህ
ነው፦ እነሆ በፊቴ በምድር መካከል ቁመቱ
እጅግ ረጅም የሆነ ዛፍ ቆሞ ተመለከትሁ።
11ዛፉም እጅግ አደገ፤ ጠነከረም፤ ጫፉም ሰማይ
ደረሰ፤ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስም ይታይ
ነበር። 12ቅጠሎቹ ያማሩ፣ ፍሬዎቹ የተን
ዠረገጉ ነበሩ፤ በላዩም ለሁሉ የሚሆን ምግብ
ነበረበት። የምድር አራዊት ከጥላው በታች
ያርፉ ነበር፤ በቅርንጫፎቹም ላይ የሰማይ
ወፎች ይኖሩ ነበር፤ ፍጥረትም ሁሉ ከእ
ርሱ ይመገብ ነበር።
13"በዐልጋዬ ላይ ተኝቼ ሳለሁ ባየሁት
ራእይ አንድ ቅዱስ መልእክተኛ[ሸ] ከሰማይ
ሲወርድ አየሁ። 14እርሱም ድምፁን ከፍ
አድርጎ እንዲህ አለ፤ 'ዛፉን ቍረጡ፤
ቅርንጫፎቹን ጨፍጭፉ፤ ቅጠሎቹን አራ
ግፉ፤ ፍሬውንም በትኑ፤ ከሥሩ ያሉት
እንስሶች፣ በቅርንጫፎቹም ላይ ያሉት ወፎች
ይሽሹ። 15ነገር ግን ጕቶውና ሥሩ በሜዳው
ሣር ላይ በብረትና በናስ ታስሮ በመሬት ውስጥ
ይቈይ።
" 'በሰማይ ጠል ይረስርስ፤ በጥሻም ውስጥ
ከአራዊት ጋር ይኑር። 16አእምሮው ከሰው
አእምሮ ይለወጥ፤ የእንስሳም አእምሮ ይሰጠው፤

4፥2 መዝ74፥9፤ ዳን3፥26
4፥3 መዝ105፥27፤ ዳን2፥44፤6፥27
4፥4 መዝ30፥6፤ ኢሳ32፥9
4፥5 ቍ19፤ዘፍ 41፥8፤ኢዮ3፥26፤ መዝ4፥4፤ዳን2፥1፡3፡2 8፤5፥6
4፥6 ዳን2፥2
4፥7 ዘፍ41፥8፤ኢ ሳ44፥25፤ዳን2፥2፡10
4፥8 ዘፍ41፥38፤ ዳን1፥7
4፥9 ዳን2፥48፤ 5፥11-12
4፥10 ቍ5፤መዝ 4፥4፤ሕዝ31፥3-4
4፥11 ሕዝ19፥11፤ 31፥5
4፥12 ሕዝ17፥23፤ ማቴ13፥32
4፥13 ቍ10፡23፤ ዘዳ33፥2፤ዳን7፥1
4፥14 አዮ24፥20 ፤ሕ ዝ31፥12፤ማቴ3፥10
4፥16 ቍ23፥32
4፥17 ቍ2፡25፤ መዝ 83፥18፤ 103፥19፤ኤር27፥5-7፤ ዳን2፥21፤ 5፥18-21፤ 11፥21፤ ሮሜ13፥1፤ማቴ 23፥12
4፥18 ቍ7-9፤ ዘፍ41፥8፡ 15፡38፤ ዳን 1፥20፤5፥8፡15
4፥19 ቍ5፤ዘፍ 40፥12፤41፥8፤ዳን7፥ 15፡28፤8፥27፤ 10፥16-17
4፥21 ሕዝ31፥6
4፥22 2ሳሙ12፥7፤ ኤር27፥7፤ዳን5፥ 18-19
4፥23 ቍ13፤ሕዝ 31፥34፤ዳን5፥21፤ 8፥13
4፥24 ኢዮ40፥12፤ መዝ107፥40፤ኤር 40፥2
4፥25 ቍ17፤አዮ 24፥8፤ኤር27፥5፤ዳን 2፥47፤5፥21
4፥26 ቍ15፤ዳን 2፥37
4፥27 ዘዳ24፥13፤ 1ነገ21፥29፤መዝ41፥3፤ ምሳ28፥13፤ኢሳ 55፥6-7፤ ኤር29፥7፤ሕዝ18፥22

ሰባት ዓመትም ይለፍበት።
17" 'ውሳኔው በመልእክተኞች ተገልጾአል፤
ፍርዱም በቅዱሳኑ ተነግሮአል፤ ይኸውም፣
ልዑል በሰዎች መንግሥታት ሁሉ ላይ እን
ደሚገዛና እነዚህንም መንግሥታት ለወደ
ደው እንደሚሰጥ፣ ከሰዎችም የተናቁትን በላ
ያቸው እንደሚሾም፣ ሕያዋን ሁሉ ያውቁ
ዘንድ ነው።'
18"እኔ ናቡከደነፆር ያየሁት ሕልም ይህ
ነው፤ አሁንም ብልጣሶር ሆይ፤ በመንግሥቴ
ካሉ ጠቢባን ሁሉ አንዳቸውም ሊተረጒሙ
ልኝ ስላልቻሉ፣ ምን ማለት እንደሆነ ንገ
ረኝ። አንተ የአማልክት መንፈስ በውስጥህ
ስላለ ልትተረጒምልኝ ትችላለህ።

## ዳንኤል ሕልሙን ተረጐመ

19ከዚያም ብልጣሶር የተባለው ዳንኤል
ለጥቂት ጊዜ በጣም ታወከ፤ ሐሳቡም አስ
ደነገጠው። ንጉሡም፣ "ብልጣሶር ሆይ፤ ሕል
ሙም ሆነ ትርጒሙ አያስደንግጥህ" አለው።
ብልጣሶርም እንዲህ ብሎ መለሰ፤ "ሕልሙ
ለሚጠሉህ ይሁን፤ ትርጒሙም ለጠላቶችህ!
20እጅግ አድጎና ጠንክሮ ያየኸው ዛፍ፣
ጫፉም እስከ ሰማይ ደርሶ በምድር ሁሉ
የሚታየው፣ 21ቅጠሎቹ የሚያምሩ፣ ፍሬ
ውም ተንዠርግጎ ለሁሉ ምግብ የሆነው፣
የዱር አራዊት መጠለያ የሆነውና በቅርን
ጫፎቹ ላይ ለሰማይ ወፎች ጎጆ መሥሪያ
ያለው፣ 22ንጉሥ ሆይ፤ ያ ዛፍ አንተ ነህ፤
ታላቅና ብርቱ ሆንህ፤ ታላቅነትህ አድጎ
እስከ ሰማይ ደረሰ፤ ግዛትህም እስከ
ምድር ዳርቻ ተንሰራፋ።
23"ንጉሥ ሆይ፤ አንተ፣ 'ዛፉን ቍረጡ፣
አጥፉትም፤ በብረትና በናስ የታሰረውን
ጕቶና ሥሩን በሜዳው ሣር ላይ በብረትና
በናስ ታስሮ በመሬት ውስጥ ይቈይ፤ በሰ
ማይ ጠል ይረስርስ፤ እንደ ዱር አራዊትም
ይኑር፤ ሰባት ዓመትም ይለፍበት' እያለ
ከሰማይ የወረደውን ቅዱሱን መልእክተኛ
አየህ።
24"ንጉሥ ሆይ፤ ትርጒሙ ይህ ነው፤ ልዑሉ
በንጉሡ በጌታዬ ላይ ያወጣው ዐዋጅ
ይህ ነው፤ 25ከሕዝብ ተለይተህ ትሰደዳለህ፤
ከዱር አራዊትም ጋር ትኖራለህ። እንደ ኮብት
ሣር ትበላለህ፤ በሰማይ ጠልም ትረሰርሳለህ፤
ልዑሉ በሰዎች መንግሥታት ሁሉ ላይ
እንደሚገዛና እነዚህንም መንግሥታት ለወ
ደደው እንደሚሰጥ እስክታውቅ ድረስ ሰባት
ዓመታት ያልፉብሃል። 26የዛፉ ጕቶ ከነ
ሥሩ እንዲቀር መታዘዙ፣ ሥልጣን ከሰማይ
መሆኑን ስታውቅ መንግሥትህ እንደሚመለ
ስልህ ያመለክታል። 27ስለዚህ ንጉሥ ሆይ፤

[ሰ]7 ወይም ከለዳውያን [ሸ]13 ወይም ጕበኛ፤ እንዲሁም፡ ቍ17 እና 23

ምክሬን ስማ፤ ኀጢአት መሥራትን ትተህ
ትክክለኛ የሆነውን አድርግ፤ ክፋትን ትተህ
ለተጨቈኑት ቸርነትን አድርግ፤ ምናልባት
በሰላም የምትኖርበት ዘመን ይራዘምልህ
ይሆናል።"

## ሕልሙ ተፈጸመ

28 ይህ ሁሉ በንጉሡ በናቡከደነፆር ላይ
ደረሰ፤ 29 ከዐሥራ ሁለት ወራት በኋላ፣ ንጉሡ
በባቢሎን ቤተ መንግሥት ሰገነት ላይ ሲመ
ላለስ ሳለ፣ 30 "በብርቱ ኀይሌ፣ ለገናናው
ክብሬ ንጉሣዊ መኖሪያ ትሆን ዘንድ ያሠ
ራኋት ታላቂቷ ባቢሎን ይህች አይደለችምን?"
አለ።

31 ንግግሩን ገና ከአፉ ሳይጨርስ፣ እንዲህ
የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ፤ "ንጉሥ ናቡ
ከደነፆር ሆይ፤ ስለ አንተ የታወጀው ይህ
ነው፤ መንግሥትህ ከአንተ ተወስዶአል፤
32 ከሕዝብ መካከል ትሰደዳለህ፤ ከዱር አራ
ዊት ጋርም ትኖራለህ፤ እንደ ከብት ሣር
ትበላለህ፤ ልዑሉ በሰዎች መንግሥት ሁሉ
ላይ ሙሉ ሥልጣን እንዳለውና እነዚህንም
መንግሥታት ለወደደው እንደሚሰጥ እስክ
ታውቅ ድረስ ሰባት ዓመት ያልፋል።"

33 ወዲያውኑ በናቡከደነፆር ላይ የተነገ
ረው ሁሉ ተፈጸመ፤ ከሕዝቡ መካከል ተሰ
ደደ፤ እንደ ከብትም ሣር በላ። የራስ ጠጕሩ
እንደ ንስር ላባና፣ ጥፍሮቹም እንደ ወፍ
ጥፍሮች እስኪያድጉ ድረስ ሰውነቱ በሰማይ
ጠል ረሰረሰ።

34 ጊዜው ከተፈጸመ በኋላ፣ እኔ ናቡከደነ
ፆር ዐይኖቼን ወደ ሰማይ አነሣሁ፤ አእም
ሮዬም ተመለሰልኝ፤ ልዑሉንም ባረክሁት፤
ለዘላለምም የሚኖረውን ወደስሁት፤ ክብር
ንም ሰጠሁት።

ግዛቱ የዘላለም ግዛት ነው፤
  መንግሥቱም ከትውልድ እስከ
    ትውልድ ይኖራል።
35 የምድር ሕዝቦች ሁሉ፣
  እንደ ኢምንት ይቈጠራሉ፤
በሰማይ ኀይላት፣
  በምድርም ሕዝቦች ላይ፣
የወደደውን ያደርጋል፤
  እጁን መከልከል የሚችል የለም፤
  'ምን ታደርጋለህ?' ብሎ የሚጠይቀውም
    የለም።

36 አእምሮዬ እንደ ተመለሰልኝ፣ ወዲ
ያው ለመንግሥቴ ክብር፣ ግርማዊነቴና
ሞገሴ ተመለሱልኝ፤ አማካሪዎቼና መኳንንቴ
ፈለጉኝ፤ ወደ ዙፋኔም ተመለስሁ፤ ከቀ
ድሞውም የበለጠ ታላቅ ሆንሁ። 37 የሰማይ
አምላክ የሚያደርገው ሁሉ ትክክል፣ መንገዱ
ቹም ሁሉ ጽድቅ ስለ ሆኑ፣ አሁንም እኔ
ናቡከደነፆር እርሱን አወድሰዋለሁ፤ ከፍ
ከፍ አደርገዋለሁ፤ አከብረዋለሁም፤ እርሱም
በትዕቢት የሚመላለሱትን ማዋረድ ይችላል።

## በግድግዳው ላይ የታየው ጽሕፈት

5 ንጉሥ ቤልሻዛር ለሺህ መኳንንቱ ታላቅ
ግብዣ አደረገ፤ በሺሁም ፊት የወ
ይን ጠጅ ይጠጣ ነበር። 2 ቤልሻዛር የወ
ይን ጠጁን እየጠጣ ሳለ፣ አባቱ[ቀ] ናቡከደነ
ፆር ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ያመጣቸ
ውን የወርቅና የብር መጠጫዎችን እር
ሱና መኳንንቱ፣ ሚስቶቹና ቍባቶቹ ይጠ
ጡባቸው ዘንድ እንዲያመጡለት አዘዘ። 3 ከዚ
ያም በኢየሩሳሌም ከነበረው ከእግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ የተወሰዱትን የወርቅ መጠ
ጫዎች አመጡ፤ ንጉሡና መኳንንቱ፣ ሚስቶ
ቹና ቍባቶቹም ጠጡባቸው። 4 የወይን ጠጁንም
እየጠጡ የወርቅና የብር፣ የናስ፣ የብረት፣
የዕንጨትና የድንጋይ አማልክትን አመሰገኑ።

5 በድንገትም የሰው እጅ ጣቶች ታዩ፤
በቤተ መንግሥቱ ውስጥ በመቅረዙ ትይዩ
ባለው ግድግዳ ልስን ላይ ጻፉ፤ ንጉሡም
ይጽፍ የነበረውን እጅ አየ፤ 6 በዚያን ጊዜ
ንጉሡ በድንጋጤ ተሞላ፤ ፊቱም ተለዋወጠ፤
እጆቹና እግሮቹ ከዱት፤ ጕልበቶቹም ተብ
ረከረኩ።

7 ንጉሡም ድምፁን ከፍ አድርጎ አስማተ
ኞችን፣ ኮከብ ቈጣሪዎችንና[በ] መተተኞችን
እንዲያስገቡለት አዘዘ፤ ለባቢሎናውያኑ ጠቢ
ባን እንዲህ አላቸው፤ "ይህን ጽሕፈት አን
ብቦ ትርጕሙን የሚነግረኝን ሐምራዊ መጐ
ናጸፊያ አለብሰዋለሁ፤ የወርቅ ሐብልም በዐ
ንገቱ ላይ አጠልቅለታለሁ፤ በመንግሥቴም
ላይ ሦስተኛ ገዥ ይሆናል።"

8 ከዚያም የንጉሡ ጠቢባን ሁሉ ገቡ፤ ነገር
ግን ጽሕፈቱን ሊያነብም ሆነ ትርጕሙ
ምን እንደ ሆነ ለንጉሡ ሊነግር የሚችል
ማንም አልነበረም። 9 ንጉሥ ቤልሻዛር ከፊት
ይልቅ ፈራ፤ ፊቱም እጅግ ተለወጠ፤ መኳንን
ቱም ግራ ገብቶአቸው ተደናገጡ።

10 ንግሥቲቱም[ተ] የንጉሡንና የመኳንንቱን
ድምፅ ሰምታ ወደ ግብዣው አዳራሽ ገባች፤
እንዲህም አለች፤ "ንጉሥ ሆይ፤ ለዘላለም
ንገሥ፤ አትደንግጥ፤ ፊትህም አይለዋወጥ!
11 በመንግሥትህ ውስጥ የቅዱሳን አማል
ክት መንፈስ ያለበት አንድ ሰው አለ፤ ይህ
ሰው በአባትህ ዘመን እንደ አማልክት ጥበብና
ማስተዋል፣ ዕውቀትም የሞላበት ሆኖ ተገ
ኝቶአል፤ አባትህ ንጉሥ ናቡከደነፆርም
የጠንቋዮች፣ የአስማተኞች፣ የኮከብ ቈጣሪ

4፥28 ዘኍ23፥19
4፥30 ኢሳ10፥13፤ 13፥19፤37፥24-25፤ ዳን5፥20፤ዕን1፥11፤ 2፥4
4፥31 2ሳሙ 22፥28፤ ዳን5፥20
4፥32 ኢዮ9፥12
4፥33 ኢዮ24፥8፤ ዳን5፥20
4፥34 ኢዮ12፥20፤ መዝ145፥13፤ኢሳ 37፥16፤ዳን2፥44፤ 5፥21፤6፥26፤12፥7፤ ሉቃ1፥33
4፥35 ዘዳ21፥8፤ 32፥39፤ኢዮ9፥4፤ መዝ115፥3፤135፥6፤ኢሳ14፥24፡27፤ 40፥17፤45፥9፤ ዳን5፥21፤ ዮና1፥14፤ሮሜ9፥20
4፥36 ምሳ22፥4፤ዳን 5፥18
4፥37 ዘፀ15፥2፤ ዘዳ 32፥4፤ኢዮ31፥4፤ 40፥11-12፤መዝ 18፥27፤33፥4-5፤ 34፥3፤119፥21፤ ኢሳ13፥11፤ ዳን5፥ 23፤ ማቴ23፥12
5፥1 ቆላ30፤ 1ነገ 3፥15፤ኤር50፥35፤ ዳን7፥1፤8፥1
5፥2 2ነገ24፥13፤ 2ዜና36፥10፤አስ1፥7፤2፥14፤ኢሳ21፥5፤ ኤር52፥19፤ዳን1፥2
5፥4 መሳ16፥24፤ አስ1፥10፤መዝ135፥ 15-18፤ ዕን2፥19፤ ራእ9፥20
5፥6 ኢዮ4፥15፤መዝ 22፥14፤ኢሳ7፥2፤ሕዝ 7፥17፤ዳን4፥5
5፥7 ዘፍ41፥8፡42፤ አስ10፥3፤ኢሳ19፥3፤ 44፥25፤ኤር50፥35፤ ዳን2፥5-6፡48፤4፥6-7
5፥8 ዘፀ8፥18፤ ዳን 2፥10፤4፥18
5፥9 መዝ48፥5፤ ኢሳ 21፥4
5፥10 ኣህ2፥3፤ ዳን 3፥9
5፥11 ቆላ14፤ ዘፍ41፥38፤ዳን1፥17፤2

[ቀ]2 ወይም *አያት፤* ወይም *ቀዳሚ ዘር* እንዲሁም ቍ11፥13 እና 18
[በ]7 ወይም *ከለዳውያን፤* እንዲሁም ቍ፡11 [ተ]10 ወይም *የንጉሡ እናት*

ዎችና የመተተኞች አለቃ አደረገው። [12]ንጉሡ
ብልጣሶር ብሎ የጠራው ይህ ዳንኤል መል
ካም መንፈስ፣ ዕውቀትና ማስተዋል ያለው
ሆኖ ተገኘ፤ ሕልምን የመተርጐም፣ እንቆ
ቅልሽን የመፍታትና የተሰወረውን የመግ
ለጥ ልዩ ችሎታም ነበረው። ስለዚህ ዳን
ኤልን አስጠራ፤ እርሱም የጽሕፈቱን ትር
ጕም ይነግርሃል።”

[13]ዳንኤልንም ወደ ንጉሡ አቀረቡት፤ ንጉሡም
እንዲህ አለው፤ “ንጉሡ አባቴ ከይሁዳ ማርኮ
ካመጣቸው መካከል አንዱ የሆንኸው ዳን
ኤል አንተ ነህን? [14]የአማልክት መንፈስ በው
ስጥህ እንዳለ፣ ዕውቀት፣ ማስተዋልና ልዩ
ጥበብ እንዳለህ ሰምቻለሁ፤ [15]ይህን ጽሕ
ፈት አንብበው ትርጕሙ ምን እንደ ሆነ
ይነግሩኝ ዘንድ ጠቢባንና አስማተኞች በፊቴ
ቀርበው ነበር፤ ነገር ግን ሊገልጡት አልቻ
ሉም። [16]አንተ ግን መተርጐምና አስቸጋሪ
የሆነውን ነገር መፍታት እንደምትችል
ሰምቻለሁ። ይህን ጽሕፈት አን ብበህ ትር
ጕሙን ብትነግረኝ፣ ሐምራዊ መጐናጸፊያ
ያለብሱሃል፤ የወርቅ ሐብል በዐንገትህ
ያጠልቁልሃል፤ የመንግሥት ሦስተኛ ገዥም
ትደረጋለህ።”

[17]ዳንኤልም ለንጉሡ እንዲህ ሲል መለሰ፤
“ስጦታዎችህን ለራስህ አድርግ፤ ሽልማቶ
ችህንም ለሌላ ሰው ስጥ፤ ይሁን እንጂ ጽሕ
ፈቱን ለንጉሡ አነባለሁ፤ ትርጕሙ ምን
እንደሆነም እነግረዋለሁ።

[18]“ንጉሥ ሆይ፤ ልዑል አምላክ ለአባትህ
ለናቡከደነፆር ገናናነትንና ታላቅነትን፣ ክብ
ርንና ግርማን ሰጠው። [19]ከሰጠው ታላቅ
ሥልጣን የተነሣ ሕዝቦችና መንግሥታት፣
ልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎችም ሁሉ
ተንቀጠቀጡለት፤ ፈሩትም። ንጉሡም ሊገ
ድል የፈለገውን ይገድል፣ ሊያድን የፈለገ
ውን ያድን፣ ሊሾም የፈለገውን ይሾም፣ ሊያ
ዋርድ የፈለገውንም ያዋርድ ነበር። [20]ነገር
ግን ልቡ በትዕቢት በጸናና በእብሪት በተ
ሞላ ጊዜ ከዙፋኑ ተወገደ፤ ክብሩም ተገ
ፈፈ። [21]ከሰው መካከል ተሰደደ፤ የእንስሳም
አእምሮ ተሰጠው፤ ከዱር አህዮች ጋር ኖረ፤
እንደ ከብትም ሣር በላ፤ ልዑል አምላክ
በሰዎች መንግሥታት ላይ እንደሚገዛና
እነርሱንም ለወደደው እንደሚሰጥ እስኪ
ያውቅ ድረስ ሰውነቱ በሰማይ ጠል ረሰ
ረሰ።

[22]“ቤልሻዛር ሆይ፤ አንተ ልጁ[ቾ] ሆነህ
ይህን ሁሉ ብታውቅም፣ ራስህን ዝቅ አላ
ደረግህም፤ [23]ይልቁንም በሰማይ አምላክ ላይ
በመታበይ፣ ራስህን ከፍ ከፍ አደረግህ፤
የመቅደሱን መጠጫዎች አስመጣህ፤ አንተና

÷22፥47-48
5፥12 ቍ14-16፤ ዘኍ12፥8፤ሕዝ28፥3፤ ዳን1፥7፤6፥3
5፥13 አስ2፥5-6፤ዳን 6፥13
5፥14 ዘፍ41፥38፤ ዳን2፥22
5፥15 ዳን4፥18
5፥16 ዘፍ41፥15፡ 42፤አስ5፥3፤ዳን2፥6
5፥17 2ነገ5፥16
5፥18 ኤር27፥7፤ 28፥14፤ዳን2፥37-38፤ 4፥36
5፥19 ዳን2፥12-13፤3፥6፤4፥22
5፥20 ኢዮ40፥12፤ ኢሳ14፥13-15፤ ኤር13፥18፤43፥10፤ ሕዝ31፥10-11፤ ዳን4፥30፡31፤8፥8
5፥21 ሕዝ17፥24፤ ዳን4፥16-17፡35
5፥22 ዘፀ10፥3
5፥23 ኢዮ12፥10፤ 31፥4፤መዝ115፥ 4-8፤ኢሳ13፥11፤ 14፥13፤ ኤር10፥23፤44፥9፤ 48፥26፤50፥29፤ ዕን2፥19 ፤ሐሥ17፥28፤ ራእ 9፥20
5፥26 ኢሳ13፥6፤ ኤር27፥7
5፥27 ኢዮ6፥2፤መዝ 62፥9
5፥28 ኢሳ13፥17፤ ኤር27፥7፤50፥41-43፤ዳን6፥28
5፥29 ዘፍ41፥42፤ ዳን2፥6
5፥30 ቍ1፤ኢሳ 2 1፥ 9፤ኤር50፥35፤51፥31
5፥31 ኢሳ13፥3፤ ኤር50፥41፤ዳን6፥1፤9፥ 1፤11፥1
6፥1 አስ1፥1፤ዳን 5፥31
6፥2 ዕዝ4፥22፤ ዳን2፥48-48
6፥3 ዘፍ41፥41፤አስ 10፥3፤ዳን1፥20፤5፥12-14
6፥4 ኤር20፥10
6፥5 ሐሥ24፥13-16

መኳንንትህ፣ ሚስቶችህና ቁባቶችህም የወ
ይን ጠጅ ጠጣችሁባቸው፤ ማየት፣ መስማት፣
ማስተዋልም የማይችሉትን የብርና የወርቅ፣
የናስና የብረት፣ የዕንጨትና የድንጋይ አማ
ልክትን አመሰገንህ። ሕይወትህንና መንገ
ድህን ሁሉ በእጁ የያዘውን አምላክላክ ግን
አላከበርህም። [24]ስለዚህ እርሱ ጽሕፈቱን የጻ
ፈውን እጅ ላከ።

[25]“የተጻፈውም ጽሕፈት፣
‘ማኔ፣ ማኔ፣ ቴቄል፣ ፋሬስ’[ነ] ይላል።
[26]“የቃሉም ትርጕም ይህ ነው፤
‘ማኔ’[ነ] ማለት እግዚአብሔር
የመንግሥትህን ዘመን ቈጠረው፤
ወደ ፍጻሜም አደረሰው ማለት ነው።
[27]‘ቴቄል’[ኘ] ማለት በሚዛን ተመዘንህ፤
ቀለህም ተገኘህ፣ ማለት ነው።
[28]‘ፋሬስ’[አ] ማለት መንግሥትህ ተከፈለ፣
ለሜዶናውያንና ለፋርስ ሰዎች ተሰጠ
ማለት ነው።

[29]ከዚህ በኋላ በቤልሻዛር ትእዛዝ ዳንኤልን
ሐምራዊ መጐናጸፊያ አለበሱት፣ የወርቅ
ሐብል በዐንገቱ ላይ አጠለቁለት፤ የመንግ
ሥቱም ሦስተኛ ገዥ ሆኖ ተሾመ።

[30]በዚያኑ ሌሊት የባቢሎናውያን[ከ] ንጉሥ
ቤልሻዛር ተገደለ፤ [31]የሥልሳ ሁለት ዓመት
ድሜ የነበረው ሜዶናዊው ዳርዮስም መንግ
ሥቱን ወሰደ።

## ዳንኤል በአንበሶች ጕድጓድ ውስጥ

**6** ዳርዮስ በመንግሥቱ ሁሉ ላይ እንዲ
ገዙ አንድ መቶ ሃያ መሳፍንትን
መሾም ፈለገ፤ [2]በእነዚህም ላይ ሦስት የበ
ላይ አስተዳዳሪዎችን አደረገ፤ ከእነርሱም
አንዱ ዳንኤል ነበረ። ንጉሡ ጕዳት እንዳይደ
ርስበት፣ መሳፍንቱ ተጠሪነታቸው ለሦስቱ
የበላይ አስተዳዳሪዎች እንዲሆን ተደረገ።
[3]ከመሳፍንቱና ከበላይ አስተዳዳሪዎቹ ሁሉ
ይልቅ ዳንኤል ልዩ የጥበብ መንፈስ የሞላ
በት ሆኖ በመገኘቱ፣ ንጉሡ በመላው ግዛቱ
ላይ ሊሾመው አሰበ። [4]በዚህ ምክንያት
የበላይ አስተዳዳሪዎቹና መሳፍንቱ ዳንኤል
በሚያከናውነው የመንግሥት ሥራ ሊከሱት
ሰበብ ፈለጉ፤ ነገር ግን አላገኙበትም፤ ዳንኤል
ታማኝ፣ ጠንቃቃና በሥራው እንከን የሌለ
በት ስለ ነበር፣ በእርሱ ላይ ስሕተት ሊያ
ገኙ አልቻሉም። [5]እነዚህም ሰዎች፣ “ከአ
ምላኩ ሕግ ጋር በተያያዘ ጕዳይ
ካልሆነ

[ቾ]22 ወይም *ዘሩ* ወይም *ምትክ* [ነ]25 በአረማይክ *ኢፋርሲን (ይኸውም ፋርሲንና ማለት ነው)* [ነ]26 *ማኔ* ማለት *የተቈጠረ* ወይም *ምናን (ራሱን የቻለ አንድ የገንዘብ ክፍል)*
[ኘ]27 *ቴቄል* ማለት *የተመዘነ* ወይም *ሰቅል* ሊሆን ይችላል።
[አ]28 *ፋሬስ፡የፋርሲን* ነጠላ ቁጥር ሲሆን *ተከፈለ* ወይም *ፐርሺያ* ወይም *የስቅል እኩሌታ* ማለት ሊሆን ይችላል።
[ከ]30 ወይም *ከለዳውያን*

በቀር፣ ይህን ሰው የምንከስበት ምንም ሰበብ
አናገኝበትም” አሉ።
6ከዚያም የበላይ አስተዳዳሪዎቹና መሳፍ
ንቱ በአንድነት ወደ ንጉሡ ሄደው እንዲህ
አሉ፤ “ንጉሥ ዳርዮስ ሆይ፤ ለዘላለም ንገሥ!
7ንጉሥ ሆይ፤ እስከ ሠላሳ ቀን ድረስ ወደ
አንተ ካልሆነ በቀር ማንም ሰው ወደ ሌላ
ሰውም ሆነ ወደ ሌላ አምላክ መጸለይ እን
ደሌለበት ንጉሡ ዐዋጅ እንዲያወጣ፣ ትእ
ዛዙም እንዲፈጸም፣ ይህንም የተላለፈ ወደ
አንበሶች ጕድጓድ እንዲጣል፣ የመንግሥት
የበላይ አስተዳዳሪዎች፣ መኳንንት፣ መሳፍ
ንት፣ አማካሪዎችና አገረ ገዦች ሁሉ
በአንድነት ተስማምተዋል። 8ንጉሥ ሆይ፤
ይህን ዐዋጅ አውጣ፤ እንደማይሻረውና እን
ደማይለወጠው የሜዶንና የፋርስ ሕግ እን
ዲሆን ትእዛዙን በጽሑፍ አድርገው።”
9ስለዚህ ንጉሥ ዳርዮስ ዐዋጁ ተጽፎ እንዲ
ወጣ አደረገ።
10ዳንኤልም ዐዋጁ እንደ ወጣ ባወቀ ጊዜ
ወደ ቤቱ ሄደ፤ መስኮቶቹ በኢየሩሳሌም
አንጻር ተከፍተው ባሉበት በሰገነቱ ቀድሞ
ያደርግ እንደ ነበረው በቀን ሦስት ጊዜ
ተንበርክኮ ጸለየ፤ አምላኩንም አመሰገነ።
11ሰዎቹም በአንድ ላይ ሄደው፣ ዳንኤልን
ሲጸልይና አምላኩን ሲማጸን አገኙት።
12ወደ ንጉሡም ሄደው፣ “ንጉሥ ሆይ፤
በሚቀጥሉት ሠላሳ ቀናት ማንም ሰው
ወደ አንተ ካልሆነ በቀር ወደ ሰውም ሆነ
ወደ ማንኛውም አምላክ ቢጸልይ፣ በአንበሶች
ጕድጓድ ውስጥ እንደሚጣል ዐዋጅ አውጥ
ተህ አልነበረምን?” ሲሉ እርሱ ስላወጣው
ዐዋጅ ጠየቁት።
ንጉሡም፣ “ዐዋጁ እንደማይሻረው እንደ
ሜዶንና እንደ ፋርስ ሕግ የጸና ነው” ሲል
መለሰ።

13እነርሱም ንጉሡን፣ “ንጉሥ ሆይ፤ ከይ
ሁዳ ምርኮኞች አንዱ የሆነው ዳንኤል፣
አንተንም ሆነ በጽሑፍ ያወጣኸውን ዐዋጅ
አያከብርም፤ አሁንም በቀን ሦስት ጊዜ
ወደ አምላኩ ይጸልያል” አሉት። 14ንጉሡ
ይህን በሰማ ጊዜ እጅግ አዘነ፤ ዳንኤልን ለ
ማዳን ወሰነ፤ ፀሓይ እስክትጠልቅም ድረስ
የተቻለውን ሁሉ አደረገ።
15ከዚያም ሰዎቹ በአንድ ላይ ወደ ንጉሡ
ቀርበው፣ “ንጉሥ ሆይ፤ በሜዶንና በፋርስ ሕግ
መሠረት፣ አንድ ንጉሥ ያወጣው ዐዋጅም ሆነ
ትእዛዝ ሊለወጥ እንደማይችል ዕወቅ” አሉት።
16ስለዚህ ንጉሡ ትእዛዝ ሰጠ፤ እነርሱም
ዳንኤልን አመጡት፤ ወደ አንበሶችም ጕድ
ጓድ ጣሉት። ንጉሡም ዳንኤልን፣ “ሁልጊዜ
የምታመልከው አምላክህ ያድንህ” አለው።

17ድንጋይ አምጥተው በጕድጓዱ አፍ
ላይ ገጠሙበት፤ ንጉሡም፣ በዳንኤል ላይ
የተፈጸመው እንዳይለወጥ በራሱ የቀለበት
ማኅተምና በመሳፍንቱ ቀለበቶች አተመ
በት። 18ንጉሡም ወደ ቤተ መንግሥቱ
ተመለሰ፤ በዚያም ሌሊት ምግብ ሳይበላ፣
የሚያዝናናውም ነገር ሳይቀርብለት ዐደረ፤
እንቅልፍም ከእርሱ ራቀ።
19በማለዳም ገና ጎሕ ሲቀድ፤ ንጉሡ
ተነሥቶ ወደ አንበሶቹ ጕድጓድ እየተጣ
ደፈ ሄደ። 20ወደ ጕድጓዱም ቀርቦ በሐ
ዘን ድምፅ ዳንኤልን፣ “የሕያው አምላክ
አገልጋይ ዳንኤል ሆይ፤ ሁልጊዜ የምታ
መልከው አምላክህ ከአንበሶቹ ሊያድንህ
ችሎአልን?” ብሎ ተጣራ።
21ዳንኤልም እንዲህ ብሎ መለሰ፤ “ንጉሥ
ሆይ፤ ለዘላለም ንገሥ፤ 22ንጉሥ ሆይ፤ በፊቱ
ቅን ሆኜ ስለ ተገኘሁ፣ በአንተም ፊት
በደል ስላልተገኘብኝ፣ አምላኬ መልአኩን
ልኮ የአንበሶቹን አፍ ዘጋ፤ እነርሱም አልጐ
ዱኝም።”
23ንጉሡ እጅግ ተደስቶ፤ ዳንኤልን ከጕድ
ጓዱ እንዲያወጡት አዘዘ። ዳንኤል በአምላኩ
ታምኖ ነበርና ከጕድጓድ በወጣ ጊዜ፣ አን
ዳች ጉዳት አልተገኘበትም።
24በንጉሡ ትእዛዝ፣ ዳንኤልን በሐሰት
የከሰሱትን ሰዎች፣ ከሚስቶቻቸውና ከልጆ
ቻቸው ጋር አምጥተው፣ በአንበሶቹ ጕድ
ጓድ ውስጥ ጣሏቸው፤ ገና ወደ ጕድጓዱ
መጨረሻ ሳይደርሱም፣ አንበሶቹ ቦጫጨ
ቋቸው፤ ዐጥንቶቻቸውንም ሁሉ ሰባበሩ።
25ከዚያ በኋላ ንጉሥ ዳርዮስ፣ በምድር
ላይ ለሚኖሩ ሕዝቦች፣ መንግሥታትና
ልዩ ልዩ ቋንቋ ለሚናገሩ ሰዎች ሁሉ እን
ዲህ የሚል መልእክት ጻፈ፤

“ሰላም ይብዛላችሁ!

26“በማንኛውም የመንግሥቴ ግዛት ሰው
ሁሉ፣ የዳንኤልን አምላክ እንዲፈራና እን
ዲያከብር ይህን ዐዋጅ አውጥቻለሁ።

“እርሱ ለዘላለም የሚኖር፣
ሕያው አምላክ ነውና፣
መንግሥቱ አይጠፋም፤
ለግዛቱም መጨረሻ የለውም።
27እርሱ ይታደጋል፤ ያድናልም፤
በሰማይና በምድር፣
ምልክቶችንና ድንቆችን ያደርጋል፤
ዳንኤልን፣
ከአንበሶች አፍ አድኖታል።”
28ስለዚህ ዳንኤል በዳርዮስ ዘመነ መንግ
ሥትና በፋርሳዊው በቂሮስ ዘመነ መንግ
ሥት ሁሉ ኑሮው ተሳካለት።

6፥6 ነህ2፥3
6፥7 መዝ59፥3፤ 64፥2-6፤ዳን3፥2፡6
6፥8 አስ1፥19
6፥10 1ነገ8፥29፤ መዝ95፥6፤ ማቴ6፥6፤ሐሥ5፥29
6፥11 1ነገ8፥48-50፤ መዝ55፥17፤1ተሰ5፥17-18
6፥12 አስ1፥19፤ ዳን3፥8-12
6፥13 አስ3፥8፤ ሕዝ14፥14፤ዳን2፥25
6፥14 ማር6፥26
6፥15 አስ8፥8
6፥16 ቍ7፤ ኢዮ5፥19፤ መዝ3 7፥39-40፤ 97፥10
6፥17 ማቴ27፥66
6፥18 2ሳሙ12፥17፤ አስ6፥1፤ዳን10፥3
6፥20 ዳን3፥17
6፥21 ነህ2፥3፤ዳን 3፥9
6፥22 ቍ27፤ዘፍ 32፥1፤መዝ91፥11-13፤ ዳን3፥28፤ሐሥ 12፥11፤ 2ጢሞ4፥ 17፤ዕብ11፥33
6፥23 1ዜና5፥20፤ ኢሳ12፥2፤ዳን3፥27
6፥24 ዘዳ19፥18-19፤ 24፥16፤2ነገ14፥6፤አስ 7፥9-10፤መዝ54፥5፤ ኢሳ38፥13
6፥25 ዳን3፥4፤4፥1
6፥26 ኢሱ2፥11፤ 3፥10፤አስ8፥17፤መዝ5 ፥7፤99፥1-3፤ኤር 10፥10፤ዳን2፥44፤3፥ 29፤12፥7፤ራእ1፥18
6፥27 ቍ22፤ዳን 3፥29፤4፥3
6፥28 2ዜና36፥22፤ ዳን1፥21፤5፥28

## ዳንኤል ስለ አራቱ አራዊት ያየው ሕልም

7 የባቢሎን ንጉሥ ቤልሻዛር በነገሠ በመ
ጀመሪያው ዓመት ዳንኤል በዐልጋው ላይ
ተኝቶ ሳለ ሕልም አለመ፤ ራእይም አየ፤
የሕልሙንም ዋና ሐሳብ ጻፈው።
2ዳንኤል እንዲህ አለ፤ “አራቱ የሰማይ
ነፋሳት ታላቁን ባሕር ሲያናውጡት ሌሊት
በራእይ አየሁ፤ 3እርስ በርሳቸው የማይመ
ሳሰሉ አራት ታላላቅ አራዊት ከባሕሩ ወጡ።
4“የመጀመሪያው፣ አንበሳ ይመስል ነበር፤
የንስርም ክንፎች ነበሩት፤ ክንፎቹ እስኪ
ነቃቀሉ ድረስ ተመለከትሁ፤ እንደ ሰው
በሁለት እግሩ እንዲቆም ከምድር ከፍ
ከፍ ተደረገ፤ የሰውም ልብ ተሰጠው።
5“እነሆም፤ ሁለተኛው አውሬ ድብ
ይመስል ነበር፤ በአንድ ጐኑ ከፍ ብሎአል፤
በአፉ ውስጥ በጥርሶቹ መካከል ሦስት
የጐድን ዐጥንቶች ነበሩት። እርሱም፤ ‘ተነሥ፤
እስክትጠግብ ድረስ ሥጋ ብላ!’ ተባለ።
6“ከዚያ በኋላ ተመለከትሁ፤ በፊቴ ነብር
የሚመስል ሌላ አውሬ ነበር፤ በጀርባውም
በኩል የወፍ ክንፍ የሚመስሉ አራት ክን
ፎች ነበሩት፤ ይህ አውሬ አራት ራስ ነበ
ረው፤ ለመግዛትም ሥልጣን ተሰጠው።
7“ከዚህ በኋላ በሌሊት ራእይ አየሁ፤
በፊቴም የሚያስፈራና የሚያስደነግጥ በጣም
ኀይለኛ የሆነ አራተኛ አውሬ ነበር፤ ትል
ልቅ የብረት ጥርሶች ነበሩት፤ ያደቅና
ይበላ፣ የቀረውንም ሁሉ በእግሮቹ ይረጋግጥ
ነበር። ከእርሱ በፊት ከነበሩት አራዊት ሁሉ
የተለየ ሲሆን፣ ዐሥር ቀንዶች ነበሩት።
8“ስለ ቀንዶቹ ሳስብ ሳለሁ፣ ከመካከላ
ቸው አንድ ሌላ ትንሽ ቀንድ ብቅ ሲል አየሁ፤
ከመጀመሪያዎቹ ቀንዶች ሦስቱ ከፊቱ
ተነቃቀሉ፤ ይህም ቀንድ የሰው ዐይኖችን
የሚመስሉ ዐይኖች፣ በትዕቢትም የሚናገር
አፍ ነበረው።

9“እኔም ስመለከት፣
“ዙፋኖች ተዘረጉ፤
ጥንታዌ ጥንቱም ተቀመጠ፤
ልብሱ እንደ በረዶ ነጭ ነበረ፤
የራሱም ጠጕር እንደ ጥጥ ነጭ ነበረ፤
ዙፋኑ የእሳት ነበልባል፣
መንኰራኵሮቹም ሁሉ እንደሚነድ እሳት
ነበሩ።
10የእሳት ወንዝ፣ ከፊት ለፊቱ ፈልቆ
ይፈስ ነበር፤
ሺህ ጊዜ ሺሆች ያገለግሉት ነበር፤
እልፍ ጊዜ እልፍ በፊቱ ቆመዋል፤
የፍርድ ጉባኤ ተሰየመ፤
መጻሕፍትም ተከፈቱ።

11“ቀንዱም ከሚናገረው የትዕቢት ቃል
የተነሣ፣ መመልከቴን ቀጠልሁ፤ አውሬው
እስኪታረድና አካሉ ደቆ ወደሚንበለበለው
እሳት እስኪጣል ድረስ ማየቴን አላቋረ
ጥሁም። 12ሌሎቹም አራዊት ሥልጣናቸው
ተገፎ ነበር፤ ነገር ግን ለተወሰነ ጊዜና ወቅት
በሕይወት እንዲኖሩ ተፈቀደላቸው።
13“ሌሊት ባየሁት ራእይ፣ የሰውን ልጅ
የሚመስል ከሰማይ ደመና ጋር ሲመጣ
አየሁ፤ ወደ ጥንታዌ ጥንቱ መጣ፤ ወደ
ፊቱም አቀረቡት። 14ሥልጣን፣ ክብርና
ታላቅ ኀይል ተሰጠው፤ በልዩ ልዩ ቋንቋ
የሚናገሩ ሰዎች፣ መንግሥታትና ሕዝቦች
ሰገዱለት፤ ግዛቱም ለዘላለም የማያልፍ
ነው፤ መንግሥቱም ፈጽሞ የማይጠፋ
ነው።

## የሕልሙ ትርጕም

15“እኔ ዳንኤል በመንፈሴ ታወክሁ፤
ያየሁትም ራእይ እጅግ አስጨነቀኝ።
16በዚያ ከቆሙት ወደ አንዱ ቀርቤ፣ የዚህ
ሁሉ እውነተኛ ትርጕም ምን እንደ ሆነ
ጠየቅሁት።
“እርሱም መለሰልኝ፤ የእነዚህንም ነገሮች
ትርጕም እንዲህ ሲል ነገረኝ፤ 17‘አራቱ ታላላቅ
አራዊት ከምድር የሚነሡ መንግሥታት ናቸው፤
18ነገር ግን የልዑሉ ቅዱሳን መንግሥቱን
ይወስዳሉ፤ ለዘላለምም ይይዙታል፤ አዎን፤
ለዘላለም ይይዙታል።
19“ከዚያም የሚያደቅቀውንና የሚበላውን፣
የቀረውንም ሁሉ በእግሮቹ የሚረጋግጠውን፣
የብረት ጥርሶችና የናስ ጥፍሮች የነበሩትን፣
ከሌሎቹ አራዊት የተለየና እጅግ አስፈሪ
የሆነውን የአራተኛውን አውሬ እውነተኛ ትር
ጕም ማወቅ ፈለግሁ። 20ደግሞም በራሱ
ላይ ስላሉት ዐሥር ቀንዶች፣ ከመካከላቸው
ብቅ ስላለው ቀንድና ከዚሁ ቀንድ ፊት
ስለ ተነቃቀሉት ሦስት ቀንዶች፣ እንደዚ
ሁም ከሌሎች ስለ በለጠው የሰው ዐይኖች
የሚመስሉ ዐይኖች፣ በትዕቢትም የሚና
ገር አፍ ስለ ነበሩት ስለዚሁ ቀንድ ማወቅ
ፈለግሁ። 21እነሆም፤ ይህ ቀንድ በቅዱሳን
ላይ ጦርነት ዐውጆ አሸነፋቸው፤ 22ይህም
የሆነው ጥንታዌ ጥንቱ እስኪመጣና ለልዑሉ
ቅዱሳን እስኪፈርድላቸው ድረስ ነበር፤
ከዚያም የልዑሉ ቅዱሳን መንግሥቱን
የሚወርሱበት ዘመን መጣ።
23“እርሱም እንዲህ አለኝ፣ ‘አራተኛው
አውሬ በምድር ላይ የሚነሣ አራተኛው
መንግሥት ነው። ከሌሎች መንግሥታት
ሁሉ የተለየ ይሆናል፤ መላውንም ምድር
እየረገጠና እያደቀቀ ይበላል። 24ዐሥሩ
ቀንዶች ከዚህ መንግሥት የሚወጡ ዐሥር

7፥1 መዝ4፥4፤ኤር 36፥4፤ሕዝ40፥2፤ ዳን1፥17፤4፥13
7፥2 ሕዝ37፥9፤ ዳን 8፥8፤11፥4፤ራእ 7፥1
7፥3 ራእ13፥1
7፥4 2ኛነገ24፥1፤ መዝ7፥2፤ኤር4፥7፤ ሕ ዝ17፥3፤ራእ13፥2
7፥5 ዳን2፥39
7፥6 ራእ13፥2
7፥7 ሕዝ40፥2፤ ዳን 2፥40፤8፥7፥10፤ ራእ 12፥3
7፥8 መዝ12፥3፤ዳን 8፥9፤ራእ9፥7፤13፥5-6
7፥9 ቍ22፤1ነገ22፥19፤ 2ዜና18፥18፤ሕዝ1፥ 15፤ 10፥6፤ማቴ19፥28፤ 28፥3፤ ራእ1፥14፤4፥2፤ 20፥4
7፥10 ዘፀ32፥32፤ ዘዳ33፥2፤መዝ50፥3፤ 56፥8፤68፥17፤97፥3፤ኢ ሳ30፥27፤ይሁ 1፥14፤ ራእ5፥11፤ 20፥11-15
7፥11 ራእ13፥5-6፤ 19፥20
7፥13 ዘዳ33፥26፤ ኢ ሳ13፥6፤ሕዝ1፥5፤ 2፥1፤ሶፎ1፥14፤ሚል 3፥2፤4፥1፤ማቴ8፥2፤ ራእ1፥7፥13፤14፥14
7፥14 መዝ72፥11፤ 102፥22፤ ኢሳ16፥5፤ ዳን2፥44፤ ማቴ28፥ 18፤ ዕብ12፥28፤ ራእ11፥15
7፥15 ኢዮ4፥15፤ ዳን4፥19
7፥16 ዳን8፥16፤ 9፥22፤ዘካ1፥9
7፥18 መዝ16፥3፤ 49፥14፤ኢሳ60፥12-14፤ ሉቃ12፥32፤ዕብ12፥ 28፤ራእ2፥26፤20፥4
7፥20 ራእ13፥5-6፤ 17፥12
7፥21 ራእ13፥7
7፥22 ማር8፥35
7፥23 ዳን2፥40
7፥24 ራእ17፥12

ነገሥታት ናቸው፤ ከዚያም በኋላ ከእነርሱ
የተለየ ሌላ ንጉሥ ይነሣል፤ ሦስቱንም ነገ
ሥታት ያንበረክካል። 25በልዑል ላይ የዐ
መፅ ቃል ይናገራል፤ የልዑልንም ቅዱሳን
ያስጨንቃል፤ ለበዓላት የተመደበውን ጊዜና
ሕግን ለመለወጥ ይሞክራል፤ ቅዱሳንም
ለዘመን፣ ለዘመናት፣ ለዘመን እኩሌታም[ኸ]
ለእርሱ ዐልፈው ይሰጣሉ።
26"ነገር ግን የፍርድ ዙፋን ይዘረጋል፤
ሥልጣኑም ይወሰድበታል፤ ፈጽሞ ለዘላለም
ይደመሰሳል። 27ከዚያም ከሰማይ በታች
ያሉ መንግሥታት ልዕልና፣ ሥልጣንና ታላ
ቅነት ለልዑሉ ሕዝብ፣ ለቅዱሳን ይሰጣል።
መንግሥቱ የዘላለም መንግሥት ይሆናል፤
ገዞች ሁሉ ያመልኩታል፤ ይታዘዙታልም።
28"የነገሩ ፍጻሜ ይህ ነው፤ እኔም ዳንኤል
በሐሳቤ እጅግ ተጨነቅሁ፤ መልኬም ተለዋ
ወጠ፤ ይሁን እንጂ ነገሩን በልቤ ጠበቅሁት።"

## ዳንኤል በራእዩ ያየው አውራ በግና ፍየል

8 ንጉሥ ብልሻዛር በነገሠ በሦስተኛው ዓመት፣
አስቀድሞ ከተገለጠልኝ ራእይ በኋላ እኔ
ዳንኤል ሌላ ራእይ አየሁ። 2በራእዩም፣ በኤ
ላም አውራጃ በሱሳ ግንብ ራሴን አየሁት፤
በራእዩም በኡባል ወንዝ አጠገብ ነበርሁ፤
3ዐይኔን አንሥቼ ስመለከት እነሆ፤ ሁለት
ቀንዶች ያሉት አውራ በግ በወንዙ አጠ
ገብ ቆሞ አየሁ፤ ቀንዶቹም ረጃጅሞች
ነበሩ፤ ከቀንዶቹም አንዱ ከሌላው ይረዝ
ማል፤ የበቀለው ግን ዘግይቶ ነበር። 4አውራ
በጉም ወደ ምዕራብ፣ ወደ ሰሜንና ወደ
ደቡብ በቀንዱ ሲጐሽም አየሁ። ምንም ዐይ
ነት እንስሳ ሊቋቋመው አልቻለም፤ ከእጁም
ሊያድን የሚችል አልነበረም፤ የፈለገውን
ሁሉ አደረገ፤ ታላቅም ሆነ።
5ስለዚህም ነገር እያሰብሁ ሳለሁ፣ በዐ
ይኖቹ መካከል ትልቅ ቀንድ ያለው አውራ
ፍየል፣ መሬት ሳይነካ ምድርን ሁሉ እያ
ቋረጠ በድንገት ከምዕራብ መጣ፤ 6በወንዙ
አጠገብ ቆሞ ወዳየሁት፣ ሁለት ቀንድ
ወዳለው አውራ በግ ተንደርድሮ መጣበት፤
በታላቅ ቍጣም መታው፤ 7እየወጋውና
ሁለቱን ቀንዶቹን እየሰበረ፣ በጭካኔ አው
ራውን በግ ሲጐዳ አየሁ፤ አውራ በጉም
ለመቋቋም ጕልበት አልነበረውም። ፍየሉ
በምድር ላይ ጥሎ ረገጠው፤ አውራ በጉንም
ከፍየሉ እጅ ለማዳን የሚችል አልነበረም።
8ፍየሉም ታላቅ ሆነ፤ ነገር ግን በኀይሉ በበ
ረታ ጊዜ፣ ትልቁ ቀንዱ ተሰበረ፤ በቦታውም
ወደ አራቱ የሰማይ ነፋሳት የሚያመለክቱ
አራት ታላላቅ ቀንዶች በቀሉ።
9ከእነዚህም ቀንዶች መካከል በአንዱ
ላይ አንድ ሌላ ትንሽ ቀንድ በቀለ፤

7፥25 ኢሳ37፥23፤ ዳን2፥21፤8፥24፤11፥36፤12፥7፤ማር1፥15፤ ሉቃ21፥8 ሐሥ1፥6-7፤ራእ11፥2፤16፥6
7፥26 ራእ19፥20
7፥27 ዘፍ14፥18፤ 2ሳሙ7፥13፤መዝ22፥27፤72፥11፤86፥9፤145፥13፤ኢሳ14፥2፤ዳን2፥44፤4፥34፤ሉቃ1፥33፤1ቆሮ6፥2፤ራእ11፥15፤22፥5
7፥28 ኢዮ4፥15፤ መዝ13፥2፤ኢሳ21፥3፤ ዳን4፥19
8፥1 ዳን1፥17፤5፥1
8፥2 ዘፍ10፥22፤ዕዝ4፥9፤አስ2፥8
8፥3 ዳን10፥5፤ራእ13፥11
8፥4 ኢሳ41፥3፤ዳን11፥3፡16
8፥7 ዳን7፥7፤ 11፥11፡16
8፥8 2ዜና26፥16-21፤ ዳን5፥20፤7፥2፤ራእ 7፥1
8፥9 ሕዝ20፥6፤ ዳን7፥8፤11፥16
8፥10 ኢሳ14፥13፤ ዳን7፥7፤ራእ8፥10፤12፥4
8፥11 ቍ25፤ሕዝ46፥13-14፤ዳን11፥ 31፡36-37፤12፥11
8፥12 ኢሳ48፥1
8፥13 ዘዳ33፥2፤ኢሳ28፥18፤ዳን4፥23፤12፥6፤ሉቃ21፥24፤ራእ 11፥2
8፥14 ዳን12፥11-12
8፥15 ቍ1፤ሕዝ2፥1፤ዳን10፥16-18
8፥16 ቍ2፤ዳን7፥16፤9፥21፤ሉቃ1፥19
8፥17 ቍ19፤ሕዝ1፥28፤44፥4፤ዳን2፥46፤ዕን2፥3፤ራእ1፥17
8፥18 ሕዝ2፥2፤ዳን10፥9፡16-18፤ዘካ4፥1
8፥19 መዝ102፥13፤ኢሳ10፥25፤ዕን 2፥3
8፥20 ሕዝ27፥10
8፥21 ዳን10፥20፤ 11፥3

ወደ ደቡብ፣ ወደ ምሥራቅና ወደ መልካ
ሚቱ ምድር በኀይል አደገ። 10ወደ ሰማይ
ሰራዊት እስኪደርስ ድረስ አደገ፤ ከከዋክ
ብት ሰራዊትም የተወሰኑትን ወደ ምድር
ጣለ፤ ረጋገጣቸውም። 11ከሰማይ ሰራዊት
አለቃ ጋር እስኪተካከል ድረስ ራሱን ከፍ
ከፍ አደረገ፤ የልዑሉንም የዘወትር መሥ
ዋዕት ወሰደበት፤ የመቅደሱንም ስፍራ አረ
ከሰ። 12ከዐመፅ የተነሣም የቅዱሳን ሰራዊት[ሠ]
ከዘወትሩ መሥዋዕት ጋር ለእርሱ አልፎ
ተሰጠ፤ የሚያደርገው ሁሉ ተከናወነለት፤
እውነትም ወደ ምድር ተጣለች።
13ከቅዱሳኑም አንዱ ሲናገር ሰማሁ፤ ሌላ
ውም ቅዱስ እንዲህ አለው፤ "ስለ ዘወትሩ
መሥዋዕት፣ ለጥፋት ምክንያት ስለ ሆነው
ዐመፅ፣ ከእግር በታች እንዲረገጡ አል
ፈው ስለሚሰጡት መቅደስና ሰራዊት የታ
የው ራእይ የሚፈጸመው መቼ ነው?"
14እርሱም፣ "እስከ ሁለት ሺህ ሦስት
መቶ ምሽቶችና ማለዳዎች ድረስ ይቈያል፤
ከዚያም መቅደሱ እንደ ገና ይነጻል" አለኝ።

## የራእዩ ትርጓሜ

15እኔ ዳንኤል ራእዩን ስመለከትና
ሳስተውል ሳለ፣ ሰውን የሚመስል ከፊት
ለፊቴ ቆመ፤ 16ከኡባልም፣ "ገብርኤል ሆይ፤
ለዚህ ሰው የራእዩን ትርጕም ንገረው" ብሎ
የሚጮኽ የሰው ድምፅ ሰማሁ።
17እኔ ወደ ቆምሁበት ስፍራ እየቀረበ ሲመጣ፣
ደንግጬ በግምባሬ ተደፋሁ፤ እርሱም፣
"የሰው ልጅ ሆይ፤ ራእዩ ስለ ዘመኑ
ፍጻሜ እንደ ሆነ አስተውል" አለኝ።
18እየተናገረኝ ሳለ፣ በምድር ላይ በግንባሬ
ተደፋሁ፤ በከባድ እንቅልፍም ተዋጥሁ፤
እርሱ ግን ዳሰሰኝና በእግሮቼ አቆመኝ።
19እርሱም እንዲህ አለኝ፤ "ራእዩ በመ
ጨረሻው ዘመን[0] ሊሆን ያለውን የሚያመ
ለክት ስለ ሆነ፣ በኋላ በቍጣው ዘመን
ምን እንደሚሆን እነግርሃለሁ፤ 20ያየኸው
ሁለት ቀንዶች የነበሩት አውራ በግ፣
የሜዶንና የፋርስን መንግሥታት ያመለክ
ታል። 21ጠጕራሙ ፍየል የግሪክ ንጉሥ
ሲሆን፣ በዐይኖቹም መካከል ያለው ትልቁ
ቀንድ የመጀመሪያው ንጉሥ ነው። 22የተሰ
በረውን ቀንድ የተኩት አራቱ ቀንዶች፣
ከመንግሥቱ የሚወጡትን አራት መንግ
ሥታት ያመለክታሉ፤ ነገር ግን በኀይል
አይተካከሉትም።
23"በዘመነ መንግሥታቸው በስተመጨ
ረሻ፣ ዐመፀኞች ፍጹም እየከፉ በሚሄዱ

[ኸ]25 ወይም *ለአንድ ዓመት፣ ለሁለት ዓመት እንዲሁም ለዓመት እኩሌታም* [ሠ]12 ወይም *ከመቅ...ሰራዊቱ* [0]19 ወይም *መጨረሻው በተወሰነው ጊዜ ስለሚሆን*

በት ጊዜ፣ አስፈሪ ፊት ያለው አታላይ
ንጉሥ ይነሣል። 24እጅግ ብርቱ ይሆናል፤
ነገር ግን በገዛ ኀይሉ አይደለም። አሠ
ቃቂ ጥፋት ይፈጽማል፤ የሚያደርገው
ሁሉ ይከናወንለታል፤ ኀያላን ሰዎችንና ቅዱሳ
ኑን ሕዝብ ያጠፋል። 25እያጭበረበረ ይበለ
ጽጋል፤ ራሱንም ታላቅ አድርጎ ይቈጥራል።
በሰላም ተደላድለን ተቀምጠናል ሲሉ፣
ብዙዎችን ያጠፋል፤ በልዑላን ልዑልም
ላይ ይነሣል፤ ይሁን እንጂ እርሱም ይጠ
ፋል፤ ነገር ግን በሰው ኀይል አይደለም።

26"የተሰጠህ የምሽቱና የማለዳው ራእይ
እውነት ነው፤ ነገር ግን ከብዙ ዘመን በኋላ
የሚሆነውን ስለሚያመለክት ራእዩን ዝጋው።"

27እኔ ዳንኤል ዐቅሜ ተሟጦ ነበር፤ ለብዙ
ቀናት ታመምሁ፤ ተኛሁም። ከዚያም በኋላ
ተነሥቼ ወደ ንጉሡ ሥራ ሄድሁ። ባየሁት
ራእይ ተደናግጬ ነበር፤ ነገሩም
አልገባኝም።

## የዳንኤል ጸሎት

9 የሜዶናዊው የአርጤክስስʺ ልጅ ዳርዮስ
በባቢሎንʺʹ በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት፣
2በዘመነ መንግሥቱ በመጀመሪያው ዓመት፣
እኔ ዳንኤል ለነቢዩ ለኤርምያስ በተሰጠው
የእግዚአብሔር ቃል መሠረት፣ የኢየሩሳ
ሌም መፈራረስ ሰባ ዓመት እንደሚቈይ ከቅ
ዱሳት መጻሕፍት አስተዋልሁ። 3ስለዚህ
ማቅ ለብሼ፣ በራሴም ላይ ዐመድ ነስንሼ፣
በጾምና በጸሎት፣ በምልጃም ፊቴን ወደ
ጌታ አምላክ አቀናሁ።

4ወደ አምላኬ ወደ እግዚአብሔር እንዲህ
ብዬ
ጸለይሁ፤ ተናዘዝሁም፤

"ከሚወዱህና ትእዛዝህን ከሚፈጽሙ ሁሉ
ጋር የፍቅር ቃል ኪዳንህን የምትጠብቅ፣
ታላቅና የተፈራህ አምላክ ጌታ ሆይ፤ 5እኛ
ኀጢአት ሠርተናል፤ በድለናልም፤ ክፋትን
አድርገናል፤ ዐምፀናልም፤ ከትእዛዝህና ከሕ
ግህ ዘወር ብለናል። 6ለንጉሦቻችን፣ ለልዑሎ
ቻችንና ለአባቶቻችን እንዲሁም ለምድሪቱ
ሕዝብ ሁሉ በአንተ ስም የተናገሩትን አገ
ልጋዮችህን ነቢያትን አልሰማንም።

7"ጌታ ሆይ፤ አንተ ጻድቅ ነህ፤ ነገር
ግን ለአንተ ታማኞች ባለመሆናችን እኛን
በበ ተንህባቸው አገሮች ሁሉ የምንገኝ
የይሁዳ ሰዎች፣ የኢየሩሳሌምና የመላው
እስራኤል ሕዝብ፣ በሩቅም ሆነ በቅርብ
ያለን በዚህ ቀን በኀፍረት ተከናንበናል።
8እግዚአ ብሔር ሆይ፤ እኛና ንጉሦቻችን፣
ልዑሎ ቻችንና አባቶቻችን በአንተ ላይ
ኀጢአት ስለ ሠራን በኀፍረት ተከናንጠ
በናል። 9ምንም እንኳ በእርሱ ላይ ያመፅን
ብንሆን፣ ጌታ አምላካችን ይቅር ባይና

8፥24 ዳን7፥25፤ 11፥36
8፥25 ዳን2፥34፤11፥21፡23፡26
8፥26 ኢሳ8፥16፤ 29፥11፤ዳን10፥1፡14፤ ራእ10፥4፤22፥10
8፥27 ኢሳ21፥3፤ዳን 2፥48፤4፥19፤10፥8
9፥1 ዕዝ4፥6፤ ዳን5፥31
9፥2 2ዜና36፥21፤ኤር 29፥10፤ዘካ1፥12፤7፥5
9፥3 2ሳሙ13፥19፤ 2ዜና20፥3፤ነህ1፥4፤ ኤር 29፥12፤ዳን 10፥12፤ዮና3፥6
9፥4 ዘዳ7፥9፡21፤ 1ነገ8፥23፡30
9፥5 ቍ11፤መዝ 106፥6፤ኢሳ53፥6፤ ኤር8፥14፤ሰቆ1፥20፤ 3፥42፤
9፥6 2ነገ18፥12፤ 2ዜና29፥6፤36፥16፤ ኤር44፥5፤ያዕ5፥10፤ ራእ10፥7
9፥7 ዘዳ4፥27፤7፥3፤ዕ ዝ 9፥7፡15፤መዝ44፥15፤ ኢሳ42፥6፤ኤር3፥25፤ 24፥9፤ሕዝ 39፥23-24፤ አሞ9፥9
9፥8 ነህ9፥33፤ኤር 14፥20፤ሕዝ16፥63
9፥9 ዘፀ34፥7፤ 2ሳሙ 24፥14፤ነህ9፥17፤ኤር1 4፥7፤42፥12
9፥10 2ነገ17፥13-15፤ 18፥12፤ራእ10፥7
9፥11 ዘዳ11፥26፤ 13፥15፤28፥15፤2ነገ 17፥23፤22፥16፤ኢሳ 1፥4-6፤ኤር2፥29፤ 8፥5-10
9፥12 ኢሳ44፥26፤ ኤር30፥7፤44፥2፡6፡23፤ ሕዝ5፥9፤ዳን12፥1፤ኢል 2፥2፤ዘካ1፥6፤7፥12
9፥13 ዘዳ4፥29፤ኢሳ 9፥13፤31፥1፤ኤር2፥30
9፥14 ዘፍ18፥25፤ 2ዜና12፥6፤ነህ9፥33፤አ ር12፥1፤18፥8፤32፥23፤ 40፥3፤44፥27
9፥15 ዘፀ3፥20፤ነህ 9፥10፤ኤር32፥21
9፥16 ዘፀ15፥17፤ መሳ5፥11፤መዝ31፥1፤ 39፥8፤48፥1፤85፥3፤ ኢሳ5፥25፤ኤር 32፥32፤ሕዝ5፥14
9፥17 ዘኍ6፥24-26፤ መዝ80፥19
9፥18 ዘዳ28፥10፤ መዝ 5፥1፤80፥14፤116፥1፤ ኢሳ37፥17፤ኤር7፥10-12፤ 25፥29፤ሉቃ18፥13
9፥19 1ሳሙ12፥22፤ መዝ44፥23
9፥20 ቍ3፤ዕዝ10፥1፤ መዝ145፥18፤ኢሳ58፥9
9፥21 ዘፀ29፥39፤ዳን 8፥16፤ሉቃ1፥19

መሓሪ ነው። 10እግዚአብሔር አምላካችንን
አልታዘዝነውም፤ ደግ ሞም በአገልጋዮቹ
በነቢያት በኩል የሰጠንን ሕግ አልጠ
በቅንም፤ 11መላው እስራኤል አንተን
ባለመታዘዝ ሕግህን ተላል ፎአል፤ ዘወርም
ብሎአል።

"በአንተ ላይ ኀጢአትን ስለ ሠራን፣ በእግዚ
አብሔር አገልጋይ በሙሴ ሕግ የተጻፈው
መሐላና ርግማን ፈሰሰብን። 12ታላቅ ጥፋት
በእኛ ላይ በማምጣት፣ በእኛና በገዦቻችን
ላይ የተነገረውን ቃል ፈጸምህብን፤ በኢ
የሩሳሌም ላይ የተደረገውን የሚያህል ከሰ
ማይ በታች ከቶ የለም።

13በሙሴም ሕግ እንደ ተጻፈው፣ ይህ
ሁሉ ጥፋት በእኛ ላይ ደረሰ፤ ሆኖም ከኀጢ
አታችን በመመለስና እውነትህን በመከተል
ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ምሕረትን
አል ፈለግንም 14አምላካችን እግዚአብሔር
በሚ ያደርገው ሁሉ ጻድቅ ነውና፣ በእኛ
ላይ እግዚአብሔር ጥፋት ከማምጣት
አልተመ ለሰም፤ እኛም አልታዘዝነውም።

15"አሁንም ሕዝብህን ከግብፅ ምድር
በብርቱ እጅ ያወጣህ፣ እስከዚህም ቀን
ድረስ ስምህ እንዲታወቅ ያደረግህ፣ ጌታ
አምላካችን ሆይ፤ እኛ ኀጢአትን ሠርተናል፤
አንተንም በድለናል። 16ጌታ ሆይ፤ ቀድሞ
እንዳደረግኸው የጽድቅ ሥራህ ሁሉ፣ ከከ
ተማህ ከኢየሩሳሌም፣ ከቅዱሱም ተራራህ
ቍጣህን መልስ፤ በእኛ ኀጢአትና በአባቶ
ቻችን በደል ምክንያት ኢየሩሳሌምና ሕዝ
ብህ በዙሪያችን ባሉት ዘንድ መሣለቂያ
ሆነዋል።

17"አሁንም አምላካችን ሆይ፤ የአገልጋይ
ህን ጸሎትና ልመና ስማ። ጌታ ሆይ፤ ስለ
ስምህ ስትል ፊትህን ወደ ፈረሰው መቅደስ
መልስ። 18አምላክ ሆይ፤ ጆሮህን አዘንብለህ
ስማ፤ ዐይንህን ገልጠህ መጥፋታችንንና
ስምህ የተጠራበትን ከተማ ተመልከት።
ልመናችንን የምናቀርበው ስለ ጽድቃችን
ሳይሆን፣ ስለ ታላቅ ምሕረትህ ነው። 19ጌታ
ሆይ፤ አድምጥ! ጌታ ሆይ፤ ይቅር በል!
ጌታ ሆይ፤ ስማ! አድርግም፤ ስምህ
በከተማህና በሕዝብህ ላይ ተጠርቶአልና
አምላኬ ሆይ፤ ስለ ስምህ ስትል አትዘግይ።"

## ሰባው ሱባዔ

20እኔም እየተናገርሁና እየጸለይሁ፣ የራ
ሴንና የሕዝቤን የእስራኤልን ኀጢአት እየ
ተናዘዝሁ፣ ስለ ቅዱስ ተራራውም እግዚአብሔር
አምላኬን እየለመንሁ፤ 21እየጸለይሁም
ሳለሁ፣ በመጀመሪያው ራእይ አይቼው
የነበረው ሰው ገብርኤል፣ በሠርክ
መሥዋዕት ጊዜ በፍጥነት እየበረረ ወደ
እኔ መጣ። 22እር

ʺ1 ወይም አህሹሩስ ʺʹ1 ወይም ከለዳውያን

ሱም እንዲህ ብሎ አስረዳኝ፤ “ዳንኤል ሆይ፤ አሁን ጥበብንና ማስተዋልን ልሰጥህ መጥቻለሁ። [23]አንተ እጅግ የተወደድህ ስለሆንህ፣ ገና መጸለይ ስትጀምር መልስ ተሰጥቶአል፤ እኔም ይህን ልነግርህ መጣሁ። ስለዚህ መልእክቱን ልብ በል፤ ራእዩንም አስተውል።

[24]“ዐመፃን ለማስቆም፣ ኀጢአትን ለማስወገድ፣[የ] በደልን ለማስተሰረይ፣ ዘላለማዊ ጽድቅን ለማምጣት፣ ራእይንና ትንቢትን ለማተምና፣ እጅግ ቅዱስ የሆነውን[ዶ] ለመቀባት ስለ ሕዝብህና ስለ ተቀደሰችው ከተማህ ሰባ ሱባዔ[ጀ] ታውጇል።

[25]“ይህንን ዕወቅ፤ አስተውለውም፤ ኢየሩሳሌምን ለማደስና ለመጠገን ዐዋጁ[ገ] ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ፣ ገዥው መሲሕ[ጠ] እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ፣ ሰባት ሱባዔና ሥልሳ ሁለት ሱባዔ ይሆናል። ኢየሩሳሌም ከጐዳናዎቿና ከቅጥሮቿ ጋር ትታደሳለች፤ ይህ የሚሆነው ግን በመከራ ጊዜ ነው። [26]ከሥልሳ ሁለቱ ሱባዔ በኋላ መሲሑ ይገደላል፤ ምንም አይቀረውም[ጨ]። የሚመጣው አለቃ ሰዎችም፣ ኢየሩሳሌምንና ቤተ መቅደሱን ይደመስሳል። ፍጻሜውም እንደ ጐርፍ ይመጣል፤ ጦርነት እስከ መጨረሻው ይቀጥላል፤ ጥፋትም ታውጆአል። [27]አለቃው ከብዙዎች ጋር ለአንድ ሱባዔ[ጰ] ቃል ኪዳኑን ያጸናል፤ በሱባዔውም እኩሌታ መሥዋዕትና ቍርባን ማቅረብን ያስቀራል። የታወጀው ፍርድ በእርሱ ላይ እስኪፈስ ድረስ፣ ጥፋትን የሚያመጣ የጥፋት ርኵሰት በቤተ መቅደሱ ውስጥ[ጸ] ያቆማል[ፀ]።

## ዳንኤል በራእይ ያየው ሰው

10 የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ በነገሠ በሦስተኛው ዓመት፣ ብልጣሶር ለተባለው ዳንኤል ራእይ ታየው። መልእክቱ እውነት ነው፤ ስለ ታላቅ ጦርነትም የሚገልጽ ነበረ[ፈ]። መልእክቱንም ይገነዘብ ዘንድ በራእይ ማስተዋል ተሰጠው።

[2]በዚያን ጊዜ እኔ ዳንኤል ለሦስት ሳምንት አለቀስሁ፤ [3]ሦስቱም ሳምንት እስኪፈጸም ድረስ ምርጥ ምግብ አልበላሁም፤ ሥጋም ሆነ የወይን ጠጅ ወደ አፌ አልገባም፤ ቅባትም አልተቀባሁም።

[4]በመጀመሪያው ወር በሃያ አራተኛው ቀን፣ በታላቁ በጤግሮስ ወንዝ ዳር ቆሜ፣ [5]ቀና ብዬ ስመለከት፣ በፊቴ በፍታ የለበሰና በወገቡም ላይ ምርጥ የወርቅ ቀበቶ የታጠቀ አንድ ሰው አየሁ። [6]አካሉ እንደ ዕንቍ፣ ፊቱ እንደ መብረቅ፣ ዐይኖቹ እንደሚንበለበል ፋና፣ ክንዶቹና እግሮቹ እንደ ጋለ ናስ የሚያብረቀርቁ፣ ድምፁም እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ ነበር።

[7]ራእዩን ያየሁት እኔ ዳንኤል ብቻ ነበርሁ፤ ከእኔ ጋር የነበሩት ሰዎች አላዩም፤ ነገር ግን ታላቅ ፍርሀት ስለ ወደቀባቸው ሸሽተው ተደበቁ። [8]ስለዚህ ይህን ታላቅ ራእይ እያየሁ ብቻዬን ቀረሁ፤ ምንም ጕልበት አልነበረኝም፤ መልኬ እጅጉን ገረጣ፤ ኀይልም አጣሁ። [9]ከዚያም የቃሉን ድምፅ ሰማሁ፤ የቃሉንም ድምፅ በሰማሁ ጊዜ፣ በግምባሬ በምድር ላይ ተደፍቼ በከባድ እንቅልፍ ተዋጥሁ።

[10]እነሆም፣ አንድ እጅ ዳሰሰኝ፤ እየተንቀጠቀጥሁም በእጄና በጕልበቴ አቆመኝ፤ [11]እርሱም፣ “እጅግ የተወደድህ ዳንኤል ሆይ፣ አሁን ወዳንተ ተልኬአለሁና፣ የምነግርህን አስተውል፤ ቀጥ ብለህም ቁም” አለኝ። ይህን ሲለኝም፣ እየተንቀጠቀጥሁ ተነሥቼ ቆምሁ።

[12]ደግሞም እንዲህ አለኝ፤ “ዳንኤል ሆይ፤ አትፍራ፣ ማስተዋልን ለማግኘትና በአምላክህም ፊት ራስህን ለማዋረድ ከወሰንህበት ከመጀመሪያው ቀን አንሥቶ ቃልህ ተሰምቶአል፤ እኔም የቃልህን መልስ ይዤ መጥቻለሁ። [13]ነገር ግን የፋርስ መንግሥት አለቃ ሃያ አንድ ቀን ተቋቋመኝ፤ ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ የሆነው ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ፤ እኔም በዚያ ከፋርስ ንጉሥ ጋር ተውሁት። [14]ራእዩ ሊፈጸም ገና ብዙ ዘመን ስለ ሚቀረው፣ ወደ ፊት በሕዝብህ ላይ የሚሆነውን ልገልጽልህ አሁን ወደ አንተ መጥቻለሁ።”

[15]ይህን እየተናገረኝ ሳለ፣ ፊቴን ወደ ምድር አቀረቀርሁ፤ የምናገረውንም አጣሁ። [16]ከዚያም የሰው ልጅ የሚመስል[ፐ] ከንፈሮቼን ዳሰሰ፤ እኔም አፌን ከፈትሁ፤ መናገርም ጀመርሁ፤ በፊቴ የነበረውንም እንዲህ አልሁት፤ “ጌታዬ ሆይ፤ ከራእዩ የተነሣ ተሠቃይቻለሁ፤ ኀይልም አጣሁ፤ [17]ጌታዬ ሆይ፤ ጕልበቴ ከዳኝ፤ መተንፈስም አቅቶኛል፣ እኔ አገልጋይህ ከአንተ ጋር መነጋገር እንዴት እችላለሁ?”

[18]እንደ ገናም፣ ሰው የሚመስለው ዳሰሰኝ፤ አበረታኝም። [19]እርሱም፣ “እጅግ የተወደድህ ሰው ሆይ፤ አትፍራ፤ ሰላም ለአንተ ይሁን፤ በርታ፤ ጽና” አለኝ።

እየተናገረኝም ሳለ፣ በረታሁና፣ “ጌታዬ ሆይ፤ አበርትተኸኛልና ተናገር” አልሁት።

9፥22 ዳን7፥16፤ 10፥14፤አሞ3፥7
9፥23 ኢሳ65፥24፤ ዳን10፥11-12፥19፤ ማቴ24፥15፤ሉቃ1፥28
9፥24 ኢሳ1፥26፤ 53፥10፤56፥1፤ዕብ9፥12
9፥25 1ሳሙ13፥14፤ ዕዝ3፥3፤4፥24፤ 6፥15፤ማቴ1፥17፤ ዮሐ 4፥25
9፥26 መዝ46፥8፤ ኢሳ28፥2፤53፥8፤ 61፥1፤ሕዝ4፥5-6፤ ዳን 11፥10፤ ናሆ1፥8፤ ሐጌ 2፥23፤ዘካ4፥14፤ ማቴ16፥21
9፥27 ኢሳ10፥22
10፥1 ዳን1፥7፥21፤ 8፥26
10፥2 ዕዝ9፥4
10፥3 ዳን6፥18
10፥4 ዘፍ2፥14፤ዳን 12፥5
10፥5 ኤር10፥9፤ሕዝ9፥2፤ዳን8፥3፤ራእ 15፥6
10፥6 ዘፀ28፥20፤ ኢዮ41፥19፤ሕዝ 1፥7፤ 24፤ማቴ17፥28፥3፤ራእ1፥15፤19፥12
10፥7 2ነገ6፥17-20፤ ሐሥ9፥7
10፥8 ዘፍ32፥34፤ ኢዮ4፥14፥15፤ ዳን 8፥27፤ዕን3፥16
10፥9 ዳን8፥18፤ ማቴ17፥6
10፥10 ኤር1፥9፤ ራእ1፥17
10፥11 ዘፍ6፥9፤ ሕዝ 2፥1፤ዳን9፥23
10፥12 ዘሌ16፥31፤ ኢሳ65፥24፤ዳን9፥3፥ 20፤ማቴ14፥27
10፥13 ቍ21፤ ኢሳ 24፥21፤ ዳን12፥1፤ይሁ1፥9
10፥14 ሕዝ12፥27፤ ዳን2፥28፤8፥26፤9፥22፤ ዕን2፥3
10፥15 ሕዝ24፥27፤ ሉቃ1፥20
10፥16 ኢሳ6፥7፤ 21፥3፤ኤር1፥9፤ዳን8፥15-18
10፥17 ዳን4፥19
10፥18 ቍ16፤ ዳን 8፥18
10፥19 ኢሱ1፥9፤ መሳ6፥23፤ኢሳ6፥1-8፤ 35፥4፤ዳን9፥23

[የ]24 ወይም *ለማስቆም* [ዶ]24 ወይም *እጅግ ቅዱስ ቦታ፤ ወይም እጅግ ቅዱስ የሆነውን* [ጀ]24 ወይም *ሳምንታት* እንዲሁም ቍ25 እና 26 [ገ]25 ወይም *ቃል* [ጠ]25 ወይም *የተቀባው* እንዲሁም ቍ26 [ጨ]26 ወይም *ይገደላል፤ ብቻውን ይቀራል፤* ወይም *ይገደላል፤ ምንም አይቀረውም* [ጰ]27 ወይም *ሳምንት* [ጸ]27 ወይም *በላዩ ላይ* [ፀ]27 ወይም *በፈረሰችው ከተማ ላይ የታወጀው ፍርድ እስኪፈስና መጨረሻው እስከሚሆን ጥፋት አምጪው በአጸያፊ ቤተ መቅደስ ጫፍ ላይ ይመጣል።* [ፈ]1 ወይም *እውነትና ከባድ ሸክም ነበር* [ፐ]16 አብዛኛ ዎቹ ማሶሬቲክ የጥንት ቅጆች እንዲሁ ሲሆኑ፣ ከማሶሬ ቴክ አንድ የጥንት ቅጂ፣ የሙት ባሕር ጥቅልሎችና ሰብዓ ሊቃናት ግን *ከዚያም የሰው እጅ የሚመስል ነገር* ይላሉ።

[20]እርሱም እንዲህ አለኝ፤ “ለምን ወደ አንተ
እንደ መጣሁ ታውቃለህ? የፋርስን አለቃ
ለመውጋት በቶሎ እመለሳለሁ፤ እኔም
ስሄድ የግሪክ አለቃ ይመጣል። [21]አስቀ
ድሜ ግን በእውነት መጽሐፍ ውስጥ የተጻ
ፈውን እነግርሃለሁ፤ ከእነዚህ አለቆች ጋር
ለመዋጋት ከአለቃችሁ ከሚካኤል በስተቀር
የሚረዳኝ የለም።

**11** እኔም፣ ሜዶናዊው ዳርዮስ በነገሠ
በመጀመሪያው ዓመት፣ እርሱን ለማ
ገዝና ለማበረታታት በአጠገቡ ቆሜ ነበር።

## የሰሜንና የደቡብ ነገሥታት

[2]“አሁንም እውነቱን እነግርሃለሁ፤ እነሆ፣
ሦስት ሌሎች ነገሥታት በፋርስ ይነሣሉ፤
አራተኛውም ከሌሎቹ ሁሉ ይልቅ እጅግ
ባለጠጋ ይሆናል። በባለጠግነቱም እጅግ
በበረታ ጊዜ፣ ሌላውን ሁሉ አሳድሞ በግ
ሪክ መንግሥት ላይ ያስነሣል። [3]ከዚያም
በታላቅ ኀይል የሚገዛና የወደደውንም
ሁሉ የሚያደርግ ኀያል ንጉሥ ይነሣል።
[4]በኀይል እየገነነ ሳለም፣ መንግሥቱ ይፈር
ሳል፤ ወደ አራቱ የሰማይ ነፋሳትም ይከፋ
ፈላል። መንግሥቱ ተወስዶ ለሌሎች ስለ
ሚሰጥ፣ ለዘሩ አይተላለፍም፤ ኀይሉም እንደ
መጀመሪያው አይሆንም።

[5]“የደቡቡ ንጉሥ ይበረታል፤ ነገር ግን
ከጦር አዛዦቹ አንዱ ከእርሱ የበለጠ የበ
ረታ ይሆናል፤ ግዛቱም ታላቅ ይሆናል።
[6]ከጥቂት ዓመታት በኋላም አንድነት ይፈ
ጥራሉ። የደቡቡ ንጉሥ ሴት ልጅ ስምምነት
ለማድረግ ወደ ሰሜኑ ንጉሥ ትሄዳለች፤ ነገር
ግን ኀይሏን ይዛ መቈየት አትችልም፤ እር
ሱም ሆነ የእርሱ ኀይል[ሀ] አይጸናም። በእነ
ዚያ ቀናት እርሷ ከቤተ መንግሥት አጃ
ቢዎቿ፣ ከአባቷና[ለ] ከደጋፊዎቿ ጋር ዐልፋ
ትሰጣለች።

[7]“ከዘመዶቿ አንዱ ስፍራዋን ሊይዝ ይነ
ሣል፤ የሰሜኑን ንጉሥ ሰራዊት ይወጋል፤
ምሽጎቹንም ጥሶ ይገባል፤ ከእነርሱም ጋር
ተዋግቶ ድል ያደርጋል። [8]አማልክታቸውን፣
የብረት ምስሎቻቸውን፣ ከብርና ከወርቅ
የተሠሩ የከበሩ ዕቃዎቻቸውን ይማርካል፤
ወደ ግብፅም ይወስዳል። ለጥቂት ዓመታ
ትም ከሰሜኑ ንጉሥ ጋር ከመዋጋት ይቈጠ
ባል። [9]የሰሜኑም ንጉሥ፣ የደቡቡን ንጉሥ
ግዛት ይወራል፤ ነገር ግን አፈግፍጎ ወደ
ገዛ አገሩ ይመለሳል። [10]ወንዶች ልጆቹም
ለጦርነት ይዘጋጃሉ፤ እስከ ጠላት ምሽግ
ደርሶ የሚዋጋና ሊቋቋሙት እንደማይቻል
ጐርፍ የሚጠራርግ ታላቅ ሰራዊት ያሰባስ
ባሉ።

[11]“ከዚያም የደቡቡ ንጉሥ በቍጣ ወጥቶ
የሰሜኑን ንጉሥ ይወጋል። የሰሜኑ ንጉሥ
ታላቅ ሰራዊት ቢያሰባስብም ይሸነፋል።
[12]የደቡቡ ንጉሥ ብዙ ሰራዊት በሚማርክ
በት ጊዜ ልቡ በትዕቢት ይሞላል፤ በብዙ
ሺህ የሚቈጠሩ ሰዎችንም ይገድላል፤ ነገር
ግን በድል አድራጊነቱ አይጸናም።
[13]የሰሜን ንጉሥ ከመጀመሪያው የሚበ
ልጥ ታላቅ ሰራዊት ያሰባስባል፤ ከብዙ ዓመ
ትም በኋላ በትጥቅ እጅግ ከተደራጀ
ታላቅ ሰራዊት ጋር ተመልሶ ይመጣል።
[14]“በዚያም ዘመን ብዙዎች በደቡብ
ንጉሥ ላይ ይነሣሉ፤ ራእዩ ይፈጸም ዘንድ፣
ከሕዝብህ መካከል ዐመፀኛ የሆኑ ሰዎች
ይነሣሉ፤ ነገር ግን አይሳካላቸውም። [15]የሰሜ
ኑም ንጉሥ መጥቶ የዐፈር ድልድል ይክ
ባል፤ የተመሸገችውንም ከተማ ይይዛል።
የደቡቡ ሰራዊትም ለመቋቋም ኀይል ያጣል፤
የተመረጡት ተዋጊዎቻቸው እንኳ ጸንተው
መዋጋት አይችሉም። [16]ወራሪው ደስ ያሰ
ኘውን ያደርጋል፤ ማንም ሊቋቋመው አይ
ችልም። በመልካሚቱ ምድር ላይ ይገዛል፤
እርሷን ለማጥፋትም ኀይል ይኖረዋል።
[17]በመንግሥቱ ያለውን ሰራዊት ሁሉ ይዞ
ለመምጣት ይወስናል፤ ከደቡብም ንጉሥ
ጋር ይስማማል፤ ይህንም መንግሥት ለመ
ጣል ሴት ልጁን ይድርለታል፤ ይሁን
እንጂ ዕቅዱ[ሐ] አይሳካለትም፤ ያሰበውም ነገር
አይጠቅመውም። [18]ከዚህም በኋላ በባሕር
ጠረፍ ወዳሉት አገሮች ፊቱን በመመለስ
ብዙዎቹን ይይዛል፤ ነገር ግን አንድ አዛዥ
ትዕቢቱን ያከሽፍበታል፤ በራሱም ላይ ይመ
ልስበታል። [19]በገዛ አገሩ ወዳሉት ምሽጎችም
ፊቱን ይመልሳል፤ ነገር ግን ተሰናክሎ
ይወድቃል፤ ዳግምም አይታይም።
[20]“በእርሱ ቦታ የሚተካውም የመንግሥቱን
ክብር ለማስጠበቅ ግብር አስገባሪ ይልካል፤
ይሁን እንጂ በቍጣ ወይም በጦርነት ሳይ
ሆን በጥቂት ዓመታት ውስጥ ይገደላል።
[21]“በእርሱም ፋንታ የተናቀ ሰው ይነግ
ሣል፤ ንጉሣዊ ክብርም አይሰጠውም፤ ሕዝቡ
በሰላም ተቀምጦ ሳለ በተንኰል መንግሥ
ቱን ይይዛል። [22]ከፊቱ የሚቆመውን ታላቅ
ሰራዊት፣ የቃል ኪዳኑንም አለቃ ሳይቀር
ይደመስሳል። [23]ከእርሱ ጋር ስምምነት ከተ
ደረገ በኋላ የማታለል ሥራውን ይሠራል፤
ከጥቂት ሰዎች ጋር ለሥልጣን ይበቃል።
[24]የበለጸጉትን ክፍለ አገሮች በሰላም ሳሉ
በድንገት ይወርራቸዋል፤ አባቶቹም ሆኑ
አያቶቹ ያላደረጉትን ነገር ያደርጋል፤ ይከና

10፥20 ዳን8፥21፤ 11፥2
10፥21 ቍ13፤ዳን 11፥2፤ይሁ1፥9
11፥1 ዳን5፥31
11፥2 ዳን10፥20፡21
11፥3 ዳን8፥4፡21
11፥4 ዳን7፥2፤ 8፥22፤ኤር42፥10
11፥7 ቍ6
11፥8 ኢሳ37፥19፤ 46፥1-2፤ ኤር43፥12፤ ዳን9፥26
11፥10 ኢሳ8፥8፤ ኤር46፥8፤ዳን9፥26
11፥11 ዳን8፥7-8
11፥15 ሕዝ 4፥2
11፥16 ኢሱ 1፥5፤ ዳን 8፥4፡7፡9
11፥17 መዝ20፥4፤ ኢሳ 66፥19፤ኤር 25፥22፤ሆሴ 12፥14
11፥19 መዝ27፥2፤ 37፥36፤46፥2፤ሕዝ 26፥21
11፥20 ኢሳ60፥17
11፥21 ዳን4፥17፤ 8፥25
11፥22 ኢሳ28፥15፤ ዳን8፥10-11
11፥23 ዳን8፥25
11፥24 ነህ9፥25

[ሀ]6 ወይም *ዘሩ* [ለ]6 ወይም *ከልጇና* (ቫልጌትንና ሱርስትን ይመ) [ሐ]17 ወይም *እርሷ*

ወንለታልም፤ ብዝበዛውን፣ ምርኮውንና የተ
ገኘውን ሀብት ሁሉ ለተከታዮቹ ያካፍላ
ቸዋል፤ ምሽጎችን ለመጣል ያሤራል፤ ይህን
የሚያደርገውም ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነው።
25“ታላቅ ሰራዊት አደራጅቶ ኀይሉንና
ብርታቱን በደቡብ ንጉሥ ላይ ያነሣሣል፤
የደቡብ ንጉሥም ቍጥሩ እጅግ ብዙ የሆነ
ኀያል ሰራዊት ይዞ ጦርነትን ያውጃል፤
ነገር ግን ከተዶለተበት ሤራ የተነሣ መቋቋም
አይችልም። 26ከንጉሥ ማዕድ አብረውት
ሲበሉ የነበሩት ሊያጠፉት ያሤራሉ፤ ሰራ
ዊቱም ይደመሰሳል፤ ብዙዎቹም በጦርነት
ይወድቃሉ። 27ልባቸው ወደ ክፉት ያዘነበ
ለው ሁለቱ ነገሥታት፣ በአንድ ገበታ
አብረው ይቀመጣሉ፤ እርስ በርሳቸውም
ሐሰትን ይነጋገራሉ፤ ነገር ግን የተወሰነው
ጊዜ ገና ስለ ሆነ አይከናወንላቸውም።
28የሰሜን ንጉሥ ብዙ ሀብት ይዞ ወደ ገዛ
አገሩ ይመለሳል፤ ነገር ግን ልቡ በተቀደሰው
ኪዳን ላይ ይነሣሣል፤ ክፉ ነገርም ያደርግ
በታል፤ ከዚያም ወደ ገዛ አገሩ ይመለሳል።
29“በተወሰነው ጊዜ ደቡቡን እንደ ገና
ይወራል፤ በዚህ ጊዜ ግን ውጤቱ ከበፊቱ
የተለየ ይሆናል። 30የኪቲም[መ] መርከቦች
ይቃወሙታል፤ ልቡም ይሸበራል። ወደ ኋላም
ይመለሳል፤ ቍጣውን በተቀደሰው ኪዳን
ላይ ያወርዳል፤ ተመልሶም የተቀደሰውን
ኪዳን የተውትን ይንከባከባል።
31“የጦር ሰራዊቶቹም ቤተ መቅደሱንና
ቅጥሩን ያረክሳሉ፤ የዘወትሩንም መሥዋዕት
ያስቀራሉ፤ በዚያም ጥፋትን የሚያመጣ
ውን የጥፋት ርኵሰት ይተክላሉ፤ 32ኪዳ
ኑን የሚተላለፉትን በማታለል ያስታል፤
አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝብ ግን
ጸንተው ይቃወሙታል፤ እርምጃም
ይወስዳሉ።
33“ለጊዜው በሰይፍ ቢወድቁም፣ ቢቃ
ጠሉም፣ ቢማረኩና ቢዘረፉም፣ ጥበበኛ
የሆኑ ሰዎች ብዙዎችን ያስተምራሉ። 34በሚ
ወድቁበት ጊዜ መጠነኛ ርዳታ ያገኛሉ፤
እውነተኛ ያልሆኑ ብዙ ሰዎችም ይተባበሯቸ
ዋል። 35ጥበበኛ ከሆኑ ሰዎች አንዳንዶቹ ይሰ
ናከላሉ፤ ይህም እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ
የጠሩ፣ የነጠሩና እንከን የሌለባቸው ይሆኑ
ዘንድ ነው፤ የተወሰነው ጊዜ ገና አልደረሰምና።

## ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ንጉሥ

36“ንጉሡ ደስ እንዳለው ያደርጋል፤ ከአማል
ክት ሁሉ በላይ ራሱን እጅግ ከፍ በማድረግ
በአማልክት አምላክ ላይ ተሰምቶ የማይታወቅ
የስድብ ቃል ይናገራል፤ የቍጣውም ዘመን
እስኪፈጸም ድረስ ይሳካለታል፤ የተወሰነው
ነገር ሁሉ መሆን አለበትና። 37ሴቶች
ለሚወዱትም ሆነ ለአባቶቹ አማልክት
ክብርን አይሰጥም፤ ማንኛውንም አምላክ
አያከብርም፤ ነገር ግን ራሱን ከእነዚህ
ሁሉ በላይ ከፍ ከፍ ያደርጋል። 38በእነ
ርሱም ምትክ የምሽጎችን አምላክ ያከብ
ራል፤ አባቶች የማያውቁትን አምላክ
በወርቅ፣ በብር፣ በከበሩ ድንጋዮችና
በውድ ስጦታዎች ያከብራል። 39በባዕድ
አምላክ ርዳታ ጽኑ ምሽጎችን ይወጋል፤
ለእርሱ የሚገዙትን በእጅጉ ያከብራቸዋል፤
በብዙ ሕዝብ ላይ ገዦች ያደርጋቸዋል፤
ምድሩንም በዋጋ ያከፋፍላቸዋል።
40“በመጨረሻው ዘመን የደቡብ ንጉሥ
ጦርነት ያውጅበታል፤ የሰሜን ንጉሥም
በፈረሰኞችና በሠረገሎች፣ በብዙ መር
ከቦችም እንደ ማዕበል ይመጣበታል፤ ብዙ
አገሮችን ይወራል፤ እንደ ጐርፍም እየጠ
ራረገ በመካከላቸው ያልፋል። 41መልካ
ሚቱንም ምድር ይወራል፤ ብዙ አገሮች በእጁ
ይወድቃሉ፤ ኤዶም፣ ሞዓብና የአሞን
መሪዎች ግን ከእጁ ያመልጣሉ። 42ሥል
ጣኑን በብዙ አገሮች ላይ ያንሰራፋል፤
ግብፅም አታመልጥም። 43የወርቅና የብር
ክምችትን፣ እንዲሁም የግብፅን ሀብት ሁሉ
በቍጥጥሩ ሥር ያደርጋል፤ የሊቢያና
የኢትዮጵያ[ሠ] ሰዎችም ይገዙለታል። 44ነገር
ግን ከምሥራቅና ከሰሜን የሚመጣ ወሬ
ያስደነግጠዋል፤ ብዙዎችንም ለማጥፋትና
ለመደምሰስ በታላቅ ቁጣ ይወጣል።
45ንጉሣዊ ድንኳኖቹን በባሕሮች መካከል[ረ]
ውብ በሆነው ቅዱስ ተራራ ላይ ይተክላል፤
ይሁን እንጂ ወደ ፍጻሜው ይመጣል፤ ማንም
አይረዳውም።

## የመጨረሻ ዘመን

12 “በዚያን ዘመን ስለ ሕዝብህ የሚቆ
መው ታላቁ አለቃ ሚካኤል
ይነሣል። መንግሥታት ከተመሠረቱበት ጊዜ
ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ ታይቶ የማ
ይታወቅ ታላቅ የመከራ ጊዜ ይሆናል።
ነገር ግን በዚያን ጊዜ ስማቸው በመጽሐፉ
ተጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ ይድናሉ።
2በምድር ዐፈር ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች
ይነቃሉ፤ አንዳንዶቹ ለዘላለም ሕይወት፣
ሌሎቹም ለውርደትና ለዘላለም ጉስቍልና
ይነሣሉ። 3ጥበበኞች[ሰ] እንደ ሰማይ ጸዳል፣
ብዙዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ
ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ። 4ዳንኤል
ሆይ፤ አንተ ግን፣ እስከ ፍጻሜው ዘመን
ድረስ የመጽሐፉን ቃል ዝጋ፤ አትመውም።
ብዙዎች ወዲያ ወዲህ ይራወጣሉ፤ ዕውቀ

[መ]30 ወይም *የምዕራብ ባሕር ዳር አገሮች* [ሠ]43 ወይም *የኑቢያ ወይም የኩሽ* [ረ]45 ወይም *በባሕርና ውብ....መካከል* [ሰ]3 ወይም *ጥበብን የሚገልጡ*

11፥27 መዝ12፥2፤ 64፥6፤ ኤር9፥5፤ዕን 2፥3
11፥30 ዘፍ10፥4፤ 1ሳሙ17፥32፤ ኢዮ 15፥13
11፥31 ኤር19፥4፤ ዳን8፥11-13፤9፥27፤ ሆሴ3፥4፤ማቴ24፥15፤ ማር 13፥14
11፥32 ሚክ5፥7-9
11፥33 ዳን12፥3፤ ሚል2፥7፤ማቴ24፥9፤ ዮሐ16፥2፤ዕብ 11፥32-38
11፥34 ማቴ7፥15፤ ሮሜ16፥18
11፥35 ኢዮ28፥1፤ መዝ78፥38፤ኢሳ48፥10፤ዳን12፥10፤ዘካ13፥9፤ዮሐ15፥2
11፥36 ዘዳ10፥17፤ ኢሳ10፥25፤14፥13-14፤26፥20፤ሕዝ35፥13፤ ዳን7፥25፤8፥11-12፥24፥25፤2ተሰ2፥4፤ይሁ 1፥16፤ራእ13፥5-6
11፥40 ኢሳ5፥28፤ 8፥7፤21፥1፤ሕዝ38፥4
11፥41 ኢሳ11፥14፤ ኤር48፥47፤ሕዝ 20፥6፤ሚል3፥12
11፥43 2ዜና12፥ 3፤ ሕዝ 30፥4፤ናሆ3፥9
11፥45 ኢሳ2፥2፥4፤ ዳን8፥9
12፥1 ዘፀ32፥32፤ መዝ56፥8፤ኤር17፥13፤ 30፥7፤ዳን9፥12፤10፥13፤ ማቴ24፥21፤ማር13፥19፤ሉቃ10፥20፤ይሁ 1፥9፤ራእ16፥18
12፥2 ኢሳ26፥19፤ ማቴ25፥46፤ዮሐ11፥24
12፥3 ምሳ4፥18፤ ኢሳ6፥7፤ዳን11፥33፤ ማቴ13፥43፤ዮሐ5፥35፤ 1ቆሮ15፥42፤ፊል2፥15
12፥4 ቍ9፥13፤ኢሳ 8፥16፤ኤር5፥1፤ራእ 22፥10
12፥5 ዳን10፥4

ትም ይበዛል።
5እኔም ዳንኤል ተመለከትሁ፤ እነሆ
ከፊት ለፊቴ ሌሎች ሁለት ቆመው ነበር፤
አንዱ ከወንዙ በዚህኛው ዳር፣ ሌላው
ደግሞ ከወንዙ በዚያኛው ዳር። 6ከእነርሱም
አንዱ፣ ከወንዙ ውሃ በላይ የነበረውንና
በፍታ የለበሰውን ሰው፣ “እነዚህ አስደናቂ
ነገሮች ሊፈጸሙ ምን ያህል ጊዜ ይቀራል?”
አለው።
7ከወንዙ ውሃ በላይ የነበረው በፍታ የለ
በሰው ሰው፣ ቀኝ እጁንና ግራ እጁን ወደ
ሰማይ አንሥቶ፣ “ለዘመን፣ ለዘመናት፣
ለዘመንም እኩሌታ[ሽ] ይሆናል፤ የተቀደሰው
ሕዝብ ኀይል መሰበር ሲያከትም፣ እነዚህ
ሁሉ ነገሮች ይፈጸማሉ” ብሎ ለዘላለም በሚ
ኖረው በእርሱ ሲምል ሰማሁ።
8እኔም ሰማሁ፤ ነገር ግን አላስተዋልሁ
ትም፤ ስለዚህ፣ ጌታዬ ሆይ፤ የዚህ ሁሉ
ፍጻሜ ምንድነው?” ብዬ ጠየቅሁ።
9እርሱም እንዲህ አለኝ፤ “ዳንኤል ሆይ፤
ቃሉ እስከ ፍጻሜው ዘመን ድረስ የተዘ
ጋና የታተመ ስለ ሆነ ሂድ፤ 10ብዙዎች
ይነጻሉ፤ ይጠራሉ፤ እንከን አልባም ይሆናሉ፤
ክፉዎች ግን በክፉታቸው ይጸናሉ፤
ከክፉዎች አንዳቸውም አያስተውሉም፤
ጠቢባን ግን ያስተውላሉ።
11“የዘወትሩ መሥዋዕት ከተቋረጠበትና
ጥፋት የሚያመጣው አስጸያፊ ርኵሰት
ከተተከለበት ጊዜ ጀምሮ አንድ ሺህ ሁለት
መቶ ዘጠና ቀን ይሆናል። 12የሚታገሥና
እስከ አንድ ሺህ ሦስት መቶ ሠላሳ አም
ስት ቀን ፍጻሜ የሚደርስ የተባረከ ነው።
13“አንተ ግን እስከ ፍጻሜው ድረስ
ሂድ፤ ታርፋለህ፤ በቀኖቹ መጨረሻም ተነ
ሥተህ የተመደበልህን ርስት ትቀበላለህ።”

12፥6 ዳን8፥13፤ሕዝ 9፥2
12፥7 ዘፍ14፥22፤ ዳን6፥26፤7፥25፤8፥24፤ ሉቃ21፥24፤ራእ 10፥5-6፤7፤11፥2
12፥9 ቁ-4፤ኢሳ 29፥11
12፥10 ኢሳ1፥25፤ 32፥7፤ዳን11፥35፤ ሆሴ14፥9፤ ራእ 22፥11
12፥11 ዘፀ29፥38፤ ዳን8፥11፤9፥27፤ ማቴ24፥15፤ማር13፥14፤ራእ11፥2
12፥12 ኢሳ30፥18፤ሕዝ4፥5-6፤ ዳን8፥14
12፥13 ቁ-4፤መዝ 16፥5፤ኢሳ57፥2፤ ማቴ 10፥22፤ያዕ1፥12፤ራእ 14፥13

[ሽ]7 ወይም *ለዓመት፣ ለሁለት ዓመታት፣ ለዓመትም እኩሌታ*

# ትንቢተ ሆሴዕ

1 በይሁዳ ነገሥታት በዖዝያን፣ በኢዮአ
ታም፣ በአካዝና በሕዝቅያስ ዘመን
እንዲሁም በእስራኤል ንጉሥ በዮአስ[ሀ] ልጅ
በኢዮርብዓም ዘመን ወደ ብኤሪ ልጅ ወደ
ሆሴዕ የመጣው *የእግዚአብሔር* ቃል ይህ
ነው፤

## የሆሴዕ ሚስትና ልጆቹ

2*እግዚአብሔር* በሆሴዕ መናገር በጀመረ
ጊዜ፣ *እግዚአብሔር* "ምድሪቱ *ከእግዚአ
ብሔር* ተለይታ ታላቅ ምንዝርና እያደረ
ገች ስለ ሆነ፣ ሂደህ አመንዝራ ሴት
አግባ፤ የምንዝርና ልጆችንም ለራስህ ውሰድ"
አለው። 3ስለዚህ እርሱ የዴቤላይምን ሴት
ልጅ ጎሜርን አገባ፤ እርሷም ፀነሰች፤ ወንድ
ልጅም ወለደችለት።
4*እግዚአብሔርም* ሆሴዕን እንዲህ አለው፤
"በኢይዝራኤል ስለ ተፈጸመው ግድያ
የኢዩን ቤት በቅርቡ ስለምቀጣና የእስራ
ኤልንም መንግሥት እንዲያከትም ስለማደ
ርግ፣ ስሙን ኢይዝራኤል ብለህ ጥራው።
5በዚያም ቀን በኢይዝራኤል ሸለቆ፣ የእ
ስራኤልን ቀስት እሰብራለሁ።"
6ጎሜር እንደ ገና ፀነሰች፤ ሴት ልጅም
ወለደች፤ *እግዚአብሔርም* ሆሴዕን እንዲህ
አለው፤ "ይቅር እላቸው ዘንድ ለእስራኤል
ቤት ከእንግዲህ ስለማልራራላቸው፣ ስሟን
ሎሩሃማ[ለ] ብለህ ጥራት። 7ነገር ግን ለይ
ሁዳ ቤት እራራለሁ፤ በቀስት ወይም በሰ
ይፍ ወይም በጦርነት ወይም በፈረሶችና
በፈረሰኞች ሳይሆን በአምላካቸው *በእግዚአ
ብሔር* አድናቸዋለሁ።"
8ጎሜር፣ ሎሩሃማን ጡት ካስጣለች
በኋላ ሌላ ወንድ ልጅ ወለደች። 9*እግዚአ
ብሔርም* እንዲህ አለው፤ "ሎዓሚ[ሐ] ብለህ
ጥራው፤ ምክንያቱም እናንተ ሕዝቤ አይደ
ላችሁም፤ እኔም አምላካችሁ
አይደለሁምና።
10"ይሁን እንጂ እስራኤላውያን ሊሰፈ
ርና ሊቈጠር እንደማይችል እንደ ባሕር
አሸዋ ይሆናሉ፤ 'ሕዝቤ አይደላችሁም'
በተባሉበት ቦታ፣ 'የሕያው አምላክ
ልጆች' ተብለው ይጠራሉ። 11የይሁዳ ሕ
ዝብና የእ ስራኤል ሕዝብ እንደ ገና
አንድ ይሆናሉ አንድ መሪም ይሾማሉ፤
አንድ ሆነውም በምድሪቱ ይገናሉ፤ የኢይዝ
ራኤል ቀን ታላቅ ይሆናልና።

2 "ወንድሞቻችሁን 'ሕዝቤ'፣ እኅቶቻች
ሁንም 'ተወዳጆቼ' ብላችሁ ጥሯቸው።

## የእስራኤል መቀጣትና መመለስ

2"እናታችሁን ምከሯት፤ ምከሯት፤
እርሷ ሚስቴ አይደለችም፤
እኔም ባሏ አይደለሁምና።
ከፊቷ የዘማዊነት አስተያየትን፣
ከጡቶቿም መካከል ምንዝርናዋን
ታስወግድ።
3አለበለዚያ ገፍፌ ዕርቃኗን
አስቀራታለሁ፤
እንደ ተወለደችበትም ቀን
አደርጋታለሁ፤
እንደ ምድረ በዳ፣
እንደ ደረቅም ምድር አደርጋታለሁ፤
በውሃ ጥምም እገድላታለሁ።
4ለልጆቿ አልራራላቸውም፤
የምንዝርና ልጆች ናቸውና።
5እናታቸው አመንዝራ ነች፤
በውርደትም ፀንሳቻዋለች፤
እርሷም፣ 'እንጀራዬንና ውሃዬን
ይሰጡኛል፤
ሱፌንና የሐር ልብሴን፣ ዘይቴንና
መጠጤን ይሰጡኛል፤
ስለዚህ ውሽሞቼን ተከትዬ እሄዳለሁ'
አለች።
6በዚህ ምክንያት መንገዷን በእሾህ
እዘጋለሁ፤
መውጫ መንገድ እንዳታገኝም
ዙሪያዋን በግንብ አጥራለሁ።
7ውሽሞቿን ተከትላ ትሄዳለች፤ ነገር ግን
አትደርስባቸውም፤
ትፈልጋቸዋለች፤ ሆኖም
አታገኛቸውም።
ከዚያም እንዲህ ትላለች፤
'ወደ ቀድሞ ባሌ እመለሳለሁ፤
የፊተኛው ኑሮዬ ከአሁኑ ይሻለኛልና።'
8እርሷም እህል፣ ዘይትና አዲስ የወይን
ጠጅ የሰጠኋት፣
ለበኣል አምልኮ ያደረጉትን፣
ብርንና ወርቅን ያበዛሁላት፣
እኔ እንደ ሆንሁ አላወቀችም።
9"ስለዚህ እህሌን በመከር ጊዜ፣
አዲሱም የወይን ጠጅ በደረሰ ጊዜ
እወስዳለሁ፤
ዕርቃኗንም እንዳትሸፍንበት፣
ሱፍና የሐር ልብሴን መልሼ

[ሀ]1 በዕብራይስጥ *ዮአስ* የሚለው ቃል *የኢዮአስ* አማራጭ ትር ጕም ነው [ለ]6 *ሎሩሃማ* ማለት *ያልተወደደች* ማለት ነው
[ሐ]9 *ሎዓሚ* ማለት *ሕዝቤ አይደለም* ማለት ነው

1፥1 2ነገ13፥13፤ 14፥21፤1ዜና3፥12፡13፤ኢሳ1፥1፤ኤር1፡2፤ ሚክ1፥1አሞ1፥1
1፥2 ዘዳ31፥16፤ኤር 3፥1፡14፤ሕዝ 23፥3ጠ 21፤ ሆሴ2፥2፡5፤ 3፥1፤5፥3
1፥3 ቍ6
1፥4 ቍ11፤1ሳሙ 29፥1፤1ነገ18፥45፤ 2ነገ10፥114፤ ሆሴ2፥22
1፥5 ኢሱ15፥56፤ 1ሳሙ29፥1፤ 2ነገ15፥29
1፥6 ቍ3፡8፤ ሆሴ2፥4፡23
1፥7 መዝ44፥6፤ ዘካ4፥6
1፥8 ቍ6
1፥9 ቍ10፤ሕዝ 11፥1920፤1ጴጥ2፥10
1፥10 ቍ9፤ዘፍ 22፥17፤ኢሱ3፥10፤ ኤር33፥22፤ሆሴ2፥23፤ ሮሜ9፥26
1፥11 ቍ4፤ኢሳ11፥ 12፡13፤ኤር23፥5-8፤ 30፥9፤ሕዝ37፥15-28
2፥1 ቍ23፤ 1ጴጥ2፥10
2፥2 ቍ5፤ኢሳ 1፥21፤50፥1፤ሕዝ 23፥45፤ሆሴ1፥2፤4፥5
2፥3 ኢሳ32፥13-14፤ ሕዝ16፥4፡22፡37
2፥4 ሕዝ8፥18፤ ሆሴ1፥6፤5፥7
2፥5 ኤር3፥6፤ 44፥1718፤ሆሴ1፥2
2፥6 ኢዮ3፥23፤ 19፥8፤ሰቆ3፥9
2፥7 ኢሳ54፥5፤ ኤር2፥2፤3፥1፤ሕዝ 16፥8፤ሆሴ5፥13
2፥8 ቍ13፤ዘኍ 18፥12፤ዘዳ8፥18፤ኢሳ 1፥3፤ሕዝ16፥1519፤ ሆሴ8፥4
2፥9 ሆሴ8፥7፤9፥2

እወስድባታለሁ፡፡
[10]አሁንም በውሽሞቿ ፊት፣
ነውሯን እገልጣለሁ፤
ከእጄም የሚያድናት የለም፡፡
[11]የደስታ በዓሎቿን ሁሉ፣
የዓመት በዓሎቿንና፣ የወር መባቻዎቿን
ሰንበቶቿንና የተመረጡ በዓሎቿን ሁሉ
አስቀራለሁ፡፡
[12]ከውሽሞቼ የተቀበልሁት ዋጋ ነው
የምትለውን፤
የወይን ተክሎቿንና የበለስ ዛፎቿን
አጠፋለሁ፤
ጫካ አደርገዋለሁ፤
የዱር አራዊትም ይበሉታል፡፡
[13]ለበኣል አማልክት፣ ዕጣን ስላጠነችባቸው
ቀናት እቀጣታለሁ፤
በጌጣ ጌጥና በቀለበቶች ራሷን አስጊ
ጣለች፤
ውሽሞቿንም ተከትላ ሄዳለች፤
እኔን ግን ረስታለች”
ይላል *እግዚአብሔር*፡፡

[14]“ስለዚህ እነሆ፤ አባብላታለሁ፤
ወደ ምድረ በዳም እወስዳታለሁ፤
በፍቅር ቃል አነጋግራታለሁ፡፡
[15]በዚያም የወይን ተክሏን እመልስላታለሁ፤
የአኮርንም[መ] ሸለቆ የተስፋ በር
እንዲሆናት አደርጋለሁ፡፡
በዚያም ከግብፅ እንደ ወጣችበት ቀን፣
እንደ ልጅነቷም ጊዜ ትዘምራለች፡፡[ሠ]

[16]“በዚያ ቀን፣ ‘ባሌ’ ብለሽ፣
ትጠሪኛለሽ”
ይላል *እግዚአብሔር*፡፡
“ከእንግዲህም፣ ‘ጌታዬ’[ረ] ብለሽ
አትጠሪኝም፡፡
[17]የበኣል አማልክትን ስም ከአንደበቷ
አስወግዳለሁ፤
ከእንግዲህም ስሞቻቸው አይነሡም፡፡
[18]በዚያን ቀን ከምድር አራዊትና ከሰማይ
ወፎች፣
በምድርም ላይ ከሚንቀሳቀሱ ፍጥረት
ጋር፣
ቃል ኪዳን አደርግላቸዋለሁ፤
ሁሉም በሰላም እንዲኖሩ፣
ቀስትን፣ ሰይፍንና ጦርነትን፣
ከምድሪቱ አስወግዳለሁ፡፡
[19]ለእኔ እንድትሆኚ ለዘላለም አጭሻለሁ፤
በጽድቅና በፍትሕ፣
በፍቅርና በርኅራኄም አጭሻለሁ፡፡
[20]በታማኝነት አጭሻለሁ፤
አንቺም *እግዚአብሔርን* ታውቂያለሽ፡፡

[21]*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“በዚያ ቀን እኔ እመልሳለሁ፤
ለሰማያት እመልሳለሁ፤
እነርሱም ለምድር ምላሽ ይሰጣሉ፤
[22]ምድርም ለእህል፣
ለአዲስ የወይን ጠጅና ለዘይት ምላሽ
ትሰጣለች፤
እነርሱም ለኢይዝራኤል[ሰ] ምላሽ
ይሰጣሉ፡፡
[23]ስለ ራሴ ስል በምድሪቱ እተክላታለሁ፤
‘ምሕረትን ያላገኘ’[ሸ] ብዬ የጠራሁትንም
እምረዋለሁ፤
‘ሕዝቤ አይደላችሁም’[ቀ] ተብለው
የተጠሩትንም፣ ‘ሕዝቤ’ እላቸዋለሁ፤
እነርሱም፣ ‘አንተ አምላኬ ነህ’
ይላሉ፡፡”

## የሆሴዕ ከሚስቱ ጋር መታረቅ

3 *እግዚአብሔር* እንዲህ አለኝ፤ “እርሷ
በሌላ ሰው የምትወደድ አመንዝራ
ብትሆንም፣ አሁንም ሂድና ሚስትህን
ውደዳት፤ ወደ ሌሎች አማልክት ዘወር
ቢሉና ለእነርሱም የተቀደሰውን የዘቢብ
ጥፍጥፍ ቢወዱም፣ *እግዚአብሔር* እስራ
ኤላውያንን እንደ ወደዳቸው አንተም
እርሷን ውደዳት፡፡”
[2]ስለዚህ በዐሥራ አምስት ሰቅል ጥሬ
ብርና በአንድ ቆሮስ ተኩል መስፈሪያ ገብስ
ገዛኋት፡፡ [3]እኔም፣ “ከእኔ ጋር ብዙ ቀን
ተቀመጪ፤[በ] አታመንዝሪ ወይም ሌላ ሰው
አትውደጂ፤ እኔም ከአንቺ ጋር እኖራ
ለሁ” ብዬ ነገርኋት፡፡
[4]እስራኤላውያን ለብዙ ዘመን ያለ ንጉ
ሥና ያለ አለቃ፣ ያለ መሥዋዕትና ያለ ዐምደ
ጣዖት፣ ያለ ኤፉድና ያለ ጣዖት ምስል
ይኖራሉና፡፡ [5]ከዚያ በኋላ እስራኤላውያን
ተመልሰው አምላካቸውን *እግዚአብሔርን*ና
ንጉ ሣቸውን ዳዊትን ይፈልጋሉ፤
በመጨረሻ ውም ዘመን በመንቀጥቀጥ ወደ
*እግዚአብሔ ር*ና ወደ በረከቱ ይመጣሉ፡፡

## በእስራኤል ላይ የቀረበ ክስ

4 በምድሪቱ በምትኖሩ በእናንተ ላይ
*እግዚአብሔር* የሚያቀርበው ክስ
ስላለው፣
እናንት እስራኤላውያን ይህን
*የእግዚአብሔርን* ቃል ስሙ፤
“ታማኝነት የለም፤ ፍቅርም የለም፤
እግዚአብሔርንም ማወቅ በምድሪቱ
የለም፡፡
[2]በዚያ ያለው ርግማን፣[ተ] መዋሸት፣

2፥10 ኤር13፥26፤ ሕዝ16፥37፤23፥10
2፥11 ኢሳ1፥14፤ 24፥8፤ኤር7፥34፤16፥9፤ሆሴ3፥4፤9፥5፤ አሞ5፥21፤8፥10
2፥12 ኢሳ5፥6፤ 7፥23፤ኤር3፥1፤5፥17፤ 8፥13፤ሆሴ5፥7፤13፥8
2፥13 ቍ8፤ኢሳ65፥ 7፤ኤር7፥9፤44፥17፤ ሕዝ16፥17፤ሆሴ4፥6፡ 13፤8፥14፤11፥2፤13፥1፡ 6
2፥14 ሕዝ19፥13
2፥15 ዘ15፥18፤ኢሱ 7፥24፡26፤ኤር2፥22፤ ሕዝ16፥22፤28፥26፤ ሆሴ12፥9
2፥16 ኢሳ54፥5
2፥17 ዘ23፥13፤ኢሱ 23፥7፤መዝ16፥4፤ ዘካ13፥2
2፥18 ኢዮ5፥22፡ 23፤መዝ46፥9፤ኢሳ 2፥4፤ኤር23፥6፤ሕዝ 34፥25፤ዘካ9፥10
2፥19 ኢሳ1፥27፤ 54፥8፤62፥4፤ 2ቆሮ11፥2
2፥20 ኤር31፥34፤ ሆሴ4፥1፤6፥6፤13፥4፤ሕ ዝ16፥8
2፥21 ኢሳ55፥10፤ ዘካ8፥12፤ሚል3፥ 10ጠ11
2፥22 ኤር31፥12፤ ሕዝ36፥2930፤ሆሴ 1፥4፤14፥7፤ኢል2፥19
2፥23 ቍ1፤ኢሳ19፥ 25፤ኤር29፥12፤31፥ 27፤ሆሴ1፥6፡10፤ሮሜ 9፥25፤1ጴጥ2፥10
3፥1 2ሳሙ6፥19፤ ሆሴ1፥2
3፥4 ዘ25፥7፤መሳ 17፥56፤18፥1417፤ስቆ 2፥9፤ዳን11፥31፤ሆሰ 2፥11፤10፥1፤13፥11፤ዘ ካ10፥2
3፥5 ዘዳ4፥29፡30፤ 1ሳሙ13፥14፤መዝ 18፥45፤ኢሳ9፥13፤ 10፥20፤ኤር50፥45፤ ሆሴ5፥15፤11፥10፤ ሚክ4፥12
4፥1 ኢዮ10፥2፤ ምሳ10፥21፤24፥2፤ ኢሳ1፥3፤ኤር2፥9፤7፥ 28፤51፥5፤ሆሴ2፥ 20፤ኢል1፥2፡14
4፥2 2ነገ21፥16፤ ኢሳ1፥15፤59፥3፤ኤር 9፥2፤ሕዝ22፥2፡9፤ሆሴ 5፥2፤6፥9፤7፥1፡3፤ 10፥4፡13፤11፥12

[መ]15 ***አኮር*** ማለት ***ችግር*** ማለት ነው [ሠ]15 ወይም ***ትሆናለች*** [ረ]16 ዕብራይስጡ ***በኣል*** ይላል [ሰ]22 ***ኢይዝራኤል*** ማለት ***እግዚ አብሔር ይተክላል*** ማለት ነው [ሸ]23 ዕብራይስጡ ***ሎሩሃማ*** ይላል [ቀ]23 ዕብራይስጡ ***ሎዓሚ*** ይላል [በ]3 ወይም ***ቈዪ*** [ተ]2 መርገምን ያመለክታል

መግደል፣
መስረቅና ማመንዘር ብቻ ነው፤
ቃል ኪዳንን ሁሉ ያፈርሳሉ፤
ደም ማፍሰስና ግድያ ይበዛል።
3ስለዚህ ምድሪቱ አለቀሰች፤[ቸ]
በውስጧም የሚኖሩ ሁሉ ኰሰመኑ፤
የምድር አራዊት፣ የሰማይ ወፎች፣
የባሕርም ዓሦች አለቁ።

4"ነገር ግን ማንም ሰው አይከራከር፤
ማንም ሌላውን አይወንጅል፤
በካህናት ላይ ክስን እንደሚያቀርቡ፣
ሕዝብህ እንደዚያው ናቸውና።
5ቀንና ሌሊት ትደናበራላችሁ፤
ነቢያትም ከእናንተ ጋር ይደናበራሉ፤
ስለዚህ እናታችሁን አጠፋታለሁ፤
6ሕዝቤ ዕውቀት ከማጣቱ የተነሣ
ጠፍቶአል።
"ዕውቀትን ስለናቃችሁ፣
እኔም ካህናት እንዳትሆኑ ናቅኋችሁ፤
የአምላካችሁን ሕግ ስለ ረሳችሁ፣
እኔም ልጆቻችሁን እረሳለሁ።
7ካህናት በበዙ ቍጥር፣
በእኔ ላይ የሚያደርጉት ኀጢአት
በዝቶአል፤
ክብራቸውንም[ነ] በውርደት ለውጠዋል።[ነ]
8የሕዝቤ ኀጢአት ለመብል ሆኖላቸዋል፤
ርኵሰታቸውንም እጅግ ወደዱ።
9ካህናትም ከሕዝቡ የተለዩ አይደሉም፤
ሁሉንም እንደ መንገዳቸው
እቀጣቸዋለሁ፤
እንደ ሥራቸውም እከፍላቸዋለሁ።

10"ይበላሉ ግን አይጠግቡም፤
ያመነዝራሉ ግን አይበዙም፤
እግዚአብሔርን በመተው፣
ራሳቸውን 11ለአመንዝራነት፣
ለአሮጌና ለአዲስ የወይን ጠጅ አሳልፈው
ሰጡ፤
በእነዚህም 12የሕዝቤ ማስተዋል
ተወሰደ፤
ከዕንጨት የተሠራውን ጣዖት ምክር
ይጠይቃሉ፤
ዘንጋቸውም ይመልስላቸዋል።
የአመንዝራነት መንፈስ ያስታቸዋል፤
ለአምላካቸውም ታማኝ አልሆኑም።
13በተራሮችም ጫፍ ላይ ይሠዋሉ፤
መልካም ጥላ ባለው፣ በባሉጥ፣
በኮምቦልና በአሆማ ዛፍ ሥር፣
በኰረብቶችም ላይ የሚቃጠል ቍርባን
ያቀርባሉ።
ስለዚህ ሴቶች ልጆቻችሁ ዘማዊ፣
ምራቶቻችሁም አመንዝራ ይሆናሉ።

4፥3 ኢሳ15፥6፤ 33፥9፤ኤር4፥25፡28፤ 9፥10፤ሕዝ38፥20፤ ሶፎ1፥3
4፥4 ዘዳ17፥12፤ ሕዝ3፥26
4፥5 ሕዝ7፥19፤ 14፥7፤ሆሴ2፥2
4፥6 ምሳ10፥21፤ ኢሳ1፥3፤ሆሴ2፥13፤ 8፥1፡12፤ሚል2፥78
4፥7 ሆሴ9፥11፤ 10፥1፡6፤13፥6፤ዕን 2፥16
4፥8 ኢሳ56፥11፤ ሆሴ14፥1፤ሚክ3፥11
4፥9 ኢሳ24፥2፤ኤር 5፥31፤ሆሴ8፥13፤9፥9፡ 15፤10፥10፤12፥2
4፥12 መዝ73፥27
4፥13 ኢሳ1፥29፤ ኤር2፥20፤3፥6፤ሆሴ 2፥13፤10፥8፤11፥2፤ አሞ7፥17
4፥14 ቆ 11፡19፤ ዘፍ38፥21፤ምሳ10፥21 ፤ሆሴ9፥10
4፥15 ኢሱ7፥2፤ ኤር4፥2፤ሆሴ5፥8፤ 9፥15፤12፥11፤ አሞ4፥4፤5፥5
4፥16 ዘ32፥9፤ኢሳ 5፥17፤7፥25፤ ኤር31፥18
4፥19 ቆ 1314፤ኢሳ 1፥29፤ሆሴ12፥1፤ 13፥15
5፥1 ኢዮ10፥2፤ ኤር5፥26፤ሆሴ6፥9፤ 9፥8
5፥2 ሆሴ4፥2፤9፥15
5፥3 ሕዝ23፥7፤ ሆሴ1፥2፤6፥10፤ አሞ5፥12
5፥4 ኤ4፥22፤ ሆሴ4፥6፡11፤7፥10

14"ሴቶች ልጆቻችሁ ዘማውያን ሲሆኑ፣
የልጆቻችሁም ሚስቶች ሲያመነዝሩ
አልቀጣቸውም።
ወንዶች ከጋለሞቶች ጋር ይሴስናሉ፤
ከቤተ ጣዖት ዘማውያን ጋር ይ
ሠዋሉና፤
የማያስተውል ሕዝብ ወደ ጥፋት
ይሄዳል!

15"እስራኤል ሆይ፤ አንቺ ብታመነዝሪም፣
ይሁዳ በበደለኛነት አትጠየቅ።

"ወደ ጌልገላ አትሂዱ፤
ወደ ቤትአዌንም[ኘ] አትውጡ፤
'ሕያው እግዚአብሔርን' ብላችሁም
አትማሉ።
16እስራኤላውያን እንደ እልኸኛ ጊደር፣
እልኸኞች ናቸው፤
ታዲያ እግዚአብሔር እነርሱን በመልካም
መስክ ውስጥ እንዳሉ የበግ ጠቦቶች
እንዴት ያሰማራቸዋል?
17ኤፍሬም ከጣዖት ጋር ተጣምሮአል፤
እስቲ ተውት፤
18መጠጣቸው ባለቀ ጊዜ እንኳ፣
ዘማዊነታቸውን አያቆሙም፤
ገዦቻቸውም ነውርን አጥብቀው
ይወዳሉ።
19ዐውሎ ነፋስ ጠራርጎ ይወስዳቸዋል፤
መሥዋዕቶቻቸውም ኀፍረት
ያመጡባቸዋል።

## በእስራኤል ላይ የተነገረ ፍርድ

5 "እናንተ ካህናት፤ ይህን ስሙ!
እናንት እስራኤላውያን፤
አስተውሉ!
የንጉሥ ቤት ሆይ፤ ስሙ!
ይህ ፍርድ በእናንተ ላይ ነው፤
በምጽጳ ወጥመድ፣
በታቦርም ላይ የተዘረጋ መረብ
ሆናችኋልና።
2ዐመፀኞች በግድያ በርትተዋል፤
ሁሉንም እቀጣቸዋለሁ።
3ስለ ኤፍሬም ሁሉን ዐውቃለሁ፤
እስራኤልም ከእኔ የተሰወረች
አይደለችም፤
ኤፍሬም፣ አንተ አሁን አመንዝረሃል፤
እስራኤልም ረክሳለች።

4"የሠሩት ሥራ፣ ወደ አምላካቸው እንዲ
መለሱ አይፈቅድላቸውም፤

[ቸ]3 ወይም *ደረቀች* [ነ]7 ማሶሬቲክ የሚለው እንዲሁ ሲሆን የጥ ንት ዕብራውያን ጸሐፍት ትውፊት ግን *ክብሬን* ይላል [ነ]7ሱርስትና የጥንት ዕብራውያን ጸሓፍት ትውፊት የሚሉት እንዲሁ ሲሆን ማሶሬቲክ ግን *እለውጠዋለሁ* ይላል [ኘ]15 *ቤትአዌን የእግዚ አብሔር ቤት የተባለችው ቤቴል ስትሆን፣ ያቃሉ ትርጒም የክፋት ቤት* ማለት ነው።

የአመንዝራነት መንፈስ በልባቸው አለ፤
እግዚአብሔርንም አያውቁትም።
5የእስራኤል ትዕቢት በራሷ ላይ ይመሰክራል፤
እስራኤላውያንና ኤፍሬምም
በኀጢአታቸው ይሰናከላሉ፤
ይሁዳም ደግሞ አብሮአቸው
ይሰናከላል።
6እግዚአብሔርን ለመሻት፣
የበግና የፍየል መንጋ እንዲሁም
የቀንድ ከብቶቻቸውን ነድተው
ሲሄዱ፣
እርሱ ስለ ተለያቸው፣
ሊያገኙት አይችሉም።
7ለእግዚአብሔር ታማኞች አልሆኑም፤
ዲቃሎች ወልደዋልና፤
ስለዚህ የወር መባቻ በዓላቸው፤
እነርሱንና ዕርሻቸውን ያጠፋል።

8“በጊብዓ መለከትን፣
በራማ እንቢልታን ንፉ፤
በቤትአዌን የማስጠንቀቂያ ድምፅ አሰሙ፤
‘ብንያም ሆይ፤ መጡብህ!’ በሉ።
9በቅጣት ቀን፣
ኤፍሬም ባድማ ይሆናል፣
በእስራኤል ነገዶች መካከል፣
በእርግጥ የሚሆነውን ዐውጃለሁ።
10የይሁዳ መሪዎች፣
የወሰን ድንጋዮችን እንደሚነቅሉ ሰዎች
ናቸው፤
እንደ ጐርፍ ውሃ፣
ቍጣዬን በላያቸው ላይ አፈስሳለሁ።
11ጣዖትን መከተል በመውደዱ፣[ሀ]
ኤፍሬም ተጨቍኖአል፤
በፍርድም ተረግጦአል።
12እኔ ለኤፍሬም እንደ ብል፣
ለይሁዳም ሕዝብ እንደ ነቀዝ ሆኛለሁ።

13“ኤፍሬም ሕመሙን፣
ይሁዳም ቍስሉን ባየ ጊዜ፣
ኤፍሬም ወደ አሦር ሄደ፤
ርዳታ ለመጠየቅ ወደ ታላቁ ንጉሥ
መልእክተኛ ላከ፤
እርሱ ግን ሊያድናችሁ፣
ቍስላችሁንም ሊፈውስ አይችልም።
14እኔ ለኤፍሬም እንደ አንበሳ፣
ለይሁዳም እንደ ደቦል አንበሳ
እሆናለሁና፤
ሰባብሬና አድቅቄአቸው እሄዳለሁ፤
ነጥቄ እወስዳቸዋለሁ፤ ማንም
ሊያድናቸው አይችልም።
15በደላቸውንም እስኪያውቁ ድረስ፣
ወደ ስፍራዬ እመለሳለሁ፤
ፊቴን ይሻሉ፤
በመከራቸውም አጥብቀው
ይፈልጉኛል።”

## የእስራኤል ንስሓ አለመግባት

6 “ኑ፤ ወደ እግዚአብሔር እንመለስ፤
እርሱ ሰባብሮናል፤
እርሱም ይጠግነናል፤
እርሱ አቍስሎናል፤
እርሱም ይፈውሰናል።
2ከሁለት ቀን በኋላ ያነቃናል፤
በእርሱም ፊት እንድንኖር፣
በሦስተኛው ቀን ያስነሣናል።
3እግዚአብሔርን እንወቀው፤
የበለጠ እናውቀውም ዘንድ እንትጋ፤
እንደ ንጋት ብርሃን፣
በእርግጥ ይገለጣል፤
ምድርን እንደሚያረሰርስ የበልግ ዝናብ፣
እንደ ክረምትም ዝናብ ወደ እኛ
ይመጣል።”

4“ኤፍሬም ሆይ፤ ምን ላድርግህ?
ይሁዳ ሆይ፤ ምን ላድርግህ?
ፍቅራችሁ እንደ ማለዳ ጉም፣
እንደሚጠፋም የጧት ጤዛ ነው።
5ስለዚህ በነቢያቴ ቈራረጥኋችሁ፤
በአፌም ቃል ገደልኋችሁ፣
ፍርዴም እንደ መብረቅ በላያችሁ አበራ።
6ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን፣
ከሚቃጠልም መሥዋዕት ይልቅ
እግዚአብሔርን ማወቅ እሻለሁና።
7እንደ አዳም[ለ] ቃል ኪዳንን ተላለፉ፤
በዚያም ለእኔ ታማኝ አልነበሩም።
8ገለዓድ በደም የተበከለች፣
የክፉዎች ሰዎች ከተማ ናት።
9ወንበዴዎች ሰውን ለማጥቃት
እንደሚያደቡ፣
ካህናትም በቡድን እንዲሁ ያደርጋሉ፤
በሴኬም መንገድ ላይ ሰዎችን ይገድላሉ፤
አሳፋሪም ወንጀል ይፈጽማሉ።
10በእስራኤል ቤት
የሚሰቀጥጥ ነገር አይቻለሁ፤
በዚያ ኤፍሬም ዘማዊ ሆነ፤
እስራኤልም ረከሰ።

11“ይሁዳ ሆይ፤ ለአንተም፣
መከር ተመድቦብሃል።
ሕዝቤን ከምርኮ አገር በመለስሁ ጊዜ፣

7 እስራኤልን በምፈውስበት ጊዜ፣
የኤፍሬም ኀጢአት፣
የሰማርያም ክፋት ይገለጣል።
እነርሱ ያጭበረብራሉ፤
ሌቦች ቤቶችን ሰብረው ይገባሉ፤
ወንበዴዎችም በየመንገድ ይዘርፋሉ።

[ሀ]11 በዕብራይስጡ የዚህ ቃል ትርጒም አይታወቅም
[ለ]7 ወይም *በአዳም እንደ ሆነው* ወይም *በሰዎች*

5፥5 ኢሳ3፥9፤2፥19፤ሕዝ14፥7፤ሆሴ7፥10፤14፥1
5፥6 ምሳ1፥28፤ኢሳ1፥15፤ሕዝ8፥6፤ሚክ6፥67፤ሚል1፥10
5፥7 ኢሳ1፥14፤24፥16፤ሆሴ2፥4፤11፥12፤6፥7
5፥8 ዘኍ10፥2፤ኢሱ7፥2፤መሳ19፥12፤ኢሳ10፥29፤ኤር4፥21፤ሕዝ33፥3፤ሆሴ4፥15፤9፥9፤10፥5፥9
5፥9 ኢሳ7፥16፤37፥3፤46፥10፤ሆሴ9፥11፥17፤ዘካ1፥6
5፥10 ዘዳ19፥14፤ሕዝ7፥8
5፥11 ሆሴ9፥16፤ሚክ6፥16
5፥12 ኢዮ13፥28፤18፥16፤ኢሳ51፥8
5፥13 ኢሳ3፥7፤7፥16፤ሰቆ5፥6፤ሕዝ23፥5፤ሆሴ2፥7፤7፥8፥11፤8፥9፤10፥6፤12፥1፤14፥3
5፥14 ዘዳ32፥39፤ኢዮ10፥16፤ኤር4፥7፤ሆሴ6፥1፤አሞ3፥4፤ሚክ5፥8
5፥15 ዘሌ26፥40፤ዘኍ21፥7፤መዝ24፥6፤50፥15፤ኢሳ18፥4፤64፥9፤ኤር2፥27፤ሕዝ20፥43፤ሆሴ3፥5
6፥1 ዘኍ12፥13፤ዘዳ32፥39፤ኢዮ5፥18፤16፥9፤ኢሳ10፥20፤19፥22፤ኤር3፥22፤30፥17፤ሰቆ3፥11፤ሆሴ5፥14፤14፥4
6፥2 መዝ30፥5፤71፥20፤80፥18፤ማቴ16፥21
6፥3 ኢዩ4፥3፤መዝ72፥6፤ሆሴ11፥10፤12፥6
6፥4 ሆሴ7፥1፤11፥8፤13፥3
6፥5 ኤር1፥910፤5፥14፥23፥29፤ዕብ4፥12
6፥6 1ሳሙ15፥22፤መዝ40፥6፤ኢሳ1፥11፤ኤር4፥22፤ሆሴ2፥20፤ሚክ6፥8፤ማቴ9፥13፤12፥7፤ማር12፥33
6፥7 ዘፍ9፥11፤ኤር11፥10፤ሆሴ5፥7፤8፥7
6፥8 ሆሴ12፥11
6፥9 መዝ10፥8፤ኤር5፥3031፤7፥9፥10፤ሕዝ22፥9፤ሆሴ4፥2፤5፥1፤7፥1
6፥10 ኤር5፥30፤23፥14፤ሕዝ23፥7፤ሆሴ5፥3
6፥11 ኤር51፥33፤ኢል3፥13
7፥1 ቍ13፤ዘፀ22፥2፤መዝ126፥1፤ሕዝ24፥13፤ሆሴ4፥2፤6፥4፥9፤12፥1፤ሶፎ2፥7

[2]ነገር ግን ክፉ ድርጊታቸውን ሁሉ
እንደማስታውስ፣
እነርሱ አይገነዘቡም፤
ኀጢአታቸው ከቦአቸዋል፤
ሁልጊዜም በፊቴ ናቸው።

[3]“ንጉሡን በክፋታቸው፣
አለቆችንም በሐሰታቸው ያስደስታሉ።
[4]ሊጡ ቦክቶ ኩፍ እንደሚል፣
ዳቦ ጋጋሪው እሳት መቈስቈስ
እስከማያስፈልገው ድረስ፣
እንደሚነድ ምድጃ፣
ሁሉም አመንዝራ ናቸው።
[5]በንጉሣችን የበዓል ቀን፣
አለቆች በወይን ጠጅ ስካር ጋሉ፤
እርሱም ከፌዘኞች ጋር ተባበረ።
[6]ልባቸው እንደ ምድጃ የጋለ ነው፤
በተንኰል ይቀርቡታል፤
ቍጣቸው ሌሊቱን ሙሉ ይጤሳል፤
እንደሚነድም እሳት በማለዳ
ይንበለበላል።
[7]ሁሉም እንደ ምድጃ የጋሉ ናቸው፤
ገዦቻቸውን ፈጁ፤
ንጉሦቻቸው ሁሉ ወደቁ፤
ከእነርሱም ወደ እኔ የቀረበ ማንም
የለም።

[8]“ኤፍሬም ከአሕዛብ ጋር ተደባለቀ፤
ኤፍሬም ያልተገላበጠ ቂጣ ነው።
[9]እንግዶች ጕልበቱን በዘበዙ፤
እርሱ ግን አላስተዋለም።
ጠጕሩም ሽበት አወጣ፤
እርሱ ግን ልብ አላለም።
[10]የእስራኤል ትዕቢት በራሱ ላይ
መሰከረበት፤
ይህ ሁሉ ሆኖ ግን፣
ወደ አምላኩ ወደ *እግዚአብሔር*
አልተመለሰም፤
እርሱንም አልፈለገም።
[11]ኤፍሬም በቀላሉ እንደምትታለል፣
አእምሮም እንደሌላት ርግብ ነው፤
አንድ ጊዜ ወደ ግብፅ ይጣራል፤
ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደ አሦር ይዞራል።
[12]ሲበሩ፣ መረቤን በላያቸው እዘረጋለሁ፤
እንደ ሰማይ ወፎችም ጐትቼ
አወርዳቸዋለሁ፤
ስለ ክፉ ሥራቸውም በጉባኤ መካከል
እቀጣቸዋለሁ።
[13]ወዮ ለእነርሱ፤
ከእኔ ርቀው ሄደዋልና!
ጥፋት ይምጣባቸው!
በእኔ ላይ ዐምፀዋልና።
ልታደጋቸው ፈለግሁ፤
እነርሱ ግን በእኔ ላይ ሐሰት ይናገራሉ።

7፥2 ኢዮ35፥15፤ ኤር2፥19፤4፥18፤14፥10፤44፥21፤ሆሴ8፥13፤9፥15
7፥3 ኤር28፥14፤ ሆሴ4፥2፤10፥13፤ ሚክ7፥3
7፥4 ኤር9፥2
7፥5 መዝ1፥1፤ኢሳ 28፥1፡7
7፥6 መዝ21፥9
7፥7 ቍ16፤መዝ 14፥4፤ኢሳ9፥13፤ሆሴ 13፥10፤ሶፎ1፥6
7፥8 ቍ11፤መዝ 106፥35፤ሆሴ5፥13
7፥9 ኢሳ1፥7፤ ሆሴ8፥7
7፥10 ቍ14፤ኢሳ 9፥13፤ሆሴ5፥4፡5
7፥11 ቍ8፡16፤ዘፍ 8፥8፤ኤር2፥18፤ሰቆ5፥6፤ሆሴ9፥3፡6፤12፥1
7፥12 ሕዝ12፥13፤ 32፥3
7፥13 ቍ1፤መዝ 116፥11፤ኤር14፥10፤51፥9፤ሕዝ34፥46፤ ሆሴ9፥12፡17፤ ማቴ23፥37
7፥14 ቍ10፤ኤር 3፥10፤ሆሴ4፥10፤9፥1፤ 13፥16፤አሞ2፥8
7፥15 መዝ2፥1፤ 140፥2፤ሆሴ11፥3፤ ናሆ1፥9፡11
7፥16 ቍ7፡11፤መዝ 78፥9፡57፤ሕዝ23፥32፤ ሆሴ9፥3፤11፥5፤ሚል 3፥14
8፥1 ዘኍ10፥2፤ ዘዳ28፥49፤ኤር4፥13፤ 11፥10፤ሆሴ4፥6፤6፥7
8፥3 ማቴ7፥23፤ ቲቶ1፥16
8፥4 ሆሴ2፥8፤ 13፥12፡10
8፥5 ቍ6፤ሆሴ 10፥5፤ኤር13፥27
8፥6 ቍ5፤ዘፀ32፥4፤ ኤር16፥20፤ሆሴ14፥3
8፥7 ዘዳ28፥38፤ኢዮ 4፥8፤ምሳ22፥8፤ኢሳ 17፥11፤66፥15፤ሆሴ2፥9፤7፥9፤9፥16፤10፥12፤13፤ናሆ1፥3፤ገላ6፥8
8፥8 ኤር22፥28፤ 51፥34
8፥9 ዘፍ16፥12፤ ኤር2፥18፤22፥20፤ ሕዝ23፥5፤ሆሴ5፥13
8፥10 ኤር42፥2፤ ሕዝ16፥37፤22፥20

[14]ከልባቸው ወደ እኔ አይጮኹም፤
ነገር ግን በዐልጋቸው ላይ ሆነው
ያለቅሳሉ።
ስለ እህልና ስለ አዲስ የወይን ጠጅ
ይሰበሰባሉ፤
ነገር ግን ከእኔ ዘወር ብለዋል።
[15]እኔ አሠለጠንኋቸው፤ አጠነከርኋቸውም፤
እነርሱ ግን አደሙብኝ።
[16]ወደ ከንቱ ነገር ተመለሱ፤
ዒላማውን እንደ ሳተ ቀስት ናቸው፤
መሪዎቻቸው ስለ ክፉ ቃላቸው፣
በሰይፍ ይወድቃሉ፤
በዚህም ምክንያት በግብፅ ምድር፣
መዘባበቻ ይሆናሉ።

## እስራኤል ዐውሎ ነፋስን ታጭዳለች

8 “መለከትን በአፍህ ላይ አድርግ፤
ሕዝቡ ቃል ኪዳኔን አፍርሰዋልና፣
በሕጌም ላይ ዐምፀዋልና፣
ንስር *በእግዚአብሔር* ቤት ላይ ነው፤
[2]እስራኤልም፣ ‘አምላካችን ሆይ፤ እኛ
እናውቅሃለን’ እያሉ፣
ወደ እኔ ይጮኻሉ።
[3]ነገር ግን እስራኤል በጎ የሆነውን ነገር
ናቁ፤
ጠላትም ያሳድዳቸዋል።
[4]ያለ እኔ ፈቃድ ነገሥታትን አነገሡ፤
እኔንም ሳይጠይቁ አለቆችን መረጡ፤
በብራቸውና በወርቃቸው፣
ለገዛ ጥፋታቸው፣
ጣዖታትን ለራሳቸው ሠሩ።
[5]ሰማርያ ሆይ፤ የጥጃ ጣዖትሽን ጣይ፤
ቍጣዬ በእነርሱ ላይ ነድዶአል፤
የማይነጹት እስከ መቼ ነው?
[6]ይህም በእስራኤል ሆነ!
ባለ እጅ የሠራው ይህ ጥጃ፣ አምላክ
አይደለም፤
ያ የሰማርያ ጥጃ፣
ተሰባብሮ ይደቃል።

[7]“ነፋስን ይዘራሉ፤
ዐውሎ ነፋስንም ያጭዳሉ፤
አገዳው ዛላ የለውም፤
ዱቄትም አይገኝበትም፤
እህል አፍርቶ ቢገኝም፣
ባዕዳን ይበሉታል።
[8]እስራኤል ተውጠዋል፤
በአሕዛብም መካከል፣
ዋጋ እንደሌለው ዕቃ ሆነዋል።
[9]ለብቻው እንደሚባዝን የዱር አህያ፣
ወደ አሦር ሄደዋልና፤
ኤፍሬም በእጅ መንሻ ወዳጅ አበጀ።
[10]በአሕዛብ መካከል ራሳቸውን ቢሸጡም፣

እኔ አሁን እሰበስባቸዋለሁ፤
በኀያል ንጉሥ ጭቈና ሥር፣
እየመነመኑ ይሄዳሉ።

11“ኤፍሬም ለኀጢአት ማስተስረያ ብዙ
መሠዊያዎችን ቢሠራም፣
እነርሱ የኀጢአት መሥሪያ
መሠዊያዎች ሆነውበታል።
12በሕጌ ውስጥ ያለውን ብዙውን ነገር
ጻፍሁላቸው፤
እነርሱ ግን እንደ እንግዳ ነገር ቈጠሩት።
13ለእኔ የሚገባውን መሥዋዕት ያቀርባሉ፤
ሥጋውንም ይበላሉ፤
*እግዚአብሔር* ግን በእነርሱ
አልተደሰተም፤
ስለዚህ ክፋታቸውን ያስታውሳል፤
ኀጢአታቸውን ይቀጣል፤
ወደ ግብፅም ይመለሳሉ።
14እስራኤል ፈጣሪውን ረሳ፤
ቤተ መንግሥቶችንም ሠራ፤
ይሁዳም የተመሸጉ ከተሞችን አበዛ፤
እኔ ግን በከተሞቻቸው ላይ እሳትን
እለቅቃለሁ፤
ምሽጎቻቸውንም ይበላል።”

## በእስራኤል ላይ የሚደርሰው ቅጣት

9 እስራኤል ሆይ፤ ደስ አይበልሽ፤
እንደ ሌሎችም ሕዝቦች ሐሤት
አታድርጊ፤
ለአምላክሽ ታማኝ አልሆንሽምና፤
በየእህል ዐውድማውም ላይ፣
ለጋለሞታ የሚከፈለውን ዋጋ ወደሻል።
2የእህል አውድማዎችና የወይን
መጭመቂያዎች ሕዝቡን አይመግቡም፤
አዲሱም የወይን ጠጅ ይጐድልባቸዋል።
3*በእግዚአብሔር* ምድር አይቀመጡም፤
ኤፍሬም ወደ ግብፅ ይመለሳል፤
የረከሰውንም ምግብ[ኸ] በአሦር ይበላል።
4የወይን ጠጅን ቍርባን *ለእግዚአብሔር*
አያፈስሱም፤
መሥዋዕታቸውም ደስ አያሰኘውም፤
እንዲህ ዐይነቱ መሥዋዕት ለእነርሱ
የሐዘንተኞች እንጀራ ይሆንባቸዋል፤
የሚበሉትም ሁሉ ይረክሳሉ።
ይህ ምግብ ለገዛ ራሳቸው ይሆናል፤
ወደ *እግዚአብሔርም* ቤተ መቅደስ
አይገባም።
5*በእግዚአብሔር* የበዓል ቀናት፣
በዓመት በዓሎቻችሁም ቀን ምን
ታደርጋላችሁ?
6ከጥፋት ቢያመልጡም እንኳ፣
ግብፅ ትሰበስባቸዋለች፤
ሜምፎስም ትቀብራቸዋለች።
የብር ሀብታቸውን ዳዋ ያለብሰዋል፤
ድንኳኖቻቸውም እሾኽ ይወርሰዋል።
7የቅጣት ቀን መጥቶአል፤
የፍርድም ቀን ቀርቦአል፤
እስራኤልም ይህን ይወቅ!
ኀጢአታችሁ ብዙ፣
ጠላትነታችሁም ታላቅ ስለ ሆነ፣
ነቢዩ እንደ ሞኝ፣
መንፈሳዊውም ሰው እንደ እብድ
ተቈጥሮአል።
8ነቢዩ ከአምላኬ ጋር ሆኖ፣
የኤፍሬም ጠባቂ ነው፤[ወ]
ዳሩ ግን በመንገዱ ሁሉ ወጥመድ፣
በአምላኩም ቤት ጠላትነት ይጠ
ብቀዋል።
9በጊብዓ እንደ ነበረው፣
በርኵሰት ውስጥ ተዘፍቀዋል፤
እግዚአብሔር ክፋታቸውን ያስባል፤
ስለ ኀጢአታቸውም ይቀጣቸዋል።

10“እስራኤልን ማግኘቴ፣
የወይንን ፍሬ፣ በምድረ በዳ የማግኘት
ያህል ነበር፤
አባቶቻችሁንም ማየቴ፣
የመጀመሪያውን የበለስ ፍሬ የማየት
ያህል ነበር፤
ወደ ብዔልፌጎር በመጡ ጊዜ ግን፣
ለዚያ አሳፋሪ ጣዖት ራሳቸውን ለዩ፤
እንደ ወደዱትም ጣዖት የረከሱ ሆኑ።
11የኤፍሬም ክብር እንደ ወፍ በሮ
ይጠፋል፤
መውለድ፣ ማርገዝና መፀነስ የለም።
12ልጆችን ቢያሳድጉ እንኳ፣
ልጅ አልባ እስኪሆኑ ድረስ
እነጥቃቸዋለሁ፤
ሬቴን ከእነርሱ በመለስሁ ጊዜ፣
ወዮ ለእነርሱ!
13ኤፍሬምን እንደ ጢሮስ፣
በመልካም ስፍራ ተተክሎ አየሁት፤
አሁን ግን ኤፍሬም ልጆቹን፣
ለነፍሰ ገዳዮች አሳልፎ ይሰጣል።”
14*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ስጣቸው፤
ምን ትሰጣቸዋለህ?
የሚጨነግፉ ማሕፀኖችን፣
የደረቁ ጡቶችን ስጣቸው።

15“በጌልገላ ካደረጉት ክፋታቸው ሁሉ
የተነሣ፣
እኔ በዚያ ጠላኋቸው፤
ስለ ሠሩት ኀጢአት፣
ከቤቴ አሳድዳቸዋለሁ፤
ከእንግዲህም አልወዳቸውም፤
መሪዎቻቸው ሁሉ ዐመፀኞች ናቸው።

[ኸ]3 በሥርዐቱ መሠረት ያልነጻ ማለት ነው
[ወ]8 ወይም *ነቢዩ የኤፍሬም ጠባቂ ነው፤ የአምላኬ ሕዝብ…*

8፥11 ሆሴ10፥1፤ 12፥11
8፥12 ቍ1
8፥13 ኤር6፥20፤7፥21፤ሆሴ4፥9፤9፥3፡4፡6፡9፤አሞ8፥7
8፥14 ዘዳ32፥18፤ መዝ95፥6፤ኢሳ17፥10፤ኤር5፥17፤17፥27፤ ሆሴ2፥13
9፥1 ዘፍ30፥15፤ መዝ73፥27፤ኢሳ22፥1213፤24፥16፤ሆሴ7፥14፤10፥5
9፥2 ኢሳ24፥7፤ሆሴ 2፥9፤ኢል1፥10
9፥3 ዘሌ25፥23፤ሕዝ 4፥13፤ሆሴ7፥11፡16፤8፥13፤10፥5፤አሞ7፥17
9፥4 ዘዳ26፥14፤ ኤር16፥7፤ሕዝ4፥13ጠ14፤ሆሴ8፥13፤ኢል1፥9፡13፤2፥14፤ሐጌ 2፥13ጠ14
9፥5 ኢሳ10፥3፤ኤር 5፥31፤ሆሴ2፥11
9፥6 ኢሳ5፥6፤19፥13፤ኤር42፥22፤ሆሴ 7፥11፤8፥13፤10፥8፤ ሶፎ1፥11
9፥7 1ሳሙ10፥11፤ ኢዩ31፥14፤ኢሳ34፥8፤44፥25፤ኤር10፥15፤16፥18፤29፥26፤ሰቆ2፥14፤ሕዝ14፥910፤ ሆሴ14፥1፤ሚክ7፥14፤ ሉቃ21፥22
9፥8 ሕዝ22፥26፤ ሆሴ5፥1
9፥9 መሳ19፥16ጠ 30፤ሆሴ4፥9፤5፥8፤8፥13፤ሶፎ3፥7
9፥10 ዘኍ25፥15፤ መዝ106፥2829፤መሓ 2፥13፤ኢሳ28፥15፤ ኤር11፥13፤ሆሴ4፥14
9፥11 ቍ14፤ኢሳ 17፥3፤ሆሴ4፥7፤10፥5
9፥12 ቍ16፤ዘዳ 31፥17፤ሕዝ24፥21፤ ሆሴ7፥13
9፥13 ኢዮ15፥22፤ መዝ78፥67፤ሰቆ2፥22፤ ሕዝ27፥3
9፥14 ቍ11፤ሉቃ 23፥29
9፥15 ኢሳ1፥23፤ ኤር12፥8፤ሆሴ4፥9፡15፤5፥2፤7፥2

16ኤፍሬም ተመታ፤
ሥራቸው ደረቀ፤
ፍሬም አያፈሩም፤
ልጆች ቢወልዱም እንኳ፣
ተንከባክበው ያሳደጓቸውን ልጆቻቸውን
እገድላለሁ።”

17ባለመታዘዛቸው ምክንያት፣
አምላኬ ይጥላቸዋል፤
በአሕዛብም መካከል ተንከራታች
ይሆናሉ።

# 10

እስራኤል የተንዠረገገ ወይን
ነበር፤
ብዙ ፍሬም አፈራ፤
ፍሬው በበዛ መጠን፣
ብዙ መሠዊያዎችን ሠራ፤
ምድሩ በበለጸገ መጠን፣
የጣዖታት ማምለኪያ ዐምዶችን አስጌጠ።
2ልባቸው አታላይ ነው፤
ስለዚህም በደላቸውን ይሸከማሉ።
እግዚአብሔር መሠዊያዎቻቸውን
ያወድማል፤
የጣዖት ማምለኪያ ዐምዶቻቸውን
ያፈራርሳል።

3እነርሱም፣ “እኛ ንጉሥ የለንም፤
እግዚአብሔርን አላከበርንምና፤
ንጉሥ ቢኖረንስ፣
ምን ሊያደርግልን ይችል ነበር?” ይላሉ።
4ከንቱ ተስፋ ይሰጣሉ፤
በሐሰት በመማል፣
ቃል ኪዳን ያደርጋሉ፤
ስለዚህም ፍርድ፣
በዕርሻ ውስጥ እንደሚገኝ መርዛማ
ዐረም ይበቅላል።
5በሰማርያ የሚኖረው ሕዝብ፣
በቤትአዌን ስላለው የጥጃ ጣዖት ይፈራል፤
ሕዝቡም ያለቅስለታል፤
በክብሩ እጅግ ደስ ያላቸው ሁሉ፣
አመንዝራ ካህናትም እንደዚሁ
ያለቅሱለታል፤
በምርኮ ከእነርሱ ተወስዶአልና።
6ለታላቁ ንጉሥ እንደ እጅ መንሻ፣
ወደ አሦር ይወሰዳል፤
ኤፍሬም ይዋረዳል፤
እስራኤልም ስለ ጣዖቱ ያፍራል።[o]
7ሰማርያና ንጉሥዋ፣
በውሃ ላይ እንዳለ ኩበት ተንሳፍፈው
ይጠፋሉ።
8የእስራኤል ኀጢአት የሆነው፣
የአዌን ማምለኪያ ኰረብታ ይጠፋል፤
እሾኽና አሜኬላ ይበቅልባቸዋል፤
መሠዊያዎቻቸውንም ይወርሳል፤

9፥16 ቍ12፤ኢዮ15፥32፤ሆሴ5፥11፤8፥7
9፥17 ዘዳ28፥65፤ኤር6፥30፤ሆሴ4፥10፤7፥13
10፥1 1ነገ14፥23፤ሕዝ15፥2፤ሆሴ3፥4፤4፥7፤8፥11፤12፥11፤13፥15
10፥2 ቍ8፤1ነገ18፥21፤ሆሴ13፥16፤ሚክ5፥13
10፥4 ሕዝ17፥19፤ሆሴ4፥2፤አሞ5፥7፤6፥12
10፥5 ቍ8፤ዘፀ32፥4፤መሳ18፥1718፤2ነገ23፥5፤ኢሳ44፥1720፤ሆሴ5፥8፤8፥5፤9፥1፡3፡11፤ሶፎ1፥4
10፥6 መሳ3፥15፤2ነገ16፥7፤ኢሳ30፥3፤ኤር48፥13፤ሆሴ4፥7፤5፥13፤11፥5
10፥7 ቍ15፤ሆሴ13፥11
10፥8 ቍ2፡5፤1ነገ12፥2830፤ኢዮ30፥6፤ኢሳ32፥15፤ሕዝ6፥6፤ሆሴ4፥13፤9፥6፤አሞ3፥1415፤7፥9፤ሉቃ23፥30፤ራእ6፥16
10፥9 ኢሱ7፥11፤ሆሴ5፥8
10፥10 ሕዝ5፥13፤ሆሴ4፥9
10፥11 ኤር15፥12፤13፥18
10፥12 ምሳ11፥18፤መክ11፥1፤ኢሳ19፥22፤ 45፥8፤ኤር4፥3፤ሆሴ12፥6፤ያዕ3፥18
10፥13 ኢዮ4፥8፤መዝ33፥16፤ምሳ11፥18፤ሆሴ7፥3፤8፥7፤11፥12፤ገላ6፥7ጠ8
10፥14 2ነገ17፥3፤ኢሳ13፥16፤17፥3፤ሆሴ13፥16፤ሚክ5፥11
10፥15 ቍ7
11፥1 ዘፀ4፥22፤ዘዳ4፥37፤ኤር2፥2፤ሕዝ16፥22፤ሆሴ12፥9፡13፤13፥4፤ማቴ2፥5
11፥2 ቍ7፤2ነገ17፥15፤ኢሳ65፥7፤ኤር18፥15፤ሆሴ2፥13፤4፥13፤13፥1

በዚያን ጊዜ ተራሮችን፣ “ሸፍኑን!”
ኰረብታዎችንም፣ “ውደቁብን!”
ይላሉ።

9“እስራኤል ሆይ፤ ከጊብዓ ጊዜ ጀምሮ
ኀጢአት ሠራችሁ፤
በዚያም ጸናችሁ፤[u]
በጊብዓ የነበሩትን ክፉ አድራጊዎች፣
ጦርነት አልጨረሳቸውምን?
10በፈለግሁ ጊዜ እቀጣቸዋለሁ፤
ስለ ድርብ ኀጢአታችሁም ይቀጧቸው
ዘንድ፣
በእነርሱ ላይ ይሰበሰባሉ፤
11ኤፍሬም ማበራየት እንደምትወድ፣
እንደ ተገራች ጊደር ነው፤
በተዋበ ጫንቃዋም ላይ፣
ቀንበርን አኖራለሁ፤
ኤፍሬምን እጠምዳለሁ፤
ይሁዳ ያርሳል፤
ያዕቆብም መሬቱን ያለሰልሳል።
12ለራሳችሁ ጽድቅን ዝሩ፤
የጽኑ ፍቅርን ፍሬ ዕጨዱ፤
ዕዳሪውንም መሬት ዕረሱ፤
እርሱም መጥቶ፣
ጽድቅን በላያችሁ እስኪያዘንብ ድረስ፣
እግዚአብሔርን የምትፈልጉበት ጊዜ
ነውና።

13እናንተ ግን ክፋትን ዘራችሁ፤
ኀጢአትንም ዐጨዳችሁ፤
የሐሰትንም ፍሬ በላችሁ።
በራሳችሁ ጕልበት፣
በተዋጊዎቻችሁም ብዛት
ታምናችኋልና፣
14ሰልማን፣ ቤትአርብኤልን በጦርነት ጊዜ
እንዳፈራረሰ፣
እናቶችንም ከልጆቻቸው ጋር በምድር
ላይ እንደ ፈጠፈጣቸው፣
ሽብር በሕዝብህ ላይ ይመጣል፤
ምሽጎችህም ሁሉ ይፈራርሳሉ፤
15ስለዚህ ቤቴል ሆይ፤ ክፋትሽ ታላቅ ስለ
ሆነ፣
በአንቺም ላይ እንደዚሁ ይሆናል፤
ያ ቀን ሲደርስም፣
የእስራኤል ንጉሥ ፈጽሞ ይጠፋል።

## የእግዚአብሔር ፍቅር ለእስራኤል

# 11

“እስራኤል ገና ሕፃን ሳለ
ወደድሁት፤
ልጄንም ከግብፅ ጠራሁት።
2እስራኤል ግን አብዝቼ በጠራኋቸው[w]
ቍጥር፣

[o]6 ወይም ስለ ምክሩ [u]9 ወይም *በዚያም አቋም ወሰዳቸው*
[w]2 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ቅጆች እንዲሁ ሲሆኑ ዕብራ ይስጡ ግን *በጠሯቸው* ይላል።

አብዝተው ከእኔ[የ] ራቁ፤
ለበኣል አማልክት ሠዉ፤
ለምስሎችም ዐጠኑ።
3ኤፍሬምን እጁን ይዤ፣
እንዲራመድ ያስተማርሁት እኔ
ነበርሁ፤
ነገር ግን የፈወስኋቸው እኔ እንደ ሆንሁ፣
እነርሱ አላስተዋሉም።
4በሰው የርኅራኄ ገመድ፣
በፍቅርም ሰንሰለት ሳብኋቸው፤
ቀንበሩን ከጫንቃቸው ላይ አነሣሁላቸው፤
ዝቅ ብዬም መገብኋቸው።

5"ታዲያ ንስሓ መግባትን እምቢ
በማለታቸው፣
ወደ ግብፅ አይመለሱምን?
አሦርስ አይገዛቸውምን?
6በከተሞቻቸው ላይ ሰይፍ ይመዘዛል፤
የበሮቻቸውን መወርወሪያ ይቈርጣል፤
ስለ ክፉ ዕቅዳቸውም ይደመስሳቸዋል።
7ሕዝቤ ከእኔ ዘወር ማለትን መረጡ፤
ወደ ልዑል ቢጣሩም፣
በምንም ዐይነት አያከብራቸውም።

8"ኤፍሬም ሆይ፤ እንዴት እጥልሃለሁ?
እስራኤል ሆይ፤ እንዴትስ አሳልፌ
እሰጥሃለሁ?
እንዴት እንደ አዳማ አደርግሃለሁ?
እንዴትስ እንደ ሲባዮ እፈጽምብሃለሁ?
ልቤ በውስጤ ተናወጠ፤
ምሕረቴም ሁሉ ተነሣሥቶአል።
9የቍጣዬን መቅሠፍት አላመጣም፤
ተመልሼም ኤፍሬምን አላጠፋም፤
እኔ በመካከላችሁ ያለሁ ቅዱስ አምላክ ነኝ
እንጂ፣
ሰው አይደለሁምና፣
በቍጣ አልመጣም።[ዶ]
10እግዚአብሔርን ይከተላሉ፤
እርሱም እንደ አንበሳ ያገሣል፤
እርሱ ሲያገሣ፣
ልጆቹ እየተንቀጠቀጡ ከምዕራብ
ይመጣሉ።
11እንደ ወፍ ከግብፅ፣
እንደ ርግብ ከአሦር፣
እየበረሩ ይመጣሉ።
እኔም በቤታቸው አኖራቸዋለሁ፤"
ይላል እግዚአብሔር።

## የእስራኤል ኀጢአት

12ኤፍሬም በሐሰት፣
የእስራኤልም ቤት በተንኰል ከበበኝ፤
ይሁዳ ለአምላክ የማይገዛ፣
የታመነውን ቅዱሱን የሚቃወም ነው።

12 ኤፍሬም የነፋስ እረኛ ነው፤
ቀኑን ሙሉ የምሥራቅን ነፋስ
ይከተላል፤
ሐሰትንና ዐመፅን ያበዛል።
ከአሦር ጋር ቃል ኪዳን ያደርጋል፤
የወይራ ዘይትንም ወደ ግብፅ ይልካል።
2እግዚአብሔር በይሁዳ ላይ የሚያቀርበው
ክስ አለው፤
ያዕቆብን[ጀ] እንደ መንገዱ ይቀጣዋል፤
እንደ ሥራውም ይከፍለዋል።
3በማሕፀን ሳለ የወንድሙን ተረከዝ ያዘ፤
ሙሉ ሰውም ሲሆን ከአምላክ ጋር
ታገለ።
4ከመልአኩም ጋር ታገለ፤ አሸነፈውም፤
በፊቱ ሞገስን ለማግኘት አልቅሶ
ለመነው፤
እርሱንም በቤቴል አገኘው፤
በዚያም ከእርሱ ጋር ተነጋገረ፤
5እርሱም ሁሉን የሚገዛ አምላክ እግዚአብሐ
ር፣
የሚታወቅበት ስሙም እግዚአብሔር
ነው።
6ስለዚህ ወደ አምላክህ ተመለስ፤
ፍቅርንና ፍትሕን ጠብቅ፤
ዘወትርም በአምላክህ ታመን።

7ነጋዴው በሐሰተኛ ሚዛን ይሸጣል፤
ማጭበርበርንም ይወዳል።
8ኤፍሬም እንዲህ እያለ ይታበያል፤
"እኔ ባለጠጋ ነኝ፤ ሀብታምም ሆኛለሁ፤
ይህ ሁሉ ሀብት እያለኝ፣
ምንም ዐይነት በደል ወይም ኀጢአት
አያገኙብኝም።"

9"ከግብፅ ምድር ያወጣኋችሁ፣[ገ]
አምላካችሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ፤
በዓመት በዓላችሁ ቀን ታደርጉ
እንደ ነበረው ሁሉ፣
እንደ ገና በድንኳኖች እንድትቀመጡ
አደርጋችኋለሁ።
10ለነቢያት ተናገርሁ፤
ራእይንም አበዛሁላቸው፤
በእነርሱም በኩል በምሳሌ ተናገርሁ።
11ገለዓድ ክፉ ነው፤
ሕዝቡም ከንቱ ናቸው፤
ኮርማዎችን በጌልገላ ይሠዋሉን?
መሠዊያዎቻቸው በታረሰ መሬት ላይ
እንዳለ፣
የድንጋይ ክምር ይሆናሉ።
12ያዕቆብ ወደ ሶርያ[ጠ] ሸሸ፤

[የ]2 ሰብዓ ሊቃናት እንዲሁ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን *ከእነርሱ* ይላል
[ዶ]9 ወይም *በማንኛውም ከተማ ላይ በተቃውሞ አልመጣም*
[ጀ]2 *ያዕቆብ* ማለት *ተረከዝ ይይዛል* ማለት ሲሆን፣ *ያታልላል* ለማለት ዘይቤአዊ አገላለጽ ነው
[ገ]9 ወይም *በግብፅ ከነበራችሁበት ጊዜ አንሥቶ*
[ጠ]12 ሰሜን መስጴጦምያን ያመለክታል

11፥3 ዘፀ15፥26፤ ዘዳ1፥31፤32፥11፤ኤር 30፥17፤ሆሴ7፥15
11፥4 ዘፀ16፥32፤ ዘሌ26፥13፤መዝ78፥ 25፤ኤር31፥23፡20
11፥5 ዘፀ13፥17፤ ሆሴ7፥16፤10፥6
11፥6 ሰቆ2፥9፤ ሆሴ13፥16
11፥7 ቆኈ2፤ኢሳ26፥ 10፤ኤር3፥67፤8፥5
11፥8 ዘፍ14፥8፤ 1ነገ3፥26፤መዝ25፥6፤ ኤር7፥29፤ሰቆ3፥32፤ሕ ዝ33፥11፤ ሆሴ6፥4፤አሞ7፥3
11፥9 ዘኁ23፥19፤ ዘዳ13፥17፤2ነገ19፥22፤ ኢሳ31፥1፤ኤር18፥8፤ 30፥11፤ሰቆ3፥22፤ ሚል3፥6
11፥10 ዝ18፥45፤ ኢ ሳ31፥4፤42፥13፤ ሆሴ3፥5፤6፥13
11፥11 ዘፍ8፥8፤ኢሳ 11፥11፤ሕዝ28፥26፤ 34፥2528
11፥12 ዘዳ7፥9፤ሆሴ 4፥2፤10፥13
12፥1 ዘፍ41፥6፤ 2ነገ17፥4፤መዝ78፥67 ፤ሕዝ17፥10፤ሆሴ4፥ 19፤5፥13፤7፥1፡11
12፥2 ዘፀ32፥34፤ ኢዮ10፥2፤ሆሴ4፥9፤ 9፥15፤አሞ2፥4፤ ሚክ6፥2
12፥3 ዘፍ25፥26፤ 32፥2429
12፥4 ዘፍ12፥8፤ 35፥15
12፥5 ዘፀ3፥15
12፥6 መዝ106፥3፤ ኢሳ19፥22፤ኤር4፥1፤ 22፥3፤ሕዝ18፥30፤ ሆሴ6፥13፤10፥12፤ ኢ ል2፥12፤ሚክ7፥7
12፥7 ዘሌ19፥36፤ አሞ8፥5
12፥8 መዝ62፥10፤ ሕዝ28፥5፤ራእ3፥17
12፥9 ዘሌ23፥43፤ ነህ8፥17፤ሆሴ2፥15፤ 11፥1
12፥10 መሳ14፥12፤ 2ነገ17፥13፤ሕዝ20፥ 49፤ኤር7፥25
12፥11 ሆሴ4፥15፤ 6፥8፤8፥11
12፥12 ዘፍ28፥5፤ 29፥18

እስራኤል ሚስት ለማግኘት ሲል
አገለገለ፤
ዋጋዋንም ለመክፈል በጎችን ጠበቀ።
13*እግዚአብሔር* በነቢይ አማካይነት
እስራኤልን ከግብፅ አወጣ፤
በነቢይም በኩል ተንከባከበው።
14ኤፍሬም ግን ክፉኛ አስቈጣው፤
ጌታ ውም የደም አፍሳሽነቱን በደል በላዩ
ላይ ያደርግበታል፤
ስለ ንቀቱም የሚገባውን ይከፍለዋል።

### የ*እግዚአብሔር* ቍጣ በእስራኤል ላይ

13 ኤፍሬም ሲናገር ሰዎች
ተንቀጠቀጡ፤
በእስራኤልም የተከበረ ነበር፤
ነገር ግን በኣልን ስላመለከ በደለ፤
ሞተም።
2አሁንም ኀጢአትን መሥራት አበዙ፤
ብራቸውን አቅልጠው ለራሳቸው ጣዖት
ሠሩ፣
በጥበብ የተሠሩ ምስሎችን አበጁ፤
ሁሉም የባለ እጅ ሥራ ናቸው።
ስለ እነዚህ ሰዎች እንዲህ ተብሎአል፤
"ሰውን መሥዋዕት አድርገው ያቀርባሉ፤
የጥጃ ጣዖቶችንም ይስማሉ።"[ጨ]
3ስለዚህ እንደ ማለዳ ጉም፣
ፈጥኖ እንደሚጠፋ የጧት ጤዛ፣
ከዐውድማ እንደሚጠረግ ዕብቅ፣
በመስኮትም እንደሚወጣ ጢስ
ይሆናሉ።
4"እኔ ግን ከግብፅ ምድር ያወጣሁህ፣[ጸ]
አምላክህ *እግዚአብሔር* ነኝ፤
ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታውቅም፤
ከእኔም በቀር ሌላ አዳኝ የለም።
5በምድረ በዳ፣
በሐሩር ምድርም ተንከባከብሁህ።
6ካበላኋቸው በኋላ ጠገቡ፤
በጠገቡ ጊዜ ታበዩ፤
ከዚያም ረሱኝ።
7ስለዚህ እንደ አንበሳ እመጣባቸዋለሁ፤
እንደ ነብርም በመንገድ
አደባባቸዋለሁ።
8ግልገሎቿን እንደ ተነጠቀች ድብ፣
እመታቸዋለሁ፤ እዘነታትላቸዋለሁ።
እንደ አንበሳም ሰልቅጬ እውጣቸዋለሁ፤
የዱር አራዊትም ይገነጣጥላቸዋል።
9"እስራኤል ሆይ፤ በእኔ ላይ ስለ ተነሣህ፣
ረዳትህንም ስለ ተቃወምህ ትጠፋለህ።
10"ንጉሥንና አለቆችን ስጠኝ፤"
ብለህ እንደ ጠየቅኸው፣
ያድንህ ዘንድ ንጉሥህ የት አለ?
በከተሞችህ ሁሉ የነበሩ ገዦችህስ የት

12፥13 ዘፀ13፥3፤14፥1922፤ኢሳ63፥11 ጠ14፤ሆሴ11፥1
12፥14 ሕዝ18፥13፤ዳን11፥18
13፥1 መሳ8፥1፤12፥1፤ሆሴ11፥2
13፥2 1ነገ19፥18፤ኢሳ44፥1720፤46፥6፤ኤር10፥4፤44፥8፤ሆሴ8፥4፤14፥3
13፥3 ኢዩ13፥25፤መዝ1፥4፤68፥2፤ኢሳ17፥13፤ዳን2፥35፤ሆሴ6፥4
13፥4 ዘፀ20፥3፤ዘዳ28፥29፤መዝ18፥46፤ኢሳ43፥11፤45፥21ጠ22፤ኤር2፥6፤ሆሴ2፥20፤12፥9
13፥5 ዘዳ1፥19
13፥6 ዘዳ32፥12፤15፥18፤ምሳ30፥79፤ኢሳ17፥10፤ኤር5፥7፤ሕዝ28፥5፤ሆሴ2፥13፤4፥7
13፥7 ኢዮ10፥16፤ኤር4፥7
13፥8 1ሳሙ17፥34፤2ሳሙ17፥8፤መዝ17፥12፤50፥22፤ሰቆ3፥10፤ሆሴ2፥12
13፥9 ዘዳ33፥29፤ኤር2፥1719
13፥10 1ሳሙ8፥6፤2ነገ17፥4፤ሆሴ7፥7፤8፥4
13፥11 ዘኍ11፥20፤ኢሱ24፥20፤1ሳሙ13፥14፤1ነገ14፥10፤ሆሴ3፥4፤10፥7
13፥12 ዘዳ32፥34
13፥13 2ነገ19፥3፤ኢሳ13፥8፤66፥9፤ሚክ4፥910
13፥14 መዝ16፥10፤49፥15፤ኢሳ25፥8፤ሕዝ37፥1213፤1ቆሮ15፥55
13፥15 ኢዮ1፥19፤ኤር20፥5፤51፥36፤ሕዝ19፥12፤ሆሴ4፥19፤10፥1
13፥16 2ነገ8፥12፤15፥16፤17፥5፤ኢሳ13፥16፤ሆሴ7፥14፤10፥2፡14፤11፥6፤አሞ1፥13
14፥1 ኢሳ19፥22፤ኤር3፥12፤ሆሴ4፥8፤5፥5፤9፥7
14፥2 ዘፀ34፥9፤መዝ51፥1617፤ሚክ7፥18 ጠ19፤ዕብ13፥15
14፥3 ቀኍ8፤መዝ10፥14፤33፥17፤68፥5፤ኢሳ31፥1፤ኤር49፥11፤ሆሴ5፥13፤8፥6፤13፥2፤ሚክ5፥10

አሉ?
11በቍጣዬ ንጉሥን ሰጠሁህ፤
በመዓቴም ሻርሁት።
12የኤፍሬም በደል ተከማችቶአል፤
ኀጢአቱም በመዝገብ ተይዞአል።
13በምጥ ላይ እንዳለች ሴት ጭንቅ
ይመጣበታል፤
እርሱ ግን ጥበብ የሌለው ልጅ ነው፤
የሚወለድበት ጊዜ ሲደርስ፣
ከእናቱ ማሕፀን መውጣት
የማይፈልግ ሕፃን ነው።
14"ከመቃብር ኀይል እታደጋቸዋለሁ፤
ከሞትም እቤዣቸዋለሁ፤
ሞት ሆይ፤ መቅሠፍትህ የት አለ?
መቃብር ሆይ፤[ጸ] ማጥፋትህ የት አለ?
"ከእንግዲህ ወዲህ አልራራለትም፤
15በወንድሞቹ መካከል ቢበለጽግም እንኳ፣
የምሥራቅ ነፋስ ከምድረ በዳ እየነፈሰ፣
ከ*እግዚአብሔር* ዘንድ ይመጣል፤
ምንጩ ይነጥፋል፤
የውሃ ጕድጓዱም ይደርቃል።
የከበረው ሀብቱ ሁሉ፣
ከግምጃ ቤቱ ይበዘበዛል።
16የሰማርያ ሰዎች በደላቸውን ይሸከማሉ፤
በአምላካቸው ላይ ዐምፀዋልና፤
በሰይፍ ይወድቃሉ፤
ሕፃኖቻቸውም በምድር ላይ
ይፈጠፈጣሉ፤
የእርጉዝ ሴቶቻቸውም ሆድ
ይቀደዳል።

### በረከትን ለማግኘት ንስሓ መግባት

14 እስራኤል ሆይ፤ በኀጢአትህ
ምክንያት ስለ ወደቅህ፣
ወደ አምላክህ ወደ *እግዚአብሔር*
ተመለስ።
2የምትሉትን ቃል ይዛችሁ፣
ወደ *እግዚአብሔር* ተመለሱ፤
እንዲህም በሉት፤
"ኀጢአታችንን ሁሉ ይቅር በለን፤
የከንፈራችንንም ፍሬ እንድናቀርብ፣[ፀ]
በምሕረትህ ተቀበለን።
3አሦር ሊያድነን አይችልም፤
በጦር ፈረሶችም ላይ አንቀመጥም፤
ከእንግዲህም የገዛ እጆቻችን የሠሯቸውን፣
'አምላኮቻችን' አንላቸውም፤
ድሃ አደጉ እንኳ ከአንተ ርኅራኄ
ያገኛልና።"

[ጨ]2 ወይም *መሥዋዕት የሚያቀርቡ ሰዎች... ይስማሉ*
[ጸ]4 ወይም *በግብፅ ከነበራችሁበት ጊዜ አንሥቶ*
[ጸ]14 በዕብራይስጥ ሲኦል ማለት ነው
[ፀ]2 ወይም *እንደ ኮርማዎች መሥዋዕት የከንፈራችንን ፍሬ እንድናቀርብ*

4“እኔ ከዳተኛነታቸውን እፈውሳለሁ፤
እንዲሁ እወዳቸዋለሁ፤
ቍጣዬ ከእነርሱ ተመልሶአልና።
5እኔ ለእስራኤል እንደ ጠል እሆናለሁ፤
እንደ ውብ አበባ ያብባል፤
እንደ ሊባኖስ ዝግባም፣
ሥር ይሰዳል፤
6ቅርንጫፉ ያድጋል፤
ውበቱ እንደ ወይራ ዛፍ፣
ሽታውም እንደ ሊባኖስ ዝግባ
ይሆናል።
7ሰዎች እንደ ገና ከጥላው በታች ያርፉሉ፤
እርሱም እንደ እህል ይለመልማል፤
እንደ ወይን ተክል ያብባል፤
ዝናውም እንደ ሊባኖስ የወይን ጠጅ
ይወጣል።
8ኤፍሬም ሆይ፤ ከእንግዲህ ከጣዖት ጋር
ምን ጒዳይ አለኝ?ሑ
የምሰማህና የምጠነቀቅልህ እኔ ነኝ፤
እኔ እንደ ለመለመ የጥድ ዛፍ ነኝ፤
ፍሬያማነትህም ከእኔ የተነሣ ነው።”
9ጥበበኛ የሆነ እነዚህን ነገሮች
ያስተውላል፤
አስተዋይም እነዚህን ነገሮች ይረዳል።
*የእግዚአብሔር መንገድ ቅን ነውና፤*
ጻድቃን ይሄዱበታል፤
ዐመፀኞች ግን ይሰናከሉበታል።

14፥4 ኢዮ13፥16፤ ኢሳ30፥26፤55፥1፤ ኤር2፥19፤31፥20፤ ሆሴ6፥1፤ሶፎ3፥17
14፥5 ዘፍ27፥28፤ ኢዮ29፥19፤መሓ 2፥1፤ኢሳ18፥4፤35፥2
14፥6 መዝ52፥8፤ 92፥12፤መሓ4፥11፤ ኤር11፥16
14፥7 ዘፍ40፥10፤ መዝ91፥14፤ሕዝ 17፥23፤ሆሴ2፥22
14፥8 ቀኈ3፤ኢሳ 37፥24
14፥9 መዝ107፥ 43፤ 111፥78፤ ምሳ10፥29፤ኢሳ1፥ 28፤26፥7፤ዳን12፥10፤ ሐሥ13፥10

ሑ8 ወይም *ከእንግዲህ ከጣዖት ጋር ኤፍሬም ሌላ ምን አለው?*

# ትንቢተ ኢዩኤል

1 ወደ ባቱኤል ልጅ ወደ ኢዩኤል የመጣው
*የእግዚአብሔር* ቃል ይህ ነው፤

## የአንበጣ ወረራ

2እናንት ሽማግሌዎች፣ ይህን ስሙ፤
በምድሪቱም የምትኖሩ ሁላችሁ፣ አድምጡ፤
በእናንተ ዘመን፣ ሆነ በአባቶቻችሁም
ዘመን፣
እንዲህ ዐይነት ነገር ሆኖ ያውቃልን?
3ይህን ለልጆቻችሁ ተናገሩ፤
ልጆቻችሁ ለልጆቻቸው ይንገሩ፤
ልጆቻቸውም ለሚቀጥለው ትውልድ ይንገሩ።
4ከአንበጣ መንጋ[ሀ] የተረፈውን፣
ትልልቁ አንበጣ በላው፤
ከትልልቁ አንበጣ የተረፈውን፣
ኵብኵባ በላው፤
ከኵብኵባ የተረፈውን፣
ሌሎች አንበጦች በሉት።

5እናንት ሰካራሞች፤ ተነሡ፤ አልቅሱ፤
እናንት የወይን ጠጅ ጠጪዎች ሁሉ፤ ዋይ
በሉ፤
ስለ አዲሱ የወይን ጠጅ ዋይ ብላችሁ
አልቅሱ፤
አፋችሁ ላይ እንዳለ ተነጥቃችኋልና።
6ኀያልና ቍጥር ስፍር የሌለው ሕዝብ፣
ምድሬን ወሮአታልና፤
ጥርሱ እንደ አንበሳ ጥርስ፣
መንጋጋውም እንደ እንስት አንበሳ
መንጋጋ ነው።
7የወይን ቦታዬን ባድማ አደረገው፤
የበለስ ዛፎቼንም ቈራረጠ፤
ቅርንጫፎቻቸው ነጭ ሆነው እስኪታዩ
ድረስ፣
ቅርፊታቸውን ልጦ፣
ወዲያ ጣላቸው።

8የልጅነት እጮኛዋን[ለ] እንዳጣች ድንግል[ሐ]፣
ማቅ ለብሳችሁ አልቅሱ።
9የእህል ቍርባንና የመጠጥ ቍርባን፣
*ከእግዚአብሔር* ቤት ተቋርጦአል፤
*በእግዚአብሔርም* ፊት የሚያገለግሉ፣
ካህናት ያለቅሳሉ።
10ዕርሻዎች ባዶአቸውን ቀርተዋል፤
ምድሩም ደርቆአል[መ]፤
እህሉ ጠፍቶአል፤
አዲሱ የወይን ጠጅ አልቆአል፤
ዘይቱም ተሟጦአል።
11እናንት ገበሬዎች፣ ዕዘኑ፤
እናንት የወይን ገበሬዎች፣ ዋይ በሉ፤
ስለ ገብሱና ስለ ስንዴው አልቅሱ፤
የዕርሻው መከር ጠፍቶአልና።
12ወይኑ ደርቆአል፤
የበለስ ዛፉም ጠውልጎአል፤
ሮማኑ፣ ተምሩና እንኮዩ፣
የዕርሻው ዛፎች ሁሉ ደርቀዋል፤
ስለዚህ ደስታ፣
ከሰው ልጆች ርቆአል።

## የንስሓ ጥሪ

13ካህናት ሆይ፤ ማቅ ለብሳችሁ አልቅሱ፤
እናንተ በመሠዊያው ፊት
የምታገለግሉ፣ ዋይ በሉ፤
እናንት በአምላኬ ፊት የምታገለግሉ፣
ኑ፤ ማቅ ለብሳችሁ ዕደሩ፤
የእህል ቍርባኑና የመጠጥ ቍርባኑ፣
ከአምላካችሁ ቤት ተቋርጦአልና።
14ቅዱስ ጾምን ዐውጁ፤
የተቀደሰንም ጉባኤ ጥሩ፤
ሽማግሌዎችን ሰብስቡ፤
በምድሪቱ የሚኖሩትን ሁሉ፣
ወደ አምላካችሁ ወደ *እግዚአብሔር* ቤት ጥሩ
፤
ወደ *እግዚአብሔርም* ጩኹ።

15ወዮ ለዚያ ቀን፤
*የእግዚአብሔር* ቀን ቀርቦአልና፤
ሁሉን ከሚችል[ሠ] አምላክ እንደ ጥፋት
ይመጣል።

16የሚበላ ምግብ፣
ከዐይናችን ፊት፣
ደስታና ተድላ፣
ከአምላካችን ቤት አልተቋረጠብንምን?
17ዘሩ በዐፈር ውስጥ[ረ]፣
በስብሶ ቀርቶአል፤
ግምጃ ቤቶቹ ፈራርሰዋል፤
ጐተራዎቹም ተሰባብረዋል፤
እህሉ ደርቆአልና።
18መንጎች እንደ ምን ጮኹ፣
ከብቶቹ ተደናግጠዋል፤
መሰማሪያ የላቸውምና፤
የበግ መንጎች እንኳ ተቸግረዋል።

19አቤቱ *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ወደ አንተ
እጣራለሁ፤
ያልተነካውን መሰማሪያ፣ እሳት በልቶታልና፤

1፥1 ኤር1፥2፤ሐሥ2፥16
1፥2 ሆሴ4፥1፤5፥1፤ ኢል2፥2፥16
1፥3 ዘ10፥2፤ መዝ71፥18
1፥4 ዘ10፥5፥14፥ 15፤ዘዳ28፥39፤ አሞ7፥1፤ናሆ3፥15
1፥5 ኢሳ24፥7፤ ኢል3፥3
1፥6 መዝ105፥34፤ ኢል2፥2፥11፥25፤ ራእ9፥8
1፥7 ኢሳ5፥6፤ አሞ4፥9
1፥8 ቀኍ13፤ ኢሳ22፥12፤አሞ8፥10
1፥9 ሆሴ9፥4፤ ኢሳ22፥12
1፥10 ዘኍ18፥12፤ ኢሳ5፥6፤24፥4፤ ኤር3፥3፤ሆሴ9፥2
1፥11 ዘ9፥31፤ ኢዮ6፥20፤ ኢሳ17፥11፤አሞ5፥16
1፥12 ዘ28፥33፤ ኢሳ15፥6፤16፥8፤ ሐጌ2፥19
1፥13 ቀኍ9፤ዘፍ37፥34፤ ኤር4፥8፤ሆሴ9፥4፤ ኢል2፥14፥17
1፥14 2ዜና20፥3፥ 4፤ሆሴ4፥1፤ዮና3፥8
1፥15 ዘፍ17፥1፤ ኢሳ2፥12፤ኤር30፥7፤ 46፥10፤ሕዝ30፥3፤ ኢል2፥1፥11፥31፤3፥14፤ አሞ5፥18፤ሶፎ1፥14፤ ዘካ14፥1፤ሚል4፥5
1፥16 ዘዳ12፥7፤ መዝ51፥8፤ኢሳ3፥7
1፥17 ኢ17፥10ኛ11
1፥18 ዘፍ47፥4፤ ኤር9፥10
1፥19 መዝ50፥15፤ 97፥3፤ኤር9፥10፤ አሞ7፥4

[ሀ]4 በዚህ ክፍል፣ ስለ አንበጦች የሚገልጹት አራት የዕብራይስጥ ቃላት፣ ትክክለኛ ትርጕም አይታወቅም። [ለ]8 ወይም *የልጅነት ባሏ* እንደ ማለት ነው። [ሐ]8 ወይም *ወጣት ሴት* እንደ ማለት ነው። [መ]10 ወይም *መሬቱ ያዝናል* ማለት ነው። [ሠ]15 ዕብራይስጡ *ሻዳይ* ይለዋል። [ረ]17 ለዚህ የገባው የዕብራይስጡ ቃል ትርጕም አይታወቅም።

የዱሩን ዛፍ ሁሉ፣ ነበልባል አቃጥሎታል።
20የዱር አራዊት እንኳ ወደ አንተ አለኸለኹ፤
ወራጁ ውሃ ደርቆአል፤
ያልተነካውንም መሰማሪያ፣ እሳት
በልቶታል።

## የአንበጣ ሰራዊት

2 በጽዮን መለከትን ንፉ፤
በቅዱሱ ተራራዬም የማስጠንቀቂያውን
ድምፅ አሰሙ፤
በምድሪቱ የሚኖሩ ሁሉ ይንቀጥቀጡ፤
*የእግዚአብሔር* ቀን ቀርቦአልና፤
እርሱም በደጅ ነው።
2ይህም የጨለማና የጭጋግ ቀን፣
የደመናና የድቅድቅ ጨለማ ቀን ነው።
የንጋት ብርሃን በተራሮች ላይ
እንደሚወጣ፣
ኀያልና ብዙ ሰራዊት ይመጣል፤
ከጥንት እንዲህ ዐይነት ከቶ አልነበረም፤
በሚመጡትም ዘመናት እንዲህ ዐይነት
ከቶ አይሆንም።

3በፊታቸው፣ እሳት ይባላል፤
በኋላቸውም ነበልባል ይለበልባል፤
በፊታቸው ምድሪቱ እንደ ዔድን ገነት ናት፤
በኋላቸውም የሚቀረው ባዶ ምድረ በዳ
ነው፤
ምንም አያመልጣቸውም።
4መልካቸው እንደ ፈረስ መልክ ነው፤
እንደ ጦር ፈረስም ይጋልባሉ።
5ገለባ እንደሚበላ እንደሚንጣጣ እሳት፣
ለጦርነት እንደ ተዘጋጀ ኀያል ሰራዊት፣
የሠረገሎችን ድምፅ የሚመስል ድምፅ
እያሰሙ፣
በተራሮች ጫፍ ላይ ይዘላሉ።
6በእነርሱ ፊት ሕዝቦች ይርዳሉ፤
የሁሉም ፊት ይገረጣል።
7እንደ ተዋጊዎች ድንገት አደጋ ይጥላሉ፤
እንደ ወታደሮችም ቅጥርን ይዘላሉ፤
ከመንገዳቸውም ሳይወጡ፣
አቅጣጫ ይዘው ይጓዛሉ።
8እርስ በርሳቸው አይገፋፉም፤
እያንዳንዱ መስመሩን ጠብቆ ይሄዳል፤
መስመራቸውን ሳይለቁ፣
መከላከያውን ሰብረው ያልፋሉ።
9ከተማዪቱን ይወራሉ፤
በቅጥሩም ላይ ይዘላሉ፤
በቤቶች ላይ ዘለው ይወጣሉ፤
እንደ ሌባም በመስኮት ይገባሉ።

10ምድር በፊታቸው ትንቀጠቀጣለች፤
ሰማይም ይናወጣል፤
ፀሓይና ጨረቃ ይጨልማሉ፤
ከዋክብትም ከእንግዲህ ወዲያ አያበሩም።

11በሰራዊቱ ፊት፣
*እግዚአብሔር* ያንጐደጕዳል፤
የሰራዊቱ ብዛት ስፍር ቍጥር የለውም፤
ትእዛዙንም የሚያደርግ እርሱ ኀያል
ነው፤
*የእግዚአብሔር* ቀን ታላቅ፣
እጅግም የሚያስፈራ ነው፤
ማንስ ሊቋቋመው ይችላል?

## ልባችሁን ቅደዱ

12“አሁንም ቢሆን፣
በጾም፣ በልቅሶና በሐዘን፣
በፍጹም ልባችሁ ወደ እኔ ተመለሱ”
ይላል *እግዚአብሔር*።

13ልባችሁን እንጂ፣
ልብሳችሁን አትቅደዱ፤
ወደ አምላካችሁ ወደ *እግዚአብሔር*
ተመለሱ፤
እርሱ መሓሪና ርኅሩኅ፣
ቍጣው የዘገየና ፍቅሩ የበዛ፣
ክፉ ነገር ከማምጣትም የሚታገሥ
ነውና።
14በምሕረቱ ተመልሶ፣
ለአምላካችሁ *ለእግዚአብሔር*
የሚሆነውን፣
የእህል ቍርባንና የመጠጥ ቍርባን እንዲ
ተርፋችሁ ፣
በረከቱን ይሰጣችሁ እንደሆነ ማን
ያውቃል?

15በጽዮን መለከትን ንፉ፤
ቅዱስ ጾምን ዐውጁ፤
የተቀደሰን ጉባኤ ጥሩ።
16ሕዝቡን ሰብስቡ፤
ጉባኤውን ቀድሱ፤
ሽማግሌዎችን በአንድነት አቅርቡ፤
ሕፃናትን ሰብስቡ፤
ጡት የሚጠቡትንም አታስቀሩ፤
ሙሽራው እልፍኙን ይተው፣
ሙሽሪትም የጫጒላ ቤቷን ትተው።
17*በእግዚአብሔር* ፊት የሚያገለግሉ
ካህናት፣
በመሠዊያውና በቤተ መቅደሱ
አደባባይ መካከል ሆነው ያልቅሱ፤
እንዲህም ይበሉ፤ “*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ሕዝብ
ህን አድን፤
ርስትህን በአሕዛብ መካከል መተረቻ፣
መሣቂያና መሣለቂያም አታድርግ፤
ለምንስ በሕዝቦች መካከል፣
‘አምላካቸው ወዴት ነው?’ ይበሉን።”

## የእግዚአብሔር መልስ

18እነሆ፤ *እግዚአብሔር* ስለ ምድሩ ይቀናል[ሀ]፤

1፥20 1ነገ17፥7፤ መዝ42፥1፤104፥21፤ኢ ል2፥22
2፥1 ቍ15፤ዘ15፥17፤ ዘኍ10፥2፥7፤ ሕዝ12፥23፤30፥3፤ ኢል1፥15፤አብ1፥15፤ ሶፎ1፥14ኛ16
2፥2 ቍ10፥31፤ ኢዮ9፥7፤ኢሳ8፥22፤ 13፥10፤ሕዝ34፥12፤ 38፥9፤ዳን9፥12፤ ኢል1፥2፥6፤አሞ5፥18፤ ሶፎ1፥15፤ማቴ24፥21፤ ራእ9፥2
2፥3 ዘፍ2፥8፤ ዘ10፥12ኛ15፤ መዝ97፥3፤105፥34ኛ35፤ ኢሳ1፥31፤14፥17
2፥4 ራእ9፥7
2፥5 ኢሳ5፥24፤ 30፥30፤ራእ9፥9
2፥6 ኢሳ13፥8፤ 29፥22
2፥7 ኢዩ16፥14፤ ምሳ30፥27፤ኢሳ5፥27
2፥9 ዘ10፥6፤ ኤር9፥21
2፥10 ቍ2፤ኢዮ9፥7፤ መዝ18፥7፤102፥26፤ኢ ሳ5፥30፤13፥10፤ ሕዝ32፥8፤38፥19፤ ናሆ1፥5፤ማቴ24፥29፤ ማር13፥24፤ራእ9፥2
2፥11 ቍ2፥25፤ መዝ 29፥3፤ኢሳ2፥12፤ሕዝ 22፥14፤30፥3፤ኢል1፥ 15፤አብ1፥15፤ሶፎ1፥ 14፤2፥11፤ራእ6፥17
2፥12 ዘዳ4፥30፤ 1ሳሙ7፥3፤ሕዝ33፥ 11፤ሆሴ12፥6
2፥13 ዘፍ37፥29፤ ዘ34፥6፤ዘኍ14፥6፤ ዘዳ4፥31፤ኢዮ1፥20፤ መዝ51፥17፤86፥5፥ 15፤ኢሳ19፥22፤57፥ 15፤ኤር18፥8፤ዮና4፥2
2፥14 ኤር26፥3፤ 31፥14፤ኢል1፥13፤ አሞ5፥15፤ዮና1፥6፤ 3፥9፤ሐጌ2፥19፤ ዘካ8፥13፤ሚል3፥10
2፥15 ቍ1፤ዘ32፥5፤ ዘኍ10፥2፥3፤2ዜና20፥3፤ ኤር36፥9
2፥16 ዘ19፥10፥22፤ መዝ19፥5፤ኢል1፥2
2፥17 ዘዳ9፥26ኛ29፤ 1ነገ9፥7፤ኢዩ17፥6፤ መዝ42፥3፤44፥13፤ ኢ ሳ22፥12፤ሕዝ8፥16፤ ኢ ል1፥13፤ማቴ23፥35
2፥18 መዝ72፥13፤ ኢሳ26፥11፤ዘካ1፥14፤ 8፥2ሕዝ34፥29

[ሀ]18 ወይም *ጌታ ቀንቶአል ... /ራርቶአል/*።

ስለ ሕዝቡም ይራራል[ሰ]፡፡

19 *እግዚአብሔርም* እንዲህ ሲል ይመልስላቸዋል፤

"እህል፣ አዲስ የወይን ጠጅና ዘይት፣
እስክትጠግቡ ድረስ እሰጣችኋለሁ፤
የሕዝቦች መዘባበቻ አላደርጋችሁም፡፡

20 "የሰሜንን ሰራዊት ከእናንተ አርቃለሁ፤
ፊቱን ወደ ምሥራቁ ባሕር[ሸ]፣
ጀርባውንም ወደ ምዕራቡ ባሕር[ቀ]
በማድረግ፣
ወደ ደረቀውና ወደ ባድማው ምድር እገ
ፋዋለሁ፤
ግማቱ ይወጣል፤
ክርፋቱም ይነሣል፡፡"

በእርግጥ እርሱ ታላቅ ነገር አድርጎአል፡፡
21 ምድር ሆይ፤ አትፍሪ፤
ደስ ይበልሽ፤ ሐሤትም አድርጊ፤
በእርግጥ *እግዚአብሔር* ታላቅ ነገር
አድርጎአል፡፡
22 የዱር እንስሳት ሆይ፤ አትፍሩ፤
መሰማሪያ መስኮቹ ለምልመዋልና፤
ዛፎቹ ፍሬያቸውን አፍርተዋል፤
የበለሱ ዛፍና የወይኑ ተክልም እጅግ
አፍርተዋል፡፡
23 የጽዮን ሰዎች ሆይ፤ ደስ ይበላችሁ፤
በአምላካችሁ *በእግዚአብሔር*፣ ሐሤት
አድርጉ፤
የበልግን ዝናብ፣
በጽድቅ ሰጥቶአችኋልና[ተ]፤
እንደ ቀድሞውም፣
የበልግንና የጸደይን ዝናብ በብዛት
ልኮላችኋል፡፡
24 ዐውድማዎቹ በእህል ይሞላሉ፤
መጥመቂያ ጉድጓዶችም፣
በአዲስ የወይን ጠጅና በዘይት
ተሞልተው ያፈሳሉ፡፡

25 "በመካከላችሁ የሰደድሁት ታላቁ ሰራዊት፣
ትልልቁ አንበጣና ትንንሹ አንበጣ፣
ሌሎች አንበጦችና የአንበጣው መንጋ[ቸ]
የበላውን፣
እነዚህ ሁሉ የበሏቸውን ዓመታት ዋጋ
እመልስላችኋለሁ፡፡
26 እስክትጠግቡ የምትበሉት ብዙ ምግብ
ይኖራችኋል፤
ድንቅ ነገሮችን ለእናንተ የሠራውን፣
የአምላካችሁን *የእግዚአብሔርን* ስም
ታመሰግናላችሁ፤
ሕዝቤም ከእንግዲህ ወዲያ አያፍርም፡፡
27 ከዚያም እኔ በእስራኤል መካከል
እንዳለሁ፣
እኔ አምላካችሁ *እግዚአብሔር* እንደ
ሆንሁ፣
እንደ እኔም ያለ፣ ሌላ እንደሌለ
ታውቃላችሁ፤
ሕዝቤም ከእንግዲህ ወዲያ አያፍርም፡፡

## የእግዚአብሔር ቀን

28 "ከዚህም በኋላ፣
መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈሳለሁ፤
ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ፤
ሽማግሌዎቻችሁ ሕልም ያልማሉ፤
ጕልማሶቻችሁም ራእይ ያያሉ፡፡
29 በእነዚያ ቀናት በወንዶችና በሴቶች
ባሪያዎች ላይ እንኳ፣
መንፈሴን አፈሳለሁ፡፡
30 ድንቆችን በሰማያት፣
እንዲሁም በምድር፣
ደምና እሳት፣ የጢስም ዐምድ አሳያለሁ፡፡
31 ታላቁና የሚያስፈራው *የእግዚአብሔር*
ቀን ከመምጣቱ በፊት፣
ፀሓይ ትጨልማለች፤
ጨረቃም ወደ ደም ትለወጣለች፡፡
32 *የእግዚአብሔርን* ስም የሚጠራ ሁሉ፣
እርሱ ይድናል፤
*እግዚአብሔርም* እንዳለው፣
በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም፣
መድኀኒት ይገኛል፤
ከትሩፋኑም መካከል
*እግዚአብሔር* የጠራቸው በዚያ ይገኛሉ፡፡

## የተፈረደባቸው ሕዝቦች

3 በዚያ ዘመን፣ በዚያ ጊዜ፣
የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ምርኮ
ስመልስ፣
2 አሕዛብን ሁሉ እሰበስባለሁ፤
ወደ ኢዮሣፍጥም[ኀ] ሸለቆ
አወርዳቸዋለሁ፤
ስለ ርስቴ፣ ስለ ሕዝቤ፣ ስለ እስራኤል፣
በዚያ ልፈርድባቸው እገባለሁ፤
ምድሬን ከፋፍለዋል፤
ሕዝቤንም በሕዝቦች መካከል
በታትነዋልና፡፡
3 በሕዝቤ ላይ ዕጣ ተጣጣሉ፤
ወንዶች ልጆችን በዝሙት አዳሪዎች ለወጡ፤
ወይን ጠጅ ለመጠጣትም፣
ሴቶች ልጆችን ሸጡ፡፡
4 "ጢሮስና ሲዶና እንዲሁም እናንተ
የፍልስጥኤም ግዛቶች ሁሉ ሆይ፤ እንግዲህ
በእኔ ላይ ምን አላችሁ? ስላደረግሁት ነገር
ብድር ልትመልሱልኝ ነውን? የምትመል
ሱልኝ ከሆነ፣ በፍጥነትና በችኰላ እናንተ
ያደረጋችሁትን በራሳችሁ ላይ መልሼ

2፥19 ዘሌ26፥5፤ መዝ4፥7፤ኤር31፥12፤
2፥20 ኢሳ34፥3፤ ኤር 1፥14ና15፤ ዘካ14፥8
2፥21 መዝ9፥2፤ 126፥3፤ኢሳ25፥1፤ 29፥22፤54፥4፤ ሰፎ3፥16ና17
2፥22 ዘኍ16፥14፤ 1ነገ4፥25፤መዝ65፥12፤ ኢል1፥18ና20፤ ዘካ8፥12
2፥23 ዘሌ26፥4፤ ኢዮ36፥28፤መዝ33፥21፤ 84፥6፤97፥12፤135፥7፤ 149፥2፤ኢሳ12፥6፤ 41፥16፤45፥8፤66፥14፤ ሕዝ34፥26፤ዕን3፥18፤ ዘካ10፥7፤ያዕ5፥7
2፥24 ዘሌ26፥10፤ ምሳ3፥10፤ኢል3፥18፤ አሞ9፥13፤ሚል3፥10
2፥25 ዘ10፥14፤ አሞ4፥9፤ዘዳ28፥39፤ኢ ል1፥6
2፥26 ዘሌ23፥40፤ 26፥5፤መዝ126፥3፤ ኢ ሳ25፥1፤29፥22፤ 62፥9
2፥27 ዘፀ 62፥7፤ ኢሳ 44፥8፤45፥17፤ 54፥4፤ ኢል 3፥17 ሶፎ 3፥11
2፥28 ዘኍ11፥17፤ 1ሳሙ19፥20፤ ኢሳ 11፥2፤44፥3፤ ኤር 23፥25፤ ማር1፥8፤ገላ3፥14
2፥29 ሕዝ36፥27፤ 1ቆሮ12፥13፤ገላ3፥28
2፥30 ማር13፥24ና25፤ ሉቃ21፥11፤
2፥31 ቍ2፤ ኢሳ22፥5፤ኤር4፥23፤ ኢል1፥5፤አብ1፥15፤ ሚል3፥2፤4፥1፤5፤ ማቴ24፥29
2፥32 ዘፍ4፥26፤ መዝ105፥1፤106፥8፤ ኢሳ1፥9፤11፥11፤ 46፥13፤ አብ1፥17፤ ሚክ4፥7፤7፥18፤ ሐሥ 2፥17ና21፥39፤ ሮሜ፥27፤10፥13
3፥1 ዘዳ30፥3፤ኤር16፥15፤ 40፥5፤ሕዝ38፥8፤ ሰፎ3፥20
3፥2 ቍ12፤ ዘፍ11፥4፤ ዘሌ26፥33፤ ኢሳ13፥9፤22፥1፤ ኤር2፥35፤ ሕዝ36፥5፤ሰፎ3፥8
3፥3 ኢዩ6፥27፤ ሕዝ24፥6፤ ኢል1፥5፤አሞ2፥6
3፥4 ዘፍ10፥15፤ ዘሌ26፥28፤መዝ87፥4፤ ኢሳ14፥29ና31፤34፥8፤ ኤር47፥1ና7፤ ሕዝ25፥15ና17፤ ዘካ9፥5ና7፤ ማቴ11፥21

[ሰ]18 ጌታ መለሰለት፡፡ [ሸ]20 የሙት ባሕር ለማለት ነው [ቀ]20 የሜዲትራ ንያን ባሕር ለማለት ነው፡፡ [ተ]23 ወይም *ለጽድቅ መምህር* [ቸ]25 በዚህ ክፍል ስለ አንበጦች የሚገልጹት አራት የዕብራይስጥ ቃላት፣ ትክክለኛ ትርጕም አይታወቅም፡፡ [ኀ]2 *ኢዮሣፍጥ*፣ የስሙ ትርጕም *እግዚ አብሔር ይፈርዳል* ማለት ነው፤ ቍ12 ላይም እንዲሁ

አደርግባችኋለሁ። 5ብሬንና ወርቄን ወስዳ
ችኋል፤ የተመረጠውንም ንብረቴን ተሸክ
ማችሁ ወደ ቤተ መቅደሳችሁ አስገብታች
ኋልና። 6ከገዛ ምድራቸው ልታርቋቸው፣
የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ሰዎች ለግሪኮች
ሸጣችኋቸው።

7"እነሆ፤ እነርሱን ከሸጣችሁባቸው ቦታ
ዎች አነሣሣቸዋለሁ፤ እናንተም ያደረጋችሁ
ትን በገዛ ራሳችሁ ላይ እመልስባችኋለሁ።
8ወንዶችንና ሴቶች ልጆቻችሁን ለይሁዳ
ሰዎች ሸጣለሁ፤ እነርሱም መልሰው በሩቅ
ላሉት ለሳባ ሰዎች ይሸጧቸዋል፤" *እግዚ
አብሔር* ይህን ተናግሮአልና።

9በሕዝቦች መካከል ይህን ዐውጁ፤
ለጦርነት ተዘጋጁ፤
ተዋጊዎችን አነሣሡ፤
ጦረኞችም ሁሉ ቀርበው ያጥቁ።
10ማረሻችሁ ሰይፍ፣
ማጭዳችሁም ጦር እንዲሆን ቀጥቅጡት፤
ደካማውም ሰው፣
"እኔ ብርቱ ነኝ" ይበል።
11እናንተ በዙሪያ ያላችሁ ሕዝቦች
ሁላችሁ፤
ፈጥናችሁ ኑ፤
በዚያም ተሰብሰቡ።

*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ተዋጊዎችህን ወደዚያ
አውርድ!
12"ሕዝቦች ይነሡ፤
ወደ ኢዮሣፍጥም ሸለቆ ፈጥነው
ይውረዱ፤
ዙሪያውን ባሉት ሕዝቦች ሁሉ ላይ
ልፈርድ፣
በዚያ እቀመጣለሁና።
13ማጭዱን ስደዱ፤
መከሩ ደርሶአልና፤
ኑ ወይኑን ርገጡ፤
የወይን መጭመቂያው ሞልቶ፣
ከጕድጓዶቹም ተርፎ ፈሶአልና፤
ክፋታቸው እንደዚህ ታላቅ ነው።"

3፥5 1ነገ15፥18፤ 1ዜና21፥16ኛ17
3፥6 ሕዝ27፥13፤ ዘካ9፥13
3፥7 ኢሳ43፥5ኛ6፤ 66፥6፤ኤር23፥8
3፥8 ዘፍ10፥7፤ 2ዜና9፥1፤ኢሳ14፥2፤ 23፥1፤60፥14፤ ኤር30፥16
3፥9 ኢሳ8፥9፤ ኤር46፥4
3፥10 ዘኍ25፥7፤ ኢሱ1፥6፤ኢሳ2፥4፤ ዘካ12፥8
3፥11 ኢሳ13፥3፤ ሕዝ38፥15ኛ16፤ሰፎ 3፥8
3፥12 ቍ2፤መዝ82፥1፤ ኢሳ2፥4
3፥13 መሳ6፥11፤ ኢሳ17፥5፤ኤር25፥30፤ ሆሴ6፥11፤ቱ13፥39፤ ማር4፥29፤ ራእ14፥15ኛ19፥20
3፥14 ኢሳ2፥4፤13፥4፤ 22፥1፤34፥2ኛ8፤ሕ ዝ36፥5፤ኢል1፥15፤ ሶፎ1፥7
3፥15 ኢዮ9፥7፤ ሕዝ32፥7
3፥16 መሳ5፥4፤ 2ሳሙ22፥3፤ኢሳ14፥ 16፤25፥4፤42፥13፤ ኤር16፥19፤ሕዝ38፥ 19፤አሞ1፥2፤ዘካ9፥12፤ 12፥8
3፥17 ዘ6፥7፤መዝ2፥6፤ 74፥2፤ኢሳ2፥2፤4፥3፤ 52፥1፤ኤር31፥40፤ ሕ ዝ44፥9፤ኢል2፥27፤ ዘካ9፥8
3፥18 ዘ3፥8፤ዘኍ25፥1፤ መኃ5፥1፤ኢሳ25፥6፤ 30፥25፤35፥6፤44፥3፤ኤ ር31፥12፤ሕዝ47፥ 1፤ኢል2፥24፤አሞ9፥ 13፤ራእ22፥1ኛ2
3፥19 ኢሳ11፥14፤ 19፥1፤34፥11፤51፥35፤ አብ1፥10
3፥20 ዕ ዝ9፥12፤አሞ9፥15
3፥21 መዝ74፥2፤ ኢ ሳ1፥15፤59፥20፤ሕ ዝ36፥25፤48፥35፤ ዘካ8፥3

14ብዙ ሕዝብ፣ በጣም ብዙ ሕዝብ፣
ፍርድ በሚሰጥበት ሸለቆ ተሰብስቦአል፤
ፍርድ በሚሰጥበት ሸለቆ፣
የ*እግዚአብሔር* ቀን ቀርቦአልና።
15ፀሓይና ጨረቃ ይጨልማሉ፤
ከዋክብትም ከእንግዲህ አያበሩም።
16*እግዚአብሔር* ከጽዮን ጮኺ ይናገራል፤
ከኢየሩሳሌም ያንጐደጕዳል፤
ሰማይና ምድርም ይናወጣሉ፤
*እግዚአብሔር* ግን ለሕዝቡ መሸሸጊያ፣
ለእስራኤልም ልጆች መጠጊያ
ይሆናል።

## በረከት ለእግዚአብሔር ሕዝብ

17"ከዚያም እኔ አምላካችሁ *እግዚአብሔ
ር*፣
በቅዱሱ ተራራዬ በጽዮን እንደምኖር
ታውቃላችሁ፤
ኢየሩሳሌም የተቀደሰች ትሆናለች፤
ከእንግዲህም ወዲያ ባዕዳን አይወሯትም።

18"በዚያ ጊዜ ተራሮች፣ አዲስ የወይን ጠጅ
ያንጠባጥባሉ፤
ኰረብቶችም ወተት ያፈሳሉ፤
በይሁዳ ያሉ ሸለቆዎች[ነ] ሁሉ ውሃ
ያጐርፋሉ፤
ከ*እግዚአብሔር* ቤት ምንጭ
ይፈልቃል፤
የሰጢምን ሸለቆ ያጠጣል።
19ግብፅ ባድማ፣
ኤዶምም ምድረ በዳ ትሆናለች፤
በምድራቸው ንጹሕ ደም በማፍሰስ፣
በይሁዳ ሕዝብ ላይ ግፍ ፈጽመዋልና።
20ይሁዳ ለዘላለም፣
ኢየሩሳሌምም ለትውልድ ሁሉ መኖሪያ
ትሆናለች፤
21ደማቸውን እበቀላለሁ፤
በደለኛውንም ንጹሕ አላደርግም።"

*እግዚአብሔር* በጽዮን ይኖራል!

[ነ]18 ወይም *የሺጢም ሸለቆ*

# ትንቢተ አሞጽ

1 በቴቁሔ ከነበሩት እረኞች መካከል
አንዱ የሆነው አሞጽ፣ ዖዝያን የይሁዳ
ንጉሥ በነበረ ጊዜ እንዲሁም የዮአስ[ሀ]
ልጅ ኢዮር ብዓም የእስራኤል ንጉሥ
በነበረ ጊዜ፣ ይኸውም የምድር መናወጥ
ከመሆኑ ከሁ ለት ዓመት በፊት ስለ እስራ
ኤል ያየውና የተናገረው ቃል ይህ ነው፤
2እርሱም እንዲህ አለ፤

“*እግዚአብሔር* ከጽዮን ድምፁን ከፍ
አድርጎ ያሰማል፤
ከኢየሩሳሌምም ያንጐደጕዳል፤
የእረኞች ማሰማሪያዎች ደርቀዋል[ለ]፤
የቀርሜሎስም ዐናት ጠውልጎአል።”

## በእስራኤል ጐረቤቶች ላይ የተሰጠ ፍርድ

3*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“ስለ ሦስቱ የደማስቆ ኀጢአት፣
ይልቁንም ስለ አራቱ፣ ቍጣዬን አልመ
ልስም፤
የብረት ጥርስ ባለው ማሄጃ፣ ገለዓድን
አሂዳለችና፤
4የወልደ አዴርን ምሽጎች እንዲበላ፣ በአዛሄል
ቤት ላይ እሳት እሰዳለሁ።
5የደማስቆን በሮች እሰባብራለሁ፤
በቤት ዔደን በትር የያዘውን፣
በአዌን[ሐ] ሸለቆ ያለውን[መ] ንጉሥ
እደመስሳለሁ፤
የሶርያም ሕዝብ ተማርኮ ወደ ቂር
ይሄዳል”
ይላል *እግዚአብሔር* ።

6*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

“ስለ ሦስቱ የጋዛ ኀጢአት፣
ይልቁንም ስለ አራቱ፣ ቍጣዬን አልመ
ልስም፤
ሕዝቡን ሁሉ ማርካ በመውሰድ፣
ለኤዶም ሸጣለችና።
7ምሽጎቿን እንዲበላ፣
በጋዛ ቅጥሮች ላይ እሳት እሰዳለሁ።
8በአስቀሎና በትር የያዘውን፣
የአሽዶድንም ንጉሥ[ሠ]
እደመስሳለሁ፤ በፍልስጥኤም ካሉት
የመጨረሻው ሰው
እስኪሞት ድረስ፣
እጄን በአቃሮን ላይ እዘረጋለሁ፤”
ይላል ጌታ *እግዚአብሔር* ።

9*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

“ስለ ሦስቱ የጢሮስ ኀጢአት፣
ይልቁንም ስለ አራቱ፣ ቍጣዬን
አልመልስም።
የወንድማማችነትን ቃል ኪዳን
በማፍረስ፣
ሕዝቡን ሁሉ ማርካ ለኤዶም ሸጣለችና።
10ምሽጎችዋን እንዲበላ፣
በጢሮስ ቅጥሮች ላይ እሳት እሰዳለሁ።”

11እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“ስለ ሦስቱ የኤዶም ኀጢአት፣
ይልቁንም ስለ አራቱ፣ ቍጣዬን አል
መልስም፤
ርኅራኄን[ረ] በመንፈግ፣
ወንድሙን በሰይፍ አሳዶታልና፤
የቍጣውንም ነበልባል ሳይገድብ፣
መዓቱን ሳያቋርጥ አውርዶበታልና፤
12የባሶራን ምሽጎች እንዲበላ፣
በቴማን ቅጥሮች ላይ እሳት
እሰዳለሁ።”

13እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“ስለ ሦስቱ የአሞን ኀጢአት፣
ይልቁንም ስለ አራቱ፣ ቍጣዬን አልመልስም፤
ድንበሩን ለማስፋት፣
የገለዓድን ነፍሰ ጡር ሴቶች ሆድ ቀዶአልና።
14በጦርነት ቀን በጩኸት ውስጥ፣
በማዕበል ቀን በዐውሎ ነፋስ ውስጥ፣
ምሽጎቿን እንዲበላ፣
በረባት ቅጥሮች ላይ እሳት እሰዳለሁ።
15ንጉሥዋ[ሰ] ከሹማምንቱ ጋር፣
በአንድነት ተማርኮ ይሄዳል፣”
ይላል እግዚአብሔር።

2 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“ስለ ሦስቱ የሞዓብ ኀጢአት፣
ይልቁንም ስለ አራቱ፣ ቍጣዬን
አልመልስም፤
የኤዶምን ንጉሥ ዐጥንት፣
ዐመድ እስኪሆን ድረስ
አቃጥሎአልና፤ 2የቂርዮትን ምሽጎች[ሸ]
እንዲበላ፣
በሞዓብ ላይ እሳት እሰዳለሁ፤
ሞዓብ በጦርነት ጩኸትና በመለከት ድምፅ
መሐል፣

1፥1 2ሳሙ14፥2፤ 2ነገ14፥21፡23፤5፤ 2ዜና26፥23፤ ሆሴ1፥1፤ዘካ14፥5
1፥2 መዝ29፥3፤ ኢሳ42፥13፤ ኤር12፥4፤አሞ9፥3፤ ኢል3፥16
1፥3 ቍ6፡9፡11፡13፡ አሳ7፥8፤8፥4፤17፥1ኛ3፤አሞ2፥6
1፥4 1ነገ19፥17፤ 20፥1፤2ነገ6፥24፤ 2ነገ8፥7ኛ15፤ ኤር17፥27፤ 49፥23ኛ27፤ሕዝ30፥8
1፥5 1ነገ16፥9፤ ኢሳ7፥16፤22፥6፤ 37፥12፤ኤር49፥27፤51፥30፤ዘካ9፥1
1፥6 ቍ3፤ ዘፍ10፥19፤ 14፥6፤ 1ሳሙ6፥17፤ አብ1፥11፤ስፎ2፥4
1፥8 2ዜና26፥6፤ መዝ81፥14፤ ኢሳ34፥8፤14፥28፤ 14፥28ኛ32፤ ሕዝ25፥16፤ ሶፎ2፥4ኛ7
1፥9 ቍ3፤1ነገ5፥1፡12፤9፥11ኛ14፤ኤር 25፥22፤ኢል3፥4፤ ማቴ11፥21
1፥10 ኢሳ23፥1ኛ18፤ 34፥8፤ኤር47፥4፤ሕዝ 26፥2ኛ4፤ዘካ9፥1ኛ4
1፥11 ዘኍ20፥14ኛ21፤1ዜና28፥17፤ መዝ63፥10፤83፥6፤ ሕዝ25፥12ኛ14፤ ዘካ1፥15
1፥12 ዘፍ36፥11፡15፤ኢሳ34፥5፤ 63፥1ኛ6፤ ኤር25፥21፤ ሕዝ25፥12ኛ14፤ 35፥1ኛ15፤አብ1፥1፤ ሚል1፥2ኛ5
1፥13 ዘፍ19፥38፤ 34፥29፤2ነገ8፥12፤ ሕዝ21፥28፤ ሆሴ13፥16
1፥14 ዘዳ3፥11፤ ኢዮ39፥25፤ ኢሳ30፥30፤ ኤር23፥19
1፥15 1ዜና20፥1፤ ኤር25፥21 ኤር49፥1፤ ሕዝ21፥28ኛ32፤
2፥1 አሳ16፥6፤ 33፥12
2፥2 ኢሱ6፥20፤ አዮ39፥25፤ ኤር48፥24

[ሀ]1 ዕብራይስጡ *ዮአስ* ያለው ለኢዮአስ ተለዋጭ ስም ሳይሆን አይቀርም።
[ለ]2 ወይም *የእረኞቹ ሐዘን* የሚሉ አሉ ።
[ሐ]5 ወይም *ነዋሪዎች*
[መ]5 *አዌን* የቃሉ ትርጕም ክፉት አንደ ማለት ነው
[ሠ]8 ወይም *ነዋሪዎች*
[ረ]11 ወይም *ሰይፍ ከእርሱ ጋር የተባበሩትን አጠፋ*
[ሰ]15 ወይም *ሞሎክ* በዕብራይስጡ *መልካም* ነው
[ሸ]2 ወይም *ከተሞቿ* የሚሉ አሉ ።

በታላቅ ሁካታ ውስጥ ይሞታል።
[3]ገዢን እደመስሳለሁ፤
አለቆቿንም ሁሉ ከንጉሥዋ ጋር
እገድላለሁ፤”
ይላል እግዚአብሔር።

[4] እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤

“ስለ ሦስቱ የይሁዳ ኀጢአት፣
ይልቁን ስለ አራቱ፣ ቍጣዬን አልመልስም፤
የእግዚአብሔርን ሕግ ንቀዋል፤
ትእዛዙንም አልጠበቁምና፤
አባቶቻቸው በተከተሏቸው[ቀ] አማልክት፣
በሐሰት[በ] አማልክት በመመራት ስተዋልና።
[5]የኢየሩሳሌምን ምሽጎች እንዲበላ፣
በይሁዳ ላይ እሳት እሰዳለሁ።

## በእስራኤል ላይ የተሰጠ ፍርድ

[6]እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“ስለ ሦስቱ የእስራኤል ኀጢአት፣
ይልቁንም ስለ አራቱ፣ ቍጣዬን አልመልስም፤
ጻድቁን ስለ ጥሬ ብር፣
ችግረኛውንም ስለ ጥንድ ጫማ
ይሸጡታልና።
[7]የድኾችን ራስ፣ በምድር ትቢያ ላይ
ይረግጣሉ፤
ፍትሕንም ከጭቍኖች ይነጥቃሉ፤
አባትና ልጅ ከአንዲት ሴት ጋር ይተኛሉ፤
እንዲህም እያደረጉ ቅዱስ ስሜን ያረክሳሉ።
[8]በመያዣነት በተወሰደው ልብስ ላይ፣
በየመሠዊያው ሥር ይተኛሉ፤
በአምላካቸው ቤት፣
በመቀጫነት የተወሰደውን የወይን ጠጅ
ይጠጣሉ።

[9]ቁመቱ እንደ ዝግባ፣
ጥንካሬውም እንደ ባሉጥ ዛፍ የነበረ
ቢሆንም፣
አሞራዊውን ከፊታቸው አጠፋሁት፣
ከላይ ፍሬውን፣
ከታችም ሥሩን አጠፋሁ።
[10]“የአሞራውያንን ምድር ልሰጣችሁ፣
ከግብፅ አወጣኋችሁ፤
አርባ ዓመትም በምድረ በዳ መራኋችሁ።
[11]ደግሞም ነቢያትን ከወንዶች ልጆቻችሁ
መካከል፣
ናዝራውያንንም ከጒልማሶቻችሁ መካከል
አስነሣሁ፤
የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፤ ይህ እውነት
አይደለምን?”
ይላል እግዚአብሔር።

[12]“እናንተ ግን ናዝራውያኑን የወይን ጠጅ
አጠጣችኋቸው፤
ነቢያቱንም ትንቢት እንዳይናገሩ
አዘዛችኋቸው።
[13]“እነሆ፤ በእህል የተሞላ ጋሪ እንደሚያደቅ፣
እኔም አደቃችኋለሁ።
[14]ፈጣኑ አያመልጥም፤
ብርቱውንም ብርታቱ አይረዳውም፤
ኀያሉም ነፍሱን አያድንም።
[15]ቀስተኛው በቦታው ጸንቶ አይቆምም፤
ፈጣኑም ተዋጊ ሮጦ አያመልጥም፤
ፈረሰኛውም ነፍሱን አያድንም።
[16]ጐበዞቹ ተዋጊዎች እንኳ፣
በዚያ ቀን ዕራቁታቸውን ይሸሻሉ፤”
ይላል እግዚአብሔር።

## በእስራኤል ላይ የተጠሩ ምስክሮች

3 የእስራኤል ልጆች ሆይ፤ እግዚአብሔር
በእናንተ ከግብፅ ባወጣሁት ሕዝብ
ሁሉ ላይ የተናገረውን ይህን ቃል ስሙ፤
[2] “ከምድር ወገን ሁሉ፣
እናንተን ብቻ መረጥሁ፤
ስለዚህ ስለ ሠራችሁት ኀጢአት ሁሉ፣
እኔ እቀጣችኋለሁ።”

[3]በውኑ ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ፣
አብረው መጓዝ ይችላሉን?
[4]አንበሳ የሚበላውን ሳያገኝ፣
በጫካ ውስጥ ይጮኻልን?
ምንም ነገርስ ሳይዝ፣
በዋሻው ውስጥ ያገሣልን?
[5]ወጥመድ ሳይዘረጋ፣
ወፍ በምድር ላይ ይጠመዳልን?
የሚይዘው ነገር ሳይኖርስ፣
ወጥመዱ ከምድር ይፈነጠራልን?
[6]የመለከት ድምፅ በከተማ ውስጥ ሲሰማ፣
ሰዎች አይደነግጡምን?
ጥፋትስ በከተማ ላይ ቢደርስ፣
ያደረገው እግዚአብሔር አይደለምን?
[7]በእውነት ጌታ እግዚአብሔር ምስጢሩን
ለአገልጋዮቹ ለነቢያት ሳይገልጥ፣
ምንም ነገር አያደርግም።

[8]አንበሳ አገሣ፤
የማይፈራ ማን ነው?
ጌታ እግዚአብሔር ተናገረ፤
ትንቢት የማይናገር ማን ነው?
[9]ለአዛጦን ምሽግ፣
ለግብፅም ምሽግ እንዲህ ብላችሁ ዐውጁ፤
“በሰማርያ ተራሮች ላይ ተሰብሰቡ፤
በውስጧ ያለውን ታላቅ ሁከት፣
በሕዝቧም መካከል ያለውን ግፍ እዩ።”
[10] “ቅሚያንና ዝርፊያን በምሽጋቸው

2፥3 መዝ2፥10፤ አሳ15፥1ኛ9፤ 16፥1ኛ14፥40፥23፤ ኤር48፥1፤ ሕዝ25፥8ኛ11፤ ሶፎ2፥8ኛ9
2፥4 ዘ34፥15፤ ዘዳ31፥20፤2ነገ17፥19፤ 22፥13፤መዝ4፥2፤ ኢሳ9፥16፤ኤር6፥19፤ 9፥14፥16፥12፤ ሕዝ20፥24፤ሆሴ12፥2
2፥5 2ነገ25፥9፤ 2ዜና36፥19፤አሞ3፥11 ኤር 17፥27፤ ሆሴ 8፥14፤
2፥6 ኢል3፥3፤ አሞ1፥3፥8፥6
2፥7 ዘሌ18፥21፤ አሞ5፥11ኛ12፥8፥4
2፥8 ዘ22፥26፤ ዘዳ24፥12ኛ13፤ ሆሴ7፥14፤አሞ4፥1፤ 6፥6፤ዕን2፥6
2፥9 ዘኍ13፥32፤ 21፥23ኛ26፤ኢሱ10፥ 12፤2ነገ19፥30፤ ኢዮ18፥16፤ መዝ29፥9፤ ኢሳ10፥33፤ ሕዝ17፥9
2፥10 ዘ3፥8፥6፥6፤ 20፥2፤ዘኍ21፥25፤ ዘዳ2፥7፥8፥2፤ኢሱ 13፥4፤አሞ3፥1፥9፥7
2፥11 ዘዳ18፥18፤ መሳ13፥5፤ኤር7፥25
2፥12 ኢሳ30፥10፤ ኤር11፥21፤አሞ7፥ 12ኛ13፤ሚክ2፥6
2፥13 አሞ7፥ 16ኛ17
2፥14 1ነገ20፥11፤ ኢዮ11፥20፤ መዝ33፥16፤ ኢሳ30፥16ኛ17
2፥15 ዘ15፥21፤ መክ9፥11፤ሕዝ39፥3፤ ዘካ10፥5
2፥16 ኤር48፥41
3፥1 አሞ2፥10፤ ሰፎ2፥5
3፥2 ቍ14፤ ዘ19፥6፤ ዘዳ7፥6፤ ኤር14፥10፤ሚክ2፥3፤ ሉቃ12፥47፤1ጴጥ4፥1 7
3፥4 መዝ104፥21፤ ኢሳ42፥13፤ሆሴ5፥14
3፥5 መዝ119፥110
3፥6 ዘኍ10፥2፤ ኢ. ዮ39፥24፤ አሳ14፥24ኛ27፥31፥2፤ ኤር4፥21
3፥7 ዘፍ18፥17፤ 1ሳሙ3፥7፤ኤር23፥22 ፤ዳን9፥22፤ዮሐ15፥15፤ ራእ10፥7
3፥8 አሳ31፥4፤ 42፥13፤ኤር20፥9፤ ዮና1፥1ኛ3፥3፥1ኛ3፤ ሐሥ4፥20
3፥9 ኢሱ13፥3፤ 2ዜና26፥6፤አሞ4፥1፥6፥1

[ቀ]4 ወይም *በውሸት* የሚሉ አሉ
[በ]4 ወይም *ውሸት* የሚሉ አሉ ።

ውስጥ የሚያከማቹ፣
በጎ ነገር ማድረግን አያውቁም፤”
ይላል እግዚአብሔር።
11 ስለዚህ ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“ጠላት ምድሪቱን ይወራል፤
ምሽጎቻችሁን ያፈርሳል፤ ድንኳኖቻችሁን
ይዘርፋል።”
12 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“እረኛ ከአንበሳ መንጋጋ፣
ሁለት የእግር ዐጥንት ወይም የጆሮ ቍራ
ጭ
እንደሚያድን፣
እንዲሁም በሰማርያ
በዐልጋቸው† ጫፍ ላይ፣
በደማስቆም በምንጣፋቸው ላይ የተቀመጡ፣
እስራኤላውያን ይድናሉ።”
13 “ይህን ስሙ፤ በያዕቆብም ቤት ላይ መስ
ክሩ” ይላል ጌታ ፣
ሁሉን የሚገዛ አምላክ *እግዚአብሔር* ።
14 “እስራኤልን ስለ ኀጢአቷ በምቀጣበት
ቀን፣
የቤቴልን መሠዊያዎች አፈርሳለሁ፤
የመሠዊያው ቀንዶች ይቈረጣሉ፤
ወደ ምድርም ይወድቃሉ።
15 የክረምቱን ቤት፣
ከበጋው ቤት ጋር እመታለሁ፤
በዝሆን ጥርስ ያጌጡ ቤቶችም ይደመሰሳሉ፤
ታላላቅ አዳራሾችም ይፈርሳሉ፤”
ይላል *እግዚአብሔር*።

## እስራኤል ወደ እግዚአብሔር አልተመ ለሰም

4 እናንተ በሰማርያ ተራራ የምትኖሩ
የባሳን ላሞች፣
ድኾችን የምትጨቁኑና ችግረኞችን
የምታስጨንቁ፣
ባሎቻችሁንም፣ “መጠጥ አቅርቡልን”
የምትሉ ሴቶች ይህን ቃል ስሙ፣
2 ጌታ *እግዚአብሔር* በቅድስናው እንዲህ
ሲል ምሎአል፤
“እነሆ፤ በመንጠቆ ተይዛችሁ
የምትወሰዱበት
ትሩፋናችሁ እንኳ በዓሣ መንጠቆ
የሚወሰድበት ጊዜ ይመጣል።
3 እያንዳንዳችሁ በቅጥሩ በተነደለው መሽሎኪያ
ወደ ሬማንም‡ ትጣላላችሁ፤”
ይላል *እግዚአብሔር*።
4 “ወደ ቤቴል ሂዱና ኀጢአትን ሥሩ፤
ወደ ጌልገላም ሂዱና ኀጢአትን አብዙ፤
በየማለዳው መሥዋዕቶቻችሁን፣
በየሦስቱ§ ዓመት ዐሥራታችሁን አቅርቡ።
5 እርሾ ያለበትን እንጀራ የምሥጋና
መሥዋዕት አድርጋችሁ አቅርቡ፤
በፈቃዳችሁም በምታቀርቡት ቍርባን
ተመኩ፤
እናንት እስራኤላውያን በእነርሱም ተኵራሩ፤
ማድረግ የምትወዱት ይህን ነውና፤”
ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*፡
6 በየከተማው ሆዳችሁን‖ ባዶ አደረግሁት፤
በየመንደሩም የምትበሉትን
አሳጣኋችሁ፤ እናንተ ግን ወደ እኔ
አልተመለሳችሁም”
ይላል *እግዚአብሔር*፡
7 “መከር ሊደርስ ሦስት ወር ሲቀረውም፣
ዝናብ ከለከልኋችሁ፤
በአንዱ ከተማ ላይ አዘነብሁ፤
በሌላው ላይ ግን እንዳይዘንብ
አደረግሁ፤ አንዱ ዕርሻ ሲዘንብለት፣
ሌላው ዝናብ አጥቶ ደረቀ።
8 ሰዎች ውሃ ፍለጋ ከከተማ ወደ ከተማ ባዘኑ፣
ይሁን እንጂ ጠጥተው አልረኩም፤
እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም፤”
ይላል *እግዚአብሔር* ።
9 “የአትክልትና የወይን ቦታዎቻችሁን ብዙ
ጊዜ መታሁ፤
በዋግና በአረማሞም አጠፋኋቸው፤
አንበጦችም የበለስና የወይራ ዛፎቻችሁን
በሉ፤
እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም፤”
ይላል *እግዚአብሔር* ።
10 “በግብፅ ላይ እንዳደረግሁት፣
መቅሠፍትን ላክሁባችሁ፤
ከተማረኩት ፈረሶቻችሁ ጋር፣
ጕልማሶቻችሁን በሰይፍ ገደልሁ፤
የሰፈራችሁ ግማት አፍንጫችሁ እንዲገባ
አደረግሁ፤
እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም”
ይላል *እግዚአብሔር* ።
11 “ሰዶምንና ገሞራን እንደ ገለበጥኋቸው፣
አንዳንዶቻችሁን ገለበጥሁ፤
ከእሳት እንደ ተነጠቀ ትንታግ ሆናችሁ፤
እናንተ ግን ወደ እኔ¶ አልተመለሳችሁም፤”
ይላል *እግዚአብሔር*።
12 “ስለዚህ እስራኤል ሆይ፤ እንደዚህ
አደርግብሃለሁ፤
እንደዚህም ስለማደርግብህ፣ እስራኤል
ሆይ፤

†12 በዕብራይስጡ ለዚህ ዐረፍተ ነገር የተሰጠው ትርጒም አይታወቅም
‡3 በተለያዩ የዕብራይስጥ ቃላት የተከፈለው የመጀመሪያው የዕብራይስጥ ቅጅ (የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ይመ) *የጭቈና ተራራ ሆይ ራቅ* ይላል።
§4 *በየሦስቱ ቀናት ዐሥራታችሁን* የሚሉ አሉ
‖6 ዕብራይስጡ *ጥርሳችሁን አጠራለሁ* ይላል።
¶11 ዕብራይስጡ *አምላክ* ይላል።

3፥10 መዝ36፥3፤ አሞ5፥7፤6፥12፤ ሚክ6፥10፤ ዕን2፥8፤ሰፎ1፥9
3፥11 አሞ2፥5፤ 6፥14
3፥12 ሳሙ17፥34፤ አስ1፥6፤አሞ6፥4
3፥13 ሕዝ2፥7
3፥14 ቍ2፤ ዘፍ12፥8፤ዙ27፥2፤ ዘሌ26፥18፤ አሞ5፥5ኛ6
3፥15 መሳ3፥20፤ 1ነገ22፥39፤ ኢሳ34፥5፤ ኤር36፥22፤ ሆሴ10፥5-8፡ 14 ኛ15፤ አሞ5፥11፤6፥11
4፥1 ዘዳ24፥14፤ መዝ22፥12፤ ኢሳ58፥6፤ ኤር44፥19፤ ሕዝ18፥12፤ አሞ2፥8፤3፥9፤ 5፥11፤8፥6
4፥2 2ነገ19፥28፤
4፥3 ሕዝ12፥5
4፥4 ዘኍ28፥3፤ ዘዳ14፥28፤ኢሱ7፥2፤ ሕዝ20፥39፤ ሆሴ4፥15፤አሞ5፥21ኛ 22፤4፥5ዘሌ7፥13፤ 22፥18ኛ21፤4፥5
4፥6 ኢሳ3፥1፤ 9፥13፤ኤር5፥3፤ ሐጌ2፥17
4፥7 ዙ9፥4፡26፤ ዘዳ11፥17፤2ዜና7፥13፤ ኢሳ5፥6፤ኤር3፥3፤ ዘካ14፥17
4፥8 ኢዩ36፥31፤ ኤር3፥7፤14፥4፤ ሕዝ4፥16ኛ17 ሐጌ1፥6
4፥9 ዙ10፥13፤ ዘዳ28፥22፤ኢሳ9፥13፤ ኤር3፥10፤ ኢል1፥7፤2፥25
4፥10 ዙ9፥3፤ 11፥5፤ ዘዳ28፥21፤ኢሳ9፥13፡ 17፤34፥3 2ዜና33፥11፤ ኢሳ19፥8፤ ኤር31፥31፤አሞ6፥8
4፥11 ዘፍ19፥24፤ ኢዮ36፥13፤ ኢሳ7፥4፤ ኤር23፥14፤ይሁ1፥23

አምላክህን ለመገናኘት ተዘጋጅ።"
13ተራሮችን የሚሠራ፣
ነፋስን የሚፈጥር፣
ሐሳቡንም ለሰው የሚገልጥ፣
ንጋትን ጨለማ የሚያደርግ፣
የምድርንም ከፍታዎች የሚረግጥ፣
ስሙ የሰራዊት አምላክ
*እግዚአብሔር* ነው።

## የእስራኤል ሕዝብ ለንስሓ መጠራት

5 የእስራኤል ቤት ሆይ፤ ስለ እናንተ የምደ
ረድረውን ይህን የሙሾ ቃል ስሙ፤
2 "ድንግሊቱ እስራኤል ወደቀች፤
ከእንግዲህም አትነሣም፤
በገዛ ምድሯ ተጣለች፤
የሚያነሣትም የለም።"
3ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
"አንድ ሺህ ብርቱዎችን ለእስራኤል
የምታዘምት ከተማ፣
አንድ መቶ ብቻ ይቀሯታል፤
አንድ መቶ ብርቱዎችን የምታዘምተውም፣
ዐሥር ብቻ ይቀሯታል።"
4*እግዚአብሔር* ለእስራኤል ቤት እንዲህ
ይላል፤
"እኔን ፈልጉ፤ በሕይወትም ትኖራ
ላችሁ።"
5ቤቴልን አትፈልጉ፤
ወደ ጌልገላ አትሂዱ፤
ወደ ቤርሳቤህም አትሻገሩ፤
ጌልገላ በእርግጥ ትማረካለች፤
ቤቴልም እንዳልነበረች[ሀ] ትሆናለችና።
6*እግዚአብሔርን* ፈልጉ፤
በሕይወትም ትኖራላችሁ፤
አለበለዚያ እንደ እሳት የዮሴፍን
ቤት ያወድማል፤
እሳቱም ቤቴልን ይበላል፤ የሚያጠፋውም
የለም።
7እናንት ፍትሕን ወደ መራርነት
የምትለውጡ፣
ጽድቅንም ወደ ምድር የምትጥሉ ወዮላችሁ!
8ሰባቱን ከዋክብትና ኦሪዮንን የሠራ፣
ጨለማውን ወደ ንጋት ብርሃን የሚለውጥ፣
ቀኑን አጨልሞ ሌሊት የሚያደርግ፣
የባሕሩንም ውሃ ጠርቶ፣
በገጸ ምድር ላይ የሚያፈስ፣
ስሙ እግዚአብሔር ነው፤
9እርሱ በብርቱው ላይ ድንገተኛ ጥፋትን፣
በተመሸገውም ከተማ ላይ ውድመትን
ያመጣል።
10እናንተ በፍርድ አደባባይ
የሚገሥጻችሁን ትጠላላችሁ፤
እውነት የሚናገረውንም ትንቃላችሁ።

11እናንተ ድኻውን ትረግጣላችሁ፤
እህል እንዲሰጣችሁም
ታስገድዱታላችሁ፤
ስለዚህ በተጠረበ ድንጋይ ቤት ብትሠሩም፣
በውስጡ ግን አትኖሩም፤
ባማሩ የወይን ተክል ቦታዎች ወይን
ብትተክሉም፣
የወይን ጠጁን ግን አትጠጡም፤
12ኀጢአታችሁ ምንኛ ታላቅ እንደ ሆነ፣
በደላችሁም የቱን ያህል እንደ በዛ እኔ
ዐውቃለሁና።
ጻድቁን ትጨቍናላችሁ፤
ጉቦም ትቀበላላችሁ፤
በፍርድ አደባባይም ከድኻው ፍትሕ
ትነጥቃላችሁ።
13ስለዚህ አስተዋይ ሰው በእንዲህ ያለ ጊዜ
ዝም ይላል፤
ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና።
14በሕይወት ትኖሩ ዘንድ፣
መልካሙን እንጂ ክፉውን አትፈልጉ፤
ከዚያ በኋላ እንደ ተናገራችሁት፣
የሰራዊት አምላክ *እግዚአብሔር*
ከእናንተ ጋር ይሆናል።
15ክፉውን ጥሉ፤ መልካሙንም ውደዱ፤
በፍርድ አደባባይም ፍትሕን
አታጓድሉ፤
ምናልባትም የሰራዊት አምላክ *እግዚአብሐ
ር*፣
ለዮሴፍ ትሩፍ ይራራ ይሆናል።
16ስለዚህ ጌታ የሰራዊት አምላክ
*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
"በየመንገዱ ሁሉ ወየው ተብሎ
ይለቀሳል፤
በአደባባዩም የሥቃይ ጩኸት
ይሆናል፤ ገበሬዎች ለልቅሶ፣
አልቃሾችም ለዋይታ ይጠራሉ።
17በየወይኑ ዕርሻ ሁሉ ወየው ተብሎ
ይለቀሳል፤
እኔ በመካከላችሁ አልፋለሁና፤"
ይላል *እግዚአብሔር* ።

## የእግዚአብሔር ቀን

18*የእግዚአብሔርን* ቀን ለምትሹ፣
ለእናንተ ወዮላችሁ!
*የእግዚአብሔርን* ቀን ለምን ትሻላችሁ?
ያ ቀን ጨለማ ነው እንጂ ብርሃን
አይደለም።
19ይህ ቀን አንድ ሰው ከአንበሳ ሲሸሽ፣
ድብ እንደሚያጋጥመው፣
ወደ ቤቱም ገብቶ፣ እጁን በግድግዳው
ላይ ሲያሳርፍ፣

3

[ሀ]5 ሐዘን

4፥13 መዝ65፥6፤135፥7፤ኢሳ47፥4፤ ዳን2፥28፤አሞ5፥8፡27፤ 9፥6፤ሚክ1፥3
5፥1 ኤር4፥8፤ ሕዝ19፥1
5፥2 2ነገ19፥21፤ ኤር14፥17፤50፥32፤ አሞ8፥14
5፥3 ኢሳ6፥13፤ አሞ6፥9
5፥4 ዘዳ4፥29፤ 32፥46ኛ47፤ ኢሳ55፥3፤ ኤር29፥13፤ ሕዝ18፥9
5፥5 ዘፍ21፥31፤ 1ሳሙ7፥16፤8፥2፤ 11፥14፤ሆሴ4፥15፤ አሞ8፥14
5፥6 ቍ14፤ ዘሌ18፥5፤አዳ4፥24፤መዝ22፥26፤105፥4፤ኢሳ31፥1፤55፥6፤ ኤር4፥4፤አሞ3፥14፤ ሶፎ2፥3
5፥7 ኢሳ5፥20፤ ሆሴ10፥4፤ አሞ3፥10፤6፥12
5፥8 ዘፍ1፥16፤ ኢዮ38፥12፡31፤ መዝ104፥20፤ 104፥6ኛ9፤ኢሳ42፥16፤ ኤር16፥21፤አሞ4፥13፤ 8፥9
5፥9 ሚክ5፥11
5፥10 1ነገ22፥8፤ ኢሳ29፥21፤ገላ4፥16
5፥11 ዘዳ28፥30፤ መሳ9፥27፤አሞ3፥15፤ 4፥1፤8፥6፤9፥14፤ ሚክ1፥6፤6፥15፤ ሶፎ1፥13
5፥12 ኢዮ5፥4፤ 36፥18፤ ኢሳ1፥23፤ 5፥23፤ኤር5፥28፤ ሕዝ22፥12፤ ሆሴ5፥3፤አሞ2፥6ኛ7
5፥13 አስ4፥14፤ ሚክ2፥3
5፥14 ቍ6
5፥15 ዘፍ18፥25፤ መዝ52፥3፤97፥40፤ ኢሳ1፥17፤29፥1፤ ኤር36፥3፤ ኢል2፥14፤ መክ5፥7ኛ8፤7፥18፤ ዘካ8፥16፤ሮሜ12፥9
5፥16 ኤር7፥34፤ 9፥17፤ኢል1፥11፤ አሞ8፥3፤ሶፎ1፥10
5፥17 ዘ11፥6፤ 12፥12፤ኢሳ16፥10፤ ኤር48፥33
5፥18 1ሳሙ2፥9፤ ኢዮ20፥28፤ ኢሳ2፥12፤5፥19፡30፤ኤር30፥5፡7፤ ኢል1፥15፤2፥2
5፥19 ዘዳ32፥24፤ ኢዮ20፥24፤ መክ10፥8፤ ኢሳ24፥17ኛ18፤ ኤር15፥2ኛ3፤48፥44፤

እባብ እንደሚነድፈው ነው።
[20]*የእግዚአብሔር ቀን ብርሃን ሳይሆን ጨለማ፣*
የብርሃን ጸዳል የሌለው ድቅድቅ ጨለማ
አይደለምን?
[21]“*ዓመት በዓላችሁን ተጸይፌአለሁ፤*
ጠልቼውማለሁ፤
ጉባኤዎቻችሁ ደስ አያሰኙኝም።
[22]የሚቃጠል *መሥዋዕትና* የእህል
ቍርባን ብታቀርቡልኝም፣
እኔ አልቀበለውም፤
ከሰቡ እንስሶቻችሁ የኅብረት *መሥዋዕት*[ከ]
ብታቀርቡልኝም፣
እኔ አልመለከተውም።
[23]የዝማሬህን ጩኸት ከእኔ አርቅ፤
የበገናህንም ዜማ አልሰማም።
[24]ነገር ግን ፍትሕ እንደ ወንዝ፣
ጽድቅም እንደማይደርቅ ምንጭ ይፍጠ
ሰስ። [25]“የእስራኤል ቤት ሆይ፤ አርባ ዓ
መት
በምድረ በዳ፣
*መሥዋዕትንና* ቍርባንን አቅርባችሁልኝ
ነበርን?
[26]ለራሳችሁ የሠራችሁትን፣
የንጉሣችሁን ቤተ ጣዖት፣
የጣዖቶቻችሁን ዐምድ፣
የአምላካችሁን[ኸ] ኮከብ አንሥታችሁ
ተሸከማችሁ።
[27]ስለዚህ ከደማስቆ ወዲያ እንድትሰደዱ
አደርጋችኋለሁ፤”
ይላል ስሙ የሰራዊት አምላክ
የሆነ
*እግዚአብሔር።*

**ተዘልላል ላለችው እስራኤል የተሰጠ ማስ ጠንቀቂያ**

6 በጽዮን ተዘልላችሁ የምትቀመጡ፣
በሰማርያ ተራራ ያለ ሥጋት የምትኖሩ፣
የእስራኤልም ሕዝብ ለርዳታ ወደ እናንተ
የሚመጡባችሁ፣
እናንት የአሕዛብ አለቆች ሆይ፤
ወዮላችሁ!
[2]ወደ ካልኔ ሂዱ፤ እርሱንም ተመልከቱ፤
ከዚያም ወደ ታላቂቱ ሐማት ሂዱ፤
ወደ ፍልስጥኤም ከተማ ወደ ጌትም ውረዱ፤
እነዚህ ከሁለቱ *መንግሥታቶቻችሁ*
ይሻላሉን?
የምድራቸውስ ስፋት ከእናንተ ይበልጣልን?
[3]ክፉውን ቀን ለምታርቁ፣
የግፍንም ወንበር ለምታቀርቡ ወዮላችሁ!
[4]በዝሆን ጥርስ ባጌጠ ዐልጋ ላይ ለምትተኙ፤
በድንክ ዐልጋችሁ ላይ ለምትዝናኑ፣
ከበጎች መንጋ ጠቦትን፣
ከጋጣም ጥጃን ለምትበሉ፤
[5]ባልተቃኘ በገና ለምትዘፍኑ፣
በሙዚቃ መሣሪያ ለመጫወት
ለምትሹ፣ [6]በፉጋ የወይን ጠጅ ለምትጠጡ፣
ምርጥ ሽቱም ለምትቀቡ፣
ስለ ዮሴፍ መከራ ግን ለማታዝኑ
ወዮላችሁ!
[7]ስለዚህ እናንተ በመጀመሪያ በምርኮ
ከሚወሰዱት መካከል ናችሁ፤
መፈንጠዛችሁና መዝናናታችሁም
ያበቃል።

**እግዚአብሔር የእስራኤልን ትዕቢት ይጸየፋል**

[8]ጌታ *እግዚአብሔር* “የያዕቆብን ትዕቢት
ተጸይፌአለሁ፤
ምሽጎቹንም ጠልቻለሁ፤
ከተማዪቱንና በውስጥዋ ያለውን ሁሉ፣
አሳልፌ እሰጣለሁ” ሲል በራሱ
ምሎአል፤
ይላል የሰራዊት አምላክ *እግዚአብሔ
ር።*
[9]በአንድ ቤት ውስጥ ዐሥር ሰዎች ቢቀሩ
እነርሱም ይሞታሉ። [10]በድኖቹንም ከቤት
አውጥቶ ማቃጠል ያለበት አንድ ዘመድ
መጥቶ ተደብቆ ያለውን ሰው፣ “ከአንተ ጋር
የቀረ ሌላ ሰው አለን?” ሲለው፣ እርሱም
“የለም” ይለዋል፤ ከዚያም በኋላ፣ “ዝም
በል፤ *የእግዚአብሔርን* ስም መጥራት አይገ
ባንም” ይለዋል።
[11]እነሆ፤ *እግዚአብሔር* ትእዛዝ ሰጥቶአልና፤
ታላላቅ ቤቶችን ያወድማቸዋል፤
ትንንሾቹንም ያደቅቃቸዋል።
[12]ፈረሶች በጭንጫ ላይ ይሮጣሉን?
ሰውስ እዚያ ላይ በበሬ ያርሳልን?
እናንተ ግን ፍትሕን ወደ መርዝነት፣
የጽድቅንም ፍሬ ወደ መራራነት
ለወጣችሁ።
[13]እናንተ ሎዶባርን[ወ] በማሸነፋችሁ ደስ
ያላችሁ፣
“ቃርናይምን[ዐ] በራሳችን ብርታት ይዘናል”
የምትሉ፣
[14]ሁሉን የሚገዛ አምላክ *እግዚአብሔር* እንዲ
ህ
ይላልና፣
“የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፤ እነሆ፤ እኔ ከሐ
ማት መግቢያ[ዘ] እስከ ዓረባ ሸለቆ ድረስ፣
የሚያስጨንቃችሁን ሕዝብ፣ በእናንተ
ላይ አስነሣለሁ።”

ሰቆ3፥10
5፥20 1ሳሙ2፥9፤ ኢሳ13፥10፤ ሕዝ7፥7፤አብ1፥15፤ ሰፎ1፥15
5፥21 ዘሌ26፥3፤ ኤር44፥4፤ ሕዝ23፥18፤ሆሴ2፥11
5፥22 ዘሌ26፥31፤ መዝ40፥6፤ ኢሳ1፥11ኛ16፤ ኤር7፥21፤14፥12፤ አሞ4፥4፤ሚክ6፥6ኛ7
5፥23 አሞ6፥5
5፥24 ኢሳ45፥8፤ ኤር22፥3፤ሚክ6፥8
5፥25 ዙ16፥35፤ ኢሳ43፥23
5፥26 ሕዝ18፥6፤ 20፥16
5፥27 ዘዳ32፥ 17ኛ19፤ ኤር38፥17፤ አሞ4፥13፤6፥7፤7፥11፡ 17፤ሚክ1፥16፤ ሐዋ7፥42ኛ43 አሞ3፥9፤ሰፎ1፥12፤ ሉቃ6፥24
6፥1 ኢዮ24፥23፤ ኢሳ32፥9ኛ11፤
6፥2 ዘፍ10፥10፤ ኢሱ11፥22፤2ነገ 17፥24፤2ዜና26፥6፤ ኤር49፥23፤ናሆ3፥8
6፥3 ኢሳ56፥12፤ ሕዝ12፥22፤አሞ9፥10
6፥4 አስ1፥6፤ ምሳ7፥17፤ ኢሳ1፥11፤ ሕዝ34፥2ኛ3፤ አሞ3፥12
6፥5 1ዜና15፥16፤ መዝ137፥2፤ ኢሳ14፥11፤አሞ5፥23
6፥6 ኢሳ28፥1፤ ሕዝ9፥4፤16፥49፤ አሞ2፥8
6፥7 አሞ 5፥27
6፥8 ዘፍ22፥16፤ ዘሌ26፥19፡30፤ ዘዳ32፥19፤መዝ47፥4፤ ኤር12፥8፤አሞ4፥2፤ ዕብ6፥13
6፥9 አሞ5፥3
6፥10 1ሳሙ31፥12፤ አሞ8፥3
6፥11 ኢሳ34፥5፤ 55፥11፤አሞ3፥15
6፥12 ኢሳ1፥21፤ ሆሴ10፥4፤አሞ3፥10፤5፥7
6፥13 ኢዮ8፥15፤ ኢሳ28፥14ኛ15
6፥14 ዘኍ13፥21፤ ኤር5፥15፤አሞ3፥11

[ከ]22 *የሰላም መሥዋዕት* በመባል የሚታወቀው ነው።
[ኸ]26 ወይም *ንጉሣችሁን ሱኮትን ከፍ ከፍ አደረጋችሁት፤ እንዲሁም ጣዖታችሁን ቀይዋን የከዋክብት አማልክታችሁን፣* ሰብዓ ሊቃናት *የሞሌክን ቤተ ጣዖት እንዲሁም የአምላካችሁን የሬፋንን ከዋክብት ከፍ አደረጋችሁ*
[ወ]13 ትርጒሙ *ምንም* ማለት ነው።
[ዐ]13 *ቃርናይም* ትርጒሙ *ቀንዶች* ማለት ነው፤ ቀንድ የጥንካሬ ምልክት ነው።
[ዘ]14 ወይም *ከመግቢያው ጀምሮ*

## አንበጣ፣ እሳትና ቱንቢ

7 ጌታ *እግዚአብሔር* ይህን አሳየኝ፤ የንጉሡ
የመከር እህል ከተሰበሰበ በኋላ ገቦው
መብቀል በጀመረ ጊዜ፣ እርሱ የአንበጣ *መንጋ*
እንዲፈለፈል አደረገ። 2አንበጦች የምድሩን
ሣር ግጠው ከጨረሱት በኋላ፣ “ጌታ *እግዚ*
*አብሔር* ሆይ፤ ይቅር እንድትል እለምንሃ
ለሁ፤ ያዕቆብ ይህን እንዴት ሊቋቋመው
ይችላል? *ታናሽ ነው* እኮ” አልሁ።
3*እግዚአብሔርም* ስለዚህ ነገር ተጸጸተ፤
*እግዚአብሔርም* ይህ አይፈጸምም አለ።
4ጌታ *እግዚአብሔር* ይህንም አሳየኝ፤ ጌታ
*እግዚአብሔር* በእሳት ሊፈርድ ተዘጋጀ፤
እሳቱም *ታላቁን* ጥልቅ አደረቀ፤ ምድሪቱንም
በላ። 5ከዚያም በኋላ፣ “ጌታ *እግዚአብሔር*
ሆይ፤ እንድትተወው እለምንሃለሁ፤ ያዕቆብ
ይህን እንዴት ሊቋቋመው ይችላል?
*ታናሽ* ነው እኮ” አልሁ።
6*እግዚአብሔር* ስለዚህ ነገር ተጸጸተ፤
ጌታ እግዚአብሔር፣ “ይህም ደግሞ
አይ ፈጸምም” አለ።
7ይህንም ደግሞ አሳየኝ፤ ጌታ በእጁ ቱምቢ
ይዞ በቱምቢ በተሠራ ቅጥር አጠገብ ቆሞ
ነበር። 8*እግዚአብሔር*፣ “አሞጽ፣ የምታየው
ምንድነው?” አለኝ።
እኔም፣ “ቱምቢ” አልሁ።
ጌታም እንዲህ አለ፤ “እነሆ፤ በሕዝቤ በእስ
ራኤል መካከል ቱምቢ እዘረጋለሁ፤
ከእንግዲህም ወዲያ አልምራቸውም።

9“የይስሐቅ ማምለኪያ ኰረብታዎች ባድማ
ይሆናሉ፤
የእስራኤል መቅደሶች ይፈርሳሉ፤
በኢዮርብዓምም ቤት ላይ በሰይፌ
እነሣለሁ።”

## አሞጽና አሜስያስ

10ከዚህ በኋላ የቤቴል ካህን አሜስያስ
ወደ እስራኤል ንጉሥ ወደ ኢዮርብዓም እን
ዲህ ሲል መልእክት ላከ፤ “አሞጽ በእስራ
ኤል ቤት መካከል በአንተ ላይ እያሤረ
ነው፤ ምድሪቱም ቃሉን ሁሉ ልትሸከም
አት ችልም፤ 11አሞጽ እንዲህ ሲል ተናግሮ
ነበርና፤

“ ‘ኢዮርብዓም በሰይፍ ይሞታል፤
እስራኤልም በእርግጥ ከትውልድ አገሩ
ተማርኮ ይሄዳል።’”

12አሜስያስም፣ አሞጽን እንዲህ አለው፤
“አንተ ባለ ራእይ ከዚህ ሂድ! ከይሁዳ ምድር
ሽሽ፤ እዚያም እንጀራህን ብላ፤ በዚያም ትንቢት
ተናገር። 13ከእንግዲህ ወዲያ ግን በቤቴል
ትንቢት አትናገር፤ የንጉሡ መቅደስ፣
*የመንግሥቱም መኖሪያ ነውና።*”
14አሞጽም ለአሜስያስ እንዲህ ሲል መለሰ፤
“እኔ እረኛና የባሉጥ ፍሬ ለቃሚ ነኝ እንጂ
ነቢይ ወይም የነቢይ ልጅ አይደለሁም፤ 15*እግዚ*
*አብሔር* ግን የበግ *መንጋ* ከምጠብቅበት ቦታ
ወስዶ፣ ‘ሂድና ለሕዝቤ ለእስራኤል
ትንቢት ተናገር’ አለኝ፤ 16እንግዲህ *የእግዚ*
*አብሔርን ቃል* ስማ።
አንተ፣ “ ‘በእስራኤል ላይ ትንቢት አትናገር፤
በይስሐቅም ቤት ላይ አትስበክ’ ትላለህ።
17“ስለዚህ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤”

‘ሚስትህ በከተማዪቱ ውስጥ *ጋለሞታ*
ትሆናለች፤
ወንዶችና ሴቶች ልጆችህም በሰይፍ
ይወድቃሉ፤
ምድርህም እየተለካ ይከፋፈላል፤
አንተ ራስህ በረከሰ[ጕ] ምድር ትሞታለህ፤

እስራኤልም ከትውልድ አገሩ፣
ተማርኮ ይሄዳል።’ ”

## የጐመራ ፍሬ የሞላበት ቅርጫት

8 ጌታ *እግዚአብሔር* ይህን አሳየኝ፤
እነሆ፤ የጎመራ ፍሬ የሞላበት ቅርጫት
ነበረ። 2እርሱም፣ “አሞጽ ሆይ፤ ምን
*ታያለህ?*” አለኝ። እኔም፣ “የጎመራ ፍሬ
የሞላበት ቅርጫት አያለሁ” አልሁ።
ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፤
“በሕዝቤ በእስራኤል ላይ ፍጻሜ መጥቶአል፤
ከእንግዲህም አልምራቸውም።”
3ጌታ *እግዚአብሔር*፣ “በዚያ ቀን የቤተ
መቅደሱ ዝማሬ ወደ ዋይታ[የ] ይለወጣል፤
እጅግ ብዙ የሆነ የሰው ሬሳ ወድቆ ይገኛል፤
ዝምታም ይሰፍናል” ይላል።

4እናንት ችግረኞችን የምትረግጡ፣
የምድሪቱንም ድኾች የምታጠፉ ይህን ስሙ፤

5እንዲህም ትላላችሁ፤
“መስፈሪያውን በማሳነስ፣
ዋጋውን ከፍ በማድረግ፣
በሐሰተኛ ሚዛን በማጭበርበር፣
እህል እንድንሸጥ፣
የወር መባቻ መቼ ያበቃል?
ስንዴም ለገበያ እንድናቀርብ፣
ሰንበት መቼ ያልፋል?”
6ድኻውን በብር፣
ችግረኛውንም በጥንድ ጫማ እንገዛለን፤
ግርዱን እንኳ በስንዴ ዋጋ
እንሸጣለን።”
7*እግዚአብሔር* በያዕቆብ ክብር እንዲህ ሲል
ምሎአል፤ “እነርሱ ያደረጉትን ሁሉ ከቶ

7፥1 ቆኑ7፤ መዝ78፥46፤ኤር51፥14፤ኢል1፥4፤አሞ8፥1
7፥2 ዘፀ10፥15፤ ኢሳ37፥4፤ሕዝ11፥13፤አሞ4፥9
7፥3 ዘፀ32፥14፤ ዘዳ32፥36፤ኤር18፥8፤26፥19፤ሆሴ11፥8
7፥4 ዘዳ32፥22፤ ኢሳ66፥16፤ኢል1፥19
7፥5 ቆኑ1፥2፤ ኢል2፥17
7፥6 ዘፀ32፥14፤ ኤር18፥8፤42፥10፤ ሕዝ9፥8፤ዮናፃ3፥10
7፥8 2ነገ21፥13፤ ኤር1፥11፡13፤15፥6፤ ሕዝ7፥2ኛ9፤አሞ8፥2
7፥9 ዘሌ26፥30፡31፤1ነገ13፥34፤2ነገ15፥9፤ኢሳ63፥18፤ ሆሴ10፥8
7፥10 ኢሱ7፥2፤ 2ነገ14፥23፡24፤ ኤር26፥8ኛ11፤38፥4
7፥11 ኤር36፥16፤ አሞ5፥27
7፥12 1ሳሙ9፥9፤ ማቴ8፥34
7፥13 ኢሱ7፥2፤ 1ነገ12፥29፤ኤር20፥2፤36፥5፤አሞ2፥12፤ ሐሥ4፥18
7፥14 1ሳሙ10፥5፤ 1ነገ10፥27፤2ነገ2፥5፤4፥37፤ኢሳ9፥10፤ ዘካ13፥5
7፥15 ዘፍ37፥2፤ 2ሳሙ7፥8፤ኢሳ6፥9፤ ኤር7፥1ኛ2፤26፥12፤ ሕዝ2፥3ኛ4
7፥16 ኤር22፥2፤ ሕዝ20፥46፤ሚክ2፥6
7፥17 2ነገ17፥6፤ ሕዝ4፥13፤ ሆሴ4፥13፤9፥3፤ አሞ2፥12ኛ13፤5፥27

8፥1 አሞ7፥1
8፥2 ዘፍ40፥16፤ ኤር1፥13፤24፥3፤ ሰቆ4፥18፤ ሕዝ7፥2ኛ9፤አሞ7፥8
8፥3 አሞ5፥16፤ 6፥10
8፥4 ኢዮ20፥19፤ መዝ14፥4፤ምሳ30፥14፤አሞ2፥7
8፥5 ዘፍ31፥7፤ ዘኍ10፥10፤ዘዳ25፥15፤2ነገ4፥23፤ነህ10፥31፤13፥15ኛ16፤ ኢሳ58፥13 ሕዝ45፥10ኛ12 ሆሴ12፥7፤ ሚክ6፥10ኛ11፤ዘካ5፥6
8፥6 አሞ2፥6፤ 4፥1፤5፥11
8፥7 ኢዮ35፥15፤ መዝ47፥4፤ሆሴ8፥13

[ጕ]17 ዕብራይስጡ *ርኩስ* ይለዋል።
[የ]3 *የቤተመቅደሱ ዘማሪያን ዋይታ ያሰማሉ* የሚሉ አሉ።

አልረሳም።
8“በዚህ ነገር ምድር አትናወጥምን?
በውስጧ የሚኖሩትስ ሁሉ አያለቅሱምን?
የምድር ሁለመና እንደ ዐባይ ወንዝ ይነሣል፤
እንደ ግብጽ ወንዝም ወደ ላይ ይፈናጠራል፤
ተመልሶም ይወርዳል።”
9ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤

“በዚያ ቀን፣ ፀሐይ በቀትር እንድትጠልቅ
አደርጋለሁ፤
ምድርንም ደማቅ ብርሃን ሳለ በቀን
አጨልማታለሁ።
10ዓመት በዓላችሁን ወደ ልቅሶ፣
ዝማሬአችሁንም ሁሉ ወደ ዋይታ
እለውጣለሁ፤
ሁላችሁም ማቅ እንድትለብሱ፣
ጠጕራችሁንም እንድትላጩ
አደርጋለሁ፤
ያን ጊዜ ለአንድያ ልጅ ሞት እንደሚለቀስበት፣
ፍጻሜውንም እንደ መራራ ቀን
አደርገዋለሁ።”

11ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“በምድር ላይ ረሐብን የምሰድበት ዘመን
ይመጣል፤
ይኸውም የእግዚአብሔርን ቃል
የመስማት ረሐብ እንጂ፣
እንጀራን የመራብ ወይም ውሃን
የመጠማት አይደለም።
12ሰዎች እግዚአብሔርን ለመሻት፣
ከባሕር ወደ ባሕር፣
ከሰሜን ወደ ምሥራቅ ይንከራተታሉ፤
ነገር ግን አያገኙትም።
13“በዚያ ቀን፣
“ሐነጃጅት ሴቶችና ብርቱዎች ጎል
ማሶች፣
ከውሃ ጥም የተነሣ ይዝላሉ።
14በሰማርያ ኀፍረት[ዶ] የሚምሉ፣
ወይም፣ ‘ዳን ሆይ፤ ሕያው አምላክህን’
የሚሉ፣
ወይም ‘ሕያው የቤርሳቤህ አምላክን[ጀ]’
ብለው የሚምሉ፣
ዳግመኛ ሳይነሡ፣ ለዘላለም
ይወድቃሉ።”

## እስራኤል ትጠፋለች

9 ጌታን በመሠዊያው አጠገብ ቆሞ
አየሁት፤ እርሱም እንዲህ አለ፤

“መድረኮቹ እንዲናወጡ፣
ጕልላቶቹን ምታ፣
በሕዝቡም ሁሉ ራስ ላይ ሰባብራቸው፤
የቀሩትን በሰይፍ እገድላቸዋለሁ፤

8፥8 ኢዮ9፥6፤
መዝ18፥7፤ኤር46፥8፤
51፥29፤አሞ9፥5
8፥9 ኢዮ5፥14፤
ኢሳ59፥9ኛ10፤
ኤር13፥16፤15፥9፤
ሕዝ32፥7፤
አሞ5፥8፤ሚክ3፥6፤
ማቴ27፥45፤
ማር15፥33፤
ሉቃ23፥44ኛ45
8፥10 ዘፍ21፥16፤
ዘሌ13፥40፤ዘሌ26፥31
፤ኢሳ3፥17፤
ኤር2፥19፤ሰቆ5፥15፤ሕ
ዝ7፥18፤ሆሴ2፥11፤
ኢል1፥8
8፥11 1ሳሙ3፥1፤
2ዜና15፥3፤ኢሳ30፥20፤
ኤር30፥3፤31፥27
8፥12 ሕዝ20፥3፥31
8፥13 ኢሳ9፥17፤
41፥17፤ሆሴ2፥3
8፥14 1ነገ12፥29፤
መዝ46፥2፤አሞ5፥2፥5፤
ሚክ1፥5
9፥1 መዝ68፥21፤
ኤር11፥11
9፥2 ኢዮ7፥9፤
ኤር51፥53፤
ሕዝ26፥20፤አብ1፥4
9፥3 ዘፍ49፥17፤
ኢዮ11፥20፤
መዝ68፥22፤139፥8ኛ
10፤ኢሳ27፥1፤
ኤር16፥16ኛ17፤
አሞ1፥2
9፥4 ዘሌ26፥33፤
ኤር21፥10፤39፥16፤
44፥11፤ሕዝ5፥12፤
15፥7፥2፤ 9፥5
መዝ46፥2 አሞ8፥8
9፥6 መዝ104፥1ኛ3፥
5ኛ6፥13፤ኤር43፥9፤
አሞ5፥8
9፥7 ዘፍ10፥14፤
ዘዳ2፥23፤2ነገ16፥9፤2ዘ
ና12፥3፤ኢሳ20፥4፤
22፥6፤43፥3፤
አሞ2፥10
9፥8 ኤር4፥27፤
44፥27
9፥9 ኢሳ30፥28፤
ኤር31፥36፤ዳን9፥7፤
ሉቃ22፥31

ከእነርሱ አንድም ሰው አይሸሽም፤
ቢሸሽም የሚያመልጥ የለም።
2መቃብር[ገ] በጥልቀት ቈፍረው
ቢወርዱም፣
እጄ ከዚያ ታወጣቸዋለች፤
ወደ ሰማይ ቢወጡም፣
ከዚያ አወርዳቸዋለሁ።
3በቀርሜሎስ ጫፍ ላይ ቢሸሸጉም፣
አድኜ ፈልጌ ከዚያ አወርዳቸዋለሁ፤
እይዛቸዋለሁም፤
በጥልቅ ባሕር ውስጥ ከእኔ ቢሸሸጉም፣
በዚያ እባቡ እንዲነድፋቸው አዘዋለሁ፤
4በጠላቶቻቸው ተነድተው ለምርኮ ቢወሰዱም፣
በዚያ እንዲገድላቸው ሰይፍን
አዛለሁ፤
ለመልካም ሳይሆን ለክፉ፣
ዓይኔን በእነርሱ ላይ አደርጋለሁ።

5ጌታ ፣ እግዚአብሔር ጸባኦት፣
ምድርን ይዳስሳል፤
እርሷም ትቀልጣለች፤
በውስጥዋ የሚኖሩ ሁሉ ያለቅሳሉ፤
የምድር ሁለመና እንደ ዐባይ ወንዝ
ይነሣል፤
እንደ ግብጽ ወንዝም ይወርዳል።
6መኖሪያውን[ጠ] በሰማይ የሚሠራ፣
መሠረቱንም[ጨ] በምድር የሚያደርግ፣
የባሕርን ውሃ የሚጠራ፣
በምድርም ገጽ ላይ የሚያፈስ፣
እርሱ ስሙ እግዚአብሔር ነው።
7“እናንት እስራኤላውያን፣
ለእኔ እንደ ኢትዮጵያውያን
አይደላችሁምን?”
ይላል እግዚአብሔር
“እስራኤልን ከግብጽ፣
ፍልስጥኤማውያንን ከከፍቶር[ጰ]፣
ሶርያውያንንም ከቂር አላወጣሁምን?
8“እነሆ፤ የጌታ እግዚአብሔር ዐይኖች፣
በኀጢአተኛ መንግሥት ላይ ናቸው፤
ከምድር ገጽ፣ ፈጽሜ አጠፋዋለሁ፤
የያዕቆብን ቤት ግን፣ ሙሉ በሙሉ
አልደመስስም፤”
ይላል እግዚአብሔር።
9“እነሆ፤ ትእዛዝ እሰጣለሁ፤
እህል በወንፊት እንደሚነፋ፣
የእስራኤልን ቤት፣
በሕዝብ ሁሉ መካከል እንዲሁ
አደርጋለሁ፤

[ዶ]14ወይም *በአሼማ* ወይም *በጣኦት* አማልክት።
[ጀ]14 ወይም *ኀይል*
[ገ]2ዕብራይስጡ *ሲኦል* ይለዋል።
[ጠ]6 ዕብራይስጡ ለዚህ ሐረግ የሰጠው ትርጕም ምን እንደሆነ አይታወቅም።
[ጨ]6 ዕብራይስጡ ለዚህ ሐረግ የሰጠው ትርጕም ምን እንደሆነ አይታወቅም።
[ጰ]7 በላይኛው ዐባይ አካባቢ ያለ ሕዝብ ነው

ነገር ግን አንዲት ቅንጣት በምድር
ላይ አትወድቅም።

[10]በሕዝቤ መካከል ያሉ፣
‘ክፉ ነገር አያገኘንም ወይም
አይደርስብንም’ የሚሉ፣
ኀጢአተኞች ሁሉ፣
በሰይፍ ይሞታሉ።

**የእስራኤል መመለስ**

[11] “በዚያ ቀን፣
የወደቀውን የዳዊትን ድንኳን አነሣለሁ፤
የተሰበረውን እጠግናለሁ፤
የፈረሰውን ዐድሳለሁ፤
ቀድሞ እንደነበረም አድርጌ እሠራዋለሁ፤
[12]ስለዚህ የኤዶምን ትሩፍ፣
በስሜ[a] የተጠሩትንም ሕዝቦች ሁሉ
ይወርሳሉ፤”
ይላል ይህን የሚያደርግ እግዚአብሔር።
[13]እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“እነሆ፤ ዐጫጁ ዐጭዶ ሳይጨርስ፣
ዐራሹ በላዩ የሚደርስበት፣
ችግኝ ተካዩም ገና ተክሎ ሳይጨርስ፣
ወይን ጨማቂው የሚደርስበት ጊዜ
ይመጣል፤
አዲስ የወይን ጠጅ ከተራሮች
ይንጠባጠባል፤
ከኰረብቶችም ሁሉ ይፈሳል።
[14]የተሰደደውን[b] ሕዝቤን እስራኤልን
እመልሳለሁ፤
እነርሱም የፈራረሱትን ከተሞች መልሰው
ሠርተው በውስጣቸው ይኖራሉ።
የወይን ተክል ተክለው፣ ጠጁን ይጠጣሉ፤
አትክልት ተክለው ፍሬውን ይበላሉ።
[15]እስራኤልን በገዛ ምድራቸው እተክላቸዋለሁ፤
ከሰጠኋቸውም ምድር፣ ዳግመኛ
አይነቀሉም”
ይላል አምላክህ እግዚአብሔር።

9፥10 ኤር5፥12፤ 23፥17፤49፥37፤ ሕዝ20፥38፤አሞ6፥3
9፥11 ዘፍ26፥22፤ መዝ53፥6፤80፥12፤ ኢሳ7፥2፤49፥8፤ ሕዝ17፥24፤ ሚክ7፥8፥11፤ዘካ12፥7፤ 14፥10
9፥12 ዘኍ24፥18፤ ኢሳ43፥7፤ ኤር25፥29፤ ሐዋ15፥16ኛ17
9፥13 ዘሌ26፥5፤ መሳ9፥27፤ ሩት2፥3፤ ኤር31፥38፤33፥14፤ ኢል2፥24፤3፥18
9፥14 2ነገ19፥29፤ ኢሳ32፥18፤ 49፥8፤61፥14፤62፥9፤ኤር29፥14፤30፥18፤31፥28፤33፥7፤ ሕዝ28፥25ኛ26፤ 34፥13ኛ14፤አሞ5፥11
9፥15 ዘ15፥17፤ኢሳ60፥21፤65፥9፤ኤር3፥18፤18፥9፤23፥8፤ 24፥6፤32፥15፤ሕዝ28፥26፤ 34፥25ኛ28፤37፥12፥35፤ኢል3፥20

[a]12 ዕብራይስጡ እንደ ሰብዓ ሊቃናቱ ትርጒም *የሕዝቡ ትሩፋንና ስሜን የሚሸከሙ ሁሉ፣ እግዚአብሔርን ይፈልጋሉ።*
[b]14 ወይም *ዕጣ ፈንታቸውን አድሳለሁ እንደማለት* ነው።

# ትንቢተ አብድዩ

**የአብድዩ ራእይ፤**

[1]ጌታ *እግዚአብሔር* ስለ ኤዶም እንዲህ
ይላል፤
*ከእግዚአብሔር* ዘንድ መልእክት
ሰምተናል፤
መልእክተኛውም ወደ አሕዛብ ተልኮ እንዲ
ህ
ብሎአል፤
“ተነሡ፤ እርሷን ለመውጋት እንውጣ።”
[2]“እነሆ፤ በአሕዛብ መካከል ታናሽ
አደርግሃለሁ፤
እጅግ የተናቅህ ትሆናለህ።
[3]አንተ በሰንጣቃ[ሀ] ዐለት ውስጥ
የምትኖር፣
መኖሪያህንም በከፍታ ስፍራ ያደረግህ፣
ለራስህም፣
‘ማን ወደ ምድር ሊያወርደኝ ይችላል?’
የምትል፣
የልብህ ትዕቢት አታልሎሃል።
[4]እንደ ንስር መጥቀህ ወደ ላይ ብትወጣ፣
ጎጆህንም በከዋክብት መካከል
ብታደርግ፣
ከዚያ አወርድሃለሁ”
ይላል *እግዚአብሔር*።
[5]“ሌቦች ወደ አንተ ቢመጡ፣
ዘራፊዎችም በሌሊት ቢገቡ፣
የሚሰርቁት የሚፈልጉትን ያህል
ብቻ አይደለምን?
ወይን ለቃሚዎች ወደ አንተ ቢመጡ፣
ጥቂት ቃርሚያ አይተዉምን?
አንተ ግን ምንኛ ጥፋት ይጠብቅሃል!
[6]ዔሳው ግን እንዴት ተዘረፈ?
የሸሸገውስ ሀብት ምንኛ ተመዘበረ!
[7]ወዳጆችህ ሁሉ ወደ ድንበር ይገፉሃል፤
ጓደኞችህ ያታልሉሃል፤ ያሸንፉህማል፤
እንጀራህን የበሉ ወጥመድ ይዘረጉብሃል፤[ሰ]
አንተ ግን አታውቀውም።
[8]“በዚያ ቀን ጥበበኛ ሰዎችን ከኤዶም፣
አስተዋዮችንም ከዔሳው ተራሮች
አልደመ
ስስምን?”
ይላል *እግዚአብሔር* ።
[9]ቴማን ሆይ፤ ተዋጊዎችህ ይደነግጣሉ፤
በዔሳውም ተራሮች ያለ ሁሉ፣
ተገድሎ ይጠፋል።
[10]በወንድምህ በያዕቆብ ላይ ስላደረግኸው
ግፍ፣
በዕፍረት ትሸፈናለህ፤
ለዘላለምም ትጠፋለህ።

[11]እንግዶች ሀብቱን ዘርፈው ሲሄዱ፣
ባዕዳንም በበሮቹ ሲገቡ፣
በኢየሩሳሌምም ላይ ዕጣ ሲጣጣሉ፣
በዚያ ቀን ገለልተኛ ሆነህ ተመለከትህ፣
አንተም ከእነርሱ እንደ አንዱ ሆንህ።
[12]ክፉ ቀን በገጠመው ጊዜ፤
በወንድምህ ሥቃይ መደሰት
አልነበረብህም፤
በጥፋታቸው ቀን፣ የይሁዳ ሕዝብ ሲያዝኑ
ሐሤት ማድረግ አልነበረብህም፤
በጭንቀታቸውም ቀን፣
በትዕቢት ልትናገር አይገባህም ነበር።
[13]በጥፋታቸው ቀን፣
በሕዝቤ በር መግባት የለብህም ነበር፤
በጥፋታቸው ቀን፣
በጭንቀታቸው መደሰት
አልነበረብህም፤
በጥፋታቸው ቀን፣
ሀብታቸውን መዝረፍ አይገባህም ነበር።
[14]ስደተኞቻቸውን ለመግደል፣
በመንታ መንገድ መጠባበቅ አይገባህም
ነበር፣
በጭንቀታቸው ቀን፣
የተረፉትን አሳልፈህ መስጠት
አልነበረብህም።
[15]“በአሕዛብ ሁሉ ላይ፣
የእግዚአብሔር ቀን ደርሶአል፤
አንተ እንዳደረግኸው፣ በአንተም ላይ ይደረጋል፤
ክፉ ሥራህም በራስህ ላይ ይመለሳል።
[16]እናንተ በቅዱሱ ተራራዬ እንደ
ጠጣችሁ፣
አሕዛብ ሁሉ ዘወትር ይጠጣሉ፤
ይጠጣሉ፤ አብዝተውም ይጠጣሉ፤
ከዚህም በፊት እንዳልሆኑት ይሆናሉ።
[17]ነገር ግን በጽዮን ተራራ ነጻ መውጣት
ይሆናል፤
የያዕቆብ ቤትም እርሷ የተቀደሰች
ትሆናለች፤
ርስታቸውን ይወርሳሉ።
[18]የያዕቆብ ቤት እሳት፣
የዮሴፍም ቤት ነበልባል ይሆናል፤
የዔሳው ቤት ገለባ ይሆናል፤
ያቃጥሉታል፤ ይበሉትማል፤
ከዔሳው ቤት የሚተርፍ፣ አይኖርም።”
*እግዚአብሔር* ተናግሮአል።
[19]የኔጌብ ሰዎች፣

[ሀ]3 ወይም *በሴላ*
[ሰ]7 የዚህ ሐረግ የዕብራይስጡ ትርጉሜ በእርግጠኝነት አይታወቅም።

1፥1 ዘፍ25፥14፤ ኢሳ1፥1፤11፥14፤ 18፥2፤34፥11፤ 63፥1-6፤ኤር6፥4-5፤ 49፥7-22፤ሕዝ 25፥12-14፤32፥29፤ አሞ1፥11-12
1፥2 ዘኍ24፥18
1፥3 2ዜና25፥11-12፤ኢሳ16፥1፡6
1፥4 ኢዮ20፥6፤ ኢሳ10፥14፤14፥13
1፥5 ዘዳ4፥27፤ 24፥21፤ኢሳ24፥13
1፥7 መዝ41፥9፤ ኤር30፥14
1፥8 ኢዮ5፥12፤ ኢሳ29፥14
1፥9 ዘፍ36፥11፡34
1፥10 መዝ137፥7፤ ሕዝ25፥12-14፤ 35፥9፤ኢል3፥19፤ አሞ1፥11-12
1፥11 ኢዮ6፥27፤ ሕዝ24፥6፤አሞ1፥6
1፥12 ኢዮ31፥29፤ መዝ137፥7፤ ምሳ17፥5፤24፥17፤ ሕዝ25፥6፤35፥15፤ ሚክ4፥11፤7፥8
1፥13 ሕዝ35፥5
1፥14 1ነገ18፥4
1፥15 ኤር46፥10፤ 50፥29፤ ሕዝ30፥3፤ ኢል2፥31፤ አሞ5፥18፤ዕን2፥8
1፥16 ዘፀ15፥17፤ ኢሳ51፥17፤ ኤር25፥15፤ 49፥12፤ሰቆ4፥21-22፤ ሕዝ25፥12-14
1፥17 መዝ69፥35፤ 74፥2፤ኢሳ4፥3፤ 14፥12፤ኢል2፥32፤ አሞ9፥11-15፤ ዘካ8፥12
1፥18 ኢሳ1፥31፤ ኤር49፥10፤ ዘካ12፥6
1፥19 ዘኍ1፥36፤ ኢሳ11፥14፤ኤር31፥5

የዔሳውን ተራራ ይይዛሉ፤
ከተራራው ግርጌ ያሉ ሰዎችም፣
የፍልስጥኤማውያንን ምድር ይወርሳሉ፤
የኤፍሬምንና የሰማርያንም ዕርሻ ይይዛሉ፤
ብንያምም ገለዓድን ይወርሳል።
20በከነዓን ያለው ይህ የእስራኤል ስደተኞች ወገን፣
እስከ ሰራጵታ ያለውን ምድር
ይወርሳል፤
በሰፋራድም ያሉ የኢየሩሳሌም ስደተኞች፣
የኔጌብን ከተሞች ይወርሳሉ።
21የዔሳውን ተራሮች ለመግዛት፣
ነጻ አውጪዎች ወደ ጽዮን ተራራ ይወጣሉ፤
መንግሥቱም የእግዚአብሔር ይሆናል።

1፥20 1ነገ17፥9-10፤ኤር33፥13፤ሉቃ4፥26 ራእ11፥15
1፥21 ዘዳ28፥29፤ መሳ3፥9፤መዝ22፥28፤ 47፥9፤ 66፥4፤ዳን 2፥44፤ዘካ14፥9፡16፤ሚ ል1፥14፤

# ትንቢተ ዮናስ

## ዮናስ ከእግዚአብሔር ኰበለለ

1 የእግዚአብሔር ቃል ወደ አማቴ ልጅ ወደ
ዮናስ እንዲህ ሲል መጣ፤ [2]“ወደ ታላቂቱ
ከተማ ወደ ነነዌ ሂደህ፣ በእርሷ ላይ ስበክ፤
ክፋቷ በእኔ ፊት ወጥቶአልና።”
[3]ዮናስ ግን ከእግዚአብሔር ፊት ኰበለለ፤
ወደ ተርሴስም ለመሄድ ተነሣ። ወደ ኢዮጴ
ወረደ፣ ወደዚያው ወደ ተርሴስ የምትሄድ
መርከብም አገኘ። የጒዞውንም ዋጋ ከከፈለ
በኋላ፣ ከእግዚአብሔር ፊት ወደ ተርሴስ
ለመኰብለል በመርከቢቱ ተሳፈረ። [4]እግዚ
አብሔርም በባሕሩ ላይ ታላቅ ነፋስን ላከ፤
ከባድ ማዕበልም ተነሥቶ መርከቢቱን አንገ
ላታት፤ ልትሰበርም ተቃረበች። [5]መርከበ
ኞቹ ሁሉ ፈሩ፤ እያንዳንዱም ሰው ወደ አም
ላኩ ጮኸ፤ የመርከቢቱም ክብደት እንዲ
ቀል፣ በውስጧ የነበረውን ዕቃ ወደ ባሕሩ
ጣሉት።
ዮናስ ግን ወደ መርከቢቱ ታችኛ ክፍል
ወርዶ ተኛ፤ በከባድም እንቅልፍ ላይ ነበር።
[6]የመርከቢቱም አዛዥ ወደ እርሱ ሄዶ፣
“እንዴት ትተኛለህ? ተነሥና አምላክህን
ጥራ እንጂ፤ ምናልባትም ያስበንና ከጥፋት
ያድነን ይሆናል” አለው።
[7]ከዚያም መርከበኞቹ እርስ በርሳቸው፣
“ይህ ክፉ ነገር በማን ምክንያት እንደ
መጣብን ለማወቅ፣ ኑ፣ ዕጣ እንጣጣል”
ተባባሉ። ዕጣም ተጣጣሉ፤ ዕጣውም በዮናስ
ላይ ወደቀ።
[8]ከዚያም፣ “ይህ ሁሉ አስጨናቂ
ነገር በማን ምክንያት እንደ መጣብን
ንገረን፤ ሥራህ ምንድን ነው? ከወዴትስ
መጣህ? አገርህስ የት ነው? ከየትኛውስ ሕዝብ
ነህ?”አሉት።
[9]እርሱም፣ “እኔ ዕብራዊ ነኝ፤ የብስንና
ባሕርን የፈጠረውን፣ የሰማይን አምላክ
እግዚ አብሔርን አመልካለሁ” አለ።
[10]እርሱ አስቀድሞ ነግሮአቸው ስለ ነበር፣
ከእግዚአብሔር እንደ ኰበለለ ዐወቁ፣ ስለዚ
ህም በሁኔታው በመደንገጥ፣ “ይህ ያደረ
ግኸው ምንድን ነው?” አሉት።
[11]የባሕሩም ማዕበል እጅግ እየበረታ ስለ
ሄደ፣ “ባሕሩ ጸጥ እንዲልልን በአንተ ላይ
ምን ብናደርግ ይሻላል?” አሉት።
[12]እርሱም፣ “ይህ ታላቅ ማዕበል በእኔ
ምክንያት እንደ መጣባችሁ ዐውቃለሁ፤
አንሥታችሁ ወደ ባሕሩ ጣሉኝ፤ ባሕሩም ጸጥ
ይላል” አላቸው።
[13]ሰዎቹ ግን ባላቸው ኀይል እየቀዘፉ
ወደ የብስ ለመጠጋት ሞከሩ፤ ይሁን
እንጂ አልቻሉም፤ ባሕሩ የባሰ ይናወጥ
ነበርና።
[14]“እግዚአብሔር ሆይ፤ እባክህ በዚህ ሰው ነፍስ
ምክንያት አታጥፋን፤ የዚህ ንጹሕ ሰው ደምም
በእኛ ላይ አይሁን፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ
የወደድኸውን አድርገሃልና” ብለው ወደ
እግዚአብሔር ጮኹ። [15]ከዚያም ዮናስን
ይዘው ወደ ባሕሩ ጣሉት፤ ባሕሩም ከመና
ወጥ ጸጥ አለ። [16]ሰዎቹም እግዚአብሔርን
እጅግ ፈሩ፤ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትም
አቀረቡ፤ ለእርሱም ስእለትን ተሳሉ።
[17]እግዚአብሔር ግን ዮናስን የሚውጥ
ትልቅ ዓሣ አዘጋጀ፤ ዮናስም በዓሣው ሆድ
ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት አደረ።

## የዮናስ ጸሎት

2 ዮናስ በዓሣው ሆድ ውስጥ ሆኖ ወደ
አምላኩ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤
[2]እንዲህም አለ፤
“ተጨንቄ ሳለሁ ወደ እግዚአብሔር
ተጣራሁ፤
እርሱም መለሰልኝ፤
ከመቃብሩም[ሀ] ጥልቅ ርዳታን ፈልጌ
ተጣራሁ፤
አንተም ጩኸቴን ሰማህ።
[3]ጥልቅ ወደ ሆነው፣
ወደ ባሕሩ መካከል ጣልኸኝ፤
ፈሳሾችም ዙሪያዬን ከበቡኝ[ለ]፤
ማዕበልህና ሞገድህ ሁሉ፣
በላዬ አለፉ።
[4]እኔም፣ ‘ከፊትህ ጠፋሁ፣
ነገር ግን እንደ ገና፣
ወደ ቅዱስ መቅደስህ፣
እመለከታለሁ’ አልሁ።
[5]ውሃ እስከ ዐንገቴ አጠለቀኝ፤
ጥልቁም ከበበኝ፤
የባሕርም ዐረም በራሴ ላይ ተጠመጠመ።
[6]ወደ ተራሮች መሠረት ሰመጥሁ፤
የምድርም በር ለዘላለም ተዘጋብኝ፤
እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤
አንተ ግን ሕይወቴን ከጒድጓድ
አወጣህ።
[7]“ነፍሴ በዛለች ጊዜ፣

[ሀ]2 የዕብራይስጡ ትርጒም ሲያል ይላል።
[ለ]5 “ውሃዎች በዙሮሮዬ ነበሩ” የሚሉ አሉ

1፥1 2ነገ14፥25፤ ማቴ12፥39ጠ41፤ 16፥4፤ሉቃ11፥29ጠ 32
1፥2 ዘፍ10፥11፤ ናሆ1፥1
1፥3 ዘፍ10፥4፤ ዘፀ4፥13፤ኢሱ19፥46፤ መዝ139፥7፤ ኤር20፥9፤አሞ3፥8፤ ሐሥ9፥36፡43
1፥4 መዝ107፥23ጠ 26
1፥5 ሐሥ27፥1819
1፥6 መዝ107፥28፤ ዮና3፥8
1፥7 ዘኁ32፥23፤ ኢሱ7፥10ጠ18፤1ሳሙ 14፥42፤ምሳ16፥33
1፥9 ዘፍ1፥9፤ነህ 9፥6፤መዝ96፥9፤ዳን 2፥18፤ሐሥ17፥24
1፥12 2ሳሙ 24፥17፤ 1ዜና21፥17
1፥13 ምሳ21፥30
1፥14 ዘዳ21፥8፤ ዳን4፥35
1፥15 መዝ107፥29፤ ሉቃ8፥24
1፥16 ዘኁ30፥2፤ መዝ66፥1314፤ማር 4፥41
1፥17 ዩና4፥6፡7፤ ማቴ12፥40፤16፥4፤ ሉቃ11፥30
2፥2 መዝ18፥6፤ 86፥13፤120፥1፤ ሰቆ3፥55
2፥3 2ሳሙ22፥5፤ መዝ42፥7፤88፥6
2፥4 1ነገ8፥48፤ መዝ31፥22፤ኤር7፥15
2፥5 መዝ69፥12
2፥6 ኢዩ17፥16፤ 28፥9፤33፥18፤ መዝ30፥3
2፥7 2ዜና30፥27፤ መዝ11፥4፤18፥6፤ 77፥11ጠ12

*እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተን ዐሰብሁ፤*
ጸሎቴም ወደ አንተ፣
ወደ ቅዱስ መቅደስህ ዐረገች።
8“ከንቱ በሆኑ ጣዖቶች ላይ የሚንጠለጠሉ፤
ሊያገኙ የሚገባቸውን ጸጋ ያጣሉ።
9እኔ ግን በምስጋና መዝሙር፣
መሥዋዕት እሠዋልሃለሁ፤
የተሳልሁትንም እሰጣለሁ፤
ድነት *ከእግዚአብሔር* ዘንድ ነው።”
10*እግዚአብሔርም* ዓሣውን አዘዘው፤ ዮናስንም
በደረቅ ምድር ላይ ተፋው።

## ዮናስ ወደ ነነዌ ሄደ

3 *የእግዚአብሔርም* ቃል ለሁለተኛ ጊዜ
እንዲህ ሲል ወደ ዮናስ መጣ፤
2“ወደ ታላቂቱ ከተማ ወደ ነነዌ ሄደህ
የምነግርህን መልእክት ስበክላት።”
3ዮናስም *የእግዚአብሔርን* ቃል ታዘዘ፤ ወደ
ነነዌም ሄደ። በዚህ ጊዜ ነነዌ ታላቅ ከተማ
ነበረች፤ እርሷንም ከዳር እስከ ዳር ለመጎ
ብኘት ሦስት ቀን ያስፈልግ ነበር። 4ዮና
ስም ወደ ከተማዪቱ ገብቶ የመጀመሪያ
ውን ቀን ከተጓዘ በኋላ “ነነዌ በአርባ ቀን
ውስጥ ትገለበጣለች” ብሎ ዐወጀ። 5የነነዌም
ሰዎች እግዚአብሔርን አመኑ፤ ጾምንም ዐወጁ፤
ሰዎቹም ሁሉ ከትልቁ እስከ ትንሹ ማቅ
ለበሱ።
6ወሬውም ወደ ነነዌ ንጉሥ በደረሰ ጊዜ፣
ከዙፋኑ ወረደ፤ ልብሱንም አወለቀ፤ ማቅም
ለብሶ በዐመድ ላይ ተቀመጠ። 7ከዚያም
እንዲህ ሲል በነነዌ ዐዋጅ አስነገረ፤

“ከንጉሡና ከመሳፍንቱ የወጣ ዐዋጅ፤

ማንም ሰው ወይም እንስሳ፣ የከ
ብት መንጋም ሆነ የበግ መንጋ፣
ምንም ነገር አይቅመስ፤ አይብላ፤
ውሃም አይጠጣ። 8ነገር ግን ሰውም
እንስሳም ማቅ ይልበስ፤ ሁሉም አጥ
ብቆ ወደ እግዚአብሔር ይጮኽ፤ ሰዎ
ችም ሁሉ ክፉ መንገዳቸውንና
የግፍ ሥራቸውን ይተዉ። 9እኛ እን
ዳንጠፋ እግዚአብሔር ራርቶ ከጽኑ
ቍጣው ይመለስም እንደ ሆነ ማን
ያውቃል?”

10እግዚአብሔርም ምን እንዳደረጉና ከክፉ
መንገዳቸውም እንዴት እንደ ተመለሱ

2፥8 ዘዳ32፥21፤ 1ሳሙ12፥21
2፥9 ዘፀ15፥2፤ዘኍ 30፥2፤መዝ3፥8፤42፥4፤ 50፥14፡23፤116፥14፤ መክ5፥45፤ዕብ13፥15
3፥1 ዮና1፥1
3፥4 ኤር18፥7ጠ10
3፥5 ዳን9፥3፤ማቴ 11፥21፤12፥41፤ሉቃ 11፥32
3፥6 አስ4፥13፤ ኢዩ2፥8፡13፤ ሕዝ27፥30-31
3፥7 2ዜና20፥3፤ ዕዝ10፥6
3፥8 ኢዩ16፥17፤ መዝ130፥1፤ኤር 7፥3፤25፥5፤ና1፥6
3፥9 2ሳሙ12፥22፤ መዝ85፥3፤ኤር18፥8፤ ኢል2፥14
3፥10 ዘፀ32፥14፤ ኤር18፥8፤አሞ7፥6
4፥1 ቍ4፤ ማቴ20፥11፤ሉቃ 15፥28
4፥2 ዘፀ22፥27፤ዘኍ 14፥18፤ዘዳ4፥31፤ መዝ86፥5፡15፤103፥8፤ ኤር20፥78፤ ኢል2፥13
4፥3 ዘኍ11፥15፤ ኢዩ7፥15፤ኤር8፥3
4፥4 ዘፍ4፥6፤ ማቴ20፥11-15
4፥6 ዮና1፥17
4፥7 ኢል1፥12
4፥8 1ነገ19፥4
4፥9 ቍ4
4፥11 ዮና1፥2፤ 3፥2፡10

ባየ ጊዜ ራራላቸው፤ በእነርሱም ላይ ሊያ
መጣ ያሰበውን ጥፋት አላደረገም።

## ዮናስ እግዚአብሔር ምሕረት በማድረጉ ተቈጣ

4 ዮናስ ግን ፈጽሞ አልተደሰተም፤ ስለዚ
ህም ተቈጣ። 2ወደ *እግዚአብሔርም*
እንዲህ ብሎ ጸለየ፤ “*እግዚአብሔር* ሆይ፤
በአገሬ ሳለሁ የተናገርሁትስ ይህን አልነበ
ረምን? ፈጥኜ ወደ ተርሴስ ለመኰብለል
የተነሣሁትም ለዚሁ ነበር፤ አንተ ቸርና
ርኅሩኅ፤ ምሕረትህ የበዛ ከቍጣ የራቅህ
አምላክ፣ ጥፋትንም ከማምጣት የምትመ
ለስ እንደ ሆንህ ዐውቃለሁ። 3አሁንም *እግ
ዚአብሔር* ሆይ፤ ነፍሴን ውሰድ፤ ከምኖር
መሞት ይሻለኛልና።”
4*እግዚአብሔር* ግን፣ “በውኑ ልትቈጣ
ይገባሃልን?” አለው።
5ዮናስም ከከተማዪቱ ወጥቶ በስተ ምሥራቅ
በአንድ ስፍራ ተቀመጠ። በዚያም ለራሱ ዳስ ሠራ፤
በከተማዪቱም የሚሆነውን ለማየት ከዳሱ ጥላ
ሥር ተቀመጠ። 6*እግዚአብሔር* አምላክም የቅል
ተክል አብቅሎ፣ የዮናስ ራስ ጥላ እንዲ
ያገኝና ሙቀትም እንዳያስጨንቀው ከበላዩ
እንዲያድግ አደረገ፣ ዮናስም ስለ ቅሉ እጅግ
ደስ አለው። 7ነገር ግን በሚቀጥለው ቀን በማ
ለዳ እግዚአብሔር ትል አመጣ፤ ትሉም ቅሉን
በላ፤ ቅሉም ደረቀ። 8ፀሓይ ስትወጣ፣ እግዚ
አብሔር የሚያቃጥል የምሥራቅ ነፋስ
አመጣ፤
ፀሓዩም የዮናስን ራስ አቃጠለ፤ እርሱም
ተዝለፈለፈ፤ መሞትም ፈልጎ፣ ‘ከመኖር መሞት
ይሻለኛል” አለ።
9እግዚአብሔር ግን ዮናስን፣ “በውኑ ስለ
ቅሉ ልትቈጣ ይገባሃልን?” አለው።

እርሱም፣ “በእርግጥ እስከ ሞት ልቈጣ
ይገባኛል” አለ።

10*እግዚአብሔር* ግን እንዲህ አለው፤ “አንተ
እንዲበቅል ወይም እንዲያድግ ሳልደከም
ክበት ለዚህ ቅል እጅግ አዝነሃል፤ በአንድ
ሌሊት በቀለ፤ በአንድ ሌሊትም ደረቀ።
11ታዲያ፣ እኔ ቀኝና ግራቸውን ለይተው
መናገር የማይችሉ፣ ከአንድ መቶ ሃያ ሺህ
በላይ ሰዎችና አያሌ እንስሶች ለሚኖሩ
ባት ለታላቋ ከተማ ለነነዌ ማዘን አይገ
ባኝምን?”

# ትንቢተ ሚክያስ

1 በይሁዳ ነገሥታት በኢዮአታም፣ በአካዝና በሕዝቅያስ ዘመን ወደ ሞሬ
ታዊው ወደ ሚክያስ የመጣው የእግዚ
አብሔር ቃል፣ ስለ ሰማርያና ስለ ኢየሩ
ሳሌም ያየው ራእይ ይህ ነው፤

2እናንተ አሕዛብ ሆይ፤ ሁላችሁም ስሙ፤
ምድር ሆይ፤ በውስጧም የምትኖሩ
ሁሉ አድምጡ፤
ጌታ ከቅዱስ መቅደሱ፣
ልዑል እግዚአብሔር በእናንተ ላይ
ይመሰክርባችኋል።

## በሰማርያና በኢየሩሳሌም ላይ የተላለፈ ፍርድ

3እነሆ፤ እግዚአብሔር ከመኖሪያ ስፍራው
ይመጣል፤
ወርዶም በምድር ከፍታዎች ላይ
ይራመዳል።
4ተራሮች ከሥሩ ይቀልጣሉ፤
ሸለቆዎችም ይሰነጠቃሉ፤
በእሳት ፊት እንዳለ ሰም፣
በገደል ላይ እንደሚወርድ ፈሳሽ ይሆናሉ።
5ይህ ሁሉ የሚሆነው ስለ ያዕቆብ በደል፣
ስለ እስራኤልም ቤት ኀጢአት ነው።
የያዕቆብ በደል ምንድን ነው?
ሰማርያ አይደለችምን?
የይሁዳስ የኰረብታ መስገጃ ምንድን ነው?
ኢየሩሳሌም አይደለችምን?

6"ስለዚህ ሰማርያን የፍርስራሽ ክምር፣
ወይን የሚተከልባትም ስፍራ
አደርጋታለሁ፤
ድንጋዮቿን ወደ ሸለቆ አወርዳለሁ፤
መሠረቷንም ባዶ አደርጋለሁ።
7ጣዖቶችዋ ሁሉ ይሰባበራሉ፤
ለቤተ መቅደሷ የቀረበው ገጸ በረከት
በእሳት ይቃጠላል፤
ምስሎችዋን ሁሉ እደመስሳለሁ፤
ገጸ በረከቷን በዝሙት አዳሪነት
እንደ ሰበሰበች ሁሉ፣
አሁንም ገጸ በረከትዋ የዝሙት
አዳሪነት ዋጋ መቀበያ ይሆናል።

## ልቅሶና ሐዘን

8በዚህ ምክንያት አለቅሳለሁ፤ ዋይ ዋይም
እላለሁ፤
ባዶ እግሬንና ዕርቃኔን እሄዳለሁ፤
እንደ ቀበሮ አላዝናለሁ፤
እንደ ጉጉትም አቃስታለሁ።

1፥1 ቍ14፤ 1ዜና3፥12፥13፤ ኢሳ1፥1፤ ኤር26፥18፤ሆሴ1፥1
1፥2 ዘፍ31፥50፤ ዘዳ4፥26፤32፥1፤ መዝ11፥4፤50፥7፤ ኢሳ1፥2፤ኤር6፥19
1፥3 ኢሳ18፥4፤ 64፥1፤አሞ4፥13
1፥4 ዘኍ16፥31፤ ኢዮ9፥5፤መዝ46፥2፤ ናሆ1፥5
1፥5 አሞ8፥14
1፥6 ዘዳ20፥6፤ ሕዝ13፥14፤አሞ5፥11
1፥7 ዘፀ32፥20፤ ዘዳ9፥21፤23፥17-18፤ ሕዝ6፥6
1፥8 ኢሳ15፥3፤ 20፥2
1፥9 2ነገ18፥13፤ ኢሳ3፥26፤ ኤር10፥19፤46፥11
1፥11 ሕዝ23፥29
1፥12 ኤር14፥19፤ 40፥2
1፥13 ኢሱ10፥3፤ መዝ9፥14
1፥14 ቍ1፤ ኢሱ15፥44፤ 2ነገ16፥8፤ ኤር15፥18
1፥15 ኢሱ12፥15፤ 15፥44

9ቍስሷ የማይሽር ነውና፤
ለይሁዳ ተርፎአል፤
እስከ ሕዝቤ መግቢያ በር፣
እስከ ኢየሩሳሌም እንኳ ደርሶአል።
10በጌት[ሀ] አታውሩት፤
ከቶም አታልቅሱ[ለ]፤
በቤትዓፍራ[ሐ]፣
በትቢያ ላይ ተንከባለሉ።
11እናንት በሻፊር[መ] የምትኖሩ፣
ዕርቃናችሁን ሆናችሁ በኀፍረት
ዕለፉ፤
በጻዓናን[ሠ] የሚኖሩ
ከዚያ አይወጡም፤
ቤትዔጼል በሐዘን ላይ ናት፤
ለእናንተም መጠጊያ ልትሆን
አትችልም።
12ከመከራው መገላገልን በመሻት፣
በማሮት[ረ] የሚኖሩ በሥቃይ
ይወራጫሉ፤
እስከ ኢየሩሳሌም በር ሳይቀር፣
ክፉ ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ
መጥቶአልና።
13እናንት በለኪሶ[ሰ] የምትኖሩ፣
ፈረሶችን ከሠረገላው ጋር አያይዙ፤
ለጽዮን ሴት ልጅ፣
የኀጢአት መጀመሪያ እናንት
ነበራችሁ፤
የእስራኤል በደል
በእናንተ ዘንድ ተገኝቶአልና።
14ስለዚህ እናንተ ለሞሬሼትጌት፣
ማጫ ትሰጣላችሁ፤
የአክዚብ[ሸ] ከተማ፣
ለእስራኤል ነገሥታት መታለያ
ትሆናለች።
15እናንት በመሪሳ[ቀ] የምትኖሩ
ድል አድራጊ አመጣባችኋለሁ፤
ያ የእስራኤል ክብር የሆነው
ወደ ዓዶላም ይመጣል።

[ሀ]10 'ጌት' የሚለው ቃል በዕብራይስጡ 'አውራ' ከሚለው ጋር ተመሳሳይ አነባበብ አለው። [ለ]10 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ሲስማማ፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ግን 'በአኮ ላይ አታልቅሱ' ይላል። 'በአኮ' የሚለው የዕብራይስጡ ቃል 'አለቀሰ' ከሚለው የዕብራይስጡ ቃል ጋር ተመሳሳይ አነባበብ አለው። [ሐ]10 'ቤት ዓፍራ' ትርጒሙ 'የትቢያ ቤት' ማለት ነው።[መ]11 'ሻር' ትርጒሙ አስደሳች ማለት ነው። [ሠ]11 'ጻዓናን' የሚለው ቃል በዕብራይስጡ 'ውጣ' ከሚለው ጋር ተመሳሳይ አነባበብ አለው። [ረ]12 'ማሮት' የሚለው ቃል በዕብራይስጡ 'መራራ' ከሚለው ጋር ተመሳሳይ አነባበብ አለው። [ሰ]13 'ለኪሶ' የሚለው ቃል በዕብራይስጡ ቡድን ከሚለው ጋር ተመሳሳይ አነባበብ አለው። [ሸ]14 'አክዚብ' ትርጒሙ አታላይ/ማታለል ማለት ነው። [ቀ]15 'መሪሳ' የሚለው ቃል በዕብራይስጡ 'ድል አድራጊ' ከሚለው ጋር ተመሳሳይ አነባበብ አለው።

16ደስ ለምትሰኙባቸው ልጆቻችሁ፣
በሐዘን ራሳችሁን ተላጩ፤
ራሳችሁን እንደ አሞራ ራስ ተመለጡት፤
ከእናንተ በምርኮ ይወሰዳሉና።

### የእግዚአብሔርና የሰው ዕቅድ

2 ክፉ ለመሥራት ለሚያቅዱ፣
በመኝታቸው ሳሉ ተንኰል
ለሚያውጠነጥኑ ወዮላቸው!
ሲነጋ በማለዳ ይፈጽሙታል፤
የሚያደርጉበት ኀይል በእጃቸው
ነውና።
2ዕርሻ ይመኛሉ፤ ይይዙታልም፤
ቤት ይመኛሉ፤ ይወስዱታልም፤
የሰውን ቤት፣
የባልንጀራን ርስት አታልለው ይወስዳሉ።
3ስለዚህ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

"እነሆ፤ በዚያ ሕዝብ ላይ ጥፋት ላመጣ
ዐቅጃለሁ፤
ከዚህም ለማምለጥ አትችሉም።
ከእንግዲህ በትዕቢት አትመላለሱም፤
የመከራ ጊዜ ይሆናልና።
4በዚያ ቀን ሰዎች ይሣለቁባችኋል፤
በሐዘን እንጕርጕሮ እንዲህ እያሉ
ያፌዙባችኋል፤
'እኛ ፈጽሞ ጠፍተናል፤
የወገኔ ርስት ተከፋፍሎአል።
ከእኔ ነጥቆ ወስዶ፣
ዕርሻዎቻችንን ላሸነፉን አከፋፈለ።'

5ስለዚህ *በእግዚአብሔር* ጉባኤ ውስጥ፣
*መሬት* በዕጣ የሚያካፍል ማንም
አይኖርም።

### ሐሰተኞች ነቢያት

6ነቢያቶቻቸው፣ "ትንቢት አትናገሩብን፤
ስለ እነዚህ ነገሮች ትንቢት አትናገር፤
ውርደት አይደርስብንም" ይላሉ።
7የያዕቆብ ቤት ሆይ፤ እንዲህ ሊባል ይገባልን?
"*የእግዚአብሔር መንፈስ የማይታገሥ ነውን?*
*እንዲህ ያሉት ነገሮችንስ ያደርጋልን?*"

"*መንገዱ* ቀና ለሆነ፣
*ቃሌ መልካም አያደርግምን?*
8በመጨረሻ በሕዝቤ ላይ ጠላት ሆናችሁ
ተነሣችሁ፤
የጦርነት ሐሳብ ሳይኖራቸው፣
በሰላም ከሚያልፉ ሰዎች ላይ፣
*ማለፊያ መጐናጸፊያ* ገፈፋችሁ።
9ከሚወዱት ቤታቸው፣
የሕዝቤን ሴቶች አስወጣችኋቸው፤
ክብሬን ከልጆቻቸው፣
ለዘላለም ወሰዳችሁ።
10ተነሡና፤ ከዚያ ሂዱ፤
ይህ ማረፊያ ቦታችሁ አይደለምና፤
ምክንያቱም ረክሶአል፤
ክፉኛም ተበላሽቶአል።
11ሐሰተኛና አታላይ ሰው መጥቶ፣
'ስለ ብዙ የወይን ጠጅና ስለሚያሰክር
መጠጥ ትንቢት እነግራችኋለሁ' ቢል፣
ለዚህ ሕዝብ ተቀባይነት ያለው ነቢይ
ይሆናል።

### የትድግና ተስፋ

12"ያዕቆብ ሆይ፤ በእርግጥ ሁላችሁንም
እሰበስባለሁ፤
የእስራኤልንም ትሩፍ በአንድነት
አመጣለሁ፤
በጉረኖ ውስጥ እንዳሉ በጎች
በመሰማሪያ ላይ እንዳለ መንጋ
በአንድነት
እሰበስባቸዋለሁ፤
ቦታውም በሕዝብ ይሞላል።
13የሚሰብረው ወጥቶ በፊታቸው ይሄዳል፤
እነርሱም በሩን በመስበር ወጥተው
ይሄዳሉ፤
*እግዚአብሔር* እየመራቸው፣
ንጉሣቸው ቀድሞአቸው ይሄዳል።

### መሪዎችና ነቢያት ተገሠጹ

3 ከዚያም እኔ እንዲህ አልሁ፤
"እናንት የያዕቆብ መሪዎች፤
እናንት የእስራኤል ቤት ገዦች ስሙ፤
ፍትሕን ማወቅ አይገባችሁምን?
2መልካሙን ጠላችሁ፤ ክፉውንም ወደዳችሁ፤
የሕዝቤን ቈዳ ገፈፋችሁ፤
ሥጋቸውንም ከዐጥንቶቻቸው ለያችሁ፤
3የሕዝቤን ሥጋ በላችሁ፤
ቈዳቸውን ገፈፋችሁ፤
ዐጥንቶቻቸውንም ሰባበራችሁ፤
በመጥበሻ እንደሚጠበስ፣
በድስት እንደሚቀቀል ሥጋ
ቈራረጣችኋቸው።
4እነርሱም ወደ *እግዚአብሔር* ይጮኻሉ፤
እርሱ ግን አይመልስላቸውም፤
ካደረጉት ክፋት የተነሣ፣
በዚያ ጊዜ ፊቱን ከእነርሱ ይሰውራል።
5 *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤

"ሕዝቤን የሚያስቱ ነቢያት፣
ሰው ሲያበላቸው፣ 'ሰላም አለ' ይላሉ፤
ሳያበላቸው ሲቀር ግን፣
ጦርነት ሊያውጁበት ይነሣሉ።
6ስለዚህ ሌሊቱ ያለ ራእይ፣
ጨለማውም ያለ ንግርት
ይመጣባችኋል፤
በነቢያት ላይ ፀሐይ ትጠልቅባቸዋለች፤
ቀኑም ይጨልምባቸዋል።

1፥16 ዘሌ13፥40፤ ዘዳ4፥27፤ኢዮ1፥20፤ አሞ5፥27
2፥1 1ሳሙ29፥20፤ መዝ36፥4
2፥2 1ሳሙ8፥14፤ ምሳ30፥14፤ ኢሳ1፥23፤5፥8፤ ሕዝ46፥18
2፥3 ኢሳ2፥12፤ ኤር18፥11፤አሞ3፥1-2
2፥4 ዘሌ26፥31፤ ኤር4፥13፤6፥12
2፥5 ዘኍ34፥13፤ ዘዳ32፥13፤ኢሱ18፥4
2፥6 መዝ44፥13፤ ኤር18፥16፤19፥8፤ 25፥18፤29፥18፤ ሚክ6፥16
2፥7 መዝ15፥2፤ 84፥11፤119፥65
2፥9 ኤር10፥20
2፥10 ዘሌ18፥25-29፤ ዘዳ12፥9፤ መዝ106፥38-39፤ ሰቆ4፥15
2፥11 ዘሌ10፥9፤ 2ዜና36፥16፤ ኢሳ30፥10፤ኤር5፥31
2፥12 ነህ1፥9፤ ሚክ4፥7፤5፥7፤7፥18
2፥13 ኢሳ52፥12፤ 60፥11
3፥1 ኤር5፥5
3፥2 መዝ53፥4፤ ሕዝ22፥27
3፥3 ኢዮ24፥14፤ መዝ14፥4፤ ሕዝ11፥7፤24፥4-5፤ 34፥4
3፥4 ዘዳ1፥45፤ 31፥17፤1ሳሙ8፥18፤ኢዮ15፥31፤ ኢሳ58፥4፤ ኤር11፥11፤ሕዝ8፥18
3፥5 ኢሳ3፥12፤ 9፥16፤53፥6፤ኤር4፥10
3፥6 ኢሳ8፥19-22፤ 29፥10፤ሕዝ7፥26፤ 12፥24፤አሞ8፥11

7ባለ ራእዮች ያፍራሉ፤
ንግርተኞችም ይዋረዳሉ፤
ሁሉም ፊታቸውን ይሸፍናሉ፤
ከእግዚአብሔር መልስ የለምና።”

8እኔ ግን፣
ለያዕቆብ በደሉን፣
ለእስራኤልም ኀጢአቱን እነግር ዘንድ፣
ኃይልን፣ በእግዚአብሔር መንፈስ፣
ፍትሕና ብርታት ተሞልቻለሁ።
9እናንት የያዕቆብ ቤት መሪዎች፣
እናንት የእስራኤል ቤት ገዦች፣
ፍትሕን የምትንቁ፤
ትክክለኛ የሆነውንም ነገር ሁሉ
የምታጣምሙ፤ ስሙ፤
10ጽዮንን ደም በማፍሰስ፣
ኢየሩሳሌምን በክፋት የምትገነቡ፤ ስሙ።
11መሪዎቿ በጒቦ ይፈርዳሉ፤
ካህናቷ ለዋጋ ሲሉ ያስተምራሉ፤
ነቢያቷም ለገንዘብ ሲሉ ይናገራሉ።
ነገር ግን በእግዚአብሔር ላይ
ተደግፈውም፣
“እግዚአብሔር በመካከላችን አይደለምን?
ምንም ዐይነት ክፉ ነገር አይደርስብንም”
ይላሉ።
12ስለዚህ በእናንተ ምክንያት፣
ጽዮን እንደ እርሻ ትታረሳለች፣
ኢየሩሳሌም የፍርስራሽ ክምር ትሆናለች፤
የቤተ መቅደሱም ኰረብታ ዐረም
የበቀለበት ጒብታ ይሆናል።

## የእግዚአብሔር ተራራ

4 በመጨረሻው ዘመን፣
የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ተራራ፣
ከተራሮች ልቆ ይታያል፤
ከኰረብቶች በላይ ከፍ ይላል፤
ሕዝቦችም ወደ እርሱ ይጐርፋሉ።

2ብዙ አሕዛብ መጥተው እንዲህ ይላሉ፤

“ኑ፤ ወደ እግዚአብሔር ተራራ፣
ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንሂድ፤
በመንገዱ እንድንሄድ፣
መንገዱን ያስተምረናል።”
ሕግ ከጽዮን ይመጣል፤
የእግዚአብሔርም ቃል ከኢየሩሳሌም።
3እርሱ በብዙ ሕዝብ መካከል ይፈርዳል፤
በሩቅና በቅርብ ባሉ ኀያላን
መንግሥታት መካከል ያለውን ግጭት
ያቆማል፤
ሰይፋቸውን ማረሻ፣
ጦራቸውንም ማጭድ ያደርጉታል።
አንዱ መንግሥት በሌላው መንግሥት
ላይ ሰይፍ አያነሣም፤

3፥7 ዘሌ13፥45፤
አስ6፥12፤
ኢሳ44፥25፤
ኤር6፥15፤
ሕዝ20፥3፤ሚክ7፥16
3፥8 ኢሳ57፥12፤
61፥2
3፥9 መዝ58፥1-2፤
ኢሳ1፥23
3፥10 ኢሳ59፥7፤
ኤር22፥13፡17፤
ሕዝ22፥27፤
ሚክ7፥2፤ናሆ3፥1፤
ዕን2፥12
3፥11 ዘፀ23፥8፤
ዘሌ19፥15፤
ኢሳ1፥23፤
10፥20፤56፥11፤
ኤር6፥13፤7፥4፤
ሰቆ4፥13፤ሕዝ13፥9፤
34፥2፤ሆሴ4፥8፡18፤
ሚል2፥9
3፥12 ዘሌ26፥31፤
2ነገ25፥9፤
ኢሳ6፥11፤
ኤር17፥3፤22፥6፤52፥13፤
ሰቆ5፥18፤ሕዝ5፥14
4፥1 መዝ22፥27፤
48፥1፤86፥9፤ኤር3፥17፤
31፥12፤ሕዝ17፥22፤
ዳን2፥35፤ዘካ8፥3
4፥2 ዘዳ18፥18፤
መዝ25፥8-9፤
119፥171፤
ኢሳ54፥13፤
ኤር31፥6፤
ሕዝ20፥40፤
ዘካ2፥11፤14፥16
4፥3 መዝ46፥9፤
ኢሳ11፥4፤ኢል3፥10፤
ዘካ8፥20-22፤9፥10
4፥4 ዘሌ26፥6፤
1ነገ4፥25፤
ኢሳ1፥20፤ሕዝ39፥26
4፥5 ኢሱ24፥14-15፤
2ነገ17፥29፤
ኢሳ26፥8፤ዘካ10፥12
4፥6 መዝ106፥47፤
ኤር31፥8፤
ሕዝ34፥13፡16፤
37፥21፤ሶፎ3፥19
4፥7 ዘፍ12፥2፤
ኢሳ2፥2፤ዳን2፥44፤
7፥14፤ኢል2፥32፤
ሚክ2፥12፤
ሉቃ1፥33፤ራእ11፥15
4፥8 ኢሳ1፥26፤
ዘካ9፥9
4፥9 ዘፍ3፥16፤
ኤር8፥19፤30፥6፤48፥41
4፥10 ዘዳ21፥10፤
2ነገ20፥18፤
ኢሳ43፥14፤48፥20
4፥11 ሰቆ2፥16፤
አብ1፥12፤ሚክ7፥8
4፥12 ዘፍ50፥20፤
ኢሳ55፥8፤
ሮሜ11፥33-34

ከእንግዲህም የጦርነት ትምህርት
አይማሩም።
4እያንዳንዱ ሰው በገዛ ወይኑ ሥር፣
ከገዛ በለሱም ሥር ይቀመጣል፤
የሚያስፈራቸው አይኖርም፤
የእግዚአብሔር ጸባኦት አፍ
ተናግሮአልና።
5አሕዛብ ሁሉ፣
በአማልክቶቻቸው ስም ይሄዳሉ፤
እኛ ግን በአምላካችን በእግዚአብሔር ስም፣
ከዘላለም እስከ ዘላለም እንሄዳለን።

## የእግዚአብሔር ዕቅድ

6እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤

“በዚያች ቀን ሽባውን እሰበስባለሁ፤
ስደተኞችንና ለሐዘን ያደረግኋቸውን፣
ወደ አንድ ቦታ አመጣለሁ።
7የሽባዎችን ትሩፍ፣
የተገፉትንም ብርቱ ሕዝብ አደርጋለሁ፤
ከዚያች ቀን አንሥቶ እስከ ዘላለም፣
እግዚአብሔር በጽዮን ተራራ በእነርሱ
ላይ
ይነግሣል።
8አንተ የመንጋው መጠበቂያ ማማ ሆይ፤
የጽዮን ሴት ልጅ ዐምባ[a] ሆይ፤
የቀድሞው ግዛትህ ይመለስልሃል፤
የመንግሥትም ሥልጣን ለኢየሩሳሌም
ሴት ልጅ ይሆናል።”

9አሁንስ እንደዚህ የምትጮኺው
ለምንድን ነው?
ንጉሥ የለሽምን?
ምጥ እንደ ያዛት ሴት የተጨነቅሽው፣
መካሪሽ ስለ ጠፋ ነውን?
10የጽዮን ሴት ልጅ ሆይ፤
ምጥ እንደ ያዛት ሴት ተጨነቂ፤
አሁንስ ከከተማ ወጥተሽ፣
በሜዳ ላይ መስፈር አለብሽና፤
ወደ ባቢሎን ትሄጃለሽ፣
በዚያ ከጠላት እጅ ትድኛለሽ፤
እግዚአብሔር በዚያ፣
ከጠላቶችሽ ይታደግሻል።

11አሁን ግን ብዙ አሕዛብ፣
በአንቺ ላይ ተሰብስበዋል፤
እነርሱም፣ “የረከሰች ትሁን፤
ዐይናችንም ጽዮንን መዘባበቻ
አድርጎ ይያት” ይላሉ።
12ነገር ግን የእግዚአብሔርን ሐሳብ
አያውቁም፤
በአውድማ ላይ እንደ ነዶ
የሚሰበስባቸውን፣
የእርሱን ዕቅድ አያስተውሉም።

[a]8 ወይም ‘ኰረብታ’

[13]የጽዮን ልጅ ሆይ፤ ተነሥተሽ አበራዪ፤
የብረት ቀንድ እሰጥሻለሁና፤
የናስ ሰኰና እሰጥሻለሁ፤
አሕዛብንም ታደቂያቸዋለሽ።”
በግፍ ያግበሰበሱትን ትርፍ
*ለእግዚአብሔር*፣
ሀብታቸውንም ለምድር ሁሉ ጌታ
ታቀርቢያለሽ።

## ከቤተ ልሔም ገዥ እንደሚመጣ የተሰጠ ተስፋ

5 አንቺ የጭፍሮች ከተማ ሆይ፤
ጭፍሮችሽን አሰልፊ[ተ]፤
ከበባ ተደርጎብናልና፤
የእስራኤልን ገዥ፣
ጕንጩን በበትር ይመቱታል።

[2]“አንቺ ግን፣ ቤተ ልሔም ኤፍራታ
ሆይ፤
ከይሁዳ ነገዶች[ቸ] መካከል ትንሿ
ብትሆኚም፣
አመጣጡ[ኀ] ከጥንት፣
ከቀድሞ ዘመን[ነ] የሆነ፣
የእስራኤል ገዥ፣
ከአንቺ ይወጣልኛል።”

[3]ስለዚህ ወላዲቱ አምጣ እስክትገላገል ድረስ፣
እስራኤል ትተዋለች፤
የተቀሩት ወንድሞቹም፣
ተመልሰው ከእስራኤላውያን ጋር
ይቀላቀላሉ።

[4]*በእግዚአብሔር* ኀይል
በአምላኩ *በእግዚአብሔር* ስም ታላቅነት፣
ጸንቶ ይቆማል፤ መንጋውንም
ይጠብቃል።
በዚያን ጊዜ ኀያልነቱ እስከ ምድር ዳርቻ
ስለሚደርስ፣
ተደላድለው ይኖራሉ።
[5]እርሱም ሰላማቸው ይሆናል።

## ትድግናና ጥፋት

አሦራዊ ምድራችንን ሲወር፣
ምሽጐቻችንንም ጥሶ ሲገባ፣
ሰባት እረኞችን፣
እንዲያውም ስምንት አለቆችን
እናስነሣበታለን።
[6]የአሦርን ምድር በሰይፍ፣
የናምሩድን ምድር[ኘ] በተመዘዘ ሰይፍ ይገዙሉ[አ]፤
አሦራዊው ምድራችንን ሲወር፣
ዳር ድንበራችንን ሲደፍር፣
እርሱ ነጻ ያወጣናል።

[7]የያዕቆብ ትሩፍ፣
በብዙ አሕዛብ መካከል
*ከእግዚአብሔር* ዘንድ እንደሚወርድ
ጠል፣
በሣር ላይ እንደሚጥል ካፊያ፣
ሰውን እንደማይጠብቅ፣
የሰውንም ልጆች ተስፋ እንደማያደርግ
ሰው ይሆናል።
[8]በዱር አራዊት መካከል እንዳለ አንበሳ፣
በእግሩ እየጨፈላለቀ እንደሚሄድ፣
የሰበረውን ማንም ሊነጥቀው እንደማይችል፣
በበግ መንጋ መካከል እንዳለ፣
እንደ ደቦል አንበሳ ሁሉ፣
የያዕቆብም ትሩፍ፣ በአሕዛብ ዘንድ፣
በብዙም ሕዝብ መካከል እንደዚሁ ይሆናል።
[9]እጅህ በጠላቶችህ ላይ በድል አድራጊነት
ከፍ ከፍ ትላለች፤
ጠላቶችህም ሁሉ ይጠፋሉ።

[10]“በዚያን ጊዜ” ይላል *እግዚአብሔር*፤

“ፈረሶቻችሁን ከመካከላችሁ አጠፋለሁ፤
ሠረገሎቻችሁን እደመስሳለሁ።
[11]የምድራችሁን ከተሞች እደመስሳለሁ፤
ምሽጎቻችሁንም ሁሉ አፈርሳለሁ።
[12]ጥንቈላችሁን አጠፋለሁ፤
ከእንግዲህም አታሟርቱም።
[13]የተቀረጹ ምስሎቻችሁን፣
የማምለኪያ ዐምዶቻችሁንም ከመካከላችሁ
አጠፋለሁ፤
ከእንግዲህ ለእጃችሁ ሥራ
አትሰግዱም።
[14]የአሼራ ምስልን ዐምድ[ከ] ከመካከላችሁ
እነቅላለሁ፤
ከተሞቻችሁንም እደመስሳለሁ።
[15]ያልታዘዙኝን አሕዛብ፣
በቍጣና በመዓት እበቀላቸዋለሁ።”

## የእግዚአብሔር ክስ በእስራኤልን ላይ

6 *እግዚአብሔር* የሚለውን ስሙ፤
“ተነሡ፤ ጕዳያችሁን በተራሮችም፤
ፊት አቅርቡ፤
ኰረብቶች እናንተ የምትሉትን ይስሙ፤
[2]ተራሮች ሆይ፤ *የእግዚአብሔርን* ክስ
አድምጡ፤
እናንት የምድር ጽኑ መሠረቶችም፤
ስሙ፤
*እግዚአብሔር* ከሕዝቡ ጋር ክርክር አለውና፤
ከእስራኤልም ጋር ይፋረዳል።
[3]“ሕዝቤ ሆይ፤ ምን አድርጌሃለሁ?
ሸክም የሆንሁብህስ እንዴት ነው?
እስቲ መልስልኝ!
[4]ከግብፅ አወጣሁህ፤

4፥13 ኢሳ21፥10፤ 23፥18፤ዳን2፥44
5፥1 ሰቆ3፥30
5፥2 ዘፍ35፥16፤ 48፥7፤ዘኍ24፥19፤ 1ሳሙ13፥4፤ 2ሳሙ6፥21፤ 2ዜና7፥18፤ መዝ102፥25፤ ማቴ2፥6፤ዮሐ7፥42
5፥3 ኤር7፥29
5፥4 ኢሳ40፥11፤ 49፥9፤52፥13፤ ሕዝ34፥11-15፤23፤ ሚክ7፥14፤ሉቃ1፥32
5፥5 ኢሳ8፥7፤ 9፥6፤10፥24-27፤ ሉቃ2፥14፤
5፥6 ዘፍ10፥8፤ ናሆ2፥11-13፤ ሶፎ2፥13
5፥7 መዝ133፥3፤ ኢሳ44፥4፤ አሞ5፥15፤ሚክ2፥12
5፥8 ዘፍ49፥9፤ መዝ50፥22፤ ኢሳ5፥29፤ ሆሴ5፥14፤ሚክ4፥13፤ ዘካ10፥5
5፥9 መዝ10፥12
5፥10 ዘፀ15፥4፡19፤ ሆሴ14፥3፤ ሐጌ2፥22፤ዘካ9፥10
5፥11 ዘዳ29፥23፤ ኢሳ6፥11፤ ሰቆ2፥2፤ሆሴ10፥14፤አሞ5፥9
5፥12 ዘዳ18፥10-12፤ ኢሳ2፥6፤8፥19
5፥13 ኢሳ2፥18፤ ሕዝ6፥9፤ ሆሴ10፥2፤ናሆ1፥14፤ዘካ13፥2
5፥14 ዘፀ34፥13፤ መሳ3፥7፤2ነገ17፥10
6፥1 መዝ50፥1፤ ሕዝ6፥2
6፥2 ዘዳ32፥1፤ መዝ50፥7፤ ኢሳ3፥13፤ ኤር2፥9፤ሆሴ12፥2
6፥3 ኤር2፥5
6፥4 ዘፀ3፥10፤ 4፥16፤6፥6፤15፥20፤ ዘኍ33፥1፤ዘዳ7፥8፤ መዝ77፥20

[ተ]1 ወይም አንቺ የተቀጠርሽ ከተማ ሆይ፤ ቅጥርሽን አጥብቂ
[ቸ]2 ወይም ‘ገዦች’ [ነ]2 ወይም *ከቀድሞ ቀናት*
[ኀ]2 ዕብራይስጡ ‘አወጣጡ’ ይላል ወይም ‘ከዘላለም የሆነ’
[ኘ]6 ወይም ‘ናምሩድን በመግቢያው በር’ [አ]6 ወይም ‘ያፈርሳሉ’

ከባርነት ምድርም ተቤዥሁህ፤
እንዲመሩህ ሙሴን፣
አሮንንና ማርያምን ላክሁልህ።
5ሕዝቤ ሆይ፤
የሞዓብ ንጉሥ ባላቅ የመከረውን፣
የቢዖር ልጅ በለዓም የመለሰለትንም
እስቲ አስቡ፤
የእግዚአብሔርን የጽድቅ ሥራ ታውቁ
ዘንድ፣
ከሰጢም እስከ ጌልገላ የተጓዛችሁትን
አስቡ።
6ምን ይዤ በእግዚአብሔር ፊት
ልቅረብ፣
በልዑል አምላክ ፊት ልስገድ?
የሚቃጠለውን መሥዋዕት፣
ከአንድ ዓመት ጥጃ ጋር ይዤ በፊቱ
ልቅረብን?
7በአንድ ሺህ አውራ በጎች፣
በዐሥር ሺህ የዘይት ፈሳሽ እግዚአብሔር
ደስ ይለዋልን?
ስለ በደሌ የበኵር ልጄን፣
ስለ ነፍሴም ኀጢአት የሆዴን ፍሬ
ላቅርብለትን?
8ሰው ሆይ፤ መልካም የሆነውን
አሳይቶሃል፤
እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው
ምንድን ነው?
ፍትሕን ታደርግ ዘንድ፣ ምሕረትንም
ትወድድ ዘንድ፣
በአምላክህም ፊት በትሕትና ትራመድ
ዘንድ አይደለምን?

## የእስራኤል በደልና ቅጣት

9ስምህን መፍራት ጥበብ ነው፤
ስሙ! እግዚአብሔር ከተማዪቱን
እንዲህ እያለ ይጣራል፤
"በትሩን አስቡ፤ ያዘጋጀውም ማን እንደ
ሆነ አስታውሱ[ኸ]።
10የክፋት ቤት ሆይ፤
በግፍ የተገኘ ሀብታችሁን፣
በሐሰተኛ መስፈሪያ የሰበሰባችሁትን
አስጸያፊ ነገር እረሳዋለሁን?
11አባይ ሚዛን የያዘውን ሰው፣
ሐሰተኛ መመዘኛ በከረጢት
የቋጠረውን ንጹሕ ላድርገውን?
12ባለጠጎቿ ግፈኞች፣
ሰዎችዋ ሐሰተኞች ናቸው፤
ምላሳቸውም አታላይ ናት።

13ስለዚህ አንተን አጠፋሃለሁ፣
ከኀጢአትህ የተነሣ አፈራርስሃለሁ።
14ትበላለህ፤ ነገር ግን አትጠግብም፤
ሆድህ እንዳለ ባዶውን[ወ] ይቀራል፤
ታከማቻለህ፤ ነገር ግን አይጠራቀምልህም፤
የሰበሰብኸውን ለሰይፍ አደርገዋለሁና።
15ትዘራለህ፤ ነገር ግን አታጭድም፤
የወይራ ዘይት ትጨምቃለህ፤ ነገር ግን
ዘይቱን አትቀባም፤
ወይንን ትቈርጣለህ፤ ነገር ግን የወይን ጠጅ
አትጠጣም።
16የዖምሪን ሥርዐት፣
የአክዓብን ቤት ልምድ ሁሉ የሙጥኝ
ብለሃል፤
ትውፊታቸውንም ተከትለሃል።
ስለዚህ አንተን ለውድመት፣
ሕዝብህን ለመዘባበቻ አሳልፌ እሰጣለሁ፤
አሕዛብም ይሣለቁብሃል[ዐ]።"

## የእስራኤል መከራ

7 ለእኔ ወዮልኝ!
የወይን ዕርሻ በሚቃረምበት ጊዜ
የበጋ ፍራፍሬ እንደሚለቅም ሰው
ሆኛለሁ፤
የሚበላ የወይን ዘለላ የለም፤
የምንጓጓለት፣ ቶሎ የሚደርሰው በለስም
አልተገኘም።
2ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረበት ሰው ከምድር
ጠፍቶአል፤
አንድም እንኳ ቅን ሰው የለም፣
ሰው ሁሉ ደም ለማፍሰስ ያደባል፤
እያንዳንዱም ወንድሙን በመረብ
ያጠምዳል።
3እጆቹ ክፉ ለማድረግ ሠልጥነዋል፤
ገዢ እጅ መንሻ ይፈልጋል፤
ፈራጁ ጉቦ ይቀበላል፤
ኀይለኞች ያሻቸውን ያስፈጽማሉ፤
ሁሉም አንድ ላይ ያሤራሉ።
4ከእነርሱ ይሻላል የተባለው እንደ
አሜከላ፣
እጅግ ቀና የተባለውም እንደ ኵርንችት
ነው፤
የጠባቂዎቻችሁ ቀን ደርሶአል፤
የእግዚአብሔር የፍርድ ቀን መጥቶአል፤
የሚሸበሩበትም ጊዜ አሁን ደርሶአል።
5ባልንጀራህን አትመን፤
በጓደኛህም አትታመን፤
በዕቅፍህ ለምትተኛዋ እንኳ፣
ስለምትነግራት ቃል ተጠንቀቅ።
6ወንድ ልጅ አባቱን ይንቃል፤

[ከ]14 አሼራ የተባለችው አምላክ ትእምርት ነው።
[ኸ]9 የዚህ ስንኝ የዕብራይስጡ ትርጒም በእርግጠኝነት አይታወቅም።
[ወ]14 የዚህ ቃል የዕብራይስጡ ትርጒም በእርግጠኝነት አይታወቅም። [ዐ]16 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ከዚህ ጋር ሲስማማ የዕብራይስጡ ግን 'የሕዝቤን ስድብ ትሸከማለህ' ይላል
[ኸ]9 የዚህ ስንኝ የዕብራይስጡ ትርጒም በእርግጠኝነት አይታወቅም።
[ወ]14 የዚህ ቃል የዕብራይስጡ ትርጒም በእርግጠኝነት አይታወቅም። [ዐ]16 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ከዚህ ጋር ሲስማማ የዕብራይስጡ ግን 'የሕዝቤን ስድብ ትሸከማለህ' ይላል

6፥5 ዘኍ22፥2፤ 25፥1፤ዘዳ11፥30፤ ኢሱ5፥9-10፤ መሳ5፥11፤1ሳሙ12፥7
6፥6 መዝ40፥6-8፤ 51፥16-17፤95፥2
6፥7 ዘሌ18፥21፤ 2ነገ3፥27፤መዝ50፥8-10፤ ኢሳ1፥11፤40፥16፤ ሆሴ5፥6፤አሞ5፥22
6፥8 ዘፍ5፥22፤ ዘዳ10፥12-13፤ 1ሳሙ15፥22፤ 2ነገ22፥19፤ ኢሳ1፥17፤ 57፥15፤ኤር22፥3፤ ሆሴ6፥6፤ዘካ7፥9-10፤ ማቴ9፥13፤23፥23፤ ማር12፥33፤ሉቃ11፥42
6፥9 ዘፍ17፥1፤ ኢሳ11፥4
6፥10 ሕዝ45፥9-10፤ አሞ3፥10፤8፥4-6
6፥11 ዘሌ19፥36፤ ዘዳ25፥13
6፥12 መዝ35፥20፤ 116፥11፤ኢሳ1፥23፤ 3፥8፤ኤር9፥3
6፥13 ኢሳ1፥17፤ 6፥11
6፥14 ኢሳ9፥20፤ 30፥6፤ሆሴ4፥10
6፥15 ዘዳ28፥38፤ ኢዮ24፥11፤ ኤር12፥13፤አሞ5፥11፤ ሶፎ1፥13
6፥16 ዘዳ28፥37፤ 1ነገ16፥25፡29፡33፤ ኤር7፥24፤25፥9፤51፥51፤ ሚክ2፥6
7፥1 መሐ2፥13
7፥2 መዝ10፥8፤ 12፥1፤ምሳ6፥17፤ ኢሳ3፥5፤ኤር2፥29፤ 5፥26፤ 8፥6፤ሚክ3፥10
7፥3 ዘፀ23፥8፤ ምሳ4፥16፤ሕዝ22፥12
7፥4 ዘኍ33፥55፤ 2ሳሙ23፥6፤ ኢዮ31፥14፤ ኢሳ22፥5፤ ሕዝ2፥6፤ሆሴ9፥7
7፥5 ኤር9፥4
7፥6 ሕዝ22፥7፤ ማቴ10፥35-36፤ ማር13፥12

ሴት ልጅ በእናቷ ላይ፣
ምራት በአማቷ ላይ ትነሣለች፤
የሰው ጠላቶች የገዛ ቤተ ሰዎቹ
ናቸውና።

7እኔ ግን *እግዚአብሔርን* ተስፋ አደርጋለሁ፤
አዳኜ የሆነውን አምላክ እጠብቃለሁ፤
አምላኬ ይሰማኛል።

## እስራኤል ትነሣለች

8ጠላቴ ሆይ፤ በእኔ ላይ በደረሰው ደስ
አይበልሽ!
ብወድቅም እንኳ እነሣለሁ፤
በጨለማ ብቀመጥ እንኳ፣
*እግዚአብሔር* ብርሃኔ ይሆናል።
9እርሱን ስለ በደልሁ፣
እስኪቆምልኝ
እስኪፈርድልኝም ድረስ፣
*የእግዚአብሔርን* ቍጣ እቀበላለሁ፤
እርሱ ወደ ብርሃን ያወጣኛል፤
እኔም ጽድቁን አያለሁ።
10ጠላቴም ታያለች፤
ኀፍረትንም ትከናነባለች፤
"አምላክህ *እግዚአብሔር* የት አለ?"
ያለችኝን፣
ዐይኖቼ ውድቀቷን ያያሉ፤
አሁንም እንኳ፣
እንደ መንገድ ጭቃ ትረገጣለች።

11ቅጥሮቻችሁን የምትሠሩበት፣
ድንበራችሁንም የምታሰፉበት ቀን
ይመጣል።
12በዚያ ቀን ሰዎች፣
ከአሦር እስከ ግብፅ ከተሞች፣
ከግብፅ እስከ ኤፍራጥስ፣
ከባሕር ወደ ባሕር፣
ከተራራ ወደ ተራራ ወደ እናንተ
ይመጣሉ።
13ከሥራቸው የተነሣ፣
በነዋሪዎቿ ምክንያት ምድር ባድማ
ትሆናለች።

## ጸሎትና ውዳሴ

14ብቻቸውን በዱር ውስጥ፣
በለመለመ መስክ″ የሚኖሩትን፣
የርስትህ መንጋ የሆኑትን፣
ሕዝብህን በበትርህ ጠብቅ፤
እንደ ቀድሞው ዘመን፣
በባሳንና በገለዓድ ይሰማሩ።

15"ከግብፅ እንደ ወጣህበት ዘመን ሁሉ፣
ታምራቴን አሳያቸዋለሁ።"

16አሕዛብ ያያሉ፣ ያፍራሉም፤
ኀይላቸውን ሁሉ ያጣሉ፤
አፋቸውን በእጃቸው ይይዛሉ፤
ጆሮአቸውም ትደነቍራለች።
17በደረታቸው እንደሚሳቡ ፍጥረታት፣
እንደ እባብም ትቢያ ይልሳሉ፤
ከዋሻቸው እየተንቀጠቀጡ ይወጣሉ፤
በፍርሀትም ወደ አምላካቸው ወደ
*እግዚአብሔር* ይመለሳሉ፤
እናንተንም ይፈራሉ።
18የርስቱን ትሩፍ፣
ኀጢአት ይቅር የሚል፣ የሚምር
እንደ አንተ ያለ አምላክ ማነው?
ለዘላለም አትቈጣም፤
ነገር ግን ምሕረት በማድረግ ደስ
ይልሃል።
19ተመልሰህ ትራራልናለህ፤
ኀጢአታችንን በእግርህ ትረግጣለህ፤
በደላችንንም ሁሉ ወደ ጥልቁ ባሕር
ትጥላለህ።
20ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ
ለአባቶቻችን በመሐላ ቃል እንደ
ገባህላቸው፣
ለያዕቆብ ታማኝነትን፣
ለአብርሃምም ምሕረትን ታደርጋለህ።

″14 ወይም 'በቀርሜሎስ መካከል'

7፥7 መዝ4፥3፤ 130፥5፤ኢሳ21፥8፤ 25፥9
7፥8 2ሳሙ22፥29፤ መዝ20፥8፤22፥17፤ 37፥24፤ምሳ24፥17፤ ኢሳ9፥2፤አሞ9፥11፤ ሚክ4፥11
7፥9 መዝ107፥10፤ 119፥154፤ ኢሳ46፥13፤ ሰቆ3፥39-40
7፥10 ሳሙ22፥43፤ ኢዮ40፥12፤ መዝ35፥26፤42፥3፤ ኢሳ5፥5፤51፥23፤ ዘካ10፥5
7፥11 ኢሳ54፥11፤ አሞ9፥11
7፥12 ኢሳ11፥11፤ 19፥23-25፤60፥4
7፥13 ኢሳ3፥10-1፤ ሕዝ12፥19፤33፥28-29
7፥14 መዝ23፥4፤ 28፥9፤95፥7፤ መሐ4፥1፤ኢሳ33፥9፤ ኤር50፥19፤ ሕዝ36፥11፤ሚክ5፥4
7፥15 ዘፀ3፥20፤ መዝ78፥12
7፥16 መሳ18፥19፤ ኢሳ26፥11
7፥17 ዘፍ3፥14፤ 2ሳሙ22፥46፤ ኢሳ25፥3፤59፥19
7፥18 ዘፀ8፥10፤ 34፥9፤1ሳሙ2፥2፤ 2ዜና6፥21፤30፥9፤ መዝ103፥8-13 ኢሳ43፥25፤54፥9፤ ኤር31፥20፤32፥41፤ 50፥20፤ሕዝ18፥23፤ ኢል2፥32፤ አሞ5፥15፤ሚክ2፥12፤ ዘካ3፥4
7፥19 ኢሳ43፥25፤ ኤር31፥34 ሉቃ1፥72

# ትንቢተ ናሆም

1 ስለ ነነዌ ጥፋት የተነገረ ንግር፤ የኤል
ቆሻዊው የናሆም የራእዩ መጽሐፍ ይህ
ነው፤

## በነነዌ ላይ የተገለጠ *የእግዚአብሔር* ቍጣ

2 *እግዚአብሔር* ቀናተኛና ተበቃይ አምላክ
ነው፤
*እግዚአብሔር* የሚበቀል፣ በመዓትም
የተሞላ ነው።
*እግዚአብሔር* ባላጋራዎቹን ይበቀላል፤
በጠላቶቹም ላይ ቍጣውን ያመጣል
3 *እግዚአብሔር* ለቍጣ የዘገየ በኀይሉም
ታላቅ ነው፤
*እግዚአብሔር* በደለኛውን ሳይቀጣ
አያልፍም፤
መንገዱ በዐውሎ ነፋስና በማዕበል ውስጥ
ነው፤
ደመናም የእግሩ ትቢያ ነው።
4 ባሕርን ይገሥጻል፤ ያደርቀዋልም፤
ወንዞችን ሁሉ ያደርቃል።
ባሳንና ቀርሜሎስ ጠውልገዋል፤
የሊባኖስም አበቦች ረግፈዋል።
5 ተራሮች በፊቱ ታወኩ፤
ኰረብቶችም ቀለጡ።
ምድር በፊቱ፣
ዓለምና በውስጧ የሚኖሩት ሁሉ ተናወጡ።
6 ቍጣውን ማን ሊቋቋም ይችላል?
ጽኑ ቍጣውንስ ማን ሊሸከም ይችላል?
መዓቱ እንደ እሳት ፈሶአል፤
ዐለቶችም በፊቱ ተሰነጣጥቀዋል።
7 *እግዚአብሔር* መልካም ነው፤
በጭንቅ ጊዜም መሸሸጊያ ነው።
ለሚታመኑበት ይጠነቀቅላቸዋል፤
8 ነነዌን ግን፣
በሚያጥለቀልቅ ጐርፍ ያጠፋታል፤
ጠላቶቹንም ወደ ጨለማ
ያሳድዳቸዋል።

9 *በእግዚአብሔር* ላይ ምንም ቢያሤሩ[ሀ]፣
እርሱ ያጠፋዋል፤
መከራም ዳግመኛ አይነሣም።
10 በእሾህ ይጠላለፋሉ፤
በወይን ጠጃቸውም ይሰክራሉ፤
እሳትም እንደ ገለባ[ለ] ይበላቸዋል።
11 ነነዌ ሆይ፤ *በእግዚአብሔር* ላይ
የሚያሤር፣
ክፋትንም የሚመክር፣
ከአንቺ ዘንድ ወጥቶአል።
12 *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
"ምንም ኀይለኞችና ብዙዎች ቢሆኑም፣
ይቈረጣሉ፤ ይጠፋሉም።
ይሁዳ ሆይ፤ ከዚህ በፊት
ባስጨንቅህም፣
ከእንግዲህ አላስጨንቅህም።
13 አሁንም ቀንበራቸውን ከዐንገትህ ላይ
አንሥቼ እሰብራለሁ፤
የታሰርህበትንም ሰንሰለት በጥሼ
እጥላለሁ።"
14 አንቺ ነነዌ፤ *እግዚአብሔር* ስለ አንቺ
እንዲህ ብሎ አዞአል፤
"ስም የሚያስጠራ ትውልድ
አይኖራችሁም፤
በአማልክቶቻችሁ ቤት ያሉትን፣
የተቀረጹትን ምስሎችና ቀልጠው
የተሠሩትን ጣዖታት እደመስሳለሁ፤
መቀበሪያህን እምስልሃለሁ፤
አንተ ክፉ ነህና።
15 እነሆ፤ የምሥራች የሚያመጣውን፣
ሰላምን የሚያውጀው ሰው እግር፣
በተራሮች ላይ ነው፤
ይሁዳ ሆይ፤ በዓላትህን አክብር፤
ስእለትህንም ፈጽም፤
ከእንግዲህ ክፉዎች አይወሩህም፤
እነርሱም ፈጽመው ይጠፋሉ።

## የነነዌ አወዳደቅ

2 ነነዌ ሆይ፤ አጥቂ መጥቶብሻል፤
ምሽግሽን ጠብቂ፤
መንገድሽን ሰልዪ፤
ወገብሽን ታጠቂ፤
ኀይልሽን ሁሉ አሰባስቢ።
2 አጥፊዎች ባድማ ቢያደርጓቸውም፣
የወይን ተክል ቦታቸውን
ቢያጠፉባቸውም፣
እንደ እስራኤል ክብር ሁሉ፣
*እግዚአብሔር* የያዕቆብንም ክብር
ይመልሳል።
3 የወታደሮቹ ጋሻ ቀይ ነው፤
ተዋጊዎቹ ቀይ ልብስ ለብሰዋል፤
ዝግጁ በሆኑበት ቀን፣
የሠረገሎቹ ብረት ያብረቀርቃል፤
የጦሩ ዘንግ ይወዛወዛል።
4 ሠረገሎች በአደባባይ ወዲያ ወዲህ
ይከንፋሉ፤
በመንገዶችም ላይ ይርመሰመሳሉ፤
የሚንበለበል ፋና ይመስላሉ፤
እንደ መብረቅም ይወረወራሉ።

[ሀ]9 *በእግዚአብሔር ላይ የምታሤሩት ምንድን ነው?* የሚሉ አሉ
[ለ]10 የዕብራይስጡ ትርጕም በትክክል አይታወቅም።

1፥1 ዘፍ10፥11፤ኢሳ 1፥1፤13፥1፤19፥1፤ ኤር23፥33፡34፤ 50፥18፤ ናሆ2፥8፤ 3፥7
1፥2 ዘፍ4፥24፤ዘፀ 20፥5፤ዘዳ7፥10፤32፥41፤ መዝ94፥1
1፥3 ዘፀ14፥21፤ 34፥7፤ 2ሳሙ22፥10፤2ነገ2፥1፤ነህ9፥17፤መዝ50፥3፤104፥3
1፥4 ዘፀ14፥22፤ 2ሳሙ 22፥16፤ኢሳ 33፥9
1፥5 ዘፀ19፥18፤ኢዮ 9፥6፤ሕዝ38፥20፤ኢል 2፥10፤ሚክ1፥4
1፥6 1ነገ19፥11፤ መዝ76፥7፤130፥3፤ ኢሳ5፥24-25፤ 42፥25፤ኤር10፥10፤ሕዝ22፥14
1፥7 መዝ1፥6፤22፥9፤ ኤር17፥17፤33፥11
1፥8 ኢሳ8፥7፤ ዳን9፥26
1፥9 ሆሴ7፥15
1፥10 2ሳሙ23፥6፤ ኢሳ5፥24፤49፥26፤ ሚል4፥1
1፥12 ኢሳ10፥34፤ 54፥6-8፤ሰቆ3፥31-32
1፥13 ኢዮ12፥18፤ መዝ107፥14፤ኢሳ9፥4
1፥14 ኢሳ14፥22፤ ኤር28፥8፤ሕዝ32፥22-23፤ሚክ5፥13
1፥15 ዘሌ23፥2-4፤ኢሳ 40፥9፤52፥1፡7፤ሐሥ 10፥36፤ሮሜ10፥15
2፥1 ኤር51፥20
2፥2 ኢሳ60፥15፤ ሕዝ 37፥23
2፥3 ሕዝ23፥14-15
2፥4 ኤር4፥13፤ሕዝ 23፥24

5ምርጥ ተዋጊዎቹን ይጠራል፤
ጻሩ ግን መንገድ ላይ ይሰናከላሉ፤
ወደ ከተማዪቱ ቅጥር ይሮጣሉ፤
መከላከያ ጋሻውም በቦታው አለ።
6የወንዙ በር ወለል ብሎ ተከፈተ፤
ቤተ መንግሥቱም ወደቀ።
7ከተማዪቱ መማረኳና መወሰዷ እንደ
ማይቀር፣
አስቀድሞ ተነግሮአል[መ]፤
ሴቶች ባሪያዎቿ እንደ ርግብ ያለቅሳሉ፤
ደረታቸውንም ይደቃሉ።
8ነነዌ እንደ ኵሬ ናት፤
ውሃዋም ይደርቃል፤
"ቁም! ቁም!" ብለው ይጮኻሉ፤
ነገር ግን ወደ ኋላ የሚመለስ የለም።
9ብሩን ዝረፉ፤
ወርቁን ንጠቁ፤
በየግምጃ ቤቱ ያለው፤
የተከማቸውም ሀብት ስፍር ቍጥር
የለውም።
10ተበዝብዛለች፤ ተዘርፋለች፤
ተራቍታለች።
ልብ ቀልጦአል፤ ጕልበት ተብረክርኮአል፤
ሰውነት ተንቀጥቅጦአል፤ ፊት ሁሉ
ገርጥቶአል።

11አሁን ታዲያ የአንበሶቹ ዋሻ፣
ደቦሎቻቸውን ያበሉበት
ወንዱና ሴቷ አንበሳ የሄዱበት፣
ግልገሎችም ሳይፈሩ የተሰማሩበት ቦታ
ወዴት ነው?

12አንበሳው ለግልገሎቹ የሚበቃውን ያህል
ገደለ፤
ለእንስቶቹም ዐንቆ ገደለላቸው፤
የገደለውን በማረፊያ ቦታው፣
የነጠቀውንም በዋሻው ሞልቶታል።

13የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤
"በእናንተ ላይ ተነሥቼባችኋለሁ፤
ሠረገሎቻችሁን አቃጥዬ አጨሳለሁ፤
ደቦል አንበሶቻችሁን ሰይፍ ይበላል፤
የምትበሉትን በምድር ላይ
አልተውላችሁም፤
የመልእክተኞቻችሁም ድምፅ፣
ከእንግዲህ ወዲያ አይሰማም።"

## ለነነዌ

3 ለደም ከተማ ወዮላት!
ሐሰት፣
ዘረፋም ሞልቶባታል፤
ብዝበዛዋ ተግዞ አያልቅም።
2የጅራፍ ድምፅ፣
የመንኰራኵር ኳኳቴ፣
የፈጣን ፈረስ ኮቴ፣
የሠረገሎች ድምፅ ተሰምቶአል
3ፈረሰኛው ይጋልባል፤
ሰይፍ ይንቦገቦጋል፤
ጦር ያብረቀርቃል፤
የሞተው ብዙ ነው፤
ሬሳ በሬሳ ሆኖአል፤
ስፍር ቍጥር የለውም፤
መተላለፊያ አልተገኘም።
4ይህ ሁሉ የሆነው ቅጥ ባጣች፣
አሳሳችና መተተኛ በሆነች ዘማዊት
ምክንያት ነው፤
እርሷም በዝሙቷ አሕዛብን፣
በጥንቈላዋም ሕዝቦችን ባሪያ ያደረገች
ናት።
5የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤
"እኔ በጠላትነት ተነሥቼብሻለሁ፤
ቀሚስሽን እስከ ፊትሽ እገልበዋለሁ፤
ዕርቃንሽን ለአሕዛብ፣
ኀፍረትሽንም ለነገሥታት አሳያለሁ።
6ቍሻሻ እደፋብሻለሁ፤
እንቅሻለሁ፤
ማላገጫም አደርግሻለሁ።
7የሚያዩሽ ሁሉ ከአንቺ እየሸሹ፣
'ነነዌ ፈራርሳለች፤ ማን ያለቅስላታል?'
ይላሉ፤
የሚያጽናናሽንስ ከወዴት አገኛለሁ?"

8አንቺ በዐባይ ወንዝ አጠገብ ካለችው፣
በውሃ ከተከበበችው፣
ከኖእ አሞን[ሠ] ትበልጫለሽን?
ወንዙ መከላከያዋ፣
ውሃውም ቅጥሯ ነው።
9ኢትዮጵያና ግብፅ ወሰን የለሽ ኀይሏ
ናቸው፤
ፉጥና ሊቢያም ረዳቶቿ ነበሩ።
10ይሁን እንጂ በምርኮ ተወሰደች፤
ተሰዳም ሄደች።
በየመንገዱ ማእዘን ላይ፣
ሕፃናቷ ተፈጠፈጡ፤
በመሳፍንቷ ላይ ዕጣ ተጣለ፤
ታላላቅ ሰዎቿ ሁሉ በሰንሰለት ታሰሩ።
11አንቺ ደግሞ ትሰክሪያለሽ፤
ትደበቂያለሽ፣
ከጠላትም መሸሸጊያ ትፈልጊያለሽ።

12ምሽጎችሽ ሁሉ ሊበሉ እንደ ደረሱ
የመጀመሪያ በለስ ፍሬ ናቸው፤
በሚወዛወዙበት ጊዜ፣
ፍሬዎቹ በበላተኛው አፍ ውስጥ

[ሐ]3 የዕብራይስጡ ትርጒም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናቱና የሱርስቱ ቅጆች ግን *ፈረሰኞች ይፈጥናሉ* ይላሉ።
[መ]7 የዕብራይስጡ ቃል ትርጒም በትክክል አይታወቅም።
[ሠ]8 አንዳንዶች *ቴብስ* ይላሉ።

2፥5 ኤር46፥12
2፥6 ኢሳ45፥1፤ ናሆ3፥13
2፥7 ዘፍ8፥8፤ኢሳ 32፥12፤59፥11
2፥10 ኢሱ2፥11፤ 7፥5፤ኢሳ29፥22
2፥11 ኢሳ5፥29
2፥12 ኢሳ37፥18፤ ኤር 4፥7፤51፥34
2፥13 2ሳሙ2፥26፤ መዝ46፥9፤ኢሳ 10፥5-13፤ኤር21፥ 13፤ሚክ5፥6፤ናሆ3፥5
3፥1 መዝ12፥2፤ሕዝ 22፥2፤ሚክ3፥10
3፥3 2ነገ19፥35፤ ኢሳ 34፥3፤ኤር47፥3
3፥4 ኢሳ23፥17፤ 47፥9፤ሕዝ16፥25-29
3፥5 ኢሳ20፥4፤ 47፥3፤ ኤር13፥22፤ ናሆ2፥13
3፥6 ዘፀ29፥14፤ 1ሳሙ2፥30፤ኢዮ9፥ 31፤ኢሳ14፥16፤ኤር 51፥37
3፥7 ኢዮ3፥14፤ኢሳ 13፥14፤31፥9፤51፥19፤ ኤር15፥5፤ናሆ1፥1
3፥8 ኢሳ19፥6-9፤ ኤር46፥25፤አሞ6፥2
3፥9 ዘፍ10፥6፤ 2ዜና12፥3፤ሕዝ27፥ 10፤30፥5
3፥10 2ነገ8፥12፤ ኢዮ6፥27፤ኢሳ 13፥16፤20፥4፤ኤር 40፥1፤ሕዝ24፥6፤ሆሴ 13፥16
3፥11 ኢሳ2፥10፤ 49፥26፤ናሆ2፥1
3፥12 ማሕ2፥13፤ ኢሳ28፥4

ይወድቃሉ።
13እነሆ፤ ጭፍሮችሽ፣
ሁሉም ሴቶች ናቸው!
የምድርሽ በሮች፣
ለጠላቶችሽ ወለል ብለው ተከፍተዋል፤
መዝጊያዎቻቸውንም እሳት በልቶአቸዋጠ
ል።
14ለከበባው ውሃ ቅጂ፤
መከላከያሽን አጠናክሪ፤
የሸክላውን ዐፈር ፈልጊ፤
ጭቃውን ርገጪ፤
ጡቡንም ሥሪ።
15በዚያ እሳት ይበላሻል፤
ሰይፍ ይቈርጥሻል፤
እንደ ኵብኵባም ይግጥሻል።
እንደ ኵብኵባ እርቢ፤
እንደ አንበጣም ተባዢ።
16ከሰማይ ከዋክብት እስኪበልጡ ድረስ፣
የነጋዴዎችሽን ቍጥር አበዛሽ፤
ምድሪቱን ግን እንደ አንበጣ ግጠው
አሟጠጡ፤

3፥13 ኢሳ19፥16፤45፥2፤ናሆ2፥6
3፥14 2ዜና32፥4፤
3፥15 2ሳሙ2፥26፤ኢሳ27፥1፤ኤር51፥14፤ኢል1፥4
3፥16 ዘፀ10፥13
3፥17 ኤር51፥27
3፥18 1ነገ22፥17፤መዝ76፥5-6፤ኢሳ56፥10፤ኤር25፥27
3፥19 ኢዮ27፥23፤ኢሳ37፥18፤ኤር30፥13፤ሰቈ2፥15፤ሚክ1፥9፤ሶፎ2፥15

ከዚያም በረው ሄዱ።
17ጠባቂዎችሽ እንደ አንበጣ፣
መኳንንቶችሽም በብርድ ቀን
በቅጥር ሥር እንደሚቀመጥ ኵብኵባ
ናቸው፤
ፀሓይ ሲወጣ ግን ይበራሉ፤
የት እንደሚበሩም አይታወቅም።
18የአሦር ንጉሥ ሆይ፤ እረኞችህ[ʻ]
አንቀላፉ፤
መኳንንትህ ዐርፈው ተኙ፤
ሕዝብህ ሰብሳቢ አጥተው፣
በተራራ ላይ ተበትነዋል።
19ቍስልህን ሊፈውስ የሚችል የለም፤
ስብራትህም ለሞት የሚያደርስ ነው፤
ስለ አንተ የሰማ ሁሉ፣
በውድቀትህ ደስ ብሎት ያጨበጭባል፤
ወሰን የሌለው ጭካኔህ፣
ያልነካው ማን አለና?

ʻ18 ገዦች ማለት ነው።

# ትንቢተ ዕንባቆም

1 ነቢዩ ዕንባቆም የተቀበለው ንግር፤

### የዕንባቆም ማጕረምረም

2እግዚአብሔር ሆይ፤ ለርዳታ እየተጣራሁ፣
አንተ የማትሰማው እስከ መቼ ነው?
“ግፍ በዛ” ብዬ እየጮኽሁ፣
አንተ የማታድነው እስከ መቼ ነው?
3ስለ ምን በደልን እንዳይ አደረግኸኝ?
እንዴትስ ግፍ ሲፈጸም ትታገሣለህ?
ጥፋትና ግፍ በፊቴ አለ፤
ጠብና ግጭት በዝቶአል።
4ስለዚህ ሕግ ላልቶአል፤
ፍትሕ ድል አይነሣም፤
ፍትሕ ይጣመም ዘንድ፣
ክፉዎች ጻድቃንን ይከባሉ።

### የእግዚአብሔር መልስ

5“ቢነገራችሁም እንኳ፣
የማታምኑትን እናንተን፣
በዘመናችሁ አንድ ነገር ስለማደርግ፣
እነሆ፤ ሕዝቡን እዩ፤ ተመልከቱም፤
እጅግም ተደነቁ።
6የራሳቸው ያልሆኑትን መኖሪያ ስፍራዎች
ለመያዝ፣
ምድርን ሁሉ የሚወሩትን፣
ጨካኝና ፈጣን የሆኑትን፣
ባቢሎናውያንን[ሀ] አስነሣለሁ።
7እነርሱም የሚያስፈሩና የሚያስደነግጡ
ናቸው፤
ፍርዳቸውና ክብራቸው፣
ከራሳቸው ይወጣል።
8ፈረሶቻቸው ከነብር ይልቅ ፈጣኖች፣
ከማታም ተኵላ ይልቅ ጨካኞች ናቸው።
ፈረሰኞቻቸው በፍጥነት ይጋልባሉ፤
ከሩቅ ስፍራም ይመጣሉ።
ነጥቆ ለመብላት እንደሚቸኵል አሞራ
ይበራሉ፤
9ሁሉም ለዐመፅ ታጥቀው ይመጣሉ።
ሰራዊታቸው[ለ] እንደ ምድረ በዳ ነፋስ
ወደ ፊት ይገሠግሣል፤
ምርኮኞችንም እንደ አሸዋ ይሰበስባል።
10ነገሥታትን ይንቃል፤
በገዥችም ላይ ያፌዛል፤
በምሽግ ሁሉ ላይ ይሥቃል፤
የዐፈር ቍልል ሠርቶም ይይዘዋል።
11ከዚያም በኋላ እንደ ነፋስ ዐልፎ
ይሄዳል፤
ጕልበታቸውን አምላካቸው ያደረጉ
በደለኞች ናቸው።

1፥1 ናሆ1፥1
1፥2 መዝ6፥3፤13፥12፤22፥12፤ኤር14፥9 ዘካ1፥12
1፥3 ቍ13፤ኢ9፥23፤ መዝ55፥9፤ ኤር20፥8
1፥4 ኢዮ19፥7፤ መዝ119፥126፤ ኢሳ፥23፤5፥20፤ 29፥21፤ሕዝ9፥9
1፥5 ኢሳ29፥9፤ ሐሥ13፥41
1፥6 ዘዳ28፥49፤ 2ነገ24፥2፤ኤር13፥20፤ 21፥7፤ራእ20፥9
1፥7 ኢሳ18፥7፤ ኤር39፥59
1፥8 ዘፍ49፥27 ኤር4፥13
1፥9 ዕን2፥5
1፥10 2ዜና36፥6፤ ኤር33፥4
1፥11 ኤር4፥1112፤ ዳን4፥30
1፥12 ዘፍ21፥33፤ 49፥24፤ዘዐ33፥22፤ መዝ118፥17፤ ኢሳ10፥6፤31፥1 ፤37፥23
1፥13 ቍ3፤ ኢዮ21፥7፤ መዝ18፥26፤25፥3፤ ሰቆ3፥34፡36
1፥15 ኢዮ18፥8፤ ኢሳ19፥8፤ኤር5፥26፤ 16፥16
1፥16 ኤር44፥8
1፥17 ኢሳ14፥6፤ 19፥8
2፥1 መዝ5፥3፤48፥13 ፤85፥8፤ኢሳ21፥8፤ ሕዝ3፥17
2፥2 ኢሳ30፥8፤ ኤር36፥2፤ሕዝ24፥2፤ ሮሜ4፥24፤ራእ19
2፥3 መዝ27፥14፤ ሕዝ12፥25፤ ዳን8፥17፤11፥27

### የዕንባቆም ዳግመኛ ማጕረምረም

12እግዚአብሔር ሆይ፤ ከዘላለም ጀምሮ ያለህ
አይደለህምን?
የእኔ አምላክ፣ የእኔ ቅዱስ እኛ አንሞትም፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ እንዲፈርዱ ሾመሃቸዋል፤
ዐለት ሆይ፤ ይቀጡ ዘንድ ሥልጣን
ሰጠሃቸው።
13ዐይኖችህ ክፉውን እንዳያዩ እጅግ ንጹሓን
ናቸው፤
አንተ በደልን መታገሥ አትችልም፤
ታዲያ፣ አታላዮችን ለምን ትታገሣለህ?
ክፉው ከራሱ ይልቅ ጻድቅ የሆነውን
ሲውጠውስ፣
ለምን ዝም ትላለህ?
14አንተ ሰዎችን በባሕር ውስጥ እንዳለ ዓሣ፣
ገዥ እንደሌላቸውም የባሕር ፍጥረታት
አደረግህ።
15ክፉ ጠላት ሁሉንም በመንጠቆ ያወጣቸዋል፤
በመረቡ ይይዛቸዋል፤
በአሽክላው ውስጥ ይሰበስባቸዋል፤
በዚህም ይደሰታል፤ ሐሤትም ያደርጋል።
16በእነርሱ ተዝናንቶ ይኖራልና፤
ምግቡም ሰብቶአል።
ስለዚህ ለመረቡ ይሠዋል፤
ለአሽክላውም ያጥናል።
17ታዲያ መረቡን ባለማቋረጥ መጣል፣
ሕዝቦችንስ ያለ ርኅራኄ መግደል
አለበትን?

2 በመጠበቂያ ላይ እቆማለሁ፤
በምሽጉ ቅጥር ላይ ወጥቼ
እቈያለሁ፤
ምን እንደሚለኝ፣
ለክርክሩም[ሐ] የምሰጠውን መልስ ለማወቅ
እጠባበቃለሁ።

### የእግዚአብሔር መልስ

2እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል መለሰ፤
“በቀላሉ እንዲነበብ፣
ራእዩን ጻፈው፤
በሰሌዳም ላይ ቅረጸው።
3ራእዩ የተወሰነለትን ጊዜ ይጠብቃልና፤
ስለ መጨረሻውም ይናገራል፤
እርሱም አይዋሽም፤
የሚዘገይ ቢመስልም ጠብቀው፤

[ሀ]6 *ከለዳውያን* ማለት ነው።
[ለ]9 የዕብራይስጡ ቃል ትርጒም በትክክል አይታወቅም።
[ሐ]1 ወይም *በተገሠጽሁ ጊዜ የምሰጠውን ምላሽ*

በእርግጥ ይመጣል[መ]፤ ከቶም አይዘገይም።
4 “እነሆ፤ እርሱ ታብዮአል፤
ምኞቱ ቀና አይደለም፤
ጻድቅ ግን በእምነት[ሠ] ይኖራል።
5 በእርግጥ የወይን ጠጅ አታሎታል፤
ትዕቢተኛ ነው፤ ከቶ አያርፍም፤
እንደ ሲኦል[ረ] ስስታም ነው፣
እንደ ሞት ከቶ አይጠግብም፤
ሕዝቦችን ለራሱ ይሰበስባል፤
ሰዎችንም ሁሉ ማርኮ ይወስዳል።
6 “ታዲያ በእንደዚህ ዐይነቱ ሰው ላይ በማፌዝና በመዘበት እንዲህ እያሉ ሁሉም አይሣለቁበትምን?
“የተሰረቀውን ሸቀጥ ለራሱ ለሚያከማች፣
ራሱን በዐመፅ ባለጠጋ ለሚያደርግ
ወዮለት!
ይህ የሚቀጥለውስ እስከ መቼ ነው?”
ባለ ዕዳ[ሰ] ያደረግሃቸው ድንገት
አይነሡብህምን?
ነቅተውስ አያስደነግጡህምን?
በእጃቸውም ትወድቃለህ።
8 አንተ ብዙ ሕዝብ ስለ ዘረፍህ፣
የተረፉት ሕዝቦች ይዘርፉሃል፤
የሰው ደም አፍሰሃልና፤
አገሮችንና ከተሞችን፣ በውስጣቸው
የሚኖሩትን ሁሉ አጥፍተሃል።
9 “በተጭበረበረ ትርፍ መኖሪያውን
ለሚገነባ፣
ከጠላት እጅ ለማምለጥ፣
ቤቱን በከፍታ ላይ ለሚሠራ ወዮለት!
10 የብዙ ሰዎች ነፍስ እንዲጠፋ አሢረሃል፤
በገዛ ቤትህ ላይ ውርደትን፣ በራስህም
ላይ ጥፋትን አምጥተሃል።
11 ድንጋይ ከቅጥሩ ውስጥ ይጮኻል፤
ከዕንጨት የተሠሩ ተሸካሚዎችም
ይመልሱለታል።
12 “ከተማን ደም በማፍሰስ ለሚሠራ፣
በወንጀልም ለሚመሠርታት ወዮለት።
13 ሰዎች ለእሳት ማገዶ እንዲሆን እንዲለፉ፣
ሕዝቦችም በከንቱ እንዲደክሙ፣
እግዚአብሔር ጸባኦት ወስኖ የለምን?
14 ውሃ ባሕርን እንደሚሸፍን ሁሉ፣
ምድርም የእግዚአብሔርን ክብር በማወቅ
ትሞላለችና።
15 “ኀፍረተ ሥጋቸውን ለማየት፤
ባልንጀሮቹን ለሚያጠጣ፣
እስኪሰክሩም ድረስ ወይን ለሚቀዳ
ላቸው ወዮለት!
16 በክብር ፈንታ ዕፍረት ትሞላለህ፤
አሁን ደግሞ ተራው የአንተ ነውና፤ ጠጣ፤
ኀፍረተ ሥጋህም ይገለጥ፤
በእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ያለው ጽዋ
ይመለስብሃል፤
ክብርህንም ውርደት ይሸፍነዋል።
17 በሊባኖስ ላይ የሠራኸው ግፍ
ያጥለቀልቅሃል፤
እንስሳቱን ማጥፋትህም ያስደነግጥሃል፤
የሰው ደም አፍሰሃልና፤
አገሮችንና ከተሞችን በውስጣቸው
የሚኖሩትንም ሁሉ አጥፍተሃልና።
18 “የሰው እጅ የቀረጸው ጣዖት፣
ሐሰትንም የሚናገር ምስል ምን ፋይዳ
አለው?
ሠሪው በገዛ እጁ ሥራ ይታመናልና፣
መናገር የማይችሉ ጣዖታትን
ይሠራልና።
19 ዕንጨቱን፣ ‘ንቃ!’
ሕይወት የሌለውንም ድንጋይ፣ ‘ተነሣ!’
ለሚል ወዮለት፤
በውኑ ማስተማር ይችላልን?
እነሆ፤ በወርቅና በብር ተለብጦአል፤
እስትንፋስም የለውም።
20 እግዚአብሔር ግን በተቀደሰ መቅደሱ አለ፣
ምድር ሁሉ በፊቱ ጸጥ ትበል።”

### የዕንባቆም ጸሎት

3 በዝማሬ የቀረበ የነቢዩ የዕንባቆም ጸሎት፤
በሽግዮኖት[ሸ]
2 እግዚአብሔር ሆይ፤ ዝናህን ሰምቻለሁ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ ሥራህም አስፈራኝ፤
በእኛ ዘመን አድሳቸው፤
በእኛም ጊዜ እንዲታወቁ አድርግ፤
በመዓት ጊዜ ምሕረትን አስብ።
3 እግዚአብሔር ከቴማን፣
ቅዱሱም ከፋራን ተራራ መጣ። ሴላ[ቀ]
ክብሩ ሰማያትን ሸፈነ፤
ውዳሴውም ምድርን ሞላ።
4 ጸዳሉ እንደ ፀሓይ ብርሃን ነው፤
ጨረር ከእጁ ወጣ፤
ኀይሉም በዚያ ተሰውሮአል።
5 መቅሠፍት በፊቱ ሄደ፤
ቸነፈርም እግር በእግር ተከተለው።
6 ቆመ፤ ምድርን አንቀጠቀጠ፤
ተመለከተ፤ ሕዝቦችን አብረከረከ፤
የዘላለም ተራሮች ተፈረካከሱ፤
የጥንት ኰረብቶችም ፈራረሱ፤
መንገዱ ዘላለማዊ ነው።

2፥4 ሕዝ18፥9፤ ሮሜ1፥17፤ገላ3፥11፤ ዕብ10፥3738
2፥5 ምሳ20፥1፤ 27፥20፤30፥1516፤ ኢሳ2፥11፤ዕን1፥9
2፥6 ኢሳ14፥4፤ አሞ2፥8
2፥7 ምሳ29፥1
2፥8 ቍ17፤ ኢሳ33፥1፤ ኤር50፥1718፤ ሕዝ39፥10፤ አብ1፥15፤ዘካ2፥89
2፥9 ኢዩ39፥27፤ኢሳ 10፥14፤ኤር22፥13፤51 ፥13
2፥10 ቍ16፤ ኤር26፥19፤ናሆ3፥6
2፥11 ኢሱ24፥27፤ ዘካ5፥4፤ሉቃ19፥40
2፥12 ሕዝ22፥2፤ ሚክ3፥10
2፥13 ኢሳ47፥13፤ 50፥11
2፥14 ዘፀ16፥7፤ ዘኍ14፥21፤ኢሳ11፥9
2፥15 ምሳ23፥20
2፥16 ቍ10፤ዘሌ 10፥9፤መዝ16፥5፤ኢሳ 51፥22፤ሰቆ4፥21፤ሕዝ 23፥32፡34፤ሆሴ4፥7
2፥17 ቍ8፤ ኤር50፥15፤51፥35
2፥18 ዘሌ26፥1፤ መሳ10፥14፤1ሳሙ 12፥21፤መዝ115፥45፤ ኢሳ40፥19፤ኤር5፥21 ፤10፥14፤14፥22፤ 1ቆሮ12፥2
2፥19 1ነገ18፥27፤ ኤር10፥4፤ዳን5፥4፡23፤ ሆሴ4፥12
2፥20 መዝ11፥4፤ ኢሳ41፥1
3፥1 መዝ7 ርእስ
3፥2 ኢዮ26፥14፤ መዝ44፥1፤85፥6፤90፥1 6፤119፥120፤ ኢሳ54፥8፤
3፥3 ዘፍ36፥11፡15፤ ዘኍ10፥12፤መዝ8፥1፤ 48፥10፤ኢሳ31፥1
3፥4 ኢዮ9፥6፤ ኢሳ18፥4
3፥5 ዘሌ26፥25
3፥6 ዘፍ21፥33፤ 49፥26፤ዘፀ19፥18፤ መዝ18፥7፤46፥2፤ 114፥16

[መ]3 የሚመጣ ሰው እንዳለ የሚያመለክቱ አሉ።
[ሠ]4 *በታማኝነቱ* የሚሉ አሉ። [ረ]5 *መቃብር* የሚሉ አሉ።
[ሰ]7 ወይም *አበዳሪ* ነው።
[ሸ]1 የሥነ ጽሑፍ ወይም የሙዚቃ ቋንቋ ሳይሆን አይቀርም
[ቀ]3 ትርጒሙ በትክክል የማይታወቅ ቢሆንም የዜማ ቃል ሳይ ሆን አይቀርም

7የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ፣
የምድያምም መኖሪያዎች ሲታወኩ
አየሁ።

8እግዚአብሔር ሆይ፤ በወንዞች ላይ ተቈጣህን?
መዓትህስ በምንጮች ላይ ነበርን?
በፈረሶችህና በድል አድራጊ ሠረገሎችህ፣
በጋለብህ ጊዜ፣
በባሕር ላይ ተቈጥተህ ነበርን?
9ቀስትህን አዘጋጀህ፤
ፍላጻም እንዲመጣልህ አዘዝህ፤
ሴላ
ምድርን በወንዞች ከፈልህ፤
10ተራሮች አዩህ፤ ተጨነቁም፤
የውሃ ሞገድ ዐልፎ ሄደ፤
ቀላዩ ደነፋ፤
ማዕበሉንም ወደ ላይ አነሣ።

11ከሚወረወሩ ፍላጾችህ፣
ከሚያብረቀርቅ የጦርህ ነጸብራቅ የተነሣም፣
ፀሓይና ጨረቃ በቦታቸው ቆሙ።
12በምድር ላይ በመዓት ተመላለስህ፤
ሕዝቦችንም በቍጣ ረገጥሃቸው።
13ሕዝብህን ለመታደግ፣
የቀባኸውንም ለማዳን ወጣህ፤
የክፋትን ምድር መሪ ቀጠቀጥህ፤
ከራስ ጠጕሩ እስከ እግር ጥፍሩም
ዕርቃኑን አስቀረኸው።

14እንደ ዐውሎ ነፋስ ሊበታትነን የመጣውን፣
ምስኪኑን በስውር በመዋጥ
የሚደሰተውን፣
የሰራዊት አለቃ ራስ፣
በገዛ ጦሩ ወጋህ።
15ታላላቅ ውሆችን በመናጥ፣
ባሕሩን በፈረሶችህ ረገጥህ።
16እኔ ሰማሁ፤ ልቤም ደነገጠብኝ፤
ከንፈሬ ከድምፁ የተነሣ ተንቀጠቀጠ፤
ፍርሀት እስከ ዐጥንቴ ዘልቆ ገባ፤
እግሬም ተብረከረከ፤
ሆኖም በሚወረን ሕዝብ ላይ እስኪመጣ
ድረስ፣
የጥፋትን ቀን በትዕግሥት እጠባበቃለሁ።
17ምንም እንኳ የበለስ ዛፍ ባያፈራ፣
ከወይን ተክልም ፍሬ ባይገኝ፣
የወይራም ዛፍ ፍሬ ባይሰጥ፣
ዕርሻዎችም ሰብል ባይሰጡ፣
የበጎች ጕረኖ እንኳ ባዶውን ቢቀር፣
ላሞችም በበረት ውስጥ ባይገኙ፣
18እኔ ግን *በእግዚአብሔር* ደስ ይለኛል፤
በድነቴ አምላክ ሐሤት አደርጋለሁ።

19ጌታ *እግዚአብሔር* ኀይሌ ነው፤
እግሮቼን እንደ ዋላ እግሮች ያደርጋል፤
በከፍታዎችም ላይ ያስሄደኛል።

ለመዘምራን አለቃ፣ በባለ አውታር
መሣሪያዎቼ የተዘመረ መዝሙር።

3፥7 ዘፍ25፥2፤ ዘፀ15፥14፤ዘኁ25፥15፤ መሳ7፥2425
3፥8 ዘፀ7፥20፤ 2ነገ2፥11፤መዝ68፥17፤77፥16
3፥9 ዘዳ32፥23፤ መዝ7፥1213
3፥10 መዝ77፥16፤ 93፥3፤98፥7
3፥11 ኢሱ10፥13፤ መዝ18፥14፤144፥6፤ ዘካ9፥14
3፥12 ኢሳ41፥15
3፥13 ዘፀ13፥21፤ 2ሳሙ23፥1፤መዝ20፥6፤28፥8፤68፥21፤ 110፥6
3፥14 መሳ7፥22 መዝ64፥25
3፥15 ዘፀ15፥8፤ ኢዮ9፥8
3፥16 ኢዮ4፥14፤ መዝ37፥7
3፥17 ኤር5፥17፤ ኢል1፥1012፥18
3፥18 ዘፀ15፥2፤ መዝ97፥12፤ ኢሳ61፥10፤ሉቃ1፥47፤ ፊል4፥4
3፥19 ዘዳ32፥13፤ 33፤29፤መዝ18፥33፤ 46፥15

# ትንቢተ ሶፎንያስ

1 በይሁዳ ንጉሥ በአሞጽ ልጅ በኢዮስ
ያስ ዘመን ወደ ሕዝቅያስ ልጅ፣ ወደ
አማርያ ልጅ፣ ወደ ጎዶልያስ ልጅ፣ ወደ
ኵሲ ልጅ ወደ ሶፎንያስ የመጣ *የእግዚአ
ብሔር* ቃል ይህ ነው፤

## ስለሚመጣው ጥፋት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

2“ማንኛውም ነገር፣
ከምድር ገጽ አጠፋለሁ”
ይላል *እግዚአብሔር*።

3“ሰውንና እንስሳን አጠፋለሁ፤
የሰማይን ወፎች፣
የባሕርንም ዓሦች አጠፋለሁ፤
ሰውን ከምድር ገጽ በማስወግድበት
ጊዜ፣
ክፉዎች የፍርስራሽ[ሀ] ክምር ይሆናሉ”
ይላል *እግዚአብሔር*።

## በይሁዳ ላይ የተነገረ ጥፋት

4“እጄን በይሁዳ፣
በኢየሩሳሌምም በሚኖሩት ሁሉ ላይ
አነሣለሁ፤
የበኣልን ትሩፍ፣
የጣዖታቱንና የአመንዝራ ካህናቱን ስም
ሁሉ ከዚህ ስፍራ አጠፋለሁ፤
5የሰማይን ሰራዊት ለማምለክ፣
በሰገነት ላይ ወጥተው የሚሰግዱትን፣
ለ*እግዚአብሔር* እየሰገዱ፣ በስሙም
እየማሉ፣
በሚልኮምም[ለ] ደግሞ የሚምሉትን፣
6*እግዚአብሔርን* ከመከተል ወደ ኋላ
የሚመለሱትን፣
*እግዚአብሔርን* የማይፈልጉትን፣
እንዲረዳቸውም የማይጠይቁትን
አጠፋለሁ።
7በልዑል *እግዚአብሔር* ፊት ዝም በሉ፤
*የእግዚአብሔር* ቀን ቀርቦአልና።
*እግዚአብሔር* መሥዋዕት አዘጋጅቶአል፤
የጠራቸውንም ቀድሶአል።
8*በእግዚአብሔር* የመሥዋዕት ቀን፣
መሳፍንቱንና የንጉሡን ልጆች፣
እንግዳ ልብስ የሚለብሱትን ሁሉ
እቀጣለሁ።
9በዚያን ቀን፣
በመድረኩ ላይ የሚዘሉትን ሁሉ፣
የአማልክቶቻቸውን ቤት፣
በዐመፅና በማጭበርበር የሚሞሉትን
እቀጣለሁ።
10*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“በዚያ ቀን ከ‘ዓሣ በር’ ጩኸት
በሁለተኛው አደባባይ ዋይታ፣
ከኰረብቶችም ታላቅ ሽብር ይሰማል።
11እናንት በመክቴሽ[ሐ] ገበያ የምትኖሩ
ዋይ በሉ፤
ነጋዴዎቻችሁ ሁሉ ይደመሰሳሉ፤
በብር የሚነግዱትም ሁሉ ይሞታሉ።
12በዚያ ዘመን ኢየሩሳሌምን በመብራት
እፈትሻለሁ፤
ተንደላቀው የሚኖሩትን፣
በዝቃጩ ላይ እንደ ቀረ የወይን ጠጅ
የሆኑትን፣
‘ክፉም ይሁን መልካም፣
*እግዚአብሔር* ምንም አያደርግም’
የሚሉትን ቸልተኞች እቀጣለሁ።
13ሀብታቸው ይዘረፋል፤
ቤታቸው ይፈራርሳል፤
ቤቶች ይሠራሉ፤
ነገር ግን አይኖሩባቸውም፤
ወይን ይተክላሉ፤
ጠጁን ግን አይጠጡም።

## ታላቁ *የእግዚአብሔር* ቀን

14“ታላቁ *የእግዚአብሔር* ቀን ቅርብ ነው፤
ቅርብ ነው ፈጥኖም ይመጣል፤
*በእግዚአብሔር* ቀን የሚሰማው ልቅሶ
መራራ ነው፤
በዚያ ጦረኛውም ምርር ብሎ
ይጮኻል፤
15ያ ቀን የመዓት ቀን፣
የመከራና የጭንቀት ቀን፣
የሁከትና የጥፋት ቀን፣
የጨለማና የጭጋግ ቀን፣
የደመናና የድቅድቅ ጨለማ ቀን
ይሆናል፤
16ያ ቀን በተመሸጉ ከተሞችና፣
በረጃጅም ግንቦች ላይ፣
የመለከት ድምፅና የጦርነት ጩኸት
የሚሰማበት ቀን ይሆናል።
17እንደ ዕውር እንዲራመዱ፣
በሰዎች ላይ ጭንቀት አመጣባቸዋለሁ፤
*በእግዚአብሔር* ላይ ኀጢአትን
ሠርተዋልና።
ደማቸው እንደ ትቢያ፣
ሥጋቸውም እንደ ጕድፍ ይጣላል።

1፥1 2ነገ22፥1፤ ዜና3፥14፤2ዜና 34፥13፤5፥25
1፥2 ዘፍ6፥7
1፥3 ቍ18፤ኤር 4፥25፤50፥3፤ሕዝ 14፥17፤ሆሴ4፥3
1፥4 ኤር6፥12፤ 15፥6፤ሆሴ10፥5፤ሚክ 5፥13፤ሶፎ2፥11
1፥5 ዘሌ18፥21፤ ኤር5፥7፤8፥2
1፥6 ኢሳ1፥4፤9፥13 ፤ኤር2፥13፤ሆሴ7፥7
1፥7 ቍ14፤ዘሌ 3፥9፤ኢሳ13፥6፤ 41፥1፤ኤር46፥10፤ ሕዝ7፥19፤ኢል 3፥14፤አሞ5፥18ጠ20
1፥8 ኢሳ24፥21፤ ኤር39፥6
1፥9 1ሳሙ5፥5፤ አሞ3፥10
1፥10 2ዜና33፥14፤ ኢሳ22፥5፤አሞ5፥16
1፥11 ሆሴ9፥6፤ ያዕ5፥1
1፥12 2ነገ21፥16፤ ኢዮ22፥13፤ኤር 48፥11፤ሕዝ8፥12፤ አሞ6፥1
1፥13 ዘዳ28፥30፡ 39፤2ነገ24፥13፤ኤር 15፥13፤ሰቆ5፥2፤ አሞ5፥11
1፥14 ቍ7፤ሕዝ 7፥7፤ዳን7፥13፤ ኢል1፥15
1፥15 1ሳሙ2፥9፤ ኢሳ22፥5፤ኢል2፥2፤ ማር13፥2425
1፥16 ዘዳ28፥52፤ ኢሳ2፥15፤ኤር 4፥19፤ኢል2፥1
1፥17 ዘዳ28፥52፤ መዝ79፥3፤83፥10፤ ኢሳ59፥10

[ሀ]3 የዕብራይስጡ ቃል ትርጕም በትክክል አይታወቅም።
[ለ]5 በዕብራይስጥ *መልካም* ይባላል
[ሐ]11 አንዳንዶች *በሞርታር* ይላሉ።

18በእግዚአብሔር የቍጣ ቀን፣
ብራቸውም ሆነ ወርቃቸው፣
ሊያድናቸው አይችልም፤
መላዪቱ ምድር፣
በቅናቱ ትበላለች፤
በምድር በሚኖሩ ሁሉ ላይ፣
ድንገተኛ ፍጻሜ ያመጣባቸዋልና።”

2 እናንት ዕረፍት የሌላችሁ ሕዝብ ሆይ፤
በአንድነት ተሰብሰቡ፤ ተከማቹም፤
2የተወሰነው ጊዜ ሳይደርስ፣
ቀኑ እንደ ገለባ ሳይጠራርጋችሁ፣
የእግዚአብሔር ጽኑ ቍጣ በእናንተ ላይ
ሳይመጣ፣
የእግዚአብሔር የመዓት ቀን
ሳይደርስባችሁ ተሰብሰቡ።
3እናንት የምድር ትሑታን ሁሉ፣
ትእዛዙን የምትፈጽሙ፣ እግዚአብሔርን
እሹ፤
ጽድቅንና ትሕትናን ፈልጉ፤
በእግዚአብሔር የቍጣ ቀን፣
ትሰወሩ ይሆናል።

## በፍልስጥኤም ላይ የተነገረ ጥፋት

4ጋዛ ባድማ ትሆናለች፤
አስቀሎናም ፈራርሳ ትቀራለች፤
አዛጦን በቀትር ባዶ ትሆናለች፤
አቃሮንም ትነቀላለች።
5እናንት በባሕር ዳርቻ የምትኖሩ፣
የከሊታውያን ሰዎች ሆይ፤ ወዮላችሁ!
የፍልስጥኤማውያን ምድር ከነዓን ሆይ፤
በአንቺ ላይ የተነገረው የእግዚአብሔር
ቃል ይህ ነው፤

“ፍጹም አጠፋሻለሁ፤
ከነዋሪዎችሽም የሚተርፍ የለም።”

6የቀርጤስ[ሠ] ሰዎች የሚኖሩበት በባሕሩ
ዳር ያለው ምድር፣
የእረኞች መኖሪያና የበጎች በረት
ይሆናል፤
7ይህም ለይሁዳ ቤት ትሩፍ ይሰጣል፤
እነርሱም በዚያ መሰማሪያ ያገኛሉ።
በአስቀሎና ቤቶች ውስጥም፣
በምሽት ይተኛሉ፤
አምላካቸው እግዚአብሔር ይጠብቃቸዋል፤
ምርኮአቸውንም ይመልስላቸዋል።

## በሞዓብና በአሞን ላይ የተነገረ ጥፋት

8“የሞዓብን ስድብ፣
የአሞናውያንንም ፌዝ ሰምቻለሁ፤
ሕዝቤን ሰድበዋል፤
በምድራቸውም ላይ ዝተዋል።
9ስለዚህ የእስራኤል አምላክ፣ ሁሉን
የሚገዛ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“በሕያውነቴ እምላለሁ!
ሞዓብ እንደ ሰዶም፣
አሞናውያን እንደ ገሞራ፣
ዐረም እንደ ዋጠው ቦታና እንደ ጨው
ጕድጓድ
ለዘላለም ጠፍ ይሆናሉ።
ከሕዝቤ የቀሩት ይዘርፏቸዋል፤
ከወገኔ የተረፉትም ምድራቸውን
ይወርሳሉ።”

10ከትዕቢታቸው የተነሣ የሚደርስባቸው
ይህ ነው፤
የሁሉን ገዥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ
ሰድበው ዘብተውበታልና፣
11እግዚአብሔር የምድሪቱን አማልክት
ሁሉ በሚደመስስበት ጊዜ፣
በእነርሱ ዘንድ የተፈራ ይሆናል፤
በየባሕሩ ጠረፍ የሚኖሩ ሕዝቦች፣
እያንዳንዳቸው በያሉበት ሆነው ለእርሱ
ይሰግዳሉ።

## በኢትዮጵያ ላይ የተነገረ ጥፋት

12“ኢትዮጵያውያን ሆይ፤ እናንተም፣
በሰይፌ ትገደላላችሁ።”

## በአሦር ላይ የተነገረ ጥፋት

13እጁን በሰሜን ላይ ይዘረጋል፤
አሦርንም ያጠፋል፤
ነነዌን ፍጹም ባድማ፣
እንደ ምድረ በዳም ደረቅ
ያደርጋታል።
14የበግና የከብት መንጋዎች፣
የፍጥረት ዐይነት ሁሉ በውስጧ
ይመሰጋሉ፤
ጕጕትና ጃርት፣
በግንቦቿ ላይ ያድራሉ።
ጩኸታቸው በየመስኮቱ ያስተጋባል፤
ፍርስራሽ በየደጃፉ ይከመራል፤
ከዝግባ የተሠሩ ተሸካሚዎችም
ይገለጣሉ።
15ተዘልላ የኖረች፣
ደስተኛዪቱ ከተማ ይህች ናት፤
እርሷም በልቧ፣
“እኔ ብቻ ነኝ፤ ከእኔ በቀር ማንም
የለም” ያለች፣
ታዲያ እንዴት የዱር አራዊት
የሚመሰጉባት፣
ባድማ ሆና ቀረች?
በአጠገቧ የሚያልፉ ሁሉ፣
ያፌዙባታል፤ እጃቸውንም በንቀት
ያወዛውዙባታል።

[ሠ]6 የዕብራይስጡ ትርጕም በትክክል አይታወቅም።

1፥18 ቍ23፤ዘፍ 6፥7፤ዘዳ29፥20፤ ኢዮ20፥20፤40፥11፤ ኤር4፥4፤ሕዝ7፥11፡ 19፤ሶፎ3፥8
2፥1 2ዜና20፥4፤ ኤር3፥3፤6፥15፤ ኢል1፥14
2፥2 ኢሳ17፥13፤ ኤር4፥4፤10፥25፤ ሰቆ4፥11፤ሕዝ 7፥19፤ሆሴ13፥3
2፥3 መዝ45፥4፤ 57፥1፤ኢሳ1፥17፤ አሞ5፥6
2፥4 ዘፍ10፥19፤ ኤር47፥5፤አሞ1፥6፡ 7ጠ8፤ዘካ9፥57
2፥5 ዘሌ26፥31፤ 1ሳሙ30፥14፤ኢሳ 14፥30፤አሞ3፥1
2፥6 ኢሳ5፥17
2፥7 ዘፍ45፥7፤ዘዳ 30፥3፤መዝ126፥4፤ ኤር32፥44፤ሆሴ6፥11፤ ኢል3፥1፤አሞ1፥68
2፥8 ዘፍ19፥37፤ ኢሳ16፥6፤ኤር 48፥27፤ሰቆ3፥61፤ ሕዝ21፥28፤25፥3
2፥9 ዘዳ23፥6፤ 29፥23፤2ነገ19፥31፤ ኢሳ11፥14፤13፥19፤ 15፥1ጠ16፥14፤ኤር 48፥147፤49፥16፡18፤ ሕዝ25፥17፤8ጠ11፤ አሞ2፥13
2፥10 ኢዮ40፥12፤ መዝ9፥6፤ኢሳ 16፥6፤ኤር48፥27
2፥11 1ዜና19፥1፤ መዝ86፥9፤ኢሳ 12፥4፤ሕዝ25፥67፤ ኢል2፥11፤ሶፎ 1፥4፤3፥9
2፥12 ዘፍ10፥6፤ ኢሳ20፥4፤ኤር46፥10
2፥13 ዘፍ10፥11፤ ኢሳ10፥5፤ሚክ5፥6፤ ናሆ1፥1፤ዘካ10፥11
2፥14 መዝ102፥6፤ ኢሳ5፥17፤14፥23፤ ራእ18፥2
2፥15 ኢሳ28፥22፤ 32፥9፤47፥8፤ኤር 49፥33፤ሕዝ27፥36፤ 28፥2፤ናሆ3፥19

### የኢየሩሳሌም የወደፊት ዕጣ

3 ለዐመፀኞቿና ለረከሰች፣
ለጨቋኞች ከተማ ወዮላት!
[2]እርሷ ለማንም አትታዘዝም፤
የማንንም ዕርምት አትቀበልም፤
በ*እግዚአብሔር* አትታመንም፤
ወደ አምላኳም አትቀርብም።
[3]ሹሞቿ የሚያገሡ አንበሶች፣
ገዦቿ ለነገ የማይሉ፣
የምሽት ተኵላዎች ናቸው።
[4]ነቢያቷ ትዕቢተኞች፣
አታላዮችም ናቸው፤
ካህናቷ መቅደሱን ያረክሳሉ፣
በሕግም ላይ ያምፃሉ።
[5]በእርሷ ውስጥ ያለው *እግዚአብሔር*
ጻድቅ ነው፤
ፈጽሞ አይሳሳትም፤
በየማለዳው ቀን ፍርድ ይሰጣል፤
በየቀኑም አይደክምም፤
ዐመፀኞች ግን ዕፍረት አያውቁም።

[6]"ሕዝቦችን አጥፍቻለሁ፤
ምሽጋቸው ተደምስሷል፤
ማንም እንዳያልፍባቸው፣
መንገዳቸውን ባድማ አደረግሁ፤
ከተሞቻቸው ተደምስሰዋል፤
አንድም ሰው የለም፤ ነዋሪም ከቶ
አይገኝባቸውም።
[7]እኔም ከተማዪቱን፣
'በእርግጥ ትፈሪኛለሽ፤
ዕርምትም ትቀበያለሽ' አልኋት፤
ስለዚህ መኖሪያዋ አይጠፋም፤
ቅጣቴም ሁሉ በእርሷ ላይ አይደርስም።
እነርሱ ግን በሚያደርጉት ሁሉ፣
ክፋትንም በመፈጸም እየተጉ ሄዱ።
[8]*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
"ስለዚህ እስከምፈርድበት‴ ቀን ድረስ
ጠብቁኝ፤
አሕዛብን ላከማች፣
መንግሥታትን ልሰበስብ፣
መዓቴንና ጽኑ ቍጣዬን፣
በላያቸው ላፈስ ወስኛለሁ፤
በቅናቴ ቍጣ እሳት፣
መላዋ ምድር ትቃጠላለችና።

[9]"በዚያ ጊዜ ሰዎች ሁሉ *የእግዚአብሔርን*
ስም እንዲጠሩ፣
ተስማምተው እንዲያገለግሉት፣
አንደበታቸውን አጠራለሁ።
[10]ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ፣
የሚያመልኩኝ፣ የተበተኑት ሕዝቤ
ቍርባን ያመጡልኛል።
[11]በእኔ ላይ ከፈጸማችሁት በደል ሁሉ
የተነሣ፣
በዚያ ቀን አታፍሩም፤
በትዕቢታቸው የሚደሰቱትን፣
ከዚህች ከተማ አስወግዳለሁና፤
ከእንግዲህ ወዲያ፣
በቅዱስ ተራራዬ ላይ አትታበዩብኝም።
[12]*በእግዚአብሔር* ስም የሚታመኑትን፣
የዋሃንንና ትሑታንን፣
በመካከላችሁ አስቀራለሁ።
[13]የእስራኤል ትሩፋን ኀጢአት
አይሠሩም፤
ሐሰትም አይናገሩም፤
በአንደበታቸውም ተንኰል አይገኝም።
ይበላሉ፤ ይተኛሉ፤
የሚያስፈራቸውም የለም።

[14]የጽዮን ልጅ ሆይ፤ ዘምሪ፤
እስራኤል ሆይ፤ እልል በይ፤
የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ፤
በፍጹም ልብሽ ደስ ይበልሽ፤ ሐሤትም
አድርጊ።
[15]*እግዚአብሔር* ቅጣትሽን አስወግዶታል፤
ጠላቶችሽን ከአንቺ መልሶአል፤
የእስራኤል ንጉሥ *እግዚአብሔር* ከአንቺ
ጋር ነው፤
ከእንግዲህ ወዲያ አንዳች ክፉ ነገር
አትፈሪም።
[16]በዚያ ቀን ኢየሩሳሌምን እንዲህ
ይሏታል፤
"ጽዮን ሆይ፤ አትፍሪ፤
እጆችሽም አይዛሉ።
[17]አምላክሽ *እግዚአብሔር* ከአንቺ ጋር
ነው፤
እርሱ የሚታደግ ኀያል ነው፤
በአንቺ እጅግ ደስ ይለዋል፤
በፍቅሩ ያሳርፍሻል፤
በዝማሬም በአንቺ ሐሤት ያደርጋል።"

[18]"ለታወቁ ክብረ በዓላት ሐዘንን፣
ከአንቺ አስወግዳለሁ፤
ሸክምና ነቀፌታ ሆነውብሻል።ʻ
[19]በዚያ ጊዜ፣
ያስጨነቁሽን ሁሉ እቀጣለሁ፤
አንካሶችን እታደጋለሁ፤
የተበተኑትንም እሰበስባለሁ፤
በተዋረዱበት ምድር ሁሉ፣
ለውዳሴና ለክብር አደርጋቸዋለሁ።
[20]በዚያን ጊዜ እሰበስባችኋለሁ፤
ያን ጊዜ ወደ አገራችሁ
እመልሳችኋለሁ፤
ዐይናችሁ እያየ፣

3፥1 ዘጸ21፥18፤ ኤር6፥6፤ሕዝ23፥30
3፥2 ዘሌ26፥23፤ ዘጸ1፥32፤መዝ73፥28፤ ኤር7፥28፤22፥21
3፥3 ዘፍ49፥27፤ መዝ22፥13፤ሚክ3፥3
3፥4 መዝ25፥3፤ ኢሳ48፥8፤ኤር3፥20፤ 9፥4፤23፥11፤ሕዝ 22፥26፤ሚል2፥10
3፥5 ዘጸ32፥4፤ዕዝ 9፥15፤መዝ5፥3፤ኤር 3፥3፤ሰቆ3፥23፤ሕዝ 18፥25
3፥6 ዘሌ26፥31
3፥7 ኤር7፥28፤ ሆሴ9፥9
3፥8 መዝ27፥14፤ 79፥6፤ኢሳ2፥3፤ ኤር10፥25፤ሰቆ4፥11፤ ኢል3፥11፤ሶፎ1፥18
3፥9 ዘፍ4፥26፤ኢሳ 19፥18፤ሶፎ2፥11
3፥10 ዘፍ10፥6፤ 2ዜና32፥23፤መዝ 68፥31፤ኢሳ60፥7
3፥11 ዘፍ50፥15፤ ዘፀ15፥17፤ዘሌ26፥19፤ መዝ59፥12፤ኢሳ 29፥22፤ኢል2፥26-27
3፥12 ኢሳ14፥32፤ ኤር29፥12፤ናሆ1፥7
3፥13 ዘሌ26፥6፤ ኢዮ16፥17፤መዝ 119፥3፤ኢሳ4፥3፤ 10፥21፤ኤር33፥16፤ ሕዝ34፥15፡25ጠ28፤ ሶፎ2፥7፤ ራእ14፥5
3፥14 መዝ9፥2፡ 14፤95፥1፤ኢሳ 12፥6፤51፥11፤ ዘካ2፥10
3፥15 ኢሳ54፥14፤ ሕዝ37፥2628፤ዘካ9፥9
3፥16 2ነገ19፥26፤ ኢዮ4፥3፤ኢሳ35፥34፤ ዕብ12፥12
3፥17 ዘጸ28፥63፤ ኢሳ40፥1፤62፥4፤ 63፥1፤ሆሴ14፥4፤ ኢል2፥21
3፥19 ኢሳ14፥2፤ 60፥18፤ሕዝ34፥16፤ ሚክ4፥6
3፥20 ዘጸ26፥19፤ ኢሳ56፥5፤60፥18፤

‴8 የሰባ ሊቃናቱና የሱርስቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ የዕብራይስጡ ትርጕም ግን *ለመበዝበዝ እስከምነሣበት ቀን ድረስ* ይላል።
ʻ18 ወይም *በበዓል ቀን የሚያዝኑትን እሰበስብልሻለሁ፤ ሐፍረትሽ ሸክም ሆኖብኛል*

ምርኮአችሁን በምመልስበት ጊዜ፣
መከበርንና መወደስን፣
በምድር ሕዝብ ሁሉ መካከል
እሰጣችኋለሁ"፤
ይላል እግዚአብሔር።

66፥22፤ኤር29፥14፤
ሕዝ37፥12፤ኢል3፥1

# ትንቢተ ሐጌ

### የእግዚአብሔርን ቤት ለመሥራት የተደረገ ጥሪ

1 ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት፣ በስድስተኛው ወር የመጀመሪያ ቀን፣ የእግዚአብሔር ቃል በነቢዩ በሐጌ በኩል ወደ ይሁዳ ገዥ ወደ ሰላትያል ልጅ ወደ ዘሩባቤልና ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ኢዮሴዴቅ ልጅ ወደ ኢያሱ[ሀ] እንዲህ ሲል መጣ፤
2 እግዚአብሔር ጸባኦት እንዲህ ይላል፤ "ይህ ሕዝብ፣ 'የእግዚአብሔር ቤት የሚሠራበት ጊዜ ገና ነው' ይላል።"

3 የእግዚአብሔርም ቃል በነቢዩ በሐጌ በኩል እንዲህ ሲል መጣ፤ 4 "ይህ ቤት ፈርሶ ሳለ፣ እናንተ ራሳችሁ በተዋቡ ቤቶቻችሁ ውስጥ ለመኖር ጊዜው ነውን?"

5 ስለዚህ እግዚአብሔር ጸባኦት እንዲህ ይላል፤ "እስቲ የሠራችሁትን ዐስቡ፤ 6 ብዙ ዘራችሁ፤ ነገር ግን ያጨዳችሁት ጥቂት ነው፤ በላችሁ ግን አልጠገባችሁም፤ ጠጣችሁ ግን አልረካችሁም፤ ለበሳችሁ ግን አልሞቃችሁም፤ ደመወዝን ተቀበላችሁ፤ ግን በቀዳዳ ኰረጆ የማስቀመጥ ያህል ነው።"

7 እግዚአብሔር ጸባኦት እንዲህ ይላል፤ "እስቲ የሠራችሁትን አስቡ፤ 8 ወደ ተራራ ውጡ፤ ዕንጨት አምጡ፤ ቤቱን ሥሩ፤ እኔም በእርሱ ደስ ይለኛል፤ እከበርበታለሁም" ይላል እግዚአብሔር።
9 ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ "ብዙ ተስፋ አደረጋችሁ፤ ያገኛችሁት ግን ጥቂት ነው፤ ወደ ቤት ያስገባችሁትንም እኔ እፍ አልሁበት፤ ይህ የሆነው ለምን ይመስላችኋል?" የእኔ ቤት ፈርሶ እያለ ሁላችሁም የራሳችሁን ቤት ለመሥራት ስለምትሮጡ ነው፤ 10 ስለዚህ በእናንተ ምክንያት ሰማያት ጠል ከለከሉ፤ ምድርም ፍሬዋን ነሣች። 11 እኔም በዕርሻዎችና በተራሮች፣ በእህሉና በአዲሱ ወይን ጠጅ፣ በዘይቱና ምድር በምታፈራው ሁሉ፣ በሰውና በእንስሳ፣ በእጆቻችሁም ሥራ ላይ ድርቅ አመጣሁ።"

12 ከዚህ በኋላ የሰላትያል ልጅ ዘሩባቤል፣ ሊቀ ካህናቱ የኢዮሴዴቅ ልጅ ኢያሱ፣ ከምርኮ የተረፉትም ሕዝብ የአምላካቸውን የእግዚአብሔርን ድምፅ፣ የነቢዩንም የሐጌን መልእክት ሰሙ፤ አምላካቸው እግዚአብሔር ልኮታልና። ሕዝቡም እግዚአብሔርን ፈሩ።

13 ቀጥሎም የእግዚአብሔር መልእክተኛ ሐጌ፣ ይህን የእግዚአብሔርን መልእክት ለሕዝቡ እንዲህ ሲል ተናገረ፤ "እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ" ይላል እግዚአብሔር።
14 ስለዚህ እግዚአብሔር የይሁዳን ገዥ፣ የሰላትያልን ልጅ የዘሩባቤልን መንፈስ፣ የሊቀ ካህናቱን የኢዮሴዴቅን ልጅ፣ የኢያሱን መንፈስና፣ ከምርኮ የተረፈውን ሕዝብ ሁሉ መንፈስ አነሣሣ፤ እነርሱም መጥተው የአምላካቸውን የእግዚአብሐር
ጸባኦት ቤት መሥራት ጀመሩ። 15 ይህ የሆነውም ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት፣ በስድስተኛው ወር፣ በሃያ አራተኛው ቀን ነበር።

### ቃል የተገባው የአዲሱ ቤት ክብር

2 በሰባተኛው ወር፣ በሃያ አንደኛ ቀን የእግዚአብሔር ቃል በነቢዩ በሐጌ በኩል እንዲህ ሲል መጣ፤ 2 "ለይሁዳ ገዥ ለሰላትያል ልጅ ለዘሩባቤል፣ ለሊቀ ካህናቱ ለኢዮሴዴቅ ልጅ ለኢያሱ፣ ከምርኮ ለተረፈውም ሕዝብ እንዲህ ብለህ ተናገር፤ እንዲህም ብለህ ጠይቃቸው፤ 3 'ይህን ቤት በቀድሞ ክብሩ ሳለ ያየ ከመካከላችሁ ማን አለ? አሁንስ ምን መስሎ ይታያችኋል? ይህ በፊታችሁ ምንም እንዳይደለ የሚቈጠር አይደለምን?
4 እግዚአብሔር ባኦት እንዲህ ይላል 'አሁን ግን ዘሩባቤል ሆይ፤ በርታ፤ የሊቀ ካህናቱ የኢዮሴዴቅ ልጅ ኢያሱ ሆይ፤ በርታ፤ እናንተም የምድሪቱ ሕዝብ ሁሉ በርቱ' ይላል እግዚአብሔር፤ 'እኔ ከእናንተ ጋር ነኝና ሥሩ' ይላል ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር፤ 5 'ከግብፅ በወጣችሁ ጊዜ የገባሁላችሁ ቃል ይህ ነው፤ መንፈሴም በመካከላችሁ ይሆናልና አትፍሩ።'

6 "ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ጸባኦት እንዲህ ይላል፤ 'በቅርብ ጊዜ እንደ ገና ሰማያትንና ምድርን፣ ባሕሩንና የብሱን አንድ ጊዜ አናውጣለሁ። 7 ሕዝቦችን ሁሉ አናውጣለሁ፤ የሕዝቦችም ሀብት ሁሉ ወደዚህ ይመጣል፤ ይህንም ቤት በክብር እሞላዋለሁ' ይላል ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር። 8 'ብሩ የእኔ ነው፤ ወርቁም የእኔ ነው' ይላል ሁሉን

[ሀ]1 የየሹዋ ተለዋጭ ስም ሲሆን በሐጌ መጽሐፍ ውስጥ በብዛት ይገኛል።

1፥1 1ዜና3፥19፤ 6፥15፤ዕዝ2፥2 3፥2፤4፥24፤5፥1፤5፥3፤ ነህ5፥14፤ዘካ3፥8፤ ማቴ1፥12-13
1፥2 ዕዝ1፥2፤ ኢሳ13፥14፤29፥13
1፥3 ዕዝ5፥1
1፥4 ቊ9፤2ሳሙ7፥2፤ ኤር33፥12
1፥5 ቊ7፤ሰቆ3፥40፤ ሐጌ2፥15፡18
1፥6 ዘሌ26፥20፤ ኢሳ5፥10፤9፥20፤ 55፥2፤አሞ4፥8፤ ሐጌ2፥16፤ዘካ8፥10
1፥7 ቊ5
1፥8 ዘፀ29፥43፤ 1ዜና14፥1፤ኢዮ22፥3፤ መዝ132፥13-14፤ ኤር13፥11
1፥9 ቊ4 ዘዳ28፥38፤ ነህ13፥11፤መዝ103፥16፤ ኢሳ5፥10፤ ሕዝ22፥21
1፥10 ዘፍ27፥28፤ ዘሌ26፥19፤ዘዳ28፥23፡24፤1ነገ17፥1
1፥11 ዘኊ18፥12፤ ዘዳ11፥26፤28፥22፡51፤ ሩት1፥1፤1ነገ17፥1፤ መዝ4፥7፤ኢሳ5፥6፤ 7፥25፤ሐጌ2፥17
1፥12 ቊ1፡14፤ዘዳ 31፥12፤ኢዮ36፥11፤ ኢሳ1፥2፡9፤ 50፥10፤ ሐጌ2፥2፤ ማቴ28፥20
1፥13 ቊ1፤ዘፍ26፥3፤ ዘኊ14፥9፤27፥21፤ 2ዜና36፥15፤ማቴ 28፥20፤ሮሜ8፥31
1፥14 ቊ12፤ 1ዜና6፥15፤ ዕዝ1፥15፡5፥2
1፥15 ቊ1፤ ዕዝ4፥24፤ሐጌ 2፥10፡20
2፥1 ቊ10፡20፤ ዘሌ23፥34፤ዕዝ5፥1፤ ዮሐ7፥37
2፥2 1ዜና6፥15፤ ሐጌ1፥1፡12
2፥3 ዕዝ3፥12፤ ኢሳ60፥7፤ዘካ4፥10
2፥4 ዘፀ33፥14፤ ዘኊ14፥9፤2ሳሙ5፥10፤ 1ዜና6፥15፤28፥20፤ ዘካ8፥9፤ሐሥ7፥9፤ ኤፌ6፥10
2፥5 ዘፍ6፥18፤ ኢዮ9፥6፤ኢሳ10፥25፤14፥16፤ሕዝ38፥19፤ ዕብ12፥26
2፥7 ዘፀ16፥7፤29፥43፤1ሳሙ9፥20፤ ኢሳ60፥7፤ሉቃ2፥32፤
2፥8 1ዜና29፥2፤

የሚገዛ *እግዚአብሔር* ጸባኦት፤ 9‘የዚህ የአሁኑ
ቤት ክብር ከቀድሞው ቤት ክብር ይበልጣል’
ይላል ሁሉን የሚገዛ *እግዚአብሔር* ጸባኦት፤
‘በዚህም ቦታ ሰላምን እሰጣለሁ’ ይላል
ሁሉን የሚገዛ *እግዚአብሔር* ጸባኦት።”

## ተግሣጽና በረከት

10ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት፣
በዘጠነኛው ወር፣ በሃያ አራተኛው ቀን
*የእግዚአብሔር* ቃል በነቢዩ በሐጌ በኩል
እንዲህ ሲል *መጣ*፤ 11“*እግዚአብሔር* ጸባኦት
እንዲህ ይላል፤ ‘ሕጉ ምን እንደሚል ካህ
ናቱን እንዲህ ብለህ ጠይቅ፤ 12አንድ ሰው
የተቀደሰውን *ሥጋ* በልብሱ ዕጥፋት ቢይዝ፣
ያም ዕጥፋት እንጀራ ወይም ወጥ፣ የወ
ይን ጠጅ ወይም ዘይት ወይም ሌላ ምግብ
ቢነካ የተቀደሰ ይሆናልን?”

ካህናቱም፣ “የተቀደሰ አይሆንም”
ብለው መለሱ።

13ሐጌም፣ “ሬሳ በመንካቱ የረከሰ ሰው፣
ከእነዚህ አንዱን ቢነካ፣ የተነካው ነገር ይረ
ክሳልን?” ሲል ጠየቀ።

ካህናቱም፣ “አዎን፣ ይረክሳል” ሲሉ
መለሱ።

14ከዚያም ሐጌ እንዲህ አለ፤ “ ‘ይህ ሕዝ
ብና ይህ ወገንም በፊቴ እንደዚሁ ነው’ ይላል
*እግዚአብሔር*፤ ‘የእጃቸው ሥራና የሚያቀ
ርቡት ሁሉ የረከሰ ነው’።

15 “ ‘እንግዲህ ከዛሬ ጀምራችሁ *በእግ
ዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ድንጋይ በድንጋይ
ላይ ከመነባበሩ በፊት የነበረውን ሁኔታ
አስተውሉ። 16አንድ ሰው ሃያ መስፈሪያ
ወደሚሆን የእህል ክምር በመጣ ጊዜ ዐሥር
ብቻ አገኘ፤ አምሳ ማድጋ የወይን ጠጅ
ለመቅዳት ወደ መጭመቂያው በሄደ ጊዜ
ሃያ ብቻ አገኘ፤ 17የእጃችሁን ሥራ ሁሉ
በዋግ፣ በአረማሞና በበረዶ መታሁት፤ እናንተ
ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም’ ይላል *እግዚ
አብሔር*፤ 18‘ከዚህ ቀን ጀምሮ፣ይኸውም
ከዘጠነኛው ወር ሃያ አራተኛ ቀን ጀምሮ
*የእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ መሠረት
እስከተጣለበት ቀን ድረስ ያለውን ዘመን
አስተውሉ፤ ልብ ብላችሁም አስቡ፤ 19በጐተራ
የቀረ ዘር አሁንም ይገኛልን? የወይኑና
የበለሱ ዛፍ፣ የሮማኑና የወይራው ዛፍ
እስካሁን አላፈሩም።

“ ‘ከዚህ ቀን ጀምሮ እባርካችኋለሁ፡’ ”

## እግዚአብሔር ለዘሩባቤል የሰጠው ተስፋ

20በወሩ ሃያ አራተኛ ቀን *የእግዚአ
ብሔር* ቃል ዳግመኛ እንዲህ ሲል ወደ ሐጌ
*መጣ*፤ 21“ለይሁዳ ገዥ ለዘሩባቤል ሰማ
ያትንና ምድርን እንደማናውጥ ንገረው፤
22የመንግሥታትን ዙፋን እገለብጣለሁ፤ የባዕ
ዳንን መንግሥታት ኀይል አጠፋለሁ፤ ሠረገ
ሎችንና ሠረገለኞችን እገለብጣለሁ፤ ፈረሶ
ችና ጋላቢዎቻቸውም በገዛ ወንድሞቻቸው
ሰይፍ ይወድቃሉ።

23“ ‘*እግዚአብሔር* ጸባኦት እንዲህ ይላል፤
‘በዚያን ቀን ባሪያዬ የሰላትያል ልጅ ዘሩ
ባቤል ሆይ፤ እኔ እወስድሃለሁ’ ይላል
*እግዚአብሔር*፤ ‘እንደ ማተሚያ ቀለበቴ
አደርግሃለሁ፤ እኔ መርጬአለሁና’ ይላል
*እግዚአብሔር ጸባኦት*።”

[a]15 ወይም *ላለፉት ቀናት* እንደ ማለት ነው።

15፥1፤ዘፀ29፥46፤
1ዜና28፥20፤
ዕዝ5፥2፤ነህ9፥20፤
ዘካ8፥13
2፥6 ዘፀ19፥18፤
2፥9 ዘሌ26፥6፤
ዕዝ3፥12፤
መዝ85፥9፤
ኢሳ11፥10፤60፥7፡17
2፥10 ቍ1፤ሐጌ1፥15
2፥11 ዘሌ10፥10-11፤
ዘዳ17፥8-11፤
33፥8፤ኤር18፥18
2፥12 ዘፍ7፥2፤
ዘሌ6፥27፤ኤር11፥15፤
ማቴ23፥19
2፥13 ዘሌ22፥4-6፤
ዘኍ19፥13
2፥14 መዝ51፥17፤
ኢሳ1፥13፤29፥13
2፥15 ዕዝ3፥10፤
4፥24፤ሐጌ1፥5
2፥16 ዘዳ28፥38፤
ሩት3፥7፤ኢዮ24፥11፤
ኢሳ5፥2፡ 10፤ሐጌ1፥6
2፥17 ዘፀ9፥18፤
ዘዳ28፥22፤መዝ78፥48፤
ኢሳ9፥13፤ኤር3፥10፤
አሞ4፥6፤ሐጌ1፥11
2፥18 ዕዝ3፥11፤
ሐጌ1፥5
2፥19 ዘፍ12፥2፤
ዘፀ28፥33፤
ዘሌ25፥21፤መዝ128፥1-6፤
ኢል1፥12፤2፥14
2፥20 ቍ1፤ዕዝ5፥1፤
ሐጌ1፥15
2፥21 ዕዝ5፥2፤
ኢሳ14፥16፤
ሕዝ38፥19-20
2፥22 ዘፍ19፥25፤
ዘፀ15፥21፤መሳ7፥22፤
ኢዮ2፥13፤
ሕዝ38፥21፤
ዳን2፥44፤ሚክ5፥10
2፥23 ዘፍ38፥18፤
ዘፀ28፥9፤ኢሳ2፥11፤
10፥20፤20፥3፤
ዳን9፥24-26፤ ዘካ4፥10፤
ማቴ1፥12፤2ቆሮ1፥22

# ትንቢተ ዘካርያስ

## ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ የቀረበ ጥሪ

1 ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት በስ
ምንተኛው ወር *የእግዚአብሔር* ቃል
ወደ አዶ ልጅ ወደ በራክዩ ልጅ ወደ ነቢዩ
ዘካርያስ እንዲህ ሲል *መጣ፤*
2 “*እግዚአብሔር* በአባቶቻችሁ ላይ እጅግ
ተቈጥቶ ነበር፤ 3 ስለዚህ ለሕዝቡ ንገር፤
*እግዚአብሔር* ጸባኦት እንዲህ ይላል፤ ‘ወደ
እኔ ተመለሱ’ ይላል *እግዚአብሔር* ጸባኦት፤
‘እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ፤’ ይላል፤
*እግዚአብሔር* ጸባኦት፤ 4 የቀደሙት ነቢያት፣
‘*እግዚአብሔር* ጸባኦት፣ “ከክፉ መንገዳ
ችሁና ከክፉ *ሥራችሁ* ተመለሱ” ይላል በማ
ለት ለአባቶቻችሁ ሰብከው ነበር፤ እነርሱ
ግን አልሰሙም፤ እኔንም አላደመጡም፤
እንደ እነርሱ አትሁኑ፤ ይላል *እግዚአብሔር*።
5 አባቶቻችሁ አሁን የት አሉ? ነቢያትስ
ለዘላለም በሕይወት ይኖራሉን? 6 ለባሪያዎቼ
ለነቢያት ያዘዝኋቸው ቃልና ሥርዐት
በአባቶቻችሁ ላይ አልደረሰምን?
“እነርሱም ንስሓ ገብተው፤ እንዲህ አሉ፤
‘*እግዚአብሔር* ጸባኦት በወሰነው መሠረት፣
ለሥራችንና ለመንገዳችን የሚገባውን አድ
ርጎብናል::’ ”

## በባርሰነት ዛፎች መካከል የቆመው ሰው

7 ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት፣ ሳባጥ
በሚባለው በዐሥራ አንደኛው ወር በሃያ
አራተኛው ቀን፣ *የእግዚአብሔር* ቃል ወደ
አዶ ልጅ ወደ በራክዩ ልጅ ወደ ነቢዩ
ዘካርያስ እንዲህ ሲል *መጣ፤*
8 በምሽት ራእይ አየሁ፤ እዚያም በፊቴ
አንድ ሰው በመጋላ ፈረስ ላይ ተቀምጦአል፤
እርሱም በሸለቆ ውስጥ በባርሰነት ዛፎች
መካከልም ቆሞ ነበር፤ ከበስተ ኋላውም
መጋላ፣ ሐመርና አንባላይ ፈረሶች ነበሩ::
9 እኔም፣ “ጌታዬ ሆይ፤ እነዚህ ምንድን
ናቸው?” አልሁ::
ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መልአክም፣
“እነዚህ ምን እንደ ሆኑ አሳይሃለሁ” አለኝ::
10 ከዚያም በባርሰነት ዛፎች መካከል የቆ
መው ሰው፣ “እነዚህ በምድር ሁሉ እንዲ
መላለሱ *እግዚአብሔር* የላካቸው ናቸው” ሲ
ል መለሰ። 11 እነርሱም በባርሰነት ዛፎች
መካ ከል ቆሞ ለነበረው *የእግዚአብሔር*
መልአክ፣ “በምድር ሁሉ ተመላለስን፤
መላዋ ምድ ርም ዐርፋ በሰላም
ተቀምጣለች” ብለው መለሱለት::
12 ከዚያም *የእግዚአብሔር* መልአክ፣
“*እግዚአብሔር* ጸባኦት ሆይ፤ በእነዚህ
ሰባ ዓመታት ውስጥ የተቈጣሃቸውን ኢየሩ
ሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች የማትምራ
ቸው እስከ መቼ ነው?” አለ:: 13 *እግዚአ
ብሔርም* ከእኔ ጋር ይነጋገር ለነበረው
መልአክ ደስ በሚያሰኝና በሚያጽናና ቃል
መለሰለት::
14 ከዚያም ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው
መልአክ እንዲህ አለኝ፤ “ይህን ቃል ተና
ገር፤ *እግዚአብሔር* ጸባኦት እንዲህ ይላል፤
‘ስለ ጽዮንና ስለ ኢየሩሳሌም እጅግ ቀንቻ
ለሁ፤ 15 ሰላም አለ በሚሉ አሕዛብ ላይ ግን
በጣም ተቈጥቻለሁ፤ በመጠኑ ተቈጥቼ ሳለሁ፣
እነርሱ ግን ጥፋቱ እንዲብስ አደረጉ::’
16 “ስለዚህ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
‘በምሕረት ወደ ኢየሩሳሌም እመለሳለሁ፤
በዚያም ቤቴ እንደ ገና ይሠራል፤ መለኪ
ያ ገመድም በኢየሩሳሌም ላይ ይዘረጋል’
ይላል *እግዚአብሔር* ጸባኦት::’
17 “ቀጥለህም እንዲህ እያልህ ስበክ፤
*እግዚአብሔር* ጸባኦት እንዲህ ይላል፤
‘ከተሞቼ እንደ ገና ብልጽግና ይትረፈረ
ፍባቸዋል፤ *እግዚአብሔርም* እንደ ገና ጽዮ
ንን ያጽናናል፤ ኢየሩሳሌምንም ይመር
ጣል::’”

## አራቱ ቀንዶችና አራቱ የእጅ ሙያተኞች

18 ከዚያም ወደ ላይ ተመለከትሁ፤ ከፊቴም
አራት ቀንዶችን አየሁ፤
19 ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረውንም መል
አክ፣ “እነዚህ ምንድን ናቸው?” አልሁት ::
እርሱም፣ “እነዚህ ይሁዳን፣ እስራኤልንና
ኢየሩሳሌምን የበታተኑ ቀንዶች ናቸው” አለኝ::
20 ከዚያም *እግዚአብሔር* አራት የእጅ
ሙያተኞችን አሳየኝ:: 21 እኔም፣ “እነዚህስ
ምን ሊያደርጉ መጡ?” አልሁ::
እርሱም፣ “እነዚህ ቀንዶች ማንም ራሱን
ቀና ማድረግ እንዳይችል ይሁዳን የበታ
ተኑ ናቸው፤ እነዚህ የእጅ ሙያተኞች ግን
የመጡት እነርሱን ሊያስደነግጧቸው፣ ሕዝ
ቡን ለመበታተን በይሁዳ ምድር ላይ ቀንዳ
ቸውን ያነሡትን የእነዚህን የአሕዛብ ቀን
ዶች ሰብሮ ለመጣል ነው” አለኝ::

1፡1 ቀኑ7፡ዕዝ4፡24፤ 5፡1፤6፡15፤ ነህ12፡4፤ማቴ23፡35፤ ሉቃ11፡51
1፡2 2ዜና36፡16
1፡3 ኢዮ22፡23፤ ሚል3፡7፤ያዕ4፡8
1፡4 2ነገ17፡13፤ 2ዜና፡24፡19፤ 36፡15፤መዝ78፡8፤ 106፡6፤ኤር6፡17፤ 17፡23፤23፡22፤ ሕዝ20፡18፤33፡4፤ ዘካ7፡7
1፡6 ዘዳ28፡2፤ ኢሳ44፡26፤ ኤር 12፡14-17፤23፡20፤ 39፡16፤44፡17፤ሰቆ 2፡17፤ዳን9፡12፤ ሆሴ5፡9
1፡7 ቀኑ1
1፡8 ዘካ6፡2-7፤ ራእ6፡4
1፡9 ዳን7፡16፤ ዘካ4፡14-5፤5፡5
1፡10 ዘካ6፡5-8
1፡11 ዘፍ16፡7፤ ኢሳ14፡7
1፡12 2ዜና 36፡21፤መዝ6፡3፤ 40፡11፤ኤር40፡5፤ ዳን9፡2
1፡13 ኢዮ15፡11፤ ኢሳ35፡4፤ዘካ4፡1
1፡14 ኢሳ26፡11፤ ኢል2፡18
1፡15 2ዜና28፡9፤ መዝ51፡18፤ ኢሳ14፡1፤40፡1፤54፡8- 10፤61፡4
1፡16 ዕዝ1፡1፤ ኢዮ38፡5፤ ዘካ2፡1-2፤8፡3
1፡17 ዕዝ9፡9፤ መዝ 51፡18፤ኢሳ14፡1፤ 40፡1፤54፡8-10፤61፡4
1፡19 አሞ6፡13
1፡21 1ነገ22፡11፤ መዝ75፡4፡10፤ኢሳ 54፡16-17፤ ዘካ12፡9

## የመለኪያ ገመድ የያዘ ሰው

2 ደግሞም ወደ ላይ ተመለከትሁ፤
እነሆ፤ በእጁ የመለኪያ ገመድ የያዘ
ሰውም በፊቴ አየሁ፤ 2እኔም፣ “የት ልት
ሄድ ነው?” አልሁት።

እርሱም፣ “የኢየሩሳሌም ርዝመትና
ስፋት ምን ያህል እንደ ሆነ ለመለካት
መሄዴ ነው” አለኝ።

3ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መልአ
ክም ሄደ፤ ሌላም መልአክ ሊገናኘው
መጣ፤ 4እንዲህም አለው፣ “ሩጥና ለዚያ
ጕልማሳ እንዲህ ብለህ ንገረው፤ ‘በውስ
ካለው የሰውና የከብት ብዛት የተነሣ፣ ኢየሩ
ሳሌም ቅጥር እንደሌላት ከተማ ትሆና
ለች፤ 5እኔ ራሴ በዙሪያዋ የእሳት ቅጥር
እሆንላታለሁ፤ ይላል *እግዚአብሔር* ‘በውስ
ጧም ክብሯ እሆናለሁ።’

6“ኑ! ኑ! ውጡ ከሰሜን ምድር አም
ልጡ” ይላል *እግዚአብሔር*፤ “ለአራቱ የሰ
ማይ ነፋሳት በትኛችኋለሁና፤” ይላል *እግ
ዚአብሔር*።

7“አንቺ ጽዮን ነዪ፤ ከባቢሎን ሴት ልጅ
ጋር የምትኖሪ ሆይ፤ ኰብልዪ።” 8*እግዚ
አብሔር* ጸባኦት እንዲህ ይላልና፤ “ካከበ
ረኝና በዘረፉአችሁ አሕዛብ ላይ ከላከኝ
በኋላ፣ የሚነካችሁ የዐይኑን ብሌን ይነ
ካል፤ 9እነሆ፤ እጄን በእነርሱ ላይ አነሣ
ለሁ፤ ባሪያዎቻቸውም ይዘርፏቸዋል፤ ከዚ
ያም *እግዚአብሔር* ጸባኦት እኔን እንደ
ላከኝ ታውቃላችሁ።

10“የጽዮን ልጅ ሆይ፤ እልል በዪ፤
ደስም ይበልሽ፤ እኔ እመጣለሁና፤ በመካ
ከልሽም እኖራለሁ” ይላል እግዚአብሔር።
11“በዚያ ቀን ብዙ አሕዛብ ወደ *እግዚአ
ብሔር* ይጠጋሉ፤ የእኔም ሕዝብ ይሆ
ናሉ። በመካከልሽ እኖራለሁ፤ *እግዚአ
ብሔር* ጸባኦት ወደ አንቺ እንደ ላከኝም
ታውቃላችሁ። 12*እግዚአብሔርም* በተቀ
ደሰችው ምድር ይሁዳን ርስቱ አድርጎ
ይወርሳል፤ ኢየሩሳሌምንም እንደ ገና ይመ
ርጣል። 13*እግዚአብሔር* ከተቀደሰ ማደ
ሪያው ተነሥቶአልና፣ ሥጋ ለባሽ ሁሉ
ሆይ፤ በፊቱ ጸጥ በል።

## ለሊቀ ካህኑ የሚሆን ንጹሕ ልብስ

3 እርሱም ሊቀ ካህኑን ኢያሱን[ሀ] *በእግዚ
አብሔር* መልአክ ፊት ቆሞ፣ ሰይጣ
ንም[ሐ] ሊከሰው በስተ ቀኙ ቆሞ አሳየኝ።
2*እግዚአብሔርም* ሰይጣንን፣ “አንተ ሰይጣን፤
*እግዚአብሔር* ይገሥጽህ፤ ኢየሩሳሌምን የመ
ረጠ *እግዚአብሔር* ይገሥጽህ፤ ይህ ሰው ከእ
ሳት የተነጠቀ ትንታግ አይደለምን?” አለው።
3ኢያሱም ያደፈ ልብስ ለብሶ በመልአኩ
ፊት ቆሞ ነበር። 4መልአኩም ከፊቱ ቆመው
የነበሩትን፣ “ያደፉ ልብሶቹን አውልቁለት”
አላቸው።

ኢያሱንም፣ “እነሆ፤ ኀጢአትህን ከአንተ
አስወግጃለሁ፤ ጥሩ ልብስም አለብስሃለሁ”
አለው።

5እኔም፣ “ንጹሕ ጥምጥም በራሱ ላይ አድር
ጉለት” አልሁ። *የእግዚአብሔርም* መልአክ
በአጠገቡ ቆሞ እያለ፣ ንጹሕ ጥምጥም በራ
ሱ ላይ አደረጉለት፤ ልብስም አለበሱት።

6*የእግዚአብሔርም* መልአክ ለኢያሱ ይህን
ማስጠንቀቂያ ሰጠው፤ 7“*እግዚአብሔር* ጸባኦት
እንዲህ ይላል፤ ‘በመንገዴ ብትሄድ፣ ትእዛ
ዜንም ብትጠብቅ፣ ቤቴን ታስተዳድራለህ፤
በአደባባዮቼም ላይ ኀላፊ ትሆናለህ፤ በዚህ
በቆሙት መካከል ቦታ እሰጥሃለሁ።

8“ ‘ሊቀ ካህኑ ኢያሱ ሆይ፤ ስማ፤ በፊትህ
የሚቀመጡትም ረዳቶችህ ገና ወደ ፊት
ለሚመጡት ምልክት የሚሆኑ ሰዎች ናቸ
ውና ይስሙ፤ እነሆ፤ ባሪያዬን ቊጥቋጡን
አመጣለሁ። 9በኢያሱ ፊት ያስቀመጥሁት
ድንጋይ እነሆ! በዚያ በአንዱ ድንጋይ ላይ
ሰባት ዐይኖች[መ] አሉ፤ በእርሱም ላይ ቅርጽ
እቀርጻለሁ፤ የዚህችንም ምድር በደል በአ
ንድ ቀን አስወግዳለሁ፤’ ይላል *እግዚአብሔር*
ጸባኦት።

10“ ‘በዚያን ቀን እያንዳንዱ በገዛ ወይኑና
በለሱ ሥር ሆኖ ባልንጀራውን ይጋብዛል፤’
” ይላል *እግዚአብሔር* ጸባኦት።

## የወርቁ መቅረዝና ሁለቱ የወይራ ዛፎች

4 ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መልአ
ክም ተመልሶ፣ አንድ ሰው ከእንቅልፉ
እንደሚነቃ አነቃኝ፤ 2እርሱም፣ “ምን ታያለህ?”
አለኝ።

እኔም እንዲህ አልሁ፤ “እነሆ፤ በዐናቱ
ላይ የዘይት ማሰሮ ያለበት ሁለንተናው
ወርቅ የሆነ መቅረዝ አየሁ፤ በመቅረዙም
ላይ ሰባት ቧንቧዎች ያሏቸው ሰባት መብ
ራቶች ነበሩ። 3ደግሞም አንዱ ከዘይቱ ማሰሮ
በስተ ቀኝ፣ ሌላውም በስተ ግራ የሆኑ ሁለት
የወይራ ዛፎች አሉ።”

4ያነጋገረኝ የነበረውንም መልአክ፣
“ጌታዬ ሆይ፤ እነዚህ ምንድንናቸው”
አልሁት።

5እርሱም፣ “ምን እንደ ሆኑ አታው
ቅምን?” አለኝ።

2፥2 ሕዝ40፥3፤ዘካ 1፥16፤ራእ21፥15
2፥4 ኢሳ49፥20፤ ኤር30፥19፤33፥22፤ ሕዝ38፥11፤ዘካ14፥11
2፥5 መዝ46፥5፤ 85፥9፤125፥2፤ኢሳ 10፥17፤11፥10፤ 24፥23፤26፥1፤ሕዝ 38፥14፤42፥20፤ ራእ21፥23
2፥6 መዝ44፥11፤ ሕዝ17፥21፤37፥9፤ ማቴ24፥31፤ማር 13፥27
2፥7 ኢሳ42፥7፤ 48፥20፤ኤር3፥18
2፥8 ዘዳ32፥10
2፥9 ኢሳ14፥2፤ 48፥16፤ኤር12፥14፤ ዕን2፥8፤ዘካ4፥9፤ 6፥15
2፥10 ዘፀ25፥8፤ ዘሌ26፥12፤ዘኍ 23፥21፤ኢሳ23፥12፤ ሶፎ3፥14፤ዘካ8፥3፤ 9፥9፤ራእ21፥3
2፥11 ኤር24፥7፤ ሚክ4፥2፤ዘካ4፥9፤ 6፥15፤8፥8፤20-22
2፥12 ዘፀ34፥9፤ዘዳ 12፥5፤መዝ33፥12፤ ኢ ሳ14፥1፤ኤር10፥16፤ 40፥5
2፥13 ዘፀ14፥14፤ ዘዳ26፥15፤ኢሳ41፥1
3፥1 2ሳሙ24፥1፤ 2ዜና18፥21፤ዕዝ2፥2፤ መዝ109፥6፤ዘካ6፥11፤ ማቴ4፥10
3፥2 ኢሳ7፥4፤ 14፥1፤ይሁ1፥9፥23
3፥4 ዘፍ41፥42፤ 2ሳሙ12፥13፤መዝ 132፥9፤ኢሳ52፥1፤ ሕዝ36፥25፤ሚክ 7፥18፤ራእ19፥8
3፥5 ዘፀ29፥6
3፥7 ዘሌ8፥35፤ ዘዳ17፥8-11፤2ዜና 23፥6፤ኤር15፥19፤ ሕዝ44፥15-16፤ዘካ 6፥15
3፥8 ዘዳ28፥46፤ ኢሳ4፥2፤49፥3፤ ሕዝ12፥11፤17፥22፤ ሐጌ1፥1
3፥9 2ሳሙ12፥13፤ 2ዜና16፥9፤ዕዝ2፥2፤ ኢሳ28፥16፤ኤር 50፥20
3፥10 ዘኍ 16፥14፤ 1ነገ4፥25፤ ኢዮ11፥18፤ሚክ4፥4
4፥1 ኤር31፥26፤ ዳን8፥18
4፥2 ዘፀ25፥31፤ ኤር1፥13፤ራእ 1፥12፤ 4፥5
4፥3 ቊ11፤ መዝ1፥3፤ራእ11፥4
4፥5 ዘካ1፥9
4፥6 1ሳሙ2፥9፤

[ሀ]1 *የየሽዋ* ለሚለው ተለዋጭ ስም ነው፤ እዚህ ላይ እንዲሁም በዘካርያስ መጽሐፍ በሌሎች ቦታ።
[ሐ]1 *ሰይጣንም* ትርጒሙ “ከሳሽ” ማለት ነው።
[መ]9 ወይም *ገጽች*

እኔም፣ “ጌታዬ ሆይ፤ አላውቅም” አልሁት።
6ከዚያም እንዲህ አለኝ፤ “ለዘሩባቤል የተላ
ከው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው፤ ‘በመን
ፈሴ እንጂ በኀይልና በብርታት አይደለም’
ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት።
7“ታላቅ ተራራ ሆይ፤ አንተ ምንድን
ነህ?[ሠ] በዘሩባቤል ፊት ደልዳላ ሜዳ
ትሆናለህ፤ ሰዎች፣ ‘ሞገስ ይሁንለት!
ሞገስ ይሁንለት!’ ብለው እየጮኹ፣
እርሱ መደምደሚያውን ድንጋይ
ያወጣል።”
8ደግሞም የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ
እንዲህ ሲል መጣ፤ 9“የዘሩባቤል እጆች የዚ
ህን ቤተ መቅደስ መሠረት ጣሉ፤ የሚፈ
ጽሙትም የእርሱ እጆች ናቸው። ከዚያም
እግዚአብሔር ጸባኦት እኔን ወደ እናንተ
እንደ ላከኝ ታውቃላችሁ።
10“የጥቂቱን ነገር ቀን የናቀ ማን ነው?
ሰዎች በዘሩባቤል እጅ ቱንቢውን ሲያዩ
ይደሰታሉ።
“እነዚህ ሰባቱ በምድር ሁሉ የሚዘዋ
ወሩ የእግዚአብሔር ዐይኖች ናቸው።”
11ከዚያም መልአኩን፣ “ከመቅረዙ በስተ
ቀኝና በስተ ግራ ያሉት እነዚህ ሁለት የወ
ይራ ዛፎች ምንድን ናቸው?” አልሁት።
12እንደ ገናም፣ “በሁለቱ የወርቅ ቧንቧ
ዎች አጠገብ የወርቅ ዘይት የሚያፈሱት
እነዚህ ሁለት የወይራ ቅርንጫፎች ምን
ድን ናቸው?” አልሁት።
13እርሱም፣ “ምን እንደ ሆኑ አታውቅ
ምን?” አለኝ።
እኔም፣ “ጌታዬ ሆይ፤ አላውቅም” አል
ሁት።
14እርሱም፣ “እነዚህ ሁለቱ የምድርን ሁሉ
ጌታ ለማገልገል የተቀቡ[ረ] ናቸው” አለኝ።

### በራሪው የመጽሐፍ ጥቅልል

5 እንደ ገናም ተመለከትሁ፤ በዚያም በፊቴ
በራሪ የመጽሐፍ ጥቅልል አየሁ።
2እርሱም፣ “ምን ታያለህ?” ሲል ጠየ
ቀኝ። እኔም፣ “ርዝመቱ ሃያ ክንድ፣ ወርዱ[ሰ]
ዐሥር ክንድ የሆነ በራሪ የመጽሐፍ ጥቅ
ልል አያለሁ” አልሁት። 3እርሱም እንዲህ
አለኝ፤ “ይህ በምድር ሁሉ ላይ የሚወጣ
ርግማን ነው፤ በአንደኛው በኩል እንደ
ተጻፈው የሚሰርቅ ሁሉ ይጠፋል፤ በሌላው
በኩል ደግሞ እንደ ተጻፈው በሐሰት
የሚምል ሁሉ ይጠፋልና። 4እግዚአብሔር
ጸባኦት ‘እኔ ርግማኑን አመጣዋለሁ፤
እርሱም ወደ ሌባው ቤትና በስሜ በሐሰት
ወደሚምለው ሰው ቤት ይገባል፤ በዚያም
ይቀመጣል፤ ቤቱን፣ እንጨቱንና ድንጋዩን

13፥22፤1ነገ19፥2፤
1ዜና3፥19፤ዕዝ5፥2፤
ነህ9፥20፤ኢሳ11፥2-4፤
ዳን2፥34፤ሆሴ1፥7
4፥7 1ዜና15፥28፤
መዝ26፥12፤
118፥22፤ኤር51፥25
4፥9 ዕዝ3፥8፡11፤
6፥15፤ዘካ2፥9፤6፥12
4፥10 2ዜና16፥9፤
ዕዝ5፥1፤ ነህ12፥1፤
ኢዮ38፥5፤ሐጌ2፥3፡
23፤ራእ5፥6
4፥11 ቍ3፤
ራእ11፥4
4፥14 ዘፀ29፥7፤
40፥15፤መዝ45፥7፤
ኢሳ20፥3፤
ዳን9፥24-26
5፥1 መዝ40፥7፤
ኤር36፥4፤ራእ5፥1
5፥2 ኤር1፥13
5፥3 ዘፀ20፥7፡15፤
ኢሳ24፥6፤
34፥2፤43፥28፤
48፥1፤ሚል3፥8፡
9፤4፥6
5፥4 ዘሌ14፥34-
45፤ምሳ3፥33፤
ዕን2፥9-11፤
ዘካ8፥17፤ሚል3፥5
5፥6 ሚክ6፥10
5፥8 ሚክ6፥11
5፥9 ዘሌ11፥19
5፥11 ዘፍ10፥10፤
ኤር29፥5፡28፤
ዳን1፥2
6፥1 ቍ5፤ 2ነገ2፥11
6፥2 ራእ6፥5
6፥3 ራእ6፥2
6፥5 ኢሱ3፥11፤
ሕዝ37፥9፤ማቴ
24፥31፤ራእ7፥1

ያጠፋል ይላል።”

### በቅርጫት ውስጥ ያለች ሴት

5ከዚያም ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው
መል አክ ወደ እኔ መጥቶ፣ “ወደ ላይ
ተመልከት፤ ይህ የሚመጣው ምን እንደ ሆነ
እይ” አለኝ።
6እኔም፣ “ምንድን ነው?” አልሁት።
እርሱም፣ “የኢፍ መስፈሪያ[ሸ] ነው” አለኝ።
ቀጥሎም “ይህ በምድሪቱ ሁሉ ላይ ያለው
የሕዝቡ በደል[ቀ] ነው” አለኝ።
7ከዚያም ከእርሳስ የተሠራው ክዳን
ተነሣ፤ የኢፍ መስፈሪያ ውስጥ አንዲት ሴት
ተቀምጣ ነበር። 8እርሱም፣ “ይህች ርኵሰት
ናት” ብሎ ወደ ኢፍ መስፈሪያ መልሶ አስ
ገባት፤ የእርሳሱንም ክዳን ወደ ቅርጫቱ
አፍ ገፍቶ ገጠመው።
9ከዚያም ወደ ላይ ተመለከትሁ፤ እነ
ሆም፣ ከፊቴ ሁለት ሴቶች ነበሩ፤ በክን
ፎቻቸውም ነፋስ ነበር፤ ክንፎቻቸውም
እንደ ሽመላ ክንፎች ነበሩ፤ የኢፍ መስ
ፈሪያውንም በምድርና በሰማይ መካከል
አነሡት።
10ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረውንም መል
አክ፣ “ቅርጫቱን የሚወስዱት ወዴት
ነው?” አልሁት።
11እርሱም፣ “ቤት ሊሠሩለት ወደ ባቢ
ሎን[በ] ምድር ይወስዱታል፤ በተዘጋጀም ጊዜ
ወስደው በቦታው ያስቀምጡታል” አለኝ።

### አራቱ ሠረገሎች

6 እንደ ገናም ወደ ላይ ተመለከትሁ፤
እነሆ አራት ሠረገሎች ከሁለት ተራራ
መካከል ሲወጡ አየሁ፤ ተራሮቹም የናስ
ተራሮች ነበሩ። 2የመጀመሪያው ሠረገላ
መጋላ፣ ሁለተኛው ዱሪ፤ 3ሦስተኛው አም
ባላይ፤ አራተኛውም ዥጕርጕር ፈረሶች
ነበሯቸው፤ ሁሉም ጠንካሮች ነበሩ። 4እኔም
ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረውን መልአክ፣
“ጌታዬ ሆይ፤ እነዚህ ምንድን ናቸው?”
አልሁት።
5መልአኩም እንዲህ አለኝ፤ “እነዚህ አራቱ
ቆመው ከነበሩበት ከምድር ሁሉ ጌታ
ፊት የወጡ የሰማይ መናፍስት[ተ] ናቸው።
6የባለ ዱሪ ፈረሶች ወደ ሰሜን፤ የባለ
አምባላይ ፈረሶች ወደ ምዕራብ[ቸ] አገር፣

[ሠ]7 ወይም *ማለት ነህ*
[ረ]14 ወይም *እና ሁለቱ ዘይትና የሚያመጡ*
[ሰ]2 ዕብራይስጡ፣ርዝመቱ ሃያ ክንድ፣ ወርዱ 10ክንድ ወይም ርዝማኔው ዘጠኝ ሜትር፣ ስፋቱ አራት ተኩል ሜትር ይሆናል
[ሸ]6 ከቍ7-11 ካለው ጭምር፣ የእህል መስፈሪያ ወይም ቍና ማለት ነው።
[ቀ]6 ወይም *መምሰል* ማለት ሊሆን ይችላል።
[በ]11 ዕብራይስጡ *ሺናር* ይለዋል።
[ተ]5 ወይም *ነፋሳት* ሊሆን ይችላል።
[ቸ]6 ወይም ከኋላቸው *ፈረሶች* እንደማለት ነው።

የባለ ዥጉርጉር ፈረሶች ወደ ደቡብ አገር
ይወጣል።” 7ጠንካሮቹ ፈረሶች ሲወጡ፣
በምድር ሁሉ ለመመላለስ አቈብቍበው
ነበር። እርሱም፣ “ወደ ምድር ሁሉ ሂዱ”
አላቸው፤ እነርሱም ወደ ምድር ሁሉ ሄዱ።
8ከዚያም ጮኾ እንዲህ አለኝ፤ “እነሆ፤ ወደ
ሰሜን አገር የሚወጡት፣ መንፈሴን በሰሜን
ምድር አሳርፈውታል።”

## ለኢያሱ የተደረገለት አክሊል

9*የእግዚአብሔር* ቃል እንዲህ ሲል
ወደ እኔ መጣ፤ 10“ከባቢሎን ከመጡት ምር
ኮኞች ከሔልዳይና ከጦቢያ ከዮዳኤም ወርቅና
ብር ውሰድ፤ በዚያው ቀን ወደ ሶፎንያስ ልጅ
ወደ ኢዮስያስ ቤት ሂድ። 11ወርቁንና ብሩ
ን ወስደህ አክሊል ሥራ፤ በኢዮሴዴቅ ልጅ
በሊቀ ካህኑ በኢያሱ ራስ ላይም አድርገው፤
12ለእርሱም *እግዚአብሔር* ጸባኦት እንዲህ
ይላል ብለህ ንገረው፤ ‘እነሆ፤ ስሙ ቅርን
ጫፍ የተባለው ሰው ይህ ነው፤ እርሱም
በቦታው ይንሰራፋል፤ *የእግዚአብሔርንም*
ቤተ መቅደስ ይሠራል። 13*የእግዚአብሔ
ርን* ቤተ መቅደስ የሚሠራው እርሱ ነው፤
ክብርን ይግጻናጸፋል፤ በዙፋኑ ተቀምጦ
ይገ ዛል፤ በዙፋኑም ላይ ካህን ይሆናል፤
በሁለ ቱም መካከል ስምምነት ይኖራል።
14አክሊሉም ለሔሌምና[ነ] ለጦቢያ፣ ለዮዳኤና
ለሶፎ ንያስ ልጅ ለሔን[ኘ] *በእግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስ ውስጥ መታሰቢያ ይሆናል። 15እነ
ዚያ በሩቅ ያሉት መጥተው የእግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ ሲሠራ ያግዛሉ፤ እናንተም
*እግዚአብሔር* ጸባኦት እንደ ላከኝ ታውቃ
ላችሁ። ለአምላካችሁ *ለእግዚአብሔር*
በጥንቃቄ ብትታዘዙ ይህ ይሆናል።”

## ፍትሕና ምሕረት የተወደደ ነው

7 ዳርዮስ በነገሠ በአራተኛው ዓመት፣
ካሴሉ በተባለው በዘጠነኛው ወር፣ በአ
ራተኛው ቀን *የእግዚአብሔር* ቃል ወደ
ዘካርያስ እንዲህ ሲል መጣ፤ 2የቤቴል ሰዎች
*እግዚአብሔርን* ለመለመን ሳራሳርንና ሬጌሜ
ሌክን አብረዋቸው ከነበሩት ሰዎች ጋር
ላኩ፤ 3እነርሱም *የእግዚአብሔር* ጸባኦት
ቤት ካህናትና ነቢያት፣ “ብዙ ዓመት እንዳ
ደረግሁት፣ በአምስተኛው ወር ማዘንና መጾም
ይገባኛልን?” ብለው ጠየቁ።
4ከዚያም *የእግዚአብሔር* ጸባኦት ቃል
እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፤ 5“የምድሩን ሕዝብ
ሁሉና ካህናቱን እንዲህ በላቸው፤ ‘ባለፉት
ሰባ ዓመታት በአምስተኛውና በሰባተኛው
ወር የጾማችሁትና ያዘናችሁት በእርግጥ
ለእኔ ነበርን? 6ትበሉና ትጠጡ የነበረውስ
ለራሳችሁ አይደለምን? 7ኢየሩሳሌምና በዙ
ሪያዋ ያሉ ከተሞች በሰላምና በብልጽግና
ላይ ሳሉ፣ የደቡብና የምዕራብ ኰረብቶች
ግርጌ የሰው መኖሪያም በነበሩበት ጊዜ፣
*እግዚአብሔር* በቀደሙት ነቢያት የተናገ
ረው ቃል ይህ አልነበረምን?’ ”
8*የእግዚአብሔር* ቃል እንደ ገና ወደ
ዘካር ያስ እንዲህ ሲል መጣ፤ 9“*እግዚአብሐ
ር* ጸባኦት እንዲህ ይላል፤ ‘እውነተኛ ፍትሕ
አስ ፍኑ፣ እርስ በርሳችሁ ምሕረትና ርኅ
ራኄን አድርጉ፤ 10*መበለቲቱን* ወይም
ድኻ አደ ጉን፣ *መጻተኛውን* ወይም
ድኻውን አታስ ጨንቁ፤ በልባችሁም
አንዳችሁ በአንዳችሁ ላይ ክፉ አታስቡ።’
11“እነርሱ ግን መስማት አልፈለጉም፤
በእልኸኝነት ጀርባቸውን አዞሩ፤ ጆሮአቸ
ውንም ደፈኑ። 12ልባቸውን እንደ ባል
ጩት አጠነከሩ፤ *እግዚአብሔር* ጸባኦት
በቀደሙት ነቢያት በኩል በመንፈሱ የላ
ከውን ቃል ወይም ሕግ አልሰሙም፤ ስለ
ዚህ *እግዚአብሔር* ጸባኦት እጅግ ተቈጣ።
13“ ‘ስጠራቸው አልሰሙም፤ ስለዚህ ሲጠ
ሩኝ አልሰማም’ ይላል *እግዚአብሔር* ጸባ
ኦት። 14በማያውቋቸው በባዕዳን አሕዛብ
መካከል በዐውሎ ነፋስ በተንኳቸው፤ ከእ
ነርሱ በኋላ ማንም እስከማይመጣባትና
እስከማይሄድባት ድረስ ምድሪቱ ባድማ
ሆነች፤ መልካሚቱን ምድር ባድማ
ያደረጓት በዚህ ሁኔታ ነው።’ ”

## *እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ለመባረክ ቃል ገባ*

8 እንደ ገናም *የእግዚአብሔር* ጸባኦት
ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፤
2*እግዚአብሔር* ጸባኦት እንዲህ ይላል፤
“ስለ ጽዮን እጅግ ቀንቻለሁ፤ ስለ እርታም
በቅናት ነድጃለሁ።
3*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ “ወደ
ጽዮን እመለሳለሁ፤ በኢየሩሳሌም እኖራ
ለሁ፤ ኢየሩሳሌምም የእውነት ከተማ ትባ
ላለች፤ *የእግዚአብሔር* ጸባኦት ተራራም
ቅዱስ ተራራ ይባላል።”
4እግዚአብሔር ጸባኦት እንዲህ ይላል፤
“ሽማግሌዎችና አሮጊቶች እንደ ገና በኢ
የሩሳሌም አደባባይ ይቀመጣሉ፤ እያንዳን
ዳቸውም ከዕድሜአቸው ብዛት የተነሣ
ምርኵዝ ይይዛሉ። 5የከተማዪቱም አደባ
ባዮች እዚያ በሚጫወቱ ወንዶችና ሴቶች
ልጆች ይሞላሉ።” 6*እግዚአብሔር* ጸባኦት
እንዲህ ይላል፤ “በዚያን ጊዜ ይህ ለቀረው

[ነ]14 ሲርያክ፤ ዕብራይስጡ ሂሊም ይላል።
[ኘ]14 ወይም *ርኅሩኁ* እንደማለት ነው።

6፥7 ኢሳ43፥6፤ ዘካ1፥8
6፥8 ሕዝ5፥13፤ 24፥13፤ዘካ1፥10
6፥10 ዕዝ7፥14-16፤ ኤር28፥6
6፥11 1ዜና 6፥15፤ዕዝ2፥2፤3፥2፤ መዝ21፥3፤ዘካ3፥1
6፥12 ዕዝ3፥8-10፤ ኢሳ4፥2፤ሕዝ17፥22፤ ዘካ4፥6፥9
6፥13 መዝ110፥4
6፥14 ዘፀ28፥12
6፥15 ኢሳ58፥12፤ 60፥10፤ኤር7፥23፤ዘካ2፥9-11፤3፥7
7፥1 ዕዝ5፥1፤ ነህ1፥1
7፥2 ኤር26፥19፤ ሐጌ2፥10-14፤ ዘካ8፥21
7፥3 2ነገ25፥9፤ ኤር52፥12-14፤ ዘካ12፥12-14
7፥5 2ነገ25፥25፤ ኢሳ58፥5፤ዳን9፥2
7፥6 ኢሳ43፥23
7፥7 ኢሳ1፥11-20፤ ኤር17፥26፤22፥21፤ 44ም4-5፤ዘካ1፥4
7፥9 ዘዳ22፥1፤ ኤር22፥3፤42፥5፤ ዘካ8፥16
7፥10 ዘፀ22፥21፡ 22፤ዘሌ25፥17፤ ኢዮ35፥8፤ ኢሳ1፥17፡23
7፥11 ኢሳ9፥9፤ ኤር5፥3፤8፥5፤11፥10፤ 17፥23፤32፥33፤ ሕዝ5፥6
7፥12 ነህ9፥29፤ ኤር5፥3፤17፥1፤ 42፥21፤ሕዝ11፥19፤ ዳን9፥12
7፥13 ምሳ1፥28፤ ኢሳ1፥15፤ኤር7፥27፤ ኤር11፥11፥14፥12፤ ሰቆ3፥44፤ሕዝ20፥31፤ ሚክ3፥4
7፥14 ዘሌ26፥33፤ ዘዳ4፥27፤28፥64-67፤መዝ44፥11፤ ኢሳ33፥8፤ኤር 7፥34፤23፥19፤ 44፥6፤ሕዝ 12፥19
8፥2 ኢል2፥18
8፥3 መዝ15፥2፤ ኢሳ1፥26፤48፥1፤ 52፥8፤ኤር26፥18፤ 33፥16፤ኢል3፥21፤ ዘካ1፥16፤2፥10፤ ሚክ4፥1
8፥4 ኢሳ65፥20
8፥5 ኤር30፥20፤ 31፥13
8፥6 መዝ 128፥23፤126፥1-3፤ ኤር32፥17፡27

የእስራኤል ሕዝብ አስደናቂ መስሎ ሊታይ
ችላል፤ ለእኔ ግን አስደናቂ ሊሆን ይችላ
ልን?” ይላል *እግዚአብሔር* ጸባኦት።
[7]*እግዚአብሔር* ጸባኦት እንዲህ ይላል፤ “ሕዝ
ቤን ከምሥራቅና ከምዕራብ አገር እታደጋ
ለሁ። [8]በኢየሩሳሌም እንዲኖሩ መልሼ አመ
ጣቸዋለሁ፤ እነርሱ ሕዝቤ ይሆናሉ፤ እኔም
በጽድቅና በታማኝነት አምላካቸው
እሆናለሁ።”
[9]*እግዚአብሔር* ጸባኦት እንዲህ ይላል፤
“*የእግዚአብሔር* ጸባኦት ቤት መሠረት ሲጣል፣
በዚያ የነበሩ ነቢያት የተናገሩትን ቃል
አሁን የምትሰሙ ሁሉ *የእግዚአብሔርን*
ቤተ መቅደስ ለመሥራት እጃችሁን አበ
ርቱ። [10]ከዚያ በፊት ለሰው ደመወዝ፣ ለእ
ንስሳም ኪራይ አይከፈልም ነበር፤ ጠላት
በመኖሩም ማንም ሥራውን በሰላም ማከና
ወን አልቻለም፤ እያንዳንዱ ሰው በባል
ንጀራው ላይ እንዲነሣ አድርጌ ነበርና።
[11]አሁን ግን ቀድሞ እንዳደረግሁት በዚህ
በቀረው ሕዝብ ላይ አላደርግም” ይላል *እግ
ዚአብሔር* ጸባኦት።
[12]“ዘሩ ጥሩ ሆኖ ይበቅላል፤ ወይኑ
ፍሬውን ያፈራል፤ ምድሪቱ አዝመራዋን
ታበረክታለች፤ ሰማያትም ጠላቸውን ይሰጣሉ፤
እነዚህን ሁሉ ነገሮች ለቀሪው ሕዝብ
ርስት አድርጌ እሰጣለሁ። [13]የይሁዳ ቤትና
የእስራኤል ቤት ሆይ፤ በአሕዛብ መካከል
የርግማን ምሳሌ ነበራችሁ፤ አሁን ግን
አድናችኋለሁ፤ እናንተም በረከት ትሆናላ
ችሁ። አትፍሩ፤ ነገር ግን እጃችሁን አበ
ርቱ።”
[14]*እግዚአብሔር* ጸባኦት እንዲህ ይላል፤
“አባቶቻችሁ ባስቈጡኝ ጊዜ ያላንዳች ሐዘ
ኔታ ጥፋት ላመጣባችሁ እንደ ወሰንሁ፣”
ይላል *እግዚአብሔር* ጸባኦት፤ [15]“አሁን ደግሞ
ለኢየሩሳሌምና ለይሁዳ መልካም ነገርን
ላደርግ ወስኛለሁ፤ አትፍሩ። [16]ልታደርጓ
ቸው የሚገባችሁ ነገሮች እነዚህ ናቸው፤
እርስ በርሳችሁ እውነትን ተነጋገሩ፤ በአደ
ባባያችሁም እውነትንና ትክክለኛ ፍርድን
አስፍኑ፤ [17]በባልንጀራችሁ ላይ ክፉትን
በልባችሁ አታውጠንጥኑ፤ በሐሰት መማ
ልን አትውደዱ፤ እነዚህን ሁሉ እጸየፋለሁ”
ይላል *እግዚአብሔር*። [18]እንደ ገናም *የእግ
ዚአብሔር* ጸባኦት ቃል እንዲህ ሲል ወደ
እኔ መጣ፤ [19]*እግዚአብሔር* ጸባኦት እንዲህ
ይላል፤ “የአራተኛው፣ የአምስተኛው፣ የሰ
ባተኛውና የዐሥረኛው ወር ጾሞች ለይ
ሁዳ ቤት የደስታ፣ የተድላና የሐሤት በዓ
ላት ይሆናሉ፤ ስለዚህ እውነትንና ሰላምን
ውደዱ።”
[20]*እግዚአብሔር* ጸባኦት እንዲህ ይላል፤

8፥7 መዝ107፥3፤ ኢሳ11፥11፤43፥5
8፥8 ኢሳ51፥16፤ ኤር11፥4፤31፥24፤ ሕዝ11፥12-20፤ 36፥28፤37፥12፤ ዘካ2፥11፤10፥6፥10፤ ዕን8፥108፥9፤ ዕዝ 3፥11፤5፥1፤ ሐጌ2፥4
8፥10 2ዜና15፥5፤ ኢሳ5፥10፤ሐጌ1፥6
8፥11 ኢሳ12፥1
8፥12 ዘፍ27፥28፤ መዝ65፥13፤67፥6፤ 85፥12፤ኢሳ60፥21፤ ሆሴ2፥21፤ኢል 2፥22፤አብ1፥17 ዘፍ12፥2፤ዘኍ5፥27፤ ዘዳ13፥15፤መዝ48፥8፤ 102፥8፤ኤር42፥18፤ ኢል2፥14
8፥13 ቀኍ9፤ሐጌ2፥5
8፥14 ሕዝ24፥14
8፥15 ቀኍ13፤ ኤር29፥11፤31፥28፤32፥42፤ሚክ7፥18-20
8፥16 መዝ15፥2፤ ኤር33፥16፤ ሕዝ18፥8፤ 45፥9፤አሞ5፥15፤ ዘካ7፥9፤ኤፌ4፥25
8፥17 ምሳ3፥29፤ 6፥16-19፤ኤር7፥9፤ ዘካ5፥4
8፥19 ቀኍ16፤2ነገ 25፥7፤25፥25፤መዝ 30፥11፤ኤር39፥2፤ 52፥4
8፥21 ዘካ7፥2፤ኤር 26፥19
8፥22 86፥9፤ 117፥1፤ኢሳ2፥2-3፤ 44፥5፤45፥14፤49፥6፤ ዘካ2፥11
8፥23 መዝ102፥22 ኢሳ14፥1፤45፥14፤ 56፥3፤1ቆሮ14፥25
9፥1 ኢሳ17፥1፤ አሞ1፥5
9፥2 ዘፍ10፥15፤ ኤር49፥23፤ ሕዝ28፥1-19
9፥3 ኢዮ27፥16፤ ሕዝ28፥4
9፥4 ኢሳ23፥1፡ 11፤ኤር25፥22፤ ሕዝ26፥3-5
9፥5 ኤር47፥5
9፥6 ኢሳ14፥30
9፥7 ኢዮ25፥2፤ ኤር47፥1፤ኢል 3፥4፤ሶፎ2፥4
9፥8 ኢሳ26፥1፤ 52፥1፤54፥14፤ኢል 3፥17፤ ዘካ14፥21

“ብዙ ሕዝቦችና የብዙ ከተሞች ነዋሪዎች
ገና ይመጣሉ፤ [21]የአንዲቱ ከተማ ነዋሪዎ
ችም፣ ‘*እግዚአብሔርን* ለመለመን *እግዚአ
ብሔር* ጸባኦትን ለመፈለግ፣ ኑ፤ በፍጥነት
እንሂድ፤ እኔም ራሴ እሄዳለሁ’ እያሉ ወደ
ሌላዪቱ ከተማ ይሄዳሉ። [22]ብዙ ሕዝብና
ኀያላን መንግሥታትም *እግዚአብሔር* ጸባ
ኦትን ለመፈለግና ለመለመን ወደ ኢየሩ
ሳሌም ይመጣሉ።” [23]*እግዚአብሔር* ጸባኦት እን
ዲህ ይላል፤ “በእነዚያም ቀናት ከየወገኑና
ከየቋንቋው ዐሥር ሰዎች የአንድን አይሁ
ዳዊ ልብስ ዘርፍ አጥብቀው በመያዝ፣
“‘*እግዚአብሔር* ከእናንተ ጋር እንዳለ ሰም
ተናልና አብረን እንሂድ’” ይሉታል።

## በእስራኤል ጠላቶች ላይ የተወሰነ ፍርድ

9 *የእግዚአብሔር* ቃል ንግር በሴድራክ
ምድር ላይ ይወርድበታል፤
በደማስቆም ላይ ያርፍበታል፤
የሰዎችና የእስራኤል ነገዶች ሁሉ ዐይን፣
*በእግዚአብሔር* ላይ[ኣ] ዐርፎአልና።
[2]ደግሞም በአዋሳኟ በሐማት፣
ጥበበኞች ቢሆኑም እንኳ በጢሮስና በሲ
ዶና ላይ ያርፍባቸዋል።
[3]ጢሮስ ለራታ ምሽግ ሠርታለች፤
ብሩን እንደ ዐፈር
ወርቁንም እንደ መንገድ ላይ ትቢያ
ቈልላለች።
[4]ጌታ ግን ሀብቷን ይወስዳል፤
በባሕር ያላትንም ኀይል ይደምስሳል፤
እርታም በእሳት ፈጽማ ትጠፋለች።
[5]አስቀሎና አይታ ትርዳለች፤
ጋዛ በሥቃይ ትቃትታለች፤
አቃሮናም እንደዚሁ ትሠቃያለች፤ ተስፋዋ
ይመነምናልና።
ጋዛ ንጉሥዋን ታጣለች፤
አስቀሎናም ባድማ ትሆናለች።
[6]ድብልቅ ሕዝቦች አዛጦንን ይይዛሉ፤
የፍልስጥኤማውያንንም ትምክሕት
እቈርጣለሁ።
[7]ደሙን ከአፉቸው፣
የተከለከለውንም ምግብ ከመንጋጋቸው
አወጣለሁ።
የተረፉት ለአምላካችን ይሆናሉ፤
በይሁዳም አለቆች ይሆናሉ፤
አቃሮንም እንደ ኢያቡሳዊ ይሆናል።
[8]እኔ ግን ቤቴን
ከዘራፊ ኀይሎች እጠብቃለሁ፤
ጨቋኝ ከእንግዲህ ሕዝቤን አይወርስም፤
አሁን ነቅቼ እጠብቃለሁና።

[ኣ]1 *ወይም ደማስቆ የእግዚአብሔር ዐይን በሰው ሁሉ ላይ ያያልና በእስራኤል ነገዶች ላይ እንደሆነው።*

## የጽዮን ንጉሥ መምጣት

9አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ፤ እጅግ ደስ ይበልሽ፤
አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ፤ እልል በዪ፤
እነሆ፤ ጻደቁና አዳኙ ንጉሥሽ[ከ]፣
ትሑት ሆኖ፣ በአህያ ላይ ተቀምጦ፣
በአህያ ግልገል፣ በውርንጫዪቱ ላይ ሆኖ
ወደ አንቺ ይመጣል።
10ሠረገሎችን ከኤፍሬም፣
የጦር ፈረሶችን ከኢየሩሳሌም እወስዳለሁ፤
የጦርነቱም ቀስት ይሰበራል፤
ሰላምን ለአሕዛብ ያውጃል፤
ግዛቱም ከባሕር እስከ ባሕር፣
ከወንዙም[ኸ] እስከ ምድር[ወ] ዳር ድረስ
ይዘረጋል።
11ለአንቺ ደግሞ፣ ከአንቺ ጋር ከገባሁት የደም
ቃል ኪዳን የተነሣ፣
እስረኞችሽን ውሃ ከሌለበት ጕድጓድ ነጻ
እለቃቸዋለሁ።
12እናንት በተስፋ የምትኖሩ እስረኞች፤ ወደ
ምሽጎቻችሁ ተመለሱ፤
አሁንም ቢሆን ሁለት ዕጥፍ አድርጌ
እንደምመልስላችሁ እናገራለሁ።
13ቀስቴን እንደ ገተርሁ፣ ይሁዳን እገትረዋለሁ፤
ኤፍሬምንም ፍላጻ አደርገዋለሁ፤
ጽዮን ሆይ፤ ልጆችሽን አስነሣለሁ፤
ግሪክ ሆይ፤ በአንቺ ልጆች ላይ ይነሣሉ፤
እንደ ተዋጊ ሰይፍም አደርግሻለሁ።

## እግዚአብሔር ይገለጣል

14*እግዚአብሔር* በእነርሱ ላይ ይገለጣል፤
ፍላጻውም እንደ መብረቅ ይወጣል፤
ጌታ *እግዚአብሔር* መለከት ይነፋል፤
በደቡብም ዐውሎ ንፋስ ውስጥ ይጓዛል፤
15*እግዚአብሔር* ጸባኦትም ይከልላቸዋል፤
ጠላቶቻቸውን ይደመስሳሉ፤
በድንጋይ ወንጭፍም ያሸንፋሉ፤
ይጠጣሉ፤ በወይን ጠጅ እንደ ሰከረ ሰው
ይጮኻሉ፤
የመሠዊያውን ማእዘኖች ለመርጨት፣
እንደ ተዘጋጀ ዕቃ[ዐ]፣
እነርሱም እንደዚሁ ተሞልተዋል።
16ሕዝቡን የራሱ መንጋ አድርጎ
በዚያ ቀን አምላካቸው *እግዚአብሔር*
ያድናቸዋል።
በአክሊል ላይ እንዳለ ዕንቍ፣
በገዛ ምድሩ ላይ ያብለጨልጫሉ።
17እንዴት ውብና አስደናቂ ይሆናሉ፤
እህል ጎልማሶችን፣
አዲስ የወይን ጠጅም ቈነጃጅትን ያሳምራል።

## እግዚአብሔር ለይሁዳ ይጠነቀቃል

10 የበልግ ዝናብ እንዲሰጣችሁ *እግዚአብሔርን* ጠይቁ፤
*ማዕበሉን ደመና የሚያደርግ እግዚአብሔር ነው*፤
እርሱ ለሰዎች በቂ ዝናብን፣
ለእያንዳንዱም የምድርን ተክል ይሰጣል።
2ተራፊም አሳሳች ነገር ይናገራል፤
ሟርተኞች የሐሰት ራእይ ያያሉ፤
የውሸት ሕልም ይናገራሉ፤
ከንቱ መጽናናት ይሰጣሉ፤
ስለዚህ ሕዝቡ እንደ በጎች ተቅበዘበዙ፤
እረኛ በማጣትም ተጨነቁ።
3"ቍጣዬ በእረኞች ላይ ነዶአል፤
መሪዎችንም እቀጣለሁ፤
*እግዚአብሔር* ጸባኦት፣
ለመንጋው ለይሁዳ ቤት ይጠነቀቃልና፤
በጦርነትም ጊዜ እንደ ክብሩ
ፈረስ ያደርጋቸዋል።
4ከይሁዳ፣ የማእዘን ድንጋይ፣
የድንኳን ካስማ፣
የጦርነት ቀስት፣
ገዥም ሁሉ ይወጣል።
5ጠላትን መንገድ ላይ እንዳለ ጭቃ ይረጋግጣሉ፤
በአንድነት[ሀ] እንደ ጦር ሰልፈኛ ይሆናሉ፤
እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ስለሆነ ተዋግተው፤
ፈረሰኞችን ያዋርዳሉ።
6"የይሁዳን ቤት አበረታለሁ፤
የዮሴፍንም ቤት እታደጋለሁ።
ስለምራራላቸው፣
ወደቦታቸው እመልሳቸዋለሁ፤
እነርሱም በእኔ እንዳልተተዉ ሰዎች
ይሆናሉ፤
እኔ አምላካቸው *እግዚአብሔር* ነኝና፣
ጸሎታቸውን እሰማለሁ።
7ኤፍሬማውያን እንደ ኀያላን ሰዎች ይሆናሉ፤
ልባቸውም የወይን ጠጅ እንደ ጠጣ
ሰው ሐሤት ያደርጋል።
ልጆቻቸው ያዩታል፤ ደስተኛም ይሆናሉ፤
ልባቸውም *በእግዚአብሔር* ደስ ይለዋል።
8በፉጨት እጠራቸዋለሁ፤
በአንድነት እሰበስባቸዋለሁ፤
በእርግጥ እቤዣቸዋለሁ፤
እንደ ቀድሞው ይበዛሉ።
9በሕዝቦች መካከል ብበትናቸውም፣
በሩቅ ምድር ሆነው ያስቡኛል፤
እነርሱና ልጆቻቸው ተርፈው፣
በሕይወት ይመለሳሉ።
10ከግብፅ እመልሳቸዋለሁ፤
ከአሦርም እሰበስባቸዋለሁ፤
ወደ ገለዓድና ወደ ሊባኖስ አመጣቸዋለሁ፤

9:9 ዘፍ49፥11፤ 1ነገ1፥33፡39፤መዝ 24፥7፤149፥2፤ኢሳ 9፥6-7፤43፥3-11፤ 62፥11፤ኤር23፥5-6፤ ሶፎ3፥14-15፤ ዘካ2፥10፤ሚክ4፥8፤ ማቴ21፥5፤ዮሐ12፥15
9፥10 መዝ72፥8፤ ኢሳ2፥4፤ሆሴ 1፥7፤2፥18፤ሚክ 4፥3፤5፥10፤ዘካ10፥4
9፥11 ዘፀ24፥8፤ ኢሳ10፥4፤ 42፥7፤ኤር38፥6፤ ማቴ26፥28፤ሉቃ 22፥20
9፥12 ዘዳ21፥17፤ ኢሳ40፥2፤ኢል3፥16
9፥13 2ሳሙ 22፥35፤ኢሳ49፥2፤ ኤር51፥20፤ኢል3፥6
9፥14 ዘሌ25፥9፤ መዝ18፥14፤ ኢሳ21፥1፤31፥5፤ 66፥15፤ዕን3፥11፤ ማቴ24፥31
9፥15 ዘፀ27፥2፤ ኢሳ31፥5፤ 37፥35፤ዘካ10፥7፤ 12፥8፤14፥3፡20፤
9፥16 ኢሳ10፥20፤ ኤር31፥11
10፥1 ዘሌ26፥4፤ 1ነገ8፥36፤ኢዮ 14፥9፤መዝ104፥13፤ 135፥7
10፥2 ዘኍ27፥17፤ ኢሳ40፥19፤44፥25፤ ኤር23፥16፤23፥1፤ ሕዝ21፥21፤ሆሴ 3፥4፤ ማቴ9፥36
10፥3 ኢሳ14፥9፤ ኤር25፥34፤ሕዝ 34፥8-10
10፥4 መዝ 118፥22፤ኢሳ22፥23፤ ዘካ9፥10፤ሐሥ4፥11
10፥5 2ሳሙ 22፥43፤አሞ2፥15፤ ሚክ7፥10፤5፥8፤ ሐጌ2፥22፤ ዘካ12፥4
10፥6 መዝ34፥17፤ 102፥13፤ኢሳ14፥1፤ 58፥9፤65፥24፤ ሕዝ30፥24፤ 36፥37፤19፤ዘካ8፥7-8፤13፥9
10፥7 1ሳሙ2፥1፤ ኢሳ60፥5፤ኢል 2፥23፤ዘካ9፥15
10፥8 ኢሳ5፥26፤ ኤር33፥22፤ሕዝ 36፥11
10፥9 ኢሳ44፥21፤ ሕዝ6፥9
10፥10 ኢሳ11፥11፤ 49፥19፤ኤር50፥19፤ ዘካ8፥8

[ከ]9 ወይም *ንጉሥ*ማለት ይሆናል
[ኸ]10 **ኤፍራጥስም ነው**
[ወ]10 ወይም፣ *ምድር ዳርቻ* ማለት ነው።
[ዐ]15 ወይም *ጽዋ*
[ሀ]5 ወይም ሁሉም ገዥች በአንድነት ማለት ነው/[5] እነርሱም

በቂ ስፍራም አይገኝላቸውም።
11በመከራ ባሕር ውስጥ ያልፋሉ፤
የባሕሩ ማዕበል ጸጥ ይላል፤
የዐባይም ጥልቅ ሁሉ ይደርቃል።
የአሦር ትምክሕት ይዋረዳል፤
የግብፅም በትረ መንግሥት ያበቃል።
12*በእግዚአብሔር* አበረታቸዋለሁ፤
በስሙም ይመላለሳሉ፤”
ይላል *እግዚአብሔር* ።

11 ሊባኖስ ሆይ፤ እሳት ዝግባሽን እንዲ
በላው፣
ደጆችሽን ክፈቺ!
2የጥድ ዛፍ ሆይ፤ ዝግባ ወድቋልና አልቅስ፤
የከበሩትም ዛፎች ጠፍተዋል!
የባሳን ወርካዎች ሆይ፤ አልቅሱ፤
ጥቅጥቅ ያለው ደን ተመንጥሮአልና!
3የእረኞችን ዋይታ ስሙ፤
ክብራቸው ተገፎአልና፤
የአንበሶችን ጩኸት ስሙ፤
ጥቅጥቅ ያለው የዮርዳኖስ ደን ወድሟልና!

## ሁለቱ እረኞች

4*እግዚአብሔር* አምላኬ እንዲህ ይላል፤
“ለዕርድ የተለዩትን በጎች አሰማራ፤ 5የገዟ
ቸው ያርዷቸዋል፤ ሳይቀጡም ይቀራሉ፤
የሸጧቸውም፣ ‘*እግዚአብሔር* ይመስገን፤
ባለ ጠጋ ሆኛለሁ!’ ይላሉ፤ ጠባቂዎቻቸውም
እንኳ አይራሩላቸውም። 6ከእንግዲህ በምድ
ሪቱ ለሚኖረው ሕዝብ አልራራምና” ይላል
*እግዚአብሔር*፤ “ሰውን ሁሉ ለባልንጀራውና
ለንጉሡ አሳልፌ እሰጣለሁ፤ እነርሱ ምድሪ
ቱን ያስጨንቃሉ፤ እኔም ከእጃቸው አላድ
ናቸውም።”

7ስለዚህ ለዕርድ የተለዩትን በጎች፣ በተለ
ይም የተጨቈኑትን አሰማራሁ። ሁለት በት
ሮች ወስጄም፣ አንዱን “ሞገስ” ሌላውንም
“አንድነት” ብዬ ጠራኋቸው፤ መንጋውንም
አሰማራሁ። 8በአንድ ወር ውስጥ ሦስቱን
እረኞች አስወገድሁ።

በጎቹ ጠሉኝ፤ እኔም፣ ሰለቸኋቸው፤
9“እረኛችሁ አልሆንም፤ የሚሞቱት ይሙቱ፤
የሚጠፉት ይጥፉ፤ የቀሩትም አንዱ የሌላ
ውን ሥጋ ይብላ” አልኋቸው።

10ከዚያም ከአሕዛብ ሁሉ ጋር የገባሁትን
ኪዳን ለማፍረስ፣ “ሞገስ” ብዬ የጠራሁትን
በትሬን ወስጄ ሰበርሁት። 11በዚያም ቀን
ኪዳኑ ፈረሰ፤ ሲመለከቱኝ የነበሩትና የተ
ጨነቁት በጎችም *የእግዚአብሔር* ቃል
መሆኑን ዐወቁ።

12እኔም፣ “የሚበጅ መስሎ ከታያችሁ ዋጋ
ዬን ክፈሉኝ፤ አይሆንም ካላችሁም ተውት”
አልኋቸው፤ ስለዚህ ሠላሳ ብር ከፈሉኝ።
13*እግዚአብሔርም* ሊከፍሉኝ የተስማሙ
በትን ጥሩ ዋጋ “በግምጃ ቤቱ ውስጥ አኑ
ረው” አለኝ፤ እኔም ሠላሳውን ብር ወስጄ
*በእግዚአብሔር* ቤት ባለው ግምጃ ቤት
አስቀመጥሁት። 14ከዚያም የእስራኤልንና
የይሁዳን ወንድማማችነት በማፍረስ፣ “አን
ድነት” ብዬ የጠራሁትን ሁለተኛውን በት
ሬን ሰበርሁት።

15*እግዚአብሔርም* እንዲህ አለኝ፤ “እንደ
ገና የሰነፍ እረኛ ዕቃ ውሰድ፤ 16እነሆ፤
በምድሪቱ ላይ እረኛ አስነሣለሁ፤ እርሱም
የጠፉውን አያስብም፤ የባዘነውን አይፈል
ግም፤ የተሰበረውን አይጠግንም፤ የዳነው
ንም አይቀልብም፤ ነገር ግን የሰባውን
ሥጋ ይበላል፤ ሰኰናውንም ሳይቀር ይቀ
ለጣጥማል።

17 “*መንጋውን ለሚተው፣*
*ለማይረባ እረኛ ወዮለት!*
*ሰይፍ ክንዱንና ቀኝ ዐይኑን ትውጋው፤*
*ክንዱ ፈጽማ ትስለል፤*
*ቀኝ ዐይኑም ጨርሶ ትታወር።”*

## የኢየሩሳሌም ጠላቶች እንደሚደመሰሱ የተነገረ ንግር

12 ስለ እስራኤል የተነገረው *የእግዚአ
ብሔር* ቃል ይህ ነው፤ ሰማያትን
የዘረጋ፣ ምድርን የመሠረተ የሰውንም መን
ፈስ በውስጡ የሠራ *እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤ 2“ኢየሩሳሌምን በዙሪያዋ ላሉት ሕዝ
ቦች ሁሉ የሚያንገደግድ ጽዋ አደርጋታ
ለሁ፤ ይሁዳም እንደ ኢየሩሳሌም ሁሉ ትከ
በባለች። 3የምድር አሕዛብ ሁሉ በእርታ ላይ
በሚሰበሰቡበት በዚያ ቀን፣ ኢየሩሳሌምን
ለአሕዛብ ሁሉ የማይነቃነቅ ዐለት አደርጋ
ታለሁ፤ ለማነቃነቅ የሚሞክሩ ሁሉ ራሳቸ
ውን ይጐዳሉ። 4በዚያን ቀን እያንዳንዱን
ፈረስ በድንጋጤ፣ የተቀመጡባቸውንም ሰዎች
በእብደት እመታለሁ” ይላል *እግዚአብሔር*።
“የይሁዳን ቤት በዐይኔ እጠብቃለሁ፤ ነገር
ግን የአሕዛብን ፈረሶች ሁሉ አሳውራለሁ።
5የይሁዳ መሪዎች በልባቸው፣ ‘የኢየሩሳሌም
ሕዝቦች ብርቱ ናቸው፤ አምላካቸው *እግዚአ
ብሔር* ጸባኦት ነውና’ ይላሉ።

6“በዚያ ቀን የይሁዳን መሪዎች በዕንጨት
ክምር ውስጥ እንዳለ የእሳት ምድጃ፣ በነ
ዶም መካከል እንዳለ የፋና ነበልባል አደር
ጋቸዋለሁ፤ በግራና በቀኝ ዙሪያውን ያሉ
ትን ሕዝቦች ይበላሉ፤ ኢየሩሳሌም ግን ከስ ፍ
ራዋ ንቅንቅ አትልም።

7“የዳዊት ቤትና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች
ክብር ከይሁዳ ክብር እንዳይበልጥ እግዚአ

10÷11 ኢሳ19÷5-7፤51÷10፤ ሕዝ29÷15፤ 30÷13፤ሶፎ2÷13
10÷12 ሕዝ 30÷24፤ሚክ4÷5
11÷1 2ዜና 16÷19፤ሕዝ31÷3፤ ዘካ12÷6
11÷2 ኢሳ2÷13፤ 10÷34፤32÷19
11÷3 ኢሳ5÷29፤ ኤር2÷15፤50÷44፤ ሕዝ19÷9
11÷4 ኤር50÷7፤ ሕዝ34÷2-3
11÷5 ኤር50÷7፤ ሕዝ34÷2-3
11÷6 ኢሳ9÷19-21፤ ኤር13÷14፤ ሰቆ2÷21፤5÷8፤ ሚክ5÷8፤7÷2-6፤ ዘካ14÷13
11÷7 ኤር25÷34
11÷8 ሕዝ14÷5
11÷9 ኢ9÷20፤ ኤር43÷11
11÷10 ቀኍ7፤መዝ 89÷39፤ኤር14÷21
11÷12 ዘፍ23÷16፤ ማቴ26÷15
11÷13 ዘፀ21÷32፤ ማቴ27÷9-10፤ ሐሥ1÷18-19
11÷17 ኢሳ13÷1፤ ኤር23÷1፤ሕዝ 30÷21-22
12÷1 ዘፍ1÷8፤ መዝ104÷2፤102፤25፤ ኢሳ57÷16፤ኤር 51÷15፤ ዕብ1÷10
12÷2 መዝ60÷3፤ 75÷8፤ኢሳ51÷23፤ ዘካ14÷14
12÷3 ኢሳ29÷8፤ 28÷16፤66÷18፤ ዳን2÷34-35፤ ዘካ 14÷2፤
12÷4 መዝ76÷6፤ ዘካ14÷2፤
12÷5 ሕዝ30÷24
12÷6 ኢሳ10÷17-18፤ አብ18፤ ዘካ11÷1፤14÷10
12÷7 ኤር30÷18፤ አሞ9÷11

ብሔር በመጀመሪያ የይሁዳን መኖሪያ
ዎች ያድናል። 8ከመካከላቸው እጅግ ደካማ
የሆነው እንደ ዳዊት፣ የዳዊት ቤትም ፊት
ፊታቸው እንደሚሄድ እንደ *እግዚአብሔር*
መልአክ፣ እንደ አምላክ ይሆንላቸው ዘንድ
በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን *እግዚአብሔር*
ይከልላቸዋል። 9በዚያ ቀን ኢየሩሳሌምን
በወጓት አሕዛብ ሁሉ ላይ እወጣለሁ።

## ስለ ወጉት የተደረገ ሐዘን

10"በዳዊት ቤትና በኢየሩሳሌም ነዋሪዎች
ላይ የርኅራኄና የልመና መንፈስ አፈሳለሁ፤
ወደ ወጉኝ ወደ[የ] እኔም ይመለከታሉ፤ እነ
ርሱም ለአንድያ ልጅ እንደሚለቀስ ያለቅ
ሱለታል፤ ለበኵር ልጅ ምርር ተብሎ እን
ደሚለቀስም አምርረው ያለቅሱለታል።"
11በዚያ ቀን በመጊዶን ሜዳ ለሐዳድሪሞን
እንደተለቀሰ ሁሉ በኢየሩሳሌም የሚለቀሰ
ውም እንደዚሁ ታላቅ ልቅሶ ይሆናል።
12ምድሪቱ ታለቅሳለች፤ የየነገዱ ወንዶች
ለየራሳቸው ያለቅሳሉ፤ ሚስቶቻቸውም ለየ
ራሳቸው ያለቅሳሉ፤ በዚህም ዐይነት የዳዊት
ቤት ነገድ ወንዶች ከነሚስቶቻቸው የና
ታን ቤት ነገድ ወንዶች ከነሚስቶቻቸው፣
13የሌዊ ቤት ነገድ ወንዶች ከነሚስቶቻቸው፣
የሰሜኢ ቤት ነገድ ወንዶች ከነሚስቶቻቸው፣
14የቀሩትም ነገዶች ወንዶች ሁሉ ከነሚስቶቻ
ቸው ያለቅሳሉ።

## ከኀጢአት መንጻት

13 "በዚያ ቀን የዳዊትን ቤትና የኢ
የሩሳሌምን ነዋሪዎች ከኀጢአትና
ከርኵሰት የሚያነጻ ምንጭ ይከፈታል።
2"በዚያ ቀን የጣዖታትን ስም ከምድሪቱ
አጠፋለሁ፤ ከእንግዲህም አይታሰቡም" ይላል
*እግዚአብሔር* ጸባኦት። "ነቢያትንና ርኵስ
መንፈስን ከምድሪቱ አስወግዳለሁ። 3ማንም
ትንቢት ቢናገር ወላጅ አባትና እናቱ፣
'በእግዚአብሔር ስም ሐሰት ተናግረሃልና
ሞት ይገባሃል' ይሉታል። ትንቢት ሲናገርም
የገዛ ወላጆቹ ይወጉታል።
4"በዚያን ቀን እያንዳንዱ ነቢይ ስለሚ
ናገረው የትንቢት ራእይ ያፍራል፤ ለማታ
ለልም የነቢያትን ጠጕራም ልብስ አይለብ
ስም። 5እርሱም፣ 'እኔ ገበሬ እንጂ ነቢይ
አይደለሁም፤ ከልጅነቴ[ጸ] ጀምሮ ኑሮዬ የተ
መሠረተውም በዕርሻ ላይ ነው' ይላል።
6አንድ ሰው፣ 'ይህ በሰውነትህ[ጀ] ላይ ያለው
ቍስል ምንድን ነው?' ብሎ ቢጠይቀው፣
'በባልንጀሮቼ ቤት ሳለሁ የቈሰልሁት ነው'
ይላል።

12፥8 መዝ82፥6፤ 91፥4፤ኢል3፥10፤ 3፥16፤ሚክ7፥8፤ ዘካ9፥15
12፥9 ኢሳ29፥7፤ ዘካ1፥21፤14፥2-3፤
12፥10 ዘፍ21፥16፤ መሳ11፥34፤መዝ22፥1 6፤ኢሳ44፥3፤ኤር 31፥19፤ሕዝ37፥9፤ 39፥29፤ኢል2፥28-29፤ዮሐ19፥34፡37
12፥11 2ነገ23፥29፤ ኤር50፥4
12፥12 ማቴ24፥30፤ ራእ1፥7
12፥14 ዘካ7፥3 ዳን11፥35፤ዘካ10፥6፤ ሚል3፥2፤1ጴጥ1፥6-7
13፥1 ዘሌ16፥30፤ መዝ51፥2፤ኤር17፥13
13፥2 1ነገ22፥22፤ ኤር23፥14-15፤ 43፥12፤ሕዝ6፥6፤ 36፥25፤ሆሴ2፥17፤ ሚክ5፥13
13፥3 ዘዳ13፥6-11፤ 18፥20፤ነህ6፥14፤ ኤር23፥34፤28፥16፤ ሕዝ14፥9
13፥4 1ነገ18፥7፤ ኢሳ20፥2፤ኤር 6፥15፤ሕዝ12፥24፤ ማቴ3፥4
13፥5 አሞ7፥14
13፥7 ማቴ26፥31፤ ማር14፥27 2ሳሙ17፥2፤
13፥8 ሕዝ5፥2-4 ፡12፤ዘካ14፥2
13፥9 ዘሌ26፥12፤ ኢዮ6፥29፤መዝ 12፥6፤50፥15፤ 86፥7፤105፥1፤ ኢሳ4፥4፤30፥19፤ 33፥14፤44፥5፤ ኤር6፥27፤29፥12፤ 30፥22፤ሕዝ20፥38፤
14፥1 ኢሳ13፥6፤ 23፥18፤ኢል1፥15፤ ሚል4፥1
14፥2 ዘፍ34፥29፤ ኢሳ2፥3፤13፥6፤ ሰቆ5፥11፤ሕዝ5፥8፤ ዘካ12፥3፤13፥8
14፥3 ኢሳ8፥9፤ ዘካ9፥14-15፤12፥9
14፥4 ዘፍ16፥31፤ ሕዝ11፥23
14፥5 ዘዳ33፥2፤ ኢሳ29፥6፤66፥15-16፤አሞ1፥1፤ ማቴ16፥27፤25፥31፤ይሁ14
14፥6 ኢሳ13፥10፤ ኤር4፥23
14፥7 ኢሳ13፥10፤ 30፥26፤ኤር30፥7፤ ራእ21፥23-25፤22፥5

## እረኛው ተመታ፤ በጎቹ ተበተኑ

7*እግዚአብሔር* ጸባኦት እንዲህ ይላል፤
"ሰይፍ ሆይ፤ በእረኛዬ፣
በቅርብ ወዳጄ ላይ ንቃ!
እረኛውን ምታ፤
በጎቹ ይበተናሉ፤
እኔም ክንዴን ወደ ታናናሾቹ አዞራለሁ።
8*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ "የምድር ሁሉ፣
ሁለት ሦስተኛው ተመትቶ ይጠፋል፤
አንድ ሦስተኛው ግን በውስጡ ይቀራል፤
9ይህን አንድ ሦስተኛውን ክፍል ወደ እሳት
አመጣለሁ፤
እንደ ብር አነጥራቸዋለሁ፤
እንደ ወርቅም እፈትናቸዋለሁ፤
እነርሱ ስሜን ይጠራሉ፤
እኔም እመልስላቸዋለሁ፤
እኔም፣ 'ሕዝቤ ናቸው' እላለሁ፤
እነርሱም፣ '*እግዚአብሔር* አምላካችን
ነው'
ይላሉ።"

## እግዚአብሔር ይመጣል፤ ይነግሣልም

14 እነሆ፤ *የእግዚአብሔር* ቀን ይመጣል፤
ብዝበዛሽንም በውስጥሽ ይካፈላሉ።
2ኢየሩሳሌምን እንዲወጉ አሕዛብን ሁሉ
እሰበስባለሁ፤ ከተማዪቱ ትያዛለች፤ ቤቶች
ይበዘበዛሉ፤ ሴቶችም ይደፈራሉ፤ የከተማ
ዪቱ እኩሌታ ይማረካል፤ የሚቀረው ሕዝብ
ግን ከከተማዪቱ አይወሰድም።
3*እግዚአብሔርም* በጦርነት ጊዜ እንደሚ
ዋጋ፣ እነዚያን አሕዛብ ሊወጋ ይወጣል።
4በዚያን ቀን እግሮቹ ከኢየሩሳሌም በስተ
ምሥራቅ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ይቆማሉ፤
የደብረ ዘይት ተራራም ታላቅ ሸለቆን በመ
ሥራት የተራራውን እኩሌታ ወደ ሰሜን፣
እኩሌታውንም ወደ ደቡብ በማድረግ ምሥ
ራቅና ምዕራብ ሆኖ ለሁለት ይከፈላል፤
5እናንተም በእግዚአብሔር ተራራ ሸለቆ
በኩል በይሁዳ ንጉሥ በዖዝያን ዘመን በም
ድር ትሸሻላችሁ፤ ሸለቆው እስከ አጻል ይደ
ርሳልና። በምድር መናወጥ[ገ] ምክንያት
ሸሽታችሁ እንደ ነበረ ትሸሻላችሁ፤ ከዚ
ያም አምላኬ *እግዚአብሔር* ይመጣል፤
ቅዱሳኑም ሁሉ አብረውት ይመጣሉ።
6በዚያ ቀን በረዶ ውርጭና ብርሃን
አይኖርም። 7ቀኑም የብርሃን ወይም የጨ
ለማ ጊዜ የሌለበት ልዩ ቀን ይሆናል፤
ያም ቀን *በእግዚአብሔር* የታወቀ ቀን
ይሆናል፤ ሲመሽም ብርሃን ይሆናል።

[የ]10 ወይም *ለእኔ ሊሆን ይችላል።*
[ጸ]5 ወይም *አራሽ፤ በወጣትነቴ የተሸጥሁ ሰው*
[ጀ]6 *በእጆችህ መካል ያሉ ቍስሎች* የሚሉ አሉ።
[ገ]5 ወይም *ተራራዬ ሸለቆ ይሮጣል እስከ አጻል ይሰፋፋል። በርዕደ መሬት ሳቢያ እንደ ተዘጋው ሁሉ ለወደፊቱም እንደዚያ ይሆናል*

[8]በዚያን ቀን የሕይወት ውሃ ከኢየሩሳሌም
ይፈልቃል፤ እኩሌታው ወደ ምሥራቁ ባሕ
ር[ጣ]፣ እኩሌታውም ወደ ምዕራቡ ባሕር[ጨ]
ይፈሳል፤ ይህም በበጋና በክረምት ይሆናል።
[9]እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ላይ ይነግ
ሣል፤ በዚያን ቀን እግዚአብሔር አንድ፣
ስሙም አንድ ብቻ ይሆናል።
[10]ምድር ሁሉ ከጌባ አንሥቶ በኢየሩሳ
ሌም ደቡብ እስካለችው ሬሞን ድረስ ተለ
ውጣ ደልዳላ ሜዳ ትሆናለች፤ ኢየሩሳሌም
ግን ከብንያም በር እስከ መጀመሪያው በር፣
ከማእዘን በርና ከሐናንኤል ግንብ እስከ
ንጉሡ የወይን ጠጅ መጥመቂያ ድረስ በዚ
ያው በቦታዋ ላይ ከፍ እንዳለች ትኖራለች።
[11]የሰው መኖሪያም ትሆናለች፤ ከቶም ዳግ
መኛ አትፈር ስም፤ ኢየሩሳሌም ያለ ሥጋት
በሰላም ትኖራለች። [12]እግዚአብሔር ኢየሩ
ሳሌምን የወጓትን አሕዛብ ሁሉ የሚመታ
በት መቅሠፍት ይህ ነው፤ ገና በእግራቸው
ቆመው ሳሉ ሥጋቸው ይበሰብሳል፤ ዐይኖ
ቻቸው በጕድጓዶቻቸው ውስጥ እንዳሉ
ይበ ሰብሳሉ፤ ምላሶቻቸውም በአፎቻቸው
ውስጥ እንዳሉ ይበሰብሳሉ። [13]በዚያ ቀን
ከእግዚአብሔር ዘንድ በሰዎች ላይ ታላቅ
ሽብር ይወርዳል፤ እያንዳንዱ ሰው የባልን
ጀራውን እጅ ይይዛል፤ አንዱም ሌላውን
ይወጋዋል። [14]ይሁዳም ደግሞ ኢየሩሳሌ
ምን ይወጋል። በዙሪያው ያሉ የአሕዛብ
ሁሉ ሀብት፣ ብዙ ወርቅ፣ ብርና ልብስ
ይሰበሰባል። [15]ይህንኑ የሚመስል መቅ
ሠፍት ፈረሶችን፣ በቅሎዎችን ግመሎችንና
አህዮችን እንዲሁም በየሰፈሩ ያሉትን እን
ስሶች ሁሉ ይመታል።
[16]ከዚያም ኢየሩሳሌምን ከወጓት አሕ
ዛብ ከሞት የተረፉት ሁሉ ለእግዚአብሔር
ጸባኦት ለመስገድና የዳስን በዓል ለማክበር
በየዓመቱ ይወጣሉ። [17]የምድር ሕዝብ ሁሉ
ለንጉሡ፣ ለእግዚአብሔር ጸባኦት ሊሰግዱ
ወደ ኢየሩሳሌም የማይወጡ ከሆነ ዝናብ
አያገኙም። [18]የግብፅም ሰዎች ወደዚያ
ሳይ ወጡ ቢቀሩ፣ ዝናብ አያገኙም፤ እግዚ
አብሔር ወጥተው የዳስ በዓልን በ
ማያከብሩ አሕዛብ ላይ የሚያደርሰውን
መቅሠፍት በእነርሱም ላይ ያመጣል።
[19]የዳስን በዓል ወጥተው ለማ ያከብሩ
ግብፃውያንና አሕዛብ ሁሉ የተወ ሰነው
ቅጣት ይህ ነው።
[20]በዚያ ቀን በፈረሶች ሻኵራ ላይ፣
"ቅዱስ ለእግዚአብሔር" የሚል ጽሑፍ ይቀ
ረጻል፤ በእግዚአብሔር ቤት ያሉ የማብሰያ
ምንቸቶች ከመሠዊያው ፊት ለፊት እን
ዳሉ ሳሕኖች የተቀደሱ ይሆናሉ። [21]በኢየሩ
ሳሌምና በይሁዳ ያሉ ምንቸቶች ሁሉ ለእግ
ዚአብሔር ጸባኦት የተቀደሱ ይሆናሉ፤ መሥ
ዋዕት ለማቅረብ የሚመጡ ሁሉ ምንቸቶ
ቹን በመውሰድ ያበስሉባቸዋል፤ በዚያን ቀን
በእግዚአብሔር ጸባኦት ቤት ከእንግዲህ ወዲያ
ከነዓናዊ[ጸ] አይገኝም።

14፥8 ዘፍ8፥22፤ ኢሳ30፥25፤ ሕዝ47፥1-12፤ ኢል2፥20፤ ዮሐ7፥38፤ራእ22፥1-2
14፥9 ዘዳ6፥4፤ መዝ22፥28፤ 47፥7፤ኢሳ45፥24፤ አብ21፤ዕን2፥14፤ ኤፌ4፥5-6፤ ራእ11፥15
14፥10 ኢሱ 15፥32፤1ነገ15፥22፤ 2ነገ14፥13፤ ነህ3፥1፤ኢሳ2፥2፤ ኤር20፥2፤30፥18፤ አሞ9፥11፤ዘካ12፥6
14፥11 መዝ 48፥8፤ሕዝ34፥25-28፤ ዘካ2፥4
14፥12 ቊ18፤ ዘሌ26፥16፤ዘዳ28፥22፤ ኢዮ18፥13፤ ኢሳ 11፥4
14፥13 ዘፍ35፥5፤ መሳ7፥22፤ዘካ11፥6
14፥14 ኢሳ23፥18፤ ዘካ12፥2
14፥15 ቊ12
14፥16 ዘፀ23፥16፤ 2ነገ19፥31፤መዝ 22፥29፤86፥9፤ኢሳ 19፥21፤60፥6-9፤ አብ21፤ሚክ4፥2
14፥17 2ዜና 32፥23፤ኤር14፥4፤ አሞ4፥7
14፥18 ቊ12፤ ዘፍ27፥29
14፥19 ዕዝ3፥4
14፥20 ዘፀ9፥30፤ ሕዝ46፥20፤ ዘካ9፥15
14፥21 ነህ8፥10፤ 11፥1፤ኤር31፥40፤ ሕዝ44፥9፤ዘካ9፥8፤ ሮሜ14፥6-7፤ 1ቆሮ10፥31

[ጣ]8 ሙት ባሕር ነው
[ጨ]8 ሜድትራኒያን ነው
[ጸ]21 ወይም ነጋዴ እነዚህ ሕዝቦች በአብዛኛው በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሳይሆኑ አይቀሩም።

# ትንቢተ ሚልክያስ

1 በሚልክያስ[ሀ] በኩል ወደ እስራኤል
የመጣው የእግዚአብሔር ቃል ንግር
ይህ ነው፤

## ያዕቆብ ተወደደ፤ ዔሳው ተጠላ

2“እኔ ወድጃችኋለሁ” ይላል እግዚአ
ብሔር፤ “እናንተ ግን፣ ‘እንዴት ወደድኸን?’
ትላላችሁ::

እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ “ዔሳው
የያዕቆብ ወንድም አልነበረምን? ያዕቆብን
ወደድሁት፤ 3ዔሳውን ግን ጠላሁት፤ ተራ
ሮቹን ባድማ አደረግሁ፤ ርስቱንም ለም
ድረ በዳ ቀበሮዎች ሰጠሁበት::”

4ኤዶምያስ፣ “ብንደመሰስም እንኳ የፈ
ረሰውን መልሰን እንሠራዋለን” ይል ይሆ
ናል:: እግዚአብሔር ጸባኦት ግን እንዲህ
ይላል፤ “እነርሱ ይሠሩ ይሆናል፤ እኔ ግን
አፈርስባቸዋለሁ፤ ክፉ ምድር፣ እግዚአብሔ
ርም ለዘላለም የተቈጣው ሕዝብ ተብለው
ይጠራሉ:: 5ይህንም በገዛ ዐይናችሁ ታያ
ላችሁ፤ እናንተም፣ ‘ከእስራኤል ዳርቻ ወዲያ
እንኳ እግዚአብሔር ታላቅ ነው!’ ትላላችሁ::

## እንከን ያለበት መሥዋዕት

6“ልጅ አባቱን፣ ባሪያም ጌታውን
ያከብራል፤ እኔ አባት ከሆንሁ፣ መከበሬ
የት አለ? ጌታስ ከሆንሁ መፈራቴ የት
አለ? ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት፤ “ካህናት
ሆይ፤ ስሜን የምታቃልሉት እናንተ
ናችሁ::

“እናንተ ግን፣ ‘ስምህን ያቃለልነው
እንዴት ነው?’ ትላላችሁ::

7“በመሠዊያዬ ላይ የረከሰ ምግብ ታስ
ቀምጣላችሁ::

“እናንተ ግን፣ ‘ያረከስንህ እንዴት
ነው?’ አላችሁ::

“የእግዚአብሔር ገበታ የተናቀ ነው በማ
ለታችሁ ነው:: 8የታወረውን እንስሳ ለመ
ሥዋዕት ስታቀርቡ፣ ያ በደል አይደለ
ምን? አንካሳውን ወይም በሽተኛውን
እንስሳ መሥዋዕት አድርጋችሁ ስታቀ
ርቡ፣ ያስ በደል አይደለምን? ያንኑ ለገ
ዥዎቻችሁ ብታቀርቡ፣ በእናንተ ደስ ይለ
ዋልን? ወይስ ይቀበለዋልን?” ይላል እግ
ዚአብሔር ጸባኦት::

9“አሁን ግን እንዲራራልን እግዚአብሔርን
ለምኑ፤ እንደዚህ ዐይነቱን መሥዋዕት ይዛ
ችሁ ስትቀርቡ ይቀበላችኋልን?” ይላል
እግዚአብሔር ጸባኦት:: 10“በመሠዊያዬ
ላይ ከንቱ እሳት እንዳታነዱ፣ ምነው ከእ
ናንተ አንዱ የቤተ መቅደሱን ደጅ በዘጋ
ኖሮ! እኔ በእናንተ ደስ አይለኝም፤ ከእ
ጃችሁም ምንም ዐይነት ቍርባን አልቀበ
ልም’ ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት:: 11ከፀ
ሓይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ
ድረስ፣ ስሜ በሕዝቦች መካከል የከበረ
ይሆናል፤ በየስፍራውም ሁሉ ለስሜ ዕጣ
ንና ንጹሕ ቍርባን ያቀርባሉ፤ ስሜ በሕ
ዝቦች መካከል የከበረ ይሆናልና” ይላል
እግዚአብሔር ጸባኦት::

12“እናንተ ግን የእግዚአብሔር ገበታ፣
‘ርኩስ ነው’ ምግቡም፣ ‘የተናቀ ነው’ በማ
ለት ታቃልላላችሁ:: 13ደግሞም፣ ‘ይህ ድካም
ነው’ በማለት በንቀት ጢቅ አላችሁበት
ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት::

“በቅሚያ የመጣውን፣ አንካሳውንና የታ
መመውን እንስሳ ቍርባን አድርጋችሁ
ስታቀርቡ ከእጃችሁ መቀበል ይገባኛ
ልን?” ይላል እግዚአብሔር፤ 14“በመንጋው
ውስጥ ተቀባይነት ያለው ተባዕት በግ
ኖሮት ይህንኑ ሊሰጥ ተስሎ ሳለ በማታ
ለል ነውር ያለበትን እንስሳ ለጌታ የሚ
ሠዋ ርጉም ይሁን፤ እኔ ታላቅ ንጉሥ
ነኝ፤ ስሜም በሕዝቦች ዘንድ ሊፈራ
የሚገባ ነውና” ይላል እግዚአብሔር
ጸባኦት::

## ለካህናት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

2 “አሁንም ካህናት ሆይ፤ ይህ ማስጠ
ንቀቂያ ለእናንተ የተሰጠ ነው፤ 2ባት
ሰሙ፣ ልባችሁንም ስሜን ለማክበር ባታ
ዘጋጁ፣ ርግማን እሰድባችኋለሁ፤ በረከታች
ሁንም ወደ መረገም እለውጠዋለሁ፤ ልታ
ከብሩኝ ልባችሁን አላዘጋጃችሁምና’ ረግሜ
ዋለሁ ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት::

3“ዘራችሁን[ለ] እገሥጻለሁ[ሐ]፤ የመሥዋታች
ሁን ፋንድያ በፊታችሁ ላይ እበትናለሁ፤
እናንተም ከእርሱ ጋር ትወገዳላችሁ፤
4ከሌዊ ጋር የገባሁት ኪዳን ይጸና ዘንድ፣
ይህን ማስጠንቀቂያ የላክሁት እኔ መሆኔ
ንም ታውቃላችሁ” ይላል እግዚአብሔር

1፥1
ናሆ1፥1፤ሐሥ7፥38፤
ሮሜ3፥1-2፤1ጴ4፥11
1፥2
ቀኍ6፥7፤ዘዳ4፥37፤
ኤር46፥27፤ሚል2፥14
፡17፤3፥7፡13፤ሮሜ
9፥13
1፥3 ኢሳ13፥22፤
34፥10፤ሉቃ14፥26
1፥4 ኢሳ9፥10፤
11፥14፤34፥5፡11፤
ሰቆ4፥22፤
ሕዝ25፥12-4፤26፥14
1፥5 መዝ35፥27፤
48፥1፤ኢሳ45፥22፤
52፥10፤አሞ1፥11-12፤
ሚክ5፥4
1፥6 ቀኍ2፤ዘሌ20፥9፤
ዘዳ31፥12፤ኢዮ5፥17፤
ኢሳ1፥2፤ማቴ15፥4፤
23፥9፤ሉቃ6፥46
1፥7 ቀኍ2፥12፤
ዘሌ21፥6፤ሕዝ23፥41
1፥8 ዘፍ32፥20፤
ዘሌ1፥3፤ዘዳ15፥21፤
ኢሳ43፥23
1፥9 ዘሌ23፥33፡44፤
መዝ51፥17፤ኤር6፥20፤
ሚክ6፥6-8፤
ሮሜ12፥1፤
ዕብ13፥16
1፥10 ቀኍ13፤
ዘሌ22፥20፤
2ዜና28፥24፤
ኢሳ1፥11-14፤
ኤር14፥12፤ሆሴ5፥6፤
ሚል2፥12
1፥11 መዝ113፥3፤
ኢሳ6፥3፤12፥4፤
19፥21፤24፥15፤
56፥6፤60፥6-7፤
ማቴ8፥11፤ዕብ13፥15፤
ራእ5፥8፤8፥3
1፥12 ቀኍ7፤ሕዝ41፥22
1፥13 ቀኍ10፤
ዘኍ14፥11፤ዘዳ15፥2
1፤ኢሳ43፥22-24
1፥14 ዘፀ12፥5፤
ዘሌ22፥18-21፤
ዘዳ28፥58፤
መዝ72፥8-11፤95፥3፤
ኤር46፥18፤ኣብ1፥21፤
1ጢሞ6፥15
2፥1 ቀኍ7
2፥2 ዘኍ6፥23-27፤
ዘዳ11፥26፤28፥20፤
ኤር13፥17፤ማቴ15፥7-9፤
ዮሐ5፥23፤1ጢሞ6፥16፤
ራእ5፥12-13
2፥3 ዘፀ29፥14፤
ዘሌ4፥11፤1ነገ14፥10፤
ኢዮ9፥31
2፥4 ዘኍ3፥12

[ሀ]1 ሚልክያስ የስሙ ትርጉም *መልእክተኛዬ* ማለት ነው::
[ለ]3 ወይም *እህላችሁ እንዲጠወልግ አደርጋለሁ::*
[ሐ]3 ወይም *እቈርጣለሁ፤* የሰብዓ ሊቃናትን ትርጉም ይመ::

ጸባኦት። 5“ከእርሱ ጋር የገባሁት ኪዳን
የሕይወትና የሰላም ኪዳን ነበር፤ እነር
ሱንም ሰጠሁት፤ ይህም ክብርን አመጣ፤
እርሱም አከበረኝ፤ ስሜንም በመፍራትም
ጸና። 6እውነተኛ ትምህርት በአፉ ነበር፤
ምንም ዐይነት የሐሰት ነገር በአንደበቱ
አልተገኘም፤ ከእኔ ጋር በሰላምና በቅንነት
ተራመደ፤ ብዙዎችንም ከኀጢአት መለሰ።
7“ካህኑ የሁሉ ገዢ፣ *የእግዚአብሔር* መል
እክተኛ ስለሆነ ከንፈሮቹ ዕውቀትን ሊጠ
ብቁ፣ ሰዎችም ከአንደበቱ ትምህርትን ሊፈ
ልጉ ይገባል፤ 8እናንተ ግን ከመንገዱ
ወጥታችኋል፤ በትምህርታችሁም ብዙዎች
እንዲሰናከሉ አድርጋችኋል፤ የሌዊንም ኪዳን
አፍርሳችኋል”ይላል *እግዚአብሔር* ጸባኦት።
9“ስለዚህ በመንገዴ ስላልሄዳችሁና በትም
ህርታችሁም አድልዎ ስላደረጋችሁ፣ በሰ
ዎች ሁሉ ፊት እንድትናቁና እንድትዋ
ረዱ አድርጌአችኋለሁ።”

### የይሁዳ አለመታመን

10ሁላችን አንድ አባት ያለን አይደለን
ምን? የፈጠረንስ አንድ አምላክ አይደለ
ምን? ታዲያ እርስ በርሳችን ታማኝነት በማ
ጕደል የአባቶቻችንን ኪዳን ለምን እና
ረክሳለን? 11ይሁዳ አልታመነም፤ በእስራ
ኤልና በኢየሩሳሌምም አስጸያፊ ነገር ተፈ
ጽሞአል፤ ይሁዳ የባዕድ አምላክ ሴት ልጅ
በማግባት *እግዚአብሔር* የሚወደውን መቅ
ደስ አርክሶአል። 12ይህን የሚያደርግ
ማንኛውም ሰው ቢሆን፣ *ለእግዚአብሔር*
ጸባኦት ቍርባን ቢያመጣም እንኳ፣ *እግዚ*
*አብሔር* ከያዕቆብ[ሠ] ድንኳን ያስወግደው።
13ሌላው የምታደርጉት ነገር ደግሞ፣
*የእግዚአብሔርን* መሠዊያ በእንባ ታጥለቀ
ልቃላችሁ፤ ከእንግዲህ ወዲያ ቍር
ባናችሁን ስለማይመለከትና በደስታም ከእጃ
ችሁ ስለማይቀበል ታለቅሳላችሁ፤ ትጮኻ
ላችሁም። 14እናንተም፣ “ለምን ይህ ሆነ?”
ብላችሁ ትጠይቃላችሁ። ይህ የሆነው
የትዳር ጓደኛህን፣ አጋርህንና የቃል ኪዳን
ሚስትህን፣ አታለሃታልና *እግዚአብሔር*
በአንተና በወጣትነት ሚስትህ መካከል
ላለው ቃል ኪዳን ምስ ክር ስለሆነ ነው።
15*እግዚአብሔር* አንድ አላደረጋቸው
ምን? በሥጋም በመንፈስም የእርሱ ናቸው።
ለምን አንድ አደረጋቸው? *ፈሪሀ እግዚአ*
*ብሔር* ያለውን[ረ] ዘር ይፈልግ ስለ ነበር
ነው። ስለዚህ በመንፈሳችሁ ራሳችሁን ጠብቁ፤
ከወጣትነት ሚስታችሁም ጋር ያላችሁን
ታማኝነት አታጓድሉ።
16“ፍችን እጠላለሁ” ይላል የእስራኤል
አምላክ *እግዚአብሔር*፤ ልብሱን በግፍ
ድር ጊት የሚሸፍነውንም ሰው[ሰ] እጠ
ላለሁ” ይላል *እግዚአብሔር* ጸባኦት።
ስለዚህ በመንፈሳችሁ ራሳ ችሁን ጠብቁ፤
ታማኝነታችሁም አይጓደል።

### የፍርድ ቀን

17*እግዚአብሔርን* በቃላችሁ አታክታች
ሁታል።
እናንተም፣ “*ያታከትነው እንዴት ነው?*”
ትላላችሁ?
“ክፉ የሚያደርግ ሁሉ *በእግዚአብሔር*
*ፊት መልካም ነው*፤ እርሱም በክፉዎች
ደስ ይለዋል” ወይም “የፍትሕ አምላክ
ወዴት ነው?” በማለታችሁ ነው።

3 “እነሆ፤ በፊቴ *መንገድ እንዲያዘጋጅ*
*መልእክተኛዬን* እልካለሁ፤ የምትፈል
ጉት ጌታ በድንገት ወደ ቤተ መቅደሱ
ይመጣል፤ ደስ የምትሰኙበትም የቃል ኪ
ዳኑ መልእክተኛ ይመጣል” ይላል *እግዚ*
*አብሔር ጸባኦት*።
2እርሱ የሚመጣበትን ቀን ማን ሊቋቋ
መው ይችላል? በሚገለጥበትስ ጊዜ በፊቱ
መቆም የሚችል ማን ነው? እርሱ እንደ
አንጥረኛ እሳት ወይም እንደ ልብስ
አጣቢ ሳሙና ነውና። 3ብርን እንደሚያነ
ጥርና እንደሚያነጻ ሰው ይቀመጣል፤ ሌዋ
ውያንንም አንጽቶ እንደ ወርቅና እንደ
ብር ያጠራቸዋል፤ ከዚያም *እግዚአብሔር*
ቍርባንን በጽድቅ የሚያቀርቡ ሰዎች
ይኖሩታል፤ 4በዚያ ጊዜ የይሁዳና የኢየሩ
ሳሌም ቍርባን እንዳለፉት ቀናትና እንደ
ቀድሞው ዘመን *እግዚአብሔርን* ደስ የሚ
ያሰኝ ይሆናል።
5“ስለዚህ እኔ ለፍርድ ወደ እናንተ
እመጣለሁ፤ በመተተኞች፣ በአመንዝራ
ዎች፣ በሐሰት በሚምሉ፣ የሠራተኞችን
ደመወዝ በሚከለክሉ፣ መበለቶችንና ድኻ

2፥5 ዘኍ25፥12፤ ዘዳ14፥23፤28፥58፤33፥9፤መዝ25፥10፤103፥18፤119፥161፤ ማቴ26፥28፤ሉቃ22፥20፤ዕብ7፥22፤12፥28
2፥6 ዘፍ5፥22፤ ዘዳ33፥10፤መዝ25፥21፤ ሉቃ2፥14፤ዮሐ14፥27፤ ሮሜ11፥14፤ገላ5፥22፤ ያዕ5፥19-20
2፥7 ዘሌ10፥11፤ ዘኍ27፥21፤ 2ዜና17፥7፤36፥15፤ ኤር18፥18፤ ማቴ11፥10፤ማር1፥2
2፥8 ዘፀ 32፥8፤ኤር2፥8፤ 18፥15፤33፥21፤ ሕዝ22፥26፤ሆሴ4፥6
2፥9 ዘፀ18፥16፤ ዘሌ19፥15፤1ሳሙ2፥17፥30፤መዝ22፥6፤ 35፥4፤ኤር3፥25፤ 51፥37፤ሐሥ8፥32-33፤ 10፥34፤ሮሜ2፥11
2፥10 ዘፀ4፥22፤ 19፥5፤2ነገ17፥15፤ ኢዮ4፥17፤ ኢሳ43፥1፤ ኤር31፥32፤ ሶፎ3፥3-4፤ ማቴ5፥16፤6፥4፥18፤ሉቃ11፥2፤1ቆሮ8፥6
2፥11 ዘፀ34፥16፤ ዘዳ4፥37፤ ነህ13፥23፤ኢሳ1፥13፤ 48፥8፤ኤር3፥7-9
2፥12 ዘኍ24፥5፤ 1ሳሙ2፥30-33፤2ሳሙ20፥1፤ ሕዝ24፥21፤፥ሚል፤1፥10
2፥13 መዝ39፥12፤ 66፥18፤ኢሳ58፥2፤ ኤር11፥11፤14፥12
2፥14 ዘፍ21፥30፤ ኢሱ24፥22፤ ምሳ5፥18፤ሕዝ16፥8፤ ሚል1፥2፤ዕብ13፥4
2፥15 ዘፍ2፥24፤ ዘዳ4፥15፤14፥2፤ ኢሳ54፥6፤ ማቴ19፥4-6፤ 1ቆሮ7፥10፥14፤ ዕብ13፥4
2፥16 ዘፍ6፥11፤ 34፥25፤ዘዳ24፥1፤ መዝ51፥10፤ምሳ4፥17፤ ማቴ5፥31-32፤19፥4-9፤ ማር10፥4-5
2፥17 ዘፍ18፥25፤ ኢዮ8፥3፤መዝ5፥4፤ ኢሳ1፥14፤ ሕዝ18፥25፤ሚል1፥2
3፥1 ዘኍ27፥21፤ 1ሳሙ9፥20፤ 2ዜና36፥15፤ኢሳ40፥3፤ 42፥6፤ ሚክ5፥2 ማቴ3፥3፤11፥10፤ማር1፥2፤ሉቃ7፥27
3፥2 1ሳሙ6፥20፤ ኢዮ9፥30፤ኢሳ1፥31፤ 30፥30፤ሕዝ7፥7፤ 22፥14፤ዳን7፥13፤ ኢል2፥31፤ዘካ13፥9፤ማቴ3፥10-12፤ 16፥27፤ያዕ5፥8፤2ጴጥ3፥4፤ራእ1፥7፤6፥17
3፥3 1ዜና23፥28፤ ኢዮ28፥1፤መዝ12፥6፤ 132፥9፤ኢሳ1፥25፤ ዳን12፥10፤1ቆሮ3፥13፤ 1ጴጥ1፥7፤ራእ3፥18
3፥4 2ዜና7፥3፡ 12፤መዝ51፥19፤ሕዝ20፥40፤ሚል1፥11
3፥5 ዘፀ7፥11፤ 20፥14፤22፥21፡ 22፤ዘሌ19፥11-12፡13፤ዘዳ24፥19፤ 31፥12፤ኢሳ1፥2፤47፥9፤ ኤር7፥9፤ሕዝ22፥7፤ያዕ2፥11፤5፥4፤ 2ጴጥ2፥12-14

[ሠ]12 ወይም ይህን ለሚያደርግ ሰው በመልካም የሚመሰክር ማንም ቢኖር፣ እግዚአብሔር ከያዕቆብ ድንኳን ይቍረጠው።
[ረ]15 ወይም “ነገር ግን አባታችን በሕይወት እስከ ኖረበት ዘመን ድረስ ይህን አላደረገም። ምን ይፈልግ ነበረ? ይፈልግ የነበረው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልጅ ለማግኘት ነበረ።
[ሰ]16 ወይም *ሚስቱ* እንደ ማለት ነው።

አደጉን በሚጨቍኑ፣ መጻተኞችን ፍትሕ
በሚነፍጉ፣ እኔንም በማይፈሩት ላይ እመ
ሰክርባቸው ዘንድ እፈጥናለሁ” ይላል
እግዚአብሔር ጸባኦት።

### እግዚአብሔርን መስረቅ

6“እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም፤ ስለዚህ
እናንተ የያዕቆብ ልጆች ሆይ፤ አልጠፋ
ችሁም። 7ከአባቶቻችሁ ዘመን ጀምሮ ከት
እዛዛቴ ፈቀቅ ብላችኋል፤ አልጠበቃችኋቸ
ውምም፤ ወደ እኔ ተመለሱ፤ እኔም ወደ
እናንተ እመለሳለሁ”
ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት።
“እናንተ ግን፣ የምንመለሰው እንዴት
ነው ትላላችሁ?”
8“ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን?” እና
ንተ ግን ትሰርቁኛላችሁ።
“እናንተ ግን፣ ‘እንዴት እንሰርቅሃ
ለን?’ ትላላችሁ።
“ዐሥራትና መባ ትሰርቁኛላችሁ፤ 9እናን
ተም፣ መላው ሕዝባችሁም ስለምትሰርቁኝ
የተረገማችሁ ናችሁ። 10በቤቴ መብል እን
ዲኖር፣ እኔንም በዚህ እንድትፈትኑኝ ዐሥ
ራቱን ሁሉ ወደ ጐተራ አስገቡ፤” ይላል
እግዚአብሔር ጸባኦት፤ “የሰማይን መስ
ኮት የማልከፍትላችሁ፣ የተትረፈረፈ በረ
ከትንም ማስቀመጫ እስኪታጣ ድረስ የማ
ላፈስላችሁ ከሆነ ተመልከቱ። 11ስለ እና
ንተ ተባዩን እገሥጻለሁ፤ አዝመራችሁን
አይበላም፤ ዕርሻ ላይ ያለ የወይን ተክላ
ችሁም ፍሬ አልባ አይሆንም” ይላል
እግዚአብሔር ጸባኦት። 12“ከዚያም በኋላ
የተድላ ምድር ስለምትሆኑ ሕዝቦች ሁሉ
የተባረከ ሕዝብ ብለው ይጠሯችኋል”
ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት።
13“በእኔ ላይ የድፍረት ቃል ተናግራች
ኋል” ይላል እግዚአብሔር።
“እናንተ ግን፣ ‘በአንተ ላይ የተናገር
ነው ምንድን ነው?’ ትላላችሁ።
14“እንዲህም ብላችኋል፤ ‘እግዚአብሔርን
ማገልገል ከንቱ ነው፤ እርሱ የሚፈልገውን
ሁሉ በማድረግና በእግዚአብሔር ጸባኦት
ፊት ሐዘንተኞች ሆነን በመመላለስ ምን
ተጠቀምን? 15አሁን ግን ትዕቢተኞችን
ቡሩካን እንላቸዋለን፤ ክፉ አድራጊዎች
ይበለጽጋሉ፤ እግዚአብሔርን የሚፈታተኑትም
ያመልጣሉ።’”
16በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን የሚፈሩ
ሰዎች እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ፤ እግዚአ
ብሔር አዳመጠ፤ ሰማቸውም፤ እግዚአ
ብሔርን ለሚፈሩና ስሙን ለሚያከብሩ
በእርሱ ፊት የመታሰቢያ መጽሐፍ ተጻፈ።
17“እኔ በምሠራበት ቀን እነርሱ የገዛ
ገንዘቤ[ሸ] ይሆናሉ” ይላል እግዚአብሔር
ጸባኦት፤ “አባት የሚያገለግለውን ልጁን
እንደሚታደግ ሁሉ እኔም እታደጋቸዋ
ለሁ። 18በዚያን ጊዜም እንደ ገና በጻድቁና
በኀጢአተኛው መካከል፣ እግዚአብሔርን
በሚያገለግለውና በማያገለግለው መካከል
ያለውን ልዩነት ታያላችሁ።

### የእግዚአብሔር ቀን

4 “እነሆ፤ እንደ ምድጃ እሳት የሚነድ
ቀን ይመጣል፤ ትዕቢተኞች ሁሉና
ክፉ አድራጊዎች በሙሉ ገለባ ይሆናሉ፤
ያ የሚመጣው ቀንም ያቃጥላቸዋል” ይላል
እግዚአብሔር ጸባኦት። “ሥርም ሆነ ቅር
ንጫፍ አያስቀርላቸውም። 2ስሜን ለምት
ፈሩ ለእናንተ ግን የጽድቅ ፀሐይ በክን
ፎቿ ፈውስ ይዛ ትወጣለች፤ እናንተም
ከጋጥ እንደ ተለቀቀ እንቦሳ እየቦረቃችሁ
ትወጣላችሁ። 3እኔ በምሠራበት ቀን ክፉ
ዎችን ትረግጣላችሁ፤ ከእግራችሁ ጫማ
በታች ዐመድ ይሆናሉ” ይላል እግዚአብሔር
ጸባኦት።
4“ለእስራኤል ሁሉ ሕጎችና ሥርዐቶች
ይሆኑ ዘንድ፣ ለአገልጋዬ ለሙሴ በኮሬብ
የሰጠሁትን ሕግ አስቡ።
5“እነሆ፤ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚ
አብሔር ቀን ከመምጣቱ በፊት፣ ነቢዩ
ኤልያስን እልክላችኋለሁ። 6መጥቼ ምድ
ርን በርግማን እንዳላጠፋ፣ እርሱ የአባቶ
ችን ልብ ወደ ልጆች፣ የልጆችንም ልብ
ወደ አባቶች ይመልሳል።”

3፥6 ዘኍ23፥19፤ ኢ
ዮ34፥15፤ ሆሴ11፥9፤
ዕብ7፥21፤ያዕ1፥17
3፥7 ዘፀ32፥8፤
ኢሳ44፥22፤
ኤር7፥26፤
ሕዝ18፥32፤
ዘካ1፥3፤ሚል1፥2፤
ሐሥ7፥51፤ያዕ4፥8
3፥8 ዘኍ13፥10-12፤
18፥21፤ዘሌ27፥30፤
ዘካ5፥3፤ሉቃ18፥12
3፥9 ዘዳ11፥26፤
28፥15-68፤ዘካ5፥3
3፥10 ዘፀ22፥29፤
ዘሌ25፥21፤2ነገ7፥2፤ነ
ህ13፥12፤
ኢሳ44፥3፤ኢል2፥14፡
24፤2ቆሮ9፥8-11
3፥11 ዘዳ28፥39፤ ዘፀ
10፥15፤
ኢሳ61፥9፤62፥4፤
ሕዝ20፥6
3፥12 ዘዳ28፥3-12፤
2ዜና31፥10፤
ኢሳ61፥9፤62፥4፤
ሕዝ20፥6
3፥13 ሚል1፥2፤
2፥17
3፥14 ኢሱ22፥5፤
መዝ73፥13፤100፥2
3፥15 ኢዮ21፥7፤
መዝ14፥1፤119፥21፤ኤ
ር7፥10
3፥16 ዘፀ32፥32፤
ዘዳ28፥58፤31፥12፤
መዝ33፥18፤34፥15፤5
6፥8፤87፥6፤ ምሳ1፥7፤
ሉቃ10፥20፤
ራእ11፥18
3፥17 ዘፀ8፥22፤
ዘዳ7፥6፤ነህ13፥22፤
መዝ103፥13፤
ኢሳ26፥20፤43፥21፤
ሉቃ15፥1-32፤
ሮሜ 8፥14፥21፤
ሉቃ15፥1-32፤ ሮሜ
8፥14፥32፤ ቲቶ2፥14
3፥18 ዘፍ18፥25፤
ዘዳ32፥4፤ማቴ25፥32-
33፥41 4፥1
2ነገ10፥11፤
ኢሳ1፥31፤
2፥2፤5፥24፤31፥9፤
ሕዝ17፥8፤ዳን7፥13፤
ኢሳ2፥31፤ ናሆ1፥10፤
ማቴ3፥10፤11፥14፤
ሐሥ2፥20
4፥2 ዘዳ28፥58፤
ዜና7፥14፤
መዝ61፥5፤111፥9፤11
8፥27፤ኢሳ9፥2፤
30፥26፤
35፥35፥6፤45፥8፤
ማቴ4፥23፤ሉቃ1፥78፤
ኤፌ5፥14፤
ራእ14፥1፤22፥2 4፥3 ኢዮ40፥12፤ መዝ40-42፤ ሕዝ28፥18
4፥4 ዘፀ3፥1፤20፥1፤ ዘዳ28፥61፤መዝ147፥19፤ማቴ5፥17፤7፥12፤
ሮሜ2፥13፤4፥15፤ ገላ3፥24 4፥5 1ነገ17፥1፤ኢል2፥31፤
ማቴ11፥14፤16፥14
4፥6 ዘዳ11፥26፤ 13፥15፤ ኢሱ6፥17፤23፥15፤ኢሳ11፥4፤
ዘካ5፥3ሉቃ1፥17፤ ራእ19፥15

[ሸ]17 ወይም ሁሉን ቻይ፤ እኔ በምሠራበት ጊዜ ንብረቴ
ይሆናሉ

# የማቴዎስ ወንጌል

## የኢየሱስ የትውልድ ሐረግ

1፥1-17 ተጓ ምብ - ሉቃ 3፥23-38
1፥3-6 ተጓ ምብ - ሩት 4፥18-22
1፥7-11 ተጓ ምብ - 1ዜና 3፥10-17

1 የዳዊት ልጅ፣ የአብርሃም ልጅ የሆ
ነው የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ
የሚከተለው ነው፤

2 አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፤
ይስሐቅ ያዕቆብን ወለደ፤
ያዕቆብ ይሁዳንና ወንድሞቹን ወለደ፤
3 ይሁዳ ከትዕማር ፋሬስንና ዛራን ወለደ፤
ፋሬስ ኤስሮምን ወለደ፤
ኤስሮምም አራምን ወለደ፤
4 አራም አሚናዳብን ወለደ፤
አሚናዳብ ነአሶንን ወለደ፤
ነአሶን ሰልሞንን ወለደ፤
5 ሰልሞን ቦዔዝን ከረዓብ ወለደ፤
ቦዔዝ ከሩት ኢዮቤድን ወለደ፤
ኢዮቤድ እሴይን ወለደ፤
6 እሴይ ንጉሥ ዳዊትን ወለደ።

ዳዊት የኦርዮ ሚስት ከነበረችው
ሰሎሞንን ወለደ፤
7 ሰሎሞን ሮብዓምን ወለደ፤
ሮብዓም አቢያን ወለደ፤
አቢያም አሣፍን ወለደ፤
8 አሣፍ ኢዮሣፍጥን ወለደ፤
ኢዮሣፍጥ ኢዮራምን ወለደ፤
ኢዮራም ዖዝያንን ወለደ፤
9 ዖዝያን ኢዮአታምን ወለደ፤
ኢዮአታም አካዝን ወለደ፤
አካዝ ሕዝቅያስን ወለደ፤
10 ሕዝቅያስ ምናሴን ወለደ፤
ምናሴ አሞንን ወለደ፤
አሞንም ኢዮስያስን ወለደ፤
11 ኢዮስያስ በባቢሎን ምርኮ ጊዜ፣
ኢኮንያንንና[ሀ] ወንድሞቹን ወለደ፤

12 ከባቢሎን ምርኮ በኋላ፣
ኢኮንያን ሰላትያልን ወለደ፤
ሰላትያልም ዘሩባቤልን ወለደ፤
13 ዘሩባቤል አብዩድን ወለደ፤
አብዩድ ኤልያቄምን ወለደ፤
ኤልያቄም አዛርን ወለደ፤
14 አዛር ሳዶቅን ወለደ፤
ሳዶቅ አኪምን ወለደ፤
አኪምም ኤልዩድን ወለደ፤
15 ኤልዩድ አልዓዛርን ወለደ፤
አልዓዛር ማታንን ወለደ፤
ማታን ያዕቆብን ወለደ፤
16 ያዕቆብ ዮሴፍን ወለደ፤
ዮሴፍም የኢየሱስ ክርስቶስ እናት
የማርያም እጮኛ ነበር።

17 እንግዲህ ከአብርሃም እስከ ዳዊት ዐሥራ
አራት ትውልድ፣ ከዳዊት እስከ ባቢሎን
ምርኮ ዐሥራ አራት ትውልድ፣ ከባቢሎን
ምርኮ እስከ ክርስቶስ[ለ] ልደት ዐሥራ አራ
ት ትውልድ ይሆናል።

## የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት

18 የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት ታሪክ እን
ዲህ ነው፤ እናቱ ማርያም ለዮሴፍ ታጭታ
ሳይገናኙ፣ በመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች።
19 እጮኛዋ ዮሴፍ ጻድቅ ሰው ስለ ነበርና
ማርያምን በሰው ፊት ሊያጋልጣት ስላል
ፈለገ በስውር ሊተዋት ወሰነ።
20 በዚህ ሐሳብ ሳለ፣ የእግዚአብሔር
መልአክ በሕልም ተገለጠለት፤ እንዲህም
አለው፤ "የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፤ እጮ
ኛህን ማርያምን ወደ ቤትህ ለመውሰድ
አትፍራ፤ የፀነሰችው በመንፈስ ቅዱስ ነውና።
21 ወንድ ልጅ ትወልዳለች፤ ስሙንም ኢየ
ሱስ[ሐ] ብለህ ትጠራዋለህ፤ ሕዝቡን ከኀጢአ
ታቸው ያድናቸዋልና።"
22 ጌታ በነቢዩ እንዲህ ሲል የተናገረው
ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆነ፤ 23 "እነሆ፤
ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም
ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል፤"
ትርጕሙም፣ "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር"
ማለት ነው።
24 ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቃ፤ ከዚያም
የጌታ መልአክ እንዳዘዘው ማርያምን ወደ
ቤቱ ወሰዳት።[መ] 25 ይሁን እንጂ የበኵር ልጇን
እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤ የተወለ
ደውንም ሕፃን፣ "ኢየሱስ" ብሎ ጠራው።

## የጠቢባን ከምሥራቅ መምጣት

2 በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን፣ ኢየሱስ በቤተ
ልሔም ይሁዳ ከተወለደ በኋላ ጠቢ
ባን ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጥ
ተው፣ 2 "የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት

1፥1 ዘፍ22፥18፤ 2ሳሙ7፥12-16፤ኢሳ 9፥6፡7፤11፥1፤ኤር23፥5፡6፤ማቴ9፥27፤ ሉቃ 1፥32፡69፤ ገላ3፥16፤ ራእ22፥16
1፥2 ዘፍ21፥3፡12፤ 25፥26፤29፥35፤ 49፥10
1፥3 ዘፍ38፥27-30
1፥5 ዕብ11፥31
1፥6 1ሳሙ16፥1፤ 17፥12፤2ሳሙ12፥24
1፥10 2ነገ20፥21
1፥11 2ነገ24፥14-16 ፤ኤር27፥20፤ 40፥1፤ዳን1፥1፡2
1፥12 1ዜና3፥17፡ 19፤ዕዝ3፥2
1፥16 ማቴ27፥17፤ ሉቃ1፥27
1፥18 ሉቃ1፥35
1፥19 ዘዳ24፥1
1፥20 ማቴ27፥19፤ ሐሥ5፥19
1፥21 መዝ130፥8፤ ሉቃ1፥31፤2፥11፤ ዮሐ3፥17፤ሐሥ5፥31፤ ሮሜ11፥14፤ቲቶ 2፥14
1፥22 ማቴ2፥15፡17 ፡23፤4፥14፤8፥17፤12፥17፤21፥4፤26፥54፡56፤27፥9፤ሉቃ4፥21፤21፥22 ፤24፥44፤ዮሐ13፥ 18፤19፥24፡28፡36
1፥23 ኢሳ7፥14፤ 8፥8፡10
1፥24 ሐሥ5፥19
1፥25 ቍ21፤ ሉቃ 1፥31
2፥1 ሉቃ1፥5፤2፥4-7

[ሀ] 11 ዮአኪን ማለት ነው፤ ቍ12 ይመ
[ለ] 17 ወይም *መሲሕ* "ክርስቶስ" (በግሪክ) እና "መሲሕ" (በዕብ ራይስጥ) ሁለቱም "የተቀባ" የሚል ትርጕም አላቸው
[ሐ] 21 ኢየሱስ በግሪኩ ሲሆን በዕብራይስጡ ኢያሱ ነው፤ ትርጕሙም እግዚአብሔር ያድናል ማለት ነው
[መ] 24 ወደ ቤቱ ወሰዳት የሚለው የግሪኩ ቃል *ሚስቱ እንድ ትሆን ወሰዳት* ይለዋል

ነው? በምሥራቅ[ሠ] ኮከቡን አይተን ልንሰግ
ድለት መጥተናልና” ሲሉ ጠየቁ።
3ንጉሡ ሄሮድስ ይህን በሰማ ጊዜ ታወከ፤
እንዲሁም መላዪቱ ኢየሩሳሌም አብራ
ታወከች። 4እርሱም የካህናት አለቆችንና
የአይሁድ ሃይማኖት መምህራንን በሙሉ
ሰብስቦ፣ ክርስቶስ[ሪ] የት እንደሚወለድ ጠየ
ቃቸው። 5እነርሱም፣ “በይሁዳ ቤተ ልሔም፤
ነቢዩ እንዲህ ብሎ ጽፎአልና አሉ፤

6“ ‘በይሁዳ ምድር የምትገኚው አንቺ
 ቤተ ልሔም፣
 ከሌሎቹ የይሁዳ ገዦች በምንም አታ
 ንሺም፤
የሕዝቤ የእስራኤል ጠባቂ የሚሆን፣
 ከአንቺ ይወጣልና።’ ”

7ከዚያም ሄሮድስ ጠቢባኑን በምስጢር
አስጠርቶ በማነጋገር ኮከቡ የታየበትን
ትክክለኛ ጊዜ ተረዳ። 8ጠቢባኑንም ወደ
ቤተ ልሔም ልኮ፣ “ሂዱና ሕፃኑን ፈልጉ፤
እኔም ደግሞ ሄጄ እንድሰግድለት፣ እንዳ
ገኛችሁት
ወደ እኔ ተመልሳችሁ የት እንዳለ
ንገሩኝ” አላቸው።
9ጠቢባኑ ንጉሡ ያለውን ከሰሙ በኋላ
ጕዞአቸውን ቀጠሉ። ይህም በምሥራቅ[ሰ]
ያዩት ኮከብ እየመራቸው ሕፃኑ እስካ
ለበት ድረስ ወሰዳቸው። 10ኮከቡንም ሲያዩ
ከመጠን በላይ ተደሰቱ። 11ወደ ቤትም
በገቡ ጊዜ ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር
አዩ፤ ተንበርክከውም ሰገዱለት። ሣጥኖቻ
ቸውን ከፍተው ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤም
አቀረቡለት። 12እግዚአብሔርም ወደ ሄሮ
ድስ እንዳይመለሱ በሕልም ባስጠነቀቃ
ቸው መሠረት፣ መንገድ አሳብረው ወደ
አገራቸው ተመለሱ።

## ወደ ግብፅ ሽሽት

13ጠቢባኑ ከሄዱ በኋላ የጌታ መልአክ
ለዮሴፍ በሕልም ተገልጦ፣ “ተነሥ! የምት
መለስበትን ጊዜ እስካስታውቅህ ድረስ ሕፃ
ኑንና እናቱን ይዘህ ወደ ግብፅ በመሸሽ
በዚያ ቈይ፤ ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው
ይሻልና” አለው።
14ስለዚህም ዮሴፍ ተነሣ፤ ሕፃኑንና እና
ቱን ይዞ በሌሊት ወደ ግብፅ ሄደ፤ 15በዚ
ያም ሄሮድስ እስከ ሞተበት ጊዜ ድረስ
ኖረ። በዚህም፣ “ልጄን ከግብፅ ምድር ጠራ
ሁት” በማለት እግዚአብሔር በነቢዩ አንደ
በት የተናገረው ቃል ተፈጸመ።
16ሄሮድስ ጠቢባኑ እንዳታለሉት በተረዳ
ጊዜ በጣም ተናደደ። ከጠቢባኑ በተነገረው
ጊዜ መሠረት ዕድሜያቸው ሁለት ዓመ

2፥2 ዘኍ24፥17፤
ኤር23፥5፤ማቴ27፥
11፤ማር15፥2፤
ሉቃ 23፥38፤
ዮሐ1፥49፤
18፥33-37
2፥5 ዮሐ7፥42
2፥6 2ሳሙ5፥2፤
ሚክ5፥2
2፥11 መዝ72፥10፤
ኢሳ60፥3
2፥12 ቍ13፥19፡22
፤ማቴ27፥19፤ዕብ
11፥7
2፥13 ቍ12፥19፡22
፤ማቴ27፥19፤ሐሥ
5፥19፤ራእ12፥4
2፥15 ቍ17፡23፤ዘፀ
4፥22፡23፤ሆሴ11፥1፤
ማቴ1፥22
2፥17 ቍ15፡23፤
ማቴ1፥22
2፥18 ዘፍ35፥19፤
ኤር31፥15
2፥19 ቍ12፡13፡
22፤ማቴ27፥19፤ሐሥ
5፥19
2፥20 ዘፀ4፥19
2፥22 ቍ12፡13፡19
፤ማቴ27፥19፤ሉቃ
2፥39
2፥23 ቍ15፡17፤
ማቴ1፥22፤ማር1፥9፡
24፤6፥1፤ሉቃ1፥26፤
2፥39፡51፤4፥16፡23፤
ዮሐ1፥45፡46
3፥1 ቍ13፡14፤9፥
14፤11፥2-14፤ 14፥
1-12፤ሉቃ1፥13፡
57-66፤3፥2-19፤ሐሥ
19፥3፡4
3፥2 ዳን7፥14፤ማቴ
4፥17፤6፥10፤7፥21፤
25፥34፤ሉቃ11፥20፤
17፥20፡21፤19፥11፤
21፥31፤ዮሐ3፥3፡5፤
ሐሥ1፥3፡6
3፥3 ኢሳ40፥3፤
ሚል3፥1፤ሉቃ1፥76፤
ዮሐ1፥23
3፥4 ዘሌ11፥22፤
2ነገ1፥8፤ማቴ3፥1
3፥6 ቍ11፤ማር1፥4
3፥7 ማቴ12፥34፤
23፥33፤ሮሜ1፥18

ትና ከዚያም በታች የሆኑትን የቤተ ልሔ
ምንና የአካባቢዋን መንደሮች ወንድ
ልጆች ሁሉ ልኮ አስገደለ። 17በዚህም በነ
ቢዩ በኤርምያስ እንዲህ ተብሎ የተነገ
ረው ተፈጸመ፤

18“የልቅሶና የታላቅ ዋይታ ድምጽ፣
 በራማ ተሰማ፤
ራሔል ስለ ልጆቿ አለቀሰች፤
 መጽናናትም አልቻለችም፤
 ልጆቿ ሁሉ አልቀዋልና።”

## ከግብፅ ወደ ናዝሬት

19ሄሮድስ ከሞተ በኋላ የእግዚአብሔር
መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ተገልጦ፣
20“ተነሣ፤ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ እስ
ራኤል ምድር ተመለስ፤ ሕፃኑን ለመግደል
የሚሹት ሞተዋልና” አለው።
21ዮሴፍም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን
በመያዝ ወደ እስራኤል ምድር ተመለሰ፤
22ነገር ግን አርኬላዎስ በአባቱ በሄሮድስ
ቦታ በይሁዳ መንገሡን በሰማ ጊዜ ወደዚያ
መሄድ ፈራ። ጌታ በሕልም ስላስጠነቀ
ቀው፣ ወደ ገሊላ አውራጃ ሄደ፤
23ናዝሬት ወደምትባል ከተማም ሄዶ
መኖር ጀመረ። በዚህም በነቢያት፣ “ናዝራ
ዊ ይባላል” ተብሎ የተነገረው ትንቢት
ተፈጸመ።

## የመጥምቁ ዮሐንስ ስብከት

3፥1-12 ተጓ ምብ - ማር 1፥3-8፤ ሉቃ 3፥2-17

3 በዚያን ወራት መጥምቁ ዮሐንስ በይ
ሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ።

2ስብከቱም፣ “መንግሥተ ሰማያት ቀርባለ
ችና ንስሓ ግቡ” የሚል ነበር። 3በነቢዩ
በኢሳይያስ እንዲህ ተብሎ የተነገረለት
እርሱ ነው፤

“በምድረ በዳ፣
 ‘የጌታን መንገድ አዘጋጁ፤
 ጎዳናውንም አስተካክሉ’ እያለ የሚጮህ
 ድምፅ።”

4የዮሐንስ ልብስ የግመል ጠጕር ሲሆን፣
ወገቡንም በጠፍር ይታጠቅ ነበር። ምግ
ቡም አንበጣና የበረሃ ማር ነበር። 5ከኢየሩ
ሳሌም፣ ከመላው ይሁዳና በዮርዳኖስ ዙሪያ
ካለው አገር ሁሉ ሰዎች ወደ ዮሐንስ ይጐ
ርፉ፣ 6ኀጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮር
ዳኖስ ወንዝ በእርሱ ይጠመቁ ነበር።
7ብዙ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ወደ
ሚያጠምቅበት ስፍራ ሲመጡ ባየ ጊዜ
እንዲህ አላቸው፤ “እናንተ የእፉኝት ልጆች!

[ሠ]2 ወይም *ኮከቡ ሲነሣ አይተን*
[ሪ]4 ወይም *መሲሕ*

ሰ9 ወይም ሲነሣ አይተው

ለመሆኑ ከሚመጣው ቍጣ እንድታመ
ልጡ ማን መከራችሁ! 8ለንስሓ የሚገባ
ፍሬ አፍሩ፤ 9‘አብርሃም አባት አለን’ በማ
ለት ራሳችሁን አታታሉ፤ እግዚአብሔር
ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያ
ስነሣ ይችላል እላችኋለሁና። 10እነሆ፤ ምሣር
የዛፎችን ሥር ሊቈርጥ ተዘጋጅቶአል፤
መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቈረ
ጣል፤ ወደ እሳትም ይጣላል።
11“እኔ ለንስሓ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤
ነገር ግን ጫማውን መሸከም የማይገባኝ፣
ከእኔ የሚበልጥ ኀያል ከእኔ በኋላ ይመ
ጣል። እርሱም በመንፈስ ቅዱስና በእሳት
ያጠምቃችኋል። 12መንሹ በእጁ ነው፤
ዐውድማውን ያጠራል፤ ስንዴውን በጐተራ
ይከታል፤ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት
ያቃጥለዋል።”

## የኢየሱስ መጠመቅ

3፥13-17 ተጓ ምብ - ማር1፥9-11፤ ሉቃ3፥21፡22፤ ዮሐ1፥31-34

13በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ለመጠ
መቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ። 14ዮሐ
ንስ ግን፣ “ይህማ አይሆንም፤ እኔ ባንተ
መጠመቅ ሲያስፈልገኝ እንዴት አንተ
ወደ እኔ ትመጣለህ?” ብሎ ተከላከለ።
15ኢየሱስም፣ “ግድ የለም ፍቀድልኝ፤
ይህን በማድረግ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም
ይገባናልና” አለው፤ ዮሐንስም በነገሩ ተስ
ማማ።
16ኢየሱስም እንደ ተጠመቀ ከውሃው
ወጣ፤ ወዲያውኑም ሰማይ ተከፍቶ የእግዚ
አብሔር መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ
በት አየ። 17እነሆ፣ “በእርሱ ደስ የሚለኝ
የምወደው ልጄ ይህ ነው” የሚል ድምፅ
ከሰማይ ተሰማ።

## የኢየሱስ መፈተን

4፥1-11 ተጓ ምብ - ማር 1፥12፡13፤ ሉቃስ 4፥1-13

4 ከዚህ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን
በዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ ወደ
ምድረ በዳ ወሰደው። 2አርባ ቀንና አርባ
ሌሊት ከጾመ በኋላ ተራበ። 3ፈታኙም
ወደ ኢየሱስ ቀርቦ፣ “የእግዚአብሔር ልጅ
ከሆንህ እነዚህን ድንጋዮች እንጀራ እንዲ
ሆኑ እዘዝ” አለው።
4ኢየሱስም፣ “ ‘ሰው ከእግዚአብሔር አፍ
በሚወጣው ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ
ብቻ አይኖርም’ ተብሎ ተጽፎአል” ሲል
መለሰለት። 5ቀጥሎም ዲያብሎስ ኢየሱስን
ወደ ቅድስት ከተማ በመውሰድ ከቤተ
መቅደሱም ዐናት ላይ አውጥቶ፣ 6“የእግዚአ
ብሔር ልጅ ከሆንህ ራስህን ወደ መሬት

3፥8 ሐሥ26፥20
3፥9 ሉቃ3፥8
3፥10 ማቴ7፥19፤ ሉቃ3፥9፤13፥6-9፤ ዮሐ15፥2፡6
3፥11 ቍ6፤ኢሳ 4፥4፤ማር1፥4፡8፤ ሐሥ 2፥3፡4
3፥12 ማቴ13፥30፤ 25፥41
3፥13 ማቴ3፥1፤ ማር1፥4
3፥16 ኢሳ11፥2፤ 42፥1፤ሕዝ1፥1፤ ዮሐ 1፥51፤ ሐሥ7፥56፤ 10፥11፤ ራእ4፥1፤ 19፥11
3፥17 ዘጻ4፥12፤ መዝ2፥7፤ኢሳ42፥1፤ ማቴ12፥18፤17፥5፤ ማር1፥11፤9፥7፤ ሉቃ 3፥22፤9፥35፤ ዮሐ12፥28፤ ሐሥ 13፥33፤ ዕብ1፥1-5፤ 5፥5፤2ጴጥ1፥17፡18
4፥1 ዘፍ3፥1-7፤ ዕብ 4፥15
4፥2 ዘፀ34፥28፤ 1ነገ19፥8
4፥3 ማቴ3፥17፤ 14፥33፤16፥16፤ 27፥ 54፤ማር3፥11፤ ሉቃ 1፥35፤22፥70፤ ዮሐ 1፥34፡49፤ 5፥25፤11፥ 27፤20፥31፤ሐሥ 9፥20፤ሮሜ1፥4፤1ተሰ 3፥5፤1ዮሐ5፥10-13፡ 20፤ራእ2፥18
4፥4 ዘዳ8፥3፤ዮሐ 4፥34
4፥5 ነህ11፥1፤ዳን 9፥24፤ማቴ27፥53
4፥6 ቍ3፤ መዝ 91፥11፡12
4፥7 ዘዳ6፥16
4፥10 ዘዳ6፥13፤ 1ዜና21፥1፤ኢዮ1፥6-9 ፤ማቴ16፥23፤ማር 4፥15፤ሉቃ10፥18፤ 13፥16፤22፥3፡31፤ ሮሜ16፥20፤2ቆሮ 2፥11፤11፥14፤2ተሰ 2፥9፤ራእ12፥9
4፥11 ማቴ26፥53፤ ሉቃ22፥43፤ዕብ1፥14 ፤ያዕ4፥7
4፥12 ማቴ14፥3፤ ማር1፥14
4፥13 ማር1፥21፤9፥33፤ ሉቃ4፥23፡31፤ ዮሐ2፥12፤4፥46፡47
4፥14 ማቴ1፥22
4፥16 ኢሳ9፥1፡2፤ ሉቃ2፥32፤ ዮሐ 1፥4፡5፡9
4፥17 ማቴ3፥2
4፥18 ማቴ15፥29፤ 16፥17፡18፤ ማር7፥31 ፤ዮሐ6፥1

ወርውር፤ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤
“ ‘እግርህ በድንጋይ እንዳይሰናከል፣
በእጃቸው ያነሡህ ዘንድ፣
መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል።’ ”

7ኢየሱስም፣ “እንደዚሁም በመጻሕፍት፣
‘እግዚአብሔር አምላክህን አትፈታተነው’
ተብሎ ተጽፎአል” በማለት መለሰለት።
8እንደ ገናም ዲያብሎስ ኢየሱስን
እጅግ ከፍ ወዳለ ተራራ አወጣው፤ የዓ
ለምንም መንግሥታት ከነክብራቸው
አሳየውና፣ 9“ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን
ሁሉ እሰጥ ሃለሁ” አለው።
10ኢየሱስም፣ “አንተ ሰይጣን ከፊቴ ራቅ!
‘ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ስገድ፤ እርሱንም
ብቻ አምልክ’ ተብሎ ተጽፎአልና” አለው።
11ከዚያም ዲያብሎስ ትቶት ሄደ፤ መላ
እክትም መጥተው አገለገሉት።

## ኢየሱስ ስብከት መጀመሩ

12ኢየሱስ የዮሐንስን መታሰር በሰማ ጊዜ
ወደ ገሊላ ተመለሰ። 13የናዝሬትንም ከተማ
ትቶ፣ በዛብሎንና በንፍታሌም አካባቢ
በባሕሩ አጠገብ በምትገኘው በቅፍርናሆም
ከተማ መኖር ጀመረ። 14በዚህም በነቢዩ ኢሳ
ይያስ እንዲህ ተብሎ የተነገረው ትንቢት
ተፈጸመ፤
15“የዛብሎን ምድር፣ የንፍታሌም ምድር፣
ከዮርዳኖስ ማዶ በባሕር መንገድ አጠገብ፣
ያለው የአሕዛብ ገሊላ፣
16በጨለማ የሚኖር ሕዝብ፣
ታላቅ ብርሃን አየ፤
በሞት ጥላ ምድር ላለው፣
ብርሃን ወጣለት።”

17ከዚያ ጊዜ አንሥቶ ኢየሱስ፣ “ንስሓ
ግቡ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለ
ችና” እያለ መስበክ ጀመረ።

## የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት መጠራት

4፥18-22 ተጓ ምብ - ማር1፥16-20፤ ሉቃ5፥2-11፤ ዮሐ1፥35-42

18ኢየሱስ በገሊላ ባሕር አጠገብ ሲ
ያልፍ፣ ሁለት ወንድማማቾች ማለትም
ጴጥሮስ የተባለውን ስምዖንንና ወንድሙን
እንድ ርያስን አያቸው። ዓሣ አጥማጆች
ነበሩና መረባቸውን ወደ ባሕሩ ይጥሉ
ነበር። 19ኢየሱስም፣ “ኑ፣ ተከተሉኝ፤
ሰዎችን አጥማጆች አደርጋችኋለሁ”
አላቸው። 20ወዲያው መረባቸውን ትተው
ተከተሉት።
21አለፍ እንዳለም፣ ሌሎች ሁለት ወንድ
ማማቾች፣ የዘብዴዎስን ልጅ ያዕቆብንና

4፥19 ቍ20፡22፤ማቴ8፥22፤ማር10፥21 ፡28፡52፤ሉቃ5፥28፤ ዮሐ1፥43፤21፥19፡22 4፥20 ቍ19 4፥21 ማቴ17፥1፤ 20፥20፤26፥37፤ማር 3፥17፤13፥3፤ሉቃ 8፥51፤ዮሐ21፥2

ወንድሙን ዮሐንስን አየ። ከአባታቸው
ከዘብዴዎስ ጋር በጀልባ ውስጥ መረባቸ
ውን ያበጁ ነበር። ኢየሱስም ጠራቸው፤
22ወዲያውኑ ጀልባቸውንም ሆነ አባታቸ
ውን ትተው ተከተሉት።

## የበሽተኞች መፈወስ

23ኢየሱስም በምኵራቦቻቸው እያስተ
ማረ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥ
ራች ቃል እየሰበከ፣ በሕዝቡ መካከል ማን
ኛውንም ደዌና ሕመም እየፈወሰ በመላው
ገሊላ ይዘዋወር ነበር።
24ከዚህም የተነሣ ዝናው በመላዋ ሶርያ
ተሰማ፤ ሕዝቡም በተለያዩ በሽታዎች የታ
መሙትን፣ በክፉ ደዌ የሚሠቃዩትን፣
አጋንንት ያደሩባቸውን፣ የሚጥል በሽታ
ያለባቸውን፣ ሽባዎችን ሁሉ ወደ እርሱ
አመጡ፤ ፈወሳቸውም።
25ከዚህም የተነሣ ከገሊላ፣ ከ'ዐሥሩ ከተ
ሞች'፣ ከኢየሩሳሌም፣ ከይሁዳና ከዮርዳ
ኖስ ማዶ የመጡ ብዙ ሰዎች ተከተሉት።

## የተራራው ስብከት

5፥3-12 ተጓ ምብ - ሉቃ 6፥20-23

5 ብዙ ሕዝብ እንደ ተሰበሰበ ባየ ጊዜ፣
ወደ ተራራ ወጣና ተቀመጠ፤ ደቀ
መዛሙርቱም ወደ እርሱ መጡ። 2እንዲ
ህም እያለ ያስተምራቸው ጀመር፤
3በመንፈስ ድኾች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፤
መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ናትና።
4የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፤
መጽናናትን ያገኛሉና።
5የዋሆች ብፁዓን ናቸው፤
ምድርን ይወርሳሉና።
6ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፤
ይጠግባሉና።
7ምሕረት የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው፤
ምሕረትን ያገኛሉና።
8ልባቸው ንጹሕ የሆነ ብፁዓን ናቸው፤
እግዚአብሔርን ያዩታልና።
9ሰላምን የሚያወርዱ ብፁዓን ናቸው፤
የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው
ይጠራሉና።
10ስለ ጽድቅ ብለው የሚሰደዱ ብፁዓን
ናቸው፤
መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ናትና።

11ሰዎች በእኔ ምክንያት ቢሰድቧችሁ፣
ቢያሳድዷችሁና ክፉውን ሁሉ በሐሰት ቢያ
ስወሩባችሁ፤ ብፁዓን ናችሁ። 12በሰማይ
የምትቀበሉት ዋጋ ታላቅ ስለ ሆነ ደስ
ይበላችሁ፤ ሐሤት አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት
የነበሩትን ነቢያት እንደዚሁ አሳደዋቸዋልና።

## ጨውና ብርሃን

13"እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው
የጨውነት ጣዕሙን ቢያጣ ጣዕሙን መልሶ
ሊያገኝ ይችላልን? ወደ ውጪ ተጥሎ በሰው
ከመረገጥ በቀር ጥቅም አይኖረውም።
14"እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ፤ በተራራ
ላይ ያለች ከተማ ልትደበቅ አትችልም፤
15ሰዎችም መብራት አብርተው ከዕንቅብ
ሥር አያስቀምጡትም፤ በቤት ውስጥ ላሉት
ሁሉ እንዲያበራ በመቅረዝ ላይ ያስቀምጡ
ታል እንጂ። 16እንደዚሁም ሰዎች ሥራች
ሁን አይተው በሰማይ ያለውን አባታችሁን
እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰዎች ፊት ይብራ።

## የሕግ ፍጻሜ

17"ሕግንና የነቢያትን ቃል ለመሻር የመ
ጣሁ አይምሰላችሁ፤ ለመፈጸም እንጂ
ለመሻር አልመጣሁም። 18እውነት እላች
ኋለሁ፤ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ
ሕግ ሁሉ ይፈጸማል እንጂ ከሕግ አንዲት
ፊደል ወይም አንዲት ነጥብ እንኳ
አትሻርም። 19ስለዚህ ማንም ከእነዚህ ትእ
ዛዛት አነስተኛዪቱን እንኳን ቢተላለፍ፣
ሌሎችንም እንዲተላለፉ ቢያስተምር በመ
ንግሥተ ሰማይ ታናሽ ተብሎ ይጠራል፤
ነገር ግን እነዚህን ትእዛዛት እየፈጸመ
ሌሎችም እንዲፈጽሙ የሚያስተምር በመ
ንግሥተ ሰማይ ታላቅ ይባላል። 20ጽድቃ
ችሁ ከፈሪሳውያንና ከኦሪት ሕግ መምህራን
ጽድቅ ልቆ ካልተገኘ መንግሥተ ሰማይ
መግባት አትችሉም።

## ነፍስ መግደል አይገባም

5፥25፡26 ተጓ ምብ - ሉቃ 12፥58፡59

21"ለቀደሙት ሰዎች፣ 'አትግደል፤ የገ
ደለ ይፈረድበታል' እንደ ተባለ ሰምታች
ኋል፤ 22እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ወንድሙን
ያለ አግባብ የሚቈጣ ይፈረድበታል፤ ማንም
ወንድሙን 'ጅል' የሚል በሸንጎ ፊት
ይጠየቅበታል፤ 'ደደብ' የሚለው ደግሞ
የገሃነመ እሳት ፍርድ ይጠብቀዋል።
23"ስለዚህ መባህን በመሠዊያው ላይ
ለእግዚአብሔር በምታቀርብበት ጊዜ ወን
ድምህ የተቀየመብህ ነገር መኖሩ ትዝ ቢልህ፣
24መባህን በዚያው በመሠዊያው ፊት ተወው፤
በመጀመሪያ ሄደህ ከወንድምህ ጋር ተስማማ፤
ከዚያም ተመልሰህ መባህን ለእግዚአብሔር
አቅርብ።
25"የከሰሰህ ባላጋራህ እንዳያስፈርድብህ፣
ዳኛውም ለአሳሪ አሳልፎ እንዳይሰጥህ፣ በወ
ህኒም እንዳትጣል፣ በመንገድ ላይ ሳለህ ከባ

4፥22 ቊ19
4፥23 ማቴ3፥2፤ 8፥16፤9፥35፤13፥54፤14፥14፤15፥30፤ማር 1፥14፡21፡39፤3፥10፤ ሉቃ4፥15፡44፤7፥22፤ ዮሐ6፥59፤18፥20፤ ሐሥ10፥38፤20፥25፤ 28፥23፡31
4፥24 ማቴ8፥6፡16፡ 28፤9፥2፡32፤12፥22፤ 15፥22፤17፥15፤ማር 1፥32፤2፥3፤5፥15፡16፡18፤ሉቃ2፥2
4፥25 ማር 3፥7፡8፤ ሉቃ6፥17
5፥3 ቊ10፡19፤ ማቴ25፥34
5፥4 ኢሳ61፥2፡3፤ ራእ7፥17
5፥5 መዝ37፥11፤ ሮሜ4፥13
5፥6 ኢሳ55፥1፡2
5፥7 ያዕ2፥13
5፥8 መዝ17፥15፤ 24፥3፡4፤42፥2፤73፥1፤ዕብ12፥14፤ራእ22፥4
5፥9 ቊ44፡45፤ ሮሜ8፥14፤14፥19፤ ያዕ 3፥18
5፥10 ቊ3፡19፤ ማቴ 25፥34፤ 1ጴጥ3፥14
5፥11 ኢሳ51፥7፤ ዮሐ15፥21
5፥12 2ዜና36፥16፤ መዝ9፥2፤ማቴ23፥31፡ 37፤ ሐሥ5፥41፤7፥52፤ 2ቆሮ6፥10፤12፥10፤ ቈላ1፥24፤1ተሰ2፥15፤ዕብ11፥32-38፤ ያዕ 1፥2፤1ጴጥ1፥6፤ 4፥13፡16
5፥13 ማር9፥50፤ ሉቃ14፥34፡35
5፥14 ዮሐ8፥12
5፥15 ማር4፥21፤ ሉቃ8፥16፤11፥33
5፥16 ማቴ9፥8፤ 1ቆሮ10፥31፤ፊል 1፥11፤ቲቶ2፥14
5፥17ዮሐ10፥34፡35፤ ሮሜ3፥31
5፥18 መዝ119፥89፤ ኢሳ40፥8፤55፥11፤ ማቴ24፥35፤ ማር13፥31፤ ሉቃ16፥17፤ 21፥33
5፥19 ያዕ2፥10
5፥20 ኢሳ26፥2፤ ማቴ18፥3፤ዮሐ3፥5
5፥21 ዘፀ20፥13፤ 21፥12፤ዘዳ5፥17
5፥22 መክ7፥9፤ ማቴ18፥9፤26፥59፤ ማር9፥43፡48፤ ሉቃ16፥24፤ ዮሐ11፥47፤ ሐሥ 5፥21፡27፡ 34፡41፤ 6፥12፤ 1ቆሮ13፥5፤

ኤፌ4፥26፤ያዕ1፥19፡ 20፤3፥6፤1ዮሐ3፥15

ላጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ። 26እውነት
እልሃለሁ፤ ካስፈረደብህ ግን የመጨረሻዋን
ሳንቲም[ሽ] እስክትከፍል ድረስ ከዚያ አትወ
ጣም።

## ማመንዘር አይገባም

27“ ‘አታመንዝር’ እንደ ተባለ ሰምታች
ኋል። 28እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ሴትን በም
ኞት ዓይን የተመለከተ ሁሉ በልቡ ከእ
ርሷ ጋር አመንዝሮአል። 29ቀኝ ዓይንህ
የኀጢአት ሰበብ ቢሆንብህ፣ አውጥተህ
ወዲያ ጣለው፤ ሰውነትህ በሙሉ ወደ ገሃ
ነም ከሚጣል ከሰውነትህ አንዱን ክፍል
ብታጣ ይሻልሃል። 30ቀኝ እጅህ የኀጢአት
ሰበብ ቢሆንብህ ቈርጠህ ወዲያ ጣለው፤
ሰውነትህ በሙሉ ወደ ገሃነም ከሚጣል
ከሰውነትህ አንዱን ክፍል ብታጣ ይሻልሃል።
31“ ‘ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ የፍቺ ወረ
ቀት መስጠት አለበት’ እንደተባለ ሰምታ
ችኋል። 32እኔ ግን እላችኋለሁ፤ በላዩ ላይ
ስታመነዝር ካላገኛት በስተቀር፣ ሚስቱን
የሚፈታ ሁሉ እንድታመነዝር ያደርጋ
ታል፤ በዚህ ሁኔታ የተፈታችውን ሴት
ያገባም እንዳመነዘረ ይቈጠራል።

## ስለ መሐላ

33“ለቀደሙት ሰዎች፣ ‘በሐሰት አትማል፤
በእግዚአብሔር ፊት የማልኸውንም ጠብቅ’
እንደ ተባለ ሰምታችኋል። 34እኔ ግን ፈጽሞ
አትማሉ እላችኋለሁ፤ በሰማይም ቢሆን
አትማሉ፤ የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና፤
35በምድርም ቢሆን አትማሉ፤ የእግዚአብሔር
የእግሩ ማረፊያ ናትና፤ በኢየሩሳሌምም
አትማሉ፤ የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና
36በራሳችሁም ቢሆን አትማሉ፤ ከጠጕራ
ችሁ መካከል አንዲቷን እንኳ ነጭ ወይም
ጥቍር ማድረግ አትችሉምና። 37ስለዚህ
ስትነጋገሩ ቃላችሁ፣ ‘አዎን’ ከሆነ፣ ‘አዎን’፤
አይደለም፣ ከሆነ ‘አይደለም’ ይሁን፤ ከዚህ
ውጭ የሆነ ሁሉ ከክፉው የሚመጣ
ነውና።

## ስለ መበቀል

38“ ‘ዓይን ስለ ዓይን፣ ጥርስ ስለ ጥርስ’
እንደ ተባለ ሰምታችኋል። 39እኔ ግን
እላችኋለሁ፤ ‘ክፉ አድራጊውን ሰው
አትቃወሙት’፤ ነገር ግን ቀኝ ጕንጭህን
ለሚመታህ ሌላውን ጕንጭህን ደግሞ
አዙርለት። 40አንድ ሰው እጀ ጠባብህን ሊወ
ስድ ቢከስህ ካባህን ጨምረህ ስጠው።
41አንድ ሰው አንድ ኪሎ ሜትር ተኩል
የሚያህል ርቀት እንድትሄድ ቢያስገድ
ድህ ዕጥፉን መንገድ አብረኸው ሂድ።

5፥27 ዘፀ20፥14፤
ዘዳ5፥18
5፥28
ምሳ6፥25፤2ጴጥ2፥14
5፥29 ቈ30፤ማቴ
18፥6፡8፡9፤ማር9፥42-
47፤ሉቃ17፥2፤
ሮሜ14፥21፤
1ቆሮ8፥13፤
2ቆሮ6፥3፤11፥29
5፥30 ቈ29
5፥31 ዘዳ24፥1-4
5፥32 ሉቃ16፥18
5፥33 ዘሌ19፥12፤
ዘኍ30፥2፤ዘዳ23፥21፤
ማቴ23፥16-22
5፥34 ኢሳ66፥1፤
ማቴ23፥22፤ያዕ5፥12
5፥35 መዝ48፥2
5፥37 ማቴ6፥13፤
13፥19፡38፤ዮሐ17፥
15፤ኤፌ6፥16፤
2ተሰ 3፥3፤ያዕ5፥12፤
1ዮሐ 2፥13፡14፤
3፥12፤ 5፥18፡19
5፥38 ዘፀ21፥24፤
ዘሌ24፥20፤ዘዳ19፥21
5፥39 ሉቃ6፥29፤
ሮሜ12፥17፡19፤
1ጴጥ3፥9
5፥42 ዘዳ15፥8፤
ሉቃ6፥30
5፥43 ዘሌ19፥18፤
ዘዳ23፥6፤መዝ139፥
21፡22፤ማቴ19፥19፤
22፥39፤ማር12፥31፤
ሉቃ10፥27፤ሮሜ13
፥9፤ገላ5፥14፤ያዕ2፥8
5፥44 ሉቃ6፥27፡28
፤23፥34፤ዮሐ15፥20፤
ሐሥ7፥60፤
ሮሜ8፥35፤12፥14፤
1ቆሮ 4፥12፤
1ጴጥ2፥23
5፥45 ቈ9፤ኢዮ
25፥3፤ሉቃ6፥35፤
ሮሜ8፥14
5፥46 ሉቃ6፥32
5፥48 ዘሌ19፥2፤
1ጴጥ1፥16
6፥1 ማቴ5፥16፤
23፥5
6፥4 ቈ6፥18፤
ቈላ 3፥23፡24
6፥5 ማር11፥25፤
ሉቃ18፥10-14
6፥6 2ነገ4፥33
6፥7 1ነገ18፥26-
29፤መክ5፥2
6፥8 ቈ32

42ለሚለምንህ ስጥ፤ ከአንተም ሊበደር
የሚሻውን ፊት አትንሣው።
43“ ‘ወዳጅህን ውደድ፤ ጠላትህን ጥላ’
እንደ ተባለ ሰምታችኋል። 44እኔ ግን ጠላ
ቶቻችሁን ውደዱ[ቀ]፤ ለሚያሳድዷችሁም
ጸልዩ እላችኋለሁ። 45እንደዚህም በማድ
ረጋችሁ በሰማይ ላለው አባታችሁ ልጆች
ትሆናላችሁ፤ እርሱ ፀሓዩን ለክፉዎችና
ለደጎች ያወጣል፤ ዝናቡንም ለኀጢአተኞ
ችና ለጻድቃን ያዘንባል። 46የሚወዷችሁን
ብቻ የምትወዱ ከሆነ ምን ዋጋ ታገኛላ
ችሁ? ቀራጮችስ ይህንኑ ያደርጉ የለ
ምን? 47ወንድሞቻችሁን ብቻ እጅ የም
ትነሡ ከሆነ ከሌሎች በምን ትሻላላችሁ?
አሕዛብስ ይህንኑ ያደርጉ የለምን? 48ስለዚህ
የሰማይ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እና
ንተም ፍጹማን ሁኑ።”

## ስለ ምጽዋት አሰጣጥ

6 “ሰዎች እንዲያዩላችሁ፣ መልካም ሥራ
ችሁን በፊታቸው ከማድረግ ተጠን
ቀቁ፤ እንዲህ ካደረጋችሁ ከሰማዩ አባታ
ችሁ ዋጋ አታገኙም።
2“በሰዎች ዘንድ ለመከበር ብለው በየ
ጎዳናውና በየምኵራቡ ጥሩምባ እንደሚያ
ስነፉ ግብዞች፣ እናንተም ለድኾች ምጽዋት
በምትሰጡበት ጊዜ ይታይልኝ ብላችሁ
አታድርጉ፤ እውነት እላችኋለሁ እንዲህ
የሚያደርጉ ዋጋቸውን በሙሉ ተቀብለ
ዋል። 3እናንተ ግን ለድኾች ስትሰጡ ቀኝ
እጃችሁ የሚያደርገውን ግራ እጃችሁ አይ
ወቅ፤ 4ምጽዋታችሁ በስውር ይሁን፤ በስ
ውር የተደረገውን የሚያይ አባታችሁም
ዋጋችሁን ይከፍላችኋል።

## ስለ ጸሎት

6፥9-13 ተጓ ምብ - ሉቃ 11፥2-4

5“ስትጸልዩ እንደ ግብዞች አትሁኑ፤ እነ
ርሱ ለሰዎች ለመታየት ሲሉ በየምኵራ
ቡና በየመንገዱ ማእዘን ላይ ቆመው መጸ
ለይ ይወዳሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፤
ሙሉ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። 6አንተ ግን
ስትጸልይ ወደ ክፍልህ ግባ፤ በሩንም ዘግ
ተህ በስውር ወዳለው አባትህ ጸልይ፤
በስውር የተደረገውን የሚያይ አባትህም
ዋጋህን ይከፍልሃል። 7ስትጸልዩ፣ ከንቱ
ቃላት በመደጋገም ጸሎታቸው የሚሰማላ
ቸው እንደሚመስላቸው አሕዛብ ነገራ
ችሁን አታስረዝሙ። 8እነርሱን አትምሰ
ሏቸው፤ አባታችሁ ከመለመናችሁ በፊት
ምን እንደሚያስፈልጋችሁ ያውቃልና።

[ሽ]26 ግሪኩ ኮድራንቴስ ይላል
[ቀ]44 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *የሚረግሟችሁን መርቁ፤ ለሚጠ
ሏችሁ መልካም አድርጉ* ይላሉ

9“እናንተ ግን እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ፤
“ ‘በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፤
ስምህ ይቀደስ፤
10መንግሥትህ ትምጣ፤
ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች፣
እንዲሁ በምድር ትሁን።
11የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን።
12እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር
እንደምንል፣
በደላችንን ይቅር በለን።
13ወደ ፈተናም አታግባን
ከክፉው አድነን እንጂ፣
(መንግሥት፣ ኃይል፣ ክብርም፣
ለዘለዓለሙ ያንተ ነውና፤ አሜን።)[ሀ]

14እናንተ የበደሏችሁን ይቅር ብትሉ የሰ
ማዩ አባታችሁ ደግሞ እናንተን ይቅር
ይላችኋል። 15ነገር ግን የሰዎችን ኀጢአት
ይቅር የማትሉ ከሆነ፣ አባታችሁም ኀጢአ
ታችሁን ይቅር አይልላችሁም።

## ስለ ጾም

16“ስትጾሙ እንደ ግብዞች አትጠ
ውልጉ፤ እነርሱ መጾማቸው እንዲ
ታወቅላቸው ሆን ብለው በፊታቸው ላይ
የሐዘን ምልክት ያሳያሉና፤ እውነት
እላችኋለሁ፤ እንዲህ የሚያደርጉ ዋጋቸውን
በሙሉ ተቀብለ ዋል።
17አንተ ግን በምትጾምበት ጊዜ ፊት
ህን ታጠብ፤ ራስህንም ተቀባ፤ 18በዚህም
መጾምህ በስውር ያለው አባትህ ብቻ የሚ
ያውቀው፣ ከሰዎች ግን የተሰወረ ይሆናል፤
በስውር የተደረገውን የሚያይ አባትህም
ዋጋህን ይከፍልሃል።

## ሰማያዊ ሀብት

6፥22፡23 ተጓ ምብ - ሉቃ 11፥34-36

19“ብል ሊበላው፣ ዝገት ሊያበላሸው፣
ሌባም ቈፍሮ ሊሰርቀው በሚችልበት በዚህ
ምድር ላይ ለራሳችሁ ሀብት አታከማቹ።
20ነገር ግን ብል ሊበላው፣ ዝገት ሊያበላ
ሸው፣ ሌባም ቈፍሮ ሊሰርቀው በማይችል
በት በዚያ በሰማይ ለራሳችሁ ሀብት አከ
ማቹ፤ 21ሀብትህ ባለበት ልብህም በዚያው
ይሆናልና።
22“ዐይን የሰውነት መብራት ነው፤ ስለዚህ
ዐይንህ ጤናማ ከሆነ መላው ሰውነትህ
በብርሃን የተሞላ ይሆናል። 23ዐይንህ ታማሚ
ከሆነ ግን መላው ሰውነትህ በጨለማ የተ
ሞላ ይሆናል። እንግዲህ በአንተ ውስጥ
ያለው ብርሃን ጨለማ ከሆነ፣ ጨለማው
እንዴት ድቅድቅ ይሆን?
24“አንድ ሰው ሁለት ጌቶችን ማገልገል
አይችልም፤ አንዱን ጠልቶ ሌላውን ይወ

6፥9 ኤር3፥19፤
ሚል 2፥10፤
1ጴጥ1፥17
6፥10 ማቴ3፥2፤
26፥39
6፥11 ምሳ30፥8
6፥12ማቴ18፥21-35
6፥13 ማቴ5፥37፤
ያዕ1፥13
6፥14ማቴ18፥21-35፤
ማር11፥25፡26፤
ኤፌ 4፥32፤
ቈላ3፥13
6፥15 ማቴ18፥35
6፥16 ዘሌ16፥29፡31
፤23፥27-32፤
ዘኍ 29፥7፤
ኢሳ58፥5፤
ዘካ 7፥5፤8፥19
6፥18 ቍ4፡6
ምሳ23፥4፤
ሉቃ12፥16-21፤
ዕብ 13፥5፤ያዕ5፥2፡3
6፥20 ማቴ19፥21፤
ሉቃ12፥33፤16፥9፤
18፥22፤1ጢሞ6፥19
6፥21 ሉቃ12፥34
6፥24 ሉቃ16፥13
6፥25 ቍ27፡28፡31፡
34፤ሉቃ10፥41፤
12፥11፡22
6፥26 ኢዮ38፥41፤
መዝ 104፥21፤136፥
25፤145፥15፤147፥9፤
ማቴ10፥29-31
6፥27 መዝ39፥5
6፥29 1ነ10፥4-7
6፥30 ማቴ8፥26፤
14፥31፥16፥8፤
ሉቃ 12፥28
6፥32 ቍ8
6፥33 መዝ37፥4፤
ማቴ3፥2፤19፥29
7፥1 ሉቃ6፥37፤
ሮሜ14፥4፡10፡13፤
1ቆሮ4፥5፤5፥12፤
ያዕ 4፥11፡12
7፥2 ሕዝ35፥11፤
ማር4፥24፤
ሉቃ6፥38፤ሮሜ2፥1

ዳል፤ ወይም አንዱን አክብሮ ሌላውን ይን
ቃል። እግዚአብሔርንና ገንዘብን በአንድ
ነት ማገልገል አይቻልም።

## አለመጨነቅ

6፥25-33 ተጓ ምብ - ሉቃ 12፥22-31

25ስለዚህ እላችኋለሁ፣ ስለ ኑሮአችሁ
ምን እንበላለን? ምን እንጠጣለን? ምንስ
እንለብሳለን? በማለት አትጨነቁ። ሕይ
ወት ከምግብ፣ ሰውነትስ ከልብስ አይበል
ጥምን? 26እስቲ የሰማይ ወፎችን ተመል
ከቱ፤ አይዘሩም፤ አያጭዱም፤ በጐተራም
አያከማቹም፤ ይሁን እንጂ የሰማዩ አባታ
ችሁ ይመግባቸዋል። እናንተ ከእነርሱ እጅግ
አትበልጡምን? 27ለመሆኑ ከእናንተ መካ ከል
ተጨንቆ በዕድሜው ላይ አንዲት ሰዓት[†]
መጨመር የሚችል አለን?
28“ደግሞስ ስለ ልብስ ለምን ትጨነቃላ
ችሁ? እስቲ የሜዳ አበቦችን ተመልከቱ፤
አይለፉም፤ ወይም አይፈትሉም። 29ስለዚህ
እላችኋለሁ፤ ያን ያህል ክብር የነበረው
ንጉሥ ሰሎሞን እንኳ ከእነዚህ አበቦች
እንደ አንዲቱ አልለበሰም። 30እናንተ እም
ነት የጐደላችሁ! እግዚአብሔር ዛሬ ታይቶ
በነጋታው እሳት ውስጥ የሚጣለውን የሜዳ
ሣር ይህን ያህል ካለበሰ እናንተንማ እን
ዴት አብልጦ አያለብሳችሁ? 31ስለዚህ፣
‘ምን እንበላለን? ምን እንጠጣለን? ምንስ
እንለብሳለን?’ ብላችሁ አትጨነቁ፤ 32አሕ
ዛብ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ለማግኘት ይጨ
ነቃሉና፤ የሰማዩ አባታችሁም እነዚህ ሁሉ
ለእናንተ እንደሚያስፈልጓችሁ ያውቃል።
33ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔ
ርን መንግሥትና ጽድቁን እሹ፤ እነዚህ
ሁሉ ይጨመሩላችኋል። 34ስለዚህ ለነገ በማ
ሰብ አትጨነቁ፤ የነገ ጭንቀት ለነገ
ይደር፤ እያንዳንዱ ዕለት የራሱ የሆነ በቂ
ችግር አለውና”።

## በሌሎች ላይ አለ መፍረድ

7፥3-5 ተጓ ምብ - ሉቃ 6፥41፡42

7 “እንዳይፈረድባችሁ በማንም ሰው ላይ
አትፍረዱ፤ 2በምትፈርዱበትም ዐይነት
ይፈረድባችኋል፤ በምትሰፍሩበትም መስፈ
ሪያ ይሰፈርላችኋል።
3“በዐይንህ ውስጥ ያለውን ግንድ ሳት
መለከት፣ በወንድምህ ዐይን ያለውን ጕድፍ
ለምን ታያለህ? 4በዐይንህ ውስጥ ግንድ
እያለ ወንድምህን፣ ‘ዐይንህ ውስጥ ያለውን
ጕድፍ ላውጣልህ’ ማለት እንዴት ትችላ
ለህ? 5አንተ ግብዝ፤ አስቀድመህ በዐይንህ

[ሀ]13 በግሪኩ ይህ የለም፤ ሆኖም በሌሎቹ የጥንት ትርጕሞች ይገኛል
[†]27 ወይም *በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ*

ውስጥ ያለውን ግንድ አውጣ፤ ከዚያም በወንድምህ ዐይን ውስጥ ያለውን ጕድፍ ለማውጣት አጥርተህ ታያለህ።

6“በእግራቸው እንዳይረግጡት፣ ተመልሰውም ነክሰው እንዳይቦጫጭቋችሁ፣ የተቀደሰ ነገር ለውሾች አትስጡ፤ ዕንቈቻችሁንም በእሪያ ፊት አትጣሉ።

### ለምኑ፤ ፈልጉ፤ አንኳኩ

7፥7-11 ተጓ ምብ - ሉቃ 11፥9-13

7“‘ለምኑ፣ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ፣ ታገኛላችሁ፤ አንኳኩ፣ በሩም ይከፈትላችኋል። 8የሚለምን ሁሉ ይሰጠዋል፤ የሚፈልግም ያገኛል፤ ለሚያንኳኳም በሩ ይከፈትለታል።

9“ከእናንተ መካከል ልጁ ዳቦ ቢለምነው፣ ድንጋይ የሚሰጥ አባት አለ? 10ወይንም ዓሣ ቢለምነው እባብ የሚሰጥ ይኖራልን? 11ታዲያ እናንተ ክፉዎች ሳላችሁ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፣ የሰማዩ አባታችሁማ ለሚለምኑት መልካም ስጦታን እንዴት አብልጦ አይሰጣቸውም? 12ሌሎች እንዲያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን ነገር እናንተም አድርጉላቸው፤ ኦሪትም፣ ነቢያትም በዚህ ይጠቃለላሉና።

### ጠባቡና ሰፊው በር

13“በጠባቡ በር ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው መንገድ ትልቅ፣ በሩም ሰፊ ነውና፤ ብዙዎችም በዚያ ይገባሉ። 14ወደ ሕይወት የሚያደርሰው ግን መንገዱ ቀጭን፣ በሩም ጠባብ ነው፤ የሚገቡበትም ጥቂቶች ብቻ ናቸው።

### ሐሰተኛ ነቢያት

15“በውስጣቸው ነጣቂ ተኵላዎች ሆነው ሳሉ የበግ ለምድ ለብሰው መካከላችሁ በመግባት ከሚያሸምቁ ሐሰተኛ ነቢያት ተጠንቀቁ። 16ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፤ ከእሾህ ቍጥቋጦ ወይን፣ ከኵርንችትስ በለስ ይለቀማልን? 17እንዲሁም ጥሩ ዛፍ ሁሉ ጥሩ ፍሬ፣ መጥፎ ዛፍ ግን መጥፎ ፍሬ ያፈራል። 18ጥሩ ዛፍ መጥፎ ፍሬ፣ መጥፎም ዛፍ ጥሩ ፍሬ ማፍራት አይችልም። 19ጥሩ ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል፤ ወደ እሳትም ይጣላል። 20ስለዚህ በፍሬአቸው ታውቋቸዋላችሁ።

21“በሰማይ ያለውን ያባቴን ፈቃድ ሳይፈጽም ‘ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤’ የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማይ አይገባም። 22በዚያ ቀን ብዙዎች፣ ‘ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤

7፥7 1ነገ3፥5፤ማቴ 18፥19፤21፥22፤ ዮሐ 14፥13፡14፤ 15፥7፡16፤16፥23፡24፤ ያዕ1፥5-8፤ 4፥2፡3፤5፥16፤ 1ዮሐ 3፥22፤ 5፥14፡15
7፥8 ምሳ8፥17፤ ኤር 29፥12፡13
7፥11 ያዕ1፥17
7፥12 ሉቃ6፥31፤ ሮሜ13፥8-10፤ገላ5፥14
7፥13 ሉቃ13፥24፤ ዮሐ10፥7፡9
7፥15 ኤር23፥16፤ ሕዝ22፥27፤ማቴ24፥24፤ሉቃ6፥26፤ሐሥ 20፥29፤2ጴጥ2፥1፤ 1ዮሐ4፥1፤ራእ16፥13
7፥16 ማቴ12፥33፤ ሉቃ6፥44፤ያዕ3፥12
7፥18 ሉቃ6፥43
7፥19 ማቴ3፥10
7፥21 ሆሴ8፥2፤ ማቴ3፥2፤12፥50፤25፥11፤ዮሐ13፥13፤ሮሜ 2፥13፤1ቆሮ12፥3፤ያዕ 1፥22፤1ዮሐ3፥18
7፥22 ማቴ10፥15፤ ሉቃ10፥20፤ሐሥ 19፥13፤1ቆሮ13፥1-3
7፥23 መዝ6፥8፤ ማቴ25፥12፡41፤ሉቃ 13፥25-27
7፥24 ቀኊ21፤ ያዕ 1፥22-25
7፥28 ማቴ11፥1፤ 13፥53፡54፤19፥1፤ 22፥33፤26፥1፤ማር 1፥22፤ 6፥2፤11፥18፤ ሉቃ4፥32፤ዮሐ7፥46
8፥2 ዘሌ13፥45፤ ማቴ9፥18፤10፥8፤ 11፥5፤15፥25፤18፥26፤ 20፥20፤26፥6፤ ሉቃ 5፥12፤17፥12
8፥4 ዘሌ14፥2-32፤ ማቴ9፥30፤12፥16፤ ማር5፥43፤7፥36፤ 8፥ 30፤ሉቃ4፥41፤ 17፥14
8፥6 ማቴ4፥24
8፥8 መዝ107፥20

በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህ አጋንንት አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ታምራት አላደረግንምን?’ ይሉኛል። 23በዚያ ጊዜ፣‘ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ክፉዎች፤ ከእኔ ራቁ!’ ብዬ በግልጽ እነግራቸዋለሁ።

### ብልኁና ሞኙ ቤት ሠሪ

7፥24-27 ተጓ ምብ - ሉቃ 6፥47-49

24“እንግዲህ ይህን ቃሌን ሰምቶ በተግባር የሚያውል፣ ቤቱን በዐለት ላይ የሠራን ብልኅ ሰው ይመስላል። 25ዶፍ ወረደ፤ ጐርፍም ጐረፈ፤ ነፋስም ነፈሰ፤ ያንን ቤት መታው፤ በዐለት መሠረትም ላይ ስለ ተመሠረተ አልወደቀም። 26ይህን ቃሌን ሰምቶ በተግባር የማያውለው ግን ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራን ሞኝ ሰው ይመስላል። 27ዶፍ ወረደ፤ ጐርፍም ጐረፈ፤ ነፋስም ነፈሰ፤ ያንን ቤት መታው፤ ቤቱም ወደቀ፤ አወዳደቁም የከፋ ነበር።”

28ኢየሱስ ማስተማሩን በፈጸመ ጊዜ፣ ሕዝቡ በትምህርቱ ተደነቁ። 29ምክንያቱም እንደ አይሁድ ሃይማኖት መምህራናቸው ሳይሆን እንደ ባለ ሥልጣን አስተምሮአቸው ስለ ነበር ነው።

### የለምጻሙ መንጻት

8፥2-4 ተጓ ምብ - ማር 1፥40-44፤ ሉቃ 5፥12-14

8 ከተራራው በወረደ ጊዜም ብዙ ሕዝብ ተከተለው። 2እነሆ፤ አንድ ለምጻም* ሰው ወደ ኢየሱስ ቀረበና ከፊቱ ተንበርክኮ እየሰገደለት፣ “ጌታ ሆይ፤ ብትፈቅድስ ልታነጻኝ ትችላለህ” አለው።

3ኢየሱስም እጁን ዘርግቶ ዳሰሰውና፣ “ፈቃዴ ነው፤ ንጻ!” አለው። ሰውየውም ወዲያውኑ ከለምጹ ነጻ። 4ከዚያም ኢየሱስ፣ “መፈወስህን ለማንም አታውራ፤ ነገር ግን ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ፤ ሙሴ ያዘዘውንም መባ አቅርብ፤ ይህም ምስክር ይሆንላቸዋል” አለው።

### የመቶ አለቃው እምነት

8፥5-13 ተጓ ምብ - ሉቃ 7፥1-10

5ኢየሱስ ቅፍርናሆም እንደ ደረሰ አንድ የመቶ አለቃ ቀርቦ፣ እንዲህ ሲል ለመነው፤ 6“ጌታ ሆይ፤ አገልጋዬ ሽባ ሆኖ እጅግ በመሠቃየት ከቤት ተኝቶአል” አለው።

7ኢየሱስም፣ “እኔ መጥቼ እፈውሰዋለሁ” አለው።

8የመቶ አለቃው ግን መልሶ እንዲህ አለ፤ “ጌታ ሆይ፤ ወደ ቤቴ እንድትገባ የሚገባኝ አይደለሁም፤ ነገር ግን ከዚሁ ሆነህ አን

*2 የግሪኩ ቃል የግድ ከለምጽ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን የተለያዩ የቆዳ በሽታዎችንም ያመለክታል

ዷት ቃል ብቻ ተናገር፤ አገልጋዬም ይፈ
ወሳል፤ 9እኔ ራሴ የምታዘዛቸው አለቆች፣
ለእኔም የሚታዘዙ የበታቾች አሉኝ፤ ከእ
ነርሱ አንዱን፣ ‘ሂድ!’ ስለው ይሄዳል፤ ሌላ
ውን፣ ‘ና!’ ስለው ይመጣል፤ አገልጋዬንም፣
‘ይህን አድርግ’ ስለው ያደርጋል።”
10ኢየሱስም በመልሱ ተደንቆ ይከተሉት
ለነበሩት እንዲህ አላቸው፤ “እውነት እላች
ኋለሁ፣ ከእስራኤል መካከል እንኳ እንዲህ
ያለ እምነት ያለው አንድ ሰው አላገኘ
ሁም፤ 11እላችኋለሁ፣ ብዙዎች ከምሥራቅና
ከምዕራብ ይመጣሉ፤ በመንግሥተ ሰማይ
ማእድ ዙሪያ ከአብርሃም፣ ከይስሐቅና ከያዕ
ቆብ ጋር ይቀመጣሉ፤ 12መንግሥተ ሰማይ
ተዘጋጅቶላቸው የነበሩት ግን ወደ ውጭ
ወደ ጨለማው ይጣላሉ። በዚያም ልቅሶና
ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።”
13ኢየሱስም መቶ አለቃውን፣ “ሂድ እንደ
እምነትህ ይሁንልህ” አለው። አገልጋዩም
በዚያች ቅጽበት ተፈወሰ።

## ኢየሱስ ብዙዎችን መፈወሱ

8፥14-16 ተጓ ምብ - ማር 1፥29-34፤ ሉቃ 4፥38-41

14ኢየሱስ ወደ ጴጥሮስ ቤት ጎራ ሲል
የጴጥሮስ ዐማት በትኵሳት ታማ ተኝታ
አገኛት። 15እጇን ዳሰሳት፤ ትኵሳቱም ለቀ
ቃት፤ ተነሥታም አገለገለችው።
16በዚያ ምሽት በአጋንንት የተያዙ ብዙ
ሰዎችን ወደ ኢየሱስ አመጡ፤ እርሱም
መናፍስትን በቃሉ አስወጣ፤ በሽተኞችንም
ሁሉ ፈወሰ። 17በዚህም ኢሳይያስ እንዲህ
ብሎ የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ፤

“እርሱ ደዌያችንን ተቀበለ፤
ሕመማችንንም ተሸከመ።”

## የኢየሱስ ተከታይ ለመሆን ውሳኔ ይጠይቃል

8፥19-22 ተጓ ምብ - ሉቃ 9፥57-60

18ኢየሱስ ብዙ ሰዎች በዙሪያው ተሰብስ
በው ባየ ጊዜ ወደ ባሕሩ ማዶ እንዲሻገሩ
አዘዛቸው። 19በዚህ ጊዜ አንድ የአይሁድ
ሃይማኖት መምህር ወደ እርሱ ቀርቦ፣
“መምህር ሆይ፤ ወደምትሄድበት ሁሉ እከ
ተልሃለሁ” አለው።
20ኢየሱስም፣ “ቀበሮዎች ጕድጓድ፣ የሰ
ማይ ወፎችም ጎጆ አላቸው፤ የሰው ልጅ
ግን ራሱን የሚያስጠጋበት ቦታ የለውም”
ሲል መለሰለት።
21ደቀ መዝሙር የሆነ አንድ ሌላ ሰው
ደግሞ፣ “ጌታ ሆይ፤ መጀመሪያ ሄጄ አባ
ቴን እንድቀብር ፍቀድልኝ” አለው።
22ኢየሱስ ግን፣ “ሙታን ሙታናቸውን
ይቅበሩ፤ አንተ ተከተለኝ” አለው።

8፥10 ማቴ15፥28
8፥11 መዝ107፥3፤ ኢሳ49፥12፤59፥19፤ ሚል1፥11፤ ሉቃ 13፥29
8፥12 ማቴ13፥38፡ 42፡50፤22፥13፤ 24፥51፤25፥30፤ ሉቃ 13፥28
8፥13 ማቴ9፥22
8፥16 ማቴ4፥23፡24
8፥17 ኢሳ53፥4፤ ማቴ1፥22
8፥18 ማር4፥35
8፥20 ዳን7፥13፤ ማቴ12፥8፡32፡40፤ 16፥13፡27፡28፤17፥9፤ 19፥28፤ ማር2፥10፤8፥31
8፥22 ማቴ4፥19
8፥26 መዝ65፥7፤ 89፥9፤107፥29፤ ማቴ6፥30
8፥28 ማቴ4፥24
8፥29 መሳ11፥12፤ 2ሳሙ16፥10፤1ነገ 17፥18፤ማር1፥24፤ ሉቃ4፥34፤ዮሐ2፥4፤ 2ጴጥ2፥4
8፥34 ሉቃ5፥8፤ ሐሥ16፥39
9፥1 ማቴ4፥13
9፥2 ቈ22፤ማቴ 4፥24፤ዮሐ16፥33፤ ሉቃ7፥48

## ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ አደረገ

8፥23-27 ተጓ ምብ - ማር 4፥36-41፤ ሉቃ 8፥22-25
8፥23-27 ማመ - ማቴ 14፥22-23

23ከዚያም ኢየሱስ ወደ ጀልባ ገባ፤ ደቀ
መዛሙርቱም ተከትለውት ገብተው ሄዱ።
24ድንገት ኀይለኛ ማዕበል ተነሥቶ ጀል
ባዪቱን እስኪሸፍን ድረስ አወካቸው፤ በዚህ
ጊዜ ግን ኢየሱስ ተኝቶ ነበር። 25ደቀ መዛ
ሙርቱም ቀርበው ቀሰቀሱትና፣ “ጌታ ሆይ!
ጠፋን፤ አድነን” አሉት።
26ኢየሱስም፣ “እናንተ እምነት የጐደላ
ችሁ፤ ለምን ይህን ያህል ፈራችሁ!” አላ
ቸው፤ ከዚያም ተነሥቶ ነፋሱንና ማዕ
በሉን ገሠጸ፤ ወዲያውም ጸጥታ ሰፈነ።
27ሰዎቹም፣ “ነፋስና ባሕር እንኳ የሚታ
ዘዙለት፣ ይህ እንዴት ያለ ሰው ነው?” እያሉ
ተደነቁ።

## ከርኩሳን መናፍስት ስለ ተፈወሱ ሁለት ሰዎች

8፥28-34 ተጓ ምብ - ማር 5፥1-17፤ ሉቃ 8፥26-27

28ባሕሩን ተሻግሮ ጌርጌሴኖን[ኀ]
ወደሚባል አገር እንደ ደረሰ፣ አጋንንት
ያደሩባቸው ሁለት ሰዎች ከሚኖሩበት
የመቃብር ቦታ ወጥተው ተገናኙት። በዚ
ያ መንገድ ሰው ማለፍ እስከማይችል
ድረስ እጅግ አደገ ኞች ነበሩ።
29እነርሱም “የእግዚአብሔር ልጅ ሆይ፤
ከእኛ ምን ጕዳይ አለህ? ጊዜው ሳይደርስ
ልታሠቃየን መጣህን?” እያሉ ጮኹ።
30ከእነርሱ ትንሽ ራቅ ብሎ፣ የብዙ ዐሣማ
መንጋ ተሰማርቶ ነበር። 31አጋንንቱም ኢየ
ሱስን፣ “የምታስወጣን ከሆነ ዐሣማዎቹ
መንጋ ውስጥ እንድንገባ ፍቀድልን” ብለው
ለመኑት። 32ኢየሱስም፣ ‘ሂዱ!’ አላቸው።
አጋንንቱም ከሰዎቹ ወጥተው ዐሣማዎቹ
ውስጥ ገቡ፤ ዐሣማዎቹም በሙሉ ከነበሩ
በት አፋፍ እየተጣደፉ ባሕሩ ውስጥ
በመግባት ውሃው ውስጥ ሰጥመው ሞቱ።
33የዐሣማዎቹ ጠባቂዎችም ሸሽተው ወደ
ከተማ በመሄድ፣ የሆነውን ሁሉና በአጋ
ንንት ተይዘው በነበሩት ሰዎች ላይ የተ
ደረገውን ነገር አወሩ። 34እነሆም፤ መላው
የከተማ ነዋሪ ኢየሱስን ለመገናኘት ወጣ፤
ባዩትም ጊዜ አገራቸውን ለቅቆ እንዲሄድ
ለመኑት።

## የሽባው ሰው መፈወስ

9፥2-8 ተጓ ምብ - ማር 2፥3-12፤ ሉቃ 5፥18-26

9 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ባሕሩን በጀልባ
ተሻግሮ ወደ ራሱ ከተማ መጣ። 2በዚያም
ሰዎች አንድ ሽባ ሰው በቃሬዛ ተሸክመው

ኀ28 አንዳንድ ቅጆች ጌራሴኖን ይላሉ

ወደ እርሱ አመጡ:: ኢየሱስም እምነታቸ
ውን አይቶ ሽባውን፣ “አይዞህ አንተ ልጅ፤
ኀጢአትህ ተሰርዮልሃል” አለው::
[3]በዚህን ጊዜ የአይሁድ ሃይማኖት መም
ህራን፣ “ይህማ እግዚአብሔርን መሳደብ
ነው” በማለት በልባቸው አጕረመረሙ::
[4]ኢየሱስ ሐሳባቸውን ተረድቶ እንዲህ
አለ፤ “ክፉ ነገር በልባችሁ ለምን ታስባ
ላችሁ? [5]ለመሆኑ፣ ‘ኀጢአትህ ይቅር ተብ
ሎልሃል’ ከማለትና ‘ተነሥተህ ሂድ’ ከማ
ለት የቱ ይቀላል? [6]ነገር ግን የሰው ልጅ
በምድር ላይ ኀጢአትን የማስተስረይ
ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ ነው’
ብሎ፣ ሽባውን፣ ‘ተነሣ! ቃሬዛህን ይዘህ ወደ
ቤትህ ሂድ’ አለው::” [7]ሽባውም ተነሥቶ
ወደ ቤቱ ሄደ:: [8]ሕዝቡም ይህን ባዩ ጊዜ
በመደነቅ፣ በፍርሃት ተሞልተው፣ እንደ
ዚህ ያለ ሥልጣን ለሰው የሰጠውን እግዚ
አብሔርን አመሰገኑ::

## የማቴዎስ መጠራት

9፥9-13 ተጓ ምብ - ማር 2፥14-17፤ ሉቃ 5፥27-32

[9]ኢየሱስ ከዚያ ተነሥቶ ሲሄድ ማቴዎስ
የሚባል አንድ ሰው በቀረጥ ማስከፈያ ኬላ
ተቀምጦ አየ፤ ‘ተከተለኝ’ አለው፤ እርሱም
ተነሥቶ ተከተለው::
[10]ኢየሱስ በማቴዎስ ቤት በማእድ ላይ ሳለ፣
ብዙ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና ኀጢአተኞች
መጥተው ከእርሱና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር
አብረው ሊበሉ ተቀመጡ:: [11]ፈሪሳውያ
ንም ይህን ባዩ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን፣
“መምህራችሁ ከቀረጥ ሰብሳቢዎችና ከኀጢ
አተኞች ጋር እንዴት አብሮ ይበላል?”
ብለው ጠየቋቸው::
[12]ኢየሱስም የተናገሩትን በመስማቱ እን
ዲህ አላቸው፤ “ሐኪም የሚያስፈልገው
ለሕመምተኞች እንጂ ለጤነኞች አይደ
ለም፤ [13]ሂዳችሁ፣ ‘ከመሥዋዕት ይልቅ
ምሕረትን እወዳለሁ፤’ ኀጢአተኞችን እንጂ
ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁምና የሚለ
ውን ቃል ትርጕም አጢኑ::”

## የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ያልጾሙበት ምክንያት

9፥14-17 ተጓ ምብ - ማር 2፥18-22፤ ሉቃ 5፥33-39

[14]የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት
ወደ ኢየሱስ ቀርበው፣ “እኛና ፈሪሳውያን
ስንጾም፣ ያንተ ደቀ መዛሙርት ግን
ለምን አይጾሙም?” ብለው ጠየቁት::
[15]ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “ሙሽራው
አብሮአቸው እያለ ሚዜዎቹ እንዴት ሊያ
ዝኑ ይችላሉ? ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድ
በት ጊዜ ይመጣል፤ በዚያን ጊዜ ይጾማሉ::
[16]በአሮጌ ልብስ ላይ አዲስ ዕራፊ የሚ
ጥፍ ሰው የለም፤ ይህ ከሆነ አዲሱ ዕራፊ
ካረጀው ልብስ ላይ ተቦጭቆ ቀዳዳውን
የባሰ ያሰፋዋል:: [17]በአሮጌ አቍማዳ አዲስ
የወይን ጠጅ ማንም አይጨምርም፤ ይህ
ከሆነ አቍማዳው ይፈነዳል፤ የወይን ጠጁም
ይፈስሳል፤ አቍማዳውም ከጥቅም ውጭ
ይሆናል:: ነገር ግን አዲስ የወይን ጠጅ
በአዲስ አቍማዳ ይጨመራል፤ በዚህ
ሁኔታ የወይን ጠጁና አቍማዳው በደህና
ተጠብቀው ይቈያሉ::

## ከሞት የተነሣችው ልጅና ከደም መፍሰስ የተፈወሰችው ሴት

9፥18-26 ተጓ ምብ - ማር 5፥22-43፤ ሉቃ 8፥41-56

[18]ኢየሱስ ሰዎቹን በማናገር ላይ ሳለ፣
አንድ ሹም ከፊቱ ተደፍቶ፣ “ልጄ ልት
ሞት ተቃርባለች፤ በሕይወት እንድትኖር
መጥተህ እጅህን ጫንባት” አለው:: [19]ኢየ
ሱስም ተነሥቶ አብሮት ሄደ፤ ደቀ መዛ
ሙርቱም ተከተሉት::
[20]ከዚያም ዐሥራ ሁለት ዓመት ሙሉ
ደም እየፈሰሳት ትሠቃይ የነበረች አንዲት
ሴት ከኋላው መጥታ የልብሱን ጫፍ ነካች::
[21]እርሷም በልቧ፣ “የልብሱን ጫፍ እንኳ
ብነካ እፈወሳለሁ” የሚል እምነት ነበራት::
[22]ኢየሱስም ወደ ኋላ ዘወር ብሎ ሴቲቱን
አያትና፣ “አይዞሽ፤ ልጄ ሆይ፤ እምነትሽ
አድኖሻል” አላት:: ሴቲቱም ወዲያውኑ
ተፈወሰች::
[23]ኢየሱስ ወደ ምኵራብ አለቃው ቤት
እንደ ደረሰ የሐዘን እምቢልተኞችንና
የሚንጫጫውን ሕዝብ አይቶ፣ [24]“ዞር በሉ፤
ልጅቱ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም”
አላቸው፤ እነርሱ ግን ሣቁበት:: [25]ሕዝቡም
ከወጣ በኋላ ወደ ውስጥ ገብቶ እጇን ያዘ፤
ልጅቱም ተነሥታ ቆመች:: [26]ወሬውም
በአካባቢው ሁሉ ተሰራጨ::

## የዐይነ ስውሮቹና የድዳው መፈወስ

[27]ኢየሱስም ከዚያ እንደ ሄደ ሁለት ዐይነ
ስውሮች፣ “የዳዊት ልጅ ሆይ፤ ማረን” በማ
ለት እየጮኹ ተከተሉት::
[28]ዐይነ ስውሮቹም ኢየሱስ ወደ ገባበት
ቤት ተከትለው ገቡ፤ ኢየሱስም፣ “ዐይናችሁን
ላበራላችሁ እንደምችል ታምናላችሁ?” ሲል
ጠየቃቸው::
እነርሱም፣ “አዎን፣ ጌታ ሆይ፤” ብለው
መለሱለት::
[29]ከዚያም ኢየሱስ ዐይናቸውን ዳስሶ፣
“እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ” አላቸው::

9፥3 ማቴ26፥65፤
ዮሐ10፥33
9፥4 መዝ94፥11፤
ማቴ12፥25፤ሉቃ6፥8፤
9፥47፤11፥17፤
ዮሐ 2፥25
9፥6 ማቴ8፥20
9፥8 ማቴ5፥16፤
15፥31፤ሉቃ7፥16፤
13፥13፤17፥15፤23፥
47፤ዮሐ15፥8፤ሐሥ
4፥21፤11፥18፤21፥20
9፥9 ማቴ4፥19
9፥11 ማቴ11፥19፤
ሉቃ5፥30፤15፥2፤
19፥7፤ገላ2፥15
9፥13 ሆሴ6፥6፤
ሚክ 6፥6-8፤
ማቴ12፥7፤
ሉቃ19፥10፤
1ጢሞ 1፥15
9፥14 ማቴ3፥1፤11፥
18፡19፤ሉቃ18፥12
9፥15 ዮሐ3፥29፤
ሐሥ13፥2፡3፤14፥23
9፥18 ማቴ8፥2፤
ማር5፥23
9፥20 ማቴ14፥36፤
ማር3፥10፤6፥56፤
ሉቃ6፥19
9፥22 ቍ2፡29፤ማቴ
8፥13፤15፥28፤ማር
10፥52፤ሉቃ7፥50፤
17፥19፤18፥42፥ዮሐ16
፥33
9፥23 2ዜና35፥25፤
ኤር9፥17፡18
9፥24መዝ76፥5፤
ዳን12፥2፤
ዮሐ11፥11-14፤
ሐሥ7፥60፤13፥36፤
20፥10፤1ቆሮ11፥30፤1
5፥6፡18፡20፤
1ተሰ 4፥13-16
9፥25 ሉቃ7፥14
9፥26 ቍ31፤
ማቴ4፥24፤14፥1፤
ማር1፥28፡45፤ሉቃ
4፥14፡37፤5፥15፤7፥17
9፥27 ማቴ1፥1፤
12፥23፤15፥22፤
20፥30፡31፤21፥9፡15፤
22፥42፤ማር10፥47
9፥28 ሐሥ14፥9
9፥29 ቍ22

30ዐይናቸውም በራ፤ ኢየሱስም፣ “ይህን
ማንም እንዳያውቅ” ብሎ በጥብቅ አስጠ
ነቀቃቸው፡፡ 31እነርሱ ግን ወጥተው በአ
ካባቢው ሁሉ ስለ ኢየሱስ አወሩ፡፡
32ከዚያም ሲወጡ፣ በጋኔን የተያዘ ድዳ
ሰው ወደ እርሱ አመጡ፡፡ 33ጋኔኑ ከወጣ
ለት በኋላ ድዳው መናገር ጀመረ፤ ሕዝ
ቡም ተደንቀው፣ “እንዲህ ያለ ነገር በእስ
ራኤል ምድር ታይቶ አያውቅም” አሉ፡፡
34ፈሪሳውያን ግን፣ “አጋንንትን የሚያወ
ጣው፣ በአጋንንት አለቃ ነው” አሉ፡፡

## ሠራተኞች ጥቂቶች ናቸው

35ኢየሱስ በምኵራቦቻቸው እያስተማረ፣
የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራች
እየሰበከ እንዲሁም ደዌንና ሕመምን ሁሉ
እየፈወሰ በከተሞቹና በመንደሮቹ ዞረ፡፡
36ሕዝቡም እረኛ እንደሌለው በግ ተጨን
ቀውና ተመልካች የለሽ ሆነው ባየ ጊዜ
አዘነላቸው፡፡
37ደቀ መዛሙርቱንም እንዲህ አላቸው፤
“መከሩ ብዙ ነው፤ የመከሩ ሠራተኞች
ግን ጥቂቶች ናቸው፤ 38ስለዚህ የመከሩ
ጌታ፣ ወደ መከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ
ለምኑት፡፡”

## የዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት መላክ

10፥2-4 ተጓ ምብ - ማር3፥16-19፤ ሉቃ6፥14-16፤ የሐሥ1፥13
10፥9-15 ተጓ ምብ - ማር 6፥8-11፤ ሉቃ 9፥3-5፤ 10፥4-12
10፥19-22 ተጓ ምብ - ማር 13፥11-13፤ ሉቃ 21፥12-17
10፥26-33 ተጓ ምብ - ሉቃ 12፥2-9
10፥34፡35 ተጓ ምብ - ሉቃ 12፥51-53

10 ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛ
ሙርት ወደ እርሱ ጠርቶ ርኵ
ሳን መናፍስትን እንዲያወጡ፣ ደዌንና ሕማ
ምን ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣንን ሰጣቸው፡፡
2የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ስም የሚከተ
ለው ነው፦ መጀመሪያ ጴጥሮስ የተባለው
ስምዖንና ወንድሙ እንድርያስ፣ የዘብዴ
ዎስ ልጅ ያዕቆብና ወንድሙ ዮሐንስ፣
3ፊልጶስና በርቶሎሜዎስ፣ ቶማስና ቀረጥ
ሰብሳቢው ማቴዎስ፣ የእልፍዮስ ልጅ ያዕ
ቆብና ታዴዎስ የተባለው ልብድዮስ፣ 4ቀነ
ናዊው[ነ] ስምዖንና በኋላ ኢየሱስን አሳልፎ
የሰጠው አስቆ ሮቱ ይሁዳ፡፡
5እነዚህን ዐሥራ ሁለቱን ኢየሱስ እንዲህ
ከሚል ትእዛዝ ጋር ላካቸው፤ “ወደ አሕ
ዛብ አትሂዱ፤ ወደ ሳምራውያንም ከተማ
አት ግቡ፡፡ 6ይልቁንስ የእስራኤል ቤት ወደ
ሆኑት ወደ ጠፉት በጎች ሂዱ፡፡ 7ሂዳ
ችሁም፣ ‘መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች’
ብላችሁ ስበኩ፡፡ 8በሽተኞችን ፈውሱ፤
ሙታንን አስነሡ፤ ለምጻሞችን[ኘ] አንጹ፤
አጋንንትን አስወጡ፤ በነጻ የተቀበላችሁት

9፥30 ማቴ8፥4
9፥31 ቍ26ማር7፥36
9፥32 ማቴ4፥24፤
12፥22-24
9፥33 ማር2፥12
9፥34 ማቴ12፥24
9፥35 ማቴ4፥23
9፥36 ዘኍ27፥17፤
1ነገ22፥17፤ሕዝ
34፥5፡ 6፤ዘካ10፥2፤
ማቴ14፥ 14፤15፥32፤
ማር8፥2
9፥37 ሉቃ10፥2፤
ዮሐ4፥35
10፥1 ማቴ4፥23፤
ማር3፥13-15፤6፥7፤
ሉቃ4፥36፤9፥1
10፥4 ማቴ26፥14-
16፡25፡47፤27፥3፤ማር
14፥10፤ዮሐ6፥71፤
12፥4፤13፥2፡26፡27፤ሐ
ሥ1፥16
10፥5 1ነገ16፥24፤
2ነገ17፥24፤ሉቃ9፥52፤
10፥33፤17፥16፥
ዮሐ 4፤4-26፡39፡40፤
8፥48፤ሐሥ8፥5፡25
10፥6 ኤር50፥6፤
ማቴ15፥24
10፥7 ማቴ3፥2
10፥9 ሉቃ22፥35
10፥10 1ጢሞ5፥18
10፥12 1ሳሙ25፥6
10፥14 ነህ5፥13፤
ማር6፥11፤ሉቃ9፥5፤
10፥11፤ሐሥ13፥51፤18፥6
10፥15 ዘፍ18፥20፤
19፥24፤ማቴ11፥22፡
24፤12፥36፤ሐሥ17፥
31፤2ጴጥ2፥6፡9፤3፥7፤
1ዮሐ4፥17፤ ይሁ6፡7
10፥16 ሉቃ10፥3፤
ሐሥ20፥29፤1ቆሮ
14፥20
10፥17 ማቴ5፥22፤
23፥34፤ማር13፥9፤
ሐሥ5፥40፤22፥19፤
26፥11
10፥18
ሐሥ25፥ 24-26
10፥19 ዘፀ4፥12
10፥20 ሉቃ12፥11፡
12፤ሐሥ4፥8
10፥21 ቍ35፡36፤
ሚክ7፥6፤ማር13፥12
10፥22 ማቴ24፥13፤
ማር13፥13፤
ሉቃ21፥19፤
ዮሐ15፥21፤
ራእ2፥10
10፥23 ሉቃ17፥30
10፥24 ዮሐ13፥16
10፥25 ማር3፥22

ንም በነጻ ስጡ፡፡ 9በመቀነታችሁ ወርቅም
ሆነ ብር ወይም መዳብ አትያዙ፡፡ 10ለመን
ገዳችሁም ከረጢት፣ ትርፍ እጀ ጠባብ
ወይም ጫማ ወይም በትር አትያዙ፤ ለሠ
ራተኛ የዕለት ጕርሱ ይገባዋልና፡፡
11“ወደ አንድ ከተማ ወይም መንደር
ስትገቡ ሊቀበላችሁ ፈቃደኛ የሆነ ሰው
ፈልጋችሁ በቤቱ ዕረፉ፤ እስክትወጡም
ድረስ በዚያው ቈዩ፡፡ 12ወደ ማንኛውም ሰው
ቤት ስትገቡ ሰላምታ አቅርቡ፡፡ 13ቤቱም
የሚገባው ሆኖ ከተገኘ፣ ሰላማችሁ ይድረ
ሰው፤ የማይገባው ከሆነ ግን ሰላማችሁ
ወደ እናንተ ይመለስላችሁ፡፡ 14ማንም ሰው
ሊያስተናግዳችሁ ወይም የምትናገሩትን
ሊሰማ ፈቃደኛ ካልሆነ፣ ከቤቱ ወይም
ከከተማው ስትወጡ የእግራችሁን ትቢያ
አራግፋችሁ ውጡ፡፡ 15እውነት እላችኋ
ለሁ፤ በፍርድ ቀን በዚያች ከተማ ከሚደር
ሰው ቅጣት ይልቅ በሰዶምና በገሞራ የሚ
ደርሰው ይቀላል፡፡
16“እንደ በጎች በተኵላዎች መካከል
እልካችኋለሁ፤ ስለዚህ እንደ እባብ ብል
ሆች እንደ ርግብ የዋሃን ሁኑ፡፡ 17ሰዎች
ይዘው ለፍርድ ወደ ሸንጎ ያቀርቧችኋል፤
በምኵራቦቻቸውም ይገርፏችኋል፤ ስለዚህ
ከእነርሱ ተጠንቀቁ፡፡ 18በእኔ ምክንያት
ወደ ገዦችና ወደ ነገሥታት ትወሰዳ
ላችሁ፤ በእነርሱና በአሕዛብም ፊት ምስ
ክር ትሆናላችሁ፡፡ 19በምትያዙበትም ጊዜ
ምን እንናገራለን፣ ምንስ እንመልሳለን
ብላችሁ አትጨነቁ፤ በዚያን ጊዜ የምት
ናገሩት ይሰጣችኋል፤ 20በእናንተ የሚና
ገረው የሰማዩ አባታችሁ መንፈስ እንጂ
እናንተ አይደላችሁምና፡፡
21“ወንድም ወንድሙን ለሞት አሳልፎ
ይሰጣል፤ አባትም ልጁን፤ ልጆች
በወላጆቻ ቸው ላይ ያምፃሉ፤
ያስገድሏቸዋልም፡፡ 22ስለ ስሜ ሰዎች ሁሉ
ይጠሏችኋል፤ ነገር ግን እስከ መጨረሻ
የሚጸና እርሱ ይድ ናል፡፡ 23በአንድ ስፍራ
ሲያሳድዷችሁ ወደ ሌላ ሽሹ፤ እውነት
እላችኋለሁ፣ የእስራኤ ልን ከተሞች
ሳታዳርሱ የሰው ልጅ ይመጣል፡፡
24“ደቀ መዝሙር ከመምህሩ፣ ሎሌም
ከጌታው አይበልጥም፤ 25ደቀ መዝሙር
መምህሩን፣ ሎሌም ጌታውን ከመሰለ ይበ
ቃዋል፡፡ ባለቤቱን ‘ብዔልዜቡል’ ካሉት
ቤተ ሰዎቹንማ እንዴት አብልጠው አይሏ
ቸውም!

[ነ]4 ቀነናዊ የሚለው ቃል አራማይክ ሲሆን፣ ቀነናውያን
የተባሉት በዚያን ጊዜ የሮምን መንግሥት የሚቃወሙ
የፖለቲካ ቡድን አባላት ነበሩ
[ኘ]8 የግሪኩ ቃል የግድ ከለምጽ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን
የቆዳ በሽታዎችን ያመለክታል

26“ስለዚህ አትፍሯቸው፤ የተሸፈነ መገለጡ፣
የተደበቀ መውጣቱ አይቀርምና:: 27በጨ
ለማ የምነግራችሁን በብርሃን አውሩት፤
በጆሮአችሁ የሰማችሁትን በአደባባይ አው
ጁት፤ 28ሥጋን መግደል እንጂ ነፍስን
መግደል የማይችሉትን አትፍሩ፤ ይልቁንስ
ነፍስንና ሥጋን በገሃነም ማጥፋት የሚቻለ
ውን ፍሩ:: 29በአንድ ሳንቲም[ሀ] ከሚሸጡት
ሁለት ድንቢጦች አንዲቷ እንኳ ያለ
አባታችሁ ፈቃድ ምድር ላይ አትወድ
ቅም:: 30የራስ ጠጕራችሁ እንኳ አንድ
ሳይቀር የተቈጠረ ነው:: 31ስለዚህ አትፍሩ፤
ከብዙ ድንቢጦች ይልቅ ዋጋችሁ የከበረ
ነው::

32“በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ፣ እኔም
በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እመሰክርለታ
ለሁ፤ 33ነገር ግን በሰው ፊት የሚክደኝን፣
እኔም በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እክደዋለሁ::

34“እኔ የመጣሁት ሰላምን በምድር ለማ
ስፈን አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ሰላምን
ለማውረድ አልመጣሁም:: 35እኔ የመጣሁት
“ ‘ልጅን ከአባት፣
ሴት ልጅን ከእናቷ
ምራትንም ከዐማቷ ለመለያየት ነው፤
36የሰው ጠላቶቹ፣
የገዛ ቤተ ሰዎቹ ይሆናሉ::’

37“ከእኔ ይልቅ እናቱን ወይም አባቱን
የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባም፤ ከእኔ
ይልቅ ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን
የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባም:: 38መስቀ
ሉን ተሸክሞ የማይከተለኝ የእኔ ሊሆን አይገ
ባውም:: 39ሕይወቱን ሊያድን የሚፈልግ
ያጠፋታል፤ ሕይወቱን ስለ እኔ አሳልፎ
የሚሰጥ ግን ያገኛታል::

40“እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤
እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል::
41ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን
ዋጋ ያገኛል፤ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚ
ቀበል የጻድቅን ዋጋ ያገኛል:: 42ስለዚህ
እውነት እላችኋለሁ፣ ማንም ሰው ከእነዚህ
ከታናናሾች ለአንዱ ደቀ መዝሙሬ በመ
ሆኑ አንድ ጽዋ ቀዝቃዛ ውሃ ቢሰጠው
ዋጋውን አያጣም::”

## መጥምቁ ዮሐንስ ወደ ኢየሱስ የላከው ጥያቄ

11፥2-19 ተጓ ምብ - ሉቃ 7፥18-35

11 ኢየሱስ ለዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛ
ሙርቱ ትእዛዙን ሰጥቶ ከጨረሰ
በኋላ ለማስተማርና ለመስበክ ወደ ገሊላ
ከተሞች[ለ] ሄደ::

2ዮሐንስ በእስር ቤት ሆኖ ክርስቶስ በ
ማ ድረግ ላይ ያለውን ነገር በሰማ ጊዜ፣
ደቀ መዛሙርቱን ወደ እርሱ ልኮ፣
3“ይመጣል ተብሎ የሚጠበቀው አንተ
ነህ? ወይስ ሌላ እንጠብቅ?” ሲል ጠየቀ::

4ኢየሱስም፣ እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፤
“ሂዳችሁ የምትሰሙትንና የምታዩትን
ለዮሐንስ ንገሩት፤ 5ዕውሮች ያያሉ፤ አንካ
ሶች ይራመዳሉ፤ ለምጻሞች[ሐ] ይነጻሉ፤ ደን
ቆሮዎች ይሰማሉ፤ ሙታን ይነሣሉ፤
ለድኾችም የምሥራች እየተሰበከ ነው፤
6በእኔ የማይሰናከልም ብፁዕ ነው::”

7የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ከሄዱ
በኋላ፣ ኢየሱስ ለሕዝቡ ስለ ዮሐንስ እንዲህ
ሲል ተናገረ፤ “ወደ ምድረ በዳ ምን
ልታዩ ወጣችሁ? ሸምበቆ በነፋስ ሲወዛወዝ?
8ወይስ ምን ልታዩ ወጣችሁ? ባማረ ልብስ
ያጌጠ ሰው? ባማረ ልብስ ያጌጡ
በነገሥታት ቤት አሉላችሁ! 9ታዲያ ምን
ልታዩ ወጣ ችሁ? ነቢይ ልታዩ? አዎን፤
ከነቢይም የሚ በልጥ ነው:: 10እንዲህ
ተብሎ የተጻፈለት እርሱ ነው፤

“ ‘በፊትህ መንገድህን ያዘጋጅልህ ዘንድ፣
ከአንተ አስቀድሜ መልእክተኛዬን
እልካለሁ::’

11እውነት እላችኋለሁ፤ ከሴት ከተወለዱት
መካከል እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ያለ አል
ተነሣም፤ ሆኖም በመንግሥተ ሰማያት
ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል:: 12ከመጥ
ምቁ ዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን
ድረስ መንግሥተ ሰማይ በብዙ ትገፋ
ለች፤ የሚያገኟትም ብርቱዎች ናቸው፤
13ነቢያትም፣ የሙሴ ሕግም ሁሉ እስከ
ዮሐንስ ድረስ ትንቢት ተናግረዋልና::
14እንግዲህ ልትቀበሉት ከፈቀዳችሁ ይመ
ጣል የተባለው ኤልያስ እርሱ ነው:: 15ሰሚ
ጆሮ ያለው ይስማ::

16“ይህን ትውልድ በምን ልመስለው?
በገበያ ተቀምጠው ጓደኞቻቸውን እንዲህ
እያሉ የሚጣሩ ልጆችን ይመስላሉ፤

17“ ‘ዋሽንት ነፋንላችሁ፤
አልጨፈራችሁም፤
ሙሾ አወረድንላችሁ፤
አላለቀሳችሁም’

18ዮሐንስ ከመብልና ከመጠጥ ተቈጥቦ
በመምጣቱ፣ ‘ጋኔን አለበት’ ይሉታልና::
19የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ መጣ፤
እነር ሱም፣ ‘በልቶ የማይጠግብ፣ ጠጪ
እንዲሁም የቀረጥ ሰብሳቢዎችና የኀጢ
አተኞች

10፥26 ማር4፥22፤
ሉቃ8፥17
10፥28
ኢሳ8፥12፡13፤
ዕብ10፥31
10፥30
1ሳሙ14፥45፤
2ሳሙ14፥11፤
1ነገ1፥52፤
ሉቃ21፥18፤
ሐሥ27፥34
10፥31
ማቴ6፥26፤ 12፥12
10፥32 ሮሜ10፥9
10፥33 ማር8፥38፤
2ጢሞ2፥12
10፥35 ቀኍ21
10፥36 ሚክ7፥6
10፥37ሉቃ፥14፥26
10፥38ማቴ16፥24፤
ሉቃ14፥27
10፥39 ዮሐ12፥25
10፥40 ዘፀ16፥8፤
ማቴ18፥5፤ሉቃ9፥48፤
10፥16፤ዮሐ12፥44፤
13፥20፤ገላ4፥14
10፥42 ምሳ14፥31፤
19፥17፤ማቴ25፥40፤
ማር9፥41፤
ሐሥ10፥4፤
ዕብ6፥10
11፥1 ማቴ7፥28
11፥2ማቴ3፥1፤14፥3
11፥3
መዝ118፥26፤
ዮሐ11፥27፤
ዕብ 10፥37
11፥5 ኢሳ35፥4-6፤
61፥1፤ማቴ15፥31፤
ሉቃ4፥18፡19
11፥6 ማቴ13፥21፤
26፥31
11፥7 ማቴ3፥1
11፥9 ማቴ14፥5፤
21፥26፤ሉቃ1፥76፤
7፥26
11፥10 ሚል3፥1፤
ማር1፥2፤ዮሐ3፥28፤
ሉቃ7፥27
11፥13 ሉቃ16፥16
11፥14 ሚል4፥5፤
ማቴ17፥10-13፤ማር
9፥11-13፤ሉቃ1፥17፤
ዮሐ1፥21
11፥15 ማቴ13፥9፡
43፤ማር4፥23፤ሉቃ
14፥35፤ራእ2፥7
11፥18 ማቴ3፥4፤
ሉቃ1፥15
11፥19 ማቴ9፥11

[ሀ]29 ግሪኩ *አንድ አሳሪዮን* ይላል
[ለ]1 ግሪኩ *ወደ ከተሞቻቸው* ይላል
[ሐ]5 የግሪኩ ቃል የግድ ከለምጽ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን የተለያዩ የቆዳ በሽታዎችንም ያመለክታል

ወዳጅ’ አሉት። ጥበብ ግን በሥራዋ ጸደ
ቀች።”

## ንስሐ ስላልገቡ ከተሞች የተነገረ ወዮታ

11፥21-23 ተጓ ምብ - ሉቃ 10፥13-15

[20]ከዚያም ኢየሱስ ብዙውን ታምራት
ያደረገባቸው ከተሞች ንስሐ ባለመግባታ
ቸው እንዲህ ሲል ወቀሳቸው፤ [21]“ወዮልሽ
ኮራዚን፤ ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ፤ በእናንተ
የተደረገው ታምራት በጢሮስና በሲዶና
ተደርጎ ቢሆን ኖሮ፣ ገና ድሮ ማቅ ለብ
ሰው፣ ዐመድ ነስንሰው ንስሐ በገቡ ነበር።
[22]ስለዚህ እላችኋለሁ፤ በፍርድ ቀን ከእና
ንተ ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና ቅጣቱ ይቀ
ልላቸዋል። [23]አንቺም ቅፍርናሆም ወደ ሰማይ
ከፍ ከፍ ማለት ፈለግሽ? ነገር ግን ወደ
ሲኦል ትወርጃለሽ፤ በአንቺ የተደረ ገው
ታምራት በሰዶም ቢደረግ ኖሮ፣ እስ
ከዛሬ በቆየች ነበር። [24]ስለዚህ እልሻለሁ፤
በፍርድ ቀን ከአንቺ ይልቅ ቅጣቱ ለሰ
ዶም ይቀልላታል።”

## ክርስቶስ የሚሰጠው ዕረፍት

11፥25-27 ተጓ ምብ - ሉቃ 10፥21-22

[25]በዚያን ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አለ፤
“የሰማይና የምድር ጌታ አባት ሆይ፤ ይህን
ከጥበበኞችና ከዐዋቂዎች ሰውረህ ለሕፃናት
ስለ ገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ፤ [26]አዎን
አባት ሆይ፤ ይህ በፊትህ በጎ ፈቃድህ
ሆኖ ተገኝቶአልና።

[27]“ሁሉ ነገር ከአባቴ ተሰጥቶኛል፤ ከአብ
ሌላ ወልድን የሚያውቅ የለም፤ ከወልድና
ወልድ ራሱ ፈቅዶ ከሚገልጥላቸው ሌላ
አብን የሚያውቅ የለም።

[28]“እናንት ሸክም የከበዳችሁና የደከማ
ችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም ዕረፍት
እሰጣችኋለሁ። [29]ቀንበሬን ተሸከሙ፤ ከእ
ኔም ተማሩ፤ እኔ በልቤ የዋህና ትሑት
ነኝና፤ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤
[30]ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀላል ነውና።

## ሰንበትን ስለ ማክበር

12፥1-8 ተጓ ምብ - ማር 2፥23-28፤ ሉቃ 6፥1-5
12፥9-14 ተጓ ምብ - ማር 3፥1-6፤ ሉቃ 6፥6-11

12 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በሰንበት ቀን
በእህል ዕርሻ ውስጥ አለፈ፤ ደቀ
መዛሙርቱም ስለ ራባቸው እሸት ቀጥ
ፈው ይበሉ ጀመር። [2]ፈሪሳውያንም ይህን
አይተው፣ “እነሆ፣ ደቀ መዛሙርትህ በሰን
በት ቀን መደረግ የሌለበትን እያደረጉ
ነው” አሉት።

[3]እርሱም እንዲህ አላቸው፤ “ዳዊትና
አብረውት የነበሩት ሰዎች በተራቡ ጊዜ
እርሱ ምን እንዳደረገ አላነበባችሁምን?
[4]ወደ እግዚአብሔር ቤት ገባ፤ ለካህናት
እንጂ ለእርሱም ሆነ አብረውት ለነበሩት
ያልተፈቀደውን የተቀደሰ ኅብስት በላ።
[5]ወይስ ካህናት ሰንበትን ሽረው በቤተ
መቅደስ ውስጥ ሥራ ቢሠሩ በደል እንደ
ማይሆንባቸው ከኦሪት ሕግ አላነበባችሁም?
[6]ነገር ግን እላችኋለሁ፤ ከቤተ መቅደስ
የሚበልጥ[ሠ] በዚህ አለ። [7]‘ከመሥዋዕት
ይልቅ ምሕረትን እወዳለሁ’ የሚለው ቃል
ምን ማለት እንደ ሆነ ብታውቁ ኖሮ፣
በንጹሐን ላይ ባልፈረዳችሁ ነበር። [8]የሰው
ልጅ የሰንበት ጌታ ነውና።”

[9]ከዚያ ስፍራ ዕልፍ ብሎ በመሄድ ወደ
ምኵራባቸው ገባ፤ [10]በዚያም አንድ እጁ
ሽባ የሆነ ሰው ነበር፤ ኢየሱስን ሊከሱት
ምክንያት ፈልገው፣ “በሰንበት ቀን መፈ
ወስ ተፈቅዶአል?” ብለው ጠየቁት።

[11]እርሱም፣ “ከእናንተ መካከል የአንዱ
ሰው በግ በሰንበት ቀን ጕድጓድ ቢገባበት
በጉን ከገባበት ጕድጓድ ጎትቶ አያወጣው
ምን? [12]ታዲያ ሰው ከበግ እጅግ አይበል
ጥምን? ስለዚህ በሰንበት ቀን በጎ ማድረግ
ተፈቅዶአል” አላቸው።

[13]ከዚያም ሰውየውን፣ “እጅህን ዘርጋ”
አለው፤ ሰውየውም እጁን ዘረጋ፤ እንደ
ሌላኛውም እጁ ደህና ሆነለት። [14]ፈሪሳው
ያን ግን ከዚያ ወጣ ብለው ኢየሱስን እን
ዴት እንደሚገድሉት ተማከሩ።

## እግዚአብሔር የመረጠው አገልጋይ

[15]ኢየሱስ ሐሳባቸውን አውቆ ከዚያ
ዘወር አለ። ብዙ ሕዝብም ተከተለው፤ ሕመ
ምተኞችን ሁሉ ፈወሰ፤ [16]ማንነቱን ለማ
ንም እንዳይናገሩ አዘዛቸው። [17]ይህም የሆ
ነው በነቢዩ በኢሳይያስ እንዲህ ተብሎ
የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ነው፤

[18]“እነሆ የመረጥሁት፣
የምወደውና በእርሱ ደስ የሚለኝ
አገልጋዬ፣
መንፈሴን በእርሱ ላይ አኖራለሁ፤
እርሱም ለአሕዛብ ፍትሕን ያውጃል።
[19]አይጨቃጨቅም ወይም አይጮኽም፤
ድምፁም በአደባባይ አይሰማም።
[20]ፍትሕን ለድል እስኪያበቃ ድረስ፣
የተቀጠቀጠውን ሸምበቆ አይሰብርም፤
የሚጤሰውንም የጧፍ ክር አያጠፋም።
[21]አሕዛብ በስሙ ተስፋ ያደርጋሉ።”

11፥21 ኢል3፥4፤ አሞ1፥9፤ዮና3፥5-9፤ ማቴ15፥21፤ማር3፥8፤ 6፥45፤8፥22፤ ሉቃ6፥17፤9፥10፤ዮሐ1፥44፤ 12፥21፤ሐሥ12፥20
11፥22 ቍ24፤ ማቴ 10፥15
11፥23 ኢሳ14፥13-15፤ማቴ4፥13
11፥24 ማቴ10፥15
11፥25 ማቴ13፥11፤16፥17፤ሉቃ22፥42፤ 23፥34፤ዮሐ11፥41፤ 12፥27፡28፤ 1ቆሮ 1፥26-29
11፥27 ማቴ28፥18፤ ዮሐ3፥35፤10፥15፤ 17፥25፡26
11፥28 ዘፀ33፥14፤ ዮሐ7፥37
11፥29 መዝ116፥7፤ኤር6፥16፤ዮሐ13፥15፤ፊል2፥5፤1ጴጥ2፥21፤1ዮሐ2፥6
11፥30 1ዮሐ5፥3
12፥1 ዘዳ23፥25
12፥2 ቍ10፤ዘፀ 20፥10፤23፥12፤ዘዳ 5፥14፤ሉቃ13፥14፤ 14፥3፤ዮሐ5፥10፤7፥23፤9፥16
12፥3 1ሳሙ21፥6
12፥4 ዘሌ24፥5፡9
12፥5 ዘኍ28፥9፡10፤ ዮሐ7፥22፡23
12፥6 ቍ41፡42
12፥7 ሆሴ6፥6፤ሚክ 6፥6-8፤ማቴ9፥13
12፥8 ማቴ8፥20
12፥10 ቍ2፤ማር 3፥2፤12፥13፤ሉቃ 11፥54፤14፥1፤20፥20
12፥11 ሉቃ14፥5
12፥12 ማቴ6፥26፤ 10፥31
12፥14 ዘፍ37፥18፤ መዝ71፥10፤ማቴ 26፥4፤27፥1፤ማር3፥6፤ ሉቃ6፥11፤ዮሐ5፥18፤ 7፥1፡19፤11፥53
12፥15 ማቴ4፥23
12፥16 ማቴ8፥4
12፥17 ማቴ1፥22
12፥18 ማቴ3፥17፤ ዮሐ3፥34
12፥21 ኢሳ42፥1-4

[ሠ]6 ወይም *አንድ ነገር፤* ቍ 41 እና 42 ይመ

## ኢየሱስ በአጋንንት ሥልጣን አጋንንትን ያወጣል መባሉ

12፥25-29 ተጓ ምብ - ማር 3፥23-27፤ ሉቃ 11፥17-22

22ከዚህ በኋላ በጋኔን ተይዞ ማየትና መና
ገር የማይችል ሰው ወደ እርሱ አመጡ፤
ኢየሱስም ፈወሰው፤ ሰውየውም ማየትና
መናገር ቻለ። 23ሕዝቡም ሁሉ ተደን
ቀው፣ “ይህ ሰው የዳዊት ልጅ ይሆንን?”
አሉ።
24ነገር ግን ፈሪሳውያን ይህን በሰሙ ጊዜ፣
“ይህ ሰው አጋንንትን የሚያወጣው በአጋን
ንት አለቃ በብዔልዜቡል ብቻ መሆን አለ
በት” አሉ።
25ኢየሱስም ሐሳባቸውን ዐውቆ እንዲህ
አላቸው፤ “እርስ በእርሱ የተከፋፈለ መንግ
ሥት ሁሉ ይወድቃል፤ እርስ በእርሱም
የተከፋፈለ ከተማ ወይም ቤት አይጸናም።
26ሰይጣንም ሰይጣንን የሚያስወጣ ከሆነ፣
እርስ በእርሱ ተለያይቷል ማለት ነው፤
እንዲህ ከሆነ ደግሞ መንግሥቱ እንዴት
ጸንቶ ሊቆም ይችላል? 27እኔ አጋንንትን
የማስወጣው በብዔልዜቡል ከሆነ፣ ልጆቻ
ችሁ በምን ሊያስወጧቸው ነው? ስለዚህ
ልጆቻችሁ ይፈርዱባችኋል። 28ነገር ግን እኔ
አጋንንትን የማስወጣው በእግዚአብሔር መን
ፈስ ከሆነ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ
እናንተ መጥታለች።
29“ወይስ አንድ ሰው ወደ ኀይለኛ ሰው
ቤት ገብቶ ንብረቱን ለመዝረፍ ቢፈልግ፣
አስቀድሞ ያንን ኀይለኛ ሰው ሳያስር እን
ዴት አድርጎ ይሳካለታል?
30“ከእኔ ጋር ያልሆነ ሁሉ ይቃወመኛል፤
ከእኔም ጋር የማይሰበስብ ሁሉ ይበትናል።
31ስለዚህ እላችኋለሁ፤ ኀጢአት መሥራ
ትና የስድብ ቃል ሁሉ መናገር ለሰዎች
ይቀር ይባልላቸዋል፤ ነገር ግን በመንፈስ
ቅዱስ ላይ የሚነገር የስድብ ቃል ይቀር
አይባልም። 32ማንም ሰው በሰው ልጅ ላይ
የሚናገረው ክፉ ቃል ይቀር ይባላል፤
በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚናገረው ክፉ ቃል
ግን በዚህም ሆነ በወዲያኛው ዓለም ይቀር
አይባልም።
33“ዛፍ ሁሉ በፍሬው ስለሚታወቅ፣
መልካም ፍሬ እንድታገኙ መልካም ዛፍ
ይኑራችሁ፤ መጥፎ ዛፍ ቢኖራችሁ ግን
መጥፎ ፍሬ ታገኛላችሁ። 34እናንተ የእ
ፉኝት ልጆች፤ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ
መልካም ነገር መናገር እንዴት ትችላ
ላችሁ? በልብ ውስጥ የሞላውን አንደበት
ይናገረዋልና። 35መልካም ሰው በልቡ ካከ
ማቸው መልካም ነገር በጎ ነገር ያወጣል፤
ክፉ ሰውም በልቡ ካከማቸው ክፉ ነገር
መጥፎ ነገር ያወጣል። 36ነገር ግን እላችኋ
ለሁ፤ ሰዎች ስለ ተናገሩት ከንቱ ቃል
ሁሉ በፍርድ ቀን ይጠየቁበታል። 37ምክ
ንያቱም ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህ፤ ከቃ
ልህም የተነሣ ይፈረድብሃልና።

## ማረጋገጫ ምልክት ስለ መሻት

12፥39-42 ተጓ ምብ - ሉቃ 11፥29-32
12፥43-45 ተጓ ምብ - ሉቃ 11፥24-26

38ከዚያም አንዳንድ የአይሁድ ሃይማ
ኖት መምህራንና ፈሪሳውያን፣ “መምህር
ሆይ፤ ከአንተ ታምራዊ ምልክት ማየት እን
ፈልጋለን” አሉት።
39እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አላቸው፤
“ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክትን
ይጠይቃል፤ ነገር ግን ከነቢዩ ዮናስ ምል
ክት በስተቀር ሌላ ምልክት አይሰጠውም።
40ዮናስ በዓሣ ዐንበሪ ሆድ ውስጥ ሦስት
ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ቈየ፣ እንዲሁ
የሰው ልጅ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት
በምድር ሆድ ውስጥ ይቈያል። 41የነነዌ
ሰዎች በፍርድ ዕለት ከዚህ ትውልድ ጋር
ተነሥተው ይፈርዱበታል፤ እነርሱ በዮናስ
ስብከት ንስሓ ገብተዋልና። እነሆ፤ ከዮናስ
የሚበልጥ እዚህ አለ። 42በፍርድ ዕለት
የደቡብ ንግሥት ከዚህ ትውልድ ጋር ተነ
ሥታ ትፈርድበታለች፤ የሰሎሞንን ጥበብ
ለመስማት ከምድር ዳርቻ መጥታለችና።
እነሆ፤ ከሰሎሞን የሚበልጥ እዚህ አለ።
43“ርኩስ መንፈስ ከሰው ከወጣ በኋላ ዕረ
ፍት ለማግኘት ውሃ በሌለበት ደረቅ ቦታ
ይንከራተታል፤ የሚሻውን ዕረፍት ግን
አያገኝም። 44ከዚያም፣ ‘ወደ ነበርሁበት
ቤት ተመልሼ ልሂድ’ ይላል፤ ሲመለስም
ቤቱ ባዶ ሆኖ፣ ጸድቶና ተዘጋጅቶ
ያገኘዋል። 45ከዚያም ይሄድና ከራሱ የባሱ
ሌሎች ሰባት ክፉ መናፍስት ይዞ
ይመጣል፤ እነርሱም ሰውየው ውስጥ
ገብተው ይኖራሉ። የዚያም ሰው የኋለኛው
ሁኔታ ከፊተኛው የከፋ ይሆናል። በዚህ ክፉ
ትውልድም ላይ እንዲሁ ይሆንበታል።”

## የኢየሱስ እናትና ወንድሞች

12፥46-50 ተጓ ምብ - ማር 3፥31-35፤ ሉቃ 8፥19-21

46ኢየሱስ ለሕዝቡ ሲናገር ሳለ፣ እናቱና
ወንድሞቹ ሊያነጋግሩት ፈልገው በውጭ
ቆመው ነበር። 47አንድ ሰውም፣ “እነሆ፣
እናትህና ወንድሞችህ ሊያነጋግሩህ ፈል
ገው በውጭ ቆመዋል” አለው።[o]
48ኢየሱስም፣ “እናቴ ማን ናት? ወንድ
ሞቼስ እነማን ናቸው?” ሲል መለሰለት።
49በእጁም ወደ ደቀ መዛሙርቱ እያመለከተ

[o]47 አንዳንድ ትርጒሞች ይህን ጥቅስ ይዘላሉ

12፥22 ማቴ4፥24
12፥23 ማቴ9፥27
12፥24 ማቴ9፥34፤ ማር3፥22
12፥25 ማቴ9፥4
12፥26 ማቴ4፥10
12፥27 ቀኍ24፤ ሐሥ 19፥13
12፥28 ማቴ3፥2
12፥30 ማር9፥40፤ ሉቃ11፥23
12፥31 ማር3፥28፡29፤ሉቃ12፥10
12፥32 ማር10፥30፤ ሉቃ20፥34፡35፤ ኤፌ 1፥21፤ ቲቶ2፥12፤ ዕብ6፥5
12፥33 ማቴ7፥16፡17፤ሉቃ6፥43፡44
12፥34 ማቴ3፥7፤ 15፥18፤23፥33፤ ሉቃ 6፥45
12፥37 ኢዮ15፥6፤ ምሳ10፥14፤18፥21፤ ያዕ3፥2
12፥38 ማቴ16፥1፤ ማር8፥11፡12፤ሉቃ11፥16፤ዮሐ2፥11፡18፤4፥48፤6፥30፤1ቆሮ1፥22
12፥39 ማቴ16፥4፤ ሉቃ11፥29
12፥40 ማቴ8፥20፤ 16፥21
12፥41ዮና1፥2፤3፥5
12፥42 1ነገ10፥1፤ 2ዜና9፥1
12፥45 2ጴጥ2፥20
12፥46 ማቴ1፥18፤ 2፥11፡13፡14፡20፤ 13፥55፤ሉቃ1፥43፤ 2፥33፡34፡48፡51፤ ዮሐ2፥1፡5፡12፤ 7፥3፡5፤19፥25፡26፤ ሐሥ1፥14 ፤1ቆሮ9፥5፤ገላ1፥19

እንዲህ አለ፤ “እናቴና ወንድሞቼ እነዚህ
ናቸው፤ 50በሰማይ ያለውን የአባቴን ፈቃድ
የሚያደርግ ሁሉ፣ ወንድሜ፣ እኅቴና እናቴም
ነው።”

## የዘሪው ምሳሌ

13፥1-15 ተጓ ምብ - ማር 4፥1-12፤ ሉቃ 8፥4-10
13፥16፡17 ተጓ ምብ - ሉቃ 10፥23፡24
13፥18-23 ተጓ ምብ - ማር 4፥13-20፤ ሉቃ 8፥11-15

13 በዚያኑ ቀን ኢየሱስ ከቤት ወጥቶ
በባሕሩ ዳር አጠገብ ተቀመጠ።
2ብዙ ሕዝብም ስለ ከበበው በባሕሩ ዳር
ትቶአቸው ጀልባ ላይ ወጥቶ ተቀመጠ።
3ብዙ ነገሮችን በምሳሌ እንዲህ ሲል ነገራ
ቸው፤ “አንድ ገበሬ ዘር ሊዘራ ወጣ። 4ሲዘ
ራም ሳለ፣ አንዳንዱ ዘር መንገድ ዳር ወደቀ፤
ወፎችም መጥተው ለቀመው በሉት። 5አን
ዳንዱ ዘር ዐፈሩ ስስ በሆነ፣ ድንጋያማ
መሬት ላይ ወደቀ፤ ዐፈሩ ስስ ስለ ሆነም
ፈጥኖ በቀለ። 6ነገር ግን ፀሓይ ሲመ
ታው ጠወለገ፤ ሥር ባለመስደዱም ደረቀ።
7አንዳንዱም ዘር በእሾኽ መካከል ወደቀ፤
እሾኹም አደገና ቡቃያውን አንቆ አስ
ቀረው፤ 8ሌላው ዘር ደግሞ በጥሩ መሬት
ላይ ወደቀ፤ ፍሬም አፈራ፤ አንዱ መቶ፣
አንዱ ሥልሳ፣ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ።
9ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ!”።
10ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ
ቀርበው፣ “ለምን ለሕዝቡ በምሳሌ ትናገራ
ለህ?” አሉት።
11እርሱም እንዲህ አላቸው፤ “ለእናንተ
የመንግሥተ ሰማይን ምስጢር ማወቅ ተሰ
ጥቶአችኋል፤ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም።
12ላለው ይጨመርለታል፤ ይበዛለትማል፤
ከሌለው ግን ያ ያለው እንኳ ይወሰድበታል።
13ስለዚህ እንዲህ በማለት በምሳሌ የምነግ
ራቸው ለዚህ ነው፤

“እያዩ ስለማያዩ፣
እየሰሙ ስለማይሰሙ ወይም
ስለማያስተውሉ ነው።

14እንዲህ ተብሎ የተነገረው የኢሳይያስ
ትንቢት በእነርሱ ይፈጸማል፤

“ ‘መስማትንስ ትሰማላችሁ፤ ነገር ግን
አታስተውሉም፤
ማየትንም ታያላችሁ፤ ነገር ግን ልብ
አትሉም።
15የሕዝቡ ልብ ደንድኖአልና፤
ጆሮአቸውም አይሰማም፤
እንዳያዩም ዐይናቸውን ጨፍነዋል፤
ይህ ባይሆን ኖሮ፣ በዐይናቸው አይተው፣
በጆሮአቸው ሰምተው፣
በልባቸውም አስተውለው፣

12፥50 ማቴ6፥10፤ ዮሐ15፥14
13፥1 ቊ36፤ ማቴ 9፥28
13፥2 ሉቃ5፥3
13፥8 ዘፍ26፥12
13፥9 ማቴ11፥15
13፥11 ማቴ3፥2፤ 11፥25፤16፥17፤19፥11፤ዮሐ6፥65፤ 1ቆሮ 2፥10፡14፤ ቈላ1፥27፤ 1ዮሐ2፥20፡27
13፥12 ማቴ25፥29
13፥13 ዘዳ29፥4፤ ኤር5፥21፤ሕዝ12፥2
13፥14 ቊ35፤ ማቴ1፥22
13፥15 ኢሳ6፥9፡10፤ ዮሐ12፥40፤ሐሥ28፥26፡27፤ሮሜ11፥8
13፥16 ማቴ16፥17
13፥17 ዮሐ8፥56፤ ዕብ11፥13፤ 1ጴጥ10-12
13፥19 ማቴ4፥23፤ 5፥37
13፥21 ማቴ11፥6፤ 26፥31
13፥22 ማቴ19፥23፤ 1ጢሞ6፥9፡10፡17
13፥23 ቊ8
13፥24 ቊ31፡33፡45፡47፤ማቴ18፥23፤ 20፥1፤22፥2፤25፥1፤ ማር4፥26፡30
13፥30 ማቴ3፥12

ወደ እኔ በተመለሱና በፈወስኋቸው ነበር።’
16የእናንተ ዐይኖች ስለሚያዩ፣ ጆሮዎቻ
ችሁም ስለሚሰሙ ግን የተባረኩ ናቸው።
17እውነት እላችኋለሁ፤ ብዙ ነቢያትና ብዙ
ጻድቃን እናንተ የምታዩትን ለማየትና
የምትሰሙትንም ለመስማት ተመኝተው
ነበር፤ ግን አልሆነላቸውም።
18“እንግዲህ የዘሪውን ምሳሌ ስሙ፤
19የእግዚአብሔርን መንግሥት ቃል ሰምቶ
ከማ ያስተውል ከማንኛውም ሰው ልብ
ውስጥ ክፉው መጥቶ የተዘራውን ዘር ይነ
ጥቃል። ይህ እንግዲህ በመንገድ ዳር የተ
ዘራው ዘር ነው። 20በድንጋያማ መሬት
ላይ የተዘራው፣ ቃሉን ሰምቶ ወዲያውኑ
በደስታ የሚቀበለውን ሰው ይመስላል።
21ነገር ግን ሥር መስደድ ባለመቻሉ ብዙ
አይቈይም፤ በቃሉ ምክንያት መከራ ወይም
ስደት ሲመጣ ወዲያውኑ ይሰናከላል።
22በእሾኽ መካከል የተዘራው ዘር ቃሉን ሰምቶ
ለዚህ ዓለም በመጨነቅና በብልጽግና ሐሳብ
በመታለል ታንቆ ያላፈራውን ሰው ይመስ
ላል። 23በጥሩ መሬት ላይ የተዘራው ዘር
ግን ቃሉን ሰምቶ የሚያስተውለውን ሰው
ይመስላል፤ በእርግጥም ፍሬ ያፈራል፤ አንዱ
መቶ፣ አንዱ ሥልሳ፣ አንዱም ሠላሳ ፍሬ
ሰጠ።”

## የእንክርዳዱ ምሳሌ

24ኢየሱስም ሌላ ምሳሌ እንዲህ ሲል ነገ
ራቸው፤ “መንግሥተ ሰማይ በዕርሻው ቦታ
ጥሩ ዘር የዘራን ሰው ትመስላለች። 25ነገር
ግን ሰው ሁሉ ተኝቶ ሳለ፣ ጠላቱ መጥቶ
በስንዴው መካከል እንክርዳድ ዘርቶ ሄደ።
26ስንዴው በቅሎ ማፍራት ሲጀምር እን
ክርዳዱም አብሮ ብቅ አለ።
27“የዕርሻው ባለቤት አገልጋዮችም ወደ
እርሱ ቀርበው፣ ‘ጌታ ሆይ፤ በዕርሻህ ቦታ
ጥሩ ዘር ዘርተህ አልነበረምን? እንክርዳዱ
ከየት መጣ?’ አሉት።
28“እርሱም፣ ‘የጠላት ሥራ ነው’ አላ
ቸው።
አገልጋዮቹም፣ ‘እንክርዳዱን ሄደን እንድ
ንነቅለው ትፈልጋለህ?’ ብለው ጠየቁት።
29“እርሱ ግን፣ ‘አይሆንም፤ ምክንያቱም
እንክርዳዱን እንነቅላለን ስትሉ ስንዴው
ንም አብራችሁ ልትነቅሉ ትችላላችሁ፤
30ተውአቸው፤ እስከ መከር ጊዜ አብረው
ይደጉ። በዚያን ጊዜ አጫጆቹን እንክር
ዳዱን አስቀድማችሁ ንቀሉ፤ በእሳትም
እንዲቃጠል በየነዶው እሰሩት፤ ስንዴውን
ግን ሰብስባችሁ በጐተራዬ ክተቱ እላቸዋ
ለሁ’ ” አላቸው።

## የሰናፍጭና የእርሾ ምሳሌ

13፥31-32 ተጓ ምብ - ማር 4፥30-32፤
13፥31-33 ተጓ ምብ - ሉቃ 13፥18-21

31ሌላ ምሳሌ እንዲህ ሲል ነገራቸው፤
"መንግሥተ ሰማይ አንድ ሰው ወስዶ በዕ
ርሻው ቦታ የዘራትን የሰናፍጭ ዘር ትመ
ስላለች። 32የሰናፍጭ ዘር ከሌሎች ዘሮች
ሁሉ ያነሰች ብትሆንም፣ ስታድግ ግን
ከቊጥቋጦዎች ሁሉ በልጣ፣ የሰማይ ወፎች
መጥተው በቅርንጫፎቿ ላይ እስኪያርፉ
ድረስ ዛፍ ትሆናለች።"
33አሁንም ሌላ ምሳሌ እንዲህ ሲል ነገራ
ቸው፤ "መንግሥተ ሰማይ ሴት ወስዳ ሊጡ
በሙሉ እስኪቦካ ድረስ በሦስት መስፈሪያ"
ዱቄት ውስጥ በመደባለቅ የሸሸገችውን
እርሾ ትመስላለች።"
34ኢየሱስ ለሕዝቡ ይህን ሁሉ በምሳሌ
ተናገረ፤ ምሳሌም ሳይጠቀም የነገራቸው
አንድም ነገር አልነበረም። 35በዚህም በነቢዩ
እንዲህ ተብሎ የተነገረው ተፈጸመ፤

"አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ፤
ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተሰወረውንም
እናገራለሁ።"

## የእንክርዳዱ ምሳሌ ትርጒም

36ከዚያም ሕዝቡን ትቶ ወደ ቤት ገባ።
ደቀ መዛሙርቱም ወደ እርሱ ቀርበው፣
"በዕርሻው ውስጥ ስላለው እንክርዳድ የተ
ናገርኸውን ምሳሌ ትርጒም ንገረን" አሉት።
37እርሱም እንዲህ ሲል መለሰ፤ "ጥሩውን
ዘር የዘራው የሰው ልጅ ነው፤ 38ዕርሻውም
ይህ ዓለም ነው፤ ጥሩው ዘር የእግዚአብሔ
ርን መንግሥት ልጆች ያመለክታል፤ እን
ክርዳዱም የክፉው ልጆች ናቸው፤ 39ዘር
ቶት የሄደው ጠላትም ዲያብሎስ ነው፤
መከሩ የዓለም መጨረሻ ሲሆን፣ አጫጆቹም
መላእክት ናቸው።
40"እንክርዳዱ ተነቅሎ በእሳት እንደሚ
ቃጠል ሁሉ በዓለም መጨረሻም እንዲሁ
ይሆናል። 41የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል፤
እነርሱም ለኀጢአት ምክንያት የሆኑት
ንና ክፉ የሚያደርጉትን ሁሉ ለቅመው
ከመንግሥቱ ያወጣሉ። 42ልቅሶና ጥርስ
ማፋጨት ወዳለበት ወደ እቶን እሳት
ይጥሏቸዋል። 43በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአ
ባታቸው መንግሥት እንደ ፀሓይ ያበራሉ።
ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ።

## የተደበቀ ሀብትና የዕንቍው ምሳሌ

44"መንግሥተ ሰማይ በዕርሻ ውስጥ የተ
ደበቀ ሀብት ትመስላለች፤ አንድ ሰው ባገ
ኛት ጊዜ መልሶ ሸሸጋት፤ ከመደሰቱም

13፥31 ቍ24፤ ማቴ17፥20፤ ሉቃ17፥6
13፥32 መዝ104፥12፤ ሕዝ17፥23፤31፥6፤ ዳን4፥12
13፥33 ቍ24፤ ዘፍ 18፥6፤ገላ5፥9
13፥34 ዮሐ16፥25
13፥35 ቍ14፤ መዝ 78፥2፤ ማቴ1፥22፤ ሮሜ 16፥25፡26፤ 1ቆሮ 2፥7፤ኤፌ3፥9፤ ቈላ 1፥26
13፥36 ማቴ15፥15
13፥37 ማቴ8፥20
13፥38 ዮሐ8፥44፡45፤1ዮሐ3፥10
13፥39 ኢዩ3፥13፤ ማቴ24፥3፤28፥20፤ ራእ14፥15
13፥41 ማቴ8፥20፤ 24፥31
13፥42 ማቴ8፥12
13፥43 ዳን12፥3፤ ማቴ11፥15
13፥44 ቍ24፤ ኢሳ 55፥1፤ ማቴ19፥21፤ ፊል 3፥7፡8
13፥45 ቍ24
13፥47 ቍ24፤ማቴ 22፥10
13፥49 ማቴ25፥32
13፥50 ማቴ8፥12
13፥53 ማቴ7፥28
13፥54 ማቴ4፥23፤ 7፥28
13፥55 ማቴ12፥46፤ ሉቃ3፥23፤ዮሐ6፥42
13፥57 ሉቃ4፥24፤ ዮሐ4፥44፤6፥61
14፥1 ማር8፥15፤ ሉቃ3፥1፡19፤9፥7-7፤ 13፥31፤23፥7፡8፤ ሐሥ4፥27፤12፥1

የተነሣ ሄዶ፤ ያለውን ሁሉ በመሸጥ ያንን
የዕርሻ ቦታ ገዛ።
45"እንዲሁም መንግሥተ ሰማይ ውብ
ዕንቍ የሚፈልግ ነጋዴ ትመስላለች፤ 46እጅግ
ውድ የሆነ ዕንቍ ባገኘም ጊዜ ሄዶ ያለ
ውን ሁሉ ሸጦ ገዛው።

## የመረቡ ምሳሌ

47"ደግሞም መንግሥተ ሰማይ ወደ ባሕር
ተጥሎ የዓሣ ዓይነቶችን የያዘ መረብ
ትመስላለች፤ 48ዓሣ አጥማጆቹ መረቡ ሲሞላላ
ቸው ጐትተው ወደ ባሕሩ ዳር አወጡት፤
ከዚያም ተቀምጠው ጥሩ ጥሩውን እየለዩ
በቅርጫት ውስጥ ጨመሩ፤ መጥፎ መጥ
ፎውን ግን ጣሉት። 49በዓለም መጨረሻም
ልክ እንደዚሁ ይሆናል፤ መላእክት መጥ
ተው ኀጢአተኞችን ከጻድቃን በመለ
የት፣ 50ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት
ወደ እቶን እሳት ይጥሏቸዋል።"
51ኢየሱስ፣ "ይህ ሁሉ ገብቷችኋል?" አላ
ቸው።
እነርሱም፣ "አዎን" አሉት።
52እርሱም፣ "ስለዚህም የመንግሥተ ሰማ
ይን ምስጢር የተረዳ ማንኛውም የኦሪት
ሕግ መምህር፣ ከከበረ ሀብቱ ክምችት
አዲሱንም አሮጌውንም የሚያወጣ ባለንብ
ረት ይመስላል" አላቸው።

## በገዛ አገሩ ያልተከበረው ነቢይ

13፥54-58 ተጓ ምብ - ማር 6፥1-6

53ኢየሱስ እነዚህን ምሳሌዎች እንደ
ጨረሰ፣ ከዚያ ስፍራ ተነሥቶ ሄደ፤ 54ወደ
ገዛ አገሩ መጣ፤ በምኵራባቸውም ሕዝቡን
ያስተምር ጀመር። እነርሱም በመገረም
እንዲህ አሉ፤ "ይህ ሰው ይህን ጥበብና እነ
ዚህን ታምራት የማድረግ ኀይል ከየት
አገኘ? 55ይህ የአናጢው ልጅ አይደለምን?
የእናቱስ ስም ማርያም አይደለምን? ወን
ድሞቹስ ያዕቆብ፣ ዮሴፍ፣ ስምዖንና ይሁዳ
አይደሉምን? 56እኅቶቹስ ከእኛው ጋር
አይደሉምን? ታዲያ ይህ ሰው ይህን ሁሉ
ከወዴት አገኘው?" 57ስለዚህም ሳይቀበሉት
ቀሩ።
ኢየሱስ ግን፣ "ነቢይ የማይከበረው በራሱ
አገርና በራሱ ቤት ነው እንጂ በሌላ ቦታ
ይከበራል" አላቸው። 58ባለማመናቸውም
ምክንያት ብዙ ታምራትን በዚያ አላደረገም።

## የመጥምቁ ዮሐንስ መሞት

14፥1-12 ተጓ ምብ - ማር 6፥14-29

14 በዚያን ጊዜ የአራተኛው ክፍል
ገዥ የነበረው፣ ሄሮድስ ስለ ኢየሱስ

"33 ምናልባት 22 ሊትር ያህል

ዝና ሰማ፤ 2ባለሟሎቹንም፣ “እንዲህ ከሆነ
መጥምቁ ዮሐንስ ከሞት ተነሥቶ መጥቶአል
ማለት ነው፤ ይህ ሁሉ ድንቅ ታምራት
በእርሱ የሚደረገውም ለዚህ ነው” አላ
ቸው።
3ቀደም ሲል ሄሮድስ፣ በወንድሙ በፊ
ልጶስ ሚስት በሄሮድያዳ ምክንያት ዮሐን
ስን አስይዞ ወህኒ አስገብቶት ነበር።
4ምክንያቱም ዮሐንስ፣ “እርሷን እንድታ
ገባ ሕግ አይፈቅድልህም” ይለው ነበር።
5ሄሮድስም ዮሐንስን ሊገድለው ፈልጎ፣ ሕዝቡ
እንደ ነቢይ ይመለከተው ስለ ነበር ፈራ።
6ሄሮድስ የልደቱን ቀን ሲያከብር፣ የሄ
ሮድያዳ ልጅ በዘፈን ደስ ስላሰኘችው፣
7የምትጠይቀውን ሁሉ ሊሰጣት በመሐላ
ቃል ገባላት። 8ልጅቷም በእናቷ ተመክራ፣
“የመጥምቁ ዮሐንስን ራስ በሳሕን ላይ
አድርገህ አሁኑኑ ስጠኝ” አለችው። 9በዚህ
ጊዜ ንጉሡ አዘነ፤ ይሁን እንጂ ስለ መሐ
ላውና ከእርሱ ጋር ስለነበሩ እንግዶች ሲል
ጥያቄዋ እንዲፈጸምላት አዘዘ። 10ልኮም
በወህኒ ውስጥ እንዳለ የዮሐንስን ራስ አስ
ቈረጠ። 11የተቈረጠውንም ራስ በሳሕን
ላይ አድርገው ለልጅቱ ሰጧት፤ ልጅቱም
ወስዳ ለእናቷ ሰጠች። 12የዮሐንስ ደቀ
መዛሙርትም አስከሬኑን ወስደው ቀበሩት፤
ከዚያም ሄደው የሆነውን ለኢየሱስ ነገሩት።

## ኢየሱስም አምስት ሺህ ሰዎችን በታምር መገበ

14፥13-21 ተጓ ምብ - ማር6፥32-44፤ሉቃ9፥10-17፤ዮሐ6፥1-13
14፥13-21 ማመ - ማቴ 15፥32-38

13ኢየሱስ የሆነውን ነገር በሰማ ጊዜ፣
ከነበረበት ተነሥቶ ወደ አንድ ገለልተኛ
ስፍራ በጀልባ ሄደ። ሕዝቡም ይህን ሰም
ተው፣ ከየከተማው በእግር ተከተሉት።
14ኢየሱስም ከጀልባው ሲወርድ ብዙ ሕዝብ
አይቶ ራራላቸው፤ ሕመምተኞቻቸውንም
ፈወሰላቸው።
15እየመሸ በመሄዱም ደቀ መዛሙርቱ
ወደ እርሱ ቀርበው፣ “ይህ ስፍራ ምንም የማ
ይገኝበት ምድረ በዳ ነው፤ ጊዜው እየመሸ
ስለሆነ፣ ወደ መንደሮች ሄደው የሚበሉት
ምግብ እንዲገዙ ሕዝቡን አሰናብት” አሉት።
16ኢየሱስ ግን፣ “መሄድ አያስፈልጋቸውም፤
የሚበሉትን እናንተ ስጧቸው” አላቸው።
17እነርሱም፣ “በዚህ ያለን አምስት እንጀ
ራና ሁለት ዓሣ ብቻ ነው” አሉት።
18እርሱም፣ “እስቲ ያለውን ወደ እኔ
አምጡት” አላቸው። 19ከዚያም ሕዝቡ
በሣሩ ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ፤ አምስቱን
እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ይዞ ዓይኑን ወደ
ሰማይ በማቅናት አመስግኖና ባርኮ እንጀራ
ውን ቈረሰ፤ ለደቀ መዛሙርቱም ሰጠ፤ እነ
ርሱም ለሕዝቡ ሰጡ። 20ሁሉም በልተው
ጠገቡ፤ ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ የተረፈ
ውን ቍርስራሽ ዐሥራ ሁለት መሶብ
ሙሉ አነሡ። 21የበሉትም ከሴቶችና ከሕፃ
ናት ሌላ አምስት ሺህ ወንዶች ያህሉ ነበር።

## ኢየሱስ በባሕር ላይ በእግሩ ሄደ

14፥22-33 ተጓ ምብ - ማር 6፥45-51፤ ዮሐ 6፥15-21፤
14፥34-36 ተጓ ምብ - ማር 6፥53-56

22ወዲያውኑ ደቀ መዛሙርቱ በጀልባ
ተሳፍረው ወደ ማዶ እንዲቀድሙት አዘዛ
ቸውና እርሱ ሕዝቡን ለማሰናበት ወደ
ኋላ ቀረት አለ። 23ሕዝቡን ካሰናበተ በኋ
ላም ለመጸለይ ብቻውን ወደ ተራራ ወጣ፤
በጨለመም ጊዜ ብቻውን በዚያው ነበር፤
24በዚያ ጊዜ ጀልባዋ ባሕሩን ዘልቃ[ሠ] እየ
ተጓዘች ሳለች ነፋስ ተነሥቶ በማዕበል ትን
ገላታ ጀመር።
25ከሌሊቱ በአራተኛው ክፍል ኢየሱስ
በባሕሩ ላይ እየተራመደ ደቀ መዛሙርቱ
ወዳሉበት መጣ። 26ደቀ መዛሙርቱም
በባሕሩ ላይ እየተራመደ ሲመጣ ባዩት ጊዜ
ፈሩ፤ እነርሱም፣ “ምትሀት ነው!” በ
ማለት በፍርሃት ጮኹ።
27ኢየሱስም ወዲያውኑ፣ “አይዞአችሁ፤
እኔ ነኝ አትፍሩ” አላቸው።
28ጴጥሮስም፣ “ጌታ ሆይ፤ አንተ ከሆን
ህስ፣ በውሃው ላይ እየተራመድሁ ወደ
አንተ እንድመጣ እዘዘኝ” አለው።
29እርሱም፣ “ና” አለው።
ጴጥሮስም፣ ከጀልባው ወርዶ በውሃው
እየተራመደ ወደ ኢየሱስ አመራ። 30ነገር
ግን የነፋሱን ኀይል ባየ ጊዜ ፈራ፤ መስጠ
ምም ሲጀምር፣ “ጌታ ሆይ፤ አድነኝ!”
ብሎ ጮኸ።
31ኢየሱስም ወዲያውኑ እጁን ዘርግቶ
ያዘውና፣ “አንተ እምነት የጐደለህ፤ ለምን
ተጠራጠርህ?” አለው።
32ጴጥሮስና ኢየሱስ ጀልባው ላይ እንደ
ወጡ ነፋሱ ጸጥ አለ። 33ከዚያም በጀ
ልባው ውስጥ የነበሩት፣ “በእውነት አንተ
የእግዚአብሔር ልጅ ነህ” ብለው ሰገዱለት።

## ፈውስ በጌንሴሬጥ

34ባሕሩን ከተሻገሩ በኋላ ጌንሴሬጥ ወደ
ተባለ ቦታ ደረሱ። 35ነዋሪዎቹም ኢየሱስ
መሆኑን ባወቁ ጊዜ፣ በዙሪያው ወዳለ አካ
ባቢ ሁሉ መልእክት ላኩ፤ የታመሙትን

14፥2 ማቴ3፥1
14፥3 ማቴ4፥12፤ 11፥2፤ሉቃ3፥19፡20
14፥4 ዘሌ18፥16፤ 20፥21
14፥5 ማቴ11፥9
14፥10 ማቴ17፥12
14፥12 ሐሥ8፥2
14፥14 ማቴ4፥23፤ 9፥36
14፥17 ማቴ16፥9
14፥19 1ሳሙ9፥13፤ ማቴ26፥26፤ ማር8፥6፤ ሉቃ9፥16፤24፥30፤ ሐሥ2፥42፤20፥7፡11፤ 27፥35፤1ቆሮ10፥16፤ 1ጢሞ4፥4
14፥23 ሉቃ3፥21
14፥26 ሉቃ24፥37
14፥27 ዳን10፥12፤ ማቴ9፥2፤17፥7፤ 28፥10፤ሉቃ1፥13፡30፤ 2፥10፤ሐሥ18፥9፤ 23፥11፤ራእ1፥17
14፥31 ማቴ6፥30
14፥33 መዝ2፥7፤ማቴ4፥3

[ሠ]24 ግሪኩ ብዙ ምዕራፍ ይላል

ሁሉ ወደ እርሱ በማስመጣት፣ [36]በሽተ
ኞቹ የልብሱን ጫፍ ብቻ ይነኩ ዘንድ
እንዲፈቅድላቸው ለመኑት፤ የነኩትም ሁሉ
ተፈወሱ።

### የፈሪሳውያን ወግ

15፥1-20 ተጓ ምብ - ማር 7፥1-23

**15** ከዚያም ከኢየሩሳሌም የመጡ
ፈሪሳውያንና የኦሪት ሕግ መምህራ
ን ወደ ኢየሱስ ቀርበው፣ [2]“ደቀ መዛ
ሙርትህ የአባቶችን ወግ የሚሽሩት ለም
ንድነው? ምግብ ሲበሉኮ እጃቸውን አይ
ታጠቡም” አሉት።
[3]ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
“እናንተስ ለወጋችሁ ስትሉ የእግዚአብሔ
ርን ትእዛዝ ለምን ትሽራላችሁ? [4]እግዚአ
ብሔር፣ ‘አባትህንና እናትህን አክብር፤
በአባቱ ወይም በእናቱ ላይ ክፉ ቃል
የሚናገር ይገደል’ ብሎ ሲያዝ፣ [5]እናንተ
ግን፣ ማንም ሰው አባቱን ወይም እናቱን፣
‘ላደርግላችሁ የሚገባውን ማንኛውንም
ነገር ለእግዚአብሔር መባ አድርጌ አቅርቤ
አለሁ’ ቢላቸው፣ [6]‘አንድ ሰው ይህን
ካደረገ ዘንድ አባቱን ወይም እናቱን
አክብሮአል’ ትላላችሁ። ስለዚህ ለወጋችሁ
ብላችሁ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራ
ላችሁ። [7]እናንተ ግብዞች፤ ኢሳይያስ ስለ
እናንተ እንዲህ ብሎ በትንቢት የተናገ
ረው ትክክል ነው፤

[8]‘ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፤
ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው፤
[9]በከንቱ ያመልኩኛል፣
ትምህርታቸውም የሰው ሥርዓት ነው።’”

[10]ሕዝቡን ወደ እርሱ ቀረብ እንዲሉ አድ
ርጎ እንዲህ አላቸው፤ “ስሙ አስተውሉም፤
[11]ሰውን የሚያረክሰው ከአፉ የሚወጣው
እንጂ ወደ አፉ የሚገባው አይደለም።”
[12]ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው፣
“ፈሪሳውያን ያልኸውን ሰምተው እንደ
ተቈጡ አወቅህ?” አሉት።
[13]እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፤ “የሰማዩ
አባቴ ያልተከለው ተክል ሁሉ ይነቀላል።
[14]ተዉአቸው፣ እነርሱ ዕውሮችን የሚ
መሩ ዕውር መሪዎች ናቸው፤ ዕውር ዕው
ርን ቢመራ ሁለቱም ተያይዘው ገደል ይገ
ባሉ።”
[15]ጴጥሮስም፣ “ምሳሌውን አስረዳን”
አለው።
[16]እርሱም እንዲህ አላቸው፤ “እናንተም
እስካሁን አላስተዋላችሁም ማለት ነውን?
[17]በአፍ የሚገባ ሁሉ ወደ ሆድ ዘልቆ፣
ከዚያም ወደ ውጪ እንደሚወጣ አታው
ቁምን? [18]ከአፍ የሚወጣ ግን ከልብ
ይመነጫል፤ ሰውንም የሚያረክሰው ይህ
ነው፤ [19]ክፉ ሐሳብ፣ ነፍስ መግደል፣ ማመ
ንዘር፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ በሐሰት መመ
ስከርና ስም ማጥፋት ከልብ ይመነጫ
ሉና። [20]ሰውን የሚያረክሱ እነዚህ ናቸው
እንጂ እጅን ሳይታጠቡ መብላት ሰውን
አያረክስም።”

### የከነዓናዊቷ ሴት እምነት

15፥21-28 ተጓ ምብ - ማር 7፥24-30

[21]ኢየሱስም ከዚያ ወጥቶ ወደ ጢሮስና
ወደ ሲዶና አገር ሄደ። [22]አንዲት ከነዓና
ዊት ሴት ከዚያ አካባቢ በመውጣት ወደ
ኢየሱስ መጥታ፣ “ጌታ ሆይ፤ የዳዊት
ልጅ፤ ራራልኝ፤ ልጄ በርኩስ መንፈስ
ተይዛ በጣም ትሠቃያለች” ብላ ጮኸች።
[23]እርሱ ግን አንድም ቃል አልመለሰላ
ትም፤ በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ
እርሱ ቀርበው፣ “እየተከተለችን ትጮኻለ
ችና ብታሰናብታትስ?” ብለው ጠየቁት።
[24]እርሱም፣ “የተላክሁት ከእስራኤል ቤት
ሆነው ወደ ጠፉት በጎች ብቻ ነው” አለ።
[25]ሴትዮዋም እግሩ ላይ ወድቃ፣ “ጌታ
ሆይ፤ ርዳኝ” አለች።
[26]እርሱም መልሶ፣ “የልጆችን እንጀራ
ወስዶ ለውሾች መወርወር አይገባም” አላት።
[27]እርሷም፣ “አዎን ጌታ ሆይ፤ ውሾችም
እኮ ከጌታቸው ማዕድ የወዳደቀውን ፍርፋሪ
ይበላሉ” አለችው።
[28]በዚህ ጊዜ ኢየሱስ፣ “አንቺ ሴት እም
ነትሽ ታላቅ ነው እንደ ፈለግሽው ይሁ
ንልሽ” አላት። ልጇም ከዚያ ሰዓት
ጀምሮ ተፈወሰች።
[29]ኢየሱስ ከዚያ ተነሥቶ በገሊላ ባሕር
አጠገብ ወዳለው ስፍራ በመሄድ ወደ ተራራ
ወጥቶ ተቀመጠ። [30]ቍጥሩ ብዙ የሆነ ሕዝ
ብም አንካሶችን፣ ዐይነ ስውሮችን፣ ሽባዎ
ችን፣ ዲዳዎችን እንዲሁም ሌሎች ብዙዎ
ችን ሕመምተኞች ይዘው ወደ እርሱ በማ
ምጣት በእግሩ ሥር አስቀመጧቸው፤ እር
ሱም ፈወሳቸው። [31]ሕዝቡም ዲዳው ሲና
ገር፣ ሽባው ደህና ሲሆን፣ አንካሳው ቀጥ
ብሎ ሲሄድ፣ ዐይነ ስውሩም ሲያይ ተመ
ልክተው ተደነቁ፤ የእስራኤልንም አምላክ
አመሰገኑ።

### ኢየሱስ አራት ሺህ ሰዎች በታምር መገበ

15፥29-31 ተጓ ምብ - ማር 7፥31-37
15፥32-39 ተጓ ምብ - ማር 8፥1-10
15፥32-39 ማመ - ማቴ 14፥13-21

[32]ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ፣

14፥36 ማቴ9፥20
15፥2 ሉቃ11፥38
15፥4 ዘፀ20፥12፤ 21፥17፤ዘሌ20፥9፤ ዘዳ5፥16፤ኤፌ6፥2
15፥9 ኢሳ29፥13፤ ሚል2፥2፤ቈላ2፥ 20-22
15፥11 ቈ18፤ ሐሥ 10፥14፡15
15፥13 ኢሳ60፥21፤ 61፥3
15፥14 ማቴ23፥16፡ 24፤ሉቃ6፥39፤ሮሜ 2፥19
15፥15 ማቴ13፥36
15፥16 ማቴ16፥9
15፥18 ማቴ12፥34 ፤ሉቃ6፥45፤ያዕ3፥6
15፥19 ገላ5፥19-21
15፥20 ሮሜ14፥14
15፥21 ማቴ11፥21
15፥22 ማቴ4፥24፤ 9፥27
15፥24 ማቴ10፥6፡ 23፤ሮሜ15፥8
15፥25 ማቴ8፥2
15፥28 ማቴ9፥22
15፥30 ማቴ4፥23
15፥31 ማቴ9፥8

“ሕዝቡ ከእኔ ጋር ሦስት ቀን ስለሆናቸ
ውና የሚበሉት ስለሌላቸው አዝንላቸዋ
ለሁ፤ በመንገድ ላይ በራብ ዝለው እንዳይ
ወድቁ ጦማቸውን ልሰዳቸው አልፈቅ
ድም” አለ።
33 ደቀ መዛሙርቱም፣ “በዚህ ምንም
በሌለበት ምድረ በዳ ይህንን ሁሉ ሕዝብ
ለማብላት በቂ እንጀራ ከየት እናገኛለን?”
በማለት መለሱለት።
34 ኢየሱስም፣ “ለመሆኑ ስንት እንጀራ
አላችሁ?” ሲል ጠየቀ።
እነርሱም፣ “ሰባት እንጀራና ጥቂት ትና
ንሽ ዓሣ” አሉት።
35 እርሱም ሕዝቡን መሬት ላይ እንዲቀ
መጡ አዘዛቸው፤ 36 ሰባቱን እንጀራና ዓሣ
ውን ይዞ ካመሰገነ በኋላ ቈርሶ ለደቀ መዛ
ሙርቱ ሰጣቸው፤ እነርሱም ለሕዝቡ አከፋ
ፈሉ። 37 ሁሉም በልተው ጠገቡ፤ ደቀ መዛ
ሙርቱም የተረፈውን ቍርስራሽ ሰባት
መሶብ ሙሉ አነሡ። 38 የበሉትም ከሴ
ቶችና ከሕፃናት ሌላ አራት ሺህ ወንዶች
ነበሩ። 39 ኢየሱስ ሕዝቡን ካሰናበተ በኋላ
በጀልባ ወደ መጌዶል ሄደ።

## ኢየሱስ ከሰማይ ምልክት እንዲያሳይ መጠየቁ

16፥1-12 ተጓ ምብ - ማር 8፥11-21

16 ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ወደ
ኢየሱስ ቀርበው ሊፈትኑት በመ
ሻት ከሰማይ ምልክት እንዲያሳያቸው ጠየ
ቁት።
2 እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፤[የ]
“ምሽት ላይ፣ ‘ሰማዩ ስለ ቀላ ብራ ይሆናል’
ትላላችሁ፤ 3 ንጋት ላይም፣ ‘ሰማዩ ቀልቶ
አል፣ ከብዶአልም፤ ስለዚህ ዝናብ ይዘን
ባል’ ትላላችሁ። የሰማዩን ገጽታ ትለያላ
ችሁ፤ ነገር ግን የዘመኑን ምልክት መለ
የት አትችሉም። 4 ክፉና አመንዝራ ትው
ልድ ምልክት ይፈልጋል፤ ነገር ግን ከዮ
ናስ ምልክት በስተቀር ሌላ ምልክት አይ
ሰጠውም።” ከዚያም ኢየሱስ ትቶአቸው
ሄደ።

## የፈሪሳውያንና የሰዱቃውያን እርሾ

5 ባሕሩን እንደ ተሻገሩም፣ ደቀ መዛ
ሙርቱ እንጀራ መያዝ ረስተው ነበር።
6 ኢየሱስም፣ “ልብ በሉ፤ ከፈሪሳውያንና
ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠበቁ” አላቸው።
7 እነርሱ ግን እርስ በርሳቸው፣ “እንጀራ
ስላልያዝን ይሆናል” ተባባሉ።
8 ኢየሱስም ሐሳባቸውን አውቆ እንዲህ
አላቸው፤ “እናንተ እምነት የጐደላችሁ፣
እርስ በርሳችሁ እንጀራ ስለ አለመያዛችሁ
ለምን ትነጋገራላችሁ? 9 አምስቱ እንጀራ
ለአምስት ሺህ ሰው በቅቶ ስንት መሶብ
ተርፎ እንዳነሣችሁ አታስታውሱምን?
10 እንዲሁም ሰባቱ እንጀራ ለአራት ሺህ
ሰው በቅቶ ስንት መሶብ ተርፎ እንዳነ
ሣችሁ ልብ አላላችሁም ማለት ነውን?
11 ታዲያ የነገርኋችሁ ስለ እንጀራ እንዳል
ሆነ እንዴት አታስተውሉም? አሁንም
ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠን
ቀቁ።” 12 በዚህ ጊዜ ያስጠነቀቃቸው እንጀራ
ውስጥ ስለሚጨመረው እርሾ ሳይሆን፣
ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ትምህርት
መሆኑ ገባቸው።

## ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ማንነት መናገሩ

16፥13-16 ተጓ ምብ - ማር 8፥27-29፤ ሉቃ 9፥18-20

13 ኢየሱስ ፊልጶስ ቂሣርያ ወደተባለው
አገር በደረሰ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን፣
“ለመሆኑ ሰዎች፣ የሰውን ልጅ ማን ነው
ይላሉ?” ብሎ ጠየቃቸው።
14 እነርሱም፣ “አንዳንዶቹ መጥምቁ ዮሐ
ንስ፣ ሌሎች ኤልያስ፣ ሌሎች ደግሞ
ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው
ይላሉ” አሉት።
15 እርሱም፣ “እናንተስ እኔን ማን ትሉ
ኛላችሁ?” አላቸው።
16 ስምዖን ጴጥሮስም፣ “አንተ ክርስቶስ[ደ]
የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ” በማለት
መለሰ።

## ኢየሱስ ስለሚደርስበት መከራ ተናገረ

16፥21-28 ተጓ ምብ - ማር 8፥31- 9፥1፤ ሉቃ 9፥22-27

17 ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ “የዮና ልጅ
ስምዖን ሆይ፣ ብፁዕ ነህ፤ ይህን የገለጠልህ
በሰማይ ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም
አይደለም። 18 አንተ ጴጥሮስ[ጀ] ነህ፤ በዚህ
ዐለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤
የገሃነም ደጆችም አያሸንፏትም።[ገ] 19 የመ
ንግሥተ ሰማይን መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤
በምድር ያሰርኸው ሁሉ በሰማይ የታሰረ
ይሆናል፤ በምድርም የፈታኸው ሁሉ በሰ
ማይ የተፈታ ይሆናል።” 20 ቀጥሎም እርሱ
ክርስቶስ መሆኑን ለማንም እንዳይናገሩ
ደቀ መዛሙርቱን አስጠነቀቃቸው።
21 ኢየሱስ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ወደ ኢየሩ
ሳሌም ይሄድ ዘንድ፣ በዚያም በሽማግሌ
ዎች፣ በካህናት አለቆችና በኦሪት ሕግ

15፥32 ማቴ9፥36
15፥36 ማቴ14፥19
15፥37 ማቴ16፥10
16፥1 ማቴ12፥38፤ ሐሥ4፥1
16፥3 ሉቃ12፥54-56
16፥4 ማቴ12፥39
16፥6 ሉቃ12፥1
16፥8 ማቴ6፥30
16፥9 ማቴ14፥17-21
16፥10 ማቴ15፥34-38
16፥12 ሐሥ4፥1
16፥14 ማቴ3፥1፤ ማር6፥15፤ዮሐ21
16፥16 መዝ42፥2፤ ኤር10፥10፤ማቴ4፥3፤ ሐሥ14፥15፤2ቆሮ 6፥16፤1ተሰ1፥9፤ 1ጢሞ3፥15፤ዕብ 10፥31፤12፥22
16፥17 ማቴ13፥11 ፤1ቆሮ15፥50፤ኤፌ 6፥12፤ዕብ2፥14
16፥18 ዮሐ1፥42፤ ኤፌ2፥20
16፥19 ኢሳ22፥22፤ ማቴ18፥18፤ዮሐ20፥ 23፤ራእ3፥7
16፥20 ማር8፥30
16፥21 መዝ22፥6፤ ኢሳ53፥3፤ሆሴ6፥2፤ ማቴ12፥40፤17፥22፡ 23፤26፥67፡68፤27፥1፡ 2፡63፤ማር9፥31፤10፥ 34፤ሉቃ9፥22፡51፤17፥ 25፤18፥31-33፤24፥ 6፡7፡21፡46፤ዮሐ2፥19 ፤18፥22፡23፤19፥3፤ ሐሥ2፥23፤3፥13፤ 1ቆሮ15፥3፡4

[የ]2 አንዳንድ የጥንት ቅጆች የቍጥር 2 ከፊልና ቍጥር 3 በሙሉ የላቸውም
[ደ]16 ወይም *መሲሕ*፤ ቍ 20 ይመ
[ጀ]18 *ጴጥሮስ* ትርጕሙ *ዐለት* ማለት ነው
[ገ]18 ወይም *ሊቋቋሟት አይችሉም*

መምህራን እጅ መከራን ይቀበልና ይገ
ደል ዘንድ፣ በሦስተኛው ቀን ከሞት ይነሣ
ዘንድ እንደሚገባው ለደቀ መዛሙርቱ
ይገልጽላቸው ጀመር።

### ኢየሱስ ስለሚደርስበት መከራ ለሁለተኛ ጊዜ ተናገረ

22ጴጥሮስም ኢየሱስን ወደ ጐን ሳብ
አድርጎ፣ “ጌታ ሆይ፤ እንዲህ ያለ ነገር ፈጽሞ
አይድረስብህ” እያለ ይገሥጸው ጀመር።
23ኢየሱስም ወደ ጴጥሮስ ዘወር ብሎ፣
“አንተ ሰይጣን፣ ሂድ ከዚህ! የሰው እንጂ
የእግዚአብሔር ነገር በሐሳብህ ስለ ሌለ
መሰናክል ሆነህብኛል!” አለው።
24ከዚያም ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን
እንዲህ አላቸው፤ “ሊከተለኝ የሚወድ ራ
ሱን ይካድ፣ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተ
ለኝ፤ 25ነፍሱን[ጠ] ሊያድን የሚፈልግ ሁሉ
ያጠፋታል፤ ነገር ግን ነፍሱን ስለ እኔ
የሚያጠፋት ያድናታል። 26ሰው ዓለምን
ሁሉ ቢያተርፍ፣ ነፍሱን ግን ቢያጣ ምን
ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው በነፍሱ ምትክ
ሊከፍለው የሚችለው ዋጋ ምንድን ነው?
27የሰው ልጅ በአባቱ ክብር ከመላእክት
ጋር ይመጣል፤ ለእያንዳንዱም ሰው እንደ
ሥራው ዋጋውን ይከፍለዋል። 28እውነት
እላችኋለሁ፣ እዚህ ከቆሙት ሰዎች መካከል
የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ እስከ
ሚያዩ ድረስ ሞትን የማይቀምሱ አሉ።”

### የኢየሱስ መልክ በቅጽበት መቀየር

17፥1-8 ተጓ ምብ - ሉቃ 9፥28-36
17፥1-13 ተጓ ምብ - ማር 9፥2-13

17 ከስድስት ቀን በኋላ ኢየሱስ፣
ጴጥሮስንና ያዕቆብን እንዲሁም
የያዕቆብን ወንድም ዮሐንስን ወደ አንድ
ከፍ ያለ ተራራ ብቻቸውን ይዞአቸው ወጣ።
2በዚያም በፊታቸው መልኩ ተቀየረ፤
ፊቱ እንደ ፀሓይ አበራ፤ ልብሱም እንደ
ብርሃን አንጸባረቀ። 3ወዲያውም ሙሴና
ኤልያስ ከኢየሱስ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው።
4ጴጥሮስም ኢየሱስን፣ “ጌታ ሆይ፤ በዚህ
ብንሆን ለእኛ መልካም ነው፤ ፈቃድህ ከሆነ፣
አንድ ለአንተ፣ አንድ ለሙሴ፣ አንድ
ለኤልያስ ሦስት ዳሶች ልሥራ” አለው።
5እርሱ እየተናገረ ሳለ፣ ብሩህ ደመና
ሸፈናቸው፤ ከደመናውም ውስጥ፣ “በእርሱ
ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤
እርሱን ስሙት” የሚል ድምፅ ተሰማ።
6ደቀ መዛሙርቱም ይህን ሲሰሙ ደን
ግጠው በግንባራቸው መሬት ላይ ተደፉ።
7ኢየሱስም ቀርቦ ነካቸውና፣ “ተነሡ፤ አት
ፍሩ” አላቸው። 8ቀና ብለው ሲመለከቱም

16፥23 ማቴ4፥10
16፥24 ማቴ10፥38፤ ሉቃ14፥27
16፥25 ዮሐ12፥25
16፥27 2ዜና6፥23፤ ኢዮ34፥11፤መዝ62፥12፤ኤር17፥10፤ሕዝ18፥20፤ማቴ8፥20፤ ሉቃ17፥30፤ ዮሐ14፥3፤ ሐሥ1፥11፤ 1ቆሮ 1፥7፤3፥12-15፤ 2ቆሮ 5፥10፤ 1ተሰ2፥19፤ 4፥16፤ ራእ1፥7፤22፥7፡12፡20
17፥1 ማቴ4፥21
17፥5 ማቴ3፥17፤ ሐሥ3፥22፡23
17፥7 ማቴ14፥27
17፥9 ማቴ8፥20፤ 16፥21፤ማር8፥30
17፥11 ሚል4፥6፤ ሉቃ1፥16፡17
17፥12 ማቴ11፥14፤ 14፥3፡10፤16፥21
17፥13 ማቴ3፥1
17፥15 ማቴ4፥24
17፥20 ማቴ13፥31፤ 21፥21፤ሉቃ17፥6፤ 1ቆሮ13፥2
17፥22 ማቴ8፥20
17፥23 ማቴ16፥21፤ሐሥ2፥23፤3፥13

ከኢየሱስ በስተቀር ሌላ ማንንም አላዩም።
9ከተራራው በመውረድ ላይ ሳሉ ኢየ
ሱስ፣ “የሰው ልጅ ከሞት እስኪነሣ ድረስ
ያያችሁትን ለማንም እንዳትናገሩ” ብሎ
አዘዛቸው።
10ደቀ መዛሙርቱም፣ “ታዲያ የኦሪት ሕግ
መምህራን፣ ኤልያስ አስቀድሞ መምጣት
አለበት የሚሉት ለምንድን ነው?” ብለው
ጠየቁት።
11እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
“ኤልያስ በእርግጥ መጥቶ ሁሉንም ነገር
ያስተካክላል፤ 12ነገር ግን እላችኋለሁ፤ ኤል
ያስ መጥቶአል፤ ሆኖም የፈለጉትን ነገር
አደረጉበት እንጂ አላወቁትም። እንዲ
ሁም የሰው ልጅ በእጃቸው መከራን ይቀ
በላል።” 13በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ኢየ
ሱስ የነገራቸው ስለ መጥምቁ ዮሐንስ
መሆኑን ተረዱ።

### ኢየሱስ የሚጥል በሽታ ያለበትን ልጅ ፈወሰ

14ወደ ሕዝቡ እንደ ተመለሱ፣ አንድ ሰው
ወደ ኢየሱስ ቀርቦ በፊቱ ተንበረከከና እን
ዲህ አለ፤ 15“ጌታ ሆይ፤ እባክህ ልጄን
ማርልኝ፤ በሚጥል በሽታ እጅግ እየተሠ
ቃየ ነው፤ ብዙ ጊዜ እሳት ውስጥ ይወ
ድቃል፤ ውሃ ውስጥም ይገባል፤ 16ወደ
ደቀ መዛሙርትህ አመጣሁት፤ ነገር ግን
ሊፈውሱት አልቻሉም።” 17ኢየሱስም፣
“አንተ የማታምን ጠማማ ትውልድ፤ እስከ
መቼ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ፤ እስከ መቼስ
እታገሣችኋለሁ። ልጁን ወደዚህ አምጡት”
አለ። 18ከዚያም ኢየሱስ ጋኔኑን ገሠጸውና
ከልጁ ወጣ፤ ልጁም ከዚያች ሰዓት ጀምሮ
ዳነ።
19ደቀ መዛሙርቱም ለብቻቸው ወደ ኢየ
ሱስ ቀርበው፣ “እኛ ጋኔኑን ማስወጣት
ያልቻልነው ለምንድን ነው?” ብለው ጠየቁት።
20እርሱም እንዲህ አላቸው፤ “እምነታ
ችሁ በማነሱ ምክንያት ነው፤ እላችኋለሁ፤
የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል እምነት ቢኖ
ራችሁ፣ ይህንን ተራራ፣ ‘ከዚህ ተነሥተህ
ወደዚያ ሂድ’ ብትሉት ይሄዳል፤ የሚሳና
ችሁም ነገር አይኖርም፤ 21የዚህ ዓይነቱ ግን
በጸሎትና በጾም ካልሆነ በስተቀር አይወ
ጣም።”
22በገሊላ ተሰባስበው ሳሉ ኢየሱስ እንዲህ
አላቸው፤ “የሰውን ልጅ አሳልፈው ለሰ
ዎች ይሰጡታል፤ 23ይገድሉታልም፤ እርሱም
በሦስተኛው ቀን ይነሣል።” ደቀ መዛ
ሙርቱም እጅግ አዘኑ።

[ጠ]25 የግሪኩ ቃል ትርጕም ሕይወት ወይም ነፍስ ነው፤ ቍ26 ይመ

### ስለ ቤተ መቅደስ ግብር ክፍያ

24ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ቅፍርናሆም
ከደረሱ በኋላ፣ የቤተ መቅደሱ ግብር
ተቀ ባዮች ወደ ጴጥሮስ ቀርበው “መምህ
ራችሁ ሁለቱን ዲናር የቤተ መቅደስ
ግብር አይከፍልምን?” አሉት።
25እርሱም፣ “ይከፍላል እንጂ” አላቸው።
ጴጥሮስ ወደ ቤት እንደ ገባ ኢየሱስ
በቅድሚያ፣ “ስምዖን፤ የምድር ነገሥታት
ግብር ወይም ቀረጥ የሚቀበሉት ከራ
ሳቸው ልጆች ወይስ ከሌሎች ይመስል
ሃል?” አለው።
26ጴጥሮስም፣ “ከሌሎች ነው የሚቀበ
ሉት” አለው።
ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ “እንግዲያውስ
ልጆች ነጻ ናቸው፤ 27ሆኖም እንዳናስቀይ
ማቸው ሂደህ መንጠቆህን ወደ ባሕር
ጣል፤ መጀመሪያ የምትይዘውን ዓሣ አፉን
ስትከፍት የምታገኘውን አንድ እስታቴር
በእኔና በአንተ ስም ክፈል።”

### በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው?

18፥1-5 ተጓ ምብ - ማር 9፥33-37፤ ሉቃ 9፥46-48

18 በዚያ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ
ኢየሱስ ቀርበው፣ “በመንግሥተ
ሰማይ ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው?” ብለው
ጠየቁት።
2ኢየሱስ አንድ ሕፃን ጠርቶ በመካከላ
ቸው አቆመና እንዲህ አላቸው፤ 3“እውነት
እላችኋለሁ፣ ካልተለወጣችሁ እንደ ሕፃናት
ካልሆናችሁ ፈጽሞ ወደ መንግሥተ ሰማይ
አትገቡም። 4ስለዚህ በመንግሥተ ሰማይ
ከሁሉ የሚበልጥ እንደዚህ ሕፃን ራሱን
ዝቅ የሚያደርግ ነው፤
5“እንደዚህ ያለውንም ሕፃን በስሜ የሚ
ቀበል እኔን ይቀበላል። 6ነገር ግን በእኔ
ከሚያምኑት ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን
የሚያሰናክል ሰው፣ ከባድ የወፍጮ ድን
ጋይ በዐንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር
ተጥሎ ቢሰጥም ይሻለዋል። 7ይህች ዓለም
የመሰናከል ምክንያት በመሆኗ ወዮላት!
መሰናክል መምጣቱ አይቀርምና፤ ነገር ግን
የመሰናከሉ ምክንያት ለሚሆነው ሰው
ወዮለት። 8እጅህ ወይም እግርህ ለመሰ
ናከል ምክንያት ቢሆንብህ፣ ቈርጠህ ጣለው፤
ሁለት እጅ ወይም ሁለት እግር ኖሮህ
ወደ ዘለዓለም እሳት ከምትጣል፣ አንካሳ
ወይም ሽባ ሆነህ ወደ ሕይወት መግባት
ይሻልሃል። 9እንዲሁም ዐይንህ ለመሰናከል
ምክንያት ቢሆንብህ፣ አውጥተህ ጣለው፤
ሁለት ዐይን ኖሮህ ወደ ገሃነመ እሳት

17፥24 ዘፀ30፥13
17፥25 ማቴ22፥17-21፤ሮሜ13፥7
17፥27 ዮሐ6፥61
18፥3 ማቴ3፥2፤ 19፥14፤1ጴጥ2፥2
18፥4 ማር9፥35
18፥5 ማቴ10፥40
18፥6 ማቴ5፥29፤ ማር9፥42፤ሉቃ17፥2
18፥7 ሉቃ17፥1
18፥8 ማቴ5፥29
18፥9 ማቴ5፥22፥29
18፥10 ዘፍ48፥16፤ መዝ34፥7፤ ሐሥ12፥11፥15፤ ዕብ1፥14
18፥15 ዘሌ19፥17፤ ሉቃ17፥3፤ገላ6፥1፤ ያዕ5፥19፥20
18፥16 ዘኍ35፥30፤ ዘዳ17፥6፤19፥15፤ ዮሐ8፥17፤ 2ቆሮ13፥1፤1ጢሞ5፥19፤ዕብ10፥ 28
18፥17ሮሜ16፥17፤ 1ቆሮ6፥1-6
18፥18 ማቴ16፥19 ፤ዮሐ20፥23
18፥19 ማቴ7፥7
18፥20 ማቴ28፥20
18፥21 ማቴ6፥14፤ ሉቃ17፥4
18፥22 ዘፍ4፥24
18፥23 ማቴ13፥24 ፤25፥19

ከምትጣል፣ አንድ ዐይን ኖሮህ ወደ ሕይ
ወት መግባት ይሻልሃል። 10“ከእነዚህ ከታ
ናናሾች መካከል አንዱን እንዳትንቁ ተጠ
ንቀቁ፤ እላችኋለሁና፤ በሰማይ ያሉት መላ
እክታቸው በሰማይ ያለውን የአባቴን ፊት
ሁልጊዜ ያያሉ፤ 11የሰው ልጅ የጠፉትን ለማ
ዳን መጥቶአልና።

### የጠፋው በግ ምሳሌ

12“እስቲ ንገሩኝ፤ አንድ ሰው መቶ በጎች
ቢኖሩትና ከእነርሱም አንዱ ቢጠፋበት ዘጠና
ዘጠኙን በተራራ ላይ ትቶ የጠፋውን ለመ
ፈለግ አይሄድምን? 13እውነት
እላችኋለሁ፣ የጠፋውን በግ ሲያገኝ፣
ካልጠፉት ከዘጠና ዘጠኙ ይልቅ በዚያ
በተገኘው ደስ ይለዋል። 14እንደዚሁም
ከእነዚህ ከታናናሾቹ መካከል አንዱ እንኳ
እንዲጠፋ በሰማያት ያለው አባታችሁ
ፈቃድ አይደለም።

### ስለ መቀያየም

15“ወንድምህ ቢበድልህ[ጨ] ሂደህ አንተና
እርሱ ብቻ ሆናችሁ ጥፋቱን ንገረው። ቢሰ
ማህ፣ ወንድምህን እንደ ገና የራስህ ታደ
ርገዋለህ። 16ባይሰማህ ግን ቃል ሁሉ በሁ
ለት ወይም በሦስት ምስክሮች ፊት ስለ
ሚጸና፣ አንድ ወይም ሁለት ሰው ይዘህ አነ
ጋግረው። 17እነርሱን ባይሰማ ለቤተ ክርስ
ቲያን ንገር፤ ቤተ ክርስቲያንንም ባይሰማ
እንደ አሕዛብና እንደ ቀረጥ ሰብሳቢ
ቍጠረው።
18“እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር ያሰራች
ሁት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በም
ድርም የፈታችሁት ሁሉ በሰማይ የተፈታ
ይሆናል።
19“ደግሞም እውነት እላችኋለሁ፤ በም
ድር ላይ ሁለት ሆናችሁ ስለ ምንም ነገር
በመስማማት ብትጠይቁ በሰማይ ያለው
አባቴ ያደርግላችኋል፤ 20ሁለት ወይም
ሦስት ሆነው በስሜ በሚሰበሰቡበት መካ
ከል በዚያ እገኛ ለሁና።”

### ይቅርታ ስለ ማድረግ

21በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ ወደ ኢየሱስ
ቀርቦ፣ “ጌታ ሆይ፤ ወንድሜ ቢበድለኝ
ስንት ጊዜ ይቅር ልበለው? እስከ ሰባት ጊዜ
ነውን? አለው። 22ኢየሱስም “እስከ ሰባ ጊዜ
ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ ብቻ አልል
ህም” አለው።
23“ስለዚህ መንግሥተ ሰማይ፣ በአገልጋ
ዮቹ እጅ የነበረውን ሂሳብ ለመተሳሰብ
የፈለገን ንጉሥ ትመስላለች። 24ሂሳቡን
ማጣራት እንደ ጀመረም ዐሥር ሺህ ታላ

[ጨ]15 አንዳንድ ቅጆች ቢበድል/ኀጢአት ቢሠራ ይላሉ

ንት* ዕዳ ያለበትን አንድ አገልጋይ አቀረ
ቡለት። 25አገልጋዩም ያለበትን ዕዳ መክ
ፈል ስላቃተው እርሱ ራሱ፣ ሚስቱ፣ ልጆ
ቹና ንብረቱ ሁሉ ተሸጠው ዕዳው እንዲከ
ፈል ጌታው አዘዘ።
26“በዚህ ጊዜ አገልጋዩ እግሩ ላይ ወድቆ፣
‘ታገሰኝ፣ ያለብኝን ዕዳ ሁሉ እከፍልሃለሁ’
ሲል ለመነው። 27ጌታውም አዘነለትና ማረው፤
ዕዳውንም ትቶለት አሰናበተው።
28“ያ አገልጋይ ከጌታው ፊት እንደ ወጣ
አንድ መቶ ዲናር* የእርሱ ዕዳ ያለበትን
አገልጋይ ባልንጀራውን አግኝቶ እንቅ
አድርጎ በመያዝ፣ ‘ያለብህን ዕዳ ክፈለኝ!’
አለው።
29“ባልንጀራው አገልጋይም ከፊቱ ወድቆ፣
‘ታገሠኝ እከፍልሃለሁ’ ብሎ ለመነው።
30“ነገር ግን ሊታገሠው ፈቃደኛ ስላልነ
በረ፣ ያለበትን ዕዳ እስኪከፍለው ድረስ
ወህኒ ቤት አስገባው። 31የሆነውን ነገር
ያዩ ሌሎች አገልጋዮችም በጣም አዘኑ፤
ሄደውም ሁኔታውን በሙሉ ለጌታቸው
ነገሩት።
32“በዚህ ጊዜ ጌታው አገልጋዩን አስጠርቶ
እንዲህ አለው፤ ‘አንተ ክፉ አገልጋይ፤ ስለ
ለመንኸኝ ያን ሁሉ ዕዳ ተውሁልህ፤ 33እኔ
እንደ ማርሁህ አንተም ባልንጀራህን ልት
ምረው አይገባህም ነበርን?’ 34በቍጣም ያለ
በትን ዕዳ ከፍሎ እስኪጨርስ ድረስ ለአሳ
ሪዎች አሳልፎ ሰጠው።
35“ስለዚህ እያንዳንዳችሁ ወንድሞቻችሁን
ከልባችሁ ይቅር ካላላችሁ፣ የሰማዩ አባቴም
እንደዚሁ ያደርግባችኋል።”

### ስለ መፋታት የቀረበ ጥያቄ

19፥1-9 ተጓ ምብ-ማር10፥1-12

19 ኢየሱስ ይህን ተናግሮ ከጨረሰ
በኋላ፣ ገሊላን ትቶ ከዮርዳኖስ ማዶ
ወዳለው ወደ ይሁዳ አውራጃ ሄደ። 2ብዙ
ሕዝብም ተከተለው፤ በዚያም ፈወሳቸው።
3ፈሪሳውያንም ሊፈትኑት ቀርበው፣
“ለመሆኑ አንድ ሰው በማንኛውም ምክን
ያት ሚስቱን መፍታት ተፈቅዶአልን?” ሲሉ
ጠየቁት።
4እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
“ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አድርጎ
እንደ ፈጠራቸው አላነበባችሁምን? 5እንዲ
ህም አለ፤ ‘ሰው አባቱንና እናቱን ይተ
ዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይጣመራል፣ ሁለቱም
አንድ ሥጋ ይሆናሉ’ የተባለው በዚህ ምክ
ንያት አይደለምን? 6ከእንግዲህ አንድ ሥጋ
ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም፤ ስለዚህ
እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው አይለየው።”

18፥25 ዘሌ25፥39፤ 2ነገ4፥1፤ነህ5፥5፡8፤ ሉቃ7፥42
18፥26 ማቴ8፥2
18፥35 ማቴ6፥14፤ ያዕ2፥13
19፥1 ማቴ7፥28
19፥2 ማቴ4፥23
19፥3 ማቴ5፥31
19፥4 ዘፍ1፥27፤5፥2
19፥5 ዘፍ2፥24፤ 1ቆሮ6፥16፤ኤፌ5፥31
19፥7 ዘዳ24፥1-4፤ ማቴ5፥31
19፥9 ሉቃ16፥18
19፥11 ማቴ13፥11፤ 1ቆሮ7፥7-9፡17
19፥13 ማር5፥23
19፥14 ማቴ18፥3፤ 25፥34፤1ጴጥ2፥2
19፥16 ማቴ25፥46 ፤ሉቃ10፥25
19፥17 ዘሌ18፥5
19፥18 ያዕ2፥11

7እነርሱም፣ “ታዲያ፣ ሙሴ አንድ ወንድ
የፍቺውን የምስክር ወረቀት ሰጥቶ ሚስቱን
እንዲያሰናብት ለምን አዘዘ?” አሉት።
8ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “ሙሴ
የልባችሁን ጥንካሬ አይቶ ሚስቶቻችሁን
እንድትፈቱ ፈቀደላችሁ እንጂ
ከመጀመሪያው እንዲህ አልነበረም፤
9እላችኋለሁ፤ በተዳሯ ላይ ዝሙት ፈጽማ
እስካልተገኘች ድረስ ሚስቱን ፈትቶ
ሌላ ሴት የሚያገባ ሁሉ አመንዝራ
ይሆናል፤ እርሷንም አመንዝራ
ያደርጋታል፣ የተፈታችውንም ሴት
የሚያገባ ያመነዝራል።”
10ደቀ መዛሙርቱም፣ “የባልና የሚስት
ጕዳይ እንዲህ ከሆነ አለማግባት ይሻላል”
አሉት።
11ኢየሱስ ግን እንዲህ አላቸው፤ “ከተሰ
ጣቸው በስተቀር ይህንን ትምህርት ማንም
ሊቀበል አይችልም፤ 12ምክንያቱም አንዳን
ዶች ጃንደረባ ሆነው ይወለዳሉ፤ ሌሎች
በሰው እጅ ተሰልበው ጃንደረባ ይሆናሉ፤
ደግሞም ለመንግሥተ ሰማይ ሲሉ ራሳቸ
ውን ጃንደረባ የሚያደርጉ አሉ። ይህን
መቀበል የሚችል ይቀበል።”

### ኢየሱስ ሕፃናትን ባረካቸው

19፥13-15 ተጓ ምብ - ማር 10፥13-16፤ ሉቃ 18፥15-17

13ከዚያም እጆቹን በላያቸው ላይ ጭኖ
እንዲጸልይላቸው ሕፃናትን ወደ እርሱ
አቀረቧቸው። ደቀ መዛሙርቱ ግን ሕፃና
ቱን ያመጡትን ሰዎች ገሠጿቸው።
14ኢየሱስም፣ “ሕፃናት ወደ እኔ ይምጡ
፤ አትከልክሏቸው፤ መንግሥተ ሰማይ
እንደ እነርሱ ላሉት ናትና” አላቸው።
15እጁንም ጭኖ ከባረካቸው በኋላ ከዚያ
ስፍራ ተነሥቶ ሄደ።

### የሀብታሙ ጥያቄ

19፥16-29 ተጓ ምብ - ማር 10፥17-30፤ ሉቃ 18፥18-30

16ከዚያም አንድ ሰው ወደ ኢየሱስ
ቀርቦ፣ “መምህር ሆይ፤ የዘላለምን ሕይወት
አገኝ ዘንድ ምን መልካም ነገር ልሥራ”
ሲል
ጠየቀው።
17ኢየሱስም፣ “ስለ መልካም ነገር ለምን
ትጠይቀኛለህ? መልካም የሆነ አንዱ ብቻ
ነው፤ ወደ ሕይወት ለመግባት ከፈለግህ
ግን ትእዛዛቱን ጠብቅ” አለው።
18ሰውየውም፣ “የትኞቹን ትእዛዛት?” ሲል
ጠየቀ።
ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ “አትግደል፣
አታመንዝር፤ አትስረቅ፤ በሐሰት አትመስ

*24 በሚሊዮን የሚቆጠር ብር የሚያህል ነው
*28 ጥቂት ብር ያህል ነው

ክር፤ 19አባትህንና እናትህን አክብር፤ ጎረቤ
ትህን እንደ ራስህ ውደድ።”
20ጐልማሳውም ሰውዬ፣ “እነዚህንማ ጠብ
ቄአለሁ፤ ከዚህ ሌላ የሚጐድለኝ ምን
አለ?” አለው።
21ኢየሱስም፣ “ፍጹም ለመሆን ከፈለ
ግህ፣ ሄደህ ንብረትህን ሁሉ ሸጠህ፣ ገንዘ
ቡን ለድኾች ስጥ፤ በሰማይም ሀብት ታገ
ኛለህ። ከዚያም መጥተህ ተከተለኝ” አለው።
22ጐልማሳው ሰውዬም ይህን ሲሰማ ብዙ
ሀብት ስለ ነበረው እያዘነ ሄደ።
23ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አለ፤
“እውነት እላችኋለሁ፣ ለሀብታም ወደ
መንግሥተ ሰማይ መግባት እጅግ አስቸ
ጋሪ ነው። 24ደግሜ እላችኋለሁ፤ ሀብታም
ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ
ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢሾልክ ይቀላል።”
25ይህን ሲሰሙ፣ ደቀ መዛሙርቱ እጅግ
በመገረም፣ “እንግዲያስ ማን ሊድን ይች
ላል?” ሲሉ ጠየቁ።
26ኢየሱስም እየተመለከታቸው፣ “ይህ በሰው
ዘንድ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ
ግን ሁሉም ነገር ይቻላል” አላቸው።
27ጴጥሮስም መልሶ፣ “እኛ ሁሉን ትተን
ተከትለንሃል፤ ታዲያ ምን እናገኝ ይሆን?”
አለው።
28ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “እውነት
እላችኋለሁ፤ በሚመጣው አዲስ ዓለም የሰው
ልጅ በክብሩ ዙፋን ላይ በሚቀመጥበት ጊዜ፣
እናንተም የተከተላችሁኝ በዐሥራ ሁለት
ዙፋን ላይ ተቀምጣችሁ በዐሥራ ሁለቱ
የእስራኤል ነገድ ላይ ትፈርዳላችሁ።
29ስለ ስሜ ብሎ ቤቶችን፣ ወንድሞችን፣
እኅቶችን፣ አባትን፣ እናትን[θ]፣ ልጆችን
ወይም ዕርሻን የሚተው ሁሉ መቶ ዕጥፍ
ይቀበላል፤ የዘላለምንም ሕይወት ይወር
ሳል። 30ነገር ግን ብዙ ፊተኞች ኋለኞች፣
ብዙ ኋለኞችም ፊተኞች ይሆናሉ።”

## የወይን ቦታው ሠራተኞች ምሳሌ

20 “መንግሥተ ሰማይ ለወይኑ ቦታ
ሠራተኞችን ለመቅጠር ማልዶ
የወጣን የአትክልት ስፍራ ባለቤት ትመስ
ላለች። 2በቀን አንዳንድ ዲናር ሊከፍላ
ቸው ከተስማሙ በኋላ ሠራተኞቹን በወ
ይኑ ቦታ አሰማራቸው።
3“ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ላይ በመውጣት
ሥራ ፈትተው በገበያ ቦታ የቆሙትን
ሌሎች ሰዎች አግኝቶ፣ 4‘እናንተም ሄዳ
ችሁ በወይኔ ቦታ ሥሩ፤ ተገቢውን ክፍያ
እሰጣችኋለሁ’ አላቸው፤ 5እነርሱም ሄዱ።
“ከቀኑ በስድስት ሰዓትና በዘጠኝ ሰዓት
ላይ ወጥቶ ሌሎች የቀን ሠራተኞችን ቀጠ
ረ። 6ከሰዓት በኋላ በዐሥራ አንድ ሰዓት
ገደማ ወጥቶ ቆመው የነበሩ ሌሎች ሰዎች
አገኘና፣ ‘ቀኑን ሙሉ ያለ ሥራ እዚህ
ለምን ትቆማላችሁ?’ በማለት ጠየቃቸው።
7“እነርሱም፣ ‘የሚቀጥረን ሰው ስለ አጣን
ነው’ አሉት።
እርሱም፣ ‘እናንተም ሄዳችሁ በወይኔ
ቦታ ሥሩ’ አላቸው።
8“በመሸም ጊዜ የወይኑ አትክልት ባለቤት
የሠራተኞቹን ተቈጣጣሪ፣ ‘ኋላ ከመጡት
ጀምረህ መጀመሪያ እስከመጡት ድረስ
ያሉትን ሠራተኞች በሙሉ ጥራና ደመ
ወዛቸውን ክፈላቸው’ አለው።
9“በዐሥራ አንደኛው ሰዓት ገደማ የተ
ቀጠሩት ሠራተኞች ቀርበው፣ እያንዳንዳ
ቸው አንዳንድ ዲናር ተቀበሉ። 10በመጀ
መሪያ የተቀጠሩት ሲቀርቡ ብልጫ ያለው
ክፍያ የሚያገኙ መስሎአቸው ነበር፤ ነገር
ግን እነርሱም አንዳንድ ዲናር ተከፈ
ላቸው። 11ክፍያውን ሲቀበሉ በባለቤቱ
ላይ በማጕረምረም፣ 12‘እነዚህ በመጨረሻ
የተቀጠሩት አንድ ሰዓት ብቻ ሲሠሩ፣
ቀኑን ሙሉ በሥራ ስንደክምና በፀሐይ
ስንንቃቃ ከዋልነው ጋር እንዴት እኩል
ትከፍለናለህ?’ አሉት።
13“እርሱም አንደኛውን ሠራተኛ እንዲህ
አለው፤ ‘ወዳጄ ሆይ፤ በደል አላደረስሁብ
ህም፤ በአንድ ዲናር ለመሥራት ከእኔ
ጋር ተስማምተህ አልነበረምን? 14በል ድር
ሻህን ይዘህ ሂድ፤ ለአንተ የሰጠሁትን
ያህል በመጨረሻ ለመጣውም ሰው መስጠት
እፈልጋለሁ። 15ታዲያ በራሴ ገንዘብ የፈለ
ግሁትን ማድረግ አልችልምን? ወይስ ቸር
በመሆኔ ምቀኝነት ያዘህን?’
16“ስለዚህ ኋለኞች ፊተኞች፣ ፊተኞችም
ኋለኞች ይሆናሉ።”

## ኢየሱስ ስለሚደርስበት መከራ ለሦስተኛ ጊዜ ተናገረ

20፥17-19 ተጓ ምብ - ማር 10፥32-34፤ ሉቃ 18፥31-33

17ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ
ላይ ሳለ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት
ለብ ቻቸው ወስዶ እንዲህ አላቸው፤
18“እንግዲህ
ወደ ኢየሩሳሌም መሄዳችን ነው፤ የሰው
ልጅ ለካህናት አለቆችና ለኦሪት ሕግ
መምህራን አልፎ ይሰጣል፤ እነርሱም እን
ዲሞት ይፈርዱበታል፤ 19እንዲያላግጡ
በት፣ እንዲገርፉትና እንዲሰቅሉት ለአሕ
ዛብ አሳልፈው ይሰጡታል፤ በሦስተኛውም
ቀን ከሞት ይነሣል።”

19፥19 ዘፀ20፥12-16፤ ዘሌ19፥18፤ ዘዳ5፥16-20፤ማቴ5፥43
19፥21 ማቴ5፥48፤ 6፥20፤ሐሥ2፥45
19፥23 ማቴ13፥22፤ 1ጢሞ6፥9፡10
19፥26 ዘፍ18፥14፤ ኢዮ42፥2፤ ኤር32፥17፤ ሉቃ1፥37፤18፥27፤ ሮሜ4፥21
19፥27 ማቴ4፥19
19፥28 ማቴ20፥21፤ 25፥31፤ሉቃ22፥28-30፤ራእ3፥21፤4፥4፤ 20፥4
19፥29 ማቴ6፥33፤ 25፥46
19፥30 ማቴ20፥16፤ ማር10፥31፤ ሉቃ 13፥30
20፥1 ማቴ13፥24፤ 21፥28፡33
20፥8 ዘሌ19፥13፤ ዘዳ24፥15
20፥11 ዮና4፥1
20፥12 ዮና4፥8፤ ሉቃ12፥55፤ያዕ1፥11
20፥13 ማቴ22፥12 ፤26፥50
20፥15 ዘዳ15፥9፤ ማር7፥22
20፥16 ማቴ19፥30
20፥18 ማቴ8፥20፤ 27፥1፡2፤ሉቃ9፥51
20፥19 ማቴ16፥21፤ ሐሥ2፥23

[θ]29 አንዳንድ ቅጆች እናትን ወይም ሚስትን ይላሉ

## በጌታ መንግሥት ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ የማግኘት ጥያቄ

20፥20-28 ተጓ ምብ - ማር 10፥35-45

20ከዚያም፣ የዘብዴዎስ ልጆች እናት
ከልጆቿ ጋር ወደ ኢየሱስ ቀርባ በጉልበቷ
በፊቱ በመንበርከክ፣ አንድ ነገር እንዲያደ
ርግላት ለመነችው።
21እርሱም፣ "ምን ትፈልጊያለሽ?" አላት።
እርሷም፣ "እነዚህ ሁለት ልጆቼ፣ በመ
ንግሥትህ አንዱ በቀኝህ፣ አንዱ በግራህ
እንዲቀመጡ ፍቀድ" አለችው።
22ኢየሱስም፣ "የምትለምኑትን አታውቁም፤
እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ ትችላላች
ሁን?" አላቸው።
እነርሱም፣ "እንችላለን" አሉት።
23እርሱም፣ "ከጽዋዬ በእርግጥ ትጠጣላ
ችሁ፤ ነገር ግን በቀኜና በግራዬ መቀመጥ
አባቴ ላዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምፈ
ቅደው ነገር አይደለም" አላቸው።
24ዐሥሩም ይህንን በሰሙ ጊዜ፣ ሁለቱን
ወንድማማቾች ተቈጧቸው። 25ኢየሱስም
አንድ ላይ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ "የአሕ
ዛብ ገዢዎች በሕዝባቸው ላይ ጌቶች እን
ደሚሆኑ፣ ባለ ሥልጣኖቻቸውም በኀይል
እንደሚገዟቸው ታውቃላችሁ፤ 26በእናንተ
መካከል ግን እንዲህ መሆን የለበትም።
ከእናንተ ትልቅ መሆን የሚፈልግ አገልጋ
ያችሁ ይሁን፤ 27የበላይ ለመሆን የሚሻም
የእናንተ የበታች ይሁን፤ 28የሰው ልጅ እን
ዲያገለግሉት ሳይሆን፣ ለማገልገልና ነፍ
ሱንም ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ለመስጠት
መጥቶአልና።"

## የሁለት ዐይነ ስውሮች መፈወስ

20፥29-34 ተጓ ምብ - ማር 10፥46-52፤ ሉቃ 18፥35-43

29ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ከኢያሪኮ
ወጥተው ሲሄዱ ብዙ ሕዝብ ተከተለው።
30በዚያም ሁለት ዐይነ ስውሮች በመንገድ
ዳር ተቀምጠው ነበር፤ ኢየሱስም በዚያ
ማለፉን ሲሰሙ፣ "ጌታ ሆይ፤ የዳዊት
ልጅ ማረን!" በማለት ጮኹ። 31ሕዝቡም
በግሣጼ ቃል ዝም እንዲሉ ነገሯቸው፤ እነ
ርሱ ግን አምርረው በመጮኽ፣ "ጌታ
ሆይ፤ የዳዊት ልጅ ማረን!" አሉ።
32ኢየሱስም ቆም ብሎ ጠራቸውና፣
"ምን እንዳደርግላችሁ ትፈልጋላችሁ?"
አላቸው።
33እነርሱም፣ "ዐይኖቻችን እንዲያዩ እን
ፈልጋለን" አሉት።
34ኢየሱስም ራራላቸው፤ ዐይኖቻቸውንም
ዳሰሰ፣ ወዲያው አዩ፤ ተከተሉትም።

20፥20 ማቴ4፥21፤ 8፥2
20፥21 ማቴ19፥28
20፥22 ኢሳ51፥17፡22፤ኤር49፥12፤ ማቴ 26፥39፡42፤ ማር14፥36፤ሉቃ22፥42፤ ዮሐ18፥11
20፥23 ሐሥ12፥2፤ ራእ1፥9
20፥24 ሉቃ22፥24፡25
20፥26 ማር9፥35
20፥28 ዘፀ30፥12፤ ኢሳ42፥1፤44፥22፤ 53፥10፤ማቴ8፥20፤ 26፥28፤ሉቃ12፥37፤ 22፥27፤ዮሐ13፥13-16፤ 2ቆሮ8፥9፤ ፊል 2፥7፤1ጢሞ2፥6፤ ቲቶ 2፥14፤ ዕብ9፥28፤ 1ጴጥ 1፥18፡19
20፥30 ማቴ9፥27

21፥1 ማቴ24፥3፤ 26፥30፤ማር14፥26፤ ሉቃ19፥37፤21፥37፤ 22፥39፤ዮሐ8፥1፤ ሐሥ1፥12
21፥4 ማቴ1፥22
21፥5 ኢሳ62፥11፤ ዘካ9፥9
21፥8 2ነገ9፥13
21፥9 ቍ15፤መዝ 118፥26፤ማቴ9፥27፤ 23፥39፤ሉቃ2፥14
21፥11 ዘዳ18፥15፤ ሉቃ7፥16፡39፤ 24፥19፤ዮሐ1፥21፡25፤ 6፥14፤7፥40
21፥12 ዘፀ30፥13፤ ዘሌ1፥14፤ዘዳ14፥26
21፥13 ኢሳ56፥7፤ ኤር7፥11

## ኢየሱስ በታላቅ ክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ

21፥1-9 ተጓ ምብ - ማር 11፥1-10፤ ሉቃ 19፥29-38
21፥4-9 ተጓ ምብ - ዮሐ 12፥12-15

21 ኢየሩሳሌም መቃረቢያ ደብረ
ዘይት ተራራ ላይ ወደምትገኘው
ቤተ ፋጌ ወደ ተባለችው ስፍራ እንደ
ደረሱ፣ ኢየሱስ ሁለት ደቀ መዛሙርት
ላከ፤ 2እንዲህ አላቸው "ባቅራቢያችሁ
ወዳለው መንደር ሂዱ፤ እንደ ደረሳችሁም
አንዲት አህያ ከነውርንጫዋ ታስራ ታገኛ
ላችሁ፤ ፈትታችሁም ወደ እኔ አምጧ
ቸው። 3ማንም ሰው ለምን እንዲህ ታደር
ጋላችሁ ቢላችሁ፣ 'ጌታ ይፈልጋቸዋል'
በሉት፤ ወዲያውኑ ይሰዳቸዋል።"
4ይህ የሆነውም በነቢዩ እንዲህ በማለት
የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ነው።

5"ለጽዮን ልጅ እንዲህ በሏት፤
'እነሆ፤ ንጉሥሽ ትሑት ሆኖ፣
በአህያዪቱና በግልገሏ፣
በውርንጫዪቱም ላይ ተቀምጦ ወደ
አንቺ ይመጣል።' "

6ደቀ መዛሙርቱም ሄደው ኢየሱስ እን
ዳዘዛቸው አደረጉ። 7አህያዪቱንና ውርን
ጫዋን አምጥተው ልብሶቻቸውን በላያ
ቸው ላይ አኖሩ፤ እርሱም ተቀመጠባቸው።
8ከሕዝቡም አብዛኛው ልብሶቻቸውን፣ በመ
ንገድ ላይ አነጠፉ፤ ሌሎቹም ከዛፎች
ቅርንጫፍ እየዘነጠፉ በመንገዱ ላይ ጣል
ጣል አደረጉ። 9ቀድሞት ከፊቱ የሚሄደ
ውና ከኋላው ይከተለው የነበረው ሕዝ
ብም እንዲህ እያለ ይጮኽ ነበር፣

"ሆሣዕና[ፊ] ለዳዊት ልጅ፤"
"በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤"
"ሆሣዕና በአርያም!"

10ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜም ከተማዋ
በመላ፣ "ይህ ማነው?" በማለት ታወከች።
11አጀቦት የመጣው ሕዝብም፣ "ይህ በገ
ሊላ ከምትገኘው ከናዝሬት የመጣው ነቢዩ
ኢየሱስ ነው" አሉ።

## ኢየሱስ በቤተ መቅደስ ሲነግዱ ያገኛቸውን አስወጣቸው

21፥12-16 ተጓ ምብ - ማር 11፥15-18፤ ሉቃ 19፥45-47

12ከዚያም ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ
ገብቶ በቤተ መቅደስ ውስጥ ይሸጡና ይገዙ
የነበሩትን አባረራቸው፤ የገንዘብ ለዋጮ
ችን ጠረጴዛና የርግብ ሻጮችን መቀመጫ
በመገለባበጥ፣ 13" 'ቤቴ የጸሎት ቤት ይባ

ላል’ ተብሎ ተጽፎአል፤ እናንተ ግን፣ ‘የዘ
ራፊዎች ዋሻ’ አደረጋችሁት” አላቸው።
14በቤተ መቅደሱም ውስጥ ዐይነ ስውሮ
ችና ሽባዎች ወደ እርሱ ቀረቡ፤ እርሱም
ፈወሳቸው። 15ነገር ግን የካህናት አለቆችና
የኦሪት ሕግ መምህራን ያደረጋቸውን
ታምራትና፣ “ሆሣዕና ፤ለዳዊት ልጅ” እያሉ
የሚጮኹትን ሕፃናት ባዩ ጊዜ በቍጣ ተሞሉ።
16እነርሱም፣ “እነዚህ ሕፃናት የሚሉትን
ትሰማለህ” አሉት።
ኢየሱስም፣ “አዎን እሰማለሁ፤ እንዲህ
የሚለውን ከቶ አላነበባችሁምን?”

“ ‘ከልጆችና ጡት ከሚጠቡ፣
ሕፃናት አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ።’ ”

17ትቶአቸው ከከተማው ወጣ፤ ወደ ቢታ
ንያም ሄዶ በዚያው አደረ።

## ፍሬ አልባ የሆነችው በለስ

21፥18-22 ተጓ ምብ - ማር 11፥12-14፡20-24

18ኢየሱስ በማግስቱ ማለዳ ወደ ከተማ
ዪቱ በመመለስ ላይ ሳለ ተራበ፤ 19በመን
ገድ ዳርም አንድ የበለስ ዛፍ አይቶ ወደ
እርሷ ሲሄድ ከቅጠል በስተቀር ምንም ስላ
ላገኘባት፣ “ከእንግዲህ ፍሬ አይኑርብሽ!”
አላት፤ የበለሷ ዛፍ ወዲያውኑ ደረቀች።
20ደቀ መዛሙርቱም የሆነውን አይተው
በመደነቅ፣ “የበለሷ ዛፍ እንዴት ባንዴ
ልትደርቅ ቻለች?” አሉ።
21ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “እውነት
እላችኋለሁ፤ እምነት ቢኖራችሁ ባትጠ
ራጠሩ፣ በበለሷ ዛፍ ላይ የሆነውን ማድ
ረግ ብቻ ሳይሆን፣ ይህንን ተራራ፣ ‘ከዚህ
ተነቅለህ ባሕር ውስጥ ግባ’ ብትሉት እንኳ
ይሆናል፤ 22እምነት ካላችሁ በጸሎት
የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ።”

## በኢየሱስ ሥልጣን ላይ የቀረበ ጥያቄ

21፥23-27 ተጓ ምብ - ማር 11፥27-33፤ ሉቃ 20፥1-8

23ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ በማ
ስተማር ላይ ሳለ፣ የካህናት አለቆችና የሕ
ዝብ ሽማግሌዎች ቀርበው፣ “ይህን ሁሉ
ነገር የምታደርገው በምን ሥልጣን ነው?
ሥልጣኑንስ የሰጠህ ማን ነው?” ብለው ጠየ
ቁት።
24ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
“እኔም አንድ ጥያቄ እጠይቃችኋለሁ፤
መልሱን ብትነግሩኝ፣ እኔም እነዚህን ነገ
ሮች በምን ሥልጣን እንደማደርግ እነግራ
ችኋለሁ፤ 25የዮሐንስ ጥምቀት የመጣው
ከየት ነበር? ከሰማይ ወይስ ከሰዎች?”
እነርሱም እርስ በርስ በመነጋገር እንዲህ
ተባባሉ፤ ‘ከሰማይ ነው?’ ካልን ‘ታዲያ
ለምን አላመናችሁበትም?’ ይለናል፤ 26‘ከሰ
ዎች ነው’ ካልን ደግሞ፣ ‘ሕዝቡ ዮሐንስን
ነቢይ ነው’ ብሎ ስለሚያምን እንፈራለን።”
27ስለዚህ፣ “አናውቅም” ብለው ለኢየሱስ
መለሱለት።
እርሱም፣ “እኔም እነዚህን ነገሮች በምን
ሥልጣን እንደማደርግ አልነግራችሁም”
አላቸው።

## የመታዘዝ ትርጕም

28ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “ምን
ይመስላችኋል? ሁለት ወንዶች ልጆች
ያሉት አንድ ሰው ነበረ፤ ወደ መጀመሪ
ያው ልጁ ሄዶ፣ ‘ልጄ ሆይ፤ ዛሬ ወደ
ወይኑ ቦታ ሄደህ ሥራ’ አለው።
29“ልጁም፣ ‘አልሄድም’ አለው፤ ኋላ
ግን ተጸጽቶ ሄደ።
30“ወደ ሁለተኛው ልጁ ሄዶ እንደዚ
ያው አለው፤ ልጁም ‘እሺ እሄዳለሁ’
አለው፤ ነገር ግን ሳይሄድ ቀረ።
31“ከሁለቱ የአባቱን ፈቃድ የፈጸመው
የትኛው ነው?”
እነርሱም፣ “የመጀመሪያው ልጅ” አሉት።
ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “እውነት
እላችኋለሁ፣ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና አመንዝ
ራዎች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት
በመግባት ይቀድሟችኋል፤ 32መጥምቁ
ዮሐንስ የጽድቅን መንገድ ሊያሳያችሁ
ወደ እናንተ መጣ፤ እናንተ አላመናችሁ
ትም፤ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና አመንዝራዎች
ግን አመኑት። የሆነውን ካያችሁ በኋላ
እንኳ ንስሓ ገብታችሁ አላመናችሁትም።

## የወይን ዕርሻ ገበሬዎች ምሳሌ

21፥33-46 ተጓ ምብ - ማር 12፥1-12፤ ሉቃ 20፥9-19

33“ሌላም ምሳሌ ስሙ፤ አንድ የወይን
ዕርሻ ባለቤት ነበረ፤ በዕርሻው ዙሪያ አጥር
አጠረ፤ ለወይኑ መጭመቂያ ጕድጓድ
ቈፈረ፤ ለጥበቃ የሚሆን ማማ ሠራ፤ ከዚ
ያም ዕርሻውን ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ
ሌላ አገር ሄደ። 34የመከር ወራት ሲደርስ፣
ፍሬውን ለመቀበል አገልጋዮቹን ወደ
ገበሬዎቹ ላካቸው።
35“ገበሬዎቹም አገልጋዮቹን ይዘው አን
ዱን ደበደቡት፤ ሌላውን ገደሉት፤ ሌላ
ውን ደግሞ በድንጋይ ወገሩት። 36እርሱም
ከፊተኞቹ የሚበልጡ ሌሎች አገልጋዮቹን
ላከ፤ገበሬዎቹም ተመሳሳይ ድርጊት ፈጸ
ሙባቸው። 37በመጨረሻም፣ ‘ልጄን ያከ
ብሩታል’ በማለት ልጁን ላከ።

[a]9 በዕብራይስጡ አገላለጽ *አሁን አድን!* ማለት ሲሆን
የምስጋና አገላለጽ ነው፤ ቍ 15 ይመ

21፥14 ማቴ4፥23
21፥15 ቍ9፤ማቴ
9፥27፤ሉቃ19፥39
21፥16 መዝ8፥2
21፥17 ማቴ26፥6፤
ማር11፥1፤ሉቃ24፥50፤ዮ
ሐ11፥1፡18፤12፥1
21፥19 ኢሳ34፥4፤
ኤር8፥13
21፥21 ማቴ17፥20
፤ሉቃ17፥6፤1ቆሮ
13፥2፤ያዕ1፥6
21፥22 ማቴ7፥7
21፥23 ሐሥ4፥7፤
7፥27
21፥26 ማቴ11፥9
21፥28 ቍ33፤
ማቴ20፥1
21፥31ሉቃ7፥29፡50
21፥32 ማቴ3፥1-12
፤ሉቃ3፥12፡13፤7፥29፡
30፡36-50
21፥33 መዝ80፥8፤
ኢሳ5፥1-7፤ማቴ25፥
14፡15
21፥34 ማቴ22፥3
21፥35 2ዜና24፥21
፤ማቴ23፥34፡37፤
ዕብ 11፥36፡37
21፥36 ማቴ22፥4

38"ነገር ግን ገበሬዎቹ ልጁን ባዩት ጊዜ፣
'ይህማ ወራሹ ነው፤ ኑ፣ እንግደለውና ርስ
ቱን እንውረስ' ተባባሉ። 39ይዘውም ከወ
ይኑ ዕርሻ ውጭ አውጥተው ገደሉት።
40"ታዲያ የወይኑ ዕርሻ ባለቤት ሲመጣ
እነዚያን ገበሬዎች ምን የሚያደርጋቸው
ይመስላችኋል?"
41እነርሱም፣ "እነዚያን ክፉዎች በአሰ
ቃቂ ሁኔታ ገድሎ ከወይኑ ዕርሻ ተገቢውን
ፍሬ በወቅቱ ለሚያስረክቡት ለሌሎች ገበ
ሬዎች ያከራያል" አሉት።
42ኢየሱስም እንዲህ ተብሎ በቅዱሳት
መጻሕፍት የተጻፈውን አላነበባችሁምን?
አላቸው፤

" 'ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣
የማእዘን ራስ[T] ሆነ፤
እግዚአብሔር ይህን አድርጎአል፤
ሥራውም ለዐይናችን ድንቅ ነው።'

43"ስለዚህ እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔር
መንግሥት ከእናንተ ተወስዳ ፍሬዋን
ለሚያፈራ ሕዝብ ትሰጣለች፤ 44በዚህ ድን
ጋይ ላይ የሚወድቅ ይሰባበራል፤ ድንጋዩ
የሚወድቅበት ሰው ግን ይደቅቃል።"[U]
45የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ምሳሌ
ዎቹን በሰሙ ጊዜ፣ ስለ እነርሱ የሚናገር
መሆኑን ዐወቁ። 46ነገር ግን ይዘው ሊያ
ስሩት ቢፈልጉም ሕዝቡ ኢየሱስን እንደ
ነቢይ አድርጎ ይመለከት ስለ ነበር ፈሩ።

## በሰርግ ድግስ ላይ የተጠሩ ሰዎች ምሳሌ

22፥2-14 ተጓ ምብ - ሉቃ 14፥16-24

22 ኢየሱስም እንደ ገና እንዲህ
የሚል ምሳሌ ነገራቸው፤ 2"መን
ግሥተ ሰማይ ለልጁ ሰርግ የደገሰ ንጉሥ
ትመስላለች፤ 3ንጉሡም የተጋበዙትን ሰዎች
እንዲጠሩ አገልጋዮቹን ላከ፤ እነርሱ ግን
አንመጣም አሉ።
4"እንደገናም ሌሎች አገልጋዮች ልኮ፣
'የተጋበዙትን፣ እነሆ፣ በሬዎችንና የሠቡ
ከብቶቼን አርጄ ድግሱን አዘጋጅቻለሁ፤
ሁሉም ነገር ዝግጁ ስለሆነ ወደ ሰርጉ ኑ
በሏቸው' አለ።
5"ተጋባዦቹ ግን ጥሪውን ችላ ብለው፣
አንዱ ወደ ዕርሻው ሌላው ወደ ንግዱ
ሄደ፤ 6የቀሩትም አገልጋዮቹን በመያዝ
አጉላልተው ገደሏቸው። 7ንጉሡም በመ
ቈጣት ሠራዊቱን ልኮ ገዳዮቻቸውን አጠፋ፤
ከተማቸውንም አቃጠለ።
8"ከዚያም አገልጋዮቹን እንዲህ አላቸው፤
'የሰርጉ ድግስ ዝግጁ ነው፤ ነገር ግን የተ
ጋበዙት የሚገባቸው ሆነው ስላልተገኙ፣

21፥38 መዝ2፥8፤ ማቴ12፥14፤ዕብ1፥2
21፥41 ማቴ8፥11፤ 12፤ሐሥ13፥46
21፥42 መዝ118፥22፥23፤ሐሥ4፥11
21፥43 ማቴ8፥12
21፥44 ሉቃ2፥34
21፥46 ቊ11፥26
22፥2 ማቴ13፥24
22፥3 ማቴ21፥34
22፥4 ማቴ21፥36
22፥7 ሉቃ19፥27
22፥9 ሕዝ21፥21
22፥10 ማቴ13፥47፥48
22፥12 ማቴ20፥13፤ 26፥50
22፥13 ማቴ8፥12
22፥14 ራእ17፥14
22፥16 ማር3፥6
22፥17 ማቴ17፥25
22፥21 ሮሜ13፥7
22፥22 ማር12፥12
22፥23 ሐሥ4፥1፤ 23፥8፤1ቆሮ15፥12
22፥24 ዘዳ25፥5-6

9ወደ መንገድ መተላለፊያ ወጥታችሁ ያገ
ኛችሁትን ሁሉ ወደ ሰርጉ ድግስ ጥሩ።'
10አገልጋዮቹም ወደ መንገድ ወጥተው ያገ
ኙትን መልካሙንም ክፉውንም ሁሉ ሰብ
ስበው የሰርጉን አዳራሽ በእንግዶች ሞሉት።
11"ንጉሡም የተጋበዙትን እንግዶች ለማ
የት ሲገባ፣ አንድ የሰርግ ልብስ ያልለበሰ
ሰው አየ፤ 12እንዲህም አለው፤ 'ወዳጄ
ሆይ፤ የሰርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት
እዚህ ልትገባ ቻልህ?' ሰውየው ግን የሚ
መልሰው ቃል አልነበረውም።
13"ንጉሡም አገልጋዮቹን፣ 'እጅና እግሩን
አስራችሁ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጥ
ታችሁ ጣሉት፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋ
ጨት ይሆናል' አላቸው፤ 14የተጠሩት ብዙ
ዎች፣ የተመረጡት ግን ጥቂቶች ናቸውና።"

## ግብር ስለ መክፈል

22፥15-22 ተጓ ምብ - ማር 12፥13-17፤ ሉቃ 20፥20-26

15ከዚህ በኋላ ፈሪሳውያን ወጥተው በመ
ሄድ በአፍ እላፊ እንዴት እንደሚያጠም
ዱት ተማከሩ። 16ደቀ መዛሙርታቸውን
ከሄሮድስ ወገኖች ጋር ወደ እርሱ ልከው
እንዲህ አሉት፤ "መምህር ሆይ፤ አንተ
እውነተኛና የእግዚአብሔርንም መንገድ
በእውነት የምታስተምር እንደ ሆንህ፣ ለማ
ንም ሳታዳላ ሁሉን በእኩልነት እንደምት
መለከት እናውቃለን፤ 17ንገረን፤ ምን ይመ
ስልሃል? ለመሆኑ ለቄሣር ግብር መክፈል
ይገባል ወይስ አይገባም?"
18ኢየሱስ ግን ተንኰላቸውን በመረዳት
እንዲህ አላቸው፤ "እናንተ ግብዞች ለምን
በነገር ልታጠምዱኝ ትሻላችሁ? 19ለግብር
የሚከፈለውን ገንዘብ እስቲ አሳዩኝ" እነር
ሱም አንድ ዲናር አመጡለት። 20እር
ሱም፣ "በዚህ ገንዘብ ላይ የሚታየው መልክ
የማንነው? ጽሕፈቱስ የማን ነው?" አላቸው።
21እነርሱም፣ "የቄሣር ነው" አሉት።
እርሱም መልሶ፣ "እንግዲያውስ የቄሣርን
ለቄሣር፣ የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር
ስጡ" አላቸው።
22ይህን ሲሰሙ ተደነቁ፤ ትተውትም ሄዱ።

## ስለ ሙታን ትንሣኤ

22፥23-33 ተጓ ምብ - ማር 12፥18-27፤ ሉቃ 20፥27-40

23የሙታን ትንሣኤ የለም ብለው የሚያ
ምኑ ሰዱቃውያን በዚያኑ ቀን ወደ ኢየ
ሱስ ቀርበው እንዲህ ብለው ጠየቁት፤
24"መምህር ሆይ፤ ሙሴ፣ 'አንድ ሰው
ከሚስቱ ልጅ ሳይወልድ ቢሞት ወንድሙ

[T]42 ወይም *የማእዘን ድንጋይ*
[U]44 አንዳንድ ቅጆች ቍጥር 44 የላቸውም

የሚቹን ሚስት አግብቶ ለእርሱ ዘር ይተ
ካለት’ ብሎአል። [25]በእኛ ዘንድ ሰባት ወን
ድማማቾች ነበሩ፤ የመጀመሪያው ሚስት
አግብቶ ልጅ ሳይወልድ በመሞቱ፣ ሚስቱን
ወንድሙ አገባት፤ [26]ሁለተኛውም ለመጀ
መሪያ ወንድሙ እንዲሁ ልጅ ሳያፈራ
ሞተ፤ በዚህ ሁኔታ ሴትዮዋ ለሰባተኛው
ወንድሙ ደረሰችው። [27]በመጨረሻ ሴት
ዮዋ ራሷ ሞተች። [28]ስለዚህ ሁሉም ስላ
ገቧት በትንሣኤ ቀን ከሰባቱ ለየትኛው
ሚስት ትሆናለች?”

[29]ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰ፤ “ቅዱ
ሳት መጻሕፍትንና የእግዚአሔርን ኀይል
ስለማታውቁ ትስታላችሁ፤ [30]ከትንሣኤ
በኋላ ሰዎች እንደ ሰማይ መላእክት ይሆ
ናሉ እንጂ አያገቡም፤ አይጋቡም። [31]ስለ
ሙታን ትንሣኤ ግን እግዚአብሔር እንዲህ
ብሎ የተናገራችሁን አላነበባችሁምን?
[32]‘እኔ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አም
ላክ፣ የያዕቆብ አምላክ ነኝ።’ እግዚአብሔር
የሕያዋን እንጂ የሙታን አምላክ አይደ
ለም።

[33]ሕዝቡም ይህን በሰሙ ጊዜ በትምህ
ርቱ ተደነቁ።

## ታላቁ ትእዛዝ

22፥34-40 ተጓ ምብ - ማር 12፥28-31

[34]ኢየሱስ ሰዱቃውያንን ዝም እንዳሰኛ
ቸው ሰምተው፣ ፈሪሳውያን በአንድነት
ተሰበሰቡ፤ [35]ከእነርሱም አንድ የኦሪት ሕግ
አዋቂ፣ ሊፈትነው ፈልጎ እንዲህ አለው፤
[36]“መምህር ሆይ፤ ከሕግ ሁሉ የሚበልጠው
የትኛው ትእዛዝ ነው?”

[37]እርሱም እንዲህ አለው፤ “ ‘ጌታ አምላ
ክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣
በፍጹም ሐሳብህ ውደድ፤’ [38]ይህ የመጀመ
ሪያውና ከሁሉ የሚበልጠው ትእዛዝ ነው፤
[39]ሁለተኛውም ያንኑ ይመስላል፤ ይህም፣
‘ጎረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ’ የሚለው
ነው፤ [40]ሕግና ነቢያት በሙሉ በእነዚህ
ሁለት ትእዛዛት ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው።”

## ክርስቶስ የማን ልጅ ነው?

22፥41-46 ተጓ ምብ - ማር 12፥35-37፤ ሉቃ 20፥41-44

[41]ፈሪሳውያን ተሰብስበው ሳሉ ኢየሱስ፣
እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፤ [42]“ስለ ክርስቶስ[ሰ]
ምን ይመስላችኋል? የማንስ ልጅ ነው?”

እነርሱም፣ “የዳዊት ልጅ ነው” አሉት።

[43]እርሱም እንዲህ አላቸው፤ “ታዲያ፣
ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ለምን ‘ጌታዬ’
ይለዋል? ለምንስ፣ እንዲህ ይለዋል?

[44]“ ‘እግዚአብሔር ጌታዬን፤
ጠላቶችህን ከእግርህ በታች እስካንበረክ
ክልህ ድረስ፣
በቀኜ ተቀመጥ።” ’

[45]ስለዚህ ዳዊት፣ ‘ጌታዬ’ ብሎ ከጠራው፣
እንዴት ልጁ ሊሆን ይችላል?” [46]አንድ
ቃል ሊመልስለት የቻለ ወይም ከዚያን
ቀን ጀምሮ ሊጠይቀው የደፈረ ማንም
አልነበረም።

## ኢየሱስ ፈሪሳውያንንና የኦሪት ሕግ መምህራንን ነቀፈ

23፥1-7 ተጓ ምብ - ማር 12፥38፡39፤ ሉቃ 20፥45-46
23፥37-39 ተጓ ምብ - ሉቃ 13፥34፡35

23 ከዚያም ኢየሱስ ለሕዝቡና ለደቀ
መዛሙርቱ እንዲህ ሲል ተናገረ፤
[2]“የኦሪት ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን
በሙሴ ወንበር ላይ ተቀምጠዋል። [3]ስለዚህ
የሚነግሯችሁን ሁሉ አድርጉ፤ ጠብቁትም፤
ነገር ግን እንደሚናገሩት አያደርጉምና ተግባ
ራቸውን አትከተሉ። [4]እንዲሁም ለመሸከም
የማይቻል ከባድ ሸክም አስረው በሰዎች
ትከሻ ላይ ይጭናሉ፤ ራሳቸው ግን በጣታ
ቸው እንኳ አይነኩትም።

[5]“ለመታየት ሲሉ የሚያደርጉትን ሁሉ
በሰው ፊት ያደርጋሉ፤ አሸንክታባቸውን[ሐ]
ያሰፋሉ፤ የቀሚሳቸውን ዘርፍ ያስረዝ
ማሉ። [6]በግብዣ ቦታ የከበሬታ ስፍራ፣
በምኵራብም የመጀመሪያውን መቀመጫ
መያዝ ይወዳሉ። [7]እንዲሁም በገበያ መካ
ከል ሰላምታ መቀበልንና በሰዎች አንደበት
‘መምህር’ ተብለው መጠራትን ይሻሉ።

[8]“እናንተ ግን ‘መምህር’ ተብላችሁ አት
ጠሩ፤ አስተማሪያችሁ አንድ ብቻ ሲሆን፣
እናንተ ሁላችሁም ወንድማማቾች ናች
ሁና። [9]በሰማይ ያለ አንድ አባት ስላላ
ችሁ፣ በምድር ማንንም ‘አባት’ ብላችሁ
አትጥሩ። [10]መምህራችሁ አንዱ ክርስቶስ
ስለሆነ፣ ‘መምህር’ ተብላችሁ አትጠሩ።
[11]ከመካከላችሁ ከሁላችሁ የሚበልጠው
አገልጋያችሁ ይሆናል፤ [12]ራሱን ከፍ ከፍ
የሚያደርግ ይዋረዳል፣ ራሱን የሚያዋርድ
ግን ይከበራል።

[13]“እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህ
ራንና ፈሪሳውያን፤ ሰዎች ወደ መንግሥተ
ሰማይ እንዳይገቡ በሰዎች ላይ በሩን ስለ
ምትዘጉባቸው ወዮላችሁ! እናንተ ራሳችሁ
አትገቡም፤ መግባት የሚፈልጉትንም አታ
ስገቡም። *[14]እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ
መምህራንና ፈሪሳውያን፤ ወዮላችሁ! የመ*

22፥29 ማቴ24፥38
22፥32 ዘፀ3፥6፤
ሐሥ7፥32
22፥33 ማቴ7፥28
22፥34 ሐሥ4፥1
22፥35 ሉቃ7፥30፤
10፥25፤11፥45፤14፥3
22፥37 ዘዳ6፥5
22፥39 ዘሌ19፥18፤
ማቴ5፥43
22፥40 ማቴ7፥12፤
ሉቃ10፥25-28
22፥42 ማቴ9፥27
22፥44 1ነገ5፥3፤
መዝ110፥1፤ሐሥ
2፥34፡35፤1ቆሮ15፥
25፤ዕብ1፥13፤10፥13
22፥46 ማር12፥34፤
ሉቃ20፥40
23፥2 ዕዝ7፥6፡25
23፥4 ሉቃ11፥46፤
ሐሥ15፥10፤ገላ6፥13
23፥5 ዘፀ13፥9፤ዘኍ
15፥38፤ዘዳ6፥8፤22፥
12፤ማቴ6፥1፡2፡5፡16
23፥6 ሉቃ11፥43፤
14፥7፤20፥46
23፥7 ቆላ8፤
ማቴ 26፥25፡49፤
ማር9፥5፤
10፥51፤ዮሐ1፥38፡49፤
3፥2፡26፤20፥16
23፥9 ሚል1፥6፤
ማቴ6፥9፤7፥11
23፥11 ማር9፥35
23፥12 1ሳሙ2፥8፤
መዝ18፥27፤ምሳ3፥34፤
ኢሳ57፥15፤ሕዝ21፥
26፤ሉቃ1፥52፤14፥11
23፥13ቆላ15፡23፡25
፡27፡29፤ሉቃ11፥52

[ሰ]42 ወይም *መሲሑ*
[ሐ]5 ከቅዱሳት መጻሕፍት የተወሰዱ ጥቅሶች የተጻፉበት በግንባርና በክንድ ላይ የሚታሰር ትንሽ ጥቅልል ነው

*በለቶችን ቤት እያራቈታችሁ፣ ለሰው
ይምሰል ረዥም ጸሎት ስለምታደርጉ የከፋ
ፍርድ ትቀበላላችሁ።**
15“እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህ
ራንና ፈሪሳውያን፤ አንድን ሰው ወደ አይ
ሁድ ሃይማኖት ለማስገባት በባሕርና በየ
ብስ ስለምትጓዙ፣ ባመነም ጊዜ ከእናንተ
በእጥፍ የባሰ የገሃነም ልጅ ስለምታደር
ጉት ወዮላችሁ።
16“እናንተ ዕውር መሪዎች፤ ወዮላችሁ!
‘ማንም በቤተ መቅደስ ቢምል ምንም አይ
ደለም፤ ነገር ግን በቤተ መቅደሱ ውስጥ
ባለው ወርቅ ቢምል መሐላው ይደርስ
በታል’ ትላላችሁ። 17እናንተ የታወራችሁ
ተላላዎች! ከወርቁና ወርቁን ከቀደሰው
ቤተ መቅደስ የቱ ይበልጣል? 18እንዲ
ሁም፣ ‘ማንም በመሠዊያው ቢምል
ምንም አይደለም፤ ነገር ግን በላዩ ላይ
ባለው መባ ቢምል መሐላው
ይደርስበታል’ ትላ ላችሁ፤ 19እናንተ ዕ
ውሮች፤ ከመባውና መባውን ከቀደሰው
መሠዊያ የቱ ይበል ጣል? 20ስለዚህ፣ በመ
ሠዊያው የማለ፣ በመሠዊያውና በላዩ ላይ
ባለው ሁሉ ይም ላል። 21እንዲሁም በቤተ
መቅደሱ የማለ፣ በቤተ መቅደሱና
በውስጡ በሚያድረው ይምላል። 22በሰማይ
የማለም በእግዚአ ብሔር ዙፋንና በዙፋኑ
ላይ በተቀመጠው ይምላል።
23“እናንት ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህ
ራንና ፈሪሳውያን፤ ወዮላችሁ! ከአዝሙድ፣
ከእንስላልና ከከሙን ዐሥራት እየሰጣችሁ
በሕጉ ውስጥ ዋነኛ የሆኑትን ማለትም
ፍትሕን፣ ምሕረትንና ታማኝነትን ግን
ንቃችኋልና፤ እነዚያን ሳትተዉ እነዚህን
ማድረግ በተገባችሁ ነበር፤ 24እናንት የታ
ወራችሁ መሪዎች፤ ትንኝን አጥርታችሁ
ትጥላላችሁ፤ ግመልን ግን ትውጣላችሁ።
25“እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህ
ራንና ፈሪሳውያን፤ ወዮላችሁ! የጽዋውንና
የወጭቱን ውጭ ትወለውላላችሁ፤ በውስ
ጣቸው ግን ቅሚያና ስስት ሞልቶባቸዋል።
26አንተ ዕውር ፈሪሳዊ! አስቀድመህ የጽዋ
ውንና የወጭቱን ውስጥ አጽዳ፤ ከዚያም
ውጪው የጸዳ ይሆናል።
27“እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህ
ራንና ፈሪሳውያን፤ ውጫቸው በኖራ ተለ
ስነው የሚያምሩ፣ ውስጣቸው ግን በሙ
ታን ዐፅምና በብዙ ርኵሰት የተሞላ መቃ
ብሮችን ስለምትመስሉ ወዮላችሁ! 28እናን
ተም በውጭ ለሰዎች ጻድቃን ትመስላላ
ችሁ፤ ውስጣችሁ ግን በግብዝነትና በክፋት
የተሞላ ነው።

29“እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህ
ራንና ፈሪሳውያን፤ ወዮላችሁ! የነቢያትን
መቃብር እየገነባችሁ፣ የጻድቃንንም ሐው
ልት እያስጌጣችሁ፣ 30‘በአባቶቻችን ዘመን
ብንኖር ኖሮ፣ የነቢያትን ደም በማፍሰስ
አንተባበራቸውም ነበር’ ትላላችሁና። 31በዚ
ህም የነቢያት ገዳዮች ለነበሩት አባቶቻ
ችሁ ልጆች መሆናችሁን በራሳችሁ ላይ
ትመሰክራላችሁ።32እንግዲህ የአባቶቻችሁን
ጅምር ተግባር ከፍጻሜ አድርሱ!
33“እናንተ እባቦች፤ የእፉኝት ልጆች!
ከገሃነም ፍርድ እንዴት ልታመልጡ ትች
ላላችሁ? 34ስለዚህ ነቢያትን፣ ጠቢባንንና
መምህራንን እልክላችኋለሁ፤ ከነዚህም
አንዳንዶቹን ትገድላላችሁ፤ አንዳንዶቹን
ትሰቅላላችሁ፤ ሌሎቹንም በምኵራቦቻችሁ
ትገርፏቸዋላችሁ፤ ከከተማ ወደ ከተማ
ታሳድዷቸዋላችሁ። 35ስለዚህ፣ ከጻድቁ ከአ
ቤል ደም ጀምሮ በመቅደሱና በመሠዊ
ያው መካከል እስከ ገደላችሁት እስከ በራ
ክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ በም
ድር ላይ ለፈሰሰው ንጹሕ ደም ሁሉ እና
ንተ ተጠያቂዎች ናችሁ። 36እውነት እላ
ችኋለሁ፤ ላለፈው ነገር ሁሉ ይህ ትውልድ
ይጠየቅበታል።
37“አንቺ ነቢያትን የምትገድዪ፣ ወደ
አንቺ የተላኩትንም በድንጋይ የምትወግሪ
ኢየሩሳሌም ሆይ፤ አንቺ ኢየሩሳሌም!
ዶሮ ጫጩቶቿን በክንፎቿ ሥር እንደም
ትሰበስብ፣ ልጆችሽን ለመሰብሰብ ስንት
ጊዜ ፈለግሁ! እናንተ ግን ፈቃደኛ አልሆ
ናችሁም፤ 38እነሆ፤ ቤታችሁ ወና ሆኖ
ይቀ ርላችኋል! 39እላችኋለሁና፤ ‘በጌታ
ስም የሚመጣ የተባረከ ነው’ እስከምትሉ
ድረስ ዳግመኛ አታዩኝም።”

## የዓለም መጨረሻ ምልክቶች

24፥1-51 ተጓ ምብ-ማር13፥1-37፤ ሉቃ21፥5-36

24 ኢየሱስ ከቤተ መቅደስ ወጥቶ
ሲሄድ፣ ደቀ መዛሙርቱ የቤተ
መቅደሱን ሕንጻ ሊያሳዩት ወደ እርሱ
ቀረቡ። 2እርሱ ግን፣ “ይህን ሁሉ ታያ
ላችሁ? እውነት እላችኋለሁ፤ ድንጋይ
በድንጋይ ላይ ተክቦ የምታዩት፣ ሳይፈርስ
እንዲህ እንዳለ የሚቀር አንድ ድንጋይ
እንኳ አይኖርም” አላቸው።
3በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ተቀምጦ
ሳለ፣ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ
እርሱ ቀርበው “እስቲ ንገረን፤ የምትለው
ሁሉ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም

23፥15 ማቴ5፥22፤ ሐሥ2፥11፤6፥5፤ 13፥43
23፥16 ቍ24፤ ኢሳ 9፥16፤ማቴ5፥33-35፤ 15፥14
23፥17 ዘፀ30፥29
23፥19 ዘፀ29፥37
23፥21 1ነገ8፥13፤ መዝ26፥8
23፥22 መዝ11፥4፤ ማቴ5፥34
23፥23 ዘሌ27፥30፤ ሚክ6፥8፤ሉቃ11፥42
23፥24 ቍ16
23፥25 ማር7፥4፤ ሉቃ11፥39
23፥27 ሉቃ11፥44፤ ሐሥ23፥3
23፥29 ሉቃ11፥47 ፥48
23፥31 ማቴ5፥12
23፥32 ሕዝ20፥4፤ 1ተሰ2፥16
23፥33 ማቴ3፥7፤ 5፥22፤12፥34
23፥34 2ዜና36፥15፥16፤ማቴ10፥17፥23፤ሉቃ11፥49
23፥35 ዘፍ4፥8፤ 2ዜና24፥21፤ዘካ1፥1፤ዕብ11፥4
23፥36 ማቴ10፥23፤ 24፥34፤ሉቃ 11፥50፥51
23፥37 2ዜና24፥21 ፤መዝ57፥1፤61፥4፤ ኢሳ31፥5፤ማቴ5፥12
23፥38 1ነገ9፥7-8፤ ኤር22፥5
23፥39 መዝ118፥26 ፤ ማቴ21፥9
24፥2 ሉቃ19፥44
24፥3 ማቴ13፥39 ፤21፥1፤28፥20፤ ሉቃ 17፥30

* አንዳንድ ትርጕሞች ይህን ክፍል አይጨምሩም

መጨረሻ ምልክትስ ምንድን ነው?”
አሉት።
4ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
“ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፤ 5ብዙ
ዎች፣ ‘እኔ ክርስቶስ[መ] ነኝ’ በማለት በስሜ
ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ። 6ስለ
ጦርነትና ጦርነትን የሚያናፍስ ወሬ ትሰ
ማላችሁ፤ እነዚህ ነገሮች የግድ መፈጸም
አለባቸው፤ ሆኖም መጨረሻው ገና ስለ
ሆነ በዚህ እንዳትደናገጡ ተጠንቀቁ።
7ሕዝብ በሕዝብ ላይ፣ መንግሥትም በመ
ንግሥት ላይ ይነሣል፤ በተለያየ ስፍራም
ራብና የመሬት መንቀጥቀጥ ይሆናል፤
8ይህ ሁሉ ግን የምጥ መጀመሪያ ነው።
9“በዚያን ጊዜ ለመከራ አሳልፈው ይሰ
ጧችኋል፣ ይገድሏችኋል፣ በስሜ ምክን
ያት በሕዝብ ሁሉ ዘንድ የተጠላችሁ ትሆ
ናላችሁ። 10በዚያን ጊዜ ብዙዎች ይሰና
ከላሉ፤ እርስ በርስ አሳልፈው ይሰጣጣሉ፤
ይጠላላሉም። 11ብዙዎች ሐሰተኛ ነቢያት
ይነሣሉ፤ ብዙዎችን ያስታሉ። 12ክፋት
ስለሚገን የብዙ ሰዎች ፍቅር ይቀዘቅዛል፤
13እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድ
ናል። 14ለሕዝብ ሁሉ ምስክር እንዲሆን፣
ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ
ይሰበካል፤ ከዚያም መጨረሻው ይመጣል።
15“እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተነገ
ረው፣ ‘የጥፋት ርኩሰት’ በተቀደሰው ስፍራ
ቆሞ ስታዩ፣ አንባቢው ያስተውል። 16በዚ
ያን ጊዜ በይሁዳ የሚገኙ ወደ ተራራዎች
ይሽሹ፤ 17በቤቱ ጣራ ላይ የሚገኝ ማንም
ሰው ዕቃውን ከቤቱ ለማውጣት አይው
ረድ፤ 18በዕርሻ ቦታው የሚገኝ ማንም ሰው
ልብሱን ለመውሰድ አይመለስ። 19‘በእነ
ዚያ ቀናት ለነፍሰ ጡሮችና ለሚያጠቡ
ወዮላቸው! 20እንግዲህ ሽሽታችሁ በክረ
ምት ወይም በሰንበት ቀን እንዳይሆን
ጸልዩ፤ 21በዚያን ጊዜ፣ ዓለም ከተፈጠረ
ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ሆኖ የማያውቅ፣
ከዚያም በኋላ የሚስተካከለው የሌለ፣
ታላቅ መከራ ይሆናል። 22ቀኖቹ ባያጥሩ
ኖሮ ሥጋ ለባሽ ሁሉ ባልተረፈ ነበረ፤ ስለ
ተመረጡት ሲባል ግን እነዚያ ቀኖች ያጥ
ራሉ። 23በዚያን ጊዜ ማንም፣ ‘ይኸውላ
ችሁ ክርስቶስ እዚህ አለ’ ወይም ‘እዚያ
አለ’ ቢላችሁ አትመኑ፤ 24ሐሰተኛ ክርስ
ቶሶችና ሐሰተኛ ነቢያት ይነሣሉና፤ ቢቻል
የተመረጡትን ለማሳት ሲሉ ታላላቅ ምል
ክቶችንና ታምራትን ያደርጋሉ። 25እነሆ፤
አስቀድሜ ነግሬአችኋለሁ።
26“ስለዚህ፣ ‘ያውላችሁ እበረሐው
ውስጥ አለላችሁ’ ቢሏችሁ ወደዚያ
አትውጡ፤ ‘ይኸውላችሁ እልፍኝ ውስጥ
አለላችሁ’ ቢሏ
ችሁ አትመኑ፤ 27መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ
ምዕራብ ድረስ እንደሚያበራ፣ የሰው ልጅ
አመጣጥም እንደዚሁ ይሆናል። 28በድን
ባለበት ስፍራ ሁሉ አሞሮች ይሰበሰባሉ።
29“ወዲያውኑ ከእነዚያ ከመከራው ቀናት
በኋላ፣‘ፀሓይ ትጨልማለች፤
ጨረቃ ብርሃኗን ትከለክላለች፤
ከዋክብት ከሰማይ ይረግፋሉ፤
የሰማይ ኃይላትም ይናጋሉ።’

30“በዚህ ጊዜ የሰው ልጅ ምልክት በሰ
ማይ ላይ ይታያል፤ የምድር ወገኖች ሁሉ
ያለቅሳሉ፤ የሰው ልጅም በሰማይ ደመና
ሆኖ በኀይልና በታላቅ ክብር ሲመጣ ያዩ
ታል፤ 31መላእክቱንም ከታላቅ የመለከት
ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፤ እነርሱም ምረጠ
ቹን ከአራቱም ነፋሳት፣ ከሰማያት ከአ
ንዱ ዳርቻ ወደ ሌላው ዳርቻ ይሰበስባሉ።
32“ከበለስ ዛፍ ይህን ትምህርት ተማሩ፤
ቅርንጫፏ ሲለመልም፣ ቅጠሏ ሲያቈጠ
ቍጥ፣ ያን ጊዜ በጋ እንደተቃረበ ታው
ቃላችሁ። 33እንደዚሁም እነዚህን ሁሉ
ስታዩ፣ እርሱ በደጅ እንደ ቀረበ ታው
ቃላችሁ። 34እውነት እላችኋለሁ፤ ይህ ሁሉ
እስኪፈጸም ድረስ ይህ ትውልድ[ሠ] አያል
ፍም። 35ሰማይና ምድር ያልፋሉ፤ ቃሌ ግን
ፈጽሞ አያልፍም።

## የሚመጣበት ቀንና ሰዓት አለመታወቁ

24፥37-39 ተጓ ምብ - ሉቃ 17፥26፡27
24፥45-51 ተጓ ምብ - ሉቃ 12፥42-46

36ያን ቀንና ሰዓት ግን ከአብ በስተቀር
የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ፣ ወልድም ቢሆን[ረ]
ማንም አያውቅም። 37ልክ በኖኅ ዘመን እንደ
ሆነው የሰው ልጅ መምጣትም እንደዚሁ
ይሆናል፤ 38ከጥፋት ውሃ በፊት ኖኅ ወደ
መርከቡ እስከገባበት ቀን ድረስ ሰዎች ሲበ
ሉና ሲጠጡ፣ ሲያገቡና ሲጋቡ እንደ ነበሩ፣
39እስከዚያ ጊዜ ድረስም ምን እንደሚመጣ
ሳያውቁ ድንገት የጥፋት ውሃ እንዳጥለቀ
ለቃቸው፣ የሰው ልጅ ሲመጣም እንደዚሁ
ይሆናል። 40በዚያን ጊዜ ሁለት ሰዎች በዕርሻ
ላይ ይውላሉ፤ አንዱ ይወሰዳል፤ ሌላው ይቀ
ራል። 41ሁለት ሴቶች በወፍጮ ይፈጫሉ፤
አንዷ ትወሰዳለች፣ ሌላዋ ትቀራለች።
42“እንግዲህ ጌታችሁ የሚመጣበትን ቀን
ስለማታውቁ ነቅታችሁ ጠብቁ። 43ይህን
ልብ በሉ፤ ባለቤት ሌሊት ሌባ በየትኛው
ሰዓት እንደሚመጣ ቢያውቅ ኖሮ፣ በነቃ፣
ቤቱም እንዳይደፈር በተጠባበቀ ነበር።

መ5 ወይም *መሲሕ፤* ቍ 23 ይመ   ሠ34 ወይም *ዘር*
ረ36 አንዳንድ ቅጆች *ወልድም ቢሆን* የሚለው የላቸውም

24፥4 ማር13፥5
24፥5 ቍ11፥23፡24፤1ዮሐ2፥18
24፥7 ኢሳ19፥2፤ ሐሥ11፥28
24፥9 ማቴ10፥17፤ ዮሐ15፥21፤16፥2
24፥11 ማቴ7፥15፤ ማር13፥5
24፥13 ማቴ10፥22
24፥14 ማቴ4፥23፤ ሉቃ2፥1፤4፥5፤ ሐሥ 11፥28፤ 17፥6፤ሮሜ10፥18፤ ራእ3፥10፤ 16፥14
24፥15 ዳን9፥27፤ 11፥31፤12፥11፤ ሐሥ 6፥13
24፥17 1ሳሙ9፥25 ፤ ማቴ10፥27፤ሉቃ 12፥3፤ሐሥ10፥9
24፥19 ሉቃ23፥29
24፥21 ሕዝ5፥9፤ ዳን 12፥1፤ኢል2፥2
24፥22 ቍ24፥31
24፥23 ሉቃ17፥23፤ 21፥8
24፥24 ዘፀ7፥11፡22 ፤2ተሰ2፥9-11፤ ራእ13፥13፤ 16፥14፤19፥20
24፥27 ሉቃ17፥24፡30፤ማቴ8፥20
24፥28 ሉቃ17፥37
24፥29 ኢሳ13፥10፤ 34፥4፤ሕዝ32፥7፤ኢል 2፥10፡31፤ሶፎ1፥15፤ራ እ6፥12፡13፤8፥12
24፥30 ራእ1፥7
24፥31 ኢሳ27፥13፤ ዘካ9፥14፤ማቴ13፥41፤ 1ቆሮ15፥52፤1ተሰ4፥ 16፤ራእ8፥2፤10፥7፤ 11፥15
24፥33 ያዕ5፥9
24፥34 ማቴ16፥28፤ 23፥36
24፥35 ማቴ5፥18
24፥36 ሐሥ1፥7
24፥37 ዘፍ6፥5፤ 7፥6-23
24፥38 ማቴ22፥30
24፥39 ሉቃ17፥30
24፥40 ሉቃ17፥34
24፥41 ሉቃ17፥35
24፥42 ማቴ25፥13፤ ሉቃ12፥40

44የሰው ልጅም ባላሰባችሁት ሰዓት ይመ
ጣልና እናንተም እንደዚሁ ዝግጁ ሁኑ።
45“በተገቢው ጊዜ ምግባቸውን እንዲ
ሰጣቸው ባለቤቱ በቤተ ሰዎቹ ላይ የሾ
መው ታማኝና ብልኀ አገልጋይ እንግዲህ
ማነው? 46ባለቤቱ ተመልሶ በሚመጣበት
ጊዜ የተጣለበትን ዐደራ እየፈጸመ የሚያ
ገኘው ያ አገልጋይ የተባረከ ነው፤ 47እው
ነት እላችኋለሁ፤ በንብረቱ ሁሉ ላይ ይሾ
መዋል። 48ነገር ግን ያ አገልጋይ ክፉ ቢሆ
ንና ለራሱ፣ ‘ጌታዬ ይዘገያል’ በማለት፣
49ተነሥቶ ሌሎች አገልጋይ ባልንጀሮቹን
መምታት ቢጀምር፣ ከሰካራሞችም ጋር ቢበ
ላና ቢጠጣ፣ 50እርሱ ባልጠበቀው ቀንና
ባላሰበው ሰዓት ጌታው መጥቶ፣ 51ይቈራ
ርጠዋል፤ ዕድል ፈንታውንም ከግብዞች
ጋር ያደርግበታል፤ በዚያም ልቅሶና ጥርስ
ማፋጨት ይሆናል።

## የዐሥሩ ልጃገረዶች ምሳሌ

25 “በዚያን ጊዜ መንግሥተ ሰማይ
መብራታቸውን ይዘው ሙሽራ
ውን ሊቀበሉ የወጡ ዐሥር ልጃገረዶችን
ትመስላለች። 2ከእነርሱም አምስቱ ልጃገ
ረዶች ዝንጉዎች፣ አምስቱ ደግሞ አስተ
ዋዮች ነበሩ፤ 3ዝንጉዎቹ መብራት ይዘው
መጠባበቂያ ዘይት አልያዙም ነበር። 4አስ
ተዋዮቹ ግን ከመብራታቸው ጋር መጠባ
በቂያ ዘይት በማሰሮ ይዘው ነበር። 5ሙሽ
ራው በዘገየ ጊዜ፣ ሁሉም እንቅልፍ ተጫ
ጫናቸውና ተኙ።
6“እኩለ ሌሊት ላይ፣ ‘ሙሽራው እየመጣ
ነው፤ ወጥታችሁ ተቀበሉት!’ የሚል ጥሪ ተሰማ።
7“በዚህ ጊዜ ልጃገረዶቹ ሁሉ ተነሥ
ተው መብራቶቻቸውን እየተረኰሱ መዘ
ጋጀት ያዙ። 8ዝንጉዎቹ አስተዋዮቹን፣
‘መብራታችን ሊጠፋብን ስለሆነ፣ ከዘይ
ታችሁ ስጡን’ አሏቸው።
9“አስተዋዮቹ ልጃገረዶች ግን መልሰው፣
‘ያለን ዘይት ለእኛም ለእናንተም ላይበቃ
ስለሚችል፣ ሄዳችሁ ከሻጮች ለራሳችሁ
ግዙ’ አሏቸው።
10“ዘይት ሊገዙ እንደ ሄዱ፣ ሙሽራው መጣ፤
ተዘጋጅተው የነበሩት ልጃገረዶችም ወደ
ሰርጉ ግብዣ አብረውት ገቡ፤ በሩም ተዘጋ።
11“ዘግየት ብለው ሌሎቹ ልጃገረዶች
መጥተው፣ ‘ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ በሩን
ክፈትልን’ አሉ።
12“እርሱ ግን መልሶ፣ ‘እውነት እላችኋ
ለሁ፣ አላውቃችሁም’ አላቸው።
13“እንግዲህ ቀኑን ወይም ሰዓቱን ስለ
ማ ታውቁ ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ።

24፥43 ሉቃ12፥39
24፥44 1ተሰ5፥6
24፥45 ማቴ25፥21 ፡23
24፥46 ራእ16፥15
24፥47 ማቴ25፥21 ፡23
24፥49 ሉቃ21፥34
24፥51 ማቴ 8፥12
25፥1 ማቴ13፥24፤ ሉቃ12፥35-38፤ሐሥ 20፥8፤ራእ4፥5፤19፥7፤ 21፥2
25፥2 ማቴ24፥45
25፥5 1ተሰ5፥6
25፥8 ሉቃ12፥35
25፥10 ራእ19፥9
25፥12 ቈ41፤ ማቴ7፥23
25፥13 ማቴ24፥42 ፡44፤ማር13፥35፤ሉቃ 12፥40
25፥14 ማቴ21፥33 ፤ሉቃ19፥12
25፥15 ማቴ18፥24፡25
25፥19 ማቴ18፥23
25፥21 ቈ23፤ማቴ 24፥45፡47፤ሉቃ 16፥10
25፥23 ቈ21
25፥29 ማቴ13፥12፤ ማር4፥25፤ሉቃ8፥18 ፤19፥26

## የሰነፉ አገልጋይ ምሳሌ

25፥14-30 ማመ - ሉቃ 19፥12-27

14“የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋዮ
ቹን ጠርቶ ያለውን ንብረት በዐደራ በመ
ስጠት ወደ ሌላ አገር ሊሄድ የተነሣ
አንድ ሰውን ትመስላለች፤ 15ለእያንዳንዱ
እንደ ችሎታው በመደልደል ለአንዱ አም
ስት ታላንት፣[a] ለሌላው ሁለት፣ ለሌላው
ደግሞ አንድ ታላንት ሰጥቶ ጕዞውን
ቀጠለ። 16አምስት ታላንት የተቀበለው
ሰውዬ ወዲያው በገንዘቡ ንግድ ጀምሮ
አምስት ታላንት አተረፈ፤ 17እንዲሁም
ሁለት ታላንት የተቀበለው ሁለት አተ
ረፈ፤ 18አንድ ታላንት የተቀበለው ግን
መሬት ቈፍሮ የጌታውን ገንዘብ ደበቀ።
19“የአገልጋዮቹም ጌታ ከብዙ ጊዜ በኋላ
ከሄደበት ተመልሶ የሰጣቸውን ገንዘብ ተሳ
ሰበ። 20አምስት ታላንት የተቀበለውም፣
ሌላ አምስት ተጨማሪ ታላንት ይዞ
በመቅረብ፣ ‘ጌታ ሆይ! አምስት ታላንት
ዐደራ ሰጥተኸኝ ነበር፤ ይኸውልህ አምስት
ተጨማሪ ታላንት አትርፌአለሁ’ አለው።
21“ጌታውም፣ ‘ደግ አድርገሃል፤ አንተ
መልካም ታማኝ አገልጋይ፤ በትንሽ ነገር
ላይ ታማኝ ስለሆንህ በብዙ ነገር ላይ እሾ
ምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ’ አለው።
22“እንዲሁም ሁለት ታላንት
የተቀበለው አገልጋይ ቀርቦ፣ ‘ጌታ ሆይ፤
ሁለት ታላ ንት ሰጥተኸኝ ነበር፤ ይኸው
ሁለት ተጨማሪ ታላንት አትርፌአለሁ’
አለው።
23“ጌታውም፣ ‘ደግ አድርገሃል፤ አንተ
መልካም ታማኝ አገልጋይ፤ በትንሽ ነገር
ላይ ታማኝ ስለ ሆንህ በብዙ ነገር ላይ
እሾምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ’ አለው።
24“አንድ ታላንት የተቀበለው አገልጋይ
ቀርቦ፣ ‘ጌታ ሆይ፤ አንተ ካልዘራህበት
የምታጭድ፣ ካልበተንህበትም የምትሰበ
ስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን ዐውቃለሁ፤
25ስለዚህ ፈራሁህ፤ ሄጄም መሬት ቈፍሬ
ታላንትህን ጕድጓድ ውስጥ ደበቅሁት፤
ገንዘብህ ይኸውልህ’ አለው።
26“ጌታውም መልሶ፣ ‘አንተ ክፉ፣ ሰነፍ
አገልጋይ፤ ካልዘራሁበት የማጭድ፣ ካል
በተንሁበትም የምሰበስብ መሆኔን ታውቅ
ኖሮአል? 27ታዲያ፣ በምመለስበት ጊዜ
ገንዘቤን ከነወለዱ እንዳገኘው ለለዋጮች
መስጠት ይገባህ ነበር።
28“ ‘በሉ እንግዲህ ታላንቱን ወስዳችሁ
ዐሥር ታላንት ላለው ስጡ፤ 29ላለው ይጨ
መርለታል፤ የተትረፈረፈም ይኖረዋል፤ ከሌ

[a]15 አንድ ታላንት በሺህ የሚቈጠር ብር የሚያህል ነው

ለው ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል።
30 ይህን የማይረባ አገልጋይ ልቅሶና ጥርስ
ማፋጨት ወዳለበት በውጭ ወዳለው ጨለማ
አውጥታችሁ ጣሉት’ አለ።

### የመጨረሻው ፍርድ

31 “የሰው ልጅ ከመላእክቱ ሁሉ ጋር
በክ ብሩ ሲመጣ፣ በክብሩ ዙፋን ላይ
ይቀመ ጣል፤ 32 ሕዝቦች ሁሉ በፊቱ
ይሰበሰባሉ፤ እርሱም፣ እረኛ በጎችን
ከፍየሎች እንደ ሚለይ፣ ሕዝቡን አንዱን
ከሌላው ይለ ያል፤ 33 በጎቹን በቀኙ፣
ፍየሎቹን ግን በግራው ያቆማቸዋል።
34 “በዚያን ጊዜ ንጉሡ በቀኙ በኩል ያሉ
ትን እንዲህ ይላቸዋል፤ ‘እናንት አባቴ
የባረካችሁ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ
የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ፤ 35 ምክ
ንያቱም ተርቤ አብልታችሁኛል፤ ተጠ
ምቼ አጠጥታችሁኛል፤ እንግዳ ሆኜ ተቀ
ብላችሁኛል፤ 36 ታርዤ አልብሳችሁኛል፤
ታምሜ አስታምማችሁኛል፤ ታስሬ ጠይቃ
ችሁኛል።’
37 “ጻድቃንም መልሰው እንዲህ ይሉ
ታል፤ ‘ጌታ ሆይ፤ ተርበህ አይተን መቼ
አበላንህ? ወይም ተጠምተህ አይተን መቼ
አጠጣንህ? 38 እንግዳ ሆነህ አይተን መቼ
ተቀበልንህ? ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ
አለበስንህ? 39 እንዲሁም ታመህ ወይም
ታስረህ አይተን መቼ ጠየቅንህ?’
40 “ንጉሡም መልሶ፣ ‘እውነት እላችኋ
ለሁ፣ ከእነዚህ አነስተኛ ከሆኑት ወንድ
ሞቼ ለአንዱ ያደረጋችሁት፣ ለእኔ እን
ዳደረጋችሁት ነው’ ይላቸዋል።
41 “ከዚያም በግራው በኩል ላሉት ደግሞ
እንዲህ ይላቸዋል፤ ‘እናንተ የተረገማችሁ፤
ለዲያብሎስና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀው
የዘላለም እሳት ከእኔ ተለይታችሁ ሂዱ፤
42 ምክንያቱም ተርቤ አላበላችሁኝም፤ ተጠ
ምቼ አላጠጣችሁኝም፤ 43 እንግዳ ሆኜ አል
ተቀበላችሁኝም፤ ታርዤ አላለበሳችሁኝም፤
ታምሜና ታስሬ አልጠየቃችሁኝም።’
44 “እነርሱም መልሰው፣ ‘ጌታ ሆይ፤
ተርበህ ወይም ተጠምተህ፣ እንግዳ ሆነህ
ወይም ታርዘህ፣ ታመህ ወይም ታስረህ ዐይ
ተን መቼ አልደረስንልህም’ ይሉታል።
45 “በዚያን ጊዜ እርሱም መልሶ፣ ‘እው
ነት እላችኋለሁ፣ ከእነዚህ አነስተኛ ከሆ
ኑት ወንድሞቼ ለአንዱ አለማድረጋችሁ፣
ለእኔ እንዳላደረጋችሁት ነው’ ይላቸዋል።
46 “እነዚህም ወደ ዘላለም ፍርድ፣ ጻድ
ቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።”

25፥30 ማቴ8፥12
25፥31 ማቴ19፥28፤ ሉቃ17፥30
25፥32 ሚል3፥18፤ ሕዝ34፥17፡20
25፥34 ማቴ3፥2፤ 5፥3፡10፡9፤19፥14፤ ሐሥ20፥32፤1ቆሮ 15፥50፤ገላ5፥21፤ ዕብ 4፥3፤ 9፥26፤ያዕ2፥5፤ ራእ13፥8፤17፥8
25፥35 ኢዮ31፥32፤ዕብ13፥2
25፥36 ኢሳ58፥7፤ ሕዝ18፥7፤2ጢሞ 1፥16፤ያዕ1፥27፤ 2፥15፡16
25፥40 ማቴ10፥40 ፡42፤ዕብ13፥2
25፥41 ኢሳ66፥24፤ ማቴ3፥12፤5፥22፤ 7፥23፤ማር9፥43፡48፤ ሉቃ3፥17፤ 2ጴጥ2፥4፤ይሁ7
25፥45 ምሳ14፥31፤ 17፥5
25፥46 ዳን12፥2፤ ማቴ19፥29፤ዮሐ3፥15 ፡16፡36፤5፥29፤17፥2፡3 ፤ሐሥ24፥15፤ሮሜ 2፥7፤ገላ6፥8፤1ዮሐ 1፥2፤5፥11፡13፡20
26፥1 ማቴ7፥28
26፥2 ዮሐ11፥55
26፥3 ቀኍ57፤መዝ 2፥2፤ሉቃ3፥2፤ዮሐ 11፥47-53፤18፥13፡ 14፡24፡28፤ሐሥ4፥6
26፥4 ማቴ12፥14
26፥5 ማቴ27፥24
26፥6 ማቴ21፥17
26፥11 ዘዳ15፥11
26፥12 ዮሐ19፥40
26፥14 ቀኍ25፡47፤ ማቴ10፥4
26፥15 ዘፀ21፥32፤ ዘካ11፥12

### አይሁድ በኢየሱስ ላይ መዶለታቸው

26፥2-5 ተጓ ምብ - ማር 14፥1፡2፤ ሉቃ 22፥1፡2

26 ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች ተናግሮ
ከጨረሰ በኋላ፣ ደቀ መዛሙርቱን፣
2 “ከሁለት ቀን በኋላ ፋሲካ እንደሚሆን
ታውቃላችሁ፤ የሰው ልጅም ሊሰቀል
አልፎ ይሰጣል” አላቸው።
3 ከዚህ በኋላ የካህናት አለቆችና የሕዝብ
ሽማግሌዎች ቀያፋ በተባለ ሊቀ ካህን
ግቢ ውስጥ ተሰብስበው፤ 4 በረቀቀ መንገድ
ኢየሱስን ለማስያዝና ለማስገደል ተማከሩ።
5 ነገር ግን፣ “በሕዝቡ መካከል ረብሻ እንዳ
ይነሣ በበዓል ቀን አይሁን” በማለት ተስ
ማሙ።

### ኢየሱስን ሽቶ የቀባችው ሴት

26፥6-13 ተጓ ምብ - ማር 14፥3-9
26፥6-13 ማመ - ሉቃ 7፥37፡38፤ ዮሐ 12፥1-8

6 ኢየሱስ በቢታንያ በለምጻሙ በስምዖን
ቤት ሳለ፣ 7 አንዲት ሴት ዋጋው እጅግ
ውድ የሆነ አንድ ብልቃጥ የአልባስጥሮስ
ሽቶ ይዛ ወደ እርሱ ቀረበች፤ በማእድ ላይ
ተቀምጦ ሳለም በራሱ ላይ አፈሰሰችው።
8 ደቀ መዛሙርቱ ይህንን በተመለከቱ
ጊዜ ተቈጥተው እንዲህ አሉ፤ “ይህ ሁሉ
ብክነት ለምንድነው? 9 ሽቶው በብዙ ዋጋ
ተሸጦ ገንዘቡን ለድኾች መስጠት ሲቻል!”
10 ኢየሱስ ይህን ዐውቆ እንዲህ አላቸው፤
“ይህችን ሴት ለምን ታስቸግሯታላችሁ?
መልካም ነገር አድርጋልኛለች፤ 11 ድኾች
ምንጊዜም ከእናንተ ጋር ናቸው፤ እኔ ግን
ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልሆንም። 12 ሽቶ
ውን በሰውነቴ ላይ በማፍሰሷ፣ እኔን ለቀ
ብር ለማዘጋጀት ነው፤ 13 እውነት እላችኋ
ለሁ፤ ይህ ወንጌል በሚሰበክበት በዓለም
ዙሪያ ሁሉ፣ በየትኛውም ስፍራ እርሷ
ያደረገችው በመታሰቢያነት ይነገርላታል።”

### ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት ተስማማ

26፥14-16 ተጓ ምብ - ማር 14፥10፡11፤ ሉቃ 22፥3-6

14 ከዚህ በኋላ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ
የነበረውና የአስቆሮቱ ይሁዳ የተባለው
ወደ ካህናት አለቆች ሄዶ፣ 15 “እርሱን አሳ
ልፌ ብሰጣችሁ እናንተስ ምን ትሰጡኛላ
ችሁ?” አላቸው። እነርሱም ሠላሳ ጥሬ
ብር ቈጥረው ሰጡት። 16 ከዚያን ጊዜ ጀምሮ
ይሁዳ፣ ኢየሱስን አሳልፎ የሚሰጥበትን
አመቺ ጊዜ ይፈልግ ነበር።

## የጌታ ራት

26፥17-19 ተጓ ምብ - ማር 14፥12-16፤ ሉቃ 27፥7-13
26፥20-24 ተጓ ምብ - ማር 14፥17-21
26፥26-29 ተጓ ምብ - ማር 14፥22-25፤ ሉቃ22፥17-20፤
1ቆሮ 11፥23-25

17በቂጣ በዓል የመጀመሪያ ቀን ደቀ
መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ ቀርበው፣ “ፋሲ
ካን እንድትበላ የት እንድናዘጋጅልህ ትፈ
ልጋለህ?” አሉት።
18እርሱም፣ “ወደ ከተማ ሄዳችሁ እገሌ
የተባለውን ሰው፣‘መምህር ጊዜዬ ተቃርቦ
አልና ከደቀ መዛሙርቴ ጋር ፋሲካን በቤ
ትህ አከብራለሁ ብሏል’ በሉት” አላቸው።
19ደቀ መዛሙርቱም ኢየሱስ ባዘዛቸው መሠ
ረት የፋሲካን ራት አዘጋጁ።
20በመሸም ጊዜ ኢየሱስ ከዐሥራ ሁለቱ
ጋር በማእድ ተቀመጠ፤ 21በመብላት ላይ
ሳሉም፣ “እውነት እላችኋለሁ፣ ከእናንተ
አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል” አላቸው።
22እነርሱም እጅግ አዝነው፣ ተራ በተራ፣
“ጌታ ሆይ፤ እኔ እሆን ይሆን?” አሉት።
23እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
“አሳ ልፎ የሚሰጠኝ ከወጭቱ ውስጥ
አብሮኝ ያጠቀሰው ነው፤ 24የሰው ልጅ ስለ
እርሱ እንደ ተጻፈው ይሄዳል፤ ነገር ግን
የሰውን ልጅ አሳልፎ ለሚሰጠው ሰው
ወዮለት፤ ለዚያ ሰው ሳይወለድ ቢቀር
ይሻለው ነበር።”
25አሳልፎ የሚሰጠው ይሁዳም፣ “መም
ህር ሆይ፣ እኔ እሆንን?” አለው።
እርሱም፣ “አንተ አልህ”[ሽ] አለው።
26እየበሉ ሳሉ፣ ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ
ባረከ፤ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ በመ
ስጠት፣ “እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ሥጋዬ
ነው” አላቸው።
27ከዚያም ጽዋውን አንሥቶ አመሰገነ፤
ለደቀ መዛሙርቱም በመስጠት እንዲህ
አላቸው፤ “ሁላችሁም ከዚህ ጠጡ፤ 28ስለ
ብዙዎች የኀጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአ
ዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው። 29እላችኋለሁ፤
በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር በአዲስ
መልክ እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ፣
ከእንግዲህ ከዚህ የወይን ፍሬ አልጠ
ጣም።”
30መዝሙር ከዘመሩ በኋላ ወደ ደብረ
ዘይት ተራራ ወጡ።

## የጴጥሮስ ክህደት አስቀድሞ መነገሩ

26፥31-35 ተጓ ምብ - ማር 14፥27-31፤ ሉቃ 23፥31-34

31ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤
“ሁላችሁም በዚህች ሌሊት በእኔ ተሰናክ
ላችሁ ትሄዳላችሁ፤ እንዲህ ተብሎ ተጽፎ
አልና፤

“ ‘እረኛውን እመታለሁ፤
የመንጋውም በጎች ይበተናሉ።’

32ነገር ግን ከተነሣሁ በኋላ ቀድሜአችሁ
ወደ ገሊላ እሄዳለሁ።”
33ጴጥሮስም መልሶ፣ “ሌሎች በሙሉ
ባንተ ምክንያት ቢሰናከሉ እንኳ እኔ በፍ
ጹም አልሰናከልም!” አለው።
34ኢየሱስም፣ “እውነት እልሃለሁ፤ በዛ
ሬዋ ሌሊት ዶሮ ከመጮኹ በፊት ሦስት
ጊዜ ትክደኛለህ” አለው።
35ጴጥሮስ ግን “ከአንተ ጋር መሞት ቢያ
ስፈልግ እንኳ ከቶ አልክድህም!” አለው።
ሌሎቹም ደቀ መዛሙርት በሙሉ እንደዚሁ
አሉ።

## የኢየሱስ ጸሎት በጌቴሴማኒ

26፥36-46 ተጓ ምብ - ማር 14፥32-42፤ ሉቃ 22፥40-46

36ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር ጌቴሴማኒ ወደሚባል ስፍራ ሄደ፤ እነ
ርሱንም፣ “ወደዚያ ሄጄ በምጸልይበት ጊዜ
እናንተ እዚህ ተቀመጡ” አላቸው። 37ከእ
ርሱም ጋር ጴጥሮስንና ሁለቱን የዘብዴ
ዎስ ልጆች ይዞ በመሄድ ይተክዝና ይጨ
ነቅ ጀመር፤ 38ከዚያም፣ “ነፍሴ እስከ ሞት
ድረስ እጅግ አዝናለች፤ ከእኔ ጋር በመ
ትጋት እዚሁ ቈዩ” አላቸው።
39ጥቂት ዕልፍ ብሎ በግንባሩ በመደ
ፋት፣ “አባቴ ሆይ፤ ቢቻል ይህ ጽዋ ከእኔ
ይለፍ፤ ነገር ግን እኔ እንደምፈልገው ሳይ
ሆን አንተ እንደምትፈልገው ይሁን” ብሎ
ጸለየ።
40ከዚያም ተመልሶ ወደ ደቀ መዛሙርቱ
ሲመጣ፣ ተኝተው አገኛቸው፤ ጴጥሮስንም
እንዲህ አለው፤ “እናንት ሰዎች፤ ከእኔ ጋር
ለአንድ ሰዓት እንኳ መትጋት አቃታችሁን?
41ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጐና ጸልዩ፤ መን
ፈስ ዝግጁ ነው፤ ሥጋ ግን ደካማ ነው።”
42እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ ሄዶ፣ “አባት
ሆይ፤ ይህ ሳልጠጣው የማያልፍ ጽዋ
ከሆነ፣ ፈቃድህ ይፈጸም” ብሎ ጸለየ።
43እንደገናም በመጣ ጊዜ ዐይኖቻቸው
በእንቅልፍ ከብደው ስለ ነበር ተኝተው
አገኛቸው።
44ትቶአቸውም እንደገና በመሄድ ለሦስ
ተኛ ጊዜ ቀደም ብሎ የጸለየውን ጸሎት
ደገመ።
45ከዚያም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ተመ
ልሶ እንዲህ አላቸው፤ “አሁንም ዐርፋችሁ
ተኝታችኋል? እነሆ፣ ሰዓቱ ቀርቦአል፤
የሰው ልጅ በኀጢአተኞች እጅ ዐልፎ ይሰ

26፥17 ዘፀ12፥18-20፤ ዘዳ16፥5-8
26፥18 ማር14፥35፡41፤ዮሐ7፥6፡8፡30፤ ዮሐ8፥20፤12፥23፤ 13፥1፤17፥1
26፥21 ሉቃ22፥21-23፤ዮሐ13፥21
26፥23 መዝ41፥9፤ ዮሐ13፥18
26፥24 ቍ31፡54፡56፤ኢሳ53፤ዳን9፥26፤ ማር9፥12፤ ሉቃ24፥25-27፡46፤ ሐሥ17፥2፡3፤ 26፥22፡23፤ 1ጴጥ1፥ 10፡11
26፥25 ማቴ10፥4፤ 23፥7
26፥26 ማቴ14፥19
26፥27 1ቆሮ10፥16
26፥28 ዘፀ24፥6-8፤ ዘካ9፥11፤ሚል2፥5፤ ማቴ20፥28፤ማር1፥4፤ ዕብ9፥20፤10፥29፤ 13፥20
26፥29 ሐሥ10፥41
26፥30 ማቴ21፥1
26፥31 ዘካ13፥7፤ ማቴ11፥6፤ዮሐ16፥32
26፥32 ማቴ28፥7፡ 10፡16
26፥34 ቍ75፤ ዮሐ 13፥38
26፥35 ዮሐ13፥37
26፥37 ማቴ4፥21
26፥38 ቍ40፡41፤ ዮሐ12፥27
26፥39 ቍ42፤ መዝ 40፥6-8፤ ኢሳ50፥5፤ ማቴ6፥10፤20፥22፤ ዮሐ4፥34፤5፥30፤ 6፥38
26፥40 ቍ38
26፥41 ማቴ6፥13
26፥42 ቍ39
26፥45 ቍ18

[ሽ]25 *“ወይም አንተ ራስህ ተናገርህ”*

ጣል፤ 46ተነሡ! እንሂድ፤ አሳልፎ የሚሰጠ
ኝም እየመጣ ነው።"

## የኢየሱስ መያዝ

26፥47-56 ተጓ ምብ - ማር 14፥43-50፤ ሉቃ 27፥47-53

47በመናገር ላይ እያለ፣ ከዐሥራ ሁለቱ
አንዱ ይሁዳ መጣ፤ ከካህናት አለቆችና
ከሕዝቡ ሽማግሌዎች ዘንድ የተላኩ ሰይ
ፍና ዱላ የያዙ ብዙ ሰዎችም አብረውት
ነበሩ። 48ይሁዳም፣ "እኔ የምስመው እርሱ
ነው፤ ያዙት" ብሎ ምልክት ሰጥቶአቸው
ስለነበር፣ 49በቀጥታ ወደ ኢየሱስ ሄዶ፣
"መምህር ሆይ፤ ሰላም ለአንተ ይሁን" በማ
ለት ሳመው።
50ኢየሱስም፣ "ወዳጄ ሆይ፤ የመጣህበ
ትን ፈጽም"* አለው።
በዚህ ጊዜ ሰዎቹ ቀርበው ኢየሱስን
ያዙት፤ አሰሩትም። 51ከኢየሱስ ጋር ከነ
በሩት አንዱ፣ ሰይፉን መዝዞ በመሰንዘር
የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ ጆሮውን ቈረጠው።
52ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "በል ሰይፍ
ህን ወደ ሰገባው መልስ፤ ሰይፍን የሚመ
ዝዙ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉ። 53ካስፈለገ
አባቴን ብጠይቀው ከዐሥራ ሁለት ክፍለ
ሰራዊት የሚበልጡ መላእክት የማይሰድ
ልኝ ይመስልሃል? 54ይህ ቢሆን ደግሞ
ቅዱሳት መጻሕፍት ይሆናል ያሉት ነገር
እንዴት ይፈጸማል?"
55በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ሕዝቡን እንዲህ
አላቸው፤ "ወንበዴ እንደሚይዝ ሰው ሰይ
ፍና ዱላ ይዛችሁ ልትይዙኝ መጣችሁ? በየዕ
ለቱ በቤተ መቅደስ ተቀምጬ ሳስተምር
አልያዛችሁኝም ነበር፤ 56ነገር ግን ይህ
ሁሉ የሆነው ነቢያት በቅዱሳት መጻሕ
ፍት የተናገሩት ይፈጸም ዘንድ ነው።"
በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ጥለ
ውት ሸሹ።

## ኢየሱስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት

26፥57-68 ተጓ ምብ - ማር 14፥53-65፤ ዮሐ 18፥12፥13፥19-24

57በዚህ ጊዜ ኢየሱስን የያዙት ሰዎች፣
የኦሪት የሕግ መምህራንና የሕዝብ ሽማ
ግሌዎች ተሰብስበው ወደ ነበሩበት፣ ወደ
ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ ወሰዱት። 58ነገር
ግን ጴጥሮስ ከርቀት ሆኖ እስከ ሊቀ ካህ
ናቱ ቅጥር ግቢ ይከተለው ነበር፤ ወደ
ውስጥ ገብቶም የሁኔታውን መጨረሻ ለማ
የት ከጠባቂዎች ጋር ተቀመጠ።
59በዚህ ጊዜ የካህናት አለቆችና የአይ
ሁድ ሸንጎ በሙሉ ኢየሱስን ለማስገደል
የሐሰት ማስረጃ ይፈልጉ ነበር፤ 60ብዙ የሐ
ሰት ምስክሮች ቢቀርቡም በቂ ማስረጃ

26፥47 ማቴ10፥4
26፥49 ቀኍ25፤
ማቴ23፥7
26፥50
ማቴ20፥13፤22፥12
26፥51 ሉቃ22፥36፤
ዮሐ18፥10
26፥52 ዘፍ9፥6፤ዘፀ
21፥12፤ራእ13፥10
26፥53 2ነገ6፥17፤
ዳን7፥10፤ማቴ4፥11
26፥54 ቀኍ24፤
ማቴ1፥22
26፥55 ማር12፥35፤
ሉቃ21፤37፤
ዮሐ7፥14፡28፥18፥20
26፥56 ቀኍ24፤
ማቴ1፥22
26፥57 ቀኍ3

26፥58 ቀኍ69፤
ማር14፥66፤15፥16፤
ሉቃ11፥21፤22፥55፤
ዮሐ7፥32፡45፡46፤
18፥15
26፥59 ማቴ5፥22
26፥60 ዘዳ19፥15፤
መዝ27፥12፤35፥11፤ሐ
ሥ6፥13
26፥61 ዮሐ2፥19
26፥63 ዘሌ5፥1፤
ማቴ4፥3፤16፥16፤
ማር14፥61፤
ሉቃ22፥67
26፥64
ማቴ27፥11፤
ማር16፥19፤ሉቃ
22፥70፤ራእ1፥7
26፥65 ማር14፥63
26፥66 ዘሌ24፥16፤
ዮሐ 19፥7
26፥67 ማቴ16፥21
26፥68
ሉቃ22፥63-65

አላገኙም፤ በኋላ ግን ሁለት ሰዎች ቀር
በው፣ 61"ይህ ሰው፣ 'የእግዚአብሔርን
ቤተ መቅደስ አፍርሼ፣ በሦስት ቀን ውስጥ
መልሼ ልሠራው እችላለሁ' ብሎአል" በማ
ለት ተናገሩ።
62በዚህ ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ተነሥቶ በመ
ቆም፣"እነዚህ ሰዎች ለሚመሰክሩብህ ሁሉ
ምንም መልስ አትሰጥምን?" አለው። 63ኢየ
ሱስ ግን ዝም አለ።
ሊቀ ካህናቱም፣ "በሕያው እግዚአብሔር
ስም አምልሃለሁ፤ አንተ ክርስቶስ⁰ የእግዚ
አብሔር ልጅ እንደ ሆንህ ንገረን" አለው።
64ኢየሱስም፣ "አንተው ራስህ ብለኸዋል፤
ነገር ግን ለሁላችሁም ልንገራችሁ፤ ወደ
ፊት የሰው ልጅ በኀያሉ ቀኝ ተቀምጦ
በሰማይ ደመና ሲመጣ ታዩታላችሁ" አለው።
65በዚህ ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ልብሱን ቀዶ፣
"በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል ተና
ግሮአል፤ ከዚህ ሌላ ምን ምስክርነት ያስ
ፈልገናል? በእግዚአብሔር ላይ የስድብ
ቃል መናገሩን እናንተው ራሳችሁ ሰም
ታችኋል፤ 66ምን ይመስላችኋል?" አላቸው።
እነርሱም፣"ሞት ይገባዋል!" ብለው መለሱ።
67በዚህ ጊዜ ፊቱ ላይ እየተፉ በጡጫ
መቱት፤ ሌሎቹም በጥፊ እየመቱት፣
68"ክርስቶስ ሆይ፤ ማነው የመታህ? እስቲ
ትንቢት ንገረን!" አሉት።

## ጴጥሮስ ኢየሱስን ካደ

26፥69-75 ተጓ ምብ - ማር 14፥66-72፤
ሉቃ 22፥55-62፤ ዮሐ 18፥16-18፥25-27

69ከዚህ በኋላ ጴጥሮስ በሊቀ ካህናቱ
ግቢ ውስጥ ተቀምጦ ሳለ አንዲት የቤት
ሠራተኛ ወደ እርሱ ቀርባ፣ "አንተም
ከገሊላው ኢየሱስ ጋር ነበርህ" አለችው።
70እርሱ ግን፣ "ምን እንደምትናገሪ አላ
ውቅም" በማለት በሁላቸውም ፊት ካደ።
71ከግቢው መውጫ ወደ ሆነው በር ሲያ
መራ ሌላዋ ሠራተኛ ተመልክታው፣ በዚያ
ለነበሩት ሰዎች፣ "ይህ ሰው ከናዝሬቱ ኢየ
ሱስ ጋር ነበር" አለች።
72እርሱም በመሐላ ቃል፣ "ሰውየውን
አላውቀውም!" ሲል ዳግመኛ ካደ።
73ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ በዚያ ቆመው የነ
በሩት ሰዎች ቀርበው ጴጥሮስን፣ "አነጋገ
ርህ ስለሚያጋልጥህ፣ በእርግጥ አንተም
ከእነርሱ አንዱ ነህ!" አሉት።
74እርሱም እየማለና እየተገዘተ፣ "እኔ
ሰውየውን አላውቀውም!" አላቸው።

*50 ወይም "ወዳጄ ሆይ፤ ለምን መጣህ?"
⁰63 ወይም "መሲሑ"፤ ቍ68 ይመ

ወዲያውም ዶሮ ጮኸ። 75በዚህ ጊዜ
ጴጥሮስ፣ “ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክ
ደኛለህ” ብሎ ኢየሱስ የተናገረው ቃል
ትዝ አለው፤ ጴጥሮስም ወደ ውጭ ወጥቶ
መራራ ልቅሶ አለቀሰ።

## ይሁዳ ራሱን ሰቀለ

27 ጠዋት በማለዳ ላይ፣ የካህናት
አለቆችና የሕዝብ ሽማግሌዎች ሁሉ
ኢየሱስ ስለሚገደልበት ሁኔታ ተመካከሩ፤
2ካሰሩትም በኋላ ወስደው ለገዥው ለጲላ
ጦስ አሳልፈው ሰጡት።
3አሳልፎ የሰጠው ይሁዳም ኢየሱስ እንደ
ተፈረደበት ባየ ጊዜ ተጸጸተ፤ የወሰደውን
ሠላሳ ጥሬ ብር ለካህናት አለቆችና ለሕ
ዝቡ ሽማግሌዎች መልሶ በመስጠት፣ 4“ንጹሕ
ሰው አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ” አለ።
እነርሱም፣ “ታዲያ እኛ ምን አገባን፤ የራ
ስህ ጉዳይ ነው!” አሉት።
5ስለዚህ ይሁዳ ብሩን በቤተ መቅደስ
ውስጥ ወርውሮ ወጣ፤ ሄዶም ራሱን ሰቅሎ
ሞተ።
6የካህናት አለቆች ብሩን አንሥተው፣
“የደም ዋጋ ስለሆነ ወደ መባ ልንጨም
ረው አይፈቀድም” አሉ፤ 7ተመካከረውም
ለእንግዶች የመቃብር ስፍራ እንዲሆን
በገንዘቡ የሸክላ ሠሪውን ቦታ ገዙበት።
8ስለዚህም ያ ቦታ እስከ ዛሬ ድረስ “የደም
መሬት” ተብሎ ይጠራል። 9በዚህም በነቢዩ
ኤርምያስ እንዲህ ተብሎ የተነገረው ተፈ
ጸመ፤ “ለእርሱ ዋጋ ይሆን ዘንድ የእስራ
ኤል ልጆች የገመቱትን ሠላሳ ጥሬ ብር
ተቀበሉ፤ 10እግዚአብሔርም ባዘዘኝ መሠ
ረት ለሸክላ ሠሪው ቦታ ከፈሉ።”

## ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት

27፥11-26 ተጓ ምብ - ማር 15፥2-15፤
ሉቃ 23፥2፡3፡18-25፤ ዮሐ 18፥29-19፥16

11በዚህ ጊዜ ኢየሱስ አገረ ገዥው ፊት
ቀረበ፤ አገረ ገዥውም፣ “አንተ የአይሁድ
ንጉሥ ነህን?” በማለት ጠየቀው።
ኢየሱስም፣ “አንተው እንዳልኸው ነው”
ሲል መለሰለት።
12የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች ሲከ
ሱት ግን ምንም መልስ አልሰጠም። 13በዚህ
ጊዜ ጲላጦስ፣ “ስንት ነገር አቅርበው እን
ደሚከሱህ አትሰማምን?” አለው። 14እርሱ
ግን አገረ ገዥው እስኪገረም ድረስ ለቀረ
በበት ክስ አንዲት ቃል እንኳ አልመለ
ሰም።
15አገረ ገዥው ሕዝቡ በበዓሉ እንዲፈታ
ላቸው የሚጠይቁትን አንድ እስረኛ የመ
ፍታት ልማድ ነበረው። 16በዚያን ጊዜ በዐ
መፅ የታወቀ በርባን የሚባል እስረኛ
ነበር። 17ሕዝቡ እንደተሰበሰቡ ጲላጦስ፣
“ከበርባንና ክርስቶስ ከሚባለው ከኢየሱስ፣
ማንን እንድፈታላችሁ ትፈልጋላችሁ?”
አላቸው፤ 18ጲላጦስም በቅናት አሳልፈው
እንደ ሰጡት ያውቅ ነበርና።
19በፍርድ ወንበር ላይ ተቀምጦ ሳለ
ሚስቱ፣ “በእርሱ ምክንያት ዛሬ በሕልም
ብዙ ስለተሠቃየሁ፣ በዚያ ንጹሕ ሰው ላይ
ምንም ነገር እንዳታደርግ” የሚል መልእ
ክት ላከችበት።
20ነገር ግን የካህናት አለቆችና ሽማግሌ
ዎች በርባን እንዲፈታላቸው ኢየሱስ ግን
እንዲገደል ይለምኑ ዘንድ ሕዝቡን ያግባቡ
ነበር።
21አገረ ገዥውም፣ “ከሁለቱ ማንን እንድ
ፈታላችሁ ትፈልጋላችሁ?” በማለት ጠየቀ።
እነርሱም፤ “በርባንን!” በማለት መለሱ።
22ጲላጦስም፣ “ታዲያ ክርስቶስ የተባለ
ውን ኢየሱስንስ ምን ላድርገው?” አላቸው።
ሁሉም፣ “ይሰቀል!” አሉ።
23ጲላጦስም፣ “ለምን? ምን ክፉ ነገር
አድርጎአል?” በማለት ጠየቃቸው።
እነርሱ ግን አብዝተው እየጮኹ፣ “ይሰ
ቀል!” አሉ።
24ጲላጦስ ሁኔታው ሽብር ከማስነሣት
በስተቀር ምንም ፋይዳ የሌለው መሆኑን
ተመልክቶ፣ “እኔ ከዚህ ሰው ደም ንጹሕ
ነኝ፤ ከእንግዲህ ኀላፊነቱ የራሳችሁ ነው”
በማለት ውሃ አስመጥቶ በሕዝቡ ፊት እጆ
ቹን ታጠበ።
25ሕዝቡም በሙሉ፣ “ደሙ በእኛና በል
ጆቻችን ላይ ይሁን!” ብለው መለሱ።
26በዚህ ጊዜ በርባንን ፈታላቸው፤ ኢየሱ
ስን ግን ካስገረፈው በኋላ እንዲሰቀል አሳ
ልፎ ሰጠው።

## ኢየሱስ በሮማውያን ወታደሮች እጅ

27፥27-31 ተጓ ምብ - ማር 15፥16-20

27ከዚያም የአገረ ገዥው ወታደሮች ኢ
የ ሱስን ወደ ገዥው ግቢ ወሰዱት፤ ሰራ
ዊቱ ንም ሁሉ በዙሪያው አሰባሰቡ።
28ልብሱን ገፈው ቀይ ልብስ አጠለቁለት፤
29እሾኽ ጉንጉነው አክሊል በመሥራት ራ
ሱ ላይ ደፉበት፤ የሸምበቆ በትር በቀኝ
እጁ በማ ስያዝ በፊቱ ተንበርክከው፣
“የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፤ ሰላም ለአንተ
ይሁን” በማ ለት አሾፉበት፤ 30ተፉበትም፤
የሸምበቆ በትሩን ከእጁ ወስደው ራሱ ላይ
በሸምበ ቆው ደግመው ደጋግመው መቱ
ት፤ 31ካሾ ፉበት በኋላም ቀዩን ልብስ
ገፈው የራሱን መጐናጸፊያ አለበሱት፤ ሊ

26፥75 ቍ34፤ ዮሐ 13፥38
27፥1 ማቴ12፥14፤ ማር15፥1፤ ሉቃ22፥66
27፥2 ማቴ20፥19፤ ማር15፥1፤ሉቃ13፥1፤ ሐሥ3፥13፤1ጢሞ 6፥13
27፥3 ማቴ10፥4፤ 26፥14፡15
27፥4 ቍ24
27፥5 ሉቃ1፥9፡21፤ ሐሥ1፥18
27፥8 ሐሥ1፥19
27፥9 ማቴ1፥22
27፥10 ኤር32፥6-9፤ ዘካ11፥12፡13
27፥11 ማቴ2፥2
27፥12 ማር14፥61
27፥13 ማቴ26፥62
27፥14 ማር14፥61
27፥15 ዮሐ18፥39
27፥17 ቍ22፤ ማቴ1፥16
27፥19 ቍ24፤ዘፍ 20፥6፤ዘኍ12፥6፤1ነገ3፥5፤ኢዮ33፥14-16፤ ማቴ1፥20፤2፥12፡13፡19፡22፤ዮሐ19፥13
27፥20 ሐሥ3፥14
27፥22 ማቴ1፥16
27፥24 ቍ4፤ዘዳ 21፤6-8፤መዝ26፥6፤ ማቴ26፥5
27፥25 ኢሱ2፥19፤ ሐሥ5፥28
27፥26 ኢሳ53፥5፤ ዮሐ19፥1
27፥27 ዮሐ18፥28፡ 33፤19፥9
27፥28 ዮሐ19፥2
27፥29 ኢሳ53፥3፤ ዮሐ19፥2፡3
27፥30 ማቴ16፥21
27፥31 ኢሳ53፥7

ሰቅሉትም ይዘ ውት ሄዱ።

## የኢየሱስ መስቀል

27፥33-44 ተጓ ምብ - ማር 15፥22-32፤ ሉቃ 23፥33-43፤
ዮሐ 19፥17-24

32ይዘውትም ሲሄዱ ስምዖን ተብሎ
የሚጠራ የቀሬና ሰው አገኙ፤ መስቀሉንም
እንዲሸከም አስገደዱት።
33ትርጒሙ፣ "የራስ ቅል" ከሆነው ጎል
ጎታ ከተባለው ቦታ ሲደርሱ፣ 34ከሐሞት
ጋር የተቀላቀለ የወይን ጠጅ እንዲጠጣ
ሰጡት፤ እርሱ ግን ቀምሶ ሊጠጣው አል
ፈቀደም። 35ከሰቀሉትም በኋላ ዕጣ ጥለው
ልብሱን ተካፈሉ፤† 36በዚያም ተቀምጠው
ይጠብቁት ነበር። ከራስጌውም፣ 37"ይህ
የአይሁድ ንጉሥ ኢየሱስ ነው" የሚል የክስ
ጽሑፍ አኖሩ። 38ሁለት ወንበዴዎች አንዱ
በቀኙ፣ አንዱ በግራው አብረውት ተሰቅ
ለው ነበር። 39መንገድ ዐላፊዎችም በጎ
ይል እየተሳደቡና ራሳቸውን እየነቀነቁ፣
40"ቤተ መቅደስን አፍርሰህ በሦስት ቀን
ውስጥ የምትሠራው፤ እስቲ ራስህን አድን!
የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ በል ከመስ
ቀል ውረድ!" ይሉት ነበር።
41የካህናት አለቆችም ከኦሪት ሕግ መም
ህራንና ከሽማግሌዎች ጋር ሆነው እያሾ
ፉበት እንዲህ ይሉ ነበር፤ 42"ሌሎችን
አዳነ፤ ራሱን ግን ማዳን አይችልም! የእስ
ራኤል ንጉሥ ከሆነ አሁን ከመስቀል ይው
ረድ፤ እኛም እናምንበታለን። 43በእግዚ
አብሔር ታምኖአል፤ 'የእግዚአብሔር ልጅ
ነኝ' ይል ስለነበር እስቲ ከወደደው አሁን
ያድነው!" 44ከእርሱ ጋር የተሰቀሉት ወን
በዴዎችም እንደዚሁ የስድብ ቃል ያወር
ዱበት ነበር።

## የኢየሱስ መሞት

27፥45-56 ተጓ ምብ - ማር 15፥33-41፤ ሉቃ 23፥44-49

45ከቀኑ ስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ
ሰዓት ድረስ በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ
ሆነ። 46በዘጠኝ ሰዓት ገደማ፣ ኢየሱስ
ድምፁን ከፍ አድርጎ፣ "ኤሎሄ! ኤሎሄ! ላማ
ሰበቅታኒ?" እያለ ጮኸ፤ ትርጒሙም
"አምላኬ፤ አምላኬ፤ ለምን ተውኸኝ?" ማለት
ነው። 47በዚያ ቆመው ከነበሩት አንዳን
ዶቹ ጩኸቱን ሲሰሙ፣ "ኤልያስን እየ
ተጣራ ነው!" አሉ።
48ወዲያውም ከእነርሱ አንዱ ሮጦ ሰፍ
ነግ በመውሰድ የኮመጠጠ ወይን ጠጅ
ውስጥ ነከረው፤ ሰፍነጉንም በሸምበቆ ዘንግ
ጫፍ ላይ በማድረግ እንዲጠጣው ለኢየሱስ
አቀረበለት። 49የቀሩት ግን፣ "ተዉት፤
እስቲ ኤልያስ መጥቶ ሲያድነው እናያ
ለን!" አሉ።
50ኢየሱስ እንደ ገና ከፍ ባለ ድምፅ
ጮኸ፤ መንፈሱንም አሳልፎ ሰጠ።
51በዚያን ጊዜ የቤተ መቅደስ መጋረጃ
ከላይ እስከ ታች ለሁለት ተቀደደ፤ ምድር
ተናወጠች፤ ዐለቶችም ተሰነጣጠቁ፤ 52መቃ
ብሮች ተከፈቱ፤ አንቀላፍተው የነበሩትም
ብዙዎች ቅዱሳን ተነሡ፤ 53ከመቃብርም
በመውጣት ከኢየሱስ ትንሣኤ በኋላ ወደ
ቅድስት ከተማ ገብተው ለብዙዎች ታዩ።
54የመቶ አለቃውና አብረውት ኢየሱስን
ይጠብቁት የነበሩት የመሬት መናወጡንና
የሆነውን ነገር ሁሉ ባዩ ጊዜ እጅግ ፈሩ፤
ከዚያም፣ "በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ
ነበር!" አሉ። 55ከገሊላ የመጡና ኢየሱስን
በሚያስፈልገው ነገር ለማገልገል የተከተ
ሉት ብዙ ሴቶች ሁኔታውን ከርቀት እየ
ተመለከቱ በአካባቢው ነበሩ። 56ከእነርሱም
መካከል ማርያም መግደላዊት፣ ማርያም
የያዕቆብና የዮሴፍ እናት እንዲሁም የዘብ
ዴዎስ ልጆች እናት ነበሩ።

## የኢየሱስ መቀበር

27፥57-61 ተጓ ምብ - ማር15፥42-47፤
ሉቃ23፥50-56፤ ዮሐ19፥38-42

57ምሽት ላይ ዮሴፍ የሚባል ሀብታም
ሰው ከአርማትያስ መጣ፤ እርሱ ራሱም
የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ነበረ። 58ጲላጦስ
ፊት ቀርቦ የኢየሱስን በድን ለመነው፤ ጲላ
ጦስም እንዲሰጠው አዘዘ። 59ዮሴፍም በድ
ኑን ወስዶ በንጹሕ የበፍታ ጨርቅ ከፈ
ነው፤ 60ለራሱ ከዐለት አስፈልፍሎ ባዘጋ
ጀው መቃብር ውስጥ አኖረው፤ ከዚያም
ትልቅ ድንጋይ አንከባሎ የመቃብሩን በር
ዘግቶ ሄደ። 61በዚህ ጊዜ ማርያም መግደ
ላዊትና ሌላዋ ማርያም ከመቃብሩ ትይዩ
ተቀምጠው ነበር።

## የመቃብሩ ጥበቃ

62በማግሥቱ፣ ከሰንበት ዝግጅት በኋላ
ባለው ቀን፣ የካህናት አለቆችና ፈሪሳው
ያን ጲላጦስ ፊት ቀርበው እንዲህ አሉት፤
63"ክቡር ሆይ፤ ያ አታላይ በሕይወት
ሳለ፣ 'ከሦስት ቀን በኋላ እነሣለሁ' ያለው
ትዝ ብሎናል፤ 64ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ
አስከሬኑን ሰርቀው ለሕዝቡ፣ 'ከሙታን
ተነሥቶአል' ብለው እንዳያስወሩ መቃብሩ
እስከ ሦስተኛው ቀን ድረስ እንዲጠበቅ

27፥32 ማር15፥21፤
ሉቃ23፥26፤ሐሥ2፥
10፤6፥9፤11፥20፤
13፥1፤ዕብ13፥12
27፥33 ዮሐ19፥17
27፥34 ቍ48፤
መዝ 69፥21
27፥35 መዝ22፥18
27፥36 ቍ54
27፥38 ኢሳ53፥12
27፥39 መዝ22፥7፤
109፥25፤ ሰቆ2፥15
27፥40 ቍ42፤
ማቴ4፥3፡6፤ዮሐ2፥19
27፥42 ዮሐ1፥49፤
3፥15፤12፥13
27፥43 መዝ22፥8
27፥45 አሞ8፥9
27፥46 መዝ22፥1
27፥48 ቍ34፤
መዝ 69፥21
27፥50 ዮሐ19፥30
27፥51 ቍ54፤
ዘፀ26፥31-33፤
ዕብ9፥3፡8 ፤10፥19፡20
27፥53 ማቴ4፥5
27፥54 ቍ36፥ማቴ
4፥3፤17፥5
27፥55 ሉቃ8፥2፡3
27፥56 ማር15፥47፤
ሉቃ24፥10፤
ዮሐ 19፥25
27፥60 ማቴ27፥66
፤28፥2፤ማር16፥4፤
ሐሥ13፥29
27፥63 ማቴ16፥21
27፥64 ማቴ28፥13

†35 ጥቂት የጥንት ቅጆች "በነቢዩ *ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፤ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ* የተባለው ይፈጸም ዘንድ" የሚል አላቸው

ትእዛዝ ስጥልን፤ አለዚያ የኋለኛው ስሕተት
ከፊተኛው የባሰ ይሆናል!”
65ጲላጦስም፣ “ጠባቂዎች አሏችሁ፤ ሄዳ
ችሁ በምታውቁት መንገድ አስጠብቁ”
አላቸው። 66እነርሱም ሄደው መቃብሩን በማኅ
ተም አሽገው ጠባቂ አቆሙበት።

## የኢየሱስ ከሙታን መነሣት

28፥1-8 ተጓ ምብ - ማር 16፥1-8፤ ሉቃ 24፥1-10

28 ሰንበት ካለፈ በኋላ፣ በሳምንቱ
መጀመሪያ ቀን ጎህ ሲቀድ፣ ማር
ያም መግደላዊትና ሌላዋ ማርያም መቃ
ብሩን ሊያዩ ሄዱ።
2በድንገት ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤
የጌታም መልአክ ከሰማይ ወርዶ ወደ
መቃብሩ በመሄድ ድንጋዩን አንከባሎ
በላዩ ላይ ተቀመጠበት፤ 3መልኩ እንደ
መብረቅ ብሩህ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ
ነበር። 4ጠባቂዎቹ መልአኩን ከመፍራት
የተነሣ ተንቀጠቀጡ፤ እንደ በድንም
ሆኑ።
5መልአኩም ሴቶቹን እንዲህ አላቸው፤
“አትፍሩ፤ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንደም
ትፈልጉ አውቃለሁና፤ 6እርሱ በዚህ የለም፤
እንደ ተናገረው ተነሥቶአል፤ ኑና ተኝቶ
በት የነበረውን ቦታ እዩ። 7አሁንም ፈጥና
ችሁ ሂዱና ለደቀ መዛሙርቱ፣ ‘ከሙታን
ተነሥቶአል፤ ቀድሞአችሁ ወደ ገሊላ ይሄ
ዳል፤ በዚያ ታዩታላችሁ’ ብላችሁ ንገሯ
ቸው። እንግዲህ ነግሬአችኋለሁ!”
8ሴቶቹም በፍርሀትና በደስታ ተሞ
ልተው ለደቀ መዛሙርቱ ለመንገር በፍጥ
ነት እየሮጡ የመቃብሩን ስፍራ ትተው
ሄዱ። 9ወዲያው ኢየሱስ አገኛቸውና፣
“ሰላም ለእናንተ ይሁን!” አላቸው። እነር
ሱም ወደ ኢየሱስ ቀርበው እግሩን ይዘው
ሰገዱለት። 10ኢየሱስም፣ “አትፍሩ፤ ሂዱና
ወደ ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ንገሯ
ቸው፤ በዚያ ያዩኛል” አላቸው።

## የጠባቂዎች ምስክርነት

11ሴቶቹ በመንገድ ላይ ሳሉ፣ ከጠባቂ
ዎቹ ጥቂቶቹ ወደ ከተማ በመሄድ የሆ
ነውን ሁሉ ለካህናት አለቆች አወሩላ
ቸው። 12የካህናት አለቆችም ከሽማግ
ሌዎች ጋር ተሰብስበው ተማከሩ፤ ለወታ
ደሮቹ በቂ ገንዘብ በመስጠት 13እንዲህ
አሏቸው፤ “‘ተኝተን ሳለን ደቀ መዛሙርቱ
በሌሊት መጥተው ሰረቁት’ በሉ፤ 14ይህ
ወሬ በገዥው ዘንድ ቢሰማ እንኳ፣ እኛ
እናስረዳዋለን፤ ምንም ክፉ ነገር እንዳ
ይደርስባችሁ አናደርጋለን።” 15ወታደሮቹም
ገንዘቡን ተቀብለው እንደ ታዘዙት አደ
ረጉ። ይህም ታሪክ እስከ ዛሬ ድረስ በአ
ይሁዶች ዘንድ በሰፊው እንደተሰራጨ
ነው።

## ታላቁ ተልእኮ

16ከዚያም ዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙ
ርት በገሊላ ወዳለው ኢየሱስ ወዳመለከ
ታቸው ተራራ ሄዱ። 17ባዩትም ጊዜ ሰገ
ዱለት፤ ጥቂቶች ግን ተጠራጠሩ። 18ኢ
የሱ ስም ደቀ መዛሙርቱ ወዳሉበት
ቀርቦ እን ዲህ አላቸው፤ “ሥልጣን ሁሉ
በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል፤ 19ስለዚህ
ሂዱና ሕዝ ቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድና
በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው
ደቀ መዛ ሙርቴ አድርጓቸው፤
20ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ
አስተምሯቸው፤ እኔም እስከ
ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ
ጋር ነኝ።”

27፥65 ቍ66፤ ማቴ28፥11
27፥66 ቍ60፤ ዳን 6፥17፤ ማቴ28፥2፡11
28፥1 ማቴ27፥56፤ ሉቃ8፥2
28፥2 ማቴ27፥51፡ 60፤ዮሐ20፥12፤ ሐሥ 5፥19
28፥3 ዳን7፥9፤ 10፥6፤ ማር9፥3፤ዮሐ20፥12
28፥5 ቍ10፤ ማቴ14፥27
28፥6 ማቴ16፥21
28፥7 ቍ10፡16፤ ማቴ26፥32
28፥9 ዮሐ20፥14-18
28፥10 ማቴ12፥50 ፤25፥40፤ ማር3፥34፤ ዮሐ20፥17፤ሮሜ 8፥29፤ዕብ2፥11-13፡ 17
28፥11 ማቴ27፥65 ፡66
28፥13 ማቴ27፥64
28፥14 ማቴ27፥2
28፥16 ቍ7፡10፤ ማቴ26፥32
28፥18 ዳን7፥13፡14 ፤ሉቃ10፥22፤ዮሐ3፥35፤13፥13፤17፥2፤1ቆሮ 15፥27፤ኤፌ1፥20-22 ፤ፊል2፥9፡10
28፥19 ኢሳ49፥6፤ ማር16፥15፡16፤ሉቃ 24፥47፤ሐሥ1፥8፤ 2፥38፤8፥16፤14፥21፤ሮሜ6፥3፡4፤ገላ3፥27፤ ቈላ2፥12
28፥20 ዘዳ31፥6፤ 1ነገ8፥57፤ሐጌ1፥13፤ ማቴ13፥39፤18፥20፤24፥3፤ዮሐ14፥26፤ ሐሥ2፥42፤18፥10

# የማርቆስ ወንጌል

## የመጥምቁ ዮሐንስ ስብከት

1፥2-8 ተጓ ምብ ማቴ 3፥1-11፤ ሉቃ 3፥2-16

1 የእግዚአብሔር ልጅ[ሀ]፣ የኢየሱስ ክርስቶስ
ወንጌል መጀመሪያ።

2በነቢዩ በኢሳይያስ፣ እንዲህ ተብሎ ተጽፎ
አል፤ "እነሆ መንገድህን የሚያዘጋጅ መልእ
ክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ፤ 3'የጌታን
መንገድ አዘጋጁ፤ ጥርጊያውንም አስተካክሉ
እያለ በበረሓ የሚጮኽ ድምፅ' ።

4ስለዚህ መጥምቁ ዮሐንስ በበረሓ እያጠ
መቀና ለኀጢአት ስርየት የንስሓ ጥምቀት
እየሰበከ መጣ። 5የይሁዳ አገር በሞላ፣ የኢ
የሩሳሌም ሰዎች በጠቅላላ ወደ እርሱ
በመ ሄድ ኀጢአታቸውን እየተናዘዙ
በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጠመቁ።
6ዮሐንስ የግመል
ጠጕር ይለብስ፣ በወገቡ ጠፍር ይታጠቅ፣
አንበጣና የበረሓ ማር ይበላ ነበር። 7ስብከ
ቱም፣ "እኔ ጐንበስ ብዬ የጫማውን
ማሰሪያ መፍታት ከማይገባኝ፣ ከእኔ
የሚበልጥ ከእኔ በኋላ ይመጣል፤ 8እኔ በውሃ
አጠምቃችኋለሁ፤ እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ
ያጠምቃችኋል" የሚል ነበር።

## የኢየሱስ መጠመቅና መፈተን

1፥9-11 ተጓ ምብ - ማቴ3፥13-17፤ ሉቃ3፥21-22
1፥12፡13 ተጓ ምብ -ማቴ 4፥1-11፤ ሉቃ 4፥1-13

9በዚህ ጊዜ ኢየሱስ የገሊላ ከተማ ከሆነችው
ከናዝሬት መጥቶ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ
እጅ ተጠመቀ። 10ከውሃው በሚወጣበትም
ጊዜ፣ ሰማያት ተከፍተው፣ መንፈስ ቅዱስ
እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ሲወርድ አየ፤
11"የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፤ በአንተ ደስ
ይለኛል" የሚል ድምፅ ከሰማይ ተሰማ።
12ወዲያውም መንፈስ ቅዱስ ወደ በረሓ
መራው፤ 13በሰይጣንም እየተፈተነ አርባ ቀን
በበረሓ ቈየ። ከአራዊትም ጋር ነበር፤ መላእ
ክትም አገለገሉት።

## የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት መመረጥ

1፥16-20 ተጓ ምብ - ማቴ 4፥18-22፤ ሉቃ 5፥2-11፤ዮሐ1፥35-42

14ዮሐንስ እስር ቤት ከገባ በኋላ፣ ኢየሱስ
የእግዚአብሔርን ወንጌል እየሰበከ ወደ ገሊላ
ሄደ፣ 15"ጊዜው ደርሶአል፤ የእግዚአብሔር
መንግ ሥት ቀርባለች፤ ንስሓ ግቡ፤
በወንጌልም እመኑ!" እያለ ይሰብክ ነበር።
16ኢየሱስ በገሊላ ባሕር አጠገብ ሲያልፍ፣
ስምዖንና ወንድሙ እንድርያስ ዓሣ አጥ
ማጆች ስለ ነበሩ፣ መረብ ወደ ባሕር ሲጥሉ
አያቸው። 17ኢየሱስም፣ "ተከተሉኝ፤ ሰው
አጥማጆች አደርጋችኋለሁ" አላቸው። 18እነር
ሱም ወዲያውኑ መረባቸውን ትተው ተከተ
ሉት።
19ትንሽ እልፍ እንዳለ፣ የዘብዴዎስ
ልጅ ያዕቆብና ወንድሙ ዮሐንስ በጀልባ
ሆነው መረባቸውን ሲያበጃጁ አያቸውና፣
20ወዲያውኑ ጠራቸው። እነርሱም
አባታቸውን ከቅ ጥር ሠራተኞቹ ጋር
በጀልባው ላይ ትተው ተከትለውት ሄዱ።

## ኢየሱስ ርኩስ መንፈስ አስወጣ

1፥21-28 ተጓ ምብ - ሉቃ4፥31-37

21ከዚያም ወደ ቅፍርናሆም ሄዱ፤ ኢየ
ሱስም ወዲያው በሰንበት ቀን ወደ ምኵራብ
ገብቶ ማስተማር ጀመረ። 22እንደ ጸሐፍት
ሳይሆን፣ እንደ ባለ ሥልጣን በማስተማሩ
ሕዝቡ በትምህርቱ ተገረሙ። 23በዚያን ጊ
ዜ በምኵራባቸው ውስጥ የነበረ ርኩስ[ሰ]
መንፈስ ያደረበት አንድ ሰው እንዲህ በ
ማለት ጮኸ፤ 24"የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፤ ከኛ
ምን ትሻለህ? ልታጠፋን መጣህን? እኔ ማን
እንደ ሆንህ
ዐውቃለሁ፤ አንተ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነህ!"
25ኢየሱስም፣ "ጸጥ በል፤ ከእርሱም ውጣ!"
ብሎ ገሠጸው። 26ርኩሱም መንፈስ ሰውየውን
በኀይል ካንፈራገጠው በኋላ እየጮኸ ወጣ።
27ሕዝቡ በሙሉ በመገረም፣ "ይህ ነገር ምን
ድን ነው? ሥልጣን ያለው አዲስ ትምህርት
መሆኑ ነው! ርኩሳን መናፍስትን እንኳ ያዛል፤
እነርሱም ይታዘዙለታል!" እያሉ እርስ በርስ
ተጠያየቁ። 28ወዲያውም ዝናው በገሊላ ዙሪያ
ባሉ ስፍራዎች ሁሉ ተዳረሰ።

## ኢየሱስ ብዙዎችን ፈወሰ

1፥29-31 ተጓ ምብ - ማቴ 8፥14-15፤ ሉቃ4፥38፡39
1፥32-34 ተጓ ምብ - ማቴ 8፥16፡17፤ ሉቃ4፥40፡41

29ወዲያው ከምኵራብ እንደ ወጡ፣ ከያዕ
ቆብና ከዮሐንስ ጋር ወደ ስምዖንና ወደ
እንድርያስ ቤት ገቡ። 30የስምዖን አማት
በትኵሳት በሽታ ታማ ተኝታ ነበር፤ ስለ እር
ሷም ነገሩት፤ 31ስለዚህም እርሱ ወደ ተኛ
ችበት በመሄድ እጇን ይዞ አስነሣት፤ ትኵሳ
ቱም ተዋት፤ ተነሥታም ታገለግላቸው ጀመር።

1፥1 ማቴ 4፥3
1፥2 ሚል3፥1፤
ማቴ11፥10፤
ሉቃ7፥27
1፥3 ኢሳ40፥3፤
ዮሐ1፥23
1፥4 ቀኑ8፤
ማቴ3፥1፤ሉቃ1፥77፤ዮ
ሐ1፥26፡33፤
ሐሥ1፥5፡22፤11፥16፤
13፥24፤18፥25፤
19፥3፡4
1፥6 ዘሌ11፥22፤
2ነገ1፥8
1፥7 ሐሥ13፥25
1፥8 ኢሳ44፥3፤
ኢል2፥23፤ዮሐ1፥33፤
ሐሥ1፥5፤2፥4፤
11፥16፤19፥4ኛ6
1፥9 ማቴ2፥23፤ 3፥1
1፥10 ዮሐ1፥32
1፥11 ማቴ3፥17
1፥13 ዘፀ24፥18፤
1ነገ19፥8፤
ማቴ4፥10፤ዕብ4፥15
1፥14 ማቴ3፥1፤
4፥12፡23
1፥15 ዮሐ3፥15፤
ሮሜ5፥6፤
ሐሥ20፥21፤ገላ4፥4፤
ኤፌ1፥10
1፥18 ማቴ4፥19
1፥21 ቀኑ39፤
ማቴ4፥23፤ማር10፥1
1፥22 ማቴ7፥28፡ 29
1፥24 መዝ16፥10፤
ኢሳ41፥14፡16፡20፤
ማቴ2፥23፤8፥29፤
ሉቃ1፥35፤24፥19፤
ዮሐ1፥45፡46፤6፥69፤
ሐሥ3፥14፤4፥10፤
24፥5፤1ዮሐ2፥20
1፥25 ቀኑ34
1፥26 ማር9፥20
1፥27 ማር10፥24፡
32
1፥28 ማቴ9፥26
1፥29 ቀኑ21፡23
1፥31 ሉቃ7፥14

[ሀ]1 አንዳንድ ቅጆች *የእግዚአብሔር ልጅ* የሚለው ሐረግ የላቸውም።
[ሰ]23 ወይም *ክፉ* ፤ እንዲሁም ቀኑ26 እና 27 ይመ

32ጀንበር ከጠለቀች በኋላ፣ ምሽት ላይ
የአካባቢው ሰዎች ሕመምተኞችንና በአጋን
ንት የተያዙትን ሁሉ ወደ እርሱ አመጡ።
33የከተማዋ ሕዝብ በሙሉ በቤቱ ደጅ ላይ
ተሰብስቦ ነበር። 34እርሱም በተለያየ በሽታ
የታመሙትን ብዙዎችን ፈወሰ፤ ብዙ አጋን
ንትም አወጣ፤ ነገር ግን አጋንንቱ የኢየሱስን
ማንነት ያውቁ ስለ ነበር እንዲናገሩ አልፈቀ
ደላቸውም።

## ኢየሱስ በገለልተኛ ስፍራ ጸለየ

1፥35-38 ተጓ ምብ - ሉቃ 4፥42፡43

35ማለዳም ገና ጎሕ ሳይቀድ፣ ኢ
የሱስ ተነሥቶ ከቤት ወጣ፤ ወደ አንድ
ገለልተኛ ስፍራም ሄዶ ይጸልይ ጀመር።
36ስምዖንና ባልደረቦቹም ተከትለው
ይፈልጉት ጀመር፤ 37ባገኙትም ጊዜ፣ "ሰዉ
ሁሉ ይፈልግሃል" አሉት።
38እርሱም፣ "ከዚህ ተነሥተን በአቅራቢያ
ወዳሉት መንደሮች እንሂድ፤ እዚያም ልስበክ፤
የመጣሁት ለዚሁ ነውና" አላቸው። 39ስለዚህ
ወደ ምኵራባቸው እየገባ በመስበክና አጋንን
ትን በማስወጣት በመላዋ ገሊላ ይዘዋወር
ጀመር።

## ኢየሱስ ለምጻሙን ሰው አነጻ

1፥40- 44 ተጓ ምብ - ማቴ 8፥2-4፤ ሉቃ5፥12-14

40አንድ ለምጻም[ሐ] ወደ እርሱ ቀርቦ ከፊቱ
በመንበርከክ፣ "ብትፈቅድ እኮ ልታነጻኝ ትች
ላለህ" በማለት ለመነው።
41ኢየሱስም ለሰውየው በመራራት እጁን
ዘርግቶ ዳሰሰውና፣ "እፈቅዳለሁ፣ ንጻ" አለው።
42እርሱም ወዲያው ከለምጹ ነጻ፤
ከበሽታውም ተፈወሰ።
43ኢየሱስም ሰውየውን አጥብቆ በማስጠ
ንቀቅ እንዲህ ሲል አሰናበተው፤ 44"ለማ
ንም አንድ ነገር እንኳ እንዳትናገር ተጠ
ንቀቅ፤ ነገር ግን ምስክር እንዲሆናቸው ሄደህ
ራስህን ለካህን አሳይ፤ ስለ መንጻትህም
ሙሴ ያዘዘውን መሥዋዕት አቅርብ" አለው።
45ሰውየው ግን በሄደበት ሁሉ ነገሩን በሰ
ፊው አወራ፣ ወሬውንም አሠራጨ። በዚህ
ምክንያት ኢየሱስ ወደ ማንኛውም ከተማ
በግልጽ መግባት አልተቻለውም፤ ከዚህም
የተነሣ ከከተማ ውጭ በሚገኙ ሰዋራ ቦታ
ዎች መኖር ጀመረ፤ ሰዎች ግን ከየአቅ
ጣጫው እርሱ ወዳለበት መምጣት አላቋ
ረጡም።

## ኢየሱስ ሽባ ፈወሰ

2፥3-12 ተጓ ምብ - ማቴ9፥2-8፤ ሉቃ5፥18-26

2 ኢየሱስ ከጥቂት ቀን በኋላ ወደ ቅፍ
ርናሆም እንደ ተመለሰ፣ ወደ ቤት
መግባቱን ሕዝቡ ሰማ። 2ስለዚህ ከበሩ

1፥32 ማቴ4፥24
1፥34 ማቴ4፥23፤
ማር3፥12፤
ሐሥ16፥17፡18
1፥35 ሉቃ3፥21
1፥38 ኢሳ60፥1
1፥39 ማቴ4፥23፡24
1፥40 ማር10፥17
1፥44 ዘሌ13፥49፤
14፥1ኛ32፤ማቴ8፥4
1፥45 ማር2፥13፤
ሉቃ5፥15፡16፡17፤
ዮሐ6፥2

2፥2 ቀ^13፤
ማር1፥45
2፥3 ማቴ4፥24
2፥5 ሉቃ7፥48
2፥7 ኢሳ43፥25
2፥10 ማቴ8፥20
2፥12 ማቴ9፥8፡33
2፥13
ማር1፥45፤ሉቃ5፥15፤
ዮሐ6፥2
2፥14 ማቴ4፥19
2፥16 ሐሥ23፥9፤
ማቴ9፥11
2፥17 ሉቃ19፥10፤
1ጢሞ1፥15

ውጭ እንኳ ሳይቀር ስፍራ እስኪታጣ
ድረስ ብዙ ሕዝብ ተሰበሰበ፤ እርሱም የእግ
ዚአብሔርን ቃል ሰበከላቸው። 3ጥቂት
ሰዎችም አንድ ሽባ በአራት ሰዎች አሸክ
መው ወደ እርሱ አመጡ። 4ከሕዝቡ ብዛት
የተነሣ ኢየሱስ ወዳለበት መቅረብ ስላል
ቻሉ፣ የቤቱን ጣራ እርሱ ባለበት በኩል
ነድለው ቀዳዳ በማበጀት ሽባው የተኛበትን
ዐልጋ በዚያ አወረዱ። 5ኢየሱስም እምነታ
ቸውን አይቶ ሽባውን፣ "አንተ ልጅ፣ ኀጢ
አትህ ተሰርዮልሃል!" አለው። 6በዚያ ተቀም
ጠው የነበሩ አንዳንድ ጸሐፍት ስለዚህ ነገር
በልባቸው እያሰላሰሉ፣ 7"ይህ ሰው
እንዴት እንዲህ ይላል? በአምላክ ላይ
የስድብ ቃል እየተናገረ እኮ ነው! ከአንዱ
ከእግዚአብሔር በስተቀር ማን ኀጢአትን ሊ
ያስተሰርይ ይችላል?" ብለው አሰቡ።
8ኢየሱስም ወዲያው በልባቸው የሚያስ
ቡትን በመንፈሱ ተረድቶ፣ "እንዴት እንዲ
ህ ታስባላችሁ? 9ሽባውን፣ 'ኀጢአትህ
ተሰርዮ ልሃል' ከማለትና፣ 'ተነሥተህ ዐልጋህን
ተሸክ መህ ሂድ' ከማለት የቱ ይቀላል?
10ነገር ግን የሰው ልጅ በምድር ላይ ኀጢ
አትን ለማስ ተስረይ ሥልጣን እንዳለው
እንድታውቁ በማለት ሽባውን፣
11"ተነሥተህ ዐልጋህን ተሸክመህ ወደ
ቤትህ ሂድ" አለው። 12እር ሱም ተነሥቶ
ሁሉም እያዩት ዐልጋውን ተሸክሞ ሄደ፤
በስፍራው የነበሩትም ሁሉ በሁኔታው
በመደነቅ፣ "የዚህ ዐይነት ነገር ፈጽሞ
አይተን አናውቅም!" በማለት ለእግዚአብሔር
ምስጋና አቀረቡ።

## የሌዊ መጠራት

2፥14-17 ተጓ ምብ - ማቴ 9፥9-13፤ሉቃ5፥27-32

13ኢየሱስም ዳግም ወደ ባሕሩ ዳርቻ
ወጣ፤
ሕዝቡም በብዛት ወደ እርሱ መጡ፤
እርሱም አስተማራቸው። 14በዚያም ሲያልፍ
የእልፍ ዮስን ልጅ ሌዊን በቀረጥ
መቀበያው ስፍራ ተቀምጦ አየውና፣
"ተከተለኝ" አለው፤ እር ሱም ተነሥቶ
ተከተለው።
15በማቴዎስ ቤት በማእድ ተቀምጦ ሳለ፣
ብዙ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና ኀጢአተኞች ተከትለ
ውት ስለ ነበር፣ ከኢየሱስና ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር ይመገቡ ነበር። 16ከፈሪሳውያን ወገን
የነበሩ ጸሐፍት ከኀጢአተኞችና ከቀረጥ
ሰብሳቢዎች ጋር ሲበላ ባዩት ጊዜ፣ ደቀ
መዛሙርቱን "ከቀረጥ ሰብሳቢዎችና ከኀጢ
አተኞች ጋር ለምን ይበላል?" ሲሉ ጠየ
ቋቸው።
17ኢየሱስም የሚናገሩትን ሰምቶ፣ "ሐኪም

[ሐ]40 *ለምጽ* የሚለው ቃል በግሪኩ አገላለጽ የተለያዩ የቆዳ
በሽታዎችን ያመለክታል

የሚያስፈልጋቸው ሕመምተኞች እንጂ ጤነ
ኞች አይደሉም፤ እኔ ኀጢአተኞችን እንጂ
ጻድቃንን ወደ ንስሓ ልጠራ አልመጣሁም”
አላቸው።

## ስለ ጾም የቀረበ ጥያቄ

2፥18-22 ተጓ ምብ - ማቴ9፥14-17፤ ሉቃ 5፥33-38

18የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና ፈሪሳውያን
ይጾሙ ነበር፤ አንዳንድ ሰዎችም መጥተው
ኢየሱስን፣ “የዮሐንስና የፈሪሳውያን ደቀ
መዛሙርት ሲጾሙ፣ የአንተ ደቀ መዛሙርት
የማይጾሙት ለምንድን ነው?” አሉት።
19ኢየሱስም፣ እንዲህ አላቸው፤ “ሙሽራው
ከእነርሱ ጋር እያለ ሚዜዎቹ ሊጾሙ ይች
ላሉን? ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ
ሊጾሙ አይችሉም፤ 20ሙሽራው ከእነርሱ
የሚወሰድበት ወቅት ይመጣል፤ በዚያን ጊዜ
ግን ይጾማሉ።
21“በአሮጌ ልብስ ላይ አዲስ ጨርቅ የሚጥፍ
ማንም የለም፤ ይህ ቢደረግ ግን፣ አዲሱ ጨርቅ
አሮጌውን ይቦጭቀዋል፤ ቀዳዳውም የባሰ
ይሰ ፋል። 22እንዲሁም አዲስ የወይን ጠ
ጅ በአሮጌ አቍማዳ የሚያስቀምጥ የለም፤
ይህ ከተደረገማ የወይን ጠጁ አቍማዳውን
ያፈነ ዳዋል፤ የወይን ጠጁም አቍማዳውም
ይበላ ሻሉ። ስለዚህ አዲስ የወይን ጠጅ
መቀመጥ ያለበት በአዲስ አቍማዳ ነው።”

## ኢየሱስ የሰንበት ጌታ ነው

2፥23-28 ተጓ ምብ - ማቴ12፥1-8፤ ሉቃ6፥1-5
3፥1-6 ተጓ ምብ - ማቴ12፥9-14፤ ሉቃ 6፥6-11

23በሰንበት ቀን ኢየሱስ በእርሻ መካከል
ሲያልፍ፣ አብረውት በመንገዝ ላይ የነበሩት
ደቀ መዛሙርቱ እሸት ይቀጥፉ ጀመር።
24ፈሪሳውያንም፣ “እነሆ፤ በሰንበት ቀን ለምን
የተከለከለ ነገር ያደርጋሉ?” ሲሉ ጠየቁት።
25እርሱም እንዲህ አላቸው፤ “ዳዊት በተራ
በና የምግብ ፍላጎት በጸናበት ጊዜ አብ
ረውት ከነበሩት ሰዎች ጋር
ያደረገውን አላነበባችሁምን? 26በሊቀ
ካህናቱ በአብ ያታር ዘመን ወደ እግዚአብሐ
ር ቤት ገብቶ፣ ካህናት ብቻ እንዲበሉት
የተፈቀደውን የተቀደሰ ኅብስት ራሱ በልቶ
አብረውት ለነበሩትም ሰዎች ሰጣቸው።”
27ደግሞም እንዲህ አላቸው፤ “ሰንበት ለሰው
ተፈጠረ እንጂ፣ ሰው ለሰንበት አልተፈጠ
ረም፤ 28ስለዚህ የሰው ልጅ የሰንበት ጌታዋ
ነው።”

3 በሌላ ጊዜ ወደ ምኵራብ ገባ፤ በዚ
ያም እጁ የሰለለች ሰው ነበር። 2በም
ክንያት ሊከሱት የሚፈልጉ ሰዎችም በሰን
በት ቀን ይፈውሰው እንደ ሆነ ለማየት
ይጠባበቁ ነበር። 3እርሱም እጁ የደረቀ
ችውን ሰው፣ “በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት
ተነሥተህ ቁም” አለው።
4ኢየሱስም፣ “በሰንበት ቀን የተፈቀደው
መልካም ማድረግ ነው ወይስ ክፉ? ሕይወት
ማዳን ነውን ወይስ ማጥፋት?” አላቸው። እነ
ርሱ ግን ዝም አሉ።
5በልባቸው ደንዳናነት አዝኖ በዙሪያው የቆ
ሙትን በቍጣ ተመለከታቸውና ሰውየውን፣
“እጅህን ዘርጋ!” አለው፤ ሰውየውም እጁን
ዘረጋ፤ እጁም ፍጹም ደኅና ሆነችለት።
6ፈሪሳውያንም እንዴት ሊያጠፉት እንደ
ሚችሉ ከሄሮድስ ወገን ከሆኑት ጋር መመ
ካከር ጀመሩ።

## ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ተከተሉ

3፥7-12 ተጓ ምብ – ማቴ 12፥15፥16፤ ሉቃ6፥17-19

7ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ባሕሩ
ሄደ፤ ከገሊላ የመጣ እጅግ ብዙ ሕዝብም
ተከተለው፤ 8የሚሠራውን ነገር የሰሙ ሰዎችም
ከይሁዳ፣ ከኢየሩሳሌም፣ ከኤዶምያስ፣ በዮር
ዳኖስ ማዶ ካለው አገር እንዲሁም ከጢሮስና
ከሲዶና አካባቢ ወደ እርሱ መጡ። 9የተሰ
በሰበውም ሕዝብ እንዳያጨናንቀው
አነስተኛ የሆነ ጀልባ እንዲያዘጋጁለት ደቀ
መዛሙርቱን አዘዛቸው። 10ብዙዎችን ፈውሶ
ስለ ነበር፣ በሕመም የሚሠቃዩ ሁሉ ሊ
ዳስሱት ይሽ ቀዳደሙ ነበር። 11ርኩሳን[መ]
መናፍስትም ባዩት ቍጥር ከፊቱ እየወደቀ
፣ “አንተ የእግ ዚአብሔር ልጅ ነህ!” በማለት
ይጮኹ ነበር። 12እርሱ ግን ማንነቱን
እንዳይገልጹ አጥብቆ ይገሥጻቸው ነበር።

## የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መሾም

3፥16-19 ተጓ ምብ ማቴ 10፥2-4፤ ሉቃ6፥14-16፤ሐሥ1፥13

13ኢየሱስ ወደ ተራራ ወጥቶ
የሚፈልጋ
ቸውን ወደ እርሱ እንዲመጡ ጠራቸው፤
እነርሱም ወደ እርሱ መጡ። 14ከእርሱ
ጋር እንዲሆኑ፣ ለስብከትም ይልካቸው ዘንድ
ዐሥራ ሁለቱን ሾማቸው፤ ሐዋርያትም ብሎ
ጠራቸው[ሠ]፤ 15አጋንንትን እንዲያስወጡም
ሥልጣን ሰጣቸው። 16የሾማቸውም ዐሥራ
ሁለቱ እነዚህ ናቸው፤ ጴጥሮስ ብሎ የጠ
ራው ስምዖን፣ 17ቦአኔርጌስ ይኸውም፣ ‘የነ
ጐድጓድ ልጆች’ ብሎ የጠራቸው የዘብዴ
ዎስ ልጆች ያዕቆብና ወንድሙ ዮሐንስ፤
18እንድርያስ፣ ፊልጶስ፣ በርቶሎሜዎስ፣
ማቴዎስ፣ ቶማስ፣ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ፣
ታዴዎስ፣ ተቀናቃኙ ስምዖን፣ 19እንዲሁም
አሳልፎ የሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ።

2፥18 ማቴ6፥16ኛ18፤ሐሥ13፥2
2፥20 ሉቃ17፥22
2፥23 ዘዳ23፥25
2፥24 ማቴ12፥2
2፥26 ዘሌ24፥5ኛ9፤ 1ሳሙ21፥1ኛ6፤ 2ሳሙ8፥17፤ 1ዜና24፥6
2፥27 ዘፀ23፥12፤ ዘዳ5፥14፤ቈላ2፥16
2፥28 ማቴ8፥20
3፥1 ማቴ4፥23፤ ሉቃ1፥21
3፥2 ማቴ12፥10፤ ሉቃ14፥1
3፥6 ማቴ12፥14፤ 22፥16፤ማር12፥13
3፥7 ማቴ4፥25
3፥8 ማቴ11፥21
3፥10 ማቴ4፥23፤ 9፥20
3፥11 ማቴ1፥23፡ 24፤4፥3
3፥12 ማቴ8፥4፤ ማር1፥24፡25፡34፤ ሐሥ16፥17፡18
3፥13 ማቴ5፥1
3፥14 ማር6፥30
3፥15 ማቴ10፥1
3፥16 ዮሐ1፥24

[መ]11 ወይም *ክፉ*፤ እንዲሁም ቍ 30 ይመ
[ሠ]14 አንዳንድ ቅጆች *ሐዋርያትም ብሎ ጠራቸው* የሚለው ሐረግ የላቸውም

## ኢየሱስና ብዔል ዜቡል
3፥23-27 ተጓ ምብ - ማቴ12፥25-29፤ሉቃ11፥17-22

[20]ከዚያም ኢየሱስ ወደ አንድ ቤት ገባ፤
እርሱና ደቀ መዛሙርቱ ምግብ መብላት
እንኳ እስኪሳናቸው ድረስ ሕዝቡ እንደ
ገና በብዛት ተሰበሰበ። [21]ሁኔታውን የሰሙ
ዘመዶቹም፣ “አእምሮውን ስቶአል” በማለት
ይዘውት ለመሄድ ወዳለበት መጡ።
[22]ከኢየሩሳሌም የመጡ ጸሐፍትም፣ “ብዔል
ዜቡልʻ አድሮበታል፤ አጋንንትን የሚያወጣው
በአጋንንት አለቃ ነው” አሉ።
[23]እርሱም ጠራቸውና በምሳሌ እንዲህ አላ
ቸው፤ “ሰይጣን ሰይጣንን እንዴት ሊያስወጣ
ይችላል? [24]እርስ በርሱ የሚከፋፈል መን
ግሥት ሊጸና አይችልም፤ [25]ቤትም እርስ
በርሱ ከተለያየ ሊቆም አይችልም። [26]እንደዚ
ሁም ሰይጣን እርስ በርሱ የሚፃረርና
የሚከፋፈል ከሆነ ሊቆም አይችልም፤ ያበ
ቃለታል። [27]ከዚህም የተነሣ አንድ ሰው
አስቀድሞ ኀይለኛውን ሰው ሳያስር ወደ ኀይ
ለኛው ሰው ቤት ሊገባና ንብረቱን ሊዘርፍ
አይችልም፤ ቤቱን መዝረፍ የሚቻለው ኀይለ
ኛውን ሰው ሲያስር ብቻ ነው። [28]እውነት
እላችኋለሁ፤ የሰው ልጆች ኀጢአትና የሚሳ
ደቡት ስድብ ሁሉ ይሰረይላቸዋል፤ [29]ነገር
ግን በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል
የሚናገር ሁሉ የዘላለም ኀጢአት ዕዳ ይሆ
ንበታል እንጂ ለዘላለም አይሰረይለትም።
[30]ይህንንም ያለው፣ “ርኩስ መንፈስ አለ
በት” ስላሉት ነበር።

## የኢየሱስ እናትና ወንድሞቹ
3፥31-35 ተጓ ምብ - ማቴ12፥46-50፤
ሉቃ8፥19-21

[31]ከዚህ በኋላ እናቱና ወንድሞቹ መጡ፤
በውጭ ቆመውም ሰው ልከውበት አስጠሩት።
[32]በዙሪያው የተቀመጡ ብዙ ሰዎችም፣ “እነሆ፤
እናትህና ወንድሞችህ ውጭ ይፈልጉሃል”
አሉት።
[33]እርሱም መልሶ፣ “እናቴ ማን ናት
ወንድሞቼስ እነማን ናቸው?” አላቸው።
[34]በዙሪያው ወደ ተቀመጡትም በመመ
ልከት፣ እንዲህ አለ፤ “እናቴና ወንድሞቼ
እነዚህ ናቸው” [35]የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያ
ደርግ ሁሉ እርሱ ወንድሜ፣ እኅቴ፣ እናቴም
ነውና።”

## የዘሪው ምሳሌ
4፥1-12 ተጓ ምብ - ማቴ13፥1-15፤ ሉቃ8፥4-10
4፥13-20 ተጓ ምብ - ማቴ13፥18-23፤ ሉቃ8፥ 11-15

4 በሌላ ጊዜ ደግሞ በባሕሩ አጠገብ ያስተ
ምር ጀመር። እርሱ ባለበት አካባቢ እጅግ
ብዙ ሕዝብ ስለ ተሰበሰበ፣ በባሕሩ ላይ
ወዳለች ጀልባ ገብቶ ተቀመጠ፤ ሕዝቡም

3፥20 ቍ7፤ ማር6፥31
3፥21 ዮሐ10፥20፤ ሐሥ26፥24
3፥22 ማቴ9፥34፤10፥25፤ 11፥18፤12፥24፤15፥1፤ ዮሐ7፥20፤8፥48፥52፤ 10፥20
3፥23 ማር4፥2፡10
3፥27 ኢሳ49፥24፡25
3፥29 ማቴ12፥31፡ 32፤ሉቃ12፥10
3፥31 ቍ21
4፥1 ማር2፥13፤3፥7
4፥2 ቍ11፤ ማር3፥23
4፥3 ቍ26
4፥8 ዮሐ15፥5፤ ቈላ1፥6
4፥9 ቍ23፤ ማቴ11፥15
4፥11 ማቴ3፥2፤ 1ቆሮ5፥12፡13፤ ቈላ4፥5፤1ተሰ4፥12፤1 ጢሞ3፥7
4፥12 ኢሳ6፥9፡10፤ ማቴ13፥13ኛ15
4፥14 ማር16፥9፤ ሉቃ1፥2፤ሐሥ4፥31፤ 8፥4፤16፥6፤17፥11፤ ፊል1፥14
4፥15 ማቴ4፥10
4፥19 ማቴ19፥23፤ 1ጢሞ6፥9፡10፡17፤ 1ዮሐ2፥15ኛ17

ሁሉ በባሕሩ ዳርቻ ባለው ስፍራ ላይ ተሰ
ብስቦ ነበር። [2]እርሱም ብዙ ነገሮችን
በምሳሌ አስተማራቸው፤ እንዲህም አላቸው፤
[3]“ስሙ፤ አንድ ዘሪ ዘር ሊዘራ ወጣ። [4]ዘሩን
በሚዘራበትም ጊዜ አንዳንዱ መንገድ ላይ
ወደቀ፤ ወፎችም መጥተው ለቀመው በሉት።
[5]ሌላው በቂ ዐፈር በሌለበት በጭንጫ ቦታ
ላይ ወደቀ፤ ዐፈሩ ጥልቀት ስላልነበረው
ወዲያው በቀለ፤ [6]ፀሓይ በወጣ ጊዜ ግን
ጠወለገ፤ ሥር ስላልነበረውም ደረቀ። [7]ሌላው
ዘር ደግሞ በእሾኽ መካከል ወደቀ፤ እሾኹም
አድጎ የዘሩን ተክል ስላነቀው ፍሬ አላፈ
ራም። [8]ሌላው ዘር ደግሞ በመልካም መሬት
ላይ ስለ ወደቀ በቅሎ አደገ፤ ፍሬም ሰጠ፤
አንዱ ሠላሣ፣ አንዱ ሥልሳ፣ ሌላውም መቶ
ፍሬ አፈራ።” [9]ቀጥሎም ኢየሱስ፣ “የሚሰማ
ጆሮ ያለው ይስማ” አለ።
[10]ብቻውን በሆነ ጊዜ፣ ዐሥራ ሁለቱና አብ
ረውት የነበሩት ሌሎች ስለ ምሳሌዎቹ ጠየ
ቁት። [11]እርሱም፣ “ለእናንተ የእግዚአብሔር
መንግሥት ምስጢር ተሰጥቶአችኋል፤
በውጭ ላሉት ግን ነገር ሁሉ በምሳሌ ይነገ
ራቸዋል፤ [12]ይኸውም፣ “ማየቱን እንዲያዩ
እንዳያስተ ውሉትም፣ መስማቱን እንዲ
ሰሙ ልብ እንዳ ይሉትም፣ እንዳይመለሱና
ኀጢአታቸው እንዳይሰረይላቸው ነው”
አላቸው።
[13]ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤ “ይህን
ምሳሌ አልተረዳችሁትምን? ታዲያ ሌሎቹን
ምሳሌዎች ሁሉ እንዴት ልትረዱ ትችላላ
ችሁ? [14]ዘሪው ቃሉን ይዘራል። [15]አንዳንድ
ሰዎች በመንገድ ላይ የወደቀውን ዘር ይመ
ስላሉ፤ ቃሉን በሚሰሙበት ጊዜ ሰይጣን
ወዲያውኑ መጥቶ በውስጣቸው የተዘራውን
ቃል ይወስደዋል። [16]እንዲሁም ሌሎች በጭ
ንጫ ቦታ ላይ የተዘራውን ዘር ይመስላሉ፤
ቃሉን በሚሰሙበት ጊዜ በደስታ ይቀበሉ
ታል፤ [17]ነገር ግን ሥር የሌላቸው ስለሆኑ
የሚቈዩት ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነው፤ በቃሉ
ምክንያት መከራ ወይም ስደት በመጣ ጊዜ
ወዲያውኑ ይሰናከላሉ። [18]ሌሎቹ ደግሞ በእ
ሾኽ መካከል የተዘራውን ዘር ይመስላሉ፤
ቃሉን መስማት ይሰማሉ፤ [19]ነገር ግን የዚህ
ዓለም ውጣ ውረድ፣ የሀብት አጓጊነት እንዲ
ሁም የሌሎች ነገሮች ምኞት ቃሉን አንቀው
በመያዝ ፍሬ እንዳያፈራ ያደርጉታል።
[20]ሌሎቹ በመልካም መሬት ላይ የተዘራውን
ዘር ይመ ስላሉ፤ እነዚህም ቃሉን ሰምተው
የሚቀበሉና ሠላሳ፣ ሥልሳ፣ መቶም ፍሬ
የሚያፈሩ ናቸው”

ʻ22 ግሪኩ ብዔዜቡል ወይም ብዔልዜቡል ይላል

## የመቅረዙ መብራት ምሳሌ

21እንዲህም አላቸው፤ “መብራት አምጥታ
ችሁ ከዕንቅብ ወይም ከዐልጋ ሥር ታስቀ
ምጣላችሁን? የምታስቀምጡት በመቅረዙ ላይ
አይደለምን? 22ስለዚህ ተደብቆ የማይገለጥ፣
ተሸሽጎ ወደ ብርሃን የማይወጣ የለም፤ 23ሰሚ
ጆሮ ያለው ይስማ።”
24በመቀጠልም፣ “ስለምትሰሙት ነገር ጥን
ቃቄ አድርጉ፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ
ይሰፈርላችኋል፤ እንዲያውም ከዚያ የበለጠ
ይጨመርላችኋል። 25ላለው ይጨመርለታል፤
ከሌለው ላይ ግን፣ ያው ያለው እንኳ ይወሰ
ድበታል” አላቸው።

## የአዳጊው ዘር ምሳሌ

26ከዚያም፣ እንዲህ አለ፤ “የእግዚአብሔር
መንግሥት ይህን ትመስላለች፤ አንድ ሰው
መሬት ላይ ዘር ይዘራል። 27ሰውየው ሌሊት
ይተኛል፤ ቀን ይነሣል ነገር ግን እርሱ
ሳያውቅ ያ ዘር በቅሎ ያድጋል፤ 28ምድርም
ራስዋ በመጀመሪያ ቡቃያውን፣ ቀጥሎ
ዛላውን፣ ከዚያም በዛላው ላይ የጐመራ ፍሬ
ታስገኛለች፤ 29ፍሬው እንደ በሰለም መከር
በመድረሱ፣ ሰውየው ወዲያው ማጭዱን አን
ሥቶ አጨዳ ይጀምራል።”

## የሰናፍጭ ቅንጣት ምሳሌ

4፥30-32፤ ተጓ ምብ - ማቴ 13፥31፡32፤ ሉቃ 13፥18፡19

30ደግሞም እንዲህ አለ፤ “የእግዚአብሔርን መን
ግሥት ከምን ጋር እናነጻጽራታለን? በምንስ
ምሳሌ እንገልጻታለን? 31በምድር ላይ ከሚ
ዘራው ዘር ሁሉ እጅግ ያነሰችውን የሰናፍጭ
ቅንጣት ትመስላለች፤ 32ተዘርታ ካደገች
በኋላ ግን፣ በአትክልቱ ቦታ ከሚገኙት ዕፀ
ዋት ሁሉ ትበልጣለች፤ የሰማይ ወፎችም
በትላልቅ ቅርንጫፎቿ ጥላ ሥር ያርፋሉ።”
33ኢየሱስም ሰዎች መረዳት በሚችሉበት
መጠን፣ እነዚህን በመሳሰሉ ብዙ ምሳሌዎች
ነገራቸው። 34ምንም ነገር ያለ ምሳሌ አይነ
ግራቸውም ነበር። እርሱና ደቀ መዛሙርቱ
ብቻ በሚሆኑበት ጊዜ ግን ሁሉንም ነገር
በዝርዝር ያስረዳቸው ነበር።

## ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ አደረገ

4፥35-41 ተጓ ምብ - ማቴ8፥18፡23-27፤ ሉቃ8፥22-25

35ያ ቀን በመሸ ጊዜ፣ “ወደ ማዶ እንሻገር”
አላቸው። 36እነርሱ ሕዝቡን ትተው በጀልባዋ
ውስጥ እንዳለ በዚያው ይዘውት ሄዱ፤ ሌሎች
ጀልባዎችም አብረውት ነበሩ። 37በዚህ ጊዜ
ኀይለኛ ዐውሎ ነፋስ ተነሣ፤ ማዕበሉም ውሃ
እስኪሞላት ድረስ ጀልባዋን ያናውጣት
ነበር። 38ኢየሱስ ግን ትራስ ተንተርሶ ከጀ
ልባዋ በስተ ኋላ በኩል ተኝቶ ነበር።

4፥21 ማቴ5፥15
4፥22 ኤር16፥17፤
ማቴ10፥26፤ሉቃ8፥17
፤12፥2
4፥23 ቍ9፤
ማቴ11፥15
4፥24 ማቴ7፥2
4፥25 ማቴ25፥29
4፥26 ማቴ13፥24
4፥29 ራእ14፥15
4፥30 ማቴ13፥24
4፥33 ዮሐ16፥12
4፥34 ዮሐ16፥12
4፥36 ቍ1፤
ማር3፥9፤5፥2፡21፤
6፥32፡45
4፥40 ማቴ14፥31፤
ማር16፥14
5፥2 ማር1፥23፤4፥1
5፥7 ማቴ4፥3፤
8፥29፤ሉቃ1፥32፤6፥35
፤ሐሥ16፥17፤
ዕብ7፥1
5፥9 ቍ15

እነርሱም ቀስቅሰውት፣ “መምህር ሆይ፤
ስናልቅ አይገድህምን?” አሉት።
39እርሱም ተነሥቶ ነፋሱን ገሠጸው፤ ባሕሩ
ንም፣ “ጸጥ፣ ረጭ በል!” አለው። ነፋሱም
ጸጥ፣ ርጭ አለ፤ ፍጹምም ጸጥታ ሆነ።
40ደቀ መዛሙርቱንም፣ “ስለ ምን እንዲህ
ፈራችሁ? እስከዚህ እምነት የላችሁምን?”
አላቸው።
41እነርሱም በፍርሀት ተውጠው እርስ በር
ሳቸው፣ “ነፋሱም ሞገዱም የሚታዘዙለት
ይህ ማን ነው?” ተባባሉ።

## አጋንንት ያደረበት ሰው መፈወሱ

5፥1-17 ተጓ ምብ - ማቴ8፥28-34፤ ሉቃ8፥26-37
5፥18-20 ተጓ ምብ - ሉቃ 8፥38፡39

5 ባሕሩን ተሻግረው ጌርሴኖን[ሰ] ወደ
ተባለ አገር መጡ። 2ኢየሱስ ከጀልባ
እንደ ወረደ፣ ርኩስ[ሸ] መንፈስ ያደረበት
ሰው ከመቃብር ቦታ ወጥቶ ሊገናኘው ወደ
እርሱ መጣ። 3ይህ ሰው በመቃብር ቦታ
ውስጥ የሚኖርና ማንም በሰንሰለት እንኳ
ሊያስረው የማይችል ነበር። 4ብዙ ጊዜ
በእግር ብረትና በሰንሰለት ይታሰር ነበር፤
ነገር ግን የእጅ ሰንሰለቱን ይበጥስ፣ የእግር
ብረቱንም ይሰብር ነበር። ማንም ይዞ ሊያ
ቈየው የሚችል አልነበረም።
5በመቃብሮቹና በተራራዎቹ መካከል ቀንና
ሌሊት እየተዘዋወረ በመጮኽ ሰውነቱን
በድንጋይ ይቈራርጥ ነበር።
6ይህም ሰው ኢየሱስን ከሩቅ ባየው ጊዜ
ወደ እርሱ ሮጦ ከፊቱ ተንበርክኮ ሰገደለት፤
7በታላቅ ድምፅ ጮኾም፣ “አንተ የልዑል
እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ፤ ከእኔ ምን
አለህ? እንዳታሠቃየኝ በእግዚአብሔር ይዠ
ሃለሁ!”
አለው። 8ይህንንም ያለው ኢየሱስ፣ “አንተ
ርኩስ መንፈስ ከዚህ ሰው ውጣ!” ብሎት
ስለ ነበር ነው።
9ከዚያም ኢየሱስ፣ “ስምህ ማን ነው” ብሎ
ጠየቀው። “ብዙ ነንና ስሜ ሌጌዎን ነው”
አለው። 10ከአገር እንዳያስወጣቸውም
አጥብቆ ለመነው።
11በአቅራቢያውም በሚገኝ ኰረብታ ላይ
ትልቅ የዐሣማ መንጋ ተሰማርቶ ነበር።
12ርኩሳን መናፍስቱም ኢየሱስን፣ “ወደ
ዐሣማዎቹ ስደደን፤ እንድንገባባቸውም ፍቀ
ድልን” ብለው ለመኑት።
13እርሱም ፈቀደላቸው። ርኩሳን መናፍስ
ቱም ወጥተው በዐሣማዎቹ ገቡባቸው፤
ሁለት ሺህ ያህል ዐሣማዎችም በገደሉ አፋፍ
በመንደርደር ቍልቍል ወርደው በባሕር ውስጥ

[ሰ]1 አንዳንድ ቅጆች ጌራሴኖች ሌሎች ደግሞ ጌርጌሴኖን ይላሉ።
[ሸ]2 ወይም ክፉ፤ እንዲሁም ቍ 8እና 13 ይመ።

ሰጠሙ።
14እረኞቹ ሸሽተው ሂዱ፤ ወሬውን በከተ
ማና በገጠር አዳረሱት፤ ሕዝቡም የሆነውን
ለማየት ካለበት ወጣ። 15ወደ ኢየሱስም
በመጡ ጊዜ፣ የአጋንንት ሰራዊት አድረው
በት የነበረው ሰው፣ ልብስ ለብሶና አእም
ሮው ተመልሶለት በዚያ ተቀምጦ አዩት፤
ፈሩም። 16ይህን ያዩ ሰዎችም አጋንንት
ስላደረበት ሰው የተደረገውንና ስለ ዐሣ
ማዎቹም ለሕዝቡ አወሩ። 17ከዚያም ሕዝቡ
አገራቸውን ለቆ እንዲሄድላቸው ኢየሱስን
ይለምኑት ጀመር።
18ኢየሱስ ወደ ጀልባዪቱ በሚገባበት
ጊዜ፣ አጋንንት አድሮበት የነበረው ሰው
አብሮት ለመሄድ ለመነው። 19ኢየሱስ አልፈቀ
ደለትም፤ ነገር ግን፣ "ወደ ቤትህ ሂድ፣
ለዘመዶችህም ጌታ ምን ያህል ታላቅ ነገር
እንዳደረገልህና ያሳየህን ምሕረት ንገራቸው"
አለው። 20ሰውየውም ሄደ፤ ኢየሱስ ያደረ
ገለትን ነገር ሁሉ ዐሥር ከተማ[ቀ] በተባለው
አገር ያወራ ጀመር፤ የሰሙትም ሁሉ ተደ
ነቁ።

## የሞተችው ልጅና የታመመችው ሴት

5፥22-43 ተጓ ምብ - ማቴ9፥18-26፤ ሉቃ8፥41-56

21ኢየሱስ እንደ ገና በጀልባ ወደ ማዶ በተ
ሻገረ ጊዜ፣ ብዙ ሕዝብ በዙሪያው ተሰባ
ሰበ፤ በባሕሩ ዳርቻም እንዳለ፣ 22ከምኵራብ
አለቆች አንዱ ኢያኢሮስ የተባለው ወደዚያ
መጥቶ ስለ ነበር፣ ኢየሱስን ባየው ጊዜ
በእግሩ ላይ ወድቆ፣ 23"ትንሿ ልጄ በሞት
አፋፍ ላይ ናትና ድና በሕይወት እንድትኖር
መጥተህ እጅህን ጫንባት" በማለት አጥብቆ
ለመነው። 24ኢየሱስም አብሮት ሄደ።
ብዙ ሕዝብም ዙሪያውን እያጨናነቀው
ተከ ተለው። 25ዐሥራ ሁለት ዓመት ደም
ሲፈሳት የኖረችም ሴት በዚያ ነበረች፤ 26በብዙ
ባለ መድኀኒቶች ዘንድ በመንከራተት ያላትን
ሁሉ ብትጨርስም፣ ሕመሙ ባሰባት እንጂ
አልተሻ ላትም ነበር። 27ስለ ኢየሱስም በሰ
ማች ጊዜ፣ ከበስተ ኋላው በሰዎች መካከል
መጥታ ልብሱን ነካች፤ 28ምክንያቱም፣ "እንደ
ምንም ብዬ ልብሱን ብቻ እንኳ ብነካ
እፈወሳለሁ" የሚል እምነት ነበራት። 29የሚ
ፈሰው ደሟ ወዲያውኑ ቆመ፤ ከሥቃይዋ መገ
ላገሏም በሰውነቷ ታወቃት።
30ወዲያውኑ ኢየሱስ፣ ኀይል ከእርሱ እንደ
ወጣ ዐውቆ፤ ወደ ሕዝቡ ዞሮ በማለት፣
"ልብሴን የነካው ማን ነው?" አለ።
31ደቀ መዛሙርቱም፣ "ሕዝቡ ተጨናንቆ
ሲጋፋህ እያየህ፣ 'ማን ነው የነካኝ?' እን
ዴት ትላለህ? አሉት።
32ኢየሱስ ግን ይህንን ያደረገው ማን እንደ
ሆነ ለማየት ዙሪያውን ተመለከተ። 33ሴት
የዋም ምን እንደ ተደረገላት ባወቀች ጊዜ
እየፈራችና እየተንቀጠቀጠች መጥታ በፊቱ
ተደፋች፤ እውነቱንም ሁሉ ነገረችው። 34እር
ሱም፣ "ልጄ ሆይ፤ እምነትሽ አድኖሻል፤
በሰላም ሂጂ፤ ከሥቃይሽም ዕረፊ" አላት።
35ኢየሱስም በመነጋገር ላይ እያለ፣ ሰዎች
ከምኵራቡ አለቃ ከኢያኢሮስ ቤት መጥ
ተው፣ "ልጅህ ሞታለች፤ ከእንግዲህ መምህ
ሩን ለምን ታደክመዋለህ?" አሉት።
36ኢየሱስ ግን ሰዎቹ የተናገሩትን ችላ በማ
ለት የምኵራቡን አለቃ፣ "እመን ብቻ እንጂ
አትፍራ፤" አለው።
37ከጴጥሮስና ከያዕቆብ እንዲሁም ከያዕ
ቆብ ወንድም ከዮሐንስ በቀር ማንም
እንዲከተለው አልፈቀደም። 38ወደ ምኵራቡ
አለቃ ቤት እንደ ደረሱ፣ ኢየሱስ ግርግሩ
ንና ሰዎቹም ዋይ ዋይ እያሉ አምርረው
ሲያለቅሱ ተመለከተ። 39ወደ ቤትም ገብቶ፣
"ይህ ሁሉ ግርግርና ልቅሶ ምንድን ነው?
ብላቴናዪቱ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም"
አላቸው። 40ሰዎቹ ግን ሣቁበት።
ሰዎቹን ሁሉ ከቤት ካስወጣ በኋላ፣
የብላቴናዪቱን አባትና እናት እንዲሁም አብረ
ውት የመጡትን ደቀ መዛሙርት አስከትሎ
ብላቴናዪቱ ወዳለችበት ገባ። 41ከዚያም የብ
ላቴናዪቱን እጅ ይዞ፣ "ጣሊታ ቁሚ!" አላት፤
ትርጒሙም፣ "አንቺ ልጅ ተነሺ" ማለት
ነው። 42ብላቴናዪቱም ወዲያውኑ ተነሥታ
ቆመች፤ ወዲያ ወዲህም ሄደች። ዕድሜ
ዋም ዐሥራ ሁለት ዓመት ነበር። ሰዎቹም
በሁኔታው እጅግ ተደነቁ። 43እርሱም ይህን
ነገር ማንም እንዳያውቅ አጥብቆ አስጠነቀ
ቃቸው፤ የሚበላ ነገር እንዲሰጧትም ነገራ
ቸው።

## ነቢይ በአገሩ አይከበርም

6፥1-6 ተጓ ምብ - ማቴ13፥54-58

6 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከዚያ ተነሥቶ
ወደ ገዛ አገሩ ሄደ፤ ደቀ መዛሙርቱም
ተከተሉት። 2ሰንበትም በደረሰ ጊዜ፣ በምኵ
ራብ ያስተምር ጀመር፤ የሰሙትም ብዙ
ሰዎች፣ ተደነቁ።
እነርሱም እንዲህ አሉ፤ "ይህ ሰው እነዚ
ህን ነገሮች ከየት አገኛቸው? ይህ የተሰጠው
ጥበብ ምንድን ነው? ደግሞም እነዚህ ታምራት
እንዴት በእጁ ይደረጋሉ! 3ይህ ዐናጢው አይደ
ለምን? የማርያም ልጅ፣ የያዕቆብና የዮሴፍ[በ]፣
የይሁዳና የስምዖን ወንድም አይደለምን? እኅቶ

5፥15 ቍ9፥16፥18፤
ማቴ4፥24
5፥19 ማቴ8፥4
5፥20 ማቴ4፥25፤
ማር7፥31
5፥21 ማቴ9፥1፤
ማር4፥1
5፥22 ቍ35፥36፥
38፤ሉቃ13፥14፤
ሐሥ13፥15፤18፥18፥
17
5፥23 ማቴ19፥13፤
ማር6፥5፤7፥32፤8፥23፤
16፥18፤ሉቃ4፥40፤
13፥13፤ሐሥ6፥6
5፥25
ዘሌ15፥25ኛ30
5፥28 ማቴ9፥20
5፥29 ቍ34
5፥30 ሉቃ5፥17፤
6፥19
5፥34 ማቴ9፥22፤
ሐሥ15፥33
5፥35 ቍ22
5፥37 ማቴ4፥21
5፥38 ቍ22
5፥39 ማቴ9፥24
5፥41 ማር1፥31፤
ሉቃ7፥14
5፥43 ማቴ8፥4
6፥1 ማቴ2፥23
6፥2 ማቴ4፥23፤
7፥28፤ማር1፥21
6፥3 ማቴ11፥6፤
12፥46፤ዮሐ6፥61

[ቀ]20 *ዐሥር ከተማ* የሚባለውን አካባቢ ግሪኩ ዴካፖሊስ ይለዋል።
[በ]3 ግሪኩ *ዮሴስ* ይላል

ቹስ እዚሁ እኛው ዘንድ አይደሉምን?” ከዚ
ህም የተነሣ ተሰናከሉበት።
4ኢየሱስም፣ “ነቢይ የማይከበረው በገዛ
አገሩ፣ በዘመዶቹ መካከልና በቤተ ሰቡ ዘንድ
ብቻ ነው” አላቸው። 5እዚያም በጥቂት ሕመ
ምተኞች ላይ እጁን ጭኖ ከመፈወሱ በስተ
ቀር ምንም ታምራት ሊሠራ አልቻለም፤ 6ባለ
ማመናቸውም ተደነቀ።

## ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ላከ

6፥7-11ተጓ ምብ - ማቴ 10፥1፡9-14፤ ሉቃ9፥1፡3-5

ከዚያም ኢየሱስ በየመንደሩ እየተዘዋወረ
ያስተምር ነበር። 7ዐሥራ ሁለቱን ወደ እርሱ
ጠርቶ፣ ሁለት ሁለቱን ላካቸው፤ በርኵሳን[+]
መናፍስትም ላይ ሥልጣን ሰጣቸው።
8ይህንንም ትእዛዝ ሰጣቸው፤ “ለመንገ
ዳችሁ ከበትር በስተቀር፣ እንጀራ ወይም
ከረጢት ወይም ደግሞ ገንዘብ በመቀነታ
ችሁ አትያዙ፤ 9ጫማ አድርጉ፤ ነገር ግን
ሁለት እጀ ጠባብ አትልበሱ፤ 10ወደ
አንድ ቤት በምትገቡበት ጊዜ ከዚያች ከተ
ማ እስ ክትወጡ ድረስ እዚያው ቈዩ፤
11የትኛውም ቦታ የማይቀበላችሁ ወይም የ
ማይሰማችሁ ከሆነ፣ ከዚያ ስፍራ ስትወጡ
ምስክር እንዲሆንባቸው ከእግራችሁ ሥር
ያለውን ትቢያ በዚያ አራግፉ።”
12እነርሱም ከዚያ ወጥተው፤ ሰዎች ንስሓ
እንዲገቡ ሰበኩ፤ 13ብዙ አጋንንት አስ
ወጡ፤ ብዙ ሕመምተኞችንም ዘይት
እየቀቡ ፈወሱ።

## የመጥምቁ ዮሐንስ መሰየፍ

6፥14-29 ተጓ ምብ - ማቴ14፥1-12
6፥14-16 ተጓ ምብ - ሉቃ9፥7-9

14የኢየሱስ ስም እየታወቀ በመምጣቱ፣
ንጉሥ ሄሮድስ ይህንኑ ሰማ። አንዳንዶችም፣
“የዚህ ዐይነት ታምር በእርሱ የሚሠራው
መጥምቁ ዮሐንስ ከሙታን ቢነሣ ነው” ይሉ
ነበር[‡]። 15ሌሎቹም፣ “ኤልያስ ነው” አሉ።
አንዳንዶች ደግሞ፣ “ከቀደምት ነቢያት እንደ
አንዱ ነቢይ ነው” ይሉ ነበር።
16ሄሮድስ ነገሩን ሲሰማ ግን፣ “እኔ ራሱን
ያስቈረጥሁት ዮሐንስ ከሙታን ተነሥቶአል
አለ።
17ሄሮድስ ራሱ የወንድሙን የፊልጶስን
ሚስት ሄሮድያዳን በማግባቱ ምክንያት፣
ተይዞ እንዲታሰር ትእዛዝ በመስጠት ዮሐ
ንስን ወህኒ ቤት አስገብቶት ነበር 18ዮሐንስ
ሄሮድስን፣ “የወንድምህን ሚስት ታገባት
ዘንድ ሕግ ይከለክልሃል” ይለው ነበርና።
19ሄሮድያዳም በዚህ ቂም ይዛበት ሊታስገ
ድለው ፈለገች፤ ነገር ግን አልሆነላትም።
20ምክንያቱም ዮሐንስ ጻድቅና ቅዱስ ሰው
መሆኑን ሄሮድስ በማወቁ ይፈራውና ይጠ
ብቀው ነበር። ዮሐንስ የሚናገረውን ሲሰማ
ሄሮድስ ቢታወክም[^] በደስታ ያደምጠው
ነበር።
21በመጨረሻም አመቺ ቀን መጣ።
ሄሮድስ በተወለደበት ዕለት ለከፍተኛ ሹ
ማምቱ፣ ለጦር አዛዦቹና በገሊላ ለታወቁ
ታላላቅ ሰዎች ግብዣ አደረገ።
22የሄሮድያዳም ልጅ ገብታ በዘፈነች ጊዜ
ሄሮድስንና ተጋባዥ ቹን ደስ አሰኘቻቸው።
ንጉሡም ብላቴናዪቱ ቱን፣ “የምትፈልጊውን
ሁሉ ጠይቂኝ እሰጥ ሻለሁ” አላት።
23ደግሞም “እስከ መንግሥቴ እኩሌታ
ድረስ እንኳ ቢሆን፣ የምትጠይቂኝን ሁሉ
እሰጥሻለሁ” ሲል በመሓላ ቃል ገባላት።
24እርሷም ወጥታ እናቷን፣ “ምን ልለምነው?”
አለቻት።
እናቷም፣ “የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ” አለ
ቻት።
25ብላቴናዪቱም ወዲያው ፈጥና ወደ ንጉሡ
በመመለስ፣ “የመጥምቁ ዮሐንስን ራስ አሁን
በሳሕን እንድትሰጠኝ እፈልጋለሁ” አለችው።
26ንጉሡ በነገሩ እጅግ አዘነ፤
በተጋበዙት እንግዶች ፊት የመሐላ ቃሉን ለ
ማጠፍ አልፈ ለገም። 27ስለዚህ አንዱን
ወታደር በፍጥነት ልኮ፣ የዮሐንስን ራስ
ቈርጦ እንዲያመጣ አዘዘው፤ እርሱም ሄዶ
በወህኒ ቤቱ ውስጥ ራሱን ቈረጠ፤ 28በሳሕን
አምጥቶ ለብላቴናዪቱ ሰጣት፤ ብላቴናዪቱም
ለእናትዋ ሰጠች። 29የዮሐንስ ደቀ
መዛሙርትም ይህን እንደ ሰሙ መጡ፤
ሬሳውንም ወስደው ቀበሩት።

## ኢየሱስ አምስት ሺህ ሰዎች መገበ

6፥32-44 ተጓ ምብ - ማቴ 14፥13-21፤ ሉቃ9፥10-17፤ ዮሐ6፥5-13
6፥32-44 ተጓ ምብ - ማር8፥2-9

30ሐዋርያትም በኢየሱስ ዙሪያ ተሰብስበው
የሠሩትንና ያስተማሩትን ሁሉ ነገሩት። 31ብዙ
ሰዎች ይመጡና ይሄዱ ስለ ነበር ምግብ እንኳ
ለመብላት ጊዜ ስላልነበራቸው፣ “እስቲ
ብቻችሁን ከእኔ ጋር ወደ አንድ ገለልተኛ
ስፍራ እንሂድና ጥቂት ዕረፉ” አላቸው።
32ስለዚህ ብቻቸውን ወደ አንድ ገለልተኛ
ስፍራ በጀልባ ሄዱ። 33እነርሱም ሲሄዱ ብዙ
ሰዎች አይተው ዐወቋቸው፤ ከከተሞችም
ሁሉ በእግር እየሮጡ ቀድመዋቸው ደረሱ።
34ኢየሱስ ከጀልባዋ በሚወርድበት ጊዜ ብዙ
ሕዝብ ተሰብስቦ አየ፤ እረኛ እንደሌላቸው
በጎች ስለ ነበሩም አዘነላቸው፤ ብዙ ነገርም
ያስተምራቸው ጀመር።
35በዚህ ጊዜ ቀኑ እየመሸ በመሄዱ ደቀ
መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀርበው እንዲህ

6፥4 ሉቃ4፥24፤ ዮሐ4፥44
6፥5 ማር5፥23
6፥6 ማቴ9፥35፤ ማር1፥39፤ ሉቃ13፥22
6፥7 ዘዳ17፥6፤ ማቴ10፥1፤ ማር3፥13፤ሉቃ10፥1
6፥11 ማቴ10፥14
6፥12 ሉቃ9፥6
6፥13 ያዕ5፥14
6፥14 ማቴ3፥1
6፥15 ሚል4፥5፤ ማቴ16፥14፤21፥11፤ ማር8፥28
6፥17 ማቴ4፥12፤ 11፥2፤ሉቃ3፥19፡20
6፥18 ዘሌ18፥16፤20፥21
6፥20 ማቴ11፥9
6፥21 አስ1፥3፤ 2፥18፤ሉቃ3፥1
6፥23 አስ5፥3፡6፤ 7፥2
6፥30 ማቴ10፥2፤ ሉቃ9፥10፤17፥5፤ 22፥14፤24፥10፤ ሐሥ1፥2፡26
6፥31 ማር3፥20
6፥32 ቍ45፤ ማር4፥36
6፥34 ማቴ9፥36

[+]7 ወይም *ክፉ*
[‡]14 አንዳንድ ቅጆች *ይል ነበር* ይላሉ
[^]20 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *ብዙ ነገር ያደርግ* ነበር ይላሉ

አሉት፤ “ይህ ቦታ ምድረ በዳ ነው፤ ቀኑም
መሽቶአል፤ 36በአካባቢው ሰው ወዳለበት
መንደር ሄደው የሚበላ ነገር ገዝተው
እንዲመገቡ ሕዝቡን አሰናብታቸው።”

37እርሱ ግን መልሶ፣ “የሚበሉትን እናንተው
ስጧቸው” አላቸው።

እነርሱም፣ “ሄደን በሁለት መቶ ዲናር
እን ጀራ ገዝተን የሚበሉትን
እንስጣቸውን?” አሉት።

38እርሱም፣ “ስንት እንጀራ አላችሁ? እስቲ
ሄዳችሁ እዩ” አላቸው።

አይተውም፣ “አምስት እንጀራና ሁለት
ዓሣ” አሉት።

39ከዚያም፣ ሕዝቡን በለመለመ ሣር ላይ
በቡድን በቡድን እንዲያስቀምጡ አዘዛቸው።
40ሕዝቡም መቶ መቶና አምሳ አምሳ ሆነው
በቡድን በቡድን ተቀመጡ። 41እርሱም አም
ስቱን እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ይዞ ወደ
ሰማይ በማየት ባረከ፤ እንጀራውንም
ቈርሶ እንዲያቀርቡላቸው ለደቀ መዛሙርቱ
ሰጠ፤ ሁለቱንም ዓሣ ለሁሉም አካፈለ።
42ሁሉም በልተው ጠገቡ፤ 43ደቀ መዛሙርተ
-ም ከተበ ላው እንጀራና ዓሣ፣ ዐሥራ
ሁለት መሶብ ሙሉ ፍርፋሪ አነሡ።
44እንጀራውንም የበሉት አምስት ሺህ
ወንዶች ነበሩ።

## ኢየሱስ በባሕር ላይ በእግሩ ሄደ

6፥45-51 ተጓ ምብ ማቴ14፥22-32፤ ዮሐ6፥15-21
6፥53-56 ተጓ ምብ - ማቴ14፥34-36

45ወዲያውም እርሱ ሕዝቡን እያሰናበተ
ሳለ፣ ደቀ መዛሙርቱ በጀልባ ወደ ቤተ
ሳይዳ ቀድመውት እንዲሻገሩ አዘዛቸው፤
46ከዚያም ትቶአቸው ሊጸልይ ወደ ተራራ
ወጣ።

47በመሸም ጊዜ ጀልባዋ ባሕሩ መካከል
ነበረች፤ እርሱም ብቻውን በምድር ላይ ነበር።
48ነፋስ በርትቶባቸው ስለ ነበር፣ ደቀ
መዛሙ ርቱ ከመቅዘፊያው ጋር ሲታገሉ
አያቸው፤ በአራተኛውም ክፍለ ሌሊት ገደ
ማ፣ በባሕር ላይ እየሄደ ወደ እነርሱ
መጣ፤ በአጠገ ባቸውም ዐልፎ ሊሄድ
ነበር። 49ነገር ግን በባሕር ላይ ሲሄድ
ባዩት ጊዜ ምትሐት መስሎአቸው ጮኹ፤
50ሁሉም እርሱን ባዩት ጊዜ ደንግጠው
ነበርና።

እርሱም ወዲያውኑ አነጋገራቸውና፣ “አይዞ
አችሁ! እኔ ነኝ፤ አትፍሩ!” አላቸው። 51እር
ሱም በጀልባዋ ላይ ወጥቶ አብሮአቸው ሆነ፤
ነፋሱም ተወ፤ እነርሱም እጅግ ተደነቁ፤
52የእንጀራውን ታምር አላስተዋሉም ነበርና፤
ልባቸውም ደንድኖ ነበር።

53በተሻገሩም ጊዜ፣ ጌንሴሬጥ ደርሰው
ወረዱ፤ ጀልባዋንም እዚያው አቆሙ። 54ወዲ

6፥37 2ነገ4፥42ኛ44
6፥38 ማቴ15፥34፤
ማር8፥5
6፥41 ማቴ14፥19
6፥45 ቍ32፤
ማቴ11፥21
6፥46 ሉቃ3፥21
6፥49 ሉቃ24፥37
6፥50 ማቴ14፥27
6፥51 ቍ32፤
ማር4፥39
6፥52 ማር8፥17ኛ21
6፥53 ዮሐ6፥24፡25

6፥56 ማቴ9፥20
7፥2 ሐሥ10፥14፡
28፤11፥8፤
ሮሜ14፥14
7፥3 ቍ5፡8፡
9፡13፤ሉቃ11፥38
7፥4 ማቴ23፥25፤
ሉቃ11፥39
7፥5 ቍ3፤ገላ1፥14፤
ቈላ2፥8
7፥7 ኢሳ29፥13
7፥8 ቍ3
7፥9 ቍ3
7፥10 ዘፀ20፥12፤
21፥17፤ዘሌ20፥9፤
ዘዳ5፥16
7፥11 ማቴ23፥16፡ 18
7፥13 ቍ3፤
ዕብ4፥12

ያው እንደ ወረዱም፣ ሕዝቡ ኢየሱስን
ዐወቁት፤ 55ወደ አካባቢውም ሁሉ በመሮጥ
ሕመምተኞችን በዐልጋ ላይ እየተሸከሙ
እርሱ ወደሚገኝበት ስፍራ ሁሉ ያመጡ ነበር።
56በየደረሰበት መንደር ወይም ከተማ ወይም
ገጠር ሁሉ ሕመምተኞችን በየአደባባዩ እያ
ስቀመጡ የልብሱን ጫፍ እንኳ ለመንካት
ይለምኑት ነበር፤ የነኩትም ሁሉ ይድኑ
ነበር።

## ኢየሱስ የአይሁድን ውጫዊ ሥርዐት ተቃወመ

7፥1-23 ተጓ ምብ - ማቴ 15፥1-20

7 ከዚህ በኋላ ፈሪሳውያንና ከኢየሩሳሌም
የመጡ አንዳንድ ጸሐፍት በዙሪያው ተሰ
በሰቡ፤ 2ከደቀ መዛሙርቱም አንዳንዶቹ
ባልነጻ ማለት ባልታጠበ እጅ እንጀራ
ሲበሉ አዩ፤ 3ፈሪሳውያንና አይሁድ ሁሉ
የአባቶችን ወግ ለመጠበቅ ሲሉ፣ በሥርዐቱ
መሠረት እጃቸውን በጥንቃቄ ሳይታጠቡ
አይበሉም ነበርና። 4ከገበያ ሲመለሱም ታጥ
በው ራሳቸውን ካላነጹ በስተቀር አይበሉም
ነበር። እንዲሁም ዋንጫን፣ ማሰሮን፣ ሳሕ
ንና ዐልጋን[ነ] እንደ ማጠብ ያሉትን ሌሎችን
ወጎች ይጠብቁ ነበር።

5ፈሪሳውያንና ጸሐፍትም፣ “ደቀ መዛሙ
ርትህ እንደ አባቶች ወግ በመኖር ፈንታ ባል
ታጠበ እጃቸው ለምን እንጀራ ይበላሉ?”
ብለው ጠየቁት።

6እርሱም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “ኢሳይ
ያስ ስለ እናንተ፣ ስለ ግብዞች በትክክል
ተንብዮአል፤ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤

‘ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን
ከእኔ የራቀ ነው፤

7በከንቱ ያመልከኛል፤ ትምህርታቸውም
ሰው ሠራሽ ሥርዐት ብቻ ነው።’

8የእግዚአብሔርን ትእዝዛዝ ትታችሁ የሰዎ
ችን ወግና ሥርዐት ታጠብቃላችሁ።”

9ደግሞም፣ እንዲህ አላቸው፤ “የራሳች
ሁን ወግ ለመጠበቅ[ኘ] ስትሉ፣ የእግዚአብሔርን
ትእዛዝ የምትተውበት ዘዴ አላችሁ። 10ሙሴ፣
‘አባትህንና እናትህን አክብር፤ አባቱን ወይም
እናቱን የሚሳደብ ፈጽሞ ይሙት ብሎ ነበ
ርና፤ 11እናንተ ግን አንድ ሰው አባቱን
ወይም እናቱን፣ ‘ከእኔ ማግኘት የሚገባችሁን
ርዳታ ሁሉ ቍርባን ይኸውም መባ አድር
ጌአለሁ ቢላቸው፣ 12እናንተም ይህ ሰው
ለአባቱም ሆነ ለእናቱ ከዚህ በኋላ ምንም
ነገር እንዲያደርግ አትፈቅዱለትም። 13ስለዚህ
ለትውልድ በምታስተላልፉት ወግ የእግዚ
አብሔርን ቃል ትሽራላችሁ፤ ይህን የመሰ
ለም ብዙ ነገር ታደርጋላችሁ!”።

[ነ]4 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *የማእድ ዐልጋ* ይላሉ
[ኘ]9 አንዳንድ ቅጆች *ለማቆም* ይላሉ

14ደግሞም ኢየሱስ ሕዝቡን ወደ እርሱ
ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ “ስሙኝ፤ ሁላች
ሁም አስተውሉ፤ 15ከውጭ ወደ ውስጥ
ገብቶ ሰውን የሚያረክሰው አንዳች ነገር
የለም፤ ይልቁን ሰውን የሚያረክሰው ከራሱ
ወደ ውጭ የሚወጣው ነገር ነው፤ ሰሚ ጆሮ
ያለው ቢኖር ይስማ[ሀ]፡፡
17ሕዝቡን ትቶ ወደ ቤት ከገባ በኋላ ደቀ
መዛሙርቱ ስለ ምሳሌው ጠየቁት፡፡ 18እር
ሱም፣ “እናንተም ነገሩ አይገባችሁምን?
ከውጭ ወደ ሰው ገብቶ ሊያረክሰው
የሚችል አንዳች ነገር የለም፤ 19ወደ ልቡ
ሳይሆን ወደ ሆዱ ይገባል፤ ከዚያም
ከሰውነቱ ይወጣልና፡፡ ኢየሱስ ይህን በ
ማለቱ ምግብ ሁሉ ንጹሕ መሆኑን ገለጠ
፡፡
20ቀጥሎም፣ እንዲህ አለ፤ “ከሰው የሚወጣ
ያ ሰውን ያረክሰዋል፤ 21ከውስጥ፣ ከሰው ልብ
የሚወጡት ክፉ ሐሳብ፣ ምንዝር፣ ስርቆት፤
ሰው መግደል፣ ዝሙት፣ 22መስገብገብ፣ ክፋት፣
ማታለል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስም
ማጥፋት፣ ትዕቢት፣ ስንፍና ናቸው፡፡ 23እነዚህ
ክፉ ነገሮች ሁሉ ከሰው ይወጣሉ ሰውንም
ያረክሱታል፡፡”

## ሲሮፊኒቃዊቷ ሴት

7፥24-30 ተጓ ምብ - ማቴ 15፥21-28

24ከዚያ ተነሥቶ ወደ ጢሮስ[ለ] አገር ሄደ፤
ወደ አንድ ቤት ገብቶ እዚያ መኖሩን
ማንም እንዳያውቅበት ፈለገ፤ ሆኖም እዚያ
መኖሩ ሊሸሸግ አልቻለም፡፡ 25ወዲያው ግን
ትንሺቱ ልጇ በርኩስ[ሐ] መንፈስ የተያዘችባት
አንዲት ሴት ስለ እርሱ ሰምታ መጣችና
በእግሩ ላይ ወደቀች፡፡ 26ሴትየዋም ግሪካዊት፣
በትውልዷም ሲሮፊኒቃዊት ነበረች፡፡ እርሷም
ኢየሱስ ርኩስ መንፈሱን ከልጇ እንዲያስወ
ጣላት ለመነችው፡፡
27እርሱ ግን፣ “የልጆችን እንጀራ ወስዶ
ለውሾች መጣል ተገቢ ስላልሆነ፣
መጀመሪያ ልጆቹ ጠግበው ይብሉ”
አላት፡፡
28እርሷም መልሳ፣ “አዎን፣ ጌታ ሆይ፤
ውሾችም ከገበታ በታች ሆነው የልጆችን
ትራፊ ይበላሉ አለችው፡፡
29እርሱም፣ “ስለዚህ ይህን ስላልሽ ሂጂ፤
ጋኔኑ ከልጅሽ ወጥቶአል” አላት፡፡
30እርሷም ወደ ቤቷ ስትመለስ ልጇ ዐልጋ
ላይ ተኝታ፣ ጋኔኑም ለቆአት አገኘቻት፡፡

## የደንቈሮውና የድዳው መፈወስ

7፥31-37 ተጓ ምብ - ማቴ 15፥29-31

31ከዚያም ኢየሱስ ከጢሮስ አገር ተነሥቶ፣
በሲዶና በኩል አድርጎ ዐሥር ከተማ[መ] በተ
ባለው አገር በማለፍ ወደ ገሊላ ባሕር
መጣ፡፡ 32በዚያም ሰዎች ደንቈሮና ዲዳ
የሆነ አንድ ሰው ወደ እርሱ አመጡ፤ እ
ጁንም እንዲጭንበት ለመኑት፡፡
33ኢየሱስም ሰውየውን ከሕዝቡ ለይቶ
ከወሰደው በኋላ፣ ጣቶቹን በጆሮው አስገባ፤
ከዚያም እንትፍ ብሎ የሰውየውን ምላስ
ዳሰሰ፡፡ 34ወደ ሰማይም ተመልክቶ ቃተ
ተና፣ “ኤፍታህ!” አለው፤ ይኸውም፣ “ተከ
ፈት” ማለት ነው፡፡ 35ወዲያውም ጆሮዎቹ
ተከፈቱ፤ ምላሱም ተፈቶ አጥርቶ መናገር
ጀመረ፡፡
36ኢየሱስ ይህን ለማንም እንዳይናገሩ አዘ
ዛቸው፤ ሆኖም እርሱ እንዳይናገሩ ባዘዛቸው
መጠን፣ ነገሩን አስፍተው አወሩት፡፡ 37ሕዝ
ቡም ከመጠን በላይ በመደነቅ፣ “ያደረገው ሁሉ
ጥሩ ነው፤ ደንቈሮዎች እንዲሰሙ፣ ድዳዎች
እንዲናገሩ እንኳ አድርጎአል” አሉ፡፡

## ኢየሱስ አራት ሺህ ሰዎች መገበ

8፥1-9 ተጓ ምብ - ማቴ 15፥32-39
8፥1-9 ማመ - ማር6፥32-44
8፥11-21 ተጓ ምብ - ማቴ 16፥1-12

8 በዚያን ጊዜ፣ እንደ ገና ብዙ ሕዝብ
ተሰበሰበ፡፡ የሚበሉት ምንም ምግብ
ስላልነበራቸው ደቀ መዛሙርቱን ወደ እርሱ
ጠርቶ፣ እንዲህ አላቸው፤ 2ከእኔ ጋር
ሦስት ቀን ስለቈዩና የሚበሉትም ስለሌላ
ቸው እነዚህ ሰዎች ያሳዝኑኛል፤ 3እንዲህ
እንደ ተራቡ ወደ ቤታቸው ብሰዳቸው አንዳ
ንዶቹ ከሩቅ የመጡ ስለ ሆኑ በመንገድ ላይ
ዝለው ይወድቃሉ፡፡”
4ደቀ መዛሙርቱም መልሰው፣ “በዚህ
ምድረ በዳ እነዚህን ለመመገብ የሚያስችል
እንጀራ ከወዴት ይገኛል?” አሉት፡፡
5እርሱም፣ “ስንት እንጀራ አላችሁ?” ብሎ
ጠየቃቸው፡፡
እነርሱም፣ “ሰባት” አሉት፡፡
6እርሱም፣ መሬት ላይ እንዲቀመጡ ሕዝ
ቡን አዘዘ፤ ሰባቱን እንጀራ ይዞ ካመሰገነ
በኋላ ቈርሶ ለሰዎቹ እንዲያድሉ ለደቀ መዛ
ሙርቱ ሰጣቸው፤ እነርሱም ለሕዝቡ አደ
ሉት፡፡ 7እንዲሁም ትንንሽ ዓሣዎች ነበሯ
ቸው፤ እርሱም ዓሣዎቹን ባርኮ እንዲያደ
ሏቸው አዘዘ፡፡ 8ሕዝቡም በልተው ጠገቡ፤ ከዚ
ያም ደቀ መዛሙርቱ የተረፈውን ቍርስራሽ
ሰባት መሶብ ሙሉ አነሡ፡፡ 9በዚያም አራት
ሺህ ያህል ሰዎች ነበሩ፤ ካሰናበታቸውም
በኋላ፣ 10ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ዳልማኑታ
ወደ ተባለ ስፍራ ሄደ፡፡
11ፈሪሳውያንም ወጥተው ከኢየሱስ ጋር
ይከራከሩ ጀመር፡፡ ሊፈትኑትም ፈልገው
ከሰ

7፥17 ማር9፥28
7፥19 ሐሥ10፥15፤ ሮሜ14፥1ኛ2፤ ቈላ2፥16፤ 1ጢሞ4፥3ኛ5
7፥22 ማቴ20፥15
7፥24 ማቴ11፥21
7፥25 ማቴ4፥24
7፥31 ቍ24፤ ማቴ4፥18፡25፤ 11፥21፤ማር5፥20
7፥32 ማቴ9፥32፤ ማር5፥23፤ ሉቃ11፥14
7፥33 ማር8፥23
7፥34 ማር6፥41፤ 8፥12፤ዮሐ11፥41
7፥35 ኢሳ35፥5፡6
7፥36 ማቴ8፥4
8፥2 ማቴ9፥36
8፥7 ማቴ14፥19
8፥8 ቍ20
8፥11 ማቴ12፥38

[ሀ]15 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ሰሚ *ጆሮ ያለው ቢኖር፣ ይስማ* የሚለው የላቸውም፡፡
[ለ]24 አያሌ የጥንት ቅጆች *ጢሮስና ሲዳና* የሚለው አላቸው
[ሐ]25 ወይም *ክፉ*
[መ]31 የግሪኩ *ዴካፖሊስ* ይለዋል

ማይ ምልክት እንዲያሳያቸው ጠየቁት።
12እርሱም በመንፈሱ እጅግ በመቃተት፣ "ይህ
ትውልድ ምልክት የሚፈልገው ለምንድን
ነው? እውነት እላችኋለሁ፤ ለዚህ ትውልድ
ምንም ምልክት አይሰጠውም!" አለ። 13ከዚ
ያም ትቶአቸው በጀልባ ወደ ማዶ ተሻገረ።

## የፈሪሳውያንና የሄሮድስ እርሾ

14ደቀ መዛሙርቱ እንጀራ መያዝ ስለ
ረሱ፣ ከአንድ እንጀራ በቀር በጀልባ
ውስጥ ምንም አልነበራቸውም። 15ኢየሱስም፣
"ተጠንቀቁ፤ ከፈሪሳውያንና ከሄሮድስ እርሾ
ተጠበቁ" ብሎ አዘዛቸው።
16እነርሱም እርስ በርሳቸው፣ "እንዲህ
የሚለን እኮ እንጀራ ስለሌለን ነው" ተባባሉ።
17ኢየሱስም ሐሳባቸውን ዐውቆ፣ እንዲህ
አላቸው፤ "እንጀራ ስለሌለን ነው በማለት
ምን ያነጋግራችኋል? አሁንም አታስተው
ሉምን? ልብስ አትሉምን? ወይስ ልባችሁ
ደንድኖአል? 18ዐይን እያላችሁ አታዩምን?
ጆሮ እያላችሁ አትሰሙምን? አታስታው
ሱምን? 19አምስቱን እንጀራ ለአምስት ሺህ
ሰው በቈረስሁ ጊዜ ስንት መሶብ ሙሉ
ትርፍራፊ አነሣችሁ?"
እነርሱም፣ "ዐሥራ ሁለት" አሉት።
20"ሰባቱን እንጀራ ለአራት ሺህ በቈረስሁ
ጊዜ ስንት መሶብ ሙሉ ትርፍራፊ አነሣ
ችሁ?" አላቸው።
እነርሱም፣ "ሰባት" አሉት።
21እርሱም፣ "እስከ አሁን አላስተዋላችሁም
ማለት ነውን" አላቸው።

## በቤተ ሳይዳ የተፈወሰው ዐይነ ስውር

22ከዚያም ወደ ቤተ ሳይዳ መጡ፤ ጥቂት
ሰዎችም አንድ ዐይነ ስውር ወደ ኢየሱስ
አምጥተው እንዲዳስሰው ለመኑት። 23እርሱም
የዐይነ ስውሩን እጅ ይዞ ከሰፈር ውጭ
አወጣው፤ በዐይኖቹም ላይ እንትፍ ብሎበት፣
እጁንም በላዩ ጭኖ፣ "ምን የሚታይህ ነገር
አለ?" ሲል ጠየቀው።
24እርሱም ቀና ብሎ አይቶ፣ "ሰዎች እንደ
ዛፍ ሲንቀሳቀሱ አያለሁ" አለ።
25ኢየሱስም እንደ ገና እጆቹን በሰውየው
ዐይኖች ላይ ጫነ፤ በዚህ ጊዜ ዐይኖቹ በሩ፤
ብርሃኑም ተመለሰለት፤ ሁሉንም ነገር አጥርቶ
ማየት ቻለ። 26ከዚያም፣ "ወደ መንደሩ አት
ግባ! በመንደሩም ለማንም አትናገር[0]" ብሎ
ወደ ቤቱ ሰደደው።

## ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ የነበረው ግንዛቤ

8÷27-29 ተጓ ምብ - ማቴ 16÷13-16፤ ሉቃ9÷18-20

27ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ፊል
ጶስ ቂሳርያ መንደሮች ሄደ፤ በመንገድ ላይ

8÷12 ማር7÷34
8÷15 ማቴ14÷1፤ ማር12÷13፤ሉቃ12÷1፤1ቆሮ5÷6ኛ8
8÷17 ኢሳ6÷9፡10፤ ማር6÷52
8÷19 ማቴ14÷20፤ ማር6÷41ኛ44፤ ሉቃ9÷17፤ዮሐ6÷13
8÷20 ቊ6ኛ9፤ ማቴ15÷37
8÷21 ማር6÷52
8÷22 ማቴ11÷21፤ ማር10÷46፤ዮሐ9÷1
8÷23 ማር5÷23፤ 7÷33
8÷28 ማቴ3÷1፤ ሚል4÷5
8÷29 ዮሐ6÷69፤ 11÷27
8÷30 ማቴ8÷4፤ 16÷20፤17÷9፤ ማር9÷9፤ሉቃ9÷21
8÷31 ማቴ8÷20፤ 16÷21፤ማቴ27÷1፡ 2፤ሐሥ2÷23፤3÷13
8÷32 ዮሐ18÷20
8÷33 ማቴ4÷10
8÷34 ማቴ10÷38፤ ሉቃ14÷27
8÷35 ዮሐ12÷25
8÷38 ማቴ8÷20፤ 10÷33፤ሉቃ12÷9፤1ተሰ2÷19
9÷1 ማቴ24÷30፤ 25÷31፤ማር13÷30፤ ሉቃ22÷18
9÷2 ማቴ4÷21

ሳሉም ደቀ መዛሙርቱን፣ "ሰዎች እኔን ማን
ይሉኛል?" ብሎ ጠየቃቸው።
28እነርሱም፣ "መጥምቁ ዮሐንስ የሚሉህ
አሉ፤ ሌሎች ኤልያስ ነው ይሉሃል፤ ሌሎች
ደግሞ ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ" ብለው
ነገሩት።
29ቀጥሎም፣ "እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ?"
ሲል ጠየቃቸው።
ጴጥሮስም፤ "አንተ ክርስቶስ["] ነህ" አለው።
30ኢየሱስም ስለ እርሱ ለማንም እንዳይ
ናገሩ አስጠነቀቃቸው።

## ኢየሱስ ስለ ሞቱ አስቀድሞ ተናገረ

8÷31-9÷1 ተጓ ምብ - ማቴ16÷21-28፤ ሉቃ9÷22-27

31ከዚያም የሰው ልጅ ብዙ መከራ እንደ
ሚቀበል፣ በሽማግሌዎች፣ በካህናት አለቆችና
በጸሐፍት እንደሚናቅ፤ እንደሚገደል፣ ከሦስት
ቀንም በኋላ እንደሚነሣ ያስተምራቸው ጀመር።
32እርሱም ይህን በግልጽ ነገራቸው። በዚህ ጊዜ
ጴጥሮስ ኢየሱስን ለብቻው ወስዶ ይገሥጸው
ጀመር።
33ኢየሱስ ግን ዘወር ብሎ ደቀ መዛሙ
ርቱን እያየ ጴጥሮስን፣ "አንተ ሰይጣን፣
ወደ ኋላዬ ሂድ! አንተ የሰውን እንጂ የእግዚ
አ ብሔርን ነገር አታስብምና" በማለት ገ
ሠጸው።
34ከዚህ በኋላ፣ ሕዝቡን ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤
"ሊከተለኝ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ፤
መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ፤ 35ነፍሱን
[‴] ለማዳን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል፤ ስለ
እኔና ስለ ወንጌል ነፍሱን የሚያጠፋት ሁሉ
ግን ያድናታል። 36ሰው ዓለሙ ሁሉ የእርሱ
ቢሆ ንና ነፍሱን ቢያጣ ምን ይጠ
ቅመዋል? 37ለመሆኑ፣ ሰው ለነፍሱ ምን
መተኪያ አለው? 38በዚህ ዘማዊና ኀጢአተኛ
ትውልድ መካ ከል በእኔና በቃሌ
የሚያፍር ሁሉ፣ የሰው ልጅም በአባቱ ግር
ማ፣ ከቅዱሳን መላእክት ጋር ሲመጣ
ያፍርበታል!።"

9 ቀጥሎም፣ "እውነት እላችኋለሁ፤ እዚህ
ከቆሙት መካከል የእግዚአብሔር መን
ግሥት በኀይል ስትመጣ እስክሚያዩ ድረስ
ሞትን የማይቀምሱ አንዳንዶች አሉ" አላ
ቸው።

## የኢየሱስ መልክ አበራ

9÷2-8 ተጓ ምብ - ሉቃ 9÷28-36
9÷2-13 ተጓ ምብ - ማቴ 17÷1-13

2ከስድስት ቀን በኋላ ኢየሱስ
ጴጥሮስን፣

[0]26 አንዳንድ ቅጆች *በመንደሩም፤ ለማንም አትናገር!* የሚለው የላቸውም።
["]29 በግሪኩ *ክርስቶስ*፣ በዕብራይስጡ *መሲሕ* የሚለው ቃል ትርጉም *የተቀባ* ማለት ነው
[‴]35 የግሪኩ ቃል *ሕይወት* ወይም *ነፍስ* ማለት ይሆናል።

ያዕቆብንና ዮሐንስን አስከትሎ ወደ አንድ
ረጅም ተራራ ይዞአቸው ወጣ፤ ብቻቸውንም
ነበሩ፤ በፊታቸውም ተለወጠ፤ 3ልብሱም
በም ድር ላይ ማንም አጣቢ አጥቦ ሊ
ያነጣው በማ ይችልበት ሁናቴ እጅግ ነጭ
ሆነ። 4ኤልያስና ሙሴም ከኢየሱስ ጋር ሲ
ነጋገሩ ታዩአቸው።
5ጴጥሮስም ኢየሱስን፣ “መምህር ሆይ፣
እዚህ ብንኖር ለእኛ መልካም ነው፤ አንድ
ለአንተ፣ አንድ ለሙሴ፣ አንድ ለኤልያስ
የሚሆኑ ሦስት ዳሶች እንሥራ” አለው።
6እጅግ ስለ ፈሩ የሚናገረውን አያውቅም
ነበር።
7ከዚያም ደመና መጥቶ ጋረዳቸው፤ ከደ
መናውም ውስጥ፣ “ይህ የምወደው ልጄ
ነው፤ እርሱን ስሙት!” የሚል ድምፅ መጣ።
8ወዲያውም ዙሪያቸውን ሲመለከቱ ከኢ
የሱስ በቀር ማንም አብሮአቸው አልነበረም።
9ከተራራው ላይ በሚወርዱበትም ጊዜ፣
የሰው ልጅ ከሙታን እስኪነሣ ድረስ ያዩትን
ለማንም እንዳይናገሩ አዘዛቸው። 10እነርሱም
የተናገራቸውን ቃል በልባቸው አሳደሩት፤
ነገር ግን፣ “ከሙታን መነሣት” ምን ማለት
እንደ ሆነ እርስ በርሳቸው ይነጋገሩ ነበር።
11ከዚያም፣ “ጸሐፍት አስቀድሞ መምጣት
ያለበት ኤልያስ ነው ለምን ይላሉ?” ሲሉ
ጠየቁት።
12ኢየሱስም፣ እንዲህ አላቸው፤ “ኤልያስ
በርግጥ አስቀድሞ መጥቶ ሁሉን ነገር እንደ
ነበረ ያደርጋል፤ ታዲያ፣ የሰው ልጅ ብዙ
መከራ መቀበልና መናቅ እንዳለበት የተጻፈው
ለምን ይመስላችኋል? 13ነገር ግን እላችኋ
ለሁ፤ ኤልያስማ መጥቶ ነበር፤ እነርሱም
ስለ እርሱ በተጻፈው መሠረት ያሻቸውን
ሁሉ አድርገውበታል።”

## ርኩስ መንፈስ ያለበት ልጅ ተፈወሰ

9፥14-28፤30፥32 ተጓ ምብ - ማቴ 17፥14-19፤ 22፡23፤
ሉቃ9፥37-45

14ወደ ቀሩት ደቀ መዛሙርት ተመልሰው
ሲመጡ፣ ብዙ ሕዝብ ከበዋቸው፣ ጸሐፍት
ከእነርሱ ጋር ሲከራከሩ አዩ። 15ሕዝቡ ሁሉ
ሲያዩት ወዲያው ተደንቀው እጅ ሊነሡት
ወደ እርሱ ሮጡ።
16እርሱም፣ “ከእነርሱ ጋር የምትከራከሩት
ስለምን ጉዳይ ነበር” ሲል ጠየቃቸው።
17ከሕዝቡ መካከል አንድ ሰው እንዲህ
አለው፤ “መምህር ሆይ፤ ርኩስ መንፈስ አድ
ሮበት ድዳ የሆነውን ልጄን ወደ አንተ አምጥ
ቼዋለሁ፤ 18በተነሣበት ጊዜ ሁሉ ይጥለዋል፤
አረፋ ይደፍቃል፤ ጥርሱንም ያፋጫል፤
ሰውነ ቱም ይደርቃል፤ ርኩስ መንፈሱን
እንዲያስወጡት ደቀ መዛሙርትህን ጠ
የቅኋቸው፤ እነርሱ ግን አልቻሉም።”

9፥3 ማቴ28፥3
9፥5 ማቴ23፥7
9፥7 ዘፀ24፥16፤
ማቴ3፥17
9፥9 ማቴ8፥20፡30
9፥12 ማቴ8፥20፤
16፥21፤ሉቃ23፥11
9፥13 ማቴ11፥14
9፥20 ማር1፥26
9፥23 ማቴ21፥21፤
ማር11፥23፤
ዮሐ11፥40
9፥25 ቆላ15
9፥28 ማር7፥17
9፥31 ቆላ12፤
ማቴ8፥20፤16፥21፤
ሐሥ2፥23፤3፥13
9፥32
ሉቃ2፥50፤9፥45፤
18፥34፤ዮሐ12፥16
9፥33 ማቴ4፥13፤
ማር1፥29
9፥34 ሉቃ22፥24

19ኢየሱስም መልሶ፣ “የማታምን ትውልድ
ሆይ፤ እስከ መቼ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ?
እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ? ልጁን ወደ እኔ
አምጡት!” አላቸው።
20ሰዎቹም ወደ እርሱ አመጡት፤ ርኩስ
መንፈሱም ኢየሱስን ባየው ጊዜ ልጁን
ወዲያውኑ አንዘፈዘፈው፤ እርሱም መሬት ላይ
ወድቆ በመንፈራገጥም አረፋ ይደፍቅ ጀመር።
21ኢየሱስም የልጁን አባት፣ “ከያዘው
ስንት ጊዜው ነው?” ብሎ ጠየቀው።
እርሱም እንዲህ አለው፤ “ከሕፃንነቱ
ጀምሮ ነው፤ 22ሊገድለው ፈልጎ ብዙ ጊዜ
እሳትም ውስጥ ውሃም ውስጥ፣ ይጥለዋል፤
የሚቻልህ ከሆነ ራራልን፤ ርዳንም።”
23ኢየሱስም፣ “የሚቻልህ ከሆነ አልህ?
ለሚያምን ሰው ሁሉም ነገር ይቻላል” አለው።
24ወዲያውኑ የልጁ አባት፣ “አምናለሁ፤
አለማመኔን ርዳው!” በማለት ጮኸ። 25ኢየ
ሱስም ሕዝቡ ወደዚያ እየተንጋጋ በሩጫ
መምጣቱን ባየ ጊዜ፣ “አንተ ደንቈሮና ድዳ
መንፈስ ከእርሱ ውጣ! ከእንግዲህም ተመል
ሰህ እንዳትገባበት አዝዛለሁ!” ብሎ ርኩሱን[የ]
መንፈስ ገሠጸው።
26ርኩሱም መንፈስ እየጮኸ ክፉኛ ካን
ፈራገጠው በኋላ ከልጁ ወጣ፤ ብዙዎቹ! “ሞቶ
አል” እስኪሉ ድረስ ልጁ እንደ በድን ሆነ።
27ኢየሱስ ግን እጁን ይዞ አስነሣው፤ ልጁም
ተነሥቶ ቆመ።
28ኢየሱስ ወደ ቤት ከገባ በኋላ ደቀ
መዛሙርቱ ለብቻቸው፣ “እኛ ልናስወጣው
ያልቻል ነው ለምንድን ነው?” ብለው ጠየ
ቁት።
29እርሱም፣ “የዚህ ዐይነቱ ሊወጣ የሚች
ለው በጸሎትና በጾም[ደ] ብቻ ነው” አላቸው።
30ከዚያም ተነሥተው በገሊላ በኩል አለፉ፤
ኢየሱስም ያሉበትን ስፍራ ማንም እንዲ
ያውቅ አልፈለገም፤ 31ለደቀ መዛሙርቱ፣
“የሰው ልጅ በሰዎች እጅ ዐልፎ ይሰጣል፤
እነርሱም ይገድሉታል፤ ከሦስት ቀንም በኋላ
ይነሣል” እያለ ያስተምራቸው ነበር። 32እነርሱ
ግን የሚላቸው አልገባቸውም፤ እንዳይጠይ
ቁትም ፈሩ።

## ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው?

9፥33-37 ተጓ ምብ - ማቴ 18፥1-5፤
ሉቃ 9፥46-48

33ከዚህ በኋላ ወደ ቅፍርናሆም መጡ።
ቤት ከገባ በኋላም፣ “በመንገድ ላይ የምትከ
ራከሩት ስለ ምን ነበር?” ብሎ ጠየቃቸው።
34እነርሱ ግን በመንገድ ላይ የተከራከሩት
ከሁሉ

[የ]25 ወይም *ክፉ*
[ደ]29 አንዳንድ ቅጆች *በጾም* የሚለው የላቸውም

የሚበልጥ ማን ነው በሚል ስለ ነበር ዝም
አሉ።
35 ከተቀመጠ በኋላ ዐሥራ ሁለቱን ጠርቶ፣
“መጀመሪያ ለመሆን የሚፈልግ፣ ከሁሉ
መጨረሻና የሁሉም አገልጋይ ይሁን” አላ
ቸው።
36 ትንሽ ልጅ አምጥቶም በመካከላቸው
አቆመ፤ አቅፎትም፣ 37 “ከእነዚህ ሕፃናት አንዱን
በስሜ የሚቀበል ሁሉ እኔን ይቀበላል፤ እኔ
ንም የሚቀበለኝ ሁሉ የሚቀበለው እኔን
ሳይሆን የላከኝን ነው” አላቸው።

## የማይቃወመን ሁሉ ከእኛ ጋር ነው

9፥38-40 ተጓ ምብ - ሉቃ 9፥49፡50

38 ዮሐንስም፣ “መምህር ሆይ፤ አንድ ሰው
በስምህ አጋንንት ሲያወጣ አየን፣ እኛን
ስለማይከተልም ከለከልነው” አለው።
39 ኢየሱስ ግን እንዲህ አለ፤ “አትከልክ
ሉት፤ ማንም በስሜ ታምር ሠርቶ ወዲያውኑ
በእኔ ላይ ክፉ መናገር አይችልም፤ 40 የማይ
ቃወመን ሁሉ ከእኛ ጋር ነውና፤ 41 እውነት
እላችኋለሁ፣ የክርስቶስ በመሆናችሁ በስሜ
አንድ ኩባያ ውሃ የሚሰጣችሁ ሁሉ ዋጋውን
አያጣም።”

## ለሌላው መሰናክል መሆን

42 “በእኔ ከሚያምኑት ከእነዚህ ከታናና
ሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ ከባድ የወ
ፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር
ቢጣል ይሻለዋል። 43 ስለዚህ እጅህ ብታሰና
ክልህ ቍረጣት፤ ሁለት እጅ ኖሮህ ወደ
ገሃነም ከመሄድ፣ ጕንድሽ ሆነህ ወደ ሕይ
ወት መግባት ይሻልሃል፤ 44 በገሃነም ትሉ
አይሞትም፤ እሳቱ አይጠፋምና[ጀ]። 45 እግርህ
ብታሰናክልህ ቍረጣት፤ ሁለት እግር ኖሮህ
ወደ ገሃነም ከመጣል፣ አንካሳ ሆነህ ወደ ሕይ
ወት መግባት ይሻልሃል፤ 46 በገሃነም ትሉ
አይሞትም እሳቱ አይጠፋምና[ጀ]። 47 ዐይንህ
ብታሰናክልህ ጐልጕለህ አውጣት፤ ሁለት
ዐይን ኖሮህ ወደ ገሃነም ከመጣል፣ አንድ
ዐይን ኖሮህ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት
መግባት ይሻልሃል፤

48 በገሃነም ትሉ አይሞትም፤
እሳቱ አይጠፋምና፤
49 ሰው ሁሉ በእሳት ይቀመማልና።
50 “ጨው መልካም ነው፤ ነገር ግን ጨው
ጨውነቱን ቢያጣ እንዴት መልሳችሁ ባዕም
እንዲኖረው ታደርጉታላችሁ? ጨው በውስጣችሁ
ይኑራችሁ፤ እርስ በርሳችሁም ተስማሙ።”

9፥35 ማቴ18፥4፤ ማር10፥43፤ ሉቃ22፥26
9፥36 ማር10፥16
9፥37 ማቴ10፥40
9፥38 ዘኍ11፥27፡29
9፥40 ማቴ12፥30፤ ሉቃ11፥23
9፥41 ማቴ10፥42
9፥42 ማቴ5፥29፤ 18፥6፤ሉቃ17፥2
9፥43 ማቴ5፥29፡30፤18፥8፤25፥41
9፥45 ማቴ5፥29፤ 18፥8
9፥47 ማቴ5፥29፤ 18፥9
9፥48 ኢሳ66፥24፤ ማቴ25፥41
9፥49 ዘሌ2፥13
9፥50 ማቴ5፥13፤ ሉቃ14፥34፡35፤ ሮሜ 12፥18፤ 2ቆሮ13፥11፤ ቈላ4፥6፤1ተሰ5፥13
10፥1 ማቴ4፥23፤ ማር1፥15፤2፥13፤ 4፥2፤6፥6፡34፤ ዮሐ10፥40፤11፥7
10፥2 ማር2፥16
10፥4 ዘዳ24፥1ኛ4፤ ማቴ5፥31
10፥5 መዝ95፥8፤ ዕብ3፥15
10፥6 ዘፍ1፥27፤ 5፥2
10፥8 ዘፍ2፥24፤ 1ቆሮ6፥16
10፥11 ሉቃ16፥18
10፥12 ሮሜ 7፥3፤1ቆሮ7፥10፡11
10፥14 ማቴ25፥34
10፥15 ማቴ18፥3
10፥16 ማር9፥36
10፥17 ማር1፥40፤ ሉቃ10፥25፤ ሐሥ20፥32

## የባልና የሚስት ፍች

10፥1-12 ተጓ ምብ - ማቴ19፥1-9

10 ኢየሱስ ከዚያ ተነሥቶ ወደ ይሁዳ
አገርና በዮርዳኖስ ማዶ ወዳለው
አካባቢ ሄደ፤ ሕዝቡም እንደ ገና በዙሪ
ያው ተሰበሰበ፤ ከዚህ ቀደም ያደርገው
እንደ ነበረውም አስተማራቸው።
2 አንዳንድ ፈሪሳውያንም መጥተው፣ “ሰው
ሚስቱን መፍታት ይገባዋልን?” ብለው ሊፈ
ትኑት ጠየቁት።
3 እርሱም መልሶ፣ “ሙሴ ምን ብሎ አዘዛ
ችሁ?” አላቸው።
4 እነርሱም፣ “ሙሴማ የፍች ወረቀት ጽፎ
እንዲፈታት ፈቅዶአል” አሉ።
5 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
“ሙሴ ይህን ሕግ የጻፈላችሁ ልባችሁ
ደንዳና በመ ሆኑ ነው። 6 ነገር ግን በፍጥረት
መጀመሪያ እግዚአብሔር ወንድና ሴት
አድርጎ ፈጠራቸው። 7 ስለዚህ ሰው አባቱንና
እናቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይጣመራ
ል[ገ]፤ 8 ሁለ ቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፤
ከእንግዲህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ሁለት
አይደሉም፤ 9 ስለዚህ እግዚአብሔር
ያጣመረውን ማንም አይለየው።”
10 እንደ ገና ወደ ቤት በገቡ ጊዜ፣ ደቀ
መዛሙርቱ ይህንኑ አንሥተው ጠየቁት።
11 እርሱም፣ “ማንም ሚስቱን ፈትቶ ሌላዪ
ቱን የሚያገባ በእርሷ ላይ ያመነዝራል፤ 12 እር
ሷም ባሏን ፈትታ ሌላ ብታገባ ታመነዝራ
ለች” አላቸው።

## ኢየሱስ ሕፃናትን ባረከ

10፥13-16 ተጓ ምብ - ማቴ 19፥13-15፤ ሉቃ18፥15-17

13 ኢየሱስ እንዲዳስሳቸው፣ ሰዎች ሕፃናትን
ወደ እርሱ አመጡ፤ ደቀ መዛሙርቱ ግን
ገሠጿቸው። 14 ኢየሱስም ይህን ሲያይ ተቈጥቶ
እንዲህ አላቸው፤ “ሕፃናት ወደ እኔ ይምጡ፤
አትከልክሏቸው፤ የእግዚአብሔር መንግሥት
እንደ እነዚህ ላሉት ናትና። 15 እውነት
እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት
እንደ ሕፃን የማይ ቀበል ሁሉ ከቶ አይጠ
ገባባትም። 16 ሕፃናቱ ንም ዐቀፋቸው፤ እ
ጁንም ጭኖ ባረካቸው።

## ሀብታሙ ወጣት

10፥17-31 ተጓ ምብ - ማቴ19፥16-30፤ ሉቃ18፥18-30

17 ከዚያ ተነሥቶ መንገዱን ሲጀምር፣ አንድ
ሰው ወደ እርሱ እየሮጠ መጣ፤ በፊቱም
በጕልበቱ ተንበርክኮ፣ “ቸር መምህር ሆይ፤
የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ ምን ማድረግ
ይገባኛል” አለው።
18 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ “ለምን

[ጀ] 44 እና 46 እነዚህ ጥቅሶች በአንዳንድ ቅጆች አይገኙም።
[ገ] 7 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *ከሚስቱ ጋር ይጣመራል* የሚለው የላቸውም።

ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በስ
ተቀር ቸር የለም፤ [19]ትእዛዛትን ታውቃለህ፤
አትግደል፤ አታመንዝር፤ አትስረቅ፤ በሐሰት
አትመስክር፤ አታታልል፤ አባትህንና እናትህን
አክብር።”
[20]ሰውየውም፣ “መምህር ሆይ፤ እነዚህን
ሁሉ ከልጅነቴ ጀምሮ ጠብቄአለሁ” አለው።
[21]ኢየሱስም ተመለከተውና ወደደው፤
“እንግዲያው አንድ ነገር ይጐድልሃል፤ ሂድና
ያለህን ሁሉ ሽጥ፤ ለድኾችም ስጥ፤ በሰማይ
የተከማቸ ሀብት ታገኛለህ፤ ከዚያ በኋላ ና፤
ተከተ ለኝም” አለው።
[22]ሰውየው ይህን ሲሰማ ክፉኛ አዘነ፤
ብዙ ሀብት ስለ ነበረውም እየተከዘ ሄደ።
[23]ኢየሱስ ዙሪያውን በመመልከት ደቀ
መዛሙርቱን፣ “ለሀብታሞች ወደ እግዚአብሐ
ር መንግሥት መግባት እንዴት ከባድ
ነገር ነው!” አላቸው።
[24]ደቀ መዛሙርቱም በንግግሩ ተገረሙ፤ ኢየ
ሱስ ግን እንደ ገና መልሶ እንዲህ አላቸው፤
“ልጆች ሆይ[ጣ]፤ ወደ እግዚአብሔር
መንግሥት መግባት እንዴት ከባድ ነገር
ነው! [25]ሀብታም ወደ እግዚአብሔር
መንግሥት ከሚገባ ይልቅ ግመል በመርፌ
ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀለዋል።”
[26]ደቀ መዛሙርቱም ይበልጥ በመገረም፣
“ታዲያ ማን ሊድን ይችላል?” ተባባሉ።
[27]ኢየሱስም አያቸውና፣ “ይህ በሰው ዘንድ
አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን እንዲ
ህ አይደለም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ
ይቻላል” አላቸው።
[28]ጴጥሮስም፣ “እነሆ እኛ ሁሉን ትተን
ተከተልንህ” አለው።
[29]ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ፤ “እውነት
እላችኋለሁ፤ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ሲል
ቤቱን ወይም ወንድሞቹን ወይም እኅቶቹን
ወይም እናቱን ወይም አባቱን ወይም ልጆቹን
ወይም ዕርሻውን የተወ ሁሉ፣ [30]አሁን በዚህ
ዘመን ከስደት ጋር ቤቶችን፣ ወንድሞችን፣
እኅቶችን፣ እናቶችን፣ ልጆችንና ዕርሻን መቶ
ዕጥፍ የማይቀበል፣ በሚመጣውም ዓለም
የዘላለም ሕይወት የማይወርስ የለም።
[31]ነገር ግን ብዙ ፊተኞች የሆኑ ኋለኞች፣
ኋለኞች የሆኑም ፊተኞች ይሆናሉ።

## ኢየሱስ ዳግም ስለ ሞቱ አስቀድሞ ተናገረ

10፥32-34 ተጓ ምብ - ማቴ 20፥17-19፤ ሉቃ 18፥31-33

[32]ወደ ኢየሩሳሌም ለመውጣት በመንገድ
ላይ ሳሉ፣ ኢየሱስ ፊት ፊታቸው ይሄድ ነበር፤
ደቀ መዛሙርቱ ተገረሙ፣ ሌሎች የተከተ
ሉት ደግሞ ፈርተው ነበር። ደግሞም ዐሥ
ራ ሁለቱን ከሕዝቡ ለይቶ ምን
እንደሚደርስበት ነገራቸው፤ [33]እንዲህም

10፥19 ዘጸ20፥12ኛ16፤ዘዳ5፥16ኛ20
10፥21 ማቴ4፥19፤ 6፥20፤ሉቃ12፥33፤ ሐሥ2፥45
10፥23 መዝ52፥7፤ 62፥10፤ማር4፥19፤ 1ጢሞ6፥9፡10፡17
10፥24 ማቴ7፥13፤ ዮሐ3፥5
10፥25 ሉቃ12፥16ኛ20፤16፥19ኛ31
10፥27 ማቴ19፥26
10፥28 ማቴ4፥19
10፥30 ማቴ6፥33፤ 12፥32፤25፥46
10፥31 ማቴ19፥30
10፥32 ማር3፥16ኛ19
10፥33 ማቴ8፥20፤ 27፥1፡2፤ሉቃ9፥51
10፥34 ማቴ16፥21፤ ሐሥ2፥23፤3፥13
10፥37 ማቴ19፥28
10፥38 ኢዩ38፥2፤ ማቴ20፥22፤ ሉቃ12፥50
10፥39 ሐሥ12፥2፤ ራእ1፥9
10፥43 ማር9፥35
10፥45 ማቴ20፥28
10፥47 ማቴ9፥27፤ ማር1፥24

አላቸው፤ “ወደ ኢየሩሳ ሌም እንወጣለን፤
የሰው ልጅ ለካህናት አለ ቆችና ለጸሐ
ፍት ዐልፎ ይሰጣል፤ እነርሱም የሞት ፍርድ
ይፈርዱበታል፤ አሳልፈው ለአሕዛብ ይሰጠ
ታል፤ [34]ያፌዙበታል፤ ይተፉበታል፣
ይገርፉታል፣ ከዚያም ይገድሉታል፤ እርሱ
ግን ከሦስት ቀን በኋላ ይነሣል።”

## የያዕቆብና የዮሐንስ ጥያቄ

10፥35-45 ተጓ ምብ - ማቴ 20፥20-28

[35]ከዚያም የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስ
ወደ እርሱ ቀርበው፣ “መምህር ሆይ፤ የምን
ለምንህን ሁሉ እንድታደርግልን እንፈልጋለን”
አሉት።
[36]እርሱም፣ “ምን እንዳደርግላችሁ ትፈል
ጋላችሁ?” አላቸው።
[37]እነርሱም፣ “በክብርህ ጊዜ አንዳችን በቀ
ኝህ፣ አንዳችን በግራህ እንድንቀመጥ ፍቀድ
ልን” አሉት።
[38]ኢየሱስም፣ “የምትለምኑትን አታውቁም፤
እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ፣ የምጠ
መቀ ውንስ ጥምቀት ልትጠመቁ
ትችላላችሁን?” አላቸው።
[39]እነርሱም፣“አዎን እንችላለን” አሉት።
ኢየሱስም፣ “እኔ የምጠጣውን ጽዋ ትጠጣላ
ችሁ፤ እኔ የምጠመቀውንም ጥምቀት ትጠ
መቃ ላችሁ፤ [40]ነገር ግን በቀኜ ወይም በግ
ራዬ መቀመጥ ለተዘጋጀላቸው የሚሆን
እንጂ እኔ የምሰጠው ነገር አይደለም”
አላቸው።
[41]ዐሥሩ ይህን ሲሰሙ፣ ያዕቆብንና ዮሐ
ንስን መቈጣት ጀመሩ። [42]ኢየሱስም በአ
ንድነት ሰብስቦ እንዲህ አላቸው፤ “የአሕ
ዛብ አለቆች ተብለው የሚታሰቡት እንደሚ
ገዟቸው፤ ሹሞቻቸውም በእነርሱ ላይ ሥልጣ
ናቸውን እንደሚያሳዩ ታውቃላችሁ፤
[43]በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ አይደለም፤
ከመካከላችሁ ታላቅ መሆን የሚፈልግ ሁሉ
አገልጋይ ይሁን፤ [44]ፊተኛ ለመሆን የሚፈልግ
ሁሉ፣ የሁሉ ባሪያ ይሁን፤ [45]የሰው ልጅ ሊ
ያገለግልና ሕይወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድ
ርጎ ሊሰጥ መጣ እንጂ ሊገለገል አልመጣ
ምና።”

## ኢየሱስ ዐይነ ስውሩን በርጤሜዎስን ፈወሰ

10፥46-52 ተጓ ምብ - ማቴ 20፥29-34፤ ሉቃ18፥35-43

[46]ከዚህ በኋላ ወደ ኢያሪኮ መጡ። ኢየሱስና
ደቀ መዛሙርቱ ከብዙ ሕዝብ ጋር ከኢ
ያሪኮ ሲወጡ ዐይነ ስውሩ የጤሜዎስ ልጅ
በርጤሜዎስ በመንገድ ዳር ተቀምጦ ይለምን
ነበር። [47]እርሱም የናዝሬቱ ኢየሱስ መሆኑን
በሰማ ጊዜ፣ “የዳዊት ልጅ፣ ኢየሱስ ሆይ፤
ማረኝ!” እያለ ይጮኽ ጀመር።

[ጣ]24 አንዳንድ ቅጆች *በሀብት ለሚታመኑ* የሚል ሐረግ አላቸው።

48ብዙዎችም ዝም እንዲል ገሠጹት፤ እርሱ
ግን፣ “የዳዊት ልጅ ሆይ፤ ማረኝ!” እያለ የባሰ
ጮኸ።
49ኢየሱስም ቆም ብሎ፣ “ጥሩት” አላቸው።
እነርሱም ዐይነ ስውሩን፣ “አይዞህ፤ ተነሥ፤
ይጠራሃል!” አሉት። 50እርሱም ልብሱን ጥሎ
ብድግ በማለት፣ ተነሥቶ ወደ ኢየሱስ መጣ።
51ኢየሱስም፣ “ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋ
ለህ?” አለው።
ዐይነ ስውሩም፣ “መምህር ሆይ፤ እንዳይ
እፈልጋለሁ” አለው።
52ኢየሱስም፣ “ሂድ፣ እምነትህ አድኖሃል”
አለው፤ ወዲያውም ዐይኑ በራለት፤ በመንገድም
ኢየሱስን ተከተሎት ሄደ።

## ኢየሱስ በታላቅ ክብር ወደ ኢየሩሳሌም ገባ

11፥1-10 ተጓ ምብ - ማቴ 21፥1-9፤
ሉቃ 19፥29-38
11፥7-10 ተጓ ምብ - ዮሐ 12፥12-15

11 ወደ ኢየሩሳሌም በደብረ ዘይት ተራራ
አጠገብ ወዳሉት ወደ ቤተ ፋጌና
ወደ ቢታንያ በቀረቡ ጊዜ፣ ኢየሱስ ከደቀ
መዛሙርቱ ሁለቱን እንዲህ በማለት ላካቸው፤
2“በፊታችሁ ወዳለው መንደር ሂዱ፣ ሰው
ተቀምጦበት የማያውቅ የአህያ ውርንጫ እዚያ
ታስሮ ታገኛላችሁ፤ ፈታችሁ አምጡት፤
3ማንም፣ ‘ምን ማድረጋችሁ ነው?’ ቢላችሁ፣
‘ለጌታ ያስፈልገዋል፤ በቶሎም መልሶ
ይልከዋል’ ብላችሁ ንገሩት።”
4እነርሱም ሄዱ፤ በአንድ ቤት በራፍ
እመንገድ ላይ የአህያ ውርንጫ ታስሮ አገ
ኙት፤ ፈቱትም። 5በዚያ ከቆሙት አንዳንድ
ሰዎች፣ “ውርንጫውን የምትፈቱት ለምንድን
ነው?” አሏቸው። 6ደቀ መዛሙርቱም ኢ
የሱስ ያላቸውን ለሰዎቹ በነገሯቸው ጊዜ
ፈቀዱ ላቸው። 7ውርንጫውንም ወደ ኢየሱስ
አም ጥተው ልብሳቸውን በጀርባው ላይ
አደረጉ፤ እርሱም ተቀመጠበት። 8ብዙ
ሰዎች ልበሳ ቸውን በመንገድ ላይ አነጠ
ፉ፤ ሌሎች ደግሞ ለምለም የዛፍ ቅርንጫፍ
እየቈረጡ ያነጥፉ ነበር። 9ከፊቱ
የቀደሙትና ከኋላው የተከተሉትም በታላቅ
ድምፅ፤ እንዲህ ይሉ ነበር፤
“ሆሣዕና![ጫ]
*በጌታ* ስም የሚመጣ የተባረከ ነው!
10የምትመጣው የአባታችን የዳዊት መንግሥት
የተባረከች ናት!
ሆሣዕና በአርአያም!”።
11ኢየሱስም ኢየሩሳሌም ደረሰ፤ ከዚያም ወደ
ቤተ መቅደስ ገባ፤ በዙሪያው ያለውንም ሁሉ
ተመለከተ፤ ቀኑም ስለመሸ ከዐሥራ ሁለቱ
ጋር ወደ ቢታንያ ወጣ።

10፥51 ማቴ23፥7
10፥52 ማቴ4፥19፤ 9፥22
11፥1 ማቴ21፥1፡ 17
11፥2 ዘኍ19፥2፤ ዘዳ21፥3፤1ሳሙ6፥7
11፥4 ማር14፥16
11፥9 መዝ118፥ 25፡26፤ማቴ23፥39
11፥10 ሉቃ2፥14
11፥11 ማቴ21፥ 12፡17
11፥13 ሉቃ13፥6ኛ9
11፥17 ኢሳ56፥7፤ ኤር7፥11
11፥18 ማቴ7፥28፤ 12፥12፤21፥46፤ ሉቃ20፥19
11፥19 ሉቃ21፥37
11፥21 ማቴ23፥7
11፥23 ማቴ21፥21
11፥24 ማቴ7፥7
11፥25 ማቴ6፥14

## ኢየሱስ ቤተ መቅደስን አጸዳ

11፥12-14 ተጓ ምብ- ማቴ21፥18-22
11፥15-18 ተጓ ምብ - ማቴ21፥12-16፤ ሉቃ19፥45-47፤
ዮሐ2፥13-16

12በማግሥቱ ከቢታንያ ሲወጡ ኢየሱስ
ተራበ።
13እርሱም ቅጠል ያላት የበለስ ዛፍ ከሩቅ
አየ፤ ምናልባት ፍሬ ይገኝባት እንደ ሆነ
ብሎ ወደ እርሷ መጣ፤ ነገር ግን የበለስ
ወራት አልነበረምና ከቅጠል በቀር ምንም
አላገኘባትም። 14ከዚያም ዛፏን፣ ‘ከአሁን ጀምሮ
ለዘላለም ማንም ፍሬ ከአንቺ አይብላ”
አላት። ደቀ መዛሙርቱም ይህን ሲናገር
ሰሙ።
15ወደ ኢየሩሳሌምም መጡ፤ ከዚያም ወደ
ቤተ መቅደስ ገብቶ፣ የሚሸጡትንና የሚገ
ዙትን ያስወጣ ጀመር። የገንዘብ መንዛሪዎችን
ጠረጴዛና የርግብ ሻጮችን መቀመጫ ገለባ
በጠ፤ 16ማንም ዕቃ ተሸክሞ በቤተ መቅደሱ
ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዳያልፍ ከለከለ።
17ሲያስተምራቸውም፣
“ ‘ቤቴ ለሕዝቦች ሁሉ የጸሎት ቤት
ይባላል’ ተብሎ አልተጻፈምን?
እናንተ ግን የሌቦች ዋሻ አደረጋችሁት!”
አላቸው።
18የካህናት አለቆችና ጸሐፍትም፣ ይህን
ሲሰሙ እንዴት እንደሚያጠፉት መንገድ
ይፈልጉ ጀመር፤ ሕዝቡ ሁሉ በትምህርቱ
በመገረማቸው ፈርተውታልና።
19በመሸም ጊዜ ከከተማዪቱ
ወጥተው ሄዱ[ጰ]።

## የበለሷ ዛፍ ደረቀች

11፥20-24 ተጓ ምብ - ማቴ 21፥19-22

20በማግስቱ ጠዋት በመንገድ ሲያልፉ፣
በለሲቱ ከነሥሯ ደርቃ አዩ። 21ጴጥሮስ
ነገሩ ትዝ አለውና ኢየሱስን፣ “መምህር
ሆይ፤ እነሆ፤ የረገምሃት በለስ ደርቃለች”
አለው። 22ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
“በእግዚአብሔር እመኑ[ጰ]፤ 23እውነት እላችኋለሁ፤
ማንም ይህን ተራራ፣ ‘ተነቅለህ ወደ ባሕር
ተወርወር’ ቢለውና ይህንንም በልቡ ሳይጠ
ራጠር ቢያምን ይሆንለታል። 24ስለዚህ
በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ እንደ ተቀበላ
ችሁት አድርጋችሁ ብታምኑ ይሆንላችኋል።
25እንዲሁም ለጸሎት በምትቆሙበት ጊዜ፣
የሰማዩ አባታችሁ ኀጢአታችሁን ይቅር እንዲ
ልላችሁ፣ እናንተም በሰው ላይ ያላችሁን
ሁሉ ይቅር በሉ። 26ይቅር ባትሉ ግን የሰማዩ

[ጫ]9 በዕብራይስጡ “አድን!” ማለት ሲሆን ምስጋናን የሚገልጽ አባባል ነው፤ እንዲሁም ቍ10 ይመ።
[ጰ]19 አንዳንድ ቅጆች *ወጥቶ ሄደ* ይላሉ።
[ጰ]22 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *በእግዚአብሔር ላይ እምነት ካላችሁ* ይላሉ።

አባታችሁ ኀጢአታችሁን ይቅር አይላች
ሁም[θ]።”

## በኢየሱስ ሥልጣን ላይ ጥያቄ ተነሣ

11፥27-33 ተጓ ምብ - ማቴ 21፥23-27፤ ሉቃ20፥1-8

27እንደ ገና ወደ ኢየሩሳሌም መጡ፤ ኢየ
ሱስ በቤተ መቅደሱ ቅጥር ግቢ ውስጥ
በሚዘዋወርበት ጊዜ፣ የካህናት አለቆች፣
ጸሐፍትና የሕዝብ ሽማግሌዎች ወደ እርሱ
ቀርበው፣ 28“እነዚህን ነገሮች የምታደርገው
በምን ሥልጣን ነው? እነዚህን እንድታደርግስ
ይህን ሥልጣን የሰጠህ ማን ነው” አሉት።
29ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
“እስቲ እኔም አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ፤
መልሱልኝ፤ እኔም እነዚህን ነገሮች በምን
ሥልጣን እንደማደርግ እነግራችኋለሁ።
30የዮሐንስ ጥምቀት ከሰማይ ነበረችን ወይስ
ከሰው? መልሱልኝ።”
31እነርሱም እርስ በርሳቸው እንዲህ
ተባባሉ፤ “ ‘ከሰማይ ነው’ ብንል፣ ‘ታዲያ
ለምን አላመና ችሁትም?’ ይለናል፤ 32‘ታዲ
ያ፣ ከሰው ነው’ እንበልን?” ሕዝቡ ሁሉ ዮሐ
ንስ እውነተኛ ነቢይ መሆኑን ያምኑ ስለ ነበር
ፈሩ።
33ስለዚህ ለኢየሱስ “አናውቅም” ብለው መለ
ሱለት።
ኢየሱስም፣ “እንግዲያው እኔም እነዚህን
ነገሮች በምን ሥልጣን እንደማደርግ አልነግ
ራችሁም” አላቸው።

## የወይን ስፍራ የተከራዩ ገበሬዎች ምሳሌ

12፥1-12 ተጓ ምብ - ማቴ 21፥33-46፤ ሉቃ20፥9-19

12 ከዚያም እንዲህ እያለ በምሳሌ
ይነግራቸው ጀመር፤ “አንድ ሰው
ወይን ተከለ፤ ዙሪያውን ዐጠረ፤ ለመጭመቂያው
ጒድጓድ ቈፈረ፤ የመጠበቂያም ማማ ሠራ
ለት፤ ከዚያም ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ
ሌላ አገር ሄደ። 2በመከር ጊዜም ከወይኑ
ፍሬ እንዲያመጣለት ከአገልጋዮቹ አንዱን
ወደ ገበሬዎቹ ላከ። 3እነርሱ ግን ይዘው
ደበደ ቡት፤ ባዶ እጁንም ሰደዱት። 4እንደ
ገናም ሌላ አገልጋይ ላከ። እነርሱም ራ
ሱን ፈንክተውና አዋርደው መለሱት”፤
5አሁንም እንደ ገና ሌላ ላከ፤ ይህኛውንም
ገደሉት፤ ከሌሎች ከብዙዎቹ መካከል
አንዳንዶቹን ደበደቡ፤ አንዳንዶቹንም
ገደሉ።
6“አሁንም የሚላክ ሌላ ነበረው፤ እርሱም
የሚወደው ልጁ ነበረ፤ “ልጄንስ ያከብሩታል”
በማለት ከሁሉ በኋላ ላከው።
7“ገበሬዎቹ ግን እርስ በርሳቸው፣ ‘ይህማ
ዋናው ወራሹ ነው፤ ኑ እንግደለው፤ ርስቱ
የእኛ ይሆናል’ ተባባሉ፤ 8ከዚያም ይዘው ገደ
ሉት፤ ከወይኑ ስፍራም አውጥተው ጣሉት።

11፥32 ማቴ11፥9
12፥1 ኢሳ5፥1ኛ7
12፥6 ዕብ1፥1ኛ3
12፥10 ሐሥ4፥11
12፥11 መዝ118፥22፡23
12፥12ማቴ22፥22፤ ማር11፥18
12፥13ማቴ12፥10፤ 22፥16፤ማር3፥6
12፥17 ሮሜ13፥7
12፥18 ሐሥ4፥1፤ 23፥8፤1ቆሮ15፥12
12፥19 ዘዳ25፥5

9“እንግዲህ የወይኑ አትክልት ባለቤት
ምን የሚያደርግ ይመስላችኋል? ይመጣል፤
ገበሬዎቹን ይገድላል፤ የወይኑንም አትክልት
ለሌሎች ይሰጣል። 10እንዲህ የሚለውን የመ
ጽሐፍ ቃል አላነበባችሁምን፤

“ ‘ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣
እርሱ የማእዘን ራስ[ፊ] ሆነ፤
11ጌታ ይህን አድርጎአል፣
ይህም ለዐይናችን ድንቅ ነው’?”

12ምሳሌውን የተናገረው ስለ እነርሱ መሆ
ኑን ስላወቁ፣ ሊይዙት ፈለጉ፤ ነገር ግን ሕዝ
ቡን ስለፈሩ ትተውት ሄዱ።

## ለቄሳር ግብር ስለ መክፈል

12፥13-17 ተጓ ምብ - ማቴ 22፥15-22፤ ሉቃ20፥20-26

13ከዚያም በነገር እንዲያጠምዱት ከፈሪሳ
ውያንና ከሄሮድስ ወገን ሰዎች ወደ እርሱ
ላኩ። 14እነርሱም መጥተው እንዲህ አሉት፤
“መምህር ሆይ፤ አንተ ትክክለኛ ሰው መሆ
ንህን እናውቃለን፤ የሰዎች ማንነት ስለማ
ይገድህም አታዳላም፤ የእግዚአብሔርን
መንገድ ብቻ በእውነት ታስተምራለህ፤
ለመሆኑ ለቄ ሳር ግብር መክፈል ይገባል
ወይስ አይገ ባም? 15እኛስ እንክፈል ወይስ
አንክፈል?”
ኢየሱስ ግን ግብዝነታቸውን ዐውቆ፣
“ለምን ልታጠምዱኝ ትፈልጋላችሁ? እስቲ
አንድ ዲናር አምጡልኝና ልየው” አላቸው።
16እነርሱም አመጡለት፣ “ይህ የማን መልክ
ነው? ጽሕፈቱስ የማን ነው?” አላቸው፤
እነርሱም፣ “የቄሳር ነው” አሉት።
17ኢየሱስም፣ “የቄሳርን ለቄሳር፣ የእግዚ
አብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ” አላቸው።
እነርሱም በእርሱ ተደነቁ።

## ጋብቻና ትንሣኤ

12፥18-27 ተጓ ምብ - ማቴ 22፥23-33፤ሉቃ20፥27-38

18ከዚህ በኋላ የሙታን ትንሣኤ የለም
የሚሉ ሰዱቃውያን ወደ እርሱ መጥተው እን
ዲህ ሲሉ ጠየቁት፤ 19“መምህር ሆይ፤
የአንድ ሰው ወንድም ሚስት አግብቶ ልጅ
ሳይወ ልድ ቢሞት፣ ይህ ሰው ሴትየዋን
አግብቶ ለወንድሙ ዘር እንዲተካ ሙሴ
ጽፎልናል። 20ታዲያ ሰባት ወንድማማቾች
ነበሩ፤ የመጀ መሪያው አግብቷት ዘር
ሳይተካ ሞተ፤ 21ሁለተኛውም ሴትየዋን አገባት፤
እርሱም ዘር ሳይተካ ሞተ፤ ሦስተኛውም
እንዲሁ፤ 22ሰባ ቱም አገቧት፤ ዘር ግን
አልተኩም፤ በመ ጨረሻም ሴትየዋ ሞተች።
23እንግዲህ፣ ሰባቱም አግብተዋታልና በትንሣኤ[T]
ለማናቸው ሚስት ልትሆን ነው?” አሉት።

[θ]26 አንዳንድ ቅጆች ቍ 26 የላቸውም።
[ፊ]10 ወይም *የማእዘን ድንጋይ*
[T]23 አንዳንድ ቅጆች *በትንሣኤ ሰዎች ከሙታን ሲነሡ የሚል* አላቸው

24ኢየሱስም፣ እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
“የምትስቱት እኮ ቅዱሳት መጻሕፍትንና
የእግዚአብሔርን ኀይል ስለማታውቁ ነው!
25ሙታን በሚነሡበት ጊዜ እንደ ሰማይ መላ
እክት ይሆናሉ እንጂ አያገቡም፤ አይጋቡም።
26ስለ ሙታን መነሣት ግን፣ በሙሴ መጽሐፍ
ይኸውም ስለ ቍጥቋጦው በተነገረው ክፍል፣
እግዚአብሔር ‘እኔ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐ
ቅ አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ ነኝ’ ያለውን
አላነበባችሁምን? 27እግዚአብሔር የሕያዋን
አምላክ እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም፤
ስለዚህ እጅግ ተሳስታችኋል።”

## ከሁሉ የሚበልጠው ትእዛዝ

12፥28-34 ተጓ ምብ - ማቴ 22፥34-40

28ከጸሐፍትም አንዱ መጥቶ ሲከራከሩ ሰማ
ቸው፤ ኢየሱስ ለቀረበለት ጥያቄ ተገቢውን
መልስ መስጠቱን አስተውሎ፣ “ለመሆኑ ከትእ
ዛዛት ሁሉ የሚበልጠው የትኛው ነው?” ሲ
ል
ጠየቀው።
29ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ “ከሁሉ
የሚበልጠው ይህ ነው፤ ‘እስራኤል ሆይ ስማ፤
ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፤ 30አንተም
ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም
ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህና በፍጹም ኀይልህ
ውደድ።’ 31ሁለተኛውም ይህ ነው፤ ‘ባልንጀ
ራህን እንደ ራስህ ውደድ።’ ከእነዚህም
የሚበልጥ ትእዛዝ የለም።”
32ጸሐፊውም እንዲህ አለው፤ “መምህር ሆይ፤
መልካም ብለሃል፤ እርሱ አንድ መሆኑን፣ ከእር
ሱም ሌላ አለመኖሩን መናገርህ ትክክል
ነው፤ 33እርሱን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም
አእምሮህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ኀይ
ልህ መውደድ፣ እንዲሁም ባልንጀራህን እንደ
ራስህ መውደድ ከሚቃጠል መሥዋዕት
ሁሉና ከሌሎችም መሥዋዕቶች ይበልጣል።”
34ኢየሱስም በማስተዋል እንደ
መለሰለት አይቶ፣ “አንተ ከእግዚአብሔር
መንግሥት የራቅህ አይደለህም” አለው።
ከዚህ በኋላ ሊጠይቀው የደፈረ ማንም
አልነበረም።

## ክርስቶስ የማን ልጅ ነው?

12፥35-37 ተጓ ምብ - ማቴ24፥41-46፤
ሉቃ 20፥41-44
12፥38-40 ተጓ ምብ - ማቴ23፥1-7፤
ሉቃ 20፥45-47

35ኢየሱስ በቤተ መቅደሱ አደባባይ በሚ
ያስተምርበት ጊዜ እንዲህ ሲል ጥያቄ አቀ
ረበ፤ “ጸሐፍት እንዴት ክርስቶስ የዳዊት
ልጅ ነው ይላሉ? 36ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ
ሲናገር፣
“ጌታ ጌታዬን፣ ‘ጠላቶችህን ከእግርህ

12፥24 2ጢሞ3፥15ኛ17
12፥25 1ቆሮ15፥42፡49፡52
12፥26 ዘፀ3፥6
12፥28 ሉቃ10፥25ኛ28፤20፥39
12፥30 ዘዳ6፥4፡5
12፥31 ዘሌ19፥18፤ማቴ5፥43
12፥32 ዘዳ4፥35፡39፤ኢሳ45፥6፡14፤46፥9
12፥33 1ሳሙ15፥22፤ሆሴ6፥6፤ሚክ6፥6ኛ8፤ዕብ10፥8
12፥34 ማቴ3፥2፤22፥46፤ሉቃ20፥24
12፥35 ማቴ9፥27፤26፥55
12፥36 2ሳሙ23፥2፤መዝ110፥1፤ማቴ22፥44
12፥37 ዮሐ12፥9
12፥39 ሉቃ11፥43
12፥41 2ነገ12፥9፤ዮሐ8፥20
12፥44 2ቆሮ8፥12
13፥2 ሉቃ19፥44
13፥3 ማቴ4፥21፤21፥1
13፥5 ቀኍ22፤ኤር29፥8፤ኤፌ5፥6፤2ተሰ2፥3፡10ኛ12፤1ጢሞ4፥1፤2ጢሞ3፥13፤1ዮሐ4፥6

በታች እስካደርጋቸው ድረስ በቀኜ ተቀመጥ’
አለው።” ይላል፤
37ታዲያ ዳዊት ራሱ ‘ጌታ’ ካለው፣ እን
ዴት ተመልሶ ልጁ ይሆናል?”።
ብዙ ሕዝብም በደስታ ይሰማው ነበር።
38በሚያስተምርበትም ጊዜ እንዲህ አለ፤
“ከጸሐፍት ተጠንቀቁ፤ የተንዘረፈፈ ቀሚስ
ለብሰው መዞርን ይወዳሉ፤ በየአደባባዩም
የአክብሮት ሰላምታ ይሻሉ፤ 39በምኵራብ
ከፍተኛውን ወንበር፣ በግብዣም ቦታ የከበ
ሬታን ስፍራ ይፈልጋሉ፤ 40በረጅም ጸሎታ
ቸው እያሳበቡ የመበለቶችን ቤት ያራቍታሉ፤
እነዚህ የባሰ ፍርድ ይቀበላሉ።”

## የመበለቲቱ ስጦታ

12፥41-44 ተጓ ምብ - ሉቃ21፥1-4

41ኢየሱስ በገንዘብ ማስቀመጫው አንጻር
ተቀምጦ ብዙ ሰዎች ስጦታቸውን ወደ
ቤተ መቅደሱ ገንዘብ ማስቀመጫ ሣጥን ሲያ
ስገቡ ይመለከት ነበር። ብዙ ሀብታሞች ብዙ
ገንዘብ አስገቡ፤ 42አንዲት ምስኪን መበለት ግን
ከአንድ ሳንቲም የማይበልጡ ሁለት የናስ
ቤሳዎች አስገባች።
43ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ፣
እንዲህ አላቸው፤ “እውነት እላችኋለሁ፤ ይህቺ
ድኻ መበለት ሣጥኑ ውስጥ ከጣሉት
ከሌሎቹ የበለጠ አስገባች። 44እነዚህ ሁሉ
ከተረፈው ሀብታቸው ሰጡ፤ እርሷ ግን
በድኽነት ዐቅሟ ያላትን ሁሉ አውጥታ
ለመኖሪያ የሚሆናትን እንዳለ ሰጠች።”

## የመጨረሻው ዘመን ምልክቶች

13፥1-37 ተጓ ምብ - ማቴ 24፥1-51፤ሉቃ21፥5-36

13 ከቤተ መቅደስ ሲወጣ ከደቀ መዛ
ሙርቱ አንዱ፣ “መምህር ሆይ፤
ድንጋዮቹ እንዴት እንደ ሆኑ፣ ሕንጻውም
እንዴት ውብ እንደ ሆነ እይ” አለው።
2ኢየሱስም መልሶ፣ “እነዚህን ታላላቅ ሕንጻ
ዎች ታያለህን? አንዱ ድንጋይ በሌላው ላይ
እንደ ሆነ አይቀርም፤ ሁሉም ፈራሽ ነው”
አለው።
3ኢየሱስ በቤተ መቅደሱ ትይዩ፣ በደ
ብረ ዘይት ተራራ ላይ ተቀምጦ ሳለ ጴጥ
ሮስ፣ ያዕቆብ፣ ዮሐንስና እንድርያስ እንዲህ
ሲሉ ጠየቁት፤ 4“ይህ መቼ እንደሚሆን ንገ
ረን፤ የዚህስ ሁሉ ፍጻሜ ምልክቱ ምንድን
ነው?”
5ኢየሱስም እንዲህ ይላቸው ጀመር፤
“ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፤ 6ብዙ
ዎች፣ ‘እኔ እርሱ ነኝ’ እያሉ በስሜ ይመ
ጣሉ፤ ብዙዎችንም ያስታሉ። 7ስለ ጦርነትና
ስለ ጦርነት ወሬ በምትሰሙበት ጊዜ አት
ደንግጡ፤ ይህማ መሆን አለበት፤ ፍጻሜው

ግን ገና ነው:: 8ሕዝብ በሕዝብ ላይ፣ መንግ
ሥት በመንግሥት ላይ ይነሣል፤ በብዙ ቦታም
የመሬት መንቀጥቀጥና ራብ ይሆናል፤ እነዚህ
ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው::
9"ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤ ለአካባቢ ሸንጎ
አሳልፈው ይሰጧችኋል፤ በምኵራብ ይገር
ፏችኋል፤ ምስክር ትሆኑም ዘንድ በእኔ
ምክንያት በገዦችና በነገሥታት ፊት ትቆማ
ላችሁ:: 10አስቀድሞ ግን ወንጌል ለሕዝብ
ሁሉ መሰበክ አለበት:: 11ተይዛችሁ ለፍርድ
በምትቀርቡበት ጊዜ፣ በዚያች ሰዓት የሚሰ
ጣችሁን ተናገሩ እንጂ ምን እንናገራለን በማ
ለት አስቀድማችሁ አትጨነቁ፤ የሚናገረው
መንፈስ ቅዱስ እንጂ እናንተ አይደላች
ሁምና::
12"ወንድም ወንድሙን፣ አባትም ልጁን
ለሞት አሳልፎ ይሰጣል፤ ልጆች በወላጆቻቸው
ላይ ያምፃሉ፤ ይገድሏቸዋልም:: 13በእኔ
ምክንያት በሰው ሁሉ ዘንድ የተጠላችሁ
ትሆናላችሁ፤ እስከ መጨረሻው የሚጸና
ግን ይድናል::
14"'የጥፋት ርኵሰት' ስፍራው ባልሆነ ቦታ
ቆሞ በምታዩት ጊዜ አንባቢው ያስተውል፤
በይሁዳ ያሉ ወደ ተራሮች ይሽሹ፤ 15በቤቱ
ጣራ ላይ ያለ አይውረድ፤ ንብረቱንም ለማው
ጣት ወደ ቤቱ አይግባ፤ 16በእርሻ ቦታ ያለ
ልብሱን ለመውሰድ አይመለስ:: 17በእነዚያ
ቀናት ለነፍሰ ጡሮችና ለሚያጠቡ ወዮላ
ቸው! 18ይህም በክረምት እንዳይሆን ጸልዩ፤
19በመጀመሪያ እግዚአብሔር ፍጥረትን ከፈጠ
ረበት ጊዜ አንሥቶ እስከ አሁን ድረስ፣
እንዲሁ ደግሞም ወደ ፊት አቻ የሌለው
ታላቅ መከራ ይሆናልና:: 20ጌታ ቀኖቹን
ባያሳጥራቸው ኖሮ ማንም ባልዳነ ነበር፤
ስለ መረጣቸው ስለ ምርጦቹ ሲል ግን
ቀኖቹን አሳጥሮአል:: 21በዚያን ጊዜ
ማንም፣ 'እነሆ፤ ክርስቶስ[ሀ] እዚህ ነው?'
ቢላችሁ ወይም፣ 'እነሆ፤ እዚያ ነው' ቢላችሁ
አትመኑ:: 22ሐሰተኛ ክርስቶሶችና ሐሰተኛ
ነቢያት ተነሥተው፣ ምልክቶችንና ድንቆችን
በማድረግ፣ ቢቻላቸው የተመረጡትን እንኳ
ያስታሉ:: 23ስለዚህ ተጠንቀቁ፤ ጊዜው
ሳይደርስ ሁሉን ነግሬአችኋለሁ::
24"በዚያን ጊዜ፣ ከመከራው በኋላ 'ፀሐይ
ትጨልማለች፣
ጨረቃም ብርሃኗን አትሰጥም፤
25ከዋክብት ከሰማይ ይረግፋሉ፤
የሰማይ ኀይላትም ይናወጣሉ::'
26"በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ በታላቅ ኀይ
ልና ግርማ በደመና ሲመጣ ያዩታል::
27እርሱም መላእክቱን ልኮ ከአራቱ ነፋሳት፣
ከምድር ዳርቻ እስከ ሰማያት ዳርቻ ምርጦ
ቹን ይሰበስባል::
28"ምሳሌውን ከበለስ ተማሩ፤ ቅርንጫፏ
ሲለመልም፣ ቅጠሏ ሲያቈጠቍጥ በጋ እንደ
ተቃረበ ታውቃላችሁ፤ 29እንዲሁ ደግሞ እነዚህ
ነገሮች መፈጸማቸውን ስታዩ እንደ ቀረበ፣
በደጅም እንደ ሆነ ዕወቁ:: 30እውነት እላች
ኋለሁ፣ እነዚህ ነገሮች እስከሚፈጸሙ
ድረስ ይህ ትውልድ[ለ] አያልፍም፤ 31ሰማይና
ምድር ያልፋሉ፤ ቃሌ ግን አያልፍም::

### ቀኑና ሰዓቱ አይታወቅም

32"ነገር ግን ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚ
ያችም ሰዓት ከአብ በቀር፣ የሰማይ መላእክ
ትም ቢሆኑ፣ ወልድም ቢሆን፣ ማንም አያው
ቅም:: 33ስለዚህ ጊዜው መቼ እንደሚሆን
አታውቁምና ተጠንቀቁ፤ ትጉ፣ ጸልዩም[ሐ]::
34ይህም ቤቱን ለአገልጋዮቹ ትቶ፣ እያንዳ
ንዱን አገልጋይ በየሥራ ድርሻው ላይ አሰ
ማርቶ፣ በረኛው ነቅቶ እንዲጠብቅ አዝዞ
የሄደውን ሰው ይመስላል:: 35እንግዲህ የቤቱ
ባለቤት በምሽት ወይም በውድቅት፣ በዶሮ
ጩኸት ወይም ጎሕ ሲቀድ እንደሚመጣ አታ
ውቁምና ተግታችሁ ጠብቁ፤ 36ድንገት ሲመጣ
ተኝታችሁ እንዳያገኛችሁ! 37ለእናንተ የም
ነግራችሁን ለሰው ሁሉ እናገራለሁ፤ ተግታ
ችሁ ጠብቁ!"

### ኢየሱስን ሽቶ የቀባችው ሴት

14፥1-11 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥2-16
14፥1፡2፡10፡11 ተጓ ምብ - ሉቃ22፥1-6
14፥3-8 ማመ - ዮሐ12፥1-8

14 ፋሲካና የቂጣ በዓል ሊከበር ሁለት
ቀን ሲቀረው፣ የካህናት አለቆችና
ጸሐፍት ኢየሱስን የሚይዙበትና የሚገድሉ
በትን ዘዴ ይፈልጉ ነበር:: 2ሆኖም፣ "ሕዝቡ
ዐመፅ እንዳያነሣ በበዓሉ ሰሞን መሆን የለ
በትም" ይባባሉ ነበር::
3እርሱም በቢታንያ በለምጻሙ ስምዖን
ቤት በማእድ ተቀምጦ ሳለ፣ አንዲት ሴት
ዋጋው እጅግ ውድ የሆነ ንጹሕ የናርዶስ
ሽቱ የተሞላበት የአልባስጥሮስ ቢልቃጥ ይዛ
መጣች፣ ቢልቃጡንም ሰብራ ሽቱውን በራሱ
ላይ አርከፈከፈችው::
4በዚያ ከነበሩት አንዳንዶቹ በድርጊቱ
ተቈጥተው እንዲህ ይባባሉ ነበር፤ "ሽቱው
ለምን በከንቱ ይባክናል? 5ከሦስት መቶ
ዲናር በላይ ተሽጦ፣ ገንዘቡን ለድኾች መስ
ጠት ይቻል ነበር::" ሴትየዋንም ነቀፏት::
6ኢየሱስ ግን እንዲህ አላቸው፤
"ተዉአት፣ ለምን ታስቸግሯታላችሁ?
መልካም ነገር አድርጋልኛለች:: 7ድኾች
ምን ጊዜም ከእና

13፥9 ማቴ10፥17
13፥11 ማቴ10፥19፡20፤ሉቃ12፥11፡12
13፥12 ሚክ7፥6፤ ማቴ10፥21፤ ሉቃ12፥51ኛ53
13፥13 ማቴ10፥22፤ ዮሐ15፥21
13፥14 ዳን9፥27፤ 11፥31፤12፥11
13፥17 ሉቃ23፥29
13፥19 ማር10፥6፤ ዳን9፥26፤12፥1፤ ኢል2፥2
13፥21 ሉቃ17፥23፤21፥8
13፥22 ማቴ7፥15፤ ዮሐ4፥48፤ 2ተሰ2፥9፡10
13፥23 2ጴጥ3፥17
13፥25 ኢሳ13፥10፤ 34፥4፤ማቴ24፥29
13፥26 ራእ1፥7
13፥27 ዘካ2፥6
13፥30 ማር9፥1፤ ሉቃ17፥25
13፥31 ማቴ 5፥18
13፥32 ሐሥ1፥7፤ 1ተሰ5፥1፡2
13፥33 1ተሰ5፥6
13፥34 ማቴ25፥14
13፥37 ሉቃ12፥35ኛ40
14፥1 ማቴ12፥14፤ ዮሐ11፥55
14፥3 ማቴ21፥17፤ ሉቃ7፥37ኛ39
14፥7 ዘዳ15፥11
14፥8 ዮሐ19፥40

[ሀ]21 ወይም መሲሑ [ለ]30 ወይም ዘር
[ሐ]33 ጸልዩ የሚለው ቃል በአንዳንድ ቅጆች አይገኝም::

ንተ ጋር ናቸው፤ በፈለጋችሁ ጊዜ ልትረዷቸው
ትችላላችሁ፤ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር
አልኖርም፤ 8እርሷ ማድረግ የምትችለውን
ያህል አድርጋለች፤ ለመቃብሬ እንዲሆን
ሰውነቴን አስቀድማ ቀብታለች። 9እውነት
እላችኋለሁ፤ ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ
በሚሰበክበት በማንኛውም ስፍራ እርሷ ያደ
ረገችው መታሰቢያ ሆኖ ይነገርላታል።”
10ከዚህ በኋላ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ የሆነው
የአስቆሮቱ ይሁዳ አሳልፎ ሊሰጠው ወደ
ካህናት አለቆች ሄደ። 11እነርሱም ይህን
ሲሰሙ ደስ አላቸው፤ ገንዘብ ሊሰጡትም ቃል
ገቡለት፤ ስለዚህ እርሱን አሳልፎ የሚሰ
ጥበትን ምቹ ጊዜ ይጠባበቅ ነበር።

### የጌታ እራት

14፥12-26 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥17-30፤ ሉቃ22፥7-23
14፥22-25 ተጓ ምብ - 1ቆሮ11፥23-25

12የፋሲካ በግ በሚታረድበት በቂጣ በዓል
የመጀመሪያው ቀን፣ ደቀ መዛሙርቱ ወደ
ኢየሱስ ቀርበው፣ “የፋሲካ እራት የት እንድ
ናዘጋጅልህ ትፈልጋለህ?” አሉት።
13እርሱም ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን እን
ዲህ ሲል ላካቸው፤ “ወደ ከተማ ሂዱ፤ እንስራ
ውሃ የተሸከመ ሰው ይገናኛችኋል፤ 14ወደሚገ
ባበት ቤትም ተከተሉት፤ የቤቱንም ጌታ፣
“ ‘መምህሩ፣ ከደቀ መዛሙርቴ ጋር የፋሲ
ካን
ራት የምበላበት የእንግዳ ማረፊያ የት
ኛው ነው?’ ” ብሎአል በሉት፤ 15እርሱም
በሰገነቱ ላይ የተሰናዳና የተነጠፈ ሰፊ አዳ
ራሽ ያሳያችኋል፤ እዚያ አዘጋጁልን።”
16ደቀ መዛሙርቱም ወጥተው ወደ ከተ
ማዪቱ ሄዱ፤ ማንኛውም ነገር ኢየሱስ
እንዳላቸው ሆኖ አገኙት፤ ፋሲካውንም አሰ
ናዱ።
17በመሸም ጊዜ ኢየሱስ ከዐሥራ ሁለቱ ጋር
መጣ። 18በማእድ ላይ ሳሉም፣ “እውነት እላች
ኋለሁ፣ ከመካከላችሁ አንዱ፣ አብሮኝ የሚበ
ላው እርሱ አሳልፎ ይሰጠኛል” አላቸው።
19እነርሱም አዘኑ፤ እያንዳንዳቸውም፣ “እኔ
እሆንን?” ይሉት ጀመር።
20እርሱም እንዲህ አላቸው፤ “ከዐሥራ ሁለቱ
አንዱ፣ ከእኔ ጋር እጁን በወጭቱ ውስጥ
የሚያጠልቀው ነው። 21የሰው ልጅስ ስለ
እርሱ እንደ ተጻፈው ይሄዳል፤ የሰውን
ልጅ አሳልፎ ለሚሰጥ ለዚያ ሰው ግን
ወዮለት፤ ያ ሰው ባይወለድ ይሻለው ነበር።”
22ሲበሉም እንጀራ አንሥቶ ባረከ፤ ቈርሶም
ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸውና፣ “እንኩ፤ ይህ
ሥጋዬ ነው” አላቸው፣
23ጽዋውንም አንሥቶ፤ አመስግኖም ሰጣቸው፤
ሁሉም ከዚያ ጠጡ።
24ደግሞም እንዲህ አላቸው፤ “ይህ ስለ
ብዙዎች የሚፈስ የአዲስ[ሠ] ኪዳን ደሜ ነው፤
25“እውነት እላችኋለሁ፤ በእግዚአብሔር መንግሥት
አዲሱን የወይን ፍሬ እስከምጠጣበት እስከዚ
ያች ቀን ድረስ ዳግም ይህን አልጠጣም።”
26ከዚህ በኋላ መዝሙር ዘምረው ወደ
ደብረ ዘይት ተራራ ወጡ።

### ጴጥሮስ እንደሚክደው ኢየሱስ አስቀድሞ ተናገረ

14፥27-31 ተጓ ምብ - ማቴ26፥31-35

27ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “እንዲህ ተብሎ
እንደተጻፈ፣ ሁላችሁ ትክዱኛላችሁ፤
‘እረኛውን እመታለሁ
በጎቹም ይበተናሉ’ ”
28ከተነሣሁ በኋላ ግን፣ ቀድሜአችሁ ወደ
ገሊላ እሄዳለሁ።”
29ጴጥሮስም፣ “ሁሉም ቢሰናከሉ እንኳ እኔ
አላደርገውም” አለ።
30ኢየሱስም፣ “እውነት እልሃለሁ፤ በዚ
ህች ሌሊት ዶሮ ሁለት[ሡ] ጊዜ ሳይጮኽ፣
ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ” አለው።
31ጴጥሮስም፣ “ከአንተ ጋር ብሞት እንኳ ከቶ
አልክድህም” በማለት ይበልጥ አጽንቶ ተና
ገረ። ሁሉም ደግሞ እንደዚሁ አሉ።

### ኢየሱስ በጌቴሴማኒ ጸለየ

14፥32-42 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥36-46፤ ሉቃ22፥40-46

32ከዚህ በኋላ ጌቴሴማኒ ወደሚባል ስፍራ
ሄዱ፤ ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን፣ “እኔ
ስጸልይ እናንተ እዚህ ቈዩ” አላቸው።
33ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስንም ይዞ ሄደ፤
እጅግ ያዝን ይጨነቅ ጀመር። 34ደግሞም፣
“ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች፤ እዚሁ
ሁኑና ነቅታችሁ ጠብቁ” አላቸው።
35ጥቂት ዕልፍ ብሎም በምድር ላይ በመ
ውደቅ ቢቻል ሰዓቱ ከእርሱ እንዲያልፍ
ጸለየና፣ 36“አባ[ሩ]፤ አባት ሆይ፤ ሁሉ ነገር
ይቻልሃልና ይህን ጽዋ ከእኔ አርቀው፤
ነገር ግን የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ
ይሁን” አለ።
37ተመልሶም ሲመጣ ደቀ መዛሙርቱን
ተኝተው አገኛቸው፤ ጴጥሮስንም እንዲህ
አለው፣ “ስምዖን ሆይ፣ ተኝተሃልን? አንድ
ሰዓት እንኳ ነቅተህ መጠበቅ አቃተህ?
38ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉ፤ ጸልዩም፤
መንፈስ ዝግጁ ነው፣ ሥጋ ግን ደካማ ነው።”
39እንደ ገናም ሄዶ መጀመሪያ የጸለየውን
ደግሞ ጸለየው። 40ዳግመኛም ሲመለስ ዐይና

14፥9 ማቴ24፥14፤ ማር16፥15
14፥10 ማቴ10፥4፤ ማር3፥16ኛ19
14፥12 ዘፀ12፥1ኛ11፤ ዘዳ16፥1ኛ4፤1ቆሮ5፥7
14፥15 ሐሥ1፥13
14፥20 ዮሐ13፥18ኛ27
14፥21 ማቴ8፥20
14፥22 ማቴ14፥19
14፥23 1ቆሮ10፥16
14፥24 ማቴ26፥28
14፥25 ማቴ3፥2
14፥26 ማቴ21፥1
14፥27 ዘካ13፥7
14፥28 ማር16፥7
14፥30 ቊ66ኛ72፤ ሉቃ22፥34፤ ዮሐ13፥38
14፥31 ሉቃ22፥33፤ ዮሐ13፥37
14፥33 ማቴ4፥21
14፥34 ዮሐ12፥27
14፥35 ቊ41፤ ማቴ26፥18
14፥36 ማቴ20፥22፤ 26፥39፤ሮሜ8፥15፤ ገላ4፥6
14፥38 ማቴ6፥13፤ ሮሜ7፥22፡23

ሠ24 አንዳንድ ቅጆች *አዲስ* የሚለው ቃል የላቸውም።
ሡ30 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *ሁለት ጊዜ* የሚለው ሐረግ የላቸውም።
ሩ36 በአራማይክ ቋንቋ አባት የሚጠራበት ነው።

ቸውን እንቅልፍ ከብዶት ተኝተው አገኛቸው፤
የሚመልሱለትንም አያውቁም ነበር።
41ሦስተኛ ጊዜም መጥቶ እንዲህ አላቸው፤
“አሁንም እንደተኛችሁና እንዳረፋችሁ ናችሁ?
ይበቃል! ሰዓቲቱ ደርሳለች፤ እነሆ፤ የሰው ልጅ
ለኀጢአተኞች እጅ አልፎ ይሰጣል። 42ተነሡ፤
እንሂድ፤ አሳልፎ የሚሰጠኝ መጥቶአል።”

## ኢየሱስ ተያዘ

14፥43-50 ተጓ ምብ - ማቴ26፥47-56፤ ሉቃ22፥47-50፤
ዮሐ18፥3-11

43ወዲያው እየተናገረ ሳለ ከዐሥራ ሁለቱ
አንዱ ይሁዳ መጣ፤ አብረውትም ሰይፍና
ዱላ የያዙ፣ ከካህናት አለቆች፣ ከጸሓፍትና
ከሽማግሌዎች የተላኩ ብዙ ሰዎች ነበሩ።
44አሳልፎ የሚሰጠውም፣ “እኔ የምስመው
እርሱ ነውና ያዙት፤ ተጠንቅቃችሁም ውሰ
ዱት” በማለት አስቀድሞ ምልክት
ሰጥቶአቸው ነበር። 45እንደ ደረሰም ወዲያው
ወደ ኢየሱስ ቀርቦ፣ “መምህር ሆይ!” ብሎ
ሳመው፤ 46ሰዎቹም ኢየሱስን ያዙት አሰሩ
ትም። 47በአቅ ራቢያው ቆመው ከነበሩት
አንዱ ሰይፉን መዞ የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ
ጆሮ ቈረጠ።
48ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “እንደ ወን
በዴ በሰይፍና በቈመጥ ልትይዙኝ መጣች
ሁን? 49በየዕለቱም በቤተ መቅደስ እያስተ
ማርሁ ከእንናተ ጋር ስኖር አልያዛችሁኝም፤
መጻሕፍት ይፈጸሙ ዘንድ ይህ ሆነ።” 50በዚህ
ጊዜ ሁሉም ትተውት ሸሹ።
51ዕርቃኑን ለመሸፈን በፍታ ያገለደመ አንድ
ወጣት ኢየሱስን ይከተል ነበር። ሰዎቹም ይህን
ወጣት በያዙት ጊዜ፣ 52ግልድሙን ጥሎ ዕራ
ቍቱን ሸሸ።

## ኢየሱስ በሸንጎ ፊት

14፥53-65 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥57-68፤ ዮሐ18፥12፡13፡19-24
14፥61-63 ተጓ ምብ - ሉቃ 22፥67-71

53ኢየሱስንም ወደ ሊቀ ካህናቱ ወሰዱት፤
በዚያም የካህናት አለቆች፣ ሽማግሌዎ
ችና ጸሓፍት ሁሉ ተሰበሰቡ። 54ጴጥሮስም
ከሩቅ እየተከተለው፣ እስከ ሊቀ ካህናቱ ግቢ
ዘለቀ፤ በዚያም ተቀምጦ ከሎሌዎቹ ጋር
እሳት ይሞቅ ነበር።
55የካህናት አለቆችና ሸንጎው በሙሉ ኢየ
ሱስን ለመግደል ምስክር ፈለጉ፤ ነገር ግን
ማግኘት አልቻሉም። 56ብዙዎች በሐሰት
ቢመሰክሩበትም፣ ቃላቸው አንድ ሊሆን
አልቻለም።
57አንዳንዶቹም ተነሥተው እንዲህ ሲሉ
በሐሰት መሰከሩበት፤ 58“ይህ፣ ‘የሰው እጅ
የሠራውን ቤተ መቅደስ አፍርሼ፣ በሦስት
ቀን ሌላ የሰው እጅ ያልሠራውን እሠራለሁ’
ሲል ሰምተነዋል።” 59ይህም ሆኖ፣ እንኳ
ምስክርነታቸው አንድ አልሆነም።

60ሊቀ ካህናቱም ተነሥቶ በፊታቸው
በመቆም፣ “እነዚህ በአንተ ላይ የሚመሰክሩት
ምንድን ነው? ለምን አትመልስም?” በማለት
ኢየሱስን ጠየቀው። 61ኢየሱስ ግን ዝም
አለ፤ ምንም መልስ አልሰጠም።
ሊቀ ካህናቱም እንደ ገና፣ የቡሩኩ ልጅ፣
ክርስቶስ[ሰ] አንተ ነህን? ሲል ጠየቀው።
62ኢየሱስም፣ “አዎን ነኝ፤ የሰው ልጅ በኀ
ያሉ ቀኝ ሲቀመጥ፣ በሰማይ ደመናም ሲመጣ
ታዩታላችሁ” አለ።
63ሊቀ ካህናቱም ልብሱን ቀደደና፣ እንዲህ
አለ፤ “ሌላ ምን ምስክር ያስፈልገናል?
64ስድቡን ሰምታችኋል፤ ታዲያ፣ ምን ይመ
ስላችኋል?”፤
እነርሱም ሞት ይገባዋል በማለት በአንድ
ቃል ፈረዱበት። 65በዚህ ጊዜ አንዳንዶቹ
ይተፉበት ጀመር፤ ዐይኑንም ሸፍነው በጡጫ
እየመቱት፣ “እስቲ ትንቢት ተናገር!”
ይሉት ነበር። ሎሌዎችም በጥፊ እየመቱ
ወሰዱት።

## ጴጥሮስ ኢየሱስን አላውቀውም አለ

14፥66-72 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥69-75፤ ሉቃ22፥56-62፤
ዮሐ18፥16-18፡25-27

66ጴጥሮስ በግቢው ውስጥ በታችኛው በኩል
ሳለ፣ ከሊቀ ካህናቱ ገረዶች አንዲቱ መጣች፤
67ጴጥሮስ እሳት ሲሞቅ አይታ ትኵር ብላ
ተመለከተችውና፣
“አንተም ከናዝሬቱ ኢየሱስ ጋር ነበርህ”
አለችው።
68እርሱ ግን፣ “የምትዪውን አላውቅም፤
አይገባኝምም” በማለት ካደ። ከዚያም ወደ
መግቢያው በር ወጣ አለ፤ በዚህ ጊዜ ዶሮ
ጮኸ[ሸ]።
69ገረዲቱም ባየችው ጊዜ እዚያ ለቆሙት፣
“ይህ ሰው ከእነርሱ አንዱ ነው” ብላ እንደ
ገና ተናገረች። 70እርሱ ግን አሁንም ካደ።
ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ በዚያ የቆሙት
ሰዎች ጴጥሮስን፣ “የገሊላ ሰው እንደ
መሆንህ መጠን፣ በእርግጥ አንተ ከእነርሱ
አንዱ ነህ” አሉት።
71እርሱ ግን፣ “እናንተ የምትሉትን
ሰው እኔ አላውቀውም” እያለ ይምል ይገዘት
ጀመር።
72ወዲያውም ዶሮ ሁለተኛ[ቀ] ጮኸ። ጴጥ
ሮስም፣ “ዶሮ ሁለት ጊዜ[በ] ከመጮኹ በፊት
ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ” ያለው የኢየሱስ ቃል
ትዝ አለው። ከዚያም ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ።

14፥41 ቍ35፤ ማቴ26፥18
14፥43 ማቴ10፥4
14፥45 ማቴ23፥7
14፥49 ኢሳ53፥7ኛ12፥ ማቴ1፥22፤ 26፥55
14፥50 ቍ27
14፥54 ማቴ26፥3፤ ዮሐ18፥18
14፥55 ማቴ5፥22
14፥58 ዮሐ2፥19
14፥61 ኢሳ53፥7፤ ማቴ16፥16፤27፥12፡14፤ማር15፥5፤ ሉቃ23፥9፤ዮሐ4፥25፡26፤19፥9
14፥62 ራእ1፥7
14፥63 ዘሌ10፥6፤ 21፥10፤ዘኍ14፥6፤ ሐሥ14፥14
14፥64 ዘሌ24፥16
14፥65 ማቴ16፥21
14፥66 ቍ54
14፥67 ቍ54፤ ማር1፥24
14፥68 ቍ30፡72
14፥70 ቍ30፡68፡72፤ሐሥ2፥7
14፥71 ቍ30፡72
14፥72 ቍ30፡68

[ሰ]61 ወይም *መሲሑ*
[ሸ]68 አንዳድ ቅጆች *ዶሮ ጮኸ* የሚለው የላቸውም።
[ቀ]72 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *ሁለተኛ* የሚለው ቃል የላቸውም።
[በ]72 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *ሁለት ጊዜ* የሚለው ሐረግ የላቸውም

## ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት

15፥2-15 ተጓ ምብ - ማቴ 27፥11-26፤ ሉቃ23፥2፡3፡18-25፤ ዮሐ18፥29-19፥16

15 ጠዋት በማለዳ የካህናት አለቆች
ከሽማግሌዎች፣ ከጸሐፍትና ከመ
ላው የሸንጎ አባላት ጋር ወዲያው ከተ
ማከሩ በኋላ ኢየሱስን አስረው ወሰዱት፤
ለጲላጦስም አሳልፈው ሰጡት።
2ጲላጦስም፣ "አንተ የአይሁድ ንጉሥ
ነህን?" ሲል ጠየቀው፤
ኢየሱስም፣ "አንተው አልኸው፣" በማ
ለት መለሰለት።
3የካህናት አለቆችም በብዙ ነገር ከሰሱት።
4ጲላጦስም፣ "ለምን መልስ አትሰጥም? እነሆ
በብዙ ነገር ከሰውሃል" ሲል እንደ ገና ጠየ
ቀው።
5ኢየሱስ ግን ምንም አልመለሰም፤ ጲላ
ጦስ ተገረመ።
6በበዓል ሕዝቡ እንዲፈታላቸው የሚጠ
ይቁትን እስረኛ የመልቀቅ ልማድ ነበር።
7በዐመፃ ተነሣሥተው ነፍስ ከገደሉ ዐመፀ
ኞች ጋር የታሰረ በርባን የሚባል አንድ ሰው
ነበረ። 8ሕዝቡም መጥተው እንደ ተለመደው
እንዲያደርግላቸው ጲላጦስን ለመኑት።
9ጲላጦስም፣ "የአይሁድን ንጉሥ እንድፈታ
ላችሁ ትፈልጋላችሁን?" ሲል ጠየቃቸው፤
10ምክንያቱም የካህናት አለቆች ኢየሱስን
አሳልፈው የሰጡት በቅናት መሆኑን ያውቅ
ነበር። 11የካህናት አለቆች ግን በርባንን በእርሱ
ምትክ እንዲፈታላቸው እንዲጠይቁ ሕዝቡን
አነሣሡ።
12ጲላጦስም እንደ ገና፣ "እንግዲያው
የአይ ሁድ ንጉሥ የምትሉትን ምን
እንዳደርገው ትፈልጋላችሁ?" አላቸው።
13እነርሱም እንደ ገና፣ "ስቀለው!" እያሉ
ጮኹ።
14ጲላጦስም፣ "ለምን? ምን የፈጸመው
ወንጀል አለ" አላቸው።
እነርሱ ግን፣ "ስቀለው!" እያሉ የባሰ ጮኹ።
15ጲላጦስም ሕዝቡን ደስ ለማሰኘት ሲል በር
ባንን ፈታላቸው፤ ኢየሱስን ግን ገርፎ እንዲ
ሰ ቀል አሳልፎ ሰጠው።

## ወታደሮች በኢየሱስ ላይ አፌዙ

15፥16-20 ተጓ ምብ - ማቴ 27፥27-31

16ወታደሮቹ ፕራይቶሪዮን ወደ ተባለ ወደ
ገዢ ግቢ ወሰዱት፤ ሰራዊቱንም ሁሉ በአንድነት
ሰበሰቡ። 17ቀይ ልብስም አለበሱት፤
የእሾኽ አክሊል ጐንጉነው በራሱ ላይ
ደፉበት። 18ከዚያም፣ "የአይሁድ ንጉሥ
ሆይ፤ ሰላም ለአንተ ይሁን!" እያሉ እጅ ነ
ሡት፤ 19ራሱንም በበትር መቱት፤
ተፉበትም፤ ተንበርክከውም ሰገዱለት።
20ካፌዙበት በኋላም ቀዩን ልብስ
ገፈፉት፤ የገዛ ልብሱን አለበሱት፤ ሊ
ሰቅሉትም ወሰዱት።

15፥1 ማቴ5፥22፤ 27፥1፡2፤ሉቃ22፥66
15፥2 ቍ9፡12፡ 18፡26፤ማቴ2፥2
15፥5 ማር14፥61
15፥9 ቍ2
15፥11 ሐሥ3፥14
15፥15 ኢሳ53፥6
15፥16 ዮሐ18፥28፡ 33፤19፥9
15፥18 ቍ2
15፥20 ዕብ13፥12
15፥21ማቴ27፥32፤ ሉቃ23፥26፤ ሮሜ16፥13
15፥23 ቍ36፤ መዝ69፥21፤ ምሳ31፥6
15፥24 ምሳ22፥18
15፥26 ቍ2
15፥29 መዝ22፥7፤ 109፥25፤ዮሐ2፥19
15፥31 መዝ22፥7
15፥32 ቍ2፤ ማር1፥61
15፥33 አሞ8፥9
15፥34 መዝ22፥1
15፥36 ቍ23፤ መዝ69፥21

## የኢየሱስ ስቅለት

15፥22-32 ተጓ ምብ - ማቴ27፥33-44፤ ሉቃ23፥33-43፤ ዮሐ19፥17-24

21የአሌክሳንድሮስና የሩፎስ አባት ስምዖን
የተባለ አንድ የቀሬና ሰው ከገጠር ሲመጣ
መስቀሉን እንዲሸከም አስገደዱት። 22ከዚ
ያም ኢየሱስን፣ ትርጒሙ "የራስ ቅል ስፍራ"
ወደ ተባለ ወደ ጎልጎታ ወሰዱት። 23ከከርቤ
ጋር የተቀላቀለ የወይን ጠጅም ሰጡት፤
እርሱ ግን አልተቀበለም። 24ከዚያም ሰቀሉት፤
እያንዳንዱም ምን እንደሚደርሰው ለማወቅ
ዕጣ ተጣጥለው ልብሱን ተከፋፈሉ።
25ሲሰቅሉትም ጊዜው ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት
ነበረ። 26የክሱ ጽሑፍም፣ "የአይሁድ
ንጉሥ" የሚል ነበር። 27ከእርሱም ጋር ሁለት
ወንበዴ ዎችን አንዱን በቀኙ አንዱን በግራው
ሰቀሉ። 28መጽሐፍ፣ "ከዐመፀኞች ጋር ተቈጠ
ረ" ያለ ውም በዚሁ ተፈጸመ†። 29በመንገድ
የሚያል ፉትም ራሳቸውን እየነቀነቁ
የስድብ ናዳ በማውረድ እንዲህ ይሉት
ነበር፤ "አዬ! ቤተ መቅደስን አፍርሰህ
በሦስት ቀን የምትሠራ አንተ ነህ፤ 30እስቲ
አሁን ከመስቀል ውረ ድና ራስህን
አድን።"
31እንዲሁም የካህናት አለቆችና ጸሐፍት
በማሾፍ እርስ በርሳቸው እንዲህ አሉ፤ "ሌሎ
ችን አዳነ፤ ራሱን ግን ማዳን አልቻለም፤
32አይተን እናምን ዘንድ ይህ ክርስቶስ‡፣ ይህ
የእስራኤል ንጉሥ እስቲ ከመስቀል ይው
ረድ።" ከእርሱ ጋር የተሰቀሉትም እንደዚሁ
የስድብ ናዳ ያወርዱበት ነበር።

## የኢየሱስ መሞት

15፥33-41 ተጓ ምብ - ማቴ 27፥45-56፤ ሉቃ23፥44-49

33ከስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት
ድረስ በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ።
34በዘጠኝም ሰዓት ኢየሱስ፣ "ኤሎሄ፣ ኤሎሄ
ላማ ሰበቅታኒ?" ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤
ትርጓሜውም "አምላኬ፣ አምላኬ ለምን
ተው
ኸኸኝ?" ማለት ነው።
35በዚያ ቆመው ከነበሩት አንዳንዶቹ ይህን
ሲሰሙ፣ "ኤልያስን ይጣራል" አሉ።
36ከዚያም አንድ ሰው ፈጥኖ ሄዶ የሆመ
ጠጠ የወይን ጠጅ በሰፍነግ ነከረ፤ በዘንግም
ሰክቶ እንዲጠጣው ለኢየሱስ አቀረበለት፤
ከዚያም፣ "ተዉት፤ እስቲ ኤልያስ መጥቶ
ሲያወርደው እናያለን" አለ።

†27 አንዳድ ቅጆች ቍ 28 የላቸውም (ኢሳ 53፥12)።
‡32 ወይም መሲሕ

37ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ ነፍሱን
ሰጠ።
38የቤተ መቅደሱም መጋረጃ ከላይ እስከ
ታች ከሁለት ተቀደደ። 39በኢየሱስ ትይዩ
ቆሞ የነበረውም የመቶ አለቃ እንደዚህ
ጮኸ[ኀ] ነፍሱን ሲሰጥ ባየ ጊዜ፣ “ይህ ሰው
በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበር” አለ።
40በዚህ ጊዜ ሴቶች ከሩቅ ሆነው ይመለ
ከቱ ነበር፤ ከእነርሱም መካከል መግደላዊት
ማርያም፣ የታናሹ ያዕቆብና የዮሳ እናት
ማርያም፣ እንዲሁም ሰሎሜ ነበሩ፤ 41እነዚህ
ሴቶች በገሊላ ሲከተሉትና ሲያገለግሉት
የነበሩ ናቸው፤ ደግሞም አብረውት ወደ ኢየሩ
ሳሌም የመጡ ሌሎች ብዙ ሴቶች ነበሩ።

### የኢየሱስ መቀበር

15፥42-47 ተጓ ምብ - ማቴ 27፥57-61፤ ሉቃ23፥50-56፤
ዮሐ19፥38-42

42ጊዜው እየመሸ መጥቶ የሰንበት ዋዜማ
ይኸውም የመዘጋጀት ቀን ሆነ፤ 43የተከበረ
የሸንጎ አባልና የእግዚአብሔርን መንግሥት
ይጠባበቅ የነበረው የአርማትያሱ ዮሴፍ
በድፍረት ወደ ጲላጦስ ሄዶ የኢየሱስን ሥጋ
ለመነው። 44ጲላጦስም እንዲህ በቶሎ መሞቱን
ሲሰማ ተደነቀ፤ የመቶ አለቃውንም ጠርቶ
ከሞተ ምን ያህል ጊዜ እንደ ሆነ ጠየቀው፤
45መሞቱንም ከመቶ አለቃው ካረጋገጠ በኋላ
ሥጋውን ለዮሴፍ ሰጠው። 46ዮሴፍም በፍታ
ገዛ፤ ሥጋውንም አውርዶ በበፍታው ከከፈ
ነው በኋላ፣ ከዐለት በተወቀረ መቃብር
አኖረው፤ የመቃብሩንም ደጃፍ በድንጋይ
ገጠመው። 47ማርያም መግደላዊትና የዮሳ
እናት ማርያም የት እንዳኖሩት ይመለከቱ
ነበር።

### ትንሣኤው

16፥1-8 ተጓ ምብ -ማቴ 28፥1-8፤ ሉቃ24፥1-10

16 ሰንበት ካለፈ በኋላ መግደላዊት
ማርያም፣ የያዕቆብ እናት ማርያ
ምና ሰሎሜ ሄደው የኢየሱስን ሥጋ ለመቀ
ባት ሽቱ ገዙ። 2በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን
ጠዋት በማለዳ፣ ገና ፀሓይ እንደ ወጣች፣ ወደ
መቃብሩ በመሄድ ላይ ሳሉ፣ 3“ድንጋዩን
ከመቃብሩ ደጃፍ ላይ ማን ያንከባልልልናል?”
በማለት እርስ በርሳቸው ይነጋገሩ ነበር።
4ቀና ብለው ሲመለከቱ፣ በጣም ትልቅ
የነበረው ድንጋይ ከደጃፉ ላይ ተንከባሎ አዩ።
5ወደ መቃብሩ እንደ ገቡም፣ ነጭ ልብስ
የለበሰ ጐልማሳ በቀኝ በኩል ተቀምጦ አዩና
ደነገጡ።

15፥37 ዮሐ19፥30
15፥38 ዕብ10፥19፡
20
15፥39 ቍ45፤
ማቴ4፥3፤
ማር1፥1፡11፤9፥7
15፥40 መዝ38፥11፤
ማር16፥1፤ሉቃ24፥10፤
ዮሐ19፥25
15፥41
ማቴ27፥55፡56፤
ሉቃ8፥2፡3
15፥42ማቴ27፥62፤
ዮሐ19፥31
15፥43 ማቴ3፥2፤
5፥22፤ሉቃ2፥25፡38
15፥45 ቍ39
15፥46 ማር16፥3
15፥47 ቍ40
16፥1 ሉቃ23፥56፤
ዮሐ19፥39፡40
16፥3 ማር15፥46
16፥5 ዮሐ20፥12
16፥6 ማር1፥24
16፥7 ማር14፥28፤
ዮሐ21፥1ኛ23
16፥9 ማር15፥47፤
ዮሐ20፥11ኛ18
16፥11 ቍ13፡14፤
ሉቃ24፥11
16፥12
ሉቃ24፥13ኛ32
16፥14
ሉቃ24፥36ኛ43
16፥15
ማቴ28፥18ኛ20፤
ሉቃ24፥47፡48፤
ሐሥ1፥8
16፥16 ዮሐ3፥16፡
18፡36፤ሐሥ16፥31
16፥17 ማር9፥38፤
ሉቃ10፥17፤
ዮሐ4፥48፤ሐሥ2፥4፤
5፥16፤8፥7፤10፥46፤
16፥18፤19፥6፡
13ኛ16፤1ቆሮ2፥10፡
28፡30፤13፥1፤
14፥2ኛ39
16፥18 ሉቃ10፥19፤
ሐሥ6፥6፤28፥3ኛ5

6እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፤ “አትደንግጡ፤
የምትፈልጉት የተሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየ
ሱስን ነው፤ እርሱ ተነሥቶአል፤ እዚህ የለም፤
እርሱን ያኖሩበት ስፍራ ይኸውላችሁ። 7ነገር
ግን ሄዳችሁ ለደቀ መዛሙርቱና ለጴጥሮስ፣
‘ቀድሞአችሁ ወደ ገሊላ ይሄዳል፤ እንደ
ነገራችሁ እዚያ ታገኙታላችሁ’ ብላችሁ ንገ
ሯቸው።”
8ሴቶቹም እየተንቀጠቀጡና እየተደነቁ
ከመቃብሩ ሸሽተው ወጡ፤ ፈርተው ስለ
ነበር ለማንም አንዳች አልተናገሩም።
9በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ማለዳ ከሙታን
ከተነሣ በኋላ፣ ሰባት አጋንንት ላወጣላት ለማ
ርያም መግደላዊት በመጀመሪያ ታየ።
10እር ሷም ሄዳ፣ ከእርሱ ጋር የነበሩት
እያዘኑ ሲያለቅሱ አግኝታ እርሱ ሕያው
መሆኑንና ለእርሷም መታየቱን ነገረቻቸው፤
11እነርሱ ግን አላመኗትም።
12ከዚህ በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱ
ወደ ገጠር ሲሄዱ በሌላ መልክ ታያቸው።
13እነርሱም ተመልሰው ይህንኑ ለቀሩት ነገ
ሯቸው፤ ይሁን እንጂ እነርሱንም አላመኗ
ቸውም።
14ከዚያም ዐሥራ አንዱ በማዕድ ላይ
ሳሉ ተገለጠላቸው፤ ከተነሣ በኋላ ያዩት
ሰዎች የነገሯቸውን ስላላመኗቸው፣ አለ
ማመናቸውንና የልባቸውን ድንዳኔ ነቀፈ።
15እንዲህም አላቸው፤ “ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤
ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፤ 16ያመነ
የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድ
በታል። 17የሚያምኑትን እነዚህ ምልክቶች
ይከተሏቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤
በአዲስ ልሳንም ይናገራሉ፤ 18እባቦችን በእ
ጃቸው ይይዛሉ፤ የሚገድል መርዝ ቢጠጡ
እንኳ አይጐዳቸውም፤ እጃቸውንም በሕመ
ምተኞች ላይ ይጭናሉ፤ እነርሱም ይፈወ
ሳሉ።”
19ጌታ ኢየሱስ ይህን ከተናገራቸው በኋላ
ወደ ሰማይ ዐረገ፤ በእግዚአብሔርም ቀኝ
ተቀ መጠ። 20ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ
ወጥተው፣ በየስፍራው ሁሉ ሰበኩ፤ ጌታም
ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር፤
ትምህርታቸውንም ተከ ትለው በሚፈጸሙ
ምልክቶች ቃሉን ያጸና ነበር[ነ]።

[ኀ]39 አንዳንድ ቅጆች *እንደዚህ ጮኾ* የሚለው ሐረግ
የላቸውም።
[ነ]20 አንዳንድ የጥንት ቅጆች በቍ9-20 ላይ ያለው ክፍል
የላቸውም።

# የሉቃስ ወንጌል

## መግቢያ

1፥1-4 ማመ ሐሥ 1፥1

1 በእኛ መካከል ስለ ተፈጸሙት[ሀ] ነገሮች
ብዙዎች ታሪኩን የተቻላቸውን ያህል
ጽፈውት ይገኛል፤ 2ይህም ታሪክ ከመጀመ
ሪያው አንሥቶ የዐይን ምስክሮችና የቃሉ
አገልጋዮች የነበሩት ያስተላለፉልን ነው።
3ክቡር ቴዎፍሎስ ሆይ፤ እኔም በበኩሌ ሁሉን
ከመሠረቱ በጥንቃቄ ከመረመርሁ በኋላ፣
ታሪኩን ቅደም ተከተሉን በጠበቀ ሁኔታ
ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ፤ 4ይህንንም
የማደርገው የተማርኸው ነገር እውነተኛ መሆ
ኑን እንድታውቅ ነው።

## የመጥምቁ ዮሐንስ መወለድ አስቀድሞ ተነገረ

5በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ዘመን፣ ከአብያ
የክህነት ምድብ የሆነ ዘካርያስ የሚባል
አንድ ካህን ነበረ፤ ሚስቱ ኤልሳቤጥም ከአሮን
ነገድ ነበረች። 6ሁለቱም የጌታን ትእዛዝና
ሥርዐት ሁሉ ጠብቀው ያለ ነቀፋ የሚኖሩ፣
በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ፤ 7ይሁን
እንጂ ኤልሳቤጥ መካን በመሆኗ ልጅ
አልነበራቸውም፤ ሁለቱም በዕድሜ የገፉ
ነበሩ።

8አንድ ቀን ዘካርያስ በምድቡ ተራ፣
በእግዚአብሔር ፊት በክህነት በሚያገለግልበት
ጊዜ፣ 9በሥርዐተ ክህነቱ መሠረት፣ ወደ ጌታ
ቤተ መቅደስ ገብቶ ለማጠን በዕጣ ተመ
ረጠ። 10ዕጣን በሚታጠንበትም ጊዜ ሕዝቡ
ሁሉ በውጭ ሆኖ ይጸልይ ነበር።

11የጌታም መልአክ ከዕጣን መሠዊያው በስተ
ቀኝ ቆሞ ታየው። 12ዘካርያስም ባየው ጊዜ ደነ
ገጠ፤ በፍርሀትም ተዋጠ። 13መልአኩ ግን እን
ዲህ አለው፤ "ዘካርያስ ሆይ፤ አትፍራ፤ ጸሎ
ትህ ተሰምቶአል፤ ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ
ልጅ ትወልድልሃለች፤ ስሙንም ዮሐንስ
ትለዋለህ። 14በእርሱ ተድላና ደስታ ታገኛ
ለህ፤ ብዙዎችም እርሱ በመወለዱ ደስ
ይላቸዋል፤ 15በጌታ ፊት ታላቅ ይሆና
ልና። የወይን ጠጅም ሆነ ሌላ የሚያሰክር
መጠጥ አይጠጣም፤ በእናቱም ማሕፀን ሳለ
በመንፈስ ቅዱስ ይሞላል። 16ከእስራኤልም
ሰዎች ብዙዎቹን ወደ ጌታ ወደ
አምላካቸው ይመልሳቸዋል፤ 17የአባቶችን
ልብ ወደ ልጆ ቻቸው፣ የማይታዘዙትንም
ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልስ ዘንድ፣ ለጌታ
የተገባ ሕዝብ ለማዘጋጀት በኤልያስ መንፈስና

1፥2 ማር1፥1፤4፥14፤ሐሥ1፥21፡22፤ዕብ2፥3፤1ጴጥ5፥1፤2ጴጥ1፥16፤1ዮሐ1፥1
1፥3 ሐሥ1፥1፤11፥4፤24፥3፤26፥25
1፥4 ዮሐ20፥31፤ሐሥ2፥42
1፥5 1ዜና24፥10፤ማቴ2፥1
1፥6 ዘፍ6፥9፤ዘዳ5፥33፤1ነገ9፥4፤ሉቃ2፥25
1፥8 1ዜና24፥19፤2ዜና8፥14
1፥9 ዘፀ30፥7፡8፤1ዜና23፥13፤2ዜና29፥11፤መዝ141፥2፤ሐሥ 1፥26
1፥10 ዘሌ16፥17
1፥11 ዘፀ30፥1-10፤ሐሥ5፥19
1፥12 መሳ6፥22፡23፤13፥22
1፥13 ቊ30፤60፡63፤ማቴ3፥1፤14፥27
1፥14 ቊ58
1፥15 ቊ41፡67፤ዘሌ10፥9፤ ዘኍ6፥3፤መሳ13፥4፤ኤር1፥5፤ሉቃ7፥33፤ሐሥ2፥4፤4፥8፡31፤6፥3፡5፤9፥17፤10፥44፤ገላ1፥15፤ኤፌ5፥18
1፥17 ቊ76፤ሚል4፥5፡6፤ማቴ3፥3፤11፥14
1፥18 ቊ34፤ዘፍ15፥8፤17፥17
1፥19 ቊ26፤ዳን8፥16፤9፥21
1፥20 ዘፀ4፥11፤ሕዝ3፥26
1፥22 ቊ62
1፥25 ዘፍ30፥23፤ኢሳ 4፥1
1፥26 ቊ19፤ማቴ2፥23
1፥27 ማቴ1፥16፡18፡20፤ሉቃ2፥4
1፥30 ቊ13፤ዘፍ6፥8፤ማቴ14፥27
1፥31 ኢሳ7፥14፤ማቴ1፥21፡25፤ሉቃ2፥21
1፥32 ቊ35፡76፤ማቴ1፥1ማር 5፥7
1፥33 2ሳሙ7፥16፤መዝ89፥3-4፤ኤር33፥17፤ዳን2፥44፤7፥14ኢሳ 9፥7፤27፤ሚክ4፥7፤ማቴ28፥18፤ዕብ1፥8

ኀይል በጌታ ፊት ይሄዳል።"

18ዘካርያስም መልአኩን፣ "ይህን በምን አው
ቃለሁ? እኔ ሽማግሌ ነኝ፤ ሚስቴም በዕ
ድሜ ገፍታለች" አለው።

19መልአኩም መልሶ እንዲህ አለው፤ "እኔ
በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ፤
ይህን እነግርህና ይህን የምሥራች አመጣልህ
ዘንድ ተልኬአለሁ፤ 20እነሆ፤ ጊዜውን ጠብቆ
የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንህ፣ ድዳ ትሆ
ናለህ፤ መናገርም አትችልም።"

21በዚህ ጊዜ ሕዝቡ ዘካርያስ ከቤተ መቅደሱ
ሳይወጣ ለምን እንደ ዘገየ በመገረም ይጠ
ባበቅ ነበር። 22ከወጣ በኋላም ሊያናግራ
ቸው አል ቻለም፤ በምልክት ከመጥቀስ
በስተቀር መና ገር ባለመቻሉ በቤተ
መቅደስ ውስጥ ራእይ እንዳየ ተገነዘቡ።

23ዘካርያስም የአገልግሎቱ ወቅት በተፈ
ጸመ ጊዜ ወደ ቤቱ ተመለሰ። 24ከዚህ
በኋላ ሚስቱ ኤልሳቤጥ ፀነሰች፤ አምስት
ወራትም ራሷን ሰወረች፤ 25እርሷም፣ "ጌታ
በምሕረቱ ነቀፌታዬን ከሰው መካከል
ሊያስወግድልኝ ተመልክቶ በዚህ ጊዜ
ይህን አድርጎልኛል" አለች።

## የኢየሱስ መወለድ አስቀድሞ ተነገረ

26በስድስተኛው ወር፣ እግዚአብሔር መል
አኩ ገብርኤልን በገሊላ ወደምትገኘው
ወደ ናዝሬት ከተማ ላከው፤ 27የተላከውም
ከዳዊት ዘር ለሆነ ዮሴፍ ለሚባል ሰው
ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ነበር፤
የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ። 28መል
አኩም እርሷ ወዳለችበት ገብቶ፣ "እጅግ
የተወደድሽ ሆይ፤ ሰላም ለአንቺ ይሁን፤
ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ የተባረክሽ
ነሽ" አላት።

29ማርያምም በንግግሩ እጅግ በጣም
ደንግጣ፣ "ይህ ምን ዐይነት ሰላምታ ይሆን?"
እያለች ነገሩን ታሰላስል ጀመር፤ 30መልአ
ኩም እንዲህ አላት፤ "ማርያም ሆይ፤ በእ
ግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ አግኝተሻልና አት
ፍሪ። 31እነሆ፤ ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅም
ትወልጃለሽ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ።
32እርሱም ታላቅ ይሆናል፤ የልዑል ልጅም
ይባላል፤ ጌታ አምላክ የአባቱን የዳዊትን
ዙፋን ይሰጠዋል፤ 33በያዕቆብም ቤት ላይ
ለዘላለም ይነግሣል፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ
የለውም።"

[ሀ]1 *በእርግጥ ስለታመኑት*

34ማርያምም መልአኩን፣ “እኔ ወንድ ስለ
ማ ላውቅ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?”
አለችው።
35መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፤ “መን
ፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑ
ልም ኀይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ የሚወ
ለደው ቅዱሱ ሕፃን፣ የእግዚአብሔር ልጅ
ይባላል። 36እነሆ፤ ዘመድሽ ኤልሳቤጥም በስተ
እርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች፤ መካን የተ
ባለችውም ስድስተኛ ወሯን ይዛለች፤ 37ለእ
ግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና።”
38ማርያምም፣ “እነሆ፤ እኔ የጌታ ባሪያ
ነኝ፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ” አለች። ከዚ
ያም መልአኩ ተለይቶአት ሄደ።

## ማርያም ኤልሳቤጥን ጥየቃ ሄደች

39ማርያምም በዚያው ሰሞን በፍጥነት
ተነሥታ ወደ ደጋው አገር፣ ወደ አንድ
የይሁዳ ከተማ ሄደች፤ 40ወደ ዘካርያስ
ቤትም ገብታ ለኤልሳቤጥ ሰላምታ አቀረ
በች። 41ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ
በሰማች ጊዜ፣ ፅንሱ በማሕፀኗ ውስጥ
ዘለለ፤ ኤልሳቤጥም በመንፈስ ቅዱስ ተሞ
ላች፤ 42ድምፅዋን ከፍ አድርጋ እንዲህ አለች፤
“አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፤
የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው። 43ለመ
ሆኑ የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ
ዘንድ እኔ ማን ነኝ? 44እነሆ፤ የሰላምታሽ
ድምፅ ጆሮዬ እንደ ገባ፣ በማሕፀኔ ያለው
ፅንስ በደስታ ዘሎአልና። 45ጌታ ይፈ
ጸማል ብሎ የነገራትን ያመነች እርሷ
የተባረከች ናት!”

## የማርያም መዝሙር

1፥46-53 ተጓ ምብ – 1 ሳሙ 2፥1-10

46ማርያምም እንዲህ አለች፤

“ነፍሴ ጌታን ከፍ ከፍ ታደርገዋለች፤
47መንፈሴም በመድኀኒቴ
በእግዚአብሔር ደስ ትሰኛለች፤
48እርሱ የባሪያውን መዋረድ
ተመልክቶአልና።
ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ
ብፅዕት ይሉኛል፤
49ኀያል የሆነው እርሱ ታላቅ
ነገር አድርጎልኛልና፤
ስሙም ቅዱስ ነው፤
50ምሕረቱም ለሚፈሩት ከትውልድ
እስከ ትውልድ ይኖራል።
51በክንዱ ብርቱ ሥራ ሠርቶአል፤
በልባቸው ሐሳብ የሚታበዩትን
በትኖአቸዋል፤
52ገዢዎችን ከዙፋናቸው አውርዶአቸዋል፤
ትሑታንን ግን ከፍ ከፍ አድርጎአቸዋል፤
53የተራቡትን በበጎ ነገር አጥግቦአቸዋል፤
ሀብታሞችን ግን ባዶአቸውን
ሰዶአቸዋል፤
54ምሕረቱን በማስታወስ፣ ባሪያውን
እስራኤልን ረድቶአል፤
55ይህም ለአባቶቻችን እንደ ተናገረ፣
ለአብርሃምና ለዘሩ ያለውን
ለዘላለም ለመጠበቅ ነው።”

56ማርያምም ሦስት ወር ያህል ኤልሳ
ቤጥ ዘንድ ከቈየች በኋላ ወደ ቤቷ ተመ
ለሰች።

## የመጥምቁ ዮሐንስ መወለድ

57የኤልሳቤጥም የመውለጃዋ ቀን ደረሰ፤
ወንድ ልጅም ወለደች። 58ጎረቤቶቿና ዘመ
ዶቿም ጌታ ታላቅ ምሕረት እንዳደረገ
ላት ሰሙ፤ የደስታዋም ተካፋዮች ሆኑ።
59በስምንተኛውም ቀን ሕፃኑን ሊገርዙት
መጡ፤ በአባቱም ስም ዘካርያስ ሊሉት
ፈለጉ፤ 60እናቱ ግን፣ “አይሆንም፤ ዮሐንስ
መባል አለበት” አለች።
61እነርሱም፣ “ከዘመዶችሽ በዚህ ስም
የተጠራ ማንም የለም” አሏት።
62አባቱንም ምን ስም ሊያወጣለት እንደ
ሚፈልግ በምልክት ጠየቁት። 63እርሱም
መጻፊያ ሰሌዳ እንዲሰጡት ለምኖ፣ “ስሙ
ዮሐንስ ነው” ብሎ ጻፈ፤ ሁሉም በነገሩ
ተደነቁ። 64ወዲያውም አፉ ተከፈተ፤ አን
ደበቱ ተፈታ፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገነ
መናገር ጀመረ። 65ጎረቤቶቹም ሁሉ በፍር
ሀት ተሞሉ፤ ይህም ሁሉ ነገር በደጋማው
የይሁዳ ምድር ሁሉ ተወራ። 66ይህንም
የሰሙ ሁሉ፣ “ይህ ሕፃን ምን ሊሆን ይሆን?”
እያሉ ነገሩን በልባቸው ያዙ፤ የጌታ እጅ
በእር ግጥ ከእርሱ ጋር ነበርና።

## የዘካርያስ ትንቢት

67የሕፃኑም አባት ዘካርያስ በመንፈስ ቅዱስ
ተሞልቶ እንዲህ ሲል ትንቢት ተናገረ፤

68“የእስራኤል አምላክ፣ ጌታ ይመስገን፤
መጥቶ ሕዝቡን ተቤዥቶአልና።
69በባሪያው በዳዊት ቤት፣
የድነት ቀንድ^ አስነሥቶልናል፤
70ይህም ጥንት በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ
እንደ ተናገረው፣
71ማዳኑም ከጠላቶቻችንና፣ ከተፃራሪዎቻችን
ሁሉ እጅ ነው፤
72ይህንም ያደረገው ለአባቶቻችን
ምሕረቱን ለማሳየት፣
ቅዱስ ኪዳኑን ለማስታወስ፣
73ለአባታችን ለአብርሃም የማለውን

1፥35 ቀኍ32፥76፤ ማቴ1፥18፤ 4፥3፤ ማር1፥24፤5፥7
1፥36 ቀኍ24
1፥37 ማቴ19፥26
1፥39 ቀኍ65
1፥41 ቀኍ15
1፥42 መሳ5፥24
1፥43 ዮሐ13፥13
1፥46 መዝ34፥2፡3
1፥47 መዝ18፥46፤ ኢሳ17፥10፤61፥10፤ ዕን3፥18፤1ጢሞ 1፥1፤2፥3፤4፥10
1፥48 ቀኍ38፤መዝ 138፥6፤ሉቃ11፥27
1፥49 መዝ71፥19፤ 111፥19
1፥50 ዘፀ20፥6፤ መዝ103፥17
1፥51 ዘፍ11፥8፤ዘፀ 18፥11፤2ሳሙ22፥28፤ መዝ98፥1፤ኢሳ 40፥10፤ኤር13፥9፤ 49፥16
1፥52 ማቴ23፥12
1፥53 መዝ107፥9
1፥54 መዝ98፥3
1፥55 ገላ3፥16
1፥59 ዘፍ17፥12፤ ዘሌ12፥3፤ሉቃ2፥21፤ ፊል3፥5
1፥60 ቀኍ13፥63፤ ማቴ3፥1
1፥62 ቀኍ22
1፥63 ቀኍ13፥60፤ ማቴ3፥1
1፥64 ቀኍ20፤ ሕዝ24፥27
1፥65 ቀኍ39
1፥66 ዘፍ39፥2፤ ሐሥ11፥21
1፥67 ቀኍ15፤ ኢል2፥28
1፥68 ዘፍ24፥27፤ 1ነገ8፥15፤መዝ72፥18 ፤111፥9፤ሉቃ7፥16
1፥69 1ሳሙ2፥1፡ 10፤2ሳሙ22፥3፤ መዝ18፥2፤89፥17፤ 132፥17፤ሕዝ 29፥21፤ማቴ1፥1
1፥70 ኤር23፥5፤ ሐሥ3፥21፤ ሮሜ1፥2፤
1፥72 መዝ105፥8፡ 9፤106፥45፤ሕዝ 16፥60፤ሚክ7፥20
1፥73 ዘፍ22፥16-18
1፥74 ዕብ9፥14፤ 1ዮሐ4፥18

^69 ቀንድ በዚህ ስፍራ ብርታትን በትእምርትነት ያሳያል

መሐላ ለማሰብ፣
74ከጠላቶቻችን እጅ አውጥቶ፣
ያለ ፍርሀት እንድናገለግለው፣
75በዘመናችንም ሁሉ በቅድስናና
በጽድቅ በፊቱ ሊያቆመን ነው።
76ደግሞም አንተ ሕፃን ሆይ፤ የልዑል
ነቢይ ትባላለህ፤
የጌታን መንገድ ለማዘጋጀት በፊቱ
ትሄዳለህና፤
77የኀጢአታቸውን ስርየት ከማግኘታቸው
የተነሣ፤
ለሕዝቡ የመዳንን ዕውቀት ትሰጥ ዘንድ፣
78ከአምላካችንም በጎ ምሕረት የተነሣ፣
የንጋት ፀሓይ ከሰማይ ወጣችልን፤
79ይኸውም በጨለማ ለሚኖሩት፣
በሞት ጥላ ውስጥም ላሉት እንዲያበራና፣
እግሮቻችንንም ወደ ሰላም
መንገድ እንዲመራ ነው።”

80ሕፃኑም አደገ፤ በመንፈስም ጠነከረ፤ ለእ
ስራኤልም ሕዝብ በይፋ እስከ ታየበት
ቀን ድረስ በበረሓ ኖረ።

### የኢየሱስ መወለድ

2 በዚያን ዘመን፣ የዓለሙ ሁሉ ሕዝብ እን
ዲቈጠርና እንዲመዘገብ ከአውግስጦስ
ቄሳር ትእዛዝ ወጣ። 2ይህም ቄሬኔዎስ የሶርያ
ገዢ በነበረበት ጊዜ የተደረገ የመጀመሪያው
የሕዝብ ቈጠራ ነበር። 3ስለዚህ እያንዳንዱ
ሰው ለመመዝገብ ወደየራሱ ከተማ ሄደ።
4ዮሴፍም ከዳዊት ቤትና ወገን ስለ ነበረ፣
በገሊላ አውራጃ ከምትገኘው ከናዝሬት ከተ
ማ ተነሥቶ የዳዊት ከተማ ወደሆነችው፣ ቤተ
ልሔም ወደምትባል ከተማ ወደ ይሁዳ ወጣ።
5ወደዚያም ለመመዝገብ የተጓዘው፣ የመ
ውለጃ ጊዜዋ ከተቃረበው ከእጮኛው ከማ
ርያም ጋር ነበር። 6በዚያም እንዳሉ የም
ትወልድበት ጊዜ ደረሰ፤ 7የበኵር ልጇ
የሆነውን ወንድ ልጅ ወለደች፤ በጨር
ቅም ጠቀለለችው፤ በእንግዶችም ማረፊያ
ቦታ ስላላገኙ በግርግም አስተኛችው።

### እረኞችና መላእክት

8በዚያው አገር በሌሊት መንጋቸውን
ሲጠብቁ በሜዳ የሚያድሩ እረኞች ነበሩ
። 9የጌታም መልአክ ድንገት መጥቶ
በአጠገባቸው ቆመ፤ የጌታም ክብር
በዙሪያቸው አበራ፤ ታላቅም ፍርሀት
ያዛቸው። 10መል አኩ ግን እንዲህ
አላቸው፤ “አትፍሩ፤ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን
ታ ላ ቅ ደ ስ ታ የ ም ሥ ራ ች
አምጥቼላችኋለሁና። 11ዛሬ በዳዊት ከተማ
መድኅን ተወልዶላችኋልና፤ እር ሱም
ጌታ ክርስቶስ[ሐ] ነው። 12ይህ ምልክት
ይሁናችሁ፤
ሕፃን ልጅ በጨርቅ ተጠቅልሎ በግር
ግም ተኝቶ ታገኛላችሁ።”
13ድንገትም ብዙ የሰማይ ሰራዊት ከመል
አኩ ጋር ታዩ፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ፣
እንዲህ አሉ፤

14“ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም፣ ሰላምም
እርሱ ለሚወዳቸው ሰዎች በምድር ይሁን!”

15መላእክቱ ከእነርሱ ተለይተው ወደ ሰማይ
ከወጡ በኋላ እረኞቹ፣ “ጌታ የገለጠልንን
ይህን የሆነውን ነገር እንድናይ ወደ ቤተ
ልሔም እንሂድ” ተባባሉ።
16እነርሱም ፈጥነው ሄዱ፤ ማርያምንና
ዮሴፍን፣ ሕፃኑንም በግርግም ተኝቶ አገኙ።
17ካዩም በኋላ፣ ስለ ሕፃኑ የተነገራቸውን
ገልጠው አወሩ። 18ይህንንም የሰሙ ሁሉ
እረኞቹ በነገሯቸው ነገር ተደነቁ፤ 19ማርያም
ግን ይህንን ሁሉ በልቧ ይዛ ታሰላስል ነበር።
20እረኞቹም ሁሉም ነገር እንደ ተነገራ
ቸው ሆኖ በማግኘታቸው፣ ስለ ሰሙትና
ስላዩት ሁሉ እግዚአብሔርን እያከበሩና እያመ
ሰገኑ ተመለሱ።

### ሕፃኑን ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ ወሰዱት

21ስምንት ቀን ሆኖት የመገረዣ ጊዜው ሲደ
ርስ፣ ከመፀነሱ በፊት መልአኩ ባወጣለት
ስም ኢየሱስ ተባለ።
22በሙሴ ሕግ መሠረት፣ የመንጻታቸው
ወቅት በተፈፀመ ጊዜ፣ ዮሴፍና ማርያም
ሕፃኑን ለጌታ ለማቅረብ ወደ ኢየሩሳሌም
ይዘውት ወጡ፤ 23ይኸውም በጌታ ሕግ፣
“ተባዕት የሆነ በኵር ሁሉ ለጌታ የተ
ቀደሰ ይሆናል” ተብሎ እንደ ተጻፈ ለመ
ፈጸምና 24ደግሞም በጌታ ሕግ፣ “ሁለት
ዋኖሶች ወይም ሁለት የርግብ ጫጩቶች
እንደ ተባለ፣” መሥዋዕት ለማቅረብ
ነበር።
25በዚያን ጊዜ ጻድቅና ትጉሕ የሆነ
ስምዖን የሚባል አንድ ሰው በኢየሩሳሌም
ይኖር ነበር፤ እርሱም የእስራኤልን መጽ
ናናት የሚጠባበቅና መንፈስ ቅዱስ በላዩ
ያደረ ሰው ነበር። 26ደግሞም የጌታን
መሲሕ ሳያይ እንደማይሞት በመንፈስ
ቅዱስ ተገልጦለት ነበር፤ 27እርሱም በዚህ
ጊዜ በመንፈስ ተመርቶ ወደ ቤተ
መቅደስ ገባ፤ የልጁም ወላጆች በሕጉ ልማድ
መሠረት ተገቢውን ሊፈጽሙለት ሕፃኑን
ኢየሱስን ይዘው በገቡ ጊዜ፣ 28ስምዖን ተቀ
ብሎ ዐቀፈው፤ እግዚአብሔርን እያመሰገነ እንዲህ
አለ፤

[ሐ]11 ወይም መሲሕ፤ *ክርስቶስ* (በግሪክ) *መሲሕ* (በዕብራይስጥ) ማለት ሲሆን የሁለቱም ትርጒም *የተቀባ* ማለት ነው፤ እንዲሁም ቍ 26 ይመ

1፥75 ኤፌ4፥24
1፥76 ቍ17፡32፡35፤ ማቴ3፥3፤11፥9፤ ማር5፥7
1፥77 ኤር31፥34፤ ማቴ1፥21ማር1፥4
1፥78 ሚል4፥2
1፥79 መዝ 107፥14፤ ኢሳ 9፥2፤ 59፥9፤ማቴ4፥16፤ ሉቃ2፥14፤ሐሥ 26፥18
1፥80 ሉቃ2፥40፡52
2፥1 ማቴ22፥17፤ 24፥14፤ሉቃ3፥1
2፥2 ማቴ4፥24፤ ሐሥ 15፥23፡41፤ 21፥3፤ ገላ1፥21
2፥4 ዮሐ7፥42
2፥5 ሉቃ1፥27
2፥9 ሐሥ5፥19
2፥11 ማቴ1፥16፡ 21፤16፥16፡20፤ዮሐ 3፥17፤4፥42፤11፥27፤ 3፥13፤ሐሥ2፥36፤ 3፥20፤5፥31፤9፥22፤ 13፥23፤ሮሜ1፥14፤1 ጢሞ4፥10፤ 1ዮሐ4፥14
2፥12 1ሳሙ2፥34፤ 10፥7፤1ነገ19፥29፤ መዝ86፥17፤ኢሳ 7፥14
2፥14 ኢሳ9፥6፤ 52፥7፤53፥5፤ሚክ5፥5፤ ሉቃ1፥79፤ዮሐ14፥27 ፤ሮሜ5፥1፤ ኤፌ2፥14፡17
2፥16 ቍ 7
2፥19 ቍ 51
2፥20 ማቴ9፥8
2፥21 ሉቃ1፥31፤ 59
2፥22 ዘሌ12፥2-8
2፥23 ዘፀ13፥2፡ 12፡15፤ዘኍ3፥13
2፥24 ዘሌ12፥8
2፥25 ቍ38፤ኢሳ 52፥9፤ሉቃ1፥6፤23፥5
2፥27 ቍ22
2፥29 ቍ26፤ሐሥ 2፥24

29“ጌታ ሆይ፤ ቃል በገባኸው መሠረት፣
አሁን ባሪያህን በሰላም አሰናብተው፤
30ዐይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን፣
31ማዳንህን አይተዋልና፡፡
32ይህም ለአሕዛብ መገለጥን የሚሰጥ ብርሃን፣
ለሕዝብህ ለእስራኤልም ክብር ነው፡፡”

33አባቱና እናቱም ስለ እርሱ በተነገረው
ነገር ተገረሙ፡፡ 34ስምዖንም ባረካቸው፤
እናቱን ማርያምንም እንዲህ አላት፤ “ይህ
ሕፃን በእስራኤል ለብዙዎች መነሣትና
መው
ደቅ ምክንያት እንዲሆን፣ ደግሞም ክፉ
ለሚያስወሩበት ምልክት እንዲሆን ተወስ
ኖአል፤ 35የብዙዎችም የልብ ሐሳብ የተገለጠ
እንዲሆን፣ የአንቺም ነፍስ ደግሞ በሰይፍ
ይወጋል፡፡”
36ደግሞም ከአሴር ወገን የሆነች የፋኑ
ኤል ልጅ፣ ሐና የምትባል ነቢይት በዚያ
ነበረች፤ እርሷም በጣም አርጅታ ነበር፤
በድንግልናዋ ካገባችው ባሏም ጋር ሰባት
ዓመት የኖረች ነበረች፤ 37ዕድሜዋም ሰማ
ንያ አራት ዓመት[ሙ] እስኪሆናት ድረስ ቀኑ
ሌሊት ከቤተ መቅደስ ሳትለይ፣ በጾምና
በጸሎት የምታገለግል መበለት ሆና ቈየች፡፡
38በዚያኑም ጊዜ ቀርባ እግዚአብሔርን አመ
ሰገነች፤ የኢየሩሳሌምንም መቤዠት ለሚጠ
ባበቁ ሁሉ ስለ ሕፃኑ ተናገረች፡፡
39ዮሴፍና ማርያም በጌታ ሕግ የታዘ
ዘውን ሁሉ ከፈጸሙ በኋላ፣ በገሊላ አውራጃ
ወዳለችው ከተማቸው ወደ ናዝሬት ተመ
ለሱ፡፡ 40ሕፃኑም እያደገና እየጠነከረ ሄደ፤
በጥበብ ተሞላ፤ የእግዚአብሔርም ጸጋ በእ
ርሱ ላይ ነበረ፡፡

## ኢየሱስ በዐሥራ ሁለት ዓመቱ ወደ ቤተ መቅደስ ሄደ

41ወላጆቹም በየዓመቱ ለፋሲካ በዓል
ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዱ ነበር፡፡ 42ልጁም
ዐሥራ ሁለት ዓመት በሆነው ጊዜ፣ እንደ
ተለመደው ወደ በዓሉ ወጡ፡፡ 43በዓሉን
ከፈጸሙ በኋላ፣ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ፣
ብላቴናው ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ቀረ፤
ወላጆቹ ግን መቅረቱን አላወቁም ነበር፡፡
44አብሮአቸው ያለ መስሎአቸው፣ የአንድ
ቀን መንገድ ተጓዙ፤ በኋላ ግን ከዘመዶቻ
ቸውና ከወዳጆቻቸው ዘንድ ይፈልጉት
ጀመር፤ 45ባጡትም ጊዜ እየፈለጉት ወደ
ኢየሩሳሌም ተመለሱ፡፡
46ከሦስት ቀንም በኋላ፣ በመምህራን መካ
ከል ተቀምጦ ሲያዳምጣቸውና ጥያቄ ሲያ
ቀርብላቸው በቤተ መቅደስ ውስጥ አገ
ኙት፤ 47የሰሙትም ሁሉ በማስተዋሉና
በመልሱ ይደነቁ ነበር፡፡ 48ወላጆቹም ባዩት
ጊዜ ተገረሙ፤ እናቱም፣ “ልጄ ሆይ፤ ለምን
እንዲህ አደረግኸን? አባትህና እኔኮ ተጨ
ንቀን ስንፈልግህ ነበር” አለችው፡፡
49እርሱም፣ “ለምን ፈለጋችሁኝ? በአባቴ
ቤት መገኘት እንደሚገባኝ አላወቃችሁ
ምን?” አላቸው፡፡ 50እነርሱ ግን የተናገራ
ቸው ነገር አልገባቸውም፡፡
51ከዚያም አብሮአቸው ወደ ናዝሬት ወረደ፤
ይታዘዝላቸውም ነበር፡፡ እናቱም ይህን
ሁሉ ነገር በልቧ ትጠብቀው ነበር፡፡ 52ኢየ
ሱስም በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚ
አብሔርና በሰው ፊት አደገ፡፡

## የመጥምቁ ዮሐንስ ስብከት

3፥2-10 ተጓ ምብ - ማቴ 3፥1-10፤ ማር 1፥3-5
3፥16-17 ተጓ ምብ - ማቴ 3፥11፡12፤ ማር 1፥7፡8

3 ጢባርዮስ ቄሣር በነገሠ በዐሥራ
አምስተኛው ዓመት፣ ይኸውም ጳን
ጥዮስ ጲላጦስ የይሁዳ ገዥ፣ ሄሮድስ የገሊላ
አራተኛው ክፍል ገዥ፣ ወንድሙ ፊልጶስ
የኢጡርያስና የጥራኮኒዶስ የአራተኛው
ክፍል ገዥ ሊሳኒዮስም የሳቢላኒስ አራተኛው
ክፍል ገዥ በነበሩበት ጊዜ፣ 2ሐናና
ቀያፋም ሊቃነ ካህናት ሳሉ፣ የእግዚአብሔር
ቃል ወደ ዘካርያስ ልጅ ወደ ዮሐንስ
በምድረ በዳ መጣ፡፡ 3እርሱም ለኀጢአት
ስርየት የሚሆን የንስሓን ጥምቀት እየ
ሰበከ በዮርዳኖስ ወንዝ አካባቢ ወዳሉት
ስፍራዎች ሁሉ መጣ፤ 4ይኸውም ነቢዩ
ኢሳይያስ በመጽሐፉ እንዲህ ሲል በጻፈው
ቃል መሠረት ነበር፤

“በበረሓ እንዲህ ብሎ የሚጮኽ ሰው ድምፅ፤
‘የጌታን መንገድ አዘጋጁ፤
ጐዳናውንም አቅኑ፤
5ሸለቆው ሁሉ ይሞላል፤
ተራራውና ኰረብታው ሁሉ ዝቅ ይላል፤
ጠማማው መንገድ ቀና፣
ሸካራውም ጐዳና ትክክል ይሆናል፤
6የሰውም ዘር ሁሉ የእግዚአብሔርን
ማዳን ያያል፡፡’ ”

7ዮሐንስም በእርሱ እጅ ሊጠመቁ የወጡ
ትን ሰዎች እንዲህ ይላቸው ነበር፤ “እና
ንት የእፉኝት ልጆች፣ ከሚመጣው ቍጣ
እንድትሸሹ ማን መከራችሁ? 8እንግዲህ ለን
ስሓ የሚገባ ፍሬ አፍሩ፤ ደግሞም በል
ባችሁ፣ ‘አብርሃም አባታችን አለን’ ማለ
ትን አትጀምሩ፤ እግዚአብሔር ከእነዚህ ድን
ጋዮች ለአብርሃም ልጆች ማስነሣት እንደ
ሚችል እነግራችኋለሁና፡፡ 9አሁን እንኳ
ምሳር በዛፎች ሥር ተቀምጦአል፤ መልካም

2፥30 ኢሳ40፥5፤ 52፥10፤ሉቃ3፥6
2፥32 ኢሳ42፥6፤ 49፥6፤ሐሥ13፥47፤ 26፥23
2፥34 ኢሳ8፥14፤ ማቴ12፥46፤21፥44፤1 ቆሮ1፥23፤ 2ቆሮ2፥16፤ገላ5፥11፤ 1ጴጥ2፥7፡8
2፥36 ሐሥ21፥9
2፥37 ሐሥ13፥3፤ 14፥23፤1ጢሞ5፥5፡9
2፥38 ቍ 25፤ ኢሳ 40፥2፤52፥9፤ ሉቃ1፥68፤24፥21
2፥39 ቍ51፤ ማቴ2፥23
2፥40 ቍ52፤ ሉቃ1፥80
2፥41 ዘፀ23፥15፤ ዘዳ16፥1-8፤ ሉቃ22፥8
2፥47 ማቴ7፥28
2፥48 ማቴ12፥46፤ ሉቃ3፥23፤4፥22
2፥49 ዮሐ2፥16
2፥50 ማር9፥32
2፥51 ቍ19፡39፤ ማቴ 2፥23
2፥52 ቍ40፤ 1ሳሙ2፥26፤ ምሳ3፥4፤ሉቃ1፥80
3፥1 ማቴ14፥1፤ 27፥2
3፥2 ማቴ3፥1፤ 26፥3፤ ሉቃ1፥13
3፥3 ቍ16፤ማር1፥4
3፥6 መዝ98፥2፤ኢሳ 40፥3-5፤42፥16፤ 52፥10፤ሉቃ2፥30
3፥7 ማቴ12፥34፤ 23፥33፤ሮሜ1፥18
3፥8 ኢሳ51፥2፤ ሉቃ19፥9፤ዮሐ8፥33፡39፤ሐሥ13፥26፤ሮሜ 4፥1፡11፡12፡16፡17፤ 9፥7፡8፤ገላ3፥7
3፥9 ማቴ3፥10

[ሙ]37 ወይም ለሰማንያ አራት ዓመት መበለት የነበረች

ፍሬ የማያፈራም ዛፍ ሁሉ ተቈርጦ ወደ
እሳት ይጣላል::”
[10]ሕዝቡም፣ “ታዲያ፣ ምን እናድርግ?”
ብለው ጠየቁት::
[11]ዮሐንስም፣ “ሁለት ልብስ ያለው ምንም
ለሌለው ያካፍል፤ ምግብ ያለውም እንዲሁ
ያድርግ” ብሎ መለሰላቸው::
[12]ቀረጥ ሰብሳቢዎችም ሊጠመቁ ወደ
እርሱ መጥተው፣ “መምህር ሆይ፤ እኛስ
ምን እናድርግ?” አሉት::
[13]እርሱም፣ “ከታዘዛችሁት በላይ ቀረጥ
አትሰብስቡ” አላቸው::
[14]ወታደሮች ደግሞ፣ “እኛስ ምን እና
ድርግ?” ብለው ጠየቁት::
እርሱም፣ “የማንንም ገንዘብ በግፍ አትን
ጠቁ፤ ሰውንም በሐሰት አትክሰሱ፤ ደመ
ወዛችሁ ይብቃችሁ” አላቸው::
[15]ሕዝቡ በጕጕት እየተጠባበቁ ሳሉ፣
“እርሱ ክርስቶስ ይሆንን?” እያሉ ሁሉም
በልባቸው ስለ ዮሐንስ ያሰላስሉ ነበር::
[16]ዮሐንስ ለሁሉም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
“እኔ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤ ነገር ግን ከእኔ
የሚበረታ ይመጣል፤ እኔም የእርሱን የጫ
ማ ማሰሪያ መፍታት የሚገባኝ
አይደለሁም፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስና
በእሳት ያጠምቃ ችኋል፤ [17]ዐውድማውን ፈ
ጽሞ ለማጥራትና ስንዴውንም ወደ ጐተራ
ው ለመክተት መንሹ በእጁ ነው፤ ገለባውን
ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል::” [18]ዮሐ
ንስም በብዙ ሌሎች የምክር ቃላት ሕ
ዝቡን እያስጠነቀቀ ወንጌልን ሰበከላቸው::
[19]ነገር ግን ዮሐንስ፣ የአራተኛውን ክፍል
ገዥ ሄሮድስን የወንድሙ ሚስት በነበረ
ችው በሄሮድያዳ ምክንያትና ስለ ሌሎች
ሥራዎቹ በገሠጸው ጊዜ፣ [20]ሄሮድስ ይህን
በሌላው ሁሉ ላይ በመጨመር፣ ዮሐንስን
ወህኒ ቤት አስገባው::

### የኢየሱስ መጠመቅና የትውልድ ሐረጉ

3፥21፡22 ተጓ ምብ - ማቴ 3፥13-17 ማር 1፥9-11
3፥23-38 ተጓ ምብ - ማቴ 1፥1-17

[21]ሕዝቡ ሁሉ ከተጠመቀ በኋላ ኢየሱ
ስም ተጠመቀ፤ እየጸለየም ሳለ ሰማይ
ተከፈተ፤ [22]መንፈስ ቅዱስም በአካላዊ ቅርጽ
እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ፤ ከሰማ
ይም፣ “የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፤ በአ
ንተ ደስ ይለኛል” የሚል ድምፅ መጣ::
[23]ኢየሱስ አገልግሎቱን ሲጀምር ዕድሜ
ው ሠላሳ ዓመት ያህል ነበር፤ ሕዝቡም
እንደ መሰላቸው የዮሴፍ ልጅ ሆኖ፣
የኤሊ ልጅ፣ [24]የማቲ ልጅ፣
የሌዊ ልጅ፣ የሚልኪ ልጅ፣
የዮና ልጅ፣ የዮሴፍ ልጅ፣
[25]የማታትዩ ልጅ፣ የአሞጽ ልጅ፣
የናሆም ልጅ፣ የኤሲሊም ልጅ፣
የናጌ ልጅ፣ [26]የማአት ልጅ፣
የማታትዩ ልጅ፣ የሴሜይ ልጅ፣
የዮሴፍ ልጅ፣ የዮዳ ልጅ፣
[27]የዮናን ልጅ፣ የሬስ ልጅ፣
የዘሩባቤል ልጅ፣ የሰላትያል ልጅ፣
የኔሪ ልጅ፣ [28]የሚልኪ ልጅ፣
የሐዲ ልጅ፣ የዮሳስ ልጅ፣ የቆሳም ልጅ፣
የኤልሞዳም ልጅ፣ የኤር ልጅ፣
[29]የዮሴዕ ልጅ፣ የኤልዓዘር ልጅ፣
የዮራም ልጅ፣ የማጣት ልጅ፣
የሌዊ ልጅ፣ [30]የስምዖን ልጅ፣
የይሁዳ ልጅ፣ የዮሴፍ ልጅ፣
የዮናም ልጅ፣ የኤልያቄም ልጅ፣
[31]የሜልያ ልጅ፣ የማይናን ልጅ፣
የማጣት ልጅ፣ የናታን ልጅ፣
የዳዊት ልጅ፣ [32]የእሴይ ልጅ፣
የኢዮቤድ ልጅ፣ የቦዔዝ ልጅ፣
የሰልሞን[ረ] ልጅ፣ የነአሶን ልጅ፣
[33]የአሚናዳብ ልጅ፣ የአራም[ሰ] ልጅ፣
የአሮኒ ልጅ፣ የኤስሮም ልጅ፣ የፋሬስ ልጅ፣
የይሁዳ ልጅ፣ [34]የያዕቆብ ልጅ፣
የይስሐቅ ልጅ፣ የአብርሃም ልጅ፣
የታራ ልጅ፣ የናኮር ልጅ፣
[35]የሴሮህ ልጅ፣ የራጋው[ሸ] ልጅ፣
የፋሌቅ ልጅ፣ የአቤር ልጅ፣
የሳላ ልጅ፣ [36]የቃይንም ልጅ፣
የአርፋክስድ ልጅ፣ የሴም ልጅ፣
የኖኅ ልጅ፣ የላሜህ ልጅ፣
[37]የማቱሳላ ልጅ፣ የሄኖክ ልጅ፣
የያሬድ ልጅ፣ የመላልኤል ልጅ፣
የቃይናን ልጅ፣ [38]የሄኖስ ልጅ፣
የሤት ልጅ፣ የአዳም ልጅ፣
የእግዚአብሔር ልጅ::

### የኢየሱስ መፈተን

4፥1-13 ተጓ ምብ – ማቴ 4፥1-11፤ ማር 1፥12፡13

4 ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ
ከዮርዳኖስ እንደ ተመለሰ መንፈስ
ወደ በረሓ ወሰደው፤ [2]በዚያም አርባ ቀን
በዲያብሎስ ተፈተነ፤ በእነዚያም ቀናት
ምንም ሳይበላ ቈይቶ በመጨረሻ ተራበ::
[3]ዲያብሎስም፣ “የእግዚአብሔር ልጅ ከሆ
ንህ፣ እስቲ ይህ ድንጋይ እንጀራ እንዲ
ሆን እዘዘው” አለው::
[4]ኢየሱስም፣ “ ‘ሰው በእንጀራ ብቻ አይ
ኖርም’ ተብሎ ተጽፎአል” ብሎ መለሰለት::

3፥10 ቍ12፡14፤ ሐሥ 2፥37፤16፥30
3፥11 ኢሳ58፥7፤ ሕዝ 18፥7
3፥12 ሉቃ7፥29
3፥13 ሉቃ19፥8
3፥14 ዘፀ23፥1፤ ዘሌ19፥11
3፥15 ማቴ3፥1፤ ዮሐ1፥19፡20፤ሐሥ 13፥25
3፥16 ቍ3፤ማር 1፥4፤ዮሐ1፥26፡33፤ 11፥16፤19፥4
3፥17 ኢሳ30፥24፤ ማቴ13፥30፤25፥41
3፥19 ቍ1፤ ማቴ14፥1
3፥20 ማቴ14፥3፡4
3፥21 ማቴ14፥23፤ ማር1፥35፤6፥46፤ ሉቃ5፥16፤6፥12፤9፥18 ፡28፤11፥1
3፥22 ኢሳ42፥1፤ ማቴ3፥17፤ዮሐ1፥32፡ 33፤ሐሥ10፥38
3፥23 ማቴ4፥17፤ ሉቃ1፥27፤ሐሥ1፥1
3፥27 ማቴ1፥12
3፥31 2ሳሙ5፥14፤ 1ዜና3፥5
3፥33 ሩት4፥18-22፤1ዜና2፥10-12
3፥34 ዘፍ11፥24፡ 26
3፥36 ዘፍ5፥28-32፤ 11፥12
3፥37 ዘፍ5፥12-25
3፥38 ዘፍ5፥1፡ 2፡6-9
4፥1 ቍ14፡18፤ሕዝ 37፥1፤ሉቃ1፥15፡35፤2 ፥27፤3፥3፡16፡21፡22፤1 0፥21
4፥2 ዘፀ34፥28፤ 1ነገ19፥8፤ዕብ4፥15
4፥3 ማቴ4፥3
4፥4 ዘዳ8፥3

[ረ]32 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ሳላ ይላሉ ሌሎች ቅጆች ይለያያሉ
[ሰ]33 አንዳንድ ቅጆች የአሚናዳብ ልጅ የአዲም ልጅ የአርኒ ልጅ ይላሉ፤
[ሸ]35 የግሪኩ ቅጅ *‘የራጋው’*

5ከዚያም ዲያብሎስ ወደ አንድ ከፍታ
ቦታ አውጥቶት የዓለምን መንግሥታት ሁሉ
በቅጽበት አሳየው፤ 6እንዲህም አለው፤ “የእ
ነዚህ መንግሥታት ሥልጣንና ክብር ሁሉ
ለእኔ ተሰጥቶአል፤ እኔም ለምወደው ስለ
ምሰጥ፣ ለአንተ እሰጥሃለሁ፤ 7ስለዚህ ብት
ሰግድልኝ ይህ ሁሉ የአንተ ይሆናል።”
8ኢየሱስም መልሶ፣ “ ‘ለጌታ ለአምላክህ ስገድ፤
እርሱንም ብቻ አምልክ’ ተብሎ ተጽፎአል”
አለው።
9ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌም ወስዶ በቤተ
መቅደስ ጒልላት ላይ አቆመውና እንዲህ
አለው፤ “የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፣ እስቲ ራ
ስ ህን ከዚህ ወደ ታች ወርውር፤ 10ምክን
ያቱም እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፤

“ ‘ይጠብቁህ ዘንድ፣
መላእክቱን ስለ አንተ ያዛቸዋል፤
11እግርህም ከድንጋይ ጋር እንዳይጋጭ፣
በእጆቻቸው ወደ ላይ አንሥተው
ይይዙሃል።’ ”

12ኢየሱስም፣ “ ‘ጌታ አምላክህን
አትፈታተ ነው’ ተብሎአል” ብሎ
መለሰለት።
13ዲያብሎስም ፈተናውን ሁሉ ከጨረሰ
በኋላ ሌላ አመቺ ጊዜ እስኪያገኝ ድረስ
ከእርሱ ተለየ።

## ኢየሱስ በናዝሬት ተቀባይነት ማጣቱ

14ኢየሱስም በመንፈስ ኀይል ወደ ገሊላ
ተመለሰ፤ ዝናውም በአካባቢው ባለው
አገር ሁሉ ወጣ። 15እርሱም በምኵራባ
ቸው ያስተምር ነበር፤ ሰውም ሁሉ ያመ
ሰግነው ነበር።
16ከዚያም ወዳደገበት ከተማ ወደ ናዝ
ሬት መጣ፤ እንደ ልማዱም በሰንበት ወደ
ምኵራብ ገባ፤ ሊያነብም ተነሥቶ ቆመ።
17የነቢዩ ኢሳይያስ ጥቅልል መጽሐፍም
ተሰጠው፤ ጥቅልሉንም መጽሐፍ በተረተ
ረው ጊዜ እንዲህ ተብሎ የተጻፈበትን
ክፍል አገኘ፤

18“የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤
ለድኾች ወንጌልን እንድሰብክ፣
እርሱ ቀብቶኛልና፤
ለታሰሩት መፈታትን፣
ለታወሩትም ማየትን እንዳውጅ፣
የተጨቈኑትን ነጻ እንዳወጣ፣
19የተወደደችውንም የጌታን ዓመት
እንዳውጅ ልኮኛል።”

20ከዚያም መጽሐፉን ጠቅልሎ ለአገል
ጋዩ መልሶ ሰጠውና ተቀመጠ፤ በምኵራብ
የነበሩትም ሁሉ ትኵር ብለው ይመለከቱት

4፥5 ማቴ24፥14
4፥6 ዮሐ12፥31፤ 14፥30፤1ዮሐ5፥19
4፥8 ዘዳ6፥13
4፥11 መዝ 91፥11፡12
4፥12 ዘዳ6፥16
4፥13 ዮሐ14፥30፤ ዕብ4፥15
4፥14 ማቴ4፥12፤ 9፥26
4፥15 ማቴ4፥23
4፥16 ማቴ2፥23፤ 13፥54፤1ጢሞ4፥13
4፥18 ማር16፥15፤ ዮሐ3፥34
4፥19 ዘሌ25፥10፤ መዝ102፥20፤103፥6፤ ኢሳ42፥7፤ 49፥8፡9፤ 58፥6፤61፥1፡2
4፥20 ቊ17፤ ማቴ26፥55
4፥21 ማቴ1፥22
4፥22 ማቴ13፥54፡ 55፤ ዮሐ 6፥42፤ 7፥15
4፥23 ቊ16፤ ማቴ2፥23፤ማር1፥21-28፤2፥1-12
4፥24 ማቴ13፥57፤ ዮሐ4፥44
4፥25 1ነገ17፥1፤ 18፥1፤ያዕ5፥17፡18፤ ራእ 11፥6
4፥26 1ነገ17፥8-16፤ ማቴ11፥21
4፥27 2ነገ5፥1-14
4፥29 ዘኍ15፥35፤ ሐሥ7፥58፤ ዕብ13፥12
4፥30 ዮሐ8፥59፤ 10፥39
4፥31 ቊ23፤ ማቴ4፥13
4፥32 ቊ36፣ ማቴ7፥28፡29
4፥34 ቊ41፤ ማቴ8፥29፤ማር1፥24፤ ያዕ2፥19
4፥35 ቊ39፡41፤ ማቴ8፥26፤ሉቃ8፥24

ነበር። 21እርሱም፣ “ይህ በጆሮአችሁ የሰማ
ችሁት የመጽሐፍ ቃል ዛሬ ተፈጸመ”
ይላቸው ጀመር።
22ሁሉም ስለ እርሱ በበጎ ይናገሩ ነበር፤
ደግሞም ከአንደበቱ በሚወጣ የጸጋ ቃል
እየተገረሙ፣ “ይህ የዮሴፍ ልጅ አይደለ
ምን?” ይሉ ነበር።
23እርሱም፣“ ‘ባለ መድኀኒት ሆይ፤ ራስ
ህን ፈውስ፤ በቅፍርናሆም ስታደርግ የሰ
ማነውን ነገር እዚህ በራስህ ከተማ ደግሞ
አድርግ’ ” የሚለውን ምሳሌ እንደም
ትጠቅሱብኝ ጥርጥር የለውም” አላቸው።
24ደግሞም እንዲህ አላቸው፤ “እውነት
እላችኋለሁ፤ ነቢይ በገዛ አገሩ አይከበ
ርም። 25ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ፤
ሰማይ ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ተዘግቶ
ጽኑ ራብ በምድሪቱ ሁሉ ላይ በነበረበት
በኤልያስ ዘመን፣ ብዙ መበለቶች በእስራ
ኤል ነበሩ፤ 26ኤልያስ ከእነዚህ መካከል
ወደ አንዷም አልተላከም፤ ነገር ግን በሲ
ዶና አገር በሰራፕታ ወደ ነበረችው መበ
ለት ተላከ። 27በነቢዩ በኤልሳዕ ዘመንም
በእስራኤል ብዙ ለምጻሞች[ሽ] ነበሩ፤ ነገር
ግን ከሶርያዊው ከንዕማን በቀር ከእነዚያ
መካካል ማንም አልነጻም።”
28በምኵራብ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ይህን
በሰሙ ጊዜ በቍጣ ገነፈሉ፤ 29ከተቀመጡብ
ትም ተነሥተው ከከተማው አስወጡት፤ ቊል
ቊል ሊጥሉትም ከተማቸው ወደ ተሠራች
በት ኰረብታ አፋፍ ወሰዱት፤ 30እርሱ
ግን በመካከላቸው ሰንጥቆ ሄደ።

## ኢየሱስ ርኩስ መንፈስ አስወጣ

4፥31-37 ተጓ ምብ – ማር 1፥21-28

31ከዚያም በገሊላ አውራጃ ወደምት
ገኘው ከተማ ወደ ቅፍርናሆም ወረደ፤ በዚ
ያም በሰንበት ዕለት ሕዝቡን ያስተምር
ጀመር፤ 32የሚናገረው በሥልጣን ስለ ነበር
በትምህርቱ ተደነቁ።
33በምኵራብም የርኩስ ጋኔን መንፈስ
ያደ ረበት ሰው ነበረ፤ እርሱም ከፍ ባለ
ድምፅ ጮኾ፣ 34“ወዮ! የናዝሬቱ ኢየሱስ
ሆይ፤ ምን የሚያገናኘን ጉዳይ አለ?
የመጣኸው ልታጠፋን ነውን? አንተ ማን
እንደ ሆንህ ዐው ቃለሁ፤ አንተ የእግዚአብሐ
ር ቅዱስ ነህ!” አለው።
35ኢየሱስም፣ “ጸጥ ብለህ ከዚህ ሰው ውጣ!”
ብሎ ገሠጸው። ጋኔኑም ሰውየውን በሕ
ዝቡ ሁሉ ፊት ጣለውና ምንም ጒዳት
ሳያደርስበት ለቆት ወጣ።

[ሽ]27 የግሪኩ ቃል የግድ ከለምጽ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን የተለያየ የቈዳ በሽታዎች ለመግለጽ ጥቅም ላይ ይውላል

[36]ሰዎቹም ሁሉ ተገረሙ፤ እርስ በእርሳቸ
ውም፣ "ለመሆኑ ይህ ትምህርት ምንድን ነው?
በሥልጣንና በኀይል ርኩሳን መናፍስትን ያዛል፤
እነርሱምኮ ይወጣሉ" ተባባሉ። [37]የእርሱም
ዝና በአካባቢው ወዳለው ስፍራ ሁሉ ወጣ።

## ኢየሱስ ብዙ በሽተኞችን ፈወሰ

4፥38-41 ተጓ ምብ – ማቴ 8፥14-17
4፥38-43 ተጓ ምብ - ማር 1፥29-38

[38]ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከምኵራብ ወጥቶ
ወደ ስምዖን ቤት ገባ። የስምዖንም አማት
ኀይለኛ ትኵሳት ይዞአት ታማ ነበር፤ እን
ዲፈውሳትም ስለ እርሷ ለመኑት። [39]እር
ሱም ወደ ተኛችበት ጠጋ ብሎ በማጐንበስ
ትኵሳቱን ገሠጸው፤ ትኵሳቱም ለቀቃትና
ወዲያው ተነሥታ አስተናገደቻቸው።
[40]ፀሓይ መጥለቂያ ሳይም፣ የተለያየ ሕመም
ያደረባቸውን ሰዎች ሁሉ ወደ እርሱ አመጡ፤
እርሱም በእያንዳንዳቸው ላይ እጁን
ጭኖ ፈወሳቸው። [41]አጋንንትም ደግሞ፣
"አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ!" እያሉና
እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ወጡ። እርሱ ግን
ገሠጻ ቸው፤ ክርስቶስ[ቀ] መሆኑንም ያውቁ
ስለ ነበር፣ አንዳች እንዲናገሩ
አልፈቀደላቸውም።
[42]ሲነጋም ኢየሱስ ወደ አንድ ገለልተኛ
ስፍራ ሄደ፤ ሕዝቡም ይፈልጉት ነበር፤ እርሱ
ወዳለበትም ቦታ መጡ፤ ከእነርሱ ተለይቶ
እንዳይሄድ ሊከለክሉት ሞከሩ። [43]እርሱ
ግን፣ "ወደ ሌሎቹም ከተሞች ሄጄ የእግዚ
አብሔርን መንግሥት ወንጌል መስበክ
ይገባኛል፤ የተ ላክሁት ለዚሁ ዐላማ ነውና"
አላቸው። [44]በይሁዳ ምኵራቦችም
መስበኩን ቀጠለ።

## የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት ተጠሩ

5፥1-11 ተጓ ምብ – ማቴ 4፥18-22፤ ማር 1፥16- 20፤ ዮሐ 1፥40-42

[5] ሕዝቡ ዙሪያውን እያጨናነቁት የሚያስ
ተምረውን የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰሙ፣
ኢየሱስ በጌንሳሬጥ[ተ] አጠገብ ቆሞ ነበር፤
[2]በዚህ ጊዜ ሁለት ጀልባዎች በባሕሩ ዳርቻ
ቆመው አየ፤ ዓሣ አጥማጆቹ ግን ከጀልባ
ዎቹ ወርደው መረባቸውን ያጥቡ ነበር።
[3]ከጀልባዎቹም መካከል የስምዖን ወደ
ነበረችው ገብቶ፣ ከምድር ጥቂት ፈቀቅ
እንዲያደርጋት ለመነው፤ ከዚያም ጀልባዋ
ላይ ተቀምጦ ሕዝቡን ያስተምር ጀመር።
[4]ንግግሩን በጨረሰ ጊዜ ስምዖንን፣ "ወደ
ጥልቁ ውሃ ፈቀቅ በልና ዓሣ ለመያዝ መረ
ባችሁን ጣሉ" አለው።
[5]ስምዖንም መልሶ፣ "መምህር ሆይ፤ ሌሊ
ቱን ሙሉ ስንደክም አድረን ምንም አል
ያዝንም፤ አንተ ካልህ ግን መረቦቹን
እጥላለሁ" አለው።

4፥36 ቀኊ32፤ ማቴ7፥28፡29፤10፥1
4፥37 ቀኊ14፤ ማቴ9፥26
4፥39 ቀኊ35፡41
4፥40 ማቴ4፥23፤ ማር5፥23
4፥41 ቀኊ35፤ማቴ 4፥3፤8፥4
4፥43 ማቴ3፥2
4፥44 ማቴ4፥23
5፥1 ማር4፥14፤ ዕብ 4፥12
5፥3 ማቴ13፥2
5፥4 ዮሐ21፥6
5፥5 ሉቃ8፥24፡45፤ 9፥33፡49፤17፥13፤ ዮሐ21፥3
5፥6 ዮሐ21፥11
5፥8 ዘፍ18፥27፤ ኢዮ 42፥6፤ኢሳ6፥5
5፥10 ማቴ14፥27
5፥11 ቀኊ28፤ ማቴ4፥19
5፥12 ማቴ8፥2
5፥14 ዘሌ14፥2-32፣ ማቴ8፥4
5፥15 ማቴ9፥26
5፥16 ሉቃ3፥21
5፥17 ማቴ15፥1፤ ማር5፥30፤ሉቃ 2፥46፤6፥19

[6]እንደዚያም ባደረጉ ጊዜ እጅግ ብዙ ዓሣ
ያዙ፤ መረባቸውም ይበጣጠስ ጀመር። [7]በሌላ
ጀልባ የነበሩት ባልንጀሮቻቸው መጥተው
እንዲያግዟቸውም በምልክት ጠሯቸው፤
እነርሱም መጥተው ሁለቱን ጀልባዎች
በዓሣ ሞሏቸው፣ ጀልባዎቹም መስመጥ
ጀመሩ።
[8]ስምዖን ጴጥሮስም ይህን ባየ ጊዜ በኢየ
ሱስ ጕልበት ላይ ወድቆ፣ "ጌታ ሆይ፤
እኔ ኀጢአተኛ ሰው ነኝና ከእኔ ተለይ"
አለው። [9]ይህንን ያለው እርሱና ከእርሱ
ጋር የነበሩት በያዙት ዓሣ ብዛት ስለ ተደ
ነቁ ነው፤ [10]ደግሞም የስምዖን ባልንጀሮች
የነበሩት የዘብዴዎስ ልጆች፣ ያዕቆብና
ዮሐንስም ተደነቁ።
ኢየሱስም ስምዖንን፣ "አትፍራ፤ ከእን
ግዲህ ሰውን የምታጠምድ ትሆናለህ" አለው።
[11]እነርሱም ጀልባዎቹን ወደ ምድር
ካስጠጉ በኋላ ሁሉን ትተው ተከተሉት።

## ለምጻሙ ሰው

5፥12-14 ተጓ ምብ - ማቴ 8፥2-4፤ ማር 1፥40-44

[12]ኢየሱስ ከከተሞች በአንዱ በነበረበት
ጊዜ፣ አንድ ለምጽ የወረሰው[ቸ] ሰው በዚያው
ከተማ ነበር፤ ይህ ሰው ኢየሱስን ባየው ጊዜ
በፊቱ ተደፋና፣ "ጌታ ሆይ፤ ብትፈቅድ
እኮ ልታነጻኝ ትችላለህ" ብሎ ለመነው።
[13]ኢየሱስም እጁን ዘርግቶ ዳሰሰውና፣ "እፈ
ቅዳለሁ፤ ንጻ!" አለው፤ ወዲያውም ለምጹ
ጠፋለት።
[14]ኢየሱስም፣ "ይህን ለማንም አትናገር፤
ነገር ግን ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ፤
ለእነርሱ ምስክር እንዲሆንም ስለ መንጻ
ትህ ሙሴ ያዘዘውን መሥዋዕት አቅርብ"
ሲል አዘዘው።
[15]ይሁን እንጂ ስለ እርሱ የሚወራው
ወሬ ይበልጥ እየሰፋ ሄደ፤ እጅግ ብዙ
ሰዎችም እርሱ የሚናገረውን ለመስማትና
ካለባቸው ደዌ ለመፈወስ ይሰበሰቡ ነበር።
[16]ኢየሱስ ግን ብዙ ጊዜ ወደ ገለልተኛ
ስፍራ ወጥቶ ይጸልይ ነበር።

## ኢየሱስ ሽባውን ሰው ፈወሰ

5፥18-26 ተጓ ምብ-ማቴ 9፥2-8፤ ማር 2፥3-12

[17]አንድ ቀን ኢየሱስ እያስተማረ ነበር፤
በዚያም ከገሊላና ከይሁዳ መንደሮች ሁሉ
እንዲሁም ከኢየሩሳሌም የመጡ ፈሪሳው
ያንና የሕግ መምህራን ተቀምጠው ነበር፤
ይፈውስም ዘንድ የጌታ ኀይል ከእርሱ
ጋር ነበረ። [18]በዚያን ጊዜም፣ ሰዎች አንድ

[ቀ]41 ወይም መሲሕ
[ተ]1 የገሊላ ባሕር ነው
[ቸ]12 የግሪኩ ቃል የግድ ከለምጽ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን የተለያዩ የቈዳ በሽታዎችንም ለመግለጽ ጥቅም ላይ ይውላል።

ሽባ በዐልጋ ተሸክመው አመጡ፤ ኢየሱስ
ፊት ለማኖርም ወደ ቤት ሊያስገቡት ሞከሩ፤
19ከሕዝቡም ብዛት የተነሣ ቤቱ ውስጥ
ማስገባት ስላቃታቸው፣ ጣራው ላይ ወጥ
ተው የቤቱን ክዳን በመንደል በሽተኛውን
ከነዐልጋው በሕዝቡ መካካል ቀጥታ ኢየ
ሱስ ፊት አወረዱት።
20ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ፣ “አንተ
ሰው፤ ኀጢአትህ ተሰርዮልሃል” አለው።
21ጸሐፍትና ፈሪሳውያንም፣ “ይህ አም
ላክን በመዳፈር እንዲህ የሚናገር ማን
ነው? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በስተቀር
ኀጢአትን ሊያስተሰረይ ማን ይችላል?”
ብለው ያስቡ ጀመር።
22ኢየሱስም ሐሳባቸውን ስለ ተረዳ እንዲህ
አላቸው፤ “ለምን በልባችሁ እንዲህ ታስባ
ላችሁ? 23‘ኀጢአትህ ተሰረየችልህ’ ከማለ
ትና ‘ተነሥተህ ሂድ’ ከማለት የትኛው
ይቀላል? 24ነገር ግን ይህን ያልሁት የሰው
ልጅ በምድር ላይ ኀጢአትን ለማስተስረይ
ሥልጣን እንዳለው ታውቁ ዘንድ ነው።”
ከዚያም ሽባውን ሰው፣ “ተነሥተህ ዐልጋ
ህን ተሸክመህ ወደ ቤትህ ሂድ እልሃለሁ”
አለው። 25እርሱም ወዲያው ተነሥቶ በፊ
ታቸው ቆመ፤ ተኝቶበት የነበረውንም ተሸ
ክሞ፣ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ወደ ቤቱ
ሄደ። 26በዚህ ጊዜ ሁሉንም መገረም ያዛ
ቸው፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ፣ “ዛሬኮ
ድንቅ ነገር አየን” እያሉ በፍርሀት ተዋጡ።

## የሌዊ መጠራት

5፥27-32 ተጓ ምብ –ማቴ 9፥9-13፤ ማር 2፥14-17

27ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከዚያ ወጥቶ ሄደ፤
ሌዊ የተባለ አንድ ቀረጥ ሰብሳቢም በቀ
ረጥ መቀበያው ቦታ ተቀምጦ አየውና፣
“ተከተለኝ” አለው፤ 28እርሱም ሁሉን ትቶ
ተነሥቶ ተከተለው።
29ሌዊም ለኢየሱስ በቤቱ ትልቅ ግብዣ
አደረገ፤ ብዙ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና ሌሎች
ሰዎችም ከእነርሱ ጋር በማእድ ተቀምጠው
ነበር። 30ፈሪሳውያንና ጸሐፍታቸውም “ከቀ
ረጥ ሰብሳቢዎችና ‘ከኀጢአተኞች’ ጋር የም
ትበሉትና የምትጠጡት ለምንድን ነው?”
እያሉ በደቀ መዛሙርቱ ላይ አጕረመረሙ።
31ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
“በሽተኞች እንጂ ጤነኞች ሐኪም አያስፈ
ልጋቸውም፤ 32እኔም ኀጢአተኞችን ወደ
ንስሓ ልመልስ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አል
መጣሁም።”

5፥20 ሉቃ7፥48፡49
5፥21 ኢሳ43፥25
5፥24 ማቴ8፥20
5፥26 ማቴ9፥8
5፥27 ማቴ4፥19
5፥28 ቍ11፤ማቴ 4፥19
5፥29 ሉቃ15፥1
5፥30 ማቴ9፥11፤ ሐሥ23፥9
5፥32 ዮሐ3፥17
5፥33 ሉቃ7፥18፤ ዮሐ1፥35፤3፥25፡26
5፥34 ዮሐ3፥29
5፥35 ሉቃ9፥22፤ 17፥22፤ዮሐ16፥5-7
6፥1 ዘዳ23፥25
6፥2 ማቴ12፥2
6፥3 ኢሳ21፥6
6፥4 ዘሌ24፥5፡9
6፥5 ማቴ8፥20
6፥6 ቍ1
6፥7 ማቴ12፥2፡10
6፥8 ማቴ9፥4

## ኢየሱስ ስለ ጾም ተጠየቀ

5፥33-39 ተጓ ምብ – ማቴ 9፥14-17፤ማር 2፥18-22

33እነርሱም፣ “የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት
አብዛኛውን ጊዜ ይጾማሉ፤ ይጸልያሉ፤ የፈ
ሪሳውያን ደቀ መዛሙርትም እንደዚሁ
ያደርጋሉ፤ የአንተዎቹ ግን ዘወትር ይበላሉ፤
ይጠጣሉ” አሉት።
34ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “ሙሽራው
አብሮአቸው እያለ ዕድምተኞቹ እንዲጾሙ
ማድረግ ይቻላልን?
35ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድ
በት ቀን ይመጣል፤ በዚያን ጊዜ ይጾማሉ።”
36ደግሞም እንዲህ ሲል ምሳሌ ነገራ
ቸው፤ “ከአዲስ ልብስ ላይ እራፊ ቀዶ
በአሮጌ ልብስ ላይ የሚጥፍ ማንም የለም፤
እንዲህ ቢያደርግ አዲሱን ልብስ ይቀደ
ዋል፤ አዲሱም እራፊ ለአሮጌው ልብስ
አይስማማውም። 37አዲስ የወይን ጠጅም
በአሮጌ አቍማዳ ጨምሮ የሚያስቀምጥ
ማንም የለም፤ እንዲህ ቢያደርግ አዲሱ የወ
ይን ጠጅ አቍማዳውን ያፈነዳዋል፤ የወ
ይን ጠጁም ይፈስሳል፤ አቍማዳውም ከጥ
ቅም ውጭ ይሆናል። 38ስለዚህ አዲስ የወ
ይን ጠጅ በአዲስ አቍማዳ መጨመር አለ
በት፤ 39እንግዲህ፣ አሮጌ የወይን ጠጅ ከጠጣ
በኋላ፣ አዲሱን የሚሻ ማንም የለም፤ ምክን
ያቱም፣ ‘አሮጌው የተሻለ ነው’ ስለሚል
ነው።”

## የሰንበት ጌታ

6፥1-11 ተጓ ምብ - ማቴ 12፥1-14 ማር 2፥23-36

6 በአንድ የሰንበት ቀን ኢየሱስ በዕርሻ
መካከል ያልፍ ነበር፤ ደቀ መዛሙር
ቱም እሸት ቀጥፈው በእጃቸው እያሹ ይበሉ
ነበር። 2ከፈሪሳውያን መካከል አንዳንዶቹ
ግን፣ “በሰንበት ቀን ሊደረግ ያልተፈቀደ
ውን ለምን ታደርጋላችሁ?” አሏቸው።
3ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
“ዳዊት በተራብ ጊዜ ከባልንጀሮቹ ጋር ያደ
ረገውን ከቶ አላነበባችሁምን? 4ወደ እግዚ
አብሔር ቤት ገብቶ ለካህናት ብቻ የተፈ
ቀደውን ኅብስተ ገጽ ወስዶ በላ፤ አብረውት
ለነበሩትም ሰጣቸው።” 5ደግሞም፣ “የሰው
ልጅ ለሰንበት ጌታዋ ነው” አላቸው።
6በሌላ ሰንበት ቀንም ወደ ምኵራብ ገብቶ
ያስተምር ነበር፤ በዚያም ቀኝ እጁ የሰለለ
አንድ ሰው ነበረ። 7ጸሐፍትና ፈሪሳው
ያንም ሊከሱት ምክንያት በመፈለግ፣ ይፈ
ውሰው እንደ ሆነ ለማየት ይጠባበቁት
ነበር። 8ኢየሱስም ሐሳባቸውን ዐውቆ እጁ
የሰለለውን ሰው፣ “ተነሥተህ በመካካል ቁም”
አለው፤ ሰውየውም ተነሥቶ ቆመ።

9ኢየሱስም፣ “እስቲ አንድ ነገር ልጠይ
ቃችሁ፤ በሰንበት ቀን የተፈቀደው በጎ
ማድረግ ነው ወይስ ክፉ ማድረግ? ነፍስ
ማዳን ነው ወይስ ማጥፋት?” አላቸው።
10ደግሞም ኢየሱስ በዙሪያው ያሉትን ሁሉ
ከተመለከተ በኋላ ሰውየውን፣ “እጅህን ዘርጋ”
አለው። ሰውየውም እንደ ተባለው አደረገ፤ እጁም
ፈጽሞ ዳነለት። 11ሰዎቹ ግን በቍጣ ተሞሉ፤
በኢየሱስ ላይ ምን ማድረግ እንዳለባቸውም
እርስ በርስ ተወያዩ።

## የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መመረጥ

6፥13-16 ተጓ ምብ - ማቴ 10፥2-4፤ ማር 3፥16-19፤ ሐሥ 1፥13

12ከእነዚያም ቀናት በአንዱ ኢየሱስ ሊ
ጸ
ልይ ወደ ተራራ ወጣ፤ ሌሊቱንም ሁሉ
ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ። 13ሲነ
ጋም ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ ከእነርሱ
ዐሥራ ሁለቱን መረጠ፤ እነዚህንም ሐዋር
ያት ብሎ ሰየማቸው፤ 14እነርሱም፣ ጴጥ
ሮስ ብሎ የጠራው ስምዖንና ወንድሙ
እንድርያስ፣ ያዕቆብ፣ ዮሐንስ፣ ፊልጶስ፣
በርተሎሜዎስ፣ 15ማቴዎስ፣ ቶማስ፣ የእል
ፍዮስ ልጅ ያዕቆብ፣ ቀናተኛ የተባለው
ስምዖን፤ 16የያዕቆብ ልጅ ይሁዳና ኋላ አሳ
ልፎ የሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ ነበሩ።

## የቡራኬና የወዮታ ስብከት

6፥20-23 ተጓ ምብ - ማቴ 5፥3-12

17ኢየሱስም አብሮአቸው ከተራራው ወርዶ
ደልዳላ ቦታ ላይ ቆመ፤ ከደቀ መዛሙ
ርቱም እጅግ ብዙ ሰዎች በዚያ ነበሩ፤
ከይሁዳ ሁሉና ከኢየሩሳሌም እንዲሁም
ከጢሮስና ከሲዶና ባሕር ጠረፍ የመጣ
ብዙ ሕዝብም በዚያ ነበረ፣ 18እነዚህም የመ
ጡት ሊሰሙትና ካለባቸው ደዌ ሊፈወሱ
ነበር። በርኩሳንኀ መናፍስት ይሠቃዩ የነ
በሩትም ተፈወሱ፤ 19ኀይል ከእርሱ እየ
ወጣ ሁሉንም ይፈውስ ስለ ነበር፣ ሰዎቹ
ሁሉ እርሱን ለመንካት ይፈልጉ ነበር።
20ወደ ደቀ መዛሙርቱም በመመልከት
እን ዲህ አለ፤

“እናንት ድኾች ብፁዓን ናችሁ፤
የእግዚአብሔር መንግሥት የእናንተ ናትና፤
21እናንት አሁን የምትራቡ ብፁዓን ናችሁ፤
ኋላ ትጠግባላችሁና፤
እናንት አሁን የምታለቅሱ ብፁዓን ናችሁ፤
ኋላ ትሥቃላችሁና፤
22ሰዎች ስለ ሰው ልጅ ሲጠሏችሁ፣
ከመካከላቸው ሲለዩአችሁና ሲነቅፏችሁ፣
ክፉ ስምም ሲሰጧችሁ ብፁዓን ናችሁ።

23“እነሆ፤ ወሮታችሁ በሰማይ ታላቅ ነውና፣
በዚያን ቀን ደስ ይበላችሁ ፈንድቁም፤

6፥11 ዮሐ5፥18
6፥12 ሉቃ3፥21
6፥13 ማር6፥30
6፥15 ማቴ9፥9
6፥17 ማቴ4፥25፤
11፥21፤ማር3፥7-8
6፥19 ማቴ9፥20፤
ማር 5፥30፤
ሉቃ5፥17
6፥20 ማቴ25፥34
6፥21 ኢሳ55፥1፡2፤
61፥2፡3፤ማቴ5፥46፤ራ
እ 7፥17
6፥22 ኢሳ51፥7፤
ዮሐ9፥22፤16፥2፤15፥2
1
6፥23 ማቴ5፥12
6፥24 ሉቃ16፥25፤
ያዕ5፥1
6፥25 ምሳ14፥13፣
ኢሳ65፥13
6፥26 ማቴ7፥15
6፥27 ቍ35፤ማቴ
5፥44፤ሮሜ12፥20
6፥28 ማቴ5፥44
6፥30 ዘዳ15፥7፡
8፡10፤ምሳ21፥26
6፥31 ማቴ7፥12
6፥32 ማቴ5፥46
6፥34 ማቴ5፥42
6፥35 ቍ27፤
ማር5፥7፤ሮሜ8፥14
6፥36 ማቴ5፥48፤
6፥1፤ሉቃ11፥2፤
12፥32፤ሮሜ8፥15፤
ኤፌ4፥6፤ያዕ2፥13፤1ጴ
ጥ1፥17፤1
ዮሐ1፥3፤3፥1
6፥37 ማቴ6፥14፤7፥1
6፥38 መዝ79፥12፤
ኢሳ65፥6፡7፤ማቴ7፥2

የቀድሞ አባቶቻቸውም በነቢያት ላይ ያደ
ረጉት ይህንኑ ነበርና።

24“ነገር ግን እናንት ሀብታሞች ወዮላችሁ፤
መጽናናታችሁን አሁኑኑ ተቀብላችኋልና።
25እናንት አሁን የጠገባችሁ ወዮላችሁ፤
ኋላ ትራባላችሁና።
እናንት አሁን የምትሥቁ ወዮላችሁ፤
ኋላ ታዝናላችሁ፤ ታለቅሳላችሁም።
26ሰዎች ሁሉ ስለ እናንተ መልካም
ሲናገሩላችሁ ወዮላችሁ፤
የቀድሞ አባቶቻቸው ለሐሰተኞች
ነቢያት ያደረጉላቸው ይህንኑ ነበርና።

## ጠላትን መውደድ

6፥29፡30 ተጓ ምብ – ማቴ 5፥39-42

27“ነገር ግን ለእናንተ ለምትሰሙ እላችኋ
ለሁ፤ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ ለሚጠሏችሁም
መልካም አድርጉ፤ 28የሚረግሟችሁን መርቁ፤
ለሚበድሏችሁም ጸልዩ። 29አንዱን ጕንጭህን
ለሚመታህ ሌላውን ጕንጭህን ደግሞ ስጠው፤
መጐናጸፊያህን ለሚወስድብህ እጀ ጠባብህን
አትከልክለው። 30ለሚለምንህ ሁሉ ስጥ፤ ንብ
ረትህን የሚወስድ እንዲመልስልህ አትጠ
ይቀው። 31ሰዎች እንዲያደርጉላችሁ የምት
ፈልጉትን እናንተም እንዲሁ አድርጉላቸው።
32“የሚወዷችሁን ብትወዱ ምን የተለየ ዋጋ
ታገኛላችሁ? ኀጢአተኞችም እንኳ የሚወ
ዷቸውን ይወዳሉና። 33መልካም ላደረጉ
ላችሁ መልካም ብታደርጉ ምን የተለየ
ዋጋ ታገኛላችሁ? ኀጢአተኞችም እንኳ
እንደዚያ ያደርጋሉና። 34ብድር ይመል
ሳሉ ለምትሉት ብታበድሩ ምን የተለየ
ዋጋ ታገኛላችሁ? ኀጢአተኞችም እንኳ ያበ
ደሩትን ያህል መልሰው ለመቀበል ‘ለኀጢ
አተኞች’ ያበድራሉ። 35ነገር ግን ጠላቶቻ
ችሁን ውደዱ፤ መልካም አድርጉ፤ መልሳ
ችሁ ለመቀበል ተስፋ ሳታደርጉም አበድሩ፤
በዚህም ወሮታችሁ ታላቅ ይሆናል፤ የልዑ
ልም ልጆች ትሆናላችሁ፤ እርሱ ለማያመ
ሰግኑና ለክፉዎች ቸር ነውና። 36አባታችሁ
ርኅሩኅ እንደ ሆነ እናንተም ርኅሩኆች
ሁኑ።

## በሌሎች አለመፍረድ

6፥37-42 ተጓ ምብ – ማቴ 7፥1-5

37“አትፍረዱ፤ አይፈረድባችሁም፤ አትኰንኑ፤
አትኰነኑም። ይቅር በሉ፤ ይቅር
ትባላላችሁ። 38ስጡ፤ ይሰጣችኋል፤
በምትሰፍሩበት መስፈ ሪያ ተመልሶ
ስለሚሰፈርላችሁ፣ ጫን በተ ደረገ፣
በተነቀነቀና በተትረፈረፈ መልካም
መስፈሪያ ተሰፍሮ በዕቅፋችሁ ይሰጣችኋል።”

ኀ18 ወይም ክፉ

39ደግሞም ይህን ምሳሌ እንዲህ ሲል
ነገራቸው፤ “ዕውር ዕውርን ሊመራ ይችላ
ልን? ሁለቱ ተያይዘው ጕድጓድ አይገቡምን?
40ደቀ መዝሙር ከመምህሩ አይበልጥም፤
ነገር ግን በሚገባ የተማረ ሰው ሁሉ እንደ
መምህሩ ይሆናል።

41“በወንድምህ ዐይን ውስጥ ያለውን ጕድፍ
ለምን ታያለህ? በራስህ ዐይን ውስጥ የተ
ጋደመውን ግንድ አትመለከትምን? 42በራ
ስህ ዐይን ውስጥ ያለውን ግንድ ሳታይ
ወንድምህን፣ ‘ወንድሜ ሆይ፤ በዐይንህ ውስጥ
ያለውን ጕድፍ ላውጣልህ’ እንዴት ልትለው
ትችላለህ? አንተ ግብዝ፤ በመጀመሪያ በዐ
ይንህ ውስጥ የተጋደመውን ግንድ አውጣ፤
ከዚያ በኋላ በወንድምህ ዐይን ውስጥ ያለ
ውን ጕድፍ ለማውጣት አጥርተህ ታያለህ።

## ዛፍና ፍሬው

6፥43፡44 ተጓ ምብ – ማቴ 7፥16፡18፡20

43“መልካም ዛፍ ሆኖ ሳለ መጥፎ ፍሬ
የሚያፈራ የለም፤ እንዲሁም መጥፎ ዛፍ
ሆኖ መልካም ፍሬ የሚያፈራ የለም።
44ዛፍ ሁሉ በፍሬው ይታወቃል፤ ከእሾኽ
የበለስ ፍሬ አይለቀምም፤ ከቀጋ ቁጥቋጦ
የወይን ፍሬ አይቈረጥም። 45መልካም ሰው
በልቡ ከሞላው መልካም ነገር መልካሙን
ያወጣል፤ ክፉ ሰውም በልቡ ከሞላው ክፉ
ነገር ክፉውን ያወጣል፤ ሰው በልቡ ሞልቶ
የተረፈውን በአፉ ይናገራልና።

## ልባምና ሰነፍ ቤተ ሠሪዎች

6፥47-49 ተጓ ምብ - ማቴ 7፥24-27

46“እኔ የምለውን ኢታደርጉም፤ ታዲያ
ለምን፣ ‘ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ’ ትሉኛላችሁ?
47ወደ እኔ የሚመጣ፣ ቃሌንም ሰምቶ
የሚፈጽም ሁሉ ማንን እንደሚመስል ላሳ
ያችሁ፤ 48ቤት ለመሥራት አጥልቆ የቈ
ፈረና በዐለት ላይ መሠረቱን የመሠረተ
ሰው ይመስላል፤ ጐርፍ በመጣ ጊዜ የውሃው
ሙላት ያን ቤት ገፋው፤ በሚገባ ስለ ታነጸም
ሊያነቃንቀው አልቻለም። 49ቃሌን ሰምቶ
የማይፈጽም ግን ቤቱን ያለ መሠረት በዐ
ፈር ላይ የሠራን ሰው ይመስላል፤ የወንዝ
ሙላትም ቤቱን በመታው ጊዜ ወዲያው
ወደቀ፤ ክፉኛም ፈራረሰ።”

## የመቶ አለቃው እምነት

7፥1-10 ተጓ ምብ – ማቴ 8፥5-13

7 ኢየሱስ ይህን ሁሉ በሕዝቡ ፊት ተናግሮ
ከጨረሰ በኋላ ወደ ቅፍርናሆም ገባ።
2በዚያም አንድ የመቶ አለቃ ነበረ፤ እጅግ
የሚወደው አገልጋዩም ታሞበት ለሞት ተቃ
ርቦ ነበር። 3እርሱም ስለ ኢየሱስ በሰማ
ጊዜ አገልጋዩን እንዲፈውስለት ይለምኑት
ዘንድ አንዳንድ የአይሁድ ሽማግሌዎችን
ላከበት። 4መልእክተኞቹም ወደ ኢየሱስ
በመጡ ጊዜ እንዲህ ብለው አጥብቀው
ለመኑት፤ “ይህን ልታደርግለት ይገባ
ዋል፤ 5ምክንያቱም ይህ ሰው ሕዝባችንን
ይወዳል፤ ምኵራባችንንም ያሠራልን እርሱ
ነው።” 6ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ሄደ።

እርሱም ወደ ቤቱ በተቃረበ ጊዜ፣ የመቶ
አለቃው ወዳጆቹን ልኮ እንዲህ አለው፤ “ጌታ
ሆይ፤ ከቤቴ ጣራ በታች ልትገባ የሚገባኝ
ሰው አይደለሁምና አትድከም፤ 7ከዚህም
የተነሣ በአንተ ፊት ለመቅረብ እንኳ
እንደሚገባኝ ራሴን አልቈጠርሁም፤ ብቻ
አንድ ቃል ተናገር፤ አገልጋዬ ይፈወሳል።
8እኔ ራሴ የበላይ አለቃ አለኝ፤ ከበታቼም
የማዛቸው ወታደሮች አሉኝ፤ አንዱን፣
‘ሂድ’ ስለው ይሄዳል፤ ሌላውን፣ ‘ና’ ስለው
ይመጣል፤ አገልጋዬንም፣ ‘ይህን አድርግ’
ስለው የታዘዘውን ያደርጋል።”

9ኢየሱስም ይህን ሲሰማ በእርሱ ተደነቀ፤
ዘወር ብሎም ይከተለው ለነበረው ሕዝብ፣
“እላችኋለሁ፤ እንዲህ ያለ ትልቅ እም
ነት በእስራኤል እንኳ አላገኘሁም” አላ
ቸው። 10የተላኩት ሰዎችም ወደ ቤት በተ
መለሱ ጊዜ፣ አገልጋዩን ድኖ አገኙት።

## ኢየሱስ የመበለቲቱን ልጅ ከሞት አስነሣው

7፥11-16 ማመ - 1ነገ 17፥17-24፤ 2ነገ 4፥32-37፤
ማር 5፥21-24፡35-43፤ ዮሐ 11፥1-44

11ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ብዙ ሳይቈይ፣ ናይን
ወደምትባል ከተማ ሄደ፤ ደቀ መዛሙርቱና
ብዙ ሕዝብም አብረውት ሄዱ። 12ወደ
ከተማዋ መግቢያ በር ሲደርስም፣ እነሆ፤
ሰዎች የአንድ ሰው አስከሬን ተሸክመው
ከከተማዋ ወጡ፤ ሟቹም ለእናቱ አንድ
ልጅ ብቻ ነበር፤ እናቱም መበለት ነበ
ረች፤ ብዙ የከተማውም ሕዝብ ከእርሷ
ጋር ነበረ። 13ጌታም ባያት ጊዜ ራራላትና፣
“አይዞሽ፤ አታልቅሺ” አላት።

14ቀረብ ብሎም ቃሬዛውን ነካ፤ የተሸ
ከሙትም ሰዎች ቀጥ ብለው ቆሙ፤ ኢየ
ሱስም፣ “አንተ ጐበዝ፤ ተነሥ እልሃለሁ!”
አለው። 15የሞተውም ሰው ቀና ብሎ ተቀ
መጠ፤ መናገርም ጀመረ። ኢየሱስም
ወስዶ ለእናቱ ሰጣት።

16ሁሉም በፍርሀት ተውጠው እግዚአብሔርን
እያመሰገኑ፣ “ታላቅ ነቢይ በመካከላችን ተነ
ሥቶአል”፤ “እግዚአብሔርም ሕዝቡን
ጐብኝቶአል” አሉ። 17ይህም የኢየሱስ ዝና
በመላው ይሁ ዳና[ን] በአካባቢው ባለው አገር
ሁሉ ወጣ።

[ን]17 ወይም *በአይሁድ ምድር*

6፥39 ማቴ15፥14
6፥40 ዮሐ13፥16
6፥44 ማቴ12፥33
6፥45 ምሳ4፥23፤
ማቴ 12፥34፡35፤
ማር7፥20
6፥46 ሚል1፥6፤ማቴ
7፥21፤ዮሐ 13፥13፤
6፥47 ሉቃ8፥21፤
11፥28፤ያዕ1፥22-25
7፥1 ማቴ7፥28
7፥7 መዝ107፥20
7፥13 ቍ19፥ሉቃ
10፥1፤13፥15፤17፥5፤
22፥61፤24፥34፤
ዮሐ11፥2
7፥14 ማቴ9፥25፤
ማር 1፥31፤ሉቃ
8፥54፤ዮሐ11፥43፤
ሐሥ9፥40
7፥16 ቍ39፤
ማቴ9፥8፤21፥11፤
ሉቃ1፥65፤1፥68
7፥17 ማቴ9፥26

## ኢየሱስና መጥምቁ ዮሐንስ

7፥18-35 ተጓ ምብ - ማቴ 11፥2-19

18የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርትም
ይህንን ሁሉ ለዮሐንስ ነገሩት፡፡ እርሱም
ከመካከላቸው ሁለቱን ጠርቶ፣ 19“ይመ
ጣል የተባለልህ አንተ ነህ? ወይስ ሌላ
እንጠብቅ? በሉት” ብሎ ወደ ጌታ ላከቸው፡፡
20ሰዎቹም ወደ ኢየሱስ መጥተው፣ “መጥ
ምቁ ዮሐንስ፣ ‘ይመጣል የተባለልህ አንተ
ነህ? ወይስ ሌላ እንጠብቅ? ብሎ ወደ አንተ
ልኮናል’ አሉት፡፡
21በዚያኑ ጊዜ ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን ከበ
ሽታ፣ ከደዌና ከርኩሳን መናፍስት ፈወሳ
ቸው፤ የብዙ ዐይነ ስውራንንም ዐይን አበራ፡፡
22ከዮሐንስ ተልከው የመጡትንም እንዲህ
አላቸው፤ “ሂዳችሁ ያያችሁትንና የሰማችሁ
ትን ለዮሐንስ ንገሩት፤ ዐይነ ስውራን
ያያሉ፤
ዐንካሶች በትክክል ይራመዳሉ፤
ለምጻሞች[፯] ነጽተዋል፤ ደንቈሮዎች ይሰ
ማሉ፤ ሙታን ተነሥተዋል፤ ለድኾችም
ወንጌል ይሰበካል፤ 23በእኔ የማይሰናከል ሰው
ሁሉ የተባረከ ነው፡፡”
24የዮሐንስ መልእክተኞች ከሄዱ በኋላ፣
ኢየሱስ ለሕዝቡ ስለ ዮሐንስ ይናገር ጀመር፤
እንዲህም አለ፤ “ወደ በረሓ የወጣችሁት ምን
ልታዩ ነው? ነፋስ የሚያወዛውዘውን ሸም
በቆ? 25እኮ! ምን ልታዩ ወጣችሁ? ያማረ
ልብስ የለበሰውን ሰው ነውን? ባማረ
ልብስ የሚሽሞነሞኑና በድሎት የሚኖሩ
በቤተ መንግሥት አሉላችሁ፡፡ 26እኮ! ምን
ልታዩ ወጣችሁ? ነቢይን ለማየት ይሆን?
አዎን፣ እላችኋለሁ፤ ለማየት የወጣችሁት
ከነቢይም የሚበልጠውን ነው፡፡ 27እንዲህ
ተብሎ የተጻፈለትም እርሱ ነው፤

“ ‘መንገድህን በፊትህ የሚያስተካክል፣
መልእክተኛዬን ከአንተ አስቀድሜ እልካለሁ፡፡’

28እላችኋለሁ፤ ከሴት ከተወለዱት መካከል
ከዮሐንስ የሚበልጥ የለም፤ በእግዚአብሔር መን
ግሥት ግን ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል፡፡”
29ቀረጥ ሰብሳቢዎች እንኳ ሳይቀሩ፣ ይህን
የኢየሱስን ቃል የሰሙ ሁሉ፣ በዮሐንስ እጅ
በመጠመቅ ለእግዚአብሔር ተገቢውን ክብር
ሰጡት፤ 30ፈሪሳውያንና ሕግ ዐዋቂዎች
ግን በዮሐንስ እጅ ባለ መጠመቃቸው፣ እግዚ
አብሔር ለእነርሱ ያለውን ዐላማ አቃለሉ፡፡
31ኢየሱስ በመቀጠል እንዲህ አለ፤ “እን
ግዲህ የዚህን ትውልድ ሰዎች በምን ልመ
ስላቸው? ምንስ ይመስላሉ? 32በገበያ ቦታ
ተቀምጠው እርስ በርሳቸው እየተጠራሩ እን
ዲህ የሚባባሉ ልጆችን ይመስላሉ፤

7፥18 ማቴ3፥1፤ ሉቃ5፥33
7፥21 ማቴ4፥23
7፥22 ኢሳ29፥18፡19፤35፥5፡6፤61፥1፡2፤ሉቃ4፥18
7፥26 ማቴ11፥9
7፥27 ሚል3፥1፤ ማቴ11፥10፤ማር1፥2
7፥28 ማቴ3፥2
7፥29 ማቴ21፥32፤ ማር1፥5፤ሉቃ3፥12
7፥30 ማቴ22፥35
7፥33 ሉቃ1፥15
7፥34 ሉቃ5፥29፡30፤15፥1፡2
7፥39 ቀኊ16፤ ማቴ21፥11
7፥44 ዘፍ18፥4፤19፥2፤43፥24፤መሳ19፥21፤ዮሐ13፥4-14፤1ጢሞ5፥10
7፥45 ሉቃ22፥47፡48፤ሮሜ16፥16

“ዋሽንት ነፋንላችሁ፤
አልጨፈራችሁም፤
ሙሾ አወረድንላችሁ፤
አላለቀሳችሁም፡፡”

33ምክንያቱም መጥምቁ ዮሐንስ እህል ሳይ
በላና የወይን ጠጅ ሳይጠጣ ቢመጣ፣ ጋኔን
አለበት አላችሁት፤ 34የሰው ልጅ ደግሞ
እየበላና እየጠጣ ቢመጣ፣ በላተኛና ጠጪ፣
የቀረጥ ሰብሳቢዎችና ‘የኀጢአተኞች’ ወዳጅ
አላችሁት፡፡ 35እንግዲህ የጥበብ ትክክለኛነት
በልጆቿ ሁሉ ዘንድ ተረጋገጠ፡፡”

## አንዲት ሴት ኢየሱስን ሽቶ ቀባች

7፥37-39 ማመ – ማቴ 26፥6-13፤ ማር 14፥3-9፤ ዮሐ 12፥1-8
7፥14፥42 ማመ - ማቴ 18፥23-34

36ከዚህ በኋላ ከፈሪሳውያን አንዱ ምግብ
አብሮት እንዲበላ ኢየሱስን ጋበዘው፤ እር
ሱም ወደ ፈሪሳዊው ቤት ሄዶ በማእድ
ተቀመጠ፡፡ 37በዚያ ከተማ የምትኖር አን
ዲት ኀጢአተኛ ሴት፣ ኢየሱስ በፈሪሳዊው
ቤት በማእድ መቀመጡን በሰማች ጊዜ
አንድ የአልባስጥሮስ ብልቃጥ ሽቶ ይዛ
መጣች፤ 38ከበስተ ኋላው እግሩ አጠገብ ቆ
ማ እያለቀሰች እግሩን በእንባዋ ታርስ፣ በ
ራሷም ጠጕር ታብሰው ጀመር፤ እግሩንም
እየሳመች ሽቱውን ቀባችው፡፡
39የጋበዘውም ፈሪሳዊ ይህን ባየ ጊዜ፣
“ይህ ሰው ነቢይ ቢሆን ኖሮ፣ የነካችው ሴት
ማን እንደ ሆነች፣ ደግሞም ምን ዐይነት ሰው
እንደ ሆነች ባወቀ ነበር፤ ኀጢአተኛ ናትና”
ብሎ በልቡ አሰበ፡፡
40ኢየሱስም፣ “ስምዖን ሆይ፤ የምነግርህ
ነገር አለኝ” አለው፡፡
እርሱም፣ “መምህር ሆይ፤ ንገረኝ” አለው፡፡
41ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ “ከአንድ
አበዳሪ ገንዘብ የተበደሩ ሁለት ሰዎች ነበሩ፤
አንደኛው አምስት መቶ ዲናር፣ ሁለተኛው
ደግሞ አምሳ ዲናር ነበረበት፡፡ 42የሚከፍ
ሉትም ቢያጡ ዕዳቸውን ለሁለቱም ተወ
ላቸው፡፡ እንግዲህ ከሁለቱ አበዳሪውን አብ
ልጦ የሚወደው የትኛው ነው?”
43ስምዖንም፣ “ብዙው ዕዳ የተተወለት ይመ
ስለኛል” ሲል መለሰ፡፡
ኢየሱስም፣ “ትክክል ፈርደሃል” አለው፡፡
44ወደ ሴቲቱም ዞወር ብሎ ስምዖንን
እንዲህ አለው፤ “ይህቺን ሴት ታያታለህን?
እኔ ወደ ቤትህ ገባሁ፤ አንተ ለእግሬ ውሃ
እንኳ አላቀረብህልኝም፤ እርሷ ግን እግሬን
በእንባዋ እያራሰች በጠጕሯ አበሰች፡፡ 45አንተ
ከቶ አልሳምኸኝም፤ እርሷ ግን ከገባሁ
ጀምራ እግሬን ከመሳም አላቋረጠችም፡፡

[፯]22 የግሪኩ ቃል የግድ ከለምጽ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን የተለያዩ የቈዳ በሽታዎች ለመግለጽ ጥቅም ላይ ይውላል

46አንተ ራሴን ዘይት አልቀባህም፤ እርሷ
ግን እግሬን ሽቶ ቀባች። 47ስለዚህ
እልሃለሁ፤ እጅግ ወዳለችና ብዙው ኀጢ
አቷ ተሰርዮ ላታል፤ በትንሹ የተሰረየለት
ግን የሚወ ደው በትንሹ ነው።”
48ኢየሱስም ሴቲቱን፣ “ኀጢአትሽ ተሰ
ርዮልሻል” አላት።
49አብረውት በማእድ ተቀምጠው የነበሩ
እንግዶችም፣ “ይህ ኀጢአትን እንኳ የሚ
ያስተሰረይ እርሱ ማን ነው?” ብለው በል
ባቸው አሰቡ።
50ኢየሱስም ሴቲቱን፣ “እምነትሽ አድኖ
ሻል፤ በሰላም ሂጂ” አላት።

### የዘሪው ምሳሌ

8፥4-15 ተጓ ምብ – ማቴ 13፥2-23፤ ማር 4፥1-20

8 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን
መንግሥት የምሥራች ቃል እየሰበከ
በየከተማውና በየመንደሩ አለፈ። ዐሥራ
ሁለቱም ከእርሱ ጋር ነበሩ፤ 2እንዲሁም
ከርኩሳን መናፍስትና ከደዌ የተፈወሱ አን
ዳንድ ሴቶች አብረውት ነበሩ፤ እነርሱም
ሰባት አጋንንት የወጡላት መግደላዊት የተባ
ለችው ማርያም፣ 3የሄሮድስ ቤት ኀላፊ
የነበረው የኩዛ ሚስት ዮሐና፣ ሶስና፣ ደግ
ሞም ሌሎች ብዙዎች ነበሩ፤ እነዚህም በግል
ንብረታቸው የሚያገለግሉት ነበሩ።
4ብዙ ሕዝብ በአንድነት ተሰብስቦ ሳለ፣
ደግሞም ሰዎች ከተለያዩ ከተሞች ወደ
እርሱ በሚጐርፉበት ጊዜ፣ ይህን ምሳሌ
እንዲህ ሲል ነገራቸው፤ 5“አንድ ዐራሽ
ዘሩን ሊዘራ ወጣ፤ ሲዘራም፣ አንዳንዱ ዘር
መንገድ ዳር፤ ወደቀ በእግርም ተረጋገጠ፤ የሰ
ማይ ወፎችም በሉት። 6አንዳንዱም ዘር
በድንጋያማ ቦታ ላይ ወደቀ፤ እንደ በቀ
ለም ርጥበት አልነበረውምና ደረቀ። 7ሌላው
ዘር ደግሞ እሾኽ መካከል ወደቀ፤ እሾኹም
አብሮት አደገና አንቆ አስቀረው። 8ሌላ
ውም ዘር በመልካም መሬት ላይ ወደቀ፤
በበቀለም ጊዜ መቶ ዕጥፍም አፈራ።”
ይህን ብሎ ሲያበቃም ድምፁን ከፍ
አድርጎ፣ “ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ” አለ።
9ደቀ መዛሙርቱም የዚህን ምሳሌ ትር
ጕም ጠየቁት። 10እርሱም እንዲህ አለ፤
“የእግዚአብሔርን መንግሥት ምስጢር
ማወቅ ለእናንተ ተሰጥቶአል፤ ለሌሎች ግን
በምሳሌ እናገራለሁ፤ ይኸውም፣

“ ‘እያዩ ልብ እንዳይሉ፣
እየሰሙም እንዳያስተውሉ ነው።’

11“እንግዲህ የምሳሌው ትርጕም ይህ
ነው፤ ዘር የተባለው የእግዚአብሔር ቃል ነው።
12በመ ንገድ ዳር የወደቀው ቃሉን

7፥46 መዝ23፥5፤ መክ9፥8
7፥48 ማቴ9፥2
7፥50 ማቴ9፥22፤ ሐሥ15፥33
8፥1 ማቴ4፥23
8፥2 ማቴ27፥55፡56
8፥3 ማቴ14፥1
8፥8 ማቴ11፥15
8፥10 ኢሳ6፥9፤ ማቴ13፥11፡13፡14
8፥11 ዕብ4፥12
8፥13 ማቴ11፥6
8፥14 ማቴ19፥23፤1 ጢሞ6፥9፡10፡17
8፥16 ማቴ5፥15
8፥17 ማቴ10፥26፤ ማር4፥22፤ሉቃ12፥2
8፥18 ማቴ25፥29
8፥20 ዮሐ7፥5
8፥21 ሉቃ6፥47፤ 11፥28፤ዮሐ14፥21
8፥24 መዝ107፥ 29፤ሉቃ4፥35፤ 5፥5፤ሉቃ39፥41፤ ዮሐ1፥15

የሚሰሙ፣ ነገር ግን አምነው እንዳይድኑ ዲ
ያብሎስ መጥቶ ቃሉን ከልባቸው
የሚወስድባቸው ናቸው። 13በድንጋያማ
ቦታ ላይ የወደቀውም ቃሉን ሲሰሙ
በደስታ የሚቀበሉ ናቸው፤ እነዚህ ለጊ
ዜው ያምናሉ እንጂ ሥር ስለሌላቸው
በፈተና ጊዜ ፈጥነው የሚክዱ ናቸው።
14በእሾኽ መካከል የወደቀውም ቃሉን የሚ
ሰሙት ናቸው፤ እነዚህም ውለው አድረው
በምድራዊ ሕይወት ጭንቀት፣ በባለጠግነትና
ተድላ ደስታ ታንቀው በሚገባ አያፈሩም።
15በመልካም መሬት ላይ የወደቀውም ቃሉን
ቅንና በጎ በሆነ ልብ ሰምተው የሚጠብቁ፣
ታግሠውም በመጽናት ፍሬ የሚያፈሩ ናቸው።

### በመቅረዝ ላይ ያለ መብራት

16“መብራትን አብርቶ ጋን ውስጥ ወይም
በዐልጋ ሥር የሚያስቀምጥ ማንም የለም፤
ይልቁንም ወደ ቤት የሚገቡ ብርሃኑን እን
ዲያዩ በመቅረዝ ላይ ያስቀምጠዋል። 17የማ
ይገለጥ የተሰወረ፣ የማይታወቅ ወደ ብር
ሃን የማይወጣ፣ የተደበቀ ነገር የለምና።
18እንግዲህ እንዴት እንደምትሰሙ ተጠን
ቀቁ፤ ላለው ይጨመርለታልና፤ ከሌለው
ሁሉ ግን ያው ያለው የሚመስለው እንኳ
ይወሰድበታል።”

### የኢየሱስ እናትና ወንድሞች

8፥19-21 ተጓ ምብ – ማቴ 12፥46-50፤ ማር 3፥31-35

19ከዚህ በኋላ የኢየሱስ እናትና ወንድሞቹ
እርሱ ወዳለበት መጡ፤ እነርሱም ከሕዝቡ
ብዛት የተነሣ ወደ እርሱ ሊቀርቡ አልቻ
ሉም። 20በዚህ ጊዜ፣ “እናትህና ወንድሞ
ችህ ሊያዩህ ፈልገው በውጭ ቆመዋል”
የሚል ወሬ ደረሰው።
21እርሱም መልሶ፣ “እናቴና ወንድሞቼስ
የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚያደርጉት
ናቸው” አላቸው።

### ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ አደረገ

8፥22-25 ተጓ ምብ – ማቴ 8፥23-27፤ ማር 4፥36-41
8፥22-25 ማመ – ማር 6፥47-52፤ ዮሐ 6፥16-21

22ከዕለታት አንድ ቀን ኢየሱስ ከደቀ
መዛሙርቱ ጋር ጀልባ ላይ ወጣ፤ ኢየሱ
ስም፤ “ወደ ባሕሩ ማዶ እንሻገር” አላቸው፤
ከዚያም ጕዞ ቀጠሉ። 23እየተጓዙ ሳሉም
ኢየሱስ እንቅልፍ ወስዶት ተኛ፤ በዚህ ጊዜ
በባሕሩ ላይ ማዕበል ተነሣ፤ ውሃውም
ጀል ባዋን ዘልቆ ስለ ገባ፣ አደጋ አፋፍ
ላይ ደረሱ።
24ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው፣ “ጌታ
ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ ማለቃችን እኮ ነው!” እያሉ
ቀሰቀሱት።

እርሱም ነቅቶ ነፋሱንና፣ የውሃውን
መናወጥ ገሠጸ፤ በዚህ ጊዜ ነፋሱም፣
ነውጡም ተወ፤ ጸጥታም ሆነ። 25እርሱም
ደቀ መዛሙርቱን፣ "እምነታችሁ የት አለ?"
አላቸው።

እነርሱም በፍርሀትና በመደነቅ፣ "ይህ
ነፋስንና ውሃን የሚያዝ፣ እነርሱም የሚታ
ዘዙለት ለመሆኑ እርሱ ማን ነው?" ተባባሉ።

## አጋንንት ያደረበት ሰው መፈወሱ

8፥26-37 ተጓ ምብ – ማቴ 8፥28-34
8፥26-39 ተጓ ምብ – ማር 5፥1-20

26ከዚህ በኋላ ከገሊላ ባሻገር ወዳለው
ወደ ጌርጌሴኖን[አ] አገር በጀልባ ተሻገሩ።
27ኢየሱስ ከጀልባዋ ወደ ምድር በወረደ ጊዜ፣
አጋንንት ያደረበት አንድ ሰው ከከተማ
ወጥቶ አገኘው፤ ይህ ሰው ለብዙ ጊዜ
ልብስ ሳይለብስ፣ በቤትም ሳይኖር የመቃ
ብርን ስፍራ ቤቱ ያደረገ ነበር። 28ኢየሱስንም
ባየው ጊዜ እየጮኸ ፊቱ ተደፋ፤ በታላቅ
ድምፅም፣ "የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ
ሆይ፤ ከእኔ ጋር ምን ጉዳይ አለህ?
እንዳታሠቃየኝ እለምንሃለሁ" አለ። 29ርኩሱ[ከ]
መንፈስ ይህን ያለው ከሰውየው እንዲወጣ
ኢየሱስ አዞት ስለ ነበር ነው። ርኩሱ
መንፈስ በየጊዜው ስለሚነሣበት ሰውየው
በሰንሰለትና በእግር ብረት እየታሰረ ቢጠ
በቅም የታሰረበትን ሰንሰለት እየበጣጠሰ
ያደረበት ጋኔን ወደ በረሓ ይነዳው
ነበር።

30ኢየሱስም፣ "ስምህ ማን ነው?" ብሎ
ጠየቀው።

እርሱም ብዙ አጋንንት ገብተውበት
ስለ ነበር፣ "ሌጌዎን" አለው። 31አጋን
ንቱም እንጦርጦስ ግቡ ብሎ እንዳያዛ
ቸውም አጥብቀው ለመኑት።

32በዚያም አካባቢ በተራራ ወገብ ላይ
የብዙ ዐሣማ መንጋ ተሰማርቶ ነበር፤ አጋ
ንንቱም ወደ ዐሣማው መንጋ ግቡ ብሎ
እንዲፈቅድላቸው ለመኑት፤ እርሱም ፈቀ
ደላቸው። 33አጋንንቱም ከሰውየው ወጥ
ተው ወደ ዐሣማዎቹ ገቡ፤ የዐሣማውም
መንጋ በገደሉ አፋፍ ቍልቍል በመንደ
ርደር ባሕሩ ውስጥ ገብቶ ሰጠመ።

34እረኞቹም የሆነውን ነገር ባዩ ጊዜ፣ ሸሽ
ተው በመሄድ በከተማውና በገጠሩ አወሩ።
35ሕዝቡም የተደረገውን ነገር ለማየት ከያሉ
በት ወጥተው ወደ ኢየሱስ መጡ። አጋ
ንንት የወጡለትም ሰው ልብስ ለብሶ፣
ወደ ልቦናው ተመልሶ፣ በኢየሱስም እግር
ሥር ተቀምጦ ባዩት ጊዜ ፈሩ። 36በአጋ
ንንት የተያዘው ሰው ሲድን ያዩትም፣
እንዴት እንደ ዳነ ለሕዝቡ አወሩላቸው።

8፥28 ማቴ8፥29፤ ማር5፥7
8፥31 ራእ9፥1፥ 2፥11፤ 11፥7፤ 17፥8፤20፥1፥3
8፥33 ቍ22፥23
8፥35 ሉቃ10፥39
8፥36 ማቴ4፥24
8፥37 ሐሥ16፥39
8፥41 ቍ49፤ ማር5፥22
8፥43 ዘሌ15፥25-30
8፥44 ማቴ9፥20
8፥45 ሉቃ5፥5
8፥46 ማቴ14፥36፤ ማር3፥10፤ሉቃ5፥17፤ 6፥19
8፥48 ማቴ9፥22፤ ሐሥ15፥33
8፥49 ቍ41

37የጌርጌሴኖን አካባቢ ሰዎችም ሁሉ ታላቅ
ፍርሀት ስላደረባቸው፣ ከዚያ እንዲሄድላ
ቸው ኢየሱስን ለመኑት፤ እርሱም ወደ
ጀልባው ገብቶ ተመልሶ ሄደ።

38አጋንንት የወጡለትም ሰው አብሮት
ለመሆን ኢየሱስን ለመነው፤ እርሱ ግን
እንዲህ ሲል አሰናበተው፤ 39"ወደ ቤትህ
ተመልሰህ፣ እግዚአብሔር ያደረገልህን ታላቅ
ነገር ተናገር።" ሰውየውም ኢየሱስ ያደረ
ገለትን ታላቅ ነገር በከተማው ሁሉ በይፋ
እየተናገረ ሄደ።

## የሞተችው ልጅና የታመመችው ሴት

8፥40-56 ተጓ ምብ – ማቴ 9፥18-26፤ ማር 5፥22-43

40ሕዝቡ ሁሉ መምጣቱን ይጠባበቁ ስለ
ነበር፣ ኢየሱስ በተመለሰ ጊዜ በደስታ
ተቀበሉት። 41በዚህ ጊዜ ኢያኢሮስ የተ
ባለ የምኵራብ አለቃ መጥቶ፣ በኢየሱስ
እግር ላይ በመውደቅ ወደ ቤቱ እንዲሄ
ድለት ለመነው፤ 42ይህን ልመና ያቀረበው
ዕድሜዋ ዐሥራ ሁለት ዓመት የሆነ አንዲት
ልጅ ስለ ነበረችው ነው፤ እርሷ በሞት
አፋፍ ላይ ነበረች። ወደዚያው እያመራ
ሳለ፣ ሕዝቡ በመጋፋት እጅግ ያጨናንቀው
ነበር። 43ዐሥራ ሁለት ዓመት ደም ሲ
ፈሳት የኖረች አንዲት ሴት ነበረች፤
ያላትን ሁሉ ለባለ መድኀኒቶች ጨርሳ[ኸ]
ሊፈውሳትም የቻለ ማንም አልነበረም።
44እርሷም ከበስተ ኋላው ተጠግታ
የልብሱን ጫፍ ነካች፤ ይፈስ የነበረው
ደሟም ወዲያው ቆመ።

45ኢየሱስም፣ "የነካኝ ማነው?" አለ።

ሁሉም መንካታቸውን በካዱ ጊዜ ጴጥ
ሮስ፣ "ጌታ ሆይ፤ ሕዝቡ ሁሉ ከቦህ በግ
ፊያ እያስጨነቀህ ነው" አለው።

46ኢየሱስ ግን፣ "አንድ ሰው ነክቶኛል፤
ኀይል ከእኔ እንደ ወጣ ዐውቃለሁና"
አለ።

47ሴትዮዋም ሳትታወቅ መሄድ እንዳል
ቻለች በተረዳች ጊዜ፣ እየተንቀጠቀጠች
መጥታ በፊቱ ተደፋች፤ ለምን እንደ ነካች
ውና እንዴት ወዲያው እንደ ተፈወሰች
በሕዝቡ ሁሉ ፊት ተናገረች። 48እርሱም፣
"ልጄ ሆይ፤ እምነትሽ ፈውሶሻል፤ በሰላም
ሂጂ" አላት።

49ኢየሱስ ገና እየተናገረ ሳለ፣ አንድ
ሰው ከምኵራብ አለቃው ከኢያኢሮስ ቤት
መጥቶ፣ "ልጅህ ሞታለች፤ ከዚህ በኋላ
መምህሩን አታድክመው" አለው።

[አ]26 *አንዳንድ ቅጆች ጋድሬኔስ፣ ሌሎች ቅጆች ደግሞ ጌርጌ ሴኔስ ይላሉ፤* ቍ 37 *ይመ*
[ከ]29 ወይም *ክፉ*
[ኸ]43 *አያሌ ቅጆች ያላትን ሁሉ ለባለ መድኃኒቶች ጨርሳ*

የሚለው የላቸውም
[50]ኢየሱስም ይህን ሰምቶ ኢያኢሮስን፣ “አይ
ዞህ አትፍራ፤ እመን ብቻ፤ ልጅህ ትድናለች”
አለው።
[51]ወደ ኢያኢሮስ ቤት ሲገባም ከጴ
ጥሮስ፣ ከዮሐንስና ከያዕቆብ እንዲሁም ከል
ጅቱ አባትና እናት በቀር ማንም አብሮት
እንዲገባ አልፈቀደም። [52]በዚህ ጊዜ ሰዎቹ
ሁሉ እያለቀሱላት ዋይ ዋይ ይሉ ነበር።
እርሱ ግን፣ “አታልቅሱ፤ ተኝታለች እንጂ
አልሞተችም” አላቸው።
[53]ሰዎቹም መሞቷን ስላወቁ ሣቁበት።
[54]እርሱ ግን እጇን ይዞ፣ “ልጄ ሆይ፤ ተነሺ”
አላት። [55]የልጅቷም መንፈስ ተመለሰ፤
ወዲያውም ተነሥታ ቆመች፤ ኢየሱስም
የሚበላ ነገር እንዲሰጧት አዘዛቸው። [56]ወላ
ጆቿም ተደነቁ፤ እርሱ ግን የሆነውን ነገር
ለማንም እንዳያወሩ አዘዛቸው።

## የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መላክ

9፥3-5 ተጓ ምብ – ማቴ 10፥9-15፤ ማር 6፥8-11
9፥7-9 ተጓ ምብ – ማቴ 14፥1፡2፤ ማር 6፥14-16

9 ኢየሱስም ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት
በአንድነት ጠርቶ አጋንንትን ሁሉ
እንዲያወጡ፣ ደዌንም እንዲፈውሱ ኀይ
ልና ሥልጣን ሰጣቸው፤ [2]ደግሞም የእግዚ
አብሔርን መንግሥት እንዲሰብኩና የታመ
ሙትን እንዲፈውሱ ላካቸው፤ [3]እንዲህም
አላቸው፤ “ለመንገዳችሁ በትር ቢሆን፣
ከረጢትም ቢሆን፣ እንጀራም ቢሆን፣ ገን
ዘብም ቢሆን፣ ሁለት ሁለት እጀ ጠባብም
መያዝ አያስፈልጋችሁም። [4]ከዚያ ከተማ
እስከምትወጡ ድረስ መጀመሪያ በገባች
ሁበት በማንኛውም ቤት ቈዩ። [5]የከተማው
ሰዎች ሳይቀበሏችሁ ቀርተው ከተማቸውን
ለቃችሁ ስትሄዱ፣ ምስክር እንዲሆንባቸው
የእግራችሁን ትቢያ አራግፉችሁ ውጡ።”
[6]እነርሱም በዚሁ መሠረት ወጥተው ወን
ጌልን እየሰበኩ በየቦታው ሁሉ ሕመምተ
ኞችን እየፈወሱ በየመንደሩ ያልፉ ነበር።
[7]የአራተኛው ክፍል ገዥ ሄሮድስም፣ በዚህ
ጊዜ የሆነውን ነገር ሁሉ ሰምቶ በሁኔታው
ተደናገረ፤ ምክንያቱም አንዳንድ ሰዎች ዮሐ
ንስ ከሙታን እንደ ተነሣ ያወሩ ነበር፤
[8]ሌሎች ኤልያስ እንደ ተገለጠ፣ ሌሎች
ደግሞ ከቀድሞዎቹ ነቢያት አንዱ ከሙ
ታን እንደ ተነሣ ይናገሩ ነበር። [9]ሄሮ
ድስም፣ “መጥምቁ ዮሐንስን እኔው ራሴ
ዐንገቱን አስቈርጬው ሞቶአል፤ ታዲያ፣
ስለ እርሱ እንዲህ ሲወራ የምሰማው ይህ
ሰው ማነው?” አለ፤ በዐይኑም ሊያየው
ይሻ ነበር።

8፥51 ማቴ4፥21
8፥52 ማቴ9፥24፤ ሉቃ23፥27
8፥54 ሉቃ7፥14
8፥56 ማቴ8፥4
9፥1 ማቴ4፥23፤ 10፥1፤ሉቃ5፥17
9፥2 ማቴ3፥2
9፥3 ሉቃ10፥4፤ 22፥35
9፥5 ማቴ10፥14
9፥7 ማቴ3፥1፤ 14፥1
9፥8 ቍ19፤ማቴ 11፥14፤ዮሐ1፥21
9፥9 ሉቃ23፥8
9፥10 ማቴ11፥21፤ ማር6፥30
9፥11 ቍ2፤ ማቴ3፥2
9፥16 ማቴ14፥19
9፥18 ሉቃ3፥21
9፥19 ቍ7፡8፤ ማቴ3፥1
9፥20 ዮሐ1፥49፤ 6፥66-69፤11፥27
9፥21 ማር8፥30

## ኢየሱስ አምስት ሺህ ሰዎችን መገበ

9፥10-17 ተጓ ምብ - ማቴ14፥13-21፤ ማር 6፥32-44፤ ዮሐ 6፥5-13
9፥13-17 ማመ - 2ነገ 4፥42-44

[10]ሐዋርያትም ተመልሰው በመጡ ጊዜ
ያደረጉትን ሁሉ ነገሩት፤ እርሱም ይዞ
አቸው ቤተ ሳይዳ ወደምትባል ከተማ
በመሄድ ለብቻው ገለል አለ። [11]ሕዝቡም
ይህንኑ ዐውቀው ተከተሉት፤ እርሱም ተቀ
ብሎአቸው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት
ይነግራቸው ነበር፤ ፈውስ የሚያስፈልጋቸ
ውንም ፈወሳቸው።
[12]ቀኑም ሊመሽ ሲል፣ ዐሥራ ሁለቱ
ወደ እርሱ ቀርበው፣ “ያለነው በምድረ
በዳ ስለ ሆነ፣ ሕዝቡ ወደ አካባቢው መን
ደርና ገጠር ሄደው ማደሪያና ምግብ እን
ዲፈልጉ አሰናብታቸው” አሉት።
[13]እርሱ ግን፣ “የሚበሉትን እናንተው
ስጧቸው” አላቸው።
እነርሱም፣ “ለዚህ ሁሉ ሕዝብ የሚበቃ
ምግብ ሄደን ካልገዛን በስተቀር፣ እኛ
ያለን ከአምስት እንጀራና ከሁለት ዓሣ
አይበልጥም” አሉት፤ [14]አምስት ሺህ ያህል
ወንዶች በዚያ ነበሩና።
ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን፣ “ሕዝቡን
በአምሳ በአምሳ ሰው መድባችሁ አስቀ
ምጧቸው” አላቸው። [15]ደቀ መዛሙርቱም
በታዘዙት መሠረት ሰዎቹ እንዲቀመጡ
አደረጉ። [16]እርሱም አምስቱን እንጀራና
ሁለቱን ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ አሻቅቦ እያየ
ባረካቸው፤ ቈርሶም ለሕዝቡ እንዲያቀርቡ
ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ። [17]ሁሉም በል
ተው ጠገቡ፤ ደቀ መዛሙርቱም ከእነርሱ
የተረፈውን ቍርስራሽ እንጀራ ዐሥራ
ሁለት መሶብ አነሡ።

## ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ማንነት መሰከረ

9፥18-20 ተጓ ምብ – ማቴ 16፥13-16፤ማር 8፥27-29
9፥22-27 ተጓ ምብ - ማቴ 16፥21-28፤ማር 8፥31-9፥1

[18]ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ብቻውን ይጸልይ
ነበር፤ ደቀ መዛሙርቱም ከእርሱ ጋር
ነበሩ፤ እርሱም፣ “ሕዝቡ እኔን ማን ነው
ይሉኛል? ” ብሎ ጠየቃቸው።
[19]እነርሱም፣ “አንዳንዶች መጥምቁ ዮሐ
ንስ፣ ሌሎች ኤልያስ፣ ሌሎች ደግሞ ከቀ
ድሞ ነቢያት አንዱ ከሙታን ተነሥቶአል
ይላሉ” አሉት።
[20]እርሱም፣ “እናንተስ ማን ነው ትሉኛላ
ችሁ?” አላቸው።
ጴጥሮስም፣ “አንተ የእግዚአብሔር መሲሕ[ሠ]
ነህ” ሲል መለሰለት።
[21]ኢየሱስም ይህን ለማንም እንዳይናገሩ

[ሠ]20 ወይም ክርስቶስ

አጥብቆ አስጠነቀቃቸው፤ 22ደግሞም፣ “የሰው
ልጅ ብዙ መከራ መቀበል ይገባዋል፤
እንዲሁም በሽማግሌዎች፣ በካህናት አለቆችና
በጸሐፍት ዘንድ መናቅ፣ መገደልና በሦ
ስተኛውም ቀን ከሙታን መነሣት አለ
በት” አላቸው።
23ከዚያም ለሁሉም እንዲህ አላቸው፤
“በኋላዬ ሊመጣ የሚፈልግ ማንም ቢኖር
ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም በየዕለቱ ተሸ
ክሞ ይከተለኝ፤ 24ምክንያቱም ነፍሱን ሊያ
ድናት የሚፈልግ ሁሉ ያጠፋታል፤ ነፍሱን
ስለ እኔ ብሎ የሚያጠፋት ግን ያድናታል።
25ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን
ቢያጠፋ ወይም ቢያጐድል ጥቅሙ ምን
ድን ነው? 26ማንም በእኔና በቃሌ ቢያ
ፍር፣ የሰው ልጅ በራሱ ክብር እንዲሁም
በአብና በቅዱሳን መላእክት ክብር ሲመጣ
ያፍርበታል። 27እውነት እላችኋለሁ፤ እዚህ
ከቆሙት መካከል የእግዚአብሔርን መንግ
ሥት ሳያዩ ሞትን የማይቀምሱ ሰዎች
አሉ።”

## የኢየሱስ መልክ መለወጥ

9፥28-36 ተጓ ምብ – ማቴ 17፥1-8፤ ማር 9፥2-8

28ኢየሱስ ይህን ከተናገረ ከስምንት ቀን
ያህል በኋላ ጴጥሮስን፣ ዮሐንስንና ያዕ
ቆብን ይዞ ሊጸልይ ወደ አንድ ተራራ
ወጣ። 29በመጸለይ ላይ እንዳለም የፊቱ
መልክ ተለወጠ፤ ልብሱም እንደ መብረቅ
የሚያንጸባርቅ ነጭ ሆነ። 30እነሆ፤ ሁለት
ሰዎች፣ እነርሱም ሙሴና ኤልያስ ከእ
ርሱ ጋር ይነጋገሩ ነበር፤ 31በክብርም ተገ
ልጠው፣ በኢየሩሳሌም ይፈጸም ዘንድ ስላ
ለው ከዚህ ዓለም ስለ መለየቱ ይናገሩ
ነበር። 32ጴጥሮስና አብረውት የነበሩት ግን
እንቅልፍ ተጭኖአቸው ነበር፤ ሲነቁ ግን
ክብሩንና ከእርሱ ጋር የቆሙትን ሁለት
ሰዎች አዩ። 33ሰዎቹም ከኢየሱስ
ተለይተው ሲሄዱ፣ ጴጥሮስ፣ “ጌታ ሆይ፤
እዚህ ብንሆን ለእኛ መልካም ነው፤ ስለዚህ
ሦስት ዳስ እንሥራ፤ አንዱ ለአንተ፣ አንዱ
ለሙሴ፣ አንዱም ለኤ ልያስ ይሆናል”
አለው፤ የሚናገረውንም አያውቅም ነበር።
34ይህንም እየተናገረ ሳለ ደመና መጥቶ
ጋረዳቸው፤ ወደ ደመናውም ሲገቡ ፈሩ።
35ከደመናውም ውስጥ፣ “የመረጥሁት ልጄ
ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት” የሚል ድምፅ
መጣ። 36ድምፁም በተሰማ ጊዜ ኢየሱስ
ብቻውን ሆኖ ተገኘ፤ ደቀ መዛሙርቱም
ነገሩን በልባቸው ያዙ እንጂ ስላዩት ነገር
በዚያን ወቅት ለማንም አልተናገሩም።

9፥22 ማቴ8፥20፤ 16፥21፤27፥1፡2፤ሐሥ 2፥23፤3፥13
9፥23 ማቴ10፥38፤ ሉቃ14፥27
9፥24 ዮሐ12፥25
9፥26 ማቴ10፥33፤ 16፥27፤ሉቃ12፥9፤2ጢሞ2፥12
9፥28 ማቴ4፥21፤ ሉቃ3፥21
9፥31 2ጴጥ1፥15
9፥32 ማቴ26፥43
9፥33 ሉቃ5፥5
9፥35 ኢሳ42፥1፤ ማቴ3፥17
9፥36 ማቴ17፥9
9፥41 ዘዳ32፥5
9፥44 ቊ22
9፥45 ማር9፥32
9፥46 ሉቃ22፥24
9፥47 ማቴ9፥4
9፥48 ማቴ10፥40፤ ማር9፥35
9፥49 ሉቃ5፥5
9፥50 ማቴ12፥30፤ ሉቃ11፥23
9፥51 ማር16፥19፤ ሉቃ13፥22፤17፥11፤18፥31፤19፥28

## ኢየሱስ ርኩስ መንፈስ ያለበትን ልጅ ፈወሰ

9፥37-42፡43-45 ተጓ ምብ – ማቴ17፥14-18፤22፡23፤ ማር 9፥14-27፤30-32

37በማግሥቱ ከተራራው ከወረዱ በኋላ፣
ብዙ ሕዝብ መጥቶ ኢየሱስን አገኘው።
38በዚህ ጊዜ ከሕዝቡ መካከል አንድ ሰው
ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲህ አለ፤
“መምህር ሆይ፤ ያለኝ ልጅ እርሱ ብቻ
ስለሆነ ልጄን እንድታይልኝ
እለምንሃለሁ። 39መንፈስ ሲይዘው
በድንገት ይጮኻል፤ አረፋ እያስ ደፈቀው
ያንፈራግጠዋል፤ ጕዳትም ካደረ ሰበት
በኋላ በስንት መከራ ይተወዋል፤ 40ደቀ
መዛሙርትህ እንዲያወጡለት ለመ
ንኋቸው፤ ነገር ግን አልቻሉም።”
41ኢየሱስም “እምነት የለሽ ጠማማ ትው
ልድ፤ እስከ መቼ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ?
እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ? በል ልጅህን
ወደዚህ አምጣው” አለ።
42ልጁ በመምጣት ላይ ሳለም ጋኔኑ መሬት
ላይ ጥሎ አንፈራገጠው፤ ኢየሱስ ግን ርኩ
ሱን[0] መንፈስ ገሥጾ ልጁን ፈወሰው፤ ለአ
ባቱም መልሶ ሰጠው። 43ሰዎቹም ሁሉ
በእግዚአብሔር ታላቅነት ተገረሙ።
እርሱ ባደረገው ሁሉ ሰዎች ሁሉ እየ
ተገረሙ ሳሉ፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን፣
44“ይህን የምነግራችሁን ነገር ከቶ እንዳት
ዘነጉ፤ የሰው ልጅ አልፎ በሰዎች እጅ ይሰ
ጣልና” አለ። 45እነርሱ ግን ይህን አባባል
አልተረዱም፤ እንዳያስተውሉ ነገሩ ተሰው
ሮባቸው ነበር፤ መልሰው እንዳይጠይቁ
ትም ፈሩ።

## ከሁሉ የሚበልጥ ማን ይሆን?

9፥46-48 ተጓ ምብ – ማቴ 18፥1-5
9፥46-50 ተጓ ምብ - ማቴ 9፥33-40

46ከእነርሱ ማን እንደሚበልጥ በደቀ መዛ
ሙርቱ መካከል ክርክር ተነሣ። 47ኢየ
ሱስም የልባቸውን ሐሳብ ተረድቶ፣ አንድ
ሕፃን ይዞ በአጠገቡ አቆመ፤ 48እንዲህም
አላቸው፤ “ይህን ሕፃን በስሜ የሚቀበል
ማንም ቢኖር እኔን ይቀበላል፤ እኔን
የሚቀበል ደግሞ የላከኝን ይቀበላል፤ ከሁላ
ችሁ የሚያንስ እርሱ ከሁሉ
ይበልጣልና።”
49ዮሐንስም፣ “ጌታ ሆይ፤ አንድ ሰው በስ
ምህ አጋንንት ሲያወጣ አየን፤ ከእኛ ጋር ሆኖ
ስለማይከተል ልንከለክለው ሞከርን” አለው።
50ኢየሱስም፣ አትከልክሉት “የማይቃወማ
ችሁ ሁሉ እርሱ ከእናንተ ጋር ነውና” አለው።

## የሰማርያ ሰዎች ተቃውሞ

51ኢየሱስ ወደ ሰማይ የሚያርግበት ጊዜ
በመቃረቡ፣ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ቈርጦ

[0]42 ወይም ክፉ

ተነሣ፤ [52]አስቀድሞም መልእክተኞችን ወደ
ዚያ ላከ። እነርሱም ሁኔታዎችን አስቀድ
መው ሊያመቻቹለት ወደ አንድ የሳምራ
ውያን መንደር ገቡ። [53]ሕዝቡ ግን ወደ
ኢየሩሳሌም እያመራ መሆኑን ስላወቁ
አልተቀበሉትም። [54]ደቀ መዛሙርቱም ያዕ
ቆብና ዮሐንስ ይህን ሲያዩ፣ “ጌታ ሆይ፤
ኤልያስ እንዳደረገው ሁሉ [″]እሳት ከሰማይ
ወርዶ እንዲያጠፋቸው እንድናዝ ትፈቅ
ዳለህን?” አሉት። [55]ኢየሱስ ግን ዘወር
ብሎ ገሠጻቸውና[‴] “እናንተ ከምን ዐይነት
መንፈስ እንደ ሆናችሁ አታውቁም፤ የሰው
ልጅ የመጣው የሰውን ሕይወት ለማዳን
ነው እንጂ ለማጥፋት አይደለምና” አላቸው
[56]ወደ ሌላ መንደርም ሄዱ።

### ደቀ መዝሙርነት የሚያስከፍለው ዋጋ

9፥57-60 ተጓ ምብ – ማቴ 8፥19-22

[57]በመንገድ ሲሄዱም አንድ ሰው ቀርቦ፣
“ወደምትሄድበት ሁሉ እከተልሃለሁ” አለው።
[58]ኢየሱስም፣ “ቀበሮዎች ጒድጓድ፣ የሰ
ማይ ወፎችም ጎጆ አላቸው፤ የሰው ልጅ
ግን ዐንገቱን እንኳ የሚያስገባበት የለውም”
አለው።
[59]ሌላውን ሰው ግን፣ “ተከተለኝ” አለው።
ሰውየውም፣ “ጌታ ሆይ፤ አስቀድሜ ልሂ
ድና አባቴን ልቅበር” አለው።
[60]ኢየሱስም፣ “ሙታን ሙታናቸውን እን
ዲቀብሩ ተዋቸው፤ አንተ ግን ሄደህ የእግዚ
አብሔርን መንግሥት ስበክ” አለው።
[61]ሌላ ሰው ደግሞ፣ “ጌታ ሆይ፤ መከተ
ልስ እከተልሃለሁ፤ ነገር ግን ልመለስና መጀ
መሪያ የቤቴን ሰዎች እንድሰናበት ፍቀድ
ልኝ” አለ።
[62]ኢየሱስ ግን፣ “ዕርፍ ጨብጦ ወደ ኋላ
የሚመለከት ሰው ለእግዚአብሔር
መንግሥት የተገባ አይደለም” አለው።

### ኢየሱስ ሰባ ሁለቱን ላካቸው

10፥4-12 ተጓ ምብ - ሉቃ 9፥3-5
10፥13-15፥21፥22 ተጓ ምብ – ማቴ 11፥21-23፥25-27
10፥23፥24 ተጓ ምብ -ማቴ 13፥16፥17

**10** ከዚህ በኋላ ጌታ ሌሎች ሰባ
ሁለት ሰዎችን መርጦ ሾመ፤ ወደ
ሚሄድበትም ከተማና ቦታ ሁሉ እንዲቀ
ድሙት፣ ሁለት ሁለት አድርጎ ላካቸው፤
[2]እንዲህም አላቸው፤ “መከሩ ብዙ ነው፤ ሠራ
ተኞች ግን ጥቂት ናቸው፤ ስለዚህ የመከሩ
ጌታ ሠራተኞችን ወደ መከሩ ቦታ እንዲ
ልክ ለምኑት። [3]እንግዲህ ሂዱ፤ እንደ
በጎች በተኵላዎች መካከል እልካችኋለሁ።
[4]ኰረጆ ወይም ከረጢት፣ ወይም ጫማ
አትያዙ፤ በመንገድ ላይም ለማንም ሰላምታ
አትስጡ።
[5]“ወደ ማንኛውም ቤት ስትገቡ አስቀድ
ማችሁ፣ ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን በሉ፤
[6]የሰላም ሰው በዚያ ካለ፣ ሰላማችሁ ያርፍ
በታል፤ አለዚያም ሰላማችሁ ለእናንተው
ይመለሳል። [7]ያቀረቡላችሁን ሁሉ እየበላችሁና
እየጠጣችሁ በዚያ ቤት ተቀመጡ፤ የሚ
ሠራ ደመወዝ ማግኘት ይገባዋልና። ከአንዱ
ቤት ወደ ሌላው ቤት አትዘዋወሩ።
[8]“ወደ ማንኛውም ከተማ ስትገቡ ሰዎቹ
ከተቀበሏችሁ፣ ያቀረቡላችሁን ብሉ። [9]በዚያ
የሚገኙትን በሽተኞች እየፈወሳችሁ፣ ‘የእግ
ዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ቀርባ
ለች’ በሏቸው። [10]ነገር ግን ወደ አንድ
ከተማ ገብታችሁ ካልተቀበሏችሁ፣ ወደ
አደባባዩ ውጡና እንዲህ በሉ፤ [11]‘በእግ
ራችን ላይ ያለውን የከተማችሁን ትቢያ
እንኳ እናራግፍላችኋለን፤ ነገር ግን የእግዚ
አብሔር መንግሥት እንደ ቀረበች
ይህን
ዕወቁ።’ [12]እላችኋለሁ፤ በዚያን ዕለት ከዚ
ያች ከተማ ይልቅ ለሰዶም ቀላል ይሆ
ንላታል።
[13]“ወዮልሽ ኮራዚን! ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ!
በእናንተ የተደረገው ታምራት በጢሮስና
በሲዶና ተደርጎ ቢሆን ኖሮ፣ ገና ዱሮ
ማቅ ለብሰው፣ ዐመድ ነስንሰው ንስሓ
በገቡ ነበር። [14]ነገር ግን በፍርድ ጊዜ ከእ
ናንተ ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና ይቀልላ
ቸዋል። [15]አንቺም ቅፍርናሆም፣ ወደ ሰማይ
ከፍ ከፍ አልሽን? ወደ ሲኦል[°] ትወርጃ
ለሽ።
[16]“እናንተን የሚሰማ እኔን ይሰማል፤
እናንተን የማይቀበል እኔን አይቀበልም፤
እኔንም የማይቀበል የላከኝን አይቀበልም።”
[17]ሰባ ሁለቱም ደስ እያላቸው ተመል
ሰው፣ “ጌታ ሆይ፤ አጋንንት እንኳ በስ
ምህ ተገዙልን” አሉት።
[18]እርሱም እንዲህ አላቸው፤ “ሰይጣን
እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ።
[19]እነ ግዲህ እባቡንና ጊንጡን
እንድትረግጡ፣ በጠላትም ኀይል ሁሉ ላይ
ሥልጣን ሰጥቻችሁ ኋለሁ፤ የሚጐዳችሁም
አንዳች ነገር አይ ኖርም። [20]ይሁን እንጂ
መናፍስት ስለ ተገዙላችሁ በዚያ ደስ
አይበላችሁ፤ ስማ ችሁ ግን በሰማይ ስለ
ተጻፈ ደስ ይበላ ችሁ።”

9፥52 ማቴ10፥5
9፥54 2ነገ1፥10፡12፤ማቴ4፥21
9፥58 ማቴ8፥20
9፥59 ማቴ4፥19
9፥60 ማቴ3፥2
9፥61 1ነገ19፥20
10፥1 ማቴ10፥1፤ማር6፥7፤ሉቃ7፥13፤9፥1፡2፡51፡52
10፥2 ማቴ9፥37፡38፤ዮሐ4፥35
10፥3 ማቴ10፥16
10፥7 1ጢሞ5፥18
10፥8 1ቆሮ10፥27
10፥9 ማቴ3፥2
10፥11 ቀኍ9፤ማቴ10፥14
10፥12 ማቴ10፥15፤ማቴ11፥24
10፥13 ሉቃ6፥24-26፤ራእ11፥3
10፥15 ማቴ4፥13
10፥16 ማቴ10፥40
10፥17 ቀኍ1፤ማር16፥17
10፥18 ኢሳ14፥12፤ማቴ4፥10፤ራእ9፥1፤12፥8፡9
10፥19 ማር16፥18፤ሐሥ28፥3-5
10፥20 ራእ20፥12

[″]54 አንዳንድ ቅጆች *ኤልያስ እንዳደረገው ሁሉ* የሚለው የላቸውም
[‴]55 56 አንዳንድ ቅጆች *ገሠጻቸው፤ [56]ከዚያም ወደ ሌላ መንደር ሄዱ* ይላሉ።
በቍ 55 ላይ በትእምርተ ጥቅሱ ውስጥ የሚገኘው ዐረፍተ ነገር ተአማኒ በሆኑ ብዙ የጥንት ቅጆች ላይ አይገኝም።
[°]15 ወይም *ወደ ጥልቁ*

²¹በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በመንፈስ
ቅዱስ ሐሤት አድርጎ እንዲህ አለ፤ “የሰ
ማይና የምድር ጌታ፤ አባት ሆይ፤ ይህን
ሁሉ ከጥበበኞችና ከዐዋቂዎች ሰውረህ ለሕ
ፃናት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ፤
አዎን፣ አባት ሆይ፤ ይህ የአንተ በጎ ፈቃድ
ሆኖአልና።
²²“ሁሉ ከአባቴ ዘንድ ተሰጥቶኛል፤ ደግ
ሞም ወልድ ማን እንደ ሆነ ከአብ በቀር
የሚያውቅ የለም፤ አብ ማን እንደ ሆነም
ከወልድ በቀር፣ ወልድም ሊገልጥለት
ከሚፈቅደው በቀር የሚያውቅ የለም።”
²³ወደ ደቀ መዛሙርቱም ዘወር ብሎ
ለብቻቸው እንዲህ አላቸው፤ “እናንተ የም
ታዩትን የሚያዩ ዐይኖች ብፁዓን ናቸው፤
²⁴እላችኋለሁና፤ ብዙ ነቢያትና ነገሥታት
እናንተ የምታዩትን ለማየት ፈልገው አላ
ዩም፤ የምትሰሙትንም ለመስማት ፈል
ገው አልሰሙም።”

### ደጉ ሳምራዊ

10፥25-28 ተጓ ምብ - ማቴ 23፥34-40፤ ማር 12፥28-31

²⁵እነሆም አንድ ቀን፣ አንድ ሕግ ዐዋቂ
ኢየሱስን ሊፈትነው ተነሥቶ፣ “መምህር
ሆይ፤ የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ ምን
ላድርግ? ” አለው።
²⁶ኢየሱስም፣ “በሕግ የተጻፈው ምን
ድን ነው? እንዴትስ ታነበዋለህ?” ሲል
መለሰለት።
²⁷ሰውየውም መልሶ፣ “ጌታ አምላክህን
በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም
ኀይልህና በፍጹም ሐሳብህ ውደድ፤ ባል
ንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ ይላል”
አለው።
²⁸ኢየሱስም፣ “በትክክል መልሰሃል፤ አን
ተም እንደዚሁ አድርግ፤ በሕይወት ትኖራ
ለህ” አለው።
²⁹ሰውየውም ራሱን ጻድቅ ለማድረግ
ፈልጎ፣ “ለመሆኑ ባልንጀራዬ ማን ነው?”
አለው።
³⁰ኢየሱስም እንዲህ ሲል መልስ ሰጠው፤
“አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ
ሲወርድ በወንበዴዎች እጅ ወደቀ፤ ልብ
ሱንም ገፈው ደበደቡት፤ በሞት አፋፍ
ላይ ጥለውት ሄዱ። ³¹አንድ ካህን በአ
ጋጣሚ በዚያው መንገድ ቍልቍል ሲወ
ርድ አየውና ገለል ብሎ አለፈ። ³²ደግ
ሞም አንድ ሌዋዊ እዚያ ቦታ ሲደርስ
አየውና እርሱም ገለል ብሎ አለፈ።
³³አንድ ሳምራዊ ግን እግረ መንገዱን
ሲሄድ ሰውየው ወዳለበት ቦታ ደረሰ፤ ባየ
ውም ጊዜ ዐዘነለት፤ ³⁴ቀርቦም ቍስሎቹ
ላይ ዘይትና የወይን ጠጅ አፍስሶ አሰ
ረለት፤ በራሱም አህያ ላይ አስቀምጦት
ወደ እንግዶች ማረፊያ ቤት ወሰደው፤
በዚያም ተንከባከበው። ³⁵በማግሥቱም
ሁለት ዲናር[ጀ] አውጥቶ ለማረፊያ ቤቱ ባለ
ቤት ሰጠና፣ ይህን ሰው ዐደራ አስታ
መው፤ ከዚህ በላይ የምታወጣውንም
ወጪ እኔ ስመለስ እከፍልሃለሁ” አለው።
³⁶“እንግዲህ፣ ከእነዚህ ከሦስቱ በወንበዴ
ዎች እጅ ለወደቀው ሰው ባልንጀራ የሆ
ነው የትኛው ይመስልሃል?”
³⁷ሕግ ዐዋቂውም፣ “የራራለት ነዋ” አለ።
ኢየሱስም፣ “አንተም ሂድና እንዲሁ አድ
ርግ” አለው።

### ኢየሱስ በማርታና በማርያም ቤት

³⁸ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ መንገድ ሲሄዱ፣
ኢየሱስ ወደ አንድ መንደር ገባ፤ ማርታ
የተባለች አንዲት ሴትም በቤቷ ተቀበለ
ችው። ³⁹እርሷም ማርያም የተባለች እኅት
ነበረቻት፤ ማርያምም ቃሉን እየሰማች በጌታ
እግር ሥር ተቀምጣ ነበር። ⁴⁰ማርታ
ግን በሥራ ብዛት ትባክን ነበርና ወደ
እርሱ ቀርባ፣ “ጌታ ሆይ፤ እኅቴ ሥራውን
ለእኔ ብቻ ጥላ ስትቀመጥ ዝም ትላለህን?
እንድታግዘኝ ንገራት እንጂ” አለችው።
⁴¹ጌታ ግን እንዲህ ሲል መለሰላት፤
“ማርታ፣ ማርታ፤ ስለ ብዙ ነገር
ትጨነቂያለሽ፤ ትዋከቢአለሽም፤
⁴²የሚያስፈልገው ግን አንድ ነገር ብቻ
ነው[ገ]፤ ማርያም እኮ የሚሻለውን ድርሻ
መርጣለች፤ ይህም ከእርሷ አይወ
ሰድም።”

### ኢየሱስ ያስተማረው ጸሎት

11፥2-4 ተጓ ምብ – ማቴ 6፥9-13
11፥9-13 ተጓ ምብ – ማቴ 7፥7-11

11 አንድ ቀን ኢየሱስ በአንድ ስፍራ
ይጸልይ ነበር፤ ጸሎቱንም እንደ
ጨረሰ፣ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፣
“ጌታ ሆይ፤ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን
ጸሎት እንዳስተማራቸው አንተም መጸለ
ይን አስተምረን” አለው።
²እርሱም እንዲህ አላቸው፤ “ስትጸልዩ
እንዲህ በሉ፤

“አባታችን[ጠ] ሆይ፤
ስምህ ይቀደስ፤
መንግሥትህ ትምጣ፤[ጨ]
³የዕለት እንጀራችንን በየዕለቱ ስጠን፤

10፥21 1ቆሮ 1፥26-29
10፥22 ማቴ28፥18፤ ዮሐ1፥18
10፥24 1ጴጥ 1፥10-12
10፥25 ማቴ19፥16፤ ሉቃ18፥18
10፥27 ዘሌ19፥18፤ ዘዳ6፥5፤ማቴ5፥43
10፥28 ሮሜ7፥10
10፥29 ሉቃ16፥15
10፥31 ዘሌ21፥1-3
10፥33 ማቴ10፥5
10፥38 ዮሐ11፥1፤ 12፥2
10፥39 ሉቃ8፥35፤ ዮሐ11፥1፤12፥3
10፥40 ማር4፥38
10፥41 ማቴ6፥25-34፤ሉቃ12፥11:22
10፥42 መዝ27፥4
11፥1 ሉቃ3፥21፤ ዮሐ13፥13
11፥2 ማቴ3፥2

[ጀ]35 ወይም ሁለት የናስ ሳንቲሞች
[ገ]42 አንዳንድ ቅጆች የሚያስፈልገው ግን ጥቂት ብቻ ነው ይላሉ
[ጠ]2 አንዳንድ ቅጆች በሰማይ የምትኖር አባታችን ይላሉ
[ጨ]2 አንዳንድ ቅጆች ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን ይላሉ

[4]በደላችንን ይቅር በለን፤
እኛም የበደሉንን[ጸ] ሁሉ
ይቅር ብለናልና፡፡
ወደ ፈተናም አታግባን፡፡”[ጸ]

[5]ደግሞም እንዲህ አላቸው፤ “ከእናንተ
አንዱ ወዳጅ ቢኖረውና በእኩለ ሌሊት
ወደ እርሱ ሄዶ፣ “ወዳጄ ሆይ፤ ሦስት እን
ጀራ አበድረኝ፤ [6]አንድ ባልንጀራዬ ከመ
ንገድ መጥቶብኝ የማቀርብለት ምንም
ነገር የለኝምና” ብሎ ለመነው እንበል፡፡
[7]“በቤት ውስጥ ያለውም፣ “አታስቸግ
ረኝ፤ በሩ ተቈልፎአል፤ ልጆቼም አብረ
ውኝ ተኝተዋል፤ ከእንግዲህ ተነሥቼ
ልሰጥህ አልችልም” ይለዋልን? [8]እላችኋ
ለሁ፤ ወዳጁ በመሆኑ ተነሥቶ ባይሰጠው
እንኳ፣ ስለ ንዝነዛው[θ] ብቻ የሚፈልገውን
ሁሉ ይሰጠዋል፡፡
[9]“ስለዚህ እላችኋለሁ፤ ለምኑ ይሰጣች
ኋል፤ ፈልጉ ታገኛላችሁ፤ በር አንኳኩ
ይከፈትላችኋል፤ [10]ምክንያቱም የሚለምን
ሁሉ ይቀበላል፤ የሚፈልግም ያገኛል፤
በር ለሚያንኳኳም ይከፈትለታል፡፡
[11]“ከእናንተ መካከል አባት ሆኖ ሳለ ልጁ[ፊ]
ዓሣ ቢለምነው እባብ የሚሰጠው ይኖራ
ልን? [12]ወይስ ዕንቍላል ቢለምነው ጊንጥ
ይሰጠዋልን? [13]እናንተ ክፉዎች ሆናችሁ
ሳላችሁ፣ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታን
መስጠት ካወቃችሁበት፣ የሰማዩ አባታ
ችሁ ታዲያ ለሚለምኑት መንፈስ ቅዱ
ስን እንዴት አብልጦ አይሰጥ!”

## ጌታ ኢየሱስና ብዔል ዜቡል

11፥14፡15፤17-22፤ 24-26 ተጓ ምብ - ማቴ12፥22፡24-29፤ 43-45
11፥17-22 ተጓ ምብ – ማር 3፥23-37

[14]አንድ ቀን ኢየሱስ ድዳ ጋኔን ያወጣ
ነበር፤ ጋኔኑም ከወጣለት በኋላ ድዳው
ሰው ተናገረ፤ ሕዝቡም ተገረመ፡፡ [15]አንዳን
ዶቹ ግን፣ “በአጋንንት አለቃ፣ በብዔል
ዜቡል[T]፣ አጋንንትን ያወጣል” አሉ፤ [16]አን
ዳንዶቹ ደግሞ ሊፈታተኑት ከሰማይ ምል
ክት እንዲያሳያቸው ከእርሱ ይፈልጉ ነበር፡፡
[17]ኢየሱስ ግን ሐሳባቸውን ዐውቆ እንዲህ
አላቸው፤ “እርስ በርሱ የሚከፋፈል መንግ
ሥት ሁሉ ይጠፋል፤ የሚለያይ ቤትም ይወ
ድቃል፡፡ [18]ሰይጣንም እርስ በርሱ ከተከፋ
ፈለ፣ መንግሥቱ እንዴት ይጸናል? አጋ
ንንትን በብዔል ዜቡል እንደማወጣ ትናገ
ራላችሁና፡፡ [19]እንግዲህ እኔ አጋንንትን የማ
ወጣው በብዔል ዜቡል ከሆነ፣ ልጆቻችሁ
በማን ያወጧቸው ይሆን? ስለዚህ እነርሱ
ፈራጆች ይሆኑባችኋል፡፡ [20]እኔ ግን አጋን
ንትን የማወጣው በእግዚአብሔር ጣት ከሆነ፣

11፥4 ማቴ18፥35፤ 26፥41፤ማር11፥25፤ ያዕ1፥13
11፥8 ሉቃ18፥1-6
11፥9 ማቴ7፥7
11፥14 ማቴ፥32፡33
11፥15 ማቴ9፥34፤ ማር3፥22
11፥16 ማቴ12፥38
11፥17 ማቴ9፥4
11፥18 ማቴ4፥10
11፥20 ዘፀ8፥19፤ ማቴ3፥2
11፥23 ማቴ12፥30፤ማር9፥40፤ ሉቃ9፥50
11፥26 2ጴጥ2፥20
11፥27 ሉቃ23፥29
11፥28 ምሳ8፥32፤ ሉቃ6፥47፤8፥21፤ዮሐ 14፥21፤ዕብ 4፥12
11፥29 ቈ16፤ ዮና1፥17፤ ማቴ12፥38፤16፥4
11፥31 1ነገ10፥1፤ 2ዜና9፥1
11፥32 ዮና3፥5

የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ እንደ
መጣች ዕወቁ፡፡
[21]“ብርቱ ሰው በሚገባ ታጥቆ ቤቱን
ከጠበቀ፣ ንብረቱ በሰላም ይቀመጣል፡፡
[22]ነገር ግን ይበልጥ ብርቱ የሆነ ሰው
መጥቶ ካጠቃውና ካሸነፈው ታምኖበት
የነበረውን ትጥቁን ያስፈታዋል፤ ምርኮው
ንም ወስዶ ለሌሎች ያካፍላል፡፡
[23]“ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል፤ ከእኔ
ጋር የማይሰበስብም ይበትናል፡፡
[24]“ርኩስ [υ]መንፈስ ከሰው ሲወጣ ዕረ
ፍት ፍለጋ ውሃ በሌለበት ስፍራ ይንከራ
ተታል፤ ሳያገኝም ሲቀር፣ ወደ ወጣሁበት
ቤቴ እመለሳለሁ ይላል፤ [25]ሲመለስም ቤቱ
ተጠራርጐና ተስተካክሎ ያገኘዋል፡፡ [26]ከዚ
ያም በኋላ ሄዶ ሌሎች ከእርሱ የከፉ
ሰባት አጋንንት ይዞ ይመጣል፤ ገብተ
ውበትም በዚያ ይኖራሉ፤ ለዚያ ሰው
ከመጀመሪያው ይልቅ የኋለኛው ሁኔታ
የከፋ ይሆንበታል፡፡
[27]ኢየሱስ ይህን እየተናገረ እያለ፣ ከሕዝቡ
መካከል አንዲት ሴት ድምፅዋን ከፍ አድ
ርጋ፣ “የተሸከመችህ ማሕፀንና የጠባሃ
ቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው” አለችው፡፡
[28]እርሱ ግን፣ “ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን
ቃል ሰምተው የሚታዘዙት ናቸው” አለ፡፡

## የዮናስ ምልክትነት

11፥29-32 ተጓ ምብ – ማቴ 12፥39-42

[29]ብዙ ሕዝብ እየተሰበሰበ በሄደ ጊዜ
ኢየሱስ እንዲህ ይል ጀመር፤ “ይህ ትው
ልድ ክፉ ነው፤ ታምራዊ ምልክት ይፈ
ልጋል፤ ነገር ግን ከዮናስ ምልክት በስ
ተቀር ሌላ አይሰጠውም፡፡ [30]ምክንያቱም
ዮናስ ለነነዌ ሰዎች ምልክት እንደ ሆናቸው
የሰው ልጅም ለዚህ ትውልድ ምልክት
ይሆናል፡፡ [31]የደቡብ ንግሥት በፍርድ ጊዜ
ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፈርድባ
ቸዋለች፤ እርሷ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስ
ማት ከምድር ዳርቻ መጥታለችና፤ እነሆ፤
ከሰ ሎሞን የሚበልጥ እዚህ አለ፡፡ [32]የነነዌ
ሰዎ ችም በፍርድ ጊዜ ከዚህ ትውልድ
ጋር ተነሥተው ይፈርዱበታል፤ እነርሱ
የዮና ስን ስብከት ሰምተው ንስሓ
ገብተዋልና፤ እነሆ፣ ከዮናስ የሚበልጥ እዚ
ህ አለ፡፡

[ጸ]4 አንዳንድ ቅጆች *በእኛ ላይ ኀጢአት የሠሩትን* ይላሉ፡፡
[ጸ]4 አንዳንድ ቅጆች *ከክፉው ግን አድነን* ይላሉ
[θ]8 ወይም *ስለ ብዙ ልመናው*
[ፊ]11 አንዳንድ ቅጆች *ዳቦ ቢለምነው ድንጋይ የሚሰጠው አለን?* የሚል አላቸው፡፡
[T]15 ግሪኩ *ብዔዜቡል* ወይም *ብዔል ዜብል* ይላል፤ እንዲሁም ቍ 18፡19 *ይመ*
[υ]24 ወይም *ክፉ*

## የሰውነት መብራት

11፥34፡35 ተጓ ምብ - ማቴ 6፥22፡23

33"መብራት አብርቶ በስውር ቦታ
ወይም ከእንቅብ በታች የሚያስቀምጥ ማንም
የለም፤ ይልቁን የሚገቡ ሰዎች ብርሃኑን
እንዲያዩ በመቅረዝ ላይ ያስቀምጠዋል።
34የሰውነትህ ብርሃን ዐይንህ ናት፤ ዐይ
ንህ ጤናማ ስትሆን መላ ሰውነትህ ብሩህ
ይሆናል፤ ዐይንህ ታማሚ ከሆነች ግን መላ
ሰውነትህ የጨለመ ይሆናል። 35ስለዚህ በው
ስጥህ ያለው ብርሃን ጨለማ እንዳይሆን
ተጠንቀቅ። 36እንግዲህ ሰውነትህ ሁሉ ብሩ
ህ ከሆነና የጨለመ የሰውነት ክፍል ከሌለ
በት፣ የሰውነትህ ሁለንተና መብራት በወ
ገግታው ያበራልህ ያህል ይደምቃል።"

## ስድስት ዐይነት ወዮታ

37ኢየሱስ ንግግሩን እንደ ጨረሰ፣ አንድ
ፈሪሳዊ ከእርሱ ጋር ምግብ እንዲበላ ጋበ
ዘው፤ እርሱም አብሮት ገብቶ በማእድ ተቀ
መጠ። 38ፈሪሳዊውም ኢየሱስ ከምግብ በፊት
እጁን እንዳልታጠበ ባየ ጊዜ ተደነቀ።
39ጌታም እንዲህ አለው፤ "አሁን እናንተ
ፈሪሳውያን የጽዋውንና የወጭቱን ውጫዊ
ክፍል ታጸዳላችሁ፤ ውስጣችሁ ግን በስስ
ትና በክፋት የተሞላ ነው። 40እናንተ ሞኞች፤
የውጪውን የፈጠረ የውስጡንም አልፈጠ
ረምን? 41ነገር ግን በውስጥ ያለውን ምጽዋት[^]
አድርጋችሁ ስጡ፤ በዚህ ጊዜ ሁሉም
ንጹሕ ይሆንላችኋል።
42"እናንተ ፈሪሳውያን ግን ወዮላችሁ፤
ከአዝሙድና ከጤና አዳም እንዲሁም ከአ
ትክልት ሁሉ ዐሥራት ታወጣላችሁ፤ ሆኖም
ፍትሕንና እግዚአብሔርን መውደድ ቸል
ትላላችሁ፤ ነገር ግን ያንን ሳትተዉ ይኸ
ኛውን ማድረግ በተገባችሁ ነበር።
43"እናንተ ፈሪሳውያን ወዮላችሁ በምኵራብ
የክብር መቀመጫ፣ በገበያ መካከልም እጅ
መንሣትን ትወዳላችሁና።
44"ሰዎች ሳያውቁ በላዩ የሚሄዱበትን
የተሰወረ መቃብር ስለምትመስሉ፣ ወዮላችሁ"።
45ከሕግ ዐዋቂዎች አንዱ መልሶ "መም
ህር ሆይ፤ እንዲህ ስትናገር እኮ እኛንም
መስደብህ ነው" ሲል መለሰለት።
46ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ "እናንተ ሕግ
ዐዋቂዎችም ደግሞ ወዮላችሁ፤ ሰዎች ሊሸ
ከሙ የማይችሉትን ከባድ ሸክም ታሸክማ
ላችሁ፤ እናንተ ራሳችሁ ግን በጣታችሁ
እንኳ አትነኩትም።
47"አባቶቻችሁ የገደሏቸውን የነቢያትን
መቃብር ስለምታበጁ፣ ወዮላችሁ፤
48እንግ ዲህ የአባቶቻችሁን ሥራ የምታጸኑ
ምስክ ሮች ናችሁ፤ እነርሱ ነቢያትን
ገደሉ፣ እና ንተም መቃብራቸውን
ታበጃጃላችሁ። 49ስለ ዚህም የእግዚአብሔር
ጥበብ እንዲህ አለች፤ 'ነቢያትንና ሐ
ዋርያትን እልክላቸዋለሁ፤ እነ ርሱ
አንዳንዶቹን ይገድላሉ፤ ሌሎችንም
ያሳድዳሉ።' 50ስለዚህ ይህ ትውልድ ዓለም
ከተፈጠረ ጀምሮ ስለፈሰሰው፣ ስለ ነቢያት
ሁሉ ደም ተጠያቂ ነው፤ 51ከአቤል ደም
ጀምሮ፣ በመሠዊያውና በቤተ መቅደሱ
መካከል እስከ ፈሰሰው እስከ ዘካርያስ
ደም ድረስ ይፈለግበታል፤ አዎን፣ እላች
ኋለሁ፤ ይህ ትውልድ ለዚህ ተጠያቂ
ነው።
52"እናንተ ሕግ ዐዋቂዎች ወዮላችሁ፤
የዕውቀትን መክፈቻ ነጥቃችሁ ወስዳች
ኋልና፤ እናንተ ራሳችሁ አልገባችሁበትም፤
የሚገቡትንም ከልክላችኋል።"
53ኢየሱስ ከዚያ ከወጣ በኋላ፣ ጸሐፍትና
ፈሪሳውያን ክፉኛ ይቃወሙትና በጥያቄም
ያዋክቡት ጀመር፤ 54ከአፉ በሚወጣውም ቃል
ሊያጠምዱት ያደቡ ነበር።

11፥33 ማቴ5፥15
11፥37 ሉቃ7፥36፤ 14፥1
11፥38 ማር7፥3፡4
11፥39 ማቴ23፥25፡ 26፤ማር7፥20-23፤ ሉቃ7፥13
11፥40 ሉቃ12፥20፤ 1ቆሮ15፥36
11፥41 ሉቃ12፥ 33፤ሐሥ10፥15
11፥42 ዘዳ6፥5፤ ሚክ6፥8፤ማቴ23፥23፤ ሉቃ18፥12
11፥43 ማቴ23፥6፤ ሉቃ14፥7፤20፥46
11፥44 ማቴ23፥27
11፥45 ማቴ22፥35
11፥46 ማቴ23፥4
11፥48 ማቴ23፥ 29-32፤ሐሥ7፥51-53
11፥49 ማቴ23፥ 24፤1ቆሮ1፥24፡ 30፤ቈላ2፥3
11፥52 ማቴ23፥13
11፥54 ማቴ12፥10
12፥1 ማቴ16፥6፡ 11፡12
12፥2 ማር4፥22
12፥4 ዮሐ15፥14፡15
12፥5 ዕብ10፥31
12፥7 ማቴ10፥30፤ 12፥12
12፥8 ሉቃ15፥10
12፥10 ማቴ8፥20፤ 12፥31፡32፤ 1ዮሐ5፥16
12፥11 ማቴ10፥

## የማስጠንቀቂያና የማበረታቻ ቃላት

12፥2-9 ተጓ ምብ-ማቴ 10፥26-33

12 በዚያን ጊዜ፣ በብዙ ሺህ የሚቈጠር
ሕዝብ እርስ በርስ እስኪረጋገጥ
ድረስ ተሰብስቦ ሳለ፣ ኢየሱስ ለደቀ መዛ
ሙርቱ እንዲህ ይል ጀመር፤ "ከፈሪሳው
ያን እርሾ ተጠንቀቁ፤ ይህም ግብዝነት
ነው። 2የማይገለጥ የተሸፈነ፣ የማይታወቅ
የተሰወረ ምንም የለም። 3ስለዚህ በጨለማ
ያወራችሁት ሁሉ በብርሃን ይሰማል፤ በእ
ልፍኝም ውስጥ በጆሮ ያንሾካሾካችሁት
በሰገነት በይፋ ይነገራል።
4"ወዳጆቼ ሆይ፤ እላችኋለሁ ሥጋን
የሚገድሉትን፣ ከዚያ ወዲያ ግን ምንም
ማድረግ የማይችሉትን አትፍሩ። 5ነገር
ግን መፍራት የሚገባችሁን አሳያችኋለሁ፤
ከገደለ በኋላ ወደ ገሃነም ለመጣል ሥል
ጣን ያለውን እርሱን ፍሩት፤ አዎን፤
እርሱን ፍሩት እላችኋለሁ። 6አምስት ድን
ቢጦች በዐሥር ሳንቲም[ሐ] ይሸጡ የለምን?
ይሁን እንጂ ከእነርሱ አንዷ እንኳ በእግዚአብሐ
ሔር ዘንድ አትዘነጋም። 7የእናንተ የራ
ሳችሁ
ጠጕር ሁሉ እንኳ የተቈጠረ ነው፤ እንግዲህ
አትፍሩ፤ ከብዙ ድንቢጦች የበለጠ ዋጋ
አላችሁ።
8"እላችኋለሁ፤ በሰው ፊት ለሚመሰክ
ርልኝ ሁሉ የሰው ልጅ ደግሞ በእግዚአብሐ
ሔር መላእክት ፊት ይመሰክርለታል።
9በሰው ፊት የሚክደኝም በእግዚአብሔር
መላእክት

[^]41 ወይም *ያላችሁን*
[ሐ]6 ግሪኩ *ሁለት ኢሳሪያ* ይላል

ፊት ይካዳል። 10በሰው ልጅ ላይ የማቃለል ቃል የሚሰነዝር ሁሉ ይሰረይለታል፤ መንፈስ ቅዱስን የሚሳደብ ግን አይሰረይለትም።

11“ሰዎች ይዘው ወደ ምኵራብ፣ ወደ ገዥዎችና ወደ ባለ ሥልጣናት ባቀረቧችሁ ጊዜ፣ እንዴት ወይም ምን እንደምትመልሱ አትጨነቁ፤ 12በዚያ ሰዓት መንፈስ ቅዱስ መናገር የሚገባችሁን ያስተምራችኋልና።”

## የሀብታሙ ሰው ሞኝነት

13ከሕዝቡም መካከል አንድ ሰው፣ “መምህር ሆይ፤ ወንድሜ ውርስ እንዲያካፍለኝ ንገረው” አለው።

14ኢየሱስም፣ “አንተ ሰው፤ በእናንተ ላይ ፈራጅ ወይም ዳኛ ያደረገኝ ማነው?”አለው። 15ደግሞም፣ “የሰው ሕይወቱ በሀብቱ ብዛት የተመሠረተ ስላልሆነ፣ ተጠንቀቁ፤ ከስግብግብነትም ሁሉ ራሳችሁንም ጠብቁ” አላቸው።

16ቀጥሎም እንዲህ ሲል ምሳሌ ነገራቸው፤ “ዕርሻው እጅግ ፍሬያማ የሆነችለት አንድ ሀብታም ነበረ፤

17ይህም ሰው፣ ምርቴን የማከማችበት ስፍራ ስለሌለኝ ምን ላድርግ? ብሎ በልቡ አሰበ።

18“እንዲህም አለ፤ እንደዚህ አደርጋለሁ፤ ያሉኝን ጐተራዎች አፈርስና ሌሎች ሰፋ ያሉ ጐተራዎች እሠራለሁ፤ በዚያም ምርቴንና ንብረቴንም ሁሉ አከማቻለሁ፤ 19ነፍሴንም፣ “ነፍሴ ሆይ፤ ለብዙ ዘመን የሚበቃሽ ሀብት አከማችቼልሻለሁ፤ እንግዲህ ዕረፊ፤ ብዪ፤ ጠጪ፤ ደስም ይበልሽ” እላታለሁ።

20“እግዚአብሔር ግን፣ አንተ ሞኝ፤ ነፍስህን በዚህች ሌሊት ከአንተ ሊውስዱ ይፈልጓታል፤ እንግዲህ፣ ለራስህ ያከማቸኸው ለማን ይሆናል? አለው።

21“ስለዚህ ለራሱ ሀብት የሚያከማች፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ሀብታም ያልሆነ ሰው መጨረሻው ይኸው ነው።”

## አትጨነቁ

12፥23-31 ተጓ ምብ – ማቴ 6፥25-33

22ከዚያም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፤ “ስለዚህ እላችኋለሁ፣ ስለ ሕይወታችሁ ምን እንደምትበሉ፣ ወይም ስለ ሰውነታችሁ ምን እንደምትለብሱ አትጨነቁ፤ 23ሕይወት ከምግብ፣ ሰውነትም ከልብስ ይበልጣልና። 24ቁራዎችን ተመልከቱ፤ አይዘሩም፤ አያጭዱም፤ ማከማቻ ወይም ጐተራ የላቸውም፤ እግዚአብሔር ግን ይመግባቸዋል። እናንተማ ከወፎች እጅግ ትበልጡ የለምን? 25ለመሆኑ ከእናንተ ተጨንቆ በዕድሜው ላይ አንዲት ደቂቃ መጨመር የሚችል ማነው?[ሠ] 26እንግዲህ ቀላሉን ነገር እንኳ ማድረግ የማትችሉ ከሆነ፣ ስለ ሌላው ነገር ለምን ትጨነቃላችሁ?

27“እስቲ አበቦች እንዴት እንደሚያድጉ ተመልከቱ፤ አይለፉም፤ አይፈትሉም፤ ነገር ግን እላችኋለሁ፤ ሰሎሞን እንኳ በዚያ ሁሉ ክብሩ ከእነርሱ እንደ አንዷ አልለበሰም። 28እንግዲህ እግዚአብሔር ዛሬ ታይቶ ነገ ወደ እሳት የሚጣለውን የሜዳ ሣር እንዲህ የሚያለብስ ከሆነ፣ እናንተ እምነት የጐደላችሁ፣ እናንተንማ እንዴት አብልጦ አያለብሳችሁም? 29ስለዚህ ምን እንደምትበሉና ምን እንደምትጠጡ በመሻት ልባችሁ አይጨነቅ፤ 30ይህንማ በዓለም ያለ ሕዝብ ሁሉ ይፈልጋል፤ አባታችሁ እኮ ይህ ሁሉ እንደሚያስፈልጋችሁ ያውቃል። 31ይልቁንስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ በተጨማሪ ይሰጣችኋል።

32“እናንተ አነስተኛ መንጋ የሆናችሁ መንግሥትን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ መልካም ፈቃድ ነውና አትፍሩ፤ 33ያላችሁን ሽጡና ለድኾች ስጡ፤ ሌባ በማይሰርቅበት፣ ብል በማይበላበት፣ በማያረጅ ከረጢት የማያልቅ ንብረት በሰማይ አከማቹ፤ 34ልባችሁ፣ ንብረታችሁ ባለበት ቦታ ይሆናልና።

## ነቅቶ መጠበቅ

12፥35፡36 ተጓ ምብ -ማቴ 251-13፤ ማር 13፥33-37
12፥39፡40፤ 42-46 ተጓ ምብ – ማቴ 24፥ 43-51

35“በአጭር ታጥቃችሁ ተዘጋጁ፤ መብራታችሁም የበራ ይሁን፤ 36ጌታቸው ከሰርግ ግብዣ እስኪመለስ እንደሚጠባበቁና መጥቶም በር ሲያንኳኳ ወዲያው ለመክፈት ዝግጁ የሆኑ ሰዎችም ምሰሉ። 37ጌታቸው በሚመጣበት ጊዜ ነቅተው የሚያገኛቸው አገልጋዮች ብፁዓን ናቸው፤ እውነት እላችኋለሁ፤ ጌታቸውም በአጭር ይታጠቃል፤ በማእድ ያስቀምጣቸዋል፤ ቀርቦም ያስተናግዳቸዋል። 38ከሌሊቱ በሁለተኛውም ሆነ በሦስተኛው ክፍል መጥቶ እንደዚያው ነቅተው ቢያገኛቸው፣ እነዚያ አገልጋዮች ብፁዓን ናቸው። 39ይህን ግን ዕወቁ፤ ሌባ በምን ሰዓት እንደሚመጣ የቤቱ ባለቤት ቢያውቅ ኖሮ፣ ቤቱ ሲቈፈር ዝም ብሎ ባላየ ነበር። 40እናንተም ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ፤ የሰው ልጅ ባላሰባችሁት ሰዓት ይመጣልና።”

41ጴጥሮስም፣ “ጌታ ሆይ፤ ይህን ምሳሌ የምትናገረው ለእኛ ብቻ ነው ወይስ ለሁሉም ጭምር ነው?” አለው።

[ሠ]25 ወይም *በቍመት ላይ አንድ ክንድ*

17፡19፤ሉቃ21፥12፡14
**12፥12** ዘፀ4፥12፤ ማቴ10፥20፤13፥11፤ ሉቃ21፥15
**12፥15** ኢዮ20፥20፤ 31፥24፤መዝ62፥10
**12፥20** ኢዮ27፥8፤ መዝ39፥6፤49፥10፤ ኤር17፥11፤ ሉቃ11፥40
**12፥21** ቍ33
**12፥24** ኢዮ38፥41፤ መዝ147፥9
**12፥27** 1ነገ10፥4-7
**12፥28** ማቴ6፥30
**12፥30** ማቴ6፥8፤ ሉቃ6፥36
**12፥31** ማቴ3፥2፤ 19፥29
**12፥32** ማቴ14፥27፤ 25፥34
**12፥33** ማቴ6፥20፤ ሐሥ2፥45፤ያዕ5፥2
**12፥34** ማቴ6፥21
**12፥37** ማቴ20፥28፤24፥42፡46፤25፥13
**12፥39** ማቴ6፥19፤ 1ተሰ5፥2፤2ጴጥ3፥10፤ ራእ3፥3፤ 16፥15
**12፥40** ማር13፥33፤ ሉቃ21፥36

42ጌታም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “እንግዲህ፣
ምግባቸውን በተገቢው ጊዜ እንዲሰጣቸው
ጌታው በቤተ ሰዎቹ ላይ የሚሾመው ታማ
ኝና ብልህ መጋቢ ማነው? 43ጌታው ሲመ
ለስ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው አገል
ጋይ እርሱ ብፁዕ ነው። 44እውነት እላችኋ
ለሁ፤ ባለው ንብረት ሁሉ ላይ ይሾመዋል።
45ዳሩ ግን ያ አገልጋይ፣ ጌታዬ ቶሎ አይ
መጣም፤ ይዘገያል፤ ብሎ ቢያስብና ወን
ድና ሴት አገልጋዮችን ቢደበድብ፣ ደግ
ሞም እንዳሻው መብላት፣ መጠጣትና
መስከር ቢጀምር፣ 46የዚያ አገልጋይ ጌታ
ባላሰበው ቀንና ባልጠረጠረው ሰዓት ይመ
ጣበታል፤ ስለዚህ ይቈራርጠዋል፤ ዕድል
ፈንታውንም ከማያምኑ ጋር ያደርጋል።

47“የጌታውን ፍላጎት እያወቀ የማይዘጋ
ጅና ፈቃዱን የማያደርግ አገልጋይ እርሱ
ክፉኛ ይገረፋል፤ 48ነገር ግን ይህን ሳያውቅ
ቀርቶ መገረፍ የሚገባውን ያህል ያደረገ
አገልጋይ በጥቂቱ ይገረፋል። ብዙ ከተሰጠ
ው ሁሉ ብዙ ይፈለግበታል፤ ብዙ ዐደራም
ከተቀበለም ብዙ ይጠበቅበታል።

## ሰላም ሳይሆን መለያየት

12፥51-53 ተጓ ምብ – ማቴ 10፥34-36

49“እኔ የመጣሁት በምድር ላይ እሳት
ለመለኰስ ነው፤ አሁኑኑ ቢቀጣጠል ምንኛ
ደስ ባለኝ! 50ነገር ግን የምጠመቀው ጥም
ቀት አለኝ፤ እስኪፈጸምም ድረስ እንዴት
ተጨንቄአለሁ? 51በምድር ላይ ሰላምን ለማ
ምጣት የመጣሁ ይመስላችኋል? አይደ
ለም፤ እላችኋለሁ፤ እኔ የመጣሁት ለመ
ለያየት ነው። 52ከአሁን ጀምሮ እርስ በርስ
የተለያዩ በአንድ ቤተ ሰብ ውስጥ አምስት
ሰዎች ይኖራሉ፤ ሁለቱ በሦስቱ ላይ፣ ሦስ
ቱም በሁለቱ ላይ ተነሥተው ይለያያሉ፤
53አባት በወንድ ልጁ ላይ፣ ወንድ ልጅም
በአባቱ ላይ፣ እናት በሴት ልጇ ላይ፣ ሴት
ልጅም በእናቷ ላይ፣ አማት በምራቷ ላይ፣
ምራትም በአማቷ ላይ ተነሥተው
ይለያያሉ።”

## ዘመናትን መመርመር

54ደግሞም ለሕዝቡ እንዲህ አለ፤ “ደመና
በምዕራብ በኩል ሲወጣ ስታዩ ወዲያው፣
ዝናብ ሊመጣ ነው ትላላችሁ፤ እንደዚ
ያም ይሆናል፤ 55የደቡብ ነፋስም ከደቡብ
በኩል ሲነፍስ፣ ቀኑ ሞቃት ይሆናል
ትላላችሁ፤ እንደዚያም ይሆናል። 56እናንት
ግብዞች፤ የምድሩንና የሰማዩን መልክ
መመርመር ታውቁበታላችሁ፤ ታዲያ ይህን
የአሁኑን ዘመን መመርመር እንዴት ተሳ
ናችሁ?

57“ታዲያ ራሳችሁ ትክክለኛ የሆነውን

12፥42 ሉቃ7፥13
12፥46 ቀኍ40
12፥47 ዘዳ25፥2
12፥48 ዘሌ5፥17፤
ዘኍ15፥27-30
12፥50 ማር10፥38፤
ዮሐ19፥30
12፥53 ሚክ7፥6፤
ማቴ10፥21
12፥54 ማቴ16፥3
12፥58 ማቴ5፥25
12፥59 ማቴ5፥26፤
ማር12፥42
13፥1 ማቴ27፥2
13፥2 ዮሐ9፥2፡3
13፥4 ዮሐ9፥7፡11
13፥5 ማቴ3፥2፤
ሐሥ 2፥38
13፥6 ኢሳ5፥2፤
ኤር8፥13፤ማቴ21፥19
13፥7 ማቴ3፥10
13፥10 ማቴ4፥23
13፥11 ቀኍ16
13፥13 ማር5፥23
13፥14 ዘፀ20፥9፤
ማቴ12፥2፤ማር5፥22
13፥15 ሉቃ14፥5

ነገር ለምን አትፈርዱም? 58ከባላጋራህ ጋር
ወደ ዳኛ ፊት ለመቅረብ ስትሄድ፣ ገና
በመንገድ ላይ ሳለህ ለመታረቅ ጥረት
አድርግ፤ አለበ ለዚያ ጐትቶ ወደ ዳኛው
ይወስድሃል፤ ዳኛ ውም ለመኰንኑ አሳልፎ
ይሰጥሃል፤ መኰን ኑም ወደ ወህኒ
ይጥልሃል፤ 59እልሃለሁ፤ የመ ጨረሻዋን
ሳንቲም[‘] እስክትከፍል ድረስ ከዚያ
አትወጣም።

## የንስሓ ጥሪ

13 በዚህ ጊዜ መጥተው፣ ጲላጦስ ደማ
ቸውን ከመሥዋዕታቸው ጋር ስለ
ደባለቀው ስለ ገሊላ ሰዎች ያወሩለት ሰዎች
በዚያ ነበሩ። 2እርሱም እንዲህ መለሰላቸው፤
“ታዲያ እነዚህ የገሊላ ሰዎች ይህ ሥቃይ
የደረሰባቸው ከሌሎቹ የገሊላ ሰዎች ሁሉ
ይልቅ ኀጢአተኞች ስለ ነበሩ ይመስላችኋል?
3አይደለም እላችኋለሁ፤ ንስሓ ካልገባችሁ
ሁላችሁ እንደዚሁ ትጠፋላችሁ። 4ወይም
ደግሞ በሰሊሆም ግንብ ተንዶባቸው የሞቱት
ዐሥራ ስምንት ሰዎች በኢየሩሳሌም ከሚ
ኖሩት ሰዎች ሁሉ ይልቅ በደለኞች ስለ
ነበሩ ይመስላችኋል? 5አይደለም፤ እላች
ኋለሁ፤ ንስሓ ካልገባችሁ ሁላችሁ እንደዚሁ
ትጠፋላችሁ።”

6ደግሞም እንዲህ ሲል ይህን ምሳሌ
ተናገረ፤ “አንድ ሰው በወይኑ ዕርሻ ቦታ
የተተከለች አንዲት የበለስ ተክል ነበረ
ችው፤ እርሱም ፍሬ ሊፈልግባት መጥቶ
ምንም አላገኘም። 7የወይን አትክልት ሠራተ
ኛውንም፣ ‘እነሆ፤ ፍሬ ለማግኘት ልፈልግባት
ሦስት ዓመት ወደዚህች በለስ መጥቼ ምንም
አላገኘሁም፤ ስለዚህ ቍረጣት፤ ለምን ዐፈ
ሩን በከንቱ ታሟጥጣለች?’ አለው።

8“እርሱ ግን እንዲህ ሲል መለሰለት፤
ጌታ ሆይ፤ ዙሪያዋን እስክኰተኵትላትና
ፍግ እስከማደርግላት ድረስ ለዘንድሮ ብቻ
ተዋት፤ 9ለከርሞ ካፈራች መልካም ነው፤
አለበለዚያ ትቈርጣታለህ።”

## አንዲት ጐባጣ ሴት በሰንበት ቀን ተፈወሰች

10ኢየሱስ በሰንበት ቀን በአንድ ምኵራብ
ያስተምር ነበር። 11በዚያም የድካም መን
ፈስ ዐሥራ ስምንት ዓመት ሙሉ አካለ
ስንኩል ያደረጋት አንዲት ሴት ነበረች፤
እርሷም ከመጕብጧ የተነሣ ፈጽሞ ቀና
ማለት አትችልም ነበር። 12ኢየሱስም ባያት
ጊዜ ጠራትና፣ “አንቺ ሴት፤ ከሕመምሽ
ነጻ ወጥተሻል” አላት፤ 13እጁንም በላይዋ
ጫነ፤ እርሷም ወዲያው ቀጥ ብላ ቆመች፤
እግዚአብሔርንም አመሰገነች።

14የምኵራቡ አለቃ ግን፣ ኢየሱስ
በሰንበት

[‘]59 ግሪኩ ሌፕቶን ይላል

ቀን ስለ ፈወሰ ተቈጥቶ ሕዝቡን፣ “ሥራ
ሊሠራባቸው የሚገባ ስድስት ቀኖች አሉ፤
ስለዚህ በእነዚያ ቀኖች እየመጣችሁ ተፈ
ወሱ እንጂ በሰንበት ቀን አይደለም” አላ
ቸው።

15ጌታም መልሶ እንዲህ አለው፤ “እናንት
ግብዞች፤ ከእናንተ መካከል አንድ ሰው በሬ
ውን ወይም አህያውን በሰንበት ቀን ከግደ
ረያው ፈትቶ ውሃ ሊያጠጣ ይወስደው
የለምን? 16ታዲያ፣ ይህች ሴት የአብርሃም
ልጅ ሆና ሳለች ዐሥራ ስምንት ዓመት
ሙሉ በሰይጣን ታስራ ስትኖር፣ ከዚህ እስ
ራት በሰንበት ቀን መፈታት አይገባት
ምን? ”

17ይህን በተናገረ ጊዜ ተቃዋሚዎቹ
ሁሉ ዐፈሩ፤ ሕዝቡ ሁሉ ግን እርሱ ባደ
ረገው ድንቅ ሥራ ሁሉ ደስ አላቸው።

## የሰናፍጭ ቅንጣትና የእርሾ ምሳሌ

13፥18፡19 ተጓ ምብ - ማር 4፥30-32
13፥18-21 ተጓ ምብ - ማቴ13፥31-33

18ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ “የእግዚ
አብሔር መንግሥት ምን ትመስላለች?
ከም ንስ ጋር ላመሳስላት? 19አንድ ሰው
ወስዶ በዕርሻው ውስጥ የዘራትን የሰናፍጭ
ቅንጣት ትመስላለች፤ አድጋ ዛፍ ሆነች፤
የሰማይ ወፎችም በቅርንጫፎቿ ላይ ሰፈሩ
።”

20ደግሞም እንዲህ አለ፤ “የእግዚአብሔርን
መንግሥት ከምን ጋር ላመሳስላት? 21አንዲት
ሴት ወስዳ በሙሉ እስኪቦካ ድረስ በዛ ካለ[ሰ]
ዱቄት ጋር የደባለቀችውን እርሾ ትመስላ
ለች።”

## ጠባቧ በር

22ከዚያ በኋላ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም
እያመራ ሳለ፣ በሚያልፍባቸው ከተሞችና
መንደሮች እያስተማረ ያልፍ ነበር። 23አንድ
ሰውም ቀርቦ፣ “ጌታ ሆይ፤ የሚድኑት
ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸውን?” አለው።

እርሱም እንዲህ አላቸው፤ 24“በጠባቧ
በር ለመግባት ተጣጣሩ፤ እላችኋለሁ፤ ብዙ
ዎች ለመግባት ይፈልጋሉ ነገር ግን አይ
ሆንላቸውም፤ 25የቤቱ ባለቤት ተነሥቶ በሩን
ከቈለፈ በኋላ በውጭ ቆማችሁ፣ ጌታ
ሆይ፤ ክፈትልን እያላችሁ በሩን ማንኳ
ኳት ትጀምራላችሁ።

“እርሱ ግን፣ ማን እንደ ሆናችሁና ከየት
እንደ መጣችሁ አላውቅም ብሎ ይመልስ
ላችኋል።

26“እናንተም፣ ከአንተ ጋር አብረን በል
ተናል፣ ጠጥተናል፤ በአደባባያችንም አስተ
ምረሃል ትላላችሁ።

27“እርሱም፣ እላችኋለሁ፤ ማን

13፥16 ማቴ4፥10፤ ሉቃ3፥8
13፥17 ኢሳ66፥5
13፥18 ማቴ3፥2፤ 13፥24
13፥19 ማቴ13፥32፤ ሉቃ17፥6
13፥21 1ቆሮ5፥6
13፥22 ሉቃ9፥51
13፥24 ማቴ7፥13
13፥25 ማቴ7፥23፤ 25፥10–12
13፥27 ማቴ 7፥23
13፥28 ማቴ8፥12
13፥29 ማቴ8፥11
13፥30 ማቴ19፥30
13፥31 ማቴ14፥1
13፥32 ዕብ2፥10
13፥33 ማቴ21፥11
13፥34 ማቴ23፥27
13፥35 መዝ118፥26 ኤር12፥17፤22፥5፤ ሉቃ19፥38
14፥1 ማቴ12፥10፤ ሉቃ7፥36፤11፥37
14፥3 ማቴ12፥2፤ 22፥35
14፥5 ሉቃ13፥15
14፥7 ሉቃ11፥43

እንደሆናች ሁና ከየት እንደመጣችሁ
አላውቅም፤ እና ንት ዐመፀኞች ሁሉ
ከእኔ ራቁ ይላል።

28“አብርሃምን፣ ይስሐቅንና ያዕቆብን፣
ነቢያትንም ሁሉ በእግዚአብሔር መንግሥት
ውስጥ ስታዩ፣ እናንተ ግን ወደ ውጭ
ተጥላችሁ ስትቀሩ በዚያን ጊዜ ልቅሶና
ጥርስ ማፋጨት ይሆናል። 29ሰዎች ከም
ሥራቅ፣ ከምዕራብ፣ ከሰሜንና ከደቡብ
መጥተው በእግዚአብሔር መንግሥት በማእድ
ይቀመጣሉ። 30እነሆ፤ ከኋለኞች መካ
ከል ፊተኞች የሚሆኑ፣ ከፊተኞች መካ
ከልም ኋለኞች የሚሆኑ አሉ።”

## ኢየሱስ ስለ ኢየሩሳሌም ዐዘነ

13፥34፡35 ተጓ ምብ – ማቴ 23፥37-39
13፥34፡35 ማመ – ሉቃ 19፥41

31በዚያን ጊዜ ከፈሪሳውያን አንዳንዶች
መጥተው፣ “ሄሮድስ ሊገድልህ ስለሚ
ፈልግ ተነሥተህ ከዚህ ሂድ” አሉት።

32እርሱም እንዲህ አላቸው፤ “ሄዳችሁ
ለዚያ ቀበሮ፣ እነሆ፤ ዛሬና ነገ አጋንን
ትን አወጣለሁ፤ ሕመምተኞችን እፈው
ሳለሁ፤ በሦስተኛውም ቀን ከግቤ እደርሳ
ለሁ ብሎአል በሉት፤ 33ይሁን እንጂ ነቢይ
ከኢየሩሳሌም ውጭ ይሞት ዘንድ አይገ
ባምና ዛሬና ነገ፣ ከነገ ወዲያም ወደዚ
ያው ጕዞዬን እቀጥላለሁ።

34“ኢየሩሳሌም፣ ኢየሩሳሌም ሆይ፤
ነቢያትን የምትገድዪ፣ ወደ አንቺ የተ
ላኩትንም በድንጋይ የምትወግሪ! ዶሮ
ጫጩቶቿን በክንፎቿ ሥር እንደምትሰ
በስብ፣ ልጆችሽን ለመሰብሰብ ስንት ጊዜ
ፈለግሁ፤ እናንተ ግን እምቢ አላችሁ፤
35እነሆ፤ ቤታችሁ ወና ሆኖ ቀርቶአል።
እላችኋለሁ፤ በጌታ ስም የሚመጣ የተባ
ረከ ነው እስክትሉ ድረስ ከእንግዲህ
አታዩኝም።”

## ኢየሱስ በአንድ ፈሪሳዊ ቤት

14፥8-10 ማመ – ምሳ 25፥6፡7

14 አንድ ሰንበት ቀን፣ ኢየሱስ
ምግብ ሊበላ ከፈሪሳውያን አለ
ቆች አንዱ ወደ ነበረ ሰው ቤት በገባ ጊዜ፣
ሰዎች በዐይን ይከታተሉት ነበር። 2በዚ
ያም በአካል እብጠት የሚሠቃይ አንድ
ሰው ከፊት ለፊቱ ነበር። 3ኢየሱስም ሕግ
ዐዋቂዎችንና ፈሪሳውያንን፣ “በሰንበት ቀን
ሕመምተኞችን መፈወስ ተገቢ ነው ወይስ
አይደለም?” ሲል ጠየቃቸው። 4እነርሱ ግን
ዝም አሉ። እርሱም ሰውየውን ይዞ ፈወሰ
ውና አሰናበተው።

[ሰ]21 ግሪኩ *ሦስት መስፈሪያ* (22 ሊትር የሚያህል) ይላል

[5]ደግሞም፣ “ከእናንተ አንዱ፣ ልጁ[ⁿ]
ወይም በሬው በሰንበት ቀን ጕድጓድ ቢገ
ባበት ፈጥኖ የማያወጣው ማን ነው?”
አላቸው። [6]እነርሱም ለዚህ አንዳች መልስ
ሊያገኙ አልቻሉም።
[7]ኢየሱስ ተጋባዦቹ የክብር ስፍራ ሲመ
ርጡ ተመልክቶ፣ እንዲህ ሲል ይህን
ምሳሌ ለእነርሱ ነገራቸው፤ [8]“አንድ ሰው
ሰርግ ቢጠራህ፣ በክብር ስፍራ አትቀመጥ፤
በክብር ከአንተ የሚበልጥ ሰው ተጠርቶ
ከሆነ፣ [9]ሁለታችሁንም የጋበዘው መጥቶ፣
ስፍራውን ‘ለዚህ ሰው ልቀቅለት’ ይል
ሃል፤ አንተም እያፈርህ ወደ ዝቅተኛው
ስፍራ ትሄዳለህ። [10]ነገር ግን በተጠራህ ጊዜ
ዝቅተኛውን ስፍራ አይተህ ተቀመጥ፤
ጋባዥህም ሲመጣ፣ ወዳጄ ሆይ፤ ወደ
ላይ ከፍ በል ይልሃል፤ አንተም በዚያን
ጊዜ አብረውህ በማእድ በተቀመጡ ሰዎች
ሁሉ ፊት ትከበራለህ። [11]ምክንያቱም ራሱን
ከፍ ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ዝቅ ይላል፤
ራሱንም ዝቅ ዝቅ የሚያደርግ ሁሉ ከፍ
ይላል።”
[12]ኢየሱስም የጋበዘውን ሰው ደግሞ እንዲህ
አለው፤ “የምሳ ወይም የእራት ግብዣ
በምታደርግበት ጊዜ፣ በአጸፋው እንዳይጋ
ብዙህና ብድራትን እንዳይመልሱልህ፣ ወዳ
ጆችህን ወይም ወንድሞችህን ወይም ዘመ
ዶችህን ወይም ከበርቴ ጎረቤቶችህን አትጋ
ብዝ። [13]ነገር ግን ግብዣ ባዘጋጀህ ጊዜ
ድኾችን፣ አካለ ስንኩሎችን፣ ሽባዎች
ንና ዐይነ ስወሮችን ጥራ፤ [14]ትባረካለህም።
እነዚህ ብድር ሊመልሱልህ ስለማይችሉ፣
በጻድቃንም ትንሣኤ ብድራትህ ይመለስል
ሃል።”

## የትልቅ ግብዣ ምሳሌነት

14፥16-24 *ማመ* - *ማቴ* 22፥2-14

[15]ከኢየሱስ ጋር በማእድ ከተቀመጡት
መካከል አንዱ ይህን ሰምቶ “በእግዚአብሔር
መንግሥት ቀርቦ ከማእድ የሚበላ ብፁዕ
ነው” አለው።
[16]ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ “አንድ
ሰው ትልቅ ግብዣ አዘጋጅቶ ብዙ ሰው ጠራ
፤ [17]የግብዣውም ሰዓት በደረሰ ጊዜ
የተጋ በዙትን እንግዶች፣ እነሆ፤ ሁሉም
ነገር ተዘጋጅቶአልና ኑ ብሎ እንዲጠሩ
አገል ጋዩን ላከባቸው።
[18]“ነገር ግን ሁሉም የየራሳቸውን ምክን
ያት ይፈጥሩ ጀመር፤ አንደኛው፣ ገና
አሁን መሬት ስለ ገዛሁ ሄጄ ማየት
አለብኝ፤ እባ ክህ፣ ይቅርታ አድርግልኝ
አለው።
[19]“ሌላኛውም፣ ‘አምስት ጥማድ በሬዎች
ገዝቻለሁ፤ እነርሱን ልፈትናቸው ስለ ሆነ
እባክህ ይቅርታ አድርግልኝ’ አለ።
[20]“ሌላው ደግሞ፣ ‘ገና ሙሽራ ስለሆንሁ
ልመጣ አልችልም’ አለ።
[21]“አገልጋዩም ተመልሶ መጥቶ ይህንኑ
ለጌታው ነገረው። በዚህን ጊዜ የቤቱ
ጌታ ተቈጥቶ አገልጋዩን፣ ‘ቶሎ ብለህ
ወደ ከተማው አውራ ጐዳናዎችና መተላ
ለፊያ መንገዶች ውጣ፤ ድኾችንና አካለ
ስንኩሎችን፣ ዐይነ ስውሮችንና ዐንካሶችን
ወደዚህ አስገባቸው’ አለው።
[22]“አገልጋዩም፣ ‘ጌታዬ፤ ያዘዝኸው ሁሉ
ተፈጽሟል፤ ገና አሁንም ቦታ አለ’ አለው።
[23]“ጌታውም አገልጋዩን፣ ‘ወደ ጐዳናዎ
ችና ወደ ገጠር መንገዶች ውጣ፤ ቤቴም
እንዲሞላ ያገኘኸውን ሁሉ በግድ አምጥ
ተህ አስገባ፤ [24]እላችኋለሁና ከተጋበዙት
ከእነዚያ ሰዎች መካከል አንድ ሰው እንኳ
ግብዣዬን አይቀምስም አለው።”

## ደቀ መዝሙር መሆን የሚያስከፍለው ዋጋ

[25]ብዙ ሕዝብ አብሮት እየተጓዘ ሳለ፣ ኢየ
ሱስ ዞወር ብሎ እንዲህ አላቸው፤ [26]“ወደ
እኔ የሚመጣ ሁሉ አባቱንና እናቱን ሚስቱ
ንና ልጆቹን፣ ወንድሞቹንና እኅቶቹን፣ የራ
ሱንም ሕይወት እንኳ ሳይቀር ባይጠላ፣
ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም፤ [27]የራ
ሱንም መስቀል ተሸክሞ የማይከተለኝ ደቀ
መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።
[28]“ከእናንተ አንድ ሰው ሕንጻ ለመሥራ
ት ቢፈልግ፣ መደምደም መቻል
አለመቻ ሉን በመጀመሪያ ተቀምጦ
ዋጋውን የማ ይተምን ማን ነው? [29]መ
ሠረቱን ጥሎ መደምደም ቢያቅተው፣
ያዩት ሁሉ ይዘባበ ቱበታል፤ [30]እንዲህም
ይላሉ፤ ‘ይህ ሰው ማነጽ ጀምሮ ነበር፤
መደምደም ግን አቃ ተው።’
[31]“ወይም አንድ ንጉሥ ከሌላው ንጉሥ
ጋር ጦርነት ሊገጥም በሚነሣበት ጊዜ፣
ሃያ ሺህ ሰራዊት አስከትቶ የሚመጣበትን
ንጉሥ፣ በዐሥር ሺህ ሰራዊት መመከት
እንደሚችል ተቀምጦ የማይመክር ማን
ነው? [32]መቋቋም የማይችል ከሆነ፣ ሌላው
ንጉሥ ገና ሩቅ ሳለ፣ መልእክተኞች ልኮ
ዕርቅ ይጠይቃል። [33]እንደዚሁም፣ ከእናንተ
ማንም ያለውን ሁሉ የማይተው፣ ደቀ
መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።
[34]“ጨው መልካም ነው፤ ጨው ጣዕሙን
ካጣ ግን እንዴት ተመልሶ የጨውነት ጣዕም
ሊኖረው ይችላል?

14፥11 ማቴ23፥12
14፥13 ቊ21
14፥14 ሐሥ24፥15
14፥15 ኢሳ25፥6፤ ማቴ3፥2፤26፥29፤ ሉቃ13፥29፤ራእ19፥9
14፥21 ቊ13
14፥24 ማቴ21፥43፤ሐሥ 13፥46
14፥26 ማቴ10፥37፤ዮሐ12፥25
14፥27 ማቴ10፥38፤ሉቃ9፥23
14፥33 ፊል3፥7፡8
14፥34 ማር9፥50

[ⁿ]5 አንዳንድ ቅጆች አህያው ይላሉ

[35]ለመሬትም ሆነ ለማዳበሪያነት የማ
ይጠቅም በመሆኑ ወደ ውጭ ይጣላል።
"ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ።"

### የጠፋው በግ ምሳሌ

15፥4-7 ተጓ ምብ – ማቴ 18፥12-14

15 አንድ ቀን፣ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና "ኀጢ
አተኞች" ሁሉ ሊሰሙት በዙሪያው
ተሰበሰቡ። [2]ፈሪሳውያንና ጸሐፍትም፣ "ይህ
ሰው ኀጢአተኞችን ይቀበላል፤ ከእነርሱም
ጋር ይበላል" እያሉ አጒረመረሙ።
[3]ኢየሱስም እንዲህ ሲል ይህን ምሳሌ
ነገራቸው፤ [4]"ከእናንተ መካከል አንዱ መቶ
በጎች ቢኖሩትና ከእነርሱ አንዱ ቢጠፋ
በት፣ ዘጠና ዘጠኙን በሜዳ ላይ ጥሎ የጠ
ፋውን እስኪያገኝ ድረስ ሊፈልገው የማይ
ሄድ ማን ነው? [5]ባገኘውም ጊዜ ደስ ብሎት
በጫንቃው ተሸክሞ፣ [6]ወደ ቤቱ ይመለ
ሳል፤ ወዳጆቹንና ጎረቤቶቹንም በአንድነት
ጠርቶ፣ 'የጠፋውን በጌን አግኝቻለሁና ከእኔ
ጋር ደስ ይበላችሁ' ይላቸዋል። [7]እላችኋ
ለሁ፤ እንደዚሁም ንስሓ ከማያስፈልጋቸው
ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ፣ ንስሓ በሚ
ገባ በአንድ ኀጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆ
ናል።

### የጠፋው ሳንቲም ምሳሌ

[8]"ወይም ዐሥር የብር ሳንቲሞች ያላት
ሴት ከዐሥሩ አንዱ ቢጠፋባት፣ እስክታገ
ኘው ድረስ መብራት አብርታ፣ ቤቷን ጠርጋ፣
አጥብቃ የማትፈልግ ሴት ማን ናት?
[9]ባገኘችውም ጊዜ ወዳጆቿንና ጐረቤቶቿን፣
በአንድነት ጠርታ፣ 'የጠፋብኝን የብር ሳን
ቲም አግኝቻለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላ
ችሁ' ትላቸዋለች። [10]እላችኋለሁ፤ እንደዚ
ሁም ንስሓ በሚገባ በአንድ ኀጢአተኛ በእ
ግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል።

### ጠፍቶ የተገኘው ልጅ ምሳሌነት

[11]ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤
"አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት። [12]ከእ
ነርሱም ታናሹ ልጅ አባቱን፣ 'አባቴ ሆይ፤
ከሀብትህ ድርሻዬን ስጠኝ' አለው፤ አባትየ
ውም ሀብቱን ለልጆቹ አካፈላቸው።
[13]"ብዙም ቀን ሳይቈይ፣ ታናሹ ልጅ
ድርሻውን ሁሉ ጠቅልሎ ወደ ሩቅ አገር
ሄደ፤ በዚያም በማጋጣነት ንብረቱን አባ
ከነ። [14]እርሱም ያለውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ፣
በዚያ አገር ሁሉ ጽኑ ራብ ሆነ፤ ይቸገርም
ጀመር። [15]ስለዚህ ከዚያ አገር ነዋሪዎች
አንዱን ተጠጋ፤ ሰውየውም ዐሣማ እንዲቀ
ልብለት ወደ ዕርሻው ላከው። [16]ዐሣማዎቹ
የሚመገቡትን ዐሠር እንኳ ለመብላት ይመኝ
ነበር፤ ነገር ግን ይህን እንኳ የሚሰጠው
ሰው አልነበረም።
[17]"ልብ በገዛ ጊዜ ግን እንዲህ አለ፤ 'ስንቱ
የአባቴ ሠራተኛ ምግብ ተርፎታል፤ እኔ
ግን እዚህ በራብ ልሞት ተቃርቤአለሁ!
[18]ተነሥቼ ወደ አባቴ ልሂድና፣ እንዲህ
ልበለው፤ "አባቴ ሆይ፤ በሰማይና በአንተ
ፊት በድያለሁ፤ [19]ከእንግዲህ ልጅህ ተብዬ
ልጠራ አይገባኝም፤ ከተቀጠሩት አገልጋዮ
ችህ እንደ አንዱ ቍጠረኝ።' [20]ስለዚህም
ተነሥቶ ወደ አባቱ ሄደ።
"ነገር ግን፣ እርሱ ገና ሩቅ ሳለ፣ አባተ
አይቶት ራራለት፤ ወደ እርሱም
እየሮጠ ሄዶ ዐቅፎ ሳመው።
[21]"ልጁም፣ 'አባቴ ሆይ፤ በሰማይና በአ
ንተ ፊት በድያለሁ፤ ከእንግዲህ ልጅህ
ተብዬ ልጠራ አይገባኝም' አለው።[ቀ]
[22]"አባቱ ግን አገልጋዮቹን እንዲህ አላ
ቸው፤ 'ፈጥናችሁ ከሁሉ ምርጥ የሆነውን
ልብስ አምጡና አልብሱት፤ ለጣቱ ቀለበት፣
ለእግሩም ጫማ አድርጉለት፤ [23]የሰባውንም
ፍሪዳ አምጡና ዕረዱ፤ እንብላ፤ እንደሰት፤
[24]ይህ ልጄ ሞቶ ነበር፤ አሁን ግን ሕያው
ሆኖአል፤ ጠፍቶም ነበር፤ ተገኝቶአል።"
ከዚያም ይደሰቱ ጀመር።
[25]"በዚህ ጊዜ ታላቁ ልጅ በዕርሻ ቦታ
ነበረ፤ ከዚያም ተመልሶ ወደ ቤት በተቃ
ረበ ጊዜ፣ የሙዚቃና የጭፈራ ድምፅ ሰማ፤
[26]እርሱም ከአገልጋዮቹ አንዱን ጠርቶ
ነገሩ ምን እንደ ሆነ ጠየቀው።
[27]አገልጋዩም፣ 'ወንድምህ
መጥቶአል፤ በሰ ላም በጤና ስለ መጣም
አባትህ የሰባውን ፍሪዳ ዐርዶለታል'
አለው።
[28]"ታላቅ ወንድሙም ተቈጣ፤ ወደ ቤትም
መግባት አልፈለገም፤ አባቱም ወደ ውጭ
ወጥቶ እንዲገባ ለመነው። [29]እርሱ ግን
መልሶ አባቱን እንዲህ አለው፤ 'እነሆ፤ ይህን
ያህል ዘመን እንደ ባሪያ አገልግዬሃለሁ፤
ከትእዛዝህም አንዱን እንኳ አላጓደልሁም፤
አንተ ግን ከባልንጀሮቼ ጋር እንድደሰት
አንዲት የፍየል ግልገል እንኳ አልሰጠኸ
ኝም፤ [30]ነገር ግን ይህ ልጅህ ንብረትህን
ከጋለሞቶች ጋር አውድሞ ሲመጣ፣ የሰባ
ውን ፍሪዳ አረድህለት።'
[31]"አባቱም እንዲህ አለው፤ 'ልጄ ሆይ፤
አንተ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር ነህ፤ የእኔ የሆነው
ሁሉ የአንተ ነው፤ [32]ይህ ወንድምህ ግን
ሞቶ ነበር፤ ሕያው ሆነ፤ ጠፍቶ ነበር ተገኘ፤

[ቀ]21 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *ከተቀጠሩት አገልጋዮችህ እንኳ እንደ አንዱ ቈጥረህ ተቀበለኝ* የሚል አላቸው

14፥35 ማቴ5፥13፤ ማቴ11፥15
15፥1 ሉቃ5፥29
15፥2 ማቴ9፥11
15፥3 ማቴ13፥3
15፥4 መዝ23፤ 119፥176፤ኤር31፥10፤ ሕዝ34፥11-16፤ ሉቃ5፥32፤19፥10
15፥6 ቍ9
15፥7 ቍ10
15፥9 ቍ6
15፥10 ቍ7
15፥11 ማቴ21፥28
15፥12 ቍ30፤ ዘዳ21፥17
15፥13 ቍ30፤ ሉቃ16፥1
15፥15 ዘሌ11፥7
15፥18 ዘሌ26፥40፤ ማቴ3፥2
15፥20 ዘፍ45፥14፡ 15፤46፥29፤ሐሥ 20፥37
15፥21 መዝ51፥4
15፥22 ዘፍ41፥42፤ ዘካ3፥4፤ራእ6፥11
15፥24 ቍ32፤ኤፌ 2፥1፡5፤5፥14፤ 1ጢ5፥6
15፥28 ዮና4፥1
15፥30 ቍ12፡13፤ ምሳ29፥3
15፥32 ቍ24፤ ሚል3፥17

ስለዚህ ደስ ሊለንና ፍሥሐ ልናደርግ ይገ
ባናል።” ’

## የብልኍ መጋቢ ምሳሌነት

**16** ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ
አለ፤ “አንድ ሀብታም ሰው አንድ
መጋቢ ነበረው፤ ይኸው መጋቢ የሀብታ
ሙን ሰው ንብረት እንደሚያባክን ለዚሁ
ሀብታም ሰው ወሬ ደረሰው። 2ስለዚህ
አስጠራውና፣ ‘ይህ የምሰማብህ ምንድን
ነው? ከእንግዲህ አንተ መጋቢ ልትሆነኝ
ስለማትችል፣ የምታስተዳድረውን ንብረት
መቈጣጠሪያ ሒሳብ አስረክበኝ’ አለው።
3“መጋቢውም በልቡ እንዲህ አለ፤ ‘ጌታዬ
ከመጋቢነት ሊሽረኝ ነው፤ ለማረስ ጕል
በት የለኝም፤ መለመን ደግሞ ዐፍራለሁ፤
ስለዚህ ምን ላድርግ? 4ከመጋቢነት የተሻ
ርሁ እንደ ሆነ ሰዎች በቤታቸው እንዲ
ቀበሉኝ የማደርገውን ዐውቃለሁ።’
5“ስለዚህ የጌታው ዕዳ ያለባቸውን ሰዎች
እያንዳንዳቸውን ጠራ፤ የመጀመሪያውንም
ሰው ‘የጌታዬ ዕዳ ምን ያህል አለብህ?’
አለው።
6“እርሱም፣ ‘አንድ መቶ ማድጋ[∩] ዘይት
አለብኝ’ አለ።
“መጋቢውም፣ ‘የውል ወረቀትህን እንካ፤
ቶሎ ተቀምጠህ “አምሳ ማድጋ” ብለህ ጻፍ’
አለው።
7“ከዚያም ሌላውን፣ ‘አንተስ ስንት አለ
ብህ?’ አለው።
“እርሱም፣ ‘አምሳ ዳውላ[†] ስንዴ’ አለው።
“መጋቢውም፣ ‘የብድር ደብዳቤህን
እንካ፤ “አርባ ዳውላ” ብለህ ጻፍ’ አለው።
8ጌታውም አጭበርባሪውን መጋቢ በብል
ኀነቱ አደነቀው፤ የዚህ ዓለም ልጆች ከመሰ
ሎቻቸው ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት
ከብር ሃን ልጆች ይልቅ ብልዖች
ናቸውና። 9ስለዚህ እላችኋለሁ፤ የዚህ ዓ
ለም ገንዘብ ባለቀ ጊዜ በዘላለም ቤት
ተቀባይነት እንዲኖራችሁ፣ በዚሁ ገንዘብ
ወዳጆችን ለራሳችሁ አፍሩበት።
10“በትንሽ ነገር ታማኝ የሆነ በትልቁም
ይታመናል፤ በትንሽ ነገር ያልታመነ በት
ልቁም አይታመንም። 11እንግዲህ፣ በዚህ
ዓለም ሀብት ካልታመናችሁ፣ እውነተኛ
ውንማ ሀብት ማን ዐደራ ብሎ ይሰጣች
ኋል? 12በሌላው ሰው ሀብት ካልታመና
ችሁ፣ የራሳችሁ የሆነውን ሀብት ማን ይሰ
ጣችኋል?
13“በአንድ ጊዜ ሁለት ጌቶችን ማገል
ገል የሚችል ማንም ባሪያ የለም፤ አን
ዱን ጠልቶ ሌላውን ይወዳል፤ ወይም አን
ዱን ይጠጋል፤ ሌላውን ይንቃል። የእግዚ
አብሔርም የገንዘብም ባሪያ መሆን አትች
ሉም።”
14ገንዘብ የሚወዱ ፈሪሳውያን ይህን
ሁሉ ሰምተው በኢየሱስ አፌዙበት። 15እር
ሱም እንዲህ አላቸው፤ “እናንተ በሰዎች
ፊት ራሳችሁን የምታጸድቁ ናችሁ፤ እግዚ
አብሔር ግን ልባችሁን ያውቃል፤ በሰዎች
ዘንድ የከበረ፣ በእግዚአብሔር ፊት የረከሰ
ነውና።
16“ሕግና ነቢያት እስከ ዮሐንስ ድረስ ሲነ
ገሩ ኖረዋል፤ ከዚያ በኋላ ግን የእግዚአብሔር
መንግሥት የምሥራች ተሰብኮአል፤ ሰውም
ሁሉ ወደዚያ ለመግባት ይሻማል። 17ነገር
ግን ከሕግ አንዲት ነጥብ ከምትወድቅ ሰማ
ይና ምድር ቢያልፍ ይቀላል።
18“ሚስቱን ፈቶ ሌላይቱን የሚያገባ
ሁሉ ያመነዝራል፤ ከባሏ የተፋታችውንም
ሴት የሚያገባ ያመነዝራል።”

## ሀብታሙ ሰውና አልዓዛር

19ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ “ሐም
ራዊና ቀጭን በፍታ የለበሰ፣ በየቀኑም
በተድላ ደስታ የሚኖር አንድ ሀብታም
ሰው ነበረ። 20በአንጻሩም፣ መላ ሰውነቱ
በቍስል የተወረረ አንድ አልዓዛር የሚባል
ድኻ በዚህ ሀብታም ሰው ደጃፍ ይተኛ
ነበር፤ 21ከሀብታሙ ሰው ማእድ የወደ
ቀውን ፍርፋሪ እንኳ ሊመገብ ይመኝ
ነበር፤ ውሾችም ሳይቀሩ መጥተው ቍስ
ሉን ይልሱ ነበር።
22“ይህም ድኻ ሞተ፤ መላእክትም ወደ
አብርሃም ዕቅፍ ወሰዱት። ሀብታሙም ሰው
ደግሞ ሞቶ ተቀበረ። 23በሲኦልም እየተ
ሠቃየ ሳለ ቀና ብሎ ከሩቅ አብርሃምን
አየ፤ አልዓዛርንም በዕቅፉ ይዞት አየ።
24እርሱም፣ ‘አብርሃም አባት ሆይ፤ ራራ
ልኝ፤ በዚህ ነበልባል እየተሠቃየሁ ስለ ሆነ፣
አልዓዛር የጣቱን ጫፍ ውሃ ነክሮ ምላሴን
እንዲያቀዘቅዝልኝ እባክህ ላክልኝ’ እያለ
ጮኸ።
25“አብርሃም ግን እንዲህ አለው፤ ‘ልጄ
ሆይ፤ አንተ በምድራዊ ሕይወትህ ዘመን
መልካም ነገሮችን እንደ ተቀበልህ፣ አልዓ
ዛርም ደግሞ ክፉ ነገሮችን እንደ ተቀበለ
አስታውስ፤ አሁን ግን እርሱ እዚህ ሲ
ጽናና፣ አንተ በሥቃይ ላይ ትገኛለህ።
26ከሁ
ሉም በላይ ከዚህ ወደ እናንተ ለማለፍ
የሚፈልጉ እንደማይችሉ፣ እዚያ ያሉትም

[∩]6 ምናልባት *3 ሺህ ሊትር* ይሆናል
[†]7 ምናልባት *35 ሺህ ሊትር* ይሆናል

16፥1 ሉቃ15፥30፡30
16፥8 መዝ17፥14፤ መዝ18፥26፤ ዮሐ12፥36፤ ኤፌ5፥8፤ 1ተሰ5፥5
16፥9 ቀኍ11፡13፤ ማቴ19፥21፤ ሉቃ12፥33
16፥10 ማቴ25፥21፡23፤ ሉቃ19፥17
16፥11 ቀኍ9፡13
16፥13 ቀኍ9፡11፤ማቴ6፥24
16፥14 ሉቃ23፥35፤1ጢሞ3፥3
16፥15 ሉቃ10፥29፤ራእ2፥23
16፥16 ማቴ4፥23፤ 5፥17፤11፥12፡13
16፥17 ማቴ5፥18
16፥18 ማቴ5፥31፡32፤19፥9፤ማር10፥11 ሮሜ7፥2፡3፤ 1ቆሮ 7፥10፡11
16፥19 ሕዝ16፥49
16፥20 ሐሥ3፥2
16፥21 ማቴ15፥27፤ ሉቃ15፥16
16፥24 ቀኍ30፤ ማቴ 5፥22፤ ሉቃ3፥8
16፥25 መዝ17፥14፤ሉቃ6፥21፡24፡25

ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ፣ በእኛና በእ
ናንተ መካከል ትልቅ ገደል ተደርጎአል።”
27“እርሱም እንዲህ አለ፤ ‘አባት ሆይ፤
እንግዲያውስ አልዓዛርን ወደ አባቴ ቤት
እንድትሰደው እለምንሃለሁ፤ 28አምስት ወን
ድሞች ስላሉኝ፣ እነርሱም ወደዚህ የሥ
ቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ያስጠንቅቃቸው።’
29“አብርሃም ግን፣ ‘ሙሴና ነቢያት አሏ
ቸው፤ እነርሱን ይስሙ’ አለው።
30“እርሱም፣ ‘አብርሃም አባት ሆይ፤
እን ደዚህ አይደለም፤ አንድ ሰው
ከሙታን ተነሥቶ ቢሄድላቸው ንስሓ
ይገባሉ’ አለ።
31አብርሃምም፣ ‘ሙሴንና ነቢያትን የ
ማይሰሙ ከሆነ፣ አንድ ሰው ከሙታን ቢነሣ
እንኳ አያ ምኑም’ አለው።

## ኀጢአት፣ እምነት፣ ኀላፊነት

17 ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እን
ዲህ አላቸው፤ “ሰዎችን የሚያሰ
ናክል መምጣቱ አይቀርም፤ ነገር ግን
ለመሰናከሉ መምጣት ምክንያት ለሚ
ሆን ለዚያ ሰው ወዮለት። 2ይህ ሰው ከእ
ነዚህ ከታናናሾች አንዱን ከሚያሰናክል፣
የወፍጮ ድንጋይ በዐንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር
ቢጣል ይሻለው ነበር። 3ስለዚህ ለራሳችሁ
ተጠንቀቁ።
“ወንድምህ ቢበድል ገሥጸው፤ ቢጸጸት
ይቅር በለው። 4በቀን ሰባት ጊዜ ቢበድል
ህና ሰባት ጊዜ፣ ‘ተጸጽቻለሁ’ እያለ ወደ
አንተ ቢመለስ ይቅር በለው።”
5ሐዋርያትም ጌታን፣ “እምነታችንን
ጨምርልን” አሉት።
6ጌታም፣ “የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል
እምነት ቢኖራችሁ፣ ይህን ሾላ፣ ‘ተነቅለህ
ባሕር ውስጥ ተተከል’ ብትሉት ይታዘዝላ
ችኋል” አላቸው።
7ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ “ከእና
ንተ መካከል አንድ ሰው ዐራሽ ወይም
በግ ጠባቂ የሆነ አገልጋይ ቢኖረው፣ ከዕ
ርሻ የተመለሰውን አገልጋዩን፣ ‘ቶሎ ወደ
ማእድ ቅረብ’ ይለዋልን? 8ከዚህ ይልቅ፣
‘እራቴን እንድበላ አዘጋጅልኝ፣ እኔ እስ
ክበላና እስክጠጣ ድረስ ታጥቀህ አገልግ
ለኝ፤ ከዚያ በኋላ አንተ ደግሞ ትበላለህ፤
ትጠጣለህ’ አይለውምን? 9እንግዲህ ይህ
ሰው፣ አገልጋዩ የታዘዘውን በመፈጸሙ
መልሶ ያመሰግነዋልን? 10ስለዚህ እናን
ተም የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ
ጊዜ፣ ‘ከቍጥር የማንገባ አገልጋዮች ነን፤
ልናደርገው የሚገባንን ተግባር ፈጽመናል
በሉ።”

16፥28 ሐሥ2፥40፤ 20፥23፤1ተሰ4፥6
16፥29 ሉቃ4፥17፤ 24፥27፥44 ዮሐ1፥45፤ 5፤45-47፤ ሐሥ15፥21
16፥30 ቀኍ24፤ ሉቃ3፥8
17፥1 ማቴ5፥29፤ ማቴ18፥7
17፥2 ማቴ5፥29፤ ማር10፥24፤ ሉቃ10፥21
17፥3 ማቴ18፥15፤ ኤፌ4፥32፤ ቈላ3፥13
17፥4 ማቴ18፥21፥22
17፥5 ማር6፥30፤ ሉቃ7፥13
17፥6 ማቴ13፥31፤ 17፥20፤21፥21፤ ማር9፥23፤ ሉቃ13፥19
17፥8 ሉቃ12፥37
17፥10 1ቆሮ9፥16
17፥11 ሉቃ9፥51፡52፤ ዮሐ4፥3፥4
17፥12 ዘሌ13፥45፡46፤ ማቴ8፥2
17፥13 ሉቃ5፥5
17፥14 ዘሌ14፥2፤ ማቴ8፥4
17፥15 ማቴ9፥8
17፥16 ማቴ10፥5
17፥19 ማቴ9፥22
17፥20 ማቴ3፥2
17፥21 ቀኍ23
17፥22 ማቴ8፥20፤ ሉቃ5፥35
17፥23 ማቴ24፥23፤ ሉቃ21፥8
17፥24 ማቴ24፥27
17፥25 ማቴ16፥21፤ ማር13፥30፤ ሉቃ 9፥22፤ 18፥32፤21፥32
17፥26 ዘፍ6፥5-8፤7፥6-24

## ከለምጽ የነጹ ዐሥር ሰዎች

11ከዚህም በኋላ ኢየሱስ ወደ ኢየሩ
ሳሌም ሲሄድ፣ በሰማርያና በገሊላ ድንበር
በኩል ዐለፈ፤ 12ወደ አንድ መንደር እንደ
ገባም ለምጽ[ቸ] የያዛቸው ዐሥር ሰዎች አገ
ኙት፤ እነርሱም በርቀት ቆመው፣ 13በታ
ላቅ ድምፅ፣ “ኢየሱስ፤ ጌታ ሆይ፤ ራራ
ልን!” አሉት።
14እርሱም ባያቸው ጊዜ፣ “ሂዱና ራሳች
ሁን ለካህናት አሳዩ” አላቸው። እነርሱም
ወደዚያው በመሄድ ላይ ሳሉ ነጹ።
15ከእነርሱም አንዱ መፈወሱን ባየ ጊዜ
በታላቅ ድምፅ እግዚአብሔርን እያከበረ ተመለሰ፤
16በኢየሱስም እግር ላይ በፊቱ ተደፍቶ አመ
ሰገነው፤ ይህም ሰው ሳምራዊ ነበረ።
17ኢየሱስም እንዲህ ሲል ጠየቀው፤ “የነ
ጹት ዐሥር ሰዎች አልነበሩምን? ታዲያ፣
ዘጠኙ የት ደረሱ? 18ከዚህ ከባዕድ ሰው
በስተቀር ተመልሰው እግዚአብሔርን የሚያ
መሰግኑ የሉም ማለት ነውን?”። 19ሰው
የውንም፣ “ተነሥተህ ሂድ፤ እምነትህ አድኖ
ሃል” አለው።

## የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣት

17፥26፡27 ተጓ ምብ – ማቴ 24፥37-39

20ፈሪሳውያን የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ
እንደምትመጣ ኢየሱስን በጠየቁት ጊዜ
እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ “የእግዚአብሔር
መን ግሥት በሚታዩ ምልክቶች
አትመጣም፤ 21ሰዎችም፣ ‘እዚህ ነው’ ወይም
‘እዚያ ነው’ ማለት አይችሉም፤ እነሆ፤ የእግዚ
አብሔር መን ግሥት በመካከላችሁ[ኀ] ናትና።”
22ለደቀ መዛሙርቱም እንዲህ አላቸው፤
“ከሰው ልጅ ቀኖች አንዱን ለማየት የም
ትመኙበት ጊዜ ይመጣል፤ ደግሞም አታ
ዩትም። 23ሰዎች፣ ‘እዚያ ነው’ ወይም ‘እዚ
ህ ነው’ ይሏችኋል፤ ተከትላችኋቸውም አትሂዱ፤
24ምክንያቱም መብረቅ በርቆ ሰማዩን
ከጻር እስከ ጻር እንደሚያበራ፣ የሰው
ልጅም በሚመጣበት ቀን ልክ እንደዚሁ
ይሆናል። 25ነገር ግን ይህ ከመሆኑ በፊት
የሰው ልጅ ብዙ መሠቃየትና በዚህም
ትውልድ መናቅ ይኖርበታል።
26“በኖኅ ዘመን እንደ ሆነው ሁሉ፣
በሰው ልጅ ዘመንም እንደዚሁ ይሆናል።
27ኖኅ ወደ መርከቡ እስከ ገባበት ቀን
ድረስ ሰዎች ይበሉና ይጠጡ፣ ያገቡና
ይጋቡ ነበር፤ የጥፋትም ውሃ መጥቶ
ሁሉንም አጠፋቸው።

[ቸ]12 የግሪኩ ቃል ከለምጽ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን የተለያዩ የቈዳ በሽታዎችን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ይውላል።
[ኀ]21 ወይም *በውስጣቸው*

[28]“በሎጥ ዘመንም እንዲሁ ነበር፤ ሰዎች
ይበሉና ይጠጡ፣ ይገዙና ይሸጡ፣ ተክል
ይተክሉና ቤት ይሠሩ ነበር፤ [29]ሎጥ ከሰዶም
በወጣበት ዕለት ግን እሳትና ዲን ከሰማይ
ዘንቦ በሙሉ አጠፋቸው።

[30]“የሰው ልጅ በሚገለጥበትም ቀን እን
ደዚሁ ይሆናል። [31]በዚያን ቀን በቤቱ ጣራ
ላይ ያለ ማንም ሰው በቤቱ ውስጥ ያለውን
ንብረት ለመውሰድ አይውረድ፤ እንዲሁም
በዕርሻ ቦታ ያለ ሰው ወደ ኋላው አይመ
ለስ። [32]የሎጥን ሚስት አስታውሱ። [33]ሕይ
ወቱን ለማሰንበት የሚፈልግ ሁሉ ያጣ
ታል፤ ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ ግን ያቈ
ያታል። [34]እላችኋለሁ፤ በዚያች ሌሊት
ሁለት ሰዎች በአንድ ዐልጋ ይተኛሉ፤
አንዱ ይወሰዳል፤ ሌላው ይቀራል። [35]ሁለት
ሴቶች አብረው ይፈጫሉ፤ አንዷ ትወሰ
ዳለች፤ ሌላዋ ትቀራለች። [36]ሁለት ሰዎች
በዕርሻ ቦታ አብረው ይሆናሉ፤ አንዱ
ይወሰዳል፤ ሌላው ይቀራል።”[ነ]

[37]እነርሱም መልሰው፣ “ጌታ ሆይ፤ የሚ
ወሰዱት ወዴት ነው?” አሉት።

እርሱም፣ “ጥንብ ባለበት አሞሮች
ይሰበሰባሉ” አላቸው።

## ተግታ የለመነችው መበለት ምሳሌነት

18 ደቀ መዛሙርቱ ሳይታክቱ ሁል
ጊዜ መጸለይ እንደሚገባቸው ለማ
ሳየት ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ነገራቸው፤
[2]እንዲህም አላቸው፤ “በአንዲት ከተማ
የሚኖር እግዚአብሔርን የማይፈራና ሰውን
የማያከብር አንድ ዳኛ ነበረ። [3]በዚያችው
ከተማ የምትኖር አንዲት መበለት ነበረች፤
እርሷ፣ ‘ከባላጋራዬ ጋር ስላለብኝ ጉዳይ
ፍረድልኝ’ እያለች ወደ እርሱ ትመላለስ
ነበር።

[4]“ዳኛውም ለተወሰነ ጊዜ አልተቀበላትም
ነበር፤ በኋላ ግን በልቡ እንዲህ አለ፤
‘ምንም እግዚአብሔርን ባልፈራ፣ ሰውንም
ባላከብር፣ [5]ይህች መበለት ስለምትጨቀ
ጭቀኝ እፈርድላታለሁ፤ አለበለዚያ ዘወ
ትር እየተመላለሰች ታሰለቸኛለች።’”

[6]ጌታም እንዲህ አለ፤ “ዐመፀኛው ዳኛ
ያለውን ስሙ። [7]እግዚአብሔርስ ቀንና ሌሊት
ወደ እርሱ ለሚጮኹ ምርጦቹ አይፈርድ
ላቸውምን? ከመጠን በላይስ ችላ ይላቸዋ
ልን? [8]እላችኋለሁ፤ ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል፤
ነገር ግን የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ
በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆንን? ”

## የፈሪሳዊውና የቀረጥ ሰብሳቢው ምሳሌነት

[9]ራሳቸውን እንደ ጻድቃን በመቍጠር
ለሚመኩና ሌሎቹን በንቀት ዐይን ለሚ
መለከቱ ሰዎች እንዲህ ሲል ይህን ምሳሌ
ነገራቸው፤ [10]“ሁለት ሰዎች ሊጸልዩ ወደ
ቤተ መቅደስ ወጡ፣ አንዱ ፈሪሳዊ፣ ሌላው
ቀረጥ ሰብሳቢ ነበሩ። [11]ፈሪሳዊውም ቆሞ
ስለ[ፕ] ራሱ እንዲህ ይጸልይ ነበር፤ “እግዚ
አብሔር ሆይ፤ እኔ እንደ ሌላው ሰው ሁሉ
ቀማኛ፣ ዐመፀኛ፣ አመንዝራ፣ ይልቁንም
እንደዚህ ቀረጥ ሰብሳቢ ባለመሆኔ አመ
ሰግንሃለሁ፤ [12]በሳምንት ሁለት ጊዜ እጾማ
ለሁ፤ ከማገኘውም ሁሉ ዐሥራት አወጣለሁ።”

[13]“ቀረጥ ሰብሳቢው ግን በርቀት ቆሞ፣
ወደ ሰማይ ቀና ብሎ ማየት እንኳ አልፈ
ለገም፤ ነገር ግን ደረቱን እየደቃ፣ ‘እግዚአ
ብሔር ሆይ፤ እኔን ኀጢአተኛውን ማረኝ’
ይል ነበር።

[14]“እላችኋለሁ፤ ከፈሪሳዊው ይልቅ ይኸ
ኛው በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ጻድቅ ተቈ
ጥሮ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ ራሱን ከፍ ከፍ
የሚያደርግ ሁሉ ዝቅ ይላልና፤ ራሱን ዝቅ
ዝቅ የሚያደርግ ግን ከፍ ይላል።”

## ኢየሱስ ከሕፃናት ጋር

18፥15-17 ተጓ ምብ – ማቴ 19፥13-15፤ ማር 10፥13-16

[15]ኢየሱስ እንዲዳስሳቸው ሰዎች ሕፃና
ትን ወደ እርሱ ያመጡ ነበር፤ ደቀ መዛ
ሙርቱም ይህን ባዩ ጊዜ ገሠጿቸው።
[16]ኢየሱስ ግን ሕፃናቱን ወደ ራሱ ጠርቶ
እንዲህ አለ፤ “ሕፃናት ወደ እኔ እንዲ
መጡ ፍቀዱላቸው፤ አትከልክሏቸው፤ የእ
ግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት
ናትና። [17]እውነት እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔ
ርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበል
ሁሉ ከቶ አይገባባትም።”

## ሀብታሙ የአይሁድ አለቃ

18፥18-30 ተጓ ምብ - ማቴ-19፥16-29፤ ማር 10፥17-30

[18]ከአይሁድ አለቆች አንዱ፣ “ቸር መም
ህር ሆይ፤ የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ
ምን ላድርግ?” ሲል ጠየቀው።

[19]ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤
“ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚ
አብሔር በቀር ቸር ማንም የለም፤
[20]‘አታመ ንዝር፣ አትግደል፣ አትስረቅ፣
በሐሰት አት መስክር፣ አባትህንና እናትህን
አክብር’ የሚለውን ትእዛዝ ታውቃለህ።”

[21]ሰውየውም፣ “እነዚህንማ ከልጅነቴ
ጀምሬ
ጠብቄአለሁ” አለው።

[22]ኢየሱስም ይህን በሰማ ጊዜ፣ “እንግዲ
ያውስ አንድ ነገር ይቀርሃል፤ ያለህን ሁሉ

[ነ]35 አንዳንድ ቅጆች ቍ 36 የላቸውም
[ፕ]11 ወይም ለራሱ

17፥28 ዘፍ19፥1-28
17፥30 ማቴ10፥23፤16፥27፤24፥3፡27፡37፡39፤25፥31፤1ቆሮ1፥7፤1ተሰ2፥19፤2ተሰ1፥7፤2፥8፤2ጴጥ3፥4፤ራእ1፥7
17፥31 ማቴ24፥ 17፡18
17፥32 ዘፍ19፥26
17፥33 ዮሐ12፥25
17፥35 ማቴ24፥41
17፥37 ማቴ24፥28
18፥1 ኢሳ40፥31፤ ሉቃ11፥5-8፤ ሐሥ1፥14፤ ሮሜ1፥10፤12፥12፤ኤፌ6፥18፤ቆላ4፥2፤1ተሰ5፥17
18፥3 ኢሳ1፥17
18፥5 ሉቃ11፥8
18፥6 ሉቃ7፥13
18፥7 ዘፀ22፥23፤ መዝ88፥1፤ ራእ6፥10
18፥8 ማቴ8፥20፤16፥27
18፥9 ኢሳ65፥5፤ ሉቃ16፥15
18፥10 ሐሥ3፥1
18፥11 ማቴ6፥5፤ ማር11፥25
18፥12 ኢሳ58፥3፤ ሚል3፥8፤ ማቴ9፥14፤ ሉቃ11፥42
18፥13 ኢሳ66፥2፤ ኤር31፥19፤ ሉቃ5፥32፤23፥48፤ 1ጢሞ 1፥15
18፥14 ማቴ23፥12
18፥17 ማቴ11፥25፤ 18፥3
18፥18 ሉቃ10፥25
18፥20 ዘፀ20፥12-16፤ ዘዳ5፥16-20፤ ሮሜ13፥9
18፥22 ማቴ19፥26፤ሐሥ2፥45
18፥24 ምሳ11፥28

ሽጠህ ለድኾች ስጥ፤ በሰማይ መዝገብ
ይኖርሃል፤ ከዚያም መጥተህ ተከተለኝ”
አለው።
23ሰውየው ግን ይህን ሲሰማ፣ ብዙ
ሀብት ስለ ነበረው በጣም ዐዘነ። 24ኢየ
ሱስም ሰውየውን ተመልክቶ እንዲህ አለ፤
“ብዙ ሀብት ላላቸው ወደ እግዚአብሔር
መንግሥት መግባት እንዴት ጭንቅ
ነው? 25ሀብታም ወደ እግዚአብሔር
መንግሥት ከሚገባ ይልቅ ግመል
በመርፌ ቀዳዳ ቢሾ ልክ ይቀላል።”
26ይህን የሰሙ ሰዎችም፣ “ታዲያ፣ ማን
ሊድን ይችላል? ” አሉ።
27ኢየሱስም፣ “በሰው ዘንድ የማይቻል
በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል” አለ።
28ጴጥሮስም፣ “እነሆ፤ እኛ ያለንን ሁሉ
ትተን ተከትለንሃል” አለው።
29ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “እውነት
እላችኋለሁ፤ ለእግዚአብሔር መንግሥት
ብሎ ቤቱን ወይም ሚስቱን ወይም
ወንድሞቹን ወይም ወላጆቹን ወይም
ልጆቹን የተወ፣ 30በዚህ ዘመን ብዙ ዕ
ጥፍ፣ በሚመጣውም ዘመን የዘላለምን ሕ
ይወት የማይቀበል ማንም የለም።”

## ኢየሱስ ስለ ሞቱ ዳግመኛ ተናገረ

18፥31-33 ተጓ ምብ – ማቴ 20፥17-19፤ ማር 10፥32-34

31ኢየሱስም ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛ
ሙርት ለብቻ ወስዶ እንዲህ አላቸው፤
“እንግዲህ ወደ ኢየሩሳሌም ልንወጣ ነው፤
ነቢያት ስለ ሰው ልጅ የጻፉትም ሁሉ
ይፈጸማል። 32ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡ
ታል፤ እነርሱም ያፌዙበታል፤ ያንገላቱ
ታል፤ ይተፉበታል፤ ይገርፉታል፤ ከዚያም
ይገድሉታል። 33እርሱም በሦስተኛው ቀን
ከሙታን ይነሣል።”
34ደቀ መዛሙርቱ ግን ከዚህ ሁሉ የተ
ረዱት አንድም ነገር አልነበረም፤ አባባ
ሉም ተሰውሮባቸው ነበር፤ ስለ ምን እንደ
ተናገረም አላወቁም።

## የዐይነ ስውሩ መፈወስ

18፥35-43 ተጓ ምብ – ማቴ 20፥29-34፤ ማር 10፥46-52

35ኢየሱስ ወደ ኢያሪኮ በቀረበ ጊዜ፣
አንድ ዐይነ ስውር መንገድ ዳር ተቀምጦ
ይለምን ነበር። 36ዐይነ ስውሩም ሕዝቡ በዚያ
ሲያልፍ ሰምቶ ስለ ሁኔታው ጠየቃቸው።
37እነርሱም፣ “የናዝሬቱ ኢየሱስ በዚህ እያ
ለፈ ነው” ብለው ነገሩት።
38እርሱም፣ “የዳዊት ልጅ፣ ኢየሱስ
ሆይ፤ ማረኝ!” እያለ ጮኸ።
39ከፊት የሚሄዱ ሰዎችም ዝም እንዲል
ገሥጹት፤ እርሱ ግን፣ “የዳዊት ልጅ ሆይ፤
ማረኝ!” እያለ አብዝቶ ጮኸ።
40ኢየሱስም ቆም ብሎ ሰውየውን ወደ
እርሱ እንዲያመጡት አዘዘ፤ ወደ እር
ሱም በቀረበ ጊዜ፣ 41“ምን እንዳደርግልህ
ትፈልጋለህ? ” ብሎ ጠየቀው።
ዐይነ ስውሩም፣ “ጌታ ሆይ፤ ማየት እፈልጋ
ለሁ” አለው።
42ኢየሱስም፣ “እይ፤ እምነትህ አድኖሃል”
አለው። 43ሰውየውም ወዲያውኑ ማየት
ቻለ፤ እግዚአብሔርንም እያከበረ ኢየሱስን
ተከተለው። ሕዝቡም ሁሉ ይህን ሲያዩ
እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

## ቀረጥ ሰብሳቢው ዘኬዎስ

19 ኢየሱስ ወደ ኢያሪኮ ገብቶ በዚያ
አልፎ ይሄድ ነበር። 2ስሙ ዘኬ
ዎስ የተባለ አንድ ሰው በዚያ ነበረ፤ ዋና
ቀረጥ ሰብሳቢና ሀብታም ነበረ። 3እርሱም
ኢየሱስ የተባለው የትኛው እንደ ሆነ ሊያይ
ይፈልግ ነበር፤ ቁመቱ አጭር ነበረና ከሕ
ዝቡ ብዛት የተነሣ ሊያየው አልቻለም።
4ኢየሱስ በዚያ መንገድ ያልፍ ስለ ነበ
ርም፣ ወደ ፊት ሮጦ አንድ ሾላ ዛፍ ላይ
ወጣ።
5ኢየሱስም እዚያ ቦታ ሲደርስ፣ ቀና
ብሎ፣ “ዘኬዎስ ሆይ፤ ዛሬ አንተ ቤት
መዋል ይገባኛልና ፈጥነህ ውረድ” አለው።
6እርሱም ፈጥኖ ወርዶ በደስታ ተቀበለው።
7በዚያ የነበሩ ሰዎችም ይህንን አይተው፣
“ከኀጢአተኛ ቤት ገብቶ ሊስተናገድ ነው።”
በማለት ሁሉም ማጕረምረም ጀመሩ።
8ዘኬዎስ ግን ቆመና ጌታን፣ “ጌታ
ሆይ፤ እነሆ ካለኝ ሀብት ሁሉ ግማሹን
ለድኾች እሰጣለሁ፤ ማንንም በሐሰት ቀምቼ
ከሆነ፣ አራት ዕጥፍ አድርጌ እመልሳለሁ”
አለው።
9ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ “ይህ ሰው
ደግሞ የአብርሃም ልጅ ስለ ሆነ፣ ዛሬ
መዳን ወደዚህ ቤት መጥቶአል፤
10ምክንያቱም የሰው ልጅ የመጣው የጠ
ፋውን ሊፈልግና ሊያድን ነው።”

## የዐሥሩ ምናን ምሳሌ

19፥12-27 ማመ – ማቴ 25፥14-30

11ሕዝቡ ይህን እየሰሙ ሳሉ፣ በምሳሌ
መናገሩን ቀጠለ፤ ምክንያቱም ወደ ኢየሩ
ሳሌም በመቃረቡና ሰዎቹም የእግዚአብሔር
መንግሥት የሚገለጥ ስለ መሰላቸው ነው።
12ስለዚህም እንዲህ አለ፤ “አንድ መስፍን
የንጉሥነትን ማዕረግ ተቀብሎ ለመመለስ
ወደ ሩቅ አገር ሄደ። 13ከአገልጋዮቹም
መካከል ዐሥሩን ጠርቶ ዐሥር ምናን ሰጣ

18፥27 ማቴ19፥26
18፥28 ማቴ4፥19
18፥30 ማቴ12፥32፤ 25፥46
18፥31 መዝ22፤ ኢሳ 53፤ ማቴ8፥20፤ ሉቃ9፥51
18፥32 ማቴ16፥21፤ ሉቃ23፥1፤ሐሥ2፥23
18፥33 ማቴ16፥21
18፥34 ማር9፥32
18፥35 ሉቃ19፥1
18፥37 ሉቃ19፥4
18፥38 ቁ39፤ ማቴ9፥27፤17፥15፤ ሉቃ18፥13
18፥39 ቁ38
18፥42 ማቴ9፥22
18፥43 ማቴ9፥8፤ ሉቃ13፥17
19፥1 ሉቃ18፥35
19፥4 1ነገ10፥27፤ 1ዜና27፥28፤ ኢሳ 9፥10፤ሉቃ18፥37
19፥7 ማቴ9፥11
19፥8 ዘፀ22፥1፤ ዘሌ 6፥4፡5፤ ዘኍ5፥7፤ 2ሳሙ12፥6፤ ሕዝ 33፥14፡15፤ ሉቃ3፥12፡13
19፥9 ሉቃ3፥8
19፥10 ሕዝ34፥12፡16፤ዮሐ3፥17
19፥11 ማቴ3፥2፤ ሉቃ17፥20፤ ሐሥ1፥6
19፥13 ማር13፥34
19፥17 ምሳ27፥

ቸውና “ተመልሼ እስክመጣ ድረስ በዚህ
ገንዘብ ነግዱበት” አላቸው።
14“የአገሩ ሰዎች ግን ስለ ጠሉት፣ ‘ይህ
ሰው በላያችን እንዲነግሥ አንፈልግም’
ብለው ከኋላው መልእክተኞችን ላኩበት።
15“ይሁን እንጂ ይህ መስፍን ንጉሥ
ሆኖ ወደ አገሩ ተመለሰ፤ እነዚያ አገልጋ
ዮቹም እርሱ በሰጣቸው ገንዘብ ነግደው
ምን ያህል እንዳተረፉ ለማወቅ አስጠራቸው።
16“የመጀመሪያው አገልጋይ ቀርቦ፣ ‘ጌታ
ሆይ፤ የሰጠኸኝ ምናን ዐሥር ምናን ትርፍ
አስገኝቶአል’ አለው።
17“ጌታውም፣ ‘አንተ ታማኝ አገልጋይ፣
መልካም አድርገሃል፤ በትንሽ ነገር ታማኝ
ሆነህ ስለ ተገኘህ፣ በዐሥር ከተሞች ላይ
ሥልጣን ተሰጥቶሃል’ አለው።
18“ሁለተኛውም ቀርቦ፣ ‘ጌታ ሆይ፤ የሰ
ጠኸኝ ምናን አምስት ምናን ትርፍ አስገ
ኝቶአል’ አለው።
19“ጌታውም፣ ‘አንተ ደግሞ በአምስት
ከተሞች ላይ ሥልጣን ተሰጥቶሃል’ አለው።
20“ሌላውም አገልጋይ ቀርቦ እንዲህ
አለው፤ ‘ጌታ ሆይ፤ በጨርቅ ጠቅልዬ ያቈ
የሁት ምናንህ ይኸው፤ 21አንተ ያላስቀመ
ጥኸውን የምትወስድ፣ ያልዘራኸውን የም
ታጭድ ጨካኝ ሰው ስለ ሆንህ ፈራሁህ።’
22“ጌታውም እንዲህ አለው፤ ‘አንተ
ክፉ አገልጋይ! በራስህ ቃል እፈርድብሃ
ለሁ፤ ያላስቀመጥሁትን የምወስድ፣ ያልዘ
ራሁትን የማጭድ፣ ጨካኝ ሰው መሆኔን
ካወቅህ፣ 23መጥቼ ገንዘቤን ከነትርፉ እን
ድወስድ፣ ለምን ለሚሠሩበት ሰዎች አል
ሰጠህም?’
24“ጌታውም እዚያ የቆሙትን፣ ‘ምናኑን
ውሰዱበትና ዐሥር ምናን ላለው ስጡት’
አላቸው።
25“እነርሱም፣ ‘ጌታ ሆይ፤ እርሱ እኮ
ዐሥር ምናን አለው’ አሉት።
26“እርሱም እንዲህ አለ፤ ‘እላችኋለሁፍ
ላለው ሁሉ ይጨመርለታል፤ የሌለው ግን
ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል። 27ነገር
ግን እኔ በላያቸው እንዳልነግሥ የፈለጉ
ትን እነዚያን ጠላቶቼን ወደዚህ አምጡና
በፊቴ ዕረዷቸው።’ ”

## ኢየሱስ በታላቅ ክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ

19፥29-38 ተጓ ምብ – ማቴ 21፥1-9፤ ማር 11፥1-10
19፥35-38 ተጓ ምብ – ዮሐ 12፥12-15

28ኢየሱስ ይህን ከተናገረ በኋላ፣ ወደ
ኢየሩሳሌም ሊወጣ ቀድሞአቸው ይሄድ

18፤ ሉቃ6፥10
19፥21 ማቴ25፥24
19፥22 2ሳሙ1፥16፤ኢዮ15፥6፤ማቴ25፥26
19፥26 ማቴ25፥29
19፥28 ማር10፥32፤ሉቃ9፥51
19፥29 ማቴ21፥1፤21፥17
19፥32 ሉቃ22፥13
19፥36 2ነገ9፥13
19፥37 ማቴ21፥1
19፥38 መዝ118፥26፤ ሉቃ2፥14፤13፥35
19፥39 ማቴ 21፥15፥16
19፥40 ዕንባ2፥11
19፥41 ኢሳ22፥4፤ሉቃ13፥34፡35
19፥43 ኢሳ29፥3፤ኤር6፥6፤ ሕዝ 4፥2፤26፥8፤ ሉቃ21፥20
19፥44 መዝ137፥9፤ ሉቃ21፥6፤1ጴጥ2፥12
19፥46 ኢሳ56፥7፤

ነበር። 29ደብረ ዘይት በተባለው ተራራ
ወደሚገኙት፣ ወደ ቤተ ፋጌና ወደ ቢታ
ንያ ከተሞች በቀረበ ጊዜ፣ ከደቀ መዛ
ሙርቱ ሁለቱን እንዲህ ሲል ላካቸው፤
30“በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ፤
ወደዚያም ስትገቡ ማንም ገና ያለተቀ
መጠበት ውርንጫ ታስሮ ታገኛላችሁ፤
ፈትታችሁ ወደዚህ አምጡት። 31ማንም፣
‘ለምን ትፈቱታላችሁ?’ ብሎ ቢጠይቃ
ችሁ፣ ‘ለጌታ ያስፈልገዋል’ በሉት።”
32የተላኩትም ሄደው ልክ እንደ ነገራ
ቸው ሆኖ አገኙት። 33ባለቤቶቹም ውርን
ጫውን ሲፈቱ አይተው፣ “ውርንጫውን
ለምን ትፈታላችሁ?” አሏቸው።
34እነርሱም፣ “ለጌታ ያስፈልገዋል” አሉ።
35ከዚያም ውርንጫውን ወደ ኢየሱስ
አመጡት፤ ልብሳቸውንም በላዩ ጣል አድ
ርገው ኢየሱስን በውርንጫው ላይ አስቀ
መጡት። 36ሰዎችም እርሱ በሚሄድበት
መንገድ ላይ ልብሳቸውን ያነጥፉ ነበር።
37በደብረ ዘይት ተራራ ቍልቍል ወደ
ሚወስደው መንገድ በተቃረቡ ጊዜ፣ ቍጥ
ራቸው እጅግ ብዙ የሆነ ደቀ መዛሙ
ርት ስላዩት ታምራት ሁሉ ደስ እያላ
ቸው ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ እንዲህ
እያሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ጀመር፤

38“በጌታ ስም የሚመጣው ንጉሥ
የተባረከ ነው!”

“በሰማይ ሰላም፣ በአርያምም ክብር ይሁን!”

39በሕዝቡ መካከል የነበሩ አንዳንድ ፈሪ
ሳውያንም ኢየሱስን፣ “መምህር ሆይ፤ ደቀ
መዛሙርትህን ገሥጻቸው እንጂ” አሉት።
40እርሱም፣ እላችኋለሁ፤ “እነርሱ ዝም
ቢሉ፣ ድንጋዮች ይጮኻሉ” አላቸው።
41ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ሲቃረብ
ከተማዋን አይቶ አለቀሰላት፤ 42እንዲህም
አለ፤ “ሰላምሽ የሚሆነውን ምነው አንቺ
ዛሬ በተረዳሽ ኖሮ! አሁን ግን ከዐይንሽ
ተሰውሮአል፤ 43ጠላቶችሽ ዙሪያሽን ቅጥር
ሠርተው፣ ከየአቅጣጫውም ከበው አንቺን
የሚያስጨንቁበት ጊዜ ይመጣልና፤ 44አን
ቺንና በቅጥርሽ ውስጥ የሚኖሩትንም ልጆ
ችሽን ከዐፈር ይደባልቃሉ፤ ድንጋይም በድ
ንጋይ ላይ አይተዉም፤ የመጐብኛሽን ጊዜ
አላወቅሽምና።”

## ኢየሱስ በቤተ መቅደስ

19፥45፡46 ተጓ ምብ – ማቴ 21፥12-16፤ ማር 11፥15-18፤ ዮሐ 2፥13-16

45ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅ
ደስ ገብቶ፣ ሻጮችን ከዚያ አስወጣ፤

46ደግሞም “‘ቤቴ የጸሎት ቤት ይሆናል’
ተብሎ ተጽፎአል፤ እናንተ ግን ‘የወን
በዴዎች ዋሻ’ አደረጋችሁት” አላቸው።
47በየቀኑም በቤተ መቅደስ ያስተምር
ነበር፤ የካህናት አለቆች፣ ጸሐፍትና የሕ
ዝብ መሪዎችም ሊገድሉት ይፈልጉ ነበር፤
48ነገር ግን ሕዝቡ ሁሉ ከእርሱ ጋር ተቈ
ራኝተው ትምህርቱን ይከታተሉ ስለ
ነበር፣ የሚያደርጉት ግራ ገባቸው።

## የኢየሱስ ሥልጣን ለአይሁድ አጠያያቂ ሆነባቸው

20፥1-8 ተጓ ምብ-ማቴ 21፥23-27፤ማር 11፥27-33

20 አንድ ቀን ኢየሱስ ሕዝቡን በቤተ
መቅደስ ሲያስተምርና ወንጌልን
ሲሰብክ የካህናት አለቆች፣ ጸሐፍትና ሽማ
ግሌዎች ተሰብስበው ወደ እርሱ መጡ፤
2እነርሱም፣ “እነዚህን ነገሮች የምታደርገው
በምን ሥልጣን እንደ ሆነ ንገረን፤ ሥልጣንስ
የሰጠህ ለመሆኑ እርሱ ማን ነው?” ብለው
ጠየቁት።
3እርሱም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
“እኔም አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ፤ እስቲ
መልሱልኝ፤ 4የዮሐንስ ጥምቀት ከሰማይ
ነበር ወይስ ከሰው?”
5እነርሱም እንዲህ ብለው እርስ በርስ ተመ
ካከሩ፤ “ ‘ከሰማይ’ ብንል፣ ‘ታዲያ፣ ለምን አላ
መናችሁበትም?’ ይለናል፤ 6‘ከሰው’ ብንል
ሕዝቡ ሁሉ ዮሐንስ ነቢይ መሆኑን ስለ
ሚያምኑ በድንጋይ ይወግሩናል።”
7ስለዚህ፣ “ከየት እንደ ሆነ አናውቅም”
ብለው መለሱለት።
8ኢየሱስም፣ “እንግዲያውስ እኔም እነዚ
ህን ነገሮች በምን ሥልጣን እንደማደርግ
አልነግራችሁም” አላቸው።

## የጭሰኞቹ ምሳሌ

20፥9-19 ተጓ ምብ –ማቴ 21፥33-46፤ ማር 12፥1-12

9ከዚህ በኋላ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ይህን
ምሳሌ ለሕዝቡ ይነግራቸው ጀመር፤ “አንድ
ሰው የወይን ተክል ተከለ፤ ለገበሬዎችም
አከራየና ወደ ሌላ አገር ሄዶ ብዙ ጊዜ
ቈየ። 10በመከርም ወራት፣ ከወይኑ ፍሬ
እንዲልኩለት አገልጋዩን ወደ እነዚህ ገበሬዎች
ላከ፤ ገበሬዎቹ ግን አገልጋዩን ደብድበው
ባዶ እጁን ሰደዱት። 11ቀጥሎም ሌላ አገ
ልጋዩን ላከ፤ ገበሬዎቹም እርሱንም ደግሞ
ደበደቡት፤ አዋርደውም ባዶ እጁን ሰደ
ዱት። 12አሁንም ቀጥሎ ሦስተኛ አገል
ጋዩን ላከ፤ ገበሬዎቹም እርሱንም ደግሞ
አቍስለው ወደ ውጭ ጣሉት።
13“የወይኑ ተክል ባለቤትም፣ ‘እንግዲህ
ምን ላድርግ? እስቲ ደግሞ የምወደውን
ልጄን እልካለሁ፤ ምናልባት እርሱን ያከ
ብሩት ይሆናል’ አለ።
14“ገበሬዎቹ ግን ልጁን ባዩት ጊዜ፣
ይህ እኮ ወራሹ ነው፣ ኑና እንግደለው፤
በዚህም ርስቱ የእኛ ይሆናል” እየተባባሉ
ተመካከሩ፤ 15ከወይኑም ተክል ቦታ ወደ
ውጭ አውጥተው ገደሉት።
“እንግዲህ የወይኑ ተክል ባለቤት ምን
ያደርጋቸዋል? 16መጥቶ እነዚያን ገበሬ
ዎች ያጠፋቸዋል፤ የወይኑንም ተክል ቦታ
ለሌሎች ይሰጣል።”
ሕዝቡም ይህን በሰሙ ጊዜ፣ ‘እንዲህ
ያለውንስ አያምጣው’ አሉ።
17ኢየሱስም ወደ እነርሱ ተመልክቶ
እንዲህ አላቸው፤
“ ‘ታዲያ ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣
እርሱ የማእዘን ራስ[a] ሆነ’ ተብሎ
የተጻፈው ትርጕሙ ምንድን ነው?
18በዚህ ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ሁሉ
ይቀጠቀጣል፤ ድንጋዩም በላዩ የሚወድቅ
በት ሁሉ ይደቃል።”
19ጸሐፍትና የካህናት አለቆችም ይህንን
ምሳሌ የተናገረው በእነርሱ ላይ መሆኑን
ስላወቁ፣ በዚያኑ ሰዓት ሊይዙት ፈልገው
ነበር፤ ነገር ግን ሕዝቡን ፈሩ።

## ለቄሣር ግብር መክፈል

20፥20-26 ተጓ ምብ –ማቴ 22፥15-22፤ ማር 12፥13-17

20ኢየሱስን አሳልፈው ለገዥው ኀይልና
ሥልጣን ለመስጠት፣ ከአፉ በሚወጣ
ቃል ለማጥመድ ይከታተሉት ነበር፤ ስለዚ
ህም ጻድቃን መስለው የሚቀርቡ ሰላዮ
ችን ላኩበት። 21ሰላዮቹም እንዲህ ሲሉ
ጠየቁት፤ “መምህር ሆይ፤ አንተ ትክክ
ለኛውን ነገር እንደምትናገርና እንደምታ
ስተምር እንዲሁም የእግዚአብሔርን መን
ገድ በእውነት እንደምታስተምርና ለማንም
እንደማታደላ እናውቃለን። 22ለመሆኑ ለቄሳር
ግብር መክፈል ይገባል ወይስ አይገባም?”
23እርሱ ግን ተንኰላቸውን ዐውቆ እንዲህ
አላቸው፤ 24“እስቲ አንድ ዲናር አሳዩኝ፤
በላዩ ያለው የማን መልክና ጽሕፈት ነው?”
25እነርሱም፣ “የቄሳር ነው” ብለው
መለሱለት።
እርሱም፣ “እንግዲያውስ የቄሳርን ለቄ
ሳር፣ የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር ስጡ”
አላቸው።
26ስለዚህ በተናገረው ቃል በሕዝቡ ፊት
ሊያጠምዱት አልቻሉም፤ በመልሱም ተገር
መው ዝም አሉ።

[a]17 ወይም የማእዘን ድንጋይ

ኤር7፥11
19፥47 ማቴ12፥14፤ 26፥55፤ ማር11፥18
20፥1 ማቴ26፥55፤ ሉቃ8፥1
20፥2 ዮሐ2፥18፤ ሐሥ4፥7፤ 7፥27
20፥4 ማር1፥4
20፥6 ማቴ11፥9፤ ሉቃ7፥29
20፥9 ኢሳ5፥1-7፤ ማቴ25፥14
20፥13 ማቴ3፥17
20፥16 ሉቃ19፥27
20፥17 መዝ118፥22፤ሐሥ 4፥11
20፥18 ኢሳ8፥14፡15
20፥19 ማር11፥18፤ ሉቃ19፥47
20፥20 ማቴ12፥10፤27፥2
20፥21 ዮሐ3፥2
20፥25 ሉቃ23፥2፤ ሮሜ13፥7
20፥27 ሐሥ 4፥1፤

### ትንሣኤ ሙታንና ጋብቻ

20፥27-40 ተጓ ምብ – ማቴ 22፥23-33፤ ማር 12፥18-27

27ትንሣኤ ሙታን የለም ከሚሉት ሰዱ
ቃውያን አንዳንዶቹ ወደ ኢየሱስ መጥ
ተው ጥያቄ አቀረቡለት፤ 28እንዲህም አሉት፤
“መምህር ሆይ፤ አንድ ሰው ሚስት አግብቶ
ልጅ ሳይወልድ ቢሞት፣ ወንድሙ መበለቲቱን
አግብቶ ልጆች በመውለድ ለወንድሙ ዘር
እንዲተካ ሙሴ ጽፎልናል። 29ታዲያ፣ ሰባት
ወንድማማቾች ነበሩ፤ የመጀመሪያው ሚስት
አግብቶ ልጅ ሳይወልድ ሞተ፤ 30ሁለተኛ
ውም እንደዚሁ፤ 31ሦስተኛው ደግሞ አገባት፤
ሰባቱም እንዲሁ እያሉ አግብተዋት ልጆች
ሳይወልዱ ሞቱ። 32በመጨረሻም ሴትዮዋ
ሞተች። 33እንግዲህ ሰባቱም ስላገቧት፣
በትንሣኤ ጊዜ የማን ሚስት ትሆናለች?”

34ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
“የዚህ ዓለም ልጆች ያገባሉ፤ ይጋባሉም፤
35የሚመጣውን ዓለምና የሙታንን ትን
ሣኤ ማግኘት የሚገባቸው ግን አያገ
ቡም፤ አይጋቡም፤ 36እንደ መላእክትም
ስለሆኑ ከዚያ በኋላ አይሞቱም፤ የትን
ሣኤ ልጆች ስለ ሆኑም የእግዚአብሔር
ልጆች ናቸው። 37ሙሴ ስለ ቊጥቋጦ
በተጻፈው ታሪክ ውስጥ ጌታን፣ ‘የአብር
ሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብ
አምላክ’ በማለቱ ሙታን እንደሚነሡ ያሳያል፤
38ሁሉም ለእርሱ ሕያዋን ስለ ሆኑ፣ እርሱ
የሕያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አይደ
ለም።”

39አንዳንድ ጸሐፍትም፣ “መምህር ሆይ፤
መልካም ተናገርህ” አሉት። 40ከዚህ በኋላ
አንድ ሰው እንኳ ሊጠይቀው አልደፈረም።

### ክርስቶስ የማን ልጅ ነው?

20፥41-47 ተጓ ምብ – ማቴ 22፥41-23፥7፤ ማር 12፥35-40

41ከዚህ በኋላ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤
“ሰዎች ክርስቶስን[ክ] እንዴት የዳዊት ልጅ
ነው ይሉታል? 42ምክንያቱም ራሱ ዳዊት
በመዝሙራት መጽሐፉ እንዲህ ብሏል፤

“ ‘ጌታ ጌታዬን፣
“በቀኜ ተቀመጥ፤
43እኔ ጠላቶችህን፣
ለእግርህ መርገጫ እስከማደርግልህ ድረስ።’ ”

44እንግዲህ ዳዊት እርሱን፣ ‘ጌታ’
ብሎ ሲጠራው እንዴት ልጁ ይሆናል?”

45ሕዝቡ ሁሉ እየሰሙትም ለደቀ መዛ
ሙርቱ እንዲህ አላቸው፤ 46“ዘርፋፋ ቀሚስ
ለብሰው መዞር ከሚወዱ፣ በገበያ ቦታ ሰላ
ምታ ከሚሹና በምኩራብ የከበሬታ መቀ
መጫ፣ በግብዣ ቦታም የክብር ስፍራ
ከሚፈልጉ፣ ከጸሐፍት ተጠንቀቁ፤ 47እነር
ሱም የመበለቶችን ቤት የሚያራቊቱ ናቸው፤
ለታይታ ብለውም ጸሎታቸውን ያስረዝማሉ፤
እነዚህ የከፋ ፍርድ ይጠብቃቸዋል።”

### መበለቷ የሰጠችው መባ

21፥1-4 ተጓ ምብ-ማር 12፥41-44

21 ኢየሱስ ቀና ብሎ ሲመለከት ሀብታ
ሞች በቤተ መቅደሱ መባ መሰ
ብሰቢያ ውስጥ መባቸውን ሲጨምሩ አየ።
2ደግሞም አንዲት ድኻ መበለት ሁለት
ትናንሽ የናስ ሳንቲሞች በዚያ ስትጨምር
ተመለከተ፤ 3እንዲህም አለ፤ “እውነት እላ
ችኋለሁ፤ ከሁሉም ይልቅ ይህች ድኻ መበለት
የበለጠ ሰጥታለች፤ 4እነዚህ ሰዎች የሰጡት
ከትርፋቸው ላይ ሲሆን፣ እርሷ ግን የሰጠችው
በድኻ ዐቅሟ ያላትን መተዳደሪያ በሙሉ
ነው።”

### የዘመኑ መጨረሻ ምልክቶች

21፥5-36 ተጓ ምብ – ማቴ 24፤ማር13
21፥12-17 ተጓ ምብ – ማቴ 10፥17-22

5ከደቀ መዛሙርት አንዳንዶች ቤተ
መቅደሱ በውብ ድንጋዮችና በስእለት ስጦ
ታዎች እንዳማረ ሲነጋገሩ፣ ኢየሱስ እንዲህ
አለ፤ 6“ይህ የምታዩት ሁሉ ሳይፈርስ
ድንጋይ በድንጋይ ላይ እንደ ተካበ የማይ
ቀርበት ጊዜ ይመጣል።”

7እነርሱም፣ “መምህር ሆይ፤ እንግዲህ
ይህ ሁሉ የሚሆነው መቼ ነው? ደግሞም
ይህ እንደሚሆን ምልክቱ ምንድን ነው?”
ብለው ጠየቁት።

8እርሱም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ “እን
ዳትስቱ ተጠንቀቁ፤ ብዙዎች፣ ‘እኔ እርሱ
ነኝ’ በማለት፣ ደግሞም፣ ‘ጊዜው ቀርቦ
አል’ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ እናንተ ግን
እነርሱን አትከተሏቸው። 9ስለ ጦርነትና
ስለ ሕዝብ ዐመፅ ስትሰሙ አትደንግጡ፤
ይህ አስቀድሞ መሆን የሚገባው ነውና፤
መጨረሻው ግን ወዲያውኑ አይሆንም።”

10ቀጥሎም እንዲህ አላቸው፤ “ሕዝብ
በሕዝብ ላይ፣ መንግሥትም በመንግሥት
ላይ ይነሣል፤ 11ታላቅ የመሬት መናወጥ
ይሆናል፤ ራብና ቸነፈር በተለያየ ስፍራ
ይከሠታል፤ አስፈሪ ነገር እንዲሁም ከሰ
ማይ ታላቅ ምልክት ይሆናል።

12“ይህ ሁሉ ከመሆኑ በፊት ግን ሰዎች
ይይዟችኋል፤ ያሳድዷችኋል፤ ወደ ምኵራ
ብና ወደ ወህኒ ቤት ያስገቧችኋል፤ በነገ
ሥታትና በገዥዎች ፊት ያቀርቧችኋል፤
ይህም ሁሉ በስሜ ምክንያት ይደርስባች
ኋል። 13ይህም ለመመስከር ጥሩ ዕድል

[ክ]41 ወይም መሲሕ

23፥8፤1ቆሮ15፥12
20፥28 ዘዳ25፥5
20፥35 ማቴ12፥32
20፥36 ዮሐ1፥12
20፥37 ዘፀ3፥6
20፥40 ማቴ12፥34፤ 22፥46
20፥41 ማቴ1፥1
20፥43 መዝ110፥1፤ ማቴ22፥44
20፥46 ሉቃ11፥43
21፥1 ማቴ27፥6፤ ዮሐ8፥20
21፥4 2ቆሮ8፥12
21፥6 ሉቃ19፥44
21፥8 ሉቃ17፥23
21፥10 2ዜና15፥6፤ ኢሳ19፥2
21፥11 ኢሳ29፥6፤ ኢል2፥30
21፥13 ፊል1፥12
21፥14 ሉቃ12፥11

ይሆንላችኋል። 14ስለዚህ ምን መልስ እንስ
ጣለን በማለት አስቀድማችሁ እንዳትጨ
ነቁ ይህን ልብ በሉ፤ 15ተቃዋሚዎቻችሁ
ሁሉ ሊቋቋሙትና ሊያስተባብሉት የማይ
ችሉትን ቃልና ጥበብ እሰጣችኋለሁና። 16ወላ
ጆቻችሁ፣ ወንድሞቻችሁ፣ ዘመዶቻችሁና
ጓደኞቻችሁ እንኳ ሳይቀሩ አሳልፈው ይሰጡ
አችኋል፤ ከእናንተም አንዳንዶቹን
ይገድላሉ፤ 17ስለ ስሜም በሰዎች ሁሉ
ዘንድ የተጠላ ችሁ ትሆናላችሁ። 18ነገር
ግን ከራሳችሁ
ጠጕር አንዷ እንኳ አትጠፋም፤ 19ጸንታ
ችሁም በመቆም ነፍሳችሁን ታተርፋላችሁ።
20"ኢየሩሳሌም በጦር ሰራዊት ተከባ በም
ታዩበት ጊዜ፣ ጥፋቷ መቃረቡን ዕወቁ።
21በዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉ ወደ ተራሮች
ይሽሹ፤ በከተማ ያሉትም ከዚያ ይውጡ፤
በገጠር ያሉትም ወደ ከተማዪቱ አይግቡ፤
22የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይህ የበ
ቀል ጊዜ ነውና። 23በምድሪቱ ላይ ታላቅ
መከራ ይሆናል፤ በዚህም ሕዝብ ላይ
ቍጣ ይመጣል፤ ስለዚህ በዚያን ወቅት
ለነፍሰጡሮችና ለሚያጠቡ እናቶች ወዮላ
ቸው! 24በሰይፍ ይወድቃሉ፤ ወደ አሕዛ
ብም ሁሉ በምርኮ ይወሰዳሉ፤ ኢየሩሳሌ
ምም የአሕዛብ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ፣
በአሕዛብ የተረገጠች ትሆናለች።
25"በፀሓይ፣ በጨረቃና በከዋክብት ላይ
ምልክት ይሆናል፤ ከባሕሩና ከሞገድ
ድምፅ የተነሣ፣ በምድር ላይ ያሉ ሕዝቦች
ይጨነቃሉ፤ ይታወካሉም፤ 26የሰማያት
ኀይላት ስለሚናወጡ፣ ሰዎች በፍርሀትና
በዓለም ላይ ምን ይመጣ ይሆን እያሉ
በመጠባበቅ ይዝላሉ። 27በዚያን ጊዜ የሰው
ልጅ በኀይልና በታላቅ ክብር በደመና
ሲመጣ ያዩታል። 28እናንተም እነዚህ ነገ
ሮች መፈጸም ሲጀምሩ፣ መዳናችሁ ስለ
ተቃረበ፣ ቀጥ ብላችሁ ቁሙ፤ ራሳችሁ
ንም ወደ ላይ ቀና አድርጉ።"
29ቀጥሎም እንዲህ ሲል ይህን ምሳሌ ነገራ
ቸው፤ "በለስንና ዛፎችን ሁሉ ተመልከቱ፤
30ቅጠሎቻቸው አቈጥቍጠው ስታዩ፣ በዚ
ያን ጊዜ በጋ መቃረቡን ራሳችሁ ታውቃ
ላችሁ። 31እንዲሁ ደግሞ እነዚህ ነገሮች መፈ
ጸማቸውን ስታዩ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት
እንደ ቀረበች ዕወቁ።
32"እውነት እላችኋለሁ፤ ይህ ሁሉ እስኪፈ
ጸም ድረስ ይህ[h] ትውልድ አያልፍም። 33ሰማ
ይና ምድር ያልፋሉ፤ ቃሌ ግን አያልፍም።"
34"እንግዲህ በገደብ የለሽ ሕይወት፣
በመጠጥ ብዛትና ስለ ኑሮ በመጨነቅ ልባ
ችሁ እንዳይዝልና ያ ቀን እንደ ወጥመድ

21፥15 ሉቃ12፥12
21፥16 ሉቃ12፥52፡53
21፥17 ዮሐ15፥21
21፥18 ማቴ10፥30
21፥19 ማቴ10፥22
21፥20 ሉቃ19፥43
21፥21 ሉቃ17፥31
21፥22 ኢሳ63፥4፤ ዳን9፥24-27፤ ሆሴ 9፥7፤ማቴ1፥22
21፥24 ኢሳ5፥5፤ 63፥18፤ ዳን8፥13፤ ራእ11፥2
21፥25 2ጴጥ3፥10፡12
21፥26 ማቴ24፥29
21፥27 ማቴ8፥20፤ ራእ1፥7
21፥28 ሉቃ18፥7
21፥31 ማቴ3፥2
21፥32 ሉቃ 11፥50፤17፥25
21፥33 ማቴ5፥18
21፥34 ማር4፥19፤ ሉቃ12፥40፡46፤ 1ተሰ5፥2-7
21፥36 ማቴ26፥41
21፥37 ማቴ21፥1፤ 26፥55፤ ማር11፥19
21፥38 ዮሐ8፥2
22፥1 ዮሐ11፥55
22፥2 ማቴ12፥14
22፥3 ማቴ4፥10፤ ማቴ10፥4
22፥4 ቍ52፤ ሐሥ4፥1፤5፥24
22፥5 ዘካ11፥12
22፥7 ዘፀ12፥18-20፤ ዘዳ16፥5-8፤ ማር14፥12
22፥8 ሐሥ3፥1፡ 11፤ 4፥13፤19፤8፥14
22፥13 ሉቃ19፥52
22፥14 ማቴ26፥

ድንገት እንዳይደርስባችሁ ተጠንቀቁ፤ 35ይህ
በመላው ምድር በሚኖሩት ሁሉ ላይ ይደ
ርሳልና። 36ስለዚህ ከሚመጣው ሁሉ እንድ
ታመልጡና በሰው ልጅ ፊት መቆም እን
ድትችሉ ሁልጊዜ ተግታችሁ ጸልዩ።"
37ኢየሱስም ቀን ቀን በቤተ መቅደስ
እያስተማረ፣ ሌሊት ግን ደብረ ዘይት
ወደ ተባለ ተራራ ወጥቶ ያድር ነበር።
38ሕዝቡም ሁሉ ሊሰሙት ማልደው ወደ
ቤተ መቅደስ ወደ እርሱ ይመጡ ነበር።

### ይሁዳ ጌታን አሳልፎ ለመስጠት ተስማማ

22፥1፡2 ተጓ ምብ –ማቴ 26፥2-5፤ ማር 14፥1፡2፡ 10፥11

22 በዚህ ጊዜ ፋሲካ የተባለው የቂጣ
በዓል ተቃርቦ ነበር። 2የካህናት
አለቆችና ጸሐፍትም ሕዝቡን ይፈሩ ስለ
ነበር፣ እንዴት አድርገው ኢየሱስን እንደ
ሚያስወግዱት መንገድ ይፈልጉ ነበር።
3ሰይጣንም ከዐሥራ ሁለቱ ጋር በተቈጠ
ረው የአስቆሮቱ ይሁዳ በተባለው ገባበት፤
4ይሁዳም ወደ ካህናት አለቆችና ወደ ቤተ
መቅደሱ ሹሞች ሄዶ ኢየሱስን እንዴት
አሳልፎ እንደሚሰጣቸው ተነጋገረ። 5እነ
ርሱም በዚህ ደስ ተሰኝተው፣ ገንዘብ ሊ
ሰጡት ተዋዋሉ። 6እርሱም በነገሩ ተስማ
ማ፤ አሳልፎ ሊሰጣቸውም ሕዝብ የማ
ይገኝበትን ምቹ ጊዜ ይጠብቅ ጀመር።

### የመጨረሻው እራት

22፥7-13 ተጓ ምብ –ማቴ 26፥17-19፤ ማር 14፥12-16
22፥17-20 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥26-29 ማር 14፥22-25፤1 ቆሮ 11፥23-25
22፥21-23 ተጓ ምብ -ማቴ 26፥21-24፤ ማር 14፥18-21፤ ዮሐ 13፥21-30
22፥25-27 ተጓ ምብ - ማቴ 20፥25-28፤ ማር 10፥42-45
22፥33፡34 ተጓ ምብ –ማቴ 26፥33-35፤ ማር 14፥29-31፤ ዮሐ 13፥37፡38

7ከዚህ በኋላ የፋሲካ በግ የሚታረድበት
የቂጣ በዓል ደረሰ። 8ኢየሱስም፣ "የፋሲ
ካን እራት እንድንበላ ሄዳችሁ አዘጋጁልን"
ብሎ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ላካቸው።
9እነርሱም፣ "የት እንድናሰናዳ ትፈልጋ
ለህ?" አሉት።
10እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "እነሆ፤ ወደ ከተ
ማ ስትገቡ የውሃ እንስራ የተሸከመ ሰው
ያገኛችኋል፤ እርሱ ወደሚገባበት ቤት
ድረስ ተከተሉት፤ 11ለቤቱም ባለቤት፣
'መምህሩ፣ "ከደቀ መዛሙርቴ ጋር የፋሲ
ካን እራት የምበላበት የእንግዳ ክፍል
ወዴት ነው?" ይልሃል' በሉት። 12እርሱም
በሰገነት ላይ ያለውን ተነጥፎ የተዘጋጀ
ሰፊ አዳራሽ ያሳያችኋል፤ በዚያም አሰና
ዱልን።"
13እነርሱም ሄደው ልክ ኢየሱስ እንደ
ነገራቸው ሆኖ አገኙት፤ ፋሲካንም በዚያ
አዘጋጁ።

h32 ወይም በዘር

14ሰዓቱም በደረሰ ጊዜ ኢየሱስ ከሐዋር
ያቱ ጋር በማእድ ተቀመጠ፤ 15እንዲህም
አላቸው፤ “መከራ ከመቀበሌ በፊት ይህን
ፋሲካ አብሬያችሁ ለመብላት በጣም
ስመኝ ነበር፤ 16እላችኋለሁ፤ በእግዚአብሔር
መንግሥት የዚህ ትርጕም እስኪፈጸም
ድረስ ይህን ፋሲካ ዳግመኛ አልበላም።”
17ጽዋውን ተቀብሎ ካመሰገነ በኋላ እንዲህ
አላቸው፤ “እንካችሁ፤ ሁላችሁ ከዚህ ተካ
ፈሉ፤ 18እላችኋለሁና፤ ከአሁን ጀምሮ የእ
ግዚአብሔር መንግሥት እስከምትመጣ ድረስ፣
ከዚህ ወይን ፍሬ አልጠጣም።”
19እንጀራንም አንሥቶ አመሰገነ፤ ቈርሶም
ሰጣቸውና፣ “ይህ ስለ እናንተ የሚሰጥ ሥጋዬ
ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት” አለ።
20እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን
አንሥቶ እንዲህ አለ፤ “ይህ ጽዋ ስለ እና
ንተ በሚፈሰው ደሜ የሚመሠረት አዲስ
ኪዳን ነው። 21ነገር ግን አሳልፎ የሚሰጠኝ
ሰው እጅ በማእድ ከእኔ ጋር ናት። 22የሰው
ልጅስ አስቀድሞ በተወሰነው መሠረት
ይሄዳል፤ ነገር ግን እርሱን አሳልፎ ለሚ
ሰጠው ለዚያ ሰው ወዮለት።” 23እነርሱም
ከመካከላቸው ይህን የሚያደርግ ማን ሊሆን
እንደሚችል እርስ በርሳቸው ይጠያየቁ
ጀመር።
24ደግሞም ከመካከላቸው ማን እንደሚ
በልጥ በእነርሱ ዘንድ ክርክር ተነሣ። 25ኢየ
ሱስም እንዲህ አላቸው፤ “የአሕዛብ ነገሥ
ታት ሕዝቦቻቸውን በኀይል ይገዛሉ፤ በእነ
ርሱ ላይ ሥልጣን ያላቸውም በጎ አድራጊ
ዎች ተብለው ይጠራሉ። 26በእናንተ ዘንድ
ግን እንዲህ አይሁን፤ ይልቁን ከእናንተ
ታላቅ የሆነ እንደ ታናሽ፣ ገዥ የሆነም
እንደ አገልጋይ ይሁን። 27ለመሆኑ፣ በማ
እድ ከተቀመጠና ቆሞ ከሚያስተናግድ
ማን ይበልጣል? በማእድ የተቀመጠው
አይደለምን? እኔ ግን በመካከላችሁ ያለ
ሁት እንደ አንድ አገልጋይ ነው። 28እናን
ተም ሳትለዩኝ በመከራዬ ጊዜ በአጠገቤ
የቆማችሁ ናችሁ፤ 29አባቴ እኔን እንደ
ሾመኝ እኔም ደግሞ በመንግሥቴ እሾማ
ችኋለሁ፤ 30ይኸውም በመንግሥቴ ከማእዴ
እንድትበሉና እንድትጠጡ ደግሞም በዙፋን
ላይ ተቀምጣችሁ በዐሥራ ሁለቱ የእስራ
ኤል ነገድ ላይ እንድትፈርዱ ነው።”
31ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ “ስም
ዖን፣ ስምዖን ሆይ፤ እነሆ፣ ሰይጣን እንደ
ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ 32እኔ ግን እም
ነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ ጸለይሁ፤ አንተም
በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አበርታ።”
33ስምዖንም፣ “ጌታ ሆይ፤ እኔ ከአንተ ጋር

20፤ማር6፥30
14፥17፡18
22፥15 ማቴ16፥21
22፥16 ሉቃ14፥15
22፥19 ማቴ14፥19
22፥20 ዘፀ24፥8፤
ኢሳ 42፥6፤
ኤር31፥31-34
ዘካ9፥11፤ 2ቆሮ3፥6፤
ዕብ8፥6፣9፥15
22፥21 መዝ41፥9
22፥22 ማቴ8፥20፤
ሐሥ2፥23፤4፥28
22፥24 ማር9፥34፤
ሉቃ9፥46
22፥26 ማር9፥35፤
1ጴጥ5፥5
22፥27 ማቴ20፥28
22፥29 ማቴ25፥
34፤
2ጢሞ2፥12
22፥30 ማቴ19፥
28፤ ሉቃ14፥15
22፥31 ኢዮ1፥6-12፤
አሞ9፥9
22፥32 ዮሐ17፥
9፡15፤ ዮሐ21፥15-17
22፥33 ዮሐ11፥16
22፥35 ማቴ10፥
9፡10፤ ሉቃ 9፥3፤
10፥4
22፥37 ኢሳ53፥12
22፥39 ማቴ21፥1፤
ሉቃ21፥37
22፥40 ማቴ6፥13
22፥41 ሉቃ18፥11
22፥42ማቴ20፥22፤
26፥39
22፥43 ማቴ4፥11፤
ማር1፥13
22፥46 ቊ40
22፥49 ቊ38
22፥52 ቊ4

ወህኒ ለመውረድም፣ ለመሞትም ዝግጁ ነኝ”
አለው።
34ኢየሱስም፣ “ጴጥሮስ ሆይ፤ ዛሬ ዶሮ
ሳይጮኽ፣ አላውቀውም ብለህ ሦስት ጊዜ
ትክደኛለህ እልሃለሁ” አለው።
35ከዚያም ኢየሱስ፣ “ያለ ኰረጆ፣ ያለ
ከረጢትና ያለ ጫማ በላክኋችሁ ጊዜ የጐ
ደለባችሁ ነገር ነበርን? ”ብሎ ጠየቃቸው።
እነርሱም፣ “ምንም አልጐደለብንም”
አሉ።
36እርሱም እንዲህ አላቸው፤ “አሁን ግን
ኰረጆም፣ ከረጢትም ያለው ሰው ይያዝ፤
ሰይፍ የሌለውም ልብሱን ሸጦ ይግዛ።
37እላችኋለሁና፤ ‘ከዐመፀኞች ጋር ተቈጠ
ረ’ ተብሎ የተጻፈው በእኔ መፈጸም
አለበት፤ ስለ እኔ የተጻፈው ፍጻሜው
በእርግጥ ደርሶአል።”
38ደቀ መዛሙርቱም፣ “ጌታ ሆይ፤ እነሆ፤
ሁለት ሰይፎች እዚህ አሉ” አሉት።
እርሱም፣ “ይበቃል” አላቸው።

## ኢየሱስ በደብረ ዘይት ተራራ ጸለየ

2፥40-46 ተጓ ምብ – ማቴ 26 ፥36-46፤ ማር 14፥32-42

39ኢየሱስ እንደ ልማዱ ወጥቶ ወደ ደብረ
ዘይት ተራራ ሄደ፤ ደቀ መዛሙርቱም
ተከተሉት። 40እዚያም በደረሱ ጊዜ፣ “ወደ
ፈተና እንዳትገቡ ጸልዩ” አላቸው። 41ከእነ
ርሱም የድንጋይ ውርወራ ያህል ርቆ ተንበ
ርክኮ ጸለየ፤ 42እንዲህም አለ፤ አባት ሆይ፤
ፈቃድህ ከሆነ፣ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤
ነገር ግን የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ
ፈቃድ ይፈጸም።” 43መልአክም ከሰማይ
ተገልጦለት አበረታታው። 44እጅግ ተጨ
ንቆም በብርቱ ይጸልይ ነበር፤ ላቡም እንደ
ደም ነጠብጣብ ወደ ምድር[ሠ] ይፈስ ነበር።
45ከጸሎትም ተነሥቶ ወደ ደቀ መዛሙ
ርቱ መጣ፤ እነርሱም ከሐዘን የተነሣ ተኝ
ተው አገኛቸውና፣ 46“ለምን ትተኛላ
ችሁ? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተነሥታ
ችሁ ጸልዩ” አላቸው።

## ኢየሱስ ተያዘ

22፥47-53 ተጓ ምብ – ማቴ 26፥47-56፤ ማር 14፥43-50፤ ዮሐ 18፥3-11

47እርሱም ገና እየተነጋገረ ሳለ፣ ብዙ ሰዎች
መጡ፤ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ ይሁዳ የተባ
ለውም ሰው ይመራቸው ነበር፤ ሊስመ
ውም ወደ ኢየሱስ ተጠጋ። 48ኢየሱስ
ግን፣ “ይሁዳ ሆይ፤ የሰውን ልጅ በመሳም
አሳልፈህ ትሰጣለህን?” አለው።
49በኢየሱስ ዙሪያ የነበሩ ሰዎችም ሁኔታ
ውን ተመልክተው “ጌታ ሆይ፤ በሰይፍ

[ሠ]44 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ቊጥር 43 እና 44 የላቸውም

እንምታቸውን?” አሉት። 50ከእነርሱም አንዱ
የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ መትቶ ቀኝ
ጆሮውን ቈረጠው።
51ኢየሱስ ግን፣ “ተው! እዚህ ድረስም
ፍቀዱ”አለ፤ የሰውየውንም ጆሮ ዳሶ ፈወ
ሰው።
52ከዚያም ኢየሱስ ሊይዙት የመጡትን
የካህናት አለቆች፣ የቤተ መቅደስ ሹሞ
ችና ሽማግሌዎችን እንዲህ አላቸው፤ “ወን
በዴ እንደሚይዝ ሰው፣ ሰይፍና ቈመጥ
ይዛችሁ ወጣችሁን? 53በየዕለቱ በቤተ መቅ
ደስ ከእናንተ ጋር በነበርሁ ጊዜ እጃችሁን
አላነሣችሁብኝም፤ ይህ ግን ጨለማ የነገሠ
በት ጊዜያችሁ ነው።”

### ጴጥሮስ ኢየሱስን ካደ

22፥55-62 ተጓ ምብ – ማቴ 26፥69-75፤ ማር 14፥66-72፤
ዮሐ 18፥16-18፡ 25-27

54ከዚህ በኋላ ኢየሱስን ይዘው ወሰዱት፤
ወደ ሊቀ ካህናቱም ግቢ አስገቡት፤ ጴጥሮ
ስም በርቀት ይከተለው ነበር። 55ሰዎቹ በሊቀ
ካህናቱ ግቢ ውስጥ እሳት አንድደው በአን
ድነት ተቀምጠው ሳለ፣ ጴጥሮስም ከእነርሱ
ጋር ተቀምጦ ነበር። 56አንዲት የቤት ሠራ
ተኛም ጴጥሮስ እሳቱ አጠገብ ተቀምጦ
አየችውና ትኵር ብላ በመመልከት፣ “ይህ
ሰው ደግሞ ከእርሱ ጋር ነበረ” አለች።
57እርሱ ግን፣ “አንቺ ሴት፤ እኔ ዐላውቀ
ውም” ብሎ ካደ።
58ከጥቂት ጊዜ በኋላም አንድ ሌላ ሰው
አይቶት፣ “አንተም ደግሞ ከእነርሱ አንዱ
ነህ” አለው።
ጴጥሮስ ግን፣ “አንተ ሰው፤ እኔ አይደ
ለሁም” አለ።
59አንድ ሰዓት ያህል ቈይቶም፣ ሌላ
ሰው በእርግጠኝነት፣ “ይህ ሰው ገሊላዊ
ስለ ሆነ ያለ ጥርጥር ከእርሱ ጋር ነበረ”
አለ።
60ጴጥሮስ ግን፣ “አንተ ሰው፤ የምት
ለውን እኔ አላውቅም”አለ፤ ይህንም ተና
ግሮ ገና ሳይጨርስ ዶሮ ጮኸ። 61ጌታም
መለስ ብሎ ጴጥሮስን ተመለከተው፤ ጴጥ
ሮስም፣ “ዛሬ ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ
ትክደኛለህ” ብሎ ጌታ የተናገረው ቃል
ትዝ አለው። 62ጴጥሮስም ወደ ውጭ
ወጥቶ ምርር ብሎ አለቀሰ።

### ወታደሮች በኢየሱስ ላይ አፌዙበት

22፥63-65 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥67፡68፤ ማር 14፥65፤
ዮሐ 18፥22፡23

63ኢየሱስን አስረው ይጠብቁት የነበሩት
ሰዎችም ያፌዙበትና ይመቱት ጀመር፤

22፥53 ማቴ8፥12፤ 26፥55፤ ዮሐ1፥5፤ 3፥20፤12፥27
22፥54 ማቴ26፥57፡58፤ማር14፥53፡54፤ ዮሐ18፥15
22፥59 ሉቃ23፥6
22፥61 ቍ34፤ ሉቃ7፥13
22፥65 ማቴ16፥21
22፥66 ማቴ5፥22፤ 27፥1፤ ማር15፥1
22፥68 ሉቃ20-8
22፥69 ማር16፥19
22፥70 ማቴ4፥3፤ 27፥11፤ ሉቃ23፥3
23፥1 ማቴ27፥2
23፥2 ቍ14፤ ሉቃ20፥22፤ ዮሐ119፥12
23፥4 ቍ14፡ 22፡41፤ ማቴ27፥23፤ ዮሐ18፥38፤ 2ቆሮ 5፥21፤ 1ጢሞ6፥13
23፥5 ማር1፥14
23፥6 ሉቃ22፥59
23፥7 ማቴ14፥1
23፥8 ሉቃ 9፥9
23፥9 ማር14፥61

64ዐይኑንም ሸፍነው፣ “እስቲ ትንቢት ተና
ገር፤ የመታህ ማነው? እያሉ ይጠይቁት
ነበር። 65ሌላም ብዙ የስድብ ቃል እየተና
ገሩ ያቃልሉት ነበር።

### ኢየሱስ በጲላጦስና በሄሮድስ ፊት

22፥67-71 ተጓ ምብ – ማቴ 26፥63-66፤ ማር 14፥61-63፤ ዮሐ 18፥19-21
23፥2፡3 ተጓ ምብ – ማቴ 27፥11-14፤ ማር15፥2-5፤ ዮሐ 18፥29-37
23፥18-25 ተጓ ምብ – ማቴ 27፥15-26፤ ማር 15፥6-15፤
ዮሐ 18፥39-19፥16

66በነጋም ጊዜ፣ የሕዝብ ሽማግሌዎች፣
የካህናት አለቆችና ጸሐፍት ተሰበሰቡ፤
ኢየሱስንም በሸንጎአቸው ፊት አቀረ
ቡት። 67እነርሱም፣ “አንተ ክርስቶስ[°] ነህን?
እስቲ ንገረን” አሉት።
ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤“ብነግራችሁ
አታምኑኝም፤ 68ብጠይቃችሁም አትመል
ሱም። 69ነገር ግን ከአሁን ጀምሮ የሰው
ልጅ በእግዚአብሔር ኀይል ቀኝ ይቀመጣል።”
70በዚህ ጊዜ ሁሉም፣ “ታዲያ፣ አንተ
የእግዚአብሔር ልጅ ነህን?” አሉት።
እርሱም፣ “መሆኔን እኮ እናንተው ተና
ገራችሁት” አላቸው።
71እነርሱም፣ “ከእንግዲህ ሌላ ምስክር
ምን ያስፈልገናል? ራሳችን ከገዛ አንደበቱ
ሰምተናልና” አሉ።

23 በዚያ የተሰበሰቡት በሙሉ ተነሥ
ተው ኢየሱስን ወደ ጲላጦስ ወሰ
ዱት፤ 2እንዲህም እያሉ ይከሱት ጀመር፤
“ይህ ሰው ሕዝባችንን ሲያስት፣ ለቄሳር
ግብር እንዳይከፈል ሲከለክል፣ ደግሞም፣
‘እኔ ክርስቶስ[ʺ] ንጉሥ ነኝ’ ሲል አገኘ
ነው።”
3ጲላጦስም፣ “አንተ የአይሁድ ንጉሥ
ነህን? ” ብሎ ጠየቀው።
ኢየሱስም፣ “አንተውኮ አልህ” አለው።
4ጲላጦስም ለካህናት አለቆችና ለሕዝቡ፣
“እኔ በዚህ ሰው ላይ ምንም ወንጀል አላ
ገኘሁበትም” አለ።
5እነርሱ ግን፣ “ይህ ሰው ከገሊላ ጀምሮ
እዚህ ድረስ መላውን ይሁዳ ሳይቀር[‴]
እያ ወከ ነው” እያሉ አጽንተው ተናገሩ።
6ጲላጦስም ይህን ሲሰማ፣ ሰውየው የገሊላ
ሰው መሆኑን ለማረጋገጥ ጠየቀ፤ 7ኢየሱስ
ከሄድሮስ ግዛት የመጣ መሆኑን ጲላጦስ
ባወቀ ጊዜ፣ ሄሮድስ በዚያን ወቅት በኢ
የሩሳሌም ስለ ነበረ ወደ እርሱ ላከው።
8ሄሮድስም ኢየሱስን ብዙ ጊዜ ሊያየው
ይፈልግ ስለ ነበር፣ ባየው ጊዜ እጅግ ደስ

[°] 67 ወይም *መሲሕ*
[ʺ] 2 ወይም *መሲሕ፤* እንዲሁም ቍ 35 እና 39 ይመ
[‴] 5 ወይም *በመላው የአይሁድ ምድር*

አለው፤ ስለ እርሱ ሰምቶ ስለ ነበር፣ ታም
ራት ሲሠራ ለማየት ተስፋ ያደርግ ነበር።
9ብዙ ጥያቄዎችንም አቀረበለት፤ እርሱ
ግን ምንም አልመለሰለትም። 10የካህናት
አለቆችና ጸሐፍትም እዚያው ቆመው በብ
ርቱ ይወነጅሉት ነበር። 11ሄሮድስም ከወ
ታደሮቹ ጋር ናቀው፤ አፌዙበትም፤ የክ
ብር ልብስ አልብሶም ወደ ጲላጦስ መልሶ
ሰደደው። 12ሄሮድስና ጲላጦስም በዚሁ
ዕለት ተወዳጁ፤ ቀደም ሲል ግን በመካከ
ላቸው ጥል ነበረ።

13ጲላጦስም የካህናት አለቆችን፣ ገዥዎ
ችንና ሕዝቡን በአንድነት ሰብስቦ፣ 14እንዲህ
አላቸው፤ "ይህ ሰው ሕዝቡን ለዐመፅ ያነ
ሣሣል ብላችሁ ወደ እኔ አምጥታችሁት
ነበር፤ እኔም በእናንተው ፊት መርም
ሬው፣ ባቀረባችሁበት ክስ አንዳች ወን
ጀል አላገኘሁበትም። 15ደግሞም ሄሮድስ
እንዲሁ ምንም ስላላገኘበት ወደ እኛ
መል ሶታል፤ እንደምታዩት ይህ ሰው
ለሞት የሚያበቃ ምንም ነገር አልፈ
ጸመም፤ 16ስለ ዚህ ቀጥቼ እፈታዋለሁ።"
17ይህን ያለው በበዓሉ አንድ እስረኛ እንዲ
ፈታላቸው የግድ ያስፈልግ ስለ ነበረ
ነው።[የ]

18ሕዝቡም ሁሉ በአንድ ላይ፣ "ይህን
ሰው ወዲያ አስወግደው! በርባንን ፍታ
ልን!" እያሉ ጮኹ፤ 19በርባንም በከተማ
ውስጥ የሕዝብ ዐመፅ በማነሣሣትና በነ
ፍስ ግድያ የታሰረ ሰው ነበር።

20ጲላጦስም ኢየሱስን ሊፈታው ስለ
ፈለገ፣ እንደ ገና ተናገራቸው፤ 21እነርሱ
ግን፣ "ስቀለው! ስቀለው!" እያሉ ይጮኹ
ነበር።

22ጲላጦስም ሦስተኛ ጊዜ፣ "ለምን? ይህ
ሰው ምን የፈጸመው ወንጀል አለ? እኔ
ለሞት የሚያበቃ ምንም በደል አላገኘሁ
በትም፤ ስለዚህ ቀጥቼ እፈታዋለሁ" አላ
ቸው።

23እነርሱ ግን ድምፃቸውን ከፍ በማድ
ረግ እንዲሰቀል አጥብቀው ለመኑት፤ ጩኸ
ታቸውም በረታ። 24ስለዚህ ጲላጦስ የጠ
የቁት እንዲፈጸም ውሳኔ አስተላለፈ።
25የሕዝብ ዐመፅ በማነሣሣትና በነፍስ ግድያ
ታስሮ የነበረውን፣ እንዲፈታላቸውም የለመ
ኑትን ያን ሰው ፈታላቸው፤ ኢየሱስን ግን
እንዳሻቸው እንዲያደርጉት አሳልፎ ሰጣቸው።

## የኢየሱስ መስቀል

23፥33-43 ተጓ ምብ – ማቴ 27፥33-44፤ ማር 15፥22-32፤ ዮሐ 19፥17-24

26ኢየሱስንም ይዘው ሲወስዱት፣ ስምዖን
የተባለውን የቀሬናን ሰው ከገጠር ሲመጣ
አግኝተው መስቀሉን አሸክመው ኢየሱስን
ተከትሎ እንዲሄድ አስገደዱት። 27ብዙ ሕዝ
ብና ደረታቸውን እየደቁ የሚያለቅሱ
ሴቶችም ከኋላው ይከተሉት ነበር። 28ኢየ
ሱስ ግን ወደ እነርሱ ዞወር ብሎ እንዲህ
አላቸው፤ "እናንት የኢየሩሳሌም ሴቶች፤
ለራሳችሁና ለልጆቻችሁ አልቅሱ እንጂ
ለእኔ አታልቅሱ፤ 29እነሆ፤ 'መካኖችና ያል
ወለዱ ማሕፀኖች፣ ያላጠቡ ጡቶችም ብፁዓን
ናቸው' የምትሉበት ጊዜ ይመጣልና። 30በዚ
ያን ጊዜም፣

" 'ተራሮችን፣ "ውደቁብን"
ኰረብቶችንም፣ "ሸውሩን" ይላሉ።'

31እንግዲህ በእርጥብ ዕንጨት እንዲህ
ካደረጉ፣ በደረቁ ምን ያደርጉ ይሆን?"

32ከእርሱ ጋር እንዲገደሉ ሌሎች ሁለት
ወንጀለኞችን ወሰዷቸው። 33ቀራንዮ[ደ] የተ
ባለ ቦታ በደረሱ ጊዜ ሰቀሉት፤ ወንጀለ
ኞቹንም አንዱን በቀኙ፣ ሌላውን በግራው
ሰቀሏቸው። 34ኢየሱስም፣ "አባት ሆይ፤ የሚ
ያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው"[ጀ]
አለ። እነርሱም ልብሱን በዕጣ ተከፋፈሉት።

35ሕዝቡም ቆመው ይመለከቱ ነበር።
ገዦችም፣ "ሌሎችን አዳነ፤ በእግዚአብሔር
የተመረጠው ክርስቶስ እርሱ ከሆነ፣ እስቲ
ራሱን ያድን" እያሉ አፌዙበት።

36ወታደሮችም ቀርበው ያፌዙበት ነበር፤
የሖመጠጠ የወይን ጠጅ እየሰጡትም፣
37"አንተ የአይሁድ ንጉሥ ከሆንህ፣ ራስህን
አድን" ይሉት ነበር።

38ከራሱም በላይ፣ "ይህ የአይሁድ ንጉሥ
ነው" የሚል ጽሑፍ ነበር።

39ከተሰቀሉት ወንጀለኞችም አንዱ የስ
ድብ ናዳ እያወረደበት፣ "አንተ ክርስቶስ
አይደለህምን? እስቲ፣ ራስህንም እኛንም፣
አድን" ይለው ነበር።

40ሌላኛው ወንጀለኛ ግን እንዲህ ሲል ገሠ
ጸው፤ "ተመሳሳይ ፍርድ እየተቀበልህ ሳለህ፣
ከቶ እግዚአብሔርን አትፈራምን? 41እኛ
ላደረግነው ነገር ቅጣት እየተቀበልን ስለ
ሆነ፣ ተገቢ ፍርድ ላይ ነን፤ ይህ ሰው ግን
አንዳች ክፉ ነገር አላደረገም።"

42ደግሞም፣ "ኢየሱስ ሆይ፤ በመንግሥ
ትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ"[ገ] አለው።

43ኢየሱስም፣ "እውነት እልሃለሁ፤ ዛሬ
ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ" አለው።

23፥11 ማር15፥17-19፤ዮሐ19፥2፡3
23፥12 ሐሥ4፥27
23፥14 ቊ4
23፥16 ቊ22፤ ማቴ27፥26፤ ዮሐ19፥1፤ሐሥ16፥37፤ 2ቆሮ11፥23፡24
23፥18 ሐሥ3፥13፡14
23፥22 ቊ16
23፥26 ማቴ27፥32፤ማር15፥21፤ ዮሐ19፥17
23፥27 ሉቃ8፥52
23፥28 ሉቃ19፥41-44፤21፥23፡24
23፥29 ማቴ24፥19
23፥30 ኢሳ2፥19፤ ሆሴ10፥8፤ ራእ6፥16
23፥31 ሕዝ20፥47
23፥32 ኢሳ53፥12፤ማቴ27፥38፤ ማር15፥27፤ ዮሐ19፥18
23፥34 መዝ22፥18፤ ማቴ5፥44፤11፥25
23፥35 መዝ22፥17፤ኢሳ42፥1
23፥36 መዝ22፥7፤69፥21፤ ማቴ27፥48
23፥37 ሉቃ4፥3፡9
23፥38 ማቴ2፥2
23፥39 ቊ35፡37
23፥41 ቊ4
23፥42 ማቴ16፥27
23፥43 2ቆሮ12፥3፡4፤ራእ2፥7
23፥44 አሞ8፥9

[የ]17 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ይህን ቍጥር ይጨምራሉ
[ደ]33 በግሪክ ቋንቋ *የራስ ቅል* ማለት ነው፤ በዕብራይስጥ ጎልጎታ ይባላል
[ጀ]34 አንዳንድ የጥንት ቅጆች፣ ይህ ዐረፍተ ነገር የላቸውም
[ገ]42 አንዳንድ ቅጆች *በንጉሥነት ሥልጣንህ ስትመጣ* ይላሉ

## የኢየሱስ መሞት

23፥44-49 ተጓ ምብ – ማቴ 27፥45-56፤ ማር 15፥33-41

44ጊዜው ስድስት ሰዓት ያህል ነበር፤
እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስም በምድር ሁሉ
ላይ ጨለማ ሆነ፤ 45የፀሓይ ብርሃን ተከ
ልክሎአልና። የቤተ መቅደሱም መጋረጃ
ተቀዶ ለሁለት ተከፈለ። 46ኢየሱስም
በታላቅ ድምፅ ጮኸ፣ “አባት ሆይ፤
መንፈሴን በእጅህ እሰጣለሁ!” አለ፤ ይህ
ንም ብሎ ሞተ።
47የመቶ አለቃውም የሆነውን ነገር ባየ
ጊዜ፣ “ይህ ሰው በእርግጥ ጻድቅ ነበር”
ብሎ እግዚአብሔርን አመሰገነ። 48ይህንኑ ለ
ማየት በስፍራው ተሰብስበው የነበሩ
ሰዎችም ሁሉ የሆነውን ነገር በተመለከቱ ጊ
ዜ ደረታቸውን እየደቁ ተመለሱ። 49ነገር
ግን ኢየሱስን በቅ ርብ የሚያውቁት ሁሉ
እንዲሁም ከገሊላ ጀምሮ የተከተሉት ሴቶች
ይህን እየተመ ለከቱ ከሩቅ ቆመው ነበር።

## የኢየሱስ መቀበር

23፥50-56 ተጓ ምብ- ማቴ27፥57-61፤ ማር 15፥42-47፤ ዮሐ 19፥38-42

50የአይሁድ ሸንጎ አባል የሆነ፣ አንድ
ዮሴፍ የሚባል በጎና ጻድቅ ሰው ነበር።
51ይህ ሰው በሸንጎው ምክርና ድርጊት አል
ተባበረም ነበረ፣ እርሱም አርማትያስ የም
ትባል የአይሁድ ከተማ ሰው ሲሆን፣ የእ
ግዚአብሔርን መንግሥት መምጣት ይጠባ
በቅ ነበር። 52ይህም ሰው ወደ ጲላጦስ ሄዶ
የኢየሱስን ሥጋ ለመነው፤ 53በተፈቀደለ
ትም ጊዜ፣ ሥጋውን አውርዶ በበፍታ
ገነዘው፤ ከድንጋይ ተፈልፍሎ በተሠራና
ገና ማንም ባልተቀበረበት መቃብር ውስጥ
አስቀመጠው። 54ዕለቱ የመዘጋጃ ቀን
ነበረ፤ ሰንበትም ሊገባ ነበር።
55ከገሊላ ጀምሮ ከኢየሱስ ጋር የመጠ
-ት ሴቶችም ተከትለው መቃብሩን አዩ፤
ሥጋ ውንም እንዴት እንዳስቀመጡት
ተመለከቱ። 56ከዚያም ተመልሰው ሽቱና
ቅባት አዘጋጁ፤
ሕጉ በሚያዘው መሠረት በሰንበት ቀን
ዐረፉ።

## የኢየሱስ ትንሣኤ

24፥1-10 ተጓ ምብ – ማቴ 28፥1-8፤ ማር 16፥1-8፤ ዮሐ 20፥1-8

24 በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ሴቶቹ
ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው እጅግ
ማለዳ ሳለ ወደ መቃብሩ ሄዱ። 2ድንጋዩም
ከመቃብሩ ደጃፍ ተንከባሎ አገኙት፤ 3ወደ
ውስጥ ዘልቀው በገቡ ጊዜ ግን የጌታ ኢየ
ሱስን ሥጋ አላገኙም። 4በሁኔታው ግራ
ተጋብተው ሳሉ፣ እነሆ፤ እጅግ የሚያን

23፥45 ዘፀ26፥31-33፤ዕብ9፥3፡8፤10፥9፡20
23፥46 መዝ31፥5፤ ማቴ27፥50፤ ዮሐ19፥30፤ 1ጴጥ2፥23
23፥47 ማቴ9፥8
23፥48 ሉቃ18፥13
23፥49 መዝ38፥11፤ ሉቃ8፥2
23፥51 ሉቃ2፥25፡38
23፥54 ማቴ27፥62
23፥55 ቁ.40
23፥56 ዘፀ12፥16፤ 20፥10፤ ማር16፥1፤ ሉቃ24፥1
24፥1 ሉቃ23፥56
24፥3 ቁ.23፡24
24፥4 ዮሐ 20፥12
24፥6 ማቴ17፥22፡23፤ ሉቃ9፥22፤24፥24
24፥7 ማቴ8፥20፤ 16፥21
24፥8 ዮሐ2፥22
24፥10 ማር6፥30፤ ሉቃ8፥1-3
24፥11 ማር16፥11
24፥12 ዮሐ20፥3-7፡10
24፥13 ማር16፥12
24፥15 ቁ.36
24፥16 ዮሐ20፥14፤ 21፥4
24፥18 ዮሐ19፥25
24፥19 ማቴ21፥11፤ ማር1፥24
24፥20 ሉቃ23፥13
24፥21 ማቴ16፥21፤ ሉቃ 1፥68፤2፥38፤21፥28
24፥22 ቁ.1-10

ጸባርቅ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች ድን
ገት አጠገባቸው ቆሙ። 5ሴቶቹም ከመፍ
ራታቸው የተነሣ ወደ ምድር አቀርቅረው
ሳሉ፣ ሰዎቹ እንዲህ አሏቸው፤ “ሕያው
የሆነውን እርሱን ለምን ከሙታን መካከል
ትፈልጋላችሁ? 6እርሱ ተነሥቶአል! እዚህ
የለም፤ ደግሞም በገሊላ በነበረ ጊዜ ምን
እንዳላችሁ አስታውሱ፤ 7‘የሰው ልጅ
በኀጢአተኞች እጅ አልፎ ሊሰጥ፣ ሊሰቀልና
በሦስተኛውም ቀን ሊነሣ ይገባል’ ብሎ
ነበርና።” 8ሴቶቹም በዚህ ጊዜ ቃሉን
አስታወሱ።
9ሴቶቹ ከመቃብሩ ስፍራ ተመልሰው
ይህን ሁሉ ነገር ለዐሥራ አንዱና ለተቀሩት
ሁሉ ነገሯቸው። 10ይህን ለሐዋርያት የነገ
ሯቸውም፣ መግደላዊት ማርያም፣ ዮሐና፣
የያዕቆብ እናት ማርያምና ከእነርሱ ጋር የነ
በሩት ሌሎች ሴቶች ነበሩ። 11እነርሱ ግን
ሴቶቹ የተናገሩት ቃል መቀባዠር ስለ
መሰላቸው አላመኗቸውም። 12ጴጥሮስ ግን
ተነሥቶ ወደ መቃብሩ ሮጠ፤ እዚያ ደር
ሶም ጐንበስ ብሎ ወደ ውስጥ ሲመ
ለከት፣ በፍታው እንዳለ ለብቻው ተቀ
ምጦ አየ፤ በሆነውም ነገር እየተገረመ
ወደ ቤቱ ተመለሰ።

## በኤማሁስ መንገድ ላይ

13በዚሁ ቀን ከደቀ መዛሙርት ሁለቱ፣
ከኢየሩሳሌም ዐሥራ አንድ ኪሎ ሜትር[ጠ]
ያህል ወደሚርቅ፣ ኤማሁስ ወደሚባል
መንደር ይሄዱ ነበር፤ 14እነርሱም ስለ
ሆነው ነገር ሁሉ እርስ በርስ ይነጋገሩ
ነበር። 15እየተነጋገሩና እየተወያዩ ሳሉም
ኢየሱስ ራሱ ቀርቦ ከእነርሱ ጋር ይሄድ
ጀመር፤ 16ነገር ግን እንዳያውቁት ዐይ
ናቸው ተይዞ ነበር።
17እርሱም፣ “እየሄዳችሁ፣ መንገድ ላይ
እርስ በርስ እንዲህ የምትወያዩት ምን
ድን ነው?” አላቸው።
እነርሱም በሐዘን ክው ብለው ቆሙ።
18ከእነርሱም አንዱ፣ ቀለዮጳ የተባለው፣
“በእነዚህ ቀናት እዚህ በኢየሩሳሌም የሆ
ነውን ነገር የማታውቅ፣ አንተ ብቻ ለአ
ገሩ እንግዳ ነህን?” ሲል መለሰለት።
19እርሱም፣ “የሆነው ነገር ምንድን
ነው?” አላቸው።
እነርሱም እንዲህ አሉት፤ “በእግዚአብሐ
-ርና በሰው ሁሉ ፊት በተግባርና በቃል
ብርቱ ነቢይ ስለ ነበረው ስለ ናዝሬቱ ኢ
የሱስ ነው፤ 20እርሱን የካህናት አለቆችና
ገዦቻ ችን ለሞት ፍርድ አሳልፈው ሰጡ
-ት፤ ሰቀ ሉትም። 21እኛ ግን እስራኤልን
ይቤዠል

[ጠ]13 ግሪኩ ሥልሳ ምዕራፍ ይላል

ብለን ተስፋ ያደረግነው እርሱን ነበር፤
ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ ይህ ከሆነ ዛሬ
ሦስተኛው ቀን ነው። 22ደግሞም ከእኛው
መካከል አንዳንድ ሴቶች አስገረሙን፤ እነ
ርሱም ማልደው ወደ መቃብሩ ሄደው
ነበር፤ 23ሥጋውንም ባጡ ጊዜ መጥተው
እርሱ በሕይወት እንዳለ የነገሯቸውን መላ
እክት በራእይ እንዳዩ አወሩልን። 24ከእ
ኛም መካከል አንዳንዶች ወደ መቃብሩ
ሄደው፣ ልክ ሴቶቹ እንዳሉት ሆኖ አገ
ኙት፤ እርሱን ግን አላዩትም።”

25እርሱም እንዲህ አላቸው፤ “እናንተ የማ
ታስተውሉ ሰዎች፣ ልባችሁም ነቢያት
የተናገሩትን ሁሉ ከማመን የዘገየ፣ 26ክር
ስቶስጪ ይህን መከራ መቀበልና ወደ
ክብሩም መግባት አይገባውምን?” 27ከሙ
ሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ በቅዱሳት
መጻሕፍት ስለ እርሱ የተጻፈውን አስረዳ
ቸው።

28ወደሚሄዱበትም መንደር በተቃረቡ
ጊዜ፣ ኢየሱስ አልፎ የሚሄድ መሰለ።
29እነርሱ ግን፣ “ምሽት እየተቃረበ፣ ቀኑም
እየመሸ ስለ ሆነ ከእኛ ጋር እደር” ብለው
አጥብቀው ለመኑት፤ ስለዚህ ከእነርሱ
ጋር ለማደር ገባ።

30አብሮአቸውም በማእድ በተቀመጠ ጊዜ
እንጀራውን አንሥቶ ባረከ፤ ቈርሶም ሰጣ
ቸው። 31በዚህ ጊዜ ዐይናቸው ተከ
ፈተ፤ ዐወቁትም፤ እርሱም ከእነርሱ ተሰ
ወረ። 32እነርሱም፣ “በመንገድ ሳለን፣
እያነጋገረን ቅዱሳት መጻሕፍትንም ገልጦ
ሲያስረዳን፣ ልባችን እንደ እሳት ይቃጠል
ብን አልነበረምን?” ተባባሉ።

33በዚያኑም ሰዓት ተነሥተው ወደ ኢየሩ
ሳሌም ተመለሱ፤ ዐሥራ አንዱና ከእነርሱ
ጋር የነበሩትም በዚያ በአንድነት ተሰብ
ስበው አገኟቸው፤ 34“እነርሱም ጌታ በእ
ርግጥ ተነሥቶአል! ለስምዖንም ታይቶ
አል” ይባባሉ ነበር። 35ሁለቱ ደቀ መዛሙ
ርትም በመንገድ ላይ የሆነውንና ኢየሱስ
እንጀራውን በቈረሰ ጊዜ እንዴት እንዳ
ወቁት ተረኩላቸው።

## ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርት ተገለጠ

36ይህን እየተነጋገሩ ሳሉ፣ ኢየሱስ ራሱ

24፥24 ቍ12
24፥26 ዕብ2፥10፤
1ጴጥ1፥11
24፥27 ዘፍ3፥15፤
ዘኍ21፥9፤
ዘዳ18፥15፤
ኢሳ7፥14፤9፥6፤
40፥10፥11፥53፤
ሕዝ34፥23፤
ዳን9፥24፤ ክ7፥20፤
ሚል3፥1፤ ዮሐ1፥45
24፥30 ማቴ14፥19
24፥31 ቍ16
24፥32 ቍ27፥45፤
መዝ39፥3
24፥34 ሉቃ7፥13፤
1ቆሮ15፥5
24፥35 ቍ30፥31
24፥36 ዮሐ20፥19፥
21፥26፤14፥27
24፥37 ማር6፥49
24፥39 ዮሐ20፥27፤
1ዮሐ20፥27፤1ዮሐ1፥
1
24፥43 ሐሥ10፥41
24፥44 ቍ27፤
መዝ2፥16፤22፤69፤72
፤110፤118፤
ማቴ1፥22፤
16፥21፤ሉቃ9፥22፥44፥
45፤18፥31-34፤22፥37
24፥46 ማቴ16፥21
24፥47 ኢሳ2፥3፤
ማቴ28፥19፤
ማር13፥10፤ሐ
ሥ5፥31፤
10፥43፤13፥38
24፥48 ዮሐ15፥
27፤ ሐሥ1፥8፤
2፥32፤4፥20፤5፥32፤13፥
31፤1ጴጥ5፥1
24፥49 ዮሐ14፥
16፤ሐሥ1፥4
24፥50 ማቴ21፥17
24፥51 2ነገ2፥11
24፥53 ሐሥ2፥46

በመካከላቸው ቆሞ፣ “ሰላም ለእናንተ
ይሁን” አላቸው።

37እነርሱ ግን ደንግጠው በፍርሀት ተዋጠ
፤ መንፈስም ያዩ መሰላቸው። 38እርሱም
እን ዲህ አላቸው፤ “ለምን ትጨነቃላችሁ?
ለም ንስ ጥርጣሬ በልባችሁ ይገባል? 39እጆ
ቼንና እግሮቼን ተመልከቱ፤ እኔው ራሴ
ነኝ። ደግሞም ንኩኝና እዩ፤ በእኔ እን
ደምታዩት መንፈስ ሥጋና ዐጥንት የለ
ውምና።”

40ይህንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳ
ያቸው። 41እነርሱም ከመደሰትና ከመገ
ረም የተነሣ ገና ሳያምኑ፣ “በዚያ ቦታ
አንዳች የሚበላ ነገር አላችሁን?” አላቸው።
42እነርሱም ከተጠበሰ ዓሣ አንድ ቁራሽ
ሰጡት፤ 43እርሱም ተቀብሎ በፊታቸው
በላ።

44እርሱም፣ “ከእናንተ ጋር በነበርሁ
በት ጊዜ፣ ‘በሙሴ ሕግ፣ በነቢያትና በመ
ዝሙር መጻሕፍት ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ
ይፈጸም ዘንድ ይገባል’ ብዬ የነገርኋችሁ
ቃሌ ይህ ነው” አላቸው።

45በዚህ ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲ
ያስተውሉ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፤ 46እን
ዲህም አላቸው፤ “ ‘እንዲህ ተብሎ ተጽፎ
አል፤ ክርስቶስ መከራን ይቀበላል፤ በሦስ
ተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፤ 47ከኢየሩ
ሳሌም ጀምሮ ለሕዝቦች ሁሉ ንስሓና የኀጢ
አት ስርየት በስሙ ይሰበካል፤’ 48እናን
ተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ። 49እኔም
አባቴ የሰጠውን ተስፋ እልክላችኋለሁ፤
እናንተ ግን ከላይ ኀይል እስክትለብሱ
ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቈዩ።”

## የኢየሱስ ዕርገት

50ከዚህ በኋላ እስከ ቢታንያ ይዞአቸው
ወጣ፤ እጆቹንም አንሥቶ ባረካቸው።
51እየባረካቸውም ሳለ፣ ከእነርሱ ተለይቶ
ወደ ሰማይ ዐረገ። 52እነርሱም ሰገዱለት፤
በታላቅ ደስታም ወደ ኢየሩሳሌም ተመ
ለሱ፤ 53እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ ዘወትር
በቤተ መቅደስ ነበሩ።

ጪ26 ወይም መሲሕ እንዲሁም ቍ 46 ይመ

# የዮሐንስ ወንጌል

## ቃል ሥጋ ሆነ

1 በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም ከእግ
ዚአብሔር ጋር ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሐ
ͅር ነበረ። 2እርሱም በመጀመሪያ ከእግዚ
አብሔር ጋር ነበረ።
3ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሮአል፤ ከተ
ፈጠረው ሁሉ ያለ እርሱ የተፈጠረ ምንም
የለም። 4ሕይወት በእርሱ ነበረች፤ ይህች ሕይ
ወት የሰው ብርሃን ነበረች። 5ብርሃንም
በጨ ለማ ያበራል፤ ጨለማውም
አላሸነፈውም።[ሀ]
6ከእግዚአብሔር የተላከ ዮሐንስ የተባለ
አንድ ሰው ነበረ። 7ሰዎች ሁሉ በእርሱ
በኩል እንዲያምኑ፣ ስለ ብርሃን ምስክር
ሆኖ ለመቆም መጣ፤ 8ስለ ብርሃን ሊ
መሰክር መጣ እንጂ እርሱ ራሱ ብርሃን
አልነበረም። 9ለሰው ሁሉ ብርሃን ሰጪ
የሆነው እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም
እየመጣ ነበር።[ለ]
10እርሱ በዓለም ውስጥ ነበረ፤ ዓለም
የተፈጠረው በእርሱ ቢሆንም እንኳ፣ ዓለም
አላወቀውም። 11ወደ ራሱ ወገኖች መጣ፤
የገዛ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም፤ 12ለተቀ
በሉትና በስሙ ላመኑት ሁሉ ግን የእግዚ
አብሔር ልጆች የመሆን መብት ሰጣቸው።
13እነዚህም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ፣
ከደም[ሐ] ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወ
ንድ ፈቃድ አልተወለዱም።
14ቃልም ሥጋ ሆነ፤ በመካከላችንም
አደረ፤ እኛም ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ
ከአባቱ ዘንድ የመጣውን የአንድያ[መ]
ልጅን ክብር አየን።
15ዮሐንስም፣ "'ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ
በፊት ስለ ነበረ ከእኔ ይልቃል' ብዬ
የመሰከርሁለት እርሱ ነው" በማለት ጮኾ
ስለ እርሱ መሰከረ። 16ከእርሱ ሙላት
ሁላችንም በጸጋ ላይ ጸጋ ተቀብለናል፤
17ሕግ በሙሴ በኩል ተሰጥቶ ነበር፤ ጸጋና
እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል
መጣ።
18ከቶውንም እግዚአብሔርን ያየ ማንም
የለም፤ ነገር ግን በአብ እቅፍ ያለው
አንድያ ልጁ[ሠ]
የሆነው አምላክ እርሱ ገለጠው።

## መጥምቁ ዮሐንስ ራሱ ክርስቶስ እንዳልሆነ ተናገረ

19አይሁድ፣ ማንነቱን እንዲጠይቁት
ካህናትንና ሌዋውያንን ከኢየሩሳሌም ወደ
እርሱ ሲልኩ፣ ዮሐንስ የሰጠው ምስክርነት
ይህ ነበር።
20ከመመስከርም ወደ ኋላ አላለም፤ "እኔ
ክርስቶሱ[ረ] አይደለሁም" ብሎ በግልጽ መሰከረ።
21እነርሱም፣ "ታዲያ አንተ ማን ነህ? ኤልያስ
ነህ?" ብለው ጠየቁት።
እርሱም፣ "አይደለሁም" አለ።
እነርሱም፣ "ታዲያ ነቢዩ ነህ?"
አሉት።
እርሱም፣ "አይደለሁም" ሲል መለሰ።
22በመጨረሻም፣ "እንግዲያስ ማን ነህ?
ለላኩን ሰዎች መልስ እንድንሰጥ ስለ ራስህ
ምን ትላለህ?" አሉት።
23ዮሐንስም በነቢዩ በኢሳይያስ እንደተነ
ገረው፣ "'ለጌታ መንገድ አቅኑለት' እያለ
በምድረ በዳ የሚጮኽ ድምፅ እኔ ነኝ" ሲል
መለሰ።
24ከተላኩትም ፈሪሳውያን አንዳንዶቹ፣
25"ታዲያ፣ ክርስቶስ ወይም ኤልያስ ወይም
ነቢዩ ካልሆንህ፤ ለምን ታጠምቃለህ?" ብለው
ጠየቁት።
26ዮሐንስም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፤
"እኔ በውሃ[ሰ] አጠምቃለሁ፤ እናንተ የማታ
ውቁት ግን በመካከላችሁ ቆሟል፤ 27ከእኔ
በኋላ የሚመጣው፣ የጫማውን ማሰሪያ ለመ
ፍታት እንኳ የማልበቃ እርሱ ነው።"
28ይህ ሁሉ የሆነው ዮሐንስ ሲያጠምቅ
በነበረበት ከዮርዳኖስ ማዶ በቢታንያ ነበር።

## የእግዚአብሔር በግ

29ዮሐንስ በማግሥቱ፣ ኢየሱስ ወደ እርሱ
ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፤ "እነሆ! የዓ
ለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር
በግ፤ 30'ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ በፊት
ስለ ነበር ከእኔ ይልቃል" ያልሁት እርሱ ነው፤
31እኔ ራሴ አላወቅሁትም ነበር፤ በውሃ እያጠ
መቅሁ የመጣሁትም እርሱ በእስራኤል
ዘንድ እንዲገለጥ ነው።"
32ከዚያም ዮሐንስ እንዲህ ሲል ምስክር
ነቱን ሰጠ፤ "መንፈስ እንደ ርግብ ከሰማይ

1፥1 ኢሳ55፥11፤ ዮሐ17፥5፤ፊል2፥6፤ 1ዮሐ1፥2፤ራእ19፥13
1፥2 ዘፍ1፥1፤ ዮሐ 8፥58፤17፥5:24፤ 1ዮሐ1፥1፤ራእ1፥8
1፥3 ቀኍ10፤1ቆሮ 8፥6፤ቈላ1፥16፤ ዕብ1፥2
1፥4 መዝ36፥9፤ ዮሐ3፥19፤5፥26፤6፥57፤8፥12፤ 9፥5፤ 11፥25፤ 12፥46፤ ሐሥ 3፥15፤ ዕብ 7፥16፤ 1ዮሐ1፥1:2፤ 5፥20፤ራእ 1፥18፤
1፥5 መዝ18፥28፤ ዮሐ3፥19
1፥6 ማቴ3፥1
1፥7 ቀኍ12:15:19:32 ዮሐ 3፥15:26፤ 5፥33
1፥9 ኢሳ49፥6፤ 1ዮሐ 2፥8
1፥10 ቀኍ 3
1፥11 ኢሳ53፥3
1፥12 ቀኍ7፤ዘዳ 14፥1፤ዮሐ3፥15፤ ሮሜ8፥14:21፤ ኤፌ 5፥1፤1ዮሐ3፥1:2፤ 3፥23
1፥13 ዮሐ3፥6፤ ቲቶ3፥5፤1ጴጥ1፥23 ፤1ዮሐ3፥9፤4፥7፤ 5፥1:4፤ ያዕ1፥18
1፥14 ዘፀ 33፥18፤40፥34፤ ማቴ3፥11፤ ዮሐ14፥6፤ ሮሜ3፥24፤ ገላ4፥4፤ፊል2፥7:8፤ 1ጢሞ3፥16፤ ዕብ2፥14፤ 1ዮሐ1፥1:2፤4፥2
1፥15 ቀኍ7:30፤ ማቴ3፥11
1፥16 ሮሜ3፥24፤ ኤፌ1፥23፤ ቈላ1፥19፤2፥9
1፥17 ቀኍ14፤ዘዳ 32፥46፤ዮሐ7፥19
1፥18 ዘፀ33፥20፤ ዮሐ3፥16:18፤6፥46፤ ቈላ1፥15፤1ጢሞ6፥16፤1ዮሐ4፥9:12
1፥19 ማቴ3፥1፤ ዮሐ2፥18፤ 5፥10:16፤6፥41:52፤7፥1፤ 10፥24
1፥20 ሉቃ3፥15:16፤ዮሐ3፥28
1፥21 ዘዳ18፥15፤ ማቴ11፥14
1፥23 ማቴ3፥1፤ ኢሳ 40፥3

1፥26 ማር1፥4 1፥27 ቀኍ15:30፤ማር1፥7
1፥28 ዮሐ3፥26፤ 10፥40 1፥29 ቀኍ36፤ ዘፍ22፥8፤ዮሐ3፥17፤ኢሳ53፥7፤1ጴጥ1፥19 ራእ5፥6፤13፥8
1፥30 ቀኍ15:27 1፥32 ማቴ3፥16

[ሀ]5 ወይም *ጨለማው ግን አላወቀውም*
[ለ]9 ወይም *ይህ ወደ ዓለም ለሚመጣ ሰው ብርሃን የሚሰጥ እውነተኛው ብርሃን ነበረ*
[ሐ]13 *ወይም ከሰው ውሳኔ*
[መ]14 ወይም አንድ ልጁ የሆነው
[ሠ]18 አንዳንድ ቅጆች *አንድ ልጁ* ይላሉ
[ረ]20 ወይም *መሲሕ* "ክርስቶስ" (በግሪኩ ቋንቋ እና "መሲሑ" በዕብራይስጡ ሁለቱም *የተቀባ* የሚል ትርጉም አላቸው፤ ቀኍ

25 *ይመ*::
[ሰ]26 ወይም *በውሃ ውስጥ ቍ* 31 እና 33 *ይመ*

ወርዶ በእርሱ ላይ ሲያርፍ አየሁ፤ 33በውሃ
እንዳጠምቅ የላከኝም፣ ‘በመንፈስ ቅዱስ
የሚያጠምቀው፣ መንፈስ ሲወርድና በርሱ
ላይ ሲያርፍ የምታየው እርሱ ነው’ ብሎ
እስከ ነገረኝ ድረስ እኔም አላወቅሁትም
ነበር፤ 34አይቻለሁ፣ እርሱ የእግዚአብሔር
ልጅ እንደ ሆነ እመሰክራለሁ::”

## የመጀመሪያዎቹ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት

1፥40-42 ተጓ ምብ - ማቴ 4፥18-22፤ ማር 1፥16-20፤
ሉቃ 5፥2-11

35በማግሥቱ፣ ዮሐንስ ከሁለቱ ደቀ
መዛሙርቱ ጋር እንደ ገና እዚያው ቦታ
ነበር፤ 36ኢየሱስንም በዚያ ሲያልፍ አይቶ፣
“እነሆ! የእግዚአብሔር በግ” አለ::
37ሁለቱ ደቀ መዛሙርትም ይህን ሲናገር
ሰምተው ኢየሱስን ተከተሉት:: 38ኢየሱስም
ዘወር ብሎ ሲከተሉት አየና፣ “ምን ትፈል
ጋላችሁ?” ብሎ ጠየቃቸው::
እነርሱም፣ “ረቢ፣ የት ትኖራለህ?” አሉት፤
‘ረቢ’ ማለት መምህር ማለት ነው::
39እርሱም፣ “ኑና እዩ” አላቸው::
ስለዚህ ሄደው የት እንደሚኖር አዩ፤ በዚ
ያም ዕለት አብረውት ዋሉ፤ ከቀኑም
ዐሥር ሰዓት ያህል ነበር::
40ዮሐንስ የተናገረውን ሰምተው፣ ኢ
የሱስን ከተከሉት ከሁለቱ አንዱ የስምዖን
ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ ነበር::
41እንድርያስ በመ ጀመሪያ ያደረገው
ወንድሙን ስምዖንን ፈልጎ፣ “መሲሑን
አገኘነው” ብሎ መንገር ነው፤ ‘መሲሕ’
ማለት ክርስቶስ ማለት ነው:: 42ወደ ኢ
የሱስም አመጣው::
ኢየሱስም ተመለከተውና፣ “አንተ የዮና
ልጅ ስምዖን ነህ፤ ኬፋ ተብለህ ትጠራለህ”
አለው፤ ‘ኬፋ’ ማለት ጴጥሮስ ማለት ነው::[ሸ]

## ኢየሱስ ፊልጶስንና ናትናኤልን ጠራቸው

43በማግሥቱ፣ ኢየሱስ ወደ ገሊላ ለመሄድ
ፈለገ፤ ፊልጶስንም አግኝቶ፣ “ተከተለኝ” አለው::
44ፊልጶስም እንደ እንድርያስና እንደ
ጴጥ ሮስ ሁሉ የቤተ ሳይዳ ከተማ ሰው
ነበረ:: 45ፊልጶስ ናትናኤልን አግኝቶ፣
“ሙሴ በሕግ መጻሕፍት፣ ነቢያትም ስለ
እርሱ የጻፉለትን የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱ
ኢየሱስን አግኝተነ ዋል” አለው::
46ናትናኤልም፣ “ከናዝሬት በጎ ነገር ሊወጣ
ይችላልን?” አለ::
ፊልጶስም፣ “መጥተህ እይ” አለው::
47ኢየሱስም፣ ናትናኤል ወደ እርሱ ሲ
መጣ አይቶ፣ “እነሆ፤ ተንኰል የሌለበት
እውነተኛ እስራኤላዊ” አለ::
48ናትናኤልም “እንዴት አወቅኸኝ?” ሲል
ጠየቀው::
ኢየሱስም፣ “ከበለስ ዛፍ ሥር ሳለህ፣ ገና
ፊሊጶስ ሳይጠራህ አየሁህ” ሲል መለሰለት::
49ናትናኤልም መልሶ፣ “ረቢ! አንተ
የእግዚ አብሔር ልጅ ነህ፤ አንተ የእስራኤል
ንጉሥ ነህ” አለ::
50ኢየሱስም፣ “ያመንኸው ከበለስ ዛፍ ሥር
አየሁህ ስላልሁህ ነውን?[ቀ] ገና ከዚህ የሚበ
ልጥ ነገር ታያለህ” አለው፤ 51ጨምሮም፣ “እውነት
እላችኋለሁ፣ ሰማይ ተከፍቶ፣ የእግዚአብሔርም
መላእክት በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ
ታያላችሁ” አለው::

## ኢየሱስ ውሃን የወይን ጠጅ አደረገ

2 በሦስተኛው ቀን፣ በገሊላ አውራጃ፣ በቃና
ከተማ ሰርግ ነበር፤ የኢየሱስም እናት
በዚያ ነበረች፤ 2ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱም ወደ
ሰርጉ ተጠርተው ነበር:: 3የወይን ጠጅ ባለቀ
ጊዜም የኢየሱስ እናት፣ “የወይን ጠጅ እኮ
አለቀባቸው” አለችው::
4ኢየሱስም፣ “አንቺ ሴት ሆይ፤ ምን አድርግ
ትይኛለሽ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም” አላት::
5እናቱም በዚያ የነበሩትን አገልጋዮች፣
“የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ” አለቻቸው::
6በአይሁድ የመንጻት ሥርዐት መሠረት፣
ከሰባ አምስት እስከ አንድ መቶ ዐሥራ
አምስት ሊትር የሚይዙ ከድንጋይ የተሠሩ
ስድስት ጋኖች[በ] በዚያ ነበሩ::
7ኢየሱስ አገልጋዮቹን፣ “ጋኖቹን ውሃ
ሙሏቸው” አላቸው፤ እነርሱም፣ ጋኖቹን እስከ
አፋቸው ሞሏቸው::
8እርሱም፣ “ከላዩ ቀድታችሁ ለድግሱ ኀላፊ
ስጡት” አላቸው::
እነርሱም እንዳዘዛቸው አደረጉ:: 9የድግሱ
ኀላፊም ወደ ወይን ጠጅ የተለወጠውን ውሃ
ቀመሰ፤ ሆኖም ከየት እንደ መጣ
አላወቀም፤ ውሃውን የቀዱት አገልጋዮች
ግን ያውቁ ነበር:: እርሱም ሙሽራውን
ለብቻው ጠርቶ፣ 10“ሰው ሁሉ በመጀመሪያ
የሚያቀርበው ጥሩ ውን የወይን ጠጅ ነው፤
እንግዶቹም ብዙ ከጠጡ በኋላ መናኛውን
የወይን ጠጅ ያቀርባል፤ አንተ ግን ጥሩ
ውን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቈይተሃል”
አለው::
11ኢየሱስም ይህን የታምራዊ ምልክቶቹ
መጀመሪያ በገሊላ አውራጃ በቃና ከተማ
አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ፤ ደቀ መዛሙር
ቱም በእርሱ አመኑ::

1፥33 ማር1፥4:8
1፥34 ቍ49፤ማቴ 4፥3
1፥35 ማቴ3፥1
1፥36 ቍ29
1፥38 ቍ49፤ ማቴ3፥7
1፥41 ዮሐ4፥25
1፥42 ዘፍ17፥5: 15፤32፥28፤ 35፥10፤ ማቴ16፥18
1፥43 ማቴ4፥19፤ 10፥3፤ዮሐ6፥5-7፤ 12፥21:22፤14፥8:9
1፥44 ማቴ11፥21
1፥45 ማር1፥24፤ ሉቃ3፥23፤ 24፥27፤ ዮሐ21፥2
1፥46 ዮሐ7፥41: 42:52
1፥47 መዝ32፥2፤ ሮሜ9፥4:6
1፥49 ቍ34:38፤ ዘፍ28፥12፤ማቴ2፥2፤ 4፥3፤23፥7፤27፥42፤ ዮሐ12፥13
1፥51 ማቴ3፥16፤ 8፥20
2፥1 ማቴ12፥46፤ ዮሐ4፥46፤21፥2
2፥4 ማቴ8፥29፤ ዮሐ19፥26፤ 26፥18
2፥5 ዘፍ41፥55
2፥6 ማር7፥3:4፤ ዮሐ3፥25
2፥9 ዮሐ 4፥46
2፥11 ቍ23፤ ዘፀ14፥31፤ ማቴ12፥38፤ ዮሐ1፥14፤3፥2፤ 4፥48፤6፥2:14:26: 30፤12፥37፤20፥30

[ሸ]42 *ኬፋ* የሚለው የአራማይክ ቃልና *ጴጥሮስ* የሚለው የግሪኩ ያል ትርጒም ዐለት ማለት ነው::
[ቀ]50 ወይም *ከበለስ ዛፍ ሥር አየሁህ ስላልሁህ አመንህ?*
[በ]6 በግሪኩ *ሁለት ወይም ሦስት እንስራ*

## ኢየሱስ ቤተ መቅደስን አጠራ

2፥14-16 ተጓ ምብ - ማቴ 21፥12፡13፤ ማር 11፥15-17፤
ሉቃ 19፥45፡46

12ከዚህ በኋላ ከእናቱ፣ ከወንድሞቹና ከደቀ
መዛሙርቱ ጋር ወደ ቅፍርናሆም ወረደ፤
በዚያም ጥቂት ቀን ተቀመጡ።
13የአይሁድ ፋሲካም እንደ ተቃረበ፣ ኢየ
ሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። 14በቤተ መቅ
ደሱ አደባባይ ከብቶችን፣ በጎችንና ርግቦችን
የሚሸጡ እንዲሁም ተቀምጠው የገንዘብ
ምንዛሪ የሚያከናውኑ ሰዎች አገኘ። 15የገመድ
ጅራፍ አበጅቶ በጎችንና ከብቶችን ሁሉ
ከቤተ መቅደሱ ግቢ አባረረ፤ የመንዛሪዎችን
ገንዘብ በተነ፤ ጠረጴዛቻቸውንም ገለበጠ።
16ርግብ ሻጮችንም፣ "እነዚህን ከዚህ አስወ
ጧቸው፤ የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታ
ድርጉት!" አላቸው።
17ደቀ መዛሙርቱም፣ "ለቤትህ ያለኝ ቅናት
ያቃጥለኛል" ተብሎ የተጻፈው ትዝ አላቸው።
18አይሁድም፣ "ይህን ሁሉ ለማድረግ
ሥል ጣን እንዳለህ የሚያረጋግጥ ምን
ታምራዊ ምልክት ታሳየናለህ?" አሉት።
19ኢየሱስም፣ "ይህን ቤተ መቅደስ አፍር
ሱት፤ እኔም በሦስት ቀን መልሼ አነሣዋለሁ"
ብሎ መለሰላቸው።
20አይሁድም፣ "ይህን ቤተ መቅደስ
ለመሥራት አርባ ስድስት ዓመት ፈጅቶአል፤
ታዲያ አንተ እንዴት በሦስት ቀን መልሰህ ታነ
ሣዋለህ?" አሉት። 21ቤተ መቅደስ ሲል
ግን፣ ስለ ገዛ ሰውነቱ መናገሩ ነበር። 22ከሙ
ታንም ከተነሣ በኋላ፣ ደቀ መዛሙርቱ ምን
እንደተናገረ አስታወሱ፤ መጻሕፍትንና
ኢየሱስ ያለውንም ቃል አመኑ።
23በፋሲካ በዓል በኢየሩሳሌም ሳለ፣ ብዙ
ሰዎች ያደረገውን ታምራት አይተው
በስሙ አመኑ፤† 24ኢየሱስ ግን ሰውን ሁሉ
ስለሚ ያውቅ፣ አይታመንባቸውም ነበር፤
25በሰው ውስጥ ያለውን ያውቅ ስለ ነበር፣
ማንም ስለ ሰው እንዲመሰክርለት
አላስፈለገውም።

## ኢየሱስ ኒቆዲሞስን አስተማረ

3 ከፈሪሳውያን ወገን፣ ከአይሁድ አለቆች
አንዱ የሆነ ኒቆዲሞስ የተባለ ሰው ነበረ፤
2በሌሊትም ወደ ኢየሱስ መጥቶ፣ "ረቢ፤ እግ
ዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ ሰው በቀር አንተ
የምታደርጋቸውን ታምራዊ ምልክቶች ማንም
ሊያደርግ ስለማይችል፣ ከእግዚአብሔር
ዘንድ የመጣህ መምህር እንደ ሆንህ
እናውቃለን" አለው።
3ኢየሱስም መልሶ፣ "እውነት እልሃለሁ፤
ማንም ዳግመኛ ካልተወለደ‡ በቀር የእግዚ
አብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም" አለው።
4ኒቆዲሞስም፣ "ሰው ከሸመገለ በኋላ እን
ዴት ሊወለድ ይችላል? ዳግመኛ እንዲ
ወለድ ተመልሶ ወደ እናቱ ማሕፀንስ ሊገባ
ይችላልን?" አለው።
5ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ "እውነት
እልሃለሁ፤ ማንም ከውሃና ከመንፈስ ካልተ
ወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ
አይችልም፤ 6ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤
ከመንፈስ የተወለደም መንፈስ ነው። 7'ዳግመኛ
መወለድ አለባችሁ' ስላልሁህ አትገረም፤ 8ነፋስ
ወደሚወደው ይነፍሳል፤ ድምፁንም ትሰ
ማለህ፤ ነገር ግን ከየት እንደ መጣ፣
ወዴት እንደሚሄድም አታውቅም፤
ከመንፈስም የተወለደ ሁሉ እንደዚሁ
ነው።"
9ኒቆዲሞስም፣ "ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?"
ሲል ጠየቀው።
10ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ "አንተ
የእስራኤል መምህር ሆነህ ሳለ እነዚህን
ነገሮች አታውቅምን? 11እውነት እልሃለሁ፤
የምናውቀውን እንናገራለን፤ ያየነውንም
እንመሰክራለን፤ እናንተ ግን ምስክርነታችንን
አትቀበሉም። 12ስለ ምድራዊው ነገር
ነግሬአችሁ ያላመናችሁ፣ ስለ ሰማያዊው
ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ?
13ከሰማይ ከወረደው ከሰው ልጅ በቀር፣
ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም።ˀ 14ሙሴ
በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ፣ የሰው
ልጅም እንዲሁ ሊሰቀል ይገባዋል፤ 15ይኸ
ውም በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም
ሕይወት እንዲኖረው ነው።
16"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይ
ወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር
አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን
እንዲሁ ወዶአልና፤ 17እግዚአብሔር ልጁን ወደ
ዓለም የላከው በዓለም ለመፍረድ ሳይሆን፣
ዓለምን በእርሱ ለማዳን ነው። 18በእርሱ
የሚያምን ሁሉ አይፈረድበትም፤ በእርሱ
የማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ
ስምʾ ስላላመነ፣ አሁኑኑ ተፈርዶበታል።
19ፍርዱም ይህ ነው፤ ብርሃን ወደ ዓለም
መጣ፤ ሰዎች ግን ሥራቸው ክፉ ስለ ነበረ፣
ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ወደዱ፤ 20ክፉ
የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላል፤ አድ
ራጎቱም እንዳይገለጥበት ወደ ብርሃን አይ
መጣም። 21በእውነት የሚመላለስ ግን
ሥራው በእግዚአብሔር የተሠራ መሆኑ በግል
ጽ

2፥12 ማቴ4፥13፤
12፥46
2፥13 ዘጸ16፥1-6፤
ሉቃ2፥41፤
ዮሐ11፥55
2፥14 ዘሌ1፥14፤
ዘዳ14፥25፡26
2፥16 ሉቃ2፥49
2፥17 መዝ69፥9
2፥18 ቊ11፤
ማቴ12፥38፤ዮሐ1፥19
2፥19 ማቴ16፥21፤
26፥61፤27፥40፤
ማር
14፥58፤15፥29፤
ሐሥ6፥14
2፥21 1ቆሮ6፥19
2፥22 መዝ16፥10፤
ሉቃ24፥5-
8፤24፥27፤
ዮሐ12፥16፤14፥26
2፥23 ቊ11፡13፤
ዮሐ3፥15
2፥25 ዘዳ31፥21፤
1ነገ8፥39፤ኢሳ11፥3፤
ማቴ9፥4፤ዮሐ6፥61፡
64፤13፥11
3፥1 ዮሐ7፥50፤
19፥39፤ሉቃ23፥13
3፥2 ቊ11፤
ሐሥ2፥22፤10፥38፤
ማቴ23፥7፤ዮሐ2፥11
፤10፥38፤14፥10፡11
3፥3 ማቴ3፥2፤
ዮሐ1፥13
3፥5 ሐሥ22፥16፤
ቲቶ3፥5
3፥6 ዮሐ1፥13፤
1ቆሮ15፥50
3፥8 1ቆሮ2፥14-16
3፥9 ዮሐ6፥52፡60
3፥10 ሉቃ2፥46
3፥11 ቊ32፤ዮሐ
1፥18፤7፥16፡17
3፥13 ቊ31፤ምሳ
30፥4፤ማቴ8፥20፤
ዮሐ6፥38፡42፤
ሐሥ2፥34፤
ኤፌ4፥8-10፤ዕብ
4፥14፤ 9፥24
3፥14 ዘኊ21፥8፡9፤
ዮሐ12፥32
3፥15 ቊ16፡36፤
ዘፍ15፥6፤ዘኊ14፥11
ማቴ25፥46፤27፥42፤
ማር1፥15፤ዮሐ1፥7፡
12፤2፥23፤5፥24፤7፥
38፤20፥29፤20፥31፤
ሐሥ13፥39፤16፥31፤
ሮሜ
3፥22፤10፥9፡10፤
1ዮሐ 5፥1፡5፡10
3፥16 ቊ15፡36፤
ዘፍ22፥12፤
ኢሳ9፥6፤
ዮሐ1፥18፤6፥29፡40፤
11፥25፡26፤ ሮሜ8፥
32፤5፥8፤ኤፌ2፥4፤
1ዮሐ4፥9፡10
3፥17 ኢሳ53፥11፤
ማቴ1፥21፤ሉቃ2፥11
፤19፥10፤ ዮሐ1፥29፤
6፥29፡57፤10፥36፤
11፥42፤12፥47፤
17፥ 8፡21፤ 20፥21፤ሮሜ11፥14፤1ጢሞ1፥15፤2፥5፡6፤1ዮሐ2፥2፤
3፥5 3፥18 ዮሐ1፥18፤ 5፥24፤1ዮሐ4፥9
3፥19 መዝ52፥3፤ ዮሐ1፥4፤ዮሐ7፥7 3፥20 ኤፌ5፥11፡ 13

†23 ወይም *በእርሱም አመኑ*
‡3 ወይም *ከላይ ካልተወለደ፤* ቊ 7 ይመ
ˀ13 ወይም *በሰማይ ካለው . . .*
ʾ18 ወይም *በእግዚአብሔር አንድያ ልጅ*

ይታይ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል::”[ኘ]

## መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ መሰከረ

22ከዚህ በኋላ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ
ወደ ይሁዳ አገር ሄዱ፤ እዚያም ከእነርሱ
ጋር ጥቂት ተቀመጠ፤ አጠመቀም::
23በዚህ ጊዜ ዮሐንስም በሳሌም አቅራቢያ
ሄኖን በተባለ ስፍራ ብዙ ውሃ ስለ ነበረ፣
ያጠምቅ ነበር፤ ሰዎችም ለመጠመቅ ይመጠ
ነበር:: 24ይህም የሆነው ዮሐንስ
ከመታሰሩ በፊት ነበር:: 25በአንዳንድ
የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና በአንድ
አይሁዳዊ[ኣ] መካከል ስለ መንጻት ሥርዐት
ክርክር ተነሣ፤ 26ወደ ዮሐንስም መጥተው፣
“ረቢ፤ በዮርዳኖስ ማዶ ከአንተ ጋር የነበረው፣
ስለ እርሱም የመሰከር ህለት ሰው፣ እነሆ
ያጠምቃል፤ ሰውም ሁሉ ወደ እርሱ
እየሄደ ነው” አሉት::
27ዮሐንስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “ከላይ
ካልተሰጠው በቀር ማንም አንዳች ሊቀበል
አይችልም:: 28‘እኔ ክርስቶስ[ከ]
አይደለሁም፤ ነገር ግን ከእርሱ በፊት
ተልኬአለሁ’ እን ዳልሁ እናንተ ራሳችሁ
ትመሰክራላችሁ:: 29ሙሽራዪቱ የሙሽራው
ነች፤ ድምፁን ለመ ስማት በአጠገቡ
የሚቆመው ሚዜ ግን፣ የሙ ሽራውን ድምፅ
ሲሰማ እጅግ ደስ ይለዋል፤ ያ ደስታ የእኔ
ነው፤ እርሱም አሁን ተፈጽሞአል:: 30እርሱ
ሊልቅ፣ እኔ ግን ላንስ ይገባል::
31“ከላይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው፤
ከምድር የሆነው የምድር ነው፤ የምድሩ
ንም ይናገራል:: ከሰማይ የሚመጣው ከሁሉ
በላይ ነው፤ 32ያየውንና የሰማውን ይመሰክራል፤
ነገር ግን ምስክርነቱን ማንም አይቀበልም፤
33ምስክርነቱንም የተቀበለ ሰው፣ እግዚአብሔር
እውነተኛ እንደ ሆነ አረጋገጠ:: 34እግዚአብሐ
ር[ኸ] መንፈሱን ሳይሰፍር ስለሚሰጥ፣ እግዚ
አብሔር የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራ
ል:: 35አብ ወልድን ይወዳል፤ ሁሉንም ነገር
በእጁ ሰጥቶታል:: 36በወልድ የሚያምን
ሁሉ የዘላለም ሕይወት አለው፤ በወልድ የ
ማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በላዩ
ይሆናል እንጂ
ሕይወትን አያይም::”[ወ]

## ኢየሱስ ከአንዲት ሳምራዊት ጋር ተነጋገረ

4 ፈሪሳውያን ከዮሐንስ ይልቅ ኢየሱስ ብዙ
ደቀ መዛሙርትን እንዳፈራና እንዳጠመቀ
ሰሙ፤ 2ዳሩ ግን ያጠመቀው ኢየሱስ ሳይሆን
ደቀ መዛሙርቱ ነበሩ:: 3ጌታም ይህን
እንዳወቀ ይሁዳን ለቆ ወደ ገሊላ ተመልሶ
ሄደ::
4በሰማርያም በኩል ማለፍ ነበረበት:: 5ስለ
ዚህ በሰማርያ፣ ያዕቆብ ለልጁ ለዮሴፍ

3፥22 ዮሐ4፥2
3፥23 ማቴ3፥1
3፥24 ማቴ4፥12፤ 14፥3
3፥25 ዮሐ2፥6
3፥26 ማቴ23፥7፤ ዮሐ1፥7
3፥28 ዮሐ1፥20:23
3፥29 ማቴ9፥15፤ ዮሐ16፥24፤17፥13፤ ፊል2፥2፤ 1ዮሐ1፥4፤ 2ዮሐ12
3፥31 ቍ13፤ ዮሐ8፥23፤1ዮሐ4፥5
3፥32 ቍ11፤ ዮሐ8፥26፤15፥15
3፥34 ቍ17፤ ኢሳ42፥1፤ማቴ 12፥18፤ሉቃ4፥18፤ ሐሥ 10፥38
3፥35 ማቴ28፥18
3፥36 ቍ15፤ ዮሐ5፥24፤6፥47
4፥1 ዮሐ3፥22:26
4፥3 ሉቃ7፥13፤ ዮሐ3፥22
4፥4 ማቴ10፥5
4፥5 ዘፍ33፥19፤ ኢሱ24፥32
4፥7 ዘፍ24፥17፤ 1ነገ17፥10
4፥8 ቍ5:39
4፥9 ማቴ10፥5
4፥10 ኢሳ44፥3፤ 55፥1፤ ኤር2፥13፤ 17፥13፤ ዘካ14፥8፤ ዮሐ7፥37:38፤ ራእ7፥17፤21፥6፤ 22፥1:17
4፥12 ቍ6
4፥14 ኢሳ12፥3፤ 58፥11፤ማቴ25፥46፤ ዮሐ6፥35፤7፥38
4፥15 ዮሐ6፥34
4፥19 ማቴ21፥11
4፥20 ዘዳ11፥29፤ ኢሱ8፥33፤ሉቃ9፥53

በሰጠው ቦታ አጠገብ ወደ ነበረች፣ ሲካር
ወደምትባል ከተማ መጣ:: 6በዚያም የያዕ
ቆብ የውሃ ጕድጓድ ነበረ፤ ኢየሱስም ከጕዞው
የተነሣ ደክሞት ስለ ነበር በውሃው ጕድ
ጓድ አጠገብ ተቀመጠ፤ ጊዜውም ከቀኑ ስድ
ስት ሰዓት አካባቢ ነበር::
7አንዲት ሳምራዊት ሴት ውሃ ለመቅዳት
ስትመጣ ኢየሱስ፣ “እባክሽ የምጠጣው ስጪኝ”
አላት፤ 8ደቀ መዛሙርቱ ምግብ
ለመግዛት ወደ ከተማ ሄደው ነበር::
9ሳምራዊቷም፣ “አንተ አይሁዳዊ ሆነህ፣
እኔን ሳምራዊቷን እንዴት ውሃ አጠጪኝ
ትላለህ?” አለችው፤ ይህን ማለቷ አይሁድ
ከሳምራውያን ጋር ስለማይተባበሩ ነው::[ዐ]
10ኢየሱስም፣ “የእግዚአብሔርን ስጦታ
ብታውቂና ውሃ አጠጪኝ የሚልሽ ማን
መሆኑን ብትረጂ ኖሮ፣ አንቺው በጠ
የቅሽው፣ እርሱም የሕይወትን ውሃ በሰጠሽ
ነበር” ሲል መለሰላት::
11ሴትዮዋም እንዲህ አለችው፤
“ጌታዬ፣ መቅጃ የለህም፤ ጕድጓዱም ጥልቅ
ነው፤ ታዲያ ይህን የሕይወት ውሃ ከየት
ታገኛለህ? 12ለመሆኑ አንተ፣ ይህን
ጕድጓድ ከሰጠን፣ ከአባታችን ከያዕቆብ
ትበልጣለህን? እርሱ ራሱና ልጆቹ፣
እንስሳቱም ከዚሁ ጕድጓድ
ጠጥተዋል::”
13ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላት፤ “ከዚህ
ውሃ የሚጠጣ እንደ ገና ይጠማል፤ 14እኔ
ከምሰጠው ውሃ የሚጠጣ ግን ከቶ አይጠ
ማም፤ እኔ የምሰጠው ውሃ በውስጡ የሚፈልቅ
የዘላለም ሕይወት ውሃ ምንጭ ይሆናል::”
15ሴትዮዋም፣ “ጌታዬ፤ እንዳልጠማና
ውሃ ለመቅዳት እንዳልመላለስ፣ እባክህ
ይህን ውሃ ስጠኝ” አለችው::
16እርሱም፣ “ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ወደ
ዚህ ተመለሽ” አላት::
17ሴትዮዋም፣ “ባል የለኝም” ብላ መለሰች::
ኢየሱስም፣ እንዲህ አላት፤ “ባል የለኝም
ማለትሽ ትክክል ነው፤ 18በእርግጥ አምስት
ባሎች ነበሩሽ፤ አሁን ከአንቺ ጋር ያለውም
ባልሽ ስላልሆነ፣ የተናገርሽው እውነት ነው::”
19ሴትዮዋም እንዲህ አለችው፤ “ጌታዬ፣ አንተ
ነቢይ እንደ ሆንህ አያለሁ፤ 20አባቶቻችን
በዚህ ተራራ ላይ ሰገዱ፤ እናንተ አይሁድ
ግን ሰው መስገድ ያለበት በኢየሩሳሌም
ነው ትላላችሁ” አላቸው::

[ኘ]21 አንዳንድ ተርጓሚዎች ትምህርተ ጥቅሱን ከቍጥር 15 በኋላ ያደርጋለ
[ኣ]25 አንዳንድ ቅጆች *አንዳንድ አይሁድ* ይላሉ
[ከ]28 ወይም *መሲሕ*
[ኸ]34 በግሪኩ *እርሱ* ይላል
[ወ]36 አንዳንድ ተርጓሚዎች ትምሕርተ ጥቅሱን ከ30 በኋላ ያደርጋሉ::
[ዐ]9 ወይም *ሳምራውያን በተጠቀሙበት ሰሕን/ዕቃ አይጠቀሙም ነበር*

21ኢየሱስም እንዲህ አላት፤ “አንቺ ሴት፤
በዚህ ተራራም ሆነ በኢየሩሳሌም ለአብ የማ
ትሰግዱበት ጊዜ እንደሚመጣ እመኚኝ።
22እናንተ ሳምራውያን ለማታውቁት ትሰግዳ
ላችሁ፤ እኛ ግን ድነት ከአይሁድ ስለ ሆነ
ለምናውቀው እንሰግዳለን። 23በእውነት
የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚ
ሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፤ አሁንም መጥቶአል፤
አብም እንደዚህ በእውነት የሚሰግዱለትን
ይፈልጋል። 24እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤
የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰ
ግዱለት ይገባል።”
25ሴትዮዋም፣ “ክርስቶስ የተባለ መሲሕ
እንደሚመጣ ዐውቃለሁ፤ እርሱ ሲመጣ
ሁሉን ነገር ይነግረናል” አለችው።
26ኢየሱስም፣ “የማነጋግርሽ እኮ እኔ
እርሱ ነኝ” ሲል ገለጠ ነገራት።

### ደቀ መዛሙርቱ ተመልሰው መጡ

27በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ተመልሰው
መጡ፤ ከሴት ጋር ሲነጋገር በማግኘታቸው
ተደነቁ፤ ሆኖም ግን፤ “ምን ፈለግህ?” ወይም፣
“ከእርሷ ጋር የምትነጋገረው ለምንድን ነው?”
ብሎ የጠየቀው ማንም አልነበረም።
28ሴትዮዋም እንስራዋን ትታ ወደ ከተማ
ተመለሰች፤ ለሕዝቡም፣ 29“ያደረግሁትን
ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑና እዩ፤ እርሱ
ክርስቶስ" ይሆን እንዴ?” አለች፤ 30እነርሱም
ከከተማ ወጥተው እርሱ ወዳለበት አመሩ።
31በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ፣ “ረቢ፣ እህል
ቅመስ እንጂ” አሉት።
32እርሱ ግን፣ “እናንተ የማታውቁት፣
የም በላው ምግብ አለኝ” አላቸው።
33ደቀ መዛሙርቱም፣ “ሰው ምግብ አምጥ
ቶለት ይሆን እንዴ?” ተባባሉ።
34ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “የእኔ ምግብ
የላከኝን ፈቃድ ማድረግና ሥራውን መፈ
ጸም ነው፤ 35እናንተ፣ ‘ከአራት ወር በኋላ
መከር ይደርሳል’ ትሉ የለምን? እነሆ፣ አዝ
መራው ለመከር እንደ ደረሰ ቀና ብላችሁ
ማሳውን ተመልከቱ እላችኋለሁ። 36አጫጁ
አሁንም ቢሆን እንኳ ደመወዙን የተቀበለ
ነው፤ ለዘላለም ሕይወት ይሆን ዘንድ አዝ
መራውን ይሰበስባል፤ ይህም ዘሪውና አጫጁ
በጋራ ደስ እንዲላቸው ነው። 37ስለዚህ፣ ‘አንዱ
ይዘራል፤ ሌላውም ያጭዳል’ የተባለው ምሳሌ
እውነት ነው። 38ያልደከማችሁበትን እንድታጭዱ
ላክኋችሁ፤ አድካሚውን ሥራ ሌሎች ሠሩ፤
እናንተም የድካማቸውን ፍሬ ሰበሰባችሁ።”

### ብዙ ሳምራውያን አመኑ

39ሴትዮዋ፣ “ያደረግሁትን ሁሉ ነገረኝ”
ብላ ስለ መሰከረች፣ ከዚያች ከተማ ብዙ
ሳምራውያን በእርሱ አመኑ። 40ስለዚህ፣ ሳምራ
ውያኑ ወደ እርሱ በመጡ ጊዜ አብሮአቸው
እንዲቈይ አጥብቀው ለመኑት፤ እዚያም
ሁለት ቀን ቈየ። 41ከቃሉም የተነሣ ሌሎች
ብዙዎች አመኑ።
42ሴትዮዋንም፣ “ከእንግዲህ የምናምነው
አንቺ ስለ ነገርሽን ብቻ አይደለም፤ እኛ ራ
ሳ ችን ሰምተነዋል፤ ይህ ሰው በእውነት የዓ
ለም አዳኝ እንደ ሆነ እናውቃለን” አሏት።

### ኢየሱስ የሹሙን ልጅ ፈወሰ

43ከሁለቱ ቀናት በኋላም ወደ ገሊላ
ሄደ፤ 44ነቢይ በገዛ አገሩ እንደማይከበር
ኢየሱስ ራሱ ተናግሮ ነበርና። 45ገሊላ እንደ
ደረሰም የገሊላ ሰዎች በደስታ ተቀበሉት፤
ምክንያ ቱም፣ እነርሱም በፋሲካ በዓል
ኢየሩሳሌም ስለ ነበሩና በዚያ ያደረገውን
ሁሉ ስላዩ ነው።
46ኢየሱስም ውሃውን የወይን ጠጅ
ወዳደረገበት፣ በገሊላ ወደምትገኘው ወደ ቃና
ከተማ ዳግመኛ መጣ፤ በቅፍርናሆምም ልጁ
የታመመበት አንድ የቤተ መንግሥት ሹም
ነበረ፤ 47ይህም ሰው ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ
ገሊላ መምጣቱን በሰማ ጊዜ፣ ወደ እርሱ
ሄደና በሞት አፋፍ ላይ የነበረውን ልጁን
መጥቶ እንዲፈውስለት ለመነው።
48ኢየሱስም፣ “መቼውንም እናንተ ምልክቶ
ችንና ድንቅ ነገሮችን ካላያችሁ አታምኑም”
አለው።
49ሹሙም፣ “ጌታዬ፤ ልጄ ከመሞቱ
በፊት እባክህ ድረስልኝ” አለው።
50ኢየሱስም፣ “ልጅህ በሕይወት ይኖራ
ልና ሂድ” አለው።
ሰውዬውም ኢየሱስ የተናገረውን ቃል
አምኖ ሄደ፤ 51በመንገድ ላይ እንዳለም፣ አገል
ጋዮቹ አግኝተውት ልጁ በሕይወት መኖሩን
ነገሩት። 52እርሱም ልጁ በስንት ሰዓት እንደ
ተሻለው ሲጠይቃቸው፣ “ትኩሳቱ የለቀቀው
ትናንት በሰባት ሰዓት ላይ ነው” አሉት።
53አባትዮውም ሰዓቱ ኢየሱስ፣ “ልጅህ በሕ
ይወት ይኖራል” ያለበት ሰዓት መሆኑን ተገ
ነዘበ፤ እርሱና ቤተ ሰቡም ሁሉ አመኑ።
54ይህም፣ ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ
መጥቶ ያደረገው ሁለተኛው ታምራዊ ምልክት
ነው።

### በቤተ ሳይዳ የተደረገው ፈውስ

5 ከዚህ በኋላ የአይሁድ በዓል ነበረ፤ ኢየሱ
ስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። 2በኢየሩ
ሳሌም፣ በበጎች በር አጠገብ፣ አምስት

"29 ወይም መሲሕ

4፥21 ሚል1፥11፤ ዮሐ5፥28፤16፥2፤ 1ጢሞ 2፥8
4፥22 2ነገ17፥28-41፤ኢሳ2፥3፤ ሮሜ3፥1፡2፤9፥4፡5፤ 15፥8፡9
4፥23 ዮሐ5፥25፤ 16፥32፤ፊል3፥3
4፥24 ፊል3፥3
4፥25 ማቴ1፥16፤ ዮሐ1፥41
4፥26 ዮሐ8፥24፤ 9፥35-37
4፥27 ቍ8
4፥29 ቍ17፡18፤ ማቴ12፥23፤ ዮሐ7፥26፡31
4፥31 ማቴ23፥7
4፥32 ኢዮ23፥12፤ ማቴ4፥4፤ዮሐ 6፥27
4፥34 ማቴ26፥39፤ ዮሐ19፥30
4፥35 ማቴ9፥37፤ ሉቃ10፥2
4፥36 ማቴ25፥46፤ ሮሜ1፥13
4፥37 ኢዮ31፥8፤ ሚክ6፥15
4፥39 ቍ5፡29
4፥42 ሉቃ2፥11
4፥43 ቍ40
4፥44 ማቴ13፥57፤ ሉቃ4፥24
4፥45 ዮሐ2፥23
4፥46 ዮሐ2፥1-11
4፥47 ቍ3፡54
4፥48 ዳን4፥2፡3፤ ዮሐ2፥11፤ሐሥ2፥43፤14፥3፤ሮሜ15፥19፤2ቆሮ12፥12፤ ዕብ2፥4
4፥53 ሐሥ11፥14
4፥54 ቍ48፤ ዮሐ 2፥11
5፥2 ነህ3፥1፤ 12፥39፤ዮሐ19፥13፡17፡20፤20፥16፤ ሐሥ21፥40፤22፥2፤ 26፥14

ባለ መጠለያ መመላለሻዎች የነበሯት፣ በአ
ራማይክ ቋንቋ ቤተ ሳይዳ[ሠ] የተባለች አን
ዲት መጠመቂያ አለች። 3በእነዚህም መመ
ላለሻዎች ውስጥ ብዙ አካለ ስንኩላን፣ ዐይነ
ስውሮች፣ አንካሶችና ሽባዎች [የውሃውን
መንቀሳቀስ እየተጠባበቁ፣ ይተኙ ነበር።
4ዐልፎ ዐልፎ የጌታ መልአክ ወርዶ ውሃ
ውን በሚያናውጥበት ጊዜ፣ ቀድሞ ወደ
መጠመቂያዪቱ የገባ ካደረበት ማንኛውም
በሽታ ይፈወስ ነበር።][የ] 5በዚያም ለሠላሳ
ስምንት ዓመት ሕመምተኛ ሆኖ የኖረ አንድ
ሰው ነበር። 6ኢየሱስም ይህን ሰው ተኝቶ
ባገኘው ጊዜ፣ ለብዙ ጊዜ በዚህ ሁኔታ እንደ
ነበር ዐውቆ "ልትድን ትፈልጋለህን?" አለው።
7ሕመምተኛውም መልሶ፣ "ጌታዬ፣ ውሃው
በሚናወጥበት ጊዜ ወደ መጠመቂያዪቱ
የሚያወርደኝ ሰው የለኝም፤ ለመግባትም
ስሞክር ሌላው ይቀድመኛል" አለው።
8ኢየሱስም፣ "ተነሥ! መተኛህን ተሸክመህ
ሂድ" አለው። 9ሰውዬውም ወዲያው
ተፈወሰ፤ መተኛውንም ተሸክሞ ሄደ።
ይህም የሆነው በሰንበት ቀን ነበር። 10አይ
ሁድም የተፈወሰውን ሰው፣ "ሰንበት ስለ
ሆነ መተኛህን እንድትሸከም ሕጉ አይፈቀ
ድልህም" አሉት።
11እርሱ ግን፣ "ያ የፈወሰኝ ሰው፣ 'መተ
ኛህን ተሸክመህ ሂድ' ብሎኛል" ሲል መለሰላቸው።
12እነርሱም፣ "'መተኛህን ተሸክመህ ሂድ'
ያለህ እርሱ ማነው?" ብለው ጠየቁት።
13ኢየሱስ ፈቀቅ ብሎ ወደ ሕዝብ
መካከል ገብቶ ስለ ነበር፣ ሰውዬው ማን እንደ
ፈወሰው አላወቀም።
14ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ያን ሰው በቤተ
መቅደስ አግኝቶ፣ "እነሆ፣ ተፈውሰሃል፤ ከእ
ንግዲህ ግን ኀጢአት አትሥራ፤ ያለዚያ ከዚህ
የባሰ ይደርስብሃል" አለው። 15ሰውዬውም
የፈወሰው ኢየሱስ መሆኑን ሄዶ ለአይሁድ
ነገራቸው።

## ወልድ ሕይወትን ይሰጣል

16አይሁድም፣ በሰንበት ቀን እነዚህን
ድርጊቶች በመፈጸሙ፣ ኢየሱስን ያሳድዱት
ነበር። 17ኢየሱስም፣ "አባቴ እስካሁን እየሠራ
ነው፤ እኔም ደግሞ እሠራለሁ" አላቸው።
18እን ግዲህ አይሁድ፣ ኢየሱስ ሰንበትን
ስለ ሻረ ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔርን አባቱ በ
ማድረግ፣ ራሱን ከእግዚአብሔር እኩል በ
ማድረጉ፣ ሊገድሉት አጥብቀው ይፈልጉት
ነበር።
19ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"እውነት እላችኋለሁ፤ አብ ሲሠራ ያየውን
ብቻ እንጂ ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ

5÷8 ማቴ9÷5፡6
5÷9 ማቴ12÷1-14፤ ዮሐ9÷14
5÷10 ቁ16፤ነህ 13÷15-22፤ኤር17÷21፤ማቴ12÷2
5÷14 ማር2÷5፤ ዮሐ8÷11
5÷15 ዮሐ1÷19
5÷17 ሉቃ2÷49፤ ዮሐ9÷4፤14÷10
5÷18 ማቴ12÷14፤ ዮሐ10÷30፡33፤19÷7
5÷19 ቁ30፤ ዮሐ 14÷24
5÷20 ዮሐ3÷35፤ 14÷12
5÷21 ዮሐ11÷25 ሮሜ4÷17፤8÷11፤ 2ቆሮ1÷9፤ዕብ11÷19
5÷22 ቁ27፤ ዘፍ18÷25፤መሳ11÷27፤ ዮሐ9÷39፤ ሐሥ10÷42
5÷23 ሉቃ10÷16፤ 1ዮሐ2÷23
5÷24 ማቴ10÷40፤ 25÷46፤ዮሐ3÷15፡17 ፤3÷18፤1ዮሐ3÷14
5÷25 ዮሐ4÷23፤ 8÷43፡47፤16÷32
5÷26 ዘጸ30÷20፤ ኢዮ10÷12፤33÷4፤ መዝ36÷9፤ዮሐ1÷4
5÷27 ቁ22
5÷28 ዮሐ4÷21፤ 16÷2
5÷29 ማቴ25÷46
5÷30 ቁ19፤ማቴ 26÷39፤ኢሳ28÷6፤ ዮሐ8÷16
5÷31 ዮሐ8÷14
5÷32 ቁ37፤ ዮሐ 8÷18
5÷33 ዮሐ1÷7
5÷34 ሐሥ16÷30፡ 31፤ኤፌ2÷8፤ ቲቶ3÷5፤1ዮሐ5÷9
5÷35 ዳን12÷3፤ 2ጴጥ1÷19
5÷36 ዮሐ3÷17፤ 14÷11፤15÷24፤ 1ዮሐ 5÷9
5÷37 ዘጸ4÷12፤ ዮሐ1÷18፤8÷18፤ 1ጢሞ1÷17

አይችልም፤ አብ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ
ደግሞ ያደርጋልና፤ 20አብ ወልድን ስለ
ሚወድ የሚያደርገውን ሁሉ ያሳየዋል፤
ትደነቁም ዘንድ ከእነዚህም የሚበልጥ ነገር
ያሳየዋል። 21ምክንያቱም አብ ሙታንን እን
ደሚያስነሣ፣ ሕይወትንም እንደሚሰጥ፣
ወልድም ደግሞ ለሚፈቅደው ሁሉ ሕ
ይወትን ይሰጣል። 22አብ በማንም ላይ
አይፈርድም፤ ነገር ግን ፍርድን ሁሉ ለወልድ
አሳልፎ ሰጥቶ ታል፤ 23ይኸውም፣ ሁሉ አብን
እንደሚያ ከብሩ ወልድን ያከብሩት ዘንድ
ነው፤ ወል ድን የማያከብር፣ የላከውን
አብንም አያ ከብርም።
24"እውነት እላችኋለሁ፤ ቃሌን የሚሰ
ማ፣ በላከኝም የሚያምን የዘላለም ሕይወት
አለው፤ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ
ፍርድ አይመጣም። 25እውነት እላችኋለሁ፤
ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚ
ሰሙበት ጊዜ ይመጣል፤ አሁንም መጥቶአል፤
የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ። 26አብ
በራሱ ሕይወት እንዳለው ሁሉ፣ ወልድም
በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና፤
27ወልድ የሰው ልጅ ስለ ሆነም እንዲፈርድ
ሥልጣን ሰጥቶታል።
28"በዚህ አትደነቁ፤ መቃብር ውስጥ ያሉ
ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ጊዜ ይመጣል፤
29መልካም የሠሩ ለሕይወት ትንሣኤ፣ ክፉ
የሠሩ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉ። 30እኔ
ብቻዬን ከራሴ ምንም ማድረግ አልችልም፤
የምፈርደው የምሰማውን ብቻ ነው፤ የላከኝን
እንጂ የራሴን ፈቃድ ስለማልሻም ፍርዴ ትክ
ክል ነው።

## ስለ ኢየሱስ የሚናገሩ ምስክርነቶች

31"እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር፣ ምስክርነቴ
ተቀባይነት አይኖረውም። 32ስለ እኔ የሚ
መሰክር ሌላ አለ፤ እርሱ ስለ እኔ የሚሰጠ
ውም ምስክርነት እውነት እንደ ሆነ ዐው
ቃለሁ።
33"ወደ ዮሐንስ ልካችሁ ነበር፤ እርሱም ስለ
እውነት መስክሮአል፤ 34እኔ የሰው ምስክርነት
የምቀበል አይደለሁም፤ ይህን የምናገረው
ግን እናንተ እንድትድኑ ነው። 35ዮሐንስ
እየነደደ ብርሃን የሚሰጥ መብራት ነበረ፤
እናንተም ለጥቂት ጊዜ በብርሃኑ ደስ ልትሰኙ
ወደዳችሁ። 36"እኔ ግን ከዮሐንስ ምስክ
ርነት የላቀ ምስክር አለኝ፤ እንድፈጽመው
አብ የሰጠኝ፣ እኔም የምሠራው ሥራ አብ
እንደ ላከኝ ይመሰክራል። 37የላከኝ አብ
ራሱ ስለ እኔ መስክሮአል፤ እናንተም ከቶ

[ሠ]2 አንዳንድ ቅጆች *ቤተ ዛታ* ሌሎች ቅጆች *ቤተ ሳይዳ* ይላሉ
[የ]4 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ከቍ 3 የመጨረሻ ክፍል አንሥቶ እስከ ቍ 4 ድረስ ያለውን ክፍል አይጨምሩም

ድምፁን አልሰማችሁም፤ መልኩንም አላያ
ችሁም፤ 38የላከውንም ስላላመናችሁ ቃሉ
በእናንተ አይኖርም። 39በእነርሱ የዘላለም
ሕይወትን የምታገኙ እየመሰላችሁ፣ መጻሕ
ፍትን ትመረምራላችሁ፤[ዶ] እነዚሁ መጻሕ
ፍት ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው፤ 40እናንተ
ግን፣ ሕይወት እንዲኖራችሁ ወደ እኔ
መምጣት አትፈልጉም።
41"እኔ ከሰው ክብር አልቀበልም፤ 42ነገር
ግን እናንተን ዐውቃችኋለሁ፤ የእግዚአብሔርም
ፍቅር በልባችሁ እንደሌለ ዐውቃለሁ።
43እኔ በአባቴ ስም መጥቼ አልተቀበላች
ሁኝም፤ ሌላው በራሱ ስም ቢመጣ ግን ትቀ
በሉታላችሁ። 44እናንተ እርስ በርሳችሁ ክብር
የምትሰጣጡ፣ ነገር ግን ከአንዱ አምላክ[ጀ]
የሚመጣውን ክብር የማትፈልጉ ከሆነ፣ እን
ዴት ልታምኑ ትችላላችሁ?
45"ከሳሻችሁ ተስፋ የጣላችሁበት ሙሴ
እንጂ፣ እኔ በአብ ፊት የምከሳችሁ አይም
ስላችሁ፤ 46ሙሴን ብታምኑ ኖሮ፣ እኔን
ባመናችሁ ነበር፤ ምክንያቱም እርሱ የጻፈው
ስለ እኔ ነው። 47እርሱ የጻፈውን ካላመናችሁ፣
እኔ የምናገረውን እንዴት ታምናላችሁ?"

## ኢየሱስ አምስት ሺህ ሕዝብ መገበ

6፥1-13 ተጓ ምብ - ማቴ 14፥13-21፤ ማር 6፥32-44፤ ሉቃ 9፥10-17

6 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ጥብርያዶስ
የተባለውን የገሊላ ባሕር ተሻግሮ ራቅ
ወዳለው የባሕሩ ዳርቻ ሄደ። 2ብዙ ሰዎችም
በሽተኞችን በመፈወስ ያደረጋቸውን ታም
ራዊ ምልክቶች ስላዩ ተከተሉት። 3ከዚያም
ኢየሱስ ወደ ተራራ ወጥቶ ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር ተቀመጠ። 4የአይሁድ የፋሲካ በዓልም
ተቃርቦ ነበር።
5ኢየሱስም ቀና ብሎ ሲመለከት
ብዙ ሕዝብ ወደ እርሱ ሲመጣ አየ፤ ፊልጶ
ስንም፣ "እነዚህ ሰዎች እንዲበሉ እንጀራ ከየት
እንግዛ?" አለው። 6ይህን የጠየቀው ሊፈትነው
እንጂ ራሱ ሊያደርግ ያሰበውን ያውቅ
ነበር።
7ፊልጶስም፣ "እያንዳንዱ ሰው ትንሽ ትንሽ
እንዲቃመስ ለማድረግ፣ የሁለት መቶ ዲናር[ገ]
እንጀራ እንኳ አይበቃም" ሲል መለሰ።
8ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፣ የስምዖን
ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስም፣ እንዲህ
አለ፤ 9"አምስት ትንንሽ የገብስ እንጀራና
ሁለት ትንንሽ ዓሣ የያዘ አንድ ልጅ እዚህ
አለ፤ ይህ ግን ለዚህ ሁሉ ሕዝብ እንዴት
ይዳረሳል?"።
10ኢየሱስም፣ "ሰዎቹ እንዲቀመጡ አድርጉ"
አለ። በዚያ ቦታ ብዙ ሣር ነበረ፤ አምስት
ሺህ ያህል ወንዶችም ተቀመጡ። 11ኢየሱስ
አምስቱን እንጀራ አንሥቶ አመሰገነ፤ ለተቀ
መጡትም የሚፈልጉትን ያህል ዐደለ፤ ዓሣ
ውንም እንዲሁ።
12ሁሉም በልተው ከጠገቡ በኋላ፣ ደቀ
መዛሙርቱን፣ "ከተረፈው ቍርስራሽ ምንም
እንዳይባክን ሰብስቡ" አላቸው። 13እነርሱም፣
ከተበላው አምስት የገብስ እንጀራ የተረፈውን
ቍርስራሽ ሰብስበው ዐሥራ ሁለት መሶብ
ሞሉ።
14ሰዎቹም ኢየሱስ ያደረገውን ታምራዊ
ምልክት ካዩ በኋላ፣ "ወደ ዓለም የሚመጣው
ነቢይ በእርግጥ ይህ ነው" አሉ። 15ኢየሱስም
ሰዎቹ መጥተው በግድ ሊያነግሡት እን
ዳሰቡ ዐውቆ እንደ ገና ብቻውን ወደ
ተራራ ገለል አለ።

## ኢየሱስ በውሃ ላይ እየተራመደ ሄደ

6፥16-21 ተጓ ምብ - ማቴ 14፥22-33፤ ማር 6፥47-51

16በመሸም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ባሕ
ር ወረዱ፤ 17በጀልባውም ተሳፍረው ወደ
ቅፍርናሆም ለመሻገር ተነሡ። ጊዜው
መሽቶ ነበር፤ ኢየሱስም ወደ እነርሱ ገና
አልመጣም ነበር። 18ኀይለኛ ነፋስ ይነፍስ
ስለ ነበር ባሕሩ ተናወጠ። 19አምስት ወይም
ስድስት ኪሎ ሜትር[ጠ] ያህል እንደ ቀዘፉ፣ ኢ
የሱስ በውሃ ላይ እየተ ራመደ ወደ ጀልባዋ ሲ
መጣ አይተው ደነገጡ።
20እርሱ ግን፣ "እኔ ነኝ፤ አትፍሩ" አላቸው።
21እነርሱም እንዲሳፈር ፈለጉ፤ ጀልባዋም
ወዲያውኑ ወደሚሄዱበት ዳርቻ ደረሰች።
22በማግሥቱ በባሕሩ ማዶ የቀሩት ሰዎች
በዚያ አንዲት ጀልባ ብቻ እንደ ነበረች ተረዱ፤
ኢየሱስ እንዳልተሳፈረና ደቀ መዛሙርቱ
ብቻቸውን እንደ ሄዱም ዐወቁ። 23ከዚያም
በኋላ፣ ሌሎች ጀልባዎች ከጥብርያዶስ፣
ሕዝቡ ጌታ የባረከውን እንጀራ ወደ በላበት
ስፍራ መጡ። 24ሰዎቹም፣ ኢየሱስ ወይም
ደቀ መዛሙርቱ በዚያ አለመኖራቸውን እን
ዳወቁ፣ ኢየሱስን ፍለጋ በጀልባዎቹ ወደ
ቅፍርናሆም ሄዱ።

## ኢየሱስ የሕይወት እንጀራ

25ከባሕሩ ማዶ ባገኙትም ጊዜ፣ "ረቢ፤ መቼ
ወደዚህ መጣህ?" አሉት።
26ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"እውነት እላችኋለሁ የምትፈልጉኝ እንጀራ
ስለ በላችሁና ስለ ጠገባችሁ እንጂ፣ ታምራ
ዊ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም።
27ለሚጠፋ እንጀራ አትሥሩ፤ ነገር ግን
የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ለዘላለም ሕይወት
ለሚኖር ምግብ ሥሩ፤ ለዚህም እግዚአብሔር
አብ ማረ

5፥38 ኢሳ26፥10፤ ዮሐ3፥17፤1ዮሐ 1፥10፤2፥14
5፥39 ማቴ25፥46፤ ሉቃ 24፥27፡44፤ ሮሜ 2፥17፡18፤ ሐሥ13፥27
5፥40 ዮሐ6፥44
5፥41 ቍ44
5፥44 ሮሜ2፥29
5፥45 ዮሐ9፥28፤ ሮሜ2፥17
5፥46 ዘፍ3፥15፤ ሉቃ24፥27፡44፤ ሐሥ26፥22
5፥47 ሉቃ16፥29 ፡31
6፥2 ዮሐ2፥11
6፥3 ቍ15
6፥4 ዮሐ11፥55
6፥5 ዮሐ1፥43
6፥8 ዮሐ1፥40
6፥9 2ነገ4፥43
6፥11 ቍ23፤ ማቴ 14፥19
6፥14 ዘዳ18፥15፡ 18፤ማቴ11፥3፤ 21፥11፤ዮሐ2፥11
6፥15 ማቴ14፥23፤ ማር6፥46፤ ዮሐ18፥36
6፥19 ኢዮ9፥8
6፥20 ማቴ14፥27
6፥22 ቍ2፡15-21
6፥23 ቍ1፡11
6፥25 ማቴ23፥7
6፥26 ቍ24፡30፤ ዮሐ2፥11
6፥27 ቍ54፤ ኢሳ55፥2፤ ማቴ8፥20፤25፥46፤ ሮሜ4፥11፤1ቆሮ9፥2፤ 2ቆሮ1፥22፤ ኤፌ1፥13፤4፥30፤ 2ጢሞ2፥19፤ራእ7፥3

[ዶ]39 ወይም *መጻሕፍትን መርምሩ*
[ጀ]44 አንዳንድ የጥንት ቅጆች
[ገ]7 ወይም *የስምንት ወር ደመወዝ*
[ጠ]19 በግሪኩ *ሃያ አምስት ወይም ሠላሳ ምዕራፍ ቀዘፉ* ይላል

ጋገጫ ማኅተሙን በእርሱ ላይ አትሞአልና።”
28እነርሱም፣ “ታዲያ የእግዚአብሔርን ሥራ
ለመሥራት ምን ማድረግ አለብን?” አሉት።
29ኢየሱስም፣ “እርሱ በላከው ታምኑ ዘንድ፣
ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው” ሲል መለሰላቸው።
30ስለዚህ እንዲህ ብለው ጠየቁት፤ “አይተን
እንድናምንህ ምን ታምራዊ ምልክት ታደ
ርጋለህ? ምንስ ትሠራለህ? 31‘ይበሉ ዘንድ
ከሰማይ እንጀራን ሰጣቸው’ ተብሎ እንደ
ተጻፈ፣ አባቶቻችን በምድረ በዳ መና
በሉ።”
32ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “እውነት
እላችኋለሁ፤ ከሰማይ እንጀራ የሰጣችሁ
ሙሴ አይደለም፤ እውነተኛውን እንጀራ
ከሰማይ የሚሰጣችሁ ግን አባቴ ነው፤
33የእግዚአብሔር እንጀራ እርሱ ከሰማይ
የሚ ወርድ፣ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ
ነውና።”
34እነርሱም፣ “ጌታ፣ እንግዲያውስ
ይህን እንጀራ ሁልጊዜ ስጠን” አሉት።
35ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “የሕይ
ወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ
ከቶ አይራብም፤ በእኔም የሚያምን ፈጽሞ
አይጠማም። 36ነገር ግን እንደ ነገርኋችሁ፣
አይታችሁኝም እንኳ አታምኑም። 37አብ
የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፤ ወደ እኔ
የሚመጣውንም ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም፤
38ከሰማይ የወረድሁት የራሴን ፈቃድ ለማ
ድረግ ሳይሆን፣ የላከኝን የእርሱን ፈቃድ
ለመፈጸም ነውና፤ 39የላከኝም ፈቃድ፣ ከሰጠኝ
ሁሉ አንድ እንኳ ሳይጠፋብኝ በመጨረሻው
ቀን እንዳስነሣ ነው። 40የአባቴ ፈቃድ
ወልድን አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ
የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው ነው፤ እኔም
በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።”
41አይሁድም፣ “ከሰማይ የወረደ እንጀራ
እኔ ነኝ” በማለቱ ያጒረመርሙበት ጀመር።
42ደግሞም፣ “ይህ አባቱንና እናቱን የምናው
ቃቸው፣ የዮሴፍ ልጅ ኢየሱስ አይደለምን?
ታዲያ አሁን እንዴት፣ ‘ከሰማይ ወረድሁ
ይላል’ ” አሉ።
43ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ “እርስ
በርሳችሁ አታጒረምርሙ፤ 44የላከኝ አብ ካልሳ
በው በቀር ማንም ወደ እኔ መምጣት
አይችልም፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነ
ሣዋለሁ። 45በነቢያትም፣ ‘ሁሉም ከእግዚአብሔር
የተማሩ ይሆናሉ’ ተብሎ ተጽፎአል፤ አብን
የሚሰማና ከእርሱም የሚማር ሁሉ ወደ እኔ
ይመጣል። 46ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሆነው
በቀር አብን ያየ ማንም የለም፤ አብን ያየው
እርሱ ብቻ ነው። 47እውነት እላችኋለሁ፤
የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት አለው።
48የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ። 49አባቶቻችሁ
በምድረ በዳ መና በሉ፤ ይሁን እንጂ ሞቱ።
50ነገር ግን ሰው እንዳይሞት ይበላው
ዘንድ ከሰማይ የሚወርድ እንጀራ ይህ
ነው። 51ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ
ነኝ፤ ማንም ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ
ለዘላለም ይኖራል፤ ይህም እንጀራ፣ ለዓ
ለም ሕይወት እንዲሆን የምሰጠው ሥጋዬ
ነው።”
52አይሁድም፣ “እንበላ ዘንድ ይህ ሰው
ሥጋውን እንዴት ሊሰጠን ይችላል?” እያሉ
እርስ በርሳቸው አጥብቀው ይከራከሩ ጀመር።
53ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “እውነት
እላችኋለሁ፤ የሰውን ልጅ ሥጋውን ካልበላች
ሁና ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ
ሕይወት የላችሁም። 54ሥጋዬን የሚበላ፣ ደሜ
ንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፤
እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ፤
55ሥጋዬ እውነተኛ ምግብ፣ ደሜም እውነተኛ
መጠጥ ነውና፤ 56ሥጋዬን የሚበላ፣ ደሜንም
የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፤ እኔም በእርሱ እኖ
ራለሁ። 57ሕያው አብ እንደ ላከኝ፣ እኔም
ከእርሱ የተነሣ በሕይወት እንደምኖር፣
የሚበላኝም እንዲሁ ከእኔ የተነሣ በሕይወት
ይኖራል። 58ከሰማይ የወረደ እንጀራ ይህ
ነው፤ አባቶቻችሁ መና በሉ፤ ሞቱም፤
ይህን እንጀራ የሚበላ ግን ለዘላለም ይኖ
ራል።” 59ይህን የተናገረው በቅፍርናሆም፣
በምኲራብ እያስተማረ ሳለ ነበር።

### ብዙ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን መከተል ተዉ

60ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ይህን ሲሰሙ፣
“ይህ የሚያስጨንቅ ቃል ነው፤ ማንስ
ሊቀበለው ይችላል?” አሉ።
61ደቀ መዛሙርቱም በዚህ ነገር ማጒረ
ምረማቸውን ኢየሱስ በገዛ ራሱ ተረድቶ፣
እንዲህ አላቸው፤ “ይህ ዕንቅፋት ይሆን
ባችኋልን? 62ታዲያ፣ የሰው ልጅ ቀድሞ
ወደ ነበረበት ሲወጣ ብታዩ ምን ልትሉ
ነው? 63መንፈስ ሕይወትን ይሰጣል፤ ሥጋ
ግን ምንም አይጠቅምም። እኔ የነገርኋችሁ
ቃል መንፈስም ሕይወትም ነው፤ 64ይሁን
እንጂ ከእናንተ የማያምኑ አንዳንዶች አሉ።”
ይህም፣ ኢየሱስ እነማን እንዳላመኑና ማን
አሳልፎ እንደሚሰጠው ቀድሞውኑ ያውቅ
ስለ ነበር ነው።
65ቀጥሎም፣ “ ‘ከአብ ካልተሰጠው
በቀር፣ ማንም ወደ እኔ ሊመጣ አይችልም’
ያልኋችሁ ለዚህ ነው” አለ።
66ከዚህም በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች
ወደ ኋላ ተመለሱ፤ ከዚያም ወዲያ
አልተከተሉትም።
67ኢየሱስም ዐሥራ ሁለቱን፣ “እናንተም
ደግሞ መሄድ ትፈልጋላችሁ?” አላቸው።

6፥29 ዮሐ3፥17፤ 1ዮሐ3፥23
6፥30 ማቴ12፥38፤ ዮሐ2፥11
6፥31 ዘፀ16፥4:15፤ ዘኁ11፥7-9፤ነህ9፥15፤መዝ78፥24፤ 105፥40
6፥33 ቍ50፤ ዮሐ3፥13:31
6፥34 ዮሐ4፥15
6፥35 ቍ48:51፤ ዘፀ3፥14፤ ዮሐ3፥15፤ 4፥14፤8፥12፤10፥7:11፤11፥25፤14፥6፤ 15፥1
6፥37 ቍ39፤ ዮሐ17፥2:6:9:24
6፥38 ማቴ26፥39፤ ዮሐ3፥13:31፤3፥17
6፥39 ቍ40:44:54፤ኢሳ27፥3፤ኤር 23፥4፤ዮሐ10፥28፤ 17፥12፤18፥9
6፥40 ማቴ25፥46፤ ዮሐ12፥45
6፥42 ቍ38:62፤ ሉቃ4፥22፤ ዮሐ7፥27:28
6፥44 ቍ65፤ኤር 31፥3፤ዮሐ12፥32
6፥45 ኢሳ54፥13፤ ኤር31፥33:34፤ 1ቆሮ2፥13፤1ተሰ4፥9 ዕብ8፥10:11፤ 10፥16፤1ዮሐ2፥27
6፥46 ዮሐ1፥18፤ 5፥37፤7፥29
6፥47 ማቴ25፥46
6፥48 ቍ35:51
6፥49 ቍ31:58
6፥50 ቍ33
6፥51 ቍ35:41:48:58፤ዕብ10፥10
6፥52 ዮሐ1፥19፤ 7፥43፤9፥16፤10፥19
6፥53 ማቴ8፥20፤ 26፥26:28
6፥54 ቍ39
6፥56 ዮሐ15፥4-7፤ 1ዮሐ2፥24፤3፥24፤ 4፥15
6፥57 ዮሐ3፥17
6፥58 ቍ49-51፤ ዮሐ3፥36፤5፥24
6፥60 ቍ52:66
6፥61 ማቴ13፥57
6፥62 ማቴ8፥20፤ ማር16፥19፤ ዮሐ3፥13፤17፥5
6፥63 2ቆሮ3፥6
6፥64 ማቴ10፥4፤ ዮሐ2፥25
6፥65 ቍ37:44፤ ማቴ13፥11
6፥66 ቍ60
6፥67 ማቴ10፥2

68ስምዖን ጴጥሮስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤
“ጌታ ሆይ፤ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ
የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፤ 69አንተ
አንድያ የእግዚአብሔር ቅዱስ እንደ ሆንህ
አምነናል፤ ዐውቀናልም።”
70ኢየሱስም መልሶ፣ “ዐሥራ
ሁለታችሁንም የመረጥኋችሁ እኔ
አይደለሁምን? ነገር ግን ከእናንተ አንዱ ዲ
ያብሎስ ነው” አላቸው። 71የአስቆሮቱ
የስምዖን ልጅ ይሁዳ፣ ከዐሥራ ሁለቱ
አንዱ ቢሆንም፣ ኋላ አሳልፎ ስለ ሚሰጠ
ው ስለ እርሱ መናገሩ ነበር።

## ኢየሱስ የዳስ በዓል ወደሚከበርበት ሄደ

7 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ፣ በዚያ የነበሩት
አይሁድ ሊገድሉት ስለ ፈለጉ፣ በይሁዳ
አውራጃ መዘዋወር ትቶ በገሊላ ተዘዋወረ።
2የአይሁድ የዳስ በዓል በተቃረበ ጊዜ
ግን፣ 3የኢየሱስ ወንድሞች እንዲህ አሉት፤
“ደቀ መዛሙርትህም ደግሞ
የምታደርገውን ታምራት እንዲያዩ፣ ከዚህ
ወደ ይሁዳ ሂድ፤ 4ራሱን ሊገልጥ እየፈለገ
በስውር የሚሠራ ማንም የለምና። አንተም
እነዚህን ነገሮች የምታደርግ ከሆነ፣ ራስህን
ለዓለም ግለጥ።” 5የገዛ ወንድሞቹ እንኳ
አላመኑበትም ነበር።
6ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “ለእኔ
ትክክለኛው ጊዜ ገና አልደረሰም፤ ለእናንተ
ግን ማንኛውም ጊዜ ምቹ ነው። 7ዓለም
እናንተን ሊጠላ አይችልም፤ እኔ ግን፣ አድ
ራጎቱ ክፉ መሆኑን ስለምመሰክርበት ይጠ
ላኛል። 8እናንተ ወደ በዓሉ ሂዱ፤ ለእኔ
ትክክለኛው ጊዜ ስላልደረሰ[ጨ] ወደ በዓሉ
አልሄድም።” 9ይህን ብሎአቸው በገሊላ
ቈየ።
10ይሁን እንጂ፣ ወንድሞቹ ወደ በዓሉ
ከሄዱ በኋላ፣ እርሱም በግልጥ ሳይሆን
በስውር ወደ በዓሉ ሄደ። 11በበዓሉም ላይ
አይሁድ፣ “ያ ሰው የት አለ?” እያሉ
ይፈልጉት ነበር።
12ስለ እርሱ በሕዝቡ መካከል ብዙ
ጕምጕምታ ነበር። አንዳንዶች፣ “ደግ ሰው
ነው” አሉ።
ሌሎች ግን፣ “የለም፤ ሕዝቡን የሚያስት
ነው” አሉ። 13ይሁን እንጂ አይሁድን ከመፍ
ራት የተነሣ ስለ እርሱ በግልጽ የተናገረ
ማንም አልነበረም።

## ኢየሱስ በበዓሉ ላይ ተገኝቶ አስተማረ

14በበዓሉም አጋማሽ ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅ
ደስ ወጥቶ ያስተምር ጀመር። 15አይሁድም
በመደነቅ፣ “ይህ ሰው ሳይማር መጻሕፍትን
እንዴት ሊያውቅ ቻለ?” አሉ።
16ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ “የ
ማ ስተምረው ትምህርት ከራሴ ሳይሆን፣
ከላከኝ የመጣ ነው። 17ማንም የእግዚአብሔርን
ፈቃድ ለማድረግ ቢፈልግ፣ የእኔ
ትምህርት ከእግ ዚአብሔር ወይም ከራሴ
የመጣ መሆኑን ለይቶ ያውቃል፤ 18ከራሱ
የሚናገር፣ ያን የሚያደ ርገው ለራሱ
ክብርን ስለሚሻ ነው፤ ስለ ላከው ክብር
የሚሠራ ግን እርሱ እውነተኛ ነው፤ ሐ
ሰትም አይገኝበትም። 19ሙሴ ሕግን
አልሰጣችሁምን? ነገር ግን አንዳችሁም ሕ
ጉን አልጠበቃችሁም። ለምን ልትገድሉኝ
ትፈ ልጋላችሁ?”
20ሕዝቡም፣ “አንተ ጋኔን ያደረብህ! ደግሞ
አንተን ማን ሊገድል ይፈልጋል?” አሉት።
21ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ “አንድ
ሥራ ብሠራ፣ ሁላችሁም ተገረማችሁ።
22ግዝ ረት የመጣው ከአባቶች እንጂ
ከሙሴ አይደለም፤ ሆኖም ሙሴ ግዝረትን ስለ
ሰጣችሁ በሰንበት እንኳ ሕፃን ትገርዛላችሁ።
23የሙሴ
ሕግ እንዳይሻር ሕፃን በሰንበት የሚገረዝ ከሆነ፣
የሰውን ሁለንተና በሰንበት ስለ ፈወስሁ ለምን
በእኔ ላይ ትቈጣላችሁ? 24የሰውን ፊት በማ
የት መፍረድ ትታችሁ ቅን ፍርድ ፍረዱ።”

## ኢየሱስ፣ እርሱ ክርስቶስ ስለ መሆኑ

25በዚህ ጊዜ በኢየሩሳሌም የነበሩ አንዳንድ
ሰዎች እንዲህ አሉ፤ “ሊገድሉት
የሚፈልጉት ሰው ይህ አይደለምን? 26ይኸው
እርሱ በአደ ባባይ ይናገራል፤ አንድም ቃል
አይናገሩትም፤ ክርስቶስ[*] ነው ብለው ባለ
ሥልጣኖቹም ተቀብለውት ይሆን? 27ይህ
ሰው ግን ከየት እንደ ሆነ እኛ እናውቃለን፤
ክርስቶስ ሲመጣ እኮ ከየት እንደ ሆነ
ማንም አያውቅም።”
28ኢየሱስ በቤተ መቅደስ አደባባይ ሲያስ
ተምር ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲህ አለ፤
“አዎን፣ እኔን ታውቁኛላችሁ፤ ከየት እንደ
ሆንሁም ታውቃላችሁ። እኔ እዚህ ያለሁት
በገዛ ራሴ አይደለም፤ ነገር ግን የላከኝ እርሱ
እውነተኛ ነው። እናንተ አታውቁትም፤ 29እኔ
ግን ከእርሱ ዘንድ ስለ ሆንሁ፣ እርሱም
ስለ ላከኝ ዐውቀዋለሁ።”
30ስለዚህ ሊይዙት ፈለጉ፤ ነገር ግን ጊዜው
ገና ስላልደረሰ ማንም እጁን አላሳረፈበትም፤
31ሆኖም ከሕዝቡ ብዙዎች በእርሱ አምነው፣
“ታዲያ፣ ክርስቶስ ሲመጣ ይህ ሰው ከሚ
ሠራቸው ታምራዊ ምልክቶች የበለጠ ያደር
ጋል?” አሉ። 32ፈሪሳውያን፣ ሕዝቡ ስለ
እርሱ በጕም ጕምታ የሚነጋገረውን ነገር
ሰሙ፤ የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያንም
እንዲይዙት የቤተ መቅደስ ጠባቂዎችን
ላኳቸው።

6፥68 ቍ63፤ ማቴ16፥16
6፥69 ማር1፥24፤ 8፥29፤ ሉቃ9፥20
6፥70 ዮሐ13፥27፤ 15፥16፡19፤17፥12
6፥71 ማቴ10፥4፤ 26፥14
7፥1 ቍ19:25፤ ማቴ12፥14፤ ዮሐ1፥19
7፥2 ዘሌ23፥34፤ ዘዳ16፥16
7፥3 ማቴ12፥46
7፥5 መዝ69፥8፤ ማር3፥21
7፥6 ማቴ26፥18
7፥7 ዮሐ3፥19:20፤ 15፥18:19
7፥8 ቍ6፤ ማቴ26፥18
7፥11 ዮሐ11፥56
7፥12 ቍ40:43
7፥13 ዮሐ9፥22፤ 12፥42፤19፥38፤ 20፥19
7፥14 ቍ28፤ ማቴ26፥55
7፥15 ማቴ13፥54፤ ዮሐ1፥19፤ ሐሥ26፥24
7፥16 ዮሐ14፥24
7፥17 መዝ25፥14
7፥18 ዮሐ5፥41፤ 8፥50:54
7፥19 ቍ1፤ዘዳ 32፥46፤ማቴ12፥14፤ ዮሐ1፥17
7፥20 ማር3፥22
7፥21 ቍ23፤ ዮሐ5፥2-9
7፥22 ዘፍ17፥10-14፤ዘሌ12፥3
7፥24 1ሳሙ16፥7፤ ኢሳ11፥3:4፤ ዮሐ8፥15፤2ቆሮ10፥7
7፥25 ቍ1፤ ማቴ 12፥14
7፥26 ቍ48፤ ዮሐ4፥29
7፥27 ማቴ13፥55፤ ሉቃ4፥22፤ዮሐ6፥42
7፥28 ቍ14፤ ዮሐ8፥14:26:42
7፥29 ማቴ11፥17፤ ዮሐ3፥17
7፥30 ቍ32:44፤ ማቴ26፥18፤ ዮሐ10፥39
7፥31 ዮሐ2፥11፤ 8፥30፤10፥42፤ 11፥45፤12፥11:42

ጨ8 አንዳንድ ቅጆች ገና ስላልደረሰ ይላሉ
*26 ወይም መሲሑ፤ እንዲሁም ቍ 27፡31፡41 እና 42 ይመ

33ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ “ከእናንተ ጋር
የምቈየው ጥቂት ጊዜ ነው፤ ከዚያም ወደ
ላከኝ እሄዳለሁ፤ 34ትፈልጉኛላችሁ፤ ግን አታ
ገኙኝም፤ ወዳለሁበትም ልትመጡ አትችሉም።”
35አይሁድም እርስ በርሳቸው እንዲህ
ተባባሉ፤ “ይህ ሰው፣ ልናገኘው የማንችለው
ወዴት ለመሄድ ቢያስብ ነው? በግሪኮች
መካከል ተበታትነው ወደሚኖሩት ወገኖቻችን
ሄዶ ግሪኮችን ሊያስተምር ፈልጎ ይሆን?
36‘ትፈልጉኛላችሁ፤ ግን አታገኙኝም፤’ ደግሞም፣
‘እኔ ወዳለሁበት ልትመጡ አትችሉም’ ሲል
ምን ማለቱ ይሆን?”
37የበዓሉ መጨረሻ በሆነው በታላቁ ቀን፣
ኢየሱስ ቆሞ ከፍ ባለ ድምፅ እንዲህ አለ፤
“ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና
ይጠጣ፤ 38በእኔ የሚያምን፣ መጽሐፍ እንዳለ[ጸ]
የሕይወት ውሃ ምንጭ ከውስጡ ይፈልቃል።”
39ይህን ያለው በእርሱ የሚያምኑ ስለሚቀበሉት
መንፈስ ነበር፤ ምክንያቱም ኢየሱስ ገና
ስላልከበረ መንፈስ አልተሰጠም ነበር።
40ከሕዝቡ አንዳንዶቹ ቃሉን ሰምተው፣
“ይህ ሰው በእርግጥ ነቢዩ ነው” አሉ።
41ሌሎችም፣ “እርሱ ክርስቶስ ነው” አሉ።
ሌሎች ደግሞ እንዲህ አሉ፤ “ክርስቶስ ከገ
ሊላ እንዴት ሊመጣ ይችላል? 42መጽሐፍ፣
ክርስቶስ ከዳዊት ዘር[ፀ]፣ ዳዊትም ከኖረበት
ከቤተ ልሔም እንደሚመጣ ይናገር የለምን?”
43ስለዚህም በኢየሱስ ምክንያት በሕዝቡ መካ
ከል መለያየት ሆነ፤ 44አንዳንዶቹም ሊይዙት
ፈለጉ፤ ነገር ግን ማንም እጁን አላሳረፈበትም።

### የአይሁድ መሪዎች አለማመን

45በመጨረሻም የቤተ መቅደስ ጠባቂዎቹ
፣ ወደ ካህናት አለቆችና ወደ ፈሪሳውያን
ተመ ልሰው ሄዱ፤ እነርሱም ጠባቂዎቹን፣
“ለምን አላመጣችሁትም?” አሏቸው።
46ጠባቂዎቹም፣ “እንደዚህ ሰው፣ ከቶ ማንም
ተናግሮ አያውቅም” ሲሉ መለሱ።
47ፈሪሳውያንም እንዲህ ሲሉ መለሱ፤
“እና ንተም ተታላችኋል ማለት ነው?
48ለመሆኑ ከባለሥልጣኖችና ከፈሪሳውያን
በእርሱ ያመነ አለ? 49ሕጉን የማያውቅ
ይህ ሕዝብ ግን የተረገመ ነው።”
50ከዚህ ቀደም ወደ ኢየሱስ ሄዶ የነበ
ረውና ከእነርሱ አንዱ የሆነው ኒቆዲሞስ እንዲህ
አላቸው፤ 51“ሕጋችን፣ አስቀድሞ አንድን ሰው
ሳይሰማና ምን እንዳደረገ ሳይረዳ ይፈርድበ
ታልን?”
52እነርሱም፣ “አንተም ደግሞ ከገሊላ ነህን?
ነቢይ[ፈ] ከገሊላ እንደማይነሣ መርምር፤
ትደር ስበታለህ” ብለው መለሱለት።
53ከዚህ በኋላ ሁሉም ወደየቤታቸው ሄዱ።

### በምንዝር የተያዘች ሴት

8 ኢየሱስ ግን ወደ ደብረ ዘይት ሄደ። 2በ
ማ ለዳም በቤተ መቅደስ አደባባይ
እንደ ገና ታየ፤ ሕዝቡም በዙሪያው
ተሰበሰበ፤ ሊያስ ተምራቸውም ተቀመጠ።
3የኦሪት ሕግ መምህ ራንና ፈሪሳውያን
በምንዝር የተያዘች ሴት አመጡ፤ በሕ
ዝቡም ፊት አቁመዋት፣ 4ኢየ ሱስን እንዲ
ህ አሉት፤ “መምህር ሆይ፣ ይህች ሴት
ስታመነዝር ተያዘች፤ 5ሙሴም፣ እንደዚች
ያሉ ሴቶች በድንጋይ እንዲወገሩ በሕጉ
አዞናል፤ አንተስ ምን ትላለህ?” 6ይህን ጥያቄ
ያቀረቡለት፣ እርሱን የሚከሱበት
ምክንያት ለማግኘት ሲፈትኑት ነው።
ኢየሱስ ግን ጎንበስ ብሎ በጣቱ በምድር
ላይ ይጽፍ ጀመር። 7በጥያቄ ሲወተውቱት
ቀና ብሎ፣ “ከእናንተ ኀጢአት የሌለበት
እርሱ አስቀድሞ ድንጋይ ይወርውርባት”
አላቸው። 8እንደ ገናም ጎንበስ ብሎ በምድር
ላይ ጻፈ።
9ይህን እንደ ሰሙ፣ ከሽማግሌዎች
ጀምሮ አንድ በአንድ ወጡ፤ ሴትዮዋም
እዚያው ፊቱ እንደ ቆመች ኢየሱስ
ብቻውን ቀረ። 10ኢየሱስም ቀና ብሎ፣
“አንቺ ሴት፣ ሰዎቹ የት ሄዱ? የፈረደብሽ
የለምን?” አላት።
11እርሷም፣ “ጌታ ሆይ፤ አንድም የለም”
አለች።
ኢየሱስም፣ “እኔም አልፈርድብሽም፤ በይ
ሂጂ፤ ከእንግዲህ ግን ኀጢአት አትሥሪ”
አላት።]*

### የኢየሱስ ምስክርነት እውነት መሆኑ

12ኢየሱስ እንደ ገና ለሰዎቹ፣ “እኔ የዓለም
ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝም የሕይወት ብርሃን
ይሆንለታል እንጂ ከቶ በጨለማ አይመላ
ለስም” አላቸው።
13ፈሪሳውያንም፣ “አንተ ስለ ራስህ ስለምት
መሰክር፣ ምስክርነትህ ተቀባይነት የለውም”
አሉት።
14ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ “እኔ
ስለ ራሴ ብመሰክር ከየት እንደ መጣሁና
ወዴት እንደምሄድ ስለማውቅ ምስክርነቴ
እውነት ነው፤ እናንተ ግን ከየት እንደ መጣሁ
ወይም ወዴት እንደምሄድ የምታውቁት ነገር
የለም። 15እናንተ እንደ ሰው አስተሳሰብ
ትፈርዳላችሁ፤ እኔ በማንም አልፈርድም፤
16ብፈርድም፣ ከላከኝ ከአብ ጋር እንጂ
ብቻዬን ስላልሆንሁ ፍርዴ ትክክል ነው።

7፥33 ዮሐ12፥35፤ 13፥33፤16፥5፡10፡ 16፡17፡28
7፥34 ቍ36፤ ዮሐ8፥21፤13፥33
7፥35 ዮሐ12፥20፤ ሐሥ17፥4፤18፥4፤ ያዕ1፥1
7፥36 ቍ34
7፥37 ዘሌ23፥36፤ ኢሳ55፥1፤ራእ22፥17
7፥38 ዮሐ3፥15፤ 4፥10፡14፤ኢሳ58፥11
7፥39 ኢል2፥28፤ ዮሐ1፥33፤12፥23፤ 20፥22፤ሐሥ2፥17፡ 33፤13፥31፡32
7፥40 ማቴ21፥11
7፥41 ቍ52፤ ዮሐ1፥46
7፥42 ማቴ1፥1፤ 2፥5፡6፤ሉቃ2፥4፤ ሚክ5፥2
7፥43 ዮሐ6፥52፤ 9፥16፤10፥19
7፥44 ቍ30
7፥46 ማቴ7፥28
7፥47 ቍ12
7፥48 ዮሐ12፥42
7፥50 ዮሐ3፥1፤ 19፥39
7፥52 ቍ41
8፥1 ማቴ21፥1
8፥2 ቍ20፤ ማቴ 26፥55
8፥5 ዘሌ20፥10፤ ዘዳ22፥22፤ ኢዮ31፥11
8፥6 ማቴ12፥10፤ 22፥15፡18
8፥7 ዘዳ17፥7፤ ሕዝ 16፥40፤ ሮሜ2፥1፡22
8፥11 ዮሐ3፥17፤ 5፥14
8፥12 ምሳ4፥18፤ ማቴ5፥14፤ዮሐ1፥4፤ 6፥35
8፥15 ዮሐ3፥17፤ 7፥24
8፥16 ዮሐ5፥30

[ጸ]37፡38 ወይም *ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣ፤ 38በእኔ የሚያምን ይጠጣ* [ፀ]42 ወይም *ከዳዊት ቤተ ሰብ*
[ፈ]52 ሁለት የጥንት ቅጆች *ነቢዩ* ይላሉ
*ብዙ የጥንት ቅጆች ይህ ክፍል (7፥53-8፥11) የላቸውም፤ ወይም በሌላ ስፍራ ወይም በሌሎች ወንጌሎች ያስገቡታል።

17የሁለት ሰዎች ምስክርነት ተቀባይነት
እንዳለው በሕጋችሁ ተጽፎአል። 18ስለ ራሴ
የምመሰክር አንዱ እኔ ነኝ፤ ሌላውም ምስ
ክሬ የላከኝ አብ ነው።”
19ከዚያም፣ “አባትህ የት ነው?” አሉት።
ኢየሱስም፣ “አባቴንም እኔንም አታውቁም፤
እኔን ብታውቁኝ ኖሮ፣ አባቴንም ባወቃ
ችሁ ነበር” ሲል መለሰላቸው። 20ኢየሱስ
ይህን የተናገረው በቤተ መቅደሱ ግቢ፣
በግምጃ ቤት አጠገብ ሲያስተምር ነበር፤
ይሁን እንጂ ጊዜው ገና ስላልደረሰ ማንም
አልያዘውም።
21ኢየሱስም እንደ ገና፣ “እኔ እሄዳለሁ፤
እናንተም ትፈልጉኛላችሁ፤ በኀጢአታችሁም
ትሞታላችሁ፤ እኔ ወደ ምሄድበት ግን ልት
መጡ አትችሉም” አላቸው።
22አይሁድም፣ “‘እኔ ወደምሄድበት ልትመጡ
አትችሉም’ ያለው ራሱን ሊገድል ይሆን?”
አሉ።
23እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፤ “እናንተ
ከታች ናችሁ፤ እኔ ከላይ ነኝ፤ እናንተ ከዚህ
ዓለም ናችሁ፤ እኔ ከዚህ ዓለም አይደለሁም።
24በኀጢአታችሁ እንደምትሞቱ ነግሬአች
ኋለሁ፤ እኔ እርሱ ነኝ[ፐ] ስላችሁ እኔ እርሱ
እንደ ሆንሁ ካላመናችሁ፣ በኀጢአታችሁ
ትሞታላችሁና።”
25እነርሱም፣ “ለመሆኑ፣ አንተ ማን ነህ?”
አሉት።
ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ “እስካ
ሁን የነገርኋችሁ እኔ እርሱ ነኝ፤ 26በእናንተ
ላይ ብዙ የምናገረውና ብዙ የምፈርደው
ነገር አለኝ፤ ዳሩ ግን የላከኝ ታማኝ ነው፤
ከእርሱም የሰማሁትን ለዓለም እናገራ
ለሁ።”
27እነርሱም ስለ አብ እየነገራቸው እንደ
ነበር አላስተዋሉም። 28ስለዚህ ኢየሱስ እንዲ
ህ አለ፤ “የሰው ልጅን ከፍ ከፍ
ባደረጋችሁት ጊዜ፣ ያ ያልሁት እርሱ እኔ
እንደ ሆንሁና አብ ያስተማረኝን
እንደምናገር፣ በራሴም ፈቃድ ምንም
እንደማላደርግ ታውቃላችሁ፤ 29የላከኝ
እርሱ ከእኔ ጋር ነው፤ ምንጊዜም
የሚያስደስተውን ስለማደርግ ብቻዬን አልተ
ወኝም።” 30ይህንም እንደ ተናገረ ብዙዎች
በእርሱ አመኑ።

## የአብርሃም ልጆች

31ኢየሱስም በእርሱ ያመኑትን አይሁድ
እንዲህ አላቸው፤ “በትምህርቴ ብትጸኑ
እናንተ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤
32እውነትንም ታውቃላችሁ፤ እውነትም ነጻ
ያወጣችኋል።”
33እነርሱም መልሰው፣ “እኛ የአብርሃም
ልጆች ነን[ሀ]፤ ለማንም ባሪያዎች ሆነን አና
ውቅም፤ ታዲያ፣ ‘ነጻ ትወጣላችሁ’ እንዴት
ትለናለህ?” አሉት።
34ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
“እውነት እላችኋለሁ፤ ኀጢአት የሚያደርግ
የኀጢአት ባሪያ ነው፤ 35ባሪያ ለዘለቄታ በቤተ
ሰቡ ውስጥ አይኖርም፤ ልጅ ግን ምን ጊ
ዜም በቤት ይኖራል። 36እንግዲህ ወልድ
ነጻ ካወጣችሁ፣ በእውነት ነጻ ትሆናላችሁ።
37የአ ብርሃም ልጆች መሆናችሁን ዐ
ውቃለሁ፤ ነገር ግን ቃሌን ስለማትቀበሉ
ልትገድሉኝ ቈርጣችሁ ተነሥታችኋል። 38እኔ
በአባቴ ዘንድ ያየሁትን እናገራለሁ፤
እናንተም ከአባታችሁ የሰማችሁትን
ታደርጋላችሁ።”[ለ]
39እነርሱም፣ “አባታችንስ አብርሃም ነው”
ብለው መለሱለት።
ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “የአብርሃም
ልጆችስ ብትሆኑ[ሐ]፣ አብርሃም የሠራውን
ትሠሩ ነበር። 40ከእግዚአብሔር ሰምቼ እውነቱን
የነገርኋችሁን እኔን ለመግደል ቈርጣችሁ
ተነሥታችኋል፤ አብርሃም ግን እንዲህ አላደ
ረገም። 41እናንተ የምታደርጉት አባታችሁ
የሚያደርገውን ነው።”
እነርሱም፣ “እኛስ በዝሙት የተወለድን
አይደለንም፤ አባታችንም አንዱ እግዚአብሔር
ብቻ ነው” ሲሉ መለሱለት።

## የዲያብሎስ ልጆች

42ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “እግዚአብሔር
አባታችሁ ቢሆን ኖሮ፣ እኔ ከእግዚአብሔር
ወጥቼ መጥቻለሁና፣ በወደዳችሁኝ ነበር፤
እርሱ ላከኝ እንጂ በገዛ ራሴ አልመጣሁም።
43የምናገረውን ለምን አታስተውሉም? ምክን
ያቱም ቃሌን መስማት ስለማትችሉ ነው።
44እናንተ የአባታችሁ የዲያብሎስ ናችሁ፤
የአባታችሁንም ፍላጎት ለመፈጸም ትሻላችሁ።
እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበር፤
በእርሱ ዘንድ እውነት ስለሌለ በእውነት
አልጸናም፤ እርሱ ሐሰተኛ፣ የሐሰትም
አባት በመሆኑ ሐሰትን ሲናገር፣
የሚናገረው ከራሱ አፍልቆ ነው፤ 45እኔ ግን
እውነት ስለም ናገር አታምኑኝም።
46ከእናንተ ስለ ኀጢአት በማስረጃ ሊከሰኝ
የሚችል አለን? እውነት የምናገር ከሆነ፣
ለምን አታምኑኝም? 47ከእግዚአብሔር የሆነ
እግዚአብሔር የሚለውን ይሰማል፤ እናንተ
ግን ከእግዚአብሔር ስላል ሆናችሁ
አትሰሙም።”

8፥17 ማቴ18፥16
8፥18 ዮሐ5፥37
8፥19 ዮሐ16፥3፤ 1ዮሐ2፥23
8፥20 ማቴ26፥18፤ 55፤ማር12፥41
8፥21 ሕዝ3፥18፤ ዮሐ7፥34፤13፥33
8፥23 ዮሐ3፥31፤ 17፥14
8፥24 ዮሐ4፥26፤ 13፥19
8፥26 ዮሐ3፥32፤ 7፥28፤15፥15
8፥28 ዮሐ12፥32፤ 14፥24
8፥29 ቍ16፤ ኢሳ50፥5፤ዮሐ4፥34፤ 5፥30፤6፥38፤16፥32
8፥30 ዮሐ7፥31
8፥31 ዮሐ15፥7፤ 2ዮሐ9
8፥32 ቍ36፤ ሮሜ8፥2፤ 2ቆሮ 3፥17፤ገላ5፥1፡13
8፥33 ቍ37፡39፤ ሉቃ3፥8
8፥34 ሮሜ6፥16
8፥35 ገላ4፥30
8፥36 ቍ32
8፥37 ቍ39፡40
8፥38 ቍ41፡44፤ ዮሐ5፥19፡30፤ 14፥10፡24
8፥39 ቍ37፤ ሉቃ3፥8
8፥40 ቍ26፤ ማቴ12፥14
8፥41 ቍ38፡44፤ ኢሳ63፥16፤64፥8
8፥42 ዮሐ3፥17፤ 7፥28፤13፥3፤ 1ዮሐ5፥1
8፥44 ቍ38፥41፤ ዘፍ3፥4፤4፥9፤2ዜና 18፥21፤መዝ5፥6፤ 12፥2፤1ዮሐ3፥8
8፥45 ዮሐ18፥37
8፥47 ዮሐ18፥37፤ 1ዮሐ4፥6

[ፐ]24 ወይም *ያ ያልሁት እርሱ እኔ ነኝ*፤እንዲሁም ቍ 28 ይመ
[ሀ]33 በግሪኩ *ዘር* ይላል፤ ቍ 37 ይመ
[ለ]38 ወይም *ስለዚህ ከአባታችሁ የሰማችሁትን አድርጉ*
[ሐ]39 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *የአብርሃም ልጆች ከሆናችሁ* ይላሉ

### ኢየሱስ ስለ ራሱ የተናገረው

48አይሁድም መልሰው፣ “አንተ ሳምራዊ ነህ፤
ደግሞም ጋኔን አድሮብሃል ማለታችን ትክክል
አይደለምን?” አሉት።
49ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
“እኔስ አባቴን አከብረዋለሁ እንጂ ጋኔን
አላደረብኝም፤ እናንተ ግን ታዋርዱኛላችሁ።
50እኔ የራሴን ክብር አልፈልግም፤ የሚፈልግ
ግን አለ፤ ፈራጁም እርሱ ነው። 51እውነት
እላችኋለሁ፤ ማንም ቃሌን ቢጠብቅ፣ ሞትን
ፈጽሞ አያይም።”
52አይሁድም እንዲህ አሉት፤ “ጋኔን እን
ዳለብህ አሁን ዐወቅን፤ አብርሃም ሞተ፤
ነቢያትም እንዲሁ፤ አንተ ግን ማንም
ቃልህን ቢጠብቅ ሞትን ፈጽሞ እንደማይ
ቀምስ ትናገራለህ። 53አንተ ከአባታችን
ከአብርሃም ትበልጣለህን? እርሱ ሞተ፤
ነቢያቱም እንዲሁ፤ ለመሆኑ አንተ ማን ነኝ
ልትል ነው?”
54ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “እኔ
ራሴን ባከብር፣ ክብሬ ከንቱ ነው፤ የሚያ
ከብረኝ ግን እናንተ አምላካችን የምትሉት
አባቴ ነው። 55እናንተ ባታውቁትም እኔ
ዐውቀዋለሁ፤ አላውቀውም ብል፣ እኔም
እንደ እናንተው ሐሰተኛ እሆናለሁ። እኔ
ግን ዐውቀዋለሁ፤ ቃሉንም እጠብቃለሁ።
56አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ለማየት ተስፋ
በማድረግ ተደሰተ፤ አየም፤ ሐሤትም አደረገ።”
57አይሁድም፣ “ገና አምሳ ዓመት ያልሞ
ላህ፣ አንተ አብርሃምን አይተሃል!” አሉት።
58ኢየሱስም፣ “እውነት እላችኋለሁ፤ አብር
ሃም ከመወለዱ በፊት እኔ፣ እኔ ነኝ” አላቸው።
59በዚህን ጊዜ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ፤
ኢየሱስ ግን ተሰወረባቸው፤ ከቤተ
መቅደስም ወጥቶ ሄደ።

### ኢየሱስ ዐይነ ስውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ፈወሰ

9 በመንገድ ሲያልፍም ከተወለደ ጀምሮ
ዐይነ ስውር የሆነ ሰው አየ። 2ደቀ
መዛሙርቱም፣ “ረቢ፤ ይህ ሰው ዐይነ ስውር
ሆኖ እንዲወለድ ኀጢአት የሠራ ማን ነው?
እርሱ ራሱ ወይስ ወላጆቹ?” ብለው ጠየቁት።
3ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “እርሱ
ወይም ወላጆቹ ኀጢአት አልሠሩም፤ ይህ
የሆነው ግን የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ ሕይወት
እንዲገለጥ ነው። 4ቀን ሳለ፣ የላከኝን ሥራ
መሥራት አለብኝ፤ ማንም ሊሠራ የማይ
ችልበት ሌሊት ይመጣል፤ 5በዓለም ሳለሁ
የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ።”
6ይህን ካለ በኋላ፣ በምድር ላይ እንትፍ
ብሎ በምራቁ ጭቃ አበጀ፤ የሰውዬውንም
ዐይን ቀባና፣ 7“ሄደህ በሰሊሆም መጠመቂያ
ታጠብ” አለው፤ ሰሊሆም ማለት ‘የተላከ’
ማለት ነው። ሰውዬውም ሄዶ ታጠበ፤ እያየም
ተመልሶ መጣ።
8ጎረቤቶቹና ከዚህ ቀደም ብሎ ሲለ
ምን ያዩት ሰዎች፣ “ይህ ሰው ተቀምጦ
ሲለምን የነበረው አይደለምን?” አሉ። 9አንዳን
ዶቹም፣ “በእርግጥ እርሱ ነው” አሉ።
ሌሎችም፣ “ይመስለዋል እንጂ እርሱ
አይደለም” አሉ።
እርሱ ግን፣ “እኔው ነኝ” አለ።
10እነርሱም፣ “ታዲያ ዐይኖችህ እንዴት
ተከፈቱ?” ሲሉ ጠየቁት።
11እርሱም፣ “ኢየሱስ የሚሉት ሰው ጭቃ
አድርጎ ዐይኔን ቀባኝ፤ ወደ ሰሊሆም ሄጄ
እንድታጠብም ነገረኝ፤ ሄጄ ታጠብሁ፤
ማየትም ቻልሁ” ሲል መለሰ።
12እነርሱም፣ “ታዲያ፣ ያ ሰው የት አለ?”
አሉት።
እርሱም፣ “እኔ አላውቅም” አለ።

### ፈሪሳውያን ሰውየው እንዴት እንደ ተፈወሰ ማጣራት ቀጠሉ

13እነርሱም ዐይነ ስውር የነበረውን ሰው
ወደ ፈሪሳውያን ወሰዱት። 14ኢየሱስ ጭቃ
የሠራበት፣ የሰውዬውንም ዐይን የከፈ
ተበት ቀን ሰንበት ነበር። 15ስለዚህ ፈሪሳ
ውያንም እንዴት ማየት እንደ ቻለ ጠየቁት።
ሰውዬውም፣ “እርሱ ዐይኔን ጭቃ ቀባኝ፤
እኔም ታጠብሁ፤ ይኸው አያለሁ” አላቸው።
16ከፈሪሳውያንም አንዳንዶቹ፣ “ይህ ሰው
ሰንበትን ስለማያከብር፣ ከእግዚአብሔር
አይደ ለም” አሉ።
ሌሎች ግን፣ “ኀጢአተኛ፣ እንዲህ ያሉትን
ታምራዊ ምልክቶች እንዴት ሊያደርግ ይች
ላል?” አሉ። በመካከላቸውም አለመስማማት
ተፈጠረ።
17ስለዚህ፣ ዐይነ ስውር ወደ ነበረው ሰው
ተመልሰው፣ “ዐይንህን ስለ ከፈተው ሰው፣
እንግዲህ አንተ ምን ትላለህ?” አሉት።
ሰውየውም፣ “እርሱ ነቢይ ነው” አለ።
18አይሁድ ወደ ወላጆቹ ልከው እስኪ
ያስጠሯቸው ድረስ፣ ሰውየው ዐይነ ስውር
እንደ ነበረና እንዳየ አላመኑም ነበር።
19እነርሱም፣ “ዐይነ ስውር ሆኖ ተወልዶአል
የምትሉት ልጃችሁ ይህ ነውን? ታዲያ
አሁን እንዴት ሊያይ ቻለ?” አሏቸው።
20ወላጆቹም እንዲህ ሲሉ መለሱ፤ “ልጃ
ችን መሆኑንና ዐይነ ስውር ሆኖ መወለዱን
እናውቃለን፤ 21አሁን ግን እንዴት ማየት
እንደቻለና ዐይኖቹን ማን እንደ ከፈተለት
እኛ አናውቅም። ሙሉ ሰው ስለ ሆነ፣ ስለ

8፥48 ቍ52፤ ማቴ10፥5፤ማር3፥22
8፥50 ቍ54፤ ዮሐ5፥41
8፥51 ዮሐ11፥26
8፥52 ቍ48፤ ማር3፥22
8፥53 ቍ39፤ ዮሐ4፥12
8፥54 ቍ50፤ ዮሐ16፥14፤17፥1፡5
8፥55 ቍ19፤ ዮሐ7፥28፡29፤15፥10
8፥56 ቍ37፡39፤ ዘፍ18፥18፤ ማቴ13፥17
8፥58 ዘፀ3፥14፤ 6፥3፤ዮሐ1፥2
8፥59 ዘፀ17፥4፤ ዘሌ24፥16፤1ሳሙ 30፥6፤ዮሐ10፥31፤ 11፥8፤12፥36
9፥2 ቍ34፤ ዘፀ20፥5፤ኢ ዮ21፥19፤ ሕዝ18፥20፤ማቴ 23፥7፤ሉቃ13፥2፤ ሐሥ28፥4
9፥3 ዮሐ11፥4
9፥4 ዮሐ11፥9፤ 12፥35
9፥5 ዮሐ1፥4
9፥6 ማር7፥33፤ 8፥23
9፥7 ቍ11፤2ነገ 5፥10፤ኢሳ35፥5፤ ሉቃ13፥4፤ ዮሐ 11፥37
9፥8 ሐሥ3፥2፡10
9፥11 ቍ7
9፥14 ማቴ12፥1-14፤ዮሐ5፥9
9፥15 ቍ10
9፥16 ማቴ12፥2፤ ዮሐ2፥11፤6፥52
9፥17 ማቴ21፥11
9፥18 ዮሐ1፥19

ራሱ መናገር ይችላልና እርሱን ጠይቁት::”
22ኢየሱስን፣ ክርስቶስ^ ነው ብሎ የመሰከረ
ሁሉ ከምኲራብ እንዲባረር አይሁድ አስቀ
ድመው ወስነው ስለ ነበር፣ ወላጆቹ ይህን
ያሉት አይሁድን ፈርተው ነው:: 23ስለዚህ
ወላጆቹ፣ “ሙሉ ሰው ስለ ሆነ እርሱን ጠይ
ቁት” አሉ::

24ዐይነ ስውር የነበረውንም ሰው
ዳግመኛ
ጠርተው፣ “አንተ ሰው፤ እግዚአብሔርን አክብር
^፤ ይህ ሰው ኀጢአተኛ መሆኑን እኛ
እናውቃለን” አሉት::

25እርሱም፣ “ኀጢአተኛ መሆኑን እኔ አላ
ውቅም፤ ነገር ግን ዐይነ ስውር እንደ
ነበርሁ፤ አሁን ግን እንደማይ ይህን አንድ
ነገር ዐውቃለሁ” አለ::

26እነርሱም፣ “ምን አደረገልህ? እንዴትስ
ዐይንህን ከፈተ?” ብለው ጠየቁት::

27እርሱም፣ “አስቀድሜ ነገርኋችሁ፤ አላዳ
መጣችሁኝም፤ ለምን እንደ ገና መስማት
ፈለጋችሁ? እናንተም ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ
ልትሆኑ ትሻላችሁ?” አለ::

28ከዚህ በኋላ በእርሱ ላይ የስድብ ናዳ
በማውረድ እንዲህ አሉት፣ “የዚህ ሰው
ደቀ መዝሙር አንተ ነህ፤ እኛስ የሙሴ
ደቀ መዛሙርት ነን! 29እግዚአብሔር ሙሴን
እንደ ተናገረው እናውቃለን፤ ይህ ሰው
ግን ከየት እንደ መጣ እንኳ አናውቅም::”

30ሰውየውም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
“እናንተ ከየት እንደ መጣ አለማወቃችሁ
የሚያስደንቅ ነው፤ ይሁን እንጂ እርሱ
ዐይኖቼን ከፈተልኝ:: 31እግዚአብሔር የሚሰ
ማው፣ የሚፈራውንና ፈቃዱን የሚያደር
ገውን እንጂ፣ ኀጢአተኞችን እንደማይ
ሰማ እናውቃለን፤ 32ዐይነ ስውር ሆኖ የተ
ወለደን ሰው ዐይን የከፈተ አለ ሲባል፣
ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ማንም ሰምቶ አያ
ውቅም:: 33ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ባይሆን
ኖሮ ይህን ማድረግ ባልቻለ ነበር::”

34እነርሱም፣ “ሁለንተናህ በኀጢአት ተነክሮ
የተወለድህ፣ አንተ እኛን ለማስተማር እንዴት
ትደፍራለህ?” ሲሉ መለሱለት፤ አባረሩትም::

## መንፈሳዊ ዕውርነት

35ኢየሱስም ሰውየውን እንዳባረሩት ሰማ፤
ባገኘውም ጊዜ፣ “በሰው ልጅ *ታምናለህን?”
አለው::

36ሰውየውም፣ “ጌታዬ፤ አምንበት ዘንድ
እርሱ ማን ነው?” ሲል ጠየቀው::

37ኢየሱስም፣ “አይተኸዋል፤ አሁንም ከአንተ
ጋር የሚነጋገረው እርሱ ነው” አለው::

38ሰውየውም፣ “ጌታ ሆይ፤ አምናለሁ” አለ፤
ሰገደለትም::

39ኢየሱስም፣ “ዕውሮች እንዲያዩ፣ የሚ
ያዩም እንዲታወሩ፣ ለፍርድ ወደዚህ ዓለም
መጥቻለሁ” አለ::

40ከእርሱ ጋር ከነበሩት ፈሪሳውያን
አንዳንድ ዶቹ ይህን ሰምተው፣ “ምን ማለትህ
ነው? ታዲያ እኛም ዕውሮች መሆናችን
ነው?” አሉት::

41ኢየሱስም፣ “ዕውሮችስ ብትሆኑ ኀጢ
አት ባልሆነባችሁ ነበር፤ አሁን ግን እናያለን
ስለምትሉ፣ ኀጢአታችሁ እንዳለ ይኖራል”
አላቸው::

## እረኛና መንጋው

10 “እውነት እላችኋለሁ፤ ወደ በጎች
ጕረኖ በበሩ ሳይሆን፣ በሌላ በኩል
ዘሎ የሚገባ ሌባና ነጣቂ ነው፤ 2በበሩ
የሚገባ ግን እርሱ የበጎቹ እረኛ ነው፤
3በር ጠባቂው በሩን ይከፍትለታል፤ በጎቹም
ድምፁን ይሰማሉ:: የራሱንም በጎች በየስ
ማቸው እየጠራ ያወጣቸዋል:: 4የራሱ የሆኑ
ትንም ሁሉ ካወጣ በኋላ ፊት ፊታቸው
ይሄዳል፤ በጎቹም ድምፁን ስለሚያውቁ
ይከተሉታል:: 5እንግዳ የሆነውን ግን ድምፁን
ስለማያውቁ ከእርሱ ይሸሻሉ እንጂ ፈጽሞ
አይከተሉትም::” 6ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ነገራ
ቸው፤ እነርሱ ግን ምን እንደ ነገራቸው
አላስተዋሉም::

7ስለዚህ ኢየሱስ ዳግም እንዲህ አላቸው፤
“እውነት እላችኋለሁ፤ የበጎች በር እኔ
ነኝ:: 8ከእኔ በፊት የመጡት ሁሉ ሌቦችና
ቀማኞች ነበሩ፤ በጎቹ ግን አልሰሟቸውም::
9በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ በኩል የሚገባ ሁሉ
ይድ ናል^፤ ይገባል፤ ይወጣልም፤ መሰ
ማሪያም ያገኛል:: 10ሌባው ሊሰርቅ፣ ሊ
ገድልና ሊያጠፋ ብቻ ይመጣል፤ እኔ
ግን ሕይወት እንዲኖራቸውና እንዲ
ትረፈረፍላቸው መጥ ቻለሁ::”

11“መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ መልካም እረኛ
ሕይወቱን ስለ በጎቹ አሳልፎ ይሰጣል፤
12ተቀ ጣሪው እረኛ ግን በጎቹ የእርሱ
ስላልሆኑ፣ ተኵላ ሲመጣ ጥሎአቸው
ይሸሻል፤ ተኵላ ውም በጎቹን ይነጥቃል፤
ይበትናቸዋልም:: 13የሚሸሸውም ተቀጣሪ
ስለ ሆነና ለበጎቹ ደንታ ስለሌለው ነው::

14“መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ በጎቼን ዐ
ውቃ ለሁ፤ እነርሱም ያውቁኛል፤ 15ይህም
አብ እኔን

9፥22 ቀኍ34፤ ሉቃ6፥22፤ዮሐ7፥13 12፥42፤16፥2
9፥23 ቀኍ21
9፥24 ቀኍ16፤ ኢሱ7፥19
9፥27 ቀኍ15
9፥28 ዮሐ5፥45
9፥29 ዮሐ8፥14
9፥31 ዘፍ18፥23-32፤መዝ34፥15፡16፤ 66፥18፤145፥19፡20፤ ምሳ15፥29፤ ኢሳ1፥15፤59፥1፡2፤ ዮሐ 15፥7፤ 1ዮሐ5፥14-15፤ ያዕ5፥16-18
9፥33 ቀኍ16፤ ዮሐ3፥2
9፥34 ቀኍ2፡22፡35፤ ኢሳ66፥5
9፥35 ማቴ8፥20፤ ዮሐ3፥15
9፥36 ሮሜ10፥14
9፥37 ዮሐ4፥26
9፥38 ማቴ28፥9
9፥39 ማቴ13፥13፤ ሉቃ4፥18፤ዮሐ3፥19፤ 5፥22፤12፥47
9፥40 ሮሜ2፥19
9፥41 ዮሐ15፥22፡24

10፥1 ቀኍ8፡10
10፥2 ቀኍ11፡14፤ ማር6፥34
10፥3 ቀኍ4፡5፡14፡16፡27
10፥4 ቀኍ3
10፥6 ማር9፥32፤ ዮሐ16፥25
10፥7 ቀኍ9፤ ዮሐ6፥35
10፥8 ቀኍ1፤ኤር 23፥1፡2፤ሕዝ34፥2
10፥10 መዝ65፥11፤ዮሐ1፥4፤3፥15፡16፤5፥40፤20፥31፤ ሮሜ5፥17
10፥11 ቀኍ14፡15፡17፡18፤መዝ23፥1፤ ኢሳ40፥11፤ ሕዝ34፥11-16፡23፤ ማቴ2፥6፤ሉቃ12፥32 ዮሐ6፥35፤15፥13፤ ዕብ13፥20፤ 1ጴጥ2፥25፤5፥4፤ 1ዮሐ3፥16፤ራእ7፥17
10፥12 ዘካ11፥16፡17
10፥14 ቀኍ11፡27፤ ዘፀ33፥12
10፥15 ቀኍ11፡17፡18፤ማቴ11፥27

^22 ወይም *መሲሑ*
^24 እውነት ለመናገር የሚደረግ መሐላ ነው ኢሱ (7፥19 ይመ)
*አንዳንድ የጥንት ቅጆች ‘የእግዚአብሔር ልጅ’ ይላሉ::
^9 ወይም *በደኅና ይጠበቃል*

እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደ
ማውቀው ነው። ሕይወቴንም ስለ በጎቼ
አሳልፌ እሰጣ
ለሁ። 16ከዚህ ጕረኖ ያልሆኑ ሌሎች በጎች
አሉኝ፤ እነርሱንም ማምጣት አለብኝ።
እነር ሱም ድምፄን ይሰማሉ፤ አንድ መንጋም
ይሆናሉ፤ እረኛውም አንድ። 17መልሼ ለማ
ንሣት ሕይወቴን አሳልፌ ስለምሰጥ አባቴ
ይወደኛል። 18ሕይወቴን በራሴ ፈቃድ
አሳልፌ እሰጣለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወ
ስዳትም፤ አሳልፌ ለመስጠትም ሆነ ለማ
ንሣት ሥልጣን አለኝ፤ ይህን ትእዛዝ የተቀ
በልሁትም ከአባቴ ነው።”

19ከዚህም ቃል የተነሣ በአይሁድ መካከል
እንደ ገና መለያየት ተፈጠረ። 20ብዙዎቹ
ም፣ “ጋኔን ያደረበት እብድ ነው፤ ለምን
ትሰሙ ታለችሁ?” አሉ።

21ሌሎች ግን፣ “ይህ ጋኔን ያደረበት ሰው
ንግግር አይደለም፤ ጋኔን የዐይነ ስውርን ዐይን
መክፈት ይችላልን?” አሉ።

### የአይሁድ አለማመን

22በኢየሩሳሌምም የቤተ መቅደስ መታደስ
በዓል[ሰ] ሆነ፤ ጌታውም ክረምት ነበረ፤
23ኢየሱስም በቤተ መቅደስ ግቢ፣ በሰሎሞን
መመላለሻ ያልፍ ነበር፤ 24አይሁድም ከበ
ውት፣ “እስከ መቼ ልባችንን አንጠልጥለህ
ታቈየናለህ? አንተ ክርስቶስ[ሸ] ከሆንህ በግ
ልጽ ንገረን” አሉት።

25ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሳላቸው፤ “እኔ
ነግሬአችሁ ነበር፤ እናንተ ግን አታምኑም፤
በአባቴ ስም የማደርጋቸው ታምራትም ስለ እኔ
ይናገራሉ፤ 26እናንተ ግን በጎቼ ስላልሆናችሁ
አታምኑም፤ 27በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤
እኔ
ዐውቃቸዋለሁ፤ እነርሱም ይከተሉኛል፤ 28እኔ
የዘላለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ፤ ከቶ አይጠ
ፉም፤ ከእጄም ሊነጥቃቸው የሚችል ማንም
የለም። 29እነርሱን የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ
ይበልጣል[ቀ]፤ ከአባቴም እጅ ማንም ሊነጥ
ቃቸው አይችልም። 30እኔና አብ አንድ
ነን።”

31አይሁድ ሊወግሩት እንደ ገና ድንጋይ
አነሡ፤ 32ኢየሱስ ግን፣ “ከአብ የሆኑ ብዙ
ታላላቅ ታምራትን አሳየኋችሁ፤ ታዲያ
ከእነዚህ ስለ የትኛው ትወግሩኛላችሁ?” አላቸው።

33አይሁድም፣ “የምንወግርህ፣ ተራ ሰው ሆነህ
ሳለህ፣ ራስህን አምላክ በማድረግ፣ የስድብ
ቃል ስለተናገርህ ነው እንጂ ከእነዚህ ስለ
የትኛውም አይደለም” ብለው መለሱለት።

34ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
“በሕጋችሁ፣ ‘እናንተ አማልክት ናችሁ
አልሁ’ ተብሎ አልተጻፈምን? 35የእግዚአብሔር

10፥16 ኢሳ56፥8፤
ሕዝ34፥23፤37፥24፤
ዮሐ11፥52፤17፥20:
21፤ሐሥ10፥34:35፤
ኤፌ2፥11-19
10፥17ቀኁ11:15:18
10፥18 ማቴ26፥
53፤ዮሐ15፥10፤ፊል
2፥8፤ዕብ5፥8
10፥19 ዮሐ6፥52
10፥20 ማር3፥21:
22፤2ነገ9፥11፤
ኤር29፥26
10፥21 ዘፀ4፥11፤
ማቴ4፥24፤
ዮሐ9፥32:33
10፥23 ሐሥ3፥
11፤5፥12
10፥24 ዮሐ1፥19፤
16፥25:29፤
ሉቃ22፥67
10፥25 ዮሐ4፥26፤
5፥36፤8፥58፤14፥11
10፥26 ዮሐ8፥47
10፥27 ቀኁ4:14
10፥28 ኢሳ 66፥
22፤ማቴ25፥46፤
ዮሐ6፥39
10፥29 ዮሐ14፥
28፤17፥2:6:24
10፥30 ዘዳ6፥4፤
ዮሐ17፥21-23
10፥31 ዮሐ8፥59
ዮሐ5፥18 10፥34
መዝ82፥
6፤ዮሐ8፥17፤12፥34፤
15፥25፤ ሮሜ
3፥19፤1ቆሮ14፥21
10፥35 ዕብ4፥12፤
ማቴ5፥18
10፥33 ዘሌ24፥
16፤ማቴ26፥63-66፤
10፥36 ኤር1፥5፤
ዮሐ3፥17፤ 5፥17:
18፤6፥69
10፥37 ቀኁ25
10፥38 ዮሐ14፥10:
11:20፤17፥21
10፥39 ሉቃ4፥30፤
ዮሐ7፥30፤8፥59
10፥40 ዮሐ1፥28
10፥41
ዮሐ1፥26:27:
30:34፤ 2፥11
10፥42 ዮሐ7፥31
11፥1 ማቴ21፥17፤
ሉቃ10፥38
11፥2 ማር14፥3፤
ሉቃ7፥38፤ዮሐ12፥3
11፥3 ቀኁ5:36
11፥4 ቀኁ40
11፥7 ዮሐ10፥40
11፥8 ማቴ23፥7፤
ዮሐ8፥59፤10፥31
11፥9 ዮሐ9፥4፤
12፥35
11፥11 ቀኁ3፤
ማቴ9፥24

ቃል የመጣላቸውን ‘አማልክት’ ካላቸውና፣
መጻሕፍም ሊሻር የማይቻል ከሆነ፣ 36ታዲያ፣
‘የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ’ ስላልሁ፣ አብ ለራሱ
ለይቶ የቀደሰውንና ወደ ዓለም የላከውን፣
ተሳድበሃል ብላችሁ ለምን ትወነጅሉኛላችሁ?
37አባቴ የሚያደርገውን ባላደርግ አትመኑኝ፤
38የማደርገው ከሆነ ግን እኔን ባታምኑኝ
እንኳ፣ አብ በእኔ እንዳለ እኔም በአብ
እንዳለሁ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ ታምራ
ቱን እመኑ።” 39እንደ ገናም ሊይዙት ሞከሩ፤
እርሱ ግን ከእጃቸው አመለጠ።

40ከዚያም ኢየሱስ፣ ቀደም ሲል ዮሐ
ንስ ያጠምቅበት ወደ ነበረበት፣ ወደ
ዮርዳኖስ ማዶ ተመለሰ፤ በዚያም ሰነበተ፤
41ብዙ ሰዎችም ወደ እርሱ መጡ።
እነርሱም፣ “ዮሐንስ አንድም ታምራዊ
ምልክት አላደረ ገም፤ ነገር ግን ስለዚህ ሰው
የተናገረው ሁሉ እውነት ነበረ” አሉ። 42በዚ
ያም ስፍራ ብዙ ዎች በኢየሱስ አመኑ።

### የአልዓዛር መሞት

11 በማርያምና በእኅቷ በማርታ መንደር
በቢታንያ ይኖር የነበረው አልዓዛር
ታሞ ነበር።

2ይህች ወንድሟ አልዓዛር የታመመባት
ማርያም፣ በጌታ ላይ ሽቱ አፍስሳ እግሩን
በጠጕሯ ያበሰችው ነበረች። 3እኅትማማቾቹም፣
“ጌታ ሆይ፤ የምትወደው ሰው ታሞአል”
ብለው መልእክት ላኩበት።

4ኢየሱስ ይህን በሰማ ጊዜ፣ “ይህ ሕመም
የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ይከብር ዘንድ
ለእግዚአብሔር ክብር ነው እንጂ ለሞት
የሚያ ደርስ አይደለም” አለ። 5ኢየሱስም
ማርታን፣ እኅቷንና አልዓዛርን ይወዳቸው
ነበር። 6ሆኖም አልዓዛር መታመሙን በሰማ
ጊዜ በነበረበት ስፍራ ሁለት ቀን ቈየ።

7ከዚህም በኋላ ደቀ መዛሙርቱን፣ “ወደ
ይሁዳ እንመለስ” አላቸው።

8እነርሱም፣ “መምህር ሆይ፤ ከጥቂት ጊዜ
በፊት አይሁድ በድንጋይ ሊወግሩህ እየፈለጉህ
ነበር፤ እንደ ገና ወደዚያ ትሄዳለህን?” አሉት።

9ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “ቀኑ
ዐሥራ ሁለት ሰዓት ብርሃን አይደለምን?
ከዚህ ዓለም ብርሃን የተነሣ ስለሚያይ በቀን
የሚመላለስ አይሰናከልም፤ 10የሚሰናከለው
ግን በሌሊት የሚመላለስ ነው፤ ብርሃን የለው
ምና።”

11ይህን ከነገራቸው በኋላ፣ “ወዳጃችን አልዓ
ዛር ተኝቶአል፤ እኔም ከእንቅልፉ ላስነሣው
እሄዳለሁ” አላቸው።

12ደቀ መዛሙርቱም፣ “ጌታ ሆይ፤ ተኝቶ

[ሰ]22 “ሁኑካ” ማለት ነው
[ሸ]24 ወይም *መሲሑ*
[ቀ]29 ብዙ የጥንት ቅጆች *አባቴ የሰጠኝ ከሁሉ ይበልጣል* ይላሉ

ከሆነስ ይድናል” አሉት። 13ኢየሱስ ይህን
የነገራቸው ስለ ሞቱ ነበር፤ ደቀ መዛሙርቱ
ግን እንቅልፍ ስለ መተኛቱ የተናገረ
መሰላቸው።
14ስለዚህም በግልጽ እንዲህ አላቸው፤
“አልዓዛር ሞቶአል፤ 15ታምኑ ዘንድ፣ በዚያ
ባለመኖሬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል፤
አሁን ግን ወደ እርሱ እንሂድ።”
16ከዚያም ዲዲሞስ የተባለው ቶማስ
ለተቀሩት ደቀ መዛሙርት፣ “እኛም
ሄደን ከእርሱ ጋር እንሙት” አላቸው።

## ኢየሱስ የአልዓዛርን እኅቶች ማጽናናቱ

17ኢየሱስ ሲደርስ አልዓዛር ከተቀበረ አራት
ቀን ሆኖት ነበር። 18ቢታንያ ከኢየሩ
ሳሌም አሥራ አምስት ምዕራፍ[ሀ] ያህል
ትርቅ ነበር። 19ብዙዎች አይሁድም
ማርታንና ማርያምን ስለ ወንድማቸው
ሞት ሊያጽናኗቸው መጥተው ነበር፤ 20
ማርታ የኢየሱስን መምጣት ሰምታ
ልትቀበለው ወጣች፤ ማርያም ግን በቤት
ቀርታ ነበር።
21ማርታም ኢየሱስን እንዲህ አለችው፤
“ጌታ ሆይ፤ አንተ በዚህ ብትሆን ኖሮ፣
ወንድሜ ባልሞተ ነበር። 22አሁንም ቢሆን
የምትለምነውን ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚሰጥህ
ዐውቃለሁ።”
23ኢየሱስም፣ “ወንድምሽ ይነሣል” አላት።
24ማርታም፣ “በመጨረሻው ቀን፣ በትንሣኤ
እንደሚነሣ ዐውቃለሁ” አለችው።
25ኢየሱስም እንዲህ አላት፤ “ትንሣኤና ሕይ
ወት እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚያምን ቢሞት እንኳ
በሕይወት ይኖራል፤ 26በእኔ የሚኖር፣
የሚያምንብኝም ከቶ አይሞትም፤ ይህን
ታምኛለሽን?”
27እርሷም፣ “አዎን ጌታ ሆይ፤ አንተ ወደ
ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ[+] የእግዚአብሔር
ልጅ መሆንህን አምናለሁ” አለችው።
28ይህን ካለች በኋላ፣ ተመልሳ እኅቷን
ማርያምን ለብቻዋ ጠርታ፣ “መምህሩ መጥ
ቷል፤ ይፈልግሻልም” አለቻት። 29ማርያ
ምም ይህን እንደ ሰማች፣ ፈጥና ተነሥታ
ወደ እርሱ ሄደች። 30በዚህ ጊዜ ኢየሱስ፣
ማርታ እርሱን በተቀበለችበት ቦታ ነበር
እንጂ፣ ገና ወደ መንደር አልገባም ነበር።
31ማርያምን ሲያጽናኑ በቤት ውስጥ የነበሩ
አይሁድም፣ ብድግ ብላ መውጣቷን ሲያዩ፣
ወደ መቃብሩ ሄዳ የምታለቅስ መስሎአቸው
ተከተሏት።
32ማርያምም ኢየሱስ ወደ ነበረበት ቦታ
ደርሳ እንዳየችው፣ እግሩ ላይ ተደፍታ፣ “ጌታ
ሆይ፤ አንተ እዚህ ብትሆን ኖሮ፣ ወንድሜ

11፥13 ማቴ9፥24
11፥16 ማቴ10፥3፤ ዮሐ14፥5፤20፥24-28፤21፥2፤ሐሥ1፥13
11፥17 ቊ6:39
11፥18 ቊ1፤ ማቴ21፥17
11፥19 ቊ31፤ ኢዮ2፥11
11፥20 ሉቃ10፥38-42
11፥21 ቊ32:37
11፥22 ቊ41:42
11፥24 ዳን12፥2፤ ዮሐ5፥28:29፤6፥39:40፤ሐሥ24፥15
11፥25 ዮሐ1፥4፤ 3፥15፤6፥35
11፥26 ማቴ25፥46፤ዮሐ3፥15
11፥27 ማቴ4፥3፤ ሉቃ2፥11፤ዮሐ6፥14
11፥28 ማቴ26፥18፤ዮሐ13፥13
11፥30 ቊ20
11፥31 ቊ19
11፥32 ቊ21
11፥33 ቊ38፤ ዮሐ12፥27
11፥35 ሉቃ19፥41
11፥36 ቊ3
11፥37 ቊ21:32፤ ዮሐ9፥6:7
11፥38 ቊ33፤ ማቴ27፥60፤ ሉቃ24፥2፤ዮሐ20፥1
11፥39 ቊ17
11፥40 ቊ4:23-25
11፥41 ማቴ11፥25፤ዮሐ17፥1
11፥42 ዮሐ3፥17፤ 12፥30
11፥43 ሉቃ7፥14
11፥44 ዮሐ19፥40፤ 20፥7
11፥45 ቊ19፤ ዘፀ14፥31፤ዮሐ2፥23፤ 7፥31
11፥47 ቊ57፤ ማቴ5፥22፤26፥3፤ ዮሐ2፥11

ባልሞተ ነበር” አለችው።
33ኢየሱስም እርሷ ስታለቅስ፣ ተከትለዋትም
የመጡት አይሁድም ሲያለቅሱ ባየ ጊዜ
መንፈሱ በኀዘን ታውኮ፣ 34“የት ነው ያኖራ
ችሁት?” ሲል ጠየቀ።
እነርሱም፣ “ጌታ ሆይ፤ መጥተህ እይ”
አሉት።
35ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ።
36አይሁድም፣ “እንዴት ይወደው እንደ
ነበር አያችሁ!” አሉ።
37ከእነርሱ አንዳንዶቹ ግን፣ “የዐይነ ስውሩን
ዐይን የከፈተ፣ ይህም ሰው እንዳይሞት
ማድረግ አይችልም ነበር?” አሉ።

## ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ማስነሣቱ

38ኢየሱስ ልቡ ዳግመኛ በኀዘን ተነክቶ
ወደ መቃብሩ መጣ፤ መቃብሩም በድንጋይ
የተገጠመ ዋሻ ነበር፤ 39እርሱም፣ “ድንጋዩን
አንሡት” አለ።
የሟቹም እኅት ማርታ፣ “ጌታ ሆይ፤ አሁን
ማ አራት ቀን ስለ ቈየ ይሸታል”
አለችው።
40ኢየሱስም፣ “ብታምኚስ የእግዚአብሔርን
ክብር ታያለሽ ብዬ አልነገርሁሽም?”
አላት።
41ስለዚህ ድንጋዩን አነሡ። ኢየሱስም ወደ
ላይ ተመልክቶ እንዲህ አለ፤ “አባት ሆይ፤
ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ፤ 42ሁልጊዜም
እንደምትሰማኝ ዐውቃለሁ፤ ይህን መናገሬ
ግን በዚህ የቆሙ ሰዎች አንተ እንደ
ላክኸኝ ያምኑ ዘንድ ነው።”
43ኢየሱስ ይህን ካለ በኋላ በታላቅ ድምፅ፣
“አልዓዛር፣ ና ውጣ!” ብሎ ተጣራ። 44የሞ
ተውም ሰው እጅና እግሩ በቀጭን ስስ ጨርቅ
እንደ ተጠቀለለ፣ ፊቱም በሻሽ እንደ ተጠ
መጠመ ወጣ።
ኢየሱስም “መግነዙን ፍቱለትና ይሂድ”
አላቸው።

## ኢየሱስን ለመግደል የተደረገ ሤራ

45ስለዚህ ወደ ማርያም ከመጡት፣ ኢየሱስ
ያደረገውን ካዩት አይሁድ ብዙዎች በእርሱ
አመኑ። 46አንዳንዶቹ ግን ሄደው ኢየሱስ
ያደረገውን ለፈሪሳውያን ተናገሩ፤ 47ከዚ
ያም የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን የአይ
ሁድን ሸንጎ ስብሰባ ጠሩ።
እነርሱም እንዲህ አሉ፤ “ይህ ሰው ብዙ
ታምራዊ ምልክቶችን እያደረገ ስለ ሆነ
ምን ብናደርግ ይሻላል? 48እንዲሁ
ብንተወው ሰው ሁሉ በእርሱ ያምናል፤ ሮ
ማውያንም መጥ ተው ሥፍራችንንና[ቶ] ሕ
ዝባችንን ይወስዱ ብናል።”

[ሀ]18 ሦስት ኪሎ ሜትር ያህል ነው
[+]27 ወይም *መሲሕ*
[ቶ]48 ወይም *መቅደሳችንን*

49ከመካከላቸውም አንዱ፣ በዚያ ዓመት ሊቀ
ካህናት የነበረው ቀያፋ እንዲህ ሲል ተና
ገረ፤ “እናንተ እኮ ምንም አታውቁም!
50ሕዝቡ ሁሉ ከሚጠፋ ስለ ሕዝቡ አንድ
ሰው ቢሞት የሚሻል መሆኑን አታስተ
ውሉም።”
51ይህን ያለው ከራሱ አልነበረም፤ ነገር ግን
በዚያች ዓመት ሊቀ ካህናት እንደ መሆኑ፣
ኢየሱስ ለአይሁድ ሕዝብ እንደ ሚሞት
ትንቢት መናገሩ ነበር፤ 52ለዚያም ሕዝብ
ብቻ ሳይሆን፣ የተበተኑትን የእግዚአብሔርን
ልጆች በአንድነት ለመሰብሰብ ነው። 53ከዚ
ያን ቀን ጀምሮም፣ ሊገድሉት አሤሩ።
54ስለዚህ ኢየሱስ ከዚያ ወዲያ በአይሁድ
መካከል በይፋ አልተመላለሰም፤ ነገር ግን
በምድረ በዳ አጠገብ ወደምትገኝ ኤፍሬም
ወደ ተባለች መንደር ገለል አለ፤ በዚያም
ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሰነበተ።
55የአይሁድ ፋሲካ እንደ ተቃረበም፣ በዓሉ
ከመድረሱ በፊት የመንጻት ሥርዐት ለማ
ድረግ ብዙዎች ከአገር ቤት ወደ ኢየሩ
ሳሌም ወጡ። 56ኢየሱስንም ይፈልጉት ነበር፤
በቤተ መቅደስም ቆመው፣ “ምን ይመስላ
ችኋል? ለበዓሉ አይመጣ ይሆን?” ተባባሉ።
57የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ግን ኢየሱስን
ይይዙት ዘንድ የት እንዳለ የሚያውቅ
ሰው እንዲጠቍም ትእዛዝ ሰጥተው ነበር።

## ኢየሱስ በቢታንያ ሽቱ መቀባቱ

12፥1-8 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥6-13፤ ማር 14፥3-9፤ ሉቃ 7፥37-39

12 የፋሲካ በዓል ስድስት ቀን ሲ
ቀረው ኢየሱስ፣ ከሞት ያስነሣው
አልዓዛር ወደሚኖርበት፣ ወደ ቢታንያ
መጣ። 2በዚያም ለኢየሱስ ሲባል ራት
ተዘጋጀ። ማርታ ስታገለግል፣ አልዓዛር
ከእርሱ ጋር በማእድ ከተቀመጡት አንዱ
ነበር። 3ማርያም ዋጋው ውድ የሆነ፣ ግማሽ
ሊትር[ጎ] ንጹሕ የናርዶስ ሽቱ አምጥታ በኢ
የሱስ እግር ላይ አፈሰሰች፤ እግሩንም በጠ
ጕሯ አበሰች፤ ቤቱንም የሽቱው መዓዛ
ሞላው።
4ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፣ ኋላ አሳልፎ
የሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ ግን በመቃወም
እንዲህ አለ፤ 5“ይህ ሽቱ በሦስት መቶ ዲናር
ተሸጦ ገንዘቡ ለድኾች ለምን አልተሰጠም?”
6ይህን የተናገረው የገንዘብ ከረጢት ያዥ
በመሆኑ፣ ከሚቀመጠው ለራሱ የሚጠቀም
ሌባ ስለ ነበር እንጂ ለድኾች ተቈርቍሮ
አልነበረም።
7ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ “ይህ ሽቱ ለቀ
ብሬ ቀን የታሰበ ስለሆነ እንድታቈየው
ተዋት፤ 8ድኾች ምንጊዜም ከእናንተ ጋር
ናቸው፤ እኔን ግን ሁል ጊዜ አታገኙኝም።”
9በዚህ ጊዜ ብዙ አይሁድ ኢየሱስ በዚያ

11፥49 ቀኍ51፤ ማቴ 26፥3፤ ዮሐ18፥13፡14
11፥50 ዮሐ18፥14
11፥52 ኢሳ49፥6፤ ዮሐ10፥16
11፥53 ማቴ12፥14
11፥54 ዮሐ7፥1
11፥55 ዘፀ12፥13፡23፡27፤2ዜና30፥17፡18፤ማቴ26፥1፡2፤ማር14፥1፤ዮሐ13፥1
11፥56 ዮሐ7፥11
12፥1 ማቴ21፥17፤ ዮሐ11፥55
12፥2 ሉቃ10፥38-42
12፥3 ማር14፥3፤ ዮሐ11፥2
12፥4 ማቴ10፥4
12፥6 ዮሐ13፥29
12፥7 ዮሐ19፥40
12፥8 ዘዳ15፥11
12፥9 ዮሐ11፥43፡44
12፥11 ቀኍ17፡18፤ ዮሐ11፥45፤7፥31
12፥13 ዘሌ23፥40፤ መዝ118፥25፡26፤ ዮሐ1፥49
12፥15 ዘካ9፥9
12፥16 ቀኍ23፤ ማር9፥32፤ዮሐ2፥22፤7፥39
12፥17 ዮሐ11፥42
12፥18 ቀኍ11፤ ሉቃ19፥37
12፥19 ዮሐ11፥47፡48
12፥20 ዮሐ7፥35፤ ሐሥ11፥20
12፥21 ማቴ11፥21
12፥23 ማቴ26፥18፤ ዮሐ13፥32፤17፥1
12፥24 1ቆሮ15፥36

መኖሩን ዐውቀው መጡ፤ የመጡትም ኢየ
ሱስን ብለው ብቻ ሳይሆን፣ እርሱ ከሙታን
ያስነሣውን አልዓዛርንም ለማየት
ነበር። 10ስለዚህ የካህናት አለቆች አልዓዛርን
ጭምር ለመግደል ተማከሩ፤ 11ይህም
በእርሱ ምክ ንያት ብዙ አይሁድ ወደ ኢ
የሱስ እየሄዱ ያምኑበት ስለ ነበር ነው።

## ኢየሱስ በክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ

12፥12-15 ተጓ ምብ - ማቴ 21፥4-9፤ ማር 11፥7-10፤ ሉቃ 19፥35-38

12በማግሥቱም ለበዓሉ የመጣው ብዙ ሕ
ዝብ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም እየመጣ
መሆኑን ሰሙ፤ 13የዘንባባም ዝንጣፊ ይዘው
ሊቀበሉት ወጡ፤ ድምፃቸውንም ከፍ
አድርገው እንዲህ አሉ፤
“ሆሣዕና![ነ]
“በጌታ ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው!”
“የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው!”
14ኢየሱስም የአህያ ውርንጭላ አግኝቶ
ተቀመጠበት፤ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤
15“የጽዮን ልጅ ሆይ፤ አትፍሪ፤
እነሆ፤ ንጉሥሽ በአህያ ግልገል ተቀምጦ
ይመጣል።”
16ደቀ መዛሙርቱ ይህን ሁሉ በመጀመሪያ
አላስተዋሉም፤ ስለ እርሱ የተጻፉትንና
ለእርሱም የተደረጉትን ልብ ያሉት ኢየሱስ
ከከበረ በኋላ ነበር።
17አልዓዛርን ከመቃብር ጠርቶ
ከሙታን ባስነሣበት ጊዜ፣ ከእርሱ ጋር
የነበሩ ሰዎች መነሣቱን ይመሰክሩ ነበር።
18ብዙ ሰዎችም ይህን ታምራዊ ምልክት
ማድረጉን ስለ ሰሙ ሊቀበሉት ወጡ።
19ስለዚህም ፈሪሳ ውያን እርስ በርሳቸው፣
“እንግዲህ ምን ማድረግ ይቻላል?
አያችሁ! ዓለሙ ሁሉ ግልብጥ ብሎ
ተከትሎታል” ተባባሉ።

## ኢየሱስ ስለ ሞቱ አስቀድሞ ተናገረ

20ለአምልኮ ወደ በዓሉ ከወጡት መካከል
የግሪክ ሰዎችም ነበሩ። 21እነርሱም በገሊላ
ከምትገኘው ከቤተ ሳይዳ ወደ ሆነው ሰው፣
ወደ ፊልጶስ መጥተው፣ “ጌታው፤ እባክህን፣
ኢየሱስን ለማየት እንፈልጋለን” አሉት።
22ፊልጶስም ፤ ለእንድርያስ ሊነግረው ሄደ፤
እንድርያስና ፊልጶስም ለኢየሱስ ነገሩት።
23ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
“የሰው ልጅ የሚከብርበት ሰዓቱ ደርሶአል፤
24እውነት እላችኋለሁ፤ የስንዴ ቅንጣት መሬት
ላይ ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤

ጎ3 በግሪኩ ሊትራ ይላል
ነ13 በዕብራይስጡ አድን! ማለት ሲሆን የምስጋና ድምፅ ነው

ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች። 25ሕይ
ወቱን የሚወድ ያጣታል፤ በዚህ ዓለም ሕይወቱ
ን የሚጠላ ግን ለዘላለም ሕይወት ይጠ
ብቃ ታል። 26የሚያገለግለኝ ቢኖር
ይከተለኝ፤ እኔም ባለሁበት አገልጋዬም በዚያ
ይሆናል፤ የሚያገለግለኝንም አባቴ ያከበ
ብረዋል።
27"አሁንስ ነፍሴ ተጨነቀች፤ ምን ልበል?
አባት ሆይ፤ ከዚች ሰዓት ታድነኝ? የለም፤
ይሁን የመጣሁት ለዚህች ሰዓት ነውና።
28አባት ሆይ፤ ስምህን አክብረው።"
ከዚያም፣ "አክብሬዋለሁ፤ ደግሞም አከብረ
ዋለሁ" የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ።
29በዚያ የነበሩት፣ ድምፁን የሰሙት
አያሌ ሰዎች፣ "ነጐድጓድ ነው" አሉ፤ ሌሎች
ደግሞ፣ "መልአክ ተናገረው" አሉ።
30ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ "ይህ ድምፅ የመ
ጣው ስለ እኔ ሳይሆን ስለ እናንተ ነው፤
31ይህ ዓለም የሚፈረድበት ጊዜ አሁን ነው፤
የዚህም ዓለም ገዥ አሁን ወደ ውጭ ይጣ
ላል። 32እኔ ግን ከምድር ከፍ ከፍ ባልሁ ጊ
ዜ ሰውን ሁሉ ወደ ራሴ እስባለሁ።"
33ይህን የተናገረው በምን ዐይነት ሞት
እንደሚሞት ለማመልከት ነበር።
34ሕዝቡም፣ "እኛስ ክርስቶስ[ኘ] ለዘላለም
እንደሚኖር ከሕግ ሰምተናል፤ ታዲያ፣ 'የሰው
ልጅ ከፍ ከፍ ማለት አለበት' እንዴት
ትላለህ? ይህስ 'የሰው ልጅ' ማን ነው?"
አሉት።
35ኢየሱስም እንዲህ ሲል ተናገራቸው፤
"ከእንግዲህ ለጥቂት ጊዜ ብርሃን አለላችሁ፤
ጨለማ ሳይመጣባችሁ፣ ብርሃን ሳለላችሁ
ተመላለሱ፤ በጨለማ የሚመላለስ ወዴት
እንደሚሄድ አያውቅም። 36የብርሃን ልጆች
እንድትሆኑ ብርሃን ሳለላችሁ በዚህ ብርሃን
እመኑ።" ኢየሱስ ይህን ተናግሮ እንደ
ጨረሰ ተለያቸው፤ ተሰወረባቸውም።

### አይሁድ ባለማመን መጽናታቸው

37ኢየሱስ እነዚህን ታምራዊ ምልክቶች
ሁሉ በፊታቸው ቢያደርግም እንኳ፣
አሁንም አላመኑበትም፤ 38ይኸውም ነቢዩ
ኢሳይያስ፣

"ጌታ ሆይ፤ ምስክርነታችንን ማን አመነ?
የጌታ ክንድስ ለማን ተገለጠ?" ያለው ቃል
እንዲፈጸም ነው።

39ስለዚህ ማመን አልቻሉም፤ ይህም ኢሳ
ይያስ በሌላ ቦታ እንዲህ ሲል እንደ ተናገረው
ነው፤

40"ዐይናቸውን አሳውሮአል፤
ልባቸውንም አደንድኖአል፤
ስለዚህ በዐይናቸው አያዩም፤
በልባቸውም አያስተውሉም፤

12፥25 ማቴ10፥39፤ 25፥46፤ማር8፥35፤ ሉቃ14፥26፤ 17፥33
12፥26 ዮሐ14፥3፤ 17፥24፤2ቆሮ5፥8፤ ፊል1፥23፤1ተሰ4፥17
12፥27 ቀኍ23፤ማቴ 11፥25፤26፥38፡39፤ ዮሐ11፥33፡38፤13፥21
12፥28 ማቴ3፥17
12፥30 ዘፀ19፥9፤ ዮሐ11፥42
12፥31 ዮሐ14፥30፤ 16፥11፤2ቆሮ4፥4፤ ኤፌ2፥2፤1ዮሐ4፥4፤ 5፥19
12፥32 ቀኍ34፤ ኢሳ1፥10፤ዮሐ3፥14፤ 6፥44፤8፥28
12፥33 ዮሐ18፥32፤ 21፥19
12፥34 መዝ110፥4፤ ኢሳ9፥7፤ሕዝ37፥25፤ ዳን7፥14፤ማቴ8፥20፤ ዮሐ3፥14፤10፥34
12፥35 ቀኍ46፤ ኤፌ5፥8፤1ዮሐ1፥6፤ 2፥11
12፥36 ቀኍ46፤ ሉቃ16፥8፤ዮሐ8፥59
12፥37 ዮሐ2፥11
12፥38 ኢሳ53፥1፤ ሮሜ10፥16
12፥40 ኢሳ6፥10፤ ማቴ13፥13፡15
12፥41 ኢሳ6፥1-4፤ ሉቃ24፥27
12፥42 ቀኍ11፤ ዮሐ7፥13፡48፤9፥22
12፥43 1ሳሙ15፥ 30፤ ሮሜ2፥29
12፥44ማቴ10፥40፤ ዮሐ5፥24
12፥45 ዮሐ14፥9
12፥46 ዮሐ1፥4
12፥47 ዮሐ3፥17
12፥48 ዮሐ5፥45
12፥49 ዮሐ14፥31
12፥50ማቴ25፥46፤ ዮሐ14፥24
13፥1 ማቴ26፥18፤ ዮሐ11፥55፤16፥28
13፥2 ማቴ10፥4
13፥3 ማቴ28፥18፤ ዮሐ8፥42፤16፥27፡ 28፡30፤17፥8
13፥4 ማቴ20፥28
13፥5 ሉቃ7፥44
13፥7 ቀኍ12

እንዳልፈውሳቸውም አይመለሱም።"
41ኢሳይያስ ይህን ያለው የኢየሱስን
ክብር ስላየ ነው፤ ስለ እርሱም ተናገረ።
42ይህም ቢሆን፣ ከአለቆች መካከል እንኳ
ሳይቀር ብዙዎች በእርሱ አመኑ፤ ይሁን
እንጂ ፈሪሳውያን ከምኵራብ
እንዳያስወጧቸው ስለ ፈሩ ማመናቸውን
አይገልጡም ነበር። 43ይህም የሆነው በእግዚ
አብሔር ከመመስገን ይልቅ በሰው
መመስገንን ስለ ወደዱ ነው።
44ከዚያም ኢየሱስ ድምፁን ከፍ አድርጎ
እንዲህ አለ፤ "ማንም በእኔ ቢያምን በእኔ
ብቻ ሳይሆን በላከኝም ማመኑ ነው፤ 45እኔንም
የሚያይ የላከኝን ያያል። 46በእኔ የሚያ
ምን በጨለማ እንዳይኖር ብርሃን ሆኜ ወደ
ዓለም መጥቻለሁ።
47"ቃሌን ሰምቶ በማይፈጽመው ላይ
የምፈርደው እኔ አይደለሁም፤ ዓለምን
ላድን እንጂ በዓለም ላይ ልፈርድ አልመ
ጣሁምና። 48በማይቀበለኝና ቃሌን በሚያ
ቃልል ላይ የሚፈርድበት አለ፤ የተናገ
ርሁት ቃል ራሱ በመጨረሻው ቀን ይፈር
ድበታል፤ ምክንያቱም 49እኔ ከራሴ አል
ተናገርሁም፤ ነገር ግን የላከኝ አብ ምን
እንደምናገርና እንዴት እንደምናገር አዘዘኝ።
50የእርሱ ትእዛዝ ወደ ዘላለም ሕይወት
እንደሚያደርስ ዐውቃለሁ፤ ስለዚህም የምለው
ሁሉ አብ እንድናገረው የነገረኝን ብቻ ነው።

### ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ማጠቡ

13 ጊዜው ልክ ከፋሲካ በዓል በፊት
ነበረ፤ ኢየሱስም ይህን ዓለም ትቶ
ወደ አብ የሚሄድበት ጊዜ እንደ
ደረሰ
ዐወቀ። በዓለም የነበሩትን፣ የራሱ የሆ
ኑትን ወደዳቸው፤ በፍጹም ፍቅሩም ወደ
ዳቸው።[ኣ]
2እራትም ቀርቦ ሳለ፣ ኢየሱስን አሳልፎ
እንዲሰጥ ዲያብሎስ የስምዖንን ልጅ የአስ
ቆሮቱን ይሁዳ ልብ አነሣሥቶ ነበር።
3ኢየሱስም፣ አብ ሁሉን ነገር በሥልጣኑ
ሥር እንዳደረገለት፣ ከእግዚአብሔር እንደ
ተላከና ወደ እግዚአብሔርም እንደሚመለስ
ዐውቆ፣ 4ከራት ተነሣ፤ መጐናጸፊያውን
አስቀመጠ፤ ወገቡንም በፎጣ ታጠቀ። 5ከዚ
ያም በመታጠቢያው ውሃ ጨምሮ የደቀ
መዛሙርቱን እግር እያጠበ በታጠቀው
ፎጣ ያብስ ጀመር።
6ወደ ስምዖን ጴጥሮስም መጣ፤ ጴጥሮስም፣
"ጌታ ሆይ፤ አንተ እግሬን ታጥባለህ?" አለው።
7ኢየሱስም መልሶ፣ "የማደርገውን አሁን
አታውቅም፤ በኋላ ግን ታስተውላለህ" አለው።

[ኘ]34 ወይም መሲሕ
[ኣ]1 ወይም እስከ መጨረሻው

[8]ጴጥሮስም፣ “የለም፤ እግሬን ከቶ አታጥ
ብም” አለው።
ኢየሱስም፣ “ካላጠብሁህማ ከእኔ ጋር ዕድል
ፈንታ የለህም” አለው።
[9]ስምዖን ጴጥሮስም፣ “ጌታ ሆይ፤ እን
ግዲያውስ እግሬን ብቻ ሳይሆን እጄንም
ራሴንም እጠበኝ” አለው።
[10]ኢየሱስም፣ “ገላውን የታጠበ ሰው የሚ
ያስፈልገው እግሩን ብቻ መታጠብ ነው፤
የቀረው አካሉ ግን ንጹሕ ነው። ሁላችሁም
ባትሆኑ፣ እናንተ ንጹሓን ናችሁ” አለው።
[11]“ሁላችሁም ንጹሓን አይደላችሁም” ያለው
አሳልፎ የሚሰጠው ማን እንደ ሆነ ያውቅ
ስለ ነበር ነው።
[12]እግራቸውን አጥቦ ካበቃ በኋላም፣
ልብሱን ለብሶ ተመልሶ በቦታው ተቀመጠ፤
እንዲህም አላቸው፣ “ያደረግሁላችሁን ታስተ
ውላላችሁን? [13] እናንተ፣ ‘መምህርና፣ ጌታ’
ትሉኛላችሁ፤ ትክክል ነው፣ እንደምትሉኝ እን
ዲሁ ነኝና። [14]እንግዲህ እኔ ጌታችሁና
መምህራችሁ ሆኜ ሳለሁ እግራችሁን ካጠ
ብሁ፣ እናንተም እንደ ዚሁ እርስ በርሳችሁ
እግራችሁን ልትተጣጠቡ ይገባችኋል።
[15]እኔ እንዳደረግሁላችሁ እናንተም እንደዚሁ
እን ድታደርጉ ምሳሌ ትቼላችኋለሁ።
[16]እውነት እላችኋለሁ፤ አገልጋይ ከጌታው፣
መልእክ ተኛም ከላከው አይበልጥም።
[17]እንግዲህ እነዚህን ነገሮች ዐውቃችሁ
ብትፈጽሙ ትባረካላችሁ።

## አልፎ እንደሚሰጥ ኢየሱስ መናገሩ

[18]“ስለ ሁላችሁ መናገሬ አይደለም፤ የመ
ረጥኋቸውን ዐውቃለሁ፤ ነገር ግን፣ ‘እንጀ
ራዬን አብሮኝ የቈረሰ ተረከዙን አነሣብኝ’
የሚለው የመጽሐፍ ቃል እንዲፈጸም ነው።
[19]“ሲፈጸም እኔ እንደ ሆንሁ ታምኑ ዘንድ፣
ይህ ከመሆኑ በፊት አሁን ነገርኋችሁ።
[20]እውነት እላችኋለሁ፤ እኔ የላክሁትን የሚ
ቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔን የተቀበለም
የላከኝን ይቀበላል።”
[21]ይህን ካለ በኋላም ኢየሱስ በመንፈሱ
ታውኮ፣ “እውነት እላችኋለሁ፤ ከእናንተ
አንዱ እኔን አሳልፎ ይሰጣል” ሲል በግልጽ
ተናገረ።
[22]ደቀ መዛሙርቱም ማንን ማለቱ
እንደ ሆነ ግራ ተጋብተው እርስ በርሳቸው
ተያዩ። [23]ከእነርሱ አንዱ፣ ኢየሱስ ይወደው
የነበረ ደቀ መዝሙር ወደ ኢየሱስ ደረት
ተጠግቶ ተቀምጦ ነበር። [24]ስምዖን ጴጥሮስም
ይህን ደቀ መዝሙር በምልክት ጠቅሶ “ማንን
ማለቱ እንደ ሆነ ጠይቀው” አለው።
[25]እርሱም ወደ ኢየሱስ ደረት ደገፍ ብሎ፣
“ጌታ ሆይ፤ ማን ይሆን?” ብሎ ጠየቀው።
[26]ኢየሱስም፣ “ይህን ቍራሽ እንጀራ
ከወጭቱ አጥቅሼ የምሰጠው እርሱ ነው”
አለው፤ ከዚያም ቍራሹን እንጀራ አጥቅሶ
ለስምዖን ልጅ ለአስቆሮቱ ይሁዳ ሰጠው።
[27]ይሁዳም ቍራሹን እንጀራ እንደ ተቀበለ
ወዲያው ሰይጣን ገባበት።
ኢየሱስም፣ “የምታደርገውን ቶሎ አድርግ”
አለው፤ [28]ይሁን እንጂ ኢየሱስ ለምን እንዲህ
እንዳለው ማንም አላወቀም ነበረ። [29]ይሁዳ
ገንዘብ ያዥ ስለ ነበር፣ አንዳንዶቹ ለበዓሉ
የሚያስፈልግ ነገር እንዲገዛ ወይም ለድኾች
እንዲሰጥ ኢየሱስ የተናገረው መሰላቸው።
[30]ይሁዳም ያን ቍራሽ እንጀራ እንደ
ተቀበለ ወጥቶ ሄደ፤ ሌሊትም ነበረ።

## ጴጥሮስ እንደሚክደው ኢየሱስ መናገሩ

13፥37-38 ተጓ ምብ – ማቴ 26፥33-35፤ ማር 14፥29-31፤
ሉቃ 22፥33-34

[31]ይሁዳ ከወጣ በኋላ፣ ኢየሱስ እንዲህ
አለ፤ “አሁን የሰው ልጅ ከበረ፤ በእርሱም
እግዚአብሔር ከበረ። [32]እንግዲህ እግዚአብሔር
በእርሱ ከከበረ[h]፣ እግዚአብሔር ልጁን በራሱ
ዘንድ ያከ ብረዋል፤ ወዲያውም ያከጠ
ብረዋል።
[33]“ልጆቼ ሆይ፤ ከእናንተ ጋር የምቈየው
ለጥቂት ጊዜ ነው፤ እናንተም ትፈልጉኛላችሁ፤
ለአይሁድ፣ ‘እኔ ወደምሄድበት ልትመጡ
አትችሉም’ እንዳልኋቸው፣ አሁንም ለእናንተ
ይህንኑ እላችኋለሁ።
[34]“አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ ይኸውም
እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ነው፤ እንግዲ
ህ እኔ እንደ ወደድኋችሁ እናንተም እርስ
በርሳችሁ ተዋደዱ። [35]እርስ በርሳችሁ ብት
ዋደዱ፣ ሰዎች ሁሉ የእኔ ደቀ መዛሙርት
እንደ ሆናችሁ በዚህ ያውቃሉ።”
[36]ስምዖን ጴጥሮስ፣ “ጌታ ሆይ፤ የምትሄ
ደው ወዴት ነው?” አለው።
ኢየሱስም፣ “ወደምሄድበት አሁን
ልትከ ተለኝ አትችልም፤ ኋላ ግን
ትከተለኛለህ” ሲል መለሰለት።
[37]ጴጥሮስም፣ ጌታ ሆይ፤ አሁን ልከተልህ
የማልችለው ለምንድን ነው? ስለ አንተ ሕይ
ወቴንም ቢሆን አሳልፌ እሰጣለሁ አለው።
[38]ኢየሱስም፣ እንዲህ ሲል መለሰ፤ “ሕይ
ወትህን በእርግጥ ለእኔ አሳልፈህ ትሰጣ
ለህን? እውነት እልሃለሁ፤ ዶሮ ሳይጮኽ
ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ።”

13፥10 ቍ18፤ ዮሐ15፥3
13፥11 ማቴ10፥4
13፥13 ማቴ26፥18፤ 28፥18፤ሉቃ1፥43፤ 2፥11፤ዮሐ11፥28፤ 6፥46፤11፥1፤ሐሥ 10፥36፤ሮሜ10፥9፡ 12፤14፥9፤1ቆሮ12፥3 ፤ፊል2፥11፤ቈላ 2፥6
13፥14 1ጴጥ5፥5
13፥15 ማቴ11፥29፤ 1ጢሞ4፥12
13፥16 ማቴ10፥24፤ ሉቃ6፥40፤ ዮሐ 15፥20
13፥17 ማቴ7፥24፡ 25፤ሉቃ11፥28፤ ያዕ1፥25
13፥18 ቍ10፤ መዝ41፥9፤ ማቴ1፥22፤26፥23፤ ዮሐ6፥70፤15፥16፡19
13፥19 ዮሐ4፥26፤ 8፥24፤14፥29፤16፥4
13፥20 ማቴ10፥40
13፥21 ማቴ26፥21፤ ዮሐ12፥27
13፥23 ዮሐ19፥26፤ 20፥2፤21፥7፡20
13፥25 ማቴ26፥22፤ ዮሐ21፥20
13፥26 ማቴ10፥4
13፥27 ሉቃ22፥3
13፥29 ቍ1፤ዮሐ 12፥5፡6
13፥30 ሉቃ22፥53
13፥31 ማቴ8፥20፤ ዮሐ7፥39፤12፥23፤ 14፥13፤17፥4፤ 1ጴጥ4፥11
13፥32 ዮሐ17፥1
13፥33 ዮሐ7፥33፡ 34
13፥34 ዘሌ19፥18፤ ዮሐ15፥12፤ኤፌ5፥2፤ 1ተሰ4፥9፤1ጴጥ1፥22፤ 1ዮሐ2፥7-11፤ 3፥11፤4፥10፡11
13፥35 1ዮሐ3፥14፤ 4፥20
13፥36 ቍ33፤ ዮሐ14፥2፤16፥5፤ 21፥18፡19፤ 2ጴጥ1፥14
13፥38 ዮሐ18፥27

[h]32 አያሌ የጥንት ቅጆች *እግዚአብሔር በእርሱ ከከበረ* የሚለው ሐረግ የላቸውም

### ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን አበረታታ

14 “ልባችሁ አይጨነቅ፤ በእግዚአብሔር
እመኑ[ኸ]፤ በእኔም ደግሞ እመኑ።
2በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ ይህ
ባይሆንማ ኖሮ እነግራችሁ ነበር፤ የምሄ
ደውም ስፍራ ላዘጋጅላችሁ ነው። 3ሄጄም
ስፍራ ካዘጋጀሁላችሁ በኋላ፣ እኔ ባለ ሁበት
እናንተም ከእኔ ጋር እንድትሆኑ ልወስ
ዳችሁ ዳግመኛ እመጣለሁ። 4እኔ ወደምሄ
ድበትም ስፍራ የሚያደርሰውን መንገድ
ታውቃላችሁ።”

### ወደ አብ የሚያደርሰው መንገድ

5ቶማስም፣ “ጌታ ሆይ፤ ወዴት እንደ ምትሄድ
አናውቅም፤ ታዲያ፣ መንገዱን እንዴት ማወቅ
እንችላለን?” አለው።
6ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ “መንገዱ እኔ
ነኝ፤ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ፤ በእኔ
በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ
የለም። 7እኔን ብታውቁኝ ኖሮ አባቴንም
ባወቃችሁት ነበር።[ሠ] ከአሁን ጀምሮ ግን
ታውቁታላችሁ፤ አይታችሁታልም።”
8ፊልጶስም፣ “ጌታ ሆይ፤ አብን አሳየንና
ይበቃናል” አለው።
9ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ “አንተ ፊል
ጶስ! ይህን ያህል ጊዜ ከእናንተ ጋር ስኖር
አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል፤
እንዴትስ፣ ‘አብን አሳየን’ ትላለህ? 10እኔ
በአብ እንዳለሁ፣ አብም በእኔ እንዳለ አታ
ምንምን? የምነግራችሁ ቃል ከራሴ አይ
ደለም፤ ነገር ግን ሥራውን የሚሠራው
በእኔ የሚኖረው አብ ነው። 11እኔ በአብ
እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ ስነግራችሁ
እመኑኝ፤ ሌላው ቢቀር ስለ ድንቅ ሥራ
ዎቹ እንኳ እመኑ። 12እውነት እላችኋለሁ፤
በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ ይሠ
ራል፤ እንዲያውም እኔ ወደ አብ ስለምሄድ፣
ከእነዚህም የሚበልጥ ያደርጋል። 13አብ በወ
ልድ እንዲከብር፣ በስሜ የምትለምኑትን
ሁሉ አደርገዋለሁ፤ 14ማንኛውንም ነገር
በስሜ ብትለምኑኝ፣ እኔ አደርገዋለሁ።

### ስለ መንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ተስፋ

15“ብትወዱኝ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ።
16እኔ አብን እለምናለሁ፤ እርሱም ከእናንተ
ጋር ለዘላለም የሚኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣ
ችኋል፤
17እርሱም የእውነት መንፈስ ነው፤ ዓለም
ስለማያየውና ስለማያውቀው ሊቀበለው
አይችልም። እናንተ ግን፣ አብሮአችሁ ስለ
ሚኖርና በውስጣችሁ ስለሚሆን[ዐ] ታውቁታ
ላችሁ። 18ወላጅ እንደሌላቸው ልጆች አልተ
ዋችሁም፤ ወደ እናንተ እመጣለሁ። 19ከጥ
ቂት ጊዜ በኋላ፣ ዓለም ከቶ አያየኝም፤
እናንተ ግን ታዩኛላችሁ። እኔ ሕያው ስለ
ሆንሁ እናንተም ሕያዋን ትሆናላችሁ። 20እኔ
በአባቴ እንዳለሁ፣ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ፣
እኔም ደግሞ በእናንተ እንዳለሁ በዚያ ቀን
ትረዳላችሁ። 21የሚወደኝ ትእዛዜን ተቀብሎ
የሚጠብቅ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወ
ደዋል፤ እኔም እወደዋለሁ፤ ራሴንም እገል
ጥለታለሁ።”
22ከዚያም የአስቆሮቱ ያልሆነው ይሁዳ፣
“ጌታ ሆይ፣ ታዲያ፣ ለዓለም ሳይሆን ራስህን
ለእኛ የምትገልጠው እንዴት ነው?”
አለው።
23ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ “የሚወደኝ
ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል፤
ወደ እርሱ እንመጣለን፤ ከእርሱም ጋር
እንኖራለን። 24የማይወደኝ ቃሌን አይጠ
ብቅም። ይህ የምትሰሙት ቃል የላከኝ
የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም።
25“አሁን ከእናንተ ጋር እያለሁ ይህን
ሁሉ ነግሬአችኋለሁ፤ 26አብ በስሜ
የሚልከው አጽ
ናኙ መንፈስ ቅዱስ ግን ሁሉን ነገር ያስ
ተምራችኋል፤ እኔ የነገርኋችሁንም ሁሉ
ያሳስባችኋል። 27ሰላምን እተውላችኋለሁ፤
ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም
እንደሚሰጣችሁ አይደለም። ልባችሁ አይጨ
ነቅ፤ አይፍራም።
28“ ‘እሄዳለሁ፤ ተመልሼም ወደ እናንተ
እመጣለሁ’ ማለቴን ሰምታችኋል፤ ብትወዱኝስ
አብ ከእኔ ስለሚበልጥ ወደ አብ በመሄዴ
ደስ ባላችሁ ነበር፤ 29የተናገርሁት ሲፈጸም
እንድታምኑ፣ ከመሆኑ በፊት አሁን ነግሬ
አችኋለሁ። 30የዚህ ዓለም ገዥ ስለሚመጣ
ከእንግዲህ ወዲህ ከእናንተ ጋር ብዙ አል
ናገርም። እርሱም በእኔ ላይ ሥልጣን
የለውም፤ 31ነገር ግን እኔ አብን እንደምወድ፣
አባቴ ያዘዘኝንም እንደማደርግ ዓለም እንዲ
ያውቅ ነው። “ተነሡ፤ ከዚህ እንሂድ።”

### የወይን ግንድና ቅርንጫፎቹ

15 “እውነተኛው የወይን ተክል እኔ
ነኝ፤ አትክልተኛውም አባቴ ነው።
2እርሱም በእኔ ያለውን፣ የማያፈራውን
ቅርንጫፍ ሁሉ ቈርጦ ይጥለዋል፤ ፍሬ የሚ
ያፈራውን ቅርንጫፍ ሁሉ ግን የበለጠ እን
ዲያፈራ ይገርዘዋል።[ዘ]

14፥1 ቀኁ27፤ መዝ4፥5፤ዮሐ3፥15
14፥2 ዮሐ13፥33፡ 36፤16፥5
14፥3 ቀኁ18፡28፤ ማቴ16፥27፤ዮሐ12፥26
14፥5 ዮሐ11፥16
14፥6 ዮሐ1፥4፡14፤ 6፥35፤10፥9፤ሐሥ 4፥12፤ኤፌ2፥18፤ ዕብ10፥20
14፥7 ዮሐ1፥18፤ 1ዮሐ2፥23
14፥8 ዮሐ1፥43
14፥9 ኢሳ9፥6፤ ዮሐ1፥14፤12፡45፤ 2ቆሮ4፥4፤ፊል2፥6፤ ቈላ1፥15፤ዕብ1፥3
14፥10 ቀኁ11፡20፡ 24፤ዮሐ10፥38፤ 17፥21
14፥11 ዮሐ5፥36፤ 10፥38
14፥12 ማቴ21፥21፤ ሉቃ10፥17
14፥13 ማቴ7፥7
14፥15 ቀኁ21፡23፤ መዝ103፥18፤ ዮሐ 15፥10፤ 1ዮሐ2፥3-5፤3፥22፡24፤ 5፥3፤2ዮሐ 6፤ ራእ12፥17፤14፡12
14፥16 ቀኁ26፤ ዮሐ 15፥26፤16፥7
14፥17 ዮሐ15፥26፤ 16፥13፤1ቆሮ2፥14፤ 1ዮሐ4፥6፤5፥6
14፥18 ቀኁ3፡28፤ 1ነገ6፥13፤ማቴ16፥27
14፥19 ዮሐ6፥57፤ 7፥33፡34፤16፥16
14፥20 ቀኁ10፡11፤ ዮሐ10፥38፤16፥23፡ 26፤17፥21፤ ሮሜ8፥10
14፥21 ቀኁ15፤ዘዳ 7፥13፤ዮሐ16፥27፤ 1ዮሐ2፥5
14፥22 ሉቃ6፥16፤ ሐሥ1፥13፤10፥41
14፥23 ቀኁ15፤ ሮሜ8፥10
14፥24 ቀኁ10፤ዘዳ 18፥18፤ዮሐ5፥19፤ 7፥16፤8፥28፤ 12፥49፡50
14፥26 ቀኁ16፤ ሐሥ2፥33፤ ዮሐ2፥22፤15፥26፤ 16፥7፡13፤ 1ዮሐ2፥20፡27
14፥27 ቀኁ1፤ ዘኁ6፥26፤መዝ85፥8፤ ሚል2፥6፤ሉቃ2፥14፤ 24፥36፤ ዮሐ16፥33፤ ፊል4፥7፤ ቈላ3፥15
14፥28 ቀኁ2-4፡18፤ ማቴ16፥27፤ዮሐ5፥18፤ 10፥29
14፥29 ዮሐ13፥19፤ 16፥4

14፥30 ዮሐ12፥31 14፥31 ዮሐ10፥18፤ 12፥49 15፥1 መዝ80፥8-11፤ ኢሳ5፥1-7፤ዮሐ6፥35 15፥2 ቀኁ6፤ መዝ92፥14፤ ማቴ3፥8፡10፤7፥20፤ገላ5፥22፤ኤፌ5፥9፤ፊል1፥11

[ኸ]1 ወይም *እናንተ በእግዚአብሔር ታምናላችሁ*
[ሠ]7 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *በእርግጥ እኔን ብታውቁ አባቴንም ታውቃላችሁ* ይላሉ
[ዐ]17 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *በውስጣችሁ ስላለ* ይላሉ
[ዘ]2 *ይገርዘዋል* የሚለው የግሪኩ ቃል *ያጠራዋል* የሚል ትርጉም አለው

3ከነገርኋችሁ ቃል የተነሣ እናንተ አሁን
ንጹሓን ናችሁ። 4በእኔ ኑሩ፤ እኔም በእ
ናንተ እኖራለሁ። ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ
ካልሆነ በቀር ብቻውን ፍሬ ሊያፈራ አይ
ችልም፤ እናንተም በእኔ ካልኖራችሁ ፍሬ
ልታፈሩ አትችሉም።
5"እኔ የወይን ተክል ነኝ፤ እናንተም ቅር
ንጫፎች ናችሁ። ማንም በእኔ ቢኖር እኔም
በእርሱ ብኖር፣ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል፤
ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና።
6በእኔ የማይኖር ተጥሎ እንደሚደርቅ ቅርን
ጫፍ ነው፤ እንዲህ ያሉት ቅርንጫፎች
ተለቅመው ወደ እሳት ይጣላሉ፤ ይቃጠላ
ሉም። 7በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ
ቢኖሩ፣ የምትፈልጉትን ማንኛውንም ነገር
ለምኑ፤ ይሰጣችኋልም። 8ብዙ ፍሬ በማፍራ
ት ደቀ መዛሙርቴ መሆናችሁን
ብትገልጡ፣ በዚህ አባቴ ይከብራል።
9"አብ እንደ ወደደኝ ሁሉ እኔም ወደ
ድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ። 10እኔ የአባቴን ትእ
ዛዝ ጠብቄ በፍቅሩ እንደምኖር፣ እናንተም
ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ።
11ደስታዬ በእናንተ እንዲሆንና ደስታችሁም
ሙሉ እንዲሆን ይህን ነግሬአችኋለሁ።
12ትእዛዜ ይህች ናት፤ እኔ እንደ ወደድ
ኋችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋ
ደዱ። 13ስለ ወዳጆቹ ሕይወቱን አሳልፎ
ከመስጠት የሚበልጥ ፍቅር ማንም የለውም፤
14የማዛችሁን ብትፈጽሙ ወዳጆቼ ናችሁ።
15ከእንግዲህ አገልጋዮች አልላችሁም፤ አገል
ጋይ ጌታው የሚሠራውን አያውቅምና፤
ነገር ግን ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ስለ ገለ
ጽሁላችሁ ወዳጆች ብያችኋለሁ። 16እኔ
መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤
እንድትሄዱና ፍሬ እንድታፈሩ ፍሬያችሁም
እንዲኖር ሾምኋችሁ። ስለዚህም አብ በስሜ
የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል። 17እርስ
በርሳችሁ እንድትዋደዱ፣ ትእዛዜ ይህቺ
ናት።

## ዓለም ደቀ መዛሙርትን መጥላቱ

18"ዓለም ቢጠላችሁ፣ ከእናንተ በፊት እኔን
እንደ ጠላኝ ዕወቁ። 19ከዓለም ብትሆኑ ኖሮ፣
ዓለም የራሱ እንደ ሆኑት አድርጎ በወደዳ
ችሁ ነበር፤ ከዓለም ለይቼ ስለ መረጥኋችሁ
የዓለም አይደላችሁም፤ ዓለም የሚጠላችሁም
ስለዚሁ ነው። 20'አገልጋይ ከጌታው
አይበልጥም' ብዬ የነገርኋችሁን ቃል
አስታውሱ። እኔን አሳደውኝ ከሆነ፣
እናንተንም ያሳድዷችኋል፤ ቃሌን ጠብቀው
ከሆነም ቃላችሁን ይጠብ ቃሉ።
21የላከኝን ስለማያውቁ፣ በስሜ ምክ ንያት
ይህን ያደርጉባችኋል። 22መጥቼ ባልነግ
ራቸው ኖሮ ኀጢአት ባልሆነባቸው ነበር፤
አሁን ግን ለኀጢአታቸው የሚሰጡት

15፥3 ዮሐ13፥10፤ 17፥17፤ኤፌ5፥26
15፥4 ዮሐ6፥56
15፥5 ቍ16
15፥6 ቍ2፤ ሕዝ15፥4፤ማቴ3፥10
15፥7 ቍ4፤ ማቴ7፥7፤ዮሐ6፥56
15፥8 ማቴ9፥8፤ ዮሐ8፥31
15፥9 ዮሐ17፥23፡ 24፡26
15፥10 ዮሐ14፥15
15፥11 ዮሐ3፥29
15፥12 ቍ17፤ ዮሐ13፥34
15፥13 ዘፍ44፥33፤ ዮሐ10፥11፤ ሮሜ 5፥7፡8
15፥14ኢዮ16፥20፤ ምሳ18፥24፤ ማቴ12፥50፤ሉቃ12፥4
15፥15 ዮሐ8፥26
15፥16 ቍ5፡19፤ ማቴ7፥7፤ዮሐ13፥18
15፥17 ቍ12
15፥18 ኢሳ66፥5፤ ዮሐ7፥7፤1ዮሐ3፥13
15፥19 ቍ16፤ ዮሐ17፥14
15፥20ዮሐ13፥16፤ 2ጢሞ3፥12
15፥21 ኢሳ66፥5፤ ማቴ5፥10፡11፤ 10፥22፤ሉቃ6፥22፤ ዮሐ16፥3፤ሐሥ5፥41 ፤1ጴጥ4፥14፤ራእ2፥3
15፥22 ሕዝ2፥5፤ 3፥7፤ዮሐ9፥41፤ሮሜ 1፥20፤2፥1
15፥24 ዮሐ5፥36፤ 9፥41
15፥25መዝ35፥19፤ 69፥4፤109፥3፤ ዮሐ10፥34
15፥26 ዮሐ14፥16 ፡17፡26፤16፥7፤ 1ዮሐ 5፥7
15፥27 ሉቃ1፥2፤ 24፥48፤ዮሐ21፥24፤ 1ዮሐ1፥2፤4፥14
16፥1 ማቴ11፥6፤ ዮሐ15፥18-27
16፥2 ዮሐ9፥22፤ 12፥42፤ ኢሳ66፥5፤ ሐሥ26፥9፡10፤ ራእ 6፥9
16፥3 ዮሐ15፥21፤ 17፥25፤1ዮሐ3፥1
16፥4 ዮሐ15፥27፤ 13፥19፤14፥29፤
16፥5 ቍ10፡17፡28፤ ዮሐ7፥33፤ 13፥36፤14፥5፤
16፥6 ቍ22
16፥7 ዮሐ7፥39፤ 14፥16፡26፤15፥26
16፥9 ዮሐ15፥22
16፥10 ቍ5፤ሐሥ 3፥14፤7፥52፤

ምክንያት የላቸውም። 23እኔን የሚጠላ፣ አባ
ቴንም ይጠላል። 24ሌላ ሰው ያላደረገውን
በመ
ካከላቸው ባላደርግ ኖሮ፣ ኀጢአት ባልሆነ
ባቸው ነበር፤ አሁን ግን እነዚህን ታምራት
አይተዋል፤ ሆኖም እኔንም አባቴንም ጠል
ተዋል። 25ይህም፣ 'ያለ ምክንያት ጠሉኝ'
ተብሎ በሕጋቸው የተጻፈው ቃል እንዲፈ
ጸም ነው።
26"እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ፣
ከአብ የሚወጣው አጽናኙ የእውነት
መንፈስ በመጣ ጊዜ፣ እርሱ ስለ እኔ
ይመሰክራል። 27እናንተም ደግሞ፣
ከመጀመሪያው ከእኔ ጋር ስለ ነበራችሁ፣
ትመሰክራላችሁ።
16 "ይህን ሁሉ የነገርኋችሁ እንዳ
ትሰናከሉ ነው። 2ከምኵራብ
ያስወጧችኋል፤ እንዲያውም የሚገድላችሁ
ሁሉ እግዚአብሔርን እንዳገለገለ የሚቈጥር
በት ጊዜ ይመጣል። 3ይህን ሁሉ የሚ
ያደርጉባችሁ፣ አብን ወይም እኔን ስላላ
ወቁ ነው። 4አስቀድሜ ይህን የነገርኋችሁ
ጊዜው ሲደርስ እንድታስታውሱ ነው፤ ከእ
ናንተ ጋር ስለ ነበርሁ፣ ይህን ከመጀመሪያው
አልነገርኋችሁም።

## የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

5"እንግዲህ ወደ ላከኝ እሄዳለሁ፤ ይሁን
እንጂ ከእናንተ፣ 'የምትሄደው የት ነው?'
ብሎ የሚጠይቀኝ የለም። 6ይህን በመና
ገሬም ልባችሁ በሐዘን ተሞልቶአል፤ 7ነገር
ግን፣ እውነት እላችኋለሁ፤ መሄዴ ይበጃ
ችኋል። እኔ ካልሄድሁ አጽናኙ ወደ እናንተ
አይመጣም፤ ከሄድሁ ግን እርሱን ወደ
እናንተ እልካለሁ፤ 8በሚመጣበትም ጊዜ
ዓለምን ስለ ኀጢአት[a]፣ ስለ ጽድቅና ስለ
ፍርድ ይወቅሳል። 9ስለ ኀጢአት ሲባል፣
ሰዎች በእኔ ስለማያምኑ ነው፤ 10ስለ ጽድቅ፣
ወደ አብ ስለምሄድና ከእንግዲህ ስለ
ማታዩኝ ነው፤ 11ስለ ፍርድም፣ የዚህ ዓለም
ገዥ ስለ ተፈረደበት ነው።
12"ብዙ የምነግራችሁ ነበረኝ፤ አሁን
ግን ልትሸከሙት አትችሉም። 13የእውነት
መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመ
ራችኋል። እርሱ ከራሱ አይናገርም፤ የሚሰ
ማውን ብቻ ይናገራል፤ እንዲሁም ወደ ፊት
ስለሚሆነው ይነግራችኋል፤ 14የእኔ ከሆነው
ወስዶ እንድ ታውቁ በማድረግ
ያከብረኛል። 15የአብ የሆ ነው ሁሉ የእኔ
ነው፤ እንግዲህ፣ 'የእኔ ከሆ

ሮሜ1፥17፤3፥21፡ 22፤1ጴጥ3፥18 16፥11 ዮሐ12፥31
16፥12 ማር4፥33፤ 1ቆሮ3፥2 16፥13 መዝ25፥5፤
ዮሐ14፥17፡26 16፥15 ዮሐ17፥10

[a]8 ወይም የዓለምን ኀጢአት ይገልጣል

ነው ወስዶ እንድታውቁ ያደርጋል’ ያልኋችሁ
ለዚሁ ነው።
[16]“ከጥቂት ጊዜ በኋላ አታዩኝም፤ ይሁን
እንጂ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ ታዩኛላችሁ።”

### የደቀ መዛሙርት ሐዘን ወደ ደስታ መለወጥ

[17]ከደቀ መዛሙርቱም አንዳንዶቹ፣ “ከጥቂት
ጊዜ በኋላ አታዩኝም፤ ይሁን እንጂ ከጥቂት
ጊዜ በኋላ ደግሞ ታዩኛላችሁ’ እንዲሁም፣
‘ወደ አብ ስለምሄድ’ ሲል ምን ማለቱ ነው?”
ተባባሉ፤ [18]“‘ጥቂት ጊዜ’ ማለቱስ ምን ይሆን?
የሚለውም ነገር አልገባንም” እያሉ ይጠያየቁ
ነበር።
[19]ኢየሱስም ሊጠይቁት እንደ ፈለጉ
ባወቀ ጊዜ እንዲህ አላቸው፤ “እኔ፣
‘ከጥቂት ጊዜ በኋላ ታዩኛላችሁ፤ ይሁን
እንጂ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ አታዩኝም’
ስላልኋችሁ፣ ምን ማለቴ እንደ ሆነ እርስ
በርሳችሁ ትጠያየቃላችሁ? [20]እውነት
እላችኋለሁ፤ እናንተ ታለቅሳላችሁ፤
ታዝናላችሁም፤ ዓለም ግን ሐሤት ያደርጋል፤
ይሁን እንጂ ሐዘናችሁ ወደ ደስታ ይለ
ወጣል። [21]ሴት ቀኗ ደርሶ ስትወልድ
ትጨነቃለች፤ ከተገላገለች በኋላ ግን፣ ሰው
ወደ ዓለም ስለ መጣ ጭንቋን ትረሳለች፤
[22]ለእናንተም እንደዚሁ አሁን የሐዘን ጊዜ
ነው፤ ሆኖም እንደገና ስለማያችሁ ደስ ይላች
ኋል፤ ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም።
[23]በዚያ ቀን ከእኔ ምንም አትለምኑም፤ እውነት
እላችኋለሁ፤ አብ በስሜ የምትለምኑትን
ሁሉ ይሰጣችኋል። [24]እስከ አሁን በስሜ ምንም
አልለመናችሁም፤ ለምኑ ትቀበላላችሁ፤ ደስታ
ችሁም ሙሉ ይሆናል።
[25]“እስከ አሁን የነገርኋችሁ በምሳሌ
ቢሆንም እንኳ፣ ከእንግዲህ ግን ስለ አብ
በምሳሌ ሳይሆን በግልጽ የምናገርበት ጊዜ
ይመጣል። [26]በዚያ ቀን በስሜ ትለም
ናላችሁ፤ ይህም በእናንተ ፈንታ አብን
እለምናለሁ ማለቴ አይደለም፤ [27]ስለ ወደዳ
ችሁኝና ከእግዚአብሔርም እንደ ወጣሁ ስላመ
ናችሁ አብ ራሱ ይወዳችኋል። [28]ከአብ ወጥቼ
ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ አሁን ግን ዓለምን
ትቼ ወደ አብ እሄዳለሁ።”
[29]ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አሉ፤
“አሁንም እኮ ያለ ምሳሌ በግልጽ እየተና
ገርህ ነው። [30]አሁን ሁሉን ነገር እንደምታ
ውቅና ማንም ሊጠይቅህ እንደማያስፈልግ
ተረድተናል፤ ይህም ከእግዚአብሔር እንደ
ወጣህ እንድናምን አድርጎናል።”
[31]ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
“አሁንስ አመናችሁ ማለት ነው?[f]
[32]እነሆ፤ ሁላችሁም በየፊናችሁ
የምትበታተኑበት ጊዜ ይመጣል፤ ያም ጊዜ
አሁን ነው። እኔንም ብቻዬን

16፥16 ቁ22፤ ዮሐ7፥33፤14፥18-24
16፥17 ቁ5፡16
16፥20 ማር16፥10፤ ሉቃ23፥27፤ ዮሐ20፥20
16፥21 ኢሳ13፥8፤ 21፥3፤26፥17፤ ሚክ4፥9፤1ተሰ5፥3
16፥22 ቁ6፡16፡20፤ ኤር31፥12
16፥23 ቁ26፤ ማቴ7፥7፤ዮሐ14፥20
16፥24 ማቴ7፥7፤ ዮሐ3፥29
16፥25 ቁ2፡29፤ መዝ78፥2፤ሕዝ 29፥49፤ማቴ13፥34፤ ማር4፥33፡34፤ ዮሐ10፥6
16፥26 ቁ23፡24
16፥27 ቁ30፤ ዮሐ13፥3፤14፥21፡23
16፥28 ቁ5፡10፡17፤ ዮሐ13፥3
16፥29 ቁ25
16፥30 ቁ27፤ 1ነገ17፥24፤ዮሐ13፥3
16፥32 ቁ2፡25፤ ማቴ26፥31፡56፤ ዮሐ8፥16፡29
16፥33 ዮሐ14፥27፤ 15፥18-21፤ ሮሜ8፥37፤1ዮሐ4፥4፤ 5፥4፤ራእ2፥7፡11፡17፡ 26፤3፥5፡12፡21፤21፥7
17፥1 ማቴ26፥18፤ ዮሐ11፥41፤12፥23፤ 13፥31፡32
17፥2 ቁ6፡9፡24፤ ዳን7፥14፤ ማቴ25፥46፤28፥18፤ ዮሐ 6፥37፡39
17፥3 ቁ8፡18፡21፡ 23፡25፤ዮሐ3፥17፤ ፊል3፥8
17፥4 ዮሐ13፥31፤ 19፥30
17፥5 ቁ1፤ ዮሐ1፥2፤ፊል2፥6
17፥6 ቁ2፡26፤ ዮሐ1፥18
17፥8 ቁ3፡14፡18፡ 21፡23፡25፡26፤ዮሐ 3፥17፤13፥3፤14፥24
17፥9 ቁ2፤ ሉቃ22፥32
17፥10 ዮሐ16፥15
17፥11 ቁ13፡21-23 መዝ133፥1፤ዮሐ 7፥33፤10፥30፤13፥1
17፥12 ማቴ1፥22፤ ዮሐ6፥39፡70
17፥13 ቁ11፤ ዮሐ 3፥29
17፥14 ቁ16፤ ዮሐ8፥23፤15፥19

ትተዉኛላችሁ፤ ይሁን እንጂ አባቴ ከእኔ
ጋር ስለ ሆነ ብቻዬን አይደለሁም።
[33]“በእኔ ሰላም እንዲኖራችሁ፣ ይህን
ነግሬአችኋለሁ። በዓለም ሳላችሁ መከራ
አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓ
ለምን አሸንፌ ዋለሁ።”

### ኢየሱስ ስለ ራሱ መጸለዩ

17 ኢየሱስ ይህን ከተናገረ በኋላ፣
ወደ ሰማይ ቀና ብሎ እንዲህ ሲል
ጸለየ፤
“አባት ሆይ፤ ጊዜው ደርሶአል፤ ልጅህ
ያከብርህ ዘንድ ልጅህን አክብረው፤ [2]ከአ
ንተ ለተቀበላቸው ሁሉ የዘላለምን ሕይ
ወት እንዲሰጥ በሰው ሁሉ ላይ ሥልጣን
ሰጥተኸዋልና። [3]እውነተኛ አምላክ የሆንኸ
ውን አንተንና የላክኸውንም ኢየሱስ
ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕ
ይወት ናት። [4]የሰጠኸኝን ሥራ በመፈጸም
በምድር አከበርሁህ። [5]እንግዲህ አባት
ሆይ፤ ዓለም ሳይፈ
ጠር ከአንተ ጋር በነበረኝ ክብር በአንተ
ዘንድ አክብረኝ።

### ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ጸለየ

[6]“ለእነዚህ ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን
ገልጬላቸዋለሁ። የአንተ ነበሩ ለእኔ ሰጠ
ኸኝ፤ እነርሱም ቃልህን ጠብቀዋል።
[7]የሰጠኸኝ ሁሉ ከአንተ እንደ ሆነ አሁን
ዐውቀዋል፤ [8]ምክንያቱም የሰጠኸኝን ቃል
ሰጥቻቸው ተቀብለዋል፤ እኔም ከአንተ
እንደ ወጣሁ በእርግጥ ዐውቀዋል፤ አንተ
እንደላክኸኝም አምነዋል፤ [9]እነርሱ የአንተ
ስለ ሆኑ እጸልይላቸዋለሁ፤ ለሰጠኸኝና የአንተ
ለሆኑት እንጂ ለዓለም አልጸልይም። [10]የእኔ
የሆነው ሁሉ የአንተ ነው፤ የአንተ የሆነ
ውም ሁሉ የእኔ ነው፤ በእነርሱም ከብሬ
አለሁ። [11]ከእንግዲህ እኔ በዓለም አልቈይም፤
እነርሱ ግን በዓለም ውስጥ ናቸው፤ እኔም
ወደ አንተ መምጣቴ ነው። ቅዱስ አባት
ሆይ፤ እኛ አንድ እንደ ሆንን፣ እነርሱም
አንድ እንዲሆኑ በሰጠኸኝ በስምህ ጠብ
ቃቸው። [12]እኔ ከእነርሱ ጋር ሳለሁ፣ በሰጠኸኝ
ስም ከለልኋቸው፤ ጠበቅኋቸውም፤ የመጽሐ
ፍ ቃል እንዲፈጸም ከአንዱ ከጥፋት ልጅ
በቀር ከእነርሱ ማንም አልጠፋም።
[13]“አሁን ወደ አንተ መምጣቴ ነው፤ ነገር
ግን ደስታዬ በእነርሱ ዘንድ የተሟላ እን
ዲሆን፣ አሁን በዓለም እያለሁ ይህን እናገ
ራለሁ።
[14]ቃልህን ሰጥቻቸዋለሁ፤ እኔ ከዓለም እንዳ
ይደለሁ፣ እነርሱም ከዓለም ባለመሆናቸው

[f]31 ወይም *በስተ መጨረሻው አመናችሁ!*

ዓለም ጠልቶአቸዋል። [15]የምለምንህም ከክ
ፉው እንድትጠብቃቸው እንጂ፣ ከዓለም
እንድታወጣቸው አይደለም። [16]እኔ ከዓለም
እንዳልሆንሁ ሁሉ፣ እነርሱም ከዓለም አይ
ደሉም። [17]ቃልህ እውነት ነው፤ በእው
ነትህ ቀድሳቸው[፩]። [18]አንተ ወደ ዓለም
እንደ ላክኸኝ እኔም ወደ ዓለም ልኬአቸ
ዋለሁ። [19]እነርሱ በእውነት የተቀደሱ እን
ዲሆኑ፣ ራሴን ስለ እነርሱ ቀድሻለሁ።

## ኢየሱስ ለአማኞች ሁሉ ጸለየ

[20]"የእነርሱን ትምህርት ተቀብለው በእኔ
ለሚያምኑ ጭምር እንጂ ለእነዚህ ብቻ አል
ጸልይም፤ [21]ይህም፣ አባት ሆይ፤ አንተ
በእኔ፣ እኔም በአንተ እንዳለሁ ሁሉም አንድ
እንዲሆኑ፣ እንዲሁም አንተ እኔን እንደ
ላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፣ እነርሱም በእኛ
እንዲሆኑ ነው። [22]እኛ አንድ እንደ ሆንን
እነርሱም አንድ እንዲሆኑ፣ የሰጠኸኝን
ክብር ሰጥቻቸዋለሁ። [23]ይህም እኔ በእነርሱ፣
አንተም በእኔ መሆንህ ነው። አንተ እንደ
ላክኸኝና እኔን በወደድኸኝ መጠን እነርሱንም
እንደ ወደድሃ ቸው ዓለም ያውቅ ዘንድ፣
አንድነታቸው ፍጹም ይሁን።

[24]"አባት ሆይ፤ እነዚህ የሰጠኸኝ፣ እኔ
ባለሁበት እንዲሆኑ ዓለም ሳይፈጠር ስለ
ወደድኸኝ የሰጠኸኝንም ክብሬን እንዲያዩ
እፈልጋለሁ።

[25]"ጻድቅ አባት ሆይ፤ ዓለም ባያውቅህም፣
እኔ ዐውቅሃለሁ፤ እነዚህም አንተ እንደ ላከኸኝ
ያውቃሉ። [26]ለእኔ ያለህ ፍቅር በእነርሱ እን
ዲሆን፣ እኔም በእነርሱ እንድሆን፣ አንተን
እንዲያውቁ[፪] አድርጌአለሁ፤ እንዲያውቁህም
አደርጋለሁ።

## ኢየሱስ በተቃዋሚዎቹ መያዙ

18፥3-11 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥47-56፤ ማር 14፥43-50፤
ሉቃ 22፥47-53

18 ኢየሱስ ይህን ካለ በኋላ ከደቀ
መዛሙርቱ ጋር ሆኖ የቄድሮንን
ሸለቆ ተሻገረ፤ ማዶ ወደ ነበረውም የአትክልት
ስፍራ ገቡ።

[2]ብዙውን ጊዜ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር በዚያ ስለሚገናኝ፣ አሳልፎ የሰጠው
ይሁ ዳም ቦታውን ያውቅ ነበር። [3]ይሁዳም
ወታደሮችን እንዲሁም ከካህናት አለቆችና
ከፈሪሳውያን የተላኩ ሎሌዎችን እየመራ
ወደ አትክልቱ ስፍራ መጣ፤ እነርሱም ችቦ፣
ፋኖስና የጦር መሣሪያ ይዘው ነበር።

[4]ኢየሱስም የሚደርስበትን ሁሉ ዐውቆ
ወጣና፣ "የምትፈልጉት ማንን ነው?" አላቸው።

[5]እነርሱም፣ "የናዝሬቱን ኢየሱስን" አሉት።

ኢየሱስም፣ "እርሱ እኔ ነኝ" አላቸው።
አሳልፎ የሰጠውም ይሁዳ ከእነርሱ ጋር

17፥15 ማቴ5፥37
17፥16 ቁ14
17፥17 ዮሐ15፥3፤
2ሳሙ 7፥28፤
1ነገ 17፥24
17፥18 ቁ3፥8፥
21፥23፥25፤ዮሐ3፥17
፤ 20፥21
17፥19 ቁ17
17፥21 ቁ3፥8፥
11፥18፥23፥25፤ኤር
32፥39፤ዮሐ፤3፥17፤
10፥38
17፥22 ዮሐ1፥14፤
14፥20፤
17፥23 ቁ3፥8፥21፥
18፥25፤ዮሐ3፥17፤
16፥27፤
17፥24 ቁ2፥5፤
ማቴ25፥34፤ዮሐ
1፥2፥14፤ 12፥26
17፥25 ቁ3፥8፥18፥
21፥23፤ ዮሐ 3፥17፤
15፥21፤ 16፥3፥27
17፥26 ቁ6፤
ዮሐ 15፥9
18፥1 ቁ26፤
2ሳሙ 15፥23፤
ማቴ21፥1፤ 26፥36
18፥2 ሉቃ21፥37፤
22፥39
18፥3 ቁ12፤
ሐሥ1፥16
18፥4 ቁ7፤
ዮሐ6፥64፤13፥1፥11
18፥5 ማር1፥24
18፥7 ቁ4
18፥9 ዮሐ6፥39
18፥11ማቴ 20፥22
18፥12 ቁ3
18፥13 ቁ24፤
ማቴ26፥3
18፥14 ዮሐ11፥49-51
18፥15 ማቴ26፥3፥
58፤ማር14፥54፤
ሉቃ 22፥54
18፥17 ቁ25
18፥18ማር14፥54፥
67፤ዮሐ21፥9

ቆሞ ነበር። [6]ኢየሱስም፣ "እርሱ እኔ ነኝ"
ባለ ጊዜ ወደ ኋላ አፈግፍገው መሬት ላይ
ወደቁ።

[7]እንደ ገናም፣ የምትፈልጉት ማንን ነው?
ሲል ጠየቃቸው።

እነርሱም፣ "የናዝሬቱን ኢየሱስን" አሉት።

[8]ኢየሱስም መልሶ፣ "'እርሱ እኔ ነኝ'
ብያ ችኋለሁ እኮ፤ እኔን የምትፈልጉ ከሆነ፣
እነዚህ፣ ይሂዱ ተዉአቸው" አለ፤ [9]ይህ
የሆነው፣ "ከሰጠኸኝ ከእነዚህ አንድም
አልጠፋብኝም" ብሎ የተናገረው ቃል
እንዲፈጸም ነው።

[10]ሰይፍ ይዞ የነበረው ስምዖን ጴጥሮስም፣
ሰይፉን መዞ የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ
ቀኝ ጆሮ ቈረጠ፤ የአገልጋዩም ስም ማልኮስ
ይባል ነበር።

[11]ኢየሱስም ጴጥሮስን፣ "ሰይፍህን ወደ
ሰገባው መልስ! አብ የሰጠኝን ጽዋ አልጠ
ጣምን?" አለው።

## ኢየሱስ በሊቀ ካህናቱ በሐና ፊት ቀረበ

18፥12፥13 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥57

[12]ወታደሮቹም ከአዛዣቸውና ከአይሁድ ሎሌ
ዎች ጋር በመሆን ኢየሱስን ያዙት፤ አስረ
ውም፣ [13]በመጀመሪያ፣ የቀያፋ አማት ወደ
ነበረው ወደ ሐና አመጡት፤ ቀያፋም የዓ
መቱ ሊቀ ካህናት ነበር። [14]ቀያፋም፣
'ለሕዝቡ ሲባል አንድ ሰው ቢሞት ይሻላል'
ብሎ አይሁድን የመከረ ነበር።

## የጴጥሮስ ክህደት

18፥16-18 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥69፥70፤ ማር 14፥66-68፤
ሉቃ 22፥55-57

[15]ስምዖን ጴጥሮስና አንድ ሌላ ደቀ መዝ
ሙር ኢየሱስን ተከተሉት። ይህም ደቀ መዝ
ሙር በሊቀ ካህናቱ ይታወቅ ስለ ነበር፣
ከኢየሱስ ጋር ወደ ሊቀ ካህናቱ ግቢ ገባ፤
[16]ጴጥሮስ ግን ከበሩ ውጭ ቀረ። በሊቀ
ካህናቱ የታወቀው ሌላው ደቀ መዝሙርም
ተመለሰና በር ጠባቂዋን አነጋግሮ ጴጥ
ሮስን ይዞት ገባ።

[17]በር ጠባቂዋም ጴጥሮስን፣ "አንተ ከዚህ
ሰው ደቀ መዛሙርት አንዱ አይደለህምን?"
አለችው።

እርሱም፣ "አይደለሁም" አለ።

[18]ብርድ ስለ ነበር አገልጋዮቹና ሎሌ
ዎቹ ባያያዙት የከሰል ፍም ዙሪያ ለመሞቅ
ቆመው ሳሉ፣ ጴጥሮስም ከእነርሱ ጋር ቆሞ
እሳት ይሞቅ ነበር።

[፩]17 በግሪኩ *ሀጊያዞ* የሚለው ቅዱስ ለሆነ ተግባር መለየት
ወይም መቀደስ ማለት ነው፤ ቍ 19 ይመ
[፪]26 በግሪኩ *ስምህን እንዲያወቁ* ይላል

## ኢየሱስ በሊቀ ካህናቱ ፊት መቅረቡ

18፥19-24 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥59-68፤ ማር 14፥55-65፤ ሉቃ 22፥63-71

19በዚያን ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ኢየሱስን ስለ
ደቀ መዛሙርቱና ስለ ትምህርቱ ጠየቀው።
20ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ “እኔ
ለዓለም በግልጽ ተናግሬአለሁ፤ አይሁድ
በተሰ በሰቡበት ምኵራብ፣ በቤተ
መቅደስም ሁልጊዜ አስተምሬአለሁ፤
በስውር የተናገ ርሁት የለም። 21ለምን
እኔን ትጠይቀኛለህ? የሰሙኝን ጠይቃቸው፤
እነሆ፤ የተናገርሁትን እነርሱ ያውቃሉ።”
22ኢየሱስ ይህን በተናገረ ጊዜ፣ አጠገቡ
ቆመው ከነበሩት ሎሌዎች አንዱ፣ “ለሊቀ
ካህናቱ የምትመልሰው እንዲህ ነውን?”
ብሎ በጥፊ መታው።
23ኢየሱስም፣ “ክፉ ተናግሬ ከሆነ ክፉ
መናገሬን መስክር፤ እውነት ከተናገርሁ
ግን ለምን ትመታኛለህ?” አለው። 24ሐናም
ኢየሱስ ታስሮ እንዳለ ወደ ሊቀ ካህናቱ
ወደ ቀያፋ ላከው።[1]

## የጴጥሮስ ሁለተኛና ሦስተኛ ክህደት

18፥25-27 ተጓ ምብ - ማቴ 26፥71-75፤ ማር 14፥69-72፤ ሉቃ 22፥58-62

25ስምዖን ጴጥሮስም ቆሞ እሳት ሲሞቅ፣
“አንተ ከእርሱ ደቀ መዛሙርት አንዱ አይ
ደለህምን?” አሉት።
እርሱም፣ “አይደለሁም” ሲል ካደ።
26ከሊቀ ካህናቱ አገልጋዮች አንዱ፣
ጴጥሮስ ጆሮውን የቈረጠው ሰው ዘመድ፣
“በአትክ ልቱ ስፍራ አንተን ከእርሱ ጋር
አላየሁህም?” ሲል ጠየቀው። 27ጴጥሮስም
እንደ ገና ካደ፤ ወዲያውም ዶሮ ጮኸ።

## ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት

18፥29-40 ተጓ ምብ - ማቴ 27፥11-18፡20-23፤ ማር 15፥2-15፤ ሉቃ 23፥2፡3፡18-25

28አይሁድም ኢየሱስን ከቀያፋ ወደ ሮማ
ዊው ገዥ ግቢ ይዘውት ሄዱ፤ ጊዜውም ማለዳ
ነበር። አይሁድም ፋሲካን መብላት እንዲችሉ፣
ላለመርከስ ወደ ገዥው ግቢ አልገቡም።
29ስለዚህ ጲላጦስ ወደ እነርሱ ወጥቶ፣ በዚህ
ሰው ላይ የምታቀርቡት ክስ ምንድን
ነው?” ብሎ ጠየቃቸው።
30እነርሱም፣ “ይህ ሰው ወንጀለኛ ባይሆን
ኖሮ፣ አንተ ፊት ባላቀረብነውም ነበር” ብለው
መለሱለት።
31ጲላጦስም፣ “እናንተ ራሳችሁ ወስዳችሁ
በሕጋችሁ መሠረት ፍረዱበት” አላቸው።
አይሁድም፣ “እኛማ በማንም ላይ የሞት
ፍርድ ለመፍረድ መብት የለንም” አሉት።
32ይህ የሆነው በምን ዐይነት ሞት እንደ
ሚሞት ለማመልከት ሲል ኢየሱስ የተናገረው

18፥20 ማቴ4፥23፤ 26፥55፤ዮሐ7፥26
18፥22 ቀኍ3፤ ማቴ16፥21፤ዮሐ19፥3
18፥23 ማቴ5፥39፤ ሐሥ23፥2-5
18፥24 ቀኍ13፤ ማቴ26፥3
18፥25 ቀኍ17፡18
18፥26 ቀኍ1፡10
18፥27 ዮሐ13፥38
18፥28 ቀኍ33፤ ማቴ27፥2፤ዮሐ 11፥55፤19፥9
18፥32 ማቴ20፥19፤ 26፥2፤ዮሐ3፥14፤ 8፥28፤12፥32፡33
18፥33 ቀኍ28፡29፤ ማቴ2፥2፤ሉቃ23፥3፤ ዮሐ19፥9
18፥36 ማቴ3፥2፤ 26፥53፤ሉቃ17፥21፤ ዮሐ6፥15
18፥37 ዮሐ3፥32፤ 8፥47፤1ዮሐ 4፥6
18፥38 ሉቃ23፥4
18፥40 ሐሥ3፥14
19፥1 ዘዳ25፥3፤ ኢሳ50፥6፤53፥5፤ ማቴ27፥26
19፥3 ማቴ27፥29፤ ዮሐ18፥22
19፥4 ቀኍ6፤ሉቃ 23፥4፤ዮሐ 18፥38
19፥5 ቀኍ2
19፥6 ቀኍ4፤ሉቃ 23፥4፤ሐሥ3፥13

ቃል እንዲፈጸም ነው።
33ጲላጦስም ወደ ግቢው ተመልሶ ኢየ
ሱስን አስጠራና፣ “አንተ የአይሁድ ንጉሥ
ነህን?” ብሎ ጠየቀው።
34ኢየሱስም፣ “ይህ ሐሳብ የራስህ ነው? ወይስ
ሌሎች ስለ እኔ የነገሩህ?” ሲል መለሰለት።
35ጲላጦስም መልሶ፣ “እኔ አይሁዳዊ ነኝን?
ወደ እኔ የላኩህ የራስህ ወገኖችና የካህናት
አለቆች ናቸው፤ ለመሆኑ ምን አድርገህ ነው?”
አለው።
36ኢየሱስም፣ “የእኔ መንግሥት ከዚህ ዓለም
አይደለም፤ ቢሆንማ ኖሮ አይሁድ
እንዳይዙኝ ሎሌዎቼ በተከላከሉልኝ ነበር፤
አሁን ግን መንግሥቴ ከዚህ አይደለም”
አለው።
37ጲላጦስም፣ “ታዲያ፣ ንጉሥ ነህ ማለት
ነዋ!” አለው።
ኢየሱስም፣ “እኔ ንጉሥ እንደ ሆንሁ መና
ገርህ ትክክል ነው፤ የተወለድሁት፣ ወደዚ
ህም ዓለም የመጣሁት ስለ እውነት ለመ
መስከር ነው፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ይሰ
ማኛል” አለው።
38ጲላጦስም፣ “እውነት ምንድን ነው?”
አለው፤ ይህን ከተናገረ በኋላም እንደ ገና ወደ
አይሁድ ወጥቶ እንዲህ አላቸው፤ “እኔ
የሚያስከስስ በደል አላገኘሁበትም፤ 39ነገር
ግን በፋሲካ አንድ እስረኛ እንድፈታላችሁ
ልማድ አላችሁ፤ ስለዚህ፣ ‘የአይሁድን
ንጉሥ’ እንድፈታላችሁ ትፈልጋላችሁን?”
40እነርሱም እንደ ገና በመጮኽ፣ “የለም፤
እርሱን አይደለም! በርባንን ፍታልን!” አሉ።
በርባን ግን ወንበዴ ነበረ።

## ኢየሱስ እንዲሰቀል ተፈረደበት

19፥1-16 ተጓ ምብ - ማቴ 27፥27-31፤ ማር 15፥16-20

# 19

ጲላጦስም ኢየሱስን ወስዶ አስገ
ረፈው። 2ወታደሮችም የእሾህ አክሊል
ጐንጕነው በራሱ ላይ አደረጉ፤ ሐምራዊ ልብ
ስም አለበሱት፤ 3እየተመላለሱም፣ “የአይ
ሁድ ንጉሥ ሆይ፤ ሰላም ለአንተ ይሁን” እያሉ
በጥፊ ይመቱት ነበር።
4ጲላጦስም እንደ ገና ወደ ውጭ ወጥቶ፣
“እንግዲህ ወደ እናንተ ያወጣሁት ለክስ
የሚያደርስ ወንጀል እንዳላገኘሁበት እንድ
ታውቁ ነው” አላቸው። 5ኢየሱስ የእሾህ አክ
ሊል ደፍቶ ሐምራዊ ልብስም ለብሶ ወጣ፤
ጲላጦስም፣ “እነሆ፤ ሰውየው!” አላቸው።
6የካህናት አለቆችና ሎሌዎቻቸውም
ባዩት ጊዜ፣ “ስቀለው! ስቀለው!” እያሉ
ጮኹ። ጲላጦስ ግን፣ “እናንተ ወስዳችሁ
ስቀሉት፤ በእኔ በኩል ለክስ የሚያደርስ
ወንጀል አላ

[1]24 ወይም ሐናም ወደ ቀያፋ እንደታሰረ ላከው

ገኘሁበትም” አላቸው።
7አይሁድም፣ “እኛ ሕግ አለን፤ ራሱን
የእግ ዚአብሔር ልጅ ስላደረገ በሕጋችን መ
ሠረት መሞት አለበት” አሉ።
8ጲላጦስ ይህን ሲሰማ የባሰውኑ ፈራ፤ 9ወደ
ግቢው ተመልሶ ኢየሱስን፣ “ከየት ነው የመ
ጣኸው?” በማለት ጠየቀው፤ ኢየሱስ ግን
ምንም አልመለሰለትም። 10ጲላጦስም፣
“አታናግረኝምን? ልፈታህ ወይም ልሰቅልህ
ሥልጣን እን ዳለኝ አታውቅም?” አለው።
11ኢየሱስም፣ “ከላይ ባይሰጥህ ኖሮ
በእኔ ላይ ሥልጣን ባልኖረህ ነበር፤ ስለዚህ
ለአንተ አሳልፎ የሰጠኝ ሰው የባሰ ኀጢአት
አለበት” አለው።
12ከዚያ በኋላ ጲላጦስ ኢየሱስን ሊፈታው
ፈለገ፤ አይሁድ ግን፣ “ይህን ሰው ብትፈታው
የቄሣር ወዳጅ አይደለህም፤ ራሱን ንጉሥ
የሚያደርግ የቄሣር ተቃዋሚ ነው” በማለት
ጩኸታቸውን ቀጠሉ።
13ጲላጦስም ይህን ሲሰማ ኢየሱስን ወደ
ውጭ አወጣው፤ ‘የድንጋይ ንጣፍ’ በተባለ፣
በአራማይክ ቋንቋ ‘ገበታ’ ብለው በሚጠሩ
ት ስፍራ፣ በፍርድ ወንበር ላይ ተቀመጠ።
14ቀኑ የፋሲካ በዓል መዘጋጃ፣ ጊዜውም
ከቀኑ ስድስት ሰዓት ያህል ነበር።
ጲላጦስም አይሁድን፣ “እነሆ፤ ንጉሣችሁ!”
አላቸው።
15እነርሱ ግን፣ አስወግደው! አስወግደው!
ስቀለው!” እያሉ ጮኹ።
ጲላጦስም፣ “ንጉሣችሁን ልስቀለውን?” አለ።
የካህናት አለቆችም፣ “ከቄሣር በቀር ሌላ
ንጉሥ የለንም” ብለው መለሱለት።
16በመጨረሻም ጲላጦስ እንዲሰቅሉት አሳ
ልፎ ሰጣቸው።

## ስቅለት

19፥17-24 ተጓ ምብ - ማቴ 27፥33-44፤ ማር 15፥22-32፤
ሉቃ 23፥33-43

ወታደሮቹም ኢየሱስን ይዘው ወሰዱት፤
17እርሱም የራሱን መስቀል ተሸክሞ በአራ
ማይክ ‘ጎልጎታ’ ተብሎ ወደሚጠራው ‘የራስ
ቅል’ ወደ ተባለው ቦታ ወጣ። 18በዚያም
ሰቀ ሉት፤ ከእርሱም ጋር ሁለት ሰዎች፣
አንዱን በዚህ በኩል፣ ሌላውን በዚያ
በኩል፣ ኢየ ሱስንም በመካከል አድርገው
ሰቀሉ።
19ጲላጦስም ጽሑፍ ጽፎ በመስቀሉ ላይ
አንጠለጠለው፤ ጽሑፉም፣ ‘የናዝሬቱ ኢየ
ሱስ፣ የአይሁድ ንጉሥ’ የሚል ነበር።
20ኢየሱስ የተሰቀለበት ቦታ ከከተማው አጠ
ገብ ስለ ነበር ብዙዎቹ አይሁድ ጽሑፉን
አነበቡት፤ ጽሑፉም፣ በአራማይክና በላቲን፣
በግሪክም ነበር። 21የአይሁድ የካህናት

19፥7 ዘሌ24፥16፤ ማቴ26፥63-66፤ ዮሐ5፥18፤10፥33
19፥9 ማር14፥61፤ ዮሐ18፥33
19፥11 ዮሐ18፥28-30፤ሐሥ3፥13፤ ሮሜ13፥1
19፥12 ሉቃ23፥2
19፥13 ማቴ27፥19፤ ዮሐ5፥2
19፥14 ቀኁ19:21 ማቴ27፥62፤ ማር 15፥25
19፥16 ማቴ27፥26፤ ማር15፥15፤ሉቃ23፥25
19፥17 ዘፍ22፥6፤ ሉቃ14፥27፤23፥33: 26፤ዮሐ5፥2
19፥18 ሉቃ23፥32
19፥19 ቀኁ14:21፤ ማር1፥24
19፥20 ዕብ13፥12
19፥21 ቀኁ14
19፥24 ቀኁ28:36: 37፤መዝ22፥18፤ ማቴ1፥22
19፥25 ማቴ12፥46፤ 27፥55:56፤ሉቃ8፥2፤ዮሐ20፥1:18
19፥26 ማቴ12፥46፤ ዮሐ13፥23
19፥28 ቀኁ24:30: 36:37፤ ማቴ1፥22፤ ዮሐ13፥1
19፥29 መዝ69፥21
19፥30 ሉቃ12፥50፤ ዮሐ4፥34፤17፥4
19፥31 ቀኁ14:42፤ ዘዳ21፥23፤ኢሱ8፥29፤ 10፥26:27
19፥32 ቀኁ18
19፥34 ዘካ12፥10፤ 1ዮሐ5፥6:8፤ራእ1፥7
19፥35 ሉቃ24፥48፤ ዮሐ15፥27፤21፥24

አለቆች ጲላጦስን በመቃወም፣ “እርሱ፣ ‘የአይ
ሁድ ንጉሥ ነኝ’ እንዳለ ጻፍ እንጂ
‘የአይሁድ ንጉሥ’ ብለህ አትጻፍ” አሉት።
22ጲላጦስም፣ “በቃ፤ የጻፍሁትን
ጽፌአለሁ” ብሎ መለሰ።
23ወታደሮቹ ኢየሱስን ከሰቀሉ በኋላ፣ እጀ
ጠባቡ ሲቀር፣ ልብሱን ወስደው
ለእያንዳንዱ አንድ አንድ እንዲደረስ ለአራ
ት ተከፋፈ ሉት፤ እጀ ጠባቡም ከላይ
እስከ ታች አንድ ወጥ ሆኖ ያለ ስፌት
የተሠራ ነበር።
24ስለዚህ፣ “ዕጣ ተጣጥለን ለሚደርሰው
ይድረስ እንጂ አንቅደደው” ተባባሉ። ይህም
የሆነው፣
“ልብሴን ተከፋፈሉት፤
በእጀ ጠባቤም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ”
የሚለው የመጽሐፍ ቃል እንዲፈጸም
ነው።

ወታደሮቹ ያደረጉትም ይህንኑ ነው።
25በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱና
የእናቱ እኅት፣ እንዲሁም የቀልዮጳ
ሚስት ማርያምና መግደላዊት ማርያም ቆመው
ነበር። 26በዚያም ኢየሱስ እናቱንና የሚወ
ደውም ደቀ መዝሙር አጠገቧ ቆሞ ሲያያ
ቸው እናቱን፣ “አንቺ ሴት ሆይ፤ ልጅሽ
ይኸው” አላት፤ 27ደቀ መዝሙሩንም፣ “እናትህ
ይህችው” አለው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ
ደቀ መዝሙር ወደ ቤቱ ወሰዳት።

## የኢየሱስ መሞት

19፥29-30 ተጓ ምብ - ማቴ 27፥48-50፤ ማር 15፥36-37፤
ሉቃ 23፥36

28ከዚያም ኢየሱስ ሁሉ ነገር እንደ ተፈ
ጸመ ዐውቆ፣ የመጽሐፍ ቃል እንዲፈጸም፣
“ተጠማሁ” አለ። 29በዚያም የሆመጠጠ ወይን
የሞላበት ዕቃ ተቀምጦ ነበር፤ እነርሱም
ሰፍነግ በወይን ጠጅ ነክረው፣ በሂሶጵ
ዘንግ ወደ አፉ አቀረቡለት፤ 30ኢየሱስም
ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ፣ “ተፈጸመ”
አለ፤ ራሱን አዘንብሎ፣ መንፈሱን አሳልፎ
ሰጠ።
31ዕለቱ ለሰንበት መዘጋጃ ቀን ነበር።
አይሁድ፣ የተሰቀሉት ሰዎች ሬሳ በሰንበት
ቀን በመስቀል ላይ እንዳይውል ስለ ፈለጉና
ያም የተለየ ሰንበት ስለ ነበር፣ የተሰቀሉት
ሰዎች ጭናቸው ተሰብሮ በድናቸው እንዲ
ወርድ ጲላጦስን ለመኑት። 32ስለዚህም ወታ
ደሮቹ መጥተው ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሎ
የነበረውን የመጀመሪያውን ሰው ጭን
ሰበሩ፤ ደግሞም የሌላውን ጭን ሰበሩ። 33ወደ
ኢየሱስ በመጡ ጊዜ ግን ሞቶ ስላገኙት
ጭኖቹን አልሰበሩም፤ 34ነገር ግን ከወታደሮቹ
አንዱ የኢየሱስን ጐን በጦር ወጋው፤ ወዲ
ያውም ደምና ውሃ ፈሰሰ። 35ይህን ያየው

ሰው ምስክርነቱን ሰጥቶአል፤ ምስክርነቱም
እውነት ነው፤ እውነትን እንደሚናገርም ያው
ቃል፤ እናንተም እንድታምኑ ይመሰክራል።
36ይህም የሆነው፣ መጽሐፍ፣ "ከአጥንቱ አንድም
አይሰበርም" ያለው እንዲፈጸም፣ 37ሌላውም
መጽሐፍ፣ "የወጉትም ያዩታል" ስለሚል
ነው።

## የኢየሱስ መቀበር
19፥38-42 ተጓ ምብ - ማቴ 27፥57-61፤ ማር 15፥42-47፤ ሉቃ 23፥50-56

38ከዚህ በኋላ የአርማትያሱ ዮሴፍ የኢየ
ሱስን በድን ለመውሰድ ጲላጦስን ለመነው፤
ዮሴፍም አይሁድን ስለ ፈራ በስውር የኢ
የሱስ ደቀ መዝሙር ነበር። እርሱም ጲላጦ
ስን ካስፈቀደ በኋላ መጥቶ በድኑን
ወሰደ። 39ከዚህ ቀደም በሌሊት ወደ ኢየሱስ
መጥቶ የነበረው ኒቆዲሞስ አራት መቶ ሊት
ራ[m] ያህል የሚመዝን የከርቤና የእሬት
ቅልቅል ይዞ መጣ። 40እነርሱም የኢ
የሱስን በድን ወስደው እንደ አይሁድ
አገናነዝ ልማድ ሽቱ ቀብተው ከተልባ እግር
በተሠራ ጨርቅ ከፈኑት። 41ኢየሱስ
በተሰቀለበት ቦታም የአትክልት ስፍራ
ነበር፤ በአትክልቱም ስፍራ ማንም
ያልተቀበረበት አዲስ መቃ ብር ነበር። 42ዕ
ለቱ ለአይሁድ የሰንበት መዘጋጃ ቀን ስለ
ነበርና መቃብሩም ቅርብ ስለ ሆነ ኢ
የሱስን በዚያ ቀበሩት።

## ኢየሱስ ከሞት ተነሣ
20፥1-8 ተጓ ምብ - ማቴ 28፥1-8፤ ማር 16፥1-8፤ ሉቃ 24፥1-10

20 በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን፣ በማለዳ
ገና ጨለማ ሳለ፣ መግደላዊት ማር
ያም ወደ መቃብሩ ሄደች፤ ድንጋዩም
ከመቃብሩ መግቢያ ተንከባሎ አየች።
2ስለዚህም ወደ ስምዖን ጴጥሮስና ኢየሱስ
ይወደው ወደ ነበረው ሌላው ደቀ መዝሙር
እየሮጠች መጥታ፣ "ጌታን ከመቃብር
አውጥተው ወስ ደውታል፤ የት እንዳኖሩ
ትም አናውቅም" አለቻቸው።
3"ከዚያም ጴጥሮስና ሌላው ደቀ መዝሙር
ወጥተው ወደ መቃብሩ ሄዱ። 4ሁለቱም
ይሮጡ ነበር፤ ሌላው ደቀ መዝሙርም
ጴጥሮስን ቀድሞት ከመቃብሩ ደረሰ።
5ጐንበስ ብሎ ሲመለከት ከተልባ እግር
የተሠራውን ከፈን በዚያው እንዳለ አየ፤
ወደ መቃብሩ ግን አልገባም። 6ይከተለው
የነበረው ስምዖን ጴጥሮስ ደረሰና ወደ
መቃብሩ ገባ፤ እርሱም ከተልባ እግር የተ
ሠራውን ከፈን አየ፤ 7እንዲሁም በኢየሱስ
ራስ ላይ ተጠምጥሞ የነበረውን ጨርቅ
አየ፤ ይህም ጨርቅ ከከፈኑ ተለይቶ እንደ
ተጠቀለለ ነበር። 8ከዚያም አስቀድሞ
ከመቃብሩ የደረሰው ሌላው ደቀ መዝሙር
ወደ ውስጥ ገባ፤ አይቶም አመነ፤ 9ይኸ
ውም ኢየሱስ ከሙታን መነሣት እንዳ
ለበት ገና ከመጽሐፍ ስላልተረዱ ነበር።

## ኢየሱስ ለመግደላዊት ማርያም ታየ

10ከዚያም በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ተመልሰው
ወደየቤታቸው ሄዱ፤ 11ማርያም ግን ከመቃብሩ
ውጭ ቆማ ታለቅስ ነበር፤ እያለቀሰችም
መቃብሩን ለማየት ጐንበስ አለች። 12የኢ
የሱስ ሥጋ በነበረበት ቦታ፣ ነጫጭ ልብስ
የለበሱ ሁለት መላእክት አንዱ በራስጌ
ሌላው በግርጌ ተቀምጠው አየች።
13እነርሱም፣ "አንቺ ሴት፤ ለምን ታለቅ
ሻለሽ?" ብለው ጠየቋት።
እርሷም፣ "ጌታዬን ወስደውታል፤ የት
እን ዳኖሩትም አላውቅም" አለች። 14ይህን
ብላ ዘወር ስትል ኢየሱስ በዚያው ቆሞ
አየች፤ ኢየሱስ መሆኑን ግን አላወቀችም።
15እርሱም፣ "አንቺ ሴት፤ ለምን ታለቅሻለሽ?
ማንንስ ትፈልጊአለሽ?" አላት።
እርሷም የአትክልቱ ቦታ ጠባቂ መስሎ
አት፣ "ጌታዬ፤ አንተ ወስደኸው ከሆነ፣
እባክህ እንድወስደው፣ የት እንዳኖርኸው
ንገረኝ" አለችው።
16ኢየሱስም፣ "ማርያም" አላት።
እርሷም፣ ወደ እርሱ ዘወር ብላ በአራ
ማይክ ቋንቋ፣ "ረቡኒ!" አለችው፤ ትርጉ
ሙም "መምህር ሆይ" ማለት ነው።
17ኢየሱስም፣ "ገና ወደ አብ ስላላረግሁ፣
አትንኪኝ፤ ይልቁንስ ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ፣
'ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፣ ወደ አምላኬና
ወደ አምላካችሁ ዐርጋለሁ' ብሎአል ብለሽ
ንገሪአቸው" አላት።
18መግደላዊት ማርያምም፣ ወደ ደቀ
መዛ ሙርቱ መጥታ፣ "ጌታን አየሁት!"
አለች፤ እርሱ ያላትንም ነገረቻቸው።

## ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ታየ

19በዚያኑ ዕለት፣ በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን
በምሽት፣ ደቀ መዛሙርቱ አይሁድን በመ
ፍራት በሮቹን ቈልፈው ተሰብስበው ሳለ፣
ኢየሱስ መጣና በመካከላቸው ቆሞ፣ "ሰላም
ለእናንተ ይሁን" አላቸው። 20ይህንም ብሎ
እጆቹንና ጐኑን አሳያቸው፤ ደቀ መዛሙርትም
ጌታን ባዩት ጊዜ እጅግ ደስ አላቸው።
21ኢየሱስም እንደ ገና፣ "ሰላም ለእናንተ
ይሁን፤ አብ እኔን እንደ ላከኝ፣ እኔም
እናንተን እልካችኋለሁ" አላቸው። 22ይህን
ካለ በኋላም፣ እፍ አለባቸውና እንዲህ
አላቸው፤ "መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፤ 23የሰዎችን
ኀጢአት ይቅር ብትሉ፣ ኀጢአታቸው ይቅር
ይባልላቸዋል፤ ኀጢአታቸውን ይቅር ባትሉ

[m]39 ሠላሳ አራት ኪሎ ግራም ያህል ነው

19፥36 ቀኍ24:28:37፤ዘፀ12፥46፤ ዘኍ 9፥12፤ መዝ34፥20፤ ማቴ1፥22
19፥37 ዘካ12፥10፤ ራእ1፥7
19፥38 ዮሐ7፥13
19፥39 ዮሐ3፥1፤ 7፥50
19፥40 ማቴ26፥12፤ ሉቃ24፥12፤ዮሐ11፥44፤20፥5:7
19፥42 ቀኍ14:31: 20:41
20፥1 ቀኍ18፤ ሉቃ 8፥2፤ ማቴ27፥60:66፤ ዮሐ19፥25
20፥2 ቀኍ13 ዮሐ13፥23፤
20፥3 ሉቃ24፥12
20፥5 ቀኍ11፤ ዮሐ19፥40
20፥7 ዮሐ11፥44
20፥8 ቀኍ4
20፥9 ሉቃ24፥26: 46፤ሐሥ2፥24፤ ማቴ 22፥29፤ ዮሐ2፥20
20፥11 ቀኍ5
20፥12 ማቴ28፥2:3፤ ማር16፥5፤ሉቃ24፥4፤ ሐሥ1፥10፤5፥19፤ 10፥30
20፥13 ቀኍ2:15
20፥14 ማር16፥9፤ ሉቃ24፥16፤ ዮሐ 21፥4
20፥15 ቀኍ13
20፥16 ማቴ23፥7፤ ዮሐ5፥2
20፥17 ማቴ28፥10፤ ዮሐ7፥33
20፥18 ቀኍ1፤ ሉቃ24፥10:22:23
20፥19 ቀኍ21:26፤ ሉቃ24፥36-39፤ ዮሐ7፥13፤14፥27
20፥20 ሉቃ24፥39: 40፤ዮሐ16፥20:22፤ 19፥34
20፥21 ቀኍ19፤ማቴ 28፥19፤ዮሐ3፥17፤ 17፥18
20፥22 ዮሐ7፥39፤ ሐሥ2፥38፤8፥15-17፤19፥2፤ገላ 3፥2
20፥23 ማቴ16፥19፤ 18፥18

ግን፣ ይቅር አይባልላቸውም፡፡”

## ኢየሱስ ለቶማስ ታየ

24በዚህ ጊዜ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ
የሆነው፣ ዲዲሞስ የተባለው ቶማስ፣ ኢ
የሱስ በመጣ ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር
አልነበረም፡፡ 25ሌሎች ደቀ መዛሙርትም፣
“ጌታን አየነው እኮ!” አሉት፡፡
እርሱ ግን፣ “በምስማር የተቸነከሩትን የእ
ጆቹን ምልክቶች ካላየሁ፣ ምስማሮቹ በነበሩ
በት ቦታ ጣቴን ካላደረግሁ፣ በጐኑም እጄን
ካላስገባሁ አላምንም” አለ፡፡
26ከስምንት ቀን በኋላም፣ ደቀ መዛሙርቱ
በቤት ውስጥ ነበሩ፤ ቶማስም ከእነርሱ
ጋር ነበር፤ በሮቹ ተቈልፈው ነበር፤ ኢየሱስ
ግን መጥቶ በመካከላቸው ቆመና፣ “ሰላም
ለእናንተ ይሁን” አላቸው፡፡ 27ከዚያም ቶማስን፣
“ጣትህን ወደዚህ አምጣ፤ እጆቼንም ተመ
ልከት፤ እጅህን ዘርጋና በጐኔ አስገባ፤
አትጠራጠር፤ እመን” አለው፡፡
28ቶማስም፣ “ጌታዬ፤ አምላኬም!”
አለው፡፡
29ኢየሱስም፣ “አንተ ስላየኸኝ አምነሃል፤
ሳያዩ የሚያምኑ ግን ብፁዓን ናቸው”
አለው፡፡
30ኢየሱስ በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፉ ሌሎች
አያሌ ታምራዊ ምልክቶችን በደቀ መዛ
ሙርቱ ፊት አድርጓል፤ 31ነገር ግን ኢየሱስ
እርሱ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔርም ልጅ እንደ
ሆነ እንድ ታምኑ[ጨ] ዘንድ፣ አምናችሁም
በስሙ ሕይወት እንዲኖራችሁ ይህ ተጽ
ፎአል፡፡

## ደቀ መዛሙርቱ ዓሣ በታምር መያዛቸው

21 ከዚያም በኋላ ኢየሱስ በጥብርያዶስ
ባሕር[ጸ] እንደ ገና ለደቀ መዛሙርቱ
ታየ፤ በዚህም ሁኔታ ተገለጠ፤ 2ስምዖን
ጴጥሮስ፣ ዲዲሞስ የተባለው ቶማስ፣ የቃና
ዘገሊላው ናትናኤል፣ የዘብዴዎስ ልጆችና
ከደቀ መዛሙርቱ ሌሎች ሁለት አንድ ላይ
ነበሩ፤ 3ስምዖን ጴጥሮስም፣ “ዓሣ ላጠምድ
መሄዴ ነው” አላቸው፤ እነርሱም፣ “እኛም
ከአንተ ጋር እንሄዳለን” አሉት፡፡ ወጥተውም
ወደ ጀልባዋ ገቡ፤ በዚያ ሌሊት ግን ምንም
አላጠመዱም፡፡
4ሲነጋም፣ ኢየሱስ በባሕሩ ዳርቻ ቆመ፤
ደቀ መዛሙርቱ ግን ኢየሱስ መሆኑን አላወቁም
ነበር፡፡
5እርሱም፣ “ልጆች፣ ዓሣ አላችሁ?” አላቸው፡፡
እነርሱም፣ “የለንም” አሉት፡፡
6እርሱም፣ “መረባችሁን ከጀልባው በስተ ቀኝ
ጣሉ፤ ዓሣ ታገኛላችሁ” አላቸው፡፡ እነርሱም
በጣሉ ጊዜ ከዓሣው ብዛት የተነሣ መረቡን

20፥24 ዮሐ11፥16
20፥25 ቍ20፤ ማር16፥11
20፥26 ቍ21፤ ዮሐ14፥27
20፥27 ቍ25፤ ሉቃ24፥40
20፥29 ዮሐ3፥15፤ 1ጴጥ1፥8
20፥30 ዮሐ2፥11፤ 21፥25
20፥31 ማቴ4፥3፤ 25፥46፤ዮሐ3፥15፤ 19፥35
21፥1 ቍ14፤ ዮሐ6፥1፤20፥19፡26
21፥2 ማቴ4፥21፤ ዮሐ1፥45፤2፥1፤ 11፥16
21፥3 ሉቃ5፥5
21፥4 ሉቃ24፥16፤ ዮሐ20፥14
21፥6 ሉቃ5፥4-7
21፥7 ዮሐ13፥23
21፥9 ቍ10፡13፤ ዮሐ18፥18
21፥13 ቍ9
21፥14 ዮሐ20፥19፡ 26
21፥15 ማቴ6፥ 33፡35፤ሉቃ12፥32፤ ዮሐ13፥37
21፥16 2ሳሙ5፥2፤ ሕዝ34፥2፤ማቴ2፥6፤ ዮሐ10፥11፤ ሐሥ20፥28፤ 1ጴጥ5፥2፡3
21፥17 ቍ16፤ ዮሐ13፥38፤16፥30

መጐተት አቃታቸው፡፡
7ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙ
ርም፣ ጴጥሮስን፣ “ጌታ እኮ ነው!” አለው፡፡
ስምዖን ጴጥሮስም፣ ‘ጌታ እኮ ነው!’ የሚለውን
ቃል በሰማ ጊዜ፣ አውልቆት የነበረውን
መደረቢያ ልብስ ታጠቀና ዘሎ ወደ ባሕሩ
ገባ፡፡ 8ሌሎች ደቀ መዛሙርት ግን ከባሕሩ
ዳርቻ የራቁት ሁለት መቶ ክንድ ያህል[ጸ]
ብቻ ስለ ነበር፣ ዓሣ የሞላበትን መረብ
እየሳቡ በጀልባዋ መጡ፡፡ 9ወደ ምድርም
በደረሱ ጊዜ፣ ዓሣ በላዩ የነበረበት የከሰል
ፍምና እንጀራ አዩ፡፡
10ኢየሱስም፣ “አሁን ካጠመዳችሁት ዓሣ
እስቲ አምጡ” አላቸው፡፡
11ስለዚህ ስምዖን ጴጥሮስ ወደ ጀልባዋ
ወጥቶ መረቡን ወደ ምድር ጐተተው፤
መረቡንም መቶ አምሳ ሦስት ትልልቅ ዓሣ
ሞልተውት ነበር፤ ይህን ያህል ቢይዝም
መረቡ አልተቀደደም፡፡ 12ኢየሱስም “ኑ፤
ቍርስ ብሉ” አላቸው፡፡ ጌታ እንደ ሆነ ዐ
ውቀው ስለ ነበር፣ ከደቀ መዛሙርቱ፣ “አንተ
ማን ነህ?” ብሎ ለመጠየቅ የደፈረ አልነበረም፡፡
13ኢየሱ ስም መጥቶ እንጀራውን አንሥቶ
ሰጣቸው፤
ዓሣውንም ሰጣቸው፡፡ 14እንግዲህ ኢየሱስ
ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ
ሲታይ ይህ ሦስተኛ ጊዜ ነው፡፡

## ኢየሱስ ጴጥሮስን ወደ ቀድሞ ቦታው መለሰው

15በልተው ካበቁ በኋላ፣ ኢየሱስ ስምዖን ጴጥ
ሮስን፣ “የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፤ ከእነዚህ
አብልጠህ ትወደኛለህን?” አለው፡፡
እርሱም፣ “አዎን፣ ጌታ ሆይ፤ እንደም
ወድህ አንተ ታውቃለህ” አለው፡፡
ኢየሱስም፣ “ጠቦቶቼን መግብ” አለው፡፡
16ኢየሱስም ለሁለተኛ ጊዜ፣ “የዮና ልጅ፣
ስምዖን ሆይ፤ በእውነት ትወደኛለህን?” አለው፡፡
እርሱም፣ “አዎን፤ ጌታ ሆይ፤ እንደም
ወድህ አንተ ታውቃለህ” አለው፡፡
ኢየሱስም፣ “በጎቼን ጠብቅ” አለው፡፡
17ሦስተኛም ጊዜ፣ “የዮና ልጅ፣ ስምዖን ሆይ፤
ትወደኛለህን?” አለው፡፡
ጴጥሮስም ሦስተኛ ጊዜ ኢየሱስ፣ ‘ትወደ
ኛለህን?’ ብሎ ስለ ጠየቀው ዐዘነ፣ “ጌታ
ሆይ፤ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤ እንደምወድህም
ታውቃለህ” አለው፡፡
ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ “በጎቼን መግብ፡፡
18እውነት እልሃለሁ፤ ወጣት ሳለህ ልብስህን
ራስህ ለብሰህ ወደ ፈለግህበት ትሄድ ነበር፤

[ጨ]31 አንዳንድ ቅጆች *በማመን እንድትድኑ* ይላሉ
[ጸ]1 የገሊላ ባሕር ማለት ነው
[ጸ]8 ዘጠና ሜትር ያህል ነው

ስትሸመግል ግን እጅህን ትዘረጋለህ፤ ሌላም
ሰው ልብስህን አስታጥቆህ ልትሄድ ወደ
ማትፈልግበት ይወስድሃል።” [19]ኢየሱስ ይህን
ያለው ጴጥሮስ በምን ዐይነት ሞት እግዚአ
ብሔርን እንደሚያከብረው ለማመልከት ነው።
ከዚህ በኋላም፣ “ተከተለኝ” አለው።

[20]ጴጥሮስ ወደ ኋላው ዞወር ሲል፣ ኢየሱስ
ይወደው የነበረ ደቀ መዝሙር ሲከተ
ላቸው አየ፤ ይህም ደቀ መዝሙር ያን ጊዜ
ራት ሲበሉ ወደ ኢየሱስ ደረት ተጠግቶ፣
“ጌታ ሆይ፤ አሳልፎ የሚሰጥህ ማን ነው?”
ያለው ነበር። [21]ጴጥሮስም ባየው ጊዜ፣ “ጌታ
ሆይ፤ እርሱስ?” ብሎ ጠየቀ።

[22]ኢየሱስም፣ “እስክመለስ ድረስ በሕይወት
እንዲኖር ብፈልግ እንኳ አንተን ምን ቸገረህ?
አንተ ራስህ ተከተለኝ” አለው። [23]በዚህ ምክ
ንያት ይህ ደቀ መዝሙር አይሞትም የሚል
ወሬ በወንድሞች መካከል ተሰራጨ። ኢየሱስ
ግን፣ “እስክመለስ ድረስ በሕይወት እንዲ
ኖር ብፈልግ አንተን ምን ቸገረህ?” አለው
እንጂ እንደማይሞት አልነገረውም።

[24]ስለ እነዚህ የሚመሰክረውና ይህን የጻፈው
ይኸው ደቀ መዝሙር ነው፤ ምስክርነቱም
እውነት እንደ ሆነ እናውቃለን።

[25]ኢየሱስ ያደረጋቸው ሌሎችም ብዙ
ነገሮች አሉ፤ ሁሉም ነገር ቢጻፍ፣ ለተጻፉት
መጻሕፍት ሁሉ ዓለም በቂ ቦታ የሚኖረው
አይመስለኝም።

21፥19 ማቴ4፥19፤ ዮሐ12፥33፤13፥36፤ 18፥32፤2ጴጥ1፥14
21፥20 ቁ7፤ ዮሐ13፥23፡25
21፥22 ቁ19፤ ማቴ4፥19፤16፥27
21፥23 ሐሥ1፥16
21፥24 ዮሐ15፥27፤ 19፥35
21፥25 ዮሐ20፥30

# የሐዋርያት ሥራ

## ኢየሱስ ወደ ሰማይ ዐረገ

1 ቴዎፍሎስ ሆይ፤ ኢየሱስ ለማድረግና
ለማስተማር የጀመረውን ሁሉ ቀደም
ባለው መጽሐፌ ጽፌልሃለሁ፤ 2ይኸውም
እስከ ዐረገበት ቀን ድረስ ለመረጣቸው ሐዋ
ርያት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሰጣ
ቸው ትእዛዝ ነው:: 3ከሕማማቱም በኋላ
ራሱ ቀርቦ ሕያው መሆኑን፣ ለእነዚሁ
በብዙ ማስረጃ አያረጋገጠላቸው አርባ
ቀንም ዐልፎ ዐልፎ እየታያቸው ስለ እግዚ
አብሔር መንግሥት ነገራቸው::
4ከእነርሱም ጋር በማእድ ተቀምጦ ሳለ
እንዲህ ሲል አዘዛቸው፤ “ከኢየሩሳሌም
አትውጡ፤ ነገር ግን እኔ ስናገር የሰ
ማችሁትን፣ አብ የሰጠውን ተስፋ ጠብቁ፤
5ዮሐንስ በውሃ አጥምቆ ነበርና፣ እናንተ
ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ
ትጠመቃላችሁ::”

6እነርሱም ተሰብስበው ሳሉ፣ “ጌታ ሆይ፤
የእስራኤልን መንግሥት መልሰህ የምታቋ
ቁምበት ጊዜው አሁን ነውን? ብለው ጠየ
ቁት::
7እርሱም እንዲህ አላቸው፤ “አብ በገዛ
ሥልጣኑ የወሰነውን ጊዜ ወይም ወቅት
ማወቁ ለእናንተ አልተሰጣችሁም፤ 8ነገር
ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወ
ርድበት ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢ
የሩሳሌም፣ በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፣ እስከ
ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ::”
9ይህን ካለ በኋላ እያዩት ወደ ላይ ዐረገ፤
ደመናም ከዐይናቸው ሰወረችው::
10እርሱም በሚሄድበት ጊዜ ትኵር ብለው
ወደ ሰማይ ሲመለከቱ፣ እነሆ፤ ነጫጭ
ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች ድንገት አጠ
ገባቸው ቆሙ፤ 11እንዲህም አሏቸው፤ “እና
ንት የገሊላ ሰዎች ሆይ፤ ወደ ሰማይ እየ
ተመለከታችሁ እዚህ የቆማችሁት ለምን
ድን ነው? ይህ ከእናንተ ዘንድ ወደ ሰማይ
ሲያርግ ያያችሁት ኢየሱስ፣ ልክ ወደ ሰማይ
ሲወጣ እንዳያችሁት በዚሁ ሁኔታ ይመለ
ሳል::”

## ማትያስ በይሁዳ ምትክ ተመረጠ

12ከዚያም ደብረ ዘይት ከተባለው ተራራ
ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፤ ይህም ተራራ
ከኢየሩሳሌም የሰንበት መንገድ ያህል[ሀ]
ይርቅ ነበር:: 13ወደ ከተማዪቱም በገቡ
ጊዜ ወደሚኖሩበት ሰገነት ወጡ፤ እነዚ
ህም ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ፣ ያዕቆብ፣ እንድር
ያስ፣ ፊልጶስ፣ ቶማስ፣ በርተሎሜዎስ፣
ማቴዎስ፣ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ፣ ቀናኢ
የተባለው ስምዖንና የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ
ነበሩ::
14እነዚህ ሁሉ ከሴቶቹና ከኢየሱስ እናት
ከማርያም ጋር እንዲሁም ከወንድሞቹ ጋር
በአንድ ልብ ሆነው ያለማቋረጥ ተግተው ይጸ
ልዩ ነበር::
15በእነዚያም ቀናት፣ ጴጥሮስ መቶ ሃያ
በሚሆኑ ወንድሞች[ለ] መካከል ቆሞ፣ 16እንዲህ
አለ፤ “ወንድሞች ሆይ፤ ኢየሱስን ለያዙት
ሰዎች መሪ ስለ ሆናቸው ስለ ይሁዳ፣ መን
ፈስ ቅዱስ አስቀድሞ በዳዊት አፍ የተናገ
ረው የመጽሐፉ ቃል መፈጸም ስላለበት፣
17እርሱ ከእኛ እንደ አንዱ ተቈጥሮ በዚህ
አገልግሎት የመሳተፍ ዕድል አግኝቶ
ነበር::”
18 “ይህ ሰው ስለ ክፉ ሥራው በተከ
ፈለው ዋጋ መሬት ገዛ፤ በዚያም በግንባሩ
ተደፍቶ ሰውነቱ እመካከሉ ላይ ፈነዳ፤
ሆድ ዕቃውም ተዘረገፈ፤ 19ይህም በኢየሩ
ሳሌም በሚኖሩት ሁሉ ዘንድ ተሰማ፤
መሬቱም በቋንቋቸው ‘አኬልዳማ’ ተብሎ
ተጠራ፤ ትርጓሜውም ‘የደም መሬት’
ማለት ነው::

20ጴጥሮስም በመቀጠል እንዲህ አለ፤
“በመዝሙር መጽሐፍ፣

‘መኖሪያው ባዶ ትሁን፤
የሚኖርባትም ሰው አይገኝ’ ደግሞም፣
‘ሹመቱን ሌላ ሰው ይውሰደው’
ተብሎ ተጽፎአል::

21ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ በመካከላችን በገባበ
ትና በወጣበት ጊዜ ሁሉ፣ ከእኛ ጋር ከነ
በሩት መካከል አንድ ሰው መምረጥ ያስ
ፈልጋል፤ 22ይኸውም፣ ከዮሐንስ ጥምቀት
ጀምሮ ኢየሱስ ከእኛ ተለይቶ እስካረገበት
ቀን ድረስ የነበረ መሆን አለበት፤ ምክን
ያቱም ከእነዚህ ሰዎች አንዱ ከእኛ ጋር
የትንሣኤው ምስክር እንዲሆን ያስፈልጋል::”
23ስለዚህ ኢዮስጦስ የሚሉትን፣ በርስያን
የተባለውን ዮሴፍንና ማቲያስን ሁለቱን
አቀረቡ፤ 24እንዲህም ብለው ጸለዩ፤ “ጌታ
ሆይ፤ አንተ የሰውን ሁሉ ልብ ታውቃለህ፤

1፥1 ሉቃ1፥1-4፤ 3፥23
1፥2 ቍ9፥11፤ ማቴ 28፥19፡20፤ ማር6፥30፤ 16፥19፤ዮሐ13፥18፤ 15፥16፡19
1፥3 ማቴ3፥2፤ 28፥17፤ ሉቃ24፥34፡36፤ ዮሐ 20፥19፡26፤ 21፥1፡14፤1ቆሮ15፥5-7
1፥4 መዝ27፥14፤ ሉቃ24፥49፤ ዮሐ14፥16፤ ሐሥ2፥33
1፥5 ማር1፥4፡8
1፥6 ማቴ17፥11፤ ሐሥ3፥21
1፥7 ዘዳ29፥29፤ መዝ 102፥13፤ ማቴ24፥36
1፥8 ማቴ28፥19፤ ሉቃ24፥48፤ሐሥ 2፥1-4፤8፥1-25
1፥9 ቍ2፤ማር 16፥19
1፥10 ዮሐ20፥12
1፥11 ማቴ16፥27፤ ሐሥ2፥7
1፥12 ማቴ21፥1፤ ሉቃ 24፥52
1፥13 ማቴ10፥2-4፤ ማር3፥16-19፤ ሉቃ 6፥14-16፤ ሐሥ 9፥37፤ 20፥8
1፥14 ማቴ12፥46፤ ሉቃ18፥1፤23፥49፡55፤ሐሥ2፥42፤4፥24፤ 6፥4፤ሮሜ1፥10
1፥16 ቍ20፤ ማቴ1፥22፤10፥4፤ ሐሥ6፥3፤11፥1፡12፡ 29፤14፥2፤18፥18፡27፤ 21፥7፤22፥5፤ሮሜ7፥1
1፥17 ቍ25፤ ዮሐ 6፥70፡71
1፥18 ማቴ26፥14፡ 15፤27፥3-10
1፥19 ዮሐ5፥2
1፥20 መዝ69፥25፤ 109፥8
1፥22 ቍ8፤ማር 1፥4፤ሉቃ24፥48
1፥24 1ሳሙ14፥41 ፤ሐሥ6፥6፤13፥3፤ 14፥23፤ራእ2፥23

ሀ12 አንድ ሺህ አንድ መቶ ሜትር ገደማ ነው::
ለ15 ወይም *አማኞች*

ከእነዚህ ከሁለቱ መካከል የመረጥኸውን
ሰው አመልክተንና 25ይሁዳ ወደ ገዛ ራሱ
ስፍራ ትቶት በሄደው በዚህ አገልግሎትና
በሐዋርያዊነት ቦታ ላይ ሹመው::” 26ከዚ
ያም ዕጣ ጣሉላቸው፤ ዕጣውም ለማትያስ
ወጣ፤ እርሱም ከዐሥራ አንዱ ሐዋርያት
ጋር ተሐጠረ::

## በበዓለ ኀምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ ወረደ

2 የበዓለ ኀምሳ ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም
በአንድነት፣ በአንድ ስፍራ ተሰብስ
በው ነበር፤ 2ድንገትም እንደ ብርቱ ዐውሎ
ነፋስ ያለ ድምፅ ከሰማይ መጥቶ ተቀምጠው
የነበሩበትን ቤት እንዳለ ሞላው:: 3የእሳት
ምላሶች የሚመስሉም ታዩአቸው፤ ተከፋፍ
ለውም በእያንዳንዳቸው ላይ ዐረፉ:: 4ሁሉም
በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤ መንፈስም እንዲ
ናገሩ በሰጣቸው መጠን በሌሎች ቋንቋዎች[ሐ]
ይናገሩ ጀመር::

5በዚህ ጊዜ ከሰማይ በታች ካለው ሕዝብ
ሁሉ የመጡና እግዚአብሔርን የሚፈሩ
አይሁድ በኢየሩሳሌም ነበሩ:: 6ይህን ድምፅ
ሲሰሙ፣ ብዙ ሕዝብ በአንድነት ተሰበሰቡ፤
እያንዳንዱም ሰው፣ ሰዎቹ በገዛ ቋንቋው
ሲናገሩ በመስማቱ ግራ ተጋባ፤ 7በመገረ
ምና በመደነቅም እንዲህ አሉ፤ “እነዚህ
የሚነጋገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉ
ምን? 8ታዲያ፣ እያንዳንዳችን በተወለድን
በት፣ በራሳችን ቋንቋ ሲናገሩ የምንሰማ
ቸው እንዴት ቢሆን ነው? 9እኛ የጳር
ቴና፣ የሜድ፣ የኢላሜጤም ሰዎች፣ በመ
ስጴጦምያ፣ በይሁዳ፣ በቀጰዶቅያ፣ በጳን
ጦስ፣ በእስያ፣ 10በፍርግያ፣ በጵንፍልያ፣
በግብፅ፣ በቀሬና አጠገብ ባሉት በሊቢያ
አውራጃዎች የምንኖር፣ ከሮም የመጣን
11አይሁድና ወደ ይሁዲነት የገባን፣ የቀ
ርጤስና የዐረብ ሰዎች ስንሆን፣ ሰዎቹ የእ
ግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በየቋንቋችን ሲና
ገሩ እንሰማቸዋለን” 12ሁሉም በአድናቆ
ትና ግራ በመጋባት፣ ይህ ነገር ምን ይሆን”
ተባባሉ::

13አንዳንዶቹ ደግሞ “ያልፈላ ብዙ የወይን
ጠጅ[መ] ጠጥተዋል” በማለት አፌዙባቸው::

## ጴጥሮስ ለሕዝቡ ንግግር አደረገ

14በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ ከዐሥራ አንዱ
ጋር ተነሥቶ ቆመ፤ ድምፁንም ከፍ አድ
ርጎ እንዲህ ሲል ለሕዝቡ ተናገረ፤ “እና
ንት የይሁዳ ሰዎች፤ በኢየሩሳሌምም የም
ትኖሩ ሁሉ፤ ይህን አንድ ነገር ዕወቁ፤
በጥሞናም አድምጡ:: 15ጊዜው ገና ከጠ
ዋቱ ሦስት ሰዓት ስለ ሆነ፣ እናንተ እን
ደምታስቡት እነዚህ ሰዎች አልሰከሩም::

1፥26 ሐሥ2፥14
2፥1 ዘሌ23፥15፡ 16፤ሐሥ1፥14፤20፥ 16፤1ቆሮ16፥8
2፥2 ሐሥ4፥31
2፥4 ማር16፥17፤ ሉቃ1፥15
2፥5 ሉቃ2፥25፤ ሐሥ 8፥2
2፥7 ቀኍ12፤ሐሥ 1፥11
2፥9 ሐሥ16፥6፡17፤ 18፥2፤19፥10፤ሮሜ 16፥5፤1ቆሮ16፥19፤2 ቆሮ1፥8፤1ጴጥ1፥1፤ ራእ1፥4
2፥10 ማቴ27፥32፤ ሐሥ13፥13፤ 14፥24፤ 15፥38፤16፥6፤18፥23፤
2፥13 1ቆሮ14፥23፤ ኤፌ5፥18
2፥15 1ተሰ5፥7
2፥17 ዘኍ11፥25፤ ኢሳ44፥3፤ሕዝ39፥ 29፤ ዮሐ7፥37-39፤ ሐሥ 10፥45፤21፥9
2፥18 ሐሥ21፥9-12
2፥19 ሉቃ21፥11
2፥20 ማቴ24፥29
2፥21 ዘፍ4፥26፤ 26፥25፤መዝ105፥1፤ኢ ዩል2፥28-32፤ ሐሥ 9፥14፤ ሮሜ10፥13፤ 1ቆሮ1፥2፤2ጢሞ2፥22
2፥22 ማር1፥24፤ ዮሐ3፥2፤4፥48
2፥23 ኢሳ53፥10፤ ማቴ16፥21፤ ሉቃ24፥20፤ ሐሥ3፥13፡18፤ 4፥28
2፥24 ቀኍ32፤ ዮሐ 20፥9፤ ሐሥ13፥30፡ 33፡34፡37፤17፥31፤ ሮሜ6፥4፤8፥11፤ 10፥9፤ 1ቆሮ6፥14፤ 15፥15፤ኤፌ1፥20፤1ቆ ሮ6፥14፤15፥15፤ ኤፌ1፥20፤ቈላ2፥12፤ዕ ብ13፥20፤ 1ጴጥ 1፥21
2፥27 ቀኍ31፤ ሐሥ 13፥35
2፥28 መዝ16፥8-11
2፥29 1ነገ2፥10፤ ነህ 3፥16፤ ሐሥ7፥8፡9፤ 13፥36፤22፥5

16ነገር ግን ይህ በነቢዩ በኢዩኤል እንዲህ
ተብሎ የተነገረ ነው፤

17“እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ በመጨረሻው
ቀን፣
መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ
አፈሳለሁ፤
ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት
ይናገራሉ፤
ጕልማሶቻችሁ ራእይ ያያሉ፤
ሽማግሌዎቻችሁ ሕልም ያልማሉ::
18በዚያ ጊዜ በወንዶችና በሴቶች
አገልጋዮቼ ላይ፣
መንፈሴን አፈሳለሁ፤
እነርሱም ትንቢት ይናገራሉ::
19በላይ በሰማያት ድንቅ ነገሮችን፣
አሳያለሁ፤
በታች በምድርም ምልክቶችን እሰጣለሁ፤
ደምና እሳት፣
የጢስም ጭጋግ ይሆናል::
20ታላቅና ክቡር የሆነው የጌታ ቀን
ከመምጣቱ በፊት፣
ፀሓይ ወደ ጨለማ፣
ጨረቃም ወደ ደም ይለወጣሉ::
21የጌታን ስም፣
የሚጠራ ሁሉ ይድናል::’

22“የእስራኤል ሰዎች ሆይ፤ ይህን ቃል
ስሙ፤ እናንት ራሳችሁ እንደምታውቁት፣
እግዚአብሔር በመካከላችሁ ታምራትን፣
ድንቅ ነገሮችንና ምልክቶችን በእርሱ
በኩል በማ ድረግ ለናዝሬቱ ኢየሱስ
መስክሮለታል:: 23እግዚአብሔር በጥንት
ውሳኔውና በቀደመው
ዕውቀቱ ይህን ሰው አሳልፎ በእጃችሁ
ሰጣችሁ፤ እናንተም በክፉ ሰዎች[ሠ] እጅ
ሰቅላችሁ ገደላችሁት:: 24እግዚአብሔር ግን
የሞትን ጣር አስወግዶ አስነሣው፤ ሞት ይዞ
ሊያስቀረው አልቻለምና:: 25ዳዊትም ስለ
እርሱ እንዲህ ይላል፤

“ጌታን ሁልጊዜ በፊቴ አየዋለሁ፤
እርሱ በቀኜ ነውና፣
ከቶ አልታወክም::
26ስለዚህ ልቤ ደስ አለው፤ አንደበቴም
ሐሤት አደረገ፤
ሥጋዬም በተስፋ ይኖራል::
27ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፤
ቅዱስህም መበስበስን እንዲያይ
አታደርግም::
28የሕይወትን መንገድ እንዳውቅ
አደረግኸኝ፤
በፊትህም በሐሤት ትሞላኛለህ::’

[ሐ]4 ወይም ልሳኖች እንዲሁም በቍ 11
[መ]13 ወይም *ጣፋጭ ወይን*
[ሠ]23 ወይም *ሕግ በሌላቸው ሰዎች (አሕዛብን ያመለክታል)*

[29]“ወንድሞች ሆይ፤ ከቀደምት አባቶች
ዳዊት ሞቶ እንደ ተቀበረ፣ መቃብሩም
እስከ ዛሬ ድረስ በመካከላችን እንደሚገኝ
በድፍረት መናገር እችላለሁ፡፡ [30]ነቢይ
በመሆኑም፣ እግዚአብሔር ከዘሮቹ አንዱን
በዙፋኑ ላይ እንደሚያስቀምጥ በመሐላ
ቃል የገባለት መሆኑን ዐወቀ፡፡ [31]ይህንን
አስቀድሞ በማየቱ እርሱ በሲኦል እንደማ
ይቀርና ሥጋውም እንደማይበሰብስ ስለ
ክርስቶስ ትንሣኤ[ረ] ተናገረ፡፡ [32]ይህን ኢየ
ሱስ፣ እግዚአብሔር ከሞት አስነሣው፤ እኛም
ሁላችን ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን፡፡ [33]ስለ
ዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ካለ
በኋላ፣ የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ ከአብ
ተቀብሎ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙ
ትን አፈሰሰው፡፡ [34]ዳዊት ወደ ሰማያት
አልወጣም፤ እርሱ ራሱ ግን እንዲህ ብሎአል፤

“ ‘ጌታ ጌታዬን፣
[35]“ጠላቶችህን ለእግርህ መረገጫ እስከ
ማደርግልህ ድረስ፣
በቀኜ ተቀመጥ” አለው፡፡

[36]“እንግዲህ፣ እግዚአብሔር ይህን እናንተ
የሰቀላችሁትን ኢየሱስን፣ ጌታም ክርስቶስም
እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ ይረዳ፟”
[37]ሕዝቡም ይህን በሰሙ ጊዜ ልባቸው
እጅግ ተነካ፤ ጴጥሮስንና ሌሎቹንም ሐዋ
ርያት፣ “ወንድሞች ሆይ፤ ታዲያ ምን እና
ድርግ?” አሏቸው፡፡
[38]ጴጥሮስም እንዲህ አላቸው፤ “ንስሓ
ግቡ፤ ኀጢአታችሁም እንዲሰረይላችሁ፣ እያ
ንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠ
መቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላ
ላችሁ፡፡ [39]የተስፋው ቃል ለእናንተና ለል
ጆቻችሁ እንዲሁም ጌታ አምላካችን ወደ ራሱ
ለሚጠራቸው፣ በሩቅ ላሉትም ሁሉ ነውና፡፡”
[40]በሌላ ብዙ ቃል እየመሰከረላቸው፣ “ከዚህ
ጠማማ ትውልድ ራሳችሁን አድኑ” በማለት
አስጠነቀቃቸው፡፡ [41]ቃሉን የተቀበሉትም ተጠ
መቁ፤ በዚያ ቀን ሦስት ሺህ ያህል ሰዎች
በቍጥራቸው ላይ ተጨመሩ፡፡

## የአማኞች የኅብረት ኑሮ

[42]እነርሱም በሐዋርያት ትምህርትና በኅ
ብረት፣ እንጀራውንም በመቍረስና በጸሎት
ይተጉ ነበር፡፡ [43]በሐዋርያት እጅ ብዙ ድን
ቅና ታምራት ይደረግ ስለ ነበር፣ ሰው
ሁሉ ፍርሀት አደረበት፡፡ [44]ያመኑት ሁሉ
በአንድነት ነበሩ፤ ያላቸውንም ሁሉ የጋራ
አደረጉ፡፡ [45]ሀብታቸውንና ንብረታቸውንም
እየሸጡ ለእያንዳንዱ ሰው የሚያስፈልገ
ውን ያህል ይሰጡት ነበር፡፡ [46]በየዕለቱ በቤተ
መቅደስ በአንድነት እየተገናኙ፣ በቤታቸ

2፥30 ማቴ1፥1
2፥31 መዝ16፥10
2፥32 ቊ24፤ሉቃ 24፥48
2፥33 ማር16፥19፤ ዮሐ7፥39፤14፥26፤ 15፥26፤ሐሥ1፥4፤ 10፥45፤ፊል2፥9
2፥35 መዝ110፥1፤ ማቴ22፥44
2፥36 ማቴ28፥18፤ ሉቃ2፥11
2፥37 ሉቃ3፥10፡ 12፡14፤ሐሥ16፥30
2፥38 ቊ41፤ ኤር 36፥3፤ማር1፥4፤ ሉቃ 24፥47፤ ዮሐ20፥22፤ ሐሥ3፥19፤8፥12፡16 ፡36፡38፤9፥18፤10፥48፤ 16፥15፡33፤19፥5፤22፥ 16፤ቈላ2፥12
2፥39 ኢሳ44፥3፤ 57፥19፤65፥23፤ ሐሥ 10፥45፤ ኤፌ2፥13
2፥40 ዘዳ32፥5፤ ፊል 2፥15
2፥41 ቊ47፤ ሐሥ 4፥4፤5፥14፤ 6፥1፡7፤ 9፥31፡35፡42፤ 11፥21፡24፤14፥1፡21፤16፥5 ፤17፥12
2፥42 ማቴ14፥ 19፤ 28፥20፤ሐሥ1፥14
2፥43 ሐሥ5፥12
2፥44 ሐሥ4፥32
2፥45 ማቴ19፥21፤ ሉቃ12፥33፤18፥22፤ሐ ሥ4፥34፡35፤6፥1
2፥46 ቊ42፥ማቴ 14፥19፤ሉቃ24፥53፤ሐ ሥ3፥1፤5፥21፡42
2፥47 ቊ41፤ሮሜ 14፥18
3፥1 መዝ55፥17፤ ሉቃ22፥8፤ሐሥ 2፥46፤10፥30
3፥2 ሉቃ16፥20፤ ዮሐ9፥8፤ሐሥ14፥8
3፥6 ቊ16፤ማር 1፥24
3፥8 ኢሳ35፥6፤ሐሥ 14፥10
3፥9 ሐሥ4፥16፡21
3፥10 ቊ2
3፥11 ሉቃ22፥8፤ ዮሐ10፥23፤ሐሥ5፥ 12

ውም እንጀራ እየሖረሱ በደስታና በቀና
ልብ ይመገቡ ነበር፤ [47]እግዚአብሔርንም እያ
መሰገኑ፣ በሕዝቡ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራ
ቸው፤ ጌታም የሚድኑትን በቍጥራቸው
ላይ ዕለት በዕለት ይጨምር ነበር፡፡

## ጴጥሮስ ሽባውን ለማኝ ፈወሰ

3 አንድ ቀን ጴጥሮስና ዮሐንስ በጸሎት
ጊዜ ይኸውም ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት፣
ወደ ቤተ መቅደስ ይወጡ ነበር፡፡ [2]ወደ
ቤተ መቅደስ ከሚገቡት ሰዎች ምጽዋት
እንዲለምን፣ ሰዎች በየዕለቱ ተሸክመው
‘ውብ’ በተባለው የቤተ መቅደስ መግቢያ
በር ላይ የሚያስቀምጡት አንድ ከተወለደ
ጀምሮ ሽባ የሆነ ሰው ነበረ፤ [3]እርሱም ጴጥ
ሮስና ዮሐንስ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገቡ
አይቶ ምጽዋት ለመናቸው፡፡ [4]ጴጥሮስም
ከዮሐንስ ጋር ወደ እርሱ ትኵር ብሎ አየ
ውና፣ “እስቲ ወደ እኛ ተመልከት” አለው፡፡
[5]ሰውየውም፣ ከእነርሱ አንድ ነገር ለማግ
ኘት አስቦ በትኵረት ተመለከታቸው፡፡
[6]ጴጥሮስ ግን፣ “እኔ ብርና ወርቅ የለኝም፤
ነገር ግን ያለኝን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየ
ሱስ ክርስቶስ ስም ተነሥተህ በእግርህ
ተመላለስ” አለው፤ [7]ቀኝ እጁንም ይዞ አስነሣው፤
ወዲያውም እግሩና ቍርጭምጭሚቱ በረታ፤
[8]ዘሎም ቀጥ ብሎ ቆመ፤ መራመድም
ጀመረ፤ ወዲህ ወዲያ እየሄደና እየዘለለም
እግዚአብሔርንም እያመሰገነ ከእነርሱ ጋር
ወደ ቤተ መቅደሱ አደባባይ ገባ፡፡ [9]ሕ
ዝቡም ሁሉ እየተራመደና እግዚአብሔርን
እያመሰገነ ሲመላለስ ባዩት ጊዜ፣ [10]ይህ
ሰው ቀደም ሲል ‘ውብ’ በተባለው የቤተ
መቅደስ መግቢያ በር ላይ ተቀምጦ ም
ጽዋት ይለ ምን የነበረው እርሱ
መሆኑን ዐወቁ፤ በእ ርሱ ላይ ከተፈ
ጸመውም ነገር የተነሣ በመ ደነቅና
በመገረም ተሞሉ፡፡

## ጴጥሮስ ለማኙ ሲፈወስ ላየው ሕዝብ ንግግር አደረገ

[11]የተፈወሰውም ለማኝ ከጴጥሮስና ዮሐ
ንስ ጋር ጥብቅ ብሎ አብሮአቸው ሳለ፣ ሕዝቡ
ሁሉ በመገረም እነርሱ ወደ ነበሩበት ‘የሰ
ሎሞን መመላለሻ’ ወደ ተባለው ስፍራ
እየሮጡ መጡ፡፡ [12]ጴጥሮስም ይህን ባየ ጊዜ
እንዲህ አላቸው፤ “የእስራኤል ሕዝብ
ሆይ፤ በዚህ ለምን ትደነቃላችሁ? ደግ
ሞም በእኛ ኀይል ወይም በእኛ ጽድቅ
ይህ ሰው ድኖ እንዲመላለስ እንዳደረግ
ነው በመቍጠር፣ ለምን ወደ እኛ አትኵ

[ረ]31 ወይም መሲሕ፤ በግሪክ ክርስቶስ፣ በዕብራይስጥ መሲህ ማለት የተቀባው ማለት ነው፤ እንዲሁም በቍ 36

ራችሁ ትመለከታላችሁ? 13የአባቶቻችን
አምላክ፣ የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ
አምላክ ብላቴናውን ኢየሱስን አከበረው፤
እናንተ ግን እንዲሞት አሳልፋችሁ ሰጣ
ችሁት፤ ጲላጦስ ሊፈታው ቢፈልግም እና
ንተ በእርሱ ፊት ካዳችሁት፤ 14ቅዱሱንና
ጻድቁን ክዳችሁ ነፍሰ ገዳዩ እንዲፈታ
ላችሁ ለመናችሁ፤ 15የሕይወት መገኛ የሆ
ነውን ገደላችሁት፤ እግዚአብሔር ግን ከሙ
ታን አስነሣው፤ እኛም ለዚህ ምስክሮች
ነን። 16ይህ የምታዩትና የምታውቁት ሰው
የበረታው በኢየሱስ ስም በማመን ነው፤
ሁላችሁም እንደምታዩት ፍጹም ፈውስ
እንዲያገኝ ያደረገው የኢየሱስ ስምና በእ
ርሱ አማካይነት የሚገኘው እምነት ነው።
17"አሁንም ወንድሞች ሆይ፤ እናንተ
ይህን ያደረጋችሁት እንደ አለቆቻችሁ
ሁሉ ባለማወቅ እንደ ሆነ ዐውቃለሁ።
18እግዚአብሔር ግን የእርሱ የሆነው ክርስ
ቶስ[ሰ] መከራን እንዲቀበል አስቀድሞ በነቢ
ያቱ ሁሉ አፍ የተናገረውን ፈጽሞአል።
19እንግዲህ ኀጢአታችሁ እንዲደመሰስ
ንስሓ ግቡ፤ ከመንገዳችሁም ተመለሱ፤
ከጌ ታም ዘንድ የመታደስ ዘመን
ይመጣላች ኋል፤ 20ደግሞም አስቀድሞ
ለእናንተ የተ መደበውን ክርስቶስን
እርሱም ኢየሱስን ይልክላችኋል። 21እግዚ
አብሔር አስቀድሞ በቅ ዱሳን ነቢያቱ አፍ
እንደተናገረ፣ ሁሉን ነገር
እስከሚያድስበት ዘመን ድረስ እርሱ በሰ
ማይ ይሖይ ዘንድ ይገባል። 22ሙሴም
እንዲህ ብሎአል፤ 'ጌታ አምላካችሁ
ከእናን ተው መካከል እንደ እኔ ያለ ነቢ
ይ ያስ ነሣላችኋል፤ እርሱ የሚነግራችሁን
ሁሉ ስሙት፤ 23ይህን ነቢይ የማትሰማ ነፍስ
ሁሉ ከሕዝቡ መካከል ተለይታ ትጥፋ።'
24"በእርግጥም ከሳሙኤል ጀምሮ የተነ
ሱት ነቢያት ሁሉ ስለ እነዚህ ጊዜያት ተና
ግረዋል። 25እናንተም የነቢያት ልጆች ናችሁ፤
ደግሞም እግዚአብሔር ለአብርሃም፣ 'በዘ
ርህ የምድር ወገኖች ሁሉ ይባረካሉ' ብሎ
የገባው ኪዳን ወራሾች ናችሁ። 26እግዚአ
ብሔር ብላቴናውን ባስነሣ ጊዜ፣ እያንዳ
ንዳችሁን ከክፋታችሁ መልሶ ይባርካችሁ
ዘንድ አስቀድሞ ወደ እናንተ ላከው።"

## ጴጥሮስና ዮሐንስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት

4 ጴጥሮስና ዮሐንስ ለሕዝቡ እየተ
ናገሩ ሳሉ፣ ካህናትና የቤተ መቅደሱ
ጥበቃ ኀላፊ እንዲሁም ሰዱቃውያን ድን
ገት ወደ እነርሱ መጡ። 2 እነርሱም ሐዋ
ርያት ሕዝቡን በማስተማራቸውና በኢየ
ሱስ ስለተገኘው ትንሣኤ ሙታን በመስ

3፥13 ዘፀ3፥6፤ማቴ 27፥2፤ሉቃ23፥4፤ሐሥ 2፥23፤5፥30፤7፥32፤ 22፥14
3፥14 ማር1፥24፤ 15፥11፤ሉቃ23፥18-25፤ሐሥ4፥27፤7፥52
3፥15 ቈ24፥48፤ ሐሥ 2፥24
3፥16 ቈ6
3፥17 ሉቃ23፥34፤ ሐሥ13፥27፤22፥5
3፥18 ማቴ1፥22፤ ሉቃ24፥27፤ሐሥ2፥ 23፤17፥2፡3፤26፥22፡23
3፥19 መዝ51፥1፤ኢሳ 43፥25፤44፥22፤ሐሥ 2፥38
3፥20 ሉቃ2፥11
3፥21 ማቴ17፥11፤ ሉቃ1፥70፤ሐሥ1፥6፡ 11
3፥22 ዘዳ18፥15፡ 18፤ሐሥ7፥37
3፥23 ዘዳ18፥19
3፥24 ሉቃ24፥27
3፥25 ዘፍ12፥3፤22፥ 18፤26፥4፤28፥14፤ሐሥ 2፥39፤ሮሜ9፥4፡5
3፥26 ቈ22፤ ሐሥ 2፥24፤13፥46፤ ሮሜ1፥16
4፥1 ማቴ3፥7፤16፥1፡ 6፤22፥23፡34፤ ሉቃ22፥4፤ ሐሥ5፥17፤23፥6-8
4፥2 ሐሥ17፥18
4፥3 ሐሥ5፥18
4፥4 ሐሥ2፥41
4፥5 ሉቃ23፥13
4፥6 ማቴ26፥3
4፥8 ቈ5፤ሉቃ1፥ 15፤23፥13
4፥9 ሐሥ3፥6
4፥10 ማር1፥24፤ሐሥ 2፥24
4፥11 መዝ118፥22፤ ኢሳ28፥16፤ዘካ10፥4፤ ማቴ21፥42፤ኤፌ 2፥20፤1ጴጥ2፥7
4፥12 ማቴ1፥21፤ ዮሐ14፥6፤ሐሥ 10፥43፤ሮሜ11፥14፤ 1ጢሞ2፥5
4፥13 ማቴ11፥25፤ ማር3፥14፤ሉቃ22፥8
4፥15 ማቴ5፥22
4፥16 ዮሐ11፥47፤ ሐሥ3፥6-10
4፥18 አሞ7፥13፤ ሐሥ5፥40
4፥19 ሐሥ5፥29

በካቸው እጅግ ተሐጡ።3ጴጥሮስና ዮሐንስን
ያዟቸው፤ ጊዜውም ምሽት ስለ ነበረ እስኪ
ነጋ ድረስ ወህኒ ቤት አሳደሯቸው።
4ይሁን እንጂ ቃሉን ከሰሙት መካከል ብዙ
ዎቹ አመኑ፤ የወንዶቹም ቍጥር ወደ
አምስት ሺህ ከፍ አለ።
5በማግስቱም አለቆቻቸውና፣ ሽማግሌ
ዎቻቸው እንዲሁም ጸሓፍት በኢየሩሳሌም
ተሰበሰቡ። 6ሊቀ ካህናቱ ሐና፣ ቀያፋ፣
ዮሐንስ፣ እስክንድሮስና የሊቀ ካህናቱ ቤተ
ዘመዶች ሁሉ በዚያ ተገኝተው ነበር።
7እነርሱም ጴጥሮስንና ዮሐንስን በመካከል
አቁመው፣ "ይህን ያደረጋችሁት በምን ኀይል
ወይም በማን ስም ነው?" ብለው ጠየቋቸው።
8በዚህ ጊዜ፣ ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ
ተሞልቶ እንዲህ አላቸው፤ "እናንተ የሕዝብ
አለቆችና ሽማግሌዎች ሆይ፤ 9ዛሬ ለዚህ
ሽባ ሰው ስለ ተደረገው በጎ ሥራ፣ እንዴት
እንደ ዳነ የምትጠይቁን ከሆነ፣ 10እናንተ
በሰቀላችሁት፣ እግዚአብሔር ግን ከሙ
ታን ባስነሣው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስ
ቶስ ስም መዳኑንና ፊታችሁ መቆሙን
እናንተም ሆናችሁ የእስራኤል ሕዝብ
ሁሉ ይህን ይወቅ። 11እርሱም፣

" 'እናንተ ግንበኞች የናቃችሁት፣
የማእዘን ራስ[ሸ] የሆነው ድንጋይ' ነው።

12ድነት በሌላ በማንም አይገኝም፤ እንድን
በት ዘንድ ለሰዎች የተሰጠ ከዚህ ስም በስ
ተቀር ሌላ ስም ከሰማይ በታች የለምና።"
13ሰዎቹም፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ እንዲህ
በድፍረት ሲናገሩ ባዩአቸው ጊዜ፣ ያልተ
ማሩ ተራ ሰዎች መሆናቸውን ተረድተው
ተደነቁ፤ ከኢየሱስ ጋር እንደ ነበሩም ተገነ
ዘቡ። 14የተፈወሰውን ሰው እዚያው ከእነ
ርሱ ጋር ቆሞ ስላዩት የሚናገሩበትን ሰበብ
አጡ። 15ስለዚህ ከሸንጎው እንዲያወጧቸው
አዘዙ፤ ከዚያም በአንድነት ተሰብስበው
ተመካከሩ፤ 16እንዲህም ተባባሉ፤ "እንግዲ
ህ እነዚህን ሰዎች ምን እናድርጋቸው? በኢ
የሩሳሌም የሚኖር ሁሉ በእነርሱ እጅ የተ
ደረገውን ድንቅ ታምር ዐውቆአል፣ ስለዚህ
ይህንን ማስተባበል አንችልም፤ 17ይሁን
እንጂ፣ ይህ ነገር ከእንግዲህ በሕዝቡ መካ
ከል ይበልጥ እንዳይሰፋፋ፣ እነዚህም ሰዎች
ዳግመኛ በዚህ ስም ለማንም እንዳይናገሩ
እናስጠንቅቃቸው።"
18ከጠሯቸውም በኋላ፣ በኢየሱስ ስም ፈ
ጽሞ እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ
አዘዟቸው። 19ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን
መልሰው እንዲህ አሏቸው፤ "ከእግዚአብሔር
ይልቅ ለእናንተ መታ

[ሰ]18 ወይም *መሲሕ፤* እንዲሁም በቍ20
[ሸ]11 ወይም *የማእዘን ድንጋይ*

ዘዝ በእግዚአብሔር ፊት ይገባ እንደሆነ
እስቲ እናንተው ፍረዱ፤ 20እኛስ ያየነውንና
የሰማነውን ከመናገር ወደ ኋላ አንልም።”
21እንደ ገና ከዛቱባቸው በኋላም ለቀቋቸው፤
ምክንያቱም ሕዝቡ ሁሉ ስለ ሆነው ነገር እግዚ
አብሔርን ያመሰግኑ ስለ ነበር ሊቀጧቸው
አልቻሉም፤ 22በዚህ ታምር የተፈወሰውም
ሰው ዕድሜው ከአርባ ዓመት በላይ ነበርና።

## የአማኞች ጸሎት

23ጴጥሮስና ዮሐንስም ከተፈቱ በኋላ
ወደ ወገኖቻቸው ተመልሰው የካህናት አለ
ቆችና ሽማግሌዎች ያሏቸውን ሁሉ ነገሯ
ቸው። 24እነርሱም ይህን በሰሙ ጊዜ ድም
ፃቸውን በአንድነት ወደ እግዚአብሔር ከፍ
አድርገው እንዲህ አሉ፤ “ልዑል ጌታ ሆይ
አንተ ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንም፣ በውስ
ጣቸውም የሚኖሩትን ሁሉ ፈጥረሃል፤ 25በመ
ንፈስ ቅዱስም አማካይነት በአገልጋይህ
በአባታችን በዳዊት አፍ እንዲህ ብለህ ተና
ግረሃል፤

“ ‘አሕዛብ ለምን በቍጣ ተነሣሡ?
ሕዝቡስ ለምን በከንቱ አሤሩ?
26የምድር ነገሥታት ተሰለፉ፤
ገዦችም በአንድነት ተሰበሰቡ፤
በጌታ ላይ፣
በተቀባውም* ላይ ተከማቹ።’

27በእርግጥም ሄሮድስና ጳንጥዮስ ጲላጦስ
ከአሕዛብና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በዚህች
ከተማ አንተ በቀባኸው በቅዱሱ ብላቴናህ
በኢየሱስ ላይ ለማሤር ተሰበ ሰቡ፤ 28ይህም
የሆነው የአንተ ክንድና ፈቃድ ጥንት
የወሰኑት እንዲፈጸም ነው። 29አሁ ንም
ጌታ ሆይ፤ ዛቻቸውን ተመልከት፤ ባሪ
ያዎችህም ቃልህን በፍጹም ድፍረት መና
ገር እንዲችሉ አድርጋቸው። 30ለመፈወስ
እጅህን ዘርጋ፤ በቅዱሱ ብላቴናህም በኢየ
ሱስ ስም ድንቅና ታምራት አድርግ።”
31ከጸለዩም በኋላ የነበሩበት ስፍራ ተና
ወጠ፤ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤ የእግ
ዚአብሔርንም ቃል በድፍረት ተናገሩ።

## የአማኞች ማኅበራዊ አኗኗር

32ያመኑትም ሁሉ በአንድ ልብና በአንድ
ሐሳብ ተስማምተው ነበር፤ ያላቸውም
ሁሉ የጋራ ነበር እንጂ የራሱ የሆነውን
ሀብት እንኳ እንደ ግሉ የሚሐጥር ማንም
አልነበረም። 33ሐዋርያትም ስለ ጌታ ኢየ
ሱስ ትንሣኤ በታላቅ ኀይል መመስከራቸ
ውን ቀጠሉ፤ በሁላቸውም ላይ ታላቅ ጸጋ
ነበር። 34ከመካከላቸውም አንድ ችግረኛ
አልነበረም፤ ምክንያቱም መሬትም ሆነ
ቤት የነበራቸውን ሁሉ እየሸጡ ዋጋውን

4፥20 ኢዩ32፥18፤ ኤር20፥9፤አሞ3፥8፤ ሉቃ24፥48
4፥21 ሐሥ5፥26፤ ማቴ9፥8
4፥24 ነህ9፥6፤ ኢዮ 41፥11፤ ኢሳ 37፥16፤ሐሥ1፥1
4፥25 ሐሥ1፥16
4፥26 መዝ2፥1፡2፤ ዳን9፥25፤ሉቃ4፥18፤ ሐሥ10፥38፤ዕብ1፥9
4፥27 ቍ30፤ ማቴ 14፥1፤27፥2፤ ሉቃ23፥12፤ ሐሥ 3፥13፡14
4፥28 ሐሥ2፥23
4፥29 ቍ13፡31፤ መዝ138፥3፤ ሐሥ 9፥27፤ 13፥46፤ 14፥3፤28፥31፤ ኤፌ6፥19፤ ፊል1፥14
4፥30 ቍ27፤ ዮሐ 4፥48
4፥31 ቍ29፤ ሉቃ 1፥15፤ ሐሥ2፥2፤ዕብ4፥12
4፥32 ሐሥ2፥44
4፥33 ሉቃ24፥48፤ ሐሥ1፥22፤ሮሜ3፥24
4፥34 ማቴ19፥21፤ሐሥ2፥45
4፥35 ቍ37፤ ሐሥ 2፥45፤5፥2፤6፥1
4፥36 ሐሥ9፥27፤ 11፥22፡30፤13፥2፤ 1ቆሮ9፥6፤ገላ2፥1፡9፡13
4፥37 ቍ35፤ ሐሥ 5፥2
5፥2 ኢሱ7፥11፤ ሐሥ 4፥35፡37
5፥3 ቍ9፤ዘዳ 23፥21፤ማቴ4፥10፤ ዮሐ 13፥2፡27
5፥4 ዘሌ6፥2፤ ዘዳ 23፥22
5፥5 ቍ10፡11፤ መዝ5፥6
5፥6 ዮሐ19፥40
5፥8 ቍ2
5፥9 ቍ3
5፥10 ቍ5፡6
5፥11 ቍ5፤ ሐሥ 19፥17
5፥12 ዮሐ4፥48፤ 10፥23፤ሐሥ2፥43፤ 3፥11፤4፥32

አምጥተው፣ 35በሐዋርያት እግር ሥር በማ
ስቀመጥ ለእያንዳንዱ በሚያስፈልገው መጠን
ያካፍሉት ነበር።
36በቆጵሮስ የሚኖር ዮሴፍ የሚባል አንድ
ሌዋዊ ነበረ፤ ሐዋርያትም ‘በርናባስ’ ብለው
ጠሩት፤ ትርጕሙም ‘የመጽናናት ልጅ’
ማለት ነው፤ 37እርሱም መሬቱን ሸጦ፣ ገን
ዘቡን አምጥቶ በሐዋርያት እግር ሥር አስ
ቀመጠ።

## ሐናንያና ሰጲራ

5 ሐናንያ የተባለ ሰው፣ ከሚስቱ ከሰጲራ
ጋር መሬት ሸጠ፤ 2ሚስቱም በሚገባ
እያወቀች ከሽያጩ የተወሰነ ገንዘብ በማ
ስቀረት የተረፈውን አምጥቶ በሐዋርያት
እግር ሥር አስቀመጠ።
3ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለ፤ “ሐናንያ ሆይ፤
መንፈስ ቅዱስን ትዋሽና ከመሬቱ ሽያጭ
ታስቀር ዘንድ ሰይጣን ልብህን ለምን
ሞላው? 4ሳትሸጠው በፊት የአንተው አል
ነበረምን? ከሸጥኸውስ በኋላ ቢሆን ገንዘቡ
በእጅህ አልነበረምን? ለመሆኑ ይህን ነገር
እንዴት በልብህ አሰብህ? የዋሸኸው እኮ
እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አይደለም።”
5ሐናንያም ይህን እንደ ሰማ ወድቆ ሞተ፤
ይህን የሰሙትም ሁሉ ታላቅ ፍርሀት ያዛ
ቸው።
6ጕልማሶችም ተነሥተው አስከሬኑን ገነ
ዙት፤ ወስደውም ቀበሩት።
7ሦስት ሰዓት ያህልም ካለፈ በኋላ፣
ሚስቱ የሆነውን ሳታውቅ መጥታ ገባች።
8ጴጥሮስም፣ “እስቲ ንገሪኝ፤ መሬታችሁን
የሸጣችሁት በዚህ ዋጋ ነውን?” አላት።

እርሷም፣ “አዎን፤ በዚሁ ዋጋ ነው” አለች።

9ጴጥሮስም፣ “የጌታን መንፈስ
ትፈታተኑ ዘንድ እንዴት እንዲህ ተስማ
ማችሁ? እነሆ፤ ባልሽን የቀበሩት ሰዎች
ተመል ሰው እግራቸው ደጃፍ ላይ ነው፤
አንቺ ንም ይዘው ይወጣሉ” አላት።
10እርሷም ወዲያውኑ እግሩ ሥር
ወድቃ ሞተች፤ ጕልማሶቹም ሲገቡ ሞታ
አገኟት፤ አውጥተውም በባሏ አጠገብ
ቀበሯት። 11መላዪቱን ቤተ ክርስቲያንና
ይህን የሰ ሙትን ሁሉ፣ ታላቅ ፍርሀት
ያዛቸው።

## በሐዋርያት እጅ ብዙ ሰው ተፈወሰ

12ሐዋርያትም በሕዝቡ መካከል ብዙ ታም
ራዊ ምልክቶችንና ድንቅ ሥራዎችን አደረጉ፤
አማኞቹም ሁሉ ‘የሰሎሞን ደጅ’ በተባለው
መመላለሻ ይሰበሰቡ ነበር። 13ከእነርሱ ጋር

*26 ወይም ክርስቶስ ወይም መሲሕ ማለት ነው።

ሊቀላቀል የደፈረ ማንም አልነበረም፤ ሆኖም
ሕዝቡ እጅግ ያከብሯቸው ነበር፤ 14ብዙ ወን
ዶችና ሴቶችም ከጊዜ ወደ ጊዜ በጌታ
እያመኑ ወደ እነርሱ ይጨመሩ ነበር።
15ከዚህም የተነሣ፣ ጴጥሮስ በዚያ ሲያልፍ፣
ቢያንስ ጥላው እንኳ በጥቂቶች ላይ እንዲ
ያርፍባቸው በማለት ሕመምተኞችን ወደ
ውጭ እያወጡ በዐልጋና በቃሬዛ በመንገድ
ላይ ያስተኙ ነበር። 16በኢየሩሳሌም አካባቢ
ከሚገኙ ከተሞች፣ ሕመምተኞችንና በር
ኵሳን[ሀ] መናፍስት የሚሠቃዩትን ይዘው
የሚመጡት ሰዎች አካባቢውን ያጨናንቁት
ነበር፤ የመጡትም ሁሉ ይፈወሱ ነበር።

## ሐዋርያት መከራና ስደት ደረሰባቸው

17ከዚህም የተነሣ ሊቀ ካህናቱና አብረ
ውት የነበሩት የሰዱቃውያን ወገን ሁሉ
በቅናት ተሞሉ፤ 18ሐዋርያትንም ይዘው
ማረፊያ ቤት ከተቷቸው። 19ይሁን እንጂ
የጌታ መልአክ በሌሊት የእስር ቤቱን ደጆች
ከፍቶ አወጣቸውና፣ 20“ሂዱ፤ በቤተ መቅደ
ሱም አደባባይ ቁሙ፤ የዚህንም ሕይወት
ቃል ሁሉ ለሕዝብ ንገሩ” አላቸው።
21እንደ ነጋም፣ በተነገራቸው መሠረት፣
ወደ ቤተ መቅደሱ አደባባይ ገብተው ሕዝ
ቡን ማስተማር ጀመሩ።
ሊቀ ካህናቱና ከእርሱ ጋር የነበሩት
መጥተው የአይሁድን ሸንጎና የእስራኤልን
ሽማግሌዎች ጉባኤ በሙሉ በአንድነት
ሰበሰቡ፤ሐዋርያትንም እንዲያመጡ ሰዎችን
ወደ እስር ቤት ላኩ። 22የተላኩትም ወደ
እስር ቤቱ ሄደው በዚያ አላገኟቸውም፤
ተመልሰውም እንዲህ አሏቸው፤ 23“እስር
ቤቱ በሚገባ ተቈልፎ፣ ጠባቂዎቹም በበሩ
ላይ ቆመው አገኘን፤ ከፍተን ስንገባ ግን
በውስጡ ማንም አልነበረም።” 24የቤተ መቅ
ደሱ ጥበቃ ሹምና የካህናት አለቆችም ይህን
በሰሙ ጊዜ በነገሩ ተገረሙ፤ ግራም ተጋቡ።
25በዚህ ጊዜ አንድ ሰው መጥቶ፣
“እነሆ፤ እስር ቤት ያስገባችኋቸው ሰዎች
በቤተ መቅደሱ አደባባይ ቆመው ሕዝቡን
እያስተማሩ ናቸው” አላቸው። 26የጥበቃ
ሹሙም ከወታደሮቹ ጋር ሄዶ፤ ይዞ አመጣ
ቸው፤የመጧቸው ግን ሕዝቡ በድንጋይ እን
ዳይወግሯቸው ስለ ፈሩ በኀይል ሳያስገድዱ
ነበር።
27ሐዋርያትንም አምጥተው በሸንጎው
ፊት አቆሟቸው፤ሊቀ ካህናቱም እንዲህ ሲ
ል ጠየ ቃቸው፤ 28“በዚህ ስም
እንዳታስተምሩ በጥ ብቅ አስጠንቅቀናችሁ
ነበር፤ እናንተ ግን ኢየሩሳሌምን
በትምህርታችሁ ሞላችኋት፤ ደግሞም

5፥13 ሐሥ2፥47፤ 4፥21
5፥14 ሐሥ2፥41
5፥15 ሐሥ19፥12
5፥16 ማቴ8፥16፤ ማር16፥17
5፥17 ሐሥ4፥1፤ 15፥5
5፥18 ሐሥ4፥3
5፥19 ዘፍ16፥7፤ ዘፀ3፥2፤ መዝ34፥7፤ማቴ 1፥20፤2፥13፡19፤ 28፥2፤ሉቃ1፥11፤2፥9 ዮሐ20፥12፤ሐሥ8፥ 26፤ 10፥3፤12፥7፡23፤16፥2 6፤27፥23
5፥20 ዮሐ6፥63፡68
5፥21 ቍ27፡34፡ 41፤ማቴ5፥22፤ሐሥ 4፥5፡6
5፥22 ሐሥ12፥18፡ 19
5፥24 ሐሥ4፥1
5፥26 ሐሥ4፥21
5፥27 ማቴ5፥22
5፥28 ማቴ23፥35፤ 27፥25፤ሐሥ2፥23፡ 36፤3፥14፡15፤ 4፥18፤ 7፥52
5፥29 ዘፀ1፥17፤ ሐሥ 4፥19
5፥30 ሐሥ 2፥24፤ 3፥13
5፥31 ማቴ1፥21፤ ማር1፥4፤16፥19፤ ሉቃ2፥11፤24፥47፤ ሐሥ 2፥38፤3፥19፤ 10፥43
5፥32 ሉቃ24፥48፤ ዮሐ15፥26
5፥33 ሐሥ2፥37፤ 7፥54
5፥34 ሉቃ2፥46፤ 5፥17፤ሐሥ22፥3
5፥37 ሉቃ2፥1፡2
5፥38 ማቴ15፥13
5፥39 2ዜና13፥12፤ ምሳ21፥30፤ኢሳ46፥10፤ ሐሥ7፥51፤11፥17
5፥40 ማቴ10፥17
5፥41 ማቴ5፥12፤ ዮሐ15፥21
5፥42 ሐሥ2፥46፤ 9፥22፤13፥32
6፥1 ሐሥ2፥41፤ 4፥35፤9፥29፡39፡41፤1 ጢሞ5፥3

እኛን ለዚህ ሰው ደም ተጠያቂ ዎች
ልታደርጉን ቈርጣችሁ ተነሣችሁ!”
29ጴጥሮስና ሌሎች ሐዋርያትም መልሰው
እንዲህ አሉ፤ “ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር
ልንታዘዝ ይገባል! 30እናንተ በዕንጨት
ላይ ሰቅላችሁ የገደላችሁትን ኢየሱስን፣
የአባቶቻችን አምላክ ከሙታን አስነሣው፤
31እርሱም ለእስራኤል ንስሓንና የኀጢአ
ትን ስርየት ይሰጥ ዘንድ፣ እግዚአብሔር
የሁሉ ራስና አዳኝ አድርጎ በቀኙ ከፍ ከፍ
አደረገው። 32እኛም ለእነዚህ ነገሮች ምስ
ክር ነን፤ ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታ
ዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር
ነው።”
33ሰዎቹም ይህን በሰሙ ጊዜ ክፉኛ ተቈጡ፤
ሊገድሏቸውም ፈለጉ። 34ነገር ግን በሕዝቡ
ሁሉ ዘንድ የተከበረ አንድ የሕግ መም
ህር፣ እርሱም ገማልያል የሚሉት ፈሪሳዊ
ተነሥቶ በሸንጎው መካከል ቆመና ሐዋርያ
ትን ወደ ውጭ አውጥተው ለጥቂት ጊዜ
እንዲያቈዩአቸው አዘዘ፤ 35ለሸንጎውም እን
ዲህ አለ፤ “የእስራኤል ሰዎች ሆይ፤ በእነዚህ
ሰዎች ላይ ልታደርጉ ስላሰባችሁት ነገር
በጥንቃቄ ልታጤኑ ይገባችኋል።
36ከዚህ ቀደም፣ ቴዎዳስ ራሱን ትልቅ
አድርጎ በመቍጠር ተነሥቶ፣ አራት
መቶ ያህል ሰዎች ተባበሩት፤ ነገር ግን
እርሱም ተገደለ፤ ተከታዮቹም ሁሉ ተበ
ታተኑ፤ ነገሩም እንዳልነበር ሆነ። 37ከእ
ርሱም በኋላ፣ በሕዝብ ቈጠራው ወቅት
ገሊላዊው ይሁዳ ተነሥቶ ብዙ ሕዝብ አሸ
ፈተ፤ ተከታይም አግኝቶ ነበር፤ እር
ሱም ጠፋ፤ ተከታዮቹም ተበተኑ። 38ስለዚህ
አሁንም የምላችሁ:- እነዚህን ሰዎች ተዉ
አቸው፤ አትንኳቸው፤ ሐሳባቸው ወይም
አድራጎታቸው ከሰው ከሆነ ይጠፋልና፤
39ከእግዚአብሔር ከሆነ ግን ልትገቷቸው አት
ችሉም፤ እንዲያውም ከእግዚአብሔር ጋር ስት
ጣሉ ትገኙ ይሆናል።”
40እነርሱም ምክሩን ተቀብለው፤ ሐዋር
ያትን አስጠርተው አስገረፏቸው፤ ዳግመ
ኛም በኢየሱስ ስም እንዳይናገሩ አዘው
ለቀ ቋቸው።
41ሐዋርያትም፣ ስለ ስሙ ውርደትን
ለመቀበል በመብቃታቸው ደስ እያላቸው
ከሸንጎው ወጥተው ሄዱ፤ 42በየዕለቱም፣
በቤተ መቅደስም ሆነ በየቤቱ፣ ኢየሱስ
እርሱ ክርስቶስ[+] መሆኑን ከማስተማርና
ከመስበክ ከቶ ወደ ኋላ አላሉም ነበር።

## የሰባቱ ዲያቆናት መመረጥ

6 የደቀ መዛሙርት ቍጥር እየጨመረ
በሄደበት በዚህ ወቅት፣ ከግሪክ አገር

[ሀ]16 ወይም *በክፉ* [+]42 ወይም *መሲሕ*

የመጡ አይሁድ በይሁዳ ይኖሩ በነበሩት
አይሁድ ላይ አጕረመረሙ፤ ምክንያቱም
በየዕለቱ በሚከናወነው ምግብ የማደል አሠ
ራር ላይ ከእነርሱ ወገን የሆኑት መበለ
ቶች ችላ ተብለው ነበር፡፡ 2ስለዚህ ዐሥራ
ሁለቱ ሐዋርያት ሌሎችን ደቀ መዛሙርት
በአንድነት ሰብስበው እንዲህ አሉ፤ "እኛ
የማእዱን አገልግሎት ለማስተናገድ ስንል
የእግዚአብሔርን ቃል አገልግሎት መተው
አይገባንም፡፡ 3ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፤
ከእ ናንተ መካከል በመንፈስ ቅዱስና
በጥበብ የተሞሉ ለመሆናቸው
የተመሰከረላቸውን ሰባት ሰዎች ምረጡ፤
ይህን ኀላፊነት ለእነ ርሱ እንሰጣለን፤ 4እኛ
ግን በጸሎትና በቃሉ አገልግሎት
እንተጋለን፡፡"
5አባባሉ ሁላቸውን ደስ አሰኘ፤ በእምነትና
በመንፈስ ቅዱስ የተሞላውን እስጢፋኖስን፣
እንዲሁም ፊልጶስን፣ ጵሮኮሮስን፣ ኒቃሮ
ናን፣ ጢሞናን፣ ጳርሜናንና ወደ ይሁዲ
ነት ገብቶ የነበረውን አንጾኪያዊውን ኒቆ
ላዎስን መረጡ፡፡ 6እነዚህንም አምጥተው
ሐዋርያት ፊት አቀረቡአቸው፤ እነርሱም
ከጸለዩ በኋላ እጃቸውን ጫኑባቸው፡፡
7የእግዚአብሔርም ቃል እየሰፋ ሄደ፤
የደቀ መዛሙርቱም ቍጥር በኢየሩሳሌም
እጅግ እየበዛ ሄደ፤ ከካህናትም ብዙዎቹ ለእ
ምነት የታዘዙ ሆኑ፡፡

## የእስጢፋኖስ መያዝ

8በዚህ ጊዜ እስጢፋኖስ ጸጋንና ኀይልን
ተሞልቶ በሕዝቡ መካከል ድንቅ ነገሮች
ንና ታምራዊ ምልክቶችን ያደርግ ነበር፡፡
9"የነጻ ወጪዎች ምኵራብ" ተብሎ የሚጠ
ራው ምኵራብ አባላት የሆኑ ከቀሬናና
ከእስክንድርያ፣ እንዲሁም ከኪልቅያና ከእ
ስያ አውራጃዎች የመጡ ሰዎችም ተቃውሞ
አስነሥተው እስጢፋኖስን ይከራከሩት ጀመር፤
10ይሁን እንጂ ይናገርበት የነበረውን ጥበ
ብና መንፈስ መቋቋም አልቻሉም፡፡
11ስለዚህ፣ "እስጢፋኖስ በሙሴና በእግ
ዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል ሲሰነዝር
ሰምተናል" የሚሉ ሰዎችን በስውር አዘጋጁ፡፡
12በዚህ ሁኔታ ሕዝቡን፣ የአገር ሽ
ማግሌ ዎቹንና የሕግ መምህራኑን በ
ማነሣሣት፣ እስጢፋኖስን አስይዘው
በአይሁድ ሸንጎ ፊት አቀረቡት፤ 13እንዲህ
ብለው የሚመሰ ክሩ የሐሰት
ምስክሮችንም አቆሙበት፤ "ይህ ሰው በዚህ
በተቀደሰው ስፍራና በሕጉ ላይ የስድብ
ቃል መናገሩን በፍጹም አልተ ወም፤
14ምክንያቱም ይህ የናዝሬቱ ኢየ ሱስ
ይህን ስፍራ እንደሚያጠፋና ከሙሴ
የተቀበልነውን ወግ እንደሚለውጥ ሲናገር

6፥2 ሐሥ11፥26፤ ዕብ4፥12
6፥3 ዘፀ18፥21፤ ነህ 13፥13፤ ሉቃ1፥15፤ ሐሥ1፥16
6፥4 ሐሥ1፥14
6፥5 ቊ8፤ ሉቃ 1፥15፤ ሐሥ7፥55-60፤ 8፥5-40፤ 11፥19፤ 21፥8፤22፥20
6፥6 ዘኍ8፥10፤ 27፥18፤ማር5፥23፤ ሐሥ 1፥24፤ 9፥17፤19፥6፤ 28፥8፤1ጢሞ4፥14
6፥7 ሐሥ2፥41፤ 12፥24፤19፥20
6፥8 ዮሐ4፥48
6፥9 ማቴ27፥32፤ ሐሥ 2፥9፤ 15፥23፥41፤ 22፥3፤23፥34
6፥10 ሉቃ21፥15
6፥11 1ነገ21፥10፤ ማቴ26፥59-61
6፥12 ማቴ5፥22
6፥13 ዘፀ23፥1፤መዝ 27፥12፤ ማቴ24፥15፤ ሐሥ 7፥48፤21፥28
6፥14 ዮሐ2፥19፤ ሐሥ 15፥1፤21፥21፤ 26፥3፤28፥17
6፥15 ማቴ5፥22
7፥2 ዘፍ11፥31፤ 15፥7፤መዝ29፥3፤ ሐሥ22፥1
7፥3 ዘፍ12፥1
7፥4 ዘፍ12፥5
7፥5 ዘፍ12፥7፤ 17፥8፤ 26፥3፤ዕብ 11፥13
7፥6 ዘፀ1፥8-11፤ 12፥40
7፥7 ዘፍ15፥13፡ 14፤ዘፀ3፥12
7፥8 ዘፍ17፥9-14፤ 21፥2-4፤25፥26፤ 29፥ 31-35፤30፥5-13፡17- 24፤35፥16-18፡ 22-26
7፥9 ዘፍ37፥4፡11፡ 28፤39፥2፡21፡23፤መዝ 105፥17፤ሐጌ 2፥4
7፥10 ዘፍ41፥37-43፤ መዝ105፥20-22
7፥11 ዘፍ41፥54
7፥12 ዘፍ42፥1፡2
7፥13 ዘፍ45፥1-4፡16
7፥14 ዘፍ45፥9፡ 10፤46፥26፡27፤ ዘፀ1፥5፤ዘዳ10፥22
7፥15 ዘፍ46፥5-7፤

ሰምተነዋል፡፡"
15በሸንጎው ተቀምጠው የነበሩትም ሁሉ
እስጢፋኖስን ትኵር ብለው ሲመለከቱት
ፊቱ የመልአክ ፊት መስሎ ታያቸው፡፡

## እስጢፋኖስ በሸንጎው ፊት ያደረገው ንግግር

7 ሊቀ ካህናቱም፣ "ይህ የቀረበብህ ክስ
እውነት ነውን?" አለው፡፡
2እስጢፋኖስም እንዲህ ሲል መለሰ፤
"ወንድ ሞችና አባቶች ሆይ፤ አድምጡ!
አባታችን አብርሃም ወደ ካራን
ከመምጣቱ በፊት፣ ገና በመስጴጦምያ ሳለ፣
የክብር አምላክ ተገ ለጠለት፤ 3ከአገርህና
ከወገንህ ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ
ምድር ሂድ አለው፡፡
4"እርሱም ከከለዳውያን ምድር ወጥቶ
በካራን ተቀመጠ፡፡ ከአባቱም ሞት በኋላ፣
አሁን እናንተ ወደምትኖሩበት ወደዚህ
አገር አመጣው፡፡ 5በዚህም ስፍራ አንዲት
ጫማ ታህል እንኳ ርስት አልሰጠውም፤
ነገር ግን በዚያን ጊዜ ምንም ልጅ ሳይኖ
ረው፣ እርሱና ከእርሱም በኋላ ዘሩ ምድሪቱን
እንደሚወርሱ እግዚአብሔር ቃል ገባለት፡፡
6ደግሞም እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ተናገረ
ው፤ ዘርህ በባዕድ አገር መጻተኛ ይሆ
ናል፤ አራት መቶ ዓመትም በባርነት
ቀንበር ሥር ይማቀቃል፡፡ 7ሆኖም በባር
ነት የሚገዛቸውን ሕዝብ እኔ ደግሞ እቀ
ጣዋለሁ፡፡ ከዚያም አገር ወጥተው በዚህች
ስፍራ ያመልኩኛል፡፡' 8ከዚያም የግዝረትን
ኪዳን ሰጠው፤ አብርሃምም ይስሐቅን ወለደ፤
በስምንተኛውም ቀን ገረዘው፡፡ ይስሐቅም
ያዕቆብን ወለደ፤ ያዕቆብም ዐሥራ ሁለቱን
የነገድ አባቶች ወለደ፡፡
9"የነገድ አባቶችም በዮሴፍ ቀንተው
በባርነት ወደ ግብፅ ሸጡት፤ እግዚአብሔር ግን
ከእርሱ ጋር ስለ ነበር፣ 10ከመከራው ሁሉ
አወጣው፤ በግብፅም ንጉሥ በፈርዖን ፊት
ሞገስና ጥበብን አጐናጸፈው፤ ፈርዖንም በግ
ብፅና በቤተ መንግሥቱ ሁሉ ላይ ኀላፊ
አድርጎ ሾመው፡፡
11"በዚያ ጊዜም በግብፅና በከነዓን አገር
ሁሉ፣ ታላቅ መከራን ያስከተለ ራብ
መጣ፤ አባቶቻችንም የሚበሉትን አጡ፡፡
12ያዕቆብም እህል በግብፅ መኖሩን በሰማ
ጊዜ፣ አባቶቻችንን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ
ግብፅ ላካቸው፤ 13ለሁለተኛ ጊዜ ሲሄዱ
ደግሞ ዮሴፍ ማንነቱን ለወንድሞቹ ገለጠ፤
ፈርዖንም ስለ ዮሴፍ ዘመዶች ተረዳ፡፡ 14ከዚህ
በኋላ፣ ዮሴፍ ልኮ አባቱን ያዕቆብንና ሰባ
አምስት ነፍስ የሚሆኑ ቤተ ዘመዶቹን
በሙሉ አስመጣ፡፡ 15ያዕቆብ ወደ ግብፅ
ወረደ፤ እርሱም አባቶቻችንም በዚያ ሞቱ፡፡

16አስከሬናቸውም ወደ ሴኬም ተወስዶ፣
አብርሃም ከዔሞር ልጆች ላይ በጥሬ ብር
በገዛው መቃብር ተቀበረ።
17“እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው
ቃል የሚፈጸምበት ጊዜ ሲቃረብም፣ በግ
ብፅ የነበረው የሕዝባችን ቍጥር እየበዛ
ሄደ። 18ከዚያ በኋላ ዮሴፍን የማያውቅ ሌላ
ንጉሥ በግብፅ ነገሠ። 19እርሱም ሕዝባችንን
በተንኰሉ አስጨነቀ፤ ገና የተወለዱ ሕፃናታ
ቸውም ይሞቱ ዘንድ ወደ ውጭ አውጥተው
እንዲጥሏቸው አስገደዳቸው።
20“በዚህ ጊዜ ሙሴ ተወለደ፤ እርሱም
በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን ያገኘ ውብ ሕፃን*
ነበር። በአባቱም ቤት ሦስት ወር በእንክ
ብካቤ አደገ። 21ወደ ውጭ በተጣለም ጊዜ
የፈርዖን ልጅ አግኝታ ወሰደችው፤ እንደ ራሷ
ልጅ አድርጋም አሳደገችው። 22ሙሴም
የግብፃውያንን ጥበብ ሁሉ ተማረ፤ በንግግሩና
በተግባሩም ብርቱ ሆነ።
23“ሙሴ አርባ ዓመት በሆነው ጊዜ፣
ወንድሞቹን የእስራኤልን ልጆች ሊጐበኝ
በልቡ አሰበ። 24እርሱም፣ አንድ ግብፃዊ
ከወገኖቹ አንዱን በደል ሲያደርስበት
አይቶ ግብፃዊውንም ገደለ፤ ለተገፋው ወገ
ኑም ተበቀለ። 25ወገኖቹም እግዚአብሔር በእ
ርሱ እጅ ነጻ እንደሚያወጣቸው የሚያስተ
ውሉ መስሎት ነበር፤ እነርሱ ግን አላስተዋ
ሉም። 26በማግስቱም ደግሞ ሁለት እስራ
ኤላውያን ሲጣሉ ደረሰ፤ ሊያስታርቃቸ
ውም ፈልጎ፣ ‘ሰዎች፤ እናንተ እኮ ወንድማ
ማቾች ናችሁ፤ እንዴት እርስ በርሳችሁ
ትጐዳዳላችሁ?’ አላቸው።
27“በባልንጀራው ላይ በደል ሲያደርስ
የነበረው ሰው ግን፣ ሙሴን ገፈተረውና
እንዲህ አለ፤ ‘አንተን ገዥና ፈራጅ አድ
ርጎ በእኛ ላይ የሾመህ ማን ነው? 28ወይስ
ትናንት ግብፃዊውን እንደ ገደልኸው እኔ
ንም ልትገድለኝ ትፈልጋለህን?’ 29ሙሴም
ይህን እንደ ሰማ ሸሽቶ በምድያም አገር
መጻተኛ ሆኖ ተቀመጠ፤ በዚያም ሁለት
ወንዶች ልጆች ወለደ።
30“ከአርባ ዓመት በኋላ፣ በሲና ተራራ
አካባቢ ባለው ምድረ በዳ፣ በሚነድ ቍጥ
ቋጦ ነበልባል ውስጥ መልአክ ተገለጠ
ለት። 31ሙሴም ባየው ነገር ተደነቀ፤ ነገሩን
ለማጣራት ወደዚያ ሲቀርብ የጌታ ድምፅ፤
32‘እኔ የአባቶችህ አምላክ፣ የአብርሃም፣
የይ ስሐቅ፣ የያዕቆብ አምላክ ነኝ’ ሲል ሰ
ማ። ሙሴም በፍርሀት ተዋጠ፤
ለመመልከትም አልደፈረም።
33“ጌታ ም እንዲህ አለው፤ ‘የእግርህን
ጫማ አውልቅ፤ የቆምህባት ስፍራ የተቀደ
ሰች ምድር ናትና። 34በግብፅ ያለውን የሕ
ዝቤን መከራ በእርግጥ አይቻለሁ፤ የጭ
ንቅ ጩኸታቸውን ሰምቻለሁ፤ ላድናቸውም
ወርጃለሁ። አሁንም ና፤ ወደ ግብፅ መልሼ
እልክሃለሁ።’
35“እንግዲህ እነዚያ፣ ‘ገዥና ፈራጅ
አድርጎ የሾመህ ማን ነው?’ ብለው የናቁ
ትን ይህንን ሙሴ እግዚአብሔር
በቍጥቋጦው ውስጥ በታየው መልአክ አ
ማካይነት ገዥና ታዳጊ አድርጎ ወደ
እነርሱ ላከው። 36እርሱም መርቶ ከግብፅ
አወጣቸው፤ በግ ብፅ፣ በቀይ ባሕርና
በምድረ በዳ አርባ ዓመት ድንቅ ነገሮችንና
ታምራዊ ምልክቶችን አደረገ።
37“የእስራኤልንም ሕዝብ፣ ‘እግዚአብሔር
እንደ እኔ ያለ ነቢይ ከመካከላችሁ ያስነ
ሣላችኋል’ ያላቸው ይህንኑ ሙሴ ነበር።
38እርሱም በሲና ተራራ ከተናገረው
መልአ ክና ከአባቶቻችን ጋር በሕዝቡ
ጉባኤ መካ ከል ነበር፤ የሕይወትንም ቃል
ወደ እኛ ለማስተላለፍ ተቀበለ።
39“አባቶቻችን ግን ተቃወሙት እንጂ
ሊታዘዙት ስላልፈለጉ በልባቸው ወደ
ግብፅ ተመለሱ። 40አሮንንም፣ ‘ፊት ፊታ
ችን የሚሄዱ አማልክት አብጅልን፤ ከግ
ብፅ ምድር መርቶ ያወጣን ያ ሙሴ ምን
እንደ ደረሰበት አናውቅምና’ አሉት።
41በዚያን ጊዜ የጥጃ ምስል ሠርተው፣ ለጣ
ዖቱ መሥዋዕት አቀረቡ፤ በእጃቸውም ሥራ
ተደሰቱ፤ ፈነጠዙም። 42እግዚአብሔር ግን
ከእነርሱ ዘወር አለ፤ ያመልኳቸውም ዘንድ
ለሰማይ ከዋክብት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ይህም
በነቢያት መጽሐፍ እንዲህ ተብሎ በተጻ
ፈው መሠረት ተፈጸመ፤

“ ‘እናንት የእስራኤል ቤት ሆይ፤ አርባ
ዓመት
በምድረ በዳ በነበራችሁ ጊዜ፣
መሥዋዕትንና መባን ለእኔ
አቀረባችሁልኝን?
43ይልቁንም ልታመልኳቸው የሠራችኋቸውን፣
የሞሎክን ድንኳንና የጣዖታችሁን፣
የሬምፋምን ኮከብ ከፍ ከፍ አድርጋችሁ
ያዛችሁ።
ስለዚህ እኔም እንድትጋዙ አደርጋለሁ፤
ከባቢሎንም ወዲያ እሰዳችኋለሁ።
44“እግዚአብሔር ለሙሴ ባሳየው ንድ
ፍና ባዘዘው መሠረት የተሠራችው የም
ስክር ድንኳን፣ ከአባቶቻችን ጋር በምድረ
በዳ ነበረች። 45አባቶቻችንም ድንኳንዋን
ከተቀበሉ በኋላ፣ እግዚአብሔር በኢያሱ
መሪነት ያሳደዳቸውን የአሕዛብን አገር

49፥33፤ዘፀ1፥6
7፥16 ዘፍ23፥16-20፤
33፥18፡19፤50፥13፤
ኢሱ 24፥32
7፥17 ዘፀ1፥7፤
መዝ 105፥24
7፥18 ዘፀ1፥8
7፥19 ዘፀ1፥10-22
7፥20 ዘፀ2፥2፤
ዕብ 11፥23
7፥21 ዘፀ2፥3-10
7፥22 1ነገ4፥30፤
ኢሳ 19፥11
7፥27 ዘፍ19፥9፤
ዘኍ 16፥13
7፥29 ዘፀ2፥11-15
7፥31 ዘፀ3፥1-4
7፥32 ዘፀ3፥6፤ሐሥ
3፥13
7፥33 ዘፀ3፥5፤ኢሱ
5፥15
7፥34 ዘፀ3፥7-10
7፥35 ቍ27
7፥36 ዘፀ11፥10፤12፥
41፤14፥21፤15፥25፤17፥5
፡6፤33፥1፤ዮሐ4፥48
7፥37 ዘዳ18፥15፡
18፤ሐሥ3፥22
7፥38 ቍ53፤ዘፀ
19፥17፤ዘሌ27፥34፤
ዘዳ32፥45-47፤
ሮሜ3፥2፤ዕብ4፥12
7፥39 ዘኍ14፥3፡4
7፥40 ዘፀ32፥1፡23
7፥41 ዘፀ32፥4-6፤
መዝ106፥19፡20፤
ራእ 9፥20
7፥42 ኢሱ24፥20፤
ኢሳ63፥10፤
ኤር 19፥13
7፥43 አሞ5፥25-27
7፥44 ዘፀ25፥8፡9፡
40፤38፥21፤
ዘኍ1፥50፤17፥7
7፥45 ኢሱ3፥14-17፤
18፥1፤23፥9፤24፥18፤2
ሳሙ7፥2፡6፤መዝ44፥2

*20 ወይም *ተራ ልጅ አልነበረም*

በወረሱ ጊዜ ይዘዋት ገቡ፤ እስከ ዳዊትም
ዘመን ድረስ በምድሪቱ ተቀመጠች፤
46 ዳዊትም በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ በማ
ግኘቱ ለያዕቆብ[ሀ] አምላክ ማደሪያ ያዘጋጅ
ዘንድ ለመነ፤ 47 ነገር ግን የማደሪያውን
ቤት የሠራለት ሰሎሞን ነበር።

48 "ይሁን እንጂ፣ ልዑል የሰው እጅ በሠ
ራው ቤት ውስጥ አይኖርም፤ ይህም ነቢዩ
እንዲህ ባለው መሠረት ነው፤

49 "ሰማይ ዙፋኔ ነው፤
ምድርም የእግሬ ማሳረፊያ ናት፤
ታዲያ ምን ዐይነት ቤት ትሠሩልኛላችሁ?
ይላል ጌታ፤
ወይንስ ማረፊያ የሚሆነኝ የትኛው ቦታ
ነው?
50 ይህን ሁሉ የሠራው እጄ አይደለምን?'

51 "እናንት ልባችሁና ጆሮአችሁ ያለተገ
ረዘ፣ አንገተ ደንዳኖች! ልክ እንደ አባቶ
ቻችሁ መንፈስ ቅዱስን ሁል ጊዜ ትቃወ
ማላችሁ። 52 ከነቢያት መካከል አባቶቻችሁ
ያላሳደዱት ማን አለ? የጻድቁን መምጣት
አስቀድመው የተናገሩትን እንኳ ገድለ
ዋል፤ እናንተም አሁን አሳልፋችሁ ሰጣች
ሁት፤ ገደላችሁትም፤ 53 በመላእክት አማካ
ይነት የተሰጣችሁንም ሕግ ተቀበላችሁ እንጂ
አልጠበቃችሁትም።"

## የእስጢፋኖስ መወገር

54 በሸንጎው ስብሰባ ላይ የነበሩትም ይህን
በሰሙ ጊዜ እጅግ ተሑጡ፤ ጥርሳቸውንም
አፋጩበት። 55 እስጢፋኖስ ግን በመንፈስ
ቅዱስ ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኵር ብሎ
ሲመለከት፣ የእግዚአብሔርን ክብር፣ እንዲ
ሁም ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየና፣
56 "እነሆ፤ ሰማያት ተከፍተው፣ የሰው ልጅም
በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ" አለ።
57 በዚህ ጊዜ በታላቅ ድምፅ እየጮኹ
ጆሮአቸውን ደፍነው እርሱ ወደ አለበት
በአንድነት ሮጡ፤ 58 ይዘውም ከከተማው
ውጭ ጣሉት፤ በድንጋይም ይወግሩት ጀመር።
ይህ በሚሆንበት ጊዜ በዚያ የነበሩ ምስክ
ሮችም ልብሳቸውን ሳውል በተባለ ጕል
ማሳ እግር አጠገብ አስቀመጡ።
59 እስጢፋኖስም እየወገሩት ሳለ፣ "ጌታ
ኢየሱስ ሆይ፤ ነፍሴን ተቀበላት" ብሎ ጸለየ፤
60 ከዚያም ተንበርክኮ፤ በታላቅ ድምፅ፣ "ጌታ
ሆይ! ይህን ኀጢአት አትቍጠርባቸው"
ብሎ ጮኸ፤ ይህን ካለ በኋላም አንቀላፋ።

8 ሳውልም በእስጢፋኖስ መገደል ተስ
ማምቶ ነበር።

## የአማኞች መሰደድና መበተን

በዚያ ቀን በኢየሩሳሌም በነበረችው
ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ተነሣ፤
ከሐዋርያትም በስተቀር አማኞች በሙሉ
በይሁዳና በሰማርያ አውራጃዎች ሁሉ
ተበተኑ፤ 2 በመንፈሳዊ ነገር የተጉ ሰዎችም
እስጢፋኖስን ቀበሩት፤ ደግሞም እጅግ
አለቀሱለት። 3 ሳውል ግን ቤተ ክርስቲያ
ንን ለማጥፋት ታጥቆ ተነሣ፤ ከቤት ወደ
ቤት በመግባትም ወንዶችንና ሴቶችን
ጐትቶ እያወጣ ወህኒ ቤት ያስገባቸው
ነበር።

## ፊልጶስ በሰማርያ

4 የተበተኑትም በሄዱበት ሁሉ ቃሉን
ሰበኩ፤ 5 ፊልጶስም ወደ አንዲት የሰማርያ
ከተማ ወርዶ ክርስቶስን[ለ] ሰበከላቸው።
6 ብዙ ሕዝብም ፊልጶስ የተናገረውን ሲሰ
ሙና ያደረገ ውንም ታምራዊ ምልክቶች
ሲያዩ፣ አንድ ልብ ሆነው ያዳምጡት
ነበር። 7 ርኵሳን[ሐ] መናፍስትም እየጮኹ
ከብዙ ሰዎች ወጡ፤ ብዙ ሽባዎችና አንካሶ
ችም ተፈወሱ፤ 8 ከዚህ የተነሣም በከተማ
ዪቱ ታላቅ ደስታ ሆነ።

## ጠንቋዩ ሲሞን

9 ነገር ግን ከዚህ ቀደም ሲል በከተማ
ዪቱ ውስጥ እየጠነቈለ የሰማርያን ሰዎች
ሁሉ ያስገረመ፣ ሲሞን የሚሉት አንድ
ሰው ነበር፤ እርሱም ራሱን እንደ ታላቅ
ሰው ይሖጥር ነበር። 10 ከታናሽ እስከ
ታላቅ ያለው ሰው ሁሉ፣ "ይህ ሰው 'ታላቁ
ኀይል' በመባል የሚታወቀው መለኮታዊ
ኀይል ነው" በማለት ከልብ ያዳምጡት
ነበር፤ 11 ከብዙ ጊዜ ጀምሮ በጥንቆላ ሥራው
ስላስገረማቸውም ትኵረት ሰጥተው ይከ
ተሉት ነበር። 12 ነገር ግን ፊልጶስ ስለ እግ
ዚአብሔር መንግሥትና ስለ ኢየሱስ ክርስ
ቶስ ስም የሰበከላቸውን አምነው በመቀበ
ላቸው ወንዶችም ሴቶችም ተጠመቁ፤
13 ራሱ ሲሞን እንኳ ሳይቀር አምኖ ተጠ
መቀ፤ ፊልጶስንም ተከትሎ ሄደ፤ የሚደ
ረገውን ምልክትና ታላቅ ታምራት አይ
ቶም ተገረመ።
14 በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት የሰ
ማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል መቀ
በላቸውን በሰሙ ጊዜ፣ ጴጥሮስንና ዮሐ
ንስን ወደ እነርሱ ላኳቸው። 15 እነርሱም
ሰማርያ በደረሱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን
እንዲቀበሉ ለሰማርያ ሰዎች ጸለዩላቸው፤
16 ምክንያቱም በዚያን ጊዜ በጌታ ኢየሱስ

7፥46 2ሳሙ7፥8-16፤ 1ነገ8፥17፤ መዝ132፥1-5
7፥47 1ነገ6፥1-38
7፥48 1ነገ8፥27፤ 2ዜና2፥6፤ማር5፥7
7፥49 ማቴ5፥34፡35
7፥50 ኢሳ66፥1፡2
7፥51 ዘፀ32፥9፤ 33፥3፡5፤ዘሌ26፥41፤ ዘዳ10፥16፤ኤር4፥4፤ 9፥26
7፥52 ማቴ5፥12፤ ሐሥ3፥14፤1ተሰ2፥15
7፥53 ቍ38፤ገላ 3፥19፤ዕብ2፥2
7፥54 ሐሥ5፥33
7፥55 ማር16፥19፤ ሉቃ1፥15
7፥56 ማቴ3፥16፤ 8፥20
7፥58 ዘሌ24፥14፡ 16፤ዘዳ17፥7፤ሉቃ4፥2 9፤ሐሥ8፥1፤22፥20
7፥59 መዝ31፥5፤ ሉቃ23፥46
7፥60 ማቴ5፥44፤ 9፥24፤ሉቃ22፥41፤ ሐ ሥ9፥40
8፥1 ቍ4፤ሐሥ7፥58፤ 9፥31፤11፥19
8፥3 ሐሥ7፥58፤ 9፥1፡13፡21፤22፥4፡19፤ 26፥10፡11፤1ቆሮ15፥9፤ ገላ1፥13፡23፤ፊል3፥6፤ 1ጢሞ1፥13
8፥4 ቍ1፤ሐሥ 15፥35
8፥5 ሐሥ6፥5፤21፥8
8፥7 ማቴ4፥24፤ማር 16፥17
8፥9 ሐሥ5፥36፤ 13፥6
8፥10 ሐሥ14፥11፤ 28፥6
8፥12 ማቴ3፥2፤ ሐሥ 2፥38
8፥13 ቍ6፤ሐሥ 19፥11
8፥14 ቍ1፤ ሉቃ 22፥8፤ዕብ4፥12
8፥15 ዮሐ20፥22
8፥16 ማቴ28፥19፤ ሐሥ2፥38፤10፥44፤ 19፥2

[ሀ]46 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *የያዕቆብ ቤት* ይላሉ።
[ለ]5 ወይም *መሲሕ*
[ሐ]7 ወይም *ክፉ*

ስም ተጠምቀው ነበር እንጂ ገና መንፈስ
ቅዱስ በአንዳቸውም ላይ አልወረደም
ነበር። 17ስለዚህ ጴጥሮስና ዮሐንስ እጃ
ቸውን ጫኑባቸው፤ እነርሱም መንፈስ
ቅዱስን ተቀበሉ።
18ሲሞንም ሐዋርያት እጃቸውን በሚጭ
ኑበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ
አይቶ፣ ገንዘብ አመጣላቸውና እንዲህ አላ
ቸው፤ 19“እጄን የምጭንበት ሰው ሁሉ
መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበል ይህን ሥል
ጣን ለእኔም ስጡኝ።”
20ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለው፤ “የእግዚአ
ብሔርን ስጦታ በገንዘብ ለመግዛት አስበሃ
ልና፣ አንተም ገንዘብህም አብራችሁ ጥፉ!
21ልብህ በእግዚአብሔር ፊት ቅን ስላል
ሆነ፣ አንተ በዚህ አገልግሎት ድርሻ
ወይም ዕድል ፈንታ የለህም። 22አሁንም
ስለዚህ ክፋትህ ንስሓ ግባ፤ ወደ ጌታም
ጸልይ፤ ምናልባት ይህን የልብህን ሐሳብ
ይቅር ይልህ ይሆናል፤ 23ምክንያቱም በመ
ራራነት ተሞልተህ፣ በዐመፅ ሰንሰለት
ተይዘህ አይሃለሁና።”
24ሲሞንም መልሶ፣ “ከተናገራችሁት ምንም
ነገር እንዳይደርስብኝ ጌታ ን ለምኑልኝ”
አላ ቸው። 25ጴጥሮስና ዮሐንስም የጌታን
ቃል ከመሰከሩና ገልጠው ከተናገሩ በኋላ፣
በብዙ የሰማርያ መንደሮች ወንጌልን
እየሰበኩ፣ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ።

### ፊልጶስና ኢትዮጲያዊው ጃንደረባ

26የጌታም መልአክ ፊልጶስን፣ “ተነሥ
ተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ
በሚያወርደው በምድረ በዳው መንገድ
ሂድ” አለው፤ 27እርሱም ተነሥቶ ሄደ።
እነሆ የኢትዮጲያ ንግሥት የህንደኬ ባለሚ
ልና የሀብት ንብረቷ ሁሉ አዛዥ የሆነ
አንድ ኢትዮጲያዊ ጃንደረባ አገኘ። ይህም
ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ
ነበር። 28ሲመለስም በሠረገላ ተቀምጦ የነ
ቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር።
29መንፈስም ፊልጶስን፣ “ሂድ፤ ወደዚህ
ሠረገላ ቅረብ” አለው።
30ፊልጶስም ፈጥኖ ወደ ሠረገላው
ሄደ፤ ጃንደረባውም የነቢዩን የኢሳይያስን
መጽ
ሐፍ ሲያነብ ሰምቶ፣ “ለመሆኑ፣ የምታ
ነበውን ታስተውለዋለህን?” አለው።
31ጃንደረባውም፣ “የሚያስረዳኝ ሰው ሳይ
ኖር እንዴት አድርጌ አስተውላለሁ” አለው፤
እርሱም ወደ ሠረገላው ወጥቶ አብሮት
እንዲቀመጥ ፊልጶስን ለመነው።
32ጃንደረባው ያነብ የነበረው የመጽሐፍ
ክፍል ይህ ነበር፤

8፥17 ዮሐ20፥22፤ ሐሥ6፥6
8፥20 2ነገ5፥16፤ ዳን5፥17፤ማቴ10፥8፤ ሐሥ2፥38
8፥21 ነህ2፥20፤ መዝ78፥37
8፥22 ሐሥ2፥38
8፥24 ዘፀ8፥8፤ዘኍ 21፥7፤1ነገ13፥6፤ኤር4 2፥2
8፥25 ቀኍ40፤ሐሥ 13፥48
8፥26 ሐሥ5፥19፤ 6፥5
8፥27 1ነገ8፥41-43፤ መዝ68፥31፤87፥4፤ኢሳ 56፥3-5፤ሶፎ3፥10፤ ዮሐ 12፥20
8፥29 ሐሥ10፥19፤ 11፥12፤13፥2፤20፥23፤ 21፥11
8፥33 ኢሳ53፥7፥8
8፥35 ማቴ5፥2፤ ሉቃ 24፥27፤ ሐሥ13፥32፤ 17፥2፤18፥28፤28፥23
8፥36 ሐሥ2፥38፤ 10፥47
8፥39 1ነገ18፥12፤ 2ነገ2፥16፤ሕዝ3፥12፡ 14፤8፥3፤11፥1፡24፤43፥5፤ 2ቆሮ12፥2፤1ተሰ4፥17፤ ራእ12፥5
8፥40 ቀኍ25፤ሐሥ 10፥1፡24፤12፥19፤ 21፥8፡16፤23፥23፡33፤ 25፥1፡4፡6፡13
9፥1 ሐሥ8፥3
9፥2 ኢሳ17፥1፤ ኤር49፥23፤ሐሥ 19፥9፡23፤22፥4፤24፥1 4፡22
9፥3 1ቆሮ15፥8
9፥4 ኢሳ6፥8
9፥6 ቀኍ16፤ሕዝ 3፥22

“እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፤
የበግ ጠቦት በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል፣
እንዲሁ አፉን አልከፈተም።
33ራሱን በማዋረዱም ፍትሕን ተነፈገ፤
ሕይወቱ ከምድር ተወግዳለችና፣
ስለ ትውልዱ ማን ሊናገር ይችላል?”
34ጃንደረባውም መልሶ ፊልጶስን፣ “ነቢዩ
ይህን የሚናገረው ስለ ማን ነው? ስለ ራሱ
ነው፣ ወይስ ስለ ሌላ ሰው? እባክህ ንገ
ረኝ” አለው። 35ፊልጶስም አፉን ከፈተ፤
ከዚሁም መጽሐፍ ክፍል ጀምሮ ስለ ኢየ
ሱስ ወንጌል ሰበከለት።
36በመንገዝ ላይ ሳሉም ውሃ ካለበት ስፍራ
ደረሱ፤ ጃንደረባውም፣ “እነሆ፤ ውሃ እዚህ
አለ፤ ታዲያ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ
ምን ነገር አለ?” አለው። 37ፊልጶስም፣
“በፍጹም ልብህ ካመንህ መጠመቅ ትች
ላለህ” አለው። ጃንደረባውም፣ “ኢየሱስ
ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ
አምናለሁ” ሲል መለሰለት፤ 38ሠረገላውም
እንዲቆም አዘዘ። ከዚያም ሁለቱ አብረው
ወደ ውሃው ወረዱ፤ ፊልጶስም ጃንደረባ
ውን አጠመቀው።ᴬ 39ከውሃውም በወጡ
ጊዜ፣ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ነጥቆ ወሰ
ደው፤ ጃንደረባውም ከዚህ በኋላ አላየ
ውም፤ ሆኖም ደስ እያለውም ጉዞውን
ቀጠለ። 40ከዚያ በኋላ ግን ፊልጶስ በአዛ
ጦን ታየ፤ ቂሳሪያም እስኪደርስ ድረስ፣
በሚያልፍባቸው ከተሞች ሁሉ ወንጌልን
ይሰብክ ነበር።

### የሳውል ማመን

9፥1-19 ተጓ ምብ – ሐሥ22፥3-16፤26፥9-18

9 ሳውል ግን የጌታን ደቀ መዛሙርት
ለመግደል አሁንም እየዛተ ወደ ሊቀ
ካህናቱ ሄደ፤ 2የጌታን መንገድ የሚከ
ተሉትን ወንዶችንም ሆኑ ሴቶችን በዚያ
ካገኘ አስሮ ወደ ኢየሩሳሌም ለመውሰድ
እንዲችል፣ በደማስቆ ለነበሩት ምኵራቦች
ደብዳቤ እንዲሰጠው ሊቀ ካህናቱን ለመ
ነው። 3ደማስቆ ለመድረስ ጥቂት ሲ
ቀረው ብርሃን ከሰማይ ድንገት በዙሪያው
አንጸባ ረቀበት፣ 4እርሱም በምድር ላይ
ወደቀ፤ በዚያ ጊዜም “ሳውል፤ ሳውል፤
ለምን ታሳድደኛለህ?” የሚል ድምፅ ሰ
ማ።
5ሳውልም፣ “ጌታ ሆይ፤ አንተ ማን ነህ?”
አለው።
እርሱም እንዲህ አለው፤ “እኔማ አንተ
የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ። 6አሁንም ተነ
ሥተህ ወደ ከተማዪቱ ግባ፤ ማድረግ የሚ
ገባህም ይነገርሃል።”

ᴬ38 አንዳንድ ቅጆች ይህን ቍጥር አይጨምሩም። ከአንዳንድ የቅርብ ጊዜ ቅጆች የተወሰደ ነው።

7ከሳውል ጋር ይጓዙ የነበሩትም ሰዎች
ድምፁን እየሰሙ ማንንም ባላዩ ጊዜ፣
አፋቸውን ይዘው ቆሙ። 8ሳውልም ከወ
ደቀበት ተነሥቶ ዐይኑን ሲገልጥ ምንም
ማየት አልቻለም፤ ስለዚህ ሰዎቹ እጁን
ይዘው እየመሩ ወደ ደማስቆ አስገቡት።
9ሦስት ቀንም ታወረ፤ እህል ውሃም አል
ቀመሰም።

10በደማስቆ ሐናንያ የሚባል አንድ ደቀ
መዝሙር ነበር፤ ጌታም በራእይ፣ "ሐናን
ያ!" ብሎ ጠራው።

እርሱም፣ "ጌታ ሆይ፤ እነሆኝ" አለ።

11ጌታም እንዲህ አለው፤ "ተነሣና 'ቀጥ
ተኛ ጐዳና' በተባለው መንገድ ይሁዳ ወደ
ተባለ ሰው ቤት ሂድ፤ እዚያም ሳውል
የሚባል አንድ የጠርሴስ ሰው እየጸለየ
ነውና ፈልገው፤ 12ምክንያቱም ሐናንያ
የሚ ባል ሰው እርሱ ወዳለበት መጥቶ እጁ
ን እንደሚጭንበትና ዐይኑ እንደሚበራ
ለት በራእይ አይቶአል።"

13ሐናንያም መልሶ እንዲህ አለው፤ "ጌታ
ሆይ፤ ይህ ሰው እኮ በኢየሩሳሌም ባሉ
ቅዱሳንህ ላይ ምን ያህል ጕዳት እንዳደ
ረሰ ከብዙ ሰው ሰምቻለሁ፤ 14ወደዚህም
የመጣው ስምህን የሚጠሩትን ሁሉ ለማሰር
ከካህናት አለቆች ሥልጣን ተቀብሎ ነው።"

15ጌታም እንዲህ አለው፤ "ሂድ፤ ይህ ሰው
በአሕዛብና በነገሥታት ፊት እንዲሁም
በእስራኤል ሕዝብ ፊት ስሜን እንዲሸከም
የተመረጠ ዕቃዬ ነው፤ 16እኔም ስለ ስሜ
ምን ያህል መከራ መቀበል እንዳለበት
አሳየዋለሁ።"

17ሐናንያ ሄዶ፤ ወደተባለውም ቤት ገባ፤
በሳውልም ላይ እጁን ጭኖ፣ "ወንድሜ
ሳውል ሆይ፤ ወደዚህ ስትመጣ በመንገድ
ላይ የተገለጠልህ ጌታ ኢየሱስ፣ ዐይንህ
እንዲበራና፣ በመንፈስ ቅዱስም እንድት
ሞላ እኔን ልኮኛል" አለው። 18ወዲያውም
ከሳውል ዐይን ላይ ቅርፊት የመሰለ ነገር
ወደቀ፤ እንደ ገና ማየት ቻለ፤ ተነሥቶም
ተጠመቀ፤ 19ምግብም በልቶ በረታ።

## ሳውል በደማስቆና በኢየሩሳሌም

ሳውል በደማስቆ ከነበሩት ደቀ መዛ
ሙርት ጋር አያሌ ቀን ተቀመጠ። 20ወዲ
ያውም፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆ
ኑን በየምኵራቦቹ መስበክ ጀመረ። 21የሰ
ሙትም ሁሉ በመገረም፣ ይህ ሰው "በኢ
የሩሳሌም ይህን ስም የሚጠሩትን ሲያጠፋ
የነበረ አይደለምን? ደግሞም ወደዚህ የመ
ጣው እነርሱን አስሮ ወደ ካህናት አለቆች
ሊወስዳቸው አልነበረምን?" አሉ። 22ሳውል
ግን እየበረታ ሄደ፤ በደማስቆ ለሚኖሩ
ትም አይሁድ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ[ከ]
መሆኑን ማስረጃ እያቀረበ አፋቸውን ያስ
ይዛቸው ነበር።

23ከብዙ ቀንም በኋላ፣ አይሁድ ሳው
ልን ለመግደል አሤሩ፤ 24እርሱ ግን ዕቅዳ
ቸውን ዐውቆ ነበር፤ እነርሱም ሊገድሉት
የከተማዋን በር ቀንና ሌሊት ይጠብቁ
ነበር፤ 25የእርሱ ተከታዮች ግን በሌሊት
በከተማዋ ቅጥር ቀዳዳ አሹልከው በቅር
ጫት አወረዱት።

26ሳውልም ወደ ኢየሩሳሌም በመጣ ጊዜ፣
ከደቀ መዛሙርት ጋር ለመቀላቀል
ሞከረ፤ እነርሱ ግን በእርግጥ ደቀ መዝ
ሙር መሆኑን ስላላመኑ ሁሉም ፈሩት።
27ይሁን እንጂ ባርናባስ ወስዶ ወደ ሐዋ
ርያት አመጣው፤ ሳውልም በጕዞው ላይ
ሳለ ጌታን እንዴት እንዳየው፣ ጌታም
እንዴት እንደ ተናገረው እንዲሁም በደ
ማስቆ የጌታን ስም እንዴት በድፍረት
እንደ ሰበከ ነገራቸው። 28ስለዚህ ሳውል
አብሮአቸው ተቀመጠ፤ በኢየሩሳሌምም
በመዘዋወር በጌታ ስም በድፍረት ይናገር
ነበር። 29ከግሪክ አገር ከመጡት አይሁድ
ጋር እየተነጋገረ፣ ይከራከር ነበር፤ እነርሱ
ግን ሊገድሉት ጥረት ያደርጉ ነበር።
30ወንድሞችም ይህን ባወቁ ጊዜ፣ ወደ
ቂሳርያ አውርደው ወደ ጠርሴስ ሰደዱት።

31በዚህ ጊዜ በይሁዳ፣ በገሊላና በሰ
ማርያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን በሰላም
መኖር ጀመረች፤ ተጠናከረችም።
ደግሞም እግዚአብሔርን በመፍራት
እየተመላለሰችና በመ ንፈስ ቅዱስ እየተ
ጽናናች በቍጥር እየ በዛች ሄደች።

## ኤንያና ዶርቃ

32ጴጥሮስም ከአገር ወደ አገር በሚዘዋ
ወርበት ጊዜ፣ በልዳ የሚኖሩትን ቅዱሳን
ለመጐብኘት ወረደ። 33በዚያም ኤንያ የተ
ባለ፣ ስምንት ዓመት የዐልጋ ቍራኛ
የነበረ አንድ ሽባ ሰው አገኘ። 34ጴጥሮ
ስም፣ "ኤንያ ሆይ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈ
ውስሃል፤ ተነሣና መኝታህን አንጥፍ"
አለው። ኤንያም ወዲያውኑ ብድግ አለ።
35በልዳና በሰሮና የሚኖሩትም ሁሉ እር
ሱን አይተው ወደ ጌታ ተመለሱ።

36በኢዮጴ ጣቢታ የተባለች አንዲት
ደቀ መዝሙር ነበረች፤ የስሟም ትርጓሜ
ዶርቃ[ኸ] ማለት ነው። እርሷም ዘወትር
በትጋት በጎ ነገር እያደረገችና ድኾችን እየ

9፥7 ዳን10፥7፤ ዮሐ 12፥29
9፥8 ቍ18
9፥10 ሐሥ10፥3፡ 17፥19፤12፥9፤16፥9፡ 10፤18፥9
9፥11 ቍ30፤ ሐሥ 11፥25፤ 21፥39፤22፥3
9፥12 ማር5፥23
9፥13 ቍ32፤ ሐሥ 8፥3፤26፥10፤ ሮሜ1፥7፤ 15፥25፡ 26፡31፤16፥2፡15፤ ኤፌ1፥1፤ፊል1፥1
9፥14 ቍ2፡21፤ ሐሥ 2፥21
9፥15 ሐሥ13፥2፤ 25፥22፡23፤26፥1፤ ሮሜ1፥1፤ 11፥13፤15፥15፡16፤ ገላ1፥15፡16፤ 2፥7፡8፤1ጢሞ1፥12
9፥16 ሐሥ20፥23፤ 21፥11፤2ቆሮ6፥4-10፤ 11፥23-27፤ 2ጢሞ 1፥8፤2፥3፡9
9፥17 ሉቃ1፥15፤ ሐሥ 6፥6
9፥18 ሐሥ2፥38
9፥19 ሐሥ11፥26፤ 26፥20
9፥20 ማቴ4፥3፤ ሐሥ 13፥5፡14፤ 14፥1፤17፥2፡ 10፡17፤18፥4፡19፤19፥8
9፥21 ቍ14፤ ሐሥ 8፥3
9፥22 ሉቃ2፥11፤ ሐሥ 5፥42፤ 17፥3፤18፥5፡28
9፥23 ሐሥ20፥3
9፥24 ሐሥ20፥3፡ 19፤23፥16፡30
9፥25 1ሳሙ19፥12፤ 2ቆሮ11፥32፡33
9፥26 ሐሥ22፥17፤ 26፥20፤ገላ1፥17፡18
9፥27 ቍ3-6፡20፡ 22፤ሐሥ4፥36
9፥29 ሐሥ6፥1፤ 2ቆሮ11፥26
9፥30 ቍ11፤ሐሥ 1፥16፤8፥40
9፥31 ሐሥ2፥41፤ 8፥1
9፥32 ቍ13
9፥34 ሐሥ3፥6፡ 16፤4፥10
9፥35 1ዜና5፥16፤ 27፥29፤መሐ2፥1፤ ኢሳ 33፥9፤35፥2፤ 65፥10፤ሐሥ2፥41
9፥36 ኢሱ19፥46፤ 2ዜና2፥16፤ዕዝ3፥7፤ ዮና1፥3፤ሐሥ10፥5፤ 1ጢሞ2፥10፤ቲቶ3፥8

[ከ]22 ወይም *መሲሕ*

[ኸ]36 *ጣቢታ* በአረማይክ ሲሆን *ዶርቃ* ደግሞ በግሪክ ነው፤ ትርጕሙም *ፌቆ* ማለት ነው።

ረዳች ትኖር ነበር፡፡ 37በዚያ ጊዜም ታማ
ሞተች፤ ሰዎችም አስከሬኗን አጥበው በሰገ
ነት ላይ ባለው ክፍል አስቀመጡት፡፡
38ልዳ ለኢዮጴ ቅርብ ስለ ነበረች፣ ደቀ
መዛሙርትም ጴጥሮስ በልዳ መሆኑን
በሰሙ ጊዜ፣ ሁለት ሰዎች ልከው፣ “እባ
ክህ ፈጥነህ ወደ እኛ ና” ሲሉ ለመኑት፡፡
39ጴጥሮስም ተነሥቶ ከእነርሱ ጋር
ሄደ፤ እዚያ በደረሰ ጊዜም ሰገነት ላይ
ወዳለው ክፍል አወጡት፡፡ መበለቶቹም
ሁሉ ዶርቃ ከእነርሱ ጋር በነበረችበት ጊዜ
ያደረገቻቸውን ቀሚሶችና ልብሶች እያሳ
ዩት ዙሪያውን ከበው ያለቅሱ ነበር፡፡
40ጴጥሮስም ሁሉንም ከክፍሉ አስወጥቶ
ተንበርክኮ ጸለየ፤ ወደ ሬሳውም ዘወር
ብሎ፣ “ጣቢታ፤ ተነሺ” አለ፡፡ እርሷም ዐይኗን
ገለጠች፤ ጴጥሮስንም ባየች ጊዜ ቀና ብላ
ተቀመጠች፤ 41እርሱም እጇን ይዞ አስነ
ሣት፤ አማኞችንና መበለቶቹንም ጠርቶ
ከነሕይወቷ አስረከባቸው፡፡ 42ይህም ነገር
በመላው ኢዮጴ ታወቀ፤ ብዙ ሰዎችም
በጌታ አመኑ፡፡ 43ጴጥሮስም ስምዖን ከተባለ
ከአንድ ቍርበት ፋቂ ጋር በኢዮጴ ብዙ
ቀን ተቀመጠ፡፡

## ቆርኔሌዎስ ጴጥሮስን አስጠራ

10 በቂሳርያ፣ ‘የኢጣሊያ ክፍለ ጦር’
በሚባለው ሰራዊት ውስጥ የመቶ
አለቃ የሆነ ቆርኔሌዎስ የተባለ አንድ
ሰው ነበረ፡፡ 2እርሱም ከመላው ቤተ ሰቡ
ጋር በመንፈሳዊ ነገር የተጋና እግዚአብሔርን
የሚፈራ፣ ለሰዎች እጅግ ምጽዋት የሚ
ሰጥ፣ አዘውትሮ ወደ እግዚአብሔር የሚ
ጸልይ ነበር፡፡ 3አንድ ቀን፣ ከቀኑ ዘጠኝ
ሰዓት ገደማ የእግዚአብሔር መልአክ በራ
እይ ወደ እርሱ መጥቶ፣ “ቆርኔሌዎስ
ሆይ!” ሲለው በግልጽ አየ፡፡
4ቆርኔሌዎስም በድንጋጤ ትኵር ብሎ
እያየው፣ “ጌታ ሆይ፤ ምንድን ነው?”
አለው፡፡ መልአኩም እንዲህ አለው፤ “ጸሎ
ትህና ምጽዋትህ ለመታሰቢያነት ወደ እግ
ዚአብሔር ፊት አርጎልሃል፡፡ 5አሁንም
ሰዎች ወደ ኢዮጴ ልከህ ጴጥሮስ የተባ
ለውን ስምዖንን አስመጣው፤ 6እርሱም
በባሕሩ አጠገብ ባለው በቍርበት ፋቂው
በስምዖን ቤት በእንግድነት ዐርፎአል፡፡”
7ቆርኔሌዎስም፣ ያነጋገረው መልአክ
ተለይቶት ከሄደ በኋላ፣ ከአገልጋዮቹ ሁለ
ቱን፣ እንዲሁም በመንፈሳዊ ነገር የተጋና
ለእርሱ ታማኝ የሆነውን አንዱን ወታደር
አስጠራ፤ 8የሆነውንም ነገር ሁሉ ከነገራቸው
በኋላ ወደ ኢዮጴ ላካቸው፡፡

9፥37 ሐሥ1፥13፤ 20፥8
9፥38 ሐሥ11፥26
9፥39 ሐሥ6፥1፤1 ጢሞ5፥3
9፥40 ማቴ9፥25፤ ሉቃ7፥14፤22፥41፤ ሐሥ7፥60
9፥42 ሐሥ2፥41
9፥43 ሐሥ10፥6
10፥1 ሐሥ8፥40
10፥2 ቍ22፡35፤ ሐሥ13፥16፡26
10፥3 መዝ55፥17፤ ሐሥ3፥1፤5፥19፤9፥10
10፥4 መዝ20፥3፤ ማቴ10፥42፤26፥13፤ራእ8፥4
10፥5 ሐሥ9፥36
10፥6 ሐሥ9፥43
10፥8 ሐሥ9፥36
10፥9 ማቴ24፥17
10፥10 ሐሥ22፥17
10፥11 ማቴ3፥16
10፥14 ዘሌ11፥4-8፡ 13-20፤20፥25፤ዘዳ 14፥3-20፤ሕዝ4፥14፤ ሐሥ9፥5
10፥15 ቍ28፤ዘፍ 9፥3፤ማቴ15፥11፤ ሉቃ11፥41፤ሐሥ 11፥9፤ሮሜ14፥14፡ 17፡20፤ 1ቆሮ10፥ 25፤1ጢሞ4፥3፡4፤ ቲቶ1፥15
10፥17 ቍ7፡8፤ ሐሥ 9፥10
10፥19 ሐሥ8፥29፤ 9፥10
10፥20 ሐሥ15፥7-9
10፥22 ቍ2፤ ሐሥ 11፥14
10፥23 ቍ45፤ ሐሥ 1፥16፤11፥12

## ጴጥሮስ ያየው ራእይ

10፥9-32 ማመ - ሐሥ11፥5-14

9የተላኩትም ሰዎች በማግስቱ ወደ ከተ
ማዪቱ እንደ ተቃረቡ፣ ጴጥሮስ እኩለ
ቀን ገደማ ሲሆን፣ ለመጸለይ ወደ ሰገነት
ወጣ፡፡ 10በዚያን ጊዜም ስለ ተራበ የሚበላ
ነገር ፈለገ፤ ምግብ እየተዘጋጀ ሳለም አሸ
ለበውና በተመስጦ ውስጥ ሆነ፤ 11ሰማይም
ተከፍቶ አንድ ትልቅ ጨርቅ የሚመስል
ነገር በአራቱ ማእዘን ተይዞ ወደ ምድር
ሲወርድ አየ፡፡ 12በጨርቁም ላይ አራት
እግር ያላቸው የተለያዩ እንስሳት፣ በም
ድር የሚሳቡ ፍጥረታትና በአየር የሚ
በሩ አዕዋፍ ነበሩበት፡፡ 13በዚህ ጊዜ፣
“ጴጥሮስ ሆይ፤ ተነሣ፤ እነዚህን ዐርደህ
ብላ” የሚል ድምፅ ወደ እርሱ መጣ፡፡
14ጴጥሮስ ግን “ጌታ ሆይ፤ ይህማ አይ
ሆንም፤ እኔ ያልተቀደሰ ወይም ርኵስ
ነገር ፈጽሞ በልቼ አላውቅምና” አለ፡፡
15ያም ድምፅ እንደ ገና ለሁለተኛ ጊዜ
ወደ እርሱ መጥቶ፣ “እግዚአብሔር ንጹሕ
ያደረገውን አንተ እንደ ርኵስ አትቍጠ
ረው” አለው፡፡
16ይህም ሦስት ጊዜ ተደጋገመ፤ ጨርቁም
ወዲያውኑ ወደ ሰማይ ተወሰደ፡፡
17ጴጥሮስም ስላየው ራእይ ትርጕም
እጅግ ተጨንቆ በማሰላሰል ላይ ሳለ፣ ቆር
ኔሌዎስ የላካቸው ሰዎች የስምዖንን ቤት
ፈልገው ካገኙ በኋላ መጥተው በሩ ላይ
ቆሙ፤ 18ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው
ጴጥሮስ የተባለው ስምዖን እዚያ ይኖር
እንደ ሆነ ጠየቁ፡፡
19ጴጥሮስ የራእዩን ነገር በማሰላሰል
ላይ ሳለ፣ መንፈስ እንዲህ አለው፤ “እነሆ፤
ሦስት[w] ሰዎች ይፈልጉሃል፤ 20ስለዚህ ተነ
ሥተህ ውረድ፤ የላክኋቸውም እኔ ስለ
ሆንሁ ሳትጠራጠር ከእነርሱ ጋር ሂድ፡፡”
21ጴጥሮስም ወርዶ፣ “እነሆ፤ የምትፈ
ልጉት ሰው እኔ ነኝ፤ የመጣችሁበት
ጕዳይ ምንድን ነው?” አላቸው፡፡
22ሰዎቹ፣ “የመጣነው ቆርኔሌዎስ ከተ
ባለው መቶ አለቃ ዘንድ ነው፤ እርሱም
ጻድቅና እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ በአይሁ
ድም ሕዝብ ሁሉ ዘንድ የተከበረ ሰው
ነው፡፡ አንተን ወደ ቤቱ እንዲያስመጣህና
የምትለውን እንዲሰማ ቅዱስ መልአክ ነግ
ሮታል” አሉት፡፡ 23ጴጥሮስም ሰዎቹን ሊያ
ስተናግዳቸው ወደ ቤት አስገባቸው፡፡

[w]19 አንድ የጥንት ቅጅ *ሁለት* ይላል፤ ሌሎች የጥንት ቅጆች ይህ ቍጥር የላቸውም፡፡

### ጴጥሮስ በቆርኔሌዎስ ቤት

ጴጥሮስም በማግስቱ ተነሥቶ ከእነርሱ
ጋር ሄደ፤ ከኢዮጴ የመጡ አንዳንድ
ወንድሞችም አብረውት ሄዱ፤ 24በሚቀ
ጥለው ቀን ቂሳርያ ገባ። ቆርኔሌዎስም
ዘመዶቹንና የቅርብ ወዳጆቹን ሰብስቦ
ይጠብቃቸው ነበር። 25ጴጥሮስም ወደ
ቤቱ በገባ ጊዜ ቆርኔሌዎስ ተቀበለው፤
እግሩም ላይ ወድቆ ሰገደለት። 26ጴጥሮስ
ግን፣ "እኔም እንዳንተው ሰው ነኝና ተነሥ!"
ብሎ አስነሣው።
27ጴጥሮስም እያነጋገረው አብሮት ሲገባ
ብዙ ሰው ተሰብስቦ አገኘ፤ 28እንዲህም አላ
ቸው፤ "አንድ አይሁዳዊ ከሌላ ወገን ጋር
እንዲተባበር ወይም እንዲቀራረብ ሕጋችን
እንደማይፈቅድ ራሳችሁ ታውቃላችሁ፤
ነገር ግን እኔ ማንንም ርኵስ ወይም ያል
ተቀደሰ ነው እንዳልል እግዚአብሔር አሳይቶ
ኛል፤ 29ስለዚህም በተጠራሁ ጊዜ፣ እነሆ
ሳላመነታ መጣሁ፤ እንግዲህ፣ ለምን እን
ደጠራችሁኝ ማወቅ እፈልጋለሁ።"
30ቆርኔሌዎስም እንዲህ አለው፤ "ከአራት
ቀን በፊት በዚህ ጊዜ ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት
በቤቴ ሆኜ እጸልይ ነበር፤ ድንገትም ብሩህ
ልብስ የለበሰ ሰው መጥቶ በፊቴ ቆመና
31እንዲህ አለኝ፤ 'ቆርኔሌዎስ ሆይ፤ ጸሎ
ትህ ተሰምቶልሃል፤ ምጽዋትህም ለመታሰ
ቢያነት በእግዚአብሔር ፊት ደርሶአል።
32ሰዎችን ወደ ኢዮጴ ልከህ ጴጥሮስ የተባ
ለውን ስምዖንን አስመጣ፤ እርሱም በባሕር
አጠገብ ባለው በቍርበት ፋቂው በስምዖን
ቤት በእንግድነት ዐርፎአል።' 33እኔም
ወዲያው ላኩብህ፤ አንተም በመምጣትህ
መልካም አድርገሃል። እንግዲህ እኛ ሁላ
ችን ጌታ ያዘዘህን ስትነግረን ለመስማት
በእግዚአብሔር ፊት አለን።
34ጴጥሮስም እንዲህ ሲል መናገር
ጀመረ፤ "እግዚአብሔር ለማንም እንደማያዳላ
በእርግጥ ተረድቻለሁ፤ 35ነገር ግን እርሱን
የሚፈሩትንና ጽድቅን የሚያደርጉትን
ሁሉ ከየትኛውም ወገን ቢሆኑ ይቀበላ
ቸዋል። 36እግዚአብሔር፣ የሁሉ ጌታ በሆነው
በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የላከውም
የሰላም የምሥራች መልእክት ይኸው
ነው። 37ዮሐንስ ከሰበከው ጥምቀት በኋላ
ከገሊላ ጀምሮ በመላው ይሁዳ የሆነውን
ታውቃ ላችሁ፤ 38እግዚአብሔር የናዝሬቱን
ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስና በኀይል ቀባው፤
እርሱም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለ ነበረ
በደረሰ በት ሁሉ መልካም እያደረገ በዲ
ያብሎስ ሥልጣን ሥር የነበሩትን ሁሉ
ፈወሰ።
39"እርሱ በአይሁድ አገርና በኢየሩ

10፥24 ሐሥ8፥40
10፥26 ሐሥ14፥15፤ ራእ19፥10፤22፥8፡9
10፥27 ቁ24
10፥28 ቁ14፡15፤ ዮሐ4፥9፤18፥28፤ ሐሥ11፥3፤15፥8፡9
10፥30 ዮሐ20፥12
10፥34 ዘዳ10፥17፤ 2ዜና19፥7፤ ኢዮ34፥19፤ ማር12፥14፤ ሮሜ2፥11፤ገላ2፥6፤ ኤፌ 6፥9፤ቈላ3፥25፤ ያዕ2፥1፤1ጴጥ1፥17
10፥35 ሐሥ15፥9
10፥36 ማቴ28፥18፤ ሉቃ2፥ 14፤ ሐሥ13፥32፤ 1ዮሐ1፥5
10፥38 ማቴ4፥23፤ ዮሐ3፥2፤ሐሥ4፥26
10፥39 ቁ41፤ ሉቃ 24፥48፤ ሐሥ5፥30
10፥40 ሐሥ2፥24
10፥41 ሉቃ24፥43፤ ዮሐ14፥17፡22፤ 21፥13፤ሐሥ1፥4
10፥42 ማቴ28፥19፡ 20፤ዮሐ5፥22፤ ሐሥ 17፥31፤ሮሜ 14፥9፤ 2ቆሮ5፥10፤ 2ጢሞ 4፥1፤ 1ጴጥ4፥5
10፥43 ኢሳ53፥11፤ ሉቃ24፥27፤ዮሐ3፥15፤ ሐሥ15፥9፤26፥22
10፥44 ሉቃ1፥15፤ ሐሥ8፥15፡16፤ 11፥15፤ 15፥8፤19፥6
10፥45 ቁ23፤ሐሥ 2፥33፡38፤11፥18፤15፥8
10፥46 ማር16፥17
10፥47 ዮሐ20፥22፤ ሐሥ8፥36፤11፥17
10፥48 ሐሥ2፥38
11፥1 ሐሥ1፥16፤ ዕብ4፥12
11፥2 ሐሥ10፥45
11፥3 ሐሥ10፥25፡ 28፤ገላ2፥12
11፥5 ሐሥ9፥10፤ 10፥9-32

ሳሌም ላደረገው ሁሉ እኛ ምስክሮች ነን፤
ደግ ሞም ሰዎች እርሱን በዕንጨት ላይ
ሰቅ ለው ገደሉት። 40እግዚአብሔር ግን
በሦስተ ኛው ቀን ከሙታን አስነሣው፤
እንዲታ ይም አደረገው፤ 41የታየውም
ለሁሉ ሰው ሳይሆን፣ ከሙታን ከተነሣ
በኋላ አብረነው ለበላንና ለጠጣን፣ እግዚ
አብሔርም አስቀድሞ ለመረጠን ለእኛ
ለምስክሮቹ ነው። 42ለሕዝቡ
እንድንሰብክና በሕያዋንና በሙታንም ላይ
እንዲፈርድ እግዚአብሔር የሾመው እርሱ
መሆኑን እንድንመሰክር እርሱ ራሱ አዘዘን፤
43በእርሱም የሚያምን ሁሉ በስሙ የኀጢ
አትን ስርየት እንደሚቀበል ነቢያት ሁሉ
ይመሰክሩለታል።"
44ጴጥሮስ ይህን እየተናገረ ሳለ፣ ቃሉን
በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደባ
ቸው። 45ከጴጥሮስ ጋር የመጡት፣ ከተገረ
ዙት ወገን የሆኑት አማኞች፣ የመንፈስ
ቅዱስ ስጦታ በአሕዛብም ላይ ደግሞ
መፍሰሱን ሲያዩ ተገረሙ፤ 46ይኸውም
በልሳን[o] ሲናገሩና እግዚአብሔርን ሲ
ያመሰግኑ ስለሰሟቸው ነው።
በዚያ ጊዜ ጴጥሮስ እንዲህ አለ፤ 47"እነ
ዚህ ሰዎች እንደ እኛ መንፈስ ቅዱስን
ስለ ተቀበሉ፣ እንግዲህ በውሃ እንዳይጠ
መቁ የሚከለክላቸው ማን ነው?" 48ስለዚህ
በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲጠመቁ አዘዛ
ቸው። ከዚህ በኋላ፣ ጴጥሮስ ጥቂት ቀን
ከእነርሱ ጋር እንዲቀመጥ ለመኑት።

### ጴጥሮስ አሕዛብ ቤት ለምን እንደገባ አስረዳ

11 ሐዋርያትና በይሁዳ የነበሩት ወን
ድሞች አሕዛብ ደግሞ የእግዚአብሔ
ርን ቃል እንደ ተቀበሉ ሰሙ። 2ስለዚህ
ጴጥሮስ ወደ ኢየሩሳሌም በወጣ ጊዜ፣
ከተገረዙት ወገን የነበሩ አማኞች
ነቀፉት፤ 3እንዲህም አሉት፤ "ወዳልተገረዙ
ሰዎች ገብ
ተህ ከእነርሱ ጋር በላህ።"
4ጴጥሮስ ግን እንዲህ ሲል ነገሩን በቅ
ደም ተከተል ያስረዳቸው ጀመር፤ 5"በኢ
ዮጴ ከተማ ስጸልይ በተመስጦ ውስጥ እያ
ለሁ ራእይ አየሁ፤ ትልቅ ጨርቅ የሚመ
ስል ነገር፣ በአራት ማእዘን ተይዞ ከሰማይ
እኔ ወደ ነበርሁበት ቦታ ሲወርድ አየሁ።
6አተኵሬም ይህን ነገር ስመለከት አራት
እግር ያላቸው እንስሳት፣ የዱር አራዊት፣
በምድር የሚሳቡ ፍጥረታትና በሰማይ
የሚበሩ አዕዋፍ አየሁ። 7በዚህ ጊዜ፣
'ጴጥሮስ ሆይ፤ ተነሣና ዐርደህ ብላ' የሚ
ለኝን ድምፅ ሰማሁ።
8"እኔም፣ 'ጌታ ሆይ፤ ይህማ አይሆንም፤

[o]46 ወይም በሌላ ቋንቋዎች

እኔ ርኩስ ወይም ያልተቀደሰ ነገር ፈጽሞ
ወደ አፌ ገብቶ አያውቅም’ አልሁ።
9“ያም ድምፅ ዳግመኛ፣ ‘እግዚአብሔር
ንጹሕ ያደረገውን አንተ እንደ ርኩስ አት
ቍጠረው’ ሲል ከሰማይ ተናገረኝ። 10ይህም
ሦስት ጊዜ ተደጋገመ፤ ከዚያ ሁሉም
እንደ ገና ወደ ሰማይ ተወሰደ።
11“ልክ በዚያው ሰዓት፣ ሦስት ሰዎች
ከቂሳርያ ወደ እኔ ተልከው መጥተው እኔ
ባለሁበት ቤት ደጅ ላይ ቆሙ፤ 12መንፈስ
ቅዱስም ምንም ሳላወላውል ከእነርሱ ጋር
እንድሄድ ነገረኝ። እነዚህም ስድስት ወን
ድሞች ከእኔ ጋር ሄዱ፤ ወደ ሰውየውም
ቤት ገባን። 13እርሱም መልአክ በቤቱ
ውስጥ ቆሞ እንደ ታየውና እንዲህ እን
ዳለው ነገረን፤ ‘ወደ ኢዮጴ ሰው ልከህ
ጴጥሮስ የተባለውን ስምዖንን አስጠራ፤
14እርሱም አንተና የቤትህ ሰዎች ሁሉ
የምትድኑበትን ቃል ይነግርሃል።’
15“እኔም ገና መናገር ስጀምር፣ መንፈስ
ቅዱስ፣ በመጀመሪያ በእኛ ላይ እንደ
ወረደ ሁሉ በእነርሱም ላይ ወረደ። 16በዚህ
ጊዜ፣ ‘ዮሐንስ በውሃ አጠመቀ፤ እናንተ
ግን በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ’ ሲ
ል ጌታ የተናገረው ቃል ትዝ አለኝ።
17እንግዲህ እግዚአብሔር በጌታ በኢየሱስ
ክርስቶስ ስናምን ለእኛ የሰጠንን ስጦታ
ለእነርሱም ከሰጣቸው፣ ታዲያ፣ እግዚአብሔ
ርን መቋቋም እችል ዘንድ እኔ ማን ነኝ?”
18ይህን በሰሙ ጊዜም የሚሉትን አጥ
ተው እንዲህ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰ
ገኑ፤ “ይህማ ከሆነ፣ አሕዛብም ወደ ሕይ
ወት ይመጡ ዘንድ፣ እግዚአብሔር ንስሓን
ሰጥቷቸዋል ማለት ነዋ።”

## በአንጾኪያ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን

19በእስጢፋኖስ ላይ በተነሣው ስደት
ምክንያት የተበተኑት አማኞች ቃሉን ለአ
ይሁድ ብቻ እየተናገሩ እስከ ፊንቄ፣ እስከ
ቆጵሮስና እስከ አንጾኪያ ድረስ ዘለቁ።
20ከቆጵሮስና ከቀሬና የመጡት አንዳንዶች
ሰዎች ግን ወደ አንጾኪያ ሄደው ለግሪኮ
ችም ጭምር በመንገር የጌታን የኢየሱስን
ወንጌል ሰበኩላቸው። 21የጌታም እጅ ከእነ
ርሱ ጋር ነበረ፤ ቍጥራቸውም እጅግ ብዙ
የሆኑ ሰዎች አምነው ወደ ጌታ ተመለሱ።
22ወሬውም በኢየሩሳሌም ከነበረችው
ቤተ ክርስቲያን ጆሮ ደረሰ፤ ቤተ ክርስቲ
ያኒቱም በርናባስን ወደ አንጾኪያ ላከ
ችው። 23እርሱም እዚያ ደርሶ እግዚአብሔር
በጸጋው የሠራውን ባየ ጊዜ ደስ አለው፤
ሁሉም በፍጹም ልብ በጌታ በመታመን
እንዲጸኑ መከራቸው። 24እርሱም መንፈስ
ቅዱስንና እምነትን የተሞላ ደግ ሰው
ነበር፤ ቍጥሩ ብዙ የሆነ ሕዝብም ወደ
ጌታ ተጨመረ።
25ከዚህ በኋላ በርናባስ፣ ሳውልን ለመ
ፈለግ ወደ ጠርሴስ ሄደ፤ 26ባገኘውም ጊዜ
ወደ አንጾኪያ አመጣው። ሁለቱም እዚያ
ካለችው ቤተ ክርስቲያን ጋር በመሆን
አንድ ዓመት ሙሉ እጅግ ብዙ ሕዝብ
አስተማሩ፤ ደቀ መዛሙርትም ለመጀመ
ሪያ ጊዜ በአንጾኪያ ‘ክርስቲያን’ ተብለው
ተጠሩ።
27በዚህ ጊዜ አንዳንድ ነቢያት ከኢየሩሳ
ሌም ወደ አንጾኪያ ወረዱ፤ 28ከእነርሱም
አንዱ አጋቦስ የተባለው ተነሥቶ በዓለም
ሁሉ ታላቅ ራብ እንደሚሆን መንፈስ
ቅዱስ አስመልክቶት ተናገረ፤ ይህም በቀ
ላውዴዎስ ቄሳር ዘመን ተፈጸመ። 29ደቀ
መዛሙርትም እያንዳንዳቸው ዐቅማቸው
በፈቀደ መጠን አዋጥተው በይሁዳ የሚ
ኖሩትን ወንድሞች ለመርዳት ወሰኑ፤
30ርዳታውንም በበርናባስና በሳውል እጅ
ለሽማግሌዎቹ በመላክ፣ ይህንኑ አደረጉ።

## ጴጥሮስ ከእስር ቤት በታምር ወጣ

12 በዚያ ዘመን ንጉሡ ሄሮድስ አንዳ
ንድ የቤተ ክርስቲያን አባላትን
እያሳደደ ያስጨንቅ ነበር፤ 2የዮሐንስንም
ወንድም ያዕቆብን በሰይፍ አስገደለ። 3ይህ
አድራጎቱ አይሁድን ደስ እንዳሰኛቸው ባየ
ጊዜ፣ ጴጥሮስን ደግሞ አስያዘው፤ ይህም
የሆነው በቂጣ በዓል ሰሞን ነበር። 4ጴጥሮ
ስን ወህኒ ቤት ካስገባው በኋላ፣ አራት አራት
ወታደሮች እየሆኑ እንዲጠብቁት በአራት
ፈረቃ ለተመደቡ ወታደሮች አስረከበው፤
ይህን ያደረገውም የፋሲካ በዓል ካለፈ
በኋላ ሕዝብ ፊት አውጥቶ ሊያስፈርድ
በት አስቦ ነው።
5ጴጥሮስም በዚህ መሠረት እስር ቤት
ተጣለ፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ ግን ስለ እርሱ
አጥብቃ ወደ እግዚአብሔር ትጸልይ
ነበር።
6ሄሮድስም ጴጥሮስን ሕዝቡ ፊት ሊያ
ቀርበው አስቦ ሳለ፣ ጴጥሮስ በዚያው ሌሊ
ት በሁለት ሰንሰለት ታስሮ፣ ከሁለት
ወታደሮች መካከል ተኝቶ ነበር፤ የወህኒ
ቤት ጠባቂዎችም እስር ቤቱ በር ላይ
ቆመው ነበር። 7የጌታ መልአክም ድንገት
ታየ፤ በክፍሉም ውስጥ ብርሃን በራ፤ መል
አኩም የጴጥሮስን ጐን መታ አድርጎ ቀሰ
ቀሰውና፣ “ቶሎ ተነሣ!” አለው፤ በዚህ ጊዜ
ሰንሰለቶቹ ከእጆቹ ወደቁ።
8መልአኩም፣ “ልብስህን ልበስ፤ ጫማህ

11፥9 ሐሥ10፥15
11፥11 ሐሥ8፥40
11፥12 ቀኍ1፡29፤
ሐሥ1፥16፤ 8፥29፤
15፥9፤ሮሜ3፥22
11፥13 ሐሥ5፥19
11፥14 ዮሐ4፥53፤
ሐሥ 10፥36፤16፥15፡
31-34፤18፥8፤
1ቆሮ 1፥11፡16
11፥15 ሐሥ2፥4፡
10፥44
11፥16 ማር1፥4፡8
11፥17 ሐሥ2፥38፤
10፥45፡47
11፥18 ሮሜ10፥12፡
13፤2 ቆሮ7፥10
11፥19 ቀኍ26፡
27፤ሐሥ8፥1፡4፤ 13፥1፤
14፥26፤18፥22፤ገላ2፥11
11፥20 ቀኍ19፤ማቴ
27፥32፤ሐሥ4፥36፤
13፥32
11፥21 ሉቃ1፥66፤
ሐሥ 2፥41
11፥22 ሐሥ4፥36
11፥23 ሐሥ13፥43፤
14፥22፡26፤15፥40፤
20፥24
11፥24 ሉቃ1፥15፤
ሐሥ2፥41
11፥25 ሐሥ9፥11
11፥26 ቀኍ29፤
ሐሥ 6፥1፡2፤
9፥19፡26፡38፤13፥52፤
26፥28፤1ጴጥ4፥16
11፥27 ሐሥ13፥1፤
15፥32፤1ቆሮ11፥4፤12፥2
8፡29፤14፥29፡32፡37፤
ኤፌ4፥11
11፥28 ማቴ24፥14፤
ሐሥ18፥2፤21፥10
11፥29 ቀኍ1፡12፡
26፤ሐሥ1፥16፤ሮሜ
15፥26፤
2ቆሮ8፥1-4፤ 9፥2
11፥30 ሐሥ4፥36፤
12፥25፤14፥23፤15፥2፡
22፤20፥17፡
1ጢሞ5፥17፤
ቲቶ 1፥5፤
ያዕ5፥14፤
1ጴጥ5፥1፤2ዮሐ1
12፥1 ማቴ14፥1
12፥2 ማቴ4፥21፤
ማር10፥39
12፥3 ዘፀ12፥15፤
23፥15፤ሐሥ20፥6፤
24፥27፤25፥9
12፥4 ዮሐ11፥55
12፥5 ሐሥ1፥14፤
ሮሜ15፥30፡31፤
ኤፌ6፥18
12፥6 ሐሥ21፥33
12፥7 መዝ107፥14፤
ሐሥ5፥19፤ 16፥26

ንም አድርግ’ አለው። ጴጥሮስም እንደታ
ዘዘው አደረገ። መልአኩም ቀጥሎ፣ “መደ
ረቢያህን ከላይ ጣል አድርገህ ተከተለኝ”
አለው። 9ጴጥሮስም ተከትሎት ከእስር
ቤት ወጣ፤ ነገር ግን ራእይ የሚያይ መሰ
ለው እንጂ መልአኩ የሚያደርገው ነገር
በእውን መሆኑን አላወቀም ነበር። 10የመ
ጀመሪያውንና ሁለተኛውን ዘብ ዐልፈው
ወደ ከተማዪቱ በሚወስደው መንገድ ላይ
ወዳለው የብረት መዝጊያ ዘንድ ደረሱ።
መዝጊያውም ራሱ ዐውቆ ተከፈተላቸው፤
እነርሱም ወጥተው ሄዱ፤ አንዲት ስላች
መንገድ እንዳለፉም ወዲያው መልአኩ
ተለየው።

11ጴጥሮስም ሲረጋጋ፣ “ጌታ መልአኩን
ልኮ ከሄሮድስ እጅና አይሁድ ካሰቡብኝ
ሁሉ እንዳወጣኝ አሁን ያለ ጥርጥር ዐወ
ቅሁ” አለ።

12ይህን ከተረዳ በኋላም፣ ብዙ ሰዎች
ተሰብስበው በአንድነት ወደሚጸልዩበት፣
ማርቆስ ወደ ተባለው ወደ ዮሐንስ እናት
ወደ ማርያም ቤት ሄደ። 13እዚያ ደርሶ
የውጭውን በር ባንኳኳ ጊዜ፣ ሮዳ የተ
ባለች አንዲት የቤት ሠራተኛ ማን እንደ
ሆነ ለማጣራት ወደ በሩ ሄደች። 14የጴጥ
ሮስ ድምፅ መሆኑንም ባወቀች ጊዜ፣
በጣም ከመደሰቷ የተነሣ በሩን ሳትከፍት
ሮጣ በመመለስ፣ ጴጥሮስ በሩ ላይ ቆሞ
እንደሚገኝ ተናገረች።

15ሰዎቹም፣ “አብደሻል እንዴ” አሏት፤
እርሷ ግን ይህንኑ ደጋግማ በነገረቻቸው
ጊዜ፣ “እንግዲያውስ የእርሱ መልአክ
ነው” አሉ።

16ጴጥሮስ ግን በር ማንኳኳቱን ቀጠለ፤
እነርሱም በሩን ከፍተው ባዩት ጊዜ ተገ
ረሙ። 17እርሱም ዝም እንዲሉ በእጁ ጠቅሶ፣
ጌታ ከእስር ቤት እንዴት እንዳወጣው
አስረዳቸው፣ “ስለ ሁኔታው ለያዕቆብና
ለወንድሞች ንገሯቸው” አላቸው፤ ከዚያም
ወደ ሌላ ስፍራ ሄደ።

18በማግስቱም ጠዋት ወታደሮቹ፣ “ጴጥ
ሮስ የት ገባ?” እያሉ በመካከላቸው ትልቅ
ትርምስ ተፈጠረ። 19ሄሮድስም ጴጥሮስን
አስፈልጎ ባጣው ጊዜ፣ ዘብ ጠባቂዎቹን
በጥብቅ ከመረመረ በኋላ እንዲገደሉ
አዘዘ።

### የሄሮድስ አሟሟት

ከዚያም ሄሮድስ ከይሁዳ ወደ ቂሳርያ
ወርዶ እዚያ ተቀመጠ። 20እርሱም ከጢ
ሮስና ከሲዶና ሰዎች ጋር ጥለኛ ነበር፤
አገራቸው ምግብ የሚያገኘው ከንጉሡ
ግዛት ስለ ነበር፣ የንጉሡን ባለሟል የብ

12፥9 ሐሥ9፥10
12፥10 ሐሥ5፥19፤ 16፥26
12፥11 መዝ34፥7፤ ዳን3፥28፤6፥22፤ሉቃ15፥17፤2ቆሮ1፥10፤ 2ጴጥ2፥9
12፥12 ቈ5፡25፤ ሐሥ 13፥5፡13፤ 15፥37፡39፤ ቈላ4፥10፤ 2ጢሞ 4፥11፤ፊሞ24፤ 1ጴጥ 5፥13
12፥13 ዮሐ18፥16፡ 17
12፥14 ሉቃ24፥41
12፥15 ማቴ18፥10
12፥17 ሐሥ1፥16፤ 13፥16፤15፥13፤19፥33፤ 21፥40
12፥19 ሐሥ8፥40፤ 16፥27
12፥20 1ነገ5፥9፡ 11፤ሕዝ27፥17፤ ማቴ 11፥21
12፥23 1ሳሙ25፥ 38፤ 2ሳሙ24፥16፡ 17፤2ነገ19፥35፤ ሐሥ 5፥19
12፥24 ሐሥ6፥7፤ 19፥20፤ዕብ4፥12
12፥25 ቈ12፤ሐሥ 4፥36፤11፥30
13፥1 ማቴ14፥1፤ 27፥32፤ሐሥ4፥36፤ 11፥19፡27፤ኤፌ4፥11
13፥2 ሐሥ8፥29፤ 9፥15፤14፥26፤22፥21
13፥3 ሐሥ6፥6፤ 14፥26
13፥4 ቈ2፡3፤4፥36
13፥5 ሐሥ9፥20፤ 12፥12፤ ዕብ4፥12
13፥6 ማቴ7፥15፤ ሐሥ8፥9
13፥7 ቈ8፡12፤ ሐሥ 18፥12፤19፥38
13፥8 ቈ7፤ ኢሳ 30፥11፤ ሐሥ6፥7፤ 8፥9
13፥9 ሉቃ1፥15
13፥10 ሆሴ14፥9፤ ማቴ13፥38፤ ዮሐ8፥44

ላስጠስን ድጋፍ ካገኙ በኋላ፣ አንድ ላይ
ሆነው ከንጉሡ ጋር ለመታረቅ ጠየቁ።
21በቀጠሮውም ቀን ሄሮድስ ልብሰ
መንግሥቱን ለብሶ በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ፤
ለሕዝቡም ንግግር አደረገ። 22ሕዝቡም፣
“ይህስ የአምላክ ድምፅ እንጂ የሰው አይ
ደለምኔ” ብለው ጮኹ። ሄሮድስም ለእግዚ
አ ብሔር ክብር ስላልሰጠ የጌታ መልአክ
ወዲያው መታው፤ በትልም ተበልቶ
ሞተ።

24የእግዚአብሔር ቃል ግን እያደገና እየ
ሰፋ ሄደ።

25በርናባስና ሳውልም ተልእኮአቸውን
ፈጽመው ከኢየሩሳሌም" ተመለሱ፤ ማር
ቆስ የተባለውን ዮሐንስንም ከእነርሱ ጋር
ይዘውት መጡ።

### በርናባስና ሳውል ተላኩ

13 በአንጾኪያ ባለችው ቤተ ክርስቲያን
ነቢያትና መምህራን ነበሩ፤ እነር
ሱም፦ በርናባስ፣ ኔጌር የተባለው ስምዖን፣
የቀሬናው ሉክዮስ፣ የአራተኛው ክፍል
ገዥ የሄሮድስ አብሮ አደግ የነበረው
ምናሔና ሳውል ነበሩ። 2እነዚህም ጌታን
እያመለኩና እየጾሙ ሳሉ፣ መንፈስ
ቅዱስ፣ “በርናባስንና ሳውልን እኔ ለጠራኋ
ቸው ሥራ ለዩልኝ” አለ። 3እነርሱም ከጾ
ሙና ከጸለዩ በኋላ እጃቸውን ጭነው አሰ
ናበቷቸው።

### በርናባስና ሳውል በቆጵሮስ

4በርናባስና ሳውልም በመንፈስ ቅዱስ
ተልከው ወደ ሴሌውቅያ ወረዱ፤ ከዚያም
በመርከብ ወደ ቆጵሮስ ሄዱ። 5ስልማና
በደረሱም ጊዜ በአይሁድ ምኵራቦች የእ
ግዚአብሔርን ቃል ሰበኩ፤ ዮሐንስም አብ
ሮአቸው ሆኖ ይረዳቸው ነበር።

6የቆጵሮስን ደሴት ከዳር እስከ ዳር አቋ
ርጠው ጳፉ በደረሱ ጊዜ፣ በርያሱስ የተ
ባለ አንድ አይሁዳዊ ጠንቋይና ሐሰተኛ
ነቢይ አገኙ፤ 7እርሱም ሰርግዮስ ጳውሎስ
ከተባለው አስተዋይ አገረ ገዥ ጋር ነበረ።
ይህ አገረ ገዥ፣ የእግዚአብሔርን ቃል
ለመስማት ፈልጎ በርናባስንና ሳውልን
አስጠራቸው። 8ጠንቋዩ ኤልማስ ግን፣
የስሙ ትርጒም እንዲህ ነበርና፣ አገረ ገ
ዡ እን ዳያምን ለማደናቀፍ ስለ ፈለገ
ተቃወማ ቸው። 9ጳውሎስ የተባለውም
ሳውል በመ ንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ፣
ትኵር ብሎ ተመ ለከተውና እንዲህ
አለው፤ 10“አንተ የጽድቅ ሁሉ ጠላት፣
ተንኰልንና ክፋትን ሁሉ የተሞላህ የዲ
ያብሎስ ልጅ፤ የጌታን ቀና

"25 አንዳንድ ቅጆች ወደ ኢየሩሳሌም ይላሉ።

መንገድ ከማጣመም አታርፍምን? 11አሁ
ንም የጌታ እጅ በአንተ ላይ ነው፤ ዕውር
ትሆናለህ፤ ከእንግዲህ የፀሓይን ብርሃን
ለአንድ አፍታ እንኳ አታይም።”

ወዲያውም ጭጋግና ጨለማ በላዩ
ወረደ፤ እጁን ይዞ የሚመራውንም ሰው
ለመፈለግ ወዲያ ወዲህ ይል ጀመር።
12አገረ ገዡም የሆነውን ነገር ባየ ጊዜ፣
በጌታ ትምህርት በመደነቅ አመነ።

## በርናባስና ጳውሎስ በጲስድያ

13ጳውሎስና ጓደኞቹ ከጳፉ ተነሥተው
በጵንፍልያ ወደምትገኘው ወደ ጴርጌን
ሄዱ፤ ዮሐንስም ከእነርሱ ተለይቶ ወደ ኢየ
ሩሳሌም ተመለሰ። 14እነርሱ ግን ከጴርጌን
ተነሥተው በጲስድያ ውስጥ ወዳለችው
ወደ አንጾኪያ ሄዱ፤ በሰንበት ቀንም ወደ
ምኵራብ ገብተው ተቀመጡ። 15የሕግና
የነቢያት መጻሕፍት ከተነበቡ በኋላ፣ የም
ኵራብ አለቆች፣ “ወንድሞች ሆይ፤ ሕዝ
ቡን የሚመክር ቃል ካላችሁ ተናገሩ” ሲሉ
ላኩባቸው።

16ጳውሎስም ተነሥቶ በእጁ በመጥቀስ
እንዲህ አለ፤ “የእስራኤል ሰዎች ሆይ፤
ደግሞም እናንተ እግዚአብሔርን የምትፈሩ
ሁሉ፤ አድምጡ። 17የዚህ የእስራኤል ሕዝብ
አምላክ፣ አባቶቻችንን መረጣቸው፤ በግብፅ
ምድር እያሉም ከፍ ከፍ አደረጋቸው፤
በኀያል ክንዱም ከዚያ አወጣቸው። 18አርባ
ዓመት ያህልም በበረሓ ታገሣቸው[ፕ]፤
19በከነዓን ምድር የነበሩትንም ሰባት መንግ
ሥታት አጥፍቶ፣ ምድራቸውን ለገዛ ሕዝቡ
ርስት አድርጎ አወረሳቸው። 20ይህም ሁሉ
የተፈጸመው በአራት መቶ አምሳ ዓመት
ያህል ጊዜ ውስጥ ነበር።

“ከዚህ በኋላ፣ እስከ ነቢዩ ሳሙኤል
ዘመን ድረስ መሳፍንትን ሰጣቸው። 21ከዚ
ያም ሕዝቡ ንጉሥ እንዲያነግሥላቸው
ለመኑት፤ እግዚአብሔርም ከብንያም ወገን፣
የቂስን ልጅ ሳኦልን ሰጣቸው፤ እርሱም
አርባ ዓመት ገዛቸው። 22ሳኦልንም ከሻ
ረው በኋላ፣ ዳዊትን አነገሣቸው፤ ስለ
እርሱም፣ ‘እንደ ልቤ የሆነና እኔ የምሻ
ውን ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊ
ትን አገኘሁ’ ሲል መሰከረለት።

23እግዚአብሔርም በገባው ቃል መሠረት
ከዚህ ሰው ዘር አዳኝ የሆነውን ኢየሱስን
ለእስራኤል አመጣ። 24ኢየሱስ ከመምጣቱ
በፊት፣ ዮሐንስ የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ
ንስሓ ገብተው እንዲጠመቁ ሰብኮላቸው
ነበር። 25ዮሐንስ ተልእኮውን በማጠናቀቅ
ላይ ሳለ፣ ‘እኔ ማን መሰልኋችሁ? እኔ
እኮ እርሱ አይደለሁም፤ ነገር ግን የእግሩን
ጫማ እንኳ መፍታት የማይገባ ከእኔ
በኋላ ይመጣል’ ይል ነበር።

26“እናንት ከአብርሃም ዘር የተወለዳችሁ
ወንድሞች፤ ደግሞም በመካከላችሁ እግዚአ
ብሔርን የሚፈሩ ሁሉ፤ ይህ የድነት መልእ
ክት የተላከው ለሁላችንም ነው። 27የኢየሩ
ሳሌም ሰዎችና አለቆቻቸው ኢየሱስን አላ
ወቁትም፤ ይሁን እንጂ በየሰንበቱ የሚነ
በበው የነቢያት ቃል እንዲፈጸም በእርሱ
ፈረዱበት። 28ለሞት የሚያበቃው አንድም
ምክንያት ባያገኙበትም እንኳ ጲላጦስ
የሞት ፍርድ እንዲፈርድበት ተማጸኑት።
29ስለ እርሱ የተጻፈውን ሁሉ ከፈጸሙ
በኋላ ከተሰቀለበት ዕንጨት አውርደው
በመቃብር ውስጥ አስገቡት። 30እግዚአብሔር
ግን ከሙታን አስነሣው። 31ከገሊላ ጀምሮ
እስከ ኢየሩሳሌም ከእነርሱ ጋር ለነበሩ
ትም ብዙ ቀን ታያቸው፤ እነርሱም አሁን
ለሕዝቡ ምስክሮቹ ናቸው።

32“እኛም እግዚአብሔር ለአባቶች ቃል
የገባውን የምሥራች ቃል ለእናንተ እንሰ
ብካለን፤ 33ኢየሱስንም ከሙታን በማስነሣቱ
ለእነርሱ የገባውን ቃል ለእኛ ለልጆቻ
ቸው ፈጽሞአል፤ ይኸውም በሁለተኛው
መዝሙር እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፤

“ ‘አንተ ልጄ ነህ፤
እኔ ዛሬ ወለድሁህ።’[የ]

34ደግሞም፣ እርሱ እንዳልበሰበሰና እግዚ
አብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው ለማረጋ
ገጥ እንዲህ ብሎአል፤

“ ‘የተቀደሰውንና የታመነውን፣
የዳዊትን በረከት እሰጣችኋለሁ።’

35ስለዚህ በሌላም ስፍራ፣

“ ‘ቅዱስህ መበስበስን እንዲያይ
አትፈቅድም’ ይላል።

36“ዳዊት በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን
ፈቃድ ካገለገለ በኋላ አንቀላፍቶአል፤ ከአ
ባቶቹም ጋር ተቀብሮ ሥጋው በስብሶአል።
37እግዚአብሔር ከሙታን ያስነሣው እርሱ
ግን መበስበስን አላየም።

38እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ የኀጢ
አት ይቅርታ የሚገኘው በኢየሱስ በኩል
መሆኑ እንደ ተሰበከላችሁ ዕወቁ፤ 39በእ
ርሱ የሚያምን ሁሉ በሙሴ ሕግ በኩል
ማግኘት ያልተቻለውን ጽድቅ ያገኛል።
40ስለዚህ ነቢያት እንዲህ ብለው የተናገሩት
እንዳይደርስባችሁ ተጠንቀቁ፤

13፥11 ዘፍ19፥10፡11፤ዘፀ9፥3፤ 1ሳሙ5፥6፡7፤ 2ነገ6፥18፤ መዝ 32፥4
13፥12 ቀኍ7
13፥13 ቀኍ6፤ ሐሥ 2፥10፤12፥12
13፥14 ቀኍ27፡42፡44፤ሐሥ9፥20፤14፥19፡21፤16፥13፤18፥4
13፥15 ሐሥ15፥21
13፥16 ሐሥ12፥17
13፥17 ዘፀ6፥6፡7፤ ዘዳ7፥6-8
13፥18 ዘኍ14፥33፤ ዘዳ1፥31፤መዝ95፥10፤ ሐሥ7፥36
13፥19 ዘዳ7፥1፤ ኢሱ 19፥51፤ መዝ78፥55፤ ሐሥ7፥45
13፥20 መሳ2፥16፤ 1ሳሙ3፥19፡20፤ ሐሥ 3፥24
13፥21 1ሳሙ8፥5፡19፤9፥1፡2፤10፥1
13፥22 1ሳሙ13፥14፤ 15፥23፡26፤16፥13፤መዝ89፥20፤ኢሳ44፥28፤ኤር3፥15
13፥23 ቀኍ32፤ 2ሳሙ 7፥11፤ 22፥51፤ ኤር30፥9፤ ማቴ1፥1፡21፤ሉቃ2፥11
13፥24 ማር1፥4
13፥25 ማቴ3፥11፤ ዮሐ1፥20፡27፤ ሐሥ 20፥24
13፥26 ሉቃ3፥8፤ ሐሥ4፥12፤ 22፥5፤28፥28
13፥27 ማቴ1፥22፤ ሉቃ24፥27፤ሐሥ3፥17
13፥28 ማቴ27፥20-25፤ሐሥ3፥14
13፥29 ማቴ1፥22፤ ሉቃ18፥31፤23፥53፤ሐሥ5፥30
13፥30 ማቴ16፥21፤ 28፥6፤ሐሥ2፥24
13፥31 ማቴ28፥16፤ ሉቃ24፥48
13፥32 ኢሳ40፥9፤ 52፥7፤ሐሥ5፥42፤ 8፥35፤10፥36፤14፥7፡15፡21፤17፥18፤26፥6፤ ሮሜ1፥2፤4፥13፤9፥4
13፥33 መዝ2፥7፤ ማቴ3፥17፤ሐሥ2፥24
13፥34 ኢሳ55፥3
13፥35 መዝ16፥10፤ሐሥ2፥27
13፥36 2ሳሙ7፥12፤1ነገ2፥10፤2ዜና 29፥28፤ ማቴ9፥24፤ ሐሥ2፥29
13፥37 ሐሥ2፥24
13፥41 ዕን1፥5
13፥42 ቀኍ14
13፥43 ሐሥ11፥23፤ 14፥22፤ሮሜ3፥24

13፥38 ሉቃ24፥47፤ሐሥ2፥38 13፥39 ዮሐ3፥15፤ ሮሜ3፥28

[ፕ]18 አንዳንድ ቅጆች *ተንከባከባቸውም* ይላሉ።
[የ]33 ወይም *አባትህ ሆንሁ*

41“ ‘እናንት ፌዘኞች፤ ተመልከቱ፤
ተደነቁ፤ ጥፉም፤
ማንም ቢነግራችሁ፣
የማታምኑትን ሥራ፣
እኔ በዘመናችሁ እሠራለሁና።” ’

42ጳውሎስና በርናባስ ከምኵራብ ሲወጡ፣
ሰዎቹ ስለዚሁ ነገር በሚቀጥለው ሰንበት
እንዲነግሯቸው ለመኗቸው። 43ጉባኤው
ከተበተነ በኋላም፣ ብዙ አይሁድና ወደ
ይሁዲ ሃይማኖት ገብተው በመንፈሳዊ
ነገር የበረቱ ሰዎች፣ ጳውሎስንና በርናባ
ስን ተከተሏቸው፤ እነርሱም አነጋግሯቸው፤
በእግዚአብሔርም ጸጋ ጸንተው እንዲኖሩ
መከሯቸው።

44በሚቀጥለውም ሰንበት የከተማው ሕዝብ፣
ጥቂቱ ሰው ብቻ ሲቀር፣ በሙሉ የእግዚአ
ብሔርን ቃል ለመስማት ተሰበሰቡ።
45አይ ሁድም ብዙ ሕዝብ ባዩ ጊዜ፣ በቅናት
ተሞሉ፤ የጳውሎስንም ንግግር እየተቃወሙ
ይሰድ ቡት ነበር።

46ጳውሎስና በርናባስም በድፍረት እንዲህ
አሏቸው፤ “የእግዚአብሔር ቃል በመጀመሪያ
ለእናንተ መነገር አለበት፤ እናንተ ግን
ናቃችሁት፤ በዚህም የዘላለም ሕይወት
እንደማይገባችሁ በራሳችሁ ላይ ስለ ፈረዳ
ችሁ፣ እኛም ወደ አሕዛብ ዞር ለማለት
እንገደዳለን። 47ደግሞም ጌታ እንዲህ ብሎ
አዞናል፤

“ ‘ድነትን እስከ ምድር ዳርቻ ታደርስ
ዘንድ፣[ደ]
ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌሃለሁ።’ ”

48አሕዛብ ይህን በሰሙ ጊዜ ደስ አላቸው፤
ለእግዚአብሔርም ቃል ክብርን ሰጡ፤ ለዘላ
ለም ሕይወት የተዘጋጁትም ሁሉ አመኑ።
49የጌታም ቃል በአካባቢው ባለው አገር
ሁሉ ተስፋፋ። 50አይሁድ ግን በመንፈሳዊ
ነገር የተጉትንና በኑሮ የከበሩትን ሴቶች
እንዲሁም የከተማውን ታላላቅ ወንዶች
ቀስቅሰው በጳውሎስና በበርናባስ ላይ ስደ
ትን አስነሡ፤ ከአገራቸውም አስወጧቸው።
51ጳውሎስና በርናባስም ተቃውሞአቸውን
ለመግለጽ የእግራቸውን ትቢያ አራግፈው
ወደ ኢቆንዮን ሄዱ። 52ደቀ መዛሙርቱም
በደስታና በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ።

## ጳውሎስና በርናባስ በኢቆንዮን

14 በኢቆንዮንም ጳውሎስና በርናባስ
አብረው ወደ አይሁድ ምኵራብ
ገቡ፤ በዚያም በሚገባ ስላስተማሩ፣ ከአይ
ሁድም ከግሪክም እጅግ ብዙ ሰዎች አመኑ።
2ያላመኑት አይሁድ ግን፣ አሕዛብን አነሣ
ሥተው ወንድሞችን እንዲጠሉ አደረጓ
ቸው። 3ጳውሎስና በርናባስም ስለ ጌታ
በድፍረት እየተናገሩ ብዙ ጊዜ እዚያው
ቈዩ፤ ጌታም የሚናገሩትን የጸጋውን ቃል
በታምራዊ ምልክትና በድንቅ ሥራ እየደ
ገፈ ያረጋግጥላቸው ነበር። 4የከተማ
ውም ሕዝብ ተከፋፈለ፤ ገሚሱ ከአይሁድ
ጋር፣ ገሚሱም ከሐዋርያት ጋር ሆነ።
5በዚህ ጊዜ አሕዛብና አይሁድ ከመሪዎቻ
ቸው ጋር ተባብረው ሊያንገላቷቸውና
በድንጋይ ሊያስወግሯቸው ሞከሩ። 6እነ
ርሱ ግን ይህን እንዳወቁ ልስጥራንና ደር
ቤን ወደተባሉት ወደ ሊቃኦንያ ከተሞ
ችና በዙሪያቸው ወዳለው አገር ሸሹ፤ 7በዚ
ያም ወንጌልን መስበክ ቀጠሉ።

## ጳውሎስና በርናባስ በልስጥራና በደርቤ

8በልስጥራንም፣ እግሩ አንካሳ የሆነና
ከተወለደ ጀምሮ ፈጽሞ በእግሩ ሄዶ የማ
ያውቅ ሽባ ሰው ተቀምጦ ነበር። 9ይህም
ሰው ጳውሎስ ሲናገር ያደምጥ ነበር።
ጳውሎስም ወደ እርሱ ትኵር ብሎ ተመ
ለከተና ለመዳን እምነት እንዳለው ባየ ጊዜ
በታላቅ ድምፅ “ቀጥ ብለህ በእግርህ ቁም!”
አለው፤ በዚህ ጊዜ ዘሎ ተነሣና መራመድ
ጀመረ።

11ሕዝቡም ጳውሎስ ያደረገውን ባዩ ጊዜ፣
በሊቃኦንያ ቋንቋ፣ “አማልክት በሰው
ተመስለው ወደ እኛ ወርደዋል!” ብለው
ጮኹ፤ 12በርናባስን ‘ድያ’ አሉት፤ ጳው
ሎስም ዋና ተናጋሪ ስለ ነበር ‘ሄርሜን’
አሉት። 13ከከተማው ወጣ ብሎ የነበረው፣
የድያ ቤተ መቅደስ ካህንም ኰርማዎች
ንና የአበባ ጕንጕኖችን ወደ ከተማው
መግቢያ አምጥቶ፣ ከሕዝቡ ጋር ሆኖ ሊሠ
ዋላቸው ፈለገ።

14ሐዋርያቱ በርናባስና ጳውሎስ ይህን
በሰሙ ጊዜ ልብሳቸውን ቀደው ወደ ሕዝቡ
መካከል ሮጡ፤ ድምፃቸውንም ከፍ አድ
ርገው እንዲህ አሉ፤ 15“እናንት ሰዎች፤
ለምን ይህን ታደርጋላችሁ? እኛም እኮ
እንደ እናንተው ሰዎች ነን። እናንተም
ደግሞ ከዚህ ከንቱ ነገር ርቃችሁ ሰማይ
ንና ምድርን፣ ባሕርንም በውስጣቸውም
የሚኖሩትን ሁሉ ወደ ፈጠረ ወደ ሕያው
እግዚአብሔር እንድትመለሱ ወንጌልን እንሰ
ብክላችኋለን። 16እርሱ ባለፉት ትውል
ዶች፣ ሕዝቦች ሁሉ በገዛ መንገዳቸው እን
ዲሄዱ ተዋቸው፤ 17ይሁን እንጂ ዝናብን
ከሰማይ እንዲሁም ፍሬያማ ወቅቶችን
በመስጠት፣ ደግሞም ልባችሁን በመብልና
በደስታ በማርካቱ መልካምን በማድረግ ራሱን

13፥45 ሐሥ18፥6፤ 1ተሰ2፥16፤ 1ጴጥ4፥4፤ይሁ10
13፥46 ቍ26፤ ማቴ21፥41፤ ሐሥ3፥26፤ 18፥6፤22፥21፤ 26፥20፤ 28፥28፤ ሮሜ11፥11
13፥47 ኢሳ49፥6፤ ሉቃ2፥32
13፥48 ቍ49፤ሐሥ 8፥25፤15፥35፡36፤ 19፥10፡20
13፥49 ቍ48
13፥50 1ተሰ2፥16
13፥51 ማቴ10፥14፤ ሐሥ14፥1፡19፡21፤ 16፥2፤2ጢሞ3፥11
13፥52 ሉቃ1፥15፤ ሐሥ11፥26
14፥1 ሐሥ2፥41፤ 9፥20፤13፥51
14፥2 ሐሥ1፥16
14፥3 ዮሐ4፥48፤ ሐሥ4፥29
14፥4 ሐሥ17፥4፡ 5፤28፥24
14፥5 ቍ19፤ሐሥ 20፥3
14፥6 ማቴ10፥23
14፥7 ቍ15፡21፤ ሐሥ13፥32፤16፥10
14፥8 ሐሥ3፥2
14፥9 ማቴ9፥28፡ 29፤13፥58
14፥10 ሕዝ2፥1፤ ሐሥ3፥8
14፥11 ሐሥ8፥10፤ 28፥6
14፥12 ዘፀ7፥1
14፥14 ማር14፥63
14፥15 ቍ7፡21፤ ዘፍ1፥1፤1ሳሙ12፥21፤ መዝ146፥6፤ማቴ16፥ 16፤ሐሥ10፥26፤13፥ 32፤1ተሰ1፥9፤ራእ 14፥7
14፥16 መዝ81፥12፤ ሚክ4፥5፤ሐሥ17፥30
14፥17 ዘዳ11፥14፤ ኢዮ5፥10፤መዝ4፥7፤ 65፥10፤ሮሜ1፥20

[ደ]47 ታደርስ ዘንድ የሚለው በግሪኩ ነጠላ ቍጥር ነው።

ያለ ምስክር አልተወም::” [18]ይህን ሁሉ
ተናግረው እንኳ፣ ሕዝቡ እንዳይሠዋላቸው
ያስተዉት በብዙ ችግር ነበር::
[19]አይሁድ ግን ከአንጾኪያና ከኢቆንዮን
መጥተው፣ ሕዝቡን አግባቡ፤ ጳውሎስንም
በድንጋይ ከወገሩት በኋላ፣ የሞተ መስሎ
አቸው ጐትተው ከከተማው ወደ ውጭ
አወጡት:: [20]ሆኖም ደቀ መዛሙርት ከበ
ውት እንዳሉ ተነሣ፤ ወደ ከተማም ገባ::
በማግስቱም ከበርናባስ ጋር ወደ ደርቤን
ሄዱ::

### ጳውሎስና በርናባስ በሶርያ ወዳለችው አንጾኪያ ተመለሱ

[21]ጳውሎስና በርናባስ በደርቤን የምሥራ
ቹን ቃል ሰብከው፣ ብዙ ደቀ መዛሙር
ትም ካፈሩ በኋላ፣ ወደ ልስጥራን፣ ወደ
ኢቆንዮንና ወደ አንጾኪያ ተመለሱ::
[22]የደቀ መዛሙርቱንም ልብ በማበረታ
ታትና በእምነታቸው ጸንተው እንዲኖሩ
በመምከር፣ “ወደ እግዚአብሔር መንግሥት
ለመግባት በብዙ መከራ ማለፍ አለብን”
አሏቸው:: [23]ከዚያም በየአብያተ ክርስቲ
ያናቱ ሽማግሌዎችን ከሾሙላቸው በኋላ፣
በጾምና በጸሎት ላመኑበት ጌታ ዐደራ
ሰጧቸው:: [24]በጲስድያም ዐልፈው ወደ
ጵንፍልያ መጡ፤ [25]በጴርጌንም ቃሉን ከሰ
በኩ በኋላ፣ ወደ አጣልያ ወረዱ::
[26]ከአጣልያም፣ እስካሁን ላከናወኑት ሥራ
፣ ለእግዚአብሔር ጸጋ በዐደራ ወደ ተሰጠ
ባት ከተማ ወደ አንጾኪያ በመርከብ
ተመለሱ:: [27]እዚያም በደረሱ ጊዜ፣ ቤተ
ክርስቲያንን በአንድነት ሰብስበው፣ እግዚ
አብሔር በእነርሱ አማካይነት ያደረገውን
ሁሉ፣ ደግሞም ለአሕዛብ እንዴት
የእምነትን በር እንደ ከፈተላቸው ተናገሩ
:: [28]በዚያም ከደቀ መዛሙርት ጋር ብዙ
ጊዜ ተቀመጡ::

### የኢየሩሳሌም ጉባኤ

15 አንዳንድ ሰዎችም ከይሁዳ ወደ
አንጾኪያ ወርደው፣“በሙሴ ሥር
ዐት መሠረት ካልተገረዛችሁ ልትድኑ
አትችሉም” በማለት ወንድሞችን ማስተ
ማር ጀመሩ:: [2]ይህም ጳውሎስንና በርናባ
ስን ከእነርሱ ጋር ወደ ከረረ ጠብና ክር
ክር ውስጥ ከተታቸው:: ስለዚህ ጳውሎስና
በርናባስ ከሌሎች አንዳንድ ምእምናን ጋር
ወደ ኢየሩሳሌም ወጥተው ስለዚሁ ጒዳይ
ሐዋርያትንና ሽማግሌዎችን እንዲጠይቁ
ተወሰነ:: [3]ቤተ ክርስቲያኒቱም እግረ
መንገዳቸውን በፊንቄና በሰማርያ በኩል እን
ዲያልፉ ላከቻቸው፤ እነርሱም በእነዚህ
ቦታዎች ለነበሩት የአሕዛብን መመለስና
ማመን ነገሯቸው፤ ወንድሞችም ሁሉ በዚህ
እጅግ ደስ አላቸው:: [4]ኢየሩሳሌም በደረሱ
ጊዜም፣ ቤተ ክርስቲያንና ሐዋር ያት
እንዲሁም ሽማግሌዎች ተቀበሏቸው፤ የተ
ላኩትም እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ሆኖ የሠ
ራውን ሁሉ ነገሯቸው::
[5]ከፈሪሳውያን ወገን ያመኑት አንዳንዶቸ
ተነሥተው በመቆም፣ “አሕዛብ እንዲገረ
ዙና የሙሴን ሕግ እንዲጠብቁ ማድረግ
አስፈላጊ ነው” አሉ::
[6]ሐዋርያትና ሽማግሌዎችም ይህንኑ
ጒዳይ ለማጤን ተሰበሰቡ:: [7]ከብዙ ክርክር
በኋላ ጴጥሮስ ተነሥቶ እንዲህ አላቸው፤
“ወንድሞች ሆይ፤ እግዚአብሔር ከጥቂት ጊዜ
በፊት በእናንተ መካከል እኔን መርጦ፣
አሕዛብ የወንጌልን ቃል ከእኔ አንደበት
ሰምተው እንዲያምኑ ማድረጉን ታው
ቃላችሁ:: [8]ልብን የሚያውቅ አምላክ
ለእኛ እንደ ሰጠን ሁሉ፣ ለእነርሱም
መንፈስ ቅዱስን በመስጠት የተቀበላቸው
መሆ ኑን መሰከረላቸው፤ [9]ልባቸውንም
በእም ነት በማንጻት በእኛና በእነርሱ
መካከል ምንም ልዩነት አላደረገም::
[10]እንግዲህ፣ አባቶቻችንም እኛም
ልንሸከመው ያልቻ ልነውን ቀንበር በደቀ
መዛሙርት ጫንቃ ላይ በመጫን ለምን
አሁን እግዚአብሔርን ትፈታተኑታላችሁ?
[11]እኛም የዳንነው ልክ እንደ እነርሱ
በጌታ በኢየሱስ ጸጋ መሆ ኑን
እናምናለን::”
[12]ጉባኤውም በሙሉ ዝም ብሎ፣ በር
ናባስና ጳውሎስ እግዚአብሔር በእነርሱ አማ
ካይነት በአሕዛብ መካከል ስላደረጋቸው
ታምራዊ ምልክቶችና ድንቅ ነገሮች ሲና
ገሩ ያዳምጣቸው ነበር:: [13]እነርሱም ተናግ
ረው ሲጨርሱ፣ ያዕቆብ ተነሥቶ በመቆም
እንዲህ አለ፤ “ወንድሞች ሆይ፤ ስሙኝ፤
[14]እግዚአብሔር ከአሕዛብ ወገን ለእርሱ የሚ
ሆነውን ሕዝብ አስቀድሞ እንዴት እንደ
ጐበኘ ስምዖን[ጀ] አስረድቶናል:: [15]እንዲህ
ተብሎ የተጻፈው የነቢያቱም ቃል ከዚህ
ጋር ይስማማል፤

[16]“ ‘ከዚህ በኋላ እመለሳለሁ፤
የፈረሰውን የዳዊትን ቤት እገነባለሁ::
ፍርስራሹን መልሼ አቆማለሁ፤
እንደ ገናም እሠራዋለሁ፤
[17]ይኸውም የቀሩት ሰዎች ጌታን እንዲ
ፈልጉ፣
ስሜን የተሸከሙ አሕዛብም እንዲሹኝ
ነው፤
እነዚህን ያደረገ ጌታ እንዲህ ይላል፤’

14፥19 ሐሥ13፥45፡ 51፤ 2ቆሮ11፥25፤ 2ጢሞ 3፥11
14፥20 ቍ22፡28፤ ሐሥ11፥26
14፥21 ሐሥ2፥41፤ 13፥32፡51
14፥22 ዮሐ16፥33፤ ሐሥ11፥23፤13፥43፤ 1ተሰ3፥3፤ 2ጢሞ 3፥12
14፥23 ሐሥ11፥ 30፤13፥3፤20፥32
14፥24 ሐሥ2፥10
14፥26 ሐሥ11፥ 19፡23፤13፥1፡3
14፥27 ሐሥ15፥4፡ 12፤21፥19፤1ቆሮ16፥9 ፤2ቆሮ2፥12፤ ቈላ4፥ 3፤ራእ3፥8
14፥28 ሐሥ11፥26
15፥1 ቍ5፡24፤ ሐሥ 1፥16፤6፥14፤ ገላ2፥12፤5፥2፡3
15፥2 ሐሥ11፥30፤ ገላ2፥2
15፥3 ሐሥ11፥19፤ 14፥27
15፥4 ቍ12፤ ሐሥ 14፥27፤21፥19
15፥5 ቍ1፤ ማቴ3፥ 7፤ሐሥ5፥17
15፥7 ሐሥ10፥1-48
15፥8 ሐሥ10፥44፡ 47፤ራእ2፥23
15፥9 ሐሥ10፥28፡ 34፡43፤11፥12
15፥10 ማቴ23፥4፤ ሐሥ5፥9፤ገላ5፥1
15፥11 ሮሜ3፥24፤ ገላ2፥16፤ኤፌ2፥5-8
15፥12 ቍ4፤ዮሐ4፥ 48፤ሐሥ14፡27፤ 21፥19
15፥13 ሐሥ12፥17፤ 21፥18፤1ቆሮ15፥7፤ ገላ1፥19፤2፥9፡12
15፥14 2ጴጥ1፥1
15፥17 አሞ9፥11፡ 12

[ጀ]14 እርሱም ጴጥሮስ ነው::

18እነርሱም ከጥንት ጀምሮ የታወቁ
ናቸው::[7]

19"ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር የተመለሱትን
አሕዛብ እንዳናስጨንቃቸው ይህ የእኔ
ውሳኔ ነው::
20ይልቁን በጣዖት ከረከሰ ነገር፣ ከዝ
ሙት ርኵሰት፣ ታንቆ የሞተ እንስሳ
ሥጋ ከመብላትና ደም ከመመገብ እንዲ
ርቁ ልንጽፍላቸው ይገባል፤ 21የሙሴ ሕግማ
ከጥንት ጀምሮ በየሰንበቱ በምኵራብ ሲነ
በብና በየከተማው ሲሰበክ ኖሮአልና::"

### ላመኑት አሕዛብ ከጉባኤው የተላከ ደብዳቤ

22በዚህ ጊዜ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች
ከመላው ቤተ ክርስቲያን ጋር ሆነው ከመ
ካከላቸው አንዳንድ ሰዎችን መርጠው፣
ከጳውሎስና ከበርንባስ ጋር ወደ አንጾኪያ
ለመላክ ወሰኑ፤ ከወንድሞችም መካከል
ዋነኛ የነበሩትን በርስያን የተባለውን ይሁ
ዳንና ሲላስን መረጡ፤ 23በእነርሱም እጅ
ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ላኩ፤
ወንድሞቻችሁ ከሆኑት ከሐዋርያትና
ከሽማግሌዎች፤

ከአሕዛብ ወገን አምነው በአንጾኪያ፣
በሶሪያና በኪልቅያ ለሚገኙ ወንድሞች፤

ሰላምታችን ይድረሳችሁ::

24አንዳንድ ሰዎች ያለ እኛ ፈቃድ ከእኛ
ዘንድ ወጥተው በንግግራቸው ልባችሁን
እንዳወኩና እንዳናወጧችሁ ሰምተናል::
25ስለዚህ ጥቂት ሰዎች መርጠን ከተወዳ
ጆቹ ከበርናባስና ከጳውሎስ ጋር ወደ እና
ንተ ለመላክ ሁላችንም ተስማምተናል፤
26በርናባስና ጳውሎስም ስለ ጌታችን ስለ
ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሕይወታቸውን አሳ
ልፈው የሰጡ ናቸው:: 27ስለዚህ እኛ የጻ
ፍነውን በቃል እንዲያረጋግጡላችሁ፣
እነሆ፤ ይሁዳንና ሲላስን ልከናል:: 28ከእነዚህ
አስፈላጊ ነገሮች በስተቀር ሌላ ተጨማሪ
ሸክም እንዳንጭንባችሁ፣ ለመንፈስ ቅዱ
ስም ለእኛም መልካም መስሎ ታይቶናል፤
ይኸውም:- 29ለጣዖት ከተሠዋ ነገር፣ ከደም፣
ታንቆ ከሞተ እንስሳ ሥጋ እንዲሁም ከዝ
ሙት ርኵሰት እንድትርቁ ነው:: ከእነዚህ
ዐይነት ነገሮች ብትርቁ ለእናንተ መል
ካም ነው::

ደኅና ሁኑ::

30የተላኩትም ሰዎች ከተሰናበቱ በኋላ
ወደ አንጾኪያም ወረዱ፤ በዚያም የምእመ
ናኑን ጉባኤ በአንድነት ሰብስበው ደብዳቤ
ውን ሰጧቸው:: 31ሕዝቡም ካነበቡት በኋላ
አበረታታች በሆነው ቃሉ ደስ ተሰኙ::

15፥18 ኢሳ45፥21
15፥20 ቍ29፤ዘፍ 9፥4፤ዘሌ3፥17፤7፥26፤17፥10-13፤19፥26፤ዘዳ12፥16-23፤1ቆሮ 8፥7-13፤10፥7፡8፡14-28፤ራእ2፥14፡20
15፥21 ሐሥ13፥ 15፤ 2ቆሮ3፥14፡15
15፥22 ቍ27፡32፡40፤ሐሥ11፥19፡30፤16፥19፡25፡29፤2ቆሮ1፥19፤1ተሰ1፥1፤2ተሰ1፥1፤1ጴጥ5፥12
15፥23 ቍ1፡41፤ሉቃ2፥2፤ሐሥ6፥9፤11፥19፤23፥25፡26፤ያዕ1፥1
15፥24 ቍ1፤ ገላ 1፥7፤5፥10
15፥26 ሐሥ9፥23-25፤14፥19፤1ቆሮ15፥30
15፥27 ቍ22
15፥28 ሐሥ5፥32
15፥29 ቍ20፤ ሐሥ 21፥25
15፥32 ቍ22፤ ሐሥ 11፥27
15፥33 1ሳሙ1፥17፤ ማር5፥34፤ሉቃ7፥50፤ ሐሥ 16፥36፤ 1ቆሮ16፥11
15፥35 ሐሥ8፥4፤ 13፥48
15፥36 ሐሥ13፥4፡13፡14፡48፡51፤14፥1፡6፡24፡25
15፥37 ሐሥ12፥12
15፥38 ሐሥ13፥13
15፥40 ቍ22፤ ሐሥ 11፥23
15፥41 ቍ23፤ ሉቃ 2፥2፤ሐሥ6፥9፤16፥5
16፥1 ሐሥ14፥6፤ 1ቆሮ4፥17፤16፥10፤2ቆሮ1፥1፡19፤ፊል1፥1፤2፥19፤1ተሰ3፥2፡6፤1ጢሞ1፥2፡18፤ 2ጢሞ 1፥2፡5፡6
16፥2 ቍ40፤ ሐሥ 1፥16፤13፥51
16፥3 ገላ2፥3
16፥4 ሐሥ11፥30፤ 15፥2፡28፡29
16፥5 ሐሥ2፥41፤ 9፥31፤15፥41

32ይሁዳና ሲላስም ራሳቸው ነቢያት ስለ
ነበሩ፣ ወንድሞችን ብዙ ንግግር በማድረግ
መከሯቸው፤ አበረቷቸውም:: 33በዚያም
ጥቂት ጊዜ ከቈዩ በኋላ፣ ከወንድሞች በሰ
ላም ተሰናብተው ወደ ላኳቸው ሰዎች
ተመለሱ:: 34ሲላስ ግን እዚያው ለመቅረት
ወሰነ[m]:: 35ጳውሎስና በርናባስም ከሌሎች
ብዙ ሰዎች ጋር ሆነው የጌታን ቃል እያ
ስተማሩና እየሰበኩ በአንጾኪያ ተቀመጡ::

### ጳውሎስና በርናባስ በሐሳብ ተለያዩ

36ጳውሎስ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በርናባ
ስን፣ "ተነሣና የጌታን ቃል ወደ ሰበክን
ባቸው ከተሞች ሁሉ እንሂድ፤ በዚያ ያሉ
ወንድሞችም በምን ሁኔታ እንዳሉ ለማ
ወቅ እንጐብኛቸው" አለው:: 37በርናባስም
ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ አብሮአቸው
እንዲሄድ ፈለገ፤ 38ጳውሎስ ግን እርሱን
ይዞ ለመሄድ አልፈለገም፤ ምክንያቱም፣
ቀደም ሲል ማርቆስ ከእነርሱ ተለይቶ
በጵንፍልያ ስለ ቀረና ወደ ሥራ አብሮ
አቸው ስላልሄደ ነበር:: 39እንዲህ የከረረ
አለመግባባት በመካከላቸው ስለ ተፈጠረ
እርስ በርስ ተለያዩ፤ ስለዚህ በርናባስ
ማርቆስን ይዞ በመርከብ ወደ ቆጵሮስ
ሄደ:: 40ጳውሎስ ግን ሲላስን መረጠ፤ ወን
ድሞችም ለጌታ ጸጋ ዐደራ ከሰጡት በኋላ
ተለይቶአቸው ሄደ፤ 41አብያተ ክርስቲያ
ናትንም እያበረታታ በሶርያና በኪልቅያ
በኩል ዐለፈ::

### ጢሞቴዎስ ከጳውሎስና ከሲላስ ጋር ተሰማራ

16 ጳውሎስ ወደ ደርቤንና ወደ ልስ
ጥራን ደረሰ:: በዚያም እናቱ አይ
ሁዳዊት ሆና በጌታ ያመነች፣ አባቱ ግን
የግሪክ ሰው የሆነ፣ ጢሞቴዎስ የተባለ
አንድ ደቀ መዝሙር ነበረ:: 2እርሱም
በልስጥራንና በኢቆንዮን በነበሩት ወንድ
ሞች ዘንድ መልካም ምስክርነት ነበረው::
3ጳውሎስም ይህ ሰው ከእርሱ ጋር እንዲ
ሄድ ፈለገ፤ ስለዚህ በዚያ አካባቢ በነበሩ
አይሁድ ምክንያት ይዞ ገረዘው፤ እነዚህ
አይሁድ በሙሉ የጢሞቴዎስ አባት የግ
ሪክ ሰው እንደ ሆነ ያውቁ ነበርና:: 4እነ
ርሱም ከአንዱ ከተማ ወደ ሌላው በሚ
ያልፉበት ጊዜ፣ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች
በኢየሩሳሌም ያሳለፉትን ውሳኔ ተቀብ
ለው እንዲጠብቁ ለምእመናኑ ይሰጡ
ነበር:: 5አብያተ ክርስቲያናትም በእምነት
እየበረቱና ዕለት ዕለትም በቍጥር እየ
ጨመሩ ይሄዱ ነበር::

[7]17-18 አንዳንድ ቅጆች ...ለጌታ ከጥንት ጀምሮ የታወቀው የ ራሱ ሥራ ነው ይላሉ::

### ጳውሎስ ስለ መቄዶንያው ሰው ያየው ራእይ

6ጳውሎስና ባልደረቦቹ ቃሉን በእስያ
እንዳይሰብኩ መንፈስ ቅዱስ ስለ ከለ
ከላቸው፣ በፍርግያና በገላትያ አገር ዐል
ፈው ሄዱ። 7ወደ ሚስያም በተቃረቡ ጊዜ፣
ወደ ቢታንያ ሊገቡ ሞከሩ፤ ነገር ግን የኢ
የሱስ መንፈስ አልፈቀደላቸውም፤ 8ስለዚህ
በሚስያ በኩል አድርገው ወደ ጢሮአዳ
ወረዱ። 9ጳውሎስም ሌሊት በራእይ አንድ
የመቄዶንያ ሰው ቆሞ፣ "ወደ መቄዶንያ
ተሻግረህ እርዳን" ሲለው አየ። 10ጳውሎስ
ይህን ራእይ ካየ በኋላ፣ እግዚአብሔር ወንጌ
ልን እንድንሰብክላቸው ጠርቶናል ብለን
በመወሰን ወዲያው ወደ መቄዶንያ ለመ
ሄድ ፈለግን።

### ልድያ በፊልጵስዩስ በጌታ አመነች

11ከጢሮአዳ በመርከብ ተነሥተን በቀ
ጥታ ተጕዘን ወደ ሳሞትራቄ መጣን፤ በማ
ግስቱም ጕዞአችንን ወደ ናጱሌ ቀጠልን፤
12ከዚያም የሮማውያን ቅኝና የአካባቢው
የመቄዶንያ ግዛት ዋና ከተማ ወደ ሆነ
ችው ወደ ፊልጵስዩስ ገባን፤ በዚያም
አያሌ ቀን ተቀመጥን።
13በሰንበት ቀንም፣ የጸሎት ስፍራ
በመፈለግ፣ ከከተማዪቱ በር ወጥተን ወደ
አንድ ወንዝ ወረድን፤ በዚያም ተቀምጠን
ተሰብስበው ለነበሩት ሴቶች መናገር ጀመ
ርን። 14ከሚያዳምጡትም ሴቶች መካከል
ልድያ የምትባል አንዲት ሴት ነበረች፤
እርሷም እግዚአብሔርን የምታመልክና ከትያ
ጥሮን ከተማ የመጣች የቀይ ሐር ነጋዴ
ነበረች። ጌታም፣ ጳውሎስ የሚናገረውን
በማስተዋል ትሰማ ዘንድ፣ ልቧን ከፈተ
ላት። 15እርሷና ቤተ ሰዎቿ ከተጠመቁ
በኋላም፣ "በጌታ ማመኔን በእርግጥ
ከተረ ዳችሁልኝ ወደ ቤቴ መጥታችሁ
ጥቂት ተቀመጡ" በማለት አጥብቃ
ለመነችን።

### ጳውሎስና ሲላስ በወህኒ ቤት

16አንድ ቀን ወደ ጸሎት ስፍራ
ስንሄድ፣ በጥንቆላ መንፈስ ትንቢት
የምትናገር አንዲት የቤት አገልጋይ
አገኘችን፤ እር ሷም በዚህ የጥንቆላ ሥራዋ
ለአሳዳሪዎ ችዋ ብዙ ገንዘብ ታስገኝላቸው
ነበር። 17ይህችው አገልጋይ ጳውሎስንና
እኛን እየተከተለች፣ "እነዚህ ሰዎች
የመዳንን መንገድ የሚነግሯችሁ፣ የልዑል
እግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው!" በማለት
ትጮኽ ነበር፤ 18ይህንም ብዙ ቀን
ደጋገመችው፤ ጳውሎስ ግን በዚህ እጅግ
በመታወኩ ዘወር ብሎ ያን መንፈስ፣
ከእርሷ እንድ ትወጣ "በጌታ በኢየሱስ
ክርስቶስ ስም አዝ
ሃለሁ!" አለው፤ መንፈሱም በዚያው ቅጽ
በት ወጣላት።
19አሳዳሪዎቿም የገንዘብ ማግኛ ተስፋ
ቸው ወጥቶ መሄዱን በተረዱ ጊዜ፣ ጳው
ሎስንና ሲላስን ይዘው እየጐተቱ ባለ
ሥልጣኖች ወዳሉበት ወደ ገበያ ቦታ
አመጧቸው። 20ገዦቹም ፊት አቅርበዋ
ቸው እንዲህ አሉ፤ "እነዚህ ሰዎች አይ
ሁድ ሆነው ሳሉ፣ ከተማችንን አውከዋል፤
21ደግሞም እኛ ሮማውያን መቀበል ወይም
መፈጸም የማይገባንን ልማድ በሕዝቡ
መካከል ይነዛሉ።"
22ሕዝቡም ተባብረው በጳውሎስና በሲ
ላስ ላይ ተነሣባቸው፤ ገዦቹም ልብሳቸው
ተገፎ በበትር እንዲደበደቡ አዘዙ። 23ክፉኛ
ከተደበደቡ በኋላም ወደ ወህኒ ቤት አስ
ገቧቸው፤ የወህኒ ቤት ጠባቂውም ተጠን
ቅቆ እንዲጠብቃቸው አዘዙት። 24እርሱም
ይህን የመሰለ ትእዛዝ ከተቀበለ በኋላ፣ ወደ
ወህኒ ቤቱ ውስጠኛ ክፍል አስገብቶ እግራ
ቸውን ከግንድ ጋር አጣብቆ አሰራቸው።
25እኩለ ሌሊት አካባቢ ጳውሎስና ሲላስ
እየጸለዩና እየዘመሩ እግዚአብሔርን ሲያመሰ
ግኑ ነበር፤ ሌሎቹ እስረኞችም ያዳምጧ
ቸው ነበር። 26ድንገትም የወህኒ ቤቱን
መሠረት የሚያናውጥ ታላቅ የመሬት
መንቀጥቀጥ ሆነ፤ ወዲያውም የወህኒ ቤቱ
በሮች ተከፈቱ፤ የሁሉም እስራት ተፈታ።
27የወህኒ ቤቱ ጠባቂም ከእንቅልፉ ነቅቶ
የወህኒ ቤቱ በሮች ተከፍተው ባየ ጊዜ፣
እስረኞቹ ያመለጡ መስሎት ራሱን ለመ
ግደል ሰይፉን መዘዘ። 28ጳውሎስ ግን
ድምፁን ከፍ አድርጎ፣ "እኛ ሁላችን እዚሁ
ስላለን፣ በራስህ ላይ ክፉ ነገር አታድርስ!"
ብሎ ጮኸ።
29የወህኒ ቤቱ ጠባቂም መብራት ለምኖ
ወደ ውስጥ ዘሎ ገባ፤ እየተንቀጠቀጠም
በጳውሎስና በሲላስ እግር ላይ ወደቀ፤
30ይዞአቸው ከወጣ በኋላ፣ "እናንት ሰዎች፤
እድን ዘንድ ምን ላድርግ?" አላቸው።
31እነርሱም፣ "በጌታ በኢየሱስ እመን፤
አንተም ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ"
አሉት። 32ከዚያም ለእርሱና በቤቱ ላሉት
ሰዎች ሁሉ የጌታን ቃል ተናገሩ። 33የወ
ህኒ ቤት ጠባቂውም ሌሊት በዚያኑ ሰዓት
ወስዶ ቍስላቸውን አጠበላቸው፤ ወዲ
ያውም እርሱና ቤተ ሰቡ ሁሉ ተጠመቁ።
34የወህኒ ቤቱ ጠባቂም ወደ ቤቱ ወስዶ
ማእድ አቀረበላቸው፤ ከቤተ ሰቡም ሁሉ
ጋር በእግዚአብሔር በማመኑ በደስታ
ተሞላ።
35ሲነጋም፣ ገዦቹ፣ "እነዚያን ሰዎች

16፥6 ሐሥ2፥9፡10፤ 18፥23፤ገላ1፥2፤3፥1
16፥7 ሮሜ8፥9፤ገላ 4፥6፤ፊል1፥19፤1ጴጥ1፥11
16፥8 ቍ11፤ ሐሥ 20፥5፤2ቆሮ2፥12፤ 2ጢሞ 4፥13
16፥9 ሐሥ9፥10፤ 19፥21፡29፤20፥1፡3፤ሮሜ15፥26፤1ቆሮ 16፥5፤1ተሰ1፥7፡8
16፥10 ቍ10-17፤ 20፥5-15፤21፥1-18፤ 27፥1-28፡16፤ ሐሥ 14፥7
16፥11 ቍ8
16፥12 ቍ9፤ሐሥ 20፥6፤ፊል1፥1፤1ተሰ2፥2
16፥13 ሐሥ13፥14
16፥14 ሉቃ24፥45፤ ራእ1፥11፤2፥18፡24
16፥15 ሐሥ2፥38፤ 11፥14
16፥16 ቍ13፤ ዘዳ18፥11፤ 1ሳሙ28፥3፡7
16፥17 ማር5፥7
16፥18 ማር16፥17
16፥19 ቍ16፤ ሐሥ 8፥3፤ 15፥22፤17፥6፤ 19፥25፡26፤21፥30፤ ያዕ2፥6
16፥20 ሐሥ17፥6
16፥21 ቍ12፤ አስ 3፥8
16፥22 2ቆሮ11፥ 25፤1ተሰ2፥2
16፥23 ቍ27፡36
16፥24 ኢዮ13፥27፤ 33፥11፤ኤር20፥2፡3፤ 29፥26
16፥25 መዝ119፥ 55፡62፤ሐሥ15፥22፤ ኤፌ5፥19
16፥26 ሐሥ4፥31፤ 5፥19፤12፥7፡10
16፥27 ሐሥ12፥19
16፥29 ሐሥ15፥22
16፥30 ሐሥ2፥37
16፥31 ዮሐ3፥15፤ ሮሜ11፥14፤ሐሥ11፥ 14
16፥33 ቍ25፤ ሐሥ 2፥38
16፥34 ሐሥ11፥14

ፈተህ ልቀቃቸው” ብለው መኰንኖቻቸ
ውን ላኩበት። 36የወህኒ ቤት ጠባቂውም፣
“ገዦቹ እንድትፈቱ አዘዋል፤ ስለዚህ ወጥ
ታችሁ በሰላም ሂዱ” ብሎ ለጳውሎስ ነገረው።
37ጳውሎስ ግን፣ “እኛ የሮም ዜጎች
ሆነን ሳለን፣ በሕዝብ ፊት ያለ ፍርድ
ደብድበው ወደ እስር ቤት ወረወሩን፤
ታዲያ አሁን በስውር ሊያስወጡን ይፈል
ጋሉ? ይህማ አይሆንም፤ እነርሱ ራሳቸው
መጥተው ያስወጡን!” አላቸው።
38መኰንኖቹም ይህንኑ ቃል ለገዦቹ
ነገሯቸው፤ እነርሱም ጳውሎስና ሲላስ
የሮም ዜጎች መሆናቸውን ሲሰሙ ደነገጡ፤
39እነርሱ ራሳቸውም መጥተው ይቅርታ
ጠይቀው ከወህኒ ቤቱ አወጧቸው፤ ከተማ
ውንም ለቀው እንዲሄዱ ለመኗቸው። 40ጳ
ውሎስና ሲላስ ከእስር ቤቱ ከወጡ በኋላ
ወደ ልድያ ቤት ሄዱ፤ በዚያም ወንድ
ሞችን አግኝተው አበረታቷቸው፤ ከዚያም
በኋላ ሄዱ።

## ጳውሎስና ሲላስ በተሰሎንቄ

17 ጳውሎስና ሲላስም በአንፊጶልና
በአጶሎንያ ዐልፈው ወደ ተሰሎ
ንቄ ሄዱ፤ በዚያም የአይሁድ ምኵራብ
ነበር። 2ጳውሎስም እንደ ልማዱ ወደ
ምኵራብ ገባ፤ ሦስት ሰንበትም ከቅዱሳት
መጻሕፍት እየጠቀሰ ከእነርሱ ጋር ተነጋ
ገረ፤ 3ክርስቶስ[ጬ] መከራን መቀበል እንዳለ
በትና ከሙታንም መነሣት እንደሚገባው
እያስረዳ በማረጋገጥ፣ “ይህ እኔ የምሰብክ
ላችሁ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ነው” አላ
ቸው። 4አይሁድም አንዳንዶቹ የሰሙትን
በመቀበል ከጳውሎስና ከሲላስ ጋር ተባ
በሩ፤ ደግሞም ቍጥራቸው ብዙ የሆነ እግ
ዚአብሔርን የሚፈሩ ግሪኮችና አያሌ ዕውቅ
ሴቶች የሰሙትን ተቀብለው ከእነርሱ ጋር
ተባበሩ።
5አይሁድ ግን ስለቀኑ ወስላቶችን ከገ
በያ ቦታ አሰባሰቡ፤ ሕዝቡንም አነሣሥ
ተው በከተማው ውስጥ ሁከት ፈጠሩ፤
ጳውሎስንና ሲላስንም አምጥተው ሕዝቡ
ፊት[ጰ] ለማቅረብ ወደ ኢያሶን ቤት እየተ
ጣደፉ ሄዱ፤ 6ነገር ግን ሊያገኟቸው አልቻ
ሉም፤ ስለዚህ ኢያሶንንና ሌሎች ወንድ
ሞችን በከተማው ባለ ሥልጣናት ፊት
እየጐተቷቸው እንዲህ እያሉ ጮኹ፤ “እነ
ዚህ ሰዎች ዓለሙን ሁሉ ሲያውኩ ሖይ
ተው፣ አሁን ደግሞ ወደዚህ መጥተዋል፤
7ኢያሶንም በቤቱ ተቀብሎአቸዋል፤ እነዚ
ህም ሁሉ፣ ‘ኢየሱስ የሚባል ሌላ ንጉሥ
አለ’ በማለት የቄሳርን ሕግ የሚጥሱ ናቸው።”

16፥36 ቍ23፡27፤ ሐሥ15፥33
16፥37 ሐሥ22፥ 25-29
16፥38 ሐሥ22፥29
16፥39 ማቴ8፥34፤ ሉቃ8፥37
16፥40 ቍ2፡14፤ ሐሥ1፥16
17፥1 ቍ11፡13፤ ፊል4፥16፤1ተሰ1፥1፤2ተሰ1፥1፤2ጢሞ4፥10
17፥2 ሐሥ8፥35፤ 9፥20፤13፥14፤18፥28
17፥3 ሉቃ24፥26፡46፤ሐሥ2፥24፤3፥18፤9፥22
17፥4 ሐሥ15፥22
17፥5 ቍ13፤ ሮሜ16፥21፤ 1ተሰ2፥16
17፥6 ማቴ24፥14፤ ሐሥ1፥16፤16፥19፡20
17፥7 ሉቃ23፥2፤ ዮሐ19፥12
17፥9 ቍ5
17፥10 ቍ13፤ ሐሥ 9፥20፤ 15፥22፤20፥4
17፥11 ቍ1፤ ዘዳ 29፥29፤ ሉቃ16፥29፤ ዮሐ5፥39
17፥12 ሐሥ2፥41
17፥13 ዕብ4፥12
17፥14 ሐሥ 9፥30፤ 15፥22፤16፥1
17፥15 ቍ16፡21፡22፤ሐሥ18፥1፡5፤ 1ተሰ3፥1
17፥17 ሐሥ9፥20
17፥18 ቍ31፡32፤ሐሥ4፥2፤13፥32
17፥19 ቍ22፤ ማር 1፥27
17፥21 ቍ15

8ሕዝቡና የከተማውም ሹማምንት ይህን
በሰሙ ጊዜ ተሸበሩ፤ 9ከዚያም ኢያሶን
ንና ሌሎቹን በዋስ ለቀቋቸው።

## ጳውሎስና ሲላስ በቤርያ

10ወንድሞችም ወዲያው ጳውሎስንና ሲላ
ስን በሌሊት ወደ ቤርያ ሰደዱአቸው፤ እነር
ሱም እዚያ በደረሱ ጊዜ፣ ወደ አይሁድ
ምኵራብ ገቡ። 11የቤርያ ሰዎች ከተሰሎ
ንቄ ሰዎች ይልቅ አስተዋዮች ነበሩ፤ ምክ
ንያቱም ነገሩ እንደዚህ ይሆንን እያሉ
መጻሕፍትን በየዕለቱ በመመርመር ቃሉን
በታላቅ ጕጕት ተቀብለዋል። 12ስለዚህ ከእ
ነርሱ ብዙዎቹ አመኑ፤ ደግሞም ከእነርሱ
ጋር ቍጥራቸው ከፍተኛ የሆነ ዕውቅ የግ
ሪክ ሴቶችና ወንዶችም አመኑ።
13በተሰሎንቄ ያሉት አይሁድም፣ ጳው
ሎስ የእግዚአብሔርን ቃል በቤርያ ጭምር
መስበኩን ባወቁ ጊዜ፣ ሕዝቡን ለመቀስቀ
ስና ለማነሣሣት ወደዚያ ደግሞ ሄዱ።
14በዚህ ጊዜ ወንድሞች ጳውሎስን ቶሎ
ብለው ወደ ባሕሩ ዳርቻ ሰደዱት፤ ሲላስና
ጢሞቴዎስ ግን እዚያው ቀሩ። 15ጳውሎ
ስን የሸኙት ሰዎችም አቴና አደረሱት፤
ከዚያም ሲላስና ጢሞቴዎስ ወደ እርሱ
በፍጥነት እንዲመጡ የሚል ትእዛዝ ተቀ
ብለው ተመለሱ።

## ጳውሎስ በአቴና

16ጳውሎስ በአቴና ሆኖ ሲጠብቃቸው
ሳለ፣ ከተማዪቱ በጣዖት የተሞላች መሆኗን
በማየት መንፈሱ ተበሳጨበት። 17ስለዚህ
በምኵራብ ሆኖ ከአይሁድና እግዚአብሔርን
ከሚፈሩ ግሪኮች ጋር፣ ደግሞም በገበያ ስፍራ
ዕለት ዕለት ከሚያገኛቸው ሰዎች ጋር ይነ
ጋገር ነበር። 18ከኤፊቆሮስና ከኢስጦኢክ
የፍልስፍና ወገን የሆኑትም ወደ እርሱ
መጥተው ይከራከሩት ነበር። አንዳንዶቹ፣
“ይህ ለፍላፊ ምን ለማለት ይፈልጋል?”
ይሉ ነበር፤ ሌሎች ደግሞ ስለ ኢየሱስና
ስለ ትንሣኤው የምሥራች ሲሰብክ ሰም
ተው፣ “ስለ አዳዲስ ባዕዳን አማልክት
የሚናገር ይመስላል” አሉ። 19ይዘውም
አርዮስፋጎስ ወደ ተባለው ስፍራ በመ
ውሰድ እንዲህ አሉት፤ “አንተ የምታስ
ተምረው ይህ አዲስ ትምህርት ምን እንደ
ሆነ እንድናውቅ ትፈቅዳለህን? 20ደግሞም
በጆሮአችን የምታሰማን እንግዳ ነገር ስለ
ሆነብን፣ ምን ማለት እንደ ሆነ ማወቅ
እንፈልጋለን።” 21የአቴና ሰዎች በሙሉ
እንዲሁም በዚያ የሚኖሩ የውጭ ሰዎች

ጬ3 ወይም *መሲሕ*
ጰ5 ወይም *በሕዝብ ጉባኤ ፊት*

ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ስለ አዳዲስ ነገ
ሮች በማውራትና በመስማት እንጂ በሌላ
ጉዳይ አልነበረም።
22ስለዚህ ጳውሎስ በአርዮስፋጎስ በተሰበ
ሰበው ሕዝብ መካከል ቆሞ እንዲህ አለ፤
“የአቴና ሰዎች ሆይ፤ በማናቸውም ረገድ፣
በጣም ሃይማኖተኞች መሆናችሁን አያ
ለሁ፤ 23እየተዘዋወርሁ ሳለሁ፣ የምታመልኳ
ቸውን ነገሮች ስመለከት፣ ‘ለማይታወቅ
አምላክ’ የሚል ጽሑፍ ያለበት አንድ መሠ
ዊያ አይቻለሁና፤ እንግዲህ ይህን ሳታውቁ
የምታመልኩትን እገልጽላችኋለሁ።
24“ዓለምንና በውስጡ ያለውን ሁሉ
የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር
ጌታ ነው፤ ስለዚህም እርሱ የሰው እጅ በሠ
ራው መቅደስ አይኖርም። 25እርሱ
ለሰዎች ሁሉ ሕይወትንና እስትንፋስን
እንዲሁም ሌላውንም ነገር ሁሉ የሚሰጥ
ስለ ሆነ፣ የሚጐድለው ነገር ባለመኖሩ
በሰው እጅ አይገለገልም። 26የሰውን ዘር
ሁሉ ከአንድ ወገን ፈጥሮ በምድር ሁሉ
ላይ እንዲኖሩ አደረገ፤ የዘመናቸውን
ልክና የመኖሪያ ስፍራቸውንም ዳርቻ
ወሰነላቸው። 27ይኸውም ሰዎች እግዚአብሔ
ርን ፈልገው ተመራምረው ምናልባት
ያገኙት እንደ ሆነ ብሎ ነው፤ ይህም ቢ
ሆን እርሱ ከእያንዳንዳችን የራቀ ሆኖ
አይደለም፤ 28የምንኖረውና
የምንቀሳቀሰው፣ ያለነውም በእርሱ
ነውና። ከራሳችሁ ባለቅኔዎችም
አንዳንዶቹ እንዳ ሉት፣ ‘እኛም ደግሞ
ልጆቹ ነን።’
29“እንግዲህ የእግዚአብሔር ልጆች
ከሆንን፣ አምላክ በሰው ሙያና ጥበብ
የተቀረጸውን ወርቅ ወይም ብር ወይም
ድንጋይ ይመስ ሳል ብለን ማሰብ አይጠ
ገባንም። 30ቀደም ሲል እግዚአብሔር እንዲህ
ያለውን አለማወቅ በትዕግሥት ዐልፎአል፤
አሁን ግን በየቦ ታው ያሉ ሰዎች ሁሉ
ንስሓ እንዲገቡ ያዛል፤ 31በመረጠው ሰው
አማካይነት በዓለም ላይ በጽድቅ
የሚፈርድበትን ቀን ወስኖአልና፤
እርሱንም ከሙታን በማስ ነሣቱ ለሰዎች
ሁሉ ይህን አረጋግጦአል።”
32እነርሱም ስለ ሙታን ትንሣኤ በሰሙ
ጊዜ፣ አንዳንዶቹ አፌዙ፤ ሌሎች ግን፣
“ስለዚህ ጉዳይ ከአንተ ዳግመኛ ለመስ
ማት እንፈልጋለን” አሉት። 33በዚህ ጊዜ
ጳውሎስ ከመካከላቸው ወጥቶ ሄደ፤ 34አን
ዳንድ ሰዎች ግን ጳውሎስ ባለው በመስማ
ማት ተከተሉት፤ አመኑም፤ ከእነዚህም ዲዮ
ናስዮስ የተባለው የአርዮስፋጎስ ፍርድ
ቤት አባል፣ ደማሪስ የተባለች ሴትና
ሌሎችም ሰዎች ነበሩ።

## ጳውሎስ በቆሮንቶስ

18 ከዚህ በኋላ ጳውሎስ ከአቴና ተነ
ሥቶ ወደ ቆሮንቶስ ሄደ። 2በዚ
ያም የጳንጦስ ተወላጅ የሆነውን፣ አቂላ
የተባለውን አይሁዳዊ አገኘ፤ እርሱም አይ
ሁድ ሁሉ ከሮም እንዲወጡ ቀላውዴዎስ
ባዘዘው መሠረት ከሚስቱ ከጵርስቅላ ጋር
በቅርብ ጊዜ ከኢጣሊያ የመጣ ነበር።
ጳውሎስም ሊያያቸው ወደ እነርሱ ሄደ፤
3እርሱም እንደ እነርሱ ድንኳን ሰፊ ስለ
ነበረ፣ ከእነርሱ ጋር ተቀምጦ በተመሳሳይ
ሥራ ላይ ተሰማራ። 4በየሰንበቱም ከአይ
ሁድና ከግሪክ ሰዎች ጋር በምኵራብ ውስጥ
እየተነጋገረ ሊያሳምናቸው ይጥር ነበር።
5ሲላስና ጢሞቴዎስ ከመቄዶንያ በወ
ረዱ ጊዜ፣ ጳውሎስ በስብከት እየተጋ፣ ኢ
የሱስ እርሱ ክርስቶስ[ሀ] እንደ ሆነ ለአ
ይሁድ ይመሰክር ነበር። 6ነገር ግን በተ
ቃወሙትና በሰደቡት ጊዜ ልብሱን አራ
ግፎ፣ “ደማችሁ በራሳችሁ ላይ ይሁን!
እኔ ንጹሕ ነኝ፤ ከእንግዲህ ወደ አሕዛብ
እሄዳለሁ” አላቸው።
7ከዚያም ወጥቶ ቲቶስ ኢዮስጦስ ወደ
ተባለ፣ እግዚአብሔርን ወደሚያመልክ ሰው
ቤት ሄደ፤ የዚህም ሰው ቤት በምኵራቡ
አጠገብ ነበር። 8የምኵራብ አለቃ የነበ
ረው ቀርስጶስ ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር
በጌታ አመነ፤ ጳውሎስ ሲናገር የሰሙ
ብዙ የቆሮንቶስ ሰዎችም አምነው ተጠመቁ።
9ጌታም ሌሊት በራእይ ጳውሎስን እን
ዲህ አለው፤ “አትፍራ፤ ተናገር፣ ዝምም
አትበል፤ 10እኔ ከአንተ ጋር ነኝና ማንም
በአንተ ላይ ተነሥቶ ሊጐዳህ አይችልም፤
በዚች ከተማ ብዙ ሰዎች አሉኝና”።
11ስለዚህ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል እያ
ስተማራቸው አንድ ዓመት ተኩል አብ
ሮአቸው ተቀመጠ።
12ጋልዮስ የአካይያ ገዥ በነበረበት ጊዜ
አይሁድ ተባብረው በጳውሎስ ላይ ተነሡ፤
ፍርድ ወንበር ፊት አቅርበውትም፣ 13“ይህ
ሰው ሕጉ በማይፈቅደው መንገድ፣ ሰዎች
እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ እያሳሳታቸው
ነው አሉ።
14ጳውሎስ ሊናገር ገና አፉን ሲከፍት፣
ጋልዮስ አይሁድን እንዲህ አላቸው፤
“የአይሁድ ሰዎች ሆይ፤ ያቀረባችሁት
ጉዳይ ስለ ዐመፅ ወይም ስለ ከባድ ወን
ጀል ቢሆን ኖሮ ላዳምጣችሁ በተገባኝ
ነበር፤ 15ነገር ግን ክርክራችሁ ስለ ቃላትና
ስለ ስሞች እንዲሁም ስለ ሕጋችሁ በመ
ሆኑ፣ እናንተው ጨርሱት፤ እኔ በእንዲህ

17፥22 ቍ16፥19
17፥23 ዮሐ4፥22
17፥24 ዘዳ10፥14፤ 1ነገ8፥27፤ኢሳ42፥5፤ 66፥1፡2፤ማቴ11፥25፤ ሐሥ7፥48፤14፥15
17፥25 መዝ50፥10-12፤ኢሳ42፥5
17፥26 ዘዳ32፥8፤ ኢዮ12፥23፤
17፥27 ዘዳ4፥7፤ኢሳ 55፥6፤ኤር23፥23፡24
17፥28 ዘዳ30፥20፤ ኢዮ12፥10፤ዳን5፥23
17፥29 ኢሳ40፥18-20፤ሮሜ1፥23
17፥30 ቍ23፤ ሉቃ 24፥47፤ ሐሥ14፥16፤ሮሜ 3፥25፤ቲቶ2፥11፡ 12፤1ጴጥ1፥14
17፥31 መዝ9፥8፤ 96፥13፤98፥9፤ ማቴ10፥15፤ሐሥ2፥ 24፤10፥42
17፥32 ቍ18፡31
17፥34 ቍ19፡22
18፥1 ሐሥ17፥15፤ 19፥1፤1ቆሮ1፥2፤2 ቆሮ1፥1፡23፤ 2ጢሞ 4፥20
18፥2 ቍ19፡26፤ ሮሜ16፥3፤ሐሥ11፥28፤ 1ቆሮ16፥19፤ 2ጢሞ 4፥19
18፥3 ሐሥ20፥34፤ 1ቆሮ4፥12፤ 1ተሰ2፥9፤2ተሰ3፥8
18፥4 ሐሥ9፥20፤ 13፥14
18፥5 ሐሥ9፥22፤ 15፥22፤16፥1፡9፤17፥1 4፡15
18፥6 2ሳሙ1፥16፤ ሕዝ3፥17-19፤33፥4፤ ማቴ10፥14፤ሐሥ 13፥45፡46፤20፥26
18፥7 ሐሥ16፥14
18፥8 ማር5፥22፤ ሐሥ11፥14፤ 1ቆሮ 1፥14
18፥9 ማቴ14፥ 27፤ሐሥ 9፥10
18፥10 ማቴ28፥20
18፥11 ዕብ4፥12
18፥12 ቍ27፤ ሐሥ 13፥7፡8፡12፤ 19፥38፤ሮሜ 15፥26፤1ቆሮ 16፥15፤2ቆሮ9፥2፤1 ተሰ1፥7፡8
18፥15 ሐሥ 23፥29፤ 25፥11፡19

[ሀ]5 ወይም መሲሕ፤ እንዲሁም ቍ 25

ዐይነት ነገር ፈራጅ ለመሆን አልሻም።”
16ስለዚህ ከፍርድ ወንበር ፊት አስወጣ
ቸው። 17በዚህ ጊዜ ሁሉም የምኵራቡን
አለቃ፣ ሶስቴንስን ይዘው በፍርድ ቤቱ
ፊት ደበደቡት፤ ጋልዮስ ግን ነገሩ ደን
ታም አልሰጠውም።

### ጵርስቅላ፣ አቂላና አጵሎስ

18ከዚህ በኋላ ጳውሎስ ብዙ ቀን በቆሮን
ቶስ ተቀመጠ፤ ከዚያም ወንድሞችን ተሰና
ብቶ ከጵርስቅላና ከአቂላ ጋር በመርከብ
ወደ ሶርያ ሄደ። ስእለትም ስለነበረበት
ክንክራኦስ በተባለ ቦታ ራሱን ተላጨ።
19ኤፌሶን በደረሰ ጊዜም ጵርስቅላንና
አቂላን እዚያው ተዋቸው፤ እርሱ ራሱ
ግን ወደ ምኵራብ ገብቶ ከአይሁድ ጋር
ይነጋገር ነበር። 20ከእነርሱ ጋር እንዲሰነ
ብት በጠየቁትም ጊዜ ፈቃደኛ አልሆ
ነም፤ 21ነገር ግን ሲለያቸው፣ “የእግዚአብሔር
ፈቃድ ከሆነ ተመልሼ እመጣለሁ” አላ
ቸው፤ ከኤፌሶንም ተነሥቶ በመርከብ
ተጓዘ። 22ቂሳርያም በደረሰ ጊዜ፣ ወጥቶ
ለቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቀረበ፤ ከዚ
ያም ወደ አንጾኪያ ወረደ።
23በአንጾኪያም ጥቂት ጊዜ ከሖየ በኋላ፣
ከዚያ ተነሥቶ በገላትያና በፍርግያ አገ
ሮች ከቦታ ቦታ በመዘዋወር ደቀ መዛ
ሙርትን ሁሉ አበረታታ።
24በዚህ ጊዜ የእስክንድርያ ተወላጅ
የሆነ አጵሎስ የሚባል አንድ አይሁዳዊ
ወደ ኤፌሶን መጣ፤ እርሱም የተማረና
ቅዱሳት መጻሕፍትን ጠንቅቆ የሚያውቅ
ሰው ነበር። 25ይህ ሰው፣ የጌታን መንገድ
የተማረ፣ ስለ ኢየሱስም በትክክል የሚና
ገርና በመንፈስ እየተቃጠለ[ፀ] የሚያስተምር
ነበር፤ ይሁን እንጂ እርሱ የሚያውቀው
የዮሐንስን ጥምቀት ብቻ ነበር። 26እርሱም
በምኵራብ በድፍረት ይናገር ጀመር፤
ጵርስቅላና አቂላም በሰሙት ጊዜ፣ ወደ
ቤታቸው ወስደው የእግዚአብሔርን መንገድ
ይበልጥ አስተካክለው አስረዱት።
27አጵሎስ ወደ አካይያ ለመሄድ በፈለገ
ጊዜ፣ ወንድሞች አበረታቱት፤ በዚያ
የነበሩት ደቀ መዛሙርትም እንዲቀበሉት
ደብዳቤ ጻፉለት። እዚያም በደረሰ ጊዜ ከጸ
ጋው የተነሣ አምነው ለነበሩት ትልቅ
ረዳት ሆናቸው፤ 28ከቅዱሳት መጻሕፍት
እያመሳከረ፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ
እንደ ሆነ ከአይሁድ ጋር በጽኑ በመከራ
ከር በሕዝብ ፊት ይረታቸው ነበርና።

18፥17 ቍ8፤ 1ቆሮ1፥1
18፥18 ቍ2:27፤ ዘኍ6፥2:5:18፤ሉቃ 2፥2፤ሐሥ1፥16፤ 21፥24፤ ሮሜ16፥1
18፥19 ቍ21:24፤ ሐሥ 19፥1:17:26፤ 1ቆሮ15፥32፤16፥8፤ ኤፌ1፥1፤1ጢሞ1፥3፤ ራእ 1፥11፤ 2፥1
18፥21 ሮሜ1፥10፤ 15፥32፤1ቆሮ4፥19፤ ያዕ4፥15
18፥22 ሐሥ8፥40፤ 11፥19
18፥23 ሐሥ2፥10፤ 14፥22፤15፥32:41፤ 16፥6
18፥24 ቍ19፤ ሐሥ 19፥1፤ 1ቆሮ1፥12፤3፥5:6:22፤ 4፥6፤16፥12፤ቲቶ3፥13
18፥25 ማር1፥4፤ ሮሜ12፥11
18፥26 ቍ2
18፥27 ቍ12: 18፤ሐሥ1፥16
18፥28 ቍ5፤ ሐሥ 8፥35፤ 9፥22፤17፥2

19፥1 ሐሥ18፥1: 19:24
19፥2 ዮሐ20፥22
19፥4 ማር1፥4፤ ዮሐ1፥7
19፥5 ሐሥ2፥38
19፥6 ማር16፥17፤ ሐሥ6፥6፤10፥44
19፥8 ማቴ3፥2፤ ሐሥ9፥20፤28፥23
19፥9 ቍ23:30፤ ሐሥ 9፥2-11፥26፤ 14፥4
19፥10 ቍ22:26: 27፤ሐሥ2፥9፤13፥48፤ 20፥31
19፥11 ሐሥ8፥13
19፥12 ሐሥ5፥15
19፥13 ማቴ12፥ 27፤ማር9፥38

### ጳውሎስ በኤፌሶን

19 አጵሎስ በቆሮንቶስ በነበረበት ጊዜ፣
ጳውሎስ በላይኛው አገር ዐልፎ
ወደ ኤፌሶን መጣ፤ በዚያም አንዳንድ
ደቀ መዛሙርትን አግኝቶ፣ 2“ባመናችሁ[ፊ]
ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?” አላ
ቸው።
እነርሱም፣ “አልተቀበልንም፤ እንዲያ
ውም መንፈስ ቅዱስ መኖሩን እንኳ አልሰ
ማንም” አሉት።
3ጳውሎስም፣ “ታዲያ፣ በምን ተጠመ
ቃችሁ?” አላቸው።
እነርሱም፣ “የዮሐንስን ጥምቀት” አሉት።
4ጳውሎስም፣ “የዮሐንስ ጥምቀትማ የን
ስሓ ጥምቀት ነበር፤ ዮሐንስም ራሱ
ሰዎች ከእርሱ በኋላ በሚመጣው በኢየሱስ
እንዲያምኑ ተናግሮአል” አላቸው። 5እነር
ሱም ይህን በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ
ስም ተጠመቁ። 6ጳውሎስም እጁን በላያ
ቸው በጫነ ጊዜ፣ መንፈስ ቅዱስ ወረ
ደባቸው፤ በሌሎች ቋንቋዎች[ፐ] ተናገሩ፤
ትንቢትም ተናገሩ። 7ሰዎቹም በአጠቃ
ላይ ዐሥራ ሁለት ያህል ነበሩ።
8ጳውሎስም ወደ ምኵራብ እየገባ፣
ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እየተነጋገረና
እያሳመናቸው ሦስት ወር ሙሉ ምንም
ሳይፈራ ፊት ለፊት ይናገር ነበር። 9አን
ዳንዶቹ ግን ግትር በመሆን፣ ለማመን
ፈቃደኞች አልነበሩም፤ የጌታንም
መንገድ በገሃድ ያጥላሉ ነበር። ስለዚህ
ጳውሎስ ትቶአቸው ሄደ፤ ደቀ
መዛሙርትንም ለብ ቻቸው ወስዶ በጢራ
ኖስ የትምህርት አዳራሽ ውስጥ በየዕለቱ
ያነጋግራቸው ነበር። 10ይህን ማድረጉንም
ሁለት ዓመት ስለ ቀጠለ፣ በእስያ አውራ
ጃ ይኖሩ የነበሩት የአይሁድና የግሪክ
ሰዎች ሁሉ የጌታን ቃል ለመስማት
ቻሉ።
11እግዚአብሔርም በጳውሎስ እጅ እጅግ
የሚያስደንቅ ታምራትን ያደርግ ነበር፤
12መሐረብ ወይም ሰውነቱን የነካ ጨርቅ
እንኳ ወደ ሕመምተኞች ሲወስዱ በሽታ
ቸው ይለቃቸው ነበር፤ ርኩሳን መናፍስ
ትም ይወጡ ነበር።
13እየዞሩ አጋንንትን ያስወጡ ከነበሩት
አይሁድ አንዳንዶቹ፣ “ጳውሎስ በሚሰ
ብከው በኢየሱስ ስም እንድትወጡ አዛች
ኋለሁ!” እያሉ የጌታን የኢየሱስን ስም
ርኩሳን መናፍስት በያዟቸው ሰዎች ላይ
ለመጥራት ሞከሩ፤ 14የአይሁዳዊው የካህናቱ

[ፀ]25 ወይም *በትልቅ ግለት*
[ፊ]2 ወይም *ካመናችሁ በኋላ*
[ፐ]6 ወይም *ልሳን*

አለቃ የአስቄዋ ሰባት ወንዶች ልጆችም
ይህንኑ ያደርጉ ነበር። 15ርኩስ መንፈ
ሱም፣ “ኢየሱስን ዐውቀዋለሁ፤ ጳውሎስ
ንም ዐውቀዋለሁ፤ እናንተ ግን እነማን
ናችሁ?” አላቸው። 16ከዚያም ርኩስ መን
ፈስ ያደረበት ሰው ዘሎ ያዛቸው፤ በረታ
ባቸውም፤ እጅግ ስላየለባቸውም ቤቱን
ጥለው ዕራቁታቸውን ሸሹ።
17ይህም በኤፌሶን በሚኖሩት፣ በአይሁ
ድና በግሪክ ሰዎች ሁሉ ዘንድ በታወቀ ጊዜ፣
ሁሉም ፍርሀት ያዛቸው፤ በዚህም የጌታ
የኢየሱስ ስም ተከበረ። 18ካመኑትም
ሰዎች ብዙዎቹ እየቀረቡ ክፉ ሥራቸውን
በግልጥ ተናዘዙ፤ 19ሲጠንቁሉ ከነበሩትም
መካከል ብዙዎች መጽሐፋቸውን ሰብስ
በው በማምጣት በሕዝብ ፊት አቃጠሉ፤
ዋጋቸውም ሲሰላ አምሳ ሺህ ብር ያህል
ሆኖ ተገኘ። 20በዚህ ሁኔታ የጌታ ቃል
በኀይል እያደገና እያሸነፈ ሄደ።
21ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ፣ ጳውሎስ በመ
ቄዶንያና በአካይያ በኩል ዐልፎ ወደ ኢየሩ
ሳሌም ለመሄድ በመንፈሱ ወስኖ፣ “እዚያ
ከደረስሁ በኋላ ሮምን ደግሞ ማየት አለ
ብኝ” አለ። 22ከረዳቶቹም ሁለቱን፣ ጢሞ
ቴዎስንና ኤርስጦንን፣ ወደ መቄዶንያ
ልኮ እርሱ ራሱ ግን በእስያ አውራጃ ጥቂት
ቀን ተቀመጠ።

## በኤፌሶን የተነሣው ሁከት

23በዚህ ጊዜ፣ ስለ ጌታ መንገድ ታላቅ
ሁከት ተፈጠረ። 24ድሜጥሮስ የተባለ
አንድ የብር አንጥረኛ የአርጤምስን ቤተ
መቅደስ ምስሎች ከብር ቀጥቅጦ እየሠራ
ለሠራተኞቹ የሚያስገኘው ገቢ ቀላል አል
ነበረም። 25እርሱም እነዚህን ሠራተኞችና
በተመሳሳይ ሙያ የሚተዳደሩትን ሌሎቹን
ሰዎች በአንድነት ሰብስቦ እንዲህ አላ
ቸው፤ “ሰዎች ሆይ፤ ይህ ሥራ ጥሩ ገቢ
እንደሚያስገኝልን ታውቃላችሁ። 26ይህ
ጳውሎስ የተባለ ሰው በኤፌሶን ብቻ
ሳይሆን፣ በመላው የእስያ አውራጃ የሚገ
ኘውን በርካታ ሕዝብ እያሳመነ እንዳሳታ
ቸው ይኸው የምታዩትና የምትሰሙት
ነገር ነው፤ በሰው እጅ የተሠሩ አማልክት
በፍጹም አማልክት እንዳልሆኑ ይናገራ
ልና። 27የዚህ የሥራችን መልካም ስም
ከመጕደፉም በላይ፣ መላው እስያና ዓለም
የሚያመልካት የታላቋ አርጤምስ ቤተ
መቅደስም ዋጋ ቢስ ይሆናል፤ ደግሞም
ገናናው ክብሯ ይዋረዳል።”
28ሰዎቹም ይህን በሰሙ ጊዜ ክፉኛ
ተሐጥተው፣ “የኤፌሶኗ አርጤምስ ታላቅ
ናት!” እያሉ ይጮኹ ጀመር። 29ወዲያ
ውም በከተማው ሁሉ ሁከት ተነሣ፤ ሕዝ
ቡም አንድ ላይ በማበር የመቄዶንያ ተወ
ላጅ የሆኑትንና ከጳውሎስ ጋር ይጓዙ የነ
በሩትን ጓደኞቹን፣ ጋይዮስንና አርስጥ
ሮኮስን ይዘው ወደ ጨዋታ ማሳያው ስፍራ
እየሮጡ ገቡ። 30ጳውሎስም ወጥቶ ሕዝቡ
ፊት ለመቅረብ ፈልጎ ነበር፤ ደቀ መዛ
ሙርት ግን ከለከሉት። 31ከአውራጃው ባለ
ሥልጣኖች አንዳንድ ወዳጆቹ እንኳ፣
ጳውሎስ ወደ ጨዋታ ማሳያው ስፍራ
ደፍሮ እንዳይገባ ሰው ልከው ለመኑት።
32ጉባኤውም ተበጣብጦ፣ አንዱ አንድ
ነገር ሲናገር ሌላውም ሌላ እየተናገረ
ይጯጯኽ ነበር፤ አብዛኛውም ሰው ለምን
እዚያ እንደ ተሰበሰበ እንኳ አያውቅም
ነበር። 33አይሁድም እስክንድሮስን ከሕዝቡ
መካከል ገፍተው ወደ ፊት ባወጡት ጊዜ፤
አንዳንዶቹ እንዲናገርላቸው ጮኹ፤ እር
ሱም ሊከራከርላቸው ፈልጎ ዝም እንዲሉ
በምልክት ጠቀሳቸው። 34ነገር ግን እርሱ
አይሁዳዊ መሆኑን ባወቁ ጊዜ ሁሉም
በአንድ ድምፅ፣ “የኤፌሶኗ አርጤምስ ታላቅ
ናት” እያሉ ሁለት ሰዓት ያህል ጮ÷□።
35የከተማዪቱም ዋና ጸሓፊ ሕዝቡን
ጸጥ አሰኝቶ እንዲህ አለ፤ “የኤፌሶን ሰዎች
ሆይ፤ የታላቋ የአርጤምስ ቤተ መቅደስና
ከሰማይ የወረደው ምስሏ ጠባቂ የኤፌሶን
ከተማ ሕዝብ መሆኑን የማያውቅ ማን
አለ? 36ስለዚህ፣ ይህ ሐቅ የማይካድ እንደ
መሆኑ መጠን፣ ልትረጋጉና አንዳች ነገር
በጥድፊያ ከመፈጸም ልትሐጠቡ ይገባች
ኋል። 37እነዚህን ሰዎች ቤተ መቅደስን
ሳይዘርፉ ወይም አምላካችንን በሆነችው
ላይ የስድብ ቃል ሳይሰነዝሩ ይዛችሁ እዚህ
ድረስ እንዲያው አምጥታችኋቸ ዋል።
38እንግዲህ፣ ድሜጥሮስና ከእርሱ ጋር
ያሉት አንጥረኞች በማንም ላይ አቤቱታ
ካላቸው፣ ፍርድ ቤቱ ክፍት ነው፤ ዳኞ
ችም አሉ፤ ክስ ማቅረብ ይችላሉ። 39ከዚህ
ሌላ ልታቀርቡ የፈለጋችሁት ነገር ካለ፣
በሕጋዊ ጉባኤ ይታያል። 40አለበለዚያ ዛሬ
ስለ ሆነው ነገር፣ በሁከት አነሣሽነት እን
ዳንከሰስ ያሠጋናል፤ አጥጋቢ ምክንያት
ስለሌለንም፣ ስለ ሁከቱ ብንጠየቅበት
መልስ መስጠት አንችልም።” 41ይህን ከተ
ናገረ በኋላም ጉባኤው እንዲበተን አደረገ ።

## ወደ መቄዶንያና ወደ ግሪክ ጕዞ

20 ሁከቱም እንደ በረደ፣ ጳውሎስ
ደቀ መዛሙርትን አስጠርቶ መከ
ራቸው፤ ተሰናበቶአቸውም ወደ መቄዶንያ
ለመሄድ ተነሣ። 2ባለፈባቸውም ስፍራ

19፥17 ሐሥ5፥5፡ 11፤18፥19
19፥20 ሐሥ6፥7፤ 12፥24፤13፥48
19፥21 ሐሥ16፥9፤ 18፥12፤20፥16፡22፤ 21፥4፡12፡15፤ ሮሜ15፥24፡25፡28
19፥22 ቀኍ10፡ 26፡27፤ሐሥ2፥9፤ 13፥5፤16፥1፤ሮሜ 16፥23፤2ጢሞ4፥20
19፥23 ሐሥ9፥2
19፥25 ሐሥ16፥ 16፡19፡20
19፥26 ዘዳ4፥28፤ መዝ115፥4፤ኢሳ44፥ 10-20፤ኤር10፥3-5፤ ሐሥ2፥9፤17፥29፤ 18፥19፤1ቆሮ8፥4፤ ራእ9፥20
19፥28 ሐሥ18፥19
19፥29 ሐሥ16፥9፤ 20፥4፤27፥2፤ሮሜ 16፥23፤1ቆሮ1፥14፤ ቈላ4፥10፤ፊሞ24
19፥30 ሐሥ11፥26
19፥32 ሐሥ21፥34
19፥33 ሐሥ12፥17
19፥34 ቀኍ28
19፥35 ሐሥ18፥19
19፥37 ሮሜ2፥22
19፥38 ቀኍ24፤ሐሥ 13፥7፡8፡12፤18፥12
20፥1 ሐሥ11፥26፤16፥9

ዎች ሕዝቡን በብዙ ቃል እየመከረ ግሪክ
አገር ደረሰ፤ [3]በዚያም ሦስት ወር ተቀ
መጠ። ወደ ሶርያ በመርከብ ለመሄድ ሲዘ
ጋጅም አይሁድ አሢረውበት ስለ ነበር፣
በመቄዶንያ በኩል አድርጎ ለመመለስ
ወሰነ። [4]የጳይሮስ ልጅ የቤርያው ሱሲጳጥ
ሮስ፣ የተሰሎንቄዎቹ አርስጥ ሮኮስና ሲኮ
ንዱስ፣ የደርቤኑ ጋይዮስ፣ ከእስያ አውራጃ
የመጡት ቲኪቆስና ጥሮፊ ሞስ፣ እንዲ
ሁም ጢሞቴዎስ አብረውት ሄዱ። [5]እነዚ
ህም ሰዎች ወደ ፊት ቀድመውን በጢሮ
አዳ ጠበቁን። [6]እኛ ግን፣ የቂጣ በዓል
ካለፈ በኋላ፣ ከፊልጵስዩስ በመርከብ ተነ
ሣን፤ ከአምስት ቀንም በኋላ ከሌሎቹ ጋር
በጢሮአዳ ተገናኘን፤ በዚያም ሰባት ቀን
ተቀመጥን።

## አውጤኪስ በጢሮአዳ ከሞት ተነሣ

[7]በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን እንጀራ
ለመቊረስ ተሰብስበን ሳለን፣ ጳውሎስ በማ
ግስቱ ለመሄድ ስላሰበ፣ ከእነርሱ ጋር ይነ
ጋገር ነበር፤ ንግግሩንም እስከ እኩለ ሌሊት
ድረስ አራዘመ። [8]በተሰበሰብንበትም ሰገ
ነት ላይ ብዙ መብራት ነበር። [9]አውጤኪስ
የተባለ አንድ ጐበዝም በመስኮት ላይ ተቀ
ምጦ ነበር፤ ጳውሎስ ንግግሩን ባስረዘመ
ጊዜ፣ እንቅልፍ እንቅልፍ አለውና ጭልጥ
ብሎ ተኛ፤ ከሦስተኛው ፎቅ ቊልቊል
ወደቀ፤ ሞቶም አነሡት። [10]ጳውሎስም
ወርዶ በላዩ ተጋድሞ ዐቀፈውና፣ “ሕይ
ወቱ በውስጡ ስላለች ሁከት አትፍጠሩ”
አላቸው። [11]ተመልሶም እንደ ገና ወደ
ፎቁ ወጣ፤ እንጀራውንም ሖርሶ በላ፤ እስ
ኪነጋም ድረስ ብዙ ከተናገረ በኋላ ተነ
ሥቶ ሄደ። [12]ሰዎችም ያን ጐበዝ ሕያው
ሆኖ ወሰዱት፤ በዚህም እጅግ ተጽናኑ።

## ጳውሎስ የኤፌሶንን ሽማግሌዎች ተሰናበተ

[13]እኛ ግን ጳውሎስን ለመቀበል ቀድ
መን ወደ መርከቡ ሄድን፤ ከዚያም በመር
ከብ ወደ አሶን ተጓዝን፤ ይህን ያደረግ
ነውም ጳውሎስ በየብስ በእግሩ ሊሄድ ስላ
ሰበ ነበር። [14]በአሶን ከተገናኘንም በኋላ፣
ተቀ ብለነው አብረን በመርከብ ወደ
ሚጢሊኒ ሄድን። [15]በማግስቱም በመርከብ
ተጕዘን ከኪዩ ደሴት ትይዩ ደረስን።
በሚቀጥለውም ቀን ወደ ሳሞን ተሻገርን፤
በማግስቱም ሚሊጢን ደረስን። [16]ጳው
ሎስም በእስያ አውራጃ ብዙ መሐየት ስላ
ልፈለገ፣ ወደ ኤፌሶን ሳይገባ ዐልፎ ለመ
ሄድ ወሰነ፤ ቢቻል በዓለ ኀምሳን በኢየሩ
ሳሌም ለመዋል ቸኵሎ ነበርና።
[17]ከሚሊጢንም ወደ ኤፌሶን ሰው ልኮ

20፥3 ቍ19፤ ሉቃ 2፥2፤ ሐሥ9፥23፡24፤ 14፥5፤16፥9፤23፥12፡15፡30፤25፥3፤2ቆሮ 11፥26፤1ተሰ2፥16
20፥4 ሐሥ2፥9፤ 16፥1፤17፥1፤19፥29፤21፥29፤ኤፌ6፥21፤ ቈላ4፥7፤2ጢሞ 4፥20፤ቲቶ3፥12
20፥5 ሐሥ16፥8፡10
20፥6 ሐሥ16፥8፡12
20፥7 ማቴ14፥19፤ 1ቆሮ16፥2፤ ራእ1፥10
20፥8 ሐሥ1፥13፤ 9፥37
20፥10 1ነገ17፥21፤ 2ነገ4፥34፤ ማቴ9፥23፡24
20፥11 ቍ7፤ ማቴ 14፥19
20፥15 ቍ17፤ 2ጢሞ 4፥20
20፥16 ሐሥ2፥1፡9፤ 18፥19፤19፥21
20፥17 ቍ15፤ ሐሥ 11፥30
20፥18 ሐሥ2፥9፤ 18፥19-21፤19፥1-41
20፥19 ቍ3፤ መዝ 6፥6
20፥20 ቍ27፤ መዝ 40፥10፤ ኤር26፥2፤42፥4
20፥21 ሐሥ2፥38፤ 18፥5፤24፥24፤26፥18፤ ኤፌ1፥15፤ ቈላ2፥5፤ፊሞ5
20፥22 ቍ16
20፥23 ሐሥ8፥29፤ 9፥16፤21፥4
20፥24 ሐሥ11፥23፤ 21፥13፤2ቆሮ4፥1፤ ገላ1፥1፤2ጢሞ4፥7፤ ቲቶ1፥3
20፥25 ቍ38፤ ማቴ 4፥23
20፥26 ሕዝ3፥17-19፤ሐሥ18፥6
20፥27 ቍ20
20፥28 ቍ29፤ ዮሐ 21፥16፤ ሮሜ3፥25፤ 1ቆሮ6፥20፤10፥32፤ 1ጢሞ3፥1
20፥29 ቍ28፤ ማቴ7፥15፤ሕዝ34፥5
20፥30 ሐሥ11፥26
20፥31 ቍ19፤ሐሥ 19፥10
20፥32 ማቴ25፥34፤ ሐሥ14፥23፤26፥18፤ ኤፌ1፥14፤ቈላ1፥12፤3፥24፤ዕብ9፥15፤ 1ጴጥ1፥4

የቤተ ክርስቲያኒቱን ሽማግሌዎች አስጠራ፤
[18]በመጡም ጊዜ እንዲህ አላቸው፤ “ወደ
እስያ አውራጃ ከገባሁባት ከመጀመሪ
ያዋ ዕለት አንሥቶ ዘወትር ከእናንተ ጋር
እንዴት እንደኖርሁ ታውቃላችሁ። [19]ምንም
እንኳ ከአይሁድ ሤራ የተነሣ መከራ ቢያ
ደርሱብኝም፣ ጌታን በታላቅ ትሕትናና
በእንባ ከማገልገል አልተሐጠብሁም [20]በአ
ደባባይም ሆነ ከቤት ቤት በመዘዋወር፣
እናንተን ከማስተማርና ይጠቅማችኋል
ብዬ ያሰብሁትን ከመስበክ ወደ ኋላ አላ
ልሁም። [21]በንስሓ ወደ እግዚአብሔር
እንዲመለሱና በጌታችን በኢየሱስ እንዲ
ያምኑ፣ ለአይሁድም ለግሪክ ሰዎችም አጥ
ብቄ መስክሬላቸዋለሁ።

[22]“አሁንም እዚያ ስደርስ የሚደርስብ
ኝን ባላውቅም፣ መንፈስ ቅዱስ ወደ ኢየሩ
ሳሌም እንድሄድ ግድ እያለኝ ነው።
[23]ነገር ግን በምሄድባቸው ከተሞች ሁሉ
እስራትና መከራ እንደሚጠብቀኝ መንፈስ
ቅዱስ ይመሰክርልኛል። [24]ይሁን እንጂ
ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን ሩጫዬንና
የእግዚአብሔርን የጸጋ ወንጌል የመመስከር
አገልግሎቴን ብፈጽም፣ ለእኔ ሕይወቴ
ከምንም እንደማይሐጠር እንደ ከንቱ ነገር
ናት።

[25]“አሁንም ቢሆን፣ በመካከላችሁ ተዘ
ዋውሬ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሰበክ
ሁላችሁ፣ እናንተ ሁላችሁ ከእንግዲህ
ወዲያ ፊቴን እንደማታዩ ዐውቃለሁ።
[26]ስለዚህ ከሰው ሁሉ ደም ንጹሕ መሆኔን
በዚች ቀን እመሰክርላችኋለሁ፤ [27]የእግዚ
አብሔርን ፈቃድ ሁሉ ለእናንተ ከመግለ
ጽ የተሐጠብሁበት ጊዜ የለምና። [28]ለራ
ሳችሁና መን ፈስ ቅዱስ ጠባቂ[ሀ] አድርጎ
በላዩ ለሾማችሁ መንጋ ሁሉ ተጠንቀቁ፤
በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን[ለ] ቤተ
ክርስ ቲያን ጠብቁ። [29]እኔ ከሄድሁ
በኋላ፣ ነጣቂ ተኵላዎች መጥተው
በመካከላችሁ ሰርገው እንደሚገቡና
ለመንጋውም እንደማይራሩ ዐውቃለሁ።
[30]ከእናንተው መካ ከል እንኳ የራሳቸውን
ደቀ መዛሙርት ለማ ፍራት እውነትን
የሚያጣምሙ ይነ ሣሉ። [31]ስለዚህ ተጠ
ንቀቁ፤ ሦስት ዓመት ሙሉ ሌሊትና ቀን
ምንም ያህል ሳላቋርጥ በእንባ
እያንዳንዳችሁን እንደ መከርኋችሁ
አስታውሱ።

[32]“አሁንም ለእግዚአብሔር፣ እንዲሁም ሊ
ያ ንጻችሁና በቅዱሳኑ ሁሉ መካከል
ርስት ሊያወርሳችሁ ለሚችለው ለጸጋው
ቃል ዐደራ

[ሀ]28 በትውፊት ጳጳሳት ሲባል የመጣው ነው
[ለ]28 ብዙ የጥንት ቅጆች የጌታን

እሰጣችኋለሁ። 33የማንንም ብር ወይም
ወርቅ ወይም ልብስ አልተመኘሁም፤ 34እነ
ዚህ እጆቼ ለእኔና ከኔ ጋር ላሉት በሚያ
ስፈልገን ነገር እንዳገለገሉን እናንተ ራሳ
ችሁ ታውቃላችሁ። 35በጒልበታችን ደክ
መን ችግረኞችን መርዳት እንዳለብን ባደ
ረግሁት ሁሉ አሳይቻችኋለሁ፤ ‘ከሚቀበል
ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው’ ያለውን የጌታ
የኢየሱስን ቃል እናስታውስ።”

36ይህን ካለ በኋላ፣ ተንበርክኮ ከሁሉም
ጋር ጸለየ። 37ሁሉም እጅግ አለቀሱ፤ ጳው
ሎስንም አንገቱን ዐቅፈው ሳሙት፤ 38ከሁ
ሉም በላይ ልባቸውን የነካው፣ ከእንግዲህ
ወዲህ ፊቱን እንደማያዩ የተናገራቸው
ቃል ነበር። ከዚያም እስከ መርከቡ ድረስ
ሸኙት።

## ወደ ኢየሩሳሌም ጒዞ

21 ከእነርሱ ከተለየን በኋላ ቀጥታ
በመርከብ ወደ ቆስ ተጓዝን፤ በማግ
ስቱም ወደ ሩድ፣ ከዚያም ወደ ጳጥራ
አመራን። 2በዚያም ወደ ፊንቄ የሚሄድ
መርከብ ስላገኘን፣ ተሳፍረን ጒዞአችንን
ቀጠልን። 3ቆጵሮስ በታየችን ጊዜ፣ ወደ
ግራ ትተናት ዐለፍንና ወደ ሶርያ አመራ
ን፤ መርከባችን ጭነቱን በጢሮስ ማራገፍ
ስለ ነበረበት፣ እኛም እዚያው ወረድን።
4ደቀ መዛሙርትንም በዚያ አግኝተን፣
ሰባት ቀን ከእነርሱ ጋር ተቀመጥን።
እነርሱም በመንፈስ ሆነው ጳውሎስ ወደ
ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ ነገሩት። 5የሖይታ
ጊዜያችን ባለቀ ጊዜ፣ ትተናቸው ጒዞ
አችንን ቀጠልን፤ ደቀ መዛሙርቱም ሁሉ
ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር እስከ
ከተማው ውጭ ድረስ ሸኙን፤ በባሕሩም
ዳር ተንበርክከን ጸለይን፤ 6ከተሰነባበት
ንም በኋላ እኛ ወደ መርከቡ ገባን፤ እነ
ርሱም ወደ ቤታቸው ተመለሱ።
7ከጢሮስ ተነሥተን ጒዞአችንን በመ
ቀጠል ጴጤሌማይስ ደረስን፤ ከመርከብ
ወርደንም ለወንድሞች ሰላምታ ካቀረብን
በኋላ፣ አንድ ቀን ከእነርሱ ጋር ሖየን።
8በማግስቱ ከዚያ ተነሥተን ቂሳርያ ደረ
ስን፤ ከሰባቱ ወንጌላውያን አንዱ በሆነው
በፊልጶስ ቤትም ዐረፍን። 9እርሱም ትንቢት
የሚናገሩ አራት ደናግል ሴቶች ልጆች
ነበሩት።
10በዚያም ብዙ ቀን ከተቀመጥን በኋላ
አጋቦስ የተባለ ነቢይ ከይሁዳ ወረደ፤
11ወደ እኛም መጣና የጳውሎስን መታጠ
ቂያ ወሰደ፤ የራሱንም እጅና እግር በማ
ሰር፣ “መንፈስ ቅዱስ፣ ‘በኢየሩሳሌም ያሉ
አይሁድ የዚህን መታጠቂያ ባለቤት እን
ዲህ አድርገው በማሰር ለአሕዛብ አሳ
ልፈው ይሰጡታል’ ይላል” አለ።
12ይህን ስንሰማ እኛና በዚያም የሚኖሩት
ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ
ለመነው። 13ጳውሎስ ግን፣ “ለምን እንዲህ
እያለቀሳችሁ ልቤን ታባቡታላችሁ? እኔ
መታሰር ቀርቶ ስለ ጌታ ኢየሱስ ስም
በኢየሩሳሌም ለመሞት እንኳን ዝግጁ ነኝ’
አላቸው። 14ምክራችንን አልቀበል ስላለን፣
“እንግዲህ የጌታ ፈቃድ ይሁን” ብለን
ተውነው።
15ከዚህ በኋላ፣ ተዘጋጅተን ወደ ኢየሩ
ሳሌም ወጣን። 16በቂሳርያ ከነበሩት ደቀ
መዛሙርትም አንዳንዶቹ ወደ ምናሶን
ቤት ይዘውን መጡ፤ እኛም በዚያው ተቀ
መጥን። ምናሶን የቆጵሮስ ሰው ሲሆን፣
ከመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት አንዱ
ነበረ።

## ጳውሎስ ኢየሩሳሌም ደረሰ

17ኢየሩሳሌም በደረስን ጊዜ፣ ወንድሞች
በደስታ ተቀበሉን። 18በማግስቱም ጳውሎ
ስና ሌሎቻችንም ያዕቆብን ለማየት
ሄድን፤ ሽማግሌዎችም ሁሉ በዚያ ነበሩ።
19ጳውሎስም ሰላምታ ካቀረበላቸው በኋላ፣
እግዚአብሔር በእርሱ አገልግሎት አማካይ
ነት በአሕዛብ መካከል ያደረገውን ሁሉ
በዝርዝር አስረዳቸው።
20እነርሱም ይህን ሲሰሙ፣ እግዚአብሔ
ርን አመሰገኑ፤ ጳውሎስንም እንዲህ አሉት፤
“ወንድም ሆይ፤ በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ
አይሁድ እንዳመኑ ተመልከት፤ ሁሉም
ደግሞ ለሙሴ ሕግ የሚቀኑ ናቸው። 21በአሕ
ዛብ መካከል የሚኖሩ አይሁድ ሁሉ
ሙሴን እንዲተዉና ልጆቻቸውን እንዳይ
ገርዙ፣ በሖየው ልማዳችን መሠረት እንዳ
ይኖሩ እንደምታስተምር ስለ አንተ ተነ
ግሮአቸዋል። 22መምጣትህን መስማታቸው
የማይቀር ነውና፣ እንግዲህ ምን እናድ
ርግ? 23ስለዚህ የምንልህን አድርግ። ስእ
ለት ያለባቸው አራት ሰዎች በእኛ ዘንድ
አሉ፤ 24እነዚህን ሰዎች ይዘህ ከእነርሱ ጋር
የመንጻቱን ሥርዐት ፈጽም፤ ራሳቸውንም
እንዲላጩ የሚጠየቀውን ገንዘቡን ክፈልላ
ቸው፤ በዚህም ስለ አንተ የተነገራቸው ሰዎች
ሁሉ፣ የሰሙት እውነት እንዳልሆነና አንተ
ራስህ ሕጉን ጠብቀህ የምትኖር መሆንህን
ያውቃሉ። 25ከአሕዛብ ወገን ያመኑትን
በተመለከተ ግን ለጣዖት የተሠዋ ምግብ፣
ደምና ታንቆ የሞተ ከብት እንዳይበሉ፣
ደግሞም ከዝሙት ርኵሰት ራሳቸውን
እንዲጠብቁ ወስነን ጽፈንላቸዋል።”

20፥33 1ሳሙ 12፥3፤1ቆሮ 9፥12፤2ቆሮ 2፥17፤7፥2፤11፥9፤12፥14-17፤1ተሰ 2፥5
20፥34 ሐሥ 18፥3
20፥36 ሉቃ 22፥41፤ሐሥ 9፥40፤21፥5
20፥37 ሉቃ 15፥20
20፥38 ቊ 25፤ ሐሥ 21፥5
21፥1 ሐሥ 16፥10
21፥2 ሐሥ 11፥19
21፥3 ሉቃ 2፥2
21፥4 ቊ 11፤ ሐሥ 11፥26፤20፥23
21፥5 ሉቃ 22፥41፤ ሐሥ 9፥40፤20፥36
21፥7 ሐሥ 1፥16፤ 12፥20
21፥8 ሐሥ 6፥5፤ 8፥5-40፤ኤፌ 4፥11፤ 2ጢሞ 4፥5
21፥9 ዘፀ 15፥20፤ መሳ 4፥4፤ነህ 6፥14፤ ሉቃ 2፥36፤ሐሥ 2፥17፤1ቆሮ 11፥5
21፥10 ሐሥ 11፥28
21፥11 ቊ 33፤1ነገ 22፥11፤ኢሳ 20፥2-4፤ ኤር 13፥1-11፤ ማቴ 20፥19፤ ሐሥ 8፥29
21፥13 ዮሐ 15፥21፤ ሐሥ 9፥16፤20፥24
21፥14 ሩት 1፥18፤ ማቴ 26፥39
21፥15 ሐሥ 19፥21
21፥16 ቊ 3፥4፤ሐሥ 8፥40
21፥17 ሐሥ 9፥30፤15፥4
21፥18 ሐሥ 11፥30፤15፥13
21፥19 ሐሥ 1፥7፤ 14፥27፤15፥4፥12
21፥20 ሐሥ 15፥1፡ 5፤22፥3፤ሮሜ 10፥2፤ ገላ 1፥14፤ፊል 3፥6
21፥21 ቊ 28፤ሐሥ 6፥14፤15፥19-21፤ 1ቆሮ 7፥18፡19
21፥23 ዘኍ 6፥2፡5፤ሐሥ 18፥18
21፥24 ቊ 26፤ ሐሥ 18፥18፤24፥18
21፥25 ሐሥ 15፥20፡29

26ጳውሎስም በማግስቱ ሰዎቹን ይዞ
ሄደ፤ አብሮአቸውም የመንጻቱን ሥርዐት
ፈጸመ። ከዚያም የመንጻቱ ሥርዐት መቼ
እንደሚያበቃና የእያንዳንዳቸውም መሥ
ዋዕት መቼ እንደሚቀርብ ለማስታወቅ ወደ
ቤተ መቅደስ ገባ።

## ጳውሎስ ተያዘ

27ሰባቱ ቀንም ሊፈጸም ሲቃረብ፣ ከእ
ስያ አውራጃ የመጡት አይሁድ ጳውሎስን
በቤተ መቅደስ ባዩት ጊዜ፣ ሕዝቡን ሁሉ
አነሣሥተው ያዙት፤ 28እንዲህም እያሉ
ጮኹ፤ "የእስራኤል ሰዎች ሆይ፤ ርዱን! ሕዝ
ባችንንና ሕጋችንን እንዲሁም ይህን ስፍራ
በማጥላላት በደረሰበት ስፍራ የሚገኙትን
ሰዎች ሁሉ የሚያስተምረው ሰው ይህ
ነው፤ ከዚህም በላይ ግሪኮችን ወደ ቤተ
መቅደስ እያስገባ ይህን የተቀደሰ ስፍራ
የሚያረክሰው እርሱ ነው።" 29ይህንም
ያሉት ቀደም ሲል፣ የኤፌሶኑን ሰው
ጥሮፊሞስን ከጳውሎስ ጋር በከተማው
ውስጥ ስላዩት፣ ጳውሎስ እርሱንም ወደ
ቤተ መቅደስ ይዞ የገባ ስለ መሰላቸው
ነበር።
30ከተማው በሙሉ ታወከ፤ ሕዝቡም ከየ
አቅጣጫው እየተሯሯጡ መጡ፤ ጳውሎስ
ንም ይዘው እየጐተቱት ከቤተ መቅደሱ
ግቢ አወጡት፤ በሮቹም ወዲያውኑ ተዘጉ።
31ሊገድሉት ሲፈልጉም የኢየሩሳሌም ከተማ
ፍጹም ታወከች፤ ወሬውም ለሮማ ጦር
አዛዥ ደረሰው። 32እርሱም ወዲያው አንዳ
ንድ የጦር መኰንኖችንና ወታደሮችን ይዞ
እየሮጠ ወደ እነርሱ ወረደ፤ እነርሱም
መኰንኖቹንና ወታደሮቹን ባዩ ጊዜ ጳው
ሎስን መደብደብ ተዉ።
33የጦር አዛዡም ቀርቦ ያዘው፤
በሁለት ሰንሰለትም እንዲታሰር ትእዛዝ
ሰጠ፤ ከዚያም ማን መሆኑንና ምን እንዳ
ደረገ ጠየቀ። 34ሕዝቡም ከፊሉ አንድ
ነገር ሲናገር፣ ከፊሉ ደግሞ ሌላ ይናገር
ነበር፤ ከጫጫታው የተነሣም አዛዡ ምንም
ነገር ሊሰማ አልቻለም፤ ስለዚህ ጳውሎስ
ወደ ጦር ሰፈር እንዲወሰድ አዘዘ። 35ከሕ
ዝቡ ሁካታ የተነሣ፣ ጳውሎስ ወደ መው
ጫው ደረጃ ሲደርስ ወታደሮቹ ይሸከ
ሙት ዘንድ ግድ ሆነባቸው። 36ከኋላ የተ
ከተለውም ሕዝብ፣ "አስወግደው!" እያለ
ይጮኽ ነበር።

## ጳውሎስ ለሕዝቡ ተናገረ

37ወታደሮቹ ወደ ጦር ሰፈር ይዘውት
ሊሄዱ ሲሉ፣ ጳውሎስ ጦር አዛዡን፣ "አንድ
ነገር እንድነግርህ ፍቀድልኝ?" አለው።
አዛዡም እንዲህ አለው፤ "የግሪክ ቋንቋ
ታውቃለህ? 38አንተ ከዚህ ቀደም ዐመፅ
አስነሥተህ፣ አራት ሺህ ነፍሰ ገዳዮችን
ወደ በረሓ ያሸፈትኸው ግብፃዊ አይደለህ
ምን?"
39ጳውሎስም፣ "እኔስ በኪልቅያ ያለችው
የታዋቂዋ የጠርሴስ ከተማ ነዋሪ የሆንሁ
አይሁዳዊ ነኝ፤ ለሕዝቡ ንግግር እንዳደርግ
ፍቀድልኝ" አለው።
40ጳውሎስም የጦር አዛዡን ካስፈቀደ
በኋላ፣ በደረጃው ላይ ቆሞ ሕዝቡን በእጁ
ጠቀሰ፤ ሁሉም ጸጥ ባሉ ጊዜ፣ በዕብራ
ይስጥ[ሐ] ቋንቋ እንዲህ አለ፤

22 "ወንድሞችና አባቶች ሆይ፤ አሁን
የማቀርብላችሁን የመከላከያ መል
ሴን ስሙኝ።"
2እነርሱም በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲናገር
በሰሙ ጊዜ ከፊት ይልቅ ጸጥ አሉ።
ጳውሎስም እንዲህ አለ፤ 3"እኔ በኪል
ቅያ በምትገኘው በጠርሴስ የተወለድሁ
አይሁዳዊ ስሆን፣ ያደግሁት ግን በዚህ
ከተማ ነው። የአባቶቻችንን ሕግ በገማ
ልያል እግር ሥር ተቀምጬ በሚገባ
ተም ሬአለሁ፤ ዛሬ እናንተ እንዲህ
የምትቀኑ ለትን ያህል እኔም ለእግዚአብሐ
ር እቀና ነበር። 4ይህን መንገድ
የሚከተሉትንም እስከ ሞት ድረስ
እያሳደድሁ፣ ወንዶ ችንም ሴቶችንም
አስሬ ወደ ወህኒ እጥላ ቸው ነበር። 5ይህን
ተግባሬን ሊቀ ካህናቱም ሆነ ሸንጎው ሁሉ
ሊመሰክሩ ይችላሉ። ከእነርሱ ደብዳቤ
ተቀብዬ ደማስቆ ወዳሉት ወንድሞቻቸው
በመሄድ፣ እነዚህን ሰዎች አሳስሬ ወደ ኢ
የሩሳሌም አም ጥቼ ለማስቀጣት ወደዚያ
እሄድ ነበር።
6"ስንጓዝም እኩለ ቀን ገደማ ወደ ደማ
ስቆ እንደ ተቃረብሁ፣ ድንገት ታላቅ
ብርሃን ከሰማይ በዙሪያዬ በራ፤ 7እኔም
ምድር ላይ ወደቅሁ፤ ከዚያም፣ 'ሳውል፤
ሳውል፤ ለምን ታሳድደኛለህ?' የሚለኝን
ድምፅ ሰማሁ።
8"እኔም፣ 'ጌታ ሆይ፤ አንተ ማን ነህ?'
አልሁት።
"እርሱም፣ 'አንተ የምታሳድደኝ የናዝ
ሬቱ ኢየሱስ ነኝ' አለኝ። 9ከእኔ ጋር የነ
በሩትም ብርሃኑን አዩ፤ ነገር ግን የሚናገ
ረኝን የእርሱን ድምፅ በትክክል አልሰ
ሙም።
10"እኔም፣ 'ጌታ ሆይ፤ ምን ላድርግ?'
አልሁት።
"ጌታም፣ 'ተነሥተህ ወደ ደማስቆ ሂድ፤

21፥26 ዘኍ6፥13-20፤ሐሥ24፥18
21፥27 ኤር26፥ 8፤ ሐሥ24፥18፤26፥21፤1ተሰ2፥16
21፥28 ማቴ24፥15፤ሐሥ6፥13፤24፥5፡6
21፥29 ሐሥ18፥19፤20፥4፤2ጢሞ4፥20
21፥30 ሐሥ16፥19፤26፥21
21፥32 ሐሥ23፥27
21፥33 ቀ11፤ ሐሥ 12፥6፤20፥23፤22፥29፤ ኤፌ6፥20፤2ጢሞ2፥9
21፥34 ቀ37፤ ሐሥ 19፥32፤22፥24፤23፥10፡16፡32
21፥35 ቀ40
21፥36 ሉቃ23፥18፤ዮሐ19፥15፤ ሐሥ 22፥22
21፥37 ቀ34
21፥38 ማቴ24፥26፤ ሐሥ5፥36
21፥39 ሐሥ6፥9፤ 9፥11
21፥40 ዮሐ5፥2፤ ሐሥ12፥17
22፥1 ሐሥ7፥2
22፥2 ዮሐ5፥2፤ሐሥ21፥40
22፥3 1ነገ19፥10፤ ሉቃ10፥39፤ሐሥ 5፥34፤6፥9፤9፥11፤21፥20፡39፤26፥5
22፥4 ቀ19፡20፤ ሐሥ8፥3፤9፥2
22፥5 ሉቃ22፥66፤ ሐሥ1፥16፤2፤29፤ 9፥2፤13፤26፤23፥1፤28፥17፡21፤ ሮሜ7፥1፤ 9፥3
22፥6 ሐሥ9፥3
22፥8 ማር1፥24
22፥9 ሐሥ9፥7፤ 26፥13
22፥10 ሐሥ16፥30

ሐ40 ወይም አራማይክ፤ እንዲሁም ቊ 22፥2

በዚያም ልታደርገው የሚገባህን ሁሉ
ይነግሩሃል’ አለኝ። [11]ከብርሃኑም ጸዳል
የተነሣ ዐይኔ ስለታወረ፣ ከእኔ ጋር የነ
በሩት እጄን ይዘው እየመሩ ወደ ደማስቆ
አደረሱኝ።
[12]“ከዚያም ሐናንያ የተባለ ሰው ሊያ
የኝ ወደ እኔ መጣ፤ እርሱም ሕግን በጥ
ንቃቄ የሚጠብቅና በዚያ በሚኖሩት
አይሁድ ሁሉ ዘንድ እጅግ የተከበረ ሰው
ነበረ። [13]በአጠገቤም ቆሞ፣ ‘ወንድም
ሳውል ሆይ፤ ዐይኖችህ ይብሩልህ!’ አለኝ፤
እኔም በዚያችው ቅጽበት አየሁት።
[14]“እርሱም ቀጥሎ እንዲህ አለ፤ ‘የአ
ባቶቻችን አምላክ ፈቃዱን እንድታውቅ፣
ጻድቁን እንድታይና ቃሉን ከአንደበቱ
እንድትሰማ መርጦሃል፤ [15]ስላየኸውና ስለ
ሰማኸው ነገር በሰው ሁሉ ፊት ምስክር
ትሆነዋለህና። [16]ታዲያ፣ አሁን ምን ትጠ
ብቃለህ? ተነሥተህ ስሙን እየጠራህ ተጠ
መቅ፤ ከኀጢአትህም ታጠብ።’
[17]“ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሼ በቤተ
መቅደስ ስጸልይም ተመሰጥሁ፤ [18]ጌታም
ሲናገረኝ አየሁ፤ እርሱም አሁኑኑ፣ ‘ፈጥነህ
ከኢየሩሳሌም ውጣ! ስለ እኔ የምትመሰ
ክረውን አይቀበሉህምና’ አለኝ።
[19]“እኔም እንዲህ አልሁት፤ ‘ጌታ ሆይ፤
በአንተ የሚያምኑትን ሰዎች ለማሰርና
ለመደብደብ፣ በየምኵራቡ ስዞር እንደ
ነበር እነዚህ ሰዎች ያውቃሉ፤ [20]ደግሞም
የአንተን ሰማዕትᵐ የእስጢፋኖስን ደም
በሚያፈሱበት ጊዜ፣ በድርጊታቸው ተስ
ማምቼ በቦታው ቆሜ የገዳዮቹን ልብስ
እጠብቅ ነበር።’

“ጌታም፣ ‘ሂድ፤ በሩቅ ወዳሉት አሕዛብ
እልክሃለሁና’ አለኝ።”

### ጳውሎስ የሮም ዜጋ መሆኑ ታወቀ

[22]ሕዝቡም ይህን ቃል እስኪናገር ድረስ
ሰሙት፤ ከዚህ በኋላ ግን ድምፃቸውን ከፍ
በማድረግ፣ “ይህስ ከምድር ገጽ ይወገድ!
በሕይወት መኖር አይገባውም!” ብለው
ጮኹበት።
[23]እነርሱም እየጮኹና ልብሳቸውን
እየ ወረወሩ፣ ትቢያም ወደ ላይ እየበተኑ
ሳሉ፣ [24]የጦር አዛዡ ጳውሎስን ወደ ጦር
ሰፈር እንዲያስገቡትና ሕዝቡ ለምን እንዲህ
እንደሚጮኹበት እየተገረፈ እንዲመረ
መር ትእዛዝ ሰጠ። [25]ጳውሎስም በጠፍር
ወጥረው ሊገርፉት ሲሉ፣ አጠገቡ የቆ
መውን የመቶ አለቃ፣ “አንድን የሮም
ዜጋ ያለ ፍርድ ለመግረፍ ሕግ ይፈቅድ
ላችኋልን?” አለው።

22፥11 ሐሥ9፥8
22፥12 ሐሥ9፥17፤ 10፥22
22፥14 ሐሥ3፥13፤ 7፥52፤1ቆሮ15፥8
22፥15 ቀኁ14፤ሐሥ 23፥11፤26፥16
22፥16 ዘሌ8፥6፤ መዝ51፥2፤ሕዝ36፥ 25፤ዮሐ3፥5፤ሐሥ2፥ 38፤ሮሜ10፥13፤ 1ቆሮ፥11፤ ኤፌ5፥26፤ ቲቶ3፥5፤ዕብ10፥22፤ 1ጴጥ3፥21
22፥17 ሐሥ9፥26፤ 10፥10
22፥19 ቀኁ4፤ማቴ 10፥17፤ሐሥ8፥3
22፥20 ሐሥ7፥57-60፤8፥1
22፥21 ሐሥ9፥15፤ 13፥46
22፥22 ሐሥ21፥ 36፤25፥24
22፥23 2ሳሙ16፥ 13፤ሐሥ7፥58
22፥24 ቀኁ29፤ሐሥ 21፥34
22፥25 ሐሥ16፥37
22፥29 ቀኁ24፡ 25፤ሐሥ16፥38፤ 21፥33
22፥30 ማቴ5፥22፤ ሐሥ21፥33፤23፥28
23፥1 ሐሥ22፥5፡ 30፤24፥16፤1ቆሮ4፥4፤ 2ቆሮ1፥12፤1ጢሞ 1፥5፡19፤3፥9፤ 2ጢሞ1፥3፤ዕብ9፥14፤ 10፥22፤13፥18፤1ጴጥ3 ፥16፥21
23፥2 ዮሐ18፥22፤ ሐሥ24፥1
23፥3 ዘሌ19፥15፤ ዘዳ25፥1፡2፤ማቴ23፥ 27፤ዮሐ7፥51
23፥5 ዘፀ22፥28
23፥6 ቀኁ7፥8፤ ሐሥ 4፥1፤22፥5፤ 24፥15፡ 21፤26፥5፡8፤ፊል3፥5

[26]የመቶ አለቃውም ይህን ሲሰማ፣
ወደ ጦር አዛዡ ቀርቦ፣ “ምን እያደረግህ
እንደ ሆነ ዐውቀሃል? ሰውየው እኮ ሮማዊ
ነው” አለው።
[27]አዛዡም ወደ ጳውሎስ ቀርቦ፣
“አንተ ሰው እስቲ ንገረኝ፤ ሮማዊ ነህን?”
አለው።
እርሱም፣ “አዎን፤ ነኝ” አለው።
[28]አዛዡም መልሶ፣ “እኔ ይህን ዜግነት
ያገኘሁት ብዙ ገንዘብ አውጥቼ ነው” አለ።
ጳውሎስም፣ “እኔ ግን ከተወለድሁ ጀምሮ
ሮማዊ ነኝ” አለው።
[29]ስለዚህ እነዚያ ሊመረምሩት ያሰ
ቡት ሰዎች ወዲያው ከእርሱ ሸሹ፤ የጦር
አዛዡም የሮም ዜጋ መሆኑን ባወቀ ጊዜ፣
በሰንሰለት አስሮት ስለ ነበር ፈራ።

### ጳውሎስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት ቀረበ

[30]በማግስቱም የጦር አዛዡ፣ አይሁድ
ጳውሎስን የከሰሱበት ትክክለኛው ምክን
ያት ምን እንደ ሆነ ለማወቅ ስለ ፈለገ
ፈታው፤ ከዚያም የካህናት አለቆችና የአይ
ሁድ ሸንጎ አባላት በሙሉ እንዲሰበሰቡ
አዘዘ፤ ጳውሎስንም ከደረጃው አውርዶ
በፊታቸው አቆመው።

23 ጳውሎስም ወደ ሸንጎው ትኵር
ብሎ በመመልከት፣ “ወንድሞች
ሆይ፤ እኔ እስከዚች ቀን ድረስ በእግዚአብሔር
ፊት በንጹሕ ሕሊና ተመላልሻለሁ” አለ።
[2]በዚህ ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ሐናንያ በጳው
ሎስ አጠገብ የቆሙትን ሰዎች አፉን እን
ዲመቱት አዘዘ። [3]ጳውሎስም፣ “አንተ በኖራ
የተለሰንህ ግድግዳ! እግዚአብሔር ደግሞ
አንተን ይመታሃል፤ በሕጉ መሠረት ልት
ፈርድብኝ ተቀምጠህ ሳለህ፣ ያለ ሕግ ስላ
ስመታኸኝ አንተ ራስህ ሕጉን ጥሰሃል”
አለው።
[4]ጳውሎስ አጠገብ ቆመው የነበሩትም፣
“የእግዚአብሔርን ሊቀ ካህናት ደፍረህ
ትሰድ ባለህን?” አሉት።
[5]ጳውሎስም፣ “ወንድሞች ሆይ፤ ሊቀ
ካህናት መሆኑን ባለማወቄ ነው፤ ‘በሕዝ
ብህ አለቃ ላይ ክፉ አትናገር’ ተብሎ ተጽ
ፎአልና” አላቸው።
[6]ጳውሎስም ሕዝቡ፣ ከፊሎቹ ሰዱቃው
ያን፣ ከፊሎቹ ፈሪሳውያን መሆናቸውን
ስላወቀ፣ “ወንድሞቼ ሆይ፤ እኔ ከፈሪሳዊ
የተወለድሁ ፈሪሳዊ ነኝ፣ ለፍርድ የቀረ
ብሁትም የሙታንን ትንሣኤ ተስፋ በማ

ᵐ20 ወይም ምስክር

ድረጌ ነው" ሲል በሸንጎው ፊት ጮኸ።
7ይህንንም በተናገረ ጊዜ፣ በፈሪሳውያንና
በሰዱቃውያን መካከል ጠብ ተነሣ፤ ሸንጎ
ውም ለሁለት ተከፈለ። 8ሰዱቃውያን
የሙታን ትንሣኤ የለም፤ መላእክትም
መናፍስትም የሉም የሚሉ ሲሆኑ፣ ፈሪሳ
ውያን ግን በእነዚህ ሁሉ መኖር የሚያ
ምኑ ነበሩ።

9ታላቅ ሁከትም ሆነ፤ ከፈሪሳውያን ወገን
የሆኑ አንዳንድ የኦሪት ሕግ መምህራንም
ተነሥተው፣ "በዚህ ሰው ላይ ምንም ጥፋት
አላገኘንበትም፤ መንፈስ ወይም መልአክ
ተናግሮትስ እንደ ሆነ ምን ይታወቃል?"
በማለት አጥብቀው ተከራከሩ። 10ጠቡ ከማ
የሉ የተነሣም አዛዡ ጳውሎስን እንዳይገ
ነጣጥሉት ፈራ፤ ስለዚህ ወታደሮቹ ወር
ደው ከመካከላቸው ነጥቀው ወደ ጦሩ
ሰፈር እንዲያስገቡት አዘዘ።

11በሚቀጥለውም ሌሊት ጌታ በአጠ
ገቡ ቆሞ፣ "ጳውሎስ ሆይ፤ አይዞህ! በኢ
የሩሳሌም እንደ መሰከርህልኝ፣ በሮምም
ደግሞ ልትመሰክርልኝ ይገባሃል" አለው።

### ጳውሎስን ለመግደል የተደረገ ሤራ

12በነጋም ጊዜ፣ አይሁድ ተሰብስበው በማ
ሤር ጳውሎስን እስኪገድሉ ድረስ እህል
ውሃ ላለመቅመስ ተማማሉ። በዚህ ሤራ
13የተማማሉትም ከአርባ በላይ ነበሩ።
14እነርሱም ወደ ካህናት አለቆችና ወደ ሽማ
ግሌዎች ሄደው እንዲህ አሉ፤ "ጳውሎስን
ሳንገድል እህል ላለመቅመስ ጽኑ መሐላ
አድርገናል። 15እንግዲህ እናንተ ከሸንጎው
ጋር ሆናችሁ፣ ስለ ጉዳዩ ትክክለኛ የሆነ
ተጨማሪ መረጃ ከእርሱ እንደምትፈልጉ
አስመስላችሁ ጳውሎስን ወደ እናንተ እን
ዲሰደው የጦር አዛዡን ለምኑት፤ እኛም
ገና ወደዚህ ሳይደርስ ልንገድለው ዝግጁ ነን።"

16ነገር ግን የጳውሎስ የእኅት ልጅ ስለ
ሤራው በመስማቱ፣ ወደ ጦሩ ሰፈር
ገብቶ ሁኔታውን ለጳውሎስ ነገረው።

17ጳውሎስም ከመቶ አለቆቹ አንዱን
ጠርቶ፣ "ይህ ልጅ ለጦር አዛዡ የሚነግረው
ነገር ስላለ ወደ እርሱ ውሰደው" አለው።
18እርሱም ወደ ጦር አዛዡ ወሰደው።

የመቶ አለቃውም፣ "እስረኛው ጳውሎስ
ጠርቶኝ፣ ይህ ጕልማሳ የሚነግርህ ነገር
ስላለው ወደ አንተ እንዳቀርበው ለመነኝ"
አለው።

19አዛዡም የጕልማሳውን እጅ ይዞ
ለብቻው ገለል በማድረግ፣ "ልትነግረኝ
የምትፈልገው ምንድን ነው?" አለው።

20ልጁም እንዲህ አለው፤ "አይሁድ ስለ

23፥8 ማቴ22፥23፤ 1ቆሮ15፥12
23፥9 ቍ29፤ኤር 26፥16፤ማር2፥16፤ ሉቃ23፥4፤ሐሥ22፥7፡ 17፡18፤25፥25፤26፥ 31፤28፥18
23፥10 ሐሥ21፥34
23፥11 ማቴ14፥27፤ ሐሥ19፥21፤28፥23
23፥12 ቍ14፡21፡ 30፤ሐሥ20፥3፤25፥3
23፥14 ቍ12
23፥15 ቍ1ሐሥ 22፥30
23፥16 ቍ10፤ ሐሥ 21፥34
23፥18 ኤፌ3፥1
23፥20 ቍ1፡14፡15
23፥21 ቍ12፡13፡14
23፥23 ቍ33፤ ሐሥ 8፥40
23፥24 ቍ26፡ 33፤ሐሥ24፥1-3፡10፤ 25፥14
23፥26 ሉቃ1፥3፤ ሐሥ15፥23፤24፥3፤ 26፥25
23፥27 ሐሥ21፥ 32፡33፤22፥25-29
23፥28 ሐሥ22፥30
23፥29 ቍ9፤ ሐሥ 18፥15፤25፥19
23፥30 ቍ20፡ 21፡35፤ሐሥ20፥3፤ 24፥19፤25፥16
23፥32 ቍ23፤ ሐሥ 21፥34
23፥33 ቍ23፡24፡ 26፤ሐሥ8፥40
23፥34 ሐሥ6፥9፤ 21፥39
23፥35 ቍ30፤ ሐሥ 24፥19፡27፤ 25፥16

እርሱ ትክክለኛ የሆነ ተጨማሪ መረጃ ለማ
ግኘት የፈለጉ በመምሰል፣ ጳውሎስን ነገ
ሸንጎው ፊት እንድታቀርብላቸው ሊለ
ምኑህ ተስማምተዋል። 21ስለዚህ እሺ አት
በላቸው፤ ምክንያቱም ከመካከላቸው ከአ
ርባ በላይ የሚሆኑት ሊገድሉት አድፍጠው
እየጠበቁት ነው፤ ደግሞም እስኪገድሉት
ድረስ እህል ውሃ ላለመቅመስ ተማምለ
ዋል፤ አሁንም ተዘጋጅተው የአንተን መልስ
እየተጠባበቁ ነው።"

22የጦር አዛዡም፣ "ይህን ለእኔ የገለጥ
ህልኝን ነገር ለማንም እንዳትናገር" ብሎ
ጕልማሳውን አስጠንቅቆ አሰናበተው።

### ጳውሎስ ወደ ቂሳርያ ተላከ

23ከዚያም ከመቶ አለቆቹ[ሠ] ሁለቱን
ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ "ከምሽቱ ሦስት
ሰዓት፣ ወደ ቂሳርያ የሚሄዱ ሁለት
መቶ ወታደሮች፣ ሰባ ፈረሰኞችና ሁለት
መቶ ባለ ጦር ጭፍራ አዘጋጁ፤ 24ደግሞም
ጳው ሎስ ተቀምጦበት ወደ አገረ ገዥ
ወደ ፊልክስ በደኅና የሚደርስበት ከብት
ይዘ ጋጅ።"

25ደብዳቤም ጻፈ፤ እንዲህ የሚል፦

26ከቀላውዴዎስ ሉስዩስ፤

ለክቡር አገረ ገዥ ለፊልክስ፤

ሰላም ለአንተ ይሁን።

አይሁድ፣ ይህን ሰው ይዘው ሊገድ
ሉት ነበር፤ ነገር ግን የሮም ዜጋ መሆኑን
ስላወቅሁ፣ ከወታደሮቼ ጋር ደርሼ አተ
ረፍሁት። 28ለምን ሊከሱት እንደ ፈለጉ
ለማወቅም፣ ወደ ሸንጎአቸው አቀረብሁት።
29የተከሰሰውም ሕጋቸውን በተመለከተ
እንጂ ለሞት ወይም ለእስራት የሚያበቃ
እንዳልሆነ ተረድቻለሁ። 30አይሁድ ግን
በዚህ ሰው ላይ ማሤራቸውን በተረዳሁ ጊዜ፣
ወዲያው ወደ አንተ ላክሁት፤ ከሳሾቹም
ከእርሱ ጋር ያላቸውን ክርክር ለአንተ እን
ዲያቀርቡ አዘዝኋቸው።

31ስለዚህ ወታደሮቹ በታዘዙት መሠ
ረት፣ ጳውሎስን ይዘው በሌሊት እስከ
አንቲጳጥሪስ ድረስ ወሰዱት። 32በማግስቱ፣
ፈረሰኞቹ ብቻ እንዲያደርሱት አድ
ርገው፣ ሌሎቹ ወደ ጦር ሰፈር ተመለሱ።
33ፈረሰኞቹም ቂሳርያ በደረሱ ጊዜ፣ ደብ
ዳቤውን ለአገረ ገዡው ሰጡት፤ ጳውሎስ
ንም አስረከቡት። 34አገረ ገዡም ደብዳቤ
ውን ካነበበ በኋላ፣ ጳውሎስን ከየትኛው
አውራጃ እንደ መጣ ጠየቀው፤ የኪልቅያ
ሰው መሆኑን ባወቀ ጊዜ፣ 35"የአንተን

[ሠ]23 በግሪኩ የዚህ ቃል ትርጉም አይታወቅም።

ጕዳይ ከሳሾችህ ሲቀርቡ አያለሁ” አለው፡፡
ከዚያም ጳውሎስ በሄሮድስ ግቢ ውስጥ
እንዲጠበቅ አዘዘ፡፡

### ጳውሎስ በፊልክስ ፊት ቀረበ

24 ከአምስት ቀን በኋላ፣ ሊቀ ካህ
ናቱ ሐናንያ ከአንዳንድ ሽማግ
ሌዎችና ጠርጡለስ ከሚባል ጠበቃ ጋር
ወደ ቂሳርያ ወረደ፤ በጳውሎስም ላይ ያላ
ቸውን ክስ ለአገረ ገዡ አቀረቡ፡፡ 2ጳው
ሎስ ተጠርቶ በቀረበ ጊዜ፣ ጠርጠሉስ
እንዲህ ሲል ክሱን አቀረበ፤ “ክቡር ፊል
ክስ ሆይ፤ በአንተ ዘመን ሰላም ለብዙ ጊዜ
ሰፍኖልናል፤ አርቆ አስተዋይነትህም ለዚህ
ሕዝብ መሻሻልን አስገኝቶለታል፤ 3በየቦታ
ውና በየጊዜው ይህን ውለታ በታላቅ ምስ
ጋና እንቀበላለን፡፡ 4ነገር ግን ይበልጥ እን
ዳላደክምህ፣ በአጭሩ እንድትሰማን መል
ካም ፈቃድህን እለምንሃለሁ፡፡
5“ይህ ሰው፣ በዓለም ባሉት አይሁድ
ሁሉ መካከል በሽታ ሆኖ ሁከት የሚያስ
ነሣ፣ ደግሞም የናዝራውያን ወገን ቀንደኛ
መሪ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ 6ከዚህም በላይ
ቤተ መቅደሱን ለማርከስ ሲሞክር አግኝ
ተን ያዝ ነው፡፡ በሕጋችንም መሠረት ልን
ፈርድበት አስበን ነበር፤ 7ነገር ግን የጦር
አዛዡ ሉስዮስ መጥቶ በታላቅ ኀይል ከእ
ጃችን ነጥቆ ወሰደው፤ ከሳሾቹም ወደ
አንተ እንዲመጡ አዘዘ፡፡ 8እንግዲህ አንተ
ራስህ መርምረኸው እርሱን የከሰስንበትን
ነገር ሁሉ እውነት መሆኑን ልታረጋግጥ
ትችላለህ፡፡”ረ
9አይሁድም ነገሩን እንደተባለው መሆ
ኑን በመደገፍ በክሱ ተባበሩ፡፡
10አገረ ገዡም እንዲናገር በእጁ ምል
ክት በሰጠው ጊዜ፣ ጳውሎስ እንዲህ ሲል
መለሰ፤ “ከብዙ ዘመን ጀምሮ የዚህ ሕዝብ
ፈራጅ መሆንህን ዐውቃለሁ፤ ስለዚህ የመ
ከላከያ መልሴን የማቀርበው በደስታ
ነው፡፡ 11ልሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም የመ
ጣሁት ከዐሥራ ሁለት ቀን በፊት መሆ
ኑን አንተው ራስህ በቀላሉ ማረጋገጥ ትች
ላለህ፡፡ 12ከሳሾቼም በቤተ መቅደስ ከማ
ንም ጋር ስከራከር ወይም በምኵራብ
ወይም በከተማ ውስጥ በየትኛውም ስፍራ ሕዝ
ብን ሳነሣሣ አላገኙኝም፡፡ 13አሁንም
ለተከሰስሁበት ነገር ማስረጃ ሊያቀርቡልህ
አይችሉም፡፡ 14ይሁን እንጂ እነርሱ ኑፋቄ
በሚሉት፣ በጌታ መንገድ የአባቶቻችንን
አምላክ አመልካለሁ፡፡ 15እኔም እንደነዚህ
ሰዎች ሁሉ፣ ጻድቃንና ኃጥኣን ከሙታን
እንደሚነሡ በእግዚአብሔር ተስፋ አለኝ፡፡
16ስለዚህ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ንጹሕ
ኅሊና እንዲኖረኝ ሁልጊዜ እጥራለሁ፡፡
17“ከብዙ ዓመት በኋላም፣ ለድዩው
ወገኔ ምጽዋትና መባ ይዤ ወደ ኢየሩሳ
ሌም መጣሁ፡፡ 18እነርሱም በቤተ መቅደስ
የመንጻት ሥርዐት ፈጽሜ ይህንኑ ሳደርግ
አገኙኝ፤ የሕዝብ ሁካታ ወይም ረብሻ አል
ነበረም፡፡ 19ነገር ግን ክስ ካላቸው አንተ
ፊት ቀርበው ሊከሱ የሚገባቸው ከእስያ
አውራጃ የመጡ አንዳንድ አይሁድ አሉ፤
20ወይም በዚህ ያሉት እነዚህ በሸንጎው
ፊት ቀርቤ በነበረበት ጊዜ ያገኙብኝ
ወንጀል ካለ ይናገሩ፤ 21በመካከላቸው በቆ
ምሁበት ጊዜ ስለሙታን ትንሣኤ ከተናገ
ርሁት አንድ ነገር በስተቀር ዛሬ ተከስሼ
የቀረብሁበት ሌላ ነገር የለም፡፡
22ፊልክስ ግን የጌታን መንገድ በሚ
ገባ ዐውቆ ስለ ነበር፣ “የጦር አዛዡ ሉስ
ዮስ ሲመጣ ለጕዳያችሁ ውሳኔ እሰጣለሁ”
ብሎ ነገሩን በቀጠሮ አሳደረው፡፡ 23ከዚ
ያም ለጳውሎስ መጠነኛ ነጻነት እየሰጠ
እንዲጠብቀውና፣ ወዳጆቹም ገብተው
እንዲጠይቁት ፈቃድ እንዲሰጣቸው የመቶ
አለቃውን አዘዘው፡፡
24ከጥቂት ቀን በኋላ፣ ፊልክስ ከአ
ይሁዳዊት ሚስቱ ከድሩሲላ ጋር መጣ፤
ጳውሎስንም አስጠርቶ በክርስቶስ ኢየሱስ
ስለ ማመን ሲናገር አዳመጠው፡፡ 25ጳው
ሎስ ስለ ጽድቅና ራስን ስለ መግዛት ስለ
ሚመጣውም ፍርድ በሚናገርበት ጊዜ
ግን ፊልክስ ፈርቶ፣ “ለጊዜው ይህ ይበ
ቃል፤ ወደ ፊት ሲመቸኝ አስጠራሃለሁ፤
አሁን ልትሄድ ትችላለህ” አለው፡፡ 26ደግ
ሞም ከጳውሎስ ጉቦ ለመቀበል ተስፋ ያደ
ርግ ስለ ነበር፣ በየጊዜው እያስጠራ ያነጋ
ግረው ነበር፡፡
27ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላም፣ ፊል
ክስ በጶርቅዮስ ፊስጦስ ተተካ፤ ፊልክስም
አይሁድን ለማስደሰት ሲል፣ ጳውሎስን
እንደ ታሰረ ተወው፡፡

### ጳውሎስ በፊስጦስ ፊት ቀረበ

25 ፊስጦስም ወደ አውራጃው ከገባ
ከሦስት ቀን በኋላ፣ ከቂሳርያ
ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ፡፡ 2የካህናት አለቆ
ችና የአይሁድ መሪዎች ፊቱ ቀርበው
ጳውሎስን ከሰሱት፡፡ 3ጳውሎስን መንገድ
ላይ አድፍጠው ሊገድሉት ስለ ፈለጉ፣
ፊስጦስ ለእነርሱ እንዲያዳላላቸውና ወደ
ኢየሩሳሌም እንዲያስመጣው አጥብቀው
ለመኑት፡፡ 4ፊስጦስም እንዲህ ሲል መለሰ
ላቸው፤ “ጳውሎስ ታስሮ በቂሳርያ እስር

ረ6-8 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ቍ7 እና የቍ6 ከፊል የላቸውም፡፡

24፥1 ሐሥ23፥2፡ 24፡30፡35
24፥3 ሉቃ1፥3፤ ሐሥ23፥26፤26፥25
24፥5 ቍ14፤ ማር1፥24፤ ሐሥ 16፥20፤ 17፥6፤ 21፥28፤26፥5፤28፥22
24፥6 ሐሥ21፥28
24፥9 1ተሰ2፥16
24፥10 ሐሥ23፥24
24፥11 ቍ1፤ሐሥ 21፥27
24፥12 ቍ18፤ሐሥ 25፥8፤28፥17
24፥13 ሐሥ25፥7
24፥14 ቍ5፤ሐሥ 3፥13፤9፥2፤26፥6፡22፤28፥23
24፥15 ማቴ25፥46፤ሐሥ23፥6፤28፥20
24፥16 ሐሥ23፥1
24፥17 ሐሥ11፥29፡30፤ሮሜ15፥25-28፡31፤1ቆሮ16፥1-4፡15፤2ቆሮ8፥1-4፤ገላ2፥10
24፥18 ቍ12፤ሐሥ 21፥26
24፥19 ሐሥ2፥9፤ 23፥30
24፥21 ሐሥ23፥6
24፥22 ሐሥ9፥2
24፥23 ሐሥ23፥16፡35፤27፥3፤28፥16
24፥24 ሐሥ20፥21
24፥25 ኤር36፥16፤ሐሥ10፥42፤ገላ5፥23፤1ተሰ5፥6፤1ጴጥ4፥7፤5፥8፤2ጴጥ1፥6
24፥27 ሐሥ12፥3፤ 23፥35፤25፥1፡4፡9፡14
25፥1 ሐሥ8፥40፤ 24፥27
25፥2 ቍ15፤ ሐሥ 24፥1
25፥3 ሐሥ20፥3
25፥4 ሐሥ8፥40፤ 24፥23

ቤት ይገኛል፤ እኔም በቅርቡ ወደዚያው
እሄዳለሁ፤ 5ስለዚህ ከባለሥልጣኖቻችሁ
መካከል አንዳንዶች ከእኔ ጋር ይምጡና
ሰውየው ጥፋት ካለበት ክሱን በዚያው
ያቅርቡ።”
6ከእነርሱም ጋር ስምንት ወይም ዐሥር
ቀን ያህል ከሰነበተ በኋላ፣ ወደ ቂሳርያ
ወረደ፤ በማግስቱም ፍርድ ወንበር ላይ
ተቀምጦ ጳውሎስን እንዲያመጡት አዘዘ።
7ጳውሎስ በቀረበ ጊዜ፣ ከኢየሩሳሌም
የመጡት አይሁድ ከበቡት፤ በማስረጃ ያል
ተደገፉ ብዙ ከባድ ክሶችም አቀረቡበት።
8ጳውሎስም፣ “እኔ በአይሁድም ሕግ
ሆነ በቤተ መቅደሱ ወይም በቄሳር ላይ
የፈጸምሁት በደል የለም” ሲል የመከላከያ
መልሱን ሰጠ።
9ፊስጦስም ለአይሁድ በጎ ለመዋል
ፈልጎ፣ ጳውሎስን “ስለዚህ ጉዳይ ወደ ኢየሩ
ሳሌም ወጥተህ በእኔ ፊት ለመፋረድ
ፈቃደኛ ነህን?” አለው።
10ጳውሎስም እንዲህ አለ፤ “አሁንም ቢሆን
ፍትሕ ማግኘት በምችልበት፣ በቄሳር
ፍርድ ወንበር ፊት ቆሜአለሁ፤ አንተ ራስህ
በሚገባ እንደምታውቀው በአይሁድ ላይ
ምንም በደል አልፈጸምሁም፤ 11ይሁን
እንጂ ለሞት የሚያበቃ በደል ከተገኘ
ብኝ፣ አልሙት አልልም፤ እነዚህ አይሁድ
የሚያቀርቡብኝ ክስ እውነት ካልሆነ ግን፣
እኔን ለእነርሱ አሳልፎ ሊሰጥ የሚችል
የለም፤ ወደ ቄሳር ይግባኝ ብያለሁ።”
12ፊስጦስ ከመማክርቱ ጋር ከተመካከረ
በኋላ፣ “ወደ ቄሳር ይግባኝ ስላልህ፣ ወደ
ቄሳር ትሄዳለህ” አለው።

## ፊስጦስ ከንጉሥ አግሪጳ ምክር ጠየቀ

13ከጥቂት ቀንም በኋላ፣ ንጉሥ
አግሪጳና በርኒቄ ፊስጦስን እጅ ሊነሡ
ወደ ቂሳርያ ወረዱ፤ 14በዚያም ብዙ ቀን
ተቀመጡ፤ ፊስጦስም የጳውሎስን ጉዳይ
አንሥቶ ለንጉሡ እንዲህ አለው፤ “ፊልክስ
በእስር ቤት የተወው አንድ ሰው እዚህ
አለ፤ 15ወደ ኢየሩሳሌም በሄድሁ ጊዜ፣
የካህናት አለቆችና የአይሁድ ሽማግሌዎች
እንድፈ ርድበት ከሰውት ነበር።
16“እኔም፣ ተከሳሽ በከሳሾቹ ፊት ቆሞ
ለተከሰሰበት ነገር መልስ ለመስጠት ዕ
ድል ሳያገኝ፣ አሳልፎ መስጠት የሮማውያን
ልማድ እንዳልሆነ ነገርኋቸው። 17ስለዚህ
ከሳሾቹ ከእኔ ጋር ወደዚህ በመጡ ጊዜ፣
ጉዳዩን ሳላጓትት በማግስቱ ችሎት ተቀ
ምጬ ያን ሰው እንዲያቀርቡት አዘዝሁ።
18ከሳሾቹም ተነሥተው በመቆም ሲናገሩ፣
እኔ ያሰብሁትን ያህል ከባድ ክስ አላቀረ
ቡበትም፤ 19ይልቁን ስለ ገዛ ሃይማኖታቸ
ውና ሞቶ ስለ ነበረው፣ ጳውሎስ ግን ሕያው
ነው ስለሚለው ሰው፣ ስለ ኢየሱስ ይከራ
ከሩት ነበር። 20እኔም ይህን ነገር እንዴት
እንደምፈታው ግራ ስለገባ፣ ወደ ኢየሩ
ሳሌም ሄዶ ስለዚሁ ጉዳይ እንዲፋረድ
ፈቃደኝነቱን ጠየቅሁት። 21ነገር ግን ጳው
ሎስ ጉዳዩ በንጉሡ ነገሥቱ እንዲታይ
ለት ይግባኝ ባለ ጊዜ፣ እኔም ወደ ቄሳር
እስከምልከው ድረስ እስር ቤት እንዲሆይ
አዘዝሁ።”
22አግሪጳም ፊስጦስን፣ “እኔም እኮ ይህ
ሰው ሲናገር መስማት እፈልግ ነበር” አለው።
እርሱም፣ “እንግዲያውስ ነገ ትሰማዋለህ”
አለው።

## ጳውሎስ በንጉሥ አግሪጳ ፊት

23በማግስቱም አግሪጳና በርኒቄ በታላቅ
ክብር መጥተው፣ ከከፍተኛ መኰንኖችና
ከከተማዪቱ ታላላቅ ሰዎች ጋር ወደ መሰ
ብሰቢያው አዳራሽ ገቡ፤ በፊስጦስም ትእ
ዛዝ ጳውሎስ እንዲቀርብ ተደረገ። 24በዚህ
ጊዜ ፊስጦስ እንዲህ አለ፤ ንጉሥ “አግሪጳ
ሆይ፤ እንዲሁም እዚህ አብራችሁን ያላ
ችሁ ሁሉ፤ ይህን ሰው ታዩታላችሁ? በኢ
የሩሳሌምና እዚህ በቂሳርያም የሚኖሩ
አይሁድ ሁሉ፣ ይህ ሰው ከእንግዲህ በሕ
ይወት መኖር አይገባውም በማለት እየ
ጮ÷ ለመኑ። 25እኔም ለሞት የሚያ
በቃ አንዳች ነገር አለማድረጉን ተረዳሁ፤
ሆኖም ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ይግባኝ በማ
ለቱ ወደ ሮም ልልከው ወሰንሁ። 26ነገር
ግን ስለ እርሱ ወደ ጌታዬ የምጽፈው የተ
ረጋገጠ ነገር አላገኘሁም፤ ስለዚህም ከተመ
ረመረ በኋላ የምጽፈውን ነገር ለማግኘት
ሁላችሁም ፊት በተለይ ደግሞ ንጉሥ አግ
ሪጳ ሆይ፤ በአንተ ፊት አቀረብሁት፤
27ይኸውም አንድ እስረኛ ወደ በላይ ሲላክ
የተከሰሰበትን ምክንያት አለ መግለጽ ትክክል
ስላልመሰለኝ ነው።”

# 26

አግሪጳም ጳውሎስን፣ “ስለ ራስህ
እንድትናገር ተፈቅዶልሃል” አለው።
በዚህ ጊዜ ጳውሎስ እጁን ዘርግቶ እንዲህ
ሲል መከላከያውን አቀረበ፤ 2“ንጉሥ አግ
ሪጳ ሆይ፤ አይሁድ በእኔ ላይ ላቀረቡት
ክስ ሁሉ ዛሬ በፊትህ የመከላከያ መልስ
ለማቅረብ በመቻሌ ራሴን እንደ ዕድለኛ
እቆጥረዋለሁ፤ 3ይኸውም አንተ በተለይ
የአይሁድን ልማድና ክርክር ሁሉ በሚገባ
ስለምታውቅ ነው፤ ስለዚህ በትዕግሥት
እንድታደምጠኝ እለምንሃለሁ።

25፥6 ቍ10፡17
25፥7 ማር15፥3፤ ሉቃ23፥2፡10፤ ሐሥ 24፥5፡6፡13
25፥8 ሐሥ6፥13፤ 24፥12፤28፥17
25፥9 ቍ20፤ ሐሥ 12፥3፤24፥27
25፥10 ቍ8
25፥11 ቍ21፡ 25፥ሐሥ26፥32፤ 28፥19
25፥13 ሐሥ8፥40
25፥14 ሐሥ24፥27
25፥15 ቍ2፤ ሐሥ 24፥1
25፥16 ቍ4፡5፤ ሐሥ23፥30
25፥17 ቍ6፡10
25፥19 ሐሥ17፥ 22፤18፥15፤23፥29
25፥20 ቍ9
25፥21 ቍ11፡12
25፥22 ሐሥ9፥15
25፥23 ቍ13፤ ሐሥ 26፥30
25፥24 ቍ2፡3፡7፤ ሐሥ22፥22
25፥25 ቍ11፤ ሐሥ23፥9
26፥1 ሐሥ9፥15፤ 12፥17፤25፥22
26፥2 መዝ119፥ 46፤ሐሥ24፥1፡5፤ 25፥2፡7፡11
26፥3 ቍ7፤ ሐሥ 6፥14፤25፥19

4"ገና ከልጅነቴ ጀምሮ፣ በአገሬም ሆነ
በኢየሩሳሌም እንዴት እንደኖርሁ አይ
ሁድ ሁሉ ያውቃሉ፤ 5ደግሞም ከብዙ ጊዜ
ጀምሮ ስለሚያውቁኝ ከሃይማኖታችን
እጅግ ጥብቅ በሆነው ወገን ውስጥ ሆኜ
እንደ አንድ ፈሪሳዊ መኖሬን ሊመሰክሩ
ፈቃደኞች ከሆኑ ቃላቸውን ሊሰጡ
ይችላሉ:: 6አሁንም ተከስሼ እዚህ የቀረ
ብሁበት ምክንያት እግዚአብሔር ለአባቶ
ቻችን ቃል የገባውን ነገር ተስፋ በማድ
ረጌ ነው:: 7ዐሥራ ሁለቱ ነገዶቻችን
ቀንና ሌሊት እግዚአብሔርን ከልብ እያገለ
ገሉ፣ ሲፈጸም ለማየት የሚተጉለትም
ተስፋ ይኸው ነው:: ንጉሥ ሆይ፤ አይሁ
ድም የሚከሱኝ ስለዚሁ ተስፋ ነው::
8ለመሆኑ፣ እግዚአብሔር ሙታንን ማስነሣት
እንደማይችል አድርጋችሁ የምትሐጥሩት
ለምንድን ነው?

9"እኔም ራሴ የናዝሬቱን የኢየሱስን
ስም በምችለው መንገድ ሁሉ መቃወም
እንዳለብኝ ወስኜ ነበር:: 10በኢየሩሳሌምም
ያደረግሁት ይህንኑ ነበር፤ ከካህናት አለ
ቆች ሥልጣን ተቀብዬ ብዙ ቅዱሳንን አሳ
ስሬአለሁ፤ በመገደላቸውም ተስማምቻለሁ፤
11ላስቀጣቸውም ብዙ ጊዜ ከምኵራብ
ምኵራብ እየተዘዋወርሁ፣ የስድብ ቃል
እንዲናገሩ አስገድጃቸው ነበር፤ በቍጣም
ተሞልቼ በውጭ አገር እስከሚገኙ ከተ
ሞች ድረስ ተከታትዬ አሳደድኋቸው::

12"በዚህ መሠረት አንድ ቀን ከካህናት
አለቆች ሥልጣንና ትእዛዝ ተቀብዬ ወደ
ደማስቆ በምጓዝበት ጊዜ፣ 13ንጉሥ ሆይ፤
እኩለ ቀን ላይ በመንገድ ሳለሁ፣ ብሩህ
ነቱ ከፀሐይ የሚበልጥ ብርሃን በእኔና በባ
ልንጀሮቼ ዙሪያ ከሰማይ ሲያበራ አየሁ፤
14ሁላችንም በምድር ላይ ወደቅን፤ እኔም
በዕብራይስጥ[ሰ] ቋንቋ፣ 'ሳውል፤ ሳውል፤
ለምን ታሳድደኛለህ? መውጊያውን መቃ
ፋት ጕዳቱ በአንተ ይብሳል' የሚለኝን
ድምፅ ሰማሁ::

15"እኔም፣ 'ጌታ ሆይ፤ አንተ ማን ነህ?' "
አልሁ::

"ጌታም እንዲህ አለኝ፤ 'እኔ፣ አንተ
የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ:: 16አሁንም፣
ተነሥና በእግርህ ቁም፤ ስለ እኔ ስላየኸ
ውና ወደ ፊትም ስለማሳይህ ነገር አገልጋ
ይና ምስክር እንድትሆን ልሾምህ ተገልጬ
ልሃለሁ:: 17ከገዛ ሕዝብህና ወደ እነርሱ
ከምልክህ ከአሕዛብ አድንሃለሁ፤ 18አን
ተም ዐይናቸውን ትከፍታለህ፤ ከጨለማ
ወደ ብርሃን፣ ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ
እግዚአብሔር ትመልሳቸዋለህ፤ እነርሱም
የኀጢአትን ይቅርታ ይቀበላሉ፤ በእኔም በማ
መን በተቀደሱት መካከል ርስት ያገኛሉ::'

19"እንግዲህ፣ ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፤ ከሰ
ማይ ለታየኝ ራእይ አልታዘዝ አላልሁም፤
20ነገር ግን በመጀመሪያ በደማስቆ ለሚ
ኖሩ፣ ቀጥሎም በኢየሩሳሌምና በይሁዳ
ላሉት ሁሉ፣ ከዚያም ለአሕዛብ፣ ንስሓ
እንዲገቡና ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ፣
የንስሓም ፍሬ እንዲያሳዩ ገልጬ ተናገ
ርሁ:: 21አይሁድም በመቅደስ ይዘው ሊገ
ድሉኝ የሞከሩት በዚሁ ምክንያት ነው::
22የእግዚአብሔር ርዳታ እስከ ዛሬ ስላልተ
ለየ፣ እነሆ፤ እዚህ ቆሜ ለትንሹም ለት
ልቁም እመሰክራለሁ፤ ነቢያትና ሙሴ
ይሆናል ይፈጸማል ካሉት በስተቀር አን
ዳች ነገር አልተናገርሁም፤ 23ይኸውም ክር
ስቶስ[ሸ] መከራን እንደሚቀበልና ከሙታን
ቀዳሚ ሆኖ በመነሣት ለሕዝቡና ለአሕዛብ
ብርሃንን እንደሚሰብክ ነው::"

24ፊስጦስም የጳውሎስን ንግግር እዚህ
ላይ በማቋረጥ ድምፁን ከፍ አድርጎ፣
"ጳውሎስ ሆይ፤ አእምሮህን ስተሃል፤ የት
ምህርትህም ብዛት አሳብዶሃል" አለው::

25ጳውሎስ ግን እንዲህ ሲል መለሰ፤
"ክቡር ፊስጦስ ሆይ፤ የምናገረው እውነ
ተኛና ትክክለኛ ነገር እንጂ እብድስ አይ
ደለሁም:: 26ይህን የምናገረውን ነገር ንጉሡ
ያውቀዋልና፤ በፊቱ በልበ ሙሉነት እናገ
ራለሁ፤ ደግሞም በድብቅ የተደረገ ነገር
ባለመኖሩ፣ ከዚህ ነገር አንድም እንደማ
ይሰወርበት እርግጠኛ ነኝ:: 27ንጉሥ አግ
ሪጳ ሆይ፤ ነቢያትን ታምን የለም ወይ?
አዎን፤ እንደምታምን ዐውቃለሁ::"

28አግሪጳም ጳውሎስን፣ "እንዲህ በቀላሉ
ክርስቲያን የምታደርገኝ ይመስልሃልን?"
አለው::

29ጳውሎስም፣ "በቀላሉም ሆነ በብዙ፣
አንተ ብቻ ሳትሆን ዛሬ የሚሰሙኝ ሁሉ፣
ከዚህ ከታሰርሁበት ሰንሰለት በስተቀር፣
እንደ እኔ ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔርን እለ
ምናለሁ" አለ::

30ከዚህ በኋላ ንጉሡም፣ አገረ ገዡም፣
በርኒቄም፣ ከእነርሱ ጋር የተቀመጡትም
ተነሡ፤ 31ወጥተውም ሲሄዱ፣ "ይህ ሰው
እንኳን ለሞት ለእስራት የሚያበቃው ነገር
አላደረገም" ተባባሉ::

32አግሪጳም ፊስጦስን፣ "ይህ ሰው ወደ
ቄሳር ይግባኝ ባይል ኖሮ መልቀቅ ይቻል
ነበር" አለው::

[ሰ]14 *ወይም አራማይክ*
[ሸ]23 *ወይም መሲሕ*

**26፥4** ገላ1፥13፡ 14፤ፊል3፥5
**26፥5** ሐሥ22፥3፤ 23፥6፤24፥5፤ፊል3፥5
**26፥6** ሐሥ13፥32፤ 23፥6፤24፥15፤28፥ 20፤ሮሜ15፥8
**26፥7** ቀኊ2፤ 1ተሰ3፥10፤ 1ጢሞ5፥5፤ያዕ 1፥1
**26፥8** ሐሥ23፥6
**26፥9** ዮሐ15፥21፤ 16፥2፤1ጢሞ1፥13
**26፥10** ሐሥ8፥3፤ 9፥2፡13፡14፡21፤22፥20
**26፥11** ማቴ10፥17
**26፥14** ዮሐ5፥2፤ ሐሥ9፥7
**26፥16** ሕዝ2፥1፤ ዳን10፥11፤ ሐሥ22፥ 14፡15
**26፥17** ኤር1፥8፡ 19፤ሐሥ9፥15፤ 13፥46
**26፥18** መዝ18፥ 28፤ኢሳ35፥5፤42፥7፡ 16፤ሉቃ24፥47፤ ሐሥ 2፥38፤20፥21፤ ኤፌ5፥8፤ቈላ1፥13፤ 1ጴጥ2፥9
**26፥19** ኢሳ50፥5
**26፥20** ኤር18፥ 11፤35፥15፤ማቴ 3፥8፤ሉቃ3፥8፤ ሐሥ 3፥19፤ 9፥15፡19-25፡ 26-29፤13፥46፤ 22፥17-20
**26፥21** ሐሥ21፥ 27፡30፡31
**26፥22** ሉቃ24፥27፡ 44፤ሐሥ10፥43፤24፥14
**26፥23** ማቴ16፥ 21፤ሉቃ2፥32፤1ቆሮ 15፥20፡23፤ቈላ1፥18፤ ራእ1፥5
**26፥24** ዮሐ7፥15፤ 10፥20፤1ቆሮ4፥10
**26፥25** ሐሥ23፥26
**26፥26** ቀኊ3
**26፥28** ሐሥ11፥26
**26፥29** ሐሥ21፥33
**26፥30** ሐሥ25፥23
**26፥31** ሐሥ23፥9
**26፥32** ሐሥ25፥ 11፤28፥18

## ጳውሎስ በመርከብ ወደ ሮም ተወሰደ

27 ወደ ኢጣሊያ እንድንሄድ በተወ
ሰነ ጊዜ፣ ጳውሎስንና ሌሎቹን
እስረኞች የንጉሠ ነገሥቱ ክፍለ ጦር
አባል ለሆነው፣ ዩልዮስ ለተባለ የመቶ
አለቃ አስረከቧቸው። 2ከአድራሚጢስ ተነ
ሥቶ በእስያ አውራጃ ባሕር ዳርቻ ላይ
ወዳሉት ወደቦች በሚሄደው መርከብ ተሳ
ፍረን የባሕር ጒዞ ጀመርን፤ በተሰሎንቄ
ይኖር የነበረው የመቄዶንያ ሰው፣ አርስጥ
ሮኮስም ከእኛ ጋር ነበረ።
3በሚቀጥለው ቀን ሲዶና ደረስን፤ ዩልዮ
ስም ለጳውሎስ ደግነት በማሳየት ወደ
ወዳጆቹ ሄዶ ርዳታ እንዲቀበል
ፈቀደለት። 4ከዚያም ተነሥተን በባሕር
ተጓዝን፤ ነፋስ ከፊት ለፊት ስለገጠመን፣
የቆጵሮስን ደሴት ተገን አድርገን ዐለፍን።
5በኪልቅያና በጵንፍልያ ዳርቻ ያለውን
ባሕር ከተሻገርን በኋላ በሉቅያ አገር ሙ
ራ የተ ባለ ቦታ ደረስን። 6ከዚያም የመቶ
አለ ቃው ወደ ኢጣሊያ የሚሄድ የእስክን
ድርያ መርከብ አግኝቶ አሳፈረን። 7ብዙ
ቀን በዝግታ እየተጓዝን ቀኒዶስ አካባቢ
በጭንቅ ደረስን፤ ነፋሱም ወደ ፊት እንዳ
ንሄድ በከለከለን ጊዜ፣ በሰልሙና አጠገብ
አድርገን በቀርጤስ ተተግነን ሄድን፤ 8ጥግ
ጥጉንም ይዘን፣ በላሲያ ከተማ አጠገብ
ወዳለው፣ ‘መልካም ወደብ’ ወደ ተባለ
ስፍራ በጭንቅ ደረስን።
9ብዙ ጊዜ ባክኖ፤ የጾሙ ጊዜ ስላለፈ*
በመርከብ መጓዙ አደገኛ ሆኖ ነበርና ጳው
ሎስ፣ 10“እናንት ሰዎች፤ ጒዞው አደገኛ
እንደሚሆን፣ በመርከቡና በጭነቱ እንዲ
ሁም በእኛ በራሳችን ላይ እንኳ ትልቅ
ጒዳት እንደሚደርስ ይታየኛል” ብሎ
አስጠነቀቃቸው። 11የመቶ አለቃው ግን
ከጳውሎስ ምክር ይልቅ የመርከቡ መሪና
የመርከቡ ባለቤት ያሉትን ይሰማ ነበር።
12ክረምቱንም በዚያ ለማሳለፍ ወደቡ
አመቺ ስላልነበረ፣ አብዛኛዎቹ ፍንቄ ወደ
ተባለው ወደብ ደርሰው በዚያ ለመክረም
ተስፋ በማድረግ ጒዞአችንን እንድንቀ
ጥል ውሳኔ አስተላለፉ፤ ወደቡም በቀርጤስ
ደቡብ ምዕራብና ሰሜን ምዕራብ ትይዩ
የሚገኝ ነበር።

## የባሕሩ ማዕበል

13መጠነኛ የደቡብ ነፋስ በነፈሰ ጊዜም
እንዳሰቡት የሆነላቸው መስሎአቸው መል
ሕቁን ነቅለው፣ የቀርጤስን ዳርቻ በመ
ያዝ ተጓዙ። 14ብዙም ሳይቈይ ግን፣ ‘ሰሜ
ናዊ ምሥራቅ’ የሚሉት ኀይለኛ ዐውሎ

27፥1 ሐሥ10፥1፤ 16፥10፤18፥2፤25፥12፡25
27፥2 ሐሥ2፥9፤ 16፥9፤17፥1፤19፥29
27፥3 ቍ43፤ ማቴ11፥21፤ ሐሥ 24፥23፤28፥16
27፥4 ቍ7
27፥5 ሐሥ2፥10፤ 6፥9
27፥6 ቍ1፤ሐሥ 18፥2፤25፥12፡25፤28፥11
27፥7 ቍ4:12፡ 13:21፤ቲቶ1፥5
27፥9 ዘሌ16፥29-31፤23፥27-29፤ ዘኍ29፥7
27፥10 ቍ21
27፥12 ቍ7
27፥14 ማር4፥37

ነፋስ ከደሴቲቱ ተነሥቶ ቍልቍል መጣ
ባቸው። 15መርከቢቱም በማዕበሉ ስለ
ተያዘች፣ ወደ ነፋሱ ልትገፋ አልቻለችም፤
ስለዚህ መንገድ ለቀን በነፋሱ ተነዳን።
16ቄዳ የተባለችውን ትንሽ ደሴት ተገን
አድርገን በማለፍ፣ የመርከቧን ሕይወት
አድን ጀልባ በብዙ ድካም ለማትረፍ
ቻልን፤ 17ጀልባዋንም ወደ ላይ ጐትተው
ካወጧት በኋላ መርከቧ እንዳትፈራርስ
ዙሪያዋን በገመድ ጠምጥመው አሰሯት፤
ስርቲስ ከተባለው አሸዋማ ደለል ጋር
ሄደው እንዳይላተሙ ስለ ፈሩም፣ የመር
ከቧን ሸራ አውርደው እንዲሁ በዘፈቀደ
እንድትነዳ አደረጉ። 18ማዕበሉም ክፉኛ
ስላንገላታን፣ በማግስቱ ጭነቱን እያነሡ
ወደ ባሕር ይጥሉ ጀመር፤ 19በሦስተኛ
ውም ቀን፣ የመርከቧን ሸራማው ጫና
ማውረጃ መሣሪያ በገዛ እጃቸው ነቃቅለው
ወደ ባሕር ጣሉት። 20ብዙ ቀን፣ ፀሓይንም
ከዋክብትንም ማየት ስላልተቻለና ነፋስ
ስለ በረታብን፣ ለመትረፍ የነበረን ተስፋ
ሁሉ ተሟጠጠ።
21ሰዎቹ እህል ሳይቀምሱ ብዙ ቀን
ከቈዩ በኋላ፣ ጳውሎስ በመካከላቸው ቆሞ
እንዲህ አለ፤ “እናንት ሰዎች ሆይ፤ የነገ
ርኋችሁን ሰምታችሁ ቢሆን ኖሮ፣ ከቀ
ርጤስ ባልተነሣችሁና ይህ ጒዳትና ጥፋት
ባልደረሰባችሁ ነበር። 22አሁንም ቢሆን
አይዟችሁ! መርከቧ እንጂ ከእናንተ አንዲት
ነፍስ እንኳ አትጠፋምና። 23በትላንትናዋ
ሌሊት፣ የእርሱ የሆንሁትና የማመልከው
እግዚአብሔር የላከው መልአክ በአጠገቤ
ቆሞ፣ 24‘ጳውሎስ ሆይ፤ አትፍራ፤ በቄሳር
ፊት መቆም ይገባሃል፤ ከአንተ ጋር የሚ
ጓዙትንም ሰዎች ሕይወት እግዚአብሔር
አት ርፎልሃል’ አለኝ። 25ስለዚህ፣ እናንት
ሰዎች ሆይ፤ አይዞአችሁ! እርሱ እንደ ነገ
ረኝ እንደዚያው እንደሚሆን በእግዚአብሔር
አምናለሁና። 26ይሁን እንጂ፣ ወደ አንዲት
ደሴት በነፋስ ተወስደን እዚያ መጣላችን
አይቀርም።”

## በመርከቡ አደጋ መድረሱ

27በዐሥራ አራተኛው ሌሊት በአድርያ[ሀ]
ባሕር ላይ ከወዲያ ወዲህ ስንገላታ፣ እኩለ
ሌሊት ገደማ መርከበኞቹ ወደ መሬት
የተቃረቡ መሰላቸው፤ 28የጥልቀት መለኪ
ያውን ገመድ ወደ ታች ጥለው ሲመለከቱት
የውሃው ጥልቀት አርባ ሜትር ያህል ሆኖ
አገኙት፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ደግመው

27፥16 ቍ30
27፥17 ቍ26፡39
27፥18 ቍ19፡38፤ ዮና1፥5
27፥21 ቍ7፡10
27፥22 ቍ25፡36
27፥23 ሐሥ5፥19፤ 18፥9፤23፥11፤ሮሜ 1፥9፤2ጢሞ4፥17
27፥24 ቍ44፤ ሐሥ 23፥11
27፥25 ቍ22፡36፤ ሮሜ4፥20፡21
27፥26 ቍ17፡39፤ ሐሥ28፥1

*9 የስርየትን ዕለት ያሳያል።
ሀ27 በጥንት ጊዜ ይህ ስም ሰፊውን የኢጣሊያ ደቡባዊ ክፍል ያመለክታል።

ሲጥሉ ጥልቀቱ፣ ሠላሳ ሜትር ያህል ሆነ።
29ከቋጥኞቹም ጋር እንዳንላተም በመፍራት፣
አራት መልሕቆች ከመርከቡ በስተኋላ
ጣሉ፤ ምነው በነጋ እያሉም ይለምኑ
ነበር። 30መርከበኞቹም ከመርከቡ በስተ
ፊት መልሕቅ የሚጥሉ መስለው፣ ትንሿን
ጀልባ በማውረድ ከመርከቧ ሊያመልጡ
ሞከሩ። 31ጳውሎስም የመቶ አለቃውንና
ወታደሮቹን፣ “እነዚህ ሰዎች መርከቡ ላይ
ካልቈዩ እናንተም ልትተርፉ አትችሉም”
አላቸው። 32በዚህ ጊዜ ወታደሮቹ ገመዶቹን
ቈርጠው ትንሿ ጀልባ ባሕሩ ላይ ተንሳፋ
እንድትቀር ለቀቋት።
33ልክ ሊነጋጋ ሲል፣ ጳውሎስ ሁሉም
ምግብ እንዲበሉ እንዲህ ሲል ለመናቸው፤
“ዐሥራ አራት ቀን ሙሉ ልባችሁ ተንጠ
ልጥሎ ምንም ሳትቀምሱ ጦማችሁን ሰነበ
ታችሁ፤ 34ስለዚህ ስለሚያበረታችሁ አሁን
እህል እንድትቀምሱ እለምናችኋለሁ፤ ከእ
ናንተ መካከል ከራሱ ጠጕር አንዲት
እንኳ የሚነካበት ማንም የለምና።” 35ይህን
ካለ በኋላም፣ እንጀራ ይዞ በሁሉም ፊት
እግዚአብሔርን አመሰገነ፤ ቈርሶም ይበላ
ጀመር። 36ሁሉም ተበራቱና እንጀራውን
ራሳቸው ወስደው በሉ። 37በመርከቡም
ላይ በአጠቃላይ ሁለት መቶ ሰባ ስድስት
ሰዎች ነበርን። 38በልተውም ከጠገቡ በኋላ
ስንዴውን ወደ ባሕር በመጣል የመርከቡን
ክብደት አቃለሉ።
39በነጋም ጊዜ፣ ወደ የብስ መቅረባቸ
ውን አላወቁም ነበር፤ ነገር ግን ዳር ዳሩ
አሸዋማ የሆነ የባሕር ሰርጥ አይተው፣ ቢቻ
ላቸው መርከቡን ገፍተው ወደዚያ ለማ
ድረስ ወሰኑ። 40ከዚያም መልሕቆቹን
ሖርጠው ባሕር ውስጥ ጥለው ሄዱ፤ የመ
ቅዘፊያውንም ገመድ በዚያው ጊዜ ፈቱ፤
የፊተኛውንም ሸራ ለነፋስ ከፍ አድርገው
ወደ ባሕሩ ዳርቻ አቀኑ። 41ነገር ግን መር
ከቡ ከአሸዋ ቊልል ጋር ተላትሞ፤
መሬት ነካ፤ የፊተኛው ክፍሉም አሸዋው
ውስጥ ተቀርቅሮ አልነቃነቅ አለ፤ የኋለ
ኛው ክፍሉም በማዕበሉ ክፉኛ ስለ
ተመታ ይሰባበር ጀመር።
42ወታደሮቹም ከእስረኞች ማንም ዋኝቶ
ለማምለጥ ቢሞክር ለመግደል ተስማሙ።
43የመቶ አለቃው ግን ጳውሎስ እንዲ
ተርፍ ስለ ፈለገ፣ ያሰቡትን እንዳይፈ
ጽሙ ከለከላቸው፤ መዋኘት የሚችሉ
ከመርከብ እየዘለሉ አስቀድመው ከባሕሩ
ወደ ምድር እንዲወጡ፣ 44የተቀሩት ደግሞ
በሳንቃዎች ወይም በመርከቡ ስብርባሪ
እየተንጠላጠሉ እንዲወጡ አዘዘ። በዚህ

27፥30 ቊ16
27፥31 ቊ24
27፥34 ማቴ10፥30
27፥35 ማቴ14፥19
27፥36 ቊ22፡25
27፥38 ቊ18፤
ዮና1፥5
27፥39 ሐሥ28፥1
27፥40 ቊ29
27፥41 2ቆሮ11፥25
27፥43 ቊ3
27፥44 ቊ22፡31

28፥1 ሐሥ16፥10፤
27፥26፡39
28፥4 ማር16፥18፤
ሉቃ13፥2፡4
28፥5 ሉቃ10፥19
28፥6 ሐሥ14፥11
28፥8 ሐሥ6፥6፤
9፥40፤ያዕ5፥14፡15
28፥10 መዝ15፥4
28፥11 ሐሥ27፥6
28፥14 ሐሥ1፥16
28፥15 ሐሥ1፥16

መንገድ ሁሉም በደኅና ወደ ምድር ደረሱ።

### ጳውሎስ በመላጥያ ደሴት

28 በደኅና ወደ ምድር ከደረስን
በኋላ፣ ደሴቲቱ መላጥያ ተብላ
እንደምትጠራ ተረዳን። 2የደሴቲቱ ነዋ
ሪዎችም የሚያስገርም ደግነት አሳዩን፤
ዝናብና ብርድ ነበርና እሳት አንድደው
ሁላችንን ተቀበሉን። 3ጳውሎስም ጭራሮ
ሰብስቦ ወደ እሳቱ ሲጨምር፣ ከሙቀቱ
የተነሣ እፉኝት ወጥታ እጁ ላይ ተጣ
በቀች። 4የደሴቲቱ ነዋሪዎች እባብ በእጁ
ላይ ተንጠልጥላ ባዩ ጊዜ፣ “ይህ ሰው
በእ ርግጥ ነፍስ ገዳይ ነው፤ ከባሕር ቢ
ያመ ልጥ እንኳ የፍርድ አምላክ በሕ
ይወት እን ዲኖር አልፈቀደለትም”
ተባባሉ። 5ጳው ሎስ ግን እባቢቱን ወደ
እሳቱ አራገፋት፤ አንዳችም ጕዳት
አልደረሰበትም። 6ሰዎቹ ከአሁን አሁን
ሰውነቱ ያብጣል ወይም ድንገት ሞቶ
ይወድቃል ብለው ይጠባበቁ ነበር፤ ነገር
ግን ብዙ ጊዜ ጠብቀው ምንም የተለየ ነገር
እንዳልደረሰበት ባዩ ጊዜ፣ ሐሳ
ባቸውን ለውጠው፣ “ይህስ አምላክ ነው”
አሉ።
7በዚያም ስፍራ አጠገብ የደሴቲቱ
አለቃ የፑፕልዮስ ርስት የሆነ መሬት
ነበረ፤ እርሱም በቤቱ ተቀብሎን ሦስት
ቀን በቸርነት አስተናገደን። 8የፑፕልዮስም
አባት በትኵሳትና በተቅማጥ ሕመም
ተይዞ ተኝቶ ነበር፤ ጳውሎስም ሊጠይቀው
ገብቶ ከጸለየለት በኋላ፣ እጁን ጭኖ
ፈወሰው። 9ይህም በሆነ ጊዜ፣ በደሴቲቱ
የነበሩ ሌሎች ሕመምተኞችም እየመጡ
ተፈወሱ። 10እኛንም በብዙ መንገድ አከ
በሩን፤ በመርከብም ለመሄድ በተዘጋጀን
ጊዜ፣ የሚያስፈልገንን ሁሉ ጫኑልን።

### ጳውሎስ ሮም ደረሰ

11ከሦስት ወር በኋላም፣ በደሴቲቱ
ክረምቱን ቆሞ በሰነበተ በአንድ መርከብ
ተነሥተን ጕዞ ጀመርን። ይህም መርከብ
የእስክንድርያ ሲሆን፣ በላዩ ላይ የመንታ
አማልክቱ የዲዮስቆሮስ አርማ ነበረበት።
12ወደ ሰራኩስ ከተማ ገብተን ሦስት ቀን
በዚያ ተቀመጥን። 13ከዚያም በመርከብ
ተጕዘን ሬጊዩም ደረስን፤ በማግስቱም የደ
ቡብ ነፋስ ስለ ተነሣ ፑቲዮሉስ የደረስነው
በሚቀጥለው ቀን ነበር። 14በዚያም ወን
ድሞችን አገኘን፤ እነርሱም ሰባት ቀን
አብረናቸው እንድንቀመጥ ለመኑን፤ ከዚ
ያም በኋላ ወደ ሮም ሄድን። 15በዚያ
የነበሩ ወንድሞችም መምጣታችንን ስለ
ሰሙ፣ እስከ አፍዩስ ፋሩስ፣ እንዲሁም

‘ሦስት ማደሪያ’ እስከሚባለው ቦታ ድረስ
ሊቀበሉን ወጡ፤ ጳውሎስም ባያቸው ጊዜ
እግዚአብሔርን አመሰገነ፤ ተጽናናም። 16ሮም
በደረስን ጊዜም፣ ጳውሎስ ይጠብቀው
ከነበረው ወታደር ጋር፣ ለብቻው በዚያ
እንዲቈይ ተፈቀደለት።

### ጳውሎስ በጥበቃ ሥር ሆኖ ሰበከ

17ከሦስት ቀንም በኋላ፣ ጳውሎስ የአይ
ሁድን መሪዎች በአንድነት ጠራ፤ በተሰበ
ሰቡም ጊዜ እንዲህ አላቸው፤ “ወንድሞች
ሆይ፤ እኔ፣ ሕዝባችንን ወይም የአባቶቻ
ችንን ሥርዐት የሚቃረን ምንም ሳላደ
ርግ፣ በኢየሩሳሌም አስረው ለሮማውያን
አሳልፈው ሰጥተውኛል። 18እነርሱም መር
ምረው ለሞት የሚያበቃ በደል ስላላገ
ኙብኝ፣ ሊፈቱኝ ፈልገው ነበር፤ 19አይሁድ
በተቃወሙ ጊዜ ግን፣ ለቄሳር ይግባኝ
ማለት ግድ ሆነብኝ እንጂ ሕዝቤን የምከ
ስበት ምክንያት ኖሮኝ አይደለም። 20እና
ንተንም ለማየትና ለማነጋገር የጠራኋ
ችሁ በዚሁ ምክንያት ነው፤ በዚህ ሰንሰ
ለት የታሰርሁትም ለእስራኤል በተሰጠው
ተስፋ ምክንያት ነው።”

21እነርሱም እንዲህ አሉት፤ “ስለ አንተ
ከይሁዳ ምድር የተጻፈ አንድም ደብዳቤ
አልደረሰንም፤ ከዚያ የመጡ ወንድሞችም
ስለ አንተ ያቀረቡት ወይም የተናገሩት
አንዳች መጥፎ ነገር የለም። 22ይሁን
እንጂ፣ ሰዎች ስለዚህ የእምነት ክፍል በየ
ቦታው ክፉ እንደሚያወሩበት እናውቃ
ለን፤ የአንተ አስተያየት ደግሞ ምን እንደ
ሆነ መስማት እንፈልጋለን።”

23ቀን ከቀጠሩለትም በኋላ፣ ብዙ ሆነው
ወደ ማረፊያ ስፍራው መጡ፤ እርሱም
ከጠዋት ጀምሮ እስከ ማታ ስለ እግዚአብሔር
መንግሥት እየመሰከረ ያብራራላቸው ነበር፤
ከሙሴ ሕግና ከነቢያትም በመጥቀስ ስለ
ኢየሱስ ሊያሳምናቸው ሞከረ። 24አንዳን
ዶቹ እርሱ የሚለውን አምነው ተቀበሉ፤
ሌሎቹ ግን አላመኑበትም፤ 25እርስ በርሳ
ቸውም አልተስማሙም፤ ጳውሎስም እንዲህ
የሚል የመጨረሻ ቃል ከተናገራቸው
በኋላ ሄዱ፤ “መንፈስ ቅዱስ በነቢዩ በኢሳ
ይያስ አማካይነት ለአባቶቻችሁ በትክ
ክል እንዲህ ብሎ ተናግሮአል፤

26“ ‘ወደዚህ ሕዝብ ሂድ፤ እንዲህም
 በላቸው፤
 “መስማትን ትሰማላችሁ፤ ነገር ግን
 አታስተውሉም፤
 ማየትን ታያላችሁ፤ ነገር ግን
 አትመለከቱም።”
27የዚህ ሕዝብ ልብ ደንድኖአልና፤
 ጆሮአቸውም ተደፍኖአል፤
 ዐይናቸውንም ጨፍነዋል።
አለዚያማ፣ በዐይናቸው አይተው፣
 በጆሮአቸው ሰምተው፣
በልባቸው አስተውለው፣
 ይመለሱና እፈውሳቸዋለሁ።’

28“ስለዚህ የእግዚአብሔር ማዳን ለአሕ
ዛብ እንደ ተላከ እንድታውቁ እፈልጋ
ለሁ፤ እነርሱም ይሰሙታል።” 29ይህንንም
ከተናገረ በኋላ፣ አይሁድ እርስ በርሳቸው
እጅግ እየተከራከሩ ሄዱ።†

30ጳውሎስም ራሱ በተከራየው ቤት
ሁለት ዓመት ሙሉ ተቀመጠ፤ ወደ እርሱ
የሚመጡትንም ሁሉ በደስታ ይቀበል
ነበር፤ 31ማንም ሳይከለክለው የእግዚአብሔርን
መንግሥት እየሰበከ፣ ስለ ጌታ ኢየሱስ
ክርስቶስ በፍጹም ግልጽነት ያስተምር
ነበር።

28፥16 ሐሥ24፥23፤27፥3
28፥17 ሐሥ6፥14፤22፥5፤25፥2፡8
28፥18 ሐሥ22፥24፤23፥9፤26፥31፡ 32
28፥19 ሐሥ25፥11
28፥20 ሐሥ21፥33፤26፥6፡7
28፥21 ሐሥ22፥5
28፥22 ሐሥ24፥5
28፥23 ማቴ3፥2፤8፥35፤17፥3፤19፥8
28፥24 ሐሥ14፥4፤17፥4፡5
28፥25 ዕብ3፥7
28፥27 መዝ119፥70፤ኢሳ6፥9፡10፤ማቴ13፥15
28፥28 ሉቃ2፥30፤ሐሥ13፥46
28፥31 ቊ23፤ማቴ4፥23፤ሐሥ4፥29

†29 አንዳንድ የጥንት ትርጒሞች ይህ ቊጥር የላቸውም።

# የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
# ወደ ሮሜ ሰዎች

1 ጳውሎስ፣ የክርስቶስ ኢየሱስ ባሪያ፣ ሐዋ
ርያ ሊሆን የተጠራና ለእግዚአብሔር ወን
ጌል የተለየ፤ 2ስለዚህ ወንጌል በነቢያቱ
በኩል በቅዱሳት መጻሕፍት አስቀድሞ ተስፋ
ተሰጠ። 3ወንጌሉም ስለ ልጁ፣ በሥጋ ከዳዊት
ዘር ስለ ሆነ፣ 4በቅድስና መንፈስ[ሀ] ደግሞ
ከሙታን በመነሣቱ የእግዚአብሔር ልጅ
መሆኑ በኀይል ስለ ተገለጠው[ለ] ስለ
ጌታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስ ነው። 5በእርሱ
በኩል ስለ ስሙ ከአሕዛብ ሁሉ መካከል
ሰዎችን በእምነት አማካይነት ወደሚገኘው
መታዘዝ ለመጥራት ጸጋንና ሐዋርያነትን
ተቀበልን። 6እናንተ ራሳችሁም ለኢየሱስ
ክርስቶስ እንዲሆኑ ከተጠሩ መካከል
ናችሁ።

7በእግዚአብሔር ለተወደዳችሁና ቅዱሳን ለመ
ሆን ለተጠራችሁ በሮም ላላችሁ ሁሉ፤ ከአ
ባታችን ከእግዚአብሔር፣ ከጌታም ከኢ
የሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።

## ሮምን ለማየት የጳውሎስ ናፍቆት

8ከሁሉ አስቀድሜ፣ እምነታችሁ በዓለም
ሁሉ በመሰማቱ፣ ስለ ሁላችሁም አምላኬን
በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ።
9ዘወትር ምን ያህል እንደማስባችሁ፣ የልጁ
ን ወንጌል በመስበክ በሙሉ ልቤ የ
ማገለግለው እግዚአብሔር ምስክሬ ነው፤ 10በ
ጸሎቴ ሁልጊዜ አስባችኋለሁ፤ አሁን
ደግሞ በመጨረሻ በእግዚአብሔር ፈቃድ
ወደ እናንተ እንድመጣ መንገድ ይከፈትልኝ
ዘንድ እጸልያለሁ።

11እንድትጸኑ የሚያስችላችሁን መንፈሳዊ
ስጦታ አካፍላችሁ ዘንድ፣ ላያችሁ እናፍ
ቃለሁ። 12ይኸውም እናንተና እኔ በእያን
ዳንዳችን እምነት እርስ በርሳችን እንድን
በረታታ ነው። 13ወንድሞች ሆይ፣ በሌሎች
አሕዛብ ዘንድ እንደ ሆነልኝ፣ በእናንተም
ዘንድ ፍሬ እንዳገኝ ብዙ ጊዜ ዐቅጄ እንደ
ነበርና፣ ሆኖም ግን፣ እስከ አሁን ድረስ
መከልከሌን እንድታውቁ እወዳለሁ።

14ግሪኮች ለሆኑትና ላልሆኑት፣
ለጥበበኞ ችና ለማያስተውሉ፣ ዕዳ አለብኝ፤
15በሮም ለምትኖሩ፣ ለእናንተም ወንጌልን
ለመስበክ የምጓጓው ለዚህ ነው።

16በወንጌል አላፍርም፤ ምክንያቱም
ለሚያ ምን ሁሉ ለድነት የሚሆን የእግዚ
አብሔር ኀይል ነው፤ ይህም በመጀመሪያ
ለአይሁድ፣ ቀጥሎም ለአሕዛብ ነው።
17በወንጌል የእግዚአብሔር ጽድቅ
ተገልጦአልና፤ ጽድቁም ከመ ጀመሪያ
እስከ መጨረሻ በእምነት[ሐ] የሆነ ነው፣
"ጻድቅ በእምነት ይኖራል" ተብሎ እንደ
ተጻፈው።

## የእግዚአብሔር ቍጣ በሰዎች ላይ

18በክፋታቸው እውነትን ዐፍነው በሚይዙ፣
በዐመፃቸውና በክፋታቸው ሁሉ ላይ የእግ
ዚአብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጣል፤ 19ስለ
እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው ለእነርሱ
ግልጽ ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር
ለእነርሱ ግልጽ አድርጎታል። 20ዓለም ከተፈጠ
ረ ጀምሮ የማይታየው የእግዚአብሔር ባሕርይ
ይኸውም ዘላለማዊ ኀይሉና መለኮትነቱ፣
ከፍጥረቱ በግልጽ ይታያል፤ ስለዚህ ሰዎች
ማመካኛ የላቸውም።

21እግዚአብሔርን ቢያውቁም እንኳ፣ እንደ
አምላክነቱ አላከበሩትም፤ ምስጋናም
አላቀረ ቡለትም፤ ነገር ግን ሐሳባቸው ፍሬ
ቢስ ሆነ፤ የማያስተውል ልባቸው ጨለመ።
22ጥበበኞች ነን ቢሉም፣ ሞኞች ሆኑ፤
23የዘላለም አም ላክን ክብር ምዉት በሆነው
ሰው፣ በወፎች፣ በእንስሳትና በምድር ላይ
በሚሳቡ ፍጥረት መልክ መሰለው ለወጡ።

24ስለዚህም እግዚአብሔር በኀጢአት በተሞ
ላው የልባቸው ምኞት እርስ በርሳቸው
የገዛ አካላቸውን እንዲያስነውሩ ቅድስና
ለሌለው ሩካቤ ሥጋ አሳልፎ ሰጣቸው።
25የእግዚአብሔርን እውነት በሐሰት ለወጡ፤
በፈጣሪ ፈንታ ፍጡር አመለኩ፤ አገለገሉም፤
ፈጣሪም ለዘላለም የተመሰገነ ነው፤ አሜን።

26በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር አሳፋሪ
ለሆነ ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፤
ሴቶቻቸውም እንኳ ለባሕርያቸው
የሚገባውን ግንኙነት ባሕርያቸው
ላልሆነው ግንኙነት ለወጡ። 27እንደዚሁም
ወንዶች ለባሕርያቸው የሚገ ባውን
ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው
በፍትወት ተቃጠሉ፤ ወንዶች ከወ ንዶች
ጋር ነውር ፈጸሙ፤ ለክፉ አድራ
ጐታቸውም የሚገባቸውን ቅጣት በገዛ
ራሳቸው ላይ አመጡ።

1፡1 ሐሥ9፡15፤ ሮሜ15፡16፤1 ቆሮ1፡1፤2ቆሮ2፡12፤ 11፡7፤1ተሰ2፡8:9፤ 1ጴጥ4፡17
1፡2 ሉቃ1፡70፤ ሐሥ13፡32፤ቲቶ1፡2፤ ሮሜ3፡21፤ገላ3፡8
1፡3 ማቴ1፡1፤ ዮሐ1፡14፤ሮሜ9፡5፤
1፡4 ማቴ4፡3፤ ሐሥ2፡24፤1ቆሮ1፡2
1፡5 ሐሥ9፡15፤ 6፡7፤ሮሜ16፡26፤ 1ጢ ሞ1፡14፤
1፡6 ይሁዳ1፤ ራ እ17፡14
1፡7 ሐሥ9፡13፤ ሮሜ8፡39፤1ቆሮ1፡3፤ ኤፌ1፡2፤1ተሰ1፡4፤1 ጢሞ1፡2፤ቲቶ1፡4፤ 1ጴጥ1፡2
1፡8 ሮሜ10፡18፤ 16፡19፤1ቆሮ1፡4፤ ኤፌ1፡16፤ 1ተሰ2፡13፤2ተሰ1፡3፤ 2ጢሞ1፡3፤
1፡9 ኢዮ16፡19፤ ኤር42፡5፤2ቆሮ1፡23፤ ገላ1፡20፤ፊል1፡8፤ 1ተሰ2፡5:10፤ 2ጢሞ1፡3፤
1፡10 ቍ13፤ 1ሳሙ12፡23፤ ሉቃ18፡1፤ሐሥ 1፡14፤ ሐሥ18፡21፤ ሮሜ15፡32፤ ኤፌ1፡16፤ፊል1፡4፤ ቈላ1፡9፤2ተሰ1፡11፤ 2ጢሞ1፡3፤ ፊሞ4
1፡11 ሮሜ15፡23፤ 1ቆሮ1፡7፤12፡1-31
1፡13 ሮሜ11፡25፤ 7፡1፤15፡22:23
1፡14 1ቆሮ9፡16
1፡15 ሮሜ15፡20
1፡16 ዮሐ3፡15፤ ሐሥ3፡26፤13፡46፤ ሮሜ2፡9:10፤ 1ቆሮ1፡18፤ 2ጢሞ1፡8፤
1፡17 ዕን2፡4፤ ሮሜ 3፡21፤9፡30፤ ፊል3፡9፤ገላ3፡11፤ ዕብ10፡38
1፡18 ዮሐ3፡36፤ ሮሜ5፡9፤ኤፌ5፡6፤ ቈላ3፡6፤1ተሰ1፡10፤ ራእ19፡15
1፡19 ሐሥ14፡17
1፡20 መዝ19፡1-6፤ ሮሜ2፡1
1፡21 ዘፍ8፡21፤ ኤር2፡5፤17፡9፤ ኤፌ4፡17:18
1፡22 1ቆሮ1፡20፡
27፤3፡18:19 1፡23 ዘዳ4፡16:17፤ መዝ106፡20፤ኤር2፡11፤ ሐሥ17፡29 1፡24 ቍ26:28፤ መዝ81፡12፤ኤፌ4፡19፤ 1ጴጥ4፡3
1፡25 ኢሳ44፡20፤ ኤር10፡14፤13፡25፤16፡19:20፤ ሮሜ9፡5፤11፡36፤ 2ቆሮ11፡31፤ 1፡26 ቍ24:28፤ ዘሌ18፡22:23፤ኤፌ4፡19፤1ተሰ4፡5፤ 1፡27 ዘሌ18፡22፤ 20፡13፤1ቆሮ6፡18

ሀ4 ወይም *በቅድስናው መንፈስ*
ለ4 ወይም *የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ በኀይል ስለ ተሾመ*
ሐ17 ወይም *ከእምነት ወደ እምነት*

28ከዚህም በላይ በሐሳባቸው እግዘአብሔርን
ማወቅ አይጠቅምም በማለታቸው፣ መደረግ
የማይገባውን እንዲያደርጉ እግዚአብሔር
ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው። 29በሁ
ሉም ዐይነት ዐመፃ፣ ክፋት፣ ስግብግብነትና
ምግባረ ብልሹነት ተሞልተዋል፤ ቅናትን፣
ነፍስ ገዳይነትን፣ ጥልን፣ አታላይነትንና
ተንኰልን የተሞሉ ናቸው፤ ሐሜተኞች፣
30ስም አጥፊዎች፣ አምላክን የሚጠሉ፣
ተሳዳቢዎች፣ ትዕቢተኞችና ትምክሕተኞች
ናቸው፤ ክፋትን የሚሠሩበትን መንገድ
ያውጠነጥናሉ፤ ለወላጆቻቸው አይታዘዙም።
31የማያስተውሉ፣ ውል የሚያፈርሱ፣ ርኅራኄ
የሌላቸውና ጨካኞች ናቸው። 32ይህን የሚያ
ደርጉ ሁሉ ሞት ይገባቸዋል የሚለውን
ትክክለኛ የሆነውን የእግዚአብሔርን ሕግ ቢ
ያ ውቁም፣ እነዚህን ነገሮች ማድረግ ብቻ
ሳይ ሆን፣ እንዲህ የሚያደርጉትንም
ያበረታታሉ።

## የእግዚአብሔር ጻድቅ ፍርድ

2 ስለዚህ አንተ በሌላው ላይ የምትፈ
ርድ፣ የምታመካኝበት የለህም፤ በሌላው
ላይ በምትፈርድበት ነገር ሁሉ፣ ራስህን
ትኰንናለህ፤ ፈራጅ የሆንኸው አንተ ያንኑ
ታደርጋለህና። 2እንደዚህ በሚያደርጉትም
ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ ትክክለኛ መሆኑን
እናውቃለን። 3እንግዲህ አንተ ሰው በሌሎች
ላይ እየፈረድህ፣ ያንኑ የምታደርግ ከሆነ
ከእግዚአብሔር ፍርድ የምታመልጥ
ይመስልሃል? 4ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ
ንስሓ የሚመራህ መሆኑን ሳትገነዘብ፣
የቸርነቱን፣ የቻይነ ቱን የትዕግሥቱን
ባለ ጠግነት ትንቃለህ?
5ነገር ግን በድንዳኔህና ንስሓ በማይገባ
ልብህ ምክንያት ትክክለኛ ፍርዱ ሲገለጥ
በእግዚአብሔር የቍጣ ቀን በራስህ ላይ
ቍጣን ታከማቻለህ። 6እግዚአብሔር
"ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ይሰጠዋል"፤ 7በጎ
የሆነውን ጸንቶ በማ ድረግ ክብርን፣ ሞገስንና
ዘላለማዊነትን ለሚሹ የዘላለም ሕይወት
ይሰጣቸዋል። 8ነገር ግን በራስ ወዳዶች፣
እውነትን ትተው ክፋትን በሚከተሉ
ፍርድና ቍጣ ይደርስ ባቸዋል። 9ክፉ
በሚያደርግ በማንኛውም ሰው፣ አስቀድሞ
በአይሁድ ከዚያም በአሕዛብ ላይ መከራና
ጭንቀት ይሆናል፤ 10ነገር ግን በጎ ለሚሠራ
ለማንኛውም፣ አስቀድሞ ለአይሁድ ከዚያም
ለአሕዛብ ክብር፣ ሞገስና ሰላም
ይሆንለታል፤ 11እግዚአብሔር ለማንም
አያደላምና።
12ሕግ ሳይኖራቸው ኀጢአት የሠሩ ሁሉ
ያለ ሕግ ይጠፋሉ፤ ሕግ እያላቸው ኀጢአት
የሠሩ በሕግ ይፈረድባቸዋል፤ 13ምክንያቱም
በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን የሚባሉት ለሕጉ

1፥28 ቀኍ24:26
1፥29 2ቆሮ12፥20፤
1ጢሞ 5፥13፤
ያዕ3፥2፤3፤ዮሐ10
1፥30 2ጢሞ3፡2
1፥31 2ጢሞ3፥3
1፥32 መዝ50፥18፤
ሉቃ11፥48፤ሐሥ8፥1፤
22፥20፤ ሮሜ6፥23፤
2፥1 2ሳሙ12፥5-7፤
ማቴ7፥1:2፤
ሮሜ1፥20፤
2፥4 ዘፀ34፥6፤
ሮሜ9፥22፤9፥23፤11፥22፤
11፥33፤ኤፌ1፥7:18፤
2፥7፤3፥8:16፤ቈላ2፥2፤
3፥25፤1ጢሞ1፥16፤
1ጴጥ3፥20፤
2ጴጥ3፥9፤2ጴጥ3፥15
2፥5 መዝ110፥5፤
ይሁዳ1፥6፤ራእ6፥17፤
2፥6 መዝ62፥12፤
ማቴ16፥27፤ምሳ24፥12
2፥7 ቀኍ10፤
ማቴ25፥46፤
1ቆሮ15፥53:54፤
2ጢሞ1፥10፤
2፥8 ሕዝ22፥31፤
2ተሰ2፥12፤
2፥9 ቀኍ10፤
መዝ32፥10፤
ሮሜ1፥16
2፥10 ቀኍ9፤
ሮሜ1፥16
2፥11 ሐሥ10፥34
2፥12 ሮሜ3፥19፤
6፥14፤ 7፥4፤
1ቆሮ 9፥20:21፤
ገላ 4፥21፤5፥18፤
2፥13 ያዕ1፥22:
23:25
2፥14 ሐሥ10፥35
2፥16 መክ12፥14፤
ሐሥ10፥42፤ሮሜ16፥
25፤1ቆሮ 4፥5፤
2ጢሞ 2፥8
2፥17 ቀኍ23፤
ኤር 8፥8፤ሚክ3፥11፤
ዮሐ 5፥45፤ሮሜ 9፥4
2፥21 ማቴ23፥3:4
2፥22 ሐሥ19፥37
2፥23 ቀኍ17
2፥24 ኢሳ52፥5፤
ሕዝ36፥22፤2ጴጥ2፥2
2፥25 ቀኍ13:27፤
ኤር 4፥4፤ 9፥25:26፤
ገላ 5፥3፤
2፥26 ሮሜ8፥4፤
1ቆሮ 7፥19
2፥27 ማቴ12፥41:42
2፥28 ማቴ3፥9፤
ዮሐ8፥39፤ሮሜ9፥6:
7፤ገላ6፥15
2፥29 ዘዳ30፥6፤
ዮሐ5፥44፤12፥43፤
ሮሜ7፥6፤ 1ቆሮ4፥5፤
2ቆሮ3፥6፤10፥18፤
ገላ1፥10፤ፊል3፥3፤
ቈላ2፥11፤1ተሰ2፥4፤
1ጴጥ3፥4
3፥2 ዘዳ4፥8፤
መዝ147፥19፤
ሐሥ7፥38፤ሮሜ9፥4:5፤

የሚታዘዙ እንጂ፣ ሕጉን የሚሰሙ አይደሉም።
14ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ሕግ የሚያዝዘውን
ነገር በተፈጥሮ ሲያደርጉ፣ ሕግ ባይኖራቸውም
እነርሱ ለራሳቸው ሕግ ናቸው። 15ኅሊናቸው
ስለሚመሰክር፣ ሐሳባቸው ስለሚከሳቸው፣
ደግሞም ስለሚከላከልላቸው የሕግ ትእዛዝ
በልባቸው የተጻፈ መሆኑን ያሳያሉ።
16ይህም በወንጌል እንደማስተምረው እግዚ
አብሔር በሰው ልብ የተሰወረውን
በክርስቶስ በኩል በሚፈርድበት ዕለት ግል
ጽ ይሆናል።

## ሕግና አይሁድ

17አንተ ይሁዲ ነኝ ካልህ፣ በሕግ የምት
ተማመንና ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ግንኙነት
የምትኰራ፣ 18በሕግ በመመራትህም ፈቃዱን
ዐውቀህ ፍጹም የሆነውን ለይተህ ከያዝህ፣
19ለዕውሮች መሪ፣ በጨለማ ላሉትም ብርሃን
መሆንህን እርግጠኛ ከሆንህ፣ 20በሕጉም ካገ
ኘኸው ዕውቀትና እውነት የተነሣ አላዋቂ
ለሆኑት መካሪ፣ ለሕፃናት አስተማሪ ከሆንህ፣
21እንግዲህ አንተ ሌሎችን የምታስተምር፣
ራስህን አታስተምርምን? አትስረቅ ብለህ
የምትሰብክ፣ ትሰርቃለህን? 22አንተ ሰዎች
ማመንዘር የለባቸውም የምትል፣ ታመነዝ
ራለህን? አንተ ጣዖትን የምትጸየፍ፣ ቤተ
መቅደስን ትመዘብራለህን? 23አንተ በሕግ
የምትመካ፣ ሕግን በመተላለፍ እግዚአብሔርን
ታዋርዳለህን? 24ይህም "በእናንተ ምክንያት
የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ ዘንድ ይሰደባል"
ተብሎ እንደ ተጻፈው መሆኑ ነው።
25ሕግን የምትፈጽም ከሆነ ግዝረት ዋጋ
አለው፤ ሕግን የምትተላለፍ ከሆነ ግን እን
ዳልተገረዝህ ትሆናለህ። 26ያልተገረዙት ሕጉ
የሚያዝዘውን የሚፈጽሙ ከሆነ፣ እንደ
ተገረዙ አይቈጠሩምን? 27አንተ የተጻፈ ሕግ፣
ግዝረትም ቢኖርህ፣ ሕግ ተላላፊ በመሆንህ፣
በሥጋ ያልተገረዘው ለሕግ በመታዘዙ ይፈር
ድብሃል።
28አንድ ሰው ለይምሰል በውጫዊው
ብቻ ይሁዲ ልሁን ቢል ይሁዲ
አይሆንም፤ እውነተኛ ግዝረትም ውጫዊና
ሥጋዊ ሥርዐት አይደለም። 29ዳሩ ግን
አንድ ሰው ይሁዲ የሚሆነው በውስጣዊ
ማንነቱ ይሁዲ ሆኖ ሲገኝ ነው። ግዝረትም
ግዝረት የሚሆ ነው በተጻፈው ሕግ ሳይሆን፣
በመንፈስ የልብ ግዝረት ሲኖር ነው። እንዲህ
ያለው ሰው ምስጋናው ከሰው ሳይሆን
ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።

## የእግዚአብሔር ታማኝነት

3 ታዲያ አይሁዳዊ መሆን ጥቅሙ ምንድን
ነው? መገረዝስ ምን ፋይዳ አለው?
2በየትኛውም መንገድ ጥቅሙ ብዙ ነው፤
ከሁሉ አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃል

በዐደራ የተሰጠው ለእነርሱ ነው።
3አንዳንዶች እምነት ባይኖራቸውስ? የእ
ነርሱ አለማመን የእግዚአብሔርን ታማኝነት
ዋጋ ያሳጣዋልን? 4ፈጽሞ አይሆንም! ሰው
ሁሉ ሐሰተኛ፣ እግዚአብሔር ግን እውነተኛ
ይሁን፤ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤

"ከቃልህ የተነሣ እውነተኛ፣
በፍርድም ፊት ረቺ ትሆናለህ።"

5የእኛ ዐመፃ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አጒልቶ
የሚያሳይ ከሆነ፣ ምን ማለት እንችላለን?
እንደ ሰው ለመከራከር ያህል እግዚአብሔር
በእኛ ላይ ቍጣውን ማምጣቱ ትክክል
አይደለም ሊባል ነውን? እንደ ሰው ሲታ
ሰብ ማለቴ ነው። 6በእርግጥ እንዲህ ሊሆን
አይችልም፤ እንዲህ ቢሆንማ ኖሮ እግዚአብሔር
በዓለም ላይ እንዴት ሊፈርድ ይችላል?
7"የእኔ ውሸተኛ መሆን የእግዚአብሔርን እው
ነተኛነት የሚያጐላ፣ ክብሩንም የሚጨም
ርለት ከሆነ፣ ኀጢአተኛ ተብዬ እስካሁን
እንዴት ይፈርድብኛል?" በማለት ሊከራ
ከር የሚችል ሰው ይኖር ይሆናል። 8ይህማ
"በጎ እንዲመጣ ክፉ እንሥራ" ይላሉ በማ
ለት አንዳንዶች እንደሚያስወሩብን ነው፤
በእነዚህ ሰዎች ላይ የሚደርሰው ፍርድ
ትክክለኛ ነው።

### ማንም ጻድቅ አይደለም

9እንግዲህ ምን እንላለን? እኛ ከእነርሱ
እንበልጣለንን?[መ] ከቶ አይደለም፤
አይሁድም ሆኑ አሕዛብ፣ ሁሉም ከኀጢአት
በታች እን ደሆኑ አስቀድመን ከሰናቸዋል፤

10እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤

"ጻድቅ ማንም የለም፤ አንድም እንኳ፤
11አስተዋይ የለም፤
እግዚአብሔርንም የሚሻ አንድም የለም።
12ሁሉም ተሳስተዋል፤
በአንድነት የማይጠቅሙ ሆነዋል፤
በጎ የሚያደርግ ማንም የለም፤
አንድም እንኳ።"
13"ጒሮሮአቸው የተከፈተ መቃብር ነው፤
አንደበታቸው ሽንገላን ያዘወትራል።"
"በከንፈሮቻቸው የእባብ መርዝ አለ።"
14"አፋቸው ርግማንና ምሬት ሞልቶበታል።"
15"እግራቸው ደም ለማፍሰስ ፈጣን ነው፤
16በመንገዳቸው ጥፋትና ጒስቍልና ይገኛል፤
17የሰላምንም መንገድ አያውቁም።"
18"በዐይናቸው ፊት የእግዚአብሔር
ፍርሀት የለም።"

19እንግዲህ አፍ ሁሉ እንዲዘጋና ዓለም
በሙሉ ለእግዚአብሔር መልስ እንዲሰጥ ሕ
ግ የሚናገረው ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት
እንደ ሆነ፣ እናውቃለን፤ 20ስለዚህ ሕግን
በመጠበቅ ማንም በእርሱ ፊት ጻድቅ ነው
ሊባል አይችልም፤ ይልቁንም በሕግ አ
ማካይነት ኀጢአትን እንገነዘባለን።

### በእምነት የሚገኝ ጽድቅ

21አሁን ግን ሕግና ነቢያት የመሰከሩ
ለት፣ ከሕግ ውጭ የሆነ፣ የእግዚአብሔር
ጽድቅ ተገልጦአል። 22ይህ የእግዚአብሔር
ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን
የሚገኝ ጽድቅ ነው። ልዩነት የለም፤
23ምክንያቱም ሁሉም ኀጢአትን
ሠርተዋል፤ የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአጠ
ቸዋል፤ 24በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነት
እንዲያው በጸጋው ጸድቀዋል፤ 25በደ ሙም
በሆነው እምነት፣ እግዚአብሔር የማስ
ተስረያ መሥዋዕት አድርጎ አቅርቦታል፤[ሠ]
ይህንም ያደረገው ቀድሞ የተፈጸመውን ኀጢ
አት ሳይቀጣ በትዕግሥት በማለፍ ጽድቁን
ለማሳየት ነው፤ 26በአሁኑ ዘመን ይህን ያደረ
ገው፣ ጽድቁን ይኸውም እርሱ ራሱ ጻድቅ
ሆኖ፣ በኢየሱስ የሚያምነውን የሚያጸድቅ
መሆኑን፣ ለማሳየት ነው።
27ታዲያ ትምክሕት ወዴት ነው? እርሱማ
ቀርቶአል። በየትኛው ሕግ? በሥራ ሕግ
ነውን? አይደለም፤ በእምነት ሕግ ነው እንጂ።
28ማንም ሰው ሕግን በመፈጸም ሳይሆን፣
በእምነት እንደሚጸድቅ እናረጋግጣለን። 29እግዚ
አብሔር የአይሁድ አምላክ ብቻ ነውን? የአሕ
ዛብስ አምላክ አይደለምን? አዎን፤ የአሕ
ዛብም አምላክ ነው፤ 30የተገረዘውን
በእምነት፣ ያልተገረዘውንም በዚያው
እምነት የሚያጸድቅ አንድ እግዚአብሔር
ብቻ ነውና። 31ታዲያ እንዲህ ከሆነ
ከእምነት የተነሣ ሕግን ዋጋ የሌለው
እናደርግ ይሆን? ፈጽሞ አይደረግም፤ ሕጉን
እናጸናለን እንጂ።

### አብርሃም በእምነት ጸደቀ

4 እንግዲህ በሥጋ የቀድሞ አባታችን
የሆነ አብርሃም በዚህ ረገድ ምን አገኘ
እንላለን? 2አብርሃም በሥራ ጸድቆ ቢሆን ኖሮ፣
የሚመካበት ነበረው፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር
ፊት መመካት አይችልም። 3መጽሐፍስ ምን
ይላል? "አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም
ሆኖ ተቈጠረለት።"
4አንድ ሰው ሥራ ከሠራ ደመወዙ እንደ
ስጦታ ሳይሆን እንደ ተገቢ ዋጋው ይቈጠር

3፥3 ሮሜ10፥16፤ 2ጢሞ2፥13፤ዕብ4፥2፤
3፥4 መዝ116፥11፤ 51፥4፤ዮሐ3፥33፤
3፥5 ሮሜ 5፥8፤ 6፥19፤ ገላ3፥15
3፥6 ዘፍ18፥25፤ ሮሜ2፥16
3፥7 ቍ4፤ ሮሜ9፥19
3፥8 ሮሜ6፥1
3፥9 ቍ1:19:23፤ 1ነገ8፥46፤ 2ዜና 6፥36፤መዝ106፥6፤ መክ7፥20፤ሮሜ5፥12፤ 11፥32፤ገላ3፥22
3፥12 መዝ14፥1-3፤ 53፥1-3፤
3፥13 መዝ5፥9፤ 140፥3
3፥14 መዝ10፥7
3፥17 ኢሳ59፥7:8
3፥18 መዝ36፥1
3፥19 ቍ9፤ መዝ63፥11፤107፥42፤ ሕዝ16፥63፤ ዮሐ10፥34፤ ሮሜ2፥12፤
3፥20 ሐሥ13፥39፤ ሮሜ4፥15፤ገላ2፥16፤
3፥21 ኢሳ46፥13፤ ኤር23፥6፤ ሐሥ10፥43፤ ሮሜ1፥2፤17፤9፥30፤
3፥22 ዮሐ3፥15፤ ሮሜ1፥17፤4፥11፤ 9፥30፤10፥4:12፤ ገላ2፥16፤3፥22፤28፤ ቆላ3፥11
3፥23 ቍ9
3፥24 መዝ130፥7፤ ዮሐ1፥14:16:17፤ ሮሜ 4፥16፤ 5፥21፤ 4፥25፤ 6፥14፤ 11፥5፤ 2ቆሮ12፥9፤ ኤፌ1፥7:14፤ 2፥8፤ 4፥7፤1ቆሮ1፥30፤ ገላ4፥5፤ቆላ1፥14፤ ቲቶ2፥11፤ዕብ 4፥16፤ዕብ9፥12
3፥25 ዘፀ25፥17፤ ዘሌ16፥10፤መዝ65፥3፤ሐ ሥ14፥16፤17፥30፤ 20፥28፤ሮሜ5፥9፤ ኤፌ1፥7፤ዕብ2፥17፤ 9፥28፤13፥12፤ 9፥12:14፤1ጴጥ1፥19፤ 1ዮሐ4፥10፤ራእ1፥5፤
3፥27 ሮሜ2፥17: 23፤4፥2፤1ቆሮ1፥29-31፤ኤፌ2፥9
3፥28 ሐሥ13፥39፤ ሮሜ3፥20:21፤ ኤፌ2፥9፤ገላ2፥16፤

3፥11፤ያዕ2፥20:24:26፤ 3፥29 ሐሥ10፥34: 35፤ሮሜ9፥24፤10፥12፤ 15፥9፤ገላ3፥28 3፥30 ሮሜ4፥11: 12፤ ገላ3፥8
4፥1 ሮሜ8፥31፤ ሉቃ3፥8 4፥2 1ቆሮ1፥31 4፥3 ቍ5:9:22፤ ዘፍ15፥6፤ገላ3፥6፤ያዕ2፥23 4፥4 ሮሜ11፥6

[መ]9 ወይም *እንብሳለንን*
[ሠ]25 ወይም *እግዚአብሔር ቍጣውን በመተው ኀጢአትን ለ ማስወገድ*

ለታል። 5ነገር ግን ለማይሠራው፣ ኃጥኡን
ሰው ጻድቅ በሚያደርግ በእግዚአብሔር ለሚ
ያምን ሰው፣ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቈጠ
ርለታል። 6ዳዊትም ጽድቅ ያለ ሥራ ስለሚቈጠ
ርለት ሰው ብፅዕና እንዲህ ብሎአል፤

7"መተላለፋቸው ይቅር የተባለላቸው፣
ኀጢአታቸው የተሰረየላቸው፣
ብፁዓን ናቸው።
8ኀጢአቱን፣ ጌታ ከቶ የማይቈጥርበት ሰው
ብፁዕ ነው።"

9ይህ ብፅዕና ለተገረዙት ብቻ ነው ወይስ
ላልተገረዙትም? የአብርሃም እምነቱ ጽድቅ
ሆኖ ተቈጠረለት ብለናል። 10ታዲያ
እንዴት ተቈጠረለት? ከተገረዘ በኋላ ነው
ወይስ ከመገረዙ በፊት? የተቈጠረለት
ከተገረዘ በኋላ ሳይሆን ከመገረዙ በፊት
ነው። 11ሳይገረዝ በነበረው እምነት ላገኘው
ጽድቅ፣ የመገረዝን ምልክት ይኸውም የ
ጽድቅን ማኅተም ተቀበለ፤ ስለዚህ
ለሚያምኑ ነገር ግን ላልተገረዙት ጽድቅ
ይቈጠርላቸው ዘንድ የሁሉ አባት ነው።
12እርሱ ለተገረዙትም አባት ነው፤ መገረዝ
ብቻ ሳይሆን፣ አባታችን አብርሃም ከመገረዙ
በፊት የነበረውን የእምነ ቱን ፈለግ
ለሚከተሉ ሁሉ ነው። 13እርሱ የዓለም ወራሽ
እንዲሆን አብርሃምና ዘሩ ተስፋን
የተቀበሉት በሕግ በኩል አልነበረም፤ ነገር
ግን በእምነት ከሆነው ጽድቅ ነው።
14በሕግ የሚኖሩት ወራሾች ከሆኑ፣ እምነት
የማይጠቅም፣ ተስፋም ከንቱ በሆነ ነበር፤
15ሕግ ቍጣን ያስከትላል፤ ሕግ በሌለበት
ግን መተላለፍ አይኖርም።
16ስለዚህ ተስፋው በእምነት መጥቶአል፤
ይኸውም ተስፋው በጸጋ እንዲሆንና ለአብ
ርሃም ዘር ሁሉ ዋስትና ይሆን ዘንድ ነው፤
ይህም በሕግ የእርሱ ለሆኑት ብቻ ሳይሆን፣
በእምነት የአብርሃም ለሆኑትም ነው፤ እር
ሱም የሁላችን አባት ነው፤ 17ይህም "የብዙ
ሕዝብ አባት አድርጌሃለሁ" ተብሎ እንደ
ተጻፈው ነው፤ እርሱም ለሙታን ሕይወትን
በሚሰጥ፣ ያልነበረውንም እንደ ነበረ በሚያ
ደርግ፣ ባመነበት አምላክ ፊት አባታችን
ነው።
18"ዘርህም እንዲሁ ይሆናል" ተብሎ
ለእርሱ በተነገረው መሠረት፣ ምንም ተስፋ
በሌለበት፣ አብርሃም በተስፋ አምኖ የብዙ
ሕዝብ አባት ሆነ። 19እርሱ የመቶ ዓመት
ሰው ሆኖ ሳለ፣ የራሱም ሰውነት ሆነ የሣራ
ማሕፀን ምውት እንደ ነበረ እያወቀ በእምነቱ
አልደከመም። 20ይልቁንም በእምነቱ በመ
ጽናት ለእግዚአብሔር ክብርን ሰጠ እንጂ፣
የእግዚአብሔርን ተስፋ አልተጠራጠረም፤
21እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ እንደሚፈ
ጽም በሙሉ ልብ እርግጠኛ ነበር።
22ስለዚህ፣ "ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት።"
23"ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት" የሚለው ቃል
የተጻፈው ለእርሱ ብቻ አይደለም፤ 24ነገር
ግን እግዚአብሔር ጽድቅ አድርጎ
ለሚቈጥርልን፣ ጌታ ችን ኢየሱስን
ከሙታን ባስነሣው በእርሱ ለምናምን
ለእኛም ጭምር ነው። 25እርሱ ስለ ኀጢ
አታችን እንዲሞት ዐልፎ ተሰጠ፤ እኛን
ጻድቅ አድርጎ ለማቅረብም ከሞት ተነሣ።

## ሰላምና ደስታ

5 እንግዲህ በእምነት ስለ ጸደቅን፣ በጌታ
ችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል
ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለንʻ። 2በእርሱም
በኩል አሁን ወደ ቆምንበት ጸጋ በእምነት
መግባት ችለናል፤ የእግዚአብሔርንም ክብር
ተስፋ በማ ድረግ ሐሤት እናደርጋለን።ʻ
3በዚህ ብቻ ሳይሆን በመከራችንም ሐሤት
እናደርጋለንʻ፤ ምክንያቱም መከራ ትዕ
ግሥትን እንደሚ ያስገኝ እናውቃለን። 4ትዕ
ግሥት ጽናትን፣ ጽናት የተፈተነ ባሕርይን፣
የተፈተነ ባሕርይ ተስፋን፤ 5ይህም ተስፋ
ለዕፍረት አይዳርግ ገንም፤ እግዚአብሔር በሰጠ
ን በመንፈስ ቅዱስ ፍቅሩን በልባችን
አፍስሶአልና።
6ገና ደካሞች ሳለን፣ ልክ ጊዜው ሲ
ደርስ፣ ክርስቶስ ስለ ኀጢአተኞች
ሞቶአልና። 7ለጻድቅ የሚሞት ሰው
ማግኘት እጅጉን ያዳግታል፤ ለደግ ሰው
ሲል ሊሞት የሚ ደፍር ምናልባት ይገኝ
ይሆናል። 8ነገር ግን ገና ኀጢአተኞች
ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞተ፤ ይህም እግዚ
አብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር
ያሳያል።
9አሁን በደሙ ከጸደቅን፣ ይልቁንማ በእ
ርሱ በኩል ከእግዚአብሔር ቍጣ እንዴት
አንድንም! 10የእግዚአብሔር ጠላቶች ሳለን
በልጁ ሞት ከእርሱ ጋር ከታረቅን፣ ዕር
ቅን ካገኘን በኋላ፣ በሕይወቱማ መዳናችን
እንዴት የላቀ አይሆንም! 11ይህ ብቻ አይ
ደለም። ነገር ግን አሁን ዕርቅን ባገኘንበት
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚ
አብሔር ደግሞ ሐሤት እናደርጋለን።

## ሞት በአዳም፣ ሕይወት በክርስቶስ

12ስለዚህ ኀጢአት በአንድ ሰው በኩል
ወደ ዓለም እንደ ገባ ሁሉ፣ ሞትም በኀጠ
አት በኩል ገብቶአል፤ በዚሁ መንገድ
ሞት ወደ ሰዎች ሁሉ መጣ፤ ምክንያቱም
ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋል፤ 13ሕግ
ከመሰጠቱ በፊት ኀጢአት በዓለም ላይ
ነበር፤ ነገር

4፥5 ቍ3፥9፥22፤ ሮሜ9፥30
4፥8 መዝ32፥1፡2፤ 103፥12፤2ቆሮ5፥19
4፥9 ቍ3፤ ሮሜ3፥30፤
4፥11 ቍ16፡17፤ ዘፍ17፥10፡11፤ ሉቃ 3፥8፤ሮሜ3፥22
4፥13 ዘፍ17፥4-6፤ ሐሥ13፥32፤ ሮሜ9፥30፤ ገላ 3፥16፡29፤
4፥14 ገላ3፥18
4፥15 ሮሜ7፥7-25፤ 7፥12፤ 3፥20፤5፥13፤ 7፥7፤1ቆሮ15፥56፤ 2ቆሮ3፥7፤ገላ3፥10፤
4፥16 ቍ11፤ ሉቃ3፥8፤ሮሜ3፥24፤ 15፥8፤ገላ3፥16
4፥17 ዘፍ17፥5፤ ኢሳ48፥13፤ዮሐ5፥21፤ 1ቆሮ1፥28
4፥18 ቍ17፤ ዘፍ15፥5
4፥19 ዘፍ17፥17፤ 18፥11፤ዕብ 11፥11፡12፤
4፥20 1ሳሙ30፥6፤ ማቴ9፥8
4፥21 ዘፍ18፥14፤ ማቴ19፥26
4፥22 ቍ3
4፥24 መዝ 102፥18፤ ዕን 2፥2፤ ሐሥ 2፥24፤ ሮሜ10፥9፤15፥4፤ 1ቆሮ 9፥10፤10፥11፤ 2ጢሞ3፥16፡17፤ 1ጴጥ1፥21
4፥25 ኢሳ53፥5፡6፤ ኢሳ 53፥11፤ሮሜ 5፥6፡8፤8፥32፤1ቆሮ 6፥11፤2ቆሮ5፥21፤ ሮሜ 3፥24፤ 5፥1፡9፡ 16፡18፤8፥30፤ 2ቆሮ5፥15
5፥1 ቍ10፤ ሉቃ2፥14፤ ሮሜ4፥25፤3፥28፤
5፥2 1ቆሮ15፥1፤ ኤፌ2፥18፤3፥12፤ ዕብ3፥6
5፥3 ማቴ5፥12፤ ዕብ10፥36
5፥5 ቍ8፤ ዮሐ3፥16፤ሐሥ2፥33፤ ሮሜ310፥45፤ ፊል1፥20፤ቲቶ3፥5፡6፤ ዕብ3፥6፤1ዮሐ3፥2፡3፤
5፥6 ቍ8፡10፤ ማር 1፥15፤ሮሜ4፥25፤ ኤፌ1፥10፤ገላ4፥4፤
5፥8 ዮሐ3፥16፤ 15፥13፤1ጴጥ3፥18፤ 1ዮሐ3፥16፤4፥10
5፥9 ሮሜ4፥25፤ 3፥25፤1፥18
5፥10 ቍ11፤ ሮሜ8፥34፤11፥15፤ 11፥28፤2ቆሮ5፥18፡19፤ ቈላ1፥20፡21፡22፤ዕብ7፥25 5፥11 ቍ10 5፥12 ቍ 14፡15፡ 16፡1718፤ዘፍ2፥17፤3፥1-7፤1ቆሮ15፥21፡22፤3፥19፤ሮሜ3፥9፤6፥23፤
5፥13 ሮሜ4፥15

ʻ5 1፡2፡3 ወይም *ሰላም ይኑረን፣ እናድርግ፣ እናድርግ*

ግን ሕግ በሌለበት ኀጢአት አይቈጠርም። 14ይሁን እንጂ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ባሉት፣ እንደ አዳም ሕግን በመጣስ ኀጢአት ባልሠሩት ላይ እንኳ ሞት ነግሦ፤ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው አምሳሉ ነበረ።

15ነገር ግን ስጦታው እንደ በደሉ መጠን አይደለም፤ በአንድ ሰው መተላለፍ ብዙዎቹ ከሞቱ፣ የእግዚአብሔር ጸጋና በአንዱ ሰው፣ ይኸውም በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የመጣው ስጦታ ለብዙዎች እንዴት አብልጦ ይትረፈረፍ! 16ደግሞ የእግዚአብሔር ስጦታ እንደ አንዱ ሰው የኀጢአት ውጤት አይደለም፤ ምክንያቱም ፍርዱ የአንድን ሰው ኀጢአት ተከትሎ ኵነኔን አመጣ፤ ስጦታው ግን አያሌ መተላለፍን ተከትሎ ጽድቅን አመጣ። 17በአንድ ሰው መተላለፍ ምክንያት ሞት በዚህ ሰው በኩል የነገሠ ከሆነ፣ የእግዚአብሔርን የተትረፈረፈ ጸጋና የጽድቅ ስጦታ የተቀበሉት፣ በአንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንዴት አብልጠው በሕይወት አይነግሡ!

18ከእንግዲህ በአንድ ሰው መተላለፍ የተነሣ ኵነኔ በሁሉ ሰው ላይ እንደ መጣ፣ እንዲሁም በአንዱ የጽድቅ ሥራ ለሰው ሁሉ ሕይወትን የሚሰጥ ጽድቅ ተገኘ። 19በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኀጢአተኞች እንደ ሆኑ፣ በአንዱ ሰው መታዘዝ ደግሞ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ።

20ሕግ በመምጣቱ መተላለፍ በዛ፤ ነገር ግን ኀጢአት በበዛበት ጸጋ አብልጦ የተትረፈረፈ ሆነ፤ 21ይህም የሆነው ኀጢአት በሞት እንደ ነገሠ ሁሉ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ደግሞ የዘላለም ሕይወት ይገኝ ዘንድ ጸጋ በጽድቅ እንዲነግሥ ነው።

## ለኀጢአት መሞት፣ በክርስቶስ ሕያው መሆን

6 እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ ኀጢአት እየሠራን እንኑር? 2ከቶ አይሆንም፤ ለኀጢአት ሞተናል፤ ታዲያ እንዴት አድርገን ከእንግዲህ በእርሱ እንኖራለን? 3ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንድንሆን የተጠመቅን፣ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? 4ስለዚህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሞት እንደ ተነሣ፣ እኛም እንዲሁ በአዲስ ሕይወት እንድንኖር በጥምቀት ሞተን ከእርሱ ጋር ተቀበርን።

5በሞቱ ከእርሱ ጋር እንደዚህ ከተባበርን፣ በትንሣኤው ደግሞ በእርግጥ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን። 6ከእንግዲህ የኀጢአት ባሮች እንዳንሆን፣ የኀጢአት ሰውነት እንዲሻር[ሀ] አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን፤ 7ምክንያቱም የሞተ ከኀጢአት ነጻ ወጥቶአል።

8ከክርስቶስ ጋር ከሞትን፣ ከእርሱ ጋር እንደምንኖር እናምናለን። 9ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶአልና፣ ዳግመኛ እንደማይሞት እናውቃለንና፤ ሞት ከእንግዲህ በእርሱ ላይ ጒልበት አይኖረውም። 10በሞተ ጊዜ፣ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለኀጢአት ሞቶአል፤ ነገር ግን በሕይወት መኖርን ለእግዚአብሔር ይኖራል።

11እንደዚሁም ለኀጢአት እንደ ሞታችሁ፣ ነገር ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን ቍጠሩ። 12ስለ ዚህ ክፉ መሻቱን ትፈጽሙ ዘንድ በሚሞት ሥጋችሁ ላይ ኀጢአት እንዲነግሥበት አታድርጉ። 13ብልቶቻችሁን የክፋት መሣሪያ አድርጋችሁ ለኀጢአት አታቅርቡ፤ ይልቁንስ ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገሩ ሰዎች አድርጋችሁ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፤ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ መሣሪያ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ። 14ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች ስላልሆናችሁ፣ ኀጢአት አይገዛችሁምና።

## የጽድቅ ባሮች

15እንግዲህ ምን ይሁን? ከሕግ በታች ሳይሆን፣ ከጸጋ በታች በመሆናችን ኀጢአት እንሥራን? በጭራሽ አይገባም! 16ራሳችሁን እንደ ባሪያ አድርጋችሁ ስታቀርቡ፣ ለምትታዘዙት ለእርሱ፣ ይኸውም ወደ ሞት ለሚወስደው ለኀጢአት ወይም ወደ ጽድቅ ለሚያደርሰው ለመታዘዝ ባሮች እንደ ሆናችሁ አታውቁምን? 17ነገር ግን የኀጢአት ባሮች የነበራችሁ ቢሆንም፣ ለተሰጣችሁለት ትምህርት በሙሉ ልብ የታዘዛችሁ በመሆናችሁ፣ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፤ 18ከኀጢአት ነጻ ወጥታችሁ፣ የጽድቅ ባሪያዎች ሆናችኋል።

19በተፈጥሮ ደካሞች ስለ ሆናችሁ፣ በሰው ቋንቋ ይህን እላለሁ፤ ብልቶቻችሁን በባርነት ለርኵሰትና እየባሰ ለሚሄድ ክፋት ታቀርቡ እንደ ነበር፣ አሁን ደግሞ ወደ ቅድስና ለሚወስደው ጽድቅ ባሪያ አድርጋችሁ አቅርቡ። 20የኀጢአት ባሮች ሳላችሁ ከጽድቅ ነጻ ነበራችሁ። 21አሁን ከምታፍሩበት ነገር ያን ጊዜ ምን ጥቅም አገኛችሁ? የዚያ ነገር ውጤት ሞት ነው። 22አሁን ግን ከኀጢአት ነጻ ወጥታችሁ የእግዚአብሔር ባሮች ሆናችኋል፤ የምትሰበስቡትም ፍሬ ወደ ቅድስና ያመራል፤ መጨረሻውም የዘላለም ሕይወት ነው። 23የኀጢአት ደመ ወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር ስጦታ ግን በጌታችን በክርስቶስ

5፥14 ዘፍ3፥11:12፤ 1ቆሮ15፥22:45
5፥15 ቍ12:18:19፤ ሐሥ15፥11
5፥17 ቍ12፤ ዮሐ10፥10
5፥18 ቍ12፤ ኢሳ53፥11፤ ሮሜ4፥25፤
5፥19 ቍ12፤ ሮሜ3፥9፤ፊል2፥8
5፥20 ሮሜ3፥20፤ 6፥1፤7፥7:8፤ገላ3፥19፤ 1ጢሞ1፥13:14
5፥21 ቍ12፥14 ማቴ25፥46፤ ሮሜ6፥16፤3፥24፤
6፥1 ቍ15፤ ሮሜ3፥5:8፤8፥31፤
6፥2 ቍ 6:10:11:18፤ሮሜ8፥13፤ ቈላ3፥5፤1ጴጥ 2፥24
6፥3 ማቴ28፥19
6፥4 ቍ6፤ ሐሥ 2፥24፤ ሮሜ 7፥6፤2ቆሮ 5፥17፤ኤፌ4፥22-24፤ ቈላ3፥10
6፥5 ቍ4:8፤ ሮሜ8፥11፤2ቆሮ4፥10፤ ኤፌ2፥6፤ፊል3፥10:11፤ቈላ2፥12፤3፥1 2ጢሞ2፥11
9፤ 5፥24፤ 6፥14፤
6፥7 ቍ 18 6፥8 ቍ 5 6፥9 ቍ 4፤ ሐሥ 2፥24፤ ራእ 1፥18 6፥10 ቍ2፤ ዕብ7፥27
6፥6 ቍ2:3-8፤16፤ ሮሜ7፥24፤2ቆሮ4፥10፤ገላ 2፥20፤5፥24፤ ኤፌ4፥22፤ፊል3፥10፤ ቈላ2፥12:20፤3፥3፤3፥6
6፥11 ቍ2
6፥12 ቍ16
6፥13 ቍ16:19፤ ሮሜ7፥5፤12፥1፤ 2ቆሮ5፥14:15፤ 1ጴጥ2፥24
6፥14 ቍ16፤ ሮሜ2፥12፤3፥24
6፥15 ቍ1:14
6፥16 ቍ 6:12: 14:17:20:23፤ ዘፍ4፥7፤መዝ51፥5፤ 119፥133፤ዮሐ8፥34፤ ሮሜ5፥21፤7፥14:23:25፤8፥2፤ 2ጴጥ2፥19፤
6፥17 ቍ16፤ ሮሜ1፥8፤2ቆሮ2፥14፤ 2ጢሞ1፥13
6፥18 ቍ2:7:22 16:22፤ሮሜ8፥2፤ 1ጴጥ4፥1፤
6፥19 ቍ13:22፤ ሮሜ3፥5፤ገላ3፥15፤
6፥20 ቍ16
6፥21 ቍ23

6፥22 ቍ18:19፤ ማቴ25፥46፤ሮሜ7፥25፤1ቆሮ7፥22፤ ኤፌ6፥6፤1ጴጥ2፥16፤ 6፥23 ቍ16:21፤ዘፍ2፥17፤ ምሳ10፥16፤ ሕዝ18፥4፤ማቴ25፥46፤ሮሜ1፥32፤5፥12፤7፥5:13፤ 8፥6:13፤ ገላ6፥7:8፤ያዕ1፥15፤

[ሀ] 6 ወይም ኀይል እንዳይኖረው

ኢየሱስ[ሽ] የዘላለም ሕይወት ነው።

## የጋብቻ ምሳሌ

**7** ወንድሞች ሆይ፤ ሕግን ለሚያውቁ ሰዎች
እናገራለሁ፤ ሕግ በአንድ ሰው ላይ
ሥልጣን የሚኖረው፣ ሰውዬው በሕይወት
እስካለ ድረስ ብቻ መሆኑን አታውቁምን?
2አንዲት ያገባች ሴት ከባሏ ጋር በሕግ
የታሰረች የምትሆነው እርሱ በሕይወት
እስካለ ድረስ ነው፤ ባሏ ቢሞት ግን ከጋ
ብቻ ሕግ ነጻ ትሆናለች። 3ነገር ግን ባሏ በሕ
ይወት እያለ ሌላ ሰው ብታገባ አመንዝራ
ትባላለች፤ ባሏ ቢሞት ግን ሌላ ሰው
ብታገባም እንኳ፣ ከዚያ ሕግ ነጻ ትሆናለች፤
አመንዝራ አትባልም።
4ስለዚህ ወንድሞቼ ሆይ፤ እናንተም በክር
ስቶስ ኢየሱስ ሥጋ ለሕግ ሞታችኋል፤
ይህም ከሙታን ለተነሣው ለእርሱ፣ ለሌላው
ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ
ነው። 5ኀጢአተኛ በሆነ ተፈጥሮ[ቀ] ቊጥጥር
ሥር ሳለን፣ ለሞት ፍሬ እንድናፈራ በሕግ
የተቀሰቀሰው የኀጢአት መሻት በሥጋችን ላይ
ይሠራ ነበር። 6አሁን ግን ቀድሞ ጠፍሮ
አስሮን ለነበረው ሞተን፣ ከሕግ ነጻ ወጥ
ተናል፤ ይህም አሮጌ በሆነው በተጻፈው ሕግ
ሳይሆን፣ አዲስ በሆነው በመንፈስ መንገድ
እንድናገለግል ነው።

## ከኀጢአት ጋር መታገል

7እንግዲህ ምን እንላለን? ሕግ በራሱ ኀጢ
አት ነውን? በፍጹም አይደለም፤ ነገር ግን
በሕግ በኩል ባይሆን ኖሮ፣ ኀጢአት ምን
እንደ ሆነ ባላወቅሁም ነበር፤ ሕጉ "አትመኝ"
ባይል ኖሮ፣ ምኞት ምን እንደ ሆነ በእር
ግጥ አላውቅም ነበር። 8ኀጢአት ግን ትእዛዙ
ባስገኘው ዕድል ተጠቅሞ በእኔ ውስጥ
ማንኛውንም ዐይነት አጕል ምኞት አስነሣ፤
ኀጢአት ያለ ሕግ ምዉት ነውና። 9ሕጉ
ሳይኖር ሕያው ነበርሁ፤ ትእዛዝ ከመጣ
በኋላ ግን፣ ኀጢአት ሕያው ሆነ፤ እኔም
ሞትሁ። 10ለሕይወት እንዲሆን የታሰበው ያ
ትእዛዝም ሞትን እንዳመጣ ተገነዘብሁ፤
11ኀጢአት በትእዛዝ በኩል የተገኘውን ዕድል
በመጠቀም አታለለኝ፤ በትእዛዝም ገደለኝ።
12ስለዚህ ሕጉ በራሱ ቅዱስ ነው፤ ትእዛዙም
ቅዱስ፣ ጻድቅና መልካም ነው።
13ታዲያ በጎ የሆነው ነገር ሞት ሆነብኝን?
ከቶ አይደለም፤ ነገር ግን ኀጢአት በኀጢአት
ነቱ ይታወቅ ዘንድ በጎ በሆነው ነገር በኩል
ሞትን አመጣብኝ፤ ይኸውም ኀጢአት በትእ
ዛዝ በኩል ይብሱን ኀጢአት ይሆን ዘንድ
ነው።
14ሕጉ መንፈሳዊ እንደ ሆነ እናውቃ

7፥1 ሐሥ1፥16፤ 22፥5፤ሮሜ1፥13፤ 1ቆሮ1፥10፤5፥11፤ 6፥6፤14፥20:26፤ ገላ3፥15፤6፥18
7፥2 1ቆሮ7፥39
7፥3 ሉቃ16፥18
7፥4 ቊ6፤ሮሜ6፥6፤ 8፥2፤ገላ2፥19:20፤ 3፥23-25፤4፥31፤5፥1፤ ቈላ1፥22፤
7፥5 ሮሜ7፥7-11፤ 6፥13-23፤ገላ5፥24፤
7፥6 ቊ4፤ ሮሜ 2፥29፤2ቆሮ3፥6
7፥7 ቊ12፤ ዘፀ20፥17፤ዘዳ5፥21፤ ሮሜ4፥15፤8፥31፤
7፥8 ቊ11፤ ሮሜ4፥15
7፥10 ዘሌ18፥5፤ ሉቃ10፥26-28፤ ሮሜ10፥5፤ገላ3፥12
7፥11 ቊ8፤ዘፍ3፥13
7፥12 ቊ7:13: 14:16፤ሮሜ4፥15፤ 8፥4፤ገላ3፥21፤ 1ጢሞ1፥8፤
7፥13 ቊ12፤ ሮሜ 6፥23፤
7፥14 1ነገ21፥20: 25፤2ነገ17፥17፤ ሮሜ6፥16፤1ቆሮ3፥1
7፥15 ቊ19፤ ገላ5፥17
7፥16 ቊ12
7፥17 ቊ20
7፥18 ቊ25፤ ገላ5፥ 24
7፥19 ቊ15
7፥20 ቊ17
7፥21 ቊ23:25
7፥22 መዝ1፥2፤ 40፥8፤ኤፌ3፥16፤
7፥23 ሮሜ6፥16፤ ገላ5፥17፤1ጴጥ2፥11፤ ያዕ4፥1፤
7፥24 ሮሜ6፥6፤ 8፥2
7፥25 ሮሜ6፥16:22፤ 2ቆሮ 2፥14፤
8፥1 ቊ34:39፤ ሮሜ16፥3
8፥2 ዮሐ8፥32:36፤ ሮሜ6፥16:18፤ 7፥25፤1ቆሮ15፥45፤ 7፥4
8፥3 ሮሜ7፥18:19፤ ፊል2፥7፤ገላ5፥24፤ ዕብ2፥14:17፤7፥18፤ 10፥1-4
8፥4 ሮሜ2፥26፤ ገላ5፥16

ለን፤ እኔ ግን ለኀጢአት እንደ ባሪያ
የተሸጥሁ ሥጋዊ ነኝ። 15የማደርገውን
አላውቅም፤ ለማድረግ የምፈልገውን
አላደርግም፤ ነገር ግን የምጠላውን ያን
አደርጋለሁና። 16ማድ ረግ የማልፈልገውን
የማደርግ ከሆነ፣ ሕጉ በጎ እንደ ሆነ
እመሰክራለሁ፤ 17እንዲህ ከሆነ፣ ይህን የ
ማደርገው እኔ ራሴ ሳልሆን፣ በእኔ ውስጥ
የሚኖረው ኀጢአት ነው። 18በእኔ፣
ማለትም ኀጢአተኛ በሆነው ተፈ ጥሮዬ[በ]
ውስጥ ምንም በጎ ነገር እንደማይኖር ዐ
ውቃለሁ፤ በጎ የሆነውን የማድረግ ምኞት
አለኝ፤ ነገር ግን ልፈጽመው አል ችልም።
19የማደርገው ላደርገው የምፈልገውን በጎ
ነገር አይደለም፤ ዳሩ ግን ለማድረግ የማ
ልፈልገውን ክፉ ነገር ነው። 20ላደርገው
የማልፈልገውን ነገር የማደርገው ከሆነ፣ ያን
የማደርገው እኔ ራሴ ሳልሆን፣ የሚያ
ደርገው በእኔ ውስጥ የሚኖረው ኀጢአት
ነው።
21ስለዚህ ይህ ሕግ እየሠራ እንደ ሆነ
ተረድቻለሁ፤ ይኸውም በጎ ነገር ለመሥራት
ስፈልግ፣ ክፋት ከእኔ ጋር አለ። 22በውስጤ
በእግዚአብሔር ሕግ ሐሤት አደርጋለሁ፤ 23ነገር
ግን በብልቶቼ ውስጥ ለሚሠራው የኀጢ
አት ሕግ እኔን እስረኛ በማድረግ፣ ከአእ
ምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋ ሌላ ሕግ
በብልቶቼ ውስጥ ሲሠራ አያለሁ። 24እኔ
ምን ዐይነት ጐስቋላ ሰው ነኝ! ከዚህ ለሞት
ከተሰጠ ሰውነት ማን ሊያድነኝ ይችላል?
25በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል
ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን።
እንግዲያስ እኔ ራሴ በአእምሮዬ ለእግዚ
አብሔር ሕግ ባሪያ ስሆን፣ በኀጢአተኛ ተፈ
ጥሮዬ ግን ለኀጢአት ሕግ ባሪያ ነኝ።

## ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ

**8** ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ[ተ] ያሉት
አሁን ኵነኔ የለባቸውም፤ 2ምክንያቱም
የሕይወት መንፈስ ሕግ በክርስቶስ ኢየሱስ
ከኀጢአትና ከሞት ሕግ ነጻ አውጥቶአችኋል።*
3ሕግ ከሥጋ ባሕርይ[ቸ] የተነሣ ደክሞ ሊፈ
ጽም ያልቻለውን፣ እግዚአብሔር የገዛ ልጁ
ን በኀጢአተኛ ሰው አምሳል፣ የኀጢአት
መሥዋ ዕት[ኀ] እንዲሆን በመላክ ፈጸመው፤
በዚህም ኀጢአትን በሥጋ[ነ] ኰነነ፤ 4ይኸውም
በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ በምንመላለስ
በእኛ፣ ሕጉ

[ሽ]23 ወይም *በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል*
[ቀ]5 ወይም *በሥጋ፤* እንዲሁም ቊ 25 ይመ
[በ]18 ወይም *ሥጋዬ*
[ተ]1 አንዳንድ የቅርብ ጊዜ ቅጆች *ስለዚህ እንደ ኀጢአተኛ ተፈጥሮ ሳይሆን እንደ መንፈስ ፈቃድ በኖረው በክርስቶስ ኢየሱስ ይላሉ።*
[ቸ]3 ወይም *ኀጢአተኛ ተፈጥሮ፤* እንዲሁም ቊ4:5:8:9:12:13 ይመ
[ኀ]3 ወይም *ስለ ኀጢአት መሥዋዕት*
[ነ]3 ወይም *በኀጢአተኛ ሰው*
*አንዳንድ የጥንት ቅጆች "አውጥቶኛል" ይላሉ።

የሚጠይቀው ጽድቅ ሙሉ በሙሉ እንዲፈ
ጸም ነው።
5እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ ልባቸውን
በሥጋ ፍላጎት ላይ ያሳርፋሉ፤ እንደ መንፈስ
ፈቃድ የሚኖሩ ግን ልባቸውን በመንፈስ
ፍላጎት ላይ ያደርጋሉ። 6የሥጋን ነገር ማሰብ[ኘ]
ሞት ነው፤ የመንፈስን ነገር ማሰብ ግን ሕይ
ወትና ሰላም ነው። 7ለኀጢአት የተገዛ
አእምሮ[አ] ከእግዚአብሔር ጋር ጠበኛ ነው፤
ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛም፤ መገዛትም አይጠ
ችልም። 8በሥጋ ፈቃድ የሚመሩትም እግዚ
አብሔርን ማስደሰት አይችሉም።
9እናንተ ግን፣ የእግዚአብሔር መንፈስ
በውስ ጣችሁ የሚኖር ከሆነ፣ በሥጋ
ሳይሆን በመ ንፈስ ናችሁ። ማንም የክ
ርስቶስ መንፈስ ከሌ ለው፣ እርሱ የክርስቶስ
አይደለም። 10ነገር ግን ክርስቶስ በውስጣችሁ
ካለ፣ ሰውነታችሁ ከኀጢአት የተነሣ ሟች
ሲሆን፣ መንፈሳችሁ ግን ከጽድቅ የተነሣ ሕ
ያው ነው። 11ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው
የእርሱ መንፈስ በእናንተ የሚኖር ከሆነ፣
ክርስቶስን ከሙታን ያስነ ሣው፣
በውስጣችሁ በሚኖረው በመንፈሱ ሟች
ለሆነው ሰውነታችሁ ሕይወትን ይሰ ጣል።
12ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፤ ግዴታ አለብን፤
ይሁን እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ እንድንኖር
ለሥጋ አይደለም። 13እንደ ሥጋ ፈቃድ
ብትኖሩ ትሞታላችሁና፤ ክፉ የሆነውን
የሥጋ ሥራ በመንፈስ ብትገድሉ ግን፣ በሕ
ይወት ትኖራላችሁ፤ 14በእግዚአብሔር መንፈስ
የሚመሩ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።
15እንደ ገና የፍርሀት ባሪያ የሚያደርጋችሁን
መንፈስ ሳይሆን፣ “አባ[ከ]፣ አባት” ብለን
የምንጠራበ ትን የልጅነት[ኸ] መንፈስ
ተቀብላችኋልና፤ 16የእግዚአብሔር ልጆች
መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን
ጋር ሆኖ ይመሰክርል ናል። 17ልጆች ከሆን
ወራሾች ደግሞ ነን፤ የክብሩ ተካፋዮች
እንሆን ዘንድ በእርግጥ የመከራው ተካፋዮች
ብንሆን፣ የእግዚአብሔር ወራሾች፣ ከክርስቶስ
ጋር አብረን ወራሾች ነን።

## የሚመጣው ክብር

18የአሁኑ ዘመን ሥቃያችን ወደ ፊት ሊገ
ለጥ ካለው ለእኛ ከተጠበቀልን ክብር ጋር
ሲነጻጸር ምንም እንዳይደለ እቈጥራለሁ።
19ፍጥረት ሁሉ የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ
በናፍቆት ይጠባበቃል። 20ፍጥረት ሁሉ ለከን
ቱነት ተዳርጎአል፤ ይኸውም በራሱ ምርጫ
ሳይሆን፣ ለተስፋ እንዲገዛ ካደረገው
ከፈቃዱ የተነሣ ነው።[ወ] 21ይህም ፍጥረት
ራሱ ከመበስበስ ባርነት ነጻ ወጥቶ ለእግዚ
አብሔር ልጆች ወደ ሆነው ወደ ከበረው
ነጻነት እንዲደርስ ነው።

8፥5 ገላ5፥19-21፡22-25
8፥6 ቍ13፤ ሮሜ6፥23፤ገላ6፥8
8፥7 ያዕ4፥4
8፥8 ገላ5፥24
8፥9 ቍ11፤ ዮሐ14፥17፤ ሐሥ16፥7፤ 1ቆሮ6፥19፤ገላ5፥24፤ 2ጢሞ1፥14፤ 1ዮሐ 4፥13
8፥10 ቍ9፤ ዘፀ29፥45፤ዮሐ14፥20፡23፤2ቆሮ13፥5፤ ገላ2፥20፤ኤፌ3፥17፤ ቆላ1፥27፤ራእ3፥20
8፥11 ዮሐ5፥21፤ ሐሥ2፥24፤ሮሜ6፥5
8፥12 ቍ4፤ ገላ5፥24
8፥13 ቍ6፤ ሮሜ6፥23፤6፥2፤ ገላ6፥8
8፥14 ቍ19፤ ሆሴ1፥10፤ሚል3፥17፤ ማቴ5፥9፤ዮሐ1፥12፤ ገላ5፥18፤ገላ3፥26፤ 4፥5፤ኤፌ1፥5፤ ራእ 21፥7
8፥15 ማር14፥36፤ ዮሐ20፥22፤ገላ4፥5፡6፤ 2ጢሞ 1፥7፤
8፥16 ቍ14፤ ዮሐ1፥12፤2ቆሮ1፥22፤ ኤፌ1፥13
8፥17 ሐሥ20፥32፤ 2ቆሮ1፥5፤ገላ3፥29፤ 4፥7፤ኤፌ3፥6፤ ቲቶ3፥7፤ 2ጢሞ2፥12፤ 1ጴጥ4፥13
8፥18 2ቆሮ4፥17፤ 1ጴጥ4፥13፤5፥1
8፥19 ቍ14
8፥20 ዘፍ3፥17-19፤ 5፥29
8፥21 ዮሐ1፥12፤ ሐሥ3፥21፤ 2ጴጥ3፥13፤ራእ21፥1፤
8፥22 ኤር12፥4
8፥23 ቍ11፤19፤ 2ቆሮ5፥2፡4፡5፤ ገላ 5፥5፤ፊል3፥21
8፥24 2ቆሮ4፥18፤ 1ተሰ5፥8፤ቲቶ3፥7፤
8፥25 መዝ37፥7
8፥26 ቍ15፡16፤ ኤፌ6፥18
8፥27 ቍ34፤ ራእ2፥23፤
8፥28 ቍ30፤ ዘፍ50፥20፤ ኢሳ38፥17፤ ኤር29፥11፤ ሮሜ11፥29፤ 1ቆሮ1፥9፤ገላ1፥6፡15፤ኤፌ1፥11፤ 4፥1፡4፤2ተሰ2፥12፤ 2ጢሞ1፥9፤ ዕብ6፥17፤9፥15፤ 1ጴጥ2፥9፤

22እስከ አሁን ድረስ ፍጥረት ሁሉ
በምጥ ጊዜ እንዳለው ሥቃይ በመቃተት
ላይ እንደሚገኝ እናውቃለን። 23እርሱ ብቻ
ሳይሆን፣ የመጀመሪያውን የመንፈስ ፍሬ
ያገኘን እኛ ራሳችን የሰውነታችን ቤዛ
የሆነውን ልጅነታችንን በናፍቆት እየተጠ
ባበቅን በውስጣችን እንቃትታለን። 24በዚህ
ተስፋ ድነናል፤ ተስፋው የሚታይ ከሆነ ግን
ተስፋ አይደለም፤ የሚያየውንማ ማን ተስፋ
ያደርገዋል? 25ነገር ግን ገና ያላየነውን ተስፋ
ብናደርግ፣ በትዕግሥት እንጠብቀዋለን።
26እንዲሁም ደግሞ መንፈስ በድካ
ማችን ያግዘናል፤ እንዴት መጸለይ
እንደሚገባን አናውቅም፤ መንፈስ ግን
በቃላት ሊገለጥ በማይችል መቃተት ለእኛ
ይማልድልናል። 27ልባችንንም
የሚመረምረው እርሱ የመን ፈስን ሐሳብ
ያውቃል፤ ምክንያቱም መንፈስ እንደ እግዚ
አብሔር ፈቃድ ለቅዱሳን ይማል ዳልና።

## ከአሸናፊዎች በላይ

28እግዚአብሔር፣ ለሚወዱትና እንደ ሐሳቡ
ለተጠሩት፣ ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲ
ሠራ እንደሚያደርግላቸው[ዐ] እናውቃለን።[ዘ]
29እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን
መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰናቸው፤
ይኸውም ከብዙ ወንድሞች መካከል እርሱ
በኵር እንዲሆን ነው። 30አስቀድሞ የወሰ
ናቸውን ጠራቸው፤ የጠራቸውን አጸደቃቸው፤
ያጸደቃቸውን አከበራቸው።
31ታዲያ ለዚህ ምን እንመልሳለን? እግዚ
አብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ፣ ማን ሊቃወመን
ይችላል? 32ለገዛ ልጁ ያልሳሳለት፣ ነገር
ግን ለሁላችንም አሳልፎ የሰጠው እርሱ፣
ሁሉንስ ነገር ከእርሱ ጋር እንደ ምን በልግስና
አይሰጠን? 33እግዚአብሔር የመረጣቸውን የሚ
ከስ ማን ነው? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር
ነው፤
34ታዲያ የሚፈርድ ማን ነው? የሞተው፣ እን
ዲሁም ከሞት የተነሣው፣ በእግዚአብሔር ቀኝ

2ጴጥ1፥10፤3፥11፤ 8፥29 ሮሜ11፥2፤ 1ቆሮ15፥49፤ 2ቆሮ3፥18፤ኤፌ1፥5፡11፤ፊል3፥21፤ቈላ1፥18፤1ጴጥ1፥2፤ 1ዮሐ3፥2፤ 8፥30 ቍ28፤ ሮሜ4፥25፤ 9፥23፤ኤፌ1፥5፡11፤ 8፥31 ዘፀ3፥12፤ መዝ56፥9፤118፥6፤ኢሳ8፥10፤41፥10፤ ኤር20፥11፤ሐ ጌ1፥13፤ሮሜ4፥1፤6፥1፤7፥7፤9፥14፡30፤ ዕብ13፥6 8፥32 ዘፍ22፥13፤ ሚል3፥17፤ዮሐ3፥16፤ሮሜ5፥8
8፥33 ኢሳ50፥8፡9 8፥34 ቍ1፤27፤ኢዮ16፥20፤ኢሳ53፥12፤ ማር16፥19፤ሐሥ2፥24፤ሮሜ 5፥6-8፤ዕብ7፥25፤ 9፥24፤1ዮሐ2፥1

[ኘ]6 ወይም *ስለ ሥጋ ማሰብ*
[አ]7 ወይም *ስለ ሥጋ የሚያስብ አእምሮ*
[ከ]15 በአራማይክ ቋንቋ አባት የሚጠራበት ስም ነው
[ኸ]15 ወይም *እንደ ልጅ*
[ወ]20፡21 ወይም *በተስፋ አስገዝቶታል።*
[ዐ]28 ወይም *በጎ የሆነውን ለማድረግ እርሱን ከሚወዱት ጋር ይሠራል።*
[ዘ]28 *አንዳንድ ቅጆች እግዚአብሔርን ለሚወዱት ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን ይላሉ።*

የተቀመጠው ክርስቶስ ኢየሱስ፣ ስለ እኛ
ይማልዳል:: [35]ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን
ማን ነው? ችግር ነው ወይስ ሥቃይ፣ ወይስ
ስደት፣ ወይስ ረሀብ፣ ወይስ ዕራቍትነት፣
ወይስ አደጋ ወይስ ሰይፍ? [36]ይህም፣

"ስለ አንተ ቀኑን ሙሉ ከሞት ጋር
እንጋፈጣለን፤
እንደሚታረዱ በጎች ተቈጠርን"

ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው::
[37]ምንም አይለየንም፤ በዚህ ሁሉ
በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች
እንበልጣለን:: [38]ይህን ተረድቻለሁ፤ ሞትም
ይሁን ሕይወት፣ መላእ ክትም ይሁኑ
አጋንንት፣[ሠ] ያለውም ይሁን የሚመጣው፣
ወይም ማንኛውም ኀይል፣ [39]ከፍታም
ይሁን ጥልቀት፣ ወይም የትኛ ውም
ፍጥረት፣ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካለው
ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይች ልም::

## የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ

**9** በክርስቶስ ሆኜ እውነት እናገራለሁ፤
አልዋሽም፤ ኅሊናዬም በመንፈስ ቅዱስ
ይመሰክርልኛል:: [2]ታላቅ ሐዘንና የማያቋርጥ
ጭንቀት በልቤ አለ:: [3]ለወገኖቼ ስል ስለ
ወንድሞቼ እኔ ራሴ የተረገምሁና ከክርስ
ቶስም ተለይቼ የተጣልሁ እንድሆን እንኳ
እወድ ነበር፤ [4]እነርሱም የእስራኤል ሕዝብ
ናቸው፤ ልጅ መሆን፣ መለኮታዊ ክብር፣
ኪዳን፣ ሕግን መቀበል፣ የቤተ መቅደስ
ሥርዐትና ተስፋ የእነርሱ ናቸውና:: [5]አባ
ቶችም የእነርሱ ናቸው፤ ክርስቶስም በሥጋ
የትውልድ ሐረጉ ሚቈጠረው ከእነርሱ ነው፤
እርሱም፣ ከሁሉ በላይ የሆነ ለዘላለም የተ
መሰገነ አምላክ ነው፤[የ] አሜን::
[6]ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ተሸሮአል
ማለት አይደለም፤ ከእስራኤል የተወለደ
ሁሉ እስራኤል አይደለምና:: [7]ከአብርሃም
ዘርም ስለሆኑ፣ ሁሉም ልጆቹ አይደሉም፤
ይልቁንስ፣ "ትውልድህ በይሥሐቅ በኩል
ይጠራልሃል" እንደ ተባለው ነው:: [8]ይህም
ማለት የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉት የሥጋ
ልጆች አይ ደሉም፤ ነገር ግን የአብርሃም
ልጆች የተባ ሉት የተስፋው ልጆች
ናቸው:: [9]"ጊዜው ሲደርስ እመለሳለሁ፤ ሳ
ራም ወንድ ልጅ ትወልዳለች" ተብሎ
ተስፋው ተሰጥቶአልና::
[10]ይህም ብቻ ሳይሆን፣ የርብቃ ልጆች
አንድ አባት አላቸው፤ እርሱም አባታችን
ይሥሐቅ ነው:: [11]መንትዮቹ ገና ሳይወለዱ፣
ወይም በጎም ሆነ ክፉ ሳያደርጉ፣ የእግዚ
አብሔር ሐሳብ በምርጫ ይጸና
ዘንድ፣ [12]በሥራ ሳይሆን ከጠሪው
በመሆኑ፣ "ታላቁ ታናሹን ያገለግላል"
ተብሎ ተነገራት:: [13]ይህም፣ "ያዕቆብን
ወደድሁ፤ ዔሳውን ግን ጠላሁ" ተብሎ እንደ
ተጻፈው ነው::
[14]እንግዲህ ምን እንላለን? እግዚአብሔር
አድ ልዎ ያደርጋልን? በፍጹም
አያደርግም! [15]ለሙሴ፣

"የምምረውን እምረዋለሁ፤
ለምራራለትም እራራለታለሁ"
ይላልና::

[16]እንግዲህ ይህ ከሰው ፍላጎት ወይም
ጥረት ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር ምሕረት
የተ ነሣ ነው:: [17]መጽሐፍ ፈርዖንን፣
"ኀይሌ በአንተ እንዲታይ፣ ስሜም
በምድር ሁሉ እንዲነገር ለዚህ አስነሣሁህ"
ይላልና:: [18]ስለ ዚህ እግዚአብሔር ሊምረው
ለሚወደው ምሕረት ያደርግለታል፤ ልቡ
እንዲደነድን የፈለገ ውንም ያደነድነዋል::
[19]ከእናንተ አንዱ፣ "ታዲያ እንደዚህ ከሆነ
እግዚአብሔር እስከ አሁን ለምን ይወቅሰናል?
ምክንያቱም ፈቃዱን ሊቋቋም የሚችል
ማን አለ?" ይለኝ ይሆናል:: [20]ነገር ግን
ለእግዚአብሔር መልስ የምትሰጥ አንተ ማን
ነህ? "ሥራ ሠሪውን፣ 'ለምን እንዲህ ሠራኸኝ?'
ይለዋልን?" [21]ሸክላ ሠሪ፣ ከሚሠራው ጭቃ፣
አንዳንዱን ሸክላ ለክብር፣ ሌላውን ደግሞ
ለተራ አገልግሎት የማድረግ መብት
የለውምን?
[22]እግዚአብሔር ቍጣውን ለማሳየት፣ ኀይ
ሉንም ለማሳወቅ ፈልጎ የቍጣው መግለጫ
የሆኑትን፣ ለጥፋትም የተዘጋጁትን እጅግ
ታግሦ ቢሆንሳ! [23]አስቀድሞ ለክብር ላዘጋ
ጃቸው፣ የምሕረቱም መግለጫዎች ለሆኑት፣
የክብሩ ባለ ጠግነት እንዲታወቅ ይህን
አድርጎ እንደ ሆነስ? [24]የጠራው ከአይሁድ
ወገን ብቻ ሳይሆን ከአሕዛብ ወገን የሆነውን
እኛን እንኳ ሳይቀር አይደለምን? [25]በሆሴዕ
እንዲህ እንደሚል፤

"ሕዝቤ ያልሆኑትን፣ 'ሕዝቤ'
ብዬ እጠራቸዋለሁ፤
ያልተወደደችውንም 'የተወደደችው'
ብዬ እጠራለሁ::
[26]ደግሞም፣ " 'ሕዝቤ አይደላችሁም'፤
ተብሎ በተነገራቸው በዚያ ቦታ፣
'የሕያው እግዚአብሔር ልጆች'
ተብለው
ይጠራሉ::"
[27]ኢሳይያስም ስለ እስራኤል እንዲህ ሲል
ይጮኻል፤

8÷35 ቍ37-39፤ 1ቆሮ4፤2ቆሮ11÷26፤ 27
8÷36 መዝ44÷22 1ቆሮ4÷9፤15÷30፡31፤ 2ቆሮ4÷11፤6÷9፤ 11÷23
8÷37 ሮሜ5÷8፤ 1ቆሮ15÷57፤ ገላ2÷20፤ኤፌ5÷2፤ ራእ1÷5፤3÷9
8÷38 1ቆሮ3÷22፤ ኤፌ1÷21፤ቈላ1÷16፤ 1ጴጥ3÷22
8÷39 ቍ1፤ ሮሜ5÷8፤16÷3
9÷1 መዝ15÷2፤ ሮሜ1÷9፤ 2ቆሮ11÷10፤ገላ1÷20፤ 1ጢሞ2÷7፤
9÷3 ዘፀ32÷32፤ ሐሥ22÷5፤ሮሜ1÷14፤ 1ቆሮ12÷3፤16÷22፤
9÷4 ዘፍ17÷2፤ ዘፀ4÷22፤6÷7፤ ዘዳ7÷6፤14÷13፤ መዝ147÷19፤ ሐሥ13÷32፤3÷25፤ ገላ3÷16፤ኤፌ2÷12፤ ዕብ9÷1፤9÷5
9÷5 ማቴ1÷1-16፤ ዮሐ1÷1፤ሮሜ1÷3፤ 1÷25፤11÷28፤ 2ቆሮ11÷31፤ቈላ2÷9፤
9÷6 ሮሜ2÷28፡29፤ ገላ 6÷16፤ ዕብ4÷12፤
9÷7 ዘፍ21÷12፤ ዕብ11÷18
9÷4 ቍ6፤
9÷8 ሮሜ 8÷14፤ ገላ3÷16
9÷9 ዘፍ18÷10፡14
9÷10 ዘፍ25÷21
9÷11 ቍ16፤ ሮሜ8÷28
9÷12 ዘፍ25÷23
9÷13 ሚል1÷2፡3
9÷14 2ዜና19÷7፤ ሮሜ8÷31፤
9÷15 ዘፀ33÷19
9÷16 ኤፌ2÷8፤ ቲቶ3÷5
9÷17 ዘፀ9÷16፤ 14÷4፤መዝ76÷10
9÷18 4÷21፤7÷3፤ 14÷4፡17፤ዘዳ2÷30፤ ኢሱ11÷20፤ ሮሜ11÷25
9÷19 2ሳሙ16÷10፤ 2ዜና20÷6፤ዳን4÷35፤ ሮሜ3÷7፤11÷19፤ 1ቆሮ15÷35፤ያዕ2÷18፤
9÷20 ኢሳ64÷8፤ 29÷16፤45÷9፤ 10÷15፤ኤር18÷6፤ ኢዮ1÷22፤9÷12፤ 40÷2፤
9÷21 2ጢሞ2÷20
9÷22 ምሳ16÷4፤ ሮሜ2÷4፤
9÷23 ሮሜ2÷4፤ 8÷30 9÷24 ሮሜ8÷28፤ 3÷29 9÷25 ሆሴ2÷23፤ 1ጴጥ2÷10 9÷26 ሆሴ1÷10፤ ማቴ16÷16፤ ሮሜ8÷14 9÷27 ዘፍ22÷17፤ ኤር44÷14፤50÷20፤ ሆሴ1÷10፤ 2ነገ19÷4፤ኢል2÷32፤ሮሜ11÷5

[ሠ]38 ወይም *በሰማይ ያሉ አለቆች*
[የ]5 ወይም *ከሁሉ በላይ የሆነ ለዘላለም የተመሰገነ አምላክ ይሁን* ወይም *ከሁሉ በላይ የሆነ አምላክ ለዘላለም የተመሰገነ ይሁን*

"የእስራኤል ልጆች ቊጥር
በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ ቢሆንም፣
ትሩፉ ብቻ ይድናል።
28ጌታ ፍርዱን በምድር ላይ፣
በፍጥነትና ለመጨረሻ ጊዜ ይፈጽማልና።"
29ይኸውም ቀደም ሲል ኢሳይያስ
እንደ ተናገረው ነው፤
"የሰራዊት ጌታ፣ ዘር ባያስቀርልን ኖሮ፣
እንደ ሰዶም በሆን ነበር፤
ገሞራንም በመሰልን ነበር።"

## የእስራኤል አለማመን

30እንግዲህ ምን እንበል? በእምነት የሆነውን
ጽድቅ፣ ለጽድቅ ያልደከሙት አሕዛብ አገ
ኙት፤ 31ነገር ግን የጽድቅን ሕግ የተከታ
ተሉት እስራኤል አላገኙትም። 32ይህ ለምን
ሆነ? በእምነት ሳይሆን በሥራ እንደ ሆነ
አድርገው በመቊጠር ስለ ተከታተሉት ነው፤
እነርሱም፣ "በማሰናከያው ድንጋይ" ተሰናከሉ።
33ይህም፣

"እነሆ፤ ሰዎችን እንዲደናቀፉ
የሚያደርግ ድንጋይ፣
እንዲወድቁ የሚያደርግ ዐለት፣
በጽዮን ላይ አስቀምጣለሁ፤
በእርሱም የሚያምን አያፍርም"
ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።

10 ወንድሞች ሆይ፤ ስለ እስራኤላው
ያን የልቤ ምኞት፣ እግዚአብሔርንም
የምለምነው እንዲድኑ ነው። 2ለእግዚአብሔር
ቀናተኛ እንደ ሆኑ ስለ እነርሱ መመስከር
እችላለሁና፤ ቅናታቸው ግን ከዕውቀት
የተነሣ አይደለም። 3ከእግዚአብሔር የሚመ
ጣውን ጽድቅ ስላላወቁና የራሳቸውን ጽድቅ
ለመመሥረት ስለ ፈለጉ፣ ለእግዚአብሔር
ጽድቅ አልተገዙም። 4ለሚያምን ሁሉ ጽድቅ
ይሆን ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ
ነውና።
5ሙሴ በሕግ በኩል የሆነውን ጽድቅ ሲገ
ልጽ፣ "እነዚህን የሚፈጽም ሰው በእነርሱ
ይኖራል" ይላል። 6ከእምነት የሆነው ጽድቅ
ግን እንዲህ ይላል፤ " 'በልብህ ማን ወደ
ሰማይ ይወጣል?' አትበል"፤ ይህ ክርስቶስን
ለማውረድ ነው፤ 7"ወይም 'ወደ ጥልቁስ ማን
ይወርዳል?' አትበል"፤ ይህም ክርስቶስን ከሙ
ታን ለማውጣት ነው። 8ነገር ግን ምን
ይላል? "ቃሉ በአጠገብህ ነው፤ በአፍህና
በልብህም ውስጥ ነው፤" የምንሰብከውም
የእምነት ቃል ይህ ነው፤ 9"ኢየሱስ ጌታ
ነው" ብለህ በአፍህ ብትመሰክር፣ እግዚ
አብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ
ብታምን፣ ትድናለህ። 10የምትጸድቀው
በልብህ አምነህ ነው፤ የምትድነውም በአ
ፍህ መስክረህ ነውና። 11መጽሐፍ እንደሚ
ለው፣ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍ
ርም።" 12በአይሁድና በአሕዛብ መካከል
ልዩነት የለም፤ አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ
ነውና፤ የሚለምኑትንም አብዝቶ ይባርካል፤
13"የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና።"
14ታዲያ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው
ይጠሩታል? ስለ እርሱስ ሳይሰሙ እንዴት
ያምኑበታል? ሰባኪ ሳይኖር እንዴት መስ
ማት ይችላሉ? 15ካልተላኩስ እንዴት
መስበክ ይችላሉ? ይህም፣ "የምሥራችን
የሚያመጡ እግሮች እንዴት ያማሩ ናቸው!"
ተብሎ እንደ ተጻፈው ነው።
16ነገር ግን የሰሙት ሁሉ የምሥራቹን
ቃል አልተቀበሉም፤ ኢሳይያስም፣ "ጌታ
ሆይ፤ መልእክታችንን ማን አምኖአል?"
ብሎአልና። 17እንግዲያስ እምነት የሚገኘው
መልእክቱን ከመስማት ነው፤ መልእክቱም
በክርስቶስ ቃል ነው። 18ነገር ግን አልሰሙ
ይሆን? ብዬ እጠይቃለሁ፤ በእርግጥ ሰም
ተዋል፤

"ድምፃቸው በምድር ሁሉ፣
ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ተሰማ።"

19ደግሜም እጠይቃለሁ፤ እስራኤል
አላስ ተዋሉ ይሆን? በቅድሚያ ሙሴ
እንዲህ ይላል፤
"ሕዝብ ባልሆኑት አስቀናችዋለሁ፤
ማስተዋል በሌለው ሕዝብ
አስቈጣችዋለሁ"
20ኢሳያስም በድፍረት፣
"ላልፈለጉኝ ተገኘሁ፤
ላልጠየቁኝ ራሴን ገለጥሁላቸው" ይላል።
21ስለ እስራኤል ግን፣
"ወደማይታዘዝና እሺ ወደማይል ሕዝብ፣
ቀኑን ሙሉ እጄን ዘረጋሁ" ይላል።

## የእስራኤል ትሩፋን

11 እንግዲህ እግዚአብሔር ሕዝቡን ተዋ
ቸውን? ብዬ እጠይቃለሁ፤ በፍጹም!
እኔ ራሴ ከብንያም ነገድ፣ የአብርሃም ዘር
የሆንሁ እስራኤላዊ ነኝ። 2እግዚአብሔር
አስቀድሞ ያወቃቸውን ሕዝብ አልጣላቸውም።
ኤልያስ በእስራኤል ላይ ክስ ወደ
እግዚአብሔር እንዴት እንዳቀረበ፣ መጽሐፍ
ስለ እርሱ ምን እንደሚል አታውቁምን?
3"ጌታ ሆይ፤ ነቢያትህን ገድለዋል፤ መ
ሠዊያዎችህን አፍርሰዋል፤ እኔም
ብቻዬን ቀረሁ፤ ሊገ ድሉኝም
ይፈልጋሉ።" 4እግዚአብሔር የሰጠው መልስ
ግን ምን ነበር? "ለበኣል ያልሰገዱትን ሰባት
ሺህ ሰዎች ለራሴ አስቀርቻለሁ።" 5በአሁኑ

9፥28 ኢሳ10፥22:23
9፥29 ዘፍ19፥24-29፤ዘዳ29፥23፤ኢሳ1፥9፤13፥19፤ኤር50፥40፤ያዕ5፥4፤
9፥30 ሮሜ8፥31፤1፥17፤3፥22፤4፥5:13፤10፥6፤ገላ2፥16፤ፊል3፥9፤ዕብ11፥7
9፥31 ዘዳ6፥25፤ኢሳ51፥1፤ሮሜ10፥2:3፤11፥7፤ገላ 5፥4
9፥32 1ጴጥ2፥8
9፥33 ኢሳ8፥14፤28፥16፤ሮሜ10፥11፤1ጴጥ 2፥6:8
10፥1 መዝ20፥4
10፥2 ሐሥ21፥20
10፥3 ሮሜ1፥17፤9፥31
10፥4 ሮሜ7፥1-4፤3፥22፤ ገላ 3፥24፤
10፥5 ዘሌ18፥5፤ዘዳ4፥1፤6፥24፤ነህ9፥29፤ምሳ19፥16፤ኢሳ55፥3፤ሕዝ20፥11:13:21፤ሮሜ7፥10
10፥6 ዘዳ30፥12፤ሮሜ9፥30፤
10፥7 ዘዳ30፥13፤ሐሥ2፥24
10፥8 ዘዳ30፥14
10፥9 ማቴ10፥32፤ዮሐ13፥13፤3፥15፤ሐሥ2፥24፤ሮሜ 11፥14
10፥11 ኢሳ28፥16፤ሮሜ9፥33
10፥12 ማቴ28፥18፤ሮሜ3፥22: 29፤
10፥13 ኢል2፥32፤ሐሥ2፥21፤
10፥15 ኢሳ52፥7፤ናሆ1፥15
10፥16 ኢሳ53፥1፤ዕብ 4፥2፤ዮሐ12፥38
10፥17 ገላ3፥2:5፤ቈላ 3፥16
10፥18 መዝ19፥4፤ማቴ24፥14፤ሮሜ1፥8፤ቈላ1፥6:23፤1ተሰ1፥8
10፥19 ዘዳ32፥21፤ሮሜ11፥11:14፤
10፥20 ኢሳ65፥1፤ሮሜ 9፥30
10፥21 ኢሳ65፥2፤ኤር35፥17
11፥1 ዘሌ26፥44፤1ሳሙ12፥22፤መዝ94፥14፤ኤር31፥37፤33፥24-26፤2ቆሮ11፥22፤ፊል3፥5
11፥2 ቍ1፤ሮሜ8፥29
11፥3 1ነገ19፥10:14
11፥4 1ነገ19፥18

ጊዜም እንደዚሁ በጸጋ የተመረጡ ትሩፋን
አሉ። [6]እንግዲህ በጸጋ ከሆነ በሥራ
አይደለም፤ በሥራ ቢሆንማ ኖሮ ጸጋ፣ ጸጋ
መሆኑ በቀረ ነበር።[ዶ]
[7]እንግዲህ ምንድን ነው? እስራኤል አጥ
ብቀው የፈለጉትን አላገኙትም፤ የተመረጡት
ግን አገኙት፤ የቀሩትም ልባቸው ደነደነ፤
[8]እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤

"ዐይናቸው እንዳያይ፣
ጆሮአቸውም እንዳይሰማ፣
እግዚአብሔር እስከዚህ ቀን ድረስ፣
የድንዛዜ መንፈስ ሰጣቸው።"
[9]ዳዊትም አለ፤
"ማእዳቸው አሽክላና ወጥመድ፣
ዕንቅፋትና ቅጣት ይሁንባቸው።
[10]ዐይኖቻቸው እንዳያዩ ይጋረዱ፤
ወገባቸውም ለዘላለም ይጕበጥ።"

## የተዳቀሉ ቅርንጫፎች

[11]ተመልሰው እስከማይድኑ ድረስ ተሰናከ
ሉን? ብዬ እንደ ገና እጠይቃለሁ፤ ከቶ
አይደለም፤ ይልቁንም እስራኤልን ለማስ
ቀናት ሲባል በእነርሱ መተላለፍ ምክንያት
ድነት ለአሕዛብ መጥቶአል። [12]ነገር ግን
የእነርሱ መተላለፍ ለዓለም በረከት ከሆነ፣
ውድቀታቸውም ለአሕዛብ በረከት ከሆነ፣
ሙላታቸው ምን ያህል ታላቅ በረከት ያመጣ
ይሆን?
[13]አሕዛብ ሆይ፤ ለእናንተ እናገራለሁ፤
የአሕዛብ ሐዋርያ እንደ መሆኔ መጠን
አገልግሎቴን በትጋት እፈጽማለሁ፤ [14]ይኸ
ውም የገዛ ወገኖቼን እንዲቀኑ አነሣሥቼ
ከእነርሱ ጥቂቱን ለማዳን ተስፋ በማድረግ
ነው። [15]የእነርሱ መተው ለዓለም ዕርቅን
ካስገኘ፣ ተቀባይነት ማግኘታቸውማ ከሞት
መነሣት ነው ከማለት በቀር ሌላ ምን ሊሆን
ይችላል? [16]በኵር ሆኖ የቀረበው የቡሖው
ክፍል ቅዱስ ከሆነ፣ ቡሖው ደግሞ ቅዱስ
ነው፤ ሥሩ ቅዱስ ከሆነ፣ ቅርንጫፎቹም
ቅዱሳን ናቸው።
[17]ከቅርንጫፎቹ አንዳንዶቹ ቢሰበሩ፣ አን
ተም የበረሓ ወይራ ሆነህ ሳለ በሌሎቹ
መካከል ገብተህ ከተጣበቅህና ከወይራው
ዘይት ሥር የሚገኘውን በረከት ተካፋይ
ከሆንህ፣ [18]በእነዚያ ቅርንጫፎች ላይ አትኵ
ራራ። ብትኵራ ግን ይህን አስተውል፤ አንተ
ሥሩን አትሸከምም፤ ሥሩ ግን አንተን
ይሸከምሃል እንጂ። [19]እንግዲህ፣ "ቅርንጫ
ፎች የተሰበሩት እኔ እንድገባ ነው" ትል
ይሆናል። [20]ትክክል ነው፤ እነርሱ የተሰበሩት
ካለማመን የተነሣ ነው፤ አንተም በእምነት
ቆመሃል፤ ፍራ እንጂ ትዕቢተኛ አትሁን።
[21]እግዚአብሔር በተፈጥሮ ቅርንጫፎች
ለሆኑት ካልራራላቸው፣ ለአንተም አይራራ
ልህምና።
[22]እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነትና
ጭካኔ ተመልከት፤ ጭካኔውም በወደቁት
ላይ ነው፤ ቸርነቱ ግን በቸርነቱ ውስጥ
እስካለህ ድረስ ለአንተ ነው፤ ያለዚያ ግን
አንተም ትቈረጣለህ። [23]እነርሱም ባለ
ማመናቸው ጸንተው ባይኖሩ፣ ተመልሰው
ይገባሉ፤ እግዚአብሔር መልሶ ሊያስገባቸው
ይችላልና። [24]የበረሓ ከሆነው የወይራ ዛፍ
የተቈረጥህና ተፈጥሮህ ወዳልሆነው ወደ
መልካሙ ወይራ የገባህ ከሆንህ፣
በተፈጥሮአቸው ቅርንጫፎቹ የሆኑት እነዚህ
ወደ ራሳቸው ወይራ ዛፍ መግባታቸውማ
ምን ያህል ይሆን?

## እስራኤል ሁሉ ይድናል

[25]ወንድሞች ሆይ፤ ልባሞች የሆናችሁ
እንዳይመስላችሁ፣ ይህን ምስጢር ሳታውቁ
እንድትቀሩ አልፈልግም፤ የአሕዛብ ሙላት
እስኪገባ ድረስ፣ እስራኤል በከፊል በድን
ዳኔ ውስጥ ዐልፋለች። [26]ስለዚህ እስራኤል
ሁሉ ይድናሉ፤ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤

"አዳኝ ከጽዮን ይወጣል፤
ከያዕቆብም ክፋትን ያስወግዳል።
[27]ኀጢአታቸውንም ሳስወግድ፣
ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳኔ ይህ
ነው።"[ጆ]

[28]እንደ ምሥራቹ ቃል ለእናንተ ሲባል
ጠላቶች ናቸው፤ እንደ ምርጫ ከሆነ ግን፣
ለአባቶች ሲባል የተወደዱ ናቸው፤ [29]የእግዚ
አብሔር ስጦታና ጥሪ ጸጸት የለበትም።
[30]እናንተም ቀድሞ ለእግዚአብሔር የ
ማትታዘዙ እንደ ነበራችሁ፣ ከእነርሱ
አለመታዘዝ የተነሣ አሁን ምሕረት
እንዳገኛችሁ ሁሉ፣ [31]እግዚአብሔር ለእናንተ
ምሕረት ከማድረጉ የተነሣ፣ እነርሱም
ምሕረት ያገኙ ዘንድ አሁን[ገ] የማይታዘዙ
ልጆች ሆነዋል፤ [32]እግዚአብሔር ለሁሉም ምሕ
ረት ያደርግ ዘንድ ሰውን ሁሉ
ባለመታዘዝ ዘግቶታልና።

## ውዳሴ

[33]የእግዚአብሔር የጥበቡና የዕውቀቱ ባለ
ጠግነት[ጠ] እንዴት ጥልቅ ነው!
ፍርዱ አይመረመርም፤
ለመንገዱም ፈለግ የለውም!
[34]"የጌታን ልብ ያወቀ ማነው?
አማካሪውስ የነበረ ማን ነው?"
[35] "እግዚአብሔር መልሶ እንዲከፍለው፣ [sic: እንደ ሰጠው፣]

11፥5 ሮሜ9፥27፤ 3፥24
11፥6 ሮሜ4፥4
11፥7 ቍ25፤ ሮሜ9፥18፤9፥31፤
11፥8 ዘዳ29፥4፤ ኢሳ 29፥10፤ ማቴ13፥13-15፤
11፥10 ቍ8፤ መዝ 69፥22:23
11፥11 ቍ1፤14፤ ሐሥ13፥46፤ ሮሜ10፥19
11፥12 ቍ25
11፥13 ሐሥ9፥15
11፥14 ቍ11፤ ማቴ1፥21፤ሉቃ2፥11፤ ዮሐ3፥17፤ሐሥ4፥12፤ 16፥31፤ሮሜ10፥19፤ 1ቆሮ1፥21፤10፥33፤ 1ተሰ2፥16፤ 1ጢሞ2፥4፤ቲቶ3፥5
11፥15 ሉቃ15፥24: 32፤ሮሜ5፥10፤
11፥16 ዘሌ23፥10: 17፤ዘኍ15፥18-21
11፥17 ኤር11፥16፤ ዮሐ15፥2፤ሐሥ 2፥39፤ኤፌ2፥11-13
11፥18 ዮሐ4፥22
11፥20 1ቆሮ10፥12፤ 2ቆሮ1፥24፤1ጢሞ6፥17፤ 1ጴጥ1፥17
11፥22 ዮሐ15፥2፤ ሮሜ2፥4፤1ቆሮ15፥2፤ ቈላ1፥23፤ዕብ3፥6፤
11፥23 2ቆሮ3፥16
11፥24 ኤር11፥16
11፥25 ቍ7፤ ሉቃ21፥24፤ ሮሜ1፥13፤9፥18፤ 12፥16፤16፥25፤ 1ቆሮ10፥1፤12፥1፤ 2ቆሮ1፥8፤1ተሰ4፥13፤
11፥26 ኢሳ45፥17፤ ኤር31፥34
11፥27 ኢሳ59፥20: 21፤27፥9፤ ዕብ 8፥10: 12
11፥28 ዘዳ7፥8፤ 10፥15፤ሮሜ5፥10፤ ሮሜ9፥5
11፥29 ሮሜ8፥28፤ ዕብ7፥21
11፥30 ኤፌ2፥2
11፥32 ሮሜ3፥9
11፥33 መዝ92፥5፤ 139፥6፤ኢዮ5፥9፤ 11፥7፤መክ8፥17፤ ኢሳ40፥28፤ሮሜ2፥4፤ ኤፌ3፥10፤ቈላ2፥3፤
11፥34 ኢዮ15፥8፤ ኢሳ40፥13:14፤ ኤር 23፥18፤36፥22፤ 1ቆሮ2፥16
11፥35 ኢዮ41፥11፤ 35፥7

[ዶ]6 አንዳንድ ቅጆች *በሥራ ቢሆንማ ኖሮ ጸጋ መሆኑ በቀረ ነበር፤ በጸጋ ከሆነም ሥራ፣ ሥራ መሆኑ ይቀራል።* ይላሉ
[ጆ]27 ወይም *ይህ ይሆናል*
[ገ]31 አንዳድ ቅጆች *አሁን* የሚለው ቃል የላቸውም
[ጠ]33 ወይም *ባለጠግነቱ፣ ጥበቡና እውቀቱ*

ለእግዚአብሔር ያበደረ ከቶ ማን ነው?”
[36]ሁሉም ከእርሱ፣ በእርሱ፣ ለእርሱ ነውና፤
ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።

## ሕያው መሥዋዕት

12 እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ሰውነታ
ችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ
የሚያሰኝ ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ
ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ
እለምናችኋለሁ፤ ይህም እንደ ባለ አእምሮ
የምታቀርቡት[ጨ] አምልኮአችሁ ነው።
[2]መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም
የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ
ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ
በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ
ይህን ዓለም አትምሰሉ።
[3]እግዚአብሔር በሰጣችሁ እምነት መጠን
ራሳችሁን በአግባቡ መዝኑ እንጂ፣ ከሆና
ችሁት በላይ ራሳችሁን ከፍ አድርጋችሁ
እንዳታስቡ በተሰጠኝ ጸጋ እያንዳንዳችሁን
እመክራለሁ። [4]እያንዳንዳችን በአንዱ አካላችን
ብዙ ብልቶች እንዳሉን፣ እነዚህም ብልቶች
አንድ ዐይነት ተግባር እንደ ሌላቸው ሁሉ፣
[5]እንዲሁም እኛ ብዙዎች ስንሆን
በክርስቶስ አንድ አካል ነን።
እያንዳንዳችንም የሌላው ብልት ነን።
[6]እንደ ተሰጠን ጸጋ የተለያዩ ስጦታዎች
አሉን፤ ለአንዱ የተሰጠው ስጦታ ትንቢት
መናገር ከሆነ፣ እንደ እምነቱ መጠን[ጸ]
ይናገር። [7]ማገልገል ቢሆን ያገልግል፤ ማስተ
ማርም ከሆነ ያስተምር፤ [8]መምከር ከሆነ
ይምከር፤ ለሌላቸው መለገስ ከሆነም
አብዝቶ ይለግስ፤ ማስተዳደር ከሆነም
በትጋት ያስ ተዳድር፤ ምሕረት ማድረግ
ከሆነም በደስታ ይማር።

## ፍቅር

[9]ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን፤ ክፉ
የሆነውን ሁሉ ተጸየፉ፤ በጎ ከሆነው ነገር
ጋር ተቈራኙ። [10]እርስ በርሳችሁ በወንድ
ማማች መዋደድ አጥብቃችሁ ተዋደዱ፤
አንዱ ሌላውን ከራሱ በማስበለጥ እርስ
በርሳችሁ ተከባበሩ። [11]ጌታን ለማገልገል
በመንፈስ የጋላችሁ ሁኑ እንጂ ከዚህ ትጋት
ወደ ኋላ አትበሉ። [12]በተስፋ ደስተኞች
ሁኑ፤ በመከራ ታገሡ፤ በጸሎት ጽኑ። [13]ችግ
ረኛ ለሆኑ ቅዱሳን ካላችሁ አካፍሉ፤
እንግዶችን ተቀበሉ።
[14]የሚያሳድዷችሁን መርቁ፤ መርቁ እንጂ
አትርገሙ። [15]ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ
ይበላችሁ፤ ከሚያዝኑም ጋር እዘኑ። [16]እርስ
በርሳችሁ በመስማማት ኑሩ። ዝቅተኛ
ኑሮ[ጸ] ውስጥ ካሉ ጋር አብራችሁ ለመሆን
ፍቀዱ እንጂ አትኵራሩ፤ በራሳችሁም
አትመኩ።
[17]ለማንም ክፉን በክፉ አትመልሱ፤ በሰው
ሁሉ ፊት በጎ የሆነውን ነገር ለማድረግ
ትጉ። [18]ቢቻላችሁስ በበኩላችሁ ከሰው
ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ። [19]ወዳጆቼ ሆይ፤ ለእግ
ዚአብሔር ቍጣ ፈንታ ስጡ እንጂ አትበቀሉ፤
“በቀል የእኔ ነው፤ እኔ ብድራትን እመል
ሳለሁ” ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፎአልና።
[20]ይልቁንስ፣

“ጠላትህ ቢራብ አብላው፤
ቢጠማም አጠጣው።
ይህን በማድረግህም የእሳት ፍም
በራሱ ላይ ትከምራለህ።”
[21]ክፉን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ
አትሸነፍ።

## ባለ ሥልጣናትን መታዘዝ

13 ማንኛውም ሰው በሥልጣን ላሉት
ሹማምንት መገዛት ይገባዋል፤ ከእግ
ዚአብሔር ካልሆነ በቀር ሥልጣን የለምና፤
ያሉትም ባለ ሥልጣናት በእግዚአብሔር የተ
ሾሙ ናቸው። [2]ስለዚህ፣ በባለ ሥልጣን
ላይ የሚያምፅ በእግዚአብሔር ሥርዐት ላይ
ማመፁ ነው፤ ይህን የሚያደርጉትም በራ
ሳቸው ላይ ፍርድን ያመጣሉ። [3]ገዦች ክፉ
ለሚሠሩ እንጂ መልካም ለሚያደርጉ የሚ
ያስፈሩ አይደሉምና። ባለ ሥልጣንን እን
ዳትፈራ ትፈልጋለህን? እንግዲያስ መልካ
ሙን አድርግ፤ እርሱም ያመሰግንሃል፤ [4]እርሱ
ለአንተ መልካሙን ለማድረግ የእግዚአብሔር
አገልጋይ ነውና። ነገር ግን ክፉ ብታደርግ
ፍራ፤ ምክንያቱም ሰይፉን በከንቱ አልታጠ
ቀም፤ ክፉ የሚያደርገውን ለመቅጣት
የቍጣ መሣሪያ የሆነ፣ የእግዚአብሔር አገ
ልጋይ ነው። [5]ስለዚህም ቅጣትን በመፍራት
ብቻ ሳይሆን፣ ለኅሊና ሲባል ለባለ ሥል
ጣናት መገዛት ተገቢ ነው።
[6]ግብር የምትከፍሉትም ደግሞ ለዚህ ነው፤
ባለ ሥልጣናቱ፣ በዚሁ ተግባር ላይ የተሠማሩ
የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸውና፤ [7]ለእያን
ዳንዱ የሚገባውን ስጡ፤ ግብር ከሆነ ግብ
ርን፣ ቀረጥ ከሆነም ቀረጥን፣ መፈራት
ለሚገባው መፈራትን፣ ክብር ለሚገባውም
ክብርን ስጡ።

## ጊዜው ተቃርቦአልና ተዋደዱ

[8]እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር የማንም

11÷36 ሮሜ16÷27፤ 1ቆሮ8÷6፤11÷12፤ ኤፌ3÷21፤ ቈላ1÷16፤ 1ጢሞ1÷17፤ 1ጴጥ5÷11፤ዕብ2÷10፤ ይሁ1÷25፤ራእ5÷13፤ 7÷12
12÷1 ሮሜ6÷13: 16:19፤ኤፌ4÷1፤ 1ቆሮ6÷20፤ 1ጴጥ2÷5:11፤
12÷2 ኤፌ4÷23፤ 5÷17፤1ቆሮ1÷20፤ 2ቆሮ10÷2፤ 1ጢሞ5÷4፤1ጴጥ1÷14፤ 1ዮሐ2÷15፤
12÷3 ሮሜ15÷15፤ 1ቆሮ15÷10፤ገላ2÷9፤ ኤፌ3÷7፤ 4÷7፤ 1ጴጥ4÷10:11
12÷4 1ቆሮ12÷12-14፤ ኤፌ4÷16
12÷5 1ቆሮ 6÷15፤ 10÷17፤12÷12:20:27፤ ኤፌ2÷16፤4÷4:25፤ 5÷30፤ቈላ3÷15
12÷6 1ቆሮ7÷7፤ 12÷4:8-10፤ኤፌ4÷11፤ 1ጴጥ4÷10:11
12÷7 ኤፌ4÷11
12÷8 ሐሥ11÷23፤ 13÷15፤15÷32፤ 2ቆሮ8÷2፤9÷5-13
12÷9 መዝ97÷10፤ አሞ5÷15፤ 2ቆሮ6÷6፤ 1ተሰ 5÷21:22፤ 1ጢሞ1÷5፤
12÷10 መዝ133÷1፤ፊል2÷3፤ 1ተሰ4÷9፤ዕብ13÷1፤ 1ጴጥ1÷22፤
12÷11 ሐሥ18÷25
12÷12 ሉቃ18÷1፤ ሮሜ5÷2፤ዕብ10÷32: 36፤
12÷13 2ነገ4÷10፤ ኢዮ31÷32፤ ሐሥ 24÷17፤ 1ጢሞ3÷2፤5÷10፤ ዕብ13÷2፤1ጴጥ4÷9
12÷14 ማቴ5÷44
12÷15 ኢዮ30÷25
12÷16 ቍ3፤ ኢሳ5÷21፤ኤር45÷5፤ መዝ131÷1፤ ሮሜ11÷25፤15÷5፤
12÷17 ቍ19፤ ምሳ20÷22፤24÷29፤ 2ቆሮ8÷21
12÷18 ማር9÷50፤ ሮሜ14÷19
12÷19 ቍ17፤ ዘፍ50÷19፤ዘሌ19÷18፤ ዘዳ32÷35፤ 1ሳሙ26÷10፤ ምሳ20÷22፤24÷29፤ 94÷1፤ኤር51÷36
12÷20 ዘፀ23÷4፤ ምሳ25÷21:22፤ ማቴ5÷44፤ሉቃ6÷27

13÷1 ዳን2÷21፤ 4÷17፤ዮሐ19÷11፤ ቲቶ3÷1፤1ጴጥ2÷13: 14፤
13÷2 ዘፀ16÷8 13÷3 1ጴጥ2÷14 13÷4 1ተሰ4÷6
13÷5 ምሳ24÷21: 22 13÷6 ማቴ22÷17 13÷7 ማቴ7÷25፤ 22÷17:21፤ሉቃ23÷2 13÷8 ቍ10፤ ማቴ5÷43፤ ዮሐ13÷34፤ቈላ3÷14

[ጨ]1 ወይም *መንፈሳዊ*
[ጸ]6 ወይም *እንደ አገልጋይ ተግባር*
[ጸ]16 ወይም *ዝቅተኛ ሥራ ለመሥራት ፍቀዱ*

ዕዳ አይኑርባችሁ፤ ባልንጀራውን የሚወድ
እርሱ ሕግን ፈጽሞአልና። 9“አታመንዝር”፣
“አትግደል”፣ “አትስረቅ”፣ “አትመኝ” የሚ
ሉትና ሌሎችም ትእዛዛት ቢኖሩም፣ “ባልን
ጀራህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ”
በሚለው በዚህ በአንድ ሕግ ተጠቃለዋል።
10ፍቅር በባልንጀራው ላይ ክፉ አያደርግም፤
ስለዚህ ፍቅር የሕግ መፈጸሚያ ነው።
11ዘመኑን በማስተዋል ይህን አድርጉ፤ ከእን
ቅልፋችሁ የምትነቁበት ጊዜ አሁን
ነው፤ መዳናችን መጀመሪያ ካመንበት ጊዜ
ይልቅ አሁን ወደ እኛ ቀርቦአልና። 12ሌሊቱ
ሊያ ልፍ፣ ቀኑም ሊጀምር ነው። ስለዚህ
የጨለማን ሥራ ጥለን፣ የብርሃንን ጦር ዕቃ
እንልበስ። 13በቀን እንደምንመላለስ
በአግባብ እንመ ላለስ። በጭፈራና በስካር
አይሁን፤ በዝሙ ትና በመዳራት አይሁን፤
በክርክርና በቅና ትም አይሁን። 14ይልቀ
ንም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፤
ምኞቱንም ይፈጽም ዘንድ ለሥጋ[θ] በሐሳባችሁ
አትመቻቹለት።

## በወንድምህ ላይ አትፍረድ

14 በእምነቱ ደካማ የሆነውን ሰው፣
አከራካሪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በአ
ቋሙ ሳትፈርዱበት ተቀበሉት። 2የአንድ ሰው
እምነቱ ማንኛውንም ነገር እንዲበላ ይፈቅድ
ለታል፤ በእምነቱ ያልጠነከረው ሌላው ሰው
ግን አትክልት ብቻ ይበላል። 3ማንኛውንም
የሚበላ የማይበላውን አይናቅ፤ የማይበላ
ውም፣ የሚበላውን አይኰንን፤ እግዚአብሔር
ተቀብሎታልና። 4ሌላውን በሚያገለግል ላይ
የምትፈርድ አንተ ማን ነህ? እርሱ ቢወ
ድቅ ወይም ቢቆም ለጌታው ነው፤ ጌታ
ሊያቆመው ስለሚችልም ይቆማል።
5አንድ ሰው አንዱን ቀን ከሌላው የተ
ሻለ ቅዱስ አድርጎ ይቈጥራል፤ ሌላው
ደግሞ ቀኖች ሁሉ እኩል እንደ ሆኑ ያስ
ባል። እያንዳንዱ የራሱን ውሳኔ ልብ ብሎ
ይወስን። 6አንድን ቀን ከሌላው የተለየ
አድርጎ የሚያስብ ሰው፣ እንዲህ የሚያደ
ርገው ለጌታ ብሎ ነው፤ ሥጋ የሚበላውም
ለጌታ ብሎ ይበላል፤ ለእግዚአብሔር ምስጋና
ያቀርባልና። የማይበላም ለጌታ ሲል አይበ
ላም፤ ለእግዚአብሔርም ምስጋና ያቀርባል።
7ከእኛ ማንም ለራሱ የሚኖር፣ ለራሱም
የሚሞት የለምና። 8ብንኖር ለጌታ እንኖ
ራለን፤ ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን፤
ስለዚህ ብንኖርም ብንሞትም የጌታ ነን።
9ለዚሁ፣ የሙታንና የሕያዋን ጌታ ይሆን
ዘንድ ክርስቶስ ሞቶአል፤ በሕይወትም
ተነሥቶአል። 10ታዲያ አንተ በወንድምህ
ላይ ለምን ትፈርዳለህ? ለምንስ ወንድምህን

13፥9 ዘፀ20፥13-15፡ 17፤ዘዳ5፥17-19፡21፤ ዘሌ19፥18፤ ማቴ5፥43፤ 7፥12
13፥10 ቍ8፥9
13፥11 1ቆሮ7፥29-31፤10፥11፤ ኤፌ5፥14፤1ተሰ5፥5፡6፤ ያዕ5፥8፤1ጴጥ4፥7፤ 1ዮሐ2፥18፤ራእ22፥10፤
13፥12 ኤፌ5፥11፤ 6፥11፡13፤1ተሰ5፥8፤ ዕብ10፥25፤ 1ዮሐ 2፥8፤
13፥13 ሉቃ21፥34፤ ገላ5፥20፡21፤ ኤፌ5፥18፤1ጴጥ4፥3
13፥14 ገላ3፥27፤ 5፥24፤ኤፌ4፥24፤ ቈላ3፥10፡12፤
14፥1 ሮሜ15፥1፤ 1ቆሮ8፥9-12፤9፥22
14፥2 ቍ14
14፥3 ቍ10፥13፤ ሉቃ18፥9፤ቈላ2፥16
14፥4 ማቴ7፥1
14፥5 ገላ4፥10፤ ቈላ2፥16
14፥6 ማቴ14፥19፤ 1ቆሮ10፥30፡31፤ 1ጢሞ4፥3፡4
14፥7 2ቆሮ5፥15፤ ገላ2፥20
14፥8 ፊል1፥20
14፥9 ሐሥ10፥42፤ 2ቆሮ5፥15፤ ራእ1፥18፤2፥8፤
14፥10 ቍ3፤ ማቴ7፥1፤2ቆሮ5፥10
14፥11 ኢሳ49፥18፤ 45፥23፤ፊል2፥10፡11
14፥12 ማቴ12፥36፤ 1ጴጥ4፥5
14፥13 ቍ1፤ ማቴ7፥1፤2ቆሮ6፥3
14፥14 ቍ20፤ ሐሥ10፥15፤ 1ቆሮ 8፥7
14፥15 ቍ20 ኤፌ5፥21ቆሮ8፥11
14፥16 1ቆሮ10፥30
14፥17 ኢሳ32፥17፤ ሮሜ15፥13፤1ቆሮ 8፥8፤ገላ5፥22
14፥18 ሉቃ2፥52፤ሐሥ24፥16፤ 2ቆሮ8፥21
14፥19 መዝ34፥14፤ ሮሜ12፥18፤15፥2፤ 1ቆሮ7፥15፤14፥3-5፡12፡17፡26፤2ቆሮ12፥19፤ኤፌ4፥12፡29፤ 2ጢሞ2፥22፤ ዕብ12፥14፤
14፥20 ቍ13፤ 14፥15፤ሐሥ10፥15፤ 1ቆሮ8፥9-12
14፥21 ማቴ5፥29
14፥22 1ዮሐ3፥21

ትንቃለህ? ሁላችንም በእግዚአብሔር የፍርድ
ወንበር ፊት እንቀርባለንና፤ 11እንዲህ ተብሎ
ተጽፎአል፤
“ ‘እኔ ሕያው ነኝና’፤
‘ጕልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል፤
ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር ይመሰክራል’ ”
ይላል ጌታ።
12ስለዚህ እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን
ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን።
13ስለዚህ እርስ በርሳችን፣ አንዱ በሌላው
ላይ ከመፍረድ እንቈጠብ፤ በዚህ ፈንታ ግን
በወንድምህ መንገድ ላይ የማሰናከያ ድንጋይ
ወይም ወጥመድ እንዳታስቀምጥ ቍርጥ
ሐሳብ አድርግ። 14በጌታ በኢየሱስ ሆኜ
በራሱ ንጹሕ ያልሆነ ምንም ምግብ[ለ] እንደ
ሌለ ተረድቻለሁ፤ ነገር ግን አንድ ሰው
አንድን ነገር ንጹሕ እንዳልሆነ የሚቈጥር
ከሆነ፣ ያ ነገር ለእርሱ ንጹሕ አይደለም።
15ወንድምህ በምትበላው ምግብ የሚያዝን
ከሆነ፣ በፍቅር አልተመላለስህም፤ ክርስቶስ
የሞተለትን ወንድምህን በመብልህ አታጥ
ፋው። 16መልካም ነው ብለህ የምታስበው
ነገር ክፉ ተብሎ እንዲነቀፍ አታድርግ።
17የእግዚአብሔር መንግሥት በመንፈስ ቅዱስ
የሆነ ጽድቅ፣ ሰላምና ሐሤት ነው እንጂ፣
የመብልና የመጠጥ ጉዳይ አይደለም፤
18በዚህ ሁኔታ ክርስቶስን የሚያገለግል
እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛልና፤ በሰውም
ዘንድ የተመሰገነ ነው።
19ስለዚህ ሰላም የሚገኝበትንና እርስ
በርሳችንም የምንታነጽበትን ማንኛውንም
ጥረት እናድርግ። 20ለምግብ ስትል የእግዚ
አብሔርን ሥራ አታፍርስ። ሁሉ ንጹሕ
ነው፤ ነገር ግን ለሌላው ሰው የመሰናከያ
ምክንያት የሚሆነውን መብላት ስሕተት
ነው። 21ለወንድምህ መሰናከል ምክንያት
የሚሆነውን ሥጋን አለመብላት፣ ወይንን
አለመጠጣት፣ ወይም አንዳች ነገርን አለ
ማድረግ መልካም ነው።
22እንግዲያስ ስለ እነዚህ ነገሮች ያለህ
እምነት በአንተና በእግዚአብሔር መካከል
የተጠበቀ ይሁን፤ ትክክል ነው ብሎ በተቀ
በለው ነገር ራሱን የማይኰንን የተባረከ
ሰው ነው። 23ነገር ግን የሚጠራጠር ሰው
ቢበላ በእምነት ስላልሆነ፣ ተፈርዶበታል፤
በእምነት ያልተደረገ ሁሉ ኀጢአት ነውና።

15 እኛ ብርቱዎች የሆን፣ የደካሞችን
ጕድለት መሸከም እንጂ ራሳችንን
ማስደሰት የለብንም። 2እያንዳንዳችን ባልን

14፥23 ቍ5 15፥1 ሮሜ14፥1፤ 1ተሰ5፥14 15፥2 ሮሜ14፥29፤ 1ቆሮ10፥24፤

[θ]14 ወይም *ለኀጢተኛ ተፈጥሮ*
[ለ]14 ወይም *ምንም ነገር*

ጀራችንን ለማነጽ፣ እርሱንም ለመጥቀም
ደስ የሚያሰኘውን ነገር ማድረግ ይገባናል፤
3ክርስቶስ ራሱን ደስ አላሰኘምና፤ ነገር
ግን፣ “አንተን የሰደቡብት ስድብ በእኔ ላይ
ደረሰብኝ” ተብሎ እንደ ተጻፈው ሆነበት።
4በጽናትና ቅዱሳት መጻሕፍት በሚሰጡት
መጽናናት ተስፋ እንዲኖረን፣ ቀደም ብሎ
የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና።
5ብርታትንና መጽናናትን የሚሰጥ አምላክ፣
ክርስቶስ ኢየሱስን ስትከተሉ፣ በመካከላችሁ
የአንድነትን መንፈስ ይስጣችሁ፤ 6ይኸ
ውም በአንድ ልብና በአንድ አፍ ሆናችሁ፣
የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክና
አባት ታከብሩ ዘንድ ነው።
7እንግዲህ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሆን
ዘንድ ክርስቶስ እንደተቀበላችሁ፣ እርስ
በርሳችሁ ተቀባበሉ። 8ለአባቶች የተሰጠ
ውን የተስፋ ቃል ያጸና ዘንድ ለእግዚአብሔር
እውነት ሲል ክርስቶስ የአይሁድ[T]
አገልጋይ እንደ ሆነ እነግራችኋለሁና፤
9እንዲሁም አሕዛብ እግዚአብሔርን ስለ ምሕ
ረቱ ያመሰግኑት ዘንድ ነው፤ እንዲህ ተብሎ
እንደ ተጻፈ፤

“ስለዚህ በአሕዛብ መካከል አመሰግንሃለሁ፤
ለስምህም እዘምራለሁ።”
10ደግሞም፣
“አሕዛብ ሆይ፤ ከሕዝቡ ጋር ደስ
ይበ
ላችሁ” ይላል።
11እንደ ገናም፣
“አሕዛብም ሁላችሁ ጌታን አመስግኑ፤
ሕዝቦች ሁሉ ወድሱት” ይላል።
12ኢሳይያስም እንዲሁ፣
“በሕዝቦች ሁሉ ላይ የሚነግሠው፣
የእሴይ ሥር ይመጣል፤
በእርሱም አሕዛብ ተስፋ ያደርጋሉ”
ይላል።

13በእርሱ በመታመናችሁ የተስፋ አምላክ
ደስታንና ሰላምን ሁሉ ይሙላባችሁ፤ ይኸ
ውም በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ተስፋ ተትረ
ፍርፎ እንዲፈስላችሁ ነው።

## የአሕዛብ አገልጋይ የሆነው ጳውሎስ

14ወንድሞቼ ሆይ፤ እናንተ ራሳችሁ በበ
ጎነት የተሞላችሁ፣ በዕውቀት ሁሉ እንደ
ተሞላችሁና አንዱ ሌላውን ለመምከር ችሎታ
ያላችሁ መሆናችሁን እኔ ራሴ እርግጠኛ
ሆኜአለሁ። 15እግዚአብሔር በሰጠኝ ጸጋ
መሠረት፣ እንደ ገና ዐሳስባችሁ ዘንድ
በአንዳንድ ጕዳዮች ላይ በድፍረት የጻፍሁ
ላችሁ፣ 16በእግዚአብሔር ወንጌል
የክህነት ተግባር፣ ለአሕዛብ የክርስቶስ
ኢየሱስ አገልጋይ ለመሆን ነው፤ ይኸውም
አሕዛብ በመንፈስ ቅዱስ ተቀድሰው በእግዚ
አብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት
እንዲሆኑ ነው።
17ስለዚህ እግዚአብሔርን በማገልገሌ በክርስ
ቶስ ኢየሱስ እመካለሁ። 18በተናገርሁትና
በአደረግሁት ነገር አሕዛብ ለእግዚአብሔር
እንዲታዘዙ፣ ክርስቶስ በእኔ ሆኖ ከፈጸመው
በቀር ሌላ ነገር ለመናገር አልደፍርም፤
19ይህም የሆነው በመንፈስ ቅዱስ ኀይል፣
በምልክቶችና በታምራት ነበር። በዚህም
ሁኔታ ከኢየሩሳሌም እስከ እልዋሪቆን ዙሪያ
ድረስ የክርስቶስን ወንጌል ፈጽሜ ሰብኬ
አለሁ። 20ሌላው በጣለው መሠረት ላይ
እንዳልገነባ ብዬ፣ ክርስቶስ ባልተጠራበት
ስፍራ ወንጌልን መስበክ የዘወትር ምኞቴ
ነበር። 21ይልቁንም፣

“ስለ እርሱ ያልተነገራቸው ያያሉ፤
ያልሰሙም ያስተውላሉ” ተብሎ
እንደ ተጻፈ ነው።

22በዚህም ምክንያት ወደ እናንተ እንዳል
መጣ ብዙ ጊዜ ተከለከልሁ።

## ሮምን ለመጐብኘት የጳውሎስ ዕቅድ

23አሁን ግን በእነዚህ አካባቢዎች የምሠ
ራው ስለሌለ፣ ከብዙ ዓመታት ጀምሮ
እናንተን ለማየት እናፍቅም ስለ ነበር፣
24ይህን ዕቅድ ወደ እስጳንያ በምሄድበት
ጊዜ ልፈጽመው አስባለሁ። በማልፍበትም
ጊዜ ልጐበኛችሁና ከእናንተ ጋር ለጥቂት
ጊዜ ቈይቼ ናፍቆቴን ከተወጣሁ በኋላ በጕ
ዞዬ እንደምትረዱኝ ተስፋ አደርጋለሁ።
25አሁን ግን በዚያ የሚገኙትን ቅዱሳን ለ
ማገልገል ወደ ኢየሩሳሌም በመጓዝ ላይ
ነኝ። 26ምክንያ ቱም መቄዶንያና አካይያ፣
በኢየሩሳሌም ካሉት ቅዱሳን መካከል
የሚገኙትን ድኾች ለመርዳት
ተነሣሥተዋልና። 27ርዳታ ለማድ ረግ
ወደዋል፤ በእርግጥም ባለ ዕዳዎቻቸው
ናቸው። አሕዛብ የአይሁድ መንፈሳዊ በረ
ከት ተካፋዮች ከሆኑ፣ ያገኙትን ምድራዊ
በረከት ከአይሁድ ጋር ይካፈሉ ዘንድ የእ
ነርሱ ባለ ዕዳዎች ናቸው። 28ስለዚህ ሥራ
ውን ከጨረስሁና ይህን ፍሬ መቀበላቸ
ውን ካረጋገጥሁ በኋላ ወደ እስጳንያ
እሄዳለሁ፤ እግረ መንገዴንም እናንተን
አያለሁ። 29ወደ እናንተም ስመጣ፣ በክር
ስቶስ በረከት ሙላት እንደምመጣ ዐው
ቃለሁ።
30ወንድሞች ሆይ፤ ስለ እኔ ወደ እግዚአ
ብሔር በመጸለይ የተጋድሎዬ አጋር እንድ
ትሆኑ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በመ
ንፈስ ፍቅር እለምናችኋለሁ። 31በይሁዳ
ካሉት ከማያምኑት እጅ እንድድንና በኢ

15፥3 መዝ69፥9፤ 2ቆሮ8፥9፤
15፥4 ሮሜ4፥23:24
15፥5 ሮሜ12፥16፤ 1ቆሮ1፥10፤ 2ቆሮ13፥11፤ ኤፌ4፥3፤ፊል2፥2፤ ቈላ3፥14፤1ጴጥ3፥8
15፥6 መዝ34፥3፤ ራ እ1፥6
15፥7 ሮሜ14፥1
15፥8 ማቴ15፥24፤ ሐሥ3፥25:26፤ 2ቆሮ 1፥20
15፥9 2ሳሙ22፥50፤ መዝ18፥49፤ ማቴ9፥8፤ሮሜ3፥29፤
15፥10 ዘዳ32፥43፤ ኢሳ 66፥10
15፥11 መዝ117፥1
15፥12 ኢሳ11፥10፤ ራ እ 5፥5፤ማቴ12፥21
15፥13 ቍ19፤ ሮሜ14፥17፤ 1ቆሮ2፥4፤4፥20፤ 1ተሰ1፥5
15፥14 ኤፌ5፥9፤ 2ቆሮ8፥7፤2ጴጥ1፥12
15፥15 ሮሜ12፥3
15፥16 ቍ19፤ ኢሳ 66፥20፤ ሐሥ9፥15፤ሮሜ1፥1፤
15፥17 ፊል3፥3፤ ዕብ2፥17
15፥18 ሐሥ15፥12፤ 21፥19፤ሮሜ1፥5፤ 16፥26
15፥19 ቍ13፤ ዮሐ4፥48፤ ሐሥ22፥17-21፤ 19፥11፤2ቆሮ 2፥12
15፥20 ሮሜ1፥15፤ 2ቆሮ10፥15:16
15፥21 ኢሳ52፥15
15፥22 ሮሜ1፥13
15፥23 ሐሥ19፥21፤ ሮሜ1፥10:11
15፥24 ቍ28፤ 1ቆሮ16፥6፤ ቲቶ 3፥13
15፥25 ሐሥ19፥21፤ 24፥17፤9፥13
15፥26 ሐሥ16፥9፤ 18፥12፤24፥17
15፥27 1ቆሮ9፥11
15፥28 ቍ24
15፥29 ሮሜ1፥10: 11
15፥30 2ቆሮ1፥11፤ ገላ5፥22፤ቈላ1፥8፤ 4፥12
15፥31 ቍ25፤ ሐሥ 9፥13፤24፥17፤ 2ቆሮ1፥10፤2ተሰ3፥2፤ 2ጢሞ3፥11፤2ጴጥ2፥9፤

T8 ግሪኩ *የመገረዝ* ይላል

የሩሳሌም ያለው አገልግሎቴም በዚያ ባሉት
ቅዱሳን ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ጸልዩ
ልኝ፤ 32ይኸውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ወደ
እናንተ በደስታ እንድመጣና ከእናንተም
ጋር እንድታደስ ነው። 33የሰላም አምላክ
ከሁላችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን።

## የግል ሰላምታ

16 በክንክራኦስ ቤተ ክርስቲያን አገል
ጋይ[ሀ] የሆነችውን እኅታችንን ፌቤ
ንን ዐደራ እላችኋለሁ። 2ለቅዱሳን ተገቢ
በሆነው አቀባበል በጌታ እንድትቀበሏትና
ከእናንተም የምትፈልገውን ማንኛውንም
ርዳታ እንድታደርጉላት አሳስባችኋለሁ፤
ለብዙ ሰዎችና ለእኔም ጭምር ታላቅ ድጋፍ
ነበረችና።
3በክርስቶስ ኢየሱስ አብረውኝ ለሚያገለ
ግሉት ለጵርስቅላና[ለ] ለአቂላ ሰላምታ አቅር
ቡልኝ። 4እነርሱም ለእኔ ሲሉ ሕይወታቸ
ውን ለአደጋ አጋልጠው ሰጡ፤ እኔ ብቻ ሳል
ሆን የአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ
ያመሰግኗቸዋል።
5በእነርሱ ቤት ላለች ቤተ ክርስቲያንም
ሰላምታ አቅርቡልኝ።
ከእስያ አገር ለመጀመሪያ ወደ ክርስቶስ
ለተመለሰው፣ ለወዳጄ ለአጤኔጦን ሰላምታ
አቅርቡልኝ።
6ለእናንተ ብዙ ለደከመችው ለማርያ ሰላ
ምታ አቅርቡልኝ።
7ከእኔ ጋር ታስረው ለነበሩት ዘመዶቼ
ለአንዲራኒቆንና ለዩልያን ሰላምታ አቅርቡ
ልኝ፤ እነርሱ በሐዋርያት መካከል ስመጥሮ
ችና በክርስቶስ በማመንም እኔን የቀደሙ
ናቸው።
8በጌታ ለምወደው ለጵልያጦን ሰላምታ
አቅርቡልኝ።
9በክርስቶስ አብሮን ለሚሠራው ለኢሩ
ባኖንና ለውድ ወዳጄ ለስንጣክን ሰላምታ
አቅርቡልኝ።
10በክርስቶስ ያለው እምነቱ ተፈትኖ ለተ
መሰገነው ለኤጤሌን ሰላምታ አቅርቡልኝ፤
ከአርስጣባሉ ቤተ ሰብ ለሆኑትም ሰላምታ
አቅርቡልኝ።
11ለዘመዴ ለሄሮድዮና ሰላምታ አቅር
ቡልኝ፤
በጌታ ላሉት ለንርቀሱ ቤተ ሰቦች ሰላምታ
አቅርቡልኝ።
12በጌታ ሆነው በትጋት ለሚሠሩት
ሴቶች፣ ለጥሮፊሞናና ለጢሮፊሞሳ ሰላምታ
አቅርቡልኝ።
በጌታ ሆና እጅግ ለደከመችው ለሴላዋ
ሴት፣ ለተወደደችው ለጠርሲዳ ሰላምታ
አቅርቡልኝ።

13በጌታ ለተመረጠው ለሩፎንና የእኔም
እናት ለሆነችው ለእናቱ ሰላምታ አቅር
ቡልኝ።
14ለአስቀሪጦንና ለአፍለሶንጳ፣ ለሄሮ
ሜን፣ ለጳጥሮባን፣ ለሄርማን፣ ከእነርሱም
ጋር ላሉት ወንድሞች ሰላምታ አቅርቡ
ልኝ።
15ለፍሌጎን፣ ለዩልያ፣ ለኔርያና ለእኅቱ፣
እንዲሁም ለአልንጦን፣ ከእነርሱም ጋር
ላሉት ቅዱሳን ሰላምታ አቅርቡልኝ።
16በተቀደሰ አሳሳም ሰላምታ ተሰጣጡ።
የክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሰላ
ምታ ያቀርቡላችኋል።
17ወንድሞች ሆይ፤ መለያየትን ከሚፈ
ጥሩትና የተማራችሁትን ትምህርት በመቃ
ወም በጕዞአችሁ መሰናክል ከሚያደርጉት
እንድትጠነቀቁ አሳስባችኋለሁ፤ ከእነርሱም
ራቁ። 18እንደ እነዚህ ያሉት ሰዎች የሚያገ
ለግሉት ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ሳይ
ሆን፣ የራሳቸውን ሆድ ነው፤ በለሰለሰ አንደ
በታቸውና በሽንገላ፣ የዋሆችን ያታልላሉ።
19የእናንተን ታዛዥነት ሁሉም ሰምተዋል፤
በዚህም እኔ እጅግ ተደስቻለሁ። ሆኖም በጎ
ስለ ሆነው ነገር ጥበበኞች፣ ክፉ ስለ
ሆነውም የዋሆች እንድትሆኑ እፈልጋለሁ።
20የሰላም አምላክ፣ ሰይጣንን ከእግራችሁ
በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል።
የጌታችን የኢየሱስ ጸጋ ከእናንተ ጋር
ይሁን።
21አብሮኝ የሚሠራው ጢሞቴዎስ፣ እንዲ
ሁም ዘመዶቼ የሆኑት ሉቂዮስ፣ ኢያሶንና
ሱሲጴጥሮስ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።
22ይህን መልእክት የጻፍሁ እኔ ጤርጥ
ዮስ፣ በጌታ ሰላምታ አቀርብላችኋለሁ።
23በመልካም መስተንግዶው እኔና በዚህ
የምትገኘዋ መላዋ ቤተ ክርስቲያን ደስ
የምንሰኝበት ጋይዮስ፣ ሰላምታ ያቀርብላ
ችኋል።
የከተማዪቱ ግምጃ ቤት ሹም የሆነው
ኤርስጦስ፣ ወንድማችንም ቍአስጥሮስ
ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። 24የጌታችን የኢ
የሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን፤
አሜን።[ሐ]
25በዘላለማዊ አምላክ ትእዛዝ ሕዝቦች
ሁሉ አምነው እንዲታዘዙ፣ በነቢያት
መጻሕፍት አሁን በተገለጠው፣ 26ላለፉት
ረጅም ዘመናት ተሰውሮ በነበረው ምስጢር
መገለጥ መሠረት፣ በአስተማርኩት
ወንጌልና በኢየሱስ ክርስቶስ መሰበክ ሊ
ያጸናችሁ

15፥32 ሐሥ18፥21፤ ሮሜ1፥10:13፤ 1ቆሮ16፥18፤ፊሞ 7
15፥33 ሮሜ16፥20፤ 2ቆሮ13፥11፤ ፊል4፥9፤1ተሰ5፥23፤ 2ተሰ3፥16፤ዕብ13፥20
16፥1 ሐሥ18፥18፤ 2ቆሮ3፥1፤
16፥2 ሐሥ9፥13፤ ፊል2፥29፤
16፥3 ቍ7:9:10፤ ሐሥ18፥2፤ ሮሜ8፥1:39፤ 1ቆሮ1፥30፤ 2ቆሮ5፥17፤ገላ1፥22፤ 5፥6፤ኤፌ1፥13፤ ፊል 2፥25፤
16፥5 ሐሥ2፥9፤ 1ቆሮ16፥15፤19፤ ቈላ 4፥15፤ፊሞ2፤
16፥7 ቍ3፤11:21: ቈላ4፥10፤ፊሞ23፤
16፥9 ቍ3
16፥10 ቍ3፤ ሐሥ11፥14
16፥11 ቍ7:21፤ ሐሥ11፥14
16፥13 ማር15፥21፤ 2ዮሐ1
16፥15 ቍ2:14፤ ሐሥ9፥13፤
16፥16 1ቆሮ16፥20፤ 2ቆሮ13፥12፤ 1ተሰ5፥26፤1ጴጥ5፥14
16፥17 ማቴ18፥15-17፤ ገላ1፥8:9፤1ቆሮ5፥11፤ 2ተሰ3፥6:14፤ 1ጢሞ 1፥3፤6፥3፤ 2ጢሞ3፥5፤ቲቶ3፥10፤ 2ዮሐ10
16፥18 2ሳሙ15፥6፤ መዝ12፥2፤ኢሳ30፥10፤ ሮሜ14፥18፤ ፊል3፥19፤ቈላ2፥4
16፥19 ሮሜ1፥8፤ 1ቆሮ14፥20
16፥20 ዘፍ3፥15፤ ማቴ4፥10፤ ሮሜ15፥33፤ 2ቆሮ13፥14፤ ገላ6፥18፤1ተሰ5፥28፤ ራእ22፥21
16፥21 ቍ7፥11፤ ሐሥ16፥1፤13፥1፤ 17፥5፤
16፥23 ሐሥ19፥22: 29፤2ጢሞ4፥20
16፥25 ኢሳ48፥6፤ ሮሜ2፥16፤2ቆሮ9፥8፤ ኤፌ1፥9፤3፥20፤ ቈላ1፥26:27፤2፥2፤ 1ጢሞ3፥16፤ 2ጢሞ2፥8፤3፥3-6:9፤ ይሁ24፤
16፥26 ሮሜ1፥2:5

[ሀ]1 ወይም *ዲያቆን*
[ለ]3 በግሪኩ *ጰርስቃ የጰርስቅላ* ተለዋጭ ስም ነው።
[ሐ]24 ቍጥር 24 የሚገኘው በአንዳንድ ቅጆዎች ብቻ ነው።

| | | |
|---|---|---|
| ለሚችለው፣<br>27እርሱ ብቻ ጥበበኛ ለሆነ አምላክ፣ በኢየሱስ | 16፥27 ሮሜ11፥36 | ክርስቶስ በኩል ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን። |

# የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
# ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች-አንደኛ

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ የክርስቶስ ኢየሱስ
ሐዋርያ እንዲሆን ከተጠራው ከጳውሎስ፣
ከወንድማችንም ከሶስቴንስ፤
[2]በቆሮንቶስ ላለችው የእግዚአብሔር ቤተ
ክርስቲያን፤ በክርስቶስ ኢየሱስ ተቀድሰው፣
የእነርሱና የእኛ ጌታ የሆነውን የጌታችንን
የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው
ሆነው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመ
ሆን ለተጠሩት፤
[3]ከእግዚአብሔር ከአባታችን፣ ከጌታም
ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ
ይሁን።

## ምስጋና

[4]በክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ተሰጣችሁ ጸጋ
ዘወትር ስለ እናንተ እግዚአብሔርን አመሰ
ግናለሁ። [5]ምክንያቱም በማናቸውም ነገር
ይኸውም በንግግር ሁሉ፣ በዕውቀትም
ሁሉ በእርሱ በልጽጋችኋል፤ [6]ስለ ክርስቶስ
የመሰከርንላችሁም በእናንተ ዘንድ ጸን
ቶአል። [7]ስለዚህ የጌታችንን የኢየሱስ
ክርስቶስን መገለጥ በጒጒት በመጠባበቅ
ላይ ሳላችሁ፣ ማንኛውም መንፈሳዊ ስጦታ
አይጐድልባችሁም። [8]በጌታችን በኢየሱስ
ክርስቶስ ቀን ያለ ነቀፋ እንድትገኙ እርሱ
እስከ መጨረሻው ድረስ አጽንቶ ይጠብቃ
ችኋል። [9]ወደ ልጁ፣ ወደ ጌታችን ኢየሱስ
ክርስቶስ ኅብረት የጠራችሁ እግዚአብሔር
የታመነ ነው።

## በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተከሠተ መለያየት

[10]ወንድሞች ሆይ፤ በመካከላችሁ መለ
ያየት እንዳይኖር፣ አንድ ልብ፣ አንድ
ሐሳብ እንዲኖራችሁ፤ እርስ በርሳችሁም
እንድትስማሙ በጌታችን በኢየሱስ ክር
ስቶስ ስም እለምናችኋለሁ። [11]ወንድ
ሞች ሆይ፤ በመካከላችሁ ክርክር እንዳለ
ከቀሎዔ ቤተ ሰብ ሰምቻለሁ፤ [12]ነገሩም
እንዲህ ነው፤ ከእናንተ አንዱ፣ "እኔ የጳው
ሎስ ነኝ" ሲል፣ ሌላው፣ "እኔ የአጵሎስ
ነኝ" ይላል፤ ደግሞም አንዱ፣ "እኔ የኬፋ[ሀ]
ነኝ" ሲል፣ ሌላው ደግሞ፣ "እኔስ የክርስቶስ
ነኝ" ይላል።
[13]ለመሆኑ ክርስቶስ ተከፍሎአልን? ጳው
ሎስስ ለእናንተ ተሰቅሎአልን? ወይስ
በጳውሎስ[ለ] ስም ተጠምቃችኋልን? [14]ከቀር
ስጶስና ከጋይዮስ በስተቀር ከእናንተ ማንንም
ስላላጠመቅሁ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤
[15]ስለዚህ በስሜ መጠመቁን የሚናገር ማንም
የለም። [16]እርግጥ የእስጢፋኖስን ቤተ ሰው
አጥምቄአለሁ፤ ከእነዚህ ሌላ ግን ማጥመቄ
ትዝ አይለኝም። [17]ክርስቶስ የላከኝ ወንጌ
ልን እንድሰብክ እንጂ እንዳጠምቅ አይደለም፤
የክርስቶስም መስቀል ከንቱ እንዳይሆን፣ በሰ
ዎች የንግግር ጥበብ አልሰብክም።

## ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኀይልና ጥበብ

[18]የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉ ሞኝነት ነው፤
ለእኛ ለምንድነው ግን የእግዚአብሔር ኀይል
ነው፤ [19]እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤
"የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ፤
የዐዋቂዎችንም ዕውቀት ከንቱ
አደርጋለሁ።"
[20]ጠቢብ የት አለ? ሊቅስ የት አለ?
የዘመኑስ ፈላስፋ የት አለ? እግዚአብሔር
የዓለምን ጥበብ ሞኝነት አላደረገምን?
[21]ከእግዚአብሔር ጥበብ የተነሣ ዓለም
በገዛ ጥበብዋ እግዚአብሔርን ማወቅ ስለ
ተሳናት፣ በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን
ያድን ዘንድ የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ
ሆኖአል። [22]መቼም አይሁድ ታምራዊ
ምልክትን ይፈልጋሉ፤ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን
ይሻሉ፤ [23]እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እን
ሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ መሰናክል፣ ለአሕ
ዛብ ደግሞ ሞኝነት ነው። [24]እግዚአብሔር ለጠ
ራቸው ግን፣ አይሁድም ሆኑ ግሪኮች፣ ክር
ስቶስ የእግዚአብሔር ኀይል፣ የእግዚአብሐ
ኄርም ጥበብ ነው። [25]ምክንያቱም ከሰው ጥበብ
ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባል፣
ከሰውም ብርታት ይልቅ የእግዚአብሔር
ድካም ይበረ ታል።
[26]ወንድሞች ሆይ፤ በተጠራችሁ ጊዜ ምን
እንደ ነበራችሁ እስቲ አስቡ። በሰው መስፈርት
ከእናንተ ብዙዎቻችሁ ዐዋቂዎች አልነበራች
ሁም፤ ብዙዎቻችሁም ኀያላን አልነበራችሁም፤
ብዙዎቻችሁም ከትልቅ ቤተ ሰብ አልተወለ
ዳችሁም። [27]ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞ
ችን ያሳፍር ዘንድ የዓለምን ሞኝ ነገር
መረጠ፤ እግዚአብሔር ብርቱዎችን ያሳፍር ዘንድ
የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ። [28]እግዚአብሔር
የተ ከበረውን እንደሌለ ለማድረግ፣ በዚህ ዓ
ለም ዝቅ ያለውንና የተናቀውን ነገር፣
ቦታም

1፥1 ሐሥ18፥17፤ ሮሜ1፥1፤2ቆሮ1፥1፤ ኤፌ1፥1፤2ጢሞ1፥1
1፥2 ሐሥ2፥21፤ 18፥1፤ ሮሜ1፥7፤ 1ቆሮ10፥32
1፥3 ሮሜ1፥7
1፥4 ሮሜ1፥8
1፥5 2ቆሮ8፥7፤ 9፥11
1፥6 2ተሰ1፥10፤ 1ጢሞ2፥6፤ራእ1፥2
1፥7 ማቴ16፥27፤ ሉቃ17፥30፤ሮሜ 1፥11፤1ቆሮ12፥1-31፤ 1ተሰ1፥10፤2፥19፤ ቲቶ2፥13፤ያዕ5፥7፡ 8፤1ጴጥ1፥13፤2ጴጥ 3፥12፤ራእ1፥7
1፥8 አሞ5፥18፤ 1ቆሮ5፥5፤ፊል1፥6፡ 10፤2፥16፤1ተሰ 3፥13፤5፥2
1፥9 ዘዳ7፥9፤ አሳ49፥7፤ሮሜ8፥28፤ 1ቆሮ10፥13፤1ተሰ 5፥24፤2ተሰ3፥3፤ 2ጢሞ2፥13፤ዕብ 10፥23፤11፥11፤ 1ዮሐ1፥3
1፥10 ሮሜ7፥1፤ 15፥5፤1ቆሮ11፥18
1፥11 ሐሥ11፥14
1፥12 ዮሐ1፥42፤ ሐሥ18፥24፤ 1ቆሮ3፥4፡22፤9፥5
1፥13 ማቴ28፥19
1፥14 ሐሥ18፥8፤ 19፥29
1፥16 ሐሥ11፥14፤ 1ቆሮ16፥15
1፥17 ዮሐ4፥2፤ ሐሥ2፥38፤1ቆሮ 2፥1፡4፡13
1፥18 ቍ21፡23፡ 24፡25፤ሐሥ2፥47፤ ሮሜ1፥16፤1ቆሮ 2፥14፤2ቆሮ2፥15፤ 4፥3፤2ተሰ2፥10
1፥19 ኢሳ29፥14
1፥20 ቍ27፤ ኢዮ 12፥17፤ኢሳ19፥11፡ 12፤44፥25፤ኤር8፥9፤ ሮሜ1፥22፤1ቆሮ2፥6፡ 8፤3፥18፡19፤2ቆሮ4፥4፤ ገላ1፥4
1፥21 ቍ27፡28፤ ሮሜ3፥22፤11፥14፤ 1ቆሮ6፥2፤11፥32
1፥22 ማቴ12፥38፤ ዮሐ2፥11፤4፥48
1፥23 ቍ18፤ ሉቃ2፥34፤1ቆሮ2፥2፤ ገላ3፥1
1፥24 ቍ18፡30፤ ሮሜ1፥16፤8፥28፤ ቈላ2፥3፤
1፥25 ቍ18፤2ቆሮ13፥4፤ 1፥26 ቍ20፤ ሮሜ8፥28፤ 1፥27
ቍ20፤ሮሜ፥22፤1ቆሮ3፥18፡19፤ያዕ2፥5፤ 1፥28 ሮሜ4፥17፤

[ሀ]12 ጴጥሮስ ማለት ነው
[ለ]13 ወይም *ወደ ጳውሎስ*፤ እንዲሁም ቍ 15 ይመ

ያልተሰጠውን ነገር መረጠ፤ 29ይኸውም ማንም
ሰው በእርሱ ፊት እንዳይመካ ነው። 30በክር
ስቶስ ኢየሱስ ለመሆን የበቃችሁት ከእርሱ
የተነሣ ነው፤ እርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ
ጥበባችን፣ ጽድቃችንና ቅድስናችን፣ ቤዛችንም
ሆኖአል። 31እንግዲህ፣ እንዲህ ተብሎ
እንደ ተጻፈ ነው፤ "የሚመካ በጌታ ይመካ።"

2 ወንድሞች ሆይ፤ ወደ እናንተ በመ
ጣሁ ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን ምስጢር[ሐ]
በረቀቀ የንግግር ችሎታ ወይም በላቀ ጥበብ
ልገልጥላችሁ አልመጣሁም። 2በመካከ
ላችሁ ሳለሁ ኢየሱስ ክርስቶስን ያውም
የተሰቀለውን፣ እርሱን ብቻ እንጂ ሌላ
እንዳላውቅ ወስኜ ነበርና። 3ወደ እናንተ
የመጣሁት በድካምና በፍርሃት፣ እንዲ
ሁም በብዙ መንቀጥቀጥ ነበር። 4ቃሌም
ስብከቴም የመንፈስን ኀይል በመግለጥ
እንጂ፣ በሚያባባል የጥበብ ቃል አለነ
በረም፤ 5ይኸውም እምነታችሁ በእግዚ
አብሔር ኀይል እንጂ በሰው ጥበብ ላይ
እንዳይመሠረት ነው።

### ከመንፈስ የተገኘ ጥበብ

6በበሰሉ ሰዎች መካከል ግን ጥበብን
እን ናገራለን፤ ይሁን እንጂ የዚችን ዓለም
ጥበብ ወይም የሚጠፉትን የዚችን ዓለም
ገዦች ጥበብ አይደለም። 7ነገር ግን
ተሰውሮ የነበ ረውን የእግዚአብሔርን ምስጢ
ር ጥበብ ነው፤ ይህም ጥበብ እግዚአብሔር
ከዘመናት በፊት ለክብራችን አስቀድሞ
የወሰነው ነው። 8ከዚህ
ዓለም ገዦች አንዳቸውም ይህን ጥበብ አልተ
ረዱትም፤ ቢረዱትማ ኖሮ የክብርን ጌታ
ባልሰቀሉት ነበር። 9ይሁን እንጂ፣ እንደ
ተጻፈው፣

"ዐይን ያላየውን፣
ጆሮ ያልሰማውን፣
የሰውም ልብ ያላሰበውን፣
እግዚአብሔር ለሚወዱት አዘጋጅቶአል"
10እግዚአብሔር ግን ይህን በመንፈሱ አማካይ
ነት ለእኛ ገልጦልናል።

መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር
እንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራል።
11በውስጡ ካለው ከራሱ መንፈስ በስተቀር
ከሰው መካከል የአንድን ሰው ሐሳብ
የሚያውቅ ማን አለ? እንደዚሁም ከእግዚ
አብሔር መንፈስ በስተቀር፣ የእግዚአብሐ
ርን ሐሳብ የሚያውቅ ማንም የለም።
12ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ፣
የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንምና፤ ይህም
እግዚአብሔር በነጻ የሰጠንን እናውቅ ዘንድ
ነው። 13እኛ የምንናገረው ይህን ነው፤ ከሰው
ጥበብ በተማርነው ቃል ሳይሆን፣
ከመንፈስ በተማርነው ቃል እንናገራ
ለን፤ መንፈ ሳዊ እውነትንም የምንገል
ጸው በመንፈሳዊ ቃል ነው[መ]። 14መንፈሳዊ
ያልሆነ ሰው ከእግዚአብሔር መንፈስ
የሆነውን ነገር ሊቀበል አይችልም፤
ምክንያቱም እንዲህ ያለው ነገር ለእርሱ
ሞኝነት ነው፤ በመንፈስም የሚ መረመር
ስለ ሆነ፣ ሊረዳው አይችልም።
15መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉንም ነገር ይመ
ረምራል፤ ራሱ ግን በማንም አይመረመርም።

16"ያስተምረው ዘንድ፣
የጌታን ልብ ማን ዐወቀው?"
እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን።

### በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተከሠተ መለያየት

3 ወንድሞች ሆይ፤ በክርስቶስ ገና ሕፃናት
እንደ መሆናችሁ፣ እንደ ሥጋው
ያን እንጂ እንደ መንፈሳውያን ልናገራችሁ
አልቻልሁም። 2ገና ስላልጠነከራችሁ ወተት
እንጂ ጠንካራ ምግብ አልመገብኋችሁም፤
አሁንም ቢሆን ገና ናችሁ። 3አሁንም
ሥጋ ውያን ናችሁ፤ በመካከላችሁ
ቅናትና ክርክር አለ፤ ታዲያ፣ ሥጋውያን
መሆ ናችሁ አይደለምን? ተግባራችሁስ
እንደ ማንኛውም ሰው ተግባር መሆኑ
አይደለ ምን? 4ምክንያቱም አንዱ፣ "እኔ
የጳውሎስ ነኝ"፣ ሌላው ደግሞ፣ "እኔ
የአጵሎስ ነኝ" ቢል፣ ሰብአዊ ፍጡር ብቻ
መሆናችሁ አይደለምን?
5ለመሆኑ አጵሎስ ምንድን ነው? ጳውሎ
ስስ ምንድን ነው? ጌታ ለእያንዳንዳቸው በሰ
ጣቸው መጠን የሚሠሩ አገልጋዮች ናቸው፤
እናንተም ወደ እምነት የመጣችሁት በእ
ነርሱ አማካይነት ነው። 6እኔ ተከልሁ፤
አጵሎስ ውሃ አጠጣ፤ ያሳደገው ግን እግዚ
አብሔር ነው። 7ስለዚህ የሚያሳድግ
እግዚአብሔር እንጂ፣ የሚተክልም ሆነ ውሃ
የሚያጠጣ ምንም አይደለም። 8የሚተክ
ልም ሆነ የሚያጠጣ አንድ ናቸው፤ እያን
ዳንዱም እንደ ሥራው መጠን የራሱን
ሽልማት ይቀበላል። 9እኛ ከእግዚአብሔር
ጋር አብረን የምንሠራ ነንና፤ እናንተም
የእግዚአብሔር ዕርሻ ናችሁ፤ የእግዚአብሔር ሕ
ንጻ ናችሁ።
10ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ ጸጋ መጠን፣
እንደ አንድ ብልኅ ግንበኛ መሠረትን
ጣልሁ፤ ሌላውም በላዩ ላይ ይገነባል፤
ነገር ግን እያንዳንዱ እንዴት እንደሚገነባ

3፥9 ኢሳ61፥3፤ማር16፥20፤2ቆሮ 6፥1፤ኤፌ2፥20-22፤
1ተሰ3፥2፤1ጴጥ2፥5፤ 3፥10 ሮሜ12፥3፤ 15፥20፤ኤፌ2፥20

[ሐ]1 አንዳንድ ቅጆች ስለ እግዚአብሔር ይላሉ
[መ]13 ወይም መንፈሳዊ እውነትንም ለመንፈሳዊ ሰው እንገልጻለን

1፥29 ኤፌ2፥9፤
1፥30 ኤር23፥5፡6፤ 33፥16፤ሮሜ3፥24፤ 16፥3፤1ቆሮ1፥2፤ 2ቆሮ5፥21፤ፊል3፥9፤1፥31
መዝ34፥2፤44፥8፤ ኤር9፥23፡24፤ 2ቆሮ10፥17፤
2፥1 ቀኁ4፡13፤ 1ቆሮ1፥17
2፥2 1ቆሮ1፥23፤ ገላ6፥14
2፥3 ሐሥ18፥1-18፤ 1ቆሮ4፥10፤9፥22፤ 2ቆሮ7፥15፤11፥29፡ 30፤12፥5፡9፡10፤13፥9
2፥4 ቀኁ1፤ ሮሜ15፥13
2፥5 2ቆሮ4፥7፤6፥7
2፥6 ቀኁ8፤መዝ 146፥4፤ 1ቆሮ1፥20፤ ኤፌ4፥13፤ፊል3፥15፤ ቈላ4፥12፤ዕብ5፥14፤ 6፥1፤ያዕ1፥4
2፥7 ቀኁ1፤ ሮሜ 16፥25
2፥8 ቀኁ6፤ መዝ 24፥7፤ሐሥ7፥2፤ 1ቆሮ1፥20፤ያዕ2፥1
2፥9 ኢሳ64፥4፤ 65፥17
2፥10 ማቴ13፥11፤ ዮሐ14፥26፤ 2ቆሮ 12፥1፡7፤ገላ1፥12፤ 2፥2፤ኤፌ3፥3፡5
2፥11 ምሳ20፥27፤ ኤር17፥9
2፥12 ሮሜ8፥15፤ 1ቆሮ1፥20፡27፤ ያዕ 2፥5
2፥13 ቀኁ1፡4፤ 1ቆሮ1፥17
2፥14 ዮሐ14፥17፤ 1ቆሮ1፥18
2፥15 1ቆሮ3፥1፤ ገላ6፥1
2፥16 ኢሳ40፥13፤ ዮሐ15፥15፤ ሮሜ 11፥34
3፥1 ሮሜ7፥14፤ 1ቆሮ2፥14፡15፤ 14፥20
3፥2 ዮሐ16፥12፤ ዕብ5፥12-14፤ 1ጴጥ 2፥2
3፥3 ሮሜ13፥13፤ 1ቆሮ1፥11፤ገላ5፥20
3፥4 1ቆሮ1፥12
3፥5 ሐሥ18፥24፤ 1ቆሮ4፥1፤2ቆሮ6፥4፤ኤፌ3፥7፤ቈላ1፥23፡25
3፥6 ሐሥ18፥4-11፤ 1ቆሮ4፥15፤9፥1፤15፥1
3፥8 ቀኁ14፤ መዝ 18፥20፤62፥12፤ ማቴ 25፥21፤ 1ቆሮ9፥17

መጠንቀቅ አለበት። 11ምክንያቱም አንድ
ጊዜ ከተመሠረተው መሠረት በቀር ሌላ
መሠረት መጣል የሚችል ማንም የለም፤
ይህም መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
12ማንም በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ
ወይም በብር፣ በከበረ ድንጋይ ወይም በዕ
ንጨት፣ በሣር ወይም በአገዳ ቢያንጽ፣
13ሥራው እንዴት እንደ ሆነ ይታያል፤
ምክንያቱም ያ ቀን ወደ ብርሃን ያመ
ጣዋል። በእሳት ስለሚገለጥ እሳቱ የእያን
ዳንዱን ሰው ሥራ ምንነት ይፈትናል።
14ማንም የገነባው ሥራ ቢጸናለት ሽል
ማቱን ይቀበላል፤ 15ሥራው የተቃጠለበት
ግን ሽልማት ይቀርበታል፤ እርሱ ራሱ ግን
ይድናል፤ ይሁን እንጂ የሚድነው በእሳት
ውስጥ በጭንቅ እንደሚያልፍ ሆኖ ነው።
16እናንተ ራሳችሁ የእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ እንደ ሆናችሁ፣ የእግዚአብሔርም
መንፈስ በውስጣችሁ እንደሚኖር አታው
ቁምን? 17ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ
መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን
ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
ቅዱስ ነውና፤ ያም ቤተ መቅደስ እናንተ
ናችሁ።
18ማንም ራሱን አያታልል፤ ከእናንተ
ማንም በዚህ ዓለም ጥበበኛ የሆነ ቢመ
ስለው፣ ጥበበኛ ይሆን ዘንድ ራሱን እንደ ሞኝ
ይቍጠር። 19የዚህ ዓለም ጥበብ በእግዚአብሔር
ፊት ሞኝነት ነውና፤ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤
"እርሱ ጥበበኞችን በራሳቸው ተንኰል ይይዛቸ
ዋል፤" 20በሌላ ስፍራ ደግሞ፣ "ጌታ የጥበበ
ኞች ሐሳብ ከንቱ መሆኑን ያውቃል" ተብሎ
ተጽፎአል፤ 21እንግዲህ ማንም በሰው አይ
መካ። ሁሉ ነገር የእናንተ ነውና፤ 22ጳው
ሎስም ሆነ አጵሎስ ወይም ኬፋ[ሠ]፣ ዓለ
ምም ሆነ ሕይወት ወይም ሞት፣ አሁን
ያለውም ሆነ ወደ ፊት የሚመጣው፣ ሁሉ
የእናንተ ነው፤ 23እናንተም የክርስቶስ ናችሁ፤
ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው።

## የክርስቶስ ሐዋርያት

4 እንግዲህ ሰው ሁሉ እኛን እንደ ክርስ
ቶስ አገልጋዮችና እንደ እግዚአብሔር ምስ
ጢር ባለ ዐደራዎች ሊቈጥረን ይገባል።
2ባለ ዐደራዎችም ታማኝ ሆነው መገኘት አለባ
ቸው። 3በእናንተም ሆነ በሰዎች የፍርድ ሸንጎ
ቢፈረድብኝ እኔ በበኩሌ ግድ የለኝም፤ እኔ
እንኳ በራሴ ላይ አልፈርድም። 4ኅሊናዬ
ንጹሕ ነው፤ ይህ ግን ጥፋት አልባ መሆ
ኔን አያረጋግጥም፤ በእኔ ላይ የሚፈርድ
ጌታ ነው። 5ስለዚህ ጊዜው ሳይደርስ በም
ንም ነገር አትፍረዱ፤ ጌታ እስኪመጣ ጠብቁ።
እርሱ በጨለማ ውስጥ የተሰወረውን ወደ
ብርሃን ያመጣዋል፤ በሰዎች ልብ ውስጥ
ያለውንም ሐሳብ ይገልጠዋል። በዚያን ጊዜ
እያንዳንዱ ሰው የሚገባውን ምስጋና
ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቀበላል።
6እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ለእናንተ ጥቅም
ብዬ በዚህ ጕዳይ እኔን ራሴንና አጵሎ
ስን ምሳሌ አድርጌ አቅርቤላችኋለሁ፤ ይህ
ንም ያደረግሁት፣ "ከተጻፈው አትለፍ" የሚ
ለውን ከእኛ እንድትማሩ ነው። ስለዚህ
አንዱን ሰው ከሌላው አብልጣችሁ አትመ
ኩበት። 7ለመሆኑ፣ አንተን ከሌላው እንድ
ትበልጥ ያደረገህ ማን ነው? ያልተቀበልኸው
የራስህ የሆነ ነገር ምን አለ? ከተቀበልህ
ታዲያ፣ እንዳልተቀበልህ ለምን ትመካለህ?
8አሁንስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አግኝ
ታችኋል! ሀብታምም ሆናችኋል! ከእኛም
ተለይታችሁ ነግሣችኋል! በእርግጥ
ብትነግሡማ እኛም ከእናንተ ጋር በነገሥን
ነበር፤ 9ምክንያቱም እግዚአብሔር እኛን ሐ
ዋርያቱን፣ ሞት እንደ ተፈረደባቸው ሰዎች
ከሰው ሁሉ መጨረሻ ያሰለፈን
ይመስለኛል፤ ለዓለም ሁሉ መላእክትም
ለሰዎችም ትርኢት ሆነ ናል። 10እኛ ስለ
ክርስቶስ ብለን ሞኞች ነን፤ እናንተ ግን
በክርስቶስ ጥበበኞች ናችሁ፤ እኛ ደካሞች
ነን፤ እናንተ ግን ብርቱዎች ናችሁ፤
እናንተ የተከበራችሁ ናችሁ፤ እኛ ግን
የተዋረድን ነን። 11እስከዚህ ሰዓት ድረስ እን
ራባለን፤ እንጠማለን፤ እንራቈታለን፤ እንደበ
ደባለን፤ ያለመጠለያ እንንከራተታለን፤ 12በገዛ
እጃችን እየሠራን እንደክማለን። ሲረግሙን
እንመርቃለን፤ ሲያሳድዱን እንታገሣለን፤
13ስማችንን ሲያጠፉ መልካም እንመልሳለን።
እስከ አሁን ድረስ የዓለም ጕድፍ፣ የምድር
ጥራጊ ሆነናል።
14ይህን የምጽፍላችሁ እንደ ተወደዳችሁ
ልጆቼ አድርጌ ልመክራችሁ እንጂ ላሳፍ
ራችሁ ብዬ አይደለም። 15ምንም እንኳ በዐ
ሥር ሺህ የሚቈጠሩ ሞግዚቶች በክርስ
ቶስ ቢኖሯችሁም፣ ብዙ አባቶች ግን የሏ
ችሁም፤ በወንጌል አማካይነት በክርስቶስ ኢየ
ሱስ ወልጄአችኋለሁና። 16ስለዚህ እኔን
እንድትመስሉ እለምናችኋለሁ። 17እንግዲህ
በጌታ የተወደደውንና የታመነውን ልጄን ጢሞ
ቴዎስን የላክሁላችሁ በዚህ ምክንያት ነው፤
እርሱም በየስፍራው በሚገኙ አብያተ ክርስ
ቲያናት ሁሉ ከማስተምረው ትምህርት
ጋር የሚስማማውን፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለ
ውን የሕይወት አካሄዴን ያሳስባችኋል።
18ከእናንተ አንዳንዶቹ ወደ እናንተ የማል
መጣ መስሎአቸው ታብየዋል፤ 19ይሁን እንጂ
የጌታ ፈቃድ ቢሆን ፈጥኜ ወደ እናንተ

3፥11 ኢሳ28፥16፤ ኤፌ2፥20
3፥13 ዘኍ31፥22፡23፤ኤር23፥28፡29፤ሚል3፥3፤1ቆሮ1፥8፤4፥5፤2ተሰ1፥7-10፤2ጢሞ1፥12፡18፤4፥8
3፥14 ቍ8
3፥15 ይሁ23
3፥16 ሮሜ 8፥9፤1ቆሮ6፥19፤2ቆሮ 6፥16፤ኤፌ2፥21፡22፤ዕብ3፥6
3፥18 ኢሳ5፥21፤ 1ቆሮ1፥20፤8፥2፤ ገላ6፥3
3፥19 ቍ18፤ኢዮ 5፥13፤ሮሜ1፥ 22፤ 1ቆሮ1፥20፡27
3፥20 መዝ94፥11
3፥21 ሮሜ8፥32፤ 1ቆሮ4፥6
3፥22 ቍ5፡6፤ ሮሜ8፥38፤1ቆሮ1፥12
3፥23 1ቆሮ15፥23፤ 2ቆሮ10፥17፤ገላ3፥29
4፥1 ሮሜ16፥25፤ 1ቆሮ3፥5፤9፥17፤ ቲቶ1፥7
4፥4 ሐሥ23፥1፤ ሮሜ2፥13፤2ቆሮ 10፥18
4፥5 ኢዮ12፥22፤ መዝ90፥8፤ማቴ7፥1፡ 2፤ሮሜ2፥29፤ 1ቆሮ 3፥13፤1ተሰ2፥19
4፥6 1ቆሮ1፥12፡ 19፡31፤3፥4፡19፡20
4፥7 ዮሐ3፥27፤ ሮሜ12፥3፡6
4፥8 ራእ3፥17፡18
4፥9 መዝ71፥7፤ ሮሜ8፥36፤ዕብ10፥33
4፥10 ሐሥ17፥18፤ 26፥24፤1ቆሮ1፥18፤ 2፥3፤3፥18፤2ቆሮ 11፥19
4፥11 ሮሜ8፥35፤ 2ቆሮ11፥23-27
4፥12 ማቴ5፥44፤ ሐሥ18፥3፤ሮሜ 12፥14፤1ጴጥ3፥9
4፥13 ኤር20፥18፤ ሰቆ3፥45
4፥14 1ቆሮ6፥5፤ 15፥34፤1ተሰ2፥11፤ 2ተሰ3፥14
4፥15 ቍ14፤1ቆሮ 9፥12፡14፡18፡23፤ 15፥1
4፥16 1ቆሮ11፥1፤ ፊል3፥17፤4፥9፤1ተሰ 1፥6፤2ተሰ3፥7፡9
4፥17 ሐሥ16፥10፤ 1ቆሮ7፥17፤16፥10፤1 ጢሞ1፥2
4፥18 ቍ21፤ኤር43፥2
4፥19 ሐሥ18፥21፤ 1ቆሮ16፥5፡6፤2ቆሮ 1፥15፡16

[ሠ] 22 ጴጥሮስ ማለት ነው

እመጣለሁ፤ ከዚያም እነዚህ ትዕቢተኞች የሚ
ናገሩትን ብቻ ሳይሆን፣ ምን ኀይል እንዳ
ላቸውም ማየት እሻለሁ። 20ምክንያቱም
የእግዚአብሔር መንግሥት የወሬ ጕዳይ ሳይ
ሆን የኀይል ጕዳይ ነው። 21ለመሆኑ የምትፈል
ጉት የቱን ነው? በትር ይዤ ልምጣ? ወይስ
በፍቅርና በገርነት መንፈስ?

## አሳፋሪ ኀጢአት በቤተ ክርስቲያን

5 በመካከላችሁ የዝሙት ርኵሰት እንዳለ
በእርግጥ ይወራል፤ እንዲህ ያለው ርኵ
ሰት በአረማውያን ዘንድ እንኳ ታይቶ የማ
ይታወቅ ነው፤ የአባቱን ሚስት ያገባ ሰው
አለና። 2ደግሞም ታብያችኋል! ይልቅስ
ሐዘን ተሰምቶአችሁ፣ ይህን ድርጊት የፈጸመ
ውን ሰው ከመካከላችሁ ልታስወግዱት አይገባ
ምን? 3ምንም እንኳ እኔ በአካል አብሬያችሁ
ባልሆንም፣ በመንፈስ ግን ከእናንተ ጋር ነኝ፤
ልክ አብሬያችሁ እንዳለሁ ሆኜ፣ ይህን ባደረገው
ሰው ላይ አሁኑኑ ፈርጄበታለሁ። 4በምትሰበሰ
ቡበት ጊዜ እኔም በመንፈስ ከእናንተ
ጋር ስለምሆን፣ በጌታችን በኢየሱስ ስምና
በመካከላችሁ በሚገኘው በጌታችን በኢየሱስ
ኀይል፣ 5ሥጋው[‹] ጠፍቶ መንፈሱ በጌታ
ቀን ትድን ዘንድ፣ እንደዚህ ዐይነቱ
ለሰይጣን ይሰጥ።

6መመካታችሁ መልካም አይደለም። ጥቂት
እርሾ ብዙውን ሊጥ እንደሚያቦካው አታው
ቁምን? 7አሁን ያለ እርሾ እንደ ሆናችሁ
ሁሉ አዲስ ሊጥ እንድትሆኑ አሮጌውን እርሾ
አስወግዱ፤ የፋሲካ በጋችን የሆነው ክርስ
ቶስ ተሠውቶአልና። 8ስለዚህ በዓሉን ግፍና
ክፋት በሞላበት እርሾ፣ በአሮጌ እርሾ ሳይ
ሆን፣ እርሾ በሌለበት ቂጣ በቅንነትና በእ
ውነት እናክብር።

9ከሴሰኞች ጋር እንዳትተባበሩ በመልእ
ክቴ ጽፌላችሁ ነበር፤ 10እንዲህም ስል በጠቅ
ላላው ከዚህ ዓለም ሴሰኞች ወይም ስግብ
ግቦችና ቀማኞች፣ ወይም ከጣዖት አምላ
ኪዎች ጋር አትተባበሩ ለማለት አይደለም፤
እንደዚያማ ቢሆን ከዚህ ዓለም ጨርሶ መለየት
ያስፈልጋችሁ ነበር። 11ነገር ግን አሁን የጻፍ
ሁላችሁ፣ “ወንድም ነኝ” እያለ ከሚሴስን
ወይም ከሚስገበገብ ወይም ጣዖትን ከሚያ
መልክ ወይም ከሚሳደብ ወይም ከሚሰክር
ወይም ከሚቀማ ጋር እንዳትተባበሩ ነው፤
ከእንደዚህ ዐይነቱ ሰው ጋር ምግብ እንኳ
አትብሉ።

12ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ባሉት ሰዎች
ላይ ለመፍረድ እኔን ምን አገባኝ? በቤተ
ክርስቲያን ውስጥ ባሉት ሰዎች ላይ እና
ንተ አትፈርዱምን? 13ከቤተ ክርስቲያን
ውጪ ባሉት ላይ የሚፈርድ ግን እግዚአብሔር

4፥20 ሮሜ14፥17፤ 15፥13
4፥21 2ቆሮ1፥23፤ 2፥1፤13፥2፡10
5፥1 ዘሌ18፥8፤ ዘዳ22፥30፤27፥20
5፥2 ቆላ13፤ 2ቆሮ7፥7-11
5፥3 ቈላ2፥5፤1ተሰ 2፥17
5፥4 2ተሰ3፥6
5፥5 ማቴ4፥10፤ ቆሮ1፥8፤1ጢሞ1፥20
5፥6 ማቴ16፥6፡ 12፤ገላ5፥9፤ያዕ4፥16
5፥7 ዘፀ12፥3-6፡ 21፤ማር14፥12፤ 1ጴጥ1፥19
5፥8 ዘፀ12፥14፡15፤ ዘዳ16፥3
5፥9 ኤፌ5፥11፤ 2ተሰ3፥6፡14
5፥10 1ቆሮ10፥27
5፥11 ሮሜ7፥1፤ 16፥17፤1ቆሮ10፥7፡ 14
5፥12 ቆላ3-5፤ማር 4፥11፤1ቆሮ6፥1-4
5፥13 ዘዳ13፥5፤ 17፥7፤19፥19፤ 22፥21፡24፤24፥7፤ መሳ20፥13

6፥1 ማቴ18፥17
6፥2 ማቴ19፥28፤ ሉቃ22፥30፤1ቆሮ5፥12
6፥5 ሐሥ1፥15፤ 1ቆሮ4፥14
6፥6 ሮሜ7፥1፤ 2ቆሮ6፥14፡15፤ 1ጢሞ 5፥8
6፥7 ማቴ5፥39፡40
6፥8 1ተሰ4፥6
6፥9 ዘሌ18፥20፡ 22፤ዘዳ22፥22፤ ኢዮ 13፥9ማቴ25፥34፤ 1ቆሮ15፥33፤ ገላ 6፥7፤ያዕ1፥16
6፥10 1ጢሞ1፥10፤ ራእ21፥8፤22፥15
6፥11 ሐሥ22፥16፤ ሮሜ4፥25፤1ቆሮ1፥2፤ ኤፌ2፥2
6፥12 1ቆሮ10፥23
6፥13 ቆላ15፡19፤ ሮሜ12፥1፤ቈላ2፥22
6፥14 ሐሥ2፥24፤ ሮሜ6፥5፤ኤፌ1፥19፡ 20፤1ተሰ4፥16
6፥15 ሮሜ12፥5

ነው፤ እንግዲህ፣ ‘ክፉውን ሰው ከመካከላችሁ
አስወግዱት።’”

## መካሰስ በክርስቲያኖች መካከል

6 ከመካከላችሁ አንድ ሰው ከሌላው ጋር
ሙግት ቢኖረው፣ ጕዳዩን በቅዱሳን ፊት
በማቅረብ ፈንታ እንዴት ደፍሮ በማያምኑ
ሰዎች ፊት ለመፋረድ ያቀርባል? 2ቅዱሳን
በዓለም ላይ እንደሚፈርዱ አታውቁምን?
በዓለም ላይ የምትፈርዱ ከሆነ፣ እንግዲያው፣
በትንሹ ነገር ላይ ለመፍረድ አትበቁምን?
3በምድራዊ ሕይወት ጕዳይ ቀርቶ፣ በመላእክት
ላይ እንኳ እንደምንፈርድ አታውቁምን? 4እን
ግዲህ እንዲህ ያለ ጕዳይ ሲያጋጥማችሁ፣
በቤተ ክርስቲያን የተናቁን ሰዎች ፈራጅ
አድርጋችሁ ሹሟ[ሰ]! 5ይህንንም የምለው ላሳ
ፍራችሁ ብዬ ነው። ለመሆኑ ከመካከላችሁ
ወንድሞችን ለማስታረቅ የሚበቃ አስተዋይ
ሰው የለምን? 6ነገር ግን ወንድም ወንድሙን
ለመክሰስ ፍርድ ቤት ይሄዳል፤ ያውም በማ
ያምኑ ሰዎች ፊት!

7እንግዲህ በመካከላችሁ መካሰስ መኖሩ
ራሱ ውድቀታችሁን ያሳያል። ብትበደሉ አይ
ሻልምን? ብትታለሉስ አይሻልምን? 8እናንተ
ግን ራሳችሁ ትበድላላችሁ፤ ታታልላላችሁም፤
ያውምኮ ወንድሞቻችሁን።

9ዐመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት
እንደማይወርሱ አታውቁምን? በዚህ ነገር
አትታለሉ፤ ሴሰኞች፣ ጣዖት አምላኪዎች፣
አመንዝሮች፣ ወንደቃዎች፣ ግብረ ሰዶ
ማውያን፣ 10ወይም ሌቦች፣ ስግብግቦች፣
ሰካራሞች፣ ተሳዳቢዎችና ቀማኞች የእግዚአ
ብሔርን መንግሥት አይወርሱም። 11ከእናንተ
አንዳንዶቻችሁ እንደዚህ ነበራችሁ፤ አሁን
ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና፣
በአምላካችን መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳ
ችኋል፤ ጸድቃችኋል።

## የዝሙት ኀጢአት

12“ሁሉ ነገር ተፈቅዶልኛል፤” ይሁን እንጂ
ሁሉም ነገር አይጠቅምም፤ ‘ሁሉ ነገር ተፈቅዶ
ልኛል፤” ይሁን እንጂ ምንም ነገር በእኔ
ላይ አይሠለጥንም። 13ደግሞም፣ “ምግብ
ለሆድ ነው፤ ሆድም ለምግብ ነው፤” እግዚአ
ብሔር ግን ሁለቱንም ያጠፋቸዋል። ሰውነት
ለጌታ ነው እንጂ ለዝሙት አይደለም፤
ጌታም ለሰውነት ነው። 14እግዚአብሔር
ጌታን ከሙ ታን አንዳስነሣው፣ እኛንም
ደግሞ በኀይሉ ከሙታን ያስነሣናል።
15ሰውነታችሁ የክር ስቶስ የአካሉ ብልቶች
እንደ ሆነ አታው

[‹]5 ወይም ኀጢአተኛ ተፈጥሮው ወይም አካሉ
[ሰ]4 ወይም በቤተ ክርስቲያን የተናቁ ሰዎችን ፈራጅ አድርጋችሁ ትሾማላችሁ?

ቁምን? ታዲያ፣ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ
ከዝሙት አዳሪ ብልቶች ጋር  አንድ ላድርገ
ውን? ከቶ አይገባም! [16]ወይስ ከዝሙት አዳሪ
ጋር የሚተባበር ሰው ከእርስዋ ጋር አንድ
ሥጋ እንደሚሆን አታውቁምን? “ሁለቱ አንድ
ሥጋ ይሆናሉ” ተብሎአልና። [17]ነገር ግን
ከጌታ ጋር የሚተባበር ከእርሱ ጋር አንድ
መን ፈስ ይሆናል።

[18]ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚሠራው ኀጢ
አት ሁሉ ከአካሉ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚፈ
ጽም ግን በገዛ አካሉ ላይ ኀጢአት ይሠራል።
[19]ለመሆኑ ሰውነታችሁ በውስጣችሁ የሚኖ
ረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ
ሆነ አታውቁምን? ይህም መንፈስ ከእግዚአብ
ሔር የተቀበላችሁት ነው። እናንተም የራሳችሁ
አይደላችሁም፤ [20]በዋጋ ተገዝታችኋልና፤ ስለዚህ
በሰውነታችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።

## ጋብቻን በተመለከተ

**7** ስለ ጻፋችሁልኝ ጉዳይ፣ ሰው ወደ ሴት
ባይደርስ መልካም ነው[ሸ]፤
[2]ነገር ግን ከዝሙት ለመጠበቅ፣ እያንዳንዱ
ሰው የራሱ ሚስት ትኑረው፤ እያንዳንዷም
ሴት የራሷ ባል ይኑራት። [3]ባል ለሚስቱ
የሚገባትን ሁሉ ያድርግላት፤ ሚስትም
እንዲሁ ለባሏ የሚገባውን ሁሉ ታድርግለት።
[4]ሚስት አካሏ የራስዋ ብቻ አይደለም፤ የባ
ሏም ነው፤ እንዲሁም ባል አካሉ የራሱ ብቻ
አይደለም፣ የሚስቱም ነው። [5]በጸሎት ለመ
ትጋት ተስማምታችሁ ለተወሰነ ጊዜ ካልሆነ
በስተቀር፣ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ፤ ራሳ
ችሁን ባለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተ
ናችሁ እንደ ገና አብራችሁ ሁኑ። [6]ይህን
የምለው ግን እንደ ትእዛዝ ሳይሆን እንደ
ምክር ነው። [7]ሰው ሁሉ እንደ እኔ ቢሆን
ምኞቴ ነው። ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው
ከእግዚአብሔር የተቀበለው  የራሱ የሆነ
ስጦታ አለው፤ አንዱ አንድ ዐይነት ስጦታ
ሲኖረው፣ ሌላው ደግሞ ሌላ ዐይነት ስጦታ
አለው።

[8]ላላገቡና ባሎቻቸው ለሞቱባቸው ሴቶች
ግን እንዲህ እላለሁ፤ ሳያገቡ እንደ እኔ
ቢኖሩ ለእነርሱ መልካም ነው። [9]ነገር ግን
ራሳቸውን መግዛት ካልቻሉ ያግቡ፤ በምኞት
ከመቃጠል ማግባት ይሻላልና።

[10]ላገቡት ይህን ትእዛዝ እሰጣለሁ፤ ይህም
ትእዛዝ የጌታ እንጂ የእኔ አይደለም። ሚስት
ከባሏ አትለያይ፤ [11]ብትለያይ ግን ሳታገባ
ትኑር፤ አለዚያ ከባሏ ጋር ትታረቅ፤ ባልም
ሚስቱን አይፍታት።

[12]ለሌሎች ደግሞ እንዲህ እላለሁ፤ ይህንም
የምለው እኔ እንጂ ጌታ አይደለም። ያላመነች
ሚስት ያለው ወንድም ቢኖርና ሚስቱ አብ
ራው ለመኖር የምትፈቅድ ከሆነ፣ ሊፈታት
አይገባውም። [13]ያላመነ ባል ያላት ሴት
ብትኖርና እርሱም አብሮአት ለመኖር
የሚፈቅድ ከሆነ፣ ልትፈታው አይገባትም።
[14]ያላመነ ባል በሚስቱ ተቀድሶአልና፤
ያላመነችም ሚስት በሚያምን ባሏ ተቀ
ድሳለች፤ አለዚያማ ልጆቻችሁ ርኩሳን
በሆኑ ነበር፤ አሁን ግን የተቀደሱ ናቸው።

[15]ነገር ግን የማያምነው ወገን መለየት
ከፈለገ ይለይ፤ አንድ ወንድም ወይም እኅት
በዚህ ሁኔታ የታሰሩ አይደሉም፤ እግዚ
አብሔር  የጠራን በሰላም እንድንኖር ነው።
[16]አንቺ ሴት፤ ባልሽን ታድኚው እንደ ሆነ
ምን ታውቂያለሽ? ወይስ አንተ ሰው፤ ሚስ
ትህን ታድናት እንደ ሆነ ምን ታውቃለህ?

[17]ብቻ እያንዳንዱ ሰው ጌታ እንደ ወሰነለት፣
እያንዳንዱም እግዚአብሔር እንደ ጠራው
በዚያው ይመላለስ። በአብያተ ክርስቲያናትም
ሁሉ የምንደነግገው ይህንኑ ነው። [18]አንድ
ሰው ተገርዞ ሳለ ቢጠራ፣ እንዳልተገረዘ ሰው
አይሁን፤ ሳይገረዝም ተጠርቶ ከሆነ
አይ ገረዝ። [19]መገረዝም ሆነ አለመገረዝ
አይጠቅምም፤ ዋናው ነገር የእግዚአብሔርን
ትእዛዝ መፈጸሙ ነው። [20]እያንዳንዱ ሰው
በተጠራበት ሁኔታ ጸንቶ ይኑር። [21]በተጠራ
ህ ጊዜ ባሪያ ነበርህን? በዚህ አትጨነቅ፤
ነጻነትህን ማግኘት ከቻልህ ግን ነጻነትህን
ተቀበል። [22]ምክንያቱም ባሪያ ሆኖ ሳለ በጌታ
የተጠራ፣ የጌታ ነጻ ሰው ነው፤ እንዲሁም
ሲጠራ ነጻ የነበረ ሰው የክርስቶስ ባሪያ
ነው። [23]በዋጋ ተገዝታችኋል፤ ስለዚህ
የሰው ባሪያ አት ሁኑ። [24]ወንድሞች ሆይ፤
እያንዳንዱ ሰው በተጠራበት ሁኔታ ከእግዚ
አብሔር ጋር ጸንቶ ይኑር።

[25]ስለ ደናግል፣ ከጌታ የተቀበልሁት ትእ
ዛዝ የለኝም፤ ይሁን እንጂ ከጌታ ምሕረት
የተነሣ እንደ ታማኝ ሰው፣ ምክሬን እሰጣ
ለሁ። [26]አሁን ካለው ችግር የተነሣ ባላችሁ
በት ሁኔታ ብትኖሩ መልካም ይመስለኛል።
[27]አግብተህ ከሆነ መፋታትን አትሻ፤ ካላገባ
ህም ሚስት ለማግባት አትፈልግ። [28]ብታገባ
ግን ኀጢአት አልሠራህም፤ ድንግሊቱም ብታ
ገባ ኀጢአት አላደረገችም። ነገር ግን የሚ
ያገቡ ሰዎች በዚህ ዓለም ብዙ ችግር ይገጥማ
ቸዋል፤ እኔም ይህ እንዳይደርስባችሁ
እወዳለሁ።

[29]ወንድሞች ሆይ፤ ሐሳቤ እንዲህ ነው፤
ዘመኑ አጭር ነው፤ ከእንግዲህ ሚስት
ያላቸው እንደሌላቸው ሆነው ይኑሩ።
[30]የሚያለቅሱ እንደማያለቅሱ፣ ደስተኞች
ደስ እንደማይላቸው ይሁኑ፤ ዕቃ የሚገዙም

[ሸ]1 ወይም *ሰው ከሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ባያደርግ መልካም ነው*

6፥16 ዘፍ2፥24፤ ማቴ19፥5፤ኤፌ5፥31
6፥17 ዮሐ17፥21-23፤ሮሜ8፥9-11፤ ገላ2፥20
6፥18 ቍ9፤ሮሜ 6፥12፤1ቆሮ5፥1፤ 2ቆሮ12፥21፤ገላ5፥19፤ ኤፌ5፥3፤1ተሰ4፥3፡4፤ ዕብ13፥4
6፥19 ዮሐ2፥21፤ ሮሜ14፥7፡8
6፥20 መዝ74፥2፤ ማቴ20፥28፤ሐሥ 20፥28፤1ቆሮ7፥23፤ ፊል1፥20፤ራእ5፥9፤ 14፥4
7፥1 ቍ8፡26
7፥3 ዘፀ21፥10፤ 1ጴጥ3፥7
7፥5 ዘፀ19፥15፤ 1ሳሙ21፥4፡5፤ማቴ 4፥10፤1ተሰ3፥5
7፥6 2ቆሮ8፥8
7፥7 ቍ8፤ማቴ 19፥11፡12፤ሮሜ 12፥6፤1ቆሮ9፥5፤ 12፥4፡11
7፥8 ቍ1፡26
7፥9 1ጢሞ5፥14
7፥10 ሚል2፥14-16፤ሉቃ16፥18
7፥11 ቍ39፤ሮሜ 7፥2፡3
7፥12 ቍ6፡10፤ 2ቆሮ11፥17
7፥14 ሚል2፥15
7፥15 ሮሜ14፥19፤ 1ቆሮ14፥33
7፥16 ሮሜ11፥14፤ 1ጴጥ3፥1
7፥17 ሮሜ12፥3፤ 1ቆሮ4፥17፤14፥33፤ 2ቆሮ8፥18፤11፥28
7፥18 ሐሥ15፥1፡2
7፥19 ሮሜ2፥25-27፤ ገላ5፥6፤6፥15፤ ቈላ3፥11
7፥20 ቍ24
7፥22 ዮሐ8፥32፡36፤ ሮሜ6፥22
7፥23 1ቆሮ6፥20
7፥24 ቍ20
7፥25 ቍ6፤2ቆሮ 8፥8፤2ቆሮ4፥1፤ 1ጢሞ1፥13፡16
7፥26 ቍ1፡8
7፥27 ቍ20፡21
7፥28 ቍ36
7፥29 ቍ31፤ ሮሜ 13፥11፡12

የገዙት ነገር የእነርሱ እንዳልሆነ ይቍጠሩ፤
31በዚህ ዓለም ነገር የሚጠቀሙም እንደማይጠ
ቀሙበት ይሁኑ፤ የዚህ ዓለም መልክ ዐላፊ
ነውና።
32እኔስ ያለ ጭንቀት እንድትኖሩ
እወዳለሁ። ያላገባ ሰው ጌታን ደስ ለ
ማሰኘት ስለ ጌታ ነገር ያስባል፤ 33ያገባ
ሰው ግን ሚስቱን ደስ ለማሰኘት የዚ
ህን ዓለም ነገር ያስባል፤ 34በዚህም ልቡ
ተከፍሎአል። ያላገባች ሴት ወይም ድንግል
ስለ ጌታ ነገር ታስባለች፤ ዓላማዋም በሥጋና
በመንፈስ ለጌታ መቀደስ ነው። ያገባች
ሴት ግን ባሏን ደስ ለማሰ ኘት የዚህን ዓ
ለም ነገር ታስባለች። 35ይህ ንም የምለው
ለእናንተ የሚበጃችሁን ነገር በማሰብ እንጂ
ላስጨንቃችሁ አይደለም፤ ዓላማዬም ልባችሁ
ሳይከፈል በጌታ ጸንታችሁ በአግባብ
እንድትኖሩ ነው።
36አንድ ሰው ያጫትን ድንግል በአግባቡ
ካልያዘ፣ እርሷም በዕድሜ እየገፋች ከሄደች፣
ሊያገባት ካሰበ የወደደውን ያድርግ፤ ኀጢ
አት የለበትምና ይጋቡ[ቀ]። 37ነገር ግን በዚህ
ጕዳይ ልቡን አረጋግቶ፣ ሳይናወጥ፣ ራሱ
ንም በመግዛት ድንግሊቱን ላለማግባት
የወሰነ ሰው መልካም አድርጎአል። 38ስለዚህ
ድንግሊቱን ያገባ መልካም አደረገ፤ ያላገባም
የተሻለ አደረገ[ቀ]።
39አንዲት ሴት ባሏ በሕይወት እስካለ
ድረስ ከእርሱ ጋር የታሰረች ናት፤ ባሏ ቢሞት
ግን፣ የፈለገችውን ሰው ለማግባት ነጻነት
አላት፤ ሰውየው ግን በጌታ መሆን አለበት።
40እንደ እኔ ከሆነ ግን ሳታገባ እንዲሁ ብት
ኖር ይበልጥ ደስተኛ ትሆናለች፤ እኔም ደግሞ
የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ያለ ይመስ
ለኛል።

### ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ

8 ለጣዖት ስለ ተሠዋ ሥጋ ደግሞ ይህን
እላለሁ፤ ሁላችንም ዕውቀት እንዳለን
እናውቃለን[በ]። ዕውቀት ያስታብያል፤ ፍቅር
ግን ያንጻል። 2ዐውቃለሁ የሚል ሰው፣ ማወቅ
የሚገባውን ያህል ገና አላወቀም። 3እግዚአ
ብሔርን የሚወድ ሰው ግን በእግዚአብሔር ዘንድ
የታወቀ ነው።
4እንግዲህ፣ ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ ስለ መብ
ላት እንዲህ እላለሁ፤ በዚህ ዓለም ጣዖት ከንቱ
እንደ ሆነና ከአንዱ ከእግዚአብሔር በስተቀር
ሌላ አምላክ እንደሌለ እናውቃለን። 5መቼም
ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች አሉ፤ በሰማ
ይም ሆነ በምድር አምላክ ተብለው የሚጠሩ
አማልክት ቢኖሩም፤ 6ለእኛ ግን ሁሉም
ነገር ከእርሱ የሆነ፣ እኛም ለእርሱ የሆን
አንድ አምላክ አብ አለን፤ ደግሞም ሁሉም
ነገር በእርሱ አማካይነት የሆነ፣ እኛም በእ
ርሱ አማካይነት የሆን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክር
ስቶስ አለን።
7ነገር ግን ይህን የሚያውቁ ሁሉም አይ
ደሉም፤ አንዳንድ ሰዎች እስከ አሁን ድረስ
ጣዖትን ማምለክ ስለለመዱ፣ እንዲህ ያለውን
ሥጋ ሲበሉ በእርግጥ ለጣዖት እንደ ተሠዋ
ያስባሉ፤ ኅሊናቸውም ደካማ ስለሆነ ይረከ
ሳል። 8ነገር ግን ምግብ ወደ እግዚአብሔር አያ
ቀርበንም፤ ባንበላ የሚጐድልብን ነገር የለም፤
ብንበላም የምናተርፈው ነገር አይኖርም።
9ነገር ግን ከነጻነታችሁ የተነሣ የምታደር
ጉት ለደካሞች ዕንቅፋት እንዳይሆን ተጠንቀቁ።
10አንተ ይህን የመሰለ ዕውቀት ኖሮህ፣ ደካማ
ኅሊና ያለው ሰው፣ በቤተ ጣዖት ስትበላ
ቢያይህ፣ ለጣዖት የተሠዋውን ምግብ ለመ
ብላት አይደፋፈርምን? 11ስለዚህ ክርስቶስ
የሞተለት ይህ ደካማ ወንድም በአንተ ዕው
ቀት ምክንያት ጠፋ ማለት ነው። 12በዚህ
መንገድ ወንድሞቻችሁን በመበደልና ደካማ
ኅሊናቸውን በማቍሰል፣ ክርስቶስን ትበድላላ
ችሁ። 13ስለዚህ እኔ የምበላው ነገር ወን
ድሜን የሚያሰናክለው ከሆነ፣ ወንድሜን
ላለማሰናከል ስል ከቶ ሥጋ አልበላም።

### የሐዋርያ መብት

9 እኔ ነጻ ሰው አይደለሁምን? ሐዋርያስ
አይደለሁምን? ጌታችንን ኢየሱስን አላየ
ሁትምን? እናንተስ በጌታ የድካሜ ፍሬዎች
አይደላችሁምን? 2ለሌሎች ሐዋርያ ባልሆን
እንኳ ለእናንተ ግን በእርግጥ ሐዋርያ ነኝ፤
ምክንያቱም በጌታ የሐዋርያነቴ ማኅተም
እናንተ ናችሁ።
3ለሚመረምሩኝ የምሰጠው መልስ ይህ
ነው። 4ለመሆኑ፣ የመብላትና የመጠጣት
መብት የለንምን? 5እንደ ሌሎቹ ሐዋር
ያት፣ እንደ ጌታ ወንድሞችና እንደ ኬፋ[ተ]
ሁሉ፣ እኛስ አማኝ ሚስት ይዘን የመዞር
መብት የለንምን? 6ወይስ ጥረን ግረን መኖር
ያለብን እኔና በርናባስ ብቻ ነን?
7ለመሆኑ በገዛ ገንዘቡ በወታደርነት የሚ
ያገለግል ማን ነው? ወይን ተክሎ ፍሬውን
የማይበላ ማን ነው? መንጋ እየጠበቀ የከብቱን
ወተት የማይጠጣ ማን ነው? 8ይህን የምናገ
ረው እንደ ሰው አስተሳሰብ ነውን? የኦሪ
ትስ ሕግ ይህንኑ ይል የለምን? 9በሙሴ ሕግ፣
"የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር" ተብሎ

7፥31 ቊ29፤ ዕብ 12፥27
7፥32 1ጢሞ5፥5
7፥34 ሉቃ2፥37
7፥35 መዝ86፥11
7፥36 ቊ28
7፥38 ዕብ13፥4
7፥39 ሮሜ7፥2፡3፤ 2ቆሮ6፥14
7፥40 ቊ25
8፥1 ቊ4፡7፡10፤ ሐሥ15፥20፤ ሮሜ15፥14
8፥2 1ቆሮ3፥18፤ 13፥8፡9፡12፤1ጢሞ 6፥4
8፥3 ኤር1፥5፤ ሮሜ8፥29፤ገላ4፥9
8፥4 ቊ1፡6፡7፡10፤ ዘፀ34፥15፤ዘዳ6፥4፤ መዝ86፥10፤ሐሥ 14፥15፤1ቆሮ10፥19፤ ገላ4፥8፤ኤፌ4፥6፤ 1ጢሞ2፥5
8፥5 2ተሰ2፥4
8፥6 ቊ4፤ሚል 2፥10፤ዮሐ1፥3፤ ሮሜ11፥36፤ኤፌ4፥5
8፥7 ቊ1፤ሮሜ 14፥14፤1ቆሮ10፥28
8፥8 ሮሜ14፥17
8፥9 ሮሜ14፥1፤2 ቆሮ6፥3፤ገላ5፥13
8፥10 ቊ1፡4፡7
8፥11 ሮሜ14፥15፡ 20
8፥12 ማቴ18፥6፤ 25፥40፡45
8፥13 ማቴ5፥29
9፥1 ቊ19፤1ቆሮ 1፥1፤3፥6፤4፥15፤15፥8፤2 ቆሮ12፥12
9፥2 2ቆሮ3፥2፡3
9፥4 ቊ14፤ ሐሥ 18፥3
9፥5 ማቴ12፥ 46፤ 1ቆሮ1፥12፤7፥7፡8፤
9፥6 ሐሥ4፥36
9፥7 ዘዳ20፥6፤ ምሳ27፥18፤1ቆሮ 3፥6፡8፤2ጢሞ2፥3፡4
9፥9 ዘዳ22፥1-4፤ 25፥4፤ምሳ12፥10፤ 1ጢሞ5፥18

[ቀ]36-38 *ወይም አንድ ሰው ድንግል የሆነችውን ልጁን በሚገባ እንዳልያዛት ካሰበና እርስዋም በዕድሜ እየገፋች ከሄደች፣ ማግባት እንዳለባት ካሰበ የወደደውን ያድርግ፤ ኀጢአት የለበትምና እንድታገባ ሊፈቅድላት ይገባል።... 38 ስለዚህ ድንግል የሆነችውን ልጁ ለጋብቻ የሰጠ መልካም አደረገ፤ ለጋብቻ ያልሰጣትም የተሻለ አደረገ።*
[በ]1 *ወይም እናንተ እንደምትሉት* "ሁላችንም ዕውቀት አለን"
[ተ]5 ጴጥሮስ ማለት ነው

ተጽፎአልና። ለመሆኑ፣ እግዚአብሔርን ያሳሰበው
የበሬ ጉዳይ ነውን?
10ይህን የተናገረው በእርግጥ ስለ እኛ
አይደለምን? የተጻፈው በትክክል ስለ እኛ
ነው፤ ዐራሹ የሚያርሰው፣ አበራዩ የሚያበ
ራየው ከምርቱ ድርሻ እንዳለው ተስፋ በማ
ድረግ ነውና። 11እኛ በእናንተ መካከል
መንፈሳዊ ዘር ዘርተን ከሆነ ለሥጋ የሚሆን
ነገር ብናጭድ ትልቅ ነገር መሆኑ ነውን?
12ሌሎች ይህን መብት ከእናንተ ማግኘት
ከቻሉ፣ እኛ ይበልጥ ማግኘት አይገባንምን?
እኛ ግን በዚህ መብት አልተጠቀምንም፤
ይል ቁንም ለክርስቶስ ወንጌል ዕንቅፋት
እንዳን ሆን ሁሉንም ነገር እንታገሣለን።
13በቤተ መቅደስ የሚያገለግሉ ምግባቸውን
ከቤተ መቅደስ እንደሚያገኙ፣ በመሠዊያውም
የሚያ ገለግሉ ከመሥዋዕቱ እንደሚካፈሉ
አታውቁ ምን? 14እንደዚሁም ወንጌልን
የሚሰብኩ ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን
ከወንጌል እንዲቀበሉ ጌታ አዞአል።
15እኔ ግን ከእነዚህ መብቶች በአንዱ
እንኳ አልተጠቀምሁም፤ አሁንም ይህን
የምጽፍላችሁ እንደነዚህ ያሉትን ነገሮች
ታደርጉልኛላችሁ በሚል ተስፋ አይደለም፤
ማንም ትምክህቴን ከንቱ ከሚያደርግብኝ ሞት
ይሻለኛልና። 16ወንጌልን መስበኬ አያስመካ
ኝም፤ የምሰብከው ግዴታዬ ስለሆነ ነው፤ ወን
ጌልን ባልሰብክ ግን ወዮልኝ።

17በፈቃደኝነት ብሰብክ ሽልማት አለኝ፤ በፈቃ
ደኝነት ካልሆነ ግን፣ የምፈጽመው ተግባር
የተጣለብኝን ዐደራ መወጣት ብቻ ይሆናል።
18ታዲያ ሽልማቴ ምንድን ነው? ሽልማቴማ
ወንጌልን ስሰብክ በመብቴ ሳልጠቀም ወንጌ
ልን ያለ ክፍያ መስበክ ነው።
19እኔ ነጻ ሰው ነኝ፤ የማንም ባሪያ አይደ
ለሁም፤ ነገር ግን ብዙዎችን እመልስ ዘንድ
ራሴን ለሰው ሁሉ ባሪያ አደርጋለሁ። 20አይሁ
ድን እመልስ ዘንድ ከአይሁድ ጋር እንደ
አይሁዳዊ ሆንሁ፤ እኔ ራሴ ከሕግ በታች
ሳልሆን፣ ከሕግ በታች ያሉትን እመልስ ዘንድ
ከሕግ በታች እንዳሉት ሆንሁ። 21እኔ ራሴ
ከእግዚአብሔር ሕግ ነጻ ያልሆንሁና፣ ለክርስቶስ
ሕግ የምገዛ ብሆንም፣ ሕግ የሌላቸውን እመ
ልስ ዘንድ፣ ሕግ እንደሌለው ሰው ሆንሁ።
22ደካሞችን እመልስ ዘንድ፣ ከደካሞች ጋር
እንደ ደካማ ሆንሁ። በሚቻለኝ ሁሉ አንዳ
ንዶችን አድን ዘንድ፣ ከሁሉም ጋር ሁሉን
ነገር ሆንሁ። 23ይህን ሁሉ የማደርገው፣ ከወን
ጌል በረከት እካፈል ዘንድ፣ ስለ ወንጌል ብዬ
ነው።
24በሩጫ ውድድር የሚሮጡ ብዙዎች እንደ
ሆኑ፣ ሽልማቱን የሚቀበለው ግን አንዱ ብቻ
እንደ ሆነ አታውቁምን? ስለዚህ ሽልማቱን
እንደሚቀበል ሰው ሩጡ። 25ለውድድር የሚ
ዘጋጅ ማንኛውም ሰው በሁሉም ነገር ራሱን
ይገዛል እነርሱ ዐላፊ ጠፊ የሆነውን አክሊል
ለማግኘት ይደክማሉ፤ እኛ ግን ለዘላለም
የማይጠፋውን አክሊል ለማግኘት እንደክ
ማለን። 26ስለዚህ እኔ ግብ እንደሌለው ሰው
በከንቱ አልሮጥም፤ ደግሞም ነፋስን እንደ
ሚጐስም ሰው እንዲያው አልታገልም፤ 27ነገር
ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ እኔ ራሴ
ውድቅ ሆኜ እንዳልቀር፣ ሰውነቴን እየጐ
ሰምሁ እንዲገዛልኝ አደርገዋለሁ።

## በእስራኤል የደረሰው እንዳይደርስብን እንጠ ንቀቅ

10 ወንድሞች ሆይ፤ አባቶቻችን ሁሉ
ከደመናው በታች እንደ ነበሩና በባሕሩ
ውስጥ እንደ ተሻገሩ ታውቁ ዘንድ እፈልጋ
ለሁ። 2እነርሱ ሁሉ ከሙሴ ጋር ለመተባ
በር በደመናና በባሕር ተጠመቁ። 3ሁሉም
ከአንድ መንፈሳዊ ምግብ በሉ፤ 4ሁሉም ከአ
ንድ መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤ ይከተላቸው
ከነበረው መንፈሳዊ ዐለት ጠጥተዋልና፤
ያ፣ ዐለት ክርስቶስ ነበረ። 5ይሁን እንጂ
እግዚአብሔር በብዙዎቹ ደስ ስላልተሰኘ በበ
ረሓ ወድቀው ቀሩ።
6እነርሱ ክፉ እንደ ተመኙ፣ እኛም ደግሞ
እንዳንመኝ እነዚህ ነገሮች ምሳሌ ሆነውልናል።
7"ሕዝቡ ሊበሉና ሊጠጡ ተቀመጡ፤ ሊዘ
ፍኑም ተነሡ" ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ ከእነርሱ
አንዳንዶቹ እንዳደረጉት ጣዖት አምላኪዎች
አትሁኑ። 8ከእነርሱ አንዳንዶቹ ዝሙት
ፈጽመው በአንድ ቀን ሀያ ሦስት ሺህ ሰው
እንደ ረገፈ፣ እኛም ዝሙት አንፈጽም።
9ከእነርሱ አንዳንዶቹ ጌታን እንደ ተፈታተ
ኑና በእባብ ተነድፈው እንደ ጠፉ፣ እኛም
ጌታን አንፈታተን። 10ከእነርሱ አንዳንዶቹ
እንዳጕረመረሙና በአጥፊው እንደ ጠፉ፣
አታጕረምርሙ።
11ይህ ሁሉ ምሳሌ ይሆን ዘንድ በእነርሱ
ላይ ደረሰ፤ የዘመናት ፍጻሜ የደረሰብንን
እኛን ለማስጠንቀቅም ተጻፈ። 12ስለዚህ ተደላ
ድዬ ቆሜአለሁ የሚል ቢኖር እንዳይወድቅ
ይጠንቀቅ። 13በሰዎች ሁሉ ላይ ከደረሰው
የተለየ ፈተና አልደረሰባችሁም፤ እግዚአብ
ሔር ታማኝ ነው፤ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ
እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በም
ትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን መታገሥ እንድት
ችሉ፣ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል።

9፥10 ምሳ11፥25፤ ሮሜ4፥ 23፡24፤ 2ጢሞ2፥6
9፥11 ቈ14፤ ሮሜ 15፥27፤ገላ6፥6
9፥12 ቍ15፡18፤ ሐሥ18፥3፤2ቆሮ6፥3፤ 11፥7-12
9፥13 ዘሌ6፥16፡26፤ ዘዳ18፥1
9፥14 1ጢሞ5፥18
9፥15 ቍ12፡18፤ ሐሥ18፥3፤2ቆሮ 11፥9፡10
9፥16 ሐሥ9፥15፤ 26፥16ጠ18፤ሮሜ1፥14
9፥17 1ቆሮ3፥8፡ 14፤4፥1፤ገላ2፥7፤ ቈላ1፥25
9፥18 ቍ12፡15፤ 2ቆሮ11፥7፤12፥13
9፥19 ቍ1፤ማቴ 18፥15፤2ቆሮ4፥5፤ ገላ5፥13፤1ጴጥ3፥1
9፥20 ሐሥ16፥3፤ 21፥20-26፤ሮሜ 2፥12፤11፥24
9፥21 ሮሜ2፥12፡14፤ ገላ6፥2
9፥22 ሮሜ11፥14፤ 14፥1፤1ቆሮ2፥3፤ 10፥33
9፥24 ቍ25፡26፤ ገላ2፥2፤5፥7፤ፊል 2፥16፤3፥14፤ ቈላ 2፥18፤2ጢሞ4፥7፤ ዕብ12፥1
9፥25 2ጢሞ2፥5፤ 4፥8፤ያዕ1፥12፤1ጴጥ 5፥4፤ራእ2፥10፤ 3፥11
9፥26 ቍ24፤ 1ጢሞ6፥12
9፥27 ቍ24፤ ሮሜ8፥13
10፥1 ዘፀ13፥21፤ 14፥22፡29፤መዝ66፥6፤ 105፥39፤ሮሜ 11፥25
10፥2 ሮሜ6፥3
10፥3 ዮሐ6፥31
10፥4 ዘፀ17፥6፤ ዘኍ20፥11፤መዝ 78፥15፤105፥41
10፥5 ዘኍ14፥29፤ ዕብ3፥17፤ይሁ5
10፥6 ቍ11 10፥7 ቍ14፤ዘፀ32፥4፡6፡19
10፥8 ዘኍ25፥1-9
10፥9 ዘፀ17፥2፤ ዘኍ21፥5፡6፤መዝ 78፥18፤95፥9፤ 106፥14
10፥10 ዘፀ12፥23፤ ዘኍ16፥41፡49፤17፥5፡ 10፤1ዜና21፥15፤ ዕብ11፥28
10፥11 ቍ6፤ ሮሜ4፥24፤13፥11
10፥14 ቍ7፤ ዕብ6፥9፤1ጴጥ2፥11፤
10፥12 ሮሜ11፥20፤ 2ቆሮ1፥24
10፥13 1ቆሮ1፥9፤ 2ጴጥ2፥9፤

## ከጣዖት ጋር አለመተባበር

14ስለዚህ ወዳጆቼ ሆይ፤ ከጣዖት አምልኮ
ሽሹ። 15ይህን የምናገረው አስተዋይ ለሆኑ
ሰዎች ነው፤ ስለምናገረው ነገር እናንተው
ፍረዱ። 16የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክር
ስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን?
የምንቈርሰውስ እንጀራ ከክርስቶስ ሥጋ
ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? 17እንጀራው
አንድ እንደ ሆነ፣ እኛም ብዙዎች ሆነን ሳለ
አንድ አካል ነን፤ ሁላችን አንዱን እንጀራ
እንካፈላለንና።
18እስቲ የእስራኤልን ሕዝብ አስቡ፤ መሥ
ዋዕቱን የሚበሉት ከመሠዊያው ጋር ኅብ
ረት አልነበራቸውምን? 19ታዲያ፣ ለጣዖት
የተሠዋ ነገርም ሆነ ጣዖቱ ራሱ ዋጋ ያለው
ነገር ነው ማለቴ ነውን? 20አይደለም፤ አሕ
ዛብ የሚሠዉት ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለአጋ
ንንት ነው፤ ከአጋንንት ጋር እንድትተባ
በሩም አልሻም። 21የጌታን ጽዋና፣ የአጋን
ንትን ጽዋ በአንድ ላይ መጠጣት አትችሉም፤
ከጌታ ማዕድና ከአጋንንት ማዕድ ተካፋይ
መሆን አትችሉም። 22ጌታ ን እናስቀናውን?
በብርታትስ ከእርሱ እንበልጣለንን?

## የአማኞች ነጻነት

23“ሁሉ ነገር ተፈቅዶአል”፤ ነገር ግን ሁሉም
ነገር አይጠቅምም፤ “ሁሉም ነገር ተፈቅዶአል”፤
ነገር ግን ሁሉም ነገር አያንጽም። 24እያን
ዳንዱ ሰው የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ
የራሱን ብቻ አይፈልግ።
25በኀሊና ምርምር ውስጥ ሳትገቡ፣ በሥጋ
ገበያ የሚሸጠውን ሁሉ ብሉ፤ 26ምድርና
በውስጥዋ ያለው ሁሉ የጌታ ነውና።
27የማያምን ሰው ጋብዞአችሁ ለመሄድ
ብትፈልጉ በኅሊና ምርምር ውስጥ ሳትገቡ
የቀረበላችሁን ሁሉ ብሉ። 28ነገር ግን አንዱ፣
ይህ ለጣዖት የተሠዋ ነው ቢላችሁ ይህን
ስለ ነገራችሁ ሰውና ለኅሊናችሁ ስትሉ
አትብሉ[ቸ]። 29ይህን የምለውም ስለዚያ ሰው
ኅሊና እንጂ ስለ አንተ አይደለም፤ ነጻነቴስ
በሌላ ሰው ኅሊና ለምን ይመዘን? 30ምግ
ቡን በምስጋና የምበላ ከሆነ፣ እግዚአብሔርን
ባመሰገንሁበት ነገር ለምን እወቀሳለሁ?
31እንግዲህ ስትበሉም ሆነ ስትጠጡ፣ ወይም
ማንኛውንም ነገር ስታደርጉ ሁሉንም ነገር
ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት። 32ለአይ
ሁድም ሆነ ለግሪኮች ወይም ለእግዚአብሔር
ቤተ ክርስቲያን መሰናክል አትሁኑ፤ 33እኔ
ሰውን ሁሉ በማንኛውም ረገድ ለማስደሰት
እንደምጥር እናንተም እንዲሁ አድርጉ፤
ብዙዎችም ይድኑ ዘንድ፣ ለራሴ የሚጠቅ
መውን ሳይሆን ለእነርሱ የሚጠቅመውን
እሻለሁና።

1ዮሐ2፥7፤5፥21፤ ይሁ3
10፥16 ማቴ14፥19፤ 26፥26-28፤ 1ቆሮ11፥23-25
10፥17 ሮሜ12፥5
10፥18 ዘሌ7፥6፡ 14፡15
10፥19 1ቆሮ8፥4 ዘዳ32፥17፤መዝ106፤37፤ራእ9፥20
10፥20 ዘሌ17፥7፤
10፥21 2ቆሮ6፥15፡16፤
10፥22 ዘዳ32፥16፡21፤ 1ነገ14፥22፤ መዝ78፥58፤ መክ6፥10፤ኢሳ45፥9፤ ኤር44፥8፤
10፥23 1ቆሮ6፥12
10፥24 ቀኈ33፤ሮሜ 15፥1፡2፤1ቆሮ13፥5፤ፊል2፥4፡21
10፥25 ሐሥ10፥15፤ 1ቆሮ8፥7
10፥26 ዘፀ9፥29፤ 19፥5፤ኢዮ41፥11፤ መዝ24፥1፤50፥12፤ 1ጢሞ4፥4
10፥27 ሉቃ 10፥7
10፥28 1ቆሮ8፥7፡ 10-12
10፥29 1ቆሮ9፥1፡19
10፥30 ሮሜ14፥6
10፥31 ዘካ14፥21፤ ቈላ3፥17፤1ጴጥ4፥11
10፥32 ማቴ5፥29፤ ሐሥ20፥28፤24፥16፤ 1ቆሮ1፥2፤11፥16፡22፤ 15፥9፤2ቆሮ6፥3፤ 1ጢሞ3፥5፡15
10፥33 ቀኈ24፤ ሮሜ11፥14፤15፥2፤ 1ቆሮ9፥22

11፥1 ሮሜ15፥3፤ 1ቆሮ4፥16፤1ጴጥ2፥21
11፥2 ቀኈ17፡22፡ 23፤1ቆሮ4፥17፤ 15፥2፡3፤2ተሰ2፥15፤ 3፥6
11፥3 ዘፍ3፥16፤ 1ቆሮ3፥23፤ኤፌ1፥22፤ 5፥23
11፥4 ሐሥ11፥27
11፥5 ዘዳ21፥12፤ ሐሥ21፥9
11፥7 ዘፍ1፥26፤ 5፥1፤9፥6፤ያዕ3፥9
11፥8 ዘፍ2፥21ጠ23፤ 1ጢሞ2፥13
11፥9 ዘፍ2፥18
11፥12 ሮሜ11፥36
11፥16 1ቆሮ7፥17፤ 10፥32

**11** እኔ የክርስቶስን ምሳሌ እንደምከ
ተል እናንተም የእኔን ተከተሉ።

## ሥርዐት ያለው አምልኮ

2በሁሉም ነገር ስለምታስቡልኝና ከእኔ
የተቀበላችሁትን ትምህርት[ኀ] አጥብቃችሁ
ስለ ያዛችሁ አመሰግናችኋለሁ።
3ነገር ግን ይህን እንድታውቁ
እወዳለሁ፤ የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ
ነው፤ የሴትም ራስ ወንድ ነው፤ የክጠ
ርስቶስም ራስ እግዚአ ብሔር ነው። 4ራሱን
ተከናንቦ የሚጸልይ ወይም ትንቢት
የሚናገር ማንኛውም ወንድ የእርሱን ራስ
ያዋርዳል፤ 5ራሷን ሳትሸፍን የምትጸልይ
ወይም ትንቢት የምትናገር ማን ኛዋም
ሴት የእርሷን ራስ ታዋርዳለች፤
ጠጕርዋን እንደ ተላጨች ይቈጠራልና።
6ሴት ራሷን የማትሸፍን ከሆነ፣ ጠጕርዋን
ትቈረጥ፤ ጠጕሯን መቈረጥ ወይም መላ
ጨት የሚያሳፍር መስሎ ከታያት ግን ራስ
ዋን ትሸፈን። 7ወንድ ራሱን መከናነብ የለ
በትም፤[ነ] ወንድ የእግዚአብሔር ምሳሌና
ክብር ነውና፤ ሴት ግን የወንድ ክብር ናት፤
8ምክ ንያቱም ሴት ከወንድ ተገኘች እንጂ
ወንድ ከሴት አልተገኘም። 9ደግሞም ሴት
ለወንድ ተፈጠረች እንጂ ወንድ ለሴት
አልተፈጠረም። 10በዚህ ምክንያት፣
በመላእክትም ምክንያት፣ ሴት በሥልጣን
ሥር መሆን ዋን የሚያሳይ ምልክት በራ
ስዋ ላይ ታድ ርግ።
11በጌታ ዘንድ ግን ሴት ያለ ወንድ፣
ወን ድም ያለ ሴት አይሆንም። 12ሴት
ከወንድ እንደ ተገኘች ሁሉ፣ ወንድም
ከሴት ይወለ ዳልና፤ ነገር ግን የሁሉም
መገኛ እግዚአብ
ሔር ነው። 13እስቲ እናንተ ፍረዱ፤ ሴት
ራስዋን ሳትሸፍን ወደ እግዚአብሔር መጸለይ
ይገባታልን? 14ወንድ ጠጕሩን ቢያስረዝም ነውር
እንደሚሆንበት ተፈጥሮ እንኳ አያስተምራ
ችሁምን? 15ሴት ግን ጠጕርዋን ብታስረ
ዝም ክብርዋ አይደለምን? ረጅም ጠጕር
የተሰጣት መጐናጸፊያ እንዲሆናት ነውና።
16እንግዲህ ማንም በዚህ ጉዳይ ላይ መከራከር
ቢፈልግ፣ እኛም ሆን የእግዚአብሔር አብያተ
ክርስቲያናት ከዚህ የተለየ ልማድ የለንም።

[ቸ]28 አንዳንድ ቅጆች *አትብሉ፤* “ምድርና በውስጧ ያለው ሁሉ የጌታ ናትና።”
[ኀ]2 ወይም *ወግ*
[ነ]4-7 ወይም የራሱን ጠጕር አስረዝሞ የሚጸልይ ወይም ትንቢት የሚናገር ማንኛውም ወንድ ራሱ የሆነውን ያዋርዳል፤ 5ራሷን ሳትከናነብ የምትጸልይ ወይም ትንቢት የምትናገር ማንኛዋም ሴት ራሷ የሆነውን ታዋርዳለች፤ ጠጕራቸውን ከተላጩ ሴቶች አንዷ ትመሰላለችና። ሴት ራሷን የማትከናነብ ከሆነ፣ ጠጓሯን ታሳጥር፤ ጠጕሯን መቈረጥ ወይም መላጨት የሚያሳፍር ስለሆነ ግን እንደገና ታሳድገው። 7ወንድ ጠጕሩን ማስረዘም የለበትም፤

### የጌታ እራት

11፥23-25 ተጓ - ምብ ማቴ 26፥26-28፤ ማር 14፥22-24፤
ሉቃ 22፥17-20

[17]ነገር ግን በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለሚጐዳ
እንጂ ለሚጠቅም ስላልሆነ፣ ይህን ትእዛዝ
ስሰጥ እያመሰገንኋችሁ አይደለም። [18]ከሁሉ
አስቀድሞ በቤተ ክርስቲያን በምትሰበ
ሰቡበት ጊዜ በመካከላችሁ መለያየት እን
ዳለ ሰምቻለሁ፤ ይህም ሊሆን እንደሚችል
በከፊል አምናለሁ፤ [19]ከእናንተ መካከል እው
ነተኞቹ ተለይተው ይታወቁ ዘንድ፣ ይህ
መለያየት በመካከላችሁ መኖሩ ግድ ነው።
[20]በምትሰበሰቡበት ጊዜ የምትበሉት የጌ
ታን እራት አይደለም፤ [21]በምትበሉበት ጊ
ዜ አንዱ ሌላውን ሳይጠብቅ ምግቡን
ይበላልና፤ አንዱ እየተራበ ሌላው ይሰክራ
ል። [22]ለመ ሆኑ የምትበሉበትና የምትጠጠ
ብት ቤት የላችሁምን? ወይስ የእግዚአብሔርን
ቤተ ክር ስቲያን በመናቅ፣ ምንም
የሌላቸውን ታሳፍ ራላችሁን? እንግዲህ ምን
ልበላችሁ? በዚህ ነገር ላመስግናችሁን? ፈጽሞ
አላመሰግናችሁም።

[23]እኔ ከጌታ የተቀበልሁትን ለእናንተ አስ
ተላልፌአለሁና፤ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተ
ሰጠባት ሌሊት፣ እንጀራን አንሥቶ [24]ከባረከ
በኋላ ቈርሶ፣ “ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ
ነው፤ ለመታሰቢያዬም አድርጉት” አለ።
[25]እንዲሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን አን
ሥቶ፣ “ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ
ኪዳን ነው፤ ስለዚህ ከጽዋው በምትጠጡ
በት ጊዜ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት”
አለ። [26]ይህን እንጀራ በምትበሉበት ጊዜ፣
ይህንም ጽዋ በምትጠጡበት ጊዜ ሁሉ ጌታ
እስከሚመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁ።

[27]እንግዲህ ማንም ሳይገባው፣ ይህን እን
ጀራ ቢበላ ወይም የጌታን ጽዋ ቢጠጣ፣
የጌታ ሥጋና ደም ባለ ዕዳ ይሆናል። [28]
ማንም ሰው ከዚህ እንጀራ ከመብላቱና ከዚህ
ጽዋ ከመጠጣቱ በፊት፣ ራሱን ይመርምር፤
[29]ምክንያቱም ማንም የጌታን ሥጋ ሳይጠ
ገባው* ቢበላና ቢጠጣ ፍርድ የሚያመጣበትን
ይበላል፤ ይጠጣል። [30]ከእናንተ መካከል
ብዙዎች የደከሙትና የታ መሙት፣
አንዳንዶችም ያንቀላፉት በዚህ ምክንያት
ነው። [31]ራሳችንን ብንመረምር ግን
ባልተፈረደብን ነበር። [32]ነገር ግን ጌታ
በሚፈርድብን ጊዜ እንገሠጻለን፤ ይኸውም
ከዓለም ጋር አብረን እንዳንኰነን ነው።

[33]ስለዚህ፣ ወንድሞቼ ሆይ፤ ለመብላት
በምትሰበሰቡበት ጊዜ እርስ በርሳችሁ ተጠ
ባበቁ። [34]በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለፍርድ እን
ዳይሆንባችሁ፣ ማንም የራበው ሰው ቢኖር
በቤቱ ይብላ። ስለ ቀረው ነገር ደግሞ
በምመጣበት ጊዜ እደነግጋለሁ።

11፥17 ቍ2፡22
11፥18 1ቆሮ 1፥10-12፤3፥3
11፥19 1ዮሐ2፥19
11፥21 2ጴጥ2፥13፤ይሁ12
11፥22 ቍ2፡17፤ቆሮ10፥32፤ያዕ2፥6
11፥23 ቍ2፤ገላ1፥12
11፥24 1ቆሮ10፥16
11፥25 ሉቃ22፥20፤1ቆሮ10፥16
11፥26 1ቆሮ1፥7
11፥27 ዕብ10፥29
11፥28 2ቆሮ13፥5
11፥30 ማቴ9፥24
11፥31 መዝ32፥5፤1ዮሐ1፥9
11፥32 መዝ94፥2፤118፥18፤ምሳ3፥11፡12፤ዮሐ15፥18፡19፤ዕብ12፥7-10፤ራእ3፥19
11፥34 ቍ21፡22፤1ቆሮ4፥19

12፥1 ሮሜ1፥11፤11፥25፤1ቆሮ1፥7፤14፥1፡37
12፥2 መዝ115፥5፤ኤር10፥5፤ዕን2፤18፡19፤ኤፌ2፥2
12፥3 ዮሐ13፥13፤ሮሜ9፥3፤1ቆሮ16፥22፤1ዮሐ 4፥2፡3
12፥4 ቍ8-11፤ሮሜ12፥4-8፤ኤፌ4፥11፤ዕብ2፥4
12፥6 ኤፌ4፥6፤ፊል2፥13
12፥7 1ቆሮ14፥12፤ኤፌ4፥12
12፥8 1ቆሮ2፥6፤2ቆሮ8፥7
12፥9 ቍ28፡30፤ማቴ10፥1፤17፥19፡20፤1ቆሮ13፥2
12፥10 ቍ28-30፤ማር16፥17፤ገላ3፥5፤ኤፌ4፥11፤1ዮሐ4፥1
12፥11 ቍ4
12፥12 ቍ27፤ሮሜ12፥5
12፥13 ዮሐ 7፥37-39፤ገላ3፥28፤ኤፌ2፥18፤ቈላ3፥11
12፥14 ቍ12፡20

### መንፈሳዊ ስጦታዎች

12 ወንድሞች ሆይ፤ አሁን ደግሞ
ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች ይህን
እንድታውቁ እፈልጋለሁ። [2]አረማውያን
በነበራችሁበት ጊዜ ወዲያና ወዲህ በመ
ነዳት ድዳ ወደ ሆኑ ጣዖታት እንደ ተወሰ
ዳችሁ ታውቃላችሁ። [3]ስለዚህ ማንም
በእግዚአብሔር መንፈስ የሚናገር፣ “ኢየሱስ
የተረገመ ነው” የሚል የለም፤ እንደዚሁም
በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር፣ ማንም
“ኢየሱስ ጌታ ነው” የሚል እንደሌለ እነግራ
ችኋለሁ።

[4]ስጦታዎች ልዩ ልዩ ሲሆኑ፣ መንፈስ ግን
አንድ ነው፤ [5]አገልግሎትም ልዩ ልዩ ሲሆን፣
ጌታ ግን አንድ ነው፤ [6]አሠራርም ልዩ ልዩ ሲሆን፣
ሁሉን በሁሉ የሚሠራው ግን ያው አንዱ
እግዚአብሔር ነው።

[7]ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ
ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም
ነው። [8]ለአንዱ በመንፈስ የጥበብን ቃል
መናገር ይሰጠዋል፤ ለሌላው ደግሞ በዚያው
መንፈስ የዕውቀትን ቃል መናገር ይሰጠዋል፤
[9]ለአንዱ በዚያው መንፈስ እምነት ይሰጠዋል፤
ለሌላው ደግሞ በዚያው በአንዱ መንፈስ
የመፈወስ ስጦታዎች ይሰጠዋል፤ [10]ለአንዱ
ታምራትን የማድረግ፣ ለሌላው ትንቢትን
የመናገር፣ ለሌላው ደግሞ መናፍስትን የመ
ለየት፣ ለአንዱ በልዩ ልዩ ልሳን የመናገር፣
ለሌላው ደግሞ በልዩ ልዩ ልሳን[፩] የተነገረውን
የመተርጐም ስጦታ ይሰጠዋል። [11]እነዚህ ሁሉ
የዚያው የአንዱ መንፈስ ስጦታዎች ሲሆኑ፣
ለእያንዳንዱ ሰው እርሱ ራሱ እንደ ፈቀደ
ይሰጠዋል።

### አንድ አካል ብዙ ብልቶች

[12]አካል ብዙ ብልቶች ቢኖሩትም አንድ
አካል ነው፤ ነገር ግን ብልቶች ብዙ ቢሆ
ኑም አካል አንድ ነው። ክርስቶስም እንደዚሁ
ነው። [13]አይሁድ ወይም የግሪክ ሰዎች ብን
ሆን፣ ባሪያ ወይም ነጻ ሰዎች ብንሆን፣ እኛ
ሁላችን አንድ አካል እንድንሆን በአንድ
መንፈስ ተጠምቀናልና፤ ሁላችንም አንዱን
መንፈስ እንድንጠጣ ተሰጥቶናል።

[14]አካል የተሠራው ከብዙ ብልቶች እንጂ
ከአንድ ብልት አይደለም። [15]እግር፣ “እኔ እጅ
ስላልሆንሁ የአካል ክፍል አይደለሁም” ቢል
ይህን በማለቱ የአካል ክፍል መሆኑ ይቀራ
ልን? [16]ጆሮም፣ “እኔ ዐይን ስላልሆንሁ የአካል
ክፍል አይደለሁም” ቢል ይህን በማለቱ የአ
ካል ክፍል መሆኑ ይቀራልን? [17]አካል በሙሉ

[፩]10 ወይም ቋንቋ፤ እንዲሁም ቍ28 ይመ

ዐይን ቢሆን ኖሮ፣ መስማት ከየት ይገኝ
ነበር? አካል በሙሉ ጆሮ ቢሆን ኖሮ፣ ማሽተት
ከየት ይገኝ ነበር? [18]ነገር ግን እግዚአብሔር
እንደ ወደደ እያንዳንዱን በየቦታው መድ
ቦአል:: [19]ሁሉም አንድ ብልት ቢሆን ኖሮ
አካል ከየት ይገኝ ነበር? [20]እንግዲህ ብል
ቶች ብዙ ናቸው፣ አካል ግን አንድ ነው::
[21]ዐይን እጅን፣ “አታስፈልገኝም” ሊለው
አይችልም፤ ራስም እግርን፣ “አታስፈልጉኝም”
ሊለው አይችልም:: [22]እንዲያውም ደካማ
የሚመስሉት የአካል ብልቶች እጅግ አስ
ፈላጊ ናቸው:: [23]የተናቁ ለሚመስሉን
ብልቶች ይበልጥ ክብር እንሰጣቸዋለን፤
ደግሞም የምናፍርባቸውን ብልቶች
ይበልጥ እንንከባከባቸዋለን፤ [24]የማናፍርባ
ቸው ብልቶቻችን ግን ይህ አያስፈልጋ
ቸውም:: እግዚአብሔር ግን የአካል ብል
ቶችን አንድ ላይ አገጣጥሞ ክብር ለሚጐድ
ላቸው የበለጠ ክብር ሰጥቶአቸዋል፤ [25]ይህንም
ያደረገው በአካል ብልቶች መካከል መለያየት
ሳይኖር፣ እርስ በርሳቸው እኩል እንዲተሳ
ሰቡ ነው:: [26]አንድ ብልት ቢሠቃይ ብልቶች
ሁሉ አብረው ይሠቃያሉ፤ አንድ ብልት ቢከ
ብር ሌሎቹም ብልቶች አብረው ደስ ይላቸ
ዋል::
[27]እንግዲህ እናንተም የክርስቶስ አካል
ናችሁ፤ እያንዳንዳችሁም የአካሉ ብል
ቶች ናችሁ:: [28]እግዚአብሔር በቤተ ክርስ
ቲያን ውስጥ አንደኛ ሐዋርያትን፣ ሁለተኛ
ነቢያትን፣ ሦስተኛ መምህራንን፣ ቀጥሎም
ታምራት አድራጊዎችን፣ የመፈወስ ስጦታዎች
ያላቸውን፣ ሌሎችን የመርዳት ስጦታ
ያላቸውን፣ የማስተዳደር ስጦታ ያላቸውንና
በልዩ ልዩ ልሳን የመናገር ስጦታ ያላቸውን
ሰዎች መድቦአል:: [29]ሁሉ ሐዋርያት ናቸውን?
ሁሉስ ነቢያት ናቸውን? ሁሉስ መምህራን
ናቸውን? ሁሉስ ታምራት ያደርጋሉን?
[30]ሁሉስ የመፈወስ ስጦታዎች አላቸውን?
ሁሉስ በልሳኖች ይናገራሉን[ሀ]? ሁሉስ
ይተረጕማሉን? [31]ነገር ግን ከሁሉ
የሚበልጠውን ስጦታ በብርቱ ፈልጉ::[ለ]

### ፍቅር

ደግሞም ከሁሉ የሚበልጠውን መንገድ
አሳያችኋለሁ::

13 በሰዎችና በመላእክት ልሳን[ሐ] ብና
ገር፣ ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚ
ጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሿሿ ጸናጽል
ነኝ:: [2]የትንቢት ስጦታ ቢኖረኝ፣ ምስጢ
ርን ሁሉና ዕውቀትን ሁሉ ባውቅ፣ ተራራ
ንም ከቦታው የሚነቅል እምነት ቢኖረኝ፣
ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ:: [3]ያለኝን ሁሉ
ለድኾች ብሰጥ፣ ሰውነቴንም እንዲቃጠል

12፥18 ቍ11፡28
12፥20 ቍ12፡14፤ ሮሜ12፥5
12፥27 ሮሜ12፥5፤ ኤፌ1፥23፤4፥12፤ ቈላ1፥18፡24
12፥28 ቍ9፡10፤ ማር16፥17፤ ሮሜ 12፥6-8፤1ቆሮ 10፥32፤ ኤፌ4፥11
12፥30 ቍ10
12፥31 1ቆሮ14፥1፡39
13፥1 ቍ8፤ ማር16፥17
13፥2 ቍ8፤ ማቴ17፥20፤21፥21፤ሐሥ11፥27፤1ቆሮ 12፥9፤14፥2፤2ቆሮ 8፥7፤ኤፌ4፥11
13፥3 ዳን3፥28፤ ሉቃ19፥8፤ሐሥ2፥45
13፥4 1ቆሮ5፥2፤ 1ተሰ5፥14
13፥5 ኢዮ14፥16፡ 17፤ምሳ10፥12፤ 17፥ 9፤ማቴ5፥22፤ 1ቆሮ10፥24፤ 1ጴጥ4፥8
13፥6 2ተሰ2፥12፤ 2ዮሐ4፤3ዮሐ3፡4
13፥7 ቍ8፡13
13፥8 ቍ1፡2
13፥9 ቍ12፤ 1ቆሮ 8፥2
13፥10 ፊል3፥12
13፥11 መዝ131፥2
13፥12 ዘፍ32፥30፤ ኢዮ19፥26፤26፥14፤ 36፥26፤1ቆሮ8፥3፤ ገላ4፥9፤1ዮሐ3፥2
13፥13 ማቴ22፥37-40፤ሮሜ5፥2-5፤ 1ቆሮ16፥14፤ገላ5፥5፡ 6፤ኤፌ4፥2-5፤ቈላ 1፥4፡5፤1ተሰ1፥3፤ 5፥8፤ዕብ6፥10-12፤ 1ዮሐ4፥7-12፡16
14፥1 ቍ39፤ 1ቆሮ12፥1፡31፤ 16፥ 14፤ኤፌ4፥11
14፥2 ቍ6-11፡16፤ ማር16፥17፤1ቆሮ13፥2
14፥3 ቍ4፡5፡12፡ 17፡26፡31፤ሮሜ 14፥19
14፥4 ቍ3፤ ማር16፥17፤1ቆሮ 13፥2
14፥5 ቍ3፤ ዘኍ11፥29

ለእሳት ብዳርግ፣[መ] ፍቅር ግን ከሌለኝ
ምንም አይጠቅመኝም::
[4]ፍቅር ታጋሽ ነው፤ ደግሞም ቸር ነው::
ፍቅር አይመቀኝም፤ አይመካም፤ አይታበይም፤
[5]ተገቢ ያልሆነ ነገር አያደርግም፤ ራስ
ወዳድ አይደለም፤ አይበሳጭም፣ በደልን
አይቈጥርም:: [6]ፍቅር ከእውነት ጋር እንጂ
በዐመፅ ደስ አይሰኝም:: [7]ፍቅር ሁልጊዜ
ይታገሣል፤ ሁልጊዜ ያምናል፤ ሁልጊዜ ተስፋ
ያደርጋል፤ ሁልጊዜ ጸንቶ ይቆማል::
[8]ፍቅር ከቶ አይወድቅም፤ ነገር ግን ትን
ቢት ቢሆን ይሻራል፤ ልሳንም ቢሆን ይቀ
ራል፤ ዕውቀትም ቢሆን ይሻራል:: [9]ምክንያ
ቱም የምናውቀው በከፊል ነው፤ ትንቢት
የምንናገረውም በከፊል ነው:: [10]ነገር ግን
ፍጹም የሆነው ሲመጣ በከፊል የነበረው
ይሻራል:: [11]ልጅ ሳለሁ እንደ ልጅ እናገር
ነበር፤ እንደ ልጅ አስብ ነበር፤ እንደ ልጅም
አሰላ ነበር:: ከጐለመስሁ በኋላ ግን
የልጅነትን ነገር እርግፍ አድርጌ ትቻ
ለሁ:: [12]አሁን የምናየው በመስተዋት ውስጥ
እንደሚታይ በድንግዝግዝ ነው፤ በዚያን ጊዜ
ግን ፊት ለፊት እናያለን:: አሁን የማውቀው
በከፊል ነው፤ በዚያን ጊዜ እኔ ራሴ ሙሉ
በሙሉ የታወቅሁትን ያህል ዐውቃለሁ::
[13]እንግዲህ እምነት፣ ተስፋ፣ ፍቅር እነዚህ
ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፤ ከእነዚህም የሚበ
ልጠው ፍቅር ነው::

### የትንቢትና የልሳን ስጦታዎች

14 ፍቅርን ተከታተሉ፤ መንፈሳዊ ስጦ
ታዎችን፣ በተለይም ትንቢት የመና
ገርን ስጦታ በብርቱ ፈልጉ:: [2]በልሳን[ሠ]
የሚናገር ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይ
ናገርምና፤ ምስጢር የሆነውን በመንፈስ[ረ]
ስለሚናገር የሚረዳው የለም:: [3]ትንቢትን
የሚናገር ግን ለማነጽ፣ ለማበረታታትና ለማ
ጽናናት ለሰው ይናገራል:: [4]በልሳን የሚናገር
ራሱን ያንጻል፤ ትንቢትን የሚናገር ግን
ቤተ ክርስቲያንን ያንጻል:: [5]ሁላችሁም
በልሳን[ሰ] ብትናገሩ እወዳለሁ፤ ከዚህ ይልቅ
ግን ትንቢትን ብትናገሩ እወዳለሁ:: ቤተ
ክርስቲያን እንድትታነጽ በልሳን የሚናገር
ሰው የተናገረውን ካልተረጐመ፣ በልሳን
ከሚናገር ይልቅ ትንቢትን የሚናገር ይበል

[ሀ]30 ወይም፣ *በሌሎች ቋንቋዎች*
[ለ]31 ወይም፣ *እናንተ ግን ከሁሉ የሚበልጠውን ስጦታ በብርቱ እየፈለጋችሁ::*
[ሐ]1 ወይም *ቋንቋዎች*
[መ]3 አንዳንድ የጥንት ቅጆች፣ *እንድታበይ ሰውነቴንም አሳልፌ ብሰጥ* ይላሉ
[ሠ]2 ወይም *በሌላ ቋንቋ*፤ እንዲሁም ቍ 4፡13፡14፡19፡26 እና 27 *ይመ*
[ረ]2 ወይም *በመንፈሱ*
[ሰ]5 ወይም *በሌሎች ቋነቋዎች*፤ እንዲሁም ቍ6፡18፡22፡23 እና 39 *ይመ*

ጣል።
6እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ወደ እናንተ
በምመጣበት ጊዜ፣ በመግለጥ ወይም በዕወ
ቀት ወይም በትንቢት ወይም በትምህርት
ካልነገርኋችሁ በልሳን ብናገር ምን እጠ
ቅማችኋለሁ? 7እንደ ዋሽንትና እንደ በገና
ያሉ ሕይወት የሌላቸው ነገሮች እንኳ የድም
ፃቸው ቃና ልዩነት ከሌለው ዜማቸውን እን
ዴት ማወቅ ይቻላል? 8ደግሞም መለከት
ትክክል ያልሆነ የጥሪ ድምፅ ካሰማ፣ ለጦር
ነት ማን ይዘጋጃል? 9እናንተም እንደዚሁ
ናችሁ፤ ከአንደበታችሁ ትርጒም ያለው
ቃል ካልወጣ፣ የምትናገሩትን ማን ሊያስ
ተውለው ይችላል? ለነፋስ የምትናገሩ ትሆ
ናላችሁ። 10በዓለም ላይ ብዙ ዐይነት ቋንቋ
ዎች አሉ፤ ትርጒም የሌለውም ቋንቋ
የለም። 11እንግዲህ አንድ ሰው የሚናገረውን
ቋንቋ ትርጒሙን ካላወቅሁ፣ ለሚናገረው
እንግዳ እሆንበታለሁ፤ እርሱም ለእኔ እን
ግዳ ይሆንብኛል። 12እናንተም እንደዚሁ
ናችሁ፤ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለማግኘት የም
ትሹ በመሆናችሁ፣ ቤተ ክርስቲያን የም
ትታነጽበትን ስጦታዎች ለማግኘት ይበልጥ
ፈልጉ።
13ስለዚህ በልሳን የሚናገር ሰው የሚናገ
ረውን መተርጐም እንዲችል ይጸልይ። 14በል
ሳን በምጸልይበት ጊዜ መንፈሴ ይጸልያል፤
አእምሮዬ ግን ያለ ፍሬ ነው። 15ታዲያ፣ ምን
ማድረግ አለብኝ? በመንፈስ እጸልያለሁ፤ በአ
እምሮም ደግሞ እጸልያለሁ፤ በመንፈስ እዘ
ምራለሁ፤ በአእምሮም ደግሞ እዘምራለሁ።
16እንዲህማ ካልሆነ እግዚአብሔርን በመንፈስ
በምታመሰግንበት ጊዜ፣ ለነገሩ እንግዳ የሆነ
ሰው[የ] አንተ የምትናገረውን ካልተረዳ፣ እን
ዴት አድርጎ ለምስጋናህ፣ "አሜን" ሊል ይች
ላል? 17አንተ በሚገባ ታመሰግን ይሆናል፤
ሌላው ሰው ግን አይታነጽበትም።
18ከሁላችሁ የበለጠ በልሳን ስለምናገር
እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። 19ነገር ግን
በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሌሎችን ለማስተ
ማር፣ ዐሥር ሺህ ቃላት በልሳን ከምናገር
ይልቅ፣ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ብናገር
ይሻላል።
20ወንድሞች ሆይ፤ በአስተሳሰባችሁ ሕፃ
ናት አትሁኑ፤ ለክፉ ነገር ሕፃናት ሁኑ፤ በአ
ስተሳሰባችሁ ግን ጐልማሶች ሁኑ። 21በሕ
ግም እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፤

"ቋንቋቸው እንግዳ በሆነ ሰዎች፣
በባዕዳንም አንደበት፣
ለዚህ ሕዝብ እናገራለሁ፤
ይህም ሆኖ አይሰሙኝም"
ይላል ጌታ ።

22ስለዚህ በልሳን መናገር ለማያምኑ የሚ
ሆን ምልክት እንጂ ለሚያምኑ
አይደለም፤ ትንቢት ግን ለሚያምኑ እንጂ
ለማያምኑ አይደለም። 23እንግዲህ የቤተ
ክርስቲያን ምእመናን በአንድነት
በተሰበሰቡበት፣ ሁሉም በልሳን በመናገር ላይ
ሳሉ፣ እንግዶች[ደ] ወይም የማያምኑ ሰዎች ወደ
ጉባኤው ቢገቡ፣ አብደ ዋል አይሉምን?
24ነገር ግን ሁሉም ትን ቢት በመናገር
ላይ ሳሉ፣ እንግዳ[ጀ] ወይም የማ ያምን ሰው ቢ
ገባ፣ በሁሉ ይወቀሳል፤ በሁሉ
ይመረመራል፤ 25በልቡም የተሰወረው ነገር
ይገለጣል፤ እንዲሁም፣ "እግዚአብሔር
በእርግጥ በመካከላችሁ ነው" በማለት በግንባሩ
ተደፍቶ ለእግዚአብሔር ይሰግዳል።

### ሥርዐት ያለው አምልኮ

26ወንድሞች ሆይ፤ እንግዲህ ምን እንበል?
በምትሰበሰቡበት ጊዜ እያንዳንዱ መዝሙር
አለው፤ ትምህርት አለው፤ መግለጥ አለው፤
በልሳን መናገር አለው፤ መተርጐም አለው።
ይህ ሁሉ ግን ለማነጽ ይሁን። 27በልሳን የሚ
ናገር ቢኖር፣ ሁለት ወይም ቢበዛ ሦስት በየተ
ራ ይናገሩ፤ ሌላው ደግሞ ይተርጒም፤
28የሚተ ረጒም ሰው ከሌለ ግን በጉባኤ
መካከል ዝም ይበልና፤ ለራሱና ለእግዚ
አብሔር ይናገር።
29ሁለት ወይም ሦስት ነቢያት ይናገሩ፤
ሌሎቹ ደግሞ የተነገረውን በጥንቃቄ ይመ
ዝኑ። 30ከተቀመጡትም መካከል አንድ ሰው
አንድ ነገር ቢገለጥለት፣ የመጀመሪያው
ተናጋሪ ዝም ይበል። 31እያንዳንዳችሁ እንድት
ማሩና እያንዳንዳችሁ እንድትበረታቱ፣ ሁላ
ችሁ በየተራ ትንቢት መናገር ትችላላችሁ።
32የነቢያት መናፍስት ለነቢያት ይታዘዛሉ፤
33እግዚአብሔር የሰላም አምላክ እንጂ
የሁከት አምላክ አይደለም።
በቅዱሳን አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ
እንዲሁ ነው፣ 34ሴቶች በጉባኤ ዝም ይበሉ፤
ሕግም እንደሚለው እንዲታዘዙ እንጂ እንዲ
ናገሩ አልተፈቀደላቸውም፤ 35ሴቶች ለማወቅ
የሚፈልጉት አንዳንድ ነገር ካለ፣ ባሎቻቸ
ውን በቤት ይጠይቁ፤ ምክንያቱም ሴት በጉ
ባኤ መካከል ብትናገር የሚያሳፍር ነው።
36የእግዚአብሔር ቃል የወጣው ከእናንተ
ነውን? ወይስ የደረሰው ወደ እናንተ ብቻ
ነውን? 37ማንም ነቢይ ነኝ የሚል ወይም
መንፈሳዊ ስጦታ አለኝ የሚል ቢኖር፣ ይህ
የጻፍሁላችሁ የጌታ ትእዛዝ መሆኑን ይወቅ፤
38ይህን የማያውቅ ቢሆን ግን እርሱም አይ
ታወቅ።[ገ]

[የ]16 ወይም *ከሚጠይቁት መካከል*
[ደ]23 ወይም *አንዳንድ የሚጠየቁ*
[ጀ]24 ወይም *የሚጠይቅ*
[ገ]38 አንዳንድ ቅጆች፣ *ይህን ለማወቅ የማይፈልግ ቢሆን እርሱም አይታወቅ* ይላሉ።

14፥6 ቍ26፤ ሮሜ 6፥17፤2ቆሮ8፥7፤ ኤፌ1፥17
14፥8 ዘኍ10፥9፤ ኤር4፥19
14፥11 ዘፍ11፥7
14፥12 ቍ3፤ 1ቆሮ12፥1
14፥13 ቍ5
14፥14 ቍ2
14፥15 ቍ2፡14፤ ኤፌ5፥19
14፥16 ዘዳ 27፥15-26፤1ዜና 16፥36፤ ነህ8፥6፤ መዝ106፥48፤ማቴ 14፥19፤1ቆሮ11፥24፤ ራእ5፥14፤7፥12
14፥17 ቍ3
14፥19 ቍ6
14፥20 ኤር4፥22፤ ማቴ10፥16፤ ሮሜ16፥19፤ 1ቆሮ3፥11፤ኤፌ4፥14፤ ዕብ5፥12፡13፤ 1ጴጥ2፥2
14፥21 ቍ34፤ ዘዳ28፥49፤ ኢሳ28፥11፡ 12፤ዮሐ10፥34
14፥22 ቍ1
14፥23 ሐሥ2፥13
14፥25 ኢሳ45፥14፤ ዘካ8፥23፤ሮሜ2፥16
14፥26 ቍ2፡6፤ ሮሜ7፥1፤14፥19፤ 1ቆሮ12፥7-10፤ ኤፌ5፥19
14፥29 ቍ32፡37፤ 1ቆሮ12፥10፤13፥2
14፥32 1ዮሐ4፥1
14፥33 ቍ40፤ ሐሥ9፥13፤ ሮሜ15፥33፤ 1ቆሮ7፥17፤10፥32
14፥34 ቍ21፤ ዘፍ3፥16፤1ቆሮ11፥5፡13፤ኤፌ5፥22፤ 1ጢሞ2፥11፡12
14፥36 ዕብ12
14፥37 ሐሥ11፥27፤ 1ቆሮ13፥2፤2፥15፤ 12፥1፤2ቆሮ10፥7፤ 1ዮሐ4፥6

39ስለዚህ፣ ወንድሞች ሆይ፤ ትንቢት ለመና
ገር በብርቱ ፈልጉ፤ በልሳን መናገርንም
አትከልክሉ፤ 40ነገር ግን ሁሉም በአግባ
ብና በሥርዐት ይሁን።

## የክርስቶስ ትንሣኤ

15 አሁንም፣ ወንድሞች ሆይ፤ የሰበክሁ
ላችሁንና የተቀበላችሁትን ደግሞም
ጸንታችሁ የቆማችሁበትን ወንጌል ላሳስ
ባችሁ እወዳለሁ፤ 2የሰበክሁላችሁን ቃል
አጥብቃችሁ ብትይዙ፣ በዚህ ወንጌል ትድ
ናላችሁ፤ አለዚያ ያመናችሁት በከንቱ ነው።
3እኔ የተቀበልሁትንና ከሁሉ በላይ የሆ
ነውን[ጠ] ለእናንተ አስተላልፌአለሁ፤ ቅዱሳት
መጻሕፍት እንደሚሉት ክርስቶስ ስለ ኀጢ
አታችን ሞተ፤ 4ተቀበረ፤ በቅዱሳት መጻሕ
ፍት እንደ ተጻፈውም በሦስተኛው ቀን
ተነሣ፤ 5ከዚያም ለኬፋ[ጨ] ታየ፤ ቀጥሎም ለዐ
ሥራ ሁለቱ ታየ፤ 6ከዚያም በኋላ ከአምስት
መቶ በላይ ለሚሆኑ ወንድሞች በአንድ ጊዜ
ታየ፤ ከእነዚህም አብዛኛዎቹ በሕይወት
አሉ፤ አንዳንዶቹ ግን አንቀላፍተዋል። 7ከዚ
ያም ለያዕቆብ ታየ፤ በኋላም ለሐዋርያት
በሙሉ ታየ፤ 8 ከሁሉም በኋላ እንደ ጭንጋፍ
ለምቈጠር ለእኔ ደግሞ ታየ።
9እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ፣ ሐዋርያ
ተብዬ ልጠራ እንኳ የማይገባኝ ነኝ፤ ምክን
ያቱም የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን አሳድ
ጃለሁ፤ 10ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ አሁን
የሆንሁትን ሆኛለሁ፤ ለእኔም የተሰጠኝ ጸጋ
ከንቱ አልሆነም፤ እንዲያውም ከሁሉም በላይ
በትጋት ሠርቻለሁ፤ ዳሩ ግን እኔ ሳልሆን
ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው።
11እንግዲህ እኔም ሆንሁ እነርሱ የምንሰ
ብከው ይህንኑ ነው፤ እናንተም ያመናችሁት
ይህንኑ ነው።

## የሙታን ትንሣኤ

12ክርስቶስ ከሙታን እንደ ተነሣ የሚሰ
በክ ከሆነ፣ ከእናንተ አንዳንዶቹ እንዴት
የሙታን ትንሣኤ የለም ይላሉ? 13የሙታን
ትንሣኤ ከሌለማ ክርስቶስም አልተነሣም
ማለት ነዋ!። 14ክርስቶስም ካልተነሣ ስብከ
ታችን ዋጋ ቢስ ነው፤ እምነታችሁም ከንቱ
ነው። 15ከዚህም በላይ፣ እግዚአብሔር ክርስ
ቶስን ከሞት አስነሥቶታል ብለን በመመስ
ከራችን፣ ሐሰተኞች የእግዚአብሔር ምስክሮች
ሆነን ተገኝተናል፤ ሙታን የማይነሡ ከሆነ፣
ክርስቶስንም አላስነሣውም ማለት ነው፤
16ምክንያቱም ሙታን ካልተነሡ፣ ክርስቶስም
አልተነሣም። 17ክርስቶስም ካልተነሣ እም
ነታችሁ ከንቱ ነው፤ እናንተም እስከ አሁን
ድረስ ከኀጢአታችሁ አላችሁ ማለት ነው።
18እንዲህም ከሆነ፣ በክርስቶስ ያንቀላፉት ጠፍ
ተዋል ማለት ነው። 19ክርስቶስን ተስፋ
ያደረግነው ለዚህች ሕይወት ብቻ ከሆነ፣
ከሰው ሁሉ ይልቅ የምናሳዝን ነን።
20ነገር ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት ሁሉ በኵ
ራት ሆኖ በእርግጥ ከሙታን ተነሥቶአል።
21ሞት በአንድ ሰው በኩል እንደ መጣ፣
የሙታንም ትንሣኤ በአንድ ሰው በኩል
ሆኖአልና። 22ሰዎች ሁሉ በአዳም እንደሚ
ሞቱ፣ እንደዚሁም ሰዎች ሁሉ በክርስቶስ
ሕያዋን ይሆናሉ፤ 23ነገር ግን እያንዳንዱ
በራሱ ተራ ይሆናል፤ መጀመሪያ በኵራት
የሆነው ክርስቶስ፣ ከዚያም በኋላ እርሱ
ሲመጣ የክርስቶስ የሆኑት። 24ከዚያም
ግዛትን፣ ሥልጣንና ኀይልን ሁሉ ከደመሰሰ
በኋላ መንግሥትን ለእግዚአብሔር አብ ሲያስ
ረክብ፣ ያን ጊዜ ፍጻሜ ይሆናል። 25ጠላቶቹን
ሁሉ ከእግሩ ሥር እስከሚያደርግ ድረስ
ሊነግሥ ይገባዋልና። 26የሚደመሰሰውም
የመጨረሻው ጠላት ሞት ነው፤ 27“ሁሉን ነገር
ከእግሩ ሥር አስገዝቶለታል ተብሎአ
ልና፤ ነገር ግን፣ ሁሉን ነገር አስገዛለት ሲል፣
ሁሉ ነገር በክርስቶስ ሥር እንዲገዛ ያደ
ረገውን እግዚአብሔርን እንደማይጨምር ግል
ጽ
ነው። 28ሁሉ ከተገዛለት በኋላ እግዚአብሔር
ሁሉ በሁሉ እንዲሆን ወልድ ራሱ ደግሞ
ሁሉን ላስገዛለት ለእርሱ ይገዛል።
29ትንሣኤ ከሌለማ ለሞቱ ሰዎች ብለው
የሚጠመቁት ምን እያደረጉ ነው? ሙታን
ከቶ የማይነሡ ከሆነ፣ ሰዎች ለእነርሱ ብለው
ለምን ይጠመቃሉ? 30እኛስ ብንሆን ዘወትር
ለአደጋ የምንጋለጠው ለምንድን ነው? 31ወንድ
ሞች ሆይ፤ እኔ በየቀኑ እሞታለሁ፤ ይህንንም
በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ በእናንተ ላይ
ባለኝ ትምክህት አረጋግጣለሁ። 32በኤፌሶን
ከአራዊት ጋር የታገልሁት ለሰው አስተያየት
ብቻ ከሆነ ትርፌ ምንድን ነው? ሙታን
የማይነሡ ከሆነ፤

“ነገ ስለምንሞት፣
እንብላ፣ እንጠጣ” እንደሚሉት መሆናችን
ነው።

33አትሳቱ፤ “መጥፎ ጓደኝነት መልካሙን
ጠባይ ያበላሻል።” 34ወደ ሰከነ ልቦናችሁ
ተመለሱ፤ ኀጢአትንም አትሥሩ፤ እግዚአብሔርን
የማያውቁ አሉና ይህንንም የምለው ላሳፍ
ራችሁ ነው።

14፥39 ቍ1፤ 1ቆሮ12፥31፤ኤፌ4፥11
14፥40 ቍ33፤ ቈላ2፥5
15፥1 ኢሳ40፥9፤ ሮሜ2፥16፤1ቆሮ3፥6፤ ገላ1፥8
15፥2 ሮሜ1፥16፤ 11፥22
15፥3 ኢሳ53፥5፤ ማቴ26፥24፤ ሉቃ24፥27፤24፥44፤ ዮሐ1፥29፤ሐሥ17፥2፤ 26፥ 22፡23፤ 1ቆሮ11፥2፤ገላ1፥4፡12፤ 1ጴጥ2፥24
15፥4 ማቴ16፥21፤ 27፥59፡60፤ዮሐ2፥21፡22 ፤ሐሥ2፥24፡25፡ 30፡31
15፥5 ማር16፥14፤ ሉቃ24፥34፡36-43
15፥6 ቍ18፡20፤ ማቴ 9፥24
15፥7 ሉቃ24፥33፡ 36፡37፤ሐሥ1፥3፡4፤ 15፥13
15፥8 ሐሥ9፥3-6፡ 17፤1ቆሮ9፥1፤ገላ1፥16
15፥9 ሐሥ8፥3፤ 1ቆሮ10፥32፤ 2ቆሮ12፥11፤ ኤፌ3፥8፤1ጢሞ1፥15
15፥10 ሮሜ3፥24፤ 12፥3፤2ቆሮ11፥23፤ ፊል2፥13፤ቈላ1፥29
15፥11 ገላ2፥6
15፥12 ቍ4፤ዮሐ 11፥24፤ሐሥ17፥32፤ 23፥8፤2ጢሞ2፥18
15፥14 1ተሰ4፥14
15፥15 ሐሥ2፥24
15፥17 ሮሜ4፥25
15፥18 ቍ6፡20፤ ማቴ9፥24
15፥19 1ቆሮ4፥9
15፥20 ቍ6፡18፡ 23፤ማቴ9፥24፤ሐሥ 26፥23፤1ጴጥ1፥3
15፥21 ቍ12፤ ሮሜ5፥12
15፥22 ሮሜ5፥14-18፤1ቆሮ6፥14
15፥23 ቍ20፡52፤ 1ቆሮ3፥23፤1ተሰ2፥19
15፥24 ዳን2፥44፤ 7፥14፡27፤ሮሜ8፥38፤ 2ጴጥ1፥11
15፥25 ቍ27፤ኢሳ 9፥7፤52፥7፤ማቴ 22፥44
15፥26 2ጢሞ1፥10፤ ራእ20፥14፤21፥4
15፥27 ቍ25፤መዝ 8፥6፤ማቴ22፥44፤ 28፥18
15፥28 1ቆሮ3፥23፤ ፊል3፥21

15፥30 2ቆሮ11፥26 15፥31 ሮሜ8፥36 15፥32 ኢሳ22፥13፤ ሉቃ12፥19፤ሐሥ 18፥19፤2ቆሮ1፥8፤15፥33 ምሳ22፥24፡25፤1ቆሮ 6፥9፤15፥34 1ቆሮ4፥14፤ገላ4፥8፤

[ጠ]3 ወይም፤ *ከሁሉ በፊት*
[ጨ]5 *ጴጥሮስን* ማለት ነው

## የትንሣኤ አካል

35ነገር ግን፣ “ሙታን እንዴት ይነሣሉ?
የሚወጡትስ በምን ዐይነት አካል ነው?”
የሚል ሰው ሊኖር ይችላል:: 36አንተ ሞኝ!
የምትዘራው ካልሞተ ሕይወት አያገኝም::
37የምትዘራውም የስንዴ ወይም የሌላ ዐይ
ነት ዘር ቅንጣት ብቻ እንጂ ወደ ፊት የም
ታገኘውን አካል አይደለም:: 38እግዚአብሔር
ግን እንደ ፈቀደ አካልን ይሰጠዋል፤ ለእያ
ንዳንዱም የዘር ዐይነት የራሱን አካል ይሰጠ
ዋል:: 39ሥጋ ሁሉ አንድ አይደለም፤ የሰው
ሥጋ አንድ ነው፤ የእንስሳት ሥጋ ሌላ ነው፤
የዓሣ ሥጋ ሌላ ዐይነት ነው:: 40እንዲሁም
ሰማያውያን አካላት አሉ፤ ምድራውያን አካ
ላት አሉ፤ ነገር ግን የሰማያዊ አካላት ክብር
አንድ ነው፤ የምድራዊም አካላት ክብር
ሌላ ነው:: 41የፀሓይ ክብር አንድ ዐይነት
ነው፤ የጨረቃ ክብር ሌላ ነው፤ የከዋክብት
ደግሞ ሌላ ነው፤ የአንዱም ኮከብ ክብር
ከሌላው ኮከብ ክብር ይለያል::
42የሙታን ትንሣኤም እንደዚሁ ነው፤
የሚበሰብስ አካል ይዘራል፤ የማይበሰብስ አካል
ሆኖ ይነሣል፤ 43በውርደት ይዘራል፤ በክብር
ይነሣል፤ በድካም ይዘራል፣ በኀይል ይነሣል፤
44ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፣ መንፈሳዊ አካል
ይነሣል::

ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል
ደግሞ አለ:: 45ስለዚህ፣ “የመጀመሪያው ሰው
አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ” ተብሎ ተጽፎአል፤
የኋለኛው አዳም ግን ሕይወትን የሚሰጥ መን
ፈስ ሆነ:: 46ነገር ግን በመጀመሪያ የመጣው
መንፈሳዊው ሳይሆን ፍጥረታዊው ነው፤
ከዚያም በኋላ መንፈሳዊው መጣ:: 47የመጀ
መሪያው ሰው ከምድር የተገኘ ምድራዊ
ነው፤ የኋለኛው ግን ከሰማይ ነው:: 48ከም
ድር የሆኑት እንደ ምድራዊው ናቸው፤
ከሰማይ የሆኑትም እንደ ሰማያዊው ናቸው::
49የምድራዊውን ሰው መልክ እንደ ለበስን፣
የሰማያዊውን ሰው መልክ ደግሞ እንለብሳ
ለን::[ጸ]

50ወንድሞች ሆይ፤ ይህን እነግራችኋለሁ፤
ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወ
ርሱም፤ የሚጠፋውም የማይጠፋውን አይወ
ርስም:: 51እነሆ፤ አንድ ምስጢር እነግራ
ችኋለሁ፤ ሁላችን አናንቀላፋም፤ ነገር ግን
ሁላችንም እንለወጣለን፤ 52ይህም የሚሆነው
የመጨረሻው መለከት ሲነፋ ድንገት በቅ
ጽበተ ዐይን ነው:: መለከት ይነፋል፤ ሙታን የ
ማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ፤ እኛም
እንለወጣለን:: 53የሚጠፋው የማይጠ
ፋውን፣ የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ
ይገባዋልና:: 54የሚጠፋው የማይጠፋውን፣
የሚሞተውም የማይሞተውን በሚለብስበት
ጊዜ፣ “ሞት በድል ተዋጠ” ተብሎ የተጻፈው
ቃል ይፈጸማል::
55እንዲሁም፣ “ሞት ሆይ፤ ድል መንሣትህ
የት አለ?
ሞት ሆይ፤ መንደፊያህስ የት አለ?”::

56የሞት መንደፊያ ኀጢአት ነው፤ የኀጢ
አትም ኀይል ሕግ ነው:: 57ነገር ግን
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድልን
ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን::
58ስለዚህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤
ጸንታችሁ ቁሙ፤ በምንም ነገር አትናወጡ::
ለጌታ ሥራ ዘወትር የምትተጉ ሁኑ፤ ምክንያ
ቱም ለጌታ የምትደክሙት በከንቱ
እንዳል ሆነ ታውቃላችሁ::

## ለቅዱሳን የተደረገ የገንዘብ መዋጮ

16 አሁን ደግሞ ለቅዱሳን ስለሚደረገው
ገንዘብ ማሰባሰብ ለገላትያ አብያተ
ክርስቲያናት በሰጠሁት ትእዛዝ መሠረት
አድርጉ:: 2ገንዘብ ማሰባሰብ የሚደረገው
እኔ በምመጣበት ጊዜ እንዳይሆን፣ ከእናንተ
እያንዳንዱ እንደ ገቢው መጠን በሳምንቱ
መጀመሪያ ቀን እየለየ ያስቀምጥ:: 3በምመ
ጣበት ጊዜ እናንተ ለመረጣችኋቸው ሰዎች
የመሸኛ ደብዳቤ ሰጥቼ ስጦታችሁን ወደ
ኢየሩሳሌም እንዲያደርሱ እልካቸዋለሁ::
4የእኔ መሄድ የሚያስፈልግ ከሆነ አብረውኝ
ይሄዳሉ::

## የሐዋርያው ዕቅድ

5በመቄዶንያ በኩል ማለፌ ስለማይቀር፣
መቄዶንያ ከደረስሁ በኋላ ወደ እናንተ
እመጣለሁ:: 6ወደምሄድበት ወደ ማናቸውም
ስፍራ በጕዞዬ እንድትረዱኝ፣ እናንተ ዘንድ
እቆይ ይሆናል፤ ምናልባትም ክረምቱን ከእና
ንተ ጋር እሰነብት ይሆናል:: 7አሁን እግረ
መንገዴን ሳልፍ ልጐበኛችሁ አልፈልግም፤
ጌታ ቢፈቅድ ረዘም ላለ ጊዜ እናንተ ዘንድ
ለመሰንበት ተስፋ አደርጋለሁ:: 8ነገር ግን
እስከ በዓለ ኀምሳ በኤፌሶን እቆያለሁ፤
9ምክንያ
ቱም ታላቅ የሥራ በር ተከፍቶልኛል፤ ብዙ
ተቃዋሚዎችም አሉብኝ::
10ጢሞቴዎስ ወደ እናንተ ከመጣ፣ አብሮ
አችሁ ያለ ፍርሃት እንዲቀመጥ አድርጉ፤
እርሱም እንደ እኔ የጌታን ሥራ የሚሠራ
ነውና:: 11ስለዚህ ማንም አይናቀው፤ በሰላም
ወደ እኔ እንዲመለስ እርዱት፤ መመለሱንም
ከወንድሞች ጋር እየጠበቅን ነው::
12ስለ ወንድማችን ስለ አጵሎስ ደግሞ፣
ከወንድሞች ጋር ወደ እናንተ እንዲመጣ
አጥብቄ ለምኜው ነበር፤ እርሱ ግን አሁን
ለመምጣት አልፈለገም፤ ሲመቸው ግን ይመ

15፥35 ሕዝ37፥3፤ ሮሜ9፥19
15፥36 ሉቃ11፥40፤ 12፥20፤ዮሐ12፥24
15፥38 ዘፍ1፥11
15፥41 መዝ8፥1፡ 3፤19፥4-6
15፥42 ቍ12፡ 50፡53፡54፤ዳን12፥3፤ ማቴ13፥43
15፥43 ፊል3፥21፤ ቈላ3፥4
15፥44 ቍ50
15፥45 ዘፍ2፥7፤ ዮሐ5፥21፤6፥57፡58፤ሮሜ5፥14፤8፥2
15፥46 ቍ44
15፥47 ዘፍ2፥7፤ 3፥19፤መዝ90፥3፤ ዮሐ3፥13፡31
15፥48 ፊል3፥20፡21
15፥49 ዘፍ5፥3፤ ሮሜ8፥29
15፥50 ቍ42፡53፡ 54፤ማቴ25፥34፤ ኤፌ6፥12፤ዕብ2፥14
15፥51 ማቴ9፥24፤ 1ቆሮ13፥2፤14፥2፤ 2ቆሮ5፥4፤ፊል3፥21
15፥52 ማቴ24፥31፤ ዮሐ5፥25
15፥53 ቍ42፡50፡ 54፤2ቆሮ5፥2፡4
15፥54 ኢሳ25፥8፤ ዕብ2፥14፤ራእ20፥14
15፥55 ሆሴ13፥14
15፥56 ሮሜ4፥15፤ 5፥12
15፥57 2ቆሮ2፥14፤ ሮሜ8፥37፤ዕብ 2፥14፡15
15፥58 ኢሳ65፥23፤ 1ቆሮ16፥10
16፥1 ሐሥ9፥13፤ 16፥6፤24፥17
16፥2 ሐሥ20፥7፤ 2ቆሮ9፥4፡5
16፥3 2ቆሮ3፥1፤ 8፥18፡19
16፥5 ሐሥ16፥9፤ 1ቆሮ4፥19
16፥6 ሮሜ15፥24፤ ቲቶ3፥13
16፥7 ሐሥ18፥21
16፥8 ሐሥ2፥1፤ 18፥19
16፥9 ሐሥ14፥27
16፥10 ሐሥ16፥1፤ 1ቆሮ15፥58
16፥11 ሐሥ15፥33፤ 2ቆሮ1፥16፤1ጢሞ4፥12፤3ዮሐ6
16፥12 ሐሥ18፥24

[ጸ]49 አንዳንድ የጥንት ቅጆች እንልበስ ይላሉ::

ጣል።

13ንቁ፤ በእምነት ጽኑ፤ በርቱ፤ ጠንክሩ፤
14የምታደርጉትን ሁሉ በፍቅር አድርጉ።
15የእስጢፋኖስ ቤተ ሰዎች በአካይያ የመ
ጀመሪያዎቹ አማኞች እንደ ሆኑና ቅዱሳ
ንንም ለማገልገል ራሳቸውን እንደ ሰጡ ታው
ቃላችሁ። ወንድሞች ሆይ፤ ይህን እለምና
ችኋለሁ፤ 16እንደ እነርሱ ላሉትና ከእነርሱም
ጋር በአገልግሎት ለሚደክሙ ሁሉ ታዘዙ።
17በእስጢፋኖስ፣ በፈርዶናጥስና በአካይቆስ
መምጣት ደስ ብሎኛል፤ ምክንያቱም እናንተ
እዚህ ባለመኖራችሁ የጐደለኝን አሟልተዋል፤
18የእኔንም የእናንተንም መንፈስ አሳርፈ
ዋታልና። ስለዚህ እንደነዚህ ያሉት ሰዎች
መታወቅ ይገባቸዋል።

## የመሰናበቻ ቃል

19በእስያ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ሰላ
ምታ ያቀርቡላችኋል። አቂላና ጵርስቅላ[ጸ]፣
በቤታቸውም ያለችው ቤተ ክርስቲያን የከ
በረ ሰላምታ በጌታ ያቀርቡላችኋል። 20ወንድ
ሞች ሁሉ ሰላምታ ያቅርቡላችኋል። እርስ
በርሳችሁ በተቀደሰ አሳሳም ሰላምታ ተሰ
ጣጡ።
21ይህን ሰላምታ በገዛ እጄ የጻፍሁላችሁ
እኔ ጳውሎስ ነኝ።
22ጌታ ን የማይወድ ቢኖር የተረገመ ይሁን።
ጌታ ሆይ፤ ና![ፀ]
23የጌታ ኢየሱስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።
24ፍቅሬ በክርስቶስ ኢየሱስ ከሁላችሁ
ጋር ነው፤ አሜን።[ፈ]

16፥13 1ቆሮ1፥8፤ 2ቆሮ1፥21፤ገላ5፥1፤ ኤፌ6፥10፤ፊል1፥27፤ 1ተሰ3፥8፤ቲቶ1፥9
16፥14 1ቆሮ14፥1
16፥15 ሐሥ9፥13፤ 18፥12፤24፥17፤ ሮሜ16፥5፤1ቆሮ1፥16
16፥16 1ተሰ5፥12፤ ዕብ13፥17
16፥17 2ቆሮ11፥9፤ ፊል2፥30
16፥18 ሮሜ15፥32፤ ፊል2፥29፤ፊሞ7
16፥19 ሐሥ2፥9፤ 18፥2፤ሮሜ16፥5
16፥20 ሮሜ16፥16
16፥21 ገላ6፥11፤ ቈላ4፥18፤2ተሰ3፥17፤ ፊሞ19
16፥22 ሮሜ9፥3፤ ኤፌ6፥24፤ራእ22፥20
16፥23 ሮሜ16፥20

[ጸ]19 በግሪኩ *ጵርስቃ* የ *ጵርስቅላ* ሌላው አጠራር ነው
[ፀ]22 በአራማይክ *ጌታ ሆይ፤ ና* ማለት *ማራናታ* ማለት ነው።
[ፈ]24 አንዳንድ ቅጆች *አሜን* የሚለው የላቸውም።

# የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
# ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች –ሁለተኛ

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ የክርስቶስ ኢ
የሱስ
ሐዋርያ ከሆነው ከጳውሎስ፣ ከወንድ
ማችንም ከጢሞቴዎስ፤

በቆሮንቶስ ላለችው ለእግዚአብሔር ቤተ ክር
ስቲያን እንዲሁም በመላው አካይያ ለሚ
ኖሩ ቅዱሳን ሁሉ፤

2ከአባታችን ከእግዚአብሔር፣ ከጌታም
ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ
ይሁን።

## የመጽናናት አምላክ

3የርኅራኄ አባት፣ የመጽናናትም ሁሉ አም
ላክ የሆነው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ
አምላክና አባት ይባረክ። 4እኛ ራሳችን
ከእግዚአብሔር በተቀበልነው መጽናናት፣
በመከራ ያሉትን ማጽናናት እንድንችል፣
እርሱ በመ ከራችን ሁሉ ያጽናናል። 5የክጠ
ርስቶስ ሥቃይ በእኛ ላይ የመብዛቱን
ያህል መጽናናታች ንም በክርስቶስ በኩል
ይበዛልናል። 6መከራ ብንቀበል ስለ እናንተ
መጽናናትና መዳን ነው። ብንጽናናም እኛ
የተቀበልነውን መከራ በመቀበል በትዕ
ግሥት እንድትጸኑ ስለ እናንተ መጽናናት
ነው። 7ስለ እናንተ ያለን ተስፋ ጽኑ ነው፤
ምክንያቱም በመከራችን እንደ
ተካፈላችሁ ሁሉ በመጽናናታችንም
እንደምትካፈሉ እናውቃለን።
8ወንድሞች ሆይ፤ በእስያ ስለ ደረሰብን
መከራ እንድታውቁ እንወዳለን፤ በሕይ
ወት ለመኖር እንኳ ተስፋ እስከምንቈርጥ
ድረስ ከዐቅማችን በላይ የሆነ ጽኑ መከራ
ደርሶብን ነበር። 9በእርግጥም የሞት ፍርድ
እንደ ተፈረደብን ይሰማን ነበር፤ ይህም
የሆነው ሙታንን በሚያስነሣ በእግዚአብሔር
እንድንታመን እንጂ፣ በራሳችን እን
ዳንታመን ነው። 10እርሱ እንዲህ ካለው
የሞት አደጋ አድኖናል፤ ያድነናልም፤ ወደ
ፊትም ደግሞ እንደሚያድነን ተስፋችንን
በእርሱ ላይ ጥለናል። 11እናንተም በጸሎታ
ችሁ ደግፉን፤ በብዙዎች ጸሎት ስለ ተሰጠን
ስጦታ ብዙ ሰዎች ስለ እኛ[ሀ] ምስጋና ያቀር
ባሉ።

## ጳውሎስ ዕቅዱን ለወጠ

12እንግዲህ ትምክህታችን ይህ ነው፤ በዚህ
ዓለም በተለይም ከእናንተ ጋር ባለን ግን
ኙነት፣ ከእግዚአብሔር በሆነ ቅድስናና ቅን
ነት እንደኖርን ኅሊናችን ይመሰክራል፤
ይህም በሰው ጥበብ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር

1፥1 ሐ16፥1፤18፥1፥12፤1ቆሮ1፥1፤10፥32፤ኤፌ1፥1፤10፥32፤ኤፌ1፥1፤ቈላ1፥1፤2ጢሞ1፥1
1፥2 ሮሜ1፥7
1፥3 ኤፌ1፥3፤1ጴጥ1፥3
1፥4ኢሳ49፥13፤51፥12 ፤66፥13፤2ቆሮ7፥6፥7፥13
1፥5 ሮሜ8፥17፤2ቆሮ4፥10፤ገላ6፥17፤ፊል3፥10፤ቈላ1፥24፤1ጴጥ4፥13
1፥6 2ቆሮ4፥15
1፥7 ቊ5
1፥8 ሐሥ2፥9፤ሮሜ11፥25፤1ቆሮ15፥32
1፥9 ኤር17፥5፥7፤ዮሐ5፥21
1፥10 ሮሜ15፥31፤1ጢሞ4፥10
1፥11 ሮሜ15፥30፤2ቆሮ4፥15፤9፥11፤ፊል1፥19
1፥12 ሐሥ23፥1፤1ቆሮ1፥17፤2፥1፥4፥13 2ቆሮ2፥17፤1ተሰ2፥10
1፥14 1ቆሮ1፥8
1፥15 ሮሜ1፥11፥13፤15፥29፤1ቆሮ4፥19
1፥16 ሐሥ16፥9፤19፥21፤1ቆሮ16፥5-7፥11፤3ዮሐ6
1፥17 2ቆሮ10፥2፥3፤11፥18
1፥18 1ቆሮ1፥9
1፥19 ማቴ4፥3፤ሐሥ 15፥22፤16፥1፤ዕብ13፥8
1፥20 ሮሜ15፥8፥9፤1ቆሮ14፥16
1፥21 1ቆሮ16፥13፤1ዮሐ2፥20፥27
1፥22 ዘፍ38፥18፤ሕዝ9፥4፤ሐጌ2፥23፤2ቆሮ5፥5
1፥23 ሮሜ1፥9፤1ቆሮ4፥21፤2ቆሮ2፥1፥3፤13፥2፥10
1፥24 ሮሜ11፥20፤1ቆሮ15፥1፤1ጴጥ5፥3
2፥1 2ቆሮ1፥23
2፥2 2ቆሮ7፥8

ጸጋ ነው። 13ልታነቡት ወይም ልትረዱት
የማትችሉትን ነገር አንጽፍላችሁም፤ ሁሉ
ንም እንደምትረዱ ተስፋ አደርጋለሁ። 14እና
ንተ በእኛ እንደምትመኩ ሁሉ እኛም በእ
ናንተ እንደምንመካ አሁን የተረዳችሁን
በከፊል ቢሆንም፣ በጌታ ኢየሱስ ቀን
ሁሉን ትረዳላችሁ።
15በዚህ እርግጠኛ ስለ ነበርሁ በዕጥፍ
እንድትጠቀሙ፣ በመጀመሪያ ልጐበኛችሁ
ዐቅጄ ነበር። 16ወደ መቄዶንያ ስሄድ እግረ
መንገዴን ልጐበኛችሁና ከመቄዶንያም
በእናንተ በኩል ተመልሼ ወደ ይሁዳ
ስሄድ በጕዞዬ እንድትረዱኝ ዐቅጄ ነበር።
17ይህን ሳቅድ በሚገባ ሳላስብ ያደረግሁት
ይመስላችኋልን? ወይስ በዓለማዊ ልማድ
አንዴ፣ "አዎን፣ አዎን" ወዲያው
ደግሞ፣ "አይደለም፣ አይደለም" የምል
ይመስላችኋ ልን?
18እግዚአብሔር ታማኝ እንደ ሆነ ሁሉ፣
ለእናንተ የምንናገረው ቃላችን፣ "አዎን" እና
"አይደለም" ሊሆን አይችልም፤ 19ምክንያቱም
እኔም ሆንሁ ሲላስና[ለ] ጢሞቴዎስ፣ እኛ
የሰበክንላችሁ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ
ክርስቶስ "አዎን" እና "አይደለም" አልነበ
ረም፤ ነገር ግን በእርሱ ዘወትር፣ "አዎን"
ነው። 20በእግዚአብሔር የተሰጡ ተስፋዎች ሁሉ፣
"አዎን" የሚሆኑት በእርሱ ነውና፤ እኛም
በእርሱ አማካይነት ለእግዚአብሔር ክብር፣
"አሜን" የምንለው በዚህ ምክንያት ነው።
21እንግዲህ፣ እኛንም እናንተንም በክርስ
ቶስ ጸንተን እንድንቆም የሚያደርገን
እግዚአብሔር ነው፤ የቀባንም እርሱ ነው፤
22የእርሱ ለመሆናችን ማኅተሙን ያተመ
ብን ደግሞም ወደ ፊት ለምናገኘው ነገር
የመንፈሱን ዋስትና በልባችን ያኖረ እርሱ
ነው።
23ወደ ቆሮንቶስ ተመልሼ ያልመጣሁት
እንዳላሳዝናችሁ ብዬ ነው፤ ይህ እውነት
ካልሆነ እግዚአብሔር ይመስክርብኝ። 24
ጸንታ ችሁ የምትቆሙት በእምነት ስለ
ሆነ፣ ደስ እንዲላችሁ ከእናንተ ጋር እንሠ
ራለን እንጂ በእምነታችሁ ላይ ለመሠልጠን
አይደ ለም።

2 እንግዲህ ላሳዝናችሁ ስላልፈለግሁ
ወደ እናንተ ዳግመኛ ላለመምጣት
ወሰንሁ፤ 2እኔ ባሳዝናችሁም እንኳ፣ ከእና
ንተው ካሳዘንኋችሁ በቀር ደስ የሚያሰኘኝ

[ሀ]11 ብዙ ቅጆች *እናንተ* ይላሉ
[ለ]19 ግሪኩ *ሶልያኑስ* ይላል

ማን አለ? 3ባለፈው ጊዜ እንደዚያ የጻፍ
ሁላችሁ ወደ እናንተ ስመጣ ደስ ሊያ
ሰኙኝ የሚገባቸው ሰዎች እንዳያሳዝኑኝ
በማለት ነው፤ ምክንያቱም የእኔ ደስታ
የሁላችሁ ደስታ እንደሚሆን አምናለሁ።
4እንደዚያ ስጽፍላችሁ በትልቅ ሐዘንና
በልብ ጭንቀት፣ በብዙም እንባ ውስጥ ነበ
ርሁ፤ ይህንንም ያደረግሁት ለእናንተ ያለ
ኝን ጽኑ ፍቅር እንድታውቁ በማለት እንጂ፣
እናንተን ለማሳዘን አልነበረም።

## በደለኛን ይቅር ማለት

5ማንም ሰውን ቢያሳዝን፣ ነገር ማጋነን
አይሁንብኝና ያሳዘነው እኔን ብቻ ሳይሆን
በመጠኑም ቢሆን ሁላችሁንም ነው። 6እን
ደዚህ ያለው ሰው ብዙዎች የወሰኑበት ቅጣት
በቂው ነው። 7ደግሞም ከልክ በላይ አዝኖ
ተስፋ እንዳይቈርጥ፣ ይቅር ልትሉትና ልታ
ጽናኑት ይገባችኋል። 8ስለዚህ አሁንም
የምትወዱት መሆናችሁን እንድትገልጹ
ለት እለምናችኋለሁ። 9የጻፍሁላችሁም፣
የሚ ያጋጥማችሁን ፈተና መቋቋማችሁንና
በሁ ሉም ነገር ታዛዦች መሆናችሁን ለ
ማወቅ ነበር። 10እናንተ ይቅር የምትሉትን
ሰው እኔም ይቅር እለዋለሁ፤ በእርግጥ
ይቅር የምለው ነገር ካለ፣ በክርስቶስ ፊት
ይቅር የምለው ስለ እናንተ ስል ነው።
11ይህን ንም የምናደርገው ሰይጣን መግቢ
ያ ቀዳዳ እንዳያገኝ ነው፤ የእርሱን ዕቅድ
አንስተው ምና።

## የአዲስ ኪዳን አገልጋዮች

12የክርስቶስን ወንጌል ለመስበክ ወደ
ጢሮአዳ በሄድሁ ጊዜ፣ ጌታ በር ከፍቶልኝ
ነበር፤ 13ይሁን እንጂ ወንድሜን
ቲቶን እዚያ ስላላገኘሁት መንፈሴ
አላረፈም፤ ስለዚህ ተሰናብቻቸው ወደ
መቄዶንያ ሄድሁ።
14ነገር ግን በክርስቶስ ሁልጊዜ በድል
አድራጊነት እያዞረ ለሚመራን፣ የዕውቀቱ
ንም መዐዛ በእኛ አማካይነት በየስፍራው
ለሚገልጥ አምላክ ምስጋና ይሁን፤ 15ምክን
ያቱም በሚድኑትና በሚጠፉት መካከል
ለእ ግዚአብሔር የክርስቶስ መዐዛ ነን።
16ለሚጠፉት ወደ ሞት የሚወስድ የሞት
ሽታ፣ ለሚድኑት ግን ወደ ሕይወት
የሚወስድ የሕይወት ሽታ ነን፤ ታዲያ፣
ለዚህ ብቁ የሚሆን ማን ነው? 17እኛከ
ትርፍ ለማ ግኘት ብለን የእግዚአብሔርን
ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃቅጡት እንደ
ብዙዎቹ አይደ ለንም፤ ነገር ግን ከእግዚ
አብሔር እንደተላኩ ሰዎች በክርስቶስ ሆነን
በእግዚአብሔር ፊት በቅንነት እንናገራለን።

2፥3 ቀኁ4፡9፤2ቆሮ 7፥8፡12፡16፤8፥22፤12፥21፤ገላ5፥10፤2ተሰ3፥4፤ፊሞ21
2፥4 ቀኁ3፡9፤2ቆሮ 7፥8፡12
2፥5 1ቆሮ5፥1፡2
2፥6 1ቆሮ5፥4፡5፤2ቆሮ7፥11
2፥7 ገላ6፥1፤ኤፌ 4፥32፤ቈላ3፥13
2፥9 ቀኁ3፡4፤2ቆሮ 7፥8፡12፡15፤10፥6
2፥11 ማቴ4፥10፤ሉቃ22፥31፤2ቆሮ4፥4፤1ጴጥ5፥8፡9
2፥12 ሐሥ14፥27፤16፥28፤ሮሜ1፥1፤2ቆሮ4፥3፡4፤8፥18፤9፥13፤1ተሰ3፥2፤ቲቶ1፥4
2፥13 ሐሥ16፥9፤2ቆሮ 7፥5፡6፡13፤8፥6፡16፡23፤12፥18፤ገላ2፥1፡3፤ቲቶ1፥4
2፥14 ሕዝ20፥41፤ሮሜ6፥17፤7፥25፤ 1ቆሮ15፥57፤2ቆሮ8፥7፤2ቆሮ9፥15፤ኤፌ5፥2፤ፊል4፥18
2፥15 ቀኁ14፤ዘፍ 8፥21፤ዘፀ29፥18፤ዘኁ 15፥3፤1ቆሮ1፥18
2፥16 ሉቃ2፥34፤ዮሐ3፥36፤2ቆሮ3፥5፡6
2፥17 ሐሥ20፥33፤1ቆሮ5፥8፤2ቆሮ1፥12፤4፥2፤12፥19፤1ተሰ2፥5

3፥1 ሐሥ18፥21፤ሮሜ16፥1፤1ቆሮ16፥3፤2ቆሮ5፥12፤10፥12፡18፤12፥11
3፥2 1ቆሮ9፥2
3፥3 ቀኁ7፤ዘፀ24፥12፤31፥18፤32፥15፡16፤ምሳ3፥3፤7፥3፤ኤር31፥33፤ሕዝ36፥26፤ማቴ
3፥7 ቀኁ9፡13፤ዘፀ 34፥29-35፤ኢሳ42፥21፤ሮሜ2፥29፤4፥15
3፥9 ቀኁ7፤ዘዳ27፥26፤ሮሜ1፥17፤3፥21፡22
3፥12 ሐሥ4፥29፤ሮሜ5፥4፡5፤8፥24፡25
3፥13 ቀኁ7፤ዘፀ 34፥33
3፥14 ቀኁ6፤ሐሥ 13፥15፤15፥21፤ሮሜ 11፥7፡8፤2ቆሮ4፥4
3፥16 ዘፀ34፥34፤ኢሳ25፥7፤ሮሜ11፥23
3፥17 ኢሳ61፥1፡2፤ዮሐ8፥32፤ገላ4፥6፡7
3፥16 ዘፀ34፥34፤ኢሳ25፥7፤ሮሜ11፥23
3፥17 ኢሳ61፥1፡2፤ዮሐ8፥32፤ገላ4፥6፡7
3፥18 ዮሐ17፥22፡24፤ሮሜ8፥29፤1ቆሮ 13፥12፤2ቆሮ4፥4፡6

3 እንደ ገና ራሳችንን ልናመሰግን እን
ጀምራለንን? ወይስ እንደ ሌሎቹ ለእ
ናንተ ወይም ከእናንተ የተጻፈ የምስጋና
ደብዳቤ ያስፈልገን ይሆንን? 2እናንተከ
ሰው ሁሉ የሚያውቃችሁና የሚያነባችሁ
በልባችን ላይ የተጻፋችሁ ደብዳቤዎቻችን
ናችሁ፤ 3እናንተ በቀለም ሳይሆን በሕያው
እግዚአብሔር መንፈስ፣ በድንጋይ ጽላት ላይ
ሳይሆን በሰው ልብ ጽላት ላይ የተጻፋች
ሁና በእኛ የተገለገላችሁ የክርስቶስ ግልጽ
ደብዳቤ ናችሁ።
4በክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ላይ ያለን
እምነት ይህን የመሰለ ነው፤ 5ብቃታችን
ከእግዚአብሔር ነው እንጂ፣ በራሳችን
ብቃት ከእኛ ነው የምንለው አንዳች ነገር
የለ ንም። 6እርሱም በፊደል ላይ ሳይሆን
በመ ንፈስ ላይ የተመሠረተውን የአዲሱ
ኪዳን አገልጋዮች እንድንሆን ብቁዎች
አደረ ገን፤ ምክንያቱም ፊደል ይገድላል፤
መን ፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል።
7እንግዲህ እስራኤላውያን ከፊቱ ክብር
የተነሣ የሙ ሴን ፊት ትኵር ብለው
ማየት እስኪሳና ቸው ድረስ፣ ያ ከጊዜ
በኋላ የሚያልፈውና በድንጋይ ላይ
በፊደል የተቀረጸው የሞት አገልግሎት
በክብር ከመጣ፣ 8ታዲያ፣ የመን ፈስ
አገልግሎት እንዴት ከዚያ የላቀ ክብር
አይኖረውም? 9ሰዎችን የሚኰንነው
አገልግሎት የከበረ ከሆነ፣ የሚያጸድቀው
አገልግሎት የቱን ያህል ይበልጥ የከበረ
ይሆን! 10ከዚህ በፊት ክቡር የነበረው የላቀ
ክብር ካለው ጋር ሲወዳደር ክብር የሌለው
ሆኖአል። 11የሚያልፈው ያን ያህል ክብር
ከነበረው፣ ጸንቶ የሚኖረውማ እንዴት
የላቀ ክብር አይኖረውም?
12እንግዲህ ይህን የመሰለ ተስፋ ስላለን፣
በድፍረት እንናገራለን። 13እስራኤላውያን
የፊቱ ማንጸባረቅ እየጠፋ ሲሄድ መጨረሻ
ውን እንዳይመለከቱ፣ ፊቱን በጨርቅ
እንደ ሸፈነው እንደ ሙሴ አይደለንም።
14ነገር ግን ብሉይ ኪዳን በተነበበ ቍጥር
ያ መሸፈኛ እስከ ዛሬ ድረስ ስላልተወገደ
ልቡናቸው እንደ ደነዘዘ ነው፤ መሸፈኛው
አሁንም አልተወገደም፤ የሚወገደው በክር
ስቶስ ብቻ ነውና። 15እስከ ዛሬም ድረስ
የሙሴ መጻሕፍት በተነበቡ ቍጥር መሸፈ
ኛው ልቡናቸውን ይሸፍናል። 16ነገር ግን
አንድ ሰው ወደ ጌታ ዘወር ሲል መሸፈ
ኛው ይወገዳል። 17ጌታ መንፈስ ነው፤
የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ ነጻነት አለ።
18እኛም ሁላችን ባልተሸፈነ ፊት የጌታን
ክብር እንደ መስተዋት እያንጸባረቅን፣[ሐ]
የእርሱን መልክ እንድንመስል ከክብር ወደ

[ሐ]18 ወይም *የጌታን ክብር በጥሞና እያሰላሰልን*

ክብር እንለወጣለን፤ ይህም የሚሆነው መን
ፈስ ከሆነ ጌታ ነው።

## በሸክላ ውስጥ የተቀመጠ ክቡር ዕቃ

4 ስለዚህ ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ
ይህ አገልግሎት ስላለን ተስፋ አንቈ
ርጥም። 2ነገር ግን ስውርና አሳፋሪ ነገሮ
ችን ትተናል፤ አናታልልም፤ የእግዚአብሔርንም
ቃል ከሐሰት ጋር አንቀላቅልም፤ ይልቁ
ንም እውነትን በግልጽ እየተናገርን በሰው
ሁሉ ኅሊና ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረን
ራሳችንን በእግዚአብሔር ፊት እናቀርባለን።
3ወንጌላችን የተከደነ ቢሆን እንኳ፣ የተ
ከደነው ለሚጠፉት ነው። 4የእግዚአብሔር
አምሳል የሆነውን የክርስቶስ፣ የክብሩን
ወንጌል ብርሃን እንዳያዩ፣ የዚህ ዓለም
አምላክ የማያምኑትን ሰዎች ልቡና አሳ
ውሮአል። 5እኛ የምንሰብከው ክርስቶስ
ኢየሱስ ጌታ መሆኑን እንጂ ራሳችንን አይ
ደለምና፤ እኛም ራሳችን ስለ ኢየሱስ ስንል
የእናንተ አገልጋዮች ሆነናል። 6በክርስቶስ
ፊት እግዚአብሔር የክብሩን ዕውቀት ብር
ሃን ይሰጠን ዘንድ፣ "በጨለማ ብርሃን
ይብራ" ያለው እግዚአብሔር ብርሃኑን በል
ባችን አብርቶአልና።
7ነገር ግን ይህ እጅግ ታላቅ ኀይል ከእግ
ዚአብሔር እንጂ ከእኛ አለመሆኑን ለማሳ
የት፣ ይህ የከበረ ነገር በሸክላ ዕቃ ውስጥ
አለን። 8ከየአቅጣጫው ብንገፋም አንንኰታኰ
ትም፤ ግራ ብንጋባም ተስፋ አንቈርጥም፤
9ብንሰደድም ተጥለን አንቀርም፤ መት
ተው ቢጥሉንም አንጠፋም። 10የኢየሱስ
ሕይወት በሰውነታችን እንዲገለጥ፣ የኢየ
ሱስን ሞት ዘወትር በሰውነታችን ተሸክመን
እንዞራለን። 11የኢየሱስ ሕይወት ሟች
በሆነው ሥጋችን እንዲገለጥ፣ እኛ ሕያዋን
የሆንን ሁልጊዜ ስለ ኢየሱስ ለሞት ዐል
ፈን እንሰጣለንና። 12እንግዲህ ሞት በእኛ
ይሠራል፤ ሕይወት ግን በእናንተ።
13"አመንሁ፤ ስለዚህም ተናገርሁ"
ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ እኛም በዚያው
የእምነት መንፈስ እናምናለን፤ ስለዚህም
እንናገራለን፤ 14ምክንያቱም ጌታ ኢየሱስን
ከሙ ታን ያስነሣው እኛንም ደግሞ ከኢ
የሱስ ጋር አስነሥቶ ከእናንተ ጋር በፊቱ
እንደ ሚያቀርበን እናውቃለን። 15ለብዙ
ሰዎች እየደረሰ ያለው ጸጋ፣ ለእግዚአብሔር
ክብር በምስጋና ላይ ምስጋናን እንዲ
ጨምር ይህ ሁሉ ለእናንተ ጥቅም
ሆኖአል።
16ስለዚህ ተስፋ አንቈርጥም፤ ውጫዊው
ሰውነታችን እየጠፋ ቢሄድም እንኳ፣ ውስ
ጣዊው ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደ
ሳል፤ 17ምክንያቱም ቀላልና ጊዜያዊ የሆ
ነው መከራችን ወደር የማይገኝለት ዘላለ
ማዊ ክብር ያስገኝልናል። 18ስለዚህ ዐይ
ኖችን የሚያተኵረው በሚታየው ነገር ላይ
ሳይሆን በማይታየው ላይ ነው፤ የሚታየው
ጊዜያዊ ነውና፤ የማይታየው ግን ዘላለማዊ
ነው።

## ሰማያዊ መኖሪያችን

5 መኖሪያችን የሆነው ምድራዊ ድንኳን
ቢፈርስም፣ በሰው እጅ ያልተሠራ
ነገር ግን ከእግዚአብሔር የሆነ ዘላለማዊ
ቤት በሰማይ እንዳለን እናውቃለን።
2እስከዚያው ግን የሰማዩን መኖሪያችንን
ለመል በስ እየናፈቅን እንቃትታለን፤
3በእርግጥ ከለ በስነው ራቍታችንን ሆነን
አንገኝም። 4በዚህ ድንኳን እስካለን ድረስ
ከብደን እንቃትታ ለን፤ ምክንያቱም
ሟች የሆነው በሕይወት እንዲዋጥ ሰ
ማያዊውን መኖሪያችንን ልንለ ብስ እንጂ
ልንገፈፍ አንፈልግም። 5ለዚህ
ዐላማ ያዘጋጀን እግዚአብሔር ነው፤ ሊመጣ
ላለው ዋስትና እንዲሆነን መንፈሱን መያዣ
አድርጎ የሰጠንም እርሱ ነው።
6ስለዚህ ሁልጊዜ በመታመን እንኖራ
ለን፤ በሥጋ እስካለን ድረስ ከጌታ ርቀን
እንደምንገኝ እናውቃለን፤ 7ምክንያቱም
የምንኖረው በእምነት እንጂ በማየት አይ
ደለም። 8ከሥጋ ተለይተን ከጌታ ጋር
መኖርን እንደምንመርጥ እርግጠኛ ሆኜ
እናገራለሁ። 9ስለዚህ በሥጋ ብንኖርም
ወይም ከሥጋ ብንለይም ዐላማችን እርሱን
ደስ ማሰኘት ነው። 10ሁላችንም በክርስቶስ
የፍርድ ወንበር ፊት እንቀርባለንና፤ እያን
ዳንዱም ሰው በሥጋው ለሠራው በጎ
ወይም ክፉ ሥራ ተገቢውን ዋጋ ይቀበ
ላል።

## የማስታረቅ አገልግሎት

11እንግዲህ ጌታን መፍራት ምን ማለት
እንደ ሆነ ስለምናውቅ፣ ሰዎች የምንናገረ
ውን እንዲቀበሉ ለማድረግ እንጥራለን።
የእኛ ማንነት በእግዚአብሔር ዘንድ የተገለጠ
ነው፤ ደግሞም በኅሊናችሁ ዘንድ ግልጽ
ነው ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። 12ይህን የም
ለው ራሳችንን በእናንተ ፊት እንደ ገና
ለማመስገን ሳይሆን፣ በእኛ እንድት
መኩ ዕድል ልሰጣችሁ ነው፤ ይኸውም
በውጭ በሚታየው ለሚመኩት እንጂ
በልብ ውስጥ ባለው ነገር ለማይመኩ መልስ
መስጠት እንድትችሉ ነው። 13ከአእምሮ
ውጪ ብንሆን ለእግዚአብሔር ብለን ነው፤
ባለ አእምሮም ብንሆን ለእናንተ ነው።
14የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና፤ ምክን
ያቱም አንዱ ስለ ሁሉ እንደ ሞተ እር

4፥1 ቀኍ16፤መዝ 18፥45፤ኢሳ40፥31፤ 1ቆሮ7፥25፤1ጢሞ 1፥13፡16
4፥2 ሮሜ6፥21፤ 1ቆሮ4፥5፤2ቆሮ2፥17፤ 5፥11፤ዕብ4፥12
4፥3 1ቆሮ1፥18፤ 2ቆሮ2፥12፤3፥14
4፥4 ቀኍ6፤ዮሐ12፥31 ፤14፥9፤1ቆሮ1፥20፤2ቆሮ3፥14
4፥5 1ቆሮ1፥13፡23 ፤9፥19
4፥6 ቀኍ4፤ዘፍ1፥3፤ መዝ18፥28፤2ጴጥ 1፥19
4፥7 መሳ7፥2፤ኢዮ 4፥19፤ኢሳ64፥8፤1ቆሮ 2፥5፤2ቆሮ6፥7፤2ጢሞ 2፥20
4፥8 2ቆሮ7፥5፤ገላ 4፥20
4፥9 መዝ37፥24፤ ምሳ24፥16፤ዮሐ15፥20፤ ሮሜ8፥35፤ዕብ13፥5
4፥10 ሮሜ6፥5፡6፤ 2ቆሮ1፥5
4፥11 ሮሜ8፥36
4፥12 2ቆሮ13፥9
4፥13 መዝ116፥10፤ 1ቆሮ12፥9
4፥14 ሐሥ2፥24፤ ኤፌ5፥27፤ቈላ1፥22፤1 ተሰ4፥14፤ይሁ24
4፥15 2ቆሮ1፥11
4፥16 ቀኍ1፤መዝ18፥ 45፤103፥5፤ኢሳ40፥31፤ ሮሜ፥22፤ቈላ3፥10
4፥17 መዝ30፥5፤ ሮሜ8፥18፤1ጴጥ1፥6፡7
4፥18 ሮሜ8፥24፤ 2ቆሮ5፥7፤ ዕብ11፥1
5፥1 ኢሳ38፥12፤1ቆሮ 15፥47፤2ጴጥ1፥13፡14
5፥2 ቀኍ4፤ሮሜ8፥23 ፤1ቆሮ15፥53፡54
5፥4 ቀኍ2፤ሮሜ8፥23 1ቆሮ15፥53፡54
5፥5 ሮሜ8፥23፤2ቆሮ 1፥22፤ኤፌ1፥13፡14
5፥7 1ቆሮ13፥12፤ 2ቆሮ4፥18
5፥8 ዮሐ12፥26
5፥9 ሮሜ14፥18፤ ኤፌ5፥10፤ቈላ1፥10፤1 ተሰ4፥1
5፥10 ማቴ16፥27፤ ሐሥ10፥42፤ሮሜ2፥16፤ 14፥10፤ኤፌ6፥8
5፥11 ኢዮ23፥15፤ 2ቆሮ4፥2፤ዕብ10፥31፤ 12፥29፤ ይሁ23
5፥12 2ቆሮ1፥14፤3፥1
5፥13 2ቆሮ11፥1፡6 ፡17፤12፥11
5፥14 ሮሜ6፥6፡7፤ ገላ2፥20፤ቈላ3፥3

ግጠኞች ሆነናል፣ ከዚህም የተነሣ ሁሉ
ሞተዋል። 15በሕይወት ያሉትም ለሞተላ
ቸውና ከሙታን ለተነሣላቸው እንጂ ከእን
ግዲህ ለራሳቸው እንዳይኖሩ እርሱ ስለ
ሁሉ ሞተ።
16ስለዚህ ከአሁን ጀምሮ ማንንም በውጫዊ
ነገር አንመዝንም፤ ከዚህ ቀደም ክርስቶስን
በዚህ መልክ መዝነነው ነበር፤ ከእንግዲህ
ግን እንደዚህ አናደርግም። 17ስለዚህ
ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት
ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፣ አዲስ
ሆኖአል። 18ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤
እርሱ በክርስቶስ አማካይነት ከራሱ ጋር
አስ ታረቀን፤ የማስታረቅንም አገልግሎት
ሰጠን፤ 19እግዚአብሔር በክርስቶስ ዓለምን ከራ
ሱ ጋር ሲያስታርቅ የሰዎችን በደል
አይቈጥርባቸ ውም ነበር፤ ለእኛም
ደግሞ የማስታረቅ ቃል ሰጠን። 20ስለዚህ
እኛ የክርስቶስ እን ደራሴዎች ነን፤ እግዚ
አብሔርም በእኛ አማካይ ነት ጥሪውን
ያቀርባል፤ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ
ብለን በክርስቶስ እንለምናችኋ ለን። 21እኛ
በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ
እንድንሆን፣ ኀጢአት የሌለበትን እርሱን
እግዚአብሔር ስለ እኛ ኀጢአት[መ]
አደረገው።

6 ከእግዚአብሔር ጋር አብረን የምንሠራ እንደ
መሆናችን መጠን፣ የተቀበላችሁትን የእ
ግዚአብሔርን ጸጋ ከንቱ እንዳታደርጉት ዐደራ
እንላችኋለን። 2እርሱ፣

"በትክክለኛው ሰዓት ሰማሁህ፤
በመዳንም ቀን ረዳሁህ" ይላልና።
እነሆ፤ ትክክለኛው ሰዓት አሁን ነው፤
የመዳንም ቀን አሁን ነው።

### ጳውሎስ የተቀበለው መከራ

3አገልግሎታችን እንዳይነቀፍ፣ ለማንም
ዕንቅፋት መሆን አንፈልግም። 4ይሁን እንጂ
በምናደርገው ነገር ሁሉ ራሳችንን እንደ
እግዚአብሔር አገልጋዮች እናቀርባለን፦ በብዙ
ትዕግሥት፣ በመከራ፣ በችግር፣ በጭንቀት፣
5በመገረፍ፣ በመታሰር፣ በሁከት፣ በሥራ
ብዛት፣ እንቅልፍ በማጣት፣ በመራብ፣
6በንጽሕና፣ በዕውቀት፣ በትዕግሥት፣ በቸር
ነት፣ በመንፈስ ቅዱስ፣ በእውነተኛ ፍቅር፣
7በእውነት ቃል፣ በእግዚአብሔር ኀይል፣ በቀ
ኝና በግራ እጅ የጽድቅ የጦር ዕቃ በመ
ያዝ፣ 8በክብርና በውርደት፣ በመመስገንና
በመሰደብ፣ ኖረናል፤ ደግሞም እውነተኞች
ስንሆን ሐሰተኞች ተብለናል፤ 9የታወቅን
ስንሆን እንዳልታወቅን ሆነናል፤ ሞተዋል
ስንባል እነሆ በሕይወት አለን፤ ብንደበደ
ብም አልተገደልንም፤ 10ሐዘንተኞች ስን
ሆን ሁል ጊዜ ደስተኞች ነን፤ ድኾች
ስንሆን ብዙዎችን ባለጠጎች እናደርጋለን፤
ምንም የሌለን ስንሆን ሁሉ የእኛ ነው።
11የቆሮንቶስ ሰዎች ሆይ፤ ሁሉን በግል
ጽ
ነግረናችኋል፤ ልባችንንም ወለል አድርገን
ከፍተንላችኋል። 12ፍቅራችሁን የነፈጋችሁን
እናንተ ናችሁ እንጂ እኛስ ፍቅራችንን
አልነፈግናችሁም። 13ልጆቼ እንደ መሆናችሁ
መጠን ይህን አሳስባችኋለሁ፤ እናንተም
በዚያው ልክ ልባችሁን ወለል አድርጋችሁ
ክፈቱልን።

### ከማያምኑ ሰዎች ጋር አለመተባበር

14ከማያምኑ ሰዎች ጋር አግባብ ባልሆነ
መንገድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዐመፅ ጋር
ምን ግንኙነት አለው? ብርሃንስ ከጨለማ
ጋር ምን ኅብረት አለው? 15ክርስቶስ ከቤ
ልሆር[ሠ] ጋር ምን ስምምነት አለው? የሚያ
ምን ከማያምን ጋር ምን ኅብረት አለው?
16የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከጣዖታት
ጋር ምን ስምምነት አለው? እኛኮ የሕ
ያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነን፤ እግዚአ
ብሔርም እንዲህ ሲል ተናግሮአል፤ "ከእነ
ርሱ ጋር እኖራለሁ፤ በመካከላቸውም እመ
ላለሳለሁ፤ አምላካቸው እሆናለሁ፤
እነርሱም
ሕዝቤ ይሆናሉ።"

17"ስለዚህ ከመካከላቸው ውጡ፤
ለእኔም የተለያችሁ ሁኑ፤
ይላል ጌታ።
ርኩስ የሆነውን ነገር አትንኩ፤
እኔም እቀበላችኋለሁ።"
18"እኔ አባት እሆናችኋለሁ፤
እናንተም ወንዶችና ሴቶች ልጆቼ
ትሆናላችሁ፤
ይላል ሁሉን የሚችል ጌታ።"

7 እንግዲህ፣ ወዳጆች ሆይ፤ ይህ የተስፋ
ቃል ስላለን፣ ሥጋንና መንፈስን ከሚ
ያረክስ ነገር ሁሉ ራሳችንን እናንጻ፤ እግዚ
አብሔርንም በመፍራት ቅድስናችንን ፍጹም
እናድርገው።

### የጳውሎስ ደስታ

2ልባችሁን አስፉልን፤ እኛ ማንንም አል
በደልንም፤ ማንንም ወደ ብልሹነት አልመ
ራንም፤ ማንንም አላታለልንም። 3ይህን
የምለው ልኰንናችሁ አይደለም፤ ምክንያ
ቱም ከዚህ በፊት እንደ ነገርኋችሁ፣ በል
ባችን ውስጥ ስፍራ አላችሁ፤ ስለዚህ ብን
ኖርም ብንሞትም አብረን ነው። 4በእና
ንተ ላይ ያለኝ እምነት ትልቅ ነው፤ በእ
ናንተም ላይ ያለኝ ትምክሕት ትልቅ ነው፤

5፥15 ሮሜ4፥25፤ 14፥7-9
5፥16 2ቆሮ10፥4፤ 11፥18
5፥17 ኢሳ65፥17፤ ዮሐ1፥13፤ሮሜ6፥4፤16፥3፤ገላ6፥15፤ራእ 21፥4፡5
5፥18 ሮሜ5፥10፤ 11፥36
5፥19 ሮሜ4፥8
5፥20 ቀኊ18፤ኢሳ 27፥5፤2ቆሮ6፥1፤ኤፌ6፥20
5፥21 ሮሜ1፥17፤ 1ቆሮ1፥30፤ዕብ4፥15፤7፥26፤1ጴጥ2፥22፡24፤1ዮሐ3፥5
6፥1 1ቆሮ3፥9፤ 15፥2፤2ቆሮ5፥20
6፥2 መዝ69፥13፤ ኢሳ49፥8፤55፥6
6፥3 ማቴ5፥29፤ሮሜ 14፥13፡20፤1ቆሮ8፥9፡13፤9፥12፤10፥32
6፥5 ሐሥ16፥23፤ 1ቆሮ4፥11፤2ቆሮ11፥23-25
6፥6 ሮሜ12፥9፤ 1ቆሮ 2፥4፤1ተሰ1፥5፤1ጢሞ1፥5
6፥7 ሮሜ13፥12፤ 2ቆሮ4፥2፡7፤10፥4፤ ኤፌ6፥10-18
6፥8 ማቴ27፥63፤1ቆሮ4፥10፡13
6፥9 ሮሜ8፥36፤ 2ቆሮ1፥8-10፤4፥10፡11
6፥10 ማቴ5፥12፤ ሐሥ3፥6፤ሮሜ8፥32፤1ቆሮ3፥21፤2ቆሮ7፥4፤8፥9፤ፊል2፥17፤4፥4፤ቈላ1፥24፤1ተሰ1፥6
6፥11 2ቆሮ7፥3
6፥13 2ቆሮ7፥2፤ 1ተሰ 2፥11
6፥14 ዘፍ24፥3፤ዘዳ 22፥10፤1ቆሮ5፥9፡10፤6፥6፤ኤፌ5፥7፡11፤ 1ዮሐ1፥6
6፥15 ሐሥ5፥14፤ 1ቆሮ6፥6፤10፥21፤
6፥16 ዘሌ26፥12፤ ኤር32፥38፤ሕዝ37፥27፤ማቴ16፥16፤1ቆሮ 3፥16፤10፥21፤ራእ21፥3
6፥17 ኢሳ52፥11፤ ሕዝ20፥34፡41፤ራእ 18፥4
6፥18 ዘፀ4፥22፤ 2ሳሙ 7፥18፡4፤1ዜና 17፥13፤ኢሳ43፥6፤ ሮሜ 8፥14
7፥1 1ቆሮ10፥14፤2ቆሮ6፥17፡18፤1ተሰ 4፥7፤1ጴጥ1፥15፡16
7፥2 2ቆሮ6፥12፡13
7፥3 2ቆሮ6፥11፡12፤ፊል1፥7
7፥4 ቀኊ13፡14፤ 2ቆሮ6፥10፤8፥24

[መ]21 ወይም የኀጢአት መሥዋዕት

እንዲሁም እጅግ ተጽናንቻለሁ፤ በመከራ
ችንም ሁሉ ደስታዬ ወሰን የለውም።
5ወደ መቄዶንያ በመጣን ጊዜ ከየአቅጣ
ጫው መከራ ደረሰብን እንጂ ሰውነታችን
ዕረፍት አላገኘም፤ ከውጭ ጠብ፣ ከውስጥ
ደግሞ ፍርሀት ነበረብን። 6ይሁን እንጂ
ሐዘንተኞችን የሚያጽናና አምላክ በቲቶ
መምጣት አጽናናን። 7የተጽናናነውም በመ
ምጣቱ ብቻ ሳይሆን፣ እርሱንም ልታጽናኑት
በመቻላችሁ ጭምር ነው። ስለ ናፍቆታ
ችሁ፣ ስለ ሐዘናችሁና ለእኔም ስላላችሁ
ቅናት ነግሮናል፤ ስለዚህ ከመቼውም ጊዜ
ይልቅ ደስ ብሎኛል።
8በመልእክቴ ባሳዝናችሁም በዚህ አል
ጸጸትም፤ ብጸጸትም እንኳ መልእክቴ ያሳ
ዘናችሁ ለጥቂት ጊዜ እንደ ሆነ ተረድቻ
ለሁ። 9አሁን ግን ደስ ብሎኛል፤ ደስታ
ዬም ስላዘናችሁ ሳይሆን፣ ሐዘናችሁ ንስሓ
ለመግባት ስላበቃችሁ ነው፤ ምክንያቱም
ሐዘናችሁ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ
ከእኛ የተነሣ ምንም አልተጐዳችሁም።
10እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ሐዘን
ወደ ድነት ለሚያደርስ ንስሓ ያበቃል፤
ጸጸትም የለበትም። ዓለማዊ ሐዘን ግን
ለሞት ያበቃል። 11ይህ እንደ እግዚአብሔር
ፈቃድ የሆነው ሐዘን እንዴት ያለ ትጋት፣
እንዴት ያለ መልስ የመስጠት ችሎታ፣ እን
ዴት ያለ ቍጣ፣ እንዴት ያለ ፍርሀት፣
እንዴት ያለ ናፍቆት፣ እንዴት ያለ በጎ
ቅናት፣ እንዴት ያለ ተግሣጽ እንዳስገኘላ
ችሁ ተመልከቱ። በዚህም ጒዳይ ንጹ
ሓን መሆናችሁን በሁሉ ረገድ አስመስ
ክራችኋል። 12እንግዲህ እኔ የጻፍሁላችሁ
ስለ በደለው ወይም ስለ ተበደለው ሰው
አይደለም፤ ነገር ግን ለእኛ ምን ያህል
ታማኞች እንደ ሆናችሁ፣ በእግዚአብሔር ፊት
ራሳችሁን እንድታዩ በማለት ነው። 13እኛም
የተጽናናነው በዚህ ምክንያት ነው።
ከእኛም መጽናናት በተጨማሪ በቲቶ
ደስታ እኛም ይበልጥ ደስ ብሎናል፤ ምክ
ንያቱም ሁላችሁም መንፈሱን አሳርፋች
ኋል። 14በእናንተ ላይ ያለኝ ትምክሕት
ለእርሱ ነግሬው ነበር፤ እናንተም አላሳፈራ
ችሁኝም። ነገር ግን ስንነግራችሁ የነበረው
ሁሉ እውነት እንደ ሆነ፣ እንደዚሁም ስለ
እናንተ ለቲቶ በትምክሕት የነገርነው እው
ነት መሆኑ ተረጋግጦአል። 15እርሱም
በፍርሀትና በመንቀጥቀጥ እንዴት እንደ
ተቀበ ላችሁትና ሁላችሁም እንደ
ታዘዛችሁ ሲያስ ታውስ ለእናንተ ያለው
ፍቅር እየበረታ ሄዶአል። 16እኔም በ
ማናቸውም ነገር ልተማ መንባችሁ በመቻሌ
ደስ ብሎኛል።

7፥5 ዘዳ32፥25፤ ሐሥ16፥9፤2ቆሮ 2፥13፤4፥8
7፥6 ቍ13፤2ቆሮ 1፥3፡4፤2፥13
7፥8 2ቆሮ2፥2፡4
7፥10 ሐሥ11፥18
7፥11 ቍ7
7፥12 ቍ8፤1ቆሮ 5፥1፡2፤2ቆሮ2፥3፡9
7፥13 ቍ6፤2ቆሮ 2፥13
7፥14 ቍ4፡6
7፥15 መዝ55፥5፤ 1ቆሮ 2፥3፤2ቆሮ2፥9 ፤10፥6፤ፊል2፥12
7፥16 2ቆሮ2፥3

8፥1 ሐሥ16፥9
8፥2 ዘፀ36፥5፤2ቆሮ 9፥11
8፥3 1ቆሮ16፥2
8፥4 ቍ1፤ሐሥ9፡ 13፤24፥17
8፥6 ቍ10፡11፡16 ፡17፡23፤2ቆሮ2፥13፤1 2፥18
8፥7 ሮሜ15፥14፤ 1ቆሮ1፥5፤12፥8፤13፥1፡ 2፤14፥6፤2ቆሮ9፥8
8፥8 1ቆሮ7፥6
8፥9 ማቴ20፥28፤ ሮሜ3፥24፤2ቆሮ 6፥10፤13፥14፤ፊል2፥6-8
8፥10 1ቆሮ7፥25፡ 40፤16፥2፡3፤2ቆሮ9፥2
8፥11 ቍ12፡19፤ዘፀ 25፥2፤2ቆሮ9፥2
8፥12 ማር12፥43፡44 ፤2ቆሮ9፥7
8፥14 ሐሥ4፥34፤ 2ቆሮ9፥12
8፥15 ዘፀ16፥18

## የልግስና አስፈላጊነት

8 ወንድሞች ሆይ፤ እግዚአብሔር በመቄዶ
ንያ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት የሰ
ጠውን ጸጋ እንድታውቁ እንፈልጋለን።
2የደረሰባቸው መከራ ጽኑ ቢሆንም ደስታ
ቸው ግን የላቀ ነበር፤ ድኽነታቸው ብርቱ
ቢሆንም ልግስናቸው ግን የበዛ ነበር።
3እንደ ዐቅማቸው ብቻ ሳይሆን፣ ከዐቅ
ማቸው በላይ በፈቃዳቸው እንደ ሰጡ
እመሰክርላቸ ዋለሁ። 4እነርሱም ቅዱሳንን
ለመርዳት በሚደረገው አገልግሎት
ለመሳተፍ ዕድል ያገኙ ዘንድ አጥብቀው
ይለምኑን ነበር። 5እኛ ከጠበቅነው በላይ፣
በመጀመሪያ ራሳ ቸውን ለጌታ ሰጡ፤
ቀጥለውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን
ለእኛ ሰጡ። 6ስለዚህ ቲቶ፣ በእናንተ
መካከል ቀደም ሲል የጀ መረውን የልጠ
ግስና ሥራ ከፍጻሜ እንዲያ ደርስ ለምነነው
ነበር። 7እናንተም በሁሉ ነገር ይኸውም
በእምነት፣ በቃል፣ በዕው ቀት፣ በፍጹም
ትጋትና ለእኛም ባላችሁ ፍቅር[ረ] ልቃችሁ
እንደተገኛችሁ፣ በዚህም የቸርነት ሥራ
ልቃችሁ እንድትገኙ ዐደራ እንላችኋለን።
8ይህን የምለው ትእዛዝ ለመስጠት ብዬ
አይደለም፤ ነገር ግን ሌሎች ከሚያሳዩት
ትጋት አንጻር የፍቅራችሁን እውነተኛነት
ለማረጋገጥ ነው። 9የጌታችንን የኢየሱስ
ክርስቶስን ጸጋ ታውቃላችሁና፤ በእርሱ
ድኽነት እናንተ ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ
እርሱ ሀብታም ሆኖ ሳለ ለእናንተ ሲል
ድኻ ሆነ።
10ስለዚህ ጒዳይ የምሰጣችሁ ጠቃሚ
ምክር ይህ ነው፤ ባለፈው ዓመት በመስጠት
ብቻ ሳይሆን ለመስጠት በማሰብም ቀዳሚ
ነበራችሁ፤ 11አሁንም የጀመራችሁትን ተግ
ባር በዐቅማችሁ መጠን ከፍጻሜ አድር
ሱት፤ ይህም ለመስጠት የነበራችሁ በጎ
ፈቃድ እውን እንዲሆን ነው። 12ለመስጠት
በጎ ፈቃድ ካለን ስጦታው ተቀባይነት
የሚያገኘው ባለን መጠን ስንሰጥ እንጂ፣
በሌለን መጠን ለመስጠት ስንሞክር አይደ
ለም።
13ይህንን የምንለው እናንተ ተቸግራችሁ
ሌሎች ይድላቸው ለማለት ሳይሆን፣ ሁላ
ችሁም እኩል እንድትሆኑ ነው። 14በአሁኑ
ጊዜ የእናንተ ትርፍ የእነርሱን ጒድለት
ያሟላል፤ የእነርሱም ደግሞ በተራው የእ
ናንተን ጒድለት ያሟላል፤ በዚህም ያላች
ሁን እኩል ትካፈላላችሁ። 15ይህም፣ “ብዙ
የሰበሰበ አላተረፈም፤ ጥቂት የሰበሰበም
አልጐደለበትም” ተብሎ እንደ ተጻፈው

[ሠ]15 ግሪኩ *ቤሌየር* [ረ]7 አንዳንድ ቅጆች *ለእናንተ ባለን ፍቅር*

ነው።

## ቲቶ ወደ ቆሮንቶስ ተላከ

16እኔ ለእናንተ ያለኝን በጎ ሐሳብ በቲቶ
ልብ ውስጥ ያኖረ አምላክ የተመሰገነ ይሁን፤
17ምክንያቱም ቲቶ ወደ እናንተ የመጣው
ልመናችንን በመቀበል ብቻ ሳይሆን፣ በታ
ላቅ ጕጕትና በራሱ ፈቃድ በመነሣሣት
ነበር። 18ከእርሱም ጋር በወንጌል ስብከት
በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የተመሰገነ
ውን ወንድም ልከነዋል። 19ከዚህም በላይ
ስጦታውን በምንወስድበት ጊዜ አብሮን
እንዲሄድ በአብያተ ክርስቲያናት ተመር
ጦአል፤ ስጦታውንም የምንወስደው ጌታን
ራሱን ለማክበርና ሌሎችን ለመርዳት
ካለን በጎ ፈቃድ የተነሣ ነው። 20በዚህ
በምናከናውነው የቸርነት ሥራ አንዳች ነቀፋ
እንዳይገኝብን እንጠነቀቃለን። 21ምክንያ
ቱም ዐላማችን በጌታ ፊት ብቻ ሳይሆን፣
በሰውም ፊት መልካም የሆነውን ነገር
ማድረግ ነው።

22ደግሞም ብዙ ጊዜ በብዙ መንገድ
ተፈትኖ ትጉ ሆኖ የተገኘውን ወንድማች
ንን ከእነርሱ ጋር ልከነዋል፤ አሁንም በእና
ንተ እጅግ ከመታመኑ የተነሣ ከመቼ
ውም ጊዜ ይልቅ እየተጋ ነው። 23ስለ
ቲቶ የሚጠይቅ ቢኖር፣ እርሱ እናንተን
ለማገልገል አብሮኝ የሚሠራ ባልደረባዬ
ነው፤ ስለ ወንድሞቻችንም የሚጠይቅ
ቢኖር እነርሱ የአብያተ ክርስቲያናት ተወ
ካዮችና የክርስቶስ ክብር ናቸው። 24ስለ
ዚህ የፍቅራችሁን እውነተኛነትና በእናን
ተም የምንታመነው የቱን ያህል እንደ
ሆነ በአብያተ ክርስቲያናት ፊት ግለጡላ
ቸው።

9 ለቅዱሳን ስለሚደረገው አገልግሎት
ልጽፍላችሁ አያስፈልግም። 2ምክንያ
ቱም ሌሎችን ለመርዳት ያላችሁን በጎ
ፈቃድ ዐውቃለሁ፤ ካለፈው ዓመት ጀምሮ
እናንተ በአካይያ የምትኖሩ ሌሎችን ለመ
ርዳት ዝግጁ እንደ ሆናችሁ ለመቄዶንያ
ሰዎች አፌን ሞልቼ ተናግሬአለሁ፤ ቅን
ፍላጎታችሁም ብዙዎችን ለበጎ ሥራ አነሣ
ሥቶአል። 3እንግዲህ በዚህ ነገር በእናንተ
ላይ ያለን ትምክሕት ከንቱ ሆኖ እንዳይ
ቀር አስቀድሞ ስለ እናንተ እንደ ተናገር
ሁት ተዘጋጅታችሁ እንድትገኙ ወንድሞችን
ልኬአለሁ። 4ምናልባት የመቄዶንያ ሰዎች
ከእኔ ጋር መጥተው ሳትዘጋጁ ቢያገኟ
ችሁ፣ እናንተ ብቻ ሳትሆኑ እኛም ያን
ያህል በእናንተ በመመካታችን እናፍራ
ለን። 5ስለዚህ ወንድሞች አስቀድመው
ወደ እናንተ እንዲመጡና ከዚህ በፊት

8፥16 2ቆሮ2፥13፡14፤ራእ17፥17
8፥17 ቁ6
8፥18 1ቆሮ7፥17፤2ቆሮ2፥12፤12፥18
8፥19 ቁ11፡12፤ሐሥ14፥23፤1ቆሮ16፥3፡4
8፥21 ሮሜ12፥17፤14፥18፤ቲቶ2፥14
8፥23 ቍ18፡22፤2ቆሮ2፥13፤ፊል2፥25፤ፊሞ17
8፥24 2ቆሮ7፥4፡14፤9፥2
9፥1 ሐሥ9፥13፤24፥17፤1ተሰ4፥9
9፥2 ሐሥ18፥12፤2ቆሮ7፥4፡14፤8፥10፡11፡12፡19፡24
9፥3 1ቆሮ16፥2፤2ቆሮ8፥23
9፥4 ሮሜ15፥26
9፥5 ቁ3፤2ቆሮ12፥17፡18፤ፊል4፥17
9፥6 ምሳ11፥24፡25፤22፥9፤ገላ6፥7፡9
9፥7 ዘፀ25፥2፤ዘዳ15፥10፤ሮሜ12፥8፤2ቆሮ8፥12
9፥8 ኤፌ3፥20፤ፊል4፥19
9፥9 መዝ112፥9፤ሚል3፥10
9፥10 ኢሳ55፥10፤ሆሴ10፥12
9፥11 ቁ5፤1ቆሮ1፥5፤2ቆሮ1፥11፤4፥15
9፥12 2ቆሮ1፥11፤8፥14
9፥13 ቁ5፤ማቴ9፥8 ፤2ቆሮ2፥12፤8፥4፤ዕብ3፥1
9፥15 ሮሜ5፥15፡16፤2ቆሮ2፥14
10፥1 ማቴ11፥29፤ገላ5፥2፤ኤፌ3፥1
10፥2 ሮሜ12፥2፤1ቆሮ4፥21
10፥3 ቁ2

ለመስጠት ቃል የገባችሁትን ስጦታ አጠ
ናቃችሁ እንድትጠብቋቸው፣ እነርሱን መለ
መን አስፈላጊ ሆኖ አግኝቻለሁ፤ እንግዲህ
በልግስና ለመስጠት ያሰባችሁት ነገር በግ
ዴታ ሳይሆን በፈቃደኝነት የተዘጋጀ ይሆ
ናል።

## በልግስና መስጠት

6ይህን አስታውሱ፤ ጥቂት የዘራ ጥቂት
ያጭዳል፤ ብዙ የዘራ ብዙ ያጭዳል። 7እያ
ንዳንዱ ሰው በቅሬታ ወይም በግዴታ ሳይ
ሆን፣ በልቡ ያሰበውን ያህል ይስጥ፤ ምክን
ያቱም እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ሰው
ይወዳል። 8ሁልጊዜ በሁሉ ነገር የሚያስ
ፈልጋችሁን ሁሉ አግኝታችሁ ለበጎ ሥራ
ሁሉ እንድትተርፉ፣ እግዚአብሔር ጸጋን
ሁሉ ሊያበዛላችሁ ይችላል፤ 9ይህም፣

"በተነ፤ ለድኾችም ሰጠ፤
ጽድቁ ለዘላለም ይኖራል"
ተብሎ እንደ ተጻፈው ነው።

10ለዘሪ ዘርን፣ ለመብላት እንጀራን የሚ
ሰጥ እርሱ የምትዘሩትን አትረፍርፎ ይሰ
ጣችኋል፤ የጽድቃችሁንም ፍሬ ያበዛላች
ኋል። 11ሁልጊዜ በልግስና መስጠት እንድ
ትችሉ በሁሉ ነገር ያበለጽጋችኋል፤ ልግስ
ናችሁም በእኛ በኩል የሚደርሳቸው ሰዎች
እግዚአብሔርን ለማመስገን ምክንያት ይሆና
ቸዋል።

12ይህ የምትሰጡት አገልግሎት የቅዱሳ
ንን ጕድለት የሚያሟላ ብቻ ሳይሆን፣ ብዙ
ምስጋና ለእግዚአብሔር የሚቀርብበት ነው።
13የክርስቶስን ወንጌል ተቀብላችሁ ስለ
ታዘዛችሁና ለእነርሱም ሆነ ለሌሎች ስላ
ሳያችሁት ልግስና ሰዎች ተፈትኖ ስላለ
ፈው አገልግሎታችሁ እግዚአብሔርን ያከብራ
ሉ፤ 14ስለ እናንተም በሚጸልዩበት ጊዜ
እግዚአ ብሔር ከሰጣችሁ ታላቅ ጸጋ የተነሣ
ይናፍ ቋችኋል። 15በቃላት ሊገለጥ ስለ
ማይቻል ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን።

## ጳውሎስ ስለ አገልግሎቱ ያቀረበው መከላከያ

10 እኔ ጳውሎስ፣ በእናንተ ፊት
ስሆን "ዐይነ ዐፋር"፣ ከእናንተ
ስርቅ ግን፣ "ደፋር" የተባልሁ በክ
ርስቶስ የዋህነትና ገርነት እለምናችኋለሁ።
2ወደ እናንተ በምመጣበት ጊዜ በዓለማዊ
መንገድ እንደምንኖር አድርገው በሚቈ
ጥሩን ሰዎች ላይ በድፍረት ለመናገር
ቈርጫለሁ፤ እናንተን ግን በዚያ ዐይነት
ድፍረት እንድናገር እንዳታደርጉኝ እለም
ናችኋለሁ። 3የምንኖረው በዚህ ዓለም ቢሆ
ንም፣ የምንዋጋው በዚህ ዓለም ስልት አይ

ደለም፡፡ [4]ደግሞም የምንዋጋበት የጦር
መሣሪያ የዚህ ዓለም መሣሪያ አይደለም፤
ይሁን እንጂ ምሽግን ለመደምሰስ የሚ
ችል መለኮታዊ ኀይል ያለው ነው፡፡ [5]በእግ
ዚአብሔር ዕውቀት ላይ በትዕቢት የሚነሣ
ውን ክርክርና ከንቱ ሐሳብ ሁሉ እናፈር
ሳለን፤ አእምሮንም ሁሉ እየማረክን ለክርስ
ቶስ እንዲታዘዝ እናደርጋለን፡፡ [6]መታዘዛ
ችሁ በተፈጸመ ጊዜ አለመታዘዝን ሁሉ
ለመቅጣት ተዘጋጅተናል፡፡
[7]እናንተ የምትመለከቱት ውጫዊውን ነገር
ብቻ ነው፡፡[ሰ] ማንም የክርስቶስ በመሆኑ ቢመካ
እርሱ የክርስቶስ እንደ ሆነ ሁሉ እኛም
የክርስቶስ መሆናችንን ሊገነዘብ ይገባ
ዋል፡፡ [8]ጌታ በሰጠን ሥልጣን እጅግ ብመ
ካም በዚህ አላፍርም፤ ሥልጣኑን የተቀበል
ነው እናንተን ለማነጽ እንጂ ለማፍረስ
አይደለምና፡፡ [9]በመልእክቶቼ የማስፈራራ
ችሁ አይምሰላችሁ፡፡ [10]አንዳንዶች፣ "መልእ
ክቶቹ ከባድና ጠንካራ ናቸው፤ ነገር ግን
ሰውነቱ ሲታይ ደካማ፣ ንግግሩም የተናቀ
ነው" ይላሉ፡፡ [11]እንዲህ የሚሉ ሰዎች በሩቅ
ሆነን በመልእክታችን የምንናገረውን ሁሉ
በቅርብ ሆነን በተግባራችን የምንገልጸውም
እንደዚያው መሆኑን መገንዘብ አለባ
ቸው፡፡
[12]ራሳቸውን ከሚያመሰግኑ ሰዎች ጋር ራሳ
ችንን ልንመድብ ወይም ልናነጻጽር አንደ
ፍርም፤ እነርሱ ራሳቸውን በራሳቸው ሲመ
ዝኑና ራሳቸውንም ከራሳቸው ጋር ሲያ
ነጻጽሩ አስተዋዮች አይደሉም፡፡ [13]እኛ ግን
ከመጠን በላይ አንመካም፤ የምንመካው
እግዚአብሔር በመደበልንና እስከ እናንተም
እንኳ በሚደርሰው የአገልግሎታችን ወሰን
ነው፡፡ [14]የክርስቶስን ወንጌል ይዘን ወደ
እናንተ በመጣን ጊዜ፣ ከተመደበልን የአገ
ልግሎት ወሰን አላለፍንም፡፡[ሸ] [15]ደግሞም
ሌሎች በደከሙበት ሥራ ከመጠን በላይ
በመመካት ከተመደበልን ወሰን አናል
ፍም፤ ይልቁንም እምነታችሁ እያደገ በሄደ
ቍጥር በእናንተ ዘንድ የተመደበልን አገ
ልግሎት እየሰፋ እንደሚሄድ ተስፋ እናደ
ርጋለን፡፡ [16]ስለዚህ በሌላው ሰው ክልል አስ
ቀድሞ በተሠራ ሥራ ሳንመካ፣ ከእናንተ
ወዲያ ባለው አገር ወንጌልን መስበክ እንች
ላለን፡፡ [17]ነገር ግን፣ "የሚመካ በጌታ ይመካ"፤
[18]ምክንያቱም ጌታ ራሱ የሚያመሰግነው
እንጂ፣ ራሱን በራሱ የሚያመሰግን ተቀባ
ይነት አይኖረውም፡፡

## ጳውሎስና ሐሰተኞች ሐዋርያት

**11** ጥቂቱን ሞኝነቴን እንደምትታገሡኝ
ተስፋ አደርጋለሁ፤ በእርግጥም እየ
ታገሣችሁኝ ነው፡፡ [2]በእግዚአብሔር ቅናት
እቀናላችኋለሁ፤ እናንተን እንደ ንጽሕት
ድንግል ለክርስቶስ ለማቅረብ ለአንድ ባል
አጭቻችኋለሁና፡፡ [3]ነገር ግን እባብ ሔዋ
ንን በተንኰል እንዳሳታት ምናልባት የእና
ንተም ልቡና ተበላሽቶ ለክርስቶስ ካላችሁ
ቅንነትና ንጽሕና እንዳትወሰዱ እሠጋለሁ፡፡
[4]ምክንያቱም አንድ ሰው ወደ እናንተ
መጥቶ እኛ ከሰበክንላችሁ ኢየሱስ ሌላ
ኢየሱስ ቢሰብክላችሁ፣ ወይም ከተቀበላች
ሁት መንፈስ የተለየ መንፈስ ብትቀበሉ
ወይም ከተቀበላችሁት ወንጌል የተለየ ወን
ጌል ብትቀበሉ፣ ነገሩን በዝምታ ታልፉታላ
ችሁ ማለት ነው፡፡ [5]እኔ ግን "ታላላቅ ሐዋ
ርያት" ከሚባሉት በምንም የማንስ አይመ
ስለኝም፡፡ [6]የንግግር ችሎታ ባይኖረኝም
እንኳ፣ ዕውቀት ግን አለኝ፤ ይህንንም
በሁሉ መንገድ በሚገባ ግልጽ አድርገንላ
ችኋል፡፡
[7]እናንተ ከፍ እንድትሉ ራሴን ዝቅ አድ
ርጌ የእግዚአብሔርን ወንጌል ያለ ዋጋ ለእናንተ
መስበኬ እንደ ኀጢአት ተቈጥሮብኝ
ይሆን? [8]እናንተን ለማገልገል ስል ከሌሎች
አብያተ ክርስቲያናት ርዳታ በመቀበሌ
እነርሱን ዘርፌአቸዋለሁ፡፡ [9]ከእናንተም ጋር
ሳለሁ አንዳች ባስፈለገኝ ጊዜ፣ ከመቄዶንያ
የመጡ ወንድሞች የሚያስፈልገኝን ስለ
ሰጡኝ ለማንም ሸክም አልሆንሁም፡፡ በእና
ንተ ላይ በምንም ነገር ሸክም እንዳልሆን
ተጠንቅቄአለሁ፤ ወደ ፊትም እጠነቀቃ
ለሁ፡፡ [10]የክርስቶስ እውነት በውስጤ እስ
ካለ ድረስ፣ በአካይያ አውራጃ ይህን ትም
ክሕቴን ማንም ሊገታው አይችልም፡፡
[11]ይህን የምለው ለምንድን ነው? ስለማል
ወዳችሁ ነውን? እንደምወዳችሁ እግዚአ
ብሔር ያውቃል፡፡ [12]ከእኛ ጋር እኩል ለመ
ሆን በሥራቸው እየተመኩ ቀን የሚጠብ
ቁትን ሰዎች ምክንያት ለማሳጣት አሁን
የማደርገውን ወደ ፊትም አደርጋለሁ፡፡
[13]እንደነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋ
ርያት ለመምሰል ራሳቸውን የሚለዋውጡ፣
ሐሰተኞች ሐዋርያትና አታላዮች ሠራተ
ኞች ናቸው፡፡ [14]ይህም የሚያስደንቅ ነገር
አይደለም፤ ምክንያቱም ሰይጣን ራሱ የብ
ርሃን መልአክ ለመምሰል ራሱን ይለዋወ
ጣል፡፡ [15]እንግዲህ የእርሱ አገልጋዮች፣
የጽድቅ አገልጋዮች ለመምሰል ራሳቸውን
ቢለውጡ የሚያስገርም አይደለም፤ ፍጻሜ

[ሰ]7 ወይም *ግልጥ የሆነውን እውነታ ብቻ ነው*
[ሸ]13-15 ወይም [13] እኛ ግን ከመጠን በላይ ስለሆኑ ነገሮች አንመ
ካም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በመደበልንና እስከ
እናንተም እንኳ በሚደርሰው እንመካለን፡፡ [14...15] ደግሞ
ሌሎች በሠሩት ሥራ ከመጠን በላይ ስለ ሆኑ ነገሮች
አንመካም፤

10፥4 ቈላ8፤ኤር1፥10፤23፥29፤1ቆሮ2፥5፤2ቆሮ6፥7፡13፥10
10፥5 ኢሳ2፥11፡12፤1ቆሮ1፥19፤2ቆሮ9፥13
10፥6 2ቆሮ2፥9፤7፥15
10፥7 ዮሐ7፥24፤1ቆሮ1፥12፤3፥23፤14፥37፤2ቆሮ5፥12፤11፥23
10፥8 ቈላ4፡13፡15፤ኤር1፥10፤2ቆሮ13፥10
10፥10 ቈላ1፤1ቆሮ1፥17፤2፥3፤2ቆሮ11፥6፤ገላ4፥13፡14
10፥12 ቈላ18፤2ቆሮ3፥1
10፥13 ቈላ15፡16፤ሮሜ12፥3
10፥14 1ቆሮ3፥6፤2ቆሮ2፥12
10፥15 ቈላ13፤ሮሜ15፥20፤2ተሰ1፥3
10፥16 ሐሥ19፥21፤ሮሜ1፥1፤2ቆሮ2፥12
10፥17 መዝ34፥2፤44፥8፤ኤር9፥24፤1ቆሮ1፥31
10፥18 ቈላ12፤ሮሜ2፥29
11፥1 ቈላ4፡16፡17፡19፡20፡21፤ማቴ17፥17፤2ቆሮ5፥13
11፥2 ሆሴ2፥19፤2ቆሮ4፥14፤ኤፌ5፥26፡27
11፥3 ዘፍ3፥1-6፡13፤1ጢሞ2፥14፤ራእ12፥9
11፥4 ቈላ1፤ሮሜ8፥15፤1ቆሮ3፥11፤ገላ1፥6-9
11፥5 2ቆር12፥11፤ገላ2፥6
11፥6 1ቆሮ1፥17፤2ቆሮ8፥7፤ኤፌ3፥4
11፥7ሮሜ1፥1፤1ቆሮ9፥18፤2ቆሮ12፥13
11፥8 ፊል4፥15፡18
11፥9 2ቆሮ12፥13፡14፡16፤ፊል4፥15፡18
11፥10 ሐሥ18፥12፤ሮሜ9፥1፤1ቆሮ9፥15
11፥11 ቈላ31፤ሮሜ1፥9፤2ቆሮ12፥15
11፥13 ማቴ7፥15፤ቲቶ1፥10፤ራእ2፥2
11፥14 ማቴ4፥10
11፥15 ማቴ16፥27፤ፊል3፥19

አቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል።

### ጳውሎስ በደረሰበት መከራ ይመካል

16እንደ ገና ይህን እላለሁ፤ ማንም ሰው
እንደ ሞኝ አይቍጠረኝ፤ እናንተም የምት
ቈጥሩኝ ከሆነ እኔም በጥቂቱ እንድመካ
እንደ ሞኝ ተቀበሉኝ። 17እንደዚህ ልበ ሙሉ
ሆኜ የምናገረው እንደ ሞኝ እንጂ እንደ
ጌታ ፈቃድ አይደለም። 18ብዙዎች በዓለ
ማዊ ነገር ስለሚመኩ እኔም ደግሞ እመካ
ለሁ። 19እናንተም ብልሆች ስለ ሆናችሁ
ሞኞችን በደስታ ትታገሣላችሁ፤ 20ማንም
ተነሥቶ ባሪያ ቢያደርጋችሁ፣ ቢበዘብዛችሁ፣
ለጥቅሙ ሲል ቢጠጋችሁ፣ ቢንቀባረርባ
ችሁ ወይም ፊታችሁን በጥፊ ቢመታችሁ
ትታገሣላችሁ። 21እኛ ግን ለዚያ እጅግ
ደካሞች መሆናችንን እያፈርሁ እናገራ
ለሁ።

ማንም በድፍረት በሚመካበት ነገር
ሁሉ እኔም ደፍሬ መመካት እንደምችል
እንደ ሞኝ እናገራለሁ። 22እነርሱ ዕብራ
ውያን ናቸውን? እኔም ነኝ፤ እስራኤላ
ውያን ናቸውን? እኔም ነኝ፤ የአብርሃም
ዘር ናቸውን? እኔም ነኝ። 23የክርስቶስ አገ
ልጋዮች ናቸውን? እንደ አበደ ሰው ልናገ
ርና እኔ እበልጣቸዋለሁ፤ ደግሞም ብዙ
ጊዜ በሥራ ደክሜአለሁ፤ ብዙ ጊዜ ታስሬ
ያለሁ፤ ብዙ ጊዜ ተገርፌአለሁ፤ ብዙ ጊዜ
ለሞት ተቃርቤአለሁ። 24አይሁድ ለአርባ
ጅራፍ አንድ የቀረው አምስት ጊዜ ገር
ፈውኛል። 25ሦስት ጊዜ በዱላ ተደብድ
ቤአለሁ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወግሬአለሁ፤
ሦስት ጊዜ የመርከብ አደጋ ደርሶብኛል፤
አንድ ሌሊትና ቀን በባሕር ላይ አድሬአ
ለሁ፤ 26ብዙ ጊዜ በጕዞ ተንከራትቻለሁ፤
ደግሞም ለወንዝ ሙላት አደጋ፣ ለወንበዴ
ዎች አደጋ፣ ለገዛ ወገኖቼ አደጋ፣ ለአሕዛብ
አደጋ፣ ለከተማ አደጋ፣ ለገጠር አደጋ፣
ለባሕር አደጋ እንዲሁም ለሐሰተኞች ወን
ድሞች አደጋ ተጋልጬ ነበር። 27ብዙ
ጥሬአለሁ፤ ብዙ ደክሜአለሁ፤ ብዙ ጊዜ
እንቅልፍ አጥቻለሁ፤ ተርቤአለሁ፤ ተጠም
ቻለሁ፤ ብዙ ጊዜ ምግብ ሳልቀምስ ኖሬአ
ለሁ፤ በብርድና በራቍትነት ተቈራምጃ
ለሁ። 28ሌላውን ነገር ሳልቈጥር፣ ዕለት ዕለት
የሚያስጨንቀኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ
ሐሳብ ነው። 29ደካማ ማን ነው? እኔስ
አብሬ አልደክምምን? በኀጢአት
የሚሰናከል ማን ነው? እኔስ አልቈጭምን?
30መመካት ካለብኝ፣ ደካማነቴን በሚያ
ሳዩ ነገሮች እመካለሁ። 31ለዘላለም የተመ
ሰገነው የጌታ የኢየሱስ አምላክና አባት
እንደማልዋሽ ያውቃል። 32ደማስቆ ሳለሁ

11፥16 ቍ1
11፥17 ቍ21፤1ቆሮ 7፥12፡25
11፥18 ቍ21፤2ቆሮ 5፥16፤10፥4፤ፊል3፥3፡4
11፥19 ቍ1፤1ቆሮ 4፥10
11፥20 ቍ1፤ገላ2፥4፤4፥9፤5፥1
11፥21 ቍ17፡18፤ 2ቆሮ10፥1፥10፤ፊል 3፥4
11፥22 ሉቃ3፥8፤ ሮሜ9፥4፤11፥1፤ፊል 3፥5
11፥23 ሐሥ16፥23፤ሮሜ8፥36፤1ቆሮ 3፥5፤15፥10፤2ቆሮ 6፥4፡5
11፥24 ዘዳ25፥3
11፥25 ሐሥ14፥19፤16፥22፤27፥1-44
11፥26 ሐሥ20፥3፤ 21፥31፤ገላ2፥4
11፥27 ሐሥ18፥3፤ 1ቆሮ4፥11፡12፤2ቆሮ 6፥5፤ቈላ1፥29
11፥28 1ቆሮ7፥17
11፥29 ማቴ5፥29፤ ሮሜ14፥1፤1ቆሮ2፥3
11፥30 ቍ16፤1ቆሮ 2፥3፤2ቆሮ12፥5፡9፤ገላ 6፥14
11፥31 ቍ11፥ሮሜ 1፥9፡25፤9፥5
11፥32 ሐሥ9፥24
11፥33 ሐሥ9፥25
12፥1 ቍ5፡7፡9፤ 1ቆሮ2፥10፤2ቆሮ 11፥16፡30
12፥2 ቍ4፡ሐሥ8፥39፤ሮሜ16፥3፤2ቆሮ 11፥11፤ኤፌ4፥10
12፥4 ቍ2፤ሉቃ 23፥43፤ራእ2፥7
12፥5 ቍ9፡10፤ 1ቆሮ2፥3
12፥6 ቍ11፤2ቆሮ 10፥8፤11፥16
12፥7 ቍ1፤ዘኍ33፥55፤ማቴ4፥10፤1ቆሮ 2፥10
12፥8 ማቴ26፥39፡44
12፥9 1ነገ19፥12፤ ሮሜ3፥24፤1ቆሮ 2፥3፤ፊል4፥13
12፥10 ማቴ5፥12፤ 2ቆሮ6፥4፤13፥4፤2ተሰ 1፥4
12፥11 1ቆሮ15፥9፡ 10፤2ቆሮ11፥1፡5
12፥12 ዮሐ4፥48
12፥13 ቍ14፤1ቆሮ 9፥12፡18፤2ቆሮ11፥7
12፥14 ምሳ19፥14፤

ከንጉሥ አርስጦስዮስ በታች የሆነው ገዥ
ሊያሲዘኝ ፈልጎ፣ የደማስቆ ሰዎችን ከተማ
ያስጠብቅ ነበር። 33ነገር ግን በግንቡ መስ
ኮት በኩል በቅርጫት አውርደውኝ ከእጁ
አመለጥሁ።

### ጳውሎስ ያየው ራእይና የተሰጠው መውጊያ

12 በመመካት የሚገኝ ጥቅም ባይኖ
ርም፣ መመካት ካስፈለገ ከጌታ
ወደ ተቀበልሁት ራእይና መገለጥ አመራ
ለሁ። 2ከዐሥራ አራት ዓመት በፊት እስከ
ሦስተኛው ሰማይ ድረስ የተነጠቀ በክር
ስቶስ አንድ ሰው ዐውቃለሁ፤ የተነጠቀው
በሥጋ ይሁን ወይም ከሥጋ ውጭ አላው
ቅም፤ እግዚአብሔር ግን ያውቃል። 3ይህ
ሰው በሥጋ ይሁን ወይም ከሥጋ ውጭ
እኔ አላውቅም፤ እግዚአብሔር ግን ያውቃል፤
4እርሱም ወደ ገነት እንደ ተነጠቀ፣ በዚያም
በሰው አንደበት ሊገለጥ የማይችል፣ ሰውም
እንዲናገረው ያልተፈቀደለት ነገር ሰማ።
5እንደዚህ ስላለው ሰው እመካለሁ፤ ስለ ራሴ
ግን ከደካማነቴ በስተቀር አልመካም።
6መመ ካት ብፈልግ እንኳ እንደ ሞኝ
መቈጠር የለብኝም፤ ምክንያቱም
የምናገረው እው ነት ነው። ነገር ግን
ማንም ስለ እኔ ከሚያየው ወይም ከሚሰማው
በላይ እንዳይገምተኝ ከመመካት እቈጠ
ባለሁ።

7ከዚህ ታላቅ መገለጥ የተነሣ እንዳልታ
በይ የሥጋዬ መውጊያ፣ እርሱም የሚያሠ
ቃየኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ።
8ይህ ነገር ከእኔ እንዲወገድልኝ፣ ጌታን
ሦስት ጊዜ ለመንሁት፤ 9እርሱ ግን፣ “ጸጋዬ
ይበቃሃል፤ ኀይሌ ፍጹም የሚሆነው በድካም
ጊዜ ነውና” አለኝ። ስለዚህ የክርስቶስ ኀይል
በእኔ ያድር ዘንድ፣ ይበልጥ ደስ እያለኝ
በድካሜ እመካለሁ። 10ስለ ክርስቶስ በድ
ካም፣ በስድብ፣ በመከራ፣ በስደትና በጭን
ቀት ደስ የምሰኘው ለዚህ ነው፤ ስደክም ያን
ጊዜ ብርቱ ነኝና።

### ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የነበረው ጭንቀት

11በመመካቴ ሞኝ ሆኛለሁ፤ ለዚህም ያበ
ቃችሁኝ እናንተ ናችሁ፤ ስለ እኔ መመስ
ከር የሚገባችሁ እናንተ ነበራችሁ። ደግሞም
እኔ ከምንም የማልቈጠር ብሆንም፣ “ታላ
ላቅ ሐዋርያት” ከሚባሉት በምንም አላን
ስም። 12የእውነተኛ ሐዋርያ ምልክቶች
በመካከላችሁ ተደርገዋል፤ እነርሱም በትዕ
ግሥት መጽናት፣ ምልክቶች፣ ድንቅ ነገሮ
ችና ታምራት ናቸው። 13በእናንተ ላይ ሸክም
ካለመሆኔ በቀር፣ ከሌሎች አብያተ ክርስ
ቲያናት በምን አነሳችሁ? ይህን በደሌን
ይቅር በሉኝ።

14ወደ እናንተ ለመምጣት ስዘጋጅ ይህ
ሦስተኛዬ ነው፤ ስመጣ በምንም ነገር
ሸክም አልሆንባችሁም፤ እኔ እናንተን
እንጂ ከእናንተ ምንም አልፈልግምና፤
ደግሞም ወላጆች ለልጆች ገንዘብ ያከማቻሉ
እንጂ ልጆች ለወላጆች አያከማቹም::
15እኔ ግን ስለ እናንተ ያለኝን ሁሉ ራሴ
ንም ጭምር ብሰጥ ደስ ይለኛል፤ ታዲያ
እኔ የምወዳችሁ ይህን ያህል ከሆነ፣ እናንተ
የምትወዱኝ በጥቂቱ ነውን? 16የሆነው
ሆኖ ሸክም አልሆንሁባችሁም፤ ነገር ግን
በተንኰልና በዘዴ ያጠመድኋችሁ ሳይመ
ስላችሁ አልቀረም! 17ለመሆኑ ወደ
እናንተ በላክኋቸው ሰዎች አማካይነት
በአንዱ እንኳ በዘበዝኋችሁን? 18ቲቶ ወደ
እናንተ እንዲመጣ ለመንሁት፤ ወንድ
ማችንንም ከእርሱ ጋር ላክሁት:: ቲቶ
በዘበዛችሁን? ከእርሱ ጋር በአንድ መንፈስ
አልተመላለ ስንምን? አካሄዳችንስ አንድ
አልነበረ ምን?

19እስከ አሁን ድረስ በእናንተ ፊት ራሳ
ችንን ስንከላከል የኖርን ይመስላችኋልን?
በክርስቶስ ሆነን በእግዚአብሔር ፊት እንናገ
ራለን፤ ደግሞም ወዳጆች ሆይ፤ ይህን ሁሉ
የምናደርገው እናንተን ለማነጽ ነው::
20ወደ እናንተ በምመጣበት ጊዜ፣ እኔ
እንደምፈልገው ሆናችሁ ላላገኛችሁ እችላ
ለሁ ወይም እናንተ እንደምትፈልጉኝ ሆኜ
ላታገኙኝ ትችላላችሁ ብዬ እፈራለሁ፤
ምናልባትም በመካከላችሁ ጥል፣ ቅናት፣
ቍጣ፣ አድመኝነት፣ ስም ማጥፋት፣
ሐሜት፣ እብሪትና ሁከት ይኖራል ብዬ
እሠጋለሁ:: 21ዳግመኛም ስመጣ አምላኬ
በእናንተ ፊት ያዋርደኝ ይሆን ብዬ እፈራ
ለሁ፤ ይኸውም ብዙዎች ከዚህ በፊት ስለ
ሠሩት ኀጢአትና ስለ ፈጸሙትም ርኵ
ሰት፣ ዝሙትና መዳራት ንስሓ ሳይገቡ
ቀርተው እንዳላዝን ነው::

## የመጨረሻ ምክር

13 ወደ እናንተ ስመጣ ይህ ሦስተ
ኛዬ መሆኑ ነው፤ “ማንኛውም
ነገር በሁለት ወይም በሦስት ምስክር ይጸ
ናል::” 2በሁለተኛው ጕብኝቴ እናንተ
ዘንድ በነበርሁበት ጊዜ አስጠንቅቄአችሁ
ነበር፤ አሁንም በሩቅ ሆኜ እንደ ገና አስጠነ

1ቆሮ4፥14፡15፤2ቆሮ13፥1
12፥15 2ቆሮ11፥11፤ፊል2፥17፤1ተሰ2፥8
12፥16 2ቆሮ11፥9
12፥18 2ቆሮ2፥13፤8፥6፡16፡18
12፥19 ሮሜ9፥1፤14፥19፤1ቆሮ10፥14፤2ቆሮ10፥8
12፥20 ሮሜ1፥29፡30፤1ቆሮ1፥11፤3፥3፤4፥18፤21፤14፥33፤2ቆሮ2፥1-4፤ገላ5፥20
12፥21 1ቆሮ6፥18፤2ቆሮ2፥1፡4፤13፥2
13፥1 ዘዳ19፥15፤ማቴ18፥16፤2ቆሮ12፥14
13፥2 ቍ10፤2ቆሮ1፥23፤12፥21
13፥3 ማቴ10፥20፤1ቆሮ5፥4
13፥4 ቍ9፤ሮሜ1፥4፤6፥4፤6፥5፤1ቆሮ1፥25፤2፥3፤6፥14፤ፊል2፥7፡8፤1ጴጥ3፥18
13፥5 ሰቆ3፥40፤ዮሐ6፥6፤ሮሜ8፥10፤1ቆሮ11፥28
13፥9 ቍ11፤1ቆሮ2፥3፤2ቆሮ2፥3፤4፥12፤ኤፌ4፥13
13፥10 2ቆሮ1፥23፤10፥8
13፥11 ማር9፥50፤ሮሜ15፥33፤ኤፌ6፥23፤1ተሰ4፥1፤2ተሰ3፥1፤1ዮሐ4፥16
13፥12 ሮሜ16፥16
13፥13 ፊል4፥22
13፥14 ሮሜ5፥5፤16፥20፤2ቆሮ8፥9፤ፊል2፥1፤ይሁ21

ቅቃችኋለሁ፤ ወደ እናንተም ተመልሼ
ስመጣ ከዚህ በፊት ኀጢአት ለሠሩትም
ሆነ ለሌሎች አልራራላቸውም፤ 3ይህም
የሚሆነው ክርስቶስ በእኔ አድሮ እንደሚ
ናገር ማስረጃ በመፈለጋችሁ ነው:: እር
ሱም በመካከላችሁ ብርቱ እንጂ ደካማ
አልነበረም:: 4የተሰቀለው በድካም ቢሆ
ንም፣ በእግዚአብሔር ኀይል ሕያው ሆኖ
ይኖራል:: እኛም በእርሱ ደካሞች
ብንሆንም፣ እናንተን ለማገልገል ግን
በእግዚአብሔር ኀይል ከእርሱ ጋር ሕያዋን
ሆነን እንኖራለን::

5በእምነት መሆናችሁን ለማወቅ ራሳች
ሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ:: ፈር
የወጣችሁ ካልሆነ በስተቀር፣ ኢየሱስ ክር
ስቶስ በውስጣችሁ እንዳለ አታውቁምን?
6እኛ ግን ብቁ መሆናችንን እንደምትገነ
ዘቡ ተስፋ አደርጋለሁ:: 7አሁንም ምንም
ክፉ ነገር እንዳታደርጉ ወደ እግዚአብሔር
እንጸልያለን፤ የምንጸልየውም እኛ ብቀ
ዎች እንደሆንን ሰዎች እንዲያዩልን
አይደለም፤ ነገር ግን እኛ ምንም እንኳ
ብቁዎች ባነሆ ንም እናንተ መልካም
የሆነውን ነገር እንድ ታደርጉ ነው::
8ለእውነት እንጂ በእውነት ላይ ምንም
ማድረግ አንችልምና:: 9እኛ ደካሞች
ስንሆን፣ እናንተ ግን ብርቱዎች ስትሆኑ
ደስ ይለናል፤ ጸሎታችንም እና ንተ ፍጹ
ማን እንድትሆኑ ነው:: 10ከእና ንተ ርቄ
ሳለሁ እነዚህን ነገሮች የምጽፍ ላችሁ ወደ
እናንተ በምመጣበት ጊዜ ሥልጣኔን
በኀይል እንዳልጠቀም ነው፤ ጌታ ም
ይህን ሥልጣን የሰጠኝ እናንተን ለማነ
ጽ እንጂ ለማፍረስ አይደለም::

## የመጨረሻ ሰላምታ

11በተረፈ ወንድሞች ሆይ፤ ደኅና ሁኑ::
ፍጹማን ሁኑ፤ ምክሬን ስሙ፤ አንድ ሐሳብ
ይኑራችሁ፤ በሰላምም ኑሩ:: የፍቅርና የሰላ
ምም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል:: 12በተ
ቀደሰ አሳሳም እርስ በርሳችሁ ሰላምታ
ተሰጣጡ:: 13ቅዱሳን ሁሉ ሰላምታ
ያቀርቡ ላችኋል::

14የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ የእግዚ
አብሔር ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት
ከሁላችሁ ጋር ይሁን::

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት
# ወደ ገላትያ ሰዎች

1 ከሰዎች ወይም በሰው ከተላከው
ሳይሆን፣ በኢየሱስ ክርስቶስና ከሙታን
ባስነሣው በእግዚአብሔር አብ ሐዋርያ ከሆነው
ከጳውሎስ፤ 2አብረውኝም ካሉት ወንድ
ሞች ሁሉ፤

## በገላትያ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት

3ከአባታችን ከእግዚአብሔር፣ ከጌታም ከኢ
የሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ
ይሁን። 4እንደ አምላካችንና እንደ አባታችን
ፈቃድ፣ ከዚህ ክፉ ዓለም ያድነን ዘንድ
ስለ ኀጢአታችን ራሱን ለሰጠ 5ከዘላለም
እስከ ዘላለም ለእርሱ ክብር ይሁን፤ አሜን።

## ወንጌል አንዲት ናት

6በክርስቶስ ጸጋ የጠራችሁን እርሱን
ትታችሁ፣ ወደ ተለየ ወንጌል እንዲህ
ፈጥናችሁ መዞራችሁ ደንቆኛል፤ 7እንደ
እውነቱ ከሆነ ሌላ ወንጌል የለም። የሚያደነ
ጋግሯችሁና የክርስቶስን ወንጌል ለማጣ
መም ጥረት የሚያደርጉ አንዳንድ ሰዎች
አሉ። 8ነገር ግን እኛም ብንሆን ወይም
የሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል
የተለየ ወንጌል ቢሰብክላችሁ እርሱ ለዘላለም
የተረገመ ይሁን። 9ቀደም ብለን እንዳልነው፣
አሁንም ደግሜ እላለሁ፤ ማንም ከተቀበላች
ሁት ሌላ የተለየ ወንጌል ቢሰብክላችሁ፣
እርሱ ለዘላለም የተረገመ ይሁን።
10አሁን እኔ ጐሽ ለመባል የምሻው በሰ
ዎች ዘንድ ነው ወይስ በእግዚአብሔር ዘንድ?
ወይስ ሰዎችን ደስ ለማሰኘት እየተጣጣርሁ
ነው? ሰዎችን ደስ ለማሰኘት የምጥር
ብሆን ኖሮ፣ የክርስቶስ አገልጋይ ባልሆንሁ
ነበር።

## ጳውሎስ በእግዚአብሔር መጠራቱ

11ወንድሞች ሆይ፤ የሰበክሁላችሁ ወንጌል
ሰው ሠራሽ አለመሆኑን እንድታውቁ እፈ
ልጋለሁ፤ 12ከማንም ሰው አልተቀበልሁትም፤
ከማንም አልተማርሁትም፤ ይልቁንስ በመ
ገለጥ ከኢየሱስ ክርስቶስ ተቀበልሁት።
13ቀድሞ በአይሁድ ሃይማኖት እንዴት
እንደኖርሁ፣ የእግዚአብሔርንም ቤተ ክርስ
ቲያን እንዴት በእጅጉ እንዳሳደድሁ፣ ለማ
ጥፋትም እንዴት እንደጣርሁ ሰምታች
ኋል፤ 14በእኔ ዕድሜ ዘመን ከነበሩት ከብ
ዙዎቹ አይሁድ ይበልጥ በአይሁድ ሃይ
ማኖት እልቅ ነበር፤ ስለ አባቶቼም ወግ
እጅግ ቀናተኛ ነበርሁ። 15ነገር ግን፣
ከእናቴ ማሕፀንυ ጀምሮ የለየኝና በጸጋው
የጠራኝ እግዚአብሔር፣ 16በአሕዛብ መካከል
ስለ እርሱ እንድሰብክ ልጁን በእኔ ሊገልጥ
በወደደ ጊዜ፣ ከማንም ሥጋ ለባሽ ጋር
አልተማከርሁም፤ 17ከእኔ በፊት ሐዋርያት
ወደ ሆኑትም ወደ ኢየሩሳሌም አልወ
ጣሁም፤ ነገር ግን ወዲያው ወደ ዐረብ
አገር ሄድሁ፤ በኋላም ወደ ደማስቆ ተመ
ለስሁ።
18ከዚያም ከሦስት ዓመት በኋላ፣
ጴጥሮስንφ አገኘው ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም
ወጣሁ፤ ከእርሱም ጋር ዐሥራ አምስት ቀን
ተቀ መጥሁ። 19ነገር ግን ከጌታ ወንድም
ከያዕቆብ በቀር፣ ከሐዋርያት ማንንም አላየ
ሁም። 20በምጽፍላችሁ ነገር በእግዚአብሔር
ፊት ሐሰት እንደማልናገር አስረግጬ እነ
ግራችኋለሁ። 21ከዚያም በኋላ፣ ወደ ሶር
ያና ወደ ኪልቅያ አገር ሄድሁ። 22በክ
ርስቶስ ያሉት የይሁዳ አብያተ ክርስ
ቲያናትም ፊቴን አይተው አያውቁም
ነበር፤ 23እነርሱ ግን፣ “ቀድሞ እኛን ሲያ
ሳድድ የነበረ ሰው፣ ከዚህ በፊት ሊያጠ
ፋው ይፈልግ የነበረውን እምነት አሁን
እየሰበከ ነው” የሚለውን ወሬ ብቻ ሰምተው
ነበር፤ 24በእኔም ምክንያት እግዚአብሔርን
አመሰገኑ።

## ጳውሎስን ሐዋርያት ተቀበሉት

2 ከዐሥራ አራት ዓመት በኋላም፣ ዳግመኛ
ወደ ኢየሩሳሌም ወጣሁ፤ በዚህ
ጊዜ ከበርናባስ ጋር ነበርሁ፤ ቲቶንም
ይዤው ሄጄ ነበር። 2ካገኘሁትም መገለጥ
የተነሣ ወደዚያ ሄድሁ፤ በአሕዛብ መካከል
የምሰብከውን ወንጌል ለእነርሱም ገለጥ
ሁላቸው። ይሁን እንጂ፣ ምናልባት በከንቱ
እየሮጥሁ ወይም ሮጬ እንዳይሆን በመ
ሥጋት፣ ዋነኞች ለሚመስሉት ብቻ በግል
ይህን አስታወቅኋቸው። 3ከእኔ ጋር የነበ
ረው ቲቶ እንኳ የግሪክ ሰው ቢሆንም፣
እንዲገረዝ አልተገደደም ነበር። 4ይህ
ጕዳይ የተነሣው አንዳንድ ሐሰተኞች
ወንድሞች በክርስቶስ ኢየሱስ ያገኘነውን
ነጻነት ሊሰልሉና ባሪያዎች ሊያደርጉን
ወደ እኛ ሾልከው በመግባታቸው ነው።
5ለእነዚህ ሰዎች ለአንድ አፍታ እንኳ አል
ተገዛንላቸውም፤ ይኸውም፣ የወንጌል እው
ነት ከእናንተ ጋር ጸንቶ እንዲኖር ነው።

υ15 ወይም *ከመወለዴ*

1፥1 ቆላ11፡12፡15፡16፤ሐሃ24፤9፤15፤20፥24፤1ቆሮ1፥1
1፥2 ሐሥ16፥6፤ፊል4፥21
1፥3 ሮሜ1፥7
1፥4 ማቴ20፥28፤ሮሜ4፥25፤1ቆሮ1፥20፤15፥3፤ገላ2፥20፤ፊል4፥20
1፥5 ሮሜ11፥36
1፥6 ቆላ15፤ሮሜ8፥28፤2ቆሮ11፥4
1፥7 ኤር23፥16፡36፤ሐሥ15፥24፤ገላ5፥10
1፥8 ቆላ11፡16፤ሮሜ9፥3፤1ቆሮ15፥1፤2ቆሮ11፥4፤ገላ2፥2
1፥9 ሮሜ16፥17
1፥10 ሮሜ2፥29
1፥11 ቆላ8፤1ቆሮ15፥1
1፥12 ቆላ1፡16፤1ቆሮ2፥10፤11፥23፤15፥3
1፥13 ሐሥ8፥3፤26፥4፡5፤1ቆሮ10፥32
1፥14 ማቴ15፥2፤ሐሥ21፥20፤ 1፥15 ኢሳ49፥1፡5፤ኤር1፥5፤ሐሥ9፥15፤ሮሜ8፥28፤
1፥16 ማቴ16፥17፤ሐሥ9፥15፤ገላ2፥9፤
1፥17 ሐሥ9፥21፤9፥22
1፥18 ሐሥ9፥22፡23፡26፤27፤
1፥19 ማቴ13፥55፤ሐሥ15፥13
1፥20 ሮሜ1፥9፤9፥1
1፥21 ሉቃ2፥2፤ሐሥ6፥9
1፥22 ሮሜ16፥3፤1ተሰ2፥14
1፥23 ሐሥ6፥7፤8፥3
1፥24 ማቴ9፥8

2፥1 ሐሥ4፥36፤15፥2ቆሮ2፥13
2፥2 ሐሥ15፥4፡12፤1ቆሮ2፥10፤9፥24
2፥3 ቆላ1፤ሐሥ16፥3፤1ቆሮ9፥21፤2ቆሮ2፥13
2፥4 ሐሥ1፥16፤2ቆሮ11፥26፤ገላ5፥1፥13፤ይሁ4
2፥5 ቆላ14

6ዋነኛ መስለው ስለሚታዩት ሰዎች ማን
ነት እኔን አይገደኝም፤ እግዚአብሔር የሰውን
ፊት አይቶ አያደላም፤ እነዚህም ሰዎች
ለመልእክቴ የጨመሩልኝ ነገር የለም::
7ነገር ግን ጴጥሮስ ለተገረዙት[ሐ] ወንጌልን
እንዲሰብክ ዐደራ እንደ ተሰጠው፣ እኔም
ላልተገረዙት[መ] ወንጌልን እንድሰብክ አደራ
እንደ ተሰጠኝ ተገነዘቡ፤ 8ጴጥሮስ ለአይ
ሁድ ሐዋርያ እንዲሆን የሠራ እግዚአብሔር፣
በእኔ የአሕዛብ ሐዋሪያዊ አገልግሎትም
ሠርቶአል:: 9እንደ አዕማድ የሚቈጠሩት
ያዕቆብ፣ ጴጥሮስና[ሠ] ዮሐንስም የተሰጠኝን
ጸጋ ባስተዋሉ ጊዜ፣ ለእኔና ለባርናባስ
የትብብር ቀኝ እጃቸውን ሰጡን፤ ከዚያም
እኛ ወደ አሕዛብ፣ እነርሱ ደግሞ ወደ
አይሁድ እንድሄድ ተስማሙ::
10አጥብቀው ዐደራ ያሉን ድኾችን
ማሰባችንን እንዳናቋርጥ ብቻ ነው፤ እኔም
ይህንኑ ለማድረግ ጕጕቴ ነበር::

### ጳውሎስ ጴጥሮስን ተቃወመው

11ጴጥሮስ ወደ አንጾኪያ በመጣ ጊዜ፣
በግልጥ ስቶ ስለ ነበር ፊት ለፊት
ተቃወምሁት:: 12አንዳንድ ሰዎች ከያዕቆብ
ዘንድ ከመምጣታቸው በፊት፣ ከአሕዛብ
ጋር ይበላ ነበር፤ እነርሱ በመጡ ጊዜ ግን
የተገረዙትን ወገኖች ፈርቶ ከአሕዛብ ራ
ሱን በመለየት ገሸሽ ማለት ጀመረ፤ 13በር
ናባስም እንኳ በእነርሱ ግብዝነት እስኪ
ወሰድ ድረስ፣ ሌሎቹም አይሁድ
በግብዝነቱ ተባበሩት:: 14ተግባራቸው
እንደ ወንጌል እውነት አለመሆኑን
በተረዳሁ ጊዜ፣ በሁሉም ፊት ጴጥሮስን
እንዲህ አልሁት፤ "አንተ አይሁዳዊ ነህ፤
ሆኖም በአሕዛብ ሥርዐት እንጂ በአይሁድ
ሥርዐት አት ኖርም፤ ታዲያ አሕዛብ
የአይሁድን ሥርዐት እንዲከተሉ እንዴት
ታስገድዳቸዋለህ? 15"እኛ በትውልዳችን
አይሁድ እንጂ፣ 'ኀጢአተ ኞች አሕዛብ'
ያልሆን፣ 16ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በ
ማመን እንጂ፣ ሕግን በመጠ በቅ እንደ
ማይጸድቅ እናውቃለን:: ስለ ዚህ ሕግን
በመጠበቅ ሳይሆን፣ በክርስቶስ በማመን
እንጸድቅ ዘንድ እኛም ደግሞ በክርስቶስ
ኢየሱስ አምነናል፤ ሕግን በመጠበቅ
ማንም አይጸድቅምና::
17"በክርስቶስ ለመጽደቅ ስንፈልግ፣ እኛ
ራሳችን ኀጢአተኞች መሆናችን ግልጽ
ነው፤ ታዲያ ክርስቶስ ኀጢአት እንዲ
ስፋፋ ያደርጋልን? ፈጽሞ አይደለም!::
18ያፈ ረስሁትን መልሼ የምገነባ ከሆነ
ማ ሕግ ተላላፊ መሆኔን አረጋግጣለሁ::
19ለእግዚአብሔር እኖር ዘንድ፣ በሕግ በኩል
ለሕግ ሞቻለሁና:: 20ከክርስቶስ ጋር
ተሰቅያለሁ፤ ከእንግዲህ እኔ አልኖርም፤
ነገር ግን ክር ስቶስ በውስጤ ይኖራል::
አሁንም በሥጋ የምኖረው ኑሮ በወደደኝና
ስለ እኔ ራሱን አሳልፎ በሰጠው በእግዚ
አብሔር ልጅ ላይ ባለኝ እምነት ነው::
21የእግዚአብሔርን ጸጋ አላቃልልም፤ ጽድቅ
በሕግ በኩል የሚገኝ ከሆነማ፣ ክርስቶስ
እንዲያው በከንቱ ሞተ ማለት ነዋ!"[ረ]

### እምነት ወይስ የኦሪትን ሕግ መጠበቅ

3 እናንተ የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች
ሆይ! ለመሆኑ ማን መተት አደረ
ገባችሁ? ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ
ሆኖ በፊት ለፊታችሁ በግልጥ ተሥሎ
ነበር:: 2ከእናንተ ዘንድ አንድ ነገር ብቻ
ማወቅ እፈልጋለሁ፤ መንፈስን የተቀበ
ላችሁት ሕግን በመጠበቅ ነው ወይስ
የተሰበከላችሁን በማመን? 3ይህን ያህል
የማታስተውሉ ናችሁን? በመንፈስ ጀምራ
ችሁ በሥጋ ፍጹም ለመሆን ትጥራ
ላችሁን? 4በእርግጥ ለከንቱ ከሆነ፣ ይህን
ያህል መከራ የተቀበላችሁት እንዲያው
ነውን? 5እግዚአብሔር መንፈሱን
የሚሰጣችሁ፣ በእናንተም ዘንድ ታምራ
ትን የሚሠራው
ሕግን ስለ ጠበቃችሁ ነው ወይስ የሰ
ማችሁትን ስላመናችሁ?
6እስቲ አብርሃምን አስቡ፤ "እርሱ እግዚአ
ብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረ
ለት::" 7እንግዲህ እነዚያ የሚያምኑት
የአብርሃም ልጆች እንደ ሆኑ አስተውሉ::
8መጽሐፍ፣ እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት
እንደሚያጸድቅ አስቀድሞ በማየት፣ "አሕ
ዛብ ሁሉ በአንተ ይባረካሉ" በማለት
ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ አስታወቀው::
9ስለዚህ በእምነት የሆኑት፣ የእምነት ሰው
ከሆነው ከአብርሃም ጋር ቡሩካን ናቸው::
10ሕግን በመጠበቅ የሚተማመኑ ሁሉ
ከእርግማን በታች ናቸው፤ "በሕግ መጻሕ
ፍት የተጻፈውን ሁሉ የማያደርግ የተረ
ገመ ነው" ተብሎ ተጽፎአልና::
11"ጻድቅ በእምነት ይኖራል" ስለ ተባለ፣
ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንደማይ
ጸድቅ ግልጽ ነው:: 12ሕግ በእምነት ላይ
የተመሠረተ አይደለም፤ ነገር ግን "ሕግ
ጋትን የሚፈጽም ሰው በእነርሱ በሕይወት
ይኖራል" ተብሎአል::

2÷6 ቍ2፤ሐሥ 10÷34፤1ቆሮ 15÷11፤ራእ2÷23
2÷7 ቍ9:11:14 ሐሥ9÷15፤1ተሰ 2÷4፤1ጢሞ1÷11
2÷8 ሐሥ1÷25፤ 1ቆሮ1÷1
2÷9 ቍ1:7:11: 14፤ሐ4÷36፤9÷15፤1 5÷13፤ሮሜ12÷3፤ 1ጢሞ3÷15 ራእ3÷12
2÷10 ሐሥ24÷17
2÷11 ቍ7ቸ9ቸ 14፤ሐሥ11÷19
2÷12 ሐሥ10÷45 11÷2፤11÷3፤15÷13
2÷13 ቍ1፤ ሐሥ 4÷36
2÷14 ቍ5:7:9: 11:12፤ ሐሥ10÷28
2÷15 1ሳሙ15÷18 ፤ሉቃ24÷7፤ ፊል3÷3:5
2÷16 ሮሜ3÷8፤ 4÷25፤9÷30
2÷17 ቍ15፤ ገላ3÷21
2÷19 ሮሜ6÷10: 11:14፤7÷4፤2ቆሮ5÷ 15
2÷20 ማቴ4÷3፤ ሮሜ 6÷6፤ 8÷10፤8÷37፤ ገላ1÷4፤1ጴጥ4÷2
2÷21 ገላ3÷21
3÷1 ሉቃ24÷25 ፤ሐሥ16÷6፤1ቆሮ 1÷23፤ገላ5÷7
3÷2 ቍ5:10፤ ዮሐ20÷22፤ሮሜ 10÷17፤ ገላ2÷16፤ዕብ 4÷2
3÷5 ቍ2ቸ10፤ 1ቆሮ12÷10፤ገላ 2÷16
3÷6 ዘፍ15÷6፤ ሮሜ4÷3
3÷7 ቍ9፤ሉቃ3÷8
3÷8 ዘፍ12÷3፤ 18÷18፤22÷18፤26÷ 4፤ ሐሥ3÷25
3÷9 ቍ7፤ሮሜ 4÷16፤ 4÷18ኛ22
3÷10 ቍ2ቸ5ቸ13፤ ዘዳ27÷26፤ኤር11÷3 ፤ሮሜ 4÷15፤ ገላ2÷16
3÷11 ዕብ2÷4፤ ሮሜ 3÷28፤9÷30፤ ዕብ 10÷38
3÷12 ዘሌ18÷5፤ ሮሜ 10÷5

[ሰ]18 ግሪኩ *ኬፋ* ይለዋል::
[ረ]21 አንዳንድ ተርጓሚዎች ትምህርተ ጥቅሱን ከቍ14 በኋላ ያደርጋሉ::
[ሐ]7 ወይም *ለአይሁድ*
[መ]7 ወይም *ለአረማዊያን* እንዲሁም ቍ8 እና 9 ይመ
[ሠ]9 ግሪኩ *ኬፋ* ይላል፤ እንዲሁም ቍ11 እና 14 ይመ

13“በዕንጨት ላይ የሚሰቀል ሁሉ የተ
ረገመ ነው” ተብሎ ስለ ተጻፈ፣ ክርስቶስ
ስለ እኛ ርግማን ሆኖ ከሕግ ርግማን
ዋጅቶናል፤ 14ለአብርሃም የተሰጠው በረከት፣
በክርስቶስ ኢየሱስ ለአሕዛብ እንዲደርስ
ዋጅቶናል፤ ይኸውም በእምነት የመንፈስን
ተስፋ እንድንቀበል ነው።

## የኦሪት ሕግና የተስፋ ቃል

15ወንድሞች ሆይ፤ ከሰው ዕለታዊ ሕይ
ወት የተለመደውን ምሳሌ አድርጌ ላቅርብ፤
የሰው ኪዳን እንኳ አንድ ጊዜ ከጸደቀ
በኋላ ማንም ሊሽረው ወይም በእርሱ ላይ
ሊጨምርበት እንደማይችል ሁሉ፣ በዚህም
ጕዳይ ቢሆን እንደዚሁ ነው። 16የተስ
ፋውም ቃል የተነገረው ለአብርሃምና
ለዘሩ ነበር፤ መጽሐፍ፣ ለብዙ ሰዎች እንደ
ሚነገር፣ “ለዘሮቹ” አይልም፤ ነገር ግን
ለአንድ ሰው እንደሚነገር፣ “ለዘርህ”
ይላል፤ እርሱም ክርስቶስ ነው። 17የምለው
እንዲህ ነው፤ ከአራት መቶ ሠላሳ ዓመት
በኋላ የተሰጠው ሕግ፣ አስቀድሞ በእግዚ
አብሔር የጸናውን ኪዳን አፍርሶ የተስፋውን
ቃል አይሽርም። 18ርስትን መውረስ
በሕግ ቢሆን ኖሮ፣ በተስፋ ቃል ባልተገኘ
ነበርና፤ እግዚአብሔር ግን በጸጋው በተስፋ
ቃል አማካይነት ለአብርሃም ሰጥቶታል።
19ታዲያ ሕግ የተሰጠበት ምክንያት
ምንድን ነው? ሕግ የተጨመረው ከመ
ተላለፍ የተነሣ ተስፋው ያመለከተው ዘር
እስኪመጣ ድረስ ነበር፤ ሕጉም የመጣው
በመላእክት በኩል፣ በአንድ መካከለኛ
እጅ ነበር። 20ሆኖም መካከለኛው አንድን
ወገን ብቻ የሚወክል አይደለም፤ እግዚአብሔር
ግን አንድ ነው። 21ታዲያ ሕግ የእግዚአብሔርን
የተስፋ ቃል የሚቃወም ነውን? ከቶ አይ
ደለም፤ ሕግ የተሰጠው ሕይወትን ለማስገኘት
ቢሆን ኖሮ፣ በእርግጥም ጽድቅ በሕግ
በኩል በተገኘ ነበር። 22መጽሐፍ ግን ዓ
ለም ሁሉ የኀጢአት እስረኛ መሆኑን
ያውጃል፤ ይኸውም በኢየሱስ ክርስቶስ በ
ማመን የሚ ገኘው ተስፋ ለሚያምኑት
ሁሉ ይሰጥ ዘንድ ነው።
23ይህ እምነት ከመምጣቱ በፊት በሕግ
አማካይነት እስረኞች ሆነን፣ እምነት እስ
ከሚገለጥ ድረስ ተዘግቶብን ነበርን።
24ስለዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ
ወደ ክርስቶስ የሚያደርሰን[ሰ] ሞግዚታችን
ሆነ። 25አሁን ግን ያ እምነት ስለ መጣ፣
ከእንግዲህ በሕግ ሞግዚትነት ሥር
አይደለንም።

3÷13 ዘዳ21÷23፤ ሐሥ5÷30፤ገላ4÷5
3÷14 ቍ2፤ኢል 2÷28፤ዮሐ20÷22፤ ሐሥ2÷33፤ ሮሜ4÷9ቸ16
3÷15 ሮሜ7÷1
3÷16 ዘፍ12÷7፤ 13÷15፤17÷7ቸ8ቸ10፤17÷19፤24÷7፤መዝ 132÷11፤ሚክ7÷20፤ሉቃ1÷55፤ሮሜ 4÷13ቸ16፤9÷4ቸ8፤ ገላ3÷29፤4÷28
3÷17 ዘፍ15÷13፡ 14፤ዘፀ12÷40፤ ሐሥ7÷6
3÷18 ሮሜ4÷14
3÷19 ቍ16፤ዘፀ 20÷19፤ዘዳ5÷5፤ 33÷2፤ሐሥ7÷53፤ ሮሜ5÷20
3÷20 1ጢ2÷5፤ ዕብ8÷6፤9÷15፤ 12÷24
3÷21 ሮሜ7÷12፤ ገላ 2÷17፤2÷21
3÷22 ሮሜ 3÷9ኛ19፤ 11÷3
3÷23 ቍ25፤ ሮሜ 11÷32
3÷24 ቍ19፤ሮሜ 4÷15፤10÷4፤ ገላ2÷16
3÷25 ሮሜ7÷4
3÷26 ሮሜ8÷14
3÷27 ማቴ 28÷19፤ሮሜ 13÷14
3÷28 ዘፍ1÷27፤ 5÷2፤ኢል2÷29፤ ዮሐ10÷16፤17÷11፤ 1ቆሮ12÷13፤ኤፌ 2÷14ቸ15፤ቈላ3÷11
3÷29 ቍ16፤ ሉቃ3÷8፤ሮሜ 8÷17፤ 1ቆሮ3÷23፤ገላ3÷16
4÷3 ቍ8ቸ9ቸ 24ቸ25፤ገላ2÷4፤ ቈላ2÷8ቸ20፤
4÷4 ማር1÷15፤ ሉቃ2÷27፤ዮሐ1÷14፤3÷17፤ሮሜ5÷6፤ ኤፌ1÷10
4÷5 ዮሐ1÷12፤ ሮሜ3÷24፤8÷14
4÷6 ሐሥ16÷7፤ ሮሜ 5÷58÷15ቸ16
4÷7ሮሜ8÷17
4÷8 ቍ3፤2ዜና 13÷9፤ኢሳ37÷19፤ ኤር2÷11፤5÷7፤ 16÷20፤ሮሜ1÷28፤ 1ቆሮ1÷21፤8÷4ቸ5፤ 15÷34
4÷9 ቍ3፤8÷3፤ ቈላ2÷20
4÷12 ሮሜ7÷1፤ ገላ 6÷18
4÷13 1ቆሮ 2÷3

## የእግዚአብሔር ልጆች

26ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን
የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ፤ 27ከክርስቶስ
ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ
ሁላችሁ ክርስቶስን ለብሳችሁታልና።
28በአይሁድና በግሪክ፣ በባሪያና በነጻ
ሰው፣ በወንድና በሴት መካከል ልዩነት
የለም፤ ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ
አንድ ናችሁ። 29የክርስቶስ ከሆናችሁ፣
እናንተ የአብርሃም ዘር ናችሁ፤ እንደ
ተስፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ።

4 እኔ የምለው ይህ ነው፤ ወራሹ ሕፃን
እስከ ሆነ ድረስ፣ ሀብት ሁሉ የእርሱ
ቢሆንም እንኳ፣ ከባሪያ የተለየ አይ
ደለም። 2አባቱ እስከ ወሰነለት ጊዜ ድረስ
በጠባቂዎችና በሞግዚቶች ሥር ነው።
3እኛም እንዲሁ ገና ልጆች በነበርንበት
ጊዜ ከዓለም መሠረታዊ ትምህርት ሥር
በመሆን በባርነት ተገዝተን ነበር። 4ነገር
ግን የተወሰነው ዘመን በደረሰ ጊዜ፣ እግዚ
አብሔር ከሴት የተወለደውን፣ ከሕግም
በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤ 5ይህም
የሆነው የልጅነትን መብት እናገኝ ዘንድ
ከሕግ በታች ያሉትን ለመዋጀት ነው።
6ልጆችም ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔር፣ “አባ[ሸ]
አባት” ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ
ወደ ልባችን ላከ።
7ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ነህ
እንጂ ባሪያ አይደለህም፤ ልጅም ስለ
ሆንህ፣ እግዚአብሔር ወራሽ አድርጎሃል።

## ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች ማሰቡ

8እግዚአብሔርን ከማወቃችሁ በፊት፣ በባሕ
ርያቸው አማልክት ላልሆኑት ባሪያዎች
ነበራችሁ፤ 9አሁን ግን እግዚአብሔርን ዐው
ቃችሁታል፤ ይልቁን ደግሞ በእግዚአብሔር
ታውቃችኋል። ታዲያ እንደ ገና ወደ ደካ
ማና ወደማይጠቅም ትምህርት እንዴት
ትመለሳላችሁ? ዳግም በእርሱ በባርነት
ለመጠመድ ትፈልጋላችሁን? 10ልዩ የሆኑ
ቀኖችን፣ ወሮችን፣ ወቅቶችንና ዓመ
ታትን ታከብራላችሁ። 11ስለ እናንተ
በከንቱ የደከምሁ እየመሰለኝ እፈራላች
ኋለሁ።
12ወንድሞች ሆይ፤ እለምናችኋለሁ፤ እኔ
እናንተን እንደ መሰልሁ እናንተም እኔን
ምሰሉ። እናንተ አንዳች አልበደላችሁኝም።
13እንደምታውቁት በመጀመሪያ ለእናንተ
ወንጌልን የሰበክሁት፣ በሕመም ምክንያት
ነበር።

[ሰ]24 ወይም *ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ*
[ሸ]6 በአረማይኩ *አባት* ማለት ነው።

14ሕመሜ ለእናንተ ፈተና ሆኖባችሁም
እንኳ፣ አልሰለቻችሁኝም፤ ወይም አልተጸየ
ፋችሁኝም፤ ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር
መልአክ፣ እንዲያውም እንደ ራሱ እንደ ኢየ
ሱስ ክርስቶስ አድርጋችሁ ተቀበላችሁኝ።
15ለመሆኑ ያ ሁሉ ደስታችሁ የት ደረሰ?
ቢቻላችሁ ዐይናችሁን ቢሆን እንኳ አውጥ
ታችሁ የምትሰጡኝ እንደ ነበራችሁ
እመሰክራለሁ። 16እውነቱን ስለ ነገርኋችሁ
ጠላት ሆንሁባችሁን ?
17እነዚያ ሰዎች ወደራሳቸው ሊወ
ስዷችሁ ይተጋሉ፤ ለበጎ ግን አይደለም፤
የሚፈልጉት እናንተን ከእኛ ነጥለው የራ
ሳቸው ሊያደርጓችሁ ነው። 18ለበጎ እስከ
ሆነ ድረስ ተቈርቋሪ መሆን መልካም ነው፤
ይህም መሆን የሚገባው ዘወትር እንጂ
እኔ ከእናንተ ጋር ሳለሁ ብቻ አይደለም።
19የምወዳችሁ ልጆቼ ሆይ፤ ክርስቶስ በውስ
ጣችሁ እስኪቀረጽ ድረስ ስለ እናንተ
እንደ ገና ምጥ ይዞኛል፤ 20ስለ እናንተ
ግራ በመጋባት ተጨንቄአለሁና፤ አሁን
በመካከላችሁ ተገኝቼ ለየት ባለ ቋንቋ
ልናገራችሁ ምን ያህል በወደድሁ!

### አጋርና ሣራ ምሳሌ መሆናቸው

21እናንት ከኦሪት ሕግ በታች ለመኖር
የምትሹ እስቲ ንገሩኝ፤ ሕግ ምን እንደ
ሚል አልሰማችሁምን? 22አብርሃም፣ አንዱ
ከባሪያዪቱ፣ ሌላው ደግሞ ከነጻዪቱ ሴት
የሆኑ ሁለት ልጆች እንደ ነበሩት
ተጽፎአልና። 23ባሪያ ከነበረችው ሴት
የተገኘው ልጅ፣ እንደ ሥጋ ልማድ ነበር፤
ከነጻዪቱ ሴት የተወለደው ግን በተስፋው
ቃል መሠረት ነው።
24እነዚህ ሴቶች ሁለቱን ኪዳኖች ስለ
ሚያመለክቱ፣ ይህ ሁኔታ እንደ ምሳሌ
የሚታይ ነው። አንደኛዋ ኪዳን ከሲና
ተራራ ስትሆን፣ ለባርነት የሚሆኑ ልጆ
ችን የምትወልድ ናት፤ እርሷም አጋር
ናት። 25እንግዲህ አጋር በዐረብ አገር
ያለችው የሲናን ተራራ በመወከል፣ አሁን
ያለችውን ኢየሩሳሌም ትመስላለች፤ ከልጇ
ጋር በባርነት ናትና። 26ከላይ የሆነችው
ኢየሩሳሌም ግን በነጻነት ትኖራለች፤
እርሷም እናታችን ናት። 27እንዲህ ተብሎ
ተጽፎአልና፤

"አንቺ የማትወልጂ መካን ሆይ፤
ደስ ይበልሽ፤
አንቺ አምጠሽ የማታውቂ፣
በእልልታ ጩኺ፤
ባል ካላት ይልቅ፣
የብቸኛዪቱ ልጆች በዝተዋልና።"

28እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ እናንተም
እንደ ይስሐቅ የተስፋው ቃል ልጆች
ናችሁ። 29በዚያን ጊዜ እንደ ሥጋ ልማድ
የተወለደው፣ ልጅ በመንፈስ ኀይል የተ
ወለደውን አሳደደው፤ አሁንም እንደዚያው
ነው። 30ነገር ግን መጽሐፍ ምን ይላል?
"ባሪያዪቱን ከልጇ ጋር አስወግዳት፤ የባ
ሪያዪቱ ልጅ ከነጻዪቱ ልጅ ጋር አይወ
ርስምና" ይላል። 31ስለዚህ ወንድሞች
ሆይ፤ እኛ የነጻዪቱ እንጂ የባሪያዪቱ ልጆች
አይደለንም።

5 ክርስቶስ ነጻ ያወጣን በነጻነት እንድን
ኖር ነው። ስለዚህ ጸንታችሁ ቁሙ፤
ዳግመኛም በባርነት ቀንበር አትጠመዱ።
2የምለውን አስተውሉ፤ ትገረዙ ዘንድ ብት
ፈልጉ፣ ክርስቶስ ፈጽሞ ለእናንተ እንደማ
ይበጃችሁ እኔ ጳውሎስ እነግራችኋለሁ።
3መገረዝ ለሚፈልግ ሁሉ ሕግን በሙሉ
የመፈጸም ግዴታ እንዳለበት እንደ ገና
ለእያንዳንዱ በግልጽ እናገራለሁ። 4በሕግ
ለመጽደቅ የምትጥሩ፣ ከክርስቶስ
ተለይታችኋል፤ ከጸጋ ርቃችኋል። 5እኛ
ግን ተስፋ የምናደርገውን ጽድቅ፣ በመ
ንፈስ አማካይነት በእምነት ሆነን በናፍቆት
እንጠባበቃለን። 6በክርስቶስ ኢየሱስ ከሆኑ፣
መገረዝ ወይም አለመገረዝ አይጠቅም
ምና፤ የሚጠቅመውስ በፍቅር የሚገለጽ
እምነት ብቻ ነው።
7ሩጫችሁ መልካም ነበር፤ ታዲያ
ያሰናከላችሁ፣ ለእውነትስ እንዳትታዘዙ
የከለከላችሁ ማን ነው? 8እንዲህ ያለው
ማባበል ከሚጠራችሁ የመጣ አይደለም፤
9"ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ ያቦካል።"
10የተለየ ሐሳብ እንደማይኖራችሁ በጌታ
እታመናለሁ። ግራ የሚያጋባችሁ ማንም
ይሁን ማን፣ ፍርዱን ይቀበላል።
11ወንድሞች ሆይ፤ እስከ ዛሬ ስለ መገ
ረዝ የምሰብክ ከሆነ፣ ታዲያ እስካሁን ለምን
ያሳድዱኛል? እንደዚያማ ቢሆን ኖሮ፣ መስ
ቀል ዕንቅፋት መሆኑ በቀረ ነበር። 12ግራ
የሚያጋቡአችሁ ሰዎች የራሳቸውን መግ
ረዝ ብቻ ሳይሆን ይጕንድሉ! 13ወንድሞቼ
ሆይ፤ ነጻ እንድትሆኑ ተጠርታችኋል፤ ነጻነ
ታችሁን ግን ሥጋዊ ምኞታችሁን* መፈ
ጸሚያ አታድርጉት፤ ይልቁንም አንዱ
ሌላውን በፍቅር ያገልግል።
14ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ተጠቃሎ
አል፤ ይኸውም፣ "ባልንጀራህን እንደ ራስህ
ውደድ" የሚል ነው። 15ነገር ግን እርስ
በርሳችሁ የምትነካከሱና የምትበላሉ ከሆነ፣

*13 ወይም ኀጢአተኛ ተፈጥሮአችሁን፤ እንዲሁም
ቍ 16፡17፡19 እና 24 ይመ።

4፥14 ማቴ10፥40
4፥16 አሞ 5፥10
4፥17 ገላ 2፥4ቍ12
4፥18 ቍ13ቍ14
4፥19 ሮሜ 8፥29፤ ኤፌ4፥13፤ 1ተሰ2፥11
4፥21 ሮሜ 2፥12
4፥22 ዘፍ16፥15፤ 21፥2
4፥23 ቍ28ቍ29፤ ዘፍ 17፥16ኛ21፤ 18፥10ኛ14፤21፥1፤ ሮሜ 9፥7ቍ8፤ ዕብ11፥11
4፥26 ዕብ12፥22፤ ራእ3፥12፤21፥2ቍ10
4፥27 ኢሳ 54፥1
4፥28 ቍ23፤ ገላ 3፥16
4፥29 ቍ23፤ ዘፍ 21፥9
4፥30 ዘፍ21፥10
4፥31 ቍ22፤ ሮሜ 7፥4
5፥1 ቍ13፤ማቴ 23፥4፤ዮሐ8፥32፤ ሮሜ7፥4፤1ቆሮ 16፥13፤ገላ2፥4
5፥2 ቍ3ቍ6ቍ 11ቍ12ሐሥ15፥1
5፥3 ሮሜ2፥25፤ ገላ3፥10፤ያዕ2፥10
5፥4 ሮሜ3፥28 ዕብ 12፥15፤ 2ጴጥ3፥17
5፥5 ሮሜ8፥23ቍ24
5፥6 ሮሜ16፥3፤ 1ቆሮ7፥19፤1ተሰ1፥3 ፤ያዕ2፥22
5፥7 1ቆሮ9፥24፤ ገላ3፥1
5፥8 ሮሜ8፥28
5፥9 1ቆሮ5፥6
5፥10 ቍ12፤2ቆሮ 2፥3፤ገላ1፥7፤ፊል 3፥15
5፥11 ሉቃ2፥34፤ ገላ 4፥29፤ 6፥12፤
5፥12 ቍ10
5፥13 ቍ1ቍ24፤ 1ቆሮ8፥9፤9፥19፤ 2ቆሮ4፥5፤ኤፌ5፥21 ፤1ጴጥ2፥16
5፥14 ዘሌ19፥18፤ ማቴ5፥43፤ገላ 6፥2

እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ።

## በመንፈስ መመላለስ

16እንግዲህ በመንፈስ ኑሩ እላለሁ፤
የሥጋንም ምኞት አትፈጽሙም። 17ሥጋ
መንፈስ የማይፈልገውን፣ መንፈስም ሥጋ
የማይፈልገውን ይመኛልና፤ እነዚህ እርስ
በርሳቸው ስለሚጋጩ፣ የምትፈልጉትን አታ
ደርጉም። 18በመንፈስ ብትመሩ ግን፣ ከሕግ
በታች አይደላችሁም።
19የሥጋ ሥራ ግልጽ ነው፦ ይኸውም
ዝሙት፣ ርኵሰት፣ መዳራት፣ 20ጣዖትን
ማምለክ፣ ሟርት፣ ጥላቻ፣ ጠብ፣ ቅናት፣
ቍጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ መለያየት፣ አድ
መኛነት፤ 21ምቀኝነት፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣
እንዲሁም እነዚህን የመሰለው ነው። አስ
ቀድሜ እንዳልሁ፣ አሁንም አስጠነቅ
ቃችኋለሁ፤ በእንዲህ ሁኔታ የሚኖሩ ሁሉ
የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።
22የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣
ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣
ታማኝነት፣ 23ገርነት፣ ራስን መግዛት
ነው። እንደነዚህ ያሉትንም የሚከለክል ሕግ
የለም። 24የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት
ሥጋን ከክፉ ምኞቱና መሻቱ ጋር ሰቅ
ለውታል። 25በመንፈስ የምንኖር ከሆን፣
በመንፈስ እንመላለስ። 26እርስ በርሳችን
እየተነካካተልንና እየተቀናናን በከንቱ ውዳሴ
አንመካ።

## ለሰው ሁሉ በጎ ማድረግ

6 ወንድሞች ሆይ፤ አንድ ሰው በኀጢ
አት ውስጥ ገብቶ ቢገኝ፣ መንፈሳውያን
የሆናችሁ እናንተ በገርነት ልትመልሱት
ይገባል። ነገር ግን አንተም እንዳትፈተን
ራስህን ጠብቅ። 2አንዱ የሌላውን ከባድ
ሸክም ይሸከም፤ በዚህም ሁኔታ የክርስቶ
ስን ሕግ ትፈጽማላችሁ። 3አንድ ሰው ምንም
ሳይሆን ትልቅ የሆነ ቢመስለው ራሱን
ያታልላል። 4እያንዳንዱ የራሱን ተግባር
ይመርምር፤ ከዚያም በኋላ፣ ከሌላ ሰው
ጋር ራሱን ሳያወዳድር፣ ስለ ራሱ የሚ
መካበትን ያገኛል፤ 5እያንዳንዱ የራሱን
ሸክም ሊሸከም ይገባዋልና።
6ማንም ቃሉን የሚማር፣ መልካም የሆነ
ውን ነገር ሁሉ ከመምህሩ ጋር ይካፈል።
7አትታለሉ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም።
ሰው የሚዘራውን ያንኑ ያጭዳል። 8ሥጋዊ
ምኞቱን ለማርካት የሚዘራ፣ ከሥጋ[n] ጥፋትን
ያጭዳል፤ መንፈስን ለማስደሰት የሚዘራ
ግን ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል።
9በጎ ነገር ከማድረግ አንታክት፤ ተስፋ
ካልቈረጥን ጊዜው ሲደርስ መከሩን እና
ጭዳለን። 10ስለዚህ ዕድሉ ካለን ለሰው ሁሉ፣
በተለይም ለእምነት ቤተ ሰቦች መልካም
እናድርግ።

## አዲስ ፍጥረት መሆን

11እንዴት ባሉ ታላላቅ ፊደላት በእጄ
እንደ ጻፍሁላችሁ ተመልከቱ።
12ውጫዊ በሆነ ነገር ለመታየት
የሚፈልጉ ሰዎች ትገረዙ ዘንድ ሊያስገ
ድዷችሁ ይጥራሉ፤ ይህንም የሚያደርጉት
ስለ ክርስቶስ መስቀል እንዳይሰደዱ ነው።
13እነርሱ በሥጋችሁ ለመመካት ሲሉ
እንድትገረዙ ፈለጉ እንጂ፣ የተገረዙት
ራሳቸው እንኳ ሕግን የሚጠብቁ አይ
ደሉም። 14ነገር ግን ዓለም ለእኔ ከተሰ
ቀለበት፣ እኔም ለዓለም ከተሰቀልሁበት
ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል
በቀር፣ ሌላው ትምክሕት ከእኔ የራቀ
ይሁን። 15መገረዝም ሆነ አለ መገረዝ
አይጠቅምም፤ የሚጠቅመው አዲስ ፍጥረት
መሆን ነው። 16ይህን ትእዛዝ በሚከተሉ
ሁሉ፣ የእግዚአብሔር በሆነው እስራኤልም ላይ
ሰላምና ምሕረት ይሁን።
17እኔ የኢየሱስን ምልክት በሥጋዬ
ተሸክሜአለሁና፣ ከእንግዲህ ወዲህ ማንም
አያስቸግረኝ።18ወንድሞች ሆይ፤ የጌታችን
የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመንፈሳችሁ ጋር
ይሁን፤ አሜን።

5፥16 ቍ18፥24፥25፤ ሮሜ 8፥2፥4ኛ6፥9፥14፤2ቆሮ5፥17
5፥17 ሮሜ7፥15ኛ23፤8፥5ኛ8
5፥18 ቍ16፤ሮሜ 2፥12፤1ጢሞ1፥9
5፥19 1ቆሮ 6፥18
5፥21 ማቴ15፥19፤25፥32፤ሮሜ13፥13
5፥22 ሚል2፥6ማቴ 7፥16ኛ20፤ ኤፌ5፥9፤ ቈላ3፥12ኛ15
5፥23 ቍ18፤ ሐሥ 24፥25
5፥24 ቍ13፥16ኛ21፥16፥17፤ ሮሜ6፥6፤7፥5፥18፤ 8፥3ኛ5፥8፥9፥12፥13፤13፥14፤ ገላ6፥8፤ቈላ2፥11
5፥25 ቍ16
5፥26 ፊል2፥3
6፥1 ማቴ18፥15፤1ቆሮ2፥15፤ 3፥1፤ 2ቆሮ2፥7
6፥2 1ቆሮ9፥21፤ ያዕ 2፥8
6፥3 ሮሜ 12፥3፤ 1ቆሮ3፥18፤8፥2
6፥4 2ቆሮ10፥12፤ 13፥15
6፥5 ቍ2፤ ኤር31፥30
6፥6 1ቆሮ9፥11፥14፤1ጢሞ 5፥17፥18
6፥8 ኢዮ 4፥8፤ ሆሴ 8፥7፤ ሮሜ 6፥23፤ያዕ 3፥18
6፥9 ኢዮ42፥12፤ መዝ126፥5፤1ቆሮ15፥58፤2ቆሮ4፥1ዕብ 12፥3፤ራእ2፥10
6፥10 ምሳ3፥27፤ ኤፌ 2፥19፤ቲቶ 2፥14፤1ጴጥ4፥17
6፥11 1ቆሮ16፥21
6፥12 ማቴ23፥25፥26፤ሐሥ15፥1፤ገላ 5፥11
6፥15 1ቆሮ7፥19፤ 2ቆሮ5፥17
6፥17 ኢሳ44፥5፤ 2ቆሮ 1፥5፤11፥23
6፥18 ሮሜ16፥20፤ ፊል4፥23፤ 2ጢሞ4፥22፤ፊሞ25

[n]8 ወይም *ኀጢአተኛ ተፈጥሮ ለማርካት የሚዘራ፣ ከዚሁ ተፈጥሮ*

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት
# ወደ ኤፌሶን ሰዎች

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ የክርስቶስ ኢየ
ሱስ ሐዋርያ ከሆነው ከጳውሎስ፤ በክር
ስቶስ ኢየሱስ ላሉ፣ ለታመኑ፣[ሀ] በኤፌሶን[ለ]
ለሚገኙ ቅዱሳን፤
2ከእግዚአብሔር ከአባታችን፣ ከጌታም
ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ
ይሁን።

## በክርስቶስ የሚገኝ መንፈሳዊ በረከት

3በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት
ሁሉ በክርስቶስ የባረከን የጌታችን የኢየ
ሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፤
4በፊቱ ቅዱሳንና ነውር አልባ
እንድንሆን ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ
በእርሱ መርጦና ልና። በፍቅር፣ 5በኢየሱስ
ክርስቶስ ልጆቹ እንሆን ዘንድ፣ እንደ በጎ
ፈቃዱ አስቀ ድሞ ወሰነን፤ 6ይኸውም፣
በሚወደው በእ ርሱ በኩል በነጻ የተሰጠን
ክቡር የሆነው ጸጋው እንዲመሰገን
ነው። 7በእርሱም እንደ እግዚአብሔር ጸጋ
ባለጠግነት መጠን፣ በደሙ በተደረገ
ቤዛነት፣ የኀጢአትን ይቅርታ አገኘን፤ 8
ጸጋውንም በጥበብና በማ ስተዋል ሁሉ
አበዛልን። 9በክርስቶስ ያቀደ ውንም
የፈቃዱን ምስጢር እንደ በጎ
ሐሳቡ እንድናውቅ[ሐ] አደረገ። 10በዘመን
ፍጻሜ ይሆን ዘንድ ያለው ሐሳቡ በሰማ
ይም በምድርም ያሉትን ነገሮች ሁሉ ራስ
በሆነው በክርስቶስ ሥር ለመጠቅለል ነው።
11ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት እንደሚ
ሠራው እንደ እርሱ ዕቅድ አስቀድሞ የተ
ወሰንን እኛ ደግሞ በእርሱ ተመርጠናል፤[መ]
12ይኸውም በክርስቶስ ተስፋ በማድረግ
የመጀመሪያ የሆንነው እኛ ለክብሩ ምስ
ጋና እንሆን ዘንድ ነው። 13እናንተም ደግሞ
የእውነትን ቃል ይህም የድነታችሁን ወን
ጌል በሰማችሁ ጊዜ ወደ ክርስቶስ ተጨም
ራችኋል፤ አምናችሁም፣ በእርሱ በመሆን
ተስፋ ሆኖ በተሰጠው በመንፈስ ቅዱስ
ማኅ ተም ታትማችኋል። 14ለክብሩ
ምስጋና ለመሆን የእግዚአብሔር የሆኑት
እስኪዋጁ ድረስ፣ እርሱ ለርስታችን
ዋስትና የሚሆን መያዣ ነው።

## የምስጋናና የልመና ጸሎት

15ስለዚህ በጌታ ኢየሱስ ስላላችሁ እም
ነት፣ ለቅዱሳንም ሁሉ ስላላችሁ ፍቅር
ከሰማሁበት ጊዜ አንሥቶ፣ 16በጸሎቴ እያ
ስታወስኋችሁ ስለ እናንተ ምስጋና ማቅረ
ብን አላቋረጥሁም። 17የክብር አባት የሆነ
ውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አም
ላክ ይበልጥ እንድታውቁት፣ የጥበብና
የመ ገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ ያለ
ማቋረጥ እለምናለሁ። 18እንዲሁም በእርሱ
የተጠራችሁ ለት ተስፋ፣ ይህም በቅዱሳኑ
ዘንድ ያለውን ክቡር የሆነውን የርስቱን
ባለ ጠግነት ምን እንደ ሆነ ታውቁ ዘንድ
የልባችሁ ዐይ ኖች እንዲበሩ 19ለእኛ
ለምናምነውም ከሁሉ በላይ ታላቅ
የሆነውን ኀይሉን እንድታ ውቁ እ
ጸልያለሁ። ይህም ኀይል እንደ እርሱ ታላቅ
ብርታት አሠራር፣ 20ክርስቶስን ከሙ ታን ሲ
ያስነሣውና በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲ
ያስቀምጠው የታየው ነው። 21የተቀ
መጠውም ከግዛትና ከሥልጣን፣ ከኀይልና
ከጌትነት እንዲሁም በአሁኑ ዘመን ብቻ
ሳይሆን በሚመጣውም ዘመን ቢሆን ሊሰ
የም ከሚቻለው ስም ሁሉ በላይ ነው።
22እግዚአብሔርም ሁሉን ከእግሩ በታች
አስገዛ ለት፤ በቤተ ክርስቲያንም፣ በ
ማንኛውም ነገር ላይ ራስ አድርጎ ሾመው።
23እርሷም ሁሉን ነገር በሁሉም ረገድ
የሚሞላው፣ የእርሱ ሙላት የሆነች አካሉ
ናት።

## በክርስቶስ ሕያው መሆን

2 እናንተ በበደላችሁና በኀጢአታችሁ
ምክንያት ሙታን ነበራችሁ፤ 2በዚ
ህም፣ የዓለምን ክፉ መንገድ ተከትላችሁ፣
በአየር ላይ ላሉት መንፈሳውያን ኀይላት
ገዥ ለሆነውና አሁንም ለእግዚአብሔር በ
ማይታዘ ዙት ሰዎች ላይ ለሚሠራው
መንፈስ እየታ ዘዛችሁ ትኖሩ ነበር። 3እኛ
ሁላችን በአንድ ወቅት የሥጋችንን ምኞት[ሠ]
እያረካን፣ መንገ ዱንም እየተከተልን
በመካከላቸው እንኖር
ነበር፤ እንደ ሌሎቹም የቍጣ ልጆች ነበ
ርን። 4ነገር ግን በምሕረቱ ባለ ጠጋ የሆነ
እግዚአብሔር ለእኛ ካለው ከታላቅ ፍቅሩ
የተነሣ፣ 5በበደላችን ሙታን ሆነን ሳለ፣
በክርስቶስ ሕያዋን አደረገን፤ የዳናችሁት
በጸጋ ነው። 6እግዚአብሔርም ከክርስቶስ ጋር
አስነሣን፤ በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ
ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን፤ 7ይኸ

1፥1 ሐሥ9፥13፤18፥19 ፤1ቆሮ1፥1፤2ቆሮ1፥1፤ቈላ1፥2
1፥2 ሮሜ1፥7
1፥3 ቍ20፤2ቆሮ1፥3፤ኤፌ2፥6፤3፥10፤6፥12፤1ጴጥ1፥3
1፥4 ዘሌ11፥44፤20፥7፤2ሳሙ22፥24፤መዝ15፥2፤ማቴ25፥34፤ኤፌ4፥2፡15፡16፤5፥27፤ቈላ1፥22፤2ተሰ2፥13
1፥5 ቍ11፤ሉቃ12፥32፤ሮሜ8፥14፡15፡29፡30፤1ቆሮ1፥21፤ቈላ1፥19
1፥6 ቍ12፡14፤ማቴ3፥17
1፥7 ቍ14፤ሮሜ2፥4፤3፥24፡25
1፥9 ቍ11፤ ሮሜ16፥25
1፥10 ማር1፥15፤ሮሜ5፥6፤ገላ4፥4፤ቈላ1፥20
1፥11 ቍ5፡9፤ሮሜ8፥28፡29፡30፤ ኤፌ3፥11፤ዕብ6፥17
1፥12 ቍ6፡14
1፥13 ዮሐ14፥16፡17፤ሮሜ16፥3፤ኤፌ4፥21፡30፤ቈላ1፥5
1፥14 ቍ6፡7፡12፤ሐሥ20፥32፤ሮሜ3፥24፤2ቆሮ5፥5
1፥15 ሐሥ20፥21፤ቈላ1፥4
1፥16 ሮሜ1፥8፡10
1፥17 ዘፀ28፥3፤ኢሳ11፥2፤ዮሐ20፥17፤ሮሜ15፥6፤ፊል1፥9፤ቈላ1፥9፤ራእ1፥6
1፥18 ቍ7፡11፤ኢዮ42፥5፤ሮሜ2፥4፤8፥28፤2ቆሮ4፥6፤ቈላ1፥12፤ዕብ6፥4
1፥19 ኢሳ40፥26፤ኤፌ3፡7፤6፥10፤ቈላ1፥29
1፥20 ቍ3፤ማር16፥19፤ሐሥ2፡24
1፥21 ማቴ12፥32፤ኤፌ3፥10፤ፊል2፥9፡10፤ቈላ1፥16
1፥22 ማቴ22፥44፤፤28፥18፤1ቆሮ11፥3፤ኤፌ4፥15፤5፥23፤ቈላ1፥18፤2፥19
1፥23 ዮሐ1፥16፤1ቆሮ12፥27፤ኤፌ3፥19፤4፥10
2፥1 ቍ5፤ቈላ2፥13
2፥2 ቍ3፡11-13፤ዮሐ12፥31፤ሮሜ11፥30፤12፥2፤1ቆሮ5፥8፤6፥11፤ኤፌ5፥6፤ቈላ3፥7፤ቲቶ3፥3፤1ጴጥ4፥3
2፥3 ቍ2፤ገላ5፥24
2፥4 ዮሐ3፥16
2፥5 ቍ1፡8፤መዝ103፤12፤ዮሐ5፥24፤ሐሥ15፥11
2፥6 ሮሜ6፥5፤ኤፌ1፥3፡20

[ሀ]1 ወይም *ለሚያምኑ*
[ለ]1 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *በኤፌሶን ለሚገኙት* የሚለው ሐረግ የላቸውም።
[ሐ]8-9 ወይም *ጸጋውን አበዛልን በጥበብና በአእምሮ ሁሉ፣ 9 ... አሳወቀን*
[መ]11 ወይም *ወራሾች ሆነናል*
[ሠ]3 ወይም *የአሮጌውን ባሕርይ ፈቃድ*

ውም በሚመጣው ዘመን በክርስቶስ ኢየ
ሱስ በቸርነቱ የገለጠልንን ወደር የሌለ
ውን የጸጋውን ባለ ጠግነት ያሳይ ዘንድ
ነው፤ 8በእምነት፣ በጸጋ ድናችኋልና፤
ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእና
ንተ አይደለም፤ 9ማንም እንዳይመካ በሥራ
አይደለም፤ 10ምክንያቱም፣ እግዚአብሔር አስ
ቀድሞ ያዘጋጀልንን መልካም ሥራ እንድን
ሠራ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእግ
ዚአብሔር እጅ ሥራዎች ነን።

## በክርስቶስ አንድ መሆን

11ስለዚህ እናንተ ቀድሞ በትውልድ
አሕዛብ የሆናችሁ፣ በአካል ላይ በሰው
እጅ ከተደረገው የተነሣ፣ ራሳቸውን "ተገርዘ
ናል" በሚሉት፣ "ያልተገረዙ" የተባላችሁ
ያን አስታውሱ፤ 12በዚያን ዘመን ከክርስቶስ
ተለይታችሁ፣ ከእስራኤል ወገንነት ርቃ
ችሁ፣ ለኪዳኑም ተስፋ ባዕዳን ሆናችሁ፣
በዓለም ላይ ያለ ተስፋና ያለ እግዚአብሔር
እንደ ነበራችሁ አስታውሱ። 13አሁን ግን
እናንተ ቀድሞ ርቃችሁ የነበራችሁ፣ በክርስ
ቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም አማ
ካይነት ቀርባችኋል።
14ሁለቱን አንድ ያደረገ፣ የሚለያየው
ንም የጥል ግድግዳ ያፈረሰ ሰላማችን እርሱ
ራሱ ነውና፤ 15ሕግንም፣ ከትእዛዛቱና ከሥ
ርዐቱ ጋር በሥጋው ሻረ። ዐላማውም ከሁ
ለቱ አንድን አዲስ ሰው በራሱ ፈጥሮ ሰላምን
ለማድረግ ነው። 16ጥልን በገደለበት በመስ
ቀሉም ሁለቱን በዚህ በአንድ አካል ከእግ
ዚአብሔር ጋር አስታረቀ። 17መጥቶም ርቃ
ችሁ ለነበራችሁት ለእናንተ፣ ቀርበው ለነ
በሩትም ለእነርሱ ሰላምን ሰበከ፤
18ሁላችንም
በእርሱ አማካይነት በአንዱ መንፈስ ወደ
አብ መቅረብ እንችላለንና።
19ከዚህ የተነሣ እናንተ ከቅዱሳን ጋር
የአንድ አገር ዜጋ፣ የእግዚአብሔርም ቤተ
ሰብ አባል ናችሁ እንጂ፣ ከእንግዲህ
ወዲህ መጻተኞችና እንግዶች አይደላች
ሁም። 20በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት
ላይ ታንጻችኋል፤ የማእዘኑ ራስ ድንጋይም
ክርስቶስ ኢየሱስ ራሱ ነው፤ 21በእርሱ
ሕንጻ ሁሉ አንድ ላይ ተገጣጥሞ በጌታ
ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል።
22እናንተም ደግሞ እግዚአብሔር በመንፈሱ
የሚኖርበት ማደሪያ ትሆኑ ዘንድ አብራችሁ
እየተገነባችሁ ነው።

## ለአሕዛብ ሐዋርያ የሆነው ጳውሎስ

3 በዚህም ምክንያት እኔ ጳውሎስ ለእና
ንተ ለአሕዛብ የክርስቶስ ኢየሱስ እስ
ረኛ ሆኛለሁ።

2፥7 ሮሜ2፥4፤ቲቶ3፥4
2፥8 ቁ5፤ሮሜ3፥24፤9፥30
2፥9 ዘዳ9፥5፤ሮሜ4፥2፤1ቆሮ1፥29፤2ጢሞ1፥9፤ቲቶ3፥5
2፥10 ኢሳ29፥23፤43፥7፤60፥21፤ ኤፌ4፥24፤ ቲቶ2፥14
2፥11 ቁ2፤ቆላ2፥11
2፥12 ኢሳ14፥1፤65፥1፤ገላ3፥17፤1ተሰ4፥13
2፥13 ቁ2፥17፤ቈላ1፥20
2፥14 ቁ15፤ዮሐ14፥27፤1ቆሮ12፥13፤ኤፌ3፥6
2፥15 ገላ3፥28፤ቈላ1፥21፥22፤2፥14
2፥16 2ቆሮ5፥18፤ቈላ1፥20፥22
2፥17 ቁ13፤ኢሳ57፥19፤መዝ148፥14፤ሉቃ2፥14
2፥18 1ቆሮ12፥13፤ኤፌ3፥12፤4፥4፤ቈላ1፥12
2፥19 ቁ12፤ገላ6፥10፤ፊል3፥20
2፥2 ማቴ16፥18፤ሐሥ4፥11፤1ቆሮ3፥9፡10፡11፤ኤፌ4፥11፤1ጴጥ2፥4-8፤ራእ21፥14
2፥21 1ቆሮ3፥16፥17
2፥22 1ቆሮ3፥16
3፥1 ሐሥ23፥18፤ኤፌ4፥1፤2ጢሞ1፥8፤ፊሞ1፥9
3፥2 ቈላ1፥25
3፥3 ሮሜ16፥25፤1ቆሮ2፥10
3፥4 2ቆሮ11፥6
3፥5 ሮሜ16፥26፤ኤፌ4፥11
3፥6 ሕዝ47፥22፤ሮሜ8፥17፤ኤፌ2፥15፥16
3፥7 ሮሜ12፥3፤1ቆሮ3፥5፤ኤፌ1፥19፤ቈላ1፥29
3፥8 ሐሥ9፥15፤ሮሜ2፥4፤1ቆሮ15፥9
3፥9 ሮሜ16፥25
3፥10 ሮሜ11፥33፤1ቆሮ2፥7፤ኤፌ1፥3፥21፤6፥12፤ቈላ2፥10፥15፤1ጴጥ1፥12
3፥11 ኤፌ1፥11
3፥12 2ቆሮ3፥4፤ኤፌ2፥18፤ዕብ3፥14፤4፥16፤10፥19፥35፤1ዮሐ2፥28፤3፥21፤4፥17
3፥14 ፊል2፥10
3፥16 ቁ8፤ሮሜ2፥4፤7፥22፤ፊል4፥13
3፥17 ሮሜ8፥10፤ቈላ2፥7
3፥18 ኢዮ11፥8፥9፤መዝ103፥11፤ኤፌ1፥15

2ለእናንተ ጥቅም ሲባል ስለ ተሰጠኝ የእ
ግዚአብሔር ጸጋ መጋቢነት በእርግጥ ሰምታ
ችኋል፤ 3ቀደም ሲል በአጭሩ እንደ ጻፍ
ሁት፣ በመገለጥ እንዳውቀው የተደረገው
ምስጢር ይህ ነው። 4እንግዲህ ይህን ስታ
ነቡ፣ የክርስቶስን ምስጢር እንዴት እንደ
ማስተውል ለመረዳት ትችላላችሁ። 5ይህም
ምስጢር አሁን ለቅዱሳኑ ሐዋርያትና ነቢ
ያት የተገለጠውን ያህል ባለፉት ዘመናት
ለነበሩ ሰዎች አልተገለጠም ነበር። 6ይህም
ምስጢር አሕዛብ በወንጌል አማካይነት
ከእስራኤል ጋር አብረው ወራሾች፣ አብረው
የአንዱ አካል ብልቶች እንዲሁም በክርስቶስ
ኢየሱስ በሆነው ተስፋ አብረው ተካፋይ
መሆናቸው ነው።
7እኔም በኀይሉ አሠራር በተሰጠኝ በእግ
ዚአብሔር የጸጋ ስጦታ የዚህ ወንጌል አገል
ጋይ ሆኛለሁ። 8ምንም እንኳ ከቅዱሳን
ሁሉ ያነስሁ ብሆንም፣ የማይመረመረውን
የክርስቶስን ባለጠግነት ለአሕዛብ እሰብክ
ዘንድ ይህ ጸጋ ለእኔ ተሰጠኝ። 9እንዲሁም
ሁሉን በፈጠረ በእግዚአብሔር ላለፉት
ዘመናት የተሰወረውን የዚህን ምስጢር አሠ
ራር ለሁሉም እገልጥ ዘንድ ተሰጠኝ።
10አሳቡም በአሁኑ ዘመን በቤተ ክርስቲያን
አማካይነት ብዙ ገጽታ ያለው የእግዚአብሔ
ር ጥበብ በሰማያዊ ስፍራ ላሉት አለቆችና
ባለ ሥልጣናት ይታወቅ ዘንድ ነው፤
11ይህም በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን በፈ
ጸመው ዘላለማዊ ዕቅዱ መሠረት ነው።
12በእርሱና በእርሱ ላይ ባለን እምነት አማካ
ይነት፣ በነጻነትና በልበ ሙሉነት ወደ
እግዚአብሔር መቅረብ እንችላለን። 13ስለዚህ
ክብራችሁ በሆነው ስለ እናንተ በደረሰብኝ
መከራ ተስፋ እንዳትቈርጡ ዐደራ እላችኋ
ለሁ።

## ለኤፌሶን ክርስቲያኖች የተደረገ ጸሎት

14በዚህም ምክንያት በአብ ፊት
እንበረከ ካለሁ፤ 15ከእርሱም በሰማይና
በምድር ያለ ቤተ ሰብ ሁሉ ስያሜ[a]
ያገኛል። 16በውስጥ ሰውነታችሁ
እንድትጠነክሩ፣ ከክብሩ ባለጠግነት
በመንፈሱ በኩል ኀይል እንዲሰጣችሁ እ
ጸልያለሁ፤ 17ይኸውም በእምነት ክርስቶስ
በልባችሁ እንዲያድር ነው። ደግ ሞም
ሥር ሰዳችሁ፣ በፍቅር ታንጻችሁ፣ 18የክ
ርስቶስ ፍቅር ስፋቱ፣ ርዝመቱ፣ ከፍታ
ውና ጥልቀቱ ምን ያህል እንደ ሆነ ከቅዱ
ሳን ሁሉ ጋር የመገንዘብ ኀይልን እንድታ
ገኙ ነው። 19እስከ እግዚአብሔር ሙላት ሁሉ
ልክ ደርሳችሁ እንድትሞሉ፣ ከመታወቅ

3፥19 ኤፌ1፥23፤ ፊል4፥7፤ቈላ2፥10

[a]15 ወይም አባትነት ሁሉ

በላይ የሆነውን የክርስቶስን ፍቅር ታውቁም
ዘንድ ነው።
20እንግዲህ በእኛ ውስጥ እንደሚሠራው
እንደ ኀይሉ መጠን፣ ከምንለምነው
ወይም ከምናስበው ሁሉ በላይ እጅግ አብልጦ
ማድረግ ለሚቻለው፣ 21በቤተ ክርስቲያን
እንዲሁም በክርስቶስ ኢየሱስ፣
በዘመናት ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም
ለእርሱ ክብር ይሁን፤ አሜን።

## በክርስቶስ አካል ያለ አንድነት

4 እንግዲህ በጌታ እስረኛ የሆንሁ እኔ፣
ለተቀበላችሁት ጥሪ የሚገባ ኑሮ
ትኖሩ ዘንድ እለምናችኋለሁ። 2ፍጹም
ትሑታንና ገሮች ሁኑ፤ እርስ በርሳችሁም
በፍቅር እየተቻቻላችሁ ትዕግሥተኞች
ሁኑ። 3በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት
ለመጠበቅ ትጉ። 4በተጠራችሁ ጊዜ ወደ
አንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ ሁሉ አንድ
አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ 5አንድ ጌታ፣
አንድ እምነትና አንድ ጥምቀት አለ፤
6ከሁሉም በላይ የሆነ፣ በሁሉም የሚሠራ፣
በሁሉ የሚኖር የሁሉም አባት የሆነ አንድ
አምላክ አለ።
7ነገር ግን ክርስቶስ በወሰነው መጠን
ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጥቶናል። 8ስለዚ
ህም እንዲህ ይላል፤

"ወደ ላይ በወጣ ጊዜ፣
ምርኮ ማረከ፤
ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ።"

9ታዲያ፣ "ወደ ላይ ወጣ" ማለት ደግሞ
ወደ ምድር ታችኛው ክፍል[ሰ] ወረደ
ማለት ካልሆነ በቀር ምን ማለት ነው?
10ወደ ታች የወረደውም፣ መላውን ፍጥ
ረተ ዓለም ይሞላ ዘንድ ከሰማያት ሁሉ
በላይ የወጣው እርሱ ራሱ ነው። 11አንዳ
ንዶቹ ሐዋርያት፣ አንዳንዶቹ ነቢያት፣
አንዳንዶቹም ወንጌል ሰባኪዎች፣ ሌሎቹ
ደግሞ እረኞችና አስተማሪዎች ይሆኑ
ዘንድ የሰጠ እርሱ ነው፤ 12ይኸውም የክር
ስቶስ አካል ይገነባ ዘንድ፣ ቅዱሳንን ለአገ
ልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት ሲሆን፣ 13ይህም
የሚሆነው፣ ሁላችንም የእግዚአብሔርን ልጅ
በማመንና በማወቅ ወደሚገኘው አንድነት
በመምጣትና ሙሉ ሰው በመሆን፣ በክርስ
ቶስ ወዳለው ፍጹምነት ደረጃ እስከምንደ
ርስ ነው።
14ከእንግዲህ በማዕበል ወደ ፊትና ወደ
ኋላ እየተነዳን፣ በልዩ ልዩ ዐይነት የትም
ህርት ነፋስ፣ በሰዎችም ረቂቅ ተንኰልና
ማታለል ወዲያና ወዲህ እየተጠ
ንገዋለልን
ሕፃናት አንሆንም። 15ይልቁንም እውነትን
በፍቅር እየተናገርን፣ ራስ ወደ ሆነው ወደ
እርሱ በነገር ሁሉ እናድጋለን፤ እርሱም
ክርስቶስ ነው፤ 16ከእርሱም የተነሣ፣ አካል
ሁሉ በሚያገናኘው ጅማት እየተያያዘና
እየተጋጠመ፣ እያንዳንዱ ክፍል የራሱን
ሥራ እያከናወነ በፍቅር ያድጋል፤ ራሱ
ንም ያንጻል።

## እንደ ብርሃን ልጆች መኖር

17ስለዚህ ይህን እነግራችኋለሁ፤ በጌታም
ዐደራ እላለሁ፤ በአስተሳሰባቸው ከንቱነት
እንደሚኖሩት እንደ አሕዛብ ልትመላለሱ
አይገባም። 18እነርሱ ከልባቸው መደንደን
የተነሣ ስለማያስተውሉ ልቦናቸው ጨል
ሞአል፤ ከእግዚአብሔርም ሕይወት ተለይተ
ዋል። 19ኅሊናቸው ስለ ደነዘዘ በማይረካ
ምኞት፣ በርኵሰት ሁሉ እንዳሻቸው
ለመኖር ቅጥ ለሌለው ብልግና ራሳቸውን
አሳልፈው ሰጥተዋል።
20እናንተ ግን ክርስቶስን ያወቃችሁት እን
ደዚህ ባለ መንገድ አይደለም፤ 21በእርግጥ ስለ
እርሱ ሰምታችኋል፤ በኢየሱስም እንዳለው
እውነት በእርሱ ተምራችኋል። 22ቀድሞ ስለ
ነበራችሁበት ሕይወትም፣ በሚያታልል ምኞቱ
የጎደፈውን አሮጌ ሰውነታችሁን አውልቃችሁ
እንድትጥሉ ተምራችኋል፤ 23ደግሞም በአእ
ምሮአችሁ መንፈስ እንድትታደሱ፣ 24እው
ነተኛ በሆነው ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና
እግዚአብሔርን እንዲመስል የተፈጠረውን
አዲሱን ሰው እንድትለብሱ ነው።
25ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፣ እያን
ዳንዳችሁ ከባልንጀራችሁ ጋር እውነትን
ተነጋገሩ፤ ሁላችንም የአንድ አካል ብልቶች
ነንና። 26ተቈጡ፤ ነገር ግን ኀጢአት አት
ሥሩ፤ በቍጣችሁ ላይ ፀሓይ አይግባ፤ 27ለዲ
ያብሎስም ስፍራ አትስጡት። 28ይሰርቅ
የነበረ ከእንግዲህ አይስረቅ፤ ነገር ግን
ለተቸገሩት የሚያካፍለው ነገር እንዲኖ
ረው በገዛ እጆቹ በጎ የሆነውን እየሠራ
ለማግኘት ይድከም።
29እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎችን የሚያን
ጹና ሰሚዎችን የሚጠቅም ቃል እንጂ
የማይረባ ቃል ከአፋችሁ አይውጣ። 30ለቤዛ
ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር
መንፈስ አታሳዝኑ። 31መራርነትን ሁሉ፣
ቍጣና ንዴትን፣ ጭቅጭቅና ስድብን
ከማንኛውም ክፋት ጋር ከእናንተ ዘንድ
አስወግዱ። 32እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር
እንዳላችሁ፣ እናንተም ይቅር ተባባሉ፤

3፥20 ቍ7፤1ነገ 3፥13፤ሮሜ16፥25፤2ቆሮ9፥8
3፥21 ሮሜ11፥36
4፥1 ሮሜ8፥28፤ኤፌ 3፥1፤ፊል1፥27፤ቈላ1፥10፤1ተሰ2፥12
4፥2 ቍ15፡16፤ኤፌ 1፥4፤ቈላ3፥12፡13
4፥3 ሮሜ15፥5፤ቈላ 3፥15
4፥4 ሮሜ8፥28፤12፥5፤1ቆሮ12፥13፤ኤፌ2፥18
4፥5 1ቆሮ8፥6
4፥6 ዘዳ6፥4፤ዘካ 14፥9፤ሮሜ11፥36
4፥7 ሮሜ3፥24፤12፥3፤1ቆሮ12፡7፡11
4፥8 መዝ68፥18፤ቈላ2፥15
4፥10 ምሳ30፥1-4፤ኤፌ1፥23፤
4፥11 ቍ8፤ሐሥ 11፥27፤13፥1፤21፥8፤ሮሜ2፥21፤12፥6፡7፣1ቆሮ12፥10፡28፤13፥2፡8፤14፥1፡26፡39፤ኤፌ2፥20፤3፥5፤1ጢሞ1፥7፤2ጢሞ 4፥5፤2ጴጥ3፥2፤ያዕ 3፥1፤ይሁ17
4፥12 ሮሜ14፥19፤1ቆሮ12፥27
4፥13 ቍ3፡5፤ዮሐ 1፥16፤1ቆሮ2፥6፤ኤፌ1፥23፤3፥19፤ፊል3፥8፤ቈላ1፥28
4፥14 ኢሳ57፥20፤1ቆሮ14፥20፤ኤፌ6፥11፤ያዕ1፥6
4፥15 ቍ2፡16፤ኤፌ1፥4፡22
4፥16 ቍ2፡15፤1ቆሮ 12፥7፤ኤፌ1፥4፤ቈላ 2፥19
4፥17 ሮሜ1፥21፤ኤፌ2፥2
4፥18 ዘዳ29፥4፤ሮሜ1፥21፤2ቆሮ 3፥14፤ኤፌ2፥12
4፥19 ሮሜ1፥24፤ቈላ3፥5፤1ጢሞ4፥2፤1ጴጥ4፥3
4፥22 ቍ25፡31፤ኤር 17፥9፤ሮሜ6፥6፤ቈላ 3፥5፡8፡9፤ዕብ3፥13፤ያዕ1፥21፤1ጴጥ2፥1
4፥23 ሮሜ12፥2፤ቈላ3፥10
4፥24 ሮሜ6፥4፤13፥14፤ኤፌ2፥10
4፥25 ዘሌ19፥11፤መዝ15፥2፤ዘካ8፥16፤ሮሜ12፥5፤ቈላ3፥9
4፥26 መዝ4፥4፤ማቴ5፥22
4፥27 2ቆ2፥10፡11
4፥28 ሐሥ20፥35፤ገላ6፥10፤1ተሰ4፥11
4፥29 ማቴ12፥36፤ሮሜ14፥19፤ኤፌ5፥4፤ቈላ3፥8
4፥30 ኢሳ63፥10፤ሮሜ8፥23፤2ቆሮ1፡22፤5፥5፤ኤፌ1፥13፤1ተሰ5፥19
4፥31 ቍ22፤ቈላ3፥8፤1ጴጥ2፥1
4፥32 ማቴ6፥14፡15፤ቈላ3፥12፡13፤1ጴጥ3፥18፤

ሰ9 ወይም ወደ ምድር ጥልቀት

እርስ በርሳችሁ ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ።

5 እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአ
ብሔርን ምሰሉ፤ 2ክርስቶስ እንደ ወደደን
ራሱንም ስለ እኛ መልካም መዐዛ ያለው
መባና መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር
እን ደሰጠ እናንተም በፍቅር ተመላለሱ።
3ማንኛውም የዝሙት ወይም የርኵሰት
ወይም የስስት ነገር ከቶ በመካከላችሁ አይ
ነሣ፤ ይህ ቅዱስ ለሆነው ለእግዚአብሔር ሕዝብ
አይገባምና። 4የሚያሳፍርና ተራ የሆነ ንግ
ግር፣ ዋዛ ፈዛዛም ለእናንተ ስለማይገባ
በመካከላችሁ አይኑር፤ ይልቁንስ የምታ
መሰግኑ ሁኑ። 5ደግሞም ይህን ዕወቁ፤
ማንም አመንዝራ ወይም ርኩስ ወይም
ስስታም ማለት ጣዖት አምላኪ በክርስቶ
ስና በእግዚአብሔር መንግሥት[ሸ] ርስት የለ
ውም። 6ማንም በከንቱ ንግግር አያታላ
ችሁ፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቍጣ በማ
ይታዘዙ ልጆች ላይ የሚመጣው በእንደ
ዚህ ዐይነት ነገር ነው። 7ስለዚህ እንዲህ
ካሉ ጋር አትተባበሩ።
8ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁ፤ አሁን ግን
በጌታ ብርሃን ናችሁ። እንደ ብርሃን ልጆች
ኑሩ፤ 9የብርሃኑ ፍሬ በበጎነት፣ በጽድቅና
በእውነት ሁሉ ዘንድ ነውና። 10እንዲሁም
ጌታን ደስ የሚያሰኘውን ፈልጉ። 11ፍሬ
ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር ምንም ዐይ
ነት ግንኙነት አይኑራችሁ፤ ይልቁን ግለ
ጡት፤ 12በድብቅ የሚሠሩትን ነገር መና
ገር ራሱ አሳፋሪ ነውና። 13ብርሃን የበራ
በት ነገር ሁሉ ግልጽ ሆኖ ይታያል፤ 14ምክ
ንያቱም ሁሉን ነገር እንዲታይ የሚያደርገው
ብርሃን ነውና፤ ስለዚህም፣

"አንተ የተኛህ ንቃ፤
ከሙታን ተነሣ፤
ክርስቶስም ያበራልሃል" ተብሎአል።

15እንግዲህ ጥበብ እንደ ሌላቸው ሳይ
ሆን እንደ ጥበበኞች እንዴት እንደምት
ኖሩ ተጠንቀቁ። 16ቀኖቹ ክፉ ናቸውና
ዘመኑን በሚገባ ዋጁ። 17ስለዚህ ሞኞች
አትሁኑ፤ የጌታ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ
አስተውሉ እንጂ። 18በመንፈስ ተሞሉ እንጂ
በወይን ጠጅ አትስከሩ፤ ይህ ብክነት
ነውና። 19በመዝሙርና በውዳሴ፣ በመንፈ
ሳዊም ዝማሬ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ በል
ባችሁ ለጌታ ተቀኙ፤ አዚሙም። 20በዚ
ህም እግዚአብሔር አብን በጌታችን በኢየሱስ
ክርስቶስ ስም ስለ ሁሉ ነገር ሁልጊዜ
አመስግኑ።
21ለክርቶስ ካላችሁ አክብሮታዊ ፍርሀት
የተነሣ አንዳችሁ ለአንዳችሁ ተገዙ።

5፥1 ማቴ5፥48፤ ሉቃ6፥36፤ዮሐ1፥12፤
5፥2 ቍ25፤ዮሐ 13፥34፤ገላ1፥4፤2፥20፤ ዕብ 7፥27፤
5፥3 1ቆሮ6፥18፤ ቈላ3፥5
5፥4 ቍ20፤ኤፌ4፥29
5፥5 ማቴ25፥34፤ ሐሥ20፥32፤ቈላ3፥5
5፥6 ማር13፥5፤ ሮሜ1፥18፤ኤፌ2፥2
5፥8 ሉቃ16፥8፤ ዮሐ 8፥12፤ ሐሥ26፥18፤ኤፌ2፥2
5፥9 ማቴ7፥16-20፤ ሮሜ15፥14፤ገላ5፥22
5፥10 1ጢሞ5፥4
5፥11 ሮሜ13፥12፤ 2ቆሮ6፥14
5፥13 ዮሐ3፥20፡21
5፥14 ኢሳ26፤19፤ 60፥1፤ሚል4፥2፤ዮሐ 5፥25፤ሮሜ13፥11
5፥15 ቍ2
5፥16 ኤፌ6፥13፤ ቈላ4፥5
5፥17 ሮሜ12፥2፤ ቈላ 1፥9፤1ተሰ4፥3
5፥18 ዘሌ10፥9 ፤ምሳ20፥1፤ኢሳ28፥7፤ ሉቃ1፥15፤ሮሜ13፥13
5፥19 መዝ27፥6፤ 95፥2፤ሐሥ16፥25፤1ቆሮ 14፥15፡26፤ቈላ3፥16
5፥20 ቍ4፤ኢዮ 1፥21፤መዝ34፥1፤ቈላ3 ፥17፤ዕብ13፥15
5፥21 ገላ5፥13፤ 1ጴጥ5፥5
5፥22 ዘፍ3፥16፤ 1ቆሮ14፥34፤ኤፌ6፥5፤ ቈላ3፥18፤2ጢሞ2፥12፤ ቲቶ2፥5፤1ጴጥ3፥1፡5፡6
5፥23 ኤፌ1፥22
5፥24 ቍ22
5፥25 ቍ2፡28፡33 ፤ቈላ3፥19
5፥26 ዮሐ17፥19፤ ሐሥ22፥16፤ዕብ2፥11 ፤10፥10፡14፤13፥12፤
5፥27 2ቆሮ4፥14፤ ኤፌ1፥4
5፥28 ቍ25
5፥30 ሮሜ12፥5፤ 1ቆሮ12፥27
5፥31 ዘፍ2፥24፤ ማቴ19፥5፤1ቆሮ6፥16
5፥33 ቍ25
6፥1 ምሳ6፥20፤ ቈላ3፥20
6፥3 ዘፀ20፥12፤ ዘዳ5፥16
6፥4 ዘፍ18፥19፤ ዘዳ6፥7፤ምሳ13፥24፤2 2፥6፤ቈላ3፥21
6፥5 ኤፌ5፥22፤ ቈላ3፥22፤1ጢሞ6፥1፤ ቲቶ2፥9፤1ጴጥ2፥18
6፥6 ሮሜ6፥22

## ባልና ሚስት

5፥22-6፥9 ተጓ ምብ-ቈላ3፥18-4፥1

22ሚስቶች ሆይ፤ ለጌታ እንደምትገዙ
ለባሎቻችሁም ተገዙ 23ክርስቶስ፣ አካሉ
ለሆነችውና አዳኟ ለሆናት ቤተ ክርስቲ
ያን ራስ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ባልም የሚስቱ
ራስ ነውና። 24እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን
ለክርስቶስ እንደምትገዛ፣ ሚስቶችም ለባ
ሎቻቸው በማንኛውም ነገር እንደዚሁ መገ
ዛት ይገባቸዋል።
25ባሎች ሆይ፤ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲ
ያንን እንደ ወደዳትና ራሱንም ስለ እርሷ
አሳልፎ እንደ ሰጠ፣ እናንተም ሚስቶቻችሁን
ውደዱ፤ 26በቃሉ አማካይነት በውሃ አጥቦ
በማንጻት እንድትቀደስ፣ 27እንዲሁም ጒድፍ
ወይም የፊት መጨማደድ ወይም አንዳች
እንከን ሳይገኝባት ቅድስትና ነውር አልባ
የሆነች ክብርት ቤተ ክርስቲያን አድርጎ
ለራሱ ሊያቀርባት ነው። 28ባሎችም እንደዚ
ሁ ሚስቶቻቸውን እንደ ገዛ ሥጋቸው
መው ደድ ይገባቸዋል። ሚስቱን የሚወድ
ራሱን ይወዳል። 29የገዛ ሥጋውን የሚጠላ
ማንም የለም፤ ይመግበዋል፤ ይንከባከበዋል፤
ክርስ ቶስም ለቤተ ክርስቲያን ያደረገው
ልክ እንደዚሁ ነው፤ 30እኛ የክርስቶስ አካል
ብል ቶች ነንና። 31"ስለዚህም ሰው አባተ
ንና እና ቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር
አንድ ይሆ ናል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ
ይሆናሉ"። 32ይህ ጥልቅ ምስጢር ነው፤
እኔም ይህን ስለ ክር ስቶስና ስለ ቤተ
ክርስቲያን እናገራለሁ። 33ሆኖም ከእናንተ
እያንዳንዱ ሚስቱን እንደ ራሱ አድርጎ
ይውደድ፤ ሚስትም ባሏን ታክብር።

## ወላጆችና ልጆች

6 ልጆች ሆይ፤ ለወላጆቻችሁ በጌታ
ታዘዙ፤ ይህ ተገቢ ነውና። 2"አባትህ
ንና እናትህን አክብር" በሚለው ቀዳሚ
ትእዛዝ ውስጥ ያለው ተስፋ፣ 3"መልካም እንዲ
ሆንልህ፣ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረ
ዝም" የሚል ነው።
4አባቶች ሆይ፤ እናንተም ልጆቻችሁን
አታስቈጧቸው፤ ነገር ግን በጌታ ምክርና
ተግሣጽ አሳድጓቸው።

## ጌቶችና ባሪያዎች

5ባሪያዎች ሆይ፤ ለክርስቶስ እንደምት
ታዘዙ፣ በምድር ጌቶቻችሁ ለሆኑት በአ
ክብሮትና በፍርሀት፣ በልብ ቅንነትም
ታዘዙ፤ 6ለታይታና ከእነርሱ ሙገሳን ለማ
ግኘት ሳይሆን እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች

ሸ5 ወይም የክርስቶስና የእግዚአብሔር መንግሥት በሆነው

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከልብ በመፈጸም ታዘዟ
ቸው:: 7ሰውን ሳይሆን ጌታን እንደምታገለ
ግሉ ሆናችሁ በሙሉ ልብ አገልግሉ፤ 8ምክ
ንያቱም፣ ባሪያም ሆነ ነጻ ሰው ለሚያደር
ገው በጎ ነገር ሁሉ ሽልማቱን ከጌታ እን
ደሚቀበል ታውቃላችሁ::
9እናንተም ጌቶች ሆይ፤ ለባሮቻችሁ እን
ዲሁ አድርጉላቸው፤ የእነርሱም፣ የእናንተም
ጌታ የሆነው በሰማይ እንዳለ፣ የሰውንም
ፊት አይቶ እንደማያደላ ታውቃላችሁና
አታስፈራሯቸው::

## የእግዚአብሔር ጦር ዕቃ

10በተረፈ በጌታና ብርቱ በሆነው ኀይሉ
ጠንክሩ:: 11የዲያብሎስን የተንኰል ሥራ
መቋቋም ትችሉ ዘንድ፣ የእግዚአብሔርን
ሙሉ የጦር ዕቃ ልበሱ:: 12ምክንያቱም
ተጋድሎ አችን ከሥጋና ከደም ጋር
ሳይሆን ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዦች፣
ከሥልጣናትና ከኀይላት እንዲሁም በሰ
ማያዊ ስፍራ ካሉ ከርኩሳን መናፍስት ሰ
ራዊት ጋር ነው:: 13ክፉው ቀን ሲመጣ
መቋቋም ትችሉ ዘንድ የእግዚአብሔርን ሙሉ
የጦር ዕቃ ልበሱ፤ ሁሉን ከፈጸማችሁ በኋላ
ጸንታችሁ መቆም ትች ላላችሁና::
14እንግዲህ ወገባችሁን በእው ነት ዝናር
ታጥቃችሁ፣ የጽድቅንም ጥሩር
ለብሳችሁ፣ 15በሰላም ወንጌል ዝግጁነት
እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ:: 16ከእነዚ

6፥7 ቈላ3፥23
6፥8 ማቴ16፥27 ፤ቆላ3፥24
6፥9 ኢዮ31፥13፡ 14፤ሐሥ10፥34
6፥10 2ሳሙ10፥12 ፤መዝ27፥14፤ሐጌ 2፥4፤1ቆሮ16፥13፤ ኤፌ1፡19፣2ጢሞ2፥1
6፥11 ቍ13፤ሮሜ 13፥12፤1ተሰ5፥8
6፥12 ሮሜ8፥38 ፤1ቆሮ15፥50፤ኤፌ1፥3 ፡21፤3፥10፤ዕብ2፥14
6፥13 ቍ11፤2ቆሮ 6፥7
6፥14 መዝ132፥9፤ ኢሳ11፥5፤59፥17፤ 1ተሰ5፥8
6፥15 ኢሳ52፥7፤ ሮሜ 10፥15
6፥16 ማቴ5፥37፤ 1ዮሐ5፥4
6፥17 ኢሳ49፥2፤ 59፥17፤ዕብ4፥12
6፥18 ማቴ26፥41፤ ሉቃ18፥1፤ሐሥ1፥14 ፤ሮሜ8፡26፡27፤ፊል 1፥4፤4፥6፤ቈላ1፥3
6፥19 ሐሥ4፥29፤ ሮሜ16፥25፤1ተሰ 5፥25
6፥20 ሐሥ21፥33፤ 2ቆሮ5፥20
6፥21 ሐሥ20፥4
6፥22ቈላ2፥2፤4፥7-9
6፥23 ገላ6፥16፤ 2ተሰ3፥16፤1ጴጥ 5፥14

ህም ሁሉ ጋር፣ የሚንበለበሉትን የክፉውን
ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን
የእምነትን ጋሻ አንሡ፤ 17የመዳንን ራስ
ቍር አድርጉ፤ የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፤
እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው:: 18በጸሎ
ትና በልመና ሁሉ፣ በማንኛውም ሁኔታ
በመንፈስ ጸልዩ፤ ይህንም በማሰብ ንቁ፤
ስለ ቅዱሳንም ሁሉ በትጋት ልመና አቅ
ርቡ::
19የወንጌልን ምስጢር ለመግለጥ አፌን
በምከፍትበት ጊዜ ሁሉ በድፍረት እንድ
ናገር ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ጸልዩልኝ:: 20በሰ
ንሰለት የታሰረ መልእክተኛ የሆንሁት ለዚ
ሁ ነውና:: ስለዚህ መናገር የሚገባኝን ያለ
ፍርሀት እንድናገር ጸልዩልኝ::

## የመጨረሻ ሰላምታ

21በምን ሁኔታ እንዳለሁና ምን እንደማ
ደርግ ታውቁ ዘንድ ተወዳጅ ወንድምና
በጌታ ታማኝ አገልጋይ የሆነው ቲኪቆስ
ሁሉንም ነገር ይነግራችኋል:: 22የእኛን ሁኔታ
እንድታውቁና ልባችሁን እንዲያበረታ
ለዚሁ ስል ወደ እናንተ ልኬዋለሁ::
23ከእግዚአብሔር አብ፣ ከጌታም ከኢየሱስ
ክርስቶስ ሰላም፣ ፍቅርም ከእምነት ጋር
ለወንድሞች ይሁን:: 24ጌታችንን ኢየሱስ
ክርስቶስን በማይጠፋ ፍቅር ለሚወዱ ሁሉ
ጸጋ ይሁን::

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት
# ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

1 የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋዮች የሆኑ ጳው
ሎስና ጢሞቴዎስ፤ ከቤተ ክርስቲያን ሽማ
ግሌዎችና[ሀ] ከዲያቆናት ጋር በፊልጵስዩስ
ላሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ቅዱሳን ለሆኑ ሁሉ፤
2ከእግዚአብሔር ከአባታችን፣ ከጌታም
ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ
ይሁን።

## ምስጋናና ጸሎት

3እናንተን ባስታወስሁ ቍጥር አምላኬን
አመሰግናለሁ። 4ዘወትር ስለ ሁላችሁ ስጸልይ፣
በደስታ እጸልያለሁ፤ 5ከመጀመሪያው ቀን አን
ሥቶ እስካሁን ድረስ በወንጌል አገልግሎት
ተካፋይ ሆናችኋልና። 6በእናንተ መልካምን ሥራ
የጀመረው እርሱ እስከ ክርስቶስ ኢየሱስ ቀን
ድረስ ከፍጻሜው እንደሚያደርሰው እርግጠኛ
ነኝ።
7በልቤ ስላላችሁ፣ ስለ ሁላችሁ እንዲህ
ማሰቤ ተገቢ ነው፤ በእስራቴም ሆነ ለወ
ንጌል ስመክትና ሳጸናው ሁላችሁም ከእኔ
ጋር የእግዚአብሔር ጸጋ ተካፋዮች ናችሁና።
8በክርስቶስ ኢየሱስ ፍቅር ሁላችሁንም ምን
ያህል እንደምናፍቃችሁ እግዚአብሔር ምስክሬ
ነው።
9ፍቅራችሁ በጥልቅ እውቀትና በማስተ
ዋል ሁሉ በዝቶ እንዲትረፈረፍ እጸልያለሁ።
10ይኸውም ከሁሉ የሚሻለውን ለይታችሁ እን
ድታውቁ፣ እስከ ክርስቶስም ቀን ድረስ ንጹ
ሓንና ነቀፋ የሌለባችሁ እንድትሆኑ፣ 11ለእግዚ
እብሔር ክብርና ምስጋና በኢየሱስ ክርስቶስ
በኩል በሚገኘው የጽድቅ ፍሬ እንድትሞሉ
ነው።

## በጳውሎስ እስራት ወንጌል መስፋፋቱ

12አሁንም ወንድሞች ሆይ፤ በእኔ ላይ የደ
ረሰው ነገር ወንጌል በይበልጥ እንዲስፋፋ
መርዳቱን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ። 13ከዚህ
የተነሣ እስራቴ ስለ ክርስቶስ እንደ ሆነ፣ በቤተ
መንግሥት ዘበኞችና[ለ] በሌሎችም ሁሉ ዘንድ
ታውቆአል። 14በእኔ መታሰር ምክንያት በጌታ
ካሉት ወንድሞች ብዙዎቹ የእግዚአብሔርን ቃል
ያለ ፍርሀት፣ በድፍረት ለመናገር ብርታት
አግኝተዋል። 15አንዳንዶች ከቅናትና ከፉክክር
የተነሣ፣ ሌሎች ግን ከበጎ ፈቃድ የተነሣ
ክርስቶስን ይሰብካሉ። 16እነዚህ፣ እኔ ለወንጌል
ለመሟገት እዚህ እንዳለሁ ስለሚያውቁ፣
በፍቅር ይህን ያደርጋሉ፤ 17እነዚያ ግን በእስራቴ
ላይ ሳለሁ መከራ ሊያጸኑብኝ አስበው በቅን
ነት ሳይሆን ለግል ምኞታቸው ሲሉ ክርስ
ቶስን ይሰብካሉ።[ሐ] 18ታዲያ ችግሩ ከምኑ ላይ ነው?
ቁም ነገሩ በቅንነትም ይሁን በማስመሰል በማ
ንኛውም መንገድ ክርስቶስ መሰበኩ ነው።
በዚህም ደስ ይለኛል።
አዎን፤ ደስ ይለኛል፤ 19በእኔ ላይ የደረሰው
ነገር፣ በጸሎታችሁ አማካይነትና ከኢየሱስ ክር
ስቶስ መንፈስ በተሰጠ ረድኤት ለመዳኔ[መ]
እንደሚሆን ዐውቃለሁና። 20በምንም ዐይነት
መንገድ ዐፍሬ እንዳልገ ጽኑ ናፍቆትና ተስፋ
አለ፤ ነገር ግን እንደ ወትሮው ሁሉ ዛሬም
በሕይወትም ሆነ በሞት ክርስቶስ በሥጋዬ እን
ዲከበር ሙሉ ድፍረት ይኖረኛል። 21ለእኔ፣
መኖር ክርስቶስ ነው፤ ሞትም ማትረፍ ነው።
22በሥጋ ከቈየሁ፣ ፍሬያማ ተግባር ይኖረኛል፤
ነገር ግን የትኛውን እንደምመርጥ አላው
ቅም። 23በእነዚህ በሁለቱ እጨነቃለሁ፤ ልሄድ፣
ከክርስቶስም ጋር ልሆን እናፍቃለሁ፤ ይህ
እጅግ የተሻለ ነውና። 24ነገር ግን በሥጋ
መኖሬ ለእናንተ ይበልጥ አስፈላጊ ነው።
25ይህን በማስተዋል፣ በእምነት እንድታድ
ጉና ደስ እንዲላችሁ፣ በሁላችሁ ዘንድ
እንደምቈይና እንደምኖር ተረድቻለሁ።
26እንደ ገና መጥቼ በእናንተ ዘንድ በምሆ
ንበት ጊዜ በእኔ ምክንያት በክርስቶስ
ኢየሱስ ያላችሁ ደስታ ይበዛላችኋል።
27ብቻ ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ ኑሩ፤
ይህ ከሆነ መጥቼ ባያችሁ ወይም በርቀት ሆኜ
ስለ እናንተ ብሰማ፣ ለወንጌል እምነት እንደ
አንድ ሰው ሆናችሁ በመጋደል በአንድ መን
ፈስ ጸንታችሁ እንደምትቆሙ ዐውቃለሁ። 28በማ
ንኛውም መንገድ በተቃዋሚዎቻችሁ አትሸበሩ፤
ይህ እነርሱ እንደሚጠፉ፣ እናንተ ግን እንደ
ምትድኑ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ምልክት ነው።
29በክርስቶስ እንድታምኑ ብቻ ሳይሆን ስለ
እርሱ መከራ እንድትቀበሉም ይህ ጸጋ
ተሰጥቶአችኋልና፤ 30ቀድሞ እንዳያችሁት
አሁንም በእኔ እንዳለ በምትሰሙት በዚ
ያው ዐይነት ተጋድሎ እናንተም እያለፋ
ችሁ ነውና።

## ትሕትናን ከክርስቶስ መማር

2 ከክርስቶስ ጋር ካላችሁ አንድነት
የተነሣ የትኛውም መበረታታት፣
ከፍቅር የሆነ መጽናናት፣ የመንፈስ
ኅብረት፣ ምሕረትና ርኅራኄ ካላችሁ፣

1፥1 ሐሥ 9፥13፤ 16፥1፡12፤2ቆሮ1፥1፤ 1ጢሞ3፥1፡8
1፥2 ሮሜ1፥7
1፥3 ሮሜ1፥8
1፥4 ሮሜ1፥10
1፥5 ሐሥ2፥42፤ 16፡12ኛ40፤ፊል 4፥15
1፥6 ቈ10፤መዝ 138፥8፤1ቆሮ1፥8
1፥7 ቈ13፡14፡16፡ 17፤ሐሥ21፥33፤ 2ቆሮ7፥3፤2ጴጥ1፥13
1፥8 ሮሜ1፥9
1፥9 ኤፌ1፥17፤ 1ተስ3፥12
1፥10 ቈ6፤ 1ቆሮ1፥8
1፥11 ያዕ3፥18
1፥13 ቈ7፡14፡17፤ ሐሥ21፥33
1፥14 ቈ7፡ 13፡17፤ሐሥ4፥29፤ 21፥33
1፥16 ቈ7፡12
1፥17 ቈ7፡13፡14፤ ሐሥ21፥33፤ፊል2፥3
1፥19 ሐሥ16፥7፤ 2ቆሮ1፥11፤ፊሞ22
1፥20 ቈ14፤ሮሜ 8፥19፤14፥8፤1ቆሮ 6፥20
1፥21 ገላ2፥20
1፥23 ዮሐ12፥26፤ 2ጢሞ4፥6
1፥27 1ቆሮ16፥13፤ ኤፌ4፥1፤ይሁ3
1፥29 ማቴ5፥11፡ 12፤ሐሥ5፥41፤ 14፥22
1፥30 ቈ13፤ሐሥ 16፥19ኛ40፤ 1ተስ2፥2፤ዕብ10፥32
2፥1 2ቆሮ13፥14፤ ሐላ3፥12
2፥2 ዮሐ3፥29፤ ሮሜ15፥5፤ፊል4፥2

[ሀ]1 ጳጳሳት
[ለ]13 ወይም በቤተ መንግሥት ሁሉ
[ሐ]16፡17 አንዳንድ ጥንታዊ ያለሆኑ ቅጆች የቍ16 እና 17 ቅደም ተከተል ለዋውጠውታል

[ሠ]19 ወይም ለትድግናዬ

[2]በአንድ ፍቅር፣ በአንድ መንፈስና
በአንድ ዐሳብ በመሆን፣ ደስታዬን ፍጹም
አድርጉልኝ።
[3]ሌሎች ከእናንተ እንደሚሻሉ በትሕትና
ቍጠሩ እንጂ፣ በራስ ወዳድነት ምኞት
ወይም ከንቱ ውዳሴ ለማግኘት አንዳች
አታድርጉ። [4]እያንዳንዳችሁ ሌሎችን የሚጠ
ቅመውንም እንጂ፣ ራሳችሁን የሚጠቅመውን
ብቻ አትመልከቱ።

[5]በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረው ያ አስተሳሰብ፣
በእናንተም ዘንድ ይሁን፤
[6]እርሱ በባሕርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ፣
ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን ሊለቀው እንደ
ማይገባ አድርጎ አልቈጠረውም፤
[7]ነገር ግን የባሪያን መልክ[ረ] ይዞ፣
በሰውም አምሳል ተገኝቶ፣
ራሱን ባዶ አደረገ፤
[8]ሰው ሆኖ ተገልጦም፣
ራሱን ዝቅ አደረገ፤
እስከ ሞት፣ ያውም በመስቀል ላይ እስከ
መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ።
[9]ስለዚህ እግዚአብሔር እጅግ ከፍ አደረገው፤
ከስምም ሁሉ በላይ የሆነውን ስም ሰጠው፤
[10]ይኸውም በሰማይና በምድር፣ ከምድርም
በታች፣
ጒልበት ሁሉ ለኢየሱስ ስም ይንበረከክ
ዘንድ፣
[11]ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር፣
ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር
ዘንድ ነው።

## እንደ ከዋክብት ማብራት

[12]ስለዚህ፣ ወዳጆቼ ሆይ፤ ሁልጊዜም ታዛዦች
እንደ ነበራችሁ ሁሉ፣ አሁንም እኔ በአጠገ
ባችሁ ሳለሁ ብቻ ሳይሆን፣ ይልቁንም አሁን
በሌለሁበት ጊዜ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራ
ሳችሁን መዳን ፈጽሙ፤ [13]እንደ በጎ ፈቃዱ
መፈለግንና ማድረግን በእናንተ ውስጥ የሚ
ሠራ እግዚአብሔር ነውና።
[14]ማንኛውንም ነገር ሳታጒረመርሙና ሳት
ከራከሩ አድርጉ፤ [15]ይኸውም በጠማማና በክፉ
ትውልድ መካከል ንጹሓንና ያለ ነቀፋ፣ ነው
ርም የሌለባቸው የእግዚአብሔር ልጆች
ሆናችሁ፣ እንደ ከዋክብት በዓለም ሁሉ
ታበሩ ዘንድ ነው። [16]የሕይወትንም ቃል
ስታቀርቡ[ሰ]፣ በከንቱ እንዳልሮጥሁ ወይም
በከንቱ እንዳልደከምሁ በክርስቶስ ቀን
የምመካበት ይሆንልኛል። [17]ነገር ግን
በእምነታችሁ መሥዋዕትና አገል ግሎት ላይ
እንደ መጠጥ ቊርባን ብፈስ እንኳ
ከሁላችሁ ጋር ደስ ይለኛል፤ ሐሤ ትም
አደርጋለሁ። [18]እናንተም እንደዚሁ ከእኔ ጋር
ደስ ልትሰኙና ሐሤት ልታደርጉ ይገባል።

2÷3 ሮሜ12÷10፤ ገላ5÷26፤1ጴጥ5÷5
2÷4 1ቆሮ10÷24
2÷5 ማቴ11÷29
2÷6 ዮሐ1÷1፤ 5÷18፤14÷9
2÷7 ማቴ20÷28፤ ዮሐ1÷14፤ሮሜ8÷3፤ 2ቆሮ8÷9፤ዕብ2÷17
2÷8 ማቴ26÷39፤ ዮሐ10÷18፤ሮሜ 5÷19፤1ቆሮ1÷23፤ ዕብ5÷8
2÷9 ኢሳ52÷13፤ 53÷12፤ዳን7÷14፤ ሐሥ2÷33፤ኤፌ 1÷20፡21፤ዕብ2÷9
2÷10 መዝ95÷6፤ ኢሳ45÷23፤ማቴ 28÷18፤ሮሜ4÷11፤ ኤፌ1÷10፤ሐላ1÷20፤
2÷11 ዮሐ13÷13
2÷12 2ቆሮ7÷15
2÷13 ዕዝ1÷5፤1ቆሮ 12÷6፤15÷10፤ገላ2÷8፤ ኤፌ1÷5፤ዕብ13÷21
2÷14 1ቆሮ10÷10፤ 1ጴጥ4÷9
2÷15 ማቴ5÷45፡ 48፤ሐሥ2÷40፤ኤፌ 5÷1፤1ተስ3÷13
2÷16 1ቆሮ1÷8፤ 9÷24፤ 1ተስ2÷19
2÷17 ሮሜ15÷16፤ 2ቆሮ6÷10፤12÷15፤ 2ጢሞ4÷6
2÷19 ቍ23፤ሐሥ 16÷1
2÷20 1ቆሮ16÷10
2÷21 1ቆሮ10÷24
2÷22 1ቆሮ4÷17፤ 1ጢሞ1÷2
2÷23 ቍ19
2÷24 ፊል1÷25
2÷25 ሮሜ 16÷3፡ 9፡21፤2ቆሮ8÷23፤ፊል4÷3፡18፤ሐላ4÷11፤ ፊሞ1፡2
2÷26 ፊል1÷8፤
2÷28 ቍ25፤
2÷29 1ቆሮ16÷18፤ 1ጢሞ5÷17
2÷30 1ቆሮ16÷17፤
3÷1 ፊል2÷18፤
3÷2 መዝ22÷16፡ 20፤ራእ22÷15፤
3÷3 ሮሜ2÷28፡29፤ 15÷17፤ገላ6÷14፡15፤ ሐላ2÷11
3÷4 2ቆሮ11÷21፤
3÷5 ሉቃ1÷59፤ ሐሥ23÷6፤ሮሜ 11÷1፤2ቆሮ11÷21፡ 22
3÷6 ቍ9፤ሐሥ 8÷3፤21÷20፤ሮሜ 9÷30፤10÷5

## ጢሞቴዎስና አፍሮዲጡ

[19]ስለ እናንተ ሰምቼ ደስ እንዲለኝ፣ ጢሞቴ
ዎስን ቶሎ ወደ እናንተ ልልክላችሁ በጌታ
ኢየሱስ ተስፋ አደርጋለሁ። [20]ስለ እናንተ
ደኅንነት ከልቡ የሚገደው እንደ እርሱ ያለ
ማንም የለኝም፤ [21]ሁሉም የኢየሱስ ክርስቶ
ስን ሳይሆን የራሳቸውን ፍላጎት ለፈፌላት
ይሯሯጣሉና። [22]ነገር ግን እንደምታውቁት ጢሞ
ቴዎስ ማንነቱን አስመስክሮአል፤ ልጅ ከአባቱ
ጋር እንደሚያገለግል፣ ከእኔ ጋር በወንጌል ሥራ
አገልግሎአልና። [23]እንግዲህ የራሴን የወደፊት
ሁኔታ እንዳጣራሁ ልልከው ተስፋ አደርጋ
ለሁ። [24]እኔም ራሴ ቶሎ እንደምመጣ በጌታ
ታምኛለሁ። [25]እንዲሁም ወንድሜን፣ የሥራ
ባልደረባዬንና አብሮኝ ወታደር የሆነውን፣ በሚ
ያስፈልገኝ ሁሉ እንዲንከባከበኝ የላካችሁትን፣
የእናንተ መልእክተኛ የሆነውን አፍሮዲጡን
መልሼ እንድልክላችሁ አስፈላጊ ሆኖ አግኝ
ቼዋለሁ። [26]እርሱ ሁላችሁንም ይናፍቃልና፤
መታመሙን ስለ ሰማችሁም ተጨንቆአል።
[27]በእርግጥም ታሞ ለሞት ተቃርቦ ነበር፤ እግዚ
አብሔር ግን ምሕረት አደረገለት፤ በሐዘን
ላይ
ሐዘን እንዳይደራረብብኝ፣ ለእኔም ጭምር እንጂ
ለእርሱ ብቻ አይደለም። [28]ስለዚህ እርሱን
እንደ ገና ስታዩ ደስ እንዲላችሁና የእኔም
ጭንቀት እንዲቀል ልልከው በጣም ጓጒቻ
ለሁ። [29]በሙሉ ደስታ በጌታ ተቀበሉት፤ እንደ
እርሱ ያሉትንም ሰዎች አክብሟቸው። [30]እር
ሱም እናንተ ልትሰጡኝ ያልቻላችሁትን አገል
ግሎት ለማሟላት ሲል ለሕይወቱ እንኳ ሳይ
ሳሳ፣ ለክርስቶስ ሥራ ከሞት አፋፍ ደርሶ ነበ
ርና።

## በሥጋ አለመመካት

3 ከዚህ በተረፈ ወንድሞቼ ሆይ፤ በጌታ
ደስ ይበላችሁ። ያንኑ ደግሜ ብጽፍላችሁ
እኔ አይሰለቸኝም፤ ለእናንተም ይጠቅማች
ራል። [2]ከእነዚያ ውሾች ተጠንቀቁ፤ ክፉትን
ከሚያደርጉና ሥጋን ከሚቈራርጡ ሰዎች
ተጠበቁ። [3]እኛ በእውነት የተገረዝን በእግ
ዚአብሔር መንፈስ የምናመልክ፣ በክርስቶስ ኢ
የ ሱስ የምንመካ፣ በሥጋም የማንታመን ነንና።
[4]ካስፈለገ እኔም በሥጋ የምመካበት አለኝ።
ማንም በሥጋ የሚመካበት ነገር ያለው
ቢመስለው፣ እኔ እበልጠዋለሁ፤ [5]በስምንተኛው
ቀን የተገረዝሁ፣ ከእስራኤል ዘር፣ ከብንያም
ወገን የተወለድሁ ስሆን፣ ከዕብራውያንም ዕብ
ራዊ ነኝ፤ ስለ ሕግ ከተነሣ፣ ፈሪሳዊ ነበርሁ፤
[6]ስለ ቅናት ከሆነ፣ የቤተ ክርስቲያን አሳዳጅ
ነበርሁ፤ ሕግን በመፈጸም ስለሚገኝ ጽድቅ
ከሆነም፣ ያለ ነቀፋ ነበርሁ።

[ሠ]6 ወይም መልክ [ረ]7 ወይም ባሕርይ
[ሰ]16 ሰትይዙ

7ነገር ግን ይጠቅመኝ የነበረውን ሁሉ አሁን
ለክርስቶስ ስል እንደ ጒድለት ቈጥሬዋለሁ።
8ከዚህም በላይ ለእርሱ ብዬ ሁሉን ነገር የተ
ውሁለትን፣ ወደር የሌለውን ጌታዬን ክርስ
ቶስ ኢየሱስን ከማወቅ ታላቅነት ጋር ሳነጻ
ጽር፣ ሁሉንም ነገር እንደ ጒድለት እቈጥረዋ
ለሁ፤ ለእርሱ ስል ሁሉን አጥቻለሁ፤ ክርስ
ቶስን አገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ ጒድፍ እቈጥ
ራለሁ፤ 9ሕግ በመጠበቅ የሚገኝ የራሴ ጽድቅ
ኖሮኝ ሳይሆን፣ በክርስቶስ በማመን ይኸውም
ከእግዚአብሔር የሚመጣ፣ ከእምነትም በሆነ ጽድቅ
በእርሱ ዘንድ እንድገኝ ነው። 10ክርስቶስንና የት
ንሣኤውን ኀይል እንዳውቅ፣ በሥቃዩ ተካፋይ
እንድሆንና በሞቱም እርሱን እንድመስል እመ
ኛለሁ፤ 11ለሙታን ትንሣኤም እንድደርስ እና
ፍቃለሁ።

## ወደ ግብ ለመድረስ መፍጠን

12ይህን ሁሉ አግኝቻለሁ ወይም ፍጹም
ሆኛለሁ ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ክርስቶስ
ኢየሱስ እኔን የራሱ ያደረገበትን ያን፣ እኔም
የራሴ ለማድረግ እጣጣራለሁ። 13ወንድሞች
ሆይ፤ እኔ ገና እንደ ያዝሁት አድርጌ ራሴን
አልቈጥርም፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋ
ለሁ፤ ከኋላዬ ያለውን እየረሳሁ ከፊቴ ወዳለው
እዘረጋለሁ። 14እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ
ወደ ላይ ስለ ጠራኝ፣ ሽልማት ለመቀዳጀት
ወደ ግቡ እፈጥናለሁ።
15እንግዲህ እኛ ብስለት ያለን ሁላችን
ነገሮችን በዚህ ሁኔታ ማየት ይኖርብናል፤
በአንዳንድ ነገር የተለያየ አስተሳሰብ ቢኖ
ራችሁ፣ እግዚአብሔር እርሱንም
ይገልጥላችኋል። 16ሆኖም በደረስንበት በዚያ
እንመላለስ።
17ወንድሞች ሆይ፤ የእኔን አርአያነት በመ
ከተል ከሌሎች ጋር ተባበሩ፤ እኛ በሰጠናችሁ
ምሳሌነት መሠረት የሚኖሩትንም አስተውሉ።
18ምክንያቱም ከዚህ በፊት ደጋግሜ እንደ ነገ
ርኋችሁ፣ አሁንም እንደ ገና፣ ያውም በእንባ
እነግራችኋለሁ፤ ብዙዎች የክርስቶስ መስቀል
ጠላቶች ሆነው ይመላለሳሉ። 19መጨረሻቸው
ጥፋት ነው፤ ሆዳቸው አምላካቸው ነው፤ ክብራ
ቸው በውርደታቸው ነው፤ ልባቸው ያረፈው በምድራዊ
ነገር ላይ ነው። 20እኛ ግን አገራችን በሰማይ
ነው፤ ከዚያ የሚመጣውንም አዳኝ፣ ጌታ ኢየ
ሱስ ክርስቶስን በናፍቆት እንጠባበቃለን፤
21እርሱም ሁሉን ለራሱ ባስገዛበት ኀይል፣
ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን
ሥጋችንን ይለውጣል።

4 ስለዚህ የምወዳችሁና የምናፍቃችሁ፣
ወንድሞቼ ደስታዬና አክሊሌ የሆናችሁ፣
እንዲሁም ወዳጆች ሆይ፤ በዚህ ሁኔታ በጌታ
ጸንታችሁ ቁሙ።

## የጳውሎስ ምክር

2በጌታ አንድ ልብ እንዲኖራቸው ኤዎድ
ያንን እለምናለሁ፤ ሲንጤኪንንም እለምና
ለሁ። 3አዎን፤ አንተ ታማኝ የሥራ ባልደረባዬ
ሆይ፤ ወንጌልን በማሰራጨት ረገድ ከእኔና ከቀ
ሌምንጦስ ጋር፣ እንዲሁም ስሞቻቸው በሕይወት
መጽሐፍ ከተጻፉት ከሌሎች የሥራ ጓደኞቼ
ጋር የተጋደሉትን እነዚህን ሴቶች እንድትረ
ዳቸው እለምንሃለሁ።
4ምንጊዜም በጌታ ደስ ይበላችሁ፤ ደግሜ
እላለሁ ደስ ይበላችሁ። 5ገርነታችሁ በሁሉ
ዘንድ የታወቀ ይሁን፤ ጌታ ቅርብ ነው።
6በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ፣ ከምስጋ
ናም ጋር ልመናችሁን በእግዚአብሔር ፊት
አቅርቡ እንጂ ስለማንኛውም ነገር አት
ጨነቁ። 7ከማስተዋል በላይ የሆነው የእግዚ
አብሔር ሰላም፣ ልባችሁንና አሳባችሁን በክ
ርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል። 8በመጨረሻም
ወንድሞች ሆይ፤ እውነት የሆነውን ሁሉ፣ ክቡር
የሆነውን ሁሉ፣ ትክክል የሆነውን ሁሉ፣ ንጹሕ
የሆነውን ሁሉ፣ ተወዳጅ የሆነውን ሁሉ፣ መል
ካም የሆነውን ሁሉ፣ በጎነት ቢሆን ወይም
ምስጋና፣ እንደ እነዚህ ስላሉት ነገሮች አስቡ።
9ከእኔ የተማራችሁትን ወይም የተቀበላች
ሁትን፣ የሰማችሁትን ወይም ያያችሁትን
ማናቸውንም ነገር አድርጉ፤ የሰላም አምላክ
ከእናንተ ጋር ይሆናል።

## ላደረጉት ችሮታ የቀረበ ምስጋና

10ከብዙ ጊዜ በኋላ በአዲስ መንፈስ ስለ
እኔ ማሰብ በመጀመራችሁ፣ በጌታ እጅግ ደስ
ይለኛል፤ በእርግጥ በተግባር ለመግለጽ ዕድሉ
አልነበራችሁም እንጂ ማሰቡንስ ታስቡልኝ
ነበር። 11ይህን የምለው ስለቸገረኝ አይደለም፤
ምክንያቱም በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ያለኝ
ይበቃኛል ማለትን፣ 12ማጣትን ዐውቀዋለሁ፤
ማግኘትንም ዐውቀዋለሁ። ብጠግብም ሆነ
ብራብም፣ ባገኝም ሆነ ባጣ በማንኛውም ሆነ
በየትኛውም ሁኔታ ያለኝ ይበቃኛል የማለ ትን
ምስጢር ተምሬአለሁ። 13ኀይልን በሚ ሰጠ
ኝ በእርሱ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ።
14ሆኖም የመከራዬ ተካፋይ ስለ ሆናችሁ
መልካም አድርጋችኋል። 15ከዚህም በላይ፣
እናንተ የፊልጵስዩስ ሰዎች ራሳችሁ እንደም
ታውቁት፣ በመጀመሪያ ወንጌልን በተቀበላ
ችሁ ጊዜ ከመቄዶንያ ስነሣ፣ ከእናንተ በቀር
በመስጠትና በመቀበል የትኛውም ቤተ ክርስ
ቲያን አልተባበረም። 16በተሰሎንቄ በነበርሁ
በት ጊዜ እንኳ፣ በችግሬ ወቅት ደጋግማችሁ
ርዳታ ልካችሁልኛልና።
17ይኸውም ትርፉ ለእናንተ እየበዛ እንዲሄድ
እንጂ ስጦታውን ጓጕቼ አይደለም። 18የሚያስፈ
ልገኝን ሁሉ፣ ከሚያስፈልገኝም በላይ ተቀ
ብያለሁ፤ የላካችሁትንም ስጦታ ከአፍሮዲጡ

3፥7 ማቴ13፥44፤ ሉቃ14፥33
3፥8 ቍ10፤መዝ 73፥25፤ኤር9፥23፡24፤ዮሐ17፥3፤ኤፌ 4፥13፤2ጴጥ1፥2
3፥9 ቍ6፤ኤር 33፥16
3፥10 ቍ8፤ሮሜ 6፥3ኛ5፤2ቆሮ1፥5
3፥11 ዮሐ11፥24፤ ሮሜ6፥5፤ራእ20፥5፡6
3፥12 ሐሥ9፥5፡6፤ 1ቆሮ13፥10፤1ጢሞ 6፥12
3፥13 ሉቃ 9፥62
3፥14 ሮሜ8፥28፤ 1ቆሮ9፥24፤ዕብ6፥1
3፥15 1ቆሮ2፥6፤ ገላ5፥10፤ኤፌ1፥17፤ 1ተሰ4፥9
3፥17 1ቆሮ4፥16፤ 1ጢሞ4፥12
3፥18 ሐሥ20፥31፤ ገላ6፥12
3፥19 መዝ73፥17፤ ሮሜ6፥21፤8፥5፡6፤ 16፥18፤ሐላ3፥2፤ ይሁ13
3፥20 1ቆሮ1፥7፤ ኤፌ2፥19፤ሐላ3፥1፤ ዕብ12፥22
3፥21 ሮሜ8፥29፤ 1ቆሮ15፥43ኛ53፤ ኤፌ1፥19፤ሐላ3፥4
4፥1 1ቆሮ16፥13፤ ፊል1፥8
4፥2 ፊል2፥2
4፥3 ፊል2፥25፤ራእ 20፥12
4፥4 መዝ85፥6፤ 97፥12፤ዕን3፥18፤ማቴ 5፥12፤ሮሜ12፥12፤ ፊል3፥1
4፥5 መዝ119፥151፤ 145፥18፤ዕብ10፥37፤ ያዕ 5፥8፡9
4፥6 ማቴ6፥25ኛ34፤ ኤፌ6፥18፤1ጢሞ 2፥1
4፥7 ኢሳ26፥3፤ ዮሐ14፥27፤ኤፌ3፥19
4፥9 ሮሜ15፥33፤ 1ቆሮ4፥16
4፥10 2ቆሮ11፥9
4፥11 1ጢሞ6፥6፡ 8፤ዕብ13፥5
4፥12 1ቆሮ 4፥11፤ 2ቆሮ11፥9
4፥13 2ቆሮ12፥9፤ ኤፌ 3፥16፤ ሐላ1፥11፤ 1ጢሞ1፥12፤2ጢሞ 4፥17
4፥14 ፊል1፥7
4፥15 ሐሥ16፥9፤ 2ቆሮ11፥8፡9፤ፊል1፥5
4፥16 ሐሥ17፥1፤ 1ተሰ2፥9
4፥17 1ቆሮ9፥11፡ 12
4፥18 2ቆሮ2፥14፤ ፊል2፥25

እጅ ተቀብዬ ተሞልቻለሁ፤ ይህም መዐዛው
የጣፈጠ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለውና
ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት ነው። 19አምላኬም
እንደ ታላቅ ባለጠግነቱ መጠን የሚያስፈልጋ
ችሁን ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ይሞላባችኋል።
20 ለአምላካችንና ለአባታችን ከዘላለም
እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።

4፥19 መዝ23፥1፤
ሮሜ2፥4፤2ቆሮ9፥8
4፥20 ሮሜ11፥36፤
ገላ1፥4፤1ተስ1፥3፤
3፥11፥13
4፥21 ገላ1፥2
4፥22 ሐሥ9፥13
4፥23 ሮሜ16፥20፤
ገላ6፥18

## የስንብት ሰላምታ

21ለቅዱሳን ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ሰላ
ምታ አቅርቡልኝ። ከእኔ ጋር ያሉት ወንድ
ሞችም ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። 22 ቅዱሳንን
ሁሉ፣ በተለይም ከቄሳር ቤተ ሰው የሆኑት
ወገኖች ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።
23የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመንፈ
ሳችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን[ሽ]።

[ሽ]23 አንዳንድ ቅጆች አሜን የሚለው የላቸውም

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት
# ወደ ቈላስይስ ሰዎች

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ የክርስቶስ ኢየሱስ
ሐዋርያ ከሆነው ከጳውሎስና ከወንድ
ማችን ከጢሞቴዎስ፤
2በሐላስይስ ለሚኖሩ፣ በክርስቶስ ለሆኑ
ቅዱሳንና ታማኝ[ሀ] ወንድሞች፤
ከእግዚአብሔር ከአባታችን[ለ] ጸጋና ሰላም
ለእናንተ ይሁን።

## ምስጋናና ጸሎት

3ስለ እናንተ በምንጸልይበት ጊዜ የጌታ
ችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን
ሁልጊዜ እናመሰግናለን፤ 4ምክንያቱም
በክርስቶስ ኢየሱስ ስላላችሁ እምነትና ለቅ
ዱሳን ሁሉ ስላላችሁ ፍቅር ሰምተናል፤ 5ይህም
የሆነው በሰማይ ተዘጋጅቶ ከተቀመጠ
ላችሁ ተስፋ የተነሣ ነው፤ ስለዚህ ተስፋ
በወንጌል የእውነት ቃል አስቀድማችሁ ሰማ
ችሁ፤ 6ይህም ወደ እናንተ ደርሶአል።
ይህንም ወንጌል ከሰማችሁበትና የእግዚአብሐ
ሔርን ጸጋ በእውነት ከተረዳችሁበት ቀን
ጀምሮ በዓለም ዙሪያ እየሠራ እንዳለ ሁሉ
በእናንተም ዘንድ ፍሬ እያፈራና እያደገ
ነው። 7ይህንም ስለ እኛ[ሐ] የክርስቶስ
ታማኝ አገልጋይ የሆነው፣ አብሮንም በአገ
ልግሎት የተጠመደው ተወዳጁ ኤጳፍራ
አስተማራችሁ፤ 8ደግሞም በመንፈስ ስላላ
ችሁ ፍቅር ነገረን።
9ከዚህ የተነሣ እኛ ደግሞ ይህን ከሰ
ማንበት ቀን ጀምሮ እግዚአብሔር የፈቃዱን ዕው
ቀት በመንፈሳዊ ጥበብና መረዳት ሁሉ
ይሞላችሁ ዘንድ ስለ እናንተ መጸለይና መለ
መን አላቋረጥንም፤ 10የምንጸልየውም ለጌታ
እንደሚገባ እንድትኖሩና በሁሉም ደስ እን
ድታሰኙት ነው፤ ይኸውም በመልካም ሥራ
ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ እግዚአብሔርን በማወቅ
እያደጋችሁ፣ 11ታላቅ ጽናትና ትዕግሥት ይኖ
ራችሁ ዘንድ፣ እንደ ክቡር ጕልበቱ መጠን
በኀይል ሁሉ እየበረታችሁ፣ ደስ እየተሰ
ኛችሁ፣ 12በቅዱሳን ርስት በብርሃን ተካፋዮች
ለመሆን ያበቃንን[መ] አብን እንድታመሰግኑ
ነው። 13እርሱ ከጨለማ አገዛዝ ታደገን፤
ወደሚወደው ልጁ መንግሥትም አሻገረን፤
14በእርሱም በደሙ[ሠ] የሆነ መዋጀትን አግኝተ
ናል፤ ይህም የኀጢአት ይቅርታ ነው።

## ክርስቶስ ከሁሉ በላይ

15እርሱ የማይታየው አምላክ አምሳል ነው፤
ከፍጥረት ሁሉ በፊት[ረ] በኵር ነው፤ 16ሁሉ
ነገር በእርሱ ተፈጥሮአል፤ በሰማይና በምድር

1፥1 ሐሥ16፥1፤ 1ቆሮ1፥1፤2ቆሮ1፥1
1፥2 ሮሜ1፥7፤ ቈላ4፥18
1፥3 ሮሜ1፥8
1፥4 ሐሥ9፥13፤ ገላ5፥6፤ኤፌ1፥15፤ ፊሞ5
1፥5 ቊ23፤ 1ተሰ5፥8፤2ጢሞ2፥15፤ ቲቶ1፥2፤1ጴጥ1፥4
1፥6 ቊ23፤ ዮሐ15፥16፤ሮሜ10፥18
1፥7 ቈላ4፥7፡12፤ ፊሞ23
1፥8 ሮሜ15፥30
1፥9 ቊ4፤ሮሜ1፥10፤ ኤፌ1፥15፡17፤5፥17
1፥10 ቊ6፤ 2ቆሮ5፥9፤ኤፌ4፥1
1፥11 ኤፌ4፥2፤ ፊል4፥13
1፥12 ሐሥ20፥32፤ 26፥18፤2ጴጥ1፥11
1፥13 ማቴ3፥17፤ ሐሥ26፥18፤ 2ጴጥ1፥11
1፥14 ሮሜ3፥24፤ ኤፌ1፥7
1፥15 ቊ18፤ ዮሐ1፥18፤ 14፥9፤1ጢሞ1፥17፤ ዕብ11፥27
1፥16 ዮሐ1፥3፤ ሮሜ11፥36፤ ኤፌ1፥20፡21
1፥17 ዮሐ1፥2
1፥18 ቊ 15፡24፤ መዝ89፥27፤ ሐሥ26፥23፤ሮሜ8፥29፤ 1ቆሮ12፥27፤ኤፌ1፥22 ዕብ1፥6፤ራእ1፥5
1፥19 ዮሐ1፥16፤ ኤፌ1፥5
1፥20 ሉቃ2፥14፤ ሮሜ5፥10፤ ኤፌ1፥10፤2፥13
1፥21 ሮሜ5፥10፤ ኤፌ2፥3
1፥22 ቊ20፤ ሮሜ5፥10፤7፥4፤ 2ቆሮ4፥14፤ኤፌ1፥4፤5፥27
1፥23 ቊ5፡6፡25፤ ሮሜ10፥18፤ 11፥22፤ 1ቆሮ3፥5፤ ኤፌ3፥17
1፥24 1ቆሮ12፥27፤ 2ቆሮ1፥5፤6፥10
1፥25 ቊ23፤ 1ቆሮ3፥5፤ኤፌ3፥2፤ ዕብ4፥12
1፥26 ሮሜ16፥25
1፥27 ማቴ13፥11፤ ሮሜ2፥4፤8፥10

ያሉ፣ የሚታዩና የማይታዩ፣ ዙፋናት ቢሆኑ
ወይም ኀይላት፣ ገዦች ቢሆኑ ወይም ባለ
ሥልጣናት፣ ሁሉም ነገር በእርሱና ለእ
ርሱ ተፈጥሮአል። 17እርሱ ከሁሉ በፊት
ነው፤ ሁሉም ነገር በአንድ ላይ ተያይዞ የጸ
ናው በእርሱ ነው። 18እርሱ አካሉ የሆነችው
የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፤ በሁሉ ነገር
የበላይነት ይኖረው ዘንድ እርሱ የመጀ
መሪያ፣ ከሙታን መካከልም በኵር ነው።
19እግዚአብሔርም ሙላቱ ሁሉ በእርሱ
ይሆን ዘንድ ወዶአልና፤ 20በመስቀሉ ላይ
በፈሰሰው ደሙ ሰላምን በማድረግ
በምድርም ሆነ በሰማይ ያለውን ነገር
ሁሉ በእርሱ በኩል ከራሱ ጋር አስታረቀ።
21ከክፉ ባሕርያችሁ የተነሣ[ሰ] ቀድሞ ከእግ
ዚአብሔር የተለያችሁ በአሳባችሁም ጠላቶች
ነበራችሁ። 22አሁን ግን ነውርና ነቀፋ የሌ
ለባችሁ ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ሊያ
ቀርባችሁ፣ በክርስቶስ ሥጋ በሞቱ በኩል
አስታረቃችሁ፤ 23ይህም የሚሆነው በእምነ
ታችሁ ተመሥርታችሁና ተደላድላችሁ በመ
ቆም ከሰማችሁት የወንጌል ተስፋ ሳትናወጡ
ጸንታችሁ ብትኖሩ ነው። እናንተ የሰማች
ሁትና ከሰማይ በታች ላለ ፍጥረት ሁሉ
የተሰበከውም ወንጌል ይኸው ነው፤ እኔም
ጳውሎስ ለዚህ ወንጌል አገልጋይ ሆንሁ።

## ጳውሎስ ስለ ቤተ ክርስቲያን ያሳየው ትጋት

24ስለ እናንተ በተቀበልሁት መከራ
አሁንም ደስ ይለኛል፤ ክርስቶስ ስለ አካሉ
ስለ ቤተ ክርስቲያን ከተቀበለው መከራ
የጐደለውን በሥጋዬ አሟላለሁ። 25የእግዚአብሔ
ርን ቃል በሙላት እንዳቀርብላችሁ ከእግዚ
አብሔር በተሰጠኝ ዐደራ የቤተ ክርስቲያን
አገልጋይ ሆኛለሁ፤ 26ይህም ቃል ከዘመናትና
ከትውልዶች ተሰውሮ ምስጢር ሆኖ
ቈይቶ ነበር፤ አሁን ግን ለቅዱሳኑ ተገልጦአጠ
ል። 27ለእነርሱም እግዚአብሔር የዚህ ምስጢር
ክብር ባለ ጠግነት በአሕዛብ መካከል ምን
ያህል እንደ ሆነ ለማሳወቅ መረጠ፤ እርሱም
የክብር ተስፋ የሆነው በእናንተ ውስጥ
ያለው ክርስቶስ ነው።
28እኛም እያንዳንዱን ሰው በክርስቶስ ፍጹም

[ሀ]2 ወይም *የሚያምኑ*
[ለ]2 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *ከአባትና ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ*
[ሐ]7 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *እናንተ* ይላሉ።
[መ]12 ወይም *ያበቃችሁን*
[ሠ]14 አንዳንድ ቅጆች *በደሙ* የሚለውን አይጨምሩም
[ረ]15 ወይም *በላይ*
[ሰ]21 ወይም *በክፉ ባሕርያችሁ እንደሚታየው*

አድርገን ማቅረብ እንችል ዘንድ፣ ሰውን ሁሉ
በጥበብ ሁሉ እየመከርንና እያስተማርን እር
ሱን እንሰብካለን፤ 29እኔም በብርታት በውስጤ
በሚሠራው በእርሱ ኀይል ሁሉ እየታገልሁ
ለዚህ ዐላማ እጥራለሁ።

2 ስለ እናንተና በሎዶቅያ ስላሉት
እንዲሁም በአካል አይተውኝ ስለ
ማያውቁ ሁሉ ምን ያህል እየተጋደልሁ እንደ
ሆነ እንድታውቁ እፈልጋለሁ፤ 2ደግሞም
ልባቸው እንዲጽናናና በፍቅር እንዲተሳሰሩ፣
ፍጹም የሆነውን የመረዳት ብልጥግና አግ
ኝተው የእግዚአብሔር ምስጢር የሆነውን ክርስ
ቶስን እንዲያውቁ እተጋለሁ፤ 3የተሰወረ
የጥበብና የዕውቀት ሀብት ሁሉ የሚገኘው
በእርሱ ዘንድ ነውና። 4ማንም ንግግር በማ
ሳመር እንዳያታልላችሁ ይህን እነግራችኋ
ለሁ። 5ምንም በሥጋ ከእናንተ ርቄ ብገኝ
በመንፈስ ከእናንተ ጋር ነኝና በሥርዐት መኖ
ራችሁንና በክርስቶስ ያላችሁን ጽኑ እም ነት
እያየሁ ደስ ይለኛል።

### ከሰው ሠራሽ ሥርዐት በክርስቶስ ነጻ መሆን

6እንግዲህ ጌታ ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ
ተቀበላችሁት እንዲሁ በእርሱ ኑሩ፤ 7በእ
ርሱ ተተክላችሁና ታንጻችሁ፣ እንደ ተማ
ራችሁት በእምነት ጸንታችሁ፣ የተትረፈረፈ
ምስጋና እያቀረባችሁ ኑሩ።

8በክርስቶስ ላይ ሳይሆን፣ በሰዎች ልማድና
በዚህ ዓለም መሠረታዊ ሕግጋት ላይ በተመ
ሠረተ ፍልስፍናና ከንቱ ማግባቢያ ማንም
ማርኮ እንዳይወስዳችሁ ተጠንቀቁ።

9የመለኮት ሙላት ሁሉ በአካል በእ
ርሱ ይኖራልና፤ 10እናንተም የገዥነትና
የሥልጣን ሁሉ ራስ በሆነው በክርስቶስ ሙሉ
ሆናችኋል። 11በእርሱ ሆናችሁ በእጅ ባልተ
ደረገ መገረዝ ተገረዛችሁ፤ በክርስቶስም መገ
ረዝ የሥጋን ኀጢአታዊ ባሕርይ አስወ
ገዳችሁ፤ 12በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራ
ችሁ፤ እርሱን ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብ
ሔር ኀይል በማመን ከእርሱ ጋር ደግሞ ተነሣ
ችሁ።

13እናንተም በበደላችሁና የሥጋችሁን ኀጢአ
ታዊ ባሕርይ ባለ መገረዝ ሙታን ሳላ
ችሁ፣ እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ሕያዋን
አደረጋችሁ[ሽ]፤ ኀጢአታችንንም ሁሉ ይቅር
አለን፤ 14ሲቃወመንና ሲጻረረን የነበረውን
የዕዳ ጽሕፈት ከነሕግጋቱ በመደምሰስ፣ በመስ
ቀል ላይ ቸንክሮ ከመንገድ አስወገደው።
15የአለቆችንና የባለ ሥልጣናትንም ማዕረግ
በመግፈፍ በመስቀሉ[ቀ] ድል ነሥቶ በአደባባይ
እያዞራቸው እንዲታዩ አደረገ።

16እንግዲህ በምትበሉትም ሆነ በም
ትጠጡት ወይም በዓልን፣ ወር መባቻንና
ሰንበትን በማክበር ነገር ማንም አይፍረ
ድባችሁ፤ 17እነዚህ ሊመጡ ላሉ ነገሮች ጥላ
ናቸውና፤ አካሉ ግን የክርስቶስ ነው። 18ዐ
ጕል ትሕትናንና የመላእክትን አምልኮ
የሚወድ ማንም ሰው እንዳያደናቅፋችሁ ተጠ
ንቀቁ። እንደዚህ ያለ ሰው ስላየው ራእይ
ከመጠን በላይ ራሱን እየካበ በሥጋዊ
አእምሮው ከንቱ ሐሳብ ተሞልቶ
ይታበያል፤ 19ይህ ሰው፣ አካል ሁሉ በጅ
ማትና በማሰሪያ እየተጋጠመ ምግብንም
እየተቀበለ እግዚአብሔር በሚሰጠው ማደግ
ከሚያድግበት ራስ ከሆ ነው ጋር ግንኙነት
የለውም።

20ለዚህ ዓለም መርሕ ከክርስቶስ ጋር
ከሞታችሁ ታዲያ ለምን እንደዚህ ዓለም
ሰው ለሕጎቹ ተገዥ ትሆናላችሁ? 21"አትያዝ!፤
አትቅመስ! አትንካ!" እንደሚሉት ዐይነት፣
22እነዚህ ሁሉ በሰው ትእዛዝና ትምህርት
ላይ የተመሠረቱ ስለ ሆኑ በተግባር ላይ ሲ
ውሉ
ጠፊ ናቸው። 23እነዚህ ነገሮች በገዛ ራስ ላይ
ከሚፈጥሩት የአምልኮ ስሜት፣ ከዐጕል ትሕ
ትናና ሰውነትን ከመጨሖን አንፃር በእርግጥ
ጥበብ ያለባቸው ይመስላሉ፤ ነገር ግን የሥ
ጋን ልቅነት ለመሖጣጠር አንዳች ፋይዳ
የላቸውም።

### የቅድስና ሕይወት መመሪያ

3 እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፣
ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ
በተቀመጠበት በላይ ያሉ ነገሮችን እሹ፤
2አሳባችሁም በላይ ባለው ላይ እንጂ
በምድራዊ ነገር ላይ አይሁን።
3ሞታችኋልና፤ ሕይወታች ሁም ከክርስቶስ
ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ተሰ ውሮአልና፤ 4ሕ
ይወታችሁ[በ] የሆነው ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊ
ዜ እናንተም በዚያን ጊዜ ከእርሱ ጋር በክብር
ትገለጣላችሁ።

5ስለዚህ ምድራዊ ምኞቶቻችሁን ግደሉ፤
እነዚህም፦ ዝሙት፣ ርኵሰት፣ ፍትወት፣ ክፉ
ምኞትና አምልኮተ ጣዖት የሆነው መጐ
ምጀት ናቸው። 6በእነዚህም ምክንያት የእ
ግዚአብሔር ቍጣ በማይታዘዙት[ተ] ላይ ይመ
ጣል፤ 7እናንተም ቀድሞ በኖራችሁ
በት ሕይወት በእነዚህ ትመላለሱ ነበር፤
8አሁን ግን ቍጣን፣ ንዴትን፣ ስድብን፣
ሐሜትንና አሳፋሪ ንግግርን የመሳሰሉት
ንም ሁሉ አስወግዱ፤ 9አሮጌውን ሰው ከሥ
ራው ጋር አውልቃችሁ ስለ ጣላችሁ

2፥1 ቈላ1፥29፤ 4፥12፡13፡15፡16፤ ራእ1፥11፤3፥14
2፥2 ሮሜ16፥25፤ ኤፌ6፥22፤ቈላ4፥8
2፥3 ኢሳ11፥2፤ ኤር23፥5፤ሮሜ 11፥33፤1ቆሮ1፥24፡30
2፥4 ሮሜ16፥18
2፥5 ሐሥ20፥21፤ 1ቆሮ5፥4፤ 14፥40፤1ተሰ2፥17፤1ጴጥ5፥9
2፥6 ዮሐ13፥13፤ ቈላ1፥10
2፥7 ኤፌ3፥17፤ 4፥21
2፥8 ቍ20፤ ገላ4፥3፤1ጢሞ6፥20
2፥9 ዮሐ1፥16
2፥10 ማቴ28፥18፤ ኤፌ1፥22
2፥11 ሮሜ2፥29፤ ገላ5፥24፤ፊል3፥3
2፥12 ማቴ28፥19፤ ሐሥ2፥24፤ሮሜ6፥5
2፥13 ኤፌ2፥1፡ 5፤4፥32
2፥14 ኤፌ2፥15፤ 1ጴጥ2፥24
2፥15 ቍ10፤ ማቴ12፥29፤ ሉቃ10፥18፤ ዮሐ12፥31፤ኤፌ6፥12
2፥16 ዘሌ23፥2፤ 1ዜና23፥31፤ ማር2፥27፡28፤7፥19፤ ሮሜ14፥3፡ 4፡5፡ 17፤ገላ4፥10
2፥17 ዕብ8፥5፤ 10፥1
2፥18 ቍ23፤ 1ቆሮ9፥24፤ ፊል3፥14
2፥19 1ቆሮ12፥27፤ ኤፌ1፥22፤ኤፌ4፥16
2፥20 ቍ8፡14፡16፤ ሮሜ6፥6፤ገላ4፥3፡9
2፥22 ኢሳ29፥13፤ ማቴ15፥9፤1ቆሮ6፥13፤ ቲቶ1፥14
2፥23 ቍ18
1፥28 ማቴ5፥48፤ 1ቆሮ2፥6፡7፤ ኤፌ5፥27፤ቈላ3፥16
1፥29 1ቆሮ15፥10፤ 2ቆሮ11፥23፤ኤፌ1፥19፤3፥7፤ ቈላ15፥10
3፥1 ማር16፥19፤ ሮሜ6፥5
3፥2 ፊል3፥19፡20
3፥3 ሮሜ6፥2፤ 2ቆሮ5፥14
3፥4 1ቆሮ1፥7፤ ገላ2፥20፤1ጴጥ1፥13፤ 1ዮሐ3፥2
3፥5 ሮሜ6፥2፤ 1ቆሮ6፥18፤ገላ5፥19፡ 21፡24፤ኤፌ4፥22፤5፥3፡5
3፥6 ሮሜ1፥18
3፥7 ኤፌ2፥2
3፥8 ኤፌ4፥22፡ 29፡31
3፥9 ሮሜ6፥6፤ ኤፌ4፥25

[ሽ]13 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *አደረገን* ይላሉ።
[ቀ]15 ወይም *በእርሱ*
[በ]4 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *የኛ ሕይወት*
[ተ]6 *በማይታዘዙት ላይ* የሚለው ሐረግ በአንዳንድ የጥንት ቅጆች ላይ ብቻ የሚገኝ ነው

እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ። 10የፈጣ
ሪውን መልክ እንዲመስል በዕውቀት የሚ
ታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችኋል፤ 11በዚያ
ግሪክ ወይም ይሁዲ፣ የተገረዘ ወይም ያል
ተገረዘ፣ አረማዊ ወይም እስኩቴስ፣ ባሪያ
ወይም ጌታ ብሎ ልዩነት የለም፤ ነገር ግን
ክርስቶስ ሁሉም ነው፤ በሁሉም ነው።
12እንግዲህ የተቀደሳችሁና የተወደዳችሁ
የእግዚአብሔር ምርጦች እንደ መሆናችሁ
ርኅራኄን፣ ቸርነትን፣ ትሕትናን፣
ጨዋነት ንና ትዕግሥትን ልበሱ፤ 13እርስ
በርሳችሁ ተቻቻሉ፤ ከእናንተ አንዱ በሌላው
ላይ ቅር የተሰኘበት ነገር ቢኖር ይቅር
ተባባሉ፤ ጌታ ይቅር እንዳላችሁ እናንተም
ሌላውን ይቅር በሉ። 14በእነዚህ ሁሉ ላይ
ሁሉን በፍጹም አንድነት የሚያስተሳስረውን
ፍቅርን ልበ ሱት።
15እንደ አንድ አካል ሆናችሁ የተጠራ
ችሁበት የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይንገሥ፤
የምታመሰግኑም ሁኑ። 16የክርስቶስ ቃል በሙ
ላት ይኑርባችሁ፤ እርስ በርሳችሁ በጥበብ ሁሉ
ተማማሩ፤ ተመካከሩ፤ በመዝሙርና በማሕሌት፣
በመንፈሳዊም ቅኔ በማመስገን በልባችሁ
ለእግዚአብሔር ዘምሩ። 17በእርሱ በኩል
ለእግዚአብሔር አብ ምስጋና እያቀረባችሁ፣
በቃልም ሆነ በተግባር የምታደርጉትን ሁሉ
በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት።

## የክርስቲያናዊ ቤተ ሰብ መመሪያ

18ሚስቶች ሆይ፤ በጌታ ዘንድ ተገቢ በመ
ሆኑ ለባሎቻችሁ ታዘዙ።
19ባሎች ሆይ፤ ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤
መራራም አትሁኑባቸው።
20ልጆች ሆይ፤ ይህ ጌታን ደስ የሚያ
ሰኝ በመሆኑ ለወላጆቻችሁ በሁሉም ነገር
ታዘዙ፤
21አባቶች ሆይ፤ ተስፋ እንዳይሐርጡ ልጆ
ቻችሁን አታስመርሯቸው።
22ባሮች ሆይ፤ ሰውን ለማስደሰትና
ለታይታ ብላችሁ ሳይሆን በቅን ልብ ጌታን
በመፍራት ለምድራዊ ጌቶቻችሁ በሁሉ ነገር
ታዘዙ። 23የምታደርጉትን ሁሉ ለሰው ሳይ
ሆን ለጌታ እንደምታደርጉት ሐጥራችሁ
በሙሉ ልባችሁ አድርጉት፤ 24ከጌታ
ዘንድ እንደ ብድራት የምትቀበሉት ርስት
እንዳለ ታውቃላችሁና፤ የምታገለግሉት ጌታ
ክርስቶስን ነው። 25በደለኛውም የእጁን ያገ
ኛል፤ አድልዎም የለም።

4 ጌቶች ሆይ፤ እናንተም በሰማይ ጌታ
እንዳላችሁ ስለምታውቁ አገልጋዮቻች
ሁን በፍትሕና በቅንነት አስተዳድሯቸው።

3፥10 ሮሜ6፥4፤
12፥2፤13፥14፤
2ቆሮ4፥16፤
ኤፌ2፥10፤4፥23
3፥11 ሮሜ10፥12፤
1ቆሮ7፥19፤12፥13፤
ገላ3፥28፤ኤፌ1፥23
3፥12 ቆላ10፤
2ቆሮ6፥6፤ገላ5፥22፡
23፤ኤፌ4፥2፤
ፊል2፥3
3፥13 ኤፌ4፥2፡32
3፥14 ሮሜ15፥5፤
1ቆሮ13፥1፡13
3፥15 ዮሐ14፥27፤
ሮሜ12፥5፤14፥19
3፥16 መዝ47፥7፤
ሮሜ10፥17፤
ኤፌ5፥19፤ቆላ1፥28
3፥17 1ቆሮ10፥31፤
ኤፌ5፥20
3፥18 ኤፌ5፥22
3፥24 ማቴ16፥27፤
ሐሥ 20፥32
3፥25 ሐሥ10፥34
4፥1 ዘሌ25፥43፡53

4፥2 ሉቃ18፥1
4፥3 ሐሥ14፥27፤
21፥33፤ሮሜ16፥25
4፥5 ማር4፥11፤
ኤፌ5፡15፡16
4፥6 ማር9፥50፤
ኤፌ4፥29፤1ጴጥ3፥15
4፥7 ሐሥ20፥4፤
ኤፌ6፥21፡22፤ቆላ1፥7
4፥8 ኤፌ6፥21፡
22፤ቆላ2፥2
4፥9 ቆላ12፤ፊሞ10
4፥10 ሐሥ4፥36፤
12፥12፤19፥29
4፥11 ፊል2፥25
4፥12 ቆላ9፤
ሮሜ15፥30፤
1ቆሮ2፥6፤ቆላ1፥7፤
ፊሞ23
4፥13 ቆላ2፥1
4፥14 2ጢሞ4፥10፡
11፤ፊሞ24
4፥15 ሮሜ16፥5፤
ቆላ2፥1
4፥16 1ተሰ3፥14፤
1ጢሞ4፥13

## ሌሎች ምክሮች

2ከማመስገን ጋር ነቅታችሁ በትጋት
ጸልዩ። 3እኔ እስረኛ የሆንሁለትን የክር
ስቶስን ምስጢር ማወጅ እንድንችል፣ እግዚ
አብሔር የቃሉን በር እንዲከፍትልን ስለ
እኛ ደግሞ ጸልዩ፤ 4ደግሞም መናገር
እንደሚገባኝ ቃሉን በግልጽ እንድናገር ጸል
ዩልኝ። 5በውጭ ካሉት ሰዎች ጋር ባላችሁ
ግንኙነት በጥበብ ተመላለሱ፤ በተገኘውም
ዕድል ሁሉ ተጠቀሙ። 6ለእያንዳንዱ ሰው
እንዴት መልስ መስጠት እንደሚገባችሁ
ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ በጨው እንደ
ተቀመመ ሁልጊዜ በጸጋ የተሞላ ይሁን።

## የስንብት ሰላምታ

7ቲኪቆስ ስላለሁበት ሁኔታ በሙሉ ይነግ
ራችኋል፤ እርሱ የተወደደ ወንድምና ታማኝ
አገልጋይ፣ በጌታም አብሮኝ ሎሌ ነው። 8ስላ
ለንበት[ቸ] ሁኔታ እንድታውቁና ልባችሁ
ንም እንዲያጽናና ለዚህ ጒዳይ ወደ እናንተ
እልከዋለሁ፤ 9እርሱም ከእናንተ ወገን ከሆነው
ከታማኙና ከተወዳጁ ወንድማችን ከአናሲ
ሞስ
ጋር ወደ እናንተ ይመጣል፤ እነርሱም እዚህ
ስላለው ሁኔታ ሁሉ ይነግሯችኋል።
10አብሮኝ የታሰረው አርስጥሮኮስና የበር
ናባስ የአክስቱ ልጅ ማርቆስ ሰላምታ ያቀ
ርቡላችኋል፤ ስለ ማርቆስ መመሪያ ደርሶ
አችኋል፤ እንግዲህ ወደ እናንተ ሲመጣ
ተቀበሉት። 11ኢዮስጦስ የተባለው ኢያሱም
ሰላምታ ያቀርብላችኋል። ከተገረዙት መካ
ከል ለእግዚአብሔር መንግሥት አብረውኝ
የሚሠሩት እኔንም ያጽናኑኝ እነዚህ ብቻ
ናቸው፤ እነርሱም አጽናንተውናል። 12ከእናንተ
ወገን የሆነው የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋይ
ኤጳፍራ ሰላምታ ያቀርብላችኋል፤ እርሱም
ፍጹም ጠንክራችሁና ሙሉ በሙሉ ተረጋ
ግታችሁ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉ ጸንታ
ችሁ እንድትቆሙ ዘወትር ስለ እናንተ በ
ጸሎት እየተጋደለ ነው። 13ደግሞም ስለ
እናንተ እንዲሁም በሎዶቅያና በኢያራ
ከተሞች ስላሉት ተግቶ እንደሚሠራ እኔ
እመሰክርለታለሁ። 14የተወደደው ሐኪሙ
ሉቃስ እንዲሁም ዴማስ ሰላምታ ያቀርቡላች
ኋል። 15በሎዶቅያ ላሉት ወንድሞች፣ ለን
ምፉን፣ በቤቷም ላለች ቤተ ክርስቲያን
ሰላምታ አቅርቡልኝ።
16ይህች መልእክት ከተነበበችላችሁ
በኋላ በሎዶቅያ ላለችው ቤተ ክርስቲያን
ደግሞ እንድትነበብ አድርጉ፤ እናንተም
ደግሞ በሎዶቅያ ያለችውን መልእክት አን
ብቡ።

[ቸ]8 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *ስለእናንተ…ያውቅ ዘንድ*

17 ለአክሪጳም፣ “በጌታ የተቀበልኸውን አገልግሎት ከፍጻሜ ለማድረስ ተጠንቀቅ” በሉልኝ።

4፥17 2ጢሞ4፥5፤ ፊሞ2
4፥18 ሐሥ21፥33፤ 1ቆሮ16፥21፤ 1ጢሞ6፥21፤ ዕብ13፥3

18 ይህን ሰላምታ በገዛ እጄ የጻፍሁት እኔ ጳውሎስ ነኝ። እስራቴን አስቡ። ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት
# ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች - አንደኛ

1 ከጳውሎስ፣ ከሲላስና[ሀ] ከጢሞቴዎስ፤
የእግዚአብሔር አብና የጌታ የኢየሱስ
ክርስቶስ ለሆኑት ለተሰሎንቄ ሰዎች ቤተ
ክርስቲያን፤
ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢ
የሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ
ይሁን[ለ]።

## ስለ ተሰሎንቄ ሰዎች እምነት የቀረበ ምስጋና

2በጸሎታችን እያስታወስናችሁ ሁልጊዜ
እግዚአብሔርን ስለ ሁላችሁ እናመሰግናለን።
3ከእምነት የሆነውን ሥራችሁን፣ ከፍቅር
የመነጨውን ድካማችሁንና በጌታችን በኢ
የሱስ ክርስቶስ ባላችሁ ተስፋ የተገኘውን
ጽናታችሁን በአምላካችንና በአባታችን ፊት
ዘወትር እናስባለን።
4በእግዚአብሔር የተወደዳችሁ ወንድሞች
ሆይ፤ እርሱ እንደ መረጣችሁ እናውቃለን፤
5ምክንያቱም ወንጌላችን ወደ እናንተ
የመጣው በኀይልና በመንፈስ ቅዱስ
በብዙም መረዳት እንጂ በቃል ብቻ
አይደለም። ደግሞ ስለ እናንተ ስንል
በመካከላችሁ እንዴት እንደኖርን
ታውቃላችሁ። 6እናንተ እኛንና ጌታን
መስላችኋል፤ ምንም እንኳ ብርቱ መከራ
ቢደርስባችሁም ቃሉን በመንፈስ ቅዱስ
ደስታ ተቀብላችኋል። 7ከዚህም የተነሣ
በመቄዶንያና በአካይያ ለሚገኙ
ምእመናን መልካም ምሳሌ ሆናችኋል።
8የጌታ ቃል ከእናንተ ወጥቶ በመቄዶንያና
በአካይያ መሰማቱ ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር
ያላችሁ እምነት በሁሉ ቦታ ታውቆአል፤
ስለዚህ እኛ በዚህ ጕዳይ ላይ ምንም
መናገር አያስፈልገንም፤ 9በእንዴት ያለ
አቀባበል እንደ ተቀበላችሁንና ሕያውና
እውነተኛ የሆነውን አምላክ ለማገልገል
ከጣ ዖታት ወደ እግዚአብሔር እንዴት እንደ
ተመለ ሳችሁ እነርሱ ራሳቸው ይናገራሉ፤
10ደግሞም ከሙታን ያስነሣውንና ከሰማይ
የሚመጣውን ልጁን፣ ከሚመጣውም ቍጣ
የሚያድነንን ኢየሱስን እንዴት
እንደምትጠባበቁ ይናገራሉ።

## የጳውሎስ አገልግሎት በተሰሎንቄ

2 ወንድሞች ሆይ፤ ወደ እናንተ የመጣ
ነው ለከንቱ እንዳልሆነ እናንተ ራሳችሁ
ታውቃላችሁ። 2እንደምታውቁት ከዚህ
ቀደም በፊልጵስዩስ መከራ ተቀብለን
ተንገላታን፤ ነገር ግን ብርቱ ተቃውሞ

1፥1 ሐሥ15፥22፤ 16፥1፤17፥1፤ ሮሜ1፥7፤2ተሰ1፥1
1፥2 ሮሜ1፥8፡10፤ ኤፌ5፥20
1፥3 ሮሜ8፥25፤ 1ቆሮ13፥13፤ገላ5፥6፤ ፊል4፥20፤1ተሰ3፥6፤2 ተሰ1፥3፡11፤ያዕ2፥14-26
1፥4 ቈላ3፥12፤ 2ተሰ2፥13
1፥5 ሮሜ1፥16፤ 15፥13፤2ቆሮ2፥12፤ 1ተሰ2፥10፤ 2ተሰ2፥14
1፥6 ሐሥ13፥52፤ 17፥5-10፤ 1ቆሮ 4፥16፤ 2ቆሮ6፥10
1፥7 ሐሥ16፥9፤ 18፥12፤1ጢሞ4፥12
1፥8 ሮሜ1፥8፤ 2ተሰ3፥1
1፥9 ማቴ16፥16፤ ሐሥ14፥15፤ 1ቆሮ12፥2፤ገላ4፥8
1፥10 ሐሥ2፥24፤ ሮሜ1፥18፤1ቆሮ1፥7

2፥1 1ተሰ1፥5፡9፤ 2ተሰ1፥10
2፥2 ሐሥ14፥19፤ 16፥12፡22፤17፥1-9፤ፊል1፥30
2፥3 2ቆሮ2፥17፤ 4፥2
2፥4 ሮሜ፥29፤ ገላ2፥7፤1ጢሞ1፥11፤ ራእ2፥23
2፥5 ቍ10፤ ሐሥ20፥33፤ ሮሜ1፥9
2፥6 ዮሐ5፥41፡44፤ 1ቆሮ9፥1፡2፤ 2ቆሮ11፥7-11
2፥7 ቍ11
2፥8 ሮሜ1፥1፤ 2ቆሮ12፥15፤ 1ዮሐ3፥16
2፥9 ሐሥ18፥3፤ 2ቆሮ11፥9፤2ተሰ3፥8
2፥10 ቍ5፤ ሮሜ1፥9፤2ቆሮ1፥12፤ 1ተሰ1፥5
2፥11 ቍ7፤1ቆሮ 4፥14፤ ገላ4፥19፤ 1ጢሞ1፥2፤ፊሞ10፤ 1ዮሐ2፥1
2፥12 ሮሜ8፥28፤ ኤፌ4፥1
2፥13 ሮሜ1፥8፤ 1ተሰ1፥2፤ዕብ4፥12
2፥14 ሐሥ17፥5፤ ገላ1፥22፤1ተሰ1፥6፤2 ተሰ1፥4

ቢደርስብንም እንኳ የእግዚአብሔርን ወንጌል
ለእናንተ እንደምናበሥር በአምላካችን ድፍረት
አገኘን። 3የምናቀርበው ልመና ከስሕተት
ወይም ከክፉ ዐላማ ወይም እናንተን
ለማታለል ከመፈለግ የመነጨ አይደለም።
4ነገር ግን ወንጌልን በዐደራ ለመቀበል
እግዚአብሔር ብቁ አድርጎ እንደ ቈጠራቸው
ሰዎች ሆነን እንናገራለን። ይህንም የም
ናደርገው ልባችንን የሚመረምረውን እግዚ
አብሔርን እንጂ ሰዎችን ደስ ለማሰኘት
ብለን አይደለም። 5የሽንገላ ቃል ከቶ
እንዳልተናገርን ወይም ሥሥትን ለመሸፈን
ብለን አስመሳዮች እንዳልሆንን ታው
ቃላችሁ፤ ለዚህም እግዚአብሔር ምስክራችን
ነው። 6ከእናንተም ሆነ ከሌሎች ከማንም፣
ከሰው የሚገኝ ክብር አልፈለግንም። የክ
ርስቶስ ሐዋርያት እንደ መሆናችን መጠን
ሸክም በሆንባችሁ ነበር፤ 7ነገር ግን እናት
ልጅዋን እንደምትንከባከብ እኛም በመካከ
ላችሁ በየዋህነት ተመላለስን።
8የእግዚአብሔርን ወንጌል ብቻ ሳይሆን ሕይ
ወታችንን ጭምር ልናካፍላችሁ ደስ እስከ
ሚለን ድረስ ወደድናችሁ፤ ምክንያቱም
እናንተ በእኛ ዘንድ ተወዳጆች ነበራችሁ።
9ወንድሞች ሆይ፤ ጥረታችንንና ድካማ
ችንን ታስታውሳላችሁ፤ በማንም ላይ ሸክም
እንዳንሆን ሌሊትና ቀን እየሠራን ወንጌል
ሰበክንላችሁ።
10በእናንተ በምታምኑት መካከል ሳለን
እንዴት በቅድስና፣ በጽድቅ እንዲሁም ያለነ
ቀፋ ሆነን እንደኖርን እናንተም እግዚአብሔርም
ምስክሮች ናችሁ። 11አባት ለገዛ ልጆቹ
እንደሚሆን እኛም ለእያንዳንዳችሁ የቱን
ያህል እንደ ሆንን ታውቃላችሁና፤ 12ወደ
መንግሥቱና ወደ ክብሩ ለጠራችሁ ለእግዚ
አብሔር እንደሚገባ ትኖሩ ዘንድ አበረታ
ታናችሁ፤ አጽናናችሁ፤ አጥብቀንም
ለመንናችሁ።
13ከእኛ የሰማችሁትን የእግዚአብሔርን
ቃል በተቀበላችሁ ጊዜ፣ በእናንተ በምታ
ምኑት ዘንድ በእርግጥ እንደሚሠራ እንደ
እግዚአብሔር ቃል እንጂ እንደ ሰው ቃል
አድርጋችሁ ስላልተቀበላችሁት እግዚአብሔርን
ያለማቋረጥ እናመሰግናለን። 14ወንድሞች
ሆይ፤ በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉትን በይሁዳ
የሚገኙትን የእግዚአብሔርን

[ሀ]1 ግሪኩ *ሰሉያኖስ* ይላል
[ለ]1አንዳንድ ቅጆች *ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ* የሚለው የላቸውም

አብያተ ክርስቲያናት መስላችኋል፤ እነዚያ
ከአይሁድ መከራ እንደ ተቀበሉ፣ እናንተም
ከገዛ ወገኖቻችሁ መከራን ተቀብላችኋል።
[15]እነርሱ ጌታ ኢየሱስንና ነቢያትን ገደሉ፤
እኛንም አሳደዱን፤ እግዚአብሔርንም ደስ
አላሰኙትም፤ የሰውም ሁሉ ፀር ሆኑ፤
[16]ይኸውም ይድኑ ዘንድ ለአሕዛብ እን
ዳንናገር ለመከልከል ነው፤ በዚህ ሁኔታ
ኀጢአታቸውን ሁልጊዜ በራሳቸው ላይ እስከ
መጨረሻው እያከማቹ ይሄዳሉ። ቍጣውም
በእነርሱ ላይ ያለልክ መጥቶአል[ሐ]።

## ጳውሎስ የተሰሎንቄን ሰዎች ለማየት የነበረው ናፍቆት

[17]ነገር ግን ወንድሞች ሆይ፤ እኛ በልባችን
ሳይሆን በአካል ለጥቂት ጊዜ ከእናንተ
ብንለይም፣ ለእናንተ ካለን ታላቅ ናፍቆት
የተነሣ ፊታችሁን ለማየት ብርቱ ጥረት
አደረግን። [18]ወደ እናንተ ለመምጣት
ፈልገን ነበር፤ በተለይም እኔ ጳውሎስ
ብዙ ጊዜ ሞክሬ ነበር፤ ነገር ግን ሰይጣን
አዘገየኝ።
[19]ጌታችን ኢየሱስ ሲመጣ በእርሱ ፊት
ተስፋችን ወይም ደስታችን ወይም አክሊ
ላችን ማን ነው? እናንተ አይደላችሁምን?
[20]በእርግጥ ክብራችንም ደስታችንም
ናችሁ።

3 ስለዚህ መታገሥ ስላልቻልን በጊዜ
በአቴና ብቻችንን መቅረት መልካም
መስሎ ታየን። [2]በእምነታችሁ እንዲያጸና
ችሁና እንዲያበረታችሁ ወንድማችንንና
በክርስቶስ ወንጌል ሥራ ከእኛ ጋር የእግዚ
አብሔር አገልጋይ[መ] የሆነውን ጢሞቴዎስን
ልከንላችኋል፤ [3]ይኸውም በዚህ ፈተና
ማንም እንዳይናወጥ ነው። እኛም ለዚህ
ነገር እንደተመደብን እናንተ ራሳችሁ ታው
ቃላችሁ። [4]በእርግጥ ከእናንተ ጋር በነበርንበት
ጊዜ መከራ እንደሚደርስብን በየጊዜው
እንነግራችሁ ነበር፤ እንደምታውቁትም እን
ዲሁ ደግሞ ሆኖአል። [5]ስለዚህ ምንም
መታገሥ ባልቻልሁ ጊዜ ስለ እምነታችሁ
ለማወቅ ላክሁ፤ ይህንንም ያደረግሁት ምናል
ባት ፈታኙ ፈትኖአችሁ ድካማችን ሁሉ
ከንቱ ሆኖአል ብዬ ስለ ፈራሁ ነው።

## ጢሞቴዎስ ይዞት የመጣው የምሥራች

[6]አሁን ግን ጢሞቴዎስ ከእናንተ ዘንድ
ወደ እኛ መጥቶ ስለ እምነታችሁና ስለ ፍቅ
ራችሁ መልካም ዜና አሰምቶናል። ደግ
ሞም እኛን ሁልጊዜ በመልካም እንደም
ታስታውሱንና እኛ እናንተን ለማየት የም
ንናፍቃችሁን ያህል እናንተም እኛን
ለማየት እንደምትናፍቁ ነግሮናል። [7]ስለዚህ
ወንድሞች ሆይ፤ በጭንቀታችንና በመከራ
ችን ሁሉ በእምነታችሁ ምክንያት በእናንተ
ተጽናናን። [8]በጌታ ጸንታችሁ ስለ ቆማችሁ
በእርግጥ አሁን በሕይወት እንኖራለን። [9]በእ
ናንተ ምክንያት በአምላካችን ፊት ስላገ
ኘነው ደስታ ሁሉ ለእግዚአብሔር ምን ያህል
ምስጋና ልናቀርብ እንችላለን? [10]እንደ ገና
ልናያችሁና በእምነታችሁ የጐደለውን ለ
ማ ሟላት ሌሊትና ቀን እጅግ ተግተን
እንጸልያለን።

[11]አሁንም ራሱ አምላካችንና አባታችን፣
ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ
እናንተ እንድንመጣ መንገዳችንን
ያቅናልን። [12]እኛ ለእናንተ ፍቅር እንዳለን
ሁሉ እርስ በርስ ያላችሁን ፍቅርና
ለሌሎችም ያላችሁን ፍቅር ጌታ ያብዛላችሁ፤
ያትረፍርፍላችሁም። [13]ጌታችን ኢየሱስ
ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር በሚመጣበት
ጊዜ በአምላካችንና በአባ ታችን ፊት ነቀፋ
የሌለባችሁና ቅዱሳን ሆናችሁ እንድትገኙ
ልባችሁን ያጽና።

## እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ አኗኗር

4 በቀረውስ ወንድሞች ሆይ፤ እግዚአብሔርን
ደስ ለማሰኘት እንዴት መኖር እንደ
ሚገባችሁ አስተምረናችኋል፤ በእርግጥም
እንደዚያው እየኖራችሁ ነው። ስለ ሆነም
በጌታ በኢየሱስ የምንለምናችሁና የምንመ
ክራችሁ ከዚህ በበለጠ ሁኔታ በዚሁ
እንድትገፉበት ነው። [2]በጌታ በኢየሱስ
ሥልጣን ምን ዐይነት ትእዛዝ እንደ ሰጠ
ናችሁ ታውቃላችሁ።

[3]የእግዚአብሔር ፈቃድ ከዝሙት ርቃችሁ
እንድትቀደሱ ነው፤ [4]ደግሞም እያንዳንዱ
የገዛ ሰውነቱን በቅድስናና በክብር መያዝ[ሠ]
እንዳለበት እንዲያውቅ ነው፤ [5]ይህም እግዚ
አብሔርን እንደማያውቁ አሕዛብ በፍትወተ
ሥጋ ምኞት አይሁን። [6]በዚህም ነገር ማንም
ተላልፎ ወንድሙን አያታል፤ ምክንያቱም
ከዚህ በፊት እንደነገርናችሁና እንዳስጠ
ነቀቅናችሁ ጌታ እንደ እነዚህ ያለውን
ኀጢአት ሁሉ የሚፈጽሙትን ይበቀላል፤
[7]እግዚአብሔር በቅድስና እንድንመላለስ እንጂ
ለርኵሰት አልጠራንምና። [8]እንግዲህ ይህን
ምክር ንቆ የማይቀበል፣ የናቀው ቅዱስ
መንፈሱን የሰጣችሁን እግዚአብሔርን እንጂ
ሰውን አይደለም።

[9]ስለ ወንድማማች መዋደድ ማንም
እንዲጽፍላችሁ አያስፈልግም፤ ምክንያቱም
እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ እናንተ
ራሳችሁ ከእግዚአብሔር ተምራችኋልና።

2፥15 ማቴ5፥12፤ ሉቃ24፥20፤ ሐሥ2፥23
2፥16 ማቴ23፥32፤ ሐሥ13፥45፡50፤ 17፥5፤20፥3፤ 21፥27፤24፥9
2፥17 1ቆሮ5፥3፤ ቈላ2፥5፤1ተሰ3፥10
2፥18 ማቴ4፥10፤ ሮሜ1፥13፤15፥22
2፥19 ኢሳ62፥3፤ ማቴ16፥27፤ሉቃ17፥30፤1ቆሮ1፥7፤4፥5፤2ቆሮ1፥14፤ፊል4፥1፤ 1ተሰ3፥13፤2ተሰ1፥8-10፤1ጴጥ1፥7፤ 1ዮሐ2፥28፤ራእ1፥7
2፥20 2ቆሮ1፥14
3፥1 ቍ5፤ ሐሥ17፥15
3፥2 ሐሥ16፥1፤ 1ቆሮ3፥9፤2ቆሮ2፥12
3፥3 ማር4፥17፤ ዮሐ16፥33፤ሐሥ9፥16፤ 14፥22፤ሮሜ 5፥3፤2ቆሮ1፥4፤ 4፥17፤ 2ጢሞ3፥12
3፥4 1ተሰ2፥14
3፥5 ቍ1፡2፤ ማቴ4፥3፤ገላ2፥2፤ ፊል2፥16
3፥6 ሐሥ16፥1፤ 18፥5፤1ተሰ1፥3፤2፥17፡18
3፥8 1ቆሮ16፥13
3፥9 1ተሰ1፥2፤ 2፥19፡20
3፥10 1ተሰ2፥17፤ 2ጢሞ1፥3
3፥11 ቍ13፤ ፊል4፥20
3፥12 ፊል1፥9፤ 1ተ ሰ4፥9፡10፤ 2ተሰ1፥3
3፥13 ቍ11፤ መዝ15፥2፤ማቴ25፥31፤ 1ቆሮ1፥8፤ ፊል2፥15፤4፥20፤ 1ተሰ2፥19፤5፥23፤ 2ተሰ1፥7፤1ጢሞ6፥14፤ 2ጴጥ3፥14
4፥1 2ቆሮ5፥9፤ 13፥11፤ኤፌ4፥1፤ 2ተሰ3፥1
4፥3 1ቆሮ6፥18፤ ኤፌ5፥17
4፥4 1ቆሮ7፥2፡9
4፥5 ሮሜ1፥26፤ ገላ4፥8፤ኤፌ4፥17
4፥6 ዘሌ25፥17፤ ዘዳ32፥35፤መዝ94፥1፤ ሮሜ2፥5-11፤12፥19፤ 1ቆሮ6፥8፤ዕብ10፥30፡31፤13፥4
4፥7 ዘሌ11፥44፤ 1ጴጥ1፥15
4፥8 ሕዝ36፥27፤ ሮሜ5፥5፤2ቆሮ1፥22፤ ገላ4፥6፤1ዮሐ3፥24

[ሐ]16 ወይም *በሙላት መጥቶአል*
[መ]2 አንዳንድ ቅጆች *ወንድማችንንና...ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ የሚሠራ* ሲሉ ሌሎች ደግሞ *ወንድማችንንና...የእግዚ አብሔር አገልጋይ* ይላሉ።
[ሠ]4 ወይም *ከገዛ ሚስቱ ጋር መኖርን መማር* ወይም *ሚስት ለማግኘት መማር*

10በመላዪቱ መቄዶንያ የሚገኙትን ወን
ድሞች ሁሉ እንደምትወዷቸው የታወቀ
ነው፤ ነገር ግን ወንድሞች ሆይ፤ ከዚህ
በበለጠ እንድትገፉበት እንመክራችኋለን።
11ከዚህ በፊት እንዳዘዝናችሁ በገዛ እጃችሁ
ሥሩ፤ በጸጥታ ኑሩ፤ በራሳችሁ ጉዳይ ላይ
ብቻ አተኵሩ። 12ይ፥ውም በዕለት ተለት
ኑሮአችሁ በውጭ ባሉት ዘንድ እንዲያስ
ከብራችሁና በማንም ሰው ላይ ሸክም እን
ዳትሆኑ ነው።

## የጌታ ዳግም ምጽአት

13ወንድሞች ሆይ፤ አንቀላፍተው ስላሉ
ሰዎች ሳታውቁ እንድትቀሩ አንፈልግም፤ ደግ
ሞም ተስፋ እንደ ሌላቸው እንደ ሌሎች
ሰዎች እንድታዝኑ አንሻም። 14ኢየሱስ እንደ
ሞተና እንደ ተነሣ ካመንን፣ በኢየሱስ ሆነው
ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር
እንደዚሁ ያመጣቸዋል። 15በጌታ ቃል
የምንላችሁ ይህን ነው፤ እኛ በሕይወት
ያለንና ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር
ያንቀላፉትን አንቀድምም፤ 16ጌታ ራሱ
በታላቅ ትእዛዝ፣ በመላእክት አለቃ
ድምፅና በእግዚአብሔር የመለከት ድምፅ
ከሰማይ ይወርዳልና። በክርስቶስ የሞቱትም
አስቀድመው ይነሣሉ። 17ከዚያም በኋላ እኛ
የቀረነው፣ በሕይወትም የምንኖረው ጌታን
በአየር ላይ ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደ
መና እንነጠቃለን፤ በዚህም መሠረት
ለዘላለም ከጌታ ጋር እንሆናለን። 18ስለዚህ
በዚህ ቃል እርስ በርሳችሁ ተጽናኑ።

5 ወንድሞች ሆይ፤ ስለ ዘመናትና ስለ
ወራት ልንጽፍላችሁ አያስፈልግም።
2ምክንያቱም ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ
የጌታም ቀን እንዲሁ እንደሚመጣ እናንተ
ራሳችሁ በሚገባ ታውቃላችሁ። 3ሰዎች፣
"ሰላምና ደኅንነት ነው' ሲሉ፣ ምጥ እርጉዝ
ሴትን እንደሚይዛት እንዲሁ ጥፋት በድን
ገት ይመጣባቸዋል፤ ከቶም አያመልጠ
ም።
4እናንተ ግን፣ ወንድሞች ሆይ፤ ይህ
ቀን እንደ ሌባ ያስደነግጣችሁ ዘንድ በጨ
ለማ ውስጥ አይደላችሁም፤ 5ሁላችሁም የብር
ሃን ልጆች፣ የቀንም ልጆች ናችሁና። እኛ
ከሌሊት ወይም ከጨለማ ወገን አይደለንም፤
6እንግዲህ እንንቃ፤ ራሳችንንም እንግዛ
እንጂ እንደሚያንቀላፉት እንደ ሌሎቹ
አንሁን። 7የሚያንቀላፉ በሌሊት ያነቀ
ላፉሉ፤ የሚሰክሩም በሌሊት ይሰክራሉና።
8እኛ ግን የቀን ሰዎች ስለ ሆንን፣
እምነትንና ፍቅርን እንደ ጥሩር ለብሰን፣
የመዳንን ተስፋ እንደ ራስ ቍር ደፍተን
ራሳችንን በመግዛት እንኑር፤ 9እግዚአብሔር
ድነትን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማ
ካይነት እንድናገኝ ነው እንጂ ለቍጣ ወስኖ
አላስቀመጠንምና። 10ብንነቃም ሆነ ብናንቀላፋ
ከእርሱ ጋር በሕይወት እንድንኖር እርሱ
ስለ እኛ ሞተ። 11ስለዚህ በእርግጥ አሁን
እንደምታደርጉት ሁሉ እርስ በርሳችሁ
ተጽናኑ፤ አንዱም ሌላውን ያንጽ።

## የመጨረሻ ምክር

12እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ በእናንተ
መካከል በትጋት የሚሠሩትን፣ በጌታም
የበላዮቻችሁና መካሪዎቻችሁ የሆኑትን
እንድታከብሯቸው እንለምናችኋለን፤ 13ስለ
ሥራቸውም በፍቅር እጅግ አክብሯቸው።
እርስ በርሳችሁም በሰላም ኑሩ። 14ወን
ድሞች ሆይ፤ ይህን እንመክራችኋለን፤ ሥራ
ፈቶችን ገሥጿቸው፤ ፈሪዎችን አደ ፋፍሯ
ቸው፤ ደካሞችን እርዷቸው፤ ሰውን ሁሉ
ታገሡ። 15ማንም በክፉ ፈንታ ክፉ
እንዳይመልስ ተጠንቀቁ፤ ነገር ግን እርስ
በርሳችሁም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ሁልጊዜ
መልካም የሆነውን ነገር ለማድረግ ተጣጣሩ።
16ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ 17ሳታ
ቋርጡ ጸልዩ፤ 18በማናቸውም ሁኔታ
አመስግኑ፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ
ኢየሱስ ለእናንተ ይህ ነውና።
19የመንፈስን እሳት አታዳፍኑ፤ 20ትንቢ
ትን አትናቁ። 21ሁሉን ነገር ፈትኑ፤ መልካም
የሆነውን ያዙ፤ 22ከማናቸውም ዐይነት ክፉ
ነገር ራቁ።
23የሰላም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን
ይቀድስ፤ መንፈሳችሁ፣ ነፍሳችሁና ሥጋችሁ
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ
ያለነቀፋ ይጠበቁ። 24የጠራችሁ የታመነ ነው፤
እርሱም ያደርገዋል።
25ወንድሞች ሆይ፤ ስለ እኛ ደግሞ[ሀ]
ጸልዩ። 26ወንድሞችን ሁሉ በተቀደሰ አሳሳም
ሰላም በሏቸው። 27ይህ መልእክት ለወን
ድሞች ሁሉ እንዲነበብ በጌታ ዐደራ እላ
ችኋለሁ።
28የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ
ከእናንተ ጋር ይሁን።

4፥9 ዮሐ6፥45፤ 13፥34፤ሮሜ 12፥10፤1ተሰ5፥1
4፥10 ሐሥ16፥9፤ 1ተሰ3፥12
4፥11 ኤፌ4፥28፤ 2ተሰ3፥10-12
4፥12 ማር4፥11
4፥13 ማቴ9፥24፤ ሮሜ11፥25፤ ኤፌ2፥12
4፥14 ሮሜ14፥9፤ 1ቆሮ15፥3፡4፤18፤ 2ቆሮ5፥15
4፥15 1ቆሮ1፥7፤ 15፥52
4፥16 ማቴ16፥27፤ 24፥31፤1ቆሮ15፥23፤2 ተሰ2፥1፤ይሁ9፤ ራእ14፥13
4፥17 ዮሐ12፥26፤ ሐሥ1፥9፤8፥39፤ 1ቆሮ15፥52፤ ራእ1፥7፤11፥12
4፥18 1ተሰ5፥11
5፥1 ሐሥ1፥7፤ 1ተሰ4፥9
5፥2 ሉቃ12፥39፤ 1ቆሮ1፥8
5፥3 ኢዮ15፥21፤ መዝ35፥8፤55፥15፤ ኢሳ29፥5፤47፥9፡11፤ ኤር4፥10፤6፥14፤ ሕዝ13፥10፤2ተሰ1፥9
5፥4 ቀኍ2፤ ሐሥ26፥18፤ 1ዮሐ2፥8
5፥5 ሉቃ16፥8
5፥6 ማቴ25፥13፤ ሐሥ24፥25፤ ሮሜ13፥11
5፥7 ሐሥ2፥15፤ ሮሜ13፥13፤ 2ጴጥ2፥13
5፥8 ቀኍ5፤ ኢሳ59፥17፤ሮሜ፥24፤ ኤፌ6፥14፡17
5፥9 1ተሰ1፥10፤ 2ተሰ2፥13፡14
5፥10ሮሜ 14፥9፤2ቆሮ5፥15
5፥11ኤፌ4፥29፤ 1ተሰ4፥18
5፥12ሮሜ16፥6፡12፤ 1ቆሮ15፥10፤ 1ጢሞ5፥17፤ ዕብ13፥17
5፥13ማር9፥50
5፥14 ሮሜ14፥1፤ 1ቆሮ8፥7-12፤ 2ተሰ3፥6፡7፡11
5፥15 ሮሜ12፥17፤ ኤፌ4፥32፤1ጴጥ3፥9
5፥16ፊል4፥4
5፥17 ሉቃ18፥1
5፥18 ኤፌ5፥20
5፥19ኤፌ4፥30
5፥20 1ቆሮ14፥1-40
5፥21 ሮሜ12፥9፤ 1ቆሮ14፥29፤ 1ዮሐ4፥1
5፥23 ሮሜ15፥33፤
5፥24 ዘኍ23፥19፤ዕብ13፥18 ሮሜ8፥28፤ 1ቆሮ1፥9፤ፊል1፥6
5፥25 ኤፌ6፥19፤ ቈላ4፥3፤2ተሰ3፥1፤
5፥26 ሮሜ16፥16
5፥27 2ተሰ3፥14፤1ጢሞ4፥13
5፥28 ሮሜ16፥20

ሀ25 አንዳንድ ትርጒሞች *ደግሞ* የሚለው ቃል የላቸውም

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች - ሁለተኛ

1 ጳውሎስ፣ ሲላስና[ሀ] ጢሞቴዎስ፤
በእግዚአብሔር በአባታችን በጌታም
በኢየሱስ ክርስቶስ ለሆኑት፣ ለተሰሎንቄ
ሰዎች ቤተ ክርስቲያን፤
2ከእግዚአብሔር አብ፣ ከጌታ ከኢየሱስ
ክርስ ቶስም ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።

## የምስጋናና የልመና ጸሎት

3ወንድሞች ሆይ፤ እምነታችሁ በየጊ
ዜው እያደገ በመሄዱና የእርስ በርስ ፍቅ
ራችሁም እየጨመረ በመምጣቱ ስለ
እናንተ እግዚአብሔርን ሁልጊዜ በሚገባ
ማመስገን አለብን። 4ስለዚህ በደረሰባችሁ
ስደትና መከራ ሁሉ በመጽናታችሁ፣ እኛ
ራሳችን ስለ ትዕግሥታችሁና ስለ እምነ
ታችሁ በእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት
ዘንድ እንመካለን።
5ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ፍርድ ቅን
መሆኑን የሚያመለክት ነው፤ ከዚህም
የተነሣ መከራን ለምትቀበሉለት ለእግዚ
አብሔር መንግሥት የበቃችሁ ሆናችሁ
ትቈጠራላችሁ። 6እግዚአብሔር ጻድቅ በመሆኑ
መከራን ለሚያመጡባችሁ መከራን ይከ
ፍላቸዋል፤ 7መከራን ለተቀበላችሁት ለእና
ንተም ሆነ ለእኛ ደግሞ ዕረፍት ይሰጠ
ናል። ይህም የሚሆነው ጌታ ኢየሱስ
በሚንበለበል እሳት ከኀያላን መላእክት
ጋር ከሰማይ በሚገለጥበት ጊዜ ነው። 8በዚ
ያ ጊዜ እግዚአብሔርን የማያውቁትንና ለጌታ
ችንም ለኢየሱስ ወንጌል የማይታዘዙትን
ይበቀላል። 9እነርሱም ከጌታ ፊትና
ከኀይሉ ክብር ተወግደው በዘላለም ጥፋት
ይቀጣሉ፤ 10የሚቀጡትም በቅዱሳኑ ዘንድ
ሊከብርና በሚያምኑበትም ሁሉ ዘንድ
ሊገረም በሚመጣበት በዚያን ቀን ይሆናል፤
እናንተም ከሚያምኑት መካከል ናችሁ፤
ምስክርነታችንን ተቀብላችኋልና።
11ይህን እያሰብን አምላካችን ለጥሪው
የበቃችሁ አድርጎ እንዲቈጥራችሁ፣ መል
ካም ለማድረግ ያላችሁን ምኞትና ከእምነት
የሆነውን ሥራችሁን ሁሉ በኀይሉ እንዲፈ
ጽምላችሁ ዘወትር ስለ እናንተ እን
ጸልያለን። 12ደግሞም እንደ አምላካችንና[ለ]
እንደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ መጠን
የጌታችን የኢየሱስ ስም በእናንተ ዘንድ
እንዲከብርና እናንተም በእርሱ እንድ
ትከብሩ ይህን እንጸልያለን።

1፥1 ሐሥ15፥22፤
16፥1፤17፥1፤
1ተሰ1፥1
1፥2ሮሜ1፥7
1፥3 ሮሜ1፥8፤
ኤፌ5፥20፤1ተሰ3፥12
1፥4 2ቆሮ7፥14፤
1ተሰ1፥3፡6፤2፥14፤
3፥3
1፥5 ሉቃ20፥35፤
ፊል1፥28
1፥6 ሉቃ18፥7፡8፤
ሮሜ12፥19፤
ቈላ3፥25፤ራእ6፥10
1፥7 ሉቃ17፥30፤
ዕብ10፥27፤12፥29፤
2ጴጥ3፥7፤ይሁ14፤
ራእ1፥14
1፥8 መዝ79፥6፤
ኢሳ66፥15፤
ኤር10፥25፤
ሮሜ2፥8፤2ቆሮ2፥12፤
ገላ4፥8
1፥9 2ነገ17፥18፤
ኢሳ2፥10፡19፤
ፊል3፥19፤1ተሰ5፥3፤2
ተሰ2፥8፤2ጴጥ3፥7
1፥10 ዮሐ17፥10፤
1ቆሮ1፥6፤3፥13
1፥11 ቍ5፤
ሮሜ1፥10፤8፥28፤
15፥14፤1ተሰ1፥3
1፥12 ኢሳ24፥15፤
ፊል2፥9-11
2፥1 ማር13፥27፤
1ተሰ2፥19፤4፥15-17
2፥2 ቍ15፤
1ቆሮ1፥8፤2ተሰ3፥17፤
2ጢሞ2፥18
2፥3 ቍ8፤ዳን7፥25፤
8፥25፤11፥36፤
ማቴ24፥10-12፤
ማር13፥5፤
ራእ13፥5፡6
2፥4 ኢሳ14፥13፡
14፤ሕዝ28፥2፤
1ቆሮ8፥5
2፥5 1ተሰ3፥4
2፥6 ቍ7
2፥7 ቍ6
2፥8 ቍ3፤ኢሳ11፥4 ፤
ሉቃ17፥30፤
ራእ2፥16፤19፥15
2፥9 ማቴ4፥10፤
24፥24፤ዮሐ4፥48፤
ራእ13፥13
2፥10 ምሳ4፥6፤
ዮሐ3፥17-
19፤1ቆሮ1፥18
2፥11 ሮሜ1፥25-28፤
ማቴ24፥5፤ማር13፥5
2፥12 ሮሜ1፥32፤ 2፥8
2፥13 ሮሜ1፥8፤
ኤፌ1፥4፤
1ተሰ5፥9፤1ጴጥ1፥2

## የዐመፅ ሰው

2 ወንድሞች ሆይ፤ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ
ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱም
ስለ መሰብሰባችን ይህን እንለምናችኋለን፤
2በመንፈስ መገለጥ ወይም በቃል ወይም
ከእኛ እንደ ተላከ መልእክት የጌታ ቀን
ደርሶአል ብላችሁ ፈጥናችሁ ከአእምሮ
አችሁ አትናወጡ፤ አትደንግጡም። 3ማንም
ሰው በምንም መንገድ አያታላችሁ፤ አስቀ
ድሞ ዐመፅ ሳይነሣ፣ ለጥፋት የተመደበውም
የዐመፅ[ሐ] ሰው ሳይገለጥ ያ ቀን አይመጣምና።
4እርሱም አምላክ ከተባለና ከሚመለከው
ነገር ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ
የሚያደርግ ተቃዋሚ ነው፤ እርሱም
በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ተቀምጦ፣
"እኔ አምላክ ነኝ" እያለ ዐዋጅ ያስነግራ
ል።
5ከእናንተ ጋር በነበርሁበት ጊዜ እነዚ
ህን ነገሮች ነግሬአችሁ እንደ ነበር ትዝ
አይላችሁምን? 6በራሱ ጊዜ ይገለጥ ዘንድ
አሁን ምን እንደሚከለክለው ታውቃ
ላችሁ። 7የዐመፅ ምስጢር አሁንም እንኳ
እየሠራ ነውና፤ ነገር ግን ይህ የሚሆነው
የሚከለክለው ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ
ብቻ ነው 8ከዚያም በኋላ ጌታ ኢየሱስ
በአፉ እስትንፋስ የሚያስወግደውና በም
ጽአቱም ክብር ፈጽሞ የሚያጠፋው ዐመፀኛ
ይገለጣል። 9የዐመፀኛው አመጣጥ በሰይ
ጣን አሠራር ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣
ይህም በሐሰተኛ ታምራት በምልክቶችና
በድንቅ ነገሮች ሁሉ ይሆናል፤ 10እንዲሁም
ይድኑ ዘንድ እውነትን ባለ መውደድ
የሚጠፉትን ሰዎች በሚያታልል በተለያየ
የክፋት ሥራ ይመጣል። 11በዚህም ምክንያት
እግዚአብሔር በሐሰት እንዲያምኑ የስሕተትን
አሠራር ይልክባቸዋል፤ 12ይህም የሚሆነው
እውነትን ያላመኑት ነገር ግን በክፋት
ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ እንዲፈረድ
ባቸው ነው።

## ጸንታችሁ ቁሙ

13በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፤
እኛ ግን ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን
ልናመሰግን ይገባናል። ምክንያቱም እግዚአብሔር
እናንተን ከመጀመሪያ አንሥቶ በመንፈስ
ተቀድሳችሁና በእውነትም አምናችሁ

[ሀ] 1ግሪኩ *ሲሉያኖስ ይላል*
[ለ]12 ወይም *እንደ አምላካችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ*
[ሐ]3 *አንዳንድ ቅጆች የኀጢአት ይላሉ*

እንድትድኑ መርጦአችኋል[መ]፡፡ 14የጌታችን
የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ተካፋዮች እንድ
ትሆኑም በወንጌላችን አማካይነት ጠርቶ
አችኋል፡፡ 15እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤
ጸንታችሁ ቁሙ፤ በአንደበታችንም ሆነ
በመልእክታችን ያስተላለፍንላችሁን ትምህ
ርት[ሠ] አጥብቃችሁ ያዙ፡፡
16ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግ
ሞም እኛን የወደደንና በጸጋው የዘላለም
መጽናናትና መልካም ተስፋን የሰጠን እግዚ
አብሔር አባታችን፣ 17ልባችሁን ያጽናኑት፤
በበጎ ሥራና በቃል ሁሉ ያበርቷችሁ፡፡

### ለጸሎት የቀረበ ጥያቄ

3 በቀረውስ ወንድሞች ሆይ፤ በእናንተ
ዘንድ እንደ ሆነው የጌታ ቃል በፍጥነት
እንዲሠራጭና እንዲከበር ለእኛ ጸልዩልን፤
2ደግሞም ሰው ሁሉ እምነት ያለው ስለ
ማይሆን ከዐመፀኞችና ከክፉ ሰዎች እንድ
ንድን ጸልዩልን፡፡ 3ጌታ ግን ታማኝ ነው፤
እርሱም ያበረታችኋል፤ ከክፉውም ይጠ
ብቃችኋል፡፡ 4እኛ ያዘዝናችሁን አሁን
አደረጋችሁ፤ ወደ ፊትም እንደምታደርጉ
በጌታ እንታመናለን፡፡ 5ጌታ ልባችሁን ወደ
እግዚአብሔር ፍቅርና ወደ ክርስቶስ ጽናት ይም
ራው፡፡

### ሥራ መፍታት እንደማይገባ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

6ወንድሞች ሆይ፤ ሥራ ፈት ከሆነና
ከእኛ በተቀበላችሁት ትምህርት[ረ] መሠረት
ከማይኖር ወንድም እንድትርቁ በጌታ በኢ
የሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን፤ 7የእኛን
ምሳሌ እንዴት መከተል እንደሚገባችሁ
እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁና፡፡ ከእናንተ
ጋር በነበርንበት ጊዜ ሥራ ፈቶች አልነ
በርንም፤ 8ደግሞም የማንንም እንጀራ በነጻ
አልበላንም፤ ነገር ግን ከእናንተ በአንዳችሁም
ላይ ሸክም እንዳንሆን ሌሊትና ቀን እን
ደክምና እንሠራ ነበር፤ 9ይህን ያደረግነው
ምሳሌነታችንን እንድትከተሉ ብለን እንጂ
የሚያስፈልገንን ነገር ከእናንተ ለማግኘት
ሥልጣን ሳይኖረን ቀርቶ አይደለም፡፡ 10ከእ
ናንተ ጋር በነበርንበት ጊዜ፣ “ሊሠራ የማ
ይወድ አይብላ” ብለን ይህን ትእዛዝ ሰጥ
ተናችሁ ነበርና፡፡ 11ከእናንተ አንዳንዶች ሥራ
ፈቶች እንደ ሆኑ ሰምተናል፤ እነርሱም
ያለ ሥራ እየዞሩ በሰው ጉዳይ ጣልቃ
የሚገቡ ናቸው፡፡ 12እንደዚህ ያሉ ሰዎች
ተግተው ሥራቸውን እንዲሠሩና እንጀ
ራቸውን እንዲበሉ በጌታ በኢየሱስ ክር
ስቶስ ስም እናዛቸዋለን፤ እንመክራቸዋ
ለንም፡፡ 13እናንተ ግን ወንድሞች ሆይ፤
መልካም ሥራን ከመሥራት ከቶ አትታክቱ፡፡
14በዚህ መልእክት ላይ ላለው ቃላችን
የማይታዘዝ ማንም ቢኖር፣ እንደዚህ ያለ
ውን ሰው በጥንቃቄ ተከታተሉት፤ በሥ
ራውም እንዲያፍር ከእርሱ ጋር አትተባበሩ፡፡
15ሆኖም እንደ ወንድም ገሥጹት እንጂ
እንደ ጠላት አትቊጠሩት፡፡

### የመጨረሻ ሰላምታ

16የሰላም ጌታ ራሱ በሁሉም ነገር
ዘወትር ሰላም ይስጣችሁ፡፡ ጌታ ከሁላችሁ
ጋር ይሁን፡፡
17ይህንን ሰላምታ በገዛ እጄ የጻፍሁት
እኔ ጳውሎስ ነኝ፤ የመልእክቶቼም ሁሉ
መለያ ይህ ነው፤ አጻጻፌም እንደዚህ ነው፡፡
18የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ
ከሁላችሁ ጋር ይሁን፡፡

2፥14 ሮሜ8፥28፤ 11፥29፤1ተሰ1፥5
2፥15 1ቆሮ11፥2፤ 16፥13
2፥16 ዮሐ3፥16፤ ፊል4፥20
2፥17 1ተሰ3፥2፤ 2ተሰ3፥3
3፥1 1ተሰ1፥8፤ 2፥13፤ 4፥1፤5፥25
3፥2 ሮሜ15፥31
3፥3 ማቴ5፥37፤ ሮሜ15፥31፤ 1ቆሮ1፥9
3፥4 2ቆሮ2፥3
3፥5 1ዜና29፥18
3፥6 ቁ7፡11፡14፤ ሮሜ16፥17፤ 1ቆሮ5፥4፤11፥2
3፥7 ቁ9፤ 1ቆሮ4፥16
3፥8 ሐሥ18፥3፤ ኤፌ4፥28
3፥9 ቁ7፤ 1ቆሮ9፥4-14፤16
3፥10 1ተሰ3፥4፤ 4፥11
3፥11 ቁ6፡7፤ 1ጢሞ5፥13
3፥12 ኤፌ4፥28፤ 1ተሰ4፥1፡11
3፥13 ገላ6፥9
3፥14 ቁ6፤ ሮሜ16፥17፤ 1ቆሮ4፥14
3፥15 ገላ6፥1፤ 1ተሰ5፥14፤ፊል16
3፥16 ሩት2፥4፤ ሮሜ15፥33
3፥17 1ቆሮ16፥21
3፥18 ሮሜ16፥20

[መ]13 አንዳንድ ቅጆች *አግዚአብሔር በኩራቱ እንድትሆኑ መርጦአ ችኋል* ይላሉ
[ሠ]15 ወይም *ወግ*
[ረ]6 ወይም *ወግ*

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት
## ወደ ጢሞቴዎስ – አንደኛ

1 በአዳኛችን በእግዚአብሔር፣ ተስፋችንም
በሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ ትእዛዝ የክ
ርስቶስ ኢየሱስ ሐዋርያ ከሆነው ከጳው
ሎስ፤
2በእምነት እውነተኛ ልጄ ለሆነው ለጢ
ሞቴዎስ፤
ከእግዚአብሔር ከአባታችን፣ ከጌታችንም
ከክርስቶስ ኢየሱስ ጸጋና ምሕረት፣ ሰላ
ምም ይሁን።

### ከሐሰተኛ የሕግ መምህራን ስለ መጠበቅ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

3ወደ መቄዶንያ በሄድሁ ጊዜ ዐደራ
እንዳልሁህ፣ አንዳንድ ሰዎች ከእንግዲህ
የሐሰት ትምህርት እንዳያስተምሩ ታዛቸው
ዘንድ በዚያው በኤፌሶን ተቀመጥ፤
4ደግሞም ለተረትና መጨረሻ ለሌለው
የትውልዶች ታሪክ ራሳቸውን አሳልፈው
እንዳይሰጡ እዘዛቸው። እነዚህ ነገሮች
በእምነት ከሆ ነው ከእግዚአብሔር ሥራ
ይልቅ ክርክርን ያነ ሣሣሉ። 5የዚህ
ትእዛዝ ዐላማ ግን ከንጹሕ ልብ፣ ከበጎ ኅሊ
ና እንዲሁም ከእውነተኛ እምነት የሚገኝ
ፍቅር ነው። 6አንዳንዶች ከእነዚህ ነገሮች
ዘወር ብለው ወደ ከንቱ ንግግር
ተመልሰዋል። 7የሕግ መምህራን ለመሆን
ይፈልጋሉ፤ ሆኖም ስለሚናገሩት ወይም
አስረግጠው ስለሚሚገቱለት ነገር አያውቀ
ም።
8ነገር ግን ሰው በአግባቡ ከተጠቀመበት፣ ሕግ
መልካም መሆኑን እናውቃለን። 9ደግሞም
ሕግ[ሀ] የተሰጠው ለጻድቃን ሳይሆን፣ ለሕግ
ተላላፊዎችና ለዐመፀኞች፣ ፈሪሃ እግዚ
አብሔር ለሌላቸውና ለኀጢአተኞች፣ ቅድ
ስና ለሌላቸውና እግዚአብሔርን ለሚንቁ፣
አባትና እናታቸውን ለሚገድሉ፣ ለነፍሰ
ገዳዮች መሆኑን እናውቃለን፤ 10እንዲሁም
ለዘማውያን፣ ከወንድ ጋር ለሚተኙ ወንዶች፣
ሰውን ለሚሸጡና ለሚገዙ፣ ለውሸተኞች፣
በሐሰት ለሚምሉ፣ ጤናማ የሆነውን ትምህ
ርት ለሚጻረሩ ሁሉ ነው፤ 11ይህ ጤናማ
ትምህርት ቡሩክ እግዚአብሔር ለእኔ በዐደራ
ከሰጠኝ የክብር ወንጌል ጋር የሚስማማ
ነው።

### ለጳውሎስ የተሰጠው የጌታ ጸጋ

12በአገልግሎቱ በመሾም ታማኝ አድርጎ
የቈጠረኝን፣ ብርታት የሰጠኝን ጌታችንን
ክርስቶስ ኢየሱስን አመሰግናለሁ።
13ምንም እንኳ ከዚህ በፊት ተሳዳቢ፣
አሳዳጅና ዐመፀኛ የነበርሁ ብሆንም፣ ባለ
ማወቅና ባለማመን ስላደረግሁት ምሕረት
ተደርጎልኛል፤ 14በክ ርስቶስ ኢየሱስ
ከሆኑት እምነትና ፍቅር ጋርም የጌታችን
ጸጋ ተትረፈረፈልኝ።
15 ‘ክርስቶስ ኢየሱስ ኀጢአተኞችን ለማ
ዳን ወደ ዓለም መጣ’ የሚለው ቃል እው
ነተኛና ሰው ሁሉ ሊቀበለው የሚገባ ነው፤
ከኀጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ። 16ነገር
ግን ክርስቶስ ኢየሱስ በእርሱ ለሚያምኑና
የዘላለምን ሕይወት ለሚቀበሉ ወሰን የሌ
ለው ትዕግሥቱን ከኀጢአተኞች ዋና በሆ
ንሁት በእኔ እንደ ምሳሌ አድርጎ ያሳይ
ዘንድ ምሕረትን አገኘሁ። 17እንግዲህ ዘላ
ለማዊ ለሆነው፣ ለማይሞተው፣ ለማይታየ
ውና ብቻውን አምላክ ለሆነው ንጉሥ ከዘ
ላለም እስከ ዘላለም ክብርና ምስጋና
ይሁን፤ አሜን።
18ልጄ ጢሞቴዎስ ሆይ፤ አስቀድሞ ስለ
አንተ በተነገረው ትንቢት መሠረት ይህን
ትእዛዝ እሰጥሃለሁ፤ ይኸውም እርሱን በመ
ከተል መልካሙን ገድል እንድትጋደል ነው።
19እምነትና በጎ ኅሊናም ይኑርህ፤ አንዳ
ንዶች ኅሊናቸውን ጥለው ባሕር ላይ አደጋ
ደርሶበት እንደሚጠፋ መርከብ እምነታ
ቸውን አጥፍተዋል። 20ከእነርሱም መካከል
እንዳይሳደቡ ትምህርት ያገኙ ዘንድ ለሰይ
ጣን አሳልፌ የሰጠኋቸው፣ ሄሜኔዎስና
እስክ ንድሮስ ይገኛሉ።

### አምልኮን በሚመለከት የተሰጠ መመሪያ

2 እንግዲህ ከሁሉ አስቀድሞ ልመናና
ጸሎት፣ ምልጃና ምስጋና ለሰዎች
ሁሉ፣ ለነገሥታትና ለባለ ሥልጣናት
ሁሉ እንዲደረግ አሳስባለሁ፤ 2ይህም
በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትና በቅድስና
ሁሉ፣ በሰላ ምና በጸጥታ እንድንኖር ነው።
3ይህ በእግዚአብሔር በአዳኛችን ፊት ደስ
የሚያሰኝ ነው፤ 4እርሱ ሰዎች ሁሉ እንዲ
ድኑና እውነ ትን ወደ ማወቅ እንዲደርሱ
ይፈልጋል። 5አንድ እግዚአብሔር አለና፤
ደግሞም በእግዚአብሔ ርና በሰዎች መካከል
አንድ አስታራቂ አለ፤ እርሱም ሰው
የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ 6ራሱንም
ለሰዎች ሁሉ ቤዛ አድርጎ ሰጠ፤ ይህም
በትክክለኛው ጊዜ ተመስክ ሮለታል።
7እኔም ለዚህ ነገር የምሥራች

1፥1 ሉቃ1፥47፤
2ቆሮ1፥1፤ቈላ1፥27፤ቲ
ቶ1፥3
1፥2 ቍ18፤ሐሥ16፥1፤
ሮሜ1፥7፤1ቆሮ4፥17፤
1ተሰ2፥11፤2ጢሞ1፥2፤
ቲቶ1፥4
1፥3 ሐሥ16፥9፤
18፥19፤ገላ1፥6፥7፤
1ጢሞ6፥3
1፥4 1ጢሞ4፥7፤ 2ጢ
ሞ2፥14፤4፥4፤
ቲቶ1፥14፤3፥9
1፥5 ሐሥ23፥1፤
ገላ5፥6፤1ጢሞ4፥2፤
2ጢሞ1፥5፤2፥22
1፥7 ኢዮ38፥2፤
ኤፌ4፥11
1፥8 ሮሜ7፥12
1፥9 ገላ3፥19፤5፥23
1፥10 1ጢሞ6፥3፤
2ጢሞ1፥13፤
4፥3፤ቲቶ1፥9፤2፥1
1፥11 ገላ2፥7፤
1ተሰ2፥4፤ቲቶ1፥3
1፥12 ሐሥ9፥15፤
ፊል4፥13
1፥13 ቍ16፤
ሐሥ8፥3፤26፥9

1፥14 2ቆሮ4፥15፤
1ተሰ1፥3፤2ጢሞ1፥13
1፥15 ማር2፥17፤
ዮሐ3፥17፤1ጢሞ3፥1፤
4፥9፤2ጢሞ2፥11፤
ቲቶ3፥8
1፥16 ቍ13፤
ማቴ25፥46፤ዮሐ3፥15፤
ሮሜ2፥4
1፥17 ሮሜ
11፥36፤ቈላ1፥15፤
1ጢሞ6፥16፤ይሁ25፤
ራእ15፥3
1፥18 ቍ2፤1ጢሞ4፥14፤
6፥12፤2ጢሞ2፥3፤
4፥7
1፥19 ቍ5፤ሐሥ23፥1፤
1ጢሞ6፥21፤
2ጢሞ2፥18
1፥20 1ቆሮ5፥5፤ 2ጢ
ሞ2፥17፤
2ጢሞ4፥14
2፥1 ኤፌ6፥18
2፥2 ዕዝ6፥10፤
ሮሜ13፥1፤
1ጢሞ3፥16፤4፥7፥
8፤6፥3፥5፥6፥11፤
2ጢሞ3፥5፤ቲቶ1፥1
2፥3 ሉቃ1፥47፤
1ጢሞ5፥4
2፥4 ሕዝ18፥23፥32፤
33፥11፤ዮሐ3፥17፤
ሮሜ11፥14፤
1ጢሞ4፥10፤2ጢሞ2፥25
ቲቶ1፥1፤2፥11፤
ዕብ10፥26፤2ጴጥ3፥9
2፥5፤ዘዳ6፥4፤
ሮሜ1፥3፤3፥29፥30፤
10፥12፤ ገላ3፥20

2፥6 ማቴ20፥28፤1ቆሮ1፥6፤1ጢሞ6፥15፤ ቲቶ1፥3 2፥7 ሐሥ9፥15፤
ሮሜ9፥1፤2ጢሞ1፥11

[ሀ]9 ወይም ሕጉ

አብሣሪና ሐዋርያ እንዲሁም ለአሕዛብ
የእውነተኛ እምነት አስተማሪ ሆኜ ተሾ
ምሁ፤ እውነቱን እናገራለሁ፤ አልዋሽም።
8እንግዲህ ወንዶች በሁሉም ቦታ ያለ
ቍጣና ያለ ክርክር የተቀደሱ እጆቻቸውን
ወደ ላይ በማንሣት እንዲጸልዩ እፈልጋለሁ።
9እንዲሁም ሴቶች በጨዋነትና ራስን በመ
ግዛት ተገቢ የሆነ ልብስ ይልበሱ እንጂ
በሹሩባ ወይም በዕንቍ ወይም ዋጋቸው ውድ
በሆኑ ልብሶች አይሽቀርቀሩ፤ 10ነገር ግን
እግዚአብሔርን እናመልካለን የሚሉ
ሴቶች ሊያደርጉ እንደሚገባ በመልካም
ተግባር ይዋቡ።
11ሴት በጸጥታና በሙሉ መገዛት ትማር።
12ሴት ዝም እንድትል እንጂ እንድታስተ
ምር ወይም በወንድ ላይ ሥልጣን እንዲኖራት
አልፈቅድም። 13ምክንያቱም አዳም ቀድሞ
ተፈጥሮአል፤ ከዚያም ሔዋን ተፈጠረች።
14ደግሞም የተታለለው አዳም አይደለም፤
የተታለለችውና ኀጢአተኛ የሆነችው ሴቷ
ናት፤ 15ይሁን እንጂ ሴት[ሰ] በእምነትና
በፍቅር፣ በቅድስናም ራሷን እየገዛች ብት
ጸና ልጅ በመውለድ ትድናለች[ሐ]።

## እረኞችና ዲያቆናት

3 "ማንም የቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ
ለመሆን ቢፈልግ፣ መልካም ሥራን
ይመኛል" የሚለው ቃል የታመነ ነው።
2እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ
የማይነቀፍ፣ የአንዲት ሚስት ባል፣
ልከኛ፣ ራሱን የሚገዛ፣ በሥርዐት የሚኖር፣
እንግዳ ተቀባይ፣ ማስተማር የሚችል፣ 3የማ
ይሰክር፣ የማይጣላ ግን ጨዋ የሆነ፣ የማይ
ጨቃጨቅ፣ ገንዘብንም የማይወድ ሊሆን
ይገባዋል። 4ልጆቹን ታዛዥና አክባሪ አድርጎ
በማሳደግ የገዛ ቤተ ሰቡን በአግባቡ የሚ
ያስተዳድር ሊሆን ይገባል። 5አንድ ሰው የራ
ሱን ቤት ማስተዳደር ካላወቀበት፣ የእግዚ
አብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ሊጠ
ብቅ ይችላል? 6በትዕቢት ተነፍቶ ዲያብሎስ
በወ ደቀበት ፍርድ እንዳይወድቅ አዲስ
ክርስ ቲያን አይሁን። 7ደግሞም ስሙ
እንዳይነ ቀፍና በዲያብሎስ ወጥመድ
ውስጥ እንዳ ይወድቅ፣ በውጭ ባሉት
ዘንድ መልካም ምስክርነት ሊኖረው
ይገባል።
8ዲያቆናትም እንደዚሁ የተከበሩ፣ ቃላቸ
ውን የማይለዋወጡ፣ ለብዙ ወይን ጠጅ የማ
ይጐመጁ፣ ያለ አግባብ የሚገኝ ጥቅምንም
የማያሳድዱ ሰዎች መሆን ይገባቸዋል፤
9የእምነትንም ጥልቅ ምስጢር በንጹሕ ኅሊና
መጠበቅ አለባቸው። 10እነርሱም አስቀድ
መው ይፈተኑ፤ ከዚያም፣ አንዳች ነቀፋ
ካልተገኘባቸው በዲቁና ያገልግሉ።
11እንዲሁ ሴቶችም[መ] የተከበሩ፣ ሐሜ
ተኞች ያልሆኑ ነገር ግን ልከኞችና በነገር
ሁሉ የታመኑ ሊሆኑ ይገባል።
12ዲያቆናት የአንዲት ሚስት ባል
መሆን ይገባቸዋል፤ ደግሞም ልጆቻቸው
ንና ቤተ ሰቦቻቸውን በአግባቡ የሚያስተ
ዳድሩ መሆን አለባቸው። 13በአግባቡ ያገለ
ገሉ ለራሳቸው ትልቅ ክብርን፣ በክርስቶስ
ኢየሱስም ባላቸው እምነት ብዙ ድፍረትን
ያገኛሉ።
14ወደ አንተ ቶሎ ለመምጣት ተስፋ
ባደርግም ይህን ትእዛዝ እጽፍልሃለሁ፤
15ይህንም የምጽፍልህ ብዘገይ እንኳ ሰዎች
በእግዚአብሔር ቤት እንዴት መኖር
እንዳለባቸው እንድታውቅ ነው፤ ቤቱም
የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ይኸ
ውም የእው ነት ዐምድና መሠረት ነው።
16የእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ምስጢር
ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፤
እርሱ[ሠ] በሥጋ[ረ] ተገለጠ፤
በመንፈስ ጸደቀ፤
በመላእክት ታየ፤
በአሕዛብ ዘንድ ተሰበከ፤
በዓለም ባሉት ታመነ፤
በክብር ዐረገ።

## ለጢሞቴዎስ የተሰጠ መመሪያ

4 በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች እምነ
ትን ክደው አታላይ መናፍስትንና የአጋ
ንንትን ትምህርት እንደሚከተሉ መንፈስ በግ
ልጥ ይናገራል። 2እንዲህ ያለው ትምህ
ርት የሚመጣው ኅሊናቸው በጋለ ብረት
የተጠበሰ ያህል ከደነዘዘባቸው ግብዝ ውሸ
ተኞች ነው። 3እነርሱ፣ ሰዎች እንዳያገቡ
ይከለክላሉ፤ የሚያምኑና እውነትን የሚያ
ውቁ ሰዎች እግዚአብሔር የፈጠረውን በምስጋ
ናም የሚቀበሉትን እንዳይበሉ ያዛሉ፤ 4እግ
ዚአብሔር የፈጠረው ማንኛውም ነገር መል
ካም ነውና፤ በምስጋና ከተቀበሉትም የሚ
ጣል ምንም ነገር የለም፣ 5በእግዚአብሔር
ቃልና በጸሎት የተቀደሰ ነውና።
6ይህን ትእዛዝ ለወንድሞች ብታሳስብ፣
በእምነት ቃልና በተቀበልኸው መልካም
ትምህርት ታንጸህ የክርስቶስ ኢየሱስ በጎ
አገልጋይ ትሆናለህ። 7እግዚአብሔርን ከማ
ያከብር ርባና ቢስ አፈ ታሪክና ከአሮጊቶች
ተረታ ተረት ራቅ፤ ይልቁንም ለእውነተኛ

2÷8 መዝ24÷4፤63÷4፤
134÷2፤141÷2፤
ሉቃ24÷50
2÷9 1ጴጥ3÷3
2÷10 ምሳ31÷13
2÷11 1ጴጥ3÷3፡4
2÷12 ኤፌ5÷22
2÷13 ዘፍ2÷7፡ 22፤
1ቆሮ11÷8
2÷14 ዘፍ3÷1-6፡13፤
2ቆሮ11÷3
2÷15 1ጢሞ1÷14
3÷1 ሐሥ20÷28፤
ፊል1÷1፤1ጢሞ1÷15፤
ቲቶ1÷7
3÷2 ቀኊ11፡12፤ ሮሜ
12÷13፤
2ጢሞ2÷24፤
ቲቶ1÷6-8፤2÷2
3÷3 ሉቃ16÷14፤
1ጢሞ6÷10፤
2ጢሞ2÷24፤3÷2፤
ቲቶ1÷7፤ዕብ13÷5፤
1ጴጥ5÷2
3÷4 ቀኊ12፤ቲቶ1÷6
3÷5 1ቆሮ10÷32
3÷6 1ጢሞ6÷4፤
2ጢሞ3÷4፤2ጴጥ2÷4
3÷7 ማር4÷11፤
2ጢሞ2÷26
3÷8 ፊል1÷1፤
1ጢሞ5÷23፤
ቲቶ1÷7፤2÷3
3÷9 ሐሥ23÷1
3÷10 1ጢሞ5÷22
3÷11 ቀኊ2፤2ጢሞ3÷3፤
ቲቶ2÷3
3÷12 ቀኊ2፡4
3÷15 ቀኊ5፤
ማቴ16÷16፤1ቆሮ10÷32
3÷16 መዝ9÷11፤
ማር16÷19፤
ዮሐ1÷14፤
ሮሜ6÷25፤ቈላ1÷23፤
1ጢሞ2÷2
4÷1 ማር13÷5፤
ዮሐ16÷13፤ሐሥ8÷29፤
1ቆሮ2÷10፤2ጢሞ3÷1፤
2ጴጥ3÷3
4÷2 ኤፌ4÷19
4÷3 ቀኊ4፤ዘፍ1÷29፤
9÷3፤ሮሜ14÷6፤
1ቆሮ10÷30፤
ቈላ2÷16፤ዕብ13÷4
4÷4 ዘፍ1÷10፡12፡
18፡21፡25፡31፤
ማር7÷181፡9፤
ሮሜ14÷14-18፤
ሐሥ10÷15
4÷5 ዕብ4÷12
4÷6 1ጢሞ1÷10፤
2ጢሞ3÷15
4÷7 1ጢሞ1÷4፤2÷2፤
2ጢሞ2÷16

[ሰ]15 ግሪኩ *እርሷ* ይላል
[ሐ]15 ወይም *ትታደሳለች*
[መ]11 ወይም *ሚስቶቻቸው* ወይም *ዲያቆናውያት*
[ሠ]16 አንዳንድ ቅጆች *አምላክ* ይላሉ።
[ረ]16 ወይም *በአካል*

መንፈሳዊ ሕይወት ራስህን አሠልጥን። [8]የአ
ካል ብቃት ልምምድ ለጥቂት ነገር ይጠቅ
ማልና፤ ለእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት
ራስን ማሠልጠን ግን ለአሁኑም ሆነ
ለሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው ለሁሉ
ቱም ይጠቅማል።
[9]ይህ ቃል የታመነና ሙሉ ለሙሉ ሊቀ
በሉት የሚገባ ነው፤ [10]ለዚህ ብለን እንጥራ
ለን፤ እንደክማለንም፤ ይኸውም ለሰዎች
ሁሉ በተለይም ለሚያምኑት አዳኝ በሆነው
በሕያው እግዚአብሔር ተስፋ ስለምናደርግ ነው።
[11]እነዚህን ነገሮች እዘዝ፤ አስተምርም።
[12]ወጣትነትህን ማንም አይናቅ፤ ነገር ግን
ለሚያምኑት በንግግርና በኑሮ፣ በፍቅር፣
በእምነትና በንጽሕና አርአያ ሁንላቸው።
[13]እኔ እስክመጣ ድረስ ለማንበብ፣ ለመምከ
ርና ለማስተማር ትጋ። [14]ሽማግሌዎች
እጃቸውን በአንተ ላይ ሲጭኑ በትንቢት
የተሰጠህን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል።
[15]ሰው ሁሉ ማደግህን ያይ ዘንድ በእነ
ዚህ ነገሮች ላይ አትኵር፤ በትጋትም ፈጽ
ማቸው፤ [16]ለሕይወትህና ለትምህርትህ ተጠ
ን ቀቅ፤ በእነዚህም ጽና፤ ይህን ብታደርግ፣ ራ
ስ ህንና የሚሰሙህንም ታድናለህና።

## ስለ መበለቶች፣ ስለ ሽማግሌዎችና ስለ ባሪያዎች የተሰጠ ምክር

5 አረጋዊውን ሰው እንደ አባትህ ቈጥ
ረህ ምከረው እንጂ በኀይለ ቃል አትናገ
ረው። ወጣት ወንዶችን እንደ ወንድሞች
ተቀበላቸው፤ [2]እንዲሁም አሮጊቶችን
እንደ እናቶች፣ ወጣት ሴቶችን ደግሞ
እንደ እኅ ቶች በፍጹም ንጽሕና
አስተናግዳቸው።
[3]በእርግጥ ችግረኛ የሆኑትን መበለቶች
ተንከባከባቸው። [4]አንዲት መበለት ግን ልጆች
ወይም የልጅ ልጆች ቢኖሯት፣ እነዚህ ልጆች
የራሳቸውን ቤተ ሰብ በመርዳትና ለወላ
ጆቻቸውም ብድራትን በመመለስ ከሁሉ
በፊት እምነታቸውን በተግባር ለማሳየት
መማር ይገባቸዋል፤ ይህ እግዚአብሔርን ደስ
የሚ ያሰኝ ነውና። [5]በእርግጥ መበለት
የሆነች፣ ብቻዋንም የምትኖር ተስፋዋን
በእግዚአብሔር ላይ ታደርጋለች፤ ለጸሎትና
የእግዚአብሔርን ርዳታ ለመለመን ሌሊትና ቀን
ትተጋለች። [6]ምድራዊ ደስታን የምትሻዋ
መበለት ግን በሕይወት ብትኖርም የሞተች
ናት። [7]ማንም የሚነቀፍበት ነገር
እንዳይኖር፣ ይህንም ትእዛዝ ለሕዝቡ
ስጥ። [8]አንድ ሰው ዘመዶ
ቹን፣ በተለይም የቅርብ ቤተ ሰቡን የማይረዳ
ከሆነ ሃይማኖቱን የካደ፣ ከማያምንም ሰው
ይልቅ የባሰ ክፉ ነው። [9]ዕድሜዋ ከሥ
ልሳ ዓመት ያነሰ መበለት በመዝገብ ላይ
አትጻፍ፤ ደግሞም የአንድ ባል ሚስት

4፥8 መዝ37፥9፡11፤
ምሳ22፥4፤ማቴ6፥33፤
ማር10፥29፡30፤
1ጢሞ6፥6
4፥9 1ጢሞ1፥15
4፥10 ማቴ16፥16፤
ሉቃ1፥47፤2፥11
4፥11 1ጢሞ5፥7፤ 6፥2
4፥12 ፊል3፥17፤
1ተሰ1፥7፤2ተሰ3፥9፤
1ጢሞ1፥14፤
2ጢሞ1፥7፤
ቲቶ2፥7፡15፤1ጴጥ5፥3
4፥13 ሉቃ4፥16፤
ሐሥ13፥14-16፤
ቈላ4፥16፤1ተሰ5፥27፤
1ጢሞ3፥14
4፥14 ሐሥ6፥6፤
11፥30፤1ጢሞ1፥18፤
2ጢሞ1፥6
4፥16 ሮሜ11፥14
5፥1 ዘሌ19፥32፤
ቲቶ2፥2፡6
5፥3 ቍ5፡16
5፥4 ቍ8፤
ሮሜ12፥2፤ኤፌ5፥10፤
6፥1፡ 2፤1ጢሞ2፥3
5፥5 ቍ3፡16፤
ሉቃ2፥37፤
ሮሜ1፥10፤
1ቆሮ7፥34፤ 1ጴጥ3፥5
5፥6 ሉቃ15፥24፤
5፥7 1ጢሞ4፥11፤
6፥2
5፥8 2ጴጥ2፥1፤
ይሁ 4
5፥10 ቍ16፤
ሉቃ7፥44፤ሐሥ9፥36፤
ሮሜ12፥13፤1ጢሞ6፥18፤
1ጴጥ2፥12
5፥13 ሮሜ1፥29፤
2ተሰ3፥11
5፥14 1ቆሮ7፥9፤ 1ጢሞ6፥1
5፥15 ማቴ4፥10
5፥16 ቍ3-5
5፥17 ሐሥ11፥30፤
ፊል2፥29፤1ተሰ5፥12
5፥18 ዘሌ19፥13፤
ዘዳ24፥14፡15፤25፥4፤
ማቴ10፥10፤ሉቃ10፥7፤
1ቆሮ9፥7-9፡14
5፥19 ማቴ18፥16፤
ሐሥ11፥30
5፥20 ዘዳ13፥11፤
2ጢሞ4፥2፤
ቲቶ1፥13፤2፥15
5፥21 1ጢሞ6፥13፤
2ጢሞ4፥1
5፥22 መዝ18፥26፤
ሐሥ6፥6፤ኤፌ5፥11
5፥23 1ጢሞ3፥8

የነበረች[ሰ] ልትሆን ይገባል፤ [10]ልጆችን በማ
ሳደግ፣ እንግዶችን በመቀበል፣ የቅዱሳንን
እግር በማጠብ፣ የተቸገሩትን በመርዳትና
ለበጎ ምግባር ሁሉ ራሷን በመስጠት በመል
ካም ሥራም የተመሰከረላት መሆን
አለባት።
[11]ወጣት መበለቶችን ግን እንዲህ ባለው
መዝገብ አትጻፋቸው፤ ምክንያቱም ሥጋዊ
ፍላጎታቸው ለክርስቶስ በገቡት ቃል ላይ
በሚያይልበት ጊዜ ለማግባት ይሻሉና።
[12]በዚ ህም ፍርድን በራሳቸው ላይ
ያመጣሉ፤ በመጀመሪያ የገቡትን ቃል ኪ
ዳን አፍርሰ ዋልና። [13]በተጨማሪም ሥራ
መፍታትንና ከቤት ቤት መዞርን
ይለምዳሉ፤ ሥራ ፈት መሆን ብቻ
ሳይሆን፣ የማይገባውን እየተ ናገሩ ሐሜ
ተኞችና በሰው ጕዳይም ጣልቃ የሚገቡ
ይሆናሉ። [14]ስለዚህ ባል የሞተባ ቸው
ወጣት ሴቶች እንዲያገቡ፣ ልጆች እንዲ
ወልዱ፣ ቤታቸውን እንዲያስተዳ ድሩ፣ ጠ
ላትም የሚነቅፍባቸውን ነገር እን ዳያገኝ
እመክራለሁ። [15]በእርግጥ ከዚህ በፊት
አንዳንዶቹ ሰይጣንን ለመከተል ዘወር
ብለዋል።
[16]አማኝ የሆነች ማንኛዋም ሴት በቤተ
ሰቧ ውስጥ መበለቶች ቢኖሯት፣ ቤተ
ክርስቲያን እውነተኛ መበለቶችን ብቻ
መርዳት እንድትችል እርሷው ትርዳቸው
እንጂ ለቤተ ክርስቲያን ሸክም እንዲሆኑ
አትተዋቸው።
[17]ቤተ ክርስቲያንን በሚገባ የሚያስተዳ
ድሩ፣ ይልቁንም በመስበክና በማስተማር
የሚተጉ ሽማግሌዎች ዕጥፍ ክብር ይገባቸ
ዋል፤ [18]መጽሐፍም፣ “እያበራየ ያለውን
በሬ አፉን አትሠር፤[ቀ]” ደግሞም፣ “ለሠራ
ተኛ ደመወዙ ይገባዋል[በ]” ይላልና። [19]በሁ
ለት ወይም በሦስት ምስክሮች ካልተደገፈ
በቀር በሽማግሌ ላይ የሚቀርብ ክስ አትቀ
በል። [20]ሌሎች አይተው እንዲጠነቀቁ ኀጢ
አት የሚሠሩትን በጉባኤ ፊት ገሥጻ
ቸው።
[21]በእግዚአብሔርና በክርስቶስ ኢየሱስ፣
በተ መረጡትም መላእክት ፊት እነዚህን
ትእ ዛዛት ያለ አድልዎ እንድትጠብቅና
አንዳ ችም ነገር በማበላለጥ
እንዳታደርግ ዐደራ እልሃለሁ።
[22]በማንም ላይ እጅ ለመጫን አትቸ
ኵል፤ ከሌሎችም ጋር በኀጢአት አትተባ
በር፤ ራስህን በንጽሕና ጠብቅ።
[23]ለሆድህና ደጋግሞ ለሚነሣብህ ሕመም፣
ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣበት እንጂ ከእን
ግዲህ ውሃ ብቻ አትጠጣ።
[24]የአንዳንድ ሰዎች ኀጢአት ግልጽ ነው፤

[ሰ]9 ወይም ለባልዋ ታማኝ የነበረች
[ቀ]18 ዘዳ 25፥4 [በ]18 ሉቃ 10፥7

ከእነርሱም ቀድሞ ፍርድ ቦታ ይደርሳል፤
ሌሎችን ግን ኀጢአታቸው ይከተላቸዋል።
25መልካም ሥራም እንደዚሁ ግልጽ ነው፤
ግልጽ ያልሆነ ቢኖርም እንኳ ተሰውሮ
አይቀርም።

6 የእግዚአብሔር ስምና ትምህርቱም እንዳ
ይሰደቡ፣ በባርነት ቀንበር ሥር ያሉ
ሁሉ፣ ጌቶቻቸው ሙሉ ክብር እንደሚገባ
ቸው አድርገው ይቍጠሩ። 2የሚያምኑ
ጌቶች ያሏቸውም፣ ወንድሞች ስለ ሆኑ
የሚገባቸውን ክብር አይንፈጓቸው፤ ይልቁ
ንም በአገልግሎታቸው የሚጠቀሙ አማኞ
ችና ወዳጆቻቸው ስለ ሆኑ የበለጠ ሊያ
ገለግሏቸው ይገባል። እነዚህን ነገሮች
አስተምር፤ ምከርም።

## የገንዘብ ፍቅር

3ማንም የሐሰት ትምህርት ቢ
ያስተምር፣ ከጌታችን ከኢየሱስ
ክርስቶስ ጤናማ ቃልና እውነተኛ
መንፈሳዊነትን ከሚያ ጐለብት ትምህርት
ጋር የማይስማማ ቢሆን፣ 4ያ ሰው በትዕቢት
ተወጥሮአል፤ አንዳችም አያስተውልም።
ስለ ቃላት ለመከራከርና ለመጣላት ክፉ
ጕጕት አለው፤ እነዚህም ቅናትን፣ ጥልን፣
ስድብን፣ መጥፎ ጥርጣ ሬን ያስከትላሉ፤
5እውነትን በተቀሙና መንፈሳዊው ነገር
ትርፍ ማግኛ በሚመስላ ቸውና አእምሮ
በጐደላቸው ሰዎች መካ ከል የማያባራ
ንትርክ ያመጣሉ።

6ነገር ግን እውነተኛ መንፈሳዊነት ባለን
ነገር ከመርካት ጋር ትልቅ ትርፍ ነው።
7ምክንያቱም ወደ ዓለም ያመጣነው ምንም
ነገር የለም፤ ምንም ነገር ይዘን መሄድም
አንችልም። 8ነገር ግን ምግብና ልብስ ካለን፣
ያ ይበቃናል። 9ባለጠጋ ለመሆን የሚፈልጉ
ግን ወደ ፈተናና ወደ ወጥመድ፣ እንዲ
ሁም ሰዎችን ወደ መፍረስና ወደ ጥፋት
ወደሚያዘቅጠው ወደ ብዙ ከንቱና ክፉ
ምኞት ይወድቃሉ። 10ምክንያቱም የገን
ዘብ ፍቅር የክፋት ሁሉ ሥር ነው፤ አንዳ
ንዶች ባለጠጋ ለመሆን ካላቸው ጕጕት
የተነሣ ከእምነት መንገድ ስተው ሄደዋል፤
ራሳቸውንም በብዙ ሥቃይ ወግተዋል።

6፥1 ኤፌ6፥5፤
1ጢሞ5፥14፤
ቲቶ2፥5፡8
6፥2 1ጢሞ4፥11፤
ፊሞ16
6፥3 1ጢሞ1፥3፡10
6፥4 1ጢሞ3፥6፤
2ጢሞ2፥14፤3፥4
6፥5 2ጢሞ3፥8፤
ቲቶ1፥15
6፥6 ፊል4፥11፤
1ጢሞ4፥8፤ዕብ13፥5
6፥7 ኢዮ1፥21፤
መዝ49፥17፤መክ5፥15
6፥8 ምሳ30፥8፤
ዕብ13፥5
6፥9 ምሳ15፥27፤
28፥20፤1ጢሞ3፥7
6፥10 ቍ21፤
ኢሱ7፥21፤
1ጢሞ3፥3፤5፥19
6፥11 ቍ3፡5፡6፤
1ጢሞ1፥14፤2፥2፤
2ጢሞ2፥22፤3፥10፤
3፥17
6፥12 ቍ19፤
ማቴ25፥46፤1ቆሮ9፥25፡
26፤ፊል3፥12፤
1ጢሞ1፥18፤ዕብ3፥1

6፥13 ቍ12፤
ዮሐ18፥33-37፤
1ጢሞ5፥21፤
2ጢሞ4፥1
6፥14 1ቆሮ1፥7፤
1ተሰ3፥13፤
2ጢሞ1፥10፤4፥1፡8
6፥15 ዘዳ10፥17፤
መዝ136፥3፤ዳን2፥47፤
1ጢሞ1፥11፡17፤
2፥6፤ቲቶ1፥3፤ራእ1፥5፤
17፥14፤19፥16
6፥16 መዝ104፥2፤
ዮሐ1፥18፤
ሮሜ11፥36፤
1ጢሞ1፥17፤
1ዮሐ1፥7

## ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሰጠው ዐደራ

11የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፤ አንተ ግን ከዚህ
ሁሉ ሽሽ፤ ጽድቅን፣ እውነተኛ መንፈሳዊ
ሕይወትን፣ እምነትን፣ ፍቅርን፣ ትዕግሥት
ንና ገርነትን ተከታተል። 12መልካሙን የእ
ምነት ገድል ተጋደል፤ በብዙ ምስክሮች
ፊት በመልካም መታመን የመሰከርህለትንና
የተጠራህበትን የዘላለም ሕይወት አጥብቀህ
ያዝ። 13ለሁሉም ሕይወትን በሚሰጥ በእግዚ
አብሔር ዘንድ እንዲሁም በጳንጥዮስ ጲላጦስ
ፊት እውነትን በመሰከረ በክርስቶስ ኢየሱስ
ፊት ዐደራ የምልህ፣ 14ጌታችን ኢየሱስ
ክርስቶስ እስኪገለጥ ድረስ፣ ይህን ትእዛዝ
ያለ ዕድፍና ያለ ነቀፋ ሆነህ እንድትጠ
ብቅ ነው፤ 15ያም መገለጥ፣ የተባረከውና
ብቻውን ገዥ የሆነው የነገሥታት ንጉሥ፣
የጌቶችም ጌታ እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ
የሚያሳየው ነው፤ 16እርሱ ብቻ ኢመዋቲ
ነው፤ ሊቀረብ በማይቻል ብርሃን ውስጥ
ይኖራል፤ እርሱን ያየ ማንም የለም፤ ሊያ
የውም የሚችል የለም። ለእርሱ ክብርና
ኀይል ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን፤
አሜን።

17በዚህ ዓለም ባለጠጎች የሆኑት እንዳይ
ታበዩ፣ ደስም እንዲለን ሁሉን ነገር አት
ረፍርፎ በሚሰጠን በእግዚአብሔር እንጂ አስ
ተማማኝነት በሌለው በሀብት ላይ ተስፋ
እንዳያደርጉ እዘዛቸው። 18መልካም እንዲሠሩ፣
ቸሮችና ለማካፈል ፈቃደኞች የሆኑ እንዲ
ሆኑ እዘዛቸው። 19በዚህ ዐይነት እውነተኛ
የሆነውን ሕይወት ያገኙ ዘንድ፣ ለሚመ
ጣው ዘመን ጽኑ መሠረት የሚሆን ሀብት
ለራሳቸው ያከማቻሉ።

20ጢሞቴዎስ ሆይ፤ በዐደራ የተቀበልኸ
ውን ሁሉ ጠብቅ፤ እግዚአብሔርን ከማያስ
ከብር ከከንቱ ልፍለፋና በውሸት ዕውቀት
ከተባለ የተቃውሞ ፍልስፍና ራቅ፤ 21የዚህ ዐይ
ነት ዕውቀት አለን ሲሉ የነበሩ አንዳን
ዶች ይህን በማድረጋቸው ከእምነት መን
ገድ ስተው ሄደዋል።

ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።

6፥17 ቍ9፤ መዝ62፥10፤ኤር49፥4፤ሉቃ12፥20፡ 21፤ሐሥ14፥17፤
1ጢሞ4፥10 6፥18 ሮሜ12፥8፡13፤ኤፌ4፥28፤1ጢሞ5፥10
6፥19 ቍ12፤ማቴ6፥20፤ኤፌ3፥12 6፥20 2ጢሞ1፥12፡
14፤2፥16 6፥21 ቍ10፤ ቈላ4፥18፤2ጢሞ2፥18

# የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
# ወደ ጢሞቴዎስ - ሁለተኛ

1 በክርስቶስ ኢየሱስ ቃል በተገባው የሕ
ይወት ተስፋ መሠረት፣ በእግዚአብሔር
ፈቃድ የክርስቶስ ኢየሱስ ሐዋርያ የሆነ
ጳውሎስ፤

2ለተወዳጁ ልጄ፣ ለጢሞቴዎስ፤

ጸጋ፣ ምሕረትና ሰላም ከእግዚአብሔር
አብ፣ ከጌታችንም ከክርስቶስ ኢየሱስ ይሁን።

### ታማኝ ስለ መሆን የተሰጠ ማበረታቻ

3ሳላቋርጥ ሌሊትና ቀን በጸሎቴ ስለ
አንተ ሳስብ፣ ቀደምት አባቶች
እንዳደረጉት በንጹሕ ኅሊና የማመልከውን
እግዚአብሔርን አመ ሰግናለሁ። 4እንባህን
እያስታወስሁ በደስታ እሞላ ዘንድ ላይህ
እናፍቃለሁ። 5ግብዝነት የሌለበት
እምነትህን አስታውሳለሁ፤ ይህ እምነት
ቀድሞ በአያትህ በሎይድ እንዲሁም
በእናትህ በኤውንቄ ዘንድ ነበረ፤ አሁን
ደግሞ በአንተ እንዳለ ተረድቻለሁ። 6ስለዚህ
በእጆቼ መጫን የተቀበልኸውን በአንተ ውስጥ
ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድ
ታቀጣጥል አሳስብሃለሁ፤ 7እግዚአብሔር የኀይልና
የፍቅር፣ ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ
የፍርሀት መንፈስ አልሰጠንምና።

8እንግዲህ፣ ስለ ጌታችን ለመመስከር ወይም
የእርሱ እስረኛ በሆንሁት በእኔ አትፈር፤
ነገር ግን በእግዚአብሔር ኀይል ስለ ወንጌል ከእኔ
ጋር መከራን ተቀበል፤ 9እኛ ስላደረግነው
አንዳች ነገር ሳይሆን ከዕቅዱና ከጸጋው
የተነሣ ያዳነን ወደ ቅዱስ ሕይወትም የጠራን
እርሱ ነው። ይህም ጸጋ ከዘላለም ዘመናት
በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን፤ 10አሁን
ግን ሞትን ደምስሶ በወንጌል አ
ማካይነት ሕይ ወትንና ኢመዋቲነትን
ወደ ብርሃን ባወ ጣው በመድኀኒታችን
በክርስቶስ ኢየሱስ መምጣት ተገልጦአል።
11እኔም ለዚህ ወን ጌል የምሥራች
ነጋሪና ሐዋርያ፣ አስተማሪም ሆኜ ተሾምሁ።
12መከራን የምቀበለውም ለዚሁ ነው፤
ሆኖም ያመንሁትን እርሱን ስለማውቅ
አላፍርበትም፤ የሰጠሁትንም ዐደራ እስከዚያች
ቀን ድረስ መጠበቅ እንደሚ ችል
ተረድቻለሁ።

13ከእኔ የሰማኸውን በክርስቶስ ኢየሱስ
ባለ እምነትና ፍቅር፣ የጤናማ ትምህርት
ምሳሌ አድርገህ ያዝ። 14የተሰጠህን መልካ
ሙን ዐደራ፣ በእኛ ውስጥ በሚኖረው
በመንፈስ ቅዱስ ጠብቅ።

15በእስያ አውራጃ ያሉት ሁሉ እንደ
ተዉኝ ታውቃለህ፤ ከእነርሱም መካከል ፊሎ

1፥1 1ቆሮ1፥1፤
2ቆሮ1፥1፤ኤፌ3፥6፤
1ጢሞ6፥19፤ቲቶ1፥2
1፥2 ሐሥ16፥1፤
ሮሜ1፥7፤1ጢሞ1፥2
1፥3 ሐሥ23፥1፤
ሮሜ1፥8፡10
1፥4 ሐሥ20፥37፤
2ጢሞ4፥9
1፥5 ሐሥ16፥1፤ 1ጢ
ሞ1፥5፤2ጢሞ3፥15
1፥6 ሐሥ6፥6፤1ጢሞ4፥14
1፥7 ኢሳ11፥2፤
ኤር42፥11፤
ሮሜ8፥15፤1ቆሮ16፥10፡
11፤ 1ጢሞ4፥12፤
ዕብ2፥15
1፥8 ቀኑ12፡16፤
ማር8፥38፤ኤፌ3፥1፤2
ጢሞ2፥3፡9፤4፥5
1፥9 ሮሜ8፥28፤
11፥14፤ኤፌ2፥9
1፥10 1ቆሮ15፥26፡
54፤ኤፌ1፥9፤
1ጢሞ6፥14
1፥11 ቀኑ8፤ሐሥ9፥15፤
1ጢሞ2፥7
1፥12 ቀኑ8፡14፡16፡
18፤ማር8፥38፤
1ቆሮ8፥38፤1ቆሮ1፥8፤
1ጢሞ6፥20፤
2ጢሞ4፥8
1፥13 ሮሜ6፥17፤
1ተሰ1፥3፤
1ጢሞ1፥10፡14፤
2ጢሞ2፥2፤ቲቶ1፥9
1፥14 ቀኑ12፤ሮሜ8፥9
1፥15 ሐሥ2፥9፤
2ጢሞ4፥19
1፥18 ቀኑ12፤
ሐሥ18፥19፤ዕብ6፥10
2፥1 ኤፌ6፥10፤ 1ጢ
ሞ1፥2
2፥2 1ጢሞ6፥12፤
2ጢሞ1፥13 2፥3
ቀኑ9፤
1ጢሞ1፥18፤
2ጢሞ1፥8፤4፥5
2፥5 1ቆሮ9፥25
2፥6 1ቆሮ9፥10
2፥8 ማቴ1፥1፤
ሐሥ2፥24፤ሮሜ2፥16፤
16፥25
2፥9 ሐሥ9፥16፤
21፥33፤ዕብ4፥12
2፥10 2ቆሮ1፥6፤
4፥17፤ቈላ1፥24፤
ቲቶ1፥1፤1ጴጥ5፥10
2፥11 ሮሜ6፥2-11፤
1ጢሞ1፥15
2፥12 ማቴ10፥33፤
ሮሜ8፥17፤1ጴጥ4፥13

ኀስና ሄርሞጌኔስ ይገኛሉ።

16ጌታ ለሄኔሲፎሩ ቤተ ሰዎች ምሕ
ረትን ይስጥ፤ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ቸር
ነት አድርጎልኛል፤ በታሰርሁበትም ሰንሰ
ለት አላፈረም። 17እንዲያውም ወደ ሮም
በመጣ ጊዜ ፈልጎ ፈልጎ አገኘኝ። 18በዚ
ያች ቀን ምሕረትን ከጌታ ያገኝ ዘንድ
ጌታ ይስጠው፤ በኤፌሶንም የቱን ያህል
እንዳገ ለገለኝ አንተ በሚገባ ታውቃለህ።

2 እንግዲህ ልጄ ሆይ፤ አንተ በክርስቶስ
ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ። 2በብዙ
ምስክር ፊት ከእኔ የሰማኸውን፣ ሌሎችን
ለማስተማር ብቃት ላላቸው ለታመኑ
ሰዎች ዐደራ ስጥ። 3እንደ ክርስቶስ ኢየ
ሱስ በጎ ወታደር፣ ከእኛ ጋር መከራን
ተቀበል። 4በውትድርና የሚያገለግል ሰው አዛ
ዡን ለማስደሰት ይጥራል እንጂ በሌላ ሥራ
ራሱን አያጠላልፍም። 5እንደዚሁም በውድድር
የሚሳተፍ ሰው፣ የውድድሩን ሕግ ጠብቆ
ካልተወዳደረ የድሉን አክሊል አያገኝም።
6ትጉህ ገበሬም ከሰብሉ ለመጠቀም የመ
ጀመሪያው ሊሆን ይገባዋል። 7እኔ
የምለውን ልብ በል፤ ጌታ በሁሉም ነገር
ማስተዋልን ይሰጥሃልና።

8ከሙታን የተነሣውን፣ ከዳዊት ዘርም የሆ
ነውን ኢየሱስ ክርስቶስን አስብ፤ የእኔም
ወንጌል ይኸው ነው፤ 9ለዚህም እንደ
ወንጀለኛ እስከ መታሰር ድረስ መከራን
እየተቀበልሁ ነው፤ የእግዚአብሔር ቃል ግን
አይታሰርም። 10ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ
ያለውን መዳን ከዘላለም ክብር ጋር እነር
ሱም ያገኙ ዘንድ፣ ለተመረጡት ስል ሁሉ
ንም በመታገሥ እጸናለሁ።

11እንዲህ የሚለው ቃል የታመነ ነው፤
ከእርሱ ጋር ከሞትን፣
ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንኖራለን።
12ብንጸና፣
ከእርሱ ጋር ደግሞ እንነግሣለን።
ብንክደው፣
እርሱ ደግሞ ይክደናል፤
13ታማኞች ሆነን ባንገ
እርሱ ታማኝ እንደ ሆነ ይኖራል፤
ራሱን መካድ አይችልምና።

### እግዚአብሔር የተቀበለው ሠራተኛ

14ስለ እነዚህ ነገሮች ማሳሰብህን አትተው፤
በቃላት እንዳይነታረኩ በእግዚአብሔር ፊት
አስጠንቅቃቸው፤ ይህ ጥቅም የሌለው፣

2፥13 ሮሜ3፥3፤ 1ቆሮ1፥9 2፥14 ቀኑ23፤ 1ጢሞ1፥4፤6፥4፤
ቲቶ3፥9

የሚሰሙትንም የሚያፈርስ ነውና። 15እንደ
ማያፍርና የእውነትን ቃል በትክክል እን
ደሚያስረዳ የተመሠከረለት ሠራተኛ፣ ራስ
ህን በእግዚአብሔር ፊት ልታቀርብ ትጋ።
16እግዚአብሔርን ከማያስከብር ከንቱ ልፍ
ለፋ ራቅ፤ በዚህ ነገር የተጠመዱ ሰዎች ከእ
ግዚአብሔር እየራቁ ይሄዳሉና። 17ትምህ
ርታቸው እንደማይሽር ቊስል ይሠራጫል፤
ከእነዚህም መካከል ሄሜኔዎስና ፊሊጦስ
ይገኛሉ፤ 18እነዚህም ከእውነት ርቀው የሚ
ባዝኑ ናቸው። እነርሱም ትንሣኤ ሙታን
ከዚህ በፊት ሆኖአል እያሉ የአንዳንዶቹን
እምነት ይገለብጣሉ። 19ይሁን እንጂ፣
“ጌታ የእርሱ የሆኑትን ያውቃል፤” ደግሞም፣
“የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ከክፋት
ይራቅ” የሚል ማኅተም ያለበት የማይ
ነቃነቅ የእግዚአብሔር መሠረት ቆሞአል።
20በአንድ ትልቅ ቤት ውስጥ የወርቅና
የብር ዕቃ ብቻ ሳይሆን፣ የዕንጨትና
የሸክላ
ዕቃም ይኖራል፤ ከእነዚህ አንዳንዶቹ
ለክበረ፣ ሌሎቹም ላልከበረ አገልግሎት
ይውላሉ። 21እንግዲህ ማንም ራሱን
ከእነዚህ ከጠቀስ ኋቸው ነገሮች ቢያነጻ
ለክቡር አገልግሎት የሚውል፣ የተቀደሰ፣
ለጌታው የሚጠቅም፣ ለመልካም ሥራም
ሁሉ የተሰናዳ ዕቃ ይሆናል።
22ከወጣትነት ክፉ ምኞት ሽሽ፤ በንጹሕ
ልብ ጌታን ከሚጠሩት ጋርም ጽድቅን፣
እምነትን፣ ፍቅርንና ሰላምን ተከታተል።
23ከማይረባና ትርጒም የለሽ ከሆነ ክርክር
ራቅ፤ ምክንያቱም እነዚህ ጠብን እንደሚያ
ስከትሉ ታውቃለህ። 24የጌታም አገልጋይ
ሊጣላ አይገባውም፤ ይልቁን ለሰው ሁሉ
ገር፣ ለማስተማር ብቃት ያለው፣ ትዕግሥ
ተኛም መሆን ይገባዋል፤ 25እውነትን ወደ
ማወቅ ይደርሱ ዘንድ፣ እግዚአብሔር ንስሓን
እንደ ሚሰጣቸው ተስፋ በማድረግ የሚቃ
ወሙትን በየዋህነት የሚያቃና መሆን ይኖ
ርበታል፤ 26ይኸውም ወደ አእምሮአቸው
ይመለሳሉ፤ ፈቃዱን ሊያስፈጽማቸው ምር
ኮኛ አድርጎ ከያዛቸው ከዲያብሎስ ወጥመ
ድም ያመልጣሉ በማለት ነው።

## ክሕደት በመጨረሻዎቹ ቀናት

3 ነገር ግን በመጨረሻው ዘመን የሚያስ
ጨንቅ ጊዜ እንደሚመጣ ይህን ዕወቅ።
2ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉ፤ ገን
ዘብን የሚወዱ፣ ትምክሕተኞች፣ ትዕቢተ
ኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ ለወላጆቻቸው የማይ
ታዘዙ፣ የማያመሰግኑ፣ ቅድስና የሌላቸው፣
3ፍቅር የሌላቸው፣ ለዕርቅ የማይሸነፉ፣ ሐሜ
ተኞች፣ ራሳቸውን የማይገዙ፣ ጨካኞች፣

2፥15 ኤፌ1፥13፤ ቈላ1፥5፤ያዕ1፥18
2፥16 1ጢሞ6፥20፤ ቲቶ3፥9
2፥17 1ጢሞ1፥20
2፥18 2ተሰ2፥2፤ 1ጢሞ1፥19፤6፥21
2፥19 ዘፀ33፥12፤ ዘኍ16፥5፤ኢሳ28፥16፤ ዮሐ10፥14፤1ቆሮ1፥2፤ 8፥3፤ገላ4፥9
2፥20 ሮሜ9፥21
2፥21 2ቆሮ9፥8፤ ኤፌ2፥10፤2ጢሞ3፥17
2፥22 ሐሥ2፥21፤ 1ጢሞ1፥5፡14
2፥23 ቀኁ14
2፥24 1ጢሞ3፥2፡3
2፥25 1ጢሞ2፥4
2፥26 1ጢሞ3፥7
3፥1 1ጢሞ4፥1፤ 2ጴጥ3፥3
3፥2 ሮሜ1፥30፤ 1ጢሞ3፥3፤ 2ጴጥ2፥10-12
3፥4 መዝ25፥3፤ 1ጢሞ3፥6፤6፥4
3፥5 ሮሜ16፥17፤ 1ጢሞ2፥2
3፥6 ይሁ 4
3፥7 1ጢሞ2፥4
3፥8 ዘፀ7፥11፤ ሐሥ13፥8፤1ጢሞ6፥5
3፥9 ዘፀ7፥12፤ 8፥18፤9፥11
3፥10 1ጢሞ4፥6
3፥11 መዝ34፥19፤ ሐሥ13፥14፡51፤ 14፥6፤ሮሜ15፥31፤ 2ቆሮ11፥23-27
3፥12 ሐ15፥20፤ ሐሥ14፥22
3፥13 ማር13፥5፤ 2ጢሞ2፥16
3፥14 2ጢሞ1፥13
3፥15 ዘዳ4፥6፤ መዝ119፥98፡99፤ ዮሐ5፥39፤2ጢሞ1፥5
3፥16 ዘዳ29፥29፤ ሮሜ4፥23፡24፤ 2ጴጥ1፥20
3፥17 1ጢሞ6፥11፤ 2ጢሞ2፥21
4፥1 ቀኁ8፤ ሐሥ10፥42፤ 1ጢሞ5፥21፤6፥13፡14
4፥2 ገላ6፥6፤ 1ጢሞ4፥13፤5፥20፤ ቲቶ1፥13፤2፥15
4፥3 ኢሳ30፥10፤ 1ጢሞ1፥10

መልካም የሆነውን የማይወዱ፣ 4ከዳተኞች፣
ችኩሎች፣ በከንቱ በትዕቢት የተወጠሩ፣
ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆ
ናሉና። 5ሃይማኖታዊ መልክ አላቸው፤
ኀይሉን ግን ክደዋል። ከእነዚህ ራቅ።
6እነርሱም በየቤቱ ሾልከው እየገቡ የኀጢ
አት ብዛት የተጫናቸውን፣ በተለያየ ክፉ
ምኞት ውስጥ ገብተው የሚዋልሉ
መንፈሰ ደካማ ሴቶችን የሚያጠምዱ
ናቸው፤ 7እንደ ነዚህ ያሉ ሴቶች ሁልጊዜ
ይማራሉ፤ ነገር ግን እውነትን ወደ ማወቅ
ፈጽሞ ሊደ ርሱ አይችሉም። 8ኢያኔስና
ኢያንበሬስ ሙሴን እንደ ተቃወሙት፣
እነዚህም እአ ምሮአቸው የጠፋባቸውና
ከእምነት የተ ጣሉ ሰዎች ደግሞ እውነትን
ይቃወማሉ። 9ይሁን እንጂ አይሳካላቸውም፤
ምክንያቱም የእነዚያ ሰዎች ሞኝነት እንደ
ተገለጠ ሁሉ፣ የእነዚህም ለሁሉ ግል
ጽ ይሆናል።

## ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሰጠው ዐደራ

10አንተ ግን ትምህርቴን፣ አካሄዴን፣
ዐላማዬን፣ እምነቴን፣ ትዕግሥቴን፣ ፍቅሬ
ንና፣ ጽናቴን ሁሉ ታውቃለህ፤ 11ስደቴንና
መከራዬን፣ በአንጾኪያና በኢቆንዮን፣ በልስጥ
ራንም የደረሰብኝን ሁሉ፣ የታገሥሁትንም
ስደት ታውቃለህ፤ ጌታ ግን ከእነዚህ ሁሉ
አዳነኝ። 12በእርግጥም በክርስቶስ ኢየሱስ
በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት መኖር
የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ። 13ክፉዎችና አታላ
ዮች ግን እየሳቱና እያሳቱ፣ በክፋትም ላይ
ክፋት እየጨመሩ ይሄዳሉ። 14አንተ ግን
በተማርኸውና በተረዳኸው ጸና፤ ይህን
ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና፤ 15ከሕ
ፃንነትህም ጀምረህ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ
በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰ
ጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን
ዐውቀሃል። 16ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ
የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤
ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናት በጽድ
ቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ፤ 17ይኸ
ውም የእግዚአብሔር ሰው ለመልካም ሥራ
ሁሉ ብቁ ሆኖ እንዲገ ነው።

4 በእግዚአብሔር ፊት እንዲሁም በሕያዋ
ንና በሙታን ሊፈርድ ባለው በክር
ስቶስ ኢየሱስ ፊት፣ መገለጡንና መንግሥቱን
በማሰብ ይህን ዐደራ እልሃለሁ፤ 2ቃሉን
ስበክ፤ ጊዜው ቢመችም ባይመችም ዝግጁ
ሁን፤ በታላቅ ትዕግሥትና በማስተማር
አቅና፤ ገሥጽ፤ አበረታታም። 3ምክንያቱም
ሰዎች ትክክለኛ የሆነውን ትምህርት የማ
ይቀበሉበት ጊዜ ይመጣል፤ ከዚህ ይልቅ
ለገዛ ምኞቶቻቸው የሚስማማውን፣ የሚያ
ሳክክ ጆሮአቸው ሊሰማ የሚፈልገውን እንዲ

ነግሯቸው በዙሪያቸው ብዙ አስተማሪዎ
ችን ይሰበስባሉ። 4እውነትን ከመስማት
ጆሮአቸውን ይመልሳሉ፤ ወደ ተረትም ዘወር
ይላሉ። 5አንተ ግን በሁኔታዎች ሁሉ የረ
ጋህ ሁን፤ መከራን ታገሥ፤ የወንጌል ሰባኪ
ን ተግባር አከናውን፤ አገልግሎትህን ፈ
ጽም።

6እኔ እንደ መጠጥ ቊርባን መሥዋዕት
ለመፍሰስ ተቃርቤአለሁ፤ ተለይቼ የምሄድ
በት ጊዜ ደርሶአል። 7መልካሙን ገድል
ተጋድያለሁ፤ ሩጫውን ጨርሻለሁ፤ ሃይ
ማኖትንም ጠብቄአለሁ። 8ወደ ፊት የጽ
ድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፤ ይህንም ጻድቅ
ፈራጅ የሆነው ጌታ በዚያ ቀን ለእኔ ይሰጠ
ኛል፤ ደግሞም ለእኔ ብቻ ሳይሆን፣ የእርሱን
መገለጥ ለናፈቁ ሁሉ ነው።

## የጳውሎስ ማሳሰቢያ

9በቶሎ ወደ እኔ ለመምጣት የተቻለህን
ሁሉ አድርግ፤ 10ዴማስ ይህን ዓለም ወዶ፣
ትቶኝ ወደ ተሰሎንቄ ሄዶአልና። ቄርቂስ
ወደ ገላትያ፣ ቲቶ ወደ ድልማጥያ ሄደዋል፤
11ከእኔ ጋር ያለው ሉቃስ ብቻ ነው። ማርቆስ
በአገልግሎቱ ስለሚረዳኝ ከአንተ ጋር ይዘኸው
ና። 12ቲኪቆስን ወደ ኤፌሶን ልኬዋለሁ።
13ስትመጣ በጢሮአዳ ከአክርጳ ዘንድ የተው
ሁትን በርኖስ፣ ጥቅልል መጻሕፍቱን በተለ
ይም የብራና መጻሕፍቱን አምጣልኝ።
14አንጥረኛው እስክንድሮስ ብዙ ጒዳት
አድርሶብኛል፤ ጌታ ግን የእጁን ይሰጠዋል።

4፥4 1ጢሞ1፥4
4፥5 ሐሥ21፥8፤ ኤፌ4፥11፤ 2ጢሞ1፥8፤2፥3
4፥6 ዘኍ15፥1-12፤ 28፥7፡24፤ፊል1፥23፤ 2፥17
4፥7 ሐሥ20፥24፤ 1ቆሮ9፥24፤1ጢሞ1፥18
4፥8 1ቆሮ9፥25፤ ቈላ1፥5፤1ጢሞ6፥14፤ 2ጢሞ1፥12፤ 1ጴጥ1፥4
4፥9 ቊ21፤ ቲቶ3፥12
4፥10 ሐሥ16፥6፤ 17፥1፤2ቆሮ2፥13፤ ቈላ4፥14፤ፊሞ24፤ 1ዮሐ2፥15
4፥11 ሐሥ12፥12፤ ቈላ4፥14፤ፊሞ24፤ 2ጢሞ1፥15
4፥12 ሐሥ18፥19፤20፥4
4፥13 ሐሥ16፥8
4፥14 መዝ28፥4፤ 109፥20፤ሐሥ19፥33፤ ሮሜ2፥6፤12፥19፤ 1ጢሞ1፥20
4፥16 ሐሥ7፥60
4፥17 1ሳሙ17፥37፤ መዝ22፥21፤ዳን6፥22፤ሐሥ9፥15፤23፥11፤ 1ቆሮ15፥32፤ፊል4፥13
4፥18 ቊ1፤ መዝ121፥7፤ ሮሜ11፥36፤ 2ጴጥ2፥9

15መልእክታችንን እጅግ ተቃውሞአልና፣
አንተም ከእርሱ ተጠንቀቅ።
16በተከሰስሁበት ነገር የመጀመሪያ መከላ
ከያዬን ሳቀርብ ማንም ሊያግዘኝ አልመ
ጣም፤ ነገር ግን ሁሉ ትተውኝ ሄዱ። ይህንም
አይቈጠርባቸው። 17ነገር ግን መልእክቱ በእኔ
አማካይነት በሙላት እንዲሰበክና አሕዛብ
ሁሉ እንዲሰሙት ጌታ በአጠገቤ ቆሞ አበረ
ታኝ፤ ከአንበሳም መንጋጋ አዳነኝ። 18ጌታ
ከክፉ ነገር ሁሉ ያድነኛል፤ ወደ ሰማያዊው
መንግሥቱም በሰላም ያደርሰኛል፤ ለእርሱ
ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤
አሜን።

## የስንብት ሰላምታ

19ለጵርስቅላና[ሀ] ለአቂላ፣ ለሄኔሲፎሩም ቤተ
ሰዎች ሰላምታ አቅርብልኝ። 20ኤርስጦስ በቆ
ሮንቶስ ቀርቶአል፤ ጥሮፊሞስም ስለ ታመመ
በሚሊጢን ትቼዋለሁ። 21ከክረምት በፊት
እዚህ ለመምጣት የተቻለህን አድርግ። ኤው
ግሎስና ጱዴስ እንዲሁም ሊኖስ፣ ቅላውዲ
ያና ወንድሞች ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡልሃል።
22ጌታ ከመንፈስህ ጋር ይሁን። ጸጋ ከእና
ንተ ጋር ይሁን።

4፥19 ሐሥ18፥2፤ 2ጢሞ1፥16 4፥20 ሐሥ19፥22፤ 20፥4፡ 15፡17፤21-29 4፥21 ቊ9፤ ቲቶ3፥12 4፥22 ገላ6፥18፤ ቈላ4፥18

[ሀ] 19 ግሪኩ ጵርስቃ ይላል።

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት
# ወደ ቲቶ

1 የእግዚአብሔርን ምርጦች እምነትና ወደ
እውነተኛ መንፈሳዊነት የሚመራውን
የእውነት ዕውቀት ለማሳደግ የእግዚአብሔር
ባሪያና የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆ
ነው ጳውሎስ፤ 2እምነቱና ዕውቀቱ የተመ
ሠረቱትም የማይዋሸው አምላክ ከዘመናት
በፊት በገባው የዘላለም ሕይወት ተስፋ ላይ
ነው፡፡ 3እርሱ በወሰነውም ጊዜ በአዳኛ
ችን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ለእኔ ዐደራ በተ
ሰጧ ስብከት በኩል ቃሉን ይፋ አደረገ፡፡
4የጋራችን በሆነው እውነተኛ እምነት
ልጄ ለሆነው ለቲቶ፤
ከእግዚአብሔር አብ፣ ከአዳኛችንም
ከክርስቶስ ኢየሱስ ጸጋና ሰላም ይሁን፡፡

### *ቲቶ በቀርጤስ የነበረው ኀላፊነት*

5አንተን በቀርጤስ የተውሁህ ገና
ያልተስተካከለውን ነገር እንድታስተካ
ክልና ባዘዝሁህ መሠረት በየከተማው ሽማ
ግሌዎችን እንድትሾም ነው፡፡ 6ሽማግሌ
ነቀፋ የሌለበት፣ የአንዲት ሚስት ባል፣
ልጆቹም አማኞችና በመዳራት ወይም ባለ
መታዘዝ ስማቸው የማይነሣ ይሁን፡፡ 7ኤጲስ
ቆጶስ የእግዚአብሔር ሥራ ባለ ዐደራ እንደ
መሆኑ የማይነቀፍ ሊሆን ይገባል፤ ይኸውም
ትምክሕተኛ፣ ግልፍተኛ፣ ሰካራም፣ ጨቅ
ጫቃና ተገቢ ባልሆነ መንገድ ለጥቅም
የሚሮጥ ሊሆን አይገባም፡፡ 8ከዚህ ይልቅ
እንግዳ ተቀባይ፣ በጎ የሆነውን ነገር የሚ
ወድ፣ ራሱን የሚገዛ፣ ቅን፣ ቅዱስና ጠን
ቃቃ ሊሆን ይገባል፡፡ 9ሌሎችን ትክክል በሆ
ነው ትምህርት እንዲያበረታታና ይህንኑ
ትምህርት የሚቃወሙትን ይወቅስ ዘንድ
እንደ ተማረው በታመነ ቃል የሚጸና መሆን
አለበት፡፡
10ዐመፀኞች፣ ለፍላፊዎችና አታላዮች
የሆኑ ብዙ ሰዎች አሉና፤ በተለይም እነዚህ
ከተገረዙት ወገን ናቸው፡፡ 11እነዚህን ዝም
ማሰኘት ተገቢ ነው፤ ምክንያቱም ትክክል
ባልሆነ መንገድ ጥቅም ለማግኘት ሲሉ
ማስተማር የማይገባቸውን ነገር በማስተማር
ቤተ ሰብን ሁሉ በመበከል ላይ ናቸውና፡፡
12ከራሳቸው ነቢያት አንዱ ስለ እነርሱ
ሲናገር፣ "የቀርጤስ ሰዎች ዘወትር ውሸታ
ሞች፣ ክፉ አውሬዎችና ሰነፍ ሆዳሞች
ናቸው" ብሎአል፡፡ 13ይህ ምስክርነት እው
ነት ነው፤ ስለዚህ አጥብቀህ ገሥጻቸው፤ ይኸ
ውም ትክክለኛ እምነት እንዲኖራቸውና
14የአይሁድን ተረት ወይም ከእውነት የራ
ቁትን ሰዎች ትእዛዝ እንዳያዳምጡ ነው፡፡
15 ለንጹሓን ሁሉም ነገር ንጹሕ ነው፤
ለርኩሳንና ለማያምኑ ግን ንጹሕ የሆነ ምንም
ነገር የለም፤ እንዲያውም አእምሮአቸውና
ኅሊናቸው የረከሰ ነው፡፡ 16እግዚአብሔርን
እናውቃለን ይላሉ፤ ዳሩ ግን በተግባራቸው
ይክዱታል፤ አስጸያፊዎች፣ የማይታዘዙና
ለበጎ ሥራ የማይበቁ ናቸው፡፡

2 አንተ ግን ከትክክለኛው ትምህርት
ጋር ተስማሚ የሆነውን አስተምር፡፡
2አረ ጋውያን ጭምቶች፣ የተከበሩ፣ ራ
ሳቸውን የሚገዙና በእምነት፣ በፍቅርና
በትዕግሥት ጤናማነት ያላቸው እንዲሆኑ
ምከራቸው፡፡
3እንዲሁም አሮጊቶች በአኗኗራቸው
የተከበሩ እንዲሆኑ፣ በጎ የሆነውን የሚያስ
ተምሩ እንጂ የሰው ስም የሚያጠፉ ወይም
በወይን ጠጅ ሱስ የተጠመዱ እንዳይ
ሆኑ አስተምራቸው፤ 4እንዲህ ከሆኑ፣
ወጣት ሴቶች ባሎቻቸውንና ልጆቻቸውን
እንዲወዱ ማስተማር ይችላሉ፤ 5የእግዚአብሔር
ቃል በማንም ዘንድ እንዳይሰደብ ራሳቸ
ውን የሚገዙና ንጹሓን፣ በቤት ውስጥ
በሥራ የተጠመዱ፣ ቸሮች፣ ለባሎቻቸው
የሚገዙ እንዲሆኑ ያስተምሯቸው፡፡
6እንዲሁም ወጣት ወንዶች ራሳቸውን
እንዲገዙ ምከራቸው፡፡ 7በማንኛውም ነገር
መልካም የሆነውን ነገር በማድረግ ራስህን
አርአያ አድርገህ አቅርብላቸው፡፡ በምታስ
ተምራቸውም ትምህርት ጭምተኛነትን፣ ቁም
ነገረኛነትን፣ 8የማይነቀፍ ጤናማ አነጋገር
አሳይ፤ ይኸውም ተቃዋሚ ስለ እኛ የሚናገረ
ውን መጥፎ ነገር በማጣት እንዲያፍር
ነው፡፡
9ባሮች ለጌቶቻቸው በማንኛውም ነገር
እንዲገዙ፣ ደስ እንዲያሰኟቸው፣ የአጸፋ
ቃል እንዳይመልሱላቸው አስተምር፤ 10አይስ
ረቁ፤ ይኸውም በሁሉም መንገድ የአዳኛችን
የእግዚአብሔር ትምህርት ይወደድ ዘንድ
ፍጹም ታማኝ መሆናቸውን እንዲያስመሰክሩ
ነው፡፡
11ድነት የሚገኝበት የእግዚአብሔር ጸጋ
ለሰዎች ሁሉ ተገልጦአልና፤ 12ይህም ጸጋ
ኃጢአት መኖርንና ዓለማዊ ምኞትን ክደን፣
በአሁኑ ዘመን ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ፣
በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት እንድንኖር

1፥1 ሮሜ1፥1፤
1ቆሮ 1፥1፤
1ጢሞ2፥2፡4፤ያዕ1፥1
1፥2 ዘኍ23፥19፤
2ጠሞ1፥1፡9፤
ቲቶ 3፥7፤ዕብ6፥18
1፥3ሉቃ1፥47፤
2ቆሮ 1፥1፡1ሞ1፥11፤
2፥6፤6፥15፤
2ጢሞ1፥10
1፥4 ሮሜ1፥7፤
2ቆሮ 2፥13፤
1ጢሞ1፥2
1፥5 ሐሥ11፥30፤
27፥7
1፥6 1ተሰ3፥13፤
1ጢሞ3፥2
1፥7 1ቆሮ4፥1፤
1ጢሞ3፥1፡3፡8
1፥8 ሮሜ12፥13፤
2ጢሞ3፥3፤ቲቶ2፥2፡
5፡6፡12
1፥9 1ቆሮ16፥13፤
1ጢሞ1፥10፡19፤
2ጢሞ1፥13፤3፥14
1፥10 ሐሥ10፥45፤
11፥2፤ 1ጢሞ1፥6
1፥11 1ጢሞ5፥13
1፥12 ሐሥ2፥11፤ 17፥28
1፥13 1ጢሞ5፥20፤
ቲቶ2፥2
1፥14 ቈላ2፥22፤
1ጢሞ1፥4፤2ጠሞ4፥4
1፥15 መዝ18፥26፤
ማቴ15፥10፡11፤
ማር 14-19፤
ሐሥ 10፥9-16፡28፤
ሮሜ14፥14፡23፤
ቈላ 2፥20-22፤
1ጢሞ 6፥5
1፥16 ኤር5፥2፤12፥2፤
ሆሴ8፥2፡3፤1ዮሐ2፥4
2፥1 1ጢሞ1፥10
2፥2 ቍ5፡6፡12፤
1ጢሞ3፥2፤5፥1፤ቲቶ1፥1፡
8፡13
2፥3 1ጢሞ3፥8፡11
2፥4 1ጢሞ5፥2
2፥5 ቍ2፡6፡12፤
ኤፌ 5፥22፤
1ጢሞ 5፥14፤
6፥1፤ቲቶ1፥8፤ዕብ 4፥12
2፥6 ቍ2፥5፡12፤
1ጢሞ5፥1፤ቲቶ1፥8
2፥7 ቍ14፤1ጢሞ 4፥12
2፥8 1ጴጥ2፥12
2፥9 ኤፌ6፥5
2፥10 ማቴ5፥16፤
ሉቃ1፥47
2፥11 ሮሜ3፥24፤
1ጢሞ 2፥4፤
2ጢሞ1፥10

2፥12 ቍ2፡5፡6፤2ጢሞ3፥12፤ቲቶ 1፥8፤3፥3

ያስተምረናል፤ 13ይህም የተባረከ ተስፋችን
የሆነውን የታላቁን የአምላካችንንና የአዳኛ
ችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ
በመጠባበቅ ነው፤ 14እርሱም ከክፋት ሊቤዠን
መልካም የሆነውን ለማድረግ የሚተጋውን
የእርሱ የሆነውን ሕዝብ ለራሱ ያነጻ ዘንድ
ራሱን ስለ እኛ ሰጥቶአል።
15እንግዲህ ልታስተምር የሚገባህ እነዚ
ህን ነው፤ በሙሉ ሥልጣን ምከር፤ ገሥ
ጽም፤ ማንም አይናቅህ።

## በጎ የሆነውን ማድረግ

3 ሰዎች ለገዦችና ለባለ ሥልጣናት እን
ዲገዙ፣ እንዲታዘዙና መልካም የሆነ
ውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ እንዲሆኑ አሳስ
ባቸው። 2እንዲሁም በማንም ላይ ክፉ እንዳ
ይናገሩ፣ ሰላማውያን እንዲሆኑ፣ ለሰዎችም
ሁሉ ከልብ የመነጨ ትሕትና እንዲያሳዩ
አስገንዝባቸው።
3ቀደም ሲል እኛ ራሳችን ማስተዋል
የጐደለን፣ የማንታዘዝ፣ የተታለልን፣ ለተለ
ያየ ምኞትና ምቾት ባሪያ ሆነን የተገዛን
ነበርን፤ እየተጣላንና እርስ በርስ እየተጠላ
ላን በክፋትና በምቀኝነት እንኖር ነበር።
4ነገር ግን የአዳኛችን የእግዚአብሔር ቸርነትና
ፍቅር በተገለጠ ጊዜ፣ 5ስላደረግነው የጽ
ድቅ ሥራ ሳይሆን፣ ከምሕረቱ የተነሣ አዳ
ነን። ያዳነንም ዳግም ልደት በሆነው
መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ
ነው፤ 6ይህንም መንፈስ እግዚአብሔር በአዳ
ኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእኛ ላይ
አትረፍርፎ አፈሰሰው፤ 7ይኸውም በጸ
ጋው ጸድቀን የዘላለምን ሕይወት ተስፋ
ይዘን ወራሾች እንድንሆን ነው። 8ይህም

2፥13 1ቆሮ1፥7፤
1ጢሞ6፥14፤2ጴጥ1፥1
2፥14 ቀኍ7፤
ዘፀ19፥5፤ዘዳ4፥20፤
14፥2፤መዝ135፥4፤
ምሳ16፥7፤ሚል3፥17፤
ማቴ 1፥21፤5፥16፤
20፥28፤2ቆሮ8፥21፤
ኤፌ 2፥10፤ቲቶ3፥1፤
8፡14፤ዕብ1፥3፤
1ጴጥ2፥9፡12፡15፤3፥1
3፤1ዮሐ1፥7
3፥1 ሮሜ13፥1፤
2ጢሞ2፥21፤
ቲቶ2፥14፤
1ጴጥ2፥13፡14
3፥2 ኤፌ4፥31
3፥3 ኤፌ2፥2
3፥4 ሉቃ1፥47፤
ኤፌ2፥7፤ቲቶ2፥11
3፥5 ሐሥ22፥16፤
ሮሜ11፥14፤12፥2፤
ኤፌ2፥9፤1ጴጥ1፥3
3፥6 ሮሜ5፥5
3፥7 ማቴ25፥46፤
ሮሜ3፥24፤8፥17፡
24፤ቲቶ1፥2
3፥8 1ጢሞ1፥15፤
ቲቶ2፥14
3፥9 2ጢሞ2፥14፡
16፤ቲቶ1፥10-16
3፥10 ሮሜ16፥17
3፥12 ሐሥ20፥4፤
2ጢሞ4፥9፡21
3፥13 ሐሥ18፥24
3፥14 ቲቶ2፥14
3፥15 ቈላ4፥18፤
1ጢሞ1፥2

የታመነ ቃል ነው። በእግዚአብሔር ያመኑቱ
መልካሙን ነገር ለማድረግ ራሳቸውን አሳ
ልፈው ይሰጡ ዘንድ እነዚህን ነገሮች አስረ
ግጠህ እንድትናገር እፈልጋለሁ። ይህ
መልካምና ለማንኛውም ሰው የሚጠቅም
ነው።
9ነገር ግን ከንቱ ከሆነ ክርክርና ከትው
ልድ ሐረግ ሖጠራ፣ ከጭቅጭቅና ስለ ሕግ
ከሚነሣ ጠብ ራቅ፤ ይህ ዋጋ ቢስና ከንቱ
ነውና። 10መከፋፈል የሚያመጣን ሰው አንድ
ጊዜ ምከረው፤ ለሁለተኛ ጊዜ አስጠንቅ
ቀው፤ ከዚያ ካለፈ ከእርሱ ጋር አንዳች ነገር
አይኑርህ። 11እንዲህ ዐይነቱ ሰው የሳተና
ኀጢአተኛ ነው፤ ራሱንም እንደሚከጻንን
ዕወቅ።

## የመጨረሻ ምክር

12አርጢሞንን ወይም ቲኪቆስን ወደ
አንተ እንደ ላክሁ እኔ ወዳለሁበት ወደ
ኒቆጵልዮን ለመምጣት የተቻለህን ሁሉ
አድርግ፤ ክረምቱን በዚያ ላሳልፍ ወስኛ
ለሁ። 13ሕግ ዐዋቂውን ዜማስንና አጵሎ
ስን በግሣዟቸው ለመርዳት የተቻለህን
ሁሉ አድርግ፤ የሚያስፈልጋቸውንም ሁሉ
አሟ ላላቸው። 14ከእኛ ወገን ለሆኑት ለዕ
ለት የሚያስፈልጋቸውን እንዲያገኙና
ኑሮአቸ ውም ፍሬ የሌለው እንዳይሆን
ለመልካም ሥራ መትጋትን ይማሩ ዘንድ
ይገባቸዋል።
15ከእኔ ጋር ያሉት ሁሉ ሰላምታ ያቀ
ርቡላችኋል። ከእምነት የተነሣ ለሚወዱን
ሰላምታ አቅርቡልን።

ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት
# ወደ ፊልሞና

1 የክርስቶስ ኢየሱስ እስረኛ ከሆነው
ከጳውሎስና ከወንድማችን ከጢሞቴዎስ፤

ለውድ ወዳጃችንና አብሮን ለሚሠራው
ለፊልሞና፣ 2ለእኅታችን ለአፍብያ፣ አብሮን
ወታደር ለሆነው ለአርክጳ በቤትህም ላለ
ችው ቤተ ክርስቲያን፤
3ከእግዚአብሔር ከአባታችን፣ ከጌታም
ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ
ይሁን፡፡
4አንተን በጸሎቴ በማስብህ ጊዜ ዘወትር
አምላኬን አመሰግናለሁ፤ 5ምክንያቱም በጌታ
በኢየሱስ ያለህን እምነትና ለቅዱሳንም
ሁሉ ያለህን ፍቅር ሰምቻለሁ፡፡ 6በክርስቶስ
ስላለን መልካም ነገር ሁሉ በሚገባ ትረዳ
ዘንድ፣ እምነትህን ለሌሎች በማካፈል
እንድትተጋ እጸልያለሁ፡፡ 7ወንድሜ ሆይ፤
የቅዱሳንን ልብ ስላሳረፍህ ከፍቅርህ ታላቅ
ደስታና መጽናናት አግኝቻለሁ፡፡
8ስለዚህ ማድረግ የሚገባህን እንድታደርግ
አዝህ ዘንድ በክርስቶስ ድፍረት ቢኖረ
ኝም 9በፍቅር እለምንሃለሁ፤ እንግዲህ ሽማ
ግሌና አሁን ደግሞ የክርስቶስ ኢየሱስ
እስረኛ የሆንሁት እኔ ጳውሎስ፣ 10በእስር
እያለሁ ስለ ወለድሁት ልጄ ስለ አናሲ
ሞስ[ሀ] እለምንሃለሁ፡፡ 11አስቀድሞ የሚጠ
ቅምህ አልነበረም፤ አሁን ግን ለአንተም ሆነ
ለእኔ የሚጠቅም ሰው ሆኖአል፡፡
12የልቤ ሰው የሆነውን እርሱን መልሼ
ወደ አንተ ልኬዋለሁ፡፡ 13ስለ ወንጌል
በታሰር ሁብት ጊዜ በአንተ ፈንታ ሆኖ
እንዲያገለግለኝ ለራሴ ላስቀረው ፈልጌ
ነበር፤

14ነገር ግን አንተ የምታደርገውን መልካም
ነገር ሁሉ በውዴታ እንጂ በግዴታ
እንዳ ይሆን ሳላማክርህ ምንም ማድረግ
አል ፈልግም፡፡ 15ምናልባት ለጥቂት ጊዜ
ከአንተ የተለየው፣ ተቀብለህ ለዘለቄታው
አንተ ዘንድ እንድታቈየው ነው፤ 16ከእን
ግዲህ ወዲህ ግን እንደ ባሪያ ሳይሆን
ከባሪያ በላይ የሆነ ተወዳጅ ወንድም ነው፡፡
ለእኔ ተወዳጅ ነው፤ ለአንተ ግን በሥጋም
በጌታም ይበልጥ ተወዳጅ ነው!፡፡
17እንግዲህ እንደ ባልንጀራ ከቈጠርኸኝ
እኔን እንደምትቀበለኝ አድርገህ ተቀበለው፡፡
18አንተን የበደለህ ነገር ቢኖር ወይም የአንተ
ብድር ቢኖርበት በእኔ ላይ ቍጠረው፡፡ 19እኔ
ጳውሎስ ይህን በእጄ ጽፌልሃለሁ፤ ያለ
በትን እኔው እከፍልሃለሁ፡፡ አንተም ራስህ
የእኔ ስለ መሆንህ ምንም አልናገርም፡፡
20ወን ድሜ ሆይ፤ በጌታ እንድትጠቅመኝ
እፈል ጋለሁ፤ በክርስቶስ ልቤን
አሳርፍልኝ፡፡ 21ታዛዥ መሆንህን በመተ
ማመን፣ ከምጠይቀውም በላይ
እንደምታደርግ በማወቅ እጽፍልሃለሁ፡፡
22ከዚህም ሌላ፣ ጸሎታችሁ መልስ አግኝቶ
ወደ እናንተ ለመምጣት ተስፋ ስለማደርግ
ማረፊያ አዘጋጅልኝ፡፡
23ከእኔ ጋር የክርስቶስ ኢየሱስ እስረኛ
የሆነውኤጳፍራ ሰላምታ ያቀርብልሃል፤
24እንዲሁም አብረውኝ የሚሠሩት ማር
ቆስ፣ አርስጥሮኮስ፣ ዴማስና ሉቃስ ሰላምታ
ያቀርቡልሃል፡፡
25የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመን
ፈሳችሁ ጋር ይሁን፡፡

1፥1 ቍ9፡23፤
ሐሥ 16፥1፤
2ቆሮ1፥1፤ኤፌ3፥1፤
ፊል2፥25
1፥2 ሮሜ16፥5፤
ፊል2፥25፤ቈላ4፥17
1፥3 ሮሜ1፥7
1፥4 ሮሜ1፥8፡10
1፥5 ሐሥ20፥21፤
ቈላ1፥4፤1ተሰ3፥6
1፥7 ቍ20፤
ሮሜ15፥32፤
1ቆሮ16፥18፤
2ቆሮ7፥4፡13
1፥9 ቍ1፡23፤
1ቆሮ 1፥10፤ኤፌ3፥1
1፥10 ሐሥ21፥33፤
ቈላ4፥9፤1ተሰ2፥11
1፥13 ቍ10፤
ሐሥ 21፥33
1፥14 2ቆሮ9፥7፤
1ጴጥ5፥2
1፥16 ማቴ23፥8፤
ሐሥ1፥16፤
1ቆሮ 7፥22፤
1ጢሞ6፥2
1፥17 2ቆሮ8፥23
1፥18 ዘፍ43፥9
1፥19 1ቆሮ16፥21
1፥20 ቍ7፤
1ቆሮ 16፥18
1፥21 2ቆሮ2፥3
1፥22 2ቆሮ1፥11፤
ፊል1፥19፡25፤2፥24፤
ዕብ13፥19
1፥23 ቍ1፤ሮሜ
16፥7፤ቈላ1፥7፤4፥10
1፥24 ቍ1፤ሐሥ
12፥12፤19፥29፤
ቈላ 4፥14፤
2ጢሞ4፥10
1፥25 ገላ6፥18

[ሀ]10 አናሲሞስ ማለት የሚጠቅም ማለት ነው

# ወደ ዕብራውያን የተጻፈ መልእክት

## ልጁ ከመላእክት በላይ ነው

1 እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በተለያየ
ጊዜና በልዩ ልዩ መንገድ በነቢያት
በኩል ለአባቶቻችን ተናግሮ፣ 2በዚህ መጨ
ረሻ ዘመን ግን ሁሉን ወራሽ ባደረገ
ውና ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ ለእኛ
ተናገረን። 3እርሱ የእግዚአብሔር ክብር ነ
ጸብራቅና የባሕርዩ ትክክለኛ ምሳሌ
ሆኖ፣ በኀ ያል ቃሉ ሁሉን ደግፎ ይዞአል፤
የኀጢአት መንጻት ካስገኘ በኋላ በሰ
ማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ። 4ስለዚ
ህ የወረሰው ስም ከመላእክት ስም
እንደሚበልጥ ሁሉ፣ እርሱም ከመላእክት
እጅግ የላቀ ሆኖአል።

5እግዚአብሔር፣
"አንተ ልጄ ነህ፤
እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ፤"[ሀ]

ወይስ ደግሞ፦
"እኔ አባት እሆነዋለሁ፤
እርሱም ልጅ ይሆነኛል" ያለው ከመ
ላእክት ከቶ ለማን ነው?
6ደግሞም እግዚአብሔር በኵሩን ወደ ዓለም
ሲያስገባ፣
"የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉ[ለ] ይስገዱለት"
ይላል።

7ስለ መላእክትም ሲናገር፣
"መላእክቱን ነፋሳት፣
አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል ያደርጋል"
ይላል።

8ስለ ልጁ ግን እንዲህ ይላል፤
"አምላክ ሆይ፤ ዙፋንህ ከዘላለም እስከ
ዘላለም ጸንቶ ይኖራል፤
ጽድቅም የመንግሥትህ በትር ይሆናል፤
9ጽድቅን ወደድህ፤ ዐመፃን ጠላህ፤
ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ ከባልንጀ
ሮችህ በላይ አስቀመጠህ፣
የደስታንም ዘይት ቀባህ

10ደግሞም እንዲህ ይላል፤ "ጌታ ሆይ፤ አንተ
በመጀመሪያ የምድርን መሠረት አኖርህ፤
ሰማያትም የእጆችህ ሥራ ናቸው።
11እነርሱ ይጠፋሉ፤ አንተ ግን ጸንተህ
ትኖራለህ፤
ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ፤
12እንደ መጐናጸፊያ ትጠቀልላቸዋለህ፤
እንደ ልብስም ይለወጣሉ።
አንተ ግን ያው አንተ ነህ፤
ዘመንህም ፍጻሜ የለውም።"

13እግዚአብሔር፣
"ጠላቶችህን የእግርህ መርገጫ እስከ
ማደርግልህ ድረስ፣
በቀኜ ተቀመጥ" ያለው ከመላእክት ኩቶ ለማን
ነው?
14መላእክት ሁሉ መዳንን የሚወርሱትን
ለማገልገል የሚላኩ አገልጋይ መናፍስት
አይደሉምን?

## ትኵረት የሚያስፈልጋቸው ነገሮች

2 ስለዚህ ከሰማነው ነገር ስተን እንዳ
ንወድቅ፣ ለሰማነው ነገር አብልጠን
ልንጠነቀቅ ይገባናል። 2ምክንያቱም በመላ
እክት በኩል የተነገረው ቃል ጽኑ ከሆነና
ማንኛውም መተላለፍና አለመታዘዝ ተገ
ቢውን ቅጣት ከተቀበለ፣ 3እኛስ እንዲህ ያለ
ውን ታላቅ ድነት ቸል ብንል እንዴት ልና
መልጥ እንችላለን? ይህ ድነት በመጀመሪያ
በጌታ ተነገረ፤ ከእርሱ የሰሙትም ለእኛ አረ
ጋገጡልን። 4እግዚአብሔርም በምልክት፣ በድን
ቅና በልዩ ልዩ ታምራት እንዲሁም እንደ
ፈቃዱ በታደሉት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ
ዎች ስለዚሁ ነገር መስክሮአል።

## ኢየሱስ ወንድሞቹን መሰለ

5ይህን የምንናገርለትን መጪውን ዓለም
ለመላእክት አላስገዛም፤ 6ነገር ግን አንዱ
በሌላ ስፍራ እንዲህ ብሎ መስክሮአል፤
"ታስታውሰው ዘንድ ሰው ምንድን ነው?
ታስብለትስ ዘንድ የሰው ልጅ ምንድን
ነው"

7ከመላእክት ጥቂት[ሐ] አሳነስኸው፤
የክብርና የምስጋና ዘውድ ጫንህለት፤
8ሁሉንም ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት።
እግዚአብሔር ሁሉን ከበታቹ ሲያስገዛለት፣
ያላስገዛለት ምንም ነገር የለም፤ ይሁን
እንጂ በአሁኑ ጊዜ ሁሉም ነገር ተገዝቶ
ለት አናይም። 9ነገር ግን በእግዚአብሔር
ጸጋ ስለ ሰው ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ
ከመ ላእክት ጥቂት እንዲያንስ ተደርጎ
የነበ ረው ኢየሱስ፣ የሞትን መከራ
በመቀበሉ አሁን የክብርና የምስጋና ዘውድ
ተጭኖለት እናየዋለን።
10ሁሉ ነገር ለእርሱና በእርሱ የሚኖር

1፥1 ዘኍ12፥6፡8፤
ሉቃ1፥70፤ዮሐ9፥29፤
ሐሥ2፥30፤ዕብ2፥2፡
3፤4፥8፤12፥25
1፥2 ቀ5፤ ዘዳ4፥30፤
መዝ2፥8፤ማቴ3፥17፤
11፥27፤ 28፥18፤ ዮሐ1፥3፤
ዕብ3፥6፡5፥8፤7፥28፤
9፥26፤11፥3፤1ጴጥ1፥20
1፥3 ማር16፥19፤
ዮሐ1፥14፤14፥9፤
ቈላ1፥17፤ቲቶ2፥14፤ዕ
ብ7፥27፤9፥11-14
1፥4 ኤፌ1፥21፤
ፊል2፥9፡10፤ዕብ8፥6
1፥5 2ሳሙ7፥14፤
መዝ2፥7፤ማቴ3፥17
1፥6 ዘዳ32፥43፤
መዝ97፥7፤ዮሐ3፥16፤
ቈላ1፥18፤ዕብ10፥5
1፥7 መዝ104፥4
1፥8 ሉቃ1፥35
1፥9 ኢሳ61፥1፡3፤
መዝ45፥6፡7፤ፊል2፥9
1፥10 መዝ8፥6፤
ዘካ12፥1
1፥11 ኢሳ34፥4፤
51፥6፤ዕብ12፥27
1፥12 መዝ102፥25-27፤
ዕብ13፥8
1፥13 ቀ3፤ኢሱ10፥24፤
መዝ110፥1፤
ማቴ22፥44፤
ማር16፥19፤ዕብ10፥13
1፥14 ዳን7፥10፤
መዝ91፥11፤103፥20፤
ማቴ25፥34፤
ማር10፥17፤
ሐሥ20፥32
ሮሜ11፥14፤
ዕብ2፥3፤5፥9፤9፥28
2፥1 ሮሜ11፥22
2፥2 ዘዳ33፥2፤
ሐሥ7፥53፤ገላ3፥19፤
ዕብ1፥1
2፥3 ሉቃ1፥2፤
ዕብ1፥2፤10፥29
2፥4 ማር16፥20፤
ዮሐ4፥48፤1ቆሮ12፥4፤
ኤፌ1፥5
2፥6 ኢዮ7፥17፤
መዝ144፥3፤ዕብ4፥4
2፥8 መዝ8፥4-6፤
ማቴ22፥44
2፥9 ቀ7፤ሐሥ3፥13፤
2ቆሮ5፥15፤ፊል2፥7-9
2፥10 ሉቃ24፥26፤
ሮሜ11፥16፤ዕብ5፥8፡
9፤7፥28

[ሀ]5 ወይም *እኔ ዛሬ አባት ሆንሁህ*
[ለ]6 የሙት ባሕር ጥቅልሎችንና ሰብዓ ሊቃናትን ይመ
[ሐ]7 ወይም *ለጥቂት ጊዜ*

እግዚአብሔር፣ ብዙ ልጆችን ወደ ክብር ለማ
ምጣት፣ የድነታቸውን መሥራች በመከራ
ፍጹም ሊያደርገው የተገባ ነበር። 11ሰዎ
ችን የሚቀድሰውና የሚቀደሱት ሰዎች
ከአንድ ቤተ ሰብ ናቸው፤ ስለዚህ ኢየሱስ
ወንድሞች ብሎ ሊጠራቸው ዐያፍርም፤ 12እንዲ
ህም ይላል፤

"ስምህን ለወንድሞቼ እነግራቸዋለሁ፤
በጉባኤም መካከል ምስጋናህን እዘምራ
ለሁ።"
13እንዲሁም፣
"እኔ በእርሱ እታመናለሁ።"
ደግሞም እንዲህ ይላል፤
"እነሆ፤ እኔና እግዚአብሔር የሰጠኝ ልጆች።"

14ልጆቹ በሥጋና በደም እንደሚካፈሉ
እርሱ ራሱ ደግሞ ያንኑ ተካፈለ፤ ይኸ
ውም በሞት ላይ ኀይል ያለውን ዲያቢሎስን
በሞቱ ኀይል እንዲደመስስ ነው፤ 15እንዲ
ሁም በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ በሞት
ፍርሀት ባርነት የታሰሩትን ነጻ እንዲ
ያወጣ ነው። 16እርሱ የመጣው መላ
እክትን ለመርዳት ሳይሆን፣ የአብርሃምን
ዘር ለመርዳት እንደ ሆነ ግልጽ ነው።
17ስለ ዚህ በሁሉም ነገር ወንድሞቹን
መምሰል ተገባው፤ ይህንም ያደረገው
መሓሪና ታማኝ ሊቀ ካህናት ሆኖ እግዚ
አብሔርን ለማ ገልገልና ለሕዝቡ የኀጢአትን
ስርየት[ሠ] ለማ ስገኘት ነው። 18እርሱ ራሱ
በተፈተነ ጊዜ መከራን ስለ ተቀበለ፣
የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና።

## ኢየሱስ ከሙሴ በላይ ነው

3 እንግዲህ የሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች
የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ፤
የእምነታችን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት የሆነ
ውን ኢየሱስን አስቡ። 2ሙሴ በእግዚአብሔር
ቤት ሁሉ ላይ ታማኝ እንደ ነበር፣ እር
ሱም ለሾመው ታማኝ ነበር። 3ቤትን የሚሠራ
ከቤቱ ይልቅ የሚበልጥ ክብር እንዳለው፣
ኢየሱስም ከሙሴ የሚበልጥ ክብር የተገ
ባው ሆኖ ተገኝቶአል፤ 4እያንዳንዱ ቤት የ
ራሱ ሠሪ አለው፤ ነገር ግን ሁሉን የሠራ
እግዚአብሔር ነው። 5ሙሴ ወደፊት ስለሚነ
ገረው ነገር እየመሰከረ፣ በእግዚአብሔር
ቤት ሁሉ ላይ እንደ አንድ ታማኝ
አገልጋይ ነበር፤ 6ክርስቶስ ግን በእግዚአብሐ
ር ቤት ላይ እንደ ታማኝ ልጅ ነው።
እኛም የም ንተማመንበትንና
የምንመካበትን ተስፋ አጥብቀን ብንይዝ
ቤቱ ነን።

## ስለ አለማመን የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

7ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል፣
"ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ፣

2፥11 ማቴ28፥10፤ ኤፌ5፥26፤ዕብ13፥12
2፥12 መዝ22፥22፤ 68፥26
2፥13 ኢሳ8፥17፡18፤ ዮሐ10፥29
2፥14 ዘፍ3፥15፤ ዮሐ1፥14፤1ቆሮ15፥50፡ 54-57፤ ኤፌ6፥12፤ 2ጢሞ1፥10፤1ዮሐ3፥8
2፥15 2ጢሞ1፥7
2፥16 ሉቃ3፥8
2፥17 ቍ14፤ ሮሜ3፥25፤ፊል2፥7፤ ዕብ3፥1፤4፥14፡15፤ 5፥1፡2፡5፡10፤7፥26፡ 28፤8፥1፡3፤9፥11
2፥18 ዕብ4፥15
3፥1 ሮሜ 8፥28፤2ቆሮ9፥13፤ 1ጢሞ6፥12፤ ዕብ2፥11፡17፤4፥14፤ 10፥23
3፥2 ቍ5፤ዘኍ12፥7
3፥3 ዘጸ34፥12
3፥4 ዘፍ1፥1
3፥5 ቍ2፤ዘፀ14፥31፤ ዘኍ12፥7
3፥6 ቍ14፤ሮሜ 5፥2፤11፥22፤ 1ቆሮ3፥16፤ 1ጢሞ3፥15፤ ዕብ1፥2፤ 4፥14፤6፥11፡ 8፡19፤7፥19፤11፥1
3፥7 ሐሥ28፥25፤ ዕብ9፥8፤10፥15
3፥8 ቍ15፤ዕብ4፥7
3፥9 ዘኍ14፥33፤ ዘጸ1፥3፤ሐሥ7፥36
3፥11 ዘጸ1፥34፡ 35፤መዝ95፥7-11፤ ዕብ4፥3፡5
3፥12 ማቴ16፥16
3፥13 ኤር17፥9፤ ኤፌ4፥22፤ ዕብ10፥24፡25
3፥14 ቍ6፤ኤፌ3፥12
3፥15 ቍ7፡8፤ መዝ95፥7፡8፤ዕብ4፥7
3፥16 ዘኍ14፥2
3፥17 ዘኍ14፥29፤ መዝ106፥26፤ 1ቆሮ10፥5
3፥18 ዘኍ14፥20-23፤ ዘጸ1፥34፡35፤ዕብ4፥6
3፥19 መዝ78፥22፤ 106፥24፤ ዮሐ3፥36
4፥1 ዕብ12፥15
4፥2 1ተሰ2፥13
4፥3 ዘጸ1፥34፡35፤ መዝ95፥11፤ዕብ3፥11

8በምድረ በዳ በፈተና ቀን፣
በዐመፅ እንዳደረጋችሁት፣
ልባችሁን አታደንድኑ።
9አባቶቻችሁ በዚያ ተፈታተኑኝ፤
መረመሩኝ፤ ያደረግሁትንም ሁሉ ለአርባ
ዓመት አዩ።
10በዚያም ትውልድ ላይ የተቈጣሁት ለዚህ
ነበር፤
እንዲህም አልሁ፤ 'ልባቸው ሁልጊዜ
ይስታል፤
መንገዴንም አላወቁም፤'
11ስለዚህ በቍጣዬ እንዲህ ብዬ ማልሁ፤
"ወደ ዕረፍቴ ከቶ አይገቡም።"

12ወንድሞች ሆይ፤ ከእናንተ ማንም ከሕ
ያው እግዚአብሔር የሚያስኰበልል፣ ኀጢ
አተኛና የማያምን ልብ እንዳይኖረው ተጠ
ንቀቁ። 13ነገር ግን ከመካከላችሁ ማንም
በኀጢአት ተታሎ ልቡ እንዳይደነድን፣
"ዛሬ" እየተባለ ሳለ በየቀኑ እርስ በርሳ
ችሁ ተጽናኑ። 14በመጀመሪያ የነበረንን
እም ነት እስከ መጨረሻው አጽንተን
ብንይዝ ከክርስቶስ ጋር ተካፋዮች
እንሆናለን፤ 15ይኸውም፣
"ዛሬ ድምጹን ብትሰሙ፣
በዐመፅ እንዳደረጋችሁት፣
አሁንም ልባችሁን አታደንድኑ" እንደ
ተባለው ነው።

16ሰምተው ያመፁት እነማን ነበሩ?
ሙሴ ከግብፅ መርቶ ያወጣቸው ሁሉ
አይደሉምን? 17አርባ ዓመት የተቈጣውስ
እነማንን ነበር? ኀጢአት ሠርተው ሬሳ
ቸው በምድረ በዳ ወድቆ የቀረውን አይደ
ለምን? 18ያልታዘዙትን[ሡ] ካልሆነ በቀር
ወደ ዕረፍቱ እንዳይገቡ የማለባቸው እነማን
ነበሩ? 19እንግዲህ ሊገቡ ያልቻሉት ካለ
ማመናቸው የተነሣ እንደ ሆነ እንረዳለን።

## የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ

4 እንግዲህ ወደ ዕረፍቱ ለመግባት የተ
ሰጠው ተስፋ አሁንም የተጠበቀ ስለ
ሆነ፣ ከእናንተ ማንም ለዚያ ሳይበቃ
እንዳይቀር እንጠንቀቅ፤ 2ለእነዚያ እንደ
ተሰበከ ለእኛም ደግሞ የምሥራቹ ቃል
ተሰብኮልናልና። ነገር ግን ሰሚዎቹ ቃሉን
ከእምነት ጋር ስላላዋሐዱት[ሢ] አልጠቀማቸ
ውም። 3እኛ ያመነው ግን ወደዚያ ዕረ
ፍት እንገባለን፤ እግዚአብሔርም፣
"ስለዚህ በቍጣዬ እንዲህ ብዬ ማልሁ፤
'ወደ ዕረፍቴ ከቶ አይገቡም'" ብሎአጠ
ል። ይሁን እንጂ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ
የእ

[ሠ]17 ወይም *ቍጣ ለመመለስ*
[ሡ]18 ወይም *ያላመኑትን*
[ሢ]2 ወይም *ከታዘዙት ጋር ስላላመኑ*

ርሱ ሥራ ተከናውኖአል። 4ስለ ሰባተኛውም
ቀን በአንድ ስፍራ፣ “በሰባተኛውም ቀን እግ
ዚአብሔር ከሥራው ሁሉ ዐረፈ” ብሎአልና።
5ቀደም ባለው ክፍል ደግሞ፣
“ወደ ዕረፍቴ ከቶ አይገቡም” ይላል።
6ወደ ዕረፍቱ ገና የሚገቡ አንዳንዶች
አሉ፤ ቀድሞ የምሥራቹ ቃል የተሰበከላ
ቸው ባለመታዘዛቸው ምክንያት ወደ ዕረ
ፍት አልገቡም። 7ስለዚህ እግዚአብሔር፣
“ዛሬ” ብሎ እንደ ገና አንድን ቀን ወሰነ፤
ይህም ከብዙ ዘመን በኋላ በዳዊት በኩል፣
“ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ፣
ልባችሁን አታደንድኑ”
ተብሎ ቀደም ሲል እንደተነገረው ነው።
8ኢያሱ ዕረፍትን ሰጥቶአቸው ቢሆን
ኖሮ፣ ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ስለ ሌላ
ቀን ባልተናገረ ነበር። 9ስለዚህ የሰንበት
ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ገና ቀርቶለ
ታል፤ 10ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር ዕረ
ፍት የሚገባ ሁሉ፣ እግዚአብሔር ከሥራው
እንዳረፈ፣ እርሱም ደግሞ ከሥራው ያር
ፋል። 11እንግዲህ ማንም የእነዚያን አለመ
ታዘዝ ምሳሌ ተከትሎ እንዳይወድቅ
ወደዚያ ዕረፍት ለመግባት እንትጋ።
12የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና የሚሠራ
ነውና፤ በሁለት በኩል ስለት ካለው ሰይፍ
ሁሉ ይልቅ ስለታም ነው፤ ነፍስንና መን
ፈስን፣ ጅማትንና ቅልጥምን እስኪለያይ
ድረስ ዘልቆ ይወጋል፤ የልብንም ሐሳብና
ምኞት ይመረምራል። 13ከእግዚአብሔር ዐይን
የተሰወረ ምንም ፍጥረት የለም፤ ስለ ራሳችን
መልስ መስጠት በሚገባን በእርሱ ፊት ሁሉም
ነገር የተራቈተና የተገለጠ ነው።

## ታላቁ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ

14እንግዲህ ወደ ሰማያት ያረገ[ሰ] ታላቅ
ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ
ስላለን፣ እምነታችንን አጥብቀን እንያዝ።
15በድካማችን የማይራራልን ሊቀ ካህናት
የለንምና፤ ነገር ግን እንደ እኛ በማንኛ
ውም ነገር የተፈተነ ሊቀ ካህናት አለን፤
ይሁን እንጂ ምንም ኀጢአት አልሠራ
ም። 16እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበልና
በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ
እንድናገኝ፣ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት
እንቅረብ።

5 እያንዳንዱ ሊቀ ካህናት ከሰዎች መካ
ከል ይመረጣል፤ የእግዚአብሔርም በሆነው
ነገር ላይ ሰዎችን በመወከል ለኀጢአት
የሚሆነውን መባንና መሥዋዕትን ለማ
ቅረብ ይሾማል። 2እርሱ ራሱ ድካም
ያለበት በመሆኑ፣ አላዋቂ ለሆኑትና
ለሚባዝኑት ሊራራላቸው ይችላል። 3ስለ
ራሱ ኀጢአትና ስለ ሌሎች ሰዎች ኀጢ
አት መሥዋ
ዕት ማቅረብ የተገባው በዚሁ ምክንያት
ነው።
4አሮን እንደ ተጠራ በእግዚአብሔር መጠ
ራት አለበት እንጂ፣ ይህን ክብር ለራሱ
የሚወስድ ማንም የለም። 5እንዲሁም
ክርስቶስ ሊቀ ካህናት የመሆንን ክብር
ለራሱ አልወሰደም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር፣
“አንተ ልጄ ነህ፤
እኔ ዛሬ አባት ሆንሁህ”[ሸ] አለው።
6እንዲሁም በሌላ ስፍራ፣
እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት፣
አንተ ለዘላለም ካህን ነህ” ይላል።
7ኢየሱስ በዚህ ምድር በኖረበት ዘመን
ከሞት ሊያድነው ወደሚችለው ጸሎትንና
ልመናን ከታላቅ ጩኸትና ከእንባ ጋር
አቀረበ፤ ፍጹም ትሑት ሆኖ በመታዘ
ዙም ጸሎቱ ተሰማለት። 8የእግዚአብሔር
ልጅ ቢሆንም እንኳ፣ ከተቀበለው መከራ
መታዘዝን ተማረ፤ 9በዚህም ፍጹም ሆኖ
ከተገኘ በኋላ፣ እርሱን ለሚታዘዙ ሁሉ
የዘላለም ድነት ምክንያት ሆነላቸው፤ 10እንደ
መልከ ጼዴቅ ሹመትም ሊቀ ካህናት
ተብሎ በእግዚአብሔር ተሾመ።

## በእምነት ስላለመጽናት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

11ስለዚህ ጉዳይ የምንናገረው ብዙ
ነገር አለን፤ ነገር ግን ለመማር ዳተኛ ስለ
ሆናችሁ ለማስረዳት አስቸጋሪ ነው።
12በዚህ ጊዜ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገ
ባችሁ፣ ገና የእግዚአብሔርን ቃል የመጀ
መሪያ ትምህርት የሚያስተምራችሁ ሰው
ያስፈልጋችኋል፤ የሚያስፈልጋችሁም ጠን
ካራ ምግብ ሳይሆን ወተት ነው። 13ወተት
የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለሆነ፣ ከጽድቅ
ትምህርት ጋር ገና አልተዋወቀም። 14ጠንካራ
ምግብ ግን መልካሙን ከክፉው ለመለየት
ራሳቸውን ላስለመዱ፣ ለበሰሉ ሰዎች
ነው።

6 ስለዚህ ስለ ክርስቶስ የተሰጠውን የመ
ጀመሪያ ትምህርት ትተን ወደ ብስለት
እንሂድ፤ ከሞተ ሥራ ንስሓ ስለ መግባ
ትና[ቀ] በእግዚአብሔር ስለ ማመን እንደ
ገና መሠረትን አንጣል፤ 2እንዲሁም ስለ
ጥምቀ ቶች፣ እጆችን ስለ መጫን፣ ስለ
ሙታን ትንሣኤና ስለ ዘላለም ፍርድ
ትምህርት እንደ ገና አንመሥርት። 3እግዚ
አብሔር ቢፈ ቅድ ይህን እናደርጋለን።

[ሰ]14 ወይም *ወደ ሰማይ የሄደ*
[ሸ]5 ወይም *ወልጄሃለሁ።*
[ቀ]1 ወይም *ከከንቱ ሥርዐት*

4፥4 ዘፍ2፥2፡3፤
ዘፀ20፥11
4፥5 ቍ3፤መዝ95፥11
4፥6 ቍ11፤ዕብ3፥18
4፥7 መዝ95፥7፡8፤
ዕብ3፥7፡8፡15
4፥8 ኢ.ሱ22፥4፤
ዕብ1፥1
4፥10 ቍ4፤ዘሌ23፥3፤
ራእ14፥13
4፥11 ቍ6፤ዕብ3፥18
4፥12 ኢ.ሳ55፥11፤
ኤር23፥29፤
ማር4፥14፤ሉ.ቃ5፥1፤
11፥28፤ዮሐ10፥35፤
ሐሥ7፥38፤12፥24፤
1ቆሮ14፥24፡25፤
ኤፌ6፥17፤1ተሰ2፥13፤
2ጢ.ሞ2፥9፤
1ጴጥ1፥23፤1ዮሐ2፥14፤
ራእ1፥2፡9፡16
4፥13 መዝ33፥13-15፤
ምሳ5፥21፤ኤር16፥17፤
23፥24፤ዳን2፥22
4፥14 ማቴ4፥3፤
ዕብ2፥17፤3፥1፤6፥20፤
8፥1፤9፥24
4፥15 2ቆሮ5፥21፤
ዕብ2፥17፡18
4፥16 ኤፌ3፥12፤
ዕብ7፥19
5፥1 ዕብ2፥17፤7፥27፤
8፥3፤9፥9
5፥2 ኢ.ሳ29፥24፤
ዕብ2፥18፤4፥15፤7፥28
5፥3 ዘሌ9፥7፤16፥6፤
ዕብ7፥27፤9፥7
5፥4 ዘፀ28፥1፤
ዘኍ14፥40፤18፥7
5፥5 መዝ2፥7፤
ማቴ3፥17፤ዮሐ8፥54፤
ዕብ1፥1፤2፥17
5፥6 ቍ10፤
ዘፍ14፥18፤
መዝ110፥4፤
ዕብ6፥20፤7፥1-22
5፥7 መዝ22፥24፤
ማቴ27፥46፡50፤
ማር14፥36፤
ሉ.ቃ22፥41-44፤
23፥46
5፥8 ፊል2፥8፤
ዕብ1፥2
5፥9 ዕብ2፥10
5፥10 ቍ5፡6፤
ዕብ2፥17
5፥12 1ቆሮ3፥2፤
ዕብ6፥1፤1ጴጥ2፥2
5፥13 1ቆሮ14፥20
5፥14 ኢ.ሳ7፥15፤
1ቆሮ2፥6
6፥1 ፊል3፥12-14፤
ዕብ5፥12፤9፥14
6፥2 ዮሐ3፥25፤
ሐሥ2፥24፤6፥6፤
17፥18፡32
6፥3 ሐሥ18፥21

4አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን፣ ሰማ
ያዊውን ስጦታ የቀመሱትን፣ ከመንፈስ
ቅዱስ ተካፋዮች የሆኑትን፣ 5መልካሙን
የእግዚአብሔር ቃልና የሚመጣውን ዓለም
ኀይል የቀመሱትን፣ 6በኋላ ግን የካዱትን
እንደ ገና ወደ ንስሓ መመለስ አይቻልም፤
ምክንያቱም እነርሱ ለገዛ ጥፋታቸው የእግዚ
አብሔርን ልጅ እንደገና ይሰቅሉታል፤
ያዋርዱታልም::

7ዝወትር በእርሷ ላይ የሚወርደውን
ዝናብ የምትጠጣና ለሚያርሷትም ፍሬ የም
ትሰጥ መሬት ከእግዚአብሔር በረከትን
ትቀበ ላለች:: 8ነገር ግን እሾህና አሜኬላ
የምታ በቅል መሬት ዋጋ ቢስ ትሆናለች፤
መረገ ሚያዋም ተቃርቦአል፤ መጨረሻዋም
በእሳት መቃጠል ነው::

9ወዳጆች ሆይ፤ ምንም እንኳ እንደዚህ
ብንናገርም፣ ከድነታችሁ ጋር የተያያዘ
ታላቅ ነገር እንዳላችሁ እርግጠኞች ነን::
10እግዚአብሔር ዐመፀኛ አይደለም፤ እርሱ ሥ
ራ ችሁን እንዲሁም በፊትም ሆነ አሁን
ቅዱ ሳንን በመርዳት ስለ ስሙ
ያሳያችሁትን ፍቅር አይረሳም:: 11የተሰጠ
ው ተስፋ እስ ኪፈጸም ድረስ
እያንዳንዳችሁ እንዲህ ያለ ውን ትጋት
እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ እንመኛለን::
12በእምነትና በትዕግሥት የተስፋውን ቃል
የሚወርሱትን እንድት መስሉ እንጂ ዳተኞች
እንድትሆኑ አንፈል ግም::

### የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል እርግጠኛነት

13እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ
በሰ
ጠው ጊዜ፣ የሚምልበት ከእርሱ የሚበ
ልጥ ሌላ ባለ መኖሩ፣ በራሱ ማለ፤ 14እን
ዲህም አለ፤ “በእርግጥ እባርክሃለሁ፤ ዘርህ
ንም አበዛዋለሁ::” 15አብርሃምም በትዕግሥት
ከጠበቀ በኋላ የተሰጠውን ተስፋ አገኘ::

16ሰዎች ከእነርሱ በሚበልጥ ይምላሉ፤
መሐላውም የተባለውን ነገር ስለሚያጸና፣
በመካከላቸው የተነሣው ክርክር ሁሉ ይወ
ገዳል:: 17እግዚአብሔር የማይለወጥ ዐላማውን
ለተስፋው ቃል ወራሾች ግልጽ ለማድረግ
ስለ ፈለገ፣ በመሐላ አጸናው፤ 18እግዚአብሔር
ከቶ ሊዋሽ አይችልም፤ እርሱ በሁለት በማ
ይለወጡ ነገሮች በፊታችን ያለውን ተስፋ
ለመያዝ ወደ እርሱ ለሸሸን ለእኛ ብርቱ
መጽናናት እንድናገ አድርጎአል:: 19እኛም
የነፍስ መልሕቅ የሆነ ጽኑና አስተማማኝ
ተስፋ አለን፤ ይህም ተስፋ ከመጋረጃው
በስተጀርባ ወዳለው ውስጠኛ መቅደስ
ይገባል:: 20ይህም ስፍራ ኢየሱስ ስለ እኛ
ቀድሞ የገባበት ነው:: እርሱም እንደ

6፥4 ገላ3፥2፤ኤፌ2፥8፤ ዕብ10፥32
6፥5 መዝ34፥8፤ ዕብ4፥12
6፥6 ማቴ4፥3፤ 2ጴጥ2፥21፤1ዮሐ5፥16
6፥8 ዘፍ3፥17፥18፤ ኢሳ5፥6፤27፥4
6፥9 1ቆሮ10፥14
6፥10 ማቴ10፥40፥42፤ 1ተሰ1፥3
6፥11 ዕብ3፥6
6፥12 2ተሰ1፥4፤ ዕብ10፥36፤13፥7፤ ያዕ1፥3፤ራእ13፥10፤ 14፥12
6፥13 ዘፍ22፥16፤ ሉቃ1፥73
6፥14 ዘፍ22፥17
6፥15 ዘፍ21፥5
6፥16 ዘፀ22፥11
6፥17 ቀኑ18፤ መዝ110፥4፤ ሮሜ4፥16፤ዕብ11፥9
6፥18 ዘኁ23፥19፤ ቲቶ1፥2፤ዕብ3፥6
6፥19 ዘሌ16፥2፤ ዕብ9፥2፥3፥7
6፥20 ዕብ2፥17፤ 4፥14፤5፥6

መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ሊቀ
ካህናት ሆኖአል::

### ካህኑ መልከ ጼዴቅ

7 ይህ መልከ ጼዴቅ የሳሌም ንጉሥና
የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር፤
እርሱም አብርሃም ነገሥታትን ድል አድርጎ ሲ
መለስ አግኝቶት ባረከው፤ 2አብርሃምም
ከሁሉ ነገር ዓሥራት አውጥቶ ሰጠው::
በመጀ መሪያ ስሙ “የጽድቅ ንጉሥ”
ማለት ነው፤ ኋላም ደግሞ “የሳሌም ንጉሥ”
ማለትም “የሰላ ም ንጉሥ ማለት” ነው:: 3አባትና
እናት ወይም የትውልድ ሐረግ የለውም፤
ለዘመኑ መጀ መሪያ፣ ለሕይወቱም
ፍጻሜ የለውም፤ ነገር ግን እንደ እግዚ
አብሔር ልጅ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራ
ል::

4እስቲ እርሱ የቱን ያህል ታላቅ
እንደ ሆነ ዐስቡ፤ ርእሰ አበው የሆነው
አብርሃም እንኳ ካገኘው ምርኮ ዓሥራት
አውጥቶ ሰጠው:: 5ክህነት የተሰጣቸው
የሌዊ ልጆች ምንም እንኳ ወንድሞቻቸው
የአብርሃም ዘሮች ቢሆኑም፣ ከሕዝቡ
ማለት ከገዛ ወንድሞቻቸው ዓሥራት እን
ዲቀበሉ ሕጉ ያዛል:: 6ይህ ግን ትውልዱ
ከሌዊ ወገን አይደለም፤ ይሁን እንጂ
ከአብርሃም ዓሥራት ተቀበለ፤ የተስፋ ቃል
የተቀበለውም ባረከው:: 7ትንሹ በትልቁ
እንደሚባረክ ጥርጥር የለውም:: 8በአንድ
በኩል ዓሥራት የሚቀበሉት ሚች ሰዎች
ናቸው፤ በሌላ በኩል ግን ሕያው ሆኖ
እንደሚኖር የተመሰከረለት ይቀበላል::
9እንዲያውም ዓሥራት የሚቀበለው ሌዊ፣
ራሱ በአብርሃም በኩል ዓሥራት ከፍሎአል
ማለት ይቻላል፤ 10ምክንያቱም መልከ ጼዴቅ
አብርሃምን ባገኘው ጊዜ፣ ሌዊ ገና በአ
ባቱ በአብርሃም አብራክ ነበር::

### ኢየሱስ እንደ መልከ ጼዴቅ

11ፍጹምነት የተገኘውና ሕጉ ለሕዝቡ
የተሰጠው በሌዊ ክህነት መሠረት ቢሆን
ኖሮ፣ እንደ አሮን ሳይሆን እንደ መልከ
ጼዴቅ ሹመት ያለው ሌላ ካህን መም
ጣቱ ለምን አስፈለገ? 12የክህነት ለውጥ
ካለ ሕጉም ሊለወጥ ግድ ነውና:: 13ይህ
ሁሉ የተነገረለት እርሱ ከሌላ ነገድ ነው፤
ከዚያም ነገድ በመሠዊያ ያገለገለ ማንም
የለም:: 14ጌታችን ከይሁዳ ነገድ እንደ
መጣ ግልጽ ነውና፤ ሙሴ ስለ ካህናት ሲና
ገር ይህን ነገድ አስመልክቶ የተናገረው ምንም
ነገር የለም:: 15እንደ መልከ ጼዴቅ ያለ ሌላ
ካህን ቢነሣ ግን እኛ የተናገርነው ይበልጥ
ግልጽ ይሆናል፤ 16እርሱ ካህን የሆነው በማ
ይጠፋ የሕይወት ኀይል መሠረት እንጂ፣

7፥1 ቀኑ6፤ ዘፍ14፥18-20፤ መዝ76፥2፤ማር5፥7
7፥3 ቀኑ6፤ማቴ4፥3
7፥4 ዘፍ14፥20፤ ሐሥ2፥29
7፥5 ዘኁ18፥21፥26
7፥6 ዘፍ14፥19፥20፤ ሮሜ4፥13
7፥8 ዕብ5፥6፤6፥20
7፥11 ቀኑ17፥8፥19፤ ዕብ5፥6፤8፥7፤10፥1
7፥13 ቀኑ11፥14
7፥14 ኢሳ11፥1፤ ማቴ1፥3፤2፥6፤ ሉቃ3፥33፤ራእ5፥5

እንደ ትውልዱ የሕግ ሥርዐት አይደለም፤
17እንዲህ ተብሎ ተመስክሮለታል፤
"እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት፣
አንተ ለዘላለም ካህን ነህ።"
18የቀድሞው ትእዛዝ ደካማና የማይጠ
ቅም በመሆኑ ተሽሮአል፤ 19ሕጉ ማንንም
ፍጹም ሊያደርግ ስለማይችል ወደ እግዚ
አብሔር የምንቀርብበት የተሻለ ተስፋ መጥ
ቶአል።
20ይህ ያለ መሐላ አልሆነም፤ ሌሎች
ካህናት የሆኑት ያለ መሐላ ነው፤ 21እርሱ
ግን ካህን የሆነው በመሐላ ነው፤ ምክንያቱም
እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ
ተናግሮለታል፤
"ጌታ ማለ፤
ዐሳቡንም አይለውጥም፤
'አንተ ለዘላለም ካህን ነህ።' "
22ከዚህ መሐላ የተነሣ፣ ኢየሱስ ለተሻለ ኪዳን
ዋስ ሆኖአል።
23በአገልግሎታቸው እንዳይቀጥሉ ሞት
ስለ ከለከላቸው፣ የቀድሞዎቹ ካህናት ቍጥ
ራቸው ብዙ ነበር፤ 24ኢየሱስ ግን
ለዘላለም የሚኖር በመሆኑ፣ ክህነቱ የማ
ይሻር ነው። 25ስለዚህ ስለ እነርሱ እየማ
ለደ ሁልጊዜ በሕይወት ስለሚኖር፣ በእ
ርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡ
ትን ፈጽሞ[ሀ] ሊያድናቸው ይችላል።
26እንግዲህ ለእኛ የሚያስፈልገን፣ ቅዱስ፣
ነቀፋ የሌለበት፣ ንጹሕ፣ ከኀጢአተኞች የተ
ለየና ከሰማያት በላይ የከበረ እንደዚህ
ያለ ሊቀ ካህናት ነው። 27እርሱም እንደ
ሌሎቹ ሊቃነ ካህናት፣ መጀመሪያ ስለራሱ
ኀጢአት ከዚያም ስለ ሕዝቡ ኀጢአት በየ
ቀኑ መሥዋዕት ማቅረብ አያስፈልገውም፤
ራሱን በሰጠ ጊዜ፣ ስለ ኀጢአታቸው
ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መሥዋዕት
አቅርቦአልና። 28ሕጉ ደካማ የሆኑትን
ሰዎች ሊቃነ ካህናት አድርጎ ይሾማልና፤
ከሕግ በኋላ የመጣው መሐላ ግን ለዘላ
ለም ፍጹም የሆነውን ልጅ ሾሞአል።

## የአዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት

8 እንግዲህ የምንናገረው ዋናው ነገር
ይህ ነው፤ በሰማያት በግርማው ዙፋን
ቀኝ የተቀመጠ እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት
አለን፤ 2እርሱም በሰው ሳይሆን በጌታ
በተተከለችው፣ እውነተኛ ድንኳን በሆነ
ችው ቤተ መቅደስ አገልጋይ ነው።
3እያንዳንዱ ሊቀ ካህናት የሚሾመው
መባንና መሥዋዕትን ለማቅረብ ነው፤ ስለ
ዚህ ይኸኛውም ሊቀ ካህን የሚያቀር
በው ነገር ያስፈልገዋል። 4እርሱ በምድር
ቢኖር ኖሮ ካህን ባልሆነም ነበር፤ ምክንያቱም
በሕግ በታዘዘው መሠረት መባን የሚያቀ
ርቡ ሰዎች አሉ። 5እነርሱ ያገለገሉት በሰ
ማይ ላለችው መቅደስ ምሳሌና ጥላ በሆነ
ችው ውስጥ ነው፤ ሙሴ ድንኳኒቱን ለመ
ሥራት በተነሣ ጊዜ፣ "በተራራው ላይ
በተገለጠልህ ምሳሌ መሠረት ሁሉን ነገር
እንድታደርግ ተጠንቀቅ" የሚል ትእዛዝ
የተሰጠው በዚህ ምክንያት ነበር። 6ነገር
ግን ኢየሱስ መካከለኛ የሆነበት ኪዳን
ከቀድሞው እንደሚበልጥ ሁሉ፣ የተቀበ
ለውም አገልግሎት ከእነርሱ አገልግሎት
ይበልጣል፤ ይህም የተመሠረተው በተሻለ
የተስፋ ቃል ላይ ነው።
7የመጀመሪያው ኪዳን ምንም ጒድ
ለት ባይገኝበት ኖሮ፣ ለሁለተኛው ስፍራ
ባለተፈለገም ነበር። 8ነገር ግን እግዚአብሔር
በሕዝቡ ላይ ጒድለት በማግኘቱ እንዲህ
ይላቸዋል[+]፤
"ከእስራኤል ቤት ጋር፣
ከይሁዳም ቤት ጋር፣
አዲስ ኪዳን የምገባበት፣
ጊዜ ይመጣል፤
ይላል ጌታ።
9ይህም እነርሱን ከግብፅ ምድር
ለማውጣት እጃቸውን በያዝሁ ጊዜ፣
ከቀድሞ አባቶቻቸው ጋር እንደ ገባሁት
ኪዳን አይደለም፤
ምክንያቱም እነርሱ በኪዳኔ አልጸኑም፤
እኔም ከእነርሱ ዘወር አልሁ፤
ይላል ጌታ።
10ከዚያን ጊዜ በኋላ፣
ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ኪዳን
ይህ ነው፤
ይላል ጌታ፤
ሕጌን በአእምሮአችው አኖራለሁ፤
በልባቸውም እጽፈዋለሁ።
እኔ አምላካቸው እሆናለሁ፤
እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ።
11ከእንግዲህ ማንም ሰው ጐረቤቱን
ወይም ወንድሙን፣
'ጌታን ዕወቅ' ብሎ አያስተምርም፤
ምክንያቱም ከታናሹ ጀምሮ እስከ
ታላቁ ድረስ፣
ሁሉም ያውቁኛል።
12በደላቸውን ይቅር እላለሁ፤ ኀጢአታቸውን
ከእንግዲህ አላስብም፤
13ይህን ኪዳን፣ "አዲስ" በማለቱ የፊ
ተኛውን ኪዳን አሮጌ አድርጎታል፤ ስለ
ዚህ ያረጀ ያፈጀው የሚጠፋበት ጊዜ ተቃር
ቦአል።

7፥17 ቍ21፤ መዝ110፥4፤ዕብ5፥6
7፥18 ሮሜ8፥3
7፥19 ቍ11፡25፤ ሮሜ3፥20፤ 7፥7፡8፤ገላ3፥21፤ ዕብ3፥6፤4፥16፤ 9፡9፤10፡1፡ዕብ22፤ ያዕ4፡8
7፥21 ዘኍ23፥19፤ 1ሳሙ15፥29፤ መዝ110፥4፤ ሚል3፥6፤ ሮሜ11፥29፤ዕብ5፥6
7፥22 ሉቃ22፥20
7፥24 ቍ28
7፥25 ቍ19፤ ሮሜ8፥34፤11፥14
7፥26 2ቆሮ5፥21፤ ዕብ2፥17፤4፥14
7፥27 ሮሜ6፥10፤ ኤፌ5፥2፤ዕብ5፥1፡ 3፤9፥12፡14፡ 26፡28፤10፥10፤ 1ጴጥ3፥18
7፥28 ዕብ1፥2፤ 2፥10፤5፥2
8፥1 ማር16፥19፤ ዕብ2፥17፤4፥14
8፥2 ዕብ9፥11፡24
8፥3 ዕብ2፥17፤ 5፥1፡9፥9፡14
8፥4 ዕብ5፥1፤9፥9
8፥5 ዘፀ25፥40፤ ቈላ2፥17፤ዕብ9፥23፤ 10፥1፤11፥7፤12፥25
8፥6 ቍ8፡13፤ ሉቃ22፥20፤ገላ3፥20
8፥7 ዕብ7፥11፡ 18፤10፥1
8፥8 ቍ6፡13፤ ሉቃ22፥20
8፥9 ዘፀ19፥5፡6፤ 20፥1-17
8፥10 ሕዝ11፥20፤ ዘካ8፥8፤ሮሜ 11፥27፤2ቆሮ3፥3፤ ዕብ10፥16
8፥11 ኢሳ54፥13፤ ዮሐ6፥45
8፥12 ኤር31፥31-34፤ ዕብ10፥17
8፥13 ቍ6፡8፤ ሉቃ22፥20፤2ቆሮ5፥17

[ሀ]25 ወይም *ለዘላለም*
[+]8 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *ጒድለት በማግኘቱ ለሕዝቡ እንዲህ ይላቸዋል*

## በምድራዊው ድንኳን የሚደረግ አምልኮ

9 የመጀመሪያው ኪዳን የአምልኮ ሥርዐ
ትና ምድራዊ መቅደስ ነበረው፡፡
2ድንኳን ተተክሎ ነበር፤ በመጀመሪያው
ክፍል መቅረዙ፣ ጠረጴዛውና የመሥዋዕቱ
ኅብስት ነበረበት፤ ይህም ስፍራ ቅድስት
ይባላል፡፡ 3ከሁለተኛው መጋረጃ በስተኋላ
ቅድስተ ቅዱሳን የተባለ ክፍል ነበር፤ 4በዚ
ያም ውስጥ የወርቅ ማዕጠንትና በወርቅ
የተለበጠው የኪዳኑ ታቦት ነበሩ፤ ይህም
ታቦት መና ያለበትን የወርቅ መሶብ፣
የለመለመችውን የአሮንን በትርና ኪዳኑ
የተጻፈበትን ጽላት ይዞአል፡፡ 5በታቦቱም
ላይ የስርየት መክደኛውን[ቶ] የሚጋርዱ
የክብር ኪሩቤል ነበሩ፤ አሁን ግን ስለ
እነዚህ ነገሮች በዝርዝር መናገር አንች
ልም፡፡

6ሁሉም በዚህ መልክ ከተዘጋጀ በኋላ፣
ካህናት አገልግሎታቸውን ለመፈጸም ዘወ
ትር ወደ ድንኳኒቱ መጀመሪያ ክፍል
ይገባሉ፡፡ 7ነገር ግን ወደ ውስጠኛው ክፍል
የሚገባው ሊቀ ካህናቱ ብቻ ነበር፤ የሚገ
ባውም በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን፣
ስለ ራሱ ኀጢአትና ሕዝቡ ባለማወቅ ስላደ
ረገው ኀጢአት የሚያቀርበውን ደም
ሳይዝ ከቶ አይገባም ነበር፡፡ 8የመጀመሪያዪቱ
ድንኳን ቆማ እስካለች ድረስ ወደ ቅድስተ
ቅዱሳን የሚወስደው መንገድ ገና እንዳል
ተገለጠ መንፈስ ቅዱስ ያሳያል፡፡ 9ይህም
ለአሁኑ ዘመን ምሳሌ ሲሆን፣ የሚቀር
ቡት መባና መሥዋዕት የሚያመልከውን
ሰው ኅሊና ፍጹም ሊያደርጉ አልቻሉም፡፡
10እነዚህ ሁሉ አዲሱ ሥርዐት እስኪመጣ
ድረስ የሚደረጉ የምግብና የመጠጥ እን
ዲሁም የተለያዩ የመንጻት ሥርዐቶች
ብቻ ናቸው፡፡

## የክርስቶስ ደም

11ክርስቶስ አሁን ስላሉት[ኀ] መልካም
ነገሮች ሊቀ ካህናት ሆኖ በመጣ ጊዜ
በሰው እጅ ወዳልተሠራችው፣ ከዚህ ፍጥ
ረት ወዳልሆነችው ታላቅና ፍጹም ድንኳን
ገባ፡፡ 12የገባውም የፍየልንና የጥጃዎችን ደም
ይዞ አይደለም፤ ነገር ግን የዘላለም ቤዛነት
ሊያስገኝ የራሱን ደም ይዞ ወደ ቅድስተ
ቅዱሳን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ገባ፡፡
13የውጭ አካላቸው ይነጻ ዘንድ በረከሱ
ሰዎች ላይ የሚረጨው የፍየሎችና የኮር
ማዎች ደም እንዲሁም የፍየሎችና የጊ
ደር ዐመድ የሚቀድሳቸው ከሆነ፣ 14በዘላ
ለም መንፈስ አማካይነት ራሱን ነውር አልባ
መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ያቀረበው
የክርስቶስ ደም ሕያው እግዚአብሔርን እንድ
ናመልክ ኅሊናችንን ከምውት ሥራ[ነ] እን
ዴት ይበልጥ ያነጻ ይሆን!

15ስለዚህም የተጠሩት፣ ተስፋ የተሰጠ
ውን የዘላለም ርስት እንዲቀበሉ ክርስቶስ
የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው፤ በመጀመሪ
ያው ኪዳን ሥር በነበሩበት ጊዜ ከሠሩት ኀጢ
አት ነጻ ለማውጣት ቤዛ ሆኖ ሞቶአልና፡፡

16ኑዛዜ[ኘ] በሚኖርበት ጊዜ የተናዛዡን
ሞት ማረጋገጥ ግድ ነው፤ 17ምክንያቱም
ኑዛዜው የሚጸናው ሰውዬው ሲሞት ብቻ
ነው፤ ነገር ግን ተናዛዡ በሕይወት እስካለ
ድረስ ኑዛዜው ዋጋ አይኖረውም፡፡ 18ስለ
ዚህ የመጀመሪያው ኪዳን እንኳ ያለ ደም
የጸና አልነበረም፡፡ 19ሙሴ እያንዳንዱን
የሕግ ትእዛዝ ለሕዝቡ ሁሉ ከተናገረ
በኋላ የጥጆችን ደም ከውሃ፣ ከቀይ የበግ
ጠጕርና ከሂሶጽ ጋር ወስዶ፣ በመጽሐፉና
በሕዝቡ ላይ ረጨው፤ 20እንዲህም አለ፤
"እንድትጠብቁት እግዚአብሔር ያዘዛችሁ
የኪዳኑ ደም ይህ ነው፡፡" 21እንዲሁም
ድንኳኒቱንና ማገልገያ ዕቃውን ሁሉ
በደም ረጨው፡፡ 22በእርግጥ ከጥቂት ነገ
ሮች በስተቀር ሁሉም ነገር በደም መን
ጻት እንዳለበት ሕጉ ያዛል፤ ደም ሳይፈስ
ስርየት የለምና፡፡

23እንግዲህ የሰማያዊው ነገሮች ምሳሌ
የሆኑት በእነዚህ ነገሮች ሊነጹ ግድ ነበር፤
በሰማይ ያሉት ነገሮች ግን ከዚህ በሚበ
ልጥ መሥዋዕት ይነጻሉ፡፡ 24ክርስቶስ የእ
ውነተኛዪቱ ድንኳን ምሳሌ ወደ ሆነች
ውና በሰው እጅ ወደ ተሠራችው መቅደስ
አልገባም፤ ነገር ግን አሁን ስለ እኛ በእግዚ
አብሔር ፊት ለመታየት፣ ወደ እርሷ ወደ
ሰማይ ገባ፡፡ 25ሊቀ ካህናት የራሱ ያልሆነ
ውን ደም ይዞ በየዓመቱ ወደ ቅድስተ
ቅዱሳን እንደሚገባ፣ ክርስቶስ ራሱን ብዙ
ጊዜ መሥዋዕት ለማድረግ ወደ ሰማይ
አልገባም፡፡ 26እንዲህ ቢሆን ኖሮ፣ ዓለም
ከተፈጠረ ጀምሮ ክርስቶስ ብዙ ጊዜ መከ
ራን መቀበል ባስፈለገው ነበር፡፡ አሁን ግን
በዘመናት መጨረሻ ራሱን መሥዋዕት በማ
ድረግ ኀጢአትን ለማስወገድ ለአንዴና
ለመጨረሻ ጊዜ ተገልጦአል፡፡ 27ሰው አንድ ጊዜ
ሊሞት ከዚያም በኋላ በፍርድ ፊት ሊቆም
ተወስኖበታል፡፡ 28ክርስቶስ የብዙ ሰዎችን
ኀጢአት ለመሸከም፣ እንዲሁ አንድ ጊዜ
መሥዋዕት ሆኖአል፤ ሁለተኛ ጊዜም
ይገለጣል፤ ይህም ለሚጠባበቁት ድነትን

9፥1 ዘፀ25፥8
9፥2 ዘፀ25፥8፡9፡ 23-29፡30፡31-39፤ 26፥33፡34፤ዘሌ24፥5-8
9፥3 ዘፀ26፥31-33
9፥4 ዘፀ16፥32፡ 33፤25፥10-22፤ 30፥1-5፤31፥18፤ 32፥15፤ዘኍ17፥10
9፥5 ዘፀ25፥17-19፤ 20-22፤26፥34
9፥6 ዘኍ28፥3
9፥7 ቍ2፡3፤ ዘሌ16፥11-19፡34፤ ዕብ5፥2፡3
9፥8 ዮሐ14፥6፤ ዕብ3፥7፤10፥19፡20
9፥9 ዕብ5፥1፤7፥19፤ 8፥3፤10፥1
9፥10 ዘሌ11፥2-23፡ 25፡28፡40፤ዘኍ6፥3፤ ቈላ2፥16፤ ዕብ2፥17፤8፥2፡10፥1
9፥11 ቍ24፤ ዮሐ2፥19፡24፡26፡28፤ ዘሌ16፥6፡15፤ ሮሜ3፥25፤ ዕብ7፥27፤10፥4
9፥13 ዘኍ19፥9፡ 17፡18፤ዕብ10፥4
9፥14 መዝ51፥2፤ 65፥3፤ኤር33፥8፤ ዘካ13፥1፤ማቴ16፥16፤ ኤፌ5፥2፤ ቲቶ2፥14፤ 1ጴጥ3፥18፤ዕብ6፥1፤ 10፥2፡22
9፥15 ሉቃ22፥20፤ ሐሥ20፥32፤ሮሜ 8፥28፤11፥29፤ገላ3፥20፤ ዕ ብ6፥15፤7፥22፤ 10፥36
9፥18 ዘፀ24፥6-8
9፥19 ቍ12፤ዘፀ 24፥6-8፤ዕብ1፥1
9፥20 ዘፀ24፥8፤ ማቴ26፥28
9፥22 ዘፀ29፥21፤ ዘሌ8፥15፤17፥11
9፥23 ዕብ8፥5
9፥24 ቍ12፤ ሮሜ8፥34፤ ዕብ4፥14፤ዕብ8፥2
9፥25 ቍ7፡8፤ ዕብ10፥19
9፥26 ቍ12፡28፤ ዕብ4፥3፤7፥27፤ 1ዮሐ3፥5
9፥27 ዘፍ3፥19፤ 2ቆሮ5፥10
9፥28 ቍ12፡26፤ ማቴ16፥27፤ 1ቆሮ1፥7፤ ዕብ5፥9፤7፥27፤ 1ጴጥ2፥24

[ቶ]5 ወይም *የማስተሰረያውን መክደኛ*
[ኀ]11 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *ሊመጡ ስላሉት* ይላሉ፡፡
[ነ]14 ወይም *ከከንቱ የዘወትር ሥርዐቶች*
[ኘ]16 ይህንን ትርጕም የሚሰጠው የግሪክ ቃል *ኪዳን* ተብሎም ሊተረጎም ይችላል፤ እንዲሁም ቍ17

ለማምጣት እንጂ ኀጢአትን ለመሸከም
አይደለም።

## ክርስቶስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ያቀረበው መሥዋዕት

10 ሕጉ ወደ ፊት ለሚመጡት መል
ካም ነገሮች ጥላ ነው እንጂ፣
እውነተኛው አካል አይደለም፤ ስለዚህም
በየዓመቱ ዘወትር ያለማቋረጥ የሚቀርበው
ተደጋጋሚ መሥዋዕት፣ ለአምልኮ የሚቀ
ርቡትን ሰዎች ፍጹም ሊያደርጋቸው ከቶ
አይችልም። 2ፍጹም ሊያደርጋቸው ቢችል
ኖሮ፣ መሥዋዕት ማቅረቡን ይተዉት
አልነበረምን? ደግሞም ለአምልኮ የሚቀርቡት
ሰዎች ለአ ንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ስለሚነ
ጹ፣ በኅሊናቸው ኀጢአተኛነት ባልተሰ
ማቸውም ነበር። 3ነገር ግን እነዚህ
መሥዋዕቶች በየዓመቱ ኀጢአትን
የሚያስታውሱ ናቸው፤ 4ምክ ንያቱም
የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኀጢአትን
ማስወገድ አይችልም።
5ስለዚህ ክርስቶስ ወደ ዓለም በመጣ
ጊዜ እንዲህ ብሎአል፤

"መሥዋዕትንና መባን አልፈለግህም፤
ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ፤
6በሚቃጠል መሥዋዕትና ለኀጢአት በሚቀ
ርብ መሥዋዕት ደስ አልተሰኘህም።
7በዚያን ጊዜ እንዲህ አልሁ፤ 'ስለ እኔ በመ
ጽሐፍ እንደ ተጻፈ፣
አምላክ ሆይ፤ እነሆኝ፤ ፈቃድህን ለማ
ድረግ መጥቻለሁ።' "[አ]
8ሕጉ ይህ እንዲደረግ ቢያዝም፣ እርሱ
ግን በመጀመሪያ፣ "መሥዋዕትንና መባን፣ የሚ
ቃጠል መሥዋዕትንና ስለ ኀጢአት የሚቀ
ርበውን መሥዋዕት አልፈለግህም፤ ደስም
አልተሰኘህበትም" ይላል። 9ቀጥሎም፣
"እነሆኝ፤ ፈቃድህን ለማድረግ መጥቻ
ለሁ" አለ፤ ሁለተኛውን ለመመሥረት የመ
ጀመሪያውን ሻረ። 10በዚህ ፈቃድ በኢ
የሱስ ክርስቶስ ሥጋ አማካይነት ለአንዴና
ለመጨረሻ ጊዜ በቀረበው መሥዋዕት
ተቀ ድሰናል።
11ካህን ሁሉ በየዕለቱ ቆሞ አገልግሎ
ቱን ያከናውናል፤ ኀጢአትን ማስወገድ
ከቶ የማይችሉትን እነዚያኑ መሥዋዕቶች
ዘወትር ያቀርባል። 12ይህኛው ካህን ግን
አን ዱን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ፣
በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦአል፤ 13ከዚያን ጊ
ዜ ጀምሮ ጠላቶቹ የእግሩ መረገጫ እስኪ
ሆኑ ድረስ ይጠብቃል፤ 14ምክንያቱም
በአንዱ መሥዋዕት እነዚያን የሚቀደሱትን
ለዘላ ለም ፍጹማን አድርጎአቸዋል።
15መንፈስ ቅዱስም ስለዚህ ነገር
ይመሰክርልናል፤ በመጀመሪያ እንዲህ
ይላል፤ 16"ከዚያም በኋላ ከእነርሱ ጋር
የምገባው ኪዳን ይህ ነው፤
ይላል ጌታ፤
ሕጌን በልባቸው አኖራለሁ፤
በአእምሮአቸውም እጽፈዋለሁ።"
17ደግሞም፣
"ኀጢአታቸውንና ዐመፃቸውን፣
ከእንግዲህ አላስብም" ይላል።
18እነዚህ ይቅር ከተባሉ በኋላ ከእንግዲህ
ስለ ኀጢአት የሚቀርብ መሥዋዕት አይኖርም።

## እስከ መጨረሻው ጸንቶ ስለ መገኘት የቀረበ ጥሪ

19እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ በኢየሱስ
ደም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለመግባት
ድፍረት አግኝተናል፤ 20ይኸውም በመጋረጃው
ማለት በሥጋው በኩል በከፈተልን አዲ
ስና ሕያው መንገድ ነው። 21በእግዚአብሔር
ቤት ላይ የተሾመ ታላቅ ሊቀ ካህናት
ስላለን 22ከክፉ ኅሊና ለመንጻት ልባች
ንን ተረጭተን፣ ሰውነታችንንም በንጹሕ
ውሃ ታጥበን፣ በእውነተኛ ልብና በሙሉ
እምነት ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ። 23የተ
ስፋን ቃል የሰጠን ታማኝ ስለሆነ፣ አም
ነን የምንናገርለትን ተስፋ አጥብቀን እን
ያዝ። 24እርስ በርሳችንም ለፍቅርና ለመ
ልካም ሥራ እንዴት እንደምንነቃቃ እናስብ።
25አንዳንዶች ማድረጉን እንደተዉት መሰ
ብሰባችንን አንተው፤ ይልቁንም ቀኑ እየ
ተቃረበ መምጣቱን ስታዩ እርስ በርሳችን
እንበረታታ።
26የእውነትን ዕውቀት ከተቀበልን በኋላ
ሆን ብለን በኀጢአት ጸንተን ብንመላ
ለስ፣ ከእንግዲህ ለኀጢአት የሚሆን ሌላ
መሥዋዕት አይኖርም፤ 27የሚቀረው ግን
የሚያስፈራ ፍርድና የእግዚአብሔርን ጠላ
ቶች የሚበላ ብርቱ እሳት መጠበቅ ብቻ
ነው። 28የሙሴን ሕግ የናቀ ማንኛውም
ሰው ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች
ከመሰከሩበት ያለ ምሕረት ይገደል ነበር።
29ታዲያ የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ፣
የተቀደሰበ ትን የኪዳኑን ደም እንደ ተ
ራ ነገር የቈጠረ፣ የጸጋንም መንፈስ
ያክፋፋ እንደ ምን ያለ የባሰ ቅጣት
ይገባው ይመስላ ችኋል? 30"በቀል የእኔ
ነው፤ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ"
ያለውን እናውቀዋለንና፤ ደግሞም፣ "ጌታ
በሕዝቡ ላይ ይፈርዳል" ይላል። 31በሕ
ያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ እጅግ
የሚያስፈራ ነው።

[አ]7 ሰብዓ ሊቃናት ይመ።

10፥1 ቀኁ4፡11፤ ቈላ2፥17፤ዕብ7፥19፤ 8፥5፤9፥11፡23
10፥2 ዕብ9፥9
10፥3 ዘሌ16፥34፤ ዕብ9፥7
10፥4 ቀኁ1፡11፡ ዕብ9፥12፡13
10፥5 ዕብ1፥6፤2፥14፤ 1ጴጥ2፥24
10፥7 ዕዝ6፥2፤ መዝ40፥6-8፤ ኤር36፥2፤ማቴ26፥39
10፥8 ቀኁ5፡6፤ ማር12፥33
10፥9 ቀኁ7
10፥10 ቀኁ14፤ ኤፌ5፥26፤ ዕብ2፥14፤7፥27፤ 1ጴጥ2፥24
10፥11 ቀኁ1፡4፤ ዕብ5፥1
10፥12 ማር16፥19፤ ዕብ5፥1
10፥13 ኢሱ10፥24፤ ዕብ1፥13
10፥14 ቀኁ1፡10፤ ኤፌ5፥26
10፥15 ዕብ3፥7
10፥16 ኤር31፥33፤ ዕብ8፥10
10፥17 ኤር31፥34፤ ዕብ8፥12
10፥19 ዘሌ16፥2፤ ኤፌ2፥18፤3፥12፤ ዕብ9፥8፤12፡25
10፥20 ዕብ6፥19፤ 9፥3፡8
10፥21 ዕብ2፥17፤ 3፥6
10፥22 ቀኁ1፤ ሕዝ36፥25፤ ሐሥ22፥16፤ኤፌ3፥12፤ ዕብ7፥19፤9፥14፤ 12፥24፤1ጴጥ1፥2
10፥23 1ቆሮ1፥9፤ ዕብ3፥1፡6
10፥24 ቲቶ2፥14
10፥25 ሐሥ2፥42፤ 1ቆሮ3፥13፤ዕብ3፥13
10፥26 ዘፀ21፥14፤ ዘኁ15፥30፤ 1ጢሞ2፥4፤ዕብ5፥2፤ 6፥4-8፤2ጴጥ2፥20
10፥27 ኢሳ26፥11፤ 2ተሰ1፥7፤ ዕብ9፥27፤12፥29
10፥28 ዘዳ17፥6፡7፤ ማቴ18፥16፤ዕብ2፥2
10፥29 ማቴ4፥3፤ 26፥28፤1ቆሮ6፥11፤ ኤፌ4፥30፤ዕብ2፥3፤ 6፥4፡6፤12፥25፤ ራእ1፥5
10፥30 ዘዳ32፥35፡ 36፤መዝ135፥14፤ ሮሜ12፥19
10፥31 ኢሳ19፥16፤ ማቴ16፥16፤ 2ቆሮ5፥11

32ብርሃን ከበራላችሁ በኋላ፣ በመከራ
ውስጥ በብርቱ ተጋድሎ ጸንታችሁ የቆ
ማችሁበትን የቀድሞውን ዘመን ዐስቡ።
33አንዳንድ ጊዜ በአደባባይ ለስድብና ለስ
ደት ተጋልጣችሁ ነበር፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ
እንደዚህ ያለ መከራ ከደረሰባቸው ሰዎች
ጋር አብራችሁ መከራን ተቀብላችኋል።
34እናንተ ራሳችሁ የተሻለና ለዘወትር የሚ
ኖር ሀብት ያላችሁ መሆናችሁን ስለምታ
ውቁ ለታሰሩት ራራችሁ፤ ንብረታችሁም
ሲዘረፍ በደስታ ተቀበላችሁ።
35ስለዚህ ታላቅ ዋጋ ያለውን መታመና
ችሁን አትጣሉ። 36የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈ
ጽ
ማችሁ የተስፋ ቃሉን እንድትቀበሉ፣ ጸን
ታችሁ መቆም ያስፈልጋችኋል፤ 37ምክ
ንያቱም ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣
"የሚመጣው እርሱ ይመጣል፤
አይዘገይም።
38ጻድቅ ግን[ካ] በእምነት ይኖራል፤
ወደ ኋላ ቢያፈገፍግ፣
ነፍሴ በእርሱ ደስ አትሰኝም።"
39እኛ ግን አምነው ከሚድኑት ወገን እንጂ፣
ወደ ኋላ አፈግፍገው ከሚጠፉት አይደ
ለንም።

### የእምነት ቋሚ ምስክሮች

11 እምነት ተስፋ ያደረግነው ነገር
እንደሚፈጸም እርግጠኛ የምንሆ
ንበት፣ የማናየውም ነገር እውን መሆኑን የም
ንረዳበት ነው። 2አባቶችም የተመሰከረላ
ቸው በዚሁ ነው።
3ዓለማት በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተፈጠ
ሩ በእምነት እንረዳለን፤ ስለዚህ
የሚታየው ነገር የተፈጠረው ከሚታየው
እንዳልሆነ እንገነዘባለን።
4አቤል ከቃየል ይልቅ የበለጠ መሥ
ዋዕት ለእግዚአብሔር በእምነት አቀረበ።
እግዚአብሔር ስለ ስጦታው በተናገረለት
ጊዜ፣ እርሱ በእምነት ጻድቅ እንደ ሆነ
ተመሰከረለት፤ ቢሞትም እንኳ እስከ
አሁን በእምነቱ ይናገራል።
5ሄኖክ ሞትን እንዳያይ ከዚህ ዓለም
በእምነት ተወሰደ፤ እግዚአብሔርም ስለ ወሰደው
አልተገኘም፤ ከመወሰዱም በፊት እግዚ
አብሔርን ደስ እንዳሰኘ ተመስክሮለታ
ልና። 6ደግሞም ያለ እምነት እግዚአብሔርን
ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ምክንያቱም ወደ
እግዚአብሔር የሚቀርብ ሁሉ እግዚአብሔር
መኖሩንና ከልብ ለሚሹትም ዋጋ እንደ
ሚሰጥ ማመን አለበት።
7ኖኅ ገና ስለማይታየው ነገር እግዚአብሔር
ባስጠነቀቀው ጊዜ፣ እግዚአብሔርን ፈርቶ
ቤተ ሰዎቹን ለማዳን መርከብን በእምነት ሠራ፤
በእምነቱ ዓለምን ኰነነ፤ በእምነትም የሚገ

10፥32 ፊል1፥29፡30፤ዕብ6፥4
10፥33 1ቆሮ4፥9፤ፊል4፥14፤1ተሰ2፥14
10፥34 ዕብ11፥16፤13፥3፤1ጴጥ1፥4፡5
10፥35 ኤፌ3፥12
10፥36 ሮሜ5፥3፤ዕብ6፥15፤9፥15፤12፥1፤ያዕ1፥3፡4፡12፤5፥11፤2ጴጥ1፥6
10፥37 ማቴ11፥3፤ራእ22፥20
10፥38 ሮሜ1፥17፤ገላ3፥11፤ዕን2፥3፡4
11፥1 2ቆሮ4፥18፤ዕብ3፥6
11፥2 ቊ4፡39
11፥3 ዘፍ1፤ዮሐ1፡3፤ዕብ1፥2፤2ጴጥ3፥5
11፥4 ቊ2፡39፤ዘፍ4፥4፤ዕብ12፥24፤1ዮሐ3፥12
11፥5 ዘፍ5፥21-24
11፥6 ዕብ7፥19
11፥7 ቊ1፤ ዘፍ6፥9፡13-22፤ሕዝ14፥14፡20፤ሮሜ9፥30፤1ጴጥ3፥20
11፥8 ዘፍ12፥1-4፡7፤ሐሥ7፥2-4
11፥9 ዘፍ12፥8፤18፥1፡9፤ሐሥ7፥5፤ዕብ6፥17
11፥10 ቊ16፤ዕብ12፥22፤13፥14፤ራእ21፥2፡14
11፥11 ዘፍ17፥17-19፤18፥11-14፤21፥2፤1ቆሮ1፥9
11፥12 ዘፍ22፥17፤ሮሜ4፥19
11፥13 ቊ39፤ዘፍ23፥4፤ዘሌ25፥23፤ማቴ13፥17፤ፊል3፥20፤1ጴጥ1፥17፤2፥11
11፥15 ዘፍ24፥6-8
11፥16 ቊ10፤ዘፍ26፥24፤28፥13፤ዘፀ3፥6፡15፤ማር8፥38፤2ጢሞ4፥18፤ዕብ13፥14
11፥17 ዘፍ22፥1-10፤ያዕ2፥21
11፥18 ዘፍ21፥12፤ሮሜ9፥7
11፥19 ሮሜ4፥21፤ዮሐ5፥21
11፥20 ዘፍ27፥27-29፡39፡40
11፥21 ዘፍ48፥1፡8-22
11፥22 ዘፍ50፥24፡25፤ዘፀ13፥19፤ኢሱ24፥32
11፥23 ዘፀ1፥16፡22፤2፥2

ኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ።
8አብርሃም ርስት አድርጎ ወደሚቀበለው
ስፍራ እንዲሄድ በተጠራ ጊዜ በእምነት
ታዘዘ፤ ወዴት እንደሚሄድ ባያውቅም፣ እሺ
ብሎ ሄደ። 9በባዕድ አገር እንዳለ መጻተኛ
በተስፋዪቱ ምድር በእምነት ተቀመጠ፤
የተስፋውን ቃል አብረውት እንደሚወርሱት
እንደ ይስሐቅና እንደ ያዕቆብ በድንኳን
ኖረ፤
10ምክንያቱም መሠረት ያላትን፣
እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተ
ማ ይጠባበቅ ነበር። 11አብርሃም[ኻ] ምንም
እንኳ
ዕድሜው ቢገፋም፣ ሣራም[ኻ] ራሷ መካን
ብትሆንም፣ ተስፋን የሰጠውን ታማኝ አድ
ርጎ ስለ ቈጠረ[ኻ] በእምነት የልጅ አባት
ለመሆን በቃ። 12ስለዚህ እንደ ሞተ ሰው
ከሚቈጠር ከዚህ ከአንድ ሰው፣ እንደ
ሰማይ ከዋክብት የበዛና እንደ ባሕር ዳር
አሸዋ ተቈጥሮ የማያልቅ ዘር ተገኘ።
13እነዚህ ሁሉ የተሰጣቸውን የተስፋ
ቃል ሳያገኙ እምነታቸውን እንደ ጠበቁ
ሞቱ፤ ሆኖም ከሩቅ አይተው ሰላም
አሉት፤ በዚህ ምድር ሲኖሩ መጻተኞችና
እንግዶች መሆናቸውን ተገንዝበው ነበርና።
14እንደዚህ የሚሉት ሰዎች የራሳቸው
የሆነውን አገር እንደሚጠባበቁ ያሳያሉ።
15ትተውት የወጡትን አገር ቢያስቡ ኖሮ፣
ወደዚያ የመመለስ ዕድል ነበራቸው።
16አሁን ግን ከዚህ የሚበልጠውን ሰማያዊ
አገር ይናፍቃሉ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላ
ካቸው ተብሎ ሊጠራ አላፈረም፤ ከተ
ማን አዘጋጅቶላቸዋልና።
17አብርሃም እግዚአብሔር በፈተነው ጊዜ፣
ይስሐቅን መሥዋዕት አድርጎ በእምነት አቀ
ረበ፤ የተስፋን ቃል የተቀበለው እርሱ፣ አንድ
ልጁን ሊሠዋ ዝግጁ ነበር፤ 18ይህም እግዚ
አብሔር፣ "ዘርህ በይስሐቅ ይጠራል"
ያለለት ነበር። 19አብርሃም እግዚአብሔር
ሙታን ንን ሊያስነሣ እንደሚችል ተገንዝቦ
ነበር፤ ይስሐቅንም ከሞት የመነሣት
አምሳያ ሆኖ አገኘው።
20ይስሐቅ ወደፊት የሚሆነውን ዐስቦ
ያዕቆብንና ዔሳውን በእምነት ባረካቸው።
21ያዕቆብ በሚሞትበት ጊዜ
እያንዳንዳ ቸውን የዮሴፍን ልጆች
በእምነት ባረካቸው፤ በበትሩም ጫፍ
ዘንበል ብሎ ሰገደ።
22ዮሴፍ ሊሞት በተቃረበ ጊዜ፣ ስለ
እስራኤል ሕዝብ ከግብፅ መውጣት በእም
ነት ተናገረ፤ ስለ ዐጽሙም ትእዛዝ ሰጠ።
23ሙሴ ከተወለደ በኋላ፣ ወላጆቹ
መልከ መልካም ሕፃን መሆኑን ስላዩ
በእምነት

[ካ]38 ወይም *የእኔ ጽድቅ ግን*
[ኻ]11 ወይም *ሣራ … አብርሃምም … ስለቈጠረች*

ሦስት ወር ሸሸጉት፤ የንጉሡንም ዐዋጅ
አልፈሩም።
24ሙሴ ካደገ በኋላ፣ የፈርዖን የልጅ
ልጅ መባልን በእምነት እምቢ አለ።
25ለጥቂት ጊዜ በኀጢአት ከሚገኝ ደስታ
ይልቅ፣ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከ
ራን መቀበል መረጠ። 26ከግብፅ ሀብት
ይልቅ ስለ ክርስቶስ መከራን መቀበል
እጅግ የሚበልጥ ሀብት መሆኑን ተገነዘበ፤
ወደፊት የሚቀበለውን ብድራት ከሩቅ
ተመልክቶአልና። 27የንጉሡን ቍጣ ሳይፈራ
ግብፅን ለቆ በእምነት ወጣ፤ የማይታየው
ንም እንዳየው አድርጎ በመቍጠር በሐሳቡ
ጸና። 28በኵሮች የሆኑትን የሚገድለው
ቀሣፊ የእስራኤልን በኵር ልጆች እንዳይ
ገድል ፋሲካን በእምነት አደረገ፤ ደምንም
ረጨ።
29ሕዝቡ በደረቅ መሬት እንደሚኼድ
ቀይ ባሕርን በእምነት ተሻገሩ፤ ግብፃው
ያን ግን እንደዚሁ ለማድረግ ሲሞክሩ ሰጠሙ።
30ሕዝቡ የኢያሪኮን ግንብ ሰባት ቀን
ከዞሩት በኋላ፣ በእምነት ወደቀ።
31ዝሙት አዳሪዋ ረዓብ፣ ሰላዮቹን በሰ
ላም ስለ ተቀበለቻቸው ከማይታዘዙት[ሠ]
ጋር ያልጠፋችው በእምነት ነው።
32እንግዲህ ከዚህ በላይ ምን ልበል? ስለ
ጌዴዎን፣ ስለ ባርቅ፣ ስለ ሳምሶን፣ ስለ ዮፍ
ታሔ፣ ስለ ዳዊት፣ ስለ ሳሙኤል፣ እንዲ
ሁም ስለ ነቢያት እንዳልተርክ ጊዜ የለ
ም። 33እነዚህ በእምነት መንግሥታትን
ድል ነሡ፤ በቅን ፈረዱ፤ የተሰጠውን የተ
ስፋ ቃል ተቀበሉ፤ የአንበሶችን አፍ ዘጉ፤
34የእሳትን ኀይል አጠፉ፤ ከሰይፍ ስለት
አመለጡ፤ ከድካማቸው በረቱ፤ በጦርነት
ኀያል ሆኑ፤ ባዕዳን ወታደሮችን አባረሩ።
35ሴቶች ሙታናቸው ተነሡላቸው። ሌሎቹ
ደግሞ የተሻለውን ትንሣኤ ለማግኘት ሲሉ፣
መትረፍን ንቀው ለሞት ለሚዳርግ ሥቃይ
ራሳቸውን ሰጡ፤ ከዚህም ነጻ ለመውጣት
አልፈለጉም። 36አንዳንዶቹ መዘባበቻ ሆኑ፤
ተገረፉ። ሌሎቹ ደግሞ ታስረው ወደ
ወህኒ ተጣሉ፤ 37በድንጋይ ተወገሩ፤ በመ
ጋዝ ለሁለት ተሰነጠቁ፤[ዐ] በሰይፍ ተወግ
ተው ሞቱ፤ እየተጐሳቈሉ፣ እየተሰደዱና
እየተንገላቱ የበግና የፍየል ቈዳ ለብሰው
ዞሩ፤ 38ዓለም ለእነርሱ አልተገባቻቸውምና።
በየበረሓውና በየተራራው፣ በየዋሻውና
በየጕድጓዱ ተንከራተቱ ።
39እነዚህ ሁሉ ስለ እምነታቸው የተመሰ
ከረላቸው ቢሆኑም ከእነርሱ ማንም የተስፋ
ውን ቃል የተቀበለ የለም። 40እግዚአብሔር ለኛ
የሚበልጥ ነገር ስላዘጋጀ፣ ያለ እኛ ፍጹማን
ሊሆኑ አልቻሉም።

11፥24 ዘፀ2፥10፡11
11፥25 ቀኍ37
11፥26 ሉቃ14፥33፤ ዕብ10፥35፤13፥13
11፥27 ዘፀ12፥50፡51
11፥28 ዘፀ12፥21-23፤ 1ቆሮ10፥10
11፥29 ዘፀ14፥21-31
11፥30 ኢሱ6፥12-20
11፥31 ኢሱ2፥1፡9-14፤ 6፥22-25፤ያዕ2፥25
11፥32 መሳ4-5፤ 6-8፤11-12፤13-16፤ 1ሳሙ1፥20፤16፥1፡13
11፥33 ዳን6፥22፤ 2ሳሙ8፥1-3
11፥34 ዘፀ18፥4፤ መሳ15፥8፤2ዜና20፥7፤ ዳን3፥19-27
11፥35 1ነገ17፥22፡ 23፤2ነገ4፥36፡37
11፥36 ዘፍ39፥20፤ ኤር20፥2፤37፥15
11፥37 1ነገ19፥10፤ 2ነገ1፥8፤2ዜና24፥21፤ ኤር26፥23
11፥38 1ነገ18፥4፤ 19፥9
11፥39 ቀኍ2፥4፡ 13፤ዕብ10፥36
11፥40 ዕብ2፥10፤ ራእ ፥11

## እግዚአብሔር ልጆቹን ይቀጣል

12 እንግዲህ እነዚህን የመሰሉ ብዙ
ምስክሮች እንደ ደመና
በዙሪያችን ካሉልን፣ ሸክም የሚሆንብንን
ሁሉ፣ በቀላሉም ተብትቦ የሚይዘንን ኀጢ
አት አስወግደን በፊታችን ያለውን ሩጫ
በጽናት እንሩጥ። 2የእምነታችን ጀማሪና
ፍጹም አድራጊ የሆነውን ኢየሱስን እንመ
ልከት፤ እርሱ በፊቱ ስላለው ደስታ መስ
ቀሉን ታግሦ፣ የመስቀሉንም ውርደት ንቆ
በእግዚአብሔር ዙፋን ቀ ተቀምጦአል። 3እንግ
ዲህ ዝላችሁ ተስፋ እንዳትቈርጡ፣ ከኀጢ
አተኞች የደረሰበትን እንዲህ ያለውን ተቃ
ውሞ የታገሠውን እርሱን ዐስቡ።
4ከኀጢአት ጋር ስትታገሉ ገና ደማች
ሁን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወማች
ሁም። 5ልጆች እንደመሆናችሁ እንዲህ በማ
ለት የተናገራችሁን ማበረታቻ ቃልም ረስ
ታችኋል፦
"ልጄ ሆይ፤ የጌታን ቅጣት አታቃል፤
በሚገሥጽህም ጊዜ ተስፋ አትቍረጥ፤
6ምክንያቱም ጌታ የሚወደውን
ይገሥጻል፤
እንደ ልጅ የሚቀበለውንም ይቀጣል።"
7እግዚአብሔር እንደ ልጆቹ ይዞአ
ችኋልና የተግሣጹን ምክር ታገሡ፤ ለመሆኑ
አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማን ነው? 8ልጆች
ሁሉ በሚቀጡበት ቅጣት ተካፋይ ካልሆ
ናችሁ፣ ዲቃሎች እንጂ ልጆች አይደላች
ሁም። 9ከዚህም በላይ፣ እኛ ሁላችን የሚ
ቀጡን ምድራዊ አባቶች ነበሩን፤ እናከብራ
ቸውም ነበር። ታዲያ ለመናፍስት አባት
እንዴት አብልጠን በመገዛት በሕይወት
አንኖርም? 10አባቶቻችን መልካም መስሎ
እንደታያቸው ለጥቂት ጊዜ ይቀጡን ነበር፤
እግዚአብሔር ግን የቅድስናው ተካፋዮች
እንድ ንሆን ለእኛ ጥቅም ሲል ይቀጣናል።
11ቅጣት ሁሉ በወቅቱ የሚያሳዝን እንጂ
ደስ የሚያሰኝ አይመስልም፤ በኋላ ግን
ለለመዱት ሰዎች የጽድቅና የሰላም ፍሬ
ያስገኝላቸዋል።
12ስለዚህ የዛለውን ክንዳችሁንና የደከ
መውን ጕልበታችሁን አበርቱ። 13ዐንካ
ሳው እንዲፈወስ እንጂ የባሰውኑ እንዳያነ
ክስ "ለእግራችሁ ቀና መንገድ አብጁ።"

## እግዚአብሔርን ስላለመታዘዝ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

14ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር
የሚቻላችሁን ሁሉ አድርጉ፤ ለመቀደስም

12፥1 1ቆሮ9፥24፤ ዕብ10፥36
12፥2 መዝ25፥15፤ ማር16፥19፤ፊል2፥8፡ 9፤ዕብ2፥9፡10፤13፥13
12፥3 ገላ6፥9፤ራእ2፥3
12፥4 ዕብ10፥32-34፤ 13፥13
12፥5 ቀኍ3
12፥6 መዝ94፥12፤ 119፥75፤ምሳ3፥11፡12፤ ራእ3፥19
12፥7 ዘዳ8፥5፤ 2ሳሙ7፥14፤ ምሳ13፥24
12፥8 1ጴጥ5፥9
12፥9 ዘኍ16፥22፤ 27፥16፤ኢሳ38፥16፤ ራእ22፥6
12፥10 2ጴጥ1፥4
12፥11 ኢሳ32፥17፤ ያዕ3፥17፡18
12፥12 ኢሳ35፥3
12፥13 ምሳ4፥26፤ ገላ6፥1
12፥14 ማቴ5፥8፤ ሮሜ6፥22፤14፥19

ሠ31 ወይም *ከማያምኑት*
ዐ37 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *በድንጋይ ተወገሩ፤ ለፈተና አልፈው ተሰጡ፤*

ፈልጉ፤ ያለ ቅድስና ማንም ጌታን ማየት
አይችልም፤ 15ከእናንተ ማንም የእግዚአብሐ
ር
ጸጋ እንዳይጐድልበት ደግሞም መራራ ሥር
በቅሎ ችግር እንዳያስከትልና ብዙዎችን እንዳ
ይበክል ተጠንቀቁ። 16ለአንድ ጊዜ መብል
ሲል ብኵርናውን እንደ ሸጠው እንደ ዔሳው
ማንም ሴሰኛ ወይም እግዚአብሔርን
የማያከብር ሆኖ እንዳይገኝ ተጠንቀቁ።
17በኋላም ይህንኑ በረከት ሊወርስ በፈለገ
ጊዜ፣ እንደ ተከለከለ ታውቃላችሁ፤
በረከ ቱን በእንባ ተግቶ ቢፈልግም
መልሶ ሊያ ገኘው አልቻለም።
18ሊዳሰስ ወደሚችለውና በእሳት ወደ
ሚቃጠለው ተራራ፣ ወደ ጨለማው፣ ወደ
ጭጋጉና ወደ ዐውሎ ነፋሱ አልደረሳች
ሁም፤ 19ወደ መለከት ድምፅ፣ ወይም ቃልን
ወደሚያሰማ ድምፅ አልመጣችሁም፤ የሰሙ
ትም ሌላ ቃል ተጨምሮ እንዳይናገራቸው
ለመኑ። 20ምክንያቱም "እንስሳ እንኳ ተራ
ራውን ቢነካ፣ በድንጋይ ተወግሮ ይሙት"
የሚለውን ትእዛዝ መሸከም አልቻሉም።
21በዚያ ይታይ የነበረውም ሁኔታ እጅግ
አስፈሪ ነበርና፣ ሙሴ "በፍርሀት
ተንቀጠቀጥሁ" አለ።
22እናንተ ግን ወደ ጽዮን ተራራ፣ ወደ
ሰማያዊት ኢየሩሳሌም፣ ወደ ሕያው እግዚ
አብሔር ከተማ መጥታችኋል፤ በደስታ ወደ
ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፣ 23ስ
ማ ቸው በሰማይ ወደ ተጻፈው ወደ በኵ
ራት ማኅበር ቀርባችኋል፤ የሁሉ ዳኛ ወደ
ሆነው ወደ እግዚአብሔር፣ ፍጹምነትን
ወዳገኙት ወደ ጻድቃን መንፈሶች፣ 24የአዲስ
ኪዳን መካከ ለኛ ወደ ሆነው ወደ ኢ
የሱስ፣ እንዲሁም ከአቤል ደም የተሻለ
ቃል ወደሚናገረው ወደ ተረጨው ደም
ደርሳችኋል።
25የሚናገረውን እርሱን እምቢ እንዳ
ትሉት ተጠንቀቁ። እነዚያ ከምድር ሆኖ
ሲያስጠነቅቃቸው የነበረውን እምቢ ባሉ ጊ
ዜ ካላመለጡ፣ እኛ ከሰማይ የመጣው ሲ
ያስጠነቅቀን ከእርሱ ብንርቅ እንዴት
ልናመ ልጥ እንችላለን? 26በዚያን ጊዜ
ድምፁ ያናወጠው ምድርን ነበር፤ አሁን
ግን፣ "ምድርን ብቻ ሳይሆን፣ ሰ
ማያትንም አንድ ጊዜ ደግሜ
አናውጣለሁ" ብሎ ቃል ገብቶአል። 27አንድ
ጊዜ "ደግሜ" የሚለው ቃል
የሚያመለክተው የማይናወጡት ጸን ተው
ይኖሩ ዘንድ፣ የሚናወጡት ይኸውም
የተፈጠሩት የሚወገዱ መሆናቸውን
ነው።
28ስለዚህ ከቶ የማይናወጥ መንግሥት
ስለምንቀበል እግዚአብሔርን እናመስግን፤
ደግሞም ደስ በሚያሰኘው መንገድ
በአክብሮ ትና በፍርሀት እናምልከው፤
29አምላካችን የሚያጠፋ እሳት ነውና።

## የመጨረሻ ምክር

13 እርስ በርሳችሁ እንደ ወንድማ
ማች ተዋደዱ። 2እንግዶችን መቀ
በል አትርሱ፤ አንዳንዶች ይህን ሲያደርጉ፣
ሳያውቁ መላእክትን አስተናግደዋልና።
3በእስር ላይ ያሉትን ከእነርሱ ጋር እንደ
ታሰራችሁ ሆናችሁ ዐስቡአቸው፤ እንዲሁም
በሰው እጅ የሚንገላቱትን ራሳችሁ መከራ
እንደምትቀበሉ አድርጋችሁ ዐስቡአቸው።
4ጋብቻ በሁሉም ዘንድ ይከበር፤ መኝታ
ውም ንጹሕ ይሁን፤ ምክንያቱም እግዚአብ
ሔር በአመንዝሮችና በሴሰኞች ሁሉ ላይ
ይፈርዳል። 5ራሳችሁን ከፍቅረ ንዋይ ጠብቁ፤
ባላችሁ ነገር ረክታችሁ ኑሩ፤ ምክንያቱም
እግዚአብሔር፣
"ከቶ አልተውህም፤
በፍጹም አልጥልህም" ብሎአል።
6ስለዚህ በሙሉ ልብ፣
"ጌታ ረዳቴ ነው፤ አልፈራም፤
ሰው ምን ሊያደርገኝ ይችላል?" እንላለን።
7የእግዚአብሔርን ቃል የነገሯችሁን መሪ
ዎቻችሁን ዐስቡ፤ የኑሮአቸውን ፍሬ ተመ
ልከቱ፤ በእምነታቸውም ምሰሉአቸው።
8ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፣ ዛሬም ለዘላለ
ምም ያው ነው።
9በልዩ ልዩ ዐይነት እንግዳ ትምህር
ቶች አትወሰዱ፤ ልባችን የሚጸናው በጸጋ
እንጂ የምግብ ሥርዐት በመጠበቅ አይደ
ለም፤ ይህንን ሥርዐት የሚጠብቁት እንኳ
በዚህ አልተጠቀሙም። 10በድንኳኒቱም
የሚያገለግሉ ከዚያ ሊበሉ መብት ያላገ
ኙበት መሠዊያ አለን።
11ሊቀ ካህናቱ ስለ ኀጢአት ስርየት
የሚሆነውን የእንስሳት ደም ይዞ ወደ
ቅድስተ ቅዱሳን ይገባል፤ የእንስሳቱ ሥጋ
ግን ከሰፈር ውጭ ይቃጠላል። 12እንዲ
ሁም ኢየሱስ በራሱ ደም አማካይነት ሕዝ
ቡን ሊቀድስ ከከተማው በር ውጭ መከራን
ተቀበለ። 13ስለዚህ እኛም እርሱ የተሸከ
መውን ውርደት ተሸክመን ከሰፈር ውጭ
ወደ እርሱ እንውጣ። 14ምክንያቱም በዚህ
ቋሚ ከተማ የለንም፤ ነገር ግን ወደፊት
የምትመጣዋን ከተማ እንጠብቃለን።
15ስለዚህ ዘወትር የምስጋናን መሥዋዕት
ይኸውም ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮ
ችን ፍሬ በኢየሱስ አማካይነት ለእግዚአብሔር

12÷15 ዘዳ29÷18፤ ገላ5÷4፤ዕብ3÷12፡4÷1
12÷16 ዘፍ25÷29-34፤ 1ቆሮ6÷18
12÷17 ዘፍ27÷30-40
12÷18 ዘፀ19÷12-22፤ 20÷18፤ዘዳ4÷11
12÷19 ዘፀ20÷18፡ 19፤ዘዳ4÷12፤5÷5፡25፤ 18÷16
12÷20 ዘፀ19÷12፡ 13
12÷21 ዘዳ9÷19
12÷22 ኢሳ24÷23፤ 60÷14፤ማቴ16÷16፤ ገላ4÷26፤ ዕብ11÷10፤ 13÷14፤ራእ14÷1
12÷23 ዘፍ18÷25፤ ዘፀ4÷22፤መዝ94÷2፤ ፊል3÷12፤ራእ20÷12
12÷24 ዘፍ4÷10፤ ገላ3÷20፤ዕብ9÷19፤ 10÷22፤11÷4፤1ጴጥ1÷2
12÷25 ዘዳ18÷19፤ ዕብ1÷1፤2÷2፡3፤ 3÷12፤8÷5፤10÷29፤ 11÷7
12÷26 ዘፀ9÷18፤ ሐጌ2÷6
12÷27 ኢሳ34÷4፤ 54÷10፤1ቆሮ7÷31፤ ዕብ1÷11፡12፤ 2ጴጥ3÷10፤1ዮሐ2÷17
12÷28 መዝ15÷5፤ ዳን2÷44፤ሚል2÷5፤ 4÷2፤ዕብ13÷15
12÷29 ዘፀ24÷17፤ ዘዳ4÷24፤9÷3፤ መዝ97÷3፤ ኢሳ33÷14፤2ተሰ1÷7
13÷1 ሮሜ12÷10
13÷2 ዘፍ18÷1-33፤ 19÷1-3፤ኢዮ31÷32፤ ማቴ25÷35፤ ሮሜ12÷13
13÷3 ማቴ25÷36፤ ቈላ4÷18፤ዕብ10÷34
13÷4 ዘዳ22÷22፤ ሚል2÷15፤1ቆሮ6÷9፤ 7÷38፤1ጢሞ4÷3፤ ራእ22÷15
13÷5 ዘዳ31÷6፡8፤ ኢሱ1÷5፤ፊል4÷11፤ 1ጢሞ3÷3፤6÷6፡8
13÷6 መዝ118÷6፡8
13÷7 ቀኍ17፡24፤ 1ቆሮ16÷16፤ ዕብ4÷12፤6÷12
13÷8 መዝ102÷27፤ ዕብ1÷12
13÷9 ኤፌ4÷14፤ ቈላ2÷7፡16፤ዕብ9÷10
13÷10 1ቆሮ9÷13፤ 10÷18፤ዕብ8÷5
13÷11 ዘፀ29÷14፤ ዘሌ4÷12፡21፤9÷11፤ 16÷15፡27
13÷12 ዮሐ19÷17፤ ሮሜ3÷25፤ኤፌ5÷26
13÷13 ሉቃ9÷23፤ ዕብ11÷26
13÷14 ፊል3÷20፤ ዕብ11÷10፤ 27፤ 12÷22፡27
13÷15 ኢሳ57÷19፤ ሆሴ14÷2፤ 1ጴጥ2÷5

እናቅርብ። 16ደግሞም መልካም ማድረግ
ንና ያላችሁንም ከሌሎች ጋር መካፈልን
አትርሱ፤ እግዚአብሔር ደስ የሚሰኘው እንደ
ዚህ ባለው መሥዋዕት ነውና።
17ለመሪዎቻችሁ ታዘዙ፤
ተገዙላቸውም። ምክንያቱም እነርሱ
በብርቱ የሚያስጠይቃ ቸው ነገር
ስላለባቸው፣ ስለ ነፍሳችሁ ጕዳይ ይተጋሉ።
ስለዚህ ሥራቸውን በሐዘን ሳይ ሆን
በደስታ ማከናወን እንዲችሉ ታዘዟ ቸው።
አለበለዚያ አይበጃችሁም።
18ለእኛ ደግሞ ጸልዩልን። በሁሉም መን
ገድ በመልካም አኗኗር ለመኖር የሚናፍቅ
ንጹሕ ኅሊና እንዳለን እርግጠኞች ነን።
19በተለይም ወደ እናንተ በፍጥነት ተመልሼ
እንድመጣ ትጸልዩልኝ ዘንድ ዐደራ እላች
ኋለሁ።
20በዘላለም ኪዳን ደም የበጎች ታላቅ
እረኛ የሆነውን ጌታችን ኢየሱስን ከሞት
ያስነሣው የሰላም አምላክ፣ 21ፈቃዱን እንድ
ታደርጉ በመልካም ነገር ሁሉ ያስታጥቃ
ችሁ፤ ደስ የሚያሰኘውንም በኢየሱስ ክር
ስቶስ በኩል በእኛ ያድርግ፤ ለእርሱ እስከ
ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን።
22ወንድሞች ሆይ፤ የጻፍሁላችሁ መል
እክት አጭር እንደ መሆኑ፣ የምክር ቃሌን
በትዕግሥት እንድትቀበሉ ዐደራ እላችኋ
ለሁ።
23ወንድማችን ጢሞቴዎስ እንደተፈታ
ታውቁ ዘንድ እፈልጋለሁ፤ ቶሎ ከመጣ፣
ከእርሱ ጋር ላያችሁ እመጣለሁ።
24ለመሪዎቻችሁ ሁሉና ለቅዱሳን ሁሉ
ሰላምታ አቅርቡልኝ። ከኢጣሊያ የሆኑ
ትም ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።
25ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

13፥16 ሮሜ12፥13፤ ፊል4፥18
13፥17 ቀኍ7፡24፤ ኢሳ62፥6፤ሐሥ20፥28
13፥18 ሐሥ23፥1፤ 1ተሰ5፥25
13፥19 ፊሞ22
13፥20 ዘፍ9፥16፤ 17፥7፡13፡19፤ ኢሳ55፥3፤61፥8፤ ሕዝ37፥26፤ ማቴ26፥28፤ ዮሐ10፥11፤ ሐሥ2፥24፤ ሮሜ15፥33
13፥21 ሮሜ11፥36፤ 2ቆሮ9፥8፤ፊል2፥13፤ 1ዮሐ3፥22
13፥22 1ጴጥ5፥12
13፥23 ሐሥ16፥1
13፥25 ቈላ4፥18
13፥24 ቀኍ7፡17፤ሐሥ18፥2

# የያዕቆብ መልእክት

1 የእግዚአብሔርና የጌታ የኢየሱስ
ክርስቶስ አገልጋይ የሆነው ያዕቆብ፤ ለዐ
ሥራ ሁለቱ ነገዶች፤
ሰላም ለእናንተ ይሁን።

## መከራና ፈተና

2ወንድሞቼ ሆይ፤ ልዩ ልዩ መከራ ሲደ
ርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት
3ምክንያቱም የእምነታችሁ መፈተን ትዕ
ግሥትን እንደሚያስገኝ ታውቃላችሁ።
4ምንም የማይጐድላችሁ ፍጹማንና ምሉኣን
እንድትሆኑ ትዕግሥት ሥራውን ይፈጽም።
5ከእናንተ ማንም ጥበብ ቢጐድለው፣ ሳይነቅፍ
በልግስና ለሁሉም የሚሰጠውን እግዚአብሔርን
ይለምን፤ ለእርሱም ይሰጠዋል። 6ዳሩ ግን
ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፤ ምክንያቱም
የሚጠራጠር ሰው በነፋስ እንደሚገፋና እን
ደሚናወጥ የባሕር ማዕበል ነው። 7ያ ሰው፣
ከጌታ አንዳች ነገር አገኛለሁ ብሎ አያስብ፤
8እርሱ በሁለት ሐሳብ የተያዘና በመንገዱ
ሁሉ የሚወላውል ነው።

9ዝቅ ያለው ወንድም ከፍ በማለቱ
ይመካ። 10ባለ ጸጋውም በመውረዱ ይመካ፤
እንደ ሣር አበባ ይረግፋልና። 11ፀሓይ በነ
ዲድ ሙቀቷ ወጥታ ሣሩን ታጠወልጋለ
ችና፤ አበባው ይረግፋል፤ ውበቱም ይጠፋል፤
እንዲሁም ባለ ጸጋ ሰው፣ በዕለት ተግ
ባሩ ሲዋትት ሳለ ይጠፋል።

12በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤
ምክ ንያቱም ፈተናን ሲቋቋም እግዚአብሔር
ለሚወ ዱት የሰጠውን ተስፋ፣ የሕይወትን
አክሊል ያገኛል።

13ማንም ሲፈተን፣ "እግዚአብሔር ፈተነኝ" አይ
በል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በክፉ አይፈተ
ንም፤ እርሱም ማንንም አይፈትንም፤
14ነገር ግን እያንዳንዱ የሚፈተነው በራሱ
ክፉ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ነው። 15ምኞ
ትም ከፀነሰች በኋላ ኀጢአትን ትወልዳለች፤
ኀጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች።

16የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤ አትታ
ለሉ። 17በጎ ስጦታና ፍጹም በረከት ሁሉ
ከላይ ከሰማይ ብርሃናት አባት ይወርዳሉ፤
በእርሱ ዘንድ መለዋወጥ ከመዞር የተነሣ
የሚያርፍ ጥላም የለም። 18የፍጥረቱ በኵራ
ት እንድንሆን በገዛ ፈቃዱ በእውነት ቃል
ወለ ደን።

## ሰምቶ በሥራ ላይ ማዋል

19የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤ ይህን
አስተውሉ፤ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ፣
ለመናገር የዘገየ፣ ለቍጣም የዘገየ ይሁን፤
20የሰው ቍጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አያመጣ
ምና። 21ስለዚህ ርኵሰትንና ተንሰራፍቶ
የሚገኘውን ክፋትን አስወግዳችሁ ነፍሳችሁን
ማዳን የሚችለውን፣ በውስጣችሁም የተተከለ
ውን ቃል በትሕትና ተቀበሉ።

22ቃሉ የሚናገረውን አድርጉ እንጂ
ሰሚዎች ብቻ ሆናችሁ ራሳችሁን አታታ
ልሉ። 23ቃሉን የሚሰማ፣ ነገር ግን የሚለ
ውን የማይፈጽም ሰው ፊቱን በመስተዋት
እንደሚያይ ሰው ነው፤ 24ራሱንም አይቶ
ይሄዳል፤ ወዲያውም ምን እንደሚመስል
ይረሳል፤ 25ነገር ግን ነጻ የሚያወጣውን
ፍጹም ሕግ ተመልክቶ የሚጸና፣ የሰማ
ውን የሚያደርግና የማይረሳ ሰው በሥራው
የተባረከ ይሆናል።

26አንደበቱን ሳይገታ፣ ልቡን እያሳተ ሃይ
ማኖተኛ ነኝ የሚል ሰው፣ ራሱን ያታል
ላል፤ ሃይማኖቱም ከንቱ ነው። 27በእግዚአብሐ
ር አብ ፊት ንጹሕና ነውር የሌለበት ሃይ
ማኖት ይህ ነው፤ ወላጆቻቸው የሞቱባቸውን
ልጆችና ባሎቻቸው የሞቱባቸውን ሴቶች
በችግራቸው መርዳትና ከዓለም ርኵሰት
ራስን መጠበቅ ነው።

## አድልዎ ማድረግ አይገባም

2 ወንድሞቼ ሆይ፤ ክቡር በሆነው በጌ
ታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የምታምኑ
እንደመሆናችሁ አድልዎ አታድርጉ። 2የወ
ርቅ ቀለበት ያደረገና ያማረ ልብስ የለበሰ
ሰው ወደ ጉባኤያችሁ ቢመጣ እንዲሁም
ያደፈ ልብስ የለበሰ ድኻ ሰው ቢገባ፣
3ያማረ ልብስ ለለበሰው የተለየ አክብሮት
በማሳየት፣ "ለአንተ የሚሆን መልካም
መቀመጫ ይኸውልህ" ብትሉትና ድኻውን
ሰው ግን፣ "አንተ በዚያ ቁም" ወይም "ከእ
ግሬ በታች በወለሉ ላይ ተቀመጥ" ብት
ሉት፣ 4በመካከላችሁ አድልዎ
ማድረጋችሁ አይደለምን? ደግሞስ
በክፉ ሐሳብ የተ ያዛችሁ ፈራጆች
መሆናችሁ አይደለምን?

5የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤ ስሙ፤
እግዚአብሔር በእምነት ባለጸጋ እንዲሆኑና
እርሱን ለሚወዱም ተስፋ የተሰጣቸውን

1፥1 ዘጸ32፥26፤ ዮሐ7፥35፤ ሐሥ15፥13፡23፤26፥7፤ሮሜ1፥1፤ ቲቶ1፥1፤1ጴጥ1፥1
1፥2 ቀ-12፤ ማቴ5፥12፤ ዕብ10፥34፤12፥11
1፥3 ዕብ10፥36፤ 1ጴጥ1፥7
1፥4 1ቆሮ2፥6
1፥5 1ነገ3፥9፡10፤ መዝ51፥6፤ምሳ2፥3-6፤ ዳን1፥17፤2፥21፤ ማቴ7፥7
1፥6 ማቴ21፥21፤ ማር11፥24
1፥8 መዝ119፥113፤ ያዕ4፥8፤2ጴጥ2፥14
1፥9 ማቴ23፥12
1፥10 ኢዮ14፥2፤ መዝ103፥15፡16፤ ኢሳ40፥6፡7፤ 1ቆሮ7፥31፤1ጴጥ1፥24
1፥11 ዝ102፥4፡11፤ ኢሳ40፥6፡8፤ማቴ20፥12
1፥12 ቀ-2፤ዘፍ22፥1፤ ዘፀ20፥6፤1ቆሮ2፥9፤ 8፥3፤9፥25፤ያዕ2፥5፤ 5፥11፤1ጴጥ3፥14
1፥14 ምሳ19፥3
1፥15 ዘፍ3፥6፤ ኢዮ15፥35፤መዝ7፥14፤ ኢሳ59፥4፤ሮሜ6፥23
1፥16 ቀ-19፤ 1ቆሮ6፥9፤ያዕ2፥5
1፥17 ዘፍ1፥16፤ ዘኍ23፥19፤መዝ85፥12፤ 102፥27፤136፥7፤ ዳን2፥22፤ሚል3፥6፤ ዮሐ3፥27፤ያዕ3፥15፡17፤1ዮሐ1፥5
1፥18 ኤር2፥3፤ ዮሐ1፥13፤2ጢሞ2፥15፤ ራእ14፥4
1፥19 ቀ-16፤ ምሳ10፥19፤ያዕ2፥5፤ 3፥3-12
1፥20 ማቴ5፥22
1፥21 ኤፌ1፥13፤ 4፥22 1፥22 ማቴ7፥21፤ ያዕ2፥14-20
1፥25 መዝ19፥7፤ ዮሐ8፥32፤13፥17፤ ገላ2፥4፤ያዕ2፥12
1፥26 መዝ34፥13፤ 39፥1፤141፥3፤ያዕ3፥2-12፤ 1ጴጥ3፥10
1፥27 ዘዳ14፥29፤ ኢዮ31፥16፡17፡21፤ መዝ146፥9፤ ኢሳ1፥17፡23፤ማቴ25፥36፤ሮሜ12፥2፤ ያዕ4፥4፤2ጴጥ1፥4፤2፥20
2፥1 ቀ-9፤ ዘሌ19፥15፤ዘዳ1፥17፤ምሳ24፥23፤ሐሥ7፥2፤ 10፥34፤1ቆሮ2፥8 2፥4 ዮሐ7፥24 2፥5 ኢዮ34፥19፤ ማቴ25፥34፤ሉቃ12፥21፤1ቆሮ1፥26-28፤ያዕ1፥12፡16፡19፤ ራእ2፥9

መንግሥት እንዲወርሱ የዚህን ዓለም
ድኾች አልመረጠምን? 6እናንተ ግን ድኾ
ችን አዋረዳችሁ፤ እናንተን የሚያስጨንቋችሁ
ሀብታሞች አይደሉምን? ወደ ፍርድ ቤት
የሚጐትቷችሁስ እነርሱ አይደሉምን?
7በእናንተ የተጠራውን ክቡር የሆነውን ስም
የሚሳደቡ እነርሱ አይደሉምን?
8በመጽሐፍ፣ “ባልንጀራህን እንደ ራስህ
አድርገህ ውደድ” ተብሎ የተጻፈውን ክቡር
ሕግ ብትፈጽሙ መልካም እያደረጋችሁ
ነው። 9አድልዎ ብታደርጉ ግን ኀጢአት
መሥራታችሁ ነው፤ በሕግም ፊት እንደ
ሕግ ተላላፊዎች ትቈጠራላችሁ፤ 10ምክንያ
ቱም ሕግን ሁሉ የሚፈጽም ነገር ግን
በአንዱ የሚሰናከል ቢኖር፣ ሁሉን እንደ
ተላለፈ ይቈጠራል። 11“አታመንዝር” ያለ
እርሱ ራሱ “አትግደልም” ብሎአልና። ባታ
መነዝር፣ ነገር ግን ብትገድል፣ ሕግ ተላ
ላፊ ሆነሃል።
12ስትናገሩም ሆነ ስታደርጉ ነጻነት በሚ
ሰጠው ሕግ እንደሚፈረድባቸው ሰዎች
ሁኑ፤ 13ምክንያቱም ምሕረት ያላደረገ
ሁሉ ያለ ምሕረት ይፈረድበታል፤ ምሕረት
በፍርድ ላይ ያይላል።

## እምነትና ሥራ

14ወንድሞቼ ሆይ፤ አንድ ሰው እምነት
አለኝ ቢል ሥራ ግን ባይኖረው ምን ይጠቅ
መዋል? እንዲህ ያለው እምነት ሊያድነው
ይችላልን? 15አንድ ወንድም ወይም አንዲት
እኅት የሚለብሱት ልብስም ሆነ የሚመገቡት
ምግብ አጥተው፣ 16ከእናንተ መካከል አንዱ፣
“በሰላም ሂዱ፤ አይብረዳችሁ፤ ጥገቡ” ቢላ
ቸው፣ ለሰውነታቸው ግን የሚያስፈልጋቸውን
ባይሰጣቸው፣ ምን ይጠቅማቸዋል? 17እንዲሁ
ሥራ የሌለው እምነት በራሱ የሞተ ነው።
18ነገር ግን አንድ ሰው “አንተ እምነት
አለህ፤ እኔ ሥራ አለኝ” ይላል። እምነትህን
ከሥራ ለይተህ አሳየኝ፤ እኔም እምነቴን
በሥራዬ አሳይሃለሁ። 19አንድ እግዚአብሔር
እንዳለ ታምናለህ፤ መልካም ነው፤ አጋን
ንትም ይህንኑ ያምናሉ፤ በፍርሀትም ይንቀጠ
ቀጣሉ።
20አንተ ከንቱ ሰው! እምነት ያለ ሥራ
ዋጋ የሌለው[ሀ] መሆኑን ለማወቅ ማስረጃ
ትፈ ልጋለህን? 21አባታችን አብርሃም ልጁ
ን ይስሐቅን በመሠዊያው ላይ ባቀረበ ጊ
ዜ በሥራ የጸደቀ አልነበረምን? 22በዚህም
እምነት ከሥራው ጋር አብሮ ይሠራ እን
ደነበር ታያለህ፤ እምነትም በሥራ ፍጹም
ሆነ። 23“አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ፤
ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት” የሚለው የመጽሐፍ
ቃል ተፈጸመ፤ እርሱም የእግዚአብሔር ወዳጅ
ተባለ። 24እንግዲህ በእምነት ብቻ ሳይሆን
በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ።
25እንዲሁም ጋለሞታዪቱ ረዓብ መልእክ
ተኞቹን ተቀብላ በሌላ መንገድ በሰደደቻ
ቸው ጊዜ በሥራ አልጸደቀችምን? 26ከመን
ፈስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ ከሥራም
የተለየ እምነት የሞተ ነው።

## አንደበትን መግታት

3 ወንድሞቼ ሆይ፤ ከእናንተ ብዙዎች
አስ ተማሪዎች አይሁኑ፤ ምክንያቱም
እኛ አስተማሪዎች የሆንን የባሰ ፍርድ
እንደ ምንቀበል ታውቃላችሁ። 2ሁላችንም
በብዙ ነገር እንሰናከላለን፤ በንግግሩ የማ
ይሰናከል ማንም ሰው ቢኖር እርሱ ሰውነ
ቱን ሁሉ መቈጣጠር የሚችል ፍጹም ሰው
ነው።
3ፈረሶች እንዲታዘዙልን ልጓም በአፋ
ቸው ውስጥ ስናስገባ፣ መላ ሰውነታቸውን
መምራት እንችላለን። 4ወይም መርከቦችን
ተመልከቱ፤ ምንም እንኳ እጅግ ትልቅና
በኀይለኛ ነፋስ የሚነዱ ቢሆኑም
የመርከቡ ነጂ በትንሽ መሪ ወደሚፈ
ልገው አቅጣጫ ይመራቸዋል። 5እንዲሁም
ምላስ ትንሽ የሰውነት ክፍል ሆና ሳለ
በታላላቅ ነገሮች ትኵራራለች፤ ትልቅ
ጫካ በትንሽ እሳት እንዴት ተቃጥሎ
እንደሚጠፋ አስተውሉ፤ 6ምላስም እንደ
እሳት ናት፤ በሰውነት ክፍሎቻችን መካ
ከል የምትገኝ የክፋት ዓለም ናት፤ ሰው
ነትን ሁሉ ታረክሳለች፤ ደግሞም የፍጥ
ረትን ሩጫ ታቃጥላለች፤ ራሷም በገሃነም
ትቃጠላለች።
7ማናቸውም ዐይነት እንስሳ፣ አዕዋፍ
እንዲሁም በምድር ላይ የሚሳቡና፥ በባሕር
ውስጥ የሚኖሩ ፍጥረታት ሁሉ መገራት
ችለዋል፤ በሰውም ተገርተዋል። 8ነገር ግን
ምላስን መግራት የሚችል ማንም ሰው
የለም፤ የሚገድል መርዝ የሞላባትና ዕ
ረፍት የሌላት ክፉ ነገር ናት።
9በምላሳችን ጌታንና አብን እንባርካለን፤
በእርስዋም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ
ትን ሰዎች እንረግማለን። 10ከአንድ አፍ
በረከትና መርገም ይወጣሉ፤ ወንድሞቼ ሆይ፤
ይህ ሊሆን አይገባም። 11ከአንድ ምንጭ
ጣፋጭ ውሃና መራራ[ለ] ውሃ ይመነጫልን?
12ወንድሞቼ ሆይ፤ በለስ ወይራን ወይንም
በለስን ሊያፈራ ይችላልን? እንዲሁም
ከጨው ውሃ ጣፋጭ ውሃ ሊገኝ አይች
ልም።

[ሀ]20 አንዳንድ ጥንታዊ ያለሆኑ ቅጆች፣ *ሙት* ይሉታል
[ለ]11 በግሪኩ፣ *ጨው*

2፥6 ሐሥ8፥3፤ 16፥19፤1ቆሮ11፥22
2፥8 ዘሌ19፥18፤ ማቴ5፥43
2፥9 ቀኍ1፤ዘዳ1፥17
2፥10 ማቴ5፥19፤ ገላ3፥10፤5፥3፤ያዕ3፥2
2፥11 ዘፀ20፥13፡ 14፤ዘዳ5፥17፡18
2፥12 ማቴ16፥27፤ ያዕ1፥25
2፥13 ማቴ5፥7፤ 9፥13፤12፥7፤18፥32-35፤ ሉቃ6፥37
2፥14 ማቴ7፥26፤ ያዕ1፥22-25
2፥15 ማቴ25፥35፡36
2፥16 ሉቃ3፥11፤ 1ዮሐ3፥17፡18
2፥17 ቀኍ20፥26፤ገላ5፥6
2፥18 ማቴ7፥16፡17፤ ሮሜ3፥28፤ዕብ11፤ ያዕ3፥13
2፥19 ዘዳ6፥4፤ ማቴ8፥29፤ማር12፥29፤ ሉቃ4፥34፤1ቆሮ8፥4-6
2፥20 ቀኍ17፡26
2፥21 ዘፍ22፥9፡12
2፥22 ዕብ11፥17፤ 1ተሰ1፥3
2፥23 ዘፍ15፥6፤ 2ዜና20፥7፤ ኢሳ4፥8፤ሮሜ4፥3
2፥25 ዕብ11፥31
2፥26 ቀኍ17፡20
3፥1 ማቴ7፥1፤ ሮሜ2፥21፤ኤፌ4፥11
3፥2 1ነገ8፥46፤ መዝ39፥1፤ምሳ10፥19፤ ማቴ12፥37፤ ሮሜ3፥9-20 ያዕ1፥26፤2፥10፤ 1ጴጥ3፥10፤1ዮሐ1፥8
3፥3 መዝ32፥9
3፥5 መዝ12፥3፡4፤ 73፥8፡9
3፥6 ምሳ16፥27፤ ማቴ5፥22፤15፥11፡18፡ 19
3፥8 መዝ140፥3፤ ሮሜ3፥13
3፥9 ዘፍ1፥26፡27፤ 1ቆሮ11፥7
3፥12 ማቴ7፥16

## ሁለት ዐይነት ጥበብ

13ከእናንተ መካከል ጥበበኛና አስተዋይ
የሆነ ሰው ማን ነው? ሥራውን ከጥበብ
በሆነ በመልካም አኗኗር ያሳይ። 14ነገር ግን
መራራ ቅንአትና ራስ ወዳድነት በልባችሁ
ቢኖር ኵራት አይሰማችሁ፤ እውነትንም
አትካዱ። 15እንዲህ ያለችዋ ጥበብ ከላይ
አይደለችም፤ ነገር ግን ከምድር ከሥጋና
ከአጋንንት ናት። 16ቅናትና ራስ ወዳድነት
ባሉበት ስፍራ በዚያ ሁከትና ክፉ ሥራ
ሁሉ ይገኛሉ።

17ከሰማይ የሆነችው ጥበብ ግን በመጀ
መሪያ ንጽሕት ናት፤ በኋላም ሰላም ወዳድ፣
ታጋሽ፣ እሺ ባይ፣ ምሕረትና መልካም
ፍሬ የሞላባት፣ አድልዎና ግብዝነት
የሌለባት ናት። 18የጽድቅም ፍሬ ሰላምን
ለሚያደ ርጉ በሰላም ይዘራል።

## ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ

4 በእናንተ መካከል ያለው ጦርነትና ጠብ
ከየት የመጣ ነው? በውስጣችሁ ከሚ
ዋጉት ምኞታችሁ አይደለምን? 2ትመኛላ
ችሁ፤ ነገር ግን አታገኙም። ትገድላላ
ችሁ፤ በብርቱም ትመኛላችሁ፤ ልታገኙም
አትችሉም። ትጣላላችሁ፤ ትዋጋላችሁ፤
አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም።
3ትለምናላችሁ ግን አትቀበሉም፤ ለራሳ
ችሁ ሥጋዊ ደስታ በማሰብ በክፉ ምኞት
ትለምናላችሁና።

4አመንዝሮች ሆይ፤ ከዓለም ጋር ወዳጅ
መሆን የእግዚአብሔር ጠላት መሆን እንደ ሆነ
አታውቁ ምን? ስለዚህ የዓለም ወዳጅ መሆን
የሚ ፈልግ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት
ሆኖአል። 5ወይስ በውስጣችን ያሳደረው
መንፈስ አብ ዝቶ ይቀናል[ሐ] በማለት መጽሐ
ፍ የተናገረው በከንቱ ይመስላችኋልን? 6ነገር
ግን ጸጋን አብ ዝቶ ይሰጠናል፤ መጽሐፍም፣

"እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤
ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል"

ያለው ስለዚህ ነው።

7እንግዲህ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ፤ ዲ
ያ ብሎስን ተቃወሙት፤ ከእናንተም ይሸሻል።
8ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ፤ እርሱም ወደ እና
ንተ ይቀርባል። እናንተ ኀጢአተኞች እጃችሁን
አንጹ፤ እናንተ በሁለት ሐሳብ የምትዋልሉ
ልባችሁን አጥሩ። 9ተጨነቁ፤ እዘኑ፤ አልቅ
ሱም። ሳቃችሁ ወደ ኀዘን፣ ደስታችሁም ወደ
ትካዜ ይለወጥ። 10በጌታ ፊት ራሳችሁን አዋ
ርዱ፣ እርሱም ከፍ ከፍ ያደርጋችኋል።

11ወንድሞች ሆይ፤ እርስ በርሳችሁ አትወነ
ጃጀሉ፤ ወንድሙን የሚወነጅልና በወንድ
ሙም ላይ የሚፈርድ በሕግ ላይ ክፉ ይና
ገራል፤ በሕግም ላይ ይፈርዳል። በሕግ ላይ
ብትፈርድ ፈራጅ እንጂ ሕግን አድራጊ አይ
ደለህም። 12ሕግን የሚሰጥና የሚፈርድ አንድ
ብቻ ነው፤ እርሱም ሊያድንና ሊያጠፋ
የሚችል ነው፤ ነገር ግን በባልንጀራህ ላይ
የምትፈርድ አንተ ማን ነህ?

## ስለ ነገ መመካት

13እናንተ "ዛሬ ወይም ነገ ወደዚህች
ወይም ወደዚያች ከተማ እንሄዳለን፤ በእር
ሷም አንድ ዓመት እንቈያለን፤ እንነግዳ
ለን፤ እናተርፋለንም" የምትሉ እንግዲህ
ስሙ። 14ነገ የሚሆነውን እንኳ አታውቁም። ሕ
ይወ ታችሁ ምንድን ናት? ለጥቂት ጊዜ
ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት ናችሁ።
15ይልቁንም፣ "የጌታ ፈቃድ ቢሆን እንኖ
ራለን፤ ይህን ወይም ያንን እናደርጋለን"
ማለት ይገባችኋል። 16አሁን ግን በትዕቢ
ታችሁ ትመካላችሁ፤ እንዲህ ያለው
ትምክህት ሁሉ ክፉ ነው። 17እንግዲህ
መልካም የሆነውን ነገር ማድረግ እንዳለበት
እያወቀ የማያ ደርግ ሰው ኀጢአት
ያደርጋል።

## ለጨካኝ ሀብታሞች የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

5 እንግዲህ እናንተ ሀብታሞች ስሙ፤
ስለ ሚደርስባችሁ መከራ አልቅሱ፤ ዋይ
ዋይም በሉ። 2ሀብታችሁ ሻግቶአል፤ ልብሳ
ችሁንም ብል በልቶታል። 3ወርቃችሁና
ብራችሁ ዝጎአል፤ ዝገቱም በእናንተ ላይ
ይመሰክራል፤ ሥጋችሁንም እንደ እሳት
ይበላዋል፤ ለመጨረሻው ዘመን ሀብትን አከ
ማችታችኋል። 4ልብ በሉ፤ እርሻችሁን ሲያ
ጭዱ ለዋሉ ሠራተኞች ያልከፈላችሁት ደመ
ወዝ በእናንተ ላይ ይጮኻል፤ የአጫጆቹም
ጩኸት ሁሉን ቻይ ወደ ሆነው ጌታ ጆሮ
ደርሶአል። 5በምድርም ላይ በምቾትና በመቀ
ማጠል ኖራችኋል፤ ለዕርድ[መ] ቀን ልባችሁን
አወፍራችኋል። 6እናንተን ያልተቃወሙትን
ንጹሐን ሰዎች ኰንናችኋል፤ ገድላችኋልም።

## በመከራ ውስጥ መታገሥ

7እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ጌታ እስከሚመጣ
ድረስ ታገሡ። ገበሬ መሬቱ መልካምን ፍሬ
እስከሚሰጥ ድረስ እንዴት እንደሚታገሥ፣
የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ እንዴት
እንደሚጠባበቅ አስተውሉ። 8እናንተም እን
ዲሁ ታገሡ፤ ልባችሁንም አጽኑ፤ ምክንያተ
ም የጌታ መምጫ ተቃርቦአል። 9ወንድሞች

3፥13 ያዕ2፥18፤ 1ጴጥ2፥12
3፥14 ቍ16፤ 2ቆሮ12፥20፤ያዕ5፥19
3፥15 ቍ17፤ 1ጢሞ4፥1፤ያዕ1፥17
3፥16 ቍ14፤ ሳ5፥20፡21
3፥17 ሉቃ6፥36፤ ሮሜ2፥9፤1ቆሮ2፥6፤ ዕብ12፥11፤ያዕ1፥17
3፥18 ምሳ11፥18፤ ኢሳ32፥17፤ ሆሴ10፥12፤ ማቴ5፥9፤ሮሜ14፥19፤ ፊል1፥11
4፥1 ሮሜ7፥23፤ ቲቶ3፥9
4፥2 ማቴ5፥21፡22፤ ያዕ5፥6፤1ዮሐ3፥15
4፥3 መዝ18፥41፤ 66፥18፤ማቴ7፥7፤ 1ዮሐ3፥22፤5፥14
4፥4 ኢሳ54፥5፤ ኤር3፥20፤ሆሴ2፥2-5፤ 3፥1፤9፥1፤ዮሐ15፥19 ሮሜ8፥7፤ያዕ1፥27፤ 1ዮሐ2፥15
4፥5 1ቆሮ6፥19
4፥6 ምሳ3፥34፤ ማቴ23፥12
4፥7 ኤፌ4፥27፤ 6፥11፤1ጴጥ5፥6-9
4፥8 መዝ24፥4፤ 73፥28፤119፥113፤ ኢሳ1፥16፤ ኤር4፥14፤ዘካ1፥3፤ ሚል3፥7ዕብ7፥19፤ ያዕ1፥8
4፥9 ሉቃ6፥25
4፥10 ቍ6፤ ኢዮ5፥11፤1ጴጥ5፥6
4፥11 ማቴ7፥1፤ ሮሜ1፥30፤ 2ቆሮ12፥20፤ያዕ1፥22፤ 2፥8፤1ጴጥ2፥1
4፥12 ኢሳ33፥22፤ ማቴ7፥1፤10፥28፤ ያዕ5፥9
4፥13 ምሳ27፥1፤ ሉቃ12፥18-20፤ያዕ5፥1
4፥14 ኢዮ7፥7፤ መዝ39፥5፤102፥3፤ 144፥4፤ኢሳ2፥22
4፥15 ሐሥ18፥21 ዮሐ9፥41
4፥16 1ቆሮ5፥6
4፥17 ሉቃ12፥47፤ ሕዝ30፥2፤ሉቃ6፥24፤ 1ጢሞ6፥9፤ያዕ2፥2-6፤ 4፥13
5፥1 ኢሳ13፥6፤
5፥2 ኢዩ13፥28፤ መዝ39፥11፤ኢሳ50፥9፤ ማቴ6፥19፡20
5፥3 ቍ7፡8 5፥4 ዘሌ19፥13፤ ዳ24፥15፤ ኤር22፥13፤ ሚል3፥5፤ ሮሜ9፥29

5፥5 ኤር12፥3፤ 25፥34፤ሕዝ16፥49፤ አሞ6፥1፤ሉቃ16፥19 5፥6 ዕብ10፥38፤ ያዕ4፥2 5፥7 ዘዳ11፥14፤ ኤር5፥24፤ ኢል2፥23፤ 1ቆሮ1፥7፤ገላ6፥9 5፥8 1ቆሮ1፥7፤ ሮሜ13፥11 5፥9 መዝ94፥2፤ ማቴ24፥33፤1ቆሮ4፥5፤ ያዕ4፥11፡12፤1ጴጥ4፥5

[ሐ]5 ወይም፣ *እግዚአብሔር በውስጣችን እንዲኖር ስላደረገው መንፈስ በቅናት ይመኛል፤ ወይም በውስጣችን እንዲኖረው ያደረገው መንፈስ በቅናት ይመኛል ማለት ነው።*

ሆይ፤ እርስ በርሳችሁ አታጒረምርሙ፤ ያለ
ዚያ ይፈረድባችኋል፤ እነሆ ፈራጁ በበር ላይ
ቆሞአል።
10 ወንድሞች ሆይ፤ በጌታ ስም የተናገሩ
ትን ነቢያት የመከራና የትዕግሥት ምሳሌ
አድርጋችሁ ተመልከቱ። 11 በትዕግሥት የጸኑትን
የተባረኩ አድርገን እንደምንቈጥር ታውቃ
ላችሁ፤ ኢዮብ እንዴት ታግሦ እንደ ጸና
ሰምታችኋል፤ ጌታም በመጨረሻ ያደረገ
ለትን አይታችኋል። ጌታ እጅግ ርኅሩኅና
መሓሪ ነው።
12 ከሁሉም በላይ ወንድሞቼ ሆይ፤ በሰማይ
ወይም በምድር ወይም በማናቸውም ነገር
ቢሆን አትማሉ፤ "አዎ" ቢሆን አዎ
ይሁን፤ "አይደለም" ቢሆን አይደለም
ይሁን፤ ያለዚያ ይፈረድባችኋል።

## ከእምነት የሆነ ጸሎት

13 ከእናንተ መካከል በመከራ ውስጥ ያለ
አለ? እርሱ ይጸልይ፤ የተደሰተ አለ? የምስ
ጋና መዝሙር ይዘምር። 14 ከእናንተ መካከል
የታመመ ሰው አለ? የቤተ ክርስቲያን ሽማ
ግሌዎችን ይጥራ፤ እነርሱም በጌታ ስም
ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት። 15 በእምነት
የቀረበ ጸሎት የታመመውን ሰው ይፈው
ሰዋል፤ ጌታም ያስነሣዋል፤ ኀጢአትም ሠርቶ
ከሆነ፣ ይቅር ይባላል። 16 ስለዚህ ኀጢ
አታችሁን እርስ በርሳችሁ ተናዘዙ፤ ትፈወ
ሱም ዘንድ አንዱ ለሌላው ይጸልይ። የጻ
ድቅ ሰው ጸሎት ኀይል አለው፤ ታላቅ
ነገርም ያደርጋል።
17 ኤልያስ እንደ እኛ ሰው ነበረ፤ ዝናብ
እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፤ በምድርም ላይ
ሦስት ዓመት ተኩል ዝናብ አልዘነበም።
18 እንደ ገናም ጸለየ፤ ዝናብም ከሰማይ
ዘነበ፤ ምድርም ፍሬዋን ሰጠች።
19 ወንድሞቼ ሆይ፤ ከእናንተ አንዱ
ከእውነት ቢስትና ሌላው ቢመልሰው፣ 20 ይህን
አስተውሉ፤ ኀጢአተኛን ከተሳሳተበት መን
ገድ የሚመልስ ሰው ነፍሱን ከሞት
ያድነዋል፤ ብዙ ኀጢአትንም ይሸፍናል።

5፥10 ማቴ5፥12
5፥11 ዘፀ34፥6፤ ዘኍ14፥18፤ኢዩ1፥21፡ 22፤2፥10፤42፥10፡12-17፤ መዝ103፥8፤ማቴ5፥10፤ ዕብ10፥36
5፥12 ማቴ5፥34-37
5፥13 መዝ50፥15፤ ቈላ3፥16
5፥14 መዝ23፥5፤ ኢሳ1፥6፤ማር6፥13፤ 16፥18፤ሉቃ10፥34፤ሐ ሥ11፥30
5፥15 ያዕ1፥6 5፥16 ማቴ3፥6፤7፥7፤ዮሐ9፥31፤ ሐ ሥ19፥18፤ዕብ12፥13፤ 1ጴጥ2፥24
5፥17 1ነገ17፥1፤ ሉቃ4፥25፤ሐሥ14፥15
5፥18 1ነገ18፥41-45
5፥19 ማቴ18፥15፤ ያዕ3፥14
5፥20 ሮሜ11፥14፤ 1ጴጥ4፥8

መ5 ወይም ለድግስ

# የሐዋርያው ጴጥሮስ መልእክት – አንደኛ

**1** የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ጴጥሮስ፤
በጳንጦስ፥ በገላትያ፥ በቀጰዶቅያ፥ በእስ
ያና በቢታንያ ተበትነው በመጻተኝነት
ለሚኖሩ ለእግዚአብሔር ምርጦች፤ 2 እግዚ
አብሔር አብ አስቀድሞ ካወቃቸው፣ ኢየሱስ
ክርስቶስን ለመታዘዝ በደሙ ለተረጩትና
በመንፈስ አማካይነት ለተቀደሱት፤
ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።

## ሕያው ስለ ሆነው ተስፋ ለእግዚአብሔር የቀረበ ምስጋና

3የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና
አምላክ ይባረክ፤ እርሱ ከታላቅ ምሕረቱ
የተ ነሣ በኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት
መነሣት ምክንያት ለሕያው ተስፋ በሚሆን
አዲስ ልደት፣ 4እንዲሁም በሰማይ ለማይጠ
ፉ፣ ለማ ይበላሽና ለማይለወጥ ርስት
እንደገና ወለ ደን። 5እናንተም
በመጨረሻው ዘመን ሊገ ለጥ የተዘጋጀው
ድነት እስኪመጣ ድረስ በእምነት አ
ማካይነት በእግዚአብሔር ኀይል ተጠ
ብቃችኋል። 6አሁን በብዙ ዐይነት ፈተና
ውስጥ ሆናችሁ ለጥቂት ጊዜ መከራን
ብትቀበሉም እንኳ በዚህ እጅግ ደስ ይላችኋል።
7እነዚህ ነገሮች በእናንተ ላይ የደረሱት፣
በእሳት ተፈትኖ ቢጠራም፣ ጠፊ ከሆነው
ወርቅ ይልቅ እጅግ የከበረው እምነታችሁ
እውነተኛ መሆኑ እንደተረጋገጠና ኢየሱስ
ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ምስጋናን ክብ
ርንና፥ ውዳሴን እንዲያስገኝላችሁ ነው።
8እርሱንም ሳታዩት ትወዱታላችሁ፤ አሁን
ባታዩትም በእርሱ ታምናላችሁ መግለጽ በማ
ይቻልና ክብር በሞላበት ሐሤት ደስ
ብሎአችኋል፤ 9የእምነታችሁን ፍጻሜ
እርሱም የነፍሳችሁን ድነት እየተቀበላችሁ
ነውና።

10ለእናንተ ስለሚሰጠው ጸጋ ትንቢት
የተናገሩት ነቢያት ስለዚህ ድነት ተግተው
በጥንቃቄ ይመረምሩ ነበር፤ 11በእነርሱ
ውስጥ የነበረው የክርስቶስ መንፈስ ስለ
ክርስቶስ መከራ እንዲሁም ከመከራው
በኋላ ስለ ሚሆነው ክብር አስቀድሞ
በመናገር ያመ ለከታቸው ጊዜ መቼና
እንዴት እንደሚፈጸም ይመረምሩ ነበር።
12አሁን ከሰማይ በተ ላከ መንፈስ ቅዱስ
ወንጌልን ባበሠሩላችሁ ሰዎች የነገሯችሁን
ነገር ባወሩላችሁ ጊዜ እናንተን እንጂ ራ
ሳቸውን እንዳላገለገሉ ተገ ለጠላቸው።
መላእክትም እንኳ ሳይቀሩ እነዚህን ነገሮች
ይመኛሉ።

## በቅድስና መኖር

13ስለዚህ ልባችሁን አዘጋጁ፤ ራሳችሁንም
ግዙ፤ ተስፋችሁን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ
ለእናንተ በሚሰጠው ጸጋ ላይ ሙሉ
በሙሉ አድርጉ። 14ታዛዦች ልጆች እንደ
መሆናችሁ መጠን ቀድሞ ባለማወቅ ትኖሩ
በት የነበረውን ክፉ ምኞት አትከተሉ።
15ነገር ግን የጠራችሁ እርሱ ቅዱስ እንደ ሆነ
እናንተም በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ፤
16ምክንያቱም "እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም
ቅዱሳን ሁኑ" ተብሎ ተጽፎአል።

17ለሰው ሳያደላ በእያንዳንዱ ላይ
እንደ የሥራው የሚፈርደውን አባት ብላ
ችሁ የምትጠሩት ከሆነ፣ በዚህ ምድር በእ
ንግድነት ስትኖሩ በፍርሀት ኑሩ። 18ከቀ
ድሞ አባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከንቱ
ከሆነ ሕይወት የተዋጃችሁት በሚጠፉ ነገር፣
በብር ወይም በወርቅ እንዳልሆነ ታውቃላ
ችሁ፤ 19ነገር ግን እናንተ የተዋጃችሁት
ነውርና እንከን እንደ ሌለበት በግ ደም፣
በክ ርስቶስ ክቡር ደም ነው። 20እርሱ
አስቀድሞ የታወቀው ዓለም ከመፈጠሩ
በፊት ሲሆን አሁን፣ ግን በመጨረሻው
ዘመን ስለ እና ንተ ተገለጠ። 21በእርሱም
አማካይነት፣ ከሞት ባስነሣውና ክብርን
በሰጠው በእግዚአብሔር ታምናላችሁ፤ ስለዚህ
እምነታችሁና ተስፋችሁ በእግዚአብሔር ላይ
ነው።

22እንግዲህ ለእውነት በመታዘዝ ነፍሳች
ሁን ስላነጻችሁ፣ ለወንድሞቻችሁ ቅን ፍቅር
ይኑራችሁ፤ እርስ በርሳችሁም አጥብቃችሁ
ከልብሀ ተዋደዱ። 23ዳግመኛ የተወለዳችሁት
ከሚ
ጠፋ ዘር ሳይሆን ሕያው በሆነና ጸንቶ በሚ
ኖር፣ በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ከማይ
ጠፋ ዘር ነው። 24ምክንያቱም መጽሐፍ እንደ
ሚል፣

"ሥጋ ለባሽ ሁሉ እንደ ሣር ነው፤
ክብሩም ሁሉ እንደ ሜዳ አበባ ነው።
ሣሩ ይጠወልጋል፤ አበባውም ይረግፋል፤
25የጌታ ቃል ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።"

የተሰበከላችሁም የምሥራች ቃል ይህ
ነው።

**2** እንግዲህ ክፋትን ሁሉ፣ ማታለልን
ሁሉ፣ ግብዝነትን፣ ቅናትንና ሐሜትን
ሁሉ አስወግዱ፤ 2በድነታችሁ እንድታድጉ፣
አዲስ እንደ ተወለዱ ሕፃናት ንጹሑን

1፥1 ማቴ24፥22፤ ሐሥ2፥9፤16፥6፡7፤ 18፥2፤ዕብ11፥13፤ ያዕ1፥1፤2ጴጥ1፥1
1፥2 ቍ14፡22፤ ሮሜ1፥7፤8፥29፤ 2ተስ2፥13፤ ዕብ10፥22፤12፥24
1፥3 ቍ13፡21፡23፤ ዮሐ1፥13፤1ቆሮ15፥20 2ቆሮ1፥3፤ቲቶ3፥5፤ ዕብ3፥6፤1ጴጥ3፥21
1፥4 ሐሥ20፥32፤ ሮሜ8፥17፤ሖላ1፥5፤ 2ጢሞ4፥8፤1ጴጥ5፥4
1፥5 1ሳሙ2፥9፤ ዮሐ10፥28፤ ሮሜ8፥18፤11፥14
1፥6 ሮሜ5፥2፤ ያዕ1፥2፤1ጴጥ4፥12፤ 5፥10
1፥7 ቍ13፤ ኢዮ23፥10፤ መዝ66፥10፤ ምሳ17፥3፤ ኢሳ48፥10፤ 2ቆሮ4፥17፤1ተስ2፥19፤ 1ጴጥ4፥13
1፥8 ዮሐ20፥29
1፥9 ሮሜ6፥22
1፥10 ቍ13፤ ማቴ13፥17፤26፥24
1፥11 ማቴ26፥24፤ ሐሥ16፥7፤2ጴጥ1፥21
1፥12 ቍ25፤ ሉቃ24፥49፤ ሮሜ4፥24
1፥13 ቍ3፡7፡10፡ 21፤ሐሥ24፥25፤ 1ቆሮ1፥7፤ዕብ3፥6
1፥14 ቍ2፡22፤ ሮሜ12፥2፤ኤፌ4፥18
1፥15 ኢሳ35፥8፤ 1ተስ4፥7፤1ዮሐ3፥3
1፥16 ዘሌ11፥44፡ 45፤19፥2፤20፥7
1፥17 ማቴ6፥9፤ 16፥27፤ሐሥ10፥34፤ ዕብ11፥13፤12፥28
1፥18 ማቴ20፥28፤ 1ቆሮ6፥20፤ገላ4፥3
1፥19 ዘፀ12፥5፤ 1ዮሐ1፥29፤ሮሜ3፥25
1፥20 ማቴ25፥34፤ ኤፌ1፥4፤ዕብ9፥26
1፥21 ቍ3፡13፤ ሐሥ2፥24፤ ሮሜ4፥24፤ ፊል2፥7ኛ9፤ ዕብ2፥9፤ዕብ3፥6
1፥22 ቍ2፡14፤ ዮሐ13፥34፤ ሮሜ12፥10፤ያዕ4፥8
1፥23 ቍ3፤ዮሐ1፥13፤ ዕብ4፥12

2፥2 1ቆሮ3፥2፤ ኤፌ4፥15፡16፤ዕብ5፥12፡13
1፥25 ኢሳ40፥6ኛ8፤ ያዕ1፥10፡11 2፥1 ኤፌ4፥22፤ ያዕ4፥11

ሀ22 አንዳንድ የጥናት ቅጆች ከንጹሕ ልብ ይላሉ።

መንፈሳዊ ወተት ተመኙ፤ 3ጌታ መልካም
መሆኑን ቀምሳችኋልናማለት ነው።

## ሕያው ድንጋይና የተመረጠ ሕዝብ

4በሰው ዘንድ ወደ ተናቀው፣ በእግዚአብሔር
ዘንድ ግን ወደ ተመረጠውና ክቡር ወደሆ
ነው ወደዚህ ሕያው ድንጋይ እየቀረባችሁ፣
5እናንተ ደግሞ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካ
ይነት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ
መንፈሳዊ መሥዋዕት ታቀርቡ ዘንድ፣
ቅዱሳን ካህናት ለመሆን እንደ ሕያዋን
ድንጋዮች መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ትሠራ
ላችሁ። 6ምክንያቱም^ በመጽሐፍ እንዲህ
ተብሎ ተጽፎአልና፤
"እነሆ፤ የተመረጠና ክቡር የማእዘን ድንጋይ፣
በጽዮን አኖራለሁ፤
በእርሱም የሚያምን፣ ከቶ አያፍርም።"
7እንግዲህ ለእናንተ ለምታምኑት ይህ ድን
ጋይ ክቡር ነው፤ ለማያምኑት ግን፣
"ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣
እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ።"
8ደግሞም፣ "ሰዎችን የሚያሰናክል፣
የሚጥላቸውም ዐለት ሆነ።"
የሚሰናከሉት ቃሉን ባለመታዘዛቸው
ነው፤ የተመደቡት ለዚህ ነውና።
9እናንተ ግን ከጨለማ ወደ አስደናቂ
ብርሃኑ የጠራችሁን የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥ
ራ እንድታውጁ፣ የተመረጠ ትውልድ፣
የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ እግዚአብሔር ለ
ራሱ የለ ያችሁ ሕዝብ ናችሁ። 10ቀድሞ
የእርሱ ወገን አልነበራችሁም፤ አሁን ግን
የእግዚአብሔር
ሕዝብ ሆናችኋል፤ ቀድሞ ምሕረትን አላገኛች
ሁም ነበር፤ አሁን ግን ምሕረትን አግኝታችኋል።
11ወዳጆች ሆይ፤ በዚህ ዓለም እንግዶ
ችና መጻተኞች እንደ መሆናችሁ መጠን፣
ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት እንድት
ርቁ እለምናችኋለሁ። 12ምንም እንኳ ክፉ
እንደምትሠሩ አድርገው ቢያሟችሁም
ለፍርድ በሚመጣበት ጊዜ መልካሙን
ሥራችሁን ዐይተው እግዚአብሔርን እንዲ
ያከብሩ፣ በአሕዛብ መካከል
በመልካም
ሕይወት ኑሩ።

## ለአለቆችና ለጌቶች መታዘዝ

13ስለ ጌታ ብላችሁ ለምድራዊ ባለ ሥል
ጣን ሁሉ ተገዙ፤ የበላይ ባለ ሥልጣን ስለ
ሆነ ለንጉሥ ቢሆን፣ 14ወይም ክፉ አድራ
ጊዎችን ለመቅጣት፣ በጎ አድራጊዎችን ለማ
መስገን እርሱ ለሾማቸው ገዦች ታዘዙ፤
15ምክንያቱም፣ መልካም በማድረግ የአላ
ዋቂዎችን ከንቱ ንግግር ዝም እንድታሰኙ
የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። 16እንደ እግዚአብሔር
አገልጋዮች ሆናችሁ በነጻነት ኑሩ እንጂ

2፥3 መዝ34፥8፤ ዕብ6፥5
2፥4 ቍ7፤ኢሳ42፥1
2፥5 ቍ9፤ዘፀ19፥6፤ ምሳ9፥1፤ኢሳ61፥6፤ 1ቆሮ3፥9፤ኤፌ2፥20ኛ22፤ ፊል4፥18፤1ጢሞ3፥15፤ ዕብ13፥15፤ራእ1፥6፤ 5፥10፤20፥6
2፥6 ኢሳ28፥16፤ ሮሜ9፥32፡33፤ 10፥11፤ኤፌ2፥20
2፥7 ቍ4፤ መዝ118፥22፤ ሐሥ4፥11፤2ቆሮ2፥16
2፥8 ኢሳ8፥14፤ ሉቃ2፥34፤ሮሜ9፥22
2፥9 ቍ5፤ዘፀ19፥6፤ ዘዳ7፥6፤10፥15፤ 1ሳሙ12፥22፤ ኢሳ62፥12፤ ሐሥ26፥18፤ ቲቶ2፥14
2፥10 ሆሴ1፥9፡10፤ 2፥23፤ሮሜ9፥25፡26
2፥11 ሮሜ13፥14፤ 1ቆሮ10፥14፤ገላ5፥16፤ ዕብ11፥13፤ ያዕ4፥1
2፥12 ማቴ9፥8፤ ፊል2፥15፤ቲቶ2፥8፡ 14፤1ጴጥ3፥16
2፥13 ሮሜ13፥1፤ ቲቶ3፥1
2፥14 ሮሜ13፥3፡4
2፥15 ቍ12፤1ጴጥ3፥17፤ 4፥19
2፥16 ዮሐ8፥32፤ ሮሜ6፥22፤ገላ5፥13
2፥17 ምሳ24፥21፤ ሮሜ12፥10፤13፥7
2፥18 ኤፌ6፥5፤ ያዕ3፥17
2፥19 1ጴጥ3፥14፡ 17
2፥20 1ጴጥ3፥17
2፥21 ማቴ11፥29፤ 16፥24፤ሐሥ14፥22፤ ሮሜ8፥28፤ፊል1፥29፤ 1ጴጥ3፥9፡18፤4፥1፡13
2፥22 ኢሳ53፥9፤ 2ቆሮ5፥21
2፥23 መዝ9፥4፤ ኢሳ53፥7፤ ሉቃ23፥46፤ ዕብ12፥3፤1ጴጥ3፥9
2፥24 ዘዳ32፥29፤ መዝ103፥3፤ ኢሳ53፥4፡5፡11፤ ዕብ9፥28፤12፥13፤ ያዕ5፥16
2፥25 ኢዩ10፥12፤ ኢሳ 53፥6፤ ዮሐ10፥11
3፥1 1ቆሮ7፥16፤ 9፥19፤ኤፌ5፥22፤ 1ጴጥ2፥18
3፥3 ኢሳ3፥18ኛ23፤ 1ጢሞ2፥9

ነጻነታችሁን የክፋት መሸፈኛ አታድር
ጉት። 17ለሰው ሁሉ ተገቢውን አክብሮት
ስጡ፤ ወንድሞችን ውደዱ፤ እግዚአብሔርን ፍሩ፤
ንጉሥን አክብሩ።
18እናንተ አገልጋዮች ሆይ፤ ለደጎችና
ለገሮች ጌቶቻችሁ ብቻ ሳይሆን ለክፉዎችም
በፍጹም አክብሮት ታዘዙ። 19ስለ እግዚአብሔር
ሲል የግፍ መከራን የሚቀበል ሰው ምስጋ
ናን ያገኛል። 20ክፉ ሥራ ሠርታችሁ ብትቀጡ
-ና ብትታገሡ ምን ምስጋና ይኖራችኋል?
ነገር ግን መልካም ሥራ ሠርታችሁ መከራ
ብትቀ በሉና ብትታገሡ ይህ በእግዚአብሔር
ዘንድ ምስጋና ያስገኝላችኋል። 21የተጠራ
ችሁትም ለዚሁ ነው፤ ምክንያቱም ክርስቶስ
ስለ እና ንተ መከራን የተቀበለው የእርሱን
ፈለግ እንድ ትከተሉ ምሳሌን ሊተውላችሁ
ነው።
22"እርሱ ኀጢአት አላደረገም፤
በአፉም ተንኰል አልተገኘበትም።"
23ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም፤ መከ
ራ ሲደርስበት አልዛተም፤ ነገር ግን በ
ጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ።
24ለኀጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ
ራሱ በሥጋው ኀጢአታችንን በእንጨት
መስቀል ላይ ተሸከመ፤ በእርሱ ቍስል
እናንተ ተፈው ሳችኋል። 25ቀድሞ እንደ ጠ
ፉ በጎች ትቅበዘ በዙ ነበር፤ አሁን ግን ወደ
ነፍሳችሁ እረኛና
ጠባቂ ተመልሳችኋል።

## በባልና በሚስት መካከል ሊኖር የሚገባ ግንኙነት

3 ሚስቶች ሆይ፤ እናንተም እንደዚሁ
ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ አንዳንድ ለቃሉ
የማይታዘዙ ቢኖሩ፣ ያለ ቃል በሚስቶቻቸው
አኗኗር ተማርከው ይመለሳሉ፤ 2ይህም
የሚሆነው ንጹሕና ፍጹም አክብሮት
የተሞላውን ኑሮአችሁን ሲመለከቱ ነው።
3ውበታችሁ በውጫዊ ነገሮች በመሽሞንሞን
ይኸውም ሹሩባ በመሥራት፣ በወርቅ በማጌ
ጥና በልብስ አይሁን፤ 4ነገር ግን ውበታ
ችሁ በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ
የከበረ፣ ገርና ጭምት መንፈስ ያለበት፣
ምንጊዜም የማይጠፋ የውስጥ ሰውነት
ውበት ይሁን። 5ተስፋቸውን በእግዚአብሔር
ላይ የጣሉ የቀድሞ ቅዱሳት ሴቶች ራሳ
ቸውን ያስዋቡት በዚህ ዐይነት ለባሎቻ
ቸው በመገዛት ነበርና። 6ሣራም አብር
ሃምን "ጌታዬ" እያለች ትታዘዘው ነበር፣
እናንተም ምንም ሳትፈሩ መልካም ብታደ
ርጉ የእርሷ ልጆች ናችሁ።
7ባሎች ሆይ፤ እናንተም ደግሞ ጸሎታ

3፥4 ሮሜ2፥29፤7፥22፤ኤፌ3፥16 3፥5 አስ2፥15፤1ጢሞ5፥5 3፥6 ዘፍ18፥12 3፥7 ኤፌ5፥25ኛ33፤ ሐላ3፥19

^7 ወይም *የማእዘን ድንጋይ*

ችሁ እንዳይደናቀፍ በኑሮአችሁ ሁሉ
ለሚስቶቻችሁ አስቡላቸው፣ ደካሞች ስለ
ሆኑና የሕይወትንም በረከት አብረዋችሁ
ስለሚወርሱ አክብሯቸው፡፡

### መልካም በማድረግ መከራን መቀበል

8በመጨረሻም ሁላችሁ በአንድ ሐሳብ
ተስማሙ፤ እርስ በርሳችሁ ተሳሰቡ፤ እንደ
ወንድማማቾች ተዋደዱ፤ ርኅሩዎችና ትሑ
ታን ሁኑ፡፡ 9ክፉን በክፉ ወይም ስድብን
በስድብ ፈንታ አትመልሱ፤ በዚህ ፈንታ
ባርኩ፤ ምክንያቱም እናንተ የተጠራችሁት
እንደነዚህ ያሉትን ነገሮች እያደረጋችሁ
በረከትን ለመውረስ ነው፡፡ 10ስለዚህ፣
“ሕይወትን የሚወድ፣
መልካም ቀኖችን ሊያይ የሚፈልግ፣
ምላሱን ከክፉ፣
ከንፈሮቹንም ተንኰል ከመናገር
ይከልክል፡፡
11ከክፉ ይራቅ፤ መልካምንም ያድርግ፤
ሰላምን ይፈልግ፤ ይከተላትም፤
12ምክንያቱም የጌታ ዐይኖች ጻድቃንን
ይመለከታሉና፤
ጆሮቹም ጸሎታቸውን ለመስማት
የተከፈቱ ናቸው፤
የጌታ ፊት ግን በክፉ አድራጊዎች ላይ
ነው፡፡”

13መልካም ነገር ለማድረግ ብትቀኑ
የሚጐዳችሁ ማን ነው? 14ነገር ግን ስለ
ጽድቅ እንኳ መከራ ቢደርስባችሁ ብፁዓን
ናችሁ፤ “ዛቻቸውን አትፍሩሐ፤ አትታወ
ኩም፡፡” 15ክርስቶስን ጌታ አድርጋችሁ በል
ባችሁ ቀድሱት፡፡ እናንተ ስላላችሁ ተስፋ
ምክንያትን ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ
ለመስጠት ሁልጊዜ የተዘጋጃችሁ ሁኑ፤
ነገር ግን ይህን ሁሉ በትሕትናና በአክብ
ሮት አድርጉት፤ 16በክርስቶስ ያላችሁን መል
ካም ጠባይ አክፋፍተው የሚናገሩ ሰዎች
በሐሜታቸው እንዲያፍሩ በጎ ኅሊና ይኑራ
ችሁ፡፡ 17የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲህ ከሆነ፣
ክፉ ሠርቶ መከራ ከመቀበል ይልቅ መል
ካም አድርጎ መከራ መቀበል ይሻላል፤
18እንዲሁም ክርስቶስ ለአንዴና ለመጨረሻ
ጊዜ ስለ ኀጢአት ሞቶአልና፤ ወደ እግዚ
አብሔር ያቀርባችሁ ዘንድ፣ ጻድቅ የሆነው
እርሱ ስለ ዐመፀኞች ሞተ፤ እርሱ በሥጋ
ሞተ፤ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፤
19በመንፈስም ሄዶ በወህኒ ቤት ለነበሩ
ነፍሳት ሰበከላቸው፤ 20እነዚህ በወህኒ የነበሩት
ነፍሳት ቀድሞ በኖኅ ዘመን መርከብ ሲሠራ
እግዚአብሔር በትዕግሥት ይጠብቃቸው የነበሩ
እምቢተኞች ናቸው፤ በውሃ የዳኑት ጥቂት፣
ይኸውም ስምንት ሰዎች ብቻ ነበሩ፡፡ 21ይህም
ውሃ አሁን የጥምቀት ምሳሌ ሆኖ ያድናች
ኋል፤ ይህም የሰውነትን እድፍ በማስወገድ
ሳይሆን በንጹሕ ኅሊና በእግዚአብሔር ፊት
የሚቀርብ መማፀኛመ ነው፤ የሚያድናችሁም
በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ አማካይነት ነው፤
22እርሱም ወደ ሰማይ ወጥቶ በእግዚአብሔር ቀ
ኝ አለ፤ መላእክትና ሥልጣናት፣ ኀይላትም
ተገዝተውለታል፡፡

### ለእግዚአብሔር መኖር

4 እንግዲህ ክርስቶስ በሥጋው መከራን
ስለ ተቀበለ እናንተም በዚሁ ዐላማ
ታጥ ቃችሁ ተነሡ፤ ምክንያቱም በሥጋው
መከራን የሚቀበል ሰው ኀጢአትን
ትቶአል፡፡ 2ከዚህም የተነሣ ከእንግዲህ
በሚቀረው ምድራዊ ሕይ ወት እንደ እግዚአብሐ
ር ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ምኞት
አይኖርም፡፡ 3አሕዛብ ፈቅ ደው
እንደሚያደርጉት በመዳራት፣ በሥጋዊ
ምኞት፣ በስካር፣ በጭፈራ፣ ያለ ልክ
በመጠጣት፣ በአስጸያፊ የጣዖት አምልኮ
የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበ
ቃል፡፡ 4ይህን በመሰለ ብኩን ሕይወት ከእነ
ርሱ ጋር ስለማትሮጡ እንግዳ ሆኖባቸው
በመደነቅ ይሰድቧችኋል፡፡ 5ነገር ግን በሕ
ያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ ለተዘጋ
ጀው መልስ ይሰጣሉ፡፡ 6ወንጌል ለሙታን
እንኳ ሳይቀር የተሰበከው በዚህ ምክንያት
ነው፤ ስለዚህ እንደ ማንኛውም ሰው
በሥጋ ይፈረድባቸዋል፤ በመንፈስ ግን
እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ይኖራሉ፡፡

7የሁሉ ነገር መጨረሻ ተቃርቦአል፤
ስለዚህ መጸለይ እንድትችሉ ንጹሕ አእምሮ
ይኑራችሁ፤ ራሳችሁንም የምትገዙ ሁኑ፡፡
8ፍቅር ብዙ ኀጢአትን ይሸፍናልና ከሁሉ
በላይ እርስ በርሳችሁ ከልብ ተዋደዱ፤
9እርስ በርሳችሁ ያለ ማጕረምረም
እንግድነት ተቀባበሉ፡፡ 10እንደ ታማኝ
የእግዚአብሔር ልዩ ልዩ ጸጋ መጋቢ
እያንዳንዱ ሰው በተቀ በለው የጸጋ ስጦታ
ሌላውን ያገልግል፤ 11ከእናንተ ማንም
የሚናገር ቢኖር እንደ እግዚአብሔር ቃል
ይናገር፤ የሚያገለግልም ቢኖር እግዚአብሔር
በሚሰጠው ብርታት ያገ ልግል፤ ይኸውም
እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስ ቶስ አማካይነት
እንዲከብር ነው፤ ክብርና ኀይል ለእርሱ
ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን፤ አሜን፡፡

### ክርስቲያን በመሆን የሚደርስ መከራ

12ወዳጆች ሆይ፤ እንደ እሳት የሚፈትን
ብርቱ መከራ በመቀበላችሁ እንግዳ ነገር
እንደ ደረሰባችሁ በመቍጠር አትደነቁ፤

3፥8 ሮሜ12፥10፤
15፥5፤ኤፌ4፥2፤
1ጴጥ5፥5
3፥9 ማቴ5፥44፤
ሮሜ8፥28፤
ሮሜ12፥17፤
1ተስ5፥15፤
ዕብ6፥14፤
1ጴጥ2፥21፡23
3፥12 መዝ34፥12ና16
3፥13 ቲቶ2፥14
3፥14 ቍ17፤
ኢሳ8፥12፡13፤
1ጴጥ2፥19፡20፤4፥15፡16
3፥15 ሐላ4፥6፤
ዕብ3፥6
3፥16 ቍ21፤
ሐሥ23፥1፤
1ጴጥ2፥12፡15
3፥17 1ጴጥ2፥15፤
20፤4፥15፡16፡19
3፥18 ሮሜ5፥2፤
ሐላ1፥22፤ዕብ7፥27፤
1ጴጥ2፥21፤4፥1፡6፡13
3፥19 1ጴጥ4፥6
3፥20 ዘፍ6፥3፡5፡
13፡14፤8፥18፤
ሮሜ2፥4፤ዕብ11፥7
3፥21 ቍ16፤
ሐሥ22፥16፤
23፥1፤1ጴጥ1፥3
3፥22 ማቴ28፥18፤
ማር16፥19፤
ሮሜ8፥38፤ዕብ4፥14
4፥1 ሮሜ
6፥18፤1ጴጥ2፥21
4፥2 ሮሜ6፥2፤
1ጴጥ1፥14
4፥3 ሮሜ13፥13፤
ኤፌ2፥2
4፥4 1ጴጥ3፥16
4፥5 ሐሥ10፥42
4፥6 1ጴጥ3፥19
4፥7 ሐሥ24፥25፤
ሮሜ13፥11
4፥8 ምሳ10፥12፤
ያዕ5፥20፤1ጴጥ1፥22
4፥9 ሮሜ12፥13፤
ፊል2፥14
4፥10 ሮሜ12፥6፡7፤
1ቆሮ4፥2
4፥11 ሮሜ11፥36፤
1ቆሮ10፡31፤ኤፌ6፥10፤
1ጢሞ2፥4
4፥12 1ጴጥ1፥6፡7

ሐ14 ወይም *የሚፈሩትን አትፍሩ*
መ21 ወይም *ምላሽ*

13ነገር ግን ክብሩ በሚገለጥበት ጊዜ ደስ
ታችሁ ታላቅ እንዲሆን የክርስቶስ መከራ
ተካፋዮች በመሆናችሁ ደስ ይበላችሁ።
14ስለ ክርስቶስ ስም ብትሰደቡ፣ የክብር
መንፈስ የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ
በእና ንተ ላይ ስለሚያርፍ ብፁዓን ናችሁ።
15ከእ ናንተ ማንም መከራን የሚቀበል ቢ
ኖር፣ ነፍሰ ገዳይ ወይም ሌባ ወይም
ወንጀለኛ ወይም በሰው ነገር ጣልቃ ገቢ
ሆኖ መከ ራን አይቀበል፤ 16ክርስቲያን
በመሆኑ መከራ ቢደርስበት ግን ስለዚህ ስም
እግዚአብሔርን ያመስግን እንጂ አይፈር፤
17ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት የሚጀምርበት
ጊዜ ደርሶአ ልና። እንግዲህ ፍርድ
የሚጀምረው በእኛ ከሆነ ለእግዚአብሔር
ወንጌል የማይታዘዙ ሰዎች መጨረሻቸው
ምን ይሆን?
18እንግዲህ፣

"ጻድቅ የሚድነው በጭንቅ ከሆነ፣
ዐመፀኛውና ኀጢአተኛው እንዴት ሊሆን
ይሆን?"

19ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መከ
ራ የሚቀበሉ ሁሉ ነፍሳቸውን ለታመነ
ፈጣሪ ዐደራ ሰጥተው መልካም
ማድረጋቸውን ይቀጥሉ።

## ለሽማግሌዎችና ለጎልማሶች የተሰጠ ምክር

5 እንግዲህ ከእነርሱ ጋር እኔም ሽማ
ግሌና የክርስቶስ መከራ ምስክር የሆ
ንሁ እንዲሁም ወደ ፊት የሚገለጠው
ክብር ተካፋይ የምሆን በመካከላችሁ ያሉ
ትን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ፤ 2በእና
ንተ ኀላፊነት ሥር ያለውን የእግዚአብሔርን
መንጋ ጠብቁ፤ የምትጠብቁትም ከእግዚአብ
ሔር እንደሚጠበቅባችሁ በግድ ሳይሆን
በፈቃደኝነት፣ ለጥቅም በመስገብገብ ሳይ
ሆን ለማገልገል ባላችሁ ጽኑ ፍላጎት ይሁን፤
3እንዲሁም በዐደራ ለተሰጣችሁ መንጋ መል
ካም ምሳሌ በመሆን እንጂ በላያቸው በመ
ሠልጠን አይሁን። 4የእረኞች አለቃ በሚገ
ለጥበት ጊዜ የማይጠፋውን አክሊል ትቀበ
ላላችሁ።

5ጐልማሶች ሆይ፤ እናንተም እንዲሁ ለሽ
ማግሌዎች ተገዙ፤ ሁላችሁም እርስ በርስ በመ
ከባበር ትሕትናን ልበሱ፤ ምክንያቱም፣
"እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤
ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል።"

6ስለዚህ እርሱ በወሰነው ጊዜ ከፍ እንዲ
ያደርጋችሁ ከእግዚአብሔር ብርቱ እጅ በታች ራሳ
ችሁን ዝቅ አድርጉ፤ 7እርሱ ስለ እናንተ
ስለሚያስብ የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእ
ርሱ ላይ ጣሉት።

8ራሳችሁን የምትገዙ ሁኑ፤ ንቁም፤ ጠላ
ታችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን በመፈለግ
እንደሚያገሣ አንበሳ ወዲያ ወዲህ ይዞራል።
9በዓለም ዙሪያ ያሉት ወንድሞቻችሁ ተመ
ሳሳይ መከራ እንደሚቀበሉ ዐውቃችሁ
በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት።

10በክርስቶስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራ
ችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ፣ ለጥቂት ጊዜ መከራ
ከተቀበላችሁ በኋላ እርሱ ራሱ መልሶ
ያበረታችኋል፤ አጽንቶም ያቆማችኋል።
11ኀይል ከዘላለም እስከ ዘላለም ለእርሱ
ይሁን፤ አሜን።

## የስንብት ሰላምታ

12እንደ ታማኝ ወንድም በምቈጥረው
በስልዋኖስ አማካይነት ይህንን አጭር
መልእ ክት ጽፌላችኋለሁ፤ የጻፍሁላችሁም
ልመክራችሁና ይህ እውነተኛ የእግዚአብሔር
ጸጋ መሆኑን ልመሰክርላችሁ ብዬ ነው።
በዚህ ጸጋ ጸንታችሁ ቁሙ።

13ከእናንተ ጋር የተመረጠችው፣ በባቢ
ሎን የምትገኘው[ሠ] ሰላምታ ታቀርብላችኋ
ለች፤ እንዲሁም ልጄ ማርቆስ ሰላምታ
ያቀርብላችኋል። 14በፍቅር አሳሳም እርስ
በርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ።

በክርስቶስ ላላችሁ ለሁላችሁ ሰላም
ይሁን።

4፥13 ማቴ5፥12፤ ሮሜ8፥17፤2ቆሮ1፥5፤ 1ጴጥ1፥7፤5፥1
4፥14 ማቴ5፥11፤ ዮሐ15፥21
4፥16 ሐሥ5፥41
4፥17 ኤር25፥29፤ ሕዝ9፥6፤አሞ3፥2፤ 2ተስ1፥8፤1ጢሞ3፥15
4፥18 ምሳ11፥31፤ ሉቃ23፥31
4፥19 1ጴጥ2፥15፤ 3፥17
5፥1 ሉቃ24፥48፤ ሐሥ11፥30፤ 1ጴጥ1፥5፡7፤4፥13፤ ራእ1፥9
5፥2 ዮሐ21፥16፤ 2ቆሮ9፥7፤1ጢሞ3፥3፤ ፊሞ14
5፥3 ሕዝ34፥4፤ ማቴ20፥25ኛ28፤ 1ጢሞ4፥12
5፥4 ዮሐ10፥11፤ 1ቆሮ9፥25፤1ጴጥ1፥4
5፥5 ምሳ3፥34፤ ማቴ23፥12፤ኤፌ5፥21 ፤1ጴጥ3፥8
5፥6 ኢዮ5፥11፤ ያዕ4፥10
5፥7 መዝ37፥5፤ 55፥22፤ማቴ6፥25፤ ዕብ13፥5
5፥8 ኢዮ1፥7፤ ሐሥ24፥25፤2ጢሞ4፥17
5፥9 ሐሥ14፥22፤ ሐሳ2፥5፤ያዕ4፥7
5፥10 መዝ18፥32፤ ሮሜ8፥28፤2ቆሮ4፥17፤ 2ተስ2፥17፤ 2ጢሞ2፥10፤1ጴጥ1፥6
5፥11 ሮሜ11፥36
5፥12 ሐሥ15፥22፤ 1ቆሮ16፥13፤ ዕብ13፥22
5፥13 ሐሥ12፥12
5፥14 ሮሜ16፥16፤ ኤፌ6፥23

[ሠ]13 በአንዳንድ ጥንታዊ ቅጆች ላይ *በባቢሎን የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን* ይላል።

# የሐዋርያው ጴጥሮስ መልእክት - ሁለተኛ

1 የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይና ሐዋርያ
ስምዖን ጴጥሮስ፤ በአምላካችንና በአዳ
ኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ በኩል
እንደ ተቀበልነው ዐይነት ክቡር እምነት
ለተቀበሉት፤
2እግዚአብሔርን ጌታችን ኢየሱስን በማወቅ
ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።

## መጠራትንና መመረጥን ማረጋገጥ

3በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን እርሱን
በማወቅ ለሕይወትና ለእውነተኛ መንፈሳ
ዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ የመለኮቱ ኀይል
ሰጥቶናል። 4ከክፉ ምኞት የተነሣ በዓለም
ካለው ምግባረ ብልሹ ሕይወት አምልጣችሁ
ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች እንድ
ትሆኑ በእነዚህ ነገሮች አማካይነት እጅግ
ታላቅና ክቡር የሆነውን ተስፋ ሰጥቶናል።
5በዚህም ምክንያት በሙሉ ትጋት
በእምነታችሁ ላይ በጎነትን ለመጨመር
ጣሩ፤ በበጎነት ላይ ዕውቀትን፣ 6በዕውቀት
ላይ ራስን መግዛት፣ ራስን በመግዛት ላይ
መጽናትን፣ በመጽናት ላይ እውነተኛ
መንፈሳዊነትን፤ 7በእውነተኛ መንፈሳዊነት
ላይ ወንድማዊ መተሳሰብን፣ በወንድማዊ
መተሳሰብ ላይ ፍቅርን ጨምሩ። 8እነዚህ
ባሕርያት ተትረፍርፈው ቢኖሯችሁ ጌታችን
ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ዳተኞችና ፍሬ
ቢሶች ከመሆን ይጠብቋችኋል። 9እነዚህ
ባሕርያት የሌሉት ግን የሩቁን የማያይ
ወይም ዕውር ነው፤ ከቀድሞው ኀጢአቱ
መንጻቱንም ረስቶአል።
10ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፤ መጠራታች
ሁንና መመረጣችሁን ለማጽናት ከፊት
ይልቅ ትጉ፤ ምክንያቱም እነዚህን
ብታደርጉ ከቶ አትሰናከሉም፤ 11በዚህም
ወደ ጌታችንና አዳኛችን ወደ ኢየሱስ
ክርስቶስ ዘላለማዊ መንግሥት መግባት
በሙላት ይሰጣችኋል።

## የቅዱሳት መጻሕፍት ትንቢት

12ስለዚህ ምንም እንኳ እነዚህን ነገሮች
ብታውቋቸውና በያዛችሁት እውነት ብት
ጸኑም፣ ስለ እነዚህ ነገሮች እናንተን ዘወትር
ከማሳሰብ ቸል አልልም። 13በዚህ ምድራዊ
ድንኳን ውስጥ እስካለሁ ድረስ እናንተን
መጐትጐት ትክክል ሆኖ ይታየኛል፤ 14ምክን
ያቱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ
ገለጠልኝ ይህን ምድራዊ ድንኳን ቶሎ ጥዬ
እንደምሄድ ዐውቃለሁ፤ 15እነዚህን ነገሮች
ከተለየኋችሁም በኋላ ዘወትር ታስቡ
ዘንድ እተጋለሁ።
16ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኀይልና
ስለ መምጣቱ የነገርናችሁ እኮ የእርሱን
ግርማ በዐይናችን አይተን እንጂ፣ በሰዎች
ጥበብ የተፈጠረውን ተረት ተከትለን አይ
ደለም፤ 17ምክንያቱም ከግርማዊው ክብር
"በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ
ነው" የሚል ድምፅ በመጣለት ጊዜ ከእግዚ
አብሔር አብ ክብርና ሞገስ ተቀብሎአል፤
18እኛም ከእርሱ ጋር በቅዱሱ ተራራ ላይ
በነበርንበት ጊዜ ይህ ድምፅ ከሰማይ ሲመጣ
ሰምተናል።
19እንግዲያስ ትንቢታዊው ቃል ይበ
ልጥ ተረጋግጦልናል፤ ሌሊቱ እስኪነጋና
የንጋት ኮከብ በልባችሁ እስኪበራ ድረስ፣
በጨለማ ስፍራ ለሚበራ መብራት ጥን
ቃቄ እንደሚደረግ እናንተም ለዚህ ቃል
ብትጠነቀቁ መልካም ታደርጋላችሁ።
20ከሁሉ አስቀድሞ ይህን ልታውቁ ይገባ
ችኋል፤ በመጽሐፍ ያለው የትንቢት ቃል
ሁሉ ማንም ሰው በገዛ ራሱ መንገድ
የሚተረጕመው አይደለም፤ 21ምክንያቱም
ትንቢት ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች በመ
ንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩት እንጂ
ከቶ በሰው ፈቃድ የመጣ አይደለም።

## ሐሰተኛ መምህራንና መጨረሻቸው

2 ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት በሕዝቡ
መካከል እንደ ነበሩ እንዲሁም በእናንተ
መካከል ሐሰተኞች መምህራን ይነሣሉ፤
እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ክደው
ጥፋት የሚያስከትል የስሕተት ትምህርት
በስውር ያስገባሉ፤ በዚህም በራሳቸው ላይ
ድንገተኛ ጥፋት ያመጣሉ። 2ብዙዎች አስ
ነዋሪ ድርጊቶቻቸውን ይከተላሉ፤ በእነ
ርሱም ምክንያት የእውነት መንገድ ይሰደ
ባል። 3እነዚህ ሐሰተኞች መምህራን እየተ
ስገበገቡ በፈጠራ ታሪካቸው ይበዘብዙዋ
ችኋል። ፍርዳቸው ከጥንት ጀምሮ ዝግጁ
ነው፤ መጥፊያቸውም አያንቀላፋም።
4እግዚአብሔር ኀጢአት የሠሩትን መላእ
ክት ሳይራራላቸው ወደ ገሃነም[ሀ] ከጣላቸ
ውና በጨለማ ጕድጓድ ውስጥ ለፍርድ
ካስቀመጣቸው 5የጽድቅ ሰባኪ የነበረው
ንም ኖኅን ከሌሎች ሰባት ሰዎች ጋር አድኖ
ለቀድሞው ዓለም ሳይራራ በኀጢአተ
ኞች ላይ የጥፋት ውሃ ካመጣ፣ 6ደግሞም

ሀ4 በግሪኩ *ታርታሩስ* ይለዋል

1፥1 ሮሜ1፥1፤
3፥21ኛ26፤ቲቶ2፥13፤
1ጴጥ1፥1
1፥2 ቆላ3፡8፤
ሮሜ1፥7፤ፊል3፥8፤
2ጴጥ2፥20፤3፥18
1፥3 ቆላ2፤
ሮሜ8፥28፤1ጴጥ1፥5
1፥4 2ቆሮ7፥1፤
ኤፌ4፥24፤ዕብ12፥
10፤ ያዕ1፥27፤
2ጴጥ2፥18ኛ20፤
1ዮሐ3፥2
1፥5 ቆላ2፤ሐሳ2፥3
1፥6 ቆላ3፤
ሐሥ24፥25፤
ዕብ10፥36
1፥7 ሮሜ12፥10፤
1ተሰ3፥12
1፥8 ቆላ2፤
ዮሐ15፥2፤
ሐሳ1፥10፤ቲቶ3፥14
1፥9 ማቴ1፥21፤
ኤፌ5፥26፤
1ዮሐ2፥11
1፥10 መዝ15፥5፤
ሮሜ8፥28፤2ጴጥ3፥
17፤ይሁ24
1፥11መዝ145፥13፤
2ጢሞ4፥18፤
2ጴጥ2፥20፤3፥18
1፥12 ፊል3፥1፤
1ዮሐ2፥21፤
2ዮሐ2፤ይሁ5
1፥13 ኢሳ38፥12፤
2ቆሮ5፥1፡4፤2ጴጥ3፥1
1፥14ዮሐ13፥36፤
21፥18፡19፤ 2ጢሞ4፥6
1፥15 ሉቃ9፥31
1፥16 ማቴ17፥1ኛ8፤
ማር13፥26፤14፥62
1፥17 ማቴ3፥17
1፥18 ማቴ17፥6
1፥19 መዝ119፥
105፤ ሉቃ1፥78፤
2ቆሮ4፥6፤1ጴጥ1፥10፤
ራእ22፥16
1፥20 2ጴጥ3፥3
1፥21 2ሳሙ23፥2፤
ሐሥ1፥16፤3፥18፤
2ጢሞ3፥16፤
1ጴጥ1፥11
2፥1 ዘዳ13፥1ኛ3፤
ኤር6፥13፤
ማቴ7፥15፤1ቆሮ6፥20
፤1ጢሞ4፥1፤ይሁ4
2፥2 ይሁ4
2፥3 ቆላ14፤
2ቆሮ2፥17፤1ተሰ2፥5
2፥4 ዘፍ6፥1ኛ4፤
1ጢሞ3፥6፤ይሁ6፤
ራእ20፥1፡2
2፥5 ዘፍ6፥5ኛ8፡
19፤ዕብ11፥7፤

ኀጢአት ለሚያደርጉ ሁሉ ምሳሌ እንዲ
ሆኑ የሰዶምንና የገሞራን ከተሞች ዐ
መድ እስኪሆኑ ድረስ አቃጥሎ
ከፈረደባቸው፣ 7ጻድቅ የሆነውንና በዐመፀ
ኞች ሴሰኛ ድርጊት እየተሣቀቀ የኖረውን
ሎጥን ካዳነ፣ 8ያ ጻድቅ ሰው በእነርሱ
መካከል ሲኖር በሚያየውና በሚሰማው
ነገር ነፍሱ ዕለት ዕለት በዐመፀኛ ድርጊ
ታቸው ብትጨነቅም፣ 9ጌታ፣ በእውነት
እያመለኩት የሚኖሩትን ከፈተና እንዴት
እንደሚያድናቸውና ዐመፀኞችን እየቀጣ
ለፍርድ[ለ] ቀን እንዴት ጠብቆ እንደ ሚያ
ቈያቸው ያውቃል። 10በተለይም በርኩስ
ምኞት የሥጋ ፍላጎታቸውን[ሐ] የሚከተሉትንና
ሥልጣንን የሚንቁትን ለፍርድ ጠብቆ
ያቈያቸዋል።

እነዚህ ሰዎች ደፋሮችና እብሪተኞች
ስለ ሆኑ ሰማያውያንን ፍጡራን ሲሳደቡ
አይፈሩም፤ 11ነገር ግን መላእክት ከእነርሱ
ይልቅ ብርቱና ኀያል ሆነው ሳሉ፣ በጌታ ፊት
በእነርሱ ላይ የስድብ ቃል አይሰነዝሩም።
12እነዚህ ሰዎች ግን ምንም በማያውቁት
ነገር እየገቡ ይሳደባሉ፤ እነርሱም ለመ
ያዝና ለመገደል እንደ ተወለዱ፣ በስሜ
ታቸው ብቻ እንደሚመሩና ልቦናም እንደ
ሌላቸው አራዊት ናቸው፤ የሚጠፉትም
እንደ እንስሳት ነው።

13ለዐመፃቸው የሚገባውን የዐመፅ ዋጋ
ይቀበላሉ፤ በጠራራ ፀሓይ ሲፈነጥዙ እንደ
ደስታ ይቈጥሩታል፤ በግብዣ ላይ ሳሉ
ነውረኞችና ርኩሶች ሆነው ከእናንተም ጋር
በፍቅር ግብዣ ላይ[መ] ይቀመጣሉ፤ 14ዐይናቸው
ቅንዝር የተሞላ በመሆኑ ኀጢአትን ከመ
ሥራት አይቈጠቡም፤ ጽኑ ያልሆኑትን ነፍ
ሳት ያስታሉ፤ ስስትን የለመደ ልብ አላ
ቸው፤ የተረገሙ ናቸው! 15ቀናውን መንገድ
ትተው፣ የዐመፅን ደመወዝ የወደደውን የቢ
ያርን ልጅ የበለዓምን መንገድ ተከትለው
ስተዋል፤ 16እርሱ ግን ስለ መተላለፉ
ተገሥጾአል፤ መናገር የማይችል አህያ
በሰው ቋንቋ ተናግሮ የነቢዩን እብደት
ገታ። 17እነዚህ ሰዎች የደረቁ ምንጮችና
በዐውሎ ነፋስ የሚነዱ ደመናዎች ናቸው፤
የሚጠብቃቸውም ድቅድቅ ጨለማ ነው፤
18ከንቱ ቃል እየደረደሩ በስሕተት ከሚኖ
ሩት መካከል አምልጠው የመጡትን ሰዎች
በሴሰኛ ሥጋዊ ምኞት በማባበል ያታ
ልላሉና። 19እነርሱ ራሳቸው የጥፋት ባሪያ
ዎች ሆነው ሳሉ፣ ሌሎችን ነጻ ትወጣላችሁ
እያሉ ተስፋ ይሰጧቸዋል፤ ሰው ለተገዛለት
ለዚያ ነገር ባሪያ ነውና። 20ጌታችንንና
አዳኛችንን ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ከዓ
ለም ርኵሰት ካመለጡ በኋላ እንደ ገና

1ጴጥ3፥20፤2ጴጥ3፥6
2፥6 ዘፍ19፥24፡25፤
ዘኍ26፥10፤
ማቴ10፥15፤11፥23፡2
4፤ሮሜ9፥29፤ይሁ7
2፥7 ዘፍ19፥16፤
2ጴጥ3፥17
2፥8 ዕብ11፥4
2፥9 መዝ37፥33፤
ማቴ10፥15፤
ሮሜ15፥31፤
ራእ3፥10
2፥10 2ጴጥ3፥3፤
ይሁ8፡16፡18
2፥11 ይሁ9
2፥12 መዝ49፥12፤
ይሁ10
2፥13 ሮሜ13፥13፤
1ቆሮ11፥20፡21፤
1ተሰ5፥7፤ይሁ12
2፥14 ቍ3፡18፤
ኤፌ2፥3፤2ጴጥ3፥16፤
ያዕ1፥8
2፥15 ዘኍ22፥4ኛ20፤
31፥16፤ዘዳ23፥4፤
ይሁ11፤ራእ2፥14
2፥16 ዘኍ22፥21ኛ30
2፥17 ይሁ12፥13
2፥18 ቍ20፤
2ጴጥ1፥4፤ይሁ16
2፥19 ሮሜ6፥16
2፥20 ማቴ12፥45፤
2ጴጥ1፥2፡11፤3፥18
2፥21 ሕዝ18፥24፤
ዕብ6፥4ኛ6፤
10፥26፡27
2፥22 ምሳ26፥11
3፥1 1ቆሮ10፥14፤
2ጴጥ1፥13
3፥2 ሉቃ1፥70፤
ሐሥ3፥21፤ኤፌ4፥11
3፥3 1ጢሞ4፥1፤
2ጢሞ3፥1፤
2ጴጥ2፥10፤ይሁ18
3፥4 ኢሳ5፥19፤
ሕዝ12፥22፤
ማቴ24፥48፤
ማር10፥6፤
ሉቃ17፥30
3፥5 ዘፍ1፥6፡9፤
መዝ24፥2፤ዕብ11፥3
3፥6 ዘፍ7፥21፡22፤
2ጴጥ2፥5
3፥7 ቍ10፡12፤
ማቴ10፥15፤2ተሰ1፥7
3፥8 መዝ90፥4
3፥9 ዕን2፥3፤
ሮሜ2፥4፤
1ጢሞ2፥4፤ ዕብ10፥
37፤ራእ2፥21
3፥10 ቍ7፡12፤ ኢ
ሳ34፥4፤ማቴ24፥35፤
ሉቃ12፥39፤2ተሰ1፥7፤
ራእ21፥1

ተጠላልፈው ቢሸነፉ ከመጀመሪያው ይልቅ
የኋለኛው ሁኔታቸው የከፋ ይሆንባቸዋል።
21የጽድቅን መንገድ ካወቁ በኋላ ከተ
ሰጣቸው ቅዱስ ትእዛዝ ወደ ኋላ ከሚ
መለሱ፣ ቀድሞውኑ የጽድቅን መንገድ
ባላወቁዋት ይሻላቸው ነበር። 22“ውሻ ወደ
ትፋቱ ይመለሳል” እንዲሁም “ዐሣማ
ቢታጠብም ተመልሶ በጭቃ ላይ ይንከባ
ለላል” የሚለው ምሳሌ እውን ይሆንባቸዋል።

## የጌታ ቀን

3 ወዳጆች ሆይ፤ ይህ አሁን የምጽፍ
ላችሁ ሁለተኛው መልእክት ነው።
ሁለቱንም መልእክቶች የጻፍሁላችሁ ቅን
ልቦናችሁን እንድታነቃቁ ለማሳሰብ ነው፤
2ደግሞም ቀድሞ በቅዱሳን ነቢያት የተነ
ገረውን ቃል እንዲሁም በሐዋርያት አማካ
ይነት በጌታችንና በአዳኛችን የተሰጠውን
ትእዛዝ እንድታስቡ ነው።

3ከሁሉ አስቀድሞ ይህን ዕወቁ፤ በመጨ
ረሻው ዘመን የራሳቸውን ክፉ ምኞት የሚከ
ተሉ ዘባቾች እየዘበቱ ይመጣሉ። 4እነ
ርሱም፣ “ ‘እመጣለሁ’ ያለው ታዲያ
የት አለ? አባቶች ከሞቱበት ከፍጥረት
መጀመሪያ አንሥቶ እስካሁን ድረስ ሁሉም
ነገር እንዳለ ይኖራል” ይላሉ። 5ነገር ግን
እነዚህ ሰዎች ሰማያት ከጥንት ጀምሮ በእግዚ
አብሔር ቃል ተፈጥረው እንደሚኖሩ፣ መሬትም
በውሃ መካከልና በውሃም እንደ ተሠራች
ሆን ብለው ይክዳሉ፤ 6በዚያን ጊዜ የነበ
ረው ዓለም በውሃ ተጥለቅልቆ ጠፋ።
7በዚያው ቃል ደግሞ አሁን ያሉት ሰማ
ያትና ምድር፣ ኀጢአተኞች እስከሚጠ
ፉበት እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ለእሳት
ተጠብቀዋል።

8ወዳጆች ሆይ፤ በጌታ ዘንድ አንድ ቀን
እንደ ሺህ ዓመት፣ ሺህ ዓመትም እንደ
አንድ ቀን መሆኑን ይህን አንድ ነገር
አትርሱ። 9አንዳንድ ሰዎች የዘገየ እንደ
ሚመስላቸው ጌታ የተስፋ ቃሉን ለመፈ
ጸም አይዘገይም፤ ነገር ግን ማንም እንዳ
ይጠፋ፣ ሁሉ ለንስሓ እንዲበቃ ስለ እናንተ
ይታገሣል።

10የጌታ ቀን ግን እንደ ሌባ ይመጣል፤
በዚያች ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፤
የሰማይም ፍጥረት በእሳት ይጠፋል፤ ምድርና
በእርሷም ላይ ያለ ነገር ሁሉ ይቃጠላል።[ሠ]

11እንግዲህ ሁሉም ነገር በዚህ ሁኔታ
የሚጠፋ ከሆነ፣ እናንተ እንዴት ዐይነት

[ለ] 9 ወይም *ዐመፀኞችን ለቅጣት እስከ ፍርድ ቀን ድረስ*
[ሐ] 10 ወይም *የኀጢአተኛ ባሕርያቸውን*
[መ] 13 በአንዳንድ ቅጆች *በፍቅር ግብዣቸው ላይ* የሚል የለም
[ሠ] 10 በአንዳንድ ቅጅዎች *ምድር ወና ትሆናለች* ይላል

ሰዎች ልትሆኑ ይገባችኋል? አዎን፣ በቅድ
ስናና በእውነተኛ መንፈሳዊነት ልትኖሩ
ይገባችኋል፤ 12ደግሞም የእግዚአብሔርን ቀን
እየተጠባበቃችሁ መምጫውን ልታ
ፋጥኑ[ሩ] ይገባል፡፡ በዚያን ቀን ሰማያት
በእሳት ተቃጥለው ይጠፋሉ፤ የሰማይም
ፍጥረት በታላቅ ትኵሳት ይቀልጣል፡፡
13እኛ ግን ጽድቅ የሚኖርበትን አዲስ ሰ
ማይና አዲስ ምድር በተስፋ ቃሉ
መሠረት እንጠባበቃለን፡፡
14ስለዚህ ወዳጆች ሆይ፤ እነዚህን ሁሉ
ነገሮች የምትጠባበቁ ስለ ሆናችሁ፣ ያለ
ነውርና ያለ ነቀፋ ከእርሱ ጋር በሰላም
እንድትገኙ ትጉ፡፡ 15የጌታችን ትዕግሥት
እናንተ እንድትድኑ እንደ ሆነ አስቡ፤ እንዲ
ሁም ወንድማችን ጳውሎስ እንደ ተሰጠው

3፥12 ቀኑ10፤
መዝ50፥3፤1ቆሮ1፥7
3፥13 ኢሳ65፥17፤
66፥22፤ራእ21፥1
3፥14 1ተሰ3፥13
3፥15 ቀኑ9፤
ሮሜ2፥4፤ኤፌ3፥3
3፥16 ቀኑ2፤
መዝ56፥5፤ኤር23፥36፤
ያዕ1፥8፤ 2ጴጥ2፥14
3፥17 1ቆሮ10፥12፤
2ጴጥ2፥7፡18፤
ራእ2፥5
3፥18 ሮሜ3፥24፤
11፥36፤2ጴጥ1፥2፡11፤
2፥20

ጥበብ መጠን ጻፈላችሁ፤ 16እርሱ ስለ እነዚህ
ነገሮች በመልእክቶቹ ሁሉ ጽፎአል፤
በመልእክቶቹም ውስጥ በቀላሉ ለመረዳት
የሚያዳግቱ ነገሮች አሉ፡፡ ዕውቀት
የጐደላቸውና ጽናት የሌላቸው ሰዎች ሌሎችን
ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያጣምሙ፣ እነ
ዚህንም ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ፡፡
17እንግዲህ ወዳጆች ሆይ፤ ይህን አስቀድ
ማችሁ ስላወቃችሁ፣ ጸንታችሁ ከቆማች
ሁበት መሠረት በዐመፀኞች ስሕተት ተስ
ባችሁ እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ፡፡
18ነገር ግን በጌታችንና በአዳኛችን በኢ
የሱስ ክርስቶስ ጸጋና ዕውቀት እደጉ፤
ለእርሱ አሁንም፣ ለዘላለምም ክብር ይሁን፤
አሜን፡፡

ሩ12 *ወይም የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት በናፍቆት ስትጠብቁ*

# የሐዋርያው ዮሐንስ መልእክት – አንደኛ

## የሕይወት ቃል

1 ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበ
ረውን፣ የሰማነውን፣ በዐይኖቻችን ያየነ
ውን፣ የተመለከትነውንና እጆቻችን የዳሰሱ
ትን እንናገራለን:: 2ሕይወት ተገለጠ፤ እኛም
አይተነዋል፤ እንመሰክርለታለንም:: በአብ
ዘንድ የነበረውን፣ ለእኛም የተገለጠልንን
የዘላለም ሕይወት እንነግራችኋለን፤ 3እናን
ተም ከእኛ ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ፣
ያየነውንና የሰማነውን እንነግራችኋለን፤
ኅብረታችንም ከአብ፣ ከልጁም ከኢየሱስ
ክርስቶስ ጋር ነው:: 4ደስታችንም[ሀ] ፍጹም
ይሆን ዘንድ ይህን እንጽፍላችኋለን::

## በብርሃን መመላለስ

5 ከእርሱ የሰማነው ለእናንተም የምን
ነግራችሁ መልእክት፣ እግዚአብሔር ብርሃን
ነው፤ ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም፤
የሚል ነው:: 6በጨለማ እየተመላለስን ከእ
ርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል እንዋሻለን፤
እውነትንም አንኖረውም:: 7ነገር ግን እርሱ
በብርሃን እንዳለ፣ እኛም በብርሃን ብንመ
ላለስ እርስ በእርሳችን ኅብረት አለን፤ የል
ጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት
ሁሉ[ለ] ያነጻናል::
8ኀጢአት የለብንም ብንል፣ ራሳችንን
እናስታለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም::
9ኀጢአታችንን ብንናዘዝ ኀጢአታችንን ይቅር
ሊለን፣ ከዐመፃ ሁሉ ሊያነጻን እርሱ ታማ
ኝና ጻድቅ ነው:: 10ኀጢአት አልሠራንም
ብንል፣ እርሱን ሐሰተኛ እናደርገዋለን፤
ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም::

2 ልጆቼ ሆይ፤ ይህን የምጽፍላችሁ ኀጢ
አት እንዳትሠሩ ነው፤ ነገር ግን ማንም
ኀጢአት ቢሠራ፣ በአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፤
እርሱም ጻድቁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::
2እርሱም የኀጢአታችን ማስተስረያ ነው፤
ይኸውም[ሐ] ለዓለም ሁሉ ኀጢአት እንጂ ለእኛ
ብቻ አይደለም::
3ትእዛዛቱን ብንፈጽም እርሱን ማወቃች
ንን በዚህ እርግጠኞች እንሆናለን:: 4 "እር
ሱን ዐውቃለሁ" እያለ ትእዛዙን የማይፈ
ጽም ግን ሐሰተኛ ነው፤ እውነትም በእርሱ
ውስጥ የለም:: 5ነገር ግን ማንም ቃሉን
ቢጠብቅ፣ በእውነት የእግዚአብሔር ፍቅር[መ]
በእ ርሱ ፍጹም ሆኖአል:: በእርሱ
መሆናችንን የምናውቀው በዚህ ነው፤ 6
ማንም በእርሱ እኖራለሁ የሚል፣ ኢየሱስ
እንደ ተመላ ለሰ ሊመላለስ ይገባዋል::
7ወዳጆች ሆይ፤ የምጽፍላችሁ፣ ከመጀ
መሪያ የነበራችሁን የቈየውን ትእዛዝ
እንጂ አዲስ ትእዛዝ አይደለም፤ የቈየው
ትእዛዝ የሰማችሁት ቃል ነው:: 8 በሌላ
በኩል የምጽፍላችሁ ጨለማው ዕያለፈና
እውነተኛው ብርሃን እየበራ ስለሆነ፣ በእ
ርሱም፣ በእናንተም ዘንድ እውነት የሆነ
ውን አዲስ ትእዛዝ ነው:: 9በብርሃን አለሁ
የሚል፣ ወንድሙን ግን የሚጠላ አሁንም
በጨለማ ውስጥ አለ:: 10ወንድሙን የሚ
ወድ በብርሃን ይኖራል፤ በእርሱም ዘንድ
የመሰናከያ ምክንያት የለውም:: 11ነገር ግን
ወንድሙን የሚጠላ በጨለማ ውስጥ ነው፤
በጨለማ ይመላለሳል፤ ጨለማው ስላሳወረ
ውም የት እንደሚሄድ አያውቅም::

12ልጆች ሆይ፤
ኀጢአታችሁ ስለ ስሙ ተሰርዮላችኋልና፣
እጽፍላችኋለሁ::
13አባቶች ሆይ፤
ከመጀመሪያ ያለውን እርሱን
ዐውቃችሁታልና፣
እጽፍላችኋለሁ::
ጐበዛዝት ሆይ፤ ክፉውን
አሸንፋችኋልና፣
እጽፍላችኋለሁ::
ልጆች ሆይ፤
አብን ዐውቃችሁታልና፣
እጽፍላችኋለሁ::
14አባቶች ሆይ፤
ከመጀመሪያ ያለውን እርሱን
ዐውቃችሁታልና፣
እጽፍላችኋለሁ::
ጐበዛዝት ሆይ፤
ብርቱዎች ስለሆናችሁ፣
የእግዚአብሔር ቃል በእናንተ ስለሚኖር፣
ክፉውንም ስላሸነፋችሁ፣
እጽፍላችኋለሁ::

## ዓለምን አትውደዱ

15ዓለምን ወይም በዓለም ያለውን ማናቸ
ውንም ነገር አትውደዱ፤ ማንም ዓለምን
ቢወድ፣ የአብ ፍቅር በእርሱ ዘንድ የለም፤

1፥1 ሉቃ24፡48፤ ዮሐ 1፥2፡14፤19፡35፤20፥27፤ሐሥ4፥20፤2ጴጥ1፥16፤ 1ዮሐ4፥14
1፥2 ማቴ25፥46፤ ዮሐ1፥1-4፤11፥25፤ 14፥6፤15፥27፤ቲቶ 3፥16፤1ጴጥ1፥20፤ 1ዮሐ3፥5፡814፤11፥25 ፤14፥6፤15፥27፤ቲቶ 3፥16፤1ጴጥ1፥1፥20፤1 ዮሐ3፥5፡8
1፥3 ቍ1፤1ቆሮ1፥9
1፥4 ዮሐ3፥29፤ 1ዮሐ2፥11
1፥5 1ጢሞ6፥16፤ 1ዮሐ3፥11
1፥6 ዮሐ3፥19-21፤ 8፥12፤2ቆሮ6፥14፤ ኤፌ5፥8፤1ዮሐ2፥4፡ 11፤4፥20
1፥7 ኢሳ2፥5፤ዕብ9፥14 ፤ራእ1፥5፤7፥14
1፥8 ምሳ20፥9፤ ኤር2፥35፤ዮሐ8፥44፤ ሮሜ3፥9-19፤ያዕ3፥2 ፤1ዮሐ2፥4
1፥9 ቍ7፤መዝ 32፥5፤51፥2፤ምሳ 28፥13፤ሚክ7፥18-20 ፤ዕብ10፥22
1፥10 ቍ8፤ዮሐ5፥38 ዮሐ5፥38፤1ዮሐ2፥14፤ 5፥10
2፥1 ቍ12፡13፡28፤ ሮሜ8፡34፤1ተሰ2፥11፤ 1ጢሞ2፥5፤1ዮሐ3፥7፡ 18፤4፥4፤5፥21
2፥2 ማቴ1፥21፤ዮሐ 3፥17፤ሮሜ3፥25፤1ዮሐ 4፥10፤ሚኪ7፥18-20
2፥3 ቍ4፡5፤ዮሐ 14፥15፤1ዮሐ3፥24፤ 4፥13፤5፥2
2፥4 ቍ3፤ቲቶ1፥16 ፤1ዮሐ1፥6፡8፤3፥6፤ 4፥7፡8
2፥5 ቍ3፤ዮሐ14፥15 ፤1ዮሐ4፥12
2፥6 ማቴ11፥29
2፥7 ቍ24፤1ቆሮ 10፥14፤1ዮሐ3፥11፡ 23፤4፥21፤2ዮሐ5፡6
2፥8 ዮሐ19፤13፥34፤ ሮሜ13፥12፤ኤፌ58፤ 1ተሰ5፥5፤ዕብ10፥25
2፥9 ቍ11፤ዘሌ 19፥17፤1ዮሐ1፥5፤ 3፥10፡15፡16፤4፥20፡21
2፥10 ቍ11፤መዝ 119፥165፤1ዮሐ3፥14
2፥11 ቍ9፤ዮሐ 11፥9፤12፥35፤1ዮሐ1፥6
2፥12 ቍ1፤1ዮሐ3፥23
2፥13 ቍ1፡14፤ማቴ 5፡37፤ዮሐ1፥1፤16፥33
2፥14 ቍ13፤ዮሐ 1፥1፤5፥38፤ኤፌ6፥10፤ዕብ4፥12፤1ዮሐ1፥10
2፥15 ሮሜ12፥2፤ያዕ4፥4

[ሀ]4 አንዳንዶች ቅጆች የእናንተ ይላል
[ለ]7 ወይም ከማንኛውም
[ሐ]2 ኀጢአታችንን አስወግዶ የእግዚአብሔርን ቍጣ ከእኛ የሚያርቅ እርሱ ነው ይኸውም የእኛን ኀጢአት ብቻ ሳይሆን ማለትም ነው::

16ምክንያቱም በዓለም ያለው ሁሉ፦ የሥጋ
ምኞት፣ የዐይን አምሮትና የኑሮ ትምክሕት
ከዓለም እንጂ ከአብ የሚመጣ አይደለም።
17ዓለምና ምኞቱ ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን
ፈቃድ የሚፈጽም ግን ለዘላለም ይኖራል።

## ከክርስቶስ ተቃዋሚዎች መጠንቀቅ

18ልጆች ሆይ፤ ይህ የመጨረሻው ሰዓት
ነው፤ እንደሰማችሁትም የክርስቶስ ተቃዋሚ
ይመጣል፤ አሁን እንኳ ብዙ የክርስቶስ ተቃ
ዋሚዎች መጥተዋል፤ የመጨረሻው ሰዓት
እንደ ሆነ የምናውቀውም በዚህ ነው።
19ከእኛ መካከል ወጡ፤ ይሁን እንጂ
ከእኛ ወገን አልነበሩም፤ ከእኛ ወገን ቢሆ
ኑማ ኖሮ ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር።
ነገር ግን ሁሉም ከእኛ ወገን እንዳልነበሩ
ይታወቅ ዘንድ ከእኛ ተለዩ።
20እናንተ ግን ከእርሱ ከቅዱሱ፣ ቅባት
አላችሁና፤ ሁላችሁም እውነትን[ሠ] ታውቃላ
ችሁ። 21እኔ የምጽፍላችሁ እውነትን ስለ
ማታውቁ አይደለም፤ ነገር ግን እውነትን
ስለምታውቁትና ከእውነት ምንም ውሸት
ስለማይወጣ ነው። 22ክርስቶስ አይደለም
ብሎ ኢየሱስን ከሚክድ በቀር ሐሰተኛ
ማነው? ይህ አብንና ወልድን የሚክደው
የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው። 23ወልድን
የሚክድ ሁሉ አብ የለውም፤ ወልድን
የሚያምን ሁሉ አብም አለው።
24ከመጀመሪያ የሰማችሁት በእናንተ
ውስጥ ይኑር፤ ከመጀመሪያ የሰማችሁት
በእናንተ ውስጥ ቢኖር፣ እናንተም በወልድና
በአብ ትኖራላችሁ። 25ይህ እርሱ የሰጠን
ተስፋ የዘላለም ሕይወት ነው።
26ስለሚያስቷችሁ ሰዎች ይህን ጽፌላ
ችኋለሁ። 27እናንተ ግን ከእርሱ የተቀበላ
ችሁት ቅባት በውስጣችሁ ይኖራልና፤
ማንም እንዲያስተምራችሁ አያስፈልግም፤
ነገር ግን እውነት እንጂ ሐሰት ያልሆነው
የእ ርሱ ቅባት ስለ ሁሉም ነገር
እንደሚያስተ ምራችሁ፣ ያም እውነት
እንጂ ሐሰት እን ዳልሆነ፣ እናንተንም
እንዳስተማራችሁ በእ ርሱ ኑሩ።

## የእግዚአብሔር ልጆች

28እንግዲህ ልጆች ሆይ፤ እርሱ ሲገለጥ
ድፍረት እንዲኖረን፣ በሚመጣበትም ጊዜ
በፊቱ እንዳናፍር በእርሱ ኑሩ።
29እርሱ ጻድቅ መሆኑን ካወቃችሁ፣ ጽድ
ቅን የሚያደርግ ሁሉ ከእርሱ እንደ ተወ
ለደ ታውቃላችሁ።

3 የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን እንድንጠ
ራ አብ አትረፍርፎ ያፈሰሰልን
ፍቅር ምንኛ ታላቅ ነው! እኛም እንዲሁ
ልጆቹ ነን። ዓለም እኛን የማያውቀንም
እርሱን ስላላወቀው ነው። 2ወዳጆች
ሆይ፤ እኛ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤
ወደ ፊት ምን እንደምንሆን ገና
አልተገለጠም። እርሱ በሚገለጥበት[ረ] ጊ
ዜ እናየዋለንና፣ እርሱን እንደምን መስል
እናውቃለን። 3በእ ርሱ ይህን ተስፋ
የሚያደርግ ሁሉ፣ እርሱ ንጹሕ እንደ ሆነ
ራሱን ያነጻል።
4ኀጢአት የሚያደርግ ሁሉ ዐመፅን ያደ
ርጋል፤ ኀጢአትም ዐመፅ ነው። 5እርሱ
ኀጢአትን ሊያስወግድ እንደ ተገለጠ ታው
ቃላችሁ፤ በእርሱም ኀጢአት የለም። 6በእ
ርሱም የሚኖር ኀጢአትን አያደርግም፤
ኀጢአት የሚያደርግ ግን እርሱን አላየ
ውም ወይም አላወቀውም። 7ልጆች ሆይ፤
ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፤ እርሱ
ጻድቅ እንደ ሆነ፣ ጽድቅን የሚያደርግ
ጻድቅ ነው። 8ኀጢአትን የሚያደርግ ከዲያ
ብሎስ ነው። ምክንያቱም ዲያብሎስ ከመ
ጀመሪያ አንሥቶ ኀጢአትን የሚያደርግ
ነው። የእግዚአብሔር ልጅ የተገለጠውም የዲ
ያብሎስን ሥራ ያፈርስ ዘንድ ነው። 9ከእግ
ዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኀጢአትን
አያደር ግም፤ የእርሱ ዘር በውስጡ ይኖራ
ልና፤ ከእግዚአብሔር ስለ ተወለደም ኀጢ
አትን ሊያ ደርግ አይችልም። 10የእግዚአብሔ
ር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች
ተለይተው የሚታወ ቁት በዚህ ነው፦
ጽድቅን የማያደርግ፣ ወንድሙንም የ
ማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም።

## እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ

11ከመጀመሪያ የሰማችኋት፣ እርስ በር
ሳችን ልንዋደድ ይገባናል የምትለዋ መል
እክት ይህች ናትና፤ 12የክፉው ወገን ሆኖ
ወንድሙን እንደ ገደለው እንደ ቃየን አት
ሁኑ፤ ለምን ገደለው? ምክንያቱም የእርሱ
ሥራ ክፉ፣ የወንድሙ ግን ጽድቅ ስለ
ነበረ ነው። 13ወንድሞች ሆይ፤ ዓለም ቢጠ
ላችሁ አትደነቁ። 14ወንድሞቻችንን ስለም
ንወድ ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገ
ርን እናውቃለን፤ ፍቅር የሌለው ሁሉ
በሞት ይኖራል። 15ወንድሙን የሚጠላ ነፍሰ
ገዳይ ነው፤ ነፍሰ ገዳይም የዘላለም ሕይ
ወት እንደሌለው ታውቃላችሁ።
16ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ስለ እኛ
አሳልፎ ስለ ሰጠ፣ ፍቅር ምን እንደ ሆነ
በዚህ እናውቃለን፤ እኛም ሕይወታችንን

2፥16 ዘፍ3፥6፤ምሳ 27፥20፤ሮሜ13፥14፤ ኤፌ2፥3
2፥17 ማቴ12፥50፤ ዕብ12፥27
2፥18 ቊ22፤ሮሜ 13፥11፤1ዮሐ4፥1፡3፤ 2ዮሐ 7
2፥19 ሐሥ20፥30፤ 1ቆሮ11፥19
2፥20 ቊ27፤ኤር 31፥34፤ማቴ13፥11፤ ማር1፥24፤ዮሐ14፥26፤ 2ቆሮ1፥21
2፥21 2ጴጥ1፥12፤ ይሁ5
2፥22 1ዮሐ4፥3፤ 2ዮሐ7
2፥23 ዮሐ8፥19፤ 14፥7፤ 1ዮሐ4፥15፤ 5፥1፤2ዮሐ9
2፥24 ቊ7፤ዮሐ 14፥23፤15፥4፤ዮሐ 1፥3፤2ዮሐ9
2፥25 ማቴ25፥46
2፥26 1ዮሐ3፥7
2፥27 ቊ20፤ዮሐ 15፥4፤ 1ቆሮ2፥12
2፥28 ቊ1፤ኤፌ3፥ 12፤ቈላ3፥4፤1ተሰ2፥ 19፤1ዮሐ3፥2
2፥29 ዮሐ1፥13፤ 1ዮሐ3፥7
3፥1 ቊ2፡10፤ዮሐ 1፥12፤3፥16፤15፥21፤ 16፥3
3፥2 ቊ1፡10፤ መዝ17፥15፤ዮሐ1፥12 ፤17፥24፤ ሮሜ8፥29፤ 1ቆሮ10፥14፤ 2ቆሮ3፥18፤ቈላ3፥4፤2 ጴጥ1፥4፤1ዮሐ2፥28
3፥3 መዝ18፥26፤ 2ቆሮ7፥1፤ 2ጴጥ3፥13፡14
3፥4 1ዮሐ5፥17
3፥5 ቊ8፤ዮሐ3፥17 ፤2ቆሮ5፥21
3፥6 ቊ9፤1ዮሐ2፥4 ፤5፥18፤3ዮሐ11
3፥7 1ዮሐ21፡6፡29
3፥8 ቊ10፤ማቴ4፥3 ፤ዮሐ8፥44፤ዕብ2፥14
3፥9 ቊ6፤መዝ119፥3 ፤ዮሐ1፥13፤1ጴጥ1፥23 ፤1ዮሐ5፥18
3፥10 ቊ1፡2፡8፤ዮሐ 1፥12፤1ዮሐ2፥9፤4፥8
3፥11 ዮሐ13፥24፡ 35፤15፥12፤1ዮሐ1፥5፤ 2፥7፤4፥7፡11፡21፤ 2ዮሐ5
3፥12 ዘፍ4፥8፤መዝ 38፥20፤ምሳ29፥10፤ ማቴ5፥37
3፥13 ዮሐ15፥18፡1 9፤17፥14
3፥14 ዮሐ5፥24፤ 1ዮሐ2፥9
3፥15 ማቴ5፥21፡22 ፤ዮሐ8፥44፤ገላ5፥20፡21፤ 1ዮሐ2፥9፤ራእ21፥8
3፥17 ዘዳ15፥7፡8፤
3፥16 ዮሐ10፥11፤15፥13፤ፊል2፥17፤1ተሰ2፥8

[መ]5 ወይም *ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር* ማለት ነው።
[ሠ]20 አንዳንድ ቅጆች፣ *እናንተ ሁሉንም ነገር ታውቃላችሁ ይላሉ።*
[ረ]2 ወይም *በሚታወቅበት ጊዜ*

ስለ ወንድሞቻችን አሳልፈን ልንሰጥ ይገባናል፡፡ [17]ማንም ሀብት እያለው፣ ወንድሙ ሲቸገር አይቶ ባይራራለት፣ የእግዚአብሔር ፍቅር እንዴት በእርሱ ይኖራል? [18]ልጆች ሆይ፤ በተግባርና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት ብቻ አንዋደድ፡፡ [19]እኛ የእውነት ወገን መሆናችንን በዚህ እናውቃለን፤ ልባችንንም በፊቱ እናሳርፋለን፣ [20]ይህም ልባችን በእኛ ላይ በሚፈርድብን ነገር ሁሉ ነው፡፡ እግዚአብሔር ከልባችን ይልቅ ታላቅ ነውና ሁሉን ነገር ያውቃል፡፡

[21]ወዳጆች ሆይ፤ ልባችን የማይፈርድብን ከሆነ በእግዚአብሔር ፊት ድፍረት አለን፤ [22]ትእዛዛቱንም ስለምንጠብቅና በፊቱም ደስ የሚያሰኘውን ስለምናደርግ የምንለምነውን ሁሉ ከእርሱ እንቀበላለን፡፡ [23]ትእዛዙም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ እንድናምንና እርሱ እንዳዘዘንም እርስ በርሳችን እንድንዋደድ ነው፡፡ [24]ትእዛዞቹንም የሚጠብቁ ሁሉ በእርሱ ይኖራሉ፤ እርሱም በእነርሱ ይኖራል፡፡ በእኛ መኖሩን በዚህ ይኸውም እርሱ በሰጠን መንፈስ እናውቃለን፡፡

## መናፍስትን መርምሩ

4 ወዳጆች ሆይ፤ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፤ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር መሆናቸውን መርምሩ፤ ምክንያቱም ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና፡፡ [2]የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የሚቀበል መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሐር ነው፤ [3]ኢየሱስን የማይቀበል መንፈስ ግን ከእግዚአብሔር አይደለም፤ እንደሚመጣ የሰማ ችሁት የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ ይህ ነው፤ አሁንም እንኳ በዓለም አለ፡፡

[4]ልጆች ሆይ፤ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ፤ እነርሱንም አሸንፋችኋቸዋል፤ ምክንያ ቱም በእናንተ ውስጥ ያለው በዓለም ካለው ይበልጣል፡፡ [5]እነርሱ ከዓለም ናቸው፤ ስለ ዚህ የሚናገሩት እንደ ዓለም ነው፤ ዓለ ምም ይሰማቸዋል፡፡ [6]እኛ ከእግዚአብሔር ነን፤ እግዚአብሔርን የሚያውቅ ይሰማናል፤ ከእግዚአ ብሔር ያልሆነ ግን አይሰማንም፤ በዚህም የእውነትን መንፈስና የሐሰትን መንፈስ እናውቃለን፡፡

## የእግዚአብሔር ፍቅርና የሰው ፍቅር

[7]ወዳጆች ሆይ፤ ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለ ሆነ እርስ በርሳችን እንዋደድ፤ የሚወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር የተወለደ ነው፤ እግዚአ ብሔርንም ያውቃል፡፡ [8]የማይወድ ግን እግዚአብሔርን አያውቅም፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና፡፡ [9]እግዚአብሔር ፍቅሩን በመካከላችን የገለጠው እንዲህ ነው፤ እኛ በእርሱ አማካይነት በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ወደ ዓለም ላከ፡፡ [10]ፍቅር ይህ ነው፤ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው ሳይሆን እርሱ እንደ ወደደንና ስለ ኀጢአታችን ማስተስረያ[ሀ] ይሆን ዘንድ ልጁን መላኩ ነው፡፡ [11]ወዳጆች ሆይ እግዚአብሔር እንዲህ ከወደደን፣ እኛም እርስ በእርሳችን መዋደድ ይገባናል፡፡ [12]እግዚአብሔርን ያየ ከቶ ማንም የለም፤ እርስ በርሳችን ብንዋደድ ግን እግዚአብሔር በእኛ ይኖራል፤ ፍቅሩም በእኛ ፍጹም ይሆናል፡፡

[13]መንፈሱን ስለ ሰጠን፣ እኛ በእርሱ እንደምንኖር እርሱም በእኛ እንደሚኖር እናውቃለን፡፡ [14]አብ ልጁን የዓለም አዳኝ ይሆን ዘንድ እንደላከው ዐይተናል፤ እንመሰክራለንም፡፡ [15]ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምኖ በሚመሰክር ሁሉ፣ እግዚአብሔር በእርሱ ይኖራል፤ እርሱም በእግዚአ ብሔር ይኖራል፡፡ [16]ስለዚህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር እናውቃለን፤ በፍቅሩም እና ምናለን፡፡

እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ በፍቅር የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል፤ እግዚአብሐርም በእርሱ ይኖራል፡፡ [17]በዚህም ዓለም እርሱን እንመስላለንና፡፡ በፍርድ ቀን ድፍረት ይኖ ረን ዘንድ፣ ፍቅር በዚህ ዐ ይነት በመካከላ ችን ፍጹም ሆኖአል፤ [18]በፍቅር ፍርሀት የለም፤ ፍጹም ፍቅር ግን ፍርሀትን አው ጥቶ ይጥላል፤ ፍርሀት ከቅጣት ጋር የተያ ያዘ ነውና፡፡ የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም፡፡

[19]እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን፡፡ [20]ማንም፣ "እግዚአብሔርን እወደዋ ለሁ" እያለ ወንድሙን ቢጠላ፣ እርሱ ሐሰ ተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን መውደድ አይችል ምና፡፡ [21]እርሱም "እግዚአብሔርን የሚወድ ሁሉ ወንድሙን መውደድ ይገባዋል" የሚለ ውን ይህን ትእዛዝ ሰጥቶናል፡፡

## በእግዚአብሔር ልጅ ማመን

5 ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዶ አል፤ አባትንም የሚወድ ሁሉ ልጁንም እንደዚሁ ይወዳል፡፡ [2]እግዚአብሔርን ስንወድና ትእዛዛቱን ስንፈጽም የእግዚአብሔርን ልጆች እንደምንወድ በዚህ እናውቃለን፤

[3]እግዚአብሔርን መውደድ ትእዛዛቱን መፈጸም ነውና፡፡ ትእዛዛቱም ከባድ አይደ ሉም፤ [4]ምክንያቱም ከእግዚአብሔር የተወለደ

ያዕ2፥15፡16፤ 1ዮሐ4፥20
3፥18 ሕዝ33፥31፤ ሮሜ12፥9፤1ዮሐ2፥1
3፥21 1ቆሮ10፥14፤ ኤፌ3፥12፤1ዮሐ5፥14
3፥22 ማቴ7፥7፤ ዮሐ8፥29፤14፥15፤ ዕብ13፥21
3፥23 ሉቃ24፥47፤ ዮሐ1፥12፤3፥18፤ 6፥29፤13፥34፤20፥3 1ቆሮ6፥11፤1ዮሐ5፥13
3፥24 1ተሰ4፥8፤1ዮሐ 2፥3፡6፤14፥13፡15
4፥1 ኤር29፥8፤ ማቴ7፥15፤1ቆሮ10፥14 ፤12፥10፤2ተሰ2፥2፤1ዮሐ2፥18
4፥2 ዮሐ1፥14፤1ቆሮ 12፥3፤1ዮሐ2፥23
4፥3 1ዮሐ2፥18፡ 22፤2ዮሐ7
4፥4 2ነገ6፥16፤ዮሐ 12፥31፤16፥33፤ሮሜ 8፥31፤1ዮሐ2፥1
4፥5 ዮሐ15፥19፤ 17፥14፡16
4፥6 ማር13፥5፤ ዮሐ8፥47፤14፥17
4፥7 ዮሐ1፥13፤ 1ዮሐ2፥4፤3፥11
4፥8 ቈ7፡16
4፥9 ዮሐ1፥18፤ 3፥16፡17፤1ዮሐ5፥11
4፥10 ሮሜ3፥25፤ 5፥8፡10
4፥11 ዮሐ3፥16፤ 15፥12፤1ቆሮ10፥14፤1 ዮሐ3፥11
4፥12 ቈ17፤ ዮሐ1፥18፤1ዮሐ2፥5
4፥13 1ዮሐ2፥3፤ 3፥24
4፥14 ሉቃ2፥11፤ ዮሐ3፥17፤15፥27
4፥15 1ዮሐ2፥23፤ 3፥24፤5፥5
4፥16 ቈ8፡12፡1 3፤1ዮሐ3፥24
4፥17 ቈ12፤ ማቴ10፥15፤ኤፌ3፥12 ፤1ዮሐ2፥5
4፥18 ሮሜ8፥15
4፥19 ቈ10
4፥20 ቈ12፤ ዮሐ1፥18፤1ዮሐ1፥6፤2 ፥4፡9፤3፥17
4፥21 ማቴ5፥43፤ 1ዮሐ2፥7፡9
5፥1 ዮሐ1፥13፤ 3፥15፤8፥42፤1ዮሐ 2፥22፡23፤4፥2፥15
5፥2 1ዮሐ2፥3፤ 3፥14
5፥3 ማቴ11፥30፤ 23፥4፤ዮሐ14፥15
5፥4 ዮሐ1፥13፤ 16፥33

[ሀ] 10 ወይም *ኀጢአታችንን አስወግዶ፣ ቍጣውን ያርቅልን ዘንድ*

ሁሉ ዓለምን ያሸንፋል። ዓለምን የሚያሸ
ንፈውም እምነታችን ነው። 5ኢየሱስ የእግዚ
አብሔር ልጅ እንደ ሆነ ከሚያምን በስተ
ቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማነው?
6በውሃና በደም የመጣው ይህ፣ ኢየ
ሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ በውሃና በደም
እንጂ በውሃ ብቻ አልመጣም። የሚመሰክ
ረውም መንፈስ ነው፤ መንፈስ እውነት
ነውና። 7ስለዚህ ሦስት ምስክሮች አሉት።
8እነርሱም[ሸ] መንፈሱ፣ ውሃውና ደሙ ናቸው፤
ሦስቱም ይስማማሉ። 9የሰውን ምስክርነት
ከተቀበልን፣ የእግዚአብሔር ምስክርነት ከዚያም
ይልቃል፤ ይህ ስለ ልጁ የሰጠው የእግዚአብሐ
ር ምስክርነት ነውና። 10በእግዚአብሔር ልጅ
የሚ ያምን ሁሉ በልቡ ምስክር አለው፤
ማንም እግዚአብሔርን የማያምን ሁሉ እግዚ
አብሔር ስለ ልጁ የሰጠውን ምስክርነት
ስላላመነ ሐሰ ተኛ አድርጎታል።
11ምስክርነቱም ይህ ነው፤ እግዚአብሔር
የዘላለምን ሕይወት ሰጠን፤ ይህም
ሕይወት ያለው በልጁ ነው። 12ልጁ ያለው
ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌ
ለው ሕይወት የለውም።

## ማጠቃለያ ሐሳብ

13በእግዚአብሔር ልጅ ስም የምታምኑ እና
ንተ፣ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ
ዘንድ ይህን እጽፍላችኋለሁ፤ 14በእግዚአብሔር
ፊት ለመቅረብ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤
ማንኛውንም ነገር እንደ ፈቃዱ ብንለምን
እርሱ ይሰማናል፤ 15የምንለምነውን ሁሉ
እንደሚሰማን ካወቅን፣ የለመነውንም ነገር
እንደ ተቀበልን እናውቃለን።
16ማንም ሰው ወንድሙ ለሞት የማያ
በቃ ኀጢአት ሲያደርግ ቢያየው ይጸልይ፤
እግዚአብሔርም ለሞት የማያበቃ ኀጢአት ላደ
ረጉት ሕይወትን ይሰጣል። ለሞት የሚያ
በቃም ኀጢአት አለ፤ ስለዚህኛው ግን ይጸ
ልይ አልልም። 17ዐመፅ ሁሉ ኀጢአት ነው፤
ለሞት የማያበቃም ኀጢአት አለ።
18ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኀጢአት
እንደማያደ ርግ ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጅ
እንደሚጠብቀው፣ ክፉውም እንደማይነካው
እናውቃ ለን። 19እኛ ከእግዚአብሔር
እንደሆንን፣ መላው ዓለምም በክፉው ሥር
እንደ ሆነ እናው ቃለን።
20የእግዚአብሔር ልጅ እንደ መጣ፣
እውነተኛ የሆነውን እርሱን እንድናውቅ
ማስተዋልን እንደ ሰጠን እናውቃለን፤
እኛም እውነ ተኛ በሆነው በልጁ በኢ
የሱስ ክርስቶስ አለን። እርሱ እውነተኛ
አምላክና የዘላ ለም ሕይወት ነው።
21ልጆች ሆይ፤ ራሳችሁን ከጣዖቶች ጠብቁ።

5፥5 ቆ1፤ 1ዮሐ2፥23
5፥6 ዮሐ14፥17፤ 19፥34
5፥7 ማቴ18፥16
5፥9 ማቴ3፥16፡17፤ ዮሐ5፥32፡34፡37፤8፥17፡18
5፥10 ዮሐ3፥33፤ ሮሜ8፥16፤ ገላ3፥6፤1ዮሐ1፥10
5፥11 ማቴ25፥46፤ ዮሐ1፥4
5፥12 ዮሐ3፥15፡ 16፡36
5፥13 ቆ11፤ ማቴ25፥46፤ 1ዮሐ3፥23
5፥14 ማቴ7፥7፤ ኤፌ3፥12፤ 1ዮሐ3፥21
5፥15ቆ18፡19፡20፤ 1ነገ3፥12
5፥16 ዘፀ23፥21፤ ኤር7፥16፤ 14፥11፤ዕብ6፥4-6፤ 10፥26፤ያዕ5፥15
5፥17 ቆ16፤ ዮሐ2፥1፤3፥4
5፥18 ማቴ5፥37፤ ዮሐ1፥13፤14፥30
5፥19 ዮሐ12፥31፤ 14፥30፤17፥15፤ 1ዮሐ4፥6
5፥20 ቆ5፡11፤ ማቴ25፥46፤ሉቃ24፥45፤ዮሐ17፥3
5፥21 1ቆሮ10፥14፤ 1ተሰ1፥9፤1ዮሐ2፥1

[ሸ]7፡8 ጥንታዊ ባለሆነ በቡልጌት ቅጅ ላይ *በሰማይ የሚመሰክሩት ሦስቱ ናቸው፤ እነርሱም አባት፤ ቃልና መንፈ ስ ቅዱስ ናቸው* ይላል።
8. በምድር የሚመሰክሩት ሦስቱ ናቸው (ሆኖም ይህ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በፊት በነበሩት የግሪክ ቅጆች ውስጥ አይገኝም።

# የሐዋርያው ዮሐንስ መልእክት — ሁለተኛ

1ሽማግሌው፤

በእውነት ለምወዳት እኔ ብቻ ሳልሆን
እውነትን የሚያውቁ ሁሉ ለሚወዷት ለተ
መረጠችው እመቤትና ለልጆቿ፤ 2በውስጣ
ችን ከሚኖርና ከእኛ ጋር ለዘላለም ከሚሆን
እውነት የተነሣ፣ 3ከእግዚአብሔር አብና የአብ
ልጅ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ ምሕረ
ትና ሰላም በእውነትና በፍቅር ከእኛ ጋር
ይሆናል፡፡

4ከልጆችሽ አንዳንዶቹ ከአብ በተሰጠን
ትእዛዝ መሠረት በእውነት ጸንተው እየሄዱ
በማግኘቴ እጅግ ደስ ብሎኛል፡፡ 5አሁንም
እመቤት ሆይ፤ ከመጀመሪያ የነበረችውን
እንጂ አዲስ ትእዛዝ አልጽፍልሽም፤ ይኸ
ውም እርስ በርሳችን እንዋደድ ዘንድ ነው፡፡
6ይህም ፍቅር፤ በትእዛዙ መሠረት እንመላለስ
ዘንድ ነው፡፡ ትእዛዙም ከመጀመሪያ እንደ
ሰማችሁት በፍቅር እንድትኖሩ ነው፡፡

7ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የማ
ያምኑ ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም ወጥተዋል፡፡
እንዲህ ያለ ማንኛውም ሰው አታላይና የክር
ስቶስ ተቃዋሚ ነው፡፡ 8እናንተም የደከ
ማችሁበትን ዋጋ እንዳታጡ፣ ነገር ግን ሙሉ
ሽልማት እንድትቀበሉ ለራሳችሁ ተጠንቀቀ
፡፡ 9በክርስቶስ ትምህርት የማይኖርና
ከትምህ ርቱ የሚወጣ ሁሉ አምላክ
የለውም፤ በክ ርስቶስ ትምህርት የሚኖር
ግን አብም ወልድም አለው፡፡ 10ማንም
ወደ እና ንተ ቢመጣ፣ ይህንንም
ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት፤
ሰላምም አትበሉት፤ 11የሚቀበለው ሰው፣
የክፉ ሥራው ተባባሪ ይሆናልና፡፡

12የምጽፍላችሁ ብዙ ነገር ነበረኝ፤
ይሁን እንጂ በወረቀትና በቀለም እንዲ
ሆን አልፈልግም፤ ዳሩ ግን ደስታችን ፍጹም
ይሆን ዘንድ ወደ እናንተ መጥቼ ፊት ለፊት
ላነጋግራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

13የተመረጠችው የእኅትሽ ልጆች ሰላ
ምታ ያቀርቡልሻል፡፡

1፥1 ቆ3፡13፤ ዮሐ 8፥32፤ሐሥ11፥30፤ ሮሜ16፥13፤1ጢሞ 2፥4፤1ጴጥ5፥13፤ 3ዮሐ1
1፥2 ዮሐ14፥17፤ 2ጴጥ1፥12፤1ዮሐ1፥8
1፥3 ሮሜ1፥7
1፥4 ዮሐ3፥4
1፥5 1ዮሐ2፥7
1፥6 ዮሐ14፥15፤ 1ዮሐ2፥5፡7
1፥7 ዮሐ1፥14፤ 1ዮሐ2፥18፡22፤ 4፥1፡2፡3
1፥8 ማቴ10፥42፤ማር 10፥29፡30፤1ቆሮ3፥8፤ ዕብ10፥35፡36፤ 11፥26
1፥9 ዮሐ8፥31፤ 1ዮሐ2፥23
1፥10 ሮሜ16፥17
1፥11 1ጢሞ5፥22
1፥12 ዮሐ3፥29፤ 3ዮሐ13፡14
1፥13 ቆ1

# የሐዋርያው ዮሐንስ መልእክት – ሦስተኛ

1ሽማግሌው፤

በእውነት ለምወደው ለውድ ወዳጄ፣ ለጋይዮስ፤

2ወዳጅ ሆይ፤ ነፍስህ በመልካም ሁኔታ
ላይ እንዳለች ሁሉ መልካም ጤንነት እን
ዲኖርህና በነገር ሁሉ እንዲሳካልህ እጸል
ያለሁ። 3ለእውነት ታማኝ እንደ ሆንህና
የምትመላለሰውም በእውነት እንደ ሆነ አን
ዳንድ ወንድሞች መጥተው ስለ አንተ ሲመ
ሰክሩልኝ እጅግ ደስ አለኝ። 4ልጆቼ በእ
ውነት የሚመላለሱ መሆናቸውን ከመስ
ማት የሚበልጥ ደስታ የለኝም።

5ወዳጅ ሆይ፤ ለአንተ እንግዶች ቢሆ
ኑም እንኳ ለወንድሞች በምታደርገው
ነገር ሁሉ ታማኝ ነህ። 6እነርሱ አንተ
ስላለህ ፍቅር በቤተ ክርስቲያን ፊት መስክረ
ዋል፤ በመንገዳቸውም እግዚአብሔርን ደስ በሚ
ያሰኝ ሁኔታ ብትረዳቸው መልካም ታደር
ጋለህ፤ 7ስለ ስሙ የወጡት ከአሕዛብ ምንም
ሳይቀበሉ ነውና። 8እንግዲህ አብረን ለእው
ነት እንድንሠራ እንዲህ ያሉትን ሰዎች
ልናስተናግድ ይገባናል።

1፥1 ሐሥ11፥30፤ 2ዮሐ1
1፥3 ቀኍ5፡10፤ ሐሥ1፥16፤2ዮሐ4
1፥4 ቀኍ3፤1ዮሐ2፥1
1፥5 ቀኍ3፤ ሮሜ12፥13፤ዕብ13፥2
1፥6 1ቆሮ16፥11፤ 2ቆሮ1፥16፤ኤፌ4፥1
1፥7 ዮሐ15፥21፤ ሐሥ20፥33፡35
1፥10 ቀኍ5፡14፤ ዮሐ9፥22፡34፤ 2ዮሐ12
1፥11 መዝ34፥14፤ 37፥27፤1ዮሐ2፥29፤ 3፥6፡9፡10
1፥12 ዮሐ19፥35፤ 21፥24፤1ጢሞ3፥7
1፥14 ዮሐ10፥3፤ ሮሜ1፥7፤ኤፌ6፥23፤ 2ዮሐ12

9ለቤተ ክርስቲያኒቱ ጽፌ ነበር፤ ነገር
ግን መሪ መሆን የሚወደው ዲዮጥራጢስ
አይቀበለንም። 10ስለዚህ እኔ ከመጣሁ
እርሱ በክፉ ቃላት ስማችንን ለማጥፋት
የሚያደርገውን ሁሉ ይፋ አወጣለሁ፤ ይህም
አልበቃ ብሎት ወንድሞችን አይቀበልም፤
ሊቀበሏቸው የሚፈልጉትን ይከለክላቸዋል፤
ከቤተ ክርስቲያንም ያስወጣቸዋል።

11ወዳጅ ሆይ፤ መልካም የሆነውን እንጂ
ክፉውን አትምሰል። መልካም የሆነውን
የሚያደርግ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው።
ክፉ የሚያደርግ ግን እግዚአብሔርን
አላየውም። 12ለድሜጥሮስ፣ ሰው ሁሉ
ይመሰክርለታል፤ እውነት ራሷም
ትመሰክርለታለች፤ እኛ ደግሞ
እንመሰክርለታለን፤ እናንተም ምስክርነታ
ችን እውነት እንደ ሆነ ታውቃላችሁ። 13የም
ጽፍልህ ብዙ ነገር ነበረኝ፤ ይሁን እንጂ
በቀለምና በብርዕ እንዲሆን አልፈልግም፤
14በቅርቡ ላይህ ተስፋ አደርጋለሁ፤ ፊት
ለፊትም እንነጋገራለን። 15ሰላም ለአንተ
ይሁን፤ ወዳጆች ሰላምታ ያቀርቡልሃል።
ለወዳጆች በየስማቸው ሰላምታ አቅርብልኝ።

# የያዕቆብ ወንድም የይሁዳ መልእክት

1 የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይና የያዕ
ቆብ ወንድም ይሁዳ፤
ለተጠሩት፣ በእግዚአብሔር አብ ለተወ
ደዱትና በኢየሱስ ክርስቶስ ለተጠበቁት[ሀ]፤
2ምሕረት፣ ሰላምና ፍቅር ይብዛላችሁ።

## የዐመፀኞች ኀጢአትና የሚጠብቃቸው ፍርድ

3ወዳጆች ሆይ፤ አብረን ስለምንካፈለው
ድነት ልጽፍላችሁ እጅግ ጓጉቼ ነበር፤
ነገር ግን ለቅዱሳን አንዴና ለመጨረሻ ስለ
ተሰጠው እምነት እንድትጋደሉ ለመምከር
እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ። 4ከረጅም
ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ[ለ] የተጻፉ አንዳንድ
ሰዎች ሾልከው ወደ እናንተ ገብተዋልና፤
እነርሱ ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌላቸው፣ የአም
ላካችንን ጸጋ በርኵሰት የሚለውጡና እርሱ
ብቻ ልዑል ገዥችንና ጌታችን የሆነውን
ኢየሱስ ክርስቶስን የሚክዱ ናቸው።
5ምንም እንኳ አስቀድማችሁ ይህን ሁሉ
የምታውቁ ቢሆንም፣ ጌታ[ሐ] ሕዝቡን ከግ
ብፅ ምድር እንዴት እንዳወጣ፣ በኋላ ግን
ያላመኑትን እንዳጠፋ ላስታውሳችሁ እወዳ
ለሁ። 6የሥልጣን ስፍራቸውን ያልጠበቁ
ትን ነገር ግን መኖሪያቸውን የተዉትን
መላእክት በዘላለም እስራት እስከ ታላቁ
ቀን ፍርድ ድረስ በጨለማ ጠብቆአቸ
ዋል። 7እንዲሁም ሰዶምና ገሞራ፣ በዙሪያ
ቸውም ያሉ ከተሞች ለሴሰኛነትና ከተፈጥሮ
ሥርዐት ውጭ ለሆነ ሩካቤ ሥጋ ራሳቸውን
አሳልፈው ሰጡ፤ እነርሱም በዘላለም እሳት
በመቀጣት ለሚሠቃዩት ምሳሌ ሆነዋል።
8በዚህ ሁኔታ እነዚህ ሕልም አላሚዎች
የገዛ ሥጋቸውን ያረክሳሉ፤ ሥልጣንን ይቃ
ወማሉ፤ በሰማይ ክብር ያላቸውንም ፍጥረታት
ይሳደባሉ። 9የመላእክት አለቃ የሆነው ሚካ
ኤል እንኳ ስለ ሙሴ ሥጋ ከዲያብሎስ ጋር
በተከራከረ ጊዜ፣ "ጌታ ይገሥጽህ" አለው
እንጂ የስድብ ቃል በመናገር ሊከሰው
አልደፈረም። 10እነዚህ ሰዎች ግን የማያወቁትን
ነገር ሁሉ ይሳደባሉ፤ አእምሮ እንደሌላቸው
እንስሳት በደመ ነፍስ በሚያወቁት ነገር
ይጠፋሉ።
11ወዮላቸው! በቃየን መንገድ ሄደዋል፤
ለገንዘብ ሲስገበገቡ በበለዓም ስሕተት
ውስጥ
ወድቀዋል፤ በቆሬም ዐመፅ ጠፍተዋል።
12እነዚህ ሰዎች በፍቅር ግብዣችሁ ላይ
ያለ አንዳች ኀፍረት ከእናንተ ጋር ቀርበው
የሚበሉ ነውረኞች ናቸው፤ ደግሞም ራሳ
ቸውን ብቻ የሚመግቡ እረኞች ናቸው፤
እነርሱም በነፋስ የሚነዱ ዝናብ የሌላቸው
ደመናዎች ናቸው፤ በመከር ወራት ፍሬ የ
ማይገኙ ከሥራቸው ተነቅለው
ሁለት ጊዜ የሞቱ ዛፎች ናቸው። 13የነውራ
ቸውን አረፋ የሚደፍቁ የተቈጡ የባሕር ማዕ
በል፣ ድቅ ድቅ ጨለማ ለዘላለም የሚጠ
ብቃቸው ተንከራታች ከዋክብት ናቸው።
14ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነው ሄኖክ
ስለ እነዚህ ሰዎች እንዲህ ሲል ተንብዮአል፤
"እነሆ፤ ጌታ ከእልፍ አእላፋት ቅዱሳኑ ጋር
ይመጣል፤ 15ይህም፣ በሰው ሁሉ ላይ ለመ
ፍረድ እንዲሁም ዐመፀኞችን ሁሉ በክ
ፋት መንገድ በሠሩት የዐመፅ ሥራና
በክፋት በእርሱ ላይ ስለ ተናገሩት የስድብ
ቃል ሁሉ አጥፊነታቸውን ይፋ ለማድረግ
ነው"። 16እነዚህ ሰዎች የሚያጕረመርሙና
ሌሎችን ሰዎች የሚከሱ ናቸው፤ ርኩስ
ምኞታቸውን ይከተላሉ፤ በራሳቸው ይታበ
ያሉ፤ ጥቅም ለማግኘት ሲሉ ሌሎችን ይክ
ባሉ።

## ጸንቶ ስለ መቆም የቀረበ ጥሪ

17ነገር ግን ወዳጆች ሆይ፤ የጌታችን
የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት አስቀድመው
የተናገሩትን አስታውሱ። 18እነርሱም፣ "በመ
ጨረሻው ዘመን ርኩስ ምኞታቸውን የሚከ
ተሉ ዘባቾች ይመጣሉ" ብለዋችኋል። 19እነ
ዚህ ሰዎች በመካከላችሁ መለያየትን የሚፈ
ጥሩ፣ በደመ ነፍስ የሚነዱ መንፈስ የሌላ
ቸው ናቸው።
20እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ፤ እጅግ ቅዱስ
በሆነው እምነታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ
ትጉ፤ በመንፈስ ቅዱስም ጸልዩ። 21ወደ ዘላ
ለም ሕይወት የሚያደርሳችሁን የጌታችንን
የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ
ሳለ፣ በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን
ጠብቁ።
22ተጠራጣሪ ለሆኑት ራሩላቸው፤ 23አን
ዳንዶችን ከእሳት ነጥቃችሁ አድኗ
ቸው፤ ለሌሎች ደግሞ በርኩስ ሥጋ የተ
በከለውን ልብሳቸውን እንኳ እየጠላችሁ
በፍርሀት ምሕረት አሳዩአቸው።

## ቃለ ውዳሴ

24እንዳትወድቁ ሊጠብቃችሁና ያለ
ነቀፋና በደስታ በክብሩ ፊት ሊ
ያቀርባችሁ

[ሀ]1 ወይም *የተጠበቁት* ሊሆን ይችላል
[ለ]4 ወይም *ፍርድ የተወሰነባቸውን ሰዎች*
[ሐ]5 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *ኢየሱስ* ይላሉ

1፥1 ማቴ13፥55፤ ዮሐ14፥22፤17፥12፤ ሐሥ1፥13፤ሮሜ1፥1፤6፥7
1፥2 ሮሜ1፥7፤ ገላ 6፥16፤1ጢሞ1፥2
1፥3 ቆላ20፤ ሐሥ 6፥7፤9፥13፤ 1ቆሮ 10፥14፤ 1ጢሞ6፥12፤ቲቶ1፥4
1፥4 ገላ2፥4፤ ቲቶ1፥16፤2ጴጥ2፥1፤ 1ዮሐ2፥22
1፥5 ዘኍ14፥29፤ ዘጸ 1፥32፤2፥15፤ መዝ 106፥26፤ 1ቆሮ10፥1-5፤ዕብ3፥16፥17፤2ጴጥ1፥12፥13፤3፥1፥2፤ 1ዮሐ2፥20
1፥6 2ጴጥ2፥4፥9
1፥7 ዘጸ29፥23፤ ማቴ10፥15፤25፥41፤ 2ጴጥ3፥7
1፥8 2ጴጥ2፥10
1፥9 ዘጸ34፥6፤ ዳን10፥13፥21፤12፥1፤ ዘካ3፥2፤1ተሰ4፥16፤ ራእ12፥7
1፥10 2ጴጥ2፥12
1፥11 ዘፍ4፥3-8፤ ዘኍ16፥1-3፥31-35፤ ዕብ11፥4፤2ጴጥ2፥15፤ 1ዮሐ3፥12
1፥12 ምሳ25፥14፤ ሕዝ34፥2፥8፥10፤ ማቴ15፥13፤ 1ቆሮ11፥20-22፤ ኤፌ4፥14፤ 2ጴጥ2፥13፥17
1፥13 ኢሳ57፥20፤ ፊል3፥19፤2ጴጥ2፥17
1፥14 ዘፍ5፥18፥21-24፤ዘዳ33፥2፤ ዳን7፥10፤ ዘካ14፥5፤ ማቴ16፥27፤ዕብ12፥22
1፥15 1ጢሞ1፥9፤ 2ጴጥ2፥6-9
1፥16 ቆላ18፤1ቆሮ 10፥10፤2ጴጥ2፥10፥18
1፥17 ኤፌ4፥11፤ ዕብ2፥3፤2ጴጥ3፥2
1፥18 ቆላ16፤ 1ጢሞ 4፥1፤ 2ጢሞ3፥1፤ 2ጴጥ2፥1፤3፥3
1፥19 1ቆሮ2፥14፥15
1፥20 ቆላ3፤ኤፌ6፥18፤ ቈላ2፥7፤1ተሰ5፥11
1፥21 ማቴ25፥46፤ ቲቶ2፥13፤ዕብ9፥28፤ 2ጴጥ3፥12
1፥23 አሞ4፥11፤ ዘካ 3፥2-፤1ቆሮ3፥15፤ ራእ3፥4
1፥24 ሮሜ16፥25፤ 2ቆሮ4፥14፤ቈላ1፥22

| | | |
|---|---|---|
| ለሚችለው፣ [25]እርሱ ብቻ አዳኛችን ለሆነው አምላክ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል | 1፥25 ዮሐ5፥44፤ ሮሜ11፥36፤ 1ጢሞ 1፥17፤ ዕብ13፥8 | ከዘመናት ሁሉ በፊት፣ አሁንና እስከ ዘላለምም ድረስ ክብር፣ ግርማ፣ ኀይልና ሥልጣን ይሁን፤ አሜን፡፡ |

# የዮሐንስ ራእይ

1 ቶሎ መሆን የሚገባውን ነገር ለአገ
ልጋዮቹ እንዲያሳይ፣ እግዚአብሔር
ለእርሱ የሰጠው የኢየሱስ ክርስቶስ ራእይ
ይህ ነው፤ ኢየሱስም መልአኩን ልኮ ለአ
ገልጋዩ ለዮሐንስ ገለጠለት፤ 2እርሱም
ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ኢየሱስ ክርስ
ቶስ ምስክርነት ያየውን ሁሉ መሰከረ።
3ዘመኑ ቀርቦአል፤ እንግዲህ ይህን የትን
ቢት ቃል የሚያነብ ብፁዕ ነው፤ የሚ
ሰሙትና የተጻፈውንም የሚጠብቁ ብፁዓን
ናቸው።

## ሰላምታና ውዳሴ

4ከዮሐንስ፤
በእስያ አውራጃ ለሚገኙ ለሰባቱ አብ
ያተ ክርስቲያናት፤
ካለው፣ ከነበረውና ከሚመጣው፣ በዙፋ
ኑም ፊት ካሉት ከሰባቱ መናፍስት፣[ሀ]
5እንዲሁም ታማኝ ምስክር፣ ከሙታን
በኵርና የምድር ነገሥታት ገዥ ከሆነው ከኢ
የሱስ ክርስቶስም ጸጋና ሰላም ለእናንተ
ይሁን።
ለወደደንና ከኀጢአታችንም በደሙ
ነጻ ላወጣን፣ 6አምላኩንና አባቱን
እንድናገለ ግልም መንግሥትና ካህናት
ላደረገን፣ ለእ ርሱ ክብርና ኀይል ከዘላለም
እስከ ዘላለም ይሁን! አሜን።

7እነሆ፤ በደመና ይመጣል፤
የወጉት እንኳ ሳይቀሩ፣
ዐይን ሁሉ ያየዋል፤
የምድርም ሕዝቦች ሁሉ ከእርሱ
የተነሣ ዋይ ዋይ ይላሉ።
አዎ! ይህ ሁሉ ይሆናል፤ አሜን።

8"ያለውና የነበረው፣ የሚመጣውም፣
ሁሉን ቻይ ጌታ አምላክ፣ አልፋና ዖሜጋ
እኔ ነኝ" ይላል።

## የሰውን ልጅ የሚመስለው

9እኔ ወንድማችሁ ዮሐንስ፣ ከእናንተ
ጋር አብሬ በኢየሱስ መከራውንና
መንግሥ ቱን፣ ትዕግሥቱንም ተካፋይ
የሆንሁ፣ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ኢ
የሱስ ምስክርነት ፍጥሞ በምትባል ደሴት
ነበርሁ። 10በጌታ ቀን በመንፈስ ነበርሁ፤
የመለከትን ድምፅ የሚመስል ታላቅ
ድምፅ ከበስተ ኋላዬ ሰማሁ፤ 11ድምፀ
-ም፣ "የምታየውን በጥቅልል መጽሐፍ
ጽፈሕ በኤፌሶን፣ በሰምርኔስ፣
በጴርጋሞን፣ በትያጥሮን፣ በሰርዴስ፣ በፊላ

1÷1 ቍ4፡9፡19፤ ዳን2÷28፡29፤ ዮሐ12÷49፤17÷8፤ ራእ22÷6፡8፡16
1÷2 ቍ9፤1ቆሮ1÷6፤ ዕብ4÷12፤ራእ6÷9፤ 12÷17፤19÷10
1÷3 ሉቃ11÷28፤ ሮሜ13÷11፤ራእ22÷7
1÷4 ቍ8፡11፡20፤ ኢሳ11÷2፤ሮሜ1÷7፤ራእ3÷1፤4÷5፡8፤ 5÷6፤11÷17
1÷5 መዝ89÷27፤ ኢሳ55÷4፤ዮሐ18÷37፤ ሮሜ3÷25፤8÷37፤ ቈላ1÷18፤ 1ጢሞ6÷15፤ራእ3÷14
1÷6 ሮሜ11÷36፤ 15÷6፤1ጴጥ2÷5፤ ራእ5÷10፤20÷6
1÷7 ዳን7÷13፤ዘካ 12÷10፤ማቴ16÷27፤ 24÷30፤26÷64፤ዮሐ 19÷34፡37፤ሉቃ17÷ 30፤1ቆሮ1÷7፤1ተሰ 2÷19፤ 4÷16፡17
1÷8 ቍ4፡17፤ራእ4÷8፤ 15÷3፤19÷6፤21÷6፤ 22÷13
1÷9 ቍ1፡2፡6፤ ሐሥ14÷22፤ 2ቆሮ1÷7፤ፊል4÷14፤2ጢሞ2÷12፤ዕብ4÷12
1÷10 ዘፀ20÷18፤ ሐሥ20÷7፤ራእ4÷1፡2፤17÷3፤21÷10
1÷11 ቍ4፡19፡20፤ሐሥ 16÷14፤18÷19፤ቈላ 2÷1፤ራእ2÷8፡2፡18፡24፤ 3÷1፡7
1÷12 ቍ20፤ዘፀ25÷ 31-40፤ዘካ4÷2፤ራእ2÷1
1÷13 ኢሳ6÷1፤ሕዝ 1÷26፤ዳን7÷13፤ 10÷5፡16፤ራእ2÷1፤ 14÷14፤15÷6
1÷14 ዳን7÷9፤10÷6፤ ራእ2÷18፤19÷12
1÷15 ሕዝ1÷7፤43÷2፤ ዳን10÷6፤ራእ2÷18፤ 14÷2፤19÷6
1÷16 ቍ20፤ መሳ5÷31፤ኢሳ1÷20፤ 49÷2፤ማቴ17÷2፤ ዕብ4÷12፤ራእ2÷1፡ 12፡16፤3÷1፤19÷15፡21
1÷17 ኢሳ41÷4፤44÷6፤ 48÷12፤ሕዝ1÷28፤ ዳን8÷17፡18፤ ማቴ14÷27፤ራእ2÷8፤ 22÷13
1÷18 ዘዳ32÷40፤ ዳን4÷34፤12÷7፤ ሮሜ 6÷9፤ራእ2÷8፤ 4÷9፡10፤9÷1፤10÷6፤1

ድልፍያና በሎዶቅያ ወደሚገኙት ወደ
ሰባቱ የእስያ አብያተ ክርስቲያናት ላክ"
አለ።
12እኔም የሚናገረኝን ድምፅ ለማየት
ዞር አልሁ፤ ዞር ባልሁም ጊዜ ሰባት
የወርቅ መቅረዞችን አየሁ፤ 13በመቅረዞቹም
መካከል "የሰው ልጅ የሚመስል" አየሁ፤
እርሱም እስከ እግሩ የሚደርስ መጐናጸፊያ
የለበሰ፣ ደረቱንም በወርቅ መታጠቂያ
የታጠቀ ነበር። 14ራሱና ጠጕሩም እንደ
ነጭ የበግ
ጠጕር፣ እንደ በረዶም ነጭ ነበሩ፤ ዐይኖ
ቹም የእሳት ነበልባል ይመስሉ ነበር። 15እግ
ሮቹ በእቶን እሳት የጋለ ናስ ይመስሉ ነበር፤
ድምፁም እንደ ብዙ ወራጅ ውሃ ድምፅ
ነበረ። 16በቀኝ እጁ ሰባት ከዋክብት ይዞ
ነበር፤ ከአፉም በሁለት በኩል የተሳለ ሰይፍ
ይወጣ ነበር፤ ፊቱም በሙሉ ድምቀቱ እን
ደሚያበራ ፀሐይ ነበረ።
17ባየሁት ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ
በእግሩ ሥር ወደቅሁ። እርሱም ቀኝ እጁን
በላዬ ጭኖ እንዲህ አለኝ፤ "አትፍራ፤ የመ
ጀመሪያውም የመጨረሻውም እኔ ነኝ፤
18እኔ ሕያው ነኝ፤ ሞቼ ነበር፤ እነሆ አሁን
ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፤
የሞትና የሲኦል መክፈቻም በእጄ ነው።
19"ስለዚህ ያየኸውን፣ አሁን ያለውንና
በኋላም የሚሆነውን ጻፍ። 20በቀኝ እጄ
ያየሃቸው የሰባቱ ከዋክብትና የሰባቱ የወ
ርቅ መቅረዞች ምስጢር ይህ ነው፤ ሰባቱ
ከዋክብት የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት
መላእክት[ለ] ናቸው፤ ሰባቱ መቅረዞች ደግሞ
ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው።

## በኤፌሶን ላለው ቤተ ክርስቲያን

2 "በኤፌሶን ላለው ቤተ ክርስቲያን መል
አክ[ሐ] እንዲህ ብለህ ጻፍ፤
ሰባቱን ከዋክብት በቀኝ እጁ የያ
ዘው፣ በሰባቱም የወርቅ መቅረዞች መካ
ከል የሚመላለሰው እንዲህ ይላል፤ 2ሥራ
ህን፣ ጥረትህንና ትዕግሥትህን ዐውቃ
ለሁ። ክፉዎችንም ችላ ብለህ እንዳላለ
ፍሃቸው፣ ሐዋርያት ሳይሆኑ ሐዋርያት
ነን የሚሉትንም መርምረህ ሐሰተኞች

5÷7፤20÷1 1÷19 ቍ11፤ዕን2÷2 1÷20 ቍ4፡11፡12፡16፤ማቴ 5÷14፡15 2÷1 ሐሥ18÷19፤ራእ1÷12፡13፡16 2÷2 ቍ19፤ 2ቆሮ11÷13፤1ዮሐ4÷1፤ ራእ3÷1፡8፡15

[ሀ]4 ወይም ሰባት ዕጥፍ መንፈስ
[ለ]20 ወይም መልእክተኞች
[ሐ]1 ወይም መልእክተኛ፤ እንዲሁም ቍ8፣ 12 እና 18

ሆነው እንዳገኘሃቸው ዐውቃለሁ። 3ደግ
ሞም በትዕግሥት መጽናትህንና ስለ
ስሜም መከራን መቀበልህን ዐውቃለሁ፤
በዚህ ሁሉ አልታከትህም።
4ይሁን እንጂ የምነቅፍብህ ነገር
አለኝ፤ ይኸውም የቀድሞውን ፍቅርህን
ትተሃል። 5እንግዲህ ከየት እንደ ወደ
ቅህ አስብ፤ ንስሓ ገብተህ ቀድሞ ታደ
ርገው የነበረውን ነገር አድርግ፤ ንስሓ
ካልገባህ፣ መቅረዝህን ከቦታው
እወስድብሃለሁ። 6ነገር ግን ይህ በጎ
ነገር አለህ፤ እኔ የምጠላውን የኒቆላ
ውያንን ሥራ አንተም ጠልተሃል።
7መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚ
ናገረውን፣ ጆሮ ያለው ይስማ፤ ድል
ለሚነሣ በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይ
ወት ዛፍ እንዲበላ አደርገዋለሁ።

## በሰምርኔስ ላለው ቤተ ክርስቲያን

8"በሰምርኔስ ላለው ቤተ ክርስቲያን
መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤
የመጀመሪያውና የመጨረሻው፣ ሞቶም
የነበረውና ሕያው የሆነው እንዲህ ይላል፤
9መከራህንና ድኽነትህን ዐውቃለሁ፤
ይሁን እንጂ ሀብታም ነህ፤ አይሁድ
ሳይሆኑ አይሁድ ነን እያሉ ስምህን
የሚያጠፉትን ዐውቃለሁ፤ እነርሱ ግን
የሰይጣን ማኅበር ናቸው። 10ሊደርስብህ
ያለውን መከራ አትፍራ። እነሆ፤ ዲያ
ብሎስ ሊፈትናችሁ አንዳንዶቻችሁን
ወደ እስር ቤት ይጥላል፤ ዐሥር ቀንም
መከራ ትቀበላላችሁ። እስከ ሞት ድረስ
ታማኝ ሁን፤ እኔም የሕይወትን አክሊል
እሰጥሃለሁ።
11መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት
የሚናገረውን ጆሮ ያለው ይስማ፤ ድል
የሚነሣም በሁለተኛው ሞት ከቶ አይጐ
ዳም።

## በጴርጋሞን ላለው ቤተ ክርስቲያን

12"በጴርጋሞን ላለው ቤተ ክርስቲያን
መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤
በሁለት በኩል የተሳለ ስለታም
ሰይፍ ያለው እንዲህ ይላል፤ 13የሰይጣን
ዙፋን ባለበት እንደምትኖር ዐውቃለሁ፤
ሆኖም ስሜን አጥብቀህ ይዘሃል። ሰይ
ጣን በሚኖርበት በእናንተ ከተማ የተገ
ደለው ታማኙ ምስክሬ አንቲጳስ በነበረ
በት ዘመን እንኳ፣ በእኔ ያለህን እም
ነት አልካድህም።
14ይሁን እንጂ የምነቅፍብህ ጥቂት
ነገር አለኝ፤ የእስራኤል ልጆች ለጣዖት
የተሠዋ ምግብ እንዲበሉና እንዲሴስኑ
በፊታቸው መሰናከያ ያስቀምጥ ዘንድ
ባላቅን ያስተማረውን የበለዓምን ትም
ህርት የሚከተሉ አንዳንድ ሰዎች በመ
ካከልህ አሉ፤ 15የኒቆላውያንን ትምህ
ርት የሚከተሉ ሰዎችም በአንተ ዘንድ
አሉ። 16ስለዚህ ንስሓ ግባ፤ አለዚያ
ቶሎ እመጣብሃለሁ፤ በአፌም ሰይፍ
እዋጋቸዋለሁ።
17መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚ
ናገረውን ጆሮ ያለው ይስማ፤ ድል ለሚ
ነሣ ከተሰወረው መና እሰጠዋለሁ፤ ደግ
ሞም ከሚቀበለው ሰው በስተቀር ማንም
የማያውቀውን አዲስ ስም የተጻፈበት
ነጭ ድንጋይ እሰጠዋለሁ።

## በትያጥሮን ላለው ቤተ ክርስቲያን

18"በትያጥሮን ላለው ቤተ ክርስቲያን
መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤
እንደ እሳት ነበልባል የሆኑ ዐ
ይኖችና በእሳት ቀልጦ የነጠረ ናስ
የሚመስሉ እግሮች ያሉት የእግዚአብሔር
ልጅ እንዲህ ይላል፤ 19ሥራህን፣
ፍቅርህን፣ እምነትህን፣
አገልግሎትህንና ትዕግሥትህን
ዐውቃለሁ፤ ደግሞም ከመጀመሪያው ሥራህ
ይልቅ የአሁኑ እንደሚበልጥ ዐውቃ
ለሁ።
20ይሁን እንጂ የምነቅፍብህ ነገር
አለኝ፤ ነቢይ ነኝ የምትለዋን ሴት ኤል
ዛቤልን ችላ ብለሃታል፤ እርሷ አገልጋ
ዮቼ እንዲሴስኑና ለጣዖት የተሠዋ
ምግብ እንዲበሉ በትምህርቷ ታስታቸ
ዋለች። 21ከዝሙቷ ንስሓ እንድትገባ
ጊዜ ሰጥቻት ነበር፤ እርሷ ግን ፈቃደኛ
አልሆነችም። 22ስለዚህ በመከራ ዐልጋ
ላይ እጥላታለሁ፤ ከእርሷም ጋር የሚያ
መነዝሩትን፣ ከመንገዷ ንስሓ ካልገቡ፣
ብርቱ ሥቃይ አመጣባቸዋለሁ፤ 23ልጆቿ
ንም በሞት እቀጣቸዋለሁ፤ ከዚያም አብ
ያተ ክርስቲያናት ሁሉ እኔ ልብንና
ሐሳብን የምመረምር መሆኔን ይረዳሉ፤
ለእያንዳንዳችሁም እንደ ሥራችሁ እከ
ፍላችኋለሁ። 24ትምህርቷን ላልተከተላ
ችሁና የሰይጣንም ጥልቅ ምስጢር ነው
የሚባለውን ላልተቀበላችሁ፣ በትያጥሮን
ለቀራችሁት ለእናንተ ግን ይህን እላ
ለሁ፤ በእናንተ ላይ ተጨማሪ ሸክም
አልጭንባችሁም፤ 25ብቻ እኔ እስክመጣ
ድረስ ያላችሁን አጥብቃችሁ ያዙ።
26ድል ለሚነሣና ሥራዬንም እስከ
መጨረሻው ለሚፈጽም በአሕዛብ ላይ
ሥልጣን እሰጠዋለሁ፤ እርሱም፦
27'በብረት በትር ይገዛቸዋል፤

2፥3 ዮሐ15፥21
2፥4 ኤር2፥2፤ ማቴ24፥12
2፥5 ቁ-16፡22፤ራእ 1፥20፤3፥3፡19
2፥6 ቁ-15
2፥7 ቁ-11፡17፡29፤ ዘፍ2፥9፤3፥22-24፤ ማቴ11፥15፤ሉቃ23፥ 43፤ዮሐ16፥33፤ራእ 3፥6፡13፡22፤13፥9፤ 22፥2፡14፡19
2፥8 ራእ1፥11፡17፡18
2፥9 ቁ-13፡24፤ ማቴ4፥10፤2ቆሮ6፥10፤ ያዕ2፥5፤ራእ3፥9
2፥10 ቁ-13፤ዳን1፥12፡ 14፤ማቴ10፥22፤ 1ቆሮ9፥25፤ ራእ3፥10፤17፥14
2፥11 ቁ-7፤ራእ20፥6፡ 14፤21፥8
2፥12 ቁ-16፤1፥11፡16
2፥13 ቁ-9፡24፤ ማቴ4፥10፤ራእ1፥5፤ 11፥3፤14፥12
2፥14 ቁ-20፤ ሐሥ15፥20፤ 1ቆሮ6፥13፤2ጴጥ2፥15
2፥15 ቁ-6
2፥16 ቁ-5፤2ተሰ2፥8፤ ራእ1፥16
2፥17 ቁ-7፤ኢሳ56፥5፤ 62፥2፤65፥15፤ ዮሐ6፥49፡50፤ 16፥33፤ራእ19፥12
2፥18 ቁ-24፤ማቴ4፥3፤ ሐሥ16፥14፤ ራእ1፥11፡14፡15
2፥19 ቁ-2
2፥20 ቁ-14፤1ነገ16፥31፤ 21፥25፤2ነገ9፥7፤ ሐሥ15፥20
2፥21 ሮሜ2፥4፡5፤ 2ጴጥ3፥9፤ራእ9፥20፤ 16፥9፡11
2፥22 ራእ17፥2፤18፥9
2፥23 1ሳሙ16፥7፤ 1ነገ8፥39፤መዝ139፥1፡ 2፡23፤ምሳ21፥2፤ ኤር17፥10፤ ማቴ16፥27፤ ሉቃ16፥15፤ ሮሜ8፥27፤1ተሰ2፥4
2፥24 ሐሥ15፥28
2፥25 ማቴ16፥27፤ራ እ3፥11
2፥26 መዝ2፥8፤ ማቴ10፥22፤ዮሐ16፥33፤ ራእ3፥21
2፥27 መዝ2፥9፤ ኢሳ30፥14፤ ኤር19፥11፤ራእ12፥5

እንደ ሸክላ ዕቃም ይፈጫቸዋል፤
ይህም ልክ እኔ ከአባቴ ዘንድ
ሥልጣንን እንደ ተቀበልሁ ነው፤

28እኔም የንጋትን ኮከብ እሰጠዋ
ለሁ። 29መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት
የሚናገረውን ጆሮ ያለው ይስማ።

## በሰርዴስ ላለው ቤተ ክርስቲያን

3 “በሰርዴስ ላለው ቤተ ክርስቲያን መል
አክ[ሠ] እንዲህ ብለህ ጻፍ፤

ሰባቱን የእግዚአብሔር መናፍስትና[ሰ]
ሰባቱን ከዋክብት በእጁ የያዘው እንዲህ
ይላል፤ ሥራህን ዐውቃለሁ፤ በስም ሕያው
ነህ፤ ነገር ግን ሞተሃል። 2ስለዚህ ንቃ፤
ሊሞት የተቃረበውን የቀረውን ነገር
አጽና፤ ሥራህ በአምላኬ ፊት ፍጹም
ሆኖ አላገኘሁትም። 3እንግዲህ የተቀበ
ልኸውንና የሰማኸውን አስታውስ፤ ታዘ
ዘውም፤ ንስሓም ግባ። ባትነቃ ግን
እንደ ሌባ እመጣብሃለሁ፤ በየትኛው
ሰዓት እንደምመጣብህም አታውቅም።
4ነገር ግን ልብሳቸውን ያላሳደፉ ጥቂት
ሰዎች በሰርዴስ ከአንተ ጋር አሉ፤ እነ
ርሱም ነጭ ልብስ ለብሰው ከእኔ ጋር
ይሄዳሉ፤ ይህ የሚገባቸው ነውና። 5ድል
የሚነሣም እንደ እነርሱ ነጭ ልብስ
ይለብሳል፤ እኔም በአባቴና በመላእክቱ
ፊት እመሰክርለታለሁ፤ ስሙንም ከሕ
ይወት መጽሐፍ አልደመስስም። 6መን
ፈስ ለአብያተ ክርቲያናት የሚናገረ
ውን ጆሮ ያለው ይስማ።

## በፊላድልፍያ ላለው ቤተ ክርስቲያን

7“በፊላድልፍያ ላለው ቤተ ክርስቲያን
መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤

ቅዱስና እውነተኛ የሆነው፣ የዳዊት
ንም መክፈቻ በእጁ የያዘው እንዲህ
ይላል፤ እርሱ የከፈተውን ማንም ሊዘ
ጋው አይችልም፤ የዘጋውንም ማንም
ሊከፍተው አይችልም። 8ሥራህን ዐው
ቃለሁ፤ እነሆ፤ ማንም ሊዘጋው የማይ
ችል የተከፈተ በር በፊትህ አድርጌአ
ለሁ። ኀይልህ ትንሽ እንደ ሆነ ዐውቃ
ለሁ፤ ሆኖም ቃሌን ጠብቀሃል፤ ስሜ
ንም አልካድህም። 9እነሆ፣ አይሁድ ሳይ
ሆኑ አይሁድ ነን የሚሉት፣ የሚዋ
ሹት፣ ከሰይጣን ማኅበር የሆኑት ወደ
አንተ እንዲመጡ በእግርህ ሥር እንዲ
ሰግዱ፣ እኔ እንደ ወደድሁህም እንዲ
ያውቁ አደርጋለሁ። 10በትዕግሥት እን
ድትጸና የሰጠሁህን ትእዛዜን ስለ ጠበ
ቅህ፣ እኔ ደግሞ በምድር ላይ የሚኖሩ
ትን ሊፈትናቸው በዓለም ሁሉ ላይ

2፥28 ራእ22፥16
2፥29 ቍ7
3፥1 1ጢሞ5፥6፤ ራእ1፥4፡11፡16፤ ራእ2፥2
3፥3 ሉቃ12፥39፤ ራእ2፥5
3፥4 ቍ5፡18፤ይሁ23፤ ራእ4፥4፤6፥11፤7፥9፡ 13፡14፤19፥14
3፥5 ቍ4፤ማቴ10፥32፤ ዮሐ16፥33፤ራእ20፥12
3፥6 ራእ2፥7
3፥7 ኢሳ22፥22፤ ማቴ16፥19፤ማር1፥24፤ 1ዮሐ5፥20፤ራእ1፥11፤ 6፥10፤19፥11
3፥8 ሐሥ14፥27፤ ራእ2፥2፡13
3፥9 ኢሳ43፥4፤49፥23፤ ሮሜ8፥37፤ራእ2፥9
3፥10 ማቴ24፥14፤ 2ጴጥ2፥9፤ራእ2፥10፤ 6፥10፤8፥13፤11፥10፤1 3፥8፡14፤17፥8
3፥11 ማቴ16፥27፤ 1ቆሮ9፥25፤ራእ2፥25
3፥12 ሕዝ48፥35፤ ዮሐ16፥33፤ገላ2፥9፤ 4፥26፤ራእ14፥1፤ 21፥2፡10፤22፥4
3፥13 ራእ2፥7
3፥14 ምሳ8፥22፤ ዮሐ1፥3፤18፥37፤ ቈላ1፥16፡18፤2፥1፤ ራ እ1፥5፡11
3፥15 ሮሜ12፥11፤ራ እ2፥2
3፥17 ምሳ13፥7፤ ሆሴ12፥8፤1ቆሮ4፥8
3፥18 ቍ4፤1ጴጥ1፥7፤ ራእ16፥15
3፥19 ዘዳ8፥5፤ ምሳ3፥12፤ 1ቆሮ11፥32፤ ዕብ12፥5፡ 6፤ራእ2፥5
3፥20 ማቴ24፥33፤ ሉቃ12፥36፤ሮሜ8፥10፤ ያዕ5፥9
3፥21 ማቴ19፥28፤ ዮሐ16፥33፤ራእ5፥5
3፥22 ራእ2፥7
4፥1 ማቴ3፥16፤ ራእ1፥10፡19፤11፥12፤2፥6

ከሚመጣው የፈተና ሰዓት እጠብቅሃ
ለሁ።
11ቶሎ እመጣለሁ፤ ማንም አክሊልህን
እንዳይወስድብህ ያለህን አጥብቀህ ያዝ።
12ድል የሚነሣውን በአምላኬ ቤተ መቅ
ደስ ውስጥ ዐምድ አደርገዋለሁ፤ ከዚ
ያም ከቶ አይወጣም። የአምላኬን ስምና
የአምላኬን ከተማ ስም ይኸውም
ከአምላኬ ዘንድ የምትወርደውን የአዲሲ
ቱን ኢየሩሳሌም ስም በእርሱ ላይ እ
ጽፋለሁ፤ አዲሱን ስሜንም በእርሱ
ላይ እጽፋ ለሁ። 13መንፈስ ለአብያተ
ክርስቲያናት የሚናገረውን ጆሮ ያለው
ይስማ።

## በሎዶቅያ ላለው ቤተ ክርስቲያን

14“በሎዶቅያ ላለው ቤተ ክርስቲያን መል
አክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤

አሜን የሆነው፣ ደግሞም ታማኝ እው
ነተኛ ምስክር የሆነው፣ የእግዚአብሔርም
ፍጥረት ገዥ የሆነው እንዲህ ይላል፤
15ቀዝቃዛ ወይም ትኩስ እንዳልሆንህ ሥራ
ህን ዐውቃለሁ፤ ቀዝቃዛ ወይም ትኩስ
ብትሆን በወደድሁ ነበር። 16እንግዲህ
ለብ ያልህ ብቻ እንጂ ትኩስ ወይም
ቀዝቃዛ ስላልሆንህ ከአፌ አውጥቼ
ልተፋህ ነው። 17‘ሀብታም ነኝ፤ ባለጠጋ
ነኝ እንዳችም አያስፈልገኝም’ ትላለህ፤
ነገር ግን ጐስቋላ፣ ምስኪን፣ ድኻ፣ ዕው
ርና፣ የተራቈትህ መሆንህን አታው
ቅም። 18ስለዚህ ሀብታም እንድትሆን፣
በእሳት የነጠረ ወርቅ እንድትገዛ፣ የዕራ
ቍትነትህ ኀፍረት እንዳይታይ፣ ነጭ
ልብስ እንድ ትለብስና ለማየት እንድ
ትችል ዐይንህን በኵል እንድትኳል እመ
ክርሃለሁ።
19እኔ የምወዳቸውን እገሥጻለሁ፤ እቀ
ጣለሁም። ስለዚህ ትጋ፤ ንስሓም ግባ።
20እነሆ፤ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም
ድምፄን ሰምቶ በሩን ቢከፍትልኝ ወደ
እርሱ ገብቼ ከእርሱ ጋር እበላለሁ፤ እር
ሱም ከእኔ ጋር ይበላል።
21እኔ ድል ነሥቼ ከአባቴ ጋር በእ
ርሱ ዙፋን ላይ እንደ ተቀመጥሁ፣ ድል
የሚነሣውንም ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ
እንዲቀመጥ አደርገዋለሁ። 22መንፈስ
ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረውን ጆሮ
ያለው ይስማ።

## በሰማይ ያለው ዙፋን

4 ከዚህ በኋላ እነሆ በሰማይ የተከፈተ
በር አየሁ፤ ቀድም ሲል እንደ መለ

ሠ1 ወይም መልእክተኛ ሰ1 ወይም ሰባት ዕጥፍ መንፈስ

ከት ሲናገረኝ የሰማሁት ድምፅ፣ “ወደዚህ
ና፤ ከዚህም በኋላ ሊሆን የሚገባውን ነገር
አሳይሃለሁ” አለ 2እኔም ወዲያውኑ በመን
ፈስ ነበርሁ፤ እነሆም፤ በሰማይ ዙፋን ቆሞ
አል፤ በዙፋኑም ላይ ተቀምጦ ያለ ነበረ።
3ተቀምጦም የነበረው የኢያስጲድንና የሰር
ዲኖን ዕንቍ ይመስል ነበር። የመረግድ
ዕንቍ የመሰለ ቀስተ ደመናም ዙፋኑን
ከቦት ነበር። 4በዙፋኑ ዙሪያ ሌሎች ሃያ
አራት ዙፋኖች ነበሩ፤ በእነርሱም ላይ
ነጭ ልብስ የለበሱና በራሳቸውም ላይ
የወርቅ አክሊል የደፉ ሃያ አራት ሽማግ
ሌዎች ተቀምጠው ነበር። 5ከዙፋኑም መብ
ረቅና ድምፅ፣ ነጐድጓድም ወጣ፤ በዙፋኑ
ፊት ሰባት መብራቶች ይበሩ ነበር፤ እነዚ
ህም ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት[ሬ] ናቸው።
6ደግሞም በዙፋኑ ፊት እንደ መስተዋት
የጠራ የብርጭቆ ባሕር ነበረ።

በዙፋኑ መካከል፣ በዙሪያውም ከፊትና
ከኋላ በዐይን የተሞሉ አራት ሕያዋን ፍጡ
ራን ነበሩ። 7የመጀመሪያው ሕያው ፍጡር
አንበሳ፣ ሁለተኛው በሬ ይመስሉ ነበር፤
ሦስተኛው የሰው ፊት የሚመስል ፊት ነበ
ረው፤ አራተኛው ደግሞ የሚበር ንስር
ይመስል ነበር። 8አራቱም ሕያዋን ፍጡራን
እያንዳንዳቸው ስድስት ስድስት ክንፎች
ነበሯቸው፤ በዙሪያቸውና በውስጣቸው በዐ
ይኖች የተሞሉ ነበሩ፤ ቀንና ሌሊትም፦

“ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣
የነበረው፣ ያለውና የሚመጣው፤
ሁሉን ቻይ ጌታ አምላክ”

ማለትን አያቋርጡም። 9ሕያዋን ፍጡ
ራኑ በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠውና ከዘላለም
እስከ ዘላለም ሕያው ሆኖ ለሚኖረው
ክብር፣ ሞገስና ምስጋና በሚሰጡበት ጊዜ፣
10ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በዙፋኑ ላይ
በተቀመጠው ፊት ተደፍተው፣ ከዘላለም
እስከ ዘላለም ሕያው ሆኖ ለሚኖረው ይሰ
ግዱ ነበር፤ አክሊላቸውንም በዙፋኑ ፊት
አስ ቀምጠው እንዲህ ይላሉ፤

11“ጌታችንና አምላካችን ሆይ፤
ክብርና ሞገስ፣ ኀይልም ልትቀበል
ይገባሃል፤
አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና፤
በፈቃድህም ተፈጥረዋልና፤
ሆነዋልምና።”

## ጥቅልል መጽሐፉና በጉ

5 በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው በውስጥና
በውጭ በኩል የተጻፈበት፣ በሰባት
ማኅተም የታሸገ ጥቅልል መጽሐፍ በቀኝ
እጁ ይዞ አየሁ። 2አንድ ብርቱ መልአክ
በታላቅ ድምፅ፣ “ማኅተሞቹን ለመፍታ
ትና መጽሐፉን ለመክፈት የተገባው ማን
ነው?” ብሎ ሲያውጅ አየሁ። 3ነገር ግን
በሰማይም ሆነ በምድር፣ ከምድርም በታች
መጽሐፉን ለመክፈት ወይም ገልጦ ለመ
መልከት የሚችል ማንም አልነበረም። 4እኔም
መጽሐፉን ለመክፈት ወይም ገልጦ ለመ
መልከት የተገባው ማንም ባለመኖሩ እጅግ
አለቀስሁ። 5ከዚያም ከሽማግሌዎቹ አንዱ፣
“አታልቅስ፤ እነሆ፤ ከይሁዳ ነገድ የሆነው
አንበሳ፣ የዳዊት ሥር ድል ነሥቶአል፤
እርሱ መጽሐፉን ሊከፍትና ሰባቱንም ማኅ
ተሞች ሊፈታ ይችላል” አለኝ።

6ከዚያም በዙፋኑና በአራቱ ሕያዋን
ፍጡራን፣ በሽማግሌዎቹም መካከል የታ
ረደ የሚመስል በግ ቆሞ አየሁ፤ በጉም
ሰባት ቀንዶችና ሰባት ዐይኖች ነበሩት፤
እነርሱም ወደ ምድር ሁሉ የተላኩት
ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት[ሰ] ናቸው።
7እርሱም መጥቶ በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠ
ው ቀኝ እጅ መጽሐፉን ወሰደ። 8መጽሐ
ፉን በወሰደ ጊዜ አራቱ ሕያዋን ፍጡራ
ን፣ ሃያ አራቱ ሽማግሌዎችም በበጉ ፊት
በግ ምባራቸው ተደፉ፤ እያንዳንዳቸውም
የቅ ዱሳን ጸሎት የሆኑትን በገናና ዕጣን
የሞ ላበትን የወርቅ ሙዳይ ይዘው ነበር።
9እንዲህም እያሉ አዲስ መዝሙር ዘመሩ፤

“መጽሐፉን ልትወስድ፣
ማኅተሞቹንም ልትፈታ ይገባሃል፤
ምክንያቱም ታርደሃል፤
በደምህም ከነገድ ሁሉ፣ ከቋንቋ ሁሉ፣
ከወገን ሁሉ፣ ከሕዝብ ሁሉ
ሰዎችን ለእግዚአብሔር ዋጅተሃል።
10ለአምላካችንም መንግሥትና ካህናት
አድርገሃቸዋል፤
እነርሱም በምድር ላይ ይነግሣሉ።”

11ከዚያም ተመለከትሁ፤ የብዙ መላእክ
ትን ድምፅ ሰማሁ፤ ቍጥራቸውም ሺህ ጊዜ
ሺህና እልፍ ጊዜ እልፍ ነበረ፤ እነርሱም
በዙፋኑና በሕያዋን ፍጡራኑ፣ በሽማግሌዎ
ቹም ዙሪያ ከበው ነበር፤ 12በታላቅ ድምፅም
እንዲህ ብለው ዘመሩ፤

“የታረደው በግ ኀይልና ባለ ጠግነት፣
ጥበብና ብርታት፣
ክብርና ሞገስ፣ ምስጋናም፣
ሊቀበል ይገባዋል።

13ከዚያም በሰማይና በምድር፣ ከምድር
በታችና በባሕር፣ በእነርሱ ውስጥ ያሉ

ሬ5 ወይም ሰባት ዕጥፍ መንፈስ
ሰ6 ወይም ሰባት ዕጥፍ መንፈስ

4፥2 ቀኑ9፡10፤ 1ነገ22፥19፤ኢሳ6፥1፤ ሕዝ1፥26-28፤ዳን7፥9፤ ራእ1፥10፤ 20፥11
4፥3 ሕዝ1፥28፤ ራእ10፥1፤21፥11፡19፡20
4፥4 ቀኑ10፤ራእ3፥4፡ 5፤5፥6፡8፡14፤11፥16፤ 19፥4
4፥5 ዘፀ19፥16፤ ዘካ4፥2፤ራእ1፥4፤ 8፥5፤11፥19፤16፥18
4፥6 ቀኑ8፡9፤ሕዝ1፥5፡ 18፤10፥12፤ራእ5፥6፤ 6፥1፤7፥11፤14፥3፤ 15፥2፡7፤19፥4
4፥7 ሕዝ1፥10፤ 10፥14
4፥8 ቀኑ6፤ኢሳ6፥2፡ 3፤ሕዝ1፥18፤ራእ1፥4፡ 8፡18፤14፥11
4፥9 ቀኑ2፡4፤መዝ 47፥8፤ራእ1፥18፤5፥1
4፥10 ዘዳ33፥3፤ ራእ1፥18፤5፥1
4፥11 ሐሥ14፥15፤ ራእ1፥6፤5፥12፤10፥6
5፥1 ቀኑ7፡13፤ ኢሳ29፥11፤ሕዝ2፥9፡ 10፤ዳን12፥4፤ ራእ4፥2፡9፤6፥16
5፥2 ራእ10፥1
5፥5 ዘፍ49፥9፤ ኢሳ11፥1፡10፤ ሮሜ15፥12ዕብ7፥14፤ ራእ22፥16
5፥6 ቀኑ8፡9፡12፡ 13፤ዘካ4፥10፤ዮሐ1፥29 ፤ራእ1፥4፤4፥4፡6
5፥7 ቀኑ1
5፥8 መዝ141፥2፤ ራ እ4፥4፡6፤8፥3፡ 4፤14፥2፤15፥2
5፥9 መዝ40፥3፤98፥1፤ 149፥1፤ኢሳ42፥10፤ 1ቆሮ6፥20፤ዕብ9፥12፤ ራእ4፥11፤13፥7፤ 14፥3፡4
5፥10 1ጴጥ2፥5፤ ራእ3፥21፤20፥4
5፥11 ዳን7፥10፤ ዕብ12፥22፤ይሁ14፤ ራእ4፥4፡6
5፥12 ቀኑ9፥13፤ራ እ1፥6፤4፥11
5፥13 ቀኑ1፡3፡6፡7፤ 1ዜና29፥11፤ሚል1፥6፤ 2፥2፤ሮሜ11፥36፤ ፊል2፥10፤ራእ6፥16፤ 7፥10

ፍጡራንም ሁሉ እንዲህ ብለው ሲዘምሩ
ሰማሁ፤

“በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠውና ለበጉ፣
ምስጋናና ሞገስ፣ ክብርና ኀይል፣
ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን፡፡”

14አራቱ ሕያዋን ፍጡራንም፣ “አሜን”
አሉ፤ ሽማግሌዎቹም በግምባራቸው ተደፍ
ተው ሰገዱ፡፡

## ማኅተሞቹ

6 በጉም ከሰባቱ ማኅተሞች የመጀመሪ
ያውን ሲፈታ አየሁ፤ ከዚያም ከአራቱ
ሕያዋን ፍጡራን አንዱ፣ ነጐድጓድ በሚ
መስል ድምፅ “ና!” ሲል ሰማሁ፡፡ 2እኔም
ተመለከትሁ፤ እነሆ፤ ነጭ ፈረስ ቆሞ
ነበር፤ ተቀምጦበት የነበረውም ቀስት ይዞ
ነበር፤ አክሊልም ተሰጠው፤ እርሱም እንደ
ድል አድራጊ ድል ለመንሣት ወጣ፡፡
3በጉ ሁለተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ፣
ሁለተኛው ሕያው ፍጡር፣ “ና!” ሲል
ሰማሁ፡፡ 4ሌላ ፍም የሚመስል ቀይ ፈረ
ስም ወጣ፤ ተቀምጦበት የነበረው ሰላምን
ከምድር ላይ እንዲወስድና ሰዎችም እርስ
በርሳቸው እንዲተራረዱ ለማድረግ ሥል
ጣን ተሰጠው፤ ትልቅም ሰይፍ ተሰጠው፡፡
5በጉ ሦስተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ፣
ሦስተኛው ሕያው ፍጡር፣ “ና!” ሲ
ል ሰማሁ፡፡ እኔም ተመለከትሁ፤ እነሆ፤
ጥቍር ፈረስ ቆሞ አየሁ፤ ተቀምጦበት
የነበረውም በእጁ ሚዛን ይዞ ነበር፡፡ 6ከዚ
ያም ከአራቱ
ሕያዋን ፍጡራን መካከል፣ “አንድ እርቦ[ሸ]
ስንዴ ለአንድ ቀን ደመወዝ፤ ሦስት እርቦ
ገብስም ለአንድ ቀን ደመወዝ[ቀ] ይሁን፤
ዘይቱንና የወይን ጠጁን አትጕዳ” የሚል
ድምፅ ሰማሁ፡፡
7በጉ አራተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ፣
አራተኛው ሕያው ፍጡር፣ “ና!” ሲል
ሰማሁ፡፡ 8እኔም ተመለከትሁ፤ እነሆ፤ ግራጫ
ፈረስ ቆሞ አየሁ፤ ተቀምጦበት የነበረው
ስሙ ሞት ነበር፤ ሲኦልም ከኋላ ይከተ
ለው ነበር፡፡ እነርሱም በሰይፍ፣ በራብ፣
በመቅሠፍትና በምድር አራዊት እንዲገ
ድሉ በምድር አንድ አራተኛ ላይ ሥል
ጣን ተሰጣቸው፡፡
9አምስተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ፣
ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁትም
ምስ ክርነት የታረዱትን ሰዎች ነፍሶች
ከመሠ ዊያው በታች አየሁ፡፡ 10እነርሱም
በታላቅ ድምፅ፣ “ሁሉን የምትገዛ ቅዱስና
እውነ ተኛ ጌታ ሆይ፤ እስከ መቼ
አትፈርድም? እስከ መቼስ ደማችንን
በምድር በሚኖ
ሩት ላይ አትበቀልም?” አሉ፡፡ 11ከዚያም
ለእያንዳንዳቸው ነጭ ልብስ ተሰጣቸው፤
ወደ ፊት እንደ እነርሱ የሚገደሉ የአገል
ጋይ ባልንጀሮቻቸውና ወንድሞቻቸው ቍጥር
እስኪሞላ ድረስ ጥቂት ጊዜ እንዲታገሡ
ተነገራቸው፡፡
12ስድስተኛውን ማኅተም ሲፈታ ተመ
ለከትሁ፤ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤ ፀሓ
ይም እንደ ማቅ ጠቈረች፡፡ ጨረቃም
በሙሉ እንደ ደም ቀላች፤ 13የበለስ ዛፍ
በብርቱ ነፋስ ስትወዛወዝ ያልበሰለው ፍሬ
ከእርሷ እንደሚረግፍ፣ የሰማይ ከዋክብት
ወደ ምድር ረገፉ፡፡ 14ሰማይ እንደ ጥቅ
ልል መጽሐፍ ተጠቅልሎ ዐለፈ፤ ተራ
ሮችና ደሴቶችም ሁሉ ከስፍራቸው ተወ
ገዱ፡፡
15ከዚህ በኋላ የምድር ነገሥታትና ገዦች፣
የጦር መኰንኖች፣ ሀብታሞች፣ ብርቱ
ዎች፣ ባሮችና ጌቶች ሁሉ በዋሻዎችና
በተራሮች ዐለት ውስጥ ተሸሸጉ፤ 16ተራ
ሮቹንና ዐለቶቹንም፣ “በላያችን ውደቁ፤
በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠው ፊት ከበጉም
ቍጣ ሰውሩን፤ 17ታላቁ የቍጣቸው ቀን
መጥቶአልና፤ ማንስ ሊቆም ይችላል?”
አሏቸው፡፡

## መቶ አርባ አራት ሺሁ መታተማቸው

7 ከዚህ በኋላ አራት መላእክት በአራቱ
የምድር ማእዘኖች ቆመው አየሁ፤ እነ
ርሱም ነፋስ በምድር ወይም በባሕር፣
ወይም በማንኛውም ዛፍ ላይ እንዳይነፍስ
አራቱን የምድር ነፋሶች ያዙ፡፡ 2ከዚያም
የሕያው አምላክ ማኅተም ያለው ሌላ
መል አክ ከምሥራቅ ሲመጣ አየሁ፤
እርሱም ምድርንና ባሕርን ለመጕዳት
ሥልጣን የተሰጣቸውን አራቱን መላእክት
በታላቅ ድምፅ እንዲህ አላቸው፤
3“በአምላካችን አገ ልጋዮች ግንባር ላይ
ማኅተም እስከምናደ ርግባቸው ድረስ
ምድርን ወይም ባሕርን፣ ወይም ዛፎችን
አትጕዱ፡፡” 4የታተሙት ንም ቍጥር ሰ
ማሁ፤ እነርሱም ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ
መቶ አርባ አራት ሺህ ነበሩ፤

5ከይሁዳ ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣
ከሮቤል ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣
ከጋድ ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣
6ከአሴር ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣
ከንፍታሌም ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣
ከምናሴ ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣
7ከስምዖን ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣
ከሌዊ ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣

5፥14 ራእ4፥4፡6፡9፡10
6፥1 ራእ4፥6፡7፤5፥1፡16፤ 14፥2፤19፥6
6፥2 መዝ45፥4፤ ዘካ1፥8፤6፥3፡11፤ ራእ14፥14፤19፥11፡ 12
6፥3 ራእ4፥7
6፥4 ዘካ1፥8፤6፥2፤ ማቴ10፥34
6፥5 ዘካ6፥2፤ራእ4፥7
6፥6 ሕዝ4፥16፤ ራእ4፥6፡7፤7፥1፡3፤9፥4
6፥7 ራእ4፥7
6፥8 ኤር15፥2፡3፤ 24፥10፤ሕዝ5፥12፡17 ፤ሆሴ13፥14፤ዘካ6፥3፤ ራእ1፥18፤20፥13፡14
6፥9 ዘፀ29፥12፤ ዘሌ4፥7፤ሮሜ1፥2፤ ዕብ4፥12፤ራእ14፥18፤ 16፥7፤20፥4
6፥10 ዘዳ32፥43፤ 2ነገ9፥7፤መዝ79፥10፤ 119፥84፤ዘካ1፥12፤ ሉቃ2፥29፤2ጴጥ2፥1፤ ራእ3፥7፡ 10፤16፥6፤ 18፥20፤19፥2
6፥11 ዕብ11፥40፤ ራእ3፥4
6፥12 መዝ97፥4፤ ኢሳ29፥6፤50፥3፤ ሕዝ38፥19፤ማቴ24፥29፤ ራእ8፥5፤11፥13፤ 16፥18
6፥13 ኢሳ34፥4፤ ማቴ24፥29፤ ራእ8፥10፤9፥1
6፥14 መዝ46፥2፤ ኢሳ54፥10፤ ኤር4፥24፤ ሕዝ38፥20፤ ናሆ1፥5፤ 2ጴጥ3፥10፤ራእ16፥20፤ 20፥11፤21፥1
6፥15 ኢሳ2፥10፡19፡ 21፤ራእ19፥18
6፥16 ሆሴ10፥8፤ ሉቃ23፥30፤ራእ5፥1
6፥17 መዝ76፥7፤ ኢል1፥15፤2፥1፡2፡ 11፡31፡ናሆ1፥6፤ ሶፎ1፥14፡15፤ሚል3፥2፤ ራእ16፥14
7፥1 ኢሳ11፥12፤ ኤር49፥36፤ሕዝ37፥9፤ ዳን7፥2፤ዘካ6፥5፤ ማቴ24፥31፤ራእ6፥6
7፥2 ቍ1፤ማቴ16፥16፤ ራእ9፥4፤14፥1፤22፥4
7፥3 ሕዝ9፥4፤ራእ 6፥6፤9፥4፤14፥1፤ 22፥4
7፥4 ራእ9፥16፤14፥1፡3

ሸ6 ግሪኩ *ኮኒክ* ይለዋል፤ አንድ ሊትር ገደማ ይሆናል፡፡
ቀ6 ግሪኩ *አንድ ዲናር* ይለዋል፡፡

ከይሳኮር ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣
8ከዛብሎን ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣
ከዮሴፍ ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣
ከብንያም ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ
ታተሙ።

## ነጭ ልብስ የለበሱ እጅግ ብዙ ሕዝብ

9ከዚህም በኋላ አየሁ፤ እነሆ፣ በዙፋኑና
በበጉ ፊት ማንም ሊቈጥራቸው የማይችል
ከሕዝብ፣ ከነገድ፣ ከወገን፣ ከቋንቋም ሁሉ
እጅግ ብዙ ሕዝብ ቆመው ነበር፤ እነር
ሱም ነጭ ልብስ ለብሰው፣ የዘንባባ ዝን
ጣፊ በእጃቸው ይዘው ነበር። 10በታላቅ
ድምፅም እንዲህ ብለው ጮኹ፤

"ማዳን በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው፣
የአምላካችንና የበጉ ነው።"

11መላእክቱም ሁሉ በዙፋኑና በሽማግሌ
ዎቹ፣ በአራቱም ሕያዋን ፍጡራን ዙሪያ
ቆመው ነበር፤ በዙፋኑ ፊት በግንባራቸው
ተደፍተው ለእግዚአብሔር ሰገዱ፤ 12እንዲ
ህም ይሉ ነበር፤

"አሜን፤
ውዳሴና ክብር፣
ጥበብ፣ ምስጋናና፣ ሞገስ፣
ኀይልና ብርታትም፣
ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ለአምላካችን
ይሁን፤
አሜን።"

13ከዚያም ከሽማግሌዎቹ አንዱ፣ "እነ
ዚህ ነጭ ልብስ የለበሱት እነማን ናቸው?
ከወዴትስ መጡ?" አለኝ።

14እኔም፣ "ጌታ ሆይ፤ አንተ ታውቃ
ለህ" አልሁት።

እርሱም እንዲህ አለኝ፤ እነዚህ ከታላቁ
መከራ የመጡ ናቸው፤ ልብሳቸውንም በበጉ
ደም አጥበው "አንጽተዋል። 15ስለዚህ፣

"በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ሆነው፣
ቀንና ሌሊት በመቅደሱ ያገለግሉታል፤
በዙፋኑም ላይ የተቀመጠው ድንኳኑን
በላያቸው ይዘረጋል፤
16ከእንግዲህ ወዲህ አይራቡም፤
ከዚህም በኋላ አይጠሙም፤
ፀሓይ አይመታቸውም፤
ሐሩሩም ሁሉ አያቃጥላቸውም፤
17ምክንያቱም በዙፋኑ መካከል ያለው
በግ እረኛቸው ይሆናል፤
ወደ ሕይወት ውሃ ምንጭም
ይመራቸዋል፤
እግዚአብሔር እንባን ሁሉ ከዐይናቸው
ያብሳል።"

7፥9 ቍ15፤ራእ3፥4፤ 13፥7
7፥10 መዝ3፥8፤ ራእ5፥1፤12፥10፤ 9፥1
7፥11 ራእ4፥4፥6፥10
7፥12 ሮሜ11፥36፤ራእ5፥12-14
7፥13 ራእ3፥4
7፥14 ዕብ9፥14፤ 1ዮሐ1፥7፤ራእ12፥11፤ 22፥14
7፥15 ቍ9፤ኢሳ4፥5፡ 6፤ራእ5፥1፤11፥19፤ 21፥3፤22፥3
7፥16 ኢሳ49፥10፤ ዮሐ6፥35
7፥17 ኢሳ25፥8፤ 35፥10፤51፥11፤65፥19፤ ዮሐ4፥10፤10፥11፤ ራእ21፥4

8፥1 ራእ6፥1
8፥2 ቍ6-13፤ ማቴ24፥31፤ ራእ9፥1፥13፤11፥15
8፥3 ቍ5፤ዘፀ30፡ 1-6፤ዕብ9፥4፤ራእ5፥8፤ 7፥2፤9፥13
8፥4 መዝ141፥2
8፥5 ዘሌ16፥12፥13፤ ራእ4፥5፤6፥12
8፥6 ቍ2
8፥7 ቍ2፥7-12፤ ሕዝ38፥22፤ራእ9፥4፡ 15፥18፤12፥4
8፥8 ቍ7፤ኤር51፥25፤ ራእ16፥3
8፥9 ቍ7
8፥10 ኢሳ14፥12፤ራእ6፥13፤9፥1፤14፥7፤ 16፥4
8፥11 ቍ7፤ኤር9፥15፤ 23፥15
8፥12 ቍ7፤ ዘፀ10፥21-23፤ ሕዝ32፥7፤ራእ6፥12፥13
8፥13 ራእ3፥10፤ 9፥12፤11፥14፤12፥12፤ 14፥6፤19፥17

## ሰባተኛው ማኅተምና የወርቁ ጥና

8 በጉ ሰባተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ፣
ግማሽ ሰዓት ያህል በሰማይ ዝምታ
ሆነ።
2ከዚያም በእግዚአብሔር ፊት የሚቆሙ
ትን ሰባቱን መላእክት አየሁ፤ ሰባት መለ
ከትም ተሰጣቸው።
3ሌላም መልአክ የወርቅ ጥና ይዞ መጥና
በመሠዊያው አጠገብ ቆመ፤ እርሱም በዙ
ፋኑ ፊት ባለው የወርቅ መሠዊያ ላይ
ከቅዱሳን ጸሎት ሁሉ ጋር እንዲያቀርበው
ብዙ ዕጣን ተሰጠው። 4የዕጣኑም ጢስ
ከቅዱሳኑ ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ ወደ
እግዚአብሔር ፊት ወጣ። 5መልአኩም ጥና
ውን ይዞ የመሠዊያውን እሳት ሞላበትና
ወደ ምድር ወረወረው፤ ነጐድጓድ፣ ድምፅ፣
መብረቅና የምድር መናወጥ ሆነ።

## ሰባቱ መለከቶች

6ከዚያም ሰባቱን መለከት የያዙት
ሰባቱ መላእክት ለመንፋት ተዘጋጁ።
7የመጀመሪያው መልአክ መለከቱን
ነፋ፤ ደም የተቀላቀለበት በረዶና እሳት
ወደ ምድር ተጣለ፤ የምድር አንድ ሦስ
ተኛ ተቃጠለ፤ የዛፎችም አንድ ሦስተኛ
ተቃጠለ፤ የለመለመውም ሣር ሁሉ ተቃ
ጠለ።
8ሁለተኛውም መልአክ መለከቱን ነፋ፤
ትልቅ ተራራ የሚመስል ነገር በእሳት እየ
ተቀጣጠለ ወደ ባሕር ተጣለ፤ የባሕሩ
አንድ ሦስተኛ ወደ ደም ተለወጠ፤ 9በባሕ
ሩም ውስጥ ከሚኖሩት ሕያዋን ፍጡራን
አንድ ሦስተኛ ሞተ፤ የመርከቦችም አንድ
ሦስተኛ ወደመ።
10ሦስተኛውም መልአክ መለከቱን ነፋ፤
እንደ ችቦ የሚነድ ታላቅ ኮከብ በወንዞች
አንድ ሦስተኛና በውሃ ምንጮች ላይ ከሰ
ማይ ወደቀ፤ 11የኮከቡም ስም "እሬቶ[a]"
ይባል ነበር። የውሃውም አንድ
ሦስተኛ መራራ ሆነ፤ ውሃው መራራ
ከመሆኑ የተነሣም ብዙ ሰዎች ሞቱ።
12አራተኛው መልአክ መለከቱን ነፋ፤
የብርሃናቸው አንድ ሦስተኛ ይጨልም
ዘንድ፣ የፀሓይ አንድ ሦስተኛ፣ የጨረ
ቃም አንድ ሦስተኛ፣ የከዋክብትም አንድ
ሦስተኛ ተመታ፤ የቀንም አንድ ሦስተኛ፣
የሌሊቱም አንድ ሦስተኛ ብርሃን እንዳይ
ሰጥ ተከለከለ።
13ከዚያም ተመለከትሁ፤ አንድ ንስር
በሰማይ መካከል ይበር ነበር፤ በታላቅ ድም
ፅም፣ "የቀሩት ሦስቱ መላእክት መለከት

[a]11 ምሬት ማለት ነው።

ስለሚነፉ፣ በምድር ላይ ለሚኖሩት ወዮላ
ቸው! ወዮላቸው! ወዮላቸው!" ሲል ሰማሁ።

9 አምስተኛው መልአክ መለከቱን ነፋ፤
ከሰማይ ወደ ምድር የወደቀውን
ኮከብ አየሁ፤ ኮከቡም የጥልቁ ጕድጓድ
መክፈቻ ተሰጠው። 2ጥልቁን ጕድጓድ በከ
ፈተውም ጊዜ፣ ከውስጡ ከታላቅ እቶን
እንደሚወጣ ያለ ጢስ ወጣ። ከጕድጓዱም
በወጣው ጢስ ፀሓይና ሰማይ ጨለሙ።
3ከጢሱም አንበጦች ወጥተው በምድር
ላይ ወረዱ፤ እንደ ምድር ጊንጦች ሥል
ጣን ያለ ሥልጣን ተሰጣቸው። 4እነርሱም
የምድርን ሣር ወይም ማናቸውንም የለመ
ለመ ተክል ወይም ዛፍ እንዳይጐዱ፣ ነገር
ግን የእግዚአብሔር ማኅተም በግምባራቸው
ላይ የሌለባቸውን ሰዎች ብቻ እንዲጐዱ
ተነገራቸው፤ 5እነርሱንም አምስት ወር
ብቻ እንዲያሠቃዩአቸው እንጂ እንዲገድ
ሏቸው ሥልጣን አልተሰጣቸውም፤ የሚሠ
ቃዩትም ሥቃይ ጊንጥ ሰውን ሲነድፍ
እንደሚሰማው ዐይነት ሥቃይ ነው። 6በእ
ነዚያ ቀኖች ሰዎች ሞትን ይፈልጋሉ፤ ነገር
ግን አያገኙትም፤ ለመሞትም ይመኛሉ፤
ነገር ግን ሞት ከእነርሱ ይሸሻል።
7አንበጦቹ ለጦርነት የተዘጋጁ ፈረሶች
ይመስሉ ነበር፤ በራሳቸውም ላይ የወርቅ
አክሊል የመሰለ ነገር ደፍተዋል፤ ፊታቸ
ውም የሰው ፊት ይመስል ነበር፤ 8ጠጕራ
ቸው የሴት ጠጕር፣ ጥርሳቸውም የአንበሳ
ጥርስ ይመስል ነበር። 9የብረት ጥሩር
የሚመስል ጥሩር ነበራቸው፤ የክንፎቻቸ
ውም ድምፅ ወደ ጦርነት የሚገሠግ
ሡ የብዙ ፈረሶችና ሠረገሎች ድምፅ
ይመ ስል ነበር። 10እንደ ጊንጥም ያለ ጅ
ራትና መንደፊያ ነበራቸው፤ ደግሞም
ሰዎችን አምስት ወር የሚያሠቃዩበት
ኀይል በጅራታቸው ላይ ነበር።
11በላያቸው ንጉሥ ነበራቸው፤ እርሱም
የጥልቁ ጕድጓድ መል አክ ነው፤ ስሙም
በዕብራይስጥ "አብዶን"፣ በግሪክ ደግሞ
"አጶልዮን"ᐩ ይባላል።
12የመጀመሪያው ወዮ ዐልፎአል፤ እነሆ፤
ከዚህ በኋላ ገና ሌላ ሁለት ወዮዎች ይመ
ጣሉ።
13ስድስተኛው መልአክ መለከቱን ነፋ፤
በእግዚአብሔር ፊት ካለው በወርቅ ከተሠ
ራው መሠዊያ ቀንዶች ድምፅ ሲመጣǂ
ሰማሁ፤ 14ድምፁም መለከት የያዘውን ስድ
ስተኛውን መልአክ፣ "በታላቁ ወንዝ በኤ
ፍራጥስ የታሰሩትን አራቱን መላእክት ፍታ
ቸው" አለው። 15ከሰው ዘር አንድ ሦስተኛ
ውን እንዲገድሉ፣ ለዚህች ሰዓትና ዕለት
እንዲሁም ለዚህች ወርና ዓመት ተዘጋጅ

9፥1 ቀኍ2፥11፤
ቀኍ8፥31፤ራእ1፥18፤
8፥10
9፥2 ቀኍ1፥11፤
ዘፍ19፥28፤ዘፀ19፥18፤
ኢል2፥2፥10፤ ሉቃ8፥31
9፥3 ቀኍ5፥10፤
ዘፀ10፥12-15
9፥4 ራእ6፥6፤7፥2፡
3፤8፥7
9፥5 ቀኍ3፥10
9፥6 ኢዮ3፥21፤
7፥15፤ኤር8፥3፤
ራእ6፥16
9፥7 ዳን7፥8፤ኢል2፥4
9፥8 ኢል1፥6
9፥9 ኢል2፥5
9፥10 ቀኍ3፥5፥19
9፥11 ቀኍ1፥2፡
ኢዮ26፥6፤28፥22፤
31፥12፤መዝ88፥11፤ሉ
ቃ8፥31፤ራእ16፥16
9፥12 ራእ8፥13
9፥13 ዘፀ30፥1-3፤
ራዕ8፥3
9፥14 ዘፍ15፥18፤
ዘዳ1፥7፤ኢሱ1፥4፤
ኢሳ11፥15፤ራእ11፥15፤
ራእ7፥1፤ 16፥12
9፥15 ቀኍ18፤ራእ
8፥7፤20፥7
9፥16 ራእ5፥11፤7፥4
9፥17 ቀኍ18፤
መዝ11፥6፤ኢሳ30፥33፤
ሕዝ38፥22፤ራእ11፥5፤
14፥10፤19፥20፤20፥10፤
21፥8
9፥18 ቀኍ15፥17፤
ራእ8፥7
9፥20 ዘዳ4፥28፤31፥29፤
መዝ115፥4-7፤
135፥15-17፤ኤር1፥16፤
ዳን5፥23፤ሚክ5፥13፤
ሐሥ7፥41፤1ቆሮ10፥20
9፥21 ኢሳ47፥9፥12፤
ራእ2፥21፤17፥2፥5፤18፥23
10፥1 ሕዝ1፥28፤
ማቴ17፥2፤ራእ1፥15፡
16፤4፥3፤5፥2፤18፥1፤2
0፥1
10፥2 ቀኍ5፥8-10፤ራ
እ5፥1
10፥3 ሆሴ11፥10፤ራ
እ4፥5
10፥4 ቀኍ8፤ዳን8፥26፤
12፥4፥9፤ራእ1፥11፡
19፤22፥10
10፥5 ቀኍ1፥2፤
ዘዳ32፥40፤ዳን12፥7
10፥6 ዘፍ14፥22፤
ዘፀ6፥8፤ዘኍ14፥30፤
መዝ115፥15፤146፥6፤
ራእ1፥18፤4፥1114፥7፤
16፥17
10፥7 አሞ3፥7ማቴ
24፥31፤ሮሜ16፥25

ተው የነበሩት አራቱ መላእክት ተፈቱ።
16የፈረሰኛው ሰራዊት ብዛት ሁለት መቶ
ሚሊዮን ነበር፤ ቍጥራቸውንም ሰማሁ።
17በራእዬ ያየኋቸው ፈረሶችና በላያቸ
ውም የተቀመጡት ይህን ይመስሉ ነበር፤
ጥሩራቸው እንደ እሳት ቀይ፣ እንደ ያክ
ንት ሰማያዊና እንደ ዲን ብጫ ነበር፤ የፈ
ረሶቹ ራስ የአንበሶችን ራስ ይመስል
ነበር። ከአፋቸውም እሳትና ጢስ፣ ዲንም
ይወጣ ነበር። 18ከአፋቸው በወጡት፣ በሦ
ስቱ መቅሠፍቶች፣ ማለት በእሳቱ፣ በጢ
ሱና በዲኑ አንድ ሦስተኛው የሰው ዘር
ተገደለ። 19ምክንያቱም የፈረሶቹ ኀይል
በአፋቸውና በጅራታቸው ላይ ነበር፤ ጅራ
ታቸውም እባብ ይመስል ነበር፤ ራስ ስላላ
ቸው ጕዳት የሚያደርሱት በእርሱ ነበር።
20በእነዚህ መቅሠፍቶች ሳይገደሉ የቀ
ሩት ሰዎች አሁንም ከእጃቸው ሥራ ንስሓ
አልገቡም፤ አጋንንትን እንዲሁም ማየት
ወይም መስማት ወይም መሄድ የማይች
ሉትን፣ ከወርቅ፣ ከብር፣ ከናስ፣ ከድንጋ
ይና ከዕንጨት የተሠሩትን ጣዖቶች ማም
ለክ አልተዉም፤ 21ደግሞም ከነፍስ ግድያ
ቸው፣ ከጥንቆላ ሥራቸው፣ ከዝሙት ርኵ
ሰታቸው ወይም ከስርቆት ተግባራቸው
ንስሓ አልገቡም።

## መልአኩና ትንሿ መጽሐፍ

10 ከዚህ በኋላ ሌላ ብርቱ መልአክ
ደመና ተጐናጽፎ ከሰማይ ሲወ
ርድ አየሁ፤ እርሱም በራሱ ላይ ቀስተ
ደመና ነበር። ፊቱ እንደ ፀሓይ፣ እግሮቹ
እንደ እሳት ዐምዶች ነበሩ። 2በእጁም
የተከፈተች ትንሽ ጥቅልል መጽሐፍ ይዞ
ነበር፤ ቀኝ እግሩን በባሕር ላይ፣ ግራ
እግሩን በምድር ላይ አኖረ፤ 3እንደሚያ
ገሣ አንበሳም ድምፁን ከፍ አድርጎ ጮኸ፤
በጮኸም ጊዜ የሰባቱ ነጐድጓዶች ድም
ፆች ተናገሩ። 4ሰባቱ ነጐድጓዶች በተናገሩ
ጊዜ፣ ለመጻፍ ተዘጋጀሁ፤ ነገር ግን፣
"ሰባቱ ነጐድጓዶች የተናገሩትን በማኅ
ተም ዝጋው እንጂ አትጻፍ" የሚል ድምፅ
ከሰማይ ሰማሁ።
5ከዚህ በኋላ በባሕርና በምድር ላይ
ቆሞ ያየሁት መልአክ ቀኝ እጁን ወደ
ሰማይ አነሣ፤ 6እርሱም ከዘላለም እስከ ዘላ
ለም በሚኖረው፣ ሰማይንና በውስጡ ያሉ
ትን፣ ምድርንና በውስጧ ያሉትን፣ ባሕ
ርንና በውስጡ ያሉትን በፈጠረው በእርሱ
ማለ፤ እንዲህም አለ፤ "ከእንግዲህ መዘግ
የት አይኖርም፤ 7ነገር ግን ሰባተኛው መል

ᐩ11 አብዶን ወይም አጶልዮን ትርጉሙ አጥፊ ማለት ነው።
ǂ13 ሲወጣ ማለት ነው።

አክ መለከቱን በሚነፋባቸው ቀኖች፣ ለአ
ገልጋዮቹ ለነቢያት በገለጠላቸው መሠረት
የእግዚአብሔር ምስጢር ይፈጸማል።”
8ከዚያም ከሰማይ የሰማሁት ድምፅ እንደ
ገና እንዲህ ሲል ተናገረ፤ “ሂድ፤ በባሕርና
በምድር ላይ ከቆመው መልአክ እጅ
የተከፈተችውን ጥቅልል መጽሐፍ ውሰድ።”
9እኔም ወደ መልአኩ ሄጄ ትንሿን ጥቅ
ልል መጽሐፍ እንዲሰጠኝ ጠየቅሁት፤ እር
ሱም፣ “ውሰድና ብላት፤ ሆድህን መራራ
ታደርገዋለች፤ በአፍህ ግን እንደ ማር ትጣ
ፍጣለች” አለኝ። 10ትንሿንም መጽሐፍ ከመ
ልአኩ እጅ ተቀብዬ በላኋት፤ በአፌ እንደ
ማር ጣፈጠች፤ ከበላኋት በኋላ ግን ሆዴ
መራራ ሆነ፤ 11ከዚያም፣ “ስለ ብዙ ሕዝ
ቦች፣ ወገኖች፣ ቋንቋዎችና ነገሥታት እንደ
ገና ትንቢት ልትናገር ይገባሃል” ተባ
ልሁ።

## ሁለቱ ምስክሮች

11 ከዚያም ሸምበቆ የመሰለ መለኪያ
በትር ተሰጠኝ፤ እንዲህም ተባ
ልሁ፤ “ሄደህ የእግዚአብሔርን ቤተ
መቅደስና መሠዊያውን ለካ፤ በዚያም የሚ
ያመልኩትን ቍጠር። 2የውጭውን አደባ
ባይ ግን ተወው፤ አትለካው፤ ለአሕዛብ
የተሰጠ ነውና። እነርሱ የተቀደሰችውን
ከተማ አርባ ሁለት ወር ይረግጧታል።
3ለሁለቱ ምስክሮቼ ኀይል እሰጣቸዋለሁ፤
እነርሱም ማቅ ለብሰው አንድ ሺህ ሁለት
መቶ ሥልሳ ቀን ትንቢት ይናገራሉ።”
4እነዚህም በምድር ጌታ ፊት የሚቆሙት
ሁለቱ የወይራ ዛፎችና ሁለቱ መቅረዞች
ናቸው። 5ማንም እነርሱን ሊጐዳ ቢፈልግ፣
እሳት ከአፋቸው ወጥቶ ጠላቶቻቸውን
ያጠፋል፤ ሊጐዳቸው የሚፈልግ ሁሉ
መሞት ያለበት በዚህ ዐይነት ነው። 6እነ
ዚህ ሰዎች ትንቢት በሚናገሩባቸው ወራት
ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማይን ለመዝጋት
ሥልጣን አላቸው፤ ደግሞም ውሃዎችን
ወደ ደም ለመለወጥ በሚፈልጉበት ጊዜ
ሁሉ ምድርን በማንኛውም መቅሠፍት
ለመምታት ሥልጣን አላቸው።
7ምስክርነታቸውን ከጨረሱ በኋላ ከጥ
ልቁ የሚወጣው አውሬ ይዋጋቸዋል፤ ድል
ይነሣቸዋል፤ ይገድላቸዋልም። 8ሬሳቸውም
በታላቂቱ ከተማ አደባባይ ይጣላል፤ ይህች
ከተማ ሰዶምና ግብፅ እየተባለች በምሳሌ
የምትጠራውና የእነርሱም ጌታ የተሰቀለ
ባት ናት። 9ከወገን፣ ከነገድ፣ ከቋንቋና
ከሕዝብ የመጡ ሰዎች ሬሳቸውን ሦስት
ቀን ተኩል ይመለከታሉ፤ ሬሳቸውም እን
ዳይቀበር ይከለክላሉ። 10እነዚህ ሁለት ነቢ
ያት የምድር ነዋሪዎችን ያሠቃዩ ስለ
ነበር፣ በምድር የሚኖሩ ሰዎች በእነርሱ
ላይ በደረሰው ደስ ይላቸዋል፤ እርስ በርሳ
ቸውም ስጦታ ይለዋወጣሉ።
11ከሦስቱ ቀን ተኩል በኋላ ግን፣ የሕ
ይወት እስትንፋስ ከእግዚአብሔር ዘንድ
መጥቶ ገባባቸው፤ እነርሱም ተነሥተው
በእግሮቻ ቸው ቆሙ፤ ይመለከቷቸውም
በነበሩት ላይ ታላቅ ድንጋጤ
ወረደባቸው። 12ከዚያም፣ “ወደዚህ ውጡ!”
የሚላቸውን ታላቅ ድምፅ ከሰማይ
ሰሙ፤ ጠላቶቻቸው እየተ መለከቷቸው
በደመና ወደ ሰማይ ወጡ።
13በዚያም ሰዓት ታላቅ የምድር መና
ወጥ ሆነ፤ የከተማዪቱም አንድ ዐሥረኛ
ወደመ፤ በነውጡም ሰባት ሺህ ሰዎች ሞቱ፤
የተረፉትንም ፍርሀት ያዛቸው፤ ለሰማ
ይም አምላክ ክብር ሰጡ።
14ሁለተኛው ወዮ ዐልፎአል፤ እነሆ፤ ሦስ
ተኛው ወዮ ቶሎ ይመጣል።

## ሰባተኛው መለከት

15ሰባተኛውም መልአክ መለከቱን ነፋ፤
በሰማይም እንዲህ የሚሉ ታላላቅ ድም
ፆች ተሰሙ፤

“የዓለም መንግሥት፣
የጌታችንና የእርሱ ክርስቶስ መንግሥት
ሆነች፤
እርሱም ከዘላለም እስከ ዘላለም
ይነግሣል።”

16በእግዚአብሔር ፊት በዙፋኖቻቸው ላይ
የተቀመጡት ሃያ አራቱ ሽማግሌዎችም
በግምባራቸው ተደፍተው ለእግዚአብሔር ሰገዱ፤
17እንዲህም አሉ፤

“ያለህና የነበርህ፣
ሁሉን ቻይ፤
ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፤ እናመሰግንሃለን፤
ምክንያቱም አንተ ታላቁን ኀይልህን
ይዘህ ነግሠሃል።
18አሕዛብ ተቈጥተው ነበር፤
የአንተም ቍጣ መጣች፤
በሙታን ላይ የምትፈርድበት፣
ለአገልጋዮችህ ለነቢያት፣
ለቅዱሳንና ስምህን ለሚፈሩት፣
ለታናናሾችና ለታላላቆች ዋጋቸውን
የምትሰጥበት፣
ምድርንም ያጠፉትን የምታጠፋበት
ዘመን መጣ።”

19ከዚያም በሰማይ ያለው የእግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ ተከፈተ፤ በመቅደሱም ውስጥ
የኪዳኑ ታቦት ታየ፤ መብረቅ፣ ድምፅ፣

10፥8 ቍ2፥4
10፥9 ኤር15፥16፤ ሕዝ2፥8-3፥3
10፥10 ቍ9
10፥11 ሕዝ37፥4፥9፤ ዳን3፥4፤ራእ13፥7
11፥1 ሕዝ40፥3፤ ራእ21፥15
11፥2 ቍ3፤ ሕዝ40፥17፥20፤ ዳን7፥25፤12፥7፤ሉቃ21፥24፤ራእ12፥6፥14፤13፥5፤21፥2
11፥3 ቍ2፤ዘፍ37፥34፤ 2ሳሙ3፥31፤ነህ9፥1፤ዮናን3፥5፤ራእ1፥5፤2፥13
11፥4 መዝ52፥8፤ ኤር11፥16፤ዘካ4፥3፥11፥14
11፥5 ዘኍ16፥29፥35፤2ሳሙ22፥9፤ 2ነገ1፥10፤ኤር5፥14፤ ራእ9፥17፥18
11፥6 ቍ3፤ዘፀ7፥17፥19፤ሉቃ4፥25፤ ራእ8፥8
11፥7 ዳን7፥21፤ ሉቃ8፥31፤ራእ13፥1-4፥7
11፥8 ኢሳ1፥9፤ኤር23፥14፤ሕዝ16፥46፤ዕብ13፥12፤ራእ16፥19
11፥9 መዝ79፥2፥3፤ ራእ13፥7
11፥10 ነህ8፥10፥12፤ አስ9፥19፥22፤ራእ3፥10
11፥11 ቍ9፤ ሕዝ37፥5፥9፥10፥14
11፥12 2ነገ2፥11፤ ሐሥ1፥9፤ራእ4፥1
11፥13 ራእ6፥12፤ 14፥7፤16፥9፥11፤19፥7
11፥14 ራእ8፥13
11፥15 መዝ145፥13፤ ዳን2፥44፤7፥14፥27፤ሚክ4፥7፤ዘካ14፥9፤ ማቴ24፥31፤ሉቃ1፥33፤ ራእ12፥10፤16፥17፤ 19፥1
11፥16 ራእ4፥4፥10
11፥17 መዝ30፥12፤ ራእ1፥4፥8፤19፥6
11፥18 መዝ2፥1፤ ራእ10፥7፤19፥5፤ 20፥12
11፥19 ዘፀ25፥10-22፤ 2ዜና5፥7፤ዕብ9፥4፤ ራእ4፥5፤15፥5፥8፤ 16፥21

ነጐድጓድ፣ የምድር መናወጥና ታላቅም
በረዶ ሆነ።

## ሴቲቱና ዘንዶው

12 ታላቅና አስደናቂ ምልክት በሰ
ማይ ታየ፤ ፀሓይን የለበሰች፣
ጨረቃን ከእግሮቿ በታች የረገጠችና በራ
ሷም ላይ ዐሥራ ሁለት ከዋክብት ያሉት
አክሊል የደፋች አንዲት ሴት ታየች።
2እርሷም ነፍሰጡር ነበረች፤ ልትወልድ
ስትል ምጥ ይዞአት ተጨንቃ ጮኸች።
3ከዚያም ሌላ ምልክት በሰማይ ታየ፤ እነሆ፤
ሰባት ራሶችና ዐሥር ቀንዶች የነበሩት፣
በራሶቹም ላይ ሰባት አክሊል የደፋ ታላቅ
ቀይ ዘንዶ ታየ። 4ጅራቱ የከዋክብትን
አንድ ሦስተኛ ከሰማይ ስቦ ወደ ምድር
ጣላቸው፤ እርሷም በወለደች ጊዜ ልጇን
ለመዋጥ ፈልጎ ዘንዶው ልትወልድ በተቃ
ረበችው ሴት ፊት ቆመ። 5ሕዝቦችን ሁሉ
በብረት በትር የሚገዛውን ወንድ ልጅ
ወለደች፤ ልጇም ወደ እግዚአብሔርና ወደ
ዙፋኑ ተነጠቀ። 6ሴቲቱም አንድ ሺህ
ሁለት መቶ ሥልሳ ቀን ክብካቤ እንዲ
ደረግላት እግዚአብሔር ወዳዘጋጀላት ስፍራ
ወደ በረሓ ሸሸች።

7በሰማይም ጦርነት ሆነ፤ ሚካኤልና መላ
እክቱ ከዘንዶው ጋር ተዋጉ፤ ዘንዶውና
መላእክቱም መልሰው ተዋጓቸው፤ 8ነገር
ግን ድል ተመቱ፤ በሰማይም የነበራቸውን
ስፍራ ዐጡ። 9ታላቁ ዘንዶ፣ የጥንቱ እባብ
ተጣለ፤ እርሱም ዲያብሎስ ወይም ሰይጣን
ተብሎ የሚጠራው፣ ዓለምን ሁሉ የሚያ
ስተው ነው፤ እርሱ ወደ ምድር ተጣለ፤
መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።

10ከዚህ በኋላ ታላቅ ድምፅ በሰማይ
እንዲህ ሲል ሰማሁ፤

"አሁን የአምላካችን ማዳን፣ ኀይልና
መንግሥት፣
የእርሱ ክርስቶስ ሥልጣንም
መጥቶአል።
ቀንና ሌሊት በአምላካችን ፊት ሲከሳቸው
የነበረው፣
የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልና።
11እነርሱም በበጉ ደም፣
በምስክርነታቸውም ቃል፣
ድል ነሡት፤
እስከ ሞት ድረስ እንኳ፣
ለነፍሳቸው አልሳሱም።
12ስለዚህ ሰማያት ሆይ፣
በውስጣቸውም የምትኖሩ ሆይ፣
ደስ ይበላችሁ፤
ምድርና ባሕር ግን ወዮላችሁ!

12፥1 ቈ3፤ዘፍ37፥9፤
ራእ11፥19
12፥2 ኢሳ26፥17፤
ገላ4፥19
12፥3 ቈ1፡9፡13፡
16፡17፤ዳን7፥7፡20፤
ራእ13፥1፤15፥1፤17፥3፡7፡
12፥16፤19፥15
12፥4 ዳን8፥10፤
ማቴ2፥16፤ራእ8፥7
12፥5 መዝ2፥9፤
ሐሥ8፥39፤ራእ2፥27፤
19፥15
12፥6 ራእ11፥2
12፥7 ቈ3፤
ማቴ25፥41፤ይሁ9
12፥9 ቈ15፤
ዘፍ3፥1-7፤ማቴ4፥10፤
25፥41፤ሉቃ10፥18፤
ዮሐ12፥31፤
ራእ20፥2፡3፡8፡10
12፥10 ኢዮ1፥9-11፤
ዘካ3፥1፤1ጴጥ5፥8፤
ራእ77፥10፤11፥15
12፥11 ሉቃ14፥26፤
ዮሐ16፥33፤ራእ2፥10፤
6፥9፤7፥14፤15፥2
12፥12 መዝ96፥11፤
ኢሳ44፥23፤49፥13፤
ራእ8፥13፤10፥6፤18፥20

12፥13 ቈ3፡5
12፥14 ዘፀ19፥4፤
ራእ11፥2
12፥15 ቈ9
12፥17 ዘፍ3፥15፤
ዮሐ14፥15፤
ራእ1፥2፤11፥7፤13፥7
13፥1 ዳን7፥1-6፤
11፥36፤ራእ12፥3፤
15፥2፤16፥13፤17፥3
13፥2 ዳን7፥4፡5፡6፤
ራእ2፥13፤16፥10
13፥3 ቈ12፡14፤ ራ
እ17፥8
13፥4 ዘፀ15፥11
13፥5 ዳን7፥8፡11፡20፡
25፤11፥36፤2ተሰ2፥4፤
ራእ11፥21
13፥6 ራእ12፥12
13፥7 ዳን7፥21፤
ራእ5፥9፤7፥9፤10፥11፤
11፥7፤17፥15

ምክንያቱም ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን ብቻ
እንደ ቀረው ስላወቀ፣
በታላቅ ቍጣ ተሞልቶ ወደ እናንተ
ወርዶአል።

13ዘንዶው ወደ ምድር እንደ ተጣለ
ባየ ጊዜ፣ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት
አሳደዳት። 14ሴቲቱም በበረሓ ወደ ተዘጋ
ጀላት ስፍራ በርራ መሄድ እንድትችል
ሁለት የታላቁ ንስር ክንፎች ተሰጣት፤
ይህም የሆነው በዚያ ከእባቡ ፊት ርቃ
ለአንድ ዘመን፣ ለዘመናትና ለዘመን እኩ
ሌታ በክብካቤ እንድትኖር ነው። 15እባ
ቡም ሴቲቱ በጐርፍ ተጠራርጋ እንድት
ወሰድ፣ እንደ ወንዝ ያለ ውሃ ከአፉ ተፋ።
16ምድር ግን ሴቲቱን ረዳቻት፤ አፏንም
ከፍታ ዘንዶው ከአፉ ያፈሰሰውን ወንዝ
ዋጠች። 17ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተሐጣ፤
ከቀሩት ልጆቿም ጋር ሊዋጋ ሄደ፤ እነርሱ
የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁና የኢየ
ሱስን ምስክር አጥብቀው የያዙ ናቸው።

13 ዘንዶውም[1] በባሕሩ ዳር ቆሞ
ነበር።

## ከባሕር የወጣው አውሬ

ከዚያም አንድ አውሬ ከባሕር ሲወጣ
አየሁ፤ እርሱም ዐሥር ቀንዶችና ሰባት
ራሶች ነበሩት፤ በቀንዶቹም ላይ ዐሥር
ዘውዶች፣ በራሶቹም ላይ የስድብ ስሞች
ነበሩት። 2ያየሁትም አውሬ ነብር ይመ
ስል ነበር፤ ነገር ግን እግሮቹ የድብ፣ አፉ
ደግሞ የአንበሳ አፍ ይመስል ነበር፤ ዘን
ዶው የራሱን ኀይልና የራሱን ዙፋን እን
ዲሁም ታላቅ ሥልጣን ለአውሬው ሰጠ
ው። 3ከአውሬው ራሶች አንዱ ለሞት
የሚያደ ርስ ቍስል ያለበት ይመስል
ነበር። ነገር ግን ለሞት የሚያደርሰው
ቍስሉ ዳነ፤
ዓለም በሙሉ በመደነቅ አውሬውን ተከተ
ለው። 4ሰዎችም ለዘንዶው ሰገዱለት፤ ምክ
ንያቱም ሥልጣኑን ለአው ሬው ሰጥቶ
ታል። ደግሞም፣ "አውሬውን የሚመስል
ማን ነው? ከእርሱስ ጋር ማን ሊዋጋ ይች
ላል?" በማለት ለአውሬው ሰገዱለት።

5አውሬው የትዕቢት ቃል የሚናገርበ
ትና የሚሳደብበት አፍ ተሰጠው፤ አርባ
ሁለት ወር በሥልጣን እንዲሠራም ተፈ
ቀደለት። 6እርሱም እግዚአብሔርን
ለመሳደብ እንዲሁም ስሙንና
ማደሪያውን፣ በሰማ ይም የሚኖሩትን
ለመሳደብ አፉን ከፈተ። 7ቅዱሳንን እንዲ
ዋጋና ድልም እንዲነሣ ቸው ኀይል
ተሰጠው። በነገድ፣ በወገን፣

[1] 1 አንዳንድ የጥንት ቅጆች እኔም በባሕሩ ዳር ቆሜ ነበር
ይላሉ።

በቋንቋና በሕዝብም ሁሉ ላይ ሥልጣን
ተሰጠው፡፡ 8ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ[ʼ] በታ
ረደው በግ የሕይወት መጽሐፍ ላይ ስሞ
ቻቸው ያልተጻፈ የምድር ሰዎች ሁሉ ለአ
ውሬው ይሰግዳሉ፡፡

9ጆሮ ያለው ቢኖር ይስማ፡፡

10ማንም የሚማረክ ቢኖር፣
እርሱ ይማረካል፤
ማንም በሰይፍ የሚገድል[ˀ] ቢኖር፣
እርሱ በሰይፍ ይገደላል፡፡

ይህም የቅዱሳን ትዕግሥትና እምነት
የሚታየው በዚህ እንደ ሆነ ያስገነዝባል፡፡

## ከምድር የወጣው አውሬ

11ከዚያም ሌላ አውሬ ከምድር ሲወጣ
አየሁ፤ እርሱም እንደ በግ ሁለት ቀንዶች
ነበሩት፤ ነገር ግን እንደ ዘንዶ ይናገር
ነበር፡፡ 12በመጀመሪያው አውሬ ስም በሙሉ
ሥልጣን ይሠራ ነበር፤ ምድርና በእርሷም
የሚኖሩ ሁሉ፣ ለሞት ከሚያደርሰው
ቍስል የዳነውን የመጀመሪያውን አውሬ
እንዲያ መልኩ አደረገ፡፡ 13በሰዎቹም ፊት
እሳት ከሰማይ ወደ ምድር እስኪያወርድ
ድረስ ታላላቅ ምልክቶችን አደረገ፡፡
14በመጀመ ሪያው አውሬ ስም
ምልክቶችን እንዲያደ ርግ ሥልጣን ስለ
ተሰጠው፣ በምድር የሚ ኖሩ ሰዎችን
አሳተ፤ በሰይፍ ሐስሎ ለነበ ረው፣ ነገር
ግን በሕይወት ለሚኖረው አውሬ ምስል
እንዲያቆሙም አዘዛቸው፡፡ 15ደግሞም
የመጀመሪያው አውሬ ምስል መናገር
እንዲችል ለምስሉ እስትንፋስ ለመ ስጠትና
ለዚህም ምስል የማይሰግዱ ሁሉ እንዲ
ገደሉ ለማድረግ ሥልጣን ተሰጠው፡፡
16እንዲሁም ታናናሾችና ታላላቆች፣ ሀብታ
ሞችና ድኾች፣ ጌቶችና ባሮች ሁሉ በቀኝ
እጃቸው ወይም በግምባራቸው ላይ ምል
ክት እንዲቀበሉ አስገደዳቸው፤ 17ይህም
የሆነው የአውሬው ምልክት፣ ይኸውም ስሙ
ወይም የስሙ ቍጥር የሌለው ማንም
ሰው ለመግዛትም ሆነ ለመሸጥ እንዳይችል
ነው፡፡
18ይህ ጥበብ ይጠይቃል፤ አእምሮ ያለው
ማንኛውም ሰው የአውሬውን ቍጥር ያስ
ላው፤ ምክንያቱም ቍጥሩ የሰው ቍጥር
ነው፡፡ ቍጥሩ ስድስት መቶ ሥልሳ ስድ
ስት ነው፡፡

## በጉና መቶ አርባ አራቱ ሺህ ሰዎች

14 ከዚህ በኋላ አየሁ፤ እነሆ፤ በጉ በጽ
ዮን ተራራ ላይ ቆሞ ነበር፤ ከእር
ሱም ጋር የእርሱ ስምና የአባቱ ስም በግ
ምባራቸው ላይ የተጻፈባቸው መቶ አርባ

13፥8 ቈላ12፥14፤ ማቴ25፥34፤ዮሐ1፥29፤ ራእ3፥10
13፥9 ራእ2፥7
13፥10 ኤር15፥2፤ 43፥11፤ዕብ6፥12፤ ራእ14፥12
13፥11 ቈላ1፥2፤ ራእ16፥13
13፥12 ቈላ3፥4፥14፥ 15፤ራእ14፥9፥11፤ 16፥2፤19፤20፤፤20፥4
13፥13 ነገ18፥38፤ 2ነገ1፥10፤ማቴ24፥24፤ ሉቃ9፥54፤ራእ20፥9
13፥14 ቈላ3፥12፤ 2ተሰ2፥9፥10፤ ራእ3፥10፤12፥9
13፥15 ቈላ12፤ዳን3፥3-6
13፥16 ራእ7፥3፤14፥9፤ 19፥5፤20፥4
13፥17 ቈላ18፤ ራእ14፥9፥11፤15፥2
13፥18 ራእ15፥2፤ 17፥9፤21፥17
14፥1 ቈላ3፤መዝ2፥6፤ ዕብ12፥22፤ራእ3፥12፤ 5፥6፤7፥3፥4፤22፥4
14፥2 ራእ1፥15፤ 5፥8፤6፥1፤15፥2
14፥3 ቈላ1፤ራእ4፥4፥ 6፤5፥9
14፥4 ኤር2፥3፤ 2ቆሮ11፥2፤ያዕ1፥18፤ ራእ3፥4፤5፥9፤7፥17
14፥5 መዝ32፥2፤ ሶፎ3፥13፤ዮሐ1፥47፤ኤ ፌ5፥27፤1ጴጥ2፥22
14፥6 ራእ3፥10፤ 8፥13፤13፥7፤19፥17
14፥7 መዝ34፥9፤ ራ እ8፥10፥6፤11፥13፤ 15፥4፤16፥4
14፥8 ኢሳ21፥9፤ ኤር51፥8፤ራእ16፥19፤ 17፥2፥4፥5፤18፥2፥3፥9፥10
14፥9 ራእ13፥12፥ 14፥16
14፥10 ኢሳ51፥17፤ ኤር25፥15፤51፥7፤ ራእ9፥17፤18፥6
14፥11 ቈላ9፤ኢሳ34፥10፤ ራእ4፥8፤13፥12፥ 17፤19፥3
14፥12 ዮሐ14፥15፤ ዕብ6፥12፤ራእ13፥10
14፥13 1ቆሮ15፥18፤ 1ተሰ4፥16፤ራእ2፥7፤ 22፥17

አራቱ ሺህ ሰዎች ነበሩ፡፡ 2ከሰማይ እንደ ብዙ
ውሃ ድምፅና እንደ ታላቅ ነጐድጓድ
ድምፅ የመሰለ ድምፅ ሰማሁ፤ የሰማሁት
ድምፅ በገና ደርዳሪዎች እንደሚደረድሩት
ዐይነት ነበረ፡፡ 3እነርሱም በዙፋኑ ፊት፣
በአራቱ ሕያዋን ፍጡራንና በሽማግሌዎቹ
ፊት አዲስ መዝሙር ዘመሩ፡፡ ከምድር ከተ
ዋጁት ከመቶ አርባ አራቱ ሺህ ሰዎች
በስተቀር መዝሙሩን ማንም ሊማረው አል
ቻለም፡፡ 4እነዚህ ራሳቸውን በሴቶች ያላ
ረከሱት ናቸው፤ ራሳቸውን በንጽሕና ጠብ
ቀዋልና፡፡ በጉ ወደ ሚሄድበት ሁሉ ይከተ
ሉታል፤ ለእግዚአብሔርና ለበጉ በኵራት እን
ዲሆኑ ከሰዎች መካከል የተዋጁ ናቸው፡፡
5በአፋቸው ምንም ዐይነት ውሸት አልተገ
ኘም፤ ነቀፋም የለባቸውም፡፡

## ሦስቱ መላእክት

6ከዚያም ሌላ መልአክ በሰማይ መካ
ከል ሲበር አየሁ፤ እርሱም በምድር ላይ
ለሚኖሩ ለሕዝብ፣ ለነገድ፣ ለቋንቋና ለወ
ገን ሁሉ የሚሰብከውን የዘላለም ወንጌል
ይዞ ነበር፤ 7በታላቅ ድምፅም፣ “እግዚአብሔርን
ፍሩ፤ ክብርም ስጡት፤ ምክንያቱም የፍርዱ
ሰዓት ደርሶአል፤ ሰማይንና ምድርን፣ ባሕ
ርንና የውሃ ምንጮችን ለፈጠረው ስገዱ”
አለ፡፡
8ሌላም ሁለተኛ መልአክ፣ “ሕዝቦች ሁሉ
የዝሙቷን ቍጣ ወይን ጠጅ እንዲጠጡ
ያደረገች ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች! ወደ
ቀች!” እያለ ተከተለው፡፡
9ሦስተኛውም መልአክ በታላቅ ድምፅ
እን ዲህ እያለ ተከተላቸው፤ “ማንም
ለአውሬ ውና ለምስሉ የሚሰግድ፣
ምልክቱንም በግ ምባሩ ወይም በእጁ ላይ
የሚቀበል ቢኖር፣ 10እርሱ ደግሞ ምንም
ነገር ሳይቀላቀልበት በቍጣው ጽዋ ውስጥ
የተሞላውን የእግዚአብሔ ርን ቍጣ ወይን ጠ
ጅ ይጠጣል፡፡ በቅዱሳን መላእክትና በበጉ
ፊትም በእሳትና በዲን ይሠቃያል፡፡
11የሥቃያቸውም ጢስ ከዘላለም እስከ
ዘላለም ወደ ላይ ይወጣል፡፡ ለአው ሬውና
ለምስሉ የሚሰግዱ ወይም የስሙ ን ም
ምልክት የሚቀበሉ ሁሉ ቀንና
ሌሊት ዕረፍት የላቸውም፡፡” 12የእግዚአብሔርን
ትእዛዛት የሚጠብቁና ለኢየሱስም ታማኝ
ሆነው በትዕግሥት የሚጸኑ ቅዱሳን የሚ
ታወቁት በዚህ ነው፡፡
13ከዚያም፣ “ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ
ሆነው የሚሞቱ ብፁዓን ናቸው ብለህ ጻፍ”
የሚል ድምፅ ከሰማይ ሰማሁ፡፡

[ʼ]8 *ወይም ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ስሞቻቸው በታረደው በግ የሕይወት መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈው*

[ˀ]10 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *የሚገደል* ይላሉ፡፡

መንፈስም፣ “አዎ፣ ሥራቸው ስለሚከተ
ላቸው ከድካማቸው ያርፋሉ” ይላል።

## የምድር መከር ጊዜ

14አየሁም፤ እነሆ፤ በፊቴ ነጭ ደመና
ነበረ፤ በደመናውም ላይ፣ “የሰውን ልጅ
የሚ መስል” ተቀምጦ ነበር፤ እርሱም
በራሱ ላይ የወርቅ አክሊል ደፍቶ፣ በእጁ
ም ስለ ታም ማጭድ ይዞ ነበር። 15ሌላም
መል አክ ከመቅደሱ ወጥቶ በደመናው ላይ
ለተ ቀመጠው፣ “የዐጨዳው ሰዓት ስለ
ደረሰ፣ ማጭድህን ይዘህ ዕጨድ፤ የምድር
መከር ደርሶአልና” ሲል በታላቅ ድምፅ
ጮኸ። 16ስለዚህ በደመናው ላይ የተቀመጠ
ው ማጭ ዱን ወደ ምድር ሰደደ፤
ምድርም ታጨ ደች።
17ሌላም መልአክ በሰማይ ካለው መቅ
ደስ ወጣ፤ እርሱም እንዲሁ ስለታም
ማጭድ ነበረው፤ 18በእሳት ላይ ሥልጣን
ያለው ሌላ መልአክ ከመሠዊያው ወጥቶ
ስለታም ማጭድ የያዘውን፣ “ዘለላው ስለ
በሰለ፣ ስለታም ማጭድህን ያዝና በምድር
ላይ ያሉትን የወይን ዘለላዎች ሰብስብ”
ሲል በታላቅ ድምፅ ጮኸ። 19መልአኩም
ማጭ ዱን ወደ ምድር ሰደደ፤ የምድርን
የወይን ዘለላዎች ሰብስቦ ወደ ታላቁ ወደ
እግዚአ ብሔር የቍጣ ወይን መጭመቂያ
ጣላቸው። 20ወይኑም ከከተማው ውጭ
በወይን መጭ መቂያ ውስጥ ተረገጠ፤
ከፍታው እስከ ፈረስ ልጓም የሚደርስ፣
ርዝመቱ ሦስት መቶ ኪሎ ሜትር ያህል
ደም ከመጭመ ቂያው ወጣ።

## ሰባቱ መላእክትና ሰባቱ መቅሠፍቶች

15 ሌላም ታላቅና አስደናቂ ምልክት
በሰማይ አየሁ፤ የመጨረሻዎቹን
ሰባት መቅሠፍቶች የያዙ ሰባት መላእክት
አየሁ፤ የመጨረሻ የተባሉትም የእግዚአብሔር
ቍጣ የሚፈጸመው በእርሱ በመሆኑ
ነው። 2ከእሳት ጋር የተቀላቀለ የብርጭቆ
ባሕር የሚመስል አየሁ፤ በባሕሩም አጠ
ገብ አው ሬውን፣ ምስሉንና የስሙን
ቍጥር ድል የነሡትን ቆመው አየሁ፤
እነርሱም ከእግዚአ ብሔር የተሰጣቸውን
በገና ይዘው፣ 3የእግዚአ ብሔር ባሪያ
የሆነውን የሙሴን መዝሙርና የበጉን
መዝሙር እንዲህ እያሉ ይዘምሩ ነበር፤

“ሁሉን ቻይ ጌታ አምላክ ሆይ፤
ሥራህ ታላቅና አስደናቂ ነው።
የዘመናት[ኣ] ንጉሥ ሆይ፤
መንገድህ ጽድቅና እውነት ነው።
4ጌታ ሆይ፤ አንተን የማይፈራ፣
ስምህን የማያከብርስ ማን ነው?

14፥14 ዳን7፥13፤ ማቴ17፥5፤ራእ1፥13፤ 6፥2
14፥15 ቍ17፡18፤ ኤር51፥33፤ኢል3፥13፤ ማር4፥29፤ራእ11፥19
14፥17 ቍ15
14፥18 ቍ15፤ ራእ6፥9፤ 8፥5፤16፥7
14፥19 ራእ19፥15
14፥20 ቍ19፤ ዘፍ49፥11፤ዘዳ32፥14፤ ኢሳ63፥3፤ኢል3፥13፤ ዕብ13፥12፤ራእ11፥8፤ 19፥15
15፥1 ቍ6-8፤ ዘሌ26፥21፤ ራእ9፥20፤12፥1፡3፤
15፥2 ራእ4፥6፤5፥8፤ 12፥11፤13፥1፡14፡17፤ 14፥2
15፥3 ዘፀ15፥1፤ ኢሱ1፥1፤መዝ112፥2፤ 145፥17፤ራእ1፥8፤5፥9
15፥4 መዝ86፥9፤ ኢሳ66፥23፤ኤር10፥7፤ ራእ19፥8
15፥5 ዘፀ38፥21፤ ዘኍ1፥50፤ማቴ3፥16፤ ራእ11፥19
15፥6 ቍ1፤ሕዝ9፥2፤ ዳን10፥5፤ራእ1፥13፤ 14፥15
15፥7 ቍ1፤ራእ1፥18፤ 4፥6
15፥8 ዘፀ40፥34፡ 35፤1ነገ8፥10፡11፤ 2ዜና5፥13፡14፤ኢሳ6፥4
16፥1 ቍ2-21፤ መዝ79፥6፤ሶፎ3፥8፤ራ እ11፥19፤15፥1
16፥2 ቍ11፤ ዘፀ9፥9-11፤ዘዳ28፥35፤ ራእ8፥7፤13፥15-17፤ 14፥9
16፥3 ዘፀ7፥17-21፤ ራእ8፥8፡9፤11፥6
16፥4 ዘፀ7፥17-21፤ ራእ8፥10
16፥5 ራእ1፥4፤6፥10፤ 15፥3፡4
16፥6 ኢሳ49፥26፤ ሉቃ11፥49-51፤ ራእ1፥8፤6፥9፤14፥18፤ 15፥3፤19፥2

አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና።
የጽድቅ ሥራህ ስለ ተገለጠ፣
ሕዝቦች ሁሉ ይመጣሉ፤
በፊትህም ይሰግዳሉ።

5ከዚህ በኋላም አየሁ፤ በሰማይ ያለው
ቤተ መቅደስ፣ ይኸውም የምስክሩ ድን
ኳን ተከፍቶ ነበር፤ 6ሰባቱን መቅሠፍቶች
የያዙት ሰባቱ መላእክት ከቤተ መቅደሱ
ወጡ፤ እነርሱም ከተልባ እግር የተሠራ
ንጹሕ የሚያበራ ልብስ ለብሰው፣ ደረታቸ
ውንም በወርቅ መታጠቂያ ታጥቀው ነበር።
7ከዚያም ከአራቱ ሕያዋን ፍጡራን አንዱ
ከዘላለም እስከ ዘላለም በሚኖረው አምላክ
ቍጣ የተሞሉትን ሰባት የወርቅ ጽዋዎች
ለሰባቱ መላእክት ሰጣቸው። 8ቤተ መቅደ
ሱም ከእግዚአብሔር ክብር፣ ከኀይሉም በወ
ጣው ጢስ ተሞላ፤ የሰባቱ መላእክት ሰባት
መቅሠፍቶች እስኪፈጸሙ ድረስ ማንም ወደ
ቤተ መቅደሱ መግባት አልቻለም።

## ሰባቱ የእግዚአብሔር ቍጣ ጽዋዎች

16 ከዚያም ለሰባቱ መላእክት፣ “ሂዱ፤
ሰባቱን የእግዚአብሔር ቍጣ
ጽዋ ዎች በምድር ላይ አፍስሱ” የሚል
ታላቅ ድምፅ ከቤተ መቅደሱ ሰማሁ።
2የመጀመሪያው መልአክ ሄዶ ጽዋውን
በምድር ላይ አፈሰሰ፤ የአውሬውን ምል
ክት በተቀበሉትና ለምስሉም በሰገዱት
ሰዎች ላይ ክፉኛ የሚያሠቃይ ቍስል
ወጣባቸው።
3ሁለተኛው መልአክ ጽዋውን በባሕር
ላይ አፈሰሰ፤ ባሕሩም እንደ ሞተ ሰው
ደም ሆነ፤ በባሕሩ ውስጥ የሚኖሩ ሕይ
ወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ ሞቱ።
4ሦስተኛው መልአክ ጽዋውን በወንዞ
ችና በውሃ ምንጮች ላይ አፈሰሰ፤ እነርሱም
ደም ሆኑ። 5ከዚያም በውሆች ላይ
ሥል
ጣን ያለው መልአክ እንዲህ ሲል ሰማሁ፤

“ያለህና የነበርህ ቅዱሱ ሆይ፤
እንዲህ ስለ ፈረድህ፣
አንተ ጻድቅ ነህ፤
6የቅዱሳንንና የነቢያትን ደም ስላፈሰሱ፣
አንተም ደግሞ ደም እንዲጠጡ
አደረግሃቸው፤ ይህ የሚገባቸው
ነውና።”

7እንዲሁም ከመሠዊያው እንዲህ የሚል
ድምፅ ሰማሁ፤

“አዎን፤ ሁሉን ቻይ ጌታ አምላክ ሆይ፤
ፍርድህ እውነትና ጽድቅ ነው”

[ኣ]3 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ሕዝቦች ይላሉ።

8አራተኛውም መልአክ ጽዋውን በፀ
ሓይ ላይ አፈሰሰ፤ ፀሓይም ሰዎችን በእ
ሳት እንድታቃጥል ኀይል ተሰጣት። 9እነ
ርሱም በታላቅ ሐሩር ተቃጠሉ፤ በእነዚ
ህም መቅሠፍቶች ላይ ሥልጣን ያለውን
የእግዚአብሔርን ስም ተሳደቡ እንጂ ንስሓ
አልገቡም፤ ክብርም አልሰጡትም።
10አምስተኛውም መልአክ ጽዋውን በአ
ውሬው ዙፋን ላይ አፈሰሰ፤ የአውሬውም
መንግሥት በጨለማ ተዋጠ፤ ሰዎችም
ከሥቃያቸው የተነሣ ምላሳቸውን ደኩ
ነበር፤ 11ደግሞም ከሥቃያቸውና ከቊስላ
ቸው የተነሣ የሰማይን አምላክ ተሳደቡ
እንጂ ከሥራቸው ንስሓ አልገቡም።
12ስድስተኛውም መልአክ ጽዋውን በታ
ላቁ ወንዝ በኤፍራጥስ ላይ አፈሰሰ፤ ከም
ሥራቅ ለሚመጡ ነገሥታት መንገድ እን
ዲዘጋጅላቸው የወንዙ ውሃ ደረቀ። 13ከዚ
ያም ከዘንዶው አፍ፣ ከአውሬው አፍና ከሐ
ሰተኛው ነቢይ አፍ እንቊራሪት የሚመ
ስሉ ሦስት ርኩሳን መናፍስት ሲወጡ አየሁ።
14እነርሱም ምልክቶች የሚያደርጉ የአጋን
ንት መናፍስት ናቸው፤ ሁሉን በሚ
ችል አምላክ ታላቅ ቀን ለሚሆነው
ጦርነት እንዲሰበስቧቸው ወደ ዓለም ሁሉ
ነገሥ ታት ይሄዳሉ።
15“እነሆ፤ እንደ ሌባ እመጣለሁ፤ ዕራ
ቊቱን እንዳይሆን ኀፍረቱም እንዳይታይ
ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ ሰው ብፁዕ ነው።”
16እነርሱም ነገሥታቱን በዕብራይስጥ አር
ማጌዶን በሚባል ስፍራ ሰበሰቧቸው።
17ሰባተኛውም መልአክ ጽዋውን በአየር
ላይ አፈሰሰ፤ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ካለው
ዙፋን “ተፈጸመ” የሚል ታላቅ ድምፅ
ወጣ። 18ከዚያም መብረቅ፣ ድምፅ፣
ነጐድጓድና ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤
ሰው በም ድር ላይ ከተፈጠረ ጀምሮ
እንዲህ ያለ ታላቅ የምድር መናወጥ
ታይቶ አይታወ ቅም፤ ነውጡም እጅግ
ታላቅ ነበር። 19ታላ ቂቱ ከተማ ከሦስት
ተከፈለች፤ የሕዝቦች ከተሞችም ፈራረሱ፤
እግዚአብሔርም ታላቂ ቱን ባቢሎን
አስታወሰ፤ በብርቱ ቍጣው ወይን ጠጅ
የተሞላውን ጽዋ ሰጣት። 20ደሴ ቶች ሁሉ
ሸሹ፤ ተራሮችም ሊገኙ አልቻ ሉም።
21በሚዛን ሲመዘን እያንዳንዱ አርባ አምስት
ኪሎ ግራም የሚሆን ታላቅ በረዶ በሰዎች
ላይ ከሰማይ ወረደባቸው፤ መቅሠ ፍቱ
እጅግ አሠቃቂ ስለ ነበር፣ ሰዎቹ ከበ
ረዶው መቅሠፍት የተነሣ እግዚአብሔርን
ተሳደቡ።

## በአውሬው ላይ የተቀመጠችው ሴት

17 ሰባቱን ጽዋዎች ከያዙት ከሰባቱ
መላእክት አንዱ መጥቶ እንዲህ
አለኝ፤ “ና፤ በብዙ ውሆች ላይ የተቀመጠ
ችውን የታላቂቱን አመንዝራ ፍርድ አሳ
ይሃለሁ። 2የምድር ነገሥታት ከእርሷ ጋር
አመነዘሩ፤ የምድር ነዋሪዎችም በዝሙቷ
የወይን ጠጅ ሰከሩ።”
3ቀጥሎም መልአኩ በመንፈስ ወደ
በረሓ ወሰደኝ፤ በዚያም አንዲት ሴት
በስድብ ስሞች በተሞላ፣ ሰባት ራ
ሶችና ዐሥር ቀን ዶች ባሉት ቀይ አውሬ
ላይ ተቀምጣ አየሁ። 4ሴቲቱም ሐምራ
ዊና ቀይ ልብስ ተጐናጽፋ ነበር፤ ደግሞም
በወርቅ፣ በከበሩ ድንጋዮችና በዕንቆቶችም
አጊጣ ነበር፤ በእ ጇም የሚያስጸይፍ
ነገርና የዝሙቷ ርኵ ሰት የሞላበትን
የወርቅ ጽዋ ይዛ ነበር። 5በግምባሯም
ላይ እንዲህ የሚል የምስ
ጢር ስም ተጽፎ ነበር፤

*ታላቂቱ ባቢሎን፣*
*የአመንዝሮችና*
*የምድር ርኵሰቶች እናት።*

6ሴቲቱንም በቅዱሳን ደምና በኢየሱስ
ምስክሮች ደም ሰክራ አየኋት።
ባየኋትም ጊዜ እጅግ ተደነቅሁ። 7ከዚ
ያም መልአኩ እንዲህ አለኝ፤ የምትደነ
ቀው ለምንድን ነው? የሴቲቱን፣ እርሷ
የተቀመጠችበትንም፣ እንዲሁም ሰባት
ራሶችና ዐሥር ቀንዶች ያሉትን የአውሬ
ውን ምስጢር እነግርሃለሁ። 8ያየኸው አውሬ
ቀደም ሲል ነበረ፤ አሁን ግን የለም፤ በኋ
ላም ከጥልቁ ጕድጓድ ይወጣል፤ ወደ ጥፋ
ቱም ይሄዳል። ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ
ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ ተጽፎ ያል
ተገኘ የምድር ነዋሪዎች አውሬው ቀድሞ
የነበረ፣ አሁን ግን የሌለ፣ በኋላም የሚ
መጣ መሆኑን ሲያዩ ይደነቃሉ።
9“ይህም፣ ጥበብ ያለው አእምሮ ይጠ
ይቃል። ሰባቱ ራሶች ሴቲቱ የምትቀመ
ጥባቸው ሰባት ተራሮች ናቸው፤ 10እነር
ሱም ደግሞ ሰባት ነገሥታት ናቸው።
አምስቱ ወድቀዋል፤ አንዱ አለ፤ ሌላውም
ገና አልመጣም፤ ሲመጣ ግን ሊቈይ የሚ
ገባው ለጥቂት ጊዜ ነው። 11ቀድሞ የነበረ
ውና አሁን የሌለው አውሬ ስምንተኛው
ንጉሥ ነው፤ እርሱም ከሰባቱ አንዱ ሲሆን
ወደ ጥፋቱ ይሄዳል።
12“ያየሃቸው ዐሥሩ ቀንዶች ገና መን
ግሥትን ያልተቀበሉ፣ ዐሥር ነገሥታት
ናቸው፤ ነገር ግን ከአውሬው ጋር ለአንድ

16÷8 ራእ6÷12፤ 8÷12፤14÷18
16÷9 ቊ11፡21፤ ራእ2÷21፤11÷13
16÷10 ዘፀ10÷21-23፤ ኢሳ8÷22፤ራእ8÷12፤ 9÷2፤13÷2
16÷11 ቊ2፡9፡21፤ ራእ2÷21፤11÷13
16÷12 ኢሳ11÷15፡ 16፤41÷2፤46÷11፤ ራእ9÷14
16÷13 ዘፀ8÷6፤ራእ 12÷3፤13÷1፤ 8÷2፤19÷20፤20÷10
16÷14 ማቴ24÷14፡24፤ 1ጢሞ4÷1፤ 6÷17፤17÷14፤19÷19፤ 20÷8
16÷15 ሉቃ12÷37፡ 39፤ራእ3÷18
16÷16 ቊ14፤መሳ 5÷19፤2ነገ23÷29፡29፡ 30፤ዘካ12÷11፤ራእ 9÷11
16÷17 ኤፌ2÷2፤ ራእ11÷15፤14÷15፤21÷6
16÷18 ዳን12÷1፤ ማቴ24÷21፤ ራእ4÷5፤6÷12
16÷19 ራእ14÷8፡ 10፤17÷18፤18÷5
16÷20 ራእ6÷14
16÷21 ቊ9፡11፤ ዘፀ9÷23-25፤ሕዝ 13÷13፤ 38÷22፤ ራእ8÷7፤11÷19
17÷1 ቊ5፡15፡16፤ ኢሳ23÷17፤ ኤር51÷13፤ራእ15÷1፡ 7፤16÷19፤ራእ19÷2
17÷2 ራእ14÷8
17÷3 ራእ1÷10፤ 12÷3፡6፡14፤13÷1፤ 18÷12፡16
17÷4 ቊ2፤ኤር51÷7፤ ሕዝ28÷13፤ራእ14÷8፤ 18÷6፡16
17÷5 ቊ1፡2፡7፤ ራእ14÷8
17÷6 ራእ16÷6፤ 18÷24
17÷7 ቊ3፡5፤ ራእ12÷3
17÷8 ሉቃ÷31፤ ራእ3÷10፤13÷3፡10፤ 20÷12
17÷9 ቊ3፤ራእ13÷18
17÷11 ቊ8
17÷12 ራእ12÷3፤ 18÷10፡17፡19

ሰዓት እንዲነግሡ ሥልጣን ይቀበላሉ::
13አንድ ሐሳብም አላቸው፤ ኀይላቸውንና
ሥልጣናቸውንም ለአውሬው ይሰጣሉ፤ 14እነ
ዚህ በጉን ይወጋሉ፤ በጉ ግን ድል ይነሣቸ
ዋል፤ ምክንያቱም እርሱ የጌቶች ጌታና
የነገሥታት ንጉሥ ነው፤ ከእርሱ ጋር ያሉ
የተጠሩት፣ የተመረጡትና የታመኑትም
አብረው ድል ይነሣሉ::”
15መልአኩም እንዲህ አለኝ፤ “አመንዝ
ራዪቱ ተቀምጣባቸው ያየሃቸው ውሆች:-
ወገኖች፣ ብዙ ሰዎች፣ ሕዝቦችና ቋንቋ
ዎች ናቸው:: 16አውሬውና ያየሃቸው ዐሥሩ
ቀንዶች አመንዝራዪቱን ይጠሏታል፤ ባዶ
ዋንና ዕራቍቷን ያስቀሯታል:: ሥጋዋን
ይበላሉ፤ በእሳትም ያቃጥሏታል:: 17የእግዚአ
ብሔር ቃል እስኪፈጸም ድረስ ዕቅዱን እን
ዲፈጽሙ፣ ደግሞም በአንድ ሐሳብ እንዲ
ስማሙና ሥልጣናቸውንም ለአውሬው እን
ዲሰጡ ይህን ሐሳብ በልባቸው ያኖረ እግዚ
አብሔር ነውና:: 18ያየሃትም ሴት በምድር
ነገሥታት ላይ የምትነግሥ ታላቂቱ ከተማ
ናት::

## የባቢሎን ውድቀት

18 ከዚህ በኋላ ታላቅ ሥልጣን ያለው
ሌላ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ
አየሁ፤ ከክብሩም ነጸብራቅ የተነሣ ምድር
በራች፤ 2እርሱም በብርቱ ድምፅ እንዲህ
ብሎ ጮኸ፤

“ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች! ወደቀች!
የአጋንንት መኖሪያ፣
የርኩሳን መናፍስት ሁሉ መጠጊያ[ከ]፣
የርኩስና የአስጸያፊ ወፎች ሁሉ
መጠለያ[ከ] ሆነች::
3ሕዝቦች ሁሉ የዝሙቷን ቍጣ ወይን
ጠጅ ጠጥተዋልና፤
የምድር ነገሥታት ከእርሷ ጋር
አመንዝረዋል፤
የምድርም ነጋዴዎች ከብዙ ምቾቷ ኀይል
የተነሣ በልጽገዋል::”

4ከዚያም ከሰማይ ሌላ ድምፅ እንዲህ ሲል
ሰማሁ፤
“ሕዝቤ ሆይ፤ በኀጢአቷ እንዳትተባበሩ፣
ከመቅሠፍቷም እንዳትካፈሉ፣
ከእርሷ ውጡ፤
5ኀጢአቷ እስከ ሰማይ ድረስ
ተከምሮአልና፤
እግዚአብሔርም ዐመፃዋን አስታውሶአል::
6በሰጠችው መጠን ብድራቷን መልሱላት፤
ለሠራችው ሁሉ ዕጥፍ ክፈሏት፤
በቀላቀለችውም ጽዋ ዕጥፍ አድርጋችሁ
ቀላቅሉባት::
7ለራሷ ክብርና ምቾት የሰጠችውን ያህል፣

17፥13 ቊ17
17፥14 ማቴ22፥14፤ ዮሐ16፥33፤ 1ጢሞ6፥15፤ራእ16፥14
17፥15 ቊ1፤ ኢሳ8፥7፤ኤር47፥2፤ ራእ13፥7
17፥16 ቊ1፤ሕዝ16፥37፡39፤ራእ12፥3፤18፥8፡17፡19፤19፥18
17፥17 ቊ13፤ ኤር39፥16፤2ቆሮ8፥16፤ ራእ10፥7
17፥18 ራእ16፥19፤ 18፥10፡18፡19፡21
18፥1 ሕዝ43፥2፤ ራእ10፥1፤17፥1፤20፥1
18፥2 ኢሳ13፥21፡22፤34፥11፡13-15፤ ኤር50፥39፤51፥37፤ ሶፎ2፥14፡15፡23፤ ሕዝ27፥9-25፤ ራእ14፥8፤17፥2
18፥3 ቊ7፡9፡11፡15፡23፤ሕዝ27፥9-25፤ ራእ14፥8፤17፥2
18፥4 ዘፍ19፥15፤ ኢሳ48፥20፤ ኤር50፥8፤52፥6፡9፡45፤2ቆሮ6፥17
18፥5 2ዜና28፥9፡ ዕዝ9፥6፤ኤር51፥9፤ ራእ16፥19
18፥6 መዝ137፥8፤ ኢሳ40፥2፤ኤር50፥15፡29፤ራእ14፥10፤16፥19፤17፥4
18፥7 መዝ10፥6፤ ኢሳ47፥7፡8፤ ሕዝ28፥2-8፤ ሶፎ2፥15
18፥8 ቊ10፤ ኢሳ9፥14፤47፥9፤ ኤር50፥31፡32፤ ራእ17፥16
18፥9 ቊ3፡7፡18፤ ኤር51፥8፤ኤር51፥8፤ ሕዝ26፥17፡18፤ ራእ14፥8፡11፤17፥2፡4፤19፥3
18፥10 ቊ15፡16፡17፡19፤ራእ17፥12
18፥11 ቊ3፡15፡19፤ሕዝ27፥27፡31
18፥12 ሕዝ27፥12-22፤ ራእ17
18፥13 ሕዝ27፥13፤ 1ጢሞ1፥10
18፥15 ቊ3፡10፡11፡17፡19፤ ዝ27፥31
18፥16 ቊ10፡19፤ራእ17፥4
18፥17 ቊ10፡15፤ ሕዝ27፥28-30፤ ራእ17፥12፡16

ሥቃይና ሐዘን ስጧት፤
በልቧም እንዲህ እያለች ትመካለች፤
“እንደ ንግሥት ተቀምጫለሁ፤
መበለትም አይደለሁም፤ ከቶም
አላዝንም፤”
8ስለዚህ መቅሠፍቶቿ በአንድ ቀን
ይመጡባታል፤
ሞት፣ ሐዘንና ራብ ይሆኑባታል፤
የሚፈርድባት ጌታ እግዚአብሔር ብርቱ
ስለ ሆነ፣
በእሳት ትቃጠላለች::

9“ከእርሷ ጋር ያመነዘሩና በምቾት የኖሩ
የምድር ነገሥታት፣ እርሷ ስትቃጠል የሚ
ወጣውን ጢስ ሲያዩ ስለ እርሷ ያለቅሳሉ፤
ያዝናሉም:: 10ሥቃይዋንም በመፍራት በሩቅ
ቆመው እንዲህ ይላሉ፤

“አንቺ ታላቂቱ ከተማ ወዮልሽ!
ወዮልሽ!”
አንቺ ባቢሎን ብርቱዪቱ ከተማ፣
ፍርድሽ በአንድ ሰዓት ውስጥ
መጥቶአል::”

11“ጭነታቸውን ከእንግዲህ የሚገዛ ስለ
ሌለ፣ የምድር ነጋዴዎችም ስለ እርሷ ያለ
ቅሳሉ፤ ያዝናሉ፤ 12ጭነቱም:- ወርቅ፣ ብር፣
የከበረ ድንጋይ፣ ዕንቍ፣ ከተልባ እግር
የተሠራ ቀጭን ልብስ፣ ሐምራዊ ልብስ፣ ሐ
ር ልብስ፣ ቀይ ልብስ፣ መልካም ሽታ
ያለው
ዕንጨት ሁሉ፣ ከዝሆን ጥርስ፣ ከውድ ዕን
ጨት፣ ከናስ፣ ከብረትና ከእብነ በረድ
የተሠራ ዕቃ ሁሉ፣ 13ቀረፋ፣ ቅመም፣
ከርቤ፣ ቅባት፣ ዕጣን፣ የወይን ጠጅ፣
የወይራ ዘይት፣ የተሰለቀ ዱቄት፣ ስንዴ፣
ከብቶች፣ በጎች፣ ፈረሶች፣ ሠረገሎች፣
እንዲሁም ባሮችና[ኸ] የሰዎች ነፍሶች ነው::
14“እነርሱም፣ “የተመኘሽው ፍሬ
ከአንቺ ርቆአል፤ ብልጽግናሽና ክብርሽ
ሁሉ ጠፍ ቶአል፤ ዳግመኛም ተመልሶ
አይመጣም” ይላሉ:: 15እነዚህን ነገሮች
በመሸጥ በእርሷ የበለጸጉ ነጋዴዎች
ሥቃይዋን ፈርተው በሩቅ ይቆማሉ፤
እነርሱም ያለቅሳሉ፤ ያዝናሉም፤
16ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲህ
ይላሉ፤

“ቀጭን የተልባ እግር፣ ሐምራዊና ቀይ
ልብስ የለበሰች፣
በወርቅ፣ በከበረ ድንጋይና በዕንቍም
ያጌጠች፣
ታላቂቱ ከተማ ወዮላት! ወዮላት!
17ያ ሁሉ ሀብት በአንድ ሰዓት ውስጥ
ጠፋ::”

[ከ]2 ግሪኩ *እስር ቤት ወይም ወህኒ* ይላል::
[ኸ]13 ግሪኩ *እንዲሁም ሰውነቶችና የሰዎች ነፍሶች* ይላል::

"የመርከብ አዛዦች ሁሉ፣ በመርከብ
የሚጓዙ መንገደኞች ሁሉ፣ የመርከብ ሠራ
ተኞችና ኑሮአቸውን በባሕር ላይ የመሠ
ረቱ ሁሉ በሩቅ ይቆማሉ። 18እርሷ ስት
ቃጠል የሚወጣውን ጢስ ሲያዩ፣ 'እንደዚች
ያለ ታላቅ ከተማ ከቶ የት አለ?' እያሉ
ይጮኻሉ። 19በራሳቸውም ላይ አቧራ ነስን
ሰው እያለቀሱና እያዘኑ እንዲህ ብለው
ጮኹ፤

" 'በባሕር ላይ መርከቦች ያላቸው ሁሉ፣
በእርሷም ሀብት የበለጸጉ፣
ለታላቂቱ ከተማ ወዮላት! ወዮላት!
በአንድ ሰዓት ውስጥ ጠፍታለች።
20ሰማይ ሆይ፤ በእርሷ ላይ ሐሤት
አድርግ፤
ቅዱሳን፣ ሐዋርያትና ነቢያትም ሐሤት
አድርጉ፤
በእናንተ ላይ ባደረሰችው ነገር
እግዚአብሔር ፈርዶባታልና።' "

21ከዚያም አንድ ብርቱ መልአክ፣ ትልቅ
የወፍጮ ድንጋይ የሚመስል ድንጋይ አን
ሥቶ ወደ ባሕር ወረወረው፤ እንዲህም አለ፤

"ታላቂቱ ከተማ ባቢሎን፣
እንዲህ ባለ ኀይል ትወረወራለች፤
ተመልሳም አትገኝም።
22የበገና ደርዳሪዎችና የሙዚቀኞች
ድምፅ፣
የዋሽንትና የመለከት ነፊዎች ድምፅ፣
ዳግመኛ በአንቺ ውስጥ አይሰማም፤
የእጅ ጥበብ ባለሙያ፣
ዳግመኛ በአንቺ ውስጥ አይገኝም፤
የወፍጮ ድምፅም፣
ዳግመኛ በአንቺ ውስጥ አይሰማም።
23የመብራት ብርሃን፣
ዳግመኛ በአንቺ ውስጥ አይበራም፤
የሙሽራውና የሙሽራዪቱ ድምፅ፣
ዳግመኛ በአንቺ ውስጥ አይሰማም፤
ነጋዴዎችሽ የዓለም ታላላቅ ሰዎች ነበሩ፤
በአስማትሽም ሕዝቦች ሁሉ ስተዋል።
24በእርሷም ውስጥ የነቢያትና የቅዱሳን፣
በምድርም የተገደሉት ሁሉ ደም ተገኘ።"

## ሃሌ ሉያ

# 19

"ከዚህ በኋላ የብዙ ሰዎችን ድምፅ
የሚመስል ታላቅ ድምፅ በሰማይ
እንዲህ ሲል ሰማሁ፤

ሃሌ ሉያ!
ማዳን፣ ክብርና ኀይል የአምላካችን
ነው፤
2ፍርዱ እውነትና ጽድቅ ነውና፤
በዝሙቷ ምድርን ያረከሰችውን፣
ታላቂቱን አመንዝራ ፈርዶባታል፤
ስለ አገልጋዮቹም ደም ተበቅሏታል።"
3ደግሞም እንዲህ አሉ፤
"ሃሌ ሉያ!
ጢስ ከእርሷ ከዘላለም እስከ ዘላለም
ይወጣል።"

4ሃያ አራቱ ሽማግሌዎችና አራቱ ሕያ
ዋን ፍጡራን በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው
አምላክ ወድቀው ሰገዱ፤ እንዲህም አሉ፤
"አሜን፣ ሃሌ ሉያ!"

5ከዚህ በኋላ እንዲህ የሚል ድምፅ ከዙ
ፋኑ ወጣ፤

"እናንተ አገልጋዮቹ ሁሉ፣
እርሱን የምትፈሩ፣
ታናናሾችና ታላላቆችም፣
አምላካችንን አመስግኑ!"
6ደግሞም እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ፣
እንደ ኀይለኛ ወራጅ ውሃ ድምፅ፣ እንደ
ብርቱም ነጐድጓድ ድምፅ የሚመስል እን
ዲህ ሲል ሰማሁ፤

ሃሌ ሉያ!
ሁሉን ቻይ ጌታ አምላካችን
ነግሦአልና።
7የበጉ ሰርግ ስለ ደረሰ፣
የእርሱም ሙሽራ ራሷን ስላዘጋጀች፣
ደስ ይበለን፤ ሐሤት እናድርግ
ክብርም እንስጠው።
8የሚያንጸባርቅና ንጹሕ፣
ከተልባ እግር የተሠራ ቀጭን ልብስ
እንድትለብስ ተሰጣት።"
ከተልባ እግር የተሠራው ቀጭን ልብስ
የቅዱሳን የጽድቅ ሥራ ነው።

9መልአኩም፣ " 'ወደ በጉ ሰርግ እራት
የተጠሩ ብፁዓን ናቸው' ብለህ ጻፍ" አለኝ፤
ቀጥሎም፣ "እነዚህ የእግዚአብሔር እውነተኛ
ቃሎች ናቸው" አለኝ።
10እኔም ልሰግድለት በእግሩ ሥር ተደ
ፋሁ፤ እርሱ ግን፣ "ተው! ይህን አታድ
ርግ! እኔም ከአንተና የኢየሱስን ምስክር
ከያዙት ወንድሞችህ ጋር አገልጋይ ነኝ፤
ለእግዚአብሔር ስገድ፤ የኢየሱስ ምስክር የት
ንቢት መንፈስ ነውና" አለኝ።

## በነጭ ፈረስ ላይ የተቀመጠው

11ከዚያም ሰማይም ተከፍቶ አየሁ፤ እነሆ
አንድ ነጭ ፈረስ ነበረ፤ በፈረሱም ላይ፣
"ታማኝና እውነተኛ" የሚባል ተቀምጦ ነበር፤
እርሱም በጽድቅ ይፈርዳል፤ ይዋጋልም።
12ዐይኖቹ እንደ እሳት ነበልባል ናቸው፤
በራሱም ላይ ብዙ ዘውዶች አሉ። ከእርሱ
በቀር ማንም የማያውቀው ስም በእርሱ
ላይ ተጽፎአል። 13እርሱ በደም የተነከረ

18፥18 ቍ9፤ ሕዝ27፥32፤ ራእ13፥4፤17፥18፤19፥3
18፥19 ቍ10፡11፡15፡16፤ኢሱ7፥6፤ ሰቆ2፥10፤ሕዝ27፥30፡31፤ራእ17፥16፡18
18፥20 ኤር51፥48፤ ራእ12፥12፤19፥2
18፥21 ኤር51፥63፤ ራእ5፥2፤10፥1፤ 17፥18
18፥22 ኢሳ24፥8፤ ኤር25፥10፤ሕዝ26፥13
18፥23 ቍ3፤ ኢሳ23፥8፤ኤር7፥34፤ 16፥9፤25፥10፤ናሆ3፥4
18፥24 ኤር51፥49፤ ማቴ23፥35፤ ራእ16፥6፤17፥6
19፥1 ቍ3፡4፡6፤ ራእ4፥11፤7፥10፡12፤ 11፥15፡12፥10
19፥2 ራእ6፥10፤ 16፥7፤17፥1
19፥3 ቍ1፡4፡6፤ ኢሳ34፥10፤ራእ14፥11
19፥4 ቍ1፡3፡6፤ ራእ4፥4፡6፡10
19፥5 ቍ18፤ መዝ115፥13፤134፥1፤ ራእ11፥18፤13፥16፤ 20፥12
19፥6 ቍ1፡3፡4፤ ራእ1፥8፡15፤11፥15
19፥7 ቍ9፤ ማቴ22፥2፤25፥10፤ ኤፌ5፥32፤ራእ11፥13፤ 21፥2፡9፤22፥17
19፥8 ቍ14፤ ኢሳ61፥10፤ ሕዝ44፥17፤ዘካ3፥4፤ራእ1፥2፤22፥8፡9
19፥9 ቍ10፤ ሉቃ14፥15፤ራእ1፥19፤ 21፥5፤22፥6
19፥10 ሐሥ10፥25፡26፤ራእ1፥2፤22፥8፡9
19፥11 ቍ19፡21፤ ዘፀ15፥3፤መዝ96፥13፤ ኢሳ11፥4፤ማቴ3፥16፤ ራእ6፥2፤3፥14
19፥12 ቍ16፤ ራእ1፥14፤2፥17፤6፥2፤ 12፥3
19፥13 ኢሳ63፥2፡3፤ዮሐ1፥1

ልብስ ለብሶአል፤ ስሙም የእግዚአብሔር
ቃል ነው። 14የሰማይም ሰራዊት ነጭ፣ ንጹ
ሕና ከተልባ እግር የተሠራ ቀጭን ልብስ
ለብሰው፣ በነጫጭ ፈረሶች ላይ ተቀምጠው
ይከተሉት ነበር። 15ሕዝቦችን የሚመታ
በት ስለታም ሰይፍ ከአፉ ወጣ፤ "በብረት
በትርም ይገዛቸዋል።" እርሱም ሁሉን ቻይ
የሆነውን የእግዚአብሔርን የብርቱ ቍጣ ወይን
መጭመቂያ ይረግጣል። 16በልብሱና በጭኑ
ላይ እንዲህ የሚል ስም ተጽፎአል፤

"የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ።"

17ቀጥሎም አንድ መልአክ በፀሐይ
ውስጥ ቆሞ አየሁ፤ እርሱም በሰማይ መካ
ከል ለሚበሩ ወፎች ሁሉ እንዲህ ሲል
በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ "ኑ፤ ወደ ታላቁ የእ
ግዚአብሔር እራት ተሰብሰቡ፤ 18የምትሰበሰቡ
ትም የነገሥታትን ሥጋ፣ የጦር አዛዦችን
ሥጋ፣ የብርቱ ሰዎችን ሥጋ፣ የፈረሶች
ንና የፈረሰኞችን ሥጋ እንዲሁም የሰዎችን
ሁሉ፣ ይኸውም የጌቶችንና የባሮችን፣ የታ
ናናሾችንና የታላላቆችን ሥጋ እንድትበሉ
ነው።"
19ከዚህ በኋላ አውሬው፣ የምድር
ነገሥታትና ሰራዊታቸው በፈረሱ ላይ ከተ
ቀመጠውና ከሰራዊቱ ጋር ለመዋጋት ተሰ
ብስበው አየሁ። 20ነገር ግን አውሬው
ተያዘ፤ ከእርሱም ጋር በፊቱ ምልክቶችን
ያደርግ የነበረው ሐሰተኛው ነቢይ ተያዘ።
በእነዚህ ምልክቶች የአውሬውን ምልክት
የተቀበሉትንና ለምስሉ የሰገዱትን አሳተ።
ሁለቱም በሕይወት እንዳሉ በዲን ወደሚ
ቃጠለው የእሳት ባሕር ተጣሉ። 21የቀሩት
ደግሞ በፈረሱ ላይ ከተቀመጠው አፍ
በሚወጣው ሰይፍ ተገደሉ፤ ወፎችም ሁሉ
ከሥጋቸው በልተው ጠገቡ።

### የሺህ ዓመቱ መንግሥት

20 የጥልቁን መክፈቻና ትልቅ ሰንሰ
ለት በእጁ የያዘ መልአክ ከሰማይ
ሲወርድ አየሁ። 2እርሱም የጥንቱን እባብ፣
ዘንዶውን፣ ማለትም ዲያብሎስን ወይም ሰይ
ጣንን ይዞ ሺህ ዓመት አሰረው። 3ሺሁ ዓመ
ትም እስኪፈጸምም ድረስ ከእንግዲህ
ወዲህ ሕዝቦችን እንዳያስት ወደ ጥልቁ
ጣለው፤ ዘጋውም፤ በእርሱም ላይ ማኅተም
አደረገበት። ከዚያ በኋላ ለጥቂት ጊዜ ሊ
ፈታ ይገባዋል።
4ቀጥሎም ዙፋኖችን አየሁ፤ በዙፋኖ
ቹም ላይ ለመፍረድ ሥልጣን የተሰጣቸው
ሰዎች ተቀምጠው ነበር፤ ደግሞም ስለ
ኢየሱስ ምስክርና ስለ እግዚአብሔር ቃል
የተሰየፉትን ሰዎች ነፍሶች አየሁ። እነርሱ

19፥14 ቍ8፤ራእ3፥4
19፥15 ቍ21፤ መዝ2፥9፤ኢሳ11፥4፤ 2ተሰ2፥8፤ራእ1፥16፤ 2፥27፤12፥5፤14፥20
19፥16 ቍ12፤ 1ጢሞ6፥15
19፥17 ቍ21፤ ኢሳ34፥6፤ኤር12፥9፤ 46፥10፤ሕዝ39፥17፤ ራእ8፥13፤14፥6
19፥18 ቍ5፤ ሕዝ39፥18-20፤ ራእ6፥15
19፥19 ቍ11፡21፤ራእ13፥1፤16፥14፡16
19፥20 ዳን7፥11፤ ማቴ24፥24፤ ራእ9፥17፤13፥12፡ 14፡15፡16፤20፥10፡ 14፡15፤21፥8
19፥21 ቍ11፡15፡ 17፡19፤ራእ1፥16
20፥1 ሉቃ8፥31፤ ራእ1፥18፤10፥1፤18፥1
20፥2 ኢሳ24፥22፤ ማቴ4፥10፤2ጴጥ2፥4
20፥3 ቍ1፡8፡10፤ ዳን6፥17፤ማቴ27፥66፤ ራእ12፥9
20፥4 ቍ6፤ዳን7፥9፤ ማቴ19፥28፤ዕብ4፥12፤ ራእ1፥2፤3፥21፤6፥9፤ 13፥12፡16፤22፥5
20፥5 ቍ6፤ ሉቃ14፥14፤ ፊል3፥11፤ 1ተሰ4፥16
20፥6 ቍ4፤ 1ጴጥ2፥5፤ ራእ2፥11፤14፥13፤22፥5
20፥7 ቍ2
20፥8 ቍ3፡10፤ ኢሳ11፥12፤ሕዝ7፥2፤ 38፥2፡9፡15፤39፥1፤ ዕብ11፥12፤ራእ7፥1፤ 12፥9፤16፥14
20፥9 መዝ87፥2፤ ሕዝ38፥9፡22፤39፥6፤ራእ13፥13
20፥10 ቍ3፡8፤ ራእ9፥17፤12፥9፤14፥10፡ 11፤16፥13፤19፥20
20፥11 ራእ4፥2፤6፥14
20፥12 ቍ15፤ ዘፀ32፥32፤ዘዳ29፥20፤ ኤር17፥10፤ዳን7፥10፤ 12፥1፤ሚል3፥16፤ ማቴ16፥27፤ሉቃ10፥20፤ ራእ3፥5፤11፥18፤19፥5፤ 21፥27
20፥13 ኢሳ26፥19፤ ማቴ16፥27፤ ራእ1፥18፤6፥8
20፥14 ቍ13፤ 1ቆሮ15፥26፤ ራእ2፥11፤19፥20
20፥15 ቍ12
21፥1 2ጴጥ3፥13፤ራእ6፥14

ለአውሬው
ወይም ለእርሱ ምስል አልሰገዱም፤
በግምባራቸው ወይም በእጃቸው ላይ
የአውሬውን ምልክት አልተቀበሉም፤
እነርሱም ከሞት ተነሥተው ከክርስቶስ ጋር
ሺህ ዓመት ነገሡ። 5የቀሩት ሙታን ግን
ሺሁ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ ከሞት አል
ተነሡም። ይህ የመጀመሪያው ትንሣኤ
ነው። 6በመጀመሪያው ትንሣኤ ተካፋይ
የሚሆኑ ብፁዓንና ቅዱሳን ናቸው። ሁለተ
ኛው ሞት በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም፤
ነገር ግን የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት
ይሆናሉ፤ ከእርሱም ጋር ሺህ ዓመት ይነ
ግሣሉ።

### የሰይጣን የመጨረሻ ዕጣ

7ሺሁም ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን ከእስ
ራቱ ይፈታል፤ 8በአራቱ የምድር ማእዘ
ናት ያሉትን ሕዝቦች፦ ጎግንና ማጎግን
እያሳተ ለጦርነት ሊያሰልፋቸው ይወጣል፤
ቍጥራቸው በባሕር ዳርቻ እንዳለ አሸዋ
ነው። 9እነርሱም ወደ ምድር ሁሉ ወጥ
ተው የቅዱሳንን ሰፈርና የተወደደችውን
ከተማ ከበቡ፤ ነገር ግን እሳት ከሰማይ
ወርዶ በላቻቸው። 10ያሳታቸው ዲያብሎ
ስም፣ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉ
በት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ፤
እነርሱም ቀንና ሌሊት ከዘላለም እስከ
ዘላለም ይሠቃያሉ።

### ሙታን ተፈረደባቸው

11ከዚህ በኋላ ታላቅ ነጭ ዙፋንና በእር
ሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ። ምድርና
ሰማይ ከፊቱ ሸሹ፤ ስፍራም አልተገኘላቸ
ውም። 12ሙታንን፣ ታላላቆችንና ታናናሾ
ችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ፤ መጻሕፍ
ትም ተከፈቱ። ሌላም መጽሐፍ፣ እርሱም
የሕይወት መጽሐፍ ተከፈተ፤ ሙታንም
በመጻሕፍቱ ተጽፎ በተገኘው መሠረት
እንደ ሥራቸው መጠን ተፈረደባቸው።
13ባሕርም በውስጡ የነበሩትን ሙታን ሰጠ
፤ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ውስጥ የነበሩ
ትን ሙታን ሰጡ፤ እያንዳንዱም እንደ ሥ
ራው መጠን ተፈረደበት። 14ከዚያም በኋላ
ሞትና ሲኦል ወደ እሳት ባሕር ተጣሉ፤
የእሳቱ ባሕር ሁለተኛው ሞት ነው።
15ስሙ በሕይወት መጽሐፍ ተጽፎ
ያልተገኘ ሁሉ ወደ እሳት ባሕር ተጣለ።

### አዲሲቱ ኢየሩሳሌም

21 ከዚህ በኋላ አዲስ ሰማይና አዲስ
ምድር አየሁ፤ የመጀመሪያው ሰማ
ይና የመጀመሪያዪቱ ምድር ዐልፈዋልና፤
ባሕርም ከእንግዲህ ወዲህ አይኖርም። 2ቅድ

ስቲቱ ከተማ፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለባሏ
እንደ ተዋበች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ
ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ። 3ደግ
ሞም እንዲህ የሚል ታላቅ ድምፅ ከዙፋኑ
ሲወጣ ሰማሁ፤ “እነሆ፤ የእግዚአብሔር ማደ
ሪያ በሰዎች መካከል ነው፤ እርሱ ከእነርሱ
ጋር ይኖራል፤ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ፤
እግዚአብሔር ራሱም ከእነርሱ ጋር ይኖራል፤
አምላካቸውም ይሆናል። 4እንባን ሁሉ
ከዐይናቸው ያብሳል፤ ከእንግዲህ ወዲ
ህ ሞት ወይም ሐዘን ወይም ልቅሶ
ወይም ሥቃይ አይኖርም፤ የቀድሞው
ሥርዐት ዐል ፎአልና።”

5በዙፋኑ ላይ የተቀመጠውም፣ “እነሆ፤
እኔ ሁሉን ነገር አዲስ አደርጋለሁ” አለ፤
ደግሞም፣ “ይህ ቃል የታመነና እውነት
ስለ ሆነ ጻፍ” አለ።

6እንዲህም አለኝ፤ “ተፈጸመ፤ አልፋና
ዖሜጋ፣ የመጀመሪያውና የመጨረሻው
እኔ ነኝ፤ ለተጠማ ከሕይወት ውሃ ምንጭ
ያለ ዋጋ እሰጣለሁ። 7ድል የሚነሣ ይህን
ሁሉ ይወርሳል፤ እኔም አምላክ እሆነዋለሁ፤
እርሱም ልጅ ይሆነኛል። 8ነገር ግን ፈሪ
ዎች፣ የማያምኑ፣ ርኩሶች፣ ነፍሰ ገዳ
ዮች፣ አመንዝሮች፣ አስማተኞች፣ ጣዖት
አምላኪዎች፣ ውሸተኞች ሁሉ ዕጣ ፈንታ
ቸው በዲንና በእሳት ባሕር ውስጥ መጣል
ይሆናል። ይህም ሁለተኛው ሞት ነው።”

9ሰባቱ የመጨረሻ መቅሠፍቶች የሞሉ
ባቸውን ሰባቱን ጽዋዎች ከያዙት ከሰባቱ
መላእክት አንዱ መጥቶ፣ “ና፤ የበጉ ሚስት
የሆነችውን ሙሽራ አሳይሃለሁ” አለኝ።
10በመንፈስም ወደ አንድ ትልቅና ረጅም
ተራራ ወስዶኝ፣ ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩ
ሳሌም ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወ
ርድ አሳየኝ። 11እርሷም በእግዚአብሔር
ክብር ታበራ ነበር፤ የብርሃኗም ድምቀት
እጅግ እንደ ከበረ ድንጋይ እንደ ኢ
ያስጲድ፣ እንደ መስተዋት የጠራ ነበር።
12ዐሥራ ሁለት በሮች የነበሩት ትልቅና
ረጅም ቅጥርም ነበራት፤ በበሮቹም ላይ ዐ
ሥራ ሁለት መላእክት ቆመውና የዐሥራ
ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ስም ተጽፎ
ነበር። 13በምሥራቅ ሦስት በሮች፣ በሰሜ
ን ሦስት በሮች፣ በደቡብ ሦስት በሮች፣
በምዕራብ ሦስት በሮች ነበሩ። 14የከተ
ማዪቱም ቅጥር ዐሥራ ሁለት መሠረቶች
ነበሩት፤ በእነርሱም ላይ የዐሥራ ሁለቱ
የበጉ ሐዋ ርያት ስሞች ተጽፈው
ነበር።

15ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መል
አክ የከተማዪቱን በሮች ቅጥር የሚለካ
በት የወርቅ ዘንግ ነበረው። 16ከተማዪቱም

21፥4 ኢሳ25፥8፤ 35፥10፤65፥19፤ 1ቆሮ15፥26፤2ቆሮ5፥17፤ ራእ7፥17፤20፥14
21፥2 ቍ10፤ ነህ11፥18፤ኢሳ52፥1፤ ዕብ11፥10፤12፥22፤ ራ3፥12፤ 11፥2፤ 19፥7፤22፥19
21፥3 ዘፀ25፥8፤ 2ዜና6፥18፤ሕዝ48፥35፤ ዘካ2፥10፤2ቆሮ6፥16
21፥5 ቍ4፤ራእ4፥9፤ 20፥11፤19፥9፤22፥6
21፥6 ኢሳ55፥1፤ ዮሐ4፥10፤ራእ1፥8፤ 16፥17፤22፥13
21፥7 ቍ3፤ 2ሳሙ7፥14፤ዮሐ16፥3 3፤ሮሜ 8፥14፤2ቆሮ6፥16
21፥8 ቍ27፤ መዝ5፥6፤1ቆሮ6፥9፤ ዕ ብ12፥14፤ራእ2፥11 ፤9፥17፤22፥15
21፥9 ራእ15፥1፡6፡ 7፤19፥7
21፥10 ቍ2፤ሕዝ40፥2 ፤ራእ1፥10፤17፥3
21፥11 ቍ18፡19፡23፤ ኢሳ60፥1፡2፤ሕዝ43፥2፤ ራእ4፡3፡6፤15፥8፡22፥5
21፥12 ቍ15፡21፡ 25፤ሕዝ48፥30-34፤ራእ 22፥14
21፥14 ሐሥ1፥26፤ ኤፌ2፥20፤ዕብ11፥10
21፥15 ቍ12፤ ሕዝ40፥3፤ራእ11፥1
21፥17 ራእ13፥18
21፥18 ቍ11፡21
21፥19 ቍ11፤ ዘፀ28፥17-20፤ ኢሳ54፥11፡12፤ ሕዝ28፥13
21፥20 ራእ4፥3
21፥21 ቍ12፡18፤ ኢሳ54፥12
21፥22 ዮሐ4፥21፡ 23፤ራእ1፥8፤5፥6
21፥23 ቍ11፤ ኢሳ24፥23፤60፥19፡ 20፤ራእ5፥6፤22፥5
21፥24 ቍ26፤ ኢሳ60፥3፡5
21፥25 ቍ12፤ ኢሳ60፥11፤ዘካ14፥7፤ ራእ22፥5
21፥26 ቍ24
21፥27 ኢሳ52፥1፤ ኢል3፥17፤ራእ20፥12፤ 22፥14፡15
22፥1 ቍ17፤ መዝ36፥8፤46፥4፤ ሕዝ47፥1፤ዘካ14፥8፤ ዮሐ4፥10፤ ራእ4፥6
22፥2 ሕዝ47፥1፤ ራእ2፥7
22፥3 ዘካ14፥11፤ ራእ7፥15
22፥4 ማቴ5፥8፤ ራእ7፥3

ርዝመቷና ስፋቷ እኩል ሆኖ አራት ማእ
ዘን ነበረች። እርሱም ከተማዪቱን በዘንጉ
ለካ፤ ርዝመቷም ዐሥራ ሁለት ሺህ ምዕ
ራፍ[ሠ] ሆነ፤ ስፋቷና ከፍታዋም እንዲሁ
ሆነ። 17ደግሞም የከተማዪቱን ቅጥር ለካ፤
ርዝመቱም የመልአክ መለኪያ በሆነው
በሰው መለኪያ መቶ አርባ አራት ክንድ[ዐ]
ነበር። 18ቅጥሩ የተሠራው ከኢያሰጲድ
ነበር፤ ከተማዪቱም እንደ መስተዋት ንጹሕ
ከሆነ ወርቅ የተሠራች ነበረች። 19የከተ
ማዪቱ ቅጥር መሠረቶች በሁሉም ዐይነት
የከበረ ድንጋይ ያጌጡ ነበር፤ የመጀመሪ
ያው መሠረት ኢያሰጲድ፣ ሁለተኛው
ሰን ፔር፣ ሦስተኛው ኬልቄዶን፣ አራ
ተኛው መረግድ፣ 20አምስተኛው
ሰርዶንክስ፣ ስድ ስተኛው ሰርድዮን፣
ሰባተኛው ክርስቲ ሎቤ፣ ስምንተኛው ቢ
ረሌ፣ ዘጠነኛው ወራ ውሬ፣ ዐሥረኛው
ክርስጵራስስ፣ ዐሥራ አንደኛው
ያክንት፣ ዐሥራ ሁለተኛው አሜቴስጢ
ኖስ" ነበረ። 21ዐሥራ ሁለቱም በሮች ዐሥ
ራ ሁለት ዕንቊች ነበሩ፤ እያንዳንዱም
በር ከአንድ ዕንቍ የተሠራ ነበረ። የከተ
ማዪቱም አውራ መንገድ እንደ መስተዋት
ብርሃን የሚያስተላልፍ ንጹሕ ወርቅ
ነበረ።

22ሁሉን ቻይ ጌታ አምላክና በጉ መቅ
ደሷ ስለ ሆኑ፣ በከተማዪቱ ውስጥ ቤተ
መቅደስ አላየሁም። 23የእግዚአብሔር ክብር
ብርሃን ስለሚሰጣትና በጉም መብራቷ ስለ
ሆነ፣ ከተማዋ ፀሓይ ወይም ጨረቃ
እንዲያበሩላት አያስፈልጋትም። 24ሕዝቦች
በብርሃኗ ይመላለሳሉ፤ የምድር ነገሥታ
ትም ክብራቸውን ወደ እርሷ ያመጣሉ።
25በዚያ ሌሊት ስለሌለ፣ በሮቿ በየትኛ
ውም ቀን አይዘጉም። 26የሕዝቦች ግርማና
ክብር ወደ እርሷ ይገባሉ። 27በበጉ የሕይ
ወት መጽሐፍ ከተጻፉት በስተቀር፣ ርኩ
ሰትን የሚያደርግና ውሸትን የሚናገር
ሁሉ አይገባባትም።

## የሕይወት ወንዝ

22 ከዚህ በኋላ መልአኩ ከእግዚአብሔ
ርና ከበጉ ዙፋን የሚወጣውን
እንደ መስተዋት የጠራውን የሕይወት ውሃ
ወንዝ አሳየኝ፤ 2ወንዙም በከተማዪቱ አውራ
መንገድ መካከል ይፈስ ነበር። በወንዙ
ግራና ቀኝ በየወሩ እያፈራ ዐሥራ ሁለት
ጊዜ ፍሬ የሚሰጥ የሕይወት ዛፍ ነበረ፤
የዛፉም ቅጠሎች ሕዝቦች የሚፈወሱባቸው
ነበሩ። 3ከእንግዲህ ወዲህ ርግማን ከቶ
አይኖርም፤ የእግዚአብሔርና የበጉ ዙፋን
በከተ

[ሠ]16 ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ኪሎ ሜትር ያህል ይሆናል።
[ዐ]17 ሥልሳ አምስት ሜትር ያህል ይሆናል።

ማዩ-ቱ ውስጥ ይሆናል፤ አገልጋዮቹም ያመ
ልኩታል፤ 4ፊቱን ያያሉ፤ ስሙም በግምባ
ራቸው ላይ ይሆናል፡፡ 5ከእንግዲህ ወዲህ
ሌሊት አይኖርም፤ ጌታ አምላክ ስለሚያበ
ራ ላቸው የመብራት ወይም የፀሓይ
ብርሃን አያስፈልጋቸውም፤ ከዘላለም እስከ
ዘላለም ይነግሣሉ፡፡
6መልአኩም፣ “እነዚህ ቃሎች የታመ
ኑና እውነተኞች ናቸው፡፡ የነቢያት መናፍ
ስት ጌታ አምላክ በቅርብ የሚሆነውን
ነገር ለአገልጋዮቹ እንዲያሳይ መልአኩን
ልኮ አል” አለኝ፡፡

## ኢየሱስ ይመጣል

7“እነሆ፤ ቶሎ እመጣለሁ፤ የዚህን መጽ
ሐፍ የትንቢት ቃል የሚጠብቅ ብፁዕ ነው፡፡”
8እነዚህን ነገሮች የሰማሁና ያየሁ እኔ
ዮሐንስ ነኝ፡፡ እነዚህን ነገሮች በሰማ
ሁና ባየሁ ጊዜ፣ እነዚህን ነገሮች ላሳየኝ
መልአክ ልሰግድ በእግሩ ሥር ተደፋሁ፤
9እርሱ ግን፣ “ተው!፤ ይህን አታድርግ!
እኔ ከአንተና ከወንድሞችህ ከነቢያት
እንዲሁም የዚህን መጽሐፍ ቃል ከሚጠ
ብቁት ሁሉ ጋር አገልጋይ ነኝ፤ ለእግዚ
አብሔር ስገድ” አለኝ፡፡
10እንዲህም አለኝ፤ “ጊዜው ስለ ደረሰ፣
የዚህን መጽሐፍ የትንቢት ቃል በማኅተም
አትዝጋው፤ 11ዐመፀኛው በዐመፁ ይቀ
ጥል፤ ርኩሱም ይርከስ፤ ጻድቁም ይጽደቅ፤
ቅዱ ሱም ይቀደስ፡፡”
12“እነሆ፤ ቶሎ እመጣለሁ፤ ዋጋዬ በእኔ
ዘንድ አለ፤ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው
መጠን እከፍለዋለሁ፡፡ 13አልፋና ያሜጋ፣
ፊተኛውና ኋለኛው፣ መጀመሪያውና መጨ
ረሻው እኔ ነኝ፡፡

22፥5 ኢሳ60፥19፡ 20፤ዳን7፥27፤ዘካ14፥7፤ ራእ20፥4፤21፥23፡25
22፥6 ቀኣ16፤ 1ቆሮ14፥32፤ ዕብ12፥9፤ራእ1፥1፤21፥5
22፥7 ቀኣ10፡12፡ 18፡19፡20፤ማቴ16፥27፤ ራእ1፥3፤16፥15
22፥8 ራእ1፥1፤ 19፥10
22፥9 ቀኣ10፡ 18፡19፤ራእ19፥10
22፥10 ቀኣ7፡18፡ 19፤ዳን8፥26፤ ሮሜ13፥11፤ራእ10፥4
22፥11 ሕዝ3፥27፤ ዳን12፥10
22፥12 ቀኣ7፡20፤ ኢሳ40፥10፤62፥11፤ ማቴ16፥27
22፥13 ራእ1፥8፡ 17፤21፥6
22፥14 ራእ2፥7፤ 7፥14፤21፥12፡27
22፥15 ዘዳ23፥18፤ 1ቆሮ6፥9፡10፤ገላ5፥19-21፤ፊል3፥2፤ቈላ3፥5 ፡6፤ራእ21፥8
22፥16 ቀኣ6፤ማቴ 1፥1፤2ጴጥ1፥19፤ራእ 1፥1፤4፤2፥28፤5፥5
22፥17 ዮሐ4፥10፤ራ እ2፥7፤14፥13፤ 19፥7
22፥18 ቀኣ7፡10፡ 19፤ዘዳ4፥2፤12፥32፤ 30፥6፤ራእ15፥6-16፥21
22፥19 ቀኣ7፡10፡ 18፤ዘዳ4፥2፤12፥32፤ም ሳ30፥6፤ራእ2፥7
22፥20 ቀኣ7፡12፤ ማቴ16፥27፤1ቆሮ 16፥22፤ራእ1፥2
22፥21 ሮሜ16፥20

14“ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስና በበሮ
ቿም በኩል ወደ ከተማዪቱ ለመግባት
መብት እንዲኖራቸው ልብሳቸውን የሚያ
ጥቡ ብፁዓን ናቸው፡፡ 15ውሾች፣ አስማተ
ኞች፣ ሴሰኞች፣ ነፍሰ ገዳዮች፣ ጣዖት አም
ላኪዎች፣ ውሸትን የሚወዱና የሚያደርጉ
ሁሉ በውጭ አሉ፡፡
16“እኔ ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች እንዲ
መሰክር መልአኬን ለአብያተ ክርስቲያ
ናት ልኬአለሁ፡፡ እኔ የዳዊት ሥርና ዘር
ነ፣ የሚያበራም የንጋት ኮከብ ነኝ፡፡”
17መንፈስና ሙሽራዪቱ፣ “ና” ይላሉ፤
የሚሰማም፣ “ና” ይበል፤ የተጠማም ሁሉ
ይምጣ፤የሚፈልግም ሁሉ የሕይወትን ውሃ
በነጻ ይውሰድ፡፡
18የዚህን መጽሐፍ የትንቢት ቃል የሚ
ሰማውን ሁሉ አስጠነቅቃለሁ፤ ማንም በዚህ
ቃል ላይ አንዳች ቢጨምር፣ እግዚአብሔር
በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሠፍቶች
ይጨምርበታል፤ 19ማንም በዚህ የትንቢት
መጽሐፍ ከተጻፈው ቃል አንዳች ቢያጐ
ድል፣ እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ ከተ
ጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ
ዕድሉን ያጐድልበታል፡፡
20እነዚህን ነገሮች የሚመሰክረው፣
“አዎ፣ ቶሎ እመጣለሁ” ይላል፡፡

አሜን፤ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፤ ና፡፡

21የጌታ የኢየሱስ ጸጋ ከእግዚአብሔር ሕዝብ[ሠ]
ጋር ይሁን፤ አሜን፡፡[ረ]

[መ]20 ከእነዚህ የከበሩ ድንጋዮች መካከል የአንዳንዶቹ ምንነት በውል አይታወቅም፡፡
[ሠ]21 አንዳንድ ቅጆች ... *ከቅዱሳን ጋር ይሁን* ይላሉ፡፡
[ረ]21 አንዳንድ ቅጆች *አሜን* የሚለውን አይጨምሩም፡፡